ይህም ለእኛ ውርዴት ነው
ይህም እኛን ያሳፍረናል:: እዚህ “እኛ” የያዕቆብን ወንዶች ልጆችንና የእስራኤልን ልጆች በአጠቃላይ ያመለክታል (የሚያካትትና የማያካትት እኛን ይመልከቱ)
ሴቶች ልጆቻችንን እንሰጣችኋለን የእናንተን ሴቶች ልጆች እንወስዳለን
ይህም ከያዕቆብ ቤተሰብ የሆነ ሰው በኤሞር ምድር የሚኖረውን ሰው ያገባል ማለት ነው
Genesis 34:18
ያቀረቡትም ሃሳብ ለኤሞርና ለልጁ ለሴኬም መልካም መስሎ ታየቸው
ኤሞርና ልጁ ሴኬም የያዕቆብ ወንዶች ልጆች ባቀረቡት ሃሳብ ተስማሙ
ያሉትን ለማድረግ
ለመገረዝ
የያዕቆብ ሴት ልጅ
የያዕቆብ ሴት ልጅ ዲና
ከአባቱ ቤተሰብ ሁሉ እጅግ የተከበረው
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: እጅግ ስለሚያከብሩት ሌሎች ሰዎች ለመገረዝ እንደሚስማሙ ሴኬም እንደተረዳ ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት: “እርሱ በእነርሱ ዘንድ የተከበረ በመሆኑ የአባቱ ቤተሰብ ወንዶች ሰዎች ሁሉ ለመገረዝ እንደሚስማሙ ሴኬም ያውቅ ነበር” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)::
Genesis 34:20
ወደ ከተማቸው በር
ሕጋዊ ውሳኔ ለመወሰን በከተሞች በር መሰባሰብ በመሪዎች የተለመደ ነው
እነዚህ ሰዎች
ያዕቆብ ወንዶች ልጆቹና የእስራኤል ሰዎች
በእኛ ዘንድ የሰላም ሰዎች
እዚህ “እኛ” ኤሞር ልጁንና የተናገሩአቸው በከተማው በር ያሉ ሰዎችን ሁሉ ያቀፈ ነው (ሁሉን ያቀፈ “እኛ” ይመልከቱ)
በምድራችን ይኑሩ ይነግዱበትም
በምድሪቱ ይኑሩ ይነግዱበትም
እነሆ ምድሪቱ በእርግጥ ሰፊ ናት
ለዐረፍተ ነገሩ ትኩረት ለመስጠት ሴኬም “በእርግጥ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል:: “እነሆ ምድሪቱ በእርግጥ ለእነርሱም ሰፊ ናት” ወይም “እነሆ ለእነርሱ የሚበቃ በቂ መሬት አለ”
ሴት ልጆቻቸውን እንውሰድ ለእነርሱም ሴት ልጆቻችንን እንስጥ
ይህ በአንዱ ቡድን ሴቶች በሌላው ቡድን ወንዶች መካከል የሚፈጸሙ ጋብቻዎችን ያመለክታል። በዘፍጥረት 34፡9 ተመሣሣይ ሀረጐችን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።
Genesis 34:22
አጠቃላይ መረጃ
ኤሞርና ልጁ ሴኬም ለከተማዋ ሸማግሌዎች መናገራቸውን ቀጠሉ
አንድ ሕዝብ ሆነን ከእኛ ጋር ይቀመጡ ዘንድ በዚህ ነገር ብቻ እሺ ይሉናል እነርሱ እንደተገረዙ ወንዶቻችንን ሁሉ ብንገርዝ
ሰዎቹ ከእኛ ጋር እንደ አንድ ሕዝብ ሆነው አብረውን ለመኖር ፈቃደኞች የሚሆኑት የእኛ ወንዶች እንደ እነርሱ የተገረዙ እንደሆነ ብቻ ነው
ታዲያ እንዲህ ብናደርግ ከብቶቻቸው ንብረታቸው እንስሶቻቸው ሁሉ የእኛው ይሆኑ የለምን?
የያዕቆብ እንስሶችና ንብረቶች ለሴኬም ሰዎች እንደሚሆን ሴኬም ጥያቄ ምልክት በመጠቀም አበክሮ ይናገራል:: ይህ እንደዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት: “የእነርሱ እንስሳትና ንብረት ሁሉ ለእኛ ይሆናል” አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ::
Genesis 34:24
ወንዶች ሁሉ ተገረዙ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ስለዚህ ኤሞርና ሴኬም ወንዶችን ሁሉ የሚገርዙ ነበሩአቸው (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዘበት ዐረፍት ነገር ይመልከቱ)
በሶስተኛውም ቀን
ሶስት ተራ ቁጥር ሶስት ነው:: ያለ ተራ ቁጥር ሊነገር ይችላል:: አት: “ከሁለት ቀን በኋላ”
ሁሉም ቆስለው ሳሉ
የከተማው ወንዶች ቆስለው ሳሉ
እያንዳንዱ ሰይፉን መዝዞ
ሰይፋቸውን መዘው
ከተማዋን ወጉት
ከተማ ሰዎችን ይወክላል አት እነርሱ የከተማይቱን ሰዎች ተዋጉ (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
ጥበቃ፤ እናም ወንዶችን ሁሉ ገደሉ
ይህ እንደአዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ጥበቃ፡ ስምዖንና ሌዊ የከተማይቱን ወንዶች ሁሉ ገደሉ።።”
Genesis 34:27
ሬሳዎች
የኤሞር የሴኬምና ወንዶች ስዎቻቸው ሬሳ
ከተማዋን ዘረፉ
በከተማይቱ ያለውን ጠቃሚ ነገር ሁሉ ወሰዱ
ሰዎች እህታቸውን ስላረከሱአት
ሴኬም ብቻውን ዲናን አርክሶአት ነበር ነገር ግን የያዕቆብ ልጆች የሴኬም መላው ቤተሰብና በከተማው ያለው ሁሉ ሰው ለዚህ ድርጊት ተጠያቂ አድርገው ቆጥረዋል
አረከሳት
ከእርሱ ጋር እንዲትተኛ በመድፈር ሴኬም ዲናን አዋረዳት ወይም ክብርዋን ነፈጋት/ አሳፈራት ማለት ነው:: በዘፍጥረት 34: 5 አረከሳት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ
መንጎቻቸውን ወሰዱ
የያዕቆብ ልጆች የሰዎችን መንጋ ወሰዱ
ሀብቶቻቸውን ሁሉ
ንብረታቸውንና ገንዘባቸውን ሁሉ ሕጻናቶቻቸውንና ሴቶቻቸውን ሁሉ ማረኩ
Genesis 34:30
አስጨነቃችሁኝ
ለአንድ ሰው የጭንቀት ምክንያት መሆን ጭንቀት በአንድ ሰው ላይ እንደሚመጣና እንደሚቀመጥ ዕቃ ተደርጐ ተገልጾአል አት: “ትልቅ ችግሮችን ፈጥራችሁብኛል” (ዜይቤያዊ አነጋገር ይጠቀሙ)
በዚህ አገር በሚኖሩ ዘንድ እንደጥንብ አስቆጠራችሁኝ
ያዕቆብ በዙሪያው በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ እንዲጠላ ማድረግ የያዕቆብ ልጆች እርሱን እንደ መጥፎ ሽታ እንዳደረጉ ተገልጾአል ይህ እንደ አዲስ ዐረፍት ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት: “በምድሪቱ በሚኖሩ ዘንድ የተጠላሁ እንዲሆን አድርጋችሁኛል” (ዜይቤያዊ አነጋገር ይጠቀሙ)
እኔ በቁጥር አነስተኞች ነኝ ቢያጠቁኝ እኔንና ቤተሰቤን ያጠፋሉ
እዚህ “እኔ” እና “እኔን” የሚሉ ቃላት ያዕቆብን ቤተሰብ በአጠቃላይ ይወክላሉ:: ያዕቆብ የቤተሰቡ መሪ ከመሆኑ የተነሳ “እኔ” ወይም “እኔን” ይጠቀማል:: አት: “ቤተሰብ አነስተኛ ነው … ተባብረው ቢነሡብኝና ቢያጠቁኝ ሁላችንንም ያጠፋሉ::” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ተባብረ ይነሡና ያጠቁኛል
ሠራዊት ይፈጥሩና ያጠቁኛል ወይም ሠራዊት ይፈጥሩና ያጠቁናል
እኔም እጠፋለሁ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ያጠፉኛል ወይም ያጠፉናል

ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ"
ሴኬም በሴተኛ አዳሪ/በጋለሞታ እንደሚደረግ በእኅታችን ያደርግባትን?
ሴኬም ያደረገው ጥፋትና ሞት እንደሚገባው አበክረው ለመግለጽ ሌዊና ስምዖን ጥያቄ ይጠቀማሉ:: አት: "ሴኬም እህታችንን እንደ ሴተኛ አዳሪ/ጋለሞታ አድርጐ ባልቆጠረ ነበር!" (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

---

Chapter 35
Genesis 35:1
ወደ ቤተል ውጣ
ውጣ የሚለው ቃል የተጠቀመው ቤቴል ከሴኬም በከፍታ ላይ ስለሚገኝ ነው
በዚያ መሠዊያ ሥራ
እግዚአብሔር ስለራሱ በሶስተኛ ሰው መንገድ ይናገራል:: አት: "ለእኔ ለአምላክህ መሠዊያ ሥራ" (እንደ አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው መግለጽን ይመልከቱ)
ለቤቱ ሰዎች እንዲህ አላቸው
ለቤተሰቡ እንዲህ አላቸው
በእናንተ ዘንድ ያሉትን ባዕዳን አማልእክት አስወግዱ
"ጣዖታትን አስወግዱ" ወይም "ሐሰተኞች አማልእክትን አስወግዱ"
ራሳችሁን አንጹ ልብሳችሁን ለውጡ
ይህ እግዚአብሔርን ለማምለክ ከመቅረብ በፊት በአካላዊና ሥነምግባራዊ ሕይወት ራስን የማንጻት ልምድ ነበር
ልብሳችሁን ለውጡ
አድስ ልብሶችን መልበስ ወደ እግዚአብሔር ከመቀረባቸው በፊት ራሳቸውን ንጹህ የማድረጋቸው ምልክት ነበር (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
በመከራዬ ቀን
በመከራዬ ጊዜ ወይም በጭንቀተ ጊዜ
Genesis 35:4
ስለዚህ ሰጡት
"ሁሉም የያዕቆብ ቤት ሰጠ" ወይም "የያዕቆብ ቤተሰብና አገልጋዮቻቸው ሰጡት"
በእጃቸው ያሉትን
እዚህ "በእጃቸው ያሉት" የእነርሱ የሆኑትን ይወክላል:: አት: "ሀብታቸው የሆኑትን ወይም ያላቸውን" (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
የጆሮ ጉትቾቻቸውን
ጉትቾቻቸውን ተገቢ ትርጉሞች እነሆ 1 የጆሮቻቸውን ወርቅ ብዙ ጣዖታትን ሊሠሩ ሊጠቀሙ ይችላሉ 2 እነዚህ ጉትቾች የሴኬም ከተማ ሰዎችን በተዋጉና ሁሉን ሰዎች በገደሉ ጊዜ የበዘበዙአቸው ናቸው:: ጉትቾች ስለኃጢአታቸው የሚያውሱ ይሆናሉና::
በዙሪያው ባሉ ከተሞች ሁሉ እግዚአብሔር ድንጋጤ ለቀቀባቸው
ያዕቆብንና ቤተሰቡን የከተሞች ሰዎች እንዲደነግጡ እግዚአብሔር ያደረገው ድንጋጤ እንደ አንድ ነገር በከተሞች እንደወደቀ ተደርጐ ተገልጾአል:: "ድንጋጤ" የተባለው ረቂቅ ስም እንደ "ፍርሃት" ሊገለጽ ይችላል:: አት: "እግዚአብሔር በዙሪያው ያሉ የከተሞች ሰዎች ያዕቆብንና በቤተሰቡን እንዲፈሩ አደረገ" ዘይቤያዊ አነጋገርና ረቂቅ ስሞችን ይመልከቱ
በከተሞች ላይ
"ከተሞች" በከተሞች የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላሉ::
የያዕቆብ ወንዶች ልጆች
ከያዕቆብ ቤተሰብ ማንም እንዳልተጠቃ ይገልጻል ነገር ግን የያዕቆብ ሴት ልጅ ከተደፈረች በኋላ ስምዖንና ሌዊ የሴኬምን ከነዓናዊያን ዘመዶችን አጠቁአቸው በዘፍረት 34:30 ያዕቆብ ሊበቀሉ ይፈልጉ ይሆናል ብሎ ፈርቶአል አት የያዕቆብ ቤት ወይም የያዕቆብ ቤተሰብ (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 35:6
ሎዛ
ይህ የከተማ ስም ነው:: በዘፍጥረት 28 19 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ኤል ቤቴል
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ፡፡ "ኤል ቤተል የሚለው ስም የቤተል አምላክ ማለት ነው" (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
እግዚአብሔር የተገለጠለት በዚህ ቦታ ነበር
እግዚአብሔር ራሱን ለያዕቆብ ያስታወቀበት በዚህ ቦታ ነበር
ዲቦራ
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው ስምችን ስለመተርጐም ይመልከቱ
የርብቃ ሞግዚት
ሞግዚት የሌላ ሴት ልጅን የሚትንከባከብ ሴት ማለት ነው ሞግዚት እጅግ የተከበረችና በቤተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያላት ነች
ከቤተል ዝቅ ብሎ .... ተቀበረች
"ዝቅ ብሎ" የሚለው ሀረግ የተጠቀመው እርስዋ የተቀበረችው ቦታ ከፍታ ከቤተል ዝቅ ብሎ ስለሚገኝ ነው::
አሎንባኩት
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ:: "አሎንባኩት የሚለው ስም ለቅሶ ያለበት ዋርካ ዛፍ ማለት ነው" (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
Genesis 35:9
ያዕቆብ ከጳዳን አራም በተመለሰ ጊዜ
በቤተል እንደነበሩ ግልጽ ማድረግ ይቻላል አት ያዕቆብም ከጳዳን አራም ከተመለሰ በኋላ በቤተል በነበረበት ጊዜ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ባረከውም
በረከት ለአንድ ሰው መልካም ነገር እንዲደረግለትና በዚያው ሰው ላይ የረከት ቃል መናገር ነው
ከእንግዲህ ያዕቆብ ተብለህ አትጠራም
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በየዘ መንገድ ሊተረጐም ይችላል:: አት: "ስምህ ያዕቆብ አይባልም" (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
Genesis 35:11
እግዚአብሔር እርሱን እንዲህ አለው
እግዚአብሔር ያዕቆብን እንዲህ አለው
ብዛ ተባዛ
ብዙ ልጆች እንዲኖሩት ያዕቆብ ብዙ ልጆችን እንዲወልድ እግዚአብሔር ተናገረው ብዛ የሚለው እንዴት መባዛት እዳለበት ይገልጻል በዘፍጥረት 1:22 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ድርብ ቃላትና ፈሊጣዊ ንግግር ይመልከቱ)
ሕዝብና የሕዝቦች ማኅበር ከአንተ ይወጣሉ
እዚህ ሕዝብ እና ሕዝቦች የያዕቆብ ዘሮች እነዚህን ሕዝቦች እንደሚመሠርቱ ነው:: (ተመሣሣይ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ከእርሱ.... ወደ ላይ ወጣ
ወደ ላይ ወጣ የተጠቀመው ከምድር ከፍ ብሎ እግዚአብሔር እንደምኖር ለመግለጽ ነው:: አት: "እግዚአብሔር ተለየው"
Genesis 35:14
ሐውልት
ይህ በጫፉ መከሎ/ቅርጽ ያለው ትልቅ ድንጋይ ለመታሰቢያነት የቆመ ሐውልት ነው
የመጠጥ መስዋዕትንም በእርሱ ላይ አፈሰሰ ዘይትንም አፈሰሰበት
ይህም ሐውልቱን ለእግዚአብሔር የመሰደስ ምልክት ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
በቴል
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ:: "በቴል የሚለው ስም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው" (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
Genesis 35:16
ኤፍራታ
ይህ የቤተልሔም ከተማ ሌላው ስም ነው
በከባድ ምጥ ውስጥ ሳለች
ምጡ አስጨንቆአት ሳለ
አዋላጅ
አንድ ሴት ልጅን በሚትወልድበት ጊዜ የሚታግዝ ሴት
ስትሞት ነፍስዋ በሚትወጣበት ጊዜ
"ነፍስ መውጣት" አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ የመጨረሻ እስትንፋስ ማለት ነው:: አት "ከመሞትዋ በፊት በመጨረሻዋ እስትንፋስ ጊዜ" (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ቤንኦኒ
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ:: "ቤንኦኒ የምለው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ስም የጭንቀቴ ልጅ ማለት ነው” (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ብንያምን
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ። “ብንያምን የምለው ስም የቀኝ እጄ ልጅ ማለት ነው” የቀኝ እጅ የሚለው ሀረግ ልዩ የሚወደድ ቦታ ማለት ነው::
ተቀበረች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “እነርሱ ቀበሩአት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
በሚወስድ መንገድ
በሚወስደው መንገድ
እስከዛሬም የራሔል መቃብር ምልክት ይሄው ሐውልት ነው
ይህ እስከዛሬም የራሔል መቃብር ምልክት ነው
እስከዛሬ
እስካሁን ጊዜ ይህ ጸሐፊው፤ ይህ መልእክት የጻፈበትን ጊዜ ያመለክታል።
Genesis 35:21
እስራኤልም ጉዞውን በመቀጠል
የእስራኤል ቤተሰብና አገልጋዮቹ ከእርሱ ጋር እንደነበሩ ይገልጻል የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ባላ
የራሔል ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ::
ያዕቆብ አሥራ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት
ይህ ዐረፍተ ነገር በሚከተሉት ቁጥሮች የሚቀጥለውን አድስ አንቀጽ ይጀምራል
አሥራ ሁለት ወንዶች ልጆች
12 ወንዶች ልጆች
Genesis 35:23
ባላ
የራሔል ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
Genesis 35:26
ዘለፋ
የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:24 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
በጳዳን አራም የተወለዱ ነበሩ
ይህ በከነዓን ምድር በቤተልሔም አጠገብ የተወለደውን ብንያምን እንደማያካትት ይናገራል:: አብዛኛዎቹ የተወለዱት በጳዳን አራም ስለሆነ ይህንኑን ይጠቅሳል:: የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “በከነዓን ምድር ከተወለደው ከብንያምን በስተቀር በጳዳን አራም የተወለዱለት” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ያዕቆብ ወደ ይስሐቅ መጣ
መጣ የተባለው ሄዴ በሚለው ሊተካ ይችላል (ሄዴ እና መጣ ይመልከቱ)
መምሬ
የሔብሮን ከተማ ሌላ ስምዋ ነው የአብርሃም ወዳጆች በኖሩበት በመምሬ ስም ተጠርቶ ይሆናል በዘፍጥረት 13 18 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ቅርያትአርባቅ
ይህ የከተማ ስም ነው በዘፍጥረት 23 2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
Genesis 35:28
መቶ ሰማንያ ዓመት
180 ዓመት (ቁጥሮችን ይመልከቱ)
ይስሐቅም ነፍሱን ሰጠ ሞተም
ይስሐቅም የመጨረሻውን እስትንፋስ ሰጠ ሞተም እንትንፋሱን ሰጠ/ነፍሱን ሰጠ ወይም ሞተ የሚሉ ሀረጐች በመሠረቱ አንድ ትርጉም አላቸው:: በዘፍጥረት 25:8 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት: “ይሥሐቅም ሞተ” (ድርብ ቃላት ይመልከቱ)
ነፍሱን ሰጠ
ይህ አንድ ሰው መሞቱን ትሁትና መንገድ የሚገልጽ ነው:: በዘፍጥረት 25:8 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ንኀብነት ለዛ ባለ ወይም በተዘዋዋሪ አንድን ነገር የመግለጽ ዘይቤያዊ አባባል ይመልከቱ)
ወደ ወገኖቹ ተከማቸ/ተሰበሰበ
ይስሐቅ ከሞተ በኋላ ከዚህ በፊት የሞቱ ወገኖች ነፍስ ወዳለበት ቦታ ነፍሱ ሄደች ማለት ነው ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል አት የሞቱትን የቤተሰብ አባላትን ተቀላቀለ ማለት ነው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዙ ዐረፍተ ነገሮችን ይመልከቱ)
አርጅቶ እድሜ ጠግቦ
አረጅቶ እና እድሜ ጠግቦ የሚሉ ሀረጐች በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው:: አበክረው የሚናገሩት ይስሐቅ ብዙ ዓመታትን እንደኖረ ነው:: አት: “ብዙ ዓመታትን ኖሮ ከአረጀ በኋላ” (ድርብ አባባል ይመልከቱ)

Chapter 36

Genesis 36:1
የዔሣው ትውልድ ይህ ነው እርሱም ኤዶም ነው
ኤዶም የተባለው የዔሣው ትውልድ ይህ ነው ይህ በዘፍረት 36:1-8 የተጠቀሰውን የዔሣው ትውልድን ያስታውቃል:: አት “ይህ ኤዶም የተባለው የዔሣው ትውልድ ነው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ዓዳ አህሊባማ
እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስም ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ዔሎን ኬጢያዊው
“ዔሎን የኬጥ ትውልድ” ወይም “ዔሎን የኬጥ ልጅ” ይህ የአንድ ሰው ስም ነው:: በዘፍጥረት 26:34 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ዓና … ጽብዖን …. ነባዮት
እነዚህ የመንዶች ሰዎች ስም ናቸው
ኤዋዊ
ይህ ትልቅ ሕዝብ ቡድንን ያመለክታል። በዘፍጥረት 10:17 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
ቤሴሞት
ከዔሣው ሚስቶች የአንዷ ስም ነው:: ዘፍጥረት 26:34 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ነባዮት
ከእስማኤል ወንዶች ልጆች የአንዱ ስም ነው:: ዘፍጥረት 28:9 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
Genesis 36:4
ዓዳ … ቤሴሞት … አህሊባማ
እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:2-3 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ኤልፋዝ ራጉኤል የዑስ የዕላም ቆሬ
እነዚህ የዔሣው ወንድ ልጆት ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
Genesis 36:6
በከነዓን ምድር ያፈራውን ሀብት
ይህ በከነዓን ምድር በሚኖርበት ጊዜ የሰበሰበውን ወይም ያፈራውን ሁሉን ነገር ያመለክታል አት በከነዓን ምድር በሚኖርበት ጊዜ ያፈራውን ሀብት (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ወዳለ ቦታ ሄደ
ወደ ሌላ ቦታ ሂዶ በዚው ኖረ ማለት ነው:: አት: “በሌላ ቦታ ለመኖር ሄደ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ሀብቶቻቸው
የዔሣውና የያዕቆብ ሀብቶች
ከከብቶቻቸው ብዛት የተነሣ ሊበቃቸው አልቻለም
ያዕቆብና ዔሣው ያሉአቸውን ከብቶቻቸውን ለማሠማራት ምድሪቱ በቂ አልነበረችም:: አት “ከብቶቻቸውን ለማሠማራት አልበቃቸውም” ወይም “ለያዕቆብ ከብቶችና ለዔሣው ከብቶች በቂ አልነበረም” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
የነበሩበት ሥፍራ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የነበሩበት የሚለው ቃል ወደ አንድ ቦታ የመሄድና በዚያ መኖር ያመለክታል:: አት: “የሄዱበት ሥፍራ ወይም ቦታ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 36:9

ይህ የዔሣው ትውልድ ነው

ይህ ዐረፍተ ነገር በዘፍጥረት 36: 9-43 ያለውን የዔሣው ትውልድ ዝርዝር ያስታውቃል (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በሴይር ተራራማ አገር

በሴይር ተራራ ኖረዋል ማለት ነው:: የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: “በተራራማው በሴይር አገር የኖሩ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ኤልፋዝ ... ራጉኤል

እነዚህ የዔሣው ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:4 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓዳ ... ቤሴሞት

እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:2-3 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቴማን ... ኦማር... ስፎ... ጎቶም... ቄኔዝ

እነዚህ የኤልፋዝ መንዶች ልጆች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ትምናዕ

የኤልፋዝ ቁባት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:13

ራጉኤል ... ጽብዖን ... የዑስ ... የዕላም ... ቆሬ

እነዚህ የዔሣው ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:4-5 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ናሖት ዛራ ሣማ ሚዛህ

እነዚህ የራጉኤል ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓና ... ጽብዮን

የወንድ ሰዎች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በሴሞት ... አህሊባማ

እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36 2 3 እነዚህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:15

ኤልፋዝ

ይህ ከዔሣው ወንዶች ልጆች የአንዱ ስም ነው በዘፍጥረት 36: 4 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቴማን ... ኦማር ... ስፎ ... ቄኔዝ ... ቆሬ ... ጎቶም ... አማሌቅ

የኤልፋዝ ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓዳ

ከዔሣው ሚስቶች የአንዷ ስም ነው በዘፍጥረት 36: 2-3 ስምዋን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:17

ራጉኤል ... የዑስ ... የዕላም ... ቆሬ

እነዚህ የዔሣው ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:4-5 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ናሖት ዛራ ሣማ ሚዛህ

እነዚህ የራጉኤል ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36:13 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በኤዶም ምድር

ይህም በኤዶም ምድር ኖረዋል ማለት ነው:: አት: “በኤዶም ምድር የኖሩ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

በሴሞት ... አህሊባማ

እነዚህ የዔሣው ሚስቶች ስሞች ናቸው:: በዘፍጥረት 36 :2-3 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓና

ይህ የወንድ ሰው ስም ነው በዘፍጥረት 36:2 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:20

ሴይር

ሴይር የሚለው ቃል የአንድ ወንድ ሰውና የአንድ አገር ስም ነው

ሖሪውያን

“ሖሪውያን” የሚለው ቃል የአንድ ሕዝብ ቡድን ስም ነው:: በዘፍረት 14:6 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ(ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በምድሪቱ ነዋሪዎች

ኤዶም በተባለው በሴይር የሚኖሩ

ሎጣን ሶባል ጽብዖን ዓና ዲሶን ኤጽር ዲሳን

እነዚህ የወንዶች ሰዎች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቲምናዕ

ይህ የሴት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:23

ሶባል... ጽብዖን

እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው:: በዘፍረት 36:20 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዓልዋን ...ማኔሐት... ዔባል... ስፎና አውናም ... አያና ዓና

እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:25

ዓና ዲሶን ኤጽር ዲሳን

እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው:: በዘፍረት 36: 20-21 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::

አሊህባማ

ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ሔምዳን ኤስባን ይትራንና ክራን ቢልሐን ዛዕዋንና ዓቃን

እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:29

ሖሪውያን

የአንድ ሕዝበ ወገን ስም ነው:: በዘፍጥረት 14:6 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ሎጣን ሶባል ጽብዖን ዓና ዲሶን ኤጽር ዲሳን

እነዚህ የወንድ ሰዎች ስሞች ናቸው በዘፍረት 36:20-21 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በሴይር ምድር

ይህም በሴይር ምድር ኖረዋል ማለት ነው:: አት “በሴይር ምድር የኖሩ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 36:31

ቢዖር ባላቅ ኢዮባብ ዛራ

እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የከተማውም ስም

ይህ እርሱ የኖረበት ከተማ ነበር ማለት ነው:: አት: “እርሱ የኖረበት ከተማ ስም” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ዲንሃባ ባሶራ

እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:34

ኢዮባብ

ይህ የወንድ ሰው ስም ነው በዘፍጥረት 36 33 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ሑሳም ሃዳድ ባዳድ ሠምላ

እነዚህ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የቴማኒው ምድር ሑሳም

ይህም ሑሳም በቴማኒ ምድር ኖሮአል ማለት ነው:: አት “በቴማኒ ምድር የኖረ ሑሳም” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ዓዊት ምሥሬቃ

እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ቴማኒው

ቴማኒ የተባለው ሰው ትውልድ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

የከተማው ስም

ይህ እርሱ የኖረበት ከተማ ነበር ማለት ነው:: አት: “እርሱ የኖረበት ከተማ ስም” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የመሥሬቃው ሠምላ

ከመሥሬቃ የሆነው ሠምላ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

Genesis 36:37
ሠምላ
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው:: በዘፍጥረት 36:36 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
በወንዙ አጠገብ ያለው የርሆቦቱ ሳኦል በምትኩ ነገሠ
ሳኦል በርሆቦት ይኖር ነበር:: ርሆቦት በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ነው:: ይህ መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: "ከዚያም ሳኦል በምትኩ ነገሠ:: እርሱም ከኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ከነበረችው ከርሆቦት ነው (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ርሆቦት ፋው
የቦታዎች ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
የከተማው ስም
ይህ እርሱ የኖረበት ከተማ ነበር ማለት ነው:: አት: "እርሱ የኖረበት ከተማ ስም" (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
የሜዛሃብ ልጅ መጥሬድ የወለደቻት
እርሷም የሜዛሃብ ልጅ መጥሬት የወለደቻት ነበረች
መሄጣብኤል
የሴት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
Genesis 36:40
የነገድ አለቆች
የነገድ መሪዎች
እንደየስማቸው እንደየነገዳቸውና እንደየአገራቸው
ነገዳቸውና አገራቸው በአለቆቻው ወይም በመሪዎቻቸው ስም ተሰይሞአል:: አት: "የነገዶቻቸውና የሚኖሩባቸው አገራቸው በመሪዎቻቸው ስም ተሠይሞአል" የእነርሱ ስሞች እነሆ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ቲምናዕ ዓልዋ የቴት አህሊባማ ኤላ ፋኖን ቄኔዝ ቴማን ሚብሳር መግዲኤልና ዒራም
እነዚህ የህዝብ ወገኖች ወይም የነገዶች ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
በግዛታቸው ወይም በሠፈሩባቸው ምድር
"በሚኖሩባቸው ቦታዎች" ወይም "በኖሩባቸው ቦታዎች"
ይህም ዔሣው ነው
ይህ የስም ዝርዝር ዔሣው ነው የተባለው ይህ የትውልዱ አጠቃላይ ዝርዝር ነው ማለት ነው:: አት: "ይህ የዔሣው ትውልድ ዝርዝር ነው" (ተዛማጅ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)

---

Chapter 37
Genesis 37:1
አባቱ በቆየበት አገር በከነዓን ምድር ተቀመጠ
አባቱ በኖረበት በከነዓን ምድር ተቀመጠ
የያዕቆብ ትውልድ ታሪክ ይህ ነው
ይህ ዐረፍተ ነገር በዘፍጥረት 37: 1-50:26 ያለውን የያዕቆብን ትውልድ ያስታውቃል፡፡ እዚህ ያዕቆብ መላው በተሰቡን ይወክላል፡፡ አት "ይህ የያዕቆብ ቤተሰብ ታሪክ ነው" (ክፍልን እንደሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
አሥራ ሰባት ዓመት ዕድሜ
17 ዓመት ዕድሜ
ባላ
ይህ የራሔል ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29: 29 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ዘለፋ
ይህ የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29: 24 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ሚስቶች
እነዚህ ሴቶች ልጅ እንዲወልዱ ዘንድ ለያዕቆብ የተሰጡ የልያና የራሔል አገልጋዮች ናቸው
ስለእነርሱ መጥፎ ወሬ
ስለወንድሞቹ መጥፎ ወሬ
Genesis 37:3
አሁንም
ይህ ቃል ታሪኩ ስለ እስራኤልና ዮሴፍ ዳራ መረጃ መቀየሩን የሚያመለክት ነው (ዳራ መረጃ ይመልከቱ)
ስለወደደው
ይህ ወንድማማች ፍቅር ወይም ጓደኛ ፍቅር ወይም ቤተሰብ ፍቅር ያመለክታል ይህ በጓደኛሞችና በቤተሰብ መካከል የሚገለጽ ተፈጥሮአዊ የሰው ልጅ ፍቅር ነው
በስተርጅናው
እስራኤል በአረጀ ጊዜ ዮሴፍን ወልዶአል ማለት ነው:: አት: "እስራኤል በአረጀ ጊዜ የተወለደው" (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
እርሱ ለእርሱ ......አደረገለት
እስራኤል ለዮሴፍ ..አደረገለት
በኅብረቀለማት ያገጤ እጀ ጠባብ
እጅግ የሚያምር እጄ ጠባብ
በቅን አንደበት ሊያናግሩት አልቻሉም
በሰላም ሊያናግሩት ዘንድ አልቻሉም
Genesis 37:5
ዮሴፍም ሕልምን አለመ ሕልሙንም ለወንድሞቹ ሲነግራቸው የባሰ ጠሉት
ይህ በዘፍጥረት 37:6-11 የተቀመጠው ታሪክ ማጠቃለያ ሀሳብ ነው::
የበለጠውኑ ጠሉት
የዮሴፍ ወንድሞች ከዚህ በፊት ከሚጠሉት በላይ ጠሉት
ያየሁትን ይህን ሕልም ልንገራችሁ አድምጡኝ
ሕልሜን ልንገራችሁ አድምጡኝ
Genesis 37:7
አጠቃላይ መረጃ
ስለሕልሙ ዮሴፍ ለወንድሞቹ ይናገራል
እነሆ
"እነሆ" የሚለው ቃል ለሚቀጥለው አስደናቂ ሃሳብ ትኩረት እንዲሰጠው ያነቃል
እኛ ሁላችን
"እኛ" የሚለው ቃል ዮሴፍና ወንድሞቹን ሁሉ ያጠቃልላል (ሁሉን ያቀፈ እኛ ይመልከቱ)
ነዶ እናሥር ነበር
እህል ከታጨደ በኋላ ፍሬው ከገለባው እስኪበጠር ድረስ በየነዶው ታሥሮና ተከምሮ ይጠበቃል
እንሆ
"እነሆ" የሚለው ቃል ዮሴፍ ባየው እንደተደነቀ ይገልጻል
የእኔ ነዶ በድንገት ተነሥታ ቀጥ ብላ ቆመች የእናንተ ነዶዎች ዙሪያዋን ከበው ለእኔ ነዶ ሰገዱላት
እዚህ እንደሰው ነዶዎች ሲቆሙና ሲሰግዱ ይታያል እነዚህ ነዶዎች ዮሴፍንና ወንድሞቹን ይወክላሉ (በሰውኛ መንገድ አገላለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
በላያችን ልትነግሥብን ይሆን? ልትገዛ ይሆን?
እነዚህ ሁለቱም ሀረጐች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው የዮሴፍ ወንድሞች ጥያቄዎችን በመጠቀም ዮሴፍን ማላገድ ጀመሩ እነዚህ በዐረፍተ ነገሮች መልክ ሊገለጹ ይችላሉ አት ንጉሣችን አትሆንም እኛም ለአንተ አንሠግድም (አግናኝ ጥያቄዎችንና ተዛማጅ ተመሣሣይ አባባል ይመልከቱ)
እኛን ልትገዛ
እኛ የሚለው ቃል ዮሴፍን ሳይሆን ወንድሞቹን ያመለክታል (ሁሉን አቀፍና ሁሉን የማያቅፍ "እኛ" ይመልከቱ)
ለሕልሙና ለተናገረው ቃል
ስለ ሕልሙና ልሰተናገረው ቃል
Genesis 37:9
ሌላ ሕልም አለመ
ዮሴፍ ሌላ ሕልም አለመ
አሥራ አንድ ከዋክብት
11 ከዋክብት ቁጥሮች ይመልከቱ
አባቱ ገሠጸው እንዲህም አለው
እስራኤልም ገሠጸው አለውም
ይህ ያየሄው ሕልም ምንድን ነው? እኔና እናትህ ወደ ምድር ተጐንብሰን ልንሰግድል ነው?
እስራኤል ዮሴፍን ለማረም ጥያቄዎችን ይጠቀማል:: ይህ እንደ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል:: አት: "ይህ ያየሄው ሕልም ትክክል አይደለም:: እኔ እናትህና ወንድሞችህ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በፊትህ እንሰግድልህም!" (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)
ቀኑበት
አንድ ሰው ስኬታማና እጅግ ታዋቂ ከመሆኑ የተነሣ በቁጣ መሞላት ማለት ነው
ነገሩን በልቡ ያዘው
ስለዮሴፍ ሕልም ትርጉም ማሰቡን ቀጠለ ማለት ነው:: አት: "የሕልሙ ትርጉም ምን እንደሆን ማሰቡን ቀጠለ" (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
Genesis 37:12
ወንድሞችህ በሰኬም በጎችን ይጠብቁ አይደለምን?
እስራኤል በንግግሩ ውስጥ ጥያቄ ይጠቀማል:: ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት "ወንድሞችህ በሰኬም በጎችን ይጠብቃሉ" (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)
ና
ለመሄድና ወንድሞቹን ለማየት ዮሴፍ እንዲዘጋጅ እስራኤል መጠየቁን የሚገልጽ ነው:: አት "ተዘጋጅ" (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
እነሆኝ
ለመሄድ ተዘጋጅቸአለሁ(ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
እርሱም እርሱን አለው
እስራኤል ዮሴፍን አለው
ወሬያቸውን አምጣልኝ
ወንድሞቹና በጎቹ እንዴት እንደሆኑ ዮሴፍ ተመልሶ እንዲነግረው እስራኤል ይፈልጋል አት ተመለሰው ያገኘሄውን ንገረኝ ወይም ርፖርት አቅርብልኝ (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
በሸለቆው
ከሸለቆው
Genesis 37:15
እነሆ ዮሴፍ ሜዳ ላይ ወዲያና ወዲህ ሲባዝን ነበር አንድ ሰውም ዮሴፍን አገኘው
ዮሴፍ ወዲያና ወዲህ ሲባዝን አንድ ሰው ዮሴፍን አገኘው
እነሆ
በትልቁ ታሪክ ስለሌላ ክስተት መጀመሩን የሚያመለክት ነው በቀደሙ ክስተቶች ከነበሩ ሌሎች ሰዎች የሚያሳትፍ ነው በእርስዎ ቋንቋ ይህ የሚገለጽበት መንገድ ሊኖር ይችላል
ምን እያየህ ነው ?
ምን እየፈለግህ ነው?
ወዴት ነው እባክህ ንገረኝ
ወዴት እንደሆነ እባክህ ንገረኝ
ዶታይን
ከሰኬም 22 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ያለ ቦታ ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
Genesis 37:18
በሩቅ አዩት
በሩቅ እያለ የዮሴፍ ወንድሞች አዩት
ይገድሉት ዘንድ በእርሱ ላይ ተማከሩ
እርሱን ለመግደል አቀዱ
ያ ሕልም ዐላሚ መጣ
ያ ባለ ሕልም ይሄው መጣ
ስለዚህ አሁንም ኑ
ይህ አባባል ወንድሞቹ ዕቅዳቸውን መተግበር መጀመራቸውን ያሳያል:: አት: (ስለዚህ አሁን ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ክፉ አውሬ
አደገኛ አውሬ ወይም ሰው ጨካኝ አውሬ
ቦጫጭቆ በላው
ንጥቆ በላው
ከሕልሞቹም የሚሆነውን እናያለን
ወንድሞቹ ሊገድሉት አቅደዋልና ስለዚህ እስከሞተ ድረስ ሕልሞቹ ይፈጸሙ እንደሆን መናገራቸው አሽሙራዊ/ሽሙጣዊ አባባል ነው:: አት "እስቲ ሕልሞቹ ሲፈጸሙ እናያለን" (በአሽሙር/ሽሙጥ መንገድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
Genesis 37:21
ይህን ሰማ
እነርሱ የመከሩትን ሰማ
ከእጃቸው
ከእጃቸው የሚለው አባባል ሊገድሉት ያቀዱትን የወንድሞቹን እቅድ ያመለክታል:: አት "ከእነርሱ" ወይም "ከእቅዳቸው" (ተዛማጅ ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
ሕይወቱን አናጥፋ
ሕይወት ማጥፋት የሚለው ሀረግ አንድን ሰው ስለመግደል በንጎብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል በተዘዋዋሪ የሚገልጽ ነው። አት: "ዮሴፍን አንግደለው" (ንጎብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል በተዘዋዋራ መንገድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ደም አታፍስሱ
በግሡ አሉታዊነት ተጨምሮበታል ደግሞም ደምን ማፍሰስ አንድን ሰው ስለመግደል በንጎብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል በተዘዋዋሪ የሚገልጽ ነው። አት የማንኛውንም ሰው ደም አታፍስሱ ወይም አትግደሉት (በአሉታዊነት አዎንታዊነትን የመግለጽ ዘይቤና ንጎብነት ወይም ለዛ ባለ ቃል በተዘዋዋራ መንገድ የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
እጃችሁን አታንሡበት
አታቆስሉት ወይም አትጉዱት ማለት ነው አት አትጉዱት (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ከእጃቸው ሊያተርፈው
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: "ሮቤል ይህ ያለው ዮሴፍን ሊታርፈው ዘንድ ነው"
ከእጃቸው
ከእጃቸው የሚለው አባባል ሊገድሉት ያቀዱትን የወንድሞቹን እቅድ ያመለክታል:: አት "ከእነርሱ" ወይም "ከእቅዳቸው" (ተዛማጅ ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
ሊመልሰው
እናም ሊመልሰው
Genesis 37:23
እንደ ደረሰ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ተፈላጊ ክስተት ለመጠቆም ተጠቅሞአል በቋንቋህ እንዲህ ዓይነት ካለ በዚህ ቦታ ሊጠቀሙ ይችላሉ
በኀብረ ቀለማት ያገጠች እጀ ጠባቡን ገፈፉት
በኀብረ ቀለማት ያገጠች እጀ ጠባቡን ከላዩ ላይ ቀደዱት
ያገጠች ልብስ
ያገጠች እጀ ጠባብ፤ በዘፍጥረት 37:3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ
Genesis 37:25
እንጀራም ሊበሉ ተቀመጡ
እንጀራ በአጠቃላይ መግብን ያመለክታል አት ምግባቸውን ለመብላት ተቀመጡ ወይም የያዕቆብ ወንድሞች ምግባቸውን ሊበሉ ተቀመጡ (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግልጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ዐይኖቻቸውንም አንስተው አዩ እነሆም... የግመል ጓዝ
እዚህ አንስተው አዩ አንድሰው በውኑ አይኑን አንሰቶ እንደሚያይ ተደርጐ ተነግሮአል ደግሞም እነሆ የሚለው ቃል ሰዎች ላዩት ትኩረት ለመስጠት ተጠቅሞአል:: አት: "አይኖቻቸውን አነሡ እናም ወዲያውም የግመል ጓዝ አዩ" (ዘይቤያዊ አባባል ይመልከቱ)
ተሸክመው
ጭነው
ኬርቤ
ቅመማቅመም
በለሳን
የቆዳ ቁስለትን የሚፈውስና የሚከለክል ጣፋጭ ጣዕም ያለው ቅባታማ ነገር "መድኃኒት"
ጭነው ወደ ግብጽ የሚወርዱ
ወደ ግብጽ የሚያመጡ ይህ ግለጽ ሊደረግ ይችላል አት ለመሸጥ ወደ ግብጽ የሚወርዱ ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ
ወንድማችንን መግደልና ደሙን መሸሸግ ምን ይጠቅማናል?
ይህ እንደዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል:: አት "ወንድማችንን በመግደልና አሟሟቱን በመደበቅ እንጠቀምም" (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)
ደሙን መሸሸግ
የዮሴፍን ሞት በደበቅን የሚገልጽ ምሳሌዊ አነጋገር ነው:: አት "አሟሟቱን

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መደበቅ” (ዘይቤያዊ አባባል ይመልከቱ)
Genesis 37:27
ለእስማኤላዊያን
የእስማኤል ዘር ለሆኑ ለእነዚህ ሰዎች
እጃችንን በእርሱ ላይ አናንሳ
ይህም “አናቆስለው” ወይም “አንጉዳው” ማለት ነው አት: “አንጉዳው” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ወንድማችን ሥጋችን ነው
ሥጋ የሚለው ዘመድ ለሚለው ቃለ የሚቆም ምትክ ቃል ነው:: አት: “እርሱ የሥጋ ዘመዳችን ነው” (ተዛማጅ ምትክ ቃላትን የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
ወንድሞቹም የእርሱን ነገር ሰሙት
የይሁዳ ወንድሞች ሰሙት ወይም የይሁዳ ወንድሞች በሐሳቡ ተስማሙ
ምድያማዊያን ..... እስማኤላዊያን
ሁለቱም ስሞች የዮሴፍ ወንድሞች ያገኙአቸው ተመሣሣይ ነጋዴዎችን ያመለክታል
ለሃያ ጥሬ ብር
ለሃያ ጥሬ ብር ዋጋ (ቁጥሮችን ይመልከቱ)
ዮሴፍን ወደ ግብጽ የዘውት ሄዱ
ዮሴፍን ወደ ግብጽ ወሰዱት
Genesis 37:29
ሮቤል ወደ ጉድጓዱ ተመልሶ ሲያይ ዮሴፍን በማጣቱ
ሮቤል ወደ ጉድጓዱ ተመልሶ ዮሴፍን በማጣቱ እነሆ ተገረመ:: “እነሆ” የሚለው ቃል ሮቤል ዮሴፍ በሄዱን ባወቀ ጊዜ መገረሙን ያሳያል::
ልብሱን ቀደደ
ይህ የጥልቅ ጭንቀትና ሀዘን ምልክት ነው:: ይህ በግልጽ ሊገለጽ ይችላል:: አት: እጅግም ስላዘነ ልብሱን ቀደደ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ብላቴናው የለም እንግዲህ እኔ ወዴት እሄዳለሁ?
የዮሴፍ መጥፋቱን ችግር ትኩረት ለመስጠት ሮቤል ጥያቄ ይጠቀማል:: አት: “ብላቴናው ሄዶአል እንግዲህ ወደ ቤት መመለስ አልችልም” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)
Genesis 37:31
የዮሴፍ እጀ ጠባብ
አባቱ ያዘጋጀለት ያጌጠችውን እጀ ጠባብ ያመለክታል
ደም
የፍዬል ደም
አምጥተው
እጀ በባበሩን አምጥተው
ቦጫጭቆ በልቶታል
በልቶታል
በእርግጥም ዮሴፍ ተቦጫጭቆአል
ያዕቆብ የዮሴፍን አካል ክፉ አውሬ እንደገነጣጠለ አሰበ:: አት: “በእርግጥም ዮሴፍን ቦጫጭቆታል” (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ ይመልከቱ)
Genesis 37:34
ያዕቆብ ልብሱን ቀደደ
ይህ ጥልቅ መጨነቅንና ሀዘንን የሚያመለክት ነው ይህ በግልጽ ሊገለጽ ይችላል አት ያዕቆብ እጅግ ስላዘነ ልብሱን ቀደደ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
በወገቡም ማቅ ታጥቆ
ወገብ የሰውነት መሀከለኛው አካል ነው አት ማቅ ለብሶ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ተነሡ
እዚህ አባታቸውን ለማጽናናት የልጆች መጥጣት እንደ መነሣት ተደርጐ ተገልጾአል:: አት: “ወደ እርሱ መጡ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
እርሱ ግን ሊጽናና ባለመቻሉ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት: “ነገር ግን እንዲያጽናኑት አልፈቀደም” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
ወደ ሙታን ሥፍራ እያዘንሁ እወርዳለሁ
ከዛሬ ጀምሮ እስከሚሞት ድረስ እንደሚያዝን ይገልጻል:: አት: “በሚሞትበትና ወደ ሙትን ሥፍራ በሚወርድበትም ጊዜም በእርግጥ እያዘንኩ ይሆናል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ምድያማዊያን ሸጡት
ምድያማዊያን ዮሴፍን ሸጡት
ለዘበኞች አለቃ
ንጉሡን ለሚጠብቁ ዘበኞች መሪ

---

Chapter 38
Genesis 38:1
በዚያም ወራት ይሁዳ
ይህ ስለ ይሁዳ የሚናገረውን አድስ የታሪኩን ክፍል ያስታውቃል (አድስ ክስተት መጀመር ስለማስታወቅ ይመልከቱ)
ኤራስ ወደተባለ ዓዶሎማዊ
ኤራስ በዓዶሎም የሚኖር ወንድ ሰው ስም ነው (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)
ሴዋ
ሴዋ ይሁዳን ያገባች ከነዓናዊ ሴት ነች (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)
Genesis 38:3
እርስዋም ጸነሣ
የይሁዳ ሚስት ጸነሣ
ዔር ተብሎ ተሠየመ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “አባቱ ዔር ብሎ ሰየመው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
ስሙንም ... ጠራው
ሰየመው
ክዚብ
የቦታ ወይም የሀገር ስም ነው (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)
Genesis 38:6
ዔር
ይህ የይሁዳ ወንድ ልጅ ስም ነው:: በዘፍጥረት 38:3 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነበር
በእግዚአብሔር ፊት የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር የዔርን ክፋት እንደአየው ያመለክታል:: አት: “ክፉ ነበርና እግዚአብሔር አየው” (ፈሊጣው አነጋገር ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ቀሠፈው
ክፉ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር ቀሠፈው:: ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “ስለዚህ እግዚአብሔር ቀሠፈው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 38:8
አውናን
ይህ ከይሁዳ ወንድ ልጆች የአንዱ ስም ነው በዘፍጥረት 38:4 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)
ወደ ወንድምህ ሚስት ግባ
ይህ ታላቅ ወንድም አግብቶ ሳለ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት ተከታይ ወንድሙ ወደ መበለትዋ በመግባት ሩካቤ ሥጋ በመፈጸም ዘርን የማስቀጠል ባህል እንደሆነ ያመለክታል መበለትዋ የመጀመሪያ ወንድ ከወለደች ያ ወንድ ልጅ የሞተው ወንድም ልጅ እንደሆነ በመቆጠር የሟቹን ሀብት ይወርሳል::
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነበር
በእግዚአብሔር ፊት የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር የአውናን ክፋት እንደአየው ያመለክታል:: አት: “ክፉ ነበርና እግዚአብሔር አየው” (ፈሊጣው አነጋገር ይመልከቱ)
እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ቀሠፈው
ያደረገው ነገር ክፉ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር ቀሠፈው:: ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “ስለዚህ እንዲሁ ደግሞ እግዚአብሔር ቀሠፈው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 38:11
ምራቱ
የታላቅ ወንድ ልጁ ሚስት
ወደ አባትሽ ቤት
ይህም ማለት በዚህ በአባትዋ ቤት እንዲትኖር ነው:: አት “እናም በአባትሽ ቤት... ቢትኖሪ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ልጄ ሴሎም ለአካለ መጠን እስኪደርስ ድረስ
ይሁዳ ትዕማር ሴሎም ለአካለመጠን በደረሰ ጊዜ እንዲታገባው ያስባል:: አት “ልጄ

ሴሎም ለአካለ መጠን በደረሰ ጊዜ ሊያገባሽ ይችላል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ሴሎም
ይህ ከይሁዳ ወንድ ልጆች የአንዱ ስም ነው በዘፍጥረት 38፡5 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)
እንደ ወንድሞቹ ተቀሥፎ ይሞትብኛል ብሎ ስለ ሠጋ
ሴሎም ትዕማርን ቢያገባ እንደ ወንድሞቹ ይሞትብኛል ብሎ ይሁዳ ሠግቶአል:: አት “እርሱ እርስዋን ካገባ እንደወንድሞቹ ይሞትብኛል ብሎ ስለሠጋ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 38:12
ሹዓ
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው በዘፍጥረት 38፡2 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)
ይሁዳ ከሀዘኑ ተጽናና
ይሁዳም ሀዘኑን ባቆመ ጊዜ
የበጎቹን ጸጉር ወደሚሸልቱት ሰዎች ወደ ተምና
ተምና የበጎቹንነ ጸጉም የሚሸልቱ ስዎች ወዳሉበት ሥፍራ
ተምና … ኤናይም
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
እርሱና የእርሱ ጓደኛ ዓዶላማዊው ሒራ
ከዓዶላም ጓደኛው ሒራ አብሮት ሄደ
ሒራ ዓዶላማዊው
ሒራ የወንድ ሰው ስም ነው እናም ዓዶላም እርሱ የሚኖርበት ቀበሌ ስም ነው። በዘፍረት 38፡1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ትዕማር ተነገራት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “አንድ ሰው ለትዕማር ነገራት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
እይው አማትሽ
ስሚ ፤ እዚህ “እይው” የሚለው ቃል የትዕማርን ትኩረት ለመሳብ ተጠቅሞአል።
አማትሽ
የባልሽ አባት
የመበለትነት ልብስ
መበለቶች የሚለብሱት ልብስ
ሻሽ
ሴቶች ፊታቸውንና ጭንቅላታቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙት ከስስ ጨርስ የተሰራ ልብስ
ራስዋን ተከናንባ
ይህም ሰዎች እንዳያውቃት ራስዋን በልብስ በመከናነብ ሸፈነች ማለት ነው ሴቶች ራሳቸውን መከናነብ የሚያስችላቸው ሰፋፊ ልብሶች በባህሉ የተለመዱ ናቸው አት ሰዎች እንዳያውቃት በሰፋፊ ልብሶች ተከናነበች (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
መንገድ ዳር
በመንገድ ዳር ወይም በመንገድ
ለእርሱ ሚስት ሆና አልተሰጠችም ነበር
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ይሁዳ ለሴሎም ሚስት አድርጐ አልሰጣትም ነበር” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
Genesis 38:15
ፊትዋን ስለሸፈነች
ይሁዳ እንደ ጋለሞታ ያሰባት ፊትዋን ስለሸፈነች ብቻ ሳይሆን በከተማው መግቢያም ስለተቀመጠች ነው አት ጭንቅላትዋን ስለሸፈነችና ጋለሞቶች በሚቀመጡበት ቦታ ስለተቀመጠች ነበር (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ወደ እርስዋም አዘነበለ
ትዕማር በመንገዱ ዳር ነበረች አት እርስዋም ወደተቀመጠችበት ወደ መንገዱ ዳር ሄደ ወይም አዘነበለ(ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
እባክሽ ነዪ
እባክሽ ወደ እኔ ነዪ ወይም እባክሽ አሁን ነዪ
ምራቱ
የልጁ ሚስት
Genesis 38:17
ከመንጋዬ
ከፍዬሎች መንጋዬ
ማኅተም ቀለበት ከነማሰሪያው …. በትር
ማኅተም ብር መሣይ በላዩ ላይ ቅርጽ የተቀረጸበት የቀለጠ ሰም ለመቅረጽ የሚጠቀምበት ነው ቀለበት ማኅተም ያለበትና ባለቤቱ በአንገት የሚያደረገው ነው በትር ከረጅም እንጨት የተሠራና በአዳጋች በመንገድ የሚጠቀሙበት ነው
ለእርሱም ጸነሰች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “እርሱም እርሷን አስረገዛት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
Genesis 38:19
ሻሽ
ሴቶች ፊታቸውንና ጭንቅላታቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙት ከስስ ጨርስ የተሰራ ልብስ ነበር:: በዘፍጥረት 38: 14 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ
የመበለት ልብስዋን ለበሰች
መበለቶች የሚለብሱትን ልብስ ለበሰች:: በዘፍጥረት 38: 14 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
አዶሎማዊ
በአዶሎም ቀበለ የሚኖር ሰው በዘፍጥረት 38፡ 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
መያዣ የሰጣትን
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “መያዣውን ለማስመለስ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
ከሴቲቱ እጅ
እዚህ እጅ የሚለው ቃል በእርስዋ ቁጥጥር ሥር እንደሆነ አበክሮት ይሰጣል:: የሴቲቱ እጅ ሴቲቱን ይወክላል:: አት “ከሴቲቱ” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
Genesis 38:21
አዶሎማዊ
በአዶሎም ቀበለ የሚኖር ሰው በዘፍጥረት 38 1 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
የአገሩ ሰዎች
በዚያ ከሚኖሩ ሰዎች እንዳንዶች
ቤተ ጣዖት ዝሙት አደሪዋ
በቤተ ጣዖት የሚታገለግል ዝሙት አዳሪ
ኤናይም
ይህ የቦታ ስም ነው በዘፍጥረት 38፡14 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ። (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)
አለዚያ መሳቂያ እንሆናለን
የሆነውን ነገር ሰዎች ከሰሙ በይሁዳ ይስቁበታል ይሣለቁበታል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ወይም ደግሞ የሆነውን ሰዎች ካወቁ ይስቁብናል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ እና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
Genesis 38:24
እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የታሪኩን አድስ አካል ጅማሬ ያመለክታል (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)
ለይሁዳ ተነገረው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “አንድ ሰው ለይሁዳ ነገረው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
ምራትህ ትዕማር
ትዕማር የታላቅ ልጅህ ሚስት
ከዚህም የተነሣ ጸነሰች
ከዚህ የሚለው ቃል ከዝሙት ከፈጸመችው ዝሙት ማለት ነው ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ከዚህም አረገዘች” ወይም “አረገዘች” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
አምጡአት
አውጡአት

በእሳት ትቃጠል

ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እንዲትሞት እናቃጥላታለን” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እርስዋም ባወጡአት ጊዜ

ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እነርሱ ባወጡአት ጊዜ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

አማትዋ

የባልዋ አባት

ማኅተም ቀለበት ከነማሰሪያው .... በትር

ማኅተም ብር መሣይ በላዩ ላይ ቅርጽ የተቀረጸበት የቀለጠ ሰም ለመቅረጽ የሚጠቀምበት ነው:: ቀለበት ማኅተም ያለበትና ባለቤቱ በአንገት የሚያደርገው ነው በትር ከረጅም እንጨት የተሠራና በአዳጋች በመንገድ የሚጠቀሙበት ነው:: (በዘፍጥረት 38: 18 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ)

ሴሎም

ይህ ከይሁዳ ወንድ ልጆች የአንዱ ስም ነው:: በዘፍጥረት 38:5 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተረጐም ይመልከቱ)

Genesis 38:27

በዚያን ጊዜ

ይህ ሀረግ የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ያመለክታል (አድስ ክስተት ስለማታወቅ ይመልከቱ)

እነሆ

እነሆ የሚለው ከዚህ በፊት ያልታወቀው ትዕማር መንታ ልጆችን እንደተሸከመች እንድንገረም ለማድረግ ተጠቅሞአል

ስትወልድም እንዲህ ሆነ

እንዲህ ሆነ የሚለው ሀረግ በታሪኩ ዋና ክስተት ያመለክታል በቋንቋዎ ይህን የመሰለውን የመግለጽ አባባል ካለ ይጠቀሙ

አንደኛው እጁን አወጣ

ከሕጻኖች አንደኛው እጁን አወጣ

አዋላጅ

አንድ ሴት በሚትወልድበት ጊዜ የሚረዳት ሰው ነው በዘፍረት 35:17 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ

ቀይ ክር

ደማቅ ቀይ ክር

በእጁ

በአምባሩ ዙሪያ

Genesis 38:29

እነሆ

እነሆ የሚለው ቃል ለሚከተለው የሚያስገርም መረጃ ትኩረት እንድንሰጠው ነው

እንዴት ጥሰህ መጣህ!

ይህ ሁለተኛው ሕጻን ቀድሞ ሲወጣ አዋላጅዋ በማየት የተደነቀችውን የሚያሳይ ነው:: አት “እንዴት የራስህን መንገድ ጥሰህ ወጣህ!” ወይም “ሰንጥቀህ ቀድመህ ወጣህ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመለከቱ)

ስም ተሰጠው ወይም ተሰየመ

ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት “እርስዋ ስም ሰጠችው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ፋሬስ

የወንድ ልጅ ስም ነው ተርጓሚዎች እንደሚከተለው የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ:: ፋሬስ የሚለው ስም ጥሶ መውጣት ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

ዛራ

ይህ የወንድ ልጅ ስም ነው ተርጓሚዎች እንደሚከተለው የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ:: ዛራ የሚለው ስም ቀይ ክር ወይም ደማቅ ቀይ ክር ማለት ነው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

---

Chapter 39

Genesis 39:1

ዮሴፍ ወደ ግብጽ ወርዶ ነበር

ወደ ግብጽ መጓዝ ወደ ላይ ወደ ተስፋይቱ ምድር የመጓዝ ተጻራሪ ወደ ታች መውረድ ተደርጐ ይቆጠራል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እስማኤላዊያን ዮሴፍን ወደ ግብጽ ወሰዱት” (ፈሊጣዊ አነጋገርና ተሻጋሪ ግሥ እና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የዮሴፍ ጋር ነበረ

ይህ እግዚአብሔር ዮሴፍን ረድቶታል ሁልጊዜም ከእርሱ ጋር ነበር ማለት ነው:: አት “እግዚአብሔር ዮሴፍን መራው አገዘውም” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

አሳዳሪው ቤት ኖረ

እዚህ ጸሓፊው በአሳዳሪው ቤት መሥራቱን በአሳዳሪው ቤት እንደመኖር ይናገራል:: በአሳዳሪዎቻቸው ቤት መሥራት የሚችሉት በጣም ታማኝ የሆኑ ሎሌዎች ብቻ ናቸው። አት እርሱም በቤት ውስጥ ይሠራ ነበር (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 39:3

አሳዳሪው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ አየ

አሳዳሪው እግዚአብሔር እርሱን እየረዳ እንደሆነ አየ ማለት ነው አት እግዚአብሔር እየረዳው እንደሆነ አሳዳሪው አየ (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሥራውን ሁሉ እንዳከናወነለት

እግዚአብሔር ዮሴፍ የሚሠራው ሁሉ መከናወንለት አደረገ

ዮሴፍ በእርሱ ዘንድ ሞገስ አገኘ

ሞገስ ማግኘት በአንድ ሰው ተቀባይነትን ማስረገጥ ማለት ነው በእርሱ ዘንድ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል በሰውዬው አመለካከት እንደሆነ ያመለክታል:: ተገቢ ትርጉሞች እነሆ 1) ጲጥፋራ በዮሴፍ ተደስቶአል 2) እግዚአብሔር በዮሴፍ ተደስቶአል (ፈሊጣዊ አባባል ይመልከቱ)

ጲጥፋራን አገለገለ

የጲጥፋራ የግል ሎሌው ነበር ማለት ነው

ጲጥፋራ ዮሴፍን በቤቱ ላይ ሾመው ያለውን ሀብት ሁሉ በኃላፊነት ሰጠው

ጲጥፋራ በቤቱና የጲጥፋራ በሆነው ሁሉ ላይ ለዮሴፍ በኃላፊነት ሰጠው

በእርሱ ኃላፊነት ሥር አደረገ

አንድ ነገር በአንድ ሰው ኃላፊነት ሥር ሲሆን ያ ሰው ያንን ነገር ለመንከባከብና ደኅንነቱን ለመጠበቅ ኃላፊነት አለው ማለት ነው:: አት “ዮሴፍ እንዲንከባከብ ሰጠው” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 39:5

ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤትና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር የግብጻዊውን ቤት ባረከ

ተውላጤ ስሞችን ከመጠቀምዎ በፊት “ዮሴፍ” እና “ግብጻዊው” የሚሉ ቃላትን መጠቀም ይችላሉ:: ግብጻዊው ዮሴፍን በቤቱና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ኃላፊነት ሰጠው እናም ከጊዜ ወደ ጊዜ በዮሴፍ ምክንያት እግዚአብሔር የግብጻዊውን ቤት ባረከ::

እንዲህም ሆነ

እነዚህ ሁለቱ ጥቅሶች ለሚቀጥለው ክስተት ዳራ መረጃ እንደሆኑ ለአንባቢያን ለመናገር ይህ ሀረግ ተጠቅሞአል

እርሱም እርሱን በቤቱና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ሾመው

ጲጥፋራ ዮሴፍን በቤቱና ባለው ተብት ሁሉ ላይ ሾመው

ባረከው

በሚባረከው ነገር ወይም ሰው መልካም ወይም ጠቃሚ ነገር እንዲደረግ ምክንያት መሆን ማለት ነው

የእግዚአብሔር በረከት ሆነ

እዚህ ጸሐፊው እግዚአብሔር የሰጠውን በረከት በአንድ ነገር ላይ እንደተቀመጠ መሸፈኛ አድርጐ ይናገራል:: አት: “እግዚአብሔር ባረከ” ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ

በግቢም በውጭም ባለው የጲጥፋራ ሀብት ንብረት ሁሉ

ይህ ቤት እረሻውንና ከብቶችን ያለመክታል የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “በጲጥፋራ ቤትና በከብቶችና እርሻው ሁሉ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቀ መረጃ ይመልከቱ)

ጲጥፋራ ማንኛውንም ጉዳይ በዮሴፍ ቁጥጥር ሥር አድርጐ/በዮሴፍ ላይ ጥሎ ነበር

አንድ ነገር በአንድ ሰው ቁጥጥር ሥር ሲሆን ያ ሰው ሊጠብቀውና ሊንከባከበው ኃላፊነት አለው ማለት ነው አት: “ስለዚህ ጲጥፋራ ባለው ሁሉ ላይ ለዮሴፍ ስልጣን ሰጠው”

ከሚበላው እንጀራ በቀም ምንም የሚያውቀው አልነበረም

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ምን ምግብ መመገብ እንዳለበት ከመወሰን በቀር በቤቱ ስላለው ማንኛውም ነገር አይጨነቅም ነበር ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል አት ጲጥፋራ ምን መመገብ እንደሚፈልግ ብቻ ማሰብ ነበረበት በቤቱ ስላለው ማንኛውም ነገር መጨነቅ የለበትም (ግምታዊ እውቀትና ጥልቀ መረጃ ይመልከቱ)

አሁንም

"አሁንም" የሚለው ቃል ስለ ዮሴፍ ዳራ መረጃ ለመስጠት በታሪኩ መስመር ውስጥ ጣልቃ ማስገባቱን ያመለክታል (ዳራ መረጃ ይመልከቱ)

ዮሴፍ መልከ መልካምና ውብ ነበር

ሁለቱም ቃላት ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ዮሴፍ የሚያስደስት ቁመና እንዳለው ያመለክታሉ:: ጠንካራና ጥሩ ቁመና ነበረው:: አት: "ጠንካራና መልከመልካም ነበር"

Genesis 39:7

ከዚህ በኋላ እንደዚህ ሆነ

እናም ደግሞ ይህ ሀረግ አድስ ክስተት መጀመሩን ሊያመለክት ተጠቅሞአል (አዲስ ክስተት ማታወቅ ይመልከቱ)

አይው

ስሚው ዮሴፍ የጲጥፋራን ሚስት መስብ/ትኩረት ለማግኘት ይህን ቃል ተጠቅሞአል

ጌታዬ በቤቱ ውስጥ ስላለው ሁሉ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም

"ጌታዬ በኃላፊነቴ ሥር ስላለው ስለቤቱ ሁሉ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም":: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት "ጌታዬ ስለቤቱ ያምነኛል" (ድርብ አሉታዊነት ይመልከቱ)

ጌታዬ ያለውን ሁሉ በኃላፊነት ለእኔ ስለሰጠኝ

አንድ ነገር "በአንድ ሰው ኃላፊነት ሥር" ሲሆን ያ ሰው እንዲንከባከበውና እንዲጠብቀው ኃላፊነት አለው ማለት ነው:: አት: "ያለውን ሁሉ በኃላፊነት ስለሰጠኝ" (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ለዚህ ቤት ከእኔ የሚበልጥ ሰው የለም

እዚህ ጸሓፊው ኃላፊነትን እንደ ትልቅነት ይናገራል አት: "ከማንም ሰው የበለጠ ለዚህ ቤት ኃላፊነት አለኝ" (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ከአንቺ በቀር ያልሰጠኝ ነገር የለም

ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት: "እርሱ ያለሰጠኝ ነገር ቢኖር አንቺን ብቻ ነው" (አሉታዊነትን በአዎንታዊነት የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እንዴት ይህን ክፉ ድርጊት ፈጽሜ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት አሠራለሁ

ዮሴፍ ትኩረት ለመስጠት ጥያቄ ይጠቀማል ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ይህን ክፉ ድርጊት ፈጽሜ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት አልሠራም (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

Genesis 39:10

በየዕለቱ ለዮሴፍ ትነግረው ነበር

ከእርስዋ ጋር እንዲተኛ በተደጋጋሚ ትጠይቀው ነበር ማለት ነው:: የዚህ ጥቅስ ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት: "ዮሴፍ ከእርስዋ ጋር እንዲተኛ ትጐተጉተው ነበር" (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ከእርስዋም ጋር እንዲሆን

እንዲቀርባት

እንዲህም ሆነ

"እንዲሁም ደግሞ" የሚለው ሀረግ በታሪኩ አድስ ክስተት መጀመሩን ለማመልከት ነው (አዲስ ክስተት ስለማታወቅ ይመልከቱ)

ከቤቱ አገልጋዮችም አንድም ሰው

በቤቱ ከሚያገለግሉ ሰዎች ማንም

ሸሽቶ ከቤት ወጣ

"እናም ወዲያው ሮጦ ወደ ውጪ ወጣ" ወይም "እናም ወዲያው ሮጦ ከቤት ወጣ"

Genesis 39:13

እንዲህም ሆነ .... ጠራች

ከዚያም .... ጠራች እንዲህም ሆነ የሚለው ሀረግ በታሪኩ ሁለተኛውን ክስተት ለማመልከት ተጠቅሞአል (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ሸሽቶ ወደ ውጭ ወጣ

ወዲያው ሮጦ ከቤት ወጣ

የቤትዋን ሰዎች

በቤትዋ የሚሠሩ ሰዎች

አያችሁ

"ተመልከቱ" ወይም "ሰማችሁ" ወይም "ስለሚናገረው ነገር ትኩረት አድርጉ"

ከእኔ ጋር ሊተኛ ወደ እኔ ገባ

እዚህ የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍ ሊይዛትና ከእርስዋ ጋር ሊተኛ እንደሞከረ ትከሳለች

እንዲህም ሆነ መጮሄን ሲሰማ

ድምጼን ከፍ አድርጌ መጮሄን ሲሰማ እንዲህም ሆነ የሚለው ሀረግ የተጠቀመው በታሪኩ ሁለተኛውን ክስተት ለማመልከት ነው (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

Genesis 39:16

ጌታውም

የዮሴፍ ጌታ ይህ ጲጥፋራን ያመለክታል::

እንዲህ ስትል ነገረችው

ይህን ነገር እንዲህ ብላ ነገረችው

ወደ እኛ ያመጣሄው

"እኛ" የሚለው ቃል ጲጥፋራን ሚስቱንና ሌሎች በቤት ውስጥ ያሉትን ጠቃልላል (ሁሉ አቀፍ እኛን ይመልከቱ)

መሣለቂያ ሊያደርገኝ ወደ እኔ ገባ

መሣቂያ ሊያደርገኝ ወደ እኔ ገባ መሣለቂያ የሚለው ቃል ሊይዘኝና ከእኔ ጋር ሊተኛ የሚለውን አባባል በንኀብነት ወይም አንድን ነገር ለዘብ ባለ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገለጽ ነው:: አት "ወዳለሁበት ገባ አስገድዶ ከእኔ ጋር ሊተኛ ሞከረ" (ንኀብነት ወይም አንድን ነገር ለዘብ ባለ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ

"ከዚያም" የጲጥፋራ ሚስት ይህን ሀረግ የተጠቀመችው ዮሴፍ ከእርስዋ ጋር ለመተኛት መሞከሩን ለእርሱ የሚትነግረውን የታሪኩን ሁለተኛውን ክስተት ለማመልከት ነው::(አዲስ ክስተት ስለማታወቅ ይመልከቱ)

ሸሽቶ ወደ ውጭ ወጣ

ወዲያው ሮጦ ከቤት ወጣ

Genesis 39:19

እንዲህም ሆነ

"እንዲህም ሆነ" የሚለው ሀረግ በታሪኩ አዲስ ክስተት መጀመሩን ለማመልከት ተጠቅሞአል (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

ጌታውም

የዮሴፍ ጌታ ይህ ጲጥፋራን ያመለክታል ይህ መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት የዮሴፍ ጌታ ጲጥፋራ

እጅግ ተቈጣ

ጲጥፋራ እጅግ ተቈጣ

የንጉሡ እስረኞች ወደ ተጋዙበት እስር ቤት

ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አተ ንጉሡ እስረኞችን ያኖረበት ቦታ ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ

በዚያ ነበረ

ዮሴፍ በዚያ ቆየ

Genesis 39:21

ነገር ግን እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ

እግዚአብሔር ለዮሴፍ ተጠነቀቀለት እናም ቸር ነበረ:: "ነገር ግን እግዚአብሔር ለዮሴፍ ቸር ነበር" ወይም "እግዚአብሔር ዮሴፍን ተንከባከበ" (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የቃል ኪዳን ታማኝነቱን ገለጸለት

"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ታማኝ" ወይም "በታማኝነት" ሊገለጽ ይችላል:: አት ከእርሱ ጋር ለገባው ቃል ኪዳን ታማኝ ነበር ወይም በታማኝነት ወደደው (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

በወህኒ ቤት አዛዡም ዘንድ ሞገስን ሰጠው

ይህም እግዚአብሔር የወህኑ ቤት አዛዡ ዮሴፍን እንዲቀበለውና እንዲንከባከበው አደረገው አት እግዚአብሔር የእስር ቤቱ አዛዡ በዮሴፍ እንዲደሰት አደረገው (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

የእስር ቤቱ አዛዥ

"የእስረኞች አስተዳደር" ወይም "በእስር ቤቱ ኃላፊነት የተሰጠው"

በዮሴፍ እጅ አሳልፎ ሰጣቸው

እዚህ "እጅ" የሚለው የዮሴፍን ኃይል/አቅም ወይም ታማኝ ኃላፊነት ይወክላል"" አት "ዮሴፍን አለቃ አደረገው" (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

በዚያ ለሚደረገው ማንኛውም ነገር ዮሴፍ ኃላፊ ነበር

"ዮሴፍ በዚያ ለሚደረገው ነገር ሁሉ ኃላፊ ነበር"

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበረ
ይህ እግዚአብሔር እንዴት እንደረዳውና እንደመራው የሚያመለክት ነው። አት “እግዚአብሔር ዮሴፍን ስለመራው” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
የሚያደርገውን ሁሉ እግዚአብሔር ያሳካለት ነበር
ዮሴፍ የሚያደርገውን ሁሉ እግዚአብሔር ያሳካለት ነበር

Chapter 40
Genesis 40:1
ከዚህም በኋላ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው በታሪኩ አዲስ ክስተት መጀመሩን ለማመልከት ነው። (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)
የመጠጥ አሳላፊ
ይህ ለንጉሡ መጠጥ የሚያቀርብ ሰው ነው
እንጀራ ቤቱ
ይህ ለንጉሡ ምግብ የሚያዘጋጅ ሰው ነው
ጌታቸውን በደሉት
ጌታቸውን አስቆጡት
የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃና የእንጀራ ቤቱ አዛዥ
ዋና የመጠጥ አሳላፊና ዋና እንጀራ አቅራቢ
በዘበኞቹ አለቃ ቤት ወዳለው እስር ቤት አስገባቸው
በዘበኞቹ አለቃ በሚተዳደረው የቤት ውስጥ እስር ቤት አስገባቸው
አስገባቸው
ንጉሡ ወደ እሥር ቤት አላስገባቸውም ነገር ግን እንዲታሠሩ አዘዛቸው። አት “እነርሱ እንዲያስገቡ አደረጋቸው” ወይም “ዘበኛው እንዲያስገባቸው አዘዘ” (ተዛማጅ ምትክ አባባሎችን የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
ዮሴፍ ወደጋዘበት እስር ቤት
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ይህ ዮሴፍ የነበረበት ተመሣሣይ እስር ቤት ነው ወይም ይህ ጲጥፋራ ዮሴፍን ያስገባበት ተመሣሣይ እስር ቤት ነው (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
Genesis 40:4
በእስር ቤት ጥቂት ጊዜ ቆዩ
በእስር ቤት አያለ ጊዜያት ቀን ተቀመጡ
Genesis 40:6
ዮሴፍ ወደእነርሱ ገባ
ዮሴፍ ወደ መጠጥ አሳላፊውና እንጀራ አቅራቢው ገባ
እነሆም አዝነው አያቸው
እነሆም የሚለው ቃል ባየው ነገር ዮሴፍ እንዴት እንደተገረመ የሚያሳይ ነው። አት “እነርሱን አዝነው በማየቱ ተገረመ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
አብረውት የነበሩ የፈርዖን ሹማምንት
ይህ የጠጅ አሳላፊዎች አለቃና የእንጀራ አቅራቢዎች አዛዥ ያመለክታል
በጌታው ግቢ በግዞት
በጌታው ግቢ በእስር ቤት፤ ጌታው የዮሴፍ ጌታ፤ የዘበኞች አለቃ የሚያመለክት ነው
ትርጓሜ ከእግዚአብሔር የማገኝ አይደለምን?
አጽንዖት ለመስጠት ዮሴፍ ጥያቄ ይመለከታል:: ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ትርጓሜ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው! ወይም ለሕልሞች ትርጉምን መስጠት የሚችል እግዚአብሔር ነው” (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)
እስቲ ንገሩኝ
ሕልማቸውን እንዲነግሩት ዮሴፍ ይጠይቃቸዋል:: አት “ሕልሞቻችሁን አባካችሁ ንገሩኝ”
Genesis 40:9
የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ
ለንጉሡ መጠጦችን የሚያቀርብ ዋና ሰው ነው”” በዘፍጥረት 40: 2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
በሕልሜ እነሆ የወይን ዛፍ በፊቴ ሆና አየሁ
“በሕልሜ የወይን ጣፍ በፋቴ ሆና አየሁ!” የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ባየው ነገር እንደተደነቀና ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ለማሳየት “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል::
ዘለላዎችዋም በሰሉ
ዘለላዎችዋም ተንዠርግገው በሰሉ
ጨመቅሁአቸው
ከእነዚያ የጁስ ጭማቂ አወጣሁ ማለት ነው አት ከእነዚያ ጁስ ጨምቄ አወጣሁ
(ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 40:12
የዚህ ትርጓሜ ይህ ነው
የሕልሙ ትርጓሜ ይህ ነው
ሶስቱ ሐረግ ሶስት ቀን ነው
ሶስት ሐረጐች ሶስት ቀኖች ያመለክታሉ
በሶስት ቀኖች ውስጥ
እስከ ሶስት ቀኖች
ራስህን ከፍ ከፍ ያደርጋል
እዚህ ፈርዖን ከእስር ቤት የመጠጥ አሳላፊዎችን አለቃ የሚያወጣው ፈርዖን ከፍ ከፍ እንደሚያደርገው ተደርጐ ተነግሮአል:: አት “ከእስር ቤት ያወጣሃል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ወደ ቀድሞ ሹመትህ ይመልስሃል
ወደ ሥራህ ይመልስሃል
በነበርህበት ጊዜ
በነበርህበት ጊዜ ታደርግ እንደነበረው
Genesis 40:14
ቸርነት አድርግልኝ
ቸር ሁንልኝ
ስለእኔም ለፈርዖን ንገርልኝና ከዚህም እስር ቤት አስወጣኝ
ዮሴፍም የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ስለእርሱ ለፈርዖን እንዲነግረው ከዚህም የተነሣ ፈርዖን ከእስር ቤት እንዲያስወጣው ማለት ነው:: አት: “ስለእኔ ለፈርዖን በመንገር ከእስር ቤት እንዲወጣ እርዳኝ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
በእርግጥ በአፈና ውስጥ ነኝ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “በእርግጥ ሰዎች አፍነው አምጥተውኛል” ወይም “በእርግጥ እስማኤላዊያን ይዘው አምጥተውኛል” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
ከዕብራዊያን ምድር
ዕብራዊ ሰዎች ከሚኖሩበት ምድር
አሁንም ቢሆን እዚህ እስር ቤት የተጣልሁት አንዳች ጥፋት ኖሮብኝ አይደለም
እናም ደግሞ እዚህ በግብጽ በሚርበት ጊዜ በእስር ቤት እንዲጣል የሚያደርገኝን ምንም ነገር አላደረግሁም
Genesis 40:16
የእንጀራ ቤት አዛዡም
ይህ ለንጉሡ ምግብ የሚያቀርብ መሪ ሰው እንደሆነ ያመለክታል:: በዘፍጥረት 40:2 ይህ እንዴት እንደተተረጐመ ይመልከቱ::
እኔም ደግሞ ሕልም አይቻለሁ እናም
እኔም ደግሞ ሕልም አይቻለሁ እናም በሕልሜ
እነሆም ሶስት መሶብ እንጀራ በራሴ ላይ ተሸክሜ ነበር
ሶስተ መሶብ እንጀራ በራሴ ላይ ተሸክሜ ነበር! እዚህ የእንጀራ ቤቱ አዛዡ “እነሆ” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ባየው ሕልም መገረሙንና ዮሴፍም ትኩረት እንዲሰጠው ለማሳየት ነው::
ለፈርዖን ከተዘጋጀው እንጀራ
ለፈርዖን ከተዘጋጀው ምግብ
Genesis 40:18
ፍቺው ይህ ነው
የሕልሙ ትርጉም ይህ ነው
ሶስቱ መሶቦች ሶስት ቀኖች ናቸው
ሶስት መሶቦች ሶስት ቀኖችን ይወክላሉ
ራስህን ከፍ ያደርጋል
ዮሴፍ በዘፍረት 40:13 ለመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ በሚናገርበት ጊዜ ደግሞ ራስህን ከፍ ያደርጋል የሚለውን ሀረግ ተጠቅሞአል እዚህ ግን የተለየ ትርጉም አለው አማራጭ ተገቢ ትርጉሞች: (1) በአንገትህ ገመድ በማሠር ራስህን ከፍ ያደርጋል

ወይም (2) ራስህን በመቁረጥ ከፍ ያደርግሃል::
ሥጋ
የ “ሥጋ” ቀጥታ ትርጉሙ የአንድ ሰው አካል ክፍል ማለት ነው
Genesis 40:20
እንዲህም ሆነ በሶስተኛውም ቀን
ከዚያም በኋላ በሶስተኛውም ቀን እዚህ እንዲህም ሆነ የሚለው ሀረግ የተጠቀመው አዲስ ክስተትን ለማመልከት ነው (አዲስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)
ግብር አበላ
ግብዣ ነበረው
የመጠጥ አሳላፊዎችን አለቃ
ይህ ለንጉሡ መጠጥን የሚያዘጋጅና የሚያቀርብ መሪ ሰው ነበር። በዘፍጥረት 40፡2 እነዚህ ቃላት እንዴት እንደተተረጐሙ ይመልከቱ፡
የእንጀራ ቤት አዛዡን
ይህ ለንጉሡ ምግብን የሚያዘጋጅ መሪ ሰው እንደሆነ ያመለክታል:: በዘፍጥረት 40:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ
የመጠጥ አሳላፊዎቹን አለቃ ወደ ቀድሞ ሹመቱ መለሰው
የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ሹመት ወይም ኃላፊነት እንደመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ሥራው እንደሆነ ያመለክታል አት ለመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ሥራውን መልሶ ሰጠው (ተዛማጅ ምትክ ቃላትን ስለመጠቀም ይመልከቱ)
ነገር ግን የእንጀራ ቤት አዛዡን ሰቀለው
ፈርዖን ራሱ አልሰቀለውም ይሁን እንጂ እንዲሰቀል አዘዘ አት የእንጀራ ቤት አዛዡ እንዲሰቀል አዘዘ ወይም ዘበኞቹ ወይም ጥበቃዎቹ የእንጀራ ቤት አዛዡን እንዲሰቅሉ አዘዘ (ተዛማጅ ምትክ ቃላትን ስለመጠቀም ይመልከቱ)
ልክ ዮሴፍ እንደተረጐመላቸው
ይህ ዮሴፍ ሕልማቸውን እንደተረጐመላቸው የሚለውን ያመለክታል አት የሁለቱን ሰዎች ሕልም ዮሴፍ እንደተረጐመላቸው እንዲሁ ሆነ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

---

## Chapter 41

Genesis 41:1
እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ያመለክታል በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ካለ ያን ሊጠቀሙ ይችላሉ (አዲስ ክስተትን ማስታወቅ ይመልከቱ)
ድፍን ሁለት ዓመታት ካለፈ በኋላ
በእስር ቤት ከዮሴፍ አብረውት ስለነበሩት የፈርዖን መጠጥ አሳላፊዎች አለቃና እንጀራ ቤት አዛዡ ሕልሞችን ዮሴፍ ከተረጐመላቸው ሁለት ዓመታት ካለፊ በኋላ
እነሆም ቆሞ ነበር
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል በሰፊው ታሪክ ሌላ ክስተት መጀመሩን ያመለክታል በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ሊኖር ይችላል። አት “ቆሞ በመገኘቱ ገርሞት ነበር”
ቆሞ ነበር
ፈርዖ ቆሞ ነበር
መልካምና የወፈሩ
ጤናማና የወፈሩ
በውሃውም ዳር ባለው ቀጠማ ተሰማርተው ነበር
በወንዙ ዳር የበቀለውን ሣር ይበሉ ነበር
ቀጤማ
በረግረጋማ ቦታ የሚበቅል ቀጭንና ረጅም ሣር ነው
እነሆ ሌሎች ሰባት ላሞች
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል ፈረዖን እንደገና ባየው ነገር እንደተገረመ ያሳያል
የከፉና የከሱ
ታማሚና የከሱ
ወንዝ ዳር
“በወንዝ ዳር” ወይም “ወንዝ ዳረቻ ላይ” ይህ በአንድ ወንዝ ዳር ጠርዝ የሚገኝ ከፍታ ያለው መሬት ማለት ነው::
Genesis 41:4
የከፉና የከሱ
“ደካማና የከሱ” በዘፍጥረት 41:3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
መልካምና የወፈሩ
“ጤናማና የደለቡ ወይም በደንብ የበሉ” በዘፍጥረት 41:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
ነቃ
ከእንቅልፉ ነቃ
ሁለተኛ ጊዜ
“ሁለት” የሚለው ቃል ተራ ቁጥር ሁለት ነው:: አት “እንደገና” (ተራ ቁጥሮችን ይመልከቱ)
እነሆ ዛላዎች
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል ፈረዖን ባየው ነገር እንደተገረመ የሚያሳይ ነው
የእሸት ዛላዎች
ዛላዎች ፍሬዎች የሚንዠረግጉበት የበቆሎ ተክል አካል ነው
በአንድ የእህል አገዳ ላይ
“በአንድ አገዳ ላይ ያፈራውን ወይም የተንዠረገገውን” አገዳ ወፍራምና ረጅም የተክል ክፍል ነው::
በአንዱ አገዳ ላይ የተንዠረገገና ያማረ
በአንድ አገዳ ጤናማና ያማረ
የቀጨጩና በምሥራቅ ንፋስ የተመቱ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት: “ያም ከምሥራቅ ደረቅ አየር የትነሳ የቀጨጩና በዋግ የተመቱ” (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
የምሥራቅ ንፋስ
የምሥራቅ ንፋስ ከረሃማ ተነሥቶ የሚነፍስ ነው። የምስራቅ ንፋስ ሙቀት እጅግ ጐጂ ነው።
ዛላዎች ወጡ
ዛላዎች አደጉ ወይም ተንዠረገጉ
Genesis 41:7
የቀጨጩ የእሸት ወይም የእህል ዛላዎች
እህል የተባለው ቃል የታወቀ ነው:: አት “የቀጨጩ የእህል ዛላዎች” (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ዋጡአቸው
በሉአቸው ሰው ምግብን እንደሚበላ የቀጨጩ የእሸት ዛላዎች ጤናማ የእሸት ዛላዎች ሲውጡ ፈረዖን በሕልሙ አየ
ሙሉና ፍሬያቸው የተንዠረገገውን የእሸት ዛላዎች
ጤናማና መልካም የእሸት ዛላዎች
በዘፍጥረት 41:5 የዚህ ተመሣሣይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ ነቃ
ከእንቅልፉ ነቃ
እነሆ
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል ፈርዖ ባየው ነገር እንደተገረመ ያሳያል
ሕልም ነበር
ሕልም ሲያልም ነበር
እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ለማመልከት ነው:: በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ካለ ይጠቀሙ:: (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይጠቀሙ)
መንፈሱ ታወከበት
እዚህ መንፈሱ የሚለው ቃለ የውስጥ ማንነቱን ወይም ስሜቱን ያመለክታል አት “በውስጥ ማንነቱ ታወከ” ወይም “ታወከ” (ተመሣሣይ ምትክ ቃል ስለመጠቀም ይመልከቱ)
ልኮና አስጠርቶ
አገልጋዮቹን እንደላካቸው መረዳት ይቻላል:: አት “እንዲጠሩ አገልጋዮቹን ላካቸው ወይም አገልጋዮቹ እንደጠሩ አዘዛቸው” (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
የግብጽ አስማተኞችንና ጥበበኞች
የጥንት ነገሥታት አስማተኞችንና ጥበበኞችን እንደአማካሪዎች ይጠቀሙ ነበር
Genesis 41:9

የመጠጥ አሳላፊዎችን አለቃ
ይህ ለንጉሡ መጠጥን የሚያዘጋጅና የሚያቀርብ መሪ ሰው ነበር። በዘፍጥረት 40፡2 እነዚህ ቃላት እንዴት እንደተተረጐሙ ይመልከቱ፡
የሠራሁት በደል ዛሬ ታወሰኝ
ዛሬ የሚለው ቃል የተጠቀመው አስንዎት ለመስጠት ነው በደሉ ቀደም ብሎ ለፈርዖን መናገር የነበረበት አንድ ነገር ነገር ግን ያልተናገረበት ነው:: አት “ለአንተ መናገር የረሳሁትን አሁን አስታወስኩ”
ፈርዖን ተቆጥቶ ነበር
የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ፈርዖንን እንደ ሶስተኛ ወገን ሰው ያመለክታል ይህም አነስተኛ ኃላፊነት ያለው ከፍተኛ ኃላፊነት ያለው የሚያስቀምጥበት የተለመደ መንገድ ነው እርስዎ ፈርዖን ተቆጥተው ነበር (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
ከእርሱ አገልጋዮች ጋር
እዚህ እርሱ ፈርዖንን ያመለክታል አገልጋዮች የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃና የእንጀራ ቤት አዛዥ ያመለክታል:: አት “እኛ አገልጋዮችህ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
እኔንና የእንጀራ ቤት አዛዡን በዘበኞች አለቃ ግቢ አስሮን ነበር
እኔንና የእንጀራ ቤት አዛዡን በዘበኞች አለቃ ኃላፊነት በተሰጠው እስር ቤት እስሮን ነበር:: እዚህ “ቤት” እስር ቤትን ያመለክታል::
የዘበኞች አለቃ
ንጉሡ ጠባቂዎች ላይ ኃላፊነት የተሰጠው ወታደር ነው በዘፍጥረት 20:2-3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
የእንጀራ ቤት አዛዥ
ለንጉሡ ምንብን የሚያዘጋጅ ዋና አስፈላጊ ሰው ነው። በዘፍጥረት 20:2-3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
እርሱና እኔ በአንዲት ሌሊት ሕልም አየን
“እኛ ሁለታችን በአንድ ሌሊት ሕልም አለምን” እዚህ እኛ የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃንና እንጀራ ቤት አዛዡን ያመለክታል (ነጠላና ብዙ እኛ ይመልከቱ)
የእያንዳንዳችን ሕልም የራሱ የሆነ ትርጉም ነበረው
ሕልሞቻችን የተለያየ ትርጉም ነበራቸው
Genesis 41:12
አጠቃላይ መረጃ
የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ለፈርዖ መናገሩን ቀጠለ
ከእኛ ጋር ነበር
በእስር ቤት ከእንጀራ ቤት አዛዥና ከእኔ ጋር ነበር
የዘበኞች አለቃ
ንጉሡ ጠባቂዎች ላይ ኃላፊነት የተሰጠው ወታደር ነው በዘፍጥረት 20:2-3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
ሕልሞቻችንን በነገርነው ጊዜ ፈቺውን ነገረን
ሕልሞቻችንን ነገርነው እናም እርሱ ትርጉምቻቸውን ነገረን
ለእያንዳንዳችን እንደሕልማችን ተረጐመልን
እዚህ እርሱ ወይም እያንዳንዱ የሕልሙ ተርጓሚውን ሳይሆን የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃንና የእንጀራ ቤት አዛዥ በግል የሚያመለክት ነው አት ለእያንዳንዳችን ምን ሊሆን እንዳለ አስረዳን (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አጠቃቀም ይመልከቱ)
በዚያን ጊዜ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው በታሪኩ አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት ነው በቋንቋዎ ይህን መግለጽ የሚችሉበት መንገድ ካለ ይጠቀሙ
እርሱ እንደተረጐመልን ሆነ
ስለሕልሞቻችን እንደነገረን ሆነ
ፈርዖን ወደ ሹሜቱ መለሰኝ
እዚህ የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ ማከበሩን ለመግለጽ የፈርዖን የማዕረግ ስም ይጠቀማል:: አት ወደ ሥራዬ እንዲመለስ ፈቀድክልኝ (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
እርሱን ወይም ሌላኛውን
የእንጀራ ቤት አዛዡን
እርሱ ሰቀለው
እዚህ እርሱ ፈርዖንን ያመለክታል እና ይህም የእንጀራ ቤት አዛዡን እንዲሰቅሉት ፈርዖን ወታደሮቹን ማዘዙን ይወክላል አት እንዲሰቀል እርስዎ ወታደሮችዎን አዝዘዋል:: (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽና ተዛማጅ ምትክ ቃላትን ስለመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ
Genesis 41:14
ፈርዖንም ሊኮ አስጠራ
ፈርዖን አገልጋዮቹን እንደላከ ይታወቃል አት ዮሴፍን እንዲያመጡት አገልጋዮችን ላከ (የተደበቁ ቃሎችን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ከግዞት ቤት
“ከእስር ቤት” ወይም “ከወህኒ”
ጽጉሩን ከተላጨ
በፈርዖን ፊት ለመቅረብ በመዘጋጀት ጊዜ የፊትና የራስ ጽጉርን መላጨት የተለመደ ተግባር ነበር
ፈርዖን ፊት መጣ
እዚህ መጣ የሚለው ገባ በሚለው ሊገለጽ ይችላል አት ፈርዖን ፊት ገባ (መጣ እና ገባ ይመልከቱ)
የሚተረጉመውም አልተገኘም
ሊተረጉምልኝ የቻለ አንድም ሰው አልተገኘም
አንተ የመተርጐም ችሎታ አለህ
አንተ ትርጉሙን ሊትነግረኝ ትችላለህ
ይህ በእኔ አይደለም
እኔ የመተርጐም ችሎታ የለኝም
እግዚአብሔር በደኅንነት ለፈርዖን ይመልስለታል
እግዚአብሔር ለፈርዖን የሚሻውን ትርጉም ይሰጠዋል
Genesis 41:17
እነሆ ቆሜ ነበር
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል
በዐባይ ወንዝ ዳር
በዐባይ ወንዝ ዳርቻ የለውን ከፍታ የለውን መሬት ያመለክታል:: በዘፍጥረት 41:3 የዚህ ተመሣሣይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት “በዐባይ ወንዝ ዳር”
እነሆ ሰባት ላሞች
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል
የወፈሩና ያማሩ
“የተቀለቡ/የደለቡና ጤናማ” በዘፍጥረት 41:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
በቀጠማዎች ውስጥ ወይም በመስኩ ይሰማሩ ነበር
በወንዙም ዳር ያለውን ሣር ይመገቡ ነበር:: በዘፍጥረት 41:2 የዚህ ተመሣሣይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ።
Genesis 41:19
እነሆ ሰባት ሌሎች ላሞች
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል
የከፉና የከሱ
አቅሜ ደካሞችና የከሱ ወይም የቀጨጩ በዘፍጥረት 41:3 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ
እንደዚህ የሚያስከፉ
“አስከፊ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጐም ይችላል:: አት “የሚያስከፉ ላሞች” ወይም “የማይጠቅሙ የሚመስሉ ላሞች” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)
የወፈሩ ላሞች
“የደለቡ ወይም የተቀለቡ ላሞች” በዘፍጥረት 41:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
እንደዋጧቸው ምንም ሊታወቅ አይችልም ነበር
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “የከሱ ላሞች የወፈሩትን መዋጣቸውን ማንም ሊነግረው እስከማይችል ነበር:: (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
Genesis 41:22
አጠቃላይ መረጃ
ፈርዖን ሕልሙን ለዮሴፍ መናገሩን ቀጠለ
በሕልሜ አየሁ
ይህ ፈርዖን ከነቃና ተመልሶ ከተኛ በኋላ ያየውን ሕልም ይጀምራል። አት “እንደገናም

ሕልም አለምሁ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
እነሆ ሰባት የእሸት ዛላዎች
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል::
ሰባት የእሸት ዛላዎች
የእሸት ወይም የእህል የሚለው አባባል የታወቀ ነው:: አት “ሰባት የእህል ዛላዎች” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
በአንድ አገዳ ሲወጡ
“በአንድ አገዳ ሲንዠረግጉ” አገዳ ወፍራምና ረጅም የተክል አካል ነው:: በዘፍጥረት 41:5 ይህን ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
እነሆ ሰባት ሌሎች የእሸት ዛላዎች
ስለሚያስገርመው መረጃ ዮሴፍ ትኩረት እንዲሰጠው ፈርዖን “እነሆ” የሚለውን ቃል ይጠቀማል::
የጠወለጉ
የደረቁና ፍሬ አልባ የሆኑ
በምሥራቅ ነፋስ
“ከበረሃማ ቦታ የሚነፍሰው የምሥራቅ ንፋስ” የምሥራቁ ንፋስ ሙቂት አብዛኛውን ጊዜ ለእህሎች እጅግ አደገኛ ነበር::
ተንዠረገገ
አደገ ወይም ፍሬ ሰጠ
የቀጨጩ የእሸት ወይም የእህል ዛላዎች
የእህል የሚለው ቃል የታወቀ ነው በዘፍጥረት 41:7 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ አት የቀጨጩ የእህል ዛላዎች (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ዋጧቸው
“በሉ” ፈርዖን ያለመው ሕልም ሰው ምግብን እንደሚበላ ጤናማ ያልሆኑ የበቆሎ እህሎች ጤናማ ያልሆኑትን እንደበሉ ነው:: በዘፍጥረት 41:7 የዚህ ተመሣሣይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
የሚችል ማንም አልተገኘም
የሚችል አንድም አልተገኘም ወይም ማንም አልቻለም
Genesis 41:25
የፈርዖን ሕልሞች ተመሣሣይ ናቸው
ትርጉሞችም ተመሣሣይ ናቸው የሚል አንድምታ አለው:: አት “ሁለቱም ሕልሞች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን ለፈርዖን አስታወቀው
ዮሴፍ ፈርዖንን እንደሳስተኛ ወገን ሰው ያናግረዋል ይህ አክብሮትን መግለጫ መንገድ ነው:: እንደ ሁለተኛ ወገን ሰው መግለጽ ይቻላል:: አት “ቶሎ ሊያደርግ ያለውን እያሳየህ ነው” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
Genesis 41:27
አጠቃላይ መረጃ
ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም መተርጐም ይቀጥላል።
የከሱና አስከፊ መልክ ያላቸው ላሞች
የቀጨጩና ዐቅሜ ደካማ ላሞች በዘፍጥረት 41:3 የዚህ ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ
በምሥራቅ ነፋስ የተመቱ ሰባት የቀጨጩ የእሸት ዛላዎች
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ከምሥራቁ ሙቀት አዘል ነፋስ የተነሣ የቀጨጩ ሰባት የእህል ዛላዎች” (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
ይህን ለፈርዖን የተናገርኩትን … ለፈርዖን ገልጦለታል
ዮሴፍ ፈርዖንን እንደ ሶስተኛ ወገን ሰው ያናግረዋል ይህም አክብሮች መግለጫ መንገድ ነው:: በሁለተኛ ወገን ሰው መልክ ልገለጽ ይችላል:: “እንደተናገርኩህ እነዚህ ይደረጋሉ…… ፈርዖን ለአንተ ገልጦልሃል” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
እይ ሰባት
“እኔ የሚናገረው እውነትና ጠቃሚ ነውና ትኩረት ስጥ፤ ሰባት”
በመላው የግብጸ ምድር እጅግ የተትረፈረፈ ጥጋብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ይመጣሉ
ጊዜ እንደሚመጣና በወቅቱ በአንድ ቦታ እንደሚሆን ይህ ስለጥጋብ ዓመታት ይናገራል:: አት “የተትረፈረፈ ምግብ በግብጽ በመላው የግብጽ ምድር የሚሆንበት ሰባት ዓመታት ይመጣሉ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
Genesis 41:30
አጠቃላይ መረጃ
ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልሞች መተርጐም ቀጠለ
ከዚህ በኃላ ሰባት የራብ ዓመታት ይሆናሉ
ወደ አንድ ቦታው ተንቀሳቅሶ እንደሚመጣ ነገር ተደርጐ ስለ ሰባት ዓመታት ራስ ተነግሮአል አት ከዚም በኋላ እጅግ ጥቂት ምግብ የሚሆንበት ሰባት ዓመታት ይሆናሉ (ዘይቤይዊ አነጋገር ይመልከቱ)
የራቡ ዘመን አገሪቱን እጅግ ስለሚጐዳት … የጥጋቡ ዘመን ሁሉ ጨርሶ አይታወስም::
….የሚመጣው የራብ ዘመን እጅግ ጽኑ ከመሆኑ የተነሣ የጥጋብ ዘመን ፈጽም ይረሳል:: ዮሴፍ ለጉዳዩ አጽንዖት ለመስጠት አንድን ሀሳብ በሁለት መንገድ ይገልጻል (ተመሣሣይ ተጓዳኝ አባባሎችን ይመልከቱ)
በግብጽ ምድር የጥጋብ ዘመን ሁሉ ይረሳል
ምድር ሰዎችን ያመለክታል ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “የግብጽ ሰዎች የተትረፈረፈ ምግብ የነበረበትን ዓመታት ሁሉ ይረሳሉ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤና ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
አገሪቱን ይጐዳሉ
አገር የሚለው የአገሪቷን መሬት ሰዎችና መላውን የአገሪቷን አካል ያመለክታል (ምትክ ቃላትን የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
ከሚመጣው ራብ የተነሣ
ይህ ተከትሎ እንደሚመጣ እንደ አንድ ነገር ስለሚመጣው ራብ ወይም ድርቅ ይናገራል። አት “ከዚያ በኋላ በሚሆነው ራብ ወይም ድርቅ የተነሣ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ሕልሙ ለፈርዖን በሁለት መልክ በድጋሚ መታየቱ ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቈረጠ ስለሆነ ነው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እግዚአብሔር ሁለት ሕልሞችን የሰጠህ ነገሮች በእርግጥ እንደሚከሰቱ ለማሣየት ነው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
Genesis 41:33
አጠቃላይ መረጃ
ዮሴፍ ለፈርዖን መናገሩን ቀጠለ
አሁንም
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ስለሚቀጥለው ጠቃሚ ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ነው
እንግዲህ ፈርዖን … ይፈልግ
ዮሴፍ ለፈርዖን እንደ ሶስተኛ ወገን ሰው ይናገራል ይህ አክብሮትን የመግለጫ መንገድ ነው በሁለተኛ ወገን ሰው መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “አንተ ፈርዖን ፈልግ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
በግብጽ ምድር ላይም ይሹመው
ይሹመው ማለት ኃላፊነት ይስጠው ማለት ነው። አት “በግብጽ ግዛት ላይ ኃላፊነት ይስጠው ወይም በግብጽ ግዛት ላይ ይሹመው (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
የግብጽ ምድር
እዚህ ምድር በግብጽ ምድር ያሉ ሰዎችንና ሁሉን ነገር ይወክላል (ተመሣሣይ ተዛማጅ ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልቱ)
በግብጽ ምድር ከሚገኘው የእህል ምርት አንድ አምስተአኛውን ይውሰዱ
አምስተኛ የሚለው ቃል ክፍልፋይ ነው:: የግብጽን ምድር እህል ምርት በአምስት መደብ ይክፈሉ፤ ከዚያም አንዱን እጅ ወይም መደብ ይውሰዱ (ክፍልፋዮችን ይመልከቱ)
በሰባት የጥጋብ ዓመታት
የተትረፈረፈ ምግብ ባለባቸው ሰባት ዓመታት
Genesis 41:35
አጠቃላይ መረጃ
ፈርዖንን መምከሩን ቀጠለ
እነርሱም ይሰብስቡ
ሹማምንት ወይም ኃላፊዎች እንዲሰበስቡ ይደረግ
በእነዚህ በሚመጡት ጥጋብ ዓመታት
እነዚህ ዓመታት አንድ ነገር ተጉዞ ወደ አንድ ቦታ እንደማመጣ እንደሚመጡ ይናገራል:: አት “ቶሎ ሊመጡ ያሉ የጥጋብ ዓመታት” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
በፈርዖን ሥልጣን ሥር ያከማቹ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በፈርዖን ሥልጣን ሥር የሚለው ሀረግ ፈርዖን ሥልጣን ይሰጣቸው ማለት ነው አት እህሉን ለመሰብሰብ የፈርዖንን ሥልጣን ይጠቀም ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ
እነርሱም ይህን ይጠብቁ
እነርሱ የሚለው ቃል እህሉ እንዲጠበቅ የሚያዝዙ ሹማምንቶችንና ወታደሮች ያመለክታል አት ሹማምቶች እህሉ እንዲጠበቅ በዚያው ወታደሮችን ይመድቡ ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ
እህሉ ለምድሪቱ ምግብ ይሆናል
ምድሪቱ ሰዎችን ትወክላለች አት እህሉም ለሰዎች ምግብነት ይሆናል (ምትክ ቃላት ስለመጠቀም ይመልከቱ)
በዚህ ሁኔታ ምድሪቱ በራብ አትጠፋም
እዚህ “ምድር” ሰዎችን ይወክላል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት “በዚህ መንገድ በራብ ጊዜ ሰዎች አይራቡም” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ወይም ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
Genesis 41:37
ይህ ምክር ለፈርዖንና በሎለዎቹ ፊት መልካም ሆነ
ፊት ማየትን የሚያመለክት ሲሆን ማየት ማሰብን ወይም ብያኔን ያመለክታል አት ፈርዖንና ሎሌዎቹ ይህ መልካም እቅድ ሆኖ አገኙት
ሎሌዎች
የፈርዖ ሹማምንት
እንደዚህ ያለ ሰው
ዮሴፍ የገለጸው ዓይነት ሰው
የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት
የእግዚአብሔር መንፈስ የሚኖርበት
Genesis 41:39
እንዳንተ ያለ ብልህ የለም
እንዳንተ ያለ ውሳኔ አቅራቢ የለም:: በዘፍጥረት 41:33 ብልህ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
አንተ የቤተመንግሥቴ የበላይ ትሆናለህ
እዚህ “ቤት” የፈርዖን ቤተመንግሥትና በቤተመንግሥቱ ያሉ ሰዎችን ይወክላል:: የበላይ የሚለው ሀረግ ዮሴፍ የበላይ ኃላፊነት ይሰጠዋል ማለት ነው:: አት በቤተመንግሥቴ በሁሉም ላይ ሥልጣን ይሰጥሃል:: (ምትክ ቃላት ስለመጠቀም ዘይቤና ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ሕዝቤ ሁሉ ለሥልጣኔ ይገዛል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል በሕዝቤ ላይ ገዥ ትሆናለህና አንተ የሚታዝዘውን ያደርጋሉ:: (ተሻጋሪ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
በዙፋኔ ብቻ
እዚህ ዙፋን ፈርዖን እንደንጉሥ ገዥ እንደሆነ ይገልጻል:: አት “በንጉሥነት ሚናዬ ብቻ”
እየው አድርጌሃለሁ
“እየው” የሚለው ቃል ፈርዖን በሚቀጥለው ለሚናገረው አጽንዖት ይሰጣል:: አት “እየው አድርጌሃለሁ”
በመላይቱ የግብጽ ምድር ላይ ኃላፊ አድርጌሃለሁ
የበላይ አድርጌሃለሁ ማለት ሥልጣን ሰጥቼሃለሁ ማለት ነው እዚህ ምድር ሰዎችን ያመለክታል አት በግብጽ ምድር ባለው በማንኛውም ላይ ኃላፊነት ሰጥቼሃለሁ (ምትክ ቃል የመጠቀም ዘይቤና ፈሊጣዊ አነጋገር ይጠቀሙ)
Genesis 41:42
ፈርዖንም ባለማኅተሙን ቀለበት አውልቆ .... የወርቅ ሐብል አጠለቀለት
እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች የሚያመለክቱት ዮሴፍ ያቀደውን ሁሉ እንዲያደርግ ፈርዖን ለዮሴፍ ሥልጣን መስጠቱን ነው (ምልክታዊ ድርጊት የመልከቱ)
ባለማኅተሙ ቀለበት
ይህ ቀለበት የፈርዖን ማኅተም የተቀረጸበት ነው:: ይህም ያቀደውን እንዲያከናውን ለዮሴፍ ገንዘብና ሥልጣንን ሰጠው::
ከጥሩ የተልባ እግር የተሠራ ልብስ
የተልባ እግር የተሠራ ልብስ ሰማያዊ አበባ ካለው የተልባ እግር የተሠራ ለስላሳ ጠንካራ ልብስ ነው::
የእርሱም በሆነው ሁለተኛው ሠረገላ ላይ አስቀመጠው
ይህ ድርጊት ለሰዎች ግልጽ የሚያደርገው የፈርዖን ሁለተኛ ሰው ዮሴፍ ብቻ መሆኑን ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
ስገዱ ወይም እጅ ንሡ
ስገዱና ዮሴፍን አክብሩ እጅ መንሣትና መስገድ ክብርንና አክብሮትን የመስጠት ምልክት ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
ፈርዖን በምድሪቱ ባለው ማንኛውም ላይ ሾመው
ማንኛውም ላይ ሾመው የሚለው ሀረግ ሁሉ ላይ ስልጣን ሰጠው ማለት ነው:: እዚህ ምድር ሰዎችን ያመለክታል በዘፍጥረት 41:41 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት “በግብጽ ባለው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገርና ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
Genesis 41:44
እኔ ፈርዖን ነኝ ... ያለ አንተ
ፈርዖን የራሱን ሥልጣን አጽንቶ ይናገራል። አት “እንደ ፈርዖን እኔ የማዝዘው ያለአንተ”
ያላንተ ማንም እጁንም እግሩንም አያንሣ
እዚህ “እጅና እግር” የሰዎችን ድርጊቶች ይወክላሉ:: አት “ማንኛውም ሰው ምንም ነገር ያለፈቃድህ በግብጽ አያድርግ ወይም ማንኛውም ሰው ምንም ነገር በግብጽ ከማድረጉ በፊት ያንተን ፈቃድ ይጠይቅ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
ማንም ሰው
እዚህ “ሰው” ወንድም ሆነ ሴት በአጠቃላይ ማንንም ሰው ያመለክታል:: (በወንድ ጾታ የተገለጹ ቃላት ለሴት ጾታም መሆናቸውን ይመልከቱ)
ጸፍናት ፓዕናህ
ተርጓሚዎች የሚከተውን በግርጌ ማስታወሻ ሊጠቀሱ ይችላሉ:: “ጸፍናት ፓዕናህ” የሚለው ስም “ሚስጢሮችን ገላጭ” ማለት ነው።
የሄልዮቱ ወይም ዖን ከተማ ካህን የጶጥፌራ ልጅ የሚትሆን አስናትን አጋባው
ጶጥፋራ የአስናት አባት ነው:: “ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ”
የሄልዮቱ ካህን
ዖን የጸሐይ አምላክ ራአ አምልዕኮ ማዕከል ያለባትና “የጸሐይ ከተማ” የነበረች እንዲሁም “ሄልዮቱ” ተብላ የሚትጠራ ከተማ ነች (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ዮሴፍም በመላይቱ የግብጽ ምድር ተዘዋወረ
ሊመጣ ስላለው ያልታሰበ የድርቅ ጊዜ ዝግጅት ለማድረግ ዮሴፍ በመላይቱ የግሥብ ምድር ተዘዋወረ
Genesis 41:46
ሠላሳ ዓመት ዕድሜ
30 ዓመት ዕድሜ ቁጥሮችን ይመልከቱ
ዮሴፍም በፈርዖን ፊት በቆመ ጊዜ
እዚህ በፊቱ መቆም ዮሴፍ ፈርዖንን ማገልገል መጀመሩን ያሳያል:: አት “ፈርዖንን ማገልገል በጀመረ ጊዜ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
በመላይቱ የግብጽ ምድር ተዘዋወረ
ዮሴፍ ዕቅዱን ለማከናወን ዝግጅት ሲያደርግ አገሪቱን በጥንቃቄ እንደመረመረ ነው
በሰባቱም የጥጋብ ዓመታት
በሰባቱም መልካም ዓመታት
ምድሪቱ የተትረፈረፈ ሰብል ሰጠች
ምድራቱ ብዙ እህል አመረተች
Genesis 41:48
እርሱም ምርት ሰብስቦ .... አከማቸ
እዚህ “እርሱ” የዮሴፍን አገልጋዮች ያመለክታል:: አት “ዮሴፍ አገልጋዮቹ እንዲሰበስቡ አዘዘ .... አከማቹ (ከፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ዮሴፍ እንደ ባሕር አሸዋ እጅግ ብዙ እህል አከማቸ
የእህሉን እጅግ መብዛት በአጽንዖት ለመናገር ከባሕር አሸዋ ጋር ያነጻጽራል። አት “ዮሴፍ ያከማቸው እህል ባህር ዳር እንዳለ አሸዋ እጅግ ብዙ ነበር” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ዮሴፍ አከማቸ .... እርሱም አቆመ
እዚህ ዮሴፍ እና እርሱ የዮሴፍን አገልጋዮች ይወክላል:: አት “ዮሴፍ አገልጋዮቹ እንዲያከማቹ አደረገ ... እነርሱም አቆሙ” (ከፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
Genesis 41:50
የራብ ዓመታት ከመምጣታቸው በፊት
ሰባቱ የራብ ዓመታት ከመምጣቱ በፊት ይህም አንድ ነገር ተጉዞ ወደ አንድ ቦታ

እንደሚመጣ ተደርጐ ስለሚመጡ ዓመታት ይናገራል:: አት “ሰባቱ የራብ ዓመታት ከመጀመራቸው በፊት” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
አስናት
የአንዲት ሴት ስም ነው:: በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
የዖን ካህን
ዖን የጸሐይ አምላክ ራአ አምልዕኮ ማዕከል ያለባትና “የጸሐይ ከተማ” የሆነች እንዲሁም “ሄልዮቱ” ተብላ የሚትጠራ ከተማ ነች። በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ምናሴ
ተርጓሚዎች የሚከተለውን በግርጌ ማስታወሻ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: “ሚናሴ” የሚለው ስም ለመርሳት ምክንያት መሆን ማለት ነው::
የአባቴንም ቤት
ይህ የዮሴፍ አባት ያዕቆብንና ቤተሰቡን ያመለክታል
ኤፍሬም
ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምሩ ይችላሉ:: “ኤፍሬም” የሚለው ስም “ፍሬያማ መሆን” ወይም “ልጆችን መውለድ” ማለት ነው::
ፍሬያማ አደረገኝ
“ፍሬያማ” መበልጸግ ወይም ልጆችን መውለድ ማለት ነው:: (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
በተሠቃየሁበት ምድር
“ሥቃይ” የሚለው ረቂቅ ስም “መከራ ተከበልኩ” በሚለው ሊገለጽ ይችላል:: አት “መከራን በተቀበልሁት ምድር” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

Genesis 41:53
በየአገሩ ሁሉ
ከግብጽ ባለፈ የከነዓንንም ምድር ጨምሮ በዙሪያው ባሉ አገሮች ሁሉ
በመላው የግብጽ ምድር ግን ምግብ ነበር
ይህም የሚያስረዳው በሰባት መልካም ዓመታት ሕዝቡ እህልን እንዲያጠራቅሙ የሴፍ ስላዘዛቸው ምግብ ነበራቸው (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 41:55
ራብ በመላው የግብጽ ምድር መስፋፋት ሲጀምር
እዚህ “ምድር” ሰዎችን ይወክላል:: አት “ግብጻዊያን ሁሉ በተራቡ ጊዜ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
ራቡ በአገሩ ሁሉ ፊት እየተስፋፋ ስለሄደ
እዚህ ፊት የሚለው ቃል ምድር ላይ ማለትን ያመለክታል:: አት “ራቡ በየአገሩ ተስፋፋ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
የሴፍ ጐተራዎችን ሁሉ ከፍቶ እህሉ ለግብጻዊያን እንዲሸጥ አደረገ
እዚህ “የሴፍ” የዮሴፍን አገልጋዮች ይወክላል:: አት “የሴፍ አገልጋዮቹ ጐተራዎችን ሁሉ እንዲከፍቱና ለግብጻዊያን እህል እንዲሸጥ አደረገ” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ከምድር ሁሉ ወደ ግብጽ ይመጡ ነበር
እዚህ ምድር ከሁሉ አገራት የሆኑ ሰዎችን ይወክላል:: አት “በዙሪያው ካሉ አገሮች ሁሉ ሰዎች ወደ ግብጽ ይመጡ ነበር” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
በምድር ሁሉ
በመላው ምድር በግብጻዊያንን የንግድ መሥመሮች የሚጠቀሙ በድርቅ የተጠቁ የተለያዩ የንግድ አጋሮችና አገሮች ሁሉ ወደ ግብጽ ይመጡ ነበር እንደማለት ነው

---

Chapter 42
Genesis 42:1
አሁንም ያዕቆብ ....እንዲህ አላቸው
አሁንም የሚለው ቃል የታሪኩን አዲስ ክፍል ያመለክታል (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)
ለምን እርስበርስ ትተያያላችሁ?
ስለ እህል ምንም ባለማድረጋቸው ልጆቹን ለመቆጣት ያዕቆብ ጥያቄ ይጠቀማል:: አት “እዚሁ ዝም ብላችሁ አትቀመጡ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
ወደዚያ ይውረዱ .... ወረዱ
ከከነዓን ወደ ግብጽ መሄድ ወደ ታች እንደመውረድ መናገር የተለመደ ነበር
ከግብጽ
እዚህ “ግብጽ” ሰዎች እህልን የሚሸጡበት ያመለክታል:: አት “በግብጽ እህልን ከሚሸጡ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
ያዕቆብ የዮሴፍን ወንድም ብንያምን ... አልላከውም
ብንያምና ዮሴፍ አንድ አባትና እናት ነበራቸው የዕቆብ የራሔል መጨረሻ ልጅዋ እንዲጐዳ ወይም ክፉ ነገር እንዲደርስበት አልፈለገም ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይጠቀሙ
Genesis 42:5
የእስራኤል ልጆች ለእህል ሸመታ ከመጡበት ጋር
“መጡ” የሚለው ቃል “ሄዱ” በሚለው ሊተረጐም ይችላል:: እንዲሁም እህል እና ግብጽ የተባሉ ቃላት የታወቁ ናቸው:: አት “የእስራኤል ልጆች እህል ለመሸመት ከሌሎች ሰዎች ጋር ወደ ግብጽ ሄዱ” (ሄደ እና መጣ አጠቃቀምና ድብቅ ቃላት የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
በዚህን ጊዜ ዮሴፍ
“በዚህን ጊዜ” ታሪኩ ወደ ዮሴፍ ሕይወት መረጃ መቀየሩን ያመለክታል:: (የዳራ መረጃ ይመልከቱ)
በምድሪቱ ላይ
ምድር ግብጽን ያመለክታል:: አት “በግብጽ ላይ” (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ለአገሩ ሰዎች ሁሉ
እዚህ አገር ግብጽንና ዙሪያው ያሉ አገሮችን ያጠቃልላል አት እህል ለመሸመት ከተለያዩ አገሮች ለመጡ ሰዎች ሁሉ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
የዮሴፍም ወንድሞች መጡ
“መጡ” እንደ “ሄዱ” ሊተረጐም ይችላል:: (መጣ እና ሄደ አጠቃቀም ይመልከቱ)
በግምባራቸው ወደ ምድር ጐንበስ ብለው ሰገዱለት
ይህ አክብሮትን የመስጠት ምልክት ነው:: (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
Genesis 42:7
ዮሴፍም ወንድሞቹን አይቶ አወቃቸው
ዮሴፍም ወንድዋቹን ባያቸው ጊዜ አወቃቸው
እንደማያውቃቸው ሆነ
“የእርሱ ወንድም እንዳልሆነ ታየ” ወይም “ወንድማቸው እንደሆነ እንዲያውቁት አልፈለገም”
ከየት የመጣችሁ ናችሁ?
ዮሴፍ መልሱን ቢያውቅም ይህ አግናኝ ጥያቄ አልነበረም የራሱን ማንነት ለወንድሞቹ ላለመግለጽ የመረጠው መንገድ ነበር
Genesis 42:9
ሰላዮች ናችሁ
ሰላዮች ሌላ አገርን ለመጥቅ በስውር ስለአንድ አገር መረጃ ለማግኘት የሚጥሩ ሰዎች ናቸው::
ምድሪቱ በየትኛ በኩል የተጋለጠች እንደሆነች ሊታዩ መጥታችኋል
የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት አገራችን በየትኛው በኩል እንደተጋለጠች ለማየትና ከዚያም ሊታጠቁን ለማየት መጥታችኋል (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ጌታችን ሆይ
አንድን ሰው ለማክበር የሚጠቀሙበት አባባል ነው
ባሪያዎችህ
ወንድሞቹ ራሳቸውን እንደ ባሪያዎች አድርገው ያቀርባሉ። ይህም ከፍተኛ ሥልጣን ላለው ሰው የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው።አት “እኛ ባሪያዎችህ” ወይም “እኛ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
Genesis 42:12
እርሱ ለእነርሱ አላቸው
ዮሴፍ ለወንድሞቹ አላቸው
አይደለም በየት በኩል ምድራችን ጥቃት የተጋለጠች መሆንዋን ለማየት ነው
የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “አይደለም በየት በኩል ምድራችን ለጥቃት የተጋለጠች መሆንዋን ለመሰለልና ከዚያም ሊታጠቁን ነው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
አሥራ ሁለቱ ወንድሞች
12ቱ ወንድሞች (ቁጥሮችን ይመልከቱ)
እየው ትንሹ ወንድማችን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ስማን ትንሹ ወንድማችን” “እየው” የሚለው ቃል ቀጥለው ለምነግሩት ነገር ትኩረት እንዲሰጥ ተጠቅሞአል::
ትንሹ ወንድማችን አባታችን ዘንድ ነው
“በዚህን ጊዜ ትንሹ ወንድማችን ከአባታችን ጋር ነው”
Genesis 42:14
ነገርኋች እኮ ሰላዮች ናችሁ
“እንደነገርኋችሁ ሰላዮች ናችሁ” (በዘፍጥረት 42;9 “ሰላዮች” እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ)
በዚህ ትፈተናላችሁ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “የሚፈትናችሁ በዚህ ነው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
በፈርዖን ሕይወት
ይህ ጠንከር ወይም ኮስተር ያለ መሃላ ነው አት በፈርዖን ሕይወት እምላለሁ
ከእናንተ አንዱን ላኩና ወንድማችሁን ይዞ ይመለስ
“ከእናንተ አንዱን ምረጡና ሂዶ ወንድማችሁን ይዞ ይመለስ”
እስር ቤት ትቆያላችሁ
የቀራችሁ በእሥር ቤት ትቆያላችሁ
የተናገራችሁት ቃል እውነት መሆኑ እስኪረጋገጥ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት እውነት መናገራችሁን እንዳውቅ (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልክቱ)
በግዞት ቤት
በእስር ቤት
Genesis 42:18
በሶስተኛውም ቀን
“ሶስት” የሚለው ተራ ቁጥር ነው:: አት “ከሁለተኛው ቀን በኋላ” (መቁጠሪያ ተራ ቁጥሮችን ይመልከቱ)
እንዲህ በማድረግ ሕይወታችሁን አትርፉ
የተቀመጠው መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “የሚለውን ካደረጋችሁ በሕይወት ትተርፉ አደርጋችኋለሁ” (የተደበቁ ቃላትን ስለመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን እፈራለሁና
ይህ ከልብ እግዚአብሔርን ማክበርንና ያንን ለእርሱ በመታዘዝ መግለጽን ያመለክታል
አንዱ ወንድማችሁ በእሥር ቤት ይቆይ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ልገለጽ ይችላል:: አት “እንዱን ወንድማችሁን እዚሁ እሥር ቤት ተውት” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
እናንተ ግን ሂዱ
እዚህ ሂዱ ብዙ አመላካችና በእሥር ቤት የማይቆዩ ወንድሞች ሁሉን ያመለክታል (ብዙ አመላካች እናንተ ይመልከቱ)
ለተራቡት ቤተሰቦቻችሁ እህል ትወስዱላቸዋላችሁ
እዚህ ቤቶች ቤተሰቦችን ይወክላል:: አት “በዚህ ራብ ወቅት ቤተሰቦቻችሁን ለመርዳት እህል ትወስዱላቸዋላችሁ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
የተናገራችሁት ቃል እውነተኛነት ይረጋገጣል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት የሚትነግሩ እውነት መሆኑን አውቃለሁ (ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ ይመልከቱ)
ከሞት ትተርፋላችሁ
ወንድሞቹ ሰላይ መሆናቸውን ካረጋገጠ ዮሴፍ በወታደሮቹ እንደሚያስገድላቸው የሚል ትርጉም ይኖረዋል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 42:21
ነፍሱ ስትጨነቅ አይተን
ነፍሱ ዮሴፍን ይወክላል አት ዮሴፍ እንደዚያ ሲጨነቅ አይተን ወይም ዮሴፍ እንደዚያ ሲሰቃይ አይተን (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ይህ ጭንቀት የደረሰብን በዚህ ምክንያት ነው
“ጭንቀት” የሚለው ረቂቅ ስም “መከራ” በሚለው ግሥ ሊተረጐም ይችላል:: አት “ይህ መከራ የደረሰብን በዚሁ ምክንያት ነው” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)
በዚህ ልጅ ላይ ክፉ አታድርጉ ብዬ አልነበረምን? እናንተ ግን አልሰማችሁኝም
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዞአል እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገልጽ ይችላል:: አት “በዚህ ልጅ ላይ ኃጢአት እንዳታደርጉ አልነገርኋችሁምን፤ነገር ግን” ወይም “ልጁ ላይ ክፉ እንዳታደርጉ ነግሬአችኋለሁ፤ ነገር ግን” (በጥቅሶች ውስጥ ጥቅሶችንና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
አሁንም እዩ
እዚህ አሁን በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም አሁን እና እዩ ሁለቱ የተጠቀሙት ለሚቀጥለው በጣም ጠቃሚ ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ነው
ደሙ ከእጃችን ይፈለጋል
እዚህ ደም የዮሴፍን ሞት ይወክላል ወንድሞቹ ዮሴፍ እንደሞተ አስበዋል:: “ከእጃችን ይፈለጋል” የሚለው ሀረግ ስላደረጉት ነገር ይቀጣሉ ማለት ነው:: አት “ለሞቱ የሚገባውን ቅጣት እየተቀበልን ነን” ወይም “በመግደላችን መከራ እየተቀበልን ነን” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ወይም ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
Genesis 42:23
በመካከላቸው አስተርጓሚ ነበረና .... አላወቁም
አስተርጓሚ አንድ ሰው የሚናገረውን ወደ ሌላ ቋንቋ የሚተረጉም ሰው ማለት ነው ዮሴፍ የእነርሱን ቋንቋ እንደማይናገር ለማስመሰል በራሱና በእነርሱ መካከል አስተርጓሚ አድርጐ ነበር
ከእነርሱ ዘወር ብሎ አለቀሰ
ዮሴፈ ወንድሞቹ የተናገሩትን በመስማቱ ስሜቱ ስለተነካ አለቀሰ (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ተናገራቸው
እስከዚህ ዮሴፍ ወንድሞቹን የሚያናግረው በተለየ ቋንቋ ስለሆነ አስተርጓሚ ይጠቀም ነበር (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ዐይናቸው እያየ አሠረው
እዚህ ለሚያዩት ነገር ትኩረት ለመስጠት ሰዎች በዐይኖች ተመስለዋል:: አት “በፊታቸው አሰረው” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
የመንገድ ስንቅ ይሰጡአቸው ዘንድ
ለጉዞአቸው ስንቅ እንዲሰጡአቸው
ይህም ተደረገላቸው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ዮሴፍ ያዘዘውን ሁሉ አገልጋዮቹ አደረጉላቸው (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
Genesis 42:26
ከእነርሱም አንዱ በአደረበት ሥፍራ ለአህያው ገፈራን ሊሰጥ ዘንድ ዓይበቱን ሲፈታ ብሩን አየ እነሆም በዓይበቱ አፍ ላይ ነበረች
በመንገድም አዳር ሰፍረው ሳሉ ከእነርሱ አንዱ ከያዘው እህል ላይ ለአህያው ለመስጠት ስልቻውን ሲፈታ በስልቻው አፍ ላይ ብሩን አየ
እነሆ
እዚህ እነሆ የሚለው ቃል ለሚቀጥለው አስገራሚ ሃሳብ ትኩረት እንድንሰጥ ለማድረግ ነው
ብሬ ተመልሶልኛል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት አንድ ሰው ብሬን መልሳ አስቀመጠልኝ (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
ይሄው ወደዚህ እዩ
ይሄው በስልቻዬ እዩ
ልባቸው በድንጋጤ ተሞላ
መፍራታቸው ልባቸው በድንጋጤ እንደተዋጠ እንደተሞላ ተገልጾአል እዚህ ልብ በድፍረት ተመስሎአል አት እጅግ በጣም ፈሩ
Genesis 42:29
የአገሩ ጌታ
የግብጽ ጌታ
በቁጣ ተናገረን
በክፉ ንግግር ተናገረን
ሰላዮች እንደሆንን
ሰላዮች ሌላን አገር ለመጥቀም ስለአንድ አገር በሚስጢር መረጃ የሚሰበስቡ ሰዎች ናቸው:: በዘፍጥረት 42 9 ሰላዮች የሚለውን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::እኛም እንዲህ አልነው እኛ የታመንን ሰዎች ነን። ሰላዮች አይደለንም። እኛ የአንድ አባት ልጆች የሆንን አሥራ ሁለት ወንድማማቾች ነን። እንዱ በሕይወት የለም .....በከነዓን ይገኛል ይህ በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ ይዞአል:: ይህም እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊጠቀስ ይችላል:: አት እኛ የታመንን ሰዎች እንጂ ሰላዮች

አይደለንም:: እኛ የአንድ አባት ልጆች የሆንን አሥራ ሁለት ወንድማማቾች ነን:: አንዱ በሕይወት የለም … በከነዓን ይገኛል (በጥቅስ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

አንዱ በሕይወት የለም

“ወንድም” የሚለው ቃል የታወቀ ነው አት “አንዱ ወንድማችን በሕይወት የለም” (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይጠቀሙ)

ታናሹም ….ዛሬ ከአባታችን ጋር አለ

“ወንድም” የሚለው ቃል የታወቀ ነው:: አት “ታናሽ ወንድማችን…. ዛሬ ከአባታችን ጋር አለ” (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይጠቀሙ)

Genesis 42:33

የአገሩ ጌታ

የግብጽ ጌታ

ለተራቡት ቤተሰቦቻችሁ እህል ይዛችሁላችሁ ሂዱ

ቤቶች ቤተሰብን ይወክላሉ አት በራብ ወቅት ቤተሰባችሁን ለመርዳት እህል ይዛችሁላችሁ ሂዱ (ምትክ ቃላት ስለመጠቀም ይመልከቱ)

መንገዳችሁን ሂዱ

ወደ ቤታችሁ ሂዱ ወይም ሂዱ

እናንተም በምድሪቱ ትነግዳላችሁ

በምድሪቱ እንዲትሸጡና እንዲትገዙ እፈቅድላችኋለሁ

Genesis 42:35

እንዲህም ሆነ

ይህ ሀረግ እዚህ የተጠቀመው በታሪኩ ጠቃሚ ክስተት ለማመልከት ነው በቋንቋዎ ይህን መግለጽ የማችሉበት መንገድ ካለ በዚህ ቦታ ሊጠቀሙ ይችላሉ

እነሆ እያንዳንዳቸው

ተገረሙ ምክንያቱም እያንዳንዳቸው

ልጅ አልባ አስቀራችሁኝ

ያለ ልጅ እኮ አስቀራችሁኝ ወይም ሁለቱን ልጆች እንዳጣ አደረጋችሁኝ

ይህ ሁሉ በእኔ ላይ ደረሰ

እነዚህ ሁሉ ጐዱኝ

Genesis 42:37

እርሱን በእጄ ስጠኝ

ይህ አብሮ እንዲሄድ ብንያምን እንዲሰጠውና በጉዞው እንደሚጠነቀቅለት ሮቤል የጠየቀው ጥያቄ ነው አት ለእርሱ ኃላፊነት ስጠኝ ወይም ለእርሱ እኔ ሊጠነቀቅለት ዘይቤያዊ አነጋገር ይጠቀሙ

ልጄ ወደዚያው አብሮአችሁ አይወርድም

ከከነዓን ወደ ግብጽ ጉዞ ስታሰብ እዚህ የተጠቀመው ወደታች መውረድ የሚለው አባባል የተለመደ ነው አት ልጄ ብንያምን አብሮአችሁ ወደ ግብጽ አይሄድም

ከእናንተ ጋር

እዚህ እናንተ ብዙን የሚያመለክትና የያዕቆብን ልጆች የሚገልጽ ነው( “እናንተ” አጠቃቀም ይመልከቱ)

ወንድሙ እንደሆነ ሞቶአል የቀረው እርሱ ብቻ ነው

የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት “ባለቤቴ ራሔል ሁለትልጆች ነበራት ዮሴፍ ሞቶአልና ብንያም ብቻውን ቀርቶአል” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

ስትሄዱ በመንገድ ላይ

“ወደ ግብጽ ስትሄዱና ስትመለሱ” ወይም “ርቃችሁ ስትሄዱ” እዚህ “መንገድ” “ጉዞን” ያመለክታል

ሽበቴን በመሪር ሐዘን ወደ መቃብር ታወርዱታላችሁ

ወደ መቃብር ታወርዱታለችሁ እንዲሞትና ወደ መቃብር እንዲወርድ ታደርጉታላችሁ የሚል አባባል ነው:: መቃብር በተለምዶ እንደሚታመነው ከምድር በታች ስለሆነ ታወርዱታላችሁ የሚለውን ቃል ይጠቀማል:: አት “እኔን ሽማግሌውን በሐዘን እንድሞት ታደርጉታላችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)

ሽበቴን

ይህ ያዕቆብን የሚያመለክትና ሽምግልና ዕድሜውን የሚገልጽ ነው አት “እኔ ሽማግሌ ሰው” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

---

## Chapter 43

Genesis 43:1

ራቡ በምድሪቱ ላይ እንደጸና ነበር

ከነዓን የሚለው ቃል የታወቀ ነው ይህ ሃሳብ ግልጽ ሊደረግ ይችላል አት በከነዓን ምድር ራቡ የጸና ነበር (ድብቅ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ

ይህ ሀረግ የተጠቀመው የታሪኩን አድስ ክፍል መጀመሩን ለማመልከት ነው በቋንቋዎ ይህን መግለጽ የሚችሉበት መንገድ ካለ ይጠቀሙ (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)

በልተው ከጨረሱ በኋላ

ያዕቆብና ቤተሰቡ በልተው ከጨረሱ በኋላ

ያመጡትን

የያዕቆብ ታላቅ ልጆች ያመጡትን

ለኛ ሸምቱልን

እዚህ እኛ ያዕቆብን የያዕቆብን ልጆችና የቀሩ የቤተሰብ አባላትን ያመለክታል:: (ሁሉን አካታች “እኛ” ይመልከቱ)

Genesis 43:3

ይሁዳ እንዲህ አለው

ይሁዳ ለአባቱ ለያዕቆብ እንዲህ አለው

ያ ሰው

ይህ ዮሴፍን ነው የሚያመለክተው ነገር ግን ወንድምቹ ዮሴፍ መሆኑን አላወቁትም ነበር:: እነርሱም እርሱን ያመለክቱን እንደ “ያ ሰው” ወይም በዘፍጥረት 42:30 እንደተነገረው “ያ ሰው የምድሪቱ ጌታ” ነው::

ወንድማችሁን ይዛችሁ ካልመጣችሁ ፊቴን አታዩም ብሎ አስጠንቅቆናል

ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዞአል ይህም እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ታናሽ ወንድማችንን ይዘነው ካላመጣን ፊቱን ማየት እንደማንችል አስጠንቅቆናል” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

በጥብቅ አስጠንቅቆናል

እንዲህም በማለት በጥብቅ አስጠንቀቆናል

ፊቴን አታዩም

ወደ ግብጽ አገር ያለ ብንያም መመለስ እንደማይችሉ ለአባቱ ለማጽናት በዘፍጥረት 43፡ 4-5 ይሁዳ ይህን ሀረግ ሁለት ጊዜ ይጠቀማል:: ፊቴን የሚለው የዚያ ሰው የዮሴፍ ፊት ያመለክታል:: አት “ፊቴን አታዩም” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዜይቤ ይጠቀሙ)

ወንድማችን ከእኛ ጋር

ይሁዳ ራሔል ከመሞትዋ በፊት የወለደችውን የመጨረሻ ልጅ ብንያምን ያመለክታል

እኛም ወደዚያ አንወርድም

ከከነዓን ወደ ግብጽ ጉዞ በሚነገርበት ጊዜ “ወደታች መውረድ” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው

Genesis 43:6

ለምን በደላችሁኝ?

ለምን ይህ ችግር እንዲደርስብኝ አደረጋችሁ?

ሰውየው አጥብቆ ጠየቀን

ሰውየው ብዙ ጥያቄዎችን ጠየቀን

ስለእኛ

እዚህ እኛ የሚለው በተለይ የሚያመለክተው ወደ ግብጽ የወረዱና ከሰውየው ጋር የተነጋገሩ ወንድሞችን ነው

አባታችሁ አሁን በሕይወት አለ? ሌላ ወንድም አላችሁ? ሲል ጠየቀን

ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊጠቀስ ይችላል አት አባታችን በሕይወት እንዳለና ሌላ ወንድም እንዳለን በቀጥታ ጠይቆናል:: (በጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)

እኛም ለጥያቄዎቹ መልስ ሰጠን

የጠየቀንን ጥያቄዎች መለስንለት

…ይዛችሁ እንዲትመጡ እንደሚለን እንዴት ማወቅ እንችል ነበር?

ሰውየው ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንደሚነግር ልጆቹ አለማወቃቸውን አጽንተው ለመንገር ጥያቄ ይጠቀማሉ ይህ አግናኝ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጐም ይችላል አት እንደዚህ … እንደሚለን አላወቅንም ነበር (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ወንድማችሁን ይዛችሁ ውረዱ ወይም አምጡ እንደሚለን
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል አት ወንድማችንን የዘን ወደ ግብጽ እንድንወርድ እንደሚነግረን (በጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
ወንድማችሁን ይዛችሁ ውረዱ
ከከነዓን ወደ ግብጽ ጉዞ በሚነገርበት ጊዜ "ወደታች መውረድ" የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው
Genesis 43:8
እኛና አንተ ልጆቻችንም ደግሞ እንድንድን እንዳንሞትም
እንድንድን እና እንዳንሞት የሚሉ ሀረጐች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው:: ይሁዳም በሕይወት ለመኖር ከግብጽ እህል መሸመት እንዲለባቸው በማጽናት ይናገራል:: አት "መላው ቤተሰባችን እንዲተርፍ ወደ ግብጽ ወርደን እህል መሸመት ይገባናል" (ተመሣሣይ ተጓዳኝ ንጽጽር ይመልከቱ)
እኛም ተነሥተን
እዚህ እኛ ወደ ግብጽ የሚጓዙ ወንድሞችን ያመለክታል:: (የሚያቅፍና የማያቅፍ እኛ ይመልከቱ)
እኛ እንተርፋለን
እዚህ "እኛ" ወንድሞች እስራኤልና መላውን ቤተሰብ ያመለክታል (የሚያቅ "እኛ" ይመልከቱ)
እኛ ሁለታችን
እዚህ እኛ ወንድማማቾችን ያመለክታል (የሚያቅፍና የማያቅፍ "እኛ" ይመልከቱ)
እኛ አንተም
እዚህ አንተ በነጠላ የተገለጸና እስራኤልን ያመለክታል (ሁለተኛ ወገን ሰው ወይም አንተ አጠቃቀም ይመልከቱ)
የእኛም ልጆች ወይም ልጆቻችን
እኛ ወንድሞችን ያመለክታል በረሀቡ ጊዜ ሊሞቱ የሚችሉ ትናንሽ ልጆችን ያመለክታል
እኔ ዋስ እሆንለታለሁ
"ዋስ" የተባለው ረቂቅ ስም እንደ "ተስፋ" የተባለው ግሥ ሊገለጽ ይችላል። (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)
ተጠያቂ እሆናለሁ
ያዕቆብ ይሁዳን እንዴት ተጠያቂ እንደሚያደረገው በግልጽ መነገር አለበት አት በብንያም ላይ በሚደርሰው ነገር ሁሉ ምላሽ እንዲሰጥ ታደርገኛለህ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይጠቀሙ)
እኔ ራሴ ኃላፊነትን እሸከማለሁ
ይህ አንድ ሰው እንደሚሸከመው ዕቃ ተደርጎ ኃላፊነትን መሸከም ይገልጻል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ባንዘገይ ኖሮ
ይሁዳ ቀድሞ መደረግ የነበረበት ነገር ግን ያልተደረገውን ነገር ይገጻል ተጨማሪ እህል ለመሸመት ልጆቹ ወደግብጽ ሳይሄዱ በመቆየታቸው አባቱን እንስራኤልን ይሁዳ በመውቀስ ይናገረዋል (የሚገመቱ ታሳቢ ሁኔታዎችን ይመልከቱ)
እስካሁን ሁለት ጊዜ ደርሰን መመለስ በቻልን
ሁለት ጊዜ መመላለስ በቻልን
Genesis 43:11
እንዲህ ከሆነ ይህን አድርጉ
ይህ ብቸኛ ምርጫችን ከሆነ ይህን አድረጉ
ተሸክማችሁ ውረዱ
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ መውረድ የሚለውን ቃል መጠቀም የተለመደ ነበር
በለሳን
ቆዳን ለማከምና ለመከላከል የሚጠቀሙበት ጣፊጨነት ያለው ቅባታማ ፍሬ ነው:: በዘፍጥረት 37:25 ይህን ቃል እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ:: አት "መድኃኒት"
ቅመማ ቅመሞች
የተለያዩ ቅመማ ቅመሞች በዘፍጥረት 37:25 እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ
ለውዝ
ትናንሽ አረንጓዴ ተክል ለውዞች (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ተምር
ጣፋጭ ጣዕም ያለው የዛፍ ፍሬ (ያልታወቁትን ስለመተርጐም ይመልከቱ)

በእጃችሁ ዕጥፍ ገንዘብ ያዙ
እዚህ "እጅ" ሙሉ ሰውን ይወክላል አት ዕጥፍ ገንዘብ ውሰዱ (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
በየስልቻቻችሁ አፍ የተገኘውን የተመለሰውን ብር በአጠሬታ አድርጋችሁ በእጃችሁ ውሰዱ
እዚህ እጅ ሙሉ ሰውን ይወክላል በስልቼቻችሁ አፍ የተመለሰው ብር የተባለው ሀረግ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት "አንድ ሰው በስልቻችሁ የጨመረውን ብር መልሳችሁ ወደ ግብጽ ውሰዱ" (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤና ተሻጋሪ ግሥና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
Genesis 43:13
ወንድማችሁንም ውሰዱ
ብንያምንም ደግሞ ውሰዱ
ሂዱ
ተመለሱ
ሁሉም የሚችል አምላክ በዚያ ሰው ፊት ምሕረትን ይሰጣችሁ
ምሕረት የሚለው ረቂቅ ስም ርኅራኄ በሚለው ቅጽል ሊተረጐም ይችላል:: አት "ሁሉን የሚችል አምላክ ያ ሰው እንዲራራ ያድርግላችሁ" (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)
ሌላውንም ወንድማችሁንም
ስምዖንን
እኔም ልጆቼን እንዳጣሁ አጣሁ
ልጆቼን ካጣሁ ያው አጣሁ ያዕቆብ ልጆቹን ቢያጣ እንዳጣ ሊቀበል አውቆታል ማለት ነው
በእጃቸው ... ወሰዱ
እዚህ "እጅ" ሙሉ ሰውን ይወክላል:: አት እነርሱም ... ወሰዱ (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ወደ ግብጽም ወረዱ
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ "ወደዚያ ወረደ" የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር
Genesis 43:16
ከራሳቸው ጋር ብንያምን
ብንያም ከዮሴፍ ታላቅ ወንድሞች ጋር
የቤቱን አዛዥ
የቤቱ አዛዥ የዮሴፍን ቤት ተግባራትን ለማስተዳደር ኃላፊነት ነበረው
እነዚህን ሰዎች አመጣቸው
እዚህ "አመጣቸው" እንደ "ወሰዳቸው" ሊተረጐም ይችላል:: ("መጣ" እና "ሄደ" አጠቃቀም ይመልከቱ)
ወደ ዮሴፍ ቤት
ወደ ዮሴፍ ቤት ውስጥ
Genesis 43:18
ሰዎቹም ፈሩ
የዮሴፍ ወንድሞች ፈሩ
ወደ ዮሴፍ ቤት ስለተወሰዱ
ይህ ተሻጋሪ ግስ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡፤ አት "ወደ ዮሴፍ ቤት ይሄዱ ነበር" ወይም "የቤቱ አዛዥ ወደ ዮሴፍ ቤት ይወስዳቸው ነበር" (ተሻጋሪና የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)።
ቀደም ስል እዚህ መጥተን ስንመለስ በየስልቻቻችን ውስጥ ተመልሶ በተጨመረው ብር ሰበብ ነው
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት የቤቱ አዛዥ እየወሰደን ያለው ያነ አንድ ሰው በስልቻቻችን በጨመረው ብር ሰበብ ነው (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
ሰውዬው በዚህ አጋጣሚ ሊተነኰልብን ይሆናል ሊያሥረንም ይችላል
ይህ እንደ አድስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት "ሊከሰን አጋጣሚ እየጠበቀ ስላለ ሊያስረን ይሆናል"
Genesis 43:21
አነናኝ ዐረፍተ ነገር
ወንድሞቹ ለቤቱ አዛዥ መናገር ቀጠሉ
እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ በታሪኩ ዋና ክትት ለማመልከት ተጠቅሞአል በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ካለ ይጠቀሙ::
ወደምናድርበት ቦታ በደረስን ጊዜ

ለአዳር በሠፈርንበት ቦታ በደረስን ጊዜ
እነሆ
እዚህ “እነሆ” የሚለው ቃል ወንድሞቹ ባዩት ነገር እንደተገረሙ ለማሳየት ተጠቅሞአል::
እያንዳንዳችን በስልቾቻችን አፍ ብራችንን ሙሉውን አገኘነው
እያንዳንዳችን በየስልቾቻችን ሙሉውን ብሮቻችንን አገኘው
መልሰን በእጃችን አመጣነው
እዚህ እጆች ሙሉውን ሰው ይወክላሉ አት ብሮቻችንን መልሰን የዘነው መጣን (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ደግሞም እህል መሸመቻ የሚሆነንን ተጨማሪ ገንዘብ ይዘን መጥተናል/ወርደናል
እዚህ እጆች ሙሉ ሰው ይወክላሉ:: አት “ደግሞም እህል መሸመቻ የሚሆነንን ብር ይዘን መጥተናል” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ይዘን ወርደናል
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ “ወደዚያ ወረደ” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር
ሰላም ለእናንተ ይሁን
ረቂቅ ስም ሰላም እንደ ግሥ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ዘና በሉ ወይም ተረጋጉ” (ረቂቅ ስሞችን ይመልከቱ)
አምላካችሁና የአባታችሁ አምላክ
የቤቱ አዛዡ ሁለት የተለያዩ አምላኮችን እየተናገረ አይደለም አት “አምላካችሁ አባታችሁ የሚያመለከው”
Genesis 43:24
እግሮቻቸውን የሚታጠቡበት
ይህ ባህል ረጅም ጉዞ ተጉዘው ከመጡ በኋላ የደከሙ መንገደኞች ድካማቸው እንዲቀል የሚረዱበት ነው:: የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልክቱ)
ለአህዮቻቸው የሚበሉትን ገፈራ ሰጣቸው
ገፈራ ለከበቶች የሚሆን ድርቆሽ ነው
Genesis 43:26
በእጃቸው ያመጡአቸውን እጅ መንሻዎች አበረከቱለት
“እጅ” ሙሉን ሰው ይወክላል:: አት “ወንድሞች ያመጡአቸውን እጅ መንሻቸውን” (ክፍልን እንደሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
በፊቱም ወድቀው ሰገዱለት
ይህ ክብርና አክብሮት የሚገለጽበት መንገድ ነው:: (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
Genesis 43:28
አገልጋይህ አባታችን
አባታቸውን እንደ “አገልጋይህ” ማመልከታቸው አክብሮታቸውን ለማሳየት ነው አት “አባታችን የሚያገለግልህ”
አጐንብሰው ሰገዱለት
እነዚህ ቃላት በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው በሰውየው ፊት ጐንበስ በማለት አክብሮታቸውን ገለጹ:: አት “በፊቱ ሰገዱለት” (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
የሴፍም ዐይኑን ሲቃኝ
ቀና ብሎ ሲመለከት ማለት ነው ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ
የእናቱን ልጅ እናም አለ
ይህ በአድስ ዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “የእናቱን ልጅ.. አየ:: ዮሴፍም አለ፤”
ታናሽ ወንድማችሁ ይህ ነውን?
ተገቢ አማራጭ ትርጉሞች 1 ይህ ሰው ብንያምን እንደሆነ ለማረጋገጥ ዮሴፍ በውኑ ይጠይቃቸዋል ወይም 2) ይህ አግናኝ ጥያቄ ነው:: “ደግሞ ይህ ታናሽ ወንድማችሁ .... “ (አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)
ልጄ
ይህ አንድ ሰው በዝቅተኛ ደረጃ ላለ ሌላ ሰው በጓደኝነት መንገድ የሚጠራው አጠራር ነው:: አት “ወጣቱ”
Genesis 43:30
ፈጥኖ ከክፍሉ ወጣ
ተቻኩሎ ከክፍሉ ወጣ
ወንድሙን በማየቱ ስሜቱ በጥልቅ ስለተነካ
ስሜቱ በጥልቀት የሚለው ሀረግ አንድ መልካም ነገር ሲከሰት የሚሰማ ታላቅ ስሜትን ያመለክታል:: አት “ለወንድሙ የመራራት ጠንካራ ስሜት ነበረው” ወይም “ለወንድሙ ጠንካራ የናፍቆት ስሜት ነበረው” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
አለ
ዮሴፍ እንደሚናገር ግልጽ ማድረግ ይቻላል:: አት “እናም ለአገልጋዮቹ አላቸው” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ማዕድ ይቅረብ
ሰዎች እንዲመገቡ ምግብን ማቅረብ ማለት ነው።
Genesis 43:32
አገልጋዮችም ለዮሴፍ ለብቻው ለወንድሞቹም ለብቻቸው አቀረቡላቸው:: ከእርሱ ጋር ለሚበሉ ግብጻዊያን ደግሞ ለብቻቸው አቀረቡላቸው::
ይህም ዮሴፍ ወንድሞቹና ሌሎች በአንድ ክፍል በተለያየ ቦታ ተቀምጠው ይመገባሉ ማለት ነው አገልጋዮችም ለዮሴፍ ለብቻው ለመንድሞቹም ለብቻቸው እናም ከእርሱ ጋር ለሚበሉ ግብጻዊያን ደግሞ ለብቻቸው አቀረቡላቸው
ከእርሱ ጋር ለሚበሉ ግብጻዊያን ለብቻቸው
እነዚህ ምናልባት ከእርሱ ጋር የሚበሉ የግብጽ ባለሥልጣናት ይሆናሉ ነገር ግን ከዮሴፍና ከዕብራዊያን ወንድሞቹ ተለይተው ተቀምጠዋል
ግብጻዊያን ከዕብራዊያን ጋር መመገብ አይሆንላቸውም ምክንያቱም ያ ለግብጻዊያን መርከስ ነውና
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል ይህንን ያደረጉበት ምክንያት ግብጻዊያን ከዕብራዊያን ጋር መመገብ ጸያፍ አድርገው ያስባሉ
አብረው እንጀራ አይበሉም
እዚህ እንጀራ ጠቅላላ ምግብ ይወክላል (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ወንድሞቹ በእርሱ ፊት ተቀመጡ
እያንዳንዱ ወንድም የት መቀመጥ እንዳለበት ዮሴፍ እንዳዘጋጀ ሊገመት ይገልጻል የተገለጸውን መረጃ ግልጽ ማድረግ ይቻላል አት የሚቀመጡበት ቦታ በተዘጋጀላቸው መሠረት በሰውየው/ዮሴፍ ፊት ወንድሞቹ ተቀመጡ (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይጠቀሙ)
በፊቱም በኩሩ እንደታላቂነቱ ታናሹም እንደታናሽነቱ
“በኩር”ና “ታናሽ” የተጠቀሙት ሁሉም ወንድሞች በአንድነት እንደየዕድሜያቸው በተርታ እንደተቀመጡ ለመግለጽ ነው::( ነጠላ ነገር በብዙ የመግለጽ ዘይቤ/ merism/ ይመልከቱ)
ሰዎቹም/ወንድሞቹም በአንድነት ተገረሙ
ይህን ባወቁ ጊዜ ሰዎቹ በጣም ተገረሙ
የብንያም ድርሻ ከሌሎች ወንድሞች አምስት እጥፍ ነበር
አምስት እጥፍ የሚለው ሀረግ በአጠቃላይ ብዙ በሚለው ሊገለጽ ይችላል:: አት “ብንያም የተቀበለው ድርሻ ወንድሞቹ ከተቀበሉት በጣም ብዙ ነበር”

Chapter 44
Genesis 44:1
አጠቃላይ መረጃ
ይህ በታሪኩ አድስ ክስተት ይጀምራል ይህ በተለይ ከግብዣው ሁለተኛው ቀን ማግሥት የተከሰተውን ያመለክታል።
የቤቱ አዛዥ
የቤቱ አዛዡ የዮሴፍ ቤት ተግባራትን ለማስተዳደር ኃላፊነት ያለው ነበር
የሁሉም ሰው ገንዘብ
የእነርሱ ገንዘብ በትንሽ ቦርሳ ውስጥ የተቀመጡ የብር ሳንቲሞች ነበሩ
በስልቻው አፍ
በስልቻው
ዋንጫየን የብሩን ዋንጫዬን... ጨምረው
የብሩን ዋንጫዬን ጨምረው
በታናሹ ወንድማቸው ስልቻ አፍ
ወንድም የሚለው ቃል የታወቀ ነው አት በታናሽ ወንድማቸው ስልቻ (ድብቅ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
Genesis 44:3
ጎህ ሲቀድ
የማለዳ ብርሃን ሲወጣ

ሰዎቹ ከነአህዮቻቸው ተሸኙ

ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ሰዎችን ከነአህዮቻቸው ሸኙአቸው” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ለበጎ ነገር ስለምን ክፉ መለሳችሁ?

ይህ ጥያቄ ወንድሞቹን ለመቆጣት ተጠቅሞአል:: አት እኛ “ለእናንተ መልካም ካደረግን በኋላ ክፉ መለሳችሁብን” (ሽንገላ አዘል/ rhetorical/ ጥያቄ ይመልከቱ)

ይህ ጌታዬ የሚጠጣበት የተሰወረ ነገርም የሚያውቅበት ጽዋ አይደለምን?

ይህ ጥያቄ የተጠቀመው ወንድሞቹን ለመቆጣት ነው። አት “ይህ ጽዋ ጌታዬ የሚጠጣበትና የተሰወረ ነገርንም የሚያውቅበት እንደሆነ በእርግጥ ታውቃችሁ” (ሽንገላን የያዘ ጥያቄ ይመልከቱ) ይህ ያደረጋችሁት የፈጸማችሁት ድርጊት ክፉ ነው ያደረጋችሁት የሚለውን መደጋገሙ ትኩረት ለመስጠት ነው አት የፈጸማችሁት ነገር እጅግ ክፉ ነው ተመሣሣይ ተጓዳኝ ንጽጽር ነው::

Genesis 44:6

ይህንም ቃል ነገራቸው

ዮሴፍ የነገራቸው የነገረውን ነገራቸው

ጌታዬ እንደዚህ ያለውን ቃል ለምን ይናገራል?

“ቃል” የተናገረውን ነገር:: ይወክላል ወንድሞቹ የቤቱን አዛዥ እንደ “ጌታዬ” ያመለክታሉ:: ይህ በከፍተኛ ኃላፊነት ላሌ ሰው የሚነገር መደበኛ አባባል ነው:: አት “ጌታዬ ለምን እንደዚህ ይናገራሉ?” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ዘይቤና አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

ይህን ነገር ማድረግ ከባሪያዎችህ ይራቅ

አንድ ሰው አንድን ነገር የማያደርገው ያ ሰው አንድን ዕቃ ከራሱ አርቆ እንደማስቀመጥ ተደርጐ ተገልጾአል፣ (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

Genesis 44:8

እነሆ…ብር

“እኛ ስለምንናገረው ነገር ያድምጡ እናም የምንናገረው ነገር እውነት እንደሆነ ያያሉ፤ ብሩ”

በየስልቾቻችን አፍ የተገኘውን ብር

“በየስልቾቻችን ያገኘነውን ብር ያውቃሉ”

ከከነዓን አገር መልሰን ወደ አንተ አምጥተናል

ከከነዓን መልሰን ወደ አንተ አምጥተናል

ታዲያ ብር ወይም ወርቅ ከጌታህ ቤት እንዴት እንሰርቃለን?

ወንድሞቹ ከግብጽ ጌታ እንዳልሠረቁ እትኩሮት ለመስጠት ጥያቄ ይጠቀማሉ:: አት “ስለዚህ ከጌታህ ቤት የወሰድነው ምንም ነገር የለም!” (ሽንገላ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)

ብር ወይም ወርቅ

እነዚህ በጣምራ ቃላት የተጠቀሙት ዋጋ ያለውን ምንም ነገር እንዳልሠረቁ ለመግለጽ ነው

ከአገልጋዮችህ ይህ የተገኘበት

ወንድምች ራሳቸውን እንደ “የአንተ አገልጋዮች” ይገልጻሉ:: ይህ ከፍተኛ ስልጣን ላለ ሰው የሚነገር መደበኛ መንገድ ነው:: እንዲሁም ይህ የተገኘበት ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክሊገለጽ ይችላል:: አት “ከእኛ አንዱ ጽዋውን/ዋንጫውን የሠረቀ ከተገኘ” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገለላለጽና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

እኛ ደግሞ የጌታችን ባሮች እንሁን

እዚህ ጌታችን የቤቱን አዛዥ ያመለክታል ይህ በሁለተኛ ሰው መልክ ሲገለጽ ይችላል አት እንደባሪዎች ሊትወስደን ትችላለህ (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ሰው አገለላለጽ ይመልከቱ)

አሁን እንዲሁ እንደነገራችሁ ይሁን

መልካም ነው: እንዳላችሁት አደርጋለሁ:: እዚህ “አሁን” “በዚህ ጊዜ” ማለት አይደለም ነገር ግን የሚቀጥለው ዋና ነጥብ ትኩረትን ለመሳብ ተጠቅሞአል::

ጽዋው የተገኘበት ባሪያዬ ይሆናል

ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት ከስልቾቻችን በአንዱ ጽዋውን ካገኘው ያ የተገኘበት ሰው ባሪያዬ ይሆናል (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 44:11

የየራሱን ስልቻ ወደ ምድር አወረደ

የየራሱን ስልቻ አራገፊ

ከታላቁ … እስከታናሹ

“ወንድም” የተባለው ቃል የታወቀ ነው:: “ከታላቅ ወንድም ….እስከ ታናሽ ወንድም” (የተደበቁ ቃላትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)

ጽዋው በታናሹ በብንያም ስልቻ ተገኘ

ይህ እንደ አድስ ዐረፍተ ነገርና ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊተረጐም ይችላል በታናሹ ወንድም የቤቱ አዛዥ ጽዋውን በብንያምን ስልቻ አገኘ (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

በዚህን ጊዜ እነርሱ ልብሳቸውን ቀደዱ

እዚህ እነርሱ ወንድምቹን ያመለክታል ልብስን መቅደድ የታላቅ ሐዘን ወይም ተካዜ ምልክት ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

በየአህዮቻቸው…ተመለሱ

በየአህዮቻቸው…. እናም ተመለሱ

Genesis 44:14

እርሱ ገና እዚያው ነበረ

ዮሴፍ እዚያው ነበረ

በፊቱም መሬት ላይ ተደፉ

በፊቱም መሬት ላይ ወደቁ:: ይህ ወንድምቹ ጌታው ምሕረት እንዲያደርግላቸው የመፈለጋቸው ምልክት ነው:: (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)

እንደ እኔ ያለ ሰው ምሥጢርን እንዲያውቅ አታውቁምን

ዮሴፍ ወንድሞቹን ለመቆጣት ጥያቄ ይጠቀማል:: አት “እንደ እኔ ያለ ሰው ስውር ነገርን በጥበብ እንደሚያውቅ ታውቃላችሁ” (ሽንገላን ያዘለ ጥያቄ ይመልከቱ)

Genesis 44:16

ለጌታዬ ምን እንመልሳለን? ምንስ እንናገራለን? ወይም በመን እንነጻለን?

ሶስቱም ጥያቄዎች ሁሉ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው:: የተደረገውን ለመግለጽ የሚናገሩት ምንም እንደሌለ ትኩረት ለመስጠት እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማሉ። አት “ጌታዬ የምንናገረው የለንም የሚረባ ነገር መናገር አንችልም ራሳችንን ንጹህ ማድረግ አንችልም” (ተመሣሣይ ተጓዳኝ አገላለጽ እና ሽንገላ አዘል ጥያቄዎች ይመልከቱ)

ለጌታዬ ምን እንላለን …. የጌታዬ ባሪያዎች

እዚህ ጌታዬ ዮሴፍን ያመለክታል ይህ ለአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው በሁለተኛ ወገን ሰው መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ምን እንላለን … ባሪያዎችህ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የአገልጋዮችን/የባሪያችህን በደል ገልጦአል

ወንድሞቹ ራሳቸውን እንደ ባሪያዎች ያቀርባሉ :: እዚህ ገለጠ የሚለው እግዚአብሔር ወንድሞቹ ያደረጉትን ገለጠ ማለት አይደለም:: ነገር ግን እነርሱ ስላደረጉት ነገር እግዚአብሔር እየቀጣቸው ነው የሚል ትርጉም አለው:: አት “እግዚአብሔር ላለፈው ኃጢአት እየቀጣቸው ነው”

የባሪያዎችህን በደል

ወንድሞቹ ራሳቸውን እንደ ባሪያዎች ያቀርባሉ:; ይህ ለአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: በአንደኛ ወገን ሰው መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “በደላችንን” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)

እንግዲህ ጽዋው በእጁ የተገኘበት

እዚህ “እጅ” ሙሉ ሰው ይወክላል:: እንዲሁም የተገኘበት የሚለው ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:; አት “ጽዋህን የወሰደው” (ምትክ ቃል አጠቃቀምና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

ይህን ማድረግ ከእኔ ይራቅ

አንድ ሰው የማያደርገው አንድ ነገር ያ ሰው ከራሱ አርቆ የሚያቀምጠው ዕቃ ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “ያን ነገር የሚያደርግ የእኔ ዓይነት አይደለም” (ዘይቤያዊ አነጋሃገር ይመልከቱ)

ጽዋው በእጁ የተገኘበት ሰው

እዚህ “እጅ” ሙሉ ሰው ይወክላል:: እንዲሁም የተገኘበት የሚለው ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:; አት “ጽዋዬን የወሰደው ሰው” (ምትክ ቃል አጠቃቀምና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)

Genesis 44:18

ቀረብ ብሎ

ተጠግቶ

እኔ አገልጋይህ

ይሁዳ ራሱን እንደ “አገልጋይህ ወይም ባሪያህ” ያመለክታል:: ይህ ለአንድ ከፍተኛ

ባለሥልጣን የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: ይህ በአንደኛ ወገን ሰው መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እኔ ባሪያህ ወይም አገልጋይህ”(አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
በጌታዬ ጆሮ አንዲት ቃል እንድናገር
“ጆሮ” የሚለው ለሙሉ ሰው የሚሆን ምትክ ቃል ነው። አት “ጌታዬ ሊናገርህ” (ምትክ ቃል አጠቃቀም ይመልከቱ)
በጌታዬ ጆሮ
እዚህ ጌታዬ ዮሴፍን ያመለክታል። ይህ ለአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: ይህ በሁለተኛ ወገን ሰው መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ለአንተ”(አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
እኔን አገልጋይህን ቁጣህ አያቃጥለኝ
መቆጣት እንደሚያቃጥል እሳት ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “አባክህን እኔን አገልጋይህን አትቆጣኝ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
አንተ እንደፈርዖን ነህና
ጌታው ትልቅ ሥልጣን እንዳለው ትኩረት ለመስጠት ከፈርዖን ጋር ያወዳድረዋል:: ይህም የሚገልጸው ሊቆጣውም ሊገድለውም እንደሚችል ነው አት “እንደ ፈርዖን ኃይለኛ ስለሆንህና ወታደሮችህም ሊገድሉኝ ስለሚችሉ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቀ መረጃ ይመልከቱ)
ጌታዬ ባሪያዎቹን፤ “አባት አላችሁ ወይም ወንድም?”ብሎ ጠየቀ::
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ጌታዬ አባት ወይም ወንድም እንዳለን ጠየቀን” (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
ጌታዬ ባሪያዎቹን ጠየቀ
ይሁዳ ዮሴፍን “ጌታዬ” እና “እርሱ” በሚሉ ቃላት ያመለክተዋል:: እንዲሁም ደግሞ ወንድሞቹንና ራሱን እንደ “የእርሱ ባሪያዎች” ይገልጻል:: አት “አንተ ጌታዬ ባሪያዎችህን ጠየቅሄን ወይም አንተ ጠቀየቅሄን” (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)
Genesis 44:20
አጠቃላይ መረጃ
በዮሴፍ ፊት መናገሩን ይሁዳ ቀጠለ
እኛም ለጌታዬ እንዲህ አልን ‘ሽማግሌ አባት አለን .... አባቱም ይወድደዋል’
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እናም እኛ እንዲህ አልን ‘አባት አለን አባቱም ይወድደዋል’” (ጥቅስን በጥቅስ ውሰጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
ለጌታዬ እንዲህ አልን
ይሁዳ ዮሴፍን እንደ “ጌታዬ” ያመለክተዋል:: ይህ ለአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: አት “ጌታዬ እኛም እንዲህ አልን”(አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)
አባቱም ይወድደዋል
ይህ ለጓደኛ ወዳጅ ወይም ለቤተሰብ አባል ያለውን ፍቅር ይገልጻል
ከዚያም ለባሪያዎችህ ወደእኔ አምጡት እኔም አየዋለሁ አልህ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እናም አንተ ለባሪያዎችህን ታናሽ ወንድማችሁን አምጡት እኔም አየዋለሁ አልህ’” (ጥቅስን በጥቅስ ውሰጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
ከዚያም ለባሪያዎችህ እንዲህ አልህ
ይሁዳ ወንድሞቹንና ራሱን እንደ እርሱ ባሪያዎች ያመለክታል:: አት “ከዚያም ለእኛ ለባሪያዎችህ እንዲህ አልህ”(አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)
ወደ እኔ ይዛችሁ ውረዱ
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ ሲነገር መውረድ የሚለው ቃል የተለመደ ነው:: አት “ወደ እኔ አምጡት” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ከዚያም በኋላ ጌታዬን አልነው “ብላቴናው... አይሆንለትም ...አባቱ ይሞታልና”
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “መልሰን እኛም ለጌታዬ ልጁ ....አይችልም፤ ....አባትየው ይሞታል” (ጥቅስን በጥቅስ ውሰጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
አባትዬው ይሞታል
ከማዘን የተነሣ አባታቸው እንደሚሞት ይገልጻል (ግምታዊ እውቀት ወይም ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 44:23
አጠቃላይ መረጃ
ይሁዳ ታሪኩን ለዮሴፍ መናገር ቀጠለ
ከዚያም ባሪያዎችህን እንዲህ አልሄን፤ ታናሽ ወንድማችሁ ከእናንተ ጋር ጋር ካልመጣ ዳግመኛ ፊቴን አታዩም
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ከዚያም ለባሪያዎችህ ታናሽ ወንድማችን ከእኛ ጋር ካልመጣ ፊቴን አታዩም አልሄን ” (ጥቅስን በጥቅስ ውሰጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
ከዚያም ለባሪያዎችህ አልህ
ይሁዳ ራሱንና ወንድሞቹን እንደ “እርሱ ባሪያዎች” ያመለክታል። ይህ ትልቅ ባለሥልጣን ለሆነ ለአንድ ሰው የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው። (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)
ይዞ መውረድ ...ወደ ታች መውረድ
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ ሲነገር መውረድ የሚለው ቃል የተለመደ ነው::
ዳግመኛ ፊቴን አታዩም
እዚህ “ፊት” ሙሉ ሰውን ይወክላል:: አት እንደገና አታዩኝም (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)
ከዚያም እንዲህ ሆነ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ለማመለከት ነው:: በቋንቋዎ ይህን የሚገልጹበት መንገድ ካለ ይጠቀሙ:: (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)
ወደ ባሪያህ ወደ አባታችን በወጣን ጊዜ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ ሲነገር “ወደ ላይ መውጣት” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው
የጌታዬን ቃል ነገርነው
ይሁዳ ዮሴፍን እንደ “ጌታዬ” ያመለክታል:: አት ጌታዬ የነገርከውን ቃል ነገርነው”(አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን አገላለጽ ይመልከቱ)
አባታችን ‘ተመልሳችሁ ጥቂት እህል ሸምቱልን አለ’
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “አባታችን እንደገና ወደ ግብጽ በመሄድ ለእኛና ለቤተሰቦቻችን እህል እንድንሸምት ተናገረን ” (ጥቅስን በጥቅስ ውሰጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
እኛም አልነው ‘መሄድ አንችልም ታናሽ ወንድማችን ከእኛ ጋር...’
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ የያዘ ነው እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ከዚያም ለእርሱ ወደ ግብጽ መውረድ አንችልም አልን ታናሽ ወንድማችን ከእኛ ጋር ... ከእኛ ጋር ” (ጥቅስን በጥቅስ ውሰጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
የሰውየውን ፊት ማየት
እዚህ ፊት ሙሉ ሰውን ይወክላል:: አት “ሰውየውን ለማየት” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)
Genesis 44:27
ይሁዳ ታሪኩን ለዮሴፍ መናገሩን ቀጠለ
እንዲህ አለን ሚስቴ ሁለት ወንዶች ልጆችን እንደወለደችልን እናንተ ታውቃላችሁ አንዱ ከእኔ ወጣ አውሬ በላው አላችሁኝ እስከ ዛሬም አላየሁትም ይህንም ከእኔ ለይታችሁ ደግሞ ብትወስዱ ክፉም ቢያገኘው ሽበቴን በሐዘን ወደ መቃብር ታወርዱታላችሁ ይህ ሁለት ደረጃና ሶስት ደረጃ ጥቅሶችን ይዞአል እነዚህም እንደተዘዋዋሪ ጥቅሶች ሊገለጹ ይችላሉ አት እንዲህ አለን ሚስቱ ራሔል ሁለት ወንዶች ልጆችን ብቻ እንደወለደችለት እናውቃለን ከእነርሱ አንዱ ወጣና አውሬ በላው እናም እስከ ዛሬ አላየሁትም ሌላውን ልጅ ብንወስደውና ክፉ ቢያገኘው በሐዘን እንዲሞት እናደርጋለን (ጥቅስን በጥቅስ ውሰጥ እና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)ከዚይ አለ
እኛን እንዲህ አለን
እዚህ “እኛ” ዮሴፍን አያካትትም (ነጠላና ብዙ ወይም አካታች “እኛ” ይመልከቱ)
እናንተ ታውቃላችሁ
እዚህ “እናንተ” ብዙና ወንድሞቹን ያመለክታል (“እናንተ” አጠቃቀም ዓይነት ይመልከቱ)
በእውሬ ተበላ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል አት አውሬ በላው ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ
ጉዳት ቢደርስበት
ለአንድ ሰው አንድ ክፉ ነገር የሚደርሰበት ጉዳት ወደዚያ ሰው እንደሚመጣ ተደርጐ

ተቆጥሮአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ሽበተን በሐዘን ወደ መቃብር ታወርዱታላችሁ
“ወደ መቃብር ማውረድ” እንዲሞትና ወደ መቃብር እንዲወርድ ማድረግ ማለት ነው:: “ማውረድ” የሚለውን ቃል የተጠቀመው መቃብር በመሬት ውስጥ እንደሆነ በተለምዶ የታወቀ ስለሆነ ነው:: አት “ከዚያም እኔን ሽማግሌውን በሐዘን እንዲሞት ታደርጋላችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ሽበቴን
ያዕቆብን የሚያመለክትና ሽምግልናውን አበክሮ የሚናገር ነው:: አት “እኔ ሽማግለው” (ምትክ ቃል አጠቃቀም ይመልከቱ)
Genesis 44:30
አሁን
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ጠቃሚ ነገር ትኩረት እንዲሰጥበት ተጠቅሞአል
እንግዲህ በምንመለስበት ጊዜ ... በሐዘን ወደ መቃብር
ይሁዳ ያለ ብንያምን ወደ አባቱ በሚመለስበት ጊዜ ምን ሊፈጠር እንደሚችል የሚገምተውን ነገር ግን እውነት የሆነውን ለዮሴፍ ይገልጻል (ግምታዊ ሁኔታዎችን ይመልከቱ)
ወደ ባሪያህ በሚመጣበት ጊዜ
እዚህ “መምጣት” “መሄድ” ወይም “መመለስ” በሚለው መተርጐም ይችላል::
ብላቴናው ከእኛ ጋር አለመኖር
ልጁ ከእኛ ጋር አለመኖር
ሕይወቱ ከልጁ ሕይወት ጋር የተሣሠረ ስለሆነ
አባታቸው ልጁ ከሞቴ እሞታለሁ ያለው አባባል የሁለቱ ሕይወት በአካል በጥብቅ የተሣሠረ እንደሆነ ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “እርሱም ልጁ ካልተመለሰ እሞታለሁ ስላለ” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
እንዲህም ሆነ
ይሁዳ ወደፊት ይሆናል ብሎ ስለሚገምተው ነገር በእርግጥ እደሚደረግ አድርጐ ይናገራል (ግምታዊ ሁኔታዎች ይመልከቱ)
ባሪያዎችህ የባሪያህን የአባታችንን ሽበት በሐዘን ወደ መቃብር ያወርዳሉ
ወደ መቃብር ማውረድ እንዲሞትና ወደ መቃብር እንዲወርድ ማድረግ ማለት ነው:: “ማውረድ” የሚለውን ቃል የተጠቀመው መቃብር በመሬት ውስጥ እንደሆነ በተለምዶ የታወቀ ስለሆነ ነው:: አት “እናም ሽማግሌውን አባታችንን በሐዘን እንዲሞት እናደርጋለን” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ባሪያዎችህ ወይም አገልጋዮችህ
ይሁዳ ራሱንና ወንድሞችን “ባሪያዎችህ” ብሎ ያመለክታል:: ይህ ለአንድ ትልቅ ባለሥልጣን መደበኛ መንገድ የሚነገርለት ነው:: አት “እኛ አገልጋዮችህ” ወይም “እናም እኛ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገንነ ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
የባሪያህን የአባታችንን ሽበት
እዚህ “ሽበት” ያዕቆብን የሚወክልና ሽምግልናውን የሚናገር ነው:: አት “ሽማግሌው አባታችን” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ) ስለ ልጁ ደኀንነት በአባቴ ፊት ራሴን ዋስ አድርጌአለሁ ረቂቅ ስም ዋስ ተስፋ በሚለው ግሥ ሊገለጽ ይችላል አት ልጁን በሚመለከት ለአባቴ ተስፋ ስጥቼዋለሁ ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ
ባሪያህ
ይሁዳ ራሱን “ባሪያህ” ብሎ ያመለክታል። አት “ለእኔ ለባሪያህ” ወይም “ለእኔ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
በአባቴ ፊት በደሌን እሸከማለሁ
እንደበደለኛ መቆጠር በደል እንድሰው የሚሸከመው ነገር ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “አባቴ ይወቅሰኛል” (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
Genesis 44:33
አሁን
ይህ በአሁን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ዋና ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ተጠቅሞአል::
ባሪያህ
ይሁዳ ራሱን “ባሪያህ” ብሎ ያመለክታል። አት “እኔ ለባሪያህ” ወይም “እኔ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
ልጁ... ይውጣ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ መውጣት የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር
ልጁን ሳልይዝ እንዴት ተመልሼ ወደ አባቴ እሄዳለሁ?
ብንያምን ወደ ቤት ካልተመለሰ አባቱ ሊኖረው የሚችለውን ሐዘን ለማተኮር ይሁዳ ጥያቄ ይጠቀማል:: አት “ልጁ ከእኔ ጋር ካልሆነ ወደ አባቴ መመለስ እልችልም“ (አግናኝ ወይም ሽንገላ አዘል ጥያቄዎች ይመልከቱ)
በአባቶ ላይ የሚደርሰውን መከራ እንዳላይ
ከባድ መከራ የደረሰበት ሰው በዚያው ሰው ክፉ ነገር እንደመጣበት ተደርጐ ተነግሮአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)

---

Chapter 45
Genesis 45:1
ራሱን ሊቆጣጠር አልቻለም
ስሜቱን ሊገታ አልቻለም ማለት ነው ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ማልቀስ ጀምሮ ነበር”
ከጐኑ
አጠገቡ
የፈርዖን ቤት
እዚህ “ቤት” በፈርዖን ቤተመንሥት ያሉ ሰዎችን ይወክላል። አት “በፈርዖን በተመንግሥት ያለው ሁሉ” (ምትክ ቃላት የመጠቀም ዘይቤ ይመልከቱ)
በፊቱ ተደናግጠው
እርሱን ፈርተው
Genesis 45:4
ወደ ግብጽ የሸጣችሁኝ
ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት “ወደ ግብጽ ለመጠኑኝ ነጋዴዎች እንደ ባሪያ የሸጣችሁኝ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
አትዘኑ
“አትቄጩ” ወይመ “አትጨነቁ”
ወደዚህ ስለሸጣችሁኝ
ትርጉሙም በግልጽ ሊነገር ይችላል። አት “እንደ ባሪያ ሸጣችሁኝ እናም ወደ ግብጽ ምድር ላካችሁን”
ሕይወት ለማዳን
እዚህ “ሕይወት” ዮሴፍ በረሃቡ ጊዜ ያዳናቸውን ሰዎች ይወክላል:: አት “የብዙ ሰዎችን ሕይወት እንዳድን” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)
የማይታረስባቸውና ሰብል የማይሰበሰብባቸው አምስት ዓመታት ገና አሉ
የማይታረስባቸው ወይም ሰብል የማይሰበሰባቸው አምስት ዓመታት አሉ እዚህ የማይታረስባቸውና ሰብል የማይሰበስብባቸው ሰብሎች ከድርቁ የተነሣ እንደማይመረቱ የሚገልጹ ናቸው:: አት “ረሃቡ ለተጨማሪ አምስት ዓመታት ይቀጥላል” (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)
Genesis 45:7
በምድር ላይ ቅሬታን አስቀርላችሁ ዘንድ
“እናንተና ቤተሰቦቻችሁ ከምድር ላይ ፈጽማችሁ እንዳትጠፉ” ወይም “ዘራች ከምድር ላይ እንዲኖር”
ሕይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግ
ማዳን የተባለው ረቂቅ ስም ማትረፍ በሚለው ሊገለጽ ይችላል:: አት “በታላቅ መንገድ በማትረፍ በሕይወት እንዲትኖሩ” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)
ፈርዖን አባት አድርጐኛል
ዮሴፍ ፍርያንን ማማከሩና መርዳቱ ዮሴፍ እንደፈርዖን አባት ተደርጐ ተገልጾአል:: አት “የፈርዖን መሪ ወይም አማካሪ አድርጐኛል” ወይም “የፈርዖን ዋና አማካሪ አድርጐኛል” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)
በቤቱ ሁሉ ላይ
እዚህ “ቤት” በቤተመንግሥቱ የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል:: አት “በቤተሰዎቹ ሁሉ ላይ” ወይም “በቤተመግሥቱ ላይ” (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)
በግብጽ ምድር ሁሉ ላይ ገዥ
እዚህ “ምድር” ሰዎችን ይወክላል:: አት “በግብጽ ምድር ሰዎች ሁሉ ላይ ገዥ” (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)
ገዥ
ዮሴፍ ከግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ሁለተኛ ደረጃ ገዥ ነው ማለት ነው:: ይህ የተነገረው መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)

Genesis 45:9
ወደ አባቴ ውጡ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ ሲነገር ወደ ላይ መውጣት የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር:: አት "ወደ አባቴ ሂዱ"
እንዲህም በሉት ልጅህ ዮሴፍ እዲህ ይላል "እግዚአብሔር ... ያለህን ሁሉ"
ይህ ሶስት ደረጃ ያለው ጥቅስ ነው በሁለት ደረጃዎች ቀለል ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: አት "እኔ የምለውን ንገሩት እግዚአብሔር ያለህን ሁሉ" (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥታና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
ወደ እኔ ና/ውረድ
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ ሲነገር ወደ ታች መውረድ የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር:: አት "ወደዚህ ወደ እኔ ና"
ወደ ችግር ና
ችግርን እንደ መድረሻ አድርጐ ይናገራል:: አት "ማጣት" ወይም "ረሀብ" (ዘይቤያዊ አነገር ይመልከቱ)
Genesis 45:12
የእናንተ ዐይኖች አይተዋል እናም የወንድማችሁ የብንያምም ዐይኖች አይተዋል
እዚህ "ዐይኖች" ሙሉ ሰው ይወክላሉ:: አት "እናንተ ሁላችሁና ብንያም ታያላችሁ" (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ለእናንተ የተናገረቻችሁ የእኔ አፍ እንደሆነች
እዚህ አፍ ሙሉ ሰውን ይወክላል። አት "እኔ ዮሴፍ እነግራችኋለሁ" (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
በግብጽ ስላለኝ ክብር ሁሉ
የግብጽ ሰዎች በታላቅነት እንዴት እንደሚያከብሩኝ
አባቴን ወደ ታች ወደዚህ አምጡት
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ ሲነገር ወደ ታች መውረድ የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር:: አት "አባቴን ወደዚህ አምጡት"
Genesis 45:14
የወንድሙን የብንያምንም አንገት አቀፎ አለቀሰ ብንያምም በአንገቱ ላይ አለቀሰ
ዮሴፍ ወንድሙን ብንያምን አቀፈውና ሁለቱም አለቀሱ
ወንድሞቹን ሁሉ ሳማቸው
በጥንታዊቷ ቅርብ ምሥራቅ ዘመድን በመሳም ሰላምታ መስጠት የተለመደ ነበር:: በቋንቋዎ እንዲህ የመሰለ ስሜት ገላጭ ሰላምታ አሰጣጥ ካለ ያን ይጠቀሙ:: ከሌለ ግን ተገቢ የሆነውነ ቃል ይጠቀሙ::
እየሳማቸው አለቀሰ
ይህም ዮሴፍ በሳማቸው ጊዜ እያለቀሰ ነበር ማለት ነው
ከዚያም በኋላ ወንድሞቹ ከእርሱ ጋር መነጋገር ጀመሩ
አስቀድመው ሊነጋገሩ ፈርተው ነበር:: አሁን ግን በነጻነት መነጋገር እንደሚችሉ ተሰማቸው:: የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: አት "ከዚያም በኋላ ወንድሞቹ ከእርሱ ጋር በነጻነት መነጋገር ጀመሩ" (ግምታም እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 45:16
በፈርዖን ቤት የዮሴፍ ወንድሞች መጡ ተብሎ ወሬ ተሰማ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዞአል:: እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊጠቀስ ይችላል:: እንዲሁም ደግሞ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት "የዮሴፍ ወንድሞች እንደመጡ በፈርዖን ቤተመንግሥት ያለው ማንኛውም ሰው ሰማ" (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅስ እናም ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
የፈርዖን ቤት
የፈርዖንን ቤተመንሥት ይወክላል
ለወንድሞችህ እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ ይህን አድርጉ እህዮቻችሁን ጭናችሁ ወደ ከነዓን ምድር ሂዱ፤ አባታችሁንና ቤተሰባችሁን ይዛችሁ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም እጅግ ለም ከሆነው የግብጽ ምድር እሰጣችኋለሁ፤ የምድርቱንም ስብ/በረከት ትበላላችሁ።
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዞአል:: እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊጠቀስ ይችላል:: አት "አህዮቻቸውን እንዲጭኑና ወደ አባታቸውና ቤተሰቦቻቸውው ወደ ከነዓን እንዲሄዱ ለወንድሞችህ ንገራቸው፤ ወደዚህ እንዲመጡና እኔም እጅግ ለም ከሆነው የግብጽ ምድር እንደሚጣቸው፤ የምንሰጠውን በረከት እንደሚመገቡ ደግሞም ንገራቸው" (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅስ ይመልከቱ)
እኔም መልካም ከሆነው የግብጽ ምድር እሰጣችኋለሁ፤
እኔም እጅግ ለም የሆነውን የግብጽ ምድር እሰጣችኋለሁ
የምድርቱንም ስብ ትበላላችሁ
ምድርቱ የሚትሰጠው መልካም እህል እንደ ምድሪቱ ስብ ተደርጐ ተቆጥሮአል:: አት "የምድሪቱንም እህል ትመገባላችሁ" (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
Genesis 45:19
አጠቃላይ መረጃ
ዮሴፍ ለወንድሞቹ ምን መናገር እንዳለበት ፈርዖን መናገሩን ቀጠለ
አሁን
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ጠቃሚ ነጥብ/ ቁም ነገር ትኩረት እንዲሰጥበት ተጠቅሞአል
እንዲህ ብለህ እዘዛቸው ይህን አድርጉ ከግብጽ ምድር ልጆቻችሁንና ሚስቶቻችሁን የምታጓጉዙበት ሠረገላዎች ውሰዱ አባታችሁንም ይዛችሁ ኑ ስለንብረታችሁ ምንም አታስቡ ከግብጽ ምድር እጅግ ለም የሆነው የእናንተ ነውና
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዞአል:: እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊጠቀስ ይችላል:: አት "ደግሞም ከግብጽ ምድር ልጆቻችሁንና ሚስቶቻችሁን እናም አባታችሁንም ይዘው እንዲመጡ የሚያጓጉዙበትን ሠረገላዎች እንዲወስዱ ንገራቸው እኔም በግብጽ መልካም የሆነውን ስለሚሰጣቸው ንብረታችሁን ይዘው ለመምጣት ምንም አይጨነቁ (ጥቅስን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅስ ይመልከቱ)
ታዝዘሃል
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት "ደግሞም እንትነግራቸው አዝሃለሁ ወይም ደግሞም ንገራቸው" (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
ሠረገላዎችን ይውሰዱ
ሠረገላዎች ሁለት ወይም አራት ጐማ ያላቸው የጭነት ሠረገላዎች ናቸው እንስሳት ተሳቢውን ይገትቱታል
Genesis 45:21
ለመንገድ ስንቅ ሰጣቸው
ለጉዞአቸው የሚያስፈልጋቸውን ሰጣቸው
ለሁሉም ሁለት ሁለት መለወጫ ልብስ ሰጣቸው
አምስት መለወጫ ልብስ ከተሰጠው ከብንያምን በስተቀር ሌሎች እያንዳንዳቸው ሁለት መለወጫ ልብስ ተቀብለዋል (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
ሶስት መቶ ጥሬ ብር
300 ጥሬ ብር (ቁጥሮችን ይመልከቱ)
አሥር አህዮች ... አሥር እንስት አህዮች
አህዮቹ በሥጦታው ተካትተዋል (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 45:24
አትጣሉ
ተገቢ ትርጉሞች የሚያጠቃልሉት 1) አትከራከሩ 2) አትኮራረፉ
ከግብጽ ወጥተው ወደ ላይ ወጡ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ "ወደላይ" የሚለው ቃለ መጠቀም የተለመደ ነው
በግብጽ ምድር ሁሉ ገዥ ሆኖአል
እዚህ "የግብጽ ምድር" የግብጽ ሰዎችን ይወክላል አት በግብጽ ሰዎች ሁሉ ላይ ገዥ ሆኖአል:: (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)
ልቡ ደነገጠ
እነርሱ የተናገሩትን እንደ እውነት መቀበል አቃተው
Genesis 45:27
ነገሩት
ለያዕቆብ ነገሩት
ዮሴፍ የነገራቸውን ነገር ሁሉ
ዮሴፍ የነገራቸውን ማንኛውንም ነገር
የአባታቸው የያዕቆብ መንፈስ ታደሰ
እዚህ መንፈስ ሙሉ ሰው ይወክላል። አት "አባታቸው ያዕቆብ ከጭንቀቱ/ከሐዘኑ ተሻለው" ወይም "አባታቸው ያዕቆብ እጅግ ደስተኛ ሆነ" (ምትክ ቃላት አጠቃቀም የመልከቱ)

Chapter 46

Genesis 46:1
ወደ ቤርሳቤህ ሄደ
ወደ ቤርባህ መጣ
እነሆ አለው
“አዎን እየሰማሁ ነኝ”
ወደ ግብጽ ለመውረድ
ከከነዓን ወደ ግብጽ መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ “ወደ ታች መውረድ” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው::
ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ
እዚህ አንተን የሚለው ነጠላ አገላለጽና ያዕቆብን የሚያመለክት ነው እዚህ ያዕቆብ ታላቅ የሚሆነውን የእርሱን ዘር ይወክላል አት ብዙ ትውልድ እሰጥሃለሁና እነርሱም ታላቅ ሕዝብ ይሆናሉ (አንተ የሚለውን ቃል አጠቃቀምና ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)
ወደ ግብጽ ውስጥ
ወደ ግብጽ
ከዚያም ደግሞ እኔ አወጣሃለሁ
ተሰፋ የተሰጠው ለያዕቆብ ነው ነገር ግን ተስፋው የሚፈጸመው ለእስራኤል ትውልድ ሁሉ ነው አት በእርግጥ ዘርህን ከግብጽ ምድር አወጣለሁ (አንተ የሚለውን ቃል አጠቃቀምና ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)
ደግሞም ወደ ላይ አወጣሃለሁ
ከግብጽ ወደ ከነዓን መጓዝ በሚነገርበት ጊዜ “ወደላይ መውጣት” የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነው::
የዮሴፍ የራሱ እጆች ዐይኖችህን ይገጥሟቸዋል
የራሱ እጆች ዐይኖችህን ይገጥሟቸዋል የሚለው ሀረግ እስራኤል በሚሞትበት ጊዜ ዮሴፍ እንደሚገኝና በሞቱ ጊዜ የዮሴፍ እጆች የያዕቆብን የዐይን ሽፋሽፍቶች እንደሚዘጉ የሚናገርበት መንገድ ነው:: አት “ዮሴፍም ቢሆን በሞትህ ዕለት ይገኛል” (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ዐይኖችህን ይገጥሟቸዋል
አንድ ሰው ዐይኑን ከፍቶ በሚሞበት ጊዜ የዐይኑን ሽፋሽፍቶች መበሳብ መዝጋት የተለመደ ባህል ነበር:: የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል:: (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 46:5
ተነሣ
ከዚያ ወጣ
በሠረገሎች
“ሠረገሎች” ሁለት ወይም አራት እግር ያላቸው የጭነት ሠረገሎች ናቸው እንስሳት ተሳቢውን ይጐትቱታል:: በዘፍትረት 45:19 ሠረገሎች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
ያካበቱትን
“ያገኙትን” ወይም “ያፈሩትን”
ከራሱ ጋር ይዞ አመጣቸው
ያዕቆብ ከራሱ ጋር ይዞአቸው መጣ
የልጆቹን ወንድ ልጆች
ወንድ የልጅ ልጆች
የልጆቹን ሴት ልጆች
ሴት የልጅ ልጆች
Genesis 46:8
ስማቸው ይህ ነበር
ይህ ጸሐፊው የሚዘረዝራቸውን የሰዎች ስሞች ያመለክታል።
የእስራኤል ልጆች
የእስራኤል ቤተሰብ አባላት ሄኖኀ ፈሉሶ አስሮንና ከርሚ…ይሙኤል ያሚን ኦሃድ ያኪን ጾሐርና ሳኡል …ጌድሶን ቀዓትና ሜራሪ፤ እነዚህ ሁሉ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
Genesis 46:12
ዔር አውናን ሴሎም
እነዚህ ይሁዳ ከሚስቱ ከሰዋ የወለዳቸው ወንዶች ልጆች ነበሩ:: በዘፍጥረት 38:3-5 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
ፋሬስና ዛራ
እነዚህ ይሁዳ ከምራቱ ከታማር የወለዳቸው ወንዶች ልጆች ነበሩ:: በዘፍጥረት 38:29-30 እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
ኤስሮም ሐሙል … ቶላ ፋዋ ዮብ … ሺምሮን… ሴሬድ ኤሎን… ያሕልኤል
እነዚህ ሁሉ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ዲና
ይህ የልያ ሴት ልጅ ስም ነው በዘፍጥረት 30:21 ይህን ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::(ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
የወንዶችና የሴቶች ልጆች ቁጥር ሠላሣ ሶስት ነበር
እዚህ ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች የያዕቆብ ወንዶችና ሴቶች ልጆች እና የልያ የልጅ ልጆች ያመለክታል አት በአንድነት 33 ወንዶችና ሴቶች ልጆችና የልጅ ልጆች ነበረው (ቁጥሮች ይመልከቱ)
Genesis 46:16
ጽፎን… ሐጊ ሹኒ… ኤስቦን ዔሪ አሮዲና… አርኤሊ…ዩምና …የሱዋ የሱዊና… በሪዓ …ሐቤር… መልኪኤል
እነዚህ ሁሉ የወንድ ሰው ስሞች ናቸው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ሤራሕ
ይህ የሴት ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ዘለፋ
የልያ ሴት አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:24 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ለያዕቆብ የወለደቻቸው እነዚህ ወንዶች ልጆች በአንድነት አሥራ ስድስት ናቸው
ይህ ከዘለፋ የተወለዱ አሥራ ስድስት ልጆች የልጅ ልጆችና የልጁ ልጅ ልጆች ናቸው (ቁጥሮች ይመልከቱ)
Genesis 46:19
አስናት
የሴት ስም ነው:: በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ጶጥፌራ
የወንድ ሰው ስም ነው:: በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
የኦን ካህን
ኦን የጸሐይ አምላክ ረሐ አምልዕኮ ማዕከል ያለባትና የጸሐይ ከተማ ደግሞም ሄልዮቱ የተባለች ከተማ ነች:: በዘፍጥረት 41:45 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ቤላ ቤኬር አስቤል ጌራ ናዕማን አኪ ሮስ ማንፌን ሑፊምና አርድ
እነዚህ የወንድ ሰዎች ስሞች ናቸው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
በአጠቀለይ አሥራ አራት ናቸው
ራሔል የወለደቻቸው 14 ወንዶችና የልጅ ልጆች ናቸው
Genesis 46:23
ሑሺም ያሕጽኤል ጉኒ ዬጽርና ሺሌም
እነዚህ የወንድ ሰዎች ስሞች ናቸው:: (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
ባላ
የራሔል ሴት ባሪያ ወይም አገልጋይ ስም ነው:: በዘፍጥረት 29:29 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
በአጠቃላይ ሰባት ነበሩ
ይህ ባላ የወለደቻቸው 7 ልጆችና የልጅ ልጆች እንደሆኑ ያመለክታል (ቁጥሮች ይመልከቱ)
Genesis 46:26
ስድሳ ስድስት
66 (ቁጥሮችን ይመልከቱ)
ሰባ
70 (ቁጥሮችን ይመልከቱ)
Genesis 46:28
በፊቱ የጌሤምን መንገድ እንዲያሳየው
የጌሜምን መንገድ እንዲያሳያቸው
ዮሴፍ ሰረገላውን አዘጋጀና … ወጣ
እዚህ “ዮሴፍ” አገልጋዮቹን ወይም ባሪያዎቹን ይወክላል:: አት “የዮሴፍ አገልጋዮች ሠረገላውን አዘጋጁለትና ዮሴፍም ….ወጣ” (ምትክ ቃላት ይጠቀሙ)
እስራኤልን ሊገናኘው …..ወጣ
“ወደ ላይ ወጣ” የሚለው ሀረግ የተጠቀመው ዮሴፍ አባቱን ሊገናኘው ወደ ከፍታማ

ሥፍራ ስለተጓዘ ነው:: አት “እስራኤልን ሊገናኘው ሄዴ”
እንገቱን አቀፈና ረጅም ጊዜ አለቀሰ
እንገቱ ላይ ተጠመጠመና ረጅም ጊዜ አለቀሰ
አሁን በሞት እይቆጨኝ
“አሁን ለሞት ተዘጋጅቻለሁ” ወይም “አሁን እንግዲ የሚሞተው በደስታ ነው”
አንተ ገና በሕይወት ሳለህ ፊትህን አይቻለሁና
እዚህ “ፊት” ሙሉ ሰው ይወክላል”” ያዕቆብ ዮሴፍን በማየቱ የተሰማውን ደስታ ይገልጻል:: አት “አንተን እንደገና በሕይወት ስላየሁህ” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
Genesis 46:31
የአባቱን ቤት
እዚህ ቤት ቤተሰቡን ይወክላል:: አት “የአባቱን ቤተሰብ” ወይም “የአባቱን ቤተሰዎች” (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)
ወደ ፈርዖን ወጥቼ እናገረዋለሁ
ወደ አንድ ትልቅ ባለሥልጣን ሄዶ መናገር ወደ ላይ ወጣ የሚለውን ሀረግ መጠቀም የተለመደ ነበር አት ለፈርዖን ለመናገር እሄዳለሁ
ለፈርዖን እነግረዋለሁ: ወንድሞቼ … ያላቸውን ሁሉ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል ይህ በተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ወንድሞቼ …ያላቸውን ሁሉ… ለፈርዖን እነግረዋለሁ” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
Genesis 46:33
እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የተጠቀመው በታሪኩ ስለተከሰተው ዋና ክስተት ለማመልከት ነው። በቋንቋዎ ይህንን የሚገልጹበት መንገድ ካለ የጠቀሙ
ሥራችሁ ምንደነው ብሎ ቢጠይቃችሁ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል:: ይህ በተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ምን ሥራ ታከናውናላችሁ ብሎ ቢጠይቃችሁ” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
እንዲህ በሉት እኛ ባሪያዎችህ…. እኛም አባቶቻችንም…
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል:: ይህ በተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት “እንዲህ በሉት….እኛና አባቶቻችን ሁላችን…” (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
የአንተ ባሪያዎች
የዮሴፍ ቤተሰቦች ለፈርዖን ሲናገሩ ራሳቸውን ባሪያዎችህ ብለው ማቅረብ አለባቸው:: ይህ ለአንድ ታላቅ ባለሥልጣን የሚነገርለት መንገድ ነው:: ይህም እንደ አንደኛ ወገን ሰው ሊገለጽ ይችላል:: አት “እኛ አገልጋዮችህ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
በግ ጠባቂ ሁሉ ለግብጻዊያን ርኩስ/ ጸያፍ ነውና
“ጸያፍ” የሚለው ረቂቅ ስም “የሚያስጠላ” በሚለው ቅጽል ስም ሊተረጐም ይችላል:: አት “ግብጻዊያን የከብት ጠባቂዎችን እንደ ጸያፍ ይቆጥሩ ነበር” (ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ)

---

Chapter 47
Genesis 47:1
ዮሴፍ ሄዶ ለፈርዖን ነገረው ….ከወንድሞቹም አምስት ሰዎችን ወስዶ በፈርዖን ፊት አቀረባቸው
UDB ክስተቶች በቅደም ተከተል ሲያስቀምጥ ULB ጸሐፊው እንዳስቀመጠ ይዘረዝራል (የክስተቶች ቅደም ተከተል ይመልከቱ)
Genesis 47:3
እኛ ባሪያዎችህ የበግ እርቢዎች ነን
ባሪያዎችህ በጎችን እናረባለን
ባሪያዎችህ
የዮሴፍ ወንድምች ራሳቸውን እንደ “ባሪያዎችህ” ያቀርቡታል:: ይህ ብዙ ኃላፊነት ላለው ሰው የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: ይህም እንደ አንደኛ ወገን ሰው ሊገለጽ ይችላል:: አት “እኛ ባሪያዎችህ ወይም እኛ” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
እንደ አባቶቻችን
“እኛና ቅድመ አባቶቻችን ሁላችን” ወይም “እኛና አባቶቻችን ሁሉ”
በዚህ ምድር ለጊዜው ለመኖር መጥተናል
በግብጽ ለጊዜው ለመኖር መጥተናል
በጎች የሚሠማሩበት ሥፍራ የለምና
በጎች የሚሠሩበት ሣር የለምና
አሁንም
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ዋና ነገር ትኩረት ለመስጠት ነው::
Genesis 47:5
የግብጽ ምድር በፊትህ ናት
“የግብጽ ምድር ለአንተ ክፍት ነው” ወይም “መላው የግብጽ ምድር በአንተ እጅ ነው”
በመልካም ምድር አባትህንና ወንድሞችህን አኑራቸው በጌሤም ምድር
አባትህንና ወንድሞችህን ምርጥ በሆነው በጌሤም ምድር አኑራቸው
ከመካከላቸው ልዩ ችሎታ ያላቸው መኖራቸውን የምታውቅ ከሆነ
ይህ የሚገለጸው ከብት የማርባት ችሎታ እንዳላቸው ነው:: አት “ከመካከላቸው ከብት በማርባት ትልቅ ችሎታ ያላቸውን የሚቃውቅ ከሆነ” (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 47:7
ያዕቆብ ፈርዖንን ባረከው
እዚህ “ባረከው” የሚለው ለዚያ ሰው አዎንታዊና ጠቃሚ ነገሮች እንዲሆኑለት መሻቱን ገለጸ ማለት ነው
እድሜህ ምን ያህል ነው?
እድሜህ ስንት ዓመት ነው?
የእንግድነቴ ዘመን መቶ ሠላሣ ዓመት ነው
የእንግድነቴ ዘመን የሚለው ሀረግ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመዘዋወር በምድር ላይ ምን ያህል እንደኖረ ያመለክታል:: አት “በምድር ላይ በእንግድነት ያሳለፍኩት ዘመን 130 ዓመት ነው” (ቁጥሮችን ይመልከቱ)
የሕይወቴ ዘመኖች አባቶቼ በእንግድነት ከኖሩበት ዘመን ጋር ሲነጻጸር ጥቂት ናቸው
ከአብርሃምና ከይስሐቅ የሕይወት ዘመን ጋር ስነጻጸር ዮሴፍ የሕይወቱ ዘመን አጭር እንደሆነ ይናገራል
ችግር የበዛበት
ያዕቆብ በሕይወቱ ብዙ ሥቃይና ችግር ተለማምዶአል
Genesis 47:11
ዮሴፍም አባቱንና ወንደሞቹን አኖረ
ከዚያም ዮሴፍ አባቱንና ወንድሙን ተንከባከባቸው በሚኖሩበት ሥፍራ እንዲመሠረቱ አደረገ
ራሚሴ ምድር
ይህ የጐሼም ምድር ሌላው ስም ነው (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
በየልጆቻቸው ቁጥር
እዚህ “ልጆች” በቤተሰብ ጥገኝነት ያሉ ትናንሽ ልጆች ማለት ነው:: አት “በየቤተሰቡ በሚገኙ ትናንሽ ልጆች ቁጥር”
Genesis 47:13
አሁንም
ይህ ቃል ዋናው ታሪክ በመሃል የሚቋረጥበትን ለማመልከት ተጠቅሞአል:: በዚህ ጸሐፊው የታሪኩን አድስ ክፍለ መናገር ይጀምራል::
የግብጽ ምድርና የከነዓን ምድር
ይህ በእነዚህ አገሮች የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል አት የግብጽ ሰዎችና የከነዓን ሰዎች (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)
ተጐዳ
ተቀጨ ወይም ደከመ
ዮሴፍም በግብጽ ምድርና በከነዓን ምድር በእህል ሽመት የተገኘውን ገንዘብ ሰበሰበ
ዮሴፍም የግብጽና የከነዓን ሰዎች ገንዘባቸውን ሁሉ ከዮሴፍ እህል ለመሸመት አውለዋል
ዮሴፍም ሰበሰበ… ዮሴፍም አመጣ
ገንዘቡን እንዲሰበስቡና እንዲያመጡ ዮሴፍ አገልጋዮቹን እንዳዘዘ ይገመታል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)
Genesis 47:15
የግብጽና የከነዓን ምድር ገንዘብ ባለቀ ጊዜ
እዚህ ምድር በዚያ ምድር የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ

መልክ ሊተረጐም ይችላል:: አት “የግብጽና የከነዓን ሕዝቦችም ገንዘባቸው ባለቀ ጊዜ” (ምትክ ቃላት አጠቃቀምና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
የግብጽና የከነዓን ምድሮች
ከግብጽ ምድር እና ከከነዓን ምድር
ብሩ አልቆብናልና በፊትህ ስለምን እንሞታለን?
ሰዎች እህል ለመሸመት እንዴት እንደጓጉ ትኩረት ለመሰጠት ጥቃቄ ይጠቀማሉ። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጐም ይችላል፡ አት “ገንዘባችን ስላለቀብን እባካችሁ እንድንሞት አታድርጉ!” (ሽንገላ አዘል አግናኝ ጥያቄዎችን ይመልከቱ)
እህልን መገባቸው
እህል ምግብን በአጠቃላይ ይወክላል:: አት “እህልን ሰጣቸው” ወይም “እህልን አደላቸው” (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
Genesis 47:18
እነርሱም ወደ እርሱ መጡ
ሰዎች ወደ ዮሴፍ መጡ
እኛ ከጌታችን አንሰውርም
ሰዎችን ዮሴፍን እንደ” ጌታችን” ያመለክታሉ ይህ ትልቅ ሥልጣን ላሌው ሰው የሚነገርለት መደበኛ መንገድ ነው:: ይህ እንደ ሁለተኛ ወገን ሰው ሊገለጽ ይችላል:: አት” ከጌታችን የምንሰውረው የለም” ወይም “ከአንተ የምንሰውረው የለም” (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አገላለጽ ይመልከቱ)
በጌታችን ፊት አንዳች የቀረ የለም
እዚህ ፊት ዮሴፍን ያመለክታል:: አት “ለጌታችን የምንሰጠው የቀረ የለንም” (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)
እኛ በዐይኖችህ ፊት ስለምን እንሞታለን? ምድራችንስ ስለምን ትጠፋለች?
እዚህ ዐይኖች የዮሴፍን እይታ ያመለክታሉ ሰዎች እህልን ለመግዛት ምንኛ እንደጓጉ ለማተኮር ጥያቄ ይጠቀማሉ ይህ ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: አት “እኛ ስንሞት ምድራችም ስትጐዳ እባክህን እንዲሁ ዝም ብለህ
አትመለከተን” (ምትክ ቃላት አጠቃቀምና ሽንገላ አዘል አግናኝ ጥያቄዎችን ይጠቀሙ)
እኛ ለምን እንሞታለን እኛና ምድራችን
የተዘራበት ዘር ስለሌለባት ምድሪቱ የተጐዳችና ጥቅም የሌላት መሆንዋ ምድሪቱ እንደሚትሞት ተደርጐ ተነግሮአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
Genesis 47:20
በዚህ መንገድ የግብጽ ምድር ሁሉ ለፈርዖን ገዛለት
ስለዚህ ምድሪቱ የፈርዖን ሆነች
ዮሴፍ ያልገዛው የካህናቱን መሬት ብቻ ነበር
ነገር ግን የካህናቱን መሬት አልገዛም
ካህናቱ ድርጐ ያግኙ ነበር
ድርጐ በቋሚነት አንድ ሰው ለሌላ ሰው የሚሰጠው የገንዘብ ወይም የመግብ መጠን ነው:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ፈርዖን በየዕለቱ ለካህናት የተወሰነ ምግብ ይሰጥ ነበር” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
እነርሱም ፈርዖን ከመደበላቸው ይመገቡ ነበር
ፈርዖን ከሰጣቸው ይመገቡ ነበር
Genesis 47:23
በመሬት ላይ ዝሩ
ሊትዘሩ ትችላላችሁ
በመከርም ጊዜ ፍሬውን ከአምስቱ እጅ አንዱን እጅ ለፈርዖን ስጡ አራቱም እጅ ለእናንተ ለራሳችሁ ይሆናል
አምስት እጅ የሚለው ቃል ክፍልፋይ ነው። አት “በመከር ጊዜ እህላችሁን በአምስት መደብ ትከፍላላችሁ አንዱን መደብ እንደክፍያ ለፈርዖን ትሰጡታላችሁ እናም አራቱ መደቦች ለእናንተ ይሆናሉ” (ክፍልፋዮችን ይመልከቱ) ለቤተሰቦቻችሁና ለልጆቻችሁ ምግብ ታደርጉታላችሁ (የተደበቁትን ስለመግልጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
Genesis 47:25
በዐይኖችህ ፊት ሞገስ ካገኘን
ሞገስ ማግኘት የሚለው ሀረግ በአንድ ሰው ተቀባይነትን ማግኘት የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: ደግሞም ዐይኖች ማየትንና ማየት ሃሳብንና በየናን ይወክላል:: አት “በእኛ ከተደሰትክ” (ፈሊጣዊና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
በግብጽ ምድር
“በግብጸ ምድር ላይ” ወይም “በመላው የግብጽ ምድር”
እስከ ዛሬ ድረስ
ጸሐፊው እስከጻፈበት ጊዜ ድረስ
አንድ አምስተኛ
በዘፍጥረት 47:24 አንድ እምስተኛ እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ
Genesis 47:27
ንብረትንም አፈሩ እጅግም በዙ
በዙ የሚለው ቃል እንዴት እንደአፈሩ ይገልጻል እነርሱም ብዙ ልጆች ነበሩአቸው (ድርብ ቃላት ይመልከቱ)
ፍሬያማ ነበሩ
እዚህ ፍሬያማ መበልጸግ ወይም ብዙ ልጆች መኖር ማለት ነው
አሥራ ሰባት ዓመታት
17 ዓመታት (ቁጥሮችን ይመልከቱ)
የያዕቆብም የሕይወቱ ዘመን አንድ መቶ አርባ ሰባት ዓመት ነበር
ያዕቆብ የኖረው 147 ዓመት ነው (ቁጥሮችን ይመልከቱ)
Genesis 47:29
እስራኤልም የሚሞትበት ጊዜ መቃረቡን
ይህ ጊዜ እንደሚጓዝና አንድ ቦታ እንደሚመጣ ይናገራል:: አት “እስራኤል የሚሞትበት ጊዜ እንደደረሰ” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይመልከቱ)
በዓይኖችህ ፊተ ሞገስን ካገኘሁ
እዚህ ዓይኖች የማየት ምትክ ቃል ነው እናም ማየት ሃሳብን ወይም አመለካከትን ይወክላል:: አት “በአንተ ፊት ሞገስ ካገኘሁ ወይም ካስደሰትኩህ” (ምትክ ቃላትና ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
አሁን
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ለሚቀጥለው ጠቃሚ ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ነው
ሞገስ ማግኘት
አንድ ሰው በአንድ ሰው ተቀባይነቱን ማረጋገጥ ማለት ነው ፈሊጣሊ አነጋገር ይመልከቱ
እጅህን ከጭኔ በታች አድርግ
ለጠንቃቃ ቃል መግባት የሚደረግ ምልክት ነው በዘፍጥረት 24:2 ይህን እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
በጐነትንና ታማኝነትን ሊታደርግልኝ
በጐነት እና ታማኝነት የተባሉ ረቂቅ ስሞች እንደ ቅጽል ስሞች ሊተረጐሙ ይችላሉ አት በበጐነትና በታማኝነት አድርግልኝ ረቂቅ ስሞች ይመልከቱ
እባክህን በግብጽ አትቅበረኝ
እባክህን የሚለው ለዚህ ጥያቄ እጽንዖት ይሰጣል
ከአባቶቼ ጋር ሳንቀላፋ
ማንቀላፋት መሞትን ለዘብ ባለ ቃል የሚገልጽ ነውፀፀ አት “በሚሞትበትና ከዚህ ቀደም የሞቱ ቤተሰቦቼን በሚገናኝበት ጊዜ” (ንኅብነት ወይም ለዘብ ባለና በተዘዋዋሪ መንገድ አንድን ነገር የመግልጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ቃል ግባልኝ
“ተስፋ ስጠኝ” ወይም “ማልልኝ”
ማለለት
“ተስፋ ሰጠው” ወይም “ቃል ገባለት”

---

## Chapter 48

Genesis 48:1
እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የታሪኩ አድስ ክፍል መጀመሩን ለማመልከቱ ተጠቅሞአል (አድስ ክስተት ስለማስታወቅ ይመልከቱ)
አንድ ሰው ለዮሴፍ ተናገረው
አደ ሰው ለዮሴፍ ነገረው
እየው፤ አባትህ
ስማ ፤አባትህ፤ እዚህ “እየው” የሚለው ቃል የዮሴፍን ትኩረት ለማግኘት ተጠቅሞአል::
ስለዚህ ይዞ

ስለዚህ ዮሴፍ ይዞ
ለያዕቆብ … በተነገረው ጊዜ
ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት “አንድ ሰው ለያዕቆብ በነገረው ጊዜ” (ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
ልጅህ ዮሴፍ ልያይህ ወደ አንተ መጥቶአል
ልጅህ ዮሴፍ መጥቶአል
እስራኤል ተበረታትቶ በአልጋው ላይ ተቀመጠ
እዚህ እስራኤል ተነሥቶ በአልጋው ሊቀመጥ የታገለውን አንድ ሰው አንድን ዕቃ እንደሚሰበስብ ብርታትን እንደሰበሰበ አድርጎ ጸሐፊው ይናገራል:: አት “በአልጋው ተነሥቶ ሊቀመጥ እስራኤል ከፍተኛ ጥረት አድርጐአል ወይም በአልጋው ተነሥቶ ሊቀመጥ እስራኤል ታግሎአል” (ዘይቤያዊ አገላለጽ ይጠቀሙ)
Genesis 48:3
ሎዛ
ይህ የከተማ ስም ነው:: በዘፍጥረት 28:19 የዚህን ከተማ ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ (ስሞችን ስለመተርጐም ይመልከቱ)
በከነዓን ምድር … ባረከኝም እንዲህም አለኝ
ይህ በሌላ ሀረግ እንደሚጀምር እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል:: “በከነዓን ምድር ባረከኝ እናም እንዲህ አለኝ”
ባረከኝ
እግዚአብሔር መደበኛ በረከትን በአንድ ሰው ላይ እንዳደረገ ያመለክታል
እንዲህም አለኝ እነሆ ፍሬያማ አደርግሃለሁ አበዛሃለሁ ለብዙ ሕዝብም ጉባዔ አደርግሃለሁ ይህችንም ምድር ከአንተ በኋላ ለዘላለም ርስት ለዘርህ እሰጣታለሁ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል አት ፍሬያማ እንደሚያደርገኝና እንደሚያበዛኝ ተናግሮኛል:: እናም ለብዙ ሕዝብም ጉባዔ እንደሚያደርገኝና ይህችንም ምድር ከእኔ በኋላ ለዘላለም ርስት አድርጐ ለዘሬ እንደሚሰጠኝ ነግሮኛል (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
እነሆ
እዚህ ቦታ እነሆ የተጠቀመው እግዚአብሔር ሊናገር ስላለው ነገር ያዕቆብ ትኩረት እንዲሰጥ ለማንቃት ነው
ፍሬያማ አደርግሃለሁ አበዛሃለሁ
አበዛሃለሁ የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር እንዴት ያዕቆብን ፍሬያማ እንደሚያደርገው ይገልጻል:: አት “ብዙ ዘር/ትውልድ እሰጥሃለሁ” (ድርብ ቃላትና ፈሊጣዊ አነጋገር ይጠቀሙ)
አንተን ለብዙ ሕዝብ ጉባዔ አደርግሃለሁ
እዚህ አንተ ያዕቆብን ቢያመለክትም የያዕቆብን ትውልድ ይወክላል አት “ትውልድህን ብዙ ሕዝቦች አደርጋለሁ” (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)
የዘላለም ርስት
ቋሚ ርስት
Genesis 48:5
አሁን
ይህ በዚህን ጊዜ ማለት አይደለም ነገር ግን ለሚቀጥለው ዋና ነጥብ ትኩረት እንዲሰጥበት ተጠቅሞአል
ኤፍሬምና ሚናሴ ለእኔ ናቸው
እንደ ዮሴፍ ወንድሞች ኤፍሬምና ሚናሴ ከምድሪቱ ክፍል የየራሳቸውን ርስት ይቀበላሉ
በርስታቸው በወንድሞቻቸው ስም ይጠራሉ
ተገቢ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው 1 እንደ ሚናሴና ኤፍሬም ነገዶች ሌሎች የዮሴፍ ልጆች ምድሪቱን ይወርሳሉ 2 ዮሴፍ ከኤፍሬምና ሚናሴ የተለየ ምድር የሰጠዋል እናም የዮሴፍ ሌሎች ልጆች ያን ምድር ይወርሳሉ አት በርስት ድልደላቸው በወንድሞቻቸው ስም ይቆጠራሉ
ኤፍራታ
ይህ የቤተልሔም ከተማ ስም ነው:: በዘፍጥረት 35:16 የዚህን ከተማ ስም እንዴት እንደተረጐሙ ይመልከቱ::
ያም ቤተልሔም ነው
ጸሐፊው የዳራ መረጃ ይሰጣል (የዳራ መረጃ ይመልከቱ)
Genesis 48:8
እነዚህ እነማን ናቸው?
እነዚህ የማን ወንዶች ልጆች ናቸው?
ባረካቸው
አባት ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን አብዛኛውን ጊዜ መደበኛ በረከት ይባርካል
በዚህን ጊዜ የእስራኤል ዐይኖች …. ማየት ተስኖአቸው
በዚህን ጊዜ የሚለው ቃል የተጠቀመው ታሪኩ ወደ እስራኤል ዳራ መረጃ እንደተቀየረ ለማመልከት ነው (ዳራ መረጃ ይመልከቱ)
እርሱም ሳማቸው
እስራኤል ሳማቸው
Genesis 48:11
ፊትህን እንደገና አያለሁ
እዚህ “ፊት” ሙሉ ሰው ይወክላል:: አት እንደገና አይሃለሁ (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
በእስራኤል ጉልበቶች መካከል
ዮሴፍ ልጆቹን በእስራኤል ጭን ወይም ጉልበት ላይ ማስቀመጡ እስራኤል እንደራሱ ልጆች እንደተቀበላው የሚገልጽ ምልክት ነው:: ይህም ለልጆች የወራሽነት መብት ከያዕቆብ ያስገኛል (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
በግምባሩም ወደ ምድር አጐንብሶ ሰገደ
ዮሴፍ ለአባቱ ክብርን ለመስጠት ወደ ምድር አጐንበሶ ሰገደ (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
ሚናሴንም በግራው በእስራኤል ቀኝ
እስራኤል ቀኝ እጁን በሚናሴ ላይ እንዲያደርግ ዮሴፍ ልጆቹን ያስቀምጣቸዋል ሚናሴ ታላቅ ወንድም ነው እናም ቀኝ እጅ ትልቅ በረከት የመቀበል ምልክት ነው (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
Genesis 48:14
ቀኝ እጁን ዘርግቶ በኤፍሬም ራስ ላይ አኖረ
ቀኝ እጁን በኤፍሬም ራስ ላይ ማኖር እርሱ ትልቅ በረከት እንዲቀበል ምልክት ነበር (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
እስራኤል ዮሴፍን ባረከው
ዮሴፍ ደግሞ ኤፍሬምንና ሚናሴን ይወክላል:: ዮሴፍ አባት ስለሆነ እርሱ ብቻውን ተጠቅሶአል (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ የሄዱለት እግዚአብሔር
እግዚአብሔርን ማገልገል በእግዚአብሔር ፊት እንደመሄድ ተደርጐ ተነግሮአል አት አያቴ አብርሃምና አባቴ ይስሐቅ ያገለገሉት እግዚአብሔር (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
እረኛ የሆነኝ
እረኛ በጐቹን እንደምንከባከብ እግዚአብሔር እስራኤልን ተንከባክቦታል አት እረኛ እንስሳትን እንደሚንከባከብ የተንከባከበኝ (ግምታዊ እውቀትና ጥልቅ መረጃ ይመልከቱ)
መልአክ
ተገቢ ትርጉሞች አት እግዚአብሔር ያዕቆብን ለመጠበቅ የላከውን መልአክ ያመለክታል 2 ይህ እግዚአብሔር ያዕቆብን ለመጠበቅ በመልአክ መልክ የተገለጸውን ያመለክታል
ጠበቀኝ
አዳነኝ
ስሜም የአባቶቼ የአብርሃምና የይስሐቅ ስም በእነርሱ ይጠራ
እዚህ ስም ሰውን ይወክላል ስሜ በእነርሱ ይጠራ የሚለው ሀረግ አንድ ሰው ከሌላ ሰው የተነሣ እንዲታወስ የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው:: ይህ ተሻጋሪ ግሥ በያዘ መልክ ሊገለጽ ይችላል:: አት “ከኤፍሬምና ሚናሴ የተነሣ ሰዎች አብርሃም ይስሐቅንና እኔን ያስታውሱ” (ምትክ ቃል : ፈሊጣዊ አነጋገርና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
በምድርም ላይ ይብዙ
እዚህ እነርሱ ኤፍሬምንና ሚናሴን ቢያመለክትም የእነርሱ ትውልድንም ይወክላል:: አት “በምድር ሁሉ ላይ የሚኖር ብዙ ትውልድ ይኑራቸው” (ምትክ ቃል እጠቃቀም ይመልከቱ)
Genesis 48:17
ቀኝ እጅህን እርሱ ራስ ላይ አድርግ
ቀኝ እጅ በኩር ወንድ ልጅ የሚያገኘው ትልቅ በረከት ምልክት ነበር (ምልክታዊ ድርጊት ይመልከቱ)
Genesis 48:19
እርሱ ደግሞ ሕዝብ ይሆናል ታላቅም ይሆናል

እዚህ እርሱ ሚናሴን ቢያመለክትም የእርሱን ትውልድ ይወክላል አት ታላቅ ልጅህ ብዙ ትውልድ ይኖረዋል እናም ታላቅ ሕዝብ ይሆናል (ምትክ ቃላት ይመልከቱ)
በዚያን ቀን በእነዚህ ቃላት
በዚያ ዕለት እንዲህ ብሎ
በእናንተ ስም እስራኤል እንዲህ ብሎ ይባርካል
የእስራኤልም ሰዎች ሌሎችን በሚባርኩበት ጊዜ በስማችሁ ይባርካሉ
በእናንተ ስም እንዲህ ብለው እግዚአብሔር እንደ ኤፍሬምና እንደሚናሴ ያድርጋችሁ
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስን ይዞአል ይህም እንደ ተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል:: አት "በእናንተ ስም እግዚአብሔር ሌሎችን ሰዎች እንደ ኤፍሬምና እንደ ሚናሴ እንዲያደርግ ይጠይቁታል" (ጥቅሶችን በጥቅስ ውስጥ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጥቅሶችን ይመልከቱ)
እንደ ኤፍሬምና እንደ ሚናሴ
እስራኤል ኤፍሬምን አስቀድሞ መጥራቱ ኤፍሬም ከሚናሴ ታላቅ እንደሚሆን የሚገልጽ ነው
እስራኤል ኤፍሬምን ከሚናሴ አስቀድሞታል
ለኤፍሬም ትልቁን በረከት መስጠትና ኤፍሬም ከሚናሴ የተሻለ አድርጐ መውሰድ እስራኤል በአካል ኤፍሬምን ከሚናሴ በፊት እንዳስቀመጠው ተደርጐ ተገልጾአል (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
Genesis 48:21
ከእናንተ ጋር ይሆናል ወደ አባቶቻችሁም ምድር መልሶ ያገባችኋል
እዚህ "እናንተ" "የእናንተ" ብዙና የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ ያመለክታል ("እናንተ" አጠቃቀም ይመልከቱ)
ከእናንተ ጋር ይሆናል
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚረዳና እንደሚባርካቸው የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው አት እግዚአብሔር ይረዳችኋል ወይም እግዚአብሔር ይባርካችኋል (ፈሊጣዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ወደ አባቶቻችሁም ምድር
ወደ ዘሮችሁም ወይም ትውልዳችሁም ምድር
ለአንተ ከወንድሞችህ አንድ እጅ አብልጨ ዐምባ ሰጠሁህ
ተገቢ ትርጉሞች 1 ከወንድሞቹ ይበልጥ ብዙ ክብርና ሥልጣን ለዮሴፍ መሰጠቱ እርሱ በአካል ከሌሎች የበላይ ተደርጐ ተገልጾአል:: አት "ለአንተ ከሌሎች ለሚትበልጠው የተራራውን ዐምባ ሰጠሁህ" ወይም 2)ያዕቆብ ለዮሴፍ ወንድሞች ከሚሰጠው መሬት በላይ ለዮሴፍ እንደሚሰጠው ይገልጻል:: አት "ለአንተ ለወንድሞችህ ከሰጠሁት በላይ ridge ሰጠሁህ የተራራውን ዐምባ ሰጠሁህ" (ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ)
ለአንተ
እዚህ አንተ በነጠላ የተገለጸና ዮሴፍን ያመለክታል (አንተ አጠቃቀም ይመልከቱ)
በሰይፌና በቀስቴ ከአሞራዊያን እጅ የወሰድኳትን ዐምባ
እዚህ ሰይፍ እና ቀስት በጦርነት መዋጋትን ያመለክታሉ። አት "የተዋጋሁትና ከአሞራዊያን እጅ የወሰድሁት ምድር" (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)

---

Chapter 49
Genesis 49:1
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ያዕቆብ ልጆቹን የሚባርከውን መጨረሻውን በረከት የጀምራል:: ይህም እስከ ዘፍጥረት 49:27 ይቀጥላል የያዕቆብ ምርቃቶች በግጥም መልክ ተጽፈዋል (ሥነ ግጥሞችን ይመልከቱ)
እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ ተሰብሰቡና ስሙ፤ አባታችሁ እስራኤልንም አድምጡ
ሁለቱ ዐረፍተ ነገሮች ትኩረት ለመስጠት ተመሣሣይ ሃሳብ ይናገራሉ አት ወደ አባታችሁ ኑና በጥንቃቄ አድምጡ (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)
እናንተ የያዕቆብ ልጆች አባታችሁን እስራኤልን አድምጡ
ያዕቆብ ራሱን እንደሦስተኛ ወገን ሰው ያቀርባል እንደአንደኛ ወገን ሰው ሊገለጽ ይችላል አት ልጆች ሆይ እኔን አባታችሁን ስሙ (አንደኛ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን ሰው አጠቃቀም ይመልከቱ)
Genesis 49:3
የበኩር ልጄ ኃይሌና የጉብዝናዬ መጀመሪያ
የበኩር ልጄ ኃይሌ የጉብዝናዬ መጀመሪያ የሚሉ ሀረጐች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ኃይል እና ጉብዝና የሚሉ ቃሎች የያዕቆብ ልጅ የመውለድ አቅሙን ያመለክታሉ በኩር እና መጀመሪያ የሚሉ ቃላት ሮቤል በኩር ልጁ እንደሆነ ይገልጻሉ (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)
በክብር ትልቃለህ በኃይልም ትበልጣለህ
ይህ እንደ አድስ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል አት በክብርና በኃይል የመጀመሪያ ትሆናለህ ወይም በክብርና በኃይል ማንኛውንም ሰው ትበልጣለህ
እንደ ውሃ የምትዋልል ነህ
ያዕቆብ ሮቤል ቁጣውን እንደማይችል ለማተኮር በከባድ ማዕበል እንደሚዋልል ውሃ አድርጐ ያቀርበዋልና እርሱ የተረጋጋ አይደለም (ተመሣሣይ አባባል ይመልከቱ)
አልቅና አይኖርህም
በወንድሞችህ መካከል የመጀመሪያ ወይም አለቃ አትሆንም
ወደ አባትህ መኝታ ወጥተሃልና ከዚያም አርክሰሄዋል ወደ አልጋዬም ወጥተሃል
እዚህ መኝታና አልጋ የያዕቆብን ቁባት ባላን ያመለክታሉ ያዕቆብ ሮቤል ከባላ ጋር የተኛበትን ያመለክታል (ዘፍጥረት 35:22 ይመልከቱ) አት "ወደ አልጋዬ ስለወጣህና በቁባቴ ከባላ ጋር ስለተኛህ አዋርደህኛልና" (ምትክ ቃላት አጠቃቀም ይመልከቱ)
ወደ አባትህ አልጋ ወጥተሃል ወደ አልጋዬም ወጥተሃል
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)
Genesis 49:5
ስምዖንና ሌዊ ወንድማማቾች ናቸው
ይህ በትውልድ ወንድሞች መሆናቸውን አይገልጽም ያዕቆብ የሴኬም ሰዎችን ለመግደል አብረው መሥራታቸውን ለማተኮር ነው።
ሰይፎቻቸው የዐመጽ መሣሪያ ናቸው
ሰዎችን ለመጉዳትና ለመግደል ሰይፎቻቸውን ይጠቀማሉ
ነፍሴ .... ልቤ
ያዕቆብ ራሱን ለመግለጽ ነፍሴ እና ልቤ የሚሉ ቃሎችን ይጠቀማልና ክፋን ለማድረግ ከሚያቅዱት ጋር ባለመተባበሩ ሌሎች ሰዎችና እግዚአብሔርም ደግሞ እጀግ እንዳከበሩት ይናገራል (ክፍልን እንደ ሙሉና ሙሉን እንደ ክፍል የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
ወደ ሸንጐአቸው አልግባ
ጉባዔያቸው ውስጥ አልገኝ እነዚህ ሁለቱ ሀረጐች በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ያዕቆብ ሁለቱን በማገናኘት በክፉ እቅዳቸው እንደማይሳተፍ አበክሮ ይገልጻል አት ማንኛውንም እቅድ ለማዘጋጀት ከእነርሱ ጋር አልተባበርም (ተመሣሣይ ተነጻጻሪ ይመልከቱ)
የቤሬዎችን ቋንጃ ቈራርጠዋል
ስምዖንና ለዊ ለዕይታ ብለው ቤሬዎችን አስነክሰዋል
ቋንጃ መቁረጥ ወይም ማስነከስ
ይህ የእንስሳትን ቋንጃ በመቁረጥ እንዳይራመዱ ማድረግ ነው
Genesis 49:7
ቁጣቸው ርጉም ይሁን ጽኑ ነበርና ንዴታቸው ጭከና የተሞላ ነበርና
እግዚአብሔር ስምዖንና ሌዊን የሚረግመው እግዚአብሔር ቁጣቸውንና ንዴታቸውን እንደሚረግም ተደርጐ የገልጾአል:: (ዘይቤያዊ አነጋገርና ተሻጋሪ ግሥ ወይም የማይሻገር ግሥ የያዘ ዐረፍተ ነገር ይመልከቱ)
ቁጣቸው የተረገመ ይሁን
አብዛኛውን ጊዜ ነብይ ትንቢትን ሲናገር የሚናገረው ቃል እግዚአብሔር እንደሚናገር ይቆጠራል:: ይህም የሚናገረው ነበዩና እግዚአብሔር እንዴት እንደተቆራኙ ነው::
ንዴታቸው ጭከና የተሞላ ስለነበር
እረግማለሁ የሚለው ቃል የታወቀ ነው አት ንዴታቸው ጭከናን የተሞላ ስለሆነ እረግማለሁ (የተደበቀትን የመግለጽ ዘይቤ ይመልከቱ)
በአንድ በኃላፊነት በሚገኝ ሰው ላይ ማመፅና መተቸት ልክ ለመጣላት እንደተነሱ ዓይነት ነገር ተደርጎ ተገልጿል፡፡“በሙሴ ላይ አመፁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሁለት መቶ ሃምሣ
“250”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ታዋቂ የሆኑ የማህበረሰቡ አባላት
“ዝነኛ የሆኑ የማህበረሰቡ አባላት” ወይም“በማህበረሰቡ ውስጥ ዋና የሆኑ ሰዎች”
እናንተ እጅግ አብዝታችኋል
ይሄ የሚያመለከተው አንድ ሰው ማድረግ ከሚገባው በላይ ማድረጉን ነው፡፡“ማድረግ ከሚገባችሁ በላይ አድርጋችኋል”ወይም “ሊኖራችሁ ከሚገባው በላይ የሆነ ሥልጣን ያላችሁ ይመስላችኋል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር ጉባዔ ላይ ለምን ትታበያላችሁ?
ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቁት ሙሴንና አሮንን ለመገሰፅ ብለው ነው፡፡ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡ “በተቀረው የእግዚአብሔር ጉባዔ ላይ ራሣችሁን ከፍ ማድረጋችሁ ትክክል አይደለም” (ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሌሎቹ በላይ ራሣችሁን ከፍ ማድረጋችሁ
አንድ ሰው አስፈላጊ ነኝ ብሎ የማመኑን ነገር ራስን ከፍ ከማድረግ ጋር ተነፃፅሯል፡፡“ራሣችሁን ከሌሎች የበለጠ አስፈላጊ ነን ብላችሁ ትገምታላችሁ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:4
በግምባሩ ወደቀ
ይሄ የሚያሣየው ሙሴ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ማዋረዱን ነው፡፡በእግዚአብሔርና በመረጣቸው ሰዎች ላይ በማመፃቸው እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊቀጣ ይችላል ብሎ ፈራ፡፡(ተምሣሌታዊ ድርጊት)
ለእርሱ የሚሆነውን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር ለራሱ የለየውን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:6
ማያያዣ ዓረፍተ ነገሮች


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሙሴ ለቀአትና ከቀአት ጋር ለነበሩት ሰዎች መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ጥና
ዕጣንን ለማጤስ የሚያገለግል ዕቃ፡፡
በእግዚአብሔር ፊት
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡“በእግዚአብሔር ሕልውና ፊት”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ያ ሰው ለእግዚአብሔር የተለየ ይሆናል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር ያንን ሰው ለራሱ የተለየ ያደርገዋል” (ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ እጅግ አብዝታችኋል
ይሄ የሚያመለከተው አንድ ሰው ማድረግ ከሚገባው በላይ አልፎ ማድረጉን ነው፡፡“ማድረግ ከሚገባችሁ በላይ አድርጋችኋል”ወይም “ሊኖራችሁ ከሚገባው በላይ የሆነ ሥልጣን ያላችሁ ይመሰላችኋል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:8
አይበቃችሁምን..እነርሱን ለማገልገል
ሙሴ ይህንን ጥያቄ የሚያነሣው ቀአትንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች ለመገሰፅ ብሎ ነው፡፡ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እነርሱን ማገልገል ትንሽ ነገር መስሎ ይታያቸኋል”ወይም “እነርሱን ማገልገል እንደ ትንሽ ነገር መስሎ ሊታያችሁ አይገባም፡፡”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእናንተ ትንሽ ነገር
“ለእናንተ የማይበቃችሁ” ወይም “ለእናንተ ጠቃሚ ያልሆነ”
ክህነትንም ትፈልጋላችሁ
ክህነት መፈለግን ልክ በዓይናቸው እንደሚፈልጉት ዓይነት በሚመስል መልኩ ተገልጿል፡፡“ክሀነትን ትፈልጋላችሁ” ወይም “እናንተም ካህናት መሆን ትፈልጋላችሁ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን በሚያገለግለው በአሮን ላይ ለምን ታጉረመርማላችሁ?
ሙሴ ይህንን ጥያቄ የሚያነሳበት ምክኒያት የአሮንን መልካም የሆነ ድርጊት በመጥቀስ ለመሞገት ነበር፡፡ምክኒያቱ ደግሞ አሮን እግዚአብሔር አድርግ የሚለውን ነገር የሚያደረግ ሰው ሰለነበረ ነው፡፡“የምታጉመርሙት በአሮን ላይ ሣይሆን አሮንን በሚያዝዘው በእግዚአብሔር ላይ ነው”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:12
በምድረ በዳ ትገድለን ዘንድ …ያወጣኸን አይበቃህምን?
ዳታንና አቤሮን ይህንን ጥያቄ የሚጠይቁት ሙሴን ለመገሰፅ ነው፡፡ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እኛን እዚህ ምድረ በዳ አምጥተህ በምድረ በዳ ልትገድለን ማሰብህን ምንም እንዳልሆነ ነገር ቆጥረኸዋል”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ትንሽ ነገር
“በቂ ያልሆነ”ወይም “ጠቃሚ ያልሆነ”
ወተትና ማር ወደምታፈስስ ምድር
ምድሪቱ ለከብቶችና ለዕፅዋት ተስማሚ መሆኗን ለመገለፅ ከእነዚያ እንስሳት የሚገኘው ወተትና ማር ልክ በምድሪቱ ላይ እንደሚፈስስ ነገር አድርገው ይገልፁታል፡፡ይህንን ሐረግ በኦሪት ዘኁልቁ 14፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡“ከብቶችን ለማርባትና እህልን ለማብቀል እጅግ የያመች ሥፍራ ነው”ወይም “እጅግ ለም የሆነ መሬት ነው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመገለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ልትገድለን
ሰዎቹ ነገሩን አጋንነው የሚናገሩት ከእነርሱ ውስጥ አንድ ሰው ቢሞት ሙሴን ተጠያቂ ለማድረግ በማሰብ ነው፡፡(የተጋነነ ንፅፅር እና አጠቃላይነት የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ርስት
እግዚአብሔር ለዘላለም የሚሰጣቸውን ነገር በውርስ እንደሚያገኙት ነገር አድርገው ነው የሚናገሩት፡፡(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በባዶ ተስፋ ዓይኖቻችንን ታሳውራለህን?
ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቁት ሙሴን ለመቃወም ነው፡፡ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በባዶ ተስፋ ልታሳውረን ትፈልጋለህ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ልታሳውረን
ሰዎችን ማታለል ሰዎችን እንደ ማሳወር ተደርጎ ተገልጿል፡፡“ልታታልለን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በባዶ ተስፋ
ተስፋ የተሰጣቸው ነገሮች ያለመከናወናቸውን ለመገለፅ ባዶ ከሆነ ዕቃ ማስቀመጫ ጋር ያነፃፅሩታል፡፡“የማትፈፅማቸው የተስፋ ቃሎችህ”ወይም “እነዚህ ነገሮች ይደረጋሉ እያልክ የማታከናውናቸው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:15
ከእነርሱ አንድ አህያ ስንኳ አልወሰድኩም
እዚህ ላይ አንድ “አህያ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድ ሰው ከሌላ ሰው ሊወስድ የሚችለውን ነገር ነው፡፡“ከእነርሱ አንዲት ነገር አልወሰድኩም፡፡አንድ አህያ እንኳን”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)
ጥና
ዕጣንን ለማጤስ የሚያገለግል ዕቃ፡፡
Numbers 16:20
አጠፋቸው ዘንድ
እነርሱን ማጥፋት ልክ እግዚአብሔር እንደሚበላቸው ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው፡፡“አጠፋቸው ዘንድ”ወይም “አጠፋቸዋለሁ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በግምባር መውደቅ
ይሄ የሚያሣየው ሙሴና አሮን በእግዚአብሔር ፊት ራሣቸውን ማዋረዳቸውን ነው፡፡(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ሁሉ ነፍስ አምላክ
እዚህ ላይ “ነፍስ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለመኖር ብቁ መሆንን ነው፡፡“ለሰው ሁሉ ሕይወትን የሚሰጠው እግዚአብሔር” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመገለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሰው ኃጢአት ቢሰራ በማህበሩ ሁሉ ትቆጣለህን?
ሙሴና አሮን ይህን ጥያቄ የሚጠይቁት ስለ ሕዝቡ ልመናን ለማቅረብ ብለው ነው፡፡ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“አንድ ሰው ኃጢአትን በመሥራቱ እባክህን በማህበሩ ሁሉ ላይ አትቆጣ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:25
ትጠፋላችሁ
መጥፋታቸው ልክ አንደ ምግብ እንደሚበሉ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል፡፡“ትጠፋላችሁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በኃጢአታቸውም ትጠፋላችሁ
ከኃጢአታቸው የተነሣ መጥፋታቸው ልክ ኃጢአት እንደሚያጠፋቸው ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል፡፡“በኃጢአታቸውም ትጠፋላችሁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በኃጢአታቸውም ትጠፋላችሁ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የሰራችኋቸው ኃጢአቶቻችሁ ሁሉ ያጠፏችኋል”ወይም “ከኃጢአቶቻቸው ሁሉ የተነሣ እግዚአብሔር ያጠፋችኋል” (ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:28
በዚህ ታውቃላችሁ
እዚህ ላይ “በዚህ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሴ ቀጥሎ የሚናገረውን ነገር በሚመለከት ነው፡፡
ምድር አፍዋን ከፍታ ትውጣቸዋለች
ሙሴ እዚህ ላይ የሚናገረው ልክ ምድር ሕይወት እንዳለው ነገር ሆኖ እነዚህ ሰዎች የሚወድቁበት የተከፈተ ጉድጓድ ደግሞ ሊበላቸው እንደተዘጋጀ ሠፊ አፍ አስመስሎ ነው፡፡“ከበታቻቸው ያለው መሬት ተሰነጠቀ፤ምድርም አፍዋን ከፍታ ዋጠቻቸው”(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:31
ምድርም አፍዋን ከፍታ ዋጠቻቸው
ሙሴ እዚህ ላይ የሚናገረው ልክ ምድር ሕይወት እንዳለው ነገር ሆኖ እነዚህ ሰዎች የሚወድቁበት የተከፈተው ጉድጓድ ደግሞ የምድርን አፍ አስመስሎ ነው፡፡“ከበታቻቸው ያለው መሬት እንደ ሠፊ አፍ ተከፍቶ በዚያ ወደቁና በእርሱ ውስጥ ተቀበሩ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:33
ወደ ሲኦል ወረዱ

በኦሪት ዘኁልቁ 16:30 ላይ ተመሳሳይ የሆነ ሐረግ ይገኛል።እዚያ ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
እነርሱ ተደነቁ
“እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው “እሥራኤላውያንን ሁሉ”ነው።
ምድሪቱ እኛንም እንዳትውጠን
ሰዎቹ የሚናገሩት ልክ ምድር ሕይወት እንዳላት ነገር አድርገው ነው።“ምናልባት መሬት ተከፍታ እኛንም ልትውጠን ትችላለች”ወይም “ምድር እንደገና የምትከፈት ከሆነ እኛም እዚያ ውስጥ ወድቀን ልንቀበር እንችላለን” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እሳትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥታ ሁለት መቶ ሃምሳ ሰዎች በላች
በእሣት መጥፋታቸው ልክ በእሣት እንደተበሉ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል። “እሳትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥቶ 250 ሰዎች አጠፋ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
250 ሰዎች
“ሁለት መቶ ሃምሳ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:36
ከእሳቱ ውስጥ
ይሄ 250 ሰዎች ያቃጠለውን እሳት የሚያመለክት ነው።
ሕይወታቸውን ያጡት ሰዎች
ሕይወት ማጣት የሚያመለክተው መሞታቸውን ነው።“የሞቱት ሰዎች”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ የተሰሩ ይሁኑ
“እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጥናዎቹን ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል። “ካህኑ አልዓዛር ይጠፍጥፋቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ የተቀደሱ ናቸው…እነርሱ ምልክት ይሆናሉ
“እነርሱ”እና“እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጥናዎቹን ነው።
Numbers 16:39
የተቃጠሉት ሰዎች ያቀረቧቸውን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የተቀቃጠሉት ሰዎች የተጠቀሙባቸውን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
በቆሬና በወገኑ
እንደ እነርሱ እንዴት ሊሆኑ እንደሚችሉ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ቆሬና ወገኑ እንደሞቱ መሞት”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:41
እንዲህም ሆነ
ይሄ ሐረግ ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገው በታሪኩ ውስጥ ጠቃሚ ክስተት መኖሩን ለማመልከት ነው።
በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ
“በሙሴና በአሮን ላይ ለማጉረምረም ተሰባሰቡ”
እነሆም ከደመናው
“በድንገት ደመናው” እዚህ ላይ“እነሆም”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በተመለከቱት ነገር ሰዎቹ መደነቃቸውን ነው።
Numbers 16:44
አጠፋቸው ዘንድ
እግዚአብሔር እነርሱን የማጥፋቱን ነገር እንደሚበላቸው ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።“አጠፋቸው ዘንድ”ወይም “አጠፋቸዋለሁ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በግምባራቸው ወደቁ
ይሄ የሚያመለክተው ሙሴና አሮን በእግዚአብሔር ፊት ራሣቸውን ማዋረዳቸውን ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ከእግዚአብሔር ፊት ቁጣ ወጥቶአልና
ቁጣ ከእግዚአብሔር ዘንደ ወጥቶአል የሚለው ቃል የሚያሣየው እግዚአብሔር መቆጣቱን ነው።“እግዚአብሔር መቆጣቱን እያሳየ ነው” ወይም “እግዚአብሔር በጣም ከመቆጣቱ የተነሣ ቁጣውን ወደ ተግባር እየለወጠው ነው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:47
ዕጣንም ጨመረ
ዕጣኑን በጥናው ላይ ማድረጉ የሚያመለክተው ማቃጠሉን ነው።“ዕጣኑን አቃጠለው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
መቅሰፍቱም ተከለከለ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“መቅሠፍቱ መስፋፋቱን አቆመ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 16:49
በቁጥር 14,700
“በቁጥር አሥራ አራት ሺህ ሰባት መቶ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 17
Numbers 17:1
አሥራ ሁለት
“12” (ቁጥሮች የሚለውን ይመለከቱ)
Numbers 17:3
የዓረፍተ ነገር ማያያዣ
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።
የሌዊ ነገድ
እዚህ ላይ ሌዊ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሌዊን ነገድ ነው።
ለአባቶቻቸው ቤቶች አለቃ
እዚህ ላይ “አለቃ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው “እያንዳንዱን”መሪ ነው።
የምሥክሩ ድንኳን
“የምሥክሩ ድንኳን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምሥክሩየተፃፈበት ሠሌዳ የሚቀመጥበትን ሣጥን ነው።“የምሥክሩ ድንኳን”ወይም “ምሥክሩን የሚይዘው ሣጥን”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)
የመረጥኩት ሰው በትር ታቆጠቁጣለች
“በመረጥኩት ሰው በትር ላይ የለመለመ ነገር ይወጣል”
በአንተ ላይ የሚናገሩትን የእሥራኤልን ልጆች ማጉረምረም አስቁም
እዚህ ላይ “ማጉረምረም”የሚለው አሕፅሮተ ሥም ሲሆን በግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል። “የእሥራኤል ሕዝብ በአንተ ላይ ከማጉረምረም እንዲታቀቡ አድርጋቸው”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 17:6
እያንዳንዱ አለቃ ከየአባቶቹ ቤት የተመረጠ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ከእያንዳንዱ ነገድ ሙሴ የመረጠው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
የምሥክሩ ድንኳን
“የምሥክሩ ድንኳን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምሥክሩ የተፃፉበት ሠሌዳ የሚቀመጥበትን ሣጥን ነው።“የምሥክሩ ድንኳን”ወይም “ምሥክሩን የሚይዘው ሣጥን”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 17:8
እንዲህም ሆነ
“እንዲህም ሆነ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድ ልዩ የሆነ ነገር መከናወኑን ነው።በእናንተ ቋንቋ ተመሳሳይ የሆነ አገላለፅሊኖራችሁ ይችል ይሆናል።
Numbers 17:10
የምሥክሩ ድንኳን
“የምሥክሩ ድንኳን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምሥክሩ የተፃፉበት ሠሌዳ የሚቀመጥበትን ሣጥን ነው።“የምሥክሩ ድንኳን”ወይም “ምሥክሩን የሚይዘው ሣጥን”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)
በአንተ ላይ የሚናገሩትን የእሥራኤልን ልጆች ማጉረምረም አስቁም
እዚህ ላይ “ማጉረምረም”የሚለው አሕፅሮተ ሥም ሲሆን በግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል። “የእሥራኤል ሕዝብ በአንተ ላይ ከማጉረምረም እንዲታቀቡ አድርጋቸው”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
አለበለዚያ ይሞታሉ
በማጉረምረማቸው የሚቀጥሉ ከሆነ የሚከሰተው ነገር ይሄ ነው።እግዚአብሔር ይሄ እንዳይሆን ነበር የሚሻው።“እንዳይሞቱ”(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 17:12
እንሞታለን፤ሁላችን እንጠፋለን

በመሠረቱ እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ተቀናጅተው የቀረቡበት ምክኒያት ለጉዳዩ አፅንኦት ለመስጠት ተፈልጎ ነው፡፡(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 18

Numbers 18:1

በመቅደሱ ላይ የተሰራ ኃጢአት ሁሉ

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ማንኛውም ሰው በመቅደሱ ላይ የሚሰራው ኃጢአት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በማንኛውም ሰው በክህነት አገልግሎቱ ላይ የሚሰሩ ኃጢአቶች ሁሉ

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ማንኛውም ሰው በክህነት አገልግሎቱ ላይ የሚሰራው ኃጢአት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በክህነት አገልግሎት ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሰው

“ማንኛውም ካህን”

Numbers 18:3

የዓረፍተ ነገር ማያያዣ

እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል፡፡

አንተን ማገልገል ይኖርባቸዋል..እነርሱበአንድነት ይሁኑ

“እነርሱ”የሚለው ቃል የሌዊ ነገድ አባላትን የሚያመለክት ሲሆን “አንተ”የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው አሮንን ነው፡፡(አንተ/እናንተ የሚለው ቃል በተለያየ መንገድ የሚገለፅበት የሚለውን ይመልከቱ)

ወይም አንተና እነርሱ ትሞታላችሁ

እዚህ ላይ “እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው“በቤተመቅደሱ ውስጥ ባሉት ሥፍራዎች ሁሉ”የመግባት መብት ያላቸውን ማንኛውንም የሌዊ ነገድ አባላትን ነው፡፡“እነርሱ”የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም አሮንንና በተፈቀደላቸው አገልግሎት ውስጥ የሚገኙትን ሌዋውያንን ነው፡፡“(ተውላጠ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ሌላ ሰው ወደ እናንተ አይቅረብ፡፡ኃላፊነቱን መውሰድ ይኖርባችኋል፡፡

እዚህ ላይ “እናንተ”የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር በመሆኑ የሚያመለክተው አሮንንና የተቀሩትን ሌዋውያን ነው፡፡(አንተ/እናንተ የሚለው ቃል በተለያየ መንገድ የሚገለፅበት የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣዬ በእሥራኤል ልጆች ላይ እንደገና እንዳይነድባቸው

ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እጅግ እንደተቆጣ ያመለክታል፡፡2/“በእሥራኤል ሕዝብ ላይ ዳግም በእጅጉ እንዳልቆጣ”2/ይሄ የሚያሣየው ከመቆጣቱ የተነሣ መቅጣቱን ያመለክታል፡፡“የእሥራኤልን ሕዝብ ደግሜ እንዳልቀጣ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:6

የዓረፍተ ነገር ማያያዣ

እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል፡፡

ለእናንተ ሥጦታ ናቸው

እግዚአብሔር ሌዋውያን አሮንን እንዲያግዙት የመደበበትን ሁኔታ እግዚአብሔር ለአሮን እንደተሰጠ ሥጦታ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል፡፡“ለአንተ እንደ ሥጦታ ናቸው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ የተሰጡ

ለእግዚአብሔር “የተሰጡ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ለማገልገል መለየታቸውን ነው፡፡ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ለራሴ የለየኋቸውን”ወይም“ለራሴ ለይቼያቸዋለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተና የአንተ ልጆችህ ብቻ

እዚህ ላይ“አንተ”እና “የአንተ”የሚሉት ቃላት የነጠላ ቁጥር በመሆናቸው የሚያመለክቱት አሮንን ነው፡፡በሌሎች ሥፍራዎች ላይ “እናንተ”እና“የእናንተ”የሚሉት የብዙ ቁጥር በመሆናቸው የሚያመለክቱት አሮንንና ልጆቹን ነው፡፡(አንተ/እናንተ የሚለው ቃል በተለያየ መንገድ የሚገለፅበት የሚለውን ይመልከቱ)

ክህነታችሁን ጠብቁ

“የካህናትን ተግባር አከናውኑ”

በመጋረጃው ውስጥ ያለውን ሁሉ

በመጋረጃው ውስጥ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከመጋረጃው ጀርባ የሚገኘውን የውስጥ ክፍል ነው፡፡“ከመጋረጃው ጀርባ ባለው ክፍል ውስጥ የሚገኘውን ነገር ሁሉ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እንግዳ የሆነ ሰው ቢቀርብ ይገደል

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ሌላ ሰው ቢቀርብ መገደል ይኖርበታል”ወይም “ሌላ ሰው ከቀረበ መግደል ይኖርባችኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ቢቀርብ

ሊቀርቡት የማይገባቸው ነገር ምን እንደሆነ በግልፅ ሊብራራ ይችላል፡፡“ቅዱሱን ሥፍራ የሚቀርብ ሰው”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:8

ለእኔ የቀረበው የማንሣት ቁርባን

እዚህ ላይ “ማንሳት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድን ነገር ለእግዚአብሔር መሥጠትን ወይም ማቅረብን ነው፡፡ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ሰዎች ለእኔ የሚያቀርቧቸውመሥዋዕቶች”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህን የማንሣት ቁርባኖች ለአንተ ሰጥቼሃለሁ

እግዚአብሔር ይህንን ውሳኔ ቀድሞ የወሰነ በመሆኑ ጉዳዩን እንደፈፀመው ዓይነት አድርጎ ይናገራል፡፡“እነዚህን የማንሣት ቁርባኖች ለአንተ ሰጥቼሃለሁ”

ለልጆችህ ድርሻ እንዲሆን

ድርሻ ማለት አንድ ሰው የተወሰነውን የአንድ ነገር ክፍል ሲወስድ ማለት ነው፡፡“በማይቋረጥ መልኩ የምትወስዱት ድርሻችሁ”

ከእሣቱ ከተረፈው

“በመሠዊያው ላይ ሙሉ በሙሉ የማታቃጥሉት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:10

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር

እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል

Numbers 18:12

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር

እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል

የፍሬ መጀመሪያ

ይሄ የሚያመለክተው ጥራት ያላቸውንና የሚያመርቷቸውን ዘይት፤ወይንና እህልን ነው፡፡

በቤትህ ንፁሕ የሆነ ሁሉ

በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትን ንፁሕ እንደመሆን አድርጎ አቅርቦታል፡፡“በቤትህ ውስጥ በእኔ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሰው ሁሉ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 18:14

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር

እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል

ማሕፀንን የሚከፍት ሁሉ፤በኩራት የሆነ ሁሉ

በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው፡፡“ማሕፀንን የሚከፍት ወንድ ሁሉ”(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ማሕፀንን የሚከፍት ሁሉ

“ማሕፀን መክፈት”የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገርእናት የምትወለደው የመጀመሪያ ወንድ ልጇ ማለት ነው፡፡(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በመጀመሪያ የተወለደውን ሁሉ ሰዎቸ ሊቤዡት ይገባል

መጀመሪያ የተወለደውን ወንድ ልጃቸውን መሥዋዕት ከማድረግ ይልቅ ለልጆቻቸው ሲሉ ለካህኑ ገንዘብ መክፈል ነበረባቸው፡፡

ሰዎች ከተተቤዧቸው ከአንድ ወር በኋላ ተመልሰው ሊቤዡ ይገባል

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“አንድ ወር ከሞላቸው በኋላ ሰዎች መልሰው ሊቤዧቸው ይገባል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳግም ሊቤዡ የሚገባቸው ነገሮች

ይሄ ምናልባት የሚያመለከተው ሰዎችን እንጂ ንፁሕ ያልሆኑ እንስሳትን ለማመልከት አይመስልም፡፡

አምስት ሰቅል ...ሃያ አቦሊ
በዘመናዊ የመለኪያ መንገድ መተቀም አስፈለጊ ሆኖ ከተገኘ እነዚህን ተግባራዊ የማድረጊያ መንገዶች እነሆ፡፡“አምስት ብር ቁርጥራጮች....እያንዳንዱ አምስት ግራም ያህል የሚመዝን”ወይም“በቤተመቅደሱ ውስጥ ጥቅም ላይ ባሉት የጥራት ደረጃዎች መሠረት የሚመዝን አምሳ ግራም ብር”(መፅሐፍ ቅዱሣዊመለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)
አምስት ሰቅል
ሰቅል የክብደት መለኪያ ነው፡፡የሚመዘነው ነገር ምን እንደሆነ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የቤተመቅደስሰቅል
የተለያየ ዓይነት የሰቅል ዓይነቶች ነበሩ፡፡ይሄኛው በመገናኛ ድንኳኑ ውስጥ በሚገኘው የተቀደሰው ሥፍራ ላይ ሰዎች የሚጠቀሙበት ዓይነት ነበር፡፡ሃያ አቦሊ ይመዝን ነበር፡፡ይሄ 11 ግራም ገደማ ይሆናል፡፡(መፅሐፍ ቅዱሣዊ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 18:17
ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ደማቸውን መርጨት ይኖርብሃል
በመጀመሪያ እንስሣቱን መግደል በተመለከተየበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“እንስሳቱን ገድለህ ደማቸውን ልትረጭ ይገባሃል” (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በእሣት የተቃጠለ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በእሣት የምትሰራውን”ወይም“በመሠዊያው ላይ በእሣት የምታቃጥለውን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን
እግዚአብሔር በጣፋጭ ሽታ መደሰቱ የሚያመለክተው ቁርባኑን በሚሰዋው ሰው ደስ መሰኘቱን ነው፡፡“እና እግዚአብሔር በአንተ ደስ ይለዋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ መወዘወዝ ፍርምባ እንደ ቀኙም ወርች
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የመወዝወዝ ፍርምባውንና ቀኙን ወርች እንደ መሥዋዕት የምታቀርቡልኝ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 18:19
ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ለአንተ ሰጥቼሃለሁ
እግዚአብሔር ይህንን ውሳኔ ቀድሞ የወሰነ በመሆኑ ጉዳዩን እንደፈፀመው ዓይነት አድርጎ ይናገራል፡፡“ለአንተ ሰጠሁህ”
ለልጆችህ እንደሚቀጥል ድርሻ
ድርሻ ማለት አንድ ሰው የተወሰነውን የአንድ ነገር ክፍል ሲወስድ ማለት ነው፡፡“በማይቋረጥ መልኩ እንደምትወስዱት ድርሻችሁ”
ከአንተም ጋር ለዘርህ የጨው ቃል ኪዳን ለዘለላም ነው
ሁለቱ ሐረጎች የሚያመለክቱት ተመሳሳይ የሆነ ነገርን ነው፡፡“እነዚህ ሐረጎች በጋራ በመሆን አፅንዖት የሚሰጡት ኪዳኑ ለዘላለም የሚፀና መሆኑን ነው፡፡”“ዘላለማዊ የሆነ ሥምምነት”(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
የዘላለም ጨው ቃል ኪዳን
“በጨው የተደረገ ቃል ኪዳን”ጨው ዘለቄነትን የሚያመለክት ሲሆን በመሥዋዕትና በቃል ኪዳን ወቅት በሚደረጉ ምግቦች ላይ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረግ ነበር፡፡”ዘላቂነት ያለው ኪዳን”ወይም “ዘላለማዊ ኪዳን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በምድራቸው ርስት በመካከላቸውም ድርሻ አይሆንልህም
እግዚአብሔር ሌሎች ሰዎች የሚይዙትን ምድር እንደሚወርሱት ዓይነት አድርጎ ይናገራል፡፡“ከሕዝቡ ምድር አንዱንም አትወርሱም” ወይም “እሥራኤላውያን ከሚይዟቸው መሬቶች ውስጥ አንዱንም አትወስዱም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ድርሻህና ርስትህ ርስት እኔ ነኝ
እግዚአብሔር አሮንና ዘሩ እርሱን በክህነት በማገልገላቸው የሚጠብቃቸውን ታላቅ ክብር ሲገልፅላቸው ልክ እግዚአብሔር ራሱን እንደሚወርሱት አድርጎ ነው የሚናገረው፡፡“በዚያ ምትክ የምኖራችሁ እኔ ነኝ”ወይም“በዚያ ምትክ እንድታገለግሉኝ አፈቅድላችኋለሁ፤በአገልግሎታችሁም ወቅት የሚያስፈልጋችሁን ነገር ሁሉ አዘጋጅላችኋለሁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 18:21
ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ተመልከት ሰጥቼያለሁ
እዚህ ላይ“ተመልከት”የሚለው ቃል የሚቀጥለው ነገር ላይ የበለጠ አፅንኦት እንዲደረግ ያነሳሳል፡፡“በእርግጥ እኔ ሰጥቼያለሁ”
እንደ ርስታቸው
እግዚአብሔር አሮንና ዘሩ የሚቀበሉትን ነገር እንደሚወርሱት ዓይነት አድርጎ ነው የሚናገረው፡፡“ለእሥራኤል ሁሉ የምሰጠውን እንደ ድርሻቸው መጠን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 18:23
ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለአሮን መናገሩን ይቀጥላል፡፡
በእሥራኤል ልጆች መካከል ርስት አይወርሱም
እግዚአብሔር ሌሎች የእስራኤል ሰዎች የሚይዙትን ምድር እንደሚወርሱት ዓይነት አድርጎ ይናገራል፡፡ሌዋውያን የትኛውንም ምድር አይቀበሉም”“ሌላው የእሥራኤል ሕዝብ የሚቀበለውን መሬት መቀበል አይኖርባቸውም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ርስታቸው
እግዚአብሔር አሮንና ዘሩ የሚቀበሉትን ነገር እንደሚወርሱት ዓይነት አድርጎ ነው የሚናገረው፡፡“ለእሥራኤል ሁሉ የምሰጠውን እንደ ድርሻቸው መጠን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 18:25
ከእሥራኤል ልጆች ለእናንተ ርስት አድርጌ የሰጠኋችሁን አሥራት በተቀበላችሁ ጊዜ
የእሥራኤል ሕዝብ ከሰብሎቻቸውንና ከእንስሳቶቻቸው አንድ አሥረኛውን በሥጦታ መልክ ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን እግዚአብሔር ደግሞ ይሄንን ለሌዋውያን ይሰጣቸዋል፡፡
ለእናንተ ርስት ይሆን ዘንድ
የሚወርሱት ነገር ይመስል እግዚአብሔር አሮንና ትውልዱ ስለሚቀበለው ነገር እግዚአብሔር ይናገራል፡፡”ለእሥራኤል ሁሉ ከምሰጠው የእናንተ ድርሻ የሆነው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አሥራታችሁን ማቅረብ ይኖርባችኋል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“አሥራታችሁን ለመሥጠት ማሰብ ይገባችኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 18:28
ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ሙሴ ለሌዋውያን መናገር የሚኖርበትን ነገር መናገሩን ይቀጥላል፡፡
የእርሱን የማንሣት ቁርባን ለካህኑ ለአሮን ትሰጣላችሁ
እዚህ ላይ“የእርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው፡፡በመሠረቱ የእግዚአብሔርን የማንሣት ቁርባንድርሻ መሥጠት የነበረባቸው ለእግዚአብሔር ነው፡፡“ለእግዚአብሔር መሥጠት የሚገባችሁን ቁርባንለአሮን መሥጠት ይኖርባችኋል”
ለአንተ የተሰጠህን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የእሥራኤል ሕዝብ የሰጠህን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 18:30
ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ከእርሱ የተመረጠውን
“ከእሥራኤል ሕዝብ ምርጥ የሆነውን ነገር የተቀበልከውን”
ሌሎች ሥጦታዎቻችሁ
“ሥጦታዎቹ”እሥራኤላውያን የሚያቀርቧቸው መሥዋዕቶች ሆነው ሌዋውያን የሚቀበሏቸው ነገሮች ናቸው፡፡
በመብላታችሁና በመጠጣታችሁ ምንም ዓይነት ኃጢአት አትሸከሙም
“እርሱን በምትበሉበትና በምትጠጡበት ወቅት በደለኞች አትሆኑም”

Chapter 19

Numbers 19:1

ሥርዓት/ደንብ

በመሠረቱ እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።“የሕግ ትዕዛዝ”ወይም “ሕጋዊነት ያለው ደንብ” (ሁለት ተመሳሳይ ገፅታ ያላቸው ነገሮች የሚለውን ይመልክቱ)

ለአንተ ያመጡልህ ዘንድ

እዚህ ላይ“ለአንተ”የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር በመሆኑ የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

ቀንበር ያልተጫነች ወይም ነውርም የሌለባትን

በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሣሣይ ዓይነት ትርጓሜ ያላቸው ሲሆኑ የሚያሳስበውም እንስሳው ምንም ዓይነት እንከን የማይገኝበት መሆን እንዳለበት አፅንኦት ለመሥጠት ነው።(ሁለት ተመሳሳይ ገፅታ ያላቸው የሚለውን ይመልክቱ)

Numbers 19:3

በእርሱ ፊት

“በእርሱ እይታ ሥር”ወይም“ይመለከተው ዘንድ”

ካህኑ የዝግባ እንጨት መውሰድ ይኖርበታል

“ካህኑ የሚለው ቃል የሚያመለክተው አልዓዛርን ነው።

ቀይ ግምጃ

“ደማቅ ቀይ ልብስ”

Numbers 19:7

ከዚያ በኋላ እርሱ ልብሱን ማጠብ ይኖርበታል

እዚህ ላይ“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አልዓዛርን ነው።

ርኩስ ይሆናል

በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አለማግኘት ወይም የተቀደሱ አገልግሎቶችን ለማከናወን ብቁ ያለመሆን ጉዳይ ሰውዬው ንፁሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ነው የሚነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 19:9

ንፁሕ የሆነ ሰው

በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘትናወይም የተቀደሱ አገልግሎቶችን ለማከናወን ብቁ የመሆን ጉዳይ ሰውዬው ንፁሕ እንደሆነ ተደርጎ ነው የሚነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አመዱ መከማቸት ይኖርበታል

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አመዶቹ መከማቸት ይኖርባቸዋል።”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በንፁሕ ሥፍራ ላይ

በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ንፁሕ እንደመሆን ተደርጎ ነው የሚነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ርኩስ ይሆናል

በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አለማግኘት ወይም የተቀደሱ አገልግሎቶችን ለማከናወን ብቁ ያለመሆን ጉዳይ ሰውዬው ንፁሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ነው የሚነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 19:11

አጠቃላይ መረጃ

“ንፁሕ መሆን”እና “መቀደስ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትን ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ

“ንፁሕ ያልሆነ”“መርከስ”“ቅድሰና ማጣት” እና “በኃጢአት መበከል”የሚሉት ሃሣቦች የሚያመለክቱት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አለማግኘትን ነው። (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሞተውን ሰው በድን

“የማንኛውም ሰው ሬሣ”

ራሱን ያጠራል

ይሄ ሰው አንድ ንፁሕ የሆነ ሰው ይጠራና ከውኃ ጋር የተደባለቀ የጊደር አመድ በመርጨት እንዲያጠራው ይጋብዘዋል።አንድን ሰው እንዲያጠራው በመጥራቱ ልክ ያ ሰው ራሱ እንደሚያጠራው ዓይነት ተደርጎ ነው የሚገለፀው።“አንድን ሰው እንዲያጠራው መጋበዝ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በሶስተኛው ቀን ራሱን ካላጠራ በሰባተኛው ቀንም ንፁሕ አይሆንም

ይሄ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።“በሰባተኛው ቀን ንፁሕ የሚሆነው በሶስተኛው ቀን ራሱን ያጠራ እንደሆነ ብቻ ነው”(ድርብ አሉታዎች)

ያ ሰው ተለይቶ መጥፋት አለበት

“መጥፋት”የሚል ቃል የሚያመለክተው ከማህበረሰቡ ጋር ያለው ማንኛውም ግንኙነት ተቋርጦ መባረሩን ነው።ይህንን በዘኁልቁ 9፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ያ ሰው መባረር አለበት”ወይም “ያንን ሰው ማባረር አለባችሁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ላይ ባለው ርኩሰት ላይ ውኃ አልተረጨምና

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ማንም ሰው በርኩሰቱ ላይ ውኃን አልረጨም”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በርኩሰት ላይ የሚረጭ ውኃ

“የረከሱ ነገሮች እንዲነፁ ለማድረግ የሚረጭ ውኃ”ወይም“ነገሮችን ለማንፃት የሚረጭ ውኃ”

ርኩስ ይሆናል፤ርኩሰቱ ከእርሱ ጋር ይቆያል

በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በአንድ ላይ እንዲነገሩ የተደረገው ለጉዳዩ አፅንኦት ለመስጠት ሲባል ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 19:14

አጠቃላይ መረጃ

“ንፁሕ ያልሆነ”የሚለው ሃሣብ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት አለማግኘትን ወይም ለአገልግሎት ብቁ አለመሆንን ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መክደኛው ያልታሰረ የተከፈተ ዕቃ ሁሉ ርኩስ ይሆናል

ይሄ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።“የተከፈቱ ዕቃዎች ንፁሕ የሚሆኑት መሸፈኛ የሚደረግላቸው ከሆነ ብቻ ነው።“ድርብ አሉታዊነት”

በሠይፍ የተገደለ ሰው

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሌላ ሰው በሠይፍ የገደለው ሰው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 19:17

አጠቃላይ መረጃ

“ንፁሕ ያልሆነ”የሚለው ሃሣብ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት አለማግኘትን ወይም ለአገልግሎት ብቁ አለመሆንን ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ

“ንፁሕ መሆን”እና “መቀደስ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትን ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 19:20

አጠቃላይ መረጃ

“ንፁሕ መሆን”እና “መቀደስ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት መኖሩን ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ

“ንፁሕ ያልሆነ”የሚለው ሃሣብ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት አለማግኘትን ወይም ለአገልግሎት ብቁ አለመሆንን ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 20

Numbers 20:1

የፂን ምድረ በዳ

እዚህ ላይ “ፂን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በዕብራይስጥምድረ በዳ የሚለውን ሥያሜ ነው።(ቃላትን መቅዳት ወይም መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

የመጀመሪያው ወር

በዕብራውያን የቀን አቆጣጠር መሠረት ይሄየመጀመሪያ ወራቸው ነው።እግዚአብሔር ከግብፃውያን ነፃ ያወጣቸውን ጊዜ የሚያመለክት ነው።በምዕራባውያን የቀን አቆጣጠር መሠረት የመጀመሪያ ወር የሚሆነው በመጋቢት የመጀመሪያዎቹ ቀናትና

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በየካቲት የመጀመሪያዎቹ ቀናት ወቅት ነው፡፡(የዕብራውያን ወራት የሚለውን ይመልከቱ)

ተቀበረች

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ቀበሯት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:2

እነርሱ ተሰበሰቡ

እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማህበረሰቡን ነው፡፡

በአንድነት ተሰበሰቡ

“ለአመፅ ተሰባሰቡ”

በእግዚአብሔር ፊት

ይሄ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ድንኳን ፊት መሆናቸውን ነው፡፡(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:4

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር

የእሥራኤል ሕዝብ በሙሴና በአሮን ላይ ማጉረምረማቸውን ይቀጥላሉ፡፡

የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ምድረ በዳ ለምን አመጣህ? እኛና ከብቶቻችን እንድንሞት ነውን?

ሕዝቡ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው በሙሴና በአሮን ላይ ለማጉረምርም ነው፡፡እንደ መግለጫ ሊታይ ይችላል፡፡“የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከከብቶቹ ጋር እንዲሞት ለማድረግ እዚህ በረሃ ውስጥ ማምጣት አልነበረብህም” (ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደዚህ አስከፊ ሥፍራ እንመጣ ዘንድ ከግብፅ ምድር ለምን አወጣኸን?

ሕዝቡ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው በሙሴና በአሮን ላይ ለማጉረምርም ነው፡:እንደ መግለጫ ሊታይ ይችላል፡፡“እኛን ወደዚህ አስከፊ ሥፍራ ለማምጣት ከግብፅ ምድር ልታወጣን አይገባህም ነበር”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:6

በግምባራቸው ተደፉ

ይሄ የሚያመለክተው ሙሴና አሮን በእግዚአብሔር ፊት ራሣቸውን ማዋረዳቸውን ነው፡፡(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:7

በዓይናቸው ፊት

እዚህ ላይ ሰዎቹ የሚያዩትን ነገር በሚመለከት“ዓይናቸው”እንደ ወኪል ሆኖ ቀርቧል፡፡“አንተን በሚመለከቱበት ወቅት”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት

ይሄ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ድንኳን ነው፡፡“ከእግዚአብሔር ድንኳን”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:10

ከዚህ ድንጋይ ውኃ እናውጣላችሁን?

ሙሴ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ከብስጭት የተነሣ ሲሆን ሕዝቡ በማጉረምረማቸው ሊገስፃቸው ነበር፡፡ይሄ እንደ መግለጫ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ውኃ የለም ብላችሁ አጉረምርማችኋል፡፡እንደዚህ ከሆነ ከዚህ ዓለት ውኃ እናወጣላችኋለን”ወይም“ከዚህ ዓለት ውኃ ብናወጣላችሁ እንኳን ደስተኞች አትሆኑም፡፡ቢሆንም ግን አደርገዋለሁ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ማውጣት አለብን?

እዚህ ላይ“እኛ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሴንና አሮንን ሲሆን እግዚአብሔርንም የሚያካትት ሊሆን ይችላል፡፡ሆኖም ግን ሕዝቡን አያካትትም፡፡(“እኛ”የሚለውንና አካታችና አካታች ያልሆነውን የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:12

በእሥራኤል ልጆች ዓይኖች ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ በእኔ አላመናችሁም

እዚህ ላይ ሙሴ በእግዚአብሔር ላይ አለመታመኑና እግዚአብሔርን ያለማክበሩ ነገር በእርሱ ላይ መታየቱ በግልፅ ሊብራራ ይችላል፡፡“በእሥራኤል ልጆች ዓይኖች ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ በእኔ ባለማመናችሁምክንያት እኔ በተናገርኩት መንገድ ልታደርግ ሲገባህ በራስህ ሃሣብ ተመስርተህ ዓለቱን መታህ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሥራኤል ዓይኖች ፊት

እዚህ ላይ ሰዎቹ የሚያዩትን ነገር በሚመለከት “ዓይናቸው”እንደ ወኪል ሆኖ ቀርቧል፡፡“አንተን በሚመለከቱበት ወቅት”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

የዚህ ሥፍራ ሥም

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ሰዎች ይሄንን ሥፍራ የሚጠሩት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:14

ወንድምህ እሥራኤል

ሙሴ ይሄንን ሐረግ የተጠቀመበት ምክኒያት ዘሮቻቸው የሆኑት ያዕቆበና ኤሳው ወንድማማቾች ስለሆኑ እሥራኤላውንና ኤዶማውያን ዘመዳሞች እንደሆኑ አፅንዖት ለመስጠት ፈልጎ ነው፡፡

ወደ እግዚአብሔርም በጮህን ጊዜ

“ዕርዳታ ያደርግልን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር በፀለይን ጊዜ”

ድምፃችንን ሰማ

እዚህ ላይ“ድምፅ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው መጮሃቸውንና ለእርሱ የተናገሩትን ነገር ነው፡፡“ጩኸታችንን አዳመጠ”ወይም “የጠየቅነውን ነገር ሰማን”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ

“እነሆ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ስላለፈው ነገር ማውራት ማቆማቸውንና አሁን ስላሉበት ሁኔታ እየተናገሩ መሆኑን ይገልፃል፡፡

Numbers 20:17

ማያያዣ ዓረፍተ ነገር

መልዕክተኞቹ ስለ ኤዶም ንጉሥ መናገራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

ወደ ቀኝም ወደ ግራም አንልም

“አንልም”የሚለው ቃል የሚያመለክተው መንገድ መልቀቅን ነው፡፡“በየትኛውም አቅጣጫ ቢሆን መንገዱን አንለቅም”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉሡ ጎዳና

ይሄ ሰሜናዊውን የደማስቆ የሰሜኑን ክፍል ክፍል በደቡብ ከሚገኘው የአካባ ባህረ ሰላጤ ጋርየሚያገናኝ ዋና መንገድ ነው፡፡

Numbers 20:18

በሠይፍ እንዳልገጥምህ አንተ በምድሬ ላይ አታልፍም

“አንተ”የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር በመሆኑ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ የሚወክለውን ሙሴን ነው፡፡“ሕዝብህን በሠይፍ እንዳልገጥም አንተ በምድሬ ላይ አታልፍም”(አንተ/እናንተ የሚለው ቃል በተለያየ መንገድ የሚገለፅበት የሚለውንና ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

በሠይፍ እንዳልገጥም

እዚህ ላይ “ሠይፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የንጉሡን ሠራዊት ነው፡፡“ሠራዊቴን እልካለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤል ሕዝብ

ይሄ ሐረግ የሚያመለክተው የእሥራኤልን መልዕክተኞች ነው፡፡

በእግራችን እንለፍ

ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው በዚያ በኩል በእግራቸው ለማለፍ እንደፈለጉ ብቻ ነው፡፡የኤዶምን ህዝብ ለማጥቃት በሠረገሎች አይመጡም ማለት ነው፡፡(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 20:20

ኤዶምያስም በብዙ ሕዝብና በፅኑ እጅ ሊገጥመው ወጣ

እዚህ ላይ እጅ የሚለው ቃል የሚያመለከተው የንጉሡን ጠንካራ ሠራዊት ነው፡፡“የኤዶም ንጉሥ እሥራኤልን ይዋጉ ዘንድ ብዙ ተዋጊዎች ያሉበትን ጠንካራ ሠራዊት ላከ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ድንበር ላይ ማለፍ

እዚህ ላይ “እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አዶማውያንን ነው፡፡

Numbers 20:22

የእሥራኤል ልጆች ማህበር ሁሉ

“ማህበር ሁሉ”የሚለው ቃል የሚሰጠው ያለምንም ልዩነት እዚያ የተገኘና “የእሥራኤል ሕዝብ”አካል የሆነ እያንዳንዱ ግለሰብ እዚያ ስለመገኘቱ አፅንኦት ይሰጣል፡፡ (ሁለት ተመሳሳይ ገፅታ ያላቸው የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አሮን ወደ ወገኑ ይከማች
ይሄ ጨዋ በሆነ አነጋገር አሮን መሞት አለበት ማለት ነው፡፡ይሄ የሚያመለክተው አሮን መሞት ያለበት መሆኑንና መንፈሱም አባቶቹ ወዳሉበት ሥፍራ መሄድ ያለበት መሆኑን ነው ፡፡"አሮን መሞት አለበት"(ሥርዓት የሌለውን ነገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
በቃሌ ስላመፃችሁ
"እኔ የተናገርኩትን ተግባራዊለማድረግ እምቢ አላችሁ"
Numbers 20:25
ማያያዣ ዓረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ወደ ወገኑ ይከማች፤በዚያም ይሙት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው፡፡ይሄ የሚያመለክተው አሮን መሞት ያለበት መሆኑንና መንፈሱም አባቶቹ ወዳሉበት ሥፍራ መሄድ ያለበት መሆኑን ነው፡፡(ተመሳሳይነት የሚለውንና ሥርዓት የሌለውን ነገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 20:27
ሠላሣ ቀናት
"30 ቀናት"(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 21
Numbers 21:1
ከእሥራኤልም ጋር ሠልፍ አደረገ
"ሠልፍ አደረገ"ማለት ሠራዊቱ ተዋጋ ማለት ነው፡፡"የእርሱ ሠራዊት ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር ተዋጋ"(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ስእለት ተሳለ
ይሄ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው፡፡"የእሥራኤል ሕዝብ ስእለትን ተሳለ"ወይም "እሥራኤላውያን ስእለትን ተሳሉ"(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የእሥራኤልን ድምፅ ሰማ
"ሰማ"ማለት የጠየቁትን ነገር አደረገላቸው ማለት ነው፡፡"እሥራኤል ጥያቄ ባቀረበለት መሠረት ተግባራዊ አደረገው"(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የእሥራኤል ድምፅ
እዚህ ላይ "ድምፅ"የሚለው ቃልከጥያቄያቸው ጋር የተያያዘ አባባል ነው፡፡"እሥራኤል የጠየቀውን"(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ከተሞቻቸውንም እርም ብለው አጠፉ
"የእሥራኤል ሕዝብ የከነዓናውያንን ሠራዊትና ከተሞቻቸውን ፈፅሞ አጠፉ"
የዚያን ሥፍራ ሥም ሔርማ ብለው ጠሩት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡"ያንን ሥፍራ ሔርማ ብለው ጠሩት"(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 21:4
በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ ከግብፅ ለምን አወጣችሁን?
ሕዝቡ ይሄንን ጥያቄ የጠየቀው ሙሴን ለመገሰፅ ነበር፡፡ይሄ በመግለጫ መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡"እኛን በምድረ በዳ ለመግደል ከግብፅ ልታወጣን አይገባህም ነበር"(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 21:6
በእግዚአብሔርና በአንተ ላይ ተናግረናል፡፡
"በእግዚአብሔርና በአንተ ላይ ክፉ ነገርን ተናግረናል"
እኛ ተናግረናል...ከእኛ
"እኛ"እና "ከእኛ"የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ሙሴን ሣይሆን ሕዝቡን ነው፡፡ ("እኛ"የሚለውንና አካታች ሆነውንና ያልሆነውን የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 21:8
እባብን ሥራ
ሙሴ እውነተኛ የሆነ እባብን መሥራት የማይችል በመሆኑ የእባብ ናሙና እንዲሰራ ነበር የተፈለገው፡፡ይሄ ተግባራዊ መሆን ያለበት መረጃ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡"የእባብ ምሳሌን ሥራ"(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የተነደፈውም ሁሉ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡"እባብ የሚነድፈው ሰው በሙሉ"(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
የናስ እባብ
"ከነሐስ የሰራ እባብ"
እባብም የነደፈችው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ እርሱ ዳነ
እዚህ ላይ "እርሱ"የሚለው ቃል የሚያመለክተው በእባብ የተነደፈውን "ማንኛውንም ሰው"ነው፡፡
Numbers 21:10
በሞአብ ፊት ለፊት
እዚህ ላይ "ፊት ለፊት"የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን "ከእነርሱ ማዶ"ወይም "ከእነርሱ አጠገብ"ማለት ነው፡፡"ከሞአብ በመቀጠል"(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 21:12
በሞአብና በአሞራውያን መካከል ያለ የሞአብ ዳርቻ ነው
ይሄ ማለት እነዚህ ሁለት ሕዝቦች እንደ ድንበር በሚያገለግላቸው በወንዙ አጠገብ ባሉ ክፍሎች ላይ ይኖሩ ነበር ማለት ነው፡፡አሞራውን በወንዙ ደቡብ ክፍል ሲኖሩ አሞራውያን ደግሞ በወንዙ የሰሜኑ ክፍል ነበር የሚኖሩት፡፡
Numbers 21:14
ዋሄብ በሱፋ
እነዚህ ሁለቱም የቦታ ሥሞች ናቸው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
የአርኖንም ሸለቆዎች ወደ ኤር ማደሪያ የሚወርድ በሞአብም ዳርቻ የሚጠጋ
"ወደ አርኖን ከተማ የሚያመራውና በሞአብ ድንበር ላይ ተንጣሎ የሚገኘው ሸለቆ"
Numbers 21:16
ብኤር፤ጉድጓዱ
እነዚህ እንደ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ሊገለፁ ይችላሉ፡፡"ወደ ብኤር፤በዚያ ጉድጓድ ነበረ"
ይኸውም እግዚአብሔር ሙሴን "ሕዝቡን ሰብስብ ውኃንም እሰጣቸዋለሁ ብሎ የተናገረበት ነው"
ይሄ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ጥቅስ ሊገለፅ ይችላል፡፡"ይኸውም እግዚአብሔር ሙሴን "ሕዝቡን ወደ እርሱ እንዲሰበስብ አድርጎ ውኃን ለመሥጠት የተናገረበት ነው"(ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ አባባሎች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 21:17
አንተ ምንጭ ሆይ ፍለቅ
"ምንጭ"የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጉድጓድ ውስጥ ያለውን ውኃ ነው፡፡ እሥራኤላውያን የሚያደምጣቸው ሰው ይመስል ለውኃው የሚናገሩ ሲሆን ጉድጓዱን እንዲሞላላቸው ይጠይቁታል፡፡"አንተ ውኃ ጉድጓዱን ሙላ"(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)
የሕዝብ አዛውንቶች ያጎደጎዱት፤አለቆችም የቆፈሩት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ውኃውን በመቆፈር ረገድ መሪዎች ያላቸውን ሚና አፅንኦት በመሥጠት ይናገራል፡፡ (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
በበትረ መንግሥት፤በበትራቸውም
በትረመንግሥትየያዝየነበረውሥልጣንበነበራቸውሰዎችሲሆንበትርደግሞይያዝየነበረውበሁሉምሰውነበር፡፡
እነዚህሁለቱለቁፋሮአገልግሎትየሚውሉመሣሪያዎችአይደሉም፡፡
እነዚህሁለትቁሣቁሶች የሚያሣዩት በአካባቢያቸውየሚገኙትን ነገሮች ለመጠቀም ኩራት የሚባል ነገር የሌለባቸው ስለመሆኑ አፅንኦት ለመስጠት ነው፡፡"በትረ መንግሥታቸውንና በትራቸውን እንኳን ሳይቀር ይጠቀማሉ"(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 21:19
ነሃልኤል...ባሞት
እነዚህ የቦታ ሥሞች ናቸው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
ፈስጋ ተራራ
ይሄ የተራራ ሥም ነው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
ምድረ በዳውን ከላይ ወደሚመለከተው
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡ይሄ አነጋገር ተራራው ከፍ ያለ እንደሆነ ለመግለፅ ሲሆን

ተራራው ከሥሩ የሚገኘውን ምድረ በዳ እንደሚመለከት ሕይወት እንዳለው ሰው አድርጎ ያቀርበዋል፡፡“ከምድረ በዳው ይልቅ ከፍ ያለ ነው”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:21

እሥራኤልም

እዚህ ላይ “እሥራኤል”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እሥራኤልን ሕዝብና በተለይም መሪዎቿን ነው፡፡“ከዚያ በኋላ እሥራኤላውያን”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እርሻና ወይን ቦታ አንገባም

“በየትኛውም እርሻና የወይን ቦታችሁ አንገባም”

በንጉሥ ጎዳና

ይሄ ደማስቆን በስተ ሰሜንንና የአካብን ባህረ ሠላጤ በደቡብ በኩል የሚያስተሳስር አውራ ጎዳና ነው፡፡ይሄንን በዘኁልቁ 20፡17 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡

በድንበራቸው ላይ ለማለፍ

“በእነርሱ ድንበር በኩል ለማለፍ” እዚህ ላይ “እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አሞራውያንን ነው፡፡

ያሃፅ

ይሄ የቦታ ሥም ነው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱም ከእሥራኤልም ጋር ተዋጋ

እዚህ ላይ “እርሱም”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱንና ሠራዊቱን የሚወክለው ንጉሥ ሴዎን ነው፡፡“ከእሥራኤላውያን ጋር ተዋጉ”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:24

እሥራኤልም መታ

እዚህ ላይ “እሥራኤል” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው፡፡“እሥራኤላውን ጥቃት አደረሱ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በሠይፍ ሥለት

“ስለታም በሆነው የሠይፉ ክፍል” “የሠይፍ ሥለት”የሚለው ቃል የሚያያዘው ከሞትና ፍፁም ከሆነ ጥፋት ጋር ነው፡፡“ሙሉ በሙሉ ድል ነሷቸው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱን ምድር ወረሱ

“የአሞራውያንን ምድር ድል አደረጉ” እዚህ ላይ “የእነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አሞራውያንን ነው፡፡

የአሞን ሕዝብ…አሞራውያን

“አሞናውያን..አሞራውያን”ወይም “አሞን ሕዝብ ወይም የአሞር ሕዝብ” እነዚህ ስሞች ተመሳሳይ ቢሆኑም የሚያመለክቱት ግን ሁለት የተለያዩ ሕዝቦችን ነው፡፡

የተመሸገ ነበረ

“ጠንካራ የሆነ መከላከያ ነበረው” እሥራአላውያን አሞናውያንን አላጠቁም፡፡

በሐሴቦንና በመንደሮቹ ሁሉ

እዚህ ላይ“ሁሉ”የሚለው ቃል አካታች ሲሆን የሐሴቦን ከተማ በቅርብ ካሉት መንደሮች ጋር ያለውን ግንኙነት ይገልፃል፡፡“ሐሴቦንና የሚቆጣጠራቸው በቅርብ የሚገኙ ከተሞች”

ሴዎን እርሱን ከተማዎች ሁሉ ወስዶ ነበር

እዚህ ላይ“የእርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሞአብን ንጉሥ ነው፡፡

Numbers 21:27

ሐሴቦን … የሴዎን ከተማ

እነዚህ የሚያመለክቱትለአንድ ከተማ የተሰጡ ሁለት ስሞችን ነው፡፡(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሴዎን ከተማ ይሰራ፤ይመሥረት

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“አንድ ሰው የሴዎንን ከተማ ይገንባና ይመሥርት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደገና ይገንባና ዳግም ይመሥርት

በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሣሣይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ከተማዋ ሙሉ በሙሉ የምትገነባ ስለመሆኗ አስረግጦ ለመናገር ነው፡“ሙሉ በሙሉ ዳግም ይገነባል”(ሁለት ተመሳሳይ የሆነ ገፅታ ያላቸው የሚለውን ይመልክቱ)

እሣት ከሐሴቦን፤ነበልባልም ከሴዎን ወጣ

በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሣሣይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆንውድመቱ ከሐሴቦን እንደሚጀምር አስረግጦ ይናገራል፡፡እሣቱ የሚያመለክተው አጥፊ የሆነ ሠራዊትን ነው፡፡“ንጉሥ ሴዎን ከሐሴቦን ከተማ ጠንካራ የሆነ ጦርን እየመራ መጣ” (ተመሳሳይነት የሚለውንናምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሞአብን ዔር፤የአርኖንን ተራራ አለቆች በላ

የሴዎን ሠራዊት የዔርን ከተማ እንደሚበላ አውሬ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል፡፡“በሞአብ ምድር ያለውን የኤርን ከተማ አጠፋ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:29

ሞአብ…የኮሞስ ሕዝብ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት አንድ ዓይነት ሕዝብን ነው፡፡(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የኮሞስ ሕዝብ

ኮሞስ ሞአባውያን ያመለኩት የነበረ ጣዖት ነው፡፡“ኮሞስን የሚያመልክ ሕዝብ”

የራሱ ልጆችን እርሱ ሰጠ

“እርሱ”እና “የራሱ”የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ኮሞስን ነው፡፡

እኛ ድል አድርገናል

እዚህ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዲቦን ድል የነሱትን እሥራኤላውያንን ነው፡፡

ሐሴቦን ፈራርሷል

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ሐሴቦንን ደምስሰናታል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሐሴቦን…እስከ ዴቦን ደረሰ…ከኖፋም እስከ ሜድባ ደረሰ

እነዚህ ሁሉ በሴዎን መንግሥት ውስጥ የነበሩ ቦታዎች ናቸው፡፡ይሄ የሚያሳየው እሥራኤላውያን የሴዎንን አገር ሁሉ ሙሉ በሙሉ አጥፍተውታል ማለት ነው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ሆን ብሎ አጋኖ መናገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 21:31

አባረሩ

“አሳደዷቸው”

Numbers 21:33

በእነርሱ ላይ ወጡ

“አጠቋቸው”

በአሞራውያን ንጉሥ በሴዎን እንዳደረግህ እንዲሁ ታደርግበታለህ

እሥራኤላውያን ሴዎንን ፈፅመው አጥፍተዋት ነበር፡፡“የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን እንዳጠፋህ እንዲሁ አጥፋው”

ስለዚህ ገደሉት

“ስለዚህ የእሥራኤል ሠራዊት ዓግን ገደለው፡፡

ሰውም አልቀረለትም

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የእርሱ የሆኑት ሰዎች ሁሉ ሞቱ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሩንም ወረሱ

“የእርሱን ምድር በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉት”

---

Chapter 22

Numbers 22:1

በኢያሪኮ ፊት ለፊት በዮርዳኖስ ማዶ ባለው

እሥራኤላውያን የሰፈሩት ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ በኩል ነበር፡፡ኢያሪኮ ደግሞ ከወንዙ በስተ ምዕራብ በኩል ነበር፡፡

Numbers 22:2

የሴፎር ልጅ ባላቅ

ባላቅ የሞአብ ንጉሥ ነበር፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴፎር

ሴፎር የባላቅ አባት ነው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞአብ ከሕዝቡ የተነሣ እጅግ ፈራ…ከእሥራኤልም ልጆች የተነሣ ደነገጠ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን ሞአብ ምን ያህል እንደፈራ አፅንዖት የሚሰጡ ናቸው፡፡(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ሞአብ እጅግ ፈራ

እዚህ ላይ “ሞአብ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሞአብን ሕዝብ ነው።“ሞአባውያን በሙሉ ከፍተኛ የሆነ ፍርሃት ይዟቸው ነበረ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ምክኒያቱም ብዙ ስለነበሩ

“ምክኒያቱም በቁጥር ብዙዎች ነበሩ”

የሞአብም ንጉሥ የምድያምን ሽማግሌዎች እንዲህ አላቸው

ሞአባውያንና ምድያማውያን የተለያዩ ሕዝቦች ቢሆኑም በዚያን ወቅት ምድያማውያን ይኖሩ የነበሩት በሞአብ ምድር ውስጥ ነበር።

በሬ የለመለመውን ሣር እንደሚጨርስ ይህ ጭፍራ በዙሪያችን ያለውን ሁሉ ይጨርሳል

እሥራኤላውያን ጠላቶቻቸውን የሚያጠፉበትን መንገድ በመስክ ላይ ሣርን እንደሚበሉ በሬዎች ተደርገው ተገልፀዋል።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያን ወቅት የሴፎር ልጅ ባላቅ የሞአብ ንጉሥ ነበር

ይሄ ዋናውን ታሪክ ስለ ባላቅ የኋላ ታሪክ መረጃ ወደ መስጠት ያዞረዋል።(የጀርባ ታሪክ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:5

መልክተኞችን ላከ

“ባላቅ መልዕክተኞችን ላከ”

ቢኦር

ይሄ የበለዓም አባት ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ፋቱራ

ይሄ የአንድ ከተማ ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

የራሱ አገርና የራሱ ሕዝብ

“የበለዓም አገርና ሕዝብ”

ጠራው

“ባላቅ በለዓምን ጠራው”ባላቅ በቀጥታ ከበለዓም ጋር አልተነጋገረም።ሆኖም ሃሣቡን ያስተላለፈው በላካቸው መልዕክተኞች አማካይነት ነው።

የምድሩን ፊት ሁሉ ሸፈኑ

ይሄ ብዛታቸውን ለመገለፅ ተጋንኖ የቀረበ አነጋገር ነው።“እጅግ ብዙዎች ናቸው”(የተጋነነ ንፅፅር እና አጠቃላይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የምድሪቱን ፊት

ይሄ የሚያመለክተው የምድርን ገፅ ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ላሳድዳቸው

“ላባርራቸው”

አንተ የመረቅኸው ምሩቅ የረገምኸውም ርጉም እንደሆነ አውቃለሁና

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎችን የመባረክም ሆነ የመርገም ኃይል እንዳለህ እኔ አውቃለሁ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:7

የምዋርቱን ዋጋ

“የምዋርቱን ዋጋ”የሚለው አሕፅሮተ ሥምበድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችለላል።“እሥራኤልን እንዲረግም ለበለዓም የሚከፈል ገንዘብ”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ በለዓምም መጡ

“ወደ በለዓምም ሄዱ”የሚለውን አባባል ልትመርጡ ትችሉ ይሆናል።(መሄድና መምጣት የሚለውን ይመልከቱ)

የባላቅንም ቃል ነገሩት

“ከባላቅ የተላከውን መልዕክት ነገሩት”

ባላቅ

ይሄ የሰው ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

አመጣላችኋለሁ

የበለዓም መልዕክት ልክ አንድን ዕቃ ተሸክሞ እንደሚመጣ ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።“እነግራችኋለሁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:9

እግዚአብሔርም ወደ በለዓም መጣ

“እግዚአብሔር ለበለዓም ተገለጠለት

እነዚህ በአንተ ዘንድ የመጡት ሰዎች እነማናቸው?

እግዚአብሔር ጥያቄውን ያነሳው በአዲስ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ውይይት ለመጀመር ነው።ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ በመግለጫ መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ወደ አንተ ስለመጡት ሰዎች ማንነት ንገረኝ” (አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ባላቅ..ሴፎር

እነዚህየሰው ሥሞችናቸው።ይህንን በዘኁልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ሕዝቡን ተመልከት...አሳድዳቸው

በለዓም ባላቅ ለእርሱ የላከውን መልዕክት መልሶ ይናገረዋል።እነዚህን ሐረጎች በዘኁልቁ 22:5-6 ያለውን ክፍል እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።

አሳድዳቸው

“አባርራቸው”

Numbers 22:12

የተባረከ ነውና

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የባረክኋቸው በመሆኑ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ባላቅ

ይሄ ሰው ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 22:15

ወደ በለዓምም መጡ

“ወደ በለዓምም ሄዱ”የሚለውን ልትመርጡ ትችሉ ይሆናል።(መሄድና መምጣት የሚለውን ይመልከቱ)

ባላቅ

ይሄ ሰው ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ይሄ ሕዝብ

ይሄ ነጠላ ሥም እሥራኤላውያንንየሚያየውልክ እንደ አንድ የህዝብ ስብስብ ነው።

Numbers 22:18

ባላቅ

ይሄ ሰው ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ባላቅ በቤቱ የሞላውን ወርቅና ብር ቢሰጠኝ

በለዓም ፈፅሞ ሊሆን የማይችል ነገርን እየገለፀ ነው።እግዚአብሔርን እንዳይታዘዝ ሊያደርገው የሚችል ነገር ሊኖር እንደማይችል አስረግጦ እየተናገረ ነው።(ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በትንሹ ወይም በትልቁ የአምላኬን የእግዚአብሔርን ቃል እተላለፍ ዘንድ አይቻለኝም

ይሄ የሚያሣየው በምንም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን በለዓም እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ወደ ኋላ የማይል መሆኑን ነው።

Numbers 22:21

ኮርቻውን አህያው ላይ ጫነ

ኮርቻ እንስሳት ጀርባ ላይ ለግልቢያ ሲባል የሚደረግ መቀመጫ ነው።

የእግዚአብሔርም ቁጣ ነደደ

የእግዚአብሔር ቁጣ የመጨመሩ ነገር ልክ እሣት መንደድ እንደሚጀምር ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር በኃይል ተቆጣ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በበለዓም ላይ ጥላቻ እንዳለው ሰው

“እንደ በለዓም ጠላት” ወይም “በለዓምን ለማስቆም”

የተመዘዘም ሠይፍ

ሠይፍ ጥቅም ላይ ሊውል ከሰገባው ወጥቷል።“ጥቃት ለማድረስ ሠይፉን ዝግጁ አደረገ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አህያይቱም ከመንገድ ፈቀቅ ብላ ወደ እርሻው ውስጥ ገባች

አህያይቱ ይህንን ያደረገችው ከእግዚአብሔር መልአክ ለመሸሽ ብላ ነው።

እርሷን ይመልሳት ዘንድ

አንዳንድ ጊዜ እንስሳት“የእርሷ”ወይም “እርሷ”በመባል ይጠቀሳሉ።“ሊመልሰው”

Numbers 22:24

ወደ ቅጥሩ ተጠጋች

ይሄ ሙከራ በመንገድ ላይ ቆሞ ከነበረው መልአክ ለማምለጥ የተደረገ ነው።

እርሷ ሄደች

አንዳንድ ጊዜ እንስሳት“የእርሷ”ወይም “እርሷ”በመባል ይጠቀሳሉ።“ሄደ”

የበለዓምን እግር ከቅጥሩ ጋር አጣበቀች

“የበለዓምን እግር ከቅጥሩ ጋር አጋጨችው”ወይም “የበለዓምን እግር ከቅጥሩ ጋር ስታጣብቀው እግሩ ተጎዳ”

Numbers 22:26

በለዓምም እጅግ ተቆጣ

የበለዓም ቁጣ የመጨመሩ ነገር ልክ እሣት መንደድ እንደሚጀምር ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።በዘኍልቁ 22:22 ላይ ያለውን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“በለዓም በኃይል ተናደደ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:28

እግዚአብሔርም የአህያይቱን አፍ ከፈተ

የመናገር ችሎታ አፍ ከመክፈት ጋር ተነፃፅሯል።“ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ልክ እንደ ሰው እንደሚናገር ለአህያይቱ የመናገር ችሎታን ሰጣት”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በለዓምን ተናገረችው

“አህያይቱ በለዓምን ተናገረችው”

ከብዙ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የምትቀመጥብኝ አህያህ አይደለሁምን?

ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የተጠየቀበት ምክኒያት በለዓም በአህያዋ ላይ የሰራው ጥፋት ተገቢነት የሌለው መሆኑን ለመግለፅ ነው።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ከብዙ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የምትቀመጥብኝ አህያህ ነኝ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በውኑ እንዲህ አደርግ ዘንድ ልማዴ ነውን?

ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የተጠየቀበት ምክኒያት በለዓም በአህያዋ ላይ የሰራው ጥፋት ተገቢነት የሌለው መሆኑን ለመግለፅ ነው።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለአንተ እንደዚህ ዓይነት ባህርይ የማሳየት ልማድ አልነበረኝም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:31

እግዚአብሔርም የበለዓምን ዓይኖች ከፈተ፤የእግዚአብሔርንም መልአክ አየ

የአንድ ሰው“ዓይን መክፈት” “ከማየት ችሎታ”ጋር ተነፃፅር ቀርቧል።“ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ለበለዓም የማየት ችሎታን ሰጠው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የተመዘዘም ሠይፍ ይዞ

ሠይፍ ጥቅም ላይ ሊውል ከሰገባው ወጥቷል።ይህንን በዘኍልቁ 22:23 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“ለማጥቃት ከተዘጋጀ ሠይፉ ጋር”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በለዓም ሰገደ፤በግንባሩም ወደቀ

ይሄ የሚያሣየው በዓለም ራሱን በመልአኩ ፊት ማዋረዱን ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

አህያህን ሦስት ጊዜ ለምን መታህ?

ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የተነሳበት ምክኒያት በለዓም የሰራው ሥራ ጥፋት መሆኑን ለማሳሰብ ነው።ይሄ በመገለጫ መልክ ሊተረጎም ይችለል።“አህያህን ሦስት ጊዜ መምታት አልነበረብህም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥላቻ እንዳለው ሰው

“ጠላትህ እንደሆነ ሰው” ወይም “ተቃዋሚምህ እንደሆነ ሰው”

ከፊቴ ፈቀቅ ባላለች በእውነት አንተን በገደልሁህ እርስዋንም ባዳንኋት ነበር

ይሄ ግምታዊ አባባል የሚያሣየው ሊከሰት ይችል የነበረን ነገርና ከአህያይቱ ድርጊት የተነሣ የበለዓም ሕይወት መትረፉን ነው።(በግምት ላይ የተመሰረቱ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:34

አሁን አትወድድ እንደሆነ

“ጉዞዬን እንድቀጥል የማትፈልግ ከሆነ”

ከባላቅ አለቆች ጋር

“ባላቅ ከላካቸው አለቆች ጋር” “ባላቅን” በዘኍልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 22:36

አርኖን

ይሄ የወንዝ ሥም ነው።ይህንን በዘኍልቁ 21:13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

በውኑ አንተን ለመጥራት አልላኩህብምን?

ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የተጠየቀው በለዓም በመዘግየቱ ምክኒያት ለመገሰፅ ነበር።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊረጎም ይችላል።“በእርግጥ ሰዎች እንዲጠሩህ ልኬብህ ነበር” (ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምንስ ወደ እኔ አልመጣህም?

ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የተጠየቀው በለዓም በመዘግየቱ ምክኒያት ለመገሰፅ ነበር።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊረጎም ይችላል።“ወደ እኔ መምጣት ነበረብህ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በውኑ እኔ አንተን ማክበር አልችልምን?

ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የተጠየቀው በለዓም በመዘግየቱ ምክኒያት ለመገሰፅ ነበር።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊረጎም ይችላል።“በእርግጥም ወደ እኔ ዘንድ በመምጣትህ ገንዘብ ልከፍልህ እንደምችል አንተ ታውቃለህ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 22:38

በውኑ አንዳች ነገር እናገር ዝንድ እችላለሁን?

በለዓም ይሄንን ጥያቄ የሚጠይቅበት አቢይ ምክኒያት ባላቅ እንዲያደርግ የሚፈልገውን ነገርሁሉ ለማድረግ የማይችል መሆኑን ለመናገር ነው።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊረጎም ይችላል።“ነገር ግን የምፈልገውን ነገር ሁሉ የመናገር ሥልጣን የለኝም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በአፌ የሚያስቀምጠውን ቃል እርሱን እናገራለሁ

ይሄ መልዕክት የሚነገረው ልክ አንድን ነገር እግዚአብሔር በአፉ ውስጥ እንደሚያስቀምጥ ዓይነት ተደርጎ ነው።“እግዚአብሔር እንድናገረው የሚፈልገው መልዕክት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቂርያት ሐፆት

ይሄ የከተማ ሥም ነው።

ጥቂት ሥጋ

“ከመሥዋዕቱ ጥቂት ሥጋ”

Numbers 22:41

ወደ በአል ኮረብታ

ይህንን ሃሣብ ሊገልፁ የሚችሉት 1/ይሄ በዘኍልቁ 29:11 ላይ ካለው የማምለኪያሥፍራን ያመለክታል።ማምለኪያ የሚለው ቃል ከፍታ የሆነ ሥፍራ ማለት ነው። ወይም 2/ሰዎች ለበአል መሥዋዕት የሚያቀርቡበት ሌላ ሥፍራ ነው።

## Chapter 23

Numbers 23:1

ባላቅ

ይሄ የሞአብ ንጉሥ ነው።ይህንን በዘኍልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ሰባትም ወይፈን ሰባትም አውራ በግ በዚህ አዘጋጅልኝ

“ሰባትም ወይፈን ሰባትም አውራ በግ ለመሥዋዕት እረድልኝ”

በመሥዋዕትህ ዘንድ ቆይ እኔም እሄዳለሁ

“በዚህ በመሥዋትህ ዘንድ ቆይ እኔም ራቅ ወዳለ ሥፍራ እሄዳለሁ”

Numbers 23:4

አንድ ወይፈንና አንድ አውራ በግ አሳርጌያለሁ

እነዚህን እንስሳት እንደሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ ስለማቅረቡ ቀደም ብሎ ተገልጿል።“አንድ ወይፈንና አንድ በግ አዘጋጅቼ በመሥዋዕት መልክ አቃጥያቸዋለሁ” (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርም ቃልን በበለዓም አፍ አደረገ

እግዚአብሔር በለዓም እንዲናገር የሚሰጠውን መልዕክት ልክ በአፉ እንደሚያስቀምጠው ዓይነት ተደርጎ ተነግሯል።“እግዚአብሔር ለባላቅ መነገር የሚገባውን ነገር እንዲነግረው ለበለዓም ነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:7

ባላቅ ከአራም አመጣኝ ...የሞአብምንጉሥ ከምሥራቅ ተራሮች

እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ና ያዕቆብን እርገምልኝ ...ና እሥራኤልን ተጣላልኝ ብሎ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮችተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።በለዓም የእሥራኤልን ሕዝብ እንዲረግም ጫና የሚያደርጉ ናቸው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ያልረገመውን እንዴት እረግማለሁ?እግዚአብሔር ያልተቃወመውን እንዴት እቃወማለሁ?

ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ በለዓም እግዚአብሔርን አልታዘዝም ለማለት ፈቃደኛ አለመሆኑን ያሣያል።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊተረጎም ይችላል።“ነገር ግን እግዚአብሔር ያልረገመውን ልረግም አልችልም።እግዚአብሔር ያልተጣላውን ልጣላ አልችልም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:9

በአምቦች ራስ ላይ ሆኜ አየዋለሁ…በኮረብቶችም ላይ ሆኜ እመለከተዋለሁ

እነዚህ ሁለት ሐረጎችተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።በለዓምከኮረብታ አናት ላይ ሆኖ እሥራኤልን ተመለከተ።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን አየዋለሁ..እመለከተዋለሁ

እዚህ ላይ“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እሥራኤልን ነው።

ሕዝብ አለ

“የተወሰነ የሕዝብ ክፍል አለ”

በአህዛብም መካከል አይቆጠርም

ይሄ አሉታዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የዋለው ተቃራኒው ነገር እውነት መሆኑን አስረግጦ ለመናገር ነው።“ራሣቸውን የተለየ ሕዝብ አድርገው ይቆጥራሉ”(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:10

የያዕቆብን ትቢያ ማን ይቆጥራል?የእሥራኤልንስ እርቦ ማን ይቆጠራል?

“የያዕቆብ ትቢያ”ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን የእሥራኤል ሕዝብ ቁጥር የትቢያን ያህል ብዛት እንዳለው አድርጎ ይናገራል።ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል።“ለቁጥር የሚያዳግቱ እሥራኤላውያን አሉ።ብዙ ከመሆናቸው የተነሣ አንድ አራተኛውን እንኳን መቁጠር የሚችል ሰው አይኖርም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውንና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የፃድቅ ሰው ሞት

ይሄ ሰላማዊ የሆነ ሞት እንደሆነ ግልፅ ነው።ይሄ በዚህ መልክም ሊነገርም ይችላል።“ሠላም የሞላበት የፃድቅ ሰው ሞት”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ፃድቅ ሰው … እንደ እርሱ

ይሄ የእሥራኤልን ሕዝብ እንደ አንድ ሰው አድርጎ የሚያመለክት ገላጭ ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:11

ባላቅ

ይሄ የሞአብ ንጉሥ ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

ያደረገህብኝ ምንድነው?

ባላቅ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው በለዓምን ለመውቀስ ነበር።ይሄንን ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልክም መተርጎም ይቻላል።“ይህንን በእኔ ላይ አድረገሃል ብዬ አላምንም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመልከት

ይሄ የሚያመለክተው የሚመጣውን አስደንጋጭ ድርጊት ነው።

እግዚአብሔር በአፌ ያደረገውን እናገር ዘንድ አልጠነቀቅምን?

በለዓም ይሄንን አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የሚጠይቀው ለድርጊቶቹ ምክኒያት ለመሥጠት ነው።ይሄ በመግለጫ መልክ ሊተረጎም ይችላል፡“እግዚአብሔር የተናገረኝን ነገር ብቻ ለመናገር መጠንቀቅ አለብኝ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በአፌ ያስቀመጠውን ነገር ብቻ እናገር ዘንድ

መልዕክቱ እግዚአብሔር በአፍ ውስጥ እንደሚያስቀምጠው ዓይነት ነገር ተደርጎ ነው የተገለፀው።ይህንንተመሳሳይ ሐረግ በዘኁልቁ 22:38 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“እግዚአብሔር የሚናገረኝን ብቻ ለመናገር”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:13

እዚያ ሆነህ እርገምልኝ

“እዚያ ሆነህ እሥራኤላውያንን ትረግምልኛለህ”

ወደ ፆፊምም ሜዳ

“ፆፊም”የሚለው ቃል “አጥብቆ በዓይን መከታተል”ወይም “መሰለል” የሚገልፅ የግርጌ ማስታወሻ ላይ ተርጓሚዎቹ ማስቀመጥ ሊኖርባቸው ይችል ይሆናል።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

የፈስጋ ተራራ

ይሄ የተራራ ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 21:20 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:16

ቃልንም በአፉ አደረገ

ይሄ መልዕክት ልክ እግዚአብሔር በአፉ ውስጥ እንዳደረገለት ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።ተመሰሳዩን ሐረግ በዘኁልቁ 22:38 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“መናገር ያለበትን ነገር ነገረው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህም አለ

“ከዚያ እግዚአብሔር ተናገረ”

ባላቅ ሆይ ስማ…የሴፎር ልጅ ሆይ አድምጠኝ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የተደጋገሙበት ምክኒያት ባላቅ ለጉዳዩ ትኩረት መሥጠት እንደሚኖርበት አፅንዖት ለመሥጠት ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሴፎር ልጅ

ይሄ የሚያመለክተው ባላቅን ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 23:19

እርሱ ያለውን አያደርገውምን?የተናገረውንስ አይፈፅመውምን?

እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር የሚፈፅም ስለመሆኑ አፅንዖት ይሰጣሉ።እነዚህ ሁለት አስፈላጊ የሆኑ ጥያቄዎቸ በዓረፍተ ነገር መልከ ሊገለፁ ይችላሉ።“ቃል የገባውን ነገር ተግባራዊ ሳያደርግ የቀረበት ጊዜ የለም።ምን ጊዜም ቢሆን አደርገዋለሁ ያለውን ነገር በትክክል ተግባራዊ ያደርገዋል”(ተመሳሳይነት የሚለውንና ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመባረክ ትዕዛዝን ተቀብያለሁ

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን እንድባርክ አዝዞኛል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:21

በያዕቆብ ላይ ክፉትን….በእሥራኤልም ላይ ጠማማነትን

እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት1/እግዚአብሔር ለእሥራኤል የሰጠው መልካም የሆኑ ነገሮችን ብቻ ነው።ወይም2/በእነርሱ ላይ ፍርድን ያመጣ ዘንድ በእሥራኤል ላይ ምንም ዓይነት ኃጢአት አላየም።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሥም እልልታ በመካከላቸው አለ

“እግዚአብሔር ንጉሣቸው በመሆኑ በደስታ እልል ይላሉ”

ጉልበቱ አንድ ቀንድ እንዳለው በሬ ነው

ይሄ ንፅፅር የእግዚአብሔር ኃያል ጉልበት ከበሬ ጋር የሚነፃፀር መሆኑን ነው የሚያመለክተው።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 23:23

በያዕቆብ ላይ አስማት የለም …በእሥራኤልም ላይ ምዋርት የለም

እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ማንም ሰው በእሥራኤል ላይ መርገምን ቢደርገ ሊሰራለት አይችልም ለማለት ነው።“እዚህ ላይ ያዕቆብ የሚል ቃል የሚያመለክተው እሥራኤልን ነው” (ተመሳሳይነት የሚለውንና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ይባላል

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች ሊናገሩ ይችሉ ይሆናል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ያደረገውን ተመልከቱ

እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገላቸው ነገር መልካም መሆኑን የሚያመለክት ነው።“እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገላቸውን መልካም ነገር ተመልክቱ!”

Numbers 23:24

እነሆ ሕዝቡ እንደ እንሥት አንበሳ ይነሳል…ይገድላል

ይህ ጥቅስ ረዥም የሆነ ምሣሌያዊ አነጋገር ሲሆን እሥራኤል ጠላቷን ድል የማድረጓን ጉዳይ ልክ አንበሣ ያደነውን ነገር እንደሚበላ ዓይነት አድርጎ ያቀርበዋል።

(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 23:25
ባላቅ
ይሄ የሞአብ ንጉሥ ነው፡፡ይህንን በዘኁልቁ 22፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡
እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ሁሉ አደርጋለሁ ብዬ አልተናገርሁህምን?
በለዓም ይህንን እጅግ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ የሚጠይቀው ወደ ባላቅ ከመምጣቱ በፊትም ቢሆን እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ ፈቃደኛ እንዳልሆነ ለባላቅ ማሳሰቢያን ለመሥጠት ነው፡፡ይሄ በዓረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡“ከዚያ በፊት እግዚአብሔር የሚናገረኝን ነገር ብቻ እንደምናገር ነግሬሃለሁ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 23:28
ምድረ በዳውን ከላይ ወደሚመለከተው
ይሄ ምድረ በዳ እሥራኤል ሰፍሮበት የነበረው ሥፍራ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡“እሥራኤል በነበረበት ምድረ በዳውን ከላይ ወደሚመለከተው”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 24
Numbers 24:2
ዓይኖቹን አነሳ
“ዓይኖቹን አነሳ”የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ወደ ላይ መመልከት ማለት ነው፡፡(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔርም መንፈስ በእርሱ ላይ መጣ
ይሄ ማለት ትንቢትን መናገር ይችል ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረው ማለት ነው፡፡
ይህንን ትንቢት ተቀበለ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር ይህንን ትንቢት ሰጠው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
የቢዖር ልጅ በለዓም
ቢዖር የበለዓም አባት ነበር፡፡ይህንን በዘኁልቁ 22፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡
ዓይኖቹ የተከፈቱለት
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያሣየው በሚገባ ማየቱንና መገንዘቡን ነው፡፡(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 24:4
አጠቃላይ መረጃ
በለዓም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሆኖ ትንቢት መናገሩን ይቀጥላል፡፡
እርሱ ይናገራል…እርሱ ያያል…እርሱ ይሰግዳል
እዚህ ላይ በለዓም ራሱን የሚጠራው“እርሱ” እያለ ነው፡፡
እርሱ ይሰግዳል
ይሄ የትህትና ድርጊት ነው፡፡(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ዓይኖቹ የተከፈቱለት
“ዓይኖቹ የተከፈቱለት”የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን በለዓም እግዚአብሔር መናገር የፈለገውን ነገር የማወቅ ችሎታ ተሰጥቶታል ለማለት ነው፡፡(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ያዕቆብ ሆይ ድንኳኖችህ፤እሥራኤል ሆይ ማደሪያዎችህ ምንኛ ያምራሉ?
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው፡፡ለበለዓም የእሥራኤል ሰፈር ውብ እንደሆነበት አስረግጠው የሚናገሩ ናቸው፡፡ (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 24:6
አጠቃላይ መረጃ
በለዓም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሆኖ ትንቢት መናገሩን ይቀጥላል፡፡
በሸለቆዎች ተዘርግተዋል
በለዓም እሥራኤልን በሚመለከት ሸለቆዎቹን እንኳን መሸፈን እስኪችሉ ድረስ ዘንድ በቁጥር እጅግ ብዙ እንደሆኑ አድርጎ ነው የሚናገረው፡፡(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)
በወንዝ ዳር እንዳሉ አትክልቶች
በለዓም እሥራኤላውያንን በቂ ውኃ እንደሚጠጡና የተትረፈረፈ ምርትን እንደሚያስገኙ አትክልቶች አድርጎ ያቀርባቸዋል፡፡(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር እንደተከለው እሬት
የእሬት አትክልቶች መልካም የሆነ ሽታ ያላቸው በደረቅ የአየር ሁኔታ ውስጥ እንኳን በሚገባ ማደግ የሚችሉ ናቸው፡፡በለዓም እሥራኤላውያን እንደ እሬት አትክልቶች እንደሚያድጉና መልካም እንደሚሆኑይናገራል፡፡ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር የተከለው እሬት”(ያልታወቁ ነገሮችን መተርጎም፤ተነፃፃሪ የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
በውኃም ዳር እንዳሉ ዘግባዎች
ዝግባ በእሥራኤል ውስጥ ከነበሩት ዛፎች ትልቁ ነው፡፡በለዓም እሥራኤላውያን ልክ ውኃ እንደሚጠጣ ዝግባ ዛፍ ግዙፍ ሆነው እንዳደጉ ዓይነት አድርጎ ይናገራል፡፡(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 24:7
አጠቃላይ መረጃ
በለዓም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሆኖ ትንቢት መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ውኃ ይፈስሳል…በብዙ ውኆች ይሆናል
ብዛት ያለው ውኃ በምድር ላይ እንዳሉና እግዚአብሔር እንደባረካቸው ሰብሎች ተቆጥሯል፡፡“እግዚአብሔር ለሰበሎቻቸው ይሆን ዘንድ ብዙ ውኃ በመሥጠት ይባርካቸዋል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ዘሩም በብዙ ውሆች ይሆናል
በሚገባ ውኃ የጠጣ ዘር የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተትረፈረፈ ሰብል ይኖራቸው ዘንድ የእግዚአብሔር በረከት በእነርሱ ላይ የሚመጣ መሆኑን ነው፡፡“ጤናማ የሆኑ ሰብሎችን ያበቅሉ ዘንድ ለሚዘሩት ዘር ከበቂ በላይ የሆነ ውኃን ያገኛሉ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡም ከፍ ከፍ ይላል…መንግሥቱም ይከበራል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ከሌሎች አገራት ይልቅ እጅግ እንደሚባርካቸው አፅንዖት የሚሰጥ ነው፡፡(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሥም ከአጋግ ይልቅ ከፍ ከፍ ይላል
“ከፍ ከፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ታላቅ የሆነ ክብርና ሥልጣንን ነው፡፡ይሄ የሚያመለክተው ወደፊት የሚነሣው የእሥራኤል ንጉሥ ከአጋግ ይልቅ የበለጠ ክብርና ሥልጣን የሚኖረው መሆኑን ነው፡፡አጋግ የአማሌቃውያን ንጉሥ ነበር፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ))
መንግሥቱም ይከበራል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ሌሎች ሰዎች ለመንግሥታቸው ክብርን ይሰጣሉ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 24:8
አጠቃላይ መረጃ
በለዓም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሆኖ ትንቢት መናገሩን ይቀጥላል፡፡
እግዚአብሔር አውጥቶታል
“እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን አውጥቷቸዋል”
ጉልበቱ አንድ ቀንድ እንዳለው ነው
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር አፅንዖት የሚሰጠው እሥራኤላውያን ታላቅ የሆነ ጉልበት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጠላቶቹን አህዛብን ይበላል
በለዓም እሥራኤላውያንን ልክ ዱር አውሬዎች ጠላቶቻቸውን ከሚበሉት አበላል ጋር አነፃፅሯቸዋል፡፡ይሄ ማለት ጠላቶቻቸውን ያጠፏቸዋል ማለት ነው፡፡(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 24:9
አጠቃላይ መረጃ
በለዓም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሆኖ ትንቢት መናገሩን ይቀጥላል፡፡
እንደ አንበሳ አርፎ ተኝቷል፤እንደ እንስቲቱም አንበሳ ተጋድሟል
በዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ውስጥ በለዓም እሥራኤላውያንን ከሴትና ከወንድ አንበሳ ጋር መሳስላቸዋል፡፡ይሄ ማለት አደገኞችና ሁልጊዜ ለማጥቃት ዝግጁ ናቸው ማለት ነው፡፡(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)
ማን ያስነሣዋል?

በለዓም ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው ማንም ሰው ቢሆን እሥራኤልን እንዳያስቆጣ ለማስጠንቀቅ ነው።ይሄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል።“ማንም ቢሆን እርሱን ለመረበሽ ድፍረቱ አይኖረውም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚመርቅህ ሁሉ የተመረቀ ይሁን፤የሚረግምህም ሁሉ የተረገመ ይሁን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን የሚባርኩትን ይባርክ፤የሚረግሙትንም ይርገም”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 24:10
የባላቅ ቁጣ ነደደ
የባላቅ ቁጣ የመንደዱ ጉዳይ ልክ ሊነድድ እነደጀመረ ዓይነት እሣትተደርጎ ተገልጿል።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ባላቅ በኃይል ተናደደ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
እጆቹንም አጨበጨበ
ይሄ የታላቅ ብስጭትና ንዴት ምልክት ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 24:12
ባላቅ በቤቱ የሞላውን ብርና ወርቅ ቢሰጠኝ
ባላቅ እየገለፀ ያለው ፈፅሞ ሊሆን የማይችልን ነገር ነው።ይሄ ዓረፍተ ነገር አስረግጦ የሚናገረው በምንም ዓይነት መንገድ በለዓም ለእግዚአብሔር እንዳይታዝ የሚያደርገው ነገር የማይኖር መሆኑን ነው።(ምናባዊ ሁኔታዎች)
ለላክሃቸው አልተናገርኩምን?
በለዓም ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ቀደም ሲል የተናገረውን ለባላቅ ለማሳሰብ ነው።ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልክም ሊተረጎም ይችላል።“ይህንን ነግሬያቸዋለሁ”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ይሄ ሕዝብ
“እሥራኤላውያን”
Numbers 24:15
የቢዖር ልጅ በለዓም
ቢዖር በለዓም አባት ነበረ።ይህንን በዘኁልቁ 22፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
ዓይኖቹም የተከፈቱለት
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው በሚገባ የሚያይና የሚረዳ መሆኑን ነው። ይህንን በዘኁልቁ 24፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የልዑልንም ዕውቀት የሚያውቅ
“ዕውቀት”የሚለው ረቂቅ ሥም በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ታላቁ እግዚአብሔር የገለጠለትን ነገር የሚያውቅ ሰው”(አሕፅሮተ ሥሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ይሰግዳል
ይሄ ለእግዚአብሔር የመገዛት ምልክት ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 24:17
አጠቃላይ መረጃ
በለዓም ከአራቱ ትንቢቶች መካከል አንዱን መናገር ይጀምራል።
እርሱን አየዋለሁ አሁን ግን አይደለም፤እርሱን እመለከተዋለሁ በቅርብ ግን አይደለም
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።በለዓም ወደፊት ስለሚከሰተው ነገር ራዕይ እየተመለከተ ነው።“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የወደፊቱን የእሥራኤል መሪ ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል
እዚህ ላይ“ኮከብ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በእሥራኤል ላይ ሥልጣን የሚይዘውን ንጉሥ ነው።(ተምሣሌታዊ ቋንቋ የሚለውን ይመልከቱ)
ከያዕቆብ
እዚህ ላይ“ያዕቆብ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የያዕቆብን ትውልድ ነው።“ከያዕቆብ ትውልድ መካከል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ከእሥራኤል በትር ይነሳል
ይሄ ከመጀመሪው ዓረፍተ ነገር ጋር ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያለው።እዚህ ላይ “በትር”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ብርቱ የሆነ ንጉሥን ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
ከእሥራኤል
እዚህ ላይ“እሥራኤል”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የወደፊት እሥራኤላውያንን ነው።“ወደፊት ከሚወለዱት እሥራኤላውያን መካከል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የሞዓብንም ማዕዘኖች ይመታል
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/ሞዓብ መሪዎችን አናት ይመታል2/የሞዓብን መሪዎች ያጠፋል።
የሤትንም ልጆች
ይሄ የሤት ዝርያዎች የሆኑ ሞአባውያንን የሚመለከት ነው።
Numbers 24:18
አጠቃላይ መረጃ
በለዓም የመጀመሪያዎቹን አራት ትንቢቶች መናገር ያበቃል።
ኤዶም ርስቱ ይሆናል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እሥራኤላውያን ኤዶምን በቁጥጥራቸው ሥር ያደርጓታል።”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 24:20
በለዓም አማሌቅን አይቶ
እዚህ ላይ“አማሌቅ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአማሌቅን ሕዝብ ነው።ራዕዩ የቀጠለው ወደ አሜሌቃውያን አቅጣጫ ከተመለከተ በኋላ ሲሆን ከዚያ በኋላ ስለ አማሌቃውያን መተንበዩን ይቀጥላል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ ፍፃሜ ግን
ነጠላ ሥም ጥቅም ላይ የዋለበት ምክኒያት አማሌቃውያን እንደ አንድ ግለሰብ በመታየታቸው ነው።(የመጀመሪያ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ አካል የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 24:21
ቄናውያን
ይሄ ሥም የቃየን ትውልድ ሆነ ሕዝብ ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
ማደሪያህ የፀና ነው
“የምትኖርበት ሥፍራ ከባድ መከላከያ ያለው ነው”
ጎጆህም በአምባ ላይ ተሰርቷል
ይሄ ምሣሌያዊ አነጋገር ሲሆን ደህንነቱ በተጠበቀ ሥፍራ ላይ መኖር ማለት ነው።“የምትኖርበት ሥፍራ ዓለታማ በሆኑ ከፍታ ሥፍራዎች ላይ እንዳለ ወፍ ጎጆ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን አሦር እስኪማርክህ ድረስ ቄናዊው ለጥፋት ይሆናል
እዚህ ላይ የቄናውያን መጥፋት በእሣት እንደሚቃጠሉ ዓይነት ሆኖ ተገልጿል።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ነገር ግን እናንተ ቄናዊያን አሦራውያን አንድ ነገር በእሣት እንደሚጠፋ ያጠፏችኋል፤በምርኮኝነትም ይወስዷኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 24:23
እግዚአብሔር ይህንን ሲያደርግ አወይ ማን በይወት ይኖራል?
ይሄ አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል።“እግዚአብሔር ይህንን በሚያደርግበት ወቅት ማንም በሕይወት አይኖርም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ኪቲም
ይሄ በሜዲተራንያን ባህር ውስጥ የሚገኝ የአንድ ደሴት ከተማ ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱም ደግሞ ወደ ጥፋት ይመጣሉ
“ጥፋት”የሚለው ረቂቅ ሥም በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር እነርሱንም ያጠፋቸዋል”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
ባላቅ
ይሄ የሞአብ ንጉሥ ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 22፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Chapter 25

Numbers 25:1
ሰጢም
ይሄ በሞአብ ውስጥ የሚገኝ የቦታ ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰገዱ
ይሄ የአምልኮ ሥርዓት ድርጊት ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ብኤልፌጎር
ብኤልፌጎር የተራራ ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 23፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
የእግዚአብሔርም ቁጣ ነደደ
የእግዚአብሔር ቁጣ መንደድ ከሚጀምር እሣት ጋር ተመሳስሎ ተነግሯል።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።ይህንንሐረግ በዘኁልቁ 22፡20 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።“እግዚአብሔር በጣም ተናደደ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውንና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 25:4
የእሥራኤል መሪዎች ሁሉ
ይሄ የሚያመለክተው ጣዖትን በማምለክ ጥፋተኛ የሆኑ መሪዎችን ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ጣዖትን በማምለክ ጥፋተኛ የሆኑ የሕዝብ መሪዎች ሁሉ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በፀሐዩ ፊት ወስደህ
ይሄ ማለት የሕዝቡ መሪዎች እነዚህን ሰዎች ከገደሉ በኋላ ሬሣቸውን ሰዎች ሁሉ ሊያዩ በሚችሉበት ሥፍራ ላይ ይተውታል ማለት ነው።
የእሥራኤል መሪዎች
“በጣዖት አምልኮ ውስጥ ያልተሳተፉ የእሥራኤል መሪዎች”
ፌጎር
ፌጎር የተራራ ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 23፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
Numbers 25:6
ምድያማዊቱን አንዲቱን ሴት ወደ ወንድሞቹ አመጣት
ይሄ የሚያመለክተው ወደ ሠፈሩ ከእርሷ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ለማድረግ ወደ ሠፈሩ ይዟት መምጣቱን ነው።የዚህ ሙሉ ትርጉም የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“ከምድያማዊቷ ሴት ጋር አብሮ ለመተኛት ወደ እሥራኤላውያን ሠፈር አመጣት”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በእሥራኤል ልጆች ማህበር ዓይን ፊት
“ዓይን ፊት” የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ስለ ጉዳዩ ሰምተዋል ወይም ጉዳዩን አውቃውታል ማለት ነው።
አልዓዛር
ይሄ የአሮን ልጅ ሥም ነው።ይህንን በዘኁልቁ 3፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
Numbers 25:8
ተከትሎ ገባ
“ፊንሐስ ተከትሎ ገባ”
Numbers 25:10
ቁጣዬን ከእሥራኤል ልጆች መለሰ
የእግዚአብሔር ቁጣ ለመቆም እንዲችል ወደ አንድ ሥፍራ በአካል መገፋት እንዳለበት ዓይነት ነገር ተደርጎ ነው የሚነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔም የእሥራኤልን ልጆች በቅንዓቴ አላጠፋሁም
እግዚአብሔር እዚህ ላይ የተገለፀው ልክ የእሥራኤልን ሕዝብ እንደሚበላ ጨካኝ አውሬ ተደርጎ ነው።“በእጁ የተናደድኩ ቢሆንም የእሥራኤልን ሕዝብ ግን አላጠፋሁም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 25:12
ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።ለፊንሐስ እሰጠዋለሁ…የእሥራኤልን ሕዝብ
ይሄ የእግዚአብሔርን ንግግር ካለፈው ጥቅስ እንዲቀጥል ያደርገዋል።ይሄ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ አለው።ቀጥተኛ የሆኑት ጥቅሶች ቀጥተኛ እንዳልሆኑ ጥቅሶች ሊገለፁ ይችላሉ።(በጥቅሶች ውስጥ ጥቅሶችና ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 25:14
አሁን
ይሄ ዋናውን ታሪክ ወደ ጀርባ ታሪክ በመቀየር ስለ ዘንበሪና ስለ ከስቢ ያወሳል። (የጀርባ ታሪክ የሚለውን ይመልከቱ)
የተገደለው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ፊንሐስ የገደለው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ዘንበሪ…ሰሉ…ሱር
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
ከስቢ
ይሄ የአንዲት ሴት ሥም ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 25:16
በሸነገሉት ሽንገላ
“መሸንገል”የሚለው ረቂቅ ሥም እንደ ሥም ሊገለፅ ይችላል።“እናንተን በማታለል”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ክፋት መሯችሁ
“ይህንን ክፉ ሥራ እንድትሰሩ አግባቧችሁ”
በፌጎር ጉዳይ ..በፌጎር ነገር
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ሃሣብ ያላቸው ሲሆን እነዚህ ነገሮች የተከናወኑት በፌጎር ተራራ እንደሆነ ይገልፃሉ።
ፌጎር
ፌጎር የተራራ ሥም ነበር።ይህንን በዘኁልቁ 23፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
የተገደለው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ፊንሐስ የገደለው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 26
Numbers 26:1
ማህበሩን ሁሉ ቁጠር
የሚቆጥሩት ሴቶችን ሣይሆን ወንዶችን ብቻ ነበር።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“በማህበሩ ውስጥ ያሉትን ወንዶች ሁሉ ቁጠሩ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያ በላይ
“20 ዓመትና ከዚያ በላይ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:3
“ተናገሯቸው”
ለእሥራኤል መሪዎች ተናገሩ።
ሜዳ
ሜዳ ሠፊና ለጥ ያለ መሬት ነው።
ሃያ ዓመትና ከዚያም በላይ
“20 ዓመትና ከዚያም በላይ”
Numbers 26:5
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የእሥራኤል በኩር ነበረ
እዚህ ላይ እሥራኤል የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያዕቆብ በመባል የሚታወቀውን ሰው ነው።
ከእርሱ ወንድ ልጁ
እዚህ ላይ“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሮቤልን ነው።
43,730
“አርባ ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሣ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:8
አጠቃላይ መረጃ

የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
ኤልያብ... ዳታን... አቢሮን
የእነዚህን ሰዎች ሥም በዘኍልቁ 16፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
Numbers 26:10
ምድሪቱ አፍዋን ከፍታ ዋጠቻቸው
እዚህ ላይ ምድሪቱ የተቆጠረችው ልክ አንድ ሰው አፉን ከፍቶ አንድን ነገር እንደሚበላ ዓይነት ነው።“እግዚአብሔር ምድሪቱ እንድትከፈት ካደረገ በኋላ ሰዎቹ በዚያ ጉድጓድ ውስጥ ወደቁ”(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)
እሣቲቱም 250 ሰዎችን በላቻቸው
እዚህ ላይ እሣቱ የተገለፀው ልክ አንድ ትልቅ እንስሳ አንድን ነገር እንደሚውጥ ተደርጎ ነው። “እግዚአብሔር 250 ሰዎችን ለመግደል እሣትን ተጠቀመ”(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)
250 ሰዎች
“ሁለት መቶ ሃምሣ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የቆሬ ወገኖች
“የቆሬ ቤተሰቦች በሙሉ”
ዋጠቻቸው
“መጨረሻቸው ሆነ”
Numbers 26:12
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
22,200 ሰዎች
“ሃያ ሁለት ሰሺህ ሁለት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:15
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
40,500 ሰዎች
“አርባ ሺህ አምስተ መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:19
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
76,500 ሰዎች
“ሰባ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:23
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
64,300 ሰዎች
“ስድሳ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:26
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
60,500 ሰዎች
“ስድሳ ሺህ አምስት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:28
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንይመልከቱ)
Numbers 26:30
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:33
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
52,700 ሰዎች
“አምሳ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:35
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
32,500 ሰዎች
“ሰላሳ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህ የተቆጠሩት የዮሴፍ ወገኖች ናቸው
“እነዚህ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዮሴፍ ልጆች ከሆኑት ከኤፈሬምና ከምናሴ ልጆች የተወለዱትን ትውልድ ሁሉ ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊበራራ ይችላል።“እነዚህ የያዕቆብ ልጆች ከሆኑት ከኤፍሬምና ከምናሴ ዘር የተገኙ ናቸው።እነርሱም ተቆጠሩ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በየወገናቸው ተቆጠሩ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በየወገናቸው ቆጠሯቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:38
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
45,600 ሰዎች
“አርባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:42
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
64,400 ሰዎች
“ስድሳ አራት ሺህ አራት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:44
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:48
አጠቃላይ መረጃ
የእሥራኤል መሪዎች ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎችን ከትውልዳቸውና ከነገዳቸው አንፃር እየቆጠሩ ነው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውንና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
45,400 ሰዎች
“አርባ አምስት ሺህ አራት መቶ ሰዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:51
ሙሉ ቁጥሩ
“አጠቃላይ ቁጥሩ”
601,730
“ስድስት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰላሣ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:52
ምድሪቱ ትካፈላለች


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“መሬቱን ማከፋፈል አለባችሁ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህ ሰዎች
ይሄ የሚያመለክተው ከኦሪት ዘኁልቁ 26:5 ጀምሮ በየወገናቸው የተቆጠሩትን ሁሉ ነው፡፡
በስማቸው ቁጥር መሠረት
“በእያንዳንዱ ወገን ውስጥ ባለው የሕዝብ ቁጥር መሠረት”
Numbers 26:54
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል፡፡
የበለጠ ርስት ሥጣቸው
በዚህ ምንባብ ወስጥ “ርስት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተወረሰውን መሬት ነው፡፡የዓረፍተ ነገሩ ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“እንደ ርስት አድርገህ የበለጠ ትሰጣቸዋለህ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የተቆጠሩት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የእሥራኤል መሪዎች የቆጠሯቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሪቱ መከፋፈል ይኖርባታል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ምድሪቱን ማከፋፈል አለባችሁ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
በዕጣ
“ዕጣ በመጣል”
ይከፋፈላል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ታከፋፍሉታላችሁ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእነርሱ ማከፋፈል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“መሬቱን ለእነርሱ ማከፋፈል ይኖርባችኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:57
አጠቃላይ መረጃ
ይሄ የሌዋውያን ነገድ የሥም ዝርዝር ነው፡፡ምንም መሬት ባለመቀበላቸው ምክኒያት ሙሴ ሌዋውያንን ለብቻቸው ቆጠራቸው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
በየነገዳቸው ተቆጠሩ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“መሪዎቹ በየነገዳቸው ቆጠሯቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ጌድሶን…ቀዓት…ሜራሪ..እንበረም
የእነዚህን ሰዎች ሥም በዘኁልቁ 3:17-19 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡
ለእንበረም ልጆች ወለደችለት
“እርሷና እንበረም ልጆች ነበሯቸው”
Numbers 26:60
ናዳብ…አብዮድ…ኢታምር
የእነዚህን ሰዎች ሥም በዘኁልቁ 3:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡
በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሌለውን እሳት አቀረቡ
እዚህ ላይ“እሣት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “የሚቃጠል መሥዋዕትን”ነው፡፡ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ በዘኁልቁ 3:4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡“እርሱ ባልተቀበለው ሁኔታ የሚቃጠል መሥዋዕትን አቀረቡ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የተቆጠሩት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“መሪዎቹ የቆጠሯቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ሃያ ሶስት ሺህ
“23,000”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያ በላይ ያሉ
“አንድ ወርና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያለው”
ርስት አልተሰጣቸውም ነበር
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡እዚህ ላይ “ርስት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተወረሰውን መሬት ነው፡፡የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር ምንም ዓይነት መሬት በርስትነት እአይሰጣቸውም አለ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:63
በሙሴና በካህኑ አልዓዛር የተቆጠሩት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ሙሴና ካህኑ አልዓዛር የቆጠሯቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድም ሰው አልነበረም
“ሰዎች አልነበሩም”
በሙሴና በካህኑ አሮን የተቆጠሩት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ሙሴና ካህኑ አሮን የቆጠሯቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
የእሥራኤልን ልጆች በቆጠሯቸው ጊዜ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የእሥራኤልን ትውልድ በቆጠሩበት ወቅት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 26:65
ከእነርሱ አንድ ሰው ስንኳ አልቀረም
“እነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሲና ምድረ በዳ ተቆጥረው የነበሩትን ሰዎች ሁሉ ነው፡፡ይሄ በአዎንታዊ መለኩ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እስከ አሁን ድረስ በሕይወት ያሉት ሰዎች”(ድርብ አሉታውያን)
የዮፎኒ ልጅ
ዮፎኒየካሌብ አባት ነበር፡፡ይህንን በዘኁልቁ 13:6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡
የነዌ ልጅ
ነዌ የኢያሱ አባት ነበር፡፡ይህንን በዘኁልቁ 11:28 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡

---

Chapter 27
Numbers 27:1
ከዚያም የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች ወደ ሙሴ ቀረቡ ….የዮሴፍ ልጅ
ከዚያም ከዮሴፍ ልጅ ከምናሴ ወገኖች፤የምናሴ ልጅ፤የማኪር ልጅ፤የገለዓድ ልጅ፤የኦፌር ልጅ የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች ወደ ሙሴ ቀረቡ፡፡ይሄ የትውልድን ሐረግ ይናገራል፡፡
ሰለጰዓድ የኦፌር ልጅ …ማህለህ፤ኑዓ፤ዔግላ፤ሚልካ፤ቲርጻ
ይህንን በዘኁልቁ26:33 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡
ገለዓድ….ማኪር
ይህንን በዘኁልቁ 26:29 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡
Numbers 27:2
ቀረቡ
“የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች ቀረቡ”
በቆሬ ማህበር ውስጥ ሆኖ በእግዚአብሔር ላይ ያመፀ
በቆሬ ማህበር ውስጥ የነበሩት ሰዎች ተሰባሰበው በእግዚአብሔር ላይ አመፁ፡፡እግዚአብሔር ከኃጢአታቸው የተነሣ እንዲሞቱ አደረገ፡፡የዚህ ዓረፍት ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“በእግዚአብሔር ላይ ያመፁ የቆሬ ማህበር ተከታዮች በመሆናቸው የሞቱ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በራሱ ኃጢአት
“ከራሱ ኃጢአት የተነሣ”
Numbers 27:4
ወንድ ልጅ ባይኖረው የአባታችን ስም ከወገኑ መካከል ለምን ይጠፋል?
በዚያን ዘመን መሬት የመውረስ ሥልጣን የነበረው ወንድ ልጅ ብቻ ነበር፡፡ሴቶቹ ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ውርሱን በመውረስ የዘር ሐረጉ እንዲቀጥል ለማስቻል ነበር፡፡ይሄ እንደ መግለጫ ሊያፍ ይችላል፡፡“አባታችን ወንድ ልጅ ስለሌለው ብቻ የአባታችንን ሥም ከነገድ አባልነቱ ልትፍቁት አይገባም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በአባታችን ወንድሞች መካከል ርስትን ስጠን

ይሄ የአባታቸው ዘመዶች በወረሱት ርስት አካባቢ የሚወርሱት ርስት ይሰጣቸው ዘንድ ያቀረቡት ጥያቄ ነው።የዚህ ፍቺ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“የአባታችን ዘመዶች ባሉበት ሥፍራ ላይ ርስትን ሥጠን”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 27:6

በአባታቸው ዘመዶች መካከል

ይሄ ማለት የአባታቸው ዘመዶች በወረሱት ርስት አካባቢ የሚወርሱት ርስት ይሰጣቸዋልማለት ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“የአባታቸው ወንድሞች ወደሚኖሩበት”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 27:9

አጠቃላይ መረጃ

ይሄ ክስተት አንድ ሰው ወንድ ልጅ የማይኖረው ከሆነ መሬቱን ማን ሊወርስ እንደሚችል ለመወሰን የእግዚአብሔር ሕግ እንዲወጣ ምክኒያት ሆኗል።

ለእሥራኤል ልጆች ሥርዓትና ፍርድ ይሁን

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የእሥራኤል ሕዝብ ሁሉ የሚታዘዘው ሕግ ይሁን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን አዘዘኝ

እዚህ ላይ“እኔን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

Numbers 27:12

ዓባሪም ተራራ

እነዚህ በሞአብ ውስጥ የሚገኙ የተያያዙ ተራራዎች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእሥራኤል ልጆች የሰጠኋትን

እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን እየሰጠ ያለውን ምድር ልክ ሰጥቶ እንደጨረሰ ዓይነት አድርጎ ይናገራል።በዚህ መልኩ የሚናገርበት ምክኒያት የሚሰጣቸው ስለመሆኑ አስረግጦ ለማሳሰብ ነው።“ለእሥራኤል ሕዝብ የምሰጠውን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ደግሞ ወደ ወገኖችህ ትከማቻለህ

ይሄ ጨዋ የሆነ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም ሙሴ እንደሚሞትና መንፈሱም አባቶቹ ወዳሉበት የሚሄድ መሆኑን ነው።“መሞት አለብህ”(የጨዋ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ወንድምህ እንደ አሮን

አሮን መሞቱ የታወቀ ነገር ቢሆንም የበለጠ ግን ልታብራሩት ትችላላችሁ።“ታላቅ ወንድምህ አሮን እንደሞተ”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለታችሁም አምፃችኋል

ይሄ የሚያመለክተው ሙሴና አሮንን ነው።

የጺን ምድረ በዳ

ይህንንዓረፍተ ነገርበዘኁልቁ 13፡21 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

በቁጣህ ውኃው ከዓለት ውስጥ በፈለቀበት ወቅት

ይሄ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ተአምራታዊ በሆነ መልኩ ውኃን ባወጣበት ወቅት ነበር።እግዚአብሔር ድንጋዩን እንዲናገረው ሙሴን አዘዘው።በዚህ ምትክ ግን በሕዝቡ ከመናደዱ የተነሣ ዓለቱን በበትሩ መታው።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አልቀደሳችሁኝምና

“ቅዱስ እንደሆንኩ አላሰባችሁም”

በማህበሩ ሁሉ ፊት

እዚህ ላይ ያዩትን ነገር አፅንዖት ለመስጠት ሰዎች የሚወከሉት “በዓይኖቻቸው”ነው።“ማህበሩ ሁሉ ባለበት ፊት”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

የመሪባ ውኃ

ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 20፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።

Numbers 27:15

የሥጋ ሁሉ መንፈስ አምላክ እግዚአብሔር

ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/እዚህ ላይ “መንፈስ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕዝብን ሁሉ ነው።“የሰው ዘር ሁሉ የበላይ የሆነው እግዚአብሔር”ወይም 2/“መንፈስ”የሚለው ቃልየሚያመለክተው እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ሕይወትንና ትንፋሽን መሥጠቱን ነው። “ለሰው ሁሉ ትንፋሽን የሚሰጠው እግዚአብሔር”ወይም“ለሰው ሁሉ ሕይወትን የሚሰጠው እግዚአብሔር”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

በማህበሩ ላይ

በተወሰኑ ሰዎች “ላይ”መሆን ማለት እነርሱን ለመምራት ሥልጣን መያዝ ማለት ነው።“ማህበሩን የሚመራ ሰው”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በፊታቸው የሚወጣውን፤በፊታቸውም የሚገባውን፤የሚያስወጣቸውንም የሚያስገባቸውንም ሰው

ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ሕዝቡን የሚመራና በጦርነትም ወቅት ሠራዊቱን የሚመራ ማለት ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር መንጋ እረኛ እንደሌለው መንጋ እንዳይሆን

ይሄ ንፅፅር ሲሆን የዚህ ሃሣብ ትርጉም ሕዝቡ መሪ የማይኖረው ከሆነ የተቅበዘበዘና ደካማ ይሆናል ማለት ነው።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 27:18

መንፈሴ የሚኖርበትን የነዌን ልጅ ኢያሱን ውሰድ

የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ሲል ኢያሱ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚከተልና የሚታዘዝ ነው ማለቱ ነው።

እጅህን በላዩ ጫንበት

ይሄ አንድን ሰው ለእግዚአብሔር ለመለየት የሚካሄድ ሥርዓት ነው።“እርሱን ለመቀባት እጅህን በላዩ ላይ ጫንበት”(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

መሪያቸው ይሆን ዘንድ እነርሱ እያዩ አዘዘው

እዚህ ላይ ያዩትን ነገር አፅንዖት ለመስጠት ሰዎች የሚወከሉት “በዓይኖቻቸው”ነው።“የእሥራኤልን ሕዝብ ይመራ ዘንድ በሁሉ ፊት ኢያሱን እዘዘው”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 27:20

አጠቃላይ መረጃ

እግዚአብሔር ለሙሴና ለኢያሱ መናገሩን ይቀጥላል።

ከክብርህ አኑርበት

እዚህ ላይ እግዚአብሔር ልክ በላዩ እንደሚደረግ ነገር ወይም አልባሳት ለኢያሱ ክብሩን እንዲያኖርበት ይናገረዋል።“ከሥልጣንህ የተወሰነውን ክፍል መሥጠት ይኖርብሃል”ወይም “ሰዎች ማድረግ የሚኖርባቸውን ነገር እርሱ ይወስን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኡሪም

ይሄ የተቀደሰ ድንጋይ ሲሆን ሊቀ ካህኑ በደረቱ ላይ የሚያደርገው ነገር ነው፡ በእግዚአብሔር ነገር ላይ ውሳኔ ለመሥጠት የሚጠቀምበት ነገር ነበር።(የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤል ማህበር ሁሉ በቃሉ ይውጡ በቃሉም ይግቡ

ይሄ ማለት ኢያሱ የእሥራኤልን ማህበር እንቅስቃሴዎች የማዘዝ ሥልጣን ይኖረዋል ማለት ነው።“መውታጣ”እና “መግባት”የሚሉት ቃላት በእንቅስቃሴያቸው ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዳለው አፅንዖት የሚሰጡ ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ትዕዛዛቶች ናቸው።“የማህበሩን እንቅስቃሴ ይመራል” (ሆን ብሎ አጋኖ መናገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከእርሱም ጋር የእሥራኤል ልጆች ማህበር ሁሉ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በጥምረት የቀረቡበት ምክኒያት ለጉዳዩ አፅንኦት ለመሥጠት ሲባል ነው።“እርሱና የእሥራኤል ሕዝብ ሁሉ”(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 27:22

ፊት አቆመው

“በማህበሩ ፊት እንዲቆም አዘዘው”

እርሱ እጁን በላዩ ላይ ጭኖ መሪ ይሆን ዘንድ እርሱን አዘዘው

“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሴን ሲሆን “እርሱ”የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው ኢያሱን ነው።

እጁን በላዩ ላይ ጫነበት

እጅ መጫን አንድን ሰው ለተለየ የእግዚአብሔር አገልግሎት ለመለየት የሚደረግ ሥርዓት ነው።(ተምሣሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

መምራት

ግልፅ የሆነውንና ሰዎችን የመምራትን ጉዳይ የበለጠ ልታብራሩት ትችላላችሁ።“ሰዎችን መምራት”ወይም“የእሥራኤላውያን መሪ መሆን”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር እርሱን ባዘዘው መሠረት

እዚህ ላይ “እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሴን ነው።



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 28
Numbers 28:1
በየጊዜው
“እኔ በመረጥኩኩት ቀን”
በእሳት የተደረገውን ቁርባኔን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በመሠዊያው ላይ የምታቀርቡት መብል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእኔ ጣፋጭ ሽታ
“የምወደውን ሽታ”
Numbers 28:3
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ህዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት ለሙሴ መንገሩን ይቀጥላል፡፡
በእሣት የሚደረግ ቁርባን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በእሳት የሚቃጠል ቁርባን”ወይም “በመሥዋዕቱ ላይ በእሣት ያቃጠላችሁት ቁርባን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ከ..ጋር የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
የኢፍ መሥፈሪያ አሥረኛ እጅ
“አሥረኛ እጅ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ክፍል ማለት ነው፡፡ ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“ሁለት ሊትሮች”ወይም “የኢፍ መስፈሪያ አንድ አሥረኛ”(ይሄ ሁለት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
የኢን መሥፈሪያ አንድ አራተኛ እጅ
“አራተኛ እጅ”ማለት አራት እኩል ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ክፍል ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“አንድ ሊትር”ወይም “የኢን መስፈሪያ አንድ አራተኛ”(ይሄ አንድ ሊትር ያህል ይሆናል) (ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
በተጠለለ ዘይት
“የተወቀጠ ዘይት”ወይም “ንፁህ ወይራ ዘይት”ይሄ የሚያመለክተው ከወይራ ተወቅጦ የወጣን ዘይት ነው፡፡
Numbers 28:6
በሲና ተራራ ላይ የታዘዘ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ያዘዘው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
በእሣት የቀረበ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በእሣት ላይ ያቃጠላችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
የኢን መሥፈሪያ አንድ አራተኛ እጅ
“አራተኛ እጅ”ማለት አራት እኩል ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ክፍል ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“አንድ ሊትር”ወይም “የኢን መስፈሪያ አንድ አራተኛ”(ይሄ አንድ ሊትር ያህል ይሆናል) (ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
በመቅደሱ ውስጥ ለእግዚአብሔር ለመጠጥ ቁርባን መጠጥ ታፈስሳለህ
ይሄ ዓረፍተ ነገር የሚያሣየው ከበግ ጠቦቱ ጋር አብሮ የሚቀርበውን የመጠጥ ቁርባን ነው፡፡የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“ጠንካራ የሆነ የመጠጥ ቁርባን ሊሆን የሚገባው ሲሆን በእግዚአብሔር መቅደስ ውስጥ ልታፈስሱት ይገባል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በፊት እንዳቀረብከው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“አንተ ያቀረብከው ዓይነት”
Numbers 28:9
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው፡፡
ከመሥፈሪያው ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሁለቱ ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“አራት ሊትር ተኩል”ወይም “ከመሥፈሪያው ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”(አራት ሊትር ተኩል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
በዘይት የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በዘይት የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእርሱ ጋር የመጠጥ ቁርባን
ብዙ ቁርባኖች አብሮ የመጠጥ ቁርባን እንዲቀርብ የሚጠይቁ ናቸው፡፡የዚህ ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“የመጠጥ ቁርባንም አብሮ ይቀርባል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 28:11
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው፡፡
ከመሥፈሪያው አሥር እጅ ሶስት እጅ
“ከአሥር እጅ ሶስት እጅ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሶስቱ ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“ስድስት ሊትር”ወይም “ከመሥፈሪያው ከአሥር እጅ ሶስት እጅ”(ስድስት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
በዘይት የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በዘይት የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአሥር እጅ ሁለት እጅ መልካም ዱቄት
“ኢፍ”የሚለው ቃል ግልፅ ቢሆንም የበለጠ ሊብራራ ግን ይችላል፡፡“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው፡፡“አራት ተኩል ሊትር መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንዲ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
ከመሥፈሪያው አንድ አሥረኛ እጅ
“አንድ አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች አንዱ ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“ሁለት ሊትር”ወይም “ከመሥፈሪያው አሥረኛ እጅ”(ሁለት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
በእሣት የቀረበ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በእሣት ላይ ያቃጠላችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 28:14
የኢን ግማሽ
“ግማሽ”ማለት ሁለት እኩል ከሆኑ ክፍሎች ውስጥ አንደኛው ክፍል ማለት ነው፡፡ ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“ሁለት ሊትር”ወይም “የኢን ግማሽ”(ሁለት ሊትር)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
የኢን ሢሶ
“የኢን አንድ ሶስተኛ”አንድ ሶስተኛ ማለት ሶስት እኩል ከሆኑ ክፍሎች ውስጥ አንደኛው ክፍል ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“1.2 ሊትር”ወይም “አንድ ሊትርና አንድ አምስተኛ ሊትር”(ሁለት ሊትር ማለት ነው)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
የኢን አራተኛ እጅ
“አራተኛ እጅ”ማለት አራት እኩል ከሆኑ ክፍሎች ውስጥ አንደኛው ክፍል ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“አንድ ሊትር”ወይም “የኢን አራተኛ እጅ”(አንድ ሊትር ያህል የሆነ)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
ለእግዚአብሔር አንድ አውራ ፍየል ይቀርባል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡ለኃጢአት መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል ለእግዚአብሔር ታቀርባላችሁ፡፡(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 28:16
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው፡፡
በመጀመሪያው ወር ከወሩም በአሥራ አራተኛው ቀን....ከዚህም ወር በአሥራ አምስተኛው ቀን
“በመጀሪያው ወር በወሩ በ14ኛው ቀን…በዚሁ ወር በ15ኛው ቀን” “ይሄ የሚያመለክተው የመጀመሪያውን የዕብራውያንን ወር ነው” (የዕብራውያን ወራትናተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው
“የእግዚአብሔርን ፋሲካ ልታከብሩት ይገባል”
በዓል ይሆናል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በዓል ልታደርጉ ይገባል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሾ የሌለው ቂጣ መበላት ይኖርበታል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እርሾ የሌለው ቂጣ ልትበሉ ይገባል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
በመጀመሪያው ቀን
ይሄ የሚያመለክተው የበዓሉን የመጀመሪያ ዕለት ነው፡፡ይሄ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“በበዓሉ በ1ኛው ቀን” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ጉባዔ መደረግ ይኖርበታል
“እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር መሰብሰብ ይኖርባችኋል፡፡” “የተቀደሰ ጉባዔ”የሚለው ሐረግ ሰዎች ተሰብስበው እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔርን ማምለክ የተቀደሰ ክስተት ነው፡፡
Numbers 28:19
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው፡፡
በእሣት የተደረገውን የሚቃጠለውን መሥዋዕት ታቀርባላችሁ
“የሚቃጠል”የሚለው ቃል በፍዝ መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በመሠዊያው ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ ይኖርባችኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከመሥፈሪያው ከአሥር እጅ ሶስት እጅ
“ከአሥር እጅ ሶስት እጅ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሶስቱ ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“ስድስት ሊትር”ወይም “ከመሥፈሪያው ከአሥር እጅ ሶስት እጅ”(ስድስት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
በዘይት የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በዘይት የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“የእፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል፡፡ይሄ ሊደገምም ይችላል፡፡“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው፡፡“አራት ተኩል ሊትር የሆነ መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የእፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
ከመሥፈሪያው አንድ አሥረኛ እጅ
“አንድ አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች አንዱ ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“ሁለት ሊትር”ወይም “ከመሥፈሪያውአንድ አሥረኛ እጅ”(ሁለት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
መሥዋዕትን ማቅረብ
x
Numbers 28:23
ዘወትር ማልዶ ከሚቀርበው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር በየማለዳው እንዲቀርብለት ከሚፈልገው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
እዚህ በተገለፀው መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እኔ እግዚአብሔር እዚህ በገለፅኩት መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
በእሣት የሚደረገውን የመብል ቁርባን
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የመብሉን ቁርባን በመሠዊያው ላይ ማቃጠል ይኖርባችኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእግዚአብሔር የሚሆን ጣፋጭ ሽታ
“ለእግዚአብሔር እንደ ጣፋጭ ሽታ”
መሥዋዕት መደረግ ይኖርበታል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ልትሰውት ይገባል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ጉባዔ መደረግ ይኖርበታል
“እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር መሰብሰብ ይኖርባችኋል፡፡” “የተቀደሰ ጉባዔ”የሚለው ሐረግ ሰዎች ተሰብስበው እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔርን ማምለክ የተቀደሰ ክስተት ነው፡፡
Numbers 28:26
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው፡፡
በበኩራት ቀን
በበኩራት ቀንሲባልዕለቱን ነው፡፡“ይሄ የሚያመለክተው በዓሉ በሚከበርበት ሣምንታት ውስጥ ለእግዚአብሔር የእህል ቁርባን የሚያቀርቡበትን ዕለት ነው፡፡
እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ጉባዔ መደረግ ይኖርበታል
“እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር መሰብሰብ ይኖርባችኋል፡፡” “የተቀደሰ ጉባዔ”የሚለው ሐረግ ሰዎች ተሰብስበው እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔርን ማምለክ የተቀደሰ ሁኔታ ነው፡፡
በዘይት የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በዘይት የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“የእፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል፡፡ይሄ ሊደገምም ይችላል፡፡“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው፡፡“አራት ተኩል ሊትር የሆነ መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የእፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
ከመሥፈሪያው ሶስትአሥረኛ እጅ
“ሶስት አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሶስቱ ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“ስድስት ሊትር”ወይም “የእፍ መሥፈሪያሶስት አሥረኛ”(ስድስት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“የእፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል፡፡ይሄ ሊደገምም ይችላል፡፡“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው፡፡“አራት ተኩል ሊትር የሆነ መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የእፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 28:29
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው፡፡
ከመሥፈሪያው አንድ አሥረኛ እጅ
“አንድ አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች አንዱ ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“ሁለት ሊትር”ወይም “ከመሥፈሪያው አንድ አሥረኛ እጅ”(ሁለት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እናንተ በዘይት የምትለውሱት መልካም ዱቄት” (ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
መሥዋዕትን ማቅረብ
“መሥዋዕት ማቅረብ”የሚለው ሐረግ “መሰዋት”በሚለው ሥም ሊገለፅ ይችላል፡፡ (አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
የእነርሱን የመጠጥ ቁርባን
“የእነርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እያንዳንዱ እንስሳ በሚሰዋበት ወቅት አብረው መቅረብ የሚገባቸውን የመጠጥ ቁርባኖችን ነው፡፡“ከእነርሱ ጋር አብረው የሚቀርቡት የመጠጥ ቁርባኖች”ወይም “የሚያጅቧቸው የመጠጥ ቁርባኖች”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 29


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Numbers 29:1
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው፡፡
በሰባተኛውም ወር ከወሩ በመጀመሪያ ቀን
ይሄ የሚያመለክተው የዕብራውያንን ሰባተኛ ወር ነው፡፡“በ1ኛው ወር በ7ኛው ወር”(የዕብራውያን ወራትንናተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ጉባዔ ይሁንላችሁ
“እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር በአንድነት ተሰብሰቡ” “የተቀደሰ ጉባዔ”የሚለው ቃል ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚሰበሰቡበት ሁኔታ ማለት ነው፡፡እግዚአብሔርን ማምለክ የተቀደሰ ክስተት ነው፡፡
እናንተ መለከቶችን የምትነፉበት ቀን ነው
“እናንተ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እዚህ ላይ የእሥራኤልን ሕዝብ የሚወክሉትን ካህናትን ነው፡፡ካህናት አምልኮው እንዲጀመር መለከትን ይነፋሉ ወይም ማህረሰቡ በአንድነት እንዲሰባሰብ ለማድረግ፡፡“ካህናት መለከቶችን የሚነፉበት ቀን ይሆናል”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 29:2
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው፡፡
Numbers 29:3
የእህል ቁርባናቸውን
ይሄ የሚያመለክተው እያንዳንዱ እንስሳ በሚሰዋበት ወቅት አብረው መቅረብ የሚገባቸውን የእህል ቁርባኖችን ነው፡፡“ከእነርሱ ጋር አብረው የሚቀርቡት የእህል ቁርባኖች”ወይም “የሚያጅቧቸው የእህል ቁርባኖች”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)
በዘይት የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በዘይት የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“የአፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል፡፡ይሄ ሊደገምም ይችላል፡፡“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው፡፡“አራት ተኩል ሊትር የሆነ መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የአፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
ከመሥፈሪያው ሶስት አሥረኛ እጅ
“ሶስት አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሶስቱ ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“ስድስት ሊትር”ወይም “የአፍ መሥፈሪያ ሶስት አሥረኛ”(ስድስት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
ከአሥር እጅ አንድ እጅ
“የአፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል፡፡ይሄ ሊደገምም ይችላል፡፡“ከአሥር እጅ አንድ እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ አንዱ ማለት ነው፡፡“ሁለት ሊትር መልካም የሆነ ዱቄት”ወይም “አንድ አሥረኛ የአፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
መሥዋዕትን ማቅረብ
“መሥዋዕት ማቅረብ”የሚለው ሐረግ “መሰዋት”በሚለው ሥም ሊገለፅ ይችላል፡፡ (አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 29:6
በሰባተኛው ወር..በወራቶቹ የመጀመሪያው ቀን
“በ7ኛ ወር…በእያንዳንዱ ወር በ1ኛው ቀን”“ወር”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዕብራውያንን የወር አቆጠጠር ነው፡፡(የዕብራውያን ወራትንናተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
በየወሩ፤የተለየ የሚቃጠል መሥዋዕት …ከእርሱ ጋር
“በየወሩ፤የተለየ የሚቃጠል መሥዋዕት …ከእርሱ ጋር” ይሄ በየወሩ መጀመሪያ ላይ የሚደረግ መሥዋዕት ነው፡
በዘወትርም ከሚቃጠለው መሥዋዕትና ከእህሉ ቁርባን፤ከመጠጡም ቁርባን
ይሄ የሚያመለክተው ካህናቱ በየዕለቱ መሥጠት የሚገባቸውን መሥዋዕት ነው፡፡ የእህል ቁርባኑና የመጠጡቁርባን ዘወትር ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡“ዘወትር የሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት አብረው ከሚቀርቡት ከእህል ቁርባንና ከመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)
የተደነገገውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ታደርጉታላችሁ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተግባራዊ ታደርጉታላችሁ”ወይም “እግዚአብሔር ያዘዘውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ታደርጉታላችሁ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእግዚአብሔር በእሣት የሚቀርብ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር ያቃጠላችሁት ቁርባን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 29:7
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው፡፡
በሰባተኛው ወር..በወራቶቹ የመጀመሪያው ቀን
“በ7ኛ ወር…በእያንዳንዱ ወር በ1ኛው ቀን” “ወር”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዕብራውያንን የወር አቆጠጠር ነው፡፡(የዕብራውያን ወራትንናተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ጉባዔ ይሁንላችሁ
“እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር በአንድነት ተሰብሰቡ” “የተቀደሰ ጉባዔ”የሚለው ቃል ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚሰበሰቡበት ሁኔታ ማለት ነው፡፡እግዚአብሔርን ማምለክ የተቀደሰ ክስተት ነው፡፡
Numbers 29:9
በዘይት የተለወሰ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በዘይት የለወሳችሁት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከመሥፈሪያው ሶስት አሥረኛ እጅ
“ሶስት አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሶስቱ ማለት ነው፡፡ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል፡፡“ስድስት ሊትር”ወይም “የአፍ መሥፈሪያ ሶስት አሥረኛ”(ስድስት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“የአፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል፡፡ይሄ ሊደገምም ይችላል፡፡“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው፡፡“አራት ተኩል ሊትር የሆነ መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የአፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
ከአሥር እጅ አንድ እጅ
“የአፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል፡፡ይሄ ሊደገምም ይችላል፡፡“ከአሥር እጅ አንድ እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ አንዱ ማለት ነው፡፡“ሁለት ሊትር መልካም የሆነ ዱቄት”ወይም “አንድ አሥረኛ የአፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
መሥዋዕትን ማቅረብ
“መሥዋዕት ማቅረብ”የሚለው ሐረግ “መሰዋት”በሚለው ሥም ሊገለፅ ይችላል፡፡ (አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት፡፡የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት፡፡“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 29:12
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው፡፡
በሰባተኛውም ወር..በአስራ አምስተኛው ቀን
“በ7ኛ ወር…በ15ኛው ቀን” “ወር”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዕብራውያንን የወር አቆጠጠር ነው፡፡(የዕብራውያን ወራትንናተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን ለማክበር የተቀደሰ ጉባዔ ይሁንላችሁ
“እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር በአንድነት ተሰብሰቡ” “የተቀደሰ ጉባዔ”የሚለው ቃል ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚሰበሰቡበት ሥርዓት

ማለት ነው።እግዚአብሔርን ማምለክ የተቀደሰ ሁኔታ ነው።
በዓሉን ለእርሱ ልትጠብቁት ይገባል
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።“መጠበቅ”የሚለው ቃል መከታተል ወይም ማክበር ማለት ነው።“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።“በዓሉን ለእግዚአብሔር መጠበቅ ይኖርባችኋል”ወይም “በዐሉን ለእግዚአብሔር ልታከብሩት ይገባል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእሳት የሚደረግ መሥዋዕት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በመሠዊያ ላይ ልታቃጥሉት ይገባል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
አሥራ አራት ወይፈኖች፤ሁለት አውራ በጎች፤አሥራ አራት የአንድ ዓመት ተባት ጠቦቶች
“14 ወይፈኖች፤2 አውራ በጎች፤14 የአንድ ዓመት ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 29:14
በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዘይት የለወሳችሁት መልካም ዱቄት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከመሥፈሪያው ሶስት አሥረኛ እጅ
“ሶስት አሥረኛ”ማለት አሥር እኩል ከሆኑ ክፍሎች ሶስቱ ማለት ነው።ይሄ ዘመናዊ በሆነ መለኪያ ሊፃፍ ይችላል።“ስድስት ሊትር”ወይም “የኢፍ መሥፈሪያ ሶስት አሥረኛ”(ስድስት ሊትር ያህል ይሆናል)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
ከአሥር እጅ ሁለት እጅ
“የኢፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል።ይሄ ሊደገምም ይችላል።“ከአሥር እጅ ሁለት እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ ሁለቱ ማለት ነው።“አራት ተኩል ሊትር የሆነ መልካም ዱቄት”ወይም “ሁለት አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን፤ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
ከአሥር እጅ አንድ እጅ
“የኢፍ መሥፈሪያ መልካም ዱቄት”የሚለው ቃል በበፊቱ ሐረግ ግልፅ ተደርጓል።ይሄ ሊደገምም ይችላል።“ከአሥር እጅ አንድ እጅ”ማለት እኩል ከሆኑ አሥር ክፍሎች ውስጥ አንዱ ማለት ነው።“ሁለት ሊትር መልካም የሆነ ዱቄት”ወይም “አንድ አሥረኛ የኢፍ መሥፈሪያ”(4.5 ያህል የሚሆን)(ክፍልፋዮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ሚዛን የሚለውን ይመልከቱ)
መሥዋዕትን ማቅረብ
“መሥዋዕት ማቅረብ”የሚለው ሐረግ “መሰዋት”በሚለው ሥም ሊገለፅ ይችላል። (አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባኑና የመጠጥ ቁርባኑ ዘወትር ከሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።
Numbers 29:17
በጉባዔው በሁለተኛው ቀን
“በበዓሉ 2ተኛ ቀን” እዚህ ላይ “ጉባዔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በበዓሉ ወቅት ያሉትን ሣምንታት ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
አሥራ አራት ወይፈኖች፤ሁለት አውራ በጎች፤አሥራ አራት የአንድ ዓመት ተባት ጠቦቶች
“14 ወይፈኖች፤2 አውራ በጎች፤14 የአንድ ዓመት ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በታዘዙት መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 29:20
በጉባዔው በሶስተኛው ቀን
“በበዓሉ 3ተኛ ቀን” እዚህ ላይ “ጉባዔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በበዓሉ ወቅት ያሉትን ሣምንታት ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
አሥራ አንድ ወይፈኖች፤ሁለት አውራ በጎች፤አሥራ አራት የአንድ ዓመት ተባት ጠቦቶች
“11 ወይፈኖች፤2 አውራ በጎች፤14 የአንድ ዓመት ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በታዘዙት መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 29:23
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው።
በጉባዔው በአራተኛው ቀን
“በበዓሉ 4ተኛ ቀን” እዚህ ላይ “ጉባዔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በበዓሉ ወቅት ያሉትን ሣምንታት ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
አሥራ አራት ተባት ጠቦቶች
“14 ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በታዘዙት መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 29:26
በጉባዔው በአምስተኛው ቀን
“በበዓሉ 5ተኛ ቀን” እዚህ ላይ “ጉባዔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በበዓሉ ወቅት ያሉትን ሣምንታት ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
አሥራ አራት ተባት ጠቦቶች
“14 ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በታዘዙት መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 29:29
በጉባዔው በስድስተኛው ቀን
“በበዓሉ 6ተኛ ቀን” እዚህ ላይ “ጉባዔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በበዓሉ ወቅት ያሉትን ሣምንታት ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
አሥራ አራት ተባት ጠቦቶች
“14 ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በታዘዙት መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት።የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት።“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 29:32
በጉባዔው በሰባተኛው ቀን
“በበዓሉ 7ተኛ ቀን” እዚህ ላይ “ጉባዔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በበዓሉ ወቅት ያሉትን ሣምንታት ነው።(ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አሥራ አራት ተባት ጠቦቶች
“14 ተባት ጠቦቶች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በትዕዛዙ መሠረት
“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”
ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት፡፡የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት፡፡“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 29:35
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ነገር እግዚአብሔር መንገሩን እንደቀጠለ ነው፡፡
በስምንተኛውም ቀን
“ስምንተኛው”የሚለው ቃል ስምንት ለሚለው ተከታታይ ቁጥር ነው፡፡ (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
ሌላ የተቀደሰ ጉባዔ ይሁንላችሁ
“እግዚአብሔርን ለማምለክ እንደገና ተሰብሰቡ”ይሄ ከመጀመሪው ቀን በዓል ጋር የሚመሳሰል ሌላ ጉባዔ ነው፡፡
በእሣት የሚደረግ መሥዋዕት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በመሠዊያው ላይ ማቃጠል ይኖርባችኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

Numbers 29:37
የእህል ቁርባናቸውና የመጠጥ ቁርባናቸው
እነዚህ መሥዋዕቶች መቅረብ የሚኖርባቸው ከወይፈን፤ከበግ ጠቦትና ከአውራ በግ ጋር ነበር፡፡”የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)
በታዘዙት መሠረት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእህሉ ቁርባንና ከመጠጡ ቁርባን
የእህሉ ቁርባን ከሚቃጠለው ቁርባን ጋር መቅረብ ነበረበት፡፡የመጠጥ ቁርባኑ ከኃጢአት መሥዋዕቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕቱ ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት፡፡“አብረው ከሚቀርቡት የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ጋር”(ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 29:39
የምታቀርቧቸው ነገሮች እነዚህ ናቸው
“የምታቀርቧቸው መሥዋዕቶች እነዚህ ናቸው”
በተቆረጠላቸው ቀን የሚደረጉ በዓላት
“በዕቅድ የተያዙ በዓላት”እነዚህ በዓላት በተያዘላቸው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት በቋሚነት የሚከናወኑ ናቸው፡፡“በተቆረጠላቸው”ማለት“በተመደበላቸው”ወይም“አስቀድሞ በተወሰነላቸው”ጊዜ ማለት ነው፡፡

---

## Chapter 30

Numbers 30:1
ሰው ለእግዚአብሔር ስእለት ቢሳል ወይም ራሱ በመሐላ ቢያስር
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በጋራ እንዲቀርቡ የተደረጉት ስለ ስእለትና ስለ መሐላ አፅንኦት ለመስጠት ነው፡፡ (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
ራሱ በመሐላ ቢያስር
ሙሴ እዚህ ላይ የሚናገረው አንድ ሰው አንድ ነገር ለማድረግ ቃል የመግባቱን ጉዳይ አስመልክቶ ቢሆንም የሚገባው ቃል ቁሣቁስ ይመስል ራሱ ላይ እንደሚያስረው ዓይነት አድርጎ ያቀርበዋል፡፡“አንድ ነገር ለመፈፀም ራስን መሥጠት”ወይም “አንድን ነገር ለመፈፀም ቃል መግባት” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቃሉን አይስበር፤ከአፉ እንደወጣው ሁሉ ያድርግ
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በጋራ እንዲቀርቡ የተደረጉት የገባውን ቃል ተግባራዊ ማድረግ እንደሚኖርበት አፅንኦት ለመስጠት ነው፡፡(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
ቃሉን አይስበር
“ቃሉን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰውዬውን መሐላና ቃል ኪዳን መግባት ነው፡፡ሙሴ እዚህን ነገሮች ተግባራዊ አለማድረግን ልክ አንድን ዕቃ ከመስበር ጋር አመሳስሎ ነው የሚናገረው፡፡(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ከአፉ እንደወጣው ሁሉ
እዚህ ላይ“አፍ”የሚለው ቃል ሰውዬው የሚናገረውን ነገር ለመግለፅ የዋለ ነው፡፡“አደርገዋለሁ የሚለውን ነገር ሁሉ ማድረግ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 30:3
ራሷን በስእለት ብታስር
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የመግባቷን ጉዳይ ልክ ራሷን በአንድነገር እንደምታስረው ዓይነት አድርጎ ነው ያቀረበው፡፡“የገባቸውን ቃል ለመፈፀም ራሷን ሰጠች”ወይም “አንድ ነገር ለመፈፀም ቃል ገባች”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መሐላውና ቃል መግባቱ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ነው ያላቸው፡፡አፅንኦት የሚሰጠው የገባችውን ቃል በሚመለከት ነው፡፡“መሐላው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ራሷን ባሰረችበት
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባቸውን ነገር ለመፈፀም ስትል የምታደርገውን መሠጠት ልክ ከሰውነቷጋር እንዳሰረችው ቁሣቁስ አድርጎ ነው የሚያቀርበው፡፡“የገባችውን ቃል ለመፈፀም ራሷን ሰጠች”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ብታጥፍ
“ያለችውን ነገር ብትሰረዘው”
ስእለትዋ ሁሉ ይፀናል..መሐላ ሁሉ ይፀናል
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን መሐላዋን ሁሉ መጠበቅ እንዳለባት አፅነዖት የሚሰጥ ነው፡፡(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
ይፀናል
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን መሐላዋ የፀና እንደሆነና ተግባራዊ ማድረግ እንደሚጠበቅባት የሚያስረዳ ነው፡፡“ተግባራዊ እንድታደርገው ትገደዳለች”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 30:5
መሐላዋና ቃል መግባቷ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በጣም የተመሳሰለ ትርጉም ነው ያላቸው፡፡ቃል የገባቸውን ነገር አጥብቀው የሚያሳስቡ ናቸው፡፡“መሐላዋን”(ሁለት ተመሳሳይ የሆነ ገፅታ ያላቸው የሚለውን ይመልክቱ)
ራስዋ ላይ ያደረገችው
እዚህ ላይ ሴትዬዋ መሐላዋን ለመፈፀም ራሷን መሥጠቷን ልክ መሐላውን ሰውነቷ ላይ እንደምታደርገው ልብስ ተደርጎ ተገልጿል፡፡“ራሷን የሰጠችበት”ወይም “ቃል የገባችው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይፀናል
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን መሐላዋ የፀና እንደሆነና ተግባራዊ ማድረግ እንደሚጠበቅባት የሚያስረዳ ነው፡፡ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 30፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡“ተግባራዊ እንድታደርገው ትገደዳለች”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 30:6
በተረጋጋ መንፈስ ውስጥ ሆና ራስዋን ያሰረችበት መሐላ
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባቸውን ነገር ለመፈፀም ስትል የምታደርገውን መሠጠት ልክ ከሰውነቷጋር እንዳሰረችው ቁሣቁስ አድርጎ ነው የሚያቀርበው፡፡“ ረጋ ባለ መንፈስ ቃል የገባችውን ነገር ለመፈፀም የምታደርገው መሠጠት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዝም ቢላት
እዚህ ላይ የሴትዋን ቃል ዝም ማለቱን ልክ አንድ ባለሥልጣን በሥልጣኑ እንደሚከለክላት ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል፡፡(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የፀና አይሆንም
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን መሐላዋ የፀና እንደማይሆንና ተግባራዊ ማድረግ እንደማይጠበቅባት የሚያስረዳ ነው።ይህንን ሐረግ በዘኊልቁ 30፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡“ተግባራዊ እንድታደርገው አትገደድ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርም ይቅር ይላታል
ይሄ የሚያመለክተው መሐላዋን ባትፈፀምም እንኳን እግዚአብሔር ይቅር ያላት መሆኑን ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“መሐላዋን ባትፈፀምም እግዚአብሔር ይቅር ይላታል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በእነዚያ መሐላዎች ሥር ከሆነ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።መሐላዋ የፀና እንደማይሆንና ተግባራዊ ማድረግ እንደማይጠበቅባት የሚያስረዳ ነው።ይህንን ሐረግ በዘኊልቁ 30፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡“ተግባራዊ እንድታደርገው አትገደድ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በችኮላ
በአግባቡ ሳይታሰብ የሚደረግ ነገር።
እነዚያ ግዴታዎች
“ግዴታዎች”የሚለው ቃል “ማስገደድ”በሚለው ሥም ሊገለፅ ይችላል፡፡“ራሰዋን ግዴታዎች ውስጥ ያስገባችባቸው ነገሮች”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 30:8
ያደረገችው መሐላ…በችኮላ የተናገረችው ንግግር
“ያደረገችው መሐላ…ማለትም በችኮላ የተናገረችው ንግግር” እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች የሚያመለክቱት አንድን ነገር ነው።ሁለተኛው ሐረግ ሴትዬዋ ያደረገችውን መሐላ የሚገልፅ ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
የአንደበቷ ችኩል አነጋገር
“ችኩል አነጋገር”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በችኮላ የገባችውን የተስፋ ቃል ነው።እዚህ ላይ “አንደበቷ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሷን ሴትዬዋን ነው። አንደበቷ ከምትናገረው ነገር ጋር የተያያዘ በመሆኑ “አንደበቷ”በሚለው ቃል ተወክላለች፡፡“በችኮላ የተናገረቻቸው ነገሮች” ወይም“በችኮላ ቃል መግባቷ”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)
ራሰዋን ያሰረችበትን
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባቸውን ነገር ለመፈፀም ስትል የምታደርገውን መሠጠት ልክ ከሰውነቷ ጋር እንዳሰረችው ቁሣቁስ አድርጎ ነው የሚያቀርበው፡፡“ ረጋ ባለ መንፈስ ቃል የገባችውን ነገር ለመፈፀም የምታደርገው መሠጠት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ነፃ ያወጣታል
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባችውን ነገር ባትፈፅምም እግዚአብሔር ይቅር እንደሚላት ለመግለፅ ከታሰረችበት ነገር እንደምትለቀቅ ዓይነት አድርጎ አቅርቦታል። የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር ይቅር ይላታል” “የገባችውን ቃል ባትፈፅምም እግዚአብሔር ይቅር ይላታል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ))
Numbers 30:9
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እግዚአብሔር ያዘዘውን ነገር ለነገድ መሪዎች መናገሩን ይቀጥላል።
የተፋታች ሴት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“አንድ ሰው የፈታት ሴት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ራሰዋን ያሰረችበትን
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባቸውን ነገር ለመፈፀም ስትል የምታደርገውን መሠጠት ልክ ከሰውነቷ ጋር እንዳሰረችው ቁሣቁስ አድርጎ ነው የሚያቀርበው፡፡“ቃል የገባችውን ነገር ለመፈፀም የምታደርገው መሠጠት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሷ ላይ የፀና ይሆናል
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን መሐላዋ የፀና እንደሆነና ተግባራዊ ማድረግ እንደሚጠበቅባት የሚያስረዳ ነው።ይህንን ሐረግ በዘኊልቁ 30፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡“ተግባራዊ እንድታደርገው ትገደዳለች”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሴት በባሏ ቤት ውስጥ ሳለች ብትሳል
ይሄ የሚመለከተው ያገቡ ሴቶችን ነው።የዚህን ሃሣብ የበለጠ ልታብራሩት ትችላላችሁ፡፡“ያገባች ሴት ስእለት ብትሳል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያ በኋላ መሐላዋ ሁሉ የፀና ይሆናል…መተግበሩ ግዴታ ይሆናል
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡“መተግበሩ ግዴታ ይሆናል”የሚለው ቃል የሚፀናና እርሱን ለመፈፀም ትገደዳለች ማለት ነውየዚህን ተመሳሳይ ሐረግ በኦሪት ዘኊልቁ 30፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡“ከዚያም መሐላዋን ሁሉ ተግበራዊ ማድረግ ይኖርባታል….መፈፀም ይኖርባታል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስእለትዋ ይፀናል…ራስዋንም ያሰረችበት መሐላ ሁሉ ይፀናል
በመሠረቱ እነዚህ ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ተደጋገመው የቀረቡት ለጉዳዩ አፅንዖት ለመሥጠት ሲሆን ተቀናጅተውም ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡“ስእለቷና መሐላዋ ሁሉ የፀና መሆን ይኖርበታል” (ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 30:12
ከከንፈሯ የወጣ ማንኛውም ነገር
እዚህ ላይ ሴትዬዋ የተናገረችው ንግግር ከከንፈሯ እንደወጣ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል፡፡“ከዚያ በኋላ የተናገረችው ነገር ሁሉ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የፀና አይሆንም
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን መሐላዋ የፀና እንደማይሆንና ተግባራዊ ማድረግ እንደማይጠበቅባት የሚያስረዳ ነው።ይህንን ሐረግ በዘኊልቁ 30፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡“ተግባራዊ እንድታደርገው አትገደድ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ነፃ ያወጣታል
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባችውን ነገር ባትፈፅምም እግዚአብሔር ይቅር እንደሚላት ለመግለፅ ከታሰረችበት ነገር እንደምትለቀቅ ዓይነት አድርጎ አቅርቦታል። የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር ይቅር ይላታል” “የገባችውን ቃል ባትፈፅምም እግዚአብሔር ይቅር ይላታል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውንና (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ))
Numbers 30:13
ስእለትዋን ሁሉ …መሐላዋን ሁሉ በልዋ ያጸናዋል፤ባልዋም ከንቱ ያደርገዋል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የአንዲት ሴት ባል ራሰዋን ያሰረችበትን ማንኛውንም ነገር ማለትም ስእለት ወይም መሐላ ማጽናት ወይም ማፍረስ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
የታሰረችበትን
እዚህ ላይ ሙሴ አንዲት ሴት ቃል የገባችውን ነገር ለመፈፀም ስትል የምታደርገውን መሠጠት ልክ ከሰውነቷ ጋር እንዳሰረችው ቁሣቁስ አድርጎ ነው የሚያቀርበው፡፡“ቃል የገባችውን ነገር ለመፈፀም የምታደርገው መሠጠት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አሳሪ የሆኑ ቃል ኪዳኖች
ሙሴ አንዲት ሴት የምትገባቸው ቃል ኪዳኖች እካሏን እንደሚያስሩ ነገሮች አድርጎ አቅርቧቸዋል፡፡“ግዴታዎች” “ቃል ኪዳኖች”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዝም በሏታልና
ግልፅ የሆነውን ይህንን መረጃ የበለጠ ልታብራሩት ትችላላችሁ፡፡“ጉዳዮቹን አስመልክቶ ምንም ነገር ስላልተናገረ”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 30:15
ስለ ኃጢአቷ ኃላፊነቱን እርሱ የሚወስድ ይሆናል
ስእለቷን የማትፈፀም ከሆነ በእርሷ ምትክ ኃጢአቷን ይሸከማል ማለት ነው።የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ሃሣብ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“ስእለቷን ባትፈፀም በኃጢአቷ ጥፋተኛ አትባልም፡፡እርሱ ግን በእርሷ ምትክ ጥፋተኛ የሚሆን ይሆናል፡፡”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 31
Numbers 31:1
ስለ እሥራኤል ልጆች በቀል ምድያማውያንን ተበቀል
ምድያማውያን እሥራኤላውያን ጣኦት እንዲያመልኩ በመገፋፋታቸው ምክኒያት እግዚአብሔር ሊቀጣቸው ነው፡፡
ከዚያም በኋላ ትሞታለህ ወደ ወገኖችህም ትከማቻለህ
በመሠረቱ እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው፡፡ይሄ ጨዋ በሆነ አነገገር ቡሴ የመሞቻው ጊዜ መሆኑንና መንፈሱ አባቶቹ ወዳሉበት የሚሄድ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ (ተመሳሳይነት የሚለውንና ሥርዓት የሌለውን አነጋገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 31:3
ከእናንተ መካከል ሰዎች ለጦርነት ይሰለፉ፡፡
“ከሰዎችህ መካከል ለተወሰኑት ሰዎች መሣሪያ አስታጥቃቸው”
ስለ እግዚአብሔር በቀል ምድያማውያንን ይበቀሉ
“ሄደህ ከምድያማውያን ጋር በመዋጋት ላደረጉት ነገር ቅጣትን ሥጣቸው”
አንድ ሺህ…ሁለት ሺህ
“1000…2000”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የእሥራኤል አንድ ሺህ ሰዎች
“ከእሥራኤል አንድ ሺህ ወንዶች”
ከየነገዱ አንድ ሺህ ሰው ለጦርነት የሚሰለፉ ሰዎችተሰጡ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ከእያንዳንዱ ነገድ 1000 ሰዎች ለጦርነት ተላኩ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አሥራ ሁለት ሺህ ለጦርነት የተዘጋጁ ሰዎች
የሌዊን ነገድ ጨምሮ 12ቱም ነገዶች ሰዎችን ላኩ፡፡እያንዳንዱ ነገድ 1000 ለጦርነት የሚሰለፉ ሰዎችን ላከ፡፡(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 31:6
ኤዊ…ሮቆም…ሱር…ሑር…ሪባ
እነዚህ የምድያማውያን ነገሥታት ስሞች ናቸው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
የቢኦር ልጅ በለዓም
ቢኦር የበለዓም አባት ነበር፡፡ይህንን በዘኍልቁ 22፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡
Numbers 31:9
በዘበዙ
“የምድያማውያንን ንብረቶች የራሳችው አደረጉት”
ከተሞቻቸውን ሁሉ ሰፈሮቻቸውንም ሁሉ በእሣት አቃጠሉ
“እሥራኤላውያን ሠራዊቶች ምድያማውያን የሚኖሩባቸውን የምድያማውያንን ከተሞችና የምድያማውያንን ሠፈሮች ሁሉ አጠፉ”
Numbers 31:11
ወሰዱ
“የእሥራኤል ሠራዊት ወሰደው”
ብዝበዛው
ይሄ የሚያመለክተው ቁሳቁሶቹን ሁሉ በመውሰዳቸው ምክኒያት ምድያማውያንን ከሞት መታደጋቸውን ነው፡፡
ሜዳ
ሠፊ ሆኖ ለጥ ያለ መሬት፡፡
Numbers 31:13
ሻለቆችና የመቶ አለቆች
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/እነዚህ ቁጥሮች የሚያመለክቱት ሻለቆቹ ወይም የመቶ አለቆዎቹ የሚመሯቸው በሥራቸው የሚገኙ ሠራዊቶች ትክክለኛ ቁጥር ነው፡፡“1000 ሰራዊት የሚመሩ ሻለቃዎችና 100 ሠራዊት የሚመሩ መቶ አለቃዎች”ወይም 2/“ሺዎችና መቶዎች የሚሉት ቃላት የታላላቅና የአነስተኛ የጦር ክፍሎች ስያሜዎች ናቸው እንጂ የሠራዊቱን ትክክለኛ ቁጥር የሚያመለክቱ አይደሉም” “ሠፊ የጦር ክፍል ያላቸው ሻለቃዎችና አነስተኛ የጦር ክፍል ያላቸው መቶ አለቃዎች””(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በውኑ ሴቶችን ሁሉ አላዳናችኋቸውንም?
ማን ሊድን እንደሚገባና እንደፈሚቀድለት ሕጉ በግልፅ አስቀምጦታል፡፡ሠራዊቱ ግን ሕጉን በመፃረር ሰቶችንና ልጆችን በሕይወት እንዲኖሩ አድርገዋቸዋል፡፡ይሄ የሠራዊት መሪዎቹን ለመገሰፅ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 31:16
ተመልከቱ
ይሄ ቃል እዚህ ሥፍራ ላይ ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገው ከዚህ በመቀጠል የሚነገረውን ነገር ሕዝቡ በጥሞና እንዲያዳምጥ ታስቦ ነው፡፡“አዳምጡ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከወንድ ጋር የተኛ
“ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረገ”(ሥርዓት የሌለውን ነገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 31:18
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ለእሥራኤል የጦር መሪዎች በእግዚአብሔር ፊት ንፁሕ መሆንን በተመለከተ ይነግራቸዋል፡፡
ከወንድ ጋር ተኝተን አናውቅም
ይሄ የሚያመለክተው ድንግል ሴቶችን ነው፡፡(ሥርዓት የሌለውን ነገር በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
ሁላችሁም
ሙሴ እዚህ ላይ የሚናገረው የጦር አዛዦችን ብቻ ሣይሆን ማንኛውንም በጦርነቱ ላይ ተሣትፎ ያደረጉ ሰዎችን ሁሉ ነው፡፡
ራሣችሁን ማንፃት ይኖርባችኋል
ወደ ሠፈሩ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት በመንፈሣዊ ሕይወታቸው ዳግም ንፁሕ ሊሆኑ ይገባል፡፡
ከቁርበት የተዘጋጀውን ሁሉ፤ከፍየልም ጠጉር፤ከእንጨትም የተሠራውን ሁሉ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“አንድ ሰው ከቁርበትከፍየልም ጠጉር፤ከእንጨትም የሠራውን ሁሉ” (ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 31:21
አጠቃላይ መረጃ
አልዓዛር ከሠልፍ የመጡትን ሰዎች ከጦርነት መልስ በኋላ በሕጉ ሥርዓት መሠረት እንዴት ንፁህ መሆን እንደሚገባቸው ያስተምራቸዋል፡
ወርቁን፤ብሩን፤ናሱን፤ብረቱን፤ቆርቆሮውን፤አረሩን
በዚያን ወቅት ጥቅም ላይ ይውሉ የነበሩ ብረቶች፡፡
በእሣት ውስጥ ለማለፍ የሚችለውን
“የማይቃጠለውን”
በእሣት ውስጥ ታሳልፉታላችሁ
“እሣት ውስጥ አስቀምጡት”
የማንፃት ውኃ
ይሄ የሚያመለክተው አንድ ሰው ከኃጢአት ቁርባን የወሰደውን ውኃ ከአመድ ጋር የመደባለቁን ሁኔታ ነው፡፡(ኦሪት ዘኍልቁ 19፡17-19)
ከዚያ በኋላ ንፁህ ትሆናላችሁ
እነዚህ በሚከናወኑ ሥርዓቶች በእግዚአብሔር ፊት ንፁህ ሆኖ የመገኘት ልማዶች ናቸው፡፡
Numbers 31:25
የተማረኩትን ሁሉ ቁጠሩ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ወታደሮቹ የወሰዱትን ንብረት በሙሉ ቁጠሩ” (ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
የበዘበዛችሁት
ይሄ የሚያመለክተው እስራኤላውያን በጦርነት ውስጥ ከገደሏቸው ወይም ከማረኳቸው ሰዎች የወሰዷቸውን ንብረቶችን ነው፡፡
የማህበሩም አባቶች አለቆች
“የየነገዶቹ መሪዎች”
Numbers 31:28
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል፡፡
አጠቃላይ መረጃ
“እኔ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው፡፡
ከእነዚያም ከተዋጉት ወደ ሠልፍም ከወጡት ለእኔ ያመጡ ዘንድ ቀረጥጣል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡“ወታደሮቹ ከማረኳቸው ነገሮች ላይ ቀረጥ

በመጣል ለእኔ አምጣው።(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአምስት መቶ አንድ
“በየአምስት መቶው”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ከድርሻቸው
“ከወታደሮቹ ድርሻ”
ለእኔ ይሰጥ ዘንድ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እርሱ ለእኔ የሚሰጠውን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 31:30
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።
ከእሥራኤልም ሕዝብ ድርሻ
“የእሥራኤል ሕዝብ ከበዘበዘው ከግማሹ”
ከየሃምሳው
“ከየ50”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የሚጠብቁ
የመገናኛ ድንኳኑንና ለእግዚአብሔር የሚቀርቡትን መሥዋዕቶች በበላይነት የሚቆጣጠሩና የሚጠብቁ።
Numbers 31:32
አሁን
ይሄ ቃል ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገውበዋናነት በሚሰጠው ትምህርት ላይ የተወሰነ እረፍት እንዳለ ለማሣየት ነው።እዚህ ላይ ሙሴ ከተበዘበዙት ነገሮች ውስጥ ለወታደሮቹ፤ለሕዝቡና ለእግዚአብሔር ምን ያህል እንደተሰጠ ዝርዝራቸውን ያወጣል።
675,000 በጎች
“ስድስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ በጎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰባ ሁለት ሺህ በሬዎች፤ስድሳ ሺህ አህዮች፤ሠላሳ ሁለት ሺህ ሴቶች
“72,000 በሬዎች፤60 ሺህ አህዮችና 32,000 ሴቶች” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ወንድ የማያውቁ ሴቶች
ይሄ የሚያመለክተው ድንግል የሆኑ ሴቶችን ነው።(ሥርዓት የሌለውን ቃል በመልካም ነገር መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 31:36
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ከተበዘበዙት ነገሮች ውስጥ ለወታደሮቹ የሚሰጠውንና ተቀርጦ ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ዝርዝር ማውጣት ይጀምራል።(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ይሄ በድርጊት መበዝመቻ ለነበሩ ሰዎች ድርሻ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለወታደሮቹ ከበጎቹ የሚደርሳቸው ድርሻ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
337,000 በጎች
“ሶስት መቶ ሰላሣ ሰባት ሺህ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
675 ነበር
“ስድስት መቶ ሰባ አምስት”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰላሣ ስድስት ሺህ
“36,000”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰባ ሁለት
72(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 31:39
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ከተበዘበዙት ነገሮች ውስጥ ለወታደሮቹ የሚሰጠውንና ተቀርጦ ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ዝርዝር ማውጣት ይጀምራል።(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
30,500 ነበሩ
“ሰላሣ ሺህ አምስት መቶ ነበሩ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ስድሳ አንድ
61(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
አስራ ስድስት ሺህ
16,000(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰላሣ ሁለት
32 (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ለእግዚአብሔር ለግብርነት የሚሰጡ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለእግዚአብሔር ቁርባን የሚሆነውን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 31:42
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ከተበዘበዙት ነገሮች ውስጥ ለወታደሮቹ የሚሰጠውንና ተቀርጦ ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ዝርዝር ማውጣት ይጀምራል።(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
337,500 በጎች
“ሶስት መቶ ሰላሣ ሰባት ሺህ አምስት መቶ በጎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰላሣ ስድስት ሺህ በሬዎች
“ሰላሣ ስድስት ሺህ በሬዎች”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
አሥራ ስድስት ሺህ ሴቶች
“16,000 ሴቶች”ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የተማረኩ ወንዶቹና ያገቡ ሴቶች በሙሉ በሕይወት እንዳይኖሩ ተደርጓል።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 31:47
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ ከተበዘበዙት ነገሮች ውስጥ ለወታደሮቹ የሚሰጠውንና ተቀርጦ ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ዝርዝር ማውጣት ይጀምራል።(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ
በሕዝቡ ላይ የተጣለው ግብር በወታደሮቹ ላይ ከተጣለው ግብር ይልቅ ከፍ ያለ ነበር።
Numbers 31:48
ሻለቆችና የመቶ አለቆች
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/እነዚህ ቁጥሮች የሚያመለክቱት ሻለቆቹ ወይም የመቶ አለቆዎቹ የሚመሯቸው በሥራቸው የሚገኙ ሠራዊቶች ትክክለኛ ቁጥር ነው።“1000 ሰራዊት የሚመሩ ሻለቃዎችና 100 ሠራዊት የሚመሩ መቶ አለቃዎች”ወይም 2/ “ሺዎችና መቶዎች የሚሉት ቃላት የታላላቅና የአነስተኛ የጦር ክፍሎች ስያሜዎች ናቸው እንጂ የሠራዊቱን ትክክለኛ ቁጥር የሚያመለክቱ አይደሉም” “ሠፊ የጦር ክፍል ያላቸው ሻለቃዎችና አነስተኛ የጦር ክፍል ያላቸውመቶ አለቃዎች” ይህንንተመሳሳይ ሐረግ በዘኁልቁ 31:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ባሪያዎችህ ቆጥረናል
የሠራዊት አዛዦቹ ራሣቸውን “ባሪያዎችህ” እያሉ የጠሩት ከፍተኛ ሥልጣን ካለው ሰው ጋር ንግግር በሚደረግበት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውል ትህትና ያለበት አቀራረብ ስለሆነ ነው።
አንድ ሰው አልጎደለም
ይሄ በአዎንታዊ በሆነ አገላለፅ ሊገለፅ ይችላል።“ሁሉም ሰው እዚህ እንደሚገኝ እርግጠኞች ነን”(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 31:50
አጠቃላይ መረጃ
የሠራዊቱ አዛዦች ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላሉ።
የእግር አልቦ፤አምባር፤ቀለበት፤ጉትቻ፤ድሪ
እነዚህ ሰዎች የሚያደርጓቸው ጌጣጌጦች ናቸው።
በእግዚአብሔር ፊት ያስተሰርይልን ዘንድ
“ሕይወታችንን ስላዳነን እግዚአብሔርን እናመሰግን ዘንድ”
ወርቆቹንና በልዩ ልዩ የተሰራውን ዕቃ ሁሉ
“የወርቅ ዕቃዎችን ሁሉ”ወይም “የወርቅ ጌጣጌጦችን ሁሉ”
Numbers 31:52
ሻለቆችም የመቶ አለቆችም ለእግዚአብሔር የማንሣት ቁርባን ያቀረቡት ወርቅ ሁሉ አሥራ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሰቅል ይመዝናል
“የሻለቆችቹና የመቶ አለቆቹ ለእግዚአብሔር የሰጡት የወርቅ ሥጦታ ሁሉ የመዘነው…”
ሻለቆችና የመቶ አለቆች
ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/እነዚህ ቁጥሮች የሚያመለክቱት ሻለቆቹ ወይም

የመቶ አለቆዎቹ የሚመሯቸው በሥራቸው የሚገኙ ሠራዊቶች ትክክለኛ ቁጥር ነው፡፡“1000 ሰራዊት የሚመሩ ሻለቃዎችና 100 ሠራዊት የሚመሩ መቶ አለቃዎች”ወይም 2/ “ሺዎችና መቶዎች የሚሉት ቃላት የታላላቅና የአነስተኛ የጦር ክፍሎች ስያሜዎች ናቸው እንጂ የሠራዊቱን ትክክለኛ ቁጥር የሚያመለክቱ አይደሉም” “ሠፊ የጦር ክፍል ያላቸው ሻለቃዎችና አነስተኛ የጦር ክፍል ያላቸው መቶ አለቃዎች” ይህንንተመሳሳይ ሐረግ በዘኁልቁ 31፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

16,750

“አሥራ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰቅል

አንድ ሰቅል 11 ግራም ነው፡፡(መፅሐፍ ቅዱሣዊ ገንዘብ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት ለእሥራኤላውያን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ

ወርቆቹ መታሰቢያ የሚሆኑት እግዚአብሔር ድል የሰጣቸው መሆኑን ለማሳሰብ ነው፡፡በሌላ በኩል ደግሞ በምድያማውያን ላይ ሕዝቡ የበቀል እርምጃ የወሰደ መሆኑን እግዚአብሔር ያስበው ዘንድ ነው፡፡

---

## Chapter 32

### Numbers 32:1

አሁን

ይሄ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በዋናው የታሪክ ሂደት ላይ የተወሰነ እረፍት እንዳለ ለማሣየት ነው፡፡እዚህ ላይ ሙሴ ስለ ሮቤልና ስለ ጋድ ነገዶች ስለጀርባ ታሪካቸው መረጃን ይሰጣል፡፡(የኋላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አጣሮት፤ዲቦን፤ኢያዜር፤ነምራ፤ሐሴቦን፤ኤልያሊ፤ሴባማ፤ናባው፤ባያን

እነዚህ የከተማዎቹ ስሞች ናቸው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

### Numbers 32:4

አጠቃላይ መረጃ

ከሮቤልና ከጋድ የመጡ ሰዎች ለሙሴ፤ለአልዓዛርና ለሌሎቹ መሪዎች መናገራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

እግዚአብሔር በእሥራኤል ማህበር ፊት የመታው ምድር

በዚያ ምድር የነበሩትን ሰዎች ድል እንዲያደርጓቸው እግዚአብሔር ችሎታውን የሰጣቸው ቢሆንም ልክ እግዚአብሔር ራሱ በእሥራኤላውያን ፊት ወጥቶ ጥቃት እንዳደረሰ ዓይነት ተድርጎ ተገልጿል፡፡“በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ድል እንደንነሳቸው እግዚአብሔር ችሎታውን ሰጠን” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ባሪያዎችህ

የሮቤልና የጋድ ሰዎች በዚህ መልክ ራሣቸውን የሚጠሩት ከፍ ያለ ሥልጣን ላለው ሰው አክበሮትን ለመሥጠት ነው፡፡

በዓይኖችህ ዘንድ ሞገስን አግኝተን እንደሆነ

እዚህ ላይ“ሞገስ” የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ተቀባይነትን ማግኘት ወይም መሪዎቹ በእነርሱ ደስ መሰኘታቸውን የሚያሣይ ነው፡፡እዚህ ላይ “ዓይኖች”የሚለው ቃል እይታ ለሚለው ቃል ገላጭ ሲሆን እይታ ደግሞ የማመዛዘን ችሎታውን የሚያመለክት ምሣሌያዊ አነጋገር ነው፡፡“በአንተ ዘንድ ሞገስን አግኝተን ከሆነ”ወይም “በእኛ ደስ የተሰኘህ ከሆነ”(ፈሊጣዊ አነጋገር፤ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃልንና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ርስት አድርገህ ስጠን

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ይህንን ምድር ለእኛ ስጠን”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ዮርዳኖስም ማዶ አታሻግረን

የፈለጉት ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ተሻግረው መሬት መጠየቅ ሣይሆን ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ በኩል የሚገኘውን ሥፍራ ነበር የፈለጉት፡፡“በዚያኛ በኩል ለእኛ መሬትን ለመሥጠት ብለህ የዮርዳኖስ ወንዝን እንድሻገር አታድርገን”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

### Numbers 32:6

ወንድሞቻችሁ ወደ ጦርነት ሲሄዱ እናንተ እዚህ ትቀመጣላችሁን?

ሙሴ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ሮቤልንና ጋድን ለመገሰፅ ብሎ ነው፡፡“ወንድሞቻችሁ ጦርነት ላይ እያሉ እናንተ በዚህ ምድር መቀመጣችሁ ተገቢ አይደለም”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የሰጣቸውን .....የሰውን ልብ ለምን ታደክማላችሁ?

ሙሴ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ከሮቤልና ከጋድ ሃሣብ ሕዝቡን ለመከላከል ነው፡፡“እግዚአብሔር የሰጣቸውን ..... የሰውን ልብ አታድክሙ”ወይም “ድርጊታችሁ የሰዎችን ልብ ሊያደክሙ ይችላሉ....እግዚአብሔር የሰጣቸውን”(ምላሽ የማያሻው ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤልን ሕዝብ ልብ ከመሄድ ታደክሙታላችሁ

እዚህ ላይ“ልብ”የሚለው ቃል የሚወክለው ራሣቸው ሰዎቹን ሲሆን የሚያመለክተውም የስሜታቸው መሠረት የሆነውን ነገርነው፡፡“የእሥራኤል ሕዝብ እንዳይሄድ ተስፋ ታስቆርጡታላችሁ”ወይም “የእሥራኤል ሕዝብ እንዳይሄድ ምክኒያት ትሆናላችሁ”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

### Numbers 32:8

አጠቃላይ መረጃ

ሙሴ ለሮቤልና ለጋድ ሰዎች መናገሩን ይቀጥላል፡፡

የኤሽኮል ሸለቆ

ይሄ የቦታ ሥም ነው፡፡ይህንንበዘኁልቁ 13፡23 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱን አዩ

ይሄ የሚያመለክተው በምድሪቱ ውስጥ ያለውን ነገር መመልከታቸውን ነው፡፡“በምድሪቱ ውስጥ የሚገኙትን ጠንካራ ሰዎችና ከተማዎቹን ተመለከቱ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤልን ልጆች ልብ አደከሙ

እዚህ ላይ“ልብ”የሚለው ቃል የሚወክለው ራሣቸው ሰዎቹን ሲሆን የሚያመለክተው የስሜታቸው መሠረት የሆነውን ነው፡፡ይህንንበዘኁልቁ 32፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡“የእሥራኤልን ሕዝብ ተስፋ አስቆረጡ”(ነገርን በተለየ መንገድ መረዳት የሚለውን ይመልከቱ)

### Numbers 32:10

የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደ

x

### Numbers 32:13

የእግዚአብሔርም ቁጣ በእሥራኤል ላይ ነደደ

እግዚአብሔር መናደዱን ለመግለፅ ልክ እሣት መቀጣጠል ከመጀመር ጋር ተመሳስሎ ነው የተነገረው፡፡ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር በእሥራኤል ላይ በጣም ተናደደ”(ምሣሌያዊ አነጋገርና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

አርባ ዓመት

“40 ዓመት”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ትውልድ ሁሉ...ፊት እስኪጠፉ ድረስ

ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ትውልዱን ሁሉ አጠፋ...ፊት”ወይም “ትውልዱ ሁሉ...በእግዚአብሔር ፊት ጠፋ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ ክፉ ያደረጉትን

በአንድ ሰው ፊት ማለት ሰውዬው ሊያየው በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ መሆን ማለት ነው፡፡“በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ያደረገ”ወይም “የእግዚአብሔር ሕልውና ባለበት ክፉ ነገርን ያደረገ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአባቶቻችሁ ፋንታ ቆማችኋል

የሮቤልና የጋድ ሰዎች ልክ የአባቶቻቸውን ሥራ ማድረጋቸው አባቶቻቸው ባደረጉት ሥፍራ ላይ እንደቆሙ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል፡፡“እንደ አባቶቻችሁ ማድረግ ጀምራችኋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርን መዓት በእሥራኤል ላይ ትጨምሩ ዘንድ

ሰዎች እግዚአብሔር የበለጠ እየተናደደ እንዲሄድ የሚያደርጉት ድርጊት ልክ ሰዎች በእሣቱ ላይ ነዳጅ እንደሚጨምሩ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል፡፡“እግዚአብሔር በእሥራኤል ላይ የበለጠ እንዲናደድ ምክኒያት መሆን”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህንን ሁሉ ሕዝብ

“ይሄ ሁሉ ሕዝብ”ወይም“ይሄ ሁሉ ትውልድ”

### Numbers 32:16


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንዘጋጃለን፤እንታጠቃለን
“መሣሪያችንን ታጥቀን ዝግጁዎች እንሆናለን”ወይም “በጦርነት ለመሣተፍ ዝግጁ እንሆናለን”
በተመሸጉ ከተሞች
“ደህንነታቸው በተጠበቁ ከተማዎች ውስጥ”
Numbers 32:18
አጠቃላይ መረጃ
ሮቤልና ጋድ መናገራቸውን እንቀጠሉ ነው።
ርስቱን ወስዷል
ሰዎች እንደ ቋሚ ንብረት የሚቀበሉት ንብረት ልክ እንደሚወስዱት ንብረት ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“የሚደርሰውን የመሬት ድርሻ በንብረትነት ወስዷል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 32:20
ራሣችሁን ብታስታጥቁ
“የጦር መሣሪያችሁን ብትወስዱ”
በእግዚአብሔር ፊት
የዚህ ትርጉም እግዚአብሔር በጦርነቱ ወቅት በፊታቸው በመሄድ ጠላቶቻቸውን ድል እንዲያደርጉ ጉልበትን በመሥጠት ምድራቸውን እንዲወርሱ ያደርጋል ማለት ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጠላቶቹን ከፊቱ እስኪያሳድድ ድረስ
እግዚአብሔር ጠላቶቹን ከፊቱ እስኪያሳድድ ድረስ።እዚህ ላይ የሚገኙት ተውላጠ ስሞች ሁሉ የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን ነው።እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ድል እንዲያደርጉ ያገዛቸውን ሁኔታ ልክ እግዚአበሔርየእነርሱን ጦርነት እየተዋጋ እንዳለ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል።“እግዚአብሔር ሠራዊቶቻችን ድል እንዲደርጓቸውና ከእርሱ ፊት እስኪዲያሳድዷቸው ድረስ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሪቱም በፊቱ ድል እስክትሆን ድረስ
እዚህ ላይ “ምድሪቱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኑሯቸውን በዚያ ያደረጉትን ሰዎች ነው።ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እሥራኤላውያን በዚያ ምድር የሚኖሩትን ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ድል አደረጓቸው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃልና ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ልትመለሱ ትችሉ ይሆናል
ይሄ የሚያመለክተው ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ በኩል ወደሚገኘው ሥፍራ የሚመለሱ መሆናቸውን ነው።“ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ በኩል ወደሚገኘው ሥፍራ ልትመለሱ ትችሉ ይሆናል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በእግዚአብሔርም ፊት በእሥራኤልም ዘንድ ንፁህ ትሆናላችሁ
ለዚህ ተስማሚ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/“የሚጠበቅባችሁን ግዴታ በእግዚአብሔርና በእራኤል ፊት ፈፅማችኋል”ወይም 2/“እግዚአብሔርም ሆነ የእሥራኤል ሕዝብ እናንተን የሚወቅሱበት ነገር የላቸውም”
Numbers 32:23
ኃጢአታእሁ እንዲያገኛችሁ እወቁ
ሙሴ በዚህ ሥፍራ ላይ ስለ ኃጢአት የሚናገረው ልክ አንድ ግለሰብ ጥፋተኛ የሆነን ሰው እንደሚኮንንዓይነት ነው።ይሄ ማለት ሰዎች በሰሩት ኃጢአት ልክ ከመቀጣት አይድኑም ማለት ነው።“እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችሁ እንደሚቀጣችሁ እርግጠኛ ሁኑ”(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)
ባሪያዎችህ
የጋድና የሮቤል ሰዎች ራሣቸውን “ባሪያዎችህ”እያሉ ነው የሚጠሩት።ይሄ ከፍ ያለ ሥልጣን ላለው ሰው አክበሮት ለመሥጠት የሚውል ቃል ነው።
Numbers 32:26
ይሻገራሉ
ዮርዳኖስን እንደሚሻገሩ ግልፅ ልታደርጉት ተችላላችሁ።“የዮርዳኖስን ወንዝ ይሻገራሉ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለጦርነት ዝግጁ የሆነ ሰው ሁሉ
“በጦርነት ውስጥ ለመሣተፍ የተዘጋጀ ሰው ሁሉ”
Numbers 32:28
የጦር መሣሪ የታጠቀ ሰው ሁሉ
“የጦር መሣሪያውን ዝግጁ ያደረገ ሰው ሁሉ”
ምድሪቱንም ድል ብትነሱ
እዚህ ላይ “ምድሪቱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዚያ ምድር የሚኖሩትን ሰዎች እግዚአብሔርድል እንድትነሱ የሚያደርጋችሁ ከሆነ” ወይም “በምድሪቱ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ድል እንድታደርጓቸው እነርሱ የሚያግዟችሁ ከሆነ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
በከነዓን ምድር በእናንተ መካከል ርስታቸውን ይወርሳሉ
“የጋድና የሮቤል ትውልዶች በከነዓን ምድር ርታቸውን ይወርሳሉ”
Numbers 32:31
ትጥቃችንን እንደታጠቅን እንሻገራለን
ዮርዳኖስን እንደሚሻገሩ የበለጠ ግልፅ ልታደርጉት ትችላላችሁ።“ዮርዳኖስን የምንሻገረው ለጦርነት ዝግጁ ሆነን ነው”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የምንወስደው ርስታችን
ሕዝቡ እንደ ቋሚ ንብረትነት የሚወስደውን መሬት በውርስ እንደሚወስዱት ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።“የራሣችን የምናደርገው የመሬት ድርሻችን” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእኛ ይሆናል
ይሄ ፈሊጣዊ አጋገር የሚያመለክተው የራስ ንብረት ማድረግን ነው።“የራሣችን ይሆናል”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 32:33
የሴዎን ግዛትና…የዐግ
እነዚህ ሁለት የተለያዩ ግዛቶችን የገዙ ነገሥታት ሥሞች ናቸው።“የሴዎን ግዛትና… የዐግ ግዛት”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውንና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 32:34
ዲቦን፤አጣሮት፤አሮኤል፤ዓጥሮትፋሽፋን፤ኢያዜር፤ዮግብሃን፤ቤትነምራነና
እነዚህ የከተሞች ሰሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 32:37
ሐሴቦን፤ኤልያሊ፤ቂርያታይም፤ናባው፤በኣልሜዎን..ሴባማ
እነዚህ የከተሞች ሰሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
በኋላ ላይ ስማቸው ተለወጠ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በኋላ ላይ ሰዎች የእነዚሀን ከተሞች ስሞች ለወጧቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ማኪር
ይሄ የሰው ሥም ነው።ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 26፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
Numbers 32:40
ኢያዕር…ኖባህ
እነዚህ የሰዎች ሰሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)አ
ኢያዕር…ቄናት
እነዚህ የከተሞች ሰሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 33
Numbers 33:1
ከታጠቁ ጭፍሮቻቸው በታች
“በየጦር ክፍሎቻቸው” “ይሄ የሚያሣየው እያንዳንዱ ነገድ የታጠቁና ከጠላት የሚከላከሉላቸው የራሣቸው ሰዎች ነበሯቸው ማለት ነው”“የታጠቀ ሠራዊት”የሚለውን ሐረግ በዘኁልቁ 1፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
በእግዚአብሔር ትዕዛዝ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ጉዟቸው፤አወጣጣቸው
“ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላ ሥፍራ”
Numbers 33:3
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
በመጀመሪያው ወር ከወሩም በአሥራ አምስተኛው ቀን ተጓዙ
“በመጀመሪያ”የሚለው ተከታታይ ቁጥር የሆነው አንድ ሲሆን “በአሥራ አምስተኛው”የሚለው ደግሞ ተከታታይ ቁጥር የሆነው አሥራ አምስት ነው፡፡ይሄ ለዕብራውያን የመጀመሪያው ወራቸው ነው፡፡በምዕራባውያን የቀን አቆጣጠር መሠረት አሥራ አምስተኛው ቀን የሚውለው በመጋቢት ወር መጀመሪያ ላይ ነው፡፡(የዕብራውያን ቀን አቆጣጠርናተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
የእሥራኤል ልጆች ግብፃውያን ሁሉ እያዩ ከፍ ባለች እጅ ወጡ
“እሥራኤላውያን ከግብፃውያን ሳይደበቁ ፊት ለፊት እያይዋቸው ወጡ”
በኩሮቻቸው
ይሄ የሚያመለክተው በኩር የሆኑ ወንድ ልጆችን ነው፡፡“በኩር ወንድ ልጆቻቸውን”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በአማልክቶቻቸውም ደግሞ ፈረደባቸው
እግዚአብሔር በግብፅ ከሚመለኩት ጣዖታት ይልቅ እጅግ ኃያል እንደሆነ የሚያረጋግጠውን ነገር ልክ እግዚአብሔር ጣዖቶቻቸውን እንደቀጣ ዓይነት ተደርጎ ተገልጿል፡፡“ከጣዖቶቻቸው ይልቅ ኃያል እንደሆነ አረጋገጠ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 33:5
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሆነ ሥፍራ ወጡ
“ከሆነ ቦታ ለቀቁ”
በምድረ በዳው ጫፍ
“በምድረው በዳ ድንበር”
Numbers 33:8
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
በባህሩ ውስጥ አለፉ
ይሄ የሚያመለክተው እሥራኤላውያን ከግብፃውያን ሠራዊት ያመልጡ ዘንድ እግዚአብሔር ቀይ ባህርን የከፈለበትን ሁኔታ ነው፡፡
አሥራ ሁለት የውኃ ምንጮች…ሰባ ዘንባባዎች
“12 የውኃ ምንጮች…70 ዘንባቦች”(ቁጥሮች የሚለውን ተመልከቱ)
Numbers 33:11
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
ሕዝቡ የሚጠጠው ውኃ አልነበረውም
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ሰዎች ውኃ ለማግኘት የተቸገሩበት ሁኔታ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 33:15
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 33:19
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 33:23
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 33:27
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 33:31
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 33:35
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 33:38
ከአርባኛው ዓመት በኋላ
“ከአርባኛው”የሚለው ቃል አርባ ለሚለው ቁጥር ተከታታይነትን የሚያመለክት ነው፡፡“ከ40 ዓመት በኋላ” (ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
በአምስተኛው ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን
“አምስተኛው”የሚለው ቃል አምስት ለሚለው ቁጥር ተከታታይነትን የሚያመለክት ነው፡፡“በዕብራውያን አቆጣጠር መሠረት ይሄ አምስተኛው ወር ነው”በምዕራባውያን የቀን አቆጣጠር መሠረት የመጀመሪያው ቀን የሚውለው ሐምሌ መሐል አካባቢ ነው፡፡(የዕብራውያን ቀን አቆጣጠርንና ተከታታይነት ያለው ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
ዕድሜው 123 ዓመት
“መቶ ሃያ ሶስት ዓመት”(ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 33:40
ከነዓናዊው የዓራድ ንጉሥ
“የዓራድ ከነናዊ ንጉሥ”(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
አራድ
ይሄ የከነዓናውያን ከተማ ሥም ነበር፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
የእሥራኤል ልጆች እንደመጡ ሰማ
“የእሥራኤል ልጆች እየመጡ እንደሆነ ወሬ ሰማ”
Numbers 33:41
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 33:44
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 33:47
አጠቃላይ መረጃ
ሙሴ እሥራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የተጓዙባቸውን የቦታዎች የሥም ዝርዝር መፃፍ ይጀምራል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
ሜዳ
ሠፊ የሆነና ለጥ ያለ መሬት

Numbers 33:50
ከፍ ያሉ ሥፈራዎቻቸውን ሁሉ ታፈርሳላችሁ
“ከፍ ያሉ ሥፈራዎቻቸውን ሁሉ ታፈርሳላችሁ”
Numbers 33:53
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሕዝቡ ምን ማድረግ እንደሚኖርበት ለሙሴ እየተናገረ ነው፡፡
ምድሪቱን መውረስ
ሕዝቡ እንደ ቋሚ ንብረትነት የሚወስደውን መሬት በውርስ እንደሚወስዱት ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው፡፡(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሪቱንም በየወገኖቻችሁ በዕጣ ትወርሳላቸሁ
“እያንዳንዱ ነገድ በሚወጣለት ዕጣ መሠረት መሬቱን ይረከባል”
Numbers 33:55
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሕዝቡ ምን ማድረግ እንደሚኖርበት ለሙሴ እየተናገረ ነው፡፡
ለዓይናችሁ እንደ እሾህ ለጎናችሁም እንደሚወጋ ነገር
በአንድ ሰው ወስጥ ትንሽ ነገር ዓይኑ ውስጥ ቢገባ ወይም ትንሽ እሾህ በሰው ቆዳ ውስጥ ቢገባ እንደሚያበሳጭ ሁሉ ከከነዓናውያን መካከል የተወሰኑ ሰዎች በምድሪቱ ላይ ቢቀሩ ለእሥራኤላውያን ትልቅ ችግርን ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 34
Numbers 34:1
የጺን ምድረ በዳ
ይህንን ሐረግ በዘኍልቁ 33፡12 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡
Numbers 34:4
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሙሴ ለእሥራኤላውያን የሚሰጠው መሬት ድንበሩ የት እንደሆነ ይነግረዋል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 34:6
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሙሴ ለእሥራኤላውያን የሚሰጠው መሬት ድንበሩ የት እንደሆነ ይነግረዋል፡፡
Numbers 34:7
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሙሴ ለእሥራኤላውያን የሚሰጠው መሬት ድንበሩ የት እንደሆነ ይነግረዋል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
የሖር ተራራ
ይህንን ሐረግ በዘኍልቁ 20፡22 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡
Numbers 34:10
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሙሴ ለእሥራኤላውያን የሚሰጠው መሬት ድንበሩ የት እንደሆነ ይነግረዋል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 34:13
ለዘጠኝ ነገድ ተኩል
ይሄ ማለት በከነዓን ምድር ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ በኩል ወደፊት የሚኖሩት የእሥራኤል የቀሩት ነገዶች ናቸው፡፡የሮቤል፤የጋድና ግማሹ የምናሴ ነገድ መሬታቸውን ከዮርዳኖሰ በስተ ምሥራቅ በኩል ተቀብለዋል፡፡
በየአባቶቻቸው ቤት የርስት ምደባ መሠረት
“እግዚአብሔር ንብረቱን ለአባቶቻቸው ቤት በመደበው መሠረት”
ሁለቱ ነገድና የአንዱ ነገድ እኩሌታ
“የሮቤልና የጋድ ነገዶችና ግማሹ የምናሴ ነገድ”
Numbers 34:16
ለእናንተ ርስት እንዲሆን ምድሪቱን ክፈል
እዚህ ላይ “እናንተ”የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም የእሥራኤልን ሕዝብ ነው፡፡እነዚህ ሰዎች መሬቱን ለመከፋፈል ዕጣ ይጥላሉ፡፡ከዚያ በኋላ በየነገዶቹ ያከፋፍሉታል፡፡(እናንተ የሚለውን የተለያየ አገላለፆች ይመልከቱ)
Numbers 34:19
አጠቃላይ መረጃ
ለየነገዶቹ መሬቱን ለማከፋፈል አገዛ የሚያደርጉት ሰዎች የሥም ዝርዝር እነዚህ ናቸው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 34:21
አጠቃላይ መረጃ
ለየነገዶቹ መሬቱን ለማከፋፈል አገዛ የሚያደርጉት ሰዎች የሥም ዝርዝር እነዚህ ናቸው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 34:24
አጠቃላይ መረጃ
ለየነገዶቹ መሬቱን ለማከፋፈል አገዛ የሚያደርጉት ሰዎች የሥም ዝርዝር እነዚህ ናቸው፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 34:27
አጠቃላይ መረጃ
ለየነገዶቹ መሬቱን ለማከፋፈል አገዛ የሚያደርጉት ሰዎች የሥም ዝርዝር እዚህ ላይ ይጠናቀቃል፡፡(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 35
Numbers 35:1
ሜዳ
ሠፊ ሆኖ ለጥ ያለ ሜዳ
ለሌዋውያን የሚደርሳቸውን የመሬት ድርሻ ስጧቸው
እግዚአብሔር የራሣቸው የሆነ መሬትለሌዋውያንያልሰጣቸው በመሆኑ በሌሎች ነገዶች ከተማዎች ውስጥ መቀመጥ ነበረባቸው፡፡
የግጦሽ መሬት
እንስሳት ሣር የሚግጡባቸው የመሬት ክፍል
Numbers 35:3
አንድ ሺህ ክንድ
“1000 ክንድ”ዘመናዊ የርቀት መለኪያን መጠቀም ከፈለጋችሁ ከዚህ በሚከተለው መልኩ ለማድረግ ትችላላችሁ፡፡“457 ሜትር”(ቁጥሮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ርቀት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 35:5
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ሁለት ሺህ ክንድ
“2000 ክንድ”አንድ ክንድ 46 ሴንቲ ሜትር ነው፡፡(ቁጥሮችና መፅሐፍ ቅዱሣዊ ርቀት የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 35:6
የሰው ነፍስ ያጠፋ ሰው
ይሄ የሚያመለክተው የሰው ነፍስ ያጠፉ ሰዎችን ሲሆን ነገር ግን ሰውዬውን የገደሉት ሆን ብለው ነው ወይስ ሳያስቡት ነው? የሚለውጥያቄ ግን ገና ውሳኔ ያላገኘ መሆኑን ነው፡፡
አርባ ሁለት…አርባ ስምንት
“42…48” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 35:8
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል፡፡
Numbers 35:9
በስህተት
በድንገት ወይም ሳያደፍጡ ወይም ሆን ብለው ሳይጠብቁ
Numbers 35:12
ደም ተበቃይ
ጥፋተኛ የሆነውነ ሰው ለመበቀል የሚያደባ የቅርብ ዘመድን ነው፡፡
በማህበሩ ፊት ለፊት እስኪቆም ድረስ እንዳይሞት
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ጥፋተኛው ሰው ወደ ማህበሩ ፈርዶ ፍርዱን ለማግኘቱ በፊት አንድ ሰው እንዳይገድለው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን

ይመልከቱ)
Numbers 35:14
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።
Numbers 35:16
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።
ፈፅሞ ይገደል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በእርግጥም ልትገድሉት ይገባል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውንና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 35:19
ደም ተበቃዩ
እዚህ ላይ“ደም”የሚለው ቃል መግደል ለሚለው ሃሣብ ሌላ ገላጭ ቃል ነው።“የገደለውን ሰው የሚበቀል” ወይም “ለመበቀል የሚፈልግ የቅርብ ዘመድ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ደም ተበቃዩ ባገኘው ጊዜ ነፍሰ ገዳዩን ይግደለው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው ጥፋተኛውን ሰው መግደል አለበት“ ወይም “ጥፋተኛው ሰው መሞት አለበት”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 35:22
ጥላቻ ሳይኖረው በድንገት
“ከጥላቻ የተነሣ ቀደም ሲል ጉዳዩን በተመለከተ ላይ ዕቅድ ሳይነድፍ”
ሳይሸምቅ
አንድ ሰው ሌላን ሰው ሆነ ብሎ ለመጉዳት የሚያደርገው ክትትል አንድ ሰው ለማጥቃት ደፈጣ የሚያደርግ አስመስሎ ነው የተገለፀው።“የሚጠቃውን ሰው ለመጉዳትት ሆነ ተብሎ ያልተደረገ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 35:24
ደም ተበቃዩ
እዚህ ላይ“ደም”የሚለው ቃል መግደል ለሚለው ሃሣብ ሌላ ገላጭ ቃል ነው። ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 35:19 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ማህበሩም ነፍሰ ገዳዩን ሰው ከደም ተበቃዩ እጅ ያድነዋል
ይሄ ማለት ማህበሩ ግድያው የተፈፀመው በአጋጣሚ ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ የተገደለው ሰው የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው እንዳይገድለው ያድኑታል።ነገር ግን ማህበሩ ግድያው የተፈፀመው ታስቦበት እንደሆነ ካመነ የሟች የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው ጥፋተኛውን ሰው መግደል ይኖርበታል።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በቅዱስ ዘይትም የተቀባው
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በቅዱስ ዘይት የቀባኸው ሰው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 35:26
ደም ተበቃዩ
እዚህ ላይ“ደም”የሚለው ቃል መግደል ለሚለው ሃሣብ ሌላ ገላጭ ቃል ነው። ይህንን ሐረግ በዘኁልቁ 35:19 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 35:29
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለሙሴ መናገሩን ይቀጥላል።
ለልጅ ልጃችሁ
“ከአንተ በኋላ ለሚመጡት ትውልዶቹ በሙሉ”
Numbers 35:31
እርሱ ፈፅሞ ይገደል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እርሱን ልትገድሉት ይገባቹኋል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውንና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በራሱ ንብረት ላይ እንዲቀመጥ አትፍቀዱለት
ይሄ የሚያመለክተው የመማፀኛ ከተማውን ለቅቆ ወደ ቤቱ ለመመለስ የፈለገን ሰው ነው።“የመማፀኛ ከተማውን ለቅቆ እንዲሄድ መደፍቀድ የለባችሁም።ወደ ቤቱ በመሄድ በራሱ ንብረት ላይ እንዲቀመጥ መፍቀድም የለባችሁም።”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በዚህ ሁኔታ
“የነፍስ ዋጋን በመቀበል”
Numbers 35:33
የምትኖሩባትን ምድር አታርክሷት፤በደም አፍሳሹ ደም ካልሆነ በቀር ምድሪቱ ከፈሰሰባት ደም አትነፃም
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ምድር አካሉ እንደተመረዘ ነገር ተገልጿል። ከሰው መግደል ጋር በተያያዘ የፈሰሰው ደም ምድሪቱ በእኔ ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራት የሚያደርግ በመሆኑ በዚህ ዓይነትሁኔታ ምድራችሁ በፊቴ ተቀባይነት እንዳይኖራት አታድርጉ።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በዚህ ሁኔታ
“የነፍስ ዋጋን በመቀበል”
በደም አፍሳሹ ደም ካልሆነ በቀር ምድሪቱ ከፈሰሰባት ደም አትነፃም
ይሄ የሚያመለክተው አንድ ሰው ሆነ ብሎ ሌላ ሰው የገደለ ሲሆን ነው።“አንድ ሰው በምድሪቱ ላይ ደም የሚያፈስስ ከሆነ ምድሪቱ የምትነፃው ያ ደም ያፈሰሰው ሰው ሲገደል ብቻ ነው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 36
Numbers 36:1
ማኪር
ይሄ የሰው ሥም ነው።የዚህን ሰው ሥም በዘኁልቁ 26:29 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር ታዝዞሃልና
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር አዝዞሃል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰለጰዓድ
ይሄ የሰው ሥም ነው።የዚህን ሰው ሥም በዘኁልቁ 26:33 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 36:3
ከአባቶቻችን ነገድ ርስት ይጎድላል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በአባቶቻችን ርስት ውስጥ ድርሻ አይኖረውም”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ይጨመራል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ድርሻው የሚሆነው…”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአባቶቻችን ርስት ይነቀላል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የርስታችን አካል አይሆንም”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእሥራኤልም ልጆች ኢዮቤልዩ
ይሄ የሚያመለክተው በየሃምሣ ዓመቱ የሚደረገውን በዓል ነው።በዚህ የበዓል ወቅት አንድ ሰው የሸጠው መሬትም ሆነ ንግድ ወደ መጀመሪያ ባለቤቱ መመለስ ይኖርበታል።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና የተሟላ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ድርሻቸው ይጨመራል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ድርሻቸው ….”
ርስታቸው ከአባቶቻችን ነገድ ርስት ይጎድላል
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የእኛን ነገድ የመሬት ድርሻ ይወስዱታል”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 36:5
እንደ እግዚአብሔር ቃል
“እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት”
የወደዱትን ያግቡ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ደስ ያላቸውን ሰው ያግቡ”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነገር ግን ከአባታቸው ነገድ ብቻ ያግቡ
ይሄ በድርጊት መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሚያገቡትን ሰው ግን ከአባታቸው ቤት ብቻ ነው ማግባት የሚኖርባቸው”(ገቢራዊ ወይም ፍዝ የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 36:7
ድርሻ አይኖርም
“ድርሻ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እንዳንዱ ነገድ በርስት መልክ የሚቀበለውን መሬት ነው።“ምንም ዓይነት የመሬት ድርሻ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 36:8
በአባቷ ቤት ርስት ያላት
“በነገዷ ውስጥ የመሬት ርስት ያላት”
ርስትንሊቀበል ይችላል
እያንዳንዱ ነገድ ንብረቱ የሚያደርገውን መሬት እንደሚቀበሉት ዓይነት ውርስ ተደርጎ ነው የሚነገረው። (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከአንድ ነገድ ወደ ሌላ ነገድ ምንም ርስት አይተላለለፍ
ባለቤትነትን ከአንድ ነገድ ወደ ሌላ ማስተላለፍን በተመለከተ ልክ አንድ ንብረት ከአንድ ሰው እጅ ወደ ሌላ ሰው እጅ እንደተላለፈ ዓይነት ተደርጎ ነው የሚገለፀው።“ማንም ሰው ቢሆን የመሬት ድርሻ ባለቤትነትን ከአንድ ነገድ ወደ ሌላ ነገድ ማስተላለፍ አይኖርበትም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 36:10
ማህለህ፤ቲርጻ፤ኤግላ፤ሚልካ፤ኑዓ
እነዚህን ስሞችበዘኁልቁ 26:33 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ይመልከቱ)
ርስታቸው
የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች በንብረትነት የወሰዱት መሬት ልክ እንደወረሱት ውርስ ተደርጎ ተገልጿል።“በውርስ መልክ የተቀበሉት መሬት”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Numbers 36:13
ሜዳዎች
ሰፊና ለጥ ያለ መሬት

---

Chapter 1
Deuteronomy 1:1
ከዮርዳኖስ ማዶ
ይህ የሚያመለክተው ከእስራኤል በስተምስራቅ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግሮ ያለውን ምድር ነው። ሙሴ ለእስራኤላውያን በሚናገርበት ጊዜ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ ነበር። አ.ት፡ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ
ሱፋ … ፋራን … ቶፌል … ላባ … ሐጼሮት … ዛሀብ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ከኮሬብ እስከ ቃዴስ በርኔ የአሥራ አንድ ቀን መንገድ ነው
“ከኮሬብ ወደ ቃዴስ በርኔ ለመጓዝ አሥራ አንድ ቀን ይፈጃል”
የሴይር ተራራ
ይህ ከሙት ባህር በስተደቡብ ያለ ተራራማ አካባቢ ነው። አካባቢው “ኤዶም” በመባልም ይታወቃል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
አሥራ አንድ
“11” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 1:3
ሙሴ በአርባኛው ዓመት፣ በአሥራ አንደኛው ወር፣ ከወሩም በመጀመሪያው ቀን ተናገረ
መቁጠሪያ ቁጥሮች ወደ ተራ ቁጥሮች ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “ሙሴ በተናገራቸው ጊዜ በምድረ በዳ የኖሩት ለ40 ዓመታት፣ ለ11 ወራትና ለ1 ቀን ነበር። (መቁጠሪያ ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
አርባኛ
40ኛ (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
በአሥራ አንደኛው ወር፣ ከወሩም በመጀመሪያው ቀን
ይህ በዕብራውያኑ የቀን አቆጣጠር አሥራ አንደኛው ወር ነው። የመጀመሪያው ቀን በምዕራባውያን አቆጣጠር ወደ ጥር ወር አጋማሽ ይቃረባል።(የዕብራውያን ወራት እና መቁጠሪያ ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
አሥራ አንደኛ
11ኛ (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ራሱን ለሕዝቡ የገለጠበት ስሙ ነው። ያህዌ እንዴት እንደሚተረጎም ለመረዳት የትርጉም ቃል ገጽን ተመልከት።
እግዚአብሔር ወግቷቸው ነበር
“እስራኤላውያን እንዲያሸንፉ እግዚአብሔር አስችሏቸው ነበር”
ሴዎን … ዐግ
እነዚህ የነገሥታት ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሐሴቦን … አስታሮትን በኤድራይ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 1:5
ከዮርዳኖስ በላይ
ይህ የሚያመለክተው ከእስራኤል በስተምስራቅ ከዮርዳኖስ ወንዝ ባሻገር ያለውን ምድር ነው። ሙሴ ይህንን በሚናገርበት ጊዜ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ ነበር።
እነዚህን ቃላት በዘዳግም 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት፡ “ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ”።
ለእኛ ተናገረን
“እኛ” የሚለው ቃል ሙሴንና ሌላውን የእስራኤል ሕዝብ ያመለክታል።
በዚህ ኮረብታማ አገር ብዙ ዓመት ኖራችኋል
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “ከዚህ በኋላ በዚህ ተራራ አጠገብ መቆየት አይኖርባችሁም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 1:7
ተመልሳችሁ ጉዞአችሁን ቀጥሉ
“ተመልሳችሁ” የሚለው ቃል አንድን ተግባር ለመጀመር ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “እንደገና ጉዞአችሁን ቀጥሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ኮረብታማ አገር -- ኤፍራጥስ
እግዚአብሔ ለእስራኤላውያን ለመስጠት ቃል በገባላቸው ምድር አካባቢዎቹን እያብራራላቸው ነው።
ኮረብታማ አገር
ይህ አሞራውያን ይኖሩ ከነበሩበት አቅራቢያ የሚገኝ ኮረብታማ አካባቢ ነው።
ቆላ
ዝቅና ለጥ ያለ የምድር አካባቢ
ተመልከት
“ለምናገረው ነገር ትኩረት ስጡ”
ምድሪቱን በፊታችሁ አስቀምጫለሁ
“አሁን ይህችን ምድር ሰጥቻችኋለሁ”
እግዚአብሔር የማለላችሁን ያንን
እግዚአብሔር ራሱን እንደ ሌላ አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “እኔ እግዚአብሔር ምያለሁ” (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)
አባቶች
“አባቶች” የሚለው ቃል አያት፣ ቅድም አያቶችን ሁሉ የሚወክል ነው። አ.ት፡ “አያት፣ ቅድም አያቶች” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 1:9
በዚያን ጊዜ ነገርኳችሁ
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው። “በዚያን ጊዜ” የሚለው ሐረግ እስራኤላውያን በኮሬብ፣ ይኸውም የሲና ተራራ ራሱ ነው፣ በዚያ የነበሩበትን ጊዜ ነው። አ.ት፡ “በኮሬብ በነበርንበት ጊዜ ነገርኳችሁ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ለብቻዬ ልሸከማችሁ አልችልም
እዚህ ጋ “ልሸከማችሁ” ማለት “ልመራችሁ” ወይም “ላስተዳድራችሁ” ማለት ነው። አ.ት፡ “በራሴ ልመራችሁ ይከብደኛል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እንደ ሰማይ ከዋክብት የበዛውን
ይህ ግነት ሲሆን ትርጉሙም እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን ቁጥር እጅግ አብዝቶታል ማለት ነው። አ.ት፡ “እጅግ ብዙ ሕዝብ”(ግነት፣ ጥቅል አስተያየት እና Simile)
አንድ ሺህ ጊዜ

“አንድ ሺህ” የሚለው ሐረግ “በጣም ብዙ” የሚል ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በጣም ብዙ ጊዜ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አንድ ሺህ
1000 (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 1:12
ይሁን እንጂ፣ ችግራችሁን፣ ሸክማችሁንና ክርክራችሁን ለብቻዬ እንዴት መሸከም እችላለሁ?
ሙሴ ችግሮቻቸውን በሙሉ ለብቻው መፍታት እንደማይችል አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ችግራችሁን፣ ሸክማችሁንና ክርክሮቻችሁን ለብቻዬ መሸከም አልችልም”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ችግራችሁን፣ ሸክማችሁን
ሙሴ የተሸከመውና ሊፈታቸው ያስፈልጉ የነበሩት የሕዝቡ ችግሮችና ቅሬታዎች ለእርሱ ልክ ቁስ አካል የመሸከም ያህል እንደከበዱት ይናገራል። ኢ.ት፡ “ችግሮቻችሁን፣ ቅሬታዎቻችሁን መፍታት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ክርክራችሁን
“ሙግታችሁን” ወይም “አለመግባባቶቻችሁን”
ከየነገዱ መልካም ስም ያላቸውን ሰዎች
“ከእያንዳንዱ ነገድ እስራኤላውያን የሚያከብሯቸው ሰዎች”
Deuteronomy 1:15
መልካም ስም ያላቸውን ሰዎች
“ወገኖቻችሁ የሚያከብሯችሁን ሰዎች”። ይህ በዘዳግም 1፡13 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።
የሺዎች _ የመቶዎች _ የሃምሳዎች _ የአሥሮች
የ1000 ቡድን _ የ100 ቡድን _ የ50 ቡድን _ እና የ10 ቡድን (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሻምበሎች _ መኮንኖች
እነዚህ በእስራኤል መንግሥት የተለያዩ መሪዎች የሚጠሩባቸው መጠሪያዎች ናቸው።
ነገድ በነገድ
“ከእያንዳንዳችሁ ነገድ”
በአንድ ሰውና በወንድሙ መካከል በጽድቅ ፍረዱ
“እስራኤላውያን እርስ በእርሳቸው በሚኖራቸው ክርክር ላይ ትክክለኛና ፍትሐዊ ውሳኔ ስጡ”
Deuteronomy 1:17
አድልዎ አታድርጉም
“አድልዎ አታድርጉ”
የታናሹንና የታላቁን እኩል ስሙ
“ታናሽ” እና “ታላቅ” የተባሉት እነዚህ ሁለት ጽንፎች ሕዝቡን ሁሉ ይወክላሉ። ኢ.ት፡ “ሕዝቡን ሁሉ በእኩል ትዳኙታላችሁ” (See: Merism)
የሰውን ፊት አትፈሩም
“ፊት” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “አትፈሩም” ትዕዛዝ ነው። “ማንንም አትፍሩ” (See: Synecdoche)
በዚያን ጊዜ
ይህ ማለት በኮሬብ፣ በሲና ተራራ በነበሩበት ጊዜ ማለት ነው። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 1:19
ባያችሁት አስቸጋሪ ምድረ በዳ
“ያቋረጣችሁት ያ ሰፊና አደገኛ ምድረ በዳ
Deuteronomy 1:20
ተመልከቱ _ አምላካችሁ _ በፊታችሁ፤ ተነሡ፣ ውረሱ _ አባቶቻችሁ _ ለእናንተ፤ አትፍሩ፣ ተስፋም አትቁረጡ
ሙሴ ለአንድ ሰው የሚናገር ይመስል የሚናገረው ለእስራኤላውያን ነው፤ በመሆኑም እነዚህ ቅርጾች ብዙ ሳይሆኑ ነጠላ ቁጥር ናቸው። (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)
ምድሪቱን በፊታችሁ አድርጓል
“አሁን ይህቺን ምድር ሊሰጣችሁ ነው”። ይህ በዘዳግም 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልከት
Deuteronomy 1:22
አሥራ ሁለት ሰዎች
“12 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ተመልሰው ሄዱ
መመለስ መመሪያውን ለመታዘዝ መጀመራቸውን የሚገልጽ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ያንን ስፍራ ትተው ሄዱ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የኤሽኮል ሸለቆ
ይህ ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ የሚገን በኬብሮን አውራጃ የሚገኝ ሸለቆ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ቃኙ
“መውጋት የሚችሉባቸውን አካባቢዎች ተመለከቱ”
Deuteronomy 1:25
ወሰዱ
“12ቱ ሰዎች ወሰዱ”
ከምድሪቱ ፍሬ ጥቂቱን በእጃቸው ወሰዱ
“ከምድሪቱ ፍሬ ጥቂቱን አነሡ”
ቃል አመጡልን፣ እንዲህም አሉን
ተናጋሪው “ቃል” አንድ ሰው ሊያመጣው የሚችለው ቁስ አካላዊ ነገር ይመስል ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
‘አምላካችን እግዚአብሔር የሚሰጠን ምድር ጥሩ ነው’ አሉ
ቀጥተኛው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር አምላካችን የሚሰጠን ምድር ጥሩ እንደሆነ ተነግሯል”
Deuteronomy 1:26
እናንተ ግን ለመዋጋት እምቢ አላችሁ
እስራኤላውያን አሞራውያንን እንዲወጉና እንዲያጠፏቸው እግዚአብሔር አዘዛቸው፣ ነገር ግን እስራኤላውያን ፈሩ፣ ከእነርሱ ጋር ለመዋጋትም እምቢ አሉ”። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
በአሞራውያን እጅ
እዚህ ጋ “በ እጅ” ማለት ለአሞራውያን በእነርሱ ላይ የበላይ እንዲሆኑ መስጠት ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ለአሞራውያን ኃይል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አሁን ወዴት መሄድ እንችላለን?
እዚህ ጋ ይህ ጥያቄ ምን ያህል እንደ ፈሩ አጽንዖት ይሰጣል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ምንም መሄጃ የለንም”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ልባችን እንዲቀልጥ አደረጉ
ይህ ማለት ፈርተዋል ማለት ነው። ኢ.ት፡ “በጣም እንድንፈራ አደረጉን” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እስከ ሰማይ ደረስ የታጠሩ ናቸው
ይህ ከተሞቹ ሰፊና ጠንካራ በመሆናቸው ምክንያት ሰዎቹ ምን ያህል እንደ ፈሩ አጽንዖት የሚሰጥ ግነት ነው። ኢ.ት፡ “ሰማይ የሚደርሱ የሚመስሉ ግንቦች አሏቸው” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
የኤናቅን ልጆች
እነዚህ የኤናቅ ሕዝብ ተወላጆች ሲሆኑ በጣም ረጃጅምና ኃይለኞች ነበሩ። (See: Assumed Knowl- edge and Implicit Information and ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 1:29
አልኳችሁ
“ለአባቶቻችሁ ነገርኳቸው”
በዐይኖቻችሁ ፊት
እዚህ ጋ ሰዎቹ ስላዩት ነገር አጽንዖት ለመስጠት በ”ዐይኖቻቸው” ተወክለዋል። ኢ.ት፡ “እናንተ ራሳችሁ ያያችሁት” (See: Synecdoche)
ዐይታችኋል አምላካችሁ እግዚአብሔር ተሸከማችሁ __ ሄዳችሁ __ መጣችሁ
ሙሴ፣ እስራኤላውያን አንድ ሰው የሆኑ ይመስል “አንተ” እና “የአንተ” እያለ ይናገራል፤ እነዚህ አገባቦች ሁሉ ነጠላ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)
አባት ልጁን እንደሚሸከም አምላካችሁ እግዚአብሔር እናንተን ተሸከማችሁ
እዚህ ጋ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያደርግላቸው ክብካቤ ከአባት ጋር ተነጻጽሯል። ኢ.ት፡ “አባት ልጁን እንደሚንከባከብ አምላካችሁ እግዚአብሔር ተንከባክቧችኋል” (See: Simile)
ወደዚህ ስፍራ እስክትመጡ ድረስ
“እግዚአብሔር ሊሰጣችሁ ቃል ወደገባላችሁ ወደዚህ ምድር እስክትመጡ ድረስ”
Deuteronomy 1:32

በፊታችሁ የሄደ _ አምላካችሁ እግዚአብሔር
ባለፈው ዘመን በጉዞአቸው ሁሉ እግዚአብሔር በእስራኤል ፊት የሄደባቸውን መንገዶች በሙሉ ሙሴ ያስታውሳቸዋል።
ሥፈሩ
“ድንኳኖቻችሁን ትከሉ”
Deuteronomy 1:34
የቃላችሁን ድምፅ ሰማ
“ስትናገሩ የነበረውን ሰማ”
ማለና እንዲህ አለ
በእርሱ ላይ ያመጹት እግዚአብሔር ሊሰጣቸው ቃል ወደ ገባላቸው ምድር እንዳይገቡ ማለ።
ያያሉ
“ይገባሉ”
ካሌብ ብቻ
“ከካሌብ በቀር”
ዮፎኒ
ይህ የካሌብ አባት ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
እርሱ እግዚአብሔርን ፈጽሞ ተከትሏል
እግዚአብሔር ራሱን እንደ ሌላ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እርሱ ሙሉ በሙሉ ታዞኛል” (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 1:37
እግዚአብሔር በእናንተ ምክንያት ተቆጣኝ
ይህ የሚያመለክተው ሙሴ በእስራኤል ሕዝብ ላይ በመቆጣቱ ምክንያት እግዚአብሔር እንዲያደርግ የነገረውን ያልታዘዘበትን ጊዜ ነው። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ነዌ
ይህ የኢያሱ አባት ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
በፊትህ የሚቆመው
ኢያሱ በሙሴ ፊት ለምን ይቆም እንደነበረ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እንደ አገልጋይህ በፊትህ የሚቆመው” ወይም “የሚረዳህ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 1:39
ክፉና ደጉን የማያውቁት
የትኛው ክፉ እና የትኛው ደግ እንደሆነ ገና የማያውቁ
ተመልሳችሁ ጉዞአችሁን ቀጥሉ
“ወደ ኋላችሁ ተመለሱና በመጣችሁበት መንገድ ተመልሳችሁ ሂዱ”
Deuteronomy 1:41
በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ሠርተዋል
“እርሱን ባለመታዘዝ በእግዚአብሔር ላይ አምጸናል”
እንከተላለን
“እንታዘዛለን”
ኮረብታማውን አገር ለመውጋት
እዚህ ጋ “ኮረብታማው አገር” የተባለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚወክለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። ኢ.ት፡ “በኮረብታማው አገር የሚኖሩትን ሰዎች ለመውጋት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከእናንተ ጋር አልሆንም፣ እናንተም በጠላቶቻችሁ ትሸነፋላችሁ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከእናንተ ጋር ስለማልሆን ጠላቶቻችሁ ያሸንፏችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 1:43
ኮረብታማውን አገር ወጉ
“ኮረብታማው አገር” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የቆመው በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች ነው። ኢ.ት፡ “በኮረብታማው አገር የሚኖሩትን ሰዎች ወጉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እንደ ንብ አባረሯችሁ
“ንብ” ትንሽ፣ በራሪ ነፍስ ሲሆን በመንጋ ሆኖ የሚበርና ስጋት የሚሆኑባቸውን ሰዎች የሚነድፍ ነው። ይህ ማለት በጣም ብዙ አሞራውያን የእስራኤል ወታደሮችን ከጦርነቱ እስኪሸሹ ድረስ ወግተዋቸዋል። (See: Simile and የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
ሴይር
ይህ የአንድ አስተኛ ምድር ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሔርማ
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
መቷችሁ
“ከወታደሮቻችሁ ብዙዎቹን ገደሉ”
Deuteronomy 1:45
ተመለሳችሁና አለቀሳችሁ
“ወደ ቃዴስ ተመለሳችሁና አለቀሳችሁ”

---

Chapter 2
Deuteronomy 2:1
ከዚያም ተመለስንና ጉዞአችንን ቀጠልን
“ከዚያም ተመለስንና ሄድን”
ለብዙ ቀናት በሴይር ተራራ አጠገብ ሄድን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እስራኤላውያን ሴይር ተብሎ በሚጠራው ተራራ አቅራቢያ ለረጅም ጊዜ ተጉዘዋል ወይም 2) እስራኤላውያን ሴይር ተብሎ በሚጠራው ተራራ አካባቢ ለረጅም ጊዜ ተቅበዝብዘዋል።
የሴይር ተራራ
ይህ ከሙት ባህር በስተደቡብ የሚገኝ ተራራማ አካባቢ ነው። አካባቢው “ኤዶም” በመባልም ይጠራል። ይህንን በዘዳግም 1፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ብዙ ቀናት
ይህንን አንዳንድ ቋንቋዎች “ብዙ ሌሊቶች” ብለው ይተረጉሙታል።
Deuteronomy 2:4
ወንድሞቻችሁ የኤሳው ተወላጆች
“ዘመዶቻችሁ የኤሳው ተወላጆች”
የሴይርን ተራራ ርስት አድርጌ ለኤሳው ሰጥቸዋለሁ
እግዚአብሔር ለኤሳው ተወላጆች ይህንን ክልል እንደ ሰጣቸው እስራኤላውያንን ያስታውሳቸዋል።
Deuteronomy 2:6
ከእነርሱ ምግብ ትገዛላችሁ
እግዚአብሔር የሚሰጣቸው ትዕዛዝ ሳይሆን ፈቃድ ወይም መመሪያ ነው፣ እንዳይሰርቁም ይነግራቸዋል። “ከእነርሱ ምግብ እንድትገዙ እፈቅድላችኋለሁ” ወይም “ምግብ ከፈለጋችሁ ከእነርሱ መግዛት ይኖርባችኋል”
ከእነርሱ
“ከኤሳው ተወላጆች”
በገንዘብ
ይህ ቃል የማያስፈልግ ወይም ትርጉሙን ግልጽ የማያደርግ ከሆነ መተው ይኖርብህ ይሆናል።
አምላክህ ባርኮሃል _ እጅህ _ አካሄድህ _ አምላክህ _ ከአንተ ጋር እና አላጣህም
ሙሴ እስራኤላውያንን አንድ ሰው እንደሆኑ ዓይነት አድርጎ ይናገራል፣ በመሆኑም “አንተ” እና “የአንተ” ተብለው የተነገሩት ሁሉ ነጠላ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)
በእጅህ ሥራ ሁሉ
የ “እጅህ ሥራ” የሚያመለክተው ያደረጉትን ሥራ ሁሉ ነው። ኢ.ት፡ “ሥራህን ሁሉ” (See: Synec- doche)
በመንገዳችሁ ጠብቋችኋል
እዚህ ጋ ሕዝቡ ሲጓዙ የደረሰባቸው እንደ “መንገድ” ተነግሯል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አርባ ዓመታት
“40 ዓመታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ምንም አላጣችሁም
ይህ “የምትፈልጉት ሁሉ ነበራችሁ” የተጋነነ አባባል ነው። (የተጋነነ አባባል የሚለውን ተመልከት)

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Deuteronomy 2:8
በወንድሞቻችን
“በዘመዶቻችን”
ኤላት _ ጽዮን ጋብር
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ተመለስን
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “መጓዛችንን ቀጠልን” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 2:9
ሞዓብን አታስቸግሩት
“ሞዓብ” የሚለው ቃል የሚወክለው የሞዓብን ሕዝብ ነው። ኢ.ት፡ “የሞዓብን ሕዝብ አታስቸግሯቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዔር
ይህ በሞዓብ የሚገኝ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የሎጥ ተወላጆች
የእስራኤል ሕዝብ ከሞዓብ ተወላጆች ጋር ዝምድና ነበራቸው። ሞዓብ የሎጥ ልጅ ነበር። ሎጥ ደግሞ የአብርሃም የወንድም ልጅ ነበር። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 2:10
ኤሚማውያን ይኖሩባት ነበር _ ኤሚም ብለው ይጠሯቸዋል
እነዚህ ቃላት ከሞዓባውያን በፊት በምድሪቱ ላይ ስለነበሩት ስለ ኤሚም ሕዝብ ዳራዊ መረጃ ይሰጣሉ። ቋንቋህ ዳራዊ መረጃን ለማመልከት የተለየ መንገድ ይኖረው ይሆናል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ኤሚማውያን _ ራፋይም
እነዚህ ግዙፍ እንደሆኑ የሚታሰቡ የሕዝብ ወገን ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ዔናቅ
እነዚህ በጣም ረጃጅምና ኃይለኞች የነበሩ የዔናቅ ሕዝቦች ተወላጆች ናቸው። ይህንን በዘዳግም 1፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Deuteronomy 2:12
ሖራውያን
ይህ የአንድ የሕዝብ ወገን ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ከፊታቸው አጠፏቸው
“ከእነርሱ ጋር አንዱም በሕይወት እንዳይኖር ሁሉንም ገደሏቸው” ወይም “ሁሉንም በመግደል ከአጠገባቸው አስወገዷቸው”
Deuteronomy 2:13
ስለዚህ ‘አሁን ተነሡ _ ዜሬድ’
“ከዚያም እግዚአብሔር፣ “አሁን ተነሡ _ ዜሬድ’ ስለዚህ”። ይህ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ከዚያም እግዚአብሔር ተነሥተን _ ዜሬድ ተናገረን። ስለዚህ” (ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)
ተነሡ
አንድ ነገር ለማድረግ ጀምሩ (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የዜሬድን ጅረት
ይህ ምንጭ ከደቡብ ምስራቅ ወደ ሙት ባህር በመፍሰስ በኤዶምና በሞዓብ መካከል ድንበር ያበጃል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
አሁን ቀኖቹ
“አሁን” የሚለው ቃል ከትረካው የእስራኤል ሕዝብ ለምን ያህል ጊዜ እንደተጓዙና በዚያ ትውልድ ላይ እግዚአብሔር ወደተቆጣበት ዳራዊ መረጃ መቀየሩን ያመለክታል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ሠላሳ ስምንት ዓመት
“38 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ከሕዝቡ ተለይተው ሄደው ነበር
ይህ “ሞተው ነበር” የሚል የትህትና አነጋገር ነው። (See: Euphemism)
የእግዚአብሔር እጅ በእነርሱ ላይ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ኃይሉን በእነርሱ ላይ ተጠቅሟል” ወይም “እግዚአብሔር ቀጣቸው” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 2:16
እናንተ ናችሁ - መጣችሁ - አታስቸግሯቸው - አልሰጣችሁም
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ በመሆኑም “አንተ” እና “አታስቸግሯቸው” የሚልበት ትዕዛዝ አገባብ ሁሉ ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)
ዔርን ታልፋላችሁ
ይህ በሞዓብ የሚገኝ የአንድ ከተማ ስም ነው። “ዔር”ን በዘዳግም 2፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ለሎጥ ተወላጆች
የእስራኤል ሕዝብ ከአሞን ተወላጆች ጋር ዝምድና ነበራቸው። አሞን የሎጥ ልጅ ነበር። ሎጥ ደግሞ የአብርሃም የወንድሙ ልጅ ነበር። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 2:20
ያ ደግሞ ይቆጠር ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች ያንን ደግሞ ይቆጥሩ ነበር”። (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ረፋይም
ይህ የአንድ ሕዝብ ወገን ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ዘምዙማውያን
ይህ የረፋይም ሕዝብ ወገን ሌላው ስማቸው ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ዔናቅ
ይህ የአንድ ሕዝብ ወገን ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
በአሞናውያን ፊት አጠፋቸው
“አሞናውያን እንዲያሸንፏቸው ፈቀደላቸው” ወይም “አሞናውያን ሁሉንም እንዲገድሏቸው ፈቀደላቸው”
እነርሱ ተኳቸው፣ በእነርሱ ስፍራም ኖሩ
“አሞናውያኑ ረፋይማውያን የነበራቸውን ሁሉ ወሰዱባቸው፣ ረፋይማውያን ይኖሩ በነበሩበትም ስፍራ ኖሩ”
ሖራውያን
ይህ የአንድ ሕዝብ ወገን ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2፡12 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ተኳቸው፣ በእነርሱ ስፍራም ኖሩ
“ሖራውያን የነበራቸውን ሁሉ ወሰዱባቸው፣ ሖራውያን ይኖሩ በነበሩበትም ስፍራ ኖሩ”
Deuteronomy 2:23
ኤዋውያን - ከፍቶር
እነዚህ የሕዝብ ወገን ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ከፍቶር
x
Deuteronomy 2:24
አሁን ተነሡ
ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር ለሙሴ እየነገረው ነው። “አሁን ተነሡ” ወይም “አሁን ሂዱ”
መንገዳችሁን ሂዱ
“ጉዞአችሁን ቀጥሉ”
የአርኖን ሸለቆ
ይህ የአርኖን ወንዝ ሸለቆ ስም ነው። እርሱ በሞዓብና በአሞራውያን መካከል ድንበር ያበጃል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
በእጃችሁ ሰጥቻችኋለሁ
“በእጃችሁ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም “በቁጥጥራችሁ ወይም በኃይላችሁ ሥር” ማለት ነው። ኢ.ት፡ “እንድታሸንፉ ኃይልን ሰጥቻችኋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እጃችሁ - ለመውረስ ጀምሩ - ተዋጉ - ማስፈራታችሁ - ዝናችሁ - በእናንተ ምክንያት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ በመሆኑም “አንተ” እና “የእናንተ” እንዲሁም ትዕዛዝ የሆኑት “ለመውረስ ጀምሩ” እና “ተዋጉ” ሁሉም አገባቦች ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

ሴዎን

ይህ የአንድ ንጉሥ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሐሴቦን

ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከእርሱ ጋር ተዋጋ

“ከእርሱና ከሰራዊቱ ጋር ተዋጋ”

አስፈሩ፣ አስደንግጡም

“ፍርሐት” እና “ድንጋጤ” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ቢሆንም ፍርሐቱ ታላቅ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል። ኢ.ት፡ “ከባድ ፍርሐት ጣሉባቸው” (See: Doublet)

ከሰማይ በታች ያለ ሕዝብ ሁሉ

ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በየአገሩ ያሉ ሕዝቦች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ይንቀጥቀጡና ይጨነቁ

ይህ ሕዝቡ በጭንቀት እንደሚንቀጠቀጡ አጽንዖት ይሰጣል። (See: Hendiadys)

Deuteronomy 2:26

እኔ ላክኋቸው

እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

ወደ ቄድሞት ምድረ በዳ

ይህ በአርኖን ሸለቆ አቅራቢያ የሚገኝ ቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሴዎን -- ሐሴቦን

ይህ የሰውና የቦታ ስም ነው። እነዚህን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በሰላም ቃል

“ሰላምን ባቀረብላቸው” ወይም “ስለ ሰላም ከሚጠይቅ መልዕክቴ ጋር”

ወደ ቀኝም ሆነ ወደ ግራ ዘወር አልልም

ይህ ሐረግ ሁሌም በአንድ አቅጣጫ እንደሚሄዱ አጽንዖት ይሰጣል። ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። “አቅጣጫዬን አልቀይርም” ወይም “ሁሌም መስመሬን ጠብቄ እጓዛለሁ” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 2:28

የምበላውን ምግብ በገንዘብ ትሸጥልኛለህ፤ የምጠጣውንም ውሃ በገንዘብ ስጠኝ

ሙሴ እስራኤላውያን ከአሞራውያን እንደማይሰርቁና ሴዎንና ሕዝቡ ምግብና ውሃ እንዲሸጡላቸው ሴዎንን ይጠይቀዋል እንጂ ትዕዛዝ አይሰጠውም። ኢ.ት፡ “ለምበላው ምግብና ለምጠጣው ውሃ መክፈል እንዳለብኝ አስባለሁ”

እንድበላ - ሸጥልኝ - እንድጠጣ - ስጠኝ

ሙሴ ስለራሱ አድርጎ የሚናገረው እስራኤላውያንን ሲያመለክት ነው። ኢ.ት፡ “እንበላው ዘንድ - ለእኔና ለሕዝቤ ሸጥልኝ - እንጠጣው ዘንድ - ስጠን” (See: Synecdoche)

በእግሬ እንዳልፍ ብቻ ፍቀድልኝ

“በምድርህ ተራምደን ብቻ እንለፍ”

ዔር

ይህ የቦታ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 2:30

ሴዎን - ሐሴቦን

ይህ የሰውና የቦታ ስም ነው። እነዚህን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አምላካችሁ -- ጉልበታችሁ

ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራል፣ ስለዚህ በሁሉም አገባብ “ያንተ” የሚለው ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

አሳቡን አደነደን፣ ልቡንም ግትር አደረገ

ሁለቱም ሐረጎች ትርጉማቸው ተመሳሳይ ሲሆን አጽንዖት የሚሰጠው እግዚአብሔር “በጣም ግትር እንዲሆን አደረገው” ለማለት ነው። (See: Parallelism)

ሴዎንን እና ምድሩን በፊትህ አሳልፌ ልሰጥ

“ሴዎንን እና ምድሩን ለአንተ ልሰጥህ”

ምድሩ ለአንተ ይሆን ዘንድ ለመውረስ ጀምር

“ትወርሰው ዘንድ የእርሱን ምድር ለራስህ ውሰድ”

Deuteronomy 2:32

ሴዎን

ይህ የአንድ ንጉሥ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ያሀጽ

ይህ ሞዓብ ውስጥ የነበረ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 2:34

የእርሱን ከተሞች ሁሉ ወሰድን

“የንጉሥ ሴዎንን ከተሞች በሙሉ ያዝን”

እያንዳንዱን ከተማ ፈጽሞ አጠፋን

“በየከተማው ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ሁሉ ገደልን”

Deuteronomy 2:36

አሮዔር

ይህ በአርኖን ወንዝ ሰሜናዊ ዳርቻ የሚገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የአርኖን ሸለቆ

“አርኖን” የወንዝ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2:24 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ለእኛ ከባድ የሆነ ከተማ አልነበረም

ይህ አሉታዊ አገላለጽ በጦርነት የነበራቸው ስኬት ላይ አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ምንም እንኳን ከተማው ዙሪያው በረጃጅም ቅጥር የታጠረ ቢሆንም በየከተማው ያሉትን ሕዝቦች ማሸነፍ ችለናል። (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

አልሄዳችሁም

ሙሴ እስራኤላውያኑን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ” ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

የያቦቅ ወንዝ

ይህ በሴዎን እና በአሞናውያን ምድር መካከል ድንበር ያበጀ ወንዝ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 3

Deuteronomy 3:1

ዐግ - ሴዎን

እነዚህ የነገሥታት ስሞች ናቸው። እነዚህን በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ኤድራይ -- ሐሴቦን

እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። እነዚህ በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፣ “አትፍራው -- ሰጥቼሃለሁ -- በቁጥጥርህ ስር -- በሐሴቦን -- እንዳደረግኸው

እግዚአብሔር ሙሴ እስራኤላውያንን እንደሆነ ያህል ይናገረዋል፣ ስለዚህ “አትፍራ” የሚለው ትዕዛዝና “አንተ” እና “የአንተ” የሚለው አገባብ ሁሉ ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

አትፍራው -- በእርሱ ላይ -- ሕዝቡንና ምድሩን

እዚህ ጋ “እርሱን” እና “የእርሱ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ዐግን ነው።

ድልን ሰጥቼሃለሁ

እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን አስቀድሞ እንዳደረገው ቆጥሮ ይናገራል። (See:

Predictive Past)

በሴዎን ላይ እንዳደረግኸው በእርሱ ላይ ታደርጋለህ

“በእርሱ” የሚለው ቃል”በእርሱ ሕዝብ ላይ” ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ሴዎንን እንዳደረግኸው ዐግንና ሕዝቡን ታጠፋቸዋለህ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 3:3

ሕዝቡ ሁሉ በቁጥጥራችን ሥር ሆነ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር የዐግን ሕዝብ በሙሉ በቁጥጥራችን ሥር አደረገ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የእርሱ ከሆነው ሕዝብ አንድም አልቀረለትም

አስራኤላውያን ማንንም በሕይወት እንዳላስቀሩ አጽንዖት ለመስጠት ይህ ምጸት ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት፡ “የእርሱ የሆነው ሕዝብ ሁሉ ሞተ” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

ከስልሳዎቹ ከተሞች ያልወሰድነው አንድም አልነበረም

ይህ 60ዎቹን ከተሞች በሙሉ ስለመውሰዳቸው አጽንዖት የተሰጠበት ድርብ አሉታ ነው። ኢ.ት፡ “እያንዳንዱን ስልሳ ከተማ ወሰድን” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ስልሳ ከተሞች

“60 ከተሞች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የአርጎብን አካባቢ

ይህ በባሳን ውስጥ ያለ የአንድ አካባቢ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 3:5

እነዚህ ከተሞች በሙሉ በግምብ የታጠሩ ነበሩ

“እነዚህ ከተሞች በሙሉ በ -- የተጠበቁ ነበሩ”

በጣም ብዙ ከሆኑት ጋር

“በጣም ብዙ ከሆኑት በተጨማሪ” ወይም “በጣም ብዙ የሆኑትን ሳይጨምር”

ሴዎን

ይህ የአንድ ንጉሥ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 1፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሐሴቦን

ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 1፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እያንዳንዱን ከተማ በማጥፋት

“በየከተማው የሚኖሩትን ሰዎች በሙሉ በመግደል”

Deuteronomy 3:8

ከሁለቱ ነገሥታት እጅ

እዚህ ጋ “ከእጃቸው” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር “ከቁጥጥራቸው” ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ከሁለት ነገሥታት ቁጥጥር” ወይም “ከሁለቱ ነገሥታት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አሞራውያን -- ባሳን -- ኤድራይ -- ዐግ

“የአሞራዊ ሕዝቦች -- የባሳን ምድር -- የኤድራይ ከተማ -- ንጉሥ ዐግ”። እነዚህን በዘዳግም 1፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

በዮርዳኖስ ማዶ

ይህ ከእስራኤል በስተምስራቅ ከዮርዳኖስ ወንዝ ባሻገር ያለውን ምድር ያመለክታል። ሙሴ ይህንን በሚናገርበት ጊዜ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ ነበር። ይህንን በዘዳግም 1፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ”

በአርኖን ሸለቆ

እነዚህን ቃላት በዘዳግም 2፡24 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

የአርሞንዔም ተራራ -- ሢርዮን -- ሳኔር

እነዚህ በሙሉ ከባሳን በስተሰሜን ዳርቻ ላይ ያለው የአንድ ተራራ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በሜዳ

ይህ በአርኖን ወንዝና በገለዓድ ተራራ መካከል ያለ ረጅምና ሰፊ ስፍራ ነው።

ሰልካ

ይህ በኤድረ አቅራቢያ የምትገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 3:11

የትሩፉ -- ሰዎች በሚለኩበት

ይህ የንጉሥ ዐግ ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ራፋይም

ይህንን በዘዳግም 2፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ተመልከት!

“ለምነግርህ ጠቃሚ ነገር ትኩረት ስጥ”።

የሚኖረው -- በረባት አልነበረም?

ጸሐፊው የእስራኤል ሕዝብ ወደ ረባት እንዲሄዱና ዐግ ምን ያህል ታላቅ እንደነበረ ያዩ ዘንድ ለማስታወስ ጥያቄ ያቀርባል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “የሚኖረው -- በረባት ነበር” ወይም “በረባት -- ይኖራል” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ክንድ

አንድ ክንድ 46 ሴንቲ ሜትር ይረዝማል። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የርቀት መለኪያ የሚለውን ተመልከት)

ሰዎች በሚለኩበት መንገድ

“አብዛኛው ሰው በሚጠቀምበት የክንድ መለኪያ”

Deuteronomy 3:12

አሮዔር

የዚህን ከተማ ስም በዘዳግም 2፡36 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የአርኖን ሸለቆ

እነዚህን ቃላት በዘዳግም 2፡24 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

የአርጎብን ክልል

እነዚህን ቃላት በዘዳግም 3፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ያው ወሰን የራፋይም ምድር ተብሎ ይጠራል

ጸሐፊው የእስራኤል ሕዝብ ስለ ያዙት ምድር ዳራዊ መረጃ ማቅረብ ይጀምራል። የአንተ ቋንቋ ቀጥሎ የሚመጣው ዳራዊ መረጃ መሆኑን የሚያሳይበት መንገድ ካለ እርሱን እዚህ ጋ መጠቀም አለብህ። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ራፋይም

የዚህን ምድር ስም በዘዳግም 2፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 3:14

ኢያዕር

ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ጌሹራውያን እና ማዕካታውያን

እነዚህ ከባሳን በስተምዕራብ የሚኖሩ የሕዝብ ወገን ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሓቦት ኢያዕር

ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ ያደርጉ ይሆናል፡ “ ‘ሓቦት ኢያዕር’ ማለት ‘የኢያዕር የድንኳን መንደሮች’ ወይም ‘የኢያዕር ግዛት’ ማለት ነው”።

Deuteronomy 3:15

ሰጠሁ

እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

ለማኪር

ማኪር የምናሴ ልጅ ነበር። እርሱ ሙሴ ይህንን ምድር ከመስጠቱ በፊት ሞቶ ነበር። ስሙ ለሰውየው ተወላጆች ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ለማኪር ተወላጆች” (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የአርኖን ሸለቆ

ይህ የአርኖን የወንዝ ሸለቆ ስም ነው። እርሱ በሞዓብና በአሞራውያን መካከል ድንበር ያበጃል። ይህንን በዘዳግም 2፡24 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የያቦቅ ወንዝ

ይህ በሴዎን ምድር እና በአሞናውያን ምድር መካከል ድንበር ያበጀ ወንዝ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2፡37 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 3:17

ሌላው ወሰኑ ደግሞ

“የሮቤላውያን እና የጋዳውያን ድንበር ምዕራባዊ ወሰናቸው ነው”

ኪኔሬት

የኪኔሬት ባህር “የገሊላ ባህር” ወይም “የጌንሳሬጥ ሐይቅ” ተብሎም ይጠራል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የፈስጋ ተራራ

ይህ ከአባሪም ሰንሰለታማ ተራራ በስተሰሜን የሚገን የተራራ ስም ነው። (ስሞች

እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 3:18
በዚያን ጊዜ አዘዝኋችሁ
ሌሎች እስራኤላውያን እግዚአብሔር ተስፋ የሰጣቸውን የቀረውን ምድር ድል ያደርጉ ዘንድ የሮቤል ነገድ፣ የጋድ ነገድና ከፊሉ የምናሴ ነገድ እንዲያግዟቸው ሙሴ ያስታውሳቸዋል (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
መሣሪያችሁን ይዛችሁ በፊታቸው ታልፋላችሁ
"የጦር መሣሪያዎቻችሁን ትይዙና ቀድማችሁ የዮርዳኖስን ወንዝ ትሻገራላችሁ"
ወንድሞቻችሁ የእስራኤል ሰዎች
"እስራኤላውያን ባልንጀሮቻችሁ"
Deuteronomy 3:19
እግዚአብሔር ለወንድሞቻችሁ እረፍትን እስኪሰጥ
ጸሐፊው የማረፍን ችሎታ በስጦታ እንደሚሰጥ ቁሳዊ አካል አድርጎ ይናገራል። በተጨማሪም፣ "ማረፍ" የሚለው ቃል ጦርነት የሌለበትን ሰላማዊ ኑሮ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት: "ወድሞቻችሁ እንዲያርፉ እግዚአብሔር ይፈቅዳል" ወይም "በጦርነት መዋጋትን አቁመው በሰላም እንዲኖሩ እግዚአብሔር ለወንድሞቻችሁ ይፈቅዳል" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከዮርዳኖስ ማዶ
ይህ ከእስራኤል በስተምስራቅ ከዮርዳኖስ ወንዝ ባሻገር ያለውን ምድር ያመለክታል። ሙሴ ይህንን በሚናገርበት ጊዜ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ ነበር። በዘዳግም 1:1 ላይ እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። አ.ት: "ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ"
ከዚያም ትመለሳላችሁ
እግዚአብሔር ለእነዚህ ሦስት ነገዶች ምድራቸውን እንዲወርሱ ከመፍቀዱ በፊት ሌሎቹ ነገዶች መሬታቸውን መውረስ እንዳለባቸው ሙሴ አጽንዖት ይሰጣል። "የምትመለሱት ከዚያ በኋላ ብቻ ነው"።
Deuteronomy 3:21
ዕይኖችህ ዓይተዋል
እዚህ ጋ "ዐይኖችህ" የሚያመለክተው ኢያሱን ነው። አ.ት: "አንተ ዐይተሃል" (See: Synecdoche)
Deuteronomy 3:23
ለመንሁ
እዚህ ጋ "እኔ" የሚያመለክተው ሙሴን ነው። ይህ ማለት በጣም ቅንና ስሜታዊ በሆነ መንገድ እግዚአብሔርን ጠይቆታል።
ለአገልጋይህ ለማሳየት
እዚህ ጋ "አገልጋይህ" የሚለው ቃል ለአንድ ታላቅ ሥልጣን ላለው በትህትና የመናገር መንገድ ነው። አ.ት: "ለአገልጋይህ ልታሳየኝ"
ብርቱ እጅህ
እዚህ ጋ ፈሊጣዊ የሆነው "እጅ" መቆጣጠር ወይም ኃይል ማለት ነው። አ.ት: "ኃይልህ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ማድረግ የሚችል አምላክ ማነው?
ሙሴ እግዚአብሔር ያደረጋቸውን ሥራዎች ለማድረግ ኃይል ያለው ብቸኛው አምላክ እርሱ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት በጥያቄ መልክ ያቀርባል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት: ". . . የሚያደርግ ሌላ አምላክ የለም"። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
በሰማይ ወይም በምድር ላይ
የእነዚህ ሁለት ጽንፎች ትርጉም በአንድነት "የትም ቦታ" ማለት ንው። (See: Merism)
ከዮርዳኖስ ማዶ
"ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ"። ሙሴ ይህንን ቃል ለእግዚአብሔር በሚናገርበት ጊዜ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ ሞዓብ ውስጥ ነበረ።
Deuteronomy 3:26
እግዚአብሔር በእናንተ ምክንያት ተቆጥቶኝ ነበር
ይህ የሚያመለክተው ሙሴ በእስራኤል ሕዝብ ላይ በመቆጣቱ ምክንያት እግዚአብሔር እንዲያደርግ ያዘዘውን ያልታዘዘበትን ጊዜ ነው። ይህንን በዘዳግም 1፡37 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ፈስጋ
ይህንን በዘዳግም 3፡17 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዐይኖችህን አንሣ
"ዐይኖችህን አንሣ" የሚሉት ቃላት ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን ተመልከት ማለት ነው። አ.ት: "ተመልከት" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 3:28
ቤተ ፌጎር
ይህ በፈስጋ ተራራ አጠገብ በሞዓብ ውስጥ የሚገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 4
Deuteronomy 4:1
እኔ ላስተምራችሁ ነው
እግዚአብሔር እንዲያደርጉት የሚፈልግባቸውን ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ እየነገራቸው ነው።
እንድታደርጓቸው
"እና ታዘዟቸው"
በቃሉ ላይ አትጨምሩ -- ከእርሱም አትቀንሱ
እግዚአብሔር ሕዝቡ አዲስ ሕግ እንዲያዘጋጁ ወይም አስቀድሞ የሰጣቸውን ቸል እንዲሉ አይፈልግም።
Deuteronomy 4:3
ዐይኖቻችሁ ዐይተዋል
እዚህ ጋ "ዐይኖት" የሚያመለክቱት የእስራኤልን ሕዝብ ነው። አ.ት: "ዐይታችኋል" (See: Synecdoche)
በብዔልፌጎር ምክንያት
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት: "በብዔልፌጎር በሠራችሁት ኃጢአት ምክንያት" (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ፌጎር
ይህንን በዘዳግም 3፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
አምላካችሁ እግዚአብሔር ከመካከላችሁ አጥፍቷቸዋል
ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ "የአንተ" እና "አንተ" ነጠላ ቁጥር ናቸው። (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)
ከእግዚአብሔር ጋር የተጣበቃችሁ እናንተ
ጸሐፊው በእግዚአብሔር መታመንና እርሱን መታዘዝን በአካላዊ ሁኔታ አንድን ሰው ከመያዝ ጋር አመሳስሎ ይናገራል። አ.ት: "እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ጠንቃቆች የነበራችሁ እናንተ" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 4:5
ተመልከቱ
"ልብ በሉ"
በምድሪቱ መካከል እንደዚሁ ልታደርጉ ይገባል
"በምድሪቱ በምትኖሩበት ጊዜ ልትታዘዟቸው ይገባችኋል"
ጠብቋቸው፣ አድርጓቸውም
በመሠረቱ ሁለቱም ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን እንዲታዘዟቸው አጽንዖት ይሰጣል። አ.ት: "በጥንቃቄ ታዘዟቸው" (See: Doublet)
ይህ በሕዝቦች ፊት ጥበባችሁና ማስተዋላችሁ ነው
የነገር ስም የሆኑት "ጥበብ" እና "ማስተዋል" እንደ ቅጽል ሐረግ ሊተርጎሙ ይችላሉ፣ የነገር ስም የሆነው "ፊት" ሰዎች የአንድን ነገር ዕሴት እንዴት እንደሚፈርዱ ወይም እንደሚወስኑ ያመለክታል። አ.ት: "ጥበበኞችና አስፈላጊ የሆነውን የምትረዱ መሆናችሁን ለሕዝቦች የሚያሳየው ይህ ነው" (See: የነገር ስም እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይህ ታላቅ ሕዝብ ጥበበኛና አስተዋይ ሕዝብ ነው
"መንግሥት" የሚለው ቃል ለዚያ መንግሥት ሕዝብ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት: "የዚህ ታላቅ መንግስት ሕዝብ ጥበበኞችና አስተዋዮች ናቸው" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 4:7
እንደ እርሱ ያለ ታላቅ ሕዝብ ማን አለ? ዛሬ በዚያ ማን ታላቅ ሕዝብ አለ?


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እነዚህ ምላሽ የማይፈልጉ ጥያቄዎች እንደ መግለጫ ሆነው መተርጎም ይችላሉ። ኢ.ት፡ “እንደ እርሱ ያለ ታላቅ ሕዝብ የለም። ዛሬ ሌላ ታላቅ ሕዝብ የለም”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 4:9
ብቻ አስተውሉ -- ራሳችሁን ጠብቁ -- አትርሱ -- ዐይኖቻችሁ -- ልባችሁ -- ሕይወታችሁ -- ለልጆቻችሁና ለልጅ ልጆቻችሁ እንዲታወቁ አድርጉ -- በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ቆማችኋል
ሙሴ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤላውያን ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ”፣ “የአንተ” እና “ራሳችሁ” እንዲሁም “አስተውሉ”፣ “ጠብቁ” እና “አስታውቁ” የሚሉት ትዕዛዛት በሙሉ ነጠላ ቁጥር ናቸው። (ተውላጠ ስም እና Forms of You የሚለውን ተመልከት)
ብቻ አስተውሉ፣ ራሳችሁንም በጥንቃቄ ጠብቁ
“በጥንቃቄ አስተውሉ፣ እነዚህን ነገሮች ሁል ጊዜ ለማስታወስም እርግጠኞች ሁኑ”
አትርሱ -- ከልባችሁ አይራቁ
እነዚህ ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን የእስራኤል ሕዝብ ያዩትን ማስታወስ እንዳለባቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Parallelism)
ዐይኖቻችሁ ዐይተዋል
እዚህ ጋ “ዐይኖች” ሰውን ይወክላሉ። ኢ.ት፡ “ዐይታችኋል” (See: Synecdoche)
ሕዝቡን ሰብስብልኝ
“ሕዝቡን በአንድ ላይ ሰብስበህ ወደ እኔ አምጣልኝ”
Deuteronomy 4:11
ወደ ሰማይ ልብ በሚደርስ እሳት
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። “ልብ” የአንድ ነገር “መካከል” ወይም “ውስጠኛው ክፍል” ማለት ሲሆን “ሰማይ” ደግሞ የሚያመለክተው ጠፈርን ነው። ኢ.ት፡ “ወደ ጠፈር በሚደርስ እሳት” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በጨለማ፣ ደመና እና ድቅድቅ ጨለማ
እዚህ ጋ “ድቅድቅ ጨለማ” የሚገልጸው ደመናን ነው። ኢ.ት፡ “ጥቅጥቅ ባለ ጥቁር ደመና” (See: Hendiadys)
ድቅድቅ ጨለማ
ሌላው አማራጭ ትርጉም “ከባድ ደመና” የሚለው ነው።
Deuteronomy 4:13
ዐወጀ
“እግዚአብሔር ዐወጀ”
Deuteronomy 4:15
ስለዚህ ለራሳችሁ እጅግ ተጠንቀቁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ስለዚህ በምታደርጉት ነገር በጣም መጠንቀቅ ይኖርባችኋል” ወይም 2) “ነፍሳችሁን በጥንቃቄ ጠብቁ”
ራሳችሁን አታርክሱ
“ትክክል ያልሆነውን ነገር አታድርጉ”
በመሬት ላይ የሚሳብ
“በመሬት ላይ የሚጎተት”
Deuteronomy 4:19
ዐይኖችህን እንሥተህ -- ስትመለከት -- ስትቀርብ -- አምላክህ እግዚአብሔር
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት አገባቦችና “ማንሣት”፣ “መመልከት” እና “መቅረብ” ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)
ለማምለክ አትቅረብ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ማንም ለማምለክ እንድትፈልግ እንዲያደርግህ አትፍቀድ” ወይም “ታመልክ ዘንድ ለራስህ ፈቃድን አትስጥ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የሰማይ ሰራዊትን ሁሉ
“በጠፈር ላይ ለማየት የምትችላቸውን ነገሮች ሁሉ”። ይህ በሌላ አባባል ፀሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ያመለክታል።
አምላክህ እግዚአብሔር ለሕዝቦች ሁሉ ከሰጣቸው ድርሻ
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ሙሴ፣ ምግብን እንደመሳሰሉ ትናንሽ ነገሮች እግዚአብሔር ለሕዝብ ወገኖች አከፋፍሎ እንደሚሰጣቸው የሚናገረው ስለ ከዋክብት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ከብረት ምድጃ አውጥቶ አመጣችሁ
የማብሰያው ብረት እንደሚግል ሙሴ የሚናገረው ስለ ግብፅና እስራኤላውያን እንደ ብረት ሆነው በዚያ ይሠሩ ስለነበረው ከባድ ሥራ ነው። ኢ.ት፡ “ሰዎች ከባድ ሥራ እንድትሠሩ ከሚያደርጉበት ምድር አውጥቶ አመጣችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የርስቱ ሕዝብ እንድትሆኑለት
ይህ “የእርሱ ብቻ የሚሆንለት ሕዝብ” ተብሎ ሊተረጎም የሚችል ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 4:21
በእናንተ ምክንያት እግዚአብሔር ተቆጣኝ
ሙሴ በእስራኤል ሕዝብ ላይ በመቆጣቱ ምክያንት እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ የቀረበትን ጊዜ ያመለክታል። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ይህንን በዘዳግም 1:37 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
አምላክህ እግዚአብሔር ወደሚሰጥህ
ሙሴ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤላውያን ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)
Deuteronomy 4:23
ለራሳችሁ ተጠንቀቁ
“በጥንቃቄ አስተውሉ”
አምላክህ እግዚአብሔር የከለከለውን -- አምላክህ እግዚአብሔር
ሙሴ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤላውያን ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)
አምላክህ እግዚአብሔር ቀናተኛና የሚባላ እሳት ነው
ሙሴ፣ እግዚአብሔር ሲቆጣ የሚያደርጋቸውን ነገሮችን እሳት ከሚያቃጥልበት መንገድ ጋር ያነጻጽራል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ሌሎች አማልክትን እንድታመልክ ስለማይፈልግ እሳት እንደሚያደርገው አምላክህ እግዚአብሔር በብርቱ ይቀጣሃል፣ ያጠፋሃልም”።(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 4:25
በወለድህ -- አምላክህ እግዚአብሔር
እዚህ ጋ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት ነጠላ ቁጥሮች ናቸው።
መውለድ
የአንዱ አባት ወይም አያት መሆን
ራሳችሁን ብታረክሱ
“ትክክል ያልሆነውን ብታደርጉ”። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
እርሱን ታስቆጡት ዘንድ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ብታደርጉ
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “እርሱ ክፉ ያለውን በማድረግ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ታስቆጡታላችሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ሰማይና ምድር ምስክር እንዲሆኑ እጠራቸዋለሁ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) ሙሴ ለሚናገረው በሰማይ የሚኖሩትን ሁሉና ምድርን ምስክር አድርጎ ይጠራል ወይም 2) ሙሴ፣ ሰዎችን የሆኑ ይመስል ሰማይና ምድር እርሱ ለሚናገረው ምስክር እንዲሆኑ ይጠራቸዋል። (See: (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት and Personification)
ረጅም ዘመን አትቀመጡበትም
ረጅም ቀናት የረጅም ዕድሜ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ረጅም ዘመን መኖር አትችሉም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ነገር ግን ፈጽሞ ትጠፋላችሁ
በ4:27 ላይ እንደተመለከተው እያንዳንዱ እስራኤላዊ አይገደልም። እዚህ ጋ “ፈጽሞ መጥፋት” በጥቅሉ ብዙ እስራኤላውያን እንደሚሞቱ አጽንዖት መስጫ ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ነገር ግን እግዚአብሔር ብዙዎቻችሁን ያጠፋችኋል” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 4:27
እግዚአብሔር በሕዝቦች መካከል ይበትናችኋል
ሕዝቡ ዘር የሆነ ይመስል እግዚአብሔር እርሻ ላይ እንደሚበትናቸው ሙሴ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ወደተለያዩ አገሮች ይላካችኋል፣ በዚያ እንድትኖሩም ያስገድዳችኋል”።(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አርቆ ይሰዳችኋል
“ይልካችኋል” ወይም “ጠላቶቻችሁ እንዲወስዷችሁ ያደርጋል”
የሰው የእጅ ሥራ፣ እንጨትና ድንጋይ
እዚህ ጋ “የሰው እጅ” የሚያመለክተው ሰውን ራሱን ሲሆን “ሥራ -- እንጨትና

ድንጋይ” ደግሞ የቀረጿቸውን ጣዖታት ያመለክታሉ። ኢ.ት፡ “ሰዎች የሠሯቸው የእንጨትና የድንጋይ ጣዖታት” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 4:29
ነገር ግን ከዚያ
“ነገር ግን በሌሎች አገሮች በምትኖሩበት ጊዜ”
ትፈልጉታላችሁ
እዚህ ጋ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
እርሱን በምትፈልጉበት ጊዜ
“በእርግጥ እርሱን ለመፈለግ በምትሞክሩበት ጊዜ” ወይም “እርሱን በእርግጥ ለማወቅ በምትሞክሩበት ጊዜ”
በፍጹም ልባችሁና በፍጹም ነፍሳችሁ
እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የሰውን ውስጠኛ ማንነት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች በአንድነት የተነገሩት “ሙሉ በሙሉ” ወይም “በቅንነት” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 4:30
ይመጣብሃል
“ይደርስብሃል”
በእነዚያ በኋለኞቹ ቀናት
“ከዚያ በኋላ” ወይም “ከዚያም”
ድምፁን ትሰማለህ
እዚህ ጋ “መስማት” ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን ትሩሙ ማድመጥና መታዘዝ ነው። በተጨማሪም፣ “ድምፁን” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ሆኖ እርሱ በሚናገረው ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ኢ.ት፡ “እርሱ የሚላችሁን ታዘዙት” (የአነጋገር ዘይቤ እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 4:32
እንደ እናንተ የእግዚአብሔር ድምፅ ከእሳት መካከል ሲናገር የሰማና በሕይወት የኖረ ሕዝብ አለ?
እዚህ ጋ፣ ባለፈው ጊዜ እግዚአብሔር እንዴት አስገራሚ በሆነ መንገድ እንደተናገራቸው የእስራኤል ሕዝብ እንዲያስታውሱ ተደርገዋል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ከእናንተ በስተቀር እግዚአብሔር ከእሳት መካከል ተናግሮት በሕይወት የኖረ ሌላ ሕዝብ የለም”።(ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔር ድምፅ ሲናገር የሰማ
እዚህ ጋ እግዚአብሔር በድምፁ ተወክሏል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ሲናገር ድምፁን ሰምታችኋል” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 4:34
በጽኑ እጅና በተዘረጋች ክንድ
እዚህ ጋ “ጽኑ እጅ” እና “የተዘረጋች ክንድ” የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ጽኑ ኃይሉን በማሳየት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በዐይኖቻችሁ ፊት
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚያመለክቱት የሰውን ሁለንተናውን ነው። ኢ.ት፡ “በፊት ለፊታችሁ” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 4:35
እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ታይተዋል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች አሳይቶአችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እንድትሰሙ አድርጓችኋል -- እንድታዩ አድርጓችኋል
“እንደሰማችሁ አረጋግጧል . . . እንዳያችሁ አረጋግጧል”
አድርጓችኋል -- ሰምታችኋል
ሙሴ ከብዙ ዓመታት በፊት በሲና ተራራ የተናገራቸውን እነዚያኑ ሕዝቦች ይናገር ይመስል ለሕዝቡ ይናገራል። በመሠረቱ በሲና ተራራ የነበሩት ሰዎች እነዚህን ቃላት ለሚናገራቸው ሰዎች አባቶቻቸው ነበሩ። ኢ.ት፡ “አባቶቻችሁን … አድርጓል፣ አባቶቻችሁ ሰምተዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 4:37
አባቶቻችሁ
ይህ የሚያመለክተው አብርሃምን፣ ይስሐቅን፣ ያዕቆብንና የያዕቆብን ወንዶች ልጆች ነው።
በሀልዎቱ፣ በታላቅ ኃይሉ
“ከሀልዎቱ በሚመጣ በታላቅ ኃይሉ” ወይም “በታላቅ ኃይሉ”
Deuteronomy 4:39
በልብህ አኑረው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “አስታውሰው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በላይ በሰማይና በታች በምድር
“በሰማይ” እና “በምድር” የሚሉት ሁለት ሐረጎች ሁለት ጽንፎችን የሚያሳዩ ሲሆኑ ትርጉማቸው “በሁሉ ስፍራ” ማለት ነው። ኢ.ት፡ “በሁሉ ነገር ላይ” (See: Merism)
ዕድሜህ እንዲረዝም
ረጅም ቀናት ለረጅም ሕይወት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4፡26 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ረጅም ዕድሜ ለመኖር እንድትችል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 4:41
ቦሶር -- ራሞት -- ጎላን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 4:44
ሕጉ ይህ ነው
ይህ በቀጣዮቹ ምዕራፎች ሙሴ የሚሰጣቸውን ሕግጋት ያመለክታል።
ቤተ ፌጎር
ይህ በሞዓብ ውስጥ ፈስጋ ተራራ አጠገብ የሚገኝ ከተማ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 3፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሴዎን -- አሞራውያን -- ሐሴቦን
“ንጉሥ ሴዎን … አሞራውያን ሕዝቦች … የሐሴቦን ከተማ”። እነዚህን ስሞች በዘዳግም 1፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
Deuteronomy 4:47
ምድሩን
የንጉሥ ሴዎንን ምድር
የባሳን ንጉሥ ዐግ
ይህንን በዘዳግም 1፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ከዮርዳኖስ ማዶ በስተምስራቅ -- ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ
ይህ ከእስራኤል በስተምስራቅ፣ ከዮርዳኖስ ወንዝ ባሻገር ያለውን ምድር ያመለክታል። ሙሴ ይህንን በሚናገርበት ጊዜ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ ነበር። ኢ.ት፡ “ከዮርዳኖስ ወንዝ አቅጣጫ በስተምስራቅ … ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ በኩል”
አሮዔር
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2፡36 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የአርኖን ሸለቆ
ይህ የአንድ ቦታ ስም ነው። ይህንን በዘዳግም 2፡24 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሴዎን ተራራ -- የአርሞንኤም ተራራ
እነዚህ የተራራ ስሞች ናቸው። እነዚህን ስሞች በዘዳግም 3፡8-9 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
የዓረባ ባህር -- ፈስጋ ተራራ
እነዚህን ስሞች በዘዳግም 3፡17 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

---

Chapter 5
Deuteronomy 5:1
እስራኤልን ሁሉ ጠራ
እዚህ ጋ “ሁሉ” የሚለው ቃል ግነት ነው። ሙሴ በእስራኤል ያሉ ሁሉ ቃሉን እንዲሰሙና እንዲታዘዙ ፈልጓል፣ ይሁን እንጂ ሁሉ ይሰማው ዘንድ ምናልባት ድምፁ በጣም ከፍ ያለ አልነበረም። (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
ዛሬ በጆሮአችሁ የምናገረውን
እዚህ ጋ “ጆሮ” የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተናውን ነው። ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር አጽንዖት የሚሰጠው ሰዎቹ ኃጢአትን እንዳያደርጉ ሙሴ የነገራቸውን እንደሚያውቁና

ኃጢአት መሥራታቸውን አለማወቃቸውን እንዳይናገሩ ነው። ኢ.ት፡ “ዛሬ የምነግራችሁን” (Synecdoche እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ከአባቶቻችን ጋር ይህንን ቃል ኪዳን አላደረግም
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያደረገው ከኋለኛው የእስራኤል ትውልድ ጋር ደግሞ እንጂ በኮሬብ ከነበሩት ጋር ብቻ አይደለም ወይም 2) እግዚአብሔር በሩቅ ከነበሩት አባቶቻቸው አብርሃምን፣ ይስሐቅንና ያዕቆብን ከመሳሰሉት ጋር ይህንን ቃል ኪዳን አላደረገም፤ ይልቁንም ይህ ቃል ኪዳን የጀመረው በኮሬብ ከነበሩት እስራኤላውያን ጋር ነው።
Deuteronomy 5:4
ፊት ለፊት
ለእርስ በርሳቸው ቅርበት ያላቸው ሁለት ሰዎች ሲነጋገሩ እርስ በርስ እንደሚተያዩ ለመግለጽ የቋንቋህን የአነጋገር ዘይቤ ተጠቀም። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 5:7
በፊቴ ሌሎች አማልክት አይኑሩህ
“እኔን እንጂ ሌሎች አማልክትን ማምለክ የለብህም”
ከምድር በታች ያለውን ወይም ከውሃ በታች ያለውን
ይህ በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “ከእግሮቻችሁ በታች ባለው ምድር ላይ ያለ ወይም ከምድር በታች በውሃ ውስጥ ያለ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 5:9
አትስገዱላቸው ወይም አታገልግሏቸው
“የተቀረጹትን ምስሎች አታምልኩ ወይም እነርሱ የሚያዟችሁን አታድርጉ”
አታድርግ
“መቼም ቢሆን”
እኔ ቀናተኛ አምላክ ነኝ
“እኔን ብቻ እንድታመልኩኝ እፈልጋለሁ”
ለሚወዱኝ የቃል ኪዳን ታማኝነቴን ለሺዎች የማሳይ
“ታማኝነት” የሚለው የነገር ስም “በታማኝነት” ወይም “ታማኝ” ተብሎ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የሚወዱኝን ሺዎችን በታማኝነት እወዳቸዋለሁ” ወይም “ከሚወዱኝ ከሺዎች ጋር ለቃል ኪዳን ታማኝ እሆናለሁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ለሚወዱኝ ለሺዎች
አንዳንድ ትርጓሜዎች “ለሚወዱኝ ለአንድ ሺህ ትውልዶች” በሚል ይነበባሉ። “ሺዎች” የሚለው ቃል ለመቁጠር የሚበዛውን ቁጥር ለማመልከት የሚውል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ለሚወዱኝ ለእነርሱ እስከ ዘላለም” (Assumed Knowledge and Implicit Information፣ ፈሊጣዊ አነጋገር እና ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 5:11
የእግዚአብሔርን ስም አታንሣ
“በእግዚአብሔር ስም አትጠቀም”
አታድርግ
ይህንን በዘዳግም 5፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በከንቱ
“በግድየለሽነት” ወይም “ተገቢውን አክብሮት ባለመስጠት” ወይም “ለተሳሳቱ ዓላማዎች”
እግዚአብሔር ከበደል አያነጻውም
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር በደለኛ አድርጎ ይቆጥረዋል” ወይም “እግዚአብሔር ይቀጣዋል” (ድርብ አሉታዎች የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 5:12
ቅዱስ አድርገህ እንድትጠብቀው
“ለእግዚአብሔር እንድትለየው”
ሥራህን ሁሉ ሥራ
“የተለመደውን ሥራህን ሁሉ ሥራ”
ሰባተኛው ቀን
“ቀን 7”። እዚህ ጋ “ሰባተኛው” ለሰባት ተራ ቁጥር ነው። (See: Ordinal Numbers)
በእርሱ አትሥራበት
“በዚያን ቀን ምንም አትሥራ”
በደጆችህ ውስጥ
እዚህ ጋ “ደጆች” ከተማን ራሱን የሚያመላክት ነው። ኢ.ት፡ “በማኅበረሰብህ መካከል” ወይም “በከተማህ ውስጥ” ወይም “ከአንተ ጋር የሚኖሩ” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 5:15
አስታውስ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ማስታወስ አለብህ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በጽኑ እጅና በተዘረጋች ክንድ
እዚህ ጋ “ጽኑ እጅ” እና “የተዘረጋች ክንድ” የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያሳይ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4፡34 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ጽኑ ኃይሉን በማሳየት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 5:17
አታድርግ
ይህንን በዘዳግም 5፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
አታመንዝር
“ከሚስትህ በቀር ከሌላ ከማንም ጋር አትተኛ”
በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር
“ስለ ሌላው ሰው ውሸትን አትናገር”
Deuteronomy 5:21
አታድርግ
ይህንን በዘዳግም 5፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Deuteronomy 5:23
ድምፁን ሰምታችኋል
“ድምፅ” የሚለው ቃል የቃልን ድምፅ ወይም ተናጋሪውን ሰው የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የቃሉን ድምፅ ሰምታችኋል” ወይም “እግዚአብሔር ሲናገር ሰምታችኋል” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 5:25
ታዲያ ለምን እንሞታለን?
እግዚአብሔር ከተናገራቸው እንደሚሞቱ በማሰብ ፈርተው ነበር። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እንሞታለን ብለን ፈርተናል” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ያደረገ -- ከእኛ በቀር ማን አለ?
ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “… ያደረገ ከእኛ በቀር ሌላ አንድም ሕዝብ የለም”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ሥጋ ሁሉ
ይህ ሰዎችን ሁሉ ወይም ሕያዋን ፍጥረታትን ይወክላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች ሁሉ” ወይም “ሕያዋን ፍጥረታት በሙሉ” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 5:28
በነገራችሁኝ ጊዜ
እዚህ ጋ “እኔን” የሚያመለክተው ሙሴን ነው።
ምነው በኖራቸው
የአንተ ቋንቋ ለአንድ ነገር የሞኖርን ብርቱ ፍላጎት የሚገልጽ የአነጋገር ዘይቤ ካለው እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ያስፈልግህ ይሆናል። ኢ.ት፡ “ቢኖሩ በጣም ደስ ይለኝ ነበር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 5:31
ታስተምራቸዋለሁ
“የእስራኤልን ሕዝብ ታስተምራለህ”
Deuteronomy 5:32
ጠብቁ
ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ ትዕዛዝ እየሰጠ ነው።
ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበሉ
ይህ እግዚአብሔርን የማይታዘዘውን ሰው ከትክክለኛው መንገድ ከሚወጣው ሰው ጋር ያነጻጽረዋል። ኢ.ት፡ “በየትኛውም መንገድ ለእርሱ የማትታዘዝ መሆን የለብህም” ወይም “የሚላችሁን ሁሉ ማድረግ አለባችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዕድሜአችሁ እንዲረዝም
ረጅም ቀናት የረጅም ዕድሜ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ይህንን በዘዳግም 4፡40 ላይ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ረጅም ዕድሜ መኖር እንድትችሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

## Chapter 6

### Deuteronomy 6:1

ትጠብቁት ዘንድ -- ለመጠበቅ

“ትታዘዙ ዘንድ … ለመታዘዝ”

ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ

“ከዮርዳኖስ ወንዝ ወዲያ ማዶ ሄዳችሁ”

ዕድሜአችሁ እንዲረዝም

ረጅም ቀናት የረጅም ዕድሜ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህ በዘዳግም 4፡26 እንዳለው በተመሳሳይ “ረጅም ዘመን እንድትኖሩ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ዕድሜአችሁን እንዳረዝመው” ወይም “ረጅም ዕድሜ እንድትኖሩ አደርጋችሁ ዘንድ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

### Deuteronomy 6:3

እነርሱን ስማ

እዚህ ጋ “ስማ” ማለት ታዘዝ ሲሆን “እነርሱን” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት፣ ሕግጋትና ሥርዓት ስማ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information

ጠብቃቸው

“ታዘዛቸው”

ወተትና ማር የምታፈስውን ምድር

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “የተትረፈረፈ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር” ወይም “ከብት ለማርባትና ለእርሻ ምርጥ የሆነ ምድር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

### Deuteronomy 6:4

አምላካችን እግዚአብሔር አንድ ነው

“አምላካችን እግዚአብሔር አንድና ብቸኛ አምላክ ነው”

በሙሉ ልብህ፣ በሙሉ ነፍስህና በሙሉ ኃይልህ

እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እነዚህ ሦስቱ ሐረጎች በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት “በፍጹም” ወይም “በቅንነት” ለማለት ነው። በዘዳግም 4፡29 ላይ “በሙሉ ልብህ፣ በሙሉ ነፍስህ” የሚለውን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)

### Deuteronomy 6:6

እኔ የማዝህን

ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ የሚናገረው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ነው።

በልብህ ይኑር

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ሁል ጊዜ ማስታወስ አለብህ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በትጋት አስተምረው -- ተናገረው

“በትጋት እንድታስተምረው አዝሃለሁ … እንድትናገረው አዝሃለሁ”። አንባቢው እነዚህን እንደ ትዕዛዝ ሊረዳቸው ይገባዋል።

### Deuteronomy 6:8

እሰራቸው

ይህ “እነዚህን ቃላት በብራና ላይ ጻፋቸው፣ ብራናውን በትንሽ ኪስ ውስጥ አድርገውና ኪሱን እሰረው” ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በተራው “በአካል እዚያ ያሉ ያህል እነዚህን ቃሎች ታዘዛቸው” ለሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። ኢ.ት፡ “እነዚህን ቃላት እሰራቸው”። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእጅህ ላይ እንደ ምልክት

“ሕጌን እንድታስታውስ እንደሚያደርግህ አንዳች ነገር”

እንደ ግንባር ጌጥ ያገለግሉሃል

ይህ “እነዚህን ቃላት በብራና ላይ ጻፋቸው፣ ብራናውን በትንሽ ኪስ ውስጥ አድርገውና በዚያ እንዲቀመጥ ትንሹን ኪስ በግምባርህ ላይ እሰረው” ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በተራው “በአካል እዚያ ያሉ ያህል እነዚህን ቃሎች ታዘዛቸው” ለሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። ኢ.ት፡ “ቃሎቼ እንደ ግምባር ጌጥ ያገለግላሉ”። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክታብ

አንድ ሰው በግምባሩ ላይ የሚያደርጋቸው ጌጣ ጌጦች

ጻፍ

ይህ ትዕዛዝ ነው።

### Deuteronomy 6:10

አንተ ያልሠራኻቸውን ሰፋፊና በጣም ያማሩ ከተሞች

የከነዓንን ሕዝቦች በሚያሸንፉበት ጊዜ እነዚህ ከተሞች በሙሉ የእስራኤል ሕዝብ ይሆናሉ።

ከባርነት ቤት ያወጣህ

እዚህ ጋ “የባርነት ቤት” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እስራኤላውያን ባሪያዎች የነበሩበትን ስፍራ፣ ግብፅን ነው። ኢ.ት፡ “ባሪያ ሆነህ ከኖርክበት ስፍራ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

### Deuteronomy 6:13

አምላክህን እግዚአብሔርን ታከብራለህ፤ እርሱንም ታመልካለህ፣ በእርሱም ስም ትምላለህ

“ማክበር የሚኖርብህ አምላክህን እግዚአብሔርን እንጂ ሌላውን አይደለም፤ ማምለክ ያለብህ እርሱን ብቻ ነው፣ መማል የሚኖርብህም በእርሱ ስምና በእርሱ ስም ብቻ ነው”። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ሌሎች አማልክቶችን እንዳያመልኩ ወይም እንዳያገለግሉ ስለመናገሩ ምናልባት የአንተ ቋንቋ አጽንዖት የሚሰጥበት ሌላ መንገድ ይኖር ይሆናል።

በስሙ ትምላለህ

በእግዚአብሔር ስም መማል ማለት እግዚአብሔርን የመሓላው መሠረት ወይም ኃይል ማድረግ ማለት ነው። “በስሙ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። ኢ.ት፡ “ትምላለህ፣ እግዚአብሔር እንዲያጸናውም ትጠይቃለህ” ወይም “በምትምልበት ጊዜ ስሙን ትጠራለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመካከልህ

“በመካከልህ የሚኖር”

የአምላክህ የእግዚአብሔር ቁጣ በአንተ ላይ ይነዳል

ሙሴ የእግዚአብሔርን ቁጣ አንድን ነገር ለማቃጠል እሳት ከሚለኩሱ ሰው ጋር ያነጻጽረዋል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ቁጣን መለኮስ በጣም የመቆጣት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ቁጣውን ያነዳል” ወይም “አምላክህ እግዚአብሔር በጣም ይቆጣል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከ -- ያጠፋሃል

“ምንህም እስከማይተርፍ ድረስ ያጠፋሃል”

### Deuteronomy 6:16

እግዚአብሔርን አትፈታተነው

እዚህ ጋ “መፈተን” ማለት እግዚአብሔርን መገዳደርና ትክክለኛ መሆኑን እንዲያረጋግጥ ማስገደድ ማለት ነው።

ማሳህ

ይህ በምድረ በዳው ውስጥ ያለ የቦታ ስም ነው። ተርጓሚው ምናልባት፣ “‘ማሳህ’ የሚለው ስም ትርጉም ‘መፈተን’ ማለት ነው” የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይኖርበት ይሆናል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

### Deuteronomy 6:18

በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛና መልካም የሆነውን አድርግ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ትዕዛዝና በረከት ነው። እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ከታዘዙት ከእርሱ በረከትን ይቀበላሉ። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ትክክልና መልካም የሚለውን አድርግ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

### Deuteronomy 6:20

ያዘዛችሁ የቃል ኪዳኑ ድንጋጌዎች ምንድናቸው

በዚህ ጥያቄ “የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች” ትርጉማቸውንና ዓላማቸውን ይወክላሉ። ኢ.ት፡ “የታዘዙት የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች ለአንተ ምን ትርጉም አላቸው” ወይም “የታዘዝከውን የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች መታዘዝ የሚኖርብህ ለምንድነው”(ፈሊጣዊ

አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ልጅህ
ይህ የሚያመለክተው ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል የሚነግራቸው የትልልቆቹ እስራኤላውያንን ልጆች ነው።
በጽኑ እጅ
እዚህ ጋ “ጽኑ እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። ይህንን በዘዳግም 4፡34 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡ ኢ.ት፡ “በጽኑ ኃይሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በቤቱ ሁሉ
እዚህ ጋ “ቤቱ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነው። ኢ.ት፡ “በሕዝቡ ሁሉ ላይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በዐይኖቻችን ፊት
እዚህ ጋ “ዐይኖቻችን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተናውን ነው። ኢ.ት፡ “ልናያቸው በምንችልበት” (See: Synecdoche)

ሊያስገባን
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም መብራራት ይችላል። ኢ.ት፡ “ወደ ከነዓን ሊያስገባን” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 6:24
በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሀልዎች” ወይም “እግዚአብሔር ሊያየን በሚችልበት”
ጠብቅ
ሁል ጊዜ፣ በየትኛውም ሁኔታ ታዘዝ
ይህ ጽድቃችን ይሆናል
“ይህ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠበቅን ያመለክታል። ይህ እግዚአብሔር ጻድቅ አድርጎ እንደሚቆጥራቸው የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ጻድቅ አድርጎ ይቆጥረናል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 7
Deuteronomy 7:2
አሳልፎ ይሰጥሃል
አንድ ሰው ለሌላው እንደሚሰጠው ቁሳዊ ነገር ሙሴ የሚናገረው ስለ ድል ነው። ኢ.ት፡ “እንድታሸንፋቸው ያስችልሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ስታሸንፋቸው
እዚህ ጋ “እነርሱን” የሚያመለክተው በዘዳግም 7፡1 የተጠቀሱትን ሰባት አገሮች ነው።
Deuteronomy 7:4
እነርሱ
“ልጆችህ ከሌሎች አገሮች ሕዝቦች ጋር እንዲጋቡ ብትፈቅድ፣ የሌሎች አገሮች ሰዎች”
ስለዚህ የእግዚአብሔር ቁጣ በአንተ ላይ ይነድዳል
ሙሴ የእግዚአብሕርን ቁጣ እሳትን ከሚለኩስ ሰው ጋር ያነጻጽረዋል። ይህ የሚያስቆጣውን ስለሚያጠፋበት ስለ እግዚአብሔር ኃይል አጽንዖት ይሰጣል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በአንተ ላይ እግዚአብሔር ቁጣውን ያነዳል” ወይም “ከዚያም እግዚአብሔር በአንተ ላይ በጣም ይቆጣል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በአንተ ላይ
“አንተ” የሚለው ቃል እስራኤላውያንን ሁሉ ስለሚመለከት ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
የምታደርጉት -- አፍርሱ -- ስበሩ -- ቁረጡ -- አቃጥሉ
እዚህ ጋ ሙሴ የሚናገረው ለእስራኤላውያን ሁሉ ነው፣ ስለዚህ እነዚህ ቃላት ብቁ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)
Deuteronomy 7:6
የተለየ ሕዝብ ናችሁ
እግዚአብሔር ሕዝቡን እስራኤልን የእርሱ እንዲሆኑ በተለየ ሁኔታ መምረጡ ከሌሎች ሕዝቦች እንደለያቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በምድር ፊት ከሚኖሩት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት “በምድር ላይ ከሚኖሩት” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 7:7
ፍቅሩን በእናንተ ላይ አላደረገም
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ሌሎችን ከወደደበት በላይ እናንተን አልወደዳችሁም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በጽኑ እጅ
እዚህ ጋ “ጽኑ እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። እነዚህ ቃላት በዘዳግም 4፡34 ላይ ደግሞ ይታያሉ። ኢ.ት፡ “በጽኑ ኃይሉ”(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 7:9
ለሺህ ትውልድ
“ለ1,000 ትውልድ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ለሚጠሉት በፊታቸው ይበቀላቸዋል
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም “እግዚአብሔር እንደቀጣቸው ያውቁ ዘንድ በግልጽና በፍጥነት ይበቀላቸዋል” የሚል ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በሚጠሉት በማናቸውም ላይ አይዘገይም
“አይዘገይም” የሚለው ቃል እግዚአብሔር በብርቱ ይቀጣል የሚለውን አጽንዖት ዝቅ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር የሚጠሉትን ሁሉ በብርቱ ይቀጣቸዋል” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 7:12
ያበዛሃል
“የሕዝብህ ቁጥር እንዲበዛ ያደርጋል”
የማህፀንህን ፍሬ
ይህ “ልጆችህን” የሚል የአነጋገር ዘይቤ ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የመሬትህን ፍሬ
ይህ “ምርትህን” የሚል የአነጋገር ዘይቤ ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የከብትህን ብዛት
“ከብትህ እንዲበዛ”
Deuteronomy 7:14
ከሌሎች ሕዝቦች የበለጠ ትባረካለህ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሌሎች ሕዝቦችን ከምባርክበት በበለጠ እባርክሃለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በመካከልህ ወይም በከብቶችህ መካከል የማይወልድ ወንድ ወይም መካን ሴት አይኖርም
ሙሴ ሁሉም ልጆች ሊኖሯቸው እንደሚችሉ አጽንዖት ለመስጠት አሉታዊ መግለጫዎችን ይጠቀማል። ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እናንተ ሁላችሁም ልጆች ይኖሯችኋል፣ ከብቶቻችሁም ይበዛሉ” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)
በመካከልህ -- ከብቶችህ
“አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት ብዙ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)
በሽታን ሁሉ ከአንተ አርቃለሁ
“እንደማትታመም እርግጠኛ ሁን” ወይም “ፍጹም ጤና እንድትሆን እጠብቅሃለሁ”
በአንተ ላይ -- ክፉ በሽታዎችን ሁሉ፣ ነገር ግን በሚጠሉህ ሁሉ ላይ ያመጣቸዋል
ሙሴ በሽታን እግዚአብሔር በሰዎች ጫንቃ ላይ እንደሚጭነው ከባድ ቁስ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እርሱ በየትኛውም ክፉ በሽታ እንድትታመም አያደርግህም … ነገር ግን ጠላቶችህ በእርሱ እንዲታመሙ ያደርጋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 7:16
ሕዝቦችን ሁሉ ታጠፋቸዋለህ
“ሁሉንም የሕዝብ ወገኖች ፈጽመህ እንድታጠፋቸው አዝሃለሁ”
ዐይንህ አይራራላቸው
ይህ ትዕዛዝ ነው። ሙሴ ዐይን የሚያየው ራሱን ዐይንን እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “የምታየው እንድትራራላቸው እንዲያደርግህ አትፍቀድ” ወይም “የምታደርገው እንደሚጎዳቸው በማየትህ ምክንያት አትራራላቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አታምልክ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“በፍጹም አታምልክ”
ያ ለአንተ ወጥመድ ይሆንብሃል
ሕዝቡ ሌሎች አማልክትን ካመለኩ በወጥመድ እንደሚያዝ እንስሳ ይሆናሉ፣ ከዚያም ማምለጥ አይችሉም። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 7:17
በልብህ ---- ብትል -- አትፍራ
ሀገራቱ ከእነርሱ ይልቅ ብርቱዎች እንደሆኑ ቢያስተውሉም እንኳን ሕዝቡ መፍራት የለባቸውም። ኢ.ት: “ምንም እንኳን በልብህ -- ብትናገር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በልብህ ብትናገር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ብታስብ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እንዴት ላስወጣቸው እችላለሁ?
ሕዝቡ ሌሎች አገራትን ስለ ፈሩበት ስሜት አጽንዖት ለመስጠት ሙሴ በጥያቄ መልክ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል።ኢ.ት: “ላሸንፋቸው አልችልም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አስታውስ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ማስታወስ አለብህ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ዐይኖችህ ዐይተዋል
እዚህ ጋ “ዕይኖችህ” የሚወክለው የሰውን ሁለንተና ነው። ኢ.ት: “ያየኸው” (See: Synecdoche)
ጽኑውን እጅ፣ የተዘረጋችውንም ክንድ
እዚህ ጋ “ጽኑ እጅ” እና “የተዘረጋች ክንድ” የእግዚአብሔርን ኃይል የሚገልጹ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። ይህንን በዘዳግም 4:34 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እና በጽኑ ኃይሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 7:20
ከዚህም በላይ፣ እግዚአብሔር
“በተጨማሪም፣ እግዚአብሔር”
ተርብ ይልክባቸዋል
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) ሰዎችን እንዲነድፉና እንዲያሳምሙ እግዚአብሔር ትክክለኛ በራሪ ነፍሳትን ይልክባቸዋል፣ ወይም 2) እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲፈሩና እንዲሸሹ ያደርጋቸዋል።
ከአጠገብህ ይጠፋሉ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ከዚህ በኋላ እንዳታያቸው ይሞታሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
አታያቸውም
“ከቶ”
ታላቅና የሚያስፈራ አምላክ
“ታላቅና ድንቅ አምላክ” ወይም “ሰዎቹን እንዲፈሩ የሚያደርግ ታላቅ አምላክ”
ጥቂት በጥቂት
“በዝግታ”
Deuteronomy 7:23
በእነርሱ ላይ ድልን ይሰጥሃል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “እንድታሸንፍ ያስችልሃል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በእነርሱ ላይ ድልን
“ከሌሎች ሕዝቦች በሆኑት ሰራዊቶች ላይ ድልን”
በከፍተኛ ሁኔታ ያደናግራቸዋል
“በአግባቡ ማሰብ እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል”
እስኪጠፉ ድረስ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እስክታጠፋቸው ድረስ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ከሰማይ በታች ስማቸው እንዲደመሰስ ታደርጋለህ
እስራኤላውያን የእነዚያን አገራት ሕዝቦች በሙሉ ፈጽመው ስለሚያጠፏቸው ወደፊት ማንም አያስታውሳቸውም። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በፊትህ የሚቆም
“አንተን በመቃወም የሚቆም” ወይም “አንተን በመቃወም ራሳቸውን መከላከል”
Deuteronomy 7:25
ታቃጥላለህ
ይህ ትዕዛዝ ነው።
አማልክቶቻቸውን
“የሌሎች ሕዝቦችን አማልክት”
አትቅና -- በእርሱ አትጠመድ
እነዚህ ቃላት አማልክቶቹን እንዲያቃጥሉ በተሰጣቸው መመሪያ ላይ ተጨማሪዎች ናቸው
በእርሱ ትጠመዳለህ
በጣዖታቱ ላይ ያለውን ወርቅ ወይም ብር መውሰድ እንኳን ሕዝቡ እንዲያመልኳቸው ሊያደርጋቸው ይችላል። ይህንን በማድረጋቸው በወጥመድ እንደተያዘ እንስሳ ይሆናሉ። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ወጥመድ ይሆንባችኋል” (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት))
ይህ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አስጸያፊ ነው
እነዚህ ቃላት ሕዝቡ ጣዖታቱን እንዲያቃጥሉ እግዚአብሔር ለምን እንደፈለገ ይነግሩናል። “አምላካችሁ እግዚአብሔር በጣም ስለሚጠላው ይህንን አድርጉ”
ፈጽመህ ትጠላዋለህ፣ ትጸየፈዋለህም
“መጥላት” እና “መጸየፍ” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ሆኖ ሳለ ለጥላቻው ጥልቅነት አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት: “ፈጽመህ ትጠላዋለህ” (See: Doublet)
እርሱ ለጥፋት የተለየ ነው
እግዚአብሔር አንድን ነገር መርገሙና ሊያጠፋው መማሉ ነገሩን ከየትኛውም ነገር ለይቶ እንደሚያስቀምጠው ሆኖ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “እርሱን እግዚአብሔር ለጥፋት ለይቶ አስቀምጦታል” (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊድምፅ የሚለውን ተመልከት))

---

Chapter 8
Deuteronomy 8:1
በሕይወት እንድትኖሩና እንድትበዙ፣ አባቶቻችሁ -- ገብታችሁ እንድትወርሱ -- መጠበቅ አለብህ
“አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት አገባቦች በሙሉ እንዲሁም ግሦቹ ብዙ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)
አስታውስ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ማስታወስ አለብህ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
አርባ ዓመታት
“40 ዓመታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ትሁት ሊያደርግህ
“ምን ያህል ደካማና ኃጢአተኛ እንደሆንክ ሊያሳይህ”
ለማወቅ
“ለመግለጥ” ወይም “ለማሳየት”
በልብህ የነበረውን
ልብ የሰው ባህርይ ምሳሌ ነው። ኢ.ት: “ምን ዓይነት ሕዝብ እንደሆንክ” ወይም “ባህሪህን እንዴት መግለጥ እንዳለብህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 8:3
ትሁት አደረገህ
“እግዚአብሔር ምን ያህል ደካማና ኃጢአተኛ መሆንህን አሳየህ”። በዘዳግም 8:2 ላይ “ትሁት ሊያደርግህ” የሚለው ቃል እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።
መናን መገበህ
“እንድትበላው መናን ሰጠህ”
ሰዎች በሕይወት የሚኖሩት በእንጀራ ብቻ አይደለም
እዚህ ጋ “እንጀራ” የሚወክለው ሁሉንም የምግብ ዓይነት ነው። ኢ.ት: “ሰዎች በሕይወት ለመኖር እንዲችሉ የሚፈልጉት ምግብ ብቻ አይደለም” (See: Synecdoche)
ሰዎች በሕይወት የሚኖሩት ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ነገር ሁሉ ነው
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር አፍ” በፈሊጣዊ አነጋገር እግዚአብሔር የሚናገረው ቃል ማለት ነው። ኢ.ት: “ሰዎች በሕይወት መኖር እንዲችሉ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መታዘዝ አለባቸው” ወይም “ሰዎች በሕይወት መኖር እንዲችሉ እግዚአብሔር


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚነግራቸውን መፈጸም አለባቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 8:4
አርባ ዓመታት == ልብሳችሁ
ይህ “ማስታወስ” የሚገባቸው የመጨረሻው ንብረታቸው ነው (ዘዳግም 8፡2)
አርባ ዓመታት
“40 ዓመታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
አስቡ == ጠብቁ == በመንገዱ ሂዱ፣ እርሱንም አክብሩት
ይህ በዘዳግም 8:1-2 የሚጀምረውን የትዕዛዛቱን ዝርዝር የሚቀጥል ነው።
ስለዚህ ነገር በልብህ አስብ
እዚህ ጋ ፈሊጣዊ አነጋገር የሆነው “ልብ” የሚወክለው የአንድን ሰው አሳብና ማስተዋል ነው። ኢ.ት፡ “አስተውል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 8:7
የ == ምድር
“ከ -- ምድር” ወይም “ -- ያላትን ምድር”
Deuteronomy 8:9
የምትበላውን እንጀራ የማታጣባት ምድር
ይህ ምጸታዊ አነጋገር በአዎንታዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የተትረፈረፈ ምግብ የምታገኝበትን ምድር” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)
ምንም ነገር የማታጣበትን ሀገር
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የምትፈልገውን ሁሉ የምታገኝበት” (ድርብ አሉታዊ የሚለውን ተመልከት)
ድንጋዮቹ ብረት የሆኑበት
ድንጋዮቹ በብረት ማዕድን የተሞሉ ናቸው። የብረት ማዕድን ሰይፍና ማረሻ ለመሥራት የሚያገለግል ጠንካራ ብረት ነው።
መዳብ ትቆፍራለህ
“የመዳብ ማዕድን ታወጣለህ”። መዳብ የቤት ውስጥ መገልገያዎችን ለመሥራት የሚያገለግል ለስለስ ያለ ብረት ነው።
ትበላለህ፣ ትጠግባለህም
“እስክትጠግብ ድረስ የምትበላው በቂ ምግብ ይኖርሃል”
ትባርካለህ
“ታመሰግናለህ” ወይም “ምስጋናን ታቀርባለህ”
Deuteronomy 8:11
ትዕዛዞቹን ቸል አትበል
“ትዕዛዞቹን መጠበቅህን አታቁም” ወይም “ትዕዛዛቱን መጠበቅህን ቀጥል”
በበላህና በጠገብህ ጊዜ
“የምትበላው በቂ ምግብ በሚኖርህ ጊዜ”
ልብህ ይነሣሣል
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው ውስጠኛውን ሰው ነው። መታበይና ከእንግዲህ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ እንደ ሰው ልብ መነሣሣት ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ትታበያለህ፣ ከእንግዲህም እግዚአብሔርን አትታዘዝም” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 8:13
መንጋዎችህ
“የከብትህ፣ የበግና የፍየል መንጋህ”
መብዛት
በቁጥር እጅግ መጨመር
ያለህ ሁሉ ሲበዛልህ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በጣም ብዙ ነገሮች አሉህ” ወይም “በጣም ብዙ ንብረት አለህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ልብህ ይነሣሣል
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው ውስጠኛውን ሰው ነው። መታበይና ከእንግዲህ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ እንደ ሰው ልብ መነሣሣት ሆኖ ተነግሯል። በዘዳግም 8፡ 12 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ትታበያለህ፣ ከእንግዲህም እግዚአብሔርን አትታዘዝም” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ያወጣህን
ሙሴ ለእስራኤላውያን ስለ እግዚአብሔር የሚያውቁትን ማስታወስ ጀምሯል (ለይቶ ማሳወቅ ማሳወቅን ወይም ማስታወስን ሲቃረን የሚለውን ተመልከት)
ከባርነት ቤት ያወጣህ
ይህ በግብፅ በባርነት የነበሩበትን ጊዜ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ባሪያዎች ከነበራችሁበት ስፍራ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 8:15
በመጨረሻ -- የመራህን
ሙሴ ለእስራኤላውያን ስለ እግዚአብሔር የሚያውቁትን ማስታወስ ቀጥሏል (ዘዳግም 8:14)። (ለይቶ ማሳወቅ ማሳወቅን ወይም ማስታወስን ሲቃረን የሚለውን ተመልከት)
የመራህ -- ያመጣህ -- መገበህ
“የመራህ እግዚአብሔር … ያመጣህ እግዚአብሔር … እግዚአብሔር መገበህ”
ተናዳፊ እባብ
“መርዘኛ እባብ”
የተጠማ ምድር
ይህ ሐረግ ልክ ሰው ውሃ በሚፈልግበት ጊዜ እንደሚጠማ ምድሪቱ መጠማቷን ይገልጻል። ኢ.ት፡ “ደረቅ ምድር” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
መልካም ሊያደርግልህ
“ሊረዳህ” ወይም “ለአንተ መልካም ስለነበረ”
ሆኖም በልብህ -- ትል ይሆናል
ይህ ምናልባት ሰዎች ልባቸው “በሚታበይበት” እና “እግዚአብሔርን በሚረሱበት” ጊዜ የሚያደርጉት ሦስተኛው ነገር ነው። (ዘዳግም 8፡14)። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ኃይሌና የእጄ ብርታት ይህንን ሁሉ ሀብት አስገኘልኝ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው የአንድን ሰው ኃይል ወይም ችሎታ ነው። ኢ.ት፡ “እኔ በጣም ብርቱና ኃይለኛ ስለሆንኩኝ ይህንን ሀብት አግኝቻለሁ” ወይም “እነዚህን ነገሮች ሁሉ በራሴ ኃይልና ችሎታ አገኘኋቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 8:18
ነገር ግን ትዝ ይበልህ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ትዕዛዝ ነው። ኢ.ት፡ “ነገር ግን አስታውስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ያጸና ዘንድ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እርሱ በዚህ መንገድ ያጸናል” ወይም 2) “በዚህ መንገድ እርሱ ሊያጸና የታመነ ነው”
ያ -- ዘንድ
“ስለዚህ ይችላል”
ማጽናት
እንዲቆም ወይም እንዲኖር ማድረግ
ዛሬ እንደሆነው ሁሉ
“አሁን እንደሚያደርገው ሁሉ” ወይም “ቃል ኪዳኑን አሁን እንዳጸናው ሁሉ”
ሌሎች አማልክቶችን ብትከተል
መከተል የመታዘዝ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ሌሎች አማልክቶችን ማገልገል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በአንተ ላይ -- ብት -- በፊትህ -- ትጠፋላችሁ -- አትሆኑም -- አምላክህ
“አንተ” የሚሉት እነዚህ አገባቦች ሁሉ ብዙ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)
በእናንተ ላይ እመሰክራለሁ
“አስጠነቅቃችኋለሁ” ወይም “በምስክሮች ፊት እነግራችኋለሁ”
በእርግጥ ትጠፋላችሁ
“ያለምንም ጥርጥር ትሞታላችሁ”
በፊታችሁ
“በፊት ለፊታችሁ”
የእግዚአብሔርን ድምፅ ስላልሰማችሁ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” ማለት እግዚአብሔር ያደርጉት ዘንድ ለሕዝቡ የሚነግራቸው ማለት ነው። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ስላልታዘዛችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Chapter 9


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Deuteronomy 9:1
እስራኤል ሆይ፣ ስማ
“እስራኤል” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ የሚመለከት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ ስማ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለመውረስ
“መሬታቸውን ለመውሰድ”
እስከ ሰማይ ድረስ የተመሸጉትን
ይህ ከተሞቹ በጣም ሰፊና ጠንካራ በመሆናቸው ምክንያት ሕዝቡ መፍራታቸውን አጽንዖት ለመስጠት የተደረገ ግነት ነው። በዘዳግም 1:28 ላይ ተመሳሳዩን ቃላት እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ሰማይ የሚደርሱ የሚመስሉ ግንቦች ነበሯቸው” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
የዔናቅ ልጆች
በጣም ረጃጅምና ኃያላን የነበሩ የዔናቅ ሕዝብ ተወላጆች ናቸው። ተመሳሳዮቹን ቃላት በዘዳግም 1:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።(See: Assumed Knowledge and Implicit Information እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
በዔናቅ ልጆች ፊት ማን መቆም ይችላል?
ይህ ማለት የዔናቅ ልጆች ኃያላን በመሆናቸው ሰዎች ይፈሯቸው ነበር። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “በዔናቅ ልጆች ፊት ራሱን መከላከል የሚችል አልነበረም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 9:3
ዛሬ
ሙሴ ፀሐይ ከጠለቀችበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ቀናትና ሳምንታት ስለጀመሩባት ስለዚያች ቀን ማለቱ ነው።
እንደሚባላ እሳት
እግዚአብሔር የሌሎች ሕዝቦችን ሰራዊት ለማጥፋት የሚችል ኃያል ነው። (See: Simile)
በፊትህ ድል ያደርጋቸዋል
“ልትቆጣጠራቸው እንድትችል ደካማ ያደርጋቸዋል”
Deuteronomy 9:4
በልብህ -- አትበል
እዚህ ጋ “በልብህ” ማለቱ “በአሳብህ” ለማለት ነው። ኢ.ት፡ “በራስህ አታስብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ወግቶ ያስወጣቸዋል
“ሌሎች ሕዝቦችን አሳዶ ሲያስወጣቸው”
Deuteronomy 9:5
በልብህ ቅንነት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። “ዘወትር የምታስበውና የምትመኘው ትክክለኛውን ነገር ስለሆነ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ቃሉ ይፈጸም ዘንድ
“ቃሉ” የሚለው ፈሊጣዊ በሆነ አነጋገር የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ነው። ኢ.ት፡ “ተስፋውን ይፈጽም ዘንድ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለአባቶቻችሁ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ
አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ሙሴ ለሚናገራቸው ሰዎች “አባቶቻቸው” ናቸው።
Deuteronomy 9:7
አስታውስ፣ ከቶም አትርሳ
ሙሴ በማስታወስ አስፈላጊነት ላይ አጽንዖት ለመስጠት ተመሳሳዩን ትዕዛዝ በአዎንታዊና በአሉታዊ ቃላት ይደግማቸዋል። ኢ.ት፡ “ለማስታወስ ተጠንቀቅ” (See: Doublet)
እግዚአብሔርን እንዴት ለቁጣ እንዳነሣሣኸው
እዚህ ጋ “አንተ” የሚያመለክተው ከሙሴ ጋር ያሉትንና በተጨማሪም በቀደመው ትውልድ የነበሩትን እስራኤላውያንን ነው። (See: Forms of You)
ወደዚህ ስፍራ ከመጣህ፣ አመፀኛ ነበርክ -- ለቁጣ አነሣሣኸው -- ሊያጠፋህ
“አንተ” የሚሉት ሁሉም አገባቦች ብዙ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)
ወደዚህ ስፍራ
ይህ የሚያመለክተው የዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆን ነው።
Deuteronomy 9:9
የድንጋይ ጽላቶች፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የኪዳኑን ጽላቶች
እዚህ ጋ “የድንጋይ ጽላቶች” ይኸውም እግዚአብሔር አሥሩን ትዕዛዛት የጻፈባቸውን መሆኑን ሁለተኛው ሐረግ ግልጽ ያደርጋል። (See: Parallelism)
አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
“40 days and 40 nights” “40 ቀንና 40 ሌሊት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር የነገራችሁ ቃል ሁሉ በእነርሱ ላይ ተጽፈው ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ለእናንተ የነገራችሁን እነዚያኑ ቃላት በእነርሱ ላይ ጻፋቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ከእሳት መካከል -- እግዚአብሔር ተናገራችሁ
እግዚአብሔር እንደ ሰው በእሳት መካከል ቆሞ በታላቅ ድምፅ የተናገረ ይመስል ነበር።
በጉባዔ ቀን
የነገር ስም የሆነው “ጉባዔ” እንደ ግሥ “በአንድነት መሰብሰብ” ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኢ.ት፡ “እናንተ እስራኤላውያን ሁላችሁ መጥታችሁ በአንድ ስፍራ በተገናኛችሁበት ቀን” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 9:11
አርባ ቀና አርባ ሌሊት
“40 ቀንና 40 ሌሊት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶች፣ የኪዳኑን ጽላቶች
እዚህ ጋ “ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶች” የተባሉት እግዚአብሔር አሥሩን ትዕዛዛት የጻፈባቸውን መሆኑን ሁለተኛው ሐረግ ግልጽ ያደርጋል። (See: Parallelism)
ሕዝብህ -- ራሳቸውን አርክሰዋል
“ሕዝብህ … የተሳሳተ ነገር እያደረጉ ነው” እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ካዘዝኳቸው መንገድ ዘወር ብለዋል
ሙሴ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠበቅን በመንገድ ላይ ከመሄድ ጋር አመሳስሎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ትዕዛዞቼን እምቢ ማለት ጀምረዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 9:13
ስማቸውን ከሰማይ በታች እንድደመስሰው
“ስማቸው ፈጽሞ እንዲጠፋ አደርጋለሁ” ወይም “ማንም እንዳያስታውሳቸው ሁሉንም አጠፋቸዋለሁ”። ተመሳሳዩን ሐረግ በዘዳግም 7፡24 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
Deuteronomy 9:15
ተመለከትሁ
እዚህ ጋ “ተመለከትሁ” የሚለው ቃል ሙሴ ባየው ነገር መደነቁን ያሳያል።
ቀልጦ የተሠራ ጥጃን ለራሳችሁ አበጃችሁ
የእስራኤል የቀደመው ትውልድ ያመለኩት ዘንድ የብረት ጥጃ እንዲሠራላቸው አሮንን ጠየቁት። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
እግዚአብሔር ካዘዛችሁ መንገድ ፈጥናችሁ ወጣችሁ
ሙሴ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠበቅ በመንገድ ላይ ከመሄድ ጋር አመሳስሎ ይናገራል። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 9፡12 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
Deuteronomy 9:17
በዐይኖቻችሁ ፊት ሰባበርኳቸው
እዚህ ጋ “ዐይኖቻችሁ” የእስራኤልን ሕዝብ የሚወክል ምሳሌ ነው። ኢ.ት፡ “እዚያው በፊት ለፊታችሁ ሰባበርኳቸው” ወይም “ልታዩአቸው በምትችሉበት ስፍራ ሰባበርኳቸው” (See: Synecdoche)
በግምባሬ ተደፋሁ
“በመሬት ላይ በግምባሬ ወደቅሁ”። ይህ እግዚአብሔር ታላቅ እንደሆነና ሙሴ ምንም እንዳይደለ ማሳያ መንገድ ነው።
አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
“40 ቀንና 40 ሌሊት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 9:19
እግዚአብሔር ሊያጠፋችሁ የተቆጣበትን ቁጣውንና ጽኑ ቅሬታውን ፈርቼ ነበር
“ቁጣና ጽኑ ቅሬታ” የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር ስለ ተቆጣና ቅር ስለተሰኘ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሊያደርግ ያለውን የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር በእናንተ ተቆጥቶ ነበር -- በእናንተ ላይ እጅግ አዝኖ ነበር -- እስኪያጠፋችሁ ድረስ ተቆጥቶ ነበር፣ እኔም ስለሚያደርገው ነገር ፈርቼ ነበር”

Deuteronomy 9:21

ወሰድኩ -- አቃጠልኩት -- አድቅቄ -- መሬት -- በተንሁት

ሙሴ ምናልባት ሌሎች ሰዎች ሥራውን በቀጥታ እንዲሠሩት አዝዟቸው ይሆናል። ኢ.ት፡ “የሚወስዱ … የሚያቃጥሉ … የሚሰብሩ … የሚፈጩ … የሚበትኑ ሰዎች ነበሩኝ”

ኃጢአታችሁ፣ የሠራችሁት ጥጃ

እዚህ ጋ የሠሩት የወርቅ ጥጃ ራሱ የእነርሱ “ኃጢአት” መሆኑ ተመልክቷል። ኢ.ት፡ “በኃጥአተኝነት የሠራችሁት ጥጃ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 9:22

ተቤራ -- ማሳህ -- ቂብሮት ሐታአዋ

እነዚህ የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ የሄዱባቸው የተለያዩ ቦታዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ውጡ

እግዚአብሔር ሊሰጣቸው የነገራቸው ምድር በኮረብታዎቹ ላይ ያለ ሲሆን እነርሱ የነበሩት ቆላው ላይ ነው፣ ስለዚህ ያገኙት ዘንድ ወደ ኮረብታዎቹ መውጣት ነበረባቸው።

በትዕዛዙ ላይ አመፃችሁ

“ትዕዛዝ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በእግዚአብሔር ላይ አመፃችሁ፤ ትዕዛዙንም አልጠበቃችሁም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ድምፁን መስማት

እዚህ ጋ “ድምፁን” ማለት እግዚአብሔር ተናግሮችት የነበረውን ነው። ኢ.ት፡ “የተናገረውን ታዘዙት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ካወቅኋችሁ ጊዜ ጀምሮ

“ልመራችሁ ከጀመርኩበት ጊዜ አንሥቶ”። አንዳንድ ትርጉሞች “ካወቃችሁ ጊዜ ጀምሮ”፣ ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔር እነርሱን ያወቀበት ቀን በሚል ይነበባሉ

Deuteronomy 9:25

በእግዚአብሔር ፊት በግምባር መደፋት

“በመሬት ላይ በግምባሬ ተደፋሁ”። ይህንን በዘዳግም 9፡18 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አርባ ቀንና አርባ ሌሊት

“40 ቀንና 40 ሌሊት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የተቤዠኸውን

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ገንዘብ በመክፈል ከባርነት ነጻ እንዳደረጋቸው በሚመስል መልኩ ሙሴ ይናገራል። ኢ.ት፡ “አድነሃቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በታላቅነትህ

“ታላቅነት” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ታላቅ ኃይል የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በታላቅ ኃይልህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በብርቱ እጅ

እዚህ ጋ “ብርቱ እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። ተመሳሳዮቹን ቃላት በዘዳግም 4፡34 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት፡ “በብርቱ ኃይልህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 9:27

አስብ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “አስታውስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እኛን ከዚያ ያመጣህበት ያ ምድር

“ያ ምድር” የሚሉት ቃላት የግብፅን ሕዝብ የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። “ስለዚህ የግብፅ ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይላሉ

“ሊሉ ይችላሉ”

በታላቅ ኃይልህና በተዘረጋች ጉልበትህ

እነዚህ ሐረጎች መሠረታዊ አሳባቸው አንድ ሆኖ ሕዝቡን ለማዳን እግዚአብሔር በተጠቀመበት ታላቅ ኃይሉ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)

---

Chapter 10

Deuteronomy 10:1

በዚያን ጊዜ

“ጸሎቴን ከጨረስኩ በኋላ”

የመጀመሪያው

ይህ የሚያመለክተው ሙሴ የሰበራቸውን የመጀመሪያዎቹን ጽላቶች ስብስብ ነው። ኢ.ት፡ “ቀድሞ በነበሩህ ጽላቶች” (See: Ellipsis እና ደረጃን አመልካች ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

በተራራው

ይህ የሲና ተራራን ያመለክታል።

Deuteronomy 10:3

የመጀመሪያው

ይህ የሚያመለክተው ሙሴ የሰበራቸውን የመጀመሪያዎቹን ጽላቶች ስብስብ ነው። ኢ.ት፡ “ቀድሞ በነበሩኝ ጽላቶች” (Ellipsis እና ደረጃን አመልካች ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ወደ ተራራው ወጣ

“ወደ ሲና ተራራ ወጣ”

ከእሳቱ መካከል

እግዚአብሔር እንደ ሰው በእሳት መካከል ቆሞ በታላቅ ድምፅ የሚናገር ይመስል ነበር። ይህንን በዘዳግም 9፡10 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በጉባዔው ቀን

የነገር ስም የሆነው “ጉባዔ” “በአንድነት መሰብሰብ” በሚል ግሥ መነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 9፡10 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 10:5

ተመለስኩኝ

እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

ከተራራው ወረድኩ

x

Deuteronomy 10:6

የእስራኤል ሕዝብ -- የውሃ ምንጮች ወዳሉባት ምድር

ይህ የእስራኤል ሕዝብ ወዴት እንደተጓዙ ዳራዊ መረጃ ይሰጣል። አሮንን በሞሴራ ተፈጥሮአዊ ሞት መሞቱን ደግሞ ያስታውቃል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ከብኤሮት ብኔያዕቃን ወደ ሞሴራ -- ጉድጎዳ -- ዮጥባታ

እነዚህ የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ የሄዱባቸው የተለያዩ ቦታዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ብኤሮት ብኔያዕቃን

ተርጎሚው፣ “’ብኤሮት ብኔያዕቃን’ የሚለው ስም ‘የያዕቃን ሰዎች የውሃ ጉድጓድ’ ማለት ነው” የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይኖርባቸው ይሆናል።

በዚያ ተቀበረ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እርሱን የቀበሩት በዚያ ነው” ወይም “እስራኤላውያን በዚያ ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አልዓዛር

ይህ የአሮን ልጅ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 10:8

ያገለግለው ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት እንዲቆም

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። “እግዚአብሔር የሚያዘውን መስዋዕት እንዲያቀርብ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በስሙ

እዚህ ጋ “ስም” ሥልጣንን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔር ተወካዮች ሆነው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንደዛሬው

“ዛሬ እንደሚያደርጉት”

የመሬት ድርሻም ሆነ ርስት

የሌዊ ነገድ ወደዚያ በደረሱ ጊዜ ከተስፋይቱ ምድር ድርሻቸውን አልተቀበሉም። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ መደረግ ይችል ይሆናል።(See:


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Assumed Knowledge and Implicit Informa- tion)
እግዚአብሔር ርስቱ ነው
እግዚአብሔር ሌዊና ተወላጆቹ ከእርሱ ጋር ስለሚኖራቸው የተለየ ዝምድና ሲናገር ራሱን ሊወርሱት እንደሚችሉ አንዳች ነገር አድርጎ ይናገራል። ኢት፡ “እነርሱ የሚኖራቸው እግዚአብሔር ነው” ወይም “እግዚአብሔር እርሱን እንዲያገለግሉት ይፈቅድላቸዋል፣ በዚያም አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ያቀርብላቸዋል”
አምላክህ እግዚአብሔር
እዚህ ጋ፣ ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “የአንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
ነገረው
“ለሌዊ ነገድ ተናገራቸው”
Deuteronomy 10:10
እንደ መጀመሪያው ጊዜ
“አንደኛ” የአንድ መደበኛ ቁጥር ነው። እዚህ ጋ፣ ሙሴ ለመጀመሪያ ጊዜ የድንጋይ ጽላቶችን ከእግዚአብሔር ለመቀበል ወደ ሲና ተራራ የወጣበትን ያመለክታል” (መደበኛ ቁጥር የሚለውን ተመልከት)
አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
“40 ቀንና 40 ሌሊት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሊያጠፋህ
ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
ምድሪቱን እንዲወርሱ
“ምድሪቱን ውሰድ” ወይም “ምድሪቱን ተረከብ”
ለአባቶቻቸው
ይህ የሚያመለክተው አብርሃምን፣ ይስሐቅንና ያዕቆብን ነው።
ልሰጣቸው
“የምሰጥህን፣ ለአባቶቻቸው”
Deuteronomy 10:12
አሁንም እስራኤል
እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚለው በፈሊጣዊ አነጋገር የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። ኢት፡ “አሁንም፣ የእስራኤል ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድነው? መልካም እንዲሆንልህ ትፈራው ዘንድ እንጂ
ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ለማስተማር በጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር እንድታደርገው የሚፈልገው ይህንን ነው፤ መልካም እንዲሆንልህ ትፈራው ዘንድ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
በመንገዱም ሁሉ ትሄድ ዘንድ
እግዚአብሔርን መታዘዝ በመንገድ ላይ እንደመሄድ መሆኑን ሙሴ ይናገራል። ኢት፡ “ትዕዛዙን ሁሉ ትጠብቅ ዘንድ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ
እዚህ ጋ፣ “ልብ” እና “ነፍስ” የሰውን ውስጣዊ ማንነት የሚመለከት ፈሊጣዊ ንግግር ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች “በፍጹም” ወይም “በቅንነት” ለማለት በአንድነት ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህን ሐረጎች በዘዳግም 4፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 10:14
ተመልከት
“ልነግርህ ያለሁት እውነትና ጠቃሚ ስለሆነ ለ -- አስተውል”
ሰማይ -- ምድር
እነዚህ ቃላት ሁለት ጽንፎች ተጣምረው በሁሉም ቦታ ያሉ ሁሉም ነገሮች የእግዚአብሔር መሆናቸውን ያሳያሉ። (See: Merism)
የሰማይ ሰማያት
ይህ በሰማያት ያሉትን ከፍ ያሉ ስፍራዎች ያመለክታሉ። በሰማያት ያሉ ነገሮች በሙሉ የእግዚአብሔር ናቸው።
መርጧችኋል
እዚህ ጋ፣ “አንተ” የሚለው ቃል እስራኤላውያንን በሙሉ የሚመለከት በመሆኑ ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
Deuteronomy 10:16
ስለሆነም
“በዚህ ምክንያት”
የልባችሁን ሸለፈት ግረዙት
“ሸለፈት” የሚለው ቃል በመገረዝ ጊዜ የሚወገደውን የወንድ አካል ሸፋን ያመለክታል። እዚህ ጋ፣ ሙሴ የሚያመለክተው መንፈሳዊ መገረዝን ነው። ይኸውም፣ ሕዝቡ ከሕይወታቸው ኃጢአትን ማስወገድ አለባቸው ማለት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የአማልክት አምላክ
“ገናናው እግዚአብሔር” ወይም “ብቸኛው እውነተኛ አምላክ”
የጌቶች ጌታ
“ገናናው ጌታ” ወይም “ታላቁ ጌታ”
የሚያስፈራው
“ሰዎች እንዲፈሩ የሚያደርጋቸው”
Deuteronomy 10:18
አባት ለሌላቸው በፍትሕ ይፈርዳል
“ሰዎች አባት የሌላቸውን በፍትሐዊነት እንዲይዙ እግዚአብሔር ያረጋግጣል”
አባት የሌላቸው
እነዚህ ወላጆቻቸው የሞቱባቸውና የሚንከባከባቸው ዘመድ የሌላቸው ልጆች ናቸው።
መበለት
እውነተኛ መበለት ባሏ የሞተባትና በእርጅና ዕድሜዋ የሚረዳት ልጅ የሌላት ሴት ናት።
ስለዚህ
“በዚህ ምክንያት”
Deuteronomy 10:20
እርሱን አምልከው
“ልታመልከው የሚገባህ እርሱን ነው”
ከእርሱ ጋር ተጣበቅ
ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት መኖርና በእርሱ ላይ ሙሉ በሙሉ መታመን ከእግዚአብሔር ጋር መጣበቅ በሚል መልኩ ተነግሯል። ኢት፡ “በእርሱ ላይ መታመን አለብህ” ወይም “ልትታመንበት የሚገባህ በእርሱ ላይ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በስሙም ማል
በእግዚአብሔር ስም መማል ማለት እግዚአብሔርን የተደረገው መሐላ መሠረት ወይም ኃይል ማድረግ ማለት ነው። እዚህ ጋ፣ “ስም” የሚወክለው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። በዘዳግም 6፡13 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢት፡ “ትምላለህ፣ እግዚአብሔር እንዲያጸናውም ትጠይቀዋለህ” ወይም “በምትምልበት ጊዜ ስሙን ትጠራለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዐይኖችህ ያዩትን
እዚህ ጋ፣ “ዐይኖች” የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተና ነው። ኢት፡ “አንተ ራስህ ያየኸውን” (See: Synecdoche)
እርሱ ምስጋናህ ነው
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “ልታመሰግን የሚገባህ እርሱን ነው” ወይም 2) “አንተ ስለምታመሰግነው ሌሎች ሕዝቦች ያመሰግኑሃል”
Deuteronomy 10:22
ወደ ግብፅ ወረዱ
“በስተደቡብ ወደ ግብፅ ወረዱ” ወይም “ወደ ግብፅ ሄዱ”
ሰባ ሰዎች
“70 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
እንደ ሰማይ ከዋክብት አብዝቶሃል
ይህ ከሙሴ ጋር የነበሩት እስራኤላውያን ቁጥራቸው እጅግ ብዙ እንደነበር አጽንዖት ይሰጣል። ኢት፡ “መቁጠር ከምትችለው በላይ” (See: Simile)

Chapter 11
Deuteronomy 11:1
ሁልጊዜ ጠብቅ
“ሁልጊዜ ታዘዝ”
Deuteronomy 11:2


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ያላወቁትም ሆኑ ያላዩት
“ያልተለማመዱት”
ጽኑ እጁን ወይም የተዘረጋች ክንዱን
እዚህ ጋ፣ “ጽኑ እጅ” እና “የተዘረጋች ክንድ” የተባሉት የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያመለክቱ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:34 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ወይም ጽኑ ኃይሉን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በግብፅ መካከል
“በግብፅ ውስጥ”
በሀገሩ ሁሉ ላይ
እዚህ ጋ፣ “ሀገር” የሚወክለው ሕዝቡን ነው። ኢ.ት፡ “በሕዝቡ ሁሉ ላይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 11:4
እርሱ ያደረገውን አላዩም
“እግዚአብሔር ያደረገውን ልጆቻችሁም ቢሆኑ አላዩም”
በግብፅ ሰራዊት
“በግብፅ ወታደሮች”
እናንተን አሳደዷችሁ
እዚህ ጋ “እናንተ” ማለት ከ40 ዓመታት በፊት የነበሩትን እስራኤላውያን ማለት ነው።
ወደዚህ ስፍራ
ይህ ማለት ሙሴ ወደ ከነዓን ከመሻገራቸው በፊት ሲናገራቸው የነበረበት ከዮርዳኖስ ሸለቆ አጠገብ ያለ ሜዳ ነው።
Deuteronomy 11:6
የኤልያብ ልጆች ዳታንና አቤሮን
ሙሴ የሚያመለክተው ዳታንና አቤሮን በሙሴና በአሮን ላይ ያመፁበትን ያለፈውን ጊዜ ሁነት ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ዳታን -- አቤሮን -- ኤልያብ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የሮቤል ልጅ
“የሮቤል ተወላጆች”
መሬት አፏን ከፍታ ዋጠቻቸው
እግዚአብሔር ምድሪቱ ተሰንጥቃ ሰዎች እንዲወድቁበት ማድረጉ ምድር አፍ እንዳላትና ሰዎችን የመዋጥ ችሎታ እንዳላት ተደርጎ ተነግሯል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
የተከተላቸው ሕይወት ያለው ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው አገልጋዮቻቸውንና እንስሶቻቸውን ነው።
በእስራኤላውያን ሁሉ መካከል
ይህ ማለት በዳታን፣ በአቤሮን፣ በእንስሶቻቸውና በንብረታቸው ላይ ስለሆነው ነገር የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ ምስክሮች ናችው።
ነገር ግን ዐይኖቻችሁ አይተዋል
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚወክሉት የሰውን ሁለንተና ነው። ኢ.ት፡ “ነገር ግን እናንተ አይታችኋል” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 11:8
ምድሪቱን መውረስ
“ምድሪቱን መውሰድ
ለመውረስ የምትገቡባት
የእስራኤል ሕዝብ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ወደ ከነዓን መግባት ስለነበረባቸው “የምትገቡባት” የሚለው ሐረግ ጥቅም ላይ ውሏል።
ረጅም ቀናት
ረጅም ቀናት ረጅም ዕድሜን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ረጅም ዘመን መኖር እንድትችል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ወተትና ማር የምታፈስ ምድር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በዘዳግም 6፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የተትረፈረፈ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር” ወይም “ለከብት ዕርባታና ለእርሻ ምርጥ የሆነ ምድር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 11:10
በእግርህ ውሃ እንዳጠጣሃት
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “እግር” ወደ እርሻዎቹ ውሃ የመሸከምን ከባድ ሥራ የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ውሃ ለማጠጣት ምድከሙን” ወይም 2) ውሃ የጠጣውን እርሻ በእግሮቻቸው መገልበጥ ነበረባቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አጽዋት የሚበቅሉበት ስፍራ
“የአትክልት ስፍራ” ወይም “የልዩ ልዩ አትክልት ስፍራ”
ከሰማያት የዝናብን ውሃ የምትጠጣ
ምድሪቱ ብዙ ዝናብ መቀበሏና መምጠጧ ልክ ምድሪቱ ውሃውን እንደምትጠጣው ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ከሰማይ የሚወርደው ዝናብ የተትረፈረፈ ውሃ ይሰጣታል” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
የአምላክህ የእግዚአብሔር ዐይን ዘወትር በእርሷ ላይ ነው
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚወክሉት ትኩረትንና ክብካቤን ነው። ኢ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ዘወትር ይመለከታታል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከዓመቱ መጀመሪያ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ
እዚህ ጋ “መጀመሪያ” እና “መጨረሻ” የሚሉት ሁለት ጽንፎች በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት ዓመቱን በሙሉ ለማለት ነው። ኢ.ት፡ “ሙሉውን ዓመት ባለማቋረጥ” (See: Merism)
Deuteronomy 11:13
ብታደርጉ ይሆናል
ይህ ማለት እስራኤላውያን እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ከታዘዙ እርሱ የሰጣቸውን ተስፋ ይፈጽምላቸዋል።
እኔ የማዝህን
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው።
በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ
“በሙሉ ልብህ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ “በፍጹም” ማለት ሲሆን “በ . . . ነፍስህ” ማለት “በሁለንተናህ” ማለት ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይህንን በዘዳግም 4፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት፡ “በሁለንተናህ” ወይም “በሙሉ ኃይልህ” (የአነጋገር ዘይቤ እና Doublet የሚለውን ተመልከት)
ለምድርህ ዝናብን በወቅቱ እሰጣለሁ
“በተገቢው ወቅት በምድርህ ላይ ዝናብ እንዲዘንብ አደርጋለሁ”
እሰጣለሁ
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። ይህ በሦስተኛ መደብ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይሰጣችኋል” ወይም “እርሱ ይሰጣችኋል”
የመጀመሪያውንና የኋለኛውን ዝናብ
ይህ የሚያመለክተው በመጀመሪያ በዘር ወቅት የሚዘንበውን ዝናብና ሰብሉን ለምርትነት የሚያበቃውን ዝናብ ነው። ኢ.ት፡ “የመከርንና የፀደይን ዝናብ” ወይም “ዝናብን በወቅቱ”
Deuteronomy 11:16
ለራሳችሁ ተጠንቀቁ
“ተጠንቀቁ” ወይም “ልብ በሉ”
ልባችሁ እንዳይታለል
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው የአንድን ሰው ምኞት ወይም አሳብ ነው። ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ምኞታችሁ እንዳያታልላችሁ” ወይም “ራሳችሁን እንዳታታልሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ትመለሱና ሌሎች አማልክትን ታመልካላችሁ
እግዚአብሔርን መተውና ሌሎች አማልክትን ማምለክ ሰው በአካሉ ከእግዚአብሔር ተለይቶ በሌላ አቅጣጫ እንደሚሄድ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ሌሎች አማልክትን ማምለክ ትጀምራላችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔር ቁጣ በእናንተ ላይ እንዳይነድ
የእግዚአብሔር መቆጣት መንደድ እንደ ጀመረ እሳት ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ስለዚህ እግዚአብሔር በእናንተ ላይ እንዳይቆጣ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ምድር ፍሬዋን እንዳትሰጥና ዝናብን እንዳይሰጡ ሰማያትን እንዳይዘጋቸው
እግዚአብሔር ዝናብ ከሰማይ እንዳይወርድ ማድረጉ እርሱ ሰማይን እንደሚዘጋ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “በምድሪቱ ላይ ሰብል እንዳይበቅል ዝናብ ከሰማይ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንዳይዘንብ እንዳያደርግ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 11:18
እነዚህን ቃሎቼን በልባችሁና በነፍሳችሁ ውስጥ አኑሩ
ሙሴ የሚያዝዘውን ዘወትር የሚያስብና የሚያመዛዝን ሰው ልቡና ነፍሱ መያዣ ዕቃ እንደሆኑና የሙሴ ቃላት መያዣውን እንደሚሞላ አንዳች ይዘት ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት: ኢ.ት: “የምነግራችሁን እነዚህን ቃላት ለማስታወስ በጣም ተጠንቀቁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እነዚህን ቃሎቼን
“የሰጠኋችሁን እነዚህን ትዕዛዛት”
ልባችሁንና ነፍሳችሁን
እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የሚወክሉት የአንድን ሰው አዕምሮ ወይም አሳብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አሰሯቸው
“እነዚህን ቃላት እሰሯቸው”። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በብራና ላይ የሚጽፍን፣ ብራናውን በትንሽ ኪስ መሰል ማስቀመጫ የሚከተውንና የሚያስረውን ሰው ይወክላል። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በሌላ መልኩ ሕዝቡ የሙሴን ትዕዛዛት ለመታዘዝ መጠንቀቅ አለበት የሚል ትርጉም ያለው ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። ተመሳሳዮቹን ሐረጎች በዘዳግም 6፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእጅህ ላይ እንደ ምልክት
“ሕጌን እንድታስታውስ እንደሚያደርግህ አንዳች ነገር”
በዐይኖችህ መካከል እንደ ክታብ ይሁኑልህ
“ቃሎቼ በዐይኖችህ መካከል እንደ ክታብ ይሆኑልህ”። ይህ የሙሴን ቃላት በብራና ላይ የሚጽፍ፣ ብራናውን በትንሽ ኪስ መሰል ማስቀመጫ የሚከትና በዐይኖቹ መካከል የሚያስርን ሰው የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በሌላ መልኩ ያ ሰው ሙሴ የሚያዘውን ትዕዛዝ ሁሉ ለመታዘዝ መጠንቀቅ አለበት የሚል ትርጉም ያለው ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። በዘዳግም 6፡8 ላይ ተመሳሳዮቹን ሐረጎች እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ክታቦች
አንድ ሰው በግምባሩ ላይ የሚያስራቸው ጌጣ ጌጦች
በቤትህ ስትቀመጥ፣ በመንገድ ስትሄድ፣ ስትተኛና ስትነሣ
“በቤትህ” እና “በመንገድ” የሚሉትን የተለያዩ ቦታዎች መጠቀምና ተቃራኒዎቹ “ስትተኛ” እና “ስትነሣ” ሁልጊዜ በሁሉ ቦታ ማለትን ይወክላሉ። የእስራኤል ሕዝቦች በየትኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ማጥናትና ለልጆቻቸው ማስተማር ነበረባቸው። (See: Merism)
Deuteronomy 11:20
በቤትህ መቃኖችና በከተማህ መግቢያ በሮች ላይ ጻፋቸው
እነዚህን ቃላት በዘዳግም 6፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
የአንተ ዕድሜና የልጆችህ ዕድሜ እንዲረዝም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር አንተንና ልጆችህን ረጅም ዕድሜ እንድትኖሩ እንዲያደርጋችሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ለአባቶችህ
ይህ አብርሃምን፣ ይስሐቅንና ያዕቆብን ያመለክታል።
ከምድር በላይ እስከ ሰማይ የሚደርስ ዕድሜ ይሰጣቸው ዘንድ
ሕዝቡ በምድሪቱ የሚኖሩበት ዘመን ሰማይ ከምድር በላይ ለምን ያህል ጊዜ ከመቆየቱ ጋር ተነጻጽሯል። ይህ “ለዘላለም” ብሎ የመናገር መንገድ ነው። ኢ.ት: “ለዘላለም የእነርሱ እንዲሆን ሊሰጣቸው” ወይም “በዚያ ለዘላለም እንዲኖሩ ለመፍቀድ” (See: Simile)
Deuteronomy 11:22
ታደርጓቸው ዘንድ እኔ የማዛችሁን እነዚህን ትዕዛዛት ሁሉ በትጋት ብትጠብቁ
“ያዘዝኳችሁን ሁሉ ለመፈጸም ብትጠነቀቁ”
በመንገዶቹ ሁሉ ትሄዱ
አንድ ሰው እንዴት መኖርና ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር መፈለጉ እንደ እግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና ተደርጎ ተነግሯል። አንድ ሰው እግዚአብሔርን ሲታዘዝ በእግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና እንደሄደ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከእርሱ ጋር ትጣበቁ
ከእግዚአብሔር ጋር የመልካም ግንኙነት መኖርና ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ መታመን አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚጣበቅ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት: “በእርሱ ለመታመን” ወይም “ከእርሱ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖር”። ተመሳሳዮቹ ቃላት በዘዳግም 10፡20 ላይ እንዴት እንደተተረጎሙ ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከአንተ በፊት የነበሩትን እነዚህን ሀገሮች ሁሉ፣ ሀገሮችን ታስለቅቃላችሁ
እዚህ ጋ “ሀገሮች” የሚወክሉት ቀድሞ በከነዓን ይኖሩ የነበሩትን የሕዝብ ወገኖች ነው። ኢ.ት: “ከእናንተ በፊት የነበሩትን እነዚህን የሕዝብ ወገኖች ሁሉ፣ ከሕዝብ ወገኖች ምድሪቱን ትወስዳላችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከእናንተ ይልቅ ብዙና ኃያላን የሆኑትን
የእስራኤል ሰራዊት በከነዓን ከሚኖሩት የሕዝብ ወገኖች ይልቅ ጥቂትና ደካማ ቢሆኑም እንኳን የእስራኤል ሕዝብ ድል እንዲያደርጉ እግዚአብሔር ያስችላቸዋል።
Deuteronomy 11:24
የእግራችሁ ጫማ የሚረግጠውን ስፍራ ሁሉ
እዚህ ጋ “የእግራችሁ ጫማ” የሚወክለው የሰውን ሁለንተና ነው። ኢ.ት: “የምትሄዱበት ስፍራ ሁሉ” (See: Synec- doche)
ከወንዝ፣ የኤፍራጥስ ወንዝ
“ከኤፍራጥስ ወንዝ”
በፊታችሁ መቆም የሚችል ሰው አይኖርም
“በፊታችሁ መቆም” የሚለው ሐረግ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ማንም ሊያስቆማችሁ አይችልም” ወይም “ማንም ሊቃወማችሁ አይችልም”
አምላካችሁ እግዚአብሔር ማስፈራታችሁንና ማስደንገጣችሁን በምትረግጡት ምድር ሁሉ ላይ ያኖራል
እግዚአብሔር ሕዝቡ በጣም እንዲፈሩ ማድረጉ ፍርሐትና ድንጋጤን እርሱ እንደ ዕቃ በሕዝቡ ላይ እንደሚያኖራቸው በመሰለ መልኩ ተነግሯል። ኢ.ት: “አምላካችሁ እግዚአብሔር በምትሄዱበት ስፍራ ሁሉ ሕዝቡ እንዲፈሯችሁ ያደርጋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ማስፈራታችሁና ማስደንገጣችሁ
“ፍርሐት” እና “ድንጋጤ” የሚሉት ቃላት ትርጉማቸው ተመሳሳይ ሲሆን የፍርሐቱ መጠን ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት: “ከእናንተ የተነሣ ከባድ ፍርሐት” (See: Doublet)
በምትረግጡት ምድር ሁሉ ላይ
እዚህ ጋ “ምድሪቱ” የሚለው በምድሪቱ ላይ የሚኖሩትን ሰዎች በሙሉ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “በምትሄዱበት ስፍራ ሁሉ በሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ላይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 11:26
ተመልከቱ
“ልብ በሉ”
ዛሬ በረከትን እና መርገምን በፊታችሁ አኖራለሁ
እግዚአብሔር እንዲባርካቸው ወይም እንዲረግማቸው ይፈልጉ እንደሆነ ሕዝቡ እንዲመርጡ መፍቀዱ በረከትና መርገም ሙሴ በፊታቸው እንደሚያስቀምጣቸው ቁሶች ተደርገው ተነግሮላቸዋል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር እንዲባርካችሁ ወይም እንዲረግማችሁ ዛሬ መምረጥ አለባችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በረከቱ -- መርገሙ --
የነገር ስም የሆነው “በረከት” እና “መርገም” በግሥነት ሊተረጎሙ ይችላሉ። ኢ.ት: “… ካደረጋችሁ እግዚአብሔር ይባርካችኋል፣ … እግዚአብሔር ይረግማችኋል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ሌሎች አማልክትን ለመከተል እኔ ዛሬ ከማዛችሁ መንገድ ፈቀቅ ብትሉ ግን
ሙሴ ለሕዝቡ የሚነግራቸው የእግዚአብሔር ትዕዛዝ እንደ እግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና ሆነው ተነግረዋል። ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ያለመታዘዝ ሌሎች አማልክቶችን ለመከተል በሌላ አቅጣጫ ለመመለስ ከእግዚአብሔር በአካል እንደተለዩ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት: “ሌሎች አማልክትን ለማምለክ ዛሬ እኔ የማዛችሁን ትዕዛዝ እምቢ ብትሉ ግን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የማታውቋቸውን ሌሎች አማልክት
ይህ የሚያመለክተው ሌሎች የሕዝብ ወገኖች የሚያመልኳቸውን አማልክት ነው። እስራኤላውያን ራሱን ስለገለጠላቸውና ኃይሉን ስለተለማመዱ እግዚአብሔርን ያውቁታል።
Deuteronomy 11:29
በረከቱን በገሪዛን ተራራ ላይ፣ መርገሙን በጌባል ተራራ ላይ ታስቀምጣላችሁ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በረከቱ እና መርገሙ አንድ ሰው በተራሮች ላይ እንደሚያስቀምጣቸው ቁሶች ተደርገው ተነግሮላቸዋል። ኢ.ት: “ከእናንተ ጥቂቱ በገሪዛን ተራራ እናት ላይ ቆማችሁ እግዚአብሔር እንዲባርካችሁ የሚያስደርገውን ቃል ታውጃላችሁ፣ ሌሎቹ በጌባል ተራራ እናት ላይ በመቆም እግዚአብሔር እንዲረግማችሁ የሚያስደርገውን ቃል ያውጃሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ገሪዛን ተራራ -- ጌባል ተራራ

እነዚህ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኙ ተራሮች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በሞሬ --- ከዮርዳኖስ ማዶ የሚገኙ አይደሉም?

እስራኤላውያን የሚገኙት ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ ነው። ሙሴ እነዚህ ተራሮች የሚገኙባቸውን ስፍራዎች ለማስታወስ በጥያቄ መልክ ያቀርባል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “እንደምታውቁት ሞሬ የሚገኘው ከዮርዳኖስ ማዶ ነው” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ከዮርዳኖስ ማዶ

“ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ”

ከምዕራቡ መንገድ በስተምዕራብ

“በምስራቅ”

በጌልገላ ትይዩ

“ጌልገላ አጠገብ” ይህ ምናልባት ኢያሪኮ ከተማ አጠገብ ያለው ስፍራ ላይሆን ይችላል። ምናልባት ሙሴ ሴኬም አቅራቢያ ያለውን ስፍራ እያመለከተ ይሆናል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የሞሬ በሉጥ ዛፎች

እነዚህ በጌልገላ አቅራቢያ የሚገኙ የተቀደሱ ዛፎች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 11:31

ሥርዓቶችና ሕግጋት ሁሉ

እነዚህ ሙሴ በዘዳግም 12:26 የሚሰጣቸው ሥርዓቶችና ሕግጋት ናቸው።

እኔ ዛሬ በፊታችሁ ያስቀመጥኋቸው

እነዚህ አዲስ ናቸው ማለት አይደለም። ሙሴ ከ40 ዓመታት በፊት የሰጣቸውን ሥርዓቶችና ሕግጋት እየከለሰላቸው ነው።

በፊታችሁ ያስቀመጥኋቸው

ሙሴ ለሕዝቡ የሚነግራቸው ሥርዓቶችና ሕግጋት በሕዝቡ ፊት እንደሚያስቀምጣቸው ቁሶች ተደርጎ ተነግሮላቸዋል። ኢ.ት: “እኔ የምሰጣችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 12

Deuteronomy 12:1

የምትጠብቃቸው

“መታዘዝ አለባችሁ”

በምድር ላይ በምትኖሩበት ዘመን ሁሉ

“በምድር ላይ በምትኖሩበት” የሚለው ሐረግ አንድ ሰው በሕይወት እስካለ ደረስ የሚል የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “በሕይወት እስካላችሁ ድረስ” (የአነጋገርዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ፈጽማችሁ አጥፉ

“ማጥፋት አለባችሁ”

የምታስለቅቋቸው ሕዝቦች

እዚህ ጋ “ሕዝቦች” የሚወክሉት በከነዓን የሚኖሩትን የሕዝብ ወገኖች ነው። ኢ.ት: “መሬታቸውን የምትወስዱባቸው የሕዝብ ወገኖች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 12:3

መሠዊያዎቻቸውን ማፍረስ አለባችሁ

“የእነዚያን ሕዝቦች መሠዊያ ማፈራረስ አለባችሁ” ወይም “የእነዚያን ሕዝቦች መሠዊያዎች ማጥፋት አለባችሁ”

ከስክሳችሁ ጣሉ

“ሰባብራችሁ ጣሉ” ወይም “ብትንትናቸውን አውጡ”

ስማቸውን አጥፉ

እዚህ ጋ “ስማቸውን” የሚወክለው “መታሰቢያቸውን” ነው። ኢ.ት: “ማንም እንዳያስታውሳቸው ፈጽማችሁ አጥፏቸው” ወይም “እነዚህን ሐሰተና አማልክት የሚወክል የትኛውንም ነገር አጥፉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከዚያ ስፍራ

ይህ ሕዝቦች አማልክቶታቸውን የሚያመልኩባቸውን እያንዳንዱን ስፍራ ያመለክታል።

አምላካችሁን እግዚአብሔርን በዚያ መልኩ አታምልኩ

“እነዚያ ሕዝቦች አማልክቶቻቸውን እንዳመለኩ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ማምለክ የለባችሁም”

Deuteronomy 12:5

አምላካችሁ እግዚአብሔር ስሙን ሊያስቀምጥበት ከነገዶቻችሁ ሁሉ የሚመርጠው ስፍራ

እዚህ ጋ “ስሙን” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። እግዚአብሔር የሚኖርበትን አንድ ቦታ ይመርጣል፣ ሰዎች እርሱን ለማምለክ ወደዚያ ይመጣሉ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መሄድ የሚኖርባችሁ ወደዚያ ነው

እግዚአብሔር ወደሚወስነው ስፍራ ለማምለክ ይሄዳሉ

በእጃችሁ የምታቀርቡት ስጦታ

እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ሙሉ ሰውነትን ነው። ኢ.ት: “የምታቀርቡት ስጦታ” (See: Synecdoche)

የስእለቶቻችሁንና የፈቃደኝነት ስጦታዎቻችሁን

“ስእለታችሁን የምትፈጽሙበትን ስጦታዎቻችሁን፣ የበጎ ፈቃድ ስጦታዎቻችሁን”። እነዚህ የስጦታ ዓይነቶች ናቸው።

ከቀንድ ከብቶቻችሁና ከበግና ከፍየል መንጋዎቻችሁ በኩራቱን

ሕዝቡ ከእያንዳንዱ የቤት እንስሳው በመጀመሪያ የሚወለደውን ወንድ እንዲሰጡት እግዚአብሔር ይፈልጋል

Deuteronomy 12:7

በዚያ ነው

ይህ የሚያመለክተው የእስራኤል ልጆች እንዲያመልኩበት እግዚአብሔር የሚመርጥላቸውን ስፍራ ነው።

እጃችሁ በነካው ሁሉ ደስ ይበላችሁ

እዚህ ጋ “እጃችሁ በነካው” የሚወክለው ሙሉውን ሰውና እርሱ የሠራውን ነው። ኢ.ት: “በሠራችሁት ሥራ ሁሉ ደስ ይበላችሁ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 12:8

ዛሬ እዚህ የምናደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ ማድረግ የለባችሁም

“ዛሬ እዚህ እንደምናደርገው ማድረግ የለባችሁም”። ይህ ማለት በዚያ ወቅት ከሚያመልኩበት በተለየ ሁኔታ በተስፋይቱ ምድር ማምለክ ይኖርባቸዋል።

አሁን እያንዳንዱ የሚያደርገው በዐይኑ መልካም መስሎ የታየውን ነው

ዐይን ማየትን፣ ማየትም ማሰብን ወይም መወሰንን ይወክላል። ኢ.ት: “እያንዳንዱ የሚያደርገው ልክ ነው ብሎ የሚያስበውን ነው” ወይም “አሁን እያንዳንዱ የሚያደርገው ልክ ነው ብሎ የሚወስነውን ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደ ማረፊያ

“ማረፊያ” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ወደምታርፉበት ምድር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

አምላካችሁ እግዚአብሔር ወደሚሰጣችሁ ርስት

እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የሚሰጣቸው ምድር አባት ለልጆቹ እንደሚተውላቸው ርስት ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት: “አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ ቋሚ ንብረት አድርጎ ወደሚሰጣችሁ ምድር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 12:10

በምድሪቱ ስትኖሩ

ይህ የሚያመለክተው የከነዓንን ምድር ነው።

አማላካችሁ እግዚአብሔር እንድትወርሷት በሚያደርጋችሁ ምድር ላይ

እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር ለእስራኤል ሕዝብ መስጠቱ እርሱ ለልጆቹ ርስት እንደሚሰጣቸው አባት ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በዙሪያችሁ ካሉ ከጠላቶቻችሁ ሁሉ ያሳርፋችኋል

“በዙሪያችሁ ካሉ ከጠላቶቻችሁ ሁሉ ሰላምን ይሰጣችኋል”

አምላካችሁ እግዚአብሔር ስሙ በዚያ እንዲቀመጥ በሚመርጠው ስፍራ ላይ

እዚህ ጋ “ስም” የሚወክለው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። ኢ.ት: “አምላካችሁ እግዚአብሔር ለመኖር በሚመርጠው ስፍራ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተመልከት)
በእጃችሁ የምታቀርቡት ስጦታ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ሙሉውን ሰው። አ.ት: “የምታቀርቡት ስጦታ” (See: Synecdoche)
ስለ ስእለቶቻችሁ የተመረጡትን ስጦታዎቻችሁን በሙሉ
“ስእለታችሁን ለመፈጸም የምታቀርቧቸውን የበጎ ፈቃድ ስጦታዎቻችሁን በሙሉ”
Deuteronomy 12:12
በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበላችሁ
“በእግዚአብሔር ሀልዎት ደስ ይበላችሁ”
በበራችሁ የሚኖሩ ሌዋውያን
እዚህ ጋ “በሮች” የሚያመለክተው ከተማውን ራሱን ነው። አ.ት: “በከተማችሁ ውስጥ የሚኖረው ሌዋዊ” ወይም “ከእናንተ ጋር የሚኖረው ሌዋዊ” (See: Synecdoche)
በመካከላችሁ ምንም ድርሻ ወይም ርስት ስለሌለው
እግዚአብሔር ለሌዋውያን ምንም መሬት ያለመስጠቱ እውነታ ለልጆቹ ርስት እንዳልሰጣቸው አባት ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ምንም ድርሻ የለውም
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው ሌዊን ነው። ሌዊ ተወላጆቹን በሙሉ ይወክላል። አ.ት: “ምንም ድርሻ የላቸውም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 12:13
ለራሳችሁ ትኩረት ስጡ
“ተጠንቀቁ”
በምታዩት ስፍራ ሁሉ
“ደስ በሚያሰኛችሁ ስፍራ ሁሉ” ወይም “በምትፈልጉት ስፍራ ሁሉ”
ነገር ግን እግዚአብሕር በሚመርጠው ስፍራ ነው
የሚቃጠል ስጦታ መቅረብ ያለበት በመገናኛው ድንኳን ነው። የመገናኛው ድንኳን የት መደረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ራሱ ይመርጣል።
Deuteronomy 12:15
ይሁን እንጂ፣ በየበሮቻችሁ ውስጥ እንስሶችን አርዳችሁ መብላት ትችላላችሁ
ሕዝቡ ለመሥዋዕት እንስሶችን ማረድ የሚችለው እግዚአብሔር በሚመርጠው ስፍራ ብቻ ነው። ለምግብ የሚሆኑ እንስሶችን በፈለጉበት ሁሉ ማረድ ይችላሉ። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
በየበሮቻችሁ ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” ከተማውን በሙሉ ይወክላሉ። አ.ት: “በከተማችሁ ውስጥ” ወይም “በቤታችሁ” (See: Synecdoche)
ንጹሕ ያልሆኑ ሰዎች
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀባይነት የሌለው ሰው በአካሉ ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ንጹሕ የሆኑ ሰዎች
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀባይነት ያለው ሰው በአካሉ ንጹሕ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሚዳቋና ድኩላ
እነዚህ በፍጥነት መሮጥ የሚያስችል ቀጭንና ረጅም እግሮች ያሏቸው የዱር እንስሶች ናቸው። አ.ት: “አጋዘንና ድኩላ” (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
ነገር ግን ደሙን አትብሉ
ደም ሕይወትን ስለሚወክል ሕዝቡ ደሙን ከምግባቸው ጋር እንዲበሉት እግዚአብሔር አልፈቀደላቸውም። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 12:17
በበሮችህ ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት መላውን ከተማ ይወክላሉ። አ.ት: “በከተማህ ውስጥ” ወይም “በቤትህ ውስጥ” (See: Synecdoche)
በእጅህ የምታቀርበውን ስጦታ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ሙሉውን ሰው። አ.ት: “ለእግዚአብሔር የምታቀርበውን የትኛውንም ስጦታ” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 12:18
ትበሉታላችሁ
“ስጦታዎቻችሁን ትበላላችሁ”
በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሀልዎት”
በበሮቻችሁ ውስጥ ያሉ ሌዋውያን
እዚህ ጋ “በር” የሚወክለውን መላውን ከተማ ነው። አ.ት: “በከተማችሁ ውስጥ የሚኖር ሌዋዊ ሁሉ” (See: Synecdoche)
እጅህን የምታኖርበት የትኛውም ነገር
እዚህ ጋ “እጅህን የምታኖርበት” የሚወክለው ሙሉውን ሰውና እርሱ የሚሠራውን ነው። አ.ት: “ስላሠራኸው ሥራ ሁሉ ደስ ይበልህ” (See: Synecdoche)
ለራስህ ትኩረት ስጥ
“ተጠንቀቅ”
እንዳትረሳ
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት: “በሚገባ ጠብቀው” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 12:21
ስሙን ለማስቀመጥ የመረጠው
እዚህ ጋ “ስም” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። እርሱ የሚኖርበትንና ሕዝቡ እርሱን ለማምለክ የሚመጣበትን ስፍራ እግዚአብሔር ይመርጣል። አ.ት: “መኖሪያውን ይመርጣል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በበሮችህ ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት መላውን ከተማውን ነው። አ.ት: “በከተማህ ውስጥ” ወይም “በማኅበረሰብህ መካከል” (See: Synecdoche)
ነፍስህ እንደ ተመኘች
እዚህ ጋ “ነፍስ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት: “እንደምትመኘው” (See: Synecdoche)
ሚዳቋና ድኩላ የሚበሉ እንደሆኑ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት: “ልክ ሚዳቋውን እና ድኩላውን እንደምትበላ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሚዳቋና ድኩላውን
እነዚህ በፍጥነት መሮጥ የሚችሉ ቀጭንና ረጅም እግሮች ያሏቸው የዱር እንስሶች ናቸው። እነዚህን በዘዳግም 12:15 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ንጹሕ ያልሆኑ ሰዎች
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀባይነት የሌለው ሰው በአካሉ ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ንጹሕ የሆኑ ሰዎች
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀባይነት ያለው ሰው በአካሉ ንጹሕ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 12:23
ደሙ ሕይወቱ ነው
እዚህ ጋ ደም ሕይወትን የሚያቆይበት መንገድ ደም ራሱ ሕይወት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት: “ደሙ ሕይወትን ያቆያል” ወይም “ሰዎችና እንስሳት በሕይወት እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ደም ነው።” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሕይወቱን ከሥጋው ጋር አትብላው
እዚህ ጋ፣ “ሕይወት” የሚለው ቃል የሚወክለው ሕይወትን የሚያቆየውን ደሙን ነው። አ.ት: “ሕይወትን የሚያቆየውን ከሥጋ ጋር አትብላው” ወይም “ሕይወትን የሚያቆየውን ደም ከሥጋ ጋር አትብላ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእግዚአብሔር ዐይን ትክክል የሆነውን
ዐይን ማየትን ይወክላል፣ ማየትም ማሰብን ወይም መወሰንን ይወክላል። አ.ት: “በእግዚአብሔር ውሳኔ ትክክል የሆነው” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል ነው የሚለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 12:26
ስለ ስእለቶችህ የምታቀርባቸውን ስጦታዎች
“ስእለቶችህን ለመፈጸም ስጦታዎችን” ወይም “የስእለት ስጦታዎች”
የመሥዋዕትህ ደም መፍሰስ አለበት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት: “ካህኑ የመሥዋዕቱን ደም ያፈስዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሥጋውን ትበላለህ
የእግዚአብሔር ሕግ የእንስሳው የትኛው ክፍል የሚቃጠል መሥዋዕት፣ የትኛው

ክፍል ለካህኑ እንደሚሆንና የትኛውን ክፍል አቅራቢው መብላት እንዳለበት ግልጽ ያደርጋል። የዚህ መግለቻ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከሥጋው ጥቂቱን ትበላለህ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 12:28

እኔ የማዝህን እነዚህን ቃላት በሙሉ ስማ፣ በጥንቃቄም ጠብቃቸው

“የማዝህን ሁሉ በጥንቃቄ ስማና ታዘዘው”

ለአንተና ከአንተም በኋላ ለልጆችህ መልካም እንዲሆንልህ

እዚህ ጋ “ልጆች” ማለት ተወላጆቻቸው ሁሉ ማለት ነው። አ.ት፡ “አንተና ተወላጆችህ እንድትበለጽጉ” (See: Synecdoche)

መልካምና ትክክለኛውን ነገር በምታደርግበት ጊዜ

“መልካም” እና “ትክክለኛ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ትክክለኛ ባህርይ አስፈላጊ በመሆኑ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “ትክክል የሆነውን በምታደርግበት ጊዜ” (See: Doublet)

በእግዚአብሔር ዐይን መልካምና ትክክል

ዐይን ማየትን ይወክላል፣ ማየትም ማሰብን ወይም መወሰንን ይወክላል። አ.ት፡ “በእግዚአብሔር ውሳኔ መልካምና ትክክል የሆነው” ወይም “እግዚአብሔር መልካምና ትክክል ነው የሚለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 12:29

ሕዝቦችን ይቆርጣቸዋል

እግዚአብሔር በከነዓን የሚኖሩትን የሕዝብ ወገኖች ማጥፋቱ አንድ ሰው ቁራጭ ጨርቅ ወይም ከዛፍ ላይ ቅርንጫፍን እንደሚቆርጥ እንደሚቆርጣቸው ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሕዝቦች

እዚህ ጋ “ሕዝቦች” የሚወክሉት በከነዓን የሚኖሩትን ሰዎች ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ታስወጧቸዋላችሁ፣ በምታስወጧቸው ጊዜ

“ሁሉንም ነገር በምትወስዱባቸው ጊዜ”

ለራሳችሁ ትኩረት ስጡ

“ተጠንቀቁ”

እነርሱን በመከተል እንዳትጠመዱ -- አማልክታቸውን ለመጠየቅ በመሞከር እንዳትጠመዱ

ስለ ሌሎች አማልክት የሚማርና የሚያመልክ ሰው በአዳኝ ወጥመድ እንደሚያዝ ሆኖ ተነግሮለታል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እንደ እነርሱ አታድርጉ … አማልክታቸውን የመጠየቅ ሙከራ ለማድረግ እንዳትማሩ” (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት))

እነርሱን በመከተል አትጠመዱ

የከነዓን የሕዝብ ወገኖች ጣዖታትን እንደሚያመልኩ እስራኤላውያን ጣዖታትን ማምለካቸው ከሌሎች የሕዝብ ወገኖች በስተኋላ እንደ ተከተሉ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእናንተ አስቀድሞ ከጠፉ በኋላ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በፊታችሁ ካጠፋቸው በኋላ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

‘እነዚህ ሕዝቦች አማልክታቸውን የሚያመልኩት እንዴት ነው? እኔም እንደዚያው አደርጋለሁ’ ብለህ ብትጠይቅ

ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛ የሆነው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አንተም እንደዚያው ልታደርግ እነዚያ የሕዝብ ወገኖች አማልክታቸውን እንዴት እንዳመለኩ ብትጠይቅ” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 12:31

በእርሱ ላይ አትጨምር፣ ከእርሱም አትቀንስ

ተጨማሪ ሕጎችን መፍጠርም ሆነ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሕጎች ቸል ማለት አይኖርባቸውም።

---

Chapter 13

Deuteronomy 13:1

በመካከላችሁ ቢነሣ

“በመካከላችሁ ቢመጣ” ወይም “በመካከላችሁ ነኝ ቢል”

የሕልመኛው ሕልሞች

ይህ ከእግዚአብሔር በሕልም መልዕክት የሚቀበል ሰው ነው።

ምልክትን ወይም ድንቅን

እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ የተለያዩ ተአምራቶችን ያመለክታል። (See: Doublet)

ቢሆን

“ቢከናወን” ወይም “ቢመጣ”

ቢነግርሃና፣ ‘ሌሎች አማልክትን እንከተል፣ የማታውቃቸውን እናምልክ’ ቢልህ አትስማው

ይህ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የማታውቃቸውን ሌሎች አማልክት እንድታመልክና እንድታገለግል ቢነግርህ አትስማው” (ቀጥተና እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

ከሌሎች አማልክት ኋላ እንሂድ

ሌሎች አማልክትን ማምለክ ከሌሎች አማልክት ኋላ መሄድ ወይም መከተል ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “ሌሎች አማልክትን እንከተል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከማታውቃቸው ሌሎች አማልክት ኋላ ሂድ

“ከማታውቃቸው አማልክት” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ሌሎች የሕዝብ ወገኖች የሚያመልኳቸውን አማልክት ነው። ራሱን ስለገለጠላቸውና ኃይሉን ስለተለማመዱት እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ያውቁታል።

የዚያን ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቃል አትስማ

“ያ ነቢይ የሚለውንም ሆነ ሕልም አላሚው የሚናገረውን አትስማው”

በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ

እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች “በፍጹም” ወይም “በቅንነት” የሚል ትርጉም እንዲሰጡ በአንድነት ጥቅም ላይ ውለዋል። ይህንን በዘዳግም 4፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 13:4

አምላካችሁን እግዚአብሔርን ተከተሉት

እግዚአብሔርን መታዘዝና ማምለክ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ኋላ እንደ ሄዱ ወይም እንደተከተሉት ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “እግዚአብሔርን ታዘዙ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ድምፁን ታዘዙ

እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚወክለው እግዚአብሔር የሚናገረውን ነው። አ.ት፡ “እርሱ የሚለውን ታዘዙ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእርሱ ጋር ተጣበቁ

ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት መኖሩና ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ መታመን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚጣበቅ ሆኖ ተነግሯል። አ.ት፡ “በእርሱ ተማመን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይገደል

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “መግደል አለብህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አመፅን ተናግሯልና

የነገር ስም የሆነው “አመፅ” እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እንድታምፅ ሊያደርግህ ሞክሯል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ከባርነት ቤት የተቤዠህን

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ባሪያ ከነበሩበት ከግብፅ ማዳኑ ሕዝቡን ከባርነት ለመቤዠት ገንዘብ እንደከፈለ በሚመስል መልኩ ተነግሯል። አ.ት፡ “ ባሪያዎች ከነበራችሁበት ስፍራ ያዳናችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የባርነት ቤት

እዚህ ጋ “የባርነት ቤት” የእግዚአብሔር ሕዝብ ባሪያዎች የነበሩበትን ግብፅን ይወክላል። አ.ት፡ “ባሪያዎች የነበራችሁበት ግብፅ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላካችሁ እግዚአብሔር እንድትሄዱበት ካዘዛችሁ መንገድ እንድትወጡ

እግዚአብሔር አንድ ሰው እንዴት መኖር ወይም ማድረግ እንዳለበት የሚፈልግበት ሁኔታ ሕዝቡ እንዲሄዱበት እንደሚፈልገው መንገድ ወይም ጎዳና ሆኖ ተነግሯል። አንድን ሰው እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ለማስቆም የሚሞክር በእግዚአብሔር

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መንገድ ወይም ጎዳና ላይ እንዳይሄድ እንደተከላከል ሆኖ ተነግሮለታል። ኢ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ያዘዘውን እንዳትፈጽም የሚያደርግህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስለዚህ ክፋትን ከመካከላችሁ አርቁ

እዚህ ጋ “ክፋትን” የሚያመለክተው ክፉ ሰውን ወይም ክፉ ባህርይን ነው። ይህ ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ስለዚህ ይህንን ክፉ ነገር የሚያደርገውን ሰው ከእስራኤል ሕዝብ መካከል ማስወገድ አለብህ” ወይም “ስለዚህ ይህንን ክፉ ሰው መግደል አለብህ” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 13:6

በእቅፍህ ያለች ሚስትህ

እቅፍ የሰው ድረት ነው። ይህ የአነጋገር ዘይቤ ወደ ደረቱ አስጠግቶ ይይዛታል፣ ይኸውም ይወዳታል፣ ይንከባከባታል ማለት ነው። ኢ.ት፡ “የምትወዳት ሚስትህ” ወይም “በፍቅር የምታቅፋት ሚስትህ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እንደ ነፍስህ የሆነ ጓደኛህ

እዚህ ጋ “ነፍስ” የሚወክለው የሰውን ሕይወት ነው። ይህ ማለት ሰውየው ለራሱ ሕይወት የሚገደውን ያህል ስለ ጓደኛው ይገደዋል ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ውድ ጓደኛህ” ወይም “ራስህን የምትወደውን ያህል የምትወደው ጓደኛህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በምስጢር ሊያስትህ፣ ‘በሌላው የምድር ጫፍ -- እንሂድና እናምልክ’ ቢልህ

ይህ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ወደ ሌላው የምድር ጫፍ ሄደህ እንድታመልክ ሊያሳምንህ በምስጢር ይሞክራል” (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

በክበብህ ያሉ

“በዙሪያህ ያሉ”

ከአንዱ የምድር ጫፍ እስከ ሌላኛው የምድር ጫፍ

እዚህ ጋ ሁለቱ የምድር ጽንፍ ማጣቀሻዎች “በምድር ላይ በሁሉ ስፍራ” ማለት ነው። ኢ.ት፡ “በመላው ምድር ላይ” (See: Merism)

Deuteronomy 13:8

እሺ አትበለው

“እርሱ በሚፈልገው አትስማማ”

ዐይንህ አይራራለት

እዚህ ጋ “ዐይንህ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “በርኅራኄ አትመልከተው” ወይም “አትማረው” (See: Synecdoche)

አትተወው ወይም አትደብቀው

“ምህረት ልታሳየው ወይም እርሱ ያደረገውን ከሌሎች ልትደብቅ አይገባም”

እርሱን ለመግደል መጀመሪያ የአንተ እጅ ይሁንበት

ይህ ማለት በበደለኛው ሰው ላይ የመጀመሪያውን ድንጋይ እርሱ መወርወር ነበረበት። “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “በመጀመሪያ እስኪሞት ድረስ የምትመታው አንተ መሆን አለብህ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 13:10

ከእግዚአብሔር ሊያርቅህ ሞክሯል

“ከእግዚአብሔር ሊመልስህ”። አንድ ሰው ሌላውን እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ሊገታው መሞከሩ ያንን ሰው በአካሉ እግዚአብሔርን ትቶ እንዲመለስ ለማድረግ እንደሞከረ ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔርን እንዳትታዘዝ ሊያደርግህ ሞክሯል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከባርነት ቤት

እዚህ ጋ፣ “የባርነት ቤት” የሚወክለው የእግዚአብሔር ሕዝብ ባሪያዎች የነበሩበትን ግብፅን ነው። ኢ.ት፡ “ባሪያዎች ከነበራችሁበት ስፍራ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እስራኤል ሁሉ ይሰሙና ይፈራሉ

ሕዝቡ ስለተገደለው ሰው በሚሰሙበት ጊዜ እርሱ እንዳደረገው ለማድረግ እንደሚፈሩ ያመለክታል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 13:12

አንዳንድ ክፉ ሰዎች ከመካከልህ ሄደው

“ከመካከልህ” የሚለው ሐረግ እነዚህ ክፉ ሰዎች በማኅበረሰቡ መካከል የሚኖሩ እስራኤላውያን ነበሩ ማለት ነው።

የከተማቸውን ነዋሪዎች ሰብስበው፣ ‘ሄደን የማታውቋቸውን አማልክት እናምልክ’ ቢሉ

ይህ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የማያውቋቸውን አማልክት ሄደው እንዲያመልኩ በከተማቸው የሚኖሩትን አስገድደዋል”። (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

የከተማቸውን ነዋሪዎች ሰብስበው

አንድ ሰው ሌላውን እግዚአብሔርን እንዳይታዘዝ ቢያደርገው ያ ሰው በአካሉ ከእግዚአብሔር ተለይቶ እንዲመለስ እንዳደረገው ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መረጃውን አጣራ፣ ፈትሽ፣ በሚገባ መርምር

እነዚህ ሐረጎች ሁሉ በመሠረቱ የሚሉት አንድ ነገር ነው። ሙሴ በከተማይቱ ስለሆነው ነገር እውነቱን በጥንቃቄ እንዲያጣሩ አጽንዖት እየሰጠ ነው። (See: Doublet)

እንዲህ ያለ አስጸያፊ ነገር በመካከላችሁ ተደርጎ እንደሆን

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የከተማይቱ ሰዎች እንዲህ ያለ አስከፊ ነገር አድርገው እንደሆን (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 13:15

በሰይፍ ስለት

እዚህ ጋ “ስለት” የሚወክለው ሙሉውን ሰይፉን ነው። ኢ.ት፡ በሰይፎቻችሁ” (See: Synecdoche)

ምርኮውን ሁሉ

“ብዝበዛውን ሁሉ”። ይህ ሰራዊት በጦርነት ድል ካደረገ በኋላ የሚሰበስበውን ሀብትና ንብረት ያመለክታል።

የፍርስራሽ ክምር

“የፍርስራሽ ቁልል”

ፈጽሞ ዳግመኛ አትሠራ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከተማይቱን ማንም ደግሞ አይሥራት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 13:17

ለመጥፋት ከተለዩ ከእነዚያ ነገሮች አንዳም እጅህ ላይ አይጣበቅ

እግዚአብሔር አንድን ነገር መርገሙና ሊያጠፋው መሻሉ እርሱ ቁሱን ከሌሎች ነገሮች ለይቶ እንደሚያስቀምጠው ሆኖ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር አጥፋው ብሎ ካዘዘህ ነገር ውስጥ የትኛውንም ማቆየት የለብህም” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እጅህ ላይ አይጣበቅ

ይህ አንድ ሰው የሆነ ነገርን ለራሱ የሚያቆይበት መንገድ ነው። ኢ.ት፡ “አታቆይ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ከቁጣው መዓት ይመለሳል

እግዚአብሔር ከእንግዲህ ያለመቆጣቱ ቁጣው እንደ አንድ ቁስ ተቆጥሮ እግዚአብሔር በአካል ከእርሱ እንደሚመለስ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር መቆጣቱን ይተዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለአባቶችህ

እዚህ ጋ “አባቶችህ” ማለት አያቶችህ ወይም ቅድም አያቶችህ ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምተሃል

እዚህ ጋ “ድምፅ” እግዚአብሔር የሚናገረውን ይወክላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር የሚናገረውን ታዘሃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በአምላክህ በእግዚአብሔር ዐይን ትክክል የሆነውን

ዐይን ማየትን ይወክላል፣ ማየትም ማሰብን ወይም መወሰንን ይወክላል። ኢ.ት፡ “በእግዚአብሔር ውሳኔ ትክክል የሆነውን” ወይም “አምላክህ እግዚአብሔር ትክክል እንደሆነ የሚቆጥረውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 14

Deuteronomy 14:1

እናንተ -- ሕዝብ ናችሁ -- እናንተ -- የተለየ ሕዝብ ናችሁ -- መርጧችኋል

“እናንተ” የሚለው አገባብ በሙሉ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ሙሴ የሕዝቡ አካል ሆኖ ተካቶአል። ኢ.ት፡ “እኛ… ሕዝብ ነን … እኛ የተለየን ሕዝብ ነን … መርጦናል”

ስለሞተው ራሳችሁን አትቁረጡ ወይም ከፊታችሁ የትኛውንም ክፍል አትላጩት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እነዚህ በከነዓን ይኖሩ የነበሩት የሕዝብ ወገኖች ለሞቱ ሰዎች ሐዘናቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነበር። ሙሴ እንደዚያ እንዳያደርጉ ለእስራኤል ሕዝብ ይነግራቸዋል። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Symbolic Action and Assumed Knowledge and Implicit Information)
ከፊታችሁ የትኛውንም ክፍል አትላጩት
“ከራሳችሁ ጸጉር ላይ ከፊት ያለውን አትላጩት”
በምድር ፊት -- እናንተ የተለየ ሕዝብ ናችሁ
እነዚህን ቃላት በዘዳግም 7፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር የተለየ ሕዝብ ናችሁ
እግዚአብሔር በልዩ ሁኔታ የእርሱ እንዲሆኑ የእስራኤልን ሕዝብ መምረጡ እነርሱን ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ እንደለያቸው ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አምላካችሁ እግዚአብሔር እናንተን ከሌሎች ሕዝቦች ለይቶአችኋል” (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት))
እግዚአብሔር የራሱ ንብረት የሆነ ሕዝብ እንድትሆኑ መርጧችኋል
ይህ ማለት በመሠረቱ ከዐረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ጋር ተመሳሳይ ነገር ነው። ሁለቱም የሚሉት የእስራኤል ሕዝብ በልዩ ሁኔታ የእግዚአብሔር መሆኑን ነው። (See: Parallelism)
የራሱ ንብረት የሆነ ሕዝብ
“የግል ንብረቱ የሆነ ሕዝብ” ወይም “የእርሱ ሕዝብ”
በምድር ፊት ከሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ በላይ
“በዐለም ላይ ካሉ የሕዝብ ወገኖች ሁሉ”

Deuteronomy 14:3

የትኛውንም ንጹሕ ያልሆነ ነገር አትብላ
የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር መበላት የለባቸውም ያላቸውን የትኛውንም ነገር መብላት አይጠበቅባቸውም።
አጋዘን፣ ሚዳቋ፣ ሰስ
እነዚህ የተለያዩ ዓይነት አጋዘኖች ናቸው። የአንተ ቋንቋ እያንዳንዱን እንስሳ የሚወክል ቃል ከሌለው “ልዩ ልዩ ዓይነት አጋዘን” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።
ሚዳቋ
ይህ በፍጥነት መሮጥ የሚችል ቀጭንና ረጅም እግር ያለው የዱር እንስሳ ነው። ይህንን በዘዳግም 12፡15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሰስ
የአጋዘን ዓይነት (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
ዋሊያ እና ድኩላ
እነዚህ ሁለቱም የድኩላ ዓይነቶች ናቸው። የአንተ ቋንቋ እያንዳንዱን እንስሳ የሚወክል ቃል ከሌለው “የተለያዩ የድኩላ ዓይነቶች” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።
ዋሊያ
የድኩላ ዓይነት (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:6

ሰኮናው የተከፈል
“የተሰነጠቀ ሰኮና ያለው”። ይህ ሰኮናው አንድ ሙሉ ከመሆን ይልቅ ሁለት ቦታ የተሰነጠቀ ነው።
የሚያመነዥክ
ይህ ማለት እንስሳው ምግቡን ከሆዱ ውስጥ እያመጣ እንደገና ያኘከዋል።
ጥንቸል
ይህ ረጃጅም ጆሮዎች ያሉት ትንሽ እንስሳ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ የሚኖረው ምድር ላይ በጉድጓዶች ውስጥ ነው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
ሽኮኮ
ይህ ትንሽ እንስሳ ሲሆን የሚኖረው በዐለታማ አካባቢ ነው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
እነርሱ ለእናንተ ንጹሕ አይደሉም
እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊበላው አይገባውም የሚለው አንዳች ነገር በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:8

ዐሳማ ለእናንተ ንጹሕ አይደለም
እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊበላው አይገባውም የሚለው አንዳች ነገር በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:9

በውሃ ውስጥ ከሚኖሩት እነዚህን መብላት ትችላላችሁ
“በውሃ ውስጥ ከሚኖሩት እነዚህን የመሳሰሉትን እንስሳት መብላት ትችላላችሁ”
ግልፋፊ
ዓሳ በውሃ ውስጥ ለመንቀሳቀስ የሚጠቀምበት ቀጭንና ሰፋ የሚል የአካል ክፍሉ
ቅርፊት
የዓሳውን አካል የሚሸፍኑ ትናንሽ ንብርብሮች
ለእናንተ ንጹሐን አይደሉም
እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊበላው አይገባውም የሚለው አንዳች ነገር በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:11

ንጹሕ የሆነ ወፍ ሁሉ
እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊበላው ይችላል የሚለው እንስሳ፣ ያ እንስሳ በአካላዊነቱም ንጹሕ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ንስር - ጥምብ አንሣ - ዓሳ አውጪ - ቀይ ጭልፊት - ጥቁር ጭልፊት - ገዴ
እነዚህ በሌሊት የሚንቀሳቀሱ ወይም ትናንሽ እንስሳትንና የሞቱ እንስሳትን የሚመገቡ የወፍ ዝርያዎች ናቸው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:14

ቁራ - የባህር ወፍ
እነዚህ በሌሊት የሚንቀሳቀሱ ወይም ትናንሽ እንስሳትንና የሞቱ እንስሳትን የሚመገቡ ሁሉም ዓይነት ወፎች ናቸው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:18

ሽመላ - የውሃ ወፍ፣ እርኩም
እነዚህ ትናንሽ እንስሶችንና እንሽላሊቶችን የሚመገቡ የወፍ ዓይነቶች ናቸው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
የሌሊት ወፍ
በተለይ በምሽት የሚበር፣ ነፍሳትንና ዐይጦችን የሚመገብ፣ ክንፍና ጸጉራማ አካል ያለው እንስሳ
ክንፍ ያላቸው ጥቃቅን ነፍሳት ሁሉ
ይህ ማለት በመንጋ ሆነው የሚንቀሳቀሱ በራሪ ነፍሳት ሁሉ ማለት ነው።
ለእናንተ ንጹሕ አይደሉም
እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊበላው አይገባውም የሚለው እንስሳ በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
መበላት የለባቸውም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ልትበሏቸው አይገባም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ንጹሕ ሆነው የሚበሩ ነገሮች
እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊበላው ይችላል የሚለው እንስሳ፣ ያ እንስሳ በአካላዊነቱም ንጹሕ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:21

የትኛውንም የሞተ ነገር አትብላ
ይህ በተፈጥሮአዊ ሞት የሚሞተውን እንስሳ ማለት ነው።
እንተ ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር የተለየ ሕዝብ ናችሁና
እግዚአብሔር በልዩ ሁኔታ የእርሱ እንዲሆኑ የእስራኤልን ሕዝብ መምረጡ እነርሱን ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ እንደለያቸው ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አምላካችሁ እግዚአብሔር እናንተን ከሌሎች ሕዝቦች ለይቶአችኋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:22

ከእርሻህ ከምታገኘው ምርት ሁሉ
ይህ ከምርታቸው ከየአሥሩ እጅ አንድ እጁን እንዲሰጡ ማለት ነው።
በዓመት በዓመቱ
“በየዓመቱ”
በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሀልዎት ፊት”

Deuteronomy 14:24

እርሱን ይዘህ
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው የምርቱንና የቀንድ ከብቱን አስራት ነው።
መባውን ወደ ገንዘብ ቀይረው

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“መባህን በገንዘብ ትሸጠዋለህ”
ገንዘቡን በእጅህ ይዘህ ሂድ
“ገንዘቡን በቦርሳ አድርገህ ይዘኸው ሂድ”
Deuteronomy 14:26
ያሻህን ሁሉ
“የምትፈልገውን ሁሉ”
በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሀልዎት ፊት”
በበርህ ውስጥ ያለ ሌዋዊ
እዚህ ጋ “በር” የሚወክለው ከተማውን ወይም መንደሩን በሙሉ ነው። ኢ.ት፡ “በከተማህ ውስጥ የሚኖረውን ሌዋዊ ሁሉ” (See: Synecdoche)
አትርሳው
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከአስራትህ ጥቂቱን ለሌዋዊው ስለመስጠትህ እርግጠኛ” (See: Double Negatives)
ከአንተ ጋር ድርሻም ሆነ ርስት የለውምና
የሌዊ ነገድ ርስት የሚሆናቸውን የመሬት ድርሻ አልወሰዱም። የእግዚአብሔር ካህናት ሆነው እርሱ ማገልገላቸው የእነርሱ የርስት ድርሻ ነው። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ድርሻም ሆነ ርስት የለውም
እግዚአብሔር ለሌዋውያን መሬት አለመስጠቱ ርስት እንዳልሰጣቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 14:28
በየሦስተኛው ዓመት ከምርትህ ሁሉ አስራት አቅርብ
ለሌዋውያን፣ ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች፣ ለመበለቶችና መጻተኞች እንዲሰጣቸው እስራኤላውያን በ3 ዓመት አንድ ጊዜ አስራታቸውን በየከተማቸው ማከማቸት ነበረባቸው። (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
በበሮችህ ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት ከተማውን ወይም መንደሩን በሙሉ ነው። ኢ.ት፡ “በከተማህ ውስጥ” (See: Synecdoche)
ከአንተ ጋር ድርሻም ሆነ ርስት የለውምና
እግዚአብሔር ለሌዋውያን ምንም መሬት አለመስጠቱ ርስት እንዳልሰጣቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ወላጆቻቸውን ያጡ
እነዚህ ሁለቱም ወላጆቻቸው የሞቱባቸውና የሚንከባከባቸው ዘመድ የሌላቸው ልጆች ናቸው።
መበለት
ይህቺ ባል የሞተባትና በእርጅናዋ የሚረዳት ልጅ የሌላት ሴት ናት።
በምትሠራው የእጅህ ሥራ ሁሉ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው የሰውን ሁለንተናውን ነው። ይህ የሚያመለክተው አንድ ሰው የሚሠራውን ሥራ ነው። ኢ.ት፡ “በምትሠራው ሥራ ሁሉ” (See: Synecdoche)

---

## Chapter 15

Deuteronomy 15:1
ሰባት ዓመት
“7 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ዕዳ ሰርዝ
“ሰዎች የተበደሩህን ሁሉ ተውላቸው”
ምሕረት የምታደርገው እንደዚህ ነው
“ዕዳውን የምትሰርዘው እንደዚህ ነው”
አበዳሪ
ለሌሎች ሰዎች ገንዘብ የሚያበድር ሰው
ጓደኛውን ወይም ወንድሙን
“ጓደኛ” እና “ወንድም” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም የሚጋሩ ሲሆኑ ከሌላው እስራኤላዊ ወዳጃቸው ጋር ባላቸው የቅርብ ግንኙነት ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት፡ “እስራኤላዊ ጓደኛው” (See: Doublet)
እግዚአብሔር የዕዳ ምሕረት ዐውጇአልና
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ዕዳን እንድትምር እግዚአብሔር አዞሃልና” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እጅህ መተው አለበት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “እንዲመለስልህ መጠየቅ የለብህም” ወይም “ተመልሶ እንዲከፈልህ መጠየቅ የለብህም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 15:4
ድሃ አይኖርም
“ድሃ” የሚለው ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ድሃ ሕዝብ” ውይም “ድሃ የሚሆን አንድም ሰው” (See: Nominal Adjectives)
የሚሰጣችሁ ምድር
ይህ የከነዓንን ምድር ያመለክታል።
እንድትወርሰው ርስት አድርጎ በሚሰጥህ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጣቸው ምድር ርስታቸው እንደሚሆን ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የአምላክህን የእግዚአብሔርን ድምፅ በጥንቃቄ የምትሰማ ከሆነ ብቻ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው ራሱን እግዚአብሔርን ነው። ኢ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር የሚናገረውን ለመታዘዝ ከተጠነቀቅህ ብቻ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ታበድራለህ -- አትበደርም
“ገንዘብ” የሚለው ቃል የሚታወቅ ነው። የዚህን መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ገንዘብ ታበድራለህ … ገንዘብ አትበደርም” (See: Ellipsis)
ለብዙ ሕዝቦች -- በብዙ ሕዝቦች ላይ
እዚህ ጋ “ሕዝቦች” የሚወክሉት ሰዎችን ነው። ኢ.ት፡ “ለብዙ ሀገር ሰዎች … በብዙ ሀገር ሰዎች ላይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በብዙ ሕዝቦች ላይ ትገዛለህ፣ እነርሱ ግን በአንተ ላይ አይገዙም
እዚህ ጋ “መግዛት” በገንዘብ ዐቅም መብለጥ ማለት ነው። ይህ ትርጉሙ በዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው። (See: Parallelism)
Deuteronomy 15:7
ድሃ የሆነ ሰው ቢኖር
እዚህ ጋ “ሰው” ማለት በጥቅሉ ሰው ነው። ኢ.ት፡ “ድሃ የሆነ ሰው ቢኖር”
ከወንድሞችህ አንዱ
“ከእስራኤላዊ ጓደኞችህ አንዱ”
ከበሮችህ በአንዱ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት ከተማን ወይም መንደርን በሙሉ ነው። ኢ.ት፡ “በየትኛውም ከተማህ” (See: Synecdoche)
ልብህን አታደንድን
ግትር መሆን ሰዎቹ ልባቸውን እንዳደነደኑ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ግትር አትሁን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከድኻው ወንድምህ እጅህን አትክደን
ለድኻው ሰው ለመስጠት የማይፈቅድ ሰው ድኻው ሰው ከእርሱ ምንም እንዳያገኝ እጁን እንደሚከድን ተደርጎ ተነግሮለታል። ኢ.ት፡ “ድኻ የሆነውን እስራኤላዊ ጓደኛህን ለመርዳት እምቢ አትበል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ነገር ግን እጅህን ልትዘረጋለት በእርግጥ ይገባል
ድኻውን ሰው የሚረዳ እጁን እንደ ከፈተለት ተደርጎ ተነግሮለታል። ኢ.ት፡ “ነገር ግን ልትረዳው በእርግጥ ይገባሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 15:9
የሚል ክፉ አሳብ በልብህ አይኑር
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው የሰውን አዕምሮ ነው። ኢ.ት፡ “ክፍ አሳብ አታስብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰባተኛው ዓመት፣ የምሕረት ዓመት ቀርቧል
ይህ የምሕረት ዓመት ስለቀረበ ይህንን የሚያስበው ሰው ድኻው ሰው ሊመልስለት እንደማይችል በማሰብ ድኻውን ለመርዳት እንደሚያመነታ ያመለክታል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ሰባተኛው ዓመት
“ሰባተኛው” የሚለው ቃል የሰባት ደረጃ አመልካች ቁጥር ነው። (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የምሕረት ዓመት
“ዕዳን የመሰረዝ ዓመት”
ቀርቧል
በቅርብ የሚሆን አንድ ነገር በአካል የቀረበ በሚመስል መልኩ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “በቅርቡ ይሆናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ስስታም ሆነህ ለድኻው ወንድምህ ሳትሰጠው እንዳትቀር
“አትጨክን፣ ለእስራኤላዊ ጓደኛህ የትኛውንም ነገር ከመስጠት አትንፈገው”
ወደ እግዚአብሔር ያለቅሳል
“ዕርዳታ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር ይጮኻል”
ኃጢአት ይሆንብሃል
“አንተ ያደረግኸውን እግዚአብሔር ኃጢአት ይለዋል”
ልብህን አይጸጽተው
እዚህ ጋ “ልብ” ሙሉውን ሰው ይወክላል። ኢ.ት፡ “ቅር አይበልህ” ወይም “ደስ ይበልህ” (Synecdoche እና ምጸት የሚለውን ተመልከት)
እጅህን በምታኖርበት ሁሉ
እዚህ ጋ “እጅህን በምታኖርበት” የሚወክለው ሙሉውን ሰውና እርሱ የሚሠራውን ሥራ ነው። ኢ.ት፡ “በምትሠራው ሁሉ” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 15:11
ድኻ ከምድር ላይ አይጠፋምና
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በምድር ላይ ድኾች ሁሌም ይኖራሉና” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)
ድኾች
“ድኾች” የሚለው ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሆኖ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ድኾች ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
‘በምድርህ ላይ -- እጅህን መክፈት አለብህ’ ብዬ አዝሃለሁ
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በምድርህ ላይ -- እጅህን እንድትከፍት አዝሃለሁ” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ)
ለወንድምህ፣ ለችግረኛና ለድኻው እጅህን ክፍት
አንድን ሰው ለመርዳት ፈቃደኛ የሚሆን ሰው እጁን እንደሚከፍት ተደርጎ ተነግሮለታል። ኢ.ት፡ “እስራኤላዊ ጓደኛህን፣ የተቸገሩትንና ድኾችን እርዳቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለወንድምህ፣ ለችግረኛና ለድኻው
“ችግረኛ” እና “ድኻ” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ሆኖ እነዚህ ራሳቸውን መርዳት የማችሉ ሰዎች መሆናቸው ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት፡ “ራሳቸውን መርዳት የማይችሉ እስራኤላውያን ጓደኞችህን እርዳቸው” (See: Doublet)
Deuteronomy 15:12
ወንድምህ
እዚህ ጋ “ወንድም” ማለት ወንድ ይሁን ሴት በአጠቃላይ እስራኤላዊ የሆነ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “አንድ እስራኤላዊ ጓደኛህ” ወይም “አንድ ዕብራዊ ጓደኛህ” (ተባዕታዊ ቃል ሴቶችን ሲጨምር የሚለውን ቃል ተመልከት)
ለአንተ የተሸጠ
አንድ ሰው ዕዳውን መክፈል ባይችል አንዳንድ ጊዜ የተበደረውን ለመክፈል ራሱን ለባርነት ይሸጥ ነበር። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ራሳቸውን ለአንተ የሸጡ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ስድስት ዓመት
“6 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሰባተኛ ቁጥር
“7 ዓመት”። ይህ “ሰባተኛ” የሰባት ደረጃን አመልካች ቁጥር ነው። (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)
ባዶ እጁን እንዲሄድ አታድርግ
ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ የሚያቀርበው አስፈላጊ ነገር የሌለው ሰው እጆቹ ባዶ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ለእርሱና ለቤተሰቡ የሚያቀርበው እንዲኖረው ሳትሰጠው እንዲሄድ አታድርገው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በልግስና ስጠው
“በደግነት ስጠው”
Deuteronomy 15:15
ባሪያ እንደነበርህ አስብ
እዚህ ጋ “አንተ” የሚለው ቃል ለብዙ ዓመታትባሪያዎች የነበሩትን ቅድም አያቶቹን ይጨምራል። ኢ.ት፡ “በአንድ ወቅት የአንተም ሕዝብ ባሪያዎች እንደነበሩ አስብ” (See: Forms of You)
አምላክህ እግዚአብሔር ተቤዥቶሃል
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ በግብፅ ባሪያ ከነበረበት ማዳኑ ሕዝቡን ከባርነት ለመቤዠት ገንዘብ የከፈለ በሚመስል መልኩ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
‘ከአንተ አልለይም’ ቢልህ
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛ የሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከአንተ አልለይም ቢልህ” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ
ቤትህ
እዚህ ጋ “ቤት” የሚወክለው የሰውየውን ቤተሰብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከዚያም ወስፌ ወስደህ በሩ ላይ አስደግፈህ ጆሮውን ትበሳዋለህ
“ከዚያም ራሱን በቤትህ የበር መቃን ላይ ታስደግፍና በጆሮው የጉትቻ ማንጠልጠያ ቦታ ላይ የወስፌው ጫፍ እንጨቱ ጋ እስኪደርስ ትበሳዋለህ”
ወስፌ
ቀዳዳ ለማበጀት የሚጠቅም ጫፉ የሾለና ቀጥ ያለ መሣሪያ (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
ዕድሜ ልኩን
“እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ደረስ” ወይም “እስኪሞት ድረስ”
Deuteronomy 15:18
በነጻ ማሰናበቱ አስቸጋሪ ሆኖ አይሰማህ
ይህ ማለት አንድን ሰው በነጻ በሚያሰናብቱበት ጊዜ ቅር መሰኘት የለባቸውም። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በነጻ በምታሰናብተው ጊዜ ደስ ይበልህ” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)
የቅጥር ሠራተኛውን ዕጥፍ ዋጋ ተቀብለሃል
ይህ ማለት ባለቤቱ ሥራ ለማሠራት ከሚቀጥረው ሰው ባነሰ ዋጋ ብቻ ይህንን ባሪያ አሠርቶታል ማለት ነው።
የተቀጠረ ሰው
ይህ ተከፍሎት የሚሠራ ሰው ማለት ነው።
Deuteronomy 15:19
መሸለት
ሱፍ ወይም ጸጉር መቁረጥ
በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሀልዎት ፊት”
ዓመት በዓመት
“በእያንዳንዱ ዓመት” ወይም “በየዓመቱ”
እንካሳ
ሽባ ወይም አካሉ የተጎዳ
Deuteronomy 15:22
በበሮችህ ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት ከተማውን ወይም መንደሩን ነው። ኢ.ት፡ “በማኅበረሰብህ ውስጥ” ወይም “በከተማህ ውስጥ” (See: Synecdoche)
ንጹሕ ያልሆኑ -- ሰዎች
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀባይነት የሌለው ሰው በአካሉም ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ንጹህ የሆኑ ሰዎች
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀባይነት ያለው ሰው በአካሉም ንጹሕ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሚዳቋ ወይም ድኩላ
እነዚህ በፍጥነት መሮጥ የሚያስችል ረጅምና ቀጭን እግሮች ያሏቸው የዱር እንስሳት ናቸው። እነዚህን በዘዳግም 12፡15 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ደሙን አትብላ
“ደሙን አትመገበው”። ደም ሕይወትን ስለወከለ እስራኤላውያን ደም እንዲመገቡ እግዚአብሔር አልፈቀደላቸውም። (ዘዳግም 12፡23ን ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 16
Deuteronomy 16:1
የአቢብ ወር
ይህ በዕብራውያን የቀን አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። እርሱ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ አውጥቶ ያመጣበትን ጊዜ ያስታውሳል። በምዕራባውያኑ አቆጣጠር በመጋቢት መጨረሻና በሚያዝያ መጀመሪያ አካባቢ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ፋሲካን ጠብቀው
“ፋሲካን ጠብቀው” በዓሉን ማክበርና የፋሲካን ምግብ መብላት እንዳለባቸው ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የፋሲካን ምግብ አክብር” ወይም “የፋሲካን ምግብ ብላ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Infor- mation)
ፋሲካን ትሠዋለህ
እዚህ ጋ “ፋሲካ” የሚወክለው ለፋሲካ በዓል የሚሠዋውን እንስሳ ነው። ኢ.ት፡ “ለፋሲካ መሥዋዕት ታቀርባለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 16:3
ከእርሱ ጋር
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው የሚሠዉትንና የሚበሉትን እንስሳ ነው።
ሰባት ቀን
“7 ቀን” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
የመከራን እንጀራ
ይህ እርሾ የሌለበት እንጀራ ስም ነበር። ሙሉ ትርጉሙ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ይህ እንጀራ በግብፅ በነበራችሁበት ጊዜ ምን ያህል እንደተሰቃያችሁ ያስታውሳችኋል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
በጥድፊያ ከግብፅ ምድር የወጣችሁበትን
ሕዝቡ በፍጥነት ግብፅን ለቀው መውጣት ስለነበረባቸው እርሾ ጨምረውበት እንጀራ ለመጋገር በቂ ጊዜ አልነበራቸውም። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግለጽ ሊደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “በችኮላ ከግብፅ በወጣችሁ ጊዜ እርሾ የገባበት እንጀራ ለማዘጋጀት ጊዜ አልነበራችሁም” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
በሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ ይህንን አድርጉ
“በሕይወት እስካላችሁ ድረስ”
ልብ በሉ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “አስታውሱ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በመካከላችሁ ምንም እርሾ አይታይ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በመካከላችሁ ምንም እርሾ አይኑራችሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በግዛታችሁ ሁሉ
“በክልሎቻችሁ ሁሉ ውስጥ” ወይም “በምድራችሁ ሁሉ ላይ”
የመጀመሪያ ቀን
ይህ “የመጀመሪያ” አንድን የሚያመለክት የደረጃ አመልካች ቁጥር ነው። (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 16:5
ፋሲካን መሠዋት አይኖርብህም
እዚህ ጋ “ፋሲካ” የሚወክለው የሚሠዋውን እንስሳ ነው። ኢ.ት፡ “ለፋሲካ እንስሳውን መሠዋት አይኖርባችሁም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በየትኛውም የከተማችሁ በሮች
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት ከተሞቹን ወይም መንደሮችን ነው። ኢ.ት፡ “በየትኛውም መንደሮችህ ውስጥ” (See: Synecdoche)
ፀሐይ በምትወርድበት
“ፀሐይ ስትጠልቅ”
Deuteronomy 16:7
መጥበስ ይኖርብሃል
“ማብሰል ይኖርብሃል”
ስድስት ቀን
“6 ቀን” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሰባት ቀን
“ሰባተኛ” የሰባት ደረጃን አመልካች ቁጥር ነው (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)
የተለየ ጉባዔ
“ልዩ ስብሰባ”
Deuteronomy 16:9
ሰባት ሳምንት ቁጠር
“7 ሳምንት ቁጠር” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
እህል ማጨድ ከምትጀምርበት ጊዜ ጀምሮ
“ማጨድ ከምትጀምርበት” የሚለው ሐረግ መከር መሰብሰብ የሚጀመርበትን ጊዜ ማመላከቻ መንገድ ነው። ኢ.ት፡ “እህል መሰብሰብ ከምትጀምርበት ጊዜ ጀምሮ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ማጭድ
ሣር፣ ሰብል፣ እና ወይን ለመቁረጥ የሚያገለግል ቆልማማ ምላጭ ያለው መሣሪያ ነው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
በእጅህ በምትሰጠው የበጎ ፈቃድ ስጦታ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “የበጎ ፈቃድ ስጦታህን ትሰጣለህ” (See: Synecdoche)
አምላክህ እግዚአብሔር በባረከህ መጠን
“አምላክህ እግዚአብሔር እንደ ሰጠህ ምርት መጠን”። ይህ ማለት ሰዎቹ ምን ያህል መስጠት እንደሚኖርባቸው የሚወስኑት በዚያ ዓመት ባመረቱት ምርት መጠን ይሆናል።
Deuteronomy 16:11
ወንድ ልጅህ፣ ሴት ልጅህ፣ ወንድ ባሪያህ፣ ሴት ባሪያህ፣ ሌዋዊው
እነዚህ አንድን ተለይቶ የታወቀን ሰው አያመለክቱም። የሚያመለክተው እንዲህ ያሉትን ሰዎች በአጠቃላይ ነው። ኢ.ት፡ “ወንዶች ልጆቻችሁን፣ ሴቶች ልጆቻችሁን፣ ወንዶች ባሪያዎቻችሁን፣ ሴቶች ባሪያዎቻችሁን፣ የትኛውንም ሌዋዊ” (See: Generic Noun Phrases)
በከተማህ በሮች ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክሉት ከተሞችን ወይም መንደሮችን ነው። ኢ.ት፡ “በመንደሮችህ ውስጥ” (See: Synecdoche)
መጻተኛው፣ አባት የሌላቸውንና መበለቶችን
ይህ የሚያመለክተው እንዲህ ያሉትን የመሰሉ ሰዎችን በአጠቃላይ ነው። ኢ.ት፡ “መጻተኞችን ሁሉ፣ ወላጆቻቸውን ያጡትን፣ መበለቶችን” (See: Generic Noun Phrases)
አባት የሌላቸውን
እነዚህ አባትና እናት የሞቱባቸውና የሚንከባከባቸው ዘመድ የሌላቸው ልጆች ናቸው።
መበለት
ይህ ማለት ባል የሞተባትና በእርጅናዋ የሚረዳት ልጅ የሌላት ሴት ማለት ነው።
ልብ በል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “አስታውስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 16:13
የመጠለያ በዓል
የዚህ በዓል ሌሎች ስሞች፣ “የመገናኛው ድንኳን በዓል”፣ “የዳስ በዓል”፣ እና “የመሰብሰብ በዓል”። በመከር ጊዜ ገበሬዎች በመስኩ ላይ ጊዜያዊ መጠለያ ይሠሩ ነበር። ይህ በዓል የሚደረገው የዓመቱ መከር ከተሰበሰበ በኋላ ነበር።
ሰባት ቀን
“7 ቀን” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
በበሮችህ ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮችህ” የሚለው ቃል የሚወክለው ከተሞችንና መንደሮችን ነው። “በመንደሮችህ ውስጥ” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 16:15
በዓሉን
“የመጠለያ በዓሉን”
የእጆችህን ሥራ ሁሉ
እዚህ ጋ “እጆች” የሚወክሉት ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “የምትሠራውን ሥራ ሁሉ” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 16:16
ወንዶችህ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ይቅረቡ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እግዚአብሔር ሴቶቹ እንዲመጡ ባይጠይቅም ለእነርሱም ተፈቅዶላቸዋል። ወንዶቹ መላውን ቤተሰባቸውን መወከል ይችሉ ነበር።
በእግዚአብሔር ፊት ይቅረቡ
“ይምጡና በእግዚአብሔር ሀልዎት ፊት ይቁሙ”
ማንም በእግዚአብሔር ፊት ባዶ እጁን አይታይ
“በእግዚአብሔር ፊት ስጦታ ሳይዙ አይምጡ”። እነዚህ ሁለት አሉታዊ ሐረጎች በአንድ ላይ አዎንታዊ ትርጉም አላቸው። ኢ.ት: “ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚመጣ ሁሉ ስጦታ ያምጣ” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 16:18
ዳኞችን አድርግ
“ዳኞችን ሹም” ወይም “ዳኞችን ምረጥ”
በከተሞችህ በሮች ውስጥ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚወክለው ከተማን ወይም መንደርን ነው። ኢ.ት: “በመንደሮችህ ሁሉ ውስጥ” (See: Synecdoche)
ይወስዳሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ትመርጣቸዋለህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በሕዝቡ ላይ በጽድቅ ፍርድ ዳኙ
“ሕዝቡን በፍትሐዊነት ዳኙ”
ፍትሕን በኃይል ምክንያት አታዛባ
ሙሴ ስለ ፍትሕ ሲናገር ብርቱው ሰው ከደካማው ሰው በጉልበት እንደሚቀማው አንዳች ቁሳዊ አካል አድርጎ ይናገራል። ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊነገር ይችላል። የአንተ ቋንቋ “ለመውሰድ ኃይል ተጠቀም” ለማለት አንድ ቃል ይኖረው ይሆናል። ኢ.ት: “በምትዳኝበት ጊዜ አፍትሐዊ አትሁን” ወይም “ትክክለኛ ውሳኔዎችን ስጥ” (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት and Double Negatives))
አታድርግ
እዚህ ጋ “አንተ” የሚያመለክተው እነዚያን ዳኞችና አለቆች ተደርገው የተሾሙትን ነው። (See: Forms of You)
ጉቦ የጠቢቡን ዓይኖች ያሳውራልና የጻድቁንም ቃል ያጣምማልና
ጉቦ መቀበል ሰዎችን እንደሚያበላቸው ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት: “ጉቦን የሚቀበል ጥበበኛ ሰው እንኳን ይታወራል፣ ጉቦን የሚቀበል ጻድቅ ሰውም እንኳን ሐሰትን ይናገራል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጉቦ የጠቢቡን ዓይኖች ያሳውራል
ክፉ በሆነው ነገር ላይ እንዳይናገር ጉቦን የሚቀበል ጠቢብ ሰው የሚታወር ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጠቢቡ
“ጠቢቡ” የሚለው ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ጠቢብ ሰው” ወይም “ጥበበኛ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
የጻድቁን ቃል ያጣምማል
“ጻድቅ” የሚለው ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ጻድቁን ሰው እንዲዋሽ ያደርገዋል” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ፍትሕን ተከተል፣ ፍትሕን ብቻ ተከተል
ፍትሕ በሚራመድ ሰው ተመስሎ ተነግሮለታል። ትክክለኛና ቅን የሆነውን ነገር የሚያደርግ ሰው ፍትሕን በቅርበት እንደተከተለ ተነግሮለታል። ኢ.ት: “አግባብነት ያለውን ብቻ አድርግ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አምላክህ እግዚአብሔር የሚሰጥህን ምድር ውረስ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጣቸውን ምድር መቀበል ሕዝቡ ምድሪቱን ከእግዚአብሔር እንደሚወርስ ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 16:21
ማድረግ የለብህም
እዚህ ጋ “አንተ” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ በሙሉ ነው። (See: Forms of You)
አምላክህ እግዚአብሔር የሚጠላውን የትኛውንም የድንጋይ ማምለኪያ ዐምድ
“አምላክህ እግዚአብሔር የሚጠላውን” የሚለው ሐረግ ስለ ማምለኪያ የድንጋይ ዐምድ የበለጠ መረጃ ይሰጣል። ኢ.ት: “አምላክህ እግዚአብሔር ስለሚጠላቸው የትኛውንም የማምለኪያ የድንጋይ ዐምድ” (See: Distinguishing versus Informing or Reminding)
የማምለኪያ የድንጋ ዐምድ
ይህ የሚያመለክተው ሐሰተኞችን አማልክት ለማምለክ የሚጠቀሙባቸውን ጣዖታት የሆኑ ዐምዶችን ነው።

---

Chapter 17
Deuteronomy 17:1
የትኛውም እንከን ያለበት
“እንከን ያለበት” ወይም “አንዳች ጉድለት ያለበትን”። እንስሳው ሲታይ ጤነኛና እንከን የሌለበት
ያ ለእግዚአብሔር አስጸያፊ ይሆናል
“ያ ለእግዚአብሔር አስቀያሚ ይሆናል
Deuteronomy 17:2
ቢገኝ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “አንድ ሰው ብታገኝ” ወይም “አንድ ሰው ቢኖር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በየትኛውም የከተማህ በሮች ውስጥ
እዚህ ጋ “የከተማ በሮች” ከተሞችን ወይም መንደሮችን ይወክላሉ። ኢ.ት: “ከከተሞችህ በአንዱ ቢኖር” (See: Synecdoche)
በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን
የእግዚአብሔር ፊት የእግዚአብሔርን ውሳኔ ወይም ምዘና ይወክላል። ኢ.ት: “አምላክህ እግዚአብሔር ክፉ ነው ብሎ የሚያስበው ነገር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቃል ኪዳኑን ይተላለፋል
“ቃል ኪዳኑን አይታዘዝም”
የትኛውንም የሰማይ ሰራዊት
“የትኛውንም ኮከብ”
እኔ ያላዘዝኩትን
“እንዲያደርገው ለማንም ያላዘዝኩትን”
ስለዚህ ነገር ቢነገርህ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “አንድ ሰው ስለዚህ የእምቢተኝነት ተግባር ቢነግርህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በጥንቃቄ መርምር
የነገር ስም የሆነው “ምርመራ” እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “የሆነውን ነገር በጥንቃቄ መርምር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
እንዲህ ያለ አስጸያፊ ነገር በእስራኤል ተደርጎ እንደሆን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “አንድ ሰው እንዲህ ያለውን አስከፊ ነገር በእስራኤል አድርጎ እንደሆነ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 17:5
ሞት የሚገባው ሰው በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች አፍ ይገደል
እዚህ ጋ “አፍ” የሚወክለው የመስካሪዎችን ምስክርነት ነው። ይህ ወደ አድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “በሰውየው ላይ ሁለት ወይም ሦስት ምስክሮች ከመሰከሩበት ከዚያ በኋላ ታስወግደዋለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር፣ አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ነገር ግን በአንድ ምስክር አፍ ብቻ መገደል የለበትም
እዚህ ጋ “አፍ” የሚወክለው የመስካሪውን ምስክርነት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ነገር ግን በእርሱ ላይ የሚመሰክረው አንድ ሰው ብቻ ከሆነ ያንን ሰው ማስወገድ አይኖርብህም” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እርሱን ለመግደል በመጀመሪያ የምስክሮች እጅ፣ ከዚያም የሕዝቡ ሁሉ እጅ ይረፍበት
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ምስክሮችን በሙሉ ነው። ኢ.ት: “ድንጋዮቹን ለመወርወር ምስክሮቹ ራሳቸው የመጀመሪያ ይሁኑ፣ ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ በእርሱ ላይ ድንጋይ በመወርወር ይግደሉት” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 17:8
ጉዳይ ቢነሣ
“ጉዳይ ቢኖር” ወይም “ሁኔታ ቢኖር”
የአንዱ ሰው መብትና የሌላው ሰው መብት
“መብት” አንድ ሰው አንድን ነገር የሚያደርግበት ወይም አንድ ነገር እንዲኖረው

የሚያስችለው ሕጋዊ ስልጣን ነው።
በከተማህ በሮች ውስጥ
እዚህ ጋ “የከተማ በሮች” ከተሞችን ወይም መንደሮችን ይወክላል። ኢ.ት፡ “በመንደርህ ውስጥ” (See: Synecdoche)
ምክራቸውን ጠይቅ
የነገር ስም የሆነው “ምክር” እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እንዲመክሩህ ጠይቃቸው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ውሳኔውን ይሰጡሃል
የነገር ስም የሆነው “ውሳኔ” እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 17:10
የተሰጠህን ሕግ ተከተል
ካህናትና ዳኛው የሚወስኑትን የሚታዘዝ ሰው በአካሉ ከሕግ ኋላ እንደተከተለ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ስለ ጉዳዩ ዳኛውና ካህናት የሚወስኑትን ታዘዝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 17:12
ካህኑን የማይሰማ -- ወይም ዳኛውን የማይሰማ
“ካህኑን የማይታዘዝ … ወይም ዳኛውን የማይታዘዝ
ከእስራኤል ክፉን ታርቃለህ
ስማዊ ቅጽል የሆነው “ክፉን” እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ይህንን ክፉ ነገር ያደረገውን ሰው ከእስራኤል መካክል ታስወግደዋለህ” ወይም “ይህንን ክፉ ሰው ግደለው” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ሕዝቡ ሁሉ ሰምተው ይፈራሉ፣ ከእንግዲህም የዕብሪትን ተግባር አይፈጽሙም
ሕዝቡ የዕብሪት ተግባር የፈጸመው ሰው ስለመገደሉ በሚሰሙበት ጊዜ ይፈራሉ እነርሱ ራሳቸው የዕብሪትን ተግባር አይፈጽሙም እንደ ማለት ነው። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 17:14
ወደ ምድሪቱ በምትመጡበት ጊዜ
“በምትመጡበት” የሚለው ቃል “በምትሄዱበት” ወይም “ስትገቡ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። (ሂድ እና ና የሚለውን ተመልከት)
‘በዙሪያዬ እንዳሉት ሕዝቦች በራሴ ላይ ንጉሥ አነግሣለሁ’ በምትልበት ጊዜ፣ ያን ጊዜ
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛ የሆነው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከዚያም በዙሪያህ ያሉ ሀገራት ሕዝቦች ንጉሥ እንዳላቸው አንተም እንዲኖርህ ትወስናለህ፣ ከዚያም” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)
በዙሪያዬ እንዳሉት -- በራሴ ላይ ንጉሥ አነግሣለሁ
ሙሴ እንደ አንድ ሰው ቆጥሮ የሚናገራቸው ሰዎች አሉት። ወደ ብዙ ቁጥር ተውላጠ ስም መተርጎም በይበልጥ የተለመደ ይሆናል። ኢ.ት፡ “በዙሪያችን … ለራሳችን እናነግሣለን” (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)
ለራሴ ንጉሥ አነግሣለሁ
በእስራኤል ለአንድ ሰው እንደ ንጉሥ እንዲገዛቸው ሥልጣን መስጠታቸው ሕዝቡ ያንን ሰው ከእነርሱ በላይ ባለ ቦታ ላይ እንዳስቀመጡት ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በዙሪያዬ እንዳሉት ሕዝቦች ሁሉ
“በዙሪያዬ ያሉ ሕዝቦች”
ሀገራት ሁሉ
እዚህ ጋ “ሀገራት” የሚወክሉት በሀገራቱ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከወንድሞችህ መካከል አንዱን
“እንደ አንተው እስራኤላዊ ከሆኑት አንዱን”
በራስህ ላይ ወንድምህ ያልሆነውን መጻተኛ
የእነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉም ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም የሚያመለክቱት እስራኤላዊ ያልሆነውን ሰው ነው። የእስራኤል ሕዝብ መጻተኛው እንዲገዛቸው እንዳይፈቅዱ እግዚአብሔር አጽንዖት ሰጥቷል። ኢ.ት፡ “በራስህ ላይ መጻተኛውን” ወይም “እስራኤላዊ ያልሆነውን በራስህ ላይ” (See: Doublet)
Deuteronomy 17:16
እግዚአብሔር፣ ‘በዚያ መንገድ እንዳትመለስ’ ብሎአልና።
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ሌላ ትዕምርተ ጥቅስ አለው። ቀጥተኛው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ዳግመኛ ወደ ግብፅ እንዳትመለሱ ብሏልና” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)
ልቡ እንዳይስት
እዚህ ጋ “ልብ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። ባዕዳን ሴቶችን የሚያገባና የእነርሱን ሐሰተኛ አማልክት ለማምለክ የሚጀምር እስራኤላዊ ንጉሥ ልቡ ከእግዚአብሔር እንደሚመለስ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔርን ማክበሩን በማቆም ሐሰተኞች አማልክትን ማምለክ እንዲጀምር እንዳያደርጉት” (Synecdoche and ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 17:18
በመንግሥቱ ዙፋን ላይ በሚቀመጥበት ጊዜ
እዚህ ጋ “ዙፋን” የሚወክለው ሰውየው እንደ ንጉሥ የሚኖረውን ኃይልና ሥልጣን ነው። በዙፋን መቀመጥ ንጉሥ መሆን ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ንጉሥ በሚሆንበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የዚህን ሕግ ቅጅ ለራሱ በጥቅልል ላይ ይጻፈው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “በግሉ የዚህን ሕግ ቅጅ በጥቅልል ላይ ለራሱ ይጻፍ” ወይም 2) “የዚህን ሕግ ቅጅ የሚጽፍለትን ሰው ይሹም”
ሌዋውያን በሆኑት ካህናት ፊት ካለው ሕግ
“ሌዋውያን ካህናት ከሚጠብቁት ከሕጉ ቅጅ”
የዚህን ሕግ ቃል ሁሉ እና እነዚህን ሥርዓቶች እንዲጠብቅ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን ንጉሡ የእግዚአብሔርን ሕግ በሙሉ መታዘዝ እንዳለበት አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Parallelism)
Deuteronomy 17:20
ልቡ በወንድሞቹ ላይ እንዳይታበይ
እዚህ ጋ “ልቡ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። የአንድ ንጉሥ ዕብሪተኛ መሆን ልቡ እንደ ታበየ ሆኖ ተነግሮለታል። ኢ.ት፡ “ዕብሪተኛ እንዳይሆን” ወይም “እንደ እርሱ ካለው እስራኤላዊ ይልቅ የተሻለ እንደሆነ እንዳያስብ” (Synecdoche እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከትዕዛዛቱ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ እንዳይመለስ
አንድ ንጉሥ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት አለመታዘዙ አንድ ሰው ከትክክለኛው መንገድ እንደሚወጣ በሚመስል መልኩ ተነግሯል። ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከትዕዛዛቱ የትኛውንም ሳይታዘዝ እንዳይቀር” ወይም “ትዕዛዛቱን ሁሉ እንዲጠብቅ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ምጸት የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 18
Deuteronomy 18:1
ከእስራኤል ጋር ድርሻም ሆነ ርስት አይኖራቸውም
ሌዋውያን የትኛውንም መሬት ከእግዚአብሔር አለመቀበላቸው ርስት እንዳልተቀበሉ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ከሕዝቡ መሬት የትኛውንም አይወስዱም” ወይም “እስራኤላውያን ከሚወስዱት መሬት የትኛውንም አይቀበሉም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ምንም ድርሻ
“ምንም ክፍል” ወይም “ምንም ድርሻ”
በወንድሞቻቸው መካከል
“በሌሎች የእስራኤል ነገዶች መካከል” ወይም “በሌሎች እስራኤላውያን መካከል”
ርስታቸው እግዚአብሔር ነው
አሮንና የእርሱ ተወላጆች እንደ ካህናት እግዚአብሔርን በማገልገላቸው ታላቅ ክብር እንደሚኖራቸው ሙሴ ሲናገር እግዚአብሔርን እንደሚወርሱት አንዳች ነገር አድርጎ ይናገራል። ተመሳሳዩን ሐረግ በዘዳግም 10:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ከዚያ ይልቅ እግዚአብሔር ይኖራቸዋል” ወይም “ከዚያ ይልቅ፣ እግዚአብሔር እርሱን እንዲያገለግሉት ይፈቅድላቸዋል፣ በዚያም አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ያቀርብላቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 18:3
በውስጥ ያሉትን ክፍሎች
ይህ ጨጓራና አንጀት ነው።

ትሰጠዋለህ

“ለካህኑ ትሰጠዋለህ”

መርጦታል

እዚህ ጋ “እርሱን” ሌዋውያንን ሁሉ ይወክላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእግዚአብሔር ስም ለማገልገል እንዲቆም

እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ስም” የቆመው ለራሱ ለእግዚአብሔርና ለሥልጣኑ ነው። ኢ.ት: “የእርሱ ልዩ አገልጋዮች እንዲሆኑ” ወይም “እንደ እግዚአብሔር ተወካዮች እንዲያገለግሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እርሱንና ወንዶች ልጆቹን ለዘላለም

እዚህ ጋ “እርሱን” የሚወክለው ሌዋውያንን ሁሉ ነው። ኢ.ት: “ሌዋውያንና ተወላጆቻቸው ለዘላለም” (See: Synec- doche)

Deuteronomy 18:6

በሙሉ ነፍሱ ቢፈልግ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “በብርቱ ቢፈልግ” ወይም “በእርግጠኝነት ቢፈልግ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም በአምላኩ በእግዚአብሔር ስም ያገልግል

እዚህ ጋ “ስም” የሚወክለው እግዚአብሔርን እና የእርሱን ሥልጣን ነው። ኢ.ት: “ከዚያም አምላኩን እግዚአብሔርን በካህንነት ያገልግል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእግዚአብሔር ፊት በዚያ የሚቆሙት

“በእግዚአብሔር ሀልዎት ፊት በመቅደሱ የሚያገለግሉት”

የቤተሰቡን ርስት

ካህኑ ከአባቱ የሚወርሰው ይህ ነው

Deuteronomy 18:9

በምትመጣበት ጊዜ

(ሂድ እና ና የሚለውን ተመልከት)

የእነዚያን ሕዝቦች አስጸያፊ ተግባር ለመጠበቅ አትማር

በዙሪያቸው ያሉትን ሀገራት ሰዎች ሃይማኖታዊ ተግባራት እግዚአብሔር ይጠላል። እርሱ እጅግ ክፉዎች እንደሆኑ አድርጎ ይመለክታቸዋል። እዚህ ጋ “ሀገሮች” ሰዎቹን ይወክላሉ። ኢ.ት: “የሌሎች ሀገራት ሰዎች የሚያደርጓቸውን አስከፊ ነገሮች አታድርጉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመካከልህ ማንም አይገኝ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “በመካከልህ ማንም አይኑር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ማንም የሚጠነቁል -- ከመናፍስት ጋር የሚነጋገር

እነዚህ አስማትን የሚለማመዱ የተለዩ ሰዎች ናቸው። የትኛውንም ዓይነት አስማት እግዚአብሔር ከልክሏል። ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ሁሉ የሚሆን ቃል ከሌለህ በይበልጥ ጥቅል በሆነ መልኩ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ወደፊት የሚሆነውን ለማወቅ በመሞከር፣ ዕጣ ለመጣል ወይም የሙታንን መናፍስት ለማነጋገር አስማት የሚጠቀም ማንም ቢሆን”

በሲኒ የሚገኙ ምልክቶችን የሚያነብ

በሲኒ ውስጥ ያሉ ቅርጾችንና ስዕሎችን የሚያነብና ከሚያየው ተነሥቶ ወደፊት የሚሆኑትን ሁነቶች የሚተነብይ

Deuteronomy 18:12

ያባርራቸዋል

እዚህ ጋ “እነርሱን” የሚያመለክተው አስቀድሞ በከነዓን የሚኖሩትን ሰዎች ነው።

ለእነዚህ ሕዝቦች

እዚህ ጋ “ሕዝቦች” የሚለው ቃል የቆመው በከነዓን ለሚኖሩ የሕዝብ ወገኖች ነው። ኢ.ት: “ለእነዚህ የሕዝብ ወገኖች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምታስወጧቸውን እነዚህን ሕዝቦች

“መሬታቸውን የምትወስድባቸው እነዚህ ሕዝቦች”

Deuteronomy 18:15

አምላክህ እግዚአብሔር ነቢይ ያስነሣልሃል

ነቢይ እንዲሆን እግዚአብሔር አንድን ሰው መሾሙ እግዚአብሔር ሰውየውን እንደሚያነሣው ወይም ብድግ እንደሚያደርገው ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከወንድሞችህ አንዱ

“እንዳንተው እስራኤላዊ ከሆኑት አንዱ”

የጠየቅኸው ይህንን ነው

እዚህ ጋ “አንተ” የሚያመለክተው ከ40 ዓመታት በፊት በኮሬብ ተራራ የነበሩትን እስራኤላውያንን ነው።

በኮሬብ ጉባዔ በተደረገበት ቀን

“በኮሬብ በአንድ ላይ በተሰበሰባችሁበት ቀን”

ጉባዔ በተደረገበት ቀን፣ ‘የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ድምፅ እንስማ፣ ይህንን ታላቅ እሳትም ከእንግዲህ አንይ፣ እንዲህ ካልሆነ እንሞታለን’ ስትል

ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛ የሆነው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተደርጎ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ጉባዔ በተደረገበት ቀን እንዳትሞት ፈርተህ ስለነበር የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማትም ሆነ ከእንግዲህ የእርሱን ታላቅ እሳት ማየት እንደማትፈልግ በተናገርክ ጊዜ” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ድምፅ እንደገና አንስማ

እዚህ ጋ እግዚአብሔር ለተናገረው አጽንዖት ለመስጠት የእርሱ በሆነ ”ድምፅ” ተወክሏል። ኢ.ት: “አምላካችን እግዚአብሔር እንደገና ሲናገር አንስማ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 18:17

ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ

እግዚአብሔር፣ አንድን ሰው ነቢይ እንዲሆን መሾሙ፣ እግዚአብሔር ሰውየውን እንደሚያነሣው ወይም ብድግ እንደሚያደርገው ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከወንድሞቻቸው መካከል

“እንደ እነርሱ እስራኤላዊ ከሆኑት መካከል”

ቃሌን በአፉ ላይ አኖራለሁ

ነቢዩ ምን ማለት እንዳለበት እግዚአብሔር ለእርሱ መንገሩ እግዚአብሔር በነቢዩ አፍ ውስጥ ቃልን እንደሚጨምርበት ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይነግራቸዋል

“ለእስራኤል ሕዝብ ይነግራቸዋል”

በስሜ የሚናገረውን ቃል የማይሰማ

እዚህ ጋ “ስሜ” የሚወክለው እግዚአብሔርን እና ሥልጣኑን ነው። ኢ.ት: “መልዕክቴን በሚናገርበት ጊዜ የማይሰማው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እጠይቀዋለሁ

“በኃላፊነት እጠይቀዋለሁ” ወይም “እቀጣዋለሁ”። እዚህ ጋ “እርሱን” የሚያመለክተው ነቢዩን የማይሰማውን ሰው ነው።

Deuteronomy 18:20

በትዕቢት ቃልን የሚናገር

“መልዕክት ለመናገር የሚደፍር” ወይም “በዕብሪተኝነት መልዕክት የሚናገር”

በስሜ

እዚህ ጋ “ስሜ” የሚያመለክተው ራሱን እግዚአብሔርንና ሥልጣኑን ነው። ኢ.ት: “ለእኔ” ወይም “በእኔ ሥልጣን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቃልን

“መልዕክትን”

በሌሎች አማልክት ስም የሚናገር

እዚህ ጋ “ስም” የሚወክለው አማልክቱን ራሳቸውን ወይም ሥልጣናቸውን ነው። ይህ ማለት ሐሰተኞቹ አማልክት አንድን መልዕክት እንዲናገር እንደ ነገሩት ነቢዩ ያስታውቃል ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በልብህ እንዲህ ትላለህ

እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው የሰውን አሳብ ነው። ኢ.ት: “ራስህን ትጠይቃለህ” ወይም “ለራስህ ትናገራለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መልዕክቱን እግዚአብሔር እንዳልተናገረ እንዴት እንለያለን?

“ነቢዩ የሚናገረው መልዕክት ከእግዚአብሔር መሆኑን እንዴት እናውቃለን? እዚህ ጋ “እኛ” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው።

Deuteronomy 18:22

ነቢይ የሚናገረው በእግዚአብሔር ስም ነው

እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ስም” የሚያመለክተው ራሱን እግዚአብሔርን እና ሥልጣኑን ነው። ኢ.ት: “ነቢይ እኔን ወክሎ እንደሚናገር ያስታውቃል” ወይም “ነቢይ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 19
Deuteronomy 19:1
አምላክህ እግዚአብሔር ሕዝቦችን በሚቆርጣቸው ጊዜ
እግዚአብሔር በከነዓን የሚኖሩትን ሰዎች ማጥፋቱ አንድ ሰው የጨርቅ ቁራጭ ወይም የዛፍ ቅርንጫፍ እንደሚቆርጥ እርሱም እንደሚቆርጣቸው ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሕዝቦችን
ይህ በከነዓን የሚኖሩትን የሕዝብ ወገኖች ይወክላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አምላክህ እግዚአብሔር ምድራቸውን የሚሰጥህን የእነዚያን
“አምላክህ እግዚአብሔር በሚሰጥህ ምድር ላይ ይኖሩ የነበሩት እነዚያ ሕዝቦች”
በምትመጣባቸው
“ከነዚያ ሕዝቦች ምድሪቱን ስትወስድ” ወይም “እነዚያ ሕዝቦች ከለቀቁ በኋላ ምድሪቱን የራስህ ስታደርግ”
ሦስት ከተሞችን ምረጥ
“3 ከተሞችን ምረጥ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
መንገድ ሥራ
ሰዎች ወደ እነዚህ ከተሞች ለመጓዝ እንዲቀላቸው መንገዶችን መሥራት ይኖርባቸዋል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
የምድርህን ድንበሮች በሦስት ቦታ ክፈላቸው
ከሚመርጧቸው ከተሞች አንዱ በእያንዳንዱ የምድሪቱ ክፍል ውስጥ ይሁን። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
አምላክህ እግዚአብሔር በሚያወርስህ ምድር
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ምድሪቱን መስጠቱ ሕዝቡ ምድሪቱን እንደወረሱ ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 19:4
ሕጉ ይህ ነው
“መመሪያዎቹ እነዚህ ናቸው” ወይም “አቅጣጫዎቹ እነዚህ ናቸው”
ሌላውን የገደለ
“ሰው” የሚለው ቃል እንዳለበት ይታወቃል። ኢ.ት: “ሌላውን ሰው የገደለ ሰው” (See: Ellipsis)
ወደዚያ የሚሸሽ
“ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዱ የሚያመልጥ” ወይም “ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዱ የሚሮጥ”
ለመኖር
“ሕይወቱን ለማዳን”። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “የሟች ቤተሰብ ተበቅለው እንዳይገድሉት” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ማንም ሳያውቅ ባልንጀራውን የሚገድል
እዚህ ጋ “ባልንጀራ” ማለት በአጠቃላይ የትኛውም ሰው ማለት ነው። ኢ.ት: “በድንገት ሌላውን ሰው የሚገድል የትኛውም ሰው”
አስቀድሞ ጥላቻ ሳይኖረው
“ነገር ግን ባልንጀራውን ከመግደሉ በፊት አልጠላው እንደሆነ”። ባልንጀራውን አስቦበት የሚገድልበት ምክንያት እንዳልነበረው ያመለክታል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ለምሳሌ፣ አንድ ሰው እንጨት ለመቁረጥ ወደ ጫካ ቢሄድ
ደራሲው አንድ ሰው ሌላውን በድንገት የሚገድልበትን መላ ምታዊ ሁኔታ ይሰጣል። (See: Hypothetical Situations)
ብረቱ ከእጀታው ወልቆ
የመጥረቢያው የብረት ክፍል ከእንጨቱ እጀታ ወልቆ
ባልንጀራውን መትቶ ቢገድለው
ይህ ማለት የመጥረቢያው ራስ ባልንጀራውን መትቶ ገድሎታል ማለት ነው።
ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዲቱ -- ሕይወቱን ያድን
የሟቹ ሰው ቤተሰብ ምናልባት ሊበቀሉት እንደሚሞክሩ ያመለክታል። በዚያ ያሉት ሰዎች ጥበቃ እንዲያደርጉለት እርሱን የገደለው ሰው ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዲቱ መሸሽ ይችላል (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 19:6
ደም ተበቃዩ
እዚህ ጋ “ደም” የሚወክለው የተገደለውን ሰው ነው። “ደም ተበቃዩ” ሰው የሟቹ የቅርብ ዘመድ ነው። ገዳዩን ለመቅጣት ኃላፊነቱ የዚህ ዘመድ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሕይወትን የሚያጠፋ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ሌላውን ሰው የገደለ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በንዴት ግሎ
የአንድ ሰው በጣም መቆጣት ልክ ቁጣ እንደሚግል አንዳች ነገር ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት: “በጣም ተቆጥቶ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይመታውና ይገድለዋል
"ደም ተበቃዩ ሟችን የገደለውን ሰው ይመታና ይገድለዋል”
አስቀድሞ ባልንጀራውን አልጠላውምና ያ ሰው መሞት የሚገባው ባይሆንም
“ሌላውን ሰው የገደለው በድንገት ስለሆነና ጠላቱ ስላልነበረ፣ ሰውየውን ለመጉዳትም ስላላቀደ ያ ሰው መሞት የሚገባው ባይሆንም”
Deuteronomy 19:8
ድንበርህን ያሰፋል
“የምትወርሰውን ተጨማሪ መሬት ይሰጥሃል”
ለቅድም አያቶችህ እንደማለው
“እርሱ እንደሚያደርገው ለቅድም አያቶችህ ተስፋ የሰጠውን”
ታደርጋቸው ዘንድ እነዚህን ትዕዛዛት በሙሉ ብትጠብቅ
“እነዚህን ትዕዛዛት በሙሉ ብትታዘዝ”
ዘወትር በመንገዶቹ እንድትሄድ
እግዚአብሔር፣ አንድ ሰው እንዲኖረውና እንዲያደርገው የሚፈልግበት አግባብ እንደ እግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና ተቆጥሮ ተነግሯል። እግዚአብሔርን የሚታዘዝ ሰው በእግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና እንደ ሄደ ተቆጥሮ ተነግሮለታል። ኢ.ት: “ዘወትር እንድትታዘዘው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከዚያም ሦስት ተጨማሪ ከተሞችን ለራስህ ትጨምራለህ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “ከዚያም አንድ ሰው በድንገት ሌላውን ሰው ከገደለ እንዲያመልጥበት ተጨማሪ ሦስት ከተሞችን ትመርጣለህ” (ቁጥሮች እና Assumed Knowl- edge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
ከእነዚህ ከሦስቱ በተጨማሪ
“አስቀድሞ ካዘጋጀኻቸው ከሦስቱ ከተሞች በተጨማሪ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ንጹሕ ደም እንዳይፈስ ይህንን አድርግ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “የቤተሰቡ አባላት ንጹሕ የሆነውን ሰው እንዳይገድሉ ይህንን አድርግ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ንጹሕ ደም እንዳይፈስ
እዚህ ጋ “ደም” የሚወክለው የሰውን ሕይወት ነው። ደም ማፍሰስ ማለት ሰው መግደል ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ማንም ንጹሕ የሆነውን ሰው አይግደል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በምድሪቱ መካከል
“በምድሪቱ” ወይም “በግዛቱ”
አምላክህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ በሚሰጥህ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የሚሰጣቸው ምድር ርስት እንደሆነ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የደም በደለኛ እንዳትሆን
የእስራኤል ሕዝብ “ከደም ተበቃዩ” የሚያመልጥበትን ከተማ ባለመሥራታቸው በሚሞተው ሰው ምክንያት በደለኛ መሆናቸው የሟቹ በደል በእነርሱ ላይ እንደሚሆን ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የደም በደል
እዚህ ጋ “ደም” የሚወክለው ሕይወትን ሲሆን “የደም በደለኛ” የሚያመለክተው አንድ ሰው ንጹሕ የሆነን ሰው ስለ መግደሉ የሚኖርበትን በደል ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በአንተ ላይ እንዳይሆን
ይህ ማለት አንድ የቤተሰብ አባል ንጽሕ የሆነን ሰው ቢገድል፣ ከዚያም ይህ እንዲሆን ዝም በማለታቸው የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ በደለኛ ይሆናሉ።
Deuteronomy 19:11
ባልንጀራውን
እዚህ ጋ “ባልንጀራ” ማለት በአጠቃላይ ማንኛውም ሰው ማለት ነው።
አድፍጦ ቢጠብቀው
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “እርሱን ለመግደል ተደብቆ ይጠብቀዋል” ወይም “ሊገድለው ያቅዳል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
በእርሱ ላይ ይነሣል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ያጠቃዋል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እስኪሞት ድረስ ክፉኛ ቢያቆስለው
“እስኪሞት ድረስ ቢጎዳው” ወይም “ቢገድለው”
ልከው ከዚያ መልሰው ያምጡት
“እንዲያመጡት ሰው ይላኩ፣ እርሱንም ከተከለለበት ከተማ መልሰው ያምጡት”
አሳልፈው ይስጡት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “አሳልፈው ይስጡት” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ኃላፊነት ባለበት ዘመዱ እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው የአንድን ሰው ሥልጣን ነው። ኢ.ት፡ “ኃላፊነት ላለበት ዘመዱ ሥልጣን” ወይም “ኃላፊነት ላለበት ዘመዱ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ኃላፊነት ያለበት ዘመድ
ይህ የተገደለው ሰው ዘመድ ነው። ይህ ዘመድ ገዳዩን ለመቅጣት ኃላፊ ነው።
እንዲሞት
“ገዳዩ እንዲሞት” ወይም “ኃላፊነት ያለበት ዘመድ ገዳዩን እንዲገድለው”
ዐይንህ አይራራለት
እዚህ ጋ “ዐይንህ” የሚወክለው ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “ምሕረት አታድርግለት” ወይም “አትዘንለት” (See: Synecdoche)
የደምን በደል ከእስራኤል አስወግድ
እዚህ ጋ “የደም በደል” የሚወክለው ንጹሕ የሆነውን ሰው የመግደልን በደል ነው። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ በንጹሕ ሰው ሞት ምክንያት በደለኛ እንዳይሆን ነፍሰ ገዳዩን ግደለው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከእስራኤል
እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 19:14
የባልንጀራህን የድንበር ምልክት አታንሣ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “በመሬቱ ድንበር ላይ ያለውን ምልክት በማንሣት ከባልንጀራህ መሬት አትውሰድበት” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ያስቀመጡትን
“የቀደሙት አባቶችህ ያስቀመጡትን”
ከብዙ ዓመታት በፊት
ሙሴ ይህንን የሚለው ሕዝቡ ለረጅም ዓመታት በምድሪቱ በተቀመጡ ጊዜ የቀደሙት አባቶቻቸው በመጀመሪያ ምድሪቱን በወሰዱ ጊዜ ያበጁትን ድንበር እንዳያነሡ ነው።
አምላክህ እግዚአብሔር እንድትወርሰው በሚሰጥህ ምድር፣ በምትወርሰው ርስትህ
እግዚአብሕር ለእስራኤል ሕዝብ መሬት መስጠቱ ምድሪቱን እንደወረሱ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር እንድትወርሰው በሚሰጥህ ምድር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 19:15
አንድ ብቸኛ ምስክር
“ አንድ ምስክር” ወይም “አንድ ምስክር ብቻ”
በሰው ላይ እንዳይነሣ
እዚህ ጋ “መነሣት” ማለት በፍርድ ቤት መቆምና አንድን ሰው በመቃወም ለዳኛው መናገር ማለት ነው። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ስላደረገው ክፉ ነገር ለዳኞች እንዳይናገር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ኃጢአት በሚሠራበት በየትኛውም ጉዳይ
አንድ ሰው በየትኛውም ጊዜ ክፉ ነገር ሲያደርግ”
በሁለት ምስክሮች አፍ ወይም በሦስት ምስክሮች አፍ
እዚህ ጋ “አፍ” የሚወክለው ምስክሮች የሚናገሩትን ነው። ቢያንስ ሁለት ወይም ሦስት ምስክሮች መኖር እንዳለባቸው ያመለክታል። ኢ.ት፡ “በሁለት ወይም በሦስት ሰዎች ምስክርነት” ወይም “ቢያንስ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ተፈጽሟል ያሉትን መሠረት በማድረግ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
የትኛውም ጉዳይ መረጋገጥ አለበት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰውየው በደለኛ መሆኑን ታረጋግጣለህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ቢሆን
“መቼ” ወይም “ከሆነ”
ሐሰተኛ ምስክር
“አንድን ሰው ለመጉዳት የሚሞክር ምስክር”
በማንም ላይ ክፉ ስለማድረጉ ሊመሰክርበት የሚነሣ
እዚህ ጋ “መነሣት” ማለት ፍርድ ቤት ውስጥ መቆምና አንድን ሰው በመቃወም ለዳኛው መናገር ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ሰውየውን ችግር ላይ ለመጣል ኃጢአት ሠርቷል ብሎ ለዳኛው የሚናገር” ወይም “ዳኛው እንዲቀጣው አንድን ሰው ኃጢአት ሠርቷል ብሎ ለዳኛው የሚናገር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 19:17
ክርክር በመካከላቸው ያለ
“እርስ በእርስ ያልተስማሙ”
በእግዚአብሔር ፊት ይቁሙ፣ በካህናቱና በዳኞቹ ፊት
ይህ ማለት ሁለቱ ሰዎች የእግዚአብሔር ሀልዎት ወደሚያድርበት ቅዱስ ስፍራ መሄድ አለባቸው ማለት ነው። ስለ እግዚአብሔር ሕጋዊ ውሳኔዎችን የመስጠት ሥልጣን ያላቸው ካህናትና ዳኞች በተቀደሰው ስፍራ አሉ። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
በእግዚአብሔር ፊት ይቁሙ፣ በካህናቱና በዳኞቹ ፊት
“ፊት ይቁሙ” የሚለው ሐረግ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህ ማለት ሥልጣን ወዳለው አካል መሄድና እርሱ ስለ ጉዳዩ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ ማድረግ ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ዳኞቹ በጥንቃቄ ይመርምሩ
“ዳኞቹ የሆነውን ነገር ለማወቅ ጠንክረው መሥራት አለባቸው”
ከዚያም በወንድሙ ላይ ለማድረግ የተመኘውን በእርሱ ላይ ታደርግበታለህ
“ከዚያም ሐሰተኛውን ምስክር ሌላውን ሰው እንድትቀጣ በፈለገበት መንገድ ትቀጣዋለህ”
ክፉን ከመካከልህ ታስወግዳለህ
ስማዊ ቅጽል የሆነው “ክፉን” እንደ ቅጽል ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ክፉውን ልምምድ ከመካከልህ ታርቃለህ” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 19:20
ከዚያም የቀሩት
“ሐሰተኛውን ምስክር በምትቀጣበት ጊዜ የቀረው ሕዝብ”
ሰምተው ይፈራሉ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “ስለ ቅጣቱ ይሰሙና እነርሱም እንዳይቀጡ ይፈራሉ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
እንዲህ ያለውን ክፉ ከእንግዲህ አይፈጽሙም
“እንደዚህ ያለውን ክፉ ነገር ደግመው አያደርጉም”
ዐይኖችህ አይራሩለት
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚያመለክቱት ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “አትራራለት” ወይም “ምሕረት አታድርግለት” (See: Synecdoche)
ሕይወት ስለ ሕይወት ይከፈል -- እግር ስለ እግር
እዚህ ጋ ትርጉሙ ግልጽ ስለሆነ ሐረጎቹ አጥረዋል። ይኸውም አንድ ሰው ሌላውን

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 20
Deuteronomy 20:1
ለጦርነት በጠላቶችህ ላይ በምትወጣበት ጊዜ
“ከጠላቶችህ ጋር ለመዋጋት ወደ ጦርነት በምትወጣበት ጊዜ”
ፈረሶችን፣ ሠረገላዎችን ስታይ
ሰዎች ብዙ ፈረሶችና ሠረገላዎች ያሉትን ሰራዊት በጣም ጠንካራ እንደሆነ ይቆጥሩ ነበር። የዚህ መግለዓ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ከግብፅ ምድር ያወጣህ
እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ወደ ከነዓን አምጥቷቸዋል። ከግብፅ ወደ ከነዓን የሚደረገውን ጉዞ ለማመልከት “ወደ ላይ” የሚለውን ቃል የተለመደ ነበር። ኢ.ት: “ከግብፅ ምድር መርቶ ያወጣችሁ እግዚአብሔር”
Deuteronomy 20:2
ለሕዝቡ ተናገር
“ለእስራኤል ወታደሮች ተናገር”
ልባችሁ አይሸበር። አትፍሩ ወይም አትደንግጡ። አትፍሯቸው
እነዚህ አራቱም አገላለጾች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ እንዳይፈሩ ጠንከር ያለ አጽንዖት ይሰጣሉ። የአንተ ቋንቋ ይህንን አሳብ የሚገልጹ አራት መንገዶች ከሌሉት ከአራት በሚያንሱ ቃላት መጠቀም ትችላለህ። (See: Parallelism)
ልባችሁ አይሸበር
እዚህ ጋ “ልባችሁ” የሕዝቡን የሕዝቡን ድፍረት ይወክላል። የልብ መሸበር የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን “አትፍሩ” ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ከጠላቶቻችሁ ጋር ለመዋጋት ከእናንተ ጋር የሚሄደው አምላካችሁ እግዚአብሔር ነው
እግዚአብሔር የእስራኤልን ጠላቶች ድል ማድረጉ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ሆኖ እንደሚዋጋ ጦረኛ ተደርጎ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሊያድናችሁ
“ድል ሊሰጣችሁ”
Deuteronomy 20:5
አለቆቹ ይናገሩ
ከአለቆቹ ሥራ አንዱ ከሰራዊቱ ማን መሰናበት እንዳለበት መወሰን ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
-- ማን አለ? ወደ ቤት ተመልሶ ይሂድ
“አዲስ ቤት ሠርቶ ያላስመረቀ ወታደር በዚህ ካለ ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ”
በጦርነት ላይ እንዳይሞትና ሌላ ሰው እንዳያስመርቀው
አለቃው አንድን ወታደር ሊያጋጥመው የሚችለውን ሁኔታ ይዘረዝራል። ኢ.ት: “እርሱ በጦርነት ላይ ቢሞት በእርሱ ፈንታ ሌላ ሰው ቤቱን እንዳያስመርቅ” (See: Hypothetical Situations)
Deuteronomy 20:6
- የተከለ አለ? ወደ ቤቱ ይሂድ
“እዚህ አዲስ ወይን ተክሎ ፍሬውን ያልሰበሰበ ወታደር ካለ ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ”
በጦርነት ላይ እንዳይሞትና ሌላ ሰው በፍሬው እንዳይደሰት
አለቃው አንድን ወታደር ሊያጋጥመው የሚችለውን ሁኔታ ይዘረዝራል። ኢ.ት: “እርሱ በጦርነት ላይ ቢሞት በእርሱ ፈንታ ሌላ ሰው ፍሬውን እንዳይሰበስብ” (See: Hypothetical Situations)
ሚስት ለማግባት ያጨ አለ? -- ወደ ቤቱ ይሂድ
“ሚስት ለማግባት ቃል ኪዳን ያደረገ፣ ነገር ግን ያላገባት የትኛውም ወታደር እዚህ ቢኖር ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ”
በጦርነት ላይ እንዳይሞትና ሌላ ሰው እንዳያገባት
አለቃው አንድን ወታደር ሊያጋጥመው የሚችለውን ሁኔታ ይዘረዝራል። ኢ.ት: “እርሱ በጦርነት ላይ ቢሞት በእርሱ ፈንታ ሌላ ሰው እንዳያገባት” (See: Hypothetical Situations)
Deuteronomy 20:8
የሚፈራና ልቡ የሚሸበርበት ሰው ማነው? ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ
“እዚህ ያለ የትኛውም ወታደር ቢፈራና ልቡ ቢሸበር ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ”
የሚፈራ ወይም ልቡ የሚሸበርበት
ሁለቱም ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። ኢ.ት: “በጦርነት ለመዋጋት የሚፈራ” (See: Doublet)
እንደ ራሱ ልብ የወንድሙም ልብ እንዳይቀልጥ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “እርሱ እንደፈራ ሌላውም እስራኤላዊ እንዳይፈራ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የወንድሙ ልብ -- እንደ ራሱ ልብ
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው የአንድን ሰው ድፍረት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእነርሱ ላይ አዛዦችን ይሹሙ
“የእስራኤልን ሕዝብ እንዲመሩ አለቆቹ አዛዦችን መሾም አለባቸው”
Deuteronomy 20:10
አንድን ከተማ ለመውጋት በምትዘምትበት ጊዜ
እዚህ ጋ “ከተማ” ሕዝቡን ይወክላል። ኢ.ት: “የአንድን ከተማ ሕዝብ ለመውጋት በምትሄድበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለእነዚያ ሰዎች የሰላም ጥሪ አቅርብላቸው
“በከተማው ለሚኖሩ ሰዎች እጅ እንዲሰጡ ዕድል ስጣቸው”
በሮቻቸውን ከከፈቱልህ
እዚህ ጋ “በሮች” የሚያመለክቱት የከተማይቱን በሮች ነው። “በሮቻቸውን ከከፈቱልህ” የሚለው ሐረግ የሚወክለው የሚማረኩትንና እስራኤላውያን ወደ ከተማቸው እንዲገቡ የሚፈቅዱትን ሰዎች ነው። ኢ.ት: “በሰላም ወደ ከተማቸው እንድትገባ ከፈቀዱልህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 20:12
ነገር ግን ያቀረብክላትን የሰላም ጥሪ ባይቀበል
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው ሕዝቡን የሚወክለውን ከተማውን ነው። ኢ.ት: “ነገር ግን የከተማይቱ ሰዎች እጃቸውን ባይሰጡ” ወይም “ነገር ግን የከተማይቱ ሰዎች ያቀረብክላቸውን የሰላም ጥሪህን ባይቀበሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 20:14
ሕፃናቱን
“ልጆቹን”
ብዝበዛውን ሁሉ
“የሚጠቅሙትን ነገሮች በሙሉ”
ምርኮ
እነዚህ በጦርነት ድል ያደረጉ ሰዎች ከወጓቸው ሰዎች ላይ የሚወስዷቸው ጠቃሚ ነገሮች ናቸው።
ከተሞቹ ሁሉ
እዚህ ጋ “ከተሞች” የሚወክሉት ሕዝቡን ነው። ኢ.ት: “በከተሞች የሚኖሩት ሰዎች በሙሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 20:16
አምላክህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ በሚሰጥህ በእነዚህ ሰዎች ከተሞች ውስጥ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ በከነዓን የሚሰጣቸው ከተሞች እነርሱ የሕዝቡ ርስት እንደሆኑ ተቆጥረው ተነግሮላቸዋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እስትንፋስ ያለውን ምንም ነገር አታስቀር
“ሕይወት ያለበትን ሁሉ በሕይወት አታስቀር”። ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ሕይወት ያለውን ሁሉ ግደል” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)
ፈጽመህ አጥፋቸው
x
Deuteronomy 20:19
ጦርነት ዐውጅ
“በጦርነት ተዋጋ”
በመጥረቢያ ቁረጣቸው
“ዛፎቹን በመጥረቢያ ቁረጣቸው”
ልትከበው በሜዳ ላይ ያለ ዛፍ ሰው ነውን?
ይህ ሰዎቹ አስቀድመው የሚያውቁትን ለማስታወስ የቀረበ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “የፍሬ ዛፎች

ሰዎች ስላልሆኑ ጠላቶችህ አይደሉም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ለምግብነት የማይውሉ ዛፎች መሆናቸውን ስታውቅ
“የሚበላ ፍሬ የማይሰጡ ዛፎች መሆናቸውን ስታውቅ”
ከበባ ሥራባት
እነዚህ አንድን ከተማ ለመክበብ የሚያስፈልጉ መሰላሎችና ማማዎችን የመሳሰሉ መሣሪያዎችና መዋቅሮች ናቸው።
እስኪወድቅ ድረስ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “የከተማይቱ ሰዎች በጦርነቱ እስኪሸነፉ ድረስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ይወድቃል
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚወክለው የከተማይቱን ሕዝብ የሚወክለውን ከተማ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 21
Deuteronomy 21:1
አንድ ሰው ተገድሎ ቢገኝ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ማንነቱ ባልታወቀ ሰው የተገደለን ሰው ቢያገኝ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሜዳ ላይ ወድቆ
የሞተው ሰው ሜዳ ላይ ወድቋል።
ማን እንደ ገደለው ባይታወቅ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ማን እንደ ገደለው ማንም አያውቅም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ወደ ከተሞቹ ይለኩ
“ለከተሞቹ ያለውን ርቀት ይለኩ”
የተገደለውን እርሱን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ማንነቱ ያልታወቀ ሰው የገደለውን እርሱን” ወይም “ሬሳውን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 21:3
ቀንበር ያልተሸከመ
x
Deuteronomy 21:5
ወደ ፊት ይቅረቡ
“ወደ ሸለቆው ይምጡ”
አምላክህ እግዚአብሔር እርሱን እንዲያገለግሉት መርጧቸዋልና
“ካህናቱ እርሱን እንዲያገለግሉት አምላክህ እግዚአብሔር ስለመረጣቸው”
አምላካችሁ እግዚአብሔር
ሙሴ ለአንድ ሰው እንደሚናገር አድርጎ ለእስራኤል ሕዝብ ስለሚናገር “የአንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
ባርኮት እንዲሰጡ
“የእስራኤልን ሕዝብ እንዲባርኩ”
በእግዚአብሔር ስም
እዚህ ጋ “በ -- ስም” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ራሱንና የእርሱን ሥልጣን ነው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ራሱ የሚለውንና የሚያደርገውን የሚልና የሚያደርግ እርሱ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር እና ማንኛውንም ዓይነት ክርክርና ጥቃት በቃላቸው እንዲወስኑ
“አለመግባባቶችንና የጾብ ምክንያቶችን ሁሉ የሚፈቱት እግዚአብሔር እና እነርሱ ይሆናሉ”
Deuteronomy 21:6
አንገቷ የተሰበረን ጊደር
x
Deuteronomy 21:8
የዋጀኸውን
እግዚአብሔር በግብፅ ባሪያ የነበረውን የእስራኤልን ሕዝብ ማዳኑ ሕዝቡን ከባርነት ለመቤዠት ገንዘብ እንደከፈለላቸው በሚመስል መልኩ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በንጹሕ ደም ምክንያት በሕዝብህ በእስራኤል መካከል በደልን አታኑር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ንጹሕን ሰው እንደ ገደሉ በደለኞች አድርገህ አትቁጠራቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ከዚያም ስለ ፈሰሰው ደም ይቅር ይባላሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከዚያም ስለ ንጹሑ ሰው ሞት እግዚአብሔር ሕዝቡን እስራኤልን ይቅር ይላቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ንጹሕን ደም ከመካከልህ ታስወግዳለህ
“ንጹሕን ሰው ስለ መግደልህ ከእንግዲህ በደለኛ አትሆንም”
በእግዚአብሔር ዐይን ትክክል የሆነውን
x
Deuteronomy 21:10
ውጣ
“እናንተ ወታደሮች የሆንችሁ ውጡ”
ብትመኛት
“ከእርሷ ጋር ለመተኛት ብትፈልግ” ለሚለው የትህትናን ሐረግ ተጠቀም።
ሚስትህ እንድትሆን ልትወስዳት ብትፈልግ
“ለታገባት ብትፈልግ”
ጸጉሯን ትላጨው
“ጸጉሯን ከራሷ ላይ ትመለጠው”
ጥፍሮቿን ትቆረጥ
“የጣቶቿን ጥፍር ትቁረጥ”
Deuteronomy 21:13
የለበሰችውን ልብስ ታውልቀው
ይህንን የምታደርገው በዘዳግም 21:12 እንደተጠቀሰው ሰውየው ወደ ቤቱ ካመጣትና ጸጉሯን ተቆርጣ፣ የእጅና የእግር ጣት ጥፍሮቿን ከተቆረጠች በኋላ ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “የሕዝቧን ልብስ ታወልቅና የእስራኤላውያንን ልብስ ትለብሳለች” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ተማርካ በተወሰደች ጊዜ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እርሷን በማረክህ ጊዜ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
አንድ ሙሉ ወር
“ወሩን በሙሉ” ወይም “አንድ ወር ሙሉ”
ነገር ግን ባትደሰትባት
ሰውየው ከሴቲቱ ጋር ስለ መተኛቱ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። ኢኢ.ት፡ “ነገር ግን አብረሃት ከተኛህ በኋላ ሚስትህ እንዳትሆን ከወሰንክ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ወደፈለገችበት ትሂድ
“መሄድ ወደምትፈልግበት ትሂድ”
አዋርደሃታልና
“ከእርሷ ጋር ከተኛህ በኋላ ስለ ሰደድካት አሳፍረሃታልና”
Deuteronomy 21:15
አንዷ የተወደደችና ሌላይቱ የተጠላች
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “ሰውየው ከሚስቶቹ አንደኛዋን ይወዳል፣ ሌላይቱን ሚስቱን ይተላታል” ወይም 2) “ሰውየው ሌላይቱን ሚስቱን ከሚወድበት በበለጠ አንደኛውን ሚስቱን ይወዳታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሁለቱም ልጆችን ቢወልዱለት
“ሁለቱም ሚስቶቹ ልጆችን ወልደውለታል”
በኩሩ ከተጠላችው ከሆነ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በኩሩ ሰውየው ከሚጠላት ሚስቱ የተወለደ ከሆነ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ከዚያም ሰውየው በ-- ቀን
“ሰውየው በ-- ጊዜ”
ሰውየው ያለውን ልጆቹ እንዲወርሱ ያደርጋል
“ሰውየው ንብረቱን ለልጆቹ ርስት አድርጎ ይሰጣቸዋል”
ከተወደደች ሚስቱ የተወለደውን ልጅ ከተጠላችው ሚስቱ በተወለደው ልጅ ፊት በኩር አያድርገው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ከተጠላችው ሚስቱ በተወለደው ልጅ ምትክ ከተወዳጅ ሚስቱ የተወለደውን ልጅ በኩር አያድርገው”
ዕጥፍ ድርሻ
“ሁለት ዕጥፍ”
ያ ልጅ የጉብዝናው ጅምሬ ነው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ያ ልጅ ሰውየው የወንዶች ልጆች አባት መሆኑን የሚያሳይ ነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 21:18
የአባቱን ቃል ወይም የእናቱን ቃል የማይታዘዝ
እዚህ ጋ “ድምፅ” አንድ ሰው የሚናገረውን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “አባቱ ወይም እናቱ የሚሉትን የማይታዘዝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ያርሙት
“ስለ መጥፎ ተግባሩ ይቅጡት” ወይም “ያሰልጥኑትና ያስተምሩት”
ይዘው ያምጡት
“እንዲመጣ ያስገድዱት”
Deuteronomy 21:20
ይህ የእኛ ልጅ
“ልጃችን”
ድምፃችንን አይታዘዝም
እዚህ ጋ “ድምፅ” አንድ ሰው የሚናገረውን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ወይም የሙሉው ሰው ተምሳሌት ነው። ኢ.ት፡ “እንዲያደርግ የምንነግረውን አያደርግም” ወይም “አይታዘዘንም” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)
ሆዳም
ብዙ የሚበላና የሚጠጣ ሰው
ሰካራም
አስካሪ መጠጥ አብዝቶ የሚጠጣና ብዙ ጊዜ የሚሰክር ሰው
እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ውገሩት
“እስኪሞት ድረስ ድንጋይ ወርውሩበት”
ክፉን ከመካከልህ ታርቃለህ
ቅጽሉ “ክፉ” ስማዊ ሐረግ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ይህንን ክፉ ነገር የሚያደርገውን ሰው ከእስራኤላውያን መካከል ታርቃለህ” ወይም “ይህንን ክፉ ሰው ግደለው” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
እስራኤል ሁሉ
“እስራኤል” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ስለ እርሱ ሰምተው ይፈራሉ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “በልጁ ላይ ስለሆነው ነገር ይሰማሉ፣ እነርሱንም ሕዝቡ እንዳይቀጣቸው ይፈራሉ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 21:22
አንድ ሰው ሞት የሚገባውን ኃጢአት ሠርቶ ከሆነ
“አንድ ሰው በሞት ልትቀጣው እስከሚያስፈልግህ ድረስ እጅግ የከፋ ነገር ካደረገ”
ይገደል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አስወግደው” ወይም “ግደለው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በዛፍ ላይ ስቀለው
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “ከሞተ በኋላ ዛፍ ላይ ስቀለው” ወይም 2) “ግደለውና በቋሚ እንጨት ላይ ስቀለው”
በዚያው ቀን ቅበረው
“በምታስወግደው ጊዜ በዚያው ቀን ቅበረው”
የተሰቀለ ሁሉ በእግዚአብሔር የተረገመ ነው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “ሰዎች የሚሰቅሉትን ሁሉ እግዚአብሔር ይረግማቸዋል” እና 2) “ሰዎች እግዚአብሔር የረገማቸውን በዛፍ ላይ ይሰቅሏቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ምድሪቱን አታርክስ
እግዚአብሔር የረገመውን በዛፍ ላይ ሰቅለህ በመተው

---

Chapter 22
Deuteronomy 22:1
ሲጠፋ
“ከባለቤቱ ርቆ ሲሄድ”
ራስህን ከእነርሱ አትደብቅ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “እንዳላየኻቸው አትሁን” ወይም “ምንም ነገር ሳታደርግ አትሂድ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እስራኤላዊ ወንድምህ በአቅራቢያህ ባይኖር
“እስራኤላዊ ወንድምህ ከአንተ ርቆ የሚኖር ከሆነ”
ወይም የማታውቀው ከሆነ
“ወይም የእንስሳው ባለቤት ማን እንደሆነ ካላወቅህ”
እርሱ እስኪፈልገው ድረስ በአንተ ዘንድ ይቆይ
“ባለቤቱ ፈልጎት እስኪመጣ ድረስ እንስሳው በአንተ ዘንድ ይቆይ”
Deuteronomy 22:3
በአህያውም ላይ እንደዚሁ አድርግ
“አህያውንም በተመሳሳይ መንገድ መልስለት”
በልብሱም ላይ እንደዚሁ አድርግ
“በተመሳሳይ መንገድ ልብሱን መልስለት”
Deuteronomy 22:5
ለወንድ የሚገባውን
“የወንድ ልብስ”
Deuteronomy 22:6
የወፍ ጎጆ
ወፎች ከጭራሮ፣ ሣር፣ እጽዋትና ጭቃ ለራሳቸው የሚሠሩት ቤት
ከጫጩቶቿ ወይም በውስጧ ካሉ ዕንቁላሎች ጋር
“ከትናንሽ ወፎች ወይም በጎጆው ውስጥ ካሉ ዕንቁላሎች ጋር”
በትናንሾቹ ላይ የተቀመጠች እናት
“እናቲቱ ወፍ በጫጩት ወፎች ላይ ተቀምጣለት”
ቀኖችህ እንዲረዝሙ
ረጅም ቀናት የረጅም ዕድሜ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ረጅም ዓመት መኖር እንድትችል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 22:9
ምርትህ በሙሉ በተቀደሰው ስፍራ እንዳይወረስ
“ቅዱስ ስፍራ” የሚለው ቃል በተቀደው ስፍራ የሚሠሩትን ካህናት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በእግዚአብሔር ቅዱስ ስፍራ ያሉ ካህናት ምርቱን ሁሉ እንዳይወስዱት” ወይም “ምርቱን ሁሉ እንዳታርክሰውና ካህናቱ ከመጠቀም እንዳይከለክሉህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በወይን ተክል ቦታ የሚበቅለውን
“በወይን ተክል ቦታ የሚበቅለውን ፍሬ”
ሱፍ
በበጎች ላይ የሚበቅል ለስላሳና የሚጠቀለል ጸጉር
በፍታ
ከቃጫ ተክል የሚሠራ ክር (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 22:12
ጥለት
በአንድ ላይ ታስረው በእያንዳንዱ የካባው ማዕዘን ላይ የሚንጠለጠሉ ክሮች
ካባ
አንድ ሰው በሌሎች ልብሶቹ ላይ ደርቦ የሚለብሰው ረዘም ያለ ልብስ
Deuteronomy 22:13
ከዚያም አሳፋሪ ስለሆነ ነገር ቢከሳት
“ከዚያም ከጋብቻዋ በፊት ከሌላ ሰው ጋር ስለመተኛቷ ቢከሳት”
ምስክርነቷን ያበላሻል
የነገር ስም የሆነው “ምስክርነት” እንደ ግሥ ሐረግ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ሰዎች መጥፎ ሰው እንደሆነች እንዲያስቡ ያደርጋል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:15

የድንግልናዋን ማረጋገጫ ይውሰዱ

የነገር ስም የሆኑት “ማረጋገጥ” እና “ድንግልና” እንደ ግሣዊ ሐረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “ቀደም ሲል የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳልነበራት የሚያረጋግጥ አንዳች ነገር ውሰድ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:16

ስለ አሳፋሪ ነገር ከሷታል

የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “ሳያገባት በፊት ከሌላ ሰው ጋር ስለመተኛቷ ከሷታል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ከልጅህ የድንግልና ማረጋገጫ አላገኘሁኝም

የነገር ስም የሆኑት “ማረጋገጥ” እና “ድንግልና” እንደ ግሣዊ ሐረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “ልጅህ ቀደም ሲል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ላለመፈጸሟ ማረጋገጫ ማቅረብ አልቻለችም” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ነገር ግን የልጄ ድንግልና ማስረጃው ይኸው

የነገር ስም የሆኑት “ማረጋገጥ” እና “ድንግልና” እንደ ግሣዊ ሐረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “ይሁን እንጂ ልጄ ቀደም ሲል የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳልፈጸመች ይህ ያረጋግጣል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም በከተማይቱ ሽማግሌዎች ፊት ጨርቁን ይዘረጉታል

የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “ከዚያም ድንግል እንደነበረች ማስረጃ እንዲሆን እናትና አባቷ በደም የተነከረውን ጨርቅ ለሽማግሌዎቹ ያሳያሉ።(See: Assumed Knowledge and Implicit Information

Deuteronomy 22:18

ይቅጡት

“ቅጣት እንዲከፍል ያድርጉት”

አንድ መቶ ሰቅል

“100 ሰቅል” (ገንዘብ በመጽሐፍ ቅዱስ እና ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ለልጅቱ አባት ይስጡት

“ገንዘቡን ለልጅቱ አባት ስጡት”

የእስራኤል ድንግል ምስክርነቷ እንዲበላሽ አድርጓል

የነገር ስም የሆነው “ምስክርነት” እንደ ግሣዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች የእስራኤልን ድንግል መጥፎ ሰው አድርገው እንዲያስቧት አድርጓል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እንዳይሰዳት

“እንዲፈታት በፍጹም አትፍቀድለት”

በቀኖቹ ሁሉ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ሕይወቱን ሙሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:20

ሆኖም ይህ ነገር እውነት ቢሆን

“ሆኖም እውነት ቢሆን” ወይም “ሆኖም ሰውየው የተናገረው እውነት ቢሆን”

በልጅቱ ላይ የድንግልና ማስረጃ ባይገኝ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰውየው ልጅቱ ድንግል ስለመሆኗ ማረጋገጫ አላገኘም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የድንግልና ማረጋገጫ

የነገር ስም የሆኑት “ማረጋገጫ” እና “ድንግልና” እንደ ግሣዊ ሐረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “ልጅቱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽማ እንደማታውቅ የሚያስረዳ አንዳች ነገር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም ልጅቱን ያውጧት

“ከዚያም ሽማግሌዎቹ ልጅቱን ያውጧት”

በድንጋይ ወግረው ይግደሏት

“እስክትሞት ደረስ ድንጋይ ወርውሩባት”

በእስራኤል ውስጥ አሳፋሪ ተግባር ፈጽማለችና

“በእስራኤል ውስጥ አሳፋሪ ነገር አድርጋለችና”

በአባቷ ቤት ውስጥ እንደ ሴተኛ አዳሪ ለማድረግ

“በአባቷ ቤት ውስጥ እየኖረች እንደ ሴተኛ አዳሪ ማድረግ”

ክፉን አስወግድ

ቅጽል የሆነው “ክፉ” እንደ ስማዊ ሐረግ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ይህንን ክፉ ነገር ያደረገውን ከእስራኤላውያን መካከል አስወግድ” ወይም “ይህንን ክፉ ሰው አስወግደው” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:22

አንድ ሰው --- ቢገኝ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ሌላውን ሰው ቢያገኝ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ታስወግዳለህ

“በዚህ መንገድ ታስወግዳለህ”

Deuteronomy 22:23

ለአንድ ሰው የታጨች

“አንድን ሰው እንድታገባ ቃል የተገባላት”

ውሰዱ -- እና ወግሩ

እነዚህ ትዕዛዛት ለእስራኤል እንደ ቡድን የተነገሩ ናቸው፣ በመሆኑም ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

ሁለቱንም ውሰዷቸው

“ከዚያም ልጅቱንና ከእርሷ ጋር የተኛውን ሰው አምጧቸው”

ምክንያቱም አልጮኸችም

“ምክንያቱም ለእርዳታ አልተጣራችም”

የባልንጀራውን ሚስት አርክሷልና

በዚያን ዘመን እስራኤላውያን ለጋብቻ የተጫጩ ወንድና ሴትን እንደ ባልና ሚስት ይቆጥሯቸው ነበር። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “ምክንያቱም የእስራኤላዊ ወንድሙ ከምትሆን ልጅ ጋር ተኝቷል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ክፉን ከመካከልህ አስወግድ

ቅጽሉ “ክፉ” እንደ ስማዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ይህንን ክፉ ነገር ያደረገውን ሰው ከእስራኤላውያን መካከል አስወግደው” ወይም “ይህንን ክፉ ሰው አስወግደው” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:25

የታጨችውን ልጅ

ይህ ማለት ወላጆቿ አንድን ሰው እንድታገባ የተስማሙባት፣ ሆኖም ገና ያላገባችው ልጅ ማለት ነው።

ከዚያም ከእርሷ ጋር የተኛው ሰው ብቻ ይገደል

“ከዚያም ከእርሷ ጋር የተኛውን ሰው ብቻ ግደሉ”

ልጅቱ ጋ ለሞት የሚያበቃት ኃጢአት የለም

“ስላደረገችው ነገር በሞት አትቅጧት”

ይህ ጉዳይ ባልንጀራውን ከሚያጠቃና ከሚገድለው ሰው ጋር ተመሳሳይ ነውና

“ምክንያቱም ይህ ሁኔታ አንድ ሰው ሌላውን ሰው አጥቅቶ ከሚገድልበት ሁኔታ ጋር ስለሚመሳሰል ነው”

ከሰፈር ውጪ አግኝቷታልና

“ምክንያቱም ሰውየው ልጅቱን ከሰፈር ውጪ ሥራ ላይ ሆና አግኝቷታል”

Deuteronomy 22:28

ሆኖም ያልታጨች

“ሆኖም ወላጆቿ ለሚያገባት ሰው እንደሚድሩለት ቃል ያልገቡለት”

ቢገኙ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ስለሆነው ነገር ቢያውቅ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሃምሳ ሰቅል ጥሬ ብር

አንድ ሰቅል አሥራ አንድ ግራም ይመዝናል። ኢ.ት፡ “አምሳ የጥሬ ብር ዝርዝር” ወይም “550 ግራም ጥሬ ብር” (See: Biblical Money and Numbers)

በቀኖቹ ሁሉ አይስደዳት

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ዕድሜውን ሙሉ አይፍታት” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 22:30

የአባቱን ሚስት ለራሱ ሚስት አድርጎ አይውሰድ

የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “ምንም እንኳን እናቱ ባትሆንም የቀድሞ የአባቱን ሚስት ማግባት የለበትም” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 23
Deuteronomy 23:1
ተቀጥቅጦ የቆሰለ ወይም የተቆረጠ ሰው
“የወንድ አካሉ የተቀጠቀጠ ወይም የተቆረጠበት ሰው”
ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ መግባት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ማኅበረሰብ ሙሉ አባል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ዲቃላ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ወላጆቹ ዘመዳሞች ሆነው ወይም በዝሙት የወለዱት ልጅ ወይም 2) ከሴተኛ አዳሪ የተወለደ ልጅ።
ተወላጆቹ እስከ አሥረኛ ትውልድ ደረስ
ይህ “አሥረኛ” የአሥር ደረጃን አመልካች ቁጥር ነው። ኢ.ት፡ “ከዲቃላው ልጅ ተወላጆች አሥረኛ ትውልድ በኋላ እንኳን” (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)
ማናቸውም
“ከእነዚህ ተወላጆች ማናቸውም”
Deuteronomy 23:3
ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ አይግቡ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ማኅበረሰብ ሙሉ አባል አይሁኑ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ተወላጆቹ እስከ አሥረኛ ትውልድ ደረስ
ይህ “አሥረኛ” የአሥር ደረጃን አመልካች ቁጥር ነው። ኢ.ት፡ “ከተወላጆቹ ከአሥር ትውልድ በኋላ እንኳን” (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)
በእንጀራና በውሃ አልተቀበሏችሁም
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “ምግብና መጠጥ በማቅረብ አልተቀበሏችሁም” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
በአንተ ላይ -- እንዲረግማችሁ
ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚለው ቃል እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
Deuteronomy 23:5
አልሰማም
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ትኩረት አልሰጠውም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እርግማኑን ወደ በረከት ለወጠልህ
“እንዲረግምህ ሳይሆን እንዲባርክህ አደረገው”
ሰላማቸውን ወይም ብልጽግናቸውን በፍጹም አትፈልግ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ከአሞናውያንና ከሞዓባውያን ጋር የሰላም ስምምነት ከቶ ማድረግ የለብህም” ወይም 2) “ለእነዚያ 2 የሕዝብ ወገኖች መልካም እንዲሆንላቸውና ለመበልጸግ የሚያስችላቸውን ምንም ነገር አታድርግ”
በቀኖችህ ሁሉ
x
Deuteronomy 23:7
ኤዶማዊውን አትጸየፈው
“ኤዶማዊውን አትጥላው”
ወንድምህ ነውና
“ዘመድህ ነውና”
ግብፃዊውን አትጸየፈው
“ግብፃዊውን አትጥላው”
የሚወለዱላቸው የተወላጆቻቸው ሦስተኛ ትውልድ ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ እንዲገቡ
ይህ “ሦስተኛ” የሦስት ደረጃን አመልካች ቁጥር ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ኤዶማዊ ወይም ግብፃዊ በእስራኤላውያን ማኅበረሰብ ውስጥ ለመኖር ቢመጣ፣ የልጅ ልጆቹ የዚያ ማኅበረሰብ ሙሉ አባል ሊሆኑ ይችላሉ” (See: (ደረጃን አመልካች ቁጥር እና Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት))
Deuteronomy 23:9
እንደ ሰራዊት በጠላቶችህ ላይ በምትወጣበት ጊዜ፣ ያን ጊዜ ራስህን ጠብቅ
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)
በጠላቶችህ ላይ
“ጠላቶችህን ለመውጋት”
ከክፉ ነገር ሁሉ ራስህን ጠብቅ
“መጥፎ ከሆኑ ነገሮች ሁሉ ራስህን አርቅ”
ሌሊት በሆነበት ነገር ምክንያት ንጹሕ ያልሆነ ማንኛውም ሰው
ይህ ዘር ማፍሰሱ የተነገረበት የትህትና አባባል ነው። ኢ.ት፡ “በእንቅልፍ ላይ እያለ ዘር ስለፈሰሰው ንጹሕ ያልሆነ ማንኛውም ሰው” (See: Euphemism)
Deuteronomy 23:12
የምትቆፍርበት መሣሪያ ይኑርህ
“ለመቆፈር የምትጠቀምበት መሣሪያ ይኑርህ”
Deuteronomy 23:15
ከጌታው ያመለጠ ባሪያ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “ከሌላ ሀገር ከጌታው አምልጦ ወደ እስራኤል የመጣ ባሪያ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ከአንተ ጋር ይኑር
“ባሪያው በሕዝብህ መካከል ይኑር”
Deuteronomy 23:17
የቤተ ጣዖት አመንዝራ -- የቤተ ጣዖት አመንዝራ -- ዝሙት አዳሪ -- ውሻ
እግዚአብሔር በማንኛውም ሰው በየትኛውም ምክንያት በወንድና በሴት የሚደረጉ የአመንዝራነት ዓይነቶችን የሚከለክል ዝርዝር ይሰጣቸዋል። (See: Merism)
በሴቶች ልጆች መካከል -- በወንዶች ልጆች መካከል -- የቤተ ጣዖት አመንዝራ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፤ ሙሴ፣ 1) ሴቶችና ወንዶች ወሲባዊ ተግባርን የመቅደስ አገልግሎት አካል እንዳያደርጉ ይከለክላቸዋል ወይም 2) ሴቶችና ወንዶች ገንዘብ ለማግኘት ወሲባዊ ተግባር እንዳይፈጽሙ ለመከልከል ሻል ባለ ቃል ይጠቀማል። (See: Euphemism)
የዝሙት አዳሪን ዋጋ ወደ -- ቤት አታምጣ
“በዝሙት ሥራ ገንዘብ የምታገኝ ሴት ያንን ገንዘብ ወደ -- ቤት አታምጣ”
ውሻ
ገንዘብ ለማግኘት ከእርሱ ጋር ወንዶች ወሲብ እንዲፈጽሙ የሚፈቅድ ወንድ
ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ቤት
“ወደ መቅደስ”
ለየትኛውም ስእለት
“ስእለት ለመፈጸም”
እነዚህን በሙሉ
የሴትና የወንድ ዝሙት አዳሪዎችን ዋጋ
Deuteronomy 23:19
ለእስራኤላዊ ወንድምህ በወለድ አታበድረው
“ለእስራኤላዊ ወንድምህ አንዳች ነገር ብታበድረው ካበደርከው በላይ እንዲመልስልህ አታድርገው”
በወለድ ማበደር
ለአንድ ሰው ማበደርና ያ ሰው ከተበደረው በላይ እንዲመልስ ማስገደድ
የገንዘብ ወለድ -- የትኛውም በወለድ የተሰጠ
“ለአንድ ሰው ገንዘብ፣ ምግብ ወይም የትኛውንም ነገር በምታበድርበት ጊዜ ወለድ አታስከፍለው”
እጅህን በምታሳርፍበት ሁሉ ላይ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “በምትሠራሁ ሁሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 23:21
ለመፈጸም አትዘግይ
“ስእለትህን ለመፈጸም ረጅም ጊዜ አትውሰድ”
አምላክህ እግዚአብሔር በእርግጥ ከአንተ ይፈልገዋልና
“ምክንያቱም ስእለትህን ካልፈጸምክ አምላክህ እግዚአብሔር ይነቅፍሃል፣ ይቀጣሃልም”
ሳትሳል ብትቀር ግን ኃጢአት አይሆንብህም
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “ካልተሳልክ ግን የምትፈጽመው ስእለት የለህምና ኃጢአት አትሠራም” (See: Assumed

Knowledge and Implicit Information)
ከከንፈርህ የወጣውን
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “የተናገርከው ቃል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ለአምላክህ ለእግዚአብሔር እንደተሳልከው
“ታደርገው ዘንድ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር የተሳልከውን ማንኛውንም ነገር”
በአንደበትህ ፈቅደህ ቃል የገባህበትን የትኛውንም ነገር
“ልታደርገው ስለፈለግህ ቃል ስትገባ ሰዎችህ የሰሙህን ነገር ሁሉ”
በአንደበትህ
“ስትናገር ሰዎች የሰሙህን”
Deuteronomy 23:24
የምትፈልገውን ያህል ወይን መብላት ትችላለህ
“ከዚያም እስክትጠግብ ድረስ ወይን በመብላት መደሰት ትችላለህ”
ሆኖም በቅርጫትህ ውስጥ ምንም እንዳትጨምር
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “ሆኖም ይዘህ ለመሄድ በከረጢትህ ውስጥ ምንም ወይን አትጨምር” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ወደ ባልንጀራህ የደረሰ ሰብል በምትገባበት ጊዜ
“ሰብሉ ባፈራበት የባልንጀራህ እርሻ መካከል በምታልፍበት ጊዜ”
እሸት መቅጠፍ ትችላለህ
“ከዚያም ከሰብሉ ፍሬ በእጅህ ወስደህ መብላት ትችላለህ”
ነገር ግን በደረሰው የባልንጀራህ ሰብል ላይ ማጭድ አታሳርፍበት
“ነገር ግን የባልንጀራህን የደረሰ ሰብል አጭደህ አትውሰድ”
ማጭድ
ገበሬዎች ስንዴ ለመሰብሰብ የሚጠቀሙበት ስለታም መሣሪያ

---

Chapter 24
Deuteronomy 24:1
አንድ ሰው ሚስት ወስዶ በሚያገባበት ጊዜ
“ሚስት ወስዶ” እና “በሚያገባት” የሚሉት ሐረጎች ትርጉማቸው አንድ ነው። ኢ.ት፡ “አንድ ወንድ አንዲትን ሴት በሚያገባበት ጊዜ” (See: Doublet)
በዐይኖቹ ሞገስን ባታገኝ
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚወክሉት ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “እንደማይወዳት ከወሰነ” (See: Synecdoche)
አንዳች የሚመቸውን ነገር ስላላገኘባት
“በሆነ ምክንያት ከእርሱ ጋር ሊያቆያት ያለመፈለግ ውሳኔ አድርጓል”
የፍቺ ወረቀት ጽፎ ይስጣት
“ከዚህ በኋላ በጋብቻ ውስጥ እንደሌሉ የሚገልጽ ሕጋዊ ወረቀት ለሚስቱ ይስጣት”
ሄዳ የሌላ ሰው ሚስት እንድትሆን
“ሄዳ ሌላ ሰው እንድታገባ”
Deuteronomy 24:3
ሁለተኛው ባሏ ቢጠላት
“ሁለተኛው ባሏ እንደሚጠላት ቢወስን”
የፍቺ ወረቀት
ይህ ሰውየውና ሴቲቱ ከእንግዲህ በጋብቻ ውስጥ እንዳልሆኑ የሚናገር ሕጋዊ ወረቀት ነው። ይህንን በዘዳግም 24፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በእጇ ያኑረው
“ለሴቲቱ ይስጣት”
ሚስት አድርጎ የወሰዳት ሰው
“ሴቲቱን ያገባት ሁለተኛው ሰው”
ከረከሰች በኋላ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “በፍቺውና እንደገና ሌላ ሰው በማግባቷ ከረከሰች በኋላ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ምድሪቱ በደለኛ እንድትሆን አታድርጋት
ምድር ኃጢአት ልትሠራ እንደምትችል ተደርጋ ተነግሮላታል። ኢ.ት፡ “በምድሪቱ ዙሪያ በደል እንዳታስፋፋ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 24:5
አንድ ሰው አዲስ ሚስት በሚወስደበት ጊዜ
“አንድ ሰው በቅርቡ አንዲትን ሴት በሚያገባበት ጊዜ”
የጉልበት ሥራ ለመሥራት እንዲሄድም ቢሆን አይታዘዝ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከቤቱ እንዲርቅና የትኛውንም ዓይነት ሥራ እንዲሠራ ማንም አያስገድደው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በቤቱ ለመሆን ነጻ ይሁን
“በቤቱ ለመኖር ነጻ ይሁን”
Deuteronomy 24:6
ወፍጮ
ክብደት ባላቸው ሁለት ክብ ድንጋዮች እህል በመፍጨት ዱቄት ለመሥራት የሚያስችል መሣሪያ
መጅ
ከወፍጮ ጋር ያለ የላይኛው ክብ ድንጋይ
ያ የሰውን ሕይወት በመያዣነት እንደመውሰድ ይሆናል
“ሕይወት” የሚለው ቃል አንድ ሰው ራሱን በሕይወት ለማቆየት የሚያስፈልገው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ሰውየው ለቤተሰቡ ምግብ ለማዘጋጀት የሚጠቀምበትን መውሰዱ ነውና” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 24:7
አንድ ሰው ተጠልፎ ቢገን
ይህ የአነጋገር ዘይቤ “አንድ ሰው ቢጠለፍ” እንደማለት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ሲጠልፍ ብታገኘው” (የአነጋገር ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
መጥለፍ
አንድን ንጹሕ ሰው ኃይልን በመጠቀም ከቤቱ ወስዶ ማሰር ነው
በእስራኤል ሕዝብ መካከል ከወንድሞቹ አንዱን
“የትኛውንም እስራኤላዊ ወንድሙን”
ያ ሌባ ይሙት
“ከዚያም ሌሎች እስራኤላውያን ያንን ሌባ ስለድርጊቱ በመግደል ይቅጡት”
ክፉን ከመካከልህ ታስወግዳለህ
“ክፉ” የሚለው ቅጽል እንደ ስማዊ ሐረግ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ይህንን ክፉ ነገር ያደረገውን ሰው ከእስራኤላውያን መካከል አስወግደው” ወይም “ይህንን ክፉ ሰው አስወግደው” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 24:8
አምላክህ እግዚአብሔር -- ትዝ ይበልህ -- ጥንቃቄ አድርግ -- በጥንቃቄ ጠብቅ
እዚህ ጋ ሙሴ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤላውያን ይናገራል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላትና “ጥንቃቄ አድርግ” እና “ትዝ ይበልህ” የሚሉት ትዕዛዛት ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)
የትኛውንም ለምጽ በሚመለከት ጥንቃቄ አድርግ
“የምትሠቃየው በለምጽ እንደሆነ ልብ በል” ወይም “ለምጽ ይኖርብህ እንደሆነ ልብ በል”
ካህናቱና ሌዋውያኑ የሚያስተምሩህን ለአንተ የተሰጠህን እያንዳንዱን መመሪያ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የሰጠሁህን መመሪያዎች በሙሉና ሌዋውያን የሆኑት ካህናቱ እንድታደርገው የሚያስተምሩህን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የሚያስተምሩህን -- እንድታደርገው -- ከግብፅ ከወጣችሁ
እዚህ ጋ ሙሴ ለእስራኤላውያን የሚናገረው እንደ ቡድን ነው፣ ስለዚህ “አንተ” የሚሉት እነዚህ አገባቦች ብዙ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)
እኔ እንዳዘዝኳቸው ታደርጋለህ
“እኔ እንዳዘዝኳቸው በትክክል ስለማድረግህ እርግጠኛ ሁን”
እንዳዘዝኳቸው
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋውያን የሆኑትን ካህናት ነው።
ትዝ ይበልህ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “(የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ከግብፅ በመውጣት ላይ እያለህ
“ግብፅን ስትለቅ በነበረበት ጊዜ”
Deuteronomy 24:12


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መያዣውን ለራስህ ወስደህ አታሳድርበት
“ኮቱን አታሳድርበት”
መያዣውን
ይህ የሚያመለክተው ብድሩን ባይመልስ በምትኩ ሊሰጥህ ቃል የገባውን ነገር ነው። ይህንን በዘዳግም 24:10 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
መያዣውን መልስለት
“ብድሩን እንደሚመልስልህ ለማሳየት የሰጠህን መልስለት”
Deuteronomy 24:14
የተቀጠረን አገልጋይ አትጨቁነው
“የተቀጠረን አገልጋይ አትበድለው”
የተቀጠረ አገልጋይ
በየቀኑ ለሥራው የሚከፈለው ሰው
ድኻና ችግረኛ
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ይህ ሰው ራሱን መርዳት የማይችል በመሆኑ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)
በከተማህ በሮች ውስጥ
እዚህ ጋ “የከተማ በሮች” ማለት መንደሮች ወይም ከተሞች ማለት ነው። ኢ.ት: “ከከተሞችህ በአንዱ” (See: Synecdoche)
ደሞዙን በየቀኑ ስጠው
“ሰውየው በየቀኑ ማግኘት የሚገባውን ገንዘብ ልትሰጠው ይገባል”
ይህንን ጉዳይ ሳትፈታ ፀሐይ አትጥለቅ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “እስራኤላውያኑ ፀሐይ ስትጠልቅ የአዲሱ ቀን ጅማሬ እንደሆነ ያስባሉ። ኢ.ት: “ሥራውን በሠራበት በዚያው ቀን ለሰውየው ልትከፍለው ይገባል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ድኻ በመሆኑ ይጠባበቀዋልና
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “ድኻ ስለሆነና ለቀጣይ ቀኑ ምግቡን ለመግዛት በደሞዙ ስለሚተማመን” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
በአንተ ላይ ወደ እግዚአብሔር እንዳይጮህ
“እግዚአብሔርን እንዳይጠራና እንዲቀጣህ እንዳይጠይቀው”
Deuteronomy 24:16
ወላጆች ስለ ልጆቻቸው አይገደሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ከልጆቻቸው አንዱ ባደረገው ክፉ ነገር ምክንያት ወላጆችን አትግደል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እንዲሁም ልጆች ስለ ወላጆቻቸው አይገደሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ወላጆቻቸው ባደረጉት ክፉ ነገር ምክንያት ልጆቻቸው አይገደሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እያንዳንዱ ስለ ገዛ ራሱ ኃጢአት ይገደል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “አንድን ሰው መግደል የሚኖርብህ እርሱ ራሱ ባደረገው ክፉ ነገር ምክንያት ብቻ ነው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 24:17
ከመጻተኛው ወይም አባቱን ካጣው ላይ ኃይልን በመጠቀም ፍትሕን አታስቀርበት
ሙሴ ስለፍትሕ አንድ ጉልበተኛ የሆነ ሰው ከደካማው ላይ በኃይል እንደሚቀማው አካላዊ ቁስ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “የመጻተኛውን ወይም አባቱን ያጣውን ልጅ ፍትሕ አታጓድል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አባቶቻቸውን ያጡ ልጆች
x
Deuteronomy 24:19
ከእርሻህ ላይ የደረሰውን ሰብል በምትሰበስብበት ጊዜ
“በእርሻህ ውስጥ ሰብል በምታጭድበት ጊዜ”
የእህል ነዶ
አንዳንድ ትርጉሞች ይህንን እንደ “እስር” ይተረጉሙታል። ትርጉሞቹ ሁሉ የሚያመለክቱት በቀላሉ ለመሸከም የሚቻል፣ በይበልጥም በአንድ ላይ የታሰሩ የአገዳ እህሎችን ነው።
እርሱ ለመጻተኞች፣ አባቶቻቸውን ላጡ ልጆች ወይም ለመበለቶች ይሁን
የሚታወቀውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ኢ.ት: “ነዶውን መጻተኛው፣ ወላጆቹን ያጣው ወይም መበለቲቱ እንዲወስዱት ተወው” (See: Ellipsis)
በእጆችህ ሥራ ሁሉ
እዚህ ጋ “እጆች” የሚያመለክቱት ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት: “በምትሠራው ሥራ ሁሉ” (See: Synecdoche)
የወይራ ዛፍህን በምትነቀንቅበት ጊዜ
የሚታወቀውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ኢ.ት: “ፍሬው ሲረግፍ ለማንሣት የወይራ ዛፍህን ቅርንጫፎች በምትነቀንቅበት ጊዜ” (See: Ellipsis)
በድጋሚ ወደ ቅርንጫፎቹ አትመለስ
“ከወይራ ዛፉ ላይ እያንዳንዱን ፍሬ አትልቀም”
እርሱ ለመጻተኞች፣ አባቶቻቸውን ላጡ ልጆች ወይም ለመበለቶች ይሆናል
የሚታወቀውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ኢ.ት: “በቅርንጫፎቹ ላይ የሚቀሩት የወይራ ፍሬዎች መጻተኞች፣ ወላጆቻቸውን ያጡና መበለቶች ለቅመው የሚወስዷቸው ናቸው” (See: Ellipsis)
Deuteronomy 24:21
የቀረው ለመጻተኞች፣ አባቶቻቸውን ላጡ ልጆች እና ለመበለቶች ይሆናል
“የማትለቅመው የወይን ፍሬ ለመጻተኛው፣ አባቱን ላጣውና ለመበለቲቱ ይሆናል”
ለመጻተኞች፣ አባቶቻቸውን ላጡ ልጆች እና ለመበለቶች ይሆናል
እነዚህ የሚያመለክቱት የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ነው። ኢ.ት: “ለመጻተኞች፣ ወላጆቻቸውን ላጡና ለመበለቶች” (See: Generic Noun Phrases)
ትዝ ይበልህ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “አስታውስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 25
Deuteronomy 25:1
በደለኛው ሰው መገረፍ የሚገባው ከሆነ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ዳኛው በደለኛውን ሰው እንዲገርፉት ካዘዛቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በፊቱ ይገረፍ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ሲገርፉት ያያቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ስለ ወንጀሉ የታዘዘውን የግርፋት ቁጥር
“ስላደረገው ክፉ ሥራ ባዘዘው ቁጥር ልክ”
Deuteronomy 25:3
ዳኛው አርባ ግርፋት ሊሰጠው ይችላል
“ዳኛው በደለኛውን ሰው 40 ጊዜ እንዲገርፉት ሊነግራቸው ይችላል” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሆኖም ከዚያ ቁጥር መብለጥ አይኖርበትም
“ሆኖም ዳኛው ከ40 ጊዜ በላይ እንዲገረፍ ማዘዝ አይኖርበትም”
ከዚያ ቁጥር ካለፈና ተጨማሪ ግርፋት የሚገርፈው ከሆነ
“ዳኛው ከ40 ጊዜ በላይ እንዲገርፉት የሚያዛቸው ከሆነ”
ያን ጊዜ እስራኤላዊው ወንድምህ በዐይኖችህ ፊት የተዋረደ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ያን ጊዜ በእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ፊት እስራኤላዊውን ወንድምህን ያዋርደዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በዐይኖችህ ፊት የተዋረደ ይሆናል
እዚህ ጋ ስለሚያዩት ነገር አጽንዖት ለመስጠት ሕዝቡ በ “ዐይኖቻቸው” ተወክለዋል። ኢ.ት: “ተዋርዷል፣ እናንተ ሁላችሁም አይታችሁታል” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 25:5
ወንድማማቾች በአንድነት የሚኖሩ ከሆነ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “ወንድማማቾች በአንድ ንብረት ላይ የሚኖሩ ከሆነ” ወይም 2) “ወንድማማቾች ተቀራርበው የሚኖሩ ከሆነ”
ያን ጊዜ የሟቹ ሰው ሚስት ሌላ ሰው ማግባት አይኖርባትም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ያን ጊዜ የሟች ቤተሰቦች መበለቲቱ ሌላ ሰው እንድታገባ መፍቀድ የለባቸውም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የዋርሳነቱን ተግባር ይፈጽምላት
“የሟች ወንድም እንዲያደርግ የሚጠበቅበትን ያድርግ”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በሟች ወንድሙ ስም ይጠራል
“ስም” የሚለው ቃል የሰውየውን የቤተሰብ ሐረግ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የሟች ወንድሙ የቤተሰብ ሐረግ ይቀጥላል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ስሙ ከእስራኤል እንዳይጠፋ
“ስም” የሚለው ቃል የሰውየውን የቤተሰብ ሐረግ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የቤተሰቡ ሐረግ ከእስራኤል እንዳይጠፋ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 25:7
ወደ በሩ ወደ ሽማግሌዎች ትሂድ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “ሽማግሌዎች በጉዳዮች ላይ ወደሚዳኙበት ወደ ከተማው በር ትሂድ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ለወንድሙ ስም ለማቆም እምቢ ቢል
እዚህ ጋ “ስም” የሚያመለክተው በተወላጆቹ አማካይነት የአንድን ሰው መታሰቢያ ነው። ኢ.ት፡ “ለወንድሙ ወንድ ልጅ ለመስጠት እምቢ ቢል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የዋርሳነቱን ተግባር አልፈጸመልኝም
“እኔን በማግባት ከዋርሳ የሚጠበቅበትን ተግባር አልፈጸመም”
ልወስዳት አልፈልግም
“ላገባት አልፈልግም”
Deuteronomy 25:9
በሽማግሌዎቹ ፊት ወደ እርሱ ትቅረብ
“በዚያ ያሉ ሽማግሌዎች እያዩአት ተራምዳ ትቅረበው”
የወንድሙን ቤት በማይሠራ
እዚህ ጋ “ቤት” የቤተሰብ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ለወንድሙ ወንድ ልጅ የማይሰጥና የወንድሙን የቤተሰብ ሐረግ የማያስቀጥል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ስሙ በእስራኤል ይጠራል
“በእስራኤል ያሉ ሰዎች ቤተሰቡን እንደ -- ያውቃሉ”
ጫማው እንዲወልቅ የተደረገበት ሰው ቤት
እዚህ ጋ ጫማ የማውለቁ ምሳሌ ወንድምየው ከሟች ወንድሙ ሀብት ምንም እንደማይወስድ ማሳያ ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ደግሞም ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል. ኢ.ት፡ “የወንድሙ ሚስት ጫማውን ከእግሩ ያወለቀችበት ሰው ቤት” ወይም “የወንድሙን ሚስት ያላገባው ሰው ቤተሰብ” ወይም “ሁሉም ሰው የሚንቀው ቤተሰብ” ወይም “አሳፋሪው ቤተሰብ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 25:11
ከደብዳቢው እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ደብዳቢው እንደ ገና እንዳይደበድበው” ወይም “እርሱን ከሚመታው ሰው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዐይንህ አይራራ
እዚህ ጋ “ዐይን” ማለት ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “አትዘንላት” ወይም “ምሕረት አታድርግላት” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 25:13
በቦርሳህ ውስጥ ትልቅና ትንሽ የሆኑ የተለያዩ ሚዛኖች አይኑሩህ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። በተጨማሪም የሚታወቀውን መረጃ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ነገሮችን በምትገዛበት ጊዜ ከምትናገረው የሚበልጥን ሚዛን በመጠቀም፣ በምትሸጥበት ጊዜ ደግሞ ከምትናገረው ያነሰ ሚዛን በመጠቀም ሰዎችን አታጭበርብር” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information and Ellipsis)
ሚዛኖች
ሚዛኖች አንድ ነገር ምን ያህል እንደሚከብድ ለማወቅ መለኪያው ላይ የሚቀመጡ ድንጋዮች ነበሩ
በቤትህ ውስጥ ትልቅና ትንሽ የሆኑ የተለያዩ ሚዛኖች አይኑሩህ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ በተጨማሪም፣ የሚታወቀውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ነገሮችን በምትገዛበት ጊዜ ከምትናገረው የሚበልጥ መለኪያ በመጠቀም፣ እንዲሁም በምትሸጥበት ጊዜ ከምትናገረው የሚያንስ መለኪያ በመጠቀም ሰዎችን ማጭበርበር የለብህም። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information and Ellipsis)
መለኪያዎች
መለኪያ አንድ ነገር ምን ያህል እንደሆነ የሚለካበት ቅርጫት ወይም ሌላ መያዣ ነበር።
Deuteronomy 25:15
ልክና ተገቢ
“ትክክል እና አግባብነት ያለው”
ሚዛን -- መለኪያ
እነዚህን ቃላት በዘዳግም 25፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ቀኖችህ እንዲረዝሙ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ረጅም ዘመን እንድትኖር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እንደዚህ ያሉትን ነገሮች ለሚያደርጉ፣ በእምነት አጕዳይነት ለሚያደርጉ ሁሉ
“የተለያየ መጠን ያላቸውን ሚዛኖችና መለኪያዎችን በመጠቀም ሰዎችን የሚያጭበረብሩ ሁሉ”
Deuteronomy 25:17
አማሌቅ ያደረገብህ ትዝ ይበልህ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን “አማሌቅ” አማሌቃውያን ሰዎችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “አማሌቃውያን ያደረጉብህን አስታውስ” (የአነጋገር ዘይቤ፣ ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በወጣህ ጊዜ
እዚህ ጋ “አንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
በመንገድ ላይ እንዴት እንደተገናኘህ
“በጉዞ ላይ እያለህ እንዴት እንደተገናኙህ”
ከኋላ የነበራችሁትን አጠቋችሁ
“የኋላ መስመር ላይ የነበሩትን ሰዎችህን አጠቃ”
ከበስተኋላህ የደከሙትን ሁሉ
“በኋለኛው መስመር ላይ ደካሞች የነበሩትን ሰዎች በሙሉ”
ዝለትና ድካም
እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ሕዝቡ ምን ያህል ደክመው እንደነበሩ አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት፡ “ደክመውና ዝለው” (See: Doublet)
ለእግዚአብሔር ክብርን አልሰጠም
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ቅጣት አልፈራም” ወይም “እግዚአብሔርን አላከበረም” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
የአማሌቅን መታሰቢያ ከሰማይ በታች ደምስስ
“ከእንግዲህ ማንም እንዳያስታውሳቸው አማሌቃውያንን በሙሉ ግደላቸው”

---

Chapter 26
Deuteronomy 26:1
ከመጀመሪያው ምርትህ ሁሉ ጥቂቱን
“ከምርትህ በኩራት ጥቂቱን” ወይም “ከመጀመሪያው የሰብል ምርትህ ጥቂቱን”። ይህ “መጀመሪያ” የአንድ ደረጃን ማሳያ ቁጥር ነው። (ደረጃን ማሳያ ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 26:5
ቅድመ ቅድም አያቴ ተቅበዝባዥ አራማዊ ነበር
ይህ እስራኤላዊ ወንድ ቅርጫቱን በሚያቀርብበት ጊዜ መናገር የሚኖርበት የዐረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ነው።
ተቅበዝባዥ አራማዊ
ይህ የእስራኤላውያኑ ሁሉ ቅድመ ቅድም አያት የነበረውን ያዕቆብን ያመለክታል። እርሱ ለብዙ ዓመታት በሶሪያ በሚገኝ በአራም ናሃሪም ይኖር ነበር።
በዚያ ቆየ
“ቀሪ ሕይወቱን በዚያ ኖሯል”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በዚያ እርሱ -- ሆነ
“እርሱ” የሚለው ቃል “የያዕቆብን ተወላጆች” የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ታላቅ፣ ኃያል
በመሠረቱ እነዚህ ቃላት የሚሉት አንድ ነገር ነው። እስራኤል ብዙና ኃይለኛ ሕዝብ መሆኑ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት፡ “በጣም ታላቅ” (See: Doublet)
Deuteronomy 26:6
ከፉብን፣ አስቃዩንም
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚሉት አንድ ነገር ነው። ግብፃውያን የጭካኔ ተግባር እንደ ፈጸሙባቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)
አደረገብን
እዚህ ጋ “እኛ” የሚያመለክተው በግብፅ ይኖሩ የነበሩትን የእስራኤል ሕዝብ ነው። ተናጋሪው በግብፅ ቢኖርም ባይኖርም ራሱን ከሕዝቡ አንዱ አድርጎ ይጨምራል። (See: Inclusive “We”)
ድምፃችንን ሰማ
እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው እና ጩኸቱን ወይም ጸሎቱን ነው። ኢ.ት፡ “ጩኸታችንን ሰማ” ወይም “ጸሎታችንን ሰማ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ስቃያችንን፣ ልፋታችንን እና መጨቆናችንን
“ግብፃውያን ያሰቃዩን የነበረውን፣ ስንሠራው የነበረውን በጣም ከባድ የሆነውን ሥራ እና ግብፃውያኑ ይጨቁኑን የነበረውን”
Deuteronomy 26:8
እግዚአብሔር አመጣን
እዚህ ጋ “እኛ” የሚያመለክተው በግብፅ ይኖሩ የነበሩትን የእስራኤል ሕዝብ ነው። ተናጋሪው በግብፅ ቢኖርም ባይኖርም ራሱን ከሕዝቡ አንዱ አድርጎ ይጨምራል። (See: Inclusive “We”)
በብርቱ እጅ፣ በተዘረጋች ክንድ
እዚህ ጋ “ብርቱ እጅ” እና “የተዘረጋች ክንድ” የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያመለክቱ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:34 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ብርቱ ኃይሉን በማሳየት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በታላቅ ማስደንገጥ
“ያዩአቸውን ሰዎች በሚያስፈሩ ድርጊቶች”
ወተትና ማር የምታፈስ ምድር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በዘዳግም 6፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡ ኢ.ት፡ “ብዙ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር” ወይም “ከብት ለማርባትና ለእርሻ ምርጥ የሆነች ምድር”
Deuteronomy 26:10
ከአዝመራው የመጀመሪያውን
“ከአዝመራው የመጀመሪያውን ፍሬ” ወይም “ከአዝመራው የመጀመሪያውን ሰብል”
አስቀምጠው
“ቅርጫቱን አስቀምጠው”
አምላክህ እግዚአብሔር ባደረገልህ መልካም ነገር ሁሉ ደስ ይበልህ
“አምላክህ እግዚአብሔር ስላደረገልህ መልካም ነገሮች ሁሉ ደስ ይበልህ፣ አመስግንም”
Deuteronomy 26:12
በሦስተኛው ዓመት
ይህ “ሦስተኛ” የሦስት ደረጃን አመልካች ቁጥር ነው። የእስራኤል ሕዝብ በየሦስት ዓመቱ ከአዝመራው አንድ አሥረኛውን ለድኾች ይሰጡ ነበር። (ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)
አባቶቻቸውን ያጡ
እነዚህ ሁለቱም ወላጆቻቸው የሞቱባቸውና የሚንከባከባቸው ዘመድ የሌላቸው ልጆች ናቸው።
መበለት
ይህ ማለት ባል የሞተባትና በእርጅናዋ ጊዜ የሚንከባከብ ልጅ የሌላት ሴት ማለት ነው።
በከተማህ በሮች ውስጥ ብላ፣ ጥገብም
እዚህ ጋ “በሮች” ማለት መንደሮች ወይም ከተሞች ማለት ነው። ኢ.ት፡ “እነዚያ በመንደርህ ውስጥ የሚኖሩት የሚበሉት በቂ ምግብ እንዲኖራቸው” (See: Synecdoche)
ከ -- አውጥቻችኋለሁ
እነዚህ እስራኤላዊው እንዲለው የሚጠበቅበት የሌላው አነጋገር የመጀመሪያ ቃላት ናቸው።
አልረሳኋቸውም
ይህ ማለት የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በሙሉ ታዟል።
Deuteronomy 26:14
በለቅሶዬ ጊዜ ከእርሱ ምንም አልበላሁም
“ባለቀስኩበት ወቅት የትኛውንም አስራት አልበላሁም”
ባልነጻሁበት ጊዜ
እዚህ ጋ “ያልነጻ” ማለት በሕጉ መሠረት ንጹሕ ያልሆነ ሰው ማለት ነው። ንጹሕ ያልሆነ ሰው ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን አስራት እንዲነካ እግዚአብሔር አይፈቅድለትም”። የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “በሕጉ መሠረት ንጹሕ ባልነበርኩበት ጊዜ” ወይም “ልነካው እንደማልችል ሕጉ በሚናገርበት ጊዜ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
የአምላኬን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቻለሁ፤ እንዳደርገው ያዘዝከኝን ሁሉንም ነገር ታዝዣለሁ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” እግዚአብሔር ለተናገረው የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ሁለቱም አነጋገሮች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። ሰውየው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በሙሉ ስለመታዘዙ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Parallelism የሚለውን ተመልከት))
ከምትኖርበት ከቅዱሱ ስፍራ፣ ከሰማይ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ነው። ኢ.ት፡ “ከቅዱስ ማደሪያህ፣ ከሰማይ” (See: Dou- blet)
ወተትና ማር የምታፈስ ምድር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በዘዳግም 6፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ብዙ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር” ወይም “ከብት ለማርባትና ለእርሻ ምርጥ የሆነች ምድር”
Deuteronomy 26:16
በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ
እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት የሚመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች በአንድ ላይ “ሙሉ በሙሉ” ወይም “በቅንነት” ለማለት ጥቅም ላይ ውለዋል። ይህንን በዘዳግም 4፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)
በመንገዶቹ ትሄድና ሥርዓቱን፣ ትዕዛዛቱን እና ሕጉን ትጠብቅ ዘንድ፣ ድምፁንም ትሰማ ዘንድ
እዚህ ጋ “መሄድ”፣ “መጠበቅ” እና “መስማት” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር የተናገረውን ነው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ያዘዘው ሁሉ ሙሉ በሙሉ እንድትጠብቅ” (See: Parallelism and Metonymy)
Deuteronomy 26:18
የራሱ ርስት የሆነን ሕዝብ
“የእርሱ የሚሆንን ሕዝብ”

---

Chapter 27
Deuteronomy 27:1
ዛሬ የማዛችሁን -- ትሻገራላችሁ
ሙሴ እንደ አንድ ቡድን አድርጎ የሚናገረው ለእስራኤላውያን ነው፣ ስለዚህ በሁለቱም አገባብ “አንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
የማዛችሁን
እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው። ሽማግሌዎቹ ከሙሴ ጋር ተስማምተው በዚያ አሉ፣ ሆኖም ብቸኛው ተናጋሪ እርሱ ነው።
በኖራ ቅባው
ይህ ዓይነቱ በአብዛኛው የኖራ፣ አሸዋና ውሃ ድብልቅ ሲሆን በአንድ ነገር ላይ የሚቀባ ነው። ሲደርቅ አንድ ሰው በላዩ ላይ መጻፍ እንዲችል ጠንካራና ለስላሳ ገጽታ ይኖረዋል። ኢ.ት፡ “ቅባቸው” ወይም “ልትጽፍባቸው እንዲያስችሉህ አድርግ” (See:


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Assumed Knowledge and Implicit Information)
ወተትና ማር የምታፈስ ምድር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በዘዳግም 6:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “ብዙ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር” ወይም “ለከብት እርባታና ለእርሻ ምርጥ የሆነች ምድር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 27:4
እኔ የማዝህን -- ስትሻገር -- አስቀምጥ
ሙሴ ለእስራኤላውያን የሚናገረው እንደ ቡድን አድርጎ ነው፣ ስለዚህ “አንተ” የሚልበት አገባብና “አስቀምጥ” የሚለው ትዕዛዝ ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
በኖራ ቅባው
“ቅባቸው” ወይም “ልትጽፍባቸው እንዲያስችሉህ አድርግ”። ይህንን በዘዳግም 27፡ 2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የጌባል ተራራ
ይህ በሴኬም አቅራቢያ የሚገኝ ተራራ ነው። እርሱን በዘዳግም 11:29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ድንጋዮቹን ለመጥረብ ምንም ዓይነት የብረት መሣሪያ አትጠቀም
ይህ ድንጋዮቹን በማለስለስ በተሻለ ሁኔታ በአንድ ላይ እንዲገጣጠሙ ለማድረግ የሚያገለግሉ መሮዎችን ያመለክታል። የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “የመሠዊያውን ድንጋዮች በብረት መሣሪያ አትጥረባቸው” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 27:6
ባልተጠረቡ ድንጋዮች
ማንም በብረት መሣሪያ ያልጠረባቸው በተፈጥሮ ቅርጻቸው ያሉ ድንጋዮች
በድንጋዮቹ ላይ ጻፍባቸው
ይህ በኖራ ተቀብተው በጌባል ተራራ ላይ የሚቆሙትን ድንጋዮች ያመለክታል። ይህንን በዘዳግም 27:12 እና 27:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Deuteronomy 27:9
የአምላክህን የእግዚአብሔርን ድምፅ ታዘዝ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር እርሱ የሚናገረውን ያመለክታል። ኢ.ት: “አምላክህ እግዚአብሔር የሚናገረውን ታዘዝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እኔ የማዝህን
ሙሴ እያዘዘ ነው። ሌዋውያኑ ከሙሴ ጋር በመስማማት በዚያ ይገኛሉ፣ ሆኖም የሚናገረው እርሱ ብቻ ነው።
Deuteronomy 27:11
እነዚህ ነገዶች
እዚህ ጋ “ነገዶች” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው የስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮር፣ ዮሴፍ፣ እና ብንያም ነገድ ሕዝቦችን ነው። ኢ.ት: “የእነዚህ ነገዶች ሕዝቦች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የገሪዛን ተራራ
x
Deuteronomy 27:13
የጌባል ተራራ
ይህንን በዘዳግም 11:29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
እርግማኖቹን ያውጁ
“እግዚአብሔር እስራኤልን እንዴት እንደሚረግማቸው በታላቅ ድምፅ ተናገር”
Deuteronomy 27:15
በድብቅ የሚያቆም ያ ሰው የተረገመ ይሁን
ይህ ሌዋዊው ለእስራኤል ሕዝብ በሙሉ ጮክ ብሎ የሚያደርገው ንግግር ነው። ይህ ንግግር በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “በድብቅ የሚያቆመውን ሰው እግዚአብሔር ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የባለሙያ እጅ የሠራውን
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ሰው የሠራው አንድ ነገር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ባለሙያ
ነገሮችን ጥሩ አድርጎ መሥራት የሚያውቅ ሰው

Deuteronomy 27:16
ሰውየው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ሰውየውን ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የባልንጀራውን የድንበር ምልክት የሚያስወግድ
የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “በመሬቱ ድንበር ላይ ያሉትን ምልክቶች በማንሣት ከባልንጀራው መሬት የሚወስድ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 27:18
ሰውየው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 27:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ሰውየውን ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ለመጻተኛው፣ -- ለመበለቲቱ የሚገባውን ፍትሕ ጉልበቱን ተጠቅሞ የሚነጥቅ
ሙሴ ስለ ፍትሕ የሚናገረው አንድ ጉልበተኛ የሆነ ሰው ደካማ ከሆነው ሰው ላይ በኃይል እንደሚቀማው አካላዊ ቁስ አድርጎ ነው። የአንተ ቋንቋ ምናልባት “ጉልበቱን ተጠቅሞ የሚነጥቅ” ለማለት የሚያስችል አንድ ቃል ይኖረው ይሆናል። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 24:17 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት: “መጻተኛውን -- መበለቲቱን የሚበድል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አባቶቻቸውን ያጡ ልጆች
እነዚህ ሁለቱም ወላጆቻቸው የሞቱባቸውና የሚንከባከባቸው ዘመድ የሌላቸው ልጆች ናቸው።
Deuteronomy 27:20
ሰውየው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 27:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ሰውየውን ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የአባቱን ሚስት
ይህ የአባቱን ሌላኛዋን ሚስት እንጂ የሰውየውን እናት አያመለክትም።
የአባቱን መብት ወስዷል
አንድ ሰው ሚስት በሚያገባበት ጊዜ እርሱ ብቻ ከእርሷ ጋር የመተኛት ሕጋዊ መብት ይኖረዋል። የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “የአባቱን ሕጋዊ መብት ወስዶበታል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ከየትኛውም ዓይነት እንስሳ ጋር የሚተኛ
የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከየትኛውም ዓይነት እንስሳ ጋር የሚተኛ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 27:22
ሰውየው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 27:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ሰውየውን ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ከአባቱ ሴት ልጅ ወይም ከእናቱ ሴት ልጅ ጋር
ይህ ማለት አንድ ሰው ከሌላ እናት ወይም አባት ብትወለድም እንኳን ከእህቱ ጋር ሊተኛ አይችልም።
Deuteronomy 27:24
ሰውየው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 27:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ሰውየውን ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 27:26
ሰውየው የተረገመ ይሁን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 27:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ሰውየውን ይርገመው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 28

Deuteronomy 28:1
ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ድምፅ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እርሱ የሚናገረውን ነው። ኢ.ት: “አምላክህ እግዚአብሔር ለሚናገረው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ትጠብቀው ዘንድ
“ትታዘዘው ዘንድ”
ከላይ ያደርግሃል
ሙሴ ከፍ ባለ ኮረብታ ላይ በአካል ከፍ እንደ ማለት አስፈላጊ ስለ መሆን ወይም ታላቅ ስለ መሆን ይናገራል። ኢ.ት: “ከ -- ይልቅ በጣም አስፈላጊ ያደርግሃል” ወይም “ከ-- ይልቅ ታላቅ ያደርግሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እነዚህ በረከቶች ሁሉ ይመጡብሃል፣ ይደርሱብሃልም
ሙሴ በረከቶችን የሚገልጻቸው በድንገት እንደሚያጠቃቸው ወይም አሳዶ እንደሚይዛቸው ሰው አድርጎ ነው። ኢ.ት: “ፈጽሞ በምትገረምበት እንዲህ ባለ መንገድ እግዚአብሔር ይባርክሃል፣ ይኸውም ልታመልጥ በማትችልበት መልኩ ይባርክሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 28:3
ትባረካለህ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ይባርክሃል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በከተማ - በእርሻ
ይህ ቁንጽል፣ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ይባርካቸዋል የሚል ትርጉም አለው። (See: Merism)
የአካልህ ፍሬ፣ የመሬትህ ፍሬ፣ የእንስሳህ ፍሬ
“ልጆችህ፣ ሰብልህ፣ እና እንስሶችህ” እነዚህ የአነጋገር ዘይቤዎች እስራኤላውያን ዋጋ ለሚሰጧቸው ነገሮች በሙሉ በቁንጽል አመልካቾች ናቸው። (የአነጋገር ዘይቤ እና Merism የሚለውን ተመልከት)
የእንስሳህ ፍሬ፣ የከብቶችህ ፍሬ፣ እና የበግና የፍየል ጠቦቶችህ
ይህ ጥምረት እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን እንስሶች እንደሚያበዛቸውና እንደሚያበረታቸው በሦስት መንገድ መናገሪያ ነው። ኢ.ት: “የከብቶቻችሁ ጥጃዎች እና የበግና የፍየል መንጋ ጠቦቶቻችሁ ከእንስሶቻችሁ ሁሉ ጋር” (See: Doublet)
Deuteronomy 28:5
ይባረካሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ይባርካል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ቅርጫትህና ቡሓቃህ
እስራኤላውያን ቅርጫትን ጥራጥሬ ለመሸከም ይጠቀሙበት ነበር። “ቡሓቃ” እንጀራ ለመጋገር ዱቄቱን የሚያዋህዱበት ጎድጎድ ያለ ዕቃ ነው። ኢ.ት: “የምታበቅለው እህል እና የምትበላው ምግብ ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በምትገባበት ጊዜ -- በምትወጣበት ጊዜ
ይህ ጥምረት በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ የሚኖራቸውን የሕይወት ተግባራት በሙሉ ያመለክታል። (See: Merism)
Deuteronomy 28:7
በላይህ ላይ የተነሣውን ጠላትህን በፊትህ ተመትቶ እንዲወድቅ ያደርገዋል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “የሚዋጉህን ጠላቶችህን እንድታሸንፋቸው ያደርግሃል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሆኖም በሰባት መንገድ ከአንተ ይሸሻሉ
“ሆኖም በሰባት አቅጣጫ ከአንተ በሩጫ ይሸሻሉ”
ሰባት መንገድ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ትክክለኛው ቁጥር ከሰባት ሊበልጥ ወይም ሊያንስ ይችላል። ኢ.ት: “በብዙ የተለያዩ አቅጣጫዎች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በረከት በጎተራህ እንዲመጣ እግዚአብሔር ያዘዋል
እግዚአብሔር አንድ ሰው በድንገት እስራኤላውያንን እንዲያጠቃቸው የሚያዝ በሚመስል መልኩ እግዚአብሔር እንደሚባርካቸው ሙሴ ያብራራል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር በሚባርክህ ጊዜ በጎተራህ ባለው ጥራጥሬ ብዛት ትገረማለህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
እጅህን በምታኖርበት ሁሉ ላይ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “በምትሠራው ነገር ሁሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 28:9
እግዚአብሔር ለራሱ የተለየ ሕዝብ አድርጎ ያቆምሃል
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የራሱ እንዲሆን በተለየ ሁኔታ መምረጡ ሌሎች ሕዝቦች በሙሉ ከሚኖሩበት ስፍራ ልዩ በሆነ ቦታ እግዚአብሔር እንዳስቀመጣቸው ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ለእርሱ የሚሆን ቅዱስ ሕዝብ ያደርግሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእግዚአብሔር ስም ተጠርተሃል
እዚህ ጋ “በእግዚአብሔር ስም ተጠርተሃል” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም የእርሱ መሆን ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር የራሱ አድርጎ ጠርቶሃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 28:11
በአካልህ ፍሬ፣ በከብቶችህ ፍሬ፣ በመሬትህ ፍሬ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 28:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት: “በልጆች፣ እንስሳትና ሰብል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ከሰማይ መጋዘኑ
ሙሴ ዝናቡን የሚያስቀምጥባቸው ሕንጻዎች በሚመስሉበት መልኩ ዝናብ ስለሚያዘንቡ ደመናት ይናገራል። ኢ.ት: “ደመናት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በትክክለኛው ጊዜ
“ሰብሎች በሚፈልጉት ጊዜ”
የእጆችህ ሥራ ሁሉ
“እጅ” የሚለው ቃል የሙሉው ሰው ተምሳሌት ነው። ኢ.ት: “የምትሠራው ሥራ ሁሉ” (See: Synec- doche)
Deuteronomy 28:13
ራስ እንጂ ጅራት አትሆንም
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር የእስራኤልን ሕዝብ እንደ እንስሳ ይገልጸዋል፣ ይኸውም እስራኤላውያን ሁልጊዜ የሌሎች ሕዝቦች መሪዎች ይሆናሉ እንጂ ከቶም አገልጋዮቻቸው ለመሆን ከኋላ አይከተሉም ማለት ነው። እስራኤላውያን በኃይል፣ በገንዘብና በክብር ብልጫ ያላቸው ይሆናሉ። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከላይ ብቻ ይሆናሉ -- ፈጽሞ ከበታች አይሆኑም
እስራኤላውያን በሌሎች ላይ ገዢዎች ይሆናሉ እንጂ ሌሎች አይገዟቸውም።
እኔ አዛችኋለሁ
ሙሴ የሚናገረው ለእስራኤላውያን በሙሉ ነው፣ ስለዚህ “አንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
እኔ ዛሬ ከማዝህ ቃል ሁሉ ሌሎች አማልክትን ተከትለህ ለማገልገል ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ ካልተከተልክ
እግዚአብሔርን አለመታዘዝና ሌሎች አማልክትን ማምለክ ልክ አንድ ሰው በአካሉ ከእግዚአብሔር ቃል ተመልሶ በሌላ አቅጣጫ እንደ ሄደ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት: “ሌሎች አማልክትን በማገልገል ዛሬ እኔ የማዝህን ባትታዘዝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 28:15
ነገር ግን ባትታዘዝ
እዚህ ጋ ሙሴ ሕዝቡ ባይታዘዙ የሚደርስባቸውን እርግማን መዘርዘር ይጀምራል።
የአምላክህ የእግዚአብሔር ድምፅ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉሙ እግዚአብሔር የሚናገረው ማለት ነው። ኢ.ት: “አምላክህ እግዚአብሔር የሚናገረው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከዚያም እነዚህ እርግማኖች ሁሉ ይመጡብሃል፣ ይደርሱብሃል
ሙሴ እርግማኖቹን የሚገልጻቸው በድንገት እንደሚያጠቃቸው ወይም አሳዶ እንደሚይዛቸው ሰው አድርጎ ነው። ኢ.ት: “ፈጽሞ በምትደነቅበት ሁኔታ እግዚአብሔር ይረግምሃል፣ ይህም አንተን ከሚረግምበት ከእርግማኑ ማምለጥ በማትችሉበት ሁኔታ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
ይመጡብሃል፣ ይደርሱብሃል
ይህንን በዘዳግም 28:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Deuteronomy 28:16
የተረገምክ ትሆናለህ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይረግምሃል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በከተማ -- በእርሻ
የዚህ ጥምረት ትርጉም እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ይባርካቸዋል የሚል ነው። ይህንን በዘዳግም 28፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (See: Merism)
ቅርጫትህና ቡሓቃህ
እስራኤላውያን ቅርጫትን ጥራጥሬ ለመሸከም ይጠቀሙበት ነበር። “ቡሓቃ” እንጀራ ለመጋገር ዱቄቱን የሚያዋህዱበት ጎድጎድ ያለ ዕቃ ነው። ይህንን በዘዳግም 28፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የምታበቅለው እህል እና የምትበላው ምግብ ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 28:18
የተረገመ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይረግማል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የአካልህን ፍሬ፣ የመሬትህን ፍሬ
ይህ “ልጆችህ፣ ሰብልህ” ለሚለው የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በዘዳግም 28፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የከብትህ፣ የበግና የፍየል ጠቦቶችህ ብዛት
ይህ ጥምረት እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን እንስሳ ብዙና ብርቱ እንደሚያደርጋቸው በሁለት መንገድ የተነገረበት ነው። ኢ.ት፡ “የከብቶቹ ጥጃዎች፣ የበግና የፍየል መንጋው ጠቦቶች” (See: Doublet)
በምትገባበት ጊዜ -- በምትወጣበት ጊዜ
ይህ ጥምረት የሚያመለክተው በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ የሚሆነውን የሕይወት ተግባራት በሙሉ ነው። ይህንን በዘዳግም 28፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (See: Merism)
Deuteronomy 28:20
እርግማን፣ መደናገር፣ እና ተግሳጽ
“እልቂት፣ ፍርሀት እና መሳቀቅ”
እጅህን በምታኖርበት ሁሉ ላይ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “በምትሠራው ነገር ሁሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እስክትጠፋ ደረስ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ጠላቶችህ እስኪያጠፉህ ደረስ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ይጣበቅብሃል
“በአንተ ላይ ይኖራል”
እኔን ትተኸኛል
እዚህ ጋ “እኔን” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።
ይጣበቅብሃል
“በአንተ ላይ ይኖራል”
Deuteronomy 28:22
ተላላፊ በሽታ፣ ትኩሳት፣ በሰውነት መመረዝ
“በሽታና የሚያቃጥል ትኩሳት ያደክምሃል”። እነዚህ ሁሉ የሚያመለክቱት ሰዎች እንዲዳከሙና እንዲሞቱ የሚያደርጋቸውን በሽታ ነው።
በድርቅ
“በዝናብ እጥረት”
ዋግ
በሰብል ላይ የሚበቅል ሻጋታ ሲሆን እንዲበሰብሱ ያደርጋቸዋል
እነዚህ ያሳድዱሃል
ሙሴ በእስራኤላውያን ላይ ስለሚደርስባቸው ክፉ ነገሮች ሲናገር ከእስራኤላውያን በስተኋላ ሆነው በሚያሳድዱ ሰዎች ወይም እንስሶች አስመስሎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “በእነርሱ ምክንያት ትሰቃያለህ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 28:23
ሰማይ ናስ ይሆናል
ሙሴ ዝናብ ስለማይኖር ሰማዩ እንደ ናስ እንደሚሆን ይናገራል። ኢ.ት፡ “ሰማይ -- ዝናብን አይሰጥም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ምድር -- ብረት ትሆናለች
ሙሴ ምድር ምንም ሰብል ስለማይበቅልባት እንደ ብረት እንደምትሆን ይናገራል። ኢ.ት፡ “መሬቱ ላይ ምንም ነገር አይበቅልም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የምድርህን ዝናብ እግዚአብሔር ወደ ትቢያና አቧራ ይለውጠዋል
“እግዚአብሔር በዝናብ ምትክ አሸዋ አዘል ውሽንፍር ይልካል”
እስክትጠፋ ደረስ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እስኪያጠፋህ ድረስ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 28:25
እግዚአብሔር በጠላቶችህ ፊት ተመትተህ እንድትወድቅ ያደርግሃል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ጠላቶችህን መትተው እንዲጥሉህ ያደርጋቸዋል”
በ -- ፊት ተመትተህ እንድትወድቅ
ይህንን በዘዳግም 28፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በሰባት መንገድ ከእነርሱ ትሸሻለህ
ይህ ማለት እስራኤላውያን ፈርተውና ደንግጠው ከጠላቶቻቸው ይሸሻሉ። የቃላቶቹን ተመሳሳይነት በዘዳግም 28፡7 ውስጥ ተመልከት። (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሰባት መንገዶች
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “በብዙ የተለያዩ አቅጣጫዎች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በመንግሥታት ሁሉ መካከል ትቅበዘበዛለህ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የሌሎች ሀገራት ሰዎች ከአንዱ ሕዝብ ወደ ሌላው ያባርሯችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 28:27
የግብፅን ዕባጭ
“ግብፃውያንን በረገምኩበት በዚያው የቆዳ በሽታ”
ዕባጭ -- የቆላ ቁስል፣ የደም በሽታና እከክ
እነዚህ ልዩ ልዩ ዓይነት የቆዳ በሽታዎች ናቸው።
ልትድን የማትችልበትን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ማንም ሊፈውስህ የማይችለውን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ዐይነ ሥውር በጨለማ በዳበሳ እንደሚሄድ በእኩለ ቀን በዳበሳ ትሄዳለህ
“በእኩለ ቀን እንኳን በዳበሳ እንደሚሄዱ እንደ ዐይነ ሥውራን ትሆናለህ”። እያንዳንዱ በሕይወቱ በሚደሰትበት ጊዜ እንኳን እስራኤላውያን አስቸጋሪ ሕይወት ይኖራቸዋል። (See: Simile)
ሁልጊዜ የተጨቆንክና የተዘረፍክ ትሆናለህ
“የበረቱ ሕዝቦች ሁልጊዜ ይጨቁኑሃል፣ ይዘርፉሃልም”
Deuteronomy 28:30
በዐይንህ ፊት በሬህ ይታረዳል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው በሬህን ሲያርደው ታያለህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በፊትህ አህያህ በግድ ይወሰድብሃል፣ አይመለስልህም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው አህያህን በጉልበት ይወስድብሃል፣ አይመልስልህምም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በጎችህ ለጠላቶችህ ይሰጣሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በጎችህን ለጠላቶችህ እሰጣቸዋለሁ” ወይም “ጠላቶችህ በጎችህን እንዲወስዱ እፈቅድላቸዋለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 28:32
ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ ለሌሎች ሕዝቦች ይሰጣሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ወንዶችና ሴቶች ልጆችህን ለሌሎች ሕዝቦች እሰጣቸዋለሁ” ወይም “ጠላቶችህ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህን ይወስዷቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ዐይኖችህ ቀኑን ሙሉ እነርሱን ይጠባበቃሉ፣ ሆኖም እነርሱን በመናፈቅ ይዝላሉ
እዚህ ጋ “ዐይኖችህ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “እነርሱን በመጠባበቅና ዳግመኛ ልታያቸው በመናፈቅ ትደክማለህ” (See: Synecdoche)
ምንም ብርታት በእጅህ ላይ አይኖርህም


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እዚህ ጋ “ብርታት በእጅህ ላይ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው ኃይልን ነው። ኢ.ት፡ “ስለጉዳዩ አንዳች ለማድረግ ኃይል አይኖርህም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:33

ሀገር

እዚህ ጋ “ሀገር” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሀገሩ ሕዝብ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “የሀገሩ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሁልጊዜ የተጨቆንክና የተረገጥክ ትሆናለህ

“የተጨቆንክ” እና “የተረገጥክ” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሁልጊዜ ይጨቁኗችኋል፣ ይረግጧችኋልም” ወይም “ባለማቋረጥ ይጨቁኗችኋል” (Doublet እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የሚሆነውን በማየት ታብዳለህ

“የምታየው እንድታብድ ያደርግሃል”

ልትድን በማትችልበት

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ማንም መፈወስ በማይችልበት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:36

እግዚአብሔር በሚወስድህ ሕዝቦች ሁሉ መካከል ጥላቻ፣ ምሳሌና መሳለቂያ

እዚህ ጋ “ምስሌ” እና “መሳለቂያ” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ነው። ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ተደርጎ መተርጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር በሚልክህ ስፍራ ሕዝቡ የጥላቻ፣ ስለ አንተም ምሳሌና መሳለቂያን ያደርጋል” ወይም “እግዚአብሔር ከጥላቻ የተነሣ ወደሚስቁብህና ወደሚቀልዱብህ ሕዝቦች ይልክሃል” (See: Doublet)

መሳለቂያ

ሰዎች ሌሎችን ለማሳፈር የሚጠቀሙበት ቃል ወይም ሐረግ

Deuteronomy 28:38

ነገር ግን ጥቂት ዘር ትሰበስባለህ

“ነገር ግን በጣም ጥቂት ምግብ ታከማቻለህ”

Deuteronomy 28:40

ነገር ግን ምንም ዘይት በራስህ ላይ አትቀባም

ሰዎች የቆዳቸውን ጤና ለመጠበቅ የወይራ ዘይት ይቀቡ ነበር።

የወይራ ዛፎችህ ፍሬአቸውን ያረግፋሉ

ፍሬው ከመብሰሉ በፊት እንደሚረግፍ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። ኢ.ት፡ “ፍሬው ከመብሰሉ በፊት የወይራ ዛፎችህ ፍሬአቸውን ያረግፋሉ” ወይም “የወይራው ፍሬዎች ከመብሰላቸው በፊት ከወይራ ዛፎችህ ላይ ይወድቃሉ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 28:42

መጻተኛው -- እርሱ -- ለእርሱ

ይህ ማንነቱ የታወቀ መጻተኛ አይደለም፣ ነገር ግን በጥቅሉ መጻተኞችን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “መጻተኞች የሆኑ -- እነርሱ -- ለእነርሱ” (See: Generic Noun Phrases)

ከአንተ በላይ ከፍ ከፍ ይላል፤ አንተ ራስህ ዝቅ ዝቅ እያልክ ትመጣለህ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ የሚለው ከእስራኤላውያን የበለጠ ኃይል፣ ገንዘብና ክብር መጻተኞች ይኖራቸዋል ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ ራስ ይሆናል፣ አንተ ጅራት ትሆናለህ

ይህ ማለት መጻተኞች ከእስራኤላውያን የበለጠ ኃይልና ሥልጣን ይኖራቸዋል። በዘዳግም 28፡13 ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:45

እነዚህ እርግማኖች ሁሉ እስክትጠፋ ድረስ ይመጡብሃል፣ ያሳድዱሃል፣ ይደርሱብሃልም

ሙሴ እርግማኖችን በድንገት እንደሚያጠቃቸው ወይም አሳዶ እንደሚይዛቸው ሰው አድርጎ ይገልጻቸዋል። ተመሳሳዩን በዘዳግም 28፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር እንደዚህ በሚያስገርምህ መንገድ ይረግምሃል፣ ይህም እንደሚያሳድድህና ሳይረግምህ በማታመልጠው ሁኔታ ይሆናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ድምፅ

እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር ለሚናገረው ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። ኢ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ለተናገረው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ትዕዛዙንና ሥርዓቱን

“ትዕዛዝ” እና “ሥርዓት” የሚሉት ቃላት “እግዚአብሔር እንድታደርገው ያዘዘህን ሁሉ” ለሚለው ጥምረት ናቸው። (See: Doublet)

Deuteronomy 28:47

በደስታና በልብ ሐሴት

እዚህ ጋ “በደስታ” እና “በልብ ሐሴት” ማለት ትርጉማቸው አንድ ነው። ሕዝቡ እግዚአብሔርን ለማምለክ እጅግ ደስ ይላቸው እንደነበረ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)

በአንገትህ ላይ የብረት ቀንበር ያደርጋል

x

Deuteronomy 28:49

ከሩቅ፣ ከምድር ጥግ

ሁለቱም ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ጠላት ከእስራኤል እጅግ ሩቅ ከሆነ ሀገር እንደሚመጡ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)

ከምድር ጥግ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ስለ እርሱ ከማታውቀው ስፍራ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ንስር ወደ ግዳዩ እንደሚበር

ይህ ማለት ጠላት በድንገት ስለሚመጣ እስራኤላውያን ሊያስቆሟቸው አይችሉም። (See: Simile)

አዛውንቶችን የማያከብርና ርኅራኄ የሌለው፣ ቁጡ ፊት ያለው ሀገር

“ሀገር” የሚለው ቃል የዚያን ሀገር ሕዝብ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ቁጡ ፊት ያለው፣ አዛውንቶችን የማያከብርና ርኅራኄ የሌለው ሕዝብ ሀገር”

እስክትጠፋ ድረስ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እስኪያጠፉህ ድረስ” ወይም “ምንም ነገር እስከማያስቀሩልህ ድረስ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:52

አንተን በከተማህ በሮች ሁሉ

እዚህ ጋ “የከተማ በሮች” የሚወክሉት ከተማን ነው። ኢ.ት፡ “ከተሞችህን” (See: Synecdoche)

የገዛ ሰውነትህን ፍሬ፣ የወንድና የሴት ልጆችህን ሥጋ

እዚህ ጋ “የወንድና የሴት ልጆችህን ሥጋ” የሚለው “የገዛ ሰውነትህን ፍሬ” የሚለውን ዘይቤአዊ አነጋገር ያብራራል። የጠላት ሰራዊት ከተማቸውን ከከበበ በኋላ ሕዝቡ የገዛ ልጆቻቸውን እስኪበሉ ድረስ ይራባሉ። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Parallelism የሚለውን ተመልከት)

የገዛ ሰውነትህን ፍሬ

ይህ የሚናገረው በወላጆቻቸው ሰውነት የተመረቱ ፍሬዎች በሚመስሉበት ሁኔታ ስለ ልጆች ነው። ኢ.ት፡ “የገዛ ራሳችሁ ልጆች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 28:54

በመካከላችሁ ደግና በጣም ርኅሩኅ የሆነው እርሱ

“በመካከላችሁ ደግና በጣም ርኅሩኅ የሆነ ማነው? እርሱም እንኳን--”። ሙሴ የሚለው፣ አንድ ሰው ልጆቻቸውን ይበላሉ ብሎ የሚገምታቸው ብቻ ሳይሆኑ የመጨረሻዎቹ ይሆናሉ ብሎ የሚገምታቸውም እንኳን እነርሱ ልጆቻቸውን ይበላሉ።

የከተማህ በሮች ሁሉ

እዚህ ጋ “የከተማ በሮች” የሚወክሉት ከተሞቹን ራሳቸውን ነው። ኢ.ት፡ “ከተሞችህ በሙሉ” (See: Synecdoche)

Deuteronomy 28:56

በመካከላችሁ ደግና ርኅሩኅ የሆነች ሴት -- በደግነቷ -- እርሷ

x

Deuteronomy 28:58

የተጻፉትን

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እኔ የጻፍኩትን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ይህ የአምላክህ የእግዚአብሔር ታላቅና አስፈሪ ስም

እዚህ ጋ “ስም” የተባለው ፈሊጣዊ አነጋገር ራሱን እግዚአብሔርን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ታላቅና አስፈሪ የሆነው አምላክህ እግዚአብሔር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር በአንተና በዘርህ ላይ አስከፊ መቅሠፍት ያደርግብሃል
“እግዚአብሔር በአንተና በዘርህ ላይ አስከፊ መቅሰፍት ይልካል” ወይም “እግዚአብሔር አንተንና ዘሮችህን በአስከፊ መቅሰፍቶች እንድትሰቃዩ ያደርጋል”
Deuteronomy 28:60
የግብፅን በሽታዎች ሁሉ በአንተ ላይ ያመጣል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “እንደገና በግብፅ በሽታዎች እንድትሰቃይ ያደርግሃል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በአንተ ላይ ይጣበቃሉ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “በሽታዎቹ አያቆሙም፣ ደግሞም ማንም ከእነርሱ ሊያድንህ አይችልም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እያንዳንዱ ሕመምና ያልተጻፈ መቅሰፍት
እዚህ ጋ “እያንዳንዱ” በአጠቃላይ ሲሆን “ብዙ” ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እኔ ያልጻፍኳቸው ሌሎች ህመሞችና መቅሰፍቶች እንኳን” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት፣ አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እስክትጠፋ ድረስ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እስኪያጠፋህ ድረስ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ትቀራላችሁ -- እንደ -- የነበራችሁት -- አልሰማችሁም
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ ቡድን አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚልበት አገባብ ሁሉ ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
እንደ ሰማይ ከዋክብት ብዝታችሁ ነበር
ይህ ማለት ባለፈው ጊዜ ብዙ እስራኤላውያን ነበሩ። (See: Simile)
ለእግዚአብሔር ድምፅ
እዚህ ጋ “የእግዚአብሔር ድምፅ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሚናገረውን ነው። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ለሚናገረው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 28:63
እግዚአብሔር በእናንተ ደስ ብሎት ነበር -- እናንተን በማብዛት -- እንድትደመሰሱና እንድትጠፉ በማድረግ በእናንተ ደስ ይለዋል። -- ትነቀላላችሁ።
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ ቡድን አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚልበት አገባብ ሁሉ ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
እግዚአብሔር ለእናንተ መልካም በማድረግና እናንተን በማብዛት ደስ ተሰኝቶባችሁ ነበር
“እግዚአብሔር ለእናንተ መልካም በማድረግና እንድትበዙ በማድረግ ተደስቶ ነበር"
እንድትደመሰሱ በማድረግ በእናንተ ደስ ይለዋል
“እንድትሞቱ በማድረግ ደስ ይለዋል”
ከምትወርሳት ምድር ትነቀላለህ
ሕዝቡ ፍራፍሬ የሆኑ ይመስል እግዚአብሔር እንደ ቁጥቋጦ እንደሚነቅላቸው ለመናገር ሙሴ ዘይቤአዊ አነጋገርን ይጠቀማል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ልትወርሱ ከምትገቡባት ምድር ያስወግዳችኋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በምትሄድበት -- ይበትንሃል -- ታመልካለህ -- የማታውቃቸውን -- አንተም ሆንክ አባቶችህ
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ ቡድን አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ እዚህ ጋ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት ብዙ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)
ከአንደኛው የምድር ጫፍ እስከ ሌላኛው የምድር ጫፍ
እነዚህ ሁለት ጽንፎች በአንድነት በምድር ላይ በሁሉም ስፍራ ማለት ነው። ኢ.ት: “በምድር ሁሉ” ወይም “በምድር ሁሉ ላይ” (See: Merism)
Deuteronomy 28:65
ለእግርህ መርገጫ እረፍት አይኖረውም
እዚህ ጋ “ለእግርህ መርገጫ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት: “የምታርፍበት ቋሚ ቤት ስለማይኖርህ ባለማቋረጥ ትቅበዘበዛለህ” (See: Synecdoche)
በዚያ እግዚአብሔር የሚንቀጠቀጥ ልብ፣ የሚደክም ዐይንና የሚያለቅስ ነፍስ ይሰጥሃል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “እግዚአብሔር እንድትፈራ፣ ተስፋ እንዳይኖርህና እንድታዝን ያደርግሃል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ሕይወትህ በፊትህ በጥርጣሬ ይንጠለጠላል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ትኖር ወይም ትሞት እንደሆነ አታውቅም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 28:67
በልብህ ካለው ፍርሀት የተነሣ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ከሚሰማህ ፍርሀት የተነሣ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ዐይኖችህ ከሚያዩአቸው ነገሮች የተነሣ
እዚህ ጋ “ዐይኖች” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት: “እንድታያቸው የማስገድድህን አስፈሪ ነገሮች” (See: Synecdoche and Assumed Knowledge and Implicit Information)
ተናግሬ ነበር
x

---

Chapter 29
Deuteronomy 29:1
እነዚህ ሙሴ እንዲናገር እግዚአብሔር ያዘዘው ቃሎች ናቸው
ይህ ሙሴ የሚናገረውን ቃል ያመለክታል።
በሞዓብ ምድር
ይህ እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር ከመግባታቸው በፊት ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ የቆዩበት ስፍራ ነው። “በሞዓብ ምድር እያሉ”
በኮሬብ -- በኪዳኑ ውስጥ ተጨምረው የነበሩት ቃላት
እነዚህ ተጨማሪ ትዕዛዛት በአዲሱ ምድራቸው በሚቀመጡበት ጊዜ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ኪዳን በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲያደርጉት የተሰጣቸው ነበር። እነዚህ አዲስ ትዕዛዛት የሌላ ቃል ኪዳን ሳይሆኑ በመጀመሪያው ኪዳን ላይ ተጨማሪዎች ነበሩ።
Deuteronomy 29:2
እግዚአብሔር በዐይኖቻችሁ ፊት ያደረገውን ሁሉ አይታችኋል
እግዚአብሔር ያደረገውንና እነርሱም ያዩትን እንዲያስታውሱ እግዚአብሔር ይጠብቅባቸዋል። እዚህ ጋ “ዐይኖች” ሙሉውን ሰው የሚወክሉ ሲሆኑ ሰውየው ባየው ነገር ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ያደረገውን እንድታዩና እንድታስታውሱ እርሱ ያደረገውን ሁሉ አይታችኋል። (See: Synecdoche)
ዐይኖቻችሁ ያዩአቸው ታላላቅ መከራዎች
እዚህ ጋ “ዐይኖች” ያዩትን እንዲያስታውሱ እግዚአብሔር እንደሚጠብቅባቸው አጽንዖት ይሰጣል። ኢ.ት: “ሕዝቡ በከፍተኛ ሁኔታ መሰቃየቱን እራሳችሁ አይታችኋል” (See: Synecdoche)
ዐይኖቻችሁ
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “የአንተ” የሚለው ቃል እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
ምልክቶቹንና እነዚያን ታላላቅ ድንቆች
“ምልክቶች” እና “ድንቆች” የሚሉት ቃላት ሁለቱም የሚያመለክቱት እግዚአብሔር በግብፅ ላይ የላካቸውን መቅሰፍቶች ነው። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ያደረጋቸውን ኃይለኛ ነገሮች ሁሉ” (See: Doublet)
እግዚአብሔር የሚያውቅ ልቦና፣ የሚያይ ዐይን ወይም የሚሰማ ጆሮ አልሰጣችሁም ነበር
ሕዝቡ ልብ፣ ዐይንና ጆሮ አላቸው። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ካዩትና ከሰሙት እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፣ እንዴት እና ለምን እርሱን መታዘዝ እንደሚኖርባቸው እንዲያስተውሉ አላደረጋቸውም ይላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እንድታውቁ ልብን ሰጥቷችኋል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ማስተዋል እንድትችሉ አድርጓችኋል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 29:7
የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎን እና የባሳን ንጉሥ ዐግ
እነዚህን ስሞች በዘዳግም 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
በእኛ ላይ መጡብን
እዚህ ጋ “በእኛ ላይ” የሚያመለክተው ሙሴንና የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (See: Inclusive “We”)
የዚህን ቃል ኪዳን ቃላት ጠብቁ፣ አድርጓቸውም
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መታዘዝ እንዳለባቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት: “የዚህን ቃል ኪዳን ቃሎች ሁሉ ታዘዙ” (See: Parallelism)
Deuteronomy 29:10


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በሰፈርህ ውስጥ በመካከልህ -- እንጨትህን -- ውሃህን

ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ’ እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥር ናቸው። (See: Forms of You)

በሰፍርህ ያሉ መጻተኞች፣ ከእርሱም እንጨት የሚቆርጡልህና ውሃ የሚቀዱልህ

በእስራኤላውያን መካከል ብዙ መጻተኞች ነበሩ። ኢ.ት: “በሰፈርህ ውስጥ በመካከልህ የሚኖሩ መጻተኞች፣ ከእነርሱ እንጨት የሚቆርጡልህ ውሃ የሚቀዱልህ” (See: Generic Noun Phrases)

Deuteronomy 29:12

አምላክህ እግዚአብሔር ዛሬ ከአንተ ጋር በመሓላ ወደሚያደርገው ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለመግባት

“በቃል ኪዳኑ ልትስማማ እና አምላክህ እግዚአብሔር የሚያዝህን ሁሉ ለመታዘዝ እንድትምል”

ለራሱ ሕዝብ

“ለእርሱ ብቻ የሚሆን የሕዝብ ወገን”

Deuteronomy 29:14

እኔ የማደርገውን

x

Deuteronomy 29:17

ዛሬ ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ልቡ የሚመለስ

እዚህ ጋ “ልብ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ሲሆን “መመለስ” ማለት መታዘዝን ማቆም ነው። ኢ.ት: “ከእንግዲህ አምላካችንን እግዚአብሔርን የማይታዘዝ” (See: Synecdoche)

የትኛውም መራራ መርዝ የሚያበቅል ሥር

ሙሴ በድብቅ ሌላ አምላክ ስለሚያመልክ ሰው ሲናገር እርሱን እንደ ሥር እና ያንን አምላክ ለማገልገል የሚሠራውን ክፉ ሥራና ሌሎችም እንዲያደርጉት የሚያበረታታውን ሰዎችን እንደሚመርዝ መራራ እጽዋት ቆጥሮ ይናገራል።(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ያ ሰው

በቁጥር 18 የተገለጸው ሰው ነው።

በልቡ ራሱን የሚባርክ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ራሱን እንኳን ደስ ያለህ የሚል” ወይም “ራሱን የሚያበረታታ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በልቤ ግትርነት ብመላለስም

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እምቢ እያልኩኝም እንኳን” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ይህ እርጥቡን ከደረቁ ጋር የሚያጠፋ ይሆናል

እዚህ ጋ “እርጥብ” እና “ደረቅ” የሚሉት ቃላት ጻድቅና ክፉ የሆኑትን ሰዎች የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። ይህ “እያንዳንዱን” የሚል ጥምረት ይፈጥራል። ኢ.ት: “ይህ እግዚአብሔር በምድሪቱ የሚኖሩትን ጻድቅና ክፉ የሆኑትን ሁለቱንም ዓይነት ሰዎች እንዲያጠፋቸው ያደርገዋል” (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Merism የሚለውን ተመልከት))

እርጥብ -- ደረቅ

እነዚህ ስማዊ ቅጽሎች እንደ ስም ሊተረጎሙ ይችላሉ። አብዛኛውን ጊዜ ምድሪቱ ደረቅ ስለምትሆንና ሰዎች ሰብላቸው እንዲበቅል ዝናብ ስለሚፈልጉ እነዚህ ቃላት “ሕያው - ምውት” ወይም “ጥሩ -- መጥፎ” ለሚሉት ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። ኢ.ት: “እርጥብ ነገሮች -- ደረቅ ነገሮች” ወይም “ጥሩ ሰዎች -- መጥፎ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 29:20

የእግዚአብሔር ቁጣና ቅንዓት ይነዳል

ልክ እሳት በኃይል እንደሚነድ የእግዚአብሔር ቁጣና ቅንዓትም በኃይል ሊነድ ይችላል። ኢ.ት: “የእግዚአብሔር የቅንዓቱ ቁጣ እንደ እሳት ይግላል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር ቁጣና ቅንዓቱ

እዚህ ጋ “ቅንዓት” የሚለው ቃል “የእግዚአብሔርን ቁጣ” ያብራራል። ኢ.ት: “የእግዚአብሔር የቅንዓቱ ቁጣ” (See: Hen- diadys)

የተጻፉትን

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እኔ የጻፍኩትን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በዚህ መጽሐፍ የተጻፉት እርግማኖች ይመጡበታል

ሙሴ እርግማኖቹን በድንገት በሚያጠቃቸው ሰው መስሎ ይገልጻቸዋል። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 28:15 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ስሙን ከሰማይ በታች ይደመስሰዋል

ይህ ማለት እግዚአብሔር ሰውየውንና ቤተሰቡን ፈጽሞ ያጠፋቸዋል። ወደፊት ሰዎች አያስታውሱትም። በዘዳግም 7:24 ላይ ተመሳሳይ ሐረግ ይታያል።

Deuteronomy 29:22

የሚመጣው ትውልድ፣ ከእናንተ በኋላ የሚነሡት ልጆቻችሁ

“ከእናንተ በኋላ -- ልጆቻችሁ” የሚሉት ቃላት “የሚመጣው ትውልድ” ማን መሆኑን ይናገራሉ።

በዚህች ምድር ላይ የሆኑት መቅሰፍቶችና እግዚአብሔር እንዲታመሙበት ያደረጋቸው በሽታዎች

“እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር በመቅሰፍትና በበሽታ እንዴት እንደረገማት”

ምድሩ ሁሉ ዲንና የሚቃጠል ጨው ሆነው በሚያዩበት ጊዜ

ሰዎች መሬቱ ምንም ነገር እንዳያበቅል ዲንና ጨው ያደርጉበታል። “እግዚአብሔር ምድሪቱን በዲንና በጨው እንዳቃጠላት በሚያዩበት ጊዜ”

ምንም ነገር የማይዘራበት ወይም ፍሬ የማያፈራበት ስፍራ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ማንም ዘር ሊዘራበት የማይችልበትና ሰብሉ ፍሬ የማያፈራበት ስፍራ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሰዶምና ገሞራ እንደ ተገለበጡ

“ተገለበጡ” የሚለው የነገር ስም እንደ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ፈጽሞ እንዳጠፋቸው ጊዜ”

አዳማ እና ሲባዮ

እነዚህ እግዚአብሔር ከሰዶምና ገሞራ ጋር ያጠፋቸው ከተሞች ስሞቻቸው ናቸው።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በንዴቱና በመዓቱ

የነገር ስም የሆኑት “ንዴት” እና “ቁጣ” በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ነው፣ በመሆኑም እንደ ቅጽላዊ ሐረግ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “በጣም በተቆጣ ጊዜ” (See: Doublet)

ከሌሎች ሀገሮች ሁሉ ጋር በመሆን --ምንድነው? በማለት ይናገራሉ

ይህ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ከሌሎች ሀገራት ሁሉ ጋር በመሆን እግዚአብሕር በምድሪቱ ላይ ይህንን ለምን እንዳደረገና ይህ የቁጣው ግለትስ ትርጉሙ ምንድነው በማለት ይጠይቃሉ” (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)

ከሌሎች ሀገሮች ሁሉ ጋር በመሆን -- ይናገራሉ

“ዘሮቻችሁና የሌሎች ሀገራ ሰዎች ሁሉ -- ይላሉ”

ይህ የታላቅ ቁጣ ግለት ትርጉሙ ምንድነው?

ጸሐፊው በሁለት ቃላት አማካይነት የሚያስተላልፈው አንድ አሳብ ነው። ኢ.ት: “የዚህ አስፈሪ ቁጣ ትርጉሙ ምንድነው?” (See: Hendiadys)

Deuteronomy 29:25

የአባቶቻቸውን አምላክ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ስለተዉ ነው

ይህ “እግዚአብሔር በዚህች ምድር ላይ ይህንን ያደረገው ለምንድነው?” ለሚለው መልስ ነው (ዘዳግም 29:24)። “እስራኤላውያን የቃል ኪዳኑን ተሰፋና ሕግ ስላልተከተሉ እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ ይህንን አድርጓል”

ሌሎች አማልክትን አገለገሉ፣ ሰገዱላቸውም

“ሌሎች አማልክትን ታዘዙ፣ አመለኳቸውም”

Deuteronomy 29:27

የእግዚአብሔር ቁጣ በዚህች ምድር ላይ ነዷል

ሙሴ የእግዚአብሔርን መቆጣት ከአንድ እሳት ከሚለኩስ ሰው ጋር ያነጻጽራል። ይህ እግዚአብሔር እርሱን የሚያስቆጣውን የትኛውንም ነገር ስለሚያጠፋበት ኃይሉ አጽንዖት ይሰጣል፤ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር አይችልም። ኢ.ት: “እግዚአብሔር በዚህች ምድር ላይ በጣም ተቆጥቷል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በዚህች ምድር ላይ እንዲያመጣባት

እዚህ ጋ “ምድር” ሕዝቡን የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “ያመጣባቸው ዘንድ የዚህ ምድር ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የተጻፉትን

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እኔ የጻፍኩትን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ከምድራቸው ነቅሏቸዋል -- ጥሎአቸዋል
እስራኤል እግዚአብሔር ከአትክልት ስፍራ ነቅሎ ከጣለው መጥፎ ተክል ጋር ተነጻጽሯል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ከምድራቸው አስወግዷቸዋል -- እንዲሄዱም አስገድዷቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በንዴት፣ በቁጣና በታላቅ መዓት
በመሠረቱ “ንዴት”፣ “ቁጣ” እና “መዓት” የሚሉት ቃላት ትርጉማቸው ተመሳሳይ ሲሆን በእግዚአብሔር ቁጣ ታላቅነት ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት፡ “እጅግ ታላቅ በሆነ ቁጣው” ወይም “እጅግ ስለተቆጣ” (See: Doublet)
Deuteronomy 29:29
ምስጢር የሆኑት ነገሮች የአምላካችን የእግዚአብሔር ብቻ ናቸው
“አምላካችን እግዚአብሔር ያልገለጣቸውና እርሱ ብቻ የሚያውቃቸው አንዳንድ ነገሮች”
የተገለጡት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እርሱ የገለጣቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የዚህን ሕግ ቃሎች በሙሉ እንድናደርጋቸው
x

---

Chapter 30
Deuteronomy 30:1
እነዚህ ነገሮች ሁሉ በመጡብህ ጊዜ
እዚህ ጋ “እነዚህ ነገሮች” የሚያመለክቱት በምዕራፍ 28 – 29 የተዘረዘሩትን በረከቶችና እርግማኖች ነው። “በመጡብህ” የሚለው ቃል የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙ ሲደርስብህ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “እነዚህ ነገሮች ሁሉ በሚደርሱብህ ጊዜ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በፊትህ ያስቀመጥኩት
ይህ በፊት ለፊታቸው ያስቀመጠው ዕቃ ይመስል መልኩ ሙሴ ለሕዝቡ ስለ ነገራቸው በረከቶችና እርግማኖች ይናገራል። ኢ.ት፡ “አሁን ስለነገርኳችሁ ጉዳይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ትዝ ይበሉህ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “አስታውሳቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በሌሎች ሕዝቦች ሁሉ መካከል
“በሌሎች ሕዝቦች ውስጥ በምትኖርበት ጊዜ”
አውጥቶሃል
“እንድትሄድ አስገድዶሃል”
ድምፁን ታዘዘው
እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሚናገረውን ነው። ኢ.ት፡ “እርሱ የሚለውን ታዘዝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ
እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በአንድ ላይ “ፍጹም” ወይም “በቅንነት” ለማለት ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:29 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)
ምርኮኝነትህን ይቀይረዋል
“ከምርኮኝነት ነጻ ያወጣሃል”። የነገር ስም የሆነው “ምርኮኝነት” እንደ ግሳዊ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ከማረኩህ ከእነርሱ ነጻ ያወጣሃል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 30:4
ከተማረኩት ሰዎችህ ማናቸውም እጅግ ሩቅ ስፍራ ላይ ቢሆኑ
“እነዚያ የተማረኩት ሰዎችህ እጅግ ሩቅ በሆነ ስፍራ የሚኖሩ ቢሆኑም እንኳን”
ከሰማያት በታች
“ከጠፈር በታች” ወይም “በምድር ላይ”
Deuteronomy 30:6
ልብህን ይገርዛል
ይህ በቀጥታ ሥጋን ማስወገድ አይደለም። ይህ ማለት እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ያስወግዳል፣ እርሱን እንዲወዱትና እንዲታዘዙትም ያስችላቸዋል ማለት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ
እዚህ ጋ “ልብ” እና “ነፍስ” የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በአንድ ላይ “ፍጹም” ወይም “በቅንነት” ለማለት ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:29 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔርን ድምፅ ታዘዝ
እዚህ ጋ “ድምፅ” ማለት እግዚአብሔር የሚናገረውን ማለት ነው። ኢ.ት፡
“እግዚአብሔር የሚናገረውን ታዘዝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እነዚህን እርግማኖች ሁሉ በጠላቶችህ ላይ ያደርጋል
ሙሴ እርግማኖቹን አንድ ሰው በሌላው አናት ላይ ሊያደርግ እንደሚችለው ሸክም ወይም መሸፈኛ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ጠላቶችህ በእነዚህ እርግማኖች ምክንያት እንዲሰቃዩ ያደርጋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 30:9
የእጅህን ሥራ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “በምትሠራው ሥራ ሁሉ” (See: Synecdoche)
በሰውነትህ ፍሬ -- በከብቶችህ ፍሬ -- በመሬትህ ፍሬ
እነዚህ ሦስት ሐረጎች “በልጆች -- በጥጆች -- በሰብሎች” ለሚለው የአነጋገር ዘይቤ ናቸው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 28፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
Deuteronomy 30:11
ትደርስበት ዘንድ ለአንተ እጅግ ሩቅ አይደለም
አንድ ሰው ቁሳዊ አካል ላይ ሊደርስ እንደሚችል ሁሉ ትዕዛዛቱ አንድ ሰው እንዲያደርግ የሚፈልገውን ከትዕዛዛቱ መረዳት እንደሚቻል ሙሴ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር እንድታደርግ የሚፈልግብህን ለመረዳት በጣም አስቸጋሪ አይሆንብህም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እናደርገው ዘንድ እንድንሰማው ማን ወደ ሰማይ ወጥቶ ያወርድልናል?
እዚህ ጋ ሙሴ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄን በመጠቀም የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው ማሰባቸው ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ይህ ጥያቄ እንደ ንግግር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለመማር ወደ ሰማይ መጓዝ አለበት፣ ከዚያም ልንታዘዛቸው እንችል ዘንድ ምን እንደ ሆኑ ሊነግረን መመለስ አለበት” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 30:13
እናደርገው ዘንድ ልንሰማው ማን ባህሩን ተሻግሮ ያምጣልን?
ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው ብለው የሚያስቡበትን አሳብ ይቀጥላል። ይህ ጥያቄ እንደ ንግግር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለመማር አንድ ሰው ባህሩን አቋርጦ መጓዝ ከዚያም ተመልሶ ምን እንደሆኑ ሊነግረን ያስፈልጋል” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
በአፍህና በልብህ
ይህ ማለት ሕዝቡ ቀደሞውኑ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ያውቃሉ፣ ለሌሎችም ሊነግሯቸው ይችላሉ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 30:15
በፊትህ አስቀምጫለሁ
አንድን ነገር ሌላው ሰው ሊያይ በሚችልበት ማስቀመጥ ስለ አንድ ነገር ለአንድ ሰው የመንገር ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ስለ ጉዳዩ ነግሬሃለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሕይወትንና መልካምን፣ ሞትንና ክፉን
ግልጽ ያልሆነውን መረጃ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ኢ.ት፡ “መልካም የሆነውንና በሕይወት እንድትኖር የሚያደርግህን፣ ክፉ የሆነውንና እንድትሞት የሚያደርግህን” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
መብዛት
በቁጥር እጅግ መጨመር
Deuteronomy 30:17


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ልብህ ቢመለስ -- ይልቁንም ቢማረክና ለሌሎች አማልክት ቢሰግድና ቢያመልካቸው
እዚህ ጋ “ልብ” የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ለእግዚአብሔር ያለህን ታማኝነት ብታቆም -- እና በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎች እንድትሰግድና ሌሎች አማልክትን እንድታመልክ ቢያባብሉህ” (Synecdoche እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ዛሬ ለአንተ -- ቀኖችህ እንደማይረዝሙ
x
Deuteronomy 30:19
ሰማይና ምድርን ምስክር እንዲሆኑ እጠራለሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሙሴ ለሚናገረው ምስክሮች እንዲሆኑ በሰማይና በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ይጠራል ወይም 2) ሙሴ እንደ ሰዎች ቆጥሯቸው ለሰማይና ለምድር ይናገራል፤ እርሱ ለሚናገረው ምስክሮች እንዲሆኑም ይጠራቸዋል። (See: (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት and Personification and Apostrophe)
በአንተ ላይ ምስክር እንዲሆኑ
“ክፉ ነገሮችን ስለማድረግህ ለመናገር ፈቃደኛ እንዲሆን”
ዛሬ በአንተ ላይ
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ ቡድን አድርጎ ይናገራል። (See: Forms of You)
ድምፁን ታዘዝ
እዚህ ጋ “ድምፅ” እግዚአብሔር የሚናገረውን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “እርሱ የሚለውን ታዘዝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከእርሱ ጋር እንድትጣበቅ
“በእርሱ ላይ እንድትተማመን”
እርሱ ሕይወትህና የቀኖችህ ርዝመት ነውና
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸውና እግዚአብሔርን የሚገልጹ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ሲሆኑ ሕይወትን የሚሰጥና የሰዎችን የሕይወት ዘመን የሚወስን እርሱ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት፡ “ረጅም ሕይወት እንድትኖር የሚያስችልህ እግዚአብሔር ብቻ ነው” (Doublet እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለአባቶቻችሁ የማለውን
ሞላላው ሊሞላ ይችላል። ኢ.ት፡ “ለአባቶቻችሁ ሊሰጣችሁ ምሏል” (See: Ellipsis)

---

Chapter 31
Deuteronomy 31:1
የአንድ መቶ ሃያ ዓመት ዕድሜ
“120 ዓመት ዕድሜ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ከእንግዲህ መውጣትና መግባት አልችልም
እዚህ ጋ “መውጣት” እና “መግባት” የተሰኙ ሁለት ጽንፎች በአንድ ላይ አንድ ጤነኛ ሰው ሊያደርግ የሚችለውን ሙሴ ከእንግዲህ ማድረግ አይችልም ማለት ነው። (See: Merism)
አምላክህ -- በፊትህ -- በፊትህ -- ታስወጣቸዋለህ -- በፊትህ
ሙሴ እስራኤላውያኑን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)
ታስወጣቸዋለህ
“ምድራቸውን ትወስዳለህ”
እግዚአብሔር እንደተናገረው ኢያሱ በፊታችሁ ይሄዳል
“እግዚአብሔር ቃል እንደገባው ኢያሱ መርቶ ወንዙን ያሻግራችኋል”
Deuteronomy 31:4
በአሞራውያን ነገሥታት በሴዎንና በዐግ -- አደረገ
እዚህ ጋ “ሴዎን” እና “ዐግ” ሁለቱን የአሞራውያንን ነገሥታትና ሰራዊታቸውን ያመለክታል። እነዚህን ስሞች በዘዳግም 1፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት፡ “በአሞራውያን ነገሥታት በሴዎን፣ በዐግና በሰራዊቶቻቸው ላይ -- አደረገ” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 31:7
በእስራኤል ሁሉ ፊት
ይህ ማለት የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ በዚያ ነበሩ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “በእስራኤላውያን ሁሉ ፊት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ብርቱ ሁን፣ ድፍረትም ይኑርህ
“ብርቱና ደፋር ሁን”። ይህንን በዘዳግም 31፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
እንዲወርሱት ታደርጋቸዋለህ
“ምድሪቱን እንዲወስዱ ትረዳቸዋለህ”
Deuteronomy 31:9
ለሌዊ ልጆች ለካህናቱ ሰጣቸው
“ካህናት ለሆኑት ለሌዋውያኑ ሰጣቸው”
ሰባት ዓመት
“7 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ዕዳን ለመተው የተወሰነበት
“ዕዳን ለመሰረዝ”
የመጠለያ በዓል
የዚህ በዓል ሌሎች ስሞች፣ “የመገናኛው ድንኳን በዓል”፣ “የዳስ በዓል”፣ እና “የመሰብሰብ በዓል”። በመከር ጊዜ ገበሬዎች በመስኩ ላይ ጊዜያዊ መጠለያ ይሠሩ ነበር። ይህ በዓል የሚደረገው የዓመቱ መከር ከተሰበሰበ በኋላ ነበር። ይህንን በዘዳግም 16፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
አምላክህ እግዚአብሔር -- ታነበዋለህ
ሙሴ እስራኤላውያኑን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚለው ቃል እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
በመስሚያቸው
“መስማት ይችሉ ዘንድ”
Deuteronomy 31:14
ተመልከት
“እኔ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ”
የደመና ዓምድ
ይህ በላይኛው ክፍል ቅርጽ የያዘ ጥቅጥቅ ያለ የጢስ ደመና ነበር
Deuteronomy 31:16
ተመልከት
“እኔ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ”
ከአባቶችህ ጋር ታንቀላፋለህ
ይህ “ትሞታለህ” የማለት የትህትና አገላለጽ ነው። ኢ.ት፡ “ትሞትና ከአንተ በፊት ከሞቱት ቅድመ ቅድም አያቶችህ ጋር አብረህ ትሆናለህ” (See: Euphemism)
ተነሥተው የአመንዝራን ተግባር ይፈጽማሉ
አመንዝራ መሆን ከእግዚአብሔር ሌላ ሌሎች አማልክትን ለማምለካቸው ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ለእኔ አለመታመን ይጀምራሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 31:17
ቁጣዬ በእነርሱ ላይ ይነድዳል
እግዚአብሔር ቁጣውን እሳት ከሚለኩስ ሰው ጋር ያነጻጽራል። ይህ እርሱን የሚያስቆጣውን የትኛውንም ነገር በሚያጠፋ በእግዚአብሔር ኃይል ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ቁጣዬን በእነርሱ ላይ አነድዳለሁ” ወይም “በእነርሱ ላይ እቆጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ፊቴን ከእነርሱ እደብቃለሁ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “አልረዳቸውም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ይዋጣሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እውጣቸዋለሁ” ወይም “ጠላቶቻቸው እንዲውጡአቸው እፈቅድላቸዋለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ተዋጡ
ይህ “ፈጽመው ጠፉ” ለሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ብዙ ጥፋትና መከራ ያገኛቸዋል
ይህ ጥፋቱንና መከራውን እንደ ሰው መስሎ ይገልጻቸዋል። ኢ.ት፡ “ብዙ ጥፋትና መከራ ይደርስባቸዋል” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
-- መካከል እነዚህ ጥፋቶች የመጡብን?

ይህ ጥፋቱንና መከራውን እንደ ሰው መስሎ ይገልጻቸዋል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: "-- መካከል እነዚህ ጥፋቶች እያጠፉኝ ነው" (ሰውኛ እና ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አምላካችን በመካከላችን አይደለም

"ከእንግዲህ እግዚአብሔር እየጠበቀን አይደለም" ወይም "እግዚአብሔር ለብቻችን ትቶናል"

Deuteronomy 31:19

በአፋቸው አኑረው

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: "እንዲያስላስሉትና እንዲዘምሩት አድርጋቸው" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ወተትና ማር የምታፈሰውን ምድር

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: "ብዙ ወተትና ማር የሚፈስባት ምድር" ወይም "ከብት ለማርባትና ለእርሻ ምርጥ የሆነች ምድር" ይህንን በዘዳግም 6:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 31:21

በዚህ ሕዝብ ላይ ብዙ ክፋትና መከራ በመጣባቸው ጊዜ

እዚህ ጋ ክፋትና መከራ ሰብዓዊ ፍጥረት ሆነው ሰዎችን ሊያገኙ የሚችሉ መስለው ተገልጸዋል። ኢ.ት: "ይህ ሕዝብ ብዙ ክፋትና መከራ በሚገጥመው ጊዜ" (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ይህ መዝሙር በፊታቸው እንደ ምስክር ሆኖ ይመሰክርባቸዋል

መዝሙሩ እንደ ሰብዓዊ ፍጥረት ሆኖ በፍርድ ቤት ውስጥ በእስራኤል ላይ እንደሚመሰክር ይናገራል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ በዘሮቻቸው አፍ የሚረሳ አይሆንም

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "ዘሮቻቸው በአፋቸው ውስጥ መጠበቃቸውን አይረሱም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ በዘሮቻቸው አፍ የሚረሳ አይሆንም

ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "ዘሮቻቸው በአፋቸው ውስጥ መጠበቅ እንዳለባቸው ያስታውሳሉ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ በዘሮቻቸው አፍ የሚረሳ አይሆንም

"በአፋቸው መርሳት" የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ስለ እርሱ መናገርን ማቆም ማለት ነው። ኢ.ት: "ዘሮቻቸው ለእርስ በእርሳቸው ስለ እርሱ ከመናገር አያቆሙም"

የሚሠሩትን ዕቅድ

ሰዎች ለማድረግ የሚያቅዱት እርሱ እንደ አካላዊ ቁስ ተደርጎ ተነግሮለታል። ኢ.ት: "ለማድረግ የሚያቅዱት" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተስፋ የሰጠኋችሁ ምድር

እግዚአብሔር ስለምድሪቱ የሰጠው ተስፋ ለእስራኤል ሕዝብ እንደሚሰጣቸው ነበር። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "እሰጣቸዋለሁ ብዬ ተስፋ የሰጠኋቸው ምድር" (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Deuteronomy 31:22

ብርቱ ሁን፣ ድፍረትም ይኑርህ

"ብርቱና ደፋር ሁን" ይህንን በዘዳግም 31:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Deuteronomy 31:24

በአንተ ላይ ምስክር

ሙሴ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለሌዋውያን ይናገራል፣ ስለዚህ "አንተ" የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

Deuteronomy 31:27

አመጸኛና አንገተ ደንዳና ሕዝብህ

ሙሴ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለሌዋውያን ይናገራል፣ ስለዚህ "አንተ" የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)

የአንተ አንገተ ደንዳና

በዘዳግም 9:6 ላይ "እልኸኛ" የሚለውን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከሞትኩኝ በኋላ ይልቁን እንዴት?

ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ ሕዝቡ እንዴት ያሉ አመጸኞች እንደነበሩ አጽንዖት ይሰጣል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: "እኔ ከሞትኩኝ በኋላ እንኳን በይበልጥ አመጸኛ ትሆናላችሁ" (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እነዚህን ቃላት በጆሮአቸው እንድናገር

እዚህ ጋ "በጆሮአቸው" ማለት ሕዝቡን ራሳችውን ማለት ነው። ኢ.ት: "የዚህ መዝሙር ቃሎች አነግራቸው ዘንድ" (See: Synecdoche)

በእነርሱ ላይ ምስክር እንዲሆኑ ሰማይና ምድርን እጠራለሁ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሙሴ ለሚናገረው ምስክሮች እንዲሆኑ በሰማይና በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ይጠራል ወይም 2) ሙሴ እንደ ሰዎች ቆጥሯቸው ለሰማይና ለምድር ይናገራል፣ እርሱ ለሚናገረው ምስክሮች እንዲሆኑም ይጠራቸዋል። ተመሳሳይ ሐረግ በዘዳግም 30:19 ላይ ይታያል።

ፈጽሞ ራሳችሁን ታረክሳላችሁ

"ሙሉ በሙሉ ስሕተት የሆነውን ታደርጋላችሁ"። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት፡

እኔ ካዘዝኳችሁ መንገድ ዘወር ትላላችሁ

"የሰጠኋችሁን መመሪያ መከተል ታቆማላችሁ"። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 9:12 እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን

የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው የእግዚአብሔርን ውሳኔ ወይም ምዘና ነው። ኢ.ት: "በእግዚአብሔር ውሳኔ ክፉ የሆነ" ወይም "እግዚአብሔር ክፉ ነው ብሎ የሚቆጥረውን" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእጆቻችሁ ሥራ አማካይነት

እዚህ ጋ "እጆቻችሁ" ማለት ሕዝቡን ራሳቸውን ማለት ነው። ኢ.ት: "በሠራችሁት ሥራ ምክንያት" (See: Synec- doche)

Deuteronomy 31:30

ሙሴ በእስራኤል ጉባዔ ጆሮዎች ሁሉ አሰማ

እዚህ ጋ "ጆሮዎች" የሚያመለክቱት ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት: "ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ አሰማቸው" (See: Synec- doche)

አሰማ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ዘመረ" ወይም 2) "ተናገረ"

የዚህን መዝሙር ቃላት

በውስጠ ታዋቂነት ያለውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ኢ.ት: "እግዚአብሔር እርሱን ያስተማረበትን የመዝሙሩን ቃላት" (See: Ellipsis)

---

Chapter 32

Deuteronomy 32:1

እናንተ ሰማያት ጆሮአችሁን ስጡ -- ምድርም ትስማ

እዚያ ሆነው ይሰሙ ይመስል እግዚአብሔር ለሰማያትና ለምድር ይናገራል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር የሚናገረው በሰማይና በምድር ለሚኖሩት ነው፤ ወይም 2) እግዚአብሔር እንደ ሰው ቆጥሯቸው ለሰማይና ለምድር ይናገራል። (See: Apostrophe)

ትምህርቴ እንደ ዝናብ ይንጠባጠብ፣ በተክሎች ላይ እንደጎርፍ

ይህ ማለት የእርሱን ጠቃሚ ትምህርት ሕዝቡ በትጋት እንዲቀበሉ እግዚአብሔር ይፈልጋል። (See: Simile)

የተጣራ

ጤዛ የሚታይበትን ሂደት የሚገልጽ ቃል በራስህ ቋንቋ ተጠቀም።

ጠል

ቅዝቃዜ ባለበት ጠዋት በቅጠሎችና በሣር ላይ የሚገኝ ውሃ

ለጋ ሣር

"አዲስ ተክሎች"

መጉረፍ

ከባድ ዝናብ

Deuteronomy 32:3

የእግዚአብሔርን ስም ዐውጅ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: "እግዚአብሔር መልካም መሆኑን ተናገር" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የአምላካችንን ታላቅነት አሳስቡ

"አምላካችን ታላቅ መሆኑን ሰዎች ማወቃቸውን አረጋግጡ"

ዐለቱ

ይህ እንደ ዐለት ብርቱ እና ሕዝቡን መጠበቅ ለሚችለው ለእግዚአብሔር ሙሴ የሰጠው የተፀውዖ ስም ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሥራው

"እርሱ የሚያደርገው ሁሉ"



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መንገዶቹ ሁሉ ትክክል ናቸው

መንገድ ላይ መራመድ አንድ ሰው ሕይወቱን እንዴት እንደሚኖረው የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ሁሉንም ነገር በትክክለኛ መንገድ አድርጓል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እርሱ ትክክለኛና ቀጥተኛ ነው

እነዚህ ሁለት ቃላት በመሠረቱ የሚሉት አንድ ነገር ሆኖ እግዚአብሔር ፍትሐዊና ትክክለኛውን ነገር እንዳደረገ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)

Deuteronomy 32:5

በእርሱ ላይ በእርኩሰት አድርገዋል

“ትክክል ያልሆነን ነገር በማድረግ ተቃወሙት”። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ወልጋዳና ጠማማ ትውልድ

“ወልጋዳ” እና “ጠማማ” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ነው። ሙሴ ትውልዱ ምን ያህል ክፉ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ይጠቀምባቸዋል። ኢ.ት፡ “ፈጽሞ ክፉ የሆነ ትውልድ” (See: Doublet)

-ሕዝብ ለእግዚአብሔር በዚህ መንገድ ትመልስለታለህ?

ሙሴ ሕዝቡን ለመገሰጽ ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። ኢ.ት፡ “-ሕዝብ፣ ለእግዚአብሔር ተገቢውን ምስጋና ማቅረብ አለባችሁ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

አንተ ሞኝና የማትረባ ሕዝብ

“ሞኝ” እና “የማትረባ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው ምን ያህል ሞኞች እንደሆኑ አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት፡ “እጅግ ሞኞች የሆናችሁ ሰዎች” (See: Doublet)

አባትህ -- ፈጥሮሃል -- ሠርቶሃል፣ አጽንቶሃል

ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥሮች ናቸው።

የፈጠረህ አባትህ አይደለምን?

ሙሴ ሕዝቡን ለመገሰጽ በጥያቄ መልክ ይጠቀማል። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር የፈጠረህ አባትህ ነው” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:7

ትዝ ይበልህ -- አስብ -- አባትህ -- ያሳዩሃል -- ሽማግሌዎችህ -- ይነግሩሃል

ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)

ትዝ ይበልህ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “አስታውስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የጥንቱን ዘመን

“ከረጅም ዓመታት በፊት”። ሙሴ፣ የእስራኤል ቅድመ ቅድም አያቶች ይኖሩ የነበሩበትን ጊዜ ያመለክታል።

ከብዙ ዓመታት በፊት ስለነበረው ጊዜ አስብ

ይህ ቀደም ሲል በነበረው ክፍል ሙሴ ተናግሮት የነበረው ድጋሚ ነው። ሙሴ የእስራኤል ሕዝብ እንደ ሕዝብ በታሪካቸው ላይ እንዲያተኩሩ ይፈልጋል። (See: Parallelism)

ያሳይሃል

“ግልጽ ያደርግልሃል” ወይም “እንድታስተውለው ያስችልሃል”

ለሕዝቡ ርስታቸውን ሰጣቸው

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ሕዝቡ ሊኖሩ በሚገባቸው ስፍራ ላይ አስቀመጣቸው”። “ርስት አድርጎ ወደሚሰጣችሁ” የሚሉ ተመሳሳይ ቃላት በዘዳግም 4:21 ላይ ይታያሉ። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ደግሞም የአማልክታቸውን ቁጥር በሚወስኑበት ጊዜ ለሕዝቦች ድንበሮችን አደረገላቸው

እግዚአብሔር እያንዳንዱን የሕዝብ ወገን ከአማልክቱ ጋር በራሱ ግዛት እንዲኖር ወስኗል። በዚህ መንገድ የሕዝብ ወገኖችን ጣዖታት ተጽዕኖ ገድቧል።

Deuteronomy 32:9

የእግዚአብሔር ድርሻው ሕዝቡ ነውና፤ ያዕቆብ የርስቱ ዕድል ፈንታው ነው

እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት በመሠረቱ አንድ ነገር ነው፣ ስለሆነም ሊጣመሩ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “የያዕቆብ ዘሮች የእግዚአብሔር ርስት ናቸው” (See: Parallelism)

አገኘው -- ጋረደውና ተጠነቀቀለት -- ጠበቀው

“ያዕቆብን አገኘው -- ጋረደውና ተጠነቀቀለት -- ጠበቀው”። ይህንን ምናልባት ሙሴ እንደ ብዙ ሕዝብ አድርጎ የሚናገረው ስለ እስራኤላውያን እንደሆነ መተርጎም ያስፈልግህ ይሆናል። ኢ.ት፡ “ቅድመ ቅድም አያቶቻችንን አገኛቸው -- ጋረዳቸውና ተጠነቀቀላቸው -- ጠበቃቸው”

ጭው ባለ ምድረ በዳ

እዚህ ጋ “ጭው ያለ” የሚያመለክተው ባዶ መሬት ላይ ነፋሱ ሲነፍስ የሚያሰማውን ድምፅ ነው።

እንደ ዐይኑ ብሌን ጠበቀው

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። የዐይን ብሌን የሚያመለክተው አንድ ሰው ለማየት የሚያስችለውን በዐይኑ ኳስ ውስጥ ያለውን ጥቁሩን ክፍል ነው። ይህ በጣም አስፈላጊና ጥንቃቄ የሚፈልግ የሰውነት ክፍል ነው። ይህ ማለት የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊና እርሱ ጥበቃ የሚያደርግለትም ነው። ኢ.ት፡ “በጣም ዋጋ እንዳለውና ውድ ነገር ጠብቆታል”(የአነጋገር ዘይቤ እና Simile የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:11

ንስር ጎጆዋን እንደምትጠብቅና በጫጩቶችዋ ላይ እንደምትሰፍፍ እግዚአብሔር ክንፎቹን ዘርግቶ ወሰዳቸው፣ በላባዎቹም ተሸከማቸው

ይህ ማለት እስራኤላውያን በበረሃ እያሉ እግዚአብሔር ጠብቋቸዋል፣ ተከላክሎላቸዋልም። (See: Simile)

ላባዎች

የወፍ የክንፉ ውጫዊ ጫፍ

መራው -- ከእርሱ ጋር

ሙሴ እንደገና እስራኤላውያንን “ያዕቆብ” በማለት ይናገራል (ዘዳግም 32:9-10)። ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ ብዙ ሕዝብ አድርጎ እንደተናገራቸው መተርጎም ያስፈልግህ ይሆናል። ኢ.ት፡ “መራቸው -- ከእነርሱ ጋር”

Deuteronomy 32:13

በምድሪቱ የከፍታ ስፍራ ላይ አስኬደው

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። “እርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር በምድሪቱ የከፍታ ስፍራዎች ላይ አስኪዷቸዋል” ወይም “ምድሪቱን እንዲወስዱና እንዲሰፍሩባት እግዚአብሔር ረድቶአቸዋል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አስኬደው -- መገበው -- አጠገበው

ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ “ያዕቆብ” በመቁጠር መናገሩን ይቀጥላል (ዘዳግም 32:9-10)። ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ ብዙ ሕዝብ አድርጎ እንደተናገራቸው መተርጎም ያስፈልግህ ይሆናል። “አባቶቻችንን እንዲሄዱ አደረጋቸው -- መገባቸው -- አጠገባቸው” (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)

የእርሻውን ፍሬ መገባቸው

“የሚበላው ብዙ ሰብል ወዳለበት ምድር አመጣው”

ከዐለቱ በሚወጣ ማርና ከባልጩታማ ቋጥኝ በሚገኝ ዘይት አጠገበው

ምድሪቱ በዐለት ቀዳዳዎች ውስጥ ማር የሚሠሩ ብዙ የጫካ ንቦች ነበሯት። በተጨማሪም፣ በዐለቶች፣ በኮረብቶችና በተራራዎች ላይ የሚበቅሉ ዘይት የሚሰጡ ብዙ የወይራ ዛፎች ነበሩ።

በማር አጠገበው

ይህ ልክ እናት ለሕፃን ልጇ ጡቷን እንደምትሰጠው ዓይነት ነው። “ማር እንዲጠባ ፈቀደለት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Deuteronomy 32:15

ይሹሩን

ሙሴ በሚገባ እንደ ተቀለበና ባለቤቱ ይሹሩን ብሎ እንደሰየመው እንስሳ ስለ እስራኤላውያን ይናገራል። “ ’ይሹሩን’ ማለት ‘ቀጥተኛ የሆነ’ ማለት ነው” የሚል የግርጌ ማስታወሻ ልትጨምርበት ትችላለህ። የአንተ ቋንቋ እስራኤላውያንን እንደ ይሹሩን የማይገልጻቸው ከሆነ የተከፈተው ተለዋዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንደሚያደርገው እስራኤላውያንን እንደ ብዙ ሕዝብ ማመልከት ትችላለህ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

መሰባቱን ቀጠለ፣ ረገጠም

በሚገባ የተቀለበው እንስሳ፣ ገር ከመሆን ይልቅ የሚራገጠው ይሹሩን እግዚአብሔር ቢንከባከባቸውም እንኳን ያመጹትን እስራኤላውያንን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መሰባትህን ቀጠልክ፣ በጣም ሰብተህ ነበር፣ ፍጆታህን በልተህ ነበር

ሙሴ ለይሹሩን በሚዘምረው መዝሙር እስራኤላውያንን ይገስጻቸዋል። “ሰባችሁ፣



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በጣምም ሰባችሁ፣ የሚቻላችሁን ያህልም ሰባችሁ”
የድነቱን ዐለት
ይህ ማለት እግዚአብሔር እንደ ዐለት ብርቱ ነው፣ ሕዝቡን ለመጠበቅም ይችላል ማለት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዐለቱ
ይህ ሙሴ ለእግዚአብሔር የሚሰጠው የተጸውዖ ስም እንደ ዐለት ብርቱና ሕዝቡን ለመጠበቅ የሚችል ነው። ይህንን በዘዳግም 32፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔርን አስቀኑት
እስራኤላውያን እግዚአብሔርን አስቀኑት።
Deuteronomy 32:17
ሠዉ
“የእስራኤል ሕዝብ ሠዉ”
በቅርቡ የመጡትን አማልክት
ይህ ማለት እስራኤላውያን ስለ እነዚህ አማልክት የተማሩት በቅርቡ ነው።
አባቶችህ
ሙሴ ለእስራኤላውያን እንደ ብዙ ሰው ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “የአንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
አባትህን -- ትተሃል -- ረስተሃል -- ሰጥቶሃል
ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” እና “የአንተ” የሚልበት አገባብ ሁሉ ብዙ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
ዐለቱን ትተሃል
እዚህ ጋ እግዚአብሔር ብርቱና መከላከያ ስለሆነ ዐለት ተብሎ ተጠርቷል። ኢ.ት: “የእግዚአብሔርን የመከላከል ክብካቤ ትተሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዐለቱ
ይህ ሙሴ ለእግዚአብሔር የሚሰጠው የተጸውዖ ስም እንደ ዐለት ብርቱና ሕዝቡን ለመጠበቅ የሚችል ነው። ይህንን በዘዳግም 32፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አባትህ የሆነውን -- ልጅ የሰጠህን
ይህ እግዚአብሔርን ከአባትና ከእናት ጋር ያነጻጽራል። ይኸውም፣ እግዚአብሔር በሕይወት እንዲኖሩና ሕዝብ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል ማለት ነው። ኢ.ት: “አባት ያደረጋችሁ … ሕይወትን የሰጣችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 32:19
ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ
ይህ እግዚአብሔር ሕይወትን የሰጣቸውንና ሕዝብ ያደረጋቸውን የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ፊቴን ከእነርሱ እደብቃለሁ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ከእነርሱ እርቃለሁ” ወይም “እነርሱን መርዳቴን አቆማለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
መጨረሻቸው ምን እንደሚሆን አያለሁ
“የሚደርስባቸውን አያለሁ”
Deuteronomy 32:21
እኔን አስቀንተውኛል
እዚህ ጋ “እኔን” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።
አምላክ ያልሆነውን
“ሐሰተኞች አማልክትን”
የማይጠቅሙ ነገሮች
“ነገሮች” ምን እንደሆኑ ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። ኢ.ት: “የማይጠቅሙ ጣዖታት” (See: Assumed Knowl- edge and Implicit Information)
እነዚያን ሕዝብ ያልሆኑትን
“የአንድ ሕዝብ ወገን ያልሆኑ ሰዎች”
ሞኝ ሕዝብ
“ሞኝ” የሚለውን በዘዳግም 32፡6 እንዳለው አድርገህ ተርጉመው።
Deuteronomy 32:22
በቁጣዬ እሳት ተለኩሷልና -- የተራሮች መሠረቶች
እግዚአብሔር ቁጣውን ከእሳት ጋር ያነጻጽረዋል። ይህ የሚያስቆጣውን በሚያጠፋበት ኃይሉ ላይ አጽንዖት ያደርጋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በቁጣዬ እሳት ተለኩሶ ነዶአል -- ይውጣል -- ተቀምጧል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ስለ ተቆጣሁ እሳት መለኮስ ጀምሬአለሁ፣ ይውጣል . . . የሚያጠፋ ነው . . . ተቀምጧል” ወይም “በምቆጣበት ጊዜ ጠላቶቼን እንደ እሳት አጠፋለሁ፣ በምድርና በ . . . ያለውን ሁሉ አጠፋለሁ . . . እውጣለሁ . . . አስቀምጣለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እስከ ጥልቁ ሲዖል
“እስከ ሙታን ዓለም ደረስ”
Deuteronomy 32:23
ጥፋትን አከምርባቸዋለሁ
በእስራኤላውያን አናት ላይ የሚቆልላቸው ቆሻሻዎች የሆኑ በሚመስል መልኩ በእስራኤላውያን ላይ ስለሚደርስባቸው መጥፎ ነገሮች እግዚአብሔር ይናገራል። ኢ.ት: “ብዙ መጥፎ ነገሮች እንደሚደርሱባቸው አረጋግጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ፍላጻዎቼን ሁሉ በእነርሱ ላይ እወነጭፋቸዋለሁ
እዚህ ጋ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ በእርግጠኝነት እንዲደርስባቸው የሚያደርጋቸውን መጥፎ ነገሮች አንድ ሰው በቀስቱ ፍላጻዎችን ከማስወንጨፉ ጋር ያነጻጽራል። ኢ.ት: “እነርሱን ለመግደል ማድረግ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በረሀብ ያልቃሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። የነገር ስም የሆነው “ረሀብ” “ይራባሉ” ወደሚል ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ይዝላሉ፣ በመራባቸው ምክንያትም ይሞታሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
እነርሱ -- ረሀብ እና በሚያቃጥል ሙቀትና በአሰቃቂ ጥፋት ይዋጣሉ
“የሚያቃጥል እሳት” ለሚለው ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እስራኤላውያን በንዳድ ይሰቃያሉ ወይም 2) በድርቅ ወይም በረሀብ ወቅት የአየሩ ሁኔታ ባለተለመደ መልኩ ሞቃት ይሆናል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እነርሱ . . . ረሀብ፣ የሚያቃጥል ሙቀትና አሰቃቂ ጥፋት ይውጣቸዋል” ወይም “እነርሱ . . . ረሀብ፣ በሚያቃጥል ሙቀትና በአሰቃቂ ጥፋት ይሞታሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የዱር አራዊትን ጥርስ፣ አፈር ላይ ከሚሳቡ ነገሮች መርዝ ጋር እልክባቸዋለሁ
ጥርስና መርዝ እንስሳው እነዚህን ነገሮች በመጠቀም የሚገድልባቸው ናቸው። ኢ.ት: “እንዲነክሷቸው የዱር አራዊትን፣ ነክሰው እንዲመርዟቸው በአፈር ላይ የሚሳቡትን ነገሮች እልካለሁ” (See: Synecdoche)
Deuteronomy 32:25
ሰይፍ በውጭ ያስቀራቸዋል
እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚወክለው የጠላትን ሰራዊት ነው። ኢ.ት: “እስራኤላውያን ውጪ በሚሆኑበት ጊዜ የጠላት ሰራዊት ይገድላቸዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ድንጋጤ ያደርጋል
x
Deuteronomy 32:27
የጠላትን ትንኮሳ ያልሰጋሁ ብሆን ኖሮ
“የጠላትን ትንኮሳ ሰግቼ ነበር”
የጠላት ትንኮሳ
ይህ የነገር ስም እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ጠላት እንዳይተነኩሰኝ” ወይም “ጠላት እንድቆጣ እንዳያደርገኝ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ጠላት
እግዚአብሔር የእርሱን ጠላቶች እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “ጠላቴን” ወይም “ጠላቶቼን” (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)
በስሕተት መፍረድ
“አሳስቶ መረዳት”
እጃችን ከፍ ከፍ ብሏል
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው የሰውን ጉልበት ወይም ኃይል ነው። ከፍ ከፍ ማለት ጠላትን የማሸነፍ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “እኛ ይበልጥ ኃይለኞች በመሆናችን አሸንፈናቸዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 32:28
ምነው ጥበበኞች በሆኑ፣ ይህንን ያስተውሉ ዘንድ፣ የሚመጣባቸውን ፍርድ ያውቁ ዘንድ

ሙሴ እውነት እንዲሆኑ የሚመኛቸውን አንዳንድ ነገሮች ይናገራል፤ ይሁን እንጂ ጥበበኞች እንዳልሆኑና አለመታዘዛቸው እግዚአብሔር ይህንን ጥፋት እንዲያመጣባቸው እንደሚያደርገው እንዳልተገነዘቡ ያውቃል። (See: Hypothetical Situations)
የሚመጣባቸው ፍርድ
የነገር ስም የሆነው "ፍርድ" እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ "በእነርሱ ላይ ሊደርስባቸው ያለ" (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 32:30
እግዚአብሔር አሳልፎ ካልሰጣቸው -- አንዱ አንድ ሺህ ማሳደድ እንዴት ይችላል
ሙሴ ጠላቶቻቸው ለምን እንዳሸነፏቸው ለማስተዋል ጥበበኞች ስላለመሆናቸው ጥያቄን በመጠቀም ሕዝቡን ይገስጻቸዋል። ይህ ጥያቄ ክፍት በሆነው ተለዋዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ውስጥ እንዳለው መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አንዱ አንድን ሺህ እንዴት ሊያሳድድ ይችላል፣ ሁለቱ አሥር ሺዎችን እንዲሸሹ ማድረግ እንዴ ይቻላቸዋል?
በውስጠ ታዋቂነት ያለውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ኢ.ት፡ "1 የጠላት ወታደር የእናንተን 1000 ሰዎች እንዴት ሊያሳድድ ቻለ፣ 2 የጠላት ወታደሮችስ የእናንተን 10000 ሰዎች እንዲሸሹ ለማድረግ እንዴት ቻሉ" (See: Numbers and Ellipsis)
Deuteronomy 32:32
ወይናቸው ከሰዶም ወይን ይመጣልና -- ዘለላቸው መራራ ናቸው
ሙሴ ሐሰተኛ አማልክት የሚያመልኩ ጠላቶችን በሰዶም ገሞራ ከኖሩት ክፉ ሕዝቦች እና መርዛማ ፍሬ ከሚያፈሩ የወይን ሐረጎች ጋር ያነጻጽራቸዋል። ይህ ማለት እስራኤላውያን በዙሪያቸው እንዳሉት ሕዝቦች ለማድረግ ከጀመሩ ጠላቶቻቸው ክፉዎች ስለሆኑ እስራኤላውያንን ለሞት ያበቋቸዋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ወይናቸው ከሰዶም ወይን እና ከገሞራም እርሻ ይመጣል
ወይን ለሕዝብ ወገን ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። "ወይናቸው በሰዶምና ገሞራ ይበቅል የነበረው ወይን ቅርንጫፉ ነው" ወይም ኢ.ት፡ "በሰዶምና ገሞራ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች እንዳደረጉት በተመሳሳይ መንገድ ክፉ ያደርጋሉ" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዘለላዎቻቸው
"የወይን ዘለላዎቻቸው
Deuteronomy 32:33
ወይናቸው የእባብ መርዝና የትናንሽ መርዘኛ እባቦች ጨካኝ መርዝ ነው
ሙሴ የእስራኤል ሕዝብን ጠላቶች መርዘኛ ፍሬና ወይን ከሚያበቅል የወይን ሐረግ ጋር ማነጻጸሩን ይቀጥላል። ይህ ማለት ጠላቶቻቸው ክፉዎች ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ትናንሽ መርዘኛ እባቦች
መርዘኛ እባቦች
ይህ ዕቅድ በእኔ በምስጢርነት የተጠበቀ፣ በሀብቴም መካከል ታትሞበት የተቀመጠ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ያለው ዕቅድ ዋጋ እንዳለው ሀብት በምስጢር እንደተጠበቀ አጽንዖት ይሰጣል። ምላሽ የማይፈልገው ጥያቄ እንደ ንግግር ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። ደግሞም፣ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ "ለእስራኤል ሕዝብና ለጠላቶቻቸው ለማድረግ ያቀድኩትን እኔ አውቃለሁ፣ አንድ ሰው ዋጋ ባላቸው ንብረቶቹ ላይ እንደሚቆልፍባቸው በእነዚያ ዕቅዶች ላይ ቆልፌባቸዋለሁ" (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 32:35
በቀል እኔ የምሰጠው ነው፣ ብድራትንም
"በቀል" እና "ብድራትንም" የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ትርጉማቸው ተመሳሳይ ነው። ኢ.ት፡ "እኔ እበቀላለሁ፣ የእስራኤልንም ጠላቶች እቀጣለሁ" (See: Doublet)
ብድራት
አንድ ሰው ስላደረገው ነገር ቅጣት ወይም ሽልማት
እግራቸው ይሰናከላል
መጥፎ የሆነ ነገር ደርሶባቸዋል። ኢ.ት፡ "ተስፋ የላቸውም" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ለእነርሱ የጥፋት ቀን
"እነርሱን የማጠፋበት ጊዜ"
በእነርሱ ላይ ሊመጡባቸው ያሉ ነገሮች በቶሎ ሊደርሱባቸው ይቸኩላሉ
ለቀጡአቸው በትጋት የሚሮጡ ሰዎችን በሚመስሉበት መልኩ እግዚአብሔር በጠላቶቹ ላይ ሊመጡ ስላሉት መጥፎ ነገሮች ይናገራል። ኢ.ት፡ "ፈጥኜ እቀጣቸዋለሁ" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 32:36
እግዚአብሔር ለሕዝቡ ፍትሕን ይሰጣልና
የነገር ስም የሆነው "ፍትሕ" እንደ ቅጽል ወይም ተውሳከ ግሥ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ "እግዚአብሔር ለሕዝቡ ፍትሐዊ የሆነውን ነገር ያደርግላቸዋል" (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ለአገልጋዮቹ ይራራል
"አገልጋዮቹን መርዳት እንዳለበት ይሰማዋል"
Deuteronomy 32:37
መጠጊያ ያደረጉ ዐለት፣ አማልክታቸው የት አሉ?
ከሌሎች አማልክት ከለላ ስለመፈለጋቸው የእስራኤልን ሕዝብ እግዚአብሔር ይገስጻቸዋል። ይህ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ "ተመልከቱ፣ እስራኤላውያን እንደሚጠብቋቸው ያሰቧቸው አማልክት ሊረዷቸው አልመጡም" (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የመሥዋዕቶቻቸውን ስብ የበሉ እና የመጠጥ ስጦታ የሆነውን ወይን የጠጡ አማልክት
እዚህ ጋ ለሌሎች አማልክት መሥዋዕት በማቅረባቸው የእስራኤልን ሕዝብ እግዚአብሔር ይገስጻቸዋል። ይህ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ "እስራኤላውያን ሥጋና ወይን ያቀረቡላቸው አማልክት ሊረዷቸው አልመጡም" (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ይነሡና ይርዷችሁ፤ ከለላ ይሁኗችሁ
በእስራኤላውያን ላይ ለማፌዝ እግዚአብሔር ይህንን ይናገራል። እነዚህ አማልክት ሊረዷቸው እንደማይችሉ ያውቃል። ኢ.ት፡ "እነዚህ ጣዖታት ሊነሡና ሊረዱ ወይም ሊጠብቋችሁ አይችሉም" (ምጸት የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 32:39
እኔ፣ እኔ እንኳን
"እኔ፣ እኔ ራሴ" ወይም "እኔ፣ እኔ ብቻዬን"። እግዚአብሔር እርሱ ብቻ አምላክ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት "እኔ"ን ይደጋግማል።
እጄን ወደ ሰማይ አንሥቼ እናገራለሁ
"እጄን ወደ ሰማይ አንሥቼ እምላለሁ" ወይም "ምያለሁ"። እጅን ማንሣት የመማል ምልክት ነው።
ለዘላለም እንደምኖር
"ለዘላለም መኖሬ እርግጥ የመሆኑን ያህል" ወይም "ማለቂያ በሌለው ሕይወቴ እምላለሁ"። በዘዳግም 32፡41-42 የተናገረው እንደሚፈጸም ይህ አነጋገር እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያረጋግጣል።
Deuteronomy 32:41
አብረቅራቂ ሰይፌን በምስልበት ጊዜ
"አንጸባራቂውን ሰይፌን በምስልበት ጊዜ"። ይህ ማለት እግዚአብሔር በጠላቶቹ ላይ ለመፍረድና ለመቅጣት ተዘጋጅቷል ማለት ነው። ኢ.ት፡ "በጠላቶቼ ላይ ለመፍረድ በምዘጋጅበት ጊዜ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እጄ ፍትሕን ማምጣት በሚጀምርበት ጊዜ
እዚህ ጋ "እጅ" የሚወክለው ሙሉውን ሰው ነው (See: Synec- doche)
Deuteronomy 32:42
ፍላጻዎቼ በደም እንዲሰክሩ አደርጋቸዋለሁ፣ ሰይፌም ከደም ጋር ሥጋን ይበላል
ፍላጻዎች ሰው የሆኑና የሚያሰክር መጠጥ ይሰጣቸው ይመስል እግዚአብሔር ስለ ፍላጻዎቹ ይናገራል፣ ሰይፉም ስለ ራበው ደሙ ተንጠፍጥፎ ያልወጣለትን እንስሳ እንደሚበላ ሰው መስሎ ይናገራል። እነዚህ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ብዙ ጠላቶችን ለመግደል ፍላጻዎችንና ሰይፍን የሚጠቀምን ወታደር የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። ይህ በተራው እግዚአብሔር በጦርነት ውስጥ ጠላቶቹን ስለመግደሉ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።(ዘይቤአዊ አነጋገር፣ ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
የጠላት አለቆች ከሆኑት ራስ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም "በራሳቸው ላይ ረጅም ጸጉር ካላቸው ጠላቶች" የሚለው ነው።
Deuteronomy 32:43
እናንተ ሕዝቦች ደስ ይበላችሁ

ሙሴ በዚያ ኖረው ይሰሙት ይመስል በየሀገራቱ ሁሉ ለሚኖሩ ሰዎች ይናገራል። (See: (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Apostrophe የሚለውን ተመልከት))
የአገልጋዮቹን ደም ይበቀላልና፤ በጠላቶቹ ላይ በቀልን ይመልስባቸዋል
እዚህ ጋ "የአገልጋዮቹን ደም" የሚወክለው የተገደሉትን የእርሱን ንጹሕ አገልጋዮች ሕይወት ነው። ኢ.ት: "አገልጋዮቹን የገደሉትን ጠላቶቹን ይበቀላቸዋል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 32:44
ነገራቸው -- መናገር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ተናገረ . . . መናገር" ወይም 2) "ዘመረ . . . መዘመር" ናቸው።
በሕዝቡ ጆሮ
x
Deuteronomy 32:46
ተናገራቸው
"ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ ተናገራቸው"
በልባችሁ አኑሩት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: "ለ -- ትኩረት ስጡ" ወይም "ስለ -- አስቡ" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
መስክሬላችኋለሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ባይታዘዙ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ምን እንደሚያደርግባቸው የተናገረውን ለማመልከት "መስክሬላችኋለሁ" ማለቱን ያመለክታል ወይም 2) እንዲያደርጉት እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ለማመልከት "አዝዥችኋለሁ" የሚሉት ናቸው
ልጆቻችሁ
"ልጆቻችሁና ተወላጆቻችሁ"
ይህ ነው
"ይህ ሕግ ነው"
አላስፈላጊ ነገር አይደለም
ይህ ምጸት በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "በጣም ጠቃሚ የሆነ ነገር" (ምጸት የሚለውን ተመልከት)
እርሱ ሕይወትህ ስለሆነ
የነገር ስም የሆነው "ሕይወት" "መኖር" ወደሚል ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ሕግን ራሱን የሚወክለውን የመታዘዝን ፈሊጣዊ አነጋገር ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። ኢ.ት: "ብትታዘዝው በሕይወት ትኖራለህና" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቀኖችህ እንዲረዝሙ
ረጅም ቀናት የረጅም ሕይወት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። እነዚህን ቃላት በዘዳግም 4፡26 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት: "ረጅም ጊዜ መኖር እንድትችል" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 32:48
የአባሪም ተራሮች
ይህ ሞዓብ ውስጥ የሚገን የተራራ ሰንሰለት ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
በናባው ተራራ እናት አባሪም
"አባሪም እና ናባው ተራራ ላይ ውጣ"
የናባው ተራራ
ይህ ከአባሪም ተራሮች ከፍተኛው ስፍራ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
በኢያሪኮ ትይዩ
"ከኢያሪኮ ከወንዙ በወዲያ ማዶ"
Deuteronomy 32:50
ወደ ሕዝብህ ተሰብሰብ
ይህ በሙታኑ ዓለም የሙሴ መንፈስ ከዘመዶቹ መንፈስ ጋር እንደሚገናኝ በትህትና የተነገረበት መንገድ ነው። ኢ.ት: "ከአንተ በፊት ከሞቱት አባቶችህ ጋር ተገናኝ" (See: Euphemism)
የሖር ተራራ
ይህ በኤዶም ዳርቻ የሚገኝ ተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
መሪባ
ይህ በበረሃው ውስጥ ሙሴ እግዚአብሔርን ያልታዘዘበት ስፍራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የጺን ምድረበዳ
ይህ በይሁዳ በስተደቡብ ዳርቻ የሚገኝ ምድረበዳ ስም ነው(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Chapter 33
Deuteronomy 33:1
እግዚአብሔር ከሲና መጣ፣ ከሴይርም በእነርሱ ላይ ተነሣ። ከፋራን ተራራ አበራ
ሙሴ እግዚአብሔርን ከንጋት ፀሐይ ጋር ያነጻጸራል። ኢ.ት: "እግዚአብሔር ከሲና በመጣ ጊዜ ከሴይር ወጥታ ከፋራን ተራራ የምታበራዋን ፀሐይ መስሎ ታይቷቸው ነበር" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእነርሱ ላይ
"በእስራኤል ሕዝብ ላይ"
አሥር ሺህ ቅዱሳኑ
"10000 መላእክት" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
በቀኝ እጁ የሚያበራ መብረቅ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ትርጉሞች 1) "በቀኝ እጁ የእሳት ነበልባል ነበር" ወይም 2) "የእሳትን ሕግ ሰጣቸው" ወይም 3) "ተራሮቹን ቁልቁል በመውረድ ከደቡብ መጣ"
Deuteronomy 33:3
ሕዝቡ
"የእስራኤል ሕዝብ"
ቅዱሳኑ ሁሉ በእጅህ ውስጥ ናቸው == እግርህ -- ቃሎችህ
የተጸውዖ ስሞች የሆኑት "የእርሱ" እና "የአንተ" የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን ነው። ኢ.ት: "የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሁሉ በእጁ ውስጥ ናቸው . . . እግሩ . . . ቃሎቹ" (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)
ቅዱሳኑ ሁሉ በእጅህ ውስጥ ናቸው
እጅ የኃይል እና የጥበቃ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: "ቅዱስ ሕዝቡን ሁሉ አንተ ትጠብቃለህ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ርስት
"ንብረት" ወይም "ዋጋው ውድ የሆነ ንብረት"
Deuteronomy 33:5
ንጉሥ ነበር
"እግዚአብሔር ነገሠ"
ይሹሩን
ይህ የእስራኤል ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በዘዳግም 32፡15 እንዳለው አድርገህ ተርጉመው።
ሮቤል በሕይወት ይኑር
ሙሴ እያንዳንዱን የእስራኤል ነገዶች መባረኩን በዚህ ይጀምራል።
ሆኖም የእርሱ ሰዎት ጥቂቶች ይሁኑ
ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ትርጉሞች 1) "የእርሱ ሰዎች ጥቂቶች አይሁኑ" ወይም 2) "የእርሱ ሰዎች ጥቂቶች ቢሆኑም እንኳን"
Deuteronomy 33:7
ለይሁዳ ድምፅ
እዚህ ጋ "የይሁዳ ድምፅ" የይሁዳን ሕዝብ ጩኸትና ጸሎት ያመለክታል። ኢ.ት: "የይሁዳ ሕዝብ ወደ አንተ በጸለየ ጊዜ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ረዳቱ ሁን
የነገር ስም የሆነው "ረዳት" እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: "እንዲዋጋ እርዳው" (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 33:8
ቱሚምህና ኡሪምህ
እነዚህ ሊቀ ካህናቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ በሚፈልግበት ጊዜ በደረቱ ላይ የሚሸከማቸው ቅዱስ ድንጋዮች ነበሩ። እዚህ ጋ "የአንተ" የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን ነው። (See: Forms of You እና የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
ለአንተ ታማኝ የሆነ
"ለአንተ ቅዱስ የሆነ" ወይም "አንተን ደስ ለማሰኘት የሚፈልገው"። ይህ የሌዊን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነገድ ያመለክታል።
ማሳህ
ይህንን በዘዳግም 6፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ተርጓሚው፣ “ ‘ማሳህ’ ማለት ‘መፈተን’ ማለት ነው” የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይችላል።
መሪባ
ይህንን በዘዳግም 32፡51 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ተርጓሚው፣ “ ‘መሪባ’ ማለት ‘መከራከር’ ወይም ‘መጣላት’ ማለት ነው” የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይችላል።
Deuteronomy 33:10
የአንተ == የአንተ == አንተ == የአንተ
ሙሴ ለእግዚአብሔር እየተናገረ ነው፣ ስለዚህ እነዚህ ቃላት ሁሉ ነጠላ ቁጥሮች ናቸው።
Deuteronomy 33:11
ተቀበል
በእርሱ ደስ ይበልህ
የእጆቹን ሥራ
እዚህ ጋ “እጆች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። አ.ት፡ “እርሱ የሠራውን ሥራ ሁሉ” (See: Synecdoche)
ወገባቸውን ሰባብር
ወገብ የጉልበት ማዕከል እንደሆነ ይታሰባል፣ እዚህ ጋ የሚወክለውም ጉልበትን ነው። አ.ት፡ “ጉልበታቸውን ውሰድ” ወይም “ፈጽመህ አጥፋ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ተነሥ == ተነሥ
ይህ ሐረግ ዘይቤአዊ አነጋገር ሆኖ ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “ለመዋጋት ተነሥ . . . እንዳያንሠራሩ አድርጋቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በ -- ላይ ተነሥ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አ.ት፡ “ከ -- ጋር ተዋጋ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 33:12
በእግዚአብሔር የተወደደ -- ይኖራል
እዚህ ጋ ሙሴ የሚያመለክተው የብንያም ነገድ አባላትን ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በሕይወት እንዲኖሩ የሚወድላቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በደኅንነት ይኖራል
የነገር ስም የሆነው “ደኅንነት” ግሣዊ ሐረግ በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ማንም ለጎዳው በማይችልበት ስፍራ ይኖራል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
በእግዚአብሔር ክንዶች መካከል ይኖራል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር የብንያምን ነገድ በኃይሉ ይከላከልላቸዋል ወይም 2) እግዚአብሔር በብንያም ነገድ ኮረብታማ አካባቢ ይኖራል። በሁለቱም ትርጉሞች፣ እግዚአብሔር ይንከባከባቸዋል የሚል አንድምታ አለው።
Deuteronomy 33:13
ስለ ዮሴፍ
ይህ የሚያመለክተው የኤፍሬምንና የምናሴን ነገዶች ነው። ሁለቱም ነገዶች የተገኙት ከዮሴፍ ነው።
የእርሱ ምድር በእግዚአብሔር ይባረክ
“የእርሱ” የሚለው ቃል የኤፍሬምንና የምናሴን ነገዶች የሚወክለውን ዮሴፍን ያመለክታል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ምድራቸውን ይባርክ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ከሰማይ በሆኑ የከበሩ ነገሮች፣ በጠል
“ከሰማይ በሆነ የከበረ ጠል” ወይም “ከሰማይ በሆነ የከበረ ዝናብ”
ጠል
ቅዝቃዜ ባለው ማለዳ ላይ በቅጠልና ሣር ላይ ውሃ የሚፈጥር። ይህንን በዘዳግም 32፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ከታች በሚተኛ ጥልቅ
ይህ በከርሠ ምድር ውስጥ የሚገኘውን ውሃ ያመለክታል።
Deuteronomy 33:14
የእርሱ ምድር ይባረክ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 33፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ምድሩን ይባርክ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ከፀሐይ በሚሆን የከበሩ ነገሮች መከር
“ፀሐይ እንዲበቅሉ በሚያደርጋቸው ምርጥ ሰብሎች”
ወራት በሚያስገኙት የከበሩ ነገሮች
“ከወር እስከ ወር በሚበቅሉ ምርጥ ሰብሎች”
ምርጥ ነገሮች -- የከበሩ ነገሮች
ሙሴ ምናልባት የምግብ ሰብሎችን ሳያመለክት አይቀርም። የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “እጅግ ምርጥ የሆኑ ፍሬዎች . . . የከበሩ ፍሬዎች” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
የጥንት ተራሮች
“ከረጅም ዘመን ጀምሮ የኖሩ ተራሮች”
የዘላለም ኮረብቶች
“ለዘላለም የሚኖሩ ኮረብቶች”
Deuteronomy 33:16
የእርሱ ምድር ይባረክ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ይህንን በዘዳግም 33፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት፡ “የእርሱን ምድር እግዚአብሔር ይባርክ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ብዛቱን
x
Deuteronomy 33:17
በግርማው እንደ በኩር በሬ ነው
በሬ በዘይቤአዊ አነጋገር ትልቅና ጉልበታም የሆነን ነገር ያመለክታል። “በኩር” የሚለው ቃል በዘይቤአዊ አነጋገር ክብር ማለት ነው። አ.ት፡ “ሰዎች ብዙና ኃያላን የሆኑትን የዮሴፍን ተወላጆች ያከብሯቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቀንዶቹ የ -- ቀንዶች ናቸው
ቀንድ የብርታት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “እርሱ እንደ -- ብርቱ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእነርሱ ይገፋል
በቀንዶቹ መግፋቱ ስለ ብርታቱ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “እርሱ በጣም ብርቱ ስለሆነ ይገፋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የኤፍሬም አሥር ሺዎች -- የምናሴ ሺዎች
ይህ ማለት የኤፍሬም ነገድ ከምናሴ ነገድ ይልቅ ይበረታል። አ.ት፡ “የኤፍሬም ሕዝብ ከ10000 ብዙ ዕጥፍ . . . (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 33:18
ዛብሎን በመውጣትህ፤ አንተም ይሳኮር በድንኳኖችህ ደስ ይበልህ
የዛብሎን ሕዝብ የሚገኙት በሜዲትራንያን ባህር አጠገብ ነበር። በባህር ላይ እየተጓዙ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ይገበያዩ ነበር። የይሳኮር ሕዝቦች በእርሻና ከብት በማርባት ሰላማዊ ኑሮን የሚመርጡ ነበሩ። በውስጠ ታዋቂነት ያሉ መረጃዎችን ግልጽ ልታደርጋቸው ትችላለህ። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
እነርሱ በዚያ ያቀርባሉ
“እነርሱ የሚያቀርቡት በዚያ ነው”
የጽድቅን መሥዋዕት
“ተቀባይነት ያላቸውን መሥዋዕቶች” ወይም “ተገቢነት ያላቸውን መሥዋዕቶች”
ከባህር የሚትረፈረፈውን ይጠባሉና፣ በባህር ዳር ካለው አሸዋም የሚገኘውን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በባህሩ ማዶ ካሉ ሕዝቦች ጋር ይገበያያሉ ወይም 2) አሸዋን በመጠቀም የሸክላ ሥራ መሥራት ጀምረው ነበር።
ከባህር የሚትረፈረፈውን ይጠባሉና
እዚህ ጋ “መጥባት” የሚለውን ቃል የዕብራይስጡ ትርጉም አንድ ሕፃን ልጅ የእናቱን ጡት እንዴት እንደሚመገብ ያመለክታል። ይህ ማለት አንድ ሕፃን ከእናቱ ወተት እንደሚያገኝ ሕዝቡ ከባህር ሀብት ያገኛሉ። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Deuteronomy 33:20
ጋድን የሚያሰፋው የተባረከ ይሁን

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እግዚአብሔር ጋድን ይባርከው፣ የሚኖርበትንም ብዙ መሬት ይስጠው” ወይም 2) ለጋድ የሚኖርበትን ብዙ ምድር ሰጥቶታልና ሰዎች እግዚአብሔር መልካም ነው ይበሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እንደ ሴት አንበሳ በዚያ ይኖራል፣ ክንድንና ራስንም ይገነጣጥላል
ይህ ማለት የጋድ ሕዝብ ብርቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ስለሆነ በጦርነት ጠላቶቻቸውን ያሸንፋሉ። (See: Simile)
Deuteronomy 33:22
ዳን ከባሳን ዘሎ የሚወጣ የአንበሳ ደቦል ነው
የዳን ሕዝብ እንደ አንበሳ ደቦል ብርቱዎች ናቸው፣ በባሳን የሚኖሩትን ጠላቶቻቸውን ወጉ። በውስጠ ታዋቂነት ያሉትን መረጃዎች ግልጽ ልታደርጋቸው ትችላለህ። (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Ellipsis የሚለውን ተመልከት))
Deuteronomy 33:23
ዳን ከባሳን ዘሎ የሚወጣ የአንበሳ ደቦል ነው
የዳን ሕዝብ እንደ አንበሳ ደቦል ብርቱዎች ናቸው፣ በባሳን የሚኖሩትን ጠላቶቻቸውን ወጉ። በውስጠ ታዋቂነት ያሉትን መረጃዎች ግልጽ ልታደርጋቸው ትችላለህ። (See: (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Ellipsis የሚለውን ተመልከት))
በሞገስ ረክቷል
እግዚአብሔር በንፍታሌም መደሰቱ “ሞገስ” ምግብ ሆኖ ንፍታሌም ዳግመኛ እስከማይራብ ድረስ የበላው በሚመስል መልኩ ተነግሮለታል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር በእርሱ ስለ ተደሰተበት የሚፈልገው መልካም ነገሮች ሁሉ አሉት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔር በረከት ሙላት
በረከቶች ምግብ ሆነው ንፍታሌም ተጨማሪ መያዝ እስከማይችል ድረስ የበላው በሚመስል መልኩ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ስለ ባረከው የሚፈልገው ሁሉ አለው”
ሀብት ውሰድ
ሙሴ የንፍታሌምን ነገድ እንደ አንድ ሰው እንደ ሆኑ አድርጎ ይናገራል፣ ስለዚህ እነዚህ ቃላት ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)
በስተምዕራብና በስተደቡብ ያለ ምድር
ይህ በገሊላ ሐይቅ ዙሪያ ያለውን ምድር ያመለክታል። የዚህ ንግግር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 33:24
እግሩን በወይራ ዘይት ውስጥ ያጠልቃል
የወይራ ዘይት ለምግብነትና ለፊትና ለክንድ ቆዳ ጥቅም ላይ ይውል ነበር። እግር ይቆሽሻል፣ ስለዚህ እግርን በወይራ ዘይት ውስጥ መጨመር ዋጋ ያለውን ዘይት ማበላሸት ይሆናል። የዚህ ንግግር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “ማባከን እንዲቻለው ብዙ የወይራ ዘይት ይኑረው” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
የከተማህ የበር መቀርቀሪያዎች - ቀኖችህ - ደህንነትህ
አንድ ሰው የሆኑ ይመስል ሙሴ የሚናገረው ለአሴር ነገድ ነው፣ ስለዚህ “የአንተ” የሚሉት አገባቦች ሁሉ ነጠላ ቁጥሮች ናቸው። (See: Forms of You)
የከተማህ በር መቀርቀሪያዎች ብረትና ነሐስ ይሁኑ
ከተሞች ጠላት እንዳይገባባቸው በበሮቻቸው አግድመት ላይ ረጃጅም መቀርቀሪያዎች ይኖራቸው ነበር። የዚህ ንግግር ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “በጠላቶችህ ከመጠቃት እንድትድን” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 33:26
ይሹሩን
ይህ የእስራኤል ሕዝብ ሌላው ስሙ ነው። ትርጉሙም “ቀጥተኛ የሆነ” የሚል ነው። ይህንን በዘዳግም 32፡15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።(ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
በሰማያት መካከል የሚራመድ -- በደመና ላይ
በጦር ሜዳ ላይ በሠረገላው እንደሚሄድ ንጉሥ በጠፈር መካከል በደመና ላይ የሚሄድ ይህ የእግዚአብሔር ምስል ነው። ኢ.ት፡ “ንጉሥ በጦር ሜዳ መካከል እንደሚሄድ በሰማያት መካከል ይሄዳል. . . በሠረገላው እንዳለ ንጉሥ በደመናት ላይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሊረዳህ
“አንተን ለመርዳት” ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚለው ቃል እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
Deuteronomy 33:27
የዘላለም አምላክ መጠጊያ ነው
የነገር ስም የሆነው “መጠጊያ” መጠለያ ወይም ከአደጋ ማምለጫ ስፍራ ማለት ሲሆን እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የዘላለም አምላክ ሕዝቡን ይጠብቃል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
የዘላለም ክንዶች ከበታች ናቸው
“የዘላለም ክንዶች” የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር ሕዝቡን ለዘላለም እንደሚጠብቃቸው ለሰጠው ተስፋ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ሕዝቡን ለዘላለም ይረዳቸዋል፣ ይንከባከባቸዋልም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
-በማለት ወግቶ ያስወጣቸዋል
ሙሴ እርሱ የሚናገረው የሚፈጸም ስለመሆኑ አጽንዖት ለመስጠት ወደፊት ሊሆን ያለውን ባለፈ ጊዜ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እርሱ ወግቶ ያስወጣቸዋል. . . ይላል” (See: Predictive Past)
በፊትህ -- አጥፋው
ሙሴ እስራኤላውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራቸዋል፣ ስለዚህ “አንተ” የሚለው ቃልና “አጥፋው” የሚለው ትዕዛዝ እዚህ ጋ ነጠላ ቁጥር ነው። (See: Forms of You)
“አጥፋው!” ይላል
በአንተ ቋንቋ ይህ ቀጥተኛ ትዕምርተ ጥቅስ በሚገባ የማያገለግል ከሆነ ቀጥተኛ ወዳልሆነው ትዕምርተ ጥቅስ ልትለውጠው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “እንድታጠፋቸው ይነግርሃል” (See: Direct and Indirect Quotations)
Deuteronomy 33:28
እስራኤል ይኖራል -- የያዕቆብ ምንጭ የተጠበቀ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሙሴ እርሱ የሚናገረው የሚፈጸም ስለመሆኑ አጽንዖት ለመስጠት ወደፊት ሊሆን ያለውን ባለፈ ጊዜ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። “እስራኤል ይኖራል . . . የያዕቆብ ምንጭ የተጠበቀ ይሆናል” ወይም 2) ሙሴ፣ “እስራኤል ይኑር . . . የያዕቆብ ምንጭም የተጠበቀ ይሁን” በማለት እስራኤልን እየባረከ ነው የሚሉት ናቸው። (See: Predictive Past)
የያዕቆብ ምንጭ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የያዕቆብ ቤት ወይም 2) የያዕቆብ ተወላጆች (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰማያቱ ጠልን ያንጠባጥቡ
ጠል የዝናብን ያህል አስፈላጊ ስለመሆኑ ተነግሯል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሙሴ “እንደ ዝናብ ብዙ ጠል ምድሪቱን ይሸፍናት” በማለት እስራኤልን እየባረከ ነው ወይም 2) ሙሴ “ብዙ ጠል እንደ ዝናብ ምድሪቱን ይሸፍናታል” በማለት ወደ ፊት ምን ሊሆን እንዳለ ይነግራቸዋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጠል
ቅዝቃዜ ባለበት ጠዋት በቅጠሎችና በሣር ላይ የሚገኝ ውሃ። ይህንን በዘዳግም 32፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Deuteronomy 33:29
በግርማ -- እንዳንተ ያለ፣ በእግዚአብሔር የዳነ ሕዝብ ማነው?
ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ ንግግር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ድግሞም በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እንደ አንተ ያለ እግዚአብሔር ያዳነው የሕዝብ ወገን የለም . . . በግርማ”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ጋሻ -- ሰይፍ
ይህ አገላለጽ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከጠላቶቻቸው እንደሚከላከልላቸውና ጠላቶቻቸውን እንዲወጉ እንደሚያስችላቸው ይናገራል። (See: Merism)
የረዳትህ ጋሻ
“ጋሻ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የመጠበቁና የመከላከሉ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። የነገር ስም የሆነው “ረዳት” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “አንተን የሚጠብቅህና የሚረዳህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
የግርማዊነትህ ሰይፍ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ጦርነቶችን ለማሸነፍ በሰይፍ ለመግደል ኃይል ማግኘትን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ግርማ እንዲኖርህና ጦርነቶችን

እንድታሸንፍ የሚያስችልህ እርሱን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የከፍታ ስፍራቸውን ትረግጣለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሌሎች ሕዝቦች ሐሰተኞች አማልክትን ያመለኩባቸውን ስፍራዎች እስራኤላውያን ይደመስሱታል ወይም 2) እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ድል በሚያደርጉበት ጊዜ በጀርባቸው ላይ ይረማመዱባቸዋል።

Chapter 34
Deuteronomy 34:1
የናባው ተራራ
ይህ ከአባሪም የተራራ ሰንሰለት በስተሰሜን የሚገኝ የፈስጋ ተራራ ጫፉ ነው። ይህንን በዘዳግም 32፡49 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ፈስጋ
ይህንን በዘዳግም 3፡17 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የዘንባባ ከተማ
x
Deuteronomy 34:4
ቤተ ፌጎር
ይህ በሞዓብ የነበረ መንደር ነው። ይህንን በዘዳግም 3፡29 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በዐይኖችህ ተመልከተው
“ለራስህ ተመልከተው”
እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ የሚያመለክተው ይህ የተጻፈበትን ወይም የታረመበትን ጊዜ እንጂ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ያለውን የአሁኑን ጊዜ አይደለም።
Deuteronomy 34:7
የአንድ መቶ ሃያ ዓመት ዕድሜ -- ሠላሳ ቀን
“የ120 ዓመት ዕድሜ . . . 30 ቀን” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ዐይኑ አልፈዘዘም፣ የተፈጥሮ ጉልበቱም አልደከመም
ይህ ማለት ዐይኖቹና አካሉ ገና ብርቱና ጤናማ ነበሩ ማለት ነው።
Deuteronomy 34:9
የነዌ ልጅ
ይህንን በዘዳግም 1፡38 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ኢያሱ -- በጥበብ መንፈስ ተሞልቶ ነበር
ጸሐፊው ኢያሱን አንድን ነገር እንደሚይዝ ዕቃ፣ መንፈስን ደግሞ በመያዣው ውስጥ እንደሚጨመር ቁሳዊ አካል አድርጎ ይናገራል። አ.ት፡ “ . . . በጣም ጥበበኛ እንዲሆን እግዚአብሔር ኢያሱን አስቻለው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሙሴ እጆቹን በእርሱ ላይ ጭኖበት ነበር
የዚህ ንግግር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ኢያሱ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ለመለየት ሙሴ እጆቹን በእርሱ ላይ ጭኖበት ነበር” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Deuteronomy 34:10
እግዚአብሔር ፊት ለፊት ያወቀው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔርና ሙሴ በጣም የቀረበ ግንኙነት ነበራችው ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በታላላቆቹ ሁሉ
“ታላላቆቹን ሁሉ ያደረገ”

Chapter 1
Joshua 1:1
ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለህዝቡ ራሱን የገለጸበት ስም ነው። ይህንን እንዴት እንደሚተረጉሙት ስለ ያህዌ የቃል ትርጉም ገጽ/ጽሁፍን ይመልከቱ።
ነዌ
የኢያሱ አባት (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህንን ዮርዳኖስን አቋርጡ
"ማቋረጥ" ማለት "ከወንዙ ማዶ መሄድ/ወንዙን ማቋረጥ" ማለት ነው። "ከዚህ ዳርቻ ወደ ዮርዳኖስ ወዲያኛው ዳርቻ መሄድ/ማቋረጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ እና ይህ ህዝብ ሁሉ
"አንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢያሱን ነው። (አንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮች ይመልከቱ)
ሁሉንም ስፍራ ሰጥቼሃለሁ
እግዚአብሔር ምድሪቱን በመጭው ጊዜ ለእስራኤል መስጠቱ የተገለጸው አስቀድሞ እንደሰጣቸው ተደርጎ ነው። ይህ ምድሪቱን በእርግጥ እንደሚሰጣቸው አጉልቶ ያሳያል። "ለእናንተ ሁሉንም ስፍራ እሰጣችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የወደፊት ሃላፊ ጊዜ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእናንተ ሰጥቻለሁ
"እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢያሱን እና የእስራኤል ህዝብን ሁለቱንም ነው። (አንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮችን ይመልከቱ)
የእግራችሁ ጫማ የሚረግጠውን ስፍራ ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው የዮርዳኖስን ወንዝ ሲያቋርጡ ኢያሱ እና እስራኤላውያን የሚጎዙበትን ስፍራ ሁሉ ነው። "በዚህ ምድር በምትሄዱበት ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 1:4
አጠቃላይ መረጃ ፡
ያህዌ ከኢያሱ ጋር ንግግሩን ቀጠለ
የአንተ ምድር
"የአንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢያሱን ብቻ ሳይሆን የእስራኤልን ነገዶች በሙሉ ነው። (አንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮችን ይመልከቱ)
በፊትህ ለመቆም
በቁጥር 5 "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ኢያሱን ነው። (አንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮችን ይመልከቱ)
እኔ አንተን አልተውህም ወይም አልጥልህም
"መተው" እና "መጣል" የሚሉት ቃላት በመሰረታዊነት አንድ አይነት ነገሮች ናቸው። ያህዌ እነዚህን አንድ ላይ ያጣመራቸው እነዚህን ነገሮች እንደማያደርግ ለማጉላት ነው። "በእርግጥ ሁልጊዜም ከአንተ ጋር እሆናለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ጥንድ አሉታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)
Joshua 1:6
አጠቃላይ መረጃ ፡
ያህዌ ለኢያሱ ጥብቅ ትዕዛዛትን ሰጠው (ሃላፊነቶች -ሌሎች ጥቅሞች የሚለውን ይመልከቱ)
በርታ ደግሞም ጽና
ያህዌ ኢያሱን በጽናት ፍርሃቶቹን እንዲያሸንፍ ያዘዋል። (ሃላፊነቶች -ሌሎች ጥቅሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚህ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ አትበል
ይህ በአዎንታዊ ትዕዛዝ ሊጻፍ ይችላል። "ይህንን በትክክል ተከተል" ወይም "በትክክል ተከተላቸው" (ሃላፊነቶች -ሌሎች ጥቅሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ፍሬያማ ሁን
"ግብህን ጨብጥ" ወይም "ግብህ ላይ ድረስ"
Joshua 1:8
አጠቃላይ መረጃ ፣
ያህዌ ከኢያሱ ጋር ንግግሩን ቀጠለ
ሁልጊዜም ትናገራለህ
"ሁልጊዜ" የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ መናገር ተጋኖ የተገለጸበት ነው። (ኩሸት እና ማጠቃለል የሚሉትን ይመልከቱ)
የበለጸገ እና ስኬታማ
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ አንድ ትርጉም ይዘዋል እናም ታላቅ ብልጽግናን ያጎላሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ አላዘዝኩህምን?
ይህ ያህዌ ኢያሱን ማዘዙን ያመለክታል። "እኔ አዝዤሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በርታ ደግሞም ጽና!


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ያህዌ ኢያሱን እያዘዘው ነው። (ሃላፊነቶች -ሌሎች ጥቅሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 1:10

ወደ ሰፈር ገብታችሁ 'ተዘጋጁ... ውረሱ' ብላችሁ ህዝቡን እዘዙ።'

በጥቅስ ውስጥ ቀረበው ቀጥተኛ ባለሆነ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል። "ወደ ሰፈር ግቡ ህዝቡ ለራሱ የሚሆነውን እንዲያዘጋጅ እዘዙ። በሶስት ቀናት ውስጥ ይህንን ዮርዳኖስን አቋርጠው ያህዌ አምላካቸው እንዲወርሷት የሰጣቸውን ምድር ይወርሳሉ።" (በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ የሚለውን ይጠቀሙ)

ህዝቡ

ይህ የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል። "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በሶስት ቀናት ውስጥ

እዚህ ስፍራ ያህዌ የሚገኝበትን ቀን እንደ መጀመሪያ ቀን እየቆጠረ ነበር። "ከአሁን በኋላ ሁለት ቀናት" ወይም "ከነገ በኋላ ባለው ቀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ይህንን ዮርዳኖስን አቋርጡ

"አቋርጡ" የሚለው የሚያመለክተው ከወንዙ ወዲያ ማዶ መሻገርን ነው። "ከዮርዳኖስ ወንዝ ወዲያ ማዶ ተጓዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 1:12

አጠቃላይ መረጃ፡

የሮቤል፣ የጋድ እና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምስራቅ መቀመጥ መረጡ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሮቤል ነገድ፡/ሮቤላዊያን

እነዚህ የሮቤል ትውልዶች ነበሩ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የጋድ ነገድ/ጋድአዊያን

እነዚህ የጋድ ትውልዶች ነበሩ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 1:14

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ለሮቤላዊያን፣ ለጋድአዊያን እና ለምናሴ ነገድ እኩሌታ መናገሩን ቀጠለ

ልጆቻችሁ

"የእናንተ ትናንሽ ልጆች"

ከዮርዳኖስ ባሻገር

ይህ የሚያመለክተው ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ መስራቅ ያለውን ስፍራ ነው። ቆይቶ ብዙዎቹ እስራኤላውያን ከዮርዳኖስ በስተ ምስራቅ ይኖራሉ፣ ስለዚህም ምስራቁን "ከዮርዳኖስ ማዶ" ብለው ይጠሩታል። በዚህ ጊዜ ግን ሁሉም ገና በስተ ምስራቅ ናቸው። "ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድሞቻችሁ እረፍት እስኪያገኙ

ይህ እስራኤላውያን የሚይዟቸውን በከነዓን የሚኖሩ ጠላቶቻቸውን ሁሉ እንደሚያሸንፉ ያመለክተል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ... ትወርሳላችሁ

ይህ በዚያ በምድሪቱ በሰላም እንደሚኖሩ ያመለክታል።

ፀሐይ ከምትወጣበት፣ ከዮርዳኖስ ባሻገር

ይህ የዮርዳኖስን ምስራቃዊ ጎን ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 1:16

አጠቃላይ መረጃ፡

ለኢያሱ የመለሱለት እነዚህ እስረኤላውያን፤ በተለይ ሮቤላዊያን፣ ጋድአዊያን እና ከምናሴ ነገድ እኩሌታዎቹ ነበሩ።

በትዕዛዛትህ ላይ አመጹ፣ ደግሞም ቃልህን አልታዘዙም

እነዚህ ሁለት ሀረጋት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ማናቸውንም አይነት መልክ የያዘ አለመታዘዝ እንደሚያስቀጣ አጉልተው ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይገደላል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሞት እንፈርድበታለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በርታ ደግሞም ጽና

እስራኤል እና እግዚአብሔር፤ ኢያሱ ለእስራኤል ህዝብ መሪ ሆኖ እንዲቀጥል ሁለቱም ባህርያት አስፈላጊው እንደሆኑ ይቆጥራሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 2

Joshua 2:1

ነዌ

ይህ የኢያሱ አባት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰጢም

ይህ በዮርዳኖስ ወንዝ ምስራቅ አቅጣጫ የሚገኝ ስፍራ ስም ነው። ትርጉሙ "የግራር ዛፎች" ማለት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላዮች

እነዚህ ሰዎች እስራኤላውያን ምድሪቱን እንዴት እንደሚወሯት መረጃ ለማግኘት የሄዱ ነበሩ።

Joshua 2:4

አጠቃላይ መረጃ፡

ጋለሞታይቱ ረዓብ ሁለቱን እስራኤላውያን ሰላዮች ከጉዳት ጠበቀች።

ነገር ግን ሴቲቱ ሁለቱን ሰዎች ወስዳ ደበቀቻቸው

ይህ የሆነው የንጉሡ መልዕክተኛ ከእርሷ ጋር ከመነጋገሩ አስቀድሞ ነው።

ሴቲቱ

ይህ ጋለሞታይቱን ረዓብን ያመለክታል

ማምሻ/ለዐይን ያዝ ሲያደርግ

ቀኑ ወደ ምሽቱ ጨለማ መግባት የሚጀምርበት ጊዜ ነው

Joshua 2:6

ነገር ግን እርሷ ... ወደ ሰገነቱ/ጣራ ላይ ወሰደቻቸው

ይህ ሰዎቹን እንዴት እንደ ደበቀቻቸው በኢያሱ 2:4 ላይ ሚገኝ የመረጃ ዳራ እና ማብራሪያ ነው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰገነት/ጣራ

ጣራው ጠፍጣፋ ጠንካራ ነበር፣ በመሆኑም ሰዎች በዙሪያው ሊረማመዱ ይችሉ ነበር

የተልባ እግር

ልብስ ለመስራት የሚውል፣ ክር/ቃጫ ለማግኘት የሚተከል ተክል።

ሰዎቹ ተከተሏቸው

ሰዎቹ ሰላዮቹን የተከተሏቸው ረዓብ በኢያሱ 2፡5 ላይ ከነገረቻቸው የተነሳ ነው።

መሻገሪያዎች/መልካ

የወንዝ ወይም ሌላ የውሃ አካል፣ በእርምጃ ወደ ሌላኛው ዳርቻ በእርምጃ ለመሻገር የሚቻልበት ጥልቀት የሌለው ስፍራ

Joshua 2:8

ገና ሳይጋደሙ

ይህ የሚያመለክተው በምሽቱ ወደ መኝታ መሄድን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ምድሪቱን ለእናንተ እንደሰጣችሁ አውቃለሁ

"እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክው መላውን የእስራኤል ሰዎች ነው። (እናንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮችን ይመልከቱ)

እናንተን መፍራት ወድቆብናል

ፈርተናል የሚለው የተገለጸው ፍርሃት ራሱ መጥቶ እንዳጠቃቸው ተደርጎ ነው። "እናንተን ፈራን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በፊታችሁ ቀለጥን

ይህ የፈራውን ህዝብ ከሚቀልጥና ከሚወርድ በረዶ ጋር ያነጻጽረዋል። አማራጭ ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት 1) በእስራኤላውያን ፊት ደካማ እንደሚሆኑ ወይም 2) እንደሚበታተኑ ነው። "እናንተን መቋቋም እስከማይችሉ ድረስ እጅግ ይፈራሉ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 2:10

አጠቃላይ መረጃ፡

ረዓብ ከእስራኤላውያን ሰላዮች ጋር መነጋገሯን ቀጠለች

የደንገል/ቄጤማ ባህር

ይህ የቀይባህር ሌላው ስም ነው
ሴዎን...ዐግ
እነዚህ የአሞራውያን ነገሥታት ስሞች ናቸው።(ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ልባችን ቀለጠ፣ አንዳች ድፍረት አልቀረልንም
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድ ላይ የቀረቡት ትኩረት ለመስጠት ነው። "ልባችን ቀለጠ" የሚለው ሃረግ የፈሩትን የኢያሪኮ ሰዎች ልብ እየቀለጠ ከሚወርድ በረዶ ጋር ነው ያነጻጸራል። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Joshua 2:12
አጠቃላይ መረጃ፡
ረዓብ ከእስራኤላውያን ሰላዮች ጋር መነጋገሯን ቀጠለች
አባካችሁ ማሉልኝ... እርግጠኛ የሆነ ምልክት ስጡኝ
እነዚህ ረዓብ ከሰለዮቹ እርግጠኛ የሆነ ምልክት መፈለጓን የሚገልጹ ተመሳሳይ ሃሳቦች ናቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእናንተ መልካም ነበርኩ
"እናንተ" የሚለው ቃል ሁለቱን ሰላዮች ያመለክታል። (እናንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮችን ይመልከቱ)
ህይወታችንን አድኑ... ከሞት አድኑን
"አትግደሉን" የሚለውን ትሁት በሆነ መንገድ መግለጽ። (ዩፌሚዝም/የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 2:14
አጠቃላይ መረጃ፡
እስራኤላውያን ሰላዮች ረዓብ የጠየቀችውን በኢያሱ 2፡12 ቃል የገቡላትን ፈጸሙ
እስከ ሞት ድረስ እንኳን ቢሆን፣ ህይወታችንን ለእናንተ ህይወት ይህ ፈሊጥ ቃልኪዳናቸውን ካልጠበቁ እግዚአብሔር እርግማኑን በእነርሱ ላይ እንዲያመጣባቸው የሚምሉበት እና የሚጠይቁበት መንገድ ነው። "ቃል የገባነውን ሳናደርግ ብንቀር፣ ያህዌ እኛን ያጥፋን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 2:15
አጠቃላይ መረጃ፡
እስራኤላውያኑ ሰላዮች ከረዓብ ጋር መነጋገራቸውን ቀጠሉ።
ይህንን ባታደርጊ
ይህ ሰላዮቹ ለረዓብ የገቡትን ቃል ኪዳን የሚፈጽሙበትን ሁኔታ ይገልጻል። "ይህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው " ይህንን ደማቅ ቀይ ገመድ በመስኮቱ በኩል እሰሪው " የሚለውን በኢያሱ 2፡18 የሚገኘውን ነው። (መላምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 2:18
አያያዥ ሃሳብ፡
እስራኤላውያኑ ሰላዮች በኢያሱ 2፡15 የገለጹትን ሁኔታ ያብራራሉ።
አጠቃላይ መረጃ፡
እስራኤላውያኑ ሰላዮች ከረዓብ ጋር መነጋገራቸውን ቀጠሉ።
ማናቸውም ከቤትሽ በር ውጭ የሄደ
ይህ ሃረግ መላምታዊ በመፍጠር አንድን ሁኔታ ይገልጻል። (መላምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)
ደሙ በራሳቸው ራስ ላይ ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው የሚገልጸው የአንድ ሰውን መሞት ነው። ለራሳቸው ሞት ተጠያቂነቱ የተገለጸው ደም በራሳቸው ላይ እንደሚሆን ተደርጎ ነው። "ሞታቸው የገዛ ራሳቸው ጥፋት ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
እኛ በደለኞች አንሆንም
"ንጹሃን እንሆናለን"
በማንም ላይ እጅ ቢጫን
እዚህ ስፍራ "እጅ ቢጫን" የሚለው አንድ ሰው እንዲጎዳ ምክንያት መሆን በጨዋ አገላለጽ የተገለጸበት ነው። "በማንም ላይ ጉዳት እንዲደርስ ምክንያት ብንሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፌሚዝም/የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 2:20
አጠቃላይ መረጃ፡
ሁለቱ እስራኤላውያን ሰላዮች ከረዓብ ጋር መነጋገራቸውን ቀጠሉ።
አጠቃላይ መረጃ፡
ሰላዮቹ ረዓብ ወደ እርሷ መምጣታቸውን እንዳትናገር ጠየቋት፣ ወይም ይህ ካልሆነ ቤተሰቧቿን ለማዳን ከገቡት መሃላ ነጻ ይሆናሉ።
ብትናገሪ
"አንቺ" የሚለው ረዓብን ያመለክታል። (አንቺ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮችን ይመልከቱ)
እናንተ ያላችሁት ይደረግ
ረዓብ ቤተሰቧችዋ እንዲጠበቁ ከእነርሱ የመሃላ ቃል ጋር ተስማማች
Joshua 2:22
አጠቃላይ መረጃ፡
ሁለቱ እስራኤላውያን ኢያሪኮን ለቀው ወጡ።
አሳዳጆቻቸው ተመለሱ
ወደ ኢያሪኮ ተመለሱ ማለቱ ሊረዳ ይችላል። "የእነርሱ አሳዳዶች ወደ ኢያሪኮ ከተማ ተመለሱ" በሚለው ውሰጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አንዳች አላገኙም
ይህ የሚያመለክተው ሰላዮቹን ያላገኟቸውን ሰዎች ነው
Joshua 2:23
ሁለቱ ሰዎች ተመለሱ
ሁለቱ ሰዎች ወደ እስራኤላውያን ሰፈር ተመለሱ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ዞረው፣ አቋርጠው ተመልሰው መጡ
እነዚህ እስራኤላውያን ወዳረፉበት ስፍራ መመለሳቸውን የሚገልጹ ተመሳሳይ አባባሎች ናቸው
አቋርጠው
"አቋርጠው" ማለት ከወንዙ ተቃራኒ ዳርቻ መሄድ ማለት ነው። "ከዚህኛው ዳርቻ ወደ ተቃራኒው የዮርዳኖስ ዳርቻ መሄድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ነዌ
ይህ የወንድ ስም ነው፤ የኢያሱ አባት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
እኛ
እዚህ ስፍራ "እኛ" የሚለው ቃል እስራኤልን ያመለክታል
የምድሪቱ ነዋሪዎች ቀለጡ
የምድሪቱ ነዋሪዎች ለእስራኤላዊያን ያላቸው አቋም ሲታይ በሙቀት እንደሚቀልጥ ነገር ይመስላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 3
Joshua 3:1
ተነሱ
"ተነሱ" የሚለው ሃረግ "መንቃት" ማለት ነው።
ሰጢም
እስራኤላውያን ወደ ተስፋ ምድራቸው ወደ ከነዓን ከመግባታቸው አስቀድሞ ከሰፈሩበት ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምዕራብ በሞአብ ምድር የሚገኝ ስፍራ
Joshua 3:2
አለቆች
እነዚህ የማዘዝ ወይም ስልጣን ደረጃን የያዙ ሰዎች ናቸው
ሰዎች
ይህ የእስራኤል ህዝብ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሁለት ሺህ ክንድ
"2,000 ክንድ" ክንድ የሚለው ቃል ከክርን እስከ ጣት ጫፍ ድረስ ያለው እርቀት መለኪያ ነው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀት እና ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)
Joshua 3:5


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ራሳችሁን ቀደሱ
ይህ በያህዌ ፊት ንጹህ ለመሆን የሚደረግን ልዩ ዝግጅት ያመለክታል፡፡
ያህዌ ተአምራት ያደርጋል
ያህዌ ሁሉም የሚያየው እና የሚዳስሰው ተአምራት ያደርጋል
ታቦቱን ያዙ
ይህ ሌዋውያን ታቦቱን ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ይዘው መሄዳቸውን ያመለክታል
Joshua 3:7
አጠቃላይ መረጃ፡
ካህናቱ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያህዌ ለኢያሱ ነገረው፡፡
በመላው እስራኤል ዐይኖች ፊት ታላቅ ሰው አደርግሃለሁ
ዐይኖች የሚለው ማየትን ሲወክል ፣ ማየት የሚለው ማሰብን ወይም ፍርድን ይገልጻል፡፡ "ህዝቡ የማደርገውን ያያል፣ ደግሞም አንተን ታላቅ ሰው እንዳደረግኩህ ያስተውላሉ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የዮርዳኖስ ውሃ ዳርቻ
ኢያሱ ወደ ዳርቻ ወይም ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ደረሰ
Joshua 3:9
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ምን ሊያደርግ እንደሆነ ኢያሱ ለእስራኤላውያን ነገራቸው፡፡ከፊታችሁ ሊያጠፋቸው ያህዌ በምድሪቱ የሚኖሩ ሌሎች ህዝቦችን ከምድሪቱ ይወጡ ዘንድ ወይም እንዲገደሉ ያደርጋል፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አቋርጠው
"አቋርጠው" ማለት ከወንዙ ተቃራኒ ዳርቻ መሄድ ማለት ነው፡፡ "ከዚህኛው ዳርቻ ወደ ተቃራኒው የዮርዳኖስ ዳርቻ መሄድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 3:12
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ምን ሊያደርግ እንደሆነ ኢያሱ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጠለ፡፡
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል አባቶች ቀይ ባህርን እንዳቋረጡ፣ እነዚህ ሰዎች ዮርዳኖስን በደረቅ ምድር ያቋርጣሉ
የእግራቸው ኮቴ
ይህ የሚያመለክተው የእግራቸውን ስር ነው
ከላይ የሚወርደው
ይህ ቃል የሚያመለክተው የዮርዳኖስ ወንዝ ውሃ ወደ እስራኤል የሚወርድበትን አቅጣጫ ነው
አንድ ክምር ሆኖ ቆመ
ውሃው በአንድ ነጥብ ወይም ስፍራ ላይ ይቆማል፡፡ ካህናቱ ዙሪያ አይፈስም
Joshua 3:14
የውሃ ዳርቻ፡
ይህ የውሃውን ገጽ እንዲሁም ውሃው ወደ ደረቅ ምድር የሚፈስበትን ዳርቻ ያመለክታል፡፡ (ስኔክቲኪ/ ዘይቤያዊ አነጋገር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ የሚለውን ይመልከቱ)አሁን ዮርዳኖስ ውሃ ሞልቶ እስከ መከር ጊዜ ድረስ ይፈስ ነበር ይህ የመረጃ ዳራ ያህዌ ሊያደርግ ያለውን አጉልቶ ያሳያል፡፡ (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 3:17
አጠቃላይ መረጃ፡
ተአምራዊው የዮርዳኖስ ባህር መውረዱ ቀጠለ
ዮርዳኖስ
ይህ የዮርዳኖስ ወንዝ የሚፈስበትን ያመለክታል፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አቋረጡ
ይህ ሃረግ ከወንዙ ተቃራኒ ዳርቻ መሄድ ማለት ነው፡፡ "ከዚህኛው ዳርቻ ወደ ተቃራኒው ዳርቻ መሄድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 4
Joshua 4:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ምንም እንኳን ያህዌ በቀጥታ ለኢያሱ ቢናገርም፣ አንተ የሚለው በተጠቀሰ ጊዜ ሁሉ እስራኤልን ያጠቃልላል፡፡ (ተውላጠ ስም/የስም ምትክ የሚለውን ይመልከቱ)
አቋረጠ
"አቋረጠ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከወንዙ ተቃራኒ ዳርቻ መሄድን ነው፡፡ "አቋርጦ ሄደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የ ዮርዳኖስ
የዮርዳኖስ ወንዝ ፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእነርሱ ይህንን ተዕዛዝ ስጣቸው፡'...'
በጥቅስ ውስጥ የተቀመጠው ቀጥተኛ እንዳልሆነ ጥቅስ ሊቀርብ ይችላል፡፡ "ካህናቱ በደረቅ ምድር ቀመውበት ከነበረበት ስፍራ ከዮርዳኖስ መሃል አስራ ሁለት ድንጋዮችን እንዲያነሱ ይህንን ትዕዛዝ ስጣቸው፣ እነዚያንም ድንጋዮች ይዘህ መጥተህ ዛሬ ምሽት በምታድርበት ስፍራ አኑራቸው" (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚሉትን ይመልከቱ)
Joshua 4:4
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢያሱ ለአስራ ሁለቱ ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነገራቸው፡፡ወደ ዮርዳኖስ መሃል እያንዳንዳችሁ በትከሻችሁ ድንጋይ ትሸከማላችሁ እያንዳንዳቸው አስራ ሁለቱ ሰዎች ከዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ትልልቅ ድንጋይ አንስተው መተሰቢያ ለማኖር ወደ ሌላው ዳር ተሸክመው ወሰዱ፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 4:6
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢያሱ ለእስራኤላውያን የአስራ ሁለቱ ድንጋዮች ክምር ትርጉሙ ምን እንደሆነ ነገራቸው
የዮርዳኖስ ውሃ በያህዌ የቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ተቋረጠ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ "ያህዌ የዮርዳኖስን ውሃ በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት አቋረጠው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የዮርዳኖስ ውሃዎች የነበሩት
"የዮርዳኖስ ወንዝ ነበር"
በታቦቱ ፊት ተቋርጠው ነበር
የዮርዳኖስ ወንዝ ካህናቱ ተሸክመውት እስከ ነበረው ታቦት ድረስ እንዳይፈስ እግዚአብሔር አግዶት ነበር
የዮርዳኖስ ውሃዎች ተቋርጠው ነበር
ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ቁልቁል ይፈስ የነበረው ውሃ በታቦቱ ፊት ቆመ፣ ስለዚህም ታቦቱን ጨምሮ ሁሉም በደረቅ የወንዝ መፋሰሻ ተጓዙ
Joshua 4:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢያሱ እና መላው እስራኤል ያህዌ እንዳዘዘው መስራታቸውን ቀጠሉ
ከዮርዳኖስ መሃል አስራ ሁለት ድንጋዮችን ተሸከሙ
ይህ የሚያመለክተው አስራ ሁለቱ ወንዶች ከዮርዳኖስ ወንዝ መፍሰሻ ድናጋዮችን መሸከማቸውን ነው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያ ኢያሱ በዮርዳኖስ መሃል አስራ ሁለት ድንጋዮች አስቀመጠ
እነዚህ አስራ ሁለቱ ሰዎች ከወንዙ መፋሰሻ የተሸከሟቸው ድንጋዮች ሳይሆኑ አስራ ሁለት ተጨማሪ ድንጋዮች ነበሩ፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መታሰቢያው እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ አለ
ይህ ማለት ጸሐፊው ይህንን መጽሐፍ እስከሚጽፍበት ቀን ድረስ መታሰቢያው በዚያ ነበር
Joshua 4:10
የ ዮርዳኖስ
ይህ የዮርዳኖስን ወንዝ ያመለክታል፡፡
ህዝቡ
ይህ የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አቋረጡ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ማለት ከወንዙ ተቃራኒ ዳርቻ መሄድ ነው። "ከዚህኛው ዳርቻ ወደ ተቃራኒው ዳርቻ መሄድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በህዝቡ ፊት
ይህ የሚያመለክተው በህዝቡ ፊት መሆንን ወይም በሁሉም ህዝብ እይታ ውስጥ መሆንን ነው። እያንዳንዱ ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው አይቷል። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 4:12
የሮቤል ነገድ፣ የጋድ ነገድ እና የምናሴ ነገድ እኩሌታ በወታደራዊ አሰላለፍ በእስራኤል ህዝብ ፊት አለፉ
እነዚህ እስራኤላውያንን በዮርዳኖስ ወንዝ ምስራቅ ለማስፈር እና ጦርነቱን በመምራት ግዴታቸውን የሚወጡ የሶስቱ ነገዶች ወታደሮች ነበሩ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ልክ እነርሱ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው
ሙሴን አከበሩት
ይህ ማክበርን ብቻ የሚያመለክት አይደለም፣ ነገር ግን ሙሴን ሲከተሉ ያደርጉት እንደነበረው ለእርሱ ትዕዛዛት መገዛትን እና እርሱን እንደ ሰራዊቱ አዛዥ መቀበልን ጭምር ያመለክታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 4:17
አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው ለቀደመው ትውልድ የዮርዳኖስን ወንዝ መክፈል ቀይ ባህርን ከመክፈል ልዩነት እንደሌለው ግልጽ እያደረገ ነበር የዮርዳኖስ ውሃ ወደ ቦታው ተመልሶ በዳርቻዎቹ ሞልቶ ፈሰሰ የዮርዳኖስ ወንዝ እስራኤላውያን በደረቅ ምድር ከማለፋቸው በፊት እና በኋላም በዳርቻዎቹ ሞልቶ ይፈስና አካባቢውን ያጥለቀልቅ ነበር አራት ቀናት "4 ቀናት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 4:19
ከዮርዳኖስ ወጡ
ይህ እስራኤል የዮርዳኖስ ወንዝን በደረቅ ምድር ማቋረጣቸውን ያመለክታል። በአራተኛው ወር በአስረኛው ቀን ይህ በዕብራውያን ቀን አቋጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። አስረኛው ቀን በምዕራባውያን ቀን አቋጣጣር በመጋት መጨረሻ አቅራቢያ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)
ከዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ያወጧቸው አስራ ሁለቱ ድንጋዮች ኢያሱ በደረቅ ምድር የመሻገራቸውን መታሰቢያ መገንባት ይችል ዘንድ እያንዳንዱ ነገድ ከዮርዳኖስ ወንዝ አንድ ድንጋይ መውሰድ ነበረበት። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 4:22
አጠቃላይ መረጃ
ኢያሱ ለህዝቡ ስለ ድንጋይ ክምሩ ማስታወሱን ቀጠለ። ለልጆቻችሁ ንገሩ እስራኤላውያን ልጆቻቸው ያህዌን ለዘለዓለም ያከብሩ ዘንድ የእግዚአብሔርን ተአምራቶች ለእነርሱ ማስተማር ነበረባቸው። የያህዌ እጅ ታላቅ ነው ይህ የያህዌ ሃይል ታላቅ መሆኑን ያመለክታል። "ያህዌ ታላቅ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 5
Joshua 5:1
ልቦቻቸው ቀለጡ … በውስጣቸው ነፍስ አልቀረም ነበር
እነዚህ ሁለት ሃረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የፍርሃታቸውን ጥልቀት ያጎላሉ። (ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤ/ፓራሊዝም የሚለውን ይመልከቱ)
ልቦቻቸው ቀለጡ
እዚህ ስፍራ "ልቦች" የሚለው ድፍረትን ያመለክታል። ሰም በእሳት እንደሚቀልጥ ድፍረታቸው ቀልጦ ጠፍቶ እጅግ ፈርተው ነበር። "ድፍረታቸውን ሁሉ አጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)በውስጣቸው ነፍስ አልቀረም ነበር እዚህ ስፍራ "ነፍስ" የሚለው የሚያመለክተው ለመዋጋት ያላቸውን ፈቃድ ነው። "ለመዋጋት አንዳች ፈቃድ አልነበራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 5:2
ኢያሱ የባልጩት ምላጭ አዘጋጀ… ወንዶቹን ሁሉ ገረዘ
ከ600,000 በላይ ወንዶች ነበሩ፣ ስለዚህም ኢያሱ በዚህ ተግባር ላይ በነበረበት ጊዜ ሌሎች ብዙ ሰዎች እንደረዱት ግልጽ ነው። ይህ አንባቢውን ግራ የሚያጋባው ከሆነ፣ ተርጓሚው ይህንን ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልገው ይችላል። "ኢያሱ እና እስራኤላውያኑ ራሳቸው የባልጩት ምላጭ አዘጋጅተው… ወንዶችን ሁሉ ገረዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ጊብዓዝ ዓረሎት
ይህ እስራኤል ራሳቸውን ለያህዌ ዳግም መስጠታቸውን የሚታወስበት ስፍራ ስም ነው። ትርጉሙ "የሸለፈት ኮረብታ" ማለት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 5:4
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ወንዶች ሁሉ የሚገረዙበት ምክንያት ተገልጽዋል።
የጦር ሰዎች
ወታደር ለመሆን እድሜያቸው የደረሰ ወንዶች
Joshua 5:6
የያህዌን ድምጽ ታዘዙ
እዚህ ስፍራ "ድምጽ" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ የተናገራቸውን ነገሮች ነው። "ያህዌ ያዘዛቸውን ነገሮች ታዘዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)ወተት እና ማር የምታፈስ ምድር ምድሪቱ ወተት እና ማር ከእነዚያ እንስሳት እና ተክሎች በምድሪቱ እንደሚፈስ፣ ለእንስሳት እና ተክሎች መልካም እንደሆነች እግዘአብሔር ተናገረ።"ከብቶችን ለማርባት እና እህል ለማብቀል እጅግ መልካም ሆነች ምድር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
Joshua 5:8
በዚህ ዕለት የግብጽን ውርደት ከላያችሁ አንከባልያለሁ
ውርደታቸው የተገለጸው መንገዳቸውን እንደዘጋ ትልቅ ድናጋይ/ቆጥኝ ተደርጎ ነው። እዚህ ስፍራ "አንከባልላለሁ" የሚለው "ማስወገድ" የሚል ትርጉም አለው። "በዚህ ዕለት የግብጽን ውርደት ከእናንተ ላይ አስወግጃለሁ" ወይም "በግብጽ ባሮች በነበራችሁ ጊዜ ተዋርዳችሁ ነበር። ዛሬ ግን፣ ከእንግዲህ የተዋረዳችሁ እንዳትሆኑ አድርጌያችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 5:10
በወሩ አስራ አራተኛ ቀን
ይህ በምዕራባውያን ቀን አቆጣጠር ወደ መጋቢት መጨረሻ ነው። "የመጀመሪያው ወር አስራ አራተኛ ቀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የዕብራውያን ቀን አቆጣጠር እና ተከታታይ ቁጥር እንዲሁም ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
Joshua 5:13
ዐይኖቹን አንስቶ ወደ ላይ ሲመለከት እነሆ፣ አንድ ሰው ቆሞ አየ
እዚህ ስፍራ ወደላይ አነሳ የሚለው የተነገረው ኢያሱ በቀጥታ ዐይኖቹን በእጆቹ እንዳነሳ ተደርጎ ነው። "አቅንቶ ሲመለከት አንድ ሰው ቆሞ አየ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር
እነሆ
"እነሆ" የሚለው ቃል ለአዲስ መረጃ ልዩ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል። እርስዎ የሚተረጉሙበት ቋንቋ ይህን የሚተረጉምበት የራሱ መንገድ ሊኖረው ይችላል።
ሰይፉን መዞ በእጆቹ ይዞ ነበር
እዚህ ስፍራ "እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት ሚያመለክቱት ከኢያሱ ፊት የቆመውን ሰው ነው።
Joshua 5:14
እርሱ አለ
"እርሱ" የሚለው ቃል ኢያሱ ያየውን ሰው ያመለክታል።

ከየትኛሁም

ይህ ሰውየው ለኢያሱ ጥያቄ መልስ መስጠት የጀመረበት ነው፣ "አንተ ከእኛ ወይስ ከጠላቶቻችን ጋር ነህ?" ይህ አጭር መልስ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "እኔ ከእናንተም ሆነ ከጠላቶቻችሁ ከየትኛውም ወገን አይደለሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ኢያሱ በአምልኮ ወደ ምድር ተደፋ ይህ የአምልኮ ድርት ነበር። (ትምዕርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ) ጫማህን ከእግርህ አውልቅ ይህ የውዳሴ/አምልኮ ድርጊት ነበር። (ትምዕርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 6

Joshua 6:1

አሁን

ይህ ቃል እዚህ ስፍራ ያገለገለው ዋናው የታሪክ መስመር ሌላ መስመር እንዲከተል ነው።እዚህ ላይ ተራኪው የኢያሪኮ በሮች ለምን እንደተዘጉ እና እንደተቆለፉ ይነግረናል።

ኢያሪኮን፣ ንጉሥዋን፣ እና የሰለጠኑ ወታደሮችዋን በእጃችሁ አሳላፌ ሰጥቻችኋለሁ

ያህዌ ለኢያሱ ይህንን በእርግጥ እንደሚያደርግ የሚነግረው አስቀድሞ ነገሩ ያደረገው መሆኑን በመግለጽ ነው። (ሃላፊ የትንቢት ጊዜ የሚለውን ይመልከቱ)

በእጆችህ

"እጅ" የሚለው ቃል እጅ የሚፈጽመውን ለመቆጣጠር የሚውል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። "ስለዚህ አንተ ይህንን መፈጸም ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 6:3

አያያዥ ሃሳብ፡

እግዚአብሔር ለኢያሱ ህዝቡ ማድረግ ያለበትን መናገሩን ቀጠለ

ይህንን ለስድስት ቀናት ማድረግ አለባችሁ

"ይህንን ለስድስት ቀናት በየዕለቱ በቀን አንዴ ማድረግ አለባችሁ"

ሰባት ካህናት በታቦት ፊት ሰባት ቀንደ መለከት መያዝ አለባቸው

ሰባቱ ካህናት ታቦቱን ከያዙና በከተማይቱ ዙሪያ ከሚጓዙ ሌሎች ካህናት ፊት ይሂዱ

Joshua 6:5

አያያዥ ሃሳብ፡

እግዚአብሔር ለኢያሱ ህዝቡ ማድረግ ያለበትን መናገሩን ቀጠለ

እነርሱ የመለከቱን... ድምጽ ከፍ አድርገው ይንፉት

"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰባቱን ካህናት ነው "ቀንደ መለከት" እና "መለከት" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በኢያሱ 6:4 የተጠቀሰውን ካህናቱ የሚነፉትን ቀንደ መለከት ነው

የከተማይቱ ቅጥር

"የከተማይቱ ውጫዊ ቅጥር" ወይም "ከተማይቱ የታጠረችበት ገንብ"

Joshua 6:6

ነዌ

የኢያሱ አባት ነው።(ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የቃል ኪዳኑን ታቦት ያዙ

"የቃል ኪዳኑን ታቦት ይዛችሁ ተጓዙ)

Joshua 6:8

በያህዌ ፊት

አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ያህዌን በመታዘዝ" ወይም 2) በያህዌ ታቦት ፊት ለፊት" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጸ መለከቶቹን ከፍ አድርገው ነፉ

x

Joshua 6:10

ምንም ድምጽ ከአፋችሁ አይውጣ

ከአንድ ሰው አፍ የሚወጣ ድምጽ የሚያመለክተው የዚያን ሰው ንግግር ወይም ጩኸት ነው። "አትጩሁ ወይም አትናገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያሱ ግን ህዝቡን አዘዘ

ኢያሱ ህዝቡን ከተማዋን መዞር ከመጀመራቸው አስቀድሞ አዘዛቸው። "ኢያሱ ህዝቡን አዝዞ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የድርጊቶች ቅደም ተከተል የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 6:12

ሰባት ካህናት ... ሰባት ድምጸ መለከቶች

"7 ካህናት... 7 ድምጸ መለከቶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በመለከቶቹ ከፍ ያለ ድምጽ አሰሙ

ይህ ማለት ድምጸመለከቶቻቸውን ከፍ ያለ ድምጽ እንዲያሰሙ አድርገው ደጋግመው ነፉ ማለት ነው። "ያለማቋረጥ ድምጸ መለከቶቹ ከፍ ያለ ድምጽ እንዲያሰሙ አደረጉ" ወይም "ያለ ማቋረጥ ድምጸ መለከቶቹን ነፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በሁለተኛው ቀን

በሚቀጥለው ዕለት (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ) እነርሱ ይህንን አደረጉ እስራኤል በኢያሪኮ ዙሪያ በእየለቱ አንድ ጊዜ ዞሩ

ስድስት ቀናት

"6 ቀናት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 6:15

ህዝቡ

ይህ የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል

መለከቶቹን ከፍ ባለ ድምጽ ነፉ

"ድምጸ መለከቶቹን ከፍ አድርገው ነፉ" ወይም "ድምጸ መለከቶቹን ነፉ"

ያህዌ ለእናንተ ሰጥቷችኋል

ኢያሱ ያህዌ ከተማዋን በእርግጥ ለእነርሱ እንደሚሰጥ ነገሩ ከመሆኑ አስቀድሞ እንደተፈጸመ እየተናገረ ነው። (ኃላፊ የትንቢት ጊዜ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰጥቷችኋል

"እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው መላውን የእስራኤል ህዝብ ነው። (አንተ የሚለውን ቃል መገለጫ መልኮች ይመልከቱ)

Joshua 6:17

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢያሱ ለእስራኤል ህዝብ መናገሩን ቀጠለ

ከተማይቱ እና በውስጧ የሚኖሩ ሁሉ ይጠፉ ዘንድ ለያህዌ የተለዩ ይሆናሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከተማይቱን እና በውስጣ የሚኖሩትን ሁሉ ይጠፉ ዘንድ ለያህዌ መለየት አለባችሁ" ወይም " ከተማቱን እና በውስጧ ሚኖሩትን ሁሉ በማጥፋት ለያህዌ መለየት አለባችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዳች ነገር እንዳትወስዱ ተጠንቀቁ

መጠንቀቅ የሚለው የተገለጸው ራሳቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው ተደርጎ ነው። "ነገሮቹን አለመውሰዳችሁን ጥንቃቄ አድርጉ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያ ነገር ችግር ታመጣላችሁ

በከተማይቱ ላይመጥፎ ነገር እንዲፈጠር አንዳች ነገር ማድረግ የተገለጸው በላይዋ ላይ ችግር ማምጣት በሚል ነው። "በእርሷ ላይ መጥፎ ነገር እንዲደርስ ምክንያት ትሆናላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ሃብት

ያህዌን ለማምለክ የተለዩ ነገሮች ስብስብ

Joshua 6:20

ህዝቡ በታላቅ ድምጽ ጮኸ

"የእስራኤል ሰዎች ጮኹ"

በመለከቶች ታላቅ ድምጽ አሰሙ

"መለከቶቹን ከፍ አድርገው ነፉ" ወይም "ቀንደ መለከቶቹን ነፉ"

በሰይፍ ስለት በከተማይቱ ውስጥ የነገረውን ሁሉ ሙሉ ለሙሉ አጠፉ

"የሰይፍ ስለት" የሚለው የሚገልጸው ወታደሮች በጦርነት ውስጥ የሚጠቀሙባቸውን ሰይፎች እና ሌሎች መሳሪያዎች ነው። "በሰይፎቻቸው በከተማይቱ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉ ሙሉ ለሙሉ አጠፉ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ ሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 6:23

ከተማይቱን አቃጠሉ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እስራኤላውያን ወታደሮችን ነው። ረዓብን እና ቤተሰቧቿን ከከተማይቱ ያወጡትን ሁለት ወጣት ወንዶች ብቻ የሚያመለክት አይደለም።
Joshua 6:25
እርሷ በእስራኤል ውስጥ ትኖራለች
"እርሷ" የሚለው ቃል ረዓብን እና ትውልዷቿን ያመለክታል። "የእርሷ ትውልድ በእስራኤል ይኖራል" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እስከ ዛሬ ድረስ
"አሁን" ወይም "ዛሬ ድረስ።" የመጀመሪያው ጸሐፊ ይህንን ታሪክ እንደጻፈው የረዓብ ትውልዶች አሁንም በእስራኤል ይኖራሉ
Joshua 6:26
ዳግም የሚገነባት ሰው በያህዌ ዐይኖች ፊት የተረገመ ነው
በያህዌ አይኖች ፊት የተረገመ የሚለው የሚገልጸው በያህዌ የተረገመ ማለትን ነው። "ዳግም የሚገነባት ሰው ያህዌ የረገመው ይሁን" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መሰረቱን የሚጥለው/ የሚመሰርተው በመጀመሪያ ልጁ የህይወት ዋጋ ይሁን/መሰረቱን ሲጥል የበኩር ልጁ ይሙት
ለኢያሪኮ አዲስ መሰረትን የሚጀምር ሰው የሚከፍለው ዋጋ የመጀመሪያ ልጁ መሞት ነው። ይህ የተነገረው ሰውየው ለስራው እንደሚከፍለው ተመን/ዋጋ ተደርጎ ነው። "መሰረቱን ከጣለ፣ የመጀመሪያ ወንድ ልጁን ያጣል" ወይም "መሰረቱን ከጣለ፣ የመጀመሪያ ልጁ ይሞታል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በታናሹ ልጁ የህይወት ዋጋ በሮቿን ያቆማል/በሮቿን ሲያቆም ታናሹ ልጁ ይሙት
የኢያሪኮን አዲስ በሮች የሚያቆም ሰው የሚከፍለው ዋጋ የታናሹ ልጁ መሞት ነው። ይህ የተነገረው ሰውየው ለስራው እንደሚከፍለው ተመን/ዋጋ ተደርጎ ነው። "በሮቿን ካቆመ፣ የመጨረሻ ልጁን ያጣል" ወይም " "በሮቿን ካቆመ፣ የመጨረሻ ልጁ ይሞታል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዝናው በምድሪቱ ሁሉ ተስፋፋ
ይህ የያህዌን ሳይሆን፣ የኢያሱን ዝና ያመለክታል። በምድሪቱ በሚኖሩ መሃል ታዋቂ ሆነ የሚለው የተገለጸው ዝናው እንደተስፋፋ ተደርጎ ነው። "ኢያሱ በምድሪቱ ሁሉ ዝነኛ ሆነ" ወይም "በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎች ስለ ኢያሱ አወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 7
Joshua 7:1
ለመደምሰስ/መጥፋት የተለዩ ነገሮች
"ያህዌ ፈጽማችሁ በማጥፋት/በመደምሰስ ለእኔ ለዩልኝ ያላቸው ነገሮች"
አካን…ከርሚ…ዘንበሪ…ዛራ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የያህዌ ቁጣ ነደደ
"ቁጣ" እና "ነደደ" የሚሉት የሚገልጹት በአካል እሳት እንዳለ ሳይሆን የቁጣውን ከፍተኛነት ደረጃ ነው። "የያህዌ ቁጣ እንደ እሳት ነደደ" ወይም "ያህዌ እጅግ ተቆጥቶ ነበር" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 7:2
ህዝቡ ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰራዊት ነው።
እነርሱ በቁጥር ጥቂት ናቸው
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጋይን ሰዎች ነው።
Joshua 7:4
ከሰራዊቱ ሶስት ሺህ ወንዶች ተነስተው ወጡ
እነዚህ ወንዶች የሰራዊቱ ክፍል ነበሩ። "የሰራዊቱ ክፍል የሆኑ ሶስት ሺህ ወንዶች ወጡ"
ሶስት ሺህ ወንዶች…ሰላሳ ስድስት ወንዶች
"3,000 ወንዶች… 36 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የህዝቡ ልብ ቀለጠ እንደ ውሃ ሆነ
"ቀለጠ" እና "እንደ ውሃ ሆነ" የሚሉት ሃረጋት ተመሳሳይ ትርጉምን ይጋራሉ፤ በአንድነት ተቀናጅተው የቀረቡት ሰዎቹ እጅግ ፈርተው እንደነበር አጉልቶ ለማሳየት ነው። (ትይዩ ንጽጽዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የህዝቡ ልብ ቀለጠ
እዚህ ስፍራ ላይ ህዝቡ የተገለጸው በእነርሱ "ልቦች" ነው ይህም ስሜቶቻቸውን በትኩረት ለመግለጽ ነው። "ህዝቡ እጅግ ፈርቶ ነበር" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ ሚለውን ይመልከቱ
የህዝቡ ልብ
"ህዝቡ" የሚለው ሃረግ የሚያመለክተው እስራኤላውያን ወታደሮችን ነው።
Joshua 7:6
ልብሶቹን ቀደደ… በጭንቅላታቸው አብዋራ ነስንሰው በያህዌ ታቦት ፊት በግንባራቸው ተደፉ
እነዚህን ነገሮች ያደረጉት በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል እንዳዘኑ እና እንደተጨነቁ ለማሳየት ነው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ያጠፉን ዘንድ ለአሞራውያን እጆች አሳልፈህ ልትሰጠን ነውን?
ኢያሱ እግዚአብሔር ዮርዳኖስን አሻግሮ ያመጣቸው ምክንያቱ ይህ እንደሆነ እየጠየቀ ነበር። "ይህን የደረግከው አሞራውያን ያጠፉን ዘንድ ለእነርሱ እጆች አሳልፈህ ልትሰጠን ነውን?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢሊፕሰስ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
ያጠፉን ዘንድ ለአሞራውያን እጆች አሳልፈህ ልትሰጠን ነውን?
የአሞራውያን እጆች የሚለው የሚገልጸው አቅማቸውን እና ሃይላቸውን ነው። እነርሱን ለመደምሰስ እስራኤላውያንን ለእጆቻቸው መስጠት የሚለው የሚገልጸው አሞራውያን እስራኤላውያንን እንዲቆጣጠሩ እና እንዲያጠፏቸው መፍቀድን ነው። "አሞራውያን እንዲያጠፉን ትፈቅዳለህን?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ምነው ሌላ ውሳኔ ባደረግን ኖሮ
"ባደረግን ኖሮ" የሚለው ቃል የሚያሳየው አንድ ነገር ምነው ባልሆነ ኖሮ የሚል ፍላጎትን መግለጫ ነው። "ምነው የተለየ ውሳኔ አድርገን ቢሆን ኖሮ"
Joshua 7:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢያሱ መጨነቁን ለያህዌ ይገልጻል
እስራኤል ጀርባውን ለጠላቶቹ ከሰጠ በኋላ ምን ማለት እችላለሁ?
ኢያሱ ይህን የሚናገረው ምን መናገር እንዳለበት እንኳን እስከሚረበሽ ድረስ ተስፋ መቁረጡን ለመግለጽ ነው። "ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም። እስራኤል ጀርባውን ለጠላት ሰጥቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እስራኤላውያን ጀርባቸውን በጠላቶቻቸው ፊት አዙረዋል
ይህንን ማድረግ የሚገልጸው ከጠላቶቻቸው ፊት መሸሻቸውን ነው። "እስራኤል ከጠላቶቻቸው ሸሽተዋል/ እስራኤላውያንን ጠላቶቻቸው አሳደዋቸል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ እኛን ይከባሉ፣ ደግሞም በምድር የሚኖሩ ሰዎች ስማችንን እንዲረሱ ያደርጋሉ
ሰዎች የእስራኤልን ስም እንዲረሱ ማድረግ የሚገልጸው፤ እስራኤላውያንን እንዲረሱ ማድረግን ነው። በዚህ ሁኔታ ይህንን የሚያደርጉት እስራኤላውያንን በመግደል ነው። "ይከቡናል፣ ይገድሉንማል፤ ደግሞም የምድር ህዝብ ሁሉ ይረሳናል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ለታላቁ ስምህ
"ታላቁ ስምህ" የሚለው ሃረግ እዚህ ስፍራ የሚገልጸው የእግዚአብሔርን ዝና እና ሃይል ነው። "እናም ስለዚህ አንተ ታላቅ መሆንህን ህዝቦች ያውቁ ዘንድ ምን ታደርጋለህ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ለታላቁ ስምህ ምን ታደርጋለህ?
ኢያሱ ይህንን ጥያቄ ያነሳው እስራኤላውያን ከተደመሰሱ፣ ሌሎች ህዝቦች እግዚአብሔር ታላቅ አይደለም ብለው ያስባሉ የሚለውን ለእግዚአብሔር ለማሳሰብ/ እግዚአብሔርን ለማስጠንቀቅ ነው። "ከዚያ ለስምህ ታላቅነት ልታደርገው የምትችለው ምንም ነገር አይኖርም" ወይም "ከዚያ ሰዎች አንተ ታላቅ መሆንህን አያውቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
Joshua 7:10

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እስራኤል ለምን እንደተረገመ ለኢያሱ መለሰለት።
ለምን በዚያ በፊትህ ተደፋህ?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ኢያሱ በዚያ በፊቱ መደፋቱን ለመገሰጽ ነው። "በአፍር ላይ በዚያ መደፋትህን አቁም!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ)
ተለይተው ተቀምጠው የነበሩት ነገሮች
እነዚህ በኢያሱ 6፡18-19 "እንዲጠፉ የተለዩ" ነገሮች ናቸው። "የተረገሙት ነገሮች" ወይም "እግዚአብሔር የረገማቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ሰርቀዋል ከዚያም ደግሞ ኃጢአታቸውን ደብቀዋል
ኃጢአታቸውን መደበቅ የሚለው የሚገልጸው ኃጢአት መስራታቸውን ሌሎች እንዳያውቁ ለማድረግ መሞከራቸውን ይገልጻል። "እነዚያን ነገሮች ሰርቀዋል፣ ከዚያም ቀጥሎ ኃጢአት መስራታቸውን ሰዎች እንዳያውቁ ለማድረግ ሞክረዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በጠላቶቻቸው ፊት መቆም አይችሉም
በጠላቶቻቸው ፊት መቆም የሚለው የሚወክለው ጠላቶቻቸውን ውጤታማ ሆነው መውጋት አይችሉም የሚለውን ነው። "ጠላቶቻቸውን ውጤታማ ሆነው መውጋት አይችሉም" ወይም "ጠላቶቻቸውን ማሸነፍ አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ለጠላቶቻቸው ጀርባቸውን አዞሩ/ጀርባቸውን አዙረው ሸሹ
ይህንን ማድረግ የሚወክለው ከጠላቶቻቸው መሸሻቸውን ነው። "ከጠላቶቻቸው ሸሹ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከእንግዲህ ከእናንተ ጋር አልሆንም
ከእስራኤል ጋር መሆን የሚወክለው እስራኤልን መርዳትን ነው። "ከእንግደህ በኋላ አልረዳችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 7:13
አያያዥ ሃሳብ፡
ያህዌ ከኢያሱ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ፤ ደግሞም ለህዝቡ መናገር ያለበትን ነገረው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ህዝቡ
ይህ የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል
ጠላቶቻችሁን መቋቋም አትችሉም
ከጠላቶቻቸው ፊት መቆም የሚገልጸው ከጠላቶቻቸው ጋር ተዋግተው በስኬት ማሸነፍን ነው። "ከጠላቶቻችሁ ጋር በስኬት መዋጋት አትችሉም" ወይም "ጠላቶቻችሁን ማሸነፍ አትችሉም"
Joshua 7:14
አያያዥ ሃሳብ፡
ያህዌ ከኢያሱ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ፤ ደግሞም ለህዝቡ መናገር ያለበትን ነገረው።
ራሳችሁን በየነገዳችሁ ማቅረብ አለባችሁ
የእስራኤልን ህዝብ የሚመሰርቱ አስራ ሁለት ነገዶች ነበሩ። "በየነገዶቻችሁ" የሚለው ሃረግ ትርጉሙ "በእያንዳንዱ ነገድ" ማለት ነው። "እያንዳንዳቸው ነገዶቻችሁ ራሳችሁን ለያህዌ ማቅረብ ይኖርባቸዋል " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ የሚለየው ነገድ በየጎሳው ይቀርባል
ነገድ ከበርካታ ጎሳ የሚመሰረት ነው። "ያህዌ ከለየው ነገድ፣ እያንዳንዱ ጎሳ ወደፊት ይቀርባል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ የሚለየው ነገድ
የእስራኤል መሪዎች እጣ ያወጣሉ፣ እናም ይህንን በማድረግ፣ ያህዌ የለየውን ነገድ ያውቃሉ። ይህ ይበልጥ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ በእጣ የሚለየው ነገድ" ወይም "እጣ ስናወጣ ያህዌ የሚለየው ነገድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ያህዌ የሚለየው ጎሳ በእያንዳንዱ ቤተሰብ መቅረብ ይኖርበታል
ጎሳ በብዙ ቤተሰቦች የሚመሰረት ነበር። "ያህዌ ከሚለየው ጎሳ፣ እያንዳንዱ ቤተሰብ ወደፊት መቅረብ ይኖርበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ የሚለየው ቤተሰብ በነፍስ ወከፍ መቅረብ ይኖርበታል
ቤተሰብ በርካታ ሰዎች በውስጡ ነበሩት። "ያህዌ ከለየው ቤተሰብ፣ እያንዳንዱ ሰው ወደፊት መቅረብ ይኖርበታል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የተለየው ሰው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ የለየው ሰው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ የያህዌን ቃልኪዳን አፍርሷል
ቃልኪዳንን ማፍረስ የሚለው ያለመታዘዝን ያመለክታል። "እርሱ የያህዌን ቃል ኪዳን አፍርሷል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 7:16
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢያሱ እስራኤልን በያህዌ ፊት ለማቅረብ የያህዌን ትዕዛዝ ተከተለ
እስራኤልን በየነገዱ ወደፊት አቀረበ
"በየነገዱ/ነገድ በነገድ" የሚለው ሃረግ እያንዳንዱ ነገድ ማለት ነው። "እያንዳንዱን የእስራኤል ነገድ ወደፊት አቀረበ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ነገድ ተለየ
ይህ በዐድራጊ አረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ የይሁዳን ነገድ ለየ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ።
የዛራውያንን ጎሳ በነፍስ ወከፍ አቀረበ
"በነፍስ ወከፍ/ በግለሰብ" የሚለው ሃረግ እያንዳንዱ ሰው የሚል ትርጉም የሚሰጥ ፈሊጥ ነው። በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ግለሰቦች የተባሉት የቤተሰባቸው መሪዎች/ አባወራ ነበሩ። "እርሱም የዛራውያንን ጎሳዎች እያንዳንዱን ሰው ወደፊት አቀረበ" ወይም "ከዛራውያን ጎሳ የቤተሰቡ መሪ የሆነ እያንዳንዱን ሰው ወደፊት አቀረበ" (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
የዛራውያን ጎሳ
ጎሳው ስሙን ያገኘው ዛራ ከተባለው ሰው ስም በመነሳት ነው
ዘንበሪ...አካን...ከርሚ...ዛራ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። እነዚህን በኢያሱ 7፡1 ላይ በተረጎሙበት መሰረት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 7:19
ለእርሱ ኑዛዜያችሁን/ንስሃ አቅርቡ
"ንስሃ/ኑዛዜ" የሚለው ረቂቅ ስም "ተናዘዘ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ለእርሱ ተናዘዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ነገሩን ከእኔ አትደብቅ
መረጃን መደበቅ የሚወክለው አንድ ሰው ነገሩን እንዳያውቅ ጠብቆ ለመያዝ መሞከርን ነው። "ያደረግከውን እንዳላውቅ ልትሸሽገኝ አትሞክር" (ዘይቤያዊ አነጋገርየሚለውን ይመልከቱ)
ሁለት መቶ ሰቅል
ይህ ከሁለት ኪሎ ግራም በላይ ነው።(መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)
ሃምሳ ሰቅል
ይህ ከ500 ግራም በላይ ነው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)
በመሬት ውስጥ ተደብቀዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ በመሬት ውስጥ ደብቂያቸዋለሁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 7:22
እነርሱ አዩ/አገኙ
"ኢያሱ የላካቸው ሰዎች አዩ/አገኙ"
እቃዎቹን አውጥተው ዘረጉ
በእርስዎ ቋንቋ ውስጥ የሚገኝን በርካታ ትንንሽ እቃዎችን ከትልቅ ቦርሳ/ሻንጣ መሬት ላይ መድፋትን የሚገልጽ ቃል ይጠቀሙ
Joshua 7:24
የአኮር ሸለቆ
የስሙ ትርጉም "የችግር ሸለቆ" ማለት ነው፣ ነገር ግን አኮርን በተጻፈበት አጠራሩ እንዳለ አኮር ብሎ መተርጎሙ ይመረጣል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 7:25
ለምን አስጨነቅከን?
ኢያሱ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት አካንን ለመገሰጽ ነው። "አንተ እኛን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አስጨነቅከን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሰሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚይም የቀሩትን በድንጋይ ወገሯቸው፤ ደግሞም በእሳት አቃጠሏቸው።
ሊሰጡ የሚችሉ አማራጭ ትርጉሞች 1)እስራኤላውያን የአካንን ቤተሰብ አቃጥለው ገደሉ፤ከዚያም ድንጋይ ከመሩባቸው ወይም 2) እስራኤላውያን የአካንን ቤተሰብ በድንጋይ ወግረው ገደሉ ከዚያም በድናቸውን አቃጠሉ ወይም 3) አካን እና ያለው ሁሉ በድንጋይ ተወገረ ከዚያም ተቃጠለ
ያህዌ የነድ ቁጣውን አራቀ
ቁጣውን አራቀ የሚለው የሚገልጸው ቁጣውን አቆመ ማለት ነው። የሚነድ ቁጣ የሚለው የሚወክለው ጠንካራ ቁጣን ነው። "ያህዌ ከቁጣው ተመለሰ/መቆጣቱን አቆመ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እስከ ዛሬ ድረስ
ጸሐፊው ይህንን እስከጻፈበት ጊዜ ድረስ የአኮር ሸለቆ ተብሎ ይጠራ ነበር

---

Chapter 8
Joshua 8:1
አትፍሩ፣ ተስፋ አትቁረጡ
እነዚህ ሁለት ሃረጋት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ያህዌ ያቀናጃቸው ለፍርሃት አንዳች ምክንያት ስለሌለ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የጋይን ንጉሥ... እና ምድሩን በእጃችህ አሳልፌ ሰጥቼሃለሁ
እነርሱን ለእስራኤላውያን እጆች አሳልፎ መስጠት የሚወክለው ለእስራኤል ድልን እና የበላይነትን መስጠትን ነው። "በጋይ ንጉሥ እና በህዝቡ ላይ ደግሞም በእርሱ ከተማ እና በምድሩ ላይ ድልን ሰጥቼሃለሁ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ሰጥቼሃለሁ
እግዚአብሔር ሊያደርግ ቃል የገባውን ልክ እንዳደረገው ያህል ይናገራል፣ ምክንያቱ እርሱ በእርግጥ ስለሚያደርገው ነው። "እኔ በእርግጥ ሰጥቼሃለሁ" ወይም "እኔ እሰጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትንቢታዊ ኃላፊ ጊዜ የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሷ ንጉሥ
"እርሷ" የሚለው ቃል የጋይን ከተማ ያመለክታል። ከተማዎች ብዙውን ጊዜ ሴት እንደሆኑ ተደርጎ ይነገሩ/ይገለጹ ነበር። "ንጉሥዋ" ወይም "የእነርሱ ንጉሥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 8:3
የጦርነት ሰዎች
"የእስራኤል ሰራዊት"
ሰላሳ ሺህ ወንዶች
"30,000 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 8:5
አጠቃላይ መረጃ
ኢያሱ ለወታደሮቹ የጦር ሜዳውን እቅድ መግለጹን ቀጠለ
በእጃችሁ ይሰጣችኋል
እዚህ ስፍራ "እጅ" ምሳሌነቱ እስራኤላውያን በጠላቶቻቸው ላይ ያላቸውን የበላይነት እና ሃይል የሚገልጽ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 8:8
አጠቃላይ መረጃ
ኢያሱ ለወታደሮቹ የጦር ሜዳውን እቅድ መግለጹን አጠናቀቀ።
ኢያሱ ላካቸው
ይህ ሃረግ የሚያመለክተው ኢያሱ በጋይ እንዲያደፍጡ የተመረጡ ሰላሳ ሺህ ወንዶችን መላኩን ነው
የደፈጣው ስፍራ
"ጥቃት የማድረሻው ጊዜ እስኪደርስ ድረስ እነርሱ የሚደበቁበት ስፍራ ነው"
Joshua 8:10
አምስት ሺህ ወንዶች"5,000 ወንዶች"
ይህ ቡድን ከ"ሰላሳ ሺህ ወንዶች" ውስጥ የተወሰደ ይመስላል (ኢያሱ 8:9)። 25,000 የሚያህሉት ወንዶች ከተማዋን ሲያጠቁ ይህ አነስ ያለው ቡድን አድፍጦ ቆየ። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 8:13
አጠቃላይ መረጃ፡
እስራኤላውያን ጋይን ለመውጋት ተዘጋጁ
ዋናው ሰራዊት
ይህ በደፈጣ ላይ ከሆኑት ውጭ ያለውን ትልቁን የተዋጊ ቡድን ያመለክታል
ደጀን ጦር
እነዚህ "በከተማይቱ ምዕራብ አቅጣጫ አድፍጠው የተቀመጡ" ናቸው (ኢያሱ 8፡ 12 ይመልከቱ)
Joshua 8:15
ከእነርሱ አስቀድሞ ራሳቸው ይሸነፉ
"ከጋይ ሰዎች አስቀድሞ ራሳቸው ይሸነፉ" "ከእነርሱ አስቀድሞ" የሚለው ሃረግ የሚወክለው የጋይ ሶች የሚያዩትን እና የሚያስቡትን ነው። "የጋይ ሰዎች እስራኤላውያን እንደተሸነፉ ያስቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከእነርሱ አስቀድሞ ራሳቸው ይሸነፉ
"ይሸነፉ" የሚለው ሃረግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የጋይ ሰዎች እስራኤላውያንን ያሸነፉ ይምሰላቸው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእነርሱ አስቀድሞ... ተከትለው ሄዱ... እነርሱ ተባረሩ
እዚህ ስፍራ "ከእነርሱ" እና "እነርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የጋይን ሰራዊት ነው።
እነርሱ ሸሹ ... ከእነርሱ በኋላ ተከተሉ
እዚህ ስፍራ "ከእነርሱ" እና "እነርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የእስራኤልን ሰራዊት ነው
በከተማይቱ የነበሩ ሰዎች ሁሉ በአንድነት ተጠሩ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የከተማይቱ መሪዎች የከተማይቱን ህዝብ በአንድነት ጠሩ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በከተማይቱ የነበሩ ሰዎች ሁሉ
ስለ ሁሉም ሰዎች አጠቃላይ በሆነ መንገድ ይጽፋል፣ ነገር ግን፣ "ሰዎች ሁሉ" የሚለው የሚያመለክተው መዋጋት የሚችሉትን ሰዎች ብቻ ነው። "በከተማይቱ የነበሩ የእስራኤልን ሰራዊት ማባረር የሚችሉ ሰዎች ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና ማጠቃለያ የሚሉትን ይመልከቱ።
ክፍት ትተው
"ከተማይቱን ክፍት ትተው"
Joshua 8:24
እስራኤላውያን ሁሉንም የምድሪቱን ነዋሪዎች አጥፍተው ሲጨርሱ... ሁሉም ... በሰይፍ ስለት በወደቁ ጊዜ
እዚህ ስፍራ "ወደቁ" የሚለው ሞቱ/ተገደሉ ለሚለው ኢፊሚዝም/የማያስደስትን ቃለ ሻል ባለ ቃል መጠቀም ነው። እንደዚሁም "የሰይፍ ስለት" የሚለው የሚወክለው ሰይፎችን በሙሉ ሲሆን ሰይፎች የሚለው የሚወክለው አንድም ጦርነትን ወይም የእስራኤልን ሰራዊት ነው። "በጦርነቱ ውስጥ ሞቱ" ወይም "የእስራኤል ወታደሮች በወጓቸው ጊዜ ሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢፊሚዝም/የማያስደስትን ቃለ ሻል ባለ ቃል መጠቀም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አስራ ሁለት ሺህ
"12,000" ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ
Joshua 8:27
የተተወ ስፍራ
ይህ በአንድ ወቅት ሰዎች የሚኖሩበት፣ አሁን ግን ማንም የማይኖርበት ስፍራ ነው
Joshua 8:29
እስከ ዛሬ ድረስ
"ዛሬ" ወይም "አሁን ድረስ"
Joshua 8:30
የጌባል ተራራ
በከነዓን የሚገኝ ተራራ (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 8:34
ሙሴ ካዘዘው ውስጥ ኢያሱ ያላነበበው አንዲትም ቃል እንኳን አልነበረም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ኢያሱ ሙሴ ያዘዘውን ቃል ሁሉ አነበበ"

ወይም "ኢያሱ የሙሴን ህግጋት ሁሉ አነበበ" (ድርብ አሉታዎች) ይህ የእስራኤልን መንግስት ያመለክታል
እስራኤል

Chapter 9

Joshua 9:1

የዮርዳኖስ

ለዮርዳኖስ ወንዝ አጭር ስያሜ ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)በአንድ እዝ ስር እዚህ ስፍራ "እዝ/አዛዥ" የሚለው የሚወክለው የሚያዛቸውን አዛዥ ነው። በእርሱ ስር መሆን የሚወክለው የእርሱን ትዕዛዞች መቀበልን ነው። "የአንድን መሪ ትዕዛዞች መቀበል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 9:3

የማታለል እቅድ

ኢያሱን እና እስራኤላውያንን ለማታለል የተደረገ ማጭበርበር

ደረቅ እና የሻገተ

"ደረቅ እና በሻጋታ የተሞላ" ወይም "የሻገተ እና ያረጀ

Joshua 9:6

የእስራኤል ወንዶች

ይህ መላውን የእስራኤል መንግስት ያመለክታል። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መወከል)

ሖራውያን

ይህ የገባዖናውያን ሌላ ስማቸው ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ምናልባት እናንተ በእኛ አቅራቢያ የምትኖሩ ልትሆኑ ትችላላችሁ። እንዴት ከእናንተ ጋር ቃል ኪዳን መግባት እንችላለን?

ኢያሱ የእስራኤል ህዝብ ከማናቸውም ነገር በላይ ለያህዌ ትእዛዝ ትኩረት ሰጥተው መከተል እንዳለባቸው ትኩረት ይሰጣል። "በእኛ አቅራቢያ የምትኖሩ ከሆናችሁ፣ ከእናንተ ጋር ቃል ኪዳን መግባት አንችልም" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 9:9

የዮርዳኖስ

ለዮርዳኖስ ወንዝ አጭር ስያሜ ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴዎን

ይህ የተሸነፈው የአሞራውያን ንጉሥ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሔሴቦን

x

Joshua 9:11

በእጃችሁ

የዚህ ሃረግ ትርጉም "ይዛችሁ ሂዱ" የሚል ነው። እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚወክለው ከአቅርቦት ውስጥ ገባዖናውያን ያላቸውን ነው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር ወከል)አግጃቸውና እንዲህ በሏቸው "እነሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰዎች ነው

Joshua 9:14

ኢያሱ አብረዋቸው ይኖሩ ዘንድ ከእነርሱ ጋር ሰላምን እና ቃልኪዳንን አደረገ። እንደዚሁም የህዝቡ መሪዎችም ለእነርሱ ቃለመሃላ አደረጉ።

እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ነገር መደረጉን ይናገራሉ። የእስራኤል ህዝብ መሪ ኢያሱ፣ ገባዖናውያንን እንደማይገድል ቃል ገባ። የእስራኤል ህዝብ መሪዎችም በተመሳሳዩ ይህንኑ ቃል ኪዳን ገቡ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቡ

እዚህ ስፍራ ይህ ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 9:16

ሶስተኛ ቀን

ይህ በቅደም ተከተል ቁጥር ሶስትን ያመለክታል (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከፊራ

ይህ ከገባዖን ከተሞች አንዱ ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ብኤሮት

ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቂርያትይዓይሪም

ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 9:18

ህዝቡ

እዚህ ስፍራ ይህ ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው።

Joshua 9:20

"ገባዖናውያን እንጨት ቆራጮች እና ውሃ ቀጂዎች ሆኑ"

"ገባዖናውያን እንጨት ቆራጮች እና ውሃ ቀጂዎች ሆኑ"

Joshua 9:22

የአምላኬ ቤት

እዚህ ይህ ሃረግ የሚያመለክተው የማደሪያውን ድንኳን፣ የያህዌን ማደሪያ ስፍራ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 9:24

መልካም እና ትክክል የሚመስለውን ሁሉ

"መልካም" እና "ትክክል" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ አንድ አይነት ነገር ማለት ናቸው። "ተገቢ እና ትክክል የሚመስልህን ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 9:26

ለእነርሱ

እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ገባዖናውያንን ነው።እስከዚህ ቀን ድረስ "እስከ አሁን ድረስ እንኳን።" ይህ ማለት ህዝቡ እነዚህን ነገሮች ጸሐፊው ይኖር እስከ ነበረበት ጊዜ ድረስ ጭምር ማድረጋቸውን ቀጥለው ነበር ማለት ነው

Chapter 10

Joshua 10:3

የርሙት... ለኪሶ.. ዔግሎ

እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሆሃም... ጲርአም... ያፊዓ..ዳቤር

እነዚህ የንጉሦች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እኔ ና

"እኔ ወዳለሁበት ተጓዝ።" ኢየሩሳሌም በከነአን ለሚገኙ ከተሞች ሁሉ ከፍ ባለ ስፍራ ላይ የምትገኝ ከተማ ነበረች።

Joshua 10:5

አምስት ንጉሦች

"5 ንጉሦች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የርሙት... ለኪሶ.. ዔግሎ

እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አስፋፈራቸውን ከገባዖን በተቃራኒ አደረጉ

ይህ ማለት ሰፈራቸውን በከተማቸው ዙሪያ አደረጉ። ይህ በከተማይቱ የሚኖሩትን ማዳከሚያ መንገድ ነበር። ድርጊቱ ሰዎች ከከተማይቱ እንዳያመልጡ ያግዳል፣ እንደዚሁም ሌሎች ምግብ እና ውሃ ወደ ከተማይቱ እንዳያመጡላቸው ያግዳል።

Joshua 10:6

እነርሱ እንዲህ አሉ

"እነርሱ" የሚለው ቃል እዚህ ስፍራ የሚያመለክተው ገባዖናውያንን ነው።

እጆችህን ከባሪያዎችህ አታርቅ/አታንሳ

ይህ ትሁት ልመና በሁለት አሉታዎች ተገልጾዋል፣ ይህም አዎንታዊ ድርጊት/እርዳታ ማስፈለጉን በአጽንኦት ለመግለጽ ነው። "እባክህ መጥተህ በብርቱ እጆችህ ታደገን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

እጆችህ

እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው ቃል የእስራኤልን ህዝብ ጥንካሬ ያመለክታል።

"የአንተ ጥንካሬ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:8

እነርሱን በእጆችህ አሳልፌ ሰጥቼሃለሁ

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚወክለው የእስራኤልን ህዝብ ጥንካሬ እና ጠላቶቻቸውን የማሸነፍ አቅማቸውን ነው። "እነርሱ" የሚለው ቃል አጥቂ የሆነውን ሰራዊት ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለእነርሱ ሰጥቻቸዋለሁ

እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል ጥቃት የሚጥለውን ሰራዊት ያመለክታል።

Joshua 10:9

ኢያሱ መጣ

እዚህ ስፍራ መላው የእስራኤል ሰራዊት የተጠቀሱት በመሪያቸው በኢያሱ ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)ያህዌ በእስራኤል ፊት ጠላቶቻቸውን ግራ አጋባቸው እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው መላውን የእስራኤል ሰራዊት ያመለክታል። ቤትሖሮን… ዓዜቅ… መቄዳም እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:11

ቤትሖሮን… ዓዜቅ

እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከላይ ከሰማይ ትላልቅ ድንጋይ አወረደባቸው

"ከሰማይ የበረዶ ድንጋይ አወረደባቸው"

Joshua 10:12

ፀሐይ በገባዖን ትቁም፣ ጨረቃም በኤሎን ሸለቆ ትቁም

ኢያሱ በዚህ ቀን ጊዜ ያህዌ ጊዜ መንቀሳቀሱን እንዲያቆም ጸለየ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን መልከቱ) ፀሐይ… ጨረቃ ኢያሱ ፀሐይን እና ጨረቃን እንደ ሰው አዘዛቸው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ) የኤሎን ሸለቆ ይህ የቦታ ስም ነው (ስሞች እንዴት ይተጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 10:13

ሃገሪቱ

እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የባርነታቸውን ስፍራ የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ባሮች በነበርንበት አገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በውስጣቸው አቋርጠን ባለፍንባቸው አገራት
"እኛ በውስጣቸው ባለፍንባቸው አገሮች"
Joshua 24:19
ህዝቦች
ይህ የሚያመለክው እስራኤላውያንን ነው።
እርሱ ቀናተኛ አምላክ ነው
እግዚአብሔር ህዝቡ እርሱን ብቻ እንዲያመልከው ይፈልጋል
እርሱ ያጠፋችኋል
የያህዌ ቁጣ የተገለጸው እነርሱን እንደሚያጠፋ እሳት ሆኖ ነው። "በእሳት እንደሚያጠፋ እርሱ እናንተን ያጠፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Joshua 24:21
ህዝቦች
ይህ የሚያመለክው እስራኤላውያንን ነው።
ልባችሁን ወደ ያህዌ መልሱ
ያህዌን ብቻ ለመታዘዝ መወሰን የሚለው የተነገረው ልባቸውን ወደ እርሱ እንደ ማዞር ተደርጎ ነው። እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው የሚገልጸው መላ ማንነትን ነው። በዚህ ሁኔታ፣ "ልብ" ብዙ ቁጥር ነው፤ ምክንያቱም መላውን እስራኤል እንደ አንድ ቡድን ይገልጻል። የሆነ ሆኖ፣ "የእናንተ" የሚለው ብዙ ቁጥር እንደመሆኑ ይህንን በብዙ ቁጥር መተርጎሙ እጅግ የተሻለ ይሆናል። "ራሳችሁን ወደ ያህዌ መልሱ" ወይም "ያህዌን ለመታዘዝ ወስኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር፣ ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና አንተ የሚለው ቃል መልኮች/ቅርጾች የሚሉትን ይመልከቱ)
Joshua 24:24
ህዝቦች
ይህ የሚያመለክው እስራኤላውያንን ነው።
እኛ የእርሱን ድምጽ እንሰማለን
እዚህ ስፍራ "መስማት" የሚለው መታዘዝ ማለት ነው። "እርሱ እንድናደርገው የነገረንን ነገር ሁሉ እንታዘዛለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ህግ መጽሐፍ
ይህ የሙሴ መጽሐፍት ቀጣይ ሊሆን ይችላል።
በዚያ አስቀመጠው
"በዚያ አኖረው/አደረገው"
Joshua 24:27
ህዝቦች
ይህ የሚያመለክው እስራኤላውያንን ነው።
ይህ ድንጋይ ምስክር ይሆናል... ሁሉንም ቃላት ሰምቷል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ኢያሱ ያስቀመጠው ድንጋይ የተገለጸው የተባለውን ሁሉ እንደሰማ እና የተነገረውን ለመመስከር እንደሚችል ሰው ተደርጎ ነው። (ሰውኛ የሚለውን ዘይቤ ይመልከቱ)

ሆናችሁ አትገኙ

"ሆናችሁ ባትገኙ"

Joshua 24:29

የ110 አመት ሽማግሌ

"የአንድ መቶ አስር አመት ሽማግሌ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ተምና ሴራ... ገዓስ ተራራ

የቦታ ስሞች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Joshua 24:31

ኢያሱ በሕይወት በነበረበት ዘመናት በሙሉ

ይህ የኢያሱን መላ ህይወት የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያሱ ከሞተ በኋላ የኖሩ

"ከኢያሱ በኋላ የኖሩ"

Joshua 24:32

የዮሴፍ አጽም ... በሴኬም ቀበሯቸው

የዚህን ዐረፍተ ነገር አጀማመር ስርአት መለወጥ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "የእስራኤል ህዝብ የዮሴፍን አጽም ከግብጽ አውጥተው በሴኬም ቀበሯቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

አንድ መቶ ሰቅል/ገንዘብ

"100 ሰቅል/ገንዘብ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አልዓዛር

የወንድ ስም (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጊብዓ

የቦታ ስም (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 1

Judges 1:1

አያያዥ መግለጫ

መጽሐፈ መሳፍንት የኢያሱን ታሪክ የሚቀጥል ሲሆን በተጨማሪም የአዲሱ ታሪክ ክፍል ጅማሬም ነው።

ያህዌ

ይህ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገለጠው ስሙ ነው። ያህዌን እንዴት መተርጎም እንደሚኖርብህ ለመገንዘብ የትርጉም ቃል ገጽን ተመልከት።

ከነዓናውያንን ማን ይወጋልናል

“እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ሳይሆን የእስራኤልን ሕዝብ ነው።

ይሁዳ ይወጋቸዋል

እዚህ ጋ “ይሁዳ” የሚወክለው የይሁዳ ነገድ የሆነውን ሕዝብ ነው። በመጀመሪያ እንዲወጉ እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች ያዛቸዋል። አ.ት: “የይሁዳ ሰዎች በመጀመሪያ መውጋት አለባቸው”

ተመልከቱ

“እዩ” ወይም “ስሙ” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ”

ይህቺን ምድር

ይህ ከነዓናውያን ይኖሩበት የነበረውን ምድር ያመለክታል። አ.ት: “የከነዓናውያን ምድር”

ወንድሞቻቸው

“እስራኤላውያን ባልንጀሮቻቸውን” ወይም “ዘመዶቻቸውን”

ከእኛ ጋር ውጡ

የይሁዳና የስምዖን ነገድ ሰዎች ከተቀሩት እስራኤላውያን ሕዝቦች ጋር በዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ ሰፍረው ነበር። ለይሁዳ ተሰጥቶት የነበረው ምድር ከሸለቆው በላይ በኩል፣ በኮረብታው ላይ ነበር። አንዳንድ ቋንቋዎች፣ አብዛኛውን ጊዜ ሰዎቹ ወደ ላይ መውጣታቸውን ወይም መውረዳቸውን ያመለክቱም። አ.ት: “ከእኛ ጋር ኑ” ወይም “ከእኛ ጋር ሂዱ”

ወደ ተመደበልን - ወደ ተመደበላችሁ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት: “እግዚአብሔር ወደ መደበልን … እግዚአብሔር ወደ መደበላችሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እኛም ከእናንተ ጋር እንሄዳለን

“እኛም ደግሞ ከእናንተ ጋር እንሄዳለን” ወይም “በተመሳሳይ እኛም ከእናንተ ጋር እንሄዳለን”

Judges 1:4

የይሁዳ ሰዎች ተዋጉ

በውስጠ ታዋቂ የስምዖን ሰዎችም ከይሁዳ ሰዎች ጋር ሆነው መዋጋታቸውን ያመለክታል።

አሥር ሺህ ገደሉ

“10,000 ያህሉን ገደሉ” ወይም “ብዙ ሕዝብ ገደሉ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ከእነርሱ

“የከነዓናውያንና የፌርዛውያን ወታደሮች” ወይም “ጠላቶች”

ቤዜቅ

በከነዓን ተራራዎች ላይ ያለ አካባቢ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አዶኒቤዜቅ

ይህ ሰው የከነዓናውያንና የፌርዛውያን ሰራዊት አለቃ ነበር። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እርሱን ተዋጉት

እዚህ ጋ “እርሱን” የሚያመለክተው በመሠረቱ አዶኒቤዜቅንና ሰራዊቱን ነው። አ.ት: “እርሱንና ሰራዊቱን ተዋጓቸው”

Judges 1:6

አሳደዱት

“አባረሩት”

ሰባ ነገሥታት

“70 ነገሥታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የእጅና የእግሮቻቸው አውራ ጣት የተቆረጠባቸው

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት: “የእኔ ሰዎች የእጆቻቸውንና የእግሮቻቸውን አውራ ጣቶች እንዲቆርጡ ያዘዝኳቸው” ወይም “የእጅና የእግሮቻቸውን አውራ ጣት የቆረጥናቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከጠረጴዛዬ ስር ምግባቸውን ይለቅሙ ነበር

እነዚህ ነገሥታት ፍርፋሪ እንዲለቅሙ መገደዳቸው አዶኒቤዜቅ እነዚህን ነገሥታት ምን ያህል እንዳዋረዳቸው ያሳያል። እዚህ ጋ ምግብ “መልቀም” ማለት እንደሚመገቡት ያመለክታል። አ.ት: “ከጠረጴዛዬ ስር ፍርፋሪ ይበሉ ነበር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 1:8

የኢየሩሳሌምን ከተማ እና …ወሰዷት

እዚህ ጋ “ከተማ” የሚወክለው ሕዝብን ነው። አ.ት: “በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች እና … አሸነፏቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወጓት

እዚህ ጋ “እርሷ” የሚያመለክተው ከተማን፣ ይኸውም የሚኖሩባትን ሰዎች ነው። አ.ት: “የከተማይቱን ሰዎች ወጓቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሰይፍ ስለት

“በሰይፋቸው ጫፍ”። እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚወክለው ወታደሮች በጦርነት ውስጥ የሚጠቀሙበትን ሰይፍና ሌሎች የጦር መሣሪያዎች ነው። አ.ት: “በሰይፎቻቸው” ወይም “በጦር መሣሪያዎቻቸው”

የይሁዳ ሰዎች ለመዋጋት ወረዱ

ከኢየሩሳሌም በሚጓዙበት ጊዜ “ወረዱ” የሚለውን ቃል መጠቀም የተለመደ ነበር። አ.ት: “የይሁዳ ሰዎች ለመዋጋት ሄዱ”

በኔጌብ ውስጥ

“በደቡባዊው የይሁዳ ምድረ በዳ”

የኮረብታ ግርጌ

ከተራራ በታች ያሉ ኮረብታዎች ወይም የተራራ ወገብ

የኬብሮን ስም ቀድሞ ቂርያት አርባቅ ነበር

ይህ ዳራዊ መረጃ ነው። ይህንን መጽሐፍ በመጀመሪያ ያነበቡ አንዳንድ ሰዎች ምናልባት ቂርያት አርባቅ የሚለውን ሰምተው ይሆናል፣ ነገር ግን እርሱኑ የኬብሮን

ከተማ ብለው እንደሚጠሩት አያውቁም ነበር። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ሴሲን፣ አኪመንና ተላሚን

እነዚህ በኬብሮን የሚኖሩ የሦስቱ ከነዓናውያን አለቆች ስም ነው። እያንዳንዱ አለቃ ሰራዊቱን ይወክላል። ኢ.ት፡ "ሴሲን፣ አኪመን፣ ተላሚና ሰራዊታቸው" (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 1:11

የዳቤር ስም ቀድሞ ቅርያት ሤፍር ነበር

ደራሲው ምናልባት ይህንን የጻፈው አንባቢዎቹ ከተማይቱን በዳቤር ስም ስለሚያውቋት ይሆናል። እስራኤላውያን በወጓት ጊዜ ግን ቅርያት ሤፍር በመባል ትታወቅ ነበር። ኢ.ት፡ "ቂርያትሤፍር ተብላ የምትጠራውን" (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ቀድሞ

"ባለፈው ዘመን" ወይም "በድሮ ጊዜ"

ቂርያት ሤፍርን የሚወጋና የሚወስዳት

እዚህ ጋ "ቂርያት ሤፍር" የሚወክለው ሕዝቡን ነው። ኢ.ት፡ "የቂርያት ሤፍርን ሕዝብ የሚወጋና የሚያሸንፍ ከተማቸውንም የሚወስድ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዓክሳ

ይህ የካሌብ ሴት ልጅ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል

እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 1:14

አጥብቃ ነገረችው

"ዓክሳ ለጎቶንያል አጥብቃ ነገረችው"

መሬቱን ሰጥተኸኛልና እርሻውን ስጣት

ይህ የሚያሳየው በቁጥር 14 ላይ በጠየቀችው ጊዜ እርሻውን እንደሰጣት ነው። በቁጥር 15 ደግሞ ከእርሻው በተጨማሪ የምንጩን ውሃ ትጠይቀዋለች።

በረከትን ስጠኝ

"ውለታ ዋልልኝ" ወይም "ይህንን አድርግልኝ"

የኔጌብን ምድር ሰጥተኸኛልና

ካሌብ ዓክሳን ለጎቶንያል ስለዳረለት ጎቶንያል በማረካት በኔጌብ ከተማ ከእርሱ ጋር ኖረች። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉሙ መብራራት መቻል አለበት። ኢ.ት፡ "በኔጌብ እንድኖር እስከዳርከኝ ድረስ"

Judges 1:16

የሙሴ አማት

"የሙሴ የሚስቱ አባት"

ቄናዊው አማቱ ወጣ

"ከቄናውያን ሰዎች አንዱ የሆነው አማቱ ወጣ"

ከዘንባባዎቹ ከተማ ወደ ምድረበዳው ወጣ

"የዘንባባዎቹን ከተማ ትቶ … ወደ ምድረበዳ ወጣ"

የዘንባባዎች ከተማ

ይህ የኢያሪኮ ሌላኛው ስም ነው።

አራድ

ይህ በከነዓን የሚገኝ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የወንድሞቻቸው የስምዖን ሰዎች

እዚህ ጋ "ወንድሞች" ማለት በሌላው የእስራኤል ነገድ ውስጥ የሚኖሩ ዘመዶች ማለት ነው።

ጸፋት

ይህ በከነዓን የሚገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የከተማይቱ ስም ሔርማ ተብሎ ተጠራ

እስራኤላውያን ጸፋትን ከደመሰሷት በኋላ ስሟን ሔርማ ብለው ቀየሩት። "ሔርማ" ማለት "ፈጽሞ መጥፋት" ማለት ነው። (እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 1:18

እግዚአብሔር ከይሁዳ ሕዝብ ጋር ነበር

እዚህ ላይ "ከ. . . ጋር" ማለት እግዚአሔር የይሁዳን ሕዝብ ረድቶታል ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሜዳ

ዛፍ የሌለበት፣ በጣም ሰፊ ለጥ ያለ መሬት

Judges 1:20

ኬብሮን ሙሴ እንዳለው ለካሌብ ተሰጥታ ነበር

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ "ሙሴ ኬብሮንን ለካሌብ ሰጥቶት ነበር" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሦስቱን የዔናቅ ወንዶች ልጆች

የሕዝብ ወገን መሪዎች የሆኑት መላውን ማኅበር ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት፡ "የዔናቅ ሦስቱ ወንዶች ልጆቹና ሰዎቻቸው"

ዔናቅ

ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። ዔናቅና ተወላጆቹ በረጅም ቁመታቸው የታወቁ ነበሩ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እስከ ዛሬ ድረስ

"እስካሁን ድረስ"። ይህ የሚያመለክተው መጽሐፈ መሳፍንት የተጻፈበትን ጊዜ ነው።

Judges 1:22

የዮሴፍ ቤት

እዚህ ጋ "ቤት" የሚወክለው ተወላጆችን ነው። ምናሴና ኤፍሬም የዮሴፍ ልጆች ሲሆኑ የ "ዮሴፍ ቤት" የምናሴንና የኤፍሬምን ተወላጆች ሊያመለክት ይችላል። ኢ.ት፡ "የምናሴና የኤፍሬም ተወላጆች" ወይም "የምናሴና የኤፍሬም ነገድ ሰዎች" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቤቴልን ለመውጋት

እዚህ ጋ "ቤቴል" የሚያመለክተው በቤቴል የሚኖሩትን ሰዎች ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰላይ

በምስጢር መረጃ ለማግኘት

ቀድሞ ሎዛ ተብላ ትጠራ የነበረችውን ከተማ

ይህ የዳራው መረጃ ነው። በመጀመሪያ ይህንን መጽሐፍ ያነበቡት ሰዎች ምናልባት ቤቴል ብለው የሚጠሯት ከተማ ሎዛ እንደነበረች አያውቁም ይሆናል። (ዳራዊ መረጃ እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ሰላዮች

በምስጢር መረጃ የሚያገኙ ሰዎች

Judges 1:25

ከተማይቱን ወጉ

እዚህ ጋ "ከተማ" የሚወክለው ሕዝቡን ነው። ኢ.ት፡ "የከተማይቱን ሰዎች ወጉ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሰይፍ ስለት

"በሰይፍ ጫፍ"። "ሰይፍ" እዚህ ጋ የሚወክለው ሰዎች በጦርነት ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን ሰይፍና ሌሎች የጦር መሣሪያዎችን ነው። ኢ.ት፡ "በሰይፎቻቸው" ወይም "በጦር መሣሪያዎቻቸው"

ሂድ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ "አምልጥ" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ሎዛ

በቤቴል አቅራቢያ፣ በኬጢያውያን ምድር የምትገኘው፣ እንደ አዲስ የተቆረቆረችውና ሰውየው የተዋት ይህች ከተማ በሎዛ ስም ትጠራ ነበር።

ይህ እስከ ዛሬ ድረስ ስሟ ነው

"እስካሁን ስሟ ነው"። እዚህ ጋ "እስከ ዛሬ ድረስ" የሚያመለክተው መጽሐፈ መሳፍንት የተጻፈበትን ጊዜ ነው።

Judges 1:27

ቤትሳን፣ ታዕናክ፣ ዶር፣ ይብለዓም፣ መጊዶ

እነዚህ የከተሞች ስም ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከነዓናውያን በዚያች ምድር ለመኖር ወስነው ስለነበር

"መወሰን" በአንድ ነገር ቁርጠኛ አቋም መያዝ ነው። ኢ.ት፡ "ከነዓናውያን ያችን ምድር ላለመተው ቁርጠኛ አቋም ይዘው ስለነበር"

እስራኤል በበረታ ጊዜ

እዚህ ጋ "እስራኤል" የሚወክለው ሕዝቡን ነው። ኢ.ት፡ "የእስራኤል ሕዝብ በበረታ ጊዜ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከነዓናውያን በጉልበት ሥራ እንዲያገለግሏቸው አስገደዷቸው
“ከነዓናውያን ከባድ ሥራ እንዲሠሩላቸው አስገደዷቸው”
Judges 1:29
ኤፍሬም ... አልቻሉም
እዚህ ጋ “ኤፍሬም” ማለት የኤፍሬም ነገድ ሰዎች ወይም ወታደር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጌዝር
በኤፍሬም አካባቢ ከሚገኙ ከተሞች የአንዱ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 1:30
ዛብሎን አላስወጣቸውም
እዚህ ጋ “ዛብሎን” የሚወክለው የዛብሎንን ነገድ ሰዎች ወይም ወታደሮችን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቂድሮን - ነሀሎል
እነዚህ በከነዓን ምድር የሚገኙ ከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ዛብሎን ግን አስገደዳቸው
እዚህ ጋ “ዛብሎን” የሚወክለው የዛብሎንን ነገድ ሰዎች ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከባድ ሥራ
“አስቸጋሪ ሥራ”
Judges 1:31
አሴር አላስወጣቸውም
እዚህ ጋ “አሴር” የሚወክለው የአሴርን ነገድ ሰዎች ወይም ወታደሮች ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዓኮ ... ሲዶን ... አሕላብ፣ አክዚብ፣ ሔልባ፣ አፌቅ ... ረአብ
እነዚህ በከነዓን ምድር የሚገኙ ከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 1:33
ቤት ሳሚስ - ቤት ዓናት
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የቤት ሳሚስና የቤት ዓናት ነዋሪዎች ለንፍታሌም የጉልበት ሥራ ለመሥራት ተገደዱ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የንፍታሌም ሰዎች የቤት ሳሚስንና የቤት ዓናትን ሰዎች እንደ ባሪያ እንዲሠሩላቸው አስገደዷቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 1:34
እንዲወርዱ አልፈቀዱላቸውም
“ከመውረድ አስቆሟቸው”
ሜዳ
ዛፍ የሌለበት በጣም ለጥ ያለ ሰፊ መሬት
የሔሬስ ተራራ
ይህ የኤሎን ከተማ የተሠራበት ረጅም ኮረብታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ኤሎን - ሸዓልቢም
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የዮሴፍ ቤት ወታደራዊ ኃይል ድል አደረጋቸው
“የዮሴፍ ተወላጅ የሆነው ነገድ ሕዝብ ብርቱ ሠራዊት ስለነበራቸው ድል ሊያደርጓቸው ችለዋል”
የዮሴፍ ቤት
እዚህ ጋ “ቤት” የሚወክለው ተወላጆችን ነው። ምናሴና ኤፍሬም የዮሴፍ ልጆች ሲሆኑ የ“ዮሴፍ ቤት” የምናሴንና የኤፍሬምን ተወላጆች ሊያመለክት ይችላል። ኢ.ት፡ “የምናሴና የኤፍሬም ተወላጆች” ወይም “የምናሴና የኤፍሬም ነገድ ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የአቅረቢም ኮረብታ
ይህ ከሙት ባህር በደቡብ ምዕራብ በኩል የሚገኝ መተላለፊያ ነበር። “የጊንጥ መተላለፊያ” በመባልም ይጠራል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሴላዕ
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 2
Judges 2:1
የእግዚአብሔር መልአክ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እግዚአብሔርን የሚወክል መልአክ” ወይም 2) “እግዚአብሔርን የሚያገለግል መልዕክተኛ” ወይም 3) መልአክ መስሎ ከሰው ጋር የተነጋገረውን እግዚአብሔርን ራሱን ያመለክት ይሆናል የሚሉት ናቸው።
ከጌልገላ ወደ ቦኪም ወጣ
“ጌልገላን ትቶ ወደ ቦኪም ሄደ”
ቦኪም
መልአኩ ሕዝቡን ከገሰጻቸው በኋላ እስራኤላውያን ለዚህ ስፍራ በ2:5 ላይ የሰጡት ስም ይህ ነው። “ቦኪም” ማለት “ማልቀስ” ማለት ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
አላቸው
የእግዚአብሔር መልአክ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩ ግልጽ ነው።
ከግብፅ አወጣችሁ
“ከግብፅ መራችሁ”
አባቶቻችሁ
“ቅድም አያቶቻችሁ” ወይም “የቀድሞ አባቶቻችሁ”
ከእናንተ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳኔን አፈረሱ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “አደርግላችኋለሁ ያልሁትን እንዳላደርግ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ድምፄን አልሰማችሁም
“ድምፅ” እዚህ ጋ የሚወክለው እግዚአብሔር የተናገረውን ነው። ኢ.ት፡ “ትዕዛዞቼን አልጠበቃችሁም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይህ ያደረጋችሁት ምንድነው?
ይህ ጥያቄ የተጠየቀው የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን እንዳልታዘዙና በዚህም ምክንያት መከራ እንደሚደርስባቸው እንዲገነዘቡ ነው። ኢ.ት፡ “የከፋ ነገር አድርጋችኋል” (መልስ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Judges 2:3
አሁን እናገራለሁ፣ ‘...ወጥመድ አልሆንባችሁም’
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ይህ ቀጥታ የሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “...ወጥመድ እንደማልሆንባችሁ አሁን እነግራችኋለሁ”
ለጎናችሁ እሾህ ይሆናሉ
ከነዓናውያን እስራኤላውያንን ማስቸገራቸው ለእስራኤላውያን የጎን ውጋት እንደሚሆኑባቸው ተነግሯል። ኢ.ት፡ “መከራ ያመጡባችኋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እሾኽ
እስከ 7 ሴንቲ ሜትር የሚረዝምና ከአንዳንድ እጽዋት ጋር አብሮ የሚበቅል ትናንሽ የሚወጉ ነገሮች ያሉበት እንጨት
አማልክቶቻቸው ወጥመድ ይሆኑባችኋል
እስራኤላውያኑ የከነዓናውያንን አማልክት ማምለካቸው ልክ አደን የሚያድን ሰው ያጠመደው ወጥመድ እንስሳውን ይዞ ለሞት እንደሚዳርገው ሁሉ ሐሰተኞቹ አማልክት አጥፊዎቻቸው እንደሚሆኑ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጮኹና አለቀሱ
“በብዙ ዕንባ አለቀሱ”
Judges 2:6
አሁን ኢያሱ በ ... ጊዜ
እዚህ ጋ “አሁን” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ዋነኛው ታሪክ የተገታበትን ለመለየት ነው። እዚህ ላይ ከኢያሱ በኋላ የነበረው ትውልድ እንዴት ኃጢአትን እንደ ሠሩና ሐሰተኞች አማልክትን እንዳመለኩ፣ እግዚአብሔር እንደቀጣቸው ሆኖም እንዲታደጓቸው መሳፍንትን እንደላከላቸው ተራኪው ጠቅለል ያለ ማብራሪያ

መስጠት ይጀምራል። ይህ ማጠቃለያ የሚያበቃው በ2:23 ላይ ነው።

ኢያሱ 110 ዓመት ሆኖት በሞተ ጊዜ

በ1:1-2:5 ላይ ያለው ሁነት የተፈጸመው ከኢያሱ ሞት በኋላ ነው። ይህ በኢያሱ መጽሐፍ መጨረሻ የተፈጸሙት ሁነቶች በድጋሚ የታሰቡበት ነው።

ወደ ተመደበላቸው ስፍራ

ይህ አገላለጽ በይበልጥ ግልጽ መሆን ይችላል። ኢ.ት: " እግዚአብሔር ወደ ሰጣቸው ስፍራ"

በሕይወት ዘመኑ

ይህ ማለት አንድ ሰው የኖረበት ጊዜ ማለት ነው። ኢ.ት: "ዕድሜውን ሙሉ"

ሽማግሌዎች

ይህ ማለት የሙሴን ሕግ ከማስጠበቅ አንጻር በማኅበራዊ ፍትሕና ሀይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ እስራኤላውያንን ሲረዱ የነበሩ ሰዎች ናቸው።

ከእርሱ የበለጠ ኖረዋል

ይህ ማለት ከሌላው የበለጠ ዓመት መኖር ነው። ኢ.ት: "እርሱ ከኖረው የበለጠ ኖረዋል"

ነዌ

ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

110 ዓመት ዕድሜው ላይ

"አንድ መቶ አሥር ዓመት ዕድሜው ላይ" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Judges 2:9

ወደ ተመደበለት

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "እግዚአብሔር ወደ ሰጠው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ተምና ሔሬስ

ይህ በምድሪቱ ላይ የአንድ አካባቢ ስም ነው።

ገዓስ ተራራ

ይህ የአንድ ተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ያ ትውልድ ሁሉ ደግሞ ወደ አባቶቻቸው ተሰብስበው ነበር

"ደግሞም ወደ አባቶቻቸው ተሰብስበው ነበር" የሚለው ሐረግ የዚያ ትውልድ ሰዎች ሲሞቱ ከእነርሱ በፊት የሞቱት አባቶቻቸው ወዳሉበት ወደዚያው ስፍራ ነፍሶቻቸው ሄዷል ማለት ነው። መሞታቸውን በትህትና የመግለጽ መንገድ ነው።

አባቶች

ይህ ማለት የአንድ ሰው ወይም የአንድ ሕዝብ ወገን የሆኑ አያቶች ማለት ነው።

አረጀ

"ዕድሜው ገፋ" ወይም "ሸመገለ"

እግዚአብሔርን የማያውቅ

እዚህ ጋ "የማያውቅ" ማለት የቀደመው ትውልድ ያውቅ እንደ ነበረ እግዚአብሔር ወይም የእርሱ ኃይል በሕይወታቸው የሚሠራውን ያልተለማመዱ ማለት ነው።

Judges 2:11

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን

የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው ፍርዱን ወይም ምዘናውን ነው። ኢ.ት: "በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ የሆነውን" ወይም "እግዚአብሔር ክፉ ነው ያለውን" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የበኣል አማልክትን

ይህ የበኣል ብዙ ቁጥር ነው። "በኣል" የአንድ ሐሰተኛ አምላክ ስም ሆኖ ሳለ ቃሉ አብዛኛውን ጊዜ ከበኣል ጋር ለሚመለኩ ለሌሎች የተለያየዩ አማልክትም ጥቅም ላይ ውሏል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከእግዚአብሔር ተለዩ

ከእንግዲህ እግዚአብሔርን የማይታዘዙ እስራኤላውያን፣ በአካል ከእርሱ እንደተነጠሉና እንደተዉት ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አባቶቻቸው

"አያቶቻቸው" ወይም "የቀደሙት አባቶቻቸው"

ሌሎች አማልክትን ተከተሉ

የእስራኤላውያኑ ሐሰተኞች አማልክትን ማምለክ መጀመር እስራኤላውያን ሐሰተኞች አማልክትን ተከትለው እንደሄዱ ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰገዱላቸው

ይህ የአምልኮትና ለአንድ ሰው አክብሮትን የመስጠት ተግባር ነው።

እግዚአብሔርን ለቁጣ አነሣሡት

"እግዚአብሔር እንዲቆጣ አስደረጉት"

አስታሮቶች

ይህ የአስታሮት ብዙ ቁጥር ሲሆን በተለያዩ ቅርጾች የምትመለክ እንስት አምላክ ናት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 2:14

የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ

የእግዚአብሔር ቁጣ እንደ እሳት እንደሚቃጠል ተገልጿል። ኢ.ት: "እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ላይ በጣም ተቆጣ" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሀብታቸውን ለሚቀሟቸው ለወራሪዎች አሳልፎ ሰጣቸው

"ወራሪዎች ሀብታቸውን እንዲቀሟቸው ተዋቸው"

ከእንግዲህ ራሳቸውን ከጠላቶቻቸው መከላከል እንዳይችሉ፣ በዙሪያቸው ለተገዙላቸው ጠላቶቻቸው እንደ ባሪያ ሸጣቸው።

ጠላቶች እስራኤላውያኑን እንደ ባሪያ አድርገው እንዲወስዷቸው እግዚአብሔር መፍቀዱ ለባርነት ሸጣቸው ተብሎ ተነግሯል። "ለተገዙላቸው" የሚለው ቃል በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: "እርሱ፣ ጠላቶቻቸው ድል እንዲያደርጓቸውና ባሪያ አድርገው እንዲወስዷቸው፣ ከእንግዲህም ብርቱዎቹን ጠላቶቻቸውን መቋቋም እንዳይችሉ ፈቀደ"። (ዘይቤአዊ አነጋገር፣ አድራጊና ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ይሸነፉ ዘንድ የእግዚአብሔር እጅ በእነርሱ ላይ ነበረች

እዚህ ጋ "እጅ" የሚወክለው የእግዚአብሔርን እጅ ነው። ኢ.ት: "ያሸንፏቸው ዘንድ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ረዳቸው" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እጅግ ተጨንቀው ነበር

"እጅግ ተሠቃይተው ነበር"

ከዚያም እግዚአብሔር መሳፍንትን አስነሣላቸው

እግዚአብሔር እንዲፈርዱ ሰዎችን መሾሙ ሰዎችን እንዳነሣቸው ወይም ብድግ እንዳደረጋቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእነዚያ እጅ

እዚህ ጋ "እጅ" የሚያመለክተው ኃይልን ነው። ኢ.ት: "ከጠላቶቻቸው ኃይል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መሳፍንታቸውን አልሰሙም

"መሳፍንታቸውን አልታዘዙም"

ራሳቸውን እንደ ሴተኛ አዳሪዎች ለሌሎች አማልክት ሰጡ፣ አመለኳቸውም

የሕዝቡ እግዚአብሔርን ከድቶ ሌሎች አማልክትን ማምለክ እንደ ሴተኛ አዳሪ እንዲቆጠሩ ማስደረጉ ተነግሯል። ኢ.ት: "ሐሰተኛ አማልክትን በማምለክ ከዱት"

አባቶቻቸው ከኖሩበት መንገድ ፈጥነው ተመለሱ

ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዳመለኩ እንደ ቀድሞ አባቶቻቸው ያለማድረጋቸው፣ ከአባቶቻቸው መንገድ ተመልሰው በሌላ አቅጣጫ እንደሄዱ እንዲነገርላቸው ሆኗል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አባቶቻቸው

"ቅድመ አያቶቻቸው" ወይም "የቀድሞ አባቶቻቸው"

Judges 2:18

እግዚአብሔር መሳፍንትን ባስነሣላቸው ጊዜ

እግዚአብሔር እንዲፈርዱ ሰዎችን መሾሙ ሰዎችን እንዳነሣቸው ወይም ብድግ እንዳደረጋቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መሳፍንትን ለእነርሱ ... አዳኑአቸው

"እነርሱ" የሚለው ቃል እስራኤላውያንን ያመለክታል።

የጠላቶቻቸው እጅ

እዚህ ጋ "እጅ" እስራኤልን የሚጎዱበትን የጠላትን ኃይል ያመለክታል። ኢ.ት: "የጠላቶቻቸውን ኃይል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መስፍኑ በኖረበት ዘመን ሁሉ

"መስፍኑ በሕይወት እስከ ኖረ ድረስ"

ማዘን

ለአንድ ሰው ወይም ለአንድ ነገር የርኅራኄ መኖር

በጩኹ ጊዜ

አንድ ሰው ከመከራው የተነሣ የሚጮኸው ጩኸት፣ እስራኤላውያኑ በመከራቸው ጊዜ ስቃያቸውን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት: "በተሠቃዩ ጊዜ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተመለሱ

ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ከቶ ያለመታዘዛቸው በአካል ከእግዚአብሔር እንደ ተለዩ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አባቶቻቸው
“ቅድመ አያቶቻቸው” ወይም “የቀድሞ አባቶቻቸው”
ሄደው ሌሎች አማልክቶችን አገለገሉ፣ አመለኳቸውም
የእስራኤላውያን ሌሎች አማልክትን ማምለክ ከሌሎች አማልክት ኋላ እየተራመዱ እንደሄዱ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት: “ሌሎች አማልክትን አገለገሉ፣ ሰገዱላቸውም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የትኛውንም ክፉ ሥራቸውን ወይም የእልኸኝነት መንገድ ለመተው እምቢ አሉ
“ክፉ ነገር ማድረጋቸውንና እልኸኛ መሆናቸውን ለማቆም እምቢ አሉ”። ይህ በአዎንታዊ አገላለጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ክፉ ነገር ማድረጋቸውንና እልኸኝነታቸውን ቀጠሉ”
Judges 2:20
የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ
የእግዚአብሔር ቁጣ እንደ እሳት እንደ ነደደ ተገልጿል። ይህንን በመሳፍንት 2:14 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።
ይህ ሕዝብ ተላልፏል
እዚህ ጋ “ሕዝብ” የሚወክለው ሰዎቹን ነው። ኢ.ት: “እነዚህ ሰዎች ተላልፈዋል” ወይም “እስራኤላውያኑ ተላልፈዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አባቶች
እዚህ ጋ፣ ይህ የሚያመለክተው የአንድ ሰው ወይም የአንድ ሕዝብ ወገን የሆኑ አያቶችን ነው።
እነርሱ ድምፄን አልሰሙም
እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚወክለው እግዚአብሔር የተናገረውን ነው። ኢ.ት: “እኔ ያዘዝኳቸውን አልታዘዙም” ወይም “አልታዘዙኝም”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የትኞቹም ሕዝቦች
እዚህ ጋ “ሕዝቦች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከእስራኤል በፊት በከነዓን ይኖሩ የነበሩትን የሕዝብ ወገን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እነርሱ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቃሉ፣ ይሄዱበታልም
ሰዎች እንዲኖሩት ወይም እንዲያደርጉት እግዚአብሔር የሚፈልገው ሕይወት እንደ መንገድ ወይም ጎዳና ተደርጎ ተነግሯል። እግዚአብሔርን የሚታዘዝ ሰው በመንገዱ ላይ እየሄደ እንዳለ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ፈጥኖ አስወጥቶ በኢያሱ እጅ አልሰጣቸውም
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚሉት አንድ ነገር ስለሆነ መጣመር ይችላሉ። ኢ.ት: “ኢያሱ ፈጥኖ እንዲያሸንፋቸውና እንዲያስወጣቸው አላደረገም”
በኢያሱ እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” ኃይልን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “ኢያሱ” ራሱንና ሰራዊቱን ይወክላል። ኢ.ት: “በኢያሱና በሰራዊቱ ኃይል ሥር” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 3
Judges 3:1
አሁን እግዚአብሔር
እዚህ ጋ “አሁን” የሚለው ቃል የታሪኩን አዲስ ክፍል ይጀምራል።
እነዚህ ሕዝቦች
ይህ ተራኪው በ3:3 የሚዘረዝራቸውን የሕዝብ ወገኖች ያመለክታል።
በከነዓን በተደረጉት በየትኛውም ጦርነት ያልተሳተፉትን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “በከነዓን በየትኛውም ጦርነት ያልተዋጉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ካሁን በፊት ጦርነት የማያውቁትን አዲሱን የእስራኤል ትውልድ ውጊያ ለማስተማር ይህንን አደረገ
ይህ ከዋናው የታሪክ መስመር ይነጠላል። እግዚአብሔር አንዳንድ የሕዝብ ወገኖችን ለምን በከነዓን እንዳስቀራቸው ተራኪው ዳራዊ መረጃ ይሰጣል። ኢ.ት: “ቀድሞ በጦርነት ያልተዋጉ ወጣቶችን እንዴት መዋጋት እንዳለባቸው ለማስተማር እግዚአብሔር በእስራኤላውያን መካከል ሕዝቦች እንዲቀሩ አደረገ” (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
አምስቱ ነገሥታት
እነዚህ አምስት ነገሥታት ራሳቸውንና ሕዝባቸውን ይወክላሉ። ኢ.ት: “አምስቱ ነገሥታትና ሕዝቦቻቸው”
በኣል አርሞንኤም ተራራ
ይህ በእስራኤል ረጅሙ ተራራ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሐማትስ መተላለፊያ
ይህ በሰሜናዊ የከነዓን ወሰን የሚገኝ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 3:4
እነዚህ ሕዝቦች ቀሩ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር እነዚህን ሕዝቦች በከነዓን አስቀራቸው” ወይም “እነዚህ ሕዝቦች በከነዓን መኖራቸውን እንዲቀጥሉ እግዚአብሔር ፈቀደላቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እንደ ዘዴ
“እንደ መንገድ”
እንደሆን - ለአባቶቻቸው ሰጣቸው
“እነርሱ” እና “የእነርሱ” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው።
እርሱ የሰጣቸውን ትዕዛዝ
“እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትዕዛዝ”
Judges 3:7
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን
የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው የእግዚአብሔርን ፍርድ ወይም ምዘና ነው። ይህንን በመሳፍንት 2:11 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ የሆነውን” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ያለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አምላካቸውን እግዚአብሔርን ረሱ
እዚህ ጋ “ረሱ” ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ “መታዘዛቸውን አቆሙ” የሚል ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደ
የእግዚአብሔር በጣም መቆጣት በሚቀጣጠል እሳት ተመስሎ ተነግሯል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር በጣም ተቆጣ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በኩሰርስቴም እጅ ሸጣቸው
የእስራኤል ሕዝብ እንዲሸነፍ መፍቀዱ እግዚአብሔር ለኩሰርስቴም እንደ ሸጣቸው ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት: “ኩሰርስቴምና ሰራዊቱ ድል እንዲያደርጋቸው ፈቀደላቸው”
በኩሰርስቴም እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” በፈሊጣዊ አነጋገር የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። በተጨማሪም “ኩሰርስቴም” ራሱንና ሰራዊቱን የሚወክል ተምሳሌት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የሚለውን ተመልከት)
ኩሰርስቴም
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
አራም ነሃራይም
ይህ የአንድ ሀገር ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 3:9
እግዚአብሔር አንድ ሰው አስነሣ
እግዚአብሔር አንድ የተለየ ሥራ እንዲሠራለት አንዱን መሾሙ ከተቀመጠበት እንዳስነሣው ወይም ብድግ እንዳደረገው ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጎቶንያል - ቄኔዝ
የእነዚህን ሰዎች ስም በመሳፍንት 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ሾመው
ይህ ማለት ታላቅ መሪ ለመሆን የሚያስፈልገው ብቃት እንዲኖረውና እንዲያጎለብተው እግዚአብሔር ጎቶንያልን ረዳው ማለት ነው።
በእስራኤል ላይ ፈረደ
እዚህ ጋ “ፈረደ” ማለት የእስራኤልን ሕዝብ መራቸው ማለት ነው።
ወደ ጦርነት ሄደ
በዚህ አባባል ውስጥ “እርሱ” የሚያመለክተው ጎቶንያልን ራሱንና የእስራኤልን ሰራዊት ነው። ኢ.ት: “ጎቶንያልና የእስራኤል ወታደሮች ከኩሰርስቴም ሰራዊት ጋር ለመዋጋት ሄዱ”
እግዚአብሔር በአራም ንጉሥ በኩሰርስቴም ላይ ድልን ሰጠው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እዚህ ጋ “ኩስርስቴም” የራሱን ሰራዊት ይወክላል። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሰራዊት የአራም ንጉሥ የኩስርስቴምን ሰራዊት ድል እንዲያደርግ እግዚአብሔር ረዳቸው”
የጎቶንያል እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” ሰራዊትን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የጎቶንያል ሰራዊት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ምድሪቱ ሰላም አገኘች
“ምድሪቱ” ጥቅም ላይ የዋለው በምድሪቱ የሚኖሩትን ሰዎች ለማመልከት ነው። ኢ.ት፡ “ሕዝቡ በሰላም ኖሩ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አርባ ዓመት
“40 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 3:12
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን
የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው የእግዚአብሔርን ፍርድ ወይም ምዘና ነው። ይህንን በመሳፍንት 2፡11 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ የሆነውን” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ያለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ለሞዓብ ንጉሥ ለዔግሎን ብርታትን ሰጠው
የነገር ስም የሆነው “ብርታት” እንደ ቅጽል ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር የሞዓብን ንጉሥ ዔግሎንን አበረታው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
እስራኤላውያንን ድል እንዲያደርጋቸው ለሞዓብ ንጉሥ ለዔግሎን
እዚህ ጋ “የሞዓብ ንጉሥ ዔግሎን” የሚወክለው ራሱንና ሰራዊቱን ነው። ኢ.ት፡ “የእስራኤልን ሰራዊት በሚወጉበት ጊዜ ለሞዓብ ንጉሥ ለዔግሎንና ለወታደሮቹ”
ዔግሎን
ይህ የንጉሥ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የዘንባባ ከተማ
ይህ ሌላው የኢያሪኮ ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 1፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
አሥራ ስምንት ዓመት
“18 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 3:15
ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህ ማለት በሩቅ ወዳለ ወደሌላው መጣራት ወይም ከፍ ባለ ድምፅ መናገር ማለት ነው። ደግሞም አንድ ሰው፣ በተለይም እግዚአብሔር እንዲረዳ መጠየቅ ሊሆንም ይችላል።
አንድ ሰው አስነሣላቸው
እግዚአብሔር አንድ የተለየ ሥራ እንዲሠራለት አንዱን መሾሙ ሰውየውን ከተቀመጠበት እንዳስነሣው ወይም ብድግ እንዳደረገው ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ናዖድ = ጌራ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ግራኝ
ናዖድ በግራ እጁ በተሻለ ሁኔታ ሰይፍ መያዝ ይችል ነበር።
Judges 3:16
አንድ ክንድ
ዘመናዊ የርዝመት መለኪያ መጠቀም የሚያስፈልግ ከሆነ ይህንን ለማድረግ ሁለት መንገዶች አሉ። ኢ.ት፡ “46 ሴንቲ ሜትር” ወይም “ግማሽ ሜትር ገደማ” (ርቀት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚለውን ተመልከት)
በቀኝ ታፋው በኩል በልብሱ ውስጥ ታጠቀው
“በቀኝ መታጠቂያው በኩል በልብሱ ስር ታጠቀው”
ታፋ
በወገብና በጉልበት መካከል ያለ የእግር ክፍል
በዚህ ጊዜ ዔግሎን በጣም ወፍራም ሰው ነበር
እዚህ ጋ “በዚህ ጊዜ” ጥቅም ላይ የዋለው ዋናው የታሪኩ መስመር መቆሙን ምልክት ለማድረግ ነው። እዚህ ጋ ተራኪው ስለ ዔግሎን ዳራዊ መረጃ ይሰጣል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
Judges 3:19
የተቀረጹ ምስሎች ወደተሠሩበት ቦታ ወደ ጌልጌላ አቅራቢያ በደረሰ ጊዜ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች የተቀረጹ ምስሎች ወደ ሠሩበት ወደ ጌልጌላ አቅራቢያ በደረሰ ጊዜ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በነፋሻማው የላይኛው ክፍል
ይህ ከዝቅተኛው ቀጥሎ ወደ ላይ ያለ ክፍል ሲሆን ለማረፊያነትና በቀኑ ሞቃታማ ሰዓት ቀዝቀዝ ብሎአቸው የሚቆዩበት ክፍል ነው።
ንጉሡ ከመቀመጫው ተነሣ
መቆም፣ የእርሱን መልዕክት በማድመጥ እግዚአብሔርን የማክበር ምልክት ነው።
Judges 3:21
የሰይፉ ጫፍ በጀርባው በኩል ወጣ
“የሰይፉ ስለት መጨረሻ በጀርባው በኩል ወጣ”
በረንዳ
ጣሪያው የተሸፈነና ግድግዳው አጠር ያለ ውጫዊ ክፍል
Judges 3:24
በርግጥ ራሱን እያስታገሰ ነው
ይህ ስለሚጸዳዳ ሰው የሚነገር የትህትና አነጋገር ነው።
ተግባራቸውን ቸል ያሉ ያህል እስኪሰማቸው ድረስ
አንዳች ችግር ተፈጥሮ እንደሆነና የንጉሡን የግል ክፍሉን መክፈትም ቢሆን የእነርሱ ተግባር እንደሚሆን በማሰብ ሲጨነቁ ቆዩ።
ቁልፍ ወስደው ከፈቷቸው
“ቁልፍ ወስደው በሮቹን ከፈቷቸው”
Judges 3:26
አገልጋዮቹ ሲጠባበቁት ሳሉ - ናዖድ አመለጠ
ይህ የሚነግረን አገልጋዮቹ የላይኛውን ክፍል በሮች በመክፈት ንጉሡ ሞቶ ሳያገኙት በፊት የሆነውን ነገር ነው። ኢ.ት፡ “አገልጋዮቹ ከላይኛው ክፍል ውጪ በመጠበቅ ላይ እያሉ … ናዖድ አመለጠ”
ሴርታይም
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
በደረሰ ጊዜ
ይህ በይበልጥ ግልጽ መሆን ይችላል። ኢ.ት፡ “ወደ ሴርታይም በደረሰ ጊዜ”
Judges 3:28
እግዚአብሔር ጠላቶቻችሁን ድል ያደርጋቸዋል
እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ እግዚአብሔር መርዳቱ እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ጋር ተዋግቶ ድል እንደሚያደርግ ጦረኛ ተቆጥሮ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
መሻገሪያዎቹን ያዙ
“መሻገሪያዎቹን መቆጣጠር ቻሉ”
መሻገሪያዎች
ጥልቀት የሌለውና በቀላሉ ሊሻገሩት የሚቻል የወንዝ አካባቢ
ማንም እንዲሻገር አልፈቀዱም
“ማንም እንዳይሻገር ከለከሉ”
አሥር ሺህ ሰዎች
“10,000 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ብቁ የሆኑ ሰዎች
“የሚችሉ ሰዎች” ወይም “በሚገባ መዋጋት የሚችሉ ሰዎች”
ሞዓብ ለእስራኤል ጉልበት ተገዛ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ወታደሮች ሞዓባውያንን ድል አደረጓቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የእስራኤል ጉልበት
እዚህ ጋ “ጉልበት” የሚወክለው የእስራኤልን ሰራዊት ነው።
ምድሪቱ ዐርፋ ነበር
እዚህ ጋ “ምድር” የሚወክለው ሕዝብን ነው። ኢ.ት፡ “እስራኤላውያን በሰላም ኖሩ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰማንያ ዓመት
“80 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 3:31
መስፍን
እስራኤላውያን ነገሥታት ሳይኖሯቸው በፊት፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡ በኋላ፣ በችግራቸው ጊዜ እንዲመሯቸው እግዚአብሔር መሳፍንትን ሾመላቸው። መሳፍንት

አብዛኛውን ጊዜ እስራኤላውያንን ከጠላቶቻቸው ይታደጓቸው ነበር።
ሰሜጋር
የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ዓናት
የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
600 ሰዎች
"ስድስት መቶ ሰዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
በሬዎችን ለመንዳት የሚያገለግል በትር
በበሬ የሚያርሱ ገበሬዎች በሬዎቹ ወደ ፊት እንዲሄዱላቸው ለመምታት ሹልነት ያለው በትር ይጠቀሙ ነበር። አ.ት: "በሬዎቹን ለመንዳት የሚጠቀሙበት በትር" ወይም "በሬዎችን መምሪያ በትር"
እርሱም ደግሞ እስራኤልን ከአደጋ አዳናቸው
"አደጋ" የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ለመጉዳት የሞከሩ ጠላቶቻቸውን ያመለክታል። አ.ት: "እርሱም ደግሞ የእስራኤልን ሕዝብ ከጠላቶቻቸው አዳናቸው" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 4
Judges 4:1
ናዖድ
የዚህን ሰው ስም በመሳፍንት 3:15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን
የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው የእግዚአብሔርን ፍርድ ወይም ምዘና ነው። ይህንን በመሳፍንት 2:11 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት: "በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ የሆነውን" ወይም "እግዚአብሔር ክፉ ያለውን" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር በከነዓን ንጉሥ በኢያቢስ እጅ ሸጣቸው
እዚህ ጋ "እጅ" የሚያመለክተው በእስራኤል ላይ የበረታውን የኢያቢስን ኃይል ነው። እግዚአብሔር ለኢያቢስ ኃይል ለመስጠት መወሰኑ እርሱ ሕዝቡን ለኢያቢስ እንደሸጣቸው ተነግሯል። አ.ት: "እግዚአብሔር በከነዓን ንጉሥ በኢያቢስ ኃይል እንዲሸነፉ ፈቀደ" (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ኢያቢስ - ሲሣራ
እነዚህ የወንዶቹ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሐጾር = ሐሮሼትሐጎይም
እነዚህ የከተሞች ወይም የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገላዎች
"900 የብረት ሠረገላዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሃያ ዓመት
"20 ዓመት"
Judges 4:4
አሁን
ይህ ቃል ዋነኛውን የታሪክ መስመር ለማቆም ምልክት ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል። እዚህ ጋ ተራኪው ስለ ዲቦራ ዳራዊ መረጃ ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ዲቦራ
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ለፊዶት
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
መስፍን
እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በመከራቸው ጊዜ የሚመሯቸው መሳፍንትን ሾመላቸው። አብዛኛውን ጊዜ መሳፍንቱ ከጠላቶቻቸው ያድኗቸው ነበር።
የዲቦራ ዘንባባ
ይህ ዛፍ በዲቦራ ስም ተጠርቷል።
Judges 4:6
ባራቅ - አቢኒኤም
እነዚህ የወንዶቹ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የታቦር ተራራ
ይህ የአንድ ተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
አሥር ሺህ ሰዎች
"10,000 ሰዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
አወጣዋለሁ
እዚህ ጋ "እኔ" የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።
ሲሣራን አወጣዋለሁ
እዚህ ጋ "ሲሣራ" ራሱንና ሰራዊቱን ይወክላል። አ.ት: "ሲሣራንና ሰራዊቱን አወጣለሁ"
ማውጣት
ሰዎች ከምቹ ስፍራቸው ወጥተው እንዲመጡ ማድረግ
ሲሣራ - ኢያቢስ
የእነዚህን ወንዶች ስም በመሳፍንት 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት
ቂሶን
ይህ የወንዝ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 4:8
ባርቅ
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 4:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
እየሄድክበት ያለው መንገድ ወደ ክብር አያደርስህም
ባርቅ የሚያደርገው ምርጫ የሚጓዝበትን መንገድ እንደ መምረጥ ተቆጥሯል። "ክብር"ም ለአንድ ተጓዥ እንደ መዳረሻ ተቆጥሮለታል። አ.ት: "በምታደርገው ነገር ማንም አያከብርህም" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ሲሣራን በሴት እጅ ላይ አሳልፎ ይሰጠዋል
እዚህ ጋ "እጅ" የሚያመለክተው እርሱን ለመግደል ያላትን ኃይል ነው። አ.ት: "እግዚአብሔር ሲሣራን ሴት እንድታሸንፈው ያደርጋል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሲሣራ
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዲቦራ
የዚህችን ሴት ስም በመሳፍንት 4:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Judges 4:11
አሁን
ይህ ቃል ዋነኛውን የታሪክ መስመር ለማቆም ምልክት ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል። እዚህ ጋ ተራኪው ስለ ቄናዊው ሔቤር ዳራዊ መረጃ ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ሔቤር - ኦባብ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ቄናዊ
ይህንን በመሳፍንት 1:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
የሙሴ አማች
"የሙሴ የሚስቱ አባት"
ጸዕናይም
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 4:12
ለሲሣራ በነገሩት ጊዜ
እዚህ ጋ "እነርሱ" የሚለው ቃል በተለየ ሁኔታ ማንንም አይገልጽም። አ.ት: "አንድ ሰው ለሲሣራ ሲነግረው"
ሲሣራ
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ባርቅ - አቢኒኤም - የታቦር ተራራ
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 4:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ሲሣራ ሠረገላዎቹን ሁሉ ሰበሰበ
እዚህ ጋ "ሠረገላዎች" የሚወክሉት ሠረገላዎቹን የሚነዱ ወታደሮችን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገላዎች
"900 የብረት ሠረገላዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አሪሶት ሐጎይም
የዚህችን ከተማ ስም በመሳፍንት 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የቁሶን ወንዝ
ይህንን በመሳፍንት 4:7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Judges 4:14
እግዚአብሔር ድልን ሰጥቶሃል
ዲቦራ ስለ ድሉ እርግጠኛ ስለ ነበረች ባርቅ አስቀድሞ ጦርነቱን እንዳሸነፈ አድርጋ ትናገራለች። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ድልን ይሰጥሃል”
የሚመራህ እግዚአብሔር አይደለምን?
የሚዋጉት ከእግዚአብሔር ጋር ወግነው መሆኑን ባርቅን ለማስታወስ ዲቦራ ይህንን ጥያቄ ትጠይቃለች። ኢ.ት: “እግዚአብሔር እንደሚመራህ አስታውስ” (መልስ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ከአሥር ሺህ ጋር
“ከ10,000 ጋር” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 4:15
እግዚአብሔር ሲሣራን፣ ሠረገላዎቹንና ሰራዊቱን ሁሉ አደናገራቸው
“እግዚአብሔር፣ ሲሣራን፣ ሠረገላዎቹንና ሰራዊቱን ሁሉ በአግባቡ ማሰብ እንዳይችሉ አደረጋቸው” ወይም “እግዚአብሔር፣ ሲሣራ፣ ሠረገላዎቹና ሰራዊቱ ሁሉ እንዲደነግጡ አደረጋቸው”
ሠረገላዎቹ ሁሉ
እዚህ ጋ “ሠረገላዎቹ” የሚለው ቃል ሠረገላዎቹን የሚነዱትን ወታደሮች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “ሠረገላዎቹን የሚነዱት ሰዎች ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ባርቅ አሳደደ
እዚህ ጋ “ባርቅ” የሚወክለው ራሱንና ሰራዊቱን ነው። ኢ.ት: “ባርቅና ወታደሮቹ አሳደዱ”
አሪሶት
ይህንን በመሳፍንት 4:2 ላይ በተረጎምክበት በዚያው መልክ ተርጉመው።
የሲሣራ ሰራዊት በሙሉ በሰይፍ ስለት ተገደሉ
እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚወክለው ወታደሮች በጦርነት ላይ የሚጠቀሙባቸውን ሰይፍና ሌሎች የጦር መሣሪያዎች ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ባርቅና ወታደሮቹ የሲሣራን ወታደሮች በሙሉ በሰይፍ ገደሏቸው”
Judges 4:17
ሲሣራ - ኢያቢስ - ሐጾር
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
በእግሩ ሸሸ
በፈረስ ወይም በሠረገላ ከመጋለብ ይልቅ በእግሩ መሮጡ ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ኢያዔል
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሔቤር
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 4:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ቄናዊ
ይህንን በመሳፍንት 1:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዘወር በል
ይህ ማለት ከሚደረገው ጉዞ ለማረፍ የሚደረግ የመንገድ ለውጥ ነው። ኢ.ት: “ወዲህ ና”
ብርድ ልብስ
ከሱፍ ወይም ከእንስሳት ቆዳ የሚሠራና በመኝታ ጊዜ ሙቀት እንዲሰጥ የሚለበስ ሰፊ የአካል መሸፈኛ ነው።
Judges 4:19
ተናገራት
“ሲሣራ ለኢያኤል ተናገራት”
Judges 4:21
የድንኳን ካስማ
የድንኳኑን ማዕዘን ከምድር ጋር እንዲያያይዝ እንደ ትልቅ መንጠቆ በመዶሻ የሚመታ የሾለ እንጨት ወይም ብረት
መዶሻ
የድንኳኑን ካስማ ወደ መሬት ለማጥለቅ ክብደት ካለው እንጨት የሚሠራ መምቻ
ጥልቅ እንቅልፍ
አንድ ሰው ጥልቀት ካለው ጉድጓድ ውስጥ በቀላሉ መውጣት እንደማይችል ሁሉ ጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ያለ ሰውም በቀላሉ አይነቃም። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ባርቅ ያሳድደው ነበር
“ባርቅ ያባርረው ነበር” ወይም “ባርቅ ይከተለው ነበር”
Judges 4:23
እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ፊት የከነዓንን ንጉሥ ኢያቢስን ድል አደረገው
እግዚአብሔር እስራኤላውያኑ ኢያቢስንና ሰራዊቱን እንዲያሸንፏቸው ማድረጉ የእስራኤል ሕዝብ እያዩ እግዚአብሔር ራሱ ኢያቢስን ድል እንዳደረጋቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጉልበት
“ወታደራዊ ኃይል”
ደመሰሱት
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው ራሱንና ሰራዊቱን የሚወክለውን ኢያቢስን ነው። ኢ.ት: “ኢያቢስንና ሰራዊቱን ደመሰሱ”

---

Chapter 5
Judges 5:1
በዚያች ቀን
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ኢ.ት: “እስራኤላውያን የንጉሥ ኢያቢስን ሰራዊት ድል ባደረጉበት ቀን”
ዲቦራ
ይህንን ስም በመሳፍንት 4:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ባርቅ - አቢኒኤም
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 4:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ሕዝቡ በፈቃዳቸው ራሳቸውን ለጦርነት በሰጡ ጊዜ
“ሰዎቹ ለመዋጋት በተስማሙ ጊዜ”
Judges 5:3
እናንተ ነገሥታት ስሙ! እናንት መሪዎች አድምጡ
ዲቦራና ባርቅ፣ ነገሥታትና መሪዎች እዚያ ተገኝተው መዝሙሩን ይሰሙ ይመስል ይናገራሉ።
እናንት ነገሥታቶች - እናንት መሪዎች
ይህ የሚያመለክተው በጥቅሉ ነገሥታትንና መሪዎችን እንጂ የተለዩ ነገሥታትን ወይም መሪዎችን አይደለም።
ከሴይር በወጣህ ጊዜ፣ ከኤዶም በተነሣህ ጊዜ
ይህ እስራኤላውያን በከነዓን የሚኖሩትን ድል ለማድረግ ኤዶምን ትተው የተነሡበትን ጊዜ ያመለክታል። እግዚአብሔር፣ ሕዝቡ የከነዓንን ሰዎች ድል እንዲያደርጓቸው ማብቃቱ እርሱ የእስራኤልን ሰራዊት እንደሚመራቸው ጦረኛ ተደርጎ እንዲነገርለት ሆኗል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሴይር
ሴይር በእስራኤልና በኤዶም ምድር ድንበር ላይ የሚገኝ ተራራ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ምድር ተናወጠች፤ ሰማያትም ተንቀጠቀጡ፤ ደመናትም ደግሞ ውሃን አንጠባጠቡ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ የምድር መናወጥንና ማዕበልን እንደሚፈጥር በመግለጽ ለእግዚአብሔር ኃይል አጽንዖት የሚሰጥ ሥነ ግጥማዊ ቋንቋ ነው ወይም 2) እስራኤላውያኑ በሚወጓቸው ጊዜ የከነዓን ሰዎች መፍራታቸው ሰማይና ምድር እንደተንቀጠቀጡ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 5:5
ተራሮች ተንቀጠቀጡ
ይህ እግዚአብሔርን በጣም በመፍራታቸው ተራሮች መንቀጥቀጣቸውን ለማሳየት፣ ምናልባት የምድር መናወጥን ያመለክት ይሆናል። ኢ.ት: “ተራሮች በፍርሃት ተርበደበዱ”
በእግዚአብሔር ፊት
እዚህ ጋ “ፊት” የእግዚአብሔርን ሀልዎት ያመለክታል። ኢ.ት: “በእግዚአብሔር


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሀልዎት ፊት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የሲና ተራራ እንኳን ተንቀጠቀጠ
ሙሴና እስራኤል በሲና ተራራ በነበሩ ጊዜ ተንቀጥቅጦ ነበር። ኢ.ት፡ “ከዓመታት በፊት የሲና ተራራ እንኳን ተንቀጥቅጧል”
በ... ቀናት
“በ... የሕይወት ዘመን”
ሰሜጋር = ዓናት = ኢያዔል
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። ሰሜጋርና ዓናትን በመሳፍንት 3፡31 ላይ እንዲሁም ኢያዔልን በመሳፍንት 4፡18 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የዓናት ልጅ
ሰሜጋርንና የኖረበትን ዘመን መለየት እንዲቻል ለመርዳት የሰሜጋር አባት ተጠቅሷል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
አውራ ጎዳናዎቹ ተትተዋል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር የሚችል ሲሆን መንገዶቹ የተተዉበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ኢ.ት፡ “የእስራኤልን ጠላቶች ስለ ፈሩ ሰዎች አውራ ጎዳናዎቹን መጠቀም አቆሙ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ፣ የሚለውን ተመልከት)
Judges 5:7
እኔ ዲቦራ እነሣለሁ = በእስራኤል እንደ እናት ሆነሽ ተነሽ
ዲቦራ ለትናንሽ ልጆች እንክብካቤ እንደምታደርግ እናት በእስራኤል ላይ መሪ ስለ መሆኗ ትናገራለች። ኢ.ት፡ “እኔ ዲቦራ መምራት ጀምሬአለሁ - እናት ልጆችዋን እንደምትንከባከብ እስራኤላውያንን እንከባከባለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አዳዲስ አማልክትን መረጡ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ መቻል አለበት። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ አዳዲስ አማልክትን አመለኩ”
በከተማይቱ በሮች ጦርነት ነበር
እዚህ ጋ “በሮች” መላውን ከተማውን ይወክላሉ። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉሙ በበለጠ ግልጽ መደረግ መቻል አለበት። ኢ.ት፡ “በእስራኤል ከተሞች ውስጥ ጠላት ሕዝቡን አጠቃ”
በእስራኤል በአርባ ሺዎቹ መካከል ጦር ወይም ጋሻ አልታየም
ይህ መግለጫ ምናልባት እስራኤላውያን ስለ ነበራቸው ጥቂት የጦር መሣሪያ በግነት የቀረበ ይሆናል። ኢ.ት፡ “በእስራኤል ለጦርነት የቀረው ጥቂት የጦር መሣሪያ ነው” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
በእስራኤል አርባ ሺህ
“40,000 በእስራኤል” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 5:9
ልቤ ወደ እስራኤል አዛዦች ይሄዳል
“ልብ” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ስሜት ይወክላል። “ልቤ ይሄዳል” የሚለው ሐረግ ዲቦራ ያላትን አድናቆት ወይም ምስጋና የማመልከቻ መንገድ ነው። ኢ.ት፡ “የእስራኤልን አዛዦች አደንቃለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እናንተ በነጫጭ አህዮች የምትቀመጡ - በመንገዱ ላይ የምትሄዱ
ይህ ንጽጽር የሚያመለክተው ምናልባት ባለጸጎችንና ድኾችን ይሆናል። ኢ.ት፡ “እናንት በነጫጭ አህዮች የምትቀመጡ ባለጸጎች ... እናንት በመንገዱ ላይ የምትሄዱ ድኾች”
ለኮርቻ በስጋጃዎች ላይ ተቀምጣችሁ
እነዚህ ስጋጃዎች ምናልባት ጋላቢው በይበልጥ እንዲመቸው በአህያው ጀርባ ላይ ለኮርቻነት የሚጠቀምባቸው ሳይሆኑ አይቀሩም።
Judges 5:11
የእነዚያን ድምፆች ስሙ
እዚህ ጋ “ድምፆች” የሚዘምሩትን ሰዎች ይወክላል። ኢ.ት፡ “ስሟቸው”
ወደ ከተማይቱ በሮች ወረዱ
እዚህ ጋ “በሮች” መላውን ከተማ ይወክላሉ። ኢ.ት፡ “ወደ ከተሞቻቸው ተመለሱ”
Judges 5:12
ንቂ፣ ንቂ
ተናጋሪዎች ሊሆኑ የሚችሉት 1) የእስራኤል ሕዝብ ወይም 2) ለራሷ የምትናገረው ዲቦራ ወይም 3) መዝሙሩን የጻፈው ገጣሚ ነው።
ዲቦራ
ይህንን ስም በመሳፍንት 4፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ባርቅ - አቢኒኤም
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 4፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ከጦረኞች ጋር ወደ እኔ
“እኔ” የሚለው ቃል ዲቦራን ያመለክታል።
Judges 5:14
ሥሩ በአማሌቅ ከሆነው ከኤፍሬም
የኤፍሬም ሰዎች የሚኖሩበት ምድር በመጀመሪያ የአማሌቅ ተወላጆች ይኖሩበት ስለ ነበረ የኤፍሬም ሰዎች በምድሪቱ እንደ ተተከሉና ስር እንደ ሰደዱ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “በአንድ ወቅት የአማሌቅ ተወላጆች ይኖሩ ከነበሩበት ከኤፍሬም ምድር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ተከተሉህ
እዚህ ጋ “ተከተሉህ” የሚያመለክተው የኤፍሬምን ሕዝብ ነው። በሦስተኛ መደብ ሊነገር ይቻላል። ኢ.ት፡ “ተከተሏቸው” (የአንተ ቅርጾች እና አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
ማኪር
ይህ የማኪር ተወላጆች ይኖሩ የነበሩበት ስፍራ ነው። ማኪር የምናሴ ልጅና የዮሴፍ የልጅ ልጅ ነበር። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ከዛብሎን፣ እነዚያ የአለቅነትን በትር የያዙ
ወታደራዊ አመራሮች የስልጣናቸው ምልክት በሆነው በትራቸው ይገለጻሉ። ኢ.ት፡ “የዛብሎን ወታደራዊ መሪዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 5:15
በይሳኮር ያሉ መስፍኖቼ ከዲቦራ ጋር ነበሩ
እዚህ ጋ “የእኔ” የሚያመለክተው ዲቦራን ነው። ይህ መግለጫ በአጠቃላይ በአንደኛ መደብ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “በይሳኮር የሚገኙት መስፍኖቼ ከእኔ ጋር ነበሩ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
ዲቦራ
ይህንን ስም በመሳፍንት 4፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ይሳኮር ከባርቅ ጋር ነበር
እዚህ ጋ “ይሳኮር” የይሳኮርን ነገድ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የይሳኮር ነገድ ከባርቅ ጋር ነበር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ባርቅ
ይህንን ስም በመሳፍንት 4፡6 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
መመሪያውን በመከተል ከበስተኋላው ወደ ሸለቆው ሮጡ
“መመሪያውን በመታዘዝና ወደ ሸለቆው ከበስተኋላው በመሮጥ”
ከበስተኋላው በመሮጥ
“ከኋላው በመከተል” ወይም “ከኋላው በመሮጥ”
ታላቅ የልብ ምርምር ነበር
እዚህ ጋ “ልብ” አሳብን ይወክላል። የሰዎቹ እርስ በእርስ መነጋገርና ምን ማድረግ እንዳለባቸው መወሰን አለመቻላቸው ልባቸውን እንደመረመሩ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ምን ማድረግ እንዳለባቸው ብዙ ውይይት ነበር” (ፈሊጣዊ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 5:16
እረኞች ለመንጋዎቻቸው የሚጫወቱትን ዋሽንት እየሰማችሁ እሳት በሚነድባቸው ምድጃዎች መካከል የተቀመጣችሁት ለምንድነው?
ወደ ጦርነቱ በመምጣት ለመዋጋት አልወሰኑም ነበርና ይህ ጥያቄ የተጠየቀው የሮቤልን ሰዎች ለመውቀስ ነው። ይህ እንደ መግለጫ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “በቤት ቀርታችሁ እረኞች ለመንጋዎቻቸው የሚጫወቱትን ዋሽንት ከምትሰሙ ይልቅ ስንዋጋ ልትረዱን ይገባ ነበር” (መልስ የማይሻ ጥያቄ እና የሚለውን ተመልከት)
እሳት የሚነድባቸው ምድጃዎች
አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕትሞች “የበጎች ጉረኖ” ወይም “የበግ ማሳደሪያ” ይሉታል
Judges 5:17
ገለዓድ ተቀምጧል
እዚህ ጋ “ገለዓድ” የሚያመለክተው በጦርነቱ ላይ ለመዋጋት መሄድ የነበረባቸውን የገለዓድ ወንዶች ነው። ኢ.ት፡ “የገለዓድ ሰዎች ተቀምጠዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከዮርዳኖስ ማዶ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ የዮርዳኖስን ምስራቅ ያመለክታል።

ዳን በመርከቦች ላይ ለምን ዘገየ

የዳን ነገድ ሰዎች ለእስራኤል ስላልተዋጉ ይህ ጥያቄ የተጠየቀው ቁጣን ለመግለጽ ነው። ኢ.ት: “የዳን ሰዎች በመርከቦቻቸው ውስጥ መቆየት አልነበረባቸውም” ወይም “በጦርነቱ የዳን ነገድ ሰዎች አልረዱንም። ይልቁንም በመርከቦቻቸው ውስጥ ሆነው ወዲያና ወዲህ ይቅበዘበዙ ነበር!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና የሚለውን ተመልከት)

ለምን ነበር ዳን

እዚህ ጋ “ዳን” ጦርነቱን ለመዋጋት መሄድ የነበረባቸውን የዳን ሰዎች ይወክላል። ኢ.ት: “ለምንድነው የዳን ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመርከቦች የሚቅበዘበዙት

የዳን ነገድ የሚገኘው በሜዲትራንያን ባህር አጠገብ ነበር። በንግድና ዓሳ በማስገር ገንዘብ ለማግኘት በባህሩ ላይ በመርከብ ይጓዙ ነበር።

አሴር በጠረፉ ላይ ተቀመጠ፣ በወደቡም አቅራቢያ ኖረ

የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉሙ በይበልጥ ሊብራራ ይችላል። ኢ.ት: “የአሴር ነገድ ሰዎችም ደግሞ ሳይረዱን ቀሩ። በወደቦቻቸው አቅራቢያ ብቻ ተቀመጡ”

አሴር ተቀመጠ

እዚህ ጋ “አሴር” ጦርነቱን ለመዋጋት መሄድ የነበረባቸውን የአሴር ሰዎች ይወክላል። ኢ.ት: “የአሴር ሰዎች ተቀመጡ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደቦች

ጥልቅ ውሃ ያለባቸውና መርከቦች የሚቆሙባቸው የባህር ዳርቻ አካባቢዎች

ንፍታሌምም ደግሞ

የሚታወቀውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ኢ.ት: “ንፍታሌምም ደግሞ ነፍሳቸውን እስከ ሞት ድረስ አሳልፈው ከሰጡት ነገዶች አንዱ ነበር”

Judges 5:19

ነገሥታት መጡ፣ ተዋጉም - የከነዓን ነገሥታት ተዋጉ

ራሱንና የሚያዛቸውን ሰራዊት ለማመልከት የአንድ ሕዝብ ወገን ንጉሥ የሚለው ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት: “ነገሥታትና ሰራዊቶቻቸው መጥተው ተዋጉ - የከነዓን ነገሥታትና ሰራዊቶቻቸው ተዋጉ”

እነርሱ ተዋጉ -- ተዋጉ

“እኛ” የሚለው ቃል የሚታወቅ ነው። ኢ.ት: “ወጉን - ወጉን”

ታዕናክ - መጊዶ

የእነዚህን ቦታዎች ስም በመሳፍንት 1:27 እንዳደረግኸው ተርጉማቸው።

ምንም ብር አልበዘበዙም

እዚህ ጋ “ብር” በጥቅሉ የትኛውንም ዓይነት ገንዘብ ይወክላል። ኢ.ት: “የሚበዘብዙት ብር ወይም ሌላ ሀብት አልነበረም”

ብዝበዛ

አብዛኛውን ጊዜ በጦርነት ወይም በሌቦች አማካይነት በማስገደድ የሚወሰዱ ነገሮች

ከዋክብት ከሰማይ ተዋጉ፣ ከሰማያት ጥጎቻቸው ሲሣራን ተዋጉት

እግዚአብሔር፣ እስራኤላውያን ሲሣራንና ሰራዊቱን ድል እንዲያደርጓቸው መርዳቱ ከዋክብት ራሳቸው ሲሣራንና ሰራዊቱን እንደተዋጓቸው ተደርጎ ተነግሯል። ይህ እግዚአብሔር ሲሣራን ድል ለማድረግ ተፈጥሮአዊ ግብዓቶችን በተለይም ነጎድጓድን መጠቀሙን ያመለክት ይሆናል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

በሲሣራ ላይ

እዚህ ጋ “ሲሣራ” የሚወክለው ራሱንና መላውን ሰራዊቱን ነው። ኢ.ት: “ሲሣራና ሰራዊቱ”

ሲሣራ

ይህንን ስም በመሳፍንት 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Judges 5:21

የቂሶን ወንዝ ጠራርጎ ወሰዳቸው

በከባድ ዝናብ ምክንያት ወንዙ በፍጥነት ስለሞላ ሠረገላዎቹ በጭቃ ተይዘው ስለነበር ብዙ ወታደሮች ሰመጡ። ኢ.ት: “የቂሶን ወንዝ ጎረፈና የሲሣራን ወታደሮች ጠራርጎ ወሰዳቸው”

ቂሶን

ይህንን በመሳፍንት 4:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ነፍሴ ሆይ፣ በርቺ፣ ተሰለፊ

እዚህ ጋ “ነፍስ” የሰውን ሁለንተና ያመለክታል። “የእኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዲቦራን ነው። ኢ.ት: “እንድበረታና እንድሰለፍ ለራሴ እነግራለሁ”

ከዚያም የሚጋልቡ የፈረሶች ኮቴ ድምፅ ተሰማ፣ የኃያላኑ ግልቢያ

ይህ የሚገልጸው ከጦርነት የሚሸሹ የብዙ ፈረሶችን ድምፅ ነው። ኢ.ት: “ከዚያም በሽሽት ላይ ያሉ የፈረሶችን ድምፅ ሰማሁ። ብርቱዎቹ የሲሣራ ፈረሶች እየሸሹ ነበር”

መጋለብ

በፍጥነት መሮጥ

Judges 5:23

ሜሮዝን እርገሙ

እዚህ ጋ “ሜሮዝ” የምትወክለው በዚያ የኖሩትን ሰዎች ነው። ኢ.ት: “የሜሮዝን ሰዎች እርገሙ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሜሮዝ

ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ነዋሪዎች

በአንድ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች

Judges 5:24

ኢያዔል

ይህንን ስም በመሳፍንት 4:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሔቤር

ይህንን ስም በመሳፍንት 4:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቄናዊ

የዚህን የሕዝብ ወገን ስም በመሳፍንት 1:16 ላይ እንዳደረግኸው ተርጉመው።

ቅቤ አመጣችለት

እዚህ ጋ “ቅቤ” የሚያመለክተው የረጋውን ወተት ነው። ይህ በኢያዔል ሰዎች መካከል የተመረጠ ወተትና ተወዳጅ መጠጥ ነበር። ኢ.ት: “እርጎ አመጣችለት” ወይም “የረጋ ወተት አመጣችለት”

ለልዑላን የተገባውን ማዕድ

ለልዑላን ምርጥ የሆነው ነገር ይቀርብ ስለነበር ይህ ሐረግ የሚለው ማዕዱ እጅግ ምርጥ መሆኑን ነው።

Judges 5:26

እጇን ወደ ድንኳኑ ካስማ ሰደደች

“ኢያዔል በግራ እጇ የድንኳኑን ካስማ ያዘች”

የድንኳን ካስማ

ይህ ድንኳኑን ከመሬት ጋር አገናኝቶ እንዲይዝ በመዶሻ የሚመታ እንደ ትልቅ ሚስማር የሾለ እንጨት ወይም ብረት ነው። ይህንን በመሳፍንት 4:21 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቀኝ እጇን ሠራተኛ ወደሚጠቀምበት መዶሻ

ይህ ሙሉ ዐረፍተ ነገር ሆኖ መነገር ይችላል። ኢ.ት: “በቀኝ እጇ መዶሻ ያዘች”

መዶሻ

የድንኳኑን ካስማ ወደ መሬት ለማጥለቅ ክብደት ካለው እንጨት የሚሠራ መምቻ ነው። ይህንን በመሳፍንት 4:21 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሲሣራ

የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡

መዛል

ዐቅም ማጣት ወይም መንቀሳቀስ አለመቻል

በቁጣ ተገደለ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ገደለችው” ወይም “ሞተ”(አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 5:28

ርብራብ

ይህ በመስቀልዮሽ እንጨት የተሠራ የመስኮቱ መደገፊያ ነው።

ሠረገላው ሳይመጣ ለምን ይህን ያህል ጊዜ ፈጀበት? ሠረገላዎቹን የሚጎትቱት ፈረሶች ኮቴ ድምፅ ለምን ዘገየ?

ሁለቱም ጥያቄዎች የሚሉት አንድ ነገር ነው። እነዚህ ሁለቱም መግለጫዎች መጣመር ይችላሉ። ኢ.ት: “ሲሣራ ወደ ቤት ሳይመለስ የቆየው ለምንድነው?”

ሠረገላው - ፈጀበት - ሠረገላዎቹን የሚጎትቱት ፈረሶች ኮቴ ድምፅ

ሁለቱም አነጋገሮች የሚወክሉት ሲሣራን ነው። ኢ.ት: “ሲሣራን የወሰዱት. . . እርሱ ለምን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 5:29

ጠቢብ ልዕልቶች

“ልዕልት” የንጉሥ ልጅ ናት፣ ነገር ግን “ልዕልቶች” ማለት ደግሞ ምናልባት የንጉሡን ቤተሰቦች የሚያማክሩ ሴት አማካሪዎች ማለት ሊሆን ይችላል። ኢ.ት፡ “ጠቢብ ሴቶች”

ለራሷ ተመሳሳይ ምላሽ ሰጠች

“ያንኑ ነገር ለራሷ ተናገረች”

ምርኮ አግኝተው ተከፋፍለው አልጨረሱ ይሆን?

ሴቶቹ በእርግጥ የሆነው ይኸው ነው ብለው ስላመኑበት ጉዳይ አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠቀማሉ። ኢ.ት፡ “ለመከፋፈል ጊዜ የፈጀባቸው ብዙ ምርኮ አግኝተው መሆን አለበት” (መልስ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ከበዘበዟቸው ላይ - አንድ ማህፀን፣ እያንዳንዱ ሁለት ማህፀን

ሴቶቹ በእርግጥ የሆነው ይኸው ነው ብለው ስላመኑበት ጉዳይ አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠቀማሉ። ኢ.ት፡ “ከበዘበዟቸው ላይ ለእያንዳንዱ ወንድ አንድ ማህፀን፣ ሁለት ማህፀን ደርሷቸው መሆን አለበት” (መልስ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ለእያንዳንዱ ወንድ አንድ ማህፀን፣ ሁለት ማህፀን

እዚህ ጋ “ማህፀን” የሚያመለክተው ሴትን ነው። የሲሣራ ሰዎች ብዙ ሴቶችን እንደማረኩ የሲሣራ እናት ታምናለች። ኢ.ት፡ “እያንዳንዱ ወታደር አንድ ወይም ሁለት ሴት ይደርሰዋል”

የቀለመ ጨርቅ

“ልዩ ልዩ ቀለም ያለው ልብስ” ወይም “ልዩ ልዩ ቀለም ያላቸው ልብሶች”

ማቅለም

ልዩ ልዩ ቀለማት ካላቸው ክሮች የተሠሩ ንድፎች

ለሚበዘብዙት ለአንገታቸው

እዚህ ጋ “አንገታቸው” የሚወክለው የሲሣራን ወታደሮች ነው። ኢ.ት፡ “የበዘበዙት ወታደሮች ሊለብሱት”

Judges 5:31

በብርታቷ እንደምትወጣ ፀሐይ

የየትኛውም ሀገር ሰራዊት የፀሐይን መውጣት ማስቆም ስለማይችል የእስራኤል ሕዝብ እንደ ማለዳ ፀሐይ ለመሆን ይመኛሉ።

ምድሪቱ ሰላም ነበራት

እዚህ ጋ “ምድሪቱ” የሚወክለው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ኢ.ት፡ “የእስራኤልም ሕዝብ በሰላም ኖሩ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለአርባ ዓመታት

“ለ40 ዓመታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

---

# Chapter 6

## Judges 6:1

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን

የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው ፍርዱን ወይም ምዘናውን ነው። ኢ.ት፡ “በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ የሆነውን” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ነው ያለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምድያማውያን እጅ

እዚህ ጋ “ምድያማውያን” የሚወክለው የምድያምን ሰዎች ነው። በተጨማሪም፣ “እጅ” መቆጣጠርን ይወክላል። ኢ.ት፡ “የምድያም ሰዎች መቆጣጠራቸው” ወይም “የምድያማውያን መቆጣጠር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምድያም ኃይል እስራኤልን አስጨነቀ

እዚህ ጋ “የምድያም ኃይል” የሚያመለክተው የምድያም ሰዎችን ነው። ኢ.ት፡ “የምድያም ሰዎች ከእስራኤል ሰዎች ይልቅ እጅግ በርትተው ስለነበር አስጨነቋቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዋሻ

ሊያስጠልል የሚችል በዐለታማ ሸንተረር ላይ የሚገኝ ስፍራ

## Judges 6:3

ሰራዊታቸውን ያሰፍሩ ነበር

“ሰራዊቱ ይሰፍር ነበር” ወይም “ሰራዊቱ ድንኳኑን ይተክል ነበር”

## Judges 6:5

እነርሱ ከከብቶቻቸውና ከድንኳኖቻቸው ጋር ወጥተው በሚመጡበት ጊዜ ሁሉ

የምድያም ምድር በቀይ ባህር አቅራቢያ ከእስራኤል ምድር በስተደቡብ ነበር። ከምድያም ወደ እስራኤል የሚደረግ ጉዞ በሚነገርበት ጊዜ “ወጥተው በሚመጡበት” የሚለውን ሐረግ መጠቀም የተለመደ ነበር። ኢ.ት፡ “ምድያማውያን ከብቶቻቸውንና ድንኳኖቻቸውን ወደ እስራኤል ምድር በሚያመጡበት ጊዜ ሁሉ”

እንደ አንበጣ መንጋ ይመጡ ነበር

ምድያማውያን እጅግ ብዙ ሆነው ይመጡ ስለነበርና ከብቶቻቸው የሚበቅለውን ነገር ሁሉ ይበሉት ስለነበር ከአንበጣ መንጋ ጋር ተነጻጽረዋል።

ለመቁጠር አይቻልም ነበር

ይህ ቁጥሩ በጣም ብዙ መሆኑን ለማሳየት የቀረበ ግነት ነው። (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)

ምድያም አደከማቸው

እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያምን ሕዝብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደ እግዚአብሔር ጮኹ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

## Judges 6:7

ወደ እግዚአብሔር ጮኹ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በምድያም ምክንያት

እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያምን ሕዝብ ነው። ኢ.ት፡ “በምድያማውያን ምክንያት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከግብፅ አወጣኋችሁ

“ከግብፅ መርቼ አወጣኋችሁ”

ከባርነት ቤት

ሙሴ ስለ ግብፅ ሲናገር ሰዎች ባሪያዎችን እንደሚያቆዩበት ቤት ይቆጥረዋል። ኢ.ት፡ “ባሪያዎች የነበራችሁበት ስፍራ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

## Judges 6:9

ከ… እጅ

በዚህ ሐረግ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ድምፄን አልታዘዛችሁም

እዚህ ጋ “ድምፄን” የሚወክለው እግዚአብሔር ያዘዘውን ትዕዛዝ ነው። ኢ.ት፡ “ትዕዛዜን አልጠበቁም” ወይም “አልታዘዙኝም”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

## Judges 6:11

አሁን

ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩ መስመር የተገታበትን ለማመልከት ነው። ተራኪው እዚህ ጋ የታሪኩን አዲስ ክፍል መናገር ይጀምራል።

ዖፍራ

ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

አቢዔዝራዊ

ይህ በቀድሞ አባታቸው በአቢዔዝር ስም የሚጠሩ የሕዝብ ወገን ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ወለሉ ላይ ስንዴ ይወቃ ነበር

ይህ የ “መውቃት” ሂደት ነው። ጌዴዎን የስንዴውን ምርት ከገለባው ለመለየት ወለሉ ላይ ይወቃ ነበር”

ታየው

“ወደ እርሱ ሄደ”

## Judges 6:13

ጌታዬ

ጌዴዎን “ጌታዬ” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው እንግዳ የሆነን ሰው በትህትና ሰላምታ ለመስጠት ነው። እርሱ የሚናገረው በመልአክ ወይም በሰው መልክ ከታየው ከእግዚአብሔር ጋር እንደሆነ አልተገነዘበም።

‘እግዚአብሔር ከግብፅ ያወጣን አይደለምን?’ ብለው አባቶቻችን የነገሩን ተአምራቱ ሁሉ የት አለ?

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ የነገረውን እንግዳ ለመገዳደር ጌዴዎን ጥያቄ ያቀርብለታል። ደግሞም፣ በቀጥታ የተጠቀሰው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ ባልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር አባቶቻችንን ከግብፅ ባወጣቸው ጊዜ ስላደረገላቸው የነገሩንን ዓይነት ተአምር አንድም አላየንም”።

(ምላሽ የማይሻ ጥያቄ፣ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)
በምድያማውያን እጅ ሰጥቶናል
“በ... ሰጥቶናል” የሚለው ሐረግ እስራኤላውያን እንዲሸነፉ እግዚአብሔር ፈቅዷል ማለት ነው። አ.ት: “ምድያማውያን እንዲያሸንፉን ፈቅዷል”
በ... እጅ ሰጥቶናል
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በምድያም
እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያምን ሕዝብ ነው። አ.ት: “በምድያማውያን”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 6:14
እግዚአብሔር ወደ እርሱ ተመልክቶ
“እግዚአብሔር ወደ ጌዴዎን ተመልክቶ”
ከ... እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የምድያም
እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያምን ሕዝብ ነው። አ.ት: “በምድያማውያን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አልላክሁህምን?
እግዚአብሔር ጌዴዎንን እንደ ላከው ለማስረገጥ በጥያቄ መልክ ይጠቀማል። እዚህ ጋ “መላክ” ማለት እግዚአብሔር ጌዴዎንን ለአንድ ግልጽ ለሆነ ሥራ ሾሞታል ማለት ነው። አ.ት: “የምልክህ እኔ እግዚአብሔር ነኝ!” (መልስ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ጌታው፣ እባክህን
አሁን ጌዴዎን ሰውየውን በመሳፍንት 6፡13 ላይ እንዳደረገው “ጌታዬ” ከማለት ይልቅ “ጌታው” ብሎ ይጠራዋል። እዚህ ጋ ጌዴዎን እየተነጋገረ ያለው ከእግዚአብሔር ጋር መሆኑን ያወቀ ወይም የጠረጠረ ይመስላል።
እንዴት እስራኤልን ነጻ ማውጣት እችላለሁ?
ጌዴዎን እስራኤላውያንን መታደግ እንደሚችል እንደማያስብ አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ያቀርባል። አ.ት: “እስራኤላውያንን በፍጹም ልታደጋቸው አልችልም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ቤተሰቤን ተመልከት
“እኔንና ቤተሰቤን ተመልከትና ትክክል መሆኔን ታያለህ”
ከምናሴ
“ከምናሴ ነገድ ውስጥ”
በአባቴ ቤት ውስጥ
እዚህ ጋ “ቤት” የሚወክለው ቤተሰብን ነው። አ.ት: “በአባቴ ቤተሰብ ውስጥ“ ወይም “በቤተሰቤ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 6:16
እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ
እዚህ ጋ “ከአንተ ጋር” የሚለው ሐረግ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን እግዚአብሔር ጌዴዎንን ይረዳዋል፣ ይባርከዋልም ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እንደ አንድ ሰው
ሙሉውን ትርጉም በይበልጥ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት: “ከአንድ ሰው ጋር የምትዋጋውን ያህል በቀላሉ”
በፊትህ አድርግ
“በፊት ለፊትህ አድርገው”
Judges 6:19
የኢፍ መስፈሪያ ዱቄት
ዘመናዊ መስፈሪያ መጠቀም ካስፈለገ ይህን ማድረግ የሚቻልበት አንድ መንገድ አለ። አ.ት: “ከ22 ሊትር ዱቄት ጋር”
መረቅ
እንደ ሥጋ ያለ የተቀቀለ ምግብ ያለበት ውሃ።
አቀረበለት
“ለእግዚአብሔር መልአክ አቀረበለት”
የእግዚአብሔር መልአክ
ይህ ከእግዚአብሔር መልአክ ጋር አንድ ነው። አ.ት: “በመልአክ መልክ የተገለጠ እግዚአብሔር” ወይም “እግዚአብሔር”
Judges 6:21
የእግዚአብሔር መልአክ
በ6፡11-24 እግዚአብሔር በመልአክ መልክ ለጌዴዎን ተገልጦለታል። ይህንን በመሳፍንት 6፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ተለይቶት ሄደ
“ተሰወረበት”
Judges 6:22
የእግዚአብሔር መልአክ
በ6፡11-24 እግዚአብሔር በመልአክ መልክ ለጌዴዎን ተገልጦለታል። ይህንን በመሳፍንት 6፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ጌታ እግዚአብሔር ሆይ!
እዚህ ጋ “ሆይ” የሚለው ቃል ጌዴዎን እጅግ መፍራቱን ያሳያል።
የእግዚአብሔርን መልአክ ፊት ለፊት አይቻለሁና
ይህ ሐረግ ለእርስ በእርሳቸው ቅርበት ያላቸውን ሁለት ሰዎች ያመለክታል። አ.ት: “በእርግጥ የእግዚአብሔርን መልአክ አይቻለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር አለው
እግዚአብሔር ጌዴዎንን ከሰማይ ተናገረው።
እስከዚህ ቀን ድረስ
ይህ ማለት መጽሐፈ መሳፍንት የተጻፈበት ጊዜ ማለት ነው።
ዖፍራ
የዚህን ከተማ ስም በመሳፍንት 6፡11 እንዳደረግከው በተመሳሳይ ተርጉመው።
የአቢዔዝር ጎሳ
የዚህን የሕዝብ ወገን ስም በመሳፍንት 6፡11 እንዳደረግከው ተርጉመው።
Judges 6:25
ሁለተኛውን ወይፈን
“ሁለተኛው” የሚለው ቃል የመቁጠሪያ ቁጥር “ሁለት” ነው። አ.ት: “ሌላ ወይፈን”
በአጠገቡ ያለውን
“በበኣል መሠዊያ አጠገብ ያለውን”
በዚህ የመደበቂያ ቦታ አናት ላይ
የዖፍራ ከተማ በኮረብታ አናት ላይ ነበረች። እስራኤላውያን ከምድያማውያን ለመደበቅ ወደዚያ ሸሹ።
በትክክለኛው መንገድ ሥራው
“ድንጋዮቹን ሥርዓት ባለው መልኩ አስቀምጣቸው” ወይም “በአግባቡ አነባብረው”
Judges 6:27
እግዚአብሔር እንደነገረው አደረገ
ይህ እግዚአብሔር በመሳፍንት 6፡25-26 ላይ የሰጠውን ትዕዛዝ ያመለክታል።
Judges 6:28
ተነሣ
“ከአልጋው ተነሣ” ወይም “ነቃ”
የበኣል መሠዊያ ፈርሶ፣ በአጠገቡ የነበረው የአሼራ ምስልም ተሰባብሮና ሁለተኛው ወይፈን
በተሠራው መሠዊያ ላይ ተሠውቶ ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት: “አንድ ሰው የበኣልን መሠዊያ እንዳፈረሰ፣ በአጠገቡ የነበረውን የአሼራን ምስል እንደሰባበረውና መሠዊያ ሠርቶ በእርሱ ላይ ሁለተኛውን ወይፈን እንደ ሠዋ አስተዋሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 6:30
መሞት አለበት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት: “በሞት ልንቀጣው ይገባናል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 6:31
ለበኣል ትሟገቱለታላችሁ?
ኢዮአስ ሰው ለአምላክ ጠበቃ መሆን እንደማይኖርበት አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ያቀርብላቸዋል። አ.ት: “ለበኣል ጠበቃ ልትሆኑት አይገባም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ትሟገቱለታላችሁ
“ትከላከሉለታላችሁ” ወይም “ሰበብ ትሰጡለታላችሁ”

ታድኑታላችሁ?
ኢዮአስ ሰው አምላክን መታደግ እንደማይኖርበት አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ያቀርብላቸዋል። ኢ.ት፡ “በኣልን ማዳን የለባችሁም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ትርጉሙም፣ “በኣል ራሱን ይከላከል” የሚል ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ብሏልና
“ኢዮአስ ብሏልና”
Judges 6:33
አሁን
ይህ ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩ መስመር መገታቱን ለማመልከት ነው። እዚህ ጋ ተራኪው የታሪኩን አዲስ ክፍል መናገር ይጀምራል።
በአንድነት ተሰበሰቡ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉሙ በይበልጥ መብራራት ይችላል። ኢ.ት፡ “እንደ ሰራዊት በአንድ ላይ ተሰበሰቡ”
Judges 6:34
በጌዴዎን ላይ መጡበት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ጌዴዎንን ተቆጣጠሩት” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የአቢዔዝር ጎሳ
የዚህን የሕዝብ ወገን ስም በመሳፍንት 6፡11 ላይ በተረጎምከው መልኩ ተርጉመው።
እንዲከተሉት
“ወደ ጦርነት” የሚሉት ቃላት ግልጽ ናቸው። ኢ.ት፡ “ወደ ጦርነት እንዲከተሉት”
እነርሱም ደግሞ እንዲከተሉት ተጠሩ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እንዲከተሉት ይጠራቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ወደ አሴር፣ ዛብሎንና ንፍታሌም
እነዚህ ሁሉ የእያንዳንዱን ጎሳ ሕዝብ ይወክላሉ። ኢ.ት፡ “ወደ አሴር፣ ዛብሎንና ንፍታሌም ጎሳ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 6:36
የበግ ጠጉር ባዘቶ
ሱፍነት ያለው የበግ ጠጉር
ጠል
ሌሊት ላይ እጽዋት ላይ የሚቆይ ውሃ
ከዚያም እንደምታድን ዐውቃለሁ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉሙ በይበልጥ መብራራት ይችላል። ኢ.ት፡ “ይህ ከአንተ ዘንድ ምልክት ይሆናል፣ ከዚያም እንደምታድን ዐውቃለሁ”
Judges 6:38
ጌዴዎን ተነሣ
“ጌዴዎን ከአልጋው ተነሣ”
ጨመቀው
ውሃው እንዲወጣለት አንድን ነገር ጠምዝዞ መጭመቅ

---

Chapter 7
Judges 7:1
ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ስሙን በመሳፍንት 6፡32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሰፈሩ
“የጦር ሰፈራቸውን አዘጋጁ”
የሐሮድ ምንጭ - የሞሬ ኮረብታ
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የምድያም የጦር ሰፈር በስተሰሜናቸው ነበር
እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያማውያኑን ሰራዊት ነው። ኢ.ት፡ “የምድያማውያን ሰራዊት የጦር ሰፈራቸውን ከእስራኤላውያን ሰራዊት በስተሰሜን ባለ ስፍራ አደረጉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 7:2
በምድያማውያን ላይ ድል እንድሰጥህ
“ድል” የሚለው ቃል የነገር ስም ሲሆን እንደ ግሥ ወይም ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ምድያማውያንን ታሸንፋቸው ዘንድ እንድፈቅድልህ” ወይም “በምድያማውያን ላይ ባለ ድል ላደርግህ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት”
የገዛ ራሳችን ኃይል አድኖናል
እዚህ ጋ “ኃይል” የሚወክለው ሕዝቡን ራሳቸውን ነው። ኢ.ት፡ “ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ራሳችንን አድነናል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አሁን
ይህ “በዚህ ሰዓት” ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ትኩረትን ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ጉዳይ ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል።
በሕዝቡ ጆሮ ዐውጅ
እዚህ ጋ “ጆሮ” የሰውን ሁለንተና ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ለሕዝቡ ዐውጅ”
ማንም የሚፈራ፣ ማንም የሚንቀጠቀጥ
ሁለቱም ሐረጎች ያላቸው ትርጉም አንድ ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)
የሚንቀጠቀጥ
ይህ ቃል የሚገልጸው አንድ ሰው ከፍርሐት የተነሣ ሊቆጣጠረው በማይችለው ሁኔታ መንቀጥቀጡን ነው። ኢ.ት፡ “በፍርሐት የሚንቀጠቀጥ”
ይመለስ
ወዴት እንደሚሄድ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ወደ ቤቱ ይመለስ”
ገለዓድ ተራራ
ይህ በገለዓድ አውራጃ የሚገኝ ተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሃያ ሁለት ሺህ
“22,000” (ቁጥሮችን ተመልከት)
አሥር ሺህ ቀሩ
በውስጠ ታዋቂነት “ሰዎች” ወይም “ወንዶች” የሚል ቃል መኖሩን ይረዷል። ኢ.ት፡ “10,000 ሰዎች ቀሩ” ወይም “10,000 ወንዶች ቀሩ”
አሥር ሺህ
x
Judges 7:4
በዚያ ብዛታቸውን እቀንስልሃለሁ
እዚህ ጋ “ቁጥር” ሰራዊትን ይወክላል። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በበለጠ ግልጽ መሆን ይችላል። ኢ.ት፡ “በዚያ የሰራዊቱ ቁጥር እንዲቀንስ ማንን ወደ ቤቱ እንደምትመልሰው አሳይሃለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የሚለውን ተመልከት)
Judges 7:5
ጌዴዎን አመጣ
“አመጣ” የሚለው ቃል “ወሰደ” ወይም “መራ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። (ሂድ እና ና የሚለውን ቃል ተመልከት)
በእጆቻቸው
በምላስ በመላስ መጠጣት
ሦስት መቶ ሰዎች
“300 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 7:7
ሦስት መቶ ሰዎች
“300 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
አድንሃለሁ፣ ድልንም እሰጥሃለሁ
እዚህ ጋ “አንተ” ብዙ ቁጥር ሲሆን ጌዴዎንና እስራኤላውያንን ያመለክታል።
ስለዚህ እነዚያ የተመረጡት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ስለዚህ እነዚያ እግዚአብሔር የመረጣቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ስንቃቸውንና መለከታቸውን ወሰዱ
እዚህ ጋ “እነርሱ” የሚያመለክተው ሰራዊቱን ትተው የሚመለሱትን የእስራኤል ወታደሮች ነው።
አሁን
ይህ ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩ መስመር ለአፍታ ቆም ማለቱን ለማመልከት ነው። እዚህ ጋ ተራኪው የታሪኩን አዲስ ክፍል መናገር ይጀምራል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Judges 7:9
በእነርሱ ላይ ድል ስለምሰጥህ የጦር ሰፈሩን አጥቃ
እዚህ ጋ “የጦር ሰፈር” የሚያመለክተው የምድያማውያንን ሰራዊት በሙሉ ነው። “ድል” የሚለው ቃል የነገር ስም ሲሆን እንደ ግሥ ወይም ቅጽል ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እንድታሸንፋቸው ልረዳህ ስለሆነ ምድያማውያንን በጦር ሰፈራቸው አጥቃቸው” ወይም “በእነርሱ ላይ ድል አድራጊ እንድትሆን ስለማደርግ ምድያማውያንን በጦር ሰፈራቸው አጥቃቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ለመውረድ ፈራ
የታወቀውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ወርዶ ለማጥቃት ፈራ”
ፉራ
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ድፍረትህ ይጨምራል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የምትሰማው ያበረታሃል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ኬላ
ወታደሮች የጠላትን ሰራዊት ለመቆጣጠር የሚቆሙበት አካባቢ ዳርቻ
Judges 7:12
የአንበጣው ብዛት እንደ ደመና የሚሸፍን
እዚህ ጋ “ደመና” ማለት መንጋ ነው። ደራሲው ምን ያህል ወታደሮች እንደነበሩ አጽንዖት ለመስጠት የአንበጣ መንጋ በማለት ስለ ሰራዊቱ ይናገራል።
ግመሎቻቸው በባህር ዳርቻ ከሚገኝ አሸዋ በቁጥር ይበልጥ ነበር
ደራሲው በጣም ብዙ ግመሎች መኖራቸውን በአጽንዖት ሲገልጽ ግነትን ይጠቀማል። ( ግነትና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
ግመሎቻቸው ከቁጥር በላይ ነበሩ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ግመሎቻቸው ማንም ሊቆጥራቸው ከሚችለው በላይ ነበሩ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 7:13
ይህ ከጌዴዎን ሰይፍ በስተቀር ሌላ አይደለም
እዚህ ጋ “የጌዴዎን ሰይፍ” የሚያመለክተው አጥቂውን የጌዴዎንን ሰራዊት ነው። ኢ.ት፡ “በሕልምህ ያየኸው የገብስ እንጎቻ የጌዴዎን ሰራዊት መሆን አለበት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር በምድያም ላይ ድልን ሰጠው
ይህ ወደፊታዊ ሁነት እንደ አላፊ ሁነት ሆኖ ተነግሯል። ይህ በእርግጠኝነት የሚፈጸም ስለመሆኑ አጽንዖት ይሰጣል። ኢ.ት፡ “በእርግጥ እስራኤላውያን ምድያማውያንን እንዲያሸንፉ እግዚአብሔር ይረዳቸዋል”
Judges 7:15
ሦስት መቶ ሰዎች
“300 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 7:17
ለእግዚአብሔርና ለጌዴዎን!
በውስጠ ታዋቂነት “እንዋጋለን” ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ለእግዚአብሔርና ለጌዴዎን እንዋጋለን!”
Judges 7:19
አንድ መቶ ሰዎች
“100 ሰዎች” (ቁጥሮችን ተመልከት)
ልክ በእኩለ ሌሊት ጅማሬ ላይ
የእኩለ ሌሊት ጅማሬ ከምሽቱ 4 ሰዓት ገደማ ይሆናል።
Judges 7:20
የእግዚአብሔርና የጌዴዎን ሰይፍ
እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚያመለክተው ውጊያቸውን ነው። ኢ.ት፡ “ለእግዚአብሔርና ለጌዴዎን እንዋጋለን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 7:22
ሦስት መቶ መለከቶች
“300 መለከቶች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ምድያማዊ ሰይፍ በባልንጀራው ላይ እንዲሆን አደረገ
እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚያመለክተው ሰይፍ በመጠቀም ማጥቃታቸውን ነው። ኢ.ት፡ “እያንዳንዱ ምድያማዊ ሰው ባልንጀራው ከሆነው ወታደር ጋር እንዲዋጋ እግዚአብሔር አደረገ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቤት ሺጣ - ጽሬራ - አቤላሞሖላ - ጠባት
እነዚህ የመንደሮችና የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ከንፍታሌም፣ አሴርና ምናሴ ሁሉ የእስራኤል ሰዎች ተጠርተው ወጡ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ጌዴዎን እስራኤላውያንን ከንፍታሌም፣ አሴርና ከምናሴ ነገድ ሁሉ ጠራ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 7:24
ቤት ባራ
ይህ የአነስተኛ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
እስከ ቤት ባራና ዮርዳኖስ ወንዝ ያሉትን ውሃዎች ተቆጣጠሩ
“የዮርዳኖስን ወንዝ አካባቢ እስከ ቤት ባራ ደቡብ ድረስ ተቆጣጠሩ”
በሔሬብ ዐለት - በዜብ የወይን መጭመቂያ
እስራኤላውያን ሔሬብና ዜብን በዚያ ከገደሉ በኋላ አካባቢዎቹ እነዚህ ስሞች ተሰጥተዋቸው ነበር።
ሔሬብ - ዜብ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 8
Judges 8:1
ይህ ያደረግህብን ምንድነው?
የኤፍሬም ነገድ ሰዎች በሰራዊቱ ውስጥ እነርሱን ባለማካተቱ በዚህ ምላሽ በማይፈልግ ጥያቄ ጌዴዎንን ሲወቅሱት ነበር። ይህ እንደ መግለጫ መነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በአግባቡ አላየኸንም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
በምድያም ላይ
እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያማውያንን ሰራዊት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በኃይል ተሟገቱት
“ከእርሱ ጋር በቁጣ ተከራከሩ” ወይም “ክፉኛ ወቀሱት”
Judges 8:2
ከእናንተ ጋር ሲነጻጸር እኔ አሁን ያደረግሁት ምንድነው?
ጌዴዎን ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው የኤፍሬምን ሰዎች ለማክበር ነው። ኢ.ት፡ “እናንተ ካደረጋችሁት ጋር ሲነጻጸር እኔ ያደረግሁት በጣም ጥቂት ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ከአቢዔዝር ሙሉ የወይን ምርት የኤፍሬም የወይን ቃርሚያ የሚሻል አይደለምን?
ጌዴዎን በዚህ ምላሽ በማያስፈልገው ጥያቄ አማካይነት የኤፍሬምን ሰዎች ያበረዳቸው ነበር። ኢ.ት፡ “እኛ የአቢዔዝር ተወላጆች ከሰበሰብነው ምርት በሙሉ ያለ ምንም ጥርጥር እናንተ የኤፍሬም ሰዎች የለቀማችሁት ወይን የተሻለ ነው!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ከአቢዔዝር ሙሉ የወይን ምርት የኤፍሬም ቃርሚያ የተሻለ አይደለምን?
የጌዴዎንና የሰራዊቱ ምድያማውያንን ማሸነፍ የወይን ምርት እንደመሰብሰብ ተቆጥሮ ተነግሯል። የኤፍሬም ሰዎች በጦርነቱ መጨረሻ ሔሬብና ዜብን መግደላቸው ከመከር በኋላ የወይን ቃርሚያን እንደ ለቀሙ ተቆጥሮ ተነግሮላቸዋል። ኢ.ት፡ “እኛ የአቢዔዝር ተወላጆች በመጀመሪያ ካደረግነው ይልቅ እናንተ የኤፍሬም ሰዎች በጦርነቱ መጨረሻ ላይ ያደረጋችሁት ይበልጥ ታላቅ ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አቢዔዝር
ይህ ከጌዴዎን ቅድም አያቶች የአንዱ ስም ነው። ጌዴዎን ስሙን ያገኘው ከአቢዔዝር ተወላጆችና ከምድራቸው ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሔሬብና ዜብ
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 7:25 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ከእናንተ ጋር ሲነጻጸር እኔ ያከናወንኩት ምንድነው?
ጌዴዎን ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው የኤፍሬምን ሰዎች ለማክበር ነው። ይህ እንደ

መግለጫ ሊገለጽ ይችላል። ኢ.ት፡ “እኔ ካደረግሁት ይልቅ እናንተ ያደረጋችሁት ይበልጥ ታላቅ ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
በረደ
“ቀነሰ”
Judges 8:4
ሦስት መቶው ሰዎች
“300 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ማሳደዳቸውን ቀጠሉ
“ማሳደድ” የሚለው ቃል የነገር ስም ሲሆን እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ጠላቶቻቸውን ማባረራቸውን ቀጠሉ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ዛብሄልና ስልማና
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 8:6
የዛብሄልና የስልማና እጆች አሁን በእጅህ ውስጥ አሉ?
መሪዎቹ ጥያቄ የሚያቀርቡት እስራኤላውያኑ ዛብሄልንና ስልማናን ገና ያለመማረካቸውን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ኢ.ት፡ “እስካሁን ዛብሄልና ስልማናን አልማረክኻቸውም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የዛብሄልና የስልማና እጆች
እዚህ ጋ “እጆች” የሚያመለክተው ሙሉ ሰውነትን ነው።
አሁን በእጅህ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለሰራዊትህ እንጀራ የምንሰጠው ለምንድነው?
መሪዎቹ የሚጠይቁት ለእስራኤላውያኑ እንጀራ የሚሰጡበት ምንም ምክንያት እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ኢ.ት፡ “ለሰራዊትህ እንጀራ የምንሰጥበትን አንዳች ምክንያት አላገኘንም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ቆዳችሁን በበረሃ እሾህና አሜከላ እተለትለዋለሁ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ መብራራት ይችላል። ኢ.ት፡ “በበረሃ እሾህና አሜከላ ጅራፍ በመሥራት እገርፋችኋለሁ፣ እቆራርጣችኋለሁ”
እሾህና አሜከላ
ስል፣ በሐረግ ወይም ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ጫፉ የሾለና ሰውና እንስሳን ለመቁረጥ የሚችል
Judges 8:8
ከዚያ ወጥቶ ሄደ
እዚህ ጋ በውስጠ ታዋቂነት የሚገኘው “እርሱ” የሚያመለክተው ጌዴዎንን ነው። ጌዴዎን የሚወክለው ራሱንና የሚከተሉትን ወታደሮች ነው። ኢ.ት፡ “ያንን ስፍራ ተዉ” ወይም “ጌዴዎንና 300 ሰዎቹ ያንን ስፍራ ተዉ”
ጵንኤል
የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
በዚያ ላሉ ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ ተናገሯቸው
በውስጠ ታዋቂነት ያለውን መረጃ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “እዚያም በተመሳሳይ መንገድ ምግብ እንዲሰጡት ጠየቀ” ወይም “እርሱም ደግሞ ምግብ እንዲሰጡት ጠየቃቸው”
በሰላም በምመለስበት ጊዜ
ይህ ጠላቶቹን ስለማሸነፉ የሚያመለክት የትህትና አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የምድያማውያንን ሰራዊት ሙሉ በሙሉ ካሸነፍኩኝ በኋላ”
ይህንን ግምብ አፈርሰዋለሁ
እዚህ ጋ “እኔ” ጌዴዎንን የሚያመለክት ሲሆን ራሱንና ሰራዊቱን ይወክላል። ኢ.ት፡ “እኔና የእኔ ሰዎች ይህንን ግምብ እናፈርሰዋለን”
Judges 8:10
አሁን
ይህ ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩ መስመር ለአፍታ ቆም ማለቱን ለማመልከት ነው። እዚህ ጋ ተራኪው የታሪኩን አዲስ ክፍል መናገር ይጀምራል።
ዛብሄልና ስልማና
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 8፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ቀርቀር
ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
አስራ አምስት ሺህ ሰዎች
“15,000 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ወደቁ
ይህ በጦርነት የሞቱትን ሰዎች በትህትና የማመላከት መንገድ ነው። ኢ.ት፡ “ተገድለው ነበር” ወይም “በጦርነት ሞተው ነበር”
120,000 ሰዎች
“አንድ መቶ ሃያ ሺህ ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሰይፍ ይመዙ የነበሩ ሰዎች
እዚህ ጋ ሰይፍ መምዘዝ የሚወክለው በጦርነት ውስጥ በሰይፍ መጠቀምን ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ሐረግ የሚያመለክተው በጦርነት ውስጥ በሰይፍ የሚጠቀሙ ወታደሮችን ነው። ኢ.ት፡ “ሰይፍ የታጠቁ ሰዎች” ወይም “በሰይፍ የሚዋጉ ሰዎች” ወይም 2) ይህ ሐረግ የትኛውንም ወታደር ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ወታደሮች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 8:11
ጌዴዎን ወጥቶ ሄደ
እዚህ ጋ “ጌዴዎን” የሚወክለው ራሱንና ወታደሮቹን ሁሉ ነው። ኢ.ት፡ “ጌዴዎንና ወታደሮቹ ወጥተው ሄዱ”
አሸነፈ
እዚህ ጋ በውስጠ ታዋቂነት ያለው “እርሱ” የሚያመለክተው ጌዴዎንን ራሱንና ወታደሮቹን ሁሉ ነው። ኢ.ት፡ “ጌዴዎንና ወታደሮቹ አሸነፉ”
ኖባህና ዮግብሃ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ዛብሄልና ስልማና
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 8፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ድንጋጤ
አንድ ሰው ማሰብ እንዳይችል ወይም በአግባቡ እንዳይሠራ የሚያስደርገው ታላቅ ፍርሃት ወይም ጭንቀት
Judges 8:13
የሐሬስ መተላለፊያ
ይህ በሁለት ተራራዎች መካከል የሚያልፍ መንገድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ጠየቀውጠየቀው
ጌዴዎን ታዳጊውን ወጣት የጠየቀው ጥያቄ በግልጽ መነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በከተማው ውስጥ ያሉትን መሪዎች በሙሉ ስማቸውን እንዲነግረው ጠየቀው”
ሰባ ሰባት አለቆች
“77 አለቆች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 8:15
ዛብሄልና ስልማና
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 8፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
አስቀድመህ ዛብሄልንና ስልማናን ድል አድርገሃቸዋል?
ጌዴዎን የሱኮት ሰዎች ሊሳለቁበት የጠየቁትን አባባል ይጠቅሳል። ኢ.ት፡ “ዛብሄልንና ስልማናን ገና ድል አላደረግሃቸውም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ጌዴዎን ወሰደ - ገረፋቸው - አፈረሰው
እዚህ ጋ “ጌዴዎን” የሚወክለው ራሱንና ወታደሮቹን ነው። ኢ.ት፡ “ጌዴዎንና ወታደሮቹ ወሰዱ - ገረፏቸው - አፈረሱት
እሾኽና አሜከላ
ስል፣ በሐረግ ወይም ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ የሚገኝ፣ ጫፉ የሾለና ሰውና እንስሳን ለመቁረጥ የሚችል። ይህንን በመሳፍንት 8፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ጵንኤል
የከተማይቱን ስም በመሳፍንት 8፡8 ላይ በተረጎምከው መልኩ ተርጉመው።
Judges 8:18
ዛብሄልና ስልማና
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 8፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ታቦር
የዚህችን ከተማ ስም በመሳፍንት 4፡6 ላይ በተረጎምክበት መልክ ተርጉመው
እንተኑ የሚመስሉ ነበሩ
“ልክ አንተን ይመስሉ ነበር”
ሕያው እግዚአብሔርን

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሀይማኖታዊ መሓላ ሲሆን የሚናገረው እውነት መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት፡ “ቃል እገባላችኋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 8:20
የቴር
ይህ የጌዴዎን ልጅ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የሰው ኃይሉ እንደ ሰውነቱ ነው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ሊያደርገው የሚገባው ሥራው ነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ግማሽ ክብ
ይህ ሁለት ጫፍ ያለው ግማሽ ክብ ቅርጽ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ይህ ቅርጽ የሚሆነው ጨረቃ በጥላ ስትጋረድ ነው።
ጌጣ ጌጦች
ማስዋቢያዎች
Judges 8:22
አንተ፣ ልጅህና የልጅ ልጅህ
ይህ የሚያሳየው እርሱ ከሞተ በኋላ የጌዴዎን ተወላጆች እንዲገዟቸው ነው። ኢ.ት፡ “አንተና አንተ ከሞትክ በኋላም ተወላጆችህ”
ከምድያም እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው በእስራኤል ላይ የሆነውን የምድያም ኃይል ነው። ኢ.ት፡ “ከምድያም ኃይል” ወይም “ከምድያም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የምድያም
እዚህ ጋ “ምድያም” የሚወክለው የምድያምን ሰዎች ነው። ኢ.ት፡ “ከምድያማውያን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 8:24
ጌዴዎን … አላቸው
“ጌዴዎን ለእስራኤል ሰዎች አላቸው”
ጉትቻዎች
በጆሮ ላይ የሚደረግ ጌጥ
ዘረፋ
በማስገደድ የተቀሙ ወይም በጦርነት ከተገደሉ ሰዎች የተወሰዱ ነገሮች
ምድያማውያን እስማኤላውያን ስለነበሩ የወርቅ ጉትቻዎች ነበሯቸው
እዚህ ጋ ተራኪው ስለ ምድያማውያን ዳራዊ መረጃ ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ካባ
ረዘም ካለ ክር የሚሠራና እንደ ኮት በትከሻ ላይ የሚለበስ ልብስ
Judges 8:26
1,700 ሰቅል ወርቅ
“አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰቅል ወርቅ”። ዘመናዊውን የመጠን መለኪያ መጠቀም የሚያስፈልግ ከሆነ ይህንን ማድረግ የሚያስችሉ ሁለት መንገዶች አሉ። ኢ.ት፡ “18.7 ኪ.ግ ወርቅ” ወይም “ወደ 20 ኪ.ግ የሚጠጋ ወርቅ” (ቁጥሮች እና የመጽሐፍ ቅዱስ ክብደት መለኪያ የሚሉትን ተመልከት)
ግማሽ ክብ ቅርጽ ያላቸው ጌጣ ጌጦች
ይህንን በመሳፍንት 8፡21 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
በአንገት ጌጥ ላይ የሚንጠለጠሉ ድሪዎች
በአንገት ሀብል ወይም ክር ላይ የሚንጠለጠሉ ትናንሽ ጌጣጌጦች
የምድያም ነገሥታት ይለብሱት የነበረውን
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የምድያም ነገሥታት የለበሱት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 8:27
ጌዴዎን በጉትቻዎቹ ኤፉድ ሠራ
“ጌዴዎን የወርቅ ጉትቻዎቹን ኤፉድ ለመስሪያነት ተጠቀመበት”
ዖፍራ
የከተማይቱን ስም በመሳፍንት 6፡11 እንዳደረግኸው ተርጉመው።
በዚያ እስራኤል ሁሉ አመነዘሩበት
ይህ አመንዝራነትን በሚመስል መልክ ሐሰተኛ አምላክን ስለ ማምለካቸው ይናገራል። ኢ.ት፡ “እስራኤላውያን በዚያ ኤፉዱን በማምለካቸው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ሠሩ” ( ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እስራኤል በሙሉ
እዚህ ጋ “በሙሉ” በጣም ብዙዎቹ ልብሱን ማምለካቸውን አጽንዖት ለመስጠት የተደረገ ግነት ነው። ኢ.ት፡ “በእስራኤል በጣም ብዙ ሰዎች ልብሱን አመለኩት” (ግነትና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
እርሱም ለጌዴዎንና በቤቱ ላሉት ወጥመድ ሆነባቸው
ይህ አደን የሚያድን ሰው የሚያጠምደው ወጥመድ ይመስል ጌዴዎንና ቤተሰቡ ኤፉዱን ሊያመልኩት እንደተፈተኑ ያሳያል። ኢ.ት፡ “ለጌዴዎንና ለቤተሰቡ ፈተና ሆነባቸው” ወይም “ጌዴዎንና ቤተሰቡ እርሱን በማምለክ ኃጢአትን ሠሩ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በቤቱ ላሉት
እዚህ ጋ “በቤቱ” የሚወክለው የጌዴዎንን ቤተሰብ ነው። ኢ.ት፡ “ለቤተሰቡ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ስለዚህ ምድያም ለእስራኤል ሕዝብ ተገዛላቸው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ስለዚህ እግዚአብሔር ምድያማውያን በእስራኤል ሕዝብ ፊት እንዲገዙ አደረጋቸው” ወይም “ስለዚህ እስራኤላውያን ምድያማውያንን እንዲያሸንፉ እረዳቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ራሳቸውን ቀና አላደረጉም
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “እንደገና እስራኤልን አላጠቁም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ስለዚህ ምድሪቱ ዐርፋ ነበር
እዚህ ጋ “ምድሪቱ” የሚወክለው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ኢ.ት፡ “ስለዚህ እስራኤላውያን በሰላም ኖሩ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አርባ ዓመት
x
Judges 8:29
ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ስሙን በመሳፍንት 6፡32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሰባ ወንዶች ልጆች
“70 ወንዶች ልጆች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 8:32
ረጅም ዕድሜ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “በጣም በሸመገለ ጊዜ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ዖፍራ
የዚህችን ከተማ ስም በመሳፍንት 6፡11 እንዳደረግኸው ተርጉመው።
ከአቢዔዝር ጎሳ
የዚህን የሕዝብ ወገን ስም በመሳፍንት 6፡11 እንዳደረግኸው ተርጉመው።
እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ለማመልከት ነው። በቋንቋህ ይህንን ማድረግ የሚያስችል መንገድ ካለ ልትጠቀምበት ትችላለህ።
እንደገና ተመለሱ
ሕዝቡ እግዚአብሔርን መተዋቸው በአካል ከእርሱ እንደተለዩ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔርን ማምለካቸውን አቆሙ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በኣልን በማምለክ አመነዘሩ
ሐሰተኛ አማልክትን ማምለካቸው እንደ አመንዝራነት ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “በኣልን በማምለክ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ሠሩ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በኣልብሪት
ይህ የሐሰተኛ አምላክ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 8:34
ከጠላቶቻቸው እጅ ሁሉ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። ኢ.ት፡ “ከጠላቶቻቸው ኃይል ሁሉ” ወይም “ከጠላቶቻቸው ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር

የሚለውን ተመልከት)
በየአቅጣጫው
“የከበቧቸውን “
የይሩበአል ቤት
እዚህ ጋ “የ…ቤት” የሚወክለው የአንድን ሰው ቤተሰብ ነው። አ.ት፡ “የይሩበአል ቤተሰብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በመሳፍንት 6፡32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

---

## Chapter 9

### Judges 9:1

ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በመሳፍንት 6፡32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
እባካችሁ፣ በሴኬም ያሉ መሪዎች ሁሉ እንዲሰሙ እንዲህ በሉ፣ ‘ሰባዎቹ የይሩበዓል ልጆች ቢገዟችሁ ወይስ አንዱ ብቻ ቢገዛችሁ ይሻላችኋል?’
ይህ በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያለ ትዕምርተ ጥቅስ ነው። ቀጥተኛው ትዕምርተ ጥቅስ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ሆኖ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እባካችሁ፣ የይሩበዓል ሰባ ልጆች ሁሉ እንዲገዟቸው ይፈልጉ እንደሆን ወይም ከልጆቹ አንዱ ብቻ እንዲገዛቸው ይፈልጉ እንደሆን የሴኬምን መሪዎች ጠይቋቸው” (በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ትዕምርተ ጥቅስ እና ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ የሚለውን ተመልከት)
ሰባ
“70” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
እኔ አጥንታችሁና ሥጋችሁ ነኝ
እዚህ ጋ “አጥንታችሁና ሥጋችሁ” የሚወክለው የአንድ ሰው ዘመድ መሆንን ነው። አ.ት፡ “እኔ የቤተሰባችሁ አባል ነኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

### Judges 9:3

የእናቱ ዘመዶች ስለ እርሱ ለመሪዎቹ ነገሯቸው
ይህ ማለት የአቤሜሌክ የእናቱ ዘመዶች አቤሜሌክን ንጉሣቸው እንዲያደርጉት አሳብ በማቅረብ ለመሪዎቹ ተናገሩ።
አቤሜሌክን ለመከተል ተስማሙ
“አቤሜሌክ መሪያቸው እንዲሆን ተስማሙ”
ቤቱ
እዚህ ጋ “ቤት” የሚወክለው መቅደስን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰባ ጥሬ ብር
ይህ ማለት ሰባ ሰቅል ብር ነው። አንድ ሰቅል 11 ግራም ይመዝናል። ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መተርጎም አስፈላጊ ከሆነ እንደዚህ አድርገህ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “አንድ ኪሎ የሚያህል ጥሬ ብር” (ገንዘብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚለውን ተመልከት)
ሰባ
“70” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
በኣልብሪት
ይህ የሐሰተኛ አምላክ ስም ነው። እርሱን በመሳፍንት 8፡33 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሕገ ወጦችንና ግድ የለሾችን
“ቁጡና ሞኞች”

### Judges 9:5

ዖፍራ
በመሳፍንት 6፡11 ላይ እንዳደረግኸው የዚህችን ከተማ ስም ተርጉመው።
አንድ ድንጋይ
“1 ድንጋይ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሰባ
“70” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በመሳፍንት 6፡32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ቤት ሚሎ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

### Judges 9:7

ለኢዮአታም ይህ በተነገረው ጊዜ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አቤሜሌክ ወንድሞቹን መግደሉን ኢዮአታም በሰማ ጊዜ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ገሪዛን ተራራ
ይህ ተራራ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ዛፎች በላያቸው ላይ ንጉሥ ለማንገሥ ተሰበሰቡ። የወይራውን ዛፍ ‘በእኛ ላይ ንገሥ’ አሉት
ኢዮአታም ሰዎች የሚያደርጓቸውን ነገሮች በዛፎች በመመሰል ያብራራል። (ምሳሌዎች እና ሰውኛ የሚሉትን ተመልከት)
በላያቸው ላይ ንጉሥ ለመቀባት
እዚህ ጋ በዘይት መቀባት አንድን ሰው ንጉሥ እንዲሆን መሾምን የሚወክል ምሳሌአዊ ድርጊት ነው። አ.ት፡ “በሁላቸውም ላይ እንዲገዛ ንጉሥ ለመሾም”
በእኛ ላይ ንገሥ
“ንጉሣችን ሁን”

### Judges 9:9

የወይራው ዛፍ እንዲህ አላቸው - የበለስ ዛፍ እንዲህ አላቸው
ኢዮአታም ሰዎች የሚያደርጓቸውን ነገሮች በዛፎች ምሳሌ አድርጎ ያብራራል። (ምሳሌዎች እና ሰውኛ የሚሉትን ተመልከት)
በሌሎች ዛፎች ላይ - ዘይት መስጠቴን መተው አለብኝ?
የወይራው ዛፍ ንጉሥ መሆንን እምቢ ለማለት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሌሎች ዛፎች ላይ … ዘይት መስጠቴን አላቆምም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
መወዛወዝ
“መወዛወዝ” ማለት በንፋስ ምክንያት ወደ ፊትና ወደ ኋላ ማለት ነው። ዛፉ ይህንን ሐረግ የሚጠቀመው “መግዛት” ለማለት ነው።
በሌሎች ዛፎች ላይ - ጣፋጭነቴን መተው አለብኝ?
የበለስ ዛፉ ንጉሥ መሆንን እምቢ ለማለት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሌሎች ዛፎች ላይ … ጣፋጭነቴን አላቆምም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ጣፋጭነቴንና መልካሙን ፍሬዬን
“ጣፋጭነት” የሚለው ቃል የነገር ስም ነው። በዛፉ ላይ የሚበቅለውን ፍሬ ለመግለጽ እንደ ቅጽል ሆኖ ሊነገር ይችላል። (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

### Judges 9:12

ዛፎቹ የወይንን ተክል እንዲህ አሉት
በዚህ ምሳሌ ኢዮአታም ሰዎች የሚያደርጓቸውን ነገሮች ዛፎቹና የወይን ተክል እንደሚያደርጉት አድርጎ ያብራራል። (ምሳሌዎች እና ሰውኛ የሚሉትን ተመልከት)
በሌሎች ዛፎች ላይ -- አዲሱን ወይኔን ማቆም አለብኝ?
የወይን ተክሉ ንጉሥ መሆንን እምቢ ለማለት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ መነገር ይችላል። አ.ት፡ “በሌሎች ዛፎች ላይ … አዲሱን ወይኔን አላቆምም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የእሾህ ቁጥቋጦ
እሾህ የሚጎዳ የሾለ መውጊያ አለው። ይህ ቁጥቋጦ በየቅርንጫፎቹ ላይ በርካታ ሹል መውጊያዎች አሉት።

### Judges 9:15

የእሾህ ቁጥቋጦው ለዛፎቹ እንዲህ አላቸው
በዚህ ምሳሌ ኢዮአታም የቁጥቋጦው እሾህና ዛፎቹ ሰዎች የሚያደርጓቸውን ነገሮች እንደሚያደርጉ ያብራራል። (ምሳሌዎች እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
በላያችሁ እንድነግሥ ልትቀቡኝ
አንድን ሰው በዘይት መቀባት ንጉሥ እንዲሆን የመሾም ምሳሌአዊ ድርጊት ነው። አ.ት፡ “ንጉሣችሁ አድርጋችሁ ልትቀቡኝ” (ምሳሌአዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)
ደህንነት እንዲሆንላችሁ
“ደህንነት” የሚለው ቃል የነገር ስም ሲሆን እንደ ቅጽል ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ተጠበቁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
እሳት ከእሾህ ቁጥቋጦው ይውጣ፣ የሊባኖስንም ዝግባዎች ያቃጥል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ማለት ዝግባዎቹን ለማቃጠል የእሾህ ቁጥቋጦው ይነዳል።
ከዚያም እሳት ከእሾህ ቁጥቋጦው ይውጣ
የእሾህ ቁጥቋጦው ራሱን እንደ "እሾህ ቁጥቋጦ" ያመለክታል። ኢ.ት፡ "ከዚያም እሳት ከእኔው ከእሾህ ቁጥቋጦው ይውጣ" (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
አሁን
ይህ "በዚህ ሰዓት" ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ትኩረትን ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ጉዳይ ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል።
ለይሩበአልና ለቤቱ መልካም አድርጋችሁ ከሆነና የሚገባውን ቅጣት ሰጥታችሁት ከሆነ
ኢዮአታም ያደረጉት መልካም ይሆን እንደሆነ ምርጫውን ያቀርብላቸዋል፤ ይሁን እንጂ ያደረጉት በመሠረቱ መልካም እንደሆነ ኢዮአታም አያምንም። ኢ.ት፡ "መልካም የሆነውን አድርጋችሁ ከሆነና ልጆቹን ሁሉ ትገድሉበት ዘንድ ለይሩበአል የሚገባው ከሆነ"
ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በመሳፍንት 6፡32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተምልከት።
ቤቱ
እዚህ ጋ "ቤት" የጌዴዎንን ቤተሰብ ይወክላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 9:17
ከምድያማውያን እጅ -- አባቴ እንደተዋጋላችሁ ለማሰብ
እዚህ ጋ ጌዴዎን የሴኬምን ሰዎች ለማዳን ከተዋጋ በኋላ የሴኬም ሰዎች ለጌዴዎንና ለቤተሰቡ በክፋት መመለሳቸውን ኢዮአታም ማመን እንደማይችል ይገልጻል።
ከምድያማውያን እጅ
እዚህ ጋ "እጅ" የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። ኢ.ት፡ "ከምድያማውያን ኃይል" ወይም "ከምድያማውያን" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ተነሣችሁበት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ "ተቃወማችሁ" ወይም "በእርሱ ላይ አምጻችኋል" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የአባቴ ቤት
እዚህ ጋ "ቤት" የሚወክለው ቤተሰብን ነው። ኢ.ት፡ "የአባቴ ቤተሰብ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰባ
"70" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
አንድ ድንጋይ
"1 ድንጋይ" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሴት ባሪያው
እዚህ ጋ "የእርሱ" የሚያመለክተው ጌዴዎንን ነው።
Judges 9:19
ከጌዴዎንና ከቤቱ ጋር በታማኝነትና በቅንነት አድርጋችሁ ከሆነ
ኢዮአታም ያደረጉት መልካም ይሆን እንደሆነ ምርጫውን ያቀርብላቸዋል፣ ይሁን እንጂ ያደረጉት በመሠረቱ መልካም እንደሆነ ኢዮአታም አያምንም። ኢ.ት፡ "ለይሩበአልና ለቤተሰቡ ሊደረግላቸው የሚገባቸውን አድርጋችሁላቸው ከሆነ"
ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። እንዲህ ማለትም፣ "በኣል ለራሱ ይሟገት" ማለት ነው። ይህንን በ6፡32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ለቤቱ
እዚህ ጋ "ቤት" የሚያመለክተው ቤተሰብን ነው። ኢ.ት፡ "ቤተሰቡን" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ካልሆነ ግን
ኢዮአታም ያደረጉት ክፉ መሆኑን እና እርግማን እንደሚሆንባቸው ተቃራኒውን አማራጭ ያቀርብላቸዋል። ኢዮአታም ያደረጉት ክፉ መሆኑን ያምናል። ኢ.ት፡ "ለይሩበአልና ለቤተሰቡ ሊደረግ የማይገባቸውን አድርጋችሁ ከሆነ ግን"
ከአቤሜሌክ እሳት ይውጣ፣ የሴኬምንም ሰዎች ያንድድ
ኢዮአታም የሚናገረው እርግማንን ነው። አቤሜሌክ በእሳት ያቃጥላቸው ይመስል የሴኬምን ሰዎች እንደሚያጠፋቸው ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አቤሜሌክን ለማንደድ እሳት ከሴኬምና ከቤትሚሎ ሰዎች ይውጣ
ኢዮአታም የሚናገረው እርግማንን ነው። የሴኬምና የቤትሚሎ ሰዎች በእሳት ያቃጥሉት ይመስል አቤሜሌክን እንደሚያጠፉት ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቤትሚሎ
ይህ የቦታ ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 9፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ብኤር
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 9:22
እግዚአብሔር በአቤሜሌክና በሴኬም መሪዎች መካከል ክፉ መንፈስን ላከ
ይህ ማለት ኢዮአታም በአቤሜሌክና በሴኬም መሪዎች መካከል አለመግባባትንና ጠላትነትን እንዲፈጥር ክፉ መንፈስን በመላክ ያደረገውን እርግማን እግዚአብሔር ተግባራዊ አድርጎታል ማለት ነው።
ወንድሞቹን እንዲገድል ስለረዱት -- ስላደረጉት ግፍ እግዚአብሔር ይህንን አደረገ
ተደራጊ ድምፅ ያላቸውን ሐረጎች በአድራጊ ድምፅ መናገር ይቻላል። ኢ.ት፡ "አቤሜሌክ ስለገደላቸው ሰባ ልጆችና የሴኬም ሰዎች በግድያው ስለረዱት እግዚአብሔር ለመበቀል ይህንን አደረገ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሰባ
"70" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በመሳፍንት 6፡32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Judges 9:25
አደጋ እንዲጥሉበት በኮረብታማው ስፍራ ሰዎች አድፍጠው እንዲጠብቁት አደረጉ
"ሰዎች በኮረብታው ጫፍ እንዲደበቁና አቤሜሌክን ለመግደል እንዲጠባበቁ ላካቸው"
ይህ ለአቤሜሌክ ተነገረው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ "ሰዎች ሊያጠቁት እየተጠባበቁ እንዳሉ አንድ ሰው ለአቤሜሌክ ነገረው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 9:26
ገዓል -- አቤድ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ተማምነውበት ነበር
"መተማመን" የሚለው ቃል የነገር ስም ሲሆን "መታመን" በሚል ግሥ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ "ታመኑበት" (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ወደ ሜዳ ወጡ
እዚህ ጋ "እነርሱ" የሚያመለክተው ገዓልን፣ ዘመዶቹንና የሴኬምን ሰዎች ነው።
ረገጣቸው
ይህንን ያደረጉት የወይን ጭማቂ ለማዘጋጀት ነው።
ረገጡ
"ሰባበሩ" ወይም "ጨፈለቁ"
በቤቱ ውስጥ
እዚህ ጋ "ቤት" የሚወክለው መቅደስን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 9:28
ገዓል -- ኤቤድ
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 9፡26 ላይ እንዴት እንደተርጎምከው ተመልከት።
እንድናገለግለው አቤሜሌክ ማነው? ሴኬምስ ማነው?
ገዓል የሰኬም ሰዎች አቤሜሌክን ማገልገል እንደሌለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት፡ "አቤሜሌክን ማገልገል የለብንም!" (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
እንድናገለግለው አቤሜሌክ ማነው? ሴኬምስ ማነው?
እነዚህ ሁለቱም ጥያቄዎች አንድ ናቸው። የአቤሜሌክ እናት ከሴኬም በመሆኗ ምክንያት ገዓል አቤሜሌክን ለማመልከት "ሴኬም" ይላል። ኢ.ት፡ "አቤሜሌክን ማገልገል የለብንም፣ እርሱም ሴኬም ነው!" ( እና ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተመልከት)
እርሱ የይሩበአል ልጅ አይደለምን? ዜቡልስ የእርሱ ሹም አይደለምን?
ገዓል የሰኬም ሰዎች አቤሜሌክን ማገልገል እንደሌለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት: “እርሱ የይሩበአል ልጅ ብቻ ነው፣ ዜቡልም የእርሱ ሹም ብቻ ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን በመሳፍንት 6:32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዜቡል
ይህ የሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የሴኬምን አባት የኤሞርን ሰዎች አገልግሉ
ገዓል የሚለው፣ የሴኬም ሰዎች ማገልገል ያለባቸው እውነተኛ ከነዓናውያን የሆኑትን ከኤሞር የተወለዱትን እንጂ እስራኤላዊ አባት ያለውን ሰው ማገልገል የለባቸውም።
አቤሜሌክን የምናገለግለው ለምንድነው?
ገዓል የሰኬም ሰዎች አቤሜሌክን ማገልገል እንደሌለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት: “አቤሜሌክን ማገልገል የለብንም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
እነዚህ ሰዎች ከትዕዛዜ ስር እንዲሆኑ እመኛለሁ
“የሴኬምን ሰዎች ባስተዳድር እመኛለሁ”
Judges 9:30
ዜቡል
ይህንን ስም በመሳፍንት 9:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
የኤቤድን ልጅ የገዓልን ቃል ሰሙ
“የኤቤድ ልጅ ገዓል የተናገረውን ሰሙ”
ገዓል -- ኤቤድ
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 9:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
ቁጣው ነደደ
መቆጣቱ እንደ እሳት መንደድ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት: “በጣም ተቆጣ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለማታለል
ዜቡል ገዓልንና የሴኬምን ሰዎች እያታለላቸው ነው። ኢ.ት: “በምስጢር”
ከተማይቱን በአንተ ላይ እያነሣሡ ነው
ይህ የከተማው ሰዎች በድስት ውስጥ እንዳለ ፈሳሽ መንተክተካቸውን ያሳያል። ኢ.ት: “የከተማይቱ ሰዎች በአንተ ላይ እንዲያምጹ እያነሣሧቸው ነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ከተማይቱ
እዚህ ጋ “ከተማ” የሚወክለው በከተማይቱ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 9:32
አሁን
ይህ “በዚህ ሰዓት” ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ትኩረትን ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ጉዳይ ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል።
ደፈጣ
“ተደብቆ እነርሱን በድንገት ማጥቃት”
የምትችለውን አድርግባቸው
ይህ ማለት የገዓልን ተከታዮች ለማጥፋት የፈለጉትን ማድረግ ይችላሉ።
Judges 9:34
ከእርሱ ጋር የነበሩት ሰዎች ሁሉ
“አቤሜሌክን የተከተሉ ሰዎች ሁሉ” ወይም “ለአቤሜሌክ ይዋጉ የነበሩ ሰዎች ሁሉ”
በሴኬም ላይ የሚያደፍጡትን አስቀመጡ
እዚህ ጋ “ሴኬም” የሚወክለው የሴኬምን ሰዎች ነው። ኢ.ት: “የሴኬምን ሰዎች በድንገት ለማጥቃት ተደበቁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አራት ቦታ አካፍሎ
“በ4 ቡድኖች ለያይቶ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ገዓል -- ኤቤድ
እነዚህን ስሞች በመሳፍንት 9:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
Judges 9:36
ገዓል
ይህ የሰው ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 9:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዜቡል
ይህ የሰው ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 9:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የምትመለከተው ሰዎችን የሚመስሉ የኮረብቶችን ጥላ ነው
ዜቡል ገዓልን እያደናገረውና ለጦርነት እንዳይዘጋጅ እያዘገየው ነው። ኢ.ት: “ያ ሰዎች ሳይሆኑ በኮረብቶቹ ላይ ጥላዎች ብቻ ናቸው”
አንድ ክፍል
“1 ቡድን” ወይም “1 ጓድ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 9:38
ዜቡል
በመሳፍንት 9:28 ላይ ይህንን ስም እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
አሁን የትዕቢት ቃልህ የት አለ?
ዜቡል በዚህ ምላሽ በማይፈልግ ጥያቄ በገዓል ላይ እየተሳለቀበት ነው። ኢ.ት: “አሁን በትዕቢት አትናገርም” ወይም “አሁን አትታበይም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
‘እናገለግለው ዘንድ አቤሜሌክ ማነው?’ ያልከው አንተ
ዜቡል የገዓልን የኩራት ንግግር መልሶ እየጠቀሰለት ነው። ይህ እንደ መግለጫና ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “አቤሜሌክን ማገልገል የለብንም ብለህ የነበርከው አንተ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ትዕምርተ ጥቅሶች የሚለውን ተመልከት)
እነዚህ አንተ የናቅኻቸው ሰዎች አይደሉምን?
ዜቡል በዚህ ምላሽ በማይፈልግ ጥያቄ ገዓልን እየተገዳደረው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “የናቅኻቸው ሰዎች እኾውልህ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የተናቁ
እጅግ ያልተወደዱ ወይም የተጠሉ
ገዓል
ይህንን ስም በመሳፍንት 9:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ብዙዎች ክፉኛ ቆስለው ወደቁ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ብዙ ሰዎች ቆስለው ሞቱ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 9:41
አሩማ
ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ዜቡል
ይህ የሰው ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 9:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ገዓል
ይህ የሰው ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 9:26 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ይህ ለአቤሜሌክ ተነገረው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “አንድ ሰው ይህንን ለአቤሜሌክ ነገረው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በሦስት ክፍል ከፋፈላቸው
“በ3 ቡድኖች ለያያቸው” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
በእርሻው ውስጥ የሚያደፍጡትን አኖሩ
x
Judges 9:44
ቡድኖቹ
“የወታደሮቹ ቡድኖች”
ሌሎች ሁለት
“ሌሎች 2” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
አቤሜሌክ ተዋጋ -- አጠፋ
እዚህ ጋ “አቤሜሌክ” የሚወክለው ራሱንና ወታደሮቹን ነው። ኢ.ት: “አቤሜሌክና ወታደሮቹ ተዋጉ … አጠፉ”
በከተማይቱ ላይ
እዚህ ጋ “ከተማ” የሚወክለው ሰዎችን ነው። ኢ.ት: “በሴኬም ሰዎች

ላይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አጠፉ
“አወደሙ”
ጨው ዘራባት
“በምድሪቱ ላይ ጨው ዘራ”። በምድር ላይ ጨው መዝራት በዚያ ቦታ ምንም ነገር እንዳይበቅል ያደርጋል።
Judges 9:46
ቤቱ
እዚህ ጋ ይህ የሚወክለው መቅደስን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ኤልበሪት
“ኤል” የሚለው ቃል ትርጉም “አምላክ” ማለት ነው። ይህ በመሳፍንት 8:33 እንዳለው “በኣል በሪት” ሁሉ ያው ሐሰተኛ አምላክ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ለአቤሜሌክ ተነገረው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ለአቤሜሌክ ነገረው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 9:48
ሰልሞን ተራራ
ይህ የተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ቆለለ
ይህ ማለት ቅርንጫፎቹን በብዙ መጠን እንደ ክምር መከመር ነው።
አንድ ሺህ የሚያህሉ ሰዎች
“1,000 ያህል ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 9:50
ቴመስ
ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ቴመስን ከበበ
“ከቴመስ ከተማ ውጪ ሰፈረ”
Judges 9:52
ተዋጋት
“አጠቃት”
የወፍጮ መጅ
ሁለት ትላልቅና ጠፍጣፋ ድንጋዮች ጥራጥሬ ለመፍጨት ያገለግሉ ነበር። በታችኛው ላይ በመንከባለል በመሐል ያለውን ጥራጥሬ የሚፈጨው ከላይ የሚሆነው መጅ ነው።
ጋሻ ጃግሬ
ይህ የአቤሜሌክን የጦር መሣሪያ የሚሸከመው ሰው ነው።
ወጋው
ይህ ማለት ወጣቱ አቤሜሌክን በሰይፍ ወጋው።
Judges 9:55
ሰባ
“70” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
የሴኬምን ሰዎች ክፋት ሁሉ በራሳቸው ላይ መለሰባቸው
እዚህ ጋ “ክፋት በራሳቸው ላይ ተመለሰ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ስላደረጉት ክፋት ሁሉ የሴኬምን ሰዎች ቀጣቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የይሩበአል ልጅ የኢዮአታም እርግማን ደረሰባቸው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “የይሩበአል ልጅ የኢዮአታም እርግማን መጣባቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ይሩበአል
ይህ የጌዴዎን ሌላው ስሙ ነው። ይህንን ስም በመሳፍንት 6:32 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

---

Chapter 10
Judges 10:1
ቶላ -- ፉሐ -- ዱዲ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሳምር
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
እስራኤልን ለማዳን ተነሣ
“እስራኤልን ለማዳን መጣ” ወይም “እስራኤልን ለማዳን መሪ ሆነ”
እስራኤልን ለማዳን
እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚወክለው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእስራኤል ላይ ፈረደ
እዚህ ጋ “ፈረደ” ማለት የእስራኤልን ሕዝብ መራ ማለት ነው።
ሃያ ሦስት ዓመት
“23 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 10:3
ከእርሱ ቀጥሎ ገለዓዳዊው ኢያዕር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከቶላ በኋላ ገለዓዳዊው ኢያዕር መሪ ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ኢያዕር
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ገለዓዳዊው
ኢያዕር ከገለዓድ ነገድ ነበር
በእስራኤል ላይ ፈረደ
እዚህ ጋ “ፈረደ” ማለት የእስራኤልን ሕዝብ መራ ማለት ነው።
እስራኤል
እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚወክለው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሃያ ሁለት ዓመት
“22 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሠላሳ ወንዶች ልጆች
“30 ወንዶች ልጆች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሐቮትያኢር
ይህ በአንድ ሰው ስም የሚጠራ የአውራጃ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
እስካሁን ድረስ
ይህ ማለት መጽሐፈ መሳፍንት እስከሚጻፍበት ጊዜ ድረስ ማለት ነው።
ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ቃሞን
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 10:6
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ማድረጋቸውን አበዙ
አንድ ሰው እየጨመረበት እንደሚያተልቀው አንዳች ነገር ይህ የተነገረው ስለ ክፋት ነው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ክፉ ነው ያለውን ማድረጋቸውን ቀጠሉ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእግዚአብሔር ፊት
የእግዚአብሔር ፊት የሚወክለው የእርሱን ፍርድ ወይም ምዘና ነው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር እንደሚለው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አስታሮቶች
ይህ የአስታሮት ብዙ ቁጥር ሲሆን በተለያየ ቅርጽ የምትመለክ እንስት አምላክ ነበረች። ይህንን በመሳፍንት 2:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
እግዚአብሔርን ተዉት፣ አላመለኩትምም
በመሠረቱ ደራሲው ሁለት ጊዜ የተናገረው ስለ አንድ ነገር አጽንዖት ለመስጠት ነው። እነዚህ ሊጣመሩ የሚችሉ ናቸው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔርን ማምለካቸውን ሙሉ በሙሉ አቆሙ”
እግዚአብሔርን ተዉት
ከዚያ በኋላ እግዚአብሔርን አለማምለካቸውና አለመታዘዛቸው ሰዎቹ እግዚአብሔርን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ትተው ወደ አንድ የሆነ ቦታ እንደሄዱ ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእስራኤል ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደ

ቁጣ የሚነድ እሳት ይመስል እግዚአብሔር እንደ ተቆጣ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ በጣም ተቆጣ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በፍልስጥኤማውያንና በአሞናውያን እጅ ሸጣቸው

እግዚአብሔር ፍልስጥኤማያንና አሞናውያን እስራኤላውያንን እንዲያሸንፉ መፍቀዱ እስራኤላውያንን ለእነርሱ እንደሸጠላቸው ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በ... እጅ

እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 10:8

አደቀቋቸውና አስጨነቋቸው

እነዚህ ሁለት ቃላት የሚሉት በመሠረቱ ስለ አንድ ነገር ሲሆን እስራኤላውያን ምን ያህል እንደተሰቃዩ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ኢ.ት፡ “በከፋ ሁኔታ አስጨነቋቸው”

አሥራ ስምንት ዓመት

“18 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ከዮርዳኖስ ማዶ የነበሩት

ይህ ማለት ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ ማለት ነው።

በገለዓድ ያለው

“ይህ አውራጃም ደግሞ ገለዓድ ተብሎ ተጠርቷል”

ይሁዳ - ብንያም

“ይሁዳ” እና “ብንያም” የእነዚያን ነገዶች ሕዝቦች ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የይሁዳ ነገድ ሕዝቦች ... የብንያም ነገድ ሕዝቦች”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የኤፍሬም ቤት

እዚህ ጋ “ቤት” የሚያመለክተው የኤፍሬምን ነገድ ሕዝቦች ነው። ኢ.ት፡ “የኤፍሬም ነገድ ሕዝቦች”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመሆኑም እስራኤል እጅግ ተጨነቀ

“እስራኤል” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ኢ.ት፡ “በመሆኑም የእስራኤል ሕዝብ በጣም ተሰቃየ”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 10:10

የእስራኤል ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ

ይህ ማለት የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው በፍጹም ልባቸው ጠየቁት።

አምላካችንን በመተዋችን ምክንያት

ከዚያ በኋላ እግዚአብሔርን አለማምለካቸውና አለመታዘዛቸው ሰዎቹ እግዚአብሔርን ትተው ወደ አንድ የሆነ ቦታ እንደሄዱ ሆኖ ተነግሯል። ( ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላካችንን ትተነዋል

ሕዝቡ የሚናገሩት ስለ እግዚአብሔር ሲሆን “አምላካችን” ብለው ይጠሩታል። ይህ በሁለተኛ መደብ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አምላካችን ሆይ፣ አንተን ትተንሃል” (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ሲዶናውያን -- አላዳንኋችሁምን?

ሌሎች አማልክትን ስለማምለካቸው እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ይገስጻቸዋል። ይህ መልስ የማይሻ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከሲዶናውያን ... ያዳንኋችሁ እኔ ነኝ” (መልስ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ማዖናውያን

እነዚህ ከማዖን ቤተሰብ ወይም ጎሳ የሆኑ ሕዝቦች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ከኃይላቸው

እዚህ ጋ “ኃይል” የሚወክለው አማሌቃውያንን እና ማዖናውያንን ነው። ኢ.ት፡ “ከእነርሱ”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 10:13

እንደ ገና ተዋችሁኝ

ከዚያ በኋላ እግዚአብሔርን አለማምለካቸውና አለመታዘዛቸው ሰዎቹ እግዚአብሔርን ትተው ወደ አንድ የሆነ ቦታ እንደሄዱ ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእንግዲህ ወዲህ አላድናችሁም

“ከእንግዲህ ወዲህ” የሚለው ሐረግ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም አንድ ነገር በማድረግ መቀጠል ማለት ነው። በእግዚአብሔር አነጋገር ውስጥ ግልጽ ያልሆነውን ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ኢ.ት፡ “በተደጋጋሚ እናንተን ማዳኔን አልቀጥልም” ወይም “እናንተን ማዳን ማቆሜን እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ”

Judges 10:15

በመካከላቸው ያሉትን እንግዶች አማልክት

የዚህን መግለጫ ግልጽ ያልሆነ ትርጉም ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ኢ.ት፡ “የወረሷቸውን የእንግዶች አማልክት ምስሎች”

እግዚአብሔር የእስራኤልን ስቃይ ለመታገስ አልቻለም

እዚህ ጋ እስራኤል የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ከእንግዲህ ወዲያ እንዲሰቃይ አልፈለገም”።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Judges 10:17

ከአሞናውያን ጋር በመዋጋት የሚጀምርልን ሰው ማነው?

“አሞናውያንን ለመዋጋት ሰራዊታችንን የሚመራው ማን ነው?”

---

Chapter 11

Judges 11:1

ገለዓዳዊው

ይህ ከገለዓድ አውራጃ የሆነ ግለሰብ ነው። የእርሱም አባት ስም ገለዓድ መሆኑ የአጋጣሚ ጉዳይ ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

የሚስቱ ወንዶች ልጆች ባደጉ ጊዜ

“የገለዓድ ሚስት የወለደቻቸው ወንዶች ልጆች በጎለመሱ ጊዜ”

በጦብ ምድር

ጦብ የአውራጃ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

መጡና ከእርሱ ጋር ሄዱ

“ተከተሉት” ወይም “አብረው በየስፍራው ሄዱ”

Judges 11:4

ከጥቂት ቀናት በኋላ

“ከጥቂት ጊዜ በኋላ”

ከእስራኤል ጋር ተዋጉ

“ተዋጉ” የሚለው ቃል የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም እስራኤልን ወጉ፣ በጦርነቱም ከእነርሱ ጋር ነበሩ። እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (የአነጋገር ዘይቤ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከ ... ጋር እንድንዋጋ

“ከ -- ጋር መዋጋት እንድንችል”

Judges 11:7

ከአባቴ ቤት

እዚህ ጋ “ቤት” የሚያመለክተው በቤቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ነው። ኢ.ት፡ “ቤተሰቦቼ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አሁን ወደ አንተ የመጣነው ለዚህ ነው

“ለዚህ ነው” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ዮፍታሔ በችግር ውስጥ ስለመሆናቸው የተናገረውን ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “አሁን ወደ አንተ የመጣነው በችግር ውስጥ ስለሆንን ነው”።

ከአሞን ሰዎች ጋር ተዋጋ

“የአሞንን ሰዎች ውጋቸው”

Judges 11:9

መሪና አዛዥ

እነዚህ ሁለት ቃላት መሰረታዊ ትርጉማቸው አንድ ሆኖ ሳለ የዮፍታሔን አስፈላጊነት አጽንዖት ለመስጠት ተደግመዋል። ሁለቱን ቃላት ልታጣምራቸው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “አዛዥ”።

ዮፍታሔ በምጽጳ በእግዚአብሔር ፊት በነበረ ጊዜ የተናገረውን ቃል በሙሉ ደገመው

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። እዚህ ጋ “በእግዚአብሔር ፊት” የሚለው ሐረግ የተናገረውን ቃል በእግዚአብሔር ፊት እንደ መሐላ ደገመው ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የተናገረውን ቃል በሙሉ
ይህ የሚያመለክተው መሪያቸው ለመሆን ለገለዓድ መሪዎች የተናገረውን ቃል ነው።
Judges 11:12
በመሐከላችን ያለው ይህ ጸብ ምንድነው
“በመካከላችን ለምን ጸብ ይሆናል?” ዮፍታሔ ንጉሡ በእስራኤል ላይ ለምን እንደ ተቆጣ ይጠይቃል።
መሬታችንን ለመውሰድ በኃይል የመጣኸው ለምንድነው
“አንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአሞንን ንጉሥ ሲሆን ራሱንና ወታደሮቹን ይወክላል። ኢ.ት: “ወታደሮችህ መሬታችንን ለመያዝ ለምን ይመጣሉ”
በኃይል ለመውሰድ የመጡት
“በጉልበት ለመውሰድ የመጡት”
አርኖን == ያቦቅ
እነዚህ የሁለት ወንዞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
እስከ ዮርዳኖስ
“ከዮርዳኖስ ወንዝ በወዲያ በኩል”
በሰላም
“በሰላማዊ መንገድ” ወይም “ልትከላከላቸው እንዳትሞክር”
Judges 11:14
እርሱም አለ
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለንጉሡ የሚናገረውን መልዕክተኛ ነው። ይህ ምናልባት በቡድን የሆኑትን መልዕክተኞች በሚያመለክትውና በተከፈተው ተለዋዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንዳለው “እነርሱ” ተብሎ መጻፍ ይኖርበት ይሆናል። ኢ.ት: “መልዕክተኞቹ እንዲህ እንዲሉ ዮፍታሔ ነገራቸው” ወይም “እንዲህ አሉ”።
ከግብጽ ወጥተው በመጡ ጊዜ
ሰዎች ወደ ተስፋይቱ ምድር በሚጓዙበት ጊዜ ሁሉ ወደ ተስፋይቱ ምድር “ወደ ላይ” እንደ ሄዱ ይነገርላቸዋል። እስራኤላውያን ግብፅን ለቀው በወጡ ጊዜ ወደ ተስፋይቱ ምድር በመጓዝ ላይ ነበሩ። ኢ.ት: “ግብፅን ለቀው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 11:17
እስራኤል መልዕክተኞችን በላኩ ጊዜ
መልዕክተኞቹ የተላኩት በእስራኤል መሪዎች ናበር። ኢ.ት: “የእስራኤል መሪዎች መልዕክተኞችን በላኩ ጊዜ”
በሚያልፉበት
“በመሐል ሲሄዱ” ወይም “ማቋረጥ”
አልሰማም
ይህ ቃል ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም “እምቢ” ማለት ነው። ኢ.ት: “እምቢ አለ” ወይም “ጥያቄአቸውን አልተቀበለም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ደግሞም ወደ ሞዓብ ንጉሥ መልዕክተኞችን ላኩ
እስራኤል ወደ ሞዓብ ንጉሥ መልዕክተኞችን የላኩበት ምክንያት ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “ደግሞም ወደ ሞዓብ ንጉሥ ተመሳሳዩን ጥያቄ የሚያቀርቡ መልዕክተኞችን ላኩ”
እርሱ ግን እምቢ አለ
እስራኤል በሞዓብ መካከል ለማለፍ ያቀረበውን ጥያቄ የሞዓብ ንጉሥ አልተቀበለውም። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በበለጠ ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “እርሱም ደግሞ እምቢ አለ፣ በሞዓብ ምድር መካከል እንዲያልፉም አልፈቀደላቸውም”።
አርኖን
ይህ የወንዝ ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 11:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Judges 11:19
እስራኤል ወደ ሴዎን መልዕክተኞችን ላኩ
መልዕክተኞቹ የተላኩት በእስራኤል መሪዎች ነው። ኢ.ት: “የእስራኤል መሪዎች መልዕክተኞችን በላኩ ጊዜ”
ሴዎን
ይህ የሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሐሴቦን -- ያሃድ
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሴዎን ግን እስራኤል በግዛቱ ውስጥ ያልፍ ዘንድ አላመነውም
ሴዎን በምድሩ በሰላም ያልፋል ብሎ እስራኤልን አላመነም። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “ይሁን እንጂ ሴዎን የእስራኤል ሕዝብ በግዛቱ በኩል በሰላም ያልፋል ብሎ አላመነም”።
በዚያ ተዋጋቸው
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሴዎንን ሲሆን ይህም ራሱንና ሰራዊቱን ይወክላል። ኢ.ት: “በዚያ ተዋጉ” ወይም “በዚያ ሰራዊቱ ተዋጋ”
Judges 11:21
ሴዎን
የዚህን ሰው ስም በመሳፍንት 11:19 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሴዎንና ሕዝቡን ሁሉ በእስራኤል እጅ ሰጠ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው በጦርነት የማሸነፍ ኃይልን ነው። ኢ.ት: “በሴዎንና በሕዝቡ ሁሉ ላይ ለእስራኤል ኃይልን ሰጠው”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አርኖን -- ያቦቅ
የእነዚህን ወንዞች ስም በመሳፍንት 11:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
Judges 11:23
አሁን መሬታቸውን የራስህ አድርገህ ትወስዳለህ?
ዮፍታሔ ምላሽ በማይፈልግ በዚህ ጥያቄ የአሞናውያንን ንጉሥ ይገስጸዋል። “የእነርሱ” የሚለው ቃል እስራኤልን ያመለክታል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “በመሆኑም፣ መሬታቸውን የራስህ አድርገህ መውሰድ አይኖርብህም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አምላክህ ካሞሽ የሚሰጥህን ምድር አትወስድም?
ዮፍታሔ ምላሽ በማይሻ ጥያቄ የአሞናውያንን ንጉሥ እየገሰጸው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “አምላክህ ካሞሽ የሚሰጥህን ምድር ብቻ መውሰድ ይኖርብሃል”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ውሰድ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙ አንድን ነገር በቁጥጥር ስር ማድረግ ማለት ነው። ኢ.ት: “በቁጥጥርህ ስር አድርግ” ወይም “የራስህ አድርግ”። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ካሞሽ
ይህ የሐሰተኛ አምላክ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
አሁን አንተ ከሞዓብ ንጉሥ ከሴፎር ልጅ ከባላቅ በእርግጥ ትበልጣለህ?
ዮፍታሔ ምላሽ በማይሻ ጥያቄ የአሞናውያንን ንጉሥ እየገሰጸው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “አንተ የሞዓብ ንጉሥ ከነበረው ከሴፎር ልጅ ከባላቅ አትሻልም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ባላቅ -- ሴፎር
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ከእስራኤል ጋር ለመከራከር ደፍሯል?
ዮፍታሔ ምላሽ በማይሻ ጥያቄ የአሞናውያንን ንጉሥ እየገሰጸው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ይሁን እንጂ ከእስራኤል ጋር ለመከራከር አልደፈረም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
በእነርሱስ ላይ ጦርነትን ዐውጇል?
ዮፍታሔ ምላሽ በማይሻ ጥያቄ የአሞናውያንን ንጉሥ እየገሰጸው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ከቶ በእነርሱ ላይ ጦርነትን አላወጀም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Judges 11:26
ሦስት መቶ ዓመት
“300 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሐሴቦን
በመሳፍንት 11:19 ላይ በተረጎምክበት መልኩ የዚህችን ከተማ ስም ተርጉም።
አሮዔር
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
አርኖን

በመሳፍንት 11:13 ላይ በተረጎምክበት መልኩ የዚህችን ከተማ ስም ተርጉም።
ታዲያ በዚያን ጊዜ ለምን አላስመለስካቸውም?
ዮፍታሔ ምላሽ በማይሻ ጥያቄ የአሞናውያንን ንጉሥ እየገሰጸው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “በዚያን ጊዜ ማስመለስ ነበረብህ” ወይም “ከአመታት በፊት ልታስመልሳቸው ይገባህ ነበር፤ አሁን ግን በጣም ዘግይተሃል” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
እኔ አልበደልኩህም፣ አንተ ግን እየወጋኸኝ በድለኸኛል
ዮፍታሔ የሚናገረው ሴዎንን ነው። እዚህ ጋ፣ ዮፍታሔ፣ ራሱን እንደ እስራኤላውያን፣ ንጉሣቸውን ሴዎንን እንደ አሞናውያን አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “እስራኤላውያን ሕዝብህን አልበደሉም፣ ይሁን እንጂ ሕዝብህ እየወጉን በድለውናል”።
አልበደልኩህም -- በድለኸኛል
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። አንድን ሰው መበደል ማለት እነርሱን መበደል ነው። ኢ.ት: “የማይገባውን አላደረግሁብህም … የማይገባውን አድርገህብኛል” ወይም “ኢፍትሐዊ አልሆንኩብህም … ኢፍትሐዊ ሆነህብኛል”። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 11:29
የእግዚአብሔር መንፈስ በዮፍታሔ ላይ መጣበት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም በዮፍታሔ ውሳኔዎች ላይ መንፈስ ቅዱስ ተጽዕኖ አሳድሯል ማለት ነው። ኢ.ት: “የእግዚአብሔር መንፈስ ዮፍታሔን ተቆጣጠረው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ከገለዓድ ምጽጳ -- በገለዓድና በምናሴ መሐል አለፈ
ዮፍታሔ በእነዚህ አካባቢዎች ከአሞን ሰዎች ጋር ለሚያደርገው ውጊያ ሰዎችን በሰራዊቱ ውስጥ ለማካተት እየመዘገባቸው አለፈ። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “ከምጽጳ ገለዓድ … ሰዎችን ወደ ሰራዊቱ እየሰበሰበ በገለዓድና ምናሴ መካከል አለፈ”።
እሠዋዋለሁ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙ አንድን ነገር መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ ማለት ነው። ኢ.ት: “እርሱን እሠዋልሃለሁ” ወይም “መሥዋዕት አድርጌ አቀርብልሃለሁ”። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 11:32
ስለዚህ ዮፍታሔ አለፈ -- ተዋጋ - እግዚአብሔር ድልን ሰጠው
ዮፍታሔ የሰራዊቱ መሪ በመሆኑ፣ እርሱና ሰራዊቱ በተደጋጋሚ ዮፍታሔን ራሱን ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት: “ስለዚህ ዮፍታሔና ሰራዊቱ አለፉ -- ተዋጉ -- እግዚአብሔር ድልን ሰጣቸው”
አሮኤር
የዚህችን ከተማ ስም በመሳፍንት 11:26 ላይ በተረጎምክበት መልኩ ተርጉም።
ሚኒት -- አቤል ክራሚም
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሃያ ከተሞች
“20 ከተሞችን ጨምሮ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 11:34
አታሞ
እንደ ከበሮ የሚመታበት አናት ያለው፣ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ድምፅ እንዲያሰማ በዙሪያው ቁርጥራጭ ብረቶች የሚደረጉለት የሙዚቃ መሣሪያ።
ልብሶቹን ቀደደ
ይህ ለቅሶን ወይም ታላቅ ሐዘንን የሚያሳይ ድርጊት ነው። ኢ.ት: “ልብሱን በሐዘን ቀደደ” (ምሳሌአዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)
በሐዘን ሰበርሽኝ -- ለህመም ዳረግሽኝ
ዮፍታሔ አንዱን አሳብ ሁለት ጊዜ መናገሩ እጅግ ስለ ማዘኑ አጽንዖት ለመስጠት ነው።
በሐዘን ሰበርሽኝ
እዚህ ጋ፣ ዮፍታሔ ጥልቅ ሐዘኑን እንደሚሰባብረው አንደ አንዳች ነገር ቆጥሮ ይናገራል። ኢ.ት: “ጥልቅ ሐዘን ላይ ጥለሽኛል” ወይም “በሐዘን እንድሞላ አደረግሽኝ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለህመም ዳረግሽኝ
እዚህ ጋ ዮፍታሔ የሚናገረው ጥልቅ ሐዘኑና ሥቃዩ እንደ ሕመም እንደሆነበት ነው። ኢ.ት: “አንቺ ሥቃይ እንደሚያመጣብኝ ዓይነት ሰው ሆነሻል” ወይም “ለጥልቅ ሐዘን ዳርገሽኛል”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቃሌን ማጠፍ አልችልም
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ቃልን ማጠፍ ማለት ልታደርገው ቃል የገባህበትን ጉዳይ መተው ነው። ኢ.ት: “ቃል የገባሁበትን ጉዳይ መፈጸም አለብኝ” ወይም “ቃሌን ለማጠፍ አልችልም”። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 11:36
ጠላቶችህን አሞናውያንን ተበቅሎልሃልና
ጠላቶቹን በማሸነፍ እግዚአብሔር ተበቅሎለታል። የዚህ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “በጠላቶችህ በአሞናውያን ላይ ተበቅሎልሃል”
ይህ ቃል ኪዳን ይጠበቅልኝ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ስለ እኔ ይህንን ቃል ኪዳን ጠብቅ” ወይም “እኔን በሚመለከት ይህንን ቃል ኪዳን ጠብቅ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ስለ ድንግልናዬ ላልቅስ
“ድንግል በመሆኔ ምክንያት ላልቅስ” ወይም “ከእንግዲህ ስለማላገባ ላልቅስ”
Judges 11:38
ገለዓዳዊው
ይህ አንድን ከገለዓድ የሆነን ሰው ያመለክታል። ይህንን በመሳፍንት 10:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

---

Chapter 12
Judges 12:1
ለኤፍሬም ሰዎች ጥሪ ደረሳቸው
እዚህ ጋ “ጥሪ” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “የኤፍሬም ሰዎች በአንድ ላይ ተጠሩ” ወይም “የኤፍሬም ሰዎች ወታደሮቻቸውን በአንድ ላይ ሰበሰቧቸው”። (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ጻፎን
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ተሻገሩ -- አለፉ
“መንገዳቸውን … አልፈው ሄዱ” ወይም “ጉዞአቸውን … አልፈው ተጓዙ”
ቤትህን በላይህ ላይ እናቃጥለዋለን
ይህ የአነጋገር ዘይቤ የሚያመለክተው ቤቱን በውስጡ ካሉት ሰዎች ጋር ስለ ማቃጠል ነው። ኢ.ት: “ቤትህን በውስጡ እንዳለህ እናቃጥለዋለን”። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እናንተን በጠራኋችሁ ጊዜ
እዚህ ጋ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው የኤፍሬምን ሰዎች ነው።
አላዳናችሁኝም
ዮፍታሔ “እኔ” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ራሱንና የገለዓድን ሰዎች በሙሉ ለማመልከት ነው። ኢ.ት: “አታድኑን”
Judges 12:3
እናንተ አላዳናችሁኝም
“እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን የኤፍሬምን ሰዎች ያመለክታል። ዮፍታሔ “እኔ” በሚልበት ጊዜ የሚያመለክተው ራሱን ጨምሮ የገለዓድን ሰዎች ነው። ኢ.ት: “አላዳናችሁንም”።
ሕይወቴን በእጄ ጥዬ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ በራስ ጉልበት በመደገፍ ራስን ለአደጋ መስጠት ማለት ነው። ዮፍታሔ የገለዓድን ሰዎች እንደ ራሱ አድርጎ ማመልከቱን ይቀጥላል። ኢ.ት: “በራሳችን በመተማመን ሕይወታችንን ለአደጋ ሰጥተናል”። (የአነጋገር ዘይቤ እና የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ድልን ሰጥቶኛል
በአሞናውያን ላይ እግዚአብሔር ለገለዓድ ሰዎች ድልን እንደ ሰጣቸው ዮፍታሔ ያመላክታል። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ መብራራት ይችላል። ኢ.ት: “በእነርሱ ላይ እግዚአብሔር ድልን ሰጥቶናል” ወይም “በጦርነት እንድናሸንፋቸው እግዚአብሔር ፈቅዶልናል”
ከኤፍሬም ጋር ተዋጋ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዮፍታሔንና የገለዓድን ተዋጊዎች ሁሉ ነው። ኢ.ት፡ “ከኤፍሬም ጋር ተዋጉ”

ለምን ልትወጉኝ መጣችሁ

“እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው የኤፍሬምን ሰዎች ነው። ዮፍታሔ “እኔ” በሚልበት ጊዜ የሚያመለክተው ራሱን ጨምሮ የገለዓድን ሰዎች ነው። ኢ.ት፡ “እኛን ልትወጉን ለምን መጣችሁ”

ገለዓዳውያን ኰብላዮች ናቸው

የዚህን ስድብ ትርጉም ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ይህ ቦታ ለእናንተ ለገለዓዳውያን አይገባችሁም። እናንተ በዚህ ለመኖር የመጣችሁ ሰዎች ብቻ ናችሁ”

በአሞን ሰዎች ላይ አልፈው ሄዱ

ይህ ማለት በአሞን በኩል ሲያልፉ ከአሞናውያን ጋር ተዋጉ። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “በግዛታቸው በኩል ስናልፍ ከአሞን ሰዎች ጋር ተዋጋን”

ገለዓዳውያን

የገለዓድ ሰዎች

በኤፍሬም -- በኤፍሬምና በምናሴ

“በኤፍሬምና በምናሴ አውራጃዎች” ወይም “በኤፍሬምና በምናሴ ምድር”። እዚህ ጋ “ኤፍሬም” እና “ምናሴ” የሚያመለክቱት አውራጃዎችን ሲሆን በዚያ በሚኖሩ ነገዶች ስም ተሰይመዋል።

Judges 12:5

ለኤፍሬም

“ለኤፍሬም ምድር”

ገለዓዳውያን ያዙት

“ገለዓዳውያን ተቆጣጠሩት” ወይም “ገለዓዳውያን ያዙት”

መልካ

እነዚህ ውሃው ጥልቀት የሌለው በመሆኑ በእግር ልታቋርጥ የምትችለው ወንዝ ያሉባቸው አካባቢዎች ናቸው።

ኤፍሬማዊ

ከኤፍሬም ነገድ የሆነ ሰው

ሺቦሌት -- ሲቦሌት

እነዚህ ቃላት ምንም ትርጉም የላቸውም። እነዚህን ቃላት ወደ ራስህ ቋንቋ ቅዳቸውና በቃላቱ መጀመሪያ ላይ “ሺ” እና “ሲ” የሚሉ ፊደላት ለየብቻ መተርጎማቸውን እርግጠኛ ሁን። (ቃላትን መቅዳት ወይም መዋስ የሚለውን ተመልከት)

ቃሉን መናገር

“የቃላቱን ድምፅ ማውጣት”

አርባ ሁለት ሺህ

“42,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

አርባ ሁለት ሺህ ኤፍሬማውያን ተገደሉ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አርባ ሁለት ሺህ ኤፍሬማውያንን ገደሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 12:7

ገለዓዳዊው ዮፍታሔ ሞተና ተቀበረ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ገለዓዳዊው ዮፍታሔ ሞተና ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 12:8

የቤተ ልሔሙ ኢብጻን

ይህ ከቤተ ልሔም የሆነ የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ ሠላሳ ሴቶች ልጆቹን ዳረ

እዚህ ጋ “ዳረ” የሚለው ቃል የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ልጆቹ እንዲያገቡ ፈቅዷል ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ሠላሳ ሴቶች ልጆች ነበሩትና እያንዳንዳቸው እንዲያገቡ ቅድመ ዝግጅት አደረገላቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ለወንዶች ልጆቹም ከውጭ ከሌሎች ሰዎች ሠላሳ ሴቶች ልጆችን አመጣላቸው

“ከውጭ አመጣላቸው” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ትርጉሙ ከሌላ ጎሳ የሆኑት ሴቶች ከወንዶች ልጆቹ ጋር ተጋቡ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ከራሱ ጎሳ ውጭ ካሉ ሰዎች ሠላሳ ሴቶች ልጆች የእርሱን ወንዶች ልጆች እንዲያገቡ አደረገ”። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 12:10

በቤተ ልሔም ተቀበረ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በቤተ ልሔም ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ኤሎን

ይህ የሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዛብሎናዊ

ከዛብሎን ነገድ የሆነ አንድ ሰው

ኢያሎን

የዚህን ቦታ ስም በመሳፍንት 1፡35 ላይ እንደተረጎምከው ተርጉመው።

በኢያሎን ተቀበረ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በኢያሎን ቀበሩት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Judges 12:13

አብዶን --ሂሌል

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ጲርዓቶናዊው -- ጲርዓቶን

ጲርዓቶን የቦታ ስም ሲሆን ከዚያ አካባቢ የሆነ ሰው ደግሞ ጲርዓቶናዊ ይባላል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

በሰባ አህዮች የሚቀመጡ

እነዚህ ሰዎች የሚቀመጡባቸውን ሰባ አህዮች የራሳቸው ማድረግ ችለዋል። እዚህ ጋ “መቀመጥ” የሚለው ቃል “የራስ ማድረግ” ከሚለው ይልቅ ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት፡ “ሰባ አህዮች ነበሯቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አርባ ወንዶች ልጆች -- ሠላሳ የልጅ ልጆች -- ሰባ አህዮች

“40 ወንዶች ልጆች -- 30 የልጅ ልጆች -- 70 አህዮች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 13

Judges 13:1

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን

የእግዚአብሔር ፊት የእርሱን ፍርድ ወይም ምዘና ይወክላል። ይህንን በመሳፍንት 2፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ የሆነውን” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ነው ያለውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በፍልስጥኤማውያን እጅ ሰጣቸው

እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው በጦርነት ድል ማድረጊያ ኃይልን ነው። ኢ.ት፡ “ፍልስጥኤማውያን እንዲያሸንፏቸው ፈቀደ” ወይም “በፍልስጥኤማውያን እንዲጨቆኑ ፈቀደ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አርባ ዓመት

“40 ዓመት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

ጾርዓ

ይህ በእስራኤል የነበረ ከተማ ስም ነው። እርሱ በዳን ድንበር አቅራቢያ በይሁዳ አውራጃ ነበር። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ዳናውያን

የዳን ነገድ ሰዎች

ማኑሄ

ይህ የሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 13:3

ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ

ይህ የሕፃን ልጅን መወለድ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ወንድ ልጅ መውለድ” ወይም “ወንድ ሕፃን ልጅ ይኖርሻል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ንጹሕ ያልሆነ ምንም ነገር

እግዚአብሔር መበላት የለበትም ያለው ነገር በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳይደለ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነሆ

“አስተውይ” ወይም “አድምጪ”

በራሱ ላይ ምላጭ አያርፍበትም

እዚህ ጋ “ራስ” የሚያመለክተው ጸጉሩን ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ኢ.ት፡ “ማንም ጸጉሩን እንዳይቆርጠው”(አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ምላጭ
ጸጉርን ከቆዳ አጠገብ አድርሶ ለመቁረጥ የሚያገለግል ስል ቢላዋ ነው
ለእግዚአብሔር ናዝራዊ
ይህ ማለት እንደ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ኢ.ት፡ “ለእግዚአብሔር የተሰጠ ናዝራዊ” ወይም “እንደ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተሰጠ”
ከማህፀን
እዚህ ጋ “ማህፀን” የሚያመለክተው ሕፃን ከመወለዱ በፊት ያለውን ጊዜ ነው፡፡ ኢ.ት፡ “ከመወለዱ በፊት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከፍልስጥኤማውያን እጅ
እዚህ ጋ “እጅ” መቆጣጠር ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ከፍልስጥኤማውያን ቁጥጥር” ወይም “በፍልስጥኤማውያን ቁጥጥር ስር ከመሆን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 13:6
አንድ የእግዚአብሔር ሰው
ይህ ማለት ሰውየው የተላከው በእግዚአብሔር ነው። ይህ ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር የላከው አንድ ሰው”
መልኩ በጣም የሚያስፈራ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነበር
እዚህ ጋ “በጣም የሚያስፈራ” ማለት “አስደንጋጭ” ማለት ነው። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔርን መልአክ ይመስል ስለ ነበረ በጣም ፈርቼ ነበር”
እነሆ
“አስተውል” ወይም “አድምጥ”
ወንድ ልጅ ትወልዳለች
ይህ የሕፃን ልጅ መወለድን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ወንድ ልጅ ትወልዳለች” ወይም “ወንድ ሕፃን ልጅ ይኖራታል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የትኛውንም በሕጉ ንጹህ ያልተባለውን ምግብ
እግዚአብሔር መበላት የለበትም ያለው ነገር በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳይደለ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለእግዚአብሔር ናዝራዊ
ይህ ማለት እንደ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል። ይህንን በመሳፍንት 3፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ለእግዚአብሔር የተሰጠ ናዝራዊ” ወይም “እንደ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተሰጠ”
በማህፀንሽ ከተፀነሰበት እስከሚሞትበት ጊዜ ደረስ
ይህ አጽንዖት የሚሰጠው በሕይወት ዘመኑ ሁሉ መሆን እንዳለበት ነው። ኢ.ት፡ “ሕይወቱን ሙሉ”
Judges 13:8
ማኑሄ
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 13፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ወደ ሴቲቱ መጣ
ግልጽ ያልሆኑትን የዳራውን ቃላት ግልጽ ልታደርጋቸው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ወደ ማኑሄ ሚስት መጣ”
Judges 13:10
እነሆ
“ስማ” ወይም “የምነግርህን ልብ በል”
ሰውየው
ይህ በመሳፍንት 13፡3 የእግዚአብሔርን መልአክ ያመለክታል። ይህ ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔር ሰው”
Judges 13:12
ቃሎችህ
“የተናገርከው ቃል”
የትኛውንም ከወይን የሚገኘውን
እዚህ ጋ መልአኩ ከወይን “የሚወጣ” ሲል የትኛውንም ከወይን የሚገኘውን ምግብ እንደሆነ ያመላክታል። ኢ.ት፡ “በወይን ላይ የሚበቅል ማንኛውም ነገር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ንጹሕ ያልሆነ
እግዚአብሔር መበላት የለበትም ያለው ነገር በአካላዊነቱም ንጹሕ እንዳይደለ ተነግሯል። ይህንን ሐረግ በመሳፍንት 13፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 13:15
የፍየል ጠቦት ይዘጋጅልህ
ግልጽ ያልሆነውን የማኑሄን መግለጫ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ኢ.ት፡ “እንድትበላው የፍየል ጠቦት እናብስልልህ”
Judges 13:17
ቃሎችህ ሲፈጸሙ
“የተናገርከው ሲፈጸም”
ስሜን ለምን ትጠይቃለህ?
መልአኩ በተግሳጽ መልክ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ስሜ ማን መሆኑን መጠየቅ የለብህም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ድንቅ ነው
ስሙን ለምን መጠየቅ እንደማይኖርባቸው በይበልጥ ግልጽ ማድረጉ ይጠቅም ይሆናል። ኢ.ት፡ “ለመረዳት እጅግ ያስቸግራችሁ ይሆናል”
Judges 13:19
ከእህል ቁርባኑ ጋር
ይህ ሕግ የሚቃጠል መሥዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ የእህል ቁርባን እንዲቀርብ ያዛል። ኢ.ት፡ “ከእርሱም ጋር የታዘዘውን የእህል ቁርባን” ወይም “አብሮት እንዲሆን የእህል ቁርባን”
በዐለቱ ላይ
“በመሠዊያው ላይ”። ማኑሄ መሥዋዕቱን ያቀረበበት መሠዊያ ዐለት ነበር።
አንድ ነገር አደረገ
“መልአኩ አንድ ነገር አደረገ”
የእግዚአብሔር መልአክ በመሠዊያው ነበልባል ውስጥ ወደ ላይ ወጣ
“የእግዚአብሔር መልአክ በመሠዊያው ነበልባል ውስጥ ተመልሶ ወደ ሰማይ ሄደ”
በፊታቸው በመሬት ላይ ተደፉ
“በግምባራቸው ተደፉ” ይህ የአድናቆትና የአክብሮት ምልክት ነው፣ ሆኖም እግዚአብሔርን መፍራታቸውንም ያሳያል። (ምሳሌአዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)
Judges 13:21
የእግዚአብሔር መልአክ እንደ ነበረ
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማኑሄና ሚስቱ ያዩትን ሰው ነው።
እግዚአብሔርን ስላየነው በእርግጥ መሞታችን ነው
እግዚአብሔር እንደሚገድላቸው ማሰባቸውን ያሳያል። ይህ ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ስላየነው ይገድለናል”
Judges 13:23
እነዚህን ነገሮች ሁሉ አያሳየንም ወይም በዚህ ጊዜ እንዲህ ያሉትን ነገሮች እንድንሰማ አያደርገንም ነበር
የማኑሄ ሚስት ስለ አንዱ ነገር ሁለት ጊዜ የምትናገረው አጽንዖት ለመስጠት ነው። እነዚህ ሁለት መግለጫዎች መጣመር ይችላሉ። ኢ.ት፡ “እንድናደርግ የፈለገውን አይነግረንም ነበር”
Judges 13:24
ሴቲቱ
“የማኑሄ ሚስት”
ወንድ ልጅ ወለደች
ይህ የልጅ መወለድን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ወንድ ልጅ ወለደች” ወይም “ወንድ ልጅ አገኘች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
አደገ
“ዐዋቂ ሆነ” ወይም “ጎለመሰ”
የእግዚአብሔር መንፈስ ሊያነቃቃው ጀመረ
እዚህ ጋ የእግዚአብሔር መንፈስ ሳምሶንን ማነቃቃቱ በማሰሮ ውስጥ ያለ ምግብ ከሚማሰልበት መንገድ ጋር ተነጻጽሯል። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔር መንፈስ በሳምሶን ላይ ተጽዕኖ ማድረግ ጀመረ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ማህነህ ዳን -- ኤሽታኦል
ማህነህ ዳን ለዘለቄታቸው የሚኖሩበትን በሚፈልጉበት ወቅት የዳን ነገድ በጊዜያዊነት የሰፈሩበት ቦታ ስም ነው። ኤሽታኦል የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ጾርዓ
የዚህን ከተማ ስም በመሳፍንት 13፡2 በተረጎምክበት መልኩ ተርጉመው

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 14
Judges 14:1
ሳምሶን ወደ ተምና ወረደ
“ወረደ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የአባቱ ቤት ካለበት ተምና ዝቅ ባለ ስፍራ ስለሚገኝ ነው። ተምና በሶሬቅ ሸለቆ የሚገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ከፍልስጥኤማውያን ሴቶች ልጆች አንዷ
“ሴት ልጅ” የሚለው ቃል ያላገባችን ወጣት ሴት የሚያመለክት የትህትና አገላለጽ ነው። ኢ.ት: “በፍልስጥኤም ሰዎች መካከል አንዲት ያላገባች ሴት” ወይም “ፍልስጥኤማዊት ልጃገረድ”
አሁን ሚስት እንድትሆነኝ አምጡልኝ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ሳምሶን ወላጆቹ የፍስጥኤማዊቷ ሴት ወላጆችን ለጋብቻ እንዲጠይቁለት ግድ እያላቸው ነው። ኢ.ት: “ሚስት እንድትሆነኝ አሁን አጋቡኝ” ወይም “እርሷን እንዳገባት ቅድመ ዝግጅት አድርጉልኝ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 14:3
በዘመዶችህ መካከል ወይም በሕዝባችን ሁሉ ሴት ልጆች መካከል ሴት ስለጠፋች ነው?
ይህንን ጥያቄ ሳምሶንን የሚጠይቁት ከገዛ ሕዝባቸው መካከል ሚስት ሊያገኙለት እንደሚችሉ አሳብ ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በመግለጫነት ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት: “በርግጥ ማግባት እንድትችል በሕዝብህ መካከል ሴቶች አሉ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የዘመዶችህ ሴቶች ልጆች
“ሴት ልጅ” የሚለው ቃል ያላገባችን ወጣት ሴት የሚያመለክት የትህትና አገላለጽ ነው። ኢ.ት: “በዘመዶችህ መካከል ካላገቡት ሴቶች አንዷን”
ካልተገረዙት ከፍልስጥኤማውያን ሚስት ልታገባ ነው?
ይህ ጥያቄ የተጠየቀው ሳምሶንን ለመገሰጽ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። ወላጆቹ ፍልስጥኤማዊት እንዲያገባ ያልፈለጉበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ኢ.ት: “የፍልስጥኤም ሰዎች እግዚአብሔርን ስለማያመልኩ በእርግጠኝነት ፍልስጥኤማዊት ማግባት አይኖርብህም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና የሚለውን ተመልከት)
እርሷን አምጡልኝ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ሳምሶን ስለ ጋብቻው የፍልስጥኤማዊቷን ሴት ወላጆች እንዲያነጋግሩለት ወላጆቹን ግድ እያላቸው ነበር። ኢ.ት: “አሁን ሚስት እንድትሆነኝ አዘጋጁልኝ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ታስደስተኛለች
ይህ ማለት ሴቲቱ ቆንጆ እንደ ሆነች ሳምሶን ያስባል። “ቆንጆ በመሆኗ ደስ ብሎኛል” ወይም “እርሷ ቆንጆ ናት”
ይህ ጉዳይ
ይህ የሚያመለክተው ፍልስጥኤማዊቱን ሴት ለማግባት ሳምሶን ያቀረበውን ጥያቄ ነው።
ግጭት ለመፍጠር ፈልጓልና
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።
Judges 14:5
ሳምሶን ወደ ተምና ወረደ
“ወረደ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የአባቱ ቤት ካለበት ተምና ዝቅ ባለ ስፍራ ስለሚገኝ ነው። ተምና በሶሬቅ ሸለቆ የሚገኝ ከተማ ነበር። የዚህን ከተማ ስም በመሳፍንት 14:1 እንዳደረግኸው በተመሳሳይ መንገድ ተርጉመው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
እነሆ፣ አንድ የአንበሳ ደቦል መጣበት
እዚህ ጋ “እነሆ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የአንባቢዎችን ትኩረት በታሪኩ ውስጥ ወደሚመጣው አስደናቂ ሁነት ለመሳብ ነው። “መጣበት” የሚለው ቃል ትርጉሙ አንበሳው ወደ እርሱ ቀርቧል ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እያገሳበት ነበር
“አስፈራራው”። ይህ አንበሳ አንድን እንስሳ ለማጥቃት በሚያስፈራራበት ጊዜ የሚያሰማው ዓይነት ድምፅ ነው።
የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በድንገት መጣበት
“መጣበት” የሚለው ቃል ትርጉሙ የእግዚአብሔር መንፈስ ሳምሶን ላይ ተጽዕኖ አሳደረበት ማለት ነው። በዚህ ጉዳይ፣ በኃይል አበረታው። ኢ.ት: “የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል አበረታው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ቆራረጠው
ለሁለት ቆራረጠው
በእጁ ምንም ነገር ሳይኖር
እዚህ ጋ፣ በእጁ ምንም ነገር ሳይኖር የሚለው መግለጫ የጦር መሣሪያ አልያዘም ነበር ለሚለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ኢ.ት: “የጦር መሣሪያ አልነበረውም”
Judges 14:7
ሳምሶንን አስደሰተችው
ይህ ማለት በጣም ቆንጆ እንደሆነች አሰቧል። ኢ.ት: “በቁንጅናዋ ተደስቷል” ወይም “በጣም ቆንጆ እንደ ነበረች አሰቧል”
ፈቀቅ አለ
ይህ ማለት፣ አንድ ነገር ለማድረግ መንገዱን ትቶ ወጣ አለ። ኢ.ት: “መንገዱን ትቶ ወጣ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ሬሳ
የሞተ አካል
እነሆ፣ ንቦች ወረዉት ነበር
እዚህ ጋ “እነሆ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የአንባቢዎችን ትኩረት በታሪኩ ውስጥ ወደሚመጣው አስደናቂ ሁነት ለመሳብ ነው። ኢ.ት: “ንቦች ወረዉት አገኘው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
መውረር
እጅግ የበዙ ነፍሳት
አፍሶ
“ሰብስቦ”
Judges 14:10
የሳምሶን አባት ሴቲቱ ወደነበረችበት ወረደ
“ወረደ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የሳምሶን አባት ከሚኖርበት ተምና ዝቅ ባለ ስፍራ የሚገኝ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ኢ.ት: “የሳምሶን አባት ሴቲቱ ወደምትኖርበት ሄደ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የወጣቶቹ ልማድ
ይህ የጋብቻ ልማድ እንደ ነበረ መግለጹ ጠቃሚ ይሆን ይሆናል። ኢ.ት: “የሚያገቡ ወጣቶች ልማድ”
ሠላሳ ጓደኞቻቸው
“30 ጓደኞቻቸው” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 14:12
ዕንቆቅልሽ
ተጫዋቾቹ ለአስቸጋሪው ጥያቄ መልስ ማግኘት የሚኖርባቸው ውድድር
መፍታት የሚችል
ይህ ማለት የዕንቆቅልሹን ትርጉም መንገር የሚችል ማለት ነው። ኢ.ት: “ትርጉሙን መንገር የሚችል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ሠላሳ የላይነን ቀሚስና ሠላሳ ሙሉ ልብስ
“30 የላይነን ቀሚሶችንና 30 ሙሉ ልብስ” (ቁጥሮችን ተመልከት)
ልትነግሩኝ ካልቻላችሁ ግን
እዚህ ጋ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው በግብዣው ላይ የነበሩትን እንግዶች ነው።
ላይነን
የልብስ ዓይነት
Judges 14:14
ከበላተኛው ውስጥ የሚበላ ነገር
“ከበላተኛው ውስጥ የሚበላ ነገር ተገኘ” ወይም “አንድ የሚበላ ነገር ከአንድ ከሚበላ ነገር ውስጥ ወጣ”
በላተኛው
“በላተኛው” የሚለው ስም ወደ ግሣዊ ሐረግ መነገር ይችላል። ኢ.ት: “የሚባላው ነገር”
ከብርቱው ውስጥ የሚጣፍጥ ነገር
“ከብርቱው ውስጥ የሚጣፍጥ ነገር ወጣ” ወይም “ብርቱ ከሆነው ነገር ውስጥ ጣፋጭ የሆነ ነገር ወጣ”
ብርቱው
ይህ የሚያመለክተው ብርቱ የሆነን ነገር ነው። ኢ.ት: “ብርቱው ነገር”

እንግዶቹ
“በግብዣው ላይ የነበሩት ሰዎች”
መልሱን ማግኘት አልቻሉም
እዚህ ጋ፣ የዕንቆቅልሹን መልስ መንገር እንደ አንዳች የተደበቀና እንግዶቹ ፈልገው ሊያገኙት እንደሚያስፈልጋቸው ነገር ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “መልሱን መንገር አልቻሉም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 14:15
አራተኛው ቀን
“ቀን 4”
ማታለል
እነርሱ ሊያደርጉት የማይፈልጉትን ነገር እንዲያደርግ አንድን ሰው ማሳሳት ወይም ማሞኘት
የአባትሽን ቤት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ትክክለኛውን ቤት ያመለክታል። ኢ.ት፡ “አባትሽና ቤተሰቡ የሚኖሩበትን ቤት” ወይም 2) “ቤት” የሚያመለክተው በውስጡ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። ኢ.ት፡ “ቤተሰብሽ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እናቃጥለዋለን
“እናቃጥለዋለን” የሚለው ቃል ትርጉም አንድን ነገር ሙሉ በሙሉ ማቃጠል ማለት ነው። አንድ ሰው “ከተቃጠለ” ያ ሰው ተቃጥሎ ሞቷል ማለት ነው።
የጋበዛችሁን ልታደኸዩን ነው?
ክፉ ስለማድረጓ ለመክሰስ ይህንን ይጠይቋታል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት፡ “እዚህ የጠራሽን ድኻ ልታደርጊን ነው!”
ድኻ ልታደርጊን
ዕንቆቅልሹን ካልፈቱና አዲስ ልብሶች ከገዙለት ድኻ ይሆናሉ። ኢ.ት፡ “አዲስ ልብሶች እንድንገዛለት በማስገደድ ድኻ ልታደርጊን ነው”
Judges 14:16
ፈጽሞ ጠልተኸኛል! አትወደኝም
የሳምሶን ሚስት አጽንዖት ለመስጠት ያህል ሁለት ጊዜ የምትናገረው በመሠረቱ አንድ ነው። ኢ.ት፡ “በእውነት ፈጽሞ አትወደኝም”
ዕንቆቅልሽ
ተጫዋቾቹ ለአስቸጋሪው ጥያቄ መልስ ማግኘት የሚኖርባቸው ውድድር
ወዲህ ተመልከቱ
ይህ ጥቅም ላይ የዋለው የአንድን ሰው ትኩረት ለማግኘት ነው። እዚህ ጋ “ተመልከቱ” ማለት “አድምጡ” ማለት ነው። ኢ.ት፡ “አድምጡኝ” ወይም “የምናገረውን ልብ በሉ”
ለአባቴ ወይም ለእናቴ ካልነገርኳቸው ላንቺ መንገር አለብኝ?
መልሱን እንዲነግራት ግድ ስላለችው ሳምሶን እየገሰጻት ነበር። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሆኖ ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት፡ “ለአባቴ ወይም ለእናቴ እንኳን አልነገርኳቸውም፤ አልነግርሽም” ወይም “ከአንቺ ይልቅ ቅርቤ ለሆኑት ለወላጆቼ እንኳን አልነገርኳቸውምና እንድነግርሽ ግድ ልትዪኝ አይገባም”
ግብዣቸው በሚቆይባቸው በሰባቱ ቀናት
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) “በግብዣቸው በሰባቱ ቀናት” ወይም 2) “ከሰባቱ የግብዣቸው ቀናት በቀሩት”
ሰባተኛው ቀን
“ቀን 7”
በጣም ነዘነዘችው
እዚህ ጋ “ነዘነዘችው” የሚለው ቃል ትርጉም “ግድ አለችው” የሚል ይሆናል። ኢ.ት፡ “እንዲነግራት መጨቅጨቋን ቀጠለች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 14:18
የከተማዪቱ ሰዎች
ይህ የሚያመለክተው የሳምሶን ሚስት ዘመዶችን ነው። ይህ በግልጽ መነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ወጣቶቹ” ወይም “ዘመዶቿ”
ሰባተኛው ቀን
“ቀን 7”
ከማር ይልቅ የሚጣፍጥ ምንድነው? ከአንበሳስ ይልቅ የሚበረታ ምንድነው?
ይህ የዕንቆቅልሹ መልስ ነው። በጥያቄ ፈንታ እንደ መግለጫ ሆኖ መጻፍ ይኖርበት ይሆናል። አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ መረጃ በማከል ይህ ከዕንቆቅልሹ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። ኢ.ት፡ “ማር ጣፋጭ ነው፣ አንበሳም ብርቱ ነው” ወይም “ማር ጣፋጭ ነው፣ እርሱም ከአንበሳ ውስጥ ወጣ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና የሚለውን ተመልከት)
በጥጃዬ ባታርሱ ኖሮ
ሳምሶን መልሱን ለማግኘት ሚስቱን መጠቀማቸውን አንድ ሰው የራሱን እርሻ ለማረስ የሌላውን ሰው ጥጃ ከመጠቀሙ ጋር ያነጻጽራል። ኢ.ት፡ “በሚስቴ ባትጠቀሙ ኖሮ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ማረስ
ማረስ ማለት ዐፈሩን ለዘር ለማዘጋጀት እንስሳን በመጠቀም ስለታማውን ብረት ዐፈር ውስጥ አስገብቶ መሳብ ነው።
Judges 14:19
በሳምሶን ላይ በኃይል መጣበት
“መጣበት” የሚለው ቃል ትርጉሙ የእግዚአብሔር መንፈስ ሳምሶን ላይ ተጽዕኖ አሳደረበት ማለት ነው። በዚህ ጉዳይ፣ በኃይል አበረታው። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል አበረታው” ወይም “ሳምሶንን በጣም ኃይለኛ አደረገው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ከሰዎቻቸው ሠላሳውን ገደለ
“ከሰዎቻቸው 30 ገደለ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ከሰዎቻቸው
በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች”
ብዝበዛ
አብዛኛውን ጊዜ ከውጊያ ወይም ከጦርነት በኋላ በኃይል የሚወሰዱ ነገሮች
ልብሶቻቸውን
እነዚህ ከአስቀሎና የወሰዳቸው ብዝበዛዎቹ ነበሩ። ኢ.ት፡ “የወሰዳቸውን ሙሉ ልብሶች”
በቁጣ ነዶ
“በጣም ተናዶ”
ወደ አባቱ ቤት ወጣ
እዚህ ጋ የአባቱ ቤት ከሚገኝበት አካባቢ ሳምሶን የነበረበት ተምና የመሬት አቀማመጡ ዝቅ ያለ ስለነበረ “ወጣ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ውሏል።
የሳምሶን ሚስት ለቅርብ ጓደኛው ተሰጠች
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የሚስቱ አባት እርሷን ለቅርብ ጓደኛው ሰጣት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የቅርብ ጓደኛ
“ከሌላው የቀረበ ጓደኛ”

Chapter 15
Judges 15:1
ራሱን ጠየቀ
ይህ ማሰብን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “በራሱ አሰበ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ወደ ሚስቴ ክፍል እሄዳለሁ
ሳምሶን ከሚስቱ ጋር ለመተኛት አስቦ ነበር። ይህ በግልፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አብረን እንድንተኛ ወደ ሚስቴ ክፍል እሄዳለሁ”
እንዲገባ አልፈቀደለትም
ሳምሶን ለራሱ ከተናገረው ውስጥ “የእርሷ ክፍል” የሚለውን ሐረግ መረዳት ይቻላል። ይህ እዚህ ጋር መደገም ይችላል። ኢ.ት፡ “ወደ ክፍሏ እንዲገባ አልፈቀደለትም”
ስለዚህ ለጓደኛህ ሰጠኋት
ይህ ማለት ሚስት እንድትሆነው ለጓደኛው ሰጣት ማለት ነው። ይህ በግልፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከእርሱ ጋር እንድትጋባ ለጓደኛህ ሰጠኋት”
አይደለችምን?
ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው ሳምሶን ከእርሱ ጋር ሊስማማ እንደሚገባ ለማመልከት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት፡ “እንደምትስማማ ተስፋ አደርጋለው”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
በምትኳ ውሰዳት
ሳምሶን እንደ ሚስቱ እንዲወስዳት አስተያየት እየሰጠ ነው። ይህ በግልፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በእርሷ ምትክ ሚስት እንድትሆንህ ውሰዳት”
Judges 15:3


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ፍልስጥኤማውያንን በምጎዳቸው ጊዜ ንጹሕ እሆናለሁ
ሳምሶን፣ ፍልስጤማውያን ስለበደሉት ቢያጠቃቸው ንጹሕ እንደሚሆን ያስባል። ይህ በግልፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "ስለበደሉኝ ፍልስጤማውያንን ብጎዳቸው ንጹሕ እሆናለሁ"
ሦስት መቶ ቀበሮዎች
"300 ቀበርዎች"
ቀበሮዎች
ቀበሮዎች እንደ ውሻ ያሉ ረጃጅም ጭራ ያላቸው፣ በጎጆ የሚኖሩ ወፎችንና ሌሎች ትናንሽ እንስሶችን የሚመገቡ እንስሶች ናቸው።
እያንዳንዱ ጥንድ
ጥንድ ማለት የትኛውም ነገር ሁለት ሆኖ ሲገኝ ነው፤ እንደ ሁለት ቀበርዎች ወይም ሁለት ጭራዎች።
ጭራ ከጭራ ጋር
"በጭራዎቻቸው"
ችቦዎች
ችቦ በአንደኛው ጫፉ ተቀጣጣይ ነገር የተደረገበት የእንጨት ጭራሮ ነው፤ ችቦ በአብዛኛው ሊሎች ነገሮችን ለመለኮስ ወይም ብርሃን እንዲሰጥ የሚያዝ ነው።
Judges 15:5
የቆመ እህል
በእርሻ ውስጥ ገና በአገዳው ላይ እያደገ ያለ እህል
የተከመረ እህል
ከታጨደ በኋላ ተሰብስበው የተከመሩ የእህል ነዶዎች
ተክሎች
የፍራፍሬ ዛፎች የሚበቅሉበት ቦታ ነው።
የተምናዊው አማች
የአንድ ሰው የሴት ልጁ ባል ለሰውየው "አማች" ነው።
ተምናዊው
ይህ ከተምናህ የሆነ ሰው ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የሳምሶንን ሚስት ወስዶ ለጓደኛው ሰጠው
የሳምሶን ሚስት አባት እርሷን የሳምሶን ጓደኛ እንዲያገባት ሰጠው። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "የሳምሶንን ሚስት ወስዶ የሳምሶንን ጓደኛ እንድታገባው ፈቀደላት"
ፈፅመው አቃጠሏቸው
"ፈፅመው አቃጠሏቸው" የሚለው ሐረግ አንድን ነገር ጨርሶ ማቃጠል ማለት ነው። አንድ ሰው "ፈፅሞ ተቃጠለ" ማለት ያ ሰው ተቃጥሎ ሞተ ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 15:7
እነርሱን አላቸው
"ፍልስጤማውያኑን አላቸው"
እናንተ ይህንን ካደረጋችሁ
"ይህንን ስላደረጋችሁ"
ሽንጥና ታፋቸውን ቆራረጣቸው
እዚህ ጋ "ሽንጥና ታፋ" ሙሉ ሰውነትን ያመለክታል። ይህ ሳምሶን ፍልስጥኤማውያንን እንዴት እንደገደላቸው የሚያሳይ ጉልህ ገለጻ ነው። ኢ.ት: "ሰውነታቸውን ቆራረጠው"።
ወደ ታች ወረደ
እዚህ ጋ "ወደታች ወረደ" የሚለው ሐረግ ከከፍታ መውረዱን ማመልከቱ ላይሆን ይችላል፤ እንዲያውም አንድ ሰው ወደ ሌላ ቦታ መጓዙን መግለጫ መንገድ ነው። ኢ.ት: "ሄደ" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ዋሻ
በኮረብታ ወይም ተራራ ውስጥ ያለ ክፍት ቦታ
ገደል
ከፍ ያለ ዐለታማ ኮረብታ ወይም የተራራ ጎን
ኢታም
ይህ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ያለ የዐለታማ ኮረብታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 15:9
በይሁዳ - ፍልስጥኤማውያኑ ወደ ላይ ወጡ ...
እዚህ ጋ "ወደ ላይ ወጡ" የሚለው ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው ፍልስጥኤማውያኑ እነርሱ ይጓዙበት ከነበሩበት ቦታ በከፍታ ወደሚበልጠው ይሁዳ ስለመጡ ነው።
ለጦርነት ተዘጋጅተው
"ራሳቸውን ለጦርነት አዘጋጅተው"
ሌሒ
ይህ በይሁዳ ያለ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
እርሱ እንዳደረገብን ልናደርግበት ነው
ፍልስጥኤማውያኑ ሳምሶን ብዙዎቹን ፍልስጥኤማውያን እንደገደለ እንዴት እንደሚገሉት እያነጻጸሩ ነው። ኢ.ት: "ብዙ ሰዎቻችንን እንደገደለ ግደሉት"
Judges 15:11
የይሁዳ ሶስት ሺህ ወንዶች
"3000 የይሁዳ ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
በኢታም ገደል ያለ ዋሻ
ይህንን ሐረግ በመሳፍንት 15፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ፍልስጥኤማውያን በእኛ ላይ ገዢዎች እንደሆኑ አታውቅም? በእኛ ላይ ያደረከው ይህ ምንድን ነው?
የይሁዳ ሰዎች እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቁት ሳምሶንን ለመገሰጽ ነው። እነዚህ ጥያቄዎች እንደ መግለጫ ሊጻፉ ይችሉ ይሆናል። ኢ.ት: "ፍልስጤማውያን በኛ ላይ ገዢዎች እንደሆኑ ታውቃለህ ነገር ግን አንተ የምታደርገው እንዳልሆኑ ያህል ነው። ያደረከው ነገር ከባድ ጉዳት አምጥቶብናል።" (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አደረጉብኝ፥ ስለዚህ እኔም አደረግሁባቸው
ሳምሶን ሚስቱን እንዴት እንደገደሉበትና እርሱ በበቀል እንዴት እንደገደላቸው እያመለከተ ነው። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "ሚስቴን ገድለዋታል፤ ስለዚህ እኔም ገደልኳቸው።"
Judges 15:12
የፍልስጥኤማውያን እጅ
እዚህ ጋ "እጅ" የሚያመለክተው ኃይልን ነው። ኢ.ት: "የፍልስጥኤማውያኑ መቆጣጠር" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእጃቸው አሳልፈን ልንሰጥህ
ይህ ማለት አንድን ሰው በሌላ ሰው ቁጥጥር ስር እንዲሆን ማድረግ ማለት ነው። ኢ.ት: "ለፍልስጥኤማውያኑ ልንሰጥህ" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ከዐለቱ ወደላይ
ይህ ሳምሶን በመሳፍንት 15፡8 ላይ ሄዶበት የነበረውን በኢታም ገደል የሚገኘውን ዋሻ ያመለክታል። እዚህ ጋ "ወደ ላይ" የሚለው ቃል ከዋሻው አውጥተው አምጥተውታል ማለት ነው። ኢ.ት: "በትልቁ ዐለት ውስጥ ካለው ዋሻ አውጥተው"።
Judges 15:14
በመጣ ጊዜ
ሳምሶን ብቻውን አልተጓዘም፤ በገመድ ባሰሩት ሰዎች እየተመራ ነበር። ኢ.ት: "በመጡ ጊዜ"
ሌሒ
ይህ በይሁዳ የሚገኝ ከተማ ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 15፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በእርሱ ላይ በኃይል መጣበት
"በላዩ ላይ መጣበት" የሚለው ሐረግ የእግዚአብሔር መንፈስ ሳምሶን ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል ማለት ነው። በዚህ ቦታ፤ በጣም ብርቱ አድርጎታል። ኢ.ት: "ሳምሶንን በጣም ብርቱ አደረገው" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በክንዱ ላይ የነበሩት ገመዶች እንደ ተቃጠለ ፈትል ሆኑ
ሳምሶን እጁ የታሰረበትን ገመድ በቀላሉ በጣጥሶታል። ደራሲው ገመዱን እንዴት በቀላሉ እንደበጣጠሰው ለመግለጽ እንደተቃጠለ ፈትል ይለዋል። ኢ.ት: "በክንዱ ላይ ያሉትን ገመዶች ፈትል በቀላሉ እንደሚቃጠል በጣጠሳቸው"
የተልባ ፈትል
ከተልባ ተክል የሚገኝ ቃጫና ክር ጨርቅ ለመስራት ይጠቅማል።
Judges 15:15
አዲስ መንጋጋ
ይህ ማለት አህያው በቅርብ የሞተና አጥንቶቹም ገና መበስበስ ያልጀመሩ ናቸው ማለት ነው። መንጋጋ የታችኛዎቹን ጥርሶች የሚይዝ አጥንት ነው።
አንድ ሺህ ሰዎች
"1000 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

የአህያው መንጋጋ
“የአህያ መንጋጋ”
ክምር በክምር
ይህ ሐረግ ሳምሶን ምን ያህል ሰዎችን እንደገደለ ይገልጻል። ትልቅ የሬሳ ክምር ለመሥራት የሚበቃ ሬሳ ነበር። ኢ.ት፡ “ሬሳዎች ከምሬአለሁ”
Judges 15:17
ራማት ሌሒ
ይህ የቦታ ስም ነው። ስሙም “የመንጋጋ ኮረብታ” ማለት ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
በጣም ተጠምቶ ነበር
“ውሃ መጠጣት በጣም አስፈለገው”
ነገር ግን አሁን በውሃ ጥም ሞቼ ባልተገረዙት. . . እወድቃለሁ?
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሳምሶን በጣም ከመጠማቱ የተነሳ የምር ለሞት እንደሆነ። ኢ.ት፡ “ነገር ግን አሁን በጥም እሞታለሁ፣ ሰውነቴም ባልተገረዙት … ይወድቃል”። ወይም 2) ሳምሶን በጥም ይሞት እንደሆነ በመጠየቅ ምን ያህል እንደተጠማ ያጋንናል። ኢ.ት፡ “ነገር ግን አሁን በጥሜ ምክንያት እንድደክም፤ ባልተገረዙትም … እንድወድቅ ትፈቅዳለህ?” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
በጥም መሞት
ይህ ማለት በቂ ውሃ ባለመጠጣትህ ምክንያት በሰውነትህ ውስጥ በቂ ውሃ አጥተህ መሞት ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በእነዚያ ባልተገረዙት እጅ መውደቅ
“በእጃቸው መውደቅ” የሚለው ሐረግ መማረክ ማለት ነው። “እነዚያ ያልተገረዙ” የሚለው ፍልስጤማውያንን ሲሆን “ያልተገረዘ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን የማያመልኩ ስለመሆናቸው አጽንዖት የሚሰጥ ቃል ነው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔርን በማያውቁ ፍልስጥኤማውያን መማረክ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 15:19
ተሰንጥቆ ጉድጓድ ተከፈተ
“መሬት ላይ ቀዳዳ ተከፈተ” ወይም “ዝቅ ያለው ስፍራ ተከፈተ”። ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ምንጭ እንዲፈልቅ ያደረገበትን ዝቅ ያለ ስፍራ ነው።
ሌሒ
ይህንን በመስፍንት 15:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ብርታቱ ተመለሰለትና ተነቃቃ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ሲሆን ሳምሶን እንደገና ስለ መበርታቱ አጽንዖት የሚሰጡ ናቸው። እነዚህ ሁለት መግለጫዎች መጣመር ይችላሉ። ኢ.ት፡ “እንደገና በረታ” ወይም “ተነቃቃ”
ዓይንሀቆሬ
ይህ የውሃ ምንጭ ስም ነው። ስሙ “የጸለየው የእርሱ ምንጭ” ማለት ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
እስካሁን ድረስ በሌሒ ይገኛል
ይህ ማለት ምንጩ ሳይደርቅ ቆይቷል ማለት ነው። “እስካሁን ድረስ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው የ”አሁን ጊዜ”ን ነው። ኢ.ት፡ ዛሬም እንኳን ምንጩ በሌሒ ይገኛል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በፍልስጥኤማውያኑ ዘመን
ይህ ፍልስጥኤማውያን የእስራኤልን ምድር ይቆጣጠሩ የነበረበትን ወቅት ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ይገዙ በነበረበት ጊዜ”
ለሃያ አመታት
“ለ 20 ዓመታት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Chapter 16
Judges 16:1
ከእርሷ ጋር ወደ አልጋ ሄደ
“ወደ አልጋ ሄዱ” የሚለው ሐረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግን የሚያመለክት የጨዋ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ” ወይም “ከእርሷ ጋር ተኛ”
ለጋዛ ሰዎች ተነግሯቸው ነበር
“የጋዛ ሰዎች” የሚለው ሐረግ ከጋዛ የሆኑትን ሰዎች ያመለክታል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የሆነ ሰው ለጋዛ ሰዎች ነግሯቸዋል” (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የጋዛ ሰዎች ቦታውን ከበቡት --- ሌሊቱን ሙሉ በከተማው በር ጠበቁት
ይህ የሚያመለክተው አንዳንድ የጋዛ ሰዎች ሳምሶን ያረፈበትን ቦታ መክበባቸውንና ሌሎቹ ደግሞ እንዳያመልጥ የከተማውን በር መጠበቃቸውን ነው።
ሌሊቱን ሙሉ ፀጥ አሉ
ትርጓሜዎች ሊሆኑ የሚችሉት 1) “ሌሊቱን ሙሉ ምንም ዓይነት ድምፅ አላሰሙም” ወይም 2) “ሌሊቱን ሙሉ እርሱን ለማጥቃት ምንም ዓይነት ሙከራ አላደረጉም”።
Judges 16:3
እስከ እኩለ ሌሊት
“እስከ ሌሊቱ አጋማሽ ደረስ”
ሁለቱን መቃኖች
እነዚህ ለከተማው በር ድጋፎች ናቸው። እነዚህ መቃኖች ምናልባትም ከዛፍ ግንድ የተሰሩና በምድር ውስጥ በጥልቀት የተቀበሩ ናቸው። የከተማው በር መዝጊያዎች ከነዚህ መቃኖች ጋር የተያያዙ ነበሩ።
ቋሚ ብረቱንና ሁሉንም
ቋሚው ብረት በሮቹን ከመቃኑ ጋር ያያዙ ከባድ የብረት ቋሚዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። የከተማይቱ በር መዝጊያዎች ምናልባትም ከከባድ እንጨት ወይም የብረት ቋሚዎች የተሠሩ ይሆናሉ።
ትከሻዎች
ክንድንና አንገትን ከሰውነት ጋር የሚያያይዘው የሰውነት ክፍል
ኬብሮን
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 16:4
የሶሬቅ ሸለቆ
ይህ በሳምሶን ቤት አቅራብያ የሚገኝ ሸለቆ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ተንኮል
እነርሱ ሊያደርጉት የማይፈልጉትን ነገር ሌላው ሰው እንዲያደርገው ማሳሳት ወይም ማታለል
ለማየት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን አንድን ነገር መማር ማለት ነው። ኢ.ት፡ “መረዳት” ወይም “መማር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ታላቅ ብርታቱ ያለበትን
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ኃይሉ ከየት እንደሚመጣ የሚያመለክት ነው። ኢ.ት፡ “በጣም ጠንካራ እንዲሆን የሚያደርገው ምንድነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በምን መንገድ ልናሸንፈው እንችላለን
“እንዴት እናሸንፈው እንደሆን”
1,100 የብር ሰቅል
“አንድ ሺህ አንድ መቶ የብር ሰቅል”። (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 16:6
በቁጥጥር ስር እንድትሆን የምትታሰረው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በቁጥጥር ስር እንድትሆን ለማሰር” ወይም “አስሮ ለመግታት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
አዲስ ጠፍሮች
አብዛኛውን ጊዜ ጠፍር የሚዘጋጀው ከእንስሳ ቆዳ፤ በተለይም ከጅማት ይሠራል። “አዲስ ጠፍር” የሚሉት ቃላት በቅርብ ከታረደ እንስሳ የመጣና ያልደረቀ መሆኑን ያመለክታል።
ያልደረቀ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እስካሁን ያልደረቀ” ወይም “ገና ያልደረቀ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 16:8
ያልደረቁ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እስካሁን ያልደረቁ” ወይም “ገና ያልደረቁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በእነርሱ ሳምሶንን አሰረችው
“ደሊላ ሳምሶንን በአዲሶቹ ጠፍሮች አሰረችው”
አሁን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ዋናው የትረካ መስመር ለአፍታ መገታቱን ለማሳየት ነው። እዚህ ጋ ደራሲው ደሊላ ሳምሶንን እንዲማርኩ ስለምታስጠብቃቸው ፍልስጥኤማውያን ዳራዊ መረጃ ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ፍልስጤማውያን ባንተ ላይ ናቸው
“ባንተ ላይ” የሚለው ሐረግ ሊይዙት ተዘጋጅተዋል ማለት ነው። ኢ.ት: “ፍልስጥኤማውያኑ ሊይዙህ እዚህ ናቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እሳት እንደነካው የሱፍ ክር ጠፍሮቹን በጣጠሳቸው
ደራሲው የሱፍ ክር ሲቃጠል እንደሚቀልጥ የሳምሶንን በቀላሉ ጠፍሮቹን መበጣጠስ እያነጻጸረ ያብራራል። ኢ.ት: “የሱፍ ክርን እንደሚያቃጥል ጠፍሮቹን በቀላሉ በጣጠሳቸው” ወይም “ከስስ የሱፍ ክር የተሠሩ ይመስል በቀላሉ ጠፍሮቹን በጣጠሳቸው”
Judges 16:10
እንደዚህ ነው ያታለልከኝና የዋሸኽኝ
ማታለልና መዋሸት ተመሳሳይ ሲሆኑ ደሊላ ምን ያህል እንደተናደደች አጽንዖት ለመስጠት ተነግረዋል። ኢ.ት: “እጅግ አታልለኸኛል!”
ልትሸነፍ የምትችለው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ሰዎች ሊያሸንፉህ የሚችሉት”
ፍልስጤማውያን ባንተ ላይ ናቸው
“ባንተ ላይ” የሚለው ሐረግ ሊይዙት ተዘጋጅተዋል ማለት ነው። ኢ.ት: “ፍልስጥኤማውያኑ ሊይዙህ እዚህ ናቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ተቀምጠው ይጠባበቁት ነበር
ይህ ማለት ተደብቀው ለማጥቃት ትክክለኛውን ጊዜ እየጠበቁ ነበር ማለት ነው። ኢ.ት: “ሊያጠቁት እየጠበቁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የክር ቁራጭ እንደሆኑ ያህል
ደራሲው ሳምሶን ክርን እንደሚበጣጥስ በቀላሉ ገመዶቹን እንደበጣጠሰ በማነጻጸር ያብራራል። ኢ.ት: “የክር ቁራጭ የሆኑ ያህል በቀላሉ”
Judges 16:13
አታልለኸኛል፣ ዋሽተኸኛልም
ማታለልና መዋሸት ተመሳሳይ ሲሆኑ ደሊላ ምን ያህል እንደተናደደች አጽንዖት ለመስጠት ተነግረዋል። ኢ.ት: “እጅግ አታለኸኛል”
ልትሸነፍ የምትችለው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ሰዎች ሊያሸንፉህ የሚችሉት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
መጎንጎን
የቁሳቁሶችን ቁርጥራጭ በማሰባጠር እርስ በእርስ እንዲያያዙ ማድረግ።
የፀጉሬን ጉንጉን
ትናንሽ የፀጉር ስብስቦች
ፈትል
ቁሳቁሶችን በመሸመን የሚሰራ ልብስ
የሸማኔ እቃ
የተለያዩ የክር ዓይነቶችን ልብስ አድርጎ ለማያያዝ የሚጠቅም መሳርያ። (የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)
ከሸማኔ ዕቃው ጋር ቸንክሪው
“ጨርቁን ከሸማኔው ዕቃ ጋር ቸንክሪው”
መቸንከር
የሆነን ነገር በቦታው ለመያዝ በመዶሻ ሚስማር መምታት
እንደ ማንኛውም ሰው እሆናለሁ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “እንደ ማንኛውም ሰው ደካማ እሆናለሁ”
ፍልስጤማውያን ባንተ ላይ ናቸው
“ባንተ ላይ” የሚለው ሐረግ ሊይዙት ተዘጋጅተዋል ማለት ነው። ኢ.ት: “ፍልስጥኤማውያኑ ሊይዙህ እዚህ ናቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ፈትሉና ችካሉን ነቀለው
ሳምሶን ፀጉሩን ከሸማኔው ዕቃ ላይ ሲጎትተው ከነፈትሉ ነቀለው። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ፀጉሩን ከሸማኔ ዕቃ፣ ከችካሉና ከፈትሉ ጋር ጎተተው”
ችካሉ
ፈትሉን ከሸማኔው ዕቃ ጋር የሚያያይዘው ከእንጨት የተሰራ ችንካር ወይም ችካል ነው።
Judges 16:15
ምስጢርህን ሳታክፍለኝ እንዴት “እወድሻለሁ” ትለኛለህ?
ሳምሶን በርግጥ የሚወዳት ቢሆን ኖሩ ምስጢሩን ይነግራት እንደነበር ለመናገር ደሊላ ይህንን ጥያቄ ትጠይቃለች። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት: “ምስጢርህን አታካፍለኝምና ‘እወድሻለሁ’ በምትልበት ጊዜ እየዋሸህ ነው” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ነዘነዘችው ጨቀጨቀችው
እዚህ ጋ ደራሲው ደሊላ ለማወቅ ምትፈልገውን ነገር ሳምሶን እንዲነግራት ለማሳመን ግፊት ያደረገችበት ይመስል ሳምሶንን ለማግባባት እንዴት እንደምትሞክር ይናገራል። ኢ.ት: “ልታግባባው በጣም ሞከረች … ለማግባባት መሞከሯን ቀጠለች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በቃሎቿ
“እርሱን በምትናገረው ንግግር”
ሞቱን እስኪመኝ ደረሰ
ደራሲው እዚህ ጋ ሳምሶን ምን ያህል ምሬት እንደተሰማው አጽንዖት ለመስጠት ግነትን ይጠቀማል። ኢ.ት: “ፈፅሞ እንደመረረው” ወይም “እጅግ እንዳዘነ” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
Judges 16:17
ሁሉንም ነገር ነገራት
ስለ ብርታቱ ምንጭ ሁሉንም ነገር ነገራት። ይህ በግልጽ መነገር ይችላል። ኢ.ት: “የብርታቱን ምንጭ ነገራት” ወይም “እውነቱን ነገራት”
ምላጭ
ከሰው ቆዳ ደርሶ ተጠግቶ ፀጉር ለመቁረጥ የሚያገለግል ስለታም መቁረጫ
ለእግዚአብሔር ናዝራዊ
ይህ ማለት እንደ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ነበር ማለት ነው። በመሳፍንት 13፡15 ያለውን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “ለእግዚአብሔር የተሰጠ ናዝራዊ” ወይም “እንደ ናዝራዊ ለእግዚአብሔር የተሰጠ”
ከእናቴ ማህፀን
እዚህ ጋ “ከእናቴ ማህፀን” የሚያመለክተው የተወለደበትን ጊዜ ነው። ይህ ማለት ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ናዝራዊ ነበር ማለት ነው። ኢ.ት: “ሕይወቴን በሙሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ፀጉሬ ከተላጨ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “አንድ ሰው ፀጉሬን ቢላጨኝ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ተላጨ
ወደ ቆዳ አስጠግቶ ፀጉርን በምላጭ መቁረጥ
ኃይሌ ከእኔ ይሄዳል
ሳምሶን ስለ ብርታቱ ትቶት ሊሄድ እንደሚችል ሰው አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “ከእንግዲህ ወዲህ ብርቱ አልሆንም” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
Judges 16:18
ደሊላ ተመለከተች
እዚህ ጋ “ተመለከተች” የሚለው ቃል የሆነን ነገር መገንዘብ የሚል የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ደሊላ ተገነዘበች” ወይም “ደሊላ ዐወቀች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ስለ ሁሉም ነገር እውነታውን
እዚህ ጋ “ሁሉም ነገር” የሚለው ቃል ስለ ሳምሶን ጥንካሬ ሁሉንም ነገር የሚያመለክት ነው። ኢ.ት: “ብርቱ ስለሆነበት እውነታ”
እንደገና ወደ ላይ ኑ
ደሊላ ገዢዎቹን እንደገና ወደ መኖያዋ እንዲመጡ እየነገረቻቸው ነው። የእርሷ ቤት ገዢዎቹ ከሚኀዙበት ከፍ ያለ ቦታ ላይ ሳይሆን አይቀርም።
ብሩን በእጆቻቸው ይዘው
ይህ ሳምሶንን ለመያዝ ከረዳቻቸው ሊሰጧት ቃል የገቡላትን ብር ወደ እርሷ አምጥተዋል ማለት ነው። ኢ.ት: “ሊሰጧት ቃል የገቡላትን ብር በመያዝ”
አስተኛችው
“እንቅልፍ እንዲወስደው አደረገችው”
በጭኗ ላይ
ይህ ማለት ጭንቅላቱን ጭኗ ላይ አድርጎ ተኝቷል ማለት ነው። ይህ በግልጽ መነገር ይችላል። ኢ.ት: “ጭንቅላቱ በጭኗ ላይ ሆኖ”
ጭን
ጭን ሰው ሲቀመጥ ደልደል የሚለው የላይኛው እግር ክፍል ነው።

ሰባቱን የፀጉር ጉንጉኖቹን
ሳምሶን በራሱ ላይ ሰባት የፀጉር ጉንጉኖች ነበሩት። ጉንጉኖች ትናንሽ የፀጉር ክምችቶች ናቸው። እዚህ ጋር ሰባቱ የፀጉሩ ጉንጉኖች "የእርሱ" መባላቸው የጭንቅላቱ ንብረቶች እንደሆኑ ተደርገው ተገልጸዋል። ኢ.ት: "በራሱ ላይ የነበሩት ሰባቱ የፀጉር ጉንጉኖች" (ንብረት የሚለውን ተመልከት)
አሸነፉት
"በቁጥጥር ስር አዋሉት"
ብርታቱ ተለይቶት ነበር
እዚህ ጋ የሳምሶን ብርታት ትቶት ሊሄድ እንደሚችል ሰው ተደርጎ ተገልጿል። ኢ.ት: "ብርታቱ ሄዶ ነበር" ወይም "ከእንግዲህ ብርቱ አልሆነም" (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
Judges 16:20
ዐይኖቹን አወጡት
ይህ ማለት ዐይኖቹን ከጭንቅላቱ አውጥተዉታል ማለት ነው። "ዐይኖቹን አጠፏቸው" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ወደ ታች ወደጋዛ
"ወደ ታች" የሚለው ሐረግ እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው ሳምሶንን ከያዙበት ከቤቱ በከፍታው ዝቅ ወዳለው ወደ ጋዛ ስለ ወሰዱት ነው።
በነሐስ የእግር ብረት አሰሩት
"ከነሐስ የእግር ብረት ጋር አሰሩት" ወይም "የነሐስ የእግር ብረት በመጠቀም አሰሩት"
የእግር ብረት
በሰንሰለት መጨረሻ ላይ ያለ የእስረኛውን እግር ወይም እጅ ወይም ሁለቱንም ለማሰር የሚጠቅም መቆለፊያ ያለው
በድንጋይ ወፍጮ ይፈጭ ነበር
"የድንጋይ ወፍጮውን በክብ ይጎትት ነበር"
የድንጋይ ወፍጮ
ይህ በጣም ትልቅ፣ ከባድና ክብ ድንጋይ ነው። ተለቅ ያለ እንስሳ የድንጋይ ወፍጮውን በክብ ዓይነት እየሳበ እህል መፍጨቱ የተለመደ ነበር። እዚህ ጋ ፍልስጥኤማውያን ሳምሶን እንዲጎትተው በማድረግ እያዋረዱት ነው።
ከተላጨ በኋላ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "ፍልስጥኤማውያን ከላጩት በኋላ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 16:23
ዳጎን
ከፍልስጥኤማውያን ሐሰተኛ አማልክት ዋነኛው (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ድል ስለ ሰጠን
"ስላሸነፈልን"
በእጃችን እንዲገባ ስላደረግህ
እዚህ ጋ ደራሲው በገዢዎቹ ቁጥጥር ስር ስለሆነው ሳምሶን በእጃቸው ጥብቅ ተደርጎ እንደተያዘ አንዳች ነገር አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: "በቁጥጥራችን ስር አድርጎታል" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የሀገራችን አጥፊ
ይህ የሚያመለክተው ሳምሶንን ነው። "አጥፊ" የሚለው ቃል "አጠፋ" በሚለው ግሥ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "ሀገራችንን ያጠፋው ሰው"
ከእኛ ብዙዎቹን የገደለ
እዚህ ጋ "እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፍልስጥኤማውያንን ነው። ተናጋሪዎቹ ሳሞሶን ከገደላቸው ሰዎች መካከል ራሳቸውን እየቆጠሩ አይደለም። ኢ.ት: "ከእኛ ሰዎች ብዙዎቹን የገደለ"
Judges 16:25
ሳምሶንን ጥሩት ሳምሶንን ጠሩት
ሳምሶን እስረኛ ስለነበር በቀጥታ መጠራት አይችልም ነበር፤ ነገር ግን ሰዎቹ የእስር ቤቱን ኃላፊዎች ሳምሶንን ወደ እነርሱ እንዲያመጡላቸው እየጠየቁ ነበር። ኢ.ት: "ሳምሶንን እንዲያመጡላቸው ጠየቋቸው ሳምሶንን አመጡት"
ልጁ
"ታዳጊው ልጅ" ይህ ትንሽ ልጅ አልነበረም፣ ይልቁንም ወጣት ነው።
ሕንጻው ያተደገፈበትን ምሰሶ እንድነካ ፍቀድልኝ
"ሕንጻውን ደግፈው የያዙትን ቋሚዎች እንድነካ ፍቀድልኝ"
Judges 16:27
አሁን
ይህ ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው ደራሲው ስለ ዳራዊ መረጃ ሊናገር ከዋናው ታሪክ ለአፍታ መውጣቱን ለማመልከት ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ሶስት ሺህ ወንዶችና ሴቶች
"3,000 ወንዶችና ሴቶች" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
እየተመለከቱ
"እያዩ"
ሳምሶን እያዝናናቸው እያለ
ሳምሶን እነርሱን ለማዝናናት ምን እንዳደረገ ግልጽ አይደለም። ፍልስጥኤማውያን እንዲቀልዱበት፣ ሊያዋርዱት የሚችሉ ነገሮችን ያስደረጉት ይመስላል።
Judges 16:28
ወደ እግዚአብሔር ተጣራ
"ወደ እግዚአብሔር ጸለየ"
አስበኝ
ይህ ማለት እርሱንና ያለበትን ሁኔታ እንዲያስታውስ ማለት ነው። ኢ.ት: "አስታውሰኝ" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ይህን አንድ ጊዜ ብቻ
"አንድ ጊዜ ብቻ"
በአንድ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን ላይ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ፣ ፍልስጥኤማዊያን ስላደረጉበት ነገር ፈጽሞ ለመበቀል በእነርሱ ላይ አንድ ጊዜ የኃይል ድርጊት ለመፈጸም ይፈልጋል ማለት ነው። ኢ.ት: "በፍልስጥኤማውያን ላይ በአንድ ምት" ወይም "በፍልስጥኤማውያን ላይ በአንድ ኃይለኛ ድርጊት" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ሕንጻው ያረፈበት
"ሕንጻውን ባቆመው"
Judges 16:30
በብርታቱ ገፋው
ሳምሶን ክንዶቹን ሲዘረጋ የሕንጻውን ምሰሶዎች ገፍቶ ጣላቸው። ኢ.ት: "ምሰሶዎቹን ለመጣል ብርታቱን ተጠቀመ" ወይም "ምሰሶዎቹን ለመግፋት ኃይሉን ተጠቀመ"
የሞቱት
ይህ የሞቱትን ሰዎች ያመለክታል። "የሞቱት ሰዎች"
ይበዙ ነበር
"በቁጥር ብዙ ነበሩ"
የአባቱ ቤት ሁሉ
እዚህ ጋ "ቤት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእርሱን ቤተሰብ ነው። ኢ.ት: "የአባቱ ቤተሰቦች በሙሉ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ወረዱ
"ወረዱ" የሚለው ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው የሳምሶን ቤተሰብ የተጓዘበት ቦታ ከጋዛ በከፍታ የሚበልጥ ስለነበረ ነው።
ጾርዓ ኤሽታኦል
የእነዚህን ቦታዎች ስም በመሳፍንት 13:2 እና በመሳፍንት 13:25 እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።
በአባቱ በማኑሔ የመቃብር ስፍራ
"አባቱ ማኑሔህ በተቀበረበት ስፍራ"
ማኑሔ
የዚህን ሰውዬ ስም በመሳፍንት 13:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሳምሶን ለሃያ ዓመታት በእስራኤል ላይ ፈርዶ ነበር
ይህ ዐረፍተ ነገር ራሱ በመሳፍንት 15:20 ላይ አለ። እዚህ ጋ የተደገመው ለምን ያህል ጊዜ በእስራኤል ላይ እንደፈረደ አንባቢዎችን ለማስታወስ ነው። ኢ.ት: "ሳምሶን ከመሞቱ በፊት በእስራኤል ላይ ለሃያ ዓመታት ፈርዷል"
ሃያ ዓመታት
"20 አመታት" (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)

Chapter 17


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Judges 17:1
አንድ ሰው ነበር
ይህ በታሪክ ፍሰቱ ላይ አዲስን ሰው የማስተዋወቂያ መንገድ ነው። (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቂያ የሚለውን ተመልከት)
ሚካ
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። ይህ የሚክያስን መጽሐፍ የጻፈው ሰው አይደለም። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
1,100 ሰቅል
“አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰቅል” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ከአንቺ የተወሰደው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው የሰረቀብሽ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሰርቄዋለሁ
“እኔ ነኝ የወሰድኩት”
Judges 17:3
1,100 ሰቅል
“አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰቅል” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ለየ
ይህ ማለት አንድን ነገር ለተለየ አላማ መስጠት ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ተሰጠ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የቀለጠ ብረት
የተለየ ቅርጽ ለማውጣት በቅርጽ ማውጫ ውስጥ ቀልጦ የሚጨመር ብረት
እመልስልሃለሁ
“ላንተ መልሼ እሰጥሃለሁ”
ሁለት መቶ ሰቅል ብር
“200 ሰቅል ብር” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
እነርሱ በሚካ ቤት ተቀምጠው ነበር
“እነርሱ” የሚለው ቃል የብረቱ ቅርጾቹን ያመለክታል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሚካ በቤቱ አስቀምጧቸው ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 17:5
የጣዖታት ቤት
ይህ በግልጽ ጣዖታት የሚመለኩበትን ቤት ያመለክታል። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ጣዖታትን የማምለኪያ ቤት”
ሁሉም በዐይኖቹ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር
ዐይን ዕይታን ይወክላል፤ ማየትም አሳብን ወይም ውሳኔን ይወክላል። ኢ.ት፡ “እያንዳንዱ ሰው ልክ ነው ብሎ የወሰነውን ያደርግ ነበር” ወይም “እያንዳንዱ ሰው ልክ ነው ብሎ የፈረደውን ያደርግ ነበር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 17:7
የቤተልሔም
“ከቤተልሔም”
ከይሁዳ ነገድ የሆነ
ይህ ማለት በይሁዳ ቤተሰቦች ይኸውም በይሁዳ ነገድ መካከል ይኖር ነበር ማለት ነው። ኢ.ት፡ “በይሁዳ ነገድ መካከል ይኖር የነበረ”
ኃላፊነቱን ለመወጣት በዚያ ይኖር ነበር
“በዚያ ይኖርና ይሠራ ነበር”
መኖሪያ እየፈለገ
“ሌላ የመኖርያ ቦታ ለመፈለግ”
የምኖርበትን
የሚኖርበትንና የሚሠራበትን ቦታ እየፈለገ እንደሆነ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የምኖርበትና የምሠራበትን ስፍራ”
Judges 17:10
አባትና ካህን
“አባት” የሚለው ቃል እዚህ ጋ አማካሪ ለማለት ጥቅም ላይ ውሏል እንጂ እውነተኛ አባትነትን አያመለክትም። ኢ.ት፡ “አማካሪና ካህን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በዓመት አሥር ሰቅል ብር እሰጥሃለሁ
“በየዓመቱ አሥር ጥሬ ብር እሰጥሃለሁ”
ቅያሪ ልብስ
“የልብሶች ስብስብ”
ስለዚህ ሌዋዊው ወደ እርሱ ቤት ገባ
ሌዋዊው የሚካን አሳብ መቀበሉንና ወደ ሚካ ቤት መግባቱን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ስለዚህ ሌዋዊው ግብዣውን ተቀብሎ ወደ ቤቱ ገባ”
ወጣቱ ለሚካ ከወንዶች ልጆቹ እንደ አንዱ ሆነለት
በሌዋዊውና በሚካ መካከል ያለው ግንኙነት እንደ አባትና ልጅ የጠበቀ ሆነ። ኢ.ት፡ “ወጣቱ ከሚካ ጋር በጣም ከመቀራረቡ የተነሣ ከወንዶች ልጆቹ እንደ አንዱ ሆነ”
Judges 17:12
ሚካ ሌዋዊውን ለየው
እዚህ ጋ “ለየው” ማለት ሚካ “ቀደሰው” ወይም “ሾመው” ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ሚካ ሌዋዊውን ቀደሰው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በሚካ ቤት ነበረ
እዚህ ጋ በሚካ ቤት መኖሩ በቤቱ “እንደሆነ” ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “በሚካ ቤት ኖረ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 18
Judges 18:1
በእነዚያ ቀናት
ይህ ሐረግ በታሪኩ ፍሰት ላይ ሌላ አዲስ የሁነት ጅማሬን ያስተዋውቃል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
በእነዚያ ቀናት... ከእስራኤል ነገዶች መካከል
ይህ ስለ እስራኤልና ስለዳን ነገድ ሕዝቦች ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ምንም ርስት አልተቀበለም
ይህ በግልጽ የሚኖሩበትን መሬት እንዳልወረሱ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የመሬት ርስት አልተቀበልንም”
ከነገዳቸው በሙሉ
“በሙሉ” የሚለው ቃል በነገዱ ያሉትን ሰዎች ሁሉ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “በየነገዱ መካከል ካሉት ሰዎች ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ልምድ ያላቸው ጦረኞች
“ልምድ ያላቸው ተዋጊዎች”
ጾርአ
የዚህን ከተማ ስም በመስፍንት 13፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ኤሽታኦል
የዚህን ከተማ ስም በመሳፍንት 13፡25 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ምድሪቱን በእግር ተጉዘው እንዲሰልሉ
“በእግር” የሚለው ሐረግ መራመድ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “በእርሱ ላይ በመራመድ መሰለል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ሚካ
የዚህን ሰው ስም በመሳፍንት 17፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
Judges 18:3
የወጣቱን ሌዋዊ ንግግር ለይተው ዐወቁ
ሰውየውን በሚናገርበት ድምፁ ለይተው ዐወቁት። እዚህ ጋ “ንግግር” የሚጠቁመው “ድምፁን” ነው። ኢ.ት፡ “ወጣቱ ሌዋዊ ሲናገር ሰሙትና ድምፁን ዐወቁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 18:7
ላይሽ
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ድል ያደረጋ ማንም አልነበረም
“ድል አድርገዋቸው በምድራቸው የተቀመጡ ጠላቶች አልነበሩም”
ከማንም ጋር ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም
“በውጪ ከሚኖሩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት አልነበራቸውም”፤ ይህ ማለት ከሌሎች ከተሞች ርቀውና ከሌሎች ሰዎች ተገልለው ይኖሩ ነበር ማለት ነው።
ጾርአ
የዚህችን ከተማ ስም በመሳፍንት 13፡2 ላይ እንደተረጎምከው አድርገህ ተርጉም።
ኤሽታኦል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የዚህችን ከተማ ስም በመሳፍንት 13፡25 ላይ እንደተረጎምከው አድርገህ ተርጉም።
Judges 18:9
ምንም እየሠራህ አይደለም?
ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የተጠየቀው በአሽሙር ሲሆን ትርጉሙም ተቃራኒውን ማድረግ ነበረባቸው የሚል ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት፡ “አሁን የሆነ ነገር ማድረግ አለባችሁ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)
ለማጥቃት የዘገያችሁ አትሁኑ
እነዚህ “አትሁኑ” እና “አትዘግዩ” የሚሉት አሉታዊ ቃላቶች በአንድ ላይ በቶሎ እንዲያጠቁ አዎንታዊ አሳብ ላይ አጽንዖት የሰጣሉ። “ፍጠኑ! አጥቁ” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)
ምድሪቱ ሰፊ ናት
“ምድሪቱ ታላቅ ናት” ይህ የምድሩን መጠን ይገልጻል።
ምድሪቱ ምንም ነገር ያልጎደላት
ሰዎቹ ለመኖር በጣም ተመራጭ ቦታ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ግነትን ተጠቅመዋል። ኢ.ት፡ “በዚያ የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ይኖረናል” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
ምንም ነገር ያልጎደለው
ሁለቱ አሉታዊ ቃላት በአንድነት አዎንታዊ አሳብ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት፡ “ሁሉም ነገር ያለው” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)
Judges 18:11
ስድስት መቶ ሰዎች
“600 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ቂርያትይዓሪም
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ማኽነህ ዳን
የዚህን ስፍራ ስም በመሳፍንት 13፡25 ላይ እንደተረጎምከው አድርገህ ተርጉመው።
እስከዚህ ቀን ድረስ
ይህ ማለት የሆነ ነገር እስካሁን እንደዚያው አለ ማለት ነው። “የአሁንን ” ጊዜ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “እስካሁን ስሙ እንደዚያው ነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 18:13
ላይሽ
የዚህን ከተማ ስም በመሳፍንት 18፡7 ላይ እንደተረጎምከው አድርገህ ተርጉመው።
በእነዚህ ቤቶች ውስጥ ኤፉዶች አሉ፣ ... የብረት ምስል? እናደርጋለን ወስኑ
አምስቱ ሰዎች ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ሰዎቹ ጣዖታቱን እንዲሰርቁ አሳብ ለመስጠትና ለማደፋፈር ነው። ይህ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል፤ አመልካች የመረጃ ሐረግም በቅንፍ ውስጥ ሊሰጥ ይቻላል። ኢ.ት፡ “እነዚህ ቤቶች የብረት ምስል የሆነውን ኤፉድ ይዘዋል (ሰዎቹ እንዚህን ነገሮች እንዲሰርቁ አሳብ እየሰጡ ነበር።) እናደርጋለን ... ወስኑ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና የሚለውን ተመልከት)
በእነዚህ ቤቶች ውስጥ አሉ
“ከእነዚህ ቤቶች በአንዱ ውስጥ አለ” ወይም “በእነዚህ ቤቶች መካከል አለ”
Judges 18:15
ወደዚያ ገቡ
“ገቡ”
ሰላምታ ሰጡት
“እርሱን” የሚለው ቃል ሌዋዊውን ያመለክታል።
ስድስት መቶ የዳን ሰዎች
“600 የዳን ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 18:17
ስድስት መቶ ሰዎች
“600 ወንዶች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 18:19
ለአንድ ሰው ቤት ካህን መሆን ይሻልሃል በእስራኤል ላለ አንድ ነገድ?
ይህንን ጥያቄ መልስ በማይሻ መልኩ የሚጠይቁት የነገሩን እውነትነት ለማመልከት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት፡ “ለአንድ ሰው ካህን ከመሆን ይልቅ በእስራኤል ላለ ነገድ እና ጎሳ ካህን መሆን ይሻልሃል” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የካህኑ ልብ ተደሰተ
እዚህ ጋ ካህኑ በተሰማው ስሜት ላይ አጽንዖት ለመስጠት ”ልቡ” ተብሏል። ኢ.ት፡ “ካህኑ ተደስቶ ነበር”
Judges 18:21
ትንንሾቹን ልጆች ከፊት ለፊታቸው አደረጓቸው
በዚህ መልኩ የሚጓዙት ልጆቹን ለመጠበቅ ነው። ሚካና ሰዎቹ ቢያጠቁቸው መጀመሪያ የሚያገኙት ጦረኞቹን እንጂ ልጆቹን አይሆንም። ኢ.ት፡ “ትንንሾቹን ልጆች ለመጠበቅ ከፊት ለፊታቸው አደረጓቸው”
በጥሩ ርቀት
“ጥቂት ርቀት”፣ ይህ ለመለካት የሚበቃውን ርዝመት አጭር ርቀት ይለዋል። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በሚካ ቤት አቅራብያ ባሉት ቤቶች ውስጥ የነበሩ ሰዎች አንድ ላይ ተጠርተው ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በቤቱ አቅራቢያ ባሉ ቤቶች ውስጥ የነበሩትን ሰዎች አንድ ላይ ጠራቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በዳን ሰዎች ላይ ደረሱባቸው
ይህ ከኋላ ተከትለዋቸው እንደሮጡ ያመለክታል። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከዳን ሰዎች ኋላ በመሮጥ ደረሱባቸው”
ወደ ኋላቸው ተመለሱ
“የዳን ሰዎች የሆኑት ወደ ኋላቸው ዞሩ”
ተጠራርታችሁ የተሰባሰባችሁት ለምንድነው?
ይህ የወቀሳ ጥያቄ ነው። እንደ መግለጫ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እኛን ለማሳደድ ሰዎችህን ጠርተህ መሰብሰብ አልነበረብህም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አንድ ላይ ተጠርተው ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እነዚህን ሰዎች አንድ ላይ ጠሯቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 18:24
የሰራኋቸውን አማልክቶቼን
ሚካ አማልክቶቹን አልሠራቸውም፤ የሠራቸው ባለ ሙያ የሆነ ሰው ነው። ኢ.ት፡ “ለራሴ ያሠራኋቸውን አማልክት” ወይም “ባለ ሙያ የሠራልኝን አማልክት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሌላ ምን ቀረኝ?
ሚካ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ለእርሱ አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች አሁን እንደሌሉት አጽንዖት ለመስጠት ነው። ኢ.ት፡ “ምንም የቀረኝ ነገር የለም” ወይም “ለእኔ አስፈላጊ የሆነውን ነገር በሙሉ ወስዳችሁብኛል” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
“ምን ሆንክ?” ብላችሁ እንዴት ትጠይቁኛላችሁ
ሚካ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው የዳን ሰዎች የሆኑት በእርግጥ ምን እንዳሳሰበው እንደሚያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ኢ.ት፡ “እጅግ እንዳዘንኩ ታውቃላችሁ!” ወይም “በእኔ ላይ ባደረጋችሁት ነገር ምን ያህል እንደተቸገርኩ ታውቃላችሁ!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ምንም አይነት ነገር ስትናገር እንዳንሰማህ
“ስትናገር እንዳንሰማህ” የሚለው ሐረግ የዳን ሰዎች ሚካ ስለሆነው ነገር የሚያወራውን መስማታቸውን ያመለክታል፤ ነገር ግን ሚካ ስለተፈጠረው ነገር ማውራቱን ከሌሎች ሰዎች መስማታቸውንም ይጨምራል። ኢ.ት፡ “ምን እንደተናገርክ ማወቅ እንፈልጋለን” ወይም “ስለዚህ ጉዳይ የፈለግኸውን ተናገር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ምንም አይነት ነገር ስትናገር እንዳንሰማህ
“ምንም ዓይነት ነገር” የሚለው ሐረግ የዳን ሰዎች ወደ ሚካ ቤት መጥተው ጣዖቶቹን መስረቃቸውን የሚጠቁም የትኛውንም መረጃ ያመለክታል። ይህ በግልጽ መነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ስለዚህ ጉዳይ ምንም ነገር ስትናገር እንዳንሰማህ” ወይም “ስለሆነው ነገር እንዳች ስትናገር እንዳንሰማህ”
አንተና ቤተሰቦችህ ትገደላላችሁ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንተንና ቤተሰብህን እንገላለን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
መንገዳቸውን ሄዱ
ይህ ጉዟቸውን ቀጠሉ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ጉዟቸውን ቀጠሉ” ወይም “መጓዛቸውን ቀጠሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ለእርሱ እጅግ የበረቱ ነበሩ

ይህ የሚያመለክተው ሚካና ሰዎቹ እንዳይዋጓቸው የዳን ሰዎች እጅግ ብርቱ መሆናቸውን ነው። ኢ.ት፡ “እርሱና ከእርሱ ያሉት ሰዎች እንዳይዋጓቸው እጅግ ብርቱዎች ነበሩ”

Judges 18:27

ሚካ ሠርቷቸው የነበሩት

ሚካ አማልክቶቹን አልሠራቸውም፤ ይልቁን የሠራለት ባለ ሙያ ነበር። ደግሞም ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ለሚካ የተሠሩለት ነገሮች” ወይም “የሚካ ነገሮች” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ላይሽ

ይህንን በመሳፍንት 18:17 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በሰይፍ ስለት

“በሰይፎቻቸው”። እዚህ ጋ “ሰይፉ” ወታደሮቹ በጦርነት የተጠቀሙባቸውን ሰይፍና ሌሎች የጦር መሳሪያዎች ይወክላል።

ከማንም ጋር ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም ነበር

“በውጪ ከሚኖሩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት አልነበራቸውም”፤ ይህ ማለት ከሌሎች ከተሞች ርቀውና ከሌሎች ሰዎች ተገልለው ይኖሩ ነበር ማለት ነው። ይህንን ሐረግ በመሳፍንት 18:7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቤትርዓብ

ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

Judges 18:30

x

ይህ ሚካን በካህንነት ያገለግለው የነበረው የወጣቱ ሌዋዊ ስም ነው። ይህ ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “የወጣት ሌዋዊው ስም የሙሴ ልጅ የጌርሳም ልጅ ዮናታን ነበር” ( እና ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

ምድሪቱ እስከተያዘችበት ቀን ድረስ

ይህ የዳን ሰዎች በጠላቶቻቸው የሚያዙበትን የወደፊት ጊዜ የሚያመለክት ነው። እዚህ ጋ የምድሪቱ መያዝ በጠላት እንደተማረከ እስረኛ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ጠላቶቻቸው ምድራቸውን እስኪያዙበት ቀን ድረስ” ወይም “ጠላቶቻቸው ማርከው እስከወሰዷቸው ቀን ድረስ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሠራቸው

ሚካ አማልክቶቹን አልሠራቸውም፤ ይልቁንም ባለ ሙያ ነበር የሠራለት። ኢ.ት፡ “ተሠርተዉለት የነበሩት” ወይም “የእርሱ ባለ ሙያ የሠራለት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 19

Judges 19:1

በእነዚያ ቀናት

ይህ ሐረግ በታሪክ ፍሰቱ ላይ የሌላ ሁነትን ጅማሬ ያስተዋውቃል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ሩቅ

አብዛኞቹ ሰዎች ከሚኖሩበት የራቀ

ለእርሱ ታማኝ አልነበረችም

ይህ ማለት እርሷ ለግንኙነታቸው ታማኝ አልነበረችምና ከሌሎች ወንዶች ጋር መተኛት ጀምራለች ማለት ነው። አስፈላጊ ከሆነ ይህ በግልጽ መነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከሌሎች ወንዶች ጋር መተኛት ጀመረች”

Judges 19:3

አገልጋዩና ሁለት አህዮች ከእርሱ ጋር ነበሩ

“ከእርሱ ጋር አገልጋዩንና ሁለት አህዮችን ወሰደ”

ዐማቱ፣ የልጅቱ አባት አግባባው

“ዐማቱ፣ ይኸውም የልጅቱ አባት አግባባው” ወይም “የልጅቱ አባት አግባባው”

እንዲቆይ አግባባው

“ስለተናገረው ለመቆየት ወሰነ”

Judges 19:5

አዘጋጀ

ሌዋዊው አዘጋጀ

በቁራሽ እንጀራ ራስህን አበርታ

እዚህ ጋ “እንጀራ” “ምግብ”ን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ለመጓዝ እንድትበረታ ጥቂት ምግብ ብላ”

ምሽቱን ለማሳለፍ እባክህ ፈቃድህ ይሁን

“እባክህ ደግመህ እደር”

Judges 19:7

ራስህን እያበረታህ እስከ ከሰዓት ቆይ

አማቱ በመብላት ራሱን እንዲያበረታ አሳብ እየሰጠው ነው። ለመሄድ እስከ ከሰዓት እንዲቆይም እየጠየቀው ነው። ይህ በግልጽ መነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ለመጓዝ እንድትበረታ ጥቂት ምግብ ብላ፤ እስከ ከሰዓት ቆይና ትሄዳለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የሚለውን ተመልከት)

Judges 19:9

አሁን ቀኑ ወደ መምሸቱ ቀርቧል

“ቀኑ እየተገባደደ ነው” ወይም “ምሽት ሊሆን ነው”

Judges 19:10

ይህም ኢየሩሳሌም ነው

“ከጊዜ በኋላ ኢየሩሳሌም ተብላ ተጠርታለች”

የተጫኑ ጥንድ አህዮች ነበሩት

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በሁለቱ አህዮቹ ላይ ኮርቻዎችን ጫነባቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ና፣ እንሂድ

ይህ አሳብ ለመስጠት የሚጠቅም የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ብንሄድ ይሻላል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ወደ … ጎራ እንበል

ይህ ማለት ጉዟቸውን በመግታት የሆነ ቦታ ላይ እንዲያርፉ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “እዚህ ጋ እንቆይ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 19:12

ወደ … ጎራ እንበል

ይህ ማለት ጉዟቸውን በመግታት የሆነ ቦታ ላይ እንዲያርፉ ማለት ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በመሳፍንት 19:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እዚህ ጋር እንረፍ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ና፣ እንዲህ እናድርግ

ይህ አሳብ ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋለ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “እንድ… አሳብ አቀርባለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 19:14

ጎራ አሉ

ይህ ማለት ጉዟቸውን በመግታት የሆነ ቦታ ላይ እንዲያርፉ ማለት ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በመሳፍንት 19:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ቆሙ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በከተማይቱ አደባባይ

ሰዎች ቀን ላይ የሚሰባሰቡበት የገበያ ስፍራ

ወደ ቤቱ ወሰዳቸው

የዚህ ሐረግ ትርጉም አንድ ሰው በቤቱ እንዲያድሩ ጋበዛቸው ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ያንን ሌሊት በቤታቸው እንዲያሳልፉ ጋበዟቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Judges 19:16

ብንያማውያን

ብንያማዊ ሰው የብንያም ተወላጅ ነበር። ይህንን የሕዝብ ወገን ስም በመሳፍንት 3:15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ዓይኖቹን አንስቶ

ሰውየው ቀና አለና በዙሪያው ያለውን ተመለከተ። ኢ.ት፡ “ቀና አለ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በከተማይቱ አደባባይ

ሰዎች ቀን ላይ የሚሰባሰቡበት የገበያ ስፍራ። ይህንን በመሳፍንት 19:14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Judges 19:18

ወደ ቤቱ የሚወስደኝ ማነው

ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ሌሊቱን በዚያ እንዲያሳልፍ ሌላውን ሰው ወደ ቤቱ የሚጋብዝን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “በቤቱ እንዳድር የጋበዘኝ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚወስደኝ
እዚህ ጋ ሌዋዊው “እኔ” ይላል፣ ነገር ግን እርሱ እያመለከተ ያለው ራሱን፣ አገልጋዩንና ቁባቱን ጭምር ነው። ኢ.ት፡ “የሚወስደን”
በዚያ እንጀራና ወይን አለ
ወደ አድራጊ ድምፅ ቀይረው። ኢ.ት፡ “ብዙ እንጀራና ወይን አለን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ለእኔና ለሴት አገልጋይህ፣ እንዲሁም ከአገልጋይህ ጋር ላለው ለዚህ ወጣት
ሌዋዊው አክብሮቱን ለማሳየት ራሱንና ከእርሱ ጋር ያሉትን ሌሎቹንም በሦስተኛ መደብ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እኔ፣ ቁባቴና አገልጋዬ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
የጎደለን ምንም የለም
ይህ አዎንታዊ መግለጫ ሆኖ ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት፡ “የሚያስፈልገን ሁሉ አለን”
Judges 19:20
ብቻ አትደሩ
“አትደሩ”። “ብቻ” የሚለው ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው ሌዋዊው እንዲያደርግ ስላልፈለገው ጉዳይ አጽንዖት ለመስጠት ነው።
አደባባይ
ይህ የከተማይቱን አደባባይ ያመለክታል። ይህንን በመሳፍንት 19፡17 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሌዋዊውን ወደ ቤቱ አመጣው
ይህ ማለት ሌዋዊው በቤቱ እንዲያድር ጋበዘው ማለት ነው። ሌዋዊውን በመጋበዙ ቁባቱንና አገልጋዩንም ደግሞ ጋብዟቸዋል። ኢ.ት፡ “ሌዋዊውንና አገልጋዮቹን በቤቱ እንዲያድሩ ጋበዛቸው” (የአነጋገር ዘይቤ እና የሚለውን ተመልከት)
Judges 19:22
ልባቸውን ያስደስቱ ነበር
“ልባቸውን ያሰደስቱ” የሚለው ሐረግ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ከአንድ ሰው ጋር ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “በአንድ ላይ ጥሩ ጊዜ እያሳለፉ ነበር” ወይም “ራሳቸውን ያስደስቱ ነበር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
አንዳንድ ሰዎች -- ቤቱን ከበቡት
አንዳንድ ሰዎች በቤቱ ዙሪያ ቆሙ

Judges 19:24
ተመልከቱ
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የሰዎቹን ትኩረት ለማግኘት ነው። ኢ.ት፡ “አድምጡ”
ሰዎቹ አልሰሙትም
እዚህ ጋ ደራሲው “መስማት” በማለት የሚናገረው ስለ “መስማማት” ነው። ኢ.ት፡ “ሰዎቹ ግብዣውን አለተቀበሉትም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰውየው ቁባቱን ይዞ
የሰውየው ማንነት አሻሚ ነው። ኢ.ት፡ “ሌዋዊው ቁባቱን ይዞ”
ማለዳ ላይ
“ፀሐይ በምትወጣበት ጊዜ” ወይም “ንጋት ሲሆን” ይህ ፀሐይ መውጣት የጀመረችበትን ጊዜ ያመለክታል።
ነግቶ ነበር
ይህ ውጪው ብርሃን የሆነበትን ጠዋት ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ፀሐይ ሙሉ በሙሉ ወጥታ ነበር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 19:27
ይሁን እንጂ ምንም ምላሽ አልነበረም
ሴቲቱ ሞታ ስለነበር ምላሽ አልሰጠችም። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ይሁን እንጂ ሞታ ስለነበር አልመለሰችለትም”
Judges 19:29
የተቆራረጠ አካል
“በክፍል በክፍል”። ደራሲው ይህንን ሥዕላዊ መግለጫ የሚጠቀመው ሌዋዊው አካሏን በተለየ አኳኋን በመቆራረጥ ስላደረገው ነገር አጽንዖት ለመስጠት ነው። “የተቆራረጠ አካል” የአንድን ሰው እጅና እግር ያመለክታል። በቋንቋህ ተመሳሳይ ሐረግ ከሌለ ይህ አገላለጽ ከትርጉምህ ውስጥ መቅረት ይኖርበት ይሆናል። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
አሥራ ሁለት ቁርጥራጭ
“12 ቁርጥራጭ” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ቁርጥራጮቹን በእስራኤል ምድር ወደ ሁሉም ስፍራ ላካቸው
ይህ ማለት የተለያዩ ቁርጥራጮቹን ወደ አሥራ ሁለት የእስራኤል አካባቢዎች ልኳል ማለት ነው። ኢ.ት፡ “እያንዳንዱን ቁራጭ ወደ ተለያዩ የእስራኤል ክፍሎች ልኳል”

---

Chapter 20
Judges 20:1
እንደ አንድ ሰው
ይህ ንጽጽር የሚናገረው አንድ ቡድን እንደ አንድ ሰው መንቀሳቀሱን ነው። ይህ የሚያመለክተው በቡድን የሆኑ ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ ሁሉንም ነገር በጋራ የሚያደርጉ መሆናቸውን ነው። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው የሆኑ ያህል” (ንጽጽር የሚለውን ተመልከት)
ከዳን እስከ ቤርሳቤህ
ይህ በጥቅሉ ምድሪቱን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ከአሥራ አንዱ ነገዶች በሙሉ”
እግዚአብሔር -- 400,000 እግረኛ ሰዎች
“እግዚአብሔርና በተጨማሪም 400,000 መደበኛ ወታደሮች መጡ”
ለውጊያ የተዘጋጁ
“ወደ ጦርነት ለመሄድ ብቁ የሆኑ”። የሚሄዱት እርስ በእርስ ለመዋጋት አልነበረም።
Judges 20:3
አሁን
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ዋናው የትረካ መስመር ለአፍታ መገታቱን ለማሳየት ነው። እዚህ ጋ የመጽሐፉ ደራሲ የብንያም ሰዎች ስለሚያውቁት ነገር ዳራዊ መረጃ ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ወደ ምጽጳ ወጥተው ነበር
ምጽጳ የምትገኘው ከፍ ባሉት ተራራዎች ላይ ነበር።
ሌሊቱን ለማሳለፍ
“ለሌሊቱ” ወይም “አንድ ሌሊት ለማደር”
Judges 20:5
ክፋትና የጭካኔ ተግባር
“የጭካኔ ተግባር” የሚለው ቃል “ክፋት”ን ያብራራዋል። ኢ.ት፡ “አሰቃቂ ክፋት”
አሁን
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የሌዋዊውን ንግግር መደምደሚያ ለማስተዋወቅ ነው።
እዚህ ላይ አስተያየትና ምክራችሁን ስጡ
“አስተያየት” እና “ምክር” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት አንድን ነገር ሲሆን አጽንዖት ለመስጠት ተደግመዋል። ሁለቱ ሊጣመሩ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “ስለዚህ ጉዳይ ምን ማድረግ እንደሚኖርብን ወስኑ”
Judges 20:8
እንደ አንድ
ይህ ንጽጽር የሚናገረው እንደ አንድ ሰው ስለሚንቀሳቀስ ቡድን ነው። ሁሉም በተመሳሳይ መንገድ በአንድ ላይ ተንቀሳቀሱ። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው የሆኑ ያህል” (ንጽጽር የሚለውን ተመልከት)
ከእኛ ማንም ወደ ድንኳኑ አይሄድም … ከእኛ ማንም ወደ ቤቱ አይመለስም
እነዚህ ሁለት አንቀጾች ስለ አንድ ነገር ሁለቱ መናገራቸው በመሠረቱ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ሊጣመሩ ይችላሉ። “ማንም . . . አይሄድም” እና “ማንም . . . አይመለስም” የሚሉት ቃላት ሰዎቹ በዚያ መቆየታቸውን እንዴት እንደሚቀጥሉ አጽንዖት ይሰጣል። በአዎንታዊ ድምፅ ሊነገሩ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “ሁላችንም እዚሁ እንቆያለን”
አሁን ግን
እነዚህ ቃላት ሰዎቹ ከመጀመሪያው ጩኸት በኋላ የተናገሩትን ዐቢይ ጉዳይ ያስተዋውቃሉ።
ዕጣው እንደ መራቸው
እግዚአብሔር የሚፈልገውን ለማወቅ ምልክት የተደረገባቸውን ጠጠሮች መወርወርን ወይም ማንከባለልን ያካትታል።
Judges 20:10
ከመቶ ሰዎች አሥሩ . . . ከሺህ አንድ መቶ . . . ከአሥር ሺ አንድ ሺ
“ከ100 ሰው 10፣ ከ1,000 ሰው 100፣ ከ10,000 ሰው 1,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
አቅርቦቶች
ሰዎቹ የሚያስፈልጋቸው ምግብና ሌሎች ነገሮች
በከተማይቱ ላይ ተሰበሰቡ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ከተማይቱን ለመውጋት በአንድ ላይ ተሰበሰቡ”
Judges 20:12
ለሞት አብቋቸው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “ግደሏቸው” ወይም “አስወግዷቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የወንድሞቻቸው ድምፅ
እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚያመለክተው የተናገሩትን መልዕክታቸውን ነው። ኢ.ት: “ወንድሞቻቸው የተናገሩትን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Judges 20:15
ሃያ ስድስት ሺህ
“26,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሰባት መቶ
“700” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ግራኝ
ግራኝ የሆነ ሰው ከቀኝ እጃቸው ይልቅ በግራ እጃቸው የበለጠ መሥራት ከሚችሉ ሰዎች አንዱ ነው።
ድንጋይ በማስወንጨፍ ጸጉር የማይስቱ
ይህ የሚያመለክተው በሚያስደንቅ ሁኔታ ዒላማቸውን የሚመቱ መሆናቸውን ነው። ይህ በአዎንታዊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “በጸጉር ላይ እንኳን ድንጋይ ወርውረው መምታት ይችላሉ” ወይም “እንደ ጸጉር በቀጠነ ነገር ላይ ድንጋይ ወርውረው መምታት ይችላሉ”
Judges 20:17
ሳይቆጠሩ
“ሳይጨመሩ”
400,000
“አራት መቶ ሺህ ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔርን ምሪት
“ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔርን ጠየቁ” ወይም “እንዴት መቀጠል እንዳለባቸው እግዚአብሔርን ጠየቁ”
Judges 20:19
ሠፈራቸውን ወደ ጊብዓ አዛወሩ
ስለ ዕብራይስጡ ጽሑፍ ትርጓሜ አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ። ሠፈራቸውን በጊብዓ አቅራቢያ አደረጉ ከሚለው ትርጉም ይልቅ ሰራዊቱ ተጉዞ በጊብዓ ትይዩ ለጦርነት ተዘጋጅተው ቆሙ ማለት ይሆናል።
ሃያ ሁለት ሺህ
“22,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 20:22
ራሳቸውን አበረታቱ
እዚህ ጋ “አበረታቱ” የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን እርስ በእርሳቸው ተበረታቱ ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ለጦርነት ተሰለፉ
ይህ ምናልባት እስራኤላውያኑ በመሰለፍ ለቀጣዩ ቀን ጦርነት ተዘጋጅተዋል ማለት ሊሆን ይችላል። ኢ.ት: “በቀጣዩ ቀን ለመዋጋት ተዘጋጁ”
ከእግዚአብሔር ምሪት ፈለጉ
እንዴት ባለ መንገድ እንደ ፈለጉ አልተገለጸም። ምናልባት ካህኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ዕጣ ጥሎ ይሆናል።
Judges 20:24
አሥራ ስምንት ሺህ
“18,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 20:26
በእግዚአብሔር ፊት
“በእግዚአብሔር ሀልዎት” ወይም “ለእግዚአብሔር”
Judges 20:27
የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት . . . በእነዚያ ቀናት በታቦቱ ፊት ያገለግል ነበር
ይህ አንባቢው፣ ሕዝቡ እግዚአብሔር ምላሽ እንዲሰጣቸው እንዴት እንደጠየቁ መገንዘብ እንዲችል ለመርዳት ደራሲው የጨመረው ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
በእነዚያ ቀናት በዚያ ነበር
“በእነዚያ ቀናት በቤቴል ነበር”
በታቦቱ ፊት ያገለግል ነበር
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “በታቦቱ ፊት በክህነት ያገለግል ነበር”
ማጥቃት
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “የብንያምን ሰራዊት አጥቁ”
Judges 20:29
እስራኤል ሰዎቹን ቦታ አስያዙ
እዚህ ጋ “እስራኤል” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ኢ.ት: “ እስራኤላውያን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ድብቅ ቦታዎች
“በደፈጣ”
Judges 20:31
ከሰዎቹ ጋር ተዋጉ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “ከእስራኤል ሰዎች ጋር ተዋጉ”
ከከተማይቱ ተስበው ወጡ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “የእስራኤል ሰዎች ከከተማይቱ ስበው አወጧቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ከሰዎቹ ጥቂቶቹን መግደል ጀመሩ
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “የብንያም ሰዎች ከእስራኤል ሰዎች ጥቂቶቹን መግደል ጀመሩ”
Judges 20:32
ልክ እንደ መጀመሪያው
“ልክ እንደ ቀድሞው” ወይም “ልክ እንደ መጀመሪያዎቹ ሁለት ጊዜያት”
በኣል ታማር
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ማሬህ ጊብዓ
ይህ የአንድ ቦታ ስም ነው። ሌሎች ትርጉሞች ምናልባት “የጊብዓ ሜዳዎች” ወይም “ከጊብዓ በስተምዕራብ” ወይም “ማሬህ ጌባ” (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 20:34
አሥር ሺህ
“10,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
የተመረጡ ሰዎች
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን እነዚህ በተለየ ሁኔታ ጥሩ ወታደሮች ነበሩ ማለት ነው። ኢ.ት: “በሚገባ የሰለጠኑ ወታደሮች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ጥፋታቸው እንደ ቀረበ
እዚህ ጋ የጥፋት መቅረብ አጠገባቸው እንደ ቆመ ያህል ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት: “ወዲያውኑ ፈጽሞ ሊሸነፉ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
25,100 ሰዎች
“ሃያ አምስት ሺህ አንድ መቶ ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 20:36
የእስራኤል ሰዎች ከጊብዓ ውጪ . . . ባሉት ሰዎች ስለተማመኑ ለብንያም ሰዎች አፈገፈጉላቸው
ከዚህ ዐረፍተ ነገር እስከ ቁጥር 41 መጨረሻ ድረስ ያለው የደፈጣ ተዋጊዎቹ ብንያማውያንን እንዴት እንዳሸነፏቸው ጸሐፊው ለአንባቢያን ለማብራራት የጨመረው ዳራዊ መረጃ ነው።
ለብንያማውያን አፈገፈጉላቸው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ሆን ብለው ወደ ኋላ ተመልሰዋል ማለት ነው። ኢ.ት: “ብንያማውያን ወደ ፊት እንዲመጡ ፈቅደውላቸው ነበር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በሰዎቹ ተማምነው ነበር
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን በሰዎቻቸው ታምነዋል ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 20:39
ከጦርነቱ የሚመለሱ
“ከጦርነቱ የሚያፈገፍጉ”
በፊታችን ተሸንፈዋል

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “አሸንፈናቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 20:40
ጥፋት
ታላቅ ጉዳት፣ መከራ፣ ስቃይ
መጡባቸው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ደረሰባቸው ማለት ነው። ኢ.ት: “ደረሰባቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Judges 20:42
ነገር ግን በጦርነቱ ድል ተደረጉ
ይህ አንድ ሰው ሌላውን በሚይዝበት መልኩ የተነገረው ስለ ጦርነት ነው። ኢ.ት: “ነገር ግን የእስራኤል ወታደሮች ያዟቸው” ወይም “ነገር ግን ከጦርነቱ ለማምለጥ አልቻሉም” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
Judges 20:43
ኖሃህ
ይህ የአንድ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ጨፈጨፏቸው
የብንያማውያን መደምሰስ እስራኤላውያን በሬሳዎቻቸው ላይ እንደተረማመዱ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት: “ሙሉ በሙሉ ደመሰሷቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አሥራ ስምንት ሺህ
“18,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
በጦርነት የታወቁ ነበሩ
“በጦርነት ውስጥ በጀግንነት የተዋጉ ነበሩ”
Judges 20:45
ተመልሰው ሸሹ
“የቀሩት ብንያማውያን ተመልሰው ሸሹ”
አምስት ሺህ … ሁለት ሺህ
“5,000 … 2,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ጊዶም
ይህ የአንድ ቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሃያ አምስት ሺህ
“25,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 20:47
ስድስት መቶ
“600” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
በብንያም ሰዎች ላይ ተመለሱባቸው
እነዚህ ወደ ሬሞን ዐለት የሸሹት የብንያም ሰዎች ወታደሮች ሳይሆኑ ገና በከተማው ውስጥ የነበሩት ናቸው።
ከተማው
እዚህ ጋ “ከተማው” የሚያመለክተው በዚያ ከተማ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። ኢ.ት: “በከተማው የነበረው ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በመንገዳቸው
ይህ የአነጋገር ዘይቤ የሚያመለክተው ወደ ከተማይቱ በሚሄዱበት ጊዜ ያገኙትን ነገር ሁሉ ነው። ኢ.ት: “ወደ … መጡ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 21
Judges 21:1
የእስራኤል ሰዎች ከብንያማውያን ጋር እንዳይጋቡ ቃል ኪዳን ገብተው ነበር
ይህ ዳራዊ መረጃ እስራኤላውያን ከብንያማውያን ጋር ከመዋጋታቸው በፊት ስላደረጉት ቃል ኪዳን ለአንባቢው ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ብንያማውያን
ይህ የብንያም ተወላጆች ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 3፡15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፣ ዛሬ ከነገዶቻችን አንዱን አጥተናልና ይህ ለምን በእስራኤል ላይ ሆነ?
የእስራኤል ሰዎች ይህንን ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የተጠቀሙት ጥልቅ ሐዘናቸውን ለመግለጽ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ሆይ፣ ከእስራኤል ነገዶች አንዱ ሙሉ በሙሉ በመጥፋቱ በጣም አዝነናል” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Judges 21:4
እስራኤላውያኑ፣ “ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ ያልመጣው የትኛው ነው?” አሉ
ሰዎቹ ብንያማውያንን ከመውጋታቸው በፊት በምጽጳ እያሉ የእስራኤላውያኑ ጉባዔ የተናገሩትን ያመለክታል።
በምጽጳ ወደ እግዚአብሔር ያልመጣውን ማንንም ቢሆን የሚመለከት አስፈላጊ የሆነ መሐላ አድርገው ነበር፤ እንዲህ አሉ፣ “እርሱ በእርግጥ መሞት ይገባዋል”።
ይህ እስራኤላውያኑ ብንያማውያኑን ከመውጋታቸው በፊት በምጽጳ ስላደረጉት መሐላ ለአንባቢው ለማብራራት የቀረበ ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
እርሱ በእርግጥ መሞት ይገባዋል
እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው ወደ ምጽጳ ያልሄደውን ማንኛውንም ሰው ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “በእርግጥ ያንን ሰው እንገድለዋለን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Judges 21:6
ወንድማቸው ብንያም
ይህ የሚናገረው ስለ ብንያም ነገድ ሲሆን ለነገዱ ያላቸውን ቅርበት ለማሳየት እንደ እስራኤል ወንድም ታይቷል። ኢ.ት: “የተረፉት ብንያማውያን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከእስራኤል አንድ ነገድ ተቆርጧል
የብንያም ነገድ መጥፋት ከእስራኤል በቢላዋ የተቆረጠ ያህል ተነግሯል። ይህ ግነት ነው፣ ምክንያቱም 600 ሰዎች ገና ቀርተው ነበር። ይሁን እንጂ ብንያማውያን ሴቶች ተገድለው ስለ ነበር የነገዱ የወደፊት ዕጣ ፈንታው በጥያቄ ውስጥ ነበር። ኢ.ት: “አንድ ነገድ ተደምስሷል” (ዘይቤአዊ አነጋገር፣ ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
ሴቶች ልጆቻችንን ላንድርላቸው በእግዚአብሔር ፊት መሐላ አድርገናልና ለተረፉት ለእነዚያ ሚስቶችን ማን ያመጣላቸዋል?
እስራኤላውያኑ ለተረፉት ጥቂት ብንያማውያን ሚስቶችን ለማቅረብ ፈልገዋል፣ ነገር ግን በምጽጳ ያደረጉት መሐላ ይህንን ከማድረግ አግዷቸዋል።
Judges 21:8
ኢያቢስ ገለዓድ
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሰዎች በኃላፊነት ስሜት ተሰብስበው ነበር
“በምጽጳ የተሰበሰቡት ሰዎች ተጠያቂነት ነበረባቸው”
ከኢያቢስ ገለዓድ ተወላጆች አንድም ሰው በዚያ አልነበረም
ይህ የሚያመለክተው ቀደም ሲል በምጽጳ የተደረገውን ጉባዔ ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። ኢ.ት: “ከኢያቢስ ገለዓድ ተወላጆች አንድም ሰው በምጽጳ አልተገኘም ነበር”
አሥራ ሁለት ሺህ
“12,000” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
የኢያቢስ ገለዓድን ተወላጆች፣ ሴቶችንና ልጆችን ጨምሮ በሰይፍ ስለት ምቷቸው
በዚህ ጥቅል መመሪያ ላይ የሚቀጥለው ቁጥር የማይመለከተው ማንን እንደሆነ ይጨምራል።
በሰይፍ ስለት ምቷቸው
“በሰይፎቻችሁ ግደሏቸው”
Judges 21:11
ኢያቢስ ገለዓድ
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 21፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ከወንድ ጋር ያልተኙ
ይህ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ለማመልከት በጨዋነት የተነገረ አነጋገር ነው።
አራት መቶ ወጣት ሴቶች
“400 ወጣት ሴቶች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Judges 21:13
የሰላም ጥሪ አቀረቡላቸው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የነገር ስም የሆነው “ሰላም” በግሣዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ከእነርሱ ጋር መዋጋታቸውን ለማቆም ፈለጉ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ኢያቢስ ገለዓድ
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። ይህንን በመሳፍንት 21፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ለሁሉም የሚበቁ ሴቶች አልነበሩም
ከኢያቢስ ገለዓድ የተገኙት አራት መቶ ሴቶች ብቻ ሲሆኑ ብንያማውያኑ ስድስት መቶ ሰዎች ነበሩ።
በእስራኤል ነገዶች መካከል ልዩነትን አደረገ
“የእስራኤል ነገዶች አንድ እንዳይሆኑ አደረጋቸው”
Judges 21:16
ብንያማውያን
ይህ የሚያመለክተው የብንያምን ተወላጆች ነው። ይህንን በመሳፍንት 3፡15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ብንያማውያን ሴቶች ተገድለው ነበርና
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ብንያማውያን ሴቶችን በሙሉ ገደልናቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ከእስራኤል እንዳይጠፉ … ርስት መኖር አለበት
እስራኤላውያኑ እያጋነኑ ነው። ቀደም ሲል ለአራት መቶ ብንያማውያን ሚስቶችን ሰጥተዋቸዋል፣ በመሆኑም፣ ነገዱ ሙሉ በሙሉ አይጠፋም። (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
Judges 21:18
ለብንያም ሚስትን
እዚህ ጋ ብንያም የሚያመለክተው የብንያም ተወላጅ የሆኑትን ወንዶች ነው። አ.ት፡ “ለብንያማውያን ወንዶች ሚስት”
እርሱም ከቤቴል በስተሰሜን፣ ከቤቴል ወደ ሴኬም ከሚወስደው መንገድ በስተምስራቅና ከሊብኖስ በስተደቡብ
ይህ የሴሎ ከተማ የሚገኝበትን አካባቢ ለአንባቢው ለማብራራት የተሰጠ ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ለቦና
ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Judges 21:20
እያንዳንዳችሁ ሚስት የምትሆናችሁን ጥለፉ … ተመልሳችሁ ወደ ብንያም ምድር ሂዱ
ብንያማውያኑ እነዚህን ሴቶች ይዘው ወደ ገዛ ምድራቸው ተመልሰው እንደሚሄዱ ይታወቃል። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “እያንዳንዳችሁ ከሴሎ ልጃገረዶች አንዷን መያዝና ሚስት እንድትሆናችሁ ከእናንተ ጋር ወደ ብንያም ምድር መውሰድ ይኖርባችኋል”
Judges 21:22
ምህረት አሳዩን
የነገር ስም የሆነው “ምህረት” እንደ ድርጊት ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ደግነትን አድርጉልን” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
በጦርነቱ ጊዜ ለእያንዳንዱ ወንድ ሚስት ስላላገኘንለት ነው
የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከኢያቢስ ገለዓድ ጋር በተዋጋን ጊዜ ለእያንዳንዳቸው ሚስት ስላላገኘን”
ሴት ልጆቻችሁን ለእነርሱ ላለመስጠት … ንጹሐን ናችሁ
ይህ የሚያመለክተው የሴሎን ሰዎች ነው። እነርሱ ሴቶች ልጆቻቸውን ለብንያማውያን በፈቃደኝነት አልሰጡም፣ በመሆኑም ይህንን ላለማድረግ የገቡትን መሐላ አላፈረሱም።
Judges 21:23
የሚያስፈልጓቸው ሚስቶች ቁጥር
ይህ የሚያመለክተው ከኢያቢስ ገለዓድ ሚስቶችን ላላገኙ ሁለት መቶ ብንያማውያን ለእያንዳንዳቸው አንዲት ሚስት ነው። (መሳፍንት 21፡14ን ተመልከት)።
Judges 21:25
በእስራኤል ንጉሥ አልነበረም
“እስራኤል ገና ንጉሥ አልነበራትም”
በዐይኑ ፊት ትክክል የመሰለውን
ዐይን ማየትን፣ ማየትም አሳብን ወይም ፍርድን ይወክላል። አ.ት፡ “ልክ ነው ብሎ የሚፈርደውን” ወይም “ልክ ነው ብሎ የሚያስበውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 1
Ruth 1:1
እንዲህም ሆነ
“እንዲህም ሆነ” ይሄ የተለመደ የታሪካዊ ተረካ አጀማመር ነው።
መሳፍንት በሚገዙበት ዘመን
“መሳፍንት ይፈርዱ በነበረ ጊዜ”
በምድሪቱ
ይሄ የሚያመላክተው የእስራኤልን ምድር ነው። “በአገሩ”
አንድ ሰውም
“አንድ ሰው” ይሄ አንድን ገፀባህሪ ወደ ትረካው ማስገቢያ   ማስተዋወቅያ ተልምዷዊ መንገድ ነው።
የቤተልሔም ይሁዳ የኤፍራታ ሰዎች
ከኤፍሬም ጎሳ  ነገድ  የሆኑ፤ በይሁዳ ክልል በሆነው በቤተልሄም የሰፈሩ ሰዎች ነበሩ።
Ruth 1:3
እርሷ እና ሁለቱ ልጆችዋ በቻ ቀሩ
“ኑኃሚንም ከሁለት ልጆቿ ጋር በቻዋን ቀረች“
ሚስት አገቡ   ወሰዱ
”ሴቶች ሚስት አገቡ   ወሰዱ  “ ይሄ ሚስት ማግባትን ያመላክታል
ከሞዓባውያን ሴቶች
የኑኃሚን ወንድ ልጆች ከሞዓብ ጎሳ   ነገድ  የሆኑ ሴቶች። ሞዓባውያን ሌሎች አማልክትን ያመልኩ ነበር።
የአንዲቱ ስም . . . የሁለተኛይቱም ስም
“. . . የተባሉ የሞዓብ ሴቶች“
አስር ዓመት ያህል
አቤሜሌክ እና ኑኃሚን ወደ ሞዓብ ከመጡ ከአስር ዓመት በኋላ፤ ልጆቻቸው መሓሎን እና ኬሌዎን ሞቱ።
ተለይታ ቀረች
ኑኃሚን መበለት ሆነች።
Ruth 1:6
ርሷም በሞአብ ምድር ሳለች
“እርሷም በሞአብ ሳለች”። ዜናው የመጣው ከእስራኤል አገር እንደሆነ ያመላክታል። እግዚአብሄር እስራኤልን እንደጎበኘ በሞአብ ምድር ሳለች ሰማች።
እግዚአብሔር
በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለህዝቡ የተገለጠበት ስም ነው። (የእግዛብሔርን ስም ስለመተርጎም በቃላት አተረጓጎም መምሪያ ገፁ ላይ ተመልከቱ)
ሕዝቡን እንደጎበኘ እና እህል እንደሰጣቸው
ሕዝቡን እንደጎበኘ እንጀራም እንደሰጣቸው
ምራቶቿን
ምራቶችዋ፤ ወንድ ልጆቿን ያገቡት ሴቶች
መንገድ ይዘው ጉዟቸውን ቀጠሉ
“የሚመልሳቸውን መንገድ ይዘው።” መንገድ ይዘው የሚለው በአንድ መንገድ መሄድን የሚያመላክት አባባል ነው።
Ruth 1:8
ምራቶች
የወንድ ልጆች ሚስቶች ወይንም የወንድ ልጆቿ መበለቶች
እያንዳንዳችሁ
ኑኃሚን የምታዋራው ሁለት ሰዎችን ነበር፤ ከዚህ በመቀጠልም እናንተ ብላ ስትናገር ሁለቱን በማስመልከት ነው።
ወደ እናቶቻችሁ ቤት
“ወደ እናቶቻችሁ ቤትም”
በጎ ነገር እንዳደረጋችሁ
“ቸርነትን እንዳደረጋችሁ”
በጎነት
“ቸርነት” የ ፍቅር፣ የበጎነት፣ እና ታማኝነትን ያመላክታል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ለሞቱት
“ለሞቱት ባሎቻችሁ” ን ኑኃሚን በዚህ የሞቱትን ልጆችዋን ማመላከት ነው የፈለገችው።
ያድርግላችሁ
“እንደዚሁ ያድርግላችሁ” ወይንም “እንዲደረግላችሁ ይፍቀድ”
ያሳረፋችሁ
እዚህ ጋር “ያሳርፋችሁ” የሚለው በትዳርም የሚገኘውን ደህንነትን ያጠቃልላል።
በምታገቡት ባል ቤት
ከአዳዲስ ባሎቻችሁ፣ ከሌላ ሰው ባል ጋር አይደለም። ይሄ የሚያመላክተው በባልየው ቤት ውስጥ እና ከባልየው የሃፍረት ከለላ ስር ማለት ነው።
እነርሱም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ
ድምፅን ከፍ ማድረግ ለጮክ በሎ ማውራትን የሚያመላክት አባባል ነው። ምራቶቿም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ወይንም አምርረው አለቀሱ።
ተመልሰን … እንሄዳለን
“እንመለሳለን” ዓርፋ እና ሩት “እኛ” ብለው ሲናገሩ ስለራሳቸው እንጂ ስለ ሩት አንነበረም የሚናገሩት።
ከአንቺ ጋር
እዚህ ጋር “አንቺ” የሚለው የሚያመላክተው ኑኃሚንን ነው።
Ruth 1:11
ከእኔ ጋር ለምን ትሄዳላችሁ?
ይህ ምላሽ የሚሰጥለት ጥያቄ አይነት አይደለም። “ከእኔ ጋር መሄዱ ትርጉም አይሰጥም።” ወይንም “ከእኔ ጋር መሄድ የለባችሁም።”
ባል የሚሆኗችሁ ሌሎች ልጆች ከእንግዲህ የምወልድ ይመስላችኋልን?
ኑኃሚን በዚህ ጥያቄዋ ለእነርሱ የሚሆኑ ወንድ ልጆች ከዚህ ወድያ ልትወልድላቸው እንደማትችል ትናገራለች። “መቼስ ለእናንተ ባል መሆን የሚችሉ ሌሎች ወንድ ልጆች ከዚህ በኋላ መውለድ አልችልም።”
ባል እንዳላገባ እጅግ አርጅቻለሁ
ባል የማግባቱ ምክንያት በግልፅ ተጠቅሷል። “ሌሎች ወንድ ልጆች እንዳልወልድ”
ልጆች ብወልድ
“መፀነስ” ወይንም “ወንድ ልጆች መውለድ”
እስኪያድጉ ድረስ ትጠብቃላችሁን? እነርሱን በመጠበቅ እስከዚያ ሳታገቡ ትቈያላችሁን?
እነኚህ ምላሽ የሚሰጥላቸው ጥያቄዎች አይነት አይደሉም። “ታገብዋቸው ዘንድ እስኪያድጉ አትጠብቋቸውም። አሁን ማግባትን ትመርጣላችሁ”
ሁኔታው ከእናንተ ይልቅ ለእኔ እጅግ መራራ ነው
መራራነት የሃዘን እና የሰቆቃ መገለጫ ነው፤ በዚህም የሃዘንዋ መንስኤ ምን እንደሆነ ማወቁ አያዳግትም። “የእናንተ ባል አለመኖር እኔን ያሳዝነኛል።
የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ ተነሥቶአልና
“እጅ” የሚለው የእግዚአብሔርን ኃይል ወይንም ተፃዕኖ ያሳያል። “የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ወጥቶአልና።”
Ruth 1:14
ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ
ይህ የሚያመላክተው አምርረው እንዳለቀሱ እና ጮክ ብለው እንደተጣሩ ነው።
እነሆ የባልሽ ወንድም ሚስት
“ልብ በይ፤ ምክኛቱም አሁን የምልሽ ነገር እውነትና ጠቃሚ ነው፤ ባልንጀራሽ።”
ሩት ግን ልትለያት ስላልፈለገች ተጠመጠመችባት
“ሩት ኝ ተጠጋቻት።” “ሩት ልትለያት አልወደደችም።” ወይንም “ ሩት አልለያትም አለች።”
የባልሽ ወንድም ሚስት
“ባልንጀራሽ”

አማልክትዋ
ዓርፋ እና ሩት ልጆችዋን ከማግባትዋ በፊት የሞአባውያንን አማልክት ያመልኩ ነበር። በትዳራቸዋም ውስጥ ሳሉ የኑኃሚንን አምላክ ማምለክ ጀምረው ነበር።
Ruth 1:16
ወደ ምትሄጅበት
“ወደ ምትኖሪበት”
ሕዝብሽ ሕዝቤ
ሩት በዚህ የምታመላክተው የኑኃሚንን ህዝቦች ነው፤ እስራኤላውያንን። “የአገርሽን ሕዝቦች እንደ እራሴ ሕዝቦች እቆጥራለሁ።” ወይንም “ዘመዶችሽን እንደ ዘመዶቼ እቆጥራለሁ።”
በምትሞቺበት እሞታለሁ
ይህ ሩት እስከ ዕድሜዋ ፍፃሜ ከኑኃሚን ጋር በአንድ ቦታ እና ከተማ የመሆን ፍላጎቷን ያሳያል።
ብለይሽ እግዚአብሔር ይፍረድብኝ፤ ከዚህም የከፋ ያድርግብኝ።
ይህ የሚያመላክተው ሩት አደርጋለሁ ያለችውን ባታደርግ፤ እግዚአብሔር እንዲቀጣት እየጠየቀች እንደሆነ ነው። “እግዚአብሔር አይፍቀድ እንደማለት ነው።”
ከመናገር ዝም አለች
“ኑኃሚን ሩትን መጐትጐቷን ተወች”
Ruth 1:19
እንደ ደረሱም
“እንዲህ ሆነ።” ይህ የታሪኩ አዲስ ምዕራፍ መነሻ አመላካች ነው።
ከተማው በሙሉ
“ከተማው” የሚለው በዛ የሚኖሩ ሰዎችን በሙሉ ያመላክታል። “የከተማይቱ ሰዎች ሁሉ።”
ይህች ኑኃሚን ናትን?
ኑኃሚን በቤተልሔም ከኖረች በዙ ዓመታትን አስቆጥሯል በሎም ባሏ እና ወንድ ልጆቿ አብረዋ አልነበሩም፤ እናም በዛ የነበሩት ሴቶች ኑኃሚን ስለመሆኗ መጠራጠራቸውን የሚያመናክት አባባል ነው። እንደ እውነተኛ ጥያቄ ቁጠሩት።
ኑኃሚን ብላችሁ አትጥሩኝ
“ኑኃሚን” የሚለው ስም “የእኔ ደስታ” የሚል ትርጉም ነው ያለው። ኑኃሚንም ባሏን እና ልጆቿን ስላጣች፤ ስሟ ሕይወቷን እንደሚመጥን አይሰማትም።
ማራ
መራራ፤ የስሙ ትርጉም ሲሆን፤ ብዙውን ግዜ ይህ ስም ሲተረጎም እንደሚያወጣው ስም “ማራ” ተበሎ ይተረጎማል።
በሙላት ወጣሁ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ባዶዬን መለሰኝ
ኑኃሚን ከቤተልሔም ስትወጣ በልዋ እና ሁለት ወንዶች ልጆችዋ በሕይወት ነበሩ፤ ደስተኛም ነበረጭ ኑኃሚን ለባልዋ እና ሁለት ልጆችዋ ሞት ተጠያቂ የምታደርገው እግዚአብሔርን ነው። ወደ እስራኤልም ብቻዋን እንድትመለስ ያደረገው እርሱ ነው።
አስጨንቆኛል
“ፍርድን አሳልፎብኛል።”
አዋርዶኛል
መከራ አምጥቶብኛል
Ruth 1:22
ኑኃሚንም እና . . . ሩት
“ኑኃሚንም” የሚለው ቃል መደምደምያ የሆነውን መጨረሻ ላይ የሆነውን ነገር ጠቋሚ አያያዥ ቃል ያሳያል። በእናንተ ቋንቋ ይህንን ሊተካ የሚችን ቃል ተጠቀሙ።
የገብስም መኸር በደረሰ ግዜ
“የገብስ አዝመራ” የሚለውን ስንኝ ሊተካ በሚችል ቅል ሊተረጎም ይችላል። “የገብስ አዝመራ በሚሰበሰብበት ወቅት”

Chapter 2
Ruth 2:1
ለኑኃሚን ባል የሚዘመደው
ይህ ስንኝ ትረካው ከመቀጠሉ በፊት አዲስ መረጃን ያስተዋውቃል። በእናንተ ቋንቋ አዲስ መረጃን ወደ ምንባብ ለማስተዋወቅ የምትጠቀሙበት መንገድ ካለ እርሱን ተጠቀሙ።
ኃያል ሰው
“ባለጸጋ” ይህ የሚያሳየው ቦኤዝ ባለጸጋ እና በማህበረሰቡ በመልካም ዝና የታወቀ ሰው ነበረ።

ማዓባዊቷ ሩትም
እዚህ ጋር ትረካው ይቀጥላል። በቋንቋችሁም ታሪክ ከተቋረጠ በኋላ እንዴት እንደሚቀጥል ልብ በሉ።
ማዓባዊቷ
ሴቲቱ ከሞዓብ ስለመሆኗ መጠቆምያ ሌላኛው መንገድ ነው።
ቅርሚያ የሚያስቃርም
“ከእህሉ ዘለላ እንድቃርም” ወይንም “አጨዳ ላይ ከኋላ የተተወ የእህል ዘለላ ለማንሳት”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የእህል ዘለላ
“ዕራሱ” ወይንም “ክምችቱ” የእህሉን ዋና ፍሬ የያዘ “ዘለላ”።
በፊቱ ሞገስ የማገኘውን
“በፊቱ ሞገስ ማግኘት” የሚለው አባባል በሰው ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትን ያመላክታል። ሩት ፈቃድ ማግኘትን በአንድ ሰው ፊት ሞገስን እንደማግኘት አድርጋ ትናገራለች። በፊቱ፤ የሚለው አገላለፅ በመታየት፣ በአስተሳሰብ እና በአወሳሰን ተቀባይነት ማግኘትን ያመላክታል።
ልጄ
ሩት ኑኃሚንን እንደ እናቷ ነበር የምትንከባከባት። ብትርጉም ቋንቋው ልጅን የሚተካ ቃል መጠቀም ከተቻለ እርሱን መጠቀም ይቻላል።
Ruth 2:3
እንደአጋጣሚም
ሩት ስትቃርምበት የነበረው እርሻ የኑኃሚን ዘመድ የሁነው ቦኤዝ እርሻ መሆኑን አታውቅም ነበር።
እነሆም፣ ቦኤዝ
“እነሆም” የሚለው ቃል የቦኤዝ መምጣት በታሪኩ ላይ የሚጫወተውን ትልቅ ሚና አመላካች ነው። የዚህ ዓይነት ሚና የሚጫዉት ቃል በቋንቋችሁ ካለ እርሱን መጠቀም አስፈላጊ ነው።
ከቤተልሔም መጣ
እርሻው ከቤተልሔም ያልታወቀ ዕርቀት ላይ ይገኛል።
ይባርክህ
“መልካምን ነገር ይስጥህ” ወይንም “ደስተኛ ያርግህ”
Ruth 2:5
ይህች ወጣት ሴት የማን ናት?
ቦኤዝ እዚህ ጋር እየጠየቀ ያለው 1) ስለ ሩት ባል ወይንም 2) ስለሩት ወላጆች ውይንም ጠባቂዎች ነው።
አዛዥ
“ኃላፊነት ላይ ያለው” ወይንም “እየተቆጣጠረ ያለው”
በቤት
“በጎጆ” ወይንም “በመጠለያ” ይሄ በእርሻ መሃከል ከፀሃይ ጊዜያዊ መጠለያ ወይንም የመናፈሻ ጎጆ ነበር።
Ruth 2:8
ልጄ ሆይ፣ ትሰምያለሽ
የሄ እንደ ትዕዛዝ ቃል ልንመለከተው እንችላለን። “ስሚኝ ልጄ” ወይንም የምለውን ነገር ልብ በይ ልጄ።”
ልጄ
ይሄ በዕድሜ የሚያንስ ሰወን የመናገርያ መንገድ ነው። ሩት የቦኤዝ ልጅ አይደለችም። ይህ ቃል ሲተረጎም ልጅን ለማለት ተፈልጎ አለመሆኑን ልብ የበሉ።
ወደምያጭዱበት ስፍራ ተመልከቺ
መመልከት አንደን ነገር ማየትን እና አትክሁሮት መስጠትን ያመለክታል። “እርሻውን ብቻ ተመልከቺ” ወይንም “ለእርሻው ብቻ አትክሁሮት ስጪ።”
አዝዣለሁ
“አላዘዝኩምን?” የሚል ጥያቄ አዘል፤ ንግግሩ ማስረገጫ ቃል። “ጉበዛዚቱን አዝዣለሁ።”
ወንዶቹ . . . ልጃገረዶቹ
“ወጣት ወንድ ሰራተኞች . . . ወጣት ሴት ሰራተኞች።” ወንዶሽ የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ይውላል። ወይንም ጎበዛዚቱ ይለዋል፤ ይሄ በእርሻው ላይ በአጨዳ ላይ ያሉ ሰራተኞችን ያመላክታል።
እንዳያስቸግሩሽ
ለማለት የተፈለገው፤ 1) ወንዶቹ እንዳይጎዱሽ። 2) በዚህ እርሻ ከመቃረም እንዳይከለክሉሽ።
ጎበዛዚቱ ከቀዱት ወሃ
ከቀዱት ማለት ከውሃ ገድጓድ ካወጡት ወይንም ውሃ ከማጠራቀምያው ማድጋ ካወጡጥ
Ruth 2:10
በግንባርዋም ተደፍታ፣ በምድር ላይ ሰገደችለት
ይሄ የአክብሮት የፍርሃት ማሳያ ነው። ስላደረገላት ነገር በማመስገን ለቦኤዝ አክብሮትን እያሳየች ነው። የትህትናም ማሳያ ነው።
ባይተዋር የሆንኩት እኔ . . . በፊትህ ሞገዝ ለማግኘት የበቃሁት እንዴት ነው?
ሩት ከልብዋ ትክክለኛ ጥያቄአን እየጠየቀች ነው።
ባይተዋር
ሩት በግልዋ ለእስራኤል አምላክ ተሰጥታለች፤ ነገር ግን በውጪው የምትታወቀው እንደ “ሞዓባዊቷ” ነው።
ነግረውኛል
“ሰምቻለሁ” ይሄ በቀጥተኛ መልኩ፤ “ሰዎች ነግረውኛል” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።
ሕዝብ እንደመጣሽ
ቦኤዝ መጠቆም የፈለገው ሩት በማታውቀው የኑኃሚን መንደር፣ አገር እና ኃይማኖት መሃከል ለመኖር መምጣቷን ነው።
ዋጋሽን ይክፈልሽ
“ይስጥሽ” ወይንም “መልሶ ይክፈልሽ”
ስላደረገሽው
“ለሰራሽ” ለታማኝነትሽ፤ ከኑኃሚን ጋር በቤተልሄም ለመኖር ስለመምረጥሽ እና የኑኃሚንን አምላክ ስላመንሽ።
በእግዚአብሔር ዘንድ ደሞዝሽ ፍጹም ይሁን
ይሄ ቅኔአዊ አገላለፅ ሲሆን፤ ከዚህ በፊት ካለው ዓረፍተ ነገር ጋር ይመሳሰላል። “የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ብድራትሽን አትረፍርፎ ይመልስልሽ”
በክንፉ ጠላ ሥር ለመጠለል የመጣሽበት
ቦኤዝ እግዚአብሔር የሚተማመኑበትን እንዴት አድርጎ እንደሚከልል ለመግለፅ የሚጠቀመው ንፅፅር፤ ወፎች ጫጩቶቿን በክንፏ ጥላ ስር የምታደርግላቸውን እንክብካቤ ነው። “
Ruth 2:13
በዓይንህ ሞገስ ላግኝ
“ሞገስ ላግኝ” የሚለው ተቀባይነት ማግኘትን ወይንም በእርስዋ ደስተኛ መሆንን ያመላክታል። “በዓይኖችህ” የሚለው ምልከታን የሚያሳይ ሲሆን፤ ምልከታም የእርሱን ግምገማ ለማሳየት የሚጠቅም ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው።
ከባርያዎቹ እንደ አንዲቱ ሳልሆን
ይህ ቃል ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1) ሩት ከቦኤዝ አገልጋዮች መሃከል አንዷ አልነበረችም። 2) ሩት ከ ኑኃሚን ልጆች መሃከል አንዱን ማግባቷ በቤተልሔም ምንም ዓይነት ጥቅም እንደምያስገኝላት አላሰበችም።
Ruth 2:14
በምሳም ግዜ
ይህ የሚያሳየው በዕኩለ ቀን መሆኑን ነው።
እንጀራሽንም በሆምጣጤው አጥቅሽ
ይህ በዕርሻ የሚበላ ቀላል ምግብ ነው። ሰዎች መሬት ላይ የተነጠፈ ምንጣፍ ላይ ይቀመጣሉ፤ በመሐከልም የወይን ሆምጣጥጤ ይቀመጥና በተቆረሰ እንጀራ እያጠቀሱም ይመገባሉ።
የወርይ ሆምጣጤ
በእንጀራ እየተጠቀሰ የሚበላ። እስራኤላውያን ይህንን ወይን ይበልጥ ሆምጣጤ እንዲሆን ያፈሉት ነበር።
Ruth 2:15
ደግሞም ልትቃርም በተነሳች ግዜ፤ ቦኤዝ ጎበዛዝቱን
በዚህ ትዕዛዝ ዐውድ ውስጥ፣ ቦኤዝ ይህንን መመርያ ሲሰጥ ሩት ልጸማ በማትችልበት ዕርቀት ላይ እንደነበረ እንረዳለን።
ስትነሳም
“ስትቆምም”
በነዶው መካከል እንኳ
“እንኳ” የሚለው ቃል የሚያመላክተው “ከተለመደው በላይ እና ባሻገር” መሆኑን ነው። ቦኤዝ ሩት ከነዶው ዙርያ እንድትቃርም ይፈቅዱ ዘንድ ለሰራተኞቹ ተዕዛዝ ይሰጣል። ብዙውን ግዜ የሚቃርሙ ሰዎች ወደ ነዶው እንዲጠጉ አይፈቀድም።
ከታሰረው ነዶ ላይ ጥቂት ጠቂቱን እየመዘዛቹ
“ከነዶው አስቀርታችሁ ተዉላት” ወይንም “ከነዶው ላይ የ እህሉን ዘለላ ወስዳችሁ ተዉላት”
አታስቀይሟት
“አታሳፍሯት” ወይንም “አታዋርዷት”
Ruth 2:17
ወቃችው
የሚበላውን የእህሉን ክፍል ከገለባው ለየችው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የእህሉ ዘለላ
ይሄ የሚሰበሰበወሀል የሚበላው ፍሬ ክፍል ለው
አንድ የኢፍ መስፈሪያ
አንድ የኢፍ መስፈሪያ 22 ሊትር ያክላል። “22 ሊትር የሚያህል ገብስ”
ያንንም ይዛ ወደ ከተማው ሄደች
ሩት እህሉን ተሸክማ ወደቤቷ እንደሂአደች ያመላክታል።
አማቷ . . . አየች
“ኑኃሚን”
Ruth 2:19
ዛሬ የቃረምሽው ከየት ነው? የትስ ቦታ ስትሰሪ ዋልሽ?
ኑኃሚን የጠየቀችው ጥያቄ ተመሳሳይ ሲሆን፤ ሩት ስላሳለፈችው ቀን ለማወቅ እጅግ ጓጉታ እንደሆነ ያስታውቃል።
የተባረከ ይሁን
እግዚአብሔር ቦኤዝ ለሩት እና ለኑኃሚን ስላሳያቸው ቸርነት እንዲባርካቸው እየጠየቀች ነው።
በጎነቱን . . . ያልተወ
“ታማኝነቱን ያልተወ” ትርጉሙ ሊሆን የሚችለው 1) ቦኤዝ እንደቤተሰብ ለኑኃሚን ያለበትን ኃላፊነት አስታውሷል። 2)ኑኃሚን በቦኤዝ ውስጥ ስራን እየሰራ ያለውን እግዚአብሔር ማለቷ ነው። 3) እግዚአብሔር ለሕያዋን እና ለሙታን ታማኝነቱን መጠበቁን ላማመልከት ነው።
ለሕያዋን
“በሕይወት ላሉ ሰዎች ሁሉ።” ኑኃሚን እና ሩት “ሕያዋን” ነበሩ።
ለሙታን
የኑኃሚን ባል እና ልጆች “ሞተው” ነበር። “ሙታን” የሚለውን ቃል ሊተካ የሚችል ሌላ ተተኪ ቃል ካለ እርሱን መጠቀም ይቻላል።
ዘመዳችን ነው፤ የመቤዠት ግዴታ ካለባቸው
የሁለተኛው ስንኝ መጀመርያውን የደገመዋል ያሰፋዋልም። በዕብራውያን ይህ አትክሁሮት የመስጫ መንገድ ነው።
የመቤዠት . . . ዘመዶች
የሚቤዥ ዘመድ ማለት አንዲት መበለት የገንዘብ እና ሌላ ችግር ውስጥ እንዳትገባ አግብቶ አንድ ልጆች አብሯት ወልዶ የሚያድናት ማለት ነው።
Ruth 2:21
ደግሞም . . . ብሎኛል
“ደግሞ . . . አለኝ።” ይህ የሚያመላክተው ከዚህ በኋላ ቦኤዝ አለኝ የምትለው ነገር ጠቃሚ እንደሆነ ነው።
ከሰራተኞቼ አትለዪ
ቦኤዝ ሰራተኞቹ ሊሲጧት የሚችሉትን ጥበቃ ያመላክታል።
ብትወጪ
“መሄድ ስሻልሻል።”
ጉዳት ሊያገኝሽ
ለማለት ተፈልጎ የሚሆነው 1)ሌሎች ሰራኞች ሩትን ሊጎዷት ይችላሉ እጇንም ይዘው ሊደፍሯት ይችላሉ። 2)በሌሎች እርሻ የእርሻው ባለቤተስከ መኸር መጨረሻ ደረስ እንዳትቃርም ልትከለከል ትችላለጭ
Ruth 2:23
ተጠግታ
ሩትም እስከቀኑ መጨረሻ ድረስ በቦኤዝ እርሻ ስትሰራ ዋለች፤ ደንነቷም ተጠበቀ።
ከአማቷም ጋር ኖረች
ሩት ማታ ላይ ለመተኛት ወደ ኑኃሚን ቤት ትሄድ ነበር።

---

Chapter 3
Ruth 3:1
አማቷ
ኑኃሚን የሩት ሟች ባል እናት ናት
ልጄ
ሩት የኑኃኒንን ልጅ በማግባት ብሎም አብራት ወደ ቤተልሔም በመመለስ የኑኃሚን ልጅ ሆናለች።
የሚመችሽን ቤት እንድፈልግልሽ አይገባኝምን?
“መልካም እንዲሆንልሽ እረፍት አልፈልግልሽም?” ኑኃሚን ይሄንን ጥያቄ በመጠየቅ ያቀደችላትን ለመናገር ትጠቀምበታለች። “እረፍት የመታረጊበትን ቦታ ልፈልግልሽ ይገባኛል” ወይንም “ የሚንከባከብሽ ባል ልፈልግልሽ ይገባኛል።”
የምታርፊበት ቦታ
ትርጉሙ ሊሆን የሚችለው፤ 1) በቀጥታ የምትኖርበትን ቤት ማግኘት ወይንም 2) በማስጠጋት ረገድ የሚንከባከባት ባል ስለመፈለግ። ኑኃሚን ሁለቱንም ማለት ፈልጋ ሊሆንም ይችላል።
ከሴቶች ሠራተኞቹ ጋር አብረሽ የነበርሽበት
የዚህ ግልፅ ትርጉም ከሴቶቹ ጋር እየሰራች እንደነበረ ሊያሳይ ይገባል። “ከገረዶቹ ጋር የለበርሽበት።”
ዘመዳችን አይደለምን?
ኑኃሚን ከዚህ በፊት ለሩት የነገረቻትን ነገር እያስታወሰቻት ነው የሚሆነው። “እርሱ ዘመዳችን ነው።”
አሁንም
“ልብ በይ።” ከዚህ በኋላ የምትላትን ነገር እንድታስተውል እያመለከቻት ነው።
ያበራል
“በመንሽ ይበትናል” ይህ በንፍስ ድጋፍ ሰብሉን ከገለባው የመለየት ሂደት ነው።
Ruth 3:3
ሽቶ ተቀቢ
ይህ መልካም ማዓዛ ያለው ጣሳጭ ሻታ ያለው ዘይት ሊሆን ይችላል። በሁን ግዜ ሽቶ የሚባለው ማለት ነው።
ወደ አውድማው ውረጂ
ይህ የሚያሳየው ከከተማው ወጥቶ ወደሚወቃበት ቦታ ምሄድን ነው።
እግሩን ገልጠሽ
ይህ የሚያመላክተው የለበሰውን መደረብያ እግሩ ጋር መግለጥ እና እግሮቹ እንዲበርዳቸው ማድረግ የሚለውን ነው።
ተኚ
“ከእግሩ ሳር ተኚ”
ከዚያም የምታደርጊውን ራሱ ይነግርሻል
እዚህ ጋር ያለው የባህል ልማድ በእርግጥ ባይታወቅም፤ በባህላሸው የሚታወቅ እና ተቀባይነት ያለው ሴት ልጅ አንድ ወንድ እንዲያገባት ፈቃደኛ እንደሆነች የምታስታውቅበት መንገድ ነው። ቦኤዝም ልማዱ ገብቶት መቀበልም መተውም ይሽላል።
ይነግረሻል
“ሲነሳም፣ እርሱ እራሱ።”
ደስም ከተሰኘ
ይህ በልቡ የሆነ ነገርን ያሳያል። ሰክሮ ነበር ማለት አይደለም። “ሰውነቱም ደስ ከተሰኘ” ወይንም “ከረካ በኋላ”
በቀስታ
“በድብቅ” “ድምጽ ሳታሰማ ማንም ሰው ሳይሰማ”
እግሩንም ገልጣ
“መደረብያውን ከእግሩ ላይ ገልጣ”
ተኛች
“ከእግሩ ስር ተኛች”
Ruth 3:8
እንዲህም ሆነ
በትረካው ውስጥ የሆነን እንደ ክስተት ለማስታወቅ የሚጠቅም ስንኝ ነው። በቋንቋችሁ ይህንን የሚያደርግ ቃል ካለ እርሱን መጠቀምን አስቡ።
እኩለ ሌሊት ላይ
“መንፈቀ ሌሊትም በሆነ ግዜ”
ደነገጠ
“አንዳች ነገር አስደነገጠው”
ገልበጥ ሲልም
“ዘወርም አለ”
አንዲት ሴት እግርጌው ተኝታ አገኘ
ሲቲቱ ሩት ነበረች፤ ቦኤዝ ግን ጨልሞ ስለነበር ሊያውቃት/ሊለያት አልቻለም።
አገልጋይህ
ሩት ለቦኤዝ ምላሽ የሰጠችው በትህትና ነበር
ልብስህን ጣል አርግብኝ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ጋብቻን የሚያመላክት አባባል ነው።
ቅርብ የስጋ ዘመድ
ለዘመዶቹ ኃላፊነት ያለበት ልዩ ዘመድ
Ruth 3:10
ልጄ
ቦኤዝ ይህንን የተጠቀመው ታናሹ እንዳሆነች ሴት ለሩት ያለውን አክበሮት ነው።
ከዚህ በፊት ካደረግሽው ይልቅ ያሁኑ በጎነትሽ ይበልጣል
“ከበፊተኛው ይልቅ በመጨረሻው ግዜ ቸርነት አድርገሻል።”
በመጨረሻው ግዜ ቸርነት
ይህ ሩት ቦኤዝ እንዲያገባት ስለመጠየቁ ነው። የኑኃሚንን ዘመድ በማግባት ሩት ለኑኃሚን የሚያስፈልጋትን ነገር ማቅረብ ትችላለች በዚህም ቸርነትን ታደርጋለች።
ከዚህ በፊት
ይህ የሚያሳየው ሩት ከዚህ በፊትም ለአማቷ እየቃረመች እንደተንከባከበቻት እና አብራት በለቆየት ያደረገችውን ነው።
ፈልገሽ አልሄድሽምና
“አልተከተልሽምና” ሩት ኑኃሚንን ዘንግታ ከኑኃሚን ዘመዶች ውጪ ለማግባት ባል መፈለግ ስትችል ይህንን አላደረገችም።
Ruth 3:12
ከእኔ ይልቅ . . . ቅርብ የስጋ ዘመድ
መበለቲቷን መርዳት ቅርብ የሆነው ወንድ ዘመድ ኃላፊነት ነው።
ሊቤዥሽ ከፈለገ
ቦኤዝ እየተናገረ ያለው ቅርብ ከሆነ ከሞተው የሩት ባል የስጋ ዘመድ የሚጠበቀውን ሩትን የማግባት እና የቤተሰቡን ስም የዘ የመቀጠል ሃላፊነት ነው።
በሕያው እግዚአብሔር
“ሕያው እግዚአብሔርን” ይህ በዕብራይስጥ የተለመደ መሃላ ነው።
Ruth 3:14
እግርጌው ተኛች
ሩት ከቦኤዝ እግር ስር ተኛች። ቦኤዝ አላወቃትም፣ ምንም አላደረጉም።
ሰው ተለይቶ ሊታወቅ በማይችልበት ሰዓት
ይህን አገላለፅ ከበርሃን ጋር አያይዞ መግለፅ ይቻላል። “ገና ጨለማ ሳለ”
የደረብሽውን ልብስ
በትከሻ ላይ የመደረብ ልብስ
ስድስት መስፈሪያ ገብስ
ክብደቱ በውል ባይገለፅም። ቸር የሆነ ልገሳ እንደሆነ ይገመታል፣ ነገር ግን ሩት ልትሸከመው የምትችለው ያህል።
አሸከማት
የገብሱ መጠን ሩት በራስዋ ልታነሳው የምትችለው ያክል አልነበረም።
እርሱም ወደከተማይቱ ሄደ
“ወደ ከተማ ተመለሰች” አንዳንድ ቅጂዎች “ተመለሰ” ሲሉ ሌሎች ደግሞ “ተመለሰች” ይሉታል።
Ruth 3:16
የሄድሽበት ጉዳይ እንዴት ሆነ
ኑኃሚን በዚህ ጥያቄ ማለት የፈለገችውን በሌላ ቃል ግልጽ ማድረግ ይቻላል። “ልጄ ምን ሆነ?” ወይንም “ቦኤዝ ምን ዓይነት ምላሽ ሰጠሽ?”
ሰውየው ያደረገላትን ሁሉ
“ቦኤዝ ያደረገላትን ሁሉ”
ባዶ እጅሽን አትመለሺ
“ባዶ እጅሽን አትሂጂ” ወይንም “ምንም ሳትይዢ እንዳትሄጂ” ወይንም “የሆነ ነገር የመሄድሽን እርገት፣ እኛ ሁኚ
እልባት ካላገኘ
ይህ ማን የኑኃሚንን ንብረት እንደሚገዛ እና ሩትን እንደሚያገባ የሚወሰነውን ውሳኔ ያመላክታል።
በር
“የከተማይቱ በር” ወይንም “የቤተልሔም በር” ይህ ቅጥር ወዳላት የቤተልሔም ከተማ ዋና መግቢያ በር ነው። የማህበረሰባዊ ጉዳዩች ላይ ውይይት የሚደረግበትም ክፍት ቦታ በበሩ አቅራብያ ነበር።
የቅርብ ዘመድ
በሕይወት ያላ ቅርቡ የአቤሜሌክ ዘመድ
ከከተማይቱ ሽማግሌዎች
“የከተማይቱ መሪዎች”

Chapter 4
Ruth 4:3
ኑኃሚን መሬት ልትሸጥ ነው።
ለቅርብ ዘመድ፤ የቤተዘመዱን መሬት የመግዛት እና ቤተሰቡን የመንከባከብ ኃላፊነት አለበት። አሁን ደግሞ ይህ ሰው የኑኃሚንን መሬት መግዛት፤ ሩትን ማግባት እና ኑኃሚንን መንከባከብ ይኖርበታል።
ፊት
ይህ የሚደረገውን ስምምነት ህጋዊ እና ፍፁም ያደርገዋል።
መቤዠት
ይህ ማለት መሬቱን መግዛት እና በቤተሰቡ ውስጥ እንዲቆይ ማድረግ ማለት ነው።
ከአንተ ቀጥሎ . . . ስለ ሆንሁ
ቦኤዝ በቀጣይነት መሬቱን ሊቤዡ የሚችለው ዘመድ እርሲ ነበር።
Ruth 4:5
በምትገዛበት ዕለጥ. . . አለብህ
በዚህ የቦኤዝ አነጋገር ለሰውዬው መሬቱን ከመግዛት ጋር አብሮ ያለውን ኃላኢነት ይነግረዋል።
ከኑኃሚን
“ከኑኃሚን እጀ” ይህ የሚያመለክተው መሬቱ የኑኃሚን መሆኑን ነው።
ሩትን አብረህ መውሰድ
“ሩትንም ማግባት”
የሟቹን ሚስት . . . ሩት
“ሩት የአቤሜሌክ ልጅ መበለት”
የሟቹን ስም . . . ለማስጠራት
“ንብረቱን የሚወርስ ወንድ ልጅ እንዲኖራት እና የሞተውን ባሏን ስም እንዲያስቀጠል።”
የራሴን ርስት አደጋ ላይ ሊጥል
ሩት ለምትወልድለት ልጆች ደግሞ የራሱን ሃብት ማካፈል ስለሚኖርበት
የኔን የሜቤዠት ስልጣን አንተ ውሰደው
“አንተው እራስህ ተቤዠው” ወይንም “በእኔ ፈንታ አንተ ተቤዠው።”
Ruth 4:7
ልማድ ነበረ
ጸሃፊው ሩት በነበረችበት ዘመን በልውውጥ ግዜ የሚደረገውን ነገር እያብራራ ነው።
በጥንት ግዜም
“በጥንት ዘመን።” ይህ የሚያመላክተው መጸሐፉ በተጻፈበት እና ታሪኩ በተፈፀመበት ግዜ ልማዱ እንደተለወጠ ነው።
ጫማውን
“ነጠላ ጫማውን።”
ለባልንጀራውም
ይህ የሚያመላክተው ከእርሱ ጋር ስምምነት እያደረገ ያለውን ሰው ነው። በዚህ ግዜ ቅርብ የስጋ ዘመድ የተባለው ሰው ለቦኤዝ እንደማለት ነው።
Ruth 4:9
ለሽማግሌዎቹ እና ለህዝቡ ሁሉ
ይህ ማለት በስብሰባቸው ላይ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ማለት እንጂ በከተማው ያሉ ሰዎች ሁሉ ማለት አይደለም።
የአቤሜሌክን፣ የኬሌዎንን እና የመሓሎንን ንብረት በሙሉ
ይህ የሚያመላክተው የኑኃሚን ሟች ባል እና ልጆች ሃብት በሙላ ማለት ነው።
ከኑኃሚን
“ከኑኃሚን እጅ” ለንብረቱ ሁላ ኃላፉ የነበረችው እና የምትሰጠው ኑኃሚን ለመሆኗ ማሳያ ነው።
የሟቹን ስም በርስቱ ላይ ለማስጠትራት
ሩት የምትወልደው የመጀመርያ ልጅ ህጋዊ የመሓሎን ልጅ ተደርጎ ይቆጠራል። ቦኤዝም ከኑኃሚን የገዛውን መሬት ይወርሳል። “የሞተውን ሰውዬ መሬት የሚወርስ ወንድ ልጅ እንድሰጣት።”
የሟቹ ስም ከወንድሞቹ መካከል ከአገሩ ደጅ እንዳይጠፋ
መረሳት የሚታየው ቀድሞ ይኖሩ ከነበሩ ሰዎሽ ስም ዝርዝር እንደመቆረጥ ነው።

“በወንደሞቹ ትውልድ ዘንድ እና በከተማው እንዳይረሳ።”
ከአገሩ ደጅ
ይህ የሚያመላክተው የከተማውን ደጅ ሲሆን፤ በዚህም ቦታ የመሬት ባለቤትነትን በተመለከተ ውሳኔ የሚሰጥበት ቦታ ነው።
Ruth 4:11
በከተማይቱ በር የነበሩ ሁሉ
“ሌሎች በበር አቅራብያ ይሰበሰቡ የነበሩ ሁሉ።”
ወደ ቤትህ የምትገባውን
ይህ ምሳሌያዊም ቀጥተኛም ትርጉም አለው። ሩት ቦኤዝን ስታገባው ወደቤቱ ትገባለጭ ቤት መግባት ማለት ደግሞ ቤተሰቡን መቀላቀልንም ያመላክታል።
እንደ ራሔል እና ልያ
እነኚህ የያዕቆብ ሁለት ሚስቶች ሲሆኑ ስማቸውም ወደ እስራኤል ተቀይሯል።
የእስራኤልን ቤት እንደሰሩ
“ብዙ ልጆችን ወልደው የእስራኤል ሕዝብ ያደረጉ።”
በኤፍራታ የበረታ
ኤፍራታ ቦኤዝ በቤተንሔም የሚነኝበት ነገድ ነው።
ቤትህ እንደ
እግዚአብሔር ይሁዳን በልጁ በፋሬስ እጅጉን ባርኮት ነበር፤ ሰዎቹም በተመሳሳይ መንገድ ቦኤዝን በሩት ልጆች እንዲባርከው እግዚአብሔርን ጠየቁጥ
ትዕማር ለይሁዳ እንደወለደችው
ተዕማር መበለት ነበረች። ይሁዳም ከእርሷ ወንድ ልጅ ወለደ፤ የቤተሰቡም ስም በዛ ቀጠለ።
እግዚአብሔር . . . በሚሰጥህ ዘር
እግዚአብሔር በሩት በኩል ልጅ እንደሚሰጠው
Ruth 4:13
ቦኤዝ ሩትን ወሰዳት
“ቦኤዝ ሩትን አገባት” ወይንም “ቦኤዝ ሩትን እንደ ሚስት ወሰዳት”
ወደ እርሷ ገባ
ቦኤዝ ሩትን እንዳወቃት የሚያሳይ ነው። “ቦኤዝ ሩትን ደረሰባት”
ቅርብ የስጋ ዘመድ ያላሳጣሽ
አዎንታዊ ትርጉም ሊሰጠው ይችላል። “ዛሬ የቅርብ ዘመድ የሰጠሽ”
ስሙ ይግነን
ይሄ የሚያመላክተው የኑኃሚንን የልጅ ልጅ ዝና እና ባህርይ ነው።
ሕይወትሽን ያድሳታል
ኑኃሚን በልጅ ልጇ ምክኛት እንዴት በድጋሚ ደስታን እና ተስፋን እንደምትለማመድ ሊያሳይ ይችላል። “ድስታን በድጋሚ ወደ አንቺ የሚያመጣ” ወይንም “በድጋሚ እንደ ወጣት የሚያበረታሽ።”
በእርጅና ዘመንሽም ይጦርሻል
“ባረጀሽ ግዜ የሚንከባከብሽ።”
ከሰባት ወንድ ልጆች የምትበልጥ
በእስራኤላውያን “ሰባት” የፍፁምነት ቁጥር ነው። የኑኃሚን ወንድ ልጆች ሳይወልዱላት ሞቱ፤ ሩት ግን ከቦኤዝ የልጅ ልጅ ወለደችላት። “ከምንም ዓይነት ልጅ የምትሻል።”
Ruth 4:16
ኑኃሚን ልጁን ተቀብላ
ሉጁን እንደያዘችው እንጂ ከሩት እንደወሰደችባት መታየት የለበትም።
ታቀፈችው
“ከደረቷ አስጠግታ ያዘችው።”የሄ የፍቅር እና መውደድ ማሳያ ነው።”
ለኑኃሚን ወንድ ልጅ ተወለደላት
“ልጁ ለኑኃሚን እንደልጇ ነው።” ኑኃሚን ልጁን ባትወልደውም የእርሷ የልጅ ልጅ እንደሆነ የታወቀ ነበር።
የዳዊት አባት
“የንጉስ ዳዊት አባት።” ንጉስ የሚለው ያልተጠቀሰው የመጀመርያዎቹ አንባብያን ዳዊት ንጉስ እንደነበረ ስለሚረዱ ነው።
Ruth 4:18
የፋሬስ ቤተሰብ ትውልድ
“ከእርሱ የወጡት ትውልዶች።” ከፋሬስ የተለሳበት ምክንያት ከዚህ በፊት ፋሬስ የይሁዳ ልጅ መሆኑ ስለተገለጠ ነው፤ ከእርሱም ቀጥሎ የቤተሰቡን ዝርዝር መናገር የቀጥላል።

---

Chapter 1
1 Samuel 1:1
አርማቴም
ይህ የአንዲት ትንሽ መንደር ስም ሲሆን ከኢየሩሳሌም በሰሜን ምዕራብ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ የምትገኝ ሳትሆን አትቀርም። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፡- ተመልከት)
መሴፍ
ይህ የመሴፍ ትውልድ የሆኑ የሰዎች ስብስብ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፡- ተመልከት)
ሕልቃና … ኢያሬም … ኢሊዩ … መሴፍ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፡- ተመልከት)
ፍናና
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፡- ተመልከት)
1 Samuel 1:3
ያም ሰው
"ያም ሰው' የሚለው ሕልቃናን ያመለክታል።
ያህዌ
ይህ እርሱ በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ የገለጠው የእግዚአብሔር ስም ነው። ያህዌን በሚመለከት እንዴት እንዴት እንደሚተረጎም የትርጉም ቃላት ገጽን ተመልከት።
ዔሊ፣ አፍኒንና ፊንሐስ
እንዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ፡- ተመልከት)
1 Samuel 1:5
ሐና
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። ይህንን በ1 ሳሙኤል 1:2 እንዴት እንደምትተረጉም ተመልክት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት።)
ማኅፀንዋን ዘግቶ ነበር
"መካን አድርጓት ነበር' ወይም "ወደ እርግዝና እንዳትመጣ አግዷት ነበር'
ተፎካካሪዋ በጣም ታበሳጫት ነበር
ሌላኛዋ ሚስት (ጣውንትዋ) ሐናን ብዙ ጊዜ ታሳዝናትና ታዋርዳት ነበር
1 Samuel 1:7
ተፎካካሪዋ
የሕልቃና ሌላኛዋ ሚስት ፍናና ነች። ተፎካካሪ ማለት ሌላውን ሰው በመቃወም የሚወዳደር ሰው ማለት ነው። በዚህ ጉዳይ ሕልቃና አብልጦ እንዲወዳት ፍናና ሐናን በመቃወም ትወዳደራት ነበር።
ሐና ሆይ ለምን ታለቅሻለሽ? ለምንስ አትቀምሽም? ለምንስ ልብሽ ያዝንብሻል? እኔስ ከአሥር ልጆች አልሻልልሽምን?
አስፈላጊ ከሆነ አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች በገላጭ አባባል ሊተረጎሙ ይችላሉ። አት፡- "ሐና ማልቀስ የለብሽም። እኔ ለአንቺ ከአሥር ልጆች ይልቅ ስለምሻልሽ ልትበይና ልብሽም ደስ ሊለው ይገባል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)
ከአስር ልጆች ይልቅ
ሐና ምን ያህል ለእርሱ አስፈላጊ እንደሆነች አጽንዖት ለመስጠት ሕልቃና አጋኖ እየተናገረ ነው። አት፡- "ማንኛውም ልጅ ሊሆነው ከሚችለው በላይ' (ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)
1 Samuel 1:9
አጠቃላይ መረጃ
ሐና ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ጀመረች ዔሊም ተመለከታት።
በኋላም ሐና ተነሣች
ግልጽ ያልሆነ መረጃ በዚህ ስፍራ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ወይ የሐና ድንኳን ከመገናኛው ድንኳን ቀጥሎ ነበር ወይም ለመጸለይ ከድንኳንዋ ወደ መገናኛው ድንኳን ሄዳ ነበር። አት፡- "በኋላም ሐና ተነሣች ለመጸለይም ወደ እግዚአብሔር ቤት ሄደች።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ይልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ካህኑም ዔሊ
"ም' የሚለው ቃል እየተተረከ የዋናው ታሪክ ፍሰት መቋረጡን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። በዚህ ስፍራ ጸሐፊው በታሪኩ ስለሌላ አንድ ሰው ይነግረናል። ይህም


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሰው ካህኑ ዔሊ ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ፦ ተመልከት)

የእግዚአብሔር መቅደስ

"መቅደሱ' በእርግጥ ድንኳን ነበር ነገር ግን ሕዝቡ ያመልክበት የነበረ ስፍራ ስለ ነበር፣ በዚህ ስፍራ መቅደስ ብሎ መተረጎም ይበልጥ የተመረጠ ነው።

በልባዋ ትመረር ነበር

ምንም ልጆች ስለሌላትና የባሏ ሌላኛዋ ሚስቱ ፍናና ያለማቋረጥ ታዋርዳት ስለነበር ሐና እጅግ ትታወክና ታዝን ነበር። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትንና ያልተገለጸ መረጃን ተመልከት)

1 Samuel 1:11

አያያዥ አሳብ

ሐና ወደ እግዚአብሔር የምታደርገው ጸሎት ቀጠለ።

የባርያህን መከራ

መከራ የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽ ሐረግነት ሊተረጎም ይችላል። ይህ የሚከተሉትን ሊያመለክት ይችላል፦ 1) የሐናን ማርገዝ አለመቻል። አት፦ "ማርገዝ ካለመቻሌ የተነሣ ምን ያህል መከራ እየተቀልኩ ነው' ወይም 2) ፍናን እርሷን ሁል ጊዜ የምታዋርድበትን መንገድ። አት፦ "ያቺ ሴት ምን ያህል መከራ እያሳየችኝ እንደሆነ' (የነገር ስሞች ተመልከት)

አስበኝ

እግዚአብሔር ስለ ሐና እርምጃ እንዲወስድ የቀረበ የተለየ ልመና ነው። ሐና ላይ ምን እየሆነባት እንዳለ እግዚአብሔረ ያውቃል፣ አልረሳም።

ባርያህን አትርሳ

ይህ ሐረግ የሚለው ነገር "አስበኝ' ከሚለው ጋር ተመሣሣይ ነው ማለት ይቻላል። (አጓዳኝነት ተመልከት)

1 Samuel 1:12

ዔሊ ይመለከታት ነበር

ዔሊ ሊቀ ካህናት ነበር፣ በመሆኑም በእግዚአብሔር መገናኛ ድንኳን ነበረ በእርሷም ኃላፊነት ነበረበት። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ፦ ተመልከት)

1 Samuel 1:15

እኔስ ልባዋ ያዘነባት ሴት ነኝ

"እኔ እጅግ ያዘንኩ ሴት ነኝ።'

በእግዚአብሔር ፊት ነፍሴን አፈሰስሁ

ይህ "ጥልቅ የሆነ ስሜቴን ለእግዚአብሔር እየነገርኩ ነኝ' የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ባሪያህን እንደ ... አትቁጠር

ሐና ትህትናዋን ለማሳየት ስለ ራሷ በሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም ትናገራለች። በአንደኛ መደብ ተውላጠ ስም ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "ባርያህን እንደ ... አትቁጠረኝ' ወይም "አትቁጠረኝ' (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

ከጭንቀቴና ከብስጭቴ ብዛት እስከ አሁን ተናግሬአለሁ

እንደ 1:15፣ ሐዘንተኛ ልብ እንዳላት የተነገረ ሌላ የአባባል መንገድ ነው። ብዛት፣ ጭንቀት እና ብስጭት የሚሉት የነገር ስሞች በቅጽልነት እና በማሰሪያ አንቀጽነት ሊተረጎሙ ይችላሉ። አት፦ "እስካሁን የተናገርኩት በጣም ስላዘንኩና ተፎካካሪዬ እጅግ ስላበሳጨችኝ ነው።' (የነገር ስም ተመልከት)

ጭንቀትና ብስጭት

እነዚህ ሁለቱም ቃላት ተፎካካሪዋ ታበሳጫት ስለነበር ሐና ታዝንና ትናደድ ነበር የሚል ትርጉም አላቸው። (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

ጭንቀት

ፍናና ታስቆጣትና ታናድዳት ነበር።

ብስጭት

ፍናና ክፉ ስለሆነችባት ሐና ይሰማት የነበረውን የሐዘንና የውርደት ስሜት እያመለከተች ነው።

1 Samuel 1:17

ዔሊም ... መለሰላት

ዔሊ በማደሪያው ድንኳን የሚኖር ሊቀ ካህናት ነበር።

ባርያህ ... ታግኝ

ለሊቀ ካህናቱ ለዔሊ ያላትን አክብሮት ለማሳየት ሐና ራስዋን በሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም ትተራለች። ይህ በአንደኛ መደብ ተውላጠ ስም ሊተረጎም ይችላል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

በዓይንህ ፊት ሞገስ ላግኝ

በዚህ ስፍራ "ሞገስ ላግኝ' ማለት ተቀባይነት ማግኘት ወይም የእርሱ በእርሷ መደሰት የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። በዚህ ስፍራ ዓይን ማየትን የሚያመለክት ስም ሆኖ ጥቅም ላየ ውሏል፣ ማየት ደግሞ የአንድን ነገር ዋጋ መበየንን ወይም መወሰንን ይወክላል። (ምትክ ስምና ስዕላዊ ንግግርን ተመልከት)

በላችም፣ ፊትዋም

በዚህ ስፍራ ፊትዋ የሚወክለው ራሷን ሐናን ነው። አስፈላጊ ከሆነ ይህን የተለያየ ዐረፍተ ነገር ማድረግ ትችላለህ። አት፦ "በላች። እርሷ ነበረች' ወይም "በላች። እርሷ እንደ ነበረች ሰዎች ማየት ቻሉ።' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

1 Samuel 1:19

አሰባት

ሐና ይገጥማት የነበረውን ነገር እግዚአብሔር ያውቅ ነበር፣ አልዘነጋትም። በ1 ሳሙኤል 1:11 የሚገኙትን ተመሣሣይ ቃላት እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ሐና ጸነሰች

ሐና አረገዘች

1 Samuel 1:21

ቤቱ

ቤት የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ለማመልከት ጥቅም ላይ ይውል የነበር ስዕላዊ ስም ነው። አት፦ "ቤተሰቡ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ጡት እስኪተው

ወተት መጠጣት ማቆምና ጠንካራ ምግብ ብቻ መመገብ መጀመር

በእግዚአብሔር ፊት ይታይ ዘንድ፣ በዚያም ለዘላለም ይሆን ዘንድ

ሳሙኤል ከዔሊ ጋር በቤተ መቅደስ እንዲኖርና እንዲያገለግል እንደምታደርግ ሐና ለእግዚአብሔር ቃል ገብታ ነበር (1ሳሙ 1:11)።

ልጅዋን አጠባች

"ለልጅዋ ወተት ሰጠች'

1 Samuel 1:24

አፍ

አንድ አፍ 22 ሊትር ደረቅ ነገር ያህል ነው።

ጠርሙስ

ወይን የሚቀመጠው ከእንስሳት ቆዳ በተሰራ እቃ ነው (አቁማዳ)፣ በብርጭቆ ጠርሙስ አልነበረም።

1 Samuel 1:26

ጌታዬ ሆይ በሕያው ነፍስህ እምላለሁ!

በዚህ ስፍራ "በሕያው ነፍስህ' የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ሐና ታማኝና እውነተኛ እንደሆነች ያሳያል። አት፦ "ጌታዬ ሆይ፣ የምነግርህ ፈጽሞ እውነት ነው።' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

የለመንሁትን ልመናዬን ሰጥቶኛል

"ልመና' የሚለው ስም አንድ ነገር እንዲያደርግ ለሌላ ሰው የቀረበን ይፋ ጥያቄ ያመለክታል። በማሰሪያ አንቀጽነት ሊተረጎም ይችላል። "ልመናን መስጠት' የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ሰውዬው የጠየቀውን ማድረግ ማለት ነው። አት፦ "እንዲያደርግ አጥብቄ የጠየቅሁትን ለማድረግ ተስማማ' (የነገር ስምና ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል

በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

እግዚአብሔርን አመለከ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) እርሱ የሚለው ሕልቃናን ሊያመለክት ይችላል ወይም 2) እርሱ የሚለው ሁለቱንም ሕልቃናንና ቤተ ሰቡን የሚያመለክት ተለዋጭ ስም ነው። (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

---

## Chapter 2

1 Samuel 2:1

አጠቃላይ መረጃ

ሐና ለእግዚአብሔር መዝሙር ዘመረች። (አጓዳኝነት ተመልከት)

ልቤ ፈነደቀ

"ታላቅ ደስታ አለኝ'

በእግዚአብሔር

"ከእግዚአብሔር ማንነት የተነሣ' ወይም "እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ'
ቀንዴ ከፍ ከፍ አለ
ቀንድ የብርታት ምልክት ነው። አት፡- "አሁን ብርቱ ነኝ' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
1 Samuel 2:2
አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)
እንደ አምላካችን ያለ ዓለት የለም
ይህ እግዚአብሔር ብርቱና የታመነ ነው የሚለው ሌላኛው አባባል ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)
ዓለት
ይህ ዓለት ከበስተኋላው ለመደበቅ ወይም በላዩ ላይ ለመቆም እና አንድ ሰው ከጠላቶቹ በላይ እጅግ ከፍ ለማለት በቂ የሆነ ዓለት ነው።
1 Samuel 2:3
አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። ሌሎች ሰዎች እየሰሟት እንዳሉ አድርጋ ትናገራለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)
አትታበዩ
"በትዕቢት አትናገሩ'
ሥራዎች በእርሱ ይመዘናሉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት እርሱ የሰዎችን ሥራዎች ይመዝናል ወይም ሰዎች የሚያደርጉትን ለምን እንደሚያደርጉ ያውቃል (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
የኃያላን ሰዎች ቀስት ተሰብሮአል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡፡ 1) ቀስቶቹ ራሳቸው ተሰብረዋል ወይም 2) ቀስት የያዙ ሰዎች ከማድረግ ተከለከሉ። አት፡- "ኃያላን ቀስተኞች ሰዎች ከማድረግ ተከለከሉ'
የኃያላን ሰዎች ቀስት ተሰብሮአል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር የኃያላን ሰዎችን ቀስት ይሰብራል' ወይም "እግዚአብሔር ኃያላን ሰዎችን እንኳን ደካሞች ያደርጋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ደካሞች (የሚሰናከሉ) እንደ መታጠቂያ ኃይልን ታጥቀዋል
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ከእንግዲህ ወዲህ አይሰናከሉም ነገር ግን ኃይላቸው እንደ መታጠቂያ ጠብቆ አብሯቸው ይኖራል ማለት ነው። አት፡- "የሚሰናከሉትን ብርቱዎች ያደርጋቸዋል' (˜ይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
መታጠቂያ ... ታጥቀዋል
ይህ ለሥራ ለመዘጋጀት አንድን ነገር በወገብ ዙሪያ ስለማሰረ ጥቅም ላይ የሚውል አጠቃላይ ቃል ነው።
1 Samuel 2:5
አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)
ሰባት ወልዳለች
"ሰባት ልጆች ወልዳለች'
ደክማለች
ደካማ፣ ሐዘንተኛና ብቸኛ መሆን
1 Samuel 2:6
አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)
እግዚአብሔር ይገድላል፣ ያድናል ... ያወርዳል፣ያወጣል ... ድሀ ያደርጋል፣ ባለጠጋም ያደርጋል፣ ያዋርዳል፣ ከፍ ከፍ ያደርጋል
እግዚአብሔር ሁሉን ይቆጣጠራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
1 Samuel 2:8
አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)
ከመሬት ... ከጉድፍ
በማኅበረ ሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ጥቅም ላይ የሚውል ዘይቤአዊ ንግግር ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ችግረኞች
የሚያስፈልጓቸው ነገሮች የሌሏቸው።
1 Samuel 2:9
አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)
የታማኞቹን ሰዎች እግር ይጠብቃል
በዚህ ስፍራ "እግር' የሚለው ስም አንድ ሰው ለሚሄድበት መንገድ ጥቅም ላይ የሚውል ስዕላዊ ንግግር ነው፣ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው ሕይወቱን ለመኖር የወሰነበትን መንገድ የሚያመለክት ዘይቤአዊ ንግግር ነው። አት፡- "የተሳሳተ ውሳኔ እንዳይወስኑ ታማኞቹን ይጠብቃል' ወይም "ታማኞቹን ሰዎች ተገቢ ውሳኔ እንዲወስኑ ያስችላቸዋል፡' (ስዕላዊና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ኃጢአን ግን ዝም ብለው በጨለማ ይቀመጣሉ
በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ይገድላል በሚል ሊገለጽ የሚችለው የተነገረበት የአክብሮት መንገድ ነው። አት "እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን በጨለማ ዝምታ ውስጥ ያስቀምጣል' ወይም "እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን በጨለማና በሙታን የዝምታ ዓለም ውስጥ ያስቀምጣል' (የማያስደስትን ቃል በሌላ ቃል መጠቀም ተመልከት)
ኃጢአን በዝምታ እንዲቀመጡ ይደረጋሉ
"በዝምታ እንዲቀመጡ ይደረጋሉ' የሚሉት ቃላት "ዝም እንዲሉ ይደረጋሉ' ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ናቸው። (ፈሊጣዊ ንግግር እና አድራጊና ተደረጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
በኃይሉ
"ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሳ'
1 Samuel 2:10
አያያዥ አሳብ
ሐና ለእግዚአብሔር መዘመሯን ቀጥላለች። (አጓዳኝነት ተመልከት)
እግዚአብሔርን የሚቃወሙ ይደቅቃሉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር እርሱን የሚቃወሙትን ያደቅቃቸዋል።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ያደቅቃቸዋል
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር "ያሸንፋቸዋል' ማለት ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
እስከ ምድር ዳርቻ
በሁሉ ስፍራ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "ምድር ሁሉ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
የመሲሑን ቀንድ ከፍ ከፍ ያደርጋል
ቀንድ የጥንካሬ ምልክት ነው። ተመሣሣይ ቃላትን በ1ሳሙኤል 2፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፡- "የመረጠውን መሪ ከጠላቶቹ በላይ ብርቱ ያደርገዋል' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
መሲሑ
ይህ እግዝአብሔር ሰውዬውን በዘይት እንደቀባው አድርጎ የሚናገረው እግዚብሔር ለዓላማው ስለ መረጠውና ሥልጣን ስለ ሰጠው ነው። አት፡- "የቀባው' ወይም "የመረጠው' (ዘይቤአዊ ንግግርና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽን ተመልከት)
1 Samuel 2:12
አጠቃላይ መረጃ
ሰዎች እንስሳትን በመሥዋዕትነት ሲያቀርቡ በመጀመሪያ የእንስሳውን ስብ ማቃጠል፣ ሥጋውን መቀቀልና መብላት አለባቸው።
እግዚአብሔርን አያውቁም ነበር
"እግዚአብሔርን አይሰሙም ነበር' ወይም "እግዚአብሔርን አይታዘዙም ነበር'
ልማድ
ልማድ ሰዎች በቋሚነት የሚያከናውኑት ተግባር ነው።
ወደ ድስቱ ... ወይም ምንቸቱ ... ወይም አፍላሉ ... ወይም ቶፋው
እነዚህ ምግብ የሚበስልባቸው ዕቃዎች ናቸው። ቋንቋህ ለእነዚህ ዕቃዎች የተለያዩ ቃላት ከሌለው በአጠቃላይ መልኩ ሊገለጹ ይችላላል።አት፡- "በማናቸውም ሰዎች ሥጋ በሚያበስሉባቸው ውስጥ'
ድስት
ከሸክላ የተሠራ ማብሰያ
ምንቸት
የሸክላ ድስት
አፍላላ
ተለቅ ያለ ማብሰያ ድስት
ቶፋው
አነስተኛ ማብረጃ

1 Samuel 2:15

አጠቃላይ መረጃ

ሰዎች እንስሳትን በመሥዋዕትነት ሲያቀርቡ በመጀመሪያ የእንስሳውን ስብ ማቃጠል፣ ሥጋውን መቀቀልና መብላት አለባቸው።

የባሰ፣ በፊት

"ከዚያም እንኳን የባሰ ያደርጉ ነበር። በፊት'

ያቃጥሉት

በተጨባጭ የሚያቃጥለውን ሰው ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አት፡- "መሥዋዕት ያቀርብ የነበረው ሰው መስዋዕቱን ወደ ካህናቱ ያመጣዋል፣ ካህናቱም ያቃጥሉታል።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትንና ያልተገለጸ መረጃን ተመልከት)

አጠብስለት ዘንድ ለካህኑ ሥጋ ስጠኝ

"እንዲጠብሰው ለካህኑ እሰጠው ዘንድ ሥጋ ስጠኝ'

መጥበስ

እሳት ላይ ማብሰል

መቀቀል

በፈላ ውኃ ማብሰል

ጥሬ

ያልበሰለ

የእግዚአብሔርን ቁርባን ይንቁ ነበር

እግዚአብሔር ቁርባንን በሚመለከት የሰጠውን መመሪያ ወጣቶቹ አይወዱም ትኩረትም አይሰጡትም ነበር።

1 Samuel 2:20

ለእግዚአብሔር ካቀረበችው ልመና የተነሣ

ሐና እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣት ለመነችው፣ በመቅደስም እንዲያገለግል ልጁን ለመስጠት ቃል ገባች።

በእግዚአብሔር ፊት

ይህም እግዚአብሔር እርሱን በሚያይበትና ሳሙኤል ስለ እግዚአብሔር ሊማር በሚችልበት ቦታ ማለት ነው።

1 Samuel 2:22

ስለ ምን እንዲህ ያለ ነገር ታድርጋላችሁ?

ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በገላጭ አባባል ይችላል። አት፡- "እንዲህ ዓይነት ነገር ማድረጋችሁ በጣም አሳዛኝ ነው።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

1 Samuel 2:25

ስለ እርሱ የሚናገር ማን ነው?

ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በገላጭ አባባል ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "በእርግጥ ስለ እርሱ የሚናገር ማንም የለም።'(አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ስለ እርሱ የሚናገር

"ምሕረት እንዲያደርግለት እግዚአብሔርን የሚለምንለት'

የአባታቸው ድምጽ

በዚህ ስፍራ የአባት ድምጽ አባታን ይወክላል። አት፡- "አባታቸው' ወይም "አባታቸው ያላቸውን' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

1 Samuel 2:27

የእግዚአብሔር ሰው

ብዙ ጊዜ ይህ ሃረግ የእግዚአብሔር ነቢይ ማለት ነው። አት "ከእግዚአብሔር ቃላት የሚሰማና የሚናገር ሰው'

ቤት ... ራሴን አልገለጥሁምን

ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ እንደሚከተለው ሊተረጎም ይችላል። አት "ቤት ... ራሴን እንደገለጥሁ ልታውቅ ይገባሃል።'

ለአባትህ ቤት

"ቤት' የሚለው ስም በቤቱ ውስጥ ላሉ ሰዎች ምትክ ስም ነው። አት ፡- "የአባትህ ቤተሰብ' (ምትክ ስም ተመልከት)

አባትህ

አሮን

ወደ መሠዊያዬ ይወጣ ዕጣንም ያጥን ዘንድ

ይህ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረብን ያመለክታል።

ኤፉድንም በፊቴ ይለብስ ዘንድ

"ኤፉድ መልበስ' የሚሉት ቃላት ኤፉድ ለሚለብሱት ካህናት ሥራ ምትክ ስም ነው። አት፡- "ካህናት ያደርጉ ዘንድ ያዘዝኩትን ያደርግ ዘንድ።' (ምትክ ስም ተመልከት)

1 Samuel 2:29

አያያዥ አሳብ

የእግዚአብሔር ሰው ለዔል መናገሩን ቀጠለ

በማደሪያዬ ... መሥዋዕቴን ስለምን ናቃችሁ?

ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ የሚገሥጽ ነው። በገላጭ አባባልነት ሊተረጎም ይችላል። አት "በማደሪያዬ ... መሥዋዕቴን ልትንቁ አይገባችሁም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ማደሪያዬን

"ሕዝቤ ቁርባን ለእኔ የሚያቀርቡበት ቦታ'

ከእያንዳንዱ ቁርባን በተሻለው ራሳችሁን ለማወፈር

ከቁርባኑ የተሻለው ክፍል ለእግዚአብሔር ቁርባን ሆኖ መቃጠል ነበረበት፣ ካህናቱ ግን፡ ይበሉት ነበር።

የአባትህ ቤት

"ቤት' የሚለው ስም በቤቱ ውስጥ ላሉ ሰዎች ምትክ ስም ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 2፡27 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አት ፡- "የአባትህ ቤተሰብ' (ምትክ ስም ተመልከት)

በፊቴ ልትሄድ ይገባሃል

ይህ "ለእኔ በመታዘዝ ኑር' የሚል ትርጉም ያለው ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)

ይህን ማድረግ ከእኔ ይራቅ

"በእርግጥ ቤተሰብህ እኔን ለዘላለም እንዲያገለግለኝ አልፈቅድም'

የናቁኝ በጥቂቱ ይከብራሉ

"በጥቂቱ ይከበራሉ' የሚሉት ቃላት "እጅግ ይዋረዳሉ' ለሚለው የማያስደስት ቃል በምጸት የተተካ ቃል ነው። ይህ በአድራጊ አንቀጽ እንደሚከተለው ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "የሚንቁኝን በጥቂቱ አከብራለሁ' ወይም "የሚንቁኝን በእጅጉ አዋርዳለሁ' (ምጸት፣የማያስደስትን ቃል በሌላ ቃል መጠቀም እና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

1 Samuel 2:31

እይ

"የምናገረውን በጥንቃቄ አድምጥ' ወይም "የምናገረው ነገር በጣም አስፈላጊ ነው'

የአንተንና የአባትህን ቤት ብርታት እቆርጣለሁ

"... ብርታት እቆርጣለሁ' የሚለው የብርቱዎችንና የወጣቶችን ሞት በማይከብድ ቃል ለመተካት ጥቅም ላይ የዋለ ሳይሆን አይቀርም። "የአባትህ ቤት' የሚሉት ቃላት "ቤተሰብህ' ለሚለው ምትክ ናቸው። (የማያስደስትን ቃል በሌላ ቃል መጠቀም እና ምትክ ቃል ተመልከት)

ማንኛውም ሽማግሌ ቢሆን

"ማንኛውም ሽማግሌ ቢሆን' ወይም "ያረጀ ማንኛውም ሰው ቢሆን'

ዓይኖችህ እንዲይሠሩ ያደርጋል

"እይታህን እንድታጣ ያደርጋል' ወይም "ዓይነ ስውር እንድትሆን ያደርጋል'

1 Samuel 2:34

የታመነ ካህን አስነሳለሁ

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "አንድ ሰው ካህን አደርጋለሁ።' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ለራሴ (ለእኔ)

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "እንዲያገለግለኝ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በልቤና በነፍሴ ያለውን

"እንዲያደርግ የምፈልገውንና እንዲያደርግ የምነግረውን'

የታመነ ቤት እሠራለታለሁ

በዚህ ስፍራ "ቤት' የሚለው "ትውልድን' የሚመለክት ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "ሁሌም ሊቀ ካህን ሆኖ የሚያገለግል ትውልድ እንደሚኖረው ቃል እገባለሁ።'(ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 2:36

እርሱ

እግዚአብሔር የሚያስነሳው የታመነ ካህን

ቁራሽ እንጀራ እበላ ዘንድ

በዚህ ስፍራ "ቁራሽ እንጀራ' የሚለው "ምግብን' ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት፡- "እንዳች የምበላው ነገር እንዲኖረኝ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 3

1 Samuel 3:1

የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበር

እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ለሕዝብ አይናገርም ነበር

የእግዚአብሔር መብራት

ይህ በመገናኛው ድንኳን ቅዱስ ስፍራ በሁሉም ቀን እና ባዶ እስኪሆን ድረስ ሌሊቱን ሁሉ የሚነደው ሰባት መቅረዝ ያለው መብራት ነው።

የእግዚአብሔር መቅደስ

"መቅደሱ' በእርግጥ ድነኳን ነበር ነገር ግን ሕዝቡ ያመልክበት የነበረ ስፍራ ስለ ነበር፣ በዚህ ስፍራ መቅደስ ብሎ መተርጎም ይበልጥ የተመረጠ ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 1:9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

1 Samuel 3:5

ልጄ

ዔሊ የሳሙኤል እውነተኛ አባት አልነበረም። ዔሊ የሳሙኤል አባት እንደሆነ አድርጎ መናገሩ እንዳልተበሳጨ ነገር ግን ሳሙኤል ሊሰማው እንደሚገባ ለሳሙኤል ለማሳየት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)

1 Samuel 3:7

ምንም መልእክት ከእግዚአብሔር ዘንድ ገና አልተገለጠለትም ነበር

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እግዚአብሔር ምንም መልእክት መቼም አልገለጠለትም ነበር' ወይም "እግዚአብሔር ምንም መልእክት ፈጽሞ አልገለጠለትም ነበር።' (አድጊራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመለከት)

1 Samuel 3:9

አገልጋይህ

ሳሙኤል ለእግዚአብሔር አክበሮትን ለማሳየት ራሱን እንደ ሌላ ሰው አድርጎ ሳሙኤል ለእግዚአብሔር እንዲናገር ዔሊ ነገረው። አት፦ 'እኔ ነኝ' (ተውላጠ ስም ተመልከት)

1 Samuel 3:10

እግዚአብሔርም መጥቶ ቆመ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፦ 1)እግዚአብሔር በተጨባጭ ተገልጦአል በሳሙኤልም ፊት ቆሞአል 2)እግዚአብሔር መገኘቱን ለሳሙኤል እንዲታወቅ አድርጓል

አገልጋይህ

ሳሙኤል ለእግዚአብሔር አክበሮትን ለማሳየት ራሱን እንደ ሌላ ሰው አድርጎ ለእግዚአብሔር ተናገረ። አት፦ 'እኔ ነኝ' (ተውላጠ ስም ተመልከት)

የሰማውን ሁሉ ጆሮች ጭው የሚያደርግ

በዚህ ስፍራ "ጆሮች ጭው የሚያደርግ' የሚለው ስለ ሰሙት ነገር እያንዳንዳቸው ይደነግጣሉ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፦ "የሚሰማውን እያንዳንዱን ያስደነግጣል' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ጭው

በተለምዶ ከቅዝቃዜ የተነሳ ወይም ያንን የሰውነት ክፍል ሰዎች በእጃቸው ከመምታታቸው የተነሳ አንድ ሰው በትንሽ የተሳለ ነገር በቀላሉ ሲወጋ የሚሰማው የመወጋት ስሜት ዓይነት ነው።

1 Samuel 3:12

ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ

ይህ ሙሉነትን የሚያሳይ ስዕላዊ ንግግር ነው። አት፦ "ፈጽሞ ሁሉን ነገር' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

መርገምን በራሳቸው ላይ አመጡ

"የሚያደርጓቸውን እነዚያን ሰዎች እቀጣለሁ ብሎ እግዚአብሔር የተናገረባቸውን እነዚያን ነገሮች አደረጉ'

የዔሊ ቤት ኃጢአት በመሥዋዕትና በቁርባን ፈጽሞ አይሰረይም

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "የቤቱን ኃጢአት ሊያስተሰርይ የሚችል ማንም ሊያቀርበው የሚችል መስዋዕት ወይም ቁርባን የለም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የዔሊ ቤት ኃጢአት

በቤተሰቡ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የፈጸሙት ኃጢአት ነው

1 Samuel 3:15

የእግዚአብሔር ቤት

"ቤት' የተባለው በተጨባጭ "ድንኳን' ነበር፣ ነገር ግን በዚህ ስፍራ "ቤት' ብሎ መተርጎሙ እጅግ የተሻለ ነው።

ልጄ

ዔሊ የሳሙኤል እውነተኛ አባት አልነበረም። ዔሊ የሳሙኤል አባት እንደሆነ አድርጎ መናገሩ እንዳልተበሳጨ ነገር ግን ሳሙኤል ሊመልስለት እንደሚገባ ለሳሙኤል ለማሳየት ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 3:6 እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)

1 Samuel 3:17

የተናገረውን ቃል

"እግዚአብሔር የሰጠው መልእክት'

እግዚአብሔር እንዲህ ያድርግብህ እንዲህም ይጨምርብህ

ይህ ዔሊ ምን ያህል የምሩን እንደሆነ አጽንዖት የሚሰጥ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፦ "እግዚአብሔር እኔን እንደሚቀጣ በተናገረበት ተመሳሳይ መንገድ ይቅጣህ፣ ከዚያም በላይ እንኳን ይጨምርብህ።' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 3:19

ከቃሉም አንዳች በምድር ላይ አይወድቅም ነበር

በዚህ ስፍራ ያልተፈጸሙ መልእክቶች መሬት ላይ እንደወደቁ ተገልጸዋል። ይህ አዎንታዊ በሆነ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "የተነበያቸው ነገሮች ሁሉ ይፈጸሙ ነበር' (ዘይቤአዊ ንግግርና ሁኔታን በማንበብ ላይ የተመሠረተ ትንቢት ተመልከት)

እስራኤል ሁሉ

"በእስራኤል ያሉ ሰዎች ሁሉ'

ከዳን እስከ ቤርሳቤህ

"በምድሪቱ ክፍል ሁሉ' የሚልን አሳብ የሚያመለክት ስዕላዊ ንግግር ነው። አት፦ "ከምድሪቱ አንደኛው ጫፍ እስከ ሌላኛው ጫፍ' ወይም "ከሰሜን ጥግ ከዳን እስከ ደቡብ ጥግ እስከ ቤርሳብህ'

ሳሙኤል ተሾመ

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይቻላል። አት፦ "እግዚአብሔር ሳሙኤልን ሾመ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

---

Chapter 4

1 Samuel 4:1

አቤንኤዘር ... አፌቅ

እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ፦ ተመልከት)

እስራኤላውያን በፍልጥኤማውያን ተሸነፉ የተገደሉትም

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "ፍልስጥኤማውያን እስራኤላውያንን አሸነፉ ገደሏቸውም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

አራት ሺህ የሚያህሉ ሰዎችን

በዚህ ስፍራ አራት ሺህ የሚለው ቁጥር የሚጠጋጋ ቁጥር ነው። ከዚያ ቁጥር በጥቂት ከፍም ዝቅም ሊል ይችላል። የሚያህሉ የሚለው ቁርጥ ያለ ቁጥር እንዳልሆነ አመላካች ነው። አት፦ "አራት ሺህ የሚያህሉ ሰዎች' (ቁጥሮች ተመልከት)

1 Samuel 4:3

ሕዝቡ

ጦርነቱን ይዋጉ የነበሩ ወታደሮች

እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ፊት ስለ ምን መታን? ከጠላቶቻችንም ... እናምጣ

ሽማግሌዎቹ በእርግጥ እግዚአብሔር ለምን እንደመታቸው አላወቁም ነበር፣ ነገር ግን ከእነርሱ ጋር እንዲሆን የቃል ኪዳኑን ታቦታ በማምጣት እንዴት በእርግጠኛነት ሁለተኛ እንዳይደገም እደሚያደርጉ እንደሚያውቁ በስህተት አሰቡ።

በኪሩቤልም ላይ የሚቀመጠውን

ኪሩቤል በቃል ኪዳኑ ታቦት መክደኛ ላይ የሚገኙ እንደሆኑ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግሃል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች እግዚአብሔር በላይ በሰማይ በዙፋኑ እንደተቀመጠ ሁሉ የቃልኪዳኑ ታቦት አግዚአብሔር እግሩን የሚያኖርበት የእግሩ መረገጫ እንደሆነ በአብዛኛው ይናገራሉ። አት፦ "በቃል ኪዳኑ ታቦት ከኪሩቤል በላይ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ይልተደረገ መረጃ ተመልከት)

የት ነበሩ

በሴሎ ነበሩ

1 Samuel 4:5



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ሰፈር በገባ ጊዜ
"ሕዝቡ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ሰፈር ባመጡ ጊዜ' ትርጉሙን ግልጽ ለማድረግ ለመረዳት ምቹ የሆነ መረጃን ለመጨመር ጥቂት መግለጫዎች አስፈላጊ ናቸው። አት፡- "ሕዝቡ ከአፍኒንና ከፊንሐስ ጋር የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ተሸከሙ ወደ ሰፈርም አመጡት።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ሰፈር ገባ
"ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ሰፈር አመጡት'
1 Samuel 4:7
አሉ ... አሉ
"ለራሳቸው አሉ ... ለእርስ በእርሳቸው አሉ' ወይም "ለእርስ በእርሳቸው አሉ ... ለእርስ በእርሳቸው አሉ'ሁለተኛው ሐረግ ፍልስጥኤማውያን ለርስ በርሳቸው ያሉትን በግልጽ ያመለክታል። የመጀመሪያው ሐረግ ግን ወይ ያሰቡቱን ወይም ለእርስ በእርሳቸው ያሉትን ሊያመለክት ይችላል። ከተቻለ ለማን እንደተነገረ አታመልክት።
እግዚአብሔር መጥቶአል
ፍልስጥኤማውያን በብዙ አማልክት ያመልካሉ፣ ስለዚህ ከእነዚያ አማልክት መካከል አንዱ ወይም የማያመልኩት አንዱ ወደ ሰፈር እንደመጣ አምነዋል። ሌላኛው ሊሆን የሚችለው ትርጉም "ያህዌ መጥቶአል' ሲሉ የእስራኤልን አምላክ መደበኛ ስም እየጠሩ ነበር የሚለው ነው። ምክንያቱም 4፡8 ስለ "አማልክት' ይናገራል፣ አንዳንድ ትርጉሞች "እግዚአብሔሮች መጥተዋል' ይላሉ፣ ይኼውም፣ "አማልክት መጥተዋል' ማለት ነው። (ተውላጠ ስሞች ተመልከት)
ከእነዚህ ኃያላን አማልክት እጅ ማን ያድነናል?
ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ ጥልቅ ፍርሃት መግለጫ ነው። በገላጭ አባባል ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "ከእነዚአህ ኃያላን አማልክት እጅ ሊያድነን የሚችል ማንም የለም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)
እነዚህ አማልክት ...የመቱ አማልክት
ምክንያቱም በቁጥር 7 አምላክ (ወይም እግዚአብሔር) የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር ነው፣ ሊሆኑ ከሚችሉ ብዙ አማልክት መካከል አንዳቸውን ወይም የእስራኤልን አምላክ መደበኛ ስም በመጠቀም "ይህ ኃያል እግዚአብሔር ... የመታ እግዚአብሔር' በሚያመለክት መልኩ በርካታ ትርጉሞች "ይህ ኃያል አምላክ ... የመታ አምላክ' ይላሉ። (ተውላጠ ስሞች ተመልከት)
ሰዎች ሁኑ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "ብርቱዎች ሁኑ ተዋጉ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
1 Samuel 4:10
እስራኤላም ተሸነፉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። "እስራኤል' የሚለው የእስራኤልን ሠራዊት ያመለክታል። አት፡- "የእስራኤልን ሠራዊት አሸነፉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እና ተለዋጭ ስም ተመልከት)
የእግዚአብሔር ታቦት ተወሰደ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርንም ታቦት ወሰዱ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
1 Samuel 4:12
ልብሱን ቀድዶ በራሱም ላይ ትቢያ ነስንሶ
ይህ በእስራኤል ባሕል ጥልቅ ሐዘን መግለጫ መንገድ ነው።
ልቡ ተናውጦ ነበር
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ሲሆን በጣም ፈርቶ ወይም ስለ አንድ ነገር ታውኮ ነበር ማለት ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ከተማይቱ ሁሉ
ይህ በከተማይቱ ያሉ ሰዎች ሁሉ ለሚለው ምትክ ቃል ነው። (ምትክ ቃል ተመልከት)
1 Samuel 4:14
ሰውዬው
"የብንያም ሰው'
1 Samuel 4:16
ልጄ
ዔሊ የሌላኛው ሰው እውነተኛ አባት አልነበረም። ዔሊ የሰውዬው አባት እንደሆነ አድርጎ መናገሩ እንዳልተበሳጨ ነገር ግን ሊመልስለት እንደሚገባ ለሰውዬው ለማሳየት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)
እስራኤል ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ
ይህ ስለሆነው ነገር አጠቃላይ መግለጫ ነው። የቀሩት የሰውዬው ንግግሮች ዝርዝሩን ያቀርባሉ።
ደግሞ በሕዝቡ ዘንድ ... ሁለቱም ልጆችህ ...
"አሁን አንድ የባሰ ነገር እነግርሃለሁ ... አሁን አንድ የባሰ ነገር እነግርሃለሁ' ወይም "ሕዝቡ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ሁለቱ ልጆችህም'
የእግዚአብሔር ታቦት ተወሰደ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ወሰዱ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
1 Samuel 4:18
ሰውዬው በጠቀሰ ጊዜ
ብንያማዊው ሰው በጠቀሰ ጊዜ
በጠቀሰ
"በተናገረ'
አንገቱ ተሰብረ
ይህ በአድራጊ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ስለወደቀ አንገቱ ተሰበረ' ወይም "ሲወድቅ አንገቱን ሰበረ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
1 Samuel 4:19
ምራቱ
የዔሊ ምራት
የእግዚአብሔር ታቦት ተማረከ
ይህ በአድራጊ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ማረኩ (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ያሉአትን በልባዋ አላኖረችውም
"ላሉት ምንም ትኩረት አልሰጠችም' ወይም "የተሻለ እንዲሰማት ፈቀደች'
1 Samuel 4:21
ኤካቦድ
ስሙ ሐረግ ሲሆን ክብር የለም ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ የአንድ ሰው ስም ስለ ግለሰቡ፣ ስለ ቦታ ወይም ስለ ሚያመለክተው ነገር መረጃ ይሰጣል። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ፡- ተመልከት)
የእግዚአብሔር ታቦት ስለ ተማረከ ... የእግዚአብሔር ታቦት ተማርኳልና
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ስለማረኩ ... ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ከመማረካቸው የተነሣ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

---

Chapter 5
1 Samuel 5:1
አሁን
ቃሉ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ያሳያል። ቋንቋህ ተመሳሳይ ትርጉም የሚሰጥ ቃል ወይም ሐረግ ካለ በዚህ ስፍራ ልትጠቀም ትችላለህ።
የእግዚአብሔር ታቦት
ይህንን በ1ሳሙኤል 3፡3 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። ይህ በ1ሳሙኤል 4፡ 3-4 "የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦት' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው።
የዳጎን ቤት
ይህ የፍልስጥኤማውያንን አምላክ የዳጎንን ቤተ ጣዖት የሚያመለክት ነው።
እነሆም ዳጎን
"ዳጎንን ለማየት እጅግ በአድናቆት ነበሩ'
ዳጎን በምድር ላይ በግምባሩ ወድቆ ነበር
እግዚአብሔር በሌሊት ሐውልቱ በግምባሩ እንዲወድቅ እንዳደረገ አንባቢው ማስተዋል አለበት። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
1 Samuel 5:4
ዳጎን ወደቀ
እግዚአብሔር ዳጎንን እንዲወድቅ እንዳደረገ አንባባዊ ማስተዋል አለበት።
የዳጎን ራስ እጆቹም ተቆርጠው ወድቀው ነበር
እግዚአብሔር ጠላቱን እንዳሸነፈና የጠላቱን ራስና እጆች እንደቆረጠ ወታደር ዓይነት ነበር።
ስለዚህ፣ እስከ ዛሬ ድረስ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ጸሐፊው ከዋናው ታሪክ ወጣ ያለ ጥቂት የመነሻ ታሪክ መረጃ እየሰጠ ነው። (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ተመልከት)
እስከ ዛሬ ድረስ
በዚህ ስፍራ "ዛሬ' የሚለው ቃል የሚያመለከትው ጸሐፊው መጽሐፉን እስከሚጽፈበት ድረስ የነበረውን ጊዜ ነው።
1 Samuel 5:6
የእግዚአብሔርም እጅ በላያቸው ከበደች
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። "እግዚአብሔር በጽኑ ፈረደባቸው' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
እጢ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት
አዛጦንና ድንበሯን
የከተማይቱ ስም በከተማይቱ ለሚኖሩ ሰዎች ምትክ ስም ነው። "በአዛጦን የሚኖሩ ሰዎችና በአዛጦን ዙሪያ የሚኖሩ ሰዎች' (ምትክ ቃል ተመልከት)
የአዛጦን ሰዎች አወቁ
"የአዛጦን ሰዎች አስተዋሉ'
የእስራኤል አምላክ ታቦት
ይህንን በ1ሳሙኤል 3፡3 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። ይህ በ1ሳሙኤል 4፡3-4 "የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦት' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው።
1 Samuel 5:8
የእግዚአብሔር እጅ በእነርሱ ላይ ሆነች
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። እት፡- "እግዚአብሔር ቀጣቸው' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
በታናሹም በታላቁም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) እድሜን የሚያሳይ ስዕላዊ ንግግር ነው። እት፡- "በሁሉ እድሜ የሚገኙ ሰዎች' ወይም 2) ማኅበራዊ መደብን የሚያሳይ ስዕላዊ ንግግር ነው። እት፡- "ከድሆችና ደካሞች እንስቶ እስከ ባለጸጎቹና ብርቱዎቹ ሰዎች' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
እጢ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት 1ሳሙኤል 5፡6ን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።
1 Samuel 5:10
ጮኹ
ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
1 Samuel 5:11
የእስራኤል አምላክ ታቦት
ይህንን በ1ሳሙኤል 3፡3 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። ይህ በ1ሳሙኤል 4፡3-4 "የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦት' ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው።
የእስራኤል አምላክ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) የእስራኤልን አምላክ መደበኛ ስም እየጠሩ ነበር ወይም 2) "የእስራኤል አምላክ'፣ እስራኤል ከብዙ አማልክት መካከል አንዱን ያመልኩ እንደነበር ያምኑ ነበር። 1ሳሙኤል 5፡7 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
በከተማይቱ ሁሉ የሞት ድንጋጤ ነበር
"ለሞቱ ስለሆነ የከተማይቱ ሰዎች ሁሉ ፈርተው ነበር'
የእግዚአብሔር እጅ በዚያ እጅግ ከብዳ ነበረች
እጁ የእግዚብሔር ሰዎችን ስለ መቅጣተ ምትክ ቃል ነው። "እግዚአብሔር በዚያ ሰዎችን እጅግ እየቀጣ ነበር' (ምትክ ቃል ተመልከት)
ያልሞቱትም ሰዎች
ይህ በተጨባጭ ብዙ ሰዎች እንደሞቱ ያመላክታል። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
እጢ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት 1ሳሙኤል 5፡6ን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።
የከተማይቱ ጩኸት ወደ ሰማያት ወጣ
ከተማ የሚለው ቃል ለከተማው ሕዝብ ምትክ ቃል ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) "ወደ ሰማያት ወጣ' የሚለው ቃል "ታላቅ ነበር' ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። እት፡- "የከተማይቱ ሰዎች ድምፃቸውን በጣም ከፍ አድርገው ጮኹ' ወይም 2) "ሰማያት' የሚለው ቃል ለሕዝቡ አማልክት ምትክ ቃል ነው። እት፡- "የከተማይቱ ሕዝብ ወደ አማልክቶቻቸው ጮኹ' (ምትክ ቃልና ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

---

Chapter 6
1 Samuel 6:1
ካህናትና ጠንቋይችን
እነዚህ ዳጎንን የሚያመልኩ የአሕዛብ ካህናትና ጠንቋዮች ናቸው።
እንዴት እንደምንሰደው ንገሩን
ፍልስጥኤማውያን ከዚህ ወዲያ እግዚአብሔርን ሳያስቆጡ ታቦቱን እንዴት እንደሚያስወግዱት ማወቅ ፈለጉ።
1 Samuel 6:3
የእስራኤል አምላክ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) የእስራኤልን አምላክ መደበኛ ስም እየጠሩ ነበር ወይም 2) "የእስራኤል አምላክ'፣ እስራኤል ከብዙ አማልክት መካከል አንዱን ያመልኩ እንደነበር ያምኑ ነበር። 1ሳሙኤል 5፡7 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
የበደል መሥዋዕት መልሱለት እንጂ ባዶውን አትስደዱት
ባዶውን አትስደዱት የሚሉት ቃላት አንድን ነገር አጠንክሮ መናገሪያ መንገድ ናቸው። እት፡- "የበደል መሥዋዕት መስደድ አለባችሁ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ትፈወሳላችሁ
"ከእንግዲህ ወዲህ አትታመሙ'
እናንተ
እናንተ የሚለው ተውላጠ ስም የብዙ ቁጥር እንደመሆኑ ፍልስጥኤማውያንን ሁሉ ያመለክታል። (አንተ/እናንተ ተመልከት)
እጁ ከእናንተ አለመራቁ ስለምን ነው
በዚህ ስፍራ "እጅ' የሚለው ቃል እግዚአብሔር መከራን ለማምጣትና ለመቅጣት ያለውን ኃይል ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ምትክ ቃል ነው። እት፡- "መከራችሁን ለምን አላቀለላችሁም' (ምትክ ቃል ተመልከት)
እጢ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት 1ሳሙኤል 5፡6ን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።
አይጦች
ከአንድ በላይ አይጥ
1 Samuel 6:5
ምሳሌዎች
ምሳሌ እውነተኛው ነገር የሚመስል ነገር ነው።
እጢ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት 1ሳሙኤል 5፡6ን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።
የሚያወድሙ
"የሚያጠፉ'
የእስራኤል አምላክ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) የእስራኤልን አምላክ መደበኛ ስም እየጠሩ ነበር ወይም 2) "የእስራኤል አምላክ'፣ እስራኤል ከብዙ አማልክት መካከል አንዱን ያመልኩ እንደነበር ያምኑ ነበር። 1ሳሙኤል 5፡7 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
እጁን ከእናንተና ከአማልክቶቻችሁ፣ ከምድራችሁም ያነሳል
በዚህ ስፍራ "እጅ' የሚለው ቃል እግዚአብሔር መከራን ለማምጣትና ለመቅጣት ያለውን ኃይል ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ምትክ ቃል ነው። እት፡- "እናንተን፣ አማልክቶቻችሁንና ምድራችሁን መቅጣት ያቆማል' (ምትክ ቃል ተመልከት)
ግብጻውያንና ፈርዖንም ልባቸውን እንዳደነደኑ ልባችሁን ለምን ታደነድናላችሁ?
ካህናቱና ጠንቋዮቹ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በመጠቀም፣ እግዚአብሔርን መታዘዝ እምቢ ካሉ ምን ሊሆን እንደሚችል ትኩረት ሰጥተው እንዲያስቡ ፍልስጥኤማውያንን አጥብቀው እያስገነዘቡ ነው። (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
ልባችሁን ታደነድናላችሁ
ይህ ግትር መሆንና ለእግዚብሔር ፈቃድ አለመታዘዝ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ግብጻውያን ሕዝቡን አልሰደዱአቸውምን እነርሱም አልሄዱምን?

ይህ እግዚአብሔር በግብጻውያን ላይ መከራ ማምጣቱን እንዲያቆም በስተመጨረሻ ግብጻውያን እንዴት እስራኤላውያን ከግብጽ እንዲወጡ እንዳደረጉ ፍልስጥኤማውያንን ለማሳሳብ የተጠቀሙበት አሳብ ገላጭ ጥያቄ ነው። (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

1 Samuel 6:7

ሁለት የሚያጠቡ ላሞች

እስከ አሁን ወተት የሚጠጡ ጥጆች ያሉአቸው ሁለት ላሞች

ይሄድም ዘንድ ስደዱት

እንደተለመደው ሁለቱ ላሞች ወደ ጥጆቻቸው ወደ ቤት መመለስ ይኖርባቸው ነበር።

ወደ ቤትሳሚስ ከሄደ … እግዚአብሔር ነው

ላሞቹ ጥጆቻቸው በስተኋላ በፍልስጥኤማውያን ሰፈር እያሉ ወደ ቤትሳሚስ ለመንከራተት ይመርጣሉ ብሎ ማሰብ የማይመስል ነው።

1 Samuel 6:10

ሁለት የሚያጠቡ ላሞች

እስከ አሁን ወተት የሚጠጡ ጥጆች ያሉአቸው ሁለት ላሞች። 1ሳሙኤል 6:7ን እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

አይጦች

ይህን በ1ሳሙኤል 6:4 እንዳለው ተርጉም።

የእባጮቻቸውን ቅርጾች

"የእባጮቻቸውን ምሳሌዎች'

እጢ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት 1ሳሙኤል 5:6ን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

ላሞቹ ወደ ቤትሳሚስ አቅጣጫ አቅንተው ሄዱ

በአብዛኛው የሚያጠቡ ላሞች ወደ ጥጆቻቸው ይመለሳሉ፣ ነገር ግን እነዚህ ላሞች ወደ ቤትሳሚስ ሄዱ።

እምቧ እያሉ ሄዱ

እምቧ ማለት ላሞች በድምጻቸው የሚፈጥሩት ጩኸት ነው።

ወደ ቀኝም ወደ ግራም አላሉም

"ከአውራ ጎዳናው አልወጡም።' ይህ በአዎንታ እንደሚከተለው ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "በአውራው ጎዳና ዘለቁ' ወይም "ቀጥ ብለው ወደ ፊት ይሄዱ ነበር'

1 Samuel 6:13

አሁን

ቃሉ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ያሳያል። ቋንቋህ ተመሳሳይ ትርጉም የሚሰጥ ቃል ወይም ሐረግ ካለ በዚህ ስፍራ ልትጠቀም ትችላለህ።

የቤትሳሚስ ሰዎች

እስራኤላውያን ነበሩ።

ዓይናቸውን ከፍ አድርገው

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "አሻቅበው አዩ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 6:14

ታላቅ ድንጋይ በዚያ ነበር

ሰዎች ላሞቻቸውን ሲሰው ይህን ድንጋይ እንደ መሠዊያ ይጠቀሙበት ነበር።

ሌዋውያኑ የእግዚአብሔርን ታቦት አወረዱ

ይህ የሆነው ላሞቹን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ ሰረገላውን ለማንደንድ ከመፍለጣቸው በፊት ነው።

ከእርሱ ጋር የነበረውን የወርቅ ዕቃ ያለበትን

ሳጥኑ የአይጥና የእባጭ የወርቅ ምሳሌዎች ይዟል

1 Samuel 6:16

የፍልስጥኤማውያን አምስቱ አለቆች

"የፍልስጥኤማውያን አምስቱ ነገሥታት'

1 Samuel 6:17

እጢ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጎሞች፡- 1) ከቆዳ ስር የሚወጣ የሚያሰቃይ እባጭ ወይም 2) የአህያ ኪንታሮት 1ሳሙኤል 5:6ን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት።

አይጦች

ይህን በ1ሳሙኤል 6:4 እንዳለው ተርጉም።

የተመሸጉ ከተሞች

በውስጥ ያለውን ሕዝብ ከጠላቶቻቸው ጥቃት ለመጠበቅ በዙሪያቸው ትላልቅ ቅጥሮች የተገነቡላቸው ከተሞች ናቸው።

ታላቁም ድንጋይ እስከ ዛሬ ድረስ ምስክር ሆኖ አለ

ድንጋዩ ማየት እንደሚችል እንደ አንድ ግለሰብ ተጠቅሷል። አት፡- "ታላቁ ድንጋይ … እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ አለ፣ሰዎችም በላዩ ላይ የተፈጸመውን ያስታውሳሉ።' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

ኢያሱ

የሰው ስም (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ቤትሳሚሳውያን

ይህ ከቤትሳሚስ የሆነ ሰው የሚጠራበት ነው። አት፡- "ከቤትሳሚስ' (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

እስከ ዛሬ ድረስ

ጸሐፊው መጽሐፉን እስከጻፈበት ጊዜ ድረስ

1 Samuel 6:19

ወደ ታቦቱ ውስጥ ተመልክተዋል

ታቦቱ እጅግ ቅዱስ ስለ ነበር ማንም ወደ ውስጥ እንዲመለከት አልተፈቀደለትም። ታቦቱን እንኳን ለማየት የተፈቀደላቸው ካህናት ብቻ ናቸው።

50,070 ሰዎች

"አምሳ ሺህ እና ሰባ ሰዎች' (ቁጥሮች ተመልከት)

በዚህ ቅዱስ አምላክ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ማን ይችላል?

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ሕዝቡ ስለ እግዚብሔር ያደረበትን ፍርሃት ለመግለጽ አሳብ ገላጭ ጥያቄ ነው። አት፡- "ቅዱስ ስለሆነ እግዚአብሔርን መቋቋም የሚችል ማንም የለም!' ወይም 2) መረጃ ለማግኘት የቀረበ ጥያቄ ነው። በእግዚአብሔር ፊት መቆም የሚለው ሐረግ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ካህናትን የሚያመለክት ነው። ሕዝቡ እግዚአብሔር ታቦቱን እንዲይዝ የፈቀደለትን ካህን እፈለገ መሆኑን ያመለክታል። አት፡- "በመካከላችን ይህን ቅዱስ አምላክ፣ ያህዌን ማገልገልና ታቦቱን ማስተዳደር የሚችል ካህን አለን?' (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎችንና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ታቦቱ ከእኛ ወደ ማን ይሄዳል?

መረጃ ለማግኘት የቀረበ ጥያቄ ነው። ሁለተኛ እንዳይቀጣቸው እግዚአብሔርና ታቦቱ ወደ አንድ ቦታ እንዲሄዱ ሕዝቡ እንደፈለገ ይጠቁማል። አት፡- "እግዚአብሔር ሁለተኛ እንዳይቀጣን ይህን ታቦት ወዴት መስደድ እንችላለን?' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 6:21

ቂርያትይዓሪም

ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

---

Chapter 7

1 Samuel 7:1

ቂርያትይዓሪም

ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

አሚናዳብ … አልዓዛር

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

ሀያ ዓመታት

20 ዓመታት (ቁጥሮች ተመልከት)

1 Samuel 7:3

የእስራኤል ቤት ሁሉ

"ቤት' የሚለው ቃል በቤት ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎችና ትውልዳቸውን የሚያመለክት ምትክ ቃል ነው። አት፡- "የእስራኤል ትውልድ' ሁሉ ወይም "የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

በሙሉ ልባችሁ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ

በዚህ ስፍራ "በሙሉ ልብ' የሚለው ለአንድ ነገር ፈጽሞ መሰጠት የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "እግዚአብሔርን ብቻ ለማምለክና ለመታዘዝ ፈጽማችሁ የተሰጣችሁ ሁኑ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመለክት)

1 Samuel 7:5

እስራኤል ሁሉ

"የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ' ወይም "እስራኤላውያን ሁሉ'

ውኃ ቀድተው በእግዚአብሔር ፊት አፈሰሱ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ሕዝቡ የጾም ክፍል አድርገው የራሳቸውን ወኃ አልተጠቀሙም ወይም 2) ከምንጭ ወይም ከጉድጓድ ውኃ አገኙ፣ በኃጢታቸውም ለመጸጸታቸው እንደ ውጪያዊ ምልክት በምድር ላይ አፈሰሱት። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 7:7

የፍልስጥኤማውያን አለቆች በእስራኤል ላይ ጥቃት አደረሱ

በእስራኤል ላይ ጥቃት ያደረሱት ሠራዊቶቹ እንጂ አለቆቹ ራሳቸው እንዳልሆኑ በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አት፦ "የፍልስጥኤማውየን አለቆች ሠራዊታቸውን እየመሩ በእስራኤል ላይ ጥቃት አደረሱ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ከፍልስጥኤማውያን እጅ አድነን

እጅ የሰውዬውን ኃይል የሚያሳይ ምትክ ቃል ነው። አት፦ "ከፍልስጥኤማውያን ሠረዊት አድነን' ወይም "የፍልስጥኤማውያን ሠራዊት እንዳይጎዱን አድርግ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 7:9

የሚጠባ የበግ ጠቦት

እስካሁን ድረስ የእናቱን ወተት የሚጠጣ ጠቦት

ጮኸ

"ለእርዳታ ጮኸ'

እግዚአብሔር መለሰለት

"እንዲያደርግ ሳሙኤል የጠየቀውን እግዚአብሔር አደረገ'

1 Samuel 7:10

ሳሙኤልም ... በቤትካር

ይህ ጸሐፊው "እግዚአብሔር መለሰለት' ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ያብራራል (1ሳሙኤል 7፡9)

ግራ አጋባቸው

"ግራ መጋባት' የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ ጥቅም ላየ የዋለው ፍልስጥኤማውያን በግልጽ ማሰብ አልቻሉም ለማለት ነው። አት፦ "በግልጽ ማሰብ እንዳይችሉ አደረጋቸው' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በእስራኤልም ፊት ድል ተመቱ

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፦ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር በእስራኤል ፊት ድል መታቸው ወይም 2) እስራኤል ድል መታቸው (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ድል መምታት

ሰዎችን ድል መምታት ማለት ምንም ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ማሸነፍ ነው።

ቤትካር

ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

1 Samuel 7:12

ድንጋይ ወስዶ አኖረ

በዚያ ምድር እስራኤላውያንን ሌሎች ሕዝቦች አስፈላጊ ነገሮች ሲሆኑ ለእግዚአብሔር እርዳታ ማስታወሻ እንዲሆን ትልቅ ድንጋይ ያኖራሉ።

ምጽጳ ... ሼን

እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

1 Samuel 7:13

ፍልስጥኤማውያን ተገዙ

ጸሐፊው እንዴት ፍልስጥኤማውያን እንዴት በቁጥጥር ስር እንደዋሉ መናገሩን ፈጸመ። ቋንቋህ ትረካን የሚደመድምበት መንገድ ካለው እዚህ ጋ መጠቀም ትችላለህ።

ፍልስጥኤማውያን ተገዙ

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "እግዚብሔርን ፍልስጥኤማውያንን አስገዛቸው' ወይም "እግዚአብሔር ፍልስጥኤማውያንን ጉዳት ከማድረስ አገዳቸው' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ወደ እስራኤል ድንበር አልመጡም

ፍልስጥኤማውያን ሊያጠቁአቸው ወደ እስራኤል ድንበር አይገቡም ነበር።

የእግዚአብሔር እጅ በፍልስጥኤማውያን ላይ ነበረች

እጅ የሚለው ቃል ለኃይል ምትክ ቃል ነው። አት፦ "እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ላይ ኃይሉን ይጠቀም ነበር' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ከተሞች ... ከእስራኤል ለእስራኤል ተመለሱ

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) በዚህ ስፍራ "እስራኤል' የሚለው ቃል የሚያመለክትው የእስራኤልን "ምድር' ነው። ከእስራኤል ... እግዚአብሔር ከተሞችን ለእስራኤል ምድር መለሰ ወይም 2) "እስራኤል' የሚለው ቃል በዚያ ለሚኖረው ሕዝብ ምትክ ቃል ነው። አት፦ "ከእስራኤል ... የእስራኤል ሕዝብ ከተሞቹን የኔ ናቸው ማለት ቻለ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽና ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 7:15

ይዞር ነበር

በአስቸጋሪ ዙር ከቦታ ቦታ ይጓዝ ነበር

በሙግቶች ላይ ይወስን ነበር

ሙግት ማለት ክርክር ወይም በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚፈጠር አለመስማማት ነው።

---

Chapter 8

1 Samuel 8:1

ነውረኛ ትርፍ ያሳድዱ ነበር

ጸሐፊው ሰው ወይም እንስሳ ከሳሙኤል ልጆች አምልጠው ይሮጡ የነበር ይመስል፣ የሳሙኤልም ልጆች ሰውና እንስሳ በተጨባጭ ያሳድዱ የነበሩ ይመስል፣ ሕዝቡ ለሳሙኤል ልጆች ስለሚሰጠው ገንዘብ ይናገራል። (ምትክ ቃል ተመልከት)

ፍርድን ያጣምሙ ነበር

ክፉ ለሚያደርጉ በማድላት ይፈርዳሉ

1 Samuel 8:4

በመንገድህ አይሄዱም

አንድ ሰው የሚኖርበት መንገድ እንደ ጎዳና ተገልጾአል። አት፦ አንተ የምታደርጋቸውን ነገሮች አያደርጉም ወይም አንተ ታደርገው እንደ ነበር ጽድቅ የሆነውን ነገር አያደርጉም ነበር። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

እንደ ሕዝቦች ሁሉ የሚፈርድልን ንጉሥ ሹምልን

ሊሆኑ የሚችል ትርጉሞች፣ 1) "እንዲፈርድልን የሕዝቦችን ሁሉ ነገሥታት የሚመስል ንጉሥ ሹምልን' ወይም 2) "የሕዝቦች ነገሥታት በሚፈርዱላቸው መንግድ የሚፈርድልን ንጉሥ ሹምልን'

የሚፈርድልን ንጉሥ ሹምልን

አለቆቹ በስህተት ንጉሡና ከእርሱም በኋላ ልጆቹ በጽድቅ ይገዛሉ ብለው አመኑ።

1 Samuel 8:6

የሚፈርድልን ንጉሥ ሥጠን ... ነገር ግን ሳሙኤልን አስከፋው

ሕዝቡ ምግባረ ብልሹ የሆኑ ልጆቹን አስወግዶ ሌሎች የታመኑ ፈራጆችን እንዲሾምላቸው ሳይሆን ሌሎች አገራት እንዳላቸው ዓይነት በላያቸው ላይ የሚገዛ ንጉሥ በመፈለጋቸው ሳሙኤል ደስተኛ አልሆነም።

የሕዝቡን ቃል ስማ

ቢዘህ ስፍራ "ቃል' የሕዝቡን ፈቃድና ፍላጎት የሚያመለክት ምትክ ቃል ነው። (ምትክ ቃል ተመልከት)

ነገር ግን የተቃወሙት እኔ ነው

ሕዝቡ የተቃወሙት ምግባረ ብልሹ የሆኑትን ፈራጆች ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ንጉሣቸው እንዳይሆን እየተቃወሙት እንደ ነበር እግዚአብሔር ያውቅ ነበር።

1 Samuel 8:8

ከግብጽ አወጣኋቸው

ይህ ከብዙ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ነጻ ማውጣቱን ያመለክታል።

አሁን ቃላቸውን ስማ

"አሁን እንድታደርግ የሚጠይቁህን አድርግ'

በጽኑ አስጠንቅቃቸው

ስታስጠነቅቃቸው የምር አድርገው

1 Samuel 8:10

ወጉ ይህ ነው ... ይወስዳል

የንጉሥ ወግ መውሰድ ይሆናል። ይህ የሚወስዳቸውን ነገሮች ዝርዝር ይጀምራል።

በእናንተ ላይ የሚነግሠው የንጉሥ ወግ ይህ ነው

ወግ የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽነት ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "በላያችሁ የሚነግሠው ንጉሥ የሚያደርገው እንዲህ ነው' ወይም "በላያችሁ የሚነግሠው ንግሥ የሚሠራው እንዲህ ነው' (የነገር ስም ተመልከት)

ሰረገለኞቹ ያደርጋቸዋል
ወደ ጦርነት ሰረጋላ ያስነዳቸዋል
ፈረሰኞቹ ይሆናሉ
ወደ ጦርነት ፈረሶችን ይጋልባሉ
1 Samuel 8:13
አያያዥ አሳቦች
ሳሙኤል ንጉሥ የሚሰዳቸውን ነገሮች መናገሩን ቀጠለ።
ሽቶ ቀማሚዎች
ሰውነቱን የሚቀባው መልካም ሽታ ያለው ዘይት መሥራት
የወይራ እርሻ
የወይራ ዛፍ ማሳ
የእህላቸሁን አንድ አሥረኛ
እህላቸውን በአሥር እኩል ቦታ መክፈልና ከእነዚያ ክፍሎች አንዱን ለንጉሥ አለቆችና አገልጋዮች መስጠት ይኖርባቸዋል። (ክፍልፋይ ተመልከት)
የወይናችሁን አንድ አሥረኛ
በወይን እርሻቸው ያመረቱትን በአሥር እኩል ቦታ መክፈልና ከእነዚያ ክፍሎች አንዱን ለንጉሥ አለቆችና አገልጋዮች መስጠት ይኖርባቸዋል። (ክፍልፋይ ተመልከት)
አለቆች
እነዚህ የንጉሡ ሠራዊት አዛዦች ናቸው።
1 Samuel 8:16
አያያዥ አሳቦች
ሳሙኤል ንጉሥ የሚሰዳቸውን ነገሮች መናገሩን ቀጠለ።
የመንጋችሁን አንድ አሥረኛ
መንጋቸውን በአሥር እኩል ቦታ መክፈልና ከእነዚያ ክፍሎች አንዱን ለንጉሥ አለቆችና አገልጋዮች መስጠት ይኖርባቸዋል። አንድ አሥረኛን በ1ሳሙኤል 8:15 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት (ክፍልፋዮች ተመልከት)
ባሮቹ ትሆናላችሁ
"ባሮቹ እንደሆናችሁ ይሰማችኋል'
ትጮኻላችሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦1)ከንጉሡ እንዲያድናቸው ሕዝቡ እግዚአብሔርን ይጠይቃሉ 2)የከፋ አገዛዙን እንዲያቆም ሕዝቡ ንጉሡን ይጠይቃሉ
1 Samuel 8:21
ለእግዚአብሔር ጆሮች ደገማቸው
በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ጆሮች የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል። ሕዝቡ ያሉትን ሁሉ በመድገም ሳሙኤል ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። አት፦ ለእግዚአብሔር ደገማቸው (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
ቃላቸውን ስማ
"ቃላቸውን' የሚለው ምትክ ቃል የሕዝቡን ፈቃድ ያመለክታል። አት፦ "ሕዝቡን ታዘዝ' (ምትክ ቃል ተመልከት)
አንግሥላቸው
አንድን ሰው በላያቸው ላይ አንግሥላቸው። አንድን ሰው ንጉሥ ማድረግን በሚመለከት የተለመደ ቃል በቋንቋህ ካለ ተጠቀም።
ወደ ከተማው ሂድ
"ወደ ቤት'

---

Chapter 9
1 Samuel 9:1
አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ቁጥሮች ጸሐፊው የሚሰጠው የታሪካዊ ዳራ መረጃ ለአንባቢ መናገር የሚቻልበት ሌላ መንገድ በቋንቋህ ካለ እዚህ ጋ መጠቀም ትችላለህ። (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ተመልከት)
ተሰሚነት ያለው ሰው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ባላጠጋ ሰው ነበር 2) የመሣፍንት ዘር ነበር 3) ኃያልና ኀበዝ ሰው ነበር
ቂስ ... አቢኤል ... ጽሮር ... ብኮራት ... አፌቅ
እነዚህ የሳኦል የትውልድ ሐረግ ሰዎች ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
ብንያማዊ
ብንያማዊ ከብንያም ነገድ የሆነ ሰው ነው
መልከ መልካም
ሲታይ መልካም የሆነ
ከሕዝቡም ሁሉ ይልቅ ከትከሻውና ከዚያም በላይ ቁመቱ ዘለግ ያለ ነበረ
በእስራኤል የነበሩ ሌሎች ረጃጅም ሰዎች ትከሻው ጋ አይደርሱም ነበር።
1 Samuel 9:3
አሁን
ጸሐፊው የታሪካዊ ዳራ መረጃ መስጠቱን ጨርሶ (1ሳሙኤል 9፡1-2) የታሪኩን አዲስ ዋና ክፍል ይጀምራል።
ተነሣና ሂድ
"እያደረግህ ያለውን አቁምና ሂድ'
ተራራማው የኤፍሬም አገር ... የሻሊሻ ምድር ... የሻዕሊ ምድር ... የብንያም ምድር
እነዚህ ሁሉ በእስራኤል ውስጥ ያሉ አካባቢዎች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
አላገኙአቸውም ... አልነበሩም ... አላገኙአቸውምም
ሁሉም አህዮችን የሚያመለክቱ ናቸው።
1 Samuel 9:5
የጹፍ ምድር
ይህ ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን የሚገኝ በእስራኤል ውስጥ ያለ አካባቢ ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
የእግዚአብሔር ሰው
ይህ ሐረግ በአብዛኛው የእግዚአብሔር ነቢይ ማለት ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 2፡ 27 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፦ "ከእግዚአብሔር ቃል ሰምቶ የሚናገር ሰው'
በጉዟችን የትኛውን መንገድ መሄድ እንዳለብን
"አህዮቹን ለማግኘት የትኛውን መንገድ መሄድ አለብን?'
1 Samuel 9:7
ለሰውዬው ምን እናመጣለታለን
ሥጦታ መሥጠት ለእግዚአብሔር ሰው የአክብሮት ምልክት ነው።
የእግዚአብሔር ሰው
ይህ ሐረግ በአብዛኛው የእግዚአብሔር ነቢይ ማለት ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 2፡ 27 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፦ "ከእግዚአብሔር ቃል ሰምቶ የሚናገር ሰው'
የሰቅል ሩብ
"የሰቅል አንድ አራተኛ'። ሰቅል በብሉይ ኪዳን አገልግሎት ይሰጥ የነበረ የገንዘብ ዓይነት ነው። (የመጽሐፍ ቅዱስ ገንዘቦችና ክፍልፋዮች ተመልከት)
1 Samuel 9:9
ቀድሞ በእስራኤል ... ባለ ራእይ
ይህ በዕብራዊ ጸሐፊ የተጨመረ ባሕላዊ መረጃ ነው። ይህንን መረጃ በዚህ ስፍራ ማስቀመጥ በቋንቋህ የተለመደ ካልሆነ ወደ ቁጥር 11 መጨረሻ ሊወሰድ ይችላል። (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ተመልከት)
ዛሬ ነቢይ የሚባለው ቀድሞ ባለ ራእይ ይባል ነበር
"ባለ ራእይ የሚለው ዛሬ ነቢይ ለሚባለው የጥንት መጠሪያ ነበር።'
1 Samuel 9:12
ሕዝቡ ዛሬ መሥዋዕት ያቀርባሉ
ይህ በመገናኛው ድንኳን መከናወን ያለበት የኃጢአት መሥዋዕት ሳይሆን፣ የበዓል ወይም የበኩራት መሥዋዕቶችን የሚመለክት ይመስላል።
1 Samuel 9:14
ወደ ኮረብታው መስገጃ መውጣት
ይህ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትና ቁርባን ለማቅረብ ሕዝቡ ቅዱስ ቦታ ብለው የሰየሙት ስፍራ ነው። ጸሐፊው በከተማይቱ ዙሪያ ካለው ቅጥር ውጪ ይገኝ እንደ ነበር ይጽፋል።
1 Samuel 9:15
አጠቃላይ መረጃ
ጸሐፊው ታሪኩን መናገር ያቆምና አንባቢው በመቀጠል የሚሆነውን እንዲረዳ የታሪካዊ ዳራ መረጃ ይሰጣል። (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ተመልከት)
ልዑል ይሆን ዘንድ ትቀባዋለህ
በዚህ ስፍራ ልዑል የሚለው ቃል ንጉሥ በሚለው ፈንታ ጥቅም ላይ ውሏል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን እግዚአብሔር የመረጠው ሰው ይህ ነው፡፡ (የማያስደስትን ቃል በሌላ ቃል መጠቀም ተመልከት)

የብንያም ምድር

"ከብንያም ነገድ የሆኑ ሰዎች የሚኖሩበት ምድር'

ከፍልስጥኤማውያን እጅ

በዚህ ስፍራ እጅ የሚለው ቃል ቁጥጥር ለሚለው ምትክ ቃል ነው፡፡ አት፡- "ከፍልስጥኤማውያን ቁጥጥር' ወይም "ከእንግዲህ ወዲያ ፍልስጥኤማውያን አይቆጣጠሩአቸውም'

ሕዝቤን በሐዘኔታ ተመልክቼአለሁና

"ሕዝቤ መከራ እያዩ ናቸው እኔም ልረዳቸው እፈልጋለሁ'

1 Samuel 9:17

እግዚአብሔር አለው

"እግዚአብሔር ሳሙኤልን አለው'

ባለ ራእዩ

"የእግዚአብሔር ነቢይ'

1 Samuel 9:20

የእስራኤል ምኞት ለማን ነው? ለአንተና ለአባትህ ቤት አይደለምን?

እነዚህ ጥያቄዎች ሳኦል እስራኤል የሚፈልጉት እግዚአብሔር ንጉሥ እንዲሆን የወደደው ሰው ለመሆኑ የጥልቅ መረዳት ማሳያ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹ በገላጭ አባባል ሊገለጹ ይችላሉ፡፡ አት፡- "የእስራኤል ምኞት ሁሉ ያረፈው በአንተ ላይ እንደሆነ ልታውቅ ይገባሃል፡፡ ዓይናቸውን በአንተና በአባትህ ቤት ላይ ጥለዋል፡፡' (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)

እኔ ከእስራኤል … ብንያማዊ አይደለሁምን? ከብኒያም ነገድ … አይደለሁምን? እንዲህስ ያለውን ነገር ለምን ነገርኸኝ?

ብንያም በእስራኤል ትንሹ ነገድና ሌሎች እስራኤላውያን እንደማይጠቅም ነገድ የሚቆጥሩት ስለሆነ ሳኦል ግርምቱን እየገለጠ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ ሳኦል አባል የሆነበትን ጎሳ ብንያማውያን እንደማይጠቅም ይቆጥሩት ነበር፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በገላጭ አባባል ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ አት፡- እኔ ከነገዶች ሁሉ አስፈላጊነቱ የመጨረሻ ዝቅተኛ ከሆነው ከብንያም ነገድ ነኝ፡፡ ጎሳዬም በነገዳችን አስፈላጊነቱ የመጨረሻ ዝቅተኛ ጎሳ ነው፡፡ የእስራኤል ሕዝብ እኔንና ቤተሰቤን አስፈላጊ ነገር እንድናደርግ እንደሚፈልጉን ለምን እንደምትነግረኝ ልረዳ አልቻልኩም፡፡ (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)

1 Samuel 9:22

አዳራሽ

መሥዋዕት በሚያቀርቡበት ስፍራ በአቅራቢያው ሰዎች በአንድነት የሚመገቡበት ትልቅ ሕንፃ እንደነበር አንባቢው እንደሚያውቅ ጸሐፊው ይገምታል፡፡

ራስ ስፍራ

የክብር መቀመጫ

ሠላሣ ሰዎች

"30 ሰዎች' (ቁጥሮች ተመልከት)

1 Samuel 9:23

በእርሱ ላይ የነበረውን

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ሳኦል ከስጋው ጋር ሊበላው የነበረ ሌላ ምግብ ወይም 2) የወይፈኑ ሌሎች ክፍሎች

ሳሙኤልም አለ

በመጀመሪያው ቋንቋ ተናጋሪው ማን እንደሆነ ግልጽ አይደለም፡፡ ወጥ ቤቱም ለሳኦል እየተናገረ ሊሆን ይችላል፡፡ አት፡- "ወጥ ቤቱም አለ'

1 Samuel 9:25

በሰገነቱ ላይ

ይህ ለቤተሰብና ለእንግዶች ለመብላት፣ ለመጎብኘትና ለመተኛት የተለመደ ቦታ ነው፡፡ በምሽትና በሌሊት ከቤቱ ውስጠኛ ክፍል ይልቅ የመቀዝቀዝ ሁኔታ ይታይበታል፡፡

ሳሙኤል ሳኦልን ከሰገነቱ ላይ ጠራና አለው

ሳኦል በሰገነቱ ላይ ያደርግ የነበረው ግልጽ ሊደረግ ይቻላል፡፡ አት፡- "ሳኦል በሰገነቱ ላይ ተኝቶ ሳለ፣ ሳሙኤል ጠራውና አለ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 9:27

በፊታችን እንዲያለፍ "–ብላቴናውም አለፈ –' አንተ ቁም

እነዚህን ቃላት ሁሉ ሳሙኤል ተናግሮ ሊሆን ይችላል፡፡ አት፡- "ከፊታችን ይለፍ፣ ከፊታችንም ሲያለፍ፣ አንተ ቆይ'

---

Chapter 10

1 Samuel 10:1

የዘይቱን ብርሌ ወስዶ በሳኦል ራስ ላይ አፈሰሰው

በእስራኤል ባሕል፣ አንድ ነቢይ በአንድ ሰው ራስ ላይ ዘይት ሲያፈስስ፣ ግለሰቡ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከት ይቀበላል፡፡

ብርሌ

ከተጠበሰ የሸክላ አፈር የሚሠራ ትንሽ መያዣ

በርስቱ ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር አልቀባህምን?

ሳሙኤል ለጥያቄው የሚሰጠውን መልስ ያውቃል፡፡ በእስራኤል ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር እንደመረጠው ሳኦልን እያሳሰበው ነው፡፡ አት፡- "በርስቱ ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር በእርግጥ ቀብቶሃል፡፡' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ጼልጻህ

ይህ የቦታ ስም ነው፡፡ (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

የልጄን ነገር እንዴት አደርጋለሁ?

አሁን የሳኦል አባት ስለ ሳኦል መጨነቅ ጀመረ ሊያገኘውም ፈለገ፡፡

1 Samuel 10:3

ታቦር

ይህ የቦታ ስም ነው፡፡ (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

ከእጃቸው ተቀበል

እጆች ለግለሰቦች ተለዋጭ ስም ነው፡፡ "ከእነርሱ ውሰድ' ወይም "ተቀበል' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

1 Samuel 10:5

ከበሮ

የሚመታ የታምቡር ራስ የሚመስል ያለው እና ሲንቀጠቀጥ ድምጽ የሚሰጡ የብረት ቁራጮች በጎኑ ዙሪያ ያለው የሙዚቃ መሣሪያ ነው፡፡ (የማይታወቁትን መተርጎም ተመልከት)

የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ይወርድብሃል

ይወርድባሃል የሚለው ቃል የእግዚአብሔር መንፈስ በሳኦል ላይ ተጽእኖ ያድርጋል ማለት ነው፡፡ በዚህ ስፍራ ሳኦልን እንዲተነብይና እንደ ሌላ ሰው እንዲከወን ያደርገዋል ማለት ነው፡፡ (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 10:7

እጅህ የምታገኘውን ሁሉ አድርግ

በዚህ ስፍራ ሳሙኤል ስለ ሳኦል እጆች ነገሮችን ለማግኘት እንደሚጥር ግለሰብ አድርጎ ይናገራል፡፡ አት፡- "ለማድረግ ትክክል እንደሆነ የምታስበውን ሁሉ አድርግ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

1 Samuel 10:9

እግዚአብሔር ሌላ ልብ ሰጠው

እግዚብአብሔር ሳኦልን ቀድሞ ያስብበት ከነበረበት መንገድ በተለየ መንገድ እንዲያስብ አስቻለው፡፡ (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደበት

ሳሙኤል የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ሳኦል እንደሚሮጥና እርሱንም ሙሉ ለሙሉ እንደሚቆጣጠር ግለሰብ አድርጎ ይናገራል፡፡ ይህንን በ1ሳሙኤል 10፡6 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት፡፡ አት፡- "የእግዚአብሔር መንፈስ ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጠረው' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

1 Samuel 10:11

የቂስን ልጅ ያገኘው ምንድን ነው

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ሕዝቡ መረጃ እየጠየቀ ነው 2) ሳኦል አስፈላጊ ሰው አይደለም የሚል ትርጉም ያለው አሳብ ገላጭ ጥያቄ ነው፡፡ አት፡- "ቂስ አስፈላጊ ሰው አይደለም፣ ልጁ ነቢይ ሆነ የሚለው እውነት ሊሆን አይችልም፡፡' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

የቂስ ልጅ

"ሳኦል የቂስ ልጅ'

አባታቸውስ ማን ነው

ይህ ሰው፣ ነቢይ መሆን የአንድ ሰው ወላጆች እነማን ከመሆናቸው ጋር የሚያያዝው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ምንም ነገር እንደሌለ ሕዝቡን ለማሳሳብ አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በገላጭ አባባል ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "የእነዚህ የሌሎቹ ነቢያት ወላጆች እነማን መሆናቸው አስፈላጊ ነገር አይደለም። ቁም ነገሩ፣ በሚያስገርም ሁኔታ፣ ሳኦል የእግዚአብሔርን መልእክት መናገሩ ነው።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)

ስለዚህም፡- "ሳኦል ደግሞ ከነቢያት ወገን ነውን?' የሚል አባባል ሆነ

ይህ በእስራኤላውያን መካከል ምሳሌ ሆነ። አንድ ሰው ከዚያ በፊት አድርጎት የማያውቀውን ነገር ሳይታሰብ አድርጉት ሲገኝ አድናቆትን ለመግለጽ ሰዎች በግልጽ ይህን ይላሉ። አት፡- "ሰዎች አንዳንድ ዘገባዎችን ማመን ባቃታቸው ጊዜ፣ ከዚያም የተነሳ፣ ለሳኦል ስለሆነው አሰቡና እንዲህ አሉ፣ 'በውኑ ሳኦል ከነቢያት አንዱ ነውን?'' (ምሳሌዎችንና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 10:14

ከዚያም የሰኦል አጎት እንዲህ አለው

"ከዚያም የሳኦል የአባቱ ወንድም እንዲህ አለው'

የመንግሥቱን ነገር በሚመለከት አልነገረውም

"እግዚአብሔር የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን እንደሾመው ሳኦል ለአጎቱ አልነገረውም'

1 Samuel 10:17

እስራኤልን ከግብጽ አወጣሁ

እስራኤል የሚለው ስም ለእስራኤል ሕዝብ ምትክ ስም ነው። አት፡- "የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ አወጣሁ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ዛሬ

ሳሙኤል ፀሐይ ለመጨረሻ ከጠለቀችበት አንስቶ ያለውን ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ እስራኤል እግዚአብሔርን መቃወም ከጀመሩበት አንስቶ ስላለው ጊዜ ይናገራል።

የግብጻውያን እጅ ... የመንግሥታት ሁሉ እጅ

እጅ የሚለው ቃል ለኃይል ምትክ ቃል ነው። አት፡- "የግብጻውያን ኃይል ... የመንግሥታት ሁሉ ኃይል'

ንጉሥ አንግሥልን

"የሚገዛንን ንጉሥ ስጠን'

በየነገዳችሁና በየወገናችሁ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ

"በየነገዳችሁና በየወገናችሁ በአንድ ተሰበሰቡና በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም ኑ'

1 Samuel 10:20

የብንያም ነገድ ተመረጠ ... የማጥሪን ወገን ተመረጠ ... የቂስ ልጅ ሳኦል ተመረጠ

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። እግዚአብሔር የመረጠውን ሕዝቡ ያወቀበት መንግድ ብሎ አለመተረጎም እጅግ የተሻለ ነው። አት፡- "እግዚአብሔር የብንያምን ነገድ መረጠ ... እግዚአብሔር የማጥሪንን ወገን መረጠ ... እግዚአብሔር የቂስን ልጅ ሳኦልን መረጠ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

1 Samuel 10:22

ከሕዝቡም ሁሉ ይልቅ ከትከሻውና ከዚያም በላይ ቁመቱ ዘለግ ያለ ነበረ

በእስራኤል የነበሩ ሌሎች ረጃጅም ሰዎች ትከሻው ጋ አይደርሱም ነበር። ይህን በ1ሳሙኤል 9፡2 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

1 Samuel 10:25

የንግሥና ወጎችና መመሪያዎች

ንግሥና የሚለው የነገር ስም በመጠሪያ ሐረግነት ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "ንጉሥ ሊከተላቸው የሚያስፈልጉ ወጎችና መመሪያዎች' (የነገር ስም ተመልከት)

1 Samuel 10:26

እግዚአብሔር ልባቸውን የነካ

የእግዚአብሔር የሰውን ልብ መንካት የእግዚአብሔር በአእምሮአቸው ውስጥ አንድን ነገር ማስቀመጥ ወይም አንድን ነገር እንዲያደርጉ ማንቀሳቀስ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "እግዚአብሔር አስተሳሰባቸውን ስለቀየረ ከሳኦል ጋር ለመሄድ የፈለጉ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ይህ ሰው እንዴት ያድነናል?

ይህ ማሽሟጠጥን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የሚውል አሳብ ገላጭ ጥያቄ ነው። አት፡- "ይህ ሰው ሊያድነን ኃይል የለውም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ናቁት

እጅግ አልወደዱትም ወይም ናቁት

---

## Chapter 11

1 Samuel 11:1

ናዖስ

ይህ ሰው የአብርሃም የወንድም ወይም የእኅት ልጅ የሎጥ ትውልድ የሆነ አሞናዊ ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)።

ኢያቢስ ገለዓድ

ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

አወጣለሁ

"ቆርጬ አወጣለሁ' ወይም "ጎትቼ አወጣለሁ'

ውርደት አመጣባችኋለሁ

"ውርደት አለብሳችኋለሁ' ወይም "አሳፋሪ ስም አለብሳችኋለሁ'

1 Samuel 11:3

ሰባት ቀናት

"7 ቀናት' (ቁጥሮች ተመልከት)

1 Samuel 11:4

ጊብዓ

ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

1 Samuel 11:6

የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደበት

ወረደበት የሚለው ቃል የእግዚአብሔር መንፈስ በሳኦል ላይ ተጽእኖ ያድርጋል ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ እንደ ንጉሣቸው ሕዝቡ በፍርሃት እንዲያከብሩትና ሠራዊቱን እንዲቀላቀሉ እንዲያደርግ ሳኦልን አስችሎታል። 1ሳሙኤል 10፡6ን እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ተከትሎ የማይወጣ

ናዖስንና አሞናውያንን ለመወጋት የእስራኤል ሰዎች ሁሉ እንዲመጡ ሳዖል ጥሪ እያስተላለፈ ነበር።

ከዚያም የእግዚአብሔር ድንጋጤ በሕዝቡ ላይ ወደቀ

እንደ ንጉሣቸው ሳኦልን በፍርሃት እንዲያከብሩት እግዚአብሔር ሕዝቡን አስቻለ።

በውጤቱም ሰዎቹ ከሳኦል ጋር በቤዜቅ በአንድነት ተሰበሰቡ።

ቤዜቅ

ይህ በኢያቢስ ገለዓድ አቅራቢያ የምትገኝ ከተማ ስም ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

የእስራኤል ሰዎች ሦሥት መቶ ሺህ፣ የይሁዳም ሰዎች ሠላሣ ሺህ ነበሩ

"የእስራኤል ሰዎች 300,000፣ የይሁዳም ሰዎች 30,000 ነበሩ' (ቁጥሮች ተመልከት)

1 Samuel 11:9

መልእክተኞቹን አሉአቸው

"አሉአቸው' የሚለው ሳሙኤልንና ሳሙኤልን ያመለክታል።

ፀሐይ በሞቀች ጊዜ

"ከቀኑ እጅግ ሞቃት ከሆነው ክፍል በፊት' ወይም "ከቀትር በፊት'

ኢያቢስ ገላዓድ ... ኢያቢስ

እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው። በ1ሳሙኤል 11፡1 እንዴት እንደተረጎምሃቸው ተመልከት።

ናዖስ

ይህ የንጉሥ ስም ነው። ይህንን ስም በ1ሳሙኤል 11፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

1 Samuel 11:11

በነጋውም

ይህ ከንጋት በፊት አብዛኛው ሕዝብ ገና በሰፈሩ ተኝቶ የነበረበት ጊዜ ነው።

1 Samuel 11:14

ሳኦልን በእግዚአብሔር ፊት አነገሡት

"እግዚአብሔር እያየ ሳኦልን አነገሡት'

በዚያም በእግዚአብሔር ፊት የሰላም መሥዋእት አቀረቡ

ከአሮን ወይም ከሌዊ ቤት ባይሆንም እንኳን መሥዋዕት ማቅረብ የሳሙኤል የእግዚአብሔር አገልግሎት ክፍል ነው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 12

1 Samuel 12:1

ንጉሡ በፊታችሁ ይሄዳል … እኔም በፊታችሁ ሄድሁ

እነዚህ መግለጫዎች ሳሙኤልና ሳኦል የኖሩትን የሕይወት ዓይነት ሕዝቡ በተጨባጭ ማየት ችሏል ማለት ነው። አት፡- "የንጉሡ ሕይወት ታይቷል … የእኔ ሕይወት ታይቷል' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 12:3

በዚህ አለሁ፣በእግዚአብሔርና እርሱ በቀባው ፊት መስክሩብኝ

በዚህ ንግግሩ ሳሙኤል አንዳች ተገቢ ያልሆነ ነገር በማንም ላይ አድርጎ ከሆነ ሕዝቡ እንዲናገር እየሞገተ ነው። አት፡- "አሁን በፊታችሁ ቆሜያለሁ። ምንም ዓይነት ተገቢ ያልሆነ ነገር አድርጌ ከሆነ በእግዚአብሔርና በቀባው በንጉሡ ፊት እንድትናገሩ እጠይቃችኋለሁ።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

የማንን በሬ ወሰድሁ? የማንንስ አህያ ወሰድሁ?

እንስሳቶቻቸውን ያልሰረቀባቸውን ሰዎች ለማሳሳብ ሳሙኤል አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠቀማል። አት፡- "እኔ ውድ የሆነ እንስሳ ፈጽሞ ከማንም አልሰረቅሁም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ማንንስ ሸነገልሁ

ሁልጊዜ ታማኝ እንደ ነበር ለመናገር ሳሙኤል ሌላ አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠቀማል። አት፡- "እኔ ማንንም አልታለልኩም ወይም ከማንም ጉቦ አልተቀበልሁም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

መስክሩብኝ እኔም እመልሳለሁ

"ከእነዚህ ክፉ ነገሮች ማናቸውንም አድርጌ ከሆንሁ አሁን ተናገሩ፣ የወሰድኩትንም እመለሳለሁ። ማናኛውንም ስሕተት አስተካክላለሁ።'

1 Samuel 12:4

ከማንም እጅ … በእጄ

እነዚህ ሃረጎች ግለሰቡ ምን ሃብት እንዳፈራ ወይም ከሌሎች ወሮታን ለማግኘት ምን እንዳደረገ የሚገልጽ ነው። አት፡- ይህ ምንም እንዳልሰረቀ፣ ወይም ጉቦ እንዳልሰጠና እንዳልተቀበለ የተናገረበት ጨዋ መንገድ ነው።

1 Samuel 12:6

የእግዚአብሔር የጽድቅ ሥራ ሁሉ

በመልካምነትና በዓላማ ለተሞላው፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ላደረገው ታሪክ ትኩረት እንዲሰጡ ሳሙኤል እየተጣራ ነው።

1 Samuel 12:8

ለሲሣራ … ለፍልስጥኤማውያን … ለሞአብ ንጉሥ እጅ

"ለሲሣራ … ለፍልስጥኤማውያን … ለሞአብ ንጉሥ ኃይል'

ያዕቆብ … ሙሴ … አሮን … ሲሣራ

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

አሦር

ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

ሸጣቸው

ይህ ባሮቻቸው እንዲሆኑ እግዚአብሔር ለጠላቶቻቸው አሳልፎ መስጠቱን የሚገልጽ ነው።

1 Samuel 12:10

ወደ እግዚአብሔር ጮኹ

(እነርሱ) የእስራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ነው

ይሩ ባአል

ይህ አንዳንዴ ይሩባአል በሚል ይተረጎማል። ይህ ሐሰተኛ አማልከትን ለመዋጋት የጻድቅ የክብርና የጥንካሬ ስም ነው።

እግዚአብሔር ላከ … ድልም ሰጣችሁ

ሳሙኤል ከሕዝቡ የኃጢአት ኑዛዜና የእርዳታ ጥሪ በኋላ እግዚአብሔር ምን እንዳደረገላቸው ታሪኩን ይናገራል። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ይሩ ባአል፣ ባርቅ፣ ዮፍታሔና ሳሙኤል

እነዚህ እግዚአብሔር ያስነሳቸው ጥቂት የመሳፍንት ስሞች ናቸው። ሳሙኤል ራሱን በዚህ ዝርዝር ውስጥ አካቷል። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

በአሊምንና አስታሮትን አገለገሉ

በዚህ ስፍራ ማገልገል ሐሰተኛ አማልክትን የማምለክን ተግባር ያመለክታል። አት፡- ሐሰተኛ አማልክትና ሴት አማልክትን አመለኩ (ምትክ ቃል ተመልከት)

የጠላቶቻችን እጅ

ይህ አረፍተ ነገር ኃይልን ለማመልከት "እጅ' የሚለውን ቃል ይጠቀማል። አት፡- "የጠላቶቻችን ኃይል ወይም የበላይነት' (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 12:12

እንዲህ አይሁን! ነገር ግን ንጉሥ ይንገሥልን

ይህ አረፍተ ነገር እግዚአብሔር ትናንትና ስላዳናቸው በእግዚአብሔር ስለመታመን በነገራቸው ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ ሳሙኤልን በመቃወም ስላሰዩት ብርቱ ምላሽ ይናገራል።

የመረጣችሁትንና የጠየቃችሁትን

እነዚህ ሁለት ቃላት ሕዝቡ የፈለገው ንጉሥ ይህ ነው የሚል ተመሣሣይ ትርጉምና አጽንዖት አላቸው። (አጓዳኝነት ተመልከት)

1 Samuel 12:14

ብትፈሩ … ብታገለግሉ … ብትታዘዙ … ባታምጹ

ይህ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት እነዚህ ተመሣሣይ ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል። (አጓዳኝነት ተመልከት)

በአባቶቻችሁ ላይ እንደሆነ፣ የእግዚአብሔር እጅ በእናንተ ላይ ትሆናለች

ይህ እጁ በእነርሱ ላይ እንደሆነች ሁሉ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚቀጣ ይናገራል። በዚህ ስፍራ "እጅ' የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ኃይልና የበላይነት ይወክላል። አት፡- "እግዚአብሔር አባቶቻችሁን እንደቀጣ ይቀጣችኋል' (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 12:16

በዓይኖቻችሁ ፊት

በዚህ ስፍራ "ዓይኖች' የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል። አት፡- "የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ሊያይ በሚችልበት ግልጽ ስፍራ' (ተለዋጭ ቃል ተመልከት)

የስንዴ መከር ዛሬ አይደለምን?

ሳሙኤል የመከር ጊዜ እንደሆነ ያውቃል። በአብዛኛው በዚህ ጊዜ ዝናብ እንደማይዘንብ ስለዚህ የእግዚአብሔር ፍርድ በመሆኑ ዝናቡ መከራቸውን እንደሚያጠፋ ሕዝቡ እንዲያውቅ አጽንዖት ለመስጠት አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠቀማል። አት፡- "የመከር ጊዜ ነው በአብዛኛውም በዚህ ጊዜ አይዘንብም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ነጎድጓድና ዝናብ ይልካል

ሳሙኤል በመከር ጊዜ እህሉን የሚያጠፋ ከባድ ዝናብ በመላክ ንጉስ ስለመጠየቃቸው እግዚአብሔር እሥራኤልን እንዲቀጣ ይጠይቃል።

1 Samuel 12:19

እንዳንሞት

የኃጢአት የመጨረሻ ቅጣት ሞት ነው። እግዚአብሔር ይጨቁኗቸው የነበሩትን ሕዝቦች እንዳጠፋ የእስራኤል ሕዝብ አይቷል። እንደሌሎቹ ሕዝቦች "ለጥፋት እንዳይሰጡ' ተጨንቀው ነበር።

አትፍሩ

ሕዝቡ ክፉ አደረጉ እንዳያጠፋቸውም እግዚአብሔርን ፈሩ። አት፡- "ከዚህ ኃጢአት የተነሣ እግዚአብሔር ይቆጣል ያጠፋናልም ብላችሁ አትፍሩ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ከንቱ ነገርን ለመከተል ፈቀቅ አትበሉ

"ሐሰተኛ አማልክትን ማምለክ አትከታተሉ'

1 Samuel 12:22

ስለ ታላቅ ስሙ

በዚህ ስፍራ ስም የእግዚአብሔርን ክብር ያመላክታል። አት፡- "ስለዚህ ሕዝቡ እግዚአብሔርን በማክበርና በመፍራት ይኖራል።' (ምትክ ቃል ተመልከት)

ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ

ሳሙኤል በጸለየ ጊዜ እግዚአብሔር ከላከው ዝናብና ነጎድጓድ የተነሣ ሕዝቡ በፍርሃት ተሞላ። አንዳንድ ሰዎች ሳሙኤል ጸሎቱን እነርሱን ለመጉዳት ሊጠቀምበት እንደሚችል ሳያምኑ አልቀሩም። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

Chapter 13



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

1 Samuel 13:1
አጠቃላይ መረጃ
ሳሙኤል በጌልጌላ የሳኦልን መንግሥት አደሰለት ሳሙኤልም ጌታን እንዲከተሉ ሕዝቡን አሳሰበ።
ሳኦል ሠላሣ ሁለት ዓመቱ ነበር … በእስራኤልም ላይ
በጥንት ቅጂዎች የዚህ ጥቅስ ጽሑፍ የተጎዳ ይመስላል፣ ስለዚህ የዘመናችን እትሞች የተለያዩ ትርጉሞችን ይዘዋል። ሁሉም ሊሆን የሚችለውን የተሻለውን የመጀመሪያውን ጽሑፍ ትርጉም ለማቅረብ ጥረት አድርገዋል።
ሦሥት ሺህ ሰዎች መረጠ
"3,000 ሰዎች መረጠ' (ቁጥሮች ተመልከት)
ሁለት ሺህ ሰዎች ከእርሱ ጋር ነበሩ
"2,000 ሰዎች ከእርሱ ጋር ነበር' (ቁጥሮች ተመልከት)
ማክማስ
የከተማ ስም ነው (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)
የብንያም ጊብዓ
ጊብዓ ከተማ ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 10:26 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
የቀሩትን ወታደሮች ወደ ቤት ሰደዳቸው
"የቀሩትን ወታደሮች ቤት ሰደዳቸው'
1 Samuel 13:3
የፍልስጥኤማውያን ጭፍራ
"የፍልስጥኤማውያን የጦር ሰፈር'
ናሲብ
ይህ የፍልስጥኤም ጭፍራ የሰፈረበት የከተማ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
ሳኦል እንዳሸነፈ እስራኤላውያን ሁሉ ሰሙ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ዮናታን ለፈጸመው ጥቃት ሳኦል ኃላፊነቱን እየወሰደ ነበር ወይም 2) ዮናታን በፈጸመው ጥቃት የተገኘውን ድል ሳኦል እየወሰደ ነበር
እስራኤል ለፍልስጥኤም እንደ ብስባሽ ሽታ ሆነች
ፍልስጥኤማውያን ለእስራኤል ያላቸው ጥላቻ እስራኤላውያን ፍልስጥኤማውያንን የሚረብሽ መጥፎ ሽታ እንደሆኑ ተደርጎ ተገልጾአል። አት፡- "ፍልስጥኤማውያን እስራኤላውያንን ጠሉአቸው' (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)
ወታደሮቹ ሳኦልን ለመከተል ወደ ጌልጌላ ተሰበሰቡ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- ሳኦል ወታደሮቹ እንዲከተሉት በጌልጌላ እንዲሰበሰቡ ጠራቸው (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
1 Samuel 13:5
ሦሥት ሺህ … ስድስት ሺህ
"3000 … 6000' (ቁጥሮች ተመልከት)
ወታደሮቹ በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ ብዙ ነበሩ
ለመቁጠር እስከሚያስቸግር ድረስ የወታደሮቹ ስብስብ ታላቅ ነበር የሚል ግነት ነው። (ግነትና አጠቃላይነት ተመልከት)
ማክማስ
ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
ቤትአዌን
ይህ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
1 Samuel 13:6
አጠቃላይ መረጃ
ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ለመዋጋት በአንድነት ተሰበሰቡ።
ሕዝቡ
ይህ ሐረግ የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።
ሕዝቡ ታውኮ ነበር
"ሕዝቡ በጣም ተጨንቆ ነበር'
ተንቀጥቅጠው ተከተሉት
ሕዝቡ በጣም ፈርተው ነበር
1 Samuel 13:8
ሳሙኤል በቀጠረው ቀን
"እንደሚመጣ ሳሙኤል በነገራቸው ጊዜ መሠረት'
ሕዝቡ ከሳኦል ተለይተው ተበታተኑ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሕዝቡ ሳኦልን ትቶ መሄድ ጀመረ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ)
ከዚያም የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ
የሚቃጠል መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ማቅረብ የተፈቀደው ለአሮን ወገን ብቻ ነበር
1 Samuel 13:11
ያደረግኸው ምንድር ነው?
በእውነቱ ሳሙኤል እየጠየቀ ሳይሆን ሳኦልን እየገሰጸው ነበር። ትክክል ባይሆኑም እንኳን ሳኦል ለድርጊቶቹ ሊከላከል ፈለገ። (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)
ማክማስ
ማክማስ የቦታ ስም ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 13:2 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
1 Samuel 13:13
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አልጠበቅህም
ሳሙኤል እስኪመጣና ለእግዚብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት እስኪሰዋ ድረስ ሳኦል መጠበቅ ነበረበት። እርሱ ራሱ መሠዋት አልነበረበትም።
መንግሥትህን አጽንቶልህ ነበር
"መንግሥትህን አቁሞልህ ነበር' ወይም "መንግሥትህን አውቆልህ ነበር' ወይም "መንግሥትህን መርጦ ነበር'
መንግሥትህ አይቀጥልም
ይህ በአዎንታዊ መንገድ የቀረበ ምፀት ነው። አት፡- "መንግሥትህ በቅርቡ ያከትማል' (ምፀት ተመልከት)
እንደ ልቡ የሆነ ሰው
በዚህ ስፍራ ልብ የእግዚአብሔርን ፍላጎትና ፈቃድ ይወክላል። "እንደ ልቡ የሆነ ሰው' የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር የሚፈልገውን የሚያደርግ ሰው የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "ይፈልገው የነበረ ዓይነት ሰው' ወይም "የሚታዘዘው ሰው' (ምትክ ቃልና ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
1 Samuel 13:15
ሳሙኤል ተነሣና ሄደ
"ሳሙኤል ትቶ ሄደ' ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ከጌልጌላ ተነስቶ ሄደ
ጌልጌላ ከተማ ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 7:15 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
የብንያም ጊብዓ
ጊብዓ ከተማ ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 10:26 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ስድስት መቶ ሰዎች
"600 ሰዎች' (ቁጥሮች ተመልከት)
የብንያም ጊብዓ
ጊብዓ ከተማ ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 13:03 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ፍልስጥኤማውያን በማክማስ ሰፈሩ
ማክማስ የቦታ ስም ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 13:02 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
1 Samuel 13:17
አደጋ ጣዮች መጡ
አደጋ ጣዮች በአብዛኛው ለምግባቸውና ሌሎች ቁሳ ቁሶች በጠላት መንደር ላይ ጥቃት የሚያደርሱ የጦር ሰዎች ናቸው።
ዖፍራ … ሦጋል ምድር … ቤትሖሮን … ስቦይም ሸለቆ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
1 Samuel 13:22
አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ ይቀጥላል።
ሰይፍና ጦር አልነበረም
ይህ ለምን የሳኦል ሠራዊት እንደፈሩ በከፊል ያሳያል።

---

Chapter 14
1 Samuel 14:1
አጠቃላይ መረጃ
ዮናታን በፍልስጥኤማውያን ሠራዊት ላይ ሁለተኛ ጥቃቱን ጀመረ።
ወጣቱ ጋሻ ጃግሬው
የጌታውን የጦር መሣሪያዎች የመሸከም ኃላፊነት ያለበት ከአሥራ ሦሥት እስከ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ባለ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ልጅ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የፍልስጥኤማውያን የጦር ካምፕ

ይህ የፍልስጥኤማውያን ሠራዊት የሰፈረበት የጦር ሰፈር ነው።

1 Samuel 14:2

ጊብዓ

ይህ ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን የሚገኝ የኮረብታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ከሮማኑ ዛፍ በታች

ፍሬው ወፍራም ሽፋን ያለው፣ ክብ፣ ቀይና የሚበሉ ብዙ ዘር የያዘ ዛፍ ነው

መጊዶን

መጊዶን ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን የሚገኝ የቦታ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ስድስት መቶ ሰዎች ከእርሱ ጋር ነበሩ

"600 ሰዎች ከእርሱ ጋር ነበሩ' (ቁጥሮች ተመልከት)

የአኪጦብ ልጅ (የአካቦድ ወንድም)

"አኪጦብ' እና "አካቦድ' የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

የዔሊ ልጅ ፊንሐስ

ፊንሐስ ከካህናት አንዱ ነበር። ይህንን በ1ሳሙኤል 1:03 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

1 Samuel 14:4

ሌላኛውም ሾጣጣ ድንጋይ ሴኔ ይባል ነበረ

ይህ የሌላኛው ሾጣጣ ድንጋይ ስም ነበር። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ማክማስ ... ጊብዓ

ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን የሚገኙ ከተሞች (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

1 Samuel 14:6

ወጣቱ ጋሻ ጃግሬው

የጌታውን የጦር መሣሪያዎች የመሸከም ኃላፊነት ያለበት ከአሥራ ሦሥት እስከ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ባለ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ልጅ። ይህንን በ1ሳሙኤል 14:1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ወደ እነዚህ ቆላፋን (ያልተገረዙ)

ይህ አይሁድ ላልሆኑ ወንዶች ጥቅም ላይ የሚውል ክበረ ነክ ቃል ነው።

በእኛ ፈንታ ይሠራ

"እኛን ለመደገፍ ይሠራ' ወይም "ይረዳን'

ምንም ነገር እግዚአብሔርን ከማዳን አያቆመውም

ይህ ድርብ አሉታዊ አሳብ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ማዳን ይችላል' (ድርብ አሉታዊ ተመልከት)

በብዙ ወይም በጥቂት

እነዚህ ጥጎች በመካከል ያሉትን ነገሮች ሁሉ ያካትታሉ። አት፡- "በማንኛውም የሰው ቁጥር' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በልብህ ያለውን ማንኛውንም ነገር

በዚህ ስፍራ ልብ የዮናታንን ፍልጎቶች ያመላክታል። አት፡- "ማድረግ የምትፈልገውን የትኛውንም ነገር' (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 14:8

ወደ እነርሱ እንወጣም

"ፍልስጥኤማውያን ወደ ሚገኙበት ወደ ሌላኛው የሸለቆ አቅጣጫ እንሄድም።'

በእጃችን አሳልፎ ሰጥቶአቸዋል

በዚህ ስፍራ እጅ እነርሱን ለማሸነፍ የሆነውን ኃይል ያመለክታል። አት፡- እነርሱን ለማሸነፍ ያስችለናል (ምትክ ቃል ተመልከት)

ይህ ምልክት ይሆነናል

"ይህ ጌታ ከእኛ ጋር እንደሆነ ያረጋግጥልናል'

1 Samuel 14:11

ለፍልስጥኤማውያን ጭፍራ ራሳቸውን ገለጡ

"የፍልስጥኤማውያን ወታደሮች እንዲያዩአቸው ፈቀዱ'

የጦር ሠፈር

የሠራዊት ከምፕ

ከተደበቁበት ጉድጓድ ይወጣሉ

ዕብራውያን እንደ እንስሳ በጉድጓድ ውስጥ ተደብቀው እንደ ነበር ፍልስጥኤማውያን አመለከቱ። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

አንድ ነገር እናሳያችኋለን

ይህ አንድ ትምህርት አስተምራችኋለሁ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

በእስራኤል እጅ አሳልፎ ሰጣአቸው

በዚህ ስፍራ እጅ የሚለው የሚያመለክተው ፍልስጥኤማውያንን ለማሸነፍ የሆነውን ኃይል ነው። አትለ- እስራኤላውያን እንዲያሸንፉ አስቻላቸው። (ምትክ ቃል ተመልከት)

1 Samuel 14:13

ዮናታን በእጁና በእግሩ ወጣ

ይህን ያደረገው በጣም ከፍ ያለ ስለ ነበረ ነው። ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፡- "በጣም ከፍ ያለ ስለ ነበረ ዮናታን እጆቹንና እግሮቹን በመጠቀም ወጣ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ፍልስጥኤማውያን በዮናታን ተገደሉ

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊደረግ ይቻላል። አት፡- "ዮናታን ፍልስጥኤማውያንን ገደለ' (አድራጊ ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ከእርሱ በኋላ ጋሻ ጃግሬው ጥቂቶችን ገደለ

"የዮናታን ጋሻ ጃግሬ ተከተለው የፍልስጥኤማውያንንም ወታደሮች ገደለ'

1 Samuel 14:15

በሰፈሩም በእርሻውና በሕዝቡም መካከል ሽብር ሆነ

ሽብር የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽነት ወይም በቅጽልነት ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "በሰፈርና በእርሻ የነበሩ የፍልስጥኤማውያን ወታደሮችና ከእነርሱ ጋር የነበረው ሕዝብ ሁሉ ተሸበሩ' ወይም "በሰፈርና በእርሻ የነበሩ የፍልስጥኤማውያን ወታደሮችና ከእነርሱ ጋር የነበረው ሕዝብ ሁሉ በጣም ፈሩ' (የነገር ስም ተመልከት)

ዘራፊዎች (አደጋ ጣዮች)

የእስራኤልን ከተሞች የሚዘርፉ ፍልስጥኤማውያን

ምድሪቱ ተናወጠች

ምክንያቱን መግለጽ ሊረዳ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ምድሪቱን አናወጣት' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

1 Samuel 14:16

ጊብዓ

ይህቺ ሳኦል የተወለደባት ከተማ ነበረች። "ጊብዓ'ን በ1ሳሙኤል 10:26 እንደተረጎምኸው ተርጉም። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

ወዲህና ወዲያ እየተራወጡ ተበታተኑ

እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ ወታደሮቹም በሁሉም አቅጣጫዎች ይሮጡ የነበረ በመሆኑ ላይ አጽንዖት ያደርጋሉ። (አጓዳኝነት ተመልከት)

1 Samuel 14:18

የእግዚአብሔርን ታቦት ወደዚህ አምጣ

ጥቂት ትርጉሞች በዚህ ስፍራ "የእግዚአብሔር ታቦት' በሚለው ምትክ "ኤፉድ' ይላሉ። (ልዩ ልዩ ትርጉሞች ተመልከት)

ግርግርታ

ትልቅ ድምጽና ትርምስምስ

እጅህን መልስ

ይህ "እያደረግህ ያለውን አቁም' የሚል ፈሊጣዊ ንግግር ይመስላል። እግዚአብሔርን ምሪት ለመጠየቅ አኪያ ታቦቱን እንዲጠቀም ሳኦል አልፈቀደም። አት፡- "በዚህ ጊዜ የተቀደሰውን ሰንዱቅ አታምጣ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

1 Samuel 14:20

ከእርሱ ጋር የነበሩት ሕዝብ

ከሳኦል ጋር የቀሩ የእስራኤል ሠራዊት ቅሬታ

የእያንዳንዱ ፍልስጥኤማዊ ሰይፍ በባልንጀራው ላይ ነበረ

ሰይፎችን በሚመለከት ልክ ሕያዋን ሰዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "የፍልስጥኤም ወታደሮች እርስ በእርሳቸው በሰየፎቻቸው ተጠቃቁ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

1 Samuel 14:22

በኮረብታዎቹ የተሸሸጉት የእስራኤል ሰዎች

ይህ ደፈጣን እያመለከተ አይደለም። እነዚህ ወታደሮች የተሸሸጉት ፍልስጥኤማውያንን ስለፈሩ ነበር። ይህ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አት፡- የፈሩ የእስራኤል ወታደሮች በኮረብታዎች ተሸሽገው ነበር። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ

እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ቤትአዌን
ይህ በእስራኤል የሚገኝ ቦታ ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 13፡05 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)
1 Samuel 14:24
ከወታደሮቹ ማንም ምግብ አልቀመሰም ነበር
ከሳኦል መሃላ የተነሣ ምንም መቅመስ እንዳልተፈቀደ ወታደሮቹ ተረድተው ነበር።
ሕዝቡ ወደ ዱር ገባ
የፍልስጥኤም ወታደሮች ወደ ጫካ ሸሽተው ነበር የእስራኤል ወታደሮችም ወደዚያ ተከትለዋቸው ነበር።
የሚፈስ ማር ነበር
በጫካ ውስጥ ምን ያህል ማር እንደነበር ለመግለጽ የተነገረ ግነት ነው። አት፦ "በሁሉ ሥፍራ በርካታ ማር ነበር' (ግነትና አጠቃላይነት ተመልከት)
ማንም እጁን ወደ አፉ አልዘረጋም
በዚህ ስፍራ የአንድ ሰው እጁን በአፉ ማድረጉ መብላትን የሚያሳይ ምትክ ቃል ነው። አት፦ "ማንም ምንም አልበላም' (ምትክ ቃል ተመልከት)
ሕዝቡ መሐላውን ፈርቶ
ሕዝቡ ይፈሩ የነበረው መሐላውን ሳይሆን መሐላውን ከመስበር ጋር የተያያዘውን ቅጣት ነበር። አት፦ "ሕዝቡ መሐላውን ከሰበሩ ሳኦል የሚያደርግባቸውን ፈሩ' (ምትክ ቃል ተመልከት)
1 Samuel 14:27
አጠቃላይ መረጃ
ዮናታን የአባቱን መሐላ አወቀ።
ሕዝቡን በመሐላ አሰራቸው
በዚህ ስፍራ መሐላን የመታዘዝ ግዴታን በሚመለከት ሕዝቡ በገመድ እንደታሰረ ዓይነት ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "ሕዝቡ መሐላውን እንዲያከብር አዘዘ' (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)
እጁን ወደ አፉ አደረገ
በዚህ ስፍራ እጁን ወደ አፉ የሚለው ለመብላት ምትክ ቃል ነው። አት፦ "ጥቂት ማር በላ' (ምትክ ቃል ተመልከት)
ዓይኑ በራ
በረታ የሚል ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፦ "እንደገና ብርታት አገኘ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
1 Samuel 14:29
ለምድሪቱ
የእስራኤልን ሕዝብ የሚወክል ምትክ ቃል ነው። አት፦ "ለእስራኤል' (ምትክ ቃል ተመልከት)
ዓይኔ በራ
በረታ የሚል ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፦ "እንደገና ብርታት አገኘ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ሕዝቡ ካገኙት ... ምን ያህል የተሻለ
ሕዝቡ እንዲበላ ሊፈቀድለት ይገባ እንደነበር ለመግለጽ ዮናታን ይህንን በሁኔዎች ላይ የተደገፈ ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ አሳብ ገላጭ ዐረፍተ ነገር ሊሆን ይችላል። አት፦ "ሕዝቡ ከጠላቶቻቸው የማረኩትን ዛሬ በነፃነት በልተው ቢሆን ኖሮ ድላችን የተሻለ ይሆን ነበር።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎች ተመልከት)
ምርኮ
ይህ ቃል ሕዝቡ ከጠላቶቻቸው ጋር በነበራቸው ጦርነት የወሰዷቸውን ነገሮች ያመለክታል።
ስለዚህ አሁን ግድያው ታላቅ አልሆነም
በጦርነቱ ወቅቱ ወታደሮቹ ሊበሉ ስላልቻሉ፣ ቀኑ የረዘመውን ያህል እየደከሙ ሄዱ። ከዚህ የተነሣ ብዙ ፍልስጥኤማውያንን መግደል አልቻሉም።
1 Samuel 14:31
አጠቃላይ መረጃ
የዮናታን ቃል ሠራዊቱን ከነበረባቸው ከፍተኛ ረሃብ የተነሣ እግዚአብሔርን እንዲበድሉ አደረጋቸው።
ማክማስ
ይህ የቦታ ስም ነው። ይህንን በ1ሳሙኤል 13፡02 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ኤሎን
በዛብሎን እስራኤል የሚገኝ ቦታ ነው (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
ሕዝቡ
እስራኤላውያንን ያመለክታል።
ከደማቸው ጋር በሉአቸው
በጣም ተርበው ስለነበር ከመብላታቸው በፊት ደሙን አላፈሰሱም ነበር። ይህ በሙሴ በኩል ለሕዝበ እሥራኤል የተሰጠውን ሕግ መተላለፍ ነበር። ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፦ "በሕጉ እንደታዘዘው አስቀድመው ደማቸውን ሳያፈስሱ በሏቸው' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
1 Samuel 14:33
ከደሙ ጋር በመብላታችሁ
ይህ በሙሴ በኩል ለሕዝበ እሥራኤል የተሰጠውን ሕግ መተላለፍ ነበር። ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፦ "በሕጉ እንደታዘዘው አስቀድመው ደሙን ሳያፈስሱ ሥጋ በመብላታቸው'
በታማኝነት አላደረጋችሁም
ሁሉም ወታደር ታማኝነቱን ስላላጓደለ ሳኦል ሠራዊቱን ሁሉ በታማኝነት እንዳላደረገ መክሰሱ አጠቃላይ ፍረጃ ነው። (ግነትና አጠቃላይነት ተመልከት)
አሁን ትልቅ ድንጋይ አንከባላችሁ አቅርቡልኝ
ድንጋዩ እንስሳቱን ከፍ አድርጎ ስለሚይዝ ደማቸውን ማፍሰስን ቀላል ያደርገዋል በዚህ እረዱና ብሉ ይህ ሳኦልን ደሙ ከእንስሳው በተገቢ ሁኔታ ተወግዶ መሆኑን ለማየት ያስችለዋል።
1 Samuel 14:35
አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቡ ለማረድና ለመብላት እንስሳቶቻቸውን ወደ ትልቁ ደንጋይ እንዲያመጡ ሳኦል ነገራቸው።
ሳኦል ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ
ሳኦል ይህን መሠዊያ የሠራው ሕዝቡ በ1ሳሙኤል 14፡33 ወደ እርሱ ካመጡለት ትልቅ ድንጋይ ይሁን ግልጽ አይደለም።
1 Samuel 14:36
አጠቃላይ መረጃ
ሳኦል ከፍልስጥኤማውያን ጋር የነበረውን ጦርነት ለመቀጠል ፈልጓል።
ከመካከላቸው አንድ እንኳ በሕይወት እንዲኖር አንተው
ለግድያው አጽንዖት ለመስጠት ይህ በአሉታዊ መንገድ ተገልጾአል። በአዎንታዊ መልኩም ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እያንዳንዳቸውን እንግደል' (ምጸት ተመልከት)
ደስ የሚያሰኝህን ሁሉ አድርግ
ጦርነቱን ለመቀጠል ሳኦል የሠራዊቱን ድጋፍ አግኝቶአል።
ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ
በዚህ ስፍራ "ወደ እግዚአብሔር መቅረብ' እርሱን ምክር ከመጠየቅ ጋር ተያይዟል። አት፦ "ምን ማድረግ እንዳለብን እግዚአብሔርን እንጠይቅ' (ምትክ ቃል ተመልከት)
በእስራኤል እጅ አሳልፈህ ትሰጣቸዋለህን?
በዚህ ስፍራ "እጅ' እነርሱን ለማሸነፍ የሚሆንን ኃይል ያመለክታል። አት፦"እንድናሸንፋቸው አስችለን' (ምትክ ቃል ተመልከት)
በዚያን ቀን ግን እግዚአብሔር አልመለሰለትም
ይህ እግዚአብሔር ሳኦልን ለመርዳት ፈቃደኛ እንዳልሆነ ያመላክታል።
1 Samuel 14:38
ሕዝቡ
ይህ እስራኤላውያንን ያመልከታል
ዛሬ ይህ ኃጢአት በምን እንደሆነ እወቁ
"ኃጢአት የሠራውን እወቁ'
በልጄ በዮናታን ቢሆን ፈጽሞ ይሞታል
ሳኦል ዮናታን በደለኛ እንደሆነ ስላላመነ ይህንን ሊሆን እንደ ሚችል ሁኔታ አድርጎ ገለጸ። (ሊሆን የሚችል ሁኔታ ተመልከት)
ከሕዝቡም አንድ የመለለሰለሰት ሰው አልነበረም
አብዛኛዎቹ ዮናታን የሳኦልን መሐላ እንደሰበረ ስለሚያውቁ ዝም አሉ። ይህ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አት፦ "ሰዎቹ በደለኛው ማን እንደነበረ ያውቁ ነበር ነገር ግን ማናቸውም ለሳኦል ምንም አላሉም።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
1 Samuel 14:40
እስራኤልንም ሁሉ ... አለ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በዚያ የነበሩት የእስራኤል ወታደሮች ብቻ ስለሆኑ ይህ አጠቃላይነት ነው። አት፡- "በዚያ ለነበሩት የእስራኤል ወታደሮች እንዲህ አለ' (ግነትና አጠቃላይነት ተመልከት)
ቱሚም ስጠን
በዚያን ጊዜ እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ምሪት ለመቀበል ኡሪምና ቱሚም የተባሉ የተለዩ ድንጋዮች ይጠቀሙ ነበር። አት፡- "በቱሚም አማካይነት አስታውቀን' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ቱሚም
ይህ ከመጀመሪያ ቋንቋ በትውስት የተወሰደ ነው። (ቅጂ ወይም ትውስት ቃላት ተመልከት)
ሳኦልና ዮናታን በዕጣው ተለዩ፣ ሕዝቡ ግን ነፃ ሆነ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- ዕጣዎቹ ዮናታን ወይም ሳኦል በደለኞች እንደሆኑ ነገር ግን ሠራዊቱ በደለኛ እንዳልሆነ አመለከቱ (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ከዚያም ዮናታን በዕጣው ተለየ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- ከዚያም ዕጣው ዮናታን በደለኛ እንደሆነ አመለከተ (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
1 Samuel 14:43
አጠቃላይ መረጃ
ዕጣው ዮናታን ኃጢአት እንዳደረገ አሳየ።
ያደረግኸውን ንገረኝ
"እንዴት ኃጢአት እንዳደረግህ ንገረኝ' ወይም "ያደረግኸው ስሕተት ምን እንደሆነ ንገረኝ'
እሞታለሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ለመሞት ፈቃደኛ ነኝ' ወይም 2) "ያንን ስላደረግሁ በሞት ልቀጣ ይገባኛል'
እግዚአብሔር እንዲህ ያድርግብኝ እንዲህም ይጨምርብኝ፤ ዮናታን ሆይ ፈጽም ትሞታለህ
ከአንድ ቀን ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሳኦል ትርጉም የሌለው መሐላ አደረገ። አት፡- ዮናታን፣ ካልገደልኩህ እግዚአብሔር ይግደለኝ
1 Samuel 14:45
አጠቃላይ መረጃ
ሠራዊቱ ከሳኦል ለዮናታን ተከላከለ ጠበቀውም።
በውኑ ለእስራኤል ይህን ታላቅ ድል ያደረገ ዮናታን ይሞታልን? ይህ አይሁን!
ሕዝቡ ሳኦልን ገሰፀ። ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በገላጭ አባባል ሊተረጎም ይችላል። አት፡- ዮናታን ይህን ታላቅ ድል ለእስራኤል አድርጓል። በእርግጥ ዮናታን አይሞትም። (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
ሕያው እግዚአብሔርን
ሕዝቡ በዮናታን ላይ አንዳች ነገር እንዲሆን እንዳማየፈቅዱ ቁርጠኛነታቸውን እየገለጹ ነበር።
ከራሱ ጠጉር አንዲት በምድር ላይ አትወድቅም
ይህ ግነት የእስራኤል ሕዝብ እንዴት ዮናታንን እንደሚጠብቁትና ደህንነቱን እንደሚከታተሉ ያሳያል። ይህ ምፀት በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- ከየትኛውም ጉዳት እንጠብቀዋለን (ግነትና አጠቃላይነት እና ምፀት ተመልከት)
1 Samuel 14:47
አጠቃላይ መረጃ
ለአጭር ጊዜ ሳኦል በታላቅ ድፍረት የእስራኤላውያንን ጠላቶች በማሸነፍ አገልግሏል።
እስራኤል
ይህ የእስራኤልን ሕዝብ የሚወክል ምትክ ቃል ነው። አት፡- "እስራኤላውያን' (ምትክ ቃል ተመልከት)
ሞዓብ
ይህ የሞዓብ ሕዝብን ያመለክታል። አት፡- "ሞዓባውያን' (ምትክ ቃል ተመልከት)
ኤዶም
ይህ የኤዶም ሰዎችን ያመለክታል። አት፡- "ኤዶማውያን' (ምትክ ቃል ተመልከት)
በየሄደበትም ሁሉ
"ሠራዊቱን በላከበት ሥፍራ ሁሉ'
ከ ...እጅ
እጅ የሚለው ቃል ቁጥጥርን ይወክላል። አት፡- "ከ ... ቁጥጥር' (ምትክ ቃል ተመልከት)
1 Samuel 14:49
አጠቃላይ መረጃ
ይህ በሳኦል ቤተሰብ ዙሪያ ታሪካዊ ዳራ ነው።
የሱዊ ... ሜልኪሳ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
ሜሮብ ... ሜልኮል
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
አኪናሆም ... አኪማአስ
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
አቤኔር ... ኔር ... ቂስ ... አቢኤል
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
1 Samuel 14:52
በሳኦልም እድሜ ሁሉ
"በሳኦል የሕይወት ዘመን ሁሉ'

---

Chapter 1
2 Samuel 1:1
ጸቅላግ
ይህ በይሁዳ ደቡባዊ ክፍል የሚገኝ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
በሶስተኛው ቀን
"ከሶስት ቀናት በኋላ" (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ልብሱ ተቀዶ እና በራሱ ላይ ትቢያ ነስንሶ
በዚህ ባህል፣ የራስን ልብስ መቅደድ እና በራስ ላይ አመድ መነስነስ የሃዘን መግለጫ ድርጊት ነበር። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ምድር ዝቅ ብሎ እና ራሱን ደፋቶ
ይህ አሁን የእስራኤል ንጉሥ ለሆነው ለዳዊት ራሱን ዝቅ አድርጎ ያሳየበት መንገድ ነበር። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 1:3
ብዙዎች ወደቁ ደግሞም ብዙዎች ሞቱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ብዙዎች ቆስለው ነበር ደግሞም ብዙዎች ተገድለው ነበር" ወይም 2) "ብዙዎች ቆስለው እና ተገድለው ነበር"
2 Samuel 1:6
በአጋጣሚ በዚያ ተገኝቼ ነበር
ይህ ሃሳብ ትኩረት የሚያደርገው ሰውየው ሳኦልን ለማገኘት እቅድ እንዳነበረው ነው
ሳኦል በጦሩ ላይ ዘመም ብሎ ነበር
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ሳኦል ደክሞና ጦሩን ራሱን ለመደገፊያነት ተጠቅሞበት ነበር ወይም 2) ሳኦል በራሱ ጦር ላይ በመውደቅ ራሱን ለመግደል እየሞከረ ነበር። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 1:8
'ማን ነህ?' አለኝ። እኔም እንዲህ ብዬ መለስኩለት፣ 'እኔ አማሌቃዊ ነኝ።'
ይህ ቀጥተኛ ጥቅስ በርቱዕ/ቀጥተኛ ንግግር ሊገለጽ ይችላል። "ማን እንደሆንኩ ጠየቀኝ፣ እኔም አማሌቃዊ እንደሆንኩ ነገርኩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ አማሌቃዊ ነኝ
እነዚህ ህዝቦች ዳዊት በ2 ሳሙኤል 1፡1 ላይ ድል ያደረጋቸው እነዚያው ሰዎች ናቸው።
ታላቅ መከራ አገኘኝ
የሳኦል መከራ የተገለጸው አንዳች አስጨናቂ ነገር አንቆ እንደያዘው ተደርጎ ነው። "እጅግ ተጨነቅኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ህይወቴ ገና አላለፈችም/ነፍሴ አልወጣችም
ይህ ፈሊጥ ትርጉሙ እርሱ ገና በህይወት አለ ማለት ነው። "እስከ አሁን በህይወት አለሁ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከወደቀ በኋላ በህይወት አይቀጥልም

"መሞቱ አይቀርም"
2 Samuel 1:11
ዳዊት ልብሱን ቀደደ... ከእርሱ ጋር ያሉ ሰዎችም እንደዚያው አደረጉ
ዳዊትና የእርሱ ሰዎች በንጉሥ ሳኦል ሞት ማዘናቸውን ለመግለጽ ልብሳቸውን ቀደዱ። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ለያህዌ ህዝብ፣ እና ለእስራኤል ቤት
ሁለቱ ሃሳቦች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ቤት" የሚለው ቃል የእስራኤልን ትውልዶች የሚወክል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ነገር ግን፣ "ህዝብ" እና "ቤት" የሚሉት ሁለቱም ቃላት ምናልባት የእስራኤልን ወታደሮች የሚወክሉ ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ናቸው። "ለእስራኤላውያን ወታደሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እንዲሁም ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
ያህዌ
ይህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ራሱን ለህዝቡ የገለጸበት ስም ነው። ይህ እንዴት እንደሚተረጎም የትርጉም ስለ ያህዌ የቃል ትርጉም ገጽን ይመልከቱ)
በሰይፍ ወደቁ
እዚህ ስፍራ "ወደቁ" የሚለው መገደልን በትሁት መንገድ የሚገልጽ ነው። እንደዚሁም፣ "ሰይፍ" ውጊያን ይወክላል/ይገልጻል። ይህ በዚህ ስፍራ "ተገድለዋል" ማለት ነው። "በጦርነት ሞተዋል" ወይም "ጠላቶች በጦርነቱ ገደለዋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
አንተ ከየት ነህ?
በ2ሳሙኤል 1፡8 ውስጥ ሰውየው አስቀድሞውኑ አማሌቃዊ መሆኑን ገልጽዋል። ዳዊት ሰውየው ይህንን በግልጽ እንዲያረጋግጥለት ይጠይቀዋል፣ ምክንያቱ ዳዊት በሰውየው ላይ ጽኑ ፍርድ ሊፈርድበት ስለሆነ ነው።
2 Samuel 1:14
በእጅህ... ያህዌ የቀባውን ስትገድል ስለ ምን አልፈራህም?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ያገለገለው ሰውየውን ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እጅህ... እርሱ የቀባውን ሲገድል ያህዌን መፍራት ነበረብህ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ የቀባው ንጉሥ
ይህ የሚያመለክተው ሳኦልን ነው።
በገዛ እጆችህ
ይህ ሀረግ የሚገልጸው ራስህ አንድ ነገር ማድረግህን ነው። "ራስህ" ወይም "በግል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
መትተህ ጣለው/ውደቅበት
የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም "ግደለው" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልቱ)
ደምህ በራስህ ላይ ነው
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚያመለክተው "ደም ማፍሰስ" የሚለውን ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን የሚያያዘውም ከሞት ጋር ነው። እዚህ ስፍራ "ራስህ" የሚለው ሰውየውን እና ተጠያቂ መሆኑን የሚያመለክት ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "ለሞትህ ራስህ ተጠያቂ ነህ" ወይም "ለሞትህ ምክንያት የሆንከው ራስህ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
የራስህ አፍ በራስህ ላይ መስክሯል
እዚህ ስፍራ "የራስህ አፍ" የሚለው የሚያመለክተው ሰውየውን ራሱን ነው። "በራስህ ላይ መስክረሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 1:17
አጠቃላይ መረጃ፡
ዳዊት ለሳኦልና ለዮናታን የሀዘን እንጉርጉሮ ተቀኘ
የቀስት እንጉርጉሮ
ይህ የእንጉርጉሮው ርእስ ነበር
በያሻር መጽሐፍ የተጻፈ ነበር
ይህ ለአንባቢው ወደፊት ምን ተደርጎ እንደነበር እንዲያውቅ በዝማሬው ላይ ተጨማሪ የመረጃ ዳራ ሆኖ የተጻፈ ነው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ) የያሻር መጽሐፍ "ያሻር" የሚለው ቃል ትርጉሙ "ቀጥተኛ/በተጠንቀቅ" ማለት ነው። "የውጊያ ውሎ" መጽሐፍ በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ክብር፣እስራኤል፣ ሞቷል
"የአንተ ክብር" የሚለው ሳኦልን ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሃያሉ
"ሃያል" የሚለው ሀረግ ሳኦልን እና ዮናታንን ሁለቱንም ያመለክታል። ይህ ስማዊ ቅጽል የብዙ ቁጥር ነው፤ "ሃያላኑ" ተብሎ ሊገለጽም ይችላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ስማዊ ቅጽል የሚሉትን ይመልከቱ)
ወደቀ
"ወደቀ" የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ "ሞተ" ማለት ነው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
ይህንን በጌት አትናገሩ... በአስቀሎና መንገዶችም አታውጁ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የተደገሙትም የግጥሙ እንጉርጉሮ ክፍል ሆነው ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጌት...አስቀሎና
ጌት እና አስቀሎና ከፍልስጥኤማውያን ታላላቅ ከተሞች ሁለቱ ናቸው። ሳኦልን እና ዮናታንን የገደሉት ፍልስጥኤማውያን ናቸው።
የፍልስጥኤም ሴት ልጆች ሃሴት እንዳያደርጉ... ያልተገረዙት ሴት ልጆች ክብረ በዓል እንዳያደርጉ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤የተደገሙትም የግጥሙ ክፍል ሆነው ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ያልተገረዙት ሴት ልጆች
ይህ ሀረግ የሚያመለክተው እንደ ፍልስጥኤማውያን ያሉትን ያህዌን የማይከተሉ ህዝቦችን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 1:21
የጊልቦዓ ተራሮች
ዳዊት የእርሱን እንጉርጉሮ እንደሚሰሙት አድርጎ በቀጥታ ለ"ጊልቦዓ ተራሮች" ይናገራል። (አፖስትሮፊ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠልም ሆነ ዝናብ አይገኝባችሁ
ዳዊት ንጉሥ ሳኦል በጦርነት የሞተበትን ምድር ይረግማል፣ ይህ የሚያደርገው እግዚአብሔር ለቀባው ነጉሥ ካለው ታላቅ አክብሮት/ውዳሴ የተነሳ ነው
የሃያላኑ ጋሻ ረከሰ
እዚህ ስፍራ "ሃያል" የሚለው የሚያመለክተው ሳኦልን ነው። ጋሻው የረከሰበት ምክንያት ምድር ላይ በመውደቁ እና የንጉሡ ደም በላዩ ስለፈሰሰበት ነበር። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የሳኦል ጋሻ ከእንግዲህ በዘይት አይቀባም
የሳኦል ጋሻ ከቆዳ የተሰራ ነበር። ጋሻውን ለመንከባከብ በዘይት ይወለወል ነበር። "ከእንግዲህ ለሳኦል ጋሻ ማንም ግድ አይለውም"
ከተገደሉት የፈሰሰው ደምና ከታላላቆቹ አካል የዮናታን ቀስት ወደ ኋላ አላለም፣ ደግሞም የሳኦል ሰይፍ ባዶውን አይመለስም
ሳኦል እና ዮናታን እዚህ ስፍራ ላይ የቀረቡት ብርቱ እና እጅግ ጀግና ተዋጊዎች ሆነው ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሳኦል ሰይፍ ባዶውን አይመለሰም
የሳኦል ሰይፍ የተገለጸው በገዛ ራሱ መመለስ እንደሚችል ህይወት እንዳለው ነገር ሆኖ ነው። ባዶውን ከመመለስ ይልቅ፣ የገደላቸውን የሳኦልን ጠላቶች ደም ይዞ ይመጣ ነበር። (ሰውኛ ዘይቤ እና ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 1:23
በሞታቸውም አልተለያዩም ነበር
"አልተለያዩም ነበር" የሚለው ሀረግ የዋለው ሁልጊዜም አብረው ነበሩ የሚለውን ለማጉላት ነው። "በሞት እንኳን አብረው ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ከንስር ፈጣኖች ነበሩ፣ ከአንበሶች ይልቅ ጠንካሮች ነበሩ
ሳኦል እና ዮናታን የተገለጹት ከንስር ፈጣኖች እንደ ነበሩ እና ከአንበሳ ይልቅ ጠንካሮች እንደነበሩ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማን በሐምራዊ ቀሚስና አለበሳችሁ ማንስ አስጌጣችሁ፣ ማን በልብሳችሁ ላይ የወርግ ጌጥ አደረገላችሁ
"ማን ምርጥ ልብስና ጌጥ ሰጣችሁ።" እነዚህ ሁለት ሀረጋት፣ ለሴቶቹ ውድ እና የሚስቡ ልብሶች መሰጠታቸውን የሚገልጽ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 1:25
ሀያላኑ በጦርነቱ መሃል እንዴት ወደቁ
ይህ ሀረግ በቁጥር 27 ላይ የእስራኤል ምርጥ ተዋጊዎች መሞታቸውን አጉልቶ ለማሳየት ተደግሟል። "ሀያላኑ ሰዎች በጦርነቱ ሞቱ/ ሀያላኑ እንዴት ወደቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ሀያላኑ
እዚህ ስፍራ "ሀያል" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥርን ሲያመለክት፣ ሳኦልን እና ዮናታንን ብቻ ሳይሆን መላውን የእስራኤል ወታደሮች ሊያመለክት ይችላል። "ሀያል ጦረኞች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ወደቀ
"ወደቀ" የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ "ሞተ" ማለት ነው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
ዮናታን ተገደለ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዮናታን በጦርነቱ ውስጥ ሞተ" ወይም "ጠላት ዮናታንን ገደለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በከፍታ ስፍራችሁ
ዳዊት ይህንን የግጥሙን ክፍል ለጊልቦዓ ተራሮች በ2ሳሙኤል 1:21 እንደተናገረው መናገሩን ይቀጥላል። (አፖስትሮፊ የሚለውን ይመልከቱ)
ወንድሜ ዮናታን
እዚህ ስፍራ "ወንድም" የሚለው ቃል የዋለው በጣም ቅርብ ወዳጅ/ጓደኛ በሚል ስሜት ነው።
የአንተ ፍቅር ለእኔ፣ ከሴት ፍቅር ይልቅ አስደናቂ ነበር
እዚህ ስፍራ "ፍቅር" የሚለው ቃል የዋለው በጓደኝነት እና ታማኝነት ስሜት ነው። ዮናታን ለዳዊት ያለው ታማኝነት አንዲት ሴት ለባሏ እና ለልጆችዋ ካላት ታማኝነት እንኳን የበለጠ ነበር።

Chapter 2
2 Samuel 2:1
ከዚህ በኋላ
"ዳዊት ለሳኦል እና ዮናታን ሞት ካለቀሰ/ካዘነ በኋላ"
ከይሁዳ ከተሞች ወደ አንደኛዋ ለመውጣት
በዚህን ጊዜ ዳዊት በጽቅላግ ነበር። ዳዊት "መውጣት" የሚለውን ሀረግ የተጠቀመው ጺቅላግ ከይሁዳ ይልቅ ከባህር ወለል ዝቅ ብላ ስለምትገኝ ነው። "ከይሁዳ ከተሞች ወደ አንዲቱ ወጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ዳዊት ከሁለቱ ሚስቶቹ ጋር ወጣ
በዚህን ጊዜ ዳዊት በጽቅላግ ነበር። ተራኪው "መውጣት" የሚለውን ሀረግ የተጠቀመው ጺቅላግ ከኬብሮን ይልቅ ከባህር ወለል ዝቅ ብላ ስለምትገኝ ነው። ዳዊት ከሁለቱ ሚስቶቹ ጋር ወደ ኬብሮን ወጣ።
2 Samuel 2:4
ንጉሥ ዳዊት ተቀባ
በዚህ ተምሳሌታዊ ድርጊት፣ በዳዊት ራስ ላይ ዘይት ያፈሰሱት ንጉሥ ሆኖ መመረጡን ለማሳየት ነው። (ተምሳሌታዊ/ትዕምርታዊ ድርጊት)
የይሁዳ ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የዋለው "ነገድ" በሚል ትርጉም ነው። "የይሁዳ ነገድ"
ኢያቢስ ገለዓድ
ይህ በገለዓድ ግዛት የሚገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 2:6
አጠቃላይ መረጃ፡
ዳዊት ከኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ጋር ተነጋገረ።
እነዚህ ነገሮች
ሳኦልን ቀበሩት
እጆቻችሁ ይጠንክሩ
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚያመለክተው የኢያቢስ ገለዓድን ሰዎች ነው። "ጠንክሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሥ እሆን ዘንድ ቀብተውኛል
በዚህ ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት፣ በዳዊት ራስ ላይ ዘይት ያፈሰሱት ንጉሥ ሆኖ መመረጡን ለማሳየት ነው። (ምልክታዊ/ትዕምራታዊ ድርጊት)
2 Samuel 2:8
ኔር... ኢያቡስቴ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
መሃናይም... ገለዓድ... ኢይዝራኤል
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 2:10
የይሁዳ ቤት ዳዊትን ተከተለው
የዳዊትን ተዕዛዝ መቀበል የተገለጸው እርሱን "መከተል" ተደርጎ ነው። "የይሁዳ ነገድ ዳዊትን ንጉሣቸው አድርገው ታዘዙት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኝ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የዋለው "ነገድ" በሚል ትርጉም ነው።
2 Samuel 2:12
አቤኔር... ኔር... አቤኔር...ሳኦል... ጽሩያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 2:16
አብረው ወደቁ
ሞቱ የሚለው በትሁት መንገድ የተገለጸበት ነው። "ሁለቱም ሞቱ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
የሰይፍ ምድር
ይህ በዚያ ምን እንደሆነ/እንደተፈጸመ ለሰዎች ለማስታወስ የተሰጠ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
በዚያን ቀን ውጊያው እጅግ የከፋ ነበር
ይህ የወጣቶቹን ግጥሚያ ተከትሎ የመጣ ታላቅ ጦርነት መሆኑን በሚገባ ለመግለጽ ሊረዳ ይችላል። "ከዚያ የተቀሩትም ደግሞ መዋጋት ጀመሩ። በዚያን ቀን እጅግ ጽኑ ውጊያ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 2:18
ጽሩያ... ኢዮአብ... አቢሳ... አሣሄል... አቤኔር
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አሳኤል እግሮቹ እንደ ዱር ሚዳቋ ፈጣን ነበር
እዚህ ስፍራ አሳኤል የተነጻጸረው እጅግ ፈጣን ሯጭ ከሆነው እንስሳ ከሚዳቋ ጋር ነው። "አሳኤል እጅግ ፈጥኖ መሮጥ ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የዱር ሚዳቋ
ይህ ትንሽ፣ አራት እግር ያለው እና በራሱ ላይ ሁለት ትልልቅ ቀንዶች ያሉት በፍጥነት የሚሮጥ እንስሳ ነው።
ወደ የትኛውም አቅጣጫ ዘወር ሳይል እርሱን ተከተለው
እዚህ ስፍራ "ዘወር ሳይል" የሚለው የተገለጸው የአቤኔርን ፍለጋ እንዴት በቅርበት እንደተከተለው በአሉታዊ መልኩ ትኩረት ለመስጠት ነው። "በሄደበት ሁሉ ተከተለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
2 Samuel 2:20
አሣሄል
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ዞር በል...ወደ ቀኝህ ወይም ወደ ግራህ ፈቀቅ በል
"እኔን ማሳደድህን አቁም... አቤኔርን ማሳደድህን አቁም"
ከወጣቶቹ ወንዶች መሃል አንዱን ጎበዝ ያዝና ትጥቁን ቀማው
አቤኔር አሳሄልን የአቤነርን ያህል አደገኛ ሊሆን የማይችልን ሌላ ወጣት ወታደርን እንዲገድል እና እንዲዘርፍ ይጠይቀው ነበር። እርሱ አሳሄልን ሊገድለው አልፈለገም።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"ከሌላ ወታደር ጋር ተዋግተህ መሳሪያውን ምርኮ አድርገህ ውሰድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 2:22
ለምን ከምድር ጋር ላጣብቅህ?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ አሳሄልን ስላጋጠመው አደጋ ለማስጠንቀቅ ውሏል። "ወደ ምድር ማጣበቅ" የሚለው ትሁት በሆነ አገላለጽ "መግደል" ማለት ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)
ወንድምህን ኢዮአብን እንዴት ፊቴን አቅንቼ ማየት እችላለሁ?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ አቤኔር መዋጋት እና አሳኤልን መግደል እንደማይፈልግ አጉልቶ ይገልጻል፣ ለዚህም ምክንያቱ ጉዳዩ አቤኔር ከኢዮአብ ጋር ያለውን ግንኙነት ሊያጠፋ የሚችል መሆኑ ነው። እዚህ ላይ "ፊቴን ወደ ኢዮአብ አቀናለሁ" የሚለው ኢዮአብን ለማየት እጅግ አፍራለሁ የሚል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ወንድምህን ኢዮአብን ለማየት እጅግ አፍራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)
ወደ ጎን ዘወር በል
ይህ ማለት "ቁም" ወይም "ማሳደድህን አቁም" ማለት ነው።
የጦሩ ዱልዱም ጫፍ
ይህ የሚያመለክተው ስል ያልሆነውን ወይም ምንም ነገር ለመውጋት ያልተበጀ የጦሩ መያዣ ስፍራ ነው። አቤኔር ይሞክር የነበረው አሳኤል እንዳይከተለው ማድረግ ብቻ እንጂ ሊገድለው አላሰበም የሚል አንድምታ አለው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 2:24
አቢሳ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የአማ ኮረብታ…ገባአን
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 2:26
አቤኔር ተጣራ
"አቤኔር ጮኸ"
ሰይፍ ለዘለዓለም ያጠፋልን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ አጉልቶ የሚያሳየው ጦርነቱ እጅግ ለረጅም ጊዜ መቆየቱን ነው። እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚያመለክተው ጦርነቱን ነው። በጦርነቱ ውስጥ የተካሄደው ግድያ የተገለጸው ወታደሮቹን የዱር አውሬ እንደበላቸው ተደርጎ ነው። "ሰይፎቻችንን እርስ በእርስ ለመዋጋት እና ለመገዳደል መጠቀማችንን መቀጠል የለብንም" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እንዲሁም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
በመጨረሻ ይህ መራራ እንደሚሆን አታውቅምን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተራዘመ ጦርነት ለበለጠ መከራ እንደሚዳርግ ኢዮአብ እውቅና እንዲሰጥ ለማስገደድ ውሏል። እዚህ ስፍራ "መራራ" የሚለው ቃል እጅግ አሰቃቂ የሆነን መከራ ለመግለጽ የዋለዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። " ይህ ከቀጠለ እጅግ የከፋ ችግር እንደመሆን በሚገባ ታውቃለህ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)
የአንተ ሰዎች ወንድሞቻቸውን ከማሳደድ ይመለሱ ዘንድ የማትናገረው እስከ መቼ ድረስ ነው?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ኢዮአብ እስራኤላውያን ወገኖቻቸውን መውጋት እንዲያቆም ለማሳመን የታቀደ ነው። እዚህ ስፍራ "ወንድም" የሚለው ቃል የዋለው የእስራኤል አገር ሰዎችን ለመወከል ነው። "እስራኤላውያን እርስ በእርሳቸው እንዳይገዳደሉ አሁን ይህንን አቁም!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
ሕያው እግዚአብሔርን!
ይህ በጣም ጠንካራ መሃላ ነው። "እግዚአብሔር ምስክሬ ነው" ወይም "እግዚአብሔር ያልኩት እውነት መሆኑን ያጸናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ያንን ካልተናገርክ … እስከ ማለዳ ወንድሞቻቸውን ያሳዱ
አቤኔር ለኢዮአብ በጥበብ ካልመለሰለት፣ ይህ መላምታዊ ሃሳብ ሊሆን የሚችለውን ነገር ያስረዳል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 2:28
መለከት ነፋ
መለከቶች ሩቅ ስፍራ ለሚገኙ ወታደሮች ትዕዛዝ ለማስተላለፍ ያገለግሉ ነበር። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እስራኤልን አላሳደደም
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እስራኤላውያን ወታደሮችን ነው። "እስራኤላውያን ወታደሮችን ማሳደድ አልቀጠሉም" (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ዓረባ… መሃናይም
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 2:30
አሣሄል
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአበኔር ጋር 360 የብንያም ሰዎች
"ከብንያም 360 ሰዎች አቤኔርን የተከተሉ" አቤኔር አልሞተም
360 ሰዎች
"ሶስት መቶ ስልሳ ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ከብንያም
ይህ ሀረግ "ከብንያም ነገድ" ማለት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አሣሄልን አነሱት
"የአሣሄልን በድን ይዘው ሄዱ"
በኬብሮን ቀኑ መሸቶ ነጋባቸው
"በማግስቱ ንጋት ላይ ኬብሮን ደረሱ"

Chapter 3
2 Samuel 3:1
አሁን
እዚህ ስፍራ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ላይ መቆሚያ ለማድረግ ነው። በዚህ ስፍራ ሳሙኤል በዳዊት እና በሳኦል ደጋፊዎች መካከል ስለ ተደረገው ጦርነት መረጃ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)
ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የዋለው "ደጋፊዎች" ለማለት ነው። እየበረታ እና ይበልጥ እየበረታ ሄደ ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ዳዊትን የሚደግፉት ሰዎች ጨመረ ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እየደከመ እና ይበልጥ እየደከመ ሄደ
ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር የሳኦልን ቤተሰብ የሚደግፉት ሰዎች ቀነሰ ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 3:2
ለዳዊት ወንድ ልጆች ተወለዱለት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የዳዊት ሚስቶች ስድስት ወንድ ልጆችን ወለዱ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
አንደኛ ልጅ… ሁለተኛ ልጅ… ሶስተኛ
ይህ የዳዊት ልጆች የቁጥር ቅደም ተከተል ነው። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
አኪናሆም…አቢግያ… መዓካ
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው። እነዚህ የዳዊት ሚስቶች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ኪልአብ…ናባል… ተልማይ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 3:4
አራተኛ ልጅ… አምስተኛ ልጅ… ስድስተኛው
ይህ የዳዊት ልጆች የቁጥር ቅደም ተከተል ነው። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
አዶንያስ… ሰፋጥያስ…ይትረኃም
እነዚህ የዳዊት ወንድ ልጆች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አጊት…አቢጣል…ዔግላ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እነዚህ የዳዊት ሚስቶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 3:6
እንዲህም ሆነ
ይህ በዳዊት ደጋፊዎች እና በሳኦል ቤት ትግል ታሪክ አካሄድ አዲስ ትዕይንትን ያስተዋውቃል። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
የሳኦል ቤት
ይህ ከሳኦል ቤት እና ደጋፊዎች መሃል ከሳኦል ሞት በኋላ ማን ርስቱን መቆጣጠር ይገባኛል እንደሚል የሚያመለክት ነው
የዳዊት ቤት
ይህ የዳዊትን ደጋፊዎች የሚያመለክት ነው።
ከሳኦል ቤት አቤኔር ራሱን አበረታ
የአቤኔር በሳኦል ቤት ላይ ሃይሉን እየጨመረ መሄድ የተገለጸው፣ ልክ በአካል ጠንካራ እየሆነ እንደመጣ ተደርጎ ነው። "አቤኔር በሳኦል ቤት እና ደጋፊዎች ላይ የበለጠ ሃይል አገኘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሪጽፋ...አኪ
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ኢያቡስቴ
ይህ የወንድ ስም ነው፤ የሳኦል ልጅ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአባቴ ቁባት ጋር ለምን ተኛህ?
ኢያቡስቴ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው እንደ ንጉሥ ራሱን የቆጠረውን አቤኔርን ለመገሰጽ ነበር። "ከአባቴ ቁባት ጋር ለመተኛት መብት የለህም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
አብረህ ተኛህ
ይህ ለወሲባዊ ግንኙነት ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው።
2 Samuel 3:8
እኔ ለይሁዳ የምወግን፣ የውሻ ራስ ነኝን?
አበኔር ስለ ራሱ፣ እስራኤላውያን ለመገበው ታማኝ ነው ብለው እንደሚቆጥሩት ውሻ ሁሉ እርሱ የውሻ ራስ ተደርጎ እንደተቆጠረ ይናገራል። እዚህ ስፍራ "ለይሁዳ መሆን" የሚለው የሚያመለክተው አቤኔር ዳዊት ለሚገኝበት ለይሁዳ እንጂ ለሳኦል ቤት አለመቆጠሩን ነው። "እኔ ክጄ ለይሁዳ ሆንኩን?" ወይም "እኔ ለዳዊት የምሰራ ከሃዲ አይደለሁም!" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
በዳዊት እጅ ላይ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚወክለው ለማሸነፍ ያለን አቅም ነው። "በዳዊት መሸነፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን አንተ አሁን ይህችን ሴት በሚመለከት ጥፋተኛ አድርገህ ትከሰኛለህ?
አበኔር ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው ኢያቡስቴን ለመገሰጽ ነው። አቤኔር በእርግጥ ከሪጽፋ ጋር ስለ መተኛቱ ወይም በሃሰት ስለመወንጀሉ ግልጽ የሆነ ነገር የለም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጌሜዎች እነዚህ ናቸው፡ 1) አበኔር ጥፋተኛ የሚሆነው፡ "ከዚህች ሴት ጋር በመተኛቴ ልትበሳጭ አይገባህም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው ወይም 2) አበኔር ጥፋተኛ የማይሆነው፡ "ከዚህች ሴት ጋር ተኝተሃል ብለህ ልታስብ አይገባህም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 3:9
እኔ ይህን ካላደረገኩ፣ እግዚአብሔር ይህንን በእኔ ላይ ያድርግ...ከዚህም በላይ ይጨምርብኝ
በዚያን ዘመን የዚህ አይነት መሃላ ነበር። አበኔር መሃላውን ካልጠበቀ እግዚአብሔር እጅግ አድርጎ እንዲፈርድበት ይጠይቃል። የእናንተ ቋንቋ መሃላን የሚገልጽበት መንገድ ሊኖረው ይችላል። "እኔ ይህ ካላደረግኩ እግዚአብሔር እንዲህ ይቅጣኝ " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
የሳኦል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚያመለክተው የሳኦልን ቤት እና ከሳኦል ሞት በኋላ በህይወት የተረፉትን ነው። "የሳኦል ቤትና ደጋፊዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
የዳዊት ዙፋን
ይህ ሀረግ የዳዊትን የንጉሥነት ስልጣን ያመለክታል
2 Samuel 3:12
ለዳዊት
አንዳንድ ቅጂዎች "በኬብሮን በነበረበት ጊዜ" የሚል ይጨምራሉ፣ ሌሎቹ ግን ይህን አይጨምሩም። በእናንተ ብሔራዊ ቅጂ ውስጥ ካለ ይህንን መጨመር ሊኖርባችሁ ይችላል። (የቅጂ ልዩነቶች የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የማን ምድር ነው?
የዚህ ጥያቄ የመጀመሪያው ጽሁፍ ግልጽ አይደለም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አቤኔር ምድሪቱን ለዳዊት ለመስጠት ሃይል አለው። "ይህ ምድር የእኔ ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ዳዊት ምድሪቱን ለመግዛት በእግዚአብሔር የተመረጠ ነው፡ "ምድሪቱ በትክክል የአንተ ናት!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እጄ ከአንተ ጋር ነው
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚወክለው አበኔር ለዳዊት ያቀረበለትን እርዳታ ነው። "እኔ እረዳሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በመጀመሪያ ሜልኮልን ካላመጣሃት በስተቀር ፊቴን ማየት አትችልም
ዳዊት አቤኔርን የሚገኛኝበትን ሁኔታ ገልጽዋል። እዚህ ስፍራ "ፊት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱን ዳዊትን ነው። "በመጀመሪያ ሜልኮልን ወደ እኔ ካላመጣሃት በስተቀር ልታየኝ አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ሚልኮል
ይህ የሳኦል ሴት ልጅ ስም ነው።የዳዊት የመጀመሪያ ሚስቱ ነበረች። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 3:14
አንድ መቶ የፍልስጥኤማውያን ሸለፈቶች
ይህ ሚልኮልን ለማግባት ሳኦል ይፈቅድለት ዘንድ ዳዊት የገደላቸውን ሰዎች ቁጥር ይወክላል። እነዚህ ሰዎች እዚህ ስፍራ የተቆጠሩት በ"ሸለፈቶቻቸው" ነው። "ሸለፈት" የወንድን መራቢያ ብልት የሚሸፍን የቆዳ እጥፋት ነው። (ቁጥሮች እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከባሏ ወሰዳት
ፈልጢኤል የሚልኮል ሁለተኛ ባሏ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ብራቂም
ይህ የአንድ መንደር ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 3:17
አሁን አድርጉት
"ስለዚህ አሁን ዳዊትን ንጉሣችሁ አድርጉት"
በባሪያዬ በዳዊት እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን ለማሸነፍ ያለውን ሃይል ነው። "እኔ ባርያዬን ዳዊትን አበረታዋለሁ ደግሞም" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የፍልስጥኤማውያን እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ፍልስጥኤማውያን በእስራኤላውያን ላይ ያላቸውን ሃይል ነው። "የፍልስጥኤማውያን ሃይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የጠላቶቻቸው እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው በእስራኤላውያን ላይ ያለን ሃይል ነው። "የጠላቶቻቸው ሁሉ ሃይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 3:19
የብንያም ህዝብ...መላው የብንያም ቤት
እነዚህ ሁለት ሃሳቦች፣ የእስራኤል አንድ ነገድ የነበሩትን የብንያምን ትውልድ ያመለክታሉ። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሃያዎቹ የእርሱ ሰዎች
ከአቤኔር ጋር የመጡ ወንዶች ቁጥር። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 3:21
መላው እስራኤል
ይህ ሀረግ "መላው የእስራኤል አገር" ማለት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህም ዳዊት አበኔርን አሰናበተው
በወዳጅነት ተለያዩ። ዳዊት በአበኔር አልተበሳጨም።
2 Samuel 3:22
ምርኮ
እነዚህ ከጠላት የተወሰዱ ነገሮች ናቸው
አበኔር በኬብሮን ከዳዊት ጋር አልነበረም
አበኔርወደ ቤት ለመመለስ ተነስቶ ነበር
ለኢዮአብ ነገሩት
"የሆነ ሰው ለኢዮአብ ነገረው"
ኔር
ይህ የወንድ ስም ነው። የሳኦል ቅድም አያት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 3:24
ያደረግከው ምንድን ነው?
ኢዮአብ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው አበኔርን በሰላም በማሰናበቱ ዳዊትን ለመገሰጽ ነው። "ይህን ማድረግ አልነበረብህም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ለምን አሰናበትከው፣ እና እርሱ ሄደ?
ኢዮአብ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ዳዊት አበኔር እንዲያመልጥ በመተዉ ለመገሰጽ ነው። ይህ በአረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "አበኔር እዚህ ነበር አንተ አሰናበትከው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የምታደርገውን ነገር ሁሉ…አታውቅምን?
ኢዮአብ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው አበኔር በዳዊት ላይ እያሴረ እንደሆነ ሊያሳምነው ነው። "አንተ በእርግጥ አታውቅምን… የምታደርገውን ነገር ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የሴይር ጉድጓድ
"ሴይር" የውሃ ጉድጓዱ የሚገንበት ስፍራ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 3:27
የበሩ መግቢያ መሃል
ይህ የሚያመለክተው በኬብሮን በከተማይቱ ቅጥር ካሉት በሮች አንዱን ነው። በዩዲቢ ትርጉም ውስጥ እንደተመለከተው የከተማ በሮች የተገነቡት በከተማይቱ ቅጥር እንደሚገኙ ግንቦች ክፍል ሆነው ነው። በመተላለፊያ መንገዶቹ አጠገብ ወደ እንግዶች መቀበያ እና ንግድ እንዲሁም የፍትህ ስርአቶች ወደ ሚካሄዱባቸው ክፍሎች የሚወስዱ በሮች ይገኛሉ። ኢዮአብ አበኔርን የገደለው ምናልባት ከእነዚህ ክፍሎች በአንደኛው ነው።
የአሣኤል ደም
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው ቃል የተያያዘው ከአሣኤል ሞት ጋር ነው። "የአሣኤል ሞት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አሣኤል
ይህ ወንድ የሆነ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 3:28
ኔር… አቢሳ…አሣኤል
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የአበኔር ደም
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአበኔርን ሞት ነው። ተመሳሳዩን ሀረግ በ2ሳሙኤል3:27 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "የአበኔር ሞት" ወይም "የአበኔር መገደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በኢዮአብ ራስ እና በአባቱ ቤት ሁሉ ላይ ይውደቅ
የዚህ ሀረግ ትርጉም የጥፋቱ ውጤት በኢዮአብ እና በቤቱ ላይ አንዳች ከባድ ነገር እንደሚናድባቸው ያህል ይድረስ ማለት ነው። "ሁልጊዜ ለኢዮአብ እና ለአባቱ ቤት የመከራ ምክንያት ይሁንባቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በአባቱ ቤት ላይ ሁሉ
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ትውልዶች የሚለውን ነው። "የኢዮአብ አባት ትውልዶች ሁሉ) በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የሚወድቅ አይታጣ
ይህ ድርብ አሉታ የሚያጎላው ሁሌም የተዘረዘሩት ችግሮች የሚገጥመው ሰው የማይታጣ መሆኑን ነው። "ሁሌም በዚያ ይህ ይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በሰይፍ ይገደል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሃይል የሆነ ሞትን ነው። "በሃይል ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ምግብ ይጡ
"ይራቡ"
2 Samuel 3:31
ልብሳችሁን ቅደዱ፣ ማቅ ልበሱ
እነዚህ ሀዘናቸውን እና ትካዜያቸውን ለመግለጽ ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊቶች ነበሩ። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊቶች)
ንጉሡ አነባ ጮኾም አለቀሰ
"አለቀሰ" እና "ጮኾ አለቀሰ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ዳዊት ምን ያህል ለአበኔር እንዳዘነ ትኩረት ይሰጣሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 3:33
አበኔር ሰነፍ እንደሚሞት መሞት አለበትን
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ሞቱ አግባብ የሌለው መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። "አበኔር በውርደት መሞት አልነበረበትም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እጆችህ አልታሰሩም። እግሮችህም በሰንሰለት አልተያዙም
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ሃሳብን ይገልጻሉ። በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ሊቀርቡ ይችላሉ። "በማናቸውም መንገድ በእስርቤት ያለህ ወንጀለኛ አልነበርክም" ወይም "ሙሉ ለሙሉ ከስህተት ንጹህ ነበርክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እጆችህ አልታሰሩም ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም እጆችህን አላሰረም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እግሮችህ አልታሰሩም ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም እግሮችህን በሰንሰለት አላሰረም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የፍትህ አልባነት ልጆች
ይህ የሚያመለክተው ፍትህ አልባ የሆኑ ሰዎችን ወይም ክፉዎችን ነው። "ክፉ ሰዎች"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 3:35
ህዝቡ ሁሉ መጡ
ይህ ይሁን ተብሎ የተደረገ ማጋነን የዋለው የእስራኤል ህዝብ ዳዊትን በሀዘኑ ሊያጽናኑት መፈለጋቸውን ለማሳየት ነው። "ብዙ ህዝብ መጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
እንዲህ ባላደርግ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ያድርግብኝ፣ እንዲህም ይጨምርብኝ
ይህ በዚያ ዘመን የነበረ የመሃላ አይነት ነው። ዳዊት እግዚአብሔርን ፀሐይ ከመጥለቋ አስቀድሞ አንዳች ነገር ቢቀምስ በጽኑ እንዲቀጣው ይጠይቃል። የእናንተ ቋንቋ መሃላን የሚያደርግበት መንገድ ሊኖረው ይችላል። "እንዲህ ባደርግ እግዚአብሔር እንዲቀጣኝ እጠይቃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
2 Samuel 3:37
በዛሬው ቀን በኢያሩሳሌም አንድ ልዑል እና ታላቅ ሰው እንደ ወደቀ አታውቁምን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ዳዊት ምን ያህል አበኔርን እንደሚያከብረው ለማሳየት ነው። እዚህ ስፍራ "ወደቀ" የሚለው ቃል "ሞተ" ሚለውን የሚገልጽ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ዛሬ አንድ ታላቅ ልዑል በኢየሩሳሌም መሞቱ በእርግጥ እውነት ነው!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

ልዑል እና ታላቅ ሰው

እነዚህ ሁለት ሀረጋት ሁለቱም የሚያመለክቱት አበኔርን ነው። "ታላቅ ልዑል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሄንዲያዲስ/ ሁለት በ 'እና' የሚገናኙ ቃላት አንድን ጥልቅ ሃሳብ የሚገልጹበት ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኔር...ጽሩያ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጨካኝ

እንደ- እንስሳ

---

Chapter 4

2 Samuel 4:1

ኢያቡስቴ... በዓና...ሬካብ...ሬሞን

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቹ ደከሙ

በዚህ ሀረግ "እጆቹ" የሚለው የሚወከወለው ኢያቡሰቴን ነው። "ኢያቡስቴ ደካማ ሆነ" ወይም "ኢያቡስቴ አቅሙን በሙሉ አጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህን ጊዜ...የሳኦል ልጅ ሁለት ሰዎች ነበሩት

ይህ በዓና እና ሬካብ የተባሉ ሰዎችን ወደ ታሪኩ ያስተዋውቃል። (አዲስ እና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ብኤሮት ጭምር የብንያም ክፍል ተደርጎ ስለተወሰደ፣ እና ብኤሮታውያን ወደ ጌቴም ስለሸሹ እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ ይኖራሉ

እዚህ ስፍራ ላይ ጸሐፊው ስለ ብኤሮት ለአንባቢ የመረጃ ዳራ ይሰጣል። የብኤሮት ግዛት የብንያም ነገድ ምድር ክፍል ነበር። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ብኤሮት ጌቴም

እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 4:4

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ ሀረግ ዋናውን ታሪክ ቆም አድርጎ በኢያቡስቴ በኩል ሳይሆን በዮናታን በኩል የሳኦል ትውልድ ስለሆነው ስለ ሜምፊቦስቴ የመረጃ ዳራ ይሰጣል። ሜምፊቦስቴ ቆየት ብሎ በመጽሐፉ ውስጥ ትልቅ ገጸ ባህሪ ይሆናል። (የመረጃ ዳራ እና አዲስ እና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚሉትን ይመልከቱ)

እግሩ ሽባ የሆነ

ይህ ሀረግ "መራመድ የማይችል" ማለት ነው።

ዕድሜው አምስት አመት

ይህ አባቱ በሞተ ጊዜ የዮናታን ልጅ ዕድሜ ነበር። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ሳኦል እና ዮናታን የተነገሩ ወሬዎች

ይህ የሚያመለክተው ስለ ሞታቸው የተነገረውን ወሬ ነው

ሞግዚት/ነርስ

ትንሽ ልጅን ለመንከባከብ የምትቀጠር ሴት ወይም ልጃገረድ

ሽባ ሆነ

ይህ ሜምፊቦስቴ እንዴት እንደተጎዳ እና መራመድ የማይችል እንደሆነ ይገልጻል።

ሜምፊቦስቴ

ይህ የሳኦል የልጅ ልጅ፣ የዮናታን ወጣት ወንድ ልጅ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 4:5

አጠቃላይ መረጃ

ታሪኩ በ2፡ሳሙኤል4፡2 ላይ ወደሚገኘው የበዓን እና ሬካብ ድርጊቶች ይመለሳል።

የቀኑ ሙቀት

የቀኑ እኩሌታ፣ ቀኑ ሞቃት በሚሆንበት ክፍለ ጊዜ

ስንዴ ማበጠር

"ገለባውን ከስንዴው መለየት"

2 Samuel 4:8

ህይወትህን ይፈልግ ነበር

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር "ሊገድልህ ይፈልግ ነበር" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህያው እግዚአብሔርን

ይህ ዳዊት ሊያደርግ ከሚችላቸው ጠንካራ መሃላዎች አንዱ ነው፣ያህዌ ምስክሬ ነው እንደሚለው። "በያህዌ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴን ያዳነው

እዚህ ስፍራ "ህይወት" የሚለው የሚያመለክተው ራሱን ዳዊትን ነው።ይህ ማለት ያህዌ ዳዊትን በህይወት ጠብቆታል ማለት ነው። "እኔን ያዳነኝ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 4:11

ምን ያህል ይበልጥ... አሁን የእርሱን ደም ከእናንተ እጅ ልፈልግና ከዚህ ምድር ላስወግዳችሁ አይገባኝምን?

ይህ ጥያቄ የቀለው ሰዎቹ በቸልታ የማይታለፍ ከባድ ወንጀል መፈጸማቸውን ለማሳየት ነው። በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እናንተ ይበልጥ ጥፋተኞች ናችሁ! ከእጃችሁ ደሙን መፈለግ እና እናንተን ከዚህ ምድር ማስወገድ የእኔ ሃላፊነት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእጃችሁ ደሙን መፈለግ

"ደሙን" የሚለው ሀረግ የኢያቡስቴን ህይወት ይወክላል። እዚህ ስፍራ "ከእጃችሁ" የሚለው የሚወክለው በ 2 ሳሙኤል 4፡5 የገቡትን ከብኤሮት የሆነው የሬሞን ልጆች ሬካብን እና በዓናን ነው። "በኢያቡስቴ ሞት ተጠያቂ አደርጌ እይዛችኋለሁ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቻቸውን እና እግሮቻቸውን ቆረጡ ደግሞም ሰቀሏቸው

ይህ ኢያቡስቴን ለማክበር የተደረገ ምልክታዊ ድርጊት ነበር። ይህ ተብራርቶ ሊገለጽ ይችላል። "ጭንቅላቱን በመቃብር በመቅበር ኢያቡስቴን አከበሩት" (ምልክታዊ ድርጊት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 5

2 Samuel 5:1

እኛ የአንተ ስጋ እና አጥንት ነን

ይህ ሀረግ "ዘመድ" ማለት ነው። "እኛ ከአንተ ጋር የተዛመድን ነን" ወይም "እኛ ከአንድ ቤተሰብ ነን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙም ሩቅ በማይባል ዘመን

ይህ ታሪካዊ መረጃ ነው። ሳኦል ከዳዊት አስቀድሞ ንጉሣቸው ነበር። (ታሪካዊ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቤን እስራኤልን ትጠብቃለህ፣ ደግሞም እነርሱን ትመራለህ

እነዚህ ሁለት ሀረጋት/አንቀጾች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ያህዌ ዳዊትን ለንጉሥነት እንደመረጠው አጉልተው ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቤን እስራኤልን ትጠብቃለህ፣

እዚህ ስፍራ በህዝብ ላይ መግዛት የሚለው የተገለጸው ለእነርሱ እረኛ መሆን በሚል ነው። "ለህዝብ ለእስራኤል ጥበቃ ታደርጋለህ" ወይም "ህዝቤን እስራኤልን ትመራለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 5:3

ዳዊትን በእስራኤል ላይ ንጉሥ አድርገው ቀቡት

"መቀባት" እግዚአብሔር ዳዊትን ንጉሥ አድርጎ እንደመረጠው እውቅና መስጠታቸውን የሚገልጽ ምልክታዊ ድርጊት ነው። (ምልክታዊ/ትዕምርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 5:6

አጠቃላይ መረጃ፡



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ዳዊት እና የእስራኤል ሰራዊት ኢያሩሳሌምን አጠቁ
በዕውራን እና ሽባዎች ልትባረሩ ካልፈለጋችሁ በስተቀር ወደዚህ አትመጡም
ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር መገለጽ ይችላል። "ወደዚህ ብትመጡ፣ እናንተን ዕውራን እና ሽባዎች እንኳን ሊመልሷችሁ ይችላሉ"
ዕውራን እና ሽባዎች
እዚህ ስፍራ "ዕውራን" እና "ሽባዎች" የሚሉት ስማዊ ቅጽሎች ናቸው። "ማየት የማይችሉ ሰዎች እና መራመድ የማይችሉ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 5:8
ዳዊት፣ "ኢያቡሳውያንን የሚመታ" አለ
ዳዊት የሚነጋገረው ከወታደሮቹ ጋር ነበር። "ዳዊት ለወታደሮቹ እንዲህ አለ፣ ‘የኢያቡስን ሰዎች ማስወጣት የሚፈልግ"
‘ዕውራን እና ሽባዎች'
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)ይህ የሚያመለክተው በእርግጥ ሽባ እና ዐይነ ስውር የሆኑትን ወይም 2)በኢየሩሳሌም ከተማ የሚኖሩ ኢያቡሳውያን ሁሉም ደካማ እና ስንኩላን የሆኑ ያህል የሚቆጥር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ዘይቤ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 5:11
ኪራም
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አናጢዎች
በእንጨት የሚሰሩ
ግንበኞች
በድንጋይ ወይም በጡብ የሚሰሩ
2 Samuel 5:13
ሳሙስ…ሶባብ…ናታን…ሰሎሞን…ኢያቤሐር…ኤሊሱዔ…ናፌቅ…ያፍያ…ኤሊሳማ…ኤሊዳሄ…ኤሊፋላት
እነዚህ የዳዊት ወንዶች ልጆች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእርሱ ብዙ ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ተወለዱለት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ብዙ ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ነበሩት" ወይም "ብዙ ወንዶች እና ሴቶች ልጆችን ወለዱለት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእርሱ የተወለዱለት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሚስቶቹ ለእርሱ የወለዱለት" ወይም "እርሱ ነበረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 5:17
ዳዊት በእስራኤል ላይ ንጉሥ ሆኖ ተቀብቶ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እስራኤል ዳዊትን ንጉሥ አድርጎ ቀብቶት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉም ሊፈልጉት ወጡ
እዚህ ስፍራ "ሁሉም" የሚለው የፍልስጥኤም ሰራዊትን በአጠቃላይ ለማለት ነው። "የፍልስጥኤም ሰራዊት እርሱን ለመፈለግ ወጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
ራፋይም ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 5:19
በኣልፐራሲም
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሞልቶ እንደሚፈነዳ የጎርፍ ውሃ ያህዌ ጠላቶቼን በፊቴ አፈራረሳቸው
በዚህ ስፍራ ዳዊት ያህዌ የሰጠውን ድል የሚገልጸው፣ የጎርፍ ውሃ በዙሪያው የሚገኘውን ስፍራ እንደሚያጥለቀልቅ እና ምድሩን እንደሚሸፍን ደግሞም ጥፋት እንደሚያደርስ አይነት አድርጎ ነው። "ጎርፍ ምድርን እንደሚያጥለቀልቅ ያህዌ ጠላቶቼን አፈራረሳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 5:22
ፍልስጥኤማውያን ዳግም ተመለሱ
እነርሱ "ተመለሱ" የተባለበት ምክንያት ፍልስጥኤማውያን የሚኖሩት ከዳዊት ጠንካራ ይዞታ ዝቅ ባለ ስፍራ ስለሆነ ነው።
የራፋይም ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የበለሳም እንጨቶች/ደን
"በለሳም" አዛፍ አይነት ነው፣ "እንጨቶች" የሚለው በአንድነት የበቀሉ የበለሳም ዛፎችን ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 5:24
ስትሰሙ… የፍልስጥኤም ሰራዊትን ለመጥቃት ያህዌ በፊታችሁ ይሄዳል
ይህ በ 2ሳሙኤል 5:23 ላይ ያህዌ ለዳዊት መስጠት የጀመረው ትዕዛዝ ቀጣይ ክፈል ነው። በዚህ ስፍራ ያህዌ ስለ ራሱ በሶስተኛ መደብ ይናገራል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)
በበለሳም እንጨቶች አናት ላይ በሚነፍሰው ንፋስ የሰልፍ ድምጽ ስትሰሙ
ይህ የሚናገረው ነፋስ በቅጠሎች መሃል ሲያልፍ እንደሚያሰማው አይነት የሰልፈኛ ድምጽ ስለ መስማት ነው። "ነፋስ በበለሳም ዛፎች አናት ላይ ሰልፈኞች እንደሚያሰሙት ድምጽ ሲነፍስ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይምልከቱ)
ገባዖን… ጌዝር
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 6
2 Samuel 6:1
አሁን
ይህ ቃል የታሪኩን አዲስ ክፍል ያመለክታል
የተመረጡ የእስራኤል ወንዶች በሙሉ
ይህ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/የእስራኤልን ሰራዊት ይወክላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሰላሳ ሺህ
"30,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ከይሁዳ በአል የእግዚአብሔርን ታቦት ለማምጣት
ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚወስዱ ተጠቁሟል። "ይሁዳ ውስጥ ከምትገኘው በኣላ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ለመውሰድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያ የእግዚአብሔርን ታቦት ለማምጣት
ኢየሩሳሌም ከሞላ ጎደል ከሁሉም ሌሎች የእስራኤል ስፍራዎች ከፍ ያለች ናት፣ ስለዚህ ለእስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም እንውጣ ወይም ከእርሷ እንውረድ ማለት የተለመደ ነበር።
ወደ ላይ ማምጣት
"ማምጣት" የሚለው ቃል "መውሰድ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። (መሄድ እና መምጣት የሚሉትን ይመልከቱ)
በአል
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
በሰራዊት ጌታ በያህዌ ስም የተጠራ
የያህዌ ስም በታቦቱ ላይ ተጽፎ ነበር
ከኪሩቤል በላይ በዙፋኑ የተቀመጠው
ኪሩብ በቃል ኪዳኑ ታቦት መክደኛ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። የመጸሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት ብዙውን ጊዜ የቃል ኪዳኑ ታቦት፣ በላይ በሰማይ በዙፋኑ የተቀመጠው የያህዌ እግሮች ማረፊያ እንደሆነ አድርገው ይናገራሉ። "በቃል ኪዳኑ ታቦት ከኪሩብ በላይ በዙፋኑ የተቀመጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው/የነገሰው
በዙፋን ላይ መቀመጥ
2 Samuel 6:3
አጠቃላይ መረጃ፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ዳዊት እና የእስራኤል ህዝብ ሰራዊት የቃል ኪዳኑን ታቦት አመጡ/አንቀሳቀሱ
አሚናዳብ…ዖዛ…አሒዮ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
መላው የእስራኤል ቤት
ይህ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚወክለው የእስራኤልን ህዝብ ነው። "ከእርሱ ጋር የነበሩ ሌሎች እስራኤላውያን ሁሉ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ታምቡሪኒ/ከበሮ መሰል የሙዚቃ መሳሪያ
ታምቡሪኒ ከአናቱ ከበሮ የሚመስል በዙሪያው ቁርጥራጭ ብረታ ብረት ያሉት ሲመታ ወይም ሲያርገፈግፉት ሙዚቃዊ ድምጽ የሚሰጥ መሳሪያ ነው። (ያልታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
ራትል/ የቅል ቅርጽ ያለው የሚንሸዋሸዋ /ጽናጽል መሰል የሙዚቃ መሳሪያ
በሽፋኑ ውስጥ የሚገኝና ጠጣር የሆኑ ነገሮች በውስጡ የያዘ ሲርገፈገፍ ዜማዊ ድምጽ የሚሰጥ የሙዚቃ መሳሪያ። (ያልታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
ሲምባል/ ሙዚቃ ማጀቢያ ሳህን መሰል የሙዚቃ መሳሪያ
ሁለት ስስ፣ ክብ የብረት ሳህን መሰል የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ሲጋጭ ከፍ ያለ ሙዚቃዊ ድምጽ ይሰጣል
2 Samuel 6:6
ናኮን
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የያህዌ ቁጣ ነደደ
እዚህ ስፍራ "የያህዌ ቁጣ" የተገለጸው እሳት እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ኃጢአት ሆነበት
ያህዌ ማንም ታቦቱን እንዳይነካ አዝዞ ስለነበር ዖዛ ታቦቱን መንካቱ ኃጢአት ሆኖበት ነበር። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 6:8
የዖዛ ስብራት
ይህ የቦታ ስም ነው። ተርጓሚ " 'የዖዛ ስብራት' የሚለው ስም 'የዖዛ ቅጣት' ማለት ነው" የሚል የግርጌ ማስታወሻ ሊጨምርበት ይችላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ ማለት ይህ እስከተጻፈበት ጊዜ ድረስ ማለት እንጂ እስከ አሁን እስከ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ማለት አይደለም።
የያህዌ ታቦት እንዴት ወደ እኔ ሊመጣ ይችላል?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት መፍራቱን ለማጉላት ነው። "የያህዌን ታቦት ከእኔ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ይዤ ለመምጣት እጅግ ፈርቻለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 6:10
የጌቱ አቤድ ኤዶም/አቢዳራ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱን ባረከው
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የጌቱን አቢዳራን ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 6:12
አሁን/በዚህ ጊዜ
ይህ ቃል የታሪኩን አዲስ ክፍል ይጀምራል
ለንጉሥ ዳዊት ተነገረው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ለንጉሥ ዳዊት ነገሩት" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
አቢዳራ ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ቤተሰብን ነው። "አቢዳራ እና ቤተሰቡ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔርን ታቦት አመጣ
ኢየሩሳሌም በእስራኤል ከሚገኙ ከሞላጎደል ከሌሎቹ ሁሉም ስፍራዎች ይልቅ ከፍ ያለች ነበረች፣ ስለዚህም ለእስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም መውጣት እና ከእርሷ መውረድ ብሎ መናገር የተለመደ ነገር ነበር። "የእግዚአብሔርን ታቦት አመጣ" ወይም "የእግዚአብሔርን ታቦት ወሰደ"
አመጣ
"አመጣ" የሚለው ቃል "ወሰደ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። (መሄድ እና መምጣት የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 6:14
ዳዊት በያህዌ ፊት በሙሉ አቅሙ ይጨፍር ነበር
እዚህ ስፍራ መጨፈር በደስታ ያህዌን የማምለክ ሁኔታ ነበር
በፍታ/ሊኖ
ከቃጫ ተክል ከሚገኝ ላይነን የተሰራ ልብስ
የእስራኤል ቤት በሙሉ
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክወለው የእስራኤልን ሰዎች ነው። "ከእርሱ ጋር የነበሩ ሌሎች እስራኤላውያን ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 6:16
አሁን… በእርሷ ልብ
"አሁን" የሚለው ቃል በታሪኩ ፍሰት ምልክት ያደርጋል። እዚህ ስፍራ ተራኪው ስለ ሜልኮል መረጃ ይሰጣል
ሜልኮል
ሜልኮል የንጉሥ ሳኦል ልጅ እና የዳዊት የመጀመሪያ ሚስቱ ነበረች። በ2ሳሙኤል 3:13 ይህ ስም እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።
በልቧ ናቀችው
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው የሚወክለው አስተሳሰብን ወይም ስሜትን ነው። "በማንቋሸሽ አየችው" ወይም "አፌዘችበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በያህዌ ፊት
"ለ ያህዌ"
2 Samuel 6:18
በሰራዊት ጌታ በያህዌ ስም ህዝቡን ባረከ
በ "ሰራዊት ጌታ በያህዌ ስም" መባረክ ማለት በያህዌ ሃይል እና ስልጣን ወይም የእርሱ ተወካይ ሆኖ መባረክ ማለት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የዘቢብ ቂጣ/ኬክ
ጣፋጭ ከደረቅ ወይን የተሰራ ዳቦ
2 Samuel 6:20
ወደ ውጭ መውጣት
እዚህ ስፍራ "መምጣት" የሚለው "መሄድ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። (መሄድ እና መምጣት የሚሉትን ይመልከቱ)
ዛሬ የእስራኤል ንጉሥ እንዴት ከበረ
ይህ ምፀታዊ አነጋገር ነው። ሜልኮል ተቃራኒውን ማለቷ ነበር፣ ዳዊት ያደረገው የሚያስከብረውን ነገር ነው ብላ አላመነችም። ሜልኮል ንጉሥ ዳዊት ሲጨፍር የታየበትን አለባበስ እና ባህሪይ የተናገረችው በማቃለል ነበር። (ምፀት ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በባሪያ ልጃገረዶች ዐይኖች ፊት
እዚህ ስፍራ "የባሪያ ልጃገረዶች ዐይኖች" የሚወክለው ባሪያ ልጃገረዶችን ነው። "በባሪያ ልጃገረዶች ፊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ባለጌ ተራሰው
ሜልኮል ዳዊትን ያነጻጸረችው ከባለጌ እና ሞኝ ሰዎች ጋር ነው
2 Samuel 6:21
ከአንቺ አባት በላይ እንድሆን የመረጠኝ ማን ነው
እዚህ ስፍራ "የአንቺ" የሚለው የሚያመለክተው ሜልኮልን ነው። (አንተ የሚለውን ቃል መልኮች ይመልከቱ)
በያህዌ ህዝብ ላይ፣ በእስራኤል ላይ
እዚህ ስፍራ "የያህዌ ህዝብ" እና "እስራኤል" የሚሉት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚህም ይልቅ ክብሬን እጥላለሁ
ዳዊት ምጸታዊ እየሆነ ነው፤ በቃላት ከተናገረው ተቃራኒውን እየገለጸ ነው። በእርግጥ

ያደረገው ነገር የሚያወርድ ነገር ነው ብሎ አይምንም ወይም ወደፊትም ወራዳ ተግባር አደርጋለሁ እያለ አይደለም። (ምፀት ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በራሴ ዐይኖች ፊት ራሴን አዋርዳለሁ
እዚህ ስፍራ "በራሴ ዐይኖች ፊት" የሚለው የሚወክለው አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር ስፍራ የሚሰጠውን ወይም የሚያስበውን ነው። "ራሴን ዝቅ አደርጋለሁ" ወይም "ራሴን ሞኝ እንደሆነ ሰው እቆጥራለሁ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን አንቺ ባልሻቸው በእነዚህ ባሪያ ልጃገረዶች ዘንድ እከበራለሁ
ይህ አድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንቺ ያልሻቸው ባሪያ ልጃገረዶች ያከብሩኛል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እስከ ዕለተ ሞቷ ድረስ ልጅ አልነበራትም
"አንድም ልጅ ለመውለድ አልቻለችም ነበር"

Chapter 7
2 Samuel 7:1
እንዲህ ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው የታሪኩን አዲስ ጅማሬ ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን ለማድረግ መንገድ ካለው፣ እዚህ ስፍራ ያንን ማድረግ ትችላላችሁ። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
በዙሪያው ከነበሩ ጠላቶቹ ሁሉ አሳረፈው
"ከከበቡት ጠላቶቹ ሁሉ አሳረፈው" እዚህ ስፍራ "እረፍት" የሚለው ረቂቅ ስም ነው። "የጠላት ወገን እስራኤልን ማትቃቱን እንዲያቆም አደረገ!" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ከዝግባ በተሰራ ቤት ውስጥ እኖራለሁ
ዝግባ በጥንካሬው የሚታወቅ የዛፍ አይነት ነው። በባህላችሁ እኩል የሆነ አይነት ዛፍ ካለ፣ ያንን ስም መጠቀም ትችላላችሁ፣ ካልሆነ ይህንን ለውጣችሁ መጠቀም ትችላላችሁ። "እኔ በጠንካራ፣ ቋሚነት ያለው ቤት ውስጥ እኖራለሁ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ታቦት በድንኳን ውስጥ ይኖራል
ድንኳኖች ጊዜያዊ መኖሪያ ናቸው። በባህላችሁ ድንኳን ከሌለ፣ ይህንን የተለየ ቃል ልተሰጡት ትችላላችሁ። "የእግዚአብሔር ታቦት በጊዜያዊ ስፍራ ይኖራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 7:3
በልብህ ያለውን አድርግ
እዚህ ስፍራ "ልብ"የሚለው የሚወክለው አዕምሮን ነው። "ማድረግ ያለብህን አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ ከአንተ ጋር ስለሆነ
እዚህ ስፍራ "ከአንተ ጋር" የሚለው እግዚአብሔር ዳዊትን እየረዳው እና እየባረከው ነው ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የያህዌ ቃል ወደ ናታን እንዲህ ሲል መጣ፣ "ሂድ"
"የያህዌ ቃል ወደ.. መጣ" የሚለው ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። "ያህዌ ለናታን መልዕክት ሰጠው። እንዲህም አለው፣ ‘ሂድ' ወይም "ያህዌ ለናታን ይህንን መልዕክት ተናገረው፡ ‘ሂድ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
"ሂድ እና ባሪየዬን ዳዊትን እንዲህ በለው፣ ‘ያህዌ እንዲህ ይላል፡ የምናርበትን ቤት አንተ ተሰራልኛለህን? በለው
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዟል። ቀጥተኛ ባልሆነ ጥቅስ መተገረጎሙ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "እንዲህ በለው፣ ‘ሂድና ዳዊትን እኔ የምናርበትን ቤት እሰራለሁ ብሎ ያስብ እንደሆነ ጠይቀው።" (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚሉትን ይመልከቱ)
የምኖርበትን ቤት አንተ ትሰራልኛለህን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ዳዊት የያህዌን ቤት የሚገነባው እርሱ አለመሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ምልክ ሊተረጎም ይችላል። "አንተ ለእኔ ቤት አትሰራልኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የመለውን ይመልከቱ)
ቤት ስራልኝ
እዚህ ስፍራ "ቤት" ማለት ቤተመቅደስ ማለት ነው። በ2 ሳሙኤል 7፡11 ላይ ያህዌ እንዲህ እርሱ ለዳዊት ቤት እገነባለታለሁ ይላል። በዚያ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቤተሰብን ነው። የእናንተ ቋንቋ ሁለትንም ቃላት መግለጽ የሚችል ቃል ካለው በዚህ ስፍራ እና በ2 ሳሙኤል 7:11 ላይ ተጠቀሙበት።
2 Samuel 7:6
ለየትኛው ህዝቤን እንዲመራልኝ ለቀባሁት የእስራኤል መሪ ‘ለምን ቤት አልሰራችሁልኝም?' በማለት ተናግሬያለሁን?"
ይህ በጥያቄ ውስጥ ጥያቄ ይዟል። ቀጥተኛው ጥቅስ ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅስ ተደርጎ መጻፍ ይችላል። "እስራኤልን እንዲመራ ከቀባሁት መሪ ውስጥ የትኛውን መሪ ለምን የዝግባ ቤት አልሰራህልኝም ስል የጠየቅኩት አለን?" (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚሉትን ይመልከቱ)
ለየትኛው የእስራኤል መሪ ምን ነገር ተናግሬ አውቃለሁ
ያህዌ በፍጹም የትኛውንም የእስራኤል መሪ ቤት እንዲሰራለት እንዳልጠየቀ ትኩረት ለመስጠት ይህንን ጥያቄ ተጠቅሟል። "ለየትኛውም የእስራኤል መሪ በፍጹም ምንም ነገር አላልኩም" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ህዝቤን እስራኤልን እንዲጠብቅ ለቀባሁት
የእስራኤል ህዝብ መሪዎች የተገለጹት እረኞች እንደሆኑ እና ህዝቡ ደግሞ የተገለጸው በግ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ለምን የጥድ ቤት አልሰራችሁልኝም?
ያህዌ መሪዎቹን ይህንን ጥያቄ ጠይቋቸው ቢሆን ኖሮ፣ የጥድ ቤት ስላልሰሩለት የሚገስጽ ጥያቄ ይጠቀም ነበር። ነገር ግን፣ ያህዌ አስቀድሞ ይህንን ጥያቄ እንዳልጠየቃቸው ተናግሯል። "የጥድ ቤት ልትሰሩልኝ ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 7:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ቃል ኪዳኑን ለንጉሥ ዳዊት በነብዩ ናታን በኩል ይገልጥለታል።
አሁን
ይህ "በዚህን ጊዜ" ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ለቀጣዩ ጠቃሚ ነጥብ ትኩረት ለመስጠት ውሏል።
ለባሪያዬ ለዳዊት፣ "የሰራዊት ጌታ ያህዌ የሚለው ይህንን ነው፡ ‘እኔ አነሳሁህ... ስምህን ከፍ አደርገዋለሁ፣ በምድር ላይ ስማቸው ታላቅ እንደሆኑት ታላቅ አደርግሃለሁ' በለው።
ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዟል። ቀጥተኛ የሆነውን ጥቅስ በዩዲቢ ውስጥ እንደሚገኘው ቀጥተኛ ባልሆነ ጥቅስ መተገረጎሙ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "ለባሪያዩ ለዳዊት እኔ እንዳነሳሁት... ስሙን ከፍ ታላቅ እንዳደረግኩት፣ በምድር ላይ ስማቸው ታላቅ እንደሆኑት ታላላቆች እንዳደረኩት ንገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚሉትን ይመልከቱ)
ለባሪያዬ ለዳዊት እንዲህ በለው
ያህዌ ለነብዩ ናታን አሁንም ለዳዊት መናገር ያለበትን እየነገረው ነው
ለግጦሽ ከምታሰማራበት ስፍራ አነሳሁህ
የዳዊት የእረኝነት ስራ የተገለጸው በጎቹን በሚጠብቅበት ስፍራ ነው። "እረኛ ከነበርክበት ስፍራ አነሳሁህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ከአንተ ጋር ነበርኩ
እዚህ ስፍራ "ከአንተ ጋር" የሚለው ያህዌ ዳዊትን ረድቶታል ደግሞም ባርኮታል ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጠላቶችህን ሁሉ አቆርጣለሁ
የያህዌ የዳዊትን ጠላቶች መደምሰስ የተገለጸው፣ አንድ ሰው የልብስ ቁራጭን እንደሚቆርጥ ወይም ከዛፍ ላይ ቅርንጫፉን እንደሚቆርጥ ያህዌ የዳዊትን ጠላቶች እንደቆረጣቸው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስምህን ታላቅ አደርገዋለሁ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው የሚወክለው ክብርን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ታላላቆች
"ታላላቆች" የሚለው ሀረግ ዝነኛ ሰዎች ማለት ነው።
2 Samuel 7:10
አጠቃላይ መረጃ፡

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ያህዌ በነቢዩ ናታን በኩል ለንጉሥ ዳዊት ቃል ኪዳኑን መግለጹን ቀጠለ
እኔ ቦታ እሰጣለሁ
"እኔ ቦታ እመርጣለሁ"
በዚያ እተክላቸዋለሁ
ያህዌ ህዝቡን በምድሪቱ በቋሚነት ማኖሩ እና ጥበቃው የተገለጸው በምድሪቱ እንደሚተክላቸው ተደርጎ ነው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከእንግዲህ አትጨነቁም/አትቸገሩም
ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ "ማንም ከእንግዲህ አያስጨንቃቸውም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከቀናቱ አንስቶ
"ከጊዜው አንስቶ"
ዳኞችን አዛለሁ
የእስራኤል ህዝብ ወደ ከነዓን ምድር ከገባ በኋላ እና የሚገዛቸው ንጉሥ ከማግኘታቸው በፊት፣ እግዚአብሔር "ዳኞች/ፈራጆች" ተብለው የሚጠሩ መሪዎችን በችግራቸው ጊዜ እንዲመሯቸው ይሾምላቸው ነበር፡፡
በህዝቤ በእስራኤል ላይ እንዲሆኑ
በስልጣን መሆን የተገለጸው በአንድ ሰው ላይ የበላይ መሆን ተብሎ ነው፡፡ "ህዝቤን እስራኤልን እንዲመሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አሁን ከጠላቶቻችሁ ሁሉ አሳርፋችኋለሁ... ቤት እንደምሰራላችሁ በእርግጥ እነግራችኋለሁ፡፡
በ 2ሳሙኤል 7:8-9 ቀጥተኛውን ጥቅስ፣ ቀጥተኛ ባልሆነ ጥቅስ ተርጉማችሁ ከሆነ፤ እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለውን "እርሱ" ወይም "የእርሱ" ብላችሁ መተርጎም ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ "አሁን ከጠላቶቹ ሁሉ አሳርፈዋለሁ... ቤት እንደምሰራለት በእርግጥ እነግረዋለሁ" (በጥቅስ ውስጥ የሚገኝ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች)
ከጠላቶቻችሁ ሁሉ አሳርፋችኋለሁ
"ከጠላቶቻችሁ ሁሉ እጠብቃችኋለሁ" እዚህ ስፍራ "እረፍት" የሚለው ረቂቅ ስም ነው፡፡ "ጠላቶቻችሁ ሁሉ እንንተን ማጥቃት እንዲያቆሙ አደርጋለሁ" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ቤት እሰራልሃለሁ
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው የዳዊት ትውልዶች የእስራኤል መሪ ሆነው እንደሚቀጥሉ ነው፡፡ በ 2ሳሙኤል 7:4 ያህዌ ዳዊትን እርሱ የያህዌ ቤትን የሚሰራ መሆኑን ይጠይቀዋል፡፡ በዚያ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የሚወከወለው ቤተመቅደስን ነው፡፡ ቋንቋችሁ ሁለቱንም ሃሳቦች የሚገለጽ ቃል ካለው በዚህ ስፍራ እና በ 2ሳሙኤል 7:4 ላይ ተጠቀሙበት፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 7:12
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ በነቢዩ ናታን በኩል ለንጉሥ ዳዊት ቃል ኪዳኑን መግለጹን ቀጠለ
ቀናቶቻችሁ ሲያበቁ እና ከአባቶቻችሁ ጋር ስታሸልቡ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው የተጣመሩት ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡ ሁለቱም አነላለጾች ሞትን በተሻሉ ቃላት የሚገልጹ ናቸው፡፡ (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
ከአንተ በኋላ ትውልድ አስነሳለሁ
ያህዌ የዳዊትን ትውልድ መሾሙ የተገለጸው ያህዌ እርሱን እንደሚያነሳቀው ወይም ከፍ እንደሚያደርገው ተደርጎ ነው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከአብራክህ የሚወጣው
ይፍ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ሰውየው የዳዊት ትውልድ ነው ማለት ነው፡፡ (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መንግስቱን አጸናለሁ
እዚህ ስፍራ "መንግስቱ" የሚለው የሚወክለው የመግዛት ሀይሉን ነው፡፡ "በጣም ሃያል ንጉሥ እንዲሆን አደርገዋለሁ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ለእኔ ስም ቤት
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚያመለክተው ያህዌን ነው፡፡ "ለእኔ የዘለዓለም/ቋሚ መኖሪያ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የመንግሥቱን ዙፋን ለዘለዓለም አጸነባለሁ
እዚህ ስፍራ "ዙፋን" የሚወክለው የሰውየውን እንደ ንጉሥ የመግዛት ሃይል ነው፡፡ "ግዛቱ በእስራኤል ለዘለዓለም እንዲጸና አደርጋለሁ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ለእርሱ አባት እሆናለሁ፣ እርሱም ልጄ ይሆናል
በ 2ሳሙኤል7:12-14 የቀረበው ትንቢት የዳዊትን ልጅ ሰለሞንን ይመለከታል፡፡ ነገር ግን የትንቢቱ ገጽታዎች የሚሟሉት በኢየሱስ ነው፡፡ ስለዚህ፣ እዚህ ስፍራ "አባት" እና "ልጅ" የሚሉትን ቃላት በቋንቋችሁ በሚገኘው የስጋ አባትእና ልጅ የተለመደው ቃል መተረጎሙ ይመረጣል፡፡
2 Samuel 7:15
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ በነቢዩ ናታን በኩል ለንጉሥ ዳዊት ቃል ኪዳኑን መግለጹን አጠናቀቀ
የቃል ኪዳኔ ታማኝነት ከሳኦል እንደራቀ፣ ከእርሱ ግን አልወስድበትም
"ታማኝነት" የሚለው ቃል "በታማኝነት ወዳጅ" እንደሚለው ረቂቅ ስም ነው፡፡ "ሳኦልን መውደዴን እንዳቋረጥኩት፣ እርሱን በታማኝነት መውደዴን በፍጹም አላቋርጥም"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ከአንተ በፊት፡፡ የአንተ ቤት... ከአንተ በፊት ፡፡ የአንተ ዙፋን
በ 2ሳሙኤል7:8-9 ቀጥተኛ ጥቅስን ቀጥተኛ ባልሆነ ጥቅስ ተርጉማችሁ ከሆነ፣ አሁን እዚህ ላይ "አንተ" የሚለውን "ዳዊት" ወይም "እርሱ" ወይም "የእርሱ" ብላችሁ በዩዲቢ እንደሚገኘው መተረጎም ሊያስፈልጋችሁ ይችላል፡፡ "ከዳዊት በፊት፡፡ የዳዊት ቤት... ከእርሱ በፊት፡፡ የእርሱ ዙፋን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)
ቤትህ እና መንግስትህ በፊትህ ለዘለዓለም የጸና ይሆናል፡፡ ዙፋንህ ለዘለዓለም ይመሰረታል፡፡
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም የዳዊት ስርወ መንግስት ለዘለዓለም እንደሚጸና ያጎላሉ፡፡(ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቤትህ እና መንግስትህ በፊትህ ለዘለዓለም የጸና ይሆናል፡፡
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል፣ ንጉስ ሆኖ የሚገዛውን የዳዊትን ትውልድ ይወክላል፡፡ እዚህ "መንግስት" ማለት "ቤት" የማለት ያህል ተመሳሳይ ነገር ነው፡፡ ይህ በአድርጊ ዐረፍተ ነገር ጭምር ሊጻፍ ይችላል፡፡ "ቤተሰብህን ሳጸና እና እነርሱ በእስራኤል ላይ ለዘለዓለም ሲገዙ ትመለከታለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ጥንድ ትርጉም እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ዙፋንህ ለዘለዓለም ይመሰረታል፡፡
እዚህ "ዙፋን" የሚወክለው ንጉስ ሆኖ የመግዛት ሃይልን ነው፡፡ "ትውልድህ በእስራኤል ላይ ለዘለዓለም እንዲገዛ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህ ቃላት ሁሉ
"እነዚህ ነገሮች ሁሉ፡፡" ይህ ያህዌ የተናገረውን ያመለክታል፡፡
ስለ ጠቅላላው ራዕይ ነገረው
"ያህዌ ለእርሱ ስለ ገለጠለት ነገር ሁሉ ነገረው
2 Samuel 7:18
ያህዌ አምላክ፤ እስከዚህ ደረጃ ያደረስከኝ፣ እኔ ማን ነኝ፣ ቤቴስ ምንድን ነው?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው የያህዌን አዋጅ ሲሰማ የተሰማውን ጥልቅ ስሜት ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ " ያህዌ አምላክ ሆይ፣ እኔ እና ቤተሰቤ ለዚህ ክብር የተገባን አይደለንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በአንተ ዐይኖች ፊት/በፊትህ
እዚህ ስፍራ እይታ የሚወክለው ፍርድን ወይም ሚዛንን ነው፡፡ "በአንተ ፍርድ/ሚዛን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ባሮች ቤተሰብ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ራሱን "የአንተ ባሪያ" በማለት ይገልጻል፡፡ ይህ በመጀመሪያ መደብ ሊገለጽ ይችላል፡፡ "የእኔ ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
በሚመጣው ታላቅ ጊዜ
ይህ የሚናገረው ስለ ጊዜ ነው፤ ጊዜ እየተጓዘ እንደሚመጣ እና አንድ ስፍራ እንደሚደርስ ነገር ተደርጎ ተገልጽዋል፡፡ "እና ወደፊት በእነርሱ ላይ ምን ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ባርያ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ራሱን "የአንተ ባሪያ" በማለት ይገልጻል፡፡ ይህ በመጀመሪያ መደብ

ሊገለጽ ይችላል። "የእኔ ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 7:21

ስለ ቃልህ ስትል

"ልታደርግ ቃል በገባኸው ምክንያት"

የራስህን አላማ ልትፈጽም

"ልታደርግ ያቀድከውን ለመፈጸም"

ለባሪያህ

ዳዊት ራሱን "የአንተ ባሪያ።" በማለት ይገልጻል። ይህ በመጀመሪያ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "ለ እኔ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ በገዛ ጆሮቻችን እንደ ሰማነው

"በገዛ ጆሮቻችን" የሚለው ሀረግ የዋለው ትኩረት ለመስጠት ነው። "እኛ ራሳችን እንደ ሰማነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ እንደ ሰማነው

እዚህ ስፍራ "እኛ" የሚለው የሚያመለክተው ዳዊትን እና የእስራኤልን ህዝብ ነው። (የሚያካትት እና የማያካትት "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤል እንዳንተ ያለ ህዝብ ማን ነው፣ አምላኩ እግዚአብሔር ሄዶ ያዳነው በምድር ላይ ብቸኛ ህዝብ እንዳንተ ማን ነው?

ዳዊት ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው፣ እንደ እስራል ያለ ሌላ ህዝብ እንደሌለ ትኩረት ለመስጠት ነው። "እስራኤል እንዳንተ ያለ ሌላ ህዝብ የለም፣ እግዚአብሔር ለራሱ ሄዶ በምድር ላይ ያዳነው አንድ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለራስህ ስም የለየኸው

እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው የያህዌን ክብር ነው። "ሁሉም ህዝብ አንተ ማን እንደሆንክ እንዲያውቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለምድርህ

እዚህ ስፍራ "ምድር" የሚወክለው ህዝብን ነው። "ለአንተ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ወገን ህዝብ አባረርህ

እዚህ ስፍራ "ህዝብ" የሚለው የሚወክለው በከነዓን ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን ወገን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 7:24

አጠቃላይ መረጃ

ዳዊት ከያህዌ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ።

ስለዚህ አሁን

እዚህ ስፍራ "አሁን" የሚለው "በዚህን ጊዜ" ማለት አይደለም። ነገር ግን ወደ ተከታዩ ጠቃሚ ነጥብ ትኩረትን ለመሳብ ውሏል።

ለባሪያህ እና ለቤቱ የገባኸው ቃል ኪዳን ለዘለዓለም የጸና ይሁን

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ለእኔ እና ለቤቴ የገባኸውን ቃል ኪዳን ፈጽመው፣ ቃል ኪዳንህም ለዘላለም የጸና ይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ባሪያህ እና ቤተሰቡ/ቤቱ

ዳዊት ስለ ራሱ በሶስተኛ መደብ እየተናገረ ነው። ይህ በአንደኛ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "እኔ እና የእኔ ቤት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ስምህ ለዘለዓለም ታላቅ ይሁን

እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው የያህዌን ክብር ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእኔ የባሪያህ፣ የዳዊት ቤት

እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ቤተሰብን ነው። "የእኔ ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በፊትህ የጸና ነው

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከአንተ የተነሳ የተጠበቀ ነው" ወይም "ከአንተ የተነሳ ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 7:27

ለባሪያህ ቤት ትሰራለታለህ

ዳዊት ራሱን "የአንተ ባሪያ" እያለ ይጠቅሳል/ያመለክታል። "ለእኔ ቤት ትሰራልኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ቤት ትሰራለታለህ

እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው የዳዊት ትውልድ የእስራኤል መሪ ሆኖ እንደሚቀጥል ነው። በ 2ሳሙኤል 7፡4 ያህዌ ዳዊትን እርሱ የያህዌን ቤት የሚሰራ መሆኑን ይጠይቀዋል። በዚያ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የሚወክለው ቤተመቅደስን ነው። በቋንቋችሁ ሁለቱንም ሃሳቦች የሚገልጽ ቃል ካለ በዚህ ስፍራ እና በ 2ሳሙኤል 7፡ 4 ላይ ያንን ቃል ተጠቀሙ። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን

ይህ "በዚህን ጊዜ" ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ለቀጣዩ ጠቃሚ ነጥብ ትኩረት ለመስጠት ውሏል።

ቃሎችህ የታመኑ ናቸው

"እኔ አንተ የምትናገረውን አምናለሁ"

በአንተ በረከት የባሪያህ ቤት ለዘለዓለም የተባረከ ይሆናል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ቤቴን ለዘለዓለም መባረክህን ትቀጥላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የባሪያህ ቤት

እዚህ ስፍራ ዳዊት ራሱን "የአንተ ባሪያ" በማለት ይገልጻል።" "የእኔ ቤት" ወይም "የእኔ ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤት

እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የሚወክለው የዳዊትን ቤተሰብ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 8

2 Samuel 8:1

ዳዊት አጠቃቸው

እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚወክለው ወታደሮቹን/ሰራዊቱን ነው። "ዳዊት እና ሰራዊቱ/ወታደሮቹ አጠቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 8:2

ከዚያም እርሱ አሸነፈ

እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ወታደሮቹን የሚወክለውን ዳዊትን ነው። "ከዚያ እነርሱ አሸነፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንዶቻቸውን በመስመር/ገመድ ይለካል ... የሚገድላቸውን በሁለት መስመር ሲለካ፣ በአንድ መስመር የሚቀሩት በህይወት ይተርፋሉ

እዚህ ስፍራ "መስመሩ" "ገመድ" ነው። ዳዊት ወታደሮቹን ለመለካት መሬት ላይ አጋድሞ በሶስት ቡድን ይለያቸዋል። በሁለቱ ቡድኖች የሚገኙ ወንዶች ሲገደሉ፣ ሶስተኛው ቡድን በህይወት ይተርፋል።

2 Samuel 8:3

ከዚያም ዳዊት አድርአዛርን አሸነፈ

እዚህ "ዳዊት" እና "አድርአዛር" ሁለቱም ሰራዊታቸውን ይወክላሉ። "ከዚይም ዳዊት እና ሰራዊቱ የአድርአዛርን ሰራዊት አሸነፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

አድርአዛር...ረአብ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሱባ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ በአራማ ውስጥ የሚገኝ የአካባቢ ስም ነው፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቱን ለመመለስ

"በአካባቢው ላይ ያለውን የበላይነት መልሶ ለማግኘት" ወይም "አካባቢውን መልሶ ለመያዝ"

1,700 ሰረገሎች

"አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰረገሎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ ሺህ እግረኞች

"20,000 እግረኞች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ዳዊት የፈረሶችን ቋንጃ ቆረጠ

ይህ ፈረሶች መሮጥ እንዳይችሉ በኋላ እግራቸው የሚገኝን ጅማት የመቁረጥ ልምምድ ነው

በቂ የሆነ አስቀረ

"በቂ የሆነ ነገር አቆየ" ወይም "በቂ ቆጠበ"

አንድ መቶ ሰረገሎች

"100 ሰረገሎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 8:5

ዳዊት ገደለ

ዳዊት ወታደሮቹን ይወክላል፡፡ "ዳዊት እና ወታደሮቹ ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ስኔክዶቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃያ ሁለት ሺህ ሶርያውያን ወንዶች

"22,000 የሶርያ ወንዶች/ወታደሮች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በሶርያውያን ግዛት የጦር ሰፈሮችን አቋቋመ

" ብዙ የእርሱ ወታደሮች ቡድኖች በሶርያ እንዲቆዩ አዘዘ"

2 Samuel 8:7

ዳዊት ወሰደ… ንጉስ ዳዊት ወሰደ

እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚወክለው ወታደሮቹን ነው፡፡ "የዳዊት ወታደሮች ወሰዱ…. የንጉስ ዳዊት ወታደሮች ወሰዱ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቤጣህ እና ቤሮታይ

እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 8:9

ቶዑ…አዶራም

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐማት

ይህ የቦታ ስም ነው፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳዊት አሸነፈ

እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚወክለው ሰራዊቱን ነው፡፡ "የዳዊት ሰራዊት አሸነፈ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ስኔክዶቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 8:11

አማሌቅም

"እናም አማሌቃውያን"

የተዘረፉት ንብረቶች

እነዚህ ወታደሮች ከማረኩት ህዝብ የሚወስዷቸው ዋጋ ያላቸው ነገሮች ናቸው፡፡

የሱባ ንጉስ የረአብም ልጅ አድርአዛር

በ 2ሳሙኤል 8:3 ላይ እነዚህ ስሞች እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ

2 Samuel 8:13

የዳዊት ስም በሚገባ የታወቀ ነበር

እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው የሚወክለው የዳዊትን ክብር ነው፡፡ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ "ዳዊት እጅግ ዝነኛ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የጨው ሸለቆ

ይህ የቦታ ስም ነው፡፡ ትክክለኛ ስፍራው አይታወቅም፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ ስምንት ሺህ ወንዶች

"18,000 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በመላው ኤዶም የጦር ሰፈሮች አቋቋመ

"በኤዶም ዙሪያ በሙሉ የወታደር ቡድኖቹን እንዲቆዩ አዘዘ"

2 Samuel 8:15

የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ

በ 2ሳሙኤል 2:13 ላይ እነዚህ ስሞች እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ፡፡

አሒሉድ… አሒቱብ…አቢሜሌክ… ሰራያ… ዮዳሔ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አሒሉድ ጸሐፊ ነበር

ጸሐፊ ከህዝቡ ጋር የሚነጋገር የንጉሡን ትዕዛዝም የሚነግራቸው ሰው ነበር፡፡ "አሒሉድ አዋጅ ተናጋሪ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሊታውያን… ፈሊታውያን

እነዚህ የህዝብ ወገን ስሞች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች የዳዊት ጠባቂዎች ነበሩ፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 9

2 Samuel 9:1

ስለ ዮናታን ስል

"ለዮናታን ባለኝ ፍቅር ምክንየት"

ስለ ዮናታን ስል

ዮናታን የሳኦል ልጅ እና የዳዊት የልብ ወዳጅ ነበር

ሲባ

ይህ የወንድ ስም ነው፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ የአንተ ባሪያ ነኝ

ሲባ ራሱን "የአንተ ባሪያ" በማለት ለዳዊት ያለውን ታላቅ አክብሮት ያሳያል

2 Samuel 9:3

የእግዚአብሔርን መልካምነት አደርግለት ዘንድ

"ደግነት/መልካምነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ደግ/መልካም" ተብሎ ሊጻፍ ይችላል፡፡ "ለእግዚአብሔር ቃል እንደገባሁ መልካም እሆንለታለሁ"

እግሩ ሽባ የሆነው ማን ነው

"የተጎዳው የማን እግር ነው፡፡" እዚህ ስፍራ "እግር" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመራመድን ችሎታ ነው፡፡ "መራመድ የማይችለው ማን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማኪር… ዓሚኤል

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሎዶባር

ይህ የቦታ ስም ነው፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 9:5

ንጉስ ዳዊት ላከ

ዳዊት መልዕክተኞችን መላኩ ግልጽ ነው፡፡ (ኢሊፕስስ/የተተወ ወይም የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

ሜምፊቦስቴ

ይህንን በ 2ሳሙኤል4:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡

ወደ ዳዊት መጣ

"መምጣት" የሚለው ቃል "መሄድ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ (ሄደ እና መጣ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ የአንተ ባሪያ

ሜምፊቦስቴ ራሱን "የአንተ ባሪያ" በማት የሚገልጸው ለዳዊት ያለውን ክብር ለማሳየት ነው፡፡

2 Samuel 9:7

ዮናታን፣ ለአባትህ ስል

"ዮናታን፣ አባትህን ስለምወደው"

ሁልጊዜም ከገበታዬ ትበላለህ

እዚህ ስፍራ "ገበታዬ" የሚለው የሚወክለው ከዳዊት ጋር አብሮ መሆንን ወይም የእርሱን መገኘት/አብሮነት ነው፡፡ ከንጉሱ ጋር በገበታው ቀርቦ መብላት ታላቅ ክብር

ነበር። "ሁሌም ከእኔ ጋር አብረህ ትቀርባለህ/ትበላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ሞተ ውሻ የሆንኩትን ባሪያህን በሞገስ ትመለከተኝ ዘንድ ባሪያህ ምንድን ነው?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ሜምፊቦስቴ ንጉሱ እርሱን ይንከባከበው ዘንድ የሚያበቃው ነገር እንደሌለው መረዳቱን ያሳያል። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ እንደ ሞተ ውሻ ነኝ። ደግነትን ልታሳየኝ የተገባሁ አይደለሁም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የሞተ ውሻ የምመስል
እዚህ ስፍራ ሜምፊቦስቴ የሳኦልን ትውልድ ይወክላል፣ ደግሞም ራሱን "ከሞተ ውሻ" ጋር ያነጻጽራል። ውሾች እንደ ቤት እንስሳ የማይቆጠሩ፣ እንክብካቤ የማይደረግላቸው እና ጥቅማቸው ይህ ነው የማይባሉ እንስሳት ነበሩ። የሞተ ውሻ ከዚህ ይልቅ የማይረባ ተደርጎ ይወሰዳል። "እንደ እኔ ያለው እንደ ሞተ ውሻ እርባና የሌለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 9:9
ሁሌም ከገበታዬ ትመገባለህ
እዚህ ስፍራ "ገበታ" የሚለው የሚወክለው ከዳዊት ጋር አብሮ መሆንን ወይም የእርሱን መገኘት/አብሮነት ነው። ከንጉሱ ጋር በገበታው ቀርቦ መብላት ታላቅ ክብር ነበር። "ሁሌም ከእኔ ጋር አብረህ ትቀርባለህ/ትበላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አሁን ሲባ... ባሮች
እዚህ ስፍራ "አሁን" የሚለው በዋናው የታሪክ አካሄድ ላይ የገባ ነው። ተራኪው ስለ ሲባ የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)
አስራ አምስት ወንድ ልጆች እና ሃያ ባሪያዎች
"15 ወንድ ልጆች 20 ባሪያዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 9:11
የአንተ ባሮች ጌታዬ ንጉሡ ባሮቹን ያዘዘውን ሁሉ ያደርጋሉ
ሲባ ራሱን "የአንተ ባሪያ" በማለት ሲገልጽ ዳዊትን ደግሞ " የእኔ ጌታ" በማለት ይናገራል። "እኔ፣ የአንተ ባሪያ አንተ ንጉሴ አደርገው ዘንድ ያዘዝከኝን ሁሉ አደርጋለሁ" (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ሚካ
ይህ የሜምፊቦስቴ ልጅ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
በሲባ ቤት የሚኖሩ ሁሉ
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው የሲባን ቤተሰብ ነው። "መላው የሲባ ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ሁሌም ከንጉሱ ገበታ ይበላ ነበር
እዚህ ስፍራ "ገበታ" የሚለው የሚወክለው ሁሌም ከዳዊት ጋር አብሮ መሆንን ወይም ከእርሱ ጋር መገኘትን ነው። ከንጉሱ ጋር ሆኖ ከገባታው መብላት ታላቅ ክብር ነበር። "ሁሌም ከንጉሱ ጋር ሆኖ ከገበታው ይበላ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ምንም እንኳን ሁለቱም እግሮቹ ሽባ ቢሆኑም
"ምንም እንኳን ሁለቱም እግሮቹ የተጎዱ ቢሆኑም።" እዚህ ስፍራ "እግር" የሚለው የሚወክለው መራመድ መቻልን ነው። "መራመድ የማይችል ቢሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 10
2 Samuel 10:1
አሞን... ሐኖን
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ... በእርግጥ እንዲህ ታስባለህ
መሪዎች ጥያቄውን የተጠቀሙበት የአሞን ንጉስ ዳዊትን እንዳያምነው ለመጠቆም ነው። "አንተ...እንዲህ ማሰብህ ስህተት ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ለመሰለል
ስለ ሌላ ሰው በድብቅ መረጃ ለማግኘት/ለማወቅ
ዳዊት ... እርሷን ያጠፋት አይደለምን?
መሪዎች ጥያቄውን የተጠቀሙበት የአሞን ንጉስ ዳዊትን እንዳያምነው ለመጠቆም ነው። "ዳዊት... እርሷን የጣለ እንደሆነ ልታውቅ ይገባሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሷን ይጥል/ያጠፋ ዘንድ
እዚህ ስፍራ "እርሷን" የሚለው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ከተማን የሚወክል ነው። "እኛን ይወር ዘንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከተማይቱ
እዚህ ስፍራ "ከተማይቱ" የሚለው የሚያመለክተው የአሞናውያንን ዋና ከተማ ረባትን ነው።
2 Samuel 10:4
ግማሽ ጺማቸውን ላጨ
ይህ ድርጊት ሰዎቹን ለማዋረድ መሳደብ ማለት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በጥልቅ አፍረው
እዚህ ስፍራ "በጥልቅ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "በጣም" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያ ተመለሱ
ወደ ኢየሩሳሌም መመለሳቸው ግልጽ ነው። (ኢሊፕስስ/የተተወ ወይም የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 10:6
ለዳዊት የተጠሉ/መጥፎ ሽታ ሆኑ
"የተጠሉ/መጥፎ ሽታ ሆኑ" የሚለው ሀረግ "አጥቂዎች/ጠላቶች ሆኑ" ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "እንደ መጥፎ ሽታ ለዳዊት ጠላቶች/አጥቂ ሆኑበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቤትሮዖብ...ሱባ...መዓካ...ጦብ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሃያ ሺህ... አንድ ሺህ... አስራ ሁለት ሺህ
"20,000... 1,000...12,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ከተማቸው መግቢያ በር
እዚህ ስፍራ "ከተማይቱ" የሚለው የሚያመለክተው የአሞናውያንን ዋና ከተማ ረአብን ነው።
2 Samuel 10:9
አጠቃላይ መረጃ፡
ከሶርያውያን እና ከአሞን ጋር ውጊያው ቀጠለ።
የተቀረውን ህዝቡን በወንድሙ በአቢሳ እጅ አደረጋቸው
"ወንድሙን አቢሳን ለተቀረው ሰራዊት ሃላፊ አደረገ"
2 Samuel 10:11
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮአብ ሰራዊቱን ለውጊያ ዝግጁ አደረገ
አንተ ለእኔ፣ እኔ ለአንተ፣ አቢሳ አንተ እኔን ልትረዳ ይገባሃል
እዚህ ስፍራ "እኔ" የሚለው የሚያመለክተው ኢዮአብን ነው። ኢዮአብ እና አቢሳ እራሳቸውን እና ሰራዊታቸውን ይወክላሉ። "አንተ ለእኛ፣ እኛ ለአንተ ነን፤ ኢቢሳ የአንተ ሰራዊት እኛን መታደግ አለበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 10:13
ከአቢሳ
እዚህ ስፍራ ኢቢሳ የሚወክለው ራሱን እና ወታደሮቹን ነው። "ከኢቢሳ እና ወታደሮቹ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ከተማይቱ
እዚህ ስፍራ "ከተማይቱ" የሚለው የሚያመለክተው የአሞናውያንን ዋና ከተማ ረአብን ነው።
ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ሄዱ
"ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ"

2 Samuel 10:15

ሶርያውያን በእስራኤል ፊት እንደተሸነፉ ባዩ ጊዜ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሶርያውያን እስራኤላውያን እያሸነፏቸው እንደሆነ ባወቁ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አድርአዛር... ሶባክ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ከኤፍራጥስ ወንዝ ባሻገር

ይህ ማለት በኤፍራጥስ ወንዝ ምስራቅ

ወደ ኤላም መጡ

እዚህ ስፍራ "ወደ ...መጡ" የሚለው "ወደ... ሄዱ" ወይም "በ...ተሰበሰቡ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

ኤላም

የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 10:17

ዳዊት ይህ ሲነገረው

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዳዊት ስለዚህ ሲሰማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን የመልከቱ)

መላውን እስራኤል ሰበሰበ

እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው የሚወክለው የእስራኤልን ሰራዊት ነው። "መላውን የእስራኤል ሰራዊት በአንድነት ሰበሰበ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ኤላም

ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል10፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ

በዳዊት ላይ ደግሞም እነርሱን ወጉት

እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚወክለው ራሱን እና የእርሱን ወታደሮች ነው። "በዳዊት እና ወታደሮቹ ላይ ደግሞም እነርሱን ተዋጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳዊት ገደለ

እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚወክለው ራሱን እና የእርሱን ወታደሮች ነው። "በዳዊት እና ወታደሮቹ ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባት መቶ... አርባ ሺህ

"700... 40,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊታቸው አለቃ ሶባክ ቆስሎ ነበር ደግሞም በዚያ ሞተ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እስራኤላውያን የሶርያን ጦር አለቃ ሶባክን አቆሰሉት፣ እርሱም በዚያ ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሶባክ...አድርአዛር

እነዚህ የወንድ ስሞች በ 2 ሳሙኤል10፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ

በእስራኤል እንዴት እንደ ተሸነፉ አዩ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እስራኤላውያን እንዳሸነፏቸው አወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 11

2 Samuel 11:1

በፀደይ ወቅት እንዲህ አጋጠመ

"በፀደይ ወቅት ይህ ሆነ።" ይህ በታሪኩ ፍሰት አዲስ ትዕይንትን ያስተዋውቃል። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

በጊዜው

"በአመቱ ወቅት"

ዳዊት ኢዮአብን፣ አገልጋዮቹን እና መላውን የእስራኤል ሰራዊት ላከ

ዳዊት እነርሱን ወደ ጦርነት ላከ። ይህ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። እንደዚሁም "የእርሱ" የሚለው ቃል ዳዊትን ያመለክታል። "ዳዊት ኢዮአብን፣ አገልጋዮቹን፣ እና መላውን የእስራኤል ሰራዊት ወደ ጦርነት ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የአሞን ሰራዊት

"የአሞናውያን ሰራዊት"

ረባት

ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:2

ስለዚህም እንዲህ ሆነ

"እናም እንዲህ ሆነ" ወይም "ስለዚህ እንዲህ ሆነ" ጸሐፊው ይህንን ሀረግ የተጠቀመው ቀጣዩን ትዕይንት በታሪኩ ፍሰት ውስጥ ለማስገባት ነው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ)

ሰውነቷን ትታጠብ የነበረች ሴት

ሴትየዋ በሰገነት/ጣራ ላይ አልነበረችም፣ በቤቷ አጥር ግቢ ውጭ ሆና ገላዋን እየታጠበች ሳትሆን አትቀርም። "በቤቷ አጥር ግቢ ውስጥ ትታጠብ የነበረች አንዲት ሴት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እናም ዳዊት ላከ

እዚህ ስፍራ "ላከ" የሚለው ቃል ዳዊት መልዕክተኛ ላከ ማለት ነው። "እናም ዳዊት መልዕክተኛ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመለከቱ) ስለ ሴትየዋ የሚያውቀዉ ሰዎችን ጠየቀ ዳዊት ሴትየዋ ማን እንደሆነች ለማወቅ እየሞከረ ነበር። "እርሱ" የሚለው ቃል ዳዊትን ሲያመለክት፣ ደግሞም ዳዊት ለላከው መልዕክተኛ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። መልዕክተኛው ስለ እርሷ ሰዎችን መረጃ ይጠይቅ ነበር። "መልዕክተኛው እርሷ የሚያውቁ ሰዎችን ስለማንነቷ መረጃ ይጠይቅ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህች ቤርሳቤህ አይደለችምን... እርሷስ የኬጢያዊው የኦርዮ ሚስት አይደለችምን?

ይህ ጥያቄ መረጃ ይሰጣል፣ ደግሞም በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ይህች ቤርሳቤህ ናት... እርሷም የኬጢያዊው የኦርዮ ሚስት ናት " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:4

ወሰዳት

"እናም እርሱ ወሰዳት።" እዚህ ዳዊት ሴቲቱን ወሰዳት ይላል፣ ነገር ግን በእርግጥ የሆነው፣ የወሰዷትና ወደ እርሱ ያመጧት እርሱ የላካቸው መልዕክተኞች ናቸው። "እነርሱ ወደ እርሱ አመጧት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ ወደ እርሱ መጣች፣ ደግሞም እርሱ ከእርሷ ጋር ተኛ

" እርሷ ወደ እርሱ መጣች" የሚለው ሀረግ ዳዊት ከሴቲቱ ጋር ተኛ ለሚለው ጉልህ ገለጻ ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ እናም አብረው መተኛታቸውን ለማጉላት በአንድነት ቀርበዋል። "ከእርሷ ጋር ተኛ" ወይም "ከእርሷ ጋር ግንኙነት አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የወር አበባ

የሴት ወርሃዊ የመንጻት ጊዜ

"እኔ አርግዣለሁ።" ስትል ወደ ዳዊት ልካ ነገረችው

እዚህ ስፍራ "ልካ" ማለት መልዕክተኛ ላከች ማለት ነው። ማርገዟን ወደ ዳዊት መልዕክተኛ ላከች። "እንዳረገዘች እንዲነግሩት ወደ ዳዊት መልዕክተኛ ላከችበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:6

ከዚያም ዳዊት ላከ

እዚህ ስፍራ "ላከ" የሚለው ዳዊት መልዕክተኛ ላከ ማለት ነው። "ከዚያም ዳዊት መልዕክተኛ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኢዮአብ እንዴት እንደሆነ፣ ሰራዊቱ ምን እያደረገ እንደሆነ፣ እና ጦርነቱ እንዴት እየተካሄደ እንደ ነበር

ዳዊት ኢዮአብ እና ሰራዊቱ ደህና ስለ መሆናቸው እና ስለ ጦርነቱ አካሄድ ይጠይቅ ነበር። "ኢዮአብ ደህና ከሆነ፣ ሌሎች ወታደሮችም ደህና ከሆኑ፣ ደግሞም ጦርነቱ እንዴት እየተካሄደ እንደሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ቤትህ ውረድ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"ወደ ታች ውረድ" ለሚለው ሀረግ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የኦርዮ ቤት ከንጉሱ ቤተ መንግስት ዝቅ ባለ ስፍራ ላይ ይገኝ ነበር ወይም 2) የኦርዮ ቤት ከንጉሱ ቤተ መንግስት ይልቅ ያነሰ ጠቃሚነት ነበረው። "ወደ ቤትህ ሂድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግርህን ታጠብ

ይህ ሀረግ ከእለት ስራ በኋላ ምሽቱን ለማረፍ ወደ ቤት መመለስ ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ምሽቱን እረፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሱ ለኦርዮ ስጦታ ላከለት

ዳዊት ለኦርዮ ስጦታውን እንዲያመጣለት አንድ ሰው ላከ። ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሱ ለኦርዮ ስጦታ እንዲወስድለት አንድ ሰው ላከ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:9

የእርሱ ጌታ

"የእርሱ" የሚለው ቃል ኦርዮን ያመለክታል፤ "ጌታ" የሚለው ደግሞ ዳዊትን ያመለክታል።

የመጣኸው ከመንገድ አይደለምን? ስለምን ወደ ቤትህ አትወርድም/አትሄድም?

ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ኦርዮን ሚስቱ ለማየት መሄድን መቃወሙን ለማጉላት ነው፤ ሃሳቡ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከእንዲህ አይነት ረጅም መንገድ ከመጣህ በኋላ፣ አሁን ወደ ቤትህ መውረድ አለብህ " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እስራል እና ይሁዳ

ይህ ሰራዊታቸውን ያመለክታል። "የእስራኤል እና የይሁዳ ሰራዊቶች" (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሚስቴ ጋር …. እንዴት ወደ ቤቴ መሄድ ይሆንልኛል?

ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ኦርዮ ሚስቱን ለማየት መሄዱን መቃወሙን ለማጉላት ነው፤ ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "በሰራዊቴ ውስጥ የሚገኙት ሌሎች ወታደሮች በአደጋ ላይ ሆነው ከሚስቴ ጋር ለመሆን…ወደ ቤቴ መሄድ በደል መፈጸም ይሆንብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በህያው ነፍስህ እምላለሁ፣ ይህንን በፍጹም አላደርገውም

ኦርዮ ሌሎች ወታደሮች በጦርነት ላይ እያሉ ወደ ቤቱ ሚስቱ ዘንድ እንደማይሄድ ጠንካራ የቃል ኪዳን መሃላ ያደርጋል። ይህን ቃል ኪዳን የሚያደርገው የቃል ኪዳኑን እውነተኛነት ከንጉሱ ህያውነት እርግጠኝነት ጋር በማነጻጸር ነው። " ይህንን እንደማላደርገው በጽኑ ቃል እገባለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:12

በፊቱ በላ ጠጣም

"ኦርዮ ከዳዊት ጋር በላ ጠጣም"

ወደ እርሱ ቤት መውረድ

"ወረደ" ለሚለው ቃል ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የኦርዮ ቤት ከንጉሱ ቤተ መንግስት ዝቅ ባለ ስፍራ ላይ ይገኝ ነበር ወይም 2) የኦርዮ ቤት ከንጉሱ ቤተ መንግስት ይልቅ ያነሰ ጠቃሚነት ነበረው። በ 2 ሳሙኤል 11:8 ላይ የሚገኘው "ወደ ቤትህ ውረድ" የሚለው ይህ ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ ቤትህ ውረድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:14

በኦርዮ እጅ ላከው

"የኦርዮ እጅ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ኦርዮን ራሱን ነው። " ይህን ለእርሱ እንዲያደርስ ኦርዮን ራሱን ላከው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እጅግ በተፋፋመው ጦርነት በጣም ከፊት

"በጦርነቱ ግንባር ውጊያው በከፋበት በጣም ከፊት"

ከእርሱ ይሸሹ

"ወታደሮቹን ከእርሱ ወደ ኋላ እንዲርቁ እዘዛቸው"

ተመትቶ ሊገደል ይችላል

"ሊቆስል እና ሊገደል ይችላል"

2 Samuel 11:16

ከተማይቱ ስትከበብ

"ከበባ" የሚለው ቃል "ከበበ" እና "አጠቃ" በሚሉ ግሶች ሊገለጽ ይችላል። "የእርሱ ሰራዊት ከተማዋን ከብቦ አጠቃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ጥቂት የዳዊት ወታደሮች ወደቁ

"ወደቁ" የሚለው ቃል የወታደሮቹ መገደል በተሻለ መንገድ የተገለጸበት ነው። "የዳዊት ወታደሮች ተገደሉ" ወይም "ከዳዊት ወታደሮች ጥቂቶችን ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ) እናም ኬጢያዊው ኦርዮም በዚያ ተገደለ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ኬጢያዊውን ኦርዮን ጨምሮ" ወይም "የከተማይቱ ሰዎች ኬጢያዊውን ኦርዮንም ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:18

ኢዮአብ ለዳዊት ቃል/ መልዕክት ላከ

"ቃል ላከ" የሚለው ሀረግ የሆነውን ለማድረስ መልዕክት ላከ ማለት ነው። "ኢዮአብ የሆነውን ለዳዊት ለማድረስ መልዕክት ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ወደ ግንቡ … ይህን ያህል ተጠጋችሁ?

ኢዮአብ ዳዊት እነዚህን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በመጠየቅ ይገስጸኛል ብሎ ነበር። እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር ሊጻፉ ይችላሉ። "ለመዋጋት ይህንን ያህል ወደ ከተማይቱ መቅረብ አልነበረባችሁም። በግንቡ ላይ ሆነው እንደሚመቷችሁ ማወቅ ነበረባችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከግንቡ ሆነው እንደሚወረውሩ

ይህ የሚያመለክተው የከተማዋ ሰዎች በከተማዋ ግንብ አናት ላይ ሆነው ወደ ጠላቶቻቸው ቁልቁል ቀስታቸውን እንደሚወረውሩ ነው። "ከከተማዋ ግንብ አናት ላይ ሆነው ቀስቶቻቸውን በእናንተ ላይ እንደሚወረውሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:21

የሩቤ-ሼትን ልጅ አቤሜሌክን የገደለው ማን ነው?

ኢዮአብ ዳዊት እነዚህን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በመጠየቅ ይገስጸኛል ብሎ ነበር። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " የሩቤ-ሼት ልጅ አቤሜሌክ እንዴት እንደተገደለ አስታውስ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የሩቤ-ሼት ልጅ አቤሜሌክ

ይህ የወንድ ስም ነው። አባቱ ጌድዮን በሚባልም ስም ይታወቅ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አንዲት ሴት በቴቤስ ከግንቡ የወፍጮ መጅ በጣለችበት ወቅት ሰውየው አልሞተምን?

ኢዮአብ ዳዊት እነዚህን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በመጠየቅ ይገስጸኛል ብሎ ነበር። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በቴቤስ ከግንቡ አናት ላይ ሆና የወፍጮ መጅ ስትጥልበት ሰውየው እንደሞተ አስታውሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የወፍጮ መጅ

ከባድ ድንጋይ፣ እህል ለመፍጨት የሚያገለግል

ከግንቡ

"ከከተማዋ ግንብ አናት"

ቴቤስ

ይህ የአንዲት ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ወደ ግንቡ ይህን ያህል እጅግ ተጠጋችሁ?

ኢዮአብ ዳዊት እነዚህን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በመጠየቅ ይገስጸኛል ብሎ ነበር። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወደ ግንቡ ይህን ያህል እጅግ መጠጋት አልነበረባችሁም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 11:22

በሩ/መግቢያው



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"የከተማው መግቢያ"
2 Samuel 11:24
አጭሩ ውርወራቸው
"አጭር የሚባለው የቀስት ውርወራቸው"
ጥቂት የንጉሱ ወታደሮች ተገደሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጥቂቶቹን የንጉሱን አገልጋዮች ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የንጉሱ አገልጋዮች
እዚህ ስፍራ "አገልጋዮች" የሚለው የሚያመለክተው ወታደሮችን እንጂ ባሮችን አይደለም፣ ምክንያቱም ወታደሮች የንጉሱ አገልጋዮች ነበሩ።
አገልጋይህ ኬጢያዊው ኦርዮን ተገድሏል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አገልጋይህን ኬጢያዊውን ኦርዮንን ገድለውታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰይፍ ይህንን ያንንም ይበላል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው የሚያመለክተው በሰይፍ አንድን ሰው የሚገድልን ሰው ነው። እንደዚሁም ደግሞ፣ አንድን ሰው በሰይፍ መግደል የተገለጸው ሰይፍ ሰዎችን "እንደሚበላ" ተደርጎ ነው። "አንደኛው ሰው በሰይፍ እንደሚገደል ሌላኛውም ሊገደል ይችላል" ወይም "በጦርነት ውስጥ ማንኛውም ሰው ሊሞት ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ውጊያህን ይበልጥ አጠንክረው
"ይበልጥ ጠንክረህ ተዋጋ"
2 Samuel 11:26
እጅግ አዘነች
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ሃዘኗ እጅግ ውስጧ እንደገባ አድርጎ ገልጾዋል። "እጅግ አዘነች" ወይም "በታላቅ ሁኔታ አዘነች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሀዘን
ከመከራ፣ ተስፋ ከመቁረጥ ወይም ከክፉ አጋጣሚ የሚመጣ የመከፋት ጥልቅ ስሜት
ዳዊት ልኮ ወደ ቤት አስመጣት
እዚህ ስፍራ "ልኮ" የሚለው ቃል እርሷን ለማግኘት እና ወደ እርሱ እንዲያመጧት መልዕክተኛ ላከ ማለት ነው። "ዳዊት ቤት እንዲያመጧት መልዕክተኛ ወደ እርሷ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
ያህዌን ደስ አላሰኘም
"ያህዌን አሳዘነ" ወይም "ያህዌን አስከፋ"

Chapter 12
2 Samuel 12:1
ሴት የበግ ጠቦት
ሴት ጠቦት በግ
ለእርሱ እንደ ሴት ልጁ ነበረች
ይህ የዚህን ሰው እና የግልገሉን ቅርበት ያመለክታል። "ከሴት ልጆቹ አንዲቱን የሆነች ያህል ጠቦቷን ይወዳት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 12:4
ሴት የበግ ጠቦት
ግልገል፣ ሴት በግ
ለእንግዳው
ለእንግዳው ይበላ ዘንድ ሊያቀርብለት። "ለእንገዳው እንዲመገብ ሊያቀርብለት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ዳዊት በቁጣ ነድዶ ተነሳ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ዳዊት እንዴት በጣም እንደተቆጣ የሚገልጸው ከቁጣው የተነሳ አካሉ እንደ ጋለ አድርጎ ነው። "ዳዊት በቁጣ ነደደ" ወይም "ዳዊት በጣም ተናደደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በናታን ተቆጣ
ይህ ማለት ዳዊት ናታንን በቁጣ ተናገረው
በያህዌ ህያውነት እምላለሁ
ይህ የሚገልጸው መሃላ መማሉን ወይም በጽኑ ቃል መግባቱን ነው። "በያህዌ ህያውነት እናገራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ሰው ይሙት
ይህ ማለት ይገደል ማለት ነው። እንደዚሁም፣ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሊገደል" ወይም "ሊሞት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ) የሚለውን ይመልከቱ)
የወሰደዳትን ግልገል አራት እጥፍ አድርጎ መመለስ ይገባዋል
ሃብታሙ ሰው ለድሃው እንዲመልስ የሚጠበቅበት መጠን ትንሽዋ ጠቦት ከምታወጣው አራት እጥፍ እንዲሆን ነበር። "ለድሃው የጠቦቷን ዋጋ አራት እጥፍ ሊመልስለት ይገባል" (ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ማዘን
ለተጎዳ ወይም ላልተወደደ ሰው አዘኔታና ፍቅር ማሳየት።
2 Samuel 12:7
ከሳኦል እጅ ያዳነኝ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚያመለክተው መቆጣጠርን ነው። "ከሳኦል ቁጥጥር" ወይም "ከሳኦል ሀይል" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የጌታህን ሚስቶች በክንዶችህ
እዚህ ስፍራ ያህዌ ዳዊት የጌታውን ሚስቶች እንደ ራሱ ሚስቶች ማግኘቱን የገለጸው፣ "በእርሱ ክንዶች ውስጥ" መሆናቸውን በመናገር ነው። "የጌታህን ሚስቶች እንደ ራስህ ሚስቶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤልን እና የይሁዳ ቤትን ጭምር ሰጥቼሃለሁ
እዚህ ስፍራ የያህዌ ዳዊትን እንዴት በእስራኤል እና ይሁዳ ላይ ንጉስ አድርጎ የእርሱን ስልጣን እንደሰጠው የተናገረው የእስራኤልን እና የይሁዳን ቤት እንደ ስጦታ አድርጎ እንደሰጠው በመግለጹ ነው። "የ...ቤት" የሚለው ሀረግ "የ...ሰዎች" ማለት ነው። "በእስራኤል እና ይሁዳ ሰዎች ላይ ንጉስ አድርጌ ስልጣን ሰጥቼሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ በጣም ትንሽ ቢሆን እንኳን
"በቂ ሰጥቼህ ባይሆን እንኳን"
2 Samuel 12:9
በእርሱ ዐይኖች ፊት ክፉ የሆነውን ለማድረግ... ለምን የያህዌን ነገር አቃለልህ?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ዳዊትን ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የያህዌን ነገር ማቃለል አልነበረብህም... በእርሱ ዐይኖች ፊት ክፉ የሆነውን ማድረግ አልነበረብህም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ዐይኖች ፊት ክፉ የሆነውን
እዚህ ስፍራ "እይታ/በዐይኖቹ ፊት" የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን ፈቃድ ነው። "እርሱ ክፉ የሚለው" ወይም "በያህዌ ዐይኖች ክፉ የሆነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ኬጢያዊውን ኦርዮን በሰይፍ መታኸው
ዳዊት ራሱ ኦርዮን አልገደለም፣ ይልቁንም በጦርነት ውስጥ እንዲሞት ሁኔታዎችን አበጀ። "በሰይፍ" የሚለው ሀረግ የሚገልጸው ኦርዮ በጦርነቱ ወቅት እንዴት እንደ ሞተ ነው። "ኬጢያዊው ኦርዮ በጦርነቱ ውስጥ እንዲሞት ሁኔታውን አበጀህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በአሞን ሰራዊት ሰይፍ ገደልከው
ዳዊት ራሱ ኦርዮን አልገደለም፤ ይልቁንም፣ እስራኤል ከአሞን ጋር ሲዋጋ በጦርነት ውስጥ ኦርዮ እንዲሞት ሁኔታዎችን አበጀ። "በሰይፍ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው በጦርነቱ ወስጥ እንዴት እንደ ሞተ ነው። "ከአሞን ሰራዊት ጋር ሲዋጋ በጦርነቱ ውስጥ እርሱ እንዲሞት አደራጀህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት

የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ ከቤትህ አይጠፋም

እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጦርነት የሚሞቱ ሰዎችን ነው። እንደዚሁም የዳዊት "ቤት" የሚለው የሚያመለክተው የእርሱን ትውልዶች ነው። "ከትውልድህ ጥቂቶቹ ሁሌም በጦርነት ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 12:11

ከራስህ ቤት ውስጥ

እዚህ ስፍራ የዳዊት "ቤት" የሚለው የሚያመለክተው ቤተሰቡን ነው። "ከራስህ ቤተሰብ መካከል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በገዛ ዐይኖችህ ፊት

እዚህ ስፍራ ዳዊት የተጠቀሰው በዐይኖቹ በሚለው ሲሆን ይህም የሚሆነውን እርሱ እንደሚያይ አጉልቶ ለማሳየት ነው። "አንተ እያየህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀን ብርሃን

"በእኩለ ቀን ብርሃን።" አንድን ነገር "በግልጽ" የማድረግ ሃሳብ ወይም ሰዎች የሚደረገውን ነገር በግልጽ እያወቁ ማድረግ ብዙውን ጊዜ "በቀን ብርሃን" ማድረግ በሚል ይነገራል። "በገሃድ" ወይም "የሚሆነውን ሁሉም ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአት ፈጸምክ

"በደልክ"

በእስራኤል ሁሉ ፊት

ይህ ሀረግ የሚናገረው የእስራኤል ሰዎች በሚስቶቹ ላይ የሆነውን እያወቁ በእርግጥ ሲሆን እንዳዩ አድርገው እንደመሰከሩ ተደርጎ ነው። "በመላው የእስራኤል ሰዎች ፊት" ወይም "መላው የእስራኤል ሰዎች ስለዚህ ነገር ያውቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ትቶልሃል/ምሮሃል

ያህዌ የዳዊትን ኃጢአት ይቅር ብሏል። ይህ እዚህ ስፍራ የተነገረው ያህዌ ኃጢአቱን ይቅር ያለው ተራምዶት እንዳለፈው አንድ ነገር እና እንደተወለት ተደርጎ ነው። "ይቅር የተባለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ አትሞትም/አትገደልም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። አንዳንዴ ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት ይሞታሉ፣ ነገር ግን እርሱ ከሴትየዋ ጋር በፈጸመው ኃጢአት አይሞትም። ይህ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "አትሞትም" ወይም "በዚህ ኃጢአት ምክንያት አትሞትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 12:14

ንቆሃል

እጅግ አንድን ሰው ወይም አንድን ነገር አለመውድ ወይም መጥላት

ለአንተ የሚወለደው ልጅ

"ለአንተ የሚወለደው" የሚለው ሀረግ የዳዊት ህጻን ልጅ ማለት ነው። "የሚወለደው የአንተ ልጅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ያንን ልጅ ቀጣው… እናም ታመመ

እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ያህዌ ህጻኑ እንዲታመመ ማድረጉን ያህዌ ህጻኑን እንደ ቀጣው ይናገራል። "ያህዌ ህጻኑን ቀጣው… እናም ህጻኑ በጣም ታመመ" ወይም "ያህዌ ህጻኑ … በጣም እንዲታመመ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የኦርዮ ሚስት ለዳዊት የወለደችው ልጅ

ይህ ማለት እርሷ ለዳዊት ስለ ወለደችለት ዳዊት የህጻኑ አባት ነበር። "የኦርዮ ሚስት የወለደችለት፣ የዳዊት ልጅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 12:16

ተማጸነ/ለመነ

መለመን ወይም በታከላቅ መሻት መጸለይ

ውስጥ ገባ

ዳዊት ብቻውን ወደ ክፍሉ ገባ። "ወደ ክፍሉ ውስጥ ገባ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ከመሬት ለማንሳት

"ከመሬት እንዲነሳ ለመኑት"

እንዲህም ሆነ

"እንዲህ ሆነ"

የእኛን ድምጽ/ንግግር አልሰማም

ይናገሩ እንደነበር ትኩረት ለመስጠት፣ አገልጋዮች እዚህ የተጠቀሱት በድምጻቸው ነው። "እርሱ እኛን አልሰማንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰባተኛው ቀን

"7ተኛው ቀን።" ይህ የሚያመለክተው ህጻኑ ከተወለደ ከሰባት ቀናት በኋላ ነው። "ከተወለደ ከሰባተኛ ቀን በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመልከት

ይህ የሚያገለግለው የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ልጁ መሞቱን ብንነግረው በራሱ ላይ ምን ያደርግ ይሆን?

አገልጋዮቹ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የጠየቁት ፍራቻቸውን ለመግለጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ልጁ መሞቱን ብንነግረው ራሱን ይጎዳል ብለን ፈርተናል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 12:19

እርስ በእርሳቸው ያንሾካሽኩ ነበር

"በጣም በጸጥታ እርስ በእርሳቸው ይነጋገሩ ነበር"

ዳዊት ተረዳ/አወቀ

"ዳዊት ገባው"

ዳዊት ተነሳ

"ዳዊት ብድግ አለ"

2 Samuel 12:21

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ ሀረግ፣ ዳዊት ያህዌ ይህ እንዲሆን መፍቀዱን መገንዘቡን አጉልቶ የሚያሳይ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የያዘ ነው።

ህጻኑ በህይወት እንዲኖር ያህዌ ደግነቱን ያሳየኝ ይፈቅድ እንደሆነ ማን ያውቃል?

ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የጠየቀው ያህዌ ህጻኑ በህይወት እንዲኖር ይፈቅድ እንደሆነ ማንም አለማወቁን ለማጉላት ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ ምህረት አድርጎልኝ ህጻኑ በህይወት እንዲኖር ይፍቀድ አይፍቀድ ማንም አያውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን አሁን እርሱ ሞቷል፣ ስለዚህ ስለምን እጾማለሁ?

ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የጠየቀው ከዚህ በኋላ የሚጾምበት ምክንያት እንደሌለ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አሁን እርሱ ሞቷል ከእንግዲህ መጾም ምንም ጥቅም የለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ገና ልመልሰው እችላለሁን?

ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የጠየቀው ልጁ ዳግም ወደ ህይወት ሊመለስ አለመቻሉን ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወደ ህያውነት ልመልሰው አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እርሱ እሄዳለሁ

ዳዊት ሲሞት ልጁ ወዳለበት እንደሚሄድ ይጠቁማል። "ስሞት እርሱ ወዳለበት እሄዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 12:24

ወደ እርሷ ሄደ፣ እናም ከእርሷ ጋር ተኛ

"ወደ እርሷ ሄደ" የሚለው ሀረግ ዳዊት ከእርሱ ሚስት ጋር ግንኙነት ማድረጉን



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በግልጽ የሚያሳይ ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው አብረው መተኛታቸውን ለማጉላት አገልግለዋል። "ከእርሷ ጋር ተኛ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በነቢዩ ናታን በኩል ቃል ላከ
እዚህ ስፍራ "ቃል" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ ናታን ለዳዊት እንዲነግረው የነገረውን/የላከውን መልዕክት ነው። "እንዲነግረው ናታንን ላከው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ይዲድያ
ይህ የዳዊት ልጅ የሰሎሞን ሌላው ስም ነው። ይህም ያህዌ ለእርሱ የመረጠለት ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 12:26
ኢዮአብ ተዋጋ.. እርሱ ያዘ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው "ኢዮአብ" ይላል፤ ነገር ግን እርሱ የሚያመለክተው ኢዮአብን እና አብረውት የሚዋጉትን ወታደሮቹን ነው። "ኢዮአብ እና የእርሱ ወታደሮች ተዋጉ… እነርሱ ያዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ረባት
ከዚህች ከተማ ጋር መዋጋት በቀጥታ/ቃል በቃል ከረባት ሰዎች ጋር መዋጋት ማለት ነው። በ2 ሳሙኤል 11:1 ውስጥ በተተረጎመው ተመሳሳይ መልክ ይህ ስም በተመሳሳይ ይተርጉም። "የረባት ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህም ኢዮአብ ወደ ዳዊት መልዕክተኞችን ልኮ እንዲህ አለ
"ስለዚህ ኢዮአብ ወደ ዳዊት እንዲህ ለማለት መልዕክተኞችን ላከ"
የከተማይቱን የውሃ ጣብያ/ማቀረቢያ ስፍራ ያዝ
አንድን ቦታ "መውሰድ" ወይም ምልክት ማድረግ ማለት ቦታውን መቆጠጣጠር ማለት ነው። "የከተማይቱን ውሃ ማቅረቢያ ስፍራ በቁጥጥር ስር ማድረግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ተዋጋሁ… እኔ ወሰድኩ… እኔ ብወስድ
እዚህ ስፍራ ኢዮአብ በእርግጥ ስለ ራሱ እና ስለ ወታደሮቹ ሲያመለክት ስለ ራሱ ይናገራል። "እኔ እና ወታደሮቼ ተዋጋን… ወታደሮቼ እና እኔ ያዝን…እኔ እና ወታደሮቼ ብንይዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በተቃራኒ መስፈር
ይህ ማለት መክበብ እና ማጥቃት ማለት ነው። "በጦር ሀይል መክበብ" ወይም "ከብቦ መያዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ውሰዳት…ከተማይቱን ውሰድ
አንድን ቦታ "መውሰድ" ወይም ምልክት ማድረግ ማለት ቦታውን መቆጠጣጠር ማለት ነው። "እርሷን ተቆጣጠራት…ከተማይቱን ተቆጣጠራት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስም ይሰጣታል/ትሰየማለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ይሰይሟታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 12:29
ተዋጋ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው በእርግጥ ስለ ዳዊት እና ወታደሮቹ እየተናገረ ሳለ ስለ ዳዊት ይናገራል። "ዳዊት እና ወታደሮቹ ተዋጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ታላንት
ይህ በዘመናዊ የክብደት መለኪያ ሊጻፍ ይችላል። "ወደ 33 ኪ.ግ የሚጠጋ" በሚለው ውስጥ። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)
የከበረ ድንጋይ
እንደ እንቁ፣ ሩቢ፣ ሰንፔር፣ መረገድ፣ ወይም ኦፔል የመሰሉ በጥቂቱ የሚገኙ የከበሩ ድንጋዮች
ዘውዱ በዳዊት ራስ ላይ ተጫነ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዘውዱን በዳዊት ራስ ላይ ጫኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ አባረራቸው/አስወጣቸው
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው በእርግጥ የዳዊትን ወታደሮች እያመለከተ ሳለ ስለ ዳዊት ይናገራል። "እነርሱ አባረሯቸው/አስወጧቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ዝርፊያ
ከተሸነፈ ጠላት ውድ ነገሮችን መውሰድ
በብዙ ቁጥር
"በብዙ መጠን"
2 Samuel 12:31
ህዝቡን አስወጣ
ዳዊት ህዝቡን ራሱ አላስወጣም፡ እንዲያስወጧቸው ወታደሮቹን አዝዟል። "ዳዊት ህዝቡን እንዲያስወጡ ወታደሮቹን አዘዘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
መጋዞች፣ የብረት መቆፈሪያ/ዶማ፣ እና መጥረቢያዎች
እነዚህ እንጨት መቁረጫ ወይም መሬት መቆፈሪያ መሳሪያዎች ናቸው
የጡብ ማቃጠያ
ጡቦች የሚደርቁበት እን የሚጠነክሩበት/የሚቃጠሉበት ምድጃ
የአሞን ሰዎች ሁሉም ከተሞች
ይህ የሚያመለክተው በከተሞቹ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። "የአሞን ከተሞች ነዋሪዎች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 13
2 Samuel 13:1
ከዚህም በኋላ እንዲህ ሆነ
"ከዚህ በኋላ እንዲህ ሆነ።" ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት አዲስ ትዕይንትን ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
ግማሽ እህት/በአባት ወይም በእናት ብቻ የሚገኛኙ
አምኖን እና ትዕማር አባታቸው አንድ ሲሆን በእናት ይለያያሉ
ሙሉ እህት/በአባትና በእናት የሚገናኙ
አቤሴሎም እና ትዕማር በአባትም በእናትም ይገናኛሉ
አምኖን በእህቱ በትዕማር ምክንያት እስኪታመም ድረስ እጅግ ተረብሾ ነበር
አምኖን የተረበሸው ከእህቱ ከትዕማር ጋር ለመተኛት ፍላጎት ስለነበረው ነው። "አምኖን ለእህቱ ትዕማር በነበረው ፍላጎት ህመም እስኪሰማው ድረስ እጅግ ተረብሾ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 13:3
የሳምዓ ልጅ ኢዮናዳብ፣ የዳዊት ወንድም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ሳምዓ ልጅ የዳዊት ወንድም ነበር (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ብልጥ/ነገረኛ
አታላይ ወይም አስመሳይ
ድባቴ/መጫጫን
ደስታ የማጣት ከፍተኛ ስሜት
አትነግረኝምን?
ስለ ድባቴው እየጠየቀው መሆኑ ግልጽ ነው፤ ይህ በገልጽ ሊጻፍ ይችላል። እንደዚሁም፣ ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ አምኖን ለምን እንደ ተደበተ ከኢዮናዳብ የቀረበለት ጥያቄ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ለምን እንደ ተደበትክ አትነግረኝምን?" ወይም "እባክህ፣ ለምን እንደ ተደበትክ ንገረኝ" በሚል ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 13:5
ኢዮናዳብ
በ2 ሳሙኤል 13:3 ላይ ይህ ስም እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ከእርሷ እጅ በላ… ከእርሷ እጅ እበላ/እነርስ ዘንድ
ይህ እርሷ በግል ምግብ እንድታዘጋጅለት የቀረበ ጥያቄ ነው። "ራስዋ ይህን እኔን ታገልግለኝ… መብላት እንድችል እርሷ ታቅርብልኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የታመመ መሰለ
ይህ ማለት የታመመ ለመምሰል ሀሰተኛ ገጽታ አሳየ
ለህመሜ ከእኔ ፊቴ ለፊት
ታሟልና ጉዳዩ ከምግቡ አይደለም፣ ነገር ግን ይልቁንም ያስፈለገው እንክብካቤው ነው። "ከእኔ ፊቴ ለፊት" የሚለው ሀረግ በእርሱ ፊት ምግቡን እንድታዘጋጅለት ለትዕማር የቀረበ ጥያቄ ነው። "ታምሜያለሁና ከእኔ ፊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 13:7
ዳዊት ቃል ላከ
ይህ ማለት ከትዕማር ጋር ለመነጋገር መልዕክተኛ ላከ። "ዳዊት መልዕክተኛ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሊጥ
ለመጋጋር የሚውል የዱቄት እና ፈሳሽ ድብለቅ
አቦካች
ሊጡን ለማደባለቅ እጇችዋን ተጠቀመች
እርሱ አያየ
ይህ ማለት ትዕማር ዳቦውን በፊቱ አዘጋጀች። "በእርሱ ፊት" ወይም "እርሱ ባለበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህም ሁሉም እርሱ ካለበት ወደ ውጭ ወጡ
"አንድ ሰው ከሚገኝበት መውጣት" ማለት እነርሱን ለብቻቸው መተው ማለት ነው። "ስለዚህ ሁሉም እርሱን ትቶ ወጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 13:10
ከእጅሽ አበላ/አጎርስ ዘንድ
ይህ ለእርሱ ምግቡን ታቀርብለት ዘንድ ለትዕማር የቀረበ ጥያቄ ነው። "ለእኔም ምግቡን እንድታቀርቢልኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አታስገድደኝ
ከእርሱ ጋር ስለ መተኛት ያለውን ሁኔታ እየተናገረች ነው። "ከአንተ ጋር እንድተኛ አታስገድደኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
አስፈሪ
በጣም አሳፋሪ
2 Samuel 13:13
አጠቃላይ መረጃ፡
ትዕማር ከአምኖን ጋር መነጋገሯን ቀጠለች
እኔስ እፍሬቴን እንዴት ማስወገድ እችላለሁ?
ትዕማር ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የምትጠይቀው ከወንድሟ ጋር ብትተኛ ምን ያህል እንደሚያሳፍራት ትኩረት ለመስጠት ነው። ትዕማር እፍረቷን ማስወገድን የምትገልጸው ልታመልጠው የምትፈልገው ጠላት ወይም ስቃይ አድራሽ እንደሆነ አድርጋ ነው። "ይህን ብታደርግ፣ በሄድኩበት ሁሉ ነውር ተሸካሚ እሆናለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 13:15
እኔን በማስውጣት የምታደርገው ታላቅ ክፋት የከፋ ይሆናል
"ይህ ታላቅ ክፋት" የሚለው ረቂቅ ስም፣ ግስ ሆኖ ሊጻፍ ይችላል። "እኔን ማስወጣትህ በጣም ክፉ ይሆናል! ይህ እንዲያውም የከፋ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ከኋላዋ በሩን ቀረቀረባት
ይህ ማለት ተመልሳ እንዳትገባ በሩን በላይዋ መዝጋት ማለት ነው። "ተመልሳ እንዳትገባ በሩን ዘጋባት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 13:18
ከኋላዋ በሩን ቀረቀረባት
ይህ ማለት ተመልሳ እንዳትገባ በሩን በላይዋ መዝጋት ማለት ነው። "ተመልሳ እንዳትገባ በሩን ዘጋባት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በራሷ ላይ አመድ ነሰነሰች ቀሚሷንም ደግሞ ቀደደች። እጆቿን በራሷ ላይ ጫነች
እነዚህ በእስራኤል ባህል የለቅሶ እና የሀዘን ድርጊቶች ናቸው። "በጣም ማዘኗን ለማሳየት በራሷ ላይ አመድ ነሰነሰች ቀሚሷንም ደግሞ ቀደደች። ከዚያም ሀዘኗን ለመግለጽ፣ እጆቿን ጭንቅላቷ ላይ ጫነች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊቶች)
2 Samuel 13:20
ወንድምሽ አምኖን ከአንቺ ጋር ነበርን?
ይህ በጨዋ/ትሁት መልክ አምኖን ከአንቺ ጋር ግንኙነት አድርጎ ነበርን ማለት ነው። "ወንድምሽ አምኖን ከአንቺ ጋር ተኝቶ ነበርን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
ጸጥ በይ/ዝም በይ
ይህ ማለት ስለ አንድ ነገር ለማንም አለመናገር ማለት ነው። "ስለዚህ ጉዳይ ለማንም አትናገሪ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህንን ነገር በልብሽ አትያዥው
"አንድን ነገር በልብ መያዝ" የሚለው ሀረግ "ስለዚያ ነገር መጨነቅ" ማለት ነው። "ስለሆነው ነገር አትጨነቂ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህም ትዕማር ለብቻዋ ቀረች
ይህ ማለት አላገባችም ማለት ነው።
ምንም አልተናገረም
"አልተናገረም"
2 Samuel 13:23
ከሁለት ድፍን አመታት በኋላ እንዲህ ሆነ
ይህ የሚያስረዳው ሁለት ሙሉ አመታት እንዳለፉ እና በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩ ትእይንት እንደጀመረ ነው። "ሙሉ አመታት" የሚለው ይህ ሀረግ ትርጉሙ ሙሉ አመታት ነበሩ ማለት ነው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
ሸላቾች
እነዚህ የበጎችን ፀጉር/ሱፍ የሚሸልቱ ሰዎች ናቸው
ቤላሶር
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አሁን ተመልከት
ይህ አንድ ሰው ቀጥሎ የሚነገረውን ነገር እንዲሰማ ትኩረቱን ለመሳብ የዋለ ሀረግ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
የአንተ አገልጋይ/አገልጋይህ
አቤሴሎም አክብሮቱን ለመግለጸ ራሱን "የአንተ አገልጋይ/አገልጋይህ" በማለት ይጠራል።
በግ ሸላቾች አሉት
የእስራኤል ሰዎች በጎቻቸውን ከሸለቱ በኋላ መደገሳቸው የተለመደ መበር
ንጉሡ
የሚነጋገረው ከአባቱ ጋር ቢሆንም አክብሮቱን ለመግለጽ "ንጉሡ" ብሎ ይጠራዋል እንጂ "አንተ" እያለ አያነጋግረውም።
2 Samuel 13:25
አባክህ ወንድሜ አምኖን ከእኛ ጋር ይሂድ
በእስራኤል ባህል ብዙውን ጊዜ ታላቅ ወንድም አባቱን ሊወክል ይችላል። አምኖን የዳዊት ታላቅ ልጅ ነበር።
አምኖን ለምን ከአናንተ ጋር ይሄዳል?
ዳዊት አምኖን የአቤሴሎም ወዳጅ እንዳልሆነ ያውቃል።
2 Samuel 13:27
አቤሴሎም ዳዊትን ተጫነው/አጥብቆ ጠየቀው
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው አቤሴሎም አብሯቸው እንዲሄድ ዳዊት ይፈቅድ ዘንድ አምኖን የጠየቀበትን ሁኔታ በእርሱ ላይ አካላዊ ጫና እንዳሳረፈ አድርጎ ያቀርበዋል። "አቤሴሎም አምኖን ይመጣ ዘንድ ዳዊትን ለመነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አትፍሩ
ይህ የሚያመለክተው አምኖንን በመግዳላቸው ሊከተል የሚችለው ውጤት ሊያስፈራቸው እንደማይገባ ነው። ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "የንጉሱን ልጅ በመግደላችሁ እንወነጀላለን ብላችሁ አትፍሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ

የሚለውን ይመልከቱ)
ያዘዝኳችሁ እኔ አይደለሁምን?
አቤሴሎም ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ለአምኖን መገደል እርሱ ተጠያቂ እንደሚሆን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው፤ ምክንያቱም ያዘዛቸው እርሱ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ይህን እንድታደርጉ ያዘዝኳችሁ እኔ ነኝ" ወይም "ለእርሱ መግደል ተጠያቂ የምሆነው እኔ ነኝ ምክንያቱም ይህን እንድታደርጉ እኔ አዝዣችኋለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
እናንተን አላዘዝኳችሁም
አቤሴሎም ያደርጉት ዘንድ እነርሱን ያዘዘው ነገር በጥያቄው ውስጥ ሊገለጽ ይችላል። "እርሱን እንድትገድሉት አላዘዝኳችሁም" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
የንጉሱ ወንዶች ልጆች ሁሉ
ይህ የሞቱትን አቤሴሎምን እና አምኖንን አይጨምርም። ይህ የሚያካትተው ወደ ድግሱ እንዲሄዱ ንጉሱ የፈቀደላቸውን የተቀሩትን ወንድ ልጆች ነው። "የተቀሩት የንጉሱ ወንድ ልጆች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
እያንዳንዱ ሰው
ይህ የሚያመለክተው ድግሱን ትተው የወጡትን የንጉሱን ወንዶች ልጆች ነው።
2 Samuel 13:30
ስለዚህም እንዲህ ሆነ
"እንዲህም ሆነ።" እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
በመንገድ ላይ
"በመንገድ በመጓዝ ላይ"
እንዲህ የሚል ወሬ ወደ ዳዊት ደረሰ
እዚህ ላይ አንድ ሰው በእርግጥ ደርሷ ለዳዊት ወሬውን ሲነግረው ወሬው ደረሰ ይላል። "አንድ ሰው መጥቶ ወሬውን ለዳዊት እንዲህ ሲል ነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያም ንጉሡ ተነሳ
"ከዚያ ንጉሡ ተነስቶ ቆመ"
ልብሱን ቀደደ፣ በምድርም ላይ ወደቀ
እነዚህን ነገሮች ያደረገው እጅግ ማዘኑን ለመግለጽ ነው። "ልብሱን ቀደደ፣ አምርሮ በማዘን ምድር ላይ ወደቀ" (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ልብሶቻቸውን ቀደዱ
እነርሱ ይህንን ያደረጉት ሀዘናቸውን ለመግለጽ እና ከንጉሱ ጋር ለማዘን ነው። "ልብሶቻቸውንም ቀደዱ፣ ከንጉሱ ጋር አዘኑ" (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 13:32
ኢዮናዳብ...ሳምዓ
እነዚህን የወንድ ስሞች በ2 ሳሙኤል 13:3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ
ጌታዬ ይህንን አይመን/አይቀበል
"ጌታዬ፣ ይህንን አይመን"
ጌታዬ
ኢዮአብ አክብሮቱን ለመግለጽ ዳዊትን "ጌታዬ" ይለዋል
አምኖን እህቱን አስገደዳት
ይህ አምኖን እህቱን ደፈራት የሚለውን በጨዋ/ትሁት ቋንቋ ለመግለጽ ነው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
ጌታዬ ንጉሱ አይቀበል/አያስብ
"ንጉሱ የእኔ ጌታ፣ አይቀበል/አያስብ"
ይህንን ወሬ በልቡ አያኑር
"አንድን ነገር ወደ ልብ መውሰድ/በልብ ማኖር" የሚለው ሀረግ "ስለዚያ ነገር መጨነቅ" ማለት ነው። "ስለዚህ ወሬ አትጨነቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 13:34
መጠበቁን ቀጠለ/ነቅቶ ጠበቀ
ይህ ማለት አገልጋዩ በከተማይቱ ግንብ ሲጠብቅ ሳለ ጠላትን በንቃት ይከታተል ነበር። "ይጠብቅ የነበረው" ወይም "በከተማይቱ ግንብ ይጠብቅ የነበረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዐይኖቹን አቅንቶ
እዚህ ስፍራ አገልጋዩ ያደርግ የነበረው ጥበቃ የተገለጸው ዐይኖቹን ወደ ላይ እንዳነሳ ተደርጎ ነው። "አቅንቶ ተመለከተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንተ ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
ድምጻቸውን አነሱ
እዚህ ስፍራ የወንዶች ልጆቹ ጩኸት የተነገረው ድምጻቸው ወደ ሰማይ እንዳነሱት አንድ ነገር ተደርጎ ነው። "ጮኹ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 13:37
ተልማይ... ዓሚሁድ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእርሱ ወንድ ልጅ
" ለወንድ ልጁ ለአሞን"
ለሶስት አመታት በነበረበት
"ለሶስት አመታት በቆየበት"
ንጉስ ዳዊት ናፈቀ
እዚህ ስፍራ የዳዊትን ናፍቆት ለማጉላት ያሳሰበው ሁኔታ ተገልጽዋል።
በአምኖን ሞት ከደከረሰበት ሀዘን ተጽናና
"ከዚህ በኋላ በአምኖን ሞት ማዘኑ አልቀጠለም።" ይህ የሚያመለክተው አቤሴሎም ወደ ጌሹር ከሸሸ በኋላ ያለውን ሶስት አመት ነው።

---

Chapter 14
2 Samuel 14:1
አሁን
ይህ ቃል እዚህ ስፍራ ላይ የዋለው በዋናው ታሪክ ፍሰት ላይ ማቆሚያ ምልክት ለማድረግ ነው። እዚህ ጸሐፊው በታሪኩ ውስጥ ስለ አዲስ ሰው ይናገራል።
ጽሩያም
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 2:13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ተረዳ
ይህ ማለት ኢዮአብ ዳዊት ያስብ የነበረውን ለይቶ አውቋል ወይም ተረድቷል ማለት ነው።
ወደ ቴቁሔ ቃል ላከ ደግሞም ብልህ ሴት አስመጣ
ይህ ማለት ኢዮአብ አንድ ሰው መልዕክት አስይዞ ወደ ቴቁሔ ላከ ደግሞም አንዲት ሴት ወደ እርሱ እንዲያመጡ አደረገ። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "መልዕክት አስይዞ አንድ ሰው ወደ ቴቁሄ ላከ ደግሞም አንዲት ብልህ ሴት ወደ እርሱ ይዘው መጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ቴቁሔ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የሞተው
ይህ በአጠቃላይ ስለ ሞቱ ሰዎች ሳይሆን፣ ስለ አንድ የሞተ ሰው ያመለክታል። "አንድ የሞተ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 14:4
በመሬት ላይ በፊቷ ተደፋች
ይህን ያደረገችው ለንጉሱ ያላትን ክብር እና መታዘዝ ለማሳየት ነው። "በምድር ላይ በፊቷ በመደፋት ለንጉሱ ያላትን ክብር አሳየች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
አንዱ ሌላውን መታው
"ከወንድ ልጆቼ አንዱ ሌላውን በአንድ ነገር መታው"
2 Samuel 14:7
መላው ጎሳ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"መላው ቤተሰቤ"

የአንተ አገልጋይ

ሴትየዋ ለንጉሡ ያላትን ክብር ለማሳየት ራስዋን "የአንተ አገልጋይ" ብላ ትጠራለች።

ወደ ሞት ጣሉት

ይህ መግደል ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወራሹንም ደግሞ ያጠፉታል

ጥፋተኛውን ወንድሙን ከገደሉት የቤተሰቡን ሀብት የሚወርስ ልጅ አይተርፍም። የዚህ ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ይህንን ካደረጉ፣ የቤተሰባችንን ወራሽ ያጠፋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ከሆነ የቀረኝን የሚነደውን ከሰሌን ያጠፉታል

እዚህ ስፍራ ሴትየዋ በህወት የቀረውን ብቸኛ ልጇን የምትገልጸው እንደሚነድ የከሰል ቁራጭ አድርጋው ነው። ልጇን የሚገድሉትን ሰዎች የምትገልጸው የሚነደውን ከሰል እንደሚያጠፉ አድርጋ ነው። "በዚህ መንገድ የቀረኝን ብቸኛ ልጅ ይገድሉታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለባሌ ስም ሆነ ዘር አያስቀሩለትም

ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ለባሌ ስምም ሆነ ዘር አያስቀሩለትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ/ድርብ አሉታ የሚለውን ይመልከቱ)

ስምም ሆነ ዘር/ትውልድ

ይህ የሚያመለክተው ወንድ ልጅ የቤተሰቡን ስም ወደ ተከታዩ ትውልድ የሚያሸጋግር መሆኑን ነው። "የቤተሰባችንን ስም የሚጠብቅ ወንድ ልጅ አይኖርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በምድር ገጽ

"በምድር።" ይህ ገላጭ ሀረግ የሚያጎላው ባል ከሞተ በኋላ የቤተሰቡ መስመር/ ሀረግ በምድር ላይ ሊቀጥል አለመቻሉን ነው። "የምድር ገጽ" የሚለው የሚያመለክተው ሰዎች የሚራመዱበትን ምድር ነው።

## 2 Samuel 14:8

አንዳች ነገር ለአንቺ እንዲደረግ አዛለሁ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ ስለዚህ ጉዳይሽ አዛለሁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቴቁሔ

ይህን የቦታ ስም በ2 ሳሙኤል 14፡12 ላይ እንደ ተረጎሙት ይተርጉሙት።

ጥፋቱ/ኃጢአቱ በእኔ እና በአባቴ ቤተሰብ ላይ ይሁን

ይህ ማለት ህዝቡ፣ ንጉሱ የሴትየዋን ቤተሰብ በመርዳቱ ተሳስቷል ቢል ንጉሱ ጥፋተኛ አይሆን። የዚህ ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ሊብራራ ይችላል። "የእኛን ቤተሰብ በመርዳቱ ማንም ንጉሱን ጥፋተኛ ቢያደርግ፣ በዚያ ምትክ የእኔ ቤተሰብ ጥፋተኛ ይደረግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ እና ዙፋኑ

እዚህ ስፍራ "ዙፋን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በዳዊት ስፍራ ንጉስ የሚሆነውን ሰው ነው። "ንጉሡ እና የእርሱ ትውልድ" ወይም "ንጉሱ እና ቤተሰቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጥፋተኛ አይሆኑም

"ንጹሃን ናቸው።" ይህ የሚያመለክተው ወደፊት ማንም ንጉሱን ጥፋተኛ አድርጎ ቢቆጥር፣ እርሱ በዚህ ጉዳይ ንጹህ ይሆናል። "ይህን ጉዳይ በሚመለከት ንጹህ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

## 2 Samuel 14:10

የሚናገርሽን ማናቸውንም ነገር

እዚህ ስፍራ ማስፈራራት የተገለጸው በአጠቃላይ እንደ መናገር ነው። "የሚያስፈራሽ" ወይም "በማስፈራራት የሚናገርሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክዶክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ አይነካሽም

እዚህ ስፍራ ዳዊት ሰውየው እርሷን አይነካትም በሚል፣ አንድ ሰው እርሷን አያስፈራራትም ወይም አይጎዳትም በሚል ይናገራል። ዳዊት ሴትየዋን የሚያስፈራራት ሰው ዳግም እንዲያስቸግራት እንደማይፈቅድ በውስጠ ታዋቂ ተጠቁሟል። የዚህ ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ዳግም እንደማያስፈራራሽ አረጋግጥልሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

## 2 Samuel 14:12

የአንተ አገልጋይ

ሴትየዋ ለንጉሡ ያላትን አክብሮት ለማሳየት ራሷን "የአንተ አገልጋይ" በማለት ትገልጻለች።

ሌላ ቃል ልናገር

"ስለ ሌላ ነገር መናገር።" ሴትየዋ ንጉሡን ስለ ሌላ ርዕስ እንድትናገር እየተየቀች ነው።

ተናገሪ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ንጉሡ ንግግሯን እንድትቀጥል ፈቃድ እየሰጣት ነበር። "ለእኔ መናገር ትችያለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ ለምን እንዲህ ያለ ነገር አሰብህ?

ሴትየዋ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የጠየቀችው ዳዊት በአቤሴሎም ላይ ስላደረሰው ነገር ለመገሰጽ ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አሁን የተናገርከው ራሱ ስህተት መስራትህን ያረጋግጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ጥፋት እንዳለበት ሰው/በደለኛ ነው።

ሴትየዋ ፊት ለፊት ባትናገርም ንጉሡ በደለኛ መሆኑን ለመጠቆም፣ በደለኛ ከሆነ አንድ ሰው ጋር ንጉሡን ታነጻጽራለች። "ንጉሡ ራሱን ጥፋተኛ አድርጓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የተሳደደው ልጁ

"እርሱ ያሳደደው ልጁ"

ሁላችንም ሟች ነን፣ ሁላችንም በምድር ላይ እንደ ፈሰሰ... ዳግም እንደ ማይታፈስ ውሃ ነን

እዚህ ስፍራ ሴትየዋ ስለ ሞተ አንድ ሰው በመሬት ላይ እንደ ፈሰሰ ውሃ አድርጋ ትናገራለች። "ሁላችንም ሟች ነን፣ ከሞትን በኋላ ዳግም ወደ ህይወት መመለስ አንችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር... የተጣሉት ይጠገኑ ዘንድ መንገድ አለው

ሴትየዋ ዳዊት ልጁን መልሶ መቀበል እንዳለበት እያመላከተች ነው። ይህ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ከፊቱ ያስወገደውን እየመለሰ ነው፣ አንተም ለልጅህ እንደዚያው ማድረግ ይገባሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

## 2 Samuel 14:15

ሰዎች አስፈራርተውኛልና

የታወቀው መረጃ ሊቀርብ ይችላል። "ሰዎች እንድፈራ ስላደረጉኝ መጥቻለሁ" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ አገልጋይ

ሴትየዋ ለንጉሡ ያላትን ክብር ለማሳየት ራስዋን "የአንተ አገልጋይ" ብላ ትጠራለች።

ከሰው እጅ

ይህ ሀረግ ፈሊጥ ነው። እንደዚሁም፣ "እጅ" የሚለው የሰውን የቁጥጥር አቅም የሚያመለክት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ከሰውየው ቁጥጥር ውጭ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የጌታዬ የንጉሡ ቃል

"የጌታዬ የንጉሡ መልዕክት"

ጌታዬ ክፉው ከመልካሙ ለመለየት.... ልክ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነው

እዚህ ስፍራንጉሡ ዳዊት ከ "እግኢአብሔር መልአክ" ጋር ተነጻጽሯል። "ንጉሡ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነው፣ ምክንያቱም ሁለቱም ክፉውን ከመልካሙ ለይቶ መናገር ይችላሉ" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

## 2 Samuel 14:18

እባክሽ የምጠይቅሽን ሁሉ ከእኔ አትደብቂ

እዚህ ስፍራ አሉታዊ ዐረፍተ ነገሩ የዋለው ትኩረት ለመስጠት ነው፤ ሆኖም በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "እባክሽ ስለምጠይቅሽ ነገር ሁሉ እውነቱን

ንገሪኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ላይዶልስ የሚለውን ይመልከቱ)
በዚህ ሁሉ የኢዮአብ እጅ ከአንቺ ጋር አይደለምን
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢዮአብን ተጽዕኖ ነው። "ኢዮአብ በዚህ ሁሉ ተጽዕኖ አላሳደረብሽምን" ወይም "እነዚህ ነገሮች እንድትናገሪ የላከሽ ኢዮአብ ነውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በህያው ነፍስህ
"የአንተ ህያውነት እርግጥ የሆነውን ያህል።" እዚህ ስፍራ ሴትየዋ ዳዊት የተናገረውን ነገር እርግጠኝነት እርሱ በህይወት መኖሩ እርግጥ ከመሆኑ ጋር የምታነጻጽረው የእርሱ ሃሳብ ምን ያህል እውነት እንደሆነ ለማጉላት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡ ከተናገረው ሁሉ ማንም ወደ ቀኝም ወደ ግራም .... ሊል አይችልም
እዚህ ስፍራ ሴትየዋ ከንጉሡ ጋር መነጋገር እና እውነቱን ከእርሱ መሸሸግ ያለው ያለውን አስቸጋሪነት የምትገልጸው ወደ የትኛውም አቅጣጫ ማምለጥ ካቃተው ሰው ጋር በማነጻጸር ነው። "ማንም እውነቱን ከማወቅ ሊያግድህ አይችልም" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ
አገላለጹ ሁለት ጽንፎችን ያሳያል ትርጉሙም "ወዴትም" ማለት ነው። "በፍጹም የትም" ወይም "የትም ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜሪዝም/ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)
ጌታዬ ጠቢብ ነው
"ንጉሡ ጌታዬ ጠቢብ ነው"
እንደ እግዚአብሔር መልአክ ጥበብ፣ ጠቢብ ነው
ሴትየዋ የዳዊትን ጥበብ ከመልአክ ጥበብ ጋር ያነጻጸረችው ዳዊት ምን ያህል ጥበበኛ እንደሆነ ለማጉላት ነው። "እንደ እግዚአብሔር መልአክ፣ አንተ በጣም ጠቢብ ነህ" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 14:21
ስለዚህ ንጉሡ ኢዮአብን እንዲህ አለው
በውስጠ ታዋቂነት ንጉሡ ኢዮአብን ያናግረው ዘንድ እርሱን/አቤሶሎምን እንዲያመጣው ተናግሯል። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ከዚያም ንጉሡ ኢዮአብን ጠርቶ እንዲህ አለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አሁን ተመልከት/እነሆ
ይህ ሀረግ የዋለው የአንድን ሰው ትኩረት ቀጥሎ ወደ ሚነገረው ነገር ለመሳብ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ይህ ነገር
ይህ የሚያመለክተው ኢዮአብ ንጉሡ እንዲያደርግ የሚፈልገውን ነው። የዚህ ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "እኔ አደርገው ዘንድ አንተ የምትፈልገው ነገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ኢዮአብ ፊቱን ወደ ምድር ደፍቶ እጅ ነሣ
ኢዮአብ ይህንን ያደረገው ንጉሡን ለማክበር እና የንጉሡን ታላቅነት ለማሳየት ነው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት)
የአንተ አገልጋይ
ኢዮአብ ለንጉሡ ያለውን ክብር ለማሳየት ራሱን "የአንተ አገልጋይ" ሲል ይጠራል/ያመለክታል።
በዐይኖችህ ሞገስ አገኝቻለሁ
"ሞገስ አግኝቻለሁ" የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ በአንድ ሰው ፊት ተቀባይነት ማግኘት ማለት ነው። እንደዚሁም "ዐይኖች" የሚለው ለማየት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን ደግሞም ማየት ፍርድን ወይም ምዘናን ይወክላል። "አንተ በእኔ ደስ ተሰኝተሃል" ወይም "አንተ እኔን ተቀብለሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እንዲሁም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
በዚያ ውስጥ ንጉሡ
"ምክንያቱም ንጉሡ"
ንጉሡ የአገልጋዩን ጥያቄ መለሰ
"እንድታደርግልኝ የጠየቅኩህን አደረግህ"
2 Samuel 14:23
አሁን
ይህ ቃል በዋናው ታሪክ ፍሰት መቆሚያ ያበጃል። ይህ አዲስ ክፍል ተከትሎ ለሚመጣው የታሪክ ክፍል የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የመለውን ይመልከቱ)
እንደ አቤሴሎም በውበቱ የተደነቀ ሰው ማንም አልነበረም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ማንንም ካደነቁት ይልቅ አቤሴሎምን በውበቱ አደነቁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ውበት/ቁንጅና
መልካም እና ለዕይታ ደስ የሚያሰኝ፣ በተለይ ለፊት/ገጽታ ውበት
ከእግሩ ጫማ አስከ እናቱ ጫፍ በእርሱ ላይ ነቀፊታ አልነበረም
ይህ ማለት መላ ሰውነቱ ያለ ነቀፊታ ነበር። "ከአካሉ በአንዱም ላይ ነቀፊታ አልነበረም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሚሪዝም/ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)
ሁለት መቶ ሰቅል
ይህ በዘመናዊ መለኪያ ሊጻፍ ይችላል። "ሁለት ተኩል ኪሎ ግራም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)
የንጉሡ የክብደት መለኪያ
ንጉሡ የሰቅልን መደበኛ ክብደት እና ሌሎች ክብደቶችን እና መለኪያዎችን የሚወስንበት መለኪያ አለው
ለአቤሴሎም ሶስት ወንዶች እና አንድ ሴት ልጅ ተወልደውለት ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አቤሴሎም ሶስት ወንድ ልጆች እና አንድ ሴት ልጅ ነበረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
2 Samuel 14:25
አሁን
ይህ ቃል በዋናው ታሪክ ፍሰት መቆሚያ ያበጃል። ይህ አዲስ ክፍል ተከትሎ ለሚመጣው የታሪክ ክፍል የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የመለውን ይመልከቱ)
እንደ አቤሴሎም በውበቱ የተደነቀ ሰው ማንም አልነበረም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ማንንም ካደነቁት ይልቅ አቤሴሎምን በውበቱ አደነቁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ውበት/ቁንጅና
መልካም እና ለዕይታ ደስ የሚያሰኝ፣ በተለይ ለፊት/ገጽታ ውበት
ከእግሩ ጫማ አስከ እናቱ ጫፍ በእርሱ ላይ ነቀፊታ አልነበረም
ይህ ማለት መላ ሰውነቱ ያለ ነቀፊታ ነበር። "ከአካሉ በአንዱም ላይ ነቀፊታ አልነበረም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሚሪዝም/ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)
ሁለት መቶ ሰቅል
ይህ በዘመናዊ መለኪያ ሊጻፍ ይችላል። "ሁለት ተኩል ኪሎ ግራም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)
የንጉሡ የክብደት መለኪያ
ንጉሡ የሰቅልን መደበኛ ክብደት እና ሌሎች ክብደቶችን እና መለኪያዎችን የሚወስንበት መለኪያ አለው
ለአቤሴሎም ሶስት ወንዶች እና አንድ ሴት ልጅ ተወልደውለት ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አቤሴሎም ሶስት ወንድ ልጆች እና አንድ ሴት ልጅ ነበረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
2 Samuel 14:28
የንጉሡ ፊት
እዚህ "የንጉሡ ፊት" የሚለው የሚያመለክተው ንጉሡን ራሱን ነው። "ንጉሡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
አቤሴሎም ወደ ኢዮአብ ቃል ላከ
እዚህ ስፍራ "ቃል" የሚለው "መልዕክት" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህም ማለት አቤሴሎም ጥያቄ አስይዞ ወደ ኢዮአብ መልዕክተኛ ላከ። "አቤሴሎም እርሱን ይልከው ዘንድ እየጠየቀ ወደ ኢዮአብ መልዕክተኛ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ንጉሡ ይልከው ዘንድ
አቤሴሎም ኢዮአብ ወደ እርሱ እንዲመጣ የፈለገው እርሱን እንዲያየው እና ንጉሡን

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ማየት እንዲችል እንዲያስታርቀው መሆኑ በስውር ተጠቅሷል። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ወደ እርሱ እንዲመጣ እና ንጉሡን ይመለከት ዘንድ እንዲያስታርቀው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ አቤሴሎም ለሁለተኛ ጊዜ ቃል ላከ

እዚህ ስፍራ "ቃል" የሚለው "መልዕክት" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ ማለት በተመሳሳይ ጥያቄ ወደ ኢዮአብ መልዕክተኛ ላከ። የዚህ ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ስለዚህም አቤሴሎም በተመሳሳይ ጥያቄ ዳግም ወደ ኢዮአብ መልዕክተኛ ላከ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 14:30

እዩ

እዚህ ስፍራ ይህ ቃል የዋለው ሰዎችን አንድ ነገር ለማስታወስ ነው። "እንደምታውቁት"

2 Samuel 14:32

ተመልከት/ትኩረት ስጥ

"ትኩረት ስጥ፣ ምክንያቱም የምናገረው እውነትም ጠቃሚም ነው"

ቃል ላክሁ

እዚህ ስፍራ "ቃል" የሚለው "መልዕክት" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ ማለት መልዕክተኛ ላከ ማለት ነው። "መልዕክተኛ ላክሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለንጉሡ ለመንገር

እዚህ ስፍራ ለንጉሡ መልዕክት የተጻፈው ተናጋሪው አቤሴሎም እንደሆነ ተደርጎ ነው። አቤሴሎም ኢዮአብን በእርሱ ምትክ ሆኖ መልዕክቱን እንዲናገር ይጠይቀዋል። የዚህ ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "በእኔ ምትክ ሆነህ ለንጉሡ እንድትናገር" ወይም "ንጉሡን ስለ እኔ እንድትጠይቅ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሡ ፊት

እዚህ ስፍራ "የንጉሡ ፊት" የሚለው የሚያመለክተው ንጉሡን ራሱን ነው። "ንጉሡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉሡ ፊት ወደ ምድር ዝቅ ብሎ ሰገደ

አቤሴሎም ለንጉሡ ክብር እያሳየ ነው። "ንጉሡን ለማክበር ወደ ምድር ዝቅ ብሎ ሰገደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ አቤሴሎምን ሳመው

ይህ የሚያመለክተው ንጉሡ አቤሴሎምን ይቅር ማለቱንና መልሶ መቀበሉን ነው። የዚህ ሙሉ ትርጉሙ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እንዲሁም ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 15

2 Samuel 15:1

እንዲህም ሆነ

ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንት ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ ከሚሮጡ ሀምሳ ሰዎች ጋር

እነዚህ ሰዎች አቤሴሎምን ለማክበር ከሰረገላው ፊት ይሮጣሉ። "እርሱን ለማክበር በፊቱ ከሚሮጡ ሀምሳ ሰዎች ጋር" (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ አገልጋይ

አንድ ሰው ለአቤሴሎም ጥያቄ ምላሽ በሚሰጥበት ወቅት ለእርሱ ክብር ለመስጠት "የአንተ አገልጋይ" በማለት ራሱን ይጠራ ነበር።

2 Samuel 15:3

አቤሴሎምም ያንን ሰው እንዲህ ይለው ነበር

ሰውየው ለአቤሴሎም ጉዳዩን እንደሚናገር በውስጠ ታዋቂነት ተጠቅሷል። ይህ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "አቤሴሎም ሰውየውን ችግሩ ምን እንደሆነ ይጠይቀዋል፣ ከዚያም ሰውየው ፍትህ እንደሚፈልግ ለአቤሴሎም አብራርቶ ይናገራል። ከዚያም አቤሴለም ለሰውየው እንዲህ ይላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም እና ትክክል

እነዚህ ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው በአንድነት የዋሉት የእርሱ ጉዳይ መልካም እንደሆነ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ጉዳይህን ለመስማት

ጉዳይን "መስማት" ማለት ነገሩን መስማት እና በዚያ ላይ የውሳኔ ፍርድ መስጠት ማለት ነው። "ጉዳይህን ለመበየን/በጉዳይህ ላይ ፍርድ ለመስጠት" ወይም "የአንተን ጉዳይ ከላይ ሆኖ ለማየት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 15:5

እጁን ዘርግቶ ያቅፍና ይስም ነበር

ይህ ድርጊት የወዳጅነት ሰላምታ ነው። "በማቀፍና በመሳም እንደ ወዳጅ ሰላምታ ይሰጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርድ ለማግኘት

ይህ ማለት ለክርክራቸው ብይን ለማግኘት ወደ ንጉሡ ይመጣሉ። "ለክርክራቸው ብይን ለማግኘት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ አይነት አቤሴሎም የእስራኤልን ሰዎች ልብ ሰረቀ

የዚህ ዐረፍተ ነገር ትርጉም አቤሴሎም ሰዎች ከዳዊት ይልቅ ለእርሱ ታማኝ እንዲሆኑ ያሳምናቸው ነበር ማለት ነው። እዚህ ስፍራ ጸሐፊው እርሱ ልባቸውን ሰረቀ በማለት ሰዎች እንዴት ለአቤሴሎም ታማኝ እንደሆኑ ይናገራል። "አቤሴሎም በዚህ መንገድ የእስረኤል ሰዎች ለእርሱ ታማኝ እንዲሆኑ አሳመናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 15:7

እንዲህም ሆነ

ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንት ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

አቤሴሎም ከ ... አራት አመት በኋላ

ይህ የሚያመለክተው እርሱ ከኢየሩሳሌም ከተመለሰ ከአራት አመት በኋላ ነው። "አቤሴሎም ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሰ ከአራት አመት በኋላ፣ እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እናም በኬብሮን ለያህዌ የተሳልኩትን ለመስጠት

"በኬብሮን ለያህዌ የገባሁትን ስለት ለመፈጸም"

ለአገልጋይህ

እዚህ ስፍራ አቤሴሎም ራሱን በዚህ መንገድ የሚገልጸው ንጉሡን ለማክበር ነው።

2 Samuel 15:9

ስለዚህም አቤሴሎም ተነሳ

"ስለዚህም አቤሴሎም ሄደ"

በመላው እስራኤል ነገዶች

እዚህ ስፍራ የእስራኤል ነገዶች የሚኖሩበት ስፍራ የተጠቀሰው ራሳቸውን ነገዶቹን ተደርጎ ነው። "በእስራኤል ነገዶች ምድር በሙሉ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የመለከት ደምጽ

"መለከት ሲነፋ"

2 Samuel 15:11

የተጋበዙት

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ የጋበዛቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በየዋህነታቸው ሄዱ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"በየዋህነት ሄዱ"
ወደ አኪጦፌል ላከ
ይህ ማለት አኪጦፌልን እንዲያገኙትና ወደ እርሱ እንዲያመጡት መልዕክተኛ ላከ። "… የነበረውን አኪጦፌልን አግኝተው እንዲያመጡት መልዕክተኛ ላከ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አኪጦፌል
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ጊሎ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 15:13
የእስራኤል ሰዎች ልብ ከ… በኋላ ሄደ
እዚህ ስፍራ ሰዎች "በልባቸው" የተጠቀሱት ለአቤሴሎም ያላቸውን ታማኝነት ለማጉላት ነው። "የእስራኤል ሰዎች ለ…ታማኞች ናቸው" ወይም "የእስራኤል ሰዎች… እየተከተሉ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአቤሴሎም እናምልጥ… ፈጥኖ …እናም እርሱ…ያመጣብናል
እዚህ ስፍራ ዳዊት ስለ አቤሴሎም እና ከእርሱ ጋር ስላሉት ሰዎች በአንድነት ስለ "አቤሴሎም" እንደሚናገር አድርጎ ይናገራል፤ ምክንያቱ ሰዎቹ የአቤሴሎምን ስልጣን ስለተቀበሉ/ስለተከተሉት ነው። "ከአቤሴሎም እና ከሰዎቹ እናምልጥ… እርሱ እና ሰዎቹ በፍጥነት… እናም… ያመጡብናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ከተማይቱን በሰይፍ ስለት ያጠቃታል
"ከተማይቱ" የሚለው በከተማዋ የሚኖሩ ሰዎችን የሚያመለክት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የሰይፍ ስለት" የሚለው የእስራኤላውያንን ሰይፎች የሚያመለክት እና በጦርነት ሰዎቹን መግደላቸውን የሚያጎላ ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "የከተማችንን ሰዎች ያጠቃሉ ደግሞም በሰይፎቻቸው ይገድሏቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
ጥፋት ያወርዱብናል
ይህ ጥፋት እንዲደርስ ምክንያት መሆን ማለት ነው
2 Samuel 15:16
ቤቱን እንዲጠብቁ
እዚህ ስፍራ "መጠበቅ" የሚለው ቃል ጥንቃቄ ማድረግ ማለት ነው። "ቤቱን እንዲጠብቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በመጨረሻው ቤት
ይህ የሚያመለክተው ከተማይቱን ለቀው ሲወጡ የሚመጡበትን የመጨረሻ ቤት ነው። "ከተማይቱን ለቀው ሲወጡ የመጨረሻው ቤት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሊታውያን… ፈሊታውያን
የእነዚህን የህዝብ ወገኖች ስም በ2 ሳሙኤል 8፡18 ላይ እንደ ተረጎሙት በተመሳሳይ ይተርጉሙ።
ጌትያውያን
ይህን የህዝብ ወገን ስም በ2 ሳሙኤል 6፡10 ላይ እንደ ተረጎሙት በተመሳሳይ ይተርጉሙ።
ስድስት መቶ ወንዶች
"600 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 15:19
ኢታይ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ጌትያዊ
ይህን የህዝብ ወገን ስም በ2 ሳሙኤል 6፡10 ላይ እንደ ተረጎሙት በተመሳሳይ ይተርጉሙ።
ለምን ከእኛ ጋር ትመጣለህ?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚያመለክተው ንጉሡ እርሱ ከእርሱ ጋር መሄድ አለባቸው ብሎ እንደማያስብ ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ከእኛ ጋር መሄድ አያስፈልግህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ለምን አንተ ከእኛ ጋር እንድትንከራተት አደርጋለሁ?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ዳዊት ኢታይ እንዲመጣ አለመፈለጉን ያጎላል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ከእኛ ጋር እንድትዞር ላደርግ አልፈልግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የመጣኸው ገና ትናንትን ነው
እዚህ ስፍራ "ትናንት" የሚለው በቅርብ ጊዜ የሚለውን ለማጋነን ነው። የጌት ሰው ኢታይ በዚያ ብዙ አመት ኖሯል። "በዚህ ስፍራ የኖርከው ለአጭር ጊዜ ብቻ እንደመሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
ታማኝነት እና እውነተኝነት ከአንተ ጋር ይሁኑ
ይህ ዳዊት ለእርሱ የሰጠው በረከት/ምርቃት ነው። "ያህዌ ሁሌም ለአንተ ታማኝነቱን እና እውነቱን ያድርግልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 15:21
ህያው እግዚአብሔርን! በጌታዬ በንጉሡ ህይወት እምላለሁ
እዚህ ስፍራ ተናጋሪው ብርቱ ቃል ኪዳን ይገባል። ቃል ኪዳኑን የመጠበቁን እርግጠኝነት ከያህዌ እና ከንጉሡ ህያውነት ጋር ያነጻጽራልለ። "በያህዌ እና በንጉሡ ህይወት በጽኑ ቃል እገባለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አገልጋይህ
እዚህ ስፍራ ኢታይ ራሱን በዚህ መንገድ የሚገልጸው ንጉሡን ለማክበር ነው።
በሞትም ሆነ በህይወት
"አንተን እየደገፍኩ ብገደል እንኳን"
መላው አገር በጮኸት አለቀሰ
ብዙዎቹ የእስራኤል ሰዎች ንጉሡ ለቆ ሲወጣ በጮኸት አለቀሱ። እዚህ ይህ ማጠቃለያ የቀረበው መላው አገር አለቀሰ በሚል ነው። "በመንገድ የነበረው ህዝብ ሁሉ አለቀሰ" ወይም "ብዙ ህዝብ አለቀሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
ከፍ ባለ ድምጽ
እዚህ የሚያለቅሰው ህዝብ የተነገረው ሁሉም አንድ ከፍ ያለ ድምጽ እንደተጋሩ ተደርጎ ነው። "ጮኸው/ከፍ ባለ ድምጽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቄድሮን ሸለቆ
ይህ ኢየሩሳሌም አጠገብ የሚገኝ ቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 15:24
በያህዌ ዐይኖች ሞገስ አገኝቻለሁ
እዚህ "የያህዌ ዐይኖች" የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን ፈቃድና ሃሳብ ነው። በሰዎች ዘንድ "ሞገስ ካገኘህ" በአንተ ተደስተዋል ማለት ነው። "ያህዌ በእኔ ደስ ተሰኝቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
እርሱ በሚኖርበት
"የእርሱ መገኘት ባለበት።" የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚወክለው የያህዌን መገኘት ነው። ይህ የሚያመለክተው ታቦቱ የሚገኝበትን ስፍራ ነው። "የተቀመጠበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 15:27
አኪማስ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አብያታር
ይህን የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 8፡17 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
አንተ ነቢይ አይደለህምን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ሳዶቅን ለመገሰጽ ሲውል በዐረፍተ ነገር ሊተረጎምም ይችላል። "ሊሆን ያለውን ማወቅ ትችላለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አይ/እነሆ
ይህ ቃል አድማጩ ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት እንዲሰጥ የሚያደርግ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው።
ከአንተ ቃል እስኪመጣ ድረስ
ይህ ለንጉሡ መልዕክተኛ መላክን የሚያመለክት ነው። "ለእኔ መረጃ ለመስጠት ወደ እኔ መልዕክተኛ እስክትልክ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
መረጃ እንድትሰጠኝ
እዚህ ስፍራ ንጉሡ በኢየሩሳሌም እየሆነ ስላለው መረጃ እንደሚደርሰው ይጠቁማል። "በኢየሩሳሌም እየሆነ ያለውን እንድትነግረኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 15:30
ባዶ እግር
ጫማ ወይም ነጠላ ጫማ/ሰንደል ሳይደረግ
ራሱ ተከናንቦ
ይህ የሀዘን እና ሀፍረት ምልክት ነው። "ራሱን በሀዘን ተከናንቦ " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
አኪጦፌል
ይህን የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 15፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
ሴረኞች/አድመኞች
በአንድ ሌላ ሰው ላይ በተቃውሞ አብረው የሆኑ ሰዎች
እባክህ የአኪጦፌልን ምክር ከንቱ አድርግ
ዳዊት ያህዌን የአኪጦፌልን ምክር ሞኝነት እና ጥቅም የሌለው እንዲያደርግ ይለምናል። "እባክህ አኪጦፌል የሚመክረውን ምክር ሁሉ ሞኝነት እና እርባና ቢስ አድርገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 15:32
እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ለማስተዋወቅ ነው። (አዲስ ትዕይንት ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
በመንገዱ ጫፍ
እዚህ ስፍራ"ጫፍ" ሚለው ቃል የዋለው ዳዊት ከታች ወደ ላይ ስለወጣ እና ወደ ኮረብታው ጫፍ ስለሄደ ነው። "ከኮረብታው ጫፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ይመለክበት በነበረበት ስፍራ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች በአንድ ወቅት እግዚአብሔርን ያመልኩ በነበረበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ኩሲ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አርካዊ
ይህ የአንድ ወገን ህዝብ የሆኑ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ልብሱን ቀዶ እና ራሱ ላይ አፈር ነስንሶ
ይህ ሀፍረትን እና መጸጸትን የሚገልጽ ድርጊት ነው። እዚህ ስፍራ "አፈር" የሚለው "ትቢያ" ነው። "እጅግ ማዘኑን ለማሳየት ልብሱን ቀደደ፣ በራሱም ላይ ትቢያ ነሰነሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት እና ስኔክዲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
የአኪጦፌልን ምክር ከንቱ ታደርግልኛለህ
ዳዊት ለኩሲ የአኪጦፌልን ምክር ሁሉ ከንቱ እንዲያደርግ ሀሳብ ያቀርብለታል። "የአኪጦፌልን ምክር በማፍረስ/በመቃወም ልታገለግለኝ ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 15:35
ካህናቱ ሳዶቅ እና አብያታር ከአንተ ጋር አይደሉምን?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ኩሲ ብቻውን እንደማይሆን ሊነግረው ፈልጎ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ካህናቱ ሳዶቅ እና አብያታር አንተን ለመርዳት በዚያ ይገኛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የምትሰማውን ሁሉ
ይህ አጠቃላይ አስተያየት ነው። ይህ ማለት ማናቸውንም ጠቃሚ እና መረጃ ሊሆኑ የሚችሉ የሚሰማቸውን ነገሮች ማለት እንጂ እያንዳንዷን ቃል ማለት አይደለም። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
አኪማአስ...ዮናታን
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
በእጃቸው
"እጃቸው" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ወጣት ወንዶችን ሲሆን እነርሱም መልዕክተኛ ሆነው ያገለግላሉ ማለት ነው። "ልጆቻቸው ለእኔ እንዲነግሩኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክዲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 16
2 Samuel 16:1
ሲባ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሜምፊቦስቴ
ይህን የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 4፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
ሁለት መቶ የተቦካ...አንድ መቶ ጥፍጥፍ... አንድ መቶ ዘለላ
"200 የተጋገረ...100 ጥፍጥፍ... አንድ መቶ ዘለላ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የተጋገር እንጀራ
"እንጀራ"
የዘቢብ ዘላላ... የበለስ ጥፍጥፍ
እነዚህ ሀረጎች የሚያመለክቱት በአንድነት የተጨመቁ ዘቢብ እና በለስን ነው
ዘቢብ
የደረቀ ወይን
አቁማዳ ወይን
"አቁማዳ ሙሉ ወይን"
መድከም
አቅም ማጣት እና ድካም መሰማት
2 Samuel 16:3
የጌታህ የልጅ ልጅ
" የጌታህ የልጅ ልጅ፣ ሜምፊቦስቴ"
የልጅ ልጅ
የአንድ ሰው የወንድ ወይም የሴት ልጁ ልጅ
አይ/እነሆ
ይህ ቃል አድማጩ ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት እንዲሰጥ የሚያደርግ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው።
የእስራኤል ቤት
ይህ የስስራኤልን ህዝብ ያመለክታል። "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የአባቴን መንግሥት ለእኔ ይመልሳል
እንዲገዛ የሚፈቀድለት የሳኦል ትውልድ ስለመገኘቱ የተገለጸው መንግስቱ ለቤተሰባቸው እንደሚመለስ ተደርጎ ነው። "አያቴ ይገዛው የነበረውን መንግስት እንድገዛ ትፈቅድልኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሜምፊቦስቴ
ይህን የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 4፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
ለአንተ በትህትና/ዝቅ ብዬ እሰግዳለሁ
ሲባ እዚህ ስፍራ ይህን ሲናገር በንጉሡ ፊት ወደቆ አልሰገደም። ይህ ማለት በንጉሡ ፊት ቢሰግድ በሚያሳየው በዚያው አይነቱ ትህትና ንጉሡን ያገለግላል ማለት ነው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"በታላቅ ትህትና አገለግልሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በዐይኖች ፊት ሞገስ ላግኝ
"ሞገስ ማግኘት" የሚለው ሀረግ በአንድ ሰው ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት የሚል ትርጉም አለው፡፡ እንደዚሁም "ዐይኖች" መታየት ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን፣ መታየት ፍትህን ወይም ሚዛንን ይወክላል፡፡ "አንተ በእኔ ደስ እንድትሰኝ እፈልጋለሁ" ወይም "አንተ በእኔ ደስ እንዲልህ እመኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 16:5
ብራቂም
የዚህችን ከተማ ስም በ 2 ሳሙኤል 3፡16 ላይ በተተረጎመው መሰረት ይተርጉሙ
ሳሚ...ጌራ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው፡፡
ቢኖሩም እንኳን
"ምንም እንኳን በዚያ ቢኖሩም"
ጠባቂች/የክብር ዘቦች
እነዚህ ክብር ያለውን ሰው የሚጠብቁ ሰዎች ናቸው
2 Samuel 16:7
ክፉ/ተንኮለኛ
ክፉ፣ ወንጀለኛ ወይም ህግ የማያከብር ሰው
የደም ሰው
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው የሚያመለክተው እርሱ ተጠያቂ ለሆነባቸው በጦርነት ለተገደሉ ሰዎች ሁሉ ነው፡፡ "ነብሰ ገዳይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ የስራህን እየከፈለህ ነው
ያህዌ እነርሱን በመቅጣት እየከፈላቸው ነው፡፡ ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል፡፡ "ያህዌ ቀጥቶሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በሳኦል ቤት ውስጥ ላፈሰስከው ደም
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው የሚያመለክተው ከሳኦል ቤት የተገደሉ ሰዎችን ነው፡፡ ንጉሡ ለእነርሱ መሞት ተጠያቂ ነው፡፡ "ብዙዎቹን የሳኦል ቤተሰቦች በመግደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በማን ስፍራ/የማንን ስፍራ ይዘህ ስትገዛ ኖርክ
ዳዊት ንጉሥ ሆኖ የገዛው ሳኦል አስቀድሞ ይገዛቸው የነበሩትን እነዚያኑ ህዝቦች ነው፡፡ "ንጉሥ ሆነህ የገዛኸው በማን ስፍራ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በአቤሴሎም እጅ ውስጥ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው በቁጥጥር ስር ማድረግን ነው፡፡ "በአቤሴሎም ቁጥጥር ስር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 16:9
አቢሳ
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 2፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ጽሩያ
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 2፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ለምን ይህ የሞተ ውሻ ጌታዬን ንጉሡን ይራገማል?
አቢሳ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው በሰውየው ላይ ቁጣውን ለመግለጽ ነው፡፡ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ይህ የሞተ ውሻ ንጉሡን በዚህ መንገድ መናገር የለበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ምናልባት እርሱ እኔን የሚረግምበት ምክንያት
"እኔን የሚረግምበት ምክንያት"
እርሱን ማን 'ለምን ንጉሡን ትራገማለህ' ሊለው ይችላል?
ይህ እንደ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተነገረው መልሱ "ማንም" የሚለው መሆኑን ለማጉላት ነው፡፡ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ ማንም ቢሆን 'ለምን ንጉሡን ትራገማለህ?' ብሎ ሊጠይቀው አይችልም፡፡ በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 16:11
ከአብራኬ የተወለደ የእኔው ልጅ
ዳዊት ልጁን በዚህ መንገድ የገለጸው በልጁ እና በአባቱ መሃል ያለውን ጥብቅ ትስስር ለማጉላት ነው፡፡ "የራሴ ልጅ" ወይም "ውድ ልጄ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ህይወቴን መውሰድ/ለመንጠቅ ይፈልጋል
ይህ አንድን ሰው መግደልን ሻል ባለ ቃል መግለጽ ነው፡፡ "ሊገድለኝ ይፈልጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
ይልቁንስ ይህ ብንያማዊ ምን ያህል ይበልጥ የእኔን ጥፋት ይፈልጋል?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ሰውየው ሊገድለው በመፈለጉ የማይደነቅ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ "በእርግጥ ይህ ብንያማዊ የእኔን ጥፋት ይፈልጋል!" ወይም "ይህ ብንያማዊ የእኔን ጥፋት መፈለጉ አያስደንቀኝም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ጥፋቴን ይፈልጋል
እዚህ ስፍራ ዳዊት ሰውየው እርሱን ለመግደል ያለውን ፍላጎት የሚገልጸው ሰውየው ሊያጠፋው የሚፈልገው ነገር ዳዊትን እንደሆነ አድርጎ ነው፡፡ "እኔ እንድገደል ይፈልጋል" ወይም "ሊገድለኝ ይፈልጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ተዉት ግድ የለም ይራገም
እዚህ ስፍራ "ተዉት ግድ የለም" የሚለው ሀረግ እያደረገ የሚገኘውን አለማስቆም ማለት ነው፡፡ "እኔን መራገሙን አታስቁሙት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይመለከት ይሆናል
እዚህ ስፍራ "መመልከት" የሚለው "ስፍራ ሰጥቶት/ተመልክቶ" ማለት ነው፡፡ "ዋጋ ይሰጠው ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በላዬ የተለቀቀው/የወደቀ መከራ
እዚህ ስፍራ ዳዊት መከራን የሚገልጸው ብንያማዊያን በላዩ ፈትተው እንደለቀቁት አደገኛ እንስሳ አድርጎ ነው፡፡ (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 16:13
ሳሚ ከእርሱ አጠገብ በተራራው አናት ጥግ ጥጉን ይሄድ ነበር
ምንም እንኳን ከታራው አናት ላይ ቢሆነም፣ ሳሚ ከዳዊት እና ከወታደሮቹ ትይዩ ይሄድ ነበር
2 Samuel 16:15
አኪጦፌል
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15፡12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ኩሲ
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15፡32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
እንዲህም ሆነ
"እንዲህ ሆነ፡፡" ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ለማስተዋወቅ ነው፡፡ (አዲስ ትዕይንት ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
አርካዊ
ይህ የህዝብ ወገን በ 2 ሳሙኤል 15፡32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 16:17
ታማኝነት
ብርቱ የድጋፍ እና ፍቅር ስሜት
ለወዳጅህ ያለህ ታማኝነት ይህ ነውን? ለምን ከእርሱ ጋር አልሄድክም?
እነዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የተጠየቁት ኩሲን ለመተቸት ነው፡፡ እነዚህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ "ለዳዊት ታማኝ ወዳጅ ነበርክ፡ ከእርሱ ጋር መሄድ ነበረብህ፡፡" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን

ይመልከቱ)
የህዌ እርሱን
ኩሲ እየገለጸ ያለው አቤሴሎምን ነው
እርሱን... ያ ሰው ነው... ከእርሱ ጋር
እዚህ ስፍራ ኩሲ ትኩረቱን ከእርሱ ላይ አንስቶ በያህዌ እና እርሱ በመረጠው ህዝብ ላይ ለማድረግ አቤሴሎምን በሶስተኛ መደብ እየገለጸ/እያመለከተ ነው። ይህ በሁለተኛ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ነህ... ያ ሰው አንተ ነህ... ከአንተ ጋር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 16:19
ማገልገል ያለብኝ ማንን ነው? ልጁን በስሩ ሆኜ ማገልገል የለብኝምን?
ኩሲ እነዚህን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የጠየቀው አቤሴሎምን ለማገልገል መፈለጉን ለማጉላት ነው። በዐረፍተ ነገር ሊጻፉ ይችላሉ። "ማገልገል የሚገባኝ የዳዊትን ልጅ ብቻ ነው፣ ስለዚህም እርሱን በስሩ ሆኜ አገለግላለሁ።" ወይም "አንተ የዳዊት ልጅ በመሆንህ አንተን ማገልገል ይገባኛል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 16:20
አኪጦፌል
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15:12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ቤተ መንግሥቱን እንዲጠብቁ
"ለመጠበቅ" የሚለው ሀረግ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ/እንዲንከባከቡ ማለት ነው። "ቤተ ምንግሥቱን መጠበቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ለአባትህ ክፉ ሽታ በመሆን
አኪጦፌል አቤሴሎም ለአባቱ ክፉ ሽታ የሆነ ያህል እንዲያስቆጣው ይመክረዋል። "አባትህን አስቆጣው/ስሜቱን ጉዳው" ወይም "አባታህን በታለቅ ሁኔታ ንቀፍ/ስደብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከአንተ ጋር ያሉ ሁሉ ክንድ ይጠነክራል/ይበረታል
እዚህ ስፍራ አቤሴሎምን የተከተሉ ሰዎች የተገለጹት በእጆቻቸው ነው። ወሬው ሰዎቹ ለአቤሴሎም ያላቸውን ታማኝነት ሲያጠነክር ህዝቡንም ያበረታታል። ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "የዚህ ወሬ አንተን የሚከተሉትን ሁሉ ታማኝነት ያጠነክራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 16:22
ዘረጉ
"አበጁ"
እስራኤል ሁሉ እየተመለከተ
ይህ ማለት ህዝቡ ደንኳኑን እና አቤሴሎም ከሴቶቹ ጋር ወደ ደንኳኑ ውስጥ ሲገባ እና ሲወጣ ይመለከት ነበር ማለት ነው። "መላው እስራኤል" የሚለው ሀረግ በቤተ መንግሥቱ አቅራቢያ የሚገኙ ሰዎች ብቻ ይህን ሊመለከቱ እንደሚችሉ የሚገልጽ አጠቃላይ አስተያየት ነው። "ወደ ድንኳን ሲገባ እስራኤላውያን ሊመለከቱ የሚችሉበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚለውን ይመልከቱ)
የአኪጦፌል ምክር... አንድ ሰው ...እንደ መስማት ማለት ነበር
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ሰዎች ምን ያህል የአኪጦፌልን ምክር በቀጥታ ከእግዚአብሔር መስማትን ያህል እንሚያምኑበት ያነጻጽራል። "በነዚያ ወቅት ሰዎች የአኪጦፌልን ምክር ከ... እንደ ተጠየቀ/እንደ መጣ አድርገው ያምኑበት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በቀጥታ እንደ ሰማ
እዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር አፍ የሚለው የሚወክለው ራሱን እግዚአብሔርን እና የእርሱን ቃል ነው። "እግዚአብሔር በራሱ አፍ የተናገረውን ያህል" ወይም "አንድ ሰው በራሱ በእግዘአብሔር ሲነገር የሰማውን ያህል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ተጠቃሽ ተውላጠ ስም የሚሉትን ይመልከቱ)
የአኪጦፌል ምክር በሙሉ በዳዊት እና በአቤሴሎም በሁለቱም... ይታይ/ይቆጠር ነበረው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ዳዊት እና አቤሴሎም ሁለቱም የአኤጦፌልን ምክር... ይመለከቱ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ይታይ/ይቆጠር ነበር
"ይታሰብ ነበር"

---

Chapter 17
2 Samuel 17:1
አኪጦፌል
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15:12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አስራ ሁለት ሺህ ወንዶች
"12፣000 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
መነሳት እና
"መጀምር"
መምጣት
"መድረስ"
የዛለ እና ደካማ
እነዚህ ቃላት በመሰረቱ አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው በአንድ ላይ የቀረቡት ዳዊት ምን ያህል ደካማ እንደነበር ለማጉላት ነው። "ደካማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
በፍርሃት አስጨንቀዋለሁ
እዚህ ስፍራ "ፍርሀት" የሚለው ቃል "መፍራት" ከሚለው ቅጽል ጋር ሊገለጽ ይችላል። "እርሱን አስጨንቀዋለሁ፣ ደግሞም እንዲፈራ አድረገዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡን ብቻ እመታለሁ
ንጉሡን ለመግደል ማቀዱ ተመላክቷል። ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡን ብቻ እገድለዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ህዝቡን ሁሉ እመልሳለሁ
ይህ የሚያመለክተው ከዳዊት ጋር የነበሩ ሰዎችን ሁሉ ነው። "ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎችን ሁሉ እመልሳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ባሏ እንደምትመጣ ሙሽራ
እዚህ ስፍራ አኪጦፌል የህዝቡን ደስታ የሚገልጸው ከሙሽሪት ደስታ ጋር በማነጻጸር ነው። "እናም ሙሽሪት ወደ ባሏ ስትመጣ ደሰ እንደሚላት በደስታ ይመጣሉ" ወይም "እናም በደስታ ይመጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሰላም ይሆናሉ
ይህ ማለት ሰላም ማግኘት ወይም በሰላም መኖር ማለት ነው። "በሰላም ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በስርህ
ይህ የሚያመለክተው ከንጉሡ ስልጣን በታች መሆንን ነው።"ከስልጣንህ በታች" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 17:5
አርካዊው ኩሲ
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15:32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አኪጦፌል
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15:12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 17:8
እነርሱ ልጇ እንደተነጠቀባት ድብ ናቸው
እዚህ ስፍራ የወታደሮቹ ቁጣ የተነጻጸረው ግልገሎቿ ከእርሷ ከተወሰዱባት እንዲት እናት ድብ ጋር ነው። "ግልገሎቿ እንደ ተወሰዱባት እናት ድብ ተቆጥተዋል።" ወይም "እነርሱ በጣም ተቆጥተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ድብ

በአራት እግሩ የሚራመድ ስል መንጋጋ እና ጥርሶች ያለው ግዙፍ ፀጉራም እንስሳ
የጦር ሰው ነው
ይህ ማለት በብዙ ጦርሜዳ የተዋጋ እና የጦርነት መንገዶችን በሚገባ የሚያውቅ። "በብዙ ጦርሜዳ የተዋጋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እይ/እነሆ
ይህ ቃል አድማጩ ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት እንዲሰጥ የሚያደርግ ነው። "ስማ/ አድምጥ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው።
ጉድጓድ
የተቆፈረ ጥልቅ መሬት
ወይም በሌላ አንድ ስፍራ
ይህ እርሱ ሊደበቅበት የሚችልበት ሌላ ስፍራ ነው። "ወይም በሌላ ስፍራ ተደብቋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአንተ ሰዎች ጥቂቶች በተገደሉ ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የእርሱ ወታደሮች ከአንተ ሰዎች ጥቂቶችን በገደሉ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
አቤሴሎምን በተከተሉ ወታደሮች መሃል እርድ/እልቂት ተፈጸመ
"ማረድ/ማለቀ" የሚለው ስም ብዙ ሰዎች በጭካኔ የተገደሉበት ትዕይንት ማለት ነው። ይህ እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። "አቤሴሎምን ከተከተሉት ወታደሮች ብዙዎቹ ታረደዋል" ወይም "የጠላት ወታደሮች አቤሴሎምን ከተከተሉት ወታደሮች ብዙዎችን ገድለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ልቦቻቸው እንደ አንበሳ ልብ የሆነ
እዚህ ስፍራ ወታደሮች የተገለጹት የእነርሱ "ልቦች" በሚለው ነው። እንደዚሁም፣ ጠንካራ ጀግንነታቸው ከአንበሳ ብርታት ጋር ነው። "እንደ አንበሶች ጀግና የሆኑ" ወይም "በጣም ጀግና የሆኑ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 17:11
መላው እስራኤል በአንድነት ወደ አንተ ይሰበሰብ ዘንድ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። እንደዚሁም፣ እዚህ ስፍራ "መላው እስራኤል" የሚለው የእስራኤል ወታደሮችን ብቻ ይወክላል። "እናንተ የእስራኤል ወታደሮች በአንድነት መሰብሰብ ይኖርባችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከዳን እስከ ቤርሳቤህ
ይህ ሀረግ ከሰሜናዊ የእስራኤል ድንበር አንስቶ እስከ ደቡብ ድንበር ድረስ ማለት ነው። "ከጠቅላላው የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)
በባህር ዳርቻ እንደሚገኝ አሸዋ የበዛ
ይህ የእስራኤል ወታደር ብዛት በባህር ዳርቻ እንደሚገኝ የአሸዋ ቅንጣት ብዛቱ ተጋኖ በንጽጽር የተገለጸበት ነው። "ሊቆጠር እስከማይቻል ድረስ እጅግ ብዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና ጥቅል አስተያየት እንደዚሁም ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
በየግል ወደ ጦርነት ትሄዳላችሁ
"በየግል" የሚለው ሀረግ ሌላውን ሰው መላክ ሳይሆን ይልቁንም እራስህ መሄድ ማለት ነው። "እንግዲያው አንተው ራስህ ወደ ጦርነት ምራቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ላይ ውደቅበት
ይህ ማለት ይሁን ብሎ እርሱ ወዳለበት በመሄድ ጥቃት ማድረስ ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጤዛ በምድር ላይ እንደሚወርድ እኛ እንወርድበታለን
የአቤሴሎም ሰራዊት የተገለጸው ጤዛ በማለዳ ምድርን እንደሚሸፍን በዳዊት ሰራዊት ላይ እንደሚወርድበት ተደርጎ ነው። "እኛ የዳዊትን ሰራዊት እናጠቃለን ደግሞም ሙሉ ለሙሉ እናሸንፋለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጤዛ
በምሽት ወደ ምድር ሊወድቅ የሚችል ፣ ምድርን የሚሸፍን እና በማለዳ እርጥበቱ የሚታይ ጭጋግ ወይም እርጥበት ያለው ቀዝቃዛ ውሃ
ከእርሱ ወንዶች አንድ እንኳ... በህይወት አናስተርፍም/አናስቀርም
ይህ አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ያገለገለው ትኩረት ለመስጠት ነው፤ ይህ በአዎንታ ሊጻፍ ይችላል። "የእርሱን ወንዶች በሙሉ እንገድላለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ እራሱ
እነዚህ ሁለቱም ቃላት ዳዊትን ያመለክታሉ። "ዳዊት ራሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተጠቃሽ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 17:13
ከዚያም መላው እስራኤል
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ወታደሮች እንጂ መላውን እስራኤላዊ አይደለም። "ከዚያም መላው ወታደራችን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደዚያች ከተማ ገመድ እናመጣለን ደግሞም ወደ ባህር ውስጥ እናስጥማታለን
ይህ ማለት ወታደሮች የከተማይቱ ቅጥር ያፈርሳሉ፤ ፍርስራሹንም ጎትተው ወደ ባህር ይጥላሉ። "ከተማይቱን እንደመስሳለን ደግሞም ድንጋዩቹን በገመድ ስበን ወደ ባህር እንጨምራለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ትናንሽ ድንጋይ እንኳን በዚያ እስከማይገኝ ድረስ
ይህ ከተማይቱን ምን ያህል ሙሉ ለሙሉ እንደሚያጠፏት ለመግለጽ የቀረበ ግነት ነው። ከከተማይቱ እያንዳንዷቱን ድንጋይ ጠርገው ያስወግዱም። "ከተማይቱ ሙሉ ለሙሉ እስክትጠፋ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና ጥቅል አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
አርካዊው ኩሲ
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15:32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። አርካዊ የህዝብ/ሰዎች የቡድን ስም ነው።
አኪጦፌል
ይህ የወንድ ስም በ 2 ሳሙኤል 15:12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
የአኪጦፌልን መልካም ምክር መቃወም/መጣል
"አለመቀበል/መጣል" የሚለቀው ቃል "ተቃወመ/ጣለ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "የእስራኤል ወንዶች የአኪጦፌልን መልካም ምክር ላለመቀበል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመለከቱ)
በአቤሴሎም ላይ ጥፋት ለማምጣት
በአንድ ነገር ላይ አንደን ነገር ለ "ማምጣት" ማለት በእነርሱ ላይ እንዲሆን ማለት ነው። "ጥፋት በአቤሴሎም ላይ እንዲመጣ ምክንያት መሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 17:15
ሳዶቅ... አብያታር
እነዚህን የወንድ ስሞች በ 2 ሳሙኤል 15:24-25 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
በዚህና ይህን በመሰለ መንገድ
ይህ ሀረግ፣ ማለትም "እንደዚህ አይነት" የሚለው የሚያመለክተው አኬጦፌል ቀደም ሲል በ2 ሳሙኤል 17:1-3 ላይ አቤሴሎምን የመከረውን ምክር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የመሻገሪያ ዳርቻ
መሻገሪያ ሰዎች በእግራቸው ሊያቋርጡት የሚችሉት የወንዙ ጥልቀት የሌለው የውሃ ክፍል ነው። ዳርቻ ከዮርዳኖስ ወንዝ ሁለትም ጎኖች የሚገኝ መሬት ነው
በማናቸውም ብልሃት/መንገድ
ይህ ማለት አንድ ነገር ስለ ማድረግ እርግጠኛ መሆን ነው። "ለማድረግ እርግጠኛ መሆን" ወይም "ለማድረግህ እርግጠኛ ሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡ ይዋጣል
እዚህ ንጉሡ እና ህዝቡ መገደላቸው የተገለጸው በጠላቶቻቸው "እንደሚዋጡ" ተደርጎ ነው። "ንጉሡ ይገደላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 17:17
ዮናታን...አኪማአስ
እነዚህን የወንድ ስሞች በ 2 ሳሙኤል 15:27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
መልዕክቱ ሲደርስ

እዚህ ስፍራ "መልዕክት" የሚለው የተገለጸው ወደ እነርሱ እንደሚመጣ ነገር ነው፤ እውነቱ ግን መልዕክቱን የምታደርሰው ወደዚያ የምትመጣው ሴት ናት። "መልዕክቱን ስታደርስላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በዚህ ጊዜ
"አንድ ጊዜ"
ስለዚህም ዮናታን እና አኪማአስ ሄዱ
ወጣቱ ሰው ለአቤሴሎም ስለ እነርሱ በዚያ መኖር መናገሩን እንዳወቁ ተጠቅሷል። ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ዮናታን እና አኪማአስ ወጣቱ ያደረገውን ነገር ስለ ደረሱበት/ስላወቁ ተነስተው ሄዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የሮጌል ምንጭ...ብራቂም
እነዚህ እየሩሳሌም አጠገብ የሚገኙ የቦታ ስሞች ናቸው። ብራቂም ትንሽ ከተማ ናት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ወረዱ
"ወደ ታች ገብተው/ወርደው ተደበቁ"
2 Samuel 17:19
የቤቱ ሴት
"የሰውየው ሚስት
አኪማአስ...ዮናታን
እነዚህን የወንድ ስሞች በ 2 ሳሙኤል 15:27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 17:21
እንዲህም ሆነ
"እንዲህ ሆነ።"ይህ ሀረግ በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ያመለክታል። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
በፍጥነት ውሃውን ተሻገሩ
እዚህ ስፍራ "ውሃው" የሚለው የሚያመለክተው የዮርዳኖስን ወንዝ ነው። "ባህሩን በፍጥነት ተሻገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ይህንን እና ያንን ምክር ሰጠ
"ይህንን እና ያንን" የሚለው ፈሊጥ በአንባቢው ቀደም ሲል በሚታወቅ መረጃ ስፍራ የዋለ ነው። እዚህ ቦታ ይህ የሚያመለክተው አኪጦፌል አቤሴሎምን በ 2 ሳሙኤል 17:1-3 የመከረውን ነው። ይህ መረጃ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "አሁን አንተን ለማጥቃት አቤሴሎም እርሱን ከሰራዊት ጋር እንዲልክ መክሮታል" (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
እስከ ጠዋት የዮርዳኖስን ወንዝ ያልተሻገረ ማንም አልነበረም
ይህ አሉታዊ ዐረፍተ ነገር የዋለው ሁሉም ወንዙን ማቋረጣቸውን ለማጉላት ነው። በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በማለዳ እያንዳንዳቸው ዮርዳኖስን አቋረጡ" (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 17:23
አኪጦፌል ተመለከተ
"አኪጦፌል አወቀ" ወይም "አኪጦፌል ተረዳ/ተገነዘበ"
የእርሱን ምክር አልተከተሉም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አቤሴሎም የእርሱን ምክር አልተከተለም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
አህያውን ጫነ
በላዩ ላይ ይቀመጥበት ዘንድ በአህያው ጀርባ ንጣፍ ወይም ቁረበት አደረገ።
ነገሮቹን በስርአት አደራጀ/ተሰነዳዳ
ለቤተሰቦቹ ከሞቱ በኋላ ምን ሊያደርጉ እንደሚገባ በመናገር ለህልፈቱ ተሰናዳ። "ለ ህልፈቱ/ሞቱ ተዘጋጀ/ተሰነዳዳ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 17:24
መሃናይም...ገለዓድ
የእነዚህ ቦታዎችን ስም በ2 ሳሙኤል 2:8-9 ላይ በተተረጎመው አይነት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አሜሳይ... ኢዮአብ... ዬቴር...ናዖስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ኢዮአብ እና ጽሩያ (የኢዮአብ እናት) በ 2 ሳሙኤል 2፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
እስማኤላዊ
የዚህ ቃል ትርጉም ሰውየው የእስማኤል ዘር ነው ማለት ነው። አንዳንድ ትርጉሞች እዚህ ስፍራ "እስራኤላዊ" ይላሉ። የግርጌ ማስታወሻ ይምለከቱ። በአካባቢያችሁ መጽሐፍ ቅዱስ ከተተረጎመበት በብዙዎቹ ቋንቋዎች ውስጥ የሚገኘውን ቃል መጠቀም ይችላሉ።
አቢግያ...ጽሩያ
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 17:27
እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ በታሪኩ ፍሰት ቀጣዩን ትዕይንት ያመለክታል። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
መሃናይም...ረባት... ሎዶባር...ሮግሊም
እነዚህ የከተሞች ወይም የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሾቢ...ናዖስ...ማኪር...ዓሚኤል...ቤርዜሊ
እነዚህ የሰዎች ቡድኖች/ወገን ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አሞናውያን... ገለዓዳውያን
እነዚህ የሰዎች ቡድኖች/ወገን ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
መተኛ ምንጣፎች እና ብርድ ልብሶች
ምንጣፍ ለስላሳ የሆነ ለመኝታ የሚነጠፍ ነገር ነው፣ ብርድ ልብስ ደግሞ ለሙቀት የሚለበስ ልብስ ነው
ዱቄት
እንጀራ ወይም ዳቦ ለማዘጋጀት ወደ ደቃቅነት/ልምነት የተፈጨ የእህል
የተጠበሰ
በእሳት የተዘጋጀ
ባቄላ
በስሎ የሚበላ ጥራጥሬ
ምስር
በስሎ የሚበላ የጥራጥሬ አይነት
እርጎ
የረጋ ወተት
ጥማት
ውሃ ወይም የሚጠጣ ነገር መፈለግ

---

Chapter 18
2 Samuel 18:1
ዳዊት ከእርሱ ጋር የነበሩትን ወታደሮች ቀጠረ፣ ደግሞም ሾማቸው።
ዳዊት ራሱ ህዝቡን ሁሉ አልቆጠረም፣ ህዝቡን የቆጠሩት ሌሎች ሰዎች ናቸው። ዳዊት ከእርሱ ጋር የነበሩትን የሚቆጠሩትን እና የሚሾማቸውን ወታደሮች አስተዳደረ/ለየ" ወይም "ዳዊት ከእርሱ ጋር የነበሩትን እና የሚሾማቸውን ወታደሮች አደራጀ። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሻለቆች እና የመቶ አለቆች
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቁጥሮች መሪዎቹ የሚመሯቸውን ወታደሮች ትክክለኛ ቁጥር ይወክላሉ። "የ1,000 ወታደሮች እና የ100 ወታደሮች መሪዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው ወይም 2) "ሺህ" ወይም "መቶ" በሚል የተተረጎሙት ቃላት ቁርጥ ያለ ቁጥርን አይመለክቱም፣ ነገር ግን ብዙ ወይም ትንሽ ቁጥር ያለውን የወታደር ክፍል ለመሰየም የዋለ ነው። "የትልቅ/ብዙ ወታደራዊ ክፍል አዛዥ እና አነስተኛ ቁጥር ያለው የወታደር ክፍል አዛዥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
አለቃ/አዛዥ
አለቃ በተወሰኑ የወታደር ስብስቦች/ቡድን ላይ ስልጣን ያለው ሰው
አንድ ሶስተኛ... ሌላ ሲሶ/ሶስተኛ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሰራዊቱ አንድ ሶስተኛ… የሰራዊት ሌላ ሲሶ/ሶስተኛ። "ሲሶ/አንድ ሶስተኛ" እኩል የሆኑ ሶስት ክፍሎች አንድ ክፍል/አንድ እጅ። (ክፍልፋይ የሚለውን ይመልከቱ)
አቢሳ… ጽሩያ
እነዚህ የወንድ ስሞች በ2 ሳሙኤል 2:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ኢታይ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 15:19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ጌታዊ
ይህ ከፍልስጤም ከተማ ከጌት የሆነን ሰው ያመለክታል።(ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔም ራሴ በእርግጥ ከእናንተ ጋር እወጣለሁ
ይህ ማለት ከእነርሱ ጋር ለጦርነት አብሯቸው ይመጣል ማለት ነው። ይህ ይበልጥ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "እኔ ራሴ ከእናንተ ጋር አብሬ ለጦርነት እወጣለሁ" ወይም "እኔ በግል ወደ ጦርነት አብሬያችሁ እሄዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 18:3
ከእኛ ግማሹ
"ግማሽ" የሚለው ቃል እኩል ከሆኑ ሁለት ክፍሎች አንዱን ያመለክታል። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ አንተ አስር ሺህ ከምንሆነው ይልቅ ይበልጥ አስፈላጊ ነህ
ይህ ማለት የጠላት ሰራዊት ንጉሥ ዳዊትን መግደል 10,000 ወንዶችን ከመግደል ይልቅ ይበልጥ ጠቃሚ አድርጎ ይቆጥራል ማለት ነው። እዚህ ስፍራ 10,000 የሚለው ቁጥር የዋለው በጣም ብዙ ቁጥር ያለው ሰው የሚለውን ለማጉላት ነው። "ከእኛ 10,000 ሰው ከመግደል ይልቅ አንተን ይገድላሉ" ወይም "ለእነርሱ ከእኛ ብዙ ሰው ከመግደል ይልቅ አንተን መግደል ይበልጥ ይጠቅማቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ኩሸት እንደዚሁም ጥቅል አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
አስር ሺህ
"10,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ከከተማ ሆንህ እኛን ለመርዳት ዝግጁ ሁን
ዳዊት ከከተማ ሆኖ በምክር እና ሰዎችን በመላክ ሊረዳቸው ይችላል። ይህ ይበልጥ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "አንተ እዚህ በከተማ ቆይተህ ለእኛ እርዳታ ላክልን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 18:5
አቢሳ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 2:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ኢታይ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 15:19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ እኔ ስትሉ ከወጣቱ ሰው ከአቤሴሎም ጋር የምታደርጉትን በእርጋታ/ርህራሄ አድርጉ
"ስለ እኔ ስትሉ፣ ወጣቱን አቤሴሎምን አትጉዱት/ራሩለት።" "በእርጋታ አድርጉ/ራሩለት" የሚለው ሀረግ ለአንድ ሰው መልካም መሆንና ያንን ሰው አለመጉዳት ነው።
ስለ እኔ
"የእኔ ደህንነት" ወይም "የእኔ ጉዳይ"
2 Samuel 18:6
በእስራኤል ላይ ተነስቶ ወደ ገጠር/ ሜዳ መውጣት
ይህ ማለት ወጥተው በጦርነት ገጠሟቸው ማለት ነው። "ወደ ሜዳ/ገጠር ወጥተው ከእስራኤል ጋር ተዋጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በእስራኤል ላይ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው የሚያመለክተው ወታደሮቻቸውን እንጂ መላውን እስራኤላዊ አይደለም። "በእስራኤላውያን ወታደሮች ላይ"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በዚያ ከዳዊት ወታደሮች አስቀድሞ የእስራኤል ሰራዊት ተሸነፈ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በዚያ የዳዊት ሰራዊት የእስራኤልን ሰራዊት አሸነፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ታላቅ እልቂት/መተራረድ
ብዙ ሰዎች በጭካኔ የሚገደሉበት ትዕይንት ሃያ ሺህ ወንዶች "20,000 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በሰይፍ ከሞቱት ይልቅ በጫካው የተፈጁት/የተበሉት ወንዶች በለጡ
እዚህ ስፍራ "ጫካ/ዱር" የተገለጸው ህይወት እንዳለውና እርምጃ መውሰድ እንደሚችል ተደርጎ ነው። "ሰይፍ" የሚያመለክተው በሰይፍ የሚዋጉትን የዳዊት ወታደሮች ነው። "የዳዊት ወታደሮች በሰይፍ ከገደሏቸው ይልቅ በጫካ ውስጥ አደገኛ ነገሮች የገደሏቸው ሰዎች በዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 18:9
አቤሴሎም ከዳዊት ጥቂት ወታደሮች ጋር በድንገት ተገናኘ
ይህ በጦርነቱ ወቅት ያጋጠመ ተዕይነት ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "በጦርነቱ ወቅት አቤሴሎም ከጥቂት የዳዊት ወታደሮች ጋር ተገጣጠመ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ጭንቅላቱ በግንድ ቅርንጫፎች መሃል ተይዞ ነበር
አቤሴሎም በዛፍ ቅርንጫፎች ሊያዝ የሚችል ረጅም ፀጉር ነበረው። "ፀጉሩ በዛፍ ቅርንጫፎች ተይዞ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
መወዛወዝ
መሰቀል ወይም በቀስታ መወዛወዝ
እነሆ/ተመልከት
እዚህ ስፍራ ይህ ቃል ያገለገለው ቀጥሎ ለሚነገረው የአንባቢውን ትኩረት ለመሳብ ነው። "ስማ/አድምጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ለምን መትተህ ወደ ምድር አታወርደውም ነበር?
የዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ትርጉም ሊገድለው ይገባ ነበር ማለት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "መትቶ ማውረድ" የሚለው ሀረግ መግደል ማለት ነው። "መትተህ ወደ ምድር ልታወርደው ይገባ ነበር!" ወይም "ወዲያውኑ ልትገድለው ይገባ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ))
አስር የብር ሰቅል
ይህ በዘመናዊ መለኪያ ሊጻፍ ይችላል። "አስር የብር ሳንቲም" ወይም "110 ግራም ብር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የገንዘብ መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀበቶ
ይህ ለየት ያለ ቀበቶ ሲሆን ሰውየው ታላቅ ወታደር እና ሊከበር የሚገባው መሆኑን ለሰዎች የሚያሳይ ነው።
2 Samuel 18:12
አንድ ሺህ የብር ሰቅል
"1,000 የብር ሰቅል።" ይህ በዘመናዊ መለኪያ ሊጻፍ ይችላል። "1,000 የብር ሳንቲም" ወይም "11 ኪሎ ግራም ብር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የገንዘብ መለኪያ እና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
እጄን በንጉሡ ልጅ ላይ አላሳርፍም ነበር
"እጄን አላሳርፍም" የሚለው ቃል አልመታም ማለት ነው። "የንጉሡን ልጅ አልመታም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ማንም ሊነካው አይገባም
እዚህ ስፍራ "መንካት" የሚለው የሚያመለክተው "መጉዳትን" ነው። "ማንም ሊጎዳ አይገባም" ወይም "አትጉዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሀሰተኝነት
"ሀሰተኝነት" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። እንደዚሁም፣ ይህ የንጉሡን ትዕዛዝ አለመጠበቅን ያመለክታል። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ስህተት የሆነ ነገር መፈጸም" ወይም "ንጉሡን አለመታዘዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከንጉሡ ተደብቆ የሚቀር ምንም ነገር የለም
እዚህ ሰውየው የሚናገረው ንጉሡ እንዴት ከሞላ ጎደል ስለ ሁሉም ነገር እንደሚያውቅ ሲሆን ማናቸውም ነገር የሚለውም አካላዊ ቁስ ሆኖ ንጉሡ የዚይን ስፍራ እንደሚያውቅ አድርጎ ነው። "ንጉሡ የማያውቀው አንዳች ነገር የለም" ወይም "ንጉሡ ስለሚሆነው እያንዳንዱ ነገር ይሰማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 18:14
እኔ አንተን መጠበቅ አልችልም
ኢዮአብ ከሰውየው ጋር መነጋገሬን መቀጠል አይኖርብኝም ማለቱ ነው። "ከአንተ ጋር በመነጋጋር ምንም ተጨማሪ ጊዜ አላባክንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የአቤሴሎም ልብ
እዚህ ስፍራ የአቤሴሎም ልብ የሚለው የሚያመለክተው ደረቱን ወይም የላይኛውን የሰውነት ክፍሉን ነው። "ደረት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
የጦር ትጥቅ/ልብስ
ይህ የሚያመለክተው ራሱን ለመጠበቅ ስለሚለብሰው የጦር ልብስ እና መሳሪያውን ጭምር ነው። "የጦር ልብስና ትጥቅ/መሳሪያ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 18:16
ኢዮአብ ሰራዊቱን ከልክሎ ነበርና መለከት ነፋ፣ እናም ሰራዊቱ እስራኤልን ከማሳደድ ተመለሰ
ይህ ኢዮአብ መለከት በመንፋት ምን እንዳዘዘ ይገልጻል። "ከዚያም ኢዮአብ ሰራዊቱን ወደ ኋላ ለመመለስ መለከት ነፋ፣ እናም ሰራዊቱ እስራኤልን ከማሳደድ ተመለሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እስራኤልን ከማሳደድ ተመለሰ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚያመለክተው የእስራኤላውያንን ሰራዊት ነው። "የእስራኤላውያንን ሰራዊት ከማሳደድ ተመለሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
አቤሴሎምን ወስደው ወረወሩት
"የአቤሴሎምን አካል/በድን ወስደው ወረወሩት"
በድኑን ከትልቅ የድንጋይ ክምር ስር ቀበሩ
በድኑን ጉድጓድ ውስጥ ከጨመሩ በኋላ በደንጋይ ክምር ሸፈኑት። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "በድኑን በብዙ የድንጋይ ክምር ሸፈኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መላው እስራኤል በሚሸሽበት ጊዜ
እዚህ ስፍራ "መላው እስራኤል" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ወታደሮች ነው። "መሸሽ" የሚለው ቃል "ማምለጥ" ማለት ነው። "መላው የእስራኤል ወታደሮች በሚያመልጡበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 18:18
የንጉሥ ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የስሜን መታሰቢያ የሚሸከመውን/ስሜን የሚያስቀጥለውን
አቤሴሎም "ስሜ/የእኔ ስም" የሚለውን ሀረግ የተጠቀመው ራሱን እና ቤተሰቡን ሀረግ ለማመልከቱ ነው። "ሰዎች እኔን የሚያስታውሱበትን፣ የቤተሰቤን ስም ለመሸከም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህም እስከ ዛሬ ድረስ የአቤሴሎም መታሰቢያ ተብሎ ይጠራል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ስለዚህም ሰዎች ከዚያን ጊዜ ቀን አንስቶ የአቤሴሎም መታሰቢያ ብለው ይጠሩታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እስከ ዛሬ ቀን ድረስ
እዚህ ስፍራ ዛሬ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተጻፈበትን ጊዜ ነው።
2 Samuel 18:19
አኪማአስ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 15:27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
መልካሙን ወሬ ይዞ ወደ ንጉሡ ሮጠ
እዚህ ስፍራ አኪማአስ ስለ መሮጥ የሚናገረው ወደ ንጉሡ ሄዶ መለካሙን ወሬ/ የምስራቹን እርሱ እንደተሸከመው አንድ ነገር ወይም አካል አድርጎ ነው። "መልካሙን ወሬ ለንጉሡ ለመናገር ሮጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የጠላቶቹ እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው መቆጣጠርን/መያዝነን ነው። "ጠላቶቹን መቆጣጠር/መያዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ወሬውን ያመጣው/ወሬ ነጋሪው
"ወሬን የሚያደርሰው/የሚናገረው ሰው"
ምንም ወሬ አታደርስም
ይህ የሚያመለክተው ለንጉሡ ወሬ አለማምጣትን ነው። "ወሬውን ለንጉሡ አትናገርም/አታደርስም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 18:21
ያየኸውን ለንጉሡ ተናገር
ኢዮአብ እርሱ ሄዶ ለንጉሡ ስለ ጦርነቱ ወሬውን እንዲናገር እየነገረው ነው
2 Samuel 18:24
አሁን
ይህ ቃል እዚህ ስፍራ የዋለው በዋናው ታሪክ ፍሰት ላይ መቆሚያ እና በታሪኩ አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማበጀት ነው።
ዐይኖቹን አቀና/አነሳ
እዚህ ስፍራ ጠባቂው/ዘበኛው አንድ ነገር መመልከቱ የተገለጸው ልክ ዐይኖቹን ወደ ላይ ከፍ እንዳደረገ ተደርጎ ነው። "ወደ ከተማው አሻግሮ ተመለከተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በአፉ የምስራች አለ
እዚህ ስፍራ ንጉሡ ሰውየው መልዕክት ያለው መሆኑን የገለጸው ወሬው በአፉ ላይ የሚገኝ ነገር ወይም አካል እንደሆነ አድርጎ ነው። "የሚነግረን ወሬ አለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 18:26
ከፊት የሚሮጠው ሰው አሯሯጥ የሳዶቅን ልጅ የአኪማአስን ሩጫ ይመስላል
ዘበኛው የሰውየውን አሯሯጥ ከአኪማአስ ሩጫ ጋር ያነጻጸረው አኪማአስ ይሆናል የሚል ግምት ለመስጠት ነው። "ከፊት የሚሮጠው የሳዶቅ ልጅ አኪማአስ ይመስለኛል፣ ምክንያቱም አሯሯጡ እንደ አኪማአስ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 18:28
በንጉሡ ፊት ወደ ምድር ዝቅ ብሎ ሰገደ
ይህን ያደረገው ንጉሡን ለማክበር ነው። "ንጉሡን ለማክበር ወደ ምድር ዝቅ ብሎ በንጉሡ ፊት ሰገደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ የተባረከ ይሁን
"ያህዌ ይመስገን።" እዚህ ስፍራ "መባረክ" ማለት ማወደስ ማለት ነው።
በጌታዬ በንጉሡ ላይ እጃቸውን ያነሱ ሰዎች
እዚህ ስፍራ አኪማአስ ንጉሡን የተቃወሙ ሰዎችን የገለጸው እጃቸውን በእርሱ ፊት ወደ ላይ እንዳነሱ አድርጎ ነው። "ጌታዬን ንጉሡን የተቃወሙ እና የወጉ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ታላቅ ረብሻ
ይህ ማለት ሰዎች የሚያደርጉት ነገሮች ትክክል ባልሆኑበት ሁኔታ እንደሚደረገው ያለ ነገር ነበር
ዞር በልና እዚህ ቁም
"ከመንገድ ዞር በል" ወይም "ዞር ብለህ ቁም"
2 Samuel 18:31
በተቃውሞ መነሳት

ይህ ማለት መቃወም ማለት ነው። "በተቃውሞ ተነሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የጌታዬ የንጉሡ ጠላቶች ... ያ ወጣት ሰው እንደሆነው ይሁኑ
ኩሻዊው ንጽጽሩን የተጠቀመበት ትሁት በሆነ መንገድ የአቤሴሎምን ሞት ለንጉሡ ለመናገር ነው። ይህ ይበልጥ ቀጥተኛ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ጠላቶችህ ሁሉ ያ ወጣት በሞተበት መንገድ ቢሞቱ እወዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተጻጻሪ ዘይቤ እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
ራሱን መቆጣጣር እጅግ ተስኖት ነበር
"እጅግ አዝኖ ነበር" ወይም "በሀዘን ተውጦ ነበር"

---

Chapter 19

2 Samuel 19:1

ኢዮአብ ተነገረው/ሰማ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው ለኢዮአብ ነገረው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ፣ ንጉሡ አለቀሰ
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል የዋለው የአንባቢውን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚነገረው ነገር ለመሳብ ነው። "እነሆ፣ ንጉሡ አለቀሰ"
በመሆኑም የዚያን ቀን በሰራዊቱ ዘንድ ድሉ ወደ ለቅሶ ተለወጠ
ይህ ማለት መላው ሰራዊት ድሉን ከማክበር ይልቅ አለቀሰ። "በዚያን ቀን ድሉን ከማክበር ይልቅ መላው ሰራዊት አለቀሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:3

ከጦርነት ሸሽቶ በሀፍረት እንደተመለሰ ህዝብ
ጸሐፊው ወታደሮቹ ወደ ከተማ የተመለሱበትን መንገድ ያነጻጸረው ወታደሮች ከጦርነት በሽንፈት ከሚሸሹበት ሁኔታ ጋር ነው። ይህ እንዲያፍሩ መደረጋቸውን ያጎላል። "ስላፈሩ ከጦርነት የሚሸሹ ሰዎች ወደ ኋላ እንደሚሉ ህዝቡ በተመሳሳይ መንገድ ህዝቡ ተሰርቆ/በምስጥር ገባ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በምስጥር/በስውር
በሌሎች ሳይታዩ መንቀሳቀስ/መጓዝ
ንጉሡ ፊቱን ሸፈነ
ይህ ሀዘንን እና ለቅሶን ፈግለጫ መንገድ ነው። "ንጉሡ ፊቱን በመሸፈን ሀዘኑን ገለጸ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:5

ዛሬ የወታደሮችህን ፊት ሁሉ አሳፈርክ
እዚህ ስፍራ ከሀፍረታቸው የተነሳ ወታደሮች ፊታቸውን እንዴት መደበቅ እንዳለባቸው ለማጉላት የተገለጹት በፊታቸው ነው። "ዛሬ ወታደሮችህን በሙሉ በሀፍረት ፊታቸውን እንዲሸፍኑ አድርገሃል" ወይም "ዛሬ ወታደሮችህ በሙሉ እንዲያፍሩ አድርገሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
ይህ ለአንተ ምንም ማለት አይደለም
ይህ ሀረግ ማጋነን ነው፣ ሆኖም ዳዊት ለሰራዊቱ ያሳየው በጣም ዝቅ ያለ ዋጋ ይገልጻል። "ለአንተ ዋጋቸው በጣም ያነሰ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
እኛ ሁላችንም ሞተን አቤሴሎም በህይወት ተርፎ ቢሆን ያ አንተን ባስደሰተህ ነበር
ተናጋሪው መላ ምታዊ ሁኔታን እየሰጠ ነው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:7

በያህዌ እምላለሁ
ኢዮአብ በጣም ጠንካራ መሃላ እያደረገ ነው። "በ ያህዌ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ የማትሄድ ከሆነ፣ ከአንተ ጋር አንድም ሰው አይቀርም
ይህ ማለት የዳዊት ወታደሮች ከእርሱ ጋር የሚቀሩት እርሱ ከሄደ ብቻ ነው። "አንተ ከሄድክ ብቻ ከአንተ ጋር የሚቀር ወታደር ይኖራል" (ድርብ አሉታ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሰው እንኳን ከአንተ ጋር አይቀርም
ይህ ለእርሱ ታማኝ ሆነው የሚቀሩትን ያመለክታል። "ለአንተ አንድ ሰው እንኳን ታማኝ ሆኖ አይቀርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ህዝቡ ሁሉ ሰምቶ ነበር
ይህ የተጠቃለለ አስተያየት ነው። ብዙዎቹ ሰዎች ለማለት ነው። በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እዚያ የነበሩት ብዙዎቹ ሰዎች ሌሎች ሲናገሩ ሰምተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት እንዲሁም አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
እነሆ፣ ንጉሡ ተቀምጧል
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል የዋለው የአንባቢውን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚነገረው ለመሳብ ነው። "እነሆ፣ ንጉሡ ተቀምጧል"
ህዝቡ ሁሉ
እዚህ ስፍራ "ህዝቡ" የሚለው የሚያመለክተው ዳዊትን የተከተለውን ህዝብ ነው። እዚህ "ሁሉ" የሚለው የተጠቃለለ አስተያየት ነው። ብዙ ቁጥር ያላቸው መጥተው በእርሱ ዙሪያ ተሰባሰቡ ማለት ነው። "ብዙ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
ስለዚህም እስራኤል ሸሸ፣ እያንዳንዱ ሰው ወደየ ቤቱ ሸሸ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው አቤሴሎምን የተከተለውን የእስራኤል ወታደር ያመለክታል። "እናም እያንዳዱ የእስራኤል ወታደር ወደየ ቤቱ ሸሸ" ወይም "መላው የእስራኤል ወታደር ወደየ ቤታቸው ሸሹ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

2 Samuel 19:9

ከጠላቶቻችን እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" ማለት መቆጣጠር ማለት ነው። "ከጠላቶቻችን ቁጥጥር ስር" ወይም "ከጠላቶቻችን ቁጥጥር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከፍልስጥኤማውያን እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" ማለት መቆጣጠር ማለት ነው። "ከፍልስጥኤማውያን ቁጥጥር ስር" ወይም "ከፍልስጥኤማውያን ቁጥጥር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከአቤሴሎም የተነሳ ከምድሪቱ ውጭ
ይህ ማለት ከአቤሴሎም በመሸሽ አገር ለቆ ወጥቷል ማለት ነው። ይህ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ከአቤሴሎም በመሸሽ ከአገር ወጥቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡን ስለ መመለስ ለምን አንድ ነገር አትናገሩም?
ይህ ማለት አሁን አቤሴሎም ስለ ሞተ ዳዊትን ስለ መመለስ ጉዳይ ማሰብ አለባቸው ማለት ነው። ጥያቄው በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡን ዳግም ስለ መመለስ መነጋጋር አለብን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡ
ይህ ዳዊትን ያመለክታል

2 Samuel 19:11

ወደ ሳዶቅ እና አብያታር ላከ
ይህ ማለት ዳዊት ወደ ሳዶቅ እና አብያታር መልዕክተኛ ላከ ማለት ነው። "ወደ ሳዶቅ እና አብያታር መልዕክተኛ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡን ዳግም ለመመለስ...እርሱን ወደ ቤተመንግሥቱ ለመመለስ ለምን እናንተ የመጨረሻዎቹ ትሆናላችሁ?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠየቀው በይሁዳ የሚገኙ ሽማግሌዎችን ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡን ለመቀበል እና ወደ ቤተ መንግስቱ ለመመለስ፣ የእስራኤል መንግሥት ሰዎች ሳይሆኑ እናንተ የመጀመሪያዎቹ መሆን ነበረባችሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ንግግር ንጉሡን ለማምጣት እስከ ተቀበለ ድረስ፣
"ንግግር" የሚለው ስም "ተናገረ" ወይም "አለ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "መላው እስራኤል ስለ ንጉሡ ደግፎ እስከተናገረ እና ሊመልሰው እስከ ፈለገ ድረስ" ወይም "የእስራኤል ሰዎች የሚናገሩት ንጉሡ እንዲመለስ እስከ ደገፈ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡን ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመመለስ
እዚህ ስፍራ ንጉሡ እንዲመራ ስልጣኑን መመለስ የተገለጸው እርሱን ወደ ቤተ መንግሥቱ እንደ መመለስ ተደርጎ ነው። "የንጉሡን ስልጣን እንደ ንጉሥነቱ ለማደስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ ወንድሞቼ፣ የስጋዬ ቁራጭ የአጥንቴ ፍላጭ ናችሁ
ንጉሡ እነዚህን ሀረጎች የተጠቀመው በቅርበት የተዛመዱ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው። አንድ ስጋ ነን ወይም አንድ ስጋ አለን ማለት ቤተሰብ መሆንን ወይም ከአንድ ነገድ መሆንን የሚገለጽ ዘይቤ ነው። "እናንተ ወንድሞቼ ናችሁ እኛ አንድ ስጋ እና አጥንት አለን" ወይም "እናንተ ወንድሞቼ ናችሁ፣ የቅርብ ዘመዶቼ ናችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡን ዳግም ለመመለስ እናንተ ለምን የመጨረሻዎቹ ትሆናላችሁ?
እዚህ ስፍራ ይህ ሁለተኛው ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ሲሆን የይሁዳን ሽማግሌዎችንም ጭምር ይገስጻል። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እናንተ ንጉሡን ዳግም ለመመለስ፣ የመጨረሻ ሰይሆን የመጀመሪያዎቹ መሆን ይገባችሁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 19:13
አሜሳይ
ይህንን የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 17፡25 ላይ እንዴት እንደ ተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ ስጋዬ እና አጥንቴ አይደላችሁምን?
እዚህ ስፍራ ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ዘመድ መሆናቸውን ለማጉላት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እናንተ ስጋ እና አጥንቶቼ ናችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ስጋዬ እና አጥንቴ ናችሁ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ስለ እነርሱ መዛመድ የሚናገረው አንድ አይነት ስጋ እና አጥነት አለን በማለት ነው። በ 2 ሳሙኤል 19፡12 ላይ ተመሳሳዩ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ዘመዶቼ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር እንዲህና እንዲያ ያድርግብኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ እግዚአብሔር ይግደለኝ/ያንሳኝ ማለት ነው።"እግዚአብሔር ያንሳኝ/ይግደለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ልቦቻቸውን ማረከ
እዚህ የወንዶቹ ታማኝነት የተገለጸው እንደ ልቦቻቸው ተደርጎ ነው። "ታማኝነታቸውን አገኘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ አንድ ሰው
ይህ የሚገልጸው ወንዶቹ ለንጉሡ በታማኝነታቸው እንደ አንድ ሰው በአንድ ሃሳብ መተባበራቸውን ነው። "እናም በአንድነት ተባብረው ነበር" ወይም "ለንጉሡ በታማኝነታቸው ተባብረው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ለንጉሡ ላኩ
ይህ ማለት ለንጉሡ መልዕክት ላኩ ማለት ነው። "እነርሱ ለንጉሡ መልዕክት ላኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 19:16
ጌራ…ሲባ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። "ሲባ" የሚለውን ስም በ 2 ሳሙኤል 9፡2 ላይ እንደ ተረጎሙት በተመሳሳይ ይተርጉሙት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ብራቂም
የዚህን ቦታ ስም በ 2 ሳሙኤል 3፡16 ላይ እንደ ተረጎሙት በተመሳሳይ ይተርጉሙት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሺህ ወንዶች … አስራ አምስት ወንዶች ልጆች… ሃያ አገልጋዬች
"1,000 ወንዶች… 15 ወንዶች ልጆች … 20 አገልጋዬች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡ በተገኘበት
ይህ ማለት ንጉሡ በዚያ ነበር ደግሞም የሚደረገውን ያውቅ ነበር። "ንጉሡ በነበረበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 19:19
በልብህ አኑረው
ይህ "ማታወስ" ማለት ነው። "አስታውስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ አገልጋይ
እዚህ ስፍራ ሳሚ ራሱን በዚህ መንገድ የሚገልጸው በንጉሡ ፊት ራሱን ዝቅ ለማድረግ እና ንጉሡን ለማክበር ነው።
ወደ ልብህ አታስገባው
"አንድን ነገር ወደ ልብ ማስገባት" ማለት ስለ አንድ ነገር በጥንቃቄ ማሰብ ወይም በዚያ ነገር መጨነቅ ማለት ነው። "በዚህ አትጨነቅበት" ወይም "እጅግ ግድ አይበልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 19:21
አቢሳ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 2፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ጽሩያ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 2፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ የቀባውን ሰድቧልና ሳሚ ለዚህ ስራው ሞት አይገባውምን?
አቢሳ በሳሚ ላይ እጅግ የተቆጣው ዳዊትን በመራገሙ ሲሆን ሞት እንደሚገባውም ተናግሯል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ የቀባውን ስለሰደበ ሳሚ መገደል ይገባዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ የቀባው
ይህ ዳዊትን ያመለክታል። ይህ ማለት ያህዌ ንጉሥ አድርጎ የቀባው ሰው እርሱ ነው። "ያህዌ ንጉሥ አድርጎ የቀባው ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ዛሬ እንዲህ ታማክሩኝ ዘንድ …እኔ ከእናንተ ጋር ምን አለኝ?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው አቢሳን ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " እናንተ የጽሩያ ልጆች፣ እኛ ከእናንተ ጋር የጋራ የሆነ ምንም ነገር የለንም! ዛሬ ታማክሩኝ ዘንድ አንዳች ጥሩ ምክንያት የላችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ዛሬ በእስራኤል ውስጥ አንዳች ሰው ይገደላልን? ዛሬ በእስራኤል ላይ ንጉሥ መሆኔን አላወቅኩምን?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው አቢሳን መውቀሱን ለመቀጠል ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዛሬ በእስራኤል አንዳች ሰው አይገደልም፣ ምክንያቱም ዛሬ እኔ በመላው እስራኤል ላይ ነግሻለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሰው ይገደላልን
"ይገደላልን" የሚለው ሀረግ መገደል ወይም መረሸን ማለት ነው። "አንድ ሰው ይገደላልን" ወይም "አንድ ሰው እንዲገደል ትዕዛዝ እሰጣለሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዛሬ በእስራኤል ሁሉ ላይ መንገሤን አላወቅኩምን?
የዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት አማራጮች፡ 1)"አሁንም የእስራኤል ንጉሥ መሆኔን አውቃለሁ" ወይም "ዛሬ በእስራኤል ሁሉ ላይ ንጉሥ የሆንኩት እኔ ነኝ!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 19:24
ሜምፊቦስቴ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 4፡4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእግሩ መጫሚያ አላደረገም/ጫማ አላደረገም
"ለእግሩ እንክብካቤ አላደረገም።" የሜምፊቦስቴ እግሮች ሽባ ነበሩ። የዚህ ሀረግ

ትርጉም ለአግሩ ተገቢ አንክብካቤ አላደረገም ማለት ነው።
ሜምፊቦስቴ፣ ለምን ከእኔ ጋር ሳትሄድ ቀረህ?
ዳዊት ሜምፊቦስቴን ዳዊት እና እርሱን የሚከተሉ ሰዎች ሁሉ እየሩሳሉምን ለቀው ሲሄዱ እርሱ ለምን እንዳልተከተለው ይጠይቀዋል። "ሜምፊቦስቴ፣ እኔ እየሩሳሌምን ለቅቄ ስወጣ አንተ ለምን አልተከተልከኝም?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 19:26
ሲባ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 9፡2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡ ጌታዬ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነው
እዚህ ስፍራ የዳዊት ጥበብ የተነጻጸረው ከመልአክ ጥበብ ጋር ነው። "ንጉሡ ጌታዬ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ብልህ ነው" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በዐይኖችህ ፊት መልካም መስሎ የታየህን አድርግ
ይህ ማለት ትክክል መስሎ የታየህን አድርግ ማለት ነው። "ለማድረግ ትክክል ነው ብለህ ያመንክበትን አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በንጉሡ በጌታዬ ፊት የአባቴ ቤት ሁሉ እንደ ሞቱ ሰዎች ናቸው
ሜምፊቦስቴ የእርሱ ቤተሰቦች ሞት እንደሚገባቸው የገለጸው ቀድሞውኑ እንደ ተገደሉ እና የሞቱ እንደሆኑ አድርጎ ነው። "የአባቴ ቤቱ ሁሉ ንጉሡ ጌታዬ እንዲገደሉ ትዕዛዝ ሊያወጣባቸው የተገባቸው ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የአባቴ ቤት
ይህ የአባቱን ዘመዶች ያመለክታል። "የአባቴ ቤተ ዘመዶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህ አሁንም ወደ ንጉሡ ከዚህ በላይ እጮህ/እናገር ዘንድ ምን መብት አለኝ?
ሜምፊቦስቴ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ከንጉሡ አንዳች ነገር ለመጠየቅ ምንም መብት እንደሌለው አጉልቶ ለመናገር ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ስለዚህ፣ ንጉሡ ለእኔ ሌላ ተጨማሪ ነገር እንዲያደርግ ለመጠየቅ ምንም መብት የለኝም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 19:29
ለምን ሌላ ማብራሪያ ትጨምራለህ?
ዳዊት ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ከሲባ ጋር እርሱ ስላለው ግጭት መናገሩን መቀጠል እንደማያስፈልገው ሊነግረው ስለ ፈለገ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ይህንን ከዚህ በላይ ማብራራት አያስፈልግህም።" ወይም "በእርግጥ ከዚህ በላይ መናገር አያስፈልግህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 19:31
ቤርዜሊ
ይህ የወንድ ስም በ2 ሳሙኤል 17፡27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ገለዓዳዊ
ይህ የሰዎች ቡድን/የወገን ስም በ2 ሳሙኤል 17፡27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሮግሊም...መሃናይም
እነዚህ የቦታ ስሞች በ2 ሳሙኤል 17፡27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የዮርዳኖስ
የዮርዳኖስ ወንዝ
የሰማንያ አመት አድሜ
"የ80 አመት እድሜ" (ቁጥርች የሚለውን ይመልከቱ)
ለንጉሡ የሚያስፈልገውን አዘጋጀ
"ንጉሡ የሚያስፈልገውን አቀረበ"
2 Samuel 19:34
ከንጉሡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም እሄድ ዘንድ ከእድሜዬ የምኖርበት ምን ያህል ቀናት ቀረኝና ነው?
እዚህ ቤርዜሊ ማለት ዳዊትን ለማጀብ አንዳች ምክንያት የሌለው ሽማግሌ ሰው ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "በእርግጥ የምኖርበት ዘመን እያበቃ ያለ ሰው ነኝ። ከንጉሡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በቂ ምክንያት የለኝም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰማንያ አመት አድሜ
"የ80 አመት እድሜ" (ቁጥርች የሚለውን ይመልከቱ)
በመልካሙ እና በክፉው መካከል መለየት እችላለሁን?
ቤርዜሊ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ለምን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ እንዳልፈለገ ለማጉላት ነው። እዚህ "መልካም" እና "ክፉ" የሚሉት ቃላት የዋሉት አስፈላጊ የሆነ እና ያልሆነውን ለማመልከት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "አስፈላጊ በሆነው እና ባልሆነው መሃል መለየት አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
አገልጋይህ የምበላውን ወይም የምጠጣውን ጣዕሙን መለየት እችላለሁን?
ቤርዜሊ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ለምን ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ እንዳልፈለገ ለማጉላት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "የምበላውን እና የምጠጣውን ጣዕሙን ላጣጥም አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእንግዲህ የሚዘምሩ ወንዶችና እና የሚዘምሩ ሴቶችን ድምጽ መስማት/መለየት እችላለሁን?
ቤርዜሊ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ለምን ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ እንዳልፈለገ ለማጉላት ነው።ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "የሚዘምሩ ወንዶችን እናየሚዘምሩ ሴቶችን ድምጽ በትክክል መስማት አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
አገልጋይህ ለምን ለጌታዬ ለንጉሡ ሸክም ይሆናል?
ቤርዜሊ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው በንጉሡ ላይ ሸክም መሆን አለመፈለጉን ለማጉላት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "አገልጋይህ ከአንተ ጋር በመሄድ ለአንተ ሸክም መሆን የለበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡ ለምን ለእኔ እዲህ ባለ ወረታ ይመልስልኛል?
ቤርዜሊ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ንጉሡ ለምን በእንዲህ ያለ መንገድ ወረታ እንደሚያደርግለት አለማወቁን ለማጉላት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡ ለምን እንዲህ አይነት ታላቅ ወረታ እንደሚያደርግልኝ አላውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 19:37
አጠቃላይ መረጃ፡
ቤርዜሊ የእርሱን ቦታ ከዳዊት ከመዓም እንዲወስድ ይፈቀድለት ዘንድ ጠየቀ
ከመዓም
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
በአባቴ እና በእናቴ መቃብር
ይህ ማለት ከመቃብራቸው አጠገብ መሞት ይፈልጋል ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ይልቁንም፣ እርሱ በተቀበሩበት ከተማ መቀበር ይፈልጋል ማለት ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "የአባቴ እና የእናቴ መቃብር ባለበት" ወይም "አባቴ እና እናቴ በተቀበሩበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ይሻገር
ይህ የሚያመለክተው የዮርዳኖን ወንዝ መሻገርን ነው። "እርሱ ዮርዳኖስን ይሻገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 19:38
ከመዓም ከእኔ ጋር ወንዙን ይሻገራል
ይህ የሚያመለክተው የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገርን ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ከመዓም ከእኔ ጋር ወንዙን ይሻገራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 19:40
ወደ ጌልገላ መሻገር
የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ። "ወደ ጌልገላ ወንዙን ተሻገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
ከመዓም
ይህ ስም በ2ሳሙኤል19፡37 እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት

ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
መላው የይሁዳ ሰራዊት ንጉሡን እና የእስራኤልን ሰራዊት እኩሌታ አሻገረ
"የይሁዳ ሰራዊት እና የእስራኤል ሰራዊት እኩሌታ ንጉሡን አሻገረ"
ንጉሡን አሻገሩት
የዮርዳኖስን ወንዝ ከንጉሡ ጋር ተሻገሩ። "ንጉሡ ወንዙን ሲያቋርጥ አጀቡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
ወንድሞቻችን የይሁዳ ሰዎች ... እና መላው የዳዊት ሰዎች ለምን ከእርሱ ጋር ሆኑ?
የእስራኤል ሰዎች ይህንን ጥያቄ ያዋሉት በይሁዳ ሰዎች የተካዱ ሆኖ ስለተሰማቸው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "አንተን እንደ ንጉሥ ያልደገፉህ ወንድሞቻችን የይሁዳ ሰዎች አንተን እና ቤተሰብህን ዮርዳኖስን የማሻገር እድል ማግኘታቸው አግባብ አይደለም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተን ሰረቁ
የእስራኤል ሰዎች የይሁዳ ሰዎችን ንጉሡ የእነርሱ እንዳልሆነ እና የሰረቁት ነገር ይመስል ዮርዳኖስን ሲሻገር በማጀባቸው ተናገሩ። "አንተን ከእኛ ወሰዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የዮርዳኖስ
የዮርዳኖስ ወንዝ
2 Samuel 19:42
ታዲያ ለምን ስለዚህ ነገር ተቆጣችሁ?
የይሁዳ ሰዎች ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የጠየቁት የእስራኤልን ሰዎች ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ነገር ግን እናንተ በዚህ ነገር ለመበሳጨት የሚያበቃ ምንም ምክንያት የላችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡ ወጪ የሚያደርግበትን አንዳች ነገር በልተናልን? ለእኛ አንዳች ስጦታ ሰጥቶናልን?
የይሁዳ ሰዎች ጥያቄውን የጠየቁት ከንጉሡ አንዳችም ነገር አለመውሰዳቸውን ለመግለጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡ ለቀለባችን ከፍሎ አያውቅም፣ ደግሞም አንዳች ስጦታም ሰጥቶን አያውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእናንተ ይልቅ እኛ በዳዊት ላይ የበለጠ መብት አለን
"እኛ ከእናንተ ይልቅ ከዳዊት ላይ ልንጠይቅ የምንችለው አለን።" "የበለጠ መብት" የሚለው ምን ማለት እንደሆነ ይበልጥ ግልጽ ማድረጉ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። " እኛ ከእናንተ ይልቅ ንጉሡን ለማገልገል እና ከንጉሡ ጋር ለመሆን የበለጠ መብት አለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እንዲህ ከሆነ እናንተ እኛን ስለምን ትንቁናላችሁ?
የእስራኤል ሰዎች ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቁት ቁጣቸውን ለመግለጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እኛን ልትንቁን አይገባችሁም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሣችንን ለመመለስ ያቀረብነው ሃሳብ ቅድሚያ አግኝቶ መደመጥ አልነበረበትምን?
የእስራኤል ሰዎች ይህንን ጥያቄ የጠየቁት የይሁዳን ሰዎች ስለ ነገሩ ለማስታወስ እና ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡን እንመልሰዋለን! የሚለውን ሀሳብ ለማቅረብ እኛ የመጀመሪያዎቹ ነበርን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ሰዎች ቃል ከእስራኤል ሰዎች ቃል ይልቅ ጠንካራ ነበር
"የይሁዳ ሰዎች የእስራኤል ሰዎች ከተናገሩት ይልቅ ጠንካራ ንግግር ተናገሩ"

Chapter 20
2 Samuel 20:1
በተመሳሳይ ስፍራ ለመሆን
ይህ የጌልገላን ከተማ ያመለክታል።
ሳቤዔ... ቢክሪ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
እኛ ከዳዊት ምንም ድርሻ የለንም፣ ከእሴይም ልጅ ምንም ርስት የለንም
ሁለቱም ሀሳቦች አንድን ነገር ይገልጻሉ። ሳቤዔ እርሱ እና የእስራኤል ነገድ ከዳዊት ጋር ምንም ዝምድና እንደሌላቸው ትኩረት ይሰጣል። "የዳዊት ትውልድ እና የአባቱ ቤት የእኛ ወገን አይደሉም" ወይም "እኛ የዳዊት ወይም የአባቱ ቤት ወገን አይደለንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 20:3
ቤቱን ለመጠበቅ
እዚህ ስፍራ "ለመጠበቅ" የሚለው ሀረግ እንክብካቤ ለማድረግ የሚልትርጉም አለው። "ቤቱን ለመንከባከብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በጠባቂ ስር በሚገኝ ቤት
x
2 Samuel 20:4
አሜሳይ
ይህ ሰው የዳዊት ሰራዊት የጦር አዛዥ ነው። የዚህ ሰው ስም በ2 ሳሙኤል 17፡25 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 20:6
አቢሳ
ይህ ሌላኛው የዳዊት ሰራዊት የጦር አዛዥ ነው። የዚህ ሰው ስም በ2 ሳሙኤል 2፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ብዙ ጉዳት ያደርስብናል
"የበለጠ ይጎዳናል"
የጌታችሁ አገልጋዮች፣ የእኔ ወታደሮች
"የእኔ ወታደሮች" የሚለው ሀረግ የትኞቹ "አገልጋዮች" እንደሆኑ ግልጽ ያደርጋል። ዳዊት ራሱን "የእናንተ ጌታ" በማለት ዝቅ ያለ ስልጣን ካለው ሰው ጋር ንግግር በሚደረግበት መደበኛ የአነጋገር መንገድ ይገልጻል።
ተከትለህ አባረው
"ከኋላ አሳደው"
የተመሸገ ከተማ ያገኛል
ይህ ማለት ሳቤዔ እና የእርሱ ወታደሮች ከዳዊት ሰራዊት ለመደበቅ ወደ እነዚህ ከተሞች ይገባሉ ማለት ነው። "እርሱ" የሚለው ቃል የሚወከወለው ሳቤዔን ሲሆን ነገር ግን እርሱን እና የእርሱን ወታደሮች ጭምር ያመለክታል። "እርሱ እና የእርሱ ሰዎች በተመሸገ ከተማ ራቸውን ይደብቃሉ" ወይም "እርሱ እና የእርሱ ሰዎች በተመሸጉ ከተሞች ይሸሸጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከእይታችን ውጭ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ሳቤዔ እና የእርሱ ሰዎች ሊደበቁ እንደሚችሉ እና የዳዊት ሰራዊት ሊይዛቸው እንደሚቸገር ትኩረት ለመስጠት ሰራዊቱን የሚገልጸው በእይታቸው ነው። "ከእኛ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከሊታውያን ... ፈሊታውያን
እነዚህ ንጉሥ ዳዊትን ለመጠበቅ የረዱ የሰዎች ቡድን/ የወገን ስሞች ናቸው። እነዚህ የወንድ ስሞች በ2 ሳሙኤል 8፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 20:8
እነርሱ በደረሱ ጊዜ
"ኢዮአብ እና የይሁዳ ሰዎች በደረሱ ጊዜ "
ቀበቶ
ልብስን ለመታጠቅ ወይም መሳሪያን ለማንገት የሚያገለግል የቆዳ ወይም የሌላ ነገር ቀራጭ
ሰገባ ያለው ሰይፍ
ይህ ማለት ሰይፉ በሰገባው ውስጥ ነበር።
ሰይፉ ወደቀ
ኢዮአብ አሜሳይን ለማታለል ሰይፉን በመጣል እንዳልታጠቀ አድርጎ እንዲያስብ በማድረግ አሜሳይ ወደ እርሱ እንዲቀርብ አደረገ። "ኢዮአብ ሰይፉ ወደ መሬት እንዲወቅድ የተወው አሜሳይ እርሱ እንዳልታጠቀ አድርጎ እንዲያስብ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 20:9

የአክስቴ ልጅ

አሜሳይ የኢዮአብ እናት እህት ልጅ ነበር

አሜሳይን ሊስመው በቀኝ እጁ ጺሙን ይዞ ወደ እርሱ አስጠጋው

ይህ ወንዶች እርስ በእርሳቸው ሰላምታ የሚሰጣጡበት የተለመደ መንገድ ነበር

ጩቤ

ለመደበቅ ቀላል የሆነ አጭር ሰይፍ ሲሆን ብዙውን ጊዜ ለጩበጣ ውጊያ እና ለግድያ የሚያገለግል ነው

ሆድ ዕቃው ተዘረገፈ

"አንጀቱ ተዘረገፈ"

2 Samuel 20:11

ለዳዊት የሆነ

"ለአንድ ሰው" መሆን ማለት ያንን ሰው መደገፍ ማለት ነው። "ዳዊትን የሚደግፍ" ወይም "ለዳዊት ታማኝ የሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አሜሳይ በደም ተነክሮ ወድቆ ነበር

"አሜሳይ በደሙ ተነክሮ ይንከባለል ነበር።" አሜሳይ ገና ነፍሱ ስላልወጣች በደሙ ተነክሮ ሲንከባለል ቢቆይም በዚህን ጊዜ ግን ሳይሞት አልቀረም። ይህ በዚህ መንገድ የተገለጸው አካሉ ምን ያህል በአሰቃቂ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኝ ለመግለጽ ነው። "አሜሳይ ሞቶ በደም ተነክሮ ተጋድሞ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እርሱ ሲደርሱ...ህዝቡ ሁሉ ቀጥ ብሎ ይቆም ነበር

ይህ ማለት መሄዳቸውን ያቆሙ እና የአሜሳይን በድን አትኩረው ይመለከቱ ነበር። "ሁሉም ሰዎች ቀጥ ብለው እየቆሙ የአሜሳይን በድን ይመለከቱ ነበር... ወደ እርሱ ሲደርሱ እየቆሙ በድኑን አትኩረው ይመለከቱ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አሜሳይን ተሸከመው

"የአሜሳይን በድን ተሸከመ"

አሜሳይ ከመንገድ ዘወር ከተደረገ በኋላ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰውየው አሜሳይን ከመንገድ ዞር ካደረገ በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ማሳደዱ ሲያበቃ

ይህ ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። "አሳደደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 20:14

ሳቤዔአለፈ

እዚህ ስፍራ "ሳቤዔ" የሚለው የሚያመለክተው እርሱን እና ሰራዊቱን ነው። "ሳቤዔ እና የእርሱ ሰራዊት" ወይም "ሳቤዔ እና የእርሱሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የቤት መዓካው አቤል

"አቤል ቤትመዓካ።" ሁለቱም ስሞች አንድን ቦታ ያመለክታሉ ምናልባትም ሊጣመሩ ይችላሉ። ይህ ከተማ በዳን ነገድ አቅራቢያ የሚገኝ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቢክሪያውያን

ይህ የሰዎች ቡድን/ የወገን ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ደግሞም ሳቤዔን አሳደዱ

"ደግሞም ሳቤዔን ተከተሉት"

እነርሱ ደረሱበት

"ኢዮአብ እና ወታደሮቹ እርሱ ላይ ደረሱበት"

2 Samuel 20:17

የባሪያህን ቃል አድምጥ

ሴትየዋ ራስዋን "የአንተ አገልጋይ" በማለት ትገልጻለች። ይህ በስልጣን ከፍ ካለ ሰው ጋር በትህትና መነጋገሪያ መንገድ ነው።

ያ ምክር ለነገሩ ፍጻሜ ይሰጣል

"ያ ምክር ችግሩን ይፈታል"

በእስራኤል ውስጥ እጅግ ሰላማዊ እና ትክክለኛ

ይህ ከተሞቹን ይገልጻል። "በእስራኤል እጅግ ሰላማዊ እና ትክክለኝ ከተሞች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል እናት የሆነች ከተማ

ይህ በእስራኤል አገር የዚህን ከተማ ጠቀሜታ እንደ ተከበረች እናት አድርጎ ይገልጻል። "በእስራኤል የሚኖር ሁሉ እናቱን እንደሚያከብር የሚያከብራት ከተማ" ወይም "በጣም ጠቃሚ እና እስራኤል ሁሉ የሚያከብራት ከተማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን የያህዌን ርስት ለመዋጥ ትፈልጋለህ?

እዚህ ስፍራ ሴትየዋ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመችው ለኢዮአብ ማድረግ የማይገባቸውን እንዳያደርጉ ለመጠቆም ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ ርስቱ ያደረጋትን ከተማ መደምሰስ የለባችሁም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መዋጥ

እዚህ ስፍራ ሴትየዋ ከተማይቱ የሚዋጥ ምግብ የሆነች ያህል ሰራዊቱ እንደሚደመስሳት ትገልጻለች። "መደምሰስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ርስት

እዚህ ስፍራ ከተማይቱ እንደ ያህዌ ርስት የተገለጸችው የያህዌ መሆኗን ለመጉላት ነው። "የያህዌ የሆነች ከተማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 20:20

ይህ ከእኔ ይራቅ፣ ከእኔ ይራቅ

ይህንን ሀረግ የደጋገመው ነገሩን በፍጹም የማያደርገው መሆኑን ለማጉላት ነው። "በእውነት፣ በእውነት በፍጹም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ልውጣት ወይም ልደመስሳት

ይህ የሚያመለክተው ከተማይቱን ስለ መደምሰስ ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። "ከተማችሁን ልውጣት ወይም ልደመስሳት ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

መዋጥ ወይም መደምሰስ

እነዚህ ሁለቱም ሀረጋት መደምሰስ ማለት ናቸው። በመጀመሪያው ሀረግ "መደምሰስ" የተገለጸው እንደ "መዋጥ" ተደርጎ ነው። እነዚህ በአንድነት ሊቀርቡ ይችላሉ። "ከተማይቱን ማፍረስ ወይም መደምሰስ" ወይም "መደምሰስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እጁን አነሳ

ይህ ማለት አንድን ሰው መቃወም እና መዋጋት ማለት ነው። "ተቃወመ" ወይም "በአመጸ መቃወም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ብቻ አሳልፈው እንዲሰጡ

ኢዮአብ የከተማይቱን ሰዎች ለእርሱ ሳቤዔን አሳልፈው እንዲሰጡት ጠየቀ። "ይህን ሰው ለእኛ አሳልፋችሁ ስጡን" ወይም "ይህንን ሰው ለእኛ ስጡን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከከተማይቱ እወጣለሁ

እዚህ ስፍራ "እኔ" የሚለው የሚያመለክተው ኢዮአብን እና ወታደሮቹን ጭምር ነው። "እኛ ከከተማይቱ እንወጣለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ጭንቅላቱ ተቆርጦ ይወረወራል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጭንቅላቱን እንወረውራለን/ ይጣልላችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም ሴቲቱ ወደ ህዝቡ ሁሉ በጥበብ ሄደች

ይህ ማለት ሴትየዋ በጥበብ አደረገች ደግሞም ለህዝቧ ማድረግ ያለባቸውን ተናገረች። "ከዚያም ጥበበኛዋ ሴት ለህዝቡ በሙሉ ተናገረች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ሰው ወደ የቤቱ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"እያንዳንዱ ሰው ወደ የራሱ ቤት ሄደ"
2 Samuel 20:23
አሁን
"አሁን" በዋናው ታሪክ ፍሰት ላይ አዲስ መስመር ያበጃል። ይህ አዲስ ክፍል ንጉሥ ዳዊትን ስለሚያገለግሉ ሰዎች የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)
ኢዮአብ በ... ላይ ነበረ... የዮዳሄ ልጅ በናስያ በ...ላይ ነበረ... አዶኒራም በ... ላይ ነበረ
"በ...ላይ ነበረ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው በአንድ ወገን ላይ ስልጣን ያለው መሆኑን ነው። "ኢዮአብ በ... ላይ ስልጣን ነበረው፤ የዮዳሄ ልጅ በናስያ በ... ላይ ስልጣን ነበረው፤ አዶኒራም በ...ላይ ስልጣን ነበረው" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የዳሄ... ኢዮሣፍጥ... አሒሉድ
የእነዚህን ወንዶች ስሞች በ 2 ሳሙሴል 18፡16-18 ላይ በተረጎሙት መሰረት ይተርጉሙት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሊታውያን...ፈሊታውያን
እነዚህን የሰዎች/ቡድን ወገኖች ስሞች በ 2 ሳሙሴል 18፡16-18 ላይ በተረጎሙት መሰረት ይተርጉሙት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የጉልበት ስራ እንዲሰሩ የተገደዱ ወንዶች
"ባሪያ ሰራተኞች"
አዶኒራም... ሱሳ...ዒራስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ኢያዕራውያን
ይህ የሰዎች/ቡድን ወገን ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 21
2 Samuel 21:1
የያህዌን ፊት አየ
እዚህ ስፍራ "ፊት" ለያህዌ መገኘት ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። የዚህ ትርጉም ዳዊት ስለ ድርቁ ምላሽ ለማግኘት ወደ ያህዌ ጸለየ ማለት ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በሳኦል እና በእርሱ ነብሰ ገዳይ ቤተሰብ ምክንያት
ሳኦል ብዙ ገባዖናውያንን ገድሎ ነበር፣ በመሆኑም የሳኦል ትውልድ በዚህ ኃጢአት ምክንያት ጥፋተኞች ነበሩ።
2 Samuel 21:2
አሁን
"አሁን" በዋናው ታሪክ ፍሰት ላይ አዲስ መስመር ያበጃል። ይህ አዲስ ክፍል ስለ ገባዖናውያን የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእናንተ ምን ላደርግላችሁ ይገባል? እንዴት ማስተሰረያ ቃል ኪዳን... ላደርግ እችላለሁ?
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "መልካምነቱን እና ቃል ኪዳኑን የሚወርሰውን የያህዌን ህዝብ ትባርኩ ዘንድ ይህንን ኃጢአት ለማስወገድ ምን ማድረግ እችላለሁ?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 21:4
ይህ የብር እና የወርቅ ጉዳይ አይደለም
"ችግሩን ገንዘብ አይፈታውም"
2 Samuel 21:5
"በእኛ ላይ ያሴረ"
"በእኛ ላይ ክፉ ካቀደ"
ከእርሱ ትውልድ ሰባት ወንዶች ለእኛ አሳልፋችሁ ስጡን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የአንተ ሰዎች ከእርሱ ትውልዶች ሰባት ሰዎች እንዲሰጡን አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እኛ እንሰቅላቸዋለን
"እኛ እነርሱን ሰቅለን እንገድላቸዋለን"
በሳኦል ጊብዓ
ሳኦል ከጊብዓ ከተማ ነበር።
በያህዌ የተመረጠ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ የመረጠው እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 21:7
ሜምፊቦስቴ
ሜምፊቦስቴ የዮናታን ልጅ ነበረ። በ 2 ሳሙኤል 4፡4 ላይ ይህ ስም እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ሪጽፋ... ኢዮሄል
ሪጽፋ ሴት ናት አባቷ ኢዮሄል ነበር። በ2 ሳሙኤል 3፡7 ላይ እነዚህ ስሞች እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።
ሄርሞን እና ሜምፊቦስቴ... ኤስድሪኤል... ቤርዜሊ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ ሜምፊቦስቴ የዮናታን ልጅ የሆነው ሜምፊቦስቴ አይደለም። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሜሮብ
ይህ የሴት ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
መሓላታዊያን
ይህ የሰዎች ቡድን/ የወገን ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ለገባዖናውያን አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ ስፍራ "የገባዖናውያን እጆች" የሚለው የሚወክለው የገባዖን ሰዎችን ቁጥጥር/የበላይነት ነው። "ለገባዖናውያን አሳልፎ ሰጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱም ተገደሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ገባዖናውያን እነርሱን ገደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 21:10
ሪጽፋ... ኢዮሄል
ሪጽፋ ሴት ናት አባቷ ኢዮሄል ነበር። በ2 ሳሙኤል 3፡7 ላይ እነዚህ ስሞች እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።
ይህ ለዳዊት ተነገረው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "አንድ ሰው ለዳዊት ነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 21:12
ኢያቢስ ገለዓድ
ኢያቢስ በገለዓድ አካባቢ ሚገኝ ከተማ ነው። ይህ በ2 ሳሙኤል 2፡4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
የህዝብ አደባባይ
ይህ በከተማ መግቢያ በር አጠገብ የሚገኝ ሰዎች የተለያዩ የንግድ ተግባራትን የሚያከናውኑበት ስፍራ ነው።
ቤት ሳን
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ጊልቦዓ
ይህ የቦታ ስም በ 2 ሳሙኤል 1፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
የተሰቀሉት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ገባዖናውያን በስቅላት የገደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 21:14
ጼላ
ይህ በብንያም የሚገኝ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ቂስ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ አባት
"የሳኦል አባት"
2 Samuel 21:15
ይሽቢ-ብኖብ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሶስት መቶ ሰቅል

"300 ሰቅል።" ይህ ወደ 3.4 ኪሎ ግራም የሚጠጋ ነው። (የመጽሐፍ ቅዱስ ክብደት መለኪያ እና ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የጽሩያ ልጅ አቢሳ

አቢሳ እና ጽሩያ የወንድ ስሞች ናቸው። እነዚህ ስሞች በ 2 ሳሙኤል 2፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

የእስራኤልን መብራት ማጥፋት የለብህም

"የእስራኤል መብራት" የሚለው የዳዊትን መሪነት የሚወክል እና ዳዊት ከሞተ የእስራኤል ህዝብ ግልጽ ምሪት እንደሚያጣ የሚያሳይ ዘይቤ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 21:18

ከዚህ በኋላ እንዲህ ሆነ

ይህ ሀረግ የታሪኩን አዲስ ክፈል ይጀምራል። ቋንቋችሁ ይህን ለማድረግ መንገድ ካለው፣ እዚህ ስፍራ ይህንን ለመጠቀም ትችላላችሁ።

ጎብ

ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሴቦካይ... ሳፍ... የዓሬዓርጊም ልጅ ኤልያናን... ጎልያድ

እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኩሳታዊ...ራፋማዊ... ቤተልሔማዊ... ጌታዊ

እነዚህ የሰዎች ቡድኖች/የወገኖች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ራፋይም

ይህ የህዝብ ወገን በግዙፋን ተዋጊዎቹ ይታወቅ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ጦሮቻቸው እንደ ሸማኔ መጠቅለያ ነበር

አንድ ሰው ሲሸምን የ"ሸማኔ መጠቅለያ" ተብሎ ከሚጠራ ትልቅ እንጨት ጋር በተያያዙ መቆንጠጫዎች መሃል ክሮቹን ያሳልፋል። ይህ ማለት የጎልያድ ጦር ከመደበኛው ጦር ትልቅ ነበር ማለት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 21:20

በቁጥር ሃያ አራት

"በአጠቃላይ 24 የእጅ እና የእግር ጣቶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ራፋይም

ይህ የህዝብ ወገን በግዙፋን ተዋጊዎቹ ይታወቅ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የሣማ ልጅ ዮናታን

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ሣማ የዳዊት ወንድም ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ የተገደሉት በዳዊት እና በወታደሮቹ እጅ ነበር

እዚህ ስፍራ "በ...እጅ" ማለት "አማካይነት" ወይም "በ..." ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዳዊት እና ወታደሮቹ እነርሱን ገደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

---

## Chapter 22

### 2 Samuel 22:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይጀምራል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጠላቶቹ ሁሉ እጅ፣ ደግሞም ከሳኦል እጅ

ይህ በአጠቃላይ ከሁሉም ጠላቶች ወደ አንድ የዳዊት ጠላት፣ ወደ ንጉሥ ሳኦል የሚሄድ ነው።

ከ...እጅ መዳን

ይህ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ "ከ... ሃይል መዳን" ማለት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ የእኔ አለት ነው፣ የእኔ ምሽግ

ይህ ዘይቤ የሚያሳየው ከአንድ ክፍል ከ "አለት" አጠቃላይ ወደ ሆነ ነገር ማለትም ወደ "ምሽግ" የሚደረግ ሽግግርን ነው። ምሽግ ከብዙ ትልልቅ አለቶች የሚገነባ ነው። ይህ ማለት ያህዌ የእርሱን ህዝብ ከጉዳት ለመጠበቅ ጥንካሬ አለው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

### 2 Samuel 22:3

አጠቃላይ መረጃ፡

ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር አለቴ ነው... እርሱ ጋሻዬ ነው፣ የደህንነቴ ቀንድ፣ የእኔ መሸሸጊያ

እነዚህ ዘይቤዎች በሙሉ የእግዚአብሔር ጥንካሬ እና ሃይልና ምልክቶች ናቸው። የእግዚአብሔርን ህዝቡን የመጠበቅ እና የማዳን ችሎታ ያጎላሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሊወደስ የሚገባው ማን ነው

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ውዳሴ ሊቀበል የሚገባው ማን ነው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጠላቶቼ እድናለሁ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ ከጠላቶቼ ያድነኛል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

### 2 Samuel 22:5

አጠቃላይ መረጃ፡

ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞት ማዕበል ከበበኝ፣ የጥፋት ጎርፍ ውሃ ዋጠኝ

ዳዊት ሊገድሉት የሚፈልጉትን ክፉ ሰዎች ሊውጠው ከደረሰ የጎርፍ ውሃ ጋር ያነጻጽራቸዋል። እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የዋሉትም ትኩረት ለመስጠት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የጥፋት ውሃ ጎርፍ

ይህ በመንገዱ ላይ ሚያገኘውን ሁሉ እየጠራረገ ሚያጠፋ በፍጥነት የሚወርድ የጎርፍ ውሃ ምስል ነው።

የሲኦል ገመድ ተጠመጠመብኝ፤የሞት ወጥመድ ያዘኝ

ዳዊት ስለ ሞት እና ሲኦል የሚናገረው፣ አዳኝ እንስሳን እንደሚያጠምድ ሞት እና ሲኦል እርሱን ሊያጠምዱት የሚሞክሩ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ነው። እነዚህ ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ያገለገሉትም ትኩረት ለመስጠት ነው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

### 2 Samuel 22:7

አጠቃላይ መረጃ፡

ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በጭንቀቴ

"በታላቅ መከራዬ"

ከመቅደሱ ድምጼን ሰማ

ዳዊት የሚያመለክተው ያህዌ የሚኖርበትን ሰማያዊ መቅደስ ነው። ምድራዊው መቅድ ገና አልተገነባም ነበር።

የእርዳታ ጥሪዬ ወደ ጆሮዎቹ ገባ

እዚህ ስፍራ "የእርሱ ጆሮዎች" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው ያህዌን እና ለእርዳታ የዳዊትን ጥሪ ማድመጡን ነው። "እርሱ ሊረዳኝ ልመናዬን ሰማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ጆሮዎች

ዳዊት ስለ ያህዌ ጆሮዎች እንዳሉት አድርጎ ይናገራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

### 2 Samuel 22:8

አጠቃላይ መረጃ፡

ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም ምድር ተናወጠች... በቁጣው እሳት ነደደ

ዳዊት ከጠላቶቹ ለመዳን ለእርዳታ ላሰማው ጩኸት የያህዌ ምላሽ ይህ ነው። ዳዊት የምድርን መንቀጥቀጥ እና ከያህዌ እሳት የመምጣትን ምናብ የተጠቀመው የያህድዌን አስጨናቂ ቁጣ ለማጉላት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን

ይመልከቱ)
ምድር ተናወጠች…ሰማያትም ተንቀጠቀጡ
ዳዊት ሁለቱን ጽንፎች የገለጸው በፍጥረት ውስጥ የሚገኘውን ሁሉ ለማካተት ነው። (ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ተቆጥቷል እና ተንቀጠቀጡ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የእግዚአብሔር ቁጣ አናወጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአፍንጫው…ከአፉ
ዳዊት ያህዌ እነዚህ የሰው አካሎች እንዳሉት አድርጎ ይናገራል። (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)
በቁጣው ፍም ተቀጣጠለ
እዚህ ስፍራ የያህዌ ቁጣ ከሰል እንዲቀጣጠል እና እንዲነድ የሚያደርግ ከእሳት ጋር ተወዳድሯል። "ከአፉ የሚወጣው ነበልባል እሳት ያነዳል" ወይም "እንዲሁም እርሱ የሚነድ እሳት ከአፉ ይልካል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 22:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ሰማያትን ከፈተ… በሰማያት ጥቅጥቀው ያለ የዝናብ ደመና ነበረ
ዳዊት ያህዌ እርሱን ያዳነበትን መንገድ የገለጸው በአንድ ስፍራ እንደ ተከማቸ ሀይለኛ የዝናብ ደመና ከበዙ ጠላቶች አዳነኝ በማለት ነው። ይህ የእግዚአብሔርን ሃይል እና ቁጣውንም ያጎላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከእግሮቹ ስር
ዳዊት እግአብሔር እንደ ሰው እግር እንዳለው አድርጎ ይናገራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በነፋስ ክንፎች ላይ ታየ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ በነፋስ ክንፎች ላይ ታየ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የነፋስ ክንፎች
ይህ አገላለጽ ነፋስ ወፍ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጨለማን በዙሪያው ድንኳን አደረገ
እዚህ ስፍራ ያህዌ የፈጠረው ጨለማ የተነጻጸረው እርሱን ሙሉ ለሙሉ ከሸፈነ ድንኳን ጋር ነው። "እርሱ ራሱን በጨለማ ውስጥ ሰወረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 22:13
አጠቃላይ መረጃ፡
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበው መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከፊቱ ከወጣው መብረቅ … መብረቅ ወጣ አጠፋቸውም
ዳዊት ከጠላቶቹ ሊያድነው የመጣውን፣ ከአውሎ ነፋስ ጋር የሚያነጻጽረውን ያህዌን መግለጹን ቀጥሏል። ይህ በዳዊት ጠላቶች ላይ የእግዚአብሔርን ሀይል እና ቁጣ ያጎላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከፊቱ ከወጣው መብረቅ የእሳት ነበልባል ወደቀ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ከደማቅ ብርሃኑ የሚነድ እሳት ላከ" ወይም 2) "ከእርሱ ድምቀት መብረቅ ላከ"
እጅግ ከፍ ያለው ከፍ ባለ ድምጽ ተናገረ። ቀስቶችን ወረወረ
ዳዊት አንድ ሰው እነዚህን ነገሮች እንደሚያደርግ ያህዌ ማድረጉን ይገልጻል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀስቶችን መረወረ… መብረቅ ወጣ
ዳዊት ከያህዌ አውሎ ነፋስ የሚወጣውን መብረቅ ወታደር ከሚጠቀምበት ቀስት ጋር ያነጻጽራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 22:16
አጠቃላይ መረጃ፡
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያም የባህር መንገዶች ታዩ… የአፍንጫው እስትንፋስ
ያህዌ በዳዊት ጠላቶች ላይ ሊቀጣ መነሳቱ የተነጻጸረው በውቅያኖስ ጥልቅ ክፍል እና በመሬት ላይ ነውጥ ከሚፈጥረው ሀይሉ ጋር ነው። ይህ የእርሱን ታላቅ ሀይል እና ብርቱ ቁጣ ያሳይል። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
የባህር መንገዶች ተገለጡ/ታዩ
ይህ ማለት የባህር ውሃ ስፍራቸውን ለቀው የውቅያኖስ ወለል ተገለጠ ማለት ነው።
መሰረቶች… ተራቆቱ
ዳዊት የያህዌን ቁጣ ከከምድር መናወጥ ጋር ያነጻጽራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የያህዌ ዘለፋ የምድርን መሰረቶች ገለጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 22:17
አጠቃላይ መረጃ፡
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከብዙ ውሃ አወጣኝ
ዳዊት ጠላቶቹን ሊያሰጥመው ከሚያስፈራራው የውሃ ሙላት ጋር ያነጻጽራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ከብርቱ ጠላቶቼ አዳነኝ
የዳዊት ጠላቶች ከፍ ያለ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ነበሩ። ከጠላቶቹ ሁሉ ስላዳነው እግዚአብሔርን ያመሰግናል።
2 Samuel 22:19
አጠቃላይ መረጃ፡
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል። የሚናገረውን ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በመከራዬ/ጭንቀቴ ቀን ሊቃወሙኝ በእኔ ላይ ተነሱ
"ጠላቶቼ በትልቅ ችግር በሆንኩበት ጊዜ በተቃውሞ ተነሱብኝ"
በመከራዬ ቀን
"በመከራዬ ጊዜ"
ነገር ግን ያህዌ ደጋፊዬ ነበር
"ነገር ግን ያህዌ ደገፈኝ" ወይም "ነገር ግን ያህዌ እኔን እረዳኝ"
ሰፊ ስፍራ
ይህ የሚያመለክተው አደጋ የሌለበትን እና ጠላቶቹ እርሱን ሊያጠምዱ የማይችሉበተን ስፍራ ነው።
በእጆቼ ንጽህና መጠን
እዚህ ስፍራ "የእጆቼ ንጽህና" ማለት "ጽድቅ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። "ትዕዛዛቱን ጠብቄአለሁና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 22:22
አጠቃላይ መረጃ፡
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።
የያህዌን መንገዶች ጠብቄአለሁ
እዚህ ስፍራ "የያህዌ መንገዶች" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ እርሱ የሆነ ህዝብ ማድረግ የሚፈልገውን ነገር ነው። ይህ ማለት ዳዊት ያደረገው ያህዌ ያዘዘውን ነገር ነው።
በፊቴ ነበር
ይህ ማለት ዳዊት በቀጣይነት ስለ እግዚአብሔር ትዕዛዛት/ድንጋጌዎች ያነብና ያስብ ነበር ነው።
2 Samuel 22:24
አጠቃላይ መረጃ፡
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።
ራሴን ከኃጢአት ጠብቄአለሁ
ይህ ያህዌን መበደልን አለመምረጥን ያሳያል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ዐይኖች ፊት ባለኝ ንጽህና መጠን
እዚህ ስፍራ "የእኔ ንጽህና" የሚለው ትርጉሙ "የእኔ ጽድቅ" ማለት ነው። "ምክንያቱም እርሱ ያዘዘውን ማድረጌን እርሱ ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 22:26
አጠቃላይ መረጃ፡
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።
አንተ ለጠማሞች ዘወርዋራ ነህ

እዚህ ስፍራ "ጠማማ" የሚለው የማያስደስት መሆን ወይም ተንኮለኛ ማለት ሲሆን፤ "ዘወርዋራ" ማለት መልካም እና ትክክል ከሆነው የሚርቅ ማለት ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ምን እንደሚያደርግ ያውቃል።
2 Samuel 22:28
አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።
የአንተ ዐይኖች ትዕቢተኞችን ይቃወማል
እዚህ ስፍራ "የአንተ ዐይኖች" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው ያህዌ የሚመለከተውን ነገር ነው። ይህ ማለት ያህዌ ትዕቢተኞች የሚያደርጉትን ይመለከታል ማለት ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዝቅ ታደርጋቸዋለህ
"ኩራታቸውን ታዋርዳለህ"
ያህዌ፣ አንተ ብርሃኔ ነህ። ያህዌ አንተ ጨለማዬን ታበራለህ
ይህ ዘይቤ ያህዌን ከመብራት ጋር ያነጻጽራል፤ ይህም ማለት ነገሮች ተስፋ ቢስ የሆኑ በመሰሉ ጊዜ ያህዌ ለዳዊት ብርሃን ይሰጠዋል ደግሞም እንዲመለከት ይረዳዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 22:30
አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።
በቅጥሩ ላይ መሮጥ እችላለሁ
እዚህ ስፍራ "ቅጥር" የሚለው የድንጋይ ቅጥርን ወይም አንድን የተወሰነ ወታደራዊ ቡድን/ጭፍራን ሊያመለክት ይችላል። ይህ ማለት በየትኛውም መንገድ ቢሆን እግዚአብሔር ዳዊት ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ ረድቶታል ማለት ነው።
ቅጥርን እዘላለሁ
ዳዊት የያህዌን እርዳታ አጉልቶ እየተናገረ ነው። "ከተማቸውን የከበበውን ቅጥር መውጣት እችላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
የያህዌ ቃል ንጹህ ነው
"ያህዌ የሚናገረው ሁሉ እውነት ነው"
እርሱ ጋሻ ነው
"ጋሻ" የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር የእግዚአብሔርን ህዝቡን የመጠበቅ ሀይል ያጎላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 22:32
አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።
ከያህዌ በቀር አምላክ ማን ነው፣ ደግሞስ ከአምላካችን በቀር አለት ማን ነው?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ከያህዌ በስተቀር አምላክ እንደሌለ አጉልቶ ለመናገር ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ ብቻውን አምላክ ነው። የእኛ አምላክ ብቻ አለት ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
አለት ማን ነው
ዳዊት የያህዌን ጥንካሬ እና ህዝቡን ለመጠበቅ ያለውን ችሎታ ለማጉለት ከአለት ጋር ያነጻጽረዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ነውር የሌለበተን ሰው በመንገዱ ይመራዋል
ያህዌ ነውር የሌለበትን ሰው በደህንነት ይጠብቀዋል ደግሞም እርሱን ሊጎዳ የሚችለውን ማናቸውንም ነገር ከመንገዱ ያስወግድለታል።
2 Samuel 22:34
አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።
እግሮቼን እንደ አጋዘን ፈጣን አድርጓቸዋል፤ ደግሞም እኔን በኮረብቶች ከፍታ ላይ አቁሞኛል
እዚህ ስፍራ የዳዊት እግሮች ግነትን በመጠቀም ከአጋዘን ጋር ተነጻጽረዋል። ያህዌ ለዳዊት በፍጥነት የመንቀሳቀስ ጥንካሬን፤ ደግሞም ለጥበቃ እና እረፍት አስተማማኝ ስፍራን ሰጥቶታል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ኩሸት እንዲሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
የእኔ እጆች...እና የእኔ እግሮች
እነዚህ ሁለቱም ዳዊትን የሚመለከቱ ናቸው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
የነሐስ ቀስትን ለማጠፍ
ከብረት የተሰራ ቀስትን መጠቀም የሚችለው በጣም ጠንካራ ሰው ብቻ ነው።
2 Samuel 22:36
አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።
የደህንነትህ ጋሻ
ዳዊት የያህዌ እርሱን የሚጠብቅበትን ሀይል አንድን ወታደር ከጠላቶቹ ከሚጠብቀው ጋሻ ጋር ያነጻጽራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ሞገስ
እግዚአብሔር የዳዊትን ጸሎት መልሷል፣ ደግሞም በረከትንና በጠላቶቹ ላይ ስኬትን ሰጥቶታል።
ለእግሮቼ ሰፊ ስፍራ አዘጋጅተህልኛል
ያህዌ ዳዊትን ጠላቶቹ ሊያጠምዱት በማይችሉበት አስተማማኝ ስፍራ አኑሮታል። እዚህ ስፍራ ተጠብቆ የመቆም ችሎታውን ለማጉላት ራሱን የገለጸው በእርሱ "እግሮች" ነው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 22:38
አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።
ጠላቶቼን አሳድዳቸዋለሁ
"ጠላቶቼን አባርራቸዋለሁ"
እርሱን አጠፋኋቸው/በላኋቸው ደግሞም አዋረድኳቸው
እዚህ ስፍራ ዳዊት ራሱን ከዱር እንስሳ ጋር ያነጻጽራል። "የዱር እንስሳ ያደነውን እንደሚበላ ሙሉ ለሙሉ አጠፋኋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከእግሮቼ በታች
እዚህ ሰፍራ "እግር" የሚለው የሚያመለክተው በጠላቶቹ ላይ ያለውን የድል ሀይል እና የበላይነት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 22:40
አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።
ለጦርነት እንደሚታጠቁት ቀበቶ በላዬ ጥንካሬን አደረግህ
እዚህ ሰፍራ ያህዌ የሰጠው ጥንካሬ የተነጻጸረው ዳዊት ታላላቅ ነገሮችን እንዲያደርግ ከሚረዳው የጦር ሜዳ ቀበቶ ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በላዬ የሚነሱብኝን ከበታቼ ጣልካቸው
"ተቃውመው የሚዋጉኝን እንዳሸንፋቸው ረዳኸኝ"
የጠላቶቼን ጀርባ ሰጠኸኝ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ዳዊት ጠላቶቹ ሲሸሹ ጀርባቸውን ይመለከት ነበር ወይም 2) ዳዊት ጠላቶቹን ካሸነፈ በኋላ እግሮቹን በጠላቶቹ አንገት ላይ ያደርግ ነበር
ድምጥማጣቸውን አጠፋኋቸው
"ሙሉ ለሙሉ አጠፋኋቸው"
2 Samuel 22:42
አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።
እነርሱ ጮኹ
"ጠላቶቼ ጮኹ"
ወደ ያህዌ ጮኹ፣ እርሱ ግን አልመለሰላቸውም
ያህዌ ፍርድ የሚሰጥበት ጊዜ ደረሰባቸው።
እንደ ምድር ትቢያ... እንደ መንገድ ጭቃ
ይህ ዳዊት ጠላቶቹን ሙሉ ለሙሉ አጠፋቸው ማለት ነው። "እንደ ምድር ትቢያ" እና "እንደ መንገድ ጭቃ" የሚሉት እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የማሉትም ትኩረት ለመስጠት/ሃሳቡን ለማጉላት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 22:44
አጠቃላይ መረጃ:
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከራሴ ህዝብ ከተነሳብኝ ክርክር
ይህ የሚያመለክተው ከእስራኤላውያን መሃል በንጉሥ ዳዊት ላይ ያመጹበትን ነው።
አንተ የህዝብ መሪ አደረግኸኝ
"አንተ በህዝብ ላይ መሪ አድርገኸ ሾምከኝ።" እዚህ ስፍራ "ህዝቦች" የሚለው የሚያመለክተው ከእስራኤል ህዝብ በተጨማሪ ሌላውን ህዝብ ነው።
የማላውቀው ሌላ ህዝብ
"ባዕዳን/የውጭ ሰዎች"
ባዕዳን ሊሰግዱልኝ ተገደዱ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በዕዳን ወድቀው ሰገዱልኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 22:47
አለቴ የተመሰገነ ይሁን። አምላኬ ከፍ ይበል
እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው የዋሉትም ትኩረት ለመስጠት/ለማጉላት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሁሉም ሰው አለቴን ያወድሰው/ያመስግነው። እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ ያድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
የእኔ አለት...አለቱ
ዳዊት ያህዌን ከአለት ጋር የሚያነጻጽረው ህዝቡን ለመጠበቅ ያለውን ሀይል ለማጉላት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ህዝብን ከስሬ የሚያስገዛልኝ
"ባዕድ ህዝብን ከበታቼ የሚያስገዛልኝ"
ከተነሱብኝ በላይ ከፍ ከፍ አደረግከኝ
"ከጠላቶቼ አዳንከኝ ክብርንም ሰጠኸኝ"
ከአመጸኞች ሰዎች
"ለጎዱኝ ከሚፈልጉ"
2 Samuel 22:50
አጠቃላይ መረጃ፡
ዳዊት ለያህዌ የሚያቀርበውን መዝሙር ይቀጥላል።
ለስምህ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው የያህዌን ታላቅነት/ክብር ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ለቀባው የቃል ኪዳኑን ታማኝነት አሳየ
እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚያመለክተው ያህዌ በ2 ሳሙኤል 7፡8 ላይ የገባውን ቃል ኪዳን ሊሆን ይችላል።

---

Chapter 23
2 Samuel 23:1
አሁን
ይህ የመጽሐፉን አዲስ ክፍል ጅማሬ ያሳያል።
እነዚህ የመጨረሻ ቃላት ናቸው
ይህ የሚያመለክተው ዳዊት በ2 ሳሙኤል 23፡2-7 የሚናገረውን ነው።
እጅግ የተከበረው ሰው፣ በያቆብ አምላክ የተቀባው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የያዕቆብ አምላክ እጅግ ያከበረው እና የቀባው ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በያዕቆብ አምላክ የተቀባው
መቀባት የሚካሄደው በሰውየው ራስ ላይ ዘይት በማፍሰስ ነበር። ይህ ይደረግ የነበረው እንደ ንጉሥ ወይም ካህን ሆኖ እግዚአብሔርን የሚያገለግልን ሰው ለመምረጥ ነበር። (ተምሳሌታዊ/ምልክታዊ ድርጊታዊ የሚለውን ይመልከቱ)
መዝሙረኛው
ይህ መዝሙረ ዳዊትን ወይም መዝሙሮችን የጻፈው ሰው ነው።
በእኔ
በዳዊት
የእርሱ ቃል እንደበቴ ላይ ነበር
እዚህ ስፍራ "በአንደበቴ ላይ" የሚለው ለዳዊት ንግግር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እርሱ የምናገረውን መልዕክት ሰጠኝ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 23:3
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ቀጣይ የዳዊት ማጠቃለያ ቃል ነው።
የእስራኤል አምላክ፣ የእስራኤል አለት፣ ይናገራል... እኔ
እዚህ ስፍራ "የእስራኤል አምላክ" የሚለው "የእስራኤል አለት" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለቱ ሀረጋት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ። ዳዊት እግዚአብሔርን ከአለት ጋር የሚያነጻጽረው እርሱ ህዝቡን ለመጠበቅ ያለውን ሀይል ለማጉላት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን በመፍራት የሚመራ፣ በሰዎች ላይ በጽድቅ የሚገዛ
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ንጉሡ እግዚአብሔርን እንደሚያከብር እና እግዚአብሔር እርሱ እንዲያደርግ የሚፈልገውን እንደሚያደርግ ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር ፍርሃት /እግዚአብሔርን በመፍራት
"እግዚአብሔርን መፍራት/ማክበር"
እርሱ እንደ ማለዳ ብርሃን ይሆናል... ከዝናብ በኋላ እንደሚወጣ ፀሐይ
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ንጉሡን ከማለዳ ብርሃን እና ከዝናብ በኋላ ከሚወጣ ዝናብ ጋር ያነጻጽረዋል። እነዚህ ይህ ንጉሥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ እና ለህዝቡ መባረክ ምክንያት መሆኑን የሚገልጹ መንገዶች ናቸው። "እርሱ ለሁሉም ደስታ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤያዊ የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 23:5
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ቀጣይ የዳዊት ማጠቃለያ ቃል ነው።
በውኑ የእኔ ቤት በያህዌ ፊት እንደዚህ አይደለምን?
እዚህ ስፍራ ላይ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር መስማማቱን ይናገራል። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "የእኔ ቤት በውኑ በእግዚአብሔር ፊት እንዲሁ አይደለምን!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ... መንገድ አላበጀምን?
ዳዊት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን እንዳደረገ እውቅና ይሰጣል። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ በእርግጥ... መንገድ ያበጃል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ስርአት ያለው እና እርግጠኛ
ይህ ማለት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በዳዊት ቤት የታመነ፣ በሚገባ የተቀናጀ እና የማይለወጥ ነው።
እርሱ ደህንነቴን፣ መሻቴን... ፍጹም አላደረገምን?
ዳዊት ሁልጊዜም እግዚአብሔር እንደሚረዳው እና እንደሚያበለጽገው ያምናል። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ ደህንነቴን ፍጹም ያደርጋል ደግሞም መሻቴን ሁሉ ይሰጠኛል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 23:6
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ቀጣይ የዳዊት ማጠቃለያ ቃል ነው።
ረብ የለሾች እንዳች እንደማይጠቅም እንደሚጣል እሾክ ይሆናሉ
እዚህ ስፍራ ክፉ ሰው ጥቅም ከሌለው እሾህ ጋር ተነጻጽሯል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ክፉ ሰው እንደምንጥለው እሾህ እርባና ቢስ እና አደገኛ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ምክንያቱም እነዚህ በሰው እጅ ሊሰበሰቡ አይችሉም
"ምክንያቱም ማንም ሰው ሳይጎዳው እሾህን በእጁ መልቀም አይችልም"
ባሉበት ሊቃሉ ይገባል
"እሾህ በተገኘበት በዚያው ስፍራ ሊቃጠል ይገባዋል።" ይህ እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ያጠፋቸዋል ማለት ነው።
2 Samuel 23:8
ዮሴብ
ይህ የወንድ ስም ነው። ሌሎች ቅጂዎች ዮሴብ በሴትቤት፣ ያሾብዓም፣ ኢሽባል፣

ወይም ኢያቡስቴ ይላሉ፤ ምክንያቱም የተለያዩ ጥንታዊ ቅጂዎች እነዚህ ልዩነቶች አሏቸው። ተርጓሚዎች በትርጉም ስራዎቻቸው በግርጌ ማስታወሻዎች ይህንን ማለት ሊመርጡ ይችላሉ (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሃቻሞንቲ
ይህ የህዝብ ወገን/ ቡድን ስም ነው። "የሃቻሞን ልጅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ስምንት መቶ
"800" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 23:9
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ የዳዊትን ታላላቅ ወታደሮች ዝርዝር ማቅረቡን ይቀጥላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰራዊቱ ከኤልዔዘር በኋላ ተመለሰ
ይህ ማለት ሰራዊቱ አልአዛር ከጦርነት ከተመለሰ በኋላ ተመለሰ። "የእስራኤል ሰራዊት አልዔዘር ጦርነቱን ካሸነፈ በኋላ ወደ ጦር ሜዳው ተመለሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሞቱት ለመግፈፍ ብቻ
"ከጠላቶቻቸው በድን ላይ የሚፈልጉትን ለመግፈፍ ብቻ"
2 Samuel 23:11
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ የዳዊትን ታላላቅ ወታደሮች ዝርዝር ማቅረቡን ይቀጥላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የምስር እርሻ
" ምስር የተዘራበት እርሻ"
ምስር
እንደ አተር ያለ ለምግብ የሚሆን ጠፍየፍ ያለ ፍሬ (የማይታወቀውን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)
ሰራዊቱ ሸሸ
"የእስራኤል ሰራዊት ሸሸ"
2 Samuel 23:13
ከሰላሳዎቹ ውስጥ ሶስቱ
እነዚህ በ 2ሳሙኤል 23:8-12 ውስጥ የተጠቀሱት እንዚያው ሶስቱ ወታደሮች አይደሉም
ሰላሳዎቹ
"30ዎቹ" ወይም "ሰላሳዎቹ የእስራኤል ጀግና ወታደሮች።" የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
የዓዶላም ዋሻ
"ዓዶላም ከተማ አቅራቢያ የሚገኝ ዋሻ።" ዓዶላም የሚገኘው ቤተልሔም አጠገብ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የራፋይም ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው። ይህ በ2 ሳሙኤል 5፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
በጠንካራ ይዞታው/በምሽጉ
"በተጠበቀ ቦታው"
ፍልስጥኤማውያን በቤተልሔም ይገኙ ነበር
"ጥቂት ፍልስጥኤማውያን ወታደሮች የቤተልሔምን መንደር ተቆጣጥረው ነበር"
2 Samuel 23:15
ሰራዊቱን ሰብረው
"በጠላት ሰራዊት በኩል እየተዋጉ"
ህይወታቸውን ለአደጋ አሳልፈው የሰጡትን ወታደሮች ደም እጠጣለሁን?
ዳዊት ውሃውን ከደም ጋር ያነጻጸረበት ምክንያት ወታደሮቹ ውሃውን ለእርሱ ለማምጣት ህይወታቸውን ለአደጋ አጋልጠው ስለ ነበረ ነው። ጥያቄውን የተጠቀመበት ይህን ለማጉላት ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ይህንን ውሃ መጠጣት ውሃወን ለእኔ ለማምጣት ህይወታቸውን በአደጋ ላይ የጣሉትን ወታደሮች ደም እንደ መጠጣት ነው" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 23:18
አቢሳ... ጽሩያም
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። በ2 ሳሙኤል 2፡18 ላይ በተተረጎመው መሰረት ይተርጎሙ።
በሶስቱ ላይ አለቃ
ይህ ማለት ሄደው ለዳዊት ውሃ ካመጡት ውስጥ አቢሳ የሶስቱ መሪ ነበር።
ሶስት መቶ ወንዶች
"300 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልቱ)
እርሱ ብዙ ጊዜ ከሶስቱ ወታደሮች ጋር ይጠቀስ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ብዙውን ጊዜ ስለ ሶስቱ የጀግኖች ጀግና ሲናገሩ እርሱን ይጠቅሱታል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ከሶቱ እንኳን ይበልጥ ታዋቂ አልነበረምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው እርሱ ምን ያህል ታዋቂ እንደነበረ ለማጉላት ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ ከሶቱ አንኳን ይበልጥ ታዋቂ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ይበልጥ የታወቁ ሶስት ወታደሮች
ይህ የሚያመለክተው ዮሴብ በሴትቤትን፣ ኤልዔዘርን፣ እና ሻማህን ነው። አቢሳ እንደነዚህ ሶስት ወታደሮች ዝነኛ አልነበረም።
2 Samuel 23:20
ቀብጽኤል
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ዮዳሄ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህ በ2 ሳሙኤል 8፡18 እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
አሬል
ይህ የወንድ ስም ነው።
2 Samuel 23:22
ይህን ጀብዱ ፈጽም
"ይህን ታላቅ ስራ አከናውን"
ከሶስቱ ታላላቅ ሰዎች ጋር ስሙ የተጠራ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ሶስቱን ታላላቅ ሰዎች እንደሚያመሰግኑ እርሱንም ያመሰግኑታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በአጠቃላይ ሰላሳዎቹ ወታደሮች ከሚታዩት ይልቅ እርሱ ይበልጥ የከበረ ነበር፤ ሆኖም ግን የሶስቱን ታላላቅ ሰዎች ያህል ከፍ ብሎ አይታይም ነበር።
"ከሶስቱ እጅግ ምርጥ ወታደሮች በስተቀር፤ ከሌሎቹ 30 ወታደሮች ይበልጥ ዝነኛ ነበር። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ሶስቱ ታላላቅ ወታደሮች
ይህ የሚያመለክተው ዮሴብ በሴትቤት፣ ኤልዔዘርን እን ሻማህን ነው።
የእርሱ ጠባቂ / የክብር ዘብ
ዳዊትን የሚጠብቁ ወታደሮች ቡድን
2 Samuel 23:24
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ የዳዊት ታላላቅ ወታደሮች ዝርዝር ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰላሳዎቹ
"በጣም ዝነኞቹ 30 ወታደሮች" (ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
2 Samuel 23:29
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ የዳዊት ታላላቅ ወታደሮች ዝርዝር ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 23:33
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ የዳዊት ታላላቅ ወታደሮች ዝርዝር ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
2 Samuel 23:37
አጠቃላይ መረጃ፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ የዳዊትን ታላላቅ ወታደሮች ዝርዝር ያጠቃልላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠቅላላው ሰላሳ ሰባት ነበሩ
"በጠቅላላው 37 ነበሩ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 24

2 Samuel 24:1

የያህዌ ቁጣ በእስራኤል ላይ ነድዶ ነበር

"ነደደ" የሚለው ቃል እሳት ጀመረ ማለት ነው። እዚህ ስፍራ የያህዌ ቁጣ የተነጻጸረው ከእሳት ጋር ነው። "የያህዌ ቁጣ እንደ እሳት መንደድ ጀመረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዳዊትን በእነርሱ ላይ አንቀሳቀሰ

"ዳዊት እነርሱን እንዲቃወም አደረገ"

ሂዱ፣ እስራኤልን እና ይሁዳን ቁጠሩ

በሙሴ ህግ፣ እግዚአብሔር የእስራኤል ነገሥታትን ተዋጊዎችን/ወታደሮችን እንዳይቆጥሩ ከልክሏል። የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዳን እስከ ቤርሳቤህ

ይህ ሀረግ የሁለት ቦታዎችን ስም ይዟል፤ ዳን በሩቅ ሰሜን፣ እና ቤርሳቤህ በሩቅ ደቡብ አጠቃላዩን አገሪቱን ለመወከል ተጠቅሰዋል። (ጽንፎች የሚለውን ይመልከቱ)

ለጦርነት የበቃውን/የሚሆን…ሁሉንም ህዝብ ቁጠሩ

ይህ በጣም ወጣት፣ ወይም በጣም ሽማግሌ፣ ወይም ለመዋጋት አካላቸው ብቁ ካልሆኑት በስተቀር ሌሎችን ወንዶች መቁጠር ማለት ነው።

2 Samuel 24:3

መቶ ጊዜ…ይብዛ

ይህ ማለት "አሁን ያለው እያንዳንዱ ሰው 100 እጥፍ ቢሆን።" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሡ ቃል ኢዮአብን አሸነፈ

x

2 Samuel 24:5

እነርሱ ተሻገሩ

"ኢዮአብ እና የሰራዊቱ አዛዦች ተሻገሩ"

አሮኤር

ከአርኖር ወንዝ ዳርቻ በስተ ሰሜን የሚገኝ ከተማ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያዜር

ይህ በጋድ ውስጥ የሚገኝ ከተማ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ተባሶን አዳሰይ

ይህ በሔቲ ህዝቦች ምድር የቃዴስ ከተማን ሊያመለክት ይቻላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 24:8

እነርሱ ሄዱ

"ኢዮአብ እና የጦር አዛዦቹ ሄዱ"

ዘጠኝ ወር ከ ሃያ ቀን

"9 ወር ከ 20 ቀን" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም ኢዮአብ የተቆጠሩተን የተዋጊ ወታደሮች አጠቃላይ ቁጥር ለንጉሡ አሳወቀ

"ከዚያ ኢዮአብ ለጦርነት ዝግጁ የሆኑ ወንዶችን ቁጥር ለንጉሡ ተናገረ"

በእስራኤል

ይህ የሚያመለክተው የሰሜን እስራኤል ነገድን ነው

800,000 …. 500,000

"ስምንት መቶ ሺህ… አምስት መቶ ሺህ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ መምዘዝ የሚችሉ

ይህ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው በሰራዊቱ ለውጊያ ብቁ የሆኑ ወንዶችን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከይሁዳ

ይህ የሚያመለክተው የይሁዳን ደቡባዊ ነገድ ነው።

2 Samuel 24:10

ዳዊት ልቡ አዘነ

እዚህ ስፍራ "ልብ" የዳዊትን ስሜት እና ህሊና ሁኔታ ለመግለጽ የዋለ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ዳዊት ተጸጸተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እንግዲህ፣ ያህዌ የአገልጋዮን በደል ይቅር ይበል

ዳዊት "የአገልጋዩን" ሲል የሚገልጸው ራሱን ነው። ይህ ስልጣን ያለውን ለማክበር የትህትና አገላለጽ ነው።

2 Samuel 24:11

የያህዌ ቃል ለዳዊት መልዕክት ወደሚያመጣለት ወደ ነቢዩ ጋድ መጣ፣ " ሂድ

"የያህዌ ቃል ወደ…መጣ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔር ልዩ መልእክትን ለማምጣት ነው። ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በ2 ሳሙኤል 7:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለዳዊት መልዕክት ለሚያመጣለት ለነቢዩ ጋድ መልእክት ሰጠው። እንዲህም አለው፣ 'ሂድ' ወይም "ያህዌ ለዳዊት መልዕክት ለሚያመጣለት ለነብዩ ጋድ 'ሂድ' የሚል መልዕክት ተናገረው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የዳዊት መልዕክት አምጪ/ባለ ራዕይ

ይህ ማለት ጋድ በንጉሣዊ ቤተ መንግስት በግልጽ የሚታወቅ ነቢይ ነበር።

2 Samuel 24:13

በትልቅ ችግር ውስጥ ነኝ

"እጅግ አስጨናቂ በሆነ ችግር ውስጥ ነኝ"

በሰው እጅ ከመውደቅ በያህዌ እጅ ላይ እንውደቅ

እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚያመለክተው ሀይልን ወይም የማድረግ አቅምን ነው። "ያህዌ እንጂ ሰው አይቅጣን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 24:15

የተወሰነ ጊዜ

ይህ እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ለማቆም የወሰነበት ጊዜ ነው።

ሰባ ሺህ

"70,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዳን እስከ ቤርሳቤህ

እዚህ ስፍራ በሰሜን ጫፍ የሚገኘው ዳን እና በደቡብ ጫፍ የሚገኘውን በርሳቤ መጠቀሱ መላው የእስራኤል አገር መጠቀሱ ነው። (ጽንፎች የሚለውን ይመልከቱ)

መልአኩ ኢየሩሳሌምን ሊያጠፋት እጆቹን ዘርግቶ ደረሰ

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የመልአኩን ሀይል ለመግለጽ የዋለ ነው። "መልአኩ በኢየሩሳሌ የሚኖሩ ሰዎችን ሊያጠፋ ተቃርቦ ነበር" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ከደረሰው ጥፋት የተነሳ ምህረት አደረገ

ይህ ማለት ያህዌ መልአኩ ሊያደርስ ያለውን ክፉ ነገር አስቆመ። "ያህዌ ስለ ደረሰው ጥፋት አዘነ"

እጅህን መልስ

"እጅ" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚገልጸው የመልአኩን ሀይል ነው። "ከዚህ በላይ ጉዳት አታድርስባቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ኦርና

ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዐውድማ

ዐውድማ ፍሬውን ከገለባ ለመለየት የተዘጋጀ ለጥ ያለ ወለል

2 Samuel 24:17

በድያለሁ፣ ማድረግ ከሚገባኝ የተገላቢጦሹን አድርጊያለሁ

እነዚህ ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ተያይዘው የቀረቡት ለሀሳቡ ትኩረት ለመስጠት ነው። "እጅግ በድያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ በጎች ግን ምን አደረጉ?

ዳዊት ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እና ህዝቡን ከበጎች ጋር ያነጻጸረው እነርሱ ምንም እንዳላጠፉ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እነዚህ ተራ ዜጎች ምንም ጥፋት አልፈጸሙም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እባክህ የአንተ እጅ ይቅጣኝ/በአንተ እጅ ልውደቅ

x

2 Samuel 24:18

ፊቱን ወደ ምድር ዝቅ አድርጎ ለንጉሡ ሰገደ

ለንጉሡ ጥልቅ አክብሮት እና ክብር እያሳየ ነበር። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

2 Samuel 24:21

መቅሰፍቱ ከህዝቡ ይወገድ ዘንድ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ ይህንን መቅሰፍት ከህዝቡ ያስወግድ ዘንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ዐይን/በአንተ እይታ መልካም የሆነውን

እዚህ ስፍራ ማየት የሚለው የሚገልጸው ፍርድን ወይም ሚዛን ነው። "አንተ መልካም ነው የምትለውን" ወይም "በአንተ ሚዛን መልካም የሆነውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የመውቂያ ዕቃ

ፍሬ ከገለባ የሚለይበት

2 Samuel 24:24

ዋጋ ያልከፈልኩበትን… አላቀርብም

ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "የምሰዋው … ዋጋ ያወጣሁበትን ነገር ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ድርብ አሉታ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃምሳ ሰቅል

"50 ሰቅል" (ቁጥሮች እና መጽሐፍ ቅዱሳ ገንዘብ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ምድሪቱ

"ምድር" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚወክለው የእስራኤልን ሰዎች ነው። "በእስራኤል ህዝብ ስም/ የእስራኤልን ህዝብ ወክሎ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከእስራኤል ላይ መቅሰፍቱ ተከለከለ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ይወርድ የነበረውን መቅሰፍት ከለከለ" ወይም "እግዚአብሔር ከእስራኤል መቅሰፍቱን አራቀ/ከለከለ"

---

Chapter 1

1 Kings 1:1

ልብስም ደረቡለት

እንዲሞቀውም ለንጉስ ዳዊት ብዙ ልብስ ደረቡለት

ሸመገለ እድሜው በዛ

“በጣም ያረጀ” ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የተጣመሩትም አፅንኦት ለመስጠት ነው።

1 Kings 1:3

ፈለጉ

“የንጉሡም አገልጋዮች ፈለጉ”

በእስራኤልም አገር ሁሉ

ይህ በጥቅሉ ነው። ተርጓሚ “በእስራኤል ምድር ሁሉ”

አቢሳ

ይህ የሴት ስም ነው

ሱናማይት

ከ ሱናም ከተማ የሆነ ግለሰብ

ንጉሡ

“ንጉሥ ዳዊት”

1 Kings 1:5

የአጊትም ልጅ አዶንያስ

አጊት የዳዊት ሚስት ነበረች

እሆናለሁ ብሎ ተነሳ

“መኩራራት ጀመረ”

ፈረሰኞች

እነዚህ በፈረስ የሚጎተት ሰረገላ የሚነዱ( የሚጋልቡ) ናቸው።

በፊቱም የሚሮጡ ሃምሳ ሰዎች

እነዚህ ሰዎች መንገድ ለመጥረግና (ለማቅናትና) ለጥበቃ ከሰረገሎች ፊት የሚሄዱ ናቸው።

------------ብሎ አልተቆጣውም

“አልተቆጣውም”። “ጠይቆትም አያውቅም” ወይም “ሊያናድደውም አልፈለገምና አልጠየቀውምም”

እንዲህ ለምን ታደርጋለህ?

ይህ አባት ልጁን ለመገሠፅ የሚሆን የግነት ጥያቄ ነው። ተርጓሚ “የሠራኸው ሥህተት እንደሆነ ማወቅ አለብህ።” (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

ከአቤሴሎም በኋላ ተወልዶ ነበር

ዳዊት የሁለቱም የአቤሴሎምና የአደንያስ አባት ሲሆን ነገር ግን በእናት ይለያያሉ። አቤሴሎም ተወለደ ከዚያም አዶኒያስ

1 Kings 1:7

ሴራውም........ከኢዮአብ ጋር ነበር

“አዶኒያስ እቅዱን ከኢዮአብ ጋር ተማከረ”

እዮአብ.......ፅሩያ.....አብያታ.......አዶንያስ......ሳዶቅ.....በናያስ....የዳሄ.....ናታን ....ሳሚ....ሬሰ

እነዚህ የሰዎች (ወንዶች) ሥም ናቸው

አዶንያስን ተከትለው ይረዱት ነበር

“አዶንስን ደገፉትም ረዱትም” ወይም “ለመርዳት ቃል ገቡና አዳንያስን ረዱት”

1 Kings 1:9

ፍሪዳዎች

“እንዲሠቡ ብዙ ቀለብ የተሠጣቸው ወይፈኖች” ወይም “ለመሥዋትነት የተዘጋጁ የተለዩ ጥጆዎች”

በዞሔሌት ድንጋይ

ይህ በእየሩሳሌም አቅራቢያ የሚገኝ አለታማ ሥፍራ ነው።

ዓይንሮጌል

ይህ ሰዎች ውሃ የሚያገኙበት የምንጭ ሥም ነው።

ወንድሞቹን ሁሉ ......ሰዎች ሁሉ

ይህ ጥቅል (በአንድ ላይ) ነው።

ወንድሞቹ ሁሉ...የንጉሥንም ልጆች

እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ሠዎችን ይገልፃሉ።

የንጉሥንም በሪያዎች የይሁዳ ሰዎች

እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ሠዎችን ይገልፃሉ።

1 Kings 1:11

አልሰማሽም?

የዚህ ጥያቄ አላማ ናታን ለቤርሳቤህ ሊነግራት የፈለገውን መረጃ መግቢያ ነው። ተርጓሚ “የሰማሽ አትመስይም” ወይም “ሰምተሻል?” (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

የአጊት ልጅ አዶንያስ እንደነገሠ

“የአጊት ልጅ አዶንያስ ንጉሥ ለመሆን እየሞከረ መሆኑን”

አጊት

የአዶንያስ እናት የዳዊት ሚስት

1 Kings 1:13

አጠቃላይ መረጃ

ነብዩ ናታን ለቤርሳቤህ መናገሩን ቀጥሎአል

ለባሪያህ ........በዙፋኔም .....አልማልህልኝምን?

የዚህ ጥያቄ አላማ ዳዊት ለቤርሳቤህ ቃል የገባውን ለማስታወስ ነው። ተርጓሚ “ለባሪያህ በዙፋኔ ምለሀል”

ለባሪያህ

ለዳዊት ያላትን ከበሬታ ለማሣየት ቤርሣቤህ ልክ እንደሌላ ሠው ሆና ዳዊትን ታናግራዋለች ተርጓሚ “ለእኔ ለባሪያህ”

በዙፋኔም ይቀመጣል

በዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ ለመሆን ዘይቤአዊ ንግግር ነው። (ዘይቤአዊ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተመልከት)
ስለ ምንስ አዶንያስ ይነግሣል?
ዳዊት አትኩሮት እንዲሠጥ ቤርሣቤህ ጥያቄ መጠቀሟ ነው፡፡ ተርጓሚ “ስለዚህ አዶንያስ መንገስ የለበትም”
ቃልሽንም አፀናለሁ
“የተናገርሽው እውነት መሆኑን ንገሪው”
1 Kings 1:15
ወደ ንጉሡ ወደ እልፍኝ
“ንጉሡ ወደ ተኛበት ክፍል
ሱናማይቱም አቢሳ
ይህቺ እንድትንከባከበው ያሳደጋት ወጣት ልጃ-ገረድ የንጉሥ ዳዊት አገልጋይ ነች፡፡ የ1 ነገሥት 1:3 ትርጉም ተመልከት
አጎንብሳ ለንጉሡ እጅ ነሣች
በንጉሡ ፊት ዝቅ ብላ ወደ መሬት አጎነበሰች
ምን ትፈልጊያለሽ?
“ምን ላደርግልሽ እችላለሁ?
ምለህለኛል
“አንተ ራስህ ምለህልኛል”
ለባሪያህ
ለዳዊት ያላትን ከበሬታ ለማሣየት ቤርሣቤህ ልክ እንደሌላ ሰው ሆና ዳዊትን ታናግረዋለች ተርጓሚ “እኔ ባሪያህ”
እግዚአብሔር (ያህዌ)
ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ለህዝቡ የተገለጠበት ስም ነው፡፡
በዙፋኔም ይቀመጣል
በዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ የመሆን ዘይቤአዊ ንግግር ነው፡፡ የ1 ነገሥት 1:3 ትርጉምን ተመልከት፡፡ ተርጓሚ “ልክ እኔ እንደነበርኩ ንጉሥ ይሆናል”፡፡
1 Kings 1:18
አጠቃላይ መረጃ
ቤርሣቤህ ለንጉሥ ዳዊት መናገርዋን ቀጥላለች
እነሆ
“ተመልከት” ወይም “አድምጥ” ወይም “ለምነግርህ ነገር ትኩረት ስጥ”
ብዙ በሬዎች፤ ፍሪዳዎች ፤ በጎችንም
“ብዙ በሬዎች፤ፍሪዳዎችና በጎች”
1 Kings 1:20
አጠቃላይ መረጃ
ቤርሣቤህ ለንጉሥ ዳዊት መናገርዋን ቀጥላለች
የእስራኤል አይን ሁሉ ይመለከትሃል
እዚህ ጋር “አይን” ህዝቡን ይገልፃል፡፡ እዚህ ጋር “አይን ሁሉ ይመለከትሃል” ፈሊጣዊ ሲሆን ህዝብ በጉጉት ይጠብቁሃል ለማለት ነው፡፡ ተርጓሚ “የእስራኤል ህዝብ ሁሉ በጉጉት ይጠብቁሃል”
ዙፋን ላይ የሚቀመጠውን
ዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ የመሆን ዘይቤአዊ ንግግር ነው፡፡ የ1 ነገሥት 1:3 ትርጉም ተመልከት ተርጓሚ “ንጉሥ ይሆናል”
ጌታዬ ከአባቶችህ ጋር ባንቀላፋህ ጊዜ
ለዳዊት ያላትን ከበሬታ ለማሣየት ቤርሣቤህ ልክ እንደሌላ ሠው ሆና ዳዊትን ታናግረዋለች፡፡ ተርጓሚ “ከአባቶችህ ጋር ስታንቀላፋ”
ከአባቶችህ ጋር ባንቀላፋህ
ይህ “ሞት” በትህትና ሲገለፅ ነው፡፡
እኔና ልጄ ሰለሞን እንደ ኃጥአተኞች እንቆጠራለን
ይህ በገቢር መልኩ ሊገለፅ ይችላል፡፡ ተርጓሚ አዲሱ ንጉሥ ልጄ ሰለሞንና እኔን እንደ ኃጢአተኛ ይቆጥረናል፡፡
1 Kings 1:22
አጠቃላይ መረጃ
ነብዩ ናታን ለንጉሥ ዳዊት ተናገረ
በግምባሩ...... ተደፍቶ
“በጣም አጎንብሶ”
1 Kings 1:24
አጠቃላይ መረጃ
ነብዩ ናታን ለንጉሥ ዳዊት መናገሩን ቀጥሏል፡፡
ከእኔ በኋላ አዶኒያስ ይነግሣል በዙፋኔም ላይ ይቀመጣል ብለሃልን?
ይህ በተዘዋዋሪ (ቀጥተኛ ባልሆነ) ጥቅስ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚ ከአንተ በኋላ አዶኒያስ እንደሚነግሥ በዙፋንህም ላይም እንደሚቀመጥ ተናግረሃልን?
በዙፋኔም ላይ ይቀመጣል
ዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ የመሆን ዘይቤአዊ ንግግር ነው፡፡ የመክብበ 1 1:13 ትርጉምን ተመልከት፡፡ ተርጓሚ “እርሱም እንደኔ ንጉስ ይሆናል፡፡
በፊቱ እየበሉና እየጠጡ
ምናልባት አዶኒያስ በጋበዛቸው ሰዎች ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ ሲመገቡና ሲጠጡ ይመለከታቸው ነበር፡፡ ዋናው ሃሳብ ዮናታን የጠቀሳቸው ሰዎች ከአዶኒያስ ጋር ሆነው በዓል ሲያደርጉ ነበር፡፡ ተርጓሚ “ከእርሱ ጋር መብላትና መጠጣት” ወይም “እርሱ በሚያያቸው ቦታ ላይ ሆነው መብላትና መጠጣት”
1 Kings 1:26
አጠቃላይ መረጃ
ነብዩ ናታን ለንጉሥ ዳዊት መናገሩን ቀጥሏል
በውኑ ይህ ነገር ከጌታዬ ከንጉሥ የተደረገ ነውን? ለባሪያህም ከአንተ በኋላ በጌታዬ በንጉሱ ዙፋን ላይ የሚቀመጠውን አልነገርህምን?
ናታን ዳዊትን በሦስተኛ ወገን ይወክላል ይህ ለንጉሡ ያለውን ከበሬታ ማሣያ መንገድ ነው፡፡ በሁለተኛ ወገን ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚ “አንተ በጌታዬ በንጉሡ ዙፋን ላይ የሚቀመጠው ማን እንደሆነ ለባሪያህ አልነገርህምን?”
1 Kings 1:28
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ዳዊት ለቤርሣቤህ ቃል ማሃላ አደረገ (ማለ)
ወደ ንጉሡም ገባች በንጉሡ ፊት ቆመች
“በንጉሡ ፊት ቆመች” ወይም “ወደ ንጉሡ ተመለሠች”
እንደ ማልሁልሽ
ቃል ገባ
በእኔም ፋንታ በዙፋኔ ላይ ይቀመጣል
በዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ የመሆን ዘይቤአዊ ንግግር ነው፡፡ የ1 ነገሥት 1:13 ትርጉምን ተመልከት፡፡ ተርጓሚ “በእኔም ቦታ ይሆናል እንደ እኔም ንጉሥ ይሆናል፡፡”
ጌታዬ ንጉሥ ዳዊት ለዘላለም በሕይወት ይኑር
ቤርሣቤህ ዳዊት ለዘላለም እንደማይኖር ታውቃለች፡፡ ይህ መልካም ንጉሥ መሆኑን ማሳያ ነው፡፡
1 Kings 1:32
የጌታችሁን ባሪያዎች
ናታን፤ ዮዳሄና በናያስ አሁንም ዳዊት ንጉሥ እንደሆነ እንዲያስታውሱ ዳዊት ስለሌላ ሠው የሚናገር በማስመሠል ስለ ራሱ ይናገራል፡፡ ተርጓሚ “ባሪያዎቼ”
ግዮን
ይህ የውሃ ምንጭ ሥም ነው፡፡
1 Kings 1:35
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ዳዊት በሠለሞን ቦታ ሆኖ ንጉሥ ስለ ሚሆነው መናገሩን ቀጥሏል፡፡
እርሱም መጥቶ በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ
“በዙፋን ላይ ይቀመጥ” የሚሉት ቃላት ንጉስ የመሆን ዘይቤ ናቸው፡፡ ነ1 ነገሥት 1:13 1:17 እና 1:30 እዚህ ጋር ዳዊት በቀጥታ ሰለሞን በእርሱ ዙፋን ላይ እንደሚቀመጥ ይናገራል፡፡
ይሆን ዘንድ
ተስማምተውም ንጉሥ ዳዊት ያለውን ያደርጋሉ፡፡
የጌታዬም የንጉሥ አምላክ ይህን ይናገር
በናያስ ለዳዊት ያለውን አክብሮት ለማሣየት ለሌላ ሠው የሚናገር በማስመሰል ለዳዊት ይናገራል፡፡ ተርጓሚ “ጌታዬ ንጉሡ........ ከአንተጋ እንደነበር”
ዙፋኑንም ከጌታዬ ከንጉሥ ዳዊት ዙፋን የበለጠ ያድርግ
“ዙፋን” የሚለው ቃል 1) ዙፋን ላይ የሚቀመጠው ሰው ተርጓሚ ዙፋኑ ላይ የሚቀመጠውን ሰው ከጌታዬ ከንጉሡ ዳዊት የበለጠ ያደርጋል ወይም 2) በዙፋኑ ላይ ከሚቀመጠው መንግስት የበለጠ ተርጓሚ “መንግሥቱን ከጌታዬ ከንጉሥ ዳዊት መንግስት የበለጠ ገናና ያደርጋል፡፡”
1 Kings 1:38
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ህዝብ ሠለሞንን ንጉሥ አድርገው በእስራኤል ላይ ሾሙት
ከሊታውያንና ፈሊታውያን

እነዚህ የሰዎች ስብስብ ሥሞች ናቸው
ግዮን
ይህ ንፁህ ውሃ ከምድር የሚፈልቅበት የምንጭ ስም ነው።
ከድንኳኑ የቅብዓቱን ቀንድ ወሰደ
ይህ በተለየ የእንስሳ ቀንድ የተቀመጠን የወይራ ዘይት ከተቀመጠበት ከእግዚአብሔር ድንኳን ካህኑ ሲወስድ ማለት ነው።
የቅብዓቱን ቀንድ ወስዶ
አማራጭ ትርጉሞች 1) በወይራ ዘይት የተሞላ የእንስሳ ቀንድ 2) እውነተኛውን ቀንድ የሚተካ ነገር ግን ሠዎች አሁንም ቀንድ ብለው የሚጠሩት። ተርጓሚ “የዘይት ማስቀመጫውን ወስዶ”
ሕዝቡም ሁሉ
ይህ በጥቅል ነው
1 Kings 1:41
አጠቃላይ መረጃ
አዶንያስ ታላቅ ጩኸት ሰማ ወሬውን (ዜናውን) እየጠበቀ ነው።
1 Kings 1:43
አጠቃላይ መረጃ
አዶኒያስ ሰለሞን ንጉስ እንደሆነ አወቀ
1 Kings 1:46
አጠቃላይ መረጃ
ዮናታን ሥለ ሰለሞን ለአዶንያስ መናገሩን ቀጥሏል።
በመንግስቱ ዙፋን ላይ ተቀምጦአል
አማራጭ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቃላት ንጉስ የመሆን ዘይቤአዊ ንግግሮች መሆናቸውን የ1 ነገስት 1:35 ተመሣሣይ ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ፡ አሁን ንጉስ ነው። ወይም 2) ሰለሞን በአካል በዙፋን ላይ ተቀምጦ ነበር።
ዛሬ በዙፋኔ ላይ የሚቀመጠውን
አማራጭ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቃላት ንጉሥ የመሆን ዘይቤአዊ ንግግሮች መሆናቸውን። የ 1ነገስት 1:35 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ዛሬ እንደ እኔ ንጉሥ ሊሆን ያለ” ወይም 2) ሰለሞን በአካል በዙፋን ላይ ተቀምጦ ነበር።
1 Kings 1:49
አጠቃላይ መረጃ
አዶንያስ ንጉሥ ሰለሞንን ፈራ
ተነሥተውም
ሌላ አማራጭ ትርጉም “ፈጥነው እርምጃ መውሰድ ጀመሩ” ነው።
አዶንያስም---- የመሠዊያውን ቀንድ ይዞአል
የመሠዊያው ቀንድ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይልና ጥበቃ ነው። ነገር ግን አዶንያስ በትክክል ድንኳኑ ወዳለበት ቦታ ሄደ ትክክለኛውን ቀንድ ለማንሳት ስለሄደ በዚሁ መልኩ መተርጎም አለብህ/ሽ።
አዶንያስም------ተነስቶ ሄደ
ሌላ አማራጭ ትርጉም “አዶንያስ-----ፈጥኖ ሄደ” ነው።
ሰለሞንን ፈራ
ባሪያው ለንጉስ ሰለሞን ያለውን ከበሬታ ለማሳየት እንደ ሌላ ሰው አድርጎ ንጉሥ ሰለሞንን ያናግረዋል። ተርጓሚ “ፈርቶሃል፤ንጉሥ ሰለሞን”
ባሪያውን-----እንዳይገለጥ
አዶንያስ ለንጉሥ ሰለሞን ያለውን ከበሬታ ሌሎች እንዲያውቁ ንጉስ ሰለሞንን እንደሌላ ሠው ያናግረዋል። ተርጓሚ “እርሱ አይገድለኝም”
1 Kings 1:52
አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን የአዶንያስን ነፍስ አዳነ
ከእርሱ አንዲት ጠጉር እንኳ በምድር ላይ አትወድቅም
ይህ ሰለሞን አዶንያስን እንደሚያድነው የግነት ንግግር ነው። ተርጓሚ “በራሱ ጠጉር አንዳችም አትወድቅም ” ወይም “እኔ አድነዋለው”
እርሱ--- ክፋት የተገኘበት
“ክፋት” የሚለው ስውር ስም እንደ ግስ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። በማስቀመጫ ውስጥ እንደተቀመጠ ዕቃ ሆኖ ተመስሎአል። ይህ በገቢር መልክ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “ክፉ የሆነ ነገርን አደረገ”

---

Chapter 2
1 Kings 2:1
እኔ የምድሩን ሁሉ መንገድ እሄዳለሁ
ይህ “እኔ እሞታለሁ” ብሎ የመናገር የትህትና ንግግር ነው።
ሰውም ሁን
የጎደለው ለሞላ ይችላል። ተርጓሚው “ሰው መሆንህን ለሁሉም አሣይ” ወይም “መልካም ሰው መሆንህን ሁሉም ያስተውል ዘንድ ኑር”
በመንገዱም ትሄድ ዘንድ
በመንገድ መሄድ የሰው የሕይወት አኗኗሩ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “ እርሱ እንዳዘዘ ኑሩ”
በመንገዱም ትሄድ ዘንድ
“ይከናወንልህ ዘንድ” ወይም “መልካም ይሆንልህ ዘንድ”
የተናገውን ቃል ያፀና ዘንድ ነው
“ሊያደርግ ቃል የገባውን ያደርጋልና”
ልጆችህ---አይቆረጥብህም
እግዚአብሄር ለዳዊት ሲናገር “አንተ” እና “የአንተ” በማለት ነው።
በፊቴ በእውነት ----ቢሄዱ
እግዚአብሄር ለዳዊት ይናገራል ስለዚህ “በፊቴ” የሚለው ቃል እግዚአብሄርን ይወክላል።
በፍፁም ልባቸውና በፍፁም ነፍሳቸው
በፍፁም ልባቸው የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር “ፈፅሞ” ማለት ሲሆን በፍፁም ነፍሳቸው የሚለው ደግሞ “በሙሉ ማንነት” ማለት ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው። ተርጓሚ “በሁለንተናቸው” ወይም “በሙሉ ኃይላቸው”
ከእስራኤል ዙፋን ሰው አይቆረጥብህም
“ዙፋን” የሚለው ቃል በዙፋን ላይ ለሚቀመጠው ንጉሥ ዘይቤ ነው። ምፀቱ “አይቋረጥብህም” በቀና መልኩ በዚህ መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “ዘርህ የእስራኤል ንጉሥ ከመሆን አይቋረጥም” ወይም “ከዘር ሐረግህ አንዱ ሁልጊዜ የእስራኤል ንጉሥ ይሆናል”
1 Kings 2:5
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ዳዊት ለሰለሞን እንዴት እስራኤልን መምራት እንዳለበት መናገሩን ቀጥሎአል።
ኢዮአብ---በእኔ ላይ ያደረገውና ያደረገው
ተርጓሚ “ኢዮአብ----በእኔ ላይ ያደረገው- ያ ያደረገው ነው”።
የሰልፉንም ደም በሰላም አፈሰሰ
አማራጭ ትርጉሞች 1) “ልክ በጦርነት ያለ ያክል እነዚያን ሠዎች በሰላም ጊዜ ገደለ” 2) “በጦርነት ጊዜ ሰዎችን ስለገደሉ፣ በሰላሙ ጊዜ ተበቀላቸው።”
በወገቡም ባለው ድግና በእግሩ ባለው ጫማ ንፁህ ደም አኖረ
አማራጭ ትርጉሞች 1) ኢዮአብ የገደላቸውን በጣም ከመቅረቡ የተነሳ ደማቸው በድጉና በጫማው ላይ ፈሰሰ 2) ደም የሚለው ቃል ለግድያው ተጠያቂ የዘይቤ ንግግር ሲሆን ድግና ጫማ ደግሞ የኢያአብ የአዘዥነት ሥልጣን ማሣያ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ስለዚህ ዳዊት እያለ ያለው ኢዮአብ በግድያ የተከሰሰ ስለሆነ የሠራዊቱ አዛዥ መሆን የለበትም። ወይም ደግሞ ይህንን እንዳለ መተርጎም የተሻለ ነው።
ሽበቱንም በሰላም ወደ መቃብር አታውርደው
እዚህ ጋር ሽበት የእርጅና ምልክት መሆኑን ያሳያል። ይሄውም “ሽበቱን” የሚለው ነው። ተርጓሚ “ኢዮአብ ሳያረጅ የአመፃ ሞት መሞቱን አረጋግጥ”
1 Kings 2:7
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ዳዊት ለሰለሞን እንዴት እስራኤልን መምራት እንዳለበት መናገሩን ቀጥሏል
ቤርዜሊ
የሰው (ወንድ) ስም ነው።
በማዕድህም ከሚበሉት መካከል ይሁኑ
ማዕድ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ የመመገቢያ ጠረጴዛ ማሳያ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “በቤትህ እንዲመገቡ ተቀበላቸው”
1 Kings 2:8
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ዳዊት ለሰለሞን እንዴት እስራኤልን መምራት እንዳለበት መናገሩን ቀጥሏል።
ጌራ-----ሳሚ

የሰዎች ስም( ወንዶች)
ብንያማዊው
የብንያም ነገድ
መሃናይም---ብራቂም
የቦታ ሥሞች
ያለቅጣት አትተወው
ይህ በበጎ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ “ እርሱን ለመቅጣት እርግጠኛ ሁን”
ሽበቱንም ከደም ጋር ወደ መቃብር አውርድ
ደም በአመፅ የመሞት ዘይቤ ሲሆን ሽበት ደግሞ የሙሉ ሰውነት ምሳሌአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ - “የአመፃ ሞት መሞቱን እርግጠኛ ሁን”
1 Kings 2:10
አጠቃላይ መረጃ
ዳዊትም ሞተ ሰለሞንም እርሱን ተክቶ የእስራኤል ንጉስ ሆነ
ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
የዳዊት ሞት በእንቅልፍ እንደወደቀ ተደርጎ ተነግሮአል። ተርጓሚ “ሞተ”
ዳዊትም---ተቀበረ
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል።” ተርጓሚ “ዳዊትን ----ቀበሩት”
ዳዊትም በእስራኤል ላይ የነገሠው ዘመን
“ዳዊት በእስራኤል ላይ የነገሰው ጊዜ(ዘመን) ወይም “ዳዊት በእስራኤል ላይ የነገሠበት”
በአባቱ ዙፋን ላይ ተቀመጠ
ዙፋን የንጉስን ሥልጣን ያመለክታል። ተርጓሚ “አባቱ ንጉሥ እንደነበረ፤ ዳዊት ንጉሥ ሆነ”
መንግስቱም እጅግ ፀና
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር የሰለሞንን መንግስት እጅግ አፀና” ወይም “እግዚአብሔር ሰለሞንን መንግስቱን ፈፅሞ እንዲቆጣጠር አደረገው”
1 Kings 2:13
አጠቃላይ መረጃ
አዶንያስ ቤርሳቤህን ሊናገር መጣ
በሰላም
ክፉ ማድረግ ሳይፈልግ
እስራኤልም ሁሉ
ይህ በጥቅሉ ነው።
መንግስቱ---ለወንድሜ ሆኖአል
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር መንግስቱን ለወንድሜ ሰጥቷል” ወይም “ወንድሜ ንጉስ ሆኖአል”
1 Kings 2:16
አጠቃላይ መረጃ
አዶንያስ ልመናውን ለቤርሳቤህ አቀረበ
አታሳፍረኝ----አያሣፍርሽምና
ማፈር የሚለው ቃል አንድን ሰው ለመመልከት የአለመፈለግ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ አንድ ሰው የጠየቀውን የአለማድረግ ዘይቤ ነው።ተርጓሚ “የጠየኩሽን እምቢ አትበይኝ”----የጠየቅሽውን እምቢ አይልምና።
ሱናማይቱን አቢሳን
1 ነገስት 1:3 ተመልከት
1 Kings 2:19
አጠቃላይ መረጃ
ቤርሳቤህ የአዶንያስን ልመና(ጥያቄ) ይዛ ወደ ንጉስ ሰለሞን ሄደች
ንጉሡም ------ተነሳ
“ንጉሱም ከተቀመጠበት ከዙፋኑ ተነስቶ ቆመ”
ወንበር አስመጣላት
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ - ወንበር እንዲያመጡ ለአንድ ሠው ነገረ
የንጉሡም እናት
ቤርሳቤህ
አታሳፍረኝ---አላሳፈርሽኝም
ማፈር አንድን ሰው ለማየት (ለመመልከት) የአለመፈለግ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ አንድ ሰው የጠየቀውን (የለመነውን) ነገር ያለመፈለግ ዘይቤ ነው። የ1ነገስት 2:16-17 ትርጉም ተመልከት።ተርጓሚ “እኔ የምጠይቅሽን እምቢ አትይኝም-----የምትጠይቂኝን እምቢ አልልሽም”
ሱናማይቱ አቢሳ---ለአዶንያስ ትዳርለት
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። “ሱናማይቱ አቢሳ እንዲያገባት ለአዶንያስ ፍቀድለት” ወይም “ሱናማይቱ አቢሳን ለአዶንያስ ሚስት አድርገህ ስጠው”
1 Kings 2:22
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰለሞን ለቤርሳቤህ ጥያቄ ምላሽ ሰጠ
ለአዶንያስ ለምን ትለምኝለታለሽ------መንግስትን ደግሞ ለምኚለት---ፅሩያ
ንጉሥ ሰለሞን በእናቱ ጥያቄ ተቆጥቷል። ተርጓሚ “ለአዶንያስ በመጠየቅሽ ስህተት ሰርተሻል”። ይህ እርሱ መንግስትን ከመጠየቅ ጋር አንድ ነው---ፅሩያ
አዶንያስ ይህን ቃል በሕይወቱ ላይ አለመናገሩ እንደ ሆነ እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ ይህንም ይጨምርልኝ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አዶንያስ ይህን ጥያቄ በማቅረቡ እኔ ካልቀጣሁት እግዚአብሔር እኔን ለመቅጣት ሙሉ መብት ይኖረዋል። ብሎም ሊጨምርብኝ
1 Kings 2:24
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰለሞን አዶንያስን ቀጣ
ዙፋን ላይ ያስቀመጠኝ
ዙፋን የሚለው ቃል እግዚአብሔር ሰለሞን እንዲገዛ የሰጠውን ስልጣን ይገልፃል።
ቤትን የሰራልኝ
እዚህ ጋር ቤት የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሰለሞን የሰጠው የዘር ሐረግ ከእርሱ በኋላ ስለመንገሳቸው ነው።
1 Kings 2:26
አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን አብያታርን ከክህነት አወጣው
አባቴም የተቀበለውን መከራ ሁሉ-----ተቀበልሁ
ዳዊት ወደ ንግስና ከመምጣቱ በፊት አብያታር ከዳዊት ጋር መከራን ተቀበለ
የእግዚአብሄር ቃል
“እግዚአብሄር ስለተናገራቸው ነገሮች”
ቃል ይፈፀም ዘንድ
ይህ ስለ ንጉስ ሰለሞን ነው።
1 Kings 2:28
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰለሞን ኢዮአብን እንዲገድል በናያስን አዘዘ
ለኢዮአብም ወሬ ደረሰለት
“ኢዮአብም ሰለሞን ንጉሥ ከሆነ በኋላ ያደረገውን ሰማ”
የመሠዊያውን ቀንድ
የመሠዊያው ቀንድ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይልና ጥበቃ ነው።
ሰለሞን ኢዮአብ----ሸሽቶ-----ሰማ
ይህ በገቢር ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “የሆነ ሰው ኢዮአብ እንደሸሸ ለሠለሞን ነግሮአል”
1 Kings 2:30
አጠቃላይ መረጃ
በናያስም ኢዮአብን ሊገድለው ሄደ
ኢዮአብም በከንቱ ያፈሰሰውን ደም ከእኔና ከአባቴ ቤት ታርቅ ዘንድ ገድለህ ቅበረው።
እዚህ ጋር “ቤት” ሥለ ዳዊት የዘር ሐረግ ሲሆን “ደም” ወንጀልን ይገልፃል። ተርጓሚ ኢዮአብ በከንቱ ያፈሰሰው ደም ከእኔና ከቤተሰቤ ይርቅ ዘንድ ወስደህ ቅበረው። ወይም “ኢዮአብ የሰዎች ደም በከንቱ በማፍሰሱ ምክኒያት እግዚአብሔር በእኔና በአባቴ ቤት ላይ ወንጀል አድርጎ እንዳይቆጥር ቅበረው።”
1 Kings 2:32
አጠቃላይ መረጃ
ለምን ኢዮአብ መሞት እንዳለበት ሰለሞን ያብራራል።
እግዚአብሔር ደሙን በራሱ ላይ ይመልሰው
“በራሱ” ላይ የሚለው ቃል ኢዮአብን ይገልፃል “ደም” ደግሞ የመግደል ዘይቤአዊ ንግግር ነው። “ደሙን በራሱ ላይ” የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ደግሞ ግለሰቡ በግድያ ምክኒያት እንደወንጀለኛ መቆጠሩ ማለት ነው። ተርጓሚ “ኢዮአብ ሰዎችን በመግደሉ ምክኒያት (ሰበብ) ላደረገው ድርጊት እግዚአብሔር እንደ በዳይ እንዲያየው እፈልጋለው።”።

የሚሻሉትን----ፃድቃን

እነዚህ ሁለት ቃላት ቢመሰረቱ አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው አበኔርና አሜሳይ ከኢዮአብ የተሻሉ መሆናቸውን አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ደማቸውም በኢዮአብ ራስና በዘሩ ራስ ላይ ይመልስ

“ደም” የሚለው ቃል የግድያ ዘይቤ ነው። “ደማቸው---ራስ ላይ” የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ደግሞ ግለሰቡ በግድያው ምክኒያት እንደ ወንጀለኛ መወሰድ አለበት ማለት ነው። ተርጓሚ እኔ እግዚአብሔር ኢዮአብንና ዘሩን ተጠያቂ እንዲያደርግ እፈልጋለሁ።

ለቤቱ ለዙፋኑም

“ቤት” ና “ዙፋን” የሚሉት ቃላት ለቤተሰብና ለመንግስት የዘይቤ ንግግር ናቸው። ተርጓሚ “ለዳዊት ዘርና ለዳዊት መንግስት”

1 Kings 2:34

አጠቃላይ መረጃ

በነያስ ኢዮአብን ገደለው ከዚያም የንጉሥ ሰለሞን ጦር አዛዥ ሆነ

በቤቱ ተቀበረ

ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ኢዮአብን በራሱ ቤት ውስጥ ቀበሩት”

በቤቱ

ቤት የሚያመለክተው ቤቱ ያለበት መሬት ነው። እስራኤላውያን ሰዎችን (ሙታንን) ከቤት ውጭ በመቃብር ቦታ ይቀብራሉ “ቤተሰቡ በሚኖሩበት ቦታ”

1 Kings 2:36

አጠቃላይ መረጃ

ንጉሥ ሰለሞን ለሳሚ በእየሩሳሌም እንዲቆይ አለበለዚያ ግን እንደሚሞት ነገረው።

ደምህ በራስህ ላይ ይሆናል።

እዚህ ጋር “ደም” የጥፋት ዘይቤ ሲሆን “ራስ” ደግሞ ግለሰብን ማሣያ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ ለሞትህ አንተ ራስህ ተጠያቂ ትሆናለህ

1 Kings 2:39

አጠቃላይ መረጃ

ሳሚ እየሩሳሌምን ለቀቀ

ጌት-----መዓካ----አንኩስ

የሰዎች ስም

ጌት

የፍልስጤም ከተማ

ሳሚም ተነሳ

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። “ሳሚም ፈጠነ”

1 Kings 2:41

አጠቃላይ መረጃ

ንጉሥ ሰለሞን ሳሚ እየሩሳሌምን በመልቀቁ ፈረደበት

ሰለሞንም----ሰማ

ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “የሆነ ሰው ለሰለሞን ነገረው”።

እንዳትሞት እውቅ ብዬ------አላስማልሁህምን?

ሳሚ ቃል የገባውን (የማለውን) ማሃላ ሰለሞን ሲያስታውሰው። ተርጓሚ “እንዳትሞት እውቅ ብዬ----እንዳስማልሁህ በደንብ ታውቃለህ”

1 Kings 2:43

አጠቃላይ መረጃ

ንጉሥ ሰለሞን ሳሚ እየሩሳሌም በመልቀቁ ፈረደበት

መሓላ ስለ ምን አልጠበቅህም?

አማራጭ ትርጉሞች- 1) ሰለሞን መልስ እየጠየቀው ነው? ወይም 2) “ማሃላን በማፍረስህ ስህተት ሠርተሃል”

ክፋትህን በራስህ ላይ ይመልሳል

እዚህ ጋር ራስ ግለሰቡን ይወክላል። ክፋትን ደግሞ በግለሰቡ ራስ ላይ እንደሚቀመጥ ዕቃ ወይም ፈሳሽ ነገር አድርጎ ይናገራል። ተርጓሚ “ለክፋትህ ሁሉ ተጠያቂ ያደርግሃል”

1 Kings 2:45

አጠቃላይ መረጃ

ንጉሥ ሰለሞን ሳሚ እንዲሞት ትዕዛዝ ሰጠ

የዳዊትም ዙፋን በእግዚአብሄር ፊት ለዘላለም ይፀናል።

እዚህ ጋር የዳዊት ዙፋን የዳዊትንና የእርሱን ዘር ሐረግ ስልጣንና ግዛት ይወክላል።

በሰለሞን እጅ

“እጅ” የሰለሞንን ስልጣንና ጉልበት ይገልፃል።

---

Chapter 3

1 Kings 3:1

አጠቃላይ መረጃ

ሰለሞን ግብፃዊቷን አገባ

ሰለሞን ለግብፅ ንጉሥ ለፈርዖን አማች ሆነ የፈርኦንን ልጅ አገባ

ሁለቱ ነገስታት አብረው ይሠሩና ጠላቶቻቸውን በጋራ ይወጉ ዘንድ፣ ሰለሞን የግብፅ ንጉሥ ለፈርዖን አማች ሆነ

ቅጥር ሠርቶ እስኪፈፅም ድረስ

ቅጥሩን ሠርቶ ከጨረሰ በኋላም በዳዊት ከተማ ውስጥ ነበረች

የእግዚአብሄርንም ቤት

“ቤተ- መቅደሱ”

እስከዚያም ቀን ድረስ…መቅደስ አልተሰራም

ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እስከዚያ ቀን ድረስ ማንም መቅደስ አልሰራም”

ለእግዚአብሄር ስም

“ስም” የሚለው ቃል ለአንድ ሰው ዘይቤና “ስም” የሚለው ቃል በዚህ ሐረግ ውስጥ የሚመለክ ስም መሆኑን ነው። ተርጓሚ “ሰዎች እግዚአብሄርን የሚያመልኩበትን”

በአባቱም በዳዊት ሥርዓት ይሄድ ነበር

የሰው የአኗኗር ዘይቤና መንገድ እንደሚሄድ ሰው ተደርጎ ተነግሯል። ተርጓሚ “አባቱ ዳዊት የታዘዘውን ሕግጋት መታዘዝ (ታዘዘ)”

1 Kings 3:4

አጠቃላይ መረጃ

እግዚአብሄር ለሰለሞን ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ጠየቀው

ዋና የኮረብታ መስገጃ

“መስዋዕት ለማቅረብ በጣም የተመረጠ ሥፍራ” ወይም “በጣም አስፈላጊ መሰዊያ”

ምን እንደምሰጥህ ጠይቅ

“የምትፈልገውን ነገር ጠይቀኝ እኔም እሰጥሃለሁ” ወይም “ምን ትፈልጋለህ? ጠይቅ እኔም እሰጥሃለሁ”

1 Kings 3:6

አጠቃላይ መረጃ

ሰለሞን ለእግዚአብሄር ጥያቄ ምላሽ ሰጠ

1 Kings 3:10

አጠቃላይ መረጃ

እግዚአብሔር ለሰለሞን ጥበብን አብዝቶ ሠጠው

የጠላቶችህንም ነፍስ

“ነፍስ” የመግደል ሃይል ዜይቤ ነው። ተርጓሚ “ ጠላቶችህን የመግደል አቅም (ሃይል)”

ለመንህ …….እኔ እንደቃልህ አድርጌልሃለው

“ከእኔ ጋር ስለተነጋገርህ የጠየቅከው ሁሉ አደርግልሃለው”

ጥበበኛና አስተዋይ ልቦና ሰጥቼሃለሁ

ልብ ሰው ስለሚያስበውና ስለሚመኘው ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ጥበበኛና ብዙ ነገሮችን የምትረዳ አደርግልሃለሁ”

1 Kings 3:13

ትጠብቅ ዘንድ በመንገዴ

ሕይወትን መኖር መንገድ እንደመሄድ ሆኖ ተገልፆአል። “እኔ እንደምፈልገው ኑር ታዘዝም”

እድሜህን አረዝመዋለሁ

“ረጅም እድሜ እንድትኖር አደርጋለሁ”

1 Kings 3:15

እነሆም

“እነሆም” የሚለው ቃል ሰለሞን ደስ የሚል ነገር ማየቱን ያሣያል።

1 Kings 3:16

አጠቃላይ መረጃ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሁለት ጋለሞቶች ሰለሞን ውሳኔ እንዲሰጥ ጠየቁት
1 Kings 3:18
አጠቃላይ መረጃ
ሁለቱም ጋለሞታዎች ታሪካቸውን ለሰለሞን ነገሩት
ተኛችበት
ሕፃኑን እንዲሞት አደረገው ብሎ ማስቀመጥ የተሻለ ነው። ተርጓሚ “በድንገት በልጁ ላይ በመንከባለሏ አፈነችው (ታፈነ)
ባርያህ
ሴትዬዋ ለሠለሞን ያላትን አክብሮት ለማሳየት እራሷን እንደሌላ ሠው አድርጋ ታናግረዋለች። ተርጓሚ “እኔ”
1 Kings 3:21
አጠቃላይ መረጃ
ሁለቱ ጋለሞታዎች ታሪካቸውን ለሠለሞን መንገር ቀጥለዋል።
ልጄንም አጠባ ዘንድ
ይህ ማለት ከጡቷ ወተት መስጠት ማለት ነው።
በንጉሱ ፊት
x
1 Kings 3:23
አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ለሁለቱ ሴቶች ውሳኔ ሰጠ
1 Kings 3:26
አጠቃላይ መረጃ
እውነተኛይቱ የልጅ እናት ንጉሡ የልጁን ሕይወት እንዲድን
አንጀትዋ ስለ ልጅዋ ናፍቆአልና
ይህ ሴትዬዋ ስለ ልጅዋ ብዙ ናፍቆት እንዳላት የሚያሳይ ነው። ተርጓሚ “ልጅዋን በታላቅ ፍቅር ወዳዋለች”
እስራኤል ሁሉ
ይህ ጥቅል ንግግር ነው

---

Chapter 4
1 Kings 4:1
አጠቃላይ መረጃ
ይህ የሰለሞን ባለሥልጣናት ዝርዝር ነው።
ዓዛሪያ…ሳድቅ…ኤልያፍ…አኪያ…አሒልድ…ሴባ…ኢዮሳፍጥ…በናያስ…አብያታር…ዮዳሄ
የሰዎቸህ (ወንዶች) ስም
1 Kings 4:5
አጠቃላይ መረጃ
የሰለሞን ባላስልጣናት ሥም ዝርዝር ቀጥሏል
ዓዛሪያ…ናታን…ዛቡድ…አሒሳር…አዶኒራም…ዓብዳ
የሰዎች(ወንዶች) ሥም
አስገባሪ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሰለሞን እንዲሰሩለት ያስገደዳቸው ሰዎች”
1 Kings 4:7
አጠቃላይ መረጃ
የሰለሞን ባለሥልጣናት ዝርዝር ቀጥሏል
ሑር…ዴቀር…ሔሴድ
እነኝህ የሰዎች ስም ዝርዝር ናቸው
በተራራማው ሀገር…በማቃፅ….በአሩቦት
“የተራራማው ሀገር ሹም ማን ነበረ…የማቃፅ ሹም ማን ነበረ…የአሩቦት ሹም ማን ነበረ”
ኤፍሬም…ማቃፅ…ሸዓልቢም…ቤትሳሚስ…ኤሎን ቤትሓንን…አሩቦት…ሶኮት…ኦፌር
እነኝህ የቦታ ሥሞች ናቸው
1 Kings 4:11
አጠቃላይ መረጃ
የሰለሞን ሹሞች ሥምና ማስተዳደር የጀመሩበት የቦታዎች ስም ዝርዝር ናቸው።
አሚናዳብ…ጌበር…አያዕር…ምናሴ..አሒናዳብ…ኢዶ
የሰዎች ስም ዝርዝር
በዶር…በታዕናክ…በሬማት ዘገለዓድ…በመሃናይም
የዶር ሹም አስተዳደር ማን ነበረ…የታዕናክ ሹም አስተዳደር ማን ነበር…የሬማት ዘገለዓድ ሹም አስተዳደር ማን ነበረ…የመሃናይም ሹም አስተዳደር ማን ነበር!
ጣፋት
የሴት ስም
ዶር…ቤትሳን…ፀርታን…ኢይዝራኤል…በቤትሳምና አቤልማሖላን…ዮቅምዓም በሬማት ዘገለዓድ በአርጎብ በበሳን…በመሃናይም
የቦታ ስሞች
1 Kings 4:15
አጠቃላይ መረጃ
የሰለሞን ሹሞችና የአስተዳደራቸው የቦታ ሥሞች
አኪማአስ…በዓና…ኩሲ…ኢዮሳፍጥ..ፋሩዋ
የሰዎች ስም(የወንድ)
በንፍታሌም…በአሴር…በይሳኮር
የንፍታሌም ሹም አስተዳደር ማን ነበር፣ የአሴር ሹም አስተዳደር ማን ነበር፣ የይሳኮር ሹም አስተዳደር ማን ነበር
ባስማት
የሴት ስም
ንፍታሌም…አሴር…ይሳኮር
በእስራኤል ልጆች ነገድ የተሰየሙ የቦታ ስሞች
በአሎት
የቁራሽ መሬት ስም
1 Kings 4:18
አጠቃላይ መረጃ
የሰለሞን የሹም ስሞችና የሚያስተዳድሯቸው የቦታ ስሞች ዝርዝር ቀጥሏል
ሳሚ…ኤላ…ጌበር..ኡሪ…ሴዎን..ዐግ
የሰዎች ስም(የወንድ)
ቢንያም
የእስራኤል ልጅ የነገድ ስም
ገለዓድ…ባሳን
የቁራሽ መሬት ስሞች
የሴዎን…ምድር
“ቀድሞ የሴዎን ምድር የነበረ”
አሞራውያን
የአንድ ወገን ሰዎች ስም
በምድር
እዚህ ጋር ምድር የይሁዳን ምድር ይገልፃል። የመጀመሪያዎች ሹሞች በተለያዩ የእስራኤል ቦታዎች ያስተዳድሩ ነበር።
1 Kings 4:20
ይሁዳና እስራኤልም እንደ ባህር አሸዋ ብዛት ብዙ ነበሩ
ተናጋሪው ከብዛታቸው የተነሳ ለቁጥር እንደሚያታክቱ ለመግለፅ የግነት ንግግር የተጠቀመበት ነው። ይሁዳና እስራኤል በይሁዳና በእስራኤል በሚኖሩ ሰዎች ዘይቤአዊ ንግግር ናቸው። ተርጓሚ “ልክ እንደ ባህር አሸዋ በይሁዳና በእስራኤል ምድር ብዙ ሰዎች ነበሩ” ወይም “አንድ ሰው ሊቆጥር ከሚችለው በላይ በይሁዳና በእስራኤል ብዙ ሰዎች ነበሩ”
ከወንዙ
የኤፍራታ ወንዝ
ሰላሳ ኮር
ኮር የደረቅ ነገር መለኪያ ነው
ዋላ…ሚዳቋ…የበረሀ ፍየል
በጣም ፈጣን የሆኑ ባለ አራት እግር እንስሳዎች ናቸው።
ዋላ
ከተጠቀሱት እንስሳት ከአንድ በላይ የሆነ ዝርያ
የሰቡ ወፎች
ይሰቡ ዘንድ ሰዎች የቀለቡዋቸው አእዋፍ ናቸው
1 Kings 4:24
ቲፍሳ
የቁራሽ መሬት ስም

ይሁዳና እስራኤል
ይሁዳና እስራኤል በይሁዳና በእስራኤል ምድር ለሚኖሩ ሰዎች ዘይቤ ናቸው፡፡
እያንዳንዱ ከወይኑና ከበለሱ በታች ተዘልሎ ይቀመጥ ነበር
እያንዳንዱ ቤት (ቤተሰብ) የወይንና የበለስ ቦታ ነበረው፡፡ ይህ የሚያመለክተው ጦርነት ላይ ስላልሆነ የሚያርሱበት ጊዜ ስለነበራቸው እያንዳንዱ በሰላምና በፀጥታ ይኖሩ ነበር፡፡
ከዳን ጀምሮ እስከ ቤርሳቤህ
x
1 Kings 4:26
የፈረስ ጋጥ
ጋጥ እንደ ፈረስ ያሉ እንስሳት የሚጠበቁበትና እንክብካቤ የሚደረግበት ቦታ ነው፡፡
ወደ ንጉስ ሰለሞን ማዕድ የሚቀርቡትን
"ከንጉስ ሰለሞን ጋር የሚመገቡትን" ወይም "አብረውት ይመገቡ ዘንድ ንጉሥ ሰለሞን የጋበዛቸው"
እያንዳንዱ በየወሩ
በየወሩ ምግብ ያመጡለት ዘንድ 1ነገስት 4፡7-9 ሰለሞን አስራ ሁለቱን ሹሞች እያንዳንዳቸውን ወክሏል
ምንም አያጎድሉም ነበር
ይህ በሌላ መልኩ ሊገለፅ ይችላል፡፡ ተርጓሚ "ሰለሞን የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ያቀርቡለት ነበር"
1 Kings 4:29
እግዚአብሔር ለሰለሞን እጅግ ብዙ ጥበብና ማስተዋል...ሰጠው
ጥበብና ማስተዋል የሚባሉት ስውር ቃላት እንደ ግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ እግዚአብሔር ሰጠው ማለት እግዚአብሔር እነዚህን ብቃቶች እንዲኖረው አደረገ፡፡ ተርጓሚ እግዚአብሔር ሰለሞን ጥበበኛና ብዙ ነገሮች የሚረዳ ሰው አደረገው፡፡
በባህርም ዳር እንዳለ አሸዋ የልብ ስፋት
ሰለሞን ስለብዙ ነገሮች መረዳት የቻለ ነበር "ስፋት" የሚለው ስውር ቃል እንደ ቅፅል ሊተረጎም ይችላል፡፡ ተርጓሚ "ሰለሞን ብዙ ነገሮችን መረዳት የቻለ ነበር"
የሰለሞንም ጥበብ ከሰዎች ሁሉ ጥበብ..በለጠ
ሰለሞን ከጥበበኞች ሁሉ በላይ ጥበበኛ ነበረ
1 Kings 4:32
ዝግባ...ሂሶጵ
እነዚህ ቃላት ሁሉንም ተክሎች የሚያጠቃልል ስሞች ናቸው፡፡ ተርጓሚ የዝግባ ዛፍ..."የሂሶጵተክል" ወይም "ከዛፍ ሁሉ ትልቁ...እስተኛ ጥቅም ያለው ተክል"

---

## Chapter 5

1 Kings 5:1
አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ስለቤተመቅደስ ስራው ከንጉሥ ኪራም ጋር አወራ
ኪራም ለዳዊት በዘመኑ ሁሉ ወዳጁ ነበረ
ኪራም ለዳዊት ሁልጊዜ የቅርብ ወዳጁ ነበረ
እግዚአብሔር ከእግሩ በታች እስኪጥልለት ድረስ
ጠላትን ከእግር ስር መጣል ማለት ማሸነፍ ወይም መማረክ ማለት ነው፡፡ ተርጓሚ "እግዚአብሔር ዳዊት ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ ይረዳው ነበር፡፡" ወይም " እግዚአብሔር ዳዊትን ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ ይረዳው ስለነበር ዳዊት ጊዜ አልነበረውም፡፡"
በዙሪው ስለነበረ ሰልፍ
ሌላ አማራጭ ትርጉም፡- "በጠላቶቹ ሰፍም ስለተከበበ ወይም " በሁሉም አቅጣጫ ከጠላቶቹ ጋር ፍልሚያ ላይ ስለነበር"
እግዚአብሔር ከእግሩ በታች እስኪጥልለት ድረስ
ይህ እግዚአብሔር ለዳዊት በጠላቶቹ ላይ ፍፁም በላይነትን ከእግሩ በታች ስለመጣሉ ይናገራል፡፡
1 Kings 5:4
አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ከንጉሥ ኪራም ጋር ስለ ቤተ-መቅደስ ግንባታው ማውራቱን ቀጥሏል
በዙሪያዬ...ዕረፍት ሰጥቶኛል
ሰለሞን ንጉሥ ከመሆኑ በፊት ንጉሥ ዳዊትና የእስራኤል ሕዝብ በጦርነት ላይ ነበሩ ነገር ግን አሁን ንጉሥ ሰለሞንና የእስራኤል ሕዝብ በእረፍትና በሰላም ጊዜ ላይ ነበሩ
ጠላትም ክፉም ነገር የለብኝም
ክፋትን የሚያደርግ ሰውም ጉዳት የሚያደርስ የተፈጥሮ ክስተትም፡፡ ይህ በዚህ መልኩ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚ "ከጠላቶቻችንና ከተፈጥሮ አደጋዎች ተጠብቀናል"
ክፉ ነገር
ጠላት
ጥፋት
በሰዎችና በንብረታቸው ላይ ጉዳት የሚያደርስ ክስተት
ስለዚህ
ይህ ቀጥሎ ካሉት ቃላት አፅንኦት ለመስጠት ነው፡፡ "አድምጥ(ጡ) ይህ እኔ የማደርገው ነው፡፡" "ወይም" እግዚአብሔር ለእኔ ስላደረገው ይህ እኔ የማደርገው ነው፡፡
ለስሜ...ለአምላኬ ለእግዚአብሔር ስም
"ስም" የሚለው ቃል ለግለሰብ (ለአንድ ሰው) ዘይቤ ነው፡፡ ተርጓሚ አምላኬ እግዚአብሔር የሚኖርበት ቦታ...እኔ የምኖርበት፡፡
በዙፋንህ ላይ የማስቀምጠው
እዚህ ጋር ዙፋን እንደ ንጉሥ መግዛትን ይገልፃል፡፡ ተርጓሚ "ከአንተ በኋላ ንጉስ ለማድረግ (ለመሆን ማድረግ)"
1 Kings 5:6
አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ከንጉሥ ኪራም ጋር ስለ ቤተ- መቅደስ ግንባታው ማውራቱን ቀጥሏል
ከወገኔ እንደ ሲዶናውያን እንጨት መቁረጥ የሚያውቅ እንደሌለ
ያንተ ሠራተኞች ከእኔ ሰዎች የተሻለ እንጨት መቁረጥ ይችላሉ
ሲዶናውያን
የሲዶን ከተማ ሕዝብ
1 Kings 5:7
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ኪራም ለሰለሞን መለሰ
የሰለሞንን ቃል
"ሰለሞን ያለው"
እግዚአብሔር ዛሬ ይመስገን
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚ "ዛሬ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ"
ዝግባ
ዝግባ ቤተ-መቅደስ ለመሥራት የሚያገለግል ዋጋ ያለው እንጨት ነው
1 Kings 5:9
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ኪራም ለሰለሞን መልስ መስጠቱን ቀጥሏል
በታንኳ አድርጌ
እንዲንሳፈፉ አንድ ላይ ማሰር
በዚያም እፈታዋለሁ
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ተርጓሚ ሰራተኞቼ ግንዶቹን ይፈታሉ
አንተም ፈቃዴን ታደርጋለህ
"የምፈልገውን ማድረግ ትችላለህ" ወይም "ልትከፍለኝ ትችላለህ"
1 Kings 5:10
አጠቃላይ መረጃ
ጥድ የሚለው ቃል ብዙ አይነት ዛፎችን ሊገልጽ ይችላል፡፡ ዝግባንም ጨምሮ
መስፈሪያ ስንዴ (ቆሮስ)
ይህ የደረቅ ነገር መስፈሪያ ሲሆን ኮርም ደግሞ የፈሳሽ ነገር መስፈሪያ ነው፡፡ የትኛው መስፈሪያ እንደታሰበ ግልፅ አይደለም፡፡
በየአመቱ
ከአመት ወደ አመት(በየአመቱ)
1 Kings 5:13
አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ቤተ መቅደሱ እንዲገነባ ሰዎችን አስገደደ
ከእስራኤል ሁሉ ገባሮቹን መርጦ
እንዲሠሩ ገባሮቹን ከእስራኤል ሁሉ

በየወሩ
ያ ማለት አንድ ወር በሊባኖስ ሁለት ወር ደግሞ በቤት የሚቆዩ ሦስት ወገኖች ነበሩ
አንድ ወርም በሊባኖስ ሁለት ወርም በቤታቸው
እያንዳንዱ ወገን (ግሩፕ) አንድ ወር በሊባኖስ በሥራ ላይ ከዚያ ደግሞ ሁለት ወር በእስራኤል በቤታቸው የሚቆዩ ነበሩ።
ገባሮቹን …ሰዎች
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ "እንዲሠሩለት ሰለሞን የመረጣቸው (ያስገደዳቸው) ሰዎች።"
1 Kings 5:15
አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ቤተ-መቅደሱ እንዲሠራ ሠዎችን ማስገደዱን ቀጥሏል።
ሰባ ሺህ
70,000
ሰማንያ ሺህ
80,000
ጠራቢዎች
ድንጋይ ከመሬት ቆፍረው በሚፈለገው ቅርፅ የሚጠርቡ ሰዎች
3,300 ሹሞች
"ሶስት ሺህ ሶስት መቶ ሹሞች"
1 Kings 5:17
አጠቃላይ መረጃ
ሰለሞን ቤተ-መቅደሱ እንዲሠራ ሠዎችን ማስገደዱን ቀጥሏል።
ታላለቅ ምርጥ ምርጥ ድንጋዮችን ይቆፋፍሩና ይጠርቡ ዘንድ
"ከተራራው ወስጥ ጥሩና ትልልቅ ድንጋዮችን ቆፈሩና በሚፈለገው ቅርፅ ጠረቡ"
ጌባላውያን
ከጌባል ከተማ ሕዝብ

---

## Chapter 6

1 Kings 6:1
አጠቃላይ መረጃ
ተራኪው የቤተ-መቅደሱን ልኬት (ወርድና ስፋት) ዝርዝር
ሰለሞን ……መሥራት ጀመረ
ሰለሞን ሠራተኞቹን ሕንፃውን እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "ግንባታውን እንዲጀምሩ ሠለሞን ሠራተኞቹን አዘዘ"
480ኛ …..አራተኛ
ይህ የ480 እና 4 ተራ አቀማመጥ ነው።
ዚፍ በሚባለው በሁለተኛው ወር
"ዚፍ" በእብራዊያን በቀን መቁጠሪያ የሁለተኛው ወር ስም ነው። ይህ የሚያዚያ ወር መጨረሻ ወይም የግንቦት ወር መጀመሪያ ገደማ ነው ( በአውሮፓ አቆጣጠር)
ስድሳ (ስልሳ) ክንድ ወርድ፣ ሃያ ክንድ ስፋት ና ሠላሳ ክንድ ርዝመት
60 ክንድ ወርድ፣ 20 ክንድ ስፋትና ቁመቱም ሠላሳ ክንድ። አንድ ክንድ 46 ሴ.ሜ ነው። ይህ በዘመናዊ መስፈሪያ እንደገና ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ 27.6 ሜትር ወርድ፣ 9.2 ሜትር ስፋትና 13.8 ሜትር ከፍታ (ርዝመት)
1 Kings 6:3
አጠቃላይ መረጃ
ተራኪው የቤተ- መቅደሱን ልኬት መዘርዘሩን ቀጥሏል
ወለል
በኮለን የተሰራ የአንድ ሕንፃ ክፍል ሆኖ ጣሪያው ወደ ሕንፃው መግቢያ በር ይመራል። ይህ ወለል ምናልባት ከፍተኛው የሕንፃ ግድግዳ ጋር የሚገኝና ቤተ መቅደሱን የከበበ ነው።
ሃያ ክንድ…አስር ክንድ
አንድ ክንድ= 46ሳ.ሜ ነው።ተርጓሚ "9.2ሜ…4.6ሜ"
መስኮቶች አደረገ
ሰለሞን ሠራተኞቹን ሕንፃውን እንዲሰሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "መስኮቶችን አደረጉ"
1 Kings 6:5
አጠቃላይ መረጃ
ተራኪው የቤተ-መቅደሱን ልኬት መዘርዘሩን ቀጥሏል
ሠራ….አደረገ
ሰለሞን ሠራተኞቹን ሕንፃውን እንዲሰሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "ሰሩ…. አደረጉ"
በዙሪያውም ጓዳዎችን አደረገ
"በውጭ በኩል ካለው ግድግዳ ዙሪያ ጓዳዎችን አደረገ"
የታችኛውም ደርብ…የመካከለኛውም ደርብ…የሦስተኛውም
ይህ በእያንዳንዱ ወለል ያሉትን ጓዳዎች ይወክላል
አምስት ክንድ…ስድስት ክንድ…ሰባት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴ.ሜ ነው። ተርጓሚ "2.3 ሜ ገደማ…2.8 ሜ ገደማ…3.2ሜ ገደማ"
ከቤቱ ግንብ ውጭ ዓረፍቶች አደረገ
"የትንንሽ ጓዳዎቹን አግዳሚ እንዲረዳ (እንዲደግፍ) በዋናው ግንብ ዙሪያ ሁሉ ድጋፍ አደረጉ"
አግዳሚ
አግዳሚ ሕንፃ (ቤት) የሚደግፍ ረጅምና ከባድ እንጨት ነው።
1 Kings 6:7
ቤቱም
እዚህ ጋር "ቤት" የእግዚአብሔርን ቤት (ቤተ-መቅደስን) ይገልፃል።
ፈፅመው በተወቀሩ ድንጋዮች
ውቅር (ካባ) ሠዎች በመሳሪያ ከተራራ ሥፍራ ድንጋይ ጠርበው ቅርፅ የሚሰጡበት ቦታ ነው። በካባው ቦታ ካዘጋጁ በኋላ ወደ ቤተ-መቅደሱ ያመጡታል።
የታችኛው ደርብ…መካከለኛው ደርብ…ሦስተኛው ድርብ
በአጠቃላይ ሦስት ወለሎች ነበሩ። አንዳንድ ቋንቋዎች ይህ የታችኛው ወለል፣ አንደኛ ወለል (ፎቅ) እና በሁለተኛ ወለል (ፎቅ) ይሉታል።
1 Kings 6:9
ሰለሞን ሠርቶ…ከደነው…አጋጠማቸው
ሠለሞን ሠራተኞቹን ሕንፃውን እንዲሰሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ የሰለሞን ሠራተኞች ሠሩ…ከደኑ…አጋጠሙ።
በዝግባ…ደርብ (አግዳሚ)
ደርብ (አግዳሚ) …ህንፃን (ቤትን) የሚደግፍ ረጅምና ከባድ እንጨት ነው። የ 1ነገስት 6፡6 ትርጉምን ተመልከት
በዝግባው…ሳንቃዎች
ሳንቃ ጠፍጣፋና ልሙጥ እንጨት ሲሆን ለወለልና ለግድግዳ የሚያገለግል ነው።
ቤቱን ሠርቶ
በ1ነገስት 6፡5 የተጠቀሱትን አይነት ጓዳዎች ጋር ይመሳሰላል።
በቤቱም ሁሉ ዙሪያ
ይህ ሐረግ ለተሸፈኑት ግድግዳዎች ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ የውስጠኛውን ክፍል የሸፈነ የውጭ ግድግዳ
አምስት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴ.ሜ ነው። ተርጓሚ "2.3ሜ"
በዝግባ እንጨት
እንጨት የሚለው ቃል ለግንባታ ለሚያገለግሉ እንጨቶች የወለል ስም ነው። ለምሳሌ አግዳሚና ሳንቃ
1 Kings 6:11
የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሰለሞን መጣ እንዲህ ሲል - ስለዚህ
የእግዚአብሔር ቃል…መጣ የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ከእግዚአብሔር የተለየ መልዕክት እንዳለ ለማመልከት ነው። ተርጓሚ "እግዚአብሔር ለሰለሞን መልዕክት ሰጠ።" እንዲህ ሲል "ስለዚህ" ወይም እግዚአብሔር ለሰለሞን ይህን መልዕክት ተናገረ- ስለዚህ
ስለምትሰራው ቤት
ሰለሞን ሠራተኞቹ ሕንፃውን እንዲሰሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "ሠራተኞችህ ስለሚሰሩት ቤት"
በሥርዓቴ ብትሄድ
"ብትሄድ" የሚለው ቃል "ብትኖር" ለሚለው ቃል ዘይቤ ነው። ወይም "ብትታዘዝ" ተርጓሚ "በየጊዜው ሥርዓቴን ሁሉ ታዘዝ (ጠብቅ)"
ፍርዴንም ብታደርግ
አማራጭ ትርጉሞች 1) "ሕጌን ሁሉ አድርግ (ጠብቅ)" ወይም 2) "የምትመራውን ህዝብ በቅንነት ምራ"
ትመላለስባትም ዘንድ ትዕዛዜን ሁሉ ብትጠብቅ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረቱ አንድ አይነትሲሆኑ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የመጠበቅን አስፈላጊነት አፅንዖት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "እንድታደርግ የነገርኩህን ሁሉ በጥንቃቄ ታዘዝ"
ለአባትህ ለዳዊት የነገርሁትን ቃል ከአንተ ጋር አፀናለሁ
"ለአንተ አደርጋለሁ ብዬ ለዳዊት ቃል የገባሁትን ሁሉ አደርጋለሁ"
1 Kings 6:14
ሰለሞንም ቤቱን ሰራው ፈፀመው...መሠረቱን ...ለበጠው
ሰለሞን ሠራተኞች ሕንፃውን እንዲሰሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "የሰለሞን ሠራተኞች ቤቱን ሰሩት፤ፈፀሙት...መሰረቱን ለበጡት"
የቤቱንም...ውስጡን
"በየጓዳዎቹ (ክፍሎቹ) መካከል ያሉትን ግድግዳዎች"
1 Kings 6:16
ሃያ ክንድ...ጋረደ...የቤቱንም ውስጥ ...ለበጠው
ሰለሞን ሰራተኞቹ ሕንፃውን እንዲሰሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "ሃያ ክንድ እንዲጋርዱ...የቤቱንም ውስጥ እንዲለብጡ አዘዛቸው"
ሃያውን ክንድ ጋረደ
"ሃያ ክንድ የሚረዝም ክፍል ሠራ"
ሃያ ክንድ...አርባ ክንድ
አንድ ክንድ 46ሴ.ሜ ነው። ተርጓሚ "9.2 ሜ...18.4ሜ"
ቅድስተ- ቅዱሳት
"ዋናው ክፍል (ጓዳ)"
በፈነዳ አበባ
"የፈነዳ አበባ"
1 Kings 6:19
አበጀ ............... ለበጠው
ሰለሞን ሠራተኞቹ ሕንፃውን እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "አበጁ....ለበጡት
ሀያ ክንድ
"9.2 ሜ"
ቅድስተ-ቅዱሳኑን በዝግባ እንጨት ሸፈነው
"ይህ ቅድስተ-ቅዱሳን እጣን ለማጨስ ያገለግል ነበር"
1 Kings 6:23
ሠራ
"ሰለሞን እነሱ (ሠራተኞች) እንዲሠሩት አዘዘ"
የወይራ እንጨት
ከወይራ ዛፍ የሆነ እንጨት
አስር ክንድ ....አምስት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴ.ሜ ነው። ተርጓሚ "4.6.ሜ....2.3 ሜ"
ክንፉ ደረሰ
ከአንደኛው ክንፍ ጫፍ እስከ ሌላኛ ክንፋ ጫፍ ድረስ ያለ ርቀት
አንድ መልክ
ተመሣሣይ መጠን
1 Kings 6:27
አኖራቸው ..... ለበጣቸው
ይህን ሥራ ሠለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "አኖሯቸው .....ለበጧቸው"
በውስጠኛው ቤት
በጣም ለተቀደሠ ሥፍራ የተለየ ሥም ነው
ደሠ ሥፍራ የተለየ ሥም ነው ለበጣቸው
"ሸፈነ" የ1 ነገስት 6፡21 ትርጉምን ተመልከት
1 Kings 6:29
ቀረፀ....... ለበጠ
ሰለሞን ሰራተኞቹ ሥራውን እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ " እንዲቀርፁ አዘዛቸው ..... እንዲለብጡ አደረጋቸው"
ለበጠ
ሸፈነ
1 Kings 6:31
ሰለሞን አደረገ...እርሱ ሰራ ...ለበጠ
ይህን ሥራ ሰለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል ተርጓሚ "እነርሱ አደረጉ.... እነርሱ ሰሩ..... እነርሱ ለበጡ"
መቃን
በላይኛው የበር ክፍል ያለ ማዕዘን (መቃን) ማዕዘን በአምስቱም በኩል የሚገኝ የቤተ መቅደስ ሥፍራ
1 Kings 6:33
አደረገ ...ቀረፀ ....ለበጠ
ይህን ሥራ ሰለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "እነርሱ አደረጉ ....ቀረፁ ......ለበጡ"
እንዲሁም ለመቅደሱ መግቢያ ከወይራ እንጨት አራት ማዕዘን መቃን አደረገ። ሁለቱምን ደጆች ከጥድ እንጨት ሠራ
"ሰለሞን እንዲሁ ለመቅደሱ መግቢያ አራት ማዕዘን መቃን ከወይራ እንጨት አደረገ። ሁለት የጥድ እንጨት በር ደግሞ በተመሣሣይ መልኩ አደረገ"
ማዕዘን -
በአምስት የቤተ መቅደስ ክፍል ገፅ የሚገኝ
ሁለተኛው ደጅ
"ይህ ማለት እያንዳንዱ በር ሁለት ክፍል ሲኖረው በማጠፊያ የተገናኙና በአንድ ላይ እንዲታጠፍ ተደርገዋል።"
1 Kings 6:36
ሁለተኛውንም አደባባይ... ሠራው
ይህን ሥራ ሰለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "ሁለተኛውንም አደባባይ ....ሠሩት"
በዝግባ ሳንቃ (በሌላ ቦታ አግዳሚ ተብሎ ተተርጉሟል)
ሳንቃ ሕንፃውን የሚደግፍ ረጅም ከባድ እንጨት ነው። የ1 ነገስት 6፡6 ትርጉምን ተመልከት።
1 Kings 6:37
በአራተኛው አመት ... በአሥራ አንደኛውም አመት
"አራተኛ" ና "አሥራ አንደኛ" የሚሉት ቃላት የ "አራት" ና "የአሥራ አንድ" ተራ ማሣያ ናቸው ፀሐፊው ከሚቆጥረው ተነስተህ ድርጊቱን ግልፅ ልታደርገው ትችል ይሆናል። ተርጓሚ "ሰለሞን ከነገሰበት ጊዜ ጀምሮ አራተኛው አመት....አስራ አንደኛው አመት ሠለሞን ንጉሥ ከሆነ በኋላ።"
የእግዚአብሔር ቤት
"ቤተ መቅደሱ"
ዚፉ በሚባል ወር
"ዚፉ" በእብራዊያን ቀን አቆጣጠር ሁለተኛው ወር ነው። ይህም የሚያዝያ ማገባደጃ ሳምንትና የግንቦት የመጀመሪያቹ ሳምንታት (በአውሮፓዊያኑ የቀን አቆጣጠር) ማለት ነው። የ1 ነገሥት 6፡1 ትርጉምን ተመልከት
ቡል በሚባል በስምንተኛው ወር
"ቡል" በእብራዊያን ቀን አቆጣጠር ስምንተኛው ወር ነው። ይህም የጥቅምት ወር ማገባደጃ ሳምንትና የሕዳር ወር የመጀመርያው ሳምንት (በአውሮፓዊያኑ አቆጣጠር) ማለት ነው።
ቤቱ እንደ ክፍሎቹና እንደ ሥርዓቱ ሁሉ ተጨረሰ
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል።ተርጓሚ "የቤቱን ክፍሎች ሁሉ ሠርተው ጨረሱ። ሰለሞን ሥሩ ባላቸው መሠረት ሠርተው ጨረሱ"
...ውስጥ ሠራው
ይህን ሥራ ሰለሞን ለሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። የሰለሞን ሠራተኞች... ውስጥ ሠሩ"

---

Chapter 7
1 Kings 7:1
አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ስለ ሰለሞን ቤተ-መንግስት (ቤት) እየፃፈ ነው
ሰለሞን.....በ...ሠራ
ይህን ስራ ሰለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "የሰለሞን ሠራተኞች በ...... ሠሩ"
የራሱን ቤት
"ቤተ-መንግሥት"

የሊባኖስ ዱር ቤት
“የሊባኖስ ዱር ቤት የሚባል ቤት”
አንድ መቶ ክንድ ……ሃምሳ ክንድ …ሠላሳ ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሴ.ሜ ነው። ተርጓሚ “46ሜ …..23ሜ 13.8ሜ”
አግዳሚ
አግዳሚ ረጅምና ጠንካራ እንጨት ሆኖ ግድግድና ጣሪያ ለመደገፍ የሚያገለግል ነው፡
1 Kings 7:3
አጠቃላይ መረጃ
ሥለ ሊባኖስ ዱር ቤት አወቃቀር አንዳንድ ገለፃዎች በጥልቀት ተሰጥተዋል።
ቤቱ በዝግባ ሳንቃ ተሸፍኖ ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “አናጢዎቹ ከዝግባ ሳንቃ ጣሪያ ከሠሩ በኋላ ከአግዳሚዎቹ ጋር አያያዟቸው”
አግዳሚ
አግዳሚ ረጅምና ጠንካራ እንጨት ሆኖ ግድግድና ጣሪያ ለመደገፍ የሚያገለግል ነው።
ሁለት አራት ማዕዘን
“አራት ማዕዘን” ቅርፅ ያለው ሥፉራ
1 Kings 7:6
አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ሥለ አዳራሹ ምሰሶዎች ይፅፋል።
አዕማድ
በውስን ርቀት የተደረደሩ አምዶች
ሃምሳ ክንድ …ሠላሳ ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው። ተርጓሚ “23 ሜ… 13.8 ሜ”
መድረክ ያሉበት ወለል (ኮሪደር)
የአንድ ሕንፃ ቋሚና ጣሪያ ያለው ክፍል ሲሆን ወደ ሕንፃው መግቢያ የሚወስድና የሚያገናኝ ነው። የ 1 ነገሥት 6፡ 3 ትርጉም ተመልከት።
1 Kings 7:7
አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ሥለ ዙፋኑ አዳራሽ ይፅፋል።
ሰለሞን ……አደረገ
ይህን ሥራ ሰለሞን ሠራተኞቹን እንዲሠሩ አዞ ይሆናል። ተርጓሚ “ሠለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አደረገ”
ዙፋን ያለበት የፍርድ ቤት
አማራጭ ትርጉሞች 1) “ዙፋኑን የሚያኖርበት ቤት” 2) “የንጉሡ መቀመጫ ቤት ተብሎ የተሰየመ ቤት”
በዝግባ እንጨት ተሸፍኖ ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “ሠራተኞቹ ወለሉን በዝግባ እንጨት ሸፈኑት”
1 Kings 7:8
አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ስለ ቤተ-መንግሥት ዙሪያ መፃፉን ቀጥሏል።
በሌላውም አደባባይ ወስጥ የነበረውን መኖርያ ቤት እንዲሁ ሠራ
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “ሰለሞን በዚሁ መልኩ በሌላ አደባባይ የሚሠራለት ሠው ነበረው”
እንዲሁ ሠራ
ይህን ሥራ ሰለሞን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “እንዲሁ እንዲሠሩ አዟቸው ነበር”
1 Kings 7:9
አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊ ለሕንፃው ሥራ ስለተጠቀሙት ድንጋይ ይፅፋል።
እነዚህም …..በጥሩ በተጠረበና ….በልክ በተከረከመ ድንጋይ ተሠርተው ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሠራተኞቹ በጥሩ በተጠረበና… በልክ በተከረከመ ድንጋይ አስጊጠው ነበር።”
በልክ በተከረከመ ድንጋይ…. በታላቅ ድንጋይ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሠራተኞች በልክ በከረከሙት በታላቅ ድንጋይ።”
በ…..ድንጋይ ተሠርተው ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል ተርጓሚ “ሠራተኞቹ በ…..ድንጋይ ሠርተው ነበር።”
ከመሠረቱ ጀምሮ እስከ ጉልላቱ ደረስ …….በውስጥና በውጭ
ፀሐፊው ሠራተኞቹ ለመሠረቱና በጠቅላላው ህንፃ ሥራ ውድ ድንጋዮችን መጠቀማቸውን አፅንኦት እየሠጠ ነው።
መሠረቱም ….ተሠርቶ ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሠራተኞቹ መሠረቱን …… ሠርተው ነበር።”
አስር ወይም ስምንት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ.ነው። ተርጓሚ “4.6 ሜ ገደማ 3.7 ሜ”
1 Kings 7:11
የዝግባ ሳንቃ
ሳንቃ (በሌላ ቦታ አግዳሚ) ረጅም እንጨት ሆኖ ለድጋፍ የሚያገለግል ነው
ሦስቱ ተራ በተጠረበ ድንጋይ አንዱም ተራ በዝግባ ሳንቃ
የ1ኛ ነገሥት 6፡ 36 ትርጉም ተመልከት።
1 Kings 7:13
ከጢሮስ አስመጣ
ኪራም የንጉሥ ሰለሞንን ግብዣ ተቀብሎ ወደ እዬሩሳሌም ሊመጣ
የባል አልባ ሴት ልጅ……አባቱም የጠሮስ ሰው
ባል አልባ ማለት ባሉዋ የሞተባት ሴት መሆኗን እናውቃለን
ኪራም……በጥበብና በማስተዋል በብልሃትም ተሞልቶ ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ጥበብና ማስተዋል የሚሉት ቃላት በመሠረቱ አንድ አይነት ነገር ሲሆኑ አፅንኦት ለመስጠት በጋራ ይሆናሉ። ጥበብ ልክ እንደሚፈስ ፈሳሽ እግዚአብሔር ወደ እቃ እንደሚያፈስ አይነት ነገር ሆኖ ተነግሮአል። እናም ኪራም ልክ እንደዚያ ዕቃ እንደነበር ሆኖ ተገልጿል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር ለኪራም ጥበብ ማስተዋልና ብልሃትን ሠጠው።”
1 Kings 7:15
አስራ ስምንት ክንድ ….አስራ ሁለት ክንድ …አምስት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው። 8.3 ሜ ገደማ 5.5 ሜ…..2.3 ሜ.
የዙርያውም
ዙርያ የአንድ ክብ የሆነ ነገር ርዝመት ወይም ልኬት ነው።
ሁለቱን ጉልላት
በሁለቱም ምሰሶዎች እያንዳዳቸው የተዋቡ
ከፈሰሰ ናስ
የፀሐይ ብርሃን እንዲያንፀባርቅ ነሐስ አፈሰሱ (ወለወሉ) “የሚያንፀባርቅ ነሐስ”
1 Kings 7:18
ሠራ
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዘዘ”
ሮማኖችንም …..ሁለት ተራ
ሮማን የፍራፍሬ አይነት ሲሆን ጠንካራና ቀይ ሽፋንና በውስጡ የሚጨመቁ ፍሬዎችን ይዟል። ኪራም እውነተኛውን የሮማን ፍሬ ለማስዋብያነት አልተጠቀመም የተጠቀመው ከነሃስ የተሠሩ የሮማን ፍሬዎች ናቸው።
ጉልላቶች ላይ የሱፍ አበባ የሚመስል ሥራ አራት ክንድ አድርጎ ቀረፀ
የሱፍ አበባ አበባቸው በአንድ ጥግ ሠፋ ብሎ በአንድ ጥግ ደግሞ ጠባብ ነው። እነዚህ ቃላት በገቢር መልኩ ሊቀመጡ ይችላሉ። ተርጓሚ “ ኪራም ጉልላቶቹን ከነሃስ በተሰሩ የሱፍ አበባዎች አራት ክንድ ከፍ አድርጎ አስዋበ”
በወለሉም አዕማድ
የ1 ነገስት 7፡6 ትርጉምን ተመልከት
አራት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው ተርጓሚ “1.8 ሜ. ገደማ።”
1 Kings 7:20
ሁለት መቶ ሮማኖች
“200 ሮማኖች” የነገስት 7፡18 ትርጉም ተመልከት
አቁሞ
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ ”አቆሙ”
የቀኙንም ዓምድ አቁሞ ያቁም ብሎ ጠራው
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “በቀኝ በኩል ያለው አምድ ያቁም ይባላል።”

የግራውንም ዓምድ በለዝ ብሎ ጠራው።
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “በግራ በኩል ያለው አምድ በለዝ ይባላል።”
የአዕማዱ ሥራ ተጨርሶ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ኪራም አምዶቹን ጨርሰ” ወይም “የኪራም ሰዎች አምዶቹን ጨረሱ”
1 Kings 7:23
ሠራ
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “እንዲሠራ አዘዛቸው”
ክብ ኩሬ
ይህ ከነሃስ የተሠራ የውሃ ማቆሪያ ወይም ውሃ የሚያቁር ሥፋራን ይገልፃል።
በቀለጠ……
ኪራም ነሃስ አቅልጦ ቅርፅ አበጀ
አስር ክንድ… አምስት ክንድ… ሰላሳ ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው። ተርጓሚ 4.6ሜ….2.3 ሜ…13.8ሜ
ከዳር እስከ ዳር
ከአንድ ጠርዝ እስከ ሌላኛው
ዙሪያ
ዙርያ የአንድ ክብ የሆነ ነገር ርዝመት ወይም ልኬት ነው።
ኩሬ በጉብጉቦች አዞረ
ጉብጉብ (ቅል) ጠንካራ ክብ እንደሀረግ በመሬት ላይ የሚያድግ ተክል ነው።
ክብ ሠራ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ኪራም በተሠራ ክብ”
1 Kings 7:25
ኩሬውም
ይህ ለመስዋዕትነት የተዘጋጀ የውሃ ማቋሪያ ነሃስን ወይም ጉድጓድን ይገላፃል ።
ላይ ተቀምጦ ነበር
“ከላይ ነበር”
ኩሬውም በላያቸው ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የኪራም ሠራተኞች ኩሬውን በነሃስ በተቀረፁ በሬዎች ላይ አስቀምጠው ነበር”
ከንፈሩም እንደ ፅዋ ከንፈር ተሠርቶ ነበር እንደ ሱፍ አበባዎች ሆኖ ተከርክሞ ነበር።
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ ኪራም ከንፈሩን የፅዋ ከንፈር እንዲመስል አድርጎ ሠራው ወደ ወጭም እንደ ሱፍ አበባ ሆኖ ተከረከመ።
ሁለት ሺህም የባዶስ
ባዶስ የፈሳሽ መስፈሪያ ሲሆን ከ22 ሊትር ጋር ይስተካከላል። ተርጓሚ “2,000 ባዶስ” ወይም “44,000 ሊትር”
1 Kings 7:27
ሠራ
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ ኪራምም እንዲሠሩ አዘዛቸው ወይም “እነርሱም ሠሩ”
አራት ክንድ… ሦስት ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው። ተርጓሚ “1.8 ሜ ገደማ …1.4ሜ”
የመቀመጫውም ሥራ እንዲህ ነበር
ይህ ማለት ፀሐፊው መቀመጫውን በሚከተለው መልኩ ይገልፃል።
በክፈፎቹም መካከል በነበሩ ሰንበሮች ላይ አንበሳዎችና በሬዎች ኪሩቤል ነበሩ
በአንበሳዎች፤በበሬዎችና በኪሩቤል ቅርፆች ተውበው በመቀመጫዎቹ ጎኖች ተያይዛዋል። ሰን እዚህ ጋር ሰን (የመታጠቢያ) ሞላላ ቅርፅ ያለው ነሐስን ይገልፃል።
1 Kings 7:30
አራት የናስ መንኩራኩሮች ……ወሰከምት
ለእያንዳንዱ ጥንድ መንኩራኩር አንድ ወሰከምት ነበር። ተርጓሚ “አራት የናስ መንኩራኩሮች እና ሁለት መሰከምቶች”
በአራቱ ማዕዘን
“የእያንዳንዱ መቀመጫ አራት ጎኖች
የመታጠቢያ ሰን……እግሮች
እያንዳንዱ እግር ከመታጠቢያ ሰን ጋር በአንድ ላይ ነበር። ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ኪራም እግሮቹን (ድጋፎቹን) ሞላላ ቅርፅ ካላቸው ጋር አያያዘ።”
አንድ ክንድና ተኩል …….አንድ ክንድ
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው። ተርጓሚ “70 ሳ.ሜ. ገደማ ….50 ሳ.ሜ.”
ክፈፉ ግን አራት ማዕዘን ነበር
የመቀመጫዎች ክፈፎች አራት ማዕዘን ነበሩ። ይህ ሐረግ ወደ 1ነገስት 7፡ 28- 29 ማብራርያ ይመልሰናል።
1 Kings 7:32
ሰንበሮቹ
ሰንበሮቹ ወሰከምትን ይወክላሉ ሰንበር ወሰከምቶቹ የሚገቡበትን ቧንቧ ይወክላል።
አንድ ክንድ ተኩል
አንድ ክንድ 46 ሳ.ሜ. ነው። ተርጓሚ “70 ሳ.ሜ. ገደማ
የመንኩራኩሮቹም ሥራ እንደ ሠረገላ መንኩራኩር ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ያችላል። ተርጓሚ “ኪራም መንኩራኩሮቹን እንደ አነስተኛ ሠረገላ መንኩራኩር ሠራ”
ወሰከምቶቹ……ክፈፉ……ቅትርቶቹም
“ቹም” የሚለው ቅጥያ…….መንኩራኩሩን ይወክላል።
1 Kings 7:34
በእያንዳንዱ መቀመጫ በአራቱም ማዕዘን በኩል አራት ደጋፊዎች ነበሩ
“በእያንዳንዱ መቀመጫ በአራቱም ማዕዘን መደገፊያ ነበር”
ስንዝር…ነገር ነበር
“ስንዝር” የአንድ ክንድ ግማሽ ሲሆን 1 ክንድ 46 ሳ.ሜ ነው። ተርጓሚ “23 ሳ.ሜ ስፋት”
በመቀመጫውም ላይ የነበሩ መያዣዎችና ሰንበሮች ከእርሱ ጋር ይጋጠሙ ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ኪራም በእያንዳንዱ መቀመጫ ላይ መያዣዎችና ሰንበሮችን አያይዟል።”
1 Kings 7:36
ቀረፀ…አደረገ
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሰሩ አዞ ይሆናል። ተርጓሚ “እነርሱ ቀረፁ… እንዲሰሩ አዘዛቸው”
በዙሪያውም…አደረገ
“ውም” የሚለው ቅጥያ …ኪሩቤልን፣ አንበሶችንና የወይራ ዛፍን ይወክላል።
በዙሪያውም ሻኩራ አደረገ
“ሻኩራ” የሚለው ቃል ድቡልቡል ቅርፅ ያለው ናስን ይገልፃል። ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “በሁሉም ዙሪያ ሻኩራ ነበር”
ሁሉም በምስልና በመጠን በንድፍም ትክክሎች ነበሩ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ ኪራም ሁሉንም መቀመጫዎች በአንድ ንድፍ ሠራቸው ወይም “ሁሉንም መቀመጫዎች በአንድ አይነት ንድፍ ሠሩዋቸው”
ሁሉም በምስልና በመጠን….ትክክሎች ነበሩ
ሁሉም መቀመጫ ተመሣሣይ መጠንና ምስል ነበራቸው።
1 Kings 7:38
አሥሩንም…ሠራ..አምስቱንም ….አኖራቸው…አኖረው
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሰሩ አዞ ይሆናል። ተርጓሚ “ኪራም አስር እንዲሰሩ አደረገ….ኪራም አምስት እንዲያኖሩ አደረገ…እንዲያኖሩት አዘዛቸው”
አርባ የባዶስ መስፈርያ
ባዶስ የመጠን መለኪያ ሲሆን ከ22 ሊትር ጋር ይስተካከላል። ተርጓሚ “88 ሊትር ገደማ” ወይም “90 ሊትር ገደማ”
አራት ክንድ
አንድ ክንድ 46ሣ.ሜ ነው ተርጓሚ “ 1.8ሜ ገደማ”
በቤቱ ቀኝ ……በ….ግራ
በቀኝ በኩል……... በግራ በኩል
በቤቱ ቀኝ በአዜብ በኩል
በሁለቱ አቅጣጫዎች መካከል።
1 Kings 7:40
ኪራምም …….ሠራ ጨረሰ
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ “ኪራም እንዲሠሩ አደረገ…….ጨረሱ”
ኩብ የሚመስሉትን ጉልላቶች
ጉልላቶች በኩብ ቅርፅ ተቀርፀዋል።
መርበቦች


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እርስ በርስ የተጠላለፈ የብረት ዘንጎች
1 Kings 7:42
አደረገ
ይህን ስራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "ሰሩ"
አራት መቶ ሮማኖች
400 ሮማኖች ሮማን የፍራፍሬ አይነት ሲሆን ጠንካራና በቀይ ሽፋን ተሸፋኖ በውስጡ የሚጨመቁ ፍሬዎች አሉት። የ1ነገስት 7:18 ትርጉምን ተመልከት።
1 Kings 7:44
አደረገ.........
ይህን ሥራ ኪራም ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዟቸው ይሆናል። ተርጓሚ "አደረጉ"
ይህ ዕቃ ሁሉ
"ይህ መሣሪያ (መገልገያ)ሁሉ"
የጋለ ናስ
"ፀሐይ እንዲያንፀባርቅ ሆኖ የጋለ (የተዘጋጀ) ናስ"
1 Kings 7:46
ሰለሞን.......ሳያመዛዝን አኖረ
ይህ ስራ እንዲሠራ ሠለሞን ሠራተኞቹን አዞ ይሆናል። ተርጓሚ "ሰለሞንም ......... ሳያመዛዝን ሰራተኞቹ እንዲያኖሩ አድርጓል"
በዮርዳኖስ ሜዳ
"ሜዳማ (ጠፍጣፋ) በዮርዳኖስ ወንዝ ዳር የሚገኝ ሜዳማ መሬት"
በሱኮትና በፀርታን
"የከተሞች ስም"
የናሱም ሚዛን...........አይቆጠርም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "የናሱን ሚዛን ማንም ሊቆጥር አልቻለም"
1 Kings 7:48
ሰለሞንም.......አሠራ
ይህ ሥራ እንዲሠራ ሰለሞን ሠራተኞቹን አዞ ይሆናል። ተርጓሚ "የሰለሞን ሰራተኞች ሠሩ(አሠሩ)"
የገፁም ኅብስት የነበረበትን..........ገበታ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ካህናቱ የገፁን ኅብስት የሚያኖሩበት ገበታ"
የአበባዎችና ቀንደሎች
"አበባዎችና" "ቀንዲሎች" የፋኖሱ አንድ አካል
1 Kings 7:50
ከጥሩ ወርቅ የተሠረሰሩትን ፅዋዎች......አሠራ
ይህ ሥራ እንዲሠራ ሰለሞን ሠራተኞቹን አዞ ይሆናል። ተርጓሚ "ሠራተኞቹ ከጥሩ ወርቅ ፅዋዎች እንዲሰሩ አደረገ"
ለደጆች የሚሆኑትን የወርቅ ማጠፊያዎች አሠራ
እዚህ ጋር ማጠፊያ 1) በሩ የሚያያዝበት ብረት ወይም 2)በሩ የሚንጠለጠልበት ብረት ሊሆን ይች
1 Kings 7:51
ንጉሥ ሰለሞን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያሠራው ስራ ሁሉ ተፈፀመ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ሠራተኞቹ ንጉስ ሰለሞን እንዲሠሩ ያዘዛቸውን የእግዚአብሔርን ቤት ሠርተው ፈፀሙ"

---

Chapter 8
1 Kings 8:1
የእስራኤልን ሽማግሌዎች......... ሰበሰበ
"የእስራኤልን ሽማግሌዎች አንድ ላይ ጠራ"
የእስራኤል ሰዎች
ይህ አንድም 1) በ8፡1 ላይ የተዘረዘሩትን ሰለሞን ወደ እየሩሳሌም የጠራቸው ወይም 2) "በአጠቃለይ ለድግሱ ወደ እየሩሳሌም የተጓዙትን ሁሉ" ሊገልፅ ይችላል።
በበዓሉ
ይህ የሱኮትን ድግስ (በዓል) በተለምዶ የቤተ-አምልኮ ድግስ በመባልም ይታወቃል።
ኤታኒም በሚባል በሰባተኛው ወር
ኤታኒም በዕብራዊያን የቀን አቆጣጠር ሰባተኛው ወር ሲሆን በምዕራባዊያኑ ቀን አቆጣጠር የመስከረም ወር መገባደጃ ሳምንት ወይም የጥቅምት ወር የመጀመርያዎቹ ሳምንት ነው።
1 Kings 8:3
የእስራኤል ማህበር ሁሉ
ይህ በጥቅል ነው
የማይቆጠሩትን .........በጎችና በሬዎች
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል የበዙ በጎችና በሬዎች"
1 Kings 8:6
በቤቱ በቅድስተ-ቅዱሳን ውስጥ ......በታች
"ወደ ውስጠኛው የቤቱ ክፍል ያም በጣም ወደ ተቀደሰው ስፍራ .......በታች"
መሎጊያዎቹም...........ነበሩ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። "ካህናቱ ይሸከሙበት የነበሩ መሎጊያዎች"
1 Kings 8:12
እግዚአብሔር በጨለማው..........ብሎአል
ሰለሞን ለእግዚአብሔር ያለውን ክብር ለማሳየት ከሆነ ሰው ጋር እያወራ ያለ በማስመሰል ይናገራል።
ማደርያ ቤት
በጣም የተከበረ ሰው የሚኖርበት መኖርያ ቤት
1 Kings 8:14
የእስራኤል ጉባዔ ሁሉ
"በዚያ የተሰበሰበው የእስራኤል ህዝብ ሁሉ"
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን
ይህ እንዳለ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ
በእጁም
"እጅ" በእጁ ውስጥ ላለው ጉልበት የዘይቤ ንግግር ነው። ተርጓሚ "በጉልበቱም"
ስሜ በዚያ ይሆን ዘንድ
"ስሜ" ለአንድ ሰው የዘይቤ ንግግርና የሚመለክ ሰው ስም ነው። የነገስት 3:2 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "ሰዎች ያመልኩኝ ዘንድ"
1 Kings 8:17
አባቴ ዳዊት .......በልቡ አሰበ .... በልብህ አስበሃልና......በልብህ ማሰብህ
ዳዊት የተመኘውን በመያዣ ውስጥ እንዳለ ዕቃ አድርጎ ሲናገር ልብን ደግሞ እንደ ዕቃ መያዣ አድርጎ ይናገራል። ተርጓሚ "አባቴ ዳዊት ተመኘ .....ለማድረግ መመኘት......ተመኘህ"
ለእግዚአብሔር ስም........ ለስሜ
"ስም" ለአንድ ሰው የዘይቤ ንግግርና የሚመለክ ሰው ስም ነው። የነገስት 3:2 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ቤት ....."ሰዎች እኔን የሚያመልኩበት ቤት"
1 Kings 8:20
የተናገረውን ቃል አፀና
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ "ልክ እንደተናገረው አደረገ"
በአባቴ በዳዊት ፋንታ ተነሣሁ
ከፍታ የጉልበተኛነት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ "አባቴ ዳዊት የነበረውን ጉልበት አገኘው"
በእስራኤል ዙፋን ላይ ተቀመጥሁ
"ዙፋን" በዙፋን ላይ ተቀምጠው ስለሚሠራ ሥራ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ "በእስራኤል ላይ አገዛለሁ"
ለእግዚአብሔር ስም
"ስም" ለአንድ ሰው የዘይቤ ንግግር ነውና የሚመለክ ሰው ስም ነው። 1ነገስት 3፡2 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት"
የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ባለበት....... በዚያ
እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን የፃፈበት ድንጋይ እራሱ ቃል ኪዳን እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። ተርጓሚ "እግዚአብሔር ቃልኪዳኑን የፃፈበት ድንጋይ ናቸው (በዚያ)"
1 Kings 8:22
የእስራኤል ጉባኤ ሁሉ
"የተሰበሰቡ የእስራኤል ህዝብ ሁሉ"
ለባሪያዎችህ ቃል ኪዳንና ምህረትን የምትጠብቅ
ተርጓሚ በታማኝነት ቃልኪዳንህን የምትወድ ወይም "ለቃል ኪዳንህ ታማኝ የሆንክ"
በፍፁም ልባቸው በፊትህ ለሚሄዱ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሰው የአኗኗር ዘይቤ ልክ ሰው በመንገዱ እንደሚሄድ ተደርጎ ተነግሯል። ተርጓሚ “አንተ እንዲኖሩ የምትፈልገውን ኑሮ በሙሉ ልባቸው መኖር”

በእጅህ ፈፀምኸው

“እጅ” በእጅ ውስጥ ላለው ጉልበት ዘይቤ ነው “ በጉልበትህ ያልከውን ፈፀምኽ”

1 Kings 8:25

በእስራኤል ዙፋን የሚቀመጥ

“ዙፋን” በዙፋን ላይ ተቀምጠው ለሚሰሩት ሥራ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “በእስራኤል ላይ ለመግዛት

በፊቴ እንደ ሄድህ ....... መንገዳቸውን ቢጠብቁ

የሰው የኑሮ ዘይቤ አንድ በመንገድ እንደሚሄድ ተደርጎ ተነግሮአል። ተርጓሚ “እንደምፈልገው ኖረሃል.....እኔ እንደምፈልገው ቢኖሩ”

1 Kings 8:27

በውኑ እግዚአብሔር........በምድር ላይ ይኖራልን?

አማራጭ ትርጉሞች 1)ሰለሞን ጥያቄ ጠይቆ ትክክለኛውን መልስ እየጠበቀ ነው። 2) ጥያቄው የግነት ሲሆን ሰለሞን እግዚአብሔር በመሬት ላይ ለመኖር ትልቅና ገናና ሆነ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ “በእርግጥ እግዚአብሔር በምድር ላይ ለመኖር አይቻለውም!”

በውኑ እግዚአብሔር

እዝህ ጋር ሰለሞን ስለ እግዚአብሔር እንደ ሦስተኛ ወገን አድርጎ ይናገራል።እንደ ሁለተኛ ወገን ሊቀመጥ ይችላል። “በውኑ አንተ”

ተመልከት

“እኔ ልናገር ያለው ጠቃሚ ነው” ወይም “እውነታው ያ ነው”

ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ

“ስለዚህ ይህ እኔ የሠራሁት ቤት በእርግጥ አንተን ሊይዝ አይችልም”

ወደ ባሪያህ ፀሎትና ልመና ተመልከት

“ፀሎት” ና “ልመና” የሚሉት ቃል በመሰረቱ በትርጉም ተመሣሣይ ሲሆኑ ጥያቄውን ሲያቀርብ ትሁት እንደነበር አፅንኦት ለመስጠት ነው። ሰለሞን እራሱን “ባሪያህ” ብሎ ይገልፃል።ይህም ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮት ለማሳየት ነው። ይህ እንደ አንደኛ ወገን ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እንድትረዳኝ ዛሬ ስጠራህ እኔ ባሪያህን አድምጠኝ”

1 Kings 8:29

ወደዚህ .........ዓይኖችህ ...........ይሁኑ

ዓይን የአንድ ሰው ሁለንተና ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ወደዚህ ተመልከት”

ሌሊትና ቀን

ተርጓሚ “ሁልጊዜ” ወይም “(ሳታቋርጥ)”

በዚያ ስሜ..................ስፍራ

እነዚህ ሁለት ቃላት እግዚአብሔር በመቅደስ እንደሚኖር አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ባሪያህ ...............የሚፀልየውን

ሰለሞን ስለራሱ “ባሪያህ” እያለ ይናገራል። ይህም ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮት ለማሣየት ነው። ይህ እንደ አንደኛ ወገን ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እኔ ባሪያህ… የምፀልየውን”

የባሪያህና ሕዝብህ እስራኤል ......ልመና ሰማ

ሰለሞን ስለራሱ “ባሪያህ” እያለ ይናገራል። ይህም ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮት ለማሳየት ነው። ይህ እንደ አንደኛ ወገን ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የእኔ የባሪያህንና የሕዝብህ እስራኤልን ልመና ሰማ”

1 Kings 8:31

መሐላ ቢጫን

ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የሆነ ሰው እንዲምል ጠየቀው”

በላዩም

እዚህ ጋር በላዩም የሚለው ቃል ሙሉ ሰውነትን (ሰውን) ይወክላል። ተርጓሚ “በላዩ”

እንደ ፅድቁም ክፈለው

“ፃድቅ ስለሆነ የሚገባውን መክፈል”

1 Kings 8:33

ሕዝብህ እስራኤል .......... በጠላቶቻቸው ፊት ድል በተመቱ ጊዜ

ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ጠላት ሕዝብህ እስራኤልን ድል በመታ ጊዜ”

ቢመለሱ ስምህን ሊያከብሩ

አማራጭ ትርጉሞች 1) “አንተን እንደበደሉ ቢናዘዙ ወይም 2) ቢያመሰግኑህ” ወይም 3) “ከዚህ በኋላ እንታዘዝሃለን ቢሉ”

ቢለምኑህ

ተርጓሚ “ይቅር እንድትላቸው ቢጠይቁህ”

1 Kings 8:35

ሰማይ በተዘጋ ጊዜ ዝናብም ባልዘነበ ጊዜ

“ሰማይ” ልክ እግዚአብሔር ዝናብ እንደሚያጠራቅምበት ውሃ መያዣ ተደርጎ ተነግሮአል። ተርጓሚ “ዝናብ እንዲወርድ (እንዲዘንብ) አትፈቅድም”

ስምህንም ቢያከብሩ

የ1ነገስት 8፡33 ትርጉምን ተመልከት አማራጭ ተርጉሞች 1) “አንተን እንደበደሉ ቢናዘዙ ወይም 2) ቢያመሰግኑህ” ወይም 3) “ከዚህ በኋላ እንታዘዝሃለን ቢሉ”

የሚሄዱበትንም

የሰው የኑሮ ዘይቤ በመንገድ እንደሚጓዝ ሰው ተመስሏል። ተርጓሚ “የሚኖሩበትንም”

1 Kings 8:37

ዋግ ወይም አረማሞ

እነዚህ የግብርና ቃላት ሲሆኑ በዝናብ እጥረት ወይም ብዛት የምርት መሞትን ይገልፃል።

አንበጣ ወይም ኩብኩባ

አንበጣ እህልን በመብላት የሚያጠፋ ነው። ኩብኩባ ደግሞ በማደግ ላይ ያለ አንበጣ ነው።

የሕዝብህም............ማናቸውም ሰው...........ፀሎትና ልመና ቢፀልይ

ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ማንም ሰው ወይም ሕዝብህ ሁሉ ቢፀልዩ”

ፀሎትና ልመና

ፀሎትና ልመና በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም ሲኖራቸው አንድ ሰው ልመናን ሲያቀርብ አፅንኦት ለመስጠት ነው። የ1ነገስት 8፡28 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ልመናዎች”

የልቡን ሕመም አውቆ

አማራጭ ትርጉሞች 1)የሠውየው ኃጢአት እንደሕመም ተነግሮአል። ተርጓሚ “በልቡ ያለውን ኃጢአት አውቆ” ወይም 2) “ሕመም በኃጢአት ምክንያት ለሚሆን ጥቃት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ ሕመሙ የራሱ ኃጢአት ውጤት መሆኑን አውቆ”

1 Kings 8:41

ብርቱይቱንም እጅህን የተዘረጋውንም ክንድህን

እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረቱ አንድ ሲሆኑ የእግዚአብሔርን ኃይል ይገልፃሉ

በዚህ በሠራሁት ቤት ስምህ እንደተጠራ

“ስምህ እንደተጠራ” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር የቤቱ ባለቤት መሆኑን ይገልፃል።ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ እኔ የሰራሁት ቤት ባለቤትነቱ የአንተ ነው።”

1 Kings 8:44

ሕዝብህም ..........ቢወጡ......ቢፀልዩ

ሰለሞን ሲናገር ይህ መላ-ምታዊ ሁኔታ አልተከሰተም ነገር ግን ወደፊት እንደሚከሰት ሰለሞን አውቋል።

ለስምህ

“ስም” የሚለው ቃል ለአንድ ሰው ዘይቤ ሲሆን ለ “ስም” የሚገልፀው የሚመለክ ስም መሆኑን ነው የ1ነገስት 3፡2 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “ሰዎች አንተን የሚያመልኩበት”

ፀሎታቸውንና ልመናቸውን

ፀሎትና ልመና በመሰረቱ ተመሣሣይ ትርጉም ሲኖራቸው ሠዎች ልመናን ለማድረግ ትሁት መሆናቸውን ለማሣየት አፅንኦት ለመስጠት ነው። የ1ነገስት 8፡28 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ልመናቸው”

1 Kings 8:46

ቢበድሉ..........በ....ሆነው........ንስሐ ቢገቡ

ሰለሞን ሲናገር ይህ መላ-ምታዊ ሁኔታ አልተከሰተም ነገር ግን ወደፊት እንደሚከሰት ሰለሞን አውቋል።

በተማረኩበትም አገር

ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እንደ ስደተኞች ጠላቶቻቸው ወደ ወሰዷቸው ቦታ”

ማራኪዎች

ሌሎችን እንደ እስረኛ የሚጠብቁ ሰዎች

ኃጢአት ሠርተናል በድለንማል ክፉንም አድርገናል

ሁለቱ አንድ አይነት ናቸው። ሁለቱ አንድ ላይ ምን ያህል የሰዎች ድርጊት መጥፎ እንደሆነ አፅንኦት ለመስጠት ነው።
ኃጢአት ሠርተናል በደለንማል
ሁለት አንድ አይነት ነገር ሲሆኑ ምን ያህል ሰዎች እንደበደሉ አፅንኦት ለመስጠት ነው።
1 Kings 8:48
በፍፁም ልባቸውና በፍፁም ነፍሳቸው
በፍፁም ልባቸው የሚለው ፈሊጣዊ "ፈፅሞ" ማለት ሲሆን በፍፁም ነፍሳቸው የሚለው ደግሞ በሁለንተናቸው ማለት ነው። እነዚህ ሁለቱ ሀረጎች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው የ1ነገስት 2፡4 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "በሁለንተናቸው" ወይም "በሙሉ ኃይላቸው" በ…አገር "በምድራቸው ሲኖሩ ሳለ" ወደ ምድራቸው "ወደ እነርሱ ወደ ሆነው ምድር" ይህ የእስራኤል ህዝብን ይገልፃል።
ለስምህ
"ስም" የሚለው ቃል ለአንድ ሰው ዘይቤ ሲሆን ለ "ስም" የሚገልፀው የሚመለክ ስም መሆኑን ነው። የ1ነገስት 3፡2 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "ሰዎች አንተን የሚያመልኩበት"
1 Kings 8:49
ፀሎታቸውንና ልመናቸውን
x
1 Kings 8:51
ከብረት እቶን
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ሰዎች ብረት ከሚያቀልጡበት ከእቶን"
ዓይኖችህ የተገለጡ ይሁኑ
ዓይን ለሙሉ ሰው ዘይቤ ነው ተርጓሚ "እባክህ ትኩረት ስጥ"
1 Kings 8:54
ፀሎትና ልመና
ፀሎትና ልመና በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም ሲኖራቸው አንድ ሰው ልመናን ሲያቀርብ አፅንኦት ለመስጠት ነው። የ1ነገስት 8፡28 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "ልመናዎች"
እግዚአብሔር ይመስገን
ይህ በሌላ መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ይመስገን እግዚአብሔር"
ከመልካም ተስፋ ሁሉ አንድ ቃል አልወደቀም
ይህ በሌላ መልኩ ሊቀመጥ ይችላል ተርጓሚ "እግዚአብሔር መልካም ተስፋ ቃሉን ሁሉ ፈፀመ (አደረገ)"
1 Kings 8:57
አይተወን አይጣለንም
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ በትርጉም አንድ ሲሆኑ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር እንዲሆን ለሰለሞን ምኞት አፅንኦት ለመስጠት ነው።
ልባችንን ወደ እርሱ ያዘነብል ዘንድ
እዚህ ጋር ልብ የሰዎችን ምኞትና ስሜት ይወክላል። አንድን ሰው ለማስደሰት መመኘት ወደ እዚያኛው ሰው ልብ እንደሚያዘነብል ተደርጎ ተነግሮአል። ተርጓሚ እርሱን ለማስደሰት እንድንመኝ አድርግ
በመንገዱም ሁሉ እንሄድ ዘንድ
እዚህ ጋር "በመንገዱም" እርሱ ሰዎች እንዲሄዱበት ለሚፈልገው መንገድ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ "እርሱ እንዲሚፈልግብን መኖር"
1 Kings 8:59
በቀንና በሌሊት
"ሁል ጊዜ" ወይም "ሳይቋረጥ"
ልባችሁ ንፁህ ይሁን
"ሙሉ በሙሉ የተሰጣችሁ ሁኑ"
በሥርዓቱ ትሄዱ ዘንድ
የሰው የኑሮ ዘይቤው መንገድን እንደሚጓዝ ሰው ሆኖ ተነግሮአል። ተርጓሚ "ሁል ጊዜ በሥርዓቱ ሂዱ"
1 Kings 8:62
ሀያ ሁለት ሺህ በሬዎች
22,000 በሬዎች
መቶ ሃያ ሺህ በጎች
x
1 Kings 8:65
ከእርሱም ጋር እስራኤል ሁሉ……..የእስራኤል ልጆች ሁሉ
እነዚህ ጥቅል ሐረጎች አንድም 1)1ነገስት 8፡1 ላይ የተዘረዘሩትን ሰለሞን ወደ እዬሩሳሌም የጠራቸው ወይም 2) ለግብዣው ወደ እዬሩሳሌም የተጓዙትን ነው በእስራኤል የሚኖር ሁሉ ላይሆን ይችላል።
ስምንተኛው ቀን
ስምተኛው የሚለው ቃል ለ"8" ተራ ነው
ተደስተው ሐሤትም
ሁለቱም በመሠረቱ አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው የተቀናጁትም አፅንኦት ለመስጠት ነው።

---

Chapter 9
1 Kings 9:3
ፀሎትህንና ልመናህን
ፀሎትና ልመና በመሠረቱ አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው የሰለሞን ጥያቄ ከቅንነት እንደሆነ እግዚአብሔር እውቅና እንደሠጠው አፅንኦት ለመስጠት ነው የ1ነገስት 8፡ 28 ትርጉምን ተመልከት።
ለዘላለምም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ
"ስም" ለአንድ ግለሰብ ዘይቤአዊ ነው። ተርጓሚ "ለዘላለም በዚያ ለመኖርና ባለቤትነት ማሳያ"
ዓይኖቼና ልቤም …….በዚያ ይሆናሉ
"ዓይንና ልብም" የሰውን ሙሉ ሁለንተና ዘይቤ ናቸው። ተርጓሚ "ጥበቃና ጥንቃቄ አደርግለታለው"
1 Kings 9:4
ዳዊትም አባትህ ……….. እንደ ሄደ አንተ ደግሞ በፊቴ ብትሄድ
የሰው የኑሮ ዘይቤው መንገድን እንደሚጓዝ ሰው ሆኖ ተነግሮአል። ተርጓሚ "ዳዊትም አባትህ….እንደ ኖረ አንተ ደግሞ ካንተ እንደምጠብቀው ብትኖር"
በየዋህ ልብና በቅንነት
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ ተመሣሣይ ሲሆኑ ዳዊት ምን ያህል ፃድቅ እንደነበር አፅንኦት ለመስጠት ነው።
1 Kings 9:6
ትእዛዜንና ሥርዓቴን
እዚህ ጋር ትእዛዝና ሥርዓት በመሰረቱ አንድ አይነት ነገር ሲሆኑ እግዚአብሔር እንዳዘዘ አፅንኦት ለመስጠት ነው።
ሌሎችን አማልክት ብታመልኩ ብትሰግዱላቸውም
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በመሠረቱ አንድ አይነት ሲሆኑ የተጣመሩትም አፅንኦት ለመስጠት ነው።
ለስሜም……..እጥለዋለሁ
እዚህጋር "ስም" የሚለው ቃል የሆነ ነገር ላለው ሰው ዘይቤ ነው። ተርጓሚ "ለራሴም ……..እጥለዋለሁ"
ከፊቴም እጥለዋለሁ
"ከፊቴ" የሚለው ስውር ቃል "እይታ" ከሚለው ግስ ጋር ሊገለፅ ይችላል ወደ አንድ ነገር መመልከት ለሚደረግለት ጥበቃ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ "ከዚህ ወዲህ ወደማላየው ቦታ አስቀምጠዋለሁ" ወይም "ከዚህ በኋላ ጥበቃ ስለማደርግለት አስወግደዋለው"
1 Kings 9:8
ይህ ቤት ባድማ ይሆናል
"ይህ ቤት" (ቤተ-መቅደስ) ይፈርስና ቅሪቱም ቁልል አፈር (ድንጋይም)ይሆናል።
"እያፋዋጩ …………. ይደነቃል"
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "አድናቆትና የሚያዋርድ ድምፅ ያሰማል"
ሰገዱላቸውም…………… አመለኩዋቸውም
ሁለቱ ቃላት በመሠረቱ አንድ አይነት ናቸው። "ሰገዱላቸውም" የሚለው ቃል ሰዎች ለአምልኮ የሚጠቀሙትን የሰውነት አቋም ይገልፃል።
1 Kings 9:10
ሀያ ዓመት በተፈፀመ ጊዜ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ከ20 ዓመት በኃላ”
ሰለሞንም ........ቤት የሠራበት
ቤቱን ለመስራት ሰለሞንን ሌሎች ሰዎች እንደረዱት አንባቢው በሚረዳበት መንገድ መተርጎም የተሻለ ነው፡፡
1 Kings 9:12
ወንድሜ ሆይ የሰጠኸኝ እነዚህ ከተሞች ምንድር ናቸው?
ኪራም ሰለሞንን እየገሠፀው ነው፡፡ ይህ ጥያቄ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚ “እነዚህ የሰጠኸኝ ከተሞች ለምንም የሚጠቅሙ አይደሉም”
እስከ ዛሬም ድረስ .....ተጠሩ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚ “እስከ ዛሬም ድረስ ሰዎች ይጠሩዋቸዋል”
1 Kings 9:15
ሰለሞን......ነገሮችን መልምሎ ነበር
“ሰለሞን........የሚሠሩለትን ሰዎች የፈለገበት”
ሚሎን
አማራጭ ትርጉሞች 1) “የእርከን ዘዴ” ወይም “ለባስ አፈር”
የግብፅም ንጉሥ ፈርኦን ወጥቶ ነበር
ግለሰብ የሚያዘው ሰራዊት ዘይቤ ነው፡፡ ተርጓሚ “የግብፅ ንጉስ ፈርኦን ሠራዊት ወጥቶ....ነበር”
1 Kings 9:17
ሰለሞን ጌዝርን .........ሠራ
ይህንን ለመሥራት ሰለሞንን ሌሎት ሰዎች እንደረዱት አንባቢው በሚረዳበት መንገድ መተርጎም የተሻለ ነው፡፡

1 Kings 9:22
ሰለሞን ከእስራኤል ልጆች ማንንም ባሪያ አላደረገም
ሰለሞን የእስራኤል ልጆች እንዲሠሩ አላስገደደም
1 Kings 9:23
550 ነበሩ
“አምስት መቶ ሃምሳ” ነበሩ
1 Kings 9:24
ሚሎን ሠራ
አማራጭ ትርጉሞች 1)እርከን ዘዴ ሠራ 2) ለባስ አፈር ሠራ የ1ነገስት 9፡15 ትርጉምን ተመልከት (ሚሎን የሚለውን)
1 Kings 9:25
መሰዊያ .......በእግዚአብሔር ፊት
የ1ነገስት 8፡64 ትርጉምን ተመልከት
1 Kings 9:26
ንጉስ ሰለሞን........ሠራ
ይህን ለመስራት ሰለሞንን ሌሎች ሰዎች እንደረዱት አንባቢው በሚረዳበት መንገድ መተርጎም የተሻለ ነው፡፡
መርከቦችን
“በርካታ ቁጥር ያላቸው መርከቦች”
420 መክሊት ወርቅ
“አራት መቶ ሀያ” መክሊት ወርቅ መክሊት የወርቅ መለኪያ ሲሆን ከ33 ኪ.ግ ጋር ይስተካከላል፡፡ ተርጓሚ ወደ 14,000 ኪ.ግ ገደማ ወርቅ

---

Chapter 10
1 Kings 10:1
በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የሰለሞን ዝና
እዚህ ጋር እግዚአብሔር “በስሙ” ተወክሏል፡፡አማራጭ ትርጉሞች 1) ተርጓሚ “የእግዚአብሔርን ስም የሚያከብር የሰለሞንን ዝና” ወይም 2) ተርጓሚ “እግዚአብሔር የሰጠው የሰለሞን ዝና”
በልብዋ ያለውን ሁሉ
ይህ ጥቅል ነው፡፡ ተርጓሚ “ማወቅ የምትፈልገውን ነገር ሁሉ”
1 Kings 10:3
የሎሌዎቹንም አሠራር
አማራጭ ትርጉሞች 1) “ሎሌዎቹ በማዕድ ዙሪያ እንዴት እንደተቀመጡ” ወይም 2)“ሎሌዎቹ የሚኖሩበት ሥፍራ”
ነፍስ አልቀረላትም
ይህ ፈሊጣዊ ነው፡፡ ተርጓሚ “በጣም ተገርማ ነበር”
1 Kings 10:6
በአገሬ ሳለው የሰማሁት.....ነው
“በአገሬ ሳለው ሰምቼ ነበር”
ጥበብህና ስራህ
እዚህ ጋር ጥበብ የሚለው ቃል ስራህ የሚለውን ቃል ሊገልፅ ይችላል፡፡ ተርጓሚ “በጥበብ የተሞላው አባባልህ”
በዓይኔ እስካይ ድረስ
በዓይኔ የሚለው ቃል እርሷ ራሷ እንዳየችው አፅንኦት ይሠጣል፡፡ ተርጓሚ “እኔ ለራሴ አይቼ ነበር”
ስለነገርህና ስለጥበብህ......... እኩሌታውን አልነገሩኝም
ይህ ያለ ጉልት አፃፃፍ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚ “ከነገርህና ከጥበብህ.....እኩሌታውን እንኳ አልነገሩኝም” ወይም “ከነገሩኝ በላይ እጅግ በጣም ባለጠጋና ጥበበኛ ነህ”
1 Kings 10:8
በፊትህ ሁልጊዜ የሚቆሙ
ይህ ፈሊጣዊ ነው፡፡ ተርጓሚ “ሊያገለግሉህ ሁልጊዜ በፊትህ የሚጠባበቁ”
አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚ “ሰዎች እግዚአብሔር አምላክህን ያመስግኑ”
በእስራኤል ዙፋን ያስቀመጠህ
“ዙፋን” በዙፋን ላይ ስለተቀመጠው ንጉስ ዘይቤ ነው፡፡ ተርጓሚ “የእስራኤል ንጉስ ያደረገህ”
1 Kings 10:10
120 መክሊት መርቅ
“አንድ መቶ ሀያ መክሊት ወርቅ” “መክሊት” የወርቅ መለኪያ ሲሆን ከ33 ኪ.ግ ጋር ይስተካከላል፡፡ ተርጓሚ “ወደ 4,000 ኪ.ግ ገደማ ወርቅ”
እንደሰጠችው ያለ የሽቱ ብዛት ከዚያ ወዲያ አልመጣም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚ “ንግስተ ሳባ የሰጠችውን ሽቱ ያክል ማንም ለንጉስ ሰለሞን ሰጥቶት አያውቅም”
1 Kings 10:11
ንጉሡም......አደረገ
ይህንን ለመሥራት ሰለሞንን ሌሎች ሰዎች እንደረዱት አንባቢው በሚረዳበት መንገድ መተርጎም የተሻለ ነው፡፡ ተርጓሚ “ንጉሡ ለሠራተኞቹ እንዲሠሩ አደረገ”
የሰንደል እንጨት
ምናልባት ደስ የሚያሰኝ ሽታ (መዓዛ) ያለው የእንጨት አይነት ነው፡፡
አልመጣም አልታየም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚ “እንዲህ ያለ ብዛት ማንም ዳግም አይቶ አያውቅም”
ዛሬም ድረስ
x
1 Kings 10:13
የወደደችውን ሁሉ.............የለመነችውን ሁሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ አይነት ነገር ሲሆን አፅንኦት ለመስጠት ተጣምረዋል፡፡
በገዛ እጁ
“ምክንያቱም እንደ ንጉሥ እጅግ ብዙ ነበረው፡፡”
1 Kings 10:14
በየዓመቱ
ይህ የሰለሞን የየአመቱ የንግስና ዘመን የሚገልፅ እንጂ የአንድ አመት ብቻ አይደለም
666 መክሊት ወርቅ
“ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት” መክሊት የወርቅ መለኪያ ሲሆን የ33 ኪ.ግ ልኬት ነው፡፡ ተርጓሚ “ወደ 22,000 ኪ.ግ የሚጠጋ ወርቅ”
1 Kings 10:16
ንጉሡም ሰለሞን .......አሠራ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ለአንባቢው ሌሎች ሰዎች ይህን ለመስራት ሰለሞንን እንደረዱት ተደርጎ ቢተረጎም የተሻለ ነው። ተርጓሚ “የንጉሥ ሰለሞን ሠራተኞች ሠሩት”
ሁለት መቶ አላበሽ አግሬ ጋሻ
“200 አላበሽ አግሬ ጋሻ”
1 Kings 10:18
ንጉሡም አሠራ
ለአንባቢው ሌሎች ሰዎች ይህን ለመስራት ሰለሞንን እንደረዱት ተደርጎ ቢተረጎም የተሻለ ነው። ተርጓሚ “የንጉሡ ሠራተኞች ሠሩት”
ከዝሆን ጥርስ.......ዙፋን
የዝሆን ጥርስ ጠንካራ ሆኖ ከትላልቅ እንስሳት ጥርስ የተሠራ ነጭ ቀለም ያለው ነገር ነው
ዝንጀሮ
ይህ በአፍሪካ የሚገኝ የድር እንስሳ ነው። ወደ እጅና እግር አከባቢ ከሰው ጋር የመመሣሠል ነገር ያለው ሲሆን ረጅም ጭራ አለው። አንዳንድ ሰዎች ዝንጀሮን የጦጣ ዝርያ አድርገው ያስባሉ።
1 Kings 10:23
ምድርም ሁሉ
ይህ ጥቅል ነው። ተርጓሚ “ከሁሉም ሥፍራ የመጡ ሰዎች” ወይም “ከተለያየ ቦታ የሆኑ ሰዎች”
የሰለሞንን ፊት ይመኝ ነበር
“ፊት” አንድን ሰው የማውራትና የማዳመጥ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ሰለሞንን ማዳመጥ ይመኝ ነበር” ወይም “ሰለሞንን መጎብኘት ተመኘ (ፈለገ)”
1 Kings 10:26
1400 ሰረገሎች አስራ ሁለት ሺህ ፈረሰኞች
“አንድ ሺህ አራት መቶ ሰረገሎች 12,000 ፈረሰኞች”
ንጉሡም ብሩን በኢየሩሳሌም እንደ ድንጋይ እንዲበዛ አደረገው
ፀሐፊው በኢየሩሳሌም የነበረውን ብር አጋንኖ ያሳያል። ተርጓሚ “ንጉሡ እጅግ በጣም ብዙ ብር ነበረው በመሬት ላይ ድንጋይ የሚበዛውን ያክል የሚበዛ ብር ነበረ።”
1 Kings 10:28
ከግብፅ.....አስመጣ
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “እነዚህ ነጋዴዎች በግብፅ ምድር ከነበሩ ሰዎች አመጡ”
ቀዌ
ይህ የአንድ ግዛት ስም ነው። ተርጓሚ “አንዳንድ ሰዎች ቀዌ በትንሿ እሲያ ከምትኝ ከስልቢያ ጋር ይመሣሠልባቸዋል።”
ሰረገላ.........ይወጣ ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ነጋዴዎቹ ሰረገላ ገዙ”
ስድስት መቶ.......ብር ......መቶ ሃምሳ ብር
ስድስት መቶ ሰቅል ብር.... መቶ ሃምሳ ሰቅል ብር 600ብር... 150 ብር ወይም 1ሰቅል ከ11 ግራም ጋር ስለሚስተካከል 6.6ኪ.ግ ብር......1.7ኪ.ግ ብር ሊሆን ይችላል።
ስድስት መቶ (ሰቅል)ብር
600 (ሰቅል) ብር
150 (ሰቅል) ብር
አንድ መቶ ሃምሳ (ሰቅል)ብር
ያወጡላቸው ነበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “የእርሱ ነገጋዴዎች አብዛኛዎቹን ሸጡአቸው”

---

Chapter 11
1 Kings 11:1
ንጉሱም ሰለሞን
“ንጉሡም” የሚለው ቃል በዋናው ታሪክ ውስጥ ሌላ የታሪኩን ክፍል ለማሳየት ተራኪው የተጠቀመበት ነው።
ሞዓባውያን....አሞናውያን.... ኤዶማውያን..... ሲዶናውያን..... ኬጢያውያን
“እነዚህ የሰዎች የጎሳ ስም ናቸው”
አምላኮቻቸውን ትከተሉ ዘንድ.....ልባችሁን ያዘነብላሉና
የአንድ ሰው ልብ ማዘንበል ማለት የልቡን ሃሳብ እንዲለውጥ ማሳመን ማለት ነው።“የእነርሱን አምላክ እንድታመልኩ አሳመኑአችሁ”
1 Kings 11:3
ወይዛዝር የሆኑ ሰባት መቶ ሚስቶች ሦስት መቶ ቁባቶች
ወይዛዝር የሆኑ 700 ሚስቶችና 300 ቁባቶች
ልቡን አዘነበሉት
የአንድን ሰው ልብ ማዘንበል ማለት የልቡን ሃሳብ (ፍቅር) እንዲለውጥ ማድረግ ማለት ነው። የ1ነገስት 11:01 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “ልቡን ከእግዚአብሔር መለሰ” ወይም “የእነርሱን አምላክ እንዲያመልክ አሳመኑት”
የአባቱ ዳዊት ልብ ......ፍፁም እንደነበረ.......ልቡ እንዲሁ አልነበረም
ልብን ፍፁም ማድረግ ሙሉ በሙሉ መስጠትን ወይም መውደድን ይገልፃል። ተርጓሚ “እንደ ዳዊት ሙሉ በሙሉ የተሰጠ አልነበረም”
1 Kings 11:5
አስታሮትን.......ሚልኮምን
እነዚህ የሐሰተኛ አማልክት ስሞች ናቸው።
ሲዶናውያን
ይህ የአንድ ጎሳ ህዝብ ስም ነው።
ሚልኮምን ተከተለ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገርን
“ፊት” የሚለው ቃል የአንድ ሰው አመለካከትን ይገልፃል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር እንደ ክፉ ያየውን”
1 Kings 11:7
ካሞሽ.....ሞሎክ
እነዚህ የሐሰተኛ አማልክት ሥሞች ናቸው
ለአማልክቶቻቸው.......መሥዋዕትም .....አደረገ
ይህ ሰለሞን በሰራው መስገጃ ሥፍራ መሆኑን ለማሳየት ነው።
1 Kings 11:9
ልቡን አርቆአልና
“ልብን” የሚለው ቃል ሐሳቡን ፍቅሩን መቀየሩን ያሳያል። የ1ነገስት 11:01 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “ሰለሞን እግዚአብሔርን ማምለክ አቆመ”
ሁለት ጊዜም ተገለጠለት
“እግዚአብሔር ለሰለሞን ሁለት ጊዜ ተገለጠለት”
1 Kings 11:11
መንግስትህ ከአንተ ቀዳድጄ
x
1 Kings 11:14
ሃዳድ
ይህ የሰው (የወንድ)ስም ነው።
ዳዊት በኤዶምያስ በነበረ ጊዜ .....ሃዳድ ገና ብላቴና ሳለ
ይህ ከረጅም ጊዜ በፊት የተከሰተ ነው።
1 Kings 11:18
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ክፍል በ1ነገስት 11:15 ለጀመረው መረጃ ተከታይ ነው።
ከምድያምም ....መጡ
“መጡ” የሚለው ቃል በ1ነገስት 11:17 እንደተጠቀሰው ሃዳድና ሌሎች ኤዶማውያንን ይወክላል።
ምድያም....ፋራን ...ግብፅ
እነዚህ የቦታ ሥሞች ናቸው።
ቴቄምናስ
ይህ የሴት ስም ነው።
ጌንባት.....ሃዳድ
ይህ የሰዎች (የወንድ) ስም ነው።
ዳዊት ከአባቶቹ ጋር እንዳንቀላፋ
ይህ በትህትና መልኩ የዳዊትን ሞት ይገልፃል። ተርጓሚ “ዳዊት አረፈ” ወይም “ዳዊት ሞተ”
1 Kings 11:23
ሬዘን ....ኤልያዳ ....አድርአዘር
እነዚህ የሰዎች (የወንዶች) ስሞች ናቸው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሱባ.....ዳማስቆስ..
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።
ዳዊትም .......በገደለ ጊዜ
እዚህ ጋር “ዳዊት” ዳዊትንና የዳዊትን ሠራዊት ይገልፃል። ተርጓሚ “የዳዊት ሠራዊት ድል ባደረገ ጊዜ”
በሰለሞን ዘመን ሁሉ
“ሰለሞን በሕይወት በነበረበት ጊዜ” ወይም “የሰለሞን የሕይወት ዘመን”
ሬዘን .....የእስራኤል ጠላት ነበር
“ሬዘን እስራኤልን አብዝቶ ይጠላ ነበር”
1 Kings 11:26
ናባጥ ......ኢዮርብዓም
እነዚህ የሳዎች (የወንዶች) ስም ናቸው።
ሳራራ.......ሚሎን
እነዚህ የቦታ ሥሞች ናቸው።
ፅሩዓ
ይህ የሴት ስም ነው።
በንጉሡም ያመፀበት
“ያመፀበት” የሚለው ቃል ስልጣንን፣ ጉልበትና ቁጥጥርን በመጠቀም አንድን ሰው መቃወምን ይገልፃል። ተርጓሚ “በንጉሡም ላይ አመፀበት”
ሰለሞን ሚሎን ሠራ
ሚሎን በ1ነገስት 9፡15 ላይ ባለው መሠረት ይተርጎም።
1 Kings 11:28
ፅኑ ኃይል ሰው
አማራጭ ትርጉም 1) ታላቅ ጦረኛ ወይም 2) “በጣም ብቁ ሰው” 3) “ባለጠጋና ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰው”
ሾመው
“አዛዥ አደረገው”
ሥራ ሁሉ
ሥራ የሚለው ቃል ሰለሞን ለመንግስቱ እንዲሠሩ ያዘዛቸውን ሥራ ሁሉ ይገልፃል። ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ነው።
በዮሴፍ ነገድ
ይህ ከኤፍሬምና ከምናሴ ወገን የሆኑና የዮሴፍ ነገድን ይገልፃል።
አኪያ
ይህ የሰው (ወንድ) ሥም ነው
ሴሎናዊው
ሴሎናዊው የሆነ ወገን ህዝብ ነው።
1 Kings 11:31
አለው
አለው የሚለው ቃል አኪያን (አኪያ መናገሩን) ይገልፃል።
መንግስቱን እቀድዳለሁ
እዚህ ጋር እቀድዳለሁ የሚለው ቃል በግድ ለመቀማት ዘይቤ ነው። ይህ ልክ ሰው ልብስን እንደሚቀድ ነው። የ1ነገስት 11፡11 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ
“መንግስቱን በግድ (በጉልበት) ቀማው”
ከሰለሞን እጅ
እዚህ ጋር እጅ የአንድን ሰው ሥልጣን፣ቁጥጥርና ጉልበት ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “የሰለሞን ቁጥጥር”
ሰለሞን .......ይቀርለታል
ይህ ለሰለሞን ነገድ የተነገረ ሲሆን ተርጓሚ “ለሰለሞን ልጅ ይቀርለታል።” ወይም “ለሰለሞን ነገድ ይቀርለታል
1 Kings 11:34
አጠቃላይ መረጃ
አኪያ እግዚአብሔር ለእዮርባአም ያለውን መናገሩን ቀጥሏል።
አልወስድም
አልወስድም የሚለው ቃል እግዚአብሔር መናገሩን ያሳያል
ከእጁ
እዚህ ጋር “እጅ” የአንድ ሰው ስልጣን፣ ቁጥጥርና ጉልበት ያሳያል ተርጓሚ “ከቁጥጥሩ”
እሰጥሃለው
ይህ ቃል ለእዮርባአም መሆኑን ያሳያል
በፊቴ ሁል ጊዜ መብራት ይሆንለት ዘንድ
“መብራት” የሚለው ቃል የአንድ ሰው ተፅዕኖና ምሪት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ኪዳኔን በመታዘዙ አንድ ተፅዕኖና ምሪት ሁልጊዜ የሚገዛ ነገድ (Hei)ለዳዊት ቤት ይሆናል”
1 Kings 11:37
አጠቃላይ መረጃ
አኪያ እግዚአብሔር ያለውን ለእዮርባአም መናገሩን ቀጥሏል።
አወስድሃለው
ይህ ቃል እግዚአብሔር ለእዮርባአም መናገሩን ያሳያል።
በፊቴ የቀናውን
“ፊት” የአንድ ሰው አመለካከት ወይም ሃሳብ ዘይቤ ነው። ይህ በተለምዶ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። የ1ነገሰት 11፡33 ትርጉምን ተመልከት
ፅኑ ቤት እሠራልሃለሁ
“ቤት እሰራልሃለሁ” የሚለው ሐረግ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሥርወ-መንግስትን የመመስረት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ረጅም ዘመን ያለው መንግስትን መመስረት”
1 Kings 11:40
ሺሻቅ
ይህ የሰው(የወንድ) ስም ነው።
1 Kings 11:41
በሰለሞን ታሪክ መፅሐፍ ተፅፎአል
ይህ በሌላ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ “በሰለሞን ታሪክ መፅሐፍ ልታገኘው ትችላለህ”
በሰለሞን ታሪክ መፅሐፍ
ይህ መፅሐፍ በአሁኑ ወቅት አይገኝም/የለም
ሰለሞን ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ.....ተቀበረ
x

---

Chapter 12
1 Kings 12:1
እስራኤል ሁሉ መጥተው ነበርና
እስራኤል የሚለው ቃል መዋጋት የሚችሉትን የእስራኤል ወንዶችን ሁሉ ይገልፃል። እስራኤል ሁሉ የሚለው ሀረግ ደግሞ ሁሉንም የእስራኤል ሰዎች (ወንዶችን) ይገልፃል። ተርጓሚ “ሁሉም የእስራኤል ሰዎች (ወንዶች) መጥተው ነበርና”
እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ ድርጊቱ መጀመሩን ማሳያ ነው።
እዮርብአም......ናባጥ
እነዚህ የሰዎች (ወንዶች) ስም ናቸው።
1 Kings 12:3
ጠርተውት ነበር
“ጠርተውት” የሚለው ቃል እዮርብአምን መሆኑን ያሳያል።
የከበደውን ቀንበር
“ከባድ ቀንበር” የከባድ ሥራ ወይም በጣም የሚጠበቅብን ነገር ማሳያ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ክፉኛ አንገላቱአቸው” ወይም “በጣም እንድንሠራ አስገደዱን”
1 Kings 12:6
በፊቱ ይቆሙት ከነበሩት ሽማግሌዎች
“በፊቱ መቆም” የሚለው ሐረግ ንጉሡን ማገልገላቸውን ማሳያ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “ያማክሩቱ የነበሩት ሽማግሌዎች” ወይም “ሰለሞንን ይታዘዙት የነበሩት ሽማግሌዎች”
1 Kings 12:8
አባትህ የጫነብንን ቀንበር አቃልልልን
ቀንበር ማቃለል ሸክም የማንሣትን ማሳያ ዘይቤ ነው። “አባትህ እንደጨከነብን አንተ አትጨክንብን” ወይም “አባትህ በጣም እንዳሠራን እንድንሠራ አታስገድደን”
1 Kings 12:10
ታናሺቱ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ትወፍራለች
ይህ ዘይቤ የሚያሳየው ሮብአም ከአባቱ በላይ ጨካኝና አስቸጋሪ መሆኑን ያሳያል ተርጓሚ “ሸክማችሁን ለማክበድ የማደርገው ነገር አባቴ ከጫነባችሁ እጅግ በጣም የከበደ ነው።”
አባቴ በአለንጋ ገርፎአችኋል እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ

ይህ ዘይቤ የሚያሳየው ሮብአም ያቀደው ቅጣት ከአባቱ ቅጣት የከፋ መሆኑን ነው።
ተርጓሚ “አባቴ ሊያስገድዳችሁ አለንጋ ተጠቀመ እኔ ግን የከፋ ቅጣትን እጠቀማለሁ።”

በጊንጥ እገርፋችኋለሁ

ጊንጥ የሚለው ቃል ምናልባት 1) ጫፍ ላይ ሹል ያለው መግረፍያ (አለንጋ) ወይም 2) ሸረሪት መሳይ የሚናደፉ መርዛማ ፍጡር ሊሆን ይችላል።

1 Kings 12:12

እኔ ግን በቀንበራችሁ ላይ እጨምራለሁ

ከባድ ቀንበር፤የከባድ ስራ ወይም በጣም የሚጠበቅብን ነገር ማሳያ ዘይቤ ነው ተርጓሚ “ክፉኛ እንገላቱአችሁ” ወይም “በጣም እንድትሠሩ አስገደዱአችሁ” የ1ነገስት 12:4 ትርጉምን ተመልከት።

አባቴ በአለንጋ ገርፎአችኋል እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ

ይህ ዘይቤ የሚያሳየው ሮብአም ያቀደው ቅጣት ከአባቱ ቅጣት የከፋ መሆኑን ነው።
ተርጓሚ “አባቴ ሊያስገድዳችሁ አለንጋ ተጠቀመ እኔ ግን የከፋ ቅጣትን እጠቀማለሁ።”

1 Kings 12:15

ከእግዚአብሔር ዘንድ ተመድቦ ነበርና

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ሲሆን በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ነገሮች እንዲህ እንዲሆኑ እግዚአብሔር አደረገ”

በአኪያ አድርጎ.......ለእዮርብዓም የተናገረውን

የተናገረውን የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ለሌላ ሰው የሚነገር መልዕክትን መስጠት ይገልፃል።

አኪያ.........እዮርብዓም......ናባጥ

እነዚህ የሰዎች (ወንዶች) ስሞች ናቸው።

ሴሎናዊ

ይህ ከሴሎን ከተማ የሆኑ ሰዎችን ይገልፃል።

1 Kings 12:16

እስራኤልም ሁሉ

እዚህ ጋር “እስራኤል” የሚለው ቃል መዋጋት የሚችሉትን የእስራኤል ወንዶችን ሁሉ ይገልፃል። እስራኤል ሁሉ የሚለው ሐረግ ገግሞ ጥቅል ሲሆን ሁሉንም የእስራኤል ወንዶች ማለት ነው። ተርጓሚ “የእስራኤል ወንዶች ሁሉ”

በዳዊት ዘንድ ምን ክፍል አለን?

“ክፍል” የሚለው ቃል ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም ድርሻ፣ ጣልቃ ገብነት ወይም ፍላጎት ማለት ነው። ይህ ጥያቄ በቀላል አረፍተ-ነገር ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “በዳዊት ቤት ወስጥ ምንም ድርሻ አይኖረንም”

በእሴይም ልጅ ዘንድ ርስት የለንም

“የእሴይ ልጅ” ለእሴይ ልጅ ለዳዊት ዘይቤ ነው። ርስት ደግሞ ከዳዊት ስኬት ለእነዚህ ሰዎች የቀረው ድርሻ ነው። ተርጓሚ “ከእሴይ ነገድ ጋር ምንም ነገር የለንም”

እስራኤል ሆይ ወደ ድንኳኖቻችሁ ተመለሱ

እዚህ ጋር ድንኳን የአንድን ሰው የመኖሪያ ስፍራ መግለጫ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “እስራኤል ሆይ ወደ ቤቶቻችሁ ሂዱ (ተመለሱ)”

ዳዊት ሆይ አሁን ቤትህን ተመልከት

እዚህ ጋር ቤት ለዳዊት የዘር ሀረግ ጉልበትና ክብር ማሳያ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “የዳዊት ነገድ ሆይ አሁን መንግስትህን ተንከባከብ (ጠብቅ)”

1 Kings 12:18

አዶኒራም

ይህ የሰው (ወንድ) ስም ነው።

እስራኤል ሁሉ

እዚህ ጋር “እስራኤል” የሚለው ቃል ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ዘይቤ ነው። እስራኤል ሁሉ የሚለው ሀረግ ደግሞ ጥቅል ሲሆን ሁሉም የእስራኤል ሕዝብ ማለት ነው።
ተርጓሚ “በዚያ የነበሩ የእስራኤል ህዝብ ሁሉ”

ከዳዊት ቤት

እዚህ ጋር ቤት የሚለው ቃል ቤተሰብ ወይም የዘር ሕረግን ይወክላል። ተርጓሚ “ነገሥታት ከዳዊት ዘር ሐረግ ናቸው”

1 Kings 12:20

እስራኤልም ሁሉ .....በሰሙ ጊዜ

“እስራኤልም ሁሉ” የሚለው ሐረግ ሁሉንም የእስራኤል ሊወክል ለሚችለው ብቁ ማህበረሰብ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ሁሉም የእስራኤል መሪዎች በሰሙ ጊዜ”

በእስራኤል ሁሉ ላይ አነገሡት

“እስራኤል” የሚለው ቃል በግልፅ በሮብዓም ላይ ያመፁትን የሰሜኑ አስር ነገዶች ይገልፃል። ተርጓሚ “በአስሩ የእስራኤል ነገድ ላይ አነገሡት”

የዳዊትን ቤት

“የዳዊት የዘር ሐረግ”

1 Kings 12:21

ከይሁዳ ቤት ሁሉና ከብንያም ነገድ

እዚህ ጋር “ቤት” ነገድ ወይም የዘር ሀረግን የሚገልፅ ዘይቤ ነው። ነገድ የሚለው ቃል ደግሞ በተለየ መልኩ ከዚያ ነገድ ስለሆኑት ወታደሮች ነው። ተርጓሚ “ከይሁዳና ከብንያም ነገድ የሆኑት ወታደሮች ሁሉ”

180,000 ሰልፈኞች

አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ ሰልፈኞች

የእስራኤል ቤት

እዚህ ጋር ቤት ከአሥሩ የእስራኤል ነገዶች የተመሠረተ መንግስትን ይወክላል።
ተርጓሚ “የእስራኤል መንግስት” ወይም “የአስሩ የእስራኤል ነገድ ህዝቦች”

1 Kings 12:22

የእግዚአብሔር ቃል ........እንዲህ ይላል።

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ሲሆን እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ለማስተዋወቅ ያገለግላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር ይህን መልዕክት ተናገረ ... እንዲህም አለ” ወይም “እግዚአብሔር እነዚህ ቃላት ተናገረ ..እንዲህም አለ”

ሳመያ

ይህ የሰው(ወንድ) ስም ነው።

የእግዚአብሔር ሰው

የእግዚአብሔር ሰው የሚለው ሐረግ ለእግዚአብሔር ነብይ የአክብሮት መጥሪያ ስም ነው። ተርጓሚ “የእግዚአብሔር የሆነ ሰው። ወይም “የእግዚአብሔር ነብይ”

ለይሁዳና ለብንያም ቤት ሁሉ

እነዚህ “ቤት” ነገድን ወይም የዘር ሐረግን የመግለጫ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ከይሁዳና ከብንያም ነገድ የሆኑ ህዝቦች ሁሉ

የእስራኤልንም ልጆች ወንድሞቻችሁን

“ወንድሞቻችሁን” ና የእስራኤል ልጆች የሚሉት ቃላት የተጣበቁና የሰሜኑ አስር ነገዶች የሚገልፅ ሲሆን በእነርሱ፤ በይሁዳና በብንያም መካከል ያለውን ቤተሰባዊ ግንኙነት አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ይህ ነገር ከእኔ ዘንድ ነውና

ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች እንዲሆኑ አደረኩ”

1 Kings 12:25

በልቡ.....አለ

እዚህ ጋር ልብ ለሰው የውስጥ ህሊናውን፤ሃሳቡን፤መነሣሣት ወይም ስሜት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ለራሱ....አሰበ”

ወደ ዳዊት ቤት

እዚህ ጋር “ቤት” ነገድን ወይም የዘር ሐረግን መግለጫ ዘይቤ ነው።ተርጓሚ “ከዳዊት ዘር ሀረግ የሆኑት ነገስታት”

ይህ ሕዝብ .......ቢወጣ

“ሕዝብ” የሚለው ቃል የሰሜኑን አስር የእስራኤል ነገዶች ይገልፃል።

የዚህ ህዝብ ልብ

እዚህ ጋር ልብ የሕዝብ ማዘንበል ወይም ፍቅርን መግለጫ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “የዚህ ህዝብ ማዘንበል” ተርጓሚ የዚህ ልብ ማዘንበል

ወደ ጌታቸው ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ ሮብዓም ይመለሳል።

እነዚህ ሐረጎች በመሠረቱ አንድ አይነት ሲሆኑ እዮርባዓም ሕዝቡ ወደ ሮብአም ጥያቄ ይመለሣል ብሎ መፍራቱን አፅንኦት ለመስጠት ነው።

1 Kings 12:28

ያወጡህን

ይህ ቃል ለሕዝቡ የዘር ሐረግ የሚያመለክት ዘይቤ ነው ተርጓሚ “የዘር ሐረግ ህን ያወጡትን”

1 Kings 12:31

በኮረብታቹም ላይ መስገጃዎችን ሠራ

ይህንን ሥራ በእዮርባአም ትዕዛዝ የሠሩት ሠራተኞች በራሱ በእዮርባአም ስም ተወክላዋል። ተርጓሚ “የእዮርባዓም ሠራተኞች በኮረብቶቹም ላይ መስገጃዎችን ሠሩ”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በኮረብቶቹም ላይ መስገጃዎችን
ይህ የመስገጃ (የማምለኪያ) ቤቶችን ያመለክታል። የዚህ አረፍተ-ነገር ሙሉ ትርጉሙ ግልፅ ሊደረግ ይችላል። ተርጓሚ "በኮረብቶቹም ላይ የማምለኪያ ቤቶችን"
ክህናትን አደረገ
ወንዶችን ካህናት አድርጎ ሾማቸው
በስምንተኛው ወር በአስራ አምስተኛውም ቀን
ይህ በእብራውያን ቀን አቆጣጠር ስምንተኛው ወር ነው። ለሥራ አምስተኛው ቀን በምዕራባዊያን ቀን አቆጣጠር የታህሳስ ወር መጀመሪያ አከባቢ ነው። ተርጓሚ "የስምንተኛው ወር አሥራ አምስተኛው ቀን"
መሠዊያው ላይ ሠዋ
"ላይ" የሚለው ቃል መሠዊያዎች በከፍታ ቦታ ላይ ስለሚገኙ ወደ ተቀደሰ ስፍራ የመሄድ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ "በመሠዊያ ላይ መሥዋዕት አቀረበ (ሠዋ)"
በልቡ ባሰበው ቀን
"እርሱ ባሰበው ወር ውስጥ"

Chapter 13
1 Kings 13:1
እነሆም አንድ የእግዚአብሔር ሰው በእግዚአብሔር ቃል ከይሁዳ ቤቴል መጣ።
መረጃው የሚያሳየው እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ሰው ወደ ቤቴል መላኩን ነው። ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ሰው ከይሁዳ ወደ ቤቴል ላከ"
የእግዚአብሔር ሰው
ይህ ለነብይ ሌላ የመጠሪያ ስም ነው። ተርጓሚ "ነብይ"
ከይሁዳ .....መጣ
"ከይሁዳ........መጣ"
የእግዚአብሔር ቃል
"የእግዚአብሔር መልዕክት" ወይም "መልዕክተ እግዚአብሔር"
በመሠዊያውም ላይ.......ጮኸ
እዚህ ጋር ጮኸ የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ሰው መሆኑን ያመለክታል።
በመሠዊያውም ላይ ......ጮኸ
ይህ ማለት እርሱ (ነብዩ) ከፍ ባለና ወቀሳ በተሞላበት ድምፅ ትንቢት ተናገረ። ማለት ነው። ተርጓሚ "ከፍ ባለ ድምፅ በመሠዊያ ላይ ትንቢት ተናገረ።"
መሠዊያ ሆይ መሠዊያ ሆይ
ነብዩ መሠዊያው ሰው የሆነ ያክል የሚሠማው ይመስል ይናገር ነበር ይህንንም አፅንኦት ለመስጠት ሁለት ጊዜ ተናገረ።
ስሙ አዮስያስ የሚባል ልጅ ለዳዊት ቤት ይወለዳል
x
1 Kings 13:4
በእርሱም ላይ የዘረጋት እጅ ደረቀች
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "እግዚአብሔር የነካው ሰው እጅ ደረቀች"
ደረቀች
"ጠወለገች" ወይም "ሰለለች"
መሠዊያው ተሰነጠቀ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "እግዚአብሔር መሠዊያውን ሰነጠቀ"
የእግዚአብሔር ሰው በእግዚአብሔር ቃል እንደ ሰጠው ምልክት
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "የእግዚአብሔር ሰው እንዳለው እንደ ምልከታም በእግዚአብሔር ቃል።"
የእግዚአብሔር ቃል
"የእግዚአብሔር መልዕክት" ወይም "መልዕክተ-እግዚአብሔር"
1 Kings 13:6
የአምላክህን የእግዚአብሔርን ፊት ለምን
ተርጓሚ "የአምላክህን የእግዚአብሔርን ፊት ለምንልኝ"
እጄም ወደ እኔ ትመለስ ዘንድ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "እግዚአብሔር እጄን ይመልስ ዘንድ"
የንጉሡም እጅ ወደ እርሱ ተመለሰች እንደቀድሞም ሆነች
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። "እግዚአብሔር የንጉሡን እጅ መለሠ እንደ ቀድሞም ሆነች"
ወደ ቤት ና እንጀራም ብላ
ተርጓሚ "ከእኔ ጋር ወደ ቤት ና ምግብም ብላ"
1 Kings 13:8
የቤትህን እኩሌታ
"የቤትህን ግማሽ"
እንጀራ አትብላ፤ውኃም አትጠጣ በመጣህበትም መንገድ አትመለስ
"እንጀራም አትብላ፤ ውኃም አትጠጣ ወይም በመጣህበት መንገድ እንዳትመለስ"
በሌላ መንገድ ሄደ
"በሌላ መንገድ ሆደ"
1 Kings 13:11
ልጆቹም .....የሄደበትን መንገድ አመለከቱት
ይህ መረጃ የሚያሳየው የእግዚአብሔር ሰው በየት በኩል እንደሄደ ልጆቹ ለአባታቸው ማሳየታቸውን ነው።
ጫኑልኝ
ይህ ማለት ሰው እንዲቀመጥበት (እንዲጋልብ) ኮርቻን በእንስሳ ጀርባ ማስቀመጥን ይገልፃል።
1 Kings 13:14
ሽማግሌ ነብይ
ይህ በቤቴል ይኖር የነበረውን ነብይ ይገልፃል።
አለው
ሽማግሌው ነብይ ለእግዚአብሔር ሰው አለው።
አለ
የእግዚአብሔር ሰው መልስ ሰጠው የሚለውን ይገልፃል
ከእኔ ጋር ወደ ቤቴ ና
ወደ ቤትህ ውስጥ ገባ
እዚህም ስፍራ
"በቤቴል"
በእግዚአብሔር ቃል ተብሎልኛልና
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "እግዚአብሔር በቃሉ አዘዘኝ"
የእግዚአብሔር ቃል
x
1 Kings 13:18
መልአክም........በእግዚአብሔር ቃል ተናገረኝ
"መልአክ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልዕክት አስተላለፈልኝ"
በእግዚአብሔር ቃል
"የእግዚአብሔር መልዕክት" ወይም "መልዕክተ-እግዚአብሔር"
1 Kings 13:20
በማእድም ተቀመጠው ሳሉ
ይህ መረጃ እስካሁን ምግብ በመመገብ ላይ መሆናቸውን ያመለክታል። ተርጓሚ "በመዕድ ሆነው በመመገብና በመጠጣት ላይ እያሉ"
የእግዚአብሔርም ቃል ወደ መለሰው ነብይ መጣ........ከይሁዳ ወደ መጣው ወደ እግዚአብሔር ሰው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።
የእግዚአብሔር ቃል.......መጣ የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር የተለየ መልዕክት ከእግዚአብሔር እንዳለ ለማስተዋወቅ ነው። የነገስት 6፡11 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "እግዚአብሔር ከይሁዳ ለመጣው ለነብዩ መልዕክት ሰጠው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ወይም "እግዚአብሔር ከይሁዳ ለመጣው ነብይ መልዕክት ተናገረ። እግዚአብሔር"
የእግዚአብሔር ቃል .....መጣ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር እግዚአብሔር የተለየ መልዕክት እንደለው ለማስተዋወቅ ነው። ተርጓሚ "እግዚአብሔር መልዕክት ሰጠ" ወይም "እግዚአብሔር ተናገረ"
መለሰው
ይህ ቃል ስለ እግዚአብሔር ሰው መሆኑን ይገልፃል።
ጮኸ
ይህ ድምፁን ከፍ አድርጎ ለእግዚአብሔር ሰው መናገሩን ይገልፃል።

1 Kings 13:23
አህያውን ጫነለት
ይህ ማለት የእግዚአብሔር ሰው እንዲቀመጥበት ኮርቻ በአህያ ጀርባ ላይ አስቀመጠለት የ1ነገስት 13፡13 ትርጉምን ተመልከት
ሬሳው በመንገድ ወድቆ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። “ሬሳውን በመንድ ተወ (ጣለ)”
ሬሳውን
የሞተው ሰውነቱን
መጥተውም ……አወሩ
ይህ የሚመለክተው በመንገድ ያዩትን መሆኑን ነው። ተርጓሚ “መጥተው ያዩትን አወሩ”
1 Kings 13:26
ሬሳው
የሞተ የእግዚአብሔር ሰው ሰውነት
በመንገድ ወድቆ
“በመንገድ ተንጋሎ”
1 Kings 13:29
አነሣ
ከፍ ማድረግ
ሬሳ
የሞተ ሰውነት
አለቀሱለት
ይህ ቃል ስለ ነብዩና ልጆቹ መሆኑን ያመለክታል።
ዋይ ወንድሜ ሆይ
እዚህ ጋር “ዋይ” የመራራ ሀዘን መግለጫ ቃል ነው።
1 Kings 13:31
ቀበረውም
ይህ ቃል ቀባሪው ስማባሌው ነብይ መሆኑን የተቀበረው ደግሞ የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን ያሳያል።
አጥንቶቼንም በአጥንቶቹ አጠገብ አኑሩ
እዚህ ጋር “አጥንቶቼ” የሚለው ቃል ሙሉ ሰውነቱን ይወክላል። ተርጓሚ “ ሬሳዬን ከእርሱ አጥንት አጠገብ አኑሩ”
ለኮረብታዎቹ መስገጃ
ይህ መረጃ መስገጃዎቹ የማምለኪያ ቦታ መሆናቸውን ያሳያል። ተርጓሚ “በኮረብታዎቹ ላይ የማምለኪያ ሥፍራ”
1 Kings 13:33
ይህ ነገር ለኢዮርብዓም ቤት ኃጢአት ሆነ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ይህ ነገር በማድረጉ የኢዮርብዓም ቤት ኃጢአትን አደረገ”
ይህ ነገር
ይህ ሐረግ ኢዮርብዓም ቤተ-መቅደስ ሰርቶ ካህናትን ማስቀመጡን ያሳያል።
እስኪፈርስም ከምድርም እስኪጠፋ ድረስ ……..ለኢዮርብዓም ቤት
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር የኢዮርብዓምን ቤት አፈረሰም አጠፋም”
እስኪፈርስም…………እስኪጠፋም
ይህ ከላይ ካለው ጋር ተቀራራቢ ትርጉም አለው። ተርጓሚ “ፈፅሞ መፍረስ (መጥፋት)”

---

Chapter 14
1 Kings 14:1
ለውጪና
“እራስሽን ለሌሎች ቀይርና (ለወጪና)”
እንዳትታወቂ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ማንም አያውቅሽም”
1 Kings 14:4
እነሆ ……የእዮርብዓም ምስት
“እነሆ” የሚለው ቃል ትኩረት እንዲሠጥ መፈለጉን ያሳያል።
ትጠይቅህ ዘንድ ……….ትመጣለች
ተርጓሚ “ምክር ልትጠይቅህ ወደ አንተ ትመጣለች”
እንዲህና እንዲህ በላት
x
1 Kings 14:6
ስለ ምንስ ሌላ ቤት መሰልሽ?
ይህ ጥያቄ የሚያሳየው አኪያ እራሷን እንደለወጠች ማወቁን ነው።ተርጓሚ “ሌላ ሰው መምሰልሽን ተይ (አቁሚ) እኔ ማን እንደሆንሽ አውቄሻለሁ”
እኔም ብርቱ ወሬ ይዤ ተልኬልሻለሁ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። “ብርቱ ወሬ እንድሠጥሽ (እንድነግርሽ) እግዚአብሔር ልኮኛል”
ከፍ አድርጌህ ነበር
“አሞገስኩህ”
መንግስቱን ቀድጄ ……ነበር
ልብስ እንደሚቀድ ሰው እግዚአብሔር አብዛኛውን መንግስት መጉልበት አስወግዶአል።
ተከተለኝ
“ታዘዘኝ”
1 Kings 14:9
ወደ ኋላም ጣልከኝ
ሰው የሚይፈልገውን ዕቃ ወርውሮ እንደጣለው ኢዮርብዓምም እግዚአብሔርን አላከበረውም ተርጓሚ “ፈፅሞ ተውከኝ”
እነሆ
“አትኩሮት ስጥ” ይህ ቃል የተጨመረው ቀጥሎ የሚመጣው ነገር ወሳኝ ነገር መሆኑን ለማመልከት።
አቆርጣለሁ ……..ፈፅሜ አጠርጋለሁ
እነዚህ ሁለት ቃልት በትርጉም በጣም ተመሣሣይ ሲሆኑ አፅንኦት ለመስጠት አንድ ላይ ሆነዋል።
ከእዮርብዓም …….በእስራኤል ወንድ ሁሉ አቆርጣለሁ
ቀርንጫፍን ከዛፍ እንደሚቆርጥ የእዮርብዓምን ቤት እንደሚቆርጥና ምንም የዘር ሐረግ እንዳይኖረው እግዚአብሔር ይናገራል። ተርጓሚ “በእስራኤል ያሉ ወንዶች ልጆችህን አጠፋለሁ” ሰውም ፋንድያን እስኪጠፋ ድረስ እንደሚጠርግ እኔ የእዮርብዓምን ቤት ፈፅሜ እጠርጋለሁ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የእዮርብዓምን የዘር ሐረግ መወገድ ፋንድያ ከሣርና ደረቅ ነገር ጋር ተደባልቆ ፈፅሞ እንደሚቃጠል ጋር ያነፃፅራል።
1 Kings 14:11
ከእዮርብዓምም ወገን በከተማይቱ ውስጥ የሞተውን ውሾች ይበሉታል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ውሾች ከእዮርብዓም ወገን የሆኑትንና በከተማ ውስጥ የሞተውን ይበሉታል።
በሜዳውም የሞተውን የሰማይ ወፎች ይበሉታል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። የሰማይ ወፎች በሜዳ የሞተውን ማንንም ይበላሉ።
እግርሽም ወደ ከተማ በገባ ጊዜ
እዚህ ጋር እግር የሚለው ቃል ሙሉ ሰውነትን የሚወክል ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “የእስራኤል ህዝብ”
ይቀብሩትማል
“በመቃብር መቅበር”
በእዮርብዓም ቤት
እዚህ ጋር “ቤት” የሚለው ቃል ለቤተሰብ ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “በእዮርብዓም ቤተሰብ ሁሉ”
በእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ዘንድ…….መልካም ነገር ተገኝቶበታልና
“ዘንድ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ፍርድ መይም ምዘና ይወክላል።ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ያገኘው (የፈረደው) ነገር ሁሉ መልካም ሆነ አገኘ”
1 Kings 14:14
የእዮርብዓምን ቤት ያጠፋል
ፀሐፊው፣አድሱ የእስራኤል ንጉስ ሰው የዛፍን ቅርንጫፍ እንደሚቆርጥ ሁሉ የእዮርብዓምን ቤት የዘር ሐረግ እንዳይኖረው እንደሚያጠፋው ይናገራል። ተርጓሚ

“የእዮርብዓምን የዘር ሀረግ (ትውልድ) ያጠፋል።”
ሸምበቆ በውኃ ውስጥ እንደሚንቀሳቀስ እግዚአብሔር እንዲሁ እስራኤልን ይመታል
እዚህ ጋር ፀሐፊው ንፅፅርን በመጠቀም እንዴት እግዚአብሔር ፍርድን ወደ እስራኤል እንደሚያመጣ ይገልፃል። ተርጓሚ “ሸንበቆ በውኃ ውስጥ እንደሚንቀሳስ እግዚአብሔር እንዲሁ እስራኤልን ይቀጣል”
ሸንበቆ በውኃ ውስት እንደሚንቀሳቀስ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የወንዝ ውኃ ሸምበቆ እንደሚያንቀሳቅስ ሁሉ”
ከዚች ከመልካሚቱ ምድር እስራኤልን ይነቅላል።
እግዚአብሔር እስራኤልን ከተክል ጋር በማወዳደር ከመሬት ውስጥ ፈንቅሎ ሥሩን ያወጣል። ተርጓሚ “ከዚች መልካም ምድር እስራኤልን ፈፅሞ ያጠፋል”
ይበትናቸዋል
“ይበትናቸዋል” ወይም “ይለያቸዋል”
1 Kings 14:17
ቴርሳ
ይህ ንጉሥ እዮርብዓም ይኖርበት የነበረ የከተማ ስም ነው።
እስራኤል ሁሉ ቀበሩት አለቀሱለትም
ይህ ጥቅል ሀሳብ ሲሆን የእስራኤል ህዝብ ቀብረው አለቀሱለት ማለት ነው። ተርጓሚ “ሰዎች ሊቀብሩት ብዙ ቁጥር ያለው የእስራኤል ሕዝብ በቀብሩ ላይ ተገኝተው አለቀሱለት”
እንደ ተነገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሔር እንደተናራቸው”
በ............እግዚአብሔር ቃል
“በእግዚአብሔር መልዕክት” ወይም “በመልዕክተ-እግዚአብሔር”
1 Kings 14:19
እነሆ
“ተመልከት” ወይም “ለራስህ ተመልከት”
በ.......ተፅፎአል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። “በ.........ተፅፎ ታገኛቸዋለህ” ወይም “የሆነ ሰው......በ.....ፅፎአቸዋል”
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መፅሐፍ
ይህ በአሁኑ ጊዜ የማይገኝ መፅሐፍን ይገልፃል።
ሀያ ሁለት ዓመት
“22 ዓመት”
ከአባቶቹም ጋር
ከአባቶቹም ጋር አንቀላፋ የሮብዓም ሞት እንቅልፉን እንደተኛ ሰው ተደርጎ ተነግሮአል የ1ነገስት 2:10 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ሞተ” ወይም “አረፈ”
1 Kings 14:21
አርባ አንድ አመት ......አሥራ ሰባት አመት
“41 ዓመት ......17 አመት”
ስሙን ያኖርበት ዘንድ
እዚህ ጋር ስሙን ያኖርበት ዘንድ የሚለው ሐረግ ለ “መኖር” ዘይቤ ሲሆን እግዚአብሔር የሚመለክባትን ቤተ-መቅደስ ይገልፃል። ተርጓሚ “የሚኖርበት” ወይም “የሚመለክበት”
የእናቱም ስም
ይህ ሐረግ የሚገልፀው ሮብዓምን ነው።
ናዕማ
ይህ የሴት ስም ነው።
ይሁዳም .....ሠራ
እዚህ ጋር ይሁዳ የይሁዳን ህዝብ ይወክላል። ተርጓሚ “የይሁዳ ህዝብ ሠሩ”
በእግዚአብሔር ፊት ክፉ
እዚህ ጋር የእግዚአብሔር ፊት የሚለው ሐረግ የእግዚአብሔር ፍርድን ወይም ምዘናን ይወክላል። የ1ነገስት 11:6 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ ነው ያለውን”
በ.......ኃጢአት አስቆጡት
አስቆጡት የሚለው ቃል በቅፅል መልኩ ይገለፃል። ተርጓሚ “ቁጡ አደረጉት ”
አባቶቻቸው
“የዘር ሐገቻቸው” ወይም “የዘር ግንዳቸው”
1 Kings 14:23
እነርሱም ......ሰሩ
እነርሱም የሚለው ቃል የይሁዳን ህዝብ ይገልፃል።
ለራሳቸው ሠሩ
ለራሳቸው የሚለው ቃል በኮረብታ ቦታዎች ለሚሰሩት ዘይቤ ነው። ተርጓሚ “ለራሳቸው ጥቅም ሠሩ”
ከፍ ባለው ኮረብታ ሁሉ ላይ ቅጠሉ ከለመለመ ሁሉ በታች
ይህ ምናልባት ለሐሰት አምልኮ በዚያ ሀገር ብዙ ቦታዎች መኖራቸውን ማሳያ የግነት ንግግር ነው። ተርጓሚ “ከፋ ባለ ኮረብታና በለመለመ ዛፍ ሁሉ ሥር”
ሰዶማውያን
“አምልሞታዊ መልክ ያለው” ወይም “ወንድ ጋለሞታዎችን” ይህ ምናልባት ከባዕድ አምልኮ ጋር የተያያዙ የወንድ ጋለሞታዎችን ይገልፃል።
1 Kings 14:25
ሮብዓምም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት
ይህ የሮብዓምን አምስተኛ አመት የንግስና ዘመንን (አመትን) ይገልፃል።ተርጓሚ “ሮብዓም ንጉስ በነበረበት በአምስተኛው አመት”
በአምስተኛው አመት
“በ5 ዓመት”
ሺሻቅ በእየሩሳሌም ላይ መጣ
የግብፅ ንጉስ “ሺሻቅ” እርሱንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን የግብፅ ሠራዊት ይገልፃል። ተርጓሚ “ሺሻቅ ከእርሱ ጋር የነበሩት የግብፅ ሠራዊት በእየሩሳሌም ላይ መጡ”
ሺሻቅ
ይህ የሰው (ወንድ) ስም ነው የ1ነገስት 11:40 ትርጉምን ተመልከት
ላይ መጣ
ይህ ፈሊጣዊ ሲሆን ትርጉሙም ለማጥቃት መዝመት ማለት ነው።
ሁሉንም ወሰደ
ይህ ጥቅል ነው። የተገገውን የትኛውንም ዋጋ ያለው ነገር መውሰዱን ያመለክታል።
ወሰደ
ይህ ቃል ሺሻቅንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ወታደሮች ይወክላል። ተርጓሚ ሺሻቅና ወታደሮቹ ወሰዱ
ሰለሞን የሰራውን
x
1 Kings 14:27
ንጉስ ሮብዓም....ጋሶችን ሰራ
እዚህ ጋር “ንጉስ ሮብኣም” ለእረሱ ጋሻ የሚሰራለትን ሰው ይወክላል። ተርጓሚ የንጉስ ሮብዓም ሰራተኞች ጋሾችን ሰሩ
በዘበኞች ቤት
ይህ ቤት የወርቅ ጋሾቹ የሚቀመጡበት ቤት ነበር
በዘበኞች አለቆች እጅ አኖራቸው
እዚህ ጋር “እጅ” ጥንቃቄ ወይም ሀላፊነትን ይወክላል። ተርጓሚ “የአለቆቹ ኃላፊነት አደረጋቸው”
የንጉሡም ቤት ደጅ በሚጠብቁ
እዚህ ጋር “ደጅ” መግቢያን ይወክላል። ተርጓሚ “የንጉሱንም ቤት መግቢያ በሚጠብቁ”
በዘበኞች ይሸከሙአቸው ነበር
“የነሃስ ጋሾችን የሚሸከሙ ዘበኞች”
1 Kings 14:29
በይሁዳ ነገስታት ታሪክ መፅሃፍ የተፃፈ አይደለምን
ይህ በገቢር መልኩ ሊገለፅ የሚችል መልሱም አዎንታዊ እንደሚሆን ይገመታል። ጥያቄው የግነት የግነት የሆነው አፅንኦት ለመስጠትም ነው። ተርጓሚ “በይሁዳ ነገስታት ታሪክ ተፅፈዋል” ወይም “ከይሁዳ ነገስታት ታሪክ መፅሐፍ ማንበብ ትችላላችሁ”
በይሁዳ ነገስታት ታሪክ መፅሐፍ
ይህ በአሁኑ ጊዜ የሌለን መፅሐፍ ይገልፃል።
በዘመኑ ሁሉ...ሰልፍ ነበረ
“የማቋርጥ ሰልፍ (ጦርነት) ነበረ ” ወይም “የማያቋርጥ ፍልሚያ ነበረ”
በርብዓምና በኢዮርብዓም መካከል ሰልፍ ነበር
የነገስታቱ ስም እነርሱንና ሰራዊታቸውን ይወክላል። ተርጓሚ “የሮብዓምና የኢዮርብዓም ሰራዊቶች ደጋግመው ደጋግመው በፍልሚያ ታ ተዋጉ” ወይም “የሮብዓምና ህዝቡና የኢዮርብዓም ህዝብ በተከታታይ በጦር ኔዳ ተጋጠሙ (ጦርነት

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ገጠሙ)”
ከአባቶቻቹ ጋር አንቀላፉ
የኢዮርብዓም ሞት እንቅልፍን እንደተኛ ሰው ሆኖ ተነግሮአል።የ1ነገስት 2:10

ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “ሞተ” ወይም “አረፈ”
ከ....ጋር ተቀበረ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ህዝቡ ቀበረው”

Chapter 15
1 Kings 15:1
በናባጥ ልጅ በንጉሥ ኢዮርብዓም አስራ ስምንተኛ አመት
ይህ የሚያመለክተው የኢዮርብዓምን ንግሥና አስራ ስምንተኛ አመት ነው። "ኢዮርብዓም ለ አስራ ስምንት አመታተት ያህል የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በአስራ ስምንተኛው አመት
"በ18ተኛው አመት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉንም አይነት ኃጢአቶች አደረገ/ በኃጢአት መንገድ ተራመደ
ማድረግ/መራመድ የሚወክለው በኃጢአት መኖርን ነው፣ እናም በኃጢአት መራመድ የሚለው እነዚያን ኃጢአቶች መፈጸምን ነው። "አብያ እነዚያን ኃጢአቶች ማድረጉን ቀጠለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከእርሱ ዘመን በፊት አባቱ ያደርግ የነበረውን
እነዚህ ቁጥሮች በርካታ ነገሥታትን የሚያመለክቱ እንደመሆናቸው፣ የአብያን አባት ስም ማካተቱ ሊጠቅም ይችላል። ይህ መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "አባቱ ሮብዓም፣ ከአብያ ዘመን አስቀድሞ እንዳደረገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ ዘመን
ይህ ሀረግ የሚወክለው እርሱ ንጉሥ የነበረበትን ጊዜ ነው። የዚህ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "አብያ ንጉሥ ከነበረበት ጊዜ አስቀድሞ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ
ልቡ እንደ ዳዊት ልብ...አልተሰጠም ነበር
ልብ የሚወክለው መላ ስብዕናን ነው። "እንደ ዳዊት… አብያ ልቡን የሰጠ ሰው አልነበረም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 15:4
ለእርሱ በእየሩሳሌም መብራት ሰጠው
እዚህ ስፍራ "መብራት" የሚለው ቃል የሚወክለው ዳዊት ንጉሥ እንደነበረ በእርሱ ስፍራ የሚነግሥን የእርሱን ትውልድ ነው። "ለዳዊት በእየሩሳሌም የሚነግሥ ትውልድ ሰጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከእርሱ በኋላ የእርሱን ወንድ ልጅ በማስነሳት
"ከእርሱ በኋላ የአብያን ወንድ ልጅ በማስነሳት" ወይም "ለአብያ ወንድ ልጅ በመስጠት"
በዐይኖቹ ፊት ትክክል ሆኖ የታየውን
እዚህ ስፍራ ዐይኖች የሚለው የሚወክለው ማየትን፣ ሲሆን ማየት ደግሞ ሀሳብን ወይም ፍርድን ይወክላል። "ያህዌ ትክክል ነው የሚለው" ወይም "ያህዌ ትክክል ነው ብሎ የሚቆጥረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ የህይወት ዘመን ሁሉ
"ዳዊት በኖረበት ዘመን በሙሉ" ወይም "በዳዊት የህይወት ዘመን ሁሉ"
1 Kings 15:7
የይሁዳ ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው አንባቢያን ስለ አብያ ያለው መረጃ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚገኝ ለማሳወቅ ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ በ1ነገሥት 14:29 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እነዚህ ታሪኮች የይሁዳ ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ይህንን የይሁዳ ነገሥታት ድርጊቶች በተጻፈበት መጽሐፍ ጽፎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በአብያ እና በኢዮርብዓም መሃል
"አብያ" እና "ኢዮርብዓም" የሚሉት ስሞች የሚወክሉት ንጉሦቹን እና ሰራዊቶቻቸውን ነው። "በአብያ እና በኢዮርብዓም ሰራዊቶች መሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 15:9
በእስራኤል ንጉሥ በኢዮርብዓም ሃያኛ አመት
ይህ የሚያመለክተው የኢዮርብዓምን ሃያኛ አመት ንግሥና/ዘመነ መንግሥት ነው። "ኢዮርብዓም በእስራኤል ከነገሰ ከሃያ አመታት ያህል በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በሃያኛው አመት
በ20ኛው አመት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
አርባ አንድ አመታት
"41 አመታት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በያህዌ ዐይኖች ትክክል የሆነውን
እዚህ ስፍራ ዐይኖች የሚለው የሚወክለው ማየትን ሲሆን፣ ማየት ደግሞ ፍርድን ይወክላል። ያህዌ የዓሳን ድርጊቶች ተመልክቶ አጽድቋል። "ያህዌ ተመልክቶ ትክክል ነው የሚለው" ወይም "ያህዌ ትክክል ነው የሚለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 15:12
የቤተ ጣኦት ወንደቃዎች
ይህ የሚያመለክተው ምናልባትም ከጣኦት አምልኮ ጋር የተያያዘ የወንዶች ምንዝር አዳሪነትን ሊሆን ይችላል። "ሃይማኖታዊ አመንዝሮች" ወይም "ለጣኦት አገልግሎት የሚሰጡ አመንዝሮች" ወይም "ወንድ የሆኑ በአመንዝራነት የሚሰሩ"
አሳ አስጸያፊ ምስሎችን አፈረሰ
አሳ ንጉሥ ስለ ነበረ፣ መኳንንቱን ምስሎችን እንዲፈርጡ ነግሯቸው ሊሆን ይችላል። "አሳ አስጸያፊዎቹ ምስሎች እንዲፈርሱ አደረገ" ወይም "አሳ እርሱ አስጸያፊዎቹን ምስሎች እንዲያፈርሱ አደረገ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 15:14
ነገር ግን ከፍ ያሉት ስፍራዎች አልተወሰዱም ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አሳ ግን ሰዎቹ ከፍ ያሉ ስፍራዎችን እንዲወስዱ አላዘዘም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የአሳ ልብ ሙሉ ለሙሉ የተሰጠ ነበር
ልብ ሰውየውን ይወክላል። "አሳ ሙሉ ለሙሉ የተሰጠ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በዘመኑ በሙሉ
"በኖረበት ዘመን ሁሉ" ወይም "በህይወት ዘመኑ በሙሉ"
1 Kings 15:16
በዘመናቸው ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው እንደ ነገሥታት ሲገዙ የኖሩበትን ዘመን ነው። "በይሁዳ እና በእየሩሳሌም ሲገዙ በኖሩባቸው ዘመናት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በይሁዳ ላይ በቁጣ ተነሳ
"ይሁዳን ወጋ"
ራማን ሰራት
የባኦስ ሰራዊት በመጀመሪያ ራማን እንደወረራት ተጠቁሟል። የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ራማን ወረራት ደግሞም ምሽግ አድርጎ ሰራት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 15:18

በአገልጋዮቹ እጅ ላይ አስቀመጣት

ነገሮችን በእጆቻቸው ላይ ማስቀመት የሚወክለው እነዚያን ነገሮች ለእነርሱ መስጠትን ነው። እነርሱ እንዲያደርጉ የሚፈልገውን በእርሷ እንደሚያደርጉ ተጠቁሟል። የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ይህን ለአገላጋዮቹ አደራ ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እንዲህ አለ

ይህ ማለት በአገላጋዮቹ አማካይነት ተናገረ ማለት ነው። አሳ ለአገልጋዮቹ ለቤን ሀዳድ ምን እንደሚናገሩ እና እንደሚያደርጉ ነገራቸው። የዚህ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "አሳ ለአገልጋዮቹ ለቤን ሀዳድ እንዲነግሩት ነገራቸው" ወይም "አሳ በአገልጋዮቹ በኩል ለቤን ሀዳድ እንዲህ ሲል መልዕክት ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በእኔ እና በአንተ መሃል ቃል ኪዳን ይኑር

በሁለት ሰዎች መካከል ቃል ኪዳን መኖር የሚያመለክተው ሁለቱ ሰዎች በመሃላቸው ቃል ኪዳን እንዳለ ነው። "እርስ በእርሳችን ቃል ኪዳን ይኑረን" ወይም "የሰላም ስምምነት እናድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ፣ እኔ

"እኔ፣ ከአንተ ጋር ለመተማመኛ ስምምነት እፈልጋለሁ"

ከእስራኤል ንጉሥ ከባኦስ ጋር ያለህን ቃል ኪዳን አፍርስ

ቃል ኪዳንን ማፍረስ የሚወክለው አንድ ሰው ሊያደርግ ቃል የገባውን መሰረዝን እና አለማድረግን ነው። "ከእስራኤል ንጉሥ ከባኦስ ጋር የገባኸውን ኪዳን አፍርስ" ወይም "ለእስራኤል ንጉሥ ለባኦስ ከእርሱ ጋር ኪዳን ባደረግከው መሰረት ታማኝ አትሁንለት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእስራኤል ንጉሥ ከባኦስ ጋር ያለህን ቃል ኪዳን አፍርስ

x

1 Kings 15:20

እንዲህም ሆነ

እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ ትልቅ ክንዋኔን ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህንን ለመግለጽ መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ።

ራማን መገንባት አቆመ

ንጉሥ ባኦስ ለሰራተኞቹ በመንገር ይህንን አደረገ። "ሰራተኞቹ ራማን መገንባት እንዲያቆሙ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቴርሳ

ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14፡17 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

ማንም ከዚህ ነጻ አልነበረም

ይህ በአዎንታም ሊተረጎም ይችላል። "እያንዳንዱ ሰው የንጉሥ አሳን አዋጅ መታዘዝ አለበት"

1 Kings 15:23

የይሁዳ ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?

ይህ ጥያቄ የዋለው አንባቢያን ስለ አብያ ያለው መረጃ በዚህነ ሌሎች መጽሐፍት ውስጥ እንደሚገኝ ለማሳወቅ ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ በ1ነገሥት 14፡29 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እነዚህ ታሪኮች የይሁዳ ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ይህንን የይሁዳ ነገሥታት ድርጊቶች በተጻፈበት መጽሐፍ ጽፎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አሳ ከአባቶቹ ጋር ተኛ

እዚህ ስፍራ መተኛት ሞትን የሚወክል ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። "አብያ እንደ አባቶቹ ሁሉ ሞተ" ወይም "እንደ አባቶቹ ሁሉ አብያ ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

ከእነርሱ ጋር ተቀበረ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከአባቶቹ ጋር ቀበሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አባቱ ዳዊት

እዚህ ስፍራ "አባት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጥንት አባቶችን ነው።

1 Kings 15:25

አያያዥ ሀሳብ፡

ቀሪው ምዕራፍ 15 እና 16 ስለ እስራኤል ነገሥታት ነው። እነዚህ ድርጊቶች የይሁዳ ንጉሥ አሳ በህይወት በነበረበት ወቅት የተፈጸሙ ናቸው።

የይሁዳ ንጉሥ አሳ ሁለተኛ አመት

ይህ የሚያመለክተው የአሳን ዘመነመንግሥት ሁለተኛ አመት ነው። የዚህ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል፤ "አሳ የይሁዳ ንጉሥ በነበረባቸው ለሁለት አመት ለተጠጉ ጊዜያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለሁለት አመታት በእስራኤል ላይ ነገሠ

"ናዳብ በእስራኤል ላይ ለሁለት አመታት ነገሠ"

በያህዌ እይታ ክፉ የሆነውን

የያህዌ እይታ የሚለው የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። "በያህዌ ፍርድ/ሚዛን ክፉ የሆነውን" ወይም "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአባቱ መንገድ ሄደ

እዚህ ስፍራ መሄድ የሚወክለው ድርጊትን ነው። "አባቱ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በገዛ ራሱ ኃጢአት

በራሱ ኃጢአት መራመድ የሚለው የሚገልጸው አባቱ ካደረገው በተለየ መንገድ ኃጢአት መስራቱን ነው። "በራሱ መንገድ ኃጢአት አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህም እስራኤልን ወደ ኃጢአት መራ

ሰዎች አንድ ነገር እንዲያደርጉ መምራት የሚገልጸው ያንን ነገር እንዲያደርጉ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደርን ነው። "ኃጢአት በመስራት እስራኤልም እንዲበድል ተጽዕኖ አሳደረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 15:27

በናዳብ ላይ አሴረ

"ንጉሥ ናዳብን ለመግደል በምስጢር አሴረ/ተንኮል ጠነሰሰ"

ገባቶን

ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ናዳብ እና መላው እስራኤል

"መላው እስራኤል" የሚለው ሀረግ ከእስራኤል ወታደሮች አመዛኙን የሚወክል ነው። "ናዳብ እና በርካታው እስራኤል ወታደር" ወይም "ናዳብ እና የእስራኤል ሰራዊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክዶክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ክፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እናኩሸት እንደዚሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

ገባቶንን ከበው ነበር

"ስለዚህም የገባቶን ሰዎች ለእነርሱ እጃቸውን እንዲሰጡ፣ ከተማይቱን ከበው ነበር"

በእርሱ ስፍራ ነገሠ

"በእርሱ ስፍራ" የሚለው ሀረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "በእርሱ ምትክ" ማለት ነው።" "በናዳብ ምትክ ንጉሥ ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 15:29

ባኦስ የኢዮርብዓምን ቤተሰብ በሙሉ ገደለ። አንድም የኢዮርብዓምን ትውልድ እስትንፋስ አላስቀረም።

እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የተጣመሩት ትውልዶቹ መገደላቸውን ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መላው የኢዮርብዓም ቤተሰብ

ኢዮርብዓም የንጉሥ ናዳብ አባት ነበር።
ከኢዮርብዓም ቤተሰብ አንድም በእስትንፋስ አላስቀረም
እስትንፋስ የሚወክለው በህይወት መትረፍን ነው። "ከኢዮርብዓም ቤተሰብ አንዱንም በህይወት አላስቀረም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ የንግሥና መስር
"የኢዮርብዓም የንግሥና መስመር/ዘር ሀረግ"
ያህዌ ልክ በአገልጋዩ በሴሎናዊው በአኪያ እንደተናገረው
በ1 ነገሥት 14:10-11 ላይ ያህዌ በነቢዩ አኪያ በኩል ቤተሰቡን እንደሚያጠፋ ለኢዮርብዓም ተናግሮታል።
ሴሎናዊው አኪያ
"ከሴሎና የሆነው፣ አኪያ"
ኢዮርብዓም ለፈጸማቸው ኃጢአቶች እና እስራኤልን ወደ ኃጢአት ለመምራቱ
"ኃጢአት" የሚለው ረቂቅ ስም በግሥ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። "ኢዮርብዓም ኃጢአት በመፈጸሙ ምክንያት እና በተመሳሳይ መንገድ እስራኤልን ወደ ኃጢአት በመምራቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እስራኤልን ወደ ኃጢአት በመምራቱ
ሰዎችን አንድ ነገር እንዲያደርጉ መምራት የሚገልጸው አንድ ነገር እንዲፈጸሙ ተጽዕኖ ማሳደርን ነው። "እስራኤል ኃጢአት እንዲያደርግ ተጽዕኖ በማሳደሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 15:31
የይሁዳ ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው አንባቢያን ስለ ናዳብ ያለው መረጃ በዚህነ ሌሎች መጽሐፍት ውስጥ እንደሚገኝ ለማሳወቅ ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ በ1ነገሥት 14:29 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እነዚህ ታሪኮች የይሁዳ ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ይህንን የእስራኤል ነገሥታት ድርጊቶች በተጻፈበት መጽሐፍ ጽፎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በዘመናቸው ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው ንጉሥ ሆነው የገዙበትን ዘመን በሙሉ ነው። ይህ በ1 ነገሥት 15:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በእስራኤል እና በይሁዳ በገዙባቸው ዘመናት ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
1 Kings 15:33
አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ምዕራፍ በ1 ነገሥት 15:27-28 ባለው ክፍል ባኦስ እንዴት እንደነገሠ ይናገራል። እነዚህ ቁጥሮች ባኦስ እንዴት የእስራኤል ንጉሥ መሆን እንደጀመረ መናገር ይጀምራሉ።
ቴርሳ
ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14:17 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።
በያህዌ እይታ ክፉ የሆነውን
የያህዌ እይታ የሚለው የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። "በያህዌ ፍርድ/ሚዛን ክፉ የሆነውን" ወይም "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በኢዮርብዓም መንገድ ሄደ
እዚህ ስፍራ መሄድ የሚወክለው ድርጊትን ነው። "ኢዮርብዓም ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ኃጢአት እስራኤልን ወደ በደል በመራበት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች "የእርሱ" እና "እርሱ" የሚያመለክቱት 1)በኦስን ወይም 2)ኢዮርብዓምን ነው።
እስራኤልን ወደ ኃጢአት በመምራቱ
ሰዎችን አንድ ነገር እንዲያደርጉ መምራት የሚገልጸው አንድ ነገር እንዲፈጸሙ ተጽዕኖ ማሳደርን ነው። "እስራኤል ኃጢአት እንዲያደርግ ተጽዕኖ በማሳደሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 16
1 Kings 16:1
የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር እግዚአብሔር ተናገረ ማለት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ እንዲህ ሲል መልዕክቱን ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ምንም እንኳን እኔ አንተን ከፍ ባደርግህም
ይህ እግዚአብሔር ለባኦስ ይነግረው ዘንድ ለኢዩ የሰጠው መልዕክት ነው። "አንተ" የሚለው ቃል ባኦስን ያመለክታል።
ከአፈር ላይ ከፍ አደረግሁህ
"ከአፈር ላይ አነሳሁህ።" መሬት አፈር ላይ መቀመጥ የሚገልጸው ጥቅም የሌለው መሆንን ነው። አንድን ሰው ከፍ ከፍ ማድረግ የሚገልጸው ሰውየውን ጠቃሚ ማድረግን ነው። "ጥቅም ከማይሰጥ ስፍራ አነሳሁህ" ወይም "ምንም ሀይል ወይም በሰዎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደር በማትችልበት ጊዜ አንስቼ ጠቃሚ አደረግሁህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በኢዮርብዓም መንገድ ሄድክ
መሄድ የሚወክለው ማድረግን ነው። ኢዮርብዓም እና ባኦስ ሁለቱም ኃጢአት ሰርተዋል። የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ኢዮርብዓም ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አንተም አደረግህ" ወይም "ኢዮርብዓም እንደበደለ/ኃጢአት እንደ ሰራ አንተም በደልክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
1 Kings 16:3
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለባኦስ በእርሱ ላይ የሚያደርሰውን መንገሩን ቀጥሏል።
እነሆ፣ ባኦስን እና ቤተሰቡን እኔ ሙሉ ለሙሉ ጠራርጌ አጠፋለሁ
ያህዌ ለባኦስ እየተናገረ ነው፤ "የእርሱ ቤተሰብ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የባኦስን ቤተሰብ ነው። ይህ "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉትን ቃላት በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። "ባኦስ ሆይ፣ አድምጥ። እኔ ሙሉ ለሙሉ አንተን እና የአንተን ቤተሰብ ጠርጌ አጠፋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ሙሉ ለሙሉ ጠርጌ አጠፋለሁ
ጠራርጎ ማጥፋት የሚገልጸው መደምሰስን ነው። "እኔ ሙሉ ለሙሉ አጠፋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 16:5
የእስራኤል ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የዋለው አንባቢያን ስለ ባኦስ ያለው መረጃ በዚህነ ሌሎች መጽሐፍት ውስጥ እንደሚገኝ ለማሳወቅ ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ በ1ነገሥት 15:31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እነዚህ ታሪኮች የእስራኤል ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ
የእስራኤል ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ይህንን የእስራኤል ነገሥታት ድርጊቶች በተጻፈበት መጽሐፍ ጽፎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ባኦስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ/ተኛ
እዚህ ስፍራ መተኛት ሞትን የሚወክል ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። "ባኦስ እንደ አባቶቹ ሁሉ ሞተ" ወይም "እንደ አባቶቹ ሁሉ ባኦስ ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)
ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች እርሱን ቀበሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ቴርሳ

ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14፡17 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

በእርሱ ስፍራ ነገሠ

"በእርሱ ስፍራ" የሚለው ሀረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "በእርሱ ምትክ" ማለት ነው።" "በባኦስ ምትክ ንጉሥ ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:7

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለህዝቡ አዲስ ነገርን ለማስተዋወቅ የሚውል ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በያህዌ እይታ ሲታይ እርሱ ያደረገውን ክፉ የሆነውን ሁሉ

የያህዌ እይታ የሚለው የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። "ባኦስ ያደረገው በያህዌ ፍርድ/ሚዛን ክፉ የሆነውን" ወይም "ባኦስ ያደረገውን ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን ነገር ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እንዲቆጣ ለማነሳሳት

"ቁጣ" የሚለው ረቂቅ ስም "መቆጣት" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ በጣም እንዲቆጣ የሚያደርግ" ወይም "እግዚአብሔርን በጣም የሚያስቆጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእጆቹ ስራ

እዚህ ስፍራ ባኦስ የተወከለው በ"እጆቹ" ነው። ይህ የሚናገረው ድርጊቶቹን ሁሉ እንደ እርሱ "ስራ" አድርጎ ነው። "ባኦስ ባደረጋቸው ነገሮች" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:8

ቴርሳ

ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14፡17 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

የእርሱ አገላጋይ ዘምሪ

"የኤላ አገልጋይ ዘምሪ"

የገሙሱ የእርሱ ሰረገሎች አዛዥ

እዚህ ስፍራ "ሰረገላ" የሚለው ቃል የሚወክለው ሰረገሎቹን የሚነዱትን ወታደሮች ነው። "የእርሱ ገሚሶቹ ሰረገሎች ነጂዎች አዛዦች" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ራሱ መጠጥ ጠጥቶ ነበር

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ብዙ ወይን መጠጣት እንዲሰክር አድርጎት ነበር" ወይም "ሰክሮ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በቤቱ ላይ የበላይ የነበረው

በቤቱ ላይ የበላይ መሆን በንጉሥ ኤላ ቤት ሃላፊ መሆንን ያመለክታል። "በኤላ ቤት ባሉ ነገሮች ላይ ሃላፊ የነበረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጥቅቶ ገደለው

"ኤላን አጥቅቶ ገደለው"

በእርሱ ስፍራ ንጉሥ ሆነ

"በእርሱ ስፍራ" የሚለው ሀረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "በእርሱ ምትክ" ማለት ነው። "በኤላ ምትክ ነገሠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:11

አንድም ወንድ በህይወት አልተወም

ይህ ማለት ሁሉንም አዋቂ ወንዶች እና ወንድ ልጆች ገድሏል ማለት ነው። "አንድ እንኳን ወንድ በህይወት አልተወም"

የያህዌ ቃል

"ከያህዌ ዘንድ የመጣ መልዕክት" ወይም "የያህዌ መልዕክት"

በነቢዩ በኢዩ በኩል በባኦስ ላይ እርሱ የተናገረው

"በ" ነቢይ መናገር የሚወክለው ለአንድ ነቢይ መንገር እና ነቢዩ ሲናገር ማለት ነው። "በባኦስ ላይ እንዲናገር ያህዌ ለነቢዩ ለኢዩ የነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እስራኤልን ወደ ኃጢአት መሩ

ሰዎችን አንድ ነገር እንዲያደርጉ መምራት የሚገልጸው አንድ ነገር እንዲፈጽሙ ተጽዕኖ ማሳደርን ነው። "እስራኤል ኃጢአት እንዲያደርግ ተጽዕኖ አሳደሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እስራኤልን ወደ ኃጢአት መሩ

"እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለአስሩ ሰሜናዊ የእስራኤል ነገዶች ነው። ባኦስ እና ኤላ የእነርሱ ንጉሦች ነበሩ።

የእስራኤልን አምላክ፣ ያህዌን በጣኦቶቻቸው አስቆጡት

እግዚአብሔር ህዝቡን የተቆጣው ጣኦቶችን ስላመለኩ ነው። የዚህ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ጣኦቶችን በማምለካቸው ምክንያት የእስራኤልን አምላክ ያህዌን አስቆጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል አምላክ

እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የያዕቆብ ትውልድ የሆኑትን አስራ ሁለቱንም ነገዶች በአጠቃላይ ነው።

1 Kings 16:14

የእስራኤል ንጉሦች...እነርሱ አልተጻፉምን?

ይህ ጥያቄ የዋለው በዚህ ሌላ መጽሐፍ ስለ ኤላ መረጃ እንዳለ ለአንባቢው መረጃ ለመስጠት ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፤ ይህ በ1 ነገሥት 15፡31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የእስራኤል ነገሥታት በፈጸሟቸው ድርጊቶች መጽሐፍ ውስጥ እነዚህ ተጽፈዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል... አልተጻፉምን?

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ስለ እነርሱ በእስራኤል ነገስታት ድርጊቶች መጽሐፍ ጽፏል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:15

ቴርሳ

ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14፡17 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ

ሰራዊቱ በገባቶን ሰፍሮ ነበር

"ሰራዊት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግስት ሰራዊት ነው።

ገባቶን

ይህ የከተማ ስም ነው።ይህ በ1 ነገሥት 15፡27 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመለከቱ።

በዚያ የሰፈረው ሰራዊት እንዲህ ሲሉ ሰማ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በዚያ የሰፈሩት ወታደሮች እንዲህ ሲናገሩ ሰሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መላው እስራኤል

በሁለቱም ጊዜያት ይህ ሀረግ አገልግሏል፣ ይህም የሚወክለው የእስራኤልን ሰራዊት ነው። "ሁሉም" የሚለው ቃል ትርጉም "ብዙዎቹ" የሚል ማጠቃለያ ነው። "መላው የእስራኤል ሰራዊት" ወይም "በእስራኤል ሰራዊት ውስጥ አብዛኛው ወታደር" ወይም "የእስራኤል ሰራዊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ኩሽት እንስዚሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

1 Kings 16:18

ከተማይቱ ተወስዳ/ተይዛ ነበር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ይኸውም ዖምሪ እና ሰራዊቱ ከተማይቱን ያዟት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በያህዌ ፊት ክፉ የነበረውን

የያህዌ እይታ የሚለው የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። "በያህዌ ፍርድ/ሚዛን ክፉ የሆነውን" ወይም "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በኢዮርብዓም መንገድ መሄድ

መሄድ የሚወክለው ማድረግን ነው። "ኢዮርብዓም ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አንተም አደረግህ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን ወደ ኃጢአት መምራት

ሰዎች አንድ ነገር እንዲያደርጉ መምራት የሚገልጸው አንድ ነገር እንዲፈጸሙ ተጽዕኖ ማሳደርን ነው። "እስራኤል ኃጢአት እንዲያደርግ ተጽዕኖ ማሳደር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ የፈጸመው ክህደት

ክህደቱ የሚያመለክተው ዘምሪ የእስራኤልን ንጉሥ ኤላን ለመግደል ያደረገውን ሴራ ነው። የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "በንጉሥ ኤላ እንዴት ሴራ ፈጸመ" ወይም "የእስራኤልን ንጉሥ እንዴት እንደ ገደለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?

ይህ ጥያቄ የዋለው አንባቢያን ስለ ዘምሪ ያለው መረጃ በዚነህ ሌሎች መጽሐፍት ውስጥ እንደሚገኝ ለማሳወቅ ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ በ1ነገሥት 14:29 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እነዚህ ታሪኮች የእስራኤል ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል ነገሥታት ...የተጻፈ አይደለምን?

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ይህንን የእስራኤል ነገሥታት ድርጊቶች በተጻፈበት መጽሐፍ ጽፎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:21

ታምኒንን ተከትሎ...ዖምሪን ተከትሎ

እዚህ ስፍራ "መከተል" የሚወክለው እርሱን መደገፍ ወይም ንጉሥ ለማድረግ መፈለግን ነው። "እርሱን ለማንገስ፣ የጎናትን ልጅ ታምኒን መደገፍ፣ እንደዚሁም እኩል ድጋፍ ለዖምሪ ማድረግ" ወይም "የጎናትን ልጅ ታምኒን ለማንገሥ መፈለግ፣ እና ገሚሱ ዖምሪን ለማንገሥ መፈለጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ታምኒን ከሚከተሉ ሰዎች ይልቅ ጠንካሮች ነበሩ

"ታምኒን የተከተሉትን ሰዎች አሸነፈ"

1 Kings 16:23

ቴርሳ

ይህ የከተማ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14:17 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ፡

ሳምር

ይህ የሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለት መክሊት/ታላንት ብር

ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ይችላሉ። "ወደ 66 ኪሎ ግራም የሚጠጋ ብር" (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ወቅት የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከተማ ሰራ/ገነባ

"እርሱ" የሚለው ቃል ዖምሪን ያመለክታል። ሰዎች ከተማ እንደሚመሰርቱ አዘዘ። "ዖምሪ ህዝቡ ከተማ እንዲገነባ አደረገ" ወይም "በዖምሪ ትዕዛዝ ህዝቡ ከተማ ገነባ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ

በሳምር ስም

ይህ ፈሊጥ ሲሆን "ሳምርን ለማክበር" ወይም "ህዝቡ ሳምርን ያስታውሰው ዘንድ" የሚል ትርጉም አለው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:25

በያህዌ ፊት ክፉ የነበረውን

የያህዌ እይታ የሚለው የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። "በያህዌ ፍርድ/ሚዛን ክፉ የሆነውን" ወይም "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም በሄደበት መንገድ ሁሉ ሄደ

መሄድ የሚወክለው ማድረግን ነው። "የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አደረገ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን ወደ ኃጢአት በመራበት በእርሱ ኃጢአት

"የእርሱ" ወይም "እርሱ" የሚለው ለሚያመለክተው ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)ባኦስ ወይም 2)ኢዮርብዓም

በእርሱ በደሎች

በኃጢአት መመላለስ ለሚለው ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)ኢዮርብዓም እንደ በደለ መበደል። "እርሱ ኢዮርብዓም እንደ በደለ በድሏል" ወይም 2) ኃጢአትን ልምድ አድርጎ መያዝ/መፈጸም። "እርሱ ዘወትር ይበድላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን ወደ ኃጢአት በመራበት

ሰዎች ኃጢአት እንዲሰሩ መምራት የሚገልጸው ኃጢአት እንዲፈጸሙ ተጽዕኖ ማሳደርን ነው። "እስራኤል ኃጢአት እንዲያደርግ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የእርሱ በደሎች" ወይም "እንዲህ ባለ ሁኔታ ኃጢአት በመፈጸም ሰዎች ኃጢአት እንዲሰሩ ተጽዕኖ አሳድሯል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እርባና ቢስ በሆኑ ጣኦቶቻቸው... ያህዌን ለቁጣ ማነሳሳት

እግዚአብሔር ህዝቡን የተቆጣው ጣኦቶችን ስላመለኩ ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በ1 ነገሥት 16:13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እርባና ቢስ የሆኑ ጣኦቶችን በማምለክ ምክንያት የእስራኤልን አምላክ ያህዌን ማስቆጣት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርባና ቢስ የሆኑ ጣኦቶቻቸው

እዚህ ስፍራ "እርባና ቢስ/ጥቅም የለሽ" የሚለው ቃል ጣኦቶች አንዳች ነገር ማድረግ እንደማይችሉ ሰዎችን ያሳስባል/ያስታውሳል። "እርባና ቢስ የሆኑ፣ ጣኦቶቻቸው" ወይም "ምንም ጥቅም የሌላቸው ጣኦቶቻቸው" (መለየትን ከመረጃ መስጠት ወይም ማስታወስ ጋር ማስተያየት የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል አምላክ

እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የያዕቆብ ትውልዶች የሆኑትን አስራ ሁለቱን ነገዶች በሙሉ ነው።

1 Kings 16:27

የእስራኤል ነገሥታት ስራዎች በተጻፈበት መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ አይደለምን?

ይህ ጥያቄ የዋለው አንባቢያን ስለ ዖምሪ ያለው መረጃ በዚነህ ሌሎች መጽሐፍት ውስጥ እንደሚገኝ ለማሳወቅ ወይም ለማስታወስ ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። ይህ በ1 ነገሥት 15:31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እነዚህ ታሪኮች የእስራኤል ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል ነገሥታት ...የተጻፈ አይደለምን?

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ይህንን የእስራኤል ነገሥታት ድርጊቶች በተጻፈበት መጽሐፍ ጽፎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ዖምሪ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ/ተኛ

እዚህ ስፍራ መተኛት ሞትን የሚወክል ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። "ዖምሪ እንደ አባቶቹ ሁሉ ሞተ" ወይም "እንደ አባቶቹ ሁሉ ዖምሪ ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

በእርሱ ስፍራ ነገሠ

"በእርሱ ስፍራ" የሚለው ሀረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "በእርሱ ምትክ" ማለት ነው።" "በዖምሪ ምትክ ንጉሥ ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:29

በያህዌ ፊት ክፉ የነበረውን

የያህዌ እይታ የሚለው የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። "በያህዌ ፍርድ/ሚዛን ክፉ የሆነውን" ወይም "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 16:31

በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም መንገድ መሄድን እና ኃጢአት መስራትን አክአብ እንደ ቀላል ነገር ቆጥሮት ነበር

ይህ አክአብ የከፋ ኃጢአት መስራትን ፈልጎ እንደነበር ያሳያል። የዚህ ሀሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "አክአብ በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄድን እንደ ቀላል ነገር ቆጥሮት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአክአብ ይህ ጥቂት/ እዚህ ግባ የማይባል ነገር ነበር

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ለአክአብ" የሚለው ሀረግ አክአብ አንድ ነገር አስቦ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ቀይም ተመልክቶ ነበር ማለት ነው። "አክአብ ይህ ተራ ነገር አድርጎ ተመልክቶት ነበር" ወይም "አክአብ ይህ ኃጢአት ትንሽ እንደሆነ አስቦ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር ሚለውን ይመልከቱ)

የማይረባ ነገር

"ጥቂት እንደሆነ ነገር" ወይም "በቂ እንዳልሆነ"

በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄድ

በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄድ የሚወክለው ኢዮርብዓም እንደ ሰራው ኃጢአት መስራትን ነው። "የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም እንደ በደለ መበደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዓልን ማምለክ እና ለእርሱ መስገድ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ለእርሱ መስገድ" የሚለው ሀረግ የሚገልጸው ሰዎች በአምልኮ ጊዜ የሚኖራቸውን የአቋም ሁኔታ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል አምላክ

እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አስራ ሁለቱን የእስራኤል ነዶች በሙሉ ነው።

የእስራኤል ነገሥታት

እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አስሩን ነገዶች የሚይዘውን የእስራኤልን መንግስት ነው።

1 Kings 16:34

በበኩር ልጁ በኢብሮን የህይወት ዋጋ

ከተማይቱን መገንባት የሚያስከትለው ነገር የተገለጸው አኪኤል እንደሚከፍለው ዋጋ ተደርጎ ነው። "ኃጢአቱ ሚያስከትለው የበኩር ልጁ የኢብሮንን መሞት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የመጨረሻ ልጁ ሠጉብ ህይወቱን ያጣል

ሞት የተገለጸው ህይወቱን በማጣት ነው። "የመጨረሻ ልጁ ሠጉብ፣ ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የከተማይቱን መግቢያ በሮች ሲገነባ

"አኪኤል የከተማይቱን መግቢያ በር በሚገነባበት ጊዜ"

የያህዌን ቃል ይጠበቅ ዘንድ

"በያህዌ ቃል መሰረት"

የያህዌ ቃል

"ከያህዌ ዘንድ የመጣው መልዕክት" ወይም የያህዌ መልዕክት"

በነዌ ልጅ በኢያሱ የተናገረው

"በ" አንድ ሰው መናገር የሚወክለው እንዲናገር ለአንድ ሰው መንገርን እና ያንን የሚያደርገውን ሁለቱንም ሰዎች ነው። "ያህዌ እንዲናገር ያደረገው የነዌ ልጅ ኢያሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 17

1 Kings 17:1

ቴስብያዊ

ይህ ከቴስብያ የሆኑ ሰዎች የወል ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቴስብ

ይህ በገለዓድ ግዛት የምተገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል አምላክ ህያው እግዚአብሔርን

ይህ ሀረግ እርሱ የሚናገረው እውነት መሆኑን ትኩረት የሚሰጥ መሀላ ነው።

በፊቱ የቆምኩት

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን "ማገልገል" የሚል ትርጉም አለው። "እኔ የማገለግለው እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጤዛ

በምሽት ጊዜ በተክሎች ላይ የሚፈጠር የውሃ ጠብታዎች

1 Kings 17:2

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ

የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም እግዚአብሔር ይናገራል ማለት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ የእርሱን መልዕክት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኮራት

ይህ በጣም ትንሽ የሆነ ወራጅ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ይሆናል

ይህ ሀረግ የዋለው ያህዌ በድርቅ ወቅት እንዴት ለኤልያስ እንክብካቤ እንደሚያደርግለት ለማስተዋወቅ ነው። "በዚያ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ቁራዎች

ትልቅ፣ ጥቁር ወፎች (የማይታወቁትን ነገሮች መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 17:5

የያህዌ ቃል እንደሚያዘው

እዚህ ስፍራ "ቃሉ" የሚለው የሚወክለው ያህዌን ራሱን ነው። "ያህዌ እንዳዘዘው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የኮራት ጅረት

ይህ በጣም ትንሽ የሆነ ወንዝ ስም ነው። ይህ በ1 ነገሥት 17:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድሪቱ

"በዚያ አካባቢ" ወይም "በዚያች አገር"

1 Kings 17:8

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ

የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም እግዚአብሔር ይናገራል ማለት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ የእርሱን መልዕክት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እርሱ መጣ

እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኤልያስን ነው።

ሰራፕታ

ይህ ከተማ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ፣ እኔ

"ትኩረት ስጡ፣ ምክንያቱም እኔ፡ ቀጥሎ የምናገረው እውነተኛ እና ጠቃሚም ነገር ነው"

1 Kings 17:11

በህያው አምላክህ ስም

ይህ ሀረግ እርሷ የምትናገረው እውነት መሆኑን የሚያጎላ መሃላ ነው

አንድ እፍኝ ምግብ/አንዷ የሚበላ

"ትንሽ ምግብ"

ምግብ

"ዱቄት።" ይህ ዳቦ ለመጋገር/ለማዘጋጀት የሚያገለግል ነው።

እነሆ፣ እኔ

"እኔ፣ ምን እንደማደርግ ልንገርሽ"

ሁለት እንጨት

ይህ ሁለት እንጨቶች ወይም ጥቂት ጭራሮዎችን ሊያመለክት ይችላል። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ያለቺንን በልተን፣ ከዚያ እንሞታለን

ከዚያ ወዲያ ምንም የሚበሉት ምግብ ስለሌለ እንደሚሞቱ ተጠቁሟል። "ያቺን በልተን፣ ከዚያ በኋላ በረሃብ እንሞታለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ በኋላ ለአንቺ እና ለልጅሽ አዘጋጂ

በውስጠ ታዋቂነት ተጨማሪ ዳቦ ለማዘጋጀት ዱቄት እና ዘይት እንደሚኖር ተነግሯል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 17:14

ያህዌ ዝናብ ላክ/ሰጠ

ይህ ፈሊጥ ሲሆን ያህዌ ዝናብ አዘነበ ማለት ነው። "ያህዌ ዝናብ አዘነበ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ እና ኤልያስ፣ ከባሏ ጋር፣ ለብዙ ቀን ተመገቡ

በመጀመሪያው በተጻፈበት ቋንቋ እንዲህ ይላል፣ "እናም እርሷ፣ እርሱ እና የእርሷ ባል

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ለብዙ ቀናት ተመገቡ።" "እርሱ" የተባለው ማን እንደሆነ ግልጽ አይደለም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኤልያስ፣ መበለቲቱ፣ እና የእርሷ ወንድ ልጅ ለብዙ ቀናት ተመገቡ ወይም 2) መበለቲቱ፣ እና በእርሷ ቤት የሚኖሩ ሁሉ ለብዙ ቀናት ተመገቡ።

ከቤተሰቧ ጋር

"ቤተሰብ" ለሚለው ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም 1) ይህ የመበለቲቱን ወንድ ልጅ ብቻ ያመለክታል ወይም 2) ይህ በእርሷ ቤት የሚኖሩ ሌሎች ሰዎችን ሲያመለክት ነገር ግን እነማን እነደሆኑ በታሪኩ ውስጥ አልተጠቀሰም ወይም 3) ይህ የእርሷን ወንድ ልጅ እና በእርሷ ቤት የሚኖሩ ሌሎችን ያመለክታል

ልክ የያህዌ ቃል እንደተናገረው

እዚህ ስፍራ "ቃል" የሚወክለው ያህዌን ራሱን ነው። "ልክ ያህዌ እንደ ተናገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 17:17

የቤቱ ባለቤት፣ የሴትየዋ ወንድ ልጅ

"የቤቱ ባለቤት የሆነችው ሴት ወንድ ልጅ"

በውስጡ የቀረ የህይወት እስትንፋስ አልነበረም

ይህ የልጁ መሞት ሻል ባለ ቋንቋ የተገለጸበት መንገድ ነው። "መተንፈስ አቁሞ ነበር" ወይም "ሞቶ ነበር" (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ሰው

"የእግዚአብሔር ሰው" የሚለው ሀረግ የነቢይ ሌላው መጠሪያ ነው።

የቱ ኃጢአቴ

ይህ ማለት በአጠቃላይ የተሰራን ኃጢአት እንደጂ አንድ የተለየ ኃጢአትን አያመለክትም። "የትኖቹ ኃጢአቶቼ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ክፍለ ስማዊ ሀረጎች የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 17:19

እርሱ በነበረበት ስፍራ

እዚህ ቦታ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ኤልያስን ነው።

በገዛ ራሱ አልጋ ላይ

እዚህ ቦታ "የእርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ኤልያስን ነው።

አንተም ደግሞ ተቀብላ የምታስተናግደኝ መበለት ላይ ልጇን በመግደል ጥፋትን ታመጣባታለህን?

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኤልያስ በእውነት ጥያቄ እየጠየቀ ነው። "ተቀብላ የምታስተናግደኝን መበለት፣ ልጇን በመግደል ለምን ብዙ እንድትሰቃይ ታደርጋለህ" ወይም 2) ኤልያስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ምን ያህል እንዳዘነ ለመግለጽ ነው። "በእርግጥ፣ ተቀብላ የምታስተናግደኝን መበለት ልጇን በመግደል ይበልጥ እንድተሰቃይ አታደርግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተም በመበለቲቱ ላይ ጥፋት ታመጣለህ

መበለቲቱ መሰቃየቷ የተገለጸው "ጥፋት" እንደ ዕቃ በእርሷ ላይ የተቀመጠ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ደግሞ ጥፋት ታመጣባታለህ

እዚህ ስፍራ "ደግሞ/በተጨማሪ" የሚለው ትርጉም ድርቅ ካደረሰባት ጥፋት በተጨማሪ ማለት ነው።

ራሱን በትንሹ ልጅ ላይ ዘረጋ

ይህ ፈሊጥ ነው። "በትንሹ ልጅ ላይ ተጋደመ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 17:22

ያህዌ የኤልያስን ድምጽ ሰማ

እዚህ ስፍራ "ድምጽ" የሚወክለው ኤልያስ የጸሌውን ነው። "ያህዌ ለኤልያስ ጸሎት ምላሽ ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የትንሹ ልጅ ህይወት ወደ እርሱ ተመለሰች፣ እናም ነቃ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ትንሹ ልጅ ዳግም ወደ ህይወት ተመለሰ" ወይም "ትንሹ ልጅ እንደገና ህያው ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ክፍል

እዚህ ስፍራ "የእርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ኤልያስን ነው።

እነሆ፣ ልጅሽ በህይወት አለ

እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው አስደናቂ መረጃ ያነቃናል።

የያህዌ ቃል በአፍህ እውነት ነው

"በአፍህ ያለው የያህዌ መልዕክት እውነት ነው።" "አፍ" የሚለው ቃል የሚወክለው ኤልያስ የተናገረውን ነው። "ከያህዌ ዘንድ የተናገርከው መልዕክት እውነት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 18

1 Kings 18:1

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ የእርሱን መልዕክት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በምድሪቱ ላይ ዝናብ ላክ

"በምድሪቱ ላይ እንዲዘንብ አደረገ"

አሁን ችጋሩ/ረሃቡ ታላቅ ነበር

"አሁን" የሚለው ቃል እዚህ ስፍራ የዋለው በዋናው የታሪክ አካሄድ ላይ ማረፊያ ለማበጀት ነው። እዚህ ላይ ጸሐፊው ድርቁ/ችጋሩ ምን ያህል ሰማርያን እንደጎዳት የመረጃ ዳራ ይሰጠናል። (የመረጃ ዳራ/መነሻ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 18:3

አሁን አብድዩ ያህዌን አከበረ

"አሁን" የሚለው ቃል እዚህ ስፍራ የዋለው በዋናው የታሪክ አካሄድ ላይ ማረፊያ ለማበጀት ነው። እዚህ ላይ ጸሐፊው በታሪኩ ውስጥ ስለ አዲስ ሰው ይነግረናል።

አንድ መቶ ነቢያት በሃምሳ ከፍሎ ደበቃቸው

"100 ነቢያትን በቡድን 50 እያደረገ ደበቃቸው" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 18:5

ፈረሶችን እና በቅሎዎችን በህይወት ጠበቀ...ሁሉንም እንስሳት አዳነ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ትኩረት ለመስጠት ተጣምረዋል። "ፈረሶችን እና በቅሎዎችን ከሞት አዳናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አክአብ በራሱ በአንድ መንገድ ሄደ ደግሞም አብድዩ በሌላ መንገድ ሄደ

"በራሱ" የሚለው የሚለው ሀረግ አክአብ እና አብድዩ በተለያየ አቅጣጫ መሄዳቸውን ያጎላል፣ ይህ ማለት ከአክአብ ጋር ማንም አልነበረም ማለት አይደለም። "አክአብ ቡድኑን በአንድ አቅጣጫ ሲመራ አብድዩም ቡድኑን በሌላ አቅጣጫ መርቷል። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 18:7

ጌታዬ ኤልያስ

እዚህ ስፍራ "ጌታ" የሚለው ቃል የዋለው ክብርን መግለጫ ተደርጎ ነው።

ሄደህ ለጌታህ ፣ 'እነሆ፣ ኤልያስ እዚህ አለ ብለህ ንገረው።'

እዚህ ስፍራ "ጌታ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አክዓብን ነው።

እነሆ፣ ኤልያስ

"ኤልያስ ሆይ፣ ትኩረት ስጠኝ፣ ምክንያቱም ቀጥሎ የምናገረው እውነትም ጠቃሚም ነው"

1 Kings 18:9

እርሱ ይገድለኝ ዘንድ ... እኔ ምን በድያለሁ?

አብድዩ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ንጉሥ አክአብ በኤልያስ ላይ ባለው ቁጣ ምክንያት እርሱ የሚደርስበትን አደጋ ትኩረት ለመስጠት ነው። "እርሱ ይገድለኝ ዘንድ...እኔ በአንተ ላይ ስህተት አልፈጸምኩም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አገልጋይህን ለአክዓብ እጅ አሳልፈህ ትሰጥ ዘንድ

"እጅ" ለሃይል እና ቁጥጥር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "አገልጋይህን ለአክዓብ አሳልፈህ ለመስጠት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ አገልጋይ

አብድዩ ኤልያስን ለማክበር ራሱን የኤልያስ አገልጋይ ሲል ይናገራል።



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በህያው አምላክህ እምላለሁ
ይህ መሃላ የሚያገለግለው እርሱ እየተናገረ ያለው ነገር እውነት መሆኑን ለማጉላት ነው።
ጌታዬ ሰዎችን ያላከበት አገር ወይም ግዛት የለም
እዚህ ስፍራ "አገር ወይም ግዛት የለም" የሚለው ሰዎች ኤልያስን ፍለጋ በጣም ሩቅ ስፍራ ደረስ መሄዳቸውን በማጋነን የዋለ አገላለጽነው። ይህ በአዎንታ ሊገለጽ ይችላል። "ጌታዬ ሰዎችን ወደ እርብ እና ሩቅ አገራት እና ግዛቶች ልኳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት እንደዚሁም ጥንድ አሉታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)
አሁን ግን
ይህ ሀረግ የዋለው ኤልያስ፣ አብድዩ ያደርገው ዘንድ የነገረው ነገር አደገኛ መሆኑን ለማጉላት ነው።
1 Kings 18:12
ዳቦ እና ውሃ.....አንተ አልሰማህምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ያደረግሁትን አንተ በእርግጥ ሰምተሃል...ዳቦ እና ውሃ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ጌታዬ
እዚህ ስፍራ "ጌታ" የሚለው ቃል ኤልያስን የሚያመለክት የአክብሮት አገላለጽ ነው።
አንድ መቶ የያህዌን ነቢያት በየሀምሳው
"100 የያህዌ ነቢያትን በየቡድን 50" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 18:14
ሄደህ ኤልያስ እዚህ እንደሚገኝ
እነዚህ ቃላት በ1 ነገሥት 18፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመለከቱ።
ጌታዬ
እዚህ ስፍራ "ጌታ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብን ነው።
በህያው ያህዌ ህይወት እምላለሁ
እርሱ የሚናገረው እውነት መሆኑን የሚያጎላ መሃላ ነው።
በፊቱ የቆምኩት እርሱ
"በፊቱ መቆም" አንድ ሰው ባለበት ስፍራ ለመቆም እና እርሱን ለማገልገል ዝግጁ መሆንን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "እኔ የማገለግለው እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 18:16
ኤልያስ ያለውን ለእርሱ ነገረው
"አብድዩ ለአክዓብ ኤልያስ እንዲነግረው የነገረውን መልዕክት አደረሰ/ተናገረ"
አንተ ነህን? በእስራኤል ላይ ችግር የምታደርሰወቅ አንተ ነህ!
አክዓብ ይህን ጥያቄ ያነሳው ስለ ኤልያስ ማንነት ትኩረት ሰጥቶ እርግጠኛ ለመሆን ነው። "ስለዚህም አንተ በዚህ አለህ። አንተ በእስራኤል ላይ ችግር የምታደርስ ነህ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 18:18
መላው እስራኤል
ይህ የሰሜኑን አስር የእስራኤል ግዛቶች መሪዎች እና ህዝብ የሚገልጽ ማጠቃላያ ነው። (ኩሸት እና አጠቃላ አስተያየት እንደዚሁም ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
450 ነቢያት
"አራት መቶ ሃምሳ ነቢያት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
አራት መቶ ነቢያት
400 ነቢያት (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 18:20
ወደ...ቃል ላክ ደግሞም ሰብስባቸው
"ቃል" የሚለው የሚወክለው የአክዓብን መልዕክት ሲሆን መልዕክቱን ለሚያደርሰው መልዕክተኛም ሜቶኖሚ/ ነው። ይህ ለታወቀ መልዕክት የዋለ የተለመደ ሃሳብ ነው። "ወደ... መልዕክት ላክ ከዚም ሰብስባቸው" ወይም "ሰብሰባ ለመሰብሰብ... መልዕክተኛ ላክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እንደዚሁም ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
እስከ መቼ በሃሳባችሁ እያወላወላችሁ ትቆያላችሁ?
ኤልያስ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ህዝቡ እንዲቆርጥ ለመገፋፋት ነው።፤ ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ለረጅም ጊዜ መወሰን አልቻላችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመለከቱ)
ለእርሱ አንድም ቃል አልመለሱም
"ምንም አልተናገሩም" ወይም "ዝም አሉ"
1 Kings 18:22
እኔ ብቻ፣ ብቻዬን ቀረሁ
"እኔ" የሚለው ቃል የተደጋገመው ትኩረት ለመስጠት ነው።
450 ወንዶች
"አራት መቶ ሀምሳ ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የአምላካችሁን ስም ጥሩ...የያህዌን ስም እጠራለሁ
"ስም" ለአንድ ሰው እውቅና እና ክብር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ሲሆን፣ እርሱን "መጥራት" ወደ እርሱ ማመልከትን ይገልጻል። "ወደ አምላካችሁ ተጣሩ... ወደ ያህዌ እጣራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉም ህዝብ እንዲህ ሲል መለሰ፣ "ይህ መልካም ነው።"
"ህዝቡ ሁሉ እንዲህ አሉ፣ 'ይህ መደረግ ያለበት መልካም ነገር ነው።'"
1 Kings 18:25
ይህ አዘጋጁ
"መስዋዕት ለማቅረብ ዝግጁ አድርጉ"
እናንተ ብዙ ሰዎች ናችሁ
እዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። (አንተ/አንቺ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)
ወይፈኑን ወሰዱ
"የበዓል ነቢያት ወይፈኑን ወሰዱ"
ለእነርሱ የተሰጣቸውን ወይፈን
ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ለእነርሱ የተሰጣቸውን ወይፈን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን ድምጽ አልነበረም፣ አሊያም መልስ የሚሰጥ ማንም አልነበረም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ የሃሰተኛ ነቢያቱን ጸሎት የሚመልስ ማንም አልነበረም። "ድምጽ" የሚለው ቃል የሚናገርን ክፍል ይወክላል። "ነገር ግን በዓል እንዳች አልመለሰም ወይም እንዳች አላደረገም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
1 Kings 18:27
ምናልባት በሀሳብ ላይ ይሆናል
"ምናልባት እያሰበ ይሆናል" ወይም "በሃሳብ ላይ ሆኖ ሊሆን ይችላል"
ራሱን ከህመም እያስታገሰ
ይህ ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ከባድ የሆነውን ሀሳብ ሻል ባለ መንገድ መግለጫ ነው። ኤልያስ በበዓል ላይ ያለውን ንቀት በፌዝ ይገልጻል። "በመታጠቢያ ቤት ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)
ሊቀሰቀስ ያስፈልገዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ልትቀሰቅሱት ያስፈልጋችኋል" ወይም "ከተኛበት ልታነቁት ይገባችኋል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ አሁንም ይረበሹ ነበር
"እንስሳዊ ባህሪያቸውን ማሳየታቸውን ቀጥለዋል።" ነቢያቱ ብዙውን ጊዜ ያልተለመደ መንገድ ወይም ጤናማ ያልሆነ ድርጊት ይፈጽሙ ነበር። በዚህ ሁኔታ ሲጨፍሩ በዓልን ጮኸው ይጣሩ፣ እና ራሳቸውን በስለት ይቆርጡ ነበር።
የምሽት መስዋዕት ሲያቀርቡ
"የምሽት መስዋዕት ማቅረብ"
ነገር ግን ድምጽ አልነበረም ወይም ማንም የሚመልስ አልነበረም፤ ለልመናቸው እንዳች ትኩረት የሚሰጥ አልነበረም
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ለሀሰተኛ ነቢያት ጸሎት ምላሽ የሚሰጥ አለመኖሩን ትኩረት ይሰጣሉ። "ነገር ግን በዓል እንዳች ነገር አልተናገረም ወይም አላደረገም ወይም ትኩረት እንኳን ሊሰጣቸው አልቻለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
ድምጽ አልነበረም ወይም መልስ የሚሰጥ ማንም አልነበረም
ይህ በ1 ነገሥት 18፡26 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
1 Kings 18:30


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አስራ ሁለት ድንጋዮች
"12 ድንጋዮች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በያህዌ ስም
እዚህ ስፍራ "ስም"ለክብር እና እውቅና ሜቶኖሚ/ ነው፡፡ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ያህዌን ለማክበር" ወይም 2) "በያህዌ ስልጣን፡፡" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ቦይ
ትንሽ የተቆፈረ የውሃ መሄጃ
ሁለት ሴየ/ቁና እህል፡፡ አንድ ሴየ/ቁና የአፍ አንድ ሶስተኛ ነው
ሴየ ወደ 7.7 ሊትር መጠን አለው፡፡ "ወደ 15 ኪሎ እህል የሚይዝ" (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ወቅት የመጠን መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 18:33
እንጨቱን ለማንደድ ረበረበ
በዚህ ዐረፍተ ነገር "በመሰዊያው ላይ" የሚለው እንጨቱን ያስቀመጠበትን ስፍራ ያሳያል፡፡ "እንጨቱን ለማንደድ በመሰዊያው ላይ ረበረበው/አደረገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው (ኤሊፕሲስ/የተተወ ወይም የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
አራት ገንቦ
"4 ገንቦ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ቦይ
ይህ በ 1 ነገሥት 18:30 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመለከቱ፡፡
1 Kings 18:36
እንዲህ ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አስፈላጊ እና ጥቅም የሚሰጥ ጊዜን ለማመልከት ነው፡፡ የእናንተ ቋንቋ ይህን የሚገልጽበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡
የአብርሃም፣ የይስሀቅ እና የእስራኤል አምላክ ያህዌ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው የሚያመለክተው ያዕቆብን ነው፡፡ እግዚአብሔር የያዕቆብን ስም (በዘፍጥረት 32፡28) ወደ እስራኤል ቀይሮ የያዕቆብን ትውልዶች "እስራኤል" ሲል ጠርቷል፡፡
ይህ ዛሬ ይታወቅ
ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፡፡ "ይህ ህዝብ ዛሬ እንዲታወቅ አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
አነሆ ስማኝ... አነሆ ስማኝ
ይህ ሀረግ የተደገመው ኤልያስ ወደ ያህዌ የሚያሰማውን ልመና ለማጉላት ነው፡፡
ልባቸውን ዳግም ወደ ራስህ መልስ
የሰዎች "ልብ" ለህዝቡ ታማኝነት እና ወዳጅነት ሜቶኖሚ/ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው፡፡ "ዳግም ለአንተ ታማኝ እንዲሆኑ አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 18:38
የያህዌ እሳት ወደቀ
"የያህዌ እሳት ከላይ ወረደ"
ላሰችው
እሳቱ የተነጻጸረው የተጠማ ሰው ውሃ ከመጠጣቱ ጋር ነው፡፡ (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ እርሱ አምላክ ነው! ያህዌ እርሱ አምላክ ነው!
ሀረጉ የተደጋገመው ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡
1 Kings 18:41
የብዙ ዝናብ ድምጽ ነበር
"የሀይለኛ ዝናብ እንደሚመጣ ድምጽ ተሰማ"
ወደ ምድር አጎንብሶ ፊቱን በጉልበቶቹ መሃል አደረገ
ይህ ለጸሎት የሆነ አቀማመጥን ይገልጻል፡፡
1 Kings 18:43
ሰባት ጊዜ
"ሰባት" የሚለው ቃል በቁጥር "7" ሊጻፍ ይችላል፡፡ "7 ጊዜያት" እንደሚለው፡፡ (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የሰውን እጅ የሚያክል ያህል ትንሽ
ከርቀት፣ የሰው እጅ የሚያህል ደመና ላይታይ ይችላል፡፡
1 Kings 18:45
እንዲህ ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አዲስ ደረጃ የሚያሳይ ድርጊት መጀመሩን ለማመልከት ነው፡፡ የእናንተ ቋንቋ ይህን የሚገልጽበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡
የያህዌ እጅ በኤልያስ ላይ ነበር
እዚህ ስፍራ "እጅ" ለጥንካሬ ሜቶኖሚ/ ነው፡፡ "ያህዌ ለኤልያስ ሀይሉን ሰጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ልብሱን በቀበቶው አጥብቆ ካሰረ በኋላ
ኤልያስ ረጅሙን ልብሱን በወገቡ ዙሪያ ጠበቅ አድርጎ በማሰር እንደ ልቡ እንዲሮጥ እግሮቹን ነጻ አደረገ፡፡

---

Chapter 19
1 Kings 19:1
አማልዕክት እንዲህ ያድርጉብኝ፣ እንዲህም ይጨምሩብኝ
ይህ እንደ ጥብቅ መሃላ የሚያገለግል ንጽጽር ነው፡፡ "አማልዕክት እኔን ይግደሉኝ ከዚያም የከፋ ክፉ ነገሮችን ያድርሱብኝ"
የእንተን ህይወት ከሞቱት ነቢያት እንደ አንዱ ህይወት ካላደረግሁ
"አንተ እነዚያን ነቢያት እንደ ገደልክ እኔም አንተን ካልገደልኩ"
እርሱ ተነሳ
"እርሱ ተነስቶ ቆመ"
1 Kings 19:4
እርሱ ራሱ የአንድ ቀን ጉዞ ተጓዘ
"ራሱ" የሚለው ቃል የዋለው እርሱ ብቻውን እንደሆነ ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡ "ለብቻው ብዙ ቀናት ተጓዘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ደጋጋሚ ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የመጥረጊያ ዛፍ
"የመጥረጊያ ዛፍ" በበረሃ የሚበቅል ተክል ነው፡፡ (የማይታወቀውን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)
መሞት ተመኘ/ ይሞት ዘንድ ራሱ ጥያቄ አቀረበ
"ይሞት ዘንድ ጸለየ"
ያህዌ ሆይ፣ አሁንስ ይህ ይበቃኛል
"ያህዌ ሆይ፣ እነዚህ ችግሮች እጅግ በዙብኝ"
በከሰል/ፍም ላይ የተጋገረ ዳቦ
ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፡፡ "በጋለ ድንጋይ/ፍም ላይ አንድ ሰው የጋገረው ዳቦ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የገንቦ ውሃ
"በመያዣ/ማጠራቀሚያ ውስጥ የሚገኝ ውሃ"
1 Kings 19:7
ለአንተ እጅግ ብዙ ይሆናል
"ለአንተ እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡"
በዚያ ምግብ ሃይል አርባ ቀን እና አርባ ምሽት ተጓዘ
"ያ ምግብ 40 ቀን እና 40 ምሽት ለመጓዝ ሀይል ሰጠው" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 19:9
በዚያ በሚገኝ ዋሻ
እዚህ ስፍራ "እዚያ" የሚለው ቃል የኬብሮንን ተራራ ያመለክታል፡፡ ዋሻ በተራራ አጠገብ የሚገኝ ወደ ተፈጥሮ ክፍሎች ወይም ከመሬት በታች ወደሚገኝ ክፍል የሚመራ ክፍት ስፍራ ነው፡፡
የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እርሱ መጣ፣ "ምን
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው፡፡ ይህ በ1 ነገሥት 6፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ያህዌ ለእርሱ መልዕክት ሰጠው" እንዲህም አለው፣ 'ምን" ወይም "ያህዌ ለእርሱ ይህ መልዕክት ሰጠው፡ 'ምን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ኤልያስ ሆይ፣ እዚህ ምን ታደርጋለህ?

ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ኤልያስን ለመገሰጽ እና ግዴታውን ሊያስታውሰው ነው። "ኤልያስ ሆይ፣ መገኘት ያለብህ እዚህ ስፍራ አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ብቻ፣ ብቻዬን ቀረሁ

"እኔ" የሚለው ቃል የተደጋገመው ትኩረት ለመስጠት ነው።

1 Kings 19:11

ከእኔ በፊት በተራራው ላይ

እዚህ ስፍራ "ከእኔ በፊት" የሚለው ከአንድ ሰው ፊት ለመቆም ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "እኔ ባለሁበት በተራራው ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 19:13

በመጎናጸፊያው ፊቱን ጠረገ

"ፊቱን በመጎናጸፊያው ሸፈነ።" መጎናጸፊያ ትልቅ ካባ፣ መላ ሰውነትን የሚሸፍን ጨርቅ ነው።

ከዚያም ወደ እርሱ ድምጽ መጣ

"ከዚያም ድምጽ ሰማ"

እዚህ ምን እየሰራህ ነው... ደግሞም እነርሱ ህይወቴን ከእኔ ለመውሰድ እየሞከሩ ነው

ይህ ክፍል በ1 ነገሥት 19፡9-10 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እኔ ብቻ፣ ብቻዬን ቀረሁ

"እኔ" የሚለው ቃል የተደጋገመው ትኩረት ለመስጠት ነው።

1 Kings 19:15

ነቢያት በአንተ ስፍራ

"በአንተ ምትክ ነቢያት

1 Kings 19:17

እንዲህ ይሆናል

ይህ ሀረግ የዋለው ኤልያስ ያህዌ ያደርግ ዘንድ ያዘዘውን ሲያደርግ የሚሆነውን ነገር ለማስተዋወቅ ነው። "የሚሆነው

ከአዛሄል ሰይፍ ያመለጠውን ሁሉ

"ሰይፍ" በጦርነት ለሚገደሉ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "አዛኤል በሰይፍ ያልገደላቸውን ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለራሴ አስቀራለሁ

እዚህ ስፍራ "እኔ" እና "እኔ ራሴ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ያህዌን ነው። "ከሞት አድናለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባት ሺህ ሰዎች

"7,000 ሰዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ለበዓል ጉልበቶቻቸው ያልተንበረከኩ፣ እና አፋቸው እርሱን ያልሳመ

"ወደ ታች ማጎንበስ/መንበርከክ" እና "መሳም" ሰዎች ጣኦቶችን ለማምለክ ለሚያደርጓቸው ድርጊቶች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። ድርጊቶቹ የተጣመሩት ትኩረት ለመስጠት ነው። "ለበዓል ያልሰገዱ እና በዓልን ያልሳሙ" ወይም "በዓልን ያላመለኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

1 Kings 19:19

ሳፋጥ

ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ ሁለት ጥማድ በሬዎች

"12 ጥማድ በሬዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ራሱ በአስራ ሁለቱ ጥማዶች ያርስ ነበር

"እርሱ ራሱ" የሚለው ቃል ኤልሳ በመጨረሻው ጥማድ ያርስ እንደነበር ያመለክታል፤ የተቀሩት ሰዎች በሌሎች አስራ አንዱ ጥማዶች ያርሱ ነበር። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስም እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ፣ እባክህ አለው

"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኤልሳን ነው።

1 Kings 19:21

እርሱ ይህን ለሰዎች ሰጠ

ኤልሳ የበሰለውን ስጋ ለከተማው ሰዎች ሰጣቸው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 20

1 Kings 20:1

ቤን ሀዳድ

ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላሳ ሁለት አነስተኛ ንጉሦች

"32 አነስተኛ ንጉሦች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አነስተኛ ንጉሦች

"አነስተኛ የህዝብ ቁጥር የሚገዙ ንጉሦች"

1 Kings 20:4

አንተ እንዳልከው ይሁን

ይህ ስምምነትን የሚገልጽ ፈሊጥ ነው። "ከአንተ ጋር እስማማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ነገ በዚህን ጊዜ

"ነገ ልክ በዛሬው ሰዓት"

እነርሱን በዐይናቸው ፊት ደስ እንዳሰኛቸው

እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው የሚወክለው ትኩረት ሰትተው አንዳች ነገር የሚመለከቱ እና ያንን የሚገልጹ ሰዎችን ያመለክታል። "እነርሱን ደስ የሚያሰኘውን ነገር በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:7

የአገሪቱን

"የአገሪቱ" የሚለው የሚወክለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ነው። "የእስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ልብ ብላችሁ ተመለከቱ

"ልብ በሉ" የሚለው በጥንቃቄ ምልከታ ለማድረግ ፈሊጥ ነው። "የቅርብ ትኩረት ስጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ቀድሞ ያለውን አልተቃወምኩትም

ይህ በአዎንታ ሊተረጎም ይችላል። "ለጠየቀው ስምምነቴን ገልጫለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ አሉታ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:9

አማልዕክት ይህን ያደርጉብኝ ይህንንም ይጨምሩብኝ

ይህ በትልቅ ትኩረት የተሰጠ መሃላ ነው። ይህ በ 1 ነገሥት 19፡2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የሰማርያ አመድ እኔን ለሚከተል ለእያንዳንዱ ሰው አንድ እፍኝ የሚደርስ ቢሆን እንኳን

ቤን ሀዳድ የእርሱ ሰራዊት በሰማርያ የሚገኘውን ነገር ሁሉ እንደሚያጠፋ እያስፈራራ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 20:11

ለቤን ሀዳድ እንዲህ በሉት፣ 'የጦር ልብሱን የለበሰ ማንም ሰው... እርሱ ያንን እንዳወለቀው

ይህ ምክር ለመስጠት የሚውል ገለጻ ነው። "የጦርነት ልብስ መታጠቅ" ለጦርነት ዝግጁ ለመሆን ሜቶኖሚ/ ነው። "ቤን ሀዳድን እንዲህ በሉት፣ 'ገና ያልተዋጋኸውን ጦርነት በድል እንደተወጣ ሰው አትኩራራ።'" (ምሳሌያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

1 Kings 20:13

ከዚያ እነሆ

"እነሆ" የሚለው በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሰው በድንገት ብቅ እንደሚል ያነቃናል። የእናንተ ቋንቋ ይህን የሚገልጽበት መንገድ ሊኖረው ይችላል።

ይህን ታላቅ ሰራዊት አያችሁን?

ያህዌ ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው የቤን ሀዳድን ሰራዊት መጠን እና ጥንካሬ አጉልቶ ለመግለጽ ነው። "ይህንን ታላቅ ሰራዊት ተመልከቱ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ፣ ዛሬ በእጃችሁ ላይ እጥለዋለሁ/አደርገዋለሁ

"እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው አስደናቂ መረጃ ትኩረት እንደንሰጥ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ያነቃናል።
በእጃችሁ ላይ አደርገዋለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "በዚያ ሰራዊት ላይ ድል እሰጣችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በማን?
አክዓብ 'ይህን ታደርጋለህን' የሚለውን ቃል ትቶታል። "ይህን በማን ታደርጋለህ?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢሊፕሲስ/የተተወ ወይም የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
አክዓብ ወጣት መኮንኖችን ጠራ
"አክዓብ ወጣት መኮንኖችን ሰበሰበ"
ሁሉም ወታደሮች፣ መላው የእስራኤል ሰራዊት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ተጣምረው የቀረቡት ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰባት ሺህ
"7,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 20:16
እነርሱ ወጥተው ሄዱ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤል ወታደሮችን ነው።
ሰላሳ ሁለት አነስተኛ ንጉሦች
ይህ በ1 ነገሥት 20:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ቤን ሀዳድ በወጣት ቃፊሮች መውጣት እንዲዳለበት ተነግሮት ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ቤን ሀዳድ የላካቸው ቃፊሮች መረጃ ሰጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ወጣት ቃፊሮች/ስካውቶች
"ስካውት/ቃፊር" ስለ ጠላት ሰራዊት መረጃ የሚሰበስብ ወታደር ነው።
1 Kings 20:18
ቤን ሀዳድ እንዲህ አለ
ቤን ሀዳድ ለወታደሮቹ እንሚናገር ግልጽ ነው። "ቤን ሀዳድ ለወታደሮቹ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢሊፕሲስ/የተተወ ወይም የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ... ወደ ወሰዷቸው ስፍራ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" እና "የእነርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የስስራኤልን ሰራዊት ነው
ስለዚህ ሰራዊቱ....ወጣቶቹን መኮንኖች ተከተለ
"የእስራኤል ሰራዊት...ወጣቶቹን እስራኤላውያን መኮንኖች ተከተለ"
1 Kings 20:20
እስራኤል እነርሱን ተከተለ
"እስራኤል" ለመላው የእስራኤል አገር ወታደሮች ሴኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "የእስራኤል ሰራዊት ወንዶች ሁሉ እነርሱን ተከተለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ንጉሥ ወጥቶ ጥቃት አደረሰ
"ንጉሡ" እርሱን ለሚያገለግሉ ወታደሮች እና ለንጉሡ ሴኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "የእስራኤል ንጉሥ እና የእርሱ ወታደሮች ወጥተው ጥቃት አደረሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 20:22
ራስህን አጠናክር
"ራስህን" የሚለው የሚወክለው በሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የንጉሡን ሰራዊት ነው። "ሀይልህን አጠናክር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
መረዳት እና ማቀድ
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የተጣመሩት ትኩረት ለመስጠት ነው። "መወሰን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
በሚመጣው አመት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በቀጣዩ አመነት ፀደይ ወቅት" ወይም 2) "በሚመጣው አመት በዚህን ጊዜ።"
እኛ በአንድነት እንዋጋ... እኛ ብርቱዎች ነን
"እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አገልጋዮችን፣ ንጉሡን፣ እና ጠቅላላውን ሰራዊቱን በአንድ ላይ ነው። (ሁሉንም አካታች የሆነ "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 20:24
ሁሉንም ንጉሦች ከስልጣናቸው ስፍራ አስወግዳቸው
"ወታደሮችህን የሚመሩትን ሰላሳ ሁለቱን ንጉሦች በሙሉ ማስወገድ አለብህ"
1 Kings 20:26
አፌቅ
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
በእስራኤል ላይ መነሳት/እስራኤልን መወጋት
"እስራኤል" የሚለው የሚወክለው የእስራኤልን ሰራዊት ነው። "ከእስራኤል ሰራዊት ጋር መዋጋት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ሰዎች ተሰባስበው እና አቅርቦት አግኝተው ነበር
ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የእስራኤል ሰራዊትም ደግሞ በአንድነት ተሰበሰበ፣ አዛዦችም ለጦርነት የሚያስፈልጋቸውን ትጥቅ ሰጧቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ትንንሽ ሁለት የፍየል መንጎች
ይህ ተነጻጻሪ ዘይቤ የእስራኤልን ሰራዊት ከሁለት ትንንሽ የፍየሎች መንጋ ጋር ያነጻጽራል። "የእስራኤላውያን ሰራዊት እንደ ሁለት የፍየሎች መንጋ ትንሽ እና ደካማ መስሎ ታየ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 20:28
የእግዚአብሔር ሰው
ይህ የነቢይ ሌላው መጠሪያ ነው። "ነቢይ" እንደሚለው
ይህን ታላቅ ሰራዊት በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ሀይልን ነው። "በዚህ ታላቅ ሰራዊት ላይ ለአንተ ድል እሰጥሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 20:29
ሰባት ቀናት
"7 ቀናት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
100,000
"አንድ መቶ ሺህ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
እግረኞች
"እግረኛ" በእግሩ የሚጓዝ ወታደር ነው።
አፌቅ
ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሃያ ሰባት ሺህ
"27,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 20:31
እነሆ ተመልከት/አድምጥ
ይህ እነርሱ የሚናገሩነትን ያጎላል። "አድምጠን" ወይም "የምንነግርህን ትኩረት ሰጥተህ ስማ"
በወገባችን ዙሪያ ማቅ እናደርጋለን፣ በራሳችን ላይ ገመድ እንጠመጥማለን
ይህ መማረክ ምልክት ነው
እስከ አሁን በህይወት አለን?
አክአብ ይህን ጥያቄ ያነሳው መደነቁን ለመግለጽ ነው። "እርሱ እስከ አሁን በህይወት በመኖሩ ተደንቄያለሁ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ወንድሜ ነው
እዚህ ስፍራ "ወንድሜ/የእኔ ወንድም" መልካም ወዳጅ ለሆነ ሰው ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "እርሱ ለእኔ ልክ እንደ ወንድም ነው" ወይም "እርሱ ልክ እንደ ቤተሰብ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 20:33

አሁን ሰዎቹ
"አሁን" የሚለው ቃል "በዚህ ጊዜ" ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ቀጥሎ ለሚሆነው ጠቃሚ ነጥብ ትኩረትን ለመሳብ የዋለ ነው።
ከአክዓብ ዘንድ ለሆነ ማናቸውም ምልክት
"ምልክት" ትርጉም ለሚሰጥ ድርጊት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ/ ነው። "ከአክዓብ ዘንድ ለሆነ፣ አክዓብ ምህረት ለመስጠት መፈለጉን ለሚያሳይ ማናቸውም ድርጊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 20:35
ከነቢያት ወንዶች ልጆች አንዱ
"ከነቢያት ወገን መሃል አንዱ"
የያህዌ ቃል
"ከያህዌ ዘንድ የሆነ መልዕክት" ወይም "የያህዌ መልዕክት"
1 Kings 20:39
አገልጋይህ ወጥቶ ይሄዳል
ነቢዩ ራሱን በሶስተኛ መደብ መግለጹ ለንጉሡ ላለው ክብር ምልክት ነው።
ወደ ጦርነቱ ግለት
እዚህ ስፍራ "የጦርነቱ ግለት" እጅግ ከባድ እና ከባድ የሆነውን ውጊያ የሚገልጽ ፈሊጥ ነው። "ጦርነቱ በጣም በበረታበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ህይወት በእርሱ ህይወት ምትክ ይሰጣል
"አንተ በእረሱ ስፍራ ትሞታለህ"
አንድ ታላንት/መክሊት ብር
ታላንት/መክሊት ወደ 33 ኪሎግራም የሚጠጋ የክብደት መለኪያ ነው። "33 ኪሎግራም ብር" (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ወቅት የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)
እዚህና እዚያ ማለት
በጣም መሯሯጥን እና በስራ መያዝን የሚወክል ፈሊጥ ነው። "ሌሎች ነገሮችን ማድረግ" ወይም "ይህንን እና ያንን ማድረግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 20:41
ከእጅህ ለቀኸዋል
እዚህ ስፍራ "እጅ" ለሀይል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "መልቀቅ" ወይም "ህይወትን ማዳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ህይወት በእርሱ ህይወት ስፍራ ይሆናል፣ ደግሞም
የአንተ ህዝብ በእርሱ ህዝብ ቦታ ይሆናል "አንተ በእርሱ ምትክ ትሞታለህ፣ ደግሞም ህዝብህ በእርሱ ህዝብ ምትክ ይሞታል"

---

Chapter 21
1 Kings 21:1
ከጥቂት ጊዜ በኋላ
ይህ ሀረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ያመለክታል፣ ደግሞም እነዚህ ትዕይንቶች ቆይቶ እንደሚፈጸሙ ያመለክታል፤ ናቡቴ የወይን እርሻውን ቆይቶ እንደሚወስድ አስተውሉ። የእናንተ ቋንቋ የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ የሚያመለክትበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ። "ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሆነው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
ኢይዝራኤላዊው ናቡቴ
ይህ ከኢዝራኤል የሆነው ሰው ስም ነው። (ስሞቸ እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰማርያ ንጉሥ
"ሰማርያ" የእስራኤል መንግሥት ዋና ከተማ የነበረች ስትሆን እዚህ ስፍራ መላውን አገር ትወክላለች። "የእስራኤል ንጉሥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 21:3
እኔ አሳልፌ መስጠቴን ያህዌ ይከልክል
ይህ ሀረግ ቀጣዩ ነገር እንደማይሆን ትኩረት የሚሰጥ መሃላ ነው። "ያህዌ ይህንን ባለመፍቀዱ ምክንያት፣ እኔ በፍጹም ይህን አልሰጥህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የአባቶቼን ውርስ ርስት ለአንተ እሰጥ ዘንድ
አባቶቹ ቋሚ ሀብት አድርገው የወረሱት ምድር የተገለጸው ውርሰ ርስት ተደርጎ ነው። "አባቶቼ ርስት አድርገው የተቀበሉትን መሬት ለአንተ መስጠት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 21:5
ለምን ልብህ እጅግ አዘነ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚያመለክተው የሰውን ጠቅላላ ማንነት እና ስሜት ነው። "ለምን እንዲህ እጅግ አዘንክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
እስከ አሁንስ ድረስ እስራኤልን አየገዛህ አይደለምን?
ኤልዛቤል ይህንን አሉታዊ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመችው አክዓብን ለመገሰጽ ነው። ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ እስካሁን እስራኤልን እየገዛህ ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ልብህ ደስተኛ ይሁን
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚያመለክተው የሰውን ጠቅላላ ማንነት እና ስሜት ነው። "ደስተኛ ሁን" ወይም "ተበረታታ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 21:8
በአክዓብ ስም ደብዳቤ ጻፈች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በደብዳቤው ላይ የአክዓብን ስም ጻፈች። "ደብዳቤ ጽፋ በአክዓብ ስም ፈረመችበት" ወይም 2) "ስም" የሚለው ቃል ለስልጣን ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በአክአብ ስም ደብዳቤ ጻፈች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከእነርሱ ጋር የተቀመጡ/የሚኖሩ ባለጸጎች
"ባለጸጋ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ባለጸጋ ሰዎችን ነው። "ከናቡቴ ጋር የሚኖሩ ባለጸጋ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ናቡቴን ከህዝቡ በላይ አስቀምጡ
ናቡቴን በክብር ስፍራ ማስቀመጥ የሚለው የተገለጸው፤ በዚያ ከነበሩ ሰዎች በላይ ከፍ ብሎ እንደ ተቀመጠ ተደርጎ ነው። "ናቡቴን በህዝቡ መሃል ከፍ ባለ ስፍራ አስቀምጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ላይ ይመስክሩበት
"እርሱን ወንጅሉት/በሀሰት ክሰሱት"
1 Kings 21:11
በናቡቴ ከተማ የሚኖር ባለጸጋ
"ባለጸጋ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሃብታም ሰዎችን ነው። "በናቡቴ ከተማ የሚኖሩ ባለጸጋ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
በደብዳቤዎቹ ውስጥ ተጽፎ እንደነበረው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በደብዳቤዎቹ ውስጥ እንደጻፈችው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ናቡቴን ከህዝቡ በላይ አስቀመጡት
ናቡቴን በክብር ስፍራ ማስቀመጥ የሚለው የተገለጸው፤ በዚያ ከነበሩ ሰዎች በላይ ከፍ ብሎ እንደ ተቀመጠ ተደርጎ ነው። ይህ ሀሳብ በ1 ነገሥት 21:9 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ናቡቴን በሰዎች መሃል በክብር ስፍራ አስቀምጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከናቡቴ ፊት ተቀመጡ
"ከናቡቴ ፊት ለፊት ተቀመጡ"

እነርሱ ተሸክመው አወጡት
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የከተማዋን ሰዎች ነው።
ናቡቴ በድንጋይ ተወግሮ ተገደለ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኛ ናቡቴን በድንጋይ ወገርነው፣ እርሱም ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 21:15
ናቡቴ በድንጋይ ተወግሮ ተገደለ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ናቡቴን በድንጋይ ወገሩት፣ እርሱም ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ናቡቴ በህይወት የለም፣ ሞቷል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የኤልዛቤልን ሀሳብ መፈጸም ያጎላሉ። "ናቡቴ ሞቷል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 21:17
የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም ያህዌ ተናገረ ወይም መልዕክት ላከ ማለት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 21:19
ገድላችሁት ደግሞም ርስቱን ወሰዳችሁን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው አክዓብን ለመገሰጽ ነው። "ናቡቴን ገደላችሁት ደግሞም የወይን እርሻውን ሰረቃችሁት!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተን ደም፣ የአንተን ደም
ይህ የተደገመው ትኩረት ለመስጠት ነው
ጠላቴ ሆይ፣ አገኘኸኝን?
አክዓብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው በኤልያስ ላይ ያለውን ቁጣ ለመግለጽ ነው። ይህም ኤልያስ አክዓብን "ማግኘቱ" ሊያመላክት የሚችለው ኤልያስ የአክዓብን ድርጊቶች ማወቁን እንጂ በአካል እርሱን ማግኘቱን አይደለም። "ጠላቴ ሆይ፣ አንተ እኔን አገኘኸኝ!" ወይም "ጠላቴ ሆይ፣ እኔ ያደረግኩትን ደረስክበት!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ክፉ የሆነውን ለማድረግ ራስህን አሳልፈህ ሸጥክ
ክፉ የሆነን ነገር ለማድረግ ራሱን አሳልፎ የሰጠ ሰው፣ ራሱን ለክፉ አሳልፎ እንደሸጠ ተደርጎ ይገለጻል። "ክፉ የሆነውን ነገር ለማድረግ ራስህን አሳልፈህ ሰጥተሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 21:21
እነሆ
"ተመልከት" ወይም "አድምጥ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ"
በእስራኤል ከአንተ ዘንድ ሙሉ ለሙሉ እያንዳንዱን ወንድ ልጅ እና ባሪያ እንዲሁም ነጻ ሰው ጨርሼ እቆርጣለሁ፣ አጠፋለሁ
ያህዌ የአክዓብን ቤተሰብ እንደሚያጠፋ እና ትውልድ እንዳይኖረው እንደሚያደርግ የገለጸው እሳት እንጨትን እንደሚበላ እንደዚሁም አንድ ሰው የዛፍን ቅርንጫፍ በሙሉ እንደሚቆርጥ አድርጎ ነው። "በእስራኤል የአንተን ወንድ ልጆች ሁሉ ባሪያም ሆነ ነጻ ሰው ሳላስቀር አጠፋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቤተሰብህን እንደ ኢዮርብዓም ቤተሰብ አደርጋለሁ…
እንደዚሁም እንደ ባኦስ ቤተሰብ አደርግሃለሁ ያህዌ የአክዓብን ቤተሰብ፣ የኢዮርብዓምን እና የባኦስን ቤተሰብ እንዳጠፋቸው ያጠፋል።
1 Kings 21:23
የአክዓብ የሆነ ሁሉ
"የአክዓብ ቤተሰብ የሆነ ሁሉ"
1 Kings 21:25
ክፉ የሆነውን ለማድረግ ራሱን የሸጠውን
ክፉ የሆነን ነገር ለማድረግ ራሱን አሳልፎ የሰጠ ሰው፣ ራሱን ለክፉ አሳልፎ እንደሸጠ ተደርጎ ይገለጻል። ይህ ሀሳብ በ1 ነገሥት 21:20 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ክፉ የሆነን ነገር ለማድረግ ራሱን አሳልፎ የሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በያህዌ ዕይታ ክፉ የሆነውን
"በ…እይታ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክው አስተያየት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 11፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከእስራኤል ህዝብ ፊት ያስወገዳቸው
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚያመለክተው መላውን የእስራኤል አስራ ሁለት ነገዶች እንጂ ሰሜናዊውን ግዛት ብቻ አይደለም። "ከእስራኤል ህዝብ መገኘት ያስወገዳቸው" ወይም "ከእስራኤል ህዝብ ምድር ፊት ያስወጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 21:27
የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም ያህዌ ተናገረ ወይም መልዕክት ላከ ማለት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 6፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አክዓብ እንዴት ራሱን በእኔ ፊት ትሁት እንዳደረገ አየህን?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ ያዋለው የአክዓብ መጸጸት እውነተኛ እንደሆነ ለኤልያስ ለማሳየት ነው። "አክዓብ ራሱን እንዴት በእኔ ፊት ትሁት እንዳደረገ ተመልክቻለሁ።" ወይም "አክዓብ እንዴት በእኔ ፊት ትሁት እንዳደረገ ተመልከት።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ዘመን…በልጁ ዘመን
"በእርሱ የህይወት ዘመን… በልጁ የህይወት ዘመን"

---

Chapter 22
1 Kings 22:1
ሶስት አመታት
"3 አመታት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አዲስ ደረጃ የሚያሳይ ድርጊት መጀመሩን ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን የሚገልጽበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።
1 Kings 22:3
ሬማት ገለዓድ የእኛ እንደሆነች ታውቃላችሁን፣ ነገር ግን እኛ ከአራም እጅ እርሷን ለመውሰድ ምንም እያደረግን አይደለም?
አክዓብ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው እስከ አሁን ሬማት ገለዓድን መልሰው መያዝ እንደመበረባቸው ትኩረት ለመስጠት ነው። "ሬማት ገለዓድ የእኛ ናት፣ ነገር ግን እኛ ከአራም ንጉሥ መልሰን ልንወስዳት ምንም ነገር አላደረግንም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአራም ንጉሥ መልሰን ልንወስዳት
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "ከአራም ንጉሥ ቁጥጥር ስር ነጻ ልናወጣት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ያው እንደ አንተው ነኝ፣ የእኔ ህዝብ እንዳንተ ህዝብ ነው፣ ደግሞም የእኔ ፈረሶች የአንተ ፈረሶች ናቸው
ኢዮሳፍጥ ለአክዓብ፣ የእርሱ ሰዎች እና የእርሱ ፈረሶች የአክዓብም መሆናቸውን ይነግረዋል፤ ይህም ማለት አክዓብ ደስ እንዳሰኘው ሊያዝባቸው ይቻላል ማለት ነው። "እኔ፣ የእኔ ወታደሮች፣ እንደዚሁም ፈረሶቼ አንተ በወደድከው መንገድ ልትተቀምባቸው የምትችላቸው የአንተም ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 22:5
አራት መቶ ወንዶች
"400 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ጌታ እርሷን ለንጉሡ እጆች አሳልፎ ይሰጥ እንደሆነ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "ጌታ ንጉሡ ሬማት ገለዓድን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንዲማርካት ይፈቅድ እንደሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:7

ንጉሡ ይህንን አይበል

ኢዮሳፍጥ አክዓብን በሶስተኛ መደብ የሚጠቅሰው ለእርሱ ክብርን ለማሳየት ነው። "ያንን ማለት የለብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:10

ለራሱ የብረት ቀንዶች አሰርቶ

"ለራሱ የብረት ቀንዶች አሰራ"

እስኪጠፉ ድረስ እነዚህን አረማውያን ታባርራቸዋለህ/ታስወጣቸዋለህ

የነቢያቱ ድርጊቶች አክዓብ አረማውያንን የሚያሸንፍበትን መንገድ የሚገልጽ ትምዕርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊቶች ናቸው። የአክዓብ ሰራዊት በሬ ሌላውን እንስሳ እንደሚያጠቃው በታላቅ ጥንካሬ አሸናፊ ይሆናል። (ትምዕርታው/ምልክታዊ ድርጊት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እስኪጠፉ/እስኪፈጁ ድረስ

የጠላትን ሰራዊት መደምሰስ የተገለጸው እነርሱን እንደመፍጀት ተደርጎ ነው። ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፤ "አንተ እስክትፈጃቸው ድረስ" ወይም "አንተ እስክትደመስሳቸው ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሷን ለንጉሡ እጅ አሳላፎ ይሰጣታል

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "ንጉሡ እንዲማርካት/ እንዲይዛት ፈቅዷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:13

እነሆ ተመልከት

"አድምጥ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ"

የነቢያቱ ቃል በአንድ አፍ ለንጉሡ መልካም ነገርን አወጀ

ነቢያቱ በሙሉ አንድ አይነት ነገር መናገራቸው የተገለጸው በአንድ ሰው አፍ እንደተናገሩ ተደርጎ ነው። "ሁሉም ነቢያት ተመሳሳይ የሆነ መልካም ነገሮችን ለንጉሡ አወጁ/ተናገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተም ቃል ከእነርሱ እንደ አንዱ ይሁን

እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው "የነቢያቱን ቃል ነው።" "አንተም የምትናገረው እነርሱ ከተናገሩት ጋር የተስማማ ይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መሄድ/መውጣት ይኖርብናል

"እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አክዓብን፣ ኢዮሳፍጥን፣ እና የእነርሱን ሰራዊት ሲሆን ሚክያስን አይጨምርም። (አካታች እና የማያካትት "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)

ለንጉሡ እጅ አሳልፎ ይሰጣታል

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "ንጉሡ እንዲማርካት/ እንዲይዛት ፈቅዷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:16

በያህዌ ስም…ስንት ጊዜ መጠየቅ ይኖርብኛል?

አክዓብ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ከጭንቀት የተነሳ ሚክያስን ለመገሰጽ ነው። "በያህዌ ስም… ብዙ ጊዜ ጠየቅሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በያህዌ ስም

እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ስልጣንን ነው። "እንደ ያህዌ ተወካይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን በሙሉ ተመለከትኩ

እዚህ ስፍራ "መላው እስራኤል" የሚለው የእስራኤልን ሰራዊት ያመለክታል። "መላውን የእስራኤል ሰራዊት እመለከታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እረኛ እንደሌላቸው በጎች

የህዝቡ ሰራዊት የተነጻጸሩት የሚመራቸው ማንም ከሌላቸው በጎች ጋር ነው፣ ምክንያቱም እረኛቸው፣ ንጉሡ ሞቷል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ እረኛ የላቸውም

ያህዌ ንጉሡን የሚገልጸው እረኛ እንደሆነ አድርጎ ነው። እረኛ በጎቹን ለመጠበቅ እና ለመንከባከብ ሃላፊነት እንዳለበት ሁሉ፣ ንጉሡም ህዝቡን የመምራት እና የመጠበቅ ሀላፊነት አለበት።"እነዚህ ሰዎች ከእንግዲህ መሪ አይኖራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:18

አልነገርኩህምን … እርሱ ጥፋት ብቻ?

አክዓብ ይህንን ጥያቄ ያነሳው ስለ ሚክያስ የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። "ጥፋትን ብቻ እንደሚናገር…አልነገርኩህም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በሬማት ገለዓድ ይወድቃል

የአክዓብ በጦርነት ውስጥ መሞት የተገለጸው እንደሚወድቅ ተደርጎ ነው። "በሬማት ገለዓድ ይሞታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)

ከእነርሱ አንዱ እንዲህ አለ…ደግሞም ሌላው እንዲህ አለ

"አንዱ…ደግሞም ሌላው" የሚለው የሚያመለክተው በቀደመው ቁጥር ለቀረበው ለያህዌ ጥያቄ ከሰማያት ጭፍሮች ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ መላዕክት የሚሰጡትን ምላሽ ነው።

1 Kings 22:21

በእርሱ ነቢያት ሁሉ አፍ የሀሰት መንፈስን በማስቀመጥ

እዚህ ስፍራ "መንፈስ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የነቢያትን ዝንባሌ ሲሆን "አፋቸው" የሚለው የሚወክለው እነርሱ የሚናገሩትን ነው። "የእርሱ ነቢያት ሁሉ ሀሰት እንዲናገሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ

"አድምጥ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ"

አንተ ታያለህ

"ለጥያቄህ መልሱን ታውቃለህ።" የሴዴቅያስ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ቢተረጎም፣ ይህ ሀረግ በስውር ያለውን መረጃ ለማቅረብ ይተረጎማል። "የያህዌ መንፈስ ለእኔ እንደተናገረ ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:24

የያህዌ መንፈስ አንተን የተናገረው፣ እኔን በየት መንገድ አልፎ ነው?

ሰዴቅያስ ይህንን ምጸታዊ ጥያቄ የጠየቀው ሚክያስን ለመስደብ እና ለመገሰጽ ነው። "የያህዌ መንፈስ እኔን አልፎ አንተን የሚናገርህ አይምሰልህ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ

"አድምጥ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ"

አንተ ታያለህ

"ለጥያቄህ መልሱን ታውቃለህ።" የሴዴቅያስ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ቢተረጎም፣ ይህ ሀረግ በስውር ያለውን መረጃ ለማቅረብ ይተረጎማል። "የያህዌ መንፈስ ለእኔ እንደተናገረ ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

1 Kings 22:29

አክዓብ፣ የእስራኤል ንጉሥ፣ እንዲሁም ኢዮሣፍጥ፣ የይሁዳ ንጉሥ ወጡ

እዚህ ስፍራ ንጉሦቹ በሰራዊታቸው ታጅበው ራሳቸውን ይወክላሉ። "አክአብ፣ የእስራኤል ንጉሥ፣ እና ኢዮሣፍት፣ የይሁዳ ንጉሥ ሰራዊታቸውን መሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱን ሰውሮ

ይህ ማለት የተለመደ ገጽታን ለውጦ ላለመታወቅ መሞከር ነው።

1 Kings 22:31

ሰላሳ ሁለት አዛዦች

"32 አዛዦች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ብርቱ ያልሆኑትንም ሆነ ብርቱዎቹን ወታደሮች አታጥቁ
"ብርቱ ያልሆኑ" እና "ብርቱ ወታደሮች" የሚለውን ሁለቱንም መጥቀሱ ንጉሡ መላውን ወታደር ማለቱ ነው። "የትኞቹንም ወታደሮች አታጥቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜሪዝም/ደካር እስከ ዳር/ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)
እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አዲስ ደረጃ የሚያሳይ ድርጊት መጀመሩን ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን የሚገልጽበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።
1 Kings 22:34
ቀስቱን ሳያነጣጥር አስፈነጠረ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አክዓብ መሆኑን ሳያውቅ ወደ አንድ ወታደር ዒላማ አድርጎ አነጣጠረ ወይም 2) ቀስቱን ያነጣጠረው በአይምሮው ልዩ ዒላማ ሳይኖር ነው።
1 Kings 22:35
ንጉሡ በሰረገላው ላይ ተደግፎ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው ንጉሡን በሰረገላው ላይ ደግፎት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ጩኸቱ ቀጠለ
እዚህ ስፍራ "ጩኸት" የሚወክለው ይጮሁ የነበሩ ወታደሮችን ነው። "ወታደሮቹ መጮህ ጀመሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እያንዳንዱ ሰው ወደ ከተማው መመለስ ይኖርበታል፤ ደግሞም እያንዳንዱ ሰው ወደ አካባቢው መመለስ ይኖርበታል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተጣመሩት ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 22:37
ወደ ሰማርያ አመጡት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ወታደሮቹ በድኑን ወደ ሰማርያ አመጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ቀበሩት
"ሰዎች ቀበሩት"
የያህዌ ቃል እንደተናገረው
እዚህ ስፍራ "የያህዌ ቃል" የሚወክለው ራሱን ያህዌን ነው። "ያህዌ እንደተናገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 22:39
በእስራኤል ነገሥታት ስራዎች መጽሐፍ ውስጥ ተጽፈው የሚገኙ አይደለምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፤ ደግሞም መልሱ አዎንታዊ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ጥያቄው ቃለ ምልልሳዊ ሲሆን ያለገለውም ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 15:31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እነዚህ ታሪኮች የእስራኤል ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" ወይም "በእስራኤል ንጉሦች ተግባራት መጽሐፍት ውስጥ ልታነቧቸው ትችላላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ/ተኛ
የአክዓብ መሞት የተገለጸው እንደተኛ ተደርጎ ነው። እዚህ ስፍራ መተኛት ሞትን የሚወክል ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። ይህ በ1 ነገሥት 2:10 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)
1 Kings 22:41
የሰላሳ አምስት አመት ሰው
"የ35 አመት ሰው" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ሃያ አምስት አመታት
"25 አመታት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 22:43
በአባቱ፣ በአሳ መንገድ ሄደ
የአንድ ሰው ባሕሪይ የሚገለጸው ያ ሰው በመንገድ ላይ እየሄደ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "አባቱ አሳ፣ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በያህዌ ዐይኖች ፊት ትክክል የሆነውን
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚወክለው ማየትን ሲሆን የያህዌ ሃሳብ የተነገረው እርሱ ማየት እንደሚችል ተደርጎ ነው። "ያህዌ ትክክል ነው ብሎ የሚቀበለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከፍ ያሉትን ስፍራዎች አላጠፋም ነበር
ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ ከፍ ያሉትን ስፍራዎች አላጠፋቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
1 Kings 22:45
በይሁዳ ነገሥታት ስራዎች መጽሐፍ ውስጥ ተጽፈው የሚገኙ አይደለምን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፤ ደግሞም መልሱ አዎንታዊ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ጥያቄው ቃለ ምልልሳዊ ሲሆን ያለገለውም ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ በ1 ነገሥት 14:29 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እነዚህ ታሪኮች የይሁዳ ነገሥታት የፈጸሟቸው ድርጊቶች በተጻፉባቸው መጽሐፍት ውስጥ ተጽፈዋል።" ወይም "በይሁዳ ንጉሦች ተግባራት መጽሐፍት ውስጥ ልታነቧቸው ትችላላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
1 Kings 22:48
መርከቦቹ ተሰብረው ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መርከቦቹ ተሰብረው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ/ተኛ
የኢዮሣፍጥ መሞት የተገለጸው እንደተኛ ተደርጎ ነው። ይህ በ1 ነገሥት 2:10 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን ይመልከቱ)
ከእነርሱ ጋር ተቀበረ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች እርሱን ቀበሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
1 Kings 22:51
ለሁለት አመታት ነገሠ
"ለ2 አመታተት ገዛ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በያህዌ እይታ ክፉ የሆነውን
የያህዌ እይታ የሚነገረው ያህዌ ያንን ነገር እንዳየው ተደርጎ ነው። "ያህዌ ክፉ ብሎ የሚቆጥረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በአባቱ መንገድ ሄደ፣ በእናቱ መንገድ ሄደ፣ በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም መንገድ ሄደ
የአንድ ሰው ባሕሪይ የሚገለጸው ያ ሰው በመንገድ ላይ እየሄደ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "አባቱ፣ እናቱ፣ እና የናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም ያደረጉትን ተመሳሳይ ነገር አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እስራኤልን ወደ ኃጢአት መራ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት የመረቱትን አስሩን ሰሜናዊ ነገዶች ነው።
እርሱ በዓልን አገለገለ፣ ደግሞም አመለከው
"አገለገለ" እና "አመለከ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል አምላክ
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው መላውን አስራ ሁለቱን የያዕቆብ ትውልድ ነገዶች ነው።

---

Chapter 1
2 Kings 1:1
ሞዓብ ዐመፀ
‹‹በሞዓብ የሚኖር ሕዝብ ዐመፀ››
ሰገነቱ ላይ ሳለ ከዐይነ ርግቡ

ሰገነቱ ቤተ መንግሥቱ ጣራ ላይ የተሠራ ክፍል ነው። ዐይነ ርግቡ መድረክ ወይም የመስኮት ሽፋን እንዲሆን ጌጥ ባለው ሁኔታ አንዱ በሌላው ላይ እንዲሻገር ተደርጐ ከቀጫጭን እንጨት ጣውላዎች ተሠራ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቤተ መንግሥቱ ጣራ ላይ ባለው ክፍል ዙሪያ የተሠሩ ቀጫጭን የእንጨት ጣውላዎች››

ብዔል ዜቡል

(ስሞችን እንዴት እንደምትተረጉም ተመልከት)

2 Kings 1:3

ያህዌ

ይህ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ለሕዝቡ የተገለጠ የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህን እንዴት እንደምትተረጉመው ስለ ያህዌ ከትርጒም ቃል ገጽ ተመልከት።

ቴስብያዊ

ይህ የሚያመለክተው በቴስቢ ከተማ የሚኖር ሰውን ነው።

የአቃሮንን አምላክ ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ የምትሄዱ በእስራኤል አምላክ ስለሌለ ነውን?

ይህ ብዔል ዜቡልን በመጠየቃቸው እንደ ተግሣጽ የቀረበ ጥያቄ ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። የእስራኤልን አምላክ በሚገባ ያውቁ ስለ ነበር እንዲህ መሆኑ ስላቅ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እናንት ሞኞች! እስራኤል ውስጥ አምላክ መኖሩን በሚገባ ታውቃላችሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ያንን እንደማያውቅ ሰው የአቃሮንን አምላክ ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ ሰዎች ልካችኋል!››

ቡዔል ዜቡልን ለመጠየቅ

‹‹ለመጠየቅ›› የሚለው ቃል አንድን ጉዳይ አስመልክቶ የሌላውን ሰው ሐሳብ ወይም አስተያየት መጠየቅ ማለት ነው።

ስለዚህ ያህዌ እንዲህ ይላል

ይህ ያህዌ ለንጉሥ አካዝያስ የላከው መልእክት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ለንጉሥ አካዝያስ እንዲህ ይላል››

2 Kings 1:5

መልእክተኞቹ ወደ ንጉሡ አካዝያስ ሲመለሱ

ከኤልያስ ጋር ከተገናኙ በኋላ መልእክተኞቹ ወደ አቃሮን ሳይሄዱ ወደ ንጉሡ ተመልሰዋል።

የአቃሮንን አምላክ ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ ሰዎች የምትልከው በእስራኤል አምላክ ስለሌለ ነውን?

ጥያቄው የቀረበው ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ በማሰቡ እንደ ተግሣጽ ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። የእስራኤልን አምላክ በሚገባ ያውቁ ስለ ነበር እንዲህ ማድረጋቸው ስላቅ ነው። 2 ነገሥት 3፥3 ላይ ያለውን ጥያቄ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተ ሞኝ በእስራኤል አምላክ መኖሩን በሚገባ ታውቃለህ፤ የአቃሮንን አምላክ ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ ሰዎች የላክኸው ግን ይህን እንደማያውቅ ሰው ነው!››

ከተኛህበት ዐልጋ አትነሣም

ንጉሥ አካዝያስ በተጐዳ ጊዜ ዐልጋ ላይ ተኝቶ ነበር። ከእንግዲህ እንደማይድንና ከተኛበት ዐልጋ እንደማይነሣ ያህዌ ተናገረ 2 ነገሥት 3፥4 ላይ ያለውን ዐረፍተ ነገር እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእንግዲህ አትድንም፤ ከተኛህበትም ዐልጋ አትነሣም››

2 Kings 1:7

ጠጉራም ልብስ የለበሰ

የዚህ ትርጒም፣ 1) ጠጉሩ ልብስ የሆነለት እስኪመስል ድረስ ጠጉራም ነበር ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጣም ጠጉራም ነበር።›› ወይም 2) ‹‹ልብሶቹ ከጠጉር የተሠሩ ነበሩ››

2 Kings 1:9

ከዚያም ንጉሡ አንድ የአምሳ አለቃ ከአምሳ ወታደሮች ጋር ወደ ኤልያስ ላከ

ኤልያስን ወደ እርሱ እንዲያመጣ ንጉሡ የአምሳ ወታደሮች መሪ ላከ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከዚያም ንጉሡ ኤልያስን እንዲይዙት የአምሳ አለቃውን ከአምሳ ወታደሮች ጋር ላከ››

አምሳ ወታደሮች

‹‹50 ወታደሮች ተመልከት››

እኔ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንሁ እሳት ትውረድ...

አምሳ አለቃው ኤልያስን የእግዚአብሔር ሰው ብሎታል፤ ይሁን እንጂ፣ አምሳ አለቃውና ንጉሡ ለኤልያስ ተገቢውን ክብር አልሰጡትም ኤልያስ እንዲህ ያለው እሳት ከሰማይ እንድትወርድ ኤልያስ በእርግጥ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ሆነና ክብርም እንደሚገባው ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ የእግዚአብሔር ሰው ስለሆንሁ እሳት ከሰማይ ትውረድ...›› ወይም፣ ‹‹አንተ እንዳልኸው እኔ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንሁ እሳት ከሰማይ ትውረድ...››

ከሰማይ

‹‹ከላይ ከሰማይ››

2 Kings 1:11

አምሳ ወታደሮች

‹‹50 ወታደሮች ተመልከት››

እኔ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንሁ እሳት ከሰማይ ትውረድ

አምሳ አለቃው ኤልያስን የእግዚአብሔር ሰው ብሎታል፤ ይሁን እንጂ፣ አምሳ አለቃውና ንጉሡ ለኤልያስ ተገቢውን ክብር አልሰጡትም። ኤልያስ እንዲህ ያለው እሳት ከሰማይ እንድትወርድና በእርግጥ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ሆነና ክብርም እንደሚገባው ለማሳየት ነው። 2 ነገሥት 1፥10 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ የእግዚአብሔር ሰው ስለሆንሁ እሳት ከሰማይ ትውረድ...›› ወይም፣ ‹‹አንተ እንዳልኸው እኔ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንሁ እሳት ከሰማይ ትውረድ...››

የእግዚአብሔር እሳት

እንዲህ ማለት ከእግዚአብሔር ዘንድ እሳት መጣች ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእግዚአብሔር ዘንድ እሳት››

2 Kings 1:13

አምሳ ጦረኞች

‹‹50 ጦረኞች›› ወይም፣ ‹‹50 ወታደሮች›› ‹‹ተመልከት››

ለመነው

‹‹ተማፀነው››

እነዚህ የአምሳዎቹ አገልጋዮችህ

አምሳ አለቃው ለእርሱ ክብር ለማሳየት የእርሱ አገልጋዮች የኤልያስ አገልጋዮች መሆናቸውን ተናገረ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእኔ አምሳ ወታደሮች››

የእኔና የእነዚህ... ነፍስ በፊትህ የከበረች ትሁን

እዚህ ላይ የኤልያስ፣ ‹‹ፊት›› የሚወክለው ፍርድን ወይም መመርመርን ነው። በሕይወት እንዲኖሩ አምሳ አለቃው ኤልያስን እየለመነ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እባክህን የእኔና የእነዚህ... ነፍስ በአንተ ዘንድ የከበረች ትሁን›› ወይም ‹‹የእኔና የእነዚህ ነፍስ በፊትህ ዋጋ ታግኝ፤ እኛንም አትግደለን››

ነፍሴ በፊትህ የከበረች ትሁን

እዚህ ላይ የኤልያስ ‹‹ፊት›› የሚወክለው ፍርድን ወይም መመርመርን ነው። ለእርሱ ቸርነት እንዲያደርግና እንዳይገድለው አምሳ አለቃው እንደ ገና ኤልያስን እየለመነ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እባክህን ቸርነት አድርግልኝ›› ወይም፣ ‹‹እባክህን አትግደለኝ››

2 Kings 1:15

ለመሆኑ የአቃሮንን አምላክ ብዔል ዜቡልን ስለ ራስህ ለመጠየቅ መልእክተኞች የላክኸው በእስራኤል አምላክ ስለሌለ ነውን?

ጥያቄው ያቀረበው ብዔል ዜቡልን ለመጠየቅ በማሰቡ እንደ ተግሣጽ ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። ንጉሡ በእስራኤል አምላክ መኖሩን በሚገባ ያውቅ ስለ ነበር እንዲሁ ማድረጉ ስላቅ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተ የምትጠይቀው አምላክ በእስራኤል እንደሌለ እያሰብህ ነው!›› ወይም፣ ‹‹አንተ ሞኝ! የምትጠይቀው አምላክ በእስራኤል እንዳለ በሚገባ ታውቃለህ፤ ግን እያደረግህ ያለኸው ያንን እንደማያውቅ ነው።››

ከተኛህበት ዐልጋ ፈጽሞ አትነሣም

ንጉሥ አካዝያስ በተጐዳ ጊዜ ዐልጋ ላይ ተኝቶ ነበር። ከእንግዲህ እንደማይድንና ከዐልጋ እንደማይነሣ ያህዌ ተናገረ። 2 ነገሥት 3፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእንግዲህ አትድንም፤ ከተኛህበትም ዐልጋ አትነሣም››

2 Kings 1:17

ኤልያስ እንደ ተናገረው እንደ ያህዌ ቃል

‹‹ያህዌ ለኤልያስ እንደ ነገረውና ኤልያስ እንደ ተናገረው››

የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም በይሁዳ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት

ኢዮራም በኢየሩሳሌም የነገሠው ምን ያህል ጊዜ እንደ ነበር በማሳየት ኢዮራም በእስራኤል መንግሥ የጀመረበትን ጊዜ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የኢዮሳፍጥ ልጅ ኢዮራም የይሁዳ ንጉሥ በሆነ በሁለተኛው ዓመት››

በእስራኤል... የተጻፈ አይደለምን?

ይህን በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል፤ እንደ ተሸጋሪ ግሥ ማቅረብም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእስራኤል... ተጽፈዋል›› ወይም፣ ‹‹ስለ እነዚህ ነገሮች አንድ ሰው በእስራኤል... ጽፎአል››

Chapter 2
2 Kings 2:1
እንዲህም ሆነ
‹‹እንዲህ ተደረገ›› ይህ ሐረግ ታሪኩ ውስጥ ቀጥሎ የተደረገውን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል።
በዐውሎ ነፋስ
ዙሪያውን የሚሽከረከር ከባድ ነፋስ
ሕያው ያህዌ በሕያው ነፍስህም
‹‹ያህዌ ሕያው የመሆኑንና አንተም ሕያው የመሆንህን ያህል። እዚህ ላይ ኤልሳዕ የያህዌንና የኤልያስን ሕያውነት እርሱ ከሚናገረው ነገር እርግጠኝነት ጋር ይነጻጸራል። ይህ ጠንከር ያለ ተስፋ የሚሰጠበት ቃል ነው። ‹‹ያንን በመሐላ አረጋግጥልሃለሁ››
2 Kings 2:3
የነቢያት ልጆች
እነዚህ በቀጥታ የነቢያት ልጆች ሳይሆኑ፣ የነቢያት ስብስብ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የነቢያት ስብስብ››
ሕያው ያህዌን በሕያው ነፍስህም እምላለሁ ከአንተ አልለይም
‹‹ያህዌ ሕያው እንደ መሆኑ፣ አንተም ሕያው እንደ መሆንህ ከአንተ አልለይም።›› እዚህ ላይ ኤልሳዕ የያህዌንና የኤልያስን ሕያውነት ከሚናገረው ነገር እርግጠኝነት ጋር ያነጻጽራል። ይህ ቃል ኪዳን የሚደረግበት መንገድ ነው። 2 ነገሥት 2፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአንተ እንደማልለይ እምላለሁ››
2 Kings 2:5
በኢያሪኮ የነበሩትም የነቢያት ልጆች ወደ ኤልሳዕ መጥተው እንዲህ አሉት።
‹‹ኤልያስና ኤልሳዕ ወደ ኢያሪኮ ሲመጡ እዚያ የነበሩ የነቢያት ልጆች ኤልሳዕን እንዲህ አሉት››
የነቢያት ልጆች
እነዚህ በቀጥታ የነቢያት ልጆች ሳይሆኑ የነቢያት ስብስብ ናቸው። 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የነቢያት ስብስብ››
ሕያው ያህዌን በሕያው ነፍስህም እምላለሁ
‹‹ያህዌ ሕያው እንደ መሆኑ፣ አንተም ሕያው እንደ መሆንህ ከአንተ አልለይም›› እዚህ ላይ ኤልሳዕ የያህዌንና የኤልያስን ሕያውነት ከሚናገረው ነገር እርግጠኝነት ጋር ያነጻጽራል። ይህ ቃል ኪዳን የሚደረግበት መንገድ ነው። 2 ነገሥት 2፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተገጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአንተ እንደማልለይ እምላለሁ››
2 Kings 2:7
ከልጆቹ አምሳው
‹‹ከልጆቹ 50››
የነቢያት ልጆች
እነዚህ በቀጥታ የነቢያት ልጆች ሳይሆኑ፣ የነቢያት ስብስብ ናቸው። 2 ነገሥት 2፥3 እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የነቢያት ስብስብ››
ከእነርሱ ትይዩ ቆመ
ይህ ማለት ፊታቸውን ወደ እነርሱ አድረገው ቆሙ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፊታቸውን ወደ እነርሱ አድርገው ቆመ›› ወይም፣ ‹‹እነርሱን እያዩ ቆሙ››
መጐናጸፊያ
ከላይ የሚለበስ ልብስ
ውሃው ግራና ቀኝ ተከፈለ፤ ሁለቱም በደረቅ ምድር ተሻገሩ
‹‹ኤልያስና ኤልሳዕ በደረቅ ምድር ወደ ማዶ እንዲሻገሩ የዮርዳኖስ ወንዝ ውሃ ለሁለት ተከፈለ››
በሁለቱም በኩል
‹‹ግራና ቀኝ›› ይህ የሚያመለክተው፣ ኤልያስ ውሃውን ከመታበት ግራና ቀኝ ያለውን ነው።
2 Kings 2:9
እንዲህም ሆነ
‹‹እንዲህ ተደረገ››
ተሻገሩ
ይህ የሚያመለክተው ዮርዳኖስን ወንዝ መሻገርን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዮርዳኖስ ወንዝ ተሻገሩ››
ከአንተ ከመውሰዴ በፊት
ይህን እንደ ተሻጋሪ ግሥ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እኔን ከአንተ ከመውሰዱ በፊት››
መንፈስህ በዕጥፍ እንዲያድርብኝ
እዚህ ላይ የኤልያስ መንፈስ መንፈሳዊ ኃይሉን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአንተን መንፈሳዊ ኃይል ሁለት እጅ››
2 Kings 2:11
እነሆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› የሚለው ቃል ቀጥሎ ያለውን አስደናቂ ነገር በንቃት መጠበቅ እንዳለብን ያመለክታል።
የእሳት ሠረገላና የእሳት ፈረሶች
‹‹የእሳት›› የሚለው በእሳት መከበባቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእሳ የተከበበ ሠረገላና በእሳት የተከበቡ ፈረሶች››
በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ዐረገ
‹‹በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ተወሰደ።›› ‹‹ዐውሎ ነፋስ›› የሚለውን ቃል 2 ነገሥት 2፥1 ስትተረጉም በተጠቀምህበት ቃል ተርጉመው።
አባቴ! አባቴ!
ኤልሳዕ የሚያከብረውን መሪ እየተጣራ ነው።
ከሁለት ቦታ ቀደደ
ብዙውን ጊዜ ሰዎች ልብሳቸውን የሚቀዱት በጣም ለማዘናቸውና ለመተከዛቸው ምልክት እንዲሆን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምን ያህል ማዘኑን ለማሳየት ሁለት ቦታ ቀደደው››
2 Kings 2:13
መጐናጸፊያ
መጐናጸፊያ ነቢዩ ከላይ የሚደርበው ልብስ ነው። የአገልግሎቱ ምልክት ነበር። ኤልሳዕ የኤልያስን መጐናጸፊያ ሲወስድ፣ እንደ ነቢይ የኤልያስን ቦታ መውሰዱን ማመልከቱ ነበር።
የኤልያስ አምላክ ያህዌ ወዴት ነው?
ያህዌ ከኤልያስ ጋር እንደ ነበረ ሁሉ፣ ከእርሱም ጋር መኖሩን ኤልሳዕ እየጠየቀ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኤልያስ አምላክ ያህዌ፣ ከእኔ ጋር ነህን?››
በግራና በቀኝ ተከፍሎለት ተሻገረ
ውሃው ለሁለት ተከፈለ፤ ኤልሳዕም ቀደም ሲል ከኤልያስ ጋር በነበረ ጊዜ እንደ ሆነው በደረቅ መሬት ወደ ማዶ ተሻገረ።
በሁለቱም በኩል
‹‹ግራና ቀኝ›› ይህ የሚያመለክተው ኤልያስ ውሃውን የመታበትን ግራና ቀኝ ነው።
2 Kings 2:15
የነቢያት ልጆች
እነዚህ በቀጥታ የነቢያት ልጆች ሳይሆኑ፣ የነቢያት ስብስብ ናቸው። 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ይህን እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የነቢያት ስብስብ››
በፊቱ ወደ መሬት ዝቅ ብለው እጅ ነሡ
ጥልቅ አክብሮታቸውንና እርሱን እንደ መሪ መቀበላቸውን እያሳዩ ነበር።
የኤልያስ መንፈስ በኤልሳዕ ላይ ዐርፎአል
እዚህ ላይ የኤልያስ፣ ‹‹መንፈስ›› የሚያመለክተው የእርሱን መንፈሳዊ ኀይል ነው። ይህ ክፍል ኤልያስ የነበረው መንፈስ እንደ አንዳች ግዙፍ ነገር ኤልሳዕ ላይ ማረፉን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኤልሳዕ ኤልያስ የነበረው ዐይነት መንፈሳዊ ኀይል ነበረው ወይም፣ ‹‹ኤልያስ የነበረው መንፈሳዊ ኀይል አሁን ኤልሳዕ ላይ ሆነ››
እነሆ፣ እኛ አገልጋዮችህ እዚህ አምሳ ጠንካራ ሰዎች አሉን
‹‹አምሳ ጠንካራ ሰዎች›› ሲሉ እነዚህ ሰዎች ስለ ራሳቸው እየተናገሩ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነሆ፣ እዚህ አምሳ ሰዎች አሉን፤ እኛ አገልጋዮችህ ነን፤ ስለዚህ አሁን እንሂድ››
አምሳ ጠንካራ ሰዎች
‹‹50 ጠንካራ ሰዎች››
2 Kings 2:17
ዕፍረት እስኪሰማው ድረስ ግድ አሉት
የነቢያት ልጆች፣ ‹‹አይሆንም›› ማለት እስኪቸገር ድረስ አጥበቀው ኤልሳዕን ጠየቁት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥያቄያቸውን አልቀበልም ማለት እስኪቸገር ድረስ የነቢያት ልጆች ደጋግመው ኤልሳዕን ጠየቁት››
ቀድሞንስ ቢሆን አትሂዱ ብያችሁ አልነበረምን?

ኤልሳዕ ይህን ያለው ምን እንደሚሆን ቀድሞውኑ ነግሮአቸው ለነበረው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱን ስለማታገኙ መጀመሪያውኑ አትሂዱ ብያችሁ ነበር!
2 Kings 2:19
የከተማዪቱም ሰዎች
‹‹የከተማዋ መሪዎች››
ይህች ከተማ ለኑሮ የተመቸች ናት
ይህ ማለት ከተማዋ ያለችው ጥሩ ቦታ ላይ ነው ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከተማዋ ምቹ ቦታ ላይ ናት›› ወይም፣ ‹‹ከተማዋ ጥሩ ቦታ ላይ ናት››
ጌታችን እንደምታያት
እዚህ ላይ ኤልሳዕ፣ ‹‹ጌታችን›› የተባለው እርሱን ለማክበር ነው።
ፍሬያማ
ጥሩ ፍሬ የምትሰጥ
2 Kings 2:21
ይህን ውሃ ፈውሼዋለሁ
ይህ የሚያመለክተው የመፈወስ ያህል ያህዌ ውሃውን ጥሩ ማድረጉን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ውሃውን ንጹሕ አድርጌአለሁ››
ከእንግዲህ ሞት ወይም ፍሬ ቢስ መሆን አይኖርም።
ይህ የሚያመለክተው መጥፎ ውሃ የሚያደርገውን ነገር ነው። ይህንንም አዎንታዊ በሆነ መልኩ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእንግዲህ ይህ ውሃ የሚያደርገው ሞት ወይም ፍሬ ቢስነት አይኖርም›› ወይም፣ ‹‹ከአሁን ጀምሮ ይህ ውሃ ሕይወት ያመጣል፤ ምድሪቱ ፍሬያማ እንድትሆንም ያደርጋል››
ውሃው ተፈወሰ
ይህንን፣ ‹‹ውሃው እንደ ተፈወሰ ነው›› ማለት ይቻላል።
እንደ ተናገረ… እስከ ዛሬ ደረሰ
ይህ የሚያመለክተው እስከ አሁን ደረስ ያለ ነገርን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኤልሳዕ በተናገረው ቃል መሠረት እስከ ዛሬ ደረስ ንጹሕ እንደ ሆነ አለ››
2 Kings 2:23
ከዚያ ተነሥቶ ወደ ቤቴል ወጣ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ወጣ›› የተባለው ከኢያሪኮ ይልቅ ቤቴል ከፍታ ቦታ ላይ ስለ ነበረች ነው።
ውጣ
ልጆቹ ኤልሳዕ ከዚያ እንዲሄድ ፈልገዋል፤ ይህንንም የገለጹት፣ ‹‹ውጣ›› በማለት ነበር። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከዚህ ውጣ››
መላጣ
ራሱ ላይ ጠጉር የሌለው ሰው ማለት ነው። መላጣ በመሆኑ ልጆቹ ኤልሳዕ ላይ እያፌዙ ነበር።
ከልጆቹ አርባ ሁለቱን
‹‹42 ልጆች››

Chapter 3
2 Kings 3:1
የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሳፍጥ በነገሠ በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት
ይህ የሚያመለክተው አሁን ያለው የይሁዳ ንጉሥ ምን ያህል ዓመት እንደ ገዛ በማሳየት ኢዮራም መንገሥ የጀመረበትን ጊዜ ነው። የዚህን ዐረፍተ ነገር ትርጒም በጣም ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዮሳፍጥ የይሁዳ ንጉሥ በሆነ በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት››
ዐሥራ ስምንተኛው ዓመት
‹‹18 ዓመት››
የአክአብ ልጅ ኢዮራም
አንዳንዴ ይህ ሰው ኢዮሮብዓም ተብሎ ተጠርቷል። ይህ 2 ነገሥት 1፥17 ላይ ካለው ‹‹ኢዮራም›› የተለየ ነው።
በያህዌ ፊት ክፉ የሆነውን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ፊት›› የያህዌን ሐሳብ ወይም አስተያየት ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ ብሎ የሚያስበውን›› ወይም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነውን››
አባትና እናቱ እንደ ፈጸሙት ዐይነት አልነበረም
ይህ የሚያመለክተው ወላጆቹን ያህል ባይሆንም፣ እርሱም ብዙ ኀጢአት ማድረጉን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አባቱና እናቱ ያደረጉትን ያህል ክፉ ነገር አላደረገም።››
የበአል ሐውልት
ምንም እንኳ ሐውልቱ ምን ዐይነት እንደ ነበር ባይታወቅም፣ በአልን ለማምለክ ጥቅም ላይ የሚውል ነበር። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በአል የሚመለክበት ሐውልት››
በኀጢአት ተያዘ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ‹‹በኀጢአት ተያዘ›› ያንን ማድረግ ቀጠለ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኀጢአት ማድረጉን ቀጠለ››
ናባጥ
ይህ የሰው ስም ነው።
ከዚያ ዘወር አላለም
ከአንድ ነገር፣ ‹‹ዘወር›› ማለት ያንን ማድረግ መተው ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያንን ኀጢአት ማድረጉን አልተወም›› ወይም፣ ‹‹ያንን ኀጢአት ማድረግ ቀጠለ››
2 Kings 3:4
100,000 ጠቦትና 100,000 አውራ በግ ጠጉር ለእስራኤል ንጉሥ ይገብር ነበር
ሞሳ እንዲህ ያደርግ የነበረው መንግሥቱ በእስራኤል ንጉሥ ቁጥጥር ሥር ስለ ነበር ነው። የዚህን ዐረፍተ ነገር የተሟላ ትርጒም ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መንግሥቱ በእስራኤል ንጉሥ ቁጥጥር ሥር ስለ ነበር በየዓመቱ 100,000 ጠቦትና የ100,000 አውራ በግ ጠጉር ለእስራኤል ንጉሥ የመስጠት ግዴታ ነበረበት››
100,000 ጠቦት… 100,000 አውራ በግ
‹‹አንድ መቶ ሺህ ጠቦት… አንድ መቶ ሺህ አውራ በግ››
እስራኤልን ሁሉ ለጦርነት አንቀሳቀሰ
‹‹የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ ለጦርነት ማዘጋጀት›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እስራኤል ሁሉ›› አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤል ወታሮችን ሁሉ ይመለከታል። የእስራኤል ወታደሮችን ሁሉ ለጦርነት አንቀሳቀሰ››
2 Kings 3:7
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ኢዮራም ለንጉሥ ኢዮሳፍጥ እየተናገረ ነው።
ሞዓብ ላይ አብረኸኝ ትዘምታህን?
የሚናገረው ለኢዮሳፍጥ ቢሆንም፣ እርሱንና ሰራዊቱንም ይመለከታል። እዚህ ላይ ‹‹ሞዓብ›› — ‹‹የሞዓብን ሠራዊት›› ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተና ሰራዊትህ ሞዓብ ላይ ለመዝመት ከእኔ ጋር ትሄዳላችሁን?››
አዎን አብሬህ እዘምታለሁ
እርሱና ሰራዊቱ ንጉሥ ኢዮራም ጋር አብረው ሞዓብ ላይ እንደሚዘምቱ ኢዮሳፍጥ እየተናገረ ነው። ‹‹አዎን፣ አብረንህ እንሄዳለን››
እኔ እንደ አንተው ነኝ፤ ሕዝቤ እንደ ሕዝብህ ፈረሶቼም እንደ ፈረሶችህ ናቸው
ኢዮራም በእርሱና በሕዝቡ በፈረሶቹም ለዓላማው እንዲጠቀም ኢዮሳፍጥ ራሱን እየሰጠ ነው። እርሱ የኢዮራም መሆኑን እየተናገረ ነው። የዚህን ዐረፍተ ነገር ትርጒም ይበልጥ የተሟላ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንድናደርግ ምትፈልገውን ለማድረግ ዝግጁ ነን፡ ሰራዊቴም ሆነ ፈረሶቼ አንተን ለመርዳት ዝግጁ ናቸው።
በኤዶም ምድረ በዳ
‹‹በኤዶም ምድረ በዳ ውስጥ››
2 Kings 3:9
የእስራኤል ንጉሥ ከይሁዳ ንጉሥና ከኤዶም ንጉሥ ጋር ለመዝመት ተነሣ
ይህ የሚያመለክተው በሰራዊቶቻቸው የታጀቡ ንጉሦችን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤል ንጉሥና ሰራዊቱ ከይሁዳ ንጉሥና ከሰራዊቱ እንዲሁም ከኤዶም ንጉሥና ከሰራዊቱ ጋር ዘመተ››
ሰባት ቀን ዞሩ
ይህም ማለት 1) ንጉሦቹ ወዴት እንደሚሄዱ እርግጠኞች አልነበሩም፤ ስለዚህ መንገዳቸውን ይለዋወጡ ነበር ማለት ነው፤ ወይም 2) ንጉሦቹ የሚሄዱበትን ያውቁ ነበር፤ በሞዓብ ዙሪያ ዞሩ። (2 ነገሥት 3፥8)
ወዮ! ያህዌ እኛን ሦስት ነገሥታት የጠራን ለሞዓብ አሳልፎ ሊሰጠን ነውን?
የነበሩበት ሁኔታ ምን ያህል አስጨናቂና ግራ የሚያጋባ መሆኑን ለማሳየት ንጉሡ ይህን ጠይቋል። ይህን እንደ ዐረፍተ ነገር ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኛን ሦስት ነገሥታት ያህዌ በሞዓብ እንድንያዝ የፈለገ ይመስላል!››
ለሞዓብ እጅ አሳልፎ ሊሰጠን

እዚህ ላይ፣ ‹‹ሞዓብ›› ሰራዊቱን ያመለክታል፡፡ ‹‹ለሞዓብ እጅ›› በሞዓብ ሰራዊት ‹‹ቁጥጥር›› ሥር መሆኑን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሞዓብ ቁጥጥር አሳልፎ ሊሰጠን›› ወይም፣ ‹‹የሞዓብ ሰራዊት ድል እንዲያደርገን››

2 Kings 3:11

በእርሱ አማካይነት ያህዌን ለመጠየቅ እንድንችል የያህዌ ነቢይ እዚህ የለምን?

ኢዮሳፍጥ እንዲህ በማለት የጠየቀው፣ እዚያ ነቢይ መኖሩንና እርሱን ፈልገው ማግኘት እንዳለባቸው ለማመልከት ነው፡፡ ይህን እንደ ዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚህ ቦታ የያህዌ ነቢይ እንደሚኖር እርግጠኛ ነኝ፤ በእርሱ አማካይነት ያህዌን እንድጠይቅ የት እንደማገኘው ንገሩኝ››

ሣፋጥ

ይህ የሰው ስም ነው፡፡

የኤልያስን እጅ ያስታጥብ የነበረው

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር የኤልያስ ረዳት ማለት ነው፡፡ ‹‹እጅ ማስታጠብ›› ኤልያስን ያገለግል የነበረበትን መንገድ የሚገልጽ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኤልያስ ረዳት የነበረው››

የያህዌ ቃል ከእርሱ ዘንድ ይገኛል

ይህ ማለት ነቢይ ነበር፤ መናገር ያለበትን ያህዌ ይነግረው ነበር ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የነገረውን ይናገር ነበር››

ወደ እርሱ ወረዱ

ኤልሳዕን ለማየትና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከእርሱ ለመጠየቅ ሄዱ፡፡ ይህን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኤልሳዕን ለማየትና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለመጠየቅ ወደ እርሱ ሄዱ፡፡››

2 Kings 3:13

ከአንተ ጋር ምን የሚያገናኘኝ ነገር አለ?

ኤልሳዕ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ንጉሡና እርሱ ምንም የጋራ የሆነ ነገር እንደሌላቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ ይህን እንደ ዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአንተ ጋር ምንም ጉዳይ የለኝም›› ወይም፣ ‹‹ከአንተ ጋር ምንም የምጋራው ነገር የለኝም››

በሞዓብ እጅ አሳልፎ ሊሰጣቸው

እዚህ ላይ፣ ‹‹የሞዓብ እጅ›› የሞዓብን፣ ‹‹ቁጥጥር›› ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሞዓባውያን ቁጥጥር አሳልፎ ሊሰጣቸው›› ወይም፣ ‹‹በሞዓብ ሰራዊት እንዲያዙ ለማድረግ››

በፊቱ የቆምሁት የሰራዊት ጌታ ሕያው ያህዌን

‹‹በፊቱ የቆምሁት የሰራዊት ጌታ ያህዌ በእርግጥ ሕያው እንደ ሆነ፡፡ እዚህ ላይ ኤልሳዕ የያህዌን ሕያው መሆን እርግጠኝነት፣ ለኢዮሳፍጥ ሲል እንጂ ኢዮራምን እንደ ቁም ነገር እንደማይቆጥረው ከነበረው እርግጠኝነት ጋር ያነጻጽራል፡፡ ይህ የመሐላ ያህል ነበር፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፊቱ የቆምሁት የሰራዊት ጌታ ያህዌ ሕያው የመሆኑን ያህል ይህንንም በእርግጠኝነት ነው የምነግርህ››

በፊቱ የቆምሁት

እዚህ ላይ ያህዌን ማገልገል በፊቱ መቆም እንደ ሆነ ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የማገለግለው ያህዌ››

የይሁዳን ንጉሥ ኢዮሳፍጥን ባላከብር ኖሮ፣ አንተን አላይም ወይም ጉዳዬ አልልህም ነበር

ይህን በአዎንታዊ መልኩ መጻፍ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተን የማናግርህ የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሳፍጥን ስለማከብር ነው››

የኢዮሳፍጥን ፊት አከብራለሁ

እዚህ ላይ የኢዮሳፍጥ ፊት የእርሱን መገኘት ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮሳፍጥን አከብራለሁ››

አንተን አላይም ወይም ጉዳዬ አልልህም ነበር

የእነዚህ ሁለት ሐረጐች ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን፣ ለኢዮራም ይህን ያህል ግምት እንደሌለው አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአንተ ጋር ምንም ዐይነት ጉዳይ የለኝም››

2 Kings 3:15

ከዚያም እንዲህ ሆነ

‹‹እንዲህ ተደረገ››

በገና ደርዳሪ

በገና የሚጫወት ሰው

የያህዌ እጅ በኤልሳዕ ላይ መጣ

እዚህ ላይ፣ ‹‹የያህዌ እጅ›› የያህዌን፣ ‹‹ኀይል›› ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያህዌ ኀይል በኤልሳዕ ላይ መጣ››

ሸለቆ

እዚህ ላይ ሸለቆ ውሃ እንዲጠራቀምበት ሠራተኞች የቆፈሩት ረጅም የውሃ መውረጃ ነው፡፡

ሸለቆው ውሃ ይሞላል

ይህን ተሻጋሪ ግሥ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህን የወንዝ ሸለቆ ውሃ እሞላዋሁ››

እናንተ ትጠጣላችሁ

እዚህ ላይ ያህዌ የሚሰጠውን ውሃ መጠጣትን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተም ውሃውን ትጠጣላችሁ››

2 Kings 3:18

ይህ በያህዌ ፊት ቀላል ነው

የያህዌ ፊት የያህዌን ፍርድና መርማሪነት ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ይህን እንደ ቀላል ነገር ነው የሚያየው›› ወይም፣ ‹‹ይህን ማድረግ ለያህዌ ቀላል ነገር ነው››

የተመሸገ ከተማ

የተመሸገ ከተማ ጠላት እንዳያጠቃው ዙሪያውን ረጃጅም ግንብ ያለው ከተማ ነው፡፡

መልካሙን ዕርሻ በድንጋይ ታበላሹታላችሁ

ይህ ማለት መልካሙ እርሻ ጥቅም ላይ እንዳይውል በድንጋይ ትሞሉታላችሁ ማለት ነው፡፡ ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መልካሙን እርሻ ድንጋይ በመሙላት ጥቅም እንዳይሰጥ ታደርጉታላችሁ››

2 Kings 3:20

ውሃ እየጐረፈ መጣ

‹‹ውሃ መፍሰስ ጀመረ›› ምድሪቱም ውሃ በውሃ ሆነች

‹‹ወዲያውኑ ምድሪቱ በውሃ ተሞላች›› ምድሪቱ

አገር፣ ቦታ

2 Kings 3:21

በዚህ ጊዜ

ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ዋናውን ታሪክ ገታ ለማድረግ ነው፡፡ የሞዓብ ሰራዊት ሦስቱን ነገሥታት ጦርነት ለመግጠም እያደረጉ ለነበረው ዝግጅት ጸሐፊው ዳራ የሚሆን መረጃ ያቀርባል፡፡

መሣሪያ መያዝ የቻለ ሁሉ

እዚህ ላይ፣ ‹‹መሣሪያ›› መዋጋት መቻል ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መዋጋት የሚችል ሰው ሁሉ››

ነገሥታቱ… መጡ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ነገሥታት›› ሰራዊቶቻቸውንና ነገሥታቱ ራሳቸውን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነገሥታቱ ከሰራዊቶቻቸው ጋር መጡ›› ወይም፣ ‹‹ነገሥታቱና ሰራዊቶቻቸው መጡ››

እንደ ደም ቀልቶ ታያቸው

እዚህ ላይ ውሃው ቀይ ሆኖ መታየቱን ከደም ቀለም ጋር ያነጻጽራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ደም ቀይ ሆነ››

እንግዲህ ሞዓብ

ወታደሮቹ ራሳቸውን፣ ‹‹ሞዓብ›› በማለት ነው የሚገልጹት፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሞዓብ ወታደሮች››

ወደ ምርኮህ ዙር

‹‹ንብረታቸውን መዝረፍ›› ወታደሮች ጠላቶቻቸውን ካሸነፉ በኋላ ማንኛውንም ዋጋ ያለው ነገር ከከተሞቻቸው ይዘርፉ ነበር፡፡

2 Kings 3:24

የእስራኤል ሰፈር

እዚህ ላይ ‹‹እስራኤል›› የሚያመለክተው የእስራኤልን ወታደሮች እንጂ፣ ጠቅላላውን የእስራኤል ሕዝብ አይደለም፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስራኤላውያን ድንኳኖቻቸውን ተክለው የነበረበት ቦታ››

እስራኤላውያን ወጓቸው

‹‹እስራኤላውያን›› የሚያመለክተው የእስራኤል ወታደሮችን እንጂ፣ ጠቅላላውን የእስራኤል ሕዝብ አይደለም፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ወታደሮች ወጓቸው››

ከፊታቸው ሸሹ

‹‹ከፊታቸው ሮጠው አመለጡ››

ቂር ሐራሴት

ይህ የሞዓብ ዋና ከተማ ነው፡፡

ከነድንጋይዋ ቀርታ ነበር
የከተማዋ ግንቦችና ሕንጻዎች ከድንጋይ የተሠሩ ነበሩ። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የድንጋይ ግንቦቿና ሕንፃዎቹ እንዳሉ ነበሩ።››
ባለ ወንጭፉ
‹‹ወንጭፍ›› ከእንስሳት ቆዳ የተሠራ ረጅም ገመድ ሲሆን፣ ጫፍ ላይ ድንጋይ ወይም ሌላ ጠጣር ነገር ተደርጐለት ከሩቅ ይወነጨፍ ነበር።
2 Kings 3:26
ንጉሥ ሞሳ
የዚህን ንጉሥ ስም 2 ነገሥት 3፥4 ላይ በተረጐምህበት መንገድ ተርጉመው።
በጦርነቱ መሸነፉን እንዳወቀ
‹‹ሰራዊቱ መሸነፉን…››
ሰይፍ የታጠቁ ሰባት መቶ ሰዎች
‹‹700 ሰይፍ የታጠቁ…››
ሰይፍ የታጠቁ
በሰይፍ የሚዋጉ ወታደሮች
ጥሶ ለመግባት
‹‹በኀይል አሸንፎ…›› ጦር ሜዳ ላይ የተሰለፉ ወታደሮች በጣም ብዙ ስለ ነበሩ አልፎ ለመሄድ አስቸጋሪ ነበር።
የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጐ አቀረበው
ንጉሥ ሞሳ እስኪሞት ድረስ ልጁን በእሳት አቃጠለው። ይህን ያደረገው ለሐሰተኛው አምላክ ለካሞስ መሥዋዕት እንዲሆን ነበር። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።
በእስራኤልም ላይ ታላቅ ቁጣ ሆነ
እዚህ ላይ ‹‹ቁጣ›› የሚለውን ቃል ግሥ ማድረግ ይቻላል። የተቆጣው ማን እንደ ነበር ሁለት ትርጉሞች ሊኖሩ ይችላሉ፡ 1) ሞዓባውያን ወታደሮች። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሞዓባውያን ወታደሮች እስራኤልን በጣም ተቆጡ›› ወይም 2) እግዚአብሔር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር እስራኤልን በጣም ተቆጣ››

---

Chapter 4
2 Kings 4:1
የነቢያት ልጆች
እነዚህ የነቢያት ስብስብ እንጂ፣ በቀጥታ የነቢያት ልጆች አልነበሩም። 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነቢያት››
አገልጋይህ ባሌ
‹‹አገልጋይህ የነበረው ባሌ››
ባለ ዕዳ
ለሰዎች ገንዘብ የሚያበድር ሰው
አገልጋይህ ምንም ነገር የላትም
ለእርሱ ያላትን አክብሮት ለማሳየት ሴትዮዋ የኤልሳዕ አገልጋይ እንደ ሆነች ተናገረች
ከጥቂት ዘይት በቀር በቤቷ ምንም
ይህ ማጋነን ነው። ያላት ንብረት የዘይት ማድጋ ብቻ ነበር።
2 Kings 4:3
ወደ ውስጥ ግቢ
ይህ ወደ ቤታቸው መግባት ማለት ነው። የተሟላውን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ ቤትሽ ግቢ››
2 Kings 4:5
ዕቃዎች
‹‹ማድጋዎች››
2 Kings 4:7
የእግዚአብሔር ሰው
ይህ የሚያመለክተው ኤልሳዕን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››
የተረፈው የአንቺና የልጆችሽ መተዳደሪያ ይሁን
ምግብና ልብስ የመሳሰሉ አስፈላጊ ነገሮችን ለመግዛት ገንዘቡን ተጠቀመበት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተቀረውን ገንዘብ አንቺና ልጆችሽ ለኑሮ የሚያስፈልጋችሁን ለመግዛት ተጠቀሙበት።
2 Kings 4:8
ሱነም
ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው።
ከእርሷ ጋር ምግብ እንዲበላ አጥብቃ ለመነችው
በዚያ በኩል ሲያልፍ ጐራ ብሎ እቤቷ ምግብ እንዲበላ ጠየቀችው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ ቤቷ መጥቶ ምግብ እንዲበላ ጠየቀችው››
በዚያም ባለፈ ቁጥር
‹‹በሱነም በኩል ሲያልፍ››
መሆኑን አውቃለሁ
‹‹ይህን በሚገባ እረዳለሁ››
አዘውትሮ በደጃችን የሚያልፍ
‹‹ሁልጊዜ በደጃችን በኩል የሚያልፍ››
2 Kings 4:10
አጠቃላይ መረጃ
ያቺ ሀብታም ሴት ስለ ኤልሳዕ ለባልዋ እየተናገረች ነው።
እናስገባለን
ይህ የሚያመለክተው ያቺን ሀብታም ሴትና ባልዋን ነው።
2 Kings 4:12
ግያዝ
ይህ የሰው ስም ነው።
ሱነማዪቱን ጥራት
‹‹ሰነማዪቱን ሴት ጥራት›› ይህ የሚያመለክተው ኤልሳዕ እቤቷ ይኖር የነበረውን ከሱነም የሆነችውን ሴት ነው።
ለእኛ ስትይ በጣም ተቸግረሻል
‹‹በጣም ተቸግረሻል›› የሚለው አንዳች ነገር ለማድረግ ከፍ ያለ ጥረት አድርገሻል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእኛ ይህን ለማድረግ ትልቅ ጥረት አድርገሻል›› ወይም፣ ‹‹ለእኛ ይህን ለማድረግ ከባድ ዋጋ ከፍለሻል››
ምን እንዲደረግልሽ ትፈልጊያለሽ?
ይህን፣ ‹‹ምን እናድርግልሽ?›› በማለት መተርጐም ይቻላል።
የምንነግርልሽ ጉዳይ አለን?
ለንጉሡ ወይም ለሰራዊቱ አዛዥ እንዲነግርላት የምትፈልገው ነገር ካለ ኤልሳዕ ሴትዮዋን እየጠየቀ ነው። ይህን ጥያቄ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለ አንቺ ጥያቄ እናቅርብ?››
እኔ እኮ የምኖረው በገዛ ወገኖቼ መካከል ነው
ቤተ ሰቧ የሚያስፈልጋትን ሁሉ ስለሚያደርግላት ሴትዮዋ ምንም እንደማያስፈልጋት እየተናገረች ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በቤተ ሰቤ ተከብቤ ነው ያለሁት፤ እነርሱ ስላሉ ምንም የሚጐድለኝ የለም››
2 Kings 4:14
ጥራት
‹‹እንድትመጣ ንገራት››
በጠራትም ጊዜ
‹‹እንድትመጣ ግያዝ ሲነግራት››
እበራፉ ላይ
መተላለፊያው ላይ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መውጫ መግቢያው ላይ››
ልጅ
‹‹ወንድ ልጅ››
ጌታዬ የእግዚአብሔር ሰው
ሴትዮዋ በእነዚህ ሁለት መጠሪያዎች የተጠቀመችው ኤልሳዕን ለማመልከት ነው።
አገልጋይህ
ለእርሱ ያለትን አክብሮት ለማሳየት ሴትዮዋ ራሷን አገልጋይህ አለች።
2 Kings 4:17
የዛሬ ዓመት በዚሁ ጊዜ
‹‹በሚቀጥለው ዓመት በዚሁ ጊዜ››
ራሴን! ራሴን!
ሕመም ስለ ነበረው ልጁ ይህን ተናገረ። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራሴን አሞኛል! ራሴን አሞኛል!››
እስከ እኩለ ቀን ድረስ በእናቱ ጉልበት ላይ ተቀመጠ፤ ከዚያም ሞተ
እዚህ ላይ ጉልበት ያለው የሴትዮዋን ጭን ነው። እስኪሞት ድረስ ልጁ ጭኗ ላይ

ነበር። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኩለ ቀን እስኪሆንና እስኪሞት ድረስ ጭኗ ላይ አደረገችው››
2 Kings 4:21
የእግዚአብሔር ሰው
‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››
ወደ እግዚአብሔር ሰው በፍጥነት ደርሼ እንድመለስ
ሴትዮዋ ኤልሳዕን ለማግኘት እንደምትሄድ እንጂ፣ የምትሄደው ልጇቸው ስለ ሞተ መሆኑን አልተናገረችም። ይህንን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቶሎ ወደ እግዚአብሔር ሰው ሄጄ፣ ቶሎ እንድመጣ› ልጃቸው መሞቱን ግን ለባልዋ አልተናገረችም››
2 Kings 4:23
ደህና ነው
ሴትዮዋ ይህን ያለችው ባልዋ እንደ ነገረችው ካደረገ እንደዚያ እንደሚሆን ስላወቀች ነው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ የምጠይቅህን ካደረግህ ደህና ይሆናል››
አህያውን ጭና
አህያውን የጫነው አገልጋዩ እንጂ፣ ሴትዮዋ ራሷ አይደለችም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አገልጋዩ አህያውን ጫነላት››
2 Kings 4:25
ተነሥታ የእግዚአብሔር ሰው ወዳለበት ቀርሜሎስ ተራራ ሄደች
‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ ወደ ነበረበት የቀርሜሎስ ተራራ ሄደች››
የእግዚአብሔር ሰው በሩቅ ሲያያት
‹‹ገና ሩቅ እያለች ኤልሳዕ ስትመጣ አያት››
ደህና ነው
‹‹መልካም ነው›› ወይም፣ ‹‹አዎን፣ ሁሉም ደህና ነው››
2 Kings 4:27
ተራራው
‹‹የቀርሜሎስ ተራራ››
እግሩ ላይ ተጠመጠመች
ይህም ማለት ተንበረከከች ወይም እፊቱ መሬት ላይ ተጋድማ እግሩን አጥብቃ ያዘች ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እፊቱ መሬት ላይ ወድቃ በእጆቿ እግሩን ያዘች››
ያህዌ ይህን ለምን ከእኔ እንደ ሰወረውና እንዳልነገረኝ አልገባኝም
ኤልሳዕ ሴትዮዋ ምን ያህል እንዳዘነች ማየት ችሏል፤ ያህዌ ግን የችግሯን ምክንያት አልገለጸለትም።
2 Kings 4:28
ጌታዬ፤ ለመሆኑ እኔ ልጅ እንድትሰጠኝ ጠይቄህ ነበርን? አትል ተስፋ እንዳትሰጠኝ አላልሁህምን?››
ሴትዮዋ ይህን የጠየቀችው በሆነው ነገር ምን ያህል እንደ ታወከች ለማሳየት ነበር። ወንድ ልጅ እንደምትወልድ በነገራት ጊዜ ከኤልሳዕ ጋር የተነጋገረችውን እየተናገረች ነው። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንዳትዋሸኝ ነገርሁህ እንጂ፣ ልጅ እንድትሰጠኝ አልጠየቅሁህም!››
እንግዲህ ወገብህን ታጠቅ
‹ለጉዞ ተዘጋጅ››
ሰው ብታገኝ ሰላም አትበል፤ ማንም ሰው ሰላም ቢልህ መልስ አትስጥ
ኤልሳዕ ግያዝ በተቻለ መጠን ቶሎ እንዲሄድ፣ ከሰው ጋር ለመነጋገር መንገድ ላይ እንዳይቆም ፈልጓል።
2 Kings 4:30
ሕያው ያህዌን በሕያው ነፍስህም
‹‹ሕያው ያህዌን፣ በሕያው ነፍስህም›› የሚለው እናትየው እየማለች እንደ ሆነ ያመለክታል። እናትየው የያህዌንና የኤልሳዕን ሕያውነት ከምትናገረው ነገር እርግጠኝነት ጋር አነጻጽራለች። ይህ መሐላ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ እምላለሁ››
ልጁ ግን አይናገርም ወይም አይሰማም ነበር
ይህ ማለት ሕይወት አልነበረውም ማለት ነው። ይህንን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ልጁ ግን ምንም የሕይወት ምልክት አላሳየም››
ልጁ አልነቃም
እዚህ ላይ እንቅልፍ ከሞት ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጒም ‹‹እንደ ሞተ ነው››
2 Kings 4:32
ኤልሳዕ ወደ ውስጥ ገባ፤ ከዚያም በሩን በራሱና በልጁ ላይ ዘጋ
‹‹ኤልሳዕ ልጁ ተኝቶ ወደ ነበረበት ክፍል ገብቶ በሩን ዘጋ››
2 Kings 4:35
በልጁ ላይ ተጋደመ
‹‹ልጁ ላይ ተዘረጋ››
ሱነማዪቱ
‹‹ሱነማዪቱ ሴት››
በእግሩ ላይ ወደቀች፤ በምድርም ላይ ተደፋች
የታላቅ አድናቆትና አክብሮት ምልክት በሆነ ሁኔታ ሴትዮዋ ኤልሳዕ ፊት አጐነበሰች። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ምስጋናዋን ለመግለጽ ፊትዋን ወደ መሬት አድርጋ ኤልሳዕ ፊት አጐነበሰች››
2 Kings 4:38
የነቢያት ልጆች
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እነዚህ ልጆች የነቢያት ስብስብ እንጂ፣ በቀጥታ የነቢያት ልጆች አይደለም። 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ይህን እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። ‹‹የነቢያት ስብስብ››
ወጥ
ብዙውን ጊዜ ይህ ማሰሮ ውስጥ የሚቀቀል የሥጋና የአትክልት ምግብ ነው።
ዱር በቀል ሐረግ
ይህ አትክልት ዱር የሚበቅል ማለት ማንም ያልተከለው ነበር።
በልብሱ ሙሉ ይዞ
በእጁ መያዝ ከሚችለው በላይ ብዙ የዱር ሐረግ መያዝ የሚችልበት ቦታ ለማግኘት ሲል የቀሚሱን ጠርዝ እስከ ወገቡ ድረስ አጠፈ።
ምን እንደ ሆነ ግን ማንም አላወቀም
ምን ዐይነት የዱር ሐረግ እንደ ሆነ ባለማወቃቸው ለመብል መልካም መሆን አለመሆኑን አላወቁም። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ነገር ግን ለመብል መልካም መሆን አለመሆኑን አላወቁም።
2 Kings 4:40
ወጡ ወጣ
‹‹ወጡን ሳህን ላይ አውጡት››
ምንቸቱ ውስጥ ሞት አለ
ይህ ማለት ምንቸቱ ውስጥ የሚገድል ነገር አለ ማለት እንጂ፣ አንዳች የሞተ ነገር ምንቸቱ ውስጥ አለ ማለት አይደለም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ምንቸቱ ውስጥ እኛን የሚገድል ነገር አለ››
በምንቸቱ ውስጥ ጨመረው
‹‹ምንቸቱ ውስጥ ወዳለው ወጥ ጨመረው››
ለሰዎቹ አቀረበላቸው
‹‹ሰዎቹ እንዲበሉት አቀረበላቸው››
2 Kings 4:42
በአልሻሊሻ
ይህ የከተማ ስም ነው።
ሃያ ሙልሙል
‹‹20 ሙልሙል››
ከበኩራቱ ፍሬ
‹‹መጀመሪያ ከተገኘው ፍሬ የተጋገረ››
የእሸት ዛላ
‹‹ትኩስ እሸት›› ይህ ከአዲሱ መከር የተገኘ እህል ማለት ነው።
ይህን እንዴት አድርጌ ለመቶ ሰው አቀርባለሁ?
ሰውየው ይህን የጠየቀው ለመቶ ሰው የሚበቃ እንጀራ አለመኖሩን ለማመልከት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መቶ ሰው ለመመገብ አይበቃም››
መቶ ሰው
‹‹100 ሰው››
የያህዌ ቃል
እዚህ ላይ ያህዌ ከተናገረው ጋር ተያይዞአል። ይህ ሐረግ ያህዌ ራሱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ››

Chapter 5


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

2 Kings 5:1
በጌታው ዘንድ
‹‹ዐይን›› ንጉሡ ስለ አንዳች ነገር የሚያስበውን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በንጉሡ አስተሳሰብ››
ያህዌ በዚህ ሰው አማካይነት ለሶርያ ድል ስለ ሰጠ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሶርያ›› የሶርያ ሰራዊትን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በንዕማን በኩል ያህዌ ለሶርያ ሰራዊት ድል ሰጥቶ ነበር››
ሶርያውያን ወጥተው ሄዱ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሶርያውያን›› የሶርያን ሰራዊት ያመለክታል፡፡
በቡድን ዘረፉ
‹‹የጥቂት ሰዎች ጥቃት›› እንዲህ ማት በቁጥር ጥቂት ሆነው ጠላትን ለማጥቃት ሄዱ ማለት ነው፡፡
2 Kings 5:3
ልጃገረዲቱ ለእመቤትዋ እንዲህ አለች
በሶርያውያን ሰራዊት ከእስራኤል ተማርካ የነበረችው ልጃገረድ ለንዕማን ሚስት እንዲህ አለች፡፡
ጌታዬ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ጌታዬ›› ንዕማንን ያመለክታል፡፡
2 Kings 5:5
ደብዳቤ እጽፋለሁ
ንጉሡ ለንዕን ለእስራኤል ንጉሥ የሚወስደው ደብዳቤ ሊሰጠው ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአንተ በኩል ደብዳቤ እልካለሁ››
ዐሥር መክሊት ብር፤ ስድስት ሺህ ሰቅል ወርቅ
‹‹10 መክሊት ብር፤ 6,000 ሰቅል ወርቅ›› ይህን በዘመኑ ልኬት መዳፍ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹330 ኪሎ ግራም ወርቅ፤ 6,000 ሰቅል ወርቅ››
ዐሥር ሙሉ ልብስ ይዞ ሄደ
ይህ ከሶርያ ንጉሥ ለእስራኤል ንጉሥ የተላከ ስጦታ ነበር፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእስራኤል ንጉሥ ስጦታ ዐሥር ሙሉ ልብስ ይዞ ሄደ››
2 Kings 5:7
ልብሱን ቀደደ
ሰዎች ታላቅ ሐዘን ውስጥ ሲሆኑ፣ ብዙ ጊዜ ልብሳቸውን ይቀደዱ ነበር፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማዘኑን ለማሳየት ልብሱን ቀደደ››
ከለምጹ እንድፈውሰው ይህን ሰው ወደ እኔ መላኩ እኔ ገድዬ ማዳን የምችል አምላክ ሆኜ ነውን?
ንጉሡ ይህን የጠየቀው የሶርያ ንጉሥ ጥያቄ በጣም የሚያናድድና እርሱ ማድረግ የማይችለው መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ እኔ በሞትና በሕይወት ላይ ሥልጣን ያለኝ አምላክ እንደ ሆንሁ ሳያስብ አልቀረም፤ ይህን ሰው ከለምጹ እንድፈውሰው ይፈልጋል፤ እኔ ግን ያን ማድረግ አልችልም››
እንግዲህ ጠብ ሲፈልገኝ እዩ
የእስራኤል ንጉሥ የደብዳቤው እውነተኛ ምክንያት ንዕማን እንዲፈወስ መጠየቅ መሆኑን አላመነም፤ ዋናው ምክንያት ጠብ ፍለጋ መሆኑን ነው ያሰበው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእኔ ጋር ጠብ ለመፍጠር ሰበብ እየፈለገ ይመስላል››
2 Kings 5:8
አጠቃላይ መረጃ
ኤልሳዕ ንዕማንን በተመለከተ ከእስራኤል ንጉሥ ጋር እየተነጋገረ ነው፡፡
ልብስህን ለምን ቀደድህ?
ኤልሳዕ ይህን የጠየቀው ይህን ያህል መናደድና ልብሱንም መቅደድ እንዳልነበረበት አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህን ያህል መናደድና ልብስህንም መቅደድ አልነበረብህም››
ሥጋህ ይፈወሳል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል፡፡ ‹‹ሥጋህ ደህና ይሆናል››
አንተም ትነጻለህ
ይህም ማለት ከእንግዲህ ርኩስ አይሆንም ማለት ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት በመንፈሳዊ ደረጃ ንጹሕ ያልሆነ ወይም ተቀባይነት የሌለው ሰው በአካላዊ ደረጃም ንጹሕ እንዳይደለ ይታሰብ ነበር፡፡ ለምጽ ያለበትን ሰው እግዚአብሔር እንደ ርኩስ ወይም ንጹሕ እንዳልሆነ ነበር የሚያየው፡፡
2 Kings 5:11
እነሆ
ይህ ቀጥሎ ለሚነገረው ነገር የሰውን ትኩረት ለመሳብ የሚነገር ቃል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አድምጥ››
የያህዌን ስም
እዚህ ላይ ያህዌ በስሙ ተጠርቷል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ››
ቦታው ላይ
‹‹ቆዳዬ ላይ በሽታው ያለበት ቦታ›› ወይም፣ ‹‹ለምጹ ያለበት ላይ››
አባናና ፋርፋር ከየትኞቹም የእስራኤል ውሆች አይሻሉምን?
ንዕማን ይህን የጠየቀው አባናና ፋርፋር ከዮርዳኖስ ወንዝ የተሻሉ መሆናቸውን አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአገሬ በሶርያ ያሉት የአባናና የፋርፋር ወንዞች በእስራኤል ካሉት የትኞቹም ወንዞች በጣም የተሻሉ ናቸው››
አባናና ፋርፋር
እነዚህ የወንዝ ስሞች ናቸው፡፡
በእነርሱ ታጥቤ መንጻት አልችልምን?
ንዕማን ይህን የጠየቀው በቀላሉ በሌሎች ወንዞች መታጠብ እንደሚችል አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ በእነዚህ ወንዞች መታጠብ በዮርዳኖስ እንደ መታጠብ ሊፈውሰው እንደሚችል ያምናል፡፡ ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእነዚህ ወንዞች ታጥቤ መፈወስ አለብኝ›› ወይም፣ ‹‹በእነዚህ ወንዞች ታጥቤ በቀላሉ መፈወስ እችላለሁ!››
በቁጣ ተመልሶ ሄደ››
‹‹በጣም ተቆጥቶ ሄደ››
2 Kings 5:13
አባቴ
‹‹አባቴ›› ወይም፣ ‹‹ጌታው›› ብለው በመጥራት አገልጋዮቹ ያላቸውን ክብር እያሳዩ ነው፡፡
አታደርገውም ነበርን?
አገልጋዮቹ ይህን የተናገሩት በጥንቃቄ ንዕማንን ለመገሠጽ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያንን በሚገባ ማድረግ ነበረብህ!››
ቢልህ ምን አስቸገረህ?
ከባዱን ትእዛዝ ለመፈጸም ፈቃደኛ የመሆኑን ያህል ቀላሉን ለመፈጸም የበለጠ ፈቃደኛ መሆን ይገባው እንደ ነበር አጽንዖት ለመስጠት አገልጋዩ በንጽጽር አቅርቧል፡፡ ‹‹ያንን ለመፈጸም ምንኛ መታዘዝ ይገባህ ነበር›› ወይም፣ ‹‹ከዚያ የበለጠስ ቢሆን መታዘዝ አልነበረብህም?››
ታዲያ፣ ‹‹ታጠብና ንጻ›› ቢልህ ምኑ አስቸገረህ?
አገልጋዩ ይህን የጠየቀው ኤልሳዕ ያዘዘውን ማድረግ እንዳለበት አጽንዖት ሰጥቶ ለንዕማን ለመናገር ነው፡፡ ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ‹‹ታጠብና ንጻ›› ሲልህ ከዚያ የበለጠ እንኳ መታዘዝ ነበረብህ››
የእግዚአብሔር ሰው
‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››
ሥጋውም እንደ ትንሽ ልጅ ሥጋ ሆነ፤ ነጻም
ይህ የሚናገረው ከተፈወሰ በኋላ ቆዳውን ከሕፃን ልጅ ጋር በማነጻጸር የንዕማን ቆዳ ምን ያህል ለስላሳ እንደ ሆነ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሥጋው ተፈወሰ፤ እንደ አንድ ሕፃን ልጅ ቆዳው ለሰለሰ›› ወይም፣ ‹‹ቆዳው ደህና ሆነ፣ እንደ ሕፃን ልጅ ቆዳ ለስላሳ ሆነ››
ሥጋው
‹‹ቆዳው›› ተፈወሰ ይህን በሌላ መንገድ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለምጹ ጠፋ››
2 Kings 5:15
እነሆ
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረትን ለመሳብ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አድምጥ››
በእስራኤል እንጂ በዓለም ሁሉ ሌላ አምላክ አለመኖሩን ተረድቻለሁ
‹‹በምድር ሁሉ ብቸኛው አምላክ ያለው እስራኤል ውስጥ ነው፡፡››
በፊቱ የቆየሁት ሕያው ያህዌን
‹‹በፊቱ የቆምሁት ያህዌ ሕያው መሆኑን የማውቀውን ያህል›› እዚህ ላይ ኤልሳዕ ያህዌ ሕያው የመሆኑን እርግጠኝነት ከንዕማን ስጦታ ለመቀበልም የዚያን ያህል ፈቃደኛ ካለ መሆኑ ጋር ያነጻጽራል፡፡ ይህ መሐላ የመፈጸም መንገድ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ሕያው የመሆኑን ያህል፣ እኔም ከአንተ ምንም አልቀበልም››
በፊቱ የቆምሁት
እዚህ ላይ ያህዌን ማገልገል፣ በፊቱ መቆም ማለት እንደ ሆነ ተነግሮአል፡፡ አማራጭ

ትርጒም፣ ‹‹የማገለግለው››
ምንም ነገር አልቀበልም
ይህ ስጦታ አልቀበልም ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ምንም ስጦታ አልቀበልም››
2 Kings 5:17
ከሆነ
በውስጠ ታዋቂነት የሚታወቀውን መረጃ ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያመጣሁልህን ስጦታ የማትቀበል ከሆነ››
ለባርያህ ይሰጠው
ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስጠኝ››
ሁለት የበቅሎ ጭነት ዐፈር
ንዕማን ወደ አገሩ የሚወሰድ ሁለት ጭነት ዐፈር ጠይቋል። ከዚያ በኃላ ዐፈሩ ላይ መሠዊያ ይሠራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለያህዌ መሠውያ እንድሠራበት ሁለት የበቅሎ ጭነት የሚያህል ዐፈር ከእስራኤል ይሰጠኝ››
አገልጋይህ
እርሱን ለማክበር ንዕማን ራሱን የኤልሳዕ አገልጋይ በማለት ይጠራል።
ለያህዌ እንጂ ለሌላ አምላክ የሚቃጠል ወይም ሌላ መሥዋዕት ስለማላቀርብ
ይህን በአዎንታዊ መልኩ ማስቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእንግዲህ ለያህዌ እንጂ ለሌላ አምላክ የሚቃጠል ወይም ሌላ መሥዋዕት አላቀርበም›› ወይም ‹‹የሚቃጠል ወይም ሌላ መሥዋዕት የማቀርበው ለያህዌ ብቻ ነው።››
ጌታዬ
ይህ የሚያመለክተው ንዕማን የሚያገለግለውን የሶርያንን ንጉሥ ነው
ክንዴን ሲደገፍ
‹‹ክንዴ ላይ ደገፍ ሲል›› ይህ ማለት ያረጀ ወይም ታማሚ ሰው ስለ ነበር ለሬሞን በሚሰግድበት ጊዜ ንዕማን ንጉሡን ይረዳው ነበር ማለት ነው።
በሰላም ሂድ
‹‹ወደ ቤትህ ሂድ፤ አትጨነቅ›› ወይም፣ ‹‹ምንም ሳትፈራ ሂድ››
2 Kings 5:20
እንደ ሄደ
‹‹ንዕማን ሄደ››
ግያዝ
2 ነገሥት 4፥12 ላይ የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
እነሆ
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው ቀጥሎ ለሚነገረው ነገር ትኩረት ለማሳብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አድምጥ››
ሶርያዊው ንዕማን ያመጣውን አለመቀበሉ ደግሞ አይደል
‹‹ሶርያዊው ንዕማንን በነጻ አሰናብቶታል››
አለመቀበል
‹‹ምንም ሳይቀበል››
ከእጁ
እዚህ ላይ ንዕማንን ከእጁ በሚል ቃል የገለጸው ስጦታን በሚያመላክት መልኩ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእርሱ››
ሕያው ያህዌን
‹‹ያህዌ ሕያው እንደ ሆነ›› እዚህ ላይ ግያዝ ያህዌ ሕያው የመሆኑን እርግጠኝነት፣ እርሱም ያሰበውን በእርግጠኝነት ከማድረጉ ጋር አነጻጽሮታል። ይህ መሐላ ማድረግ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ሕያው እንደ ሆነ እኔም ቃሌን እሰጣለሁ››
ከነቢያት ልጆች
ይህ ማለት የነቢያት ስብስብ እንጂ፣ በቀጥታ የነቢያት ልጆች ናቸው ማለት አይደለም። 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ይህን ሐረግ እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከነቢያት መካከል››
እባክህ አንድ መክሊት ብርና ሁለት ሙሉ ልብስ ስጣቸው
ለነቢያት ወስዶ እንዲሰጣቸው እነዚህን ነገሮች ለእርሱ እንዲሰጠው ግያዝ ንዕማንን እየጠየቀው ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለእነርሱ እንድሰጥ እባክህን አንድ መክሊት ብርና ሁለት ሙሉ ልብስ ስጠኝ››
እነሆ
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው ቀጥሎ ለሚነገረው ነገር ትኩረትን ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አድምጥ››
አንድ መክሊት ብር
ይህን በዘመኑ መለኪያ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹33 ኪሎ ግራም ብር››
2 Kings 5:23
ሁለት መክሊት
ይህን በዘመኑ መለኪያ መጻፍ ይቻላል። ይህ መክሊት ከብር የተሠራ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሁለት የብር መክሊት›› ወይም፣ ‹‹66 ኪሎ ግራም ብር››
በሁለት አደረገ
‹‹ሰጣቸው››
ንዕማን ግያዝን አስጨንቆ ለመነው
ስጦታዎቹን እንዲወስድ ንዕማን አጥብቆ ጠየቀው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስጦታዎቹን እንዲወስድ ንዕማን ግያዝን አጥብቆ ለመነው››
አገልጋይህ
እዚህ ላይ ግያዝ የንዕማን አገልጋይ መሆኑን እየተናገረ ነው።
2 Kings 5:26
ያ ሰው ሊገናኝህ ከሰረገላው ሲወርድ መንፈሴ ከአንተ ጋር አልሄደምን?
ኤልሳዕ ይህን የጠየቀው ግያዝ ያደረገውን እንዲያይ ያህዌ እንዳስቻለው አጽንኦት ለመስጠት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንዕማን ሰረገላውን አቁሞ ከአንተ ጋር ሲነጋገር መንፈሴ እንዳየህ መገንዘብ ነበረብህ››
ጊዜው ገንዘብና... ሴት አገልጋይ የሚቀበሉበት ነውን?
ኤልሳዕ ይህን የጠየቀው፣ ይህ ስጦታ የሚቀበሉበት ጊዜ አለመሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን እንደ ዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህ ገንዘብና... የሴት አገልጋይ የሚቀበሉበት ጊዜ አይደለም››
የንዕማን ለምጽ በአንተና በዘርህ ላይ ይጣበቃል
ይህ የንዕማን ለምጽ ከእርሱ ተወስዶ ለግያዝ የተሰጠው በሚመስል መልኩ ግያዝና ዘሩ የንዕማንን ለምጽ እንደሚወስዱ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንዕማን ለምጽ እንደ ነበረው አንተና ዘርህም ለምጻም ትሆናላችሁ››
ከዚያም ግያዝ ከፊቱ ወጣ
‹‹ከፊቱ›› የሚለው ሐረግ ኤልሳዕ እርሱን ማየት ከሚችልበት አካባቢ ማለት ነው። ኤልሳዕ ከነበረበት ክፍል ወጥቶ ሄደ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ግያዝ ክፍሉን ለቅቆ ሲወጣ...››
እንደ በረዶ ነጭ ሆነ
ለምጽ ቆዳን ነጭ ያደርጋል። እዚህ ላይ የግያዝ ለምጽ ከበረዶ ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጒም፣ ቆዳው እንደ በረዶ ነጭ ሆነ››

---

Chapter 6
2 Kings 6:1
የነቢያት ልጆች
እነዚህ የነቢያት ስብስብ እንጂ፣ የነቢያት ልጆች ናቸው ማለት አይደለም። 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ እንሂድ››
አገልጋዮችህ
እዚህ ላይ የነቢያት ልጆች የተባሉት ነቢያት ለእርሱ ክብር ለማሳየት የኤልሳዕ አገልጋዮች መሆናቸውን ተናግረዋል።
2 Kings 6:4
አጠቃላይ መረጃ
ኤልሳዕ ዛፎች ለመቁረጥ ከነቢያት ጋር ሄደ።
የመጥረቢያው ራስ ውሃ ውስጥ ገባ
የመጥረቢያ ራስ የሚያመለክተው ብረቱን ነው። ይህም ማለት የመጥረቢያው ብረት ከእጀታው ተለይቶ ውሃ ውስጥ ወድቋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የመጥረቢያው ብረት ከእጀታው ተለይቶ ውሃ ውስጥ ወደቀ››
አዬ ጉድ፤ አዬ ጉድ
ይህ ሰው እንዲህ ያለው ምን ያል መደንገጡን ለማሳየት ነው። በአንተ ቋንቋ ይህን የምትገልጽበት ቃል ካለህ ተጠቀምበት።
የተውሶ ነበር
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የተዋስሁት ነበር››
2 Kings 6:6
የእግዚአብሔርም ሰው አለ

‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ ጠየቀ››
እንጨት ቆርጦ ወደ ውሃው ውስጥ በመጣል የመጥረቢያው ብረት እንዲንሳፈፍ አደረገ
ተአምር ለማድረግ እግዚአብሔር በኤልሳዕ ተጠቀመ። የመጥረቢያው ብረት ውሃው ላይ ተንሳፈፈ፤ ነቢዩ እስኪወስደው እዚያው ቆየ።
ብረቱ እንዲንሳፈፍ አደረገ
‹‹ብረቱ ተንሳፈፈ››
ብረቱ
‹‹የመጥረቢያው ራስ›› የመጥረቢያው ራስ ከብረት የተሠራ ነበር።
2 Kings 6:8
በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ከእስራኤል ጋር ይዋጋ ነበር
‹‹የሶርያ ንጉሥ ከእስራኤል ጋር ይዋጋ በነበረ ጊዜ››
አሁን
ይህ ቃል እዚህ ቦታ ጥቅም ላይ የዋለው የዋናውን ታሪክ ፍሰት ገታ ለማድረግ ነው። እዚህ ላይ ጸሐፊው ስለ አዲስ የታሪኩ ክፍል መናገር ይጀምራል።
‹‹በዚህ በዚህ ቦታ እሰፍራለሁ›› አለ
የሶርያ ንጉሥ የት እንደሚሰፍር ለአማካሪዎቹ እየተናገረ ነበር። ‹‹በዚህ በዚህ›› የሚሉት ሐረጐች ቦታውን በጽሑፍ ባለ ማስፈር ስለ አካባቢው መረጃ የሚሰጡ ናቸው። ይህን ሐረግ በቋንቋህ በትክክል መተርጐም የማይቻል ከሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ አነጋገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚሰፍርበት ቦታ የት እንደ ሆነ ነገራቸው››
የእግዚአብሔር ሰው
‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››
ሶርያውያን በዚያ ታች ወርደዋልና በዚያ በኩል እንዳታልፍ ተጠንቀቅ
ሶርያውያን የሰፈሩበትን ትክክለኛ ቦታ ኤልሳዕ አወቀ፤ ራሳቸውን ለአደጋ እንዳያጋልጡ የእስራኤልን ንጉሥና ወታደሮቹን አስጠነቀቀ።
2 Kings 6:10
የእግዚአብሔር ሰው የነገረውን ቦታ አስቃኘ
ይህ የሚያመለክተው 2 ነገሥት 6፥9 ላይ ወደዚያ እንዳይሄድ ኤልሳዕ ንጉሡን ያስጠነቀቀውን ቦታ ነው።
እንደዚህ ካሉት ቦታዎች ራሱን እንዲጠብቅ ከአንድ ሁለት ጊዜ በላይ አስጠነቀቀው
አደጋው ከመምጣቱ በፊት ሕዝቡን እንዲያስጠነቅቅ፣ የሶርያ ሰራዊት የሚያጠቃበትን ቦታ ኤልሳዕ ለንጉሡ ይነግረው ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኤልሳዕ የእስራኤልን ንጉሥ ብዙ ጊዜ በዚህ መልኩ አስጠነቀቀው፤ እስራኤላውያንም ከአደጋ ተጠበቁ››
ከእስራኤል ንጉሥ ጋር የተወዳጀ እንዳለ ለምን አትነግሩኝም?
የሶርያ ንጉሥ ለእስራኤል ንጉሥ መረጃ የሚሰጥ ሰው ወታደሮቹ መካከል ሊኖር እንደሚችል አሰበ። ያ ከሐዲ ማን እንደ ሆነ ለማወቅ ይህን ጠየቀ። ይህን በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእስራኤል ንጉሥ እየሠራ ያለው ማን እንደ ሆነ ንገሩኝ!›› ወይም፣ ‹‹ዕቅዶቻችንን ለእስራኤል ንጉሥ የሚናገረው ማንኛችሁ እንደ ሆናችሁ ንገሩኝ?››
ከእስራኤል ንጉሥ ጋር
ይህም ማለት ወዳጅ የሆነ ሰው ማለት ነው። እዚህ ላይ ግን ለእስራኤል ንጉሥ መረጃ የሚሰጥ ሰው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤልን ንጉሥ የሚረዳ›› ወይም፣ ‹‹ለእስራኤል ንጉሥ ታማኝ የሆነ››
2 Kings 6:12
አላደረግንም
አገልጋዮቹ ከንጉሡ ወታደሮች አንዱ እንኳ ለእስራኤል ንጉሥ መረጃ እንዳልሰጡ ተናገሩ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኛ እንዲህ አላደረግንም››
ንጉሥ ጌታዬ
ይህ የሚያመለክተው የሦርያን ንጉሥ ነው።
አንተ በእልፍኝህ ሆነህ እንኳ የምትናገረውን
‹‹በግል መኝታ ቤትህ ውስጥ እንኳ ሆነህ የምትናገረውን››
ሰዎች ልኬ እንዳስይዘው
ንጉሡ ኤልሳዕን የሚይዙ ሰዎች መላክ ዐቅዶአል። እርሱ ራሱ ሊይዘው አላቀደም አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚይዙትን ሰዎች እልካለሁ››
እነሆ
እዚህ ላይ ቀጥሎ ለሚነገረው ነገር የንጉሡን ትኩረት ለመሳብ ይህ ቃል ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስማ››
በዶታይን ይገኛል
‹‹ኤልሳዕ በዶታይን ነው››
ዶታይን
ይህ የከተማ ስም ነው።
2 Kings 6:14
ስለዚህ ንጉሡ
ይህ የሚናገረው ስለ ሶርያ ንጉሥ ነው።
የእግዚአብሔር ሰው
‹‹ኤልሳዕ›› ወይም፣ ‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››
እነሆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› የሚለው ቃል ባየው ነገር አገልጋዩ መደነቁን ያመለክታል። ‹‹ጠዋት በማለዳ ተነሥቶ ወደ ውጭ ሲወጣ… አየ።
አገልጋዩ እንዲህ አለ
አገልጋዩ ያየውን ለንጉሡ ለመንገር ተመልሶ ገባ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አገልጋዩም ወደ ውስጥ ተመልሶ ኤልሳዕን…››
ከእኛ ጋር ያሉት ከእነርሱ ጋር ካሉት ይበልጣሉ
በጦርነት ጊዜ ከሰዎች ጋር መሆን፣ ከእነርሱ ጋር ሆኖ መዋጋት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጦርነት ከእኛ ጋር ያሉት ከእነርሱ ጋር ካሉት ይበልጣሉ››
2 Kings 6:17
ያይ ዘንድ እባክህ ዐይኖቹን ክፈትለት
አገልጋዩ ሌሎች ሰዎች ማየት ያልቻሉትን ማለት በዙሪያቸው ያሉትን የእሳት ፈረሶችና ሰረገሎች ማየት እንዲችል ኤልሳዕ እየጠየቀ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲያይ አድርገው››
እነሆም አየ
‹‹ማየት ቻለ፤ ያየውም››
እነሆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› የሚለው ባየው ነገር አገልጋዩ መደነቁን ያመለክታል። የእሳት ፈረሶችና ሰረገሎች… ተራራውን ሞልተውት ነበር። ‹‹ተራራው በፈረሶች ተሸፍኖ ነበር››
በኤልሳዕ ዙሪያ
ይህ ኤልሳዕ የነበረበትን ከተማ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኤልሳዕ በነበረበት ከተማ ዙሪያ››
ይህን ሕዝብ
ይህ የሚናገረው ስለ ሶርያ ወታደሮች ነው።
በዕውርነት ምታው
‹‹እነዚህን ሰዎች ዕውር አድርጋቸው›› ይህ የሚያመለክተው ያህዌ እንዳያዩ እንዳደረጋቸው ነው።
መንገዱ በዚህ አይደለም፤ ከተማዪቱም ይህች አይደለችም
የሚፈልጉት ከተማ ውስጥ አለመሆናቸውን በመናገር ኤልሳዕ የሶርያን ወታደሮች ግራ እያጋባቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መንገዱ ይህ አይደለም፤ የምትፈልጉትም ከተማ ይህ አይደለም››
2 Kings 6:20
በዚያን ጊዜ
‹‹እንዲህም ሆነ›› ወይም፣ ‹‹ያኔ›› እንዲያዩ የእነዚህን ሰዎች ዐይን ክፈት
ኤልሳዕ ሰዎቹ እንደ ገና እንዲያዩ ያህዌን ጠየቀ።
አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ ሰዎች እንዲያዩ አድርግ››
ያህዌም ዐይኖቻቸውን ከፈተ… አዩ
ያህዌ ሰዎቹ እንደ ገና እንዲያዩ ፈቀደ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ዕውርነታቸውን አነሣ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ አጥርተው እንዲያዩ ፈቀደ››
እነሆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› የሚለው ባዩት ነገር ሶርያውያን መደነቃቸውን ያመለክታል።
ባያቸው ጊዜ
‹‹የሶርያ ወታደሮችን ባያቸው ጊዜ››
አባቴ ሆይ
ንጉሡ ነቢዩ ኤልሳዕን እያናገረ ነው፤ አክብሮቱን ለማሳየት፣ ‹‹አባቴ›› አለው።
ልግደላቸውን? ልፍጃቸውን?
እዚህ ላይ የእስራኤል ንጉሥ ስለ ወታደሮቹ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህን የጠላት ወታደሮች እንዲገድሉ ወታደሮቼን ልዘዛቸውን?››
2 Kings 6:22
ኤልሳዕም መለሰ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ጥያቄ መልስ እየሰጠ ነው።
ለመሆኑ በሰይፍህና በቀስትህ የማረክሃቸውን ትገድላቸው ዘንድ ይገባሃልን?
ኤልሳዕ ይህን የጠየቀው ንጉሡ እነዚህን ሰዎች እንዳይገድላቸው ለመናገር ነው። ‹‹ሰይፍ›› እና፣ ‹‹ቀስት›› በጦርነት ጊዜ ወታደሮች የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ናቸው። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጦርነት የያዝሃቸውን ሰዎች እንደማትገድል ሁሉ እነዚህንም ሰዎች መግደል የለብህም››
እንዲበሉና እንዲጠጡ እንጀራና ውሃ አቅርብላቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እንጀራ›› በአጠቃላይ ምግብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚበሉትን እንጀራ፣ የሚጠጡትን ውሃ ስጣቸው››
ወደ ጌታቸውም ይሂዱ
ይህ የሚያመለክተው የሶርያን ንጉሥ ነው።
ስለዚህ ንጉሡ ብዙ ምግብ አቀረበላቸው
ምግብ እንዲያቀርቡ ንጉሡ አገልጋዮቹን አዘዘ። እርሱ ራሱ ምግቡን አላዘጋጀም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ ንጉሡ ብዙ ምግብ እንዲያቀርቡላቸው አገልጋዮቹን አዘዘ።
አደጋ ጣዮች
‹‹እነዚያ ሰዎች››
የእስራኤልን ምድር ለመውረር ከዚያ በኋላ አልተመለሱም
ይህ ማለት ለረጅም ጊዜ እስራኤልን አላጠቁም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤልን ምድር ማጥቃታቸውን ለረጅም ጊዜ አቆሙ››
2 Kings 6:24
ቤንሐዳድ
የሶርያ ንጉሥ ስም። ስሙ፣ ‹‹የሐዳድ ልጅ›› ማለት ነው።
ሰማርያን አጠቃ
ንጉሡና ሰራዊቱ ሰማርያን አጠቁ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰማርያን አጠቁ››
እነሆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› የሚለው ቃል ቀጥሎ ለምናገኘው መረጃ ያነቃናል።
የአንድ አህያ ጭንቅላት... ተሸጠ
ይህን በሌላ መልክ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአንድ አህያ ጭንቅላት በ... ተሸጠ››
በሰማንያ ሰቅል ብር
‹‹በ80 ሰቅል ብር››
ሩብ
እኩል መጠን ካላቸው አራት ክፍሎች አንዱ ክፍል አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንድ አራተኛ›› ወይም፣ ‹‹ሩብ›› ወይም ¼
የርግብ ኩስ
‹‹ተሸጠ›› የሚለውን ቃል ካለፈው ሐረግ መረዳት ይቻላል። ያንን እዚህ መድገም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የርግብ ኩስ... ተሸጠ›› ወይም፣ ‹‹የርግብ ኩስ... አወጣ››
በቅጥሩ ላይ በሚመላለስበት ጊዜ
‹‹በከተማው ግንብ ላይ ሲመላለስ››
ጌታዬ
ሴትዮዋ ንጉሡን እንዲህ በማለት የጠራቸው አክብሮትን ለማሳየት ነው።
2 Kings 6:30
ሴቲቱ ያለችውን ቃል ሲሰማ
‹‹እርሷና ሌላዋ ሴት ያደረጉትን ስትናገር ስማ››
ልብሱን ቀደደ
ንጉሡ ምን ያል እንዳዘነ ለማሳየት ከላይ የሚደርበውን መጐናጸፊያ ቀደደ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሐዘን ልብሱን ቀደደ››
በቅጥሩ ላይ በሚመላለስበትም ጊዜ
2 ነገሥት 6፥24 ላይ ሴትየዋ ስትጠራው ንጉሡ በከተማው ግንብ ላይ እየተመላለሰ ነበር፤ አሁንም እንደዚያው እያደረገ ነው።
በውስጥ ማቅ ለብሶ ነበር
ከልብሱ ውስጥ ማቅ መልበሱ ንጉሡ ምን ያህል እንዳዘነና እንደ ታወከ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከውጭ ከለበሰው ሥር ንጉሡ ማቅ ለብሶ ነበር›› ወይም፣ ‹‹በጣም አዝኖ ስለ ነበር ከካባው ሥር ማቅ ለብሶ ነበር››
እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ ከዚህም የባሰ ያምጣብኝ
በሰማርያ ከተማ ከሆነው የተነሣ ነቢዩ ኤልሳዕን ሳይቀጣው እንዲያውም ሳይገድለው ከቀረ እግዚአብሔር እንደሚቀጣው ንጉሡ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ይቅጣኝ ይግደለኝ››
የሳፋጥ ልጅ የኤልሳዕ ራስ ዛሬ በዐንገቱ ላይ ካደረ
ይህ የሚያመለክተው ኤልሳዕ አንገቱ ተቆርጦ እንደሚገደል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዛሬ የሳፋጥ ልጅ የኤልሳዕ አንገት ሳይቆረጥ ቢቀር›› ወይም፣ ‹‹ዛሬ ወታደሮቼ የሳፍጥ ልጅ የኤልሳዕን አንገት ሳይቆርጡ ካደሩ››
2 Kings 6:32
ንጉሡም መልእክተኛ ቀድሞት እንዲሄድ አደረገ
‹‹ከንጉሡ ፊት›› ማለት ከአገልጋዮቹ አንዱ መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ንጉሥ ከአገልጋዮቹ አንዱን እንደ መልእክተኛ ላከ››
የተላከውም ሰው ከመድረሱ በፊት ኤልሳዕ ለሽማግሌዎቹ
እዚህ ላይ ኤልሳዕ የንጉሡ መልእክተኞች ከመምጣታቸው በፊት ለሽማግሌዎቹ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መልእክተኛው ከመድረሱ በፊት ኤልሳዕ ለሽማግሌዎች እንዲህ አለ››
ይህ ነፍሰ ገዳይ ራሴን ለመቁረጥ ሰው መላኩን ታያላችሁ?
እዚህ ላይ ኤልሳዕ ይህን የጠየቀው ወደ ንጉሡ መልእክተኛ ትኩረት ለመሳብና ንጉሡን ለመዝለፍ ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ የነፍሰ ገዳይ ልጅ ራሴን የሚቆርጥ ሰው መላኩን ተመልከቱ››
የነፍሰ ገዳይ ልጅ
ይህም ማለት የእስራኤል ንጉሥ የነፍስ ገዳይ ባሕርይ ነበረው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ ነፍሰ ገዳይ›› ወይም፣ ‹‹ያ ነፍሰ ገዳይ››
መላኩን
አንድ ሰው መላኩ ግልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለ... ሰው ልኳል››
ራሴን ለመቁረጥ
ይህ መሰየፍ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራሴን ቆርጦ ለመጣል›› ወይም፣ ‹‹ራሴን ለመሰየፍ››
እነሆ አሁንም
እዚህ ላይ ኤልሳዕ በዚህ ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ለሚናገረው የሽማግሌዎቹን ትኩረት ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንድታደርጉ የምፈልገውን ስሙ››
በሩን ዘግታችሁ እንዳይገባ አድርጉ
በተዘጋ በር ማንም መግባት አይችልም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ ውስጥ እንዳይገባ በሩን ዝጉ››
የጌታው እግር ኮቴ ከኋላው ይሰማ የለምን?
ኤልሳዕ ይህን ለሽማግሌዎቹ የተናገረው ንጉሡ ከኋላው እየመጣ መሆኑን በእርግጠኝነት ለመናገር ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጌታው እግር ኮቴ ድምፅ ከኋላው ነው›› ወይም፣ ‹‹እርሱ ከደረሰ በኋላ ንጉሡም ወዲያው ይመጣል››
እነሆ መልእክተኛው
‹‹የምነግራችሁ ነገር እውነትና አስፈላጊ ስለሆነ ልብ በሉ››
ይህ ጥፋት
‹‹በእርግጥ ይህ ጥፋት›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› ለሚከተለው አጽንዖት ይሰጣል። ‹‹ይህ ጥፋት›› የሚለው ሐረግ በሰማርያ የሚመጣውን ራብና የሚያስከትለውን ችግር ያመለክታል።
ታዲያ፣ እኔ ከእግዚአብሔር ምን እጠብቃለሁ?
ንጉሡ ይህን የጠየቀው ያህዌ ይረዳናል ብሎ እንደማያምን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንደሚረዳን በማመን የምጸናው ለምንድነው?›› ወይም፣ ‹‹ከእንግዲህ የያህዌን ረድኤት አልጠብቅም››

Chapter 7
2 Kings 7:1
አንድ መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት በአንድ ሰቅል፣ ሁለት መስፈሪያ ገብስም በአንድ ሰቅል ይሸጣል
እስራኤላውያን ከዚያ በፊት ከነበረው ጊዜ ይልቅ ለእነዚህ ሸቀጦች አነሥተኛ ገንዘብ እንደሚከፍሉ ነው የሚጠቁመው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች አንዱን መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት በአንድ ሰቅል፣ ሁለቱን መስፈሪያ ገብስም በአንድ ሰቅል ይሸጣሉ››
አንድ መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት... ሁለት መስፈሪያ ገብስ
እዚህ ላይ፣ ‹‹መስፈሪያ›› የሚለው ቃል፣ ‹‹ሴህ›› ሲሆን፣ 7 ሊትር የሚሆን የደቃቅ

ነገሮች መለኪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹7 ሊትር ማለፊያ ዱቄት… 14 ሊትር ገብስ››
ሰቅል
ሰቅል ከ11 ግራም ጋር የሚመጣጠን መለኪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹11 ግራም ብር›› ወይም ‹‹አንድ የብር ሳንቲም››
ንጉሡ በክንዱ ላይ የተደገፈው የጦር አዛዥ
የንጉሡ የግል ረዳት የሆነው ከፍተኛ ሹም፣ ንጉሡ በክንዱ የሚደገፍበት ሰው መሆኑ ተመልክቷል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለንጉሡ ቅርብ የሆነው የጦር አዛዥ›› ወይም፣ ‹‹የንጉሡ የግል ረዳት የሆነው የጦር አዛዥ››
ያህዌ የሰማያትን መስኮት ቢከፍት እንኳ
እህሎች እንዲያድጉ ያህዌ ብዙ ዝናብ ማዝነቡ ከሰማይ መስኮቶች ብዙ ውሃ እንዲወርድ ከማድረግ ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ብዙ ዝናብ ከሰማይ ቢያዘንብ እንኳ››
ይህ ሊሆን ይችላልን?
የጦር አዛዡ ይህን የተናገረው አለማመኑን ለመግለጽ ነው። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም››
አንተው ራስህ በዐይንህ ታየዋለህ
‹‹አንተው ራስህ በዐይንህ›› የሚለው ሐረግ ኤልሳዕ የተናገረው ትንቢት ሲፈጸም በእርግጥ እንደሚያይ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ ሲሆን፣ አንተው ራስህ ትመለከታለህ››
ይሁን እንጂ ከዚያ አንዳች አትቀምስም
‹‹ከገብሱ ዱቄት ምንም አትበላም››
2 Kings 7:3
እነሆ
ይህ ቃል እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው ዋናውን የታሪክ ፍሰት ገታ ለማድረግ ነው። እዚህ ላይ ጸሐፊው የታሪኩን አዲስ ክፍል ያቀርባል።
እስክንሞት ድረስ በዚህ የምንቆየው ለምንድነው?
ሰዎቹ አራት ቢሆኑም ይህን የጠየቀው አንዱ ነው። ጥያቄው ይህን ማድረግ እንዳለባቸው አጽንዖት ይሰጣል። ይህን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስክንሞት ድረስ በፍጹም እዚህ መቀመጥ የለብንም››ዝም ካሉን ሕይወታችን ትተርፋለች፤ ከገደሉንም ያው ሞቶ መገላገል ነው።
2 Kings 7:5
መሸትሸት ሲል
ይህ የሚያመለክተው ፀሐይ ከጠለቀች በኃላ ከመጨለሙ በፊት የለውን ምሽት ነው።
ከሰፈሩ ውጪ
‹‹ዳርቻ››
የሠረገሎችንና የፈረሶችን እንዲሁም የብዙ ሰራዊት ድምፅ ሶርያውያን…
የሶርያ ሰራዊት ወደ ጦርነቱ እየመጣ ያለ የብዛ ወታደሮች ድምፅ ሰማ። ይሁን እንጂ፣ ጌታ እንዲሰሙ አድርጓቸው ነው እንጂ፣ ምንም ወታደር አልነበረም።
እርስ በርሳቸውም
‹‹የሶርያ ወታደሮች እርስ በርሳቸው››
የኬጢያውያንና የግብፃውያንን ነገሥታት
እዚህ ላይ፣ ‹‹ነገሥታት›› የሚለው ነገሥታቱንና ሰራዊቱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኬጢያውያንና የግብፃውያን ሰራዊት››
አምጥቶብናል
‹‹ሊወጉን›› ወይም፣ ‹‹ሊወርሩን››
2 Kings 7:7
አጠቃላይ መረጃ
ሶርያውያን ብዙ የጠላት ሰራዊት ወደ ሰፈራቸው እየመጣ ነው ብለው እንዲያስቡ ጌታ ካደረገ በኃላ የሆነው እንዲህ ነበር።
መሸትሸት ሲል
ይህ ፀሐይ ከጠለቀች በኃላ ጨለማ ከመሆኑ በፊት ያለው ጊዜ ነው።
ዘረፉ
ይህ አሸናፊው ሰራዊት ከተሸናፊው የሚወስደውን ነገር ያመለክታል። እዚህ ላይ፣ ‹‹ብርና ወርቅ፣ ልብሶች›› ናቸው የተጠቀሱት።
2 Kings 7:9
እስኪነጋ ድረስ
‹‹ጠዋት እስኪሆን››
ቅጣት ይደርስብናል
አራቱን ሰዎች የሚቀጣው ሰው ራሱ ቅጣት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ይቀጡናል›› ወይም፣ ‹‹አንድ ሰው ይቀጣናል››
ወደ ቤተ መንግሥት በፍጥነት ሄደን እንንገር
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቤተ መንግሥት›› ንጉሡ ቤት ውስጥ የሚኖሩትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለንጉሡና ለሰዎቹ እንንገር››
ስለዚህ ሄደው
ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወታደሮቹ እዚያው እያሉ ሄደው››
ዜናውም በቤተ መንግሥት ተሰማ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ከዚያም ሰዎቹ ቤተ መንግሥት ውስጥ ተናገሩ!›› ወይም፣ ‹‹ከዚያም ሰዎቹ ለንጉሡና ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ላሉት ተናገሩ››
2 Kings 7:12
ያደረጉብንን
‹‹ሊያደርጉብን ያሰቡትን›› ወይም፣ ‹‹እኛን ለማታለል ያደረጉትን››
ከነሕይወታቸው እንማርካቸዋለን
ይህ ማለት ከነሕይወታቸው ይይዙዋቸዋል እንጂ አይገድሏቸውም ማለት ነው።
በከተማዪቱ ውስጥ ከተረፉት ፈረሶች
አብዛኞቹ የእስራኤላውያን ፈረሶች በራብ ምክንያት ሞተዋል። ይህን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በከተማዪቱ ውስጥ በሕይወት ካሉት ፈረሶች››
ዕጣ ፈንታቸውም በዚህ ከቀሩት እስራኤላውያን ሁሉ ዕድል ጋር አንድ ነው።
ወደ ሶርያውያን ሰራዊት ሰፈር የሚሄዱት ድርሻ ከተማ ውስጥ ከቀሩት እስራኤላውያን ድርሻ ጋር እኩል ነው። በራብ ይሞታሉ ወይም በሶርያ ወታደሮች ሊያዙ ይችላሉ።
እንይ
ማየት የፈለጉትን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ ለምጻሞች የነገሩን እውነት መሆኑን እንይ››
2 Kings 7:14
ሂዱና እዩ
ንጉሡ ሄደው እንዲያዩ የፈለገውን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ ለምጻሞች የተናገሩት እውነት መሆኑን ሂዱና እዩ››
እስከ ዮርዳኖስ ድረስ ተከተሏቸው
‹‹ሶርያውያን ወታደሮች የሄዱበትን መንገድ እስከ ዮርዳኖስ ወንዝ ድረስ ተከተሉ››
ልብስና ዕቃ በየመንገዱ ላይ ተበታትኖ ነበር
ይህ ግነት ሲሆን፣ ሰዎቹ በሄዱበት መንገድ እነዚህ ነገሮች ተበታትነው አዩ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በየመንገዱ ልብሶችና ዕቃዎች ነበሩ››
2 Kings 7:16
ሰፈሩን በዘበዙ
ይህ ከተሸነፈው ሰራዊት ንብረት መውሰድ ማለት ነው።
ስለዚህ አንድ መስፈሪ ማለፊያ ዱቄት በአንድ ሰቅል፣ ሁለት መስፈሪያ ገብስም በአንድ ሰቅል ተሸጠ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህም ሰዎቹ አንዱን መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት በአንድ ሰቅል፣ ሁለቱን መስፈሪያ ገብስም በአንድ ሰቅል ሸጡ››
አንድ መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት… ሁለት መስፈሪያ ገብስ
እዚህ ላይ፣ ‹‹መስፈሪያ›› ተብሎ የተተረጐመው፣ ‹‹ሴህ›› የሚለው ቃል ሲሆን፣ ደረቅ ነገሮች በሚለኩበት መለኪያ ከ7 ሊትር ጋር እኩል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹7 ሊትር ማለፊያ ዱቄት… 14 ሊትር ገብስ››
ሰቅል
ሰቅል ከ11 ግራም ጋር የሚተካከል መለኪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹11 ግራም የሚያህል ብር›› ወይም፣ ‹‹አንድ የብር ሳንቲም››
የያህዌ ቃል እንደ ተናገረው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቃል›› ያህዌን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንደ ተናገረው››
ንጉሡ እጁን ይደገፈው የነበረው የጦር አለቃ
የንጉሡ የቅርብ ረዳት የነበረው ከፍተኛ ባለ ሥልጣን ንጉሡ እጁን ይደግፈው የነበረ ሰው እንደ ሆነ ተነግሮአል 2 ነገሥት 7፥2 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለንጉሡ ቅርብ የነበረው የጦር አዛዥ›› ወይም፣

‹‹የንጉሡ የቅርብ ረዳት የነበረው የጦር አዛዥ

ሕዝቡ ሲጋፋ ረጋገጠው

ሕዝቡ ምግብ ለማግኘት እየተጣደፉ ስለ ነበር፣ ሰውየው ጋር ተጋጩ፤ ረጋግጠውም ገደሉት።

2 Kings 7:18

አጠቃላይ መረጃ

በእነዚህ ጥቅሶች ጸሐፊው 2 ነገሥት 7፥1-2 ላይ ያለውን በድጋሚ በማቅረብ የሆነውን ነገር ያሳጥራል።

በዚህ ጊዜ

‹‹ነገ በዚህ ጊዜ››

ሁለት መስፈሪያ ገብስ… አንድ መስፈሪያ ማለፊያ ዱቄት

እዚህ ላይ፣ ‹‹መስፈሪያ›› ተብሎ የተተረጐመው፣ ‹‹ሴህ›› የተሰኘው ቃል ሲሆን፣ በደረቅ ነገር መለኪያ ከ7 ሊትር ጋር እኩል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹14 ሊትር ገብስ… 7 ሊትር ማለፊያ ዱቄት››

ሰቅል

ሰቅል ከ11 ግራም ጋር እኩል የሆነ መስፈሪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹11 ግራም የሚያህል ብር›› ወይም፣ ‹‹አንድ የብር ሳንቲም››

እይ

‹‹ተመልከት›› ወይም፣ ‹‹ስማ›› ወይም፣ ‹‹የምነግርህን ልብ በል››

ያህዌ የሰማይን መስኮቶች ቢከፍት እንኳ

እህል እንዲበቅል ያህዌ ዝናብ ማዝነቡ የሰማይ መስኮቶች ጋር ተመሳስሎአል። 2 ነገሥት 7፥2 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ከሰማይ ብዙ ቢያዘንብ እንኳ››

ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

የጦር አዛዡ እንዲህ ያለው አለማመኑን ለማሳየት ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። 2 ነገሥት 7፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ በፍጹም አይሆንም››

አንተው ራስህ በዐይንህ ታያለህ

‹‹በዐይንህ ታያለህ›› የሚለው ሐረግ ኤልሳዕ ትንቢት የተነገረውን የጦር አዛዡ በእርግጥ እንደሚያይ አጽንዖት ይሰጣል። 2 ነገሥት 7፥2 እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ ሲሆን አንተው ራስህ ታያለህ››

ግን አንዳች ነገር አትቀምስም

‹‹ከዚያ ገብስ ምንም አትበላም››

---

Chapter 8

2 Kings 8:1

በዚህ ጊዜ

ይህ ቃል እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው የዋናውን ታሪክ ፍሰት ገታ ለማድረግ ነው። ጸሐፊው የታሪኩን አዲስ ክፍል መናገር ይጀምራል።

ልጇን ከሞት ያስነሣላትን ሴት

የዚህች ሴትና የልጇ ታሪክ 2 ነገሥት 4፥8 ላይ ይገኛል።

ከሞት ያስነሣላት

‹‹ወደ ሕይወት የመለሰላት››

ተነሺና… ተነሥታ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ነገራት አደረገች

እዚህ ላይ መነሣት አንድ ሰው ሲያደርግ የነበረውን በማቆም የተነገረውን ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምነግርሽን አድርጊ… እርሷም የእግዚአብሔር ሰው የነገራትን አደረገች››

የእግዚአብሔር ሰው

‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››

2 Kings 8:3

ለንጉሡ

ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ንጉሥ ነው።

ስለ ቤቷና ስለ መሬቷ

ሴትዮዋ ስትሄድ ቤቷና ንብረቷ ተወስዶ ነበር። እንዲመለስላት እየለመነች ነው። የዚህን ትርጉም የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤቷና ንብረቷ እንዲመለስላት››

ስለ ልጇ

ይሄ የሚያመለክተው ስለ ልጇ መሞትና ኤልሳዕ እንዴት እንዳስነሣላት ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልጇ ላይ ስለሆነው ጉዳይ››

የእርሻዋን ሰብል በሙሉ

ይህ የሚያመለክተው እርሷ ከሄደች ጀምሮ እርሻዋ ማስገኘት የሚችለውን ገንዘብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእርሻዋ ማግኘት የነበረባትን ጥቅም ሁሉ››

2 Kings 8:7

ቤንሓዳድ

ይህ የሶርያ ንጉሥ ስም ነው። ስሙ፣ ‹‹የሐዳድ ልጅ›› ማለት ነው። 6፥24 ላይ የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

አዛሄል

ይህ የሰው ስም ነው።

ገጸ በረከት ይዞ

አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን አዛሄል ብዙ ገጸ በረከት ይወስዳል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙ ገጸ በረከት ወስዶ››

በእጅህ

ይህ ሐረግ፣ ስጦታዎቹን ይዞ እንዲሄድ ማለት ነው። ‹‹ይዘህ ሂድ››

የእግዚአብሔር ሰው

‹‹የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ››

በእርሱ በኩል ያህዌን ጠይቅ

‹‹እግዚአብሔርን እንዲጠይቅ ለኤልሳዕ ንገረው››

የአርባ ግመል ጭነት

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአርባ ግመል አስጭኖ››

አርባ ግመሎች

‹‹40 ግመሎች››

የሶርያ ንጉሥ ልጅህ ቤንሐዳድ

ቤንሐዳድ በቀጥታ የኤልሳዕ ልጅ አልነበረም፤ አዛሄል እንዲህ ያለው በመካከላቸው የነበረውን ጥብቅ ግንኙነት ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ልጅህ የሆነው የሶርያ ንጉሥ ቤንሐዳድ››

2 Kings 8:10

እስኪያፍር ድረስ

‹‹አዛሄል ምቾት እስኪያጣ ድረስ››

ጌታዬ

አዛሄል ኤልሳዕን እንዲህ ያለው እርሱን ለማክበር ነው።

ስለማውቅ ነው

እግዚአብሔር ለኤልሳዕ ወደ ፊት የሚሆነውን አሳይቶታል።

አንተ የምታደርገውን

አንተ የሚለው የሚወክለው አዛሄልን ቢሆንም፣ እዚህ ላይ ግን ወደ ፊት ንጉሥ ሲሆን በእርሱ ሥር የሚሆኑትን ወታደሮች ነው።

ታቃጥላለህ… ትገድላለህ

‹‹አንተ›› የሚለው የሚወክለው አዛሄልን ቢሆንም፣ እዚህ ላይ የሚያመለክተው አዛሄልን ሳይሆን ወታደሮቹን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወታደሮችህ ያቃጥላሉ… ወታደሮችህ ይገድላሉ››

ሕፃናታቸውንም በምድር ላይ ትፈጠፍጣለህ

‹‹ትንንሽ ልጆቻቸውን ትጨፈልቃለህ›› — ይህ ልጆቹን የሚገድሉ ወታደሮችን ጭካኔ ያመለክታል።

ጐልማሶቻቸውን በሰይፍ ትገድላለህ

ይህ ማለት ሰዎቹ በጦርነት ይገደላሉ ማለት ነው። ሰይፍ በጦርነት ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል ዋና መሣሪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጦርነት ሰዎቻቸውን በሰይፍ ትገድላለህ››

ያረገዙ ሴቶቻቸውን ሆድ ትቀድዳለህ

ይህ ለይቶ የሚያመክተው የማሕፀን መቀደድን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያረገዙ ሴቶቻቸውን ማሕፀን በሰይፍ ትቀድዳለህ››

2 Kings 8:13

አገልጋይህ ይህን ጀብዱ መፈጸም እንዴት ይችላል?

አዛሄል ራሱን የኤልሳዕ አገልጋይ በማለት ይጠራል። አዛሄል እንዲህ ያለው ኤልሳዕ የተናገረውን አሰቃቂ ነገር መፈጸም እችላለሁ ብሎ አለማመኑን አጽንዖት ለመስጠት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲህ ያለውን ጀብዱ ማድረግ አልችልም›› ወይም፣ ‹‹እንዲህ ያለውን ጀብዱ ለማድረግ ለመሆኑ እኔ ማን ነኝ››

ይህን ጀብዱ

‹‹ይህን አሰቃቂ ነገር›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ጀብዱ›› ሰፊ ውጤት ያለውን አሰቃቂ ነገር ለማመልከት ነው።

እንደ ውሻ የሚቆጠር

አዛሄል ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። ራሱን ከውሻ ጋር በማነጻጸር ዝቅተኛነቱንና ተፅዕኖ ማድረግ የማይችል መሆኑን እየተናገረ ነው። እዚህ ላይ ውሻ ዝቅተኛ እንስሳን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ እንደ ውሻ ዐቅመ ቢስ ነኝ›› ወይም፣ ‹‹እኔ እንደ ዝቅተኛው እንስሳ ዐቅመ ቢስ ነኝ››

ወደ ጌታው ተመለሰ

‹‹ጌታው›› የሚለው የሚያመለክተው ቤንሐዳድን ነው።

እንዲሞት ፊቱን ሸፈነው

ይህ ማለት ቤንሐዳድ በውሃ በራሰ ወፍራም ልብስ ታፈነ ማለት ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤንሐዳድ መተንፈስ ስላልቻለ ሞተ››

2 Kings 8:16

አጠቃላይ መረጃ

ኢዮራም የይሁዳ ንጉሥ ሆነ የአክዓብ ልጅ ኢዮሆራም በእስራኤል በነገሠ በአምስተኛው ዓመት ይህ የሚገልጸው የአሁኑ የእስራኤል ንጉሥ ኢዮሆራም ምን ያህል ዓመት እንደ ገዛ በመግለጽ ኢዩራም በይሁዳ ላይ መንገሥ የጀመረበትን ጊዜ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአክዓብ ልጅ ኢዮሆራም የእስራኤል ንጉሥ በሆነ አምስተኛው ዓመት›› ወይም፣ ‹‹የአክዓብ ልጅ ኢዮሆራም በእስራኤል በነገሠ አምስት ዓመት ሲሆነው››

አምስተኛ ዓመት

‹‹5 ዓመት››

ኢዮራም መግዛት ጀመረ

የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም የይሁዳ ንጉሥ ሆነ

ሰላሣ ሁለት ዓመት

‹‹32 ዓመት››

2 Kings 8:18

ኢዮራም የእስራኤልን ነገሥታት መንገድ ተከተለ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ተከተለ›› የሚለው እንደ ንጉሥ እንዴት እንደ ኖረና እንደ ገዛ የሚያመለክት ነው። በታሪክ ውስጥ በዚህ ጊዜ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የነበሩት የእስራኤል ነገሥታት ክፉዎች ነበሩ። ይህን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእርሱ በፊት እንደ ነገሡት የእስራኤል ነገሥታት ሁሉ ኢዮራም ክፉ ንጉሥ ነበር››

የአክዓብ ቤት እንዳደረገው

እዚህ ላይ የአክዓብ፣ ‹‹ቤት›› የአክዓብን ቤተ ሰብና የቅርብ ዘመዶቹን ያመለክታል። አክዓብ የኢዮራም ሚስት አባት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተቀሩት የአክዓብ ቤተ ሰቦች እንዳደረጉት››

የአክዓብን ልጅ አግብቶ ነበር

ኢዮራም ያገባው የአክዓብን ልጅ ነበር

በያህዌ ፊት ክፉ ድርጊት ፈጸመ

የያህዌ፣ ‹‹ፊት›› የያህዌን ፍርድ ወይም መለኪያ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእግዚአብሔር ፍርድ ክፉ ድርጊት›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን››

ይሁዳን ሊያጠፋ

እዚህ ላይ ‹‹ይሁዳ›› እዚያ የሚኖረው ሕዝብ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የይሁዳን ሕዝብ ሊያጠፋ››

ምንጊዜም ዘር እንደሚያሳጣው ነግሮት ነበር

‹‹ምንጊዜም ቢሆን ዘር እንደሚሰጠው ያህዌ ለዳዊት ቃል ገብቶለት ስለ ነበር›› ይህ ልጆቹ ሁሌም ይሁዳን እንደሚገዙ ያህዌ ለዳዊት የሰጠውን ተስፋ ቃል ያመለክታል። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልጆቹ ሁሌም ይሁዳን እንደሚገዙ ያህዌ ለዳዊት ነግሮት ስለ ነበር››

2 Kings 8:20

ኤዶም ዐምፆ

‹‹ኤዶም በ… ላይ ዐመፀ››

የይሁዳ እጅ

እዚህ ላይ ‹‹እጅ›› የይሁዳን ተቆጣጣሪነት፣ ‹‹ይሁዳ›› ደግሞ በተለይ የይሁዳን ንጉሥ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከይሁዳ ንጉሥ ቁጥጥር››

የራሱን ንጉሥ አነገሠ

‹‹ለራሳቸው ንጉሥ ሾሙ››

ከዚያም ኢዮራም ተሻገረ

‹‹ተሻገረ›› የሚለውን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮራም የጠላትን ድንበር ተሻገረ››

2 Kings 8:22

አጠቃላይ መረጃ

የይሁዳ ንጉሥ ኢዮራም ሞተ፤ ልጁ አካዝያስ ነገሠ

ኤዶም እስከ ዛሬ ድረስ በይሁዳ ላይ እንደ ዐመፀ ነው

ከዚያ በኋላ ኤዶም በይሁዳ ቁጥጥር ሥር አልሆነም፤ እስከ ዛሬም እንደዚያው ነው››

በይሁዳ ላይ

‹‹ይሁዳ›› የይሁዳን ንጉሥ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳ ንጉሥ ላይ›› ወይም፣ ‹‹በይሁዳ ንጉሥ ሥልጣን ላይ››

እስከ ዛሬ ድረስ

ይህ እስከ ተጻፈ ድረስ

ልብናም በዚሁ ጊዜ ዐምፆ ነበር

እንደ ኤዶም ሁሉ ልብና በይሁዳ ንጉሥ ላይ ዐመፀ። ‹‹ልብና›› እዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የልብና ሕዝብ››

በኢዮራም ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው ነገር

‹‹ስለ ኢዮራም ታሪክና ያደረገውን ለማንበብ››

በይሁዳ… ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?

ጥያቄው የቀረበው ኢዮራምን የሚመለከት መረጃ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚገኝ ለአንባቢ ለመንገር ወይም ለማሳሰብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ ነገሮች በይሁዳ… ተጽፈዋል›› ወይም፣ ‹‹ስለዚያ ሁሉ በይሁዳ… ተጽፎአል››

ኢዮራም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ ከእነርሱም ጋር ተቀበረ

‹‹አንቀላፋ›› ማለት ‹‹ሞተ›› የሚለው ሌላ ቃል ነው። ከሞተ በኋላ አባቶቹ በተቀበሩበት መቃብር ተቀበረ። ‹‹ተቀበረ›› የሚለውን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮራም እንደ አባቶቹ አንቀላፋ፤ ከአባቶቹም ጋር ቀበሩት››

ልጁ አካዝያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ

‹‹ከዚያም የኢዮራም ልጅ አካዝያስ ነገሠ››

2 Kings 8:25

አጠቃላይ መረጃ

አካዝያስ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ

የአክዓብ ልጅ ኢዮራም በነገሠ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት

የአሁኑ ንጉሥ ኢዮራም ምን ያህል ዘመን በእስራኤል እንደ ነገሠ በመግለጽ አካዝያስ በይሁዳ መንገሥ የጀመረበትን ዘመን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአክዓብ ልጅ ኢዮራም የእስራኤል ንጉሥ በሆነ በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት››

ዐሥራ ሁለተኛ ዓመት

‹‹12ኛ ዓመት››

ሃያ ሁለት ዓመት

‹‹22 ዓመት››

ጎቶልያ… ዖምሪ

ጎቶልያ የአንድ ሴት ስም ነው። ዖምሪ የአንድ ሰው ስም ነው።

አካዝያስ በ… መንገድ ሄደ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ሄደ›› የሰውን ጸባይ ወይም አኗኗር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አካዝያስ እንደ ሌሎቹ ኖረ››

የአክዓብ ቤት

እዚህ ላይ፣ የአክዓብ፣ ‹‹ቤት›› ቤተ ሰቡን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአክዓብ ቤተ ሰብ››

በያህዌ ፊት ክፉ የሆነውን

የያህዌ ፊት የያህዌን ፍርድና መለኪያ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነውን›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ እንደ ክፉ የሚያስበውን››

የአክዓብን ልጅ አገባ

ይህ የሚያመለክተው አካዝያስ ከአክዓብ ጋር ያለውን ቀረቤታ ነው። የአካዝያስ አባት የአክዓብን ልጅ አግብቶ ነበር። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ

ትርጒም፣ ‹‹የአክዓብን ልጅ ያገባ ሰው ልጅ›› ወይም፣ ‹‹የንጉሥ አክዓብ የአማች ልጅ››

2 Kings 8:28

አካዝያስ ከአክዓብ ልጅ ከኢዮራም ጋር ሆኖ የሶርያ ንጉሥ አዛሄል ላይ ዘመተ

እዚህ ላይ የተጠቀሰው የሦስት ነገሥታት ስም አብረዋቸው ያሉ ሰራዊቶችንም ይመለከታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአካዝያስ ሰራዊት፣ የሶርያ ንጉሥ አዛሄልን ለመውጋት ከእስራኤል ንጉሥ ኢዮራም ሰራዊት ጋር ተባበረ››

ለማገገም

ይህን፣ ‹‹እንዲፈወስ›› ወይም፣ ‹‹እንዲሻለው›› በማለት መተርጐም ይቻላል።

የሶርያ ንጉሥ አዛሄል ላይ

‹‹አዛሄል›› የሚለው ራሱንና ሰራዊቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ አዛሄል ሰራዊት››

ኢዮራም ቆስሎ ነበር

ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሶርያውያን ኢዮራምን አቁስለውት ነበር››

---

Chapter 9

2 Kings 9:1

የነቢያት ልጆች

ይህ የነቢያት ስብስብ ማለት እንጂ፣ የነቢያት ልጆች ነበሩ ማለት አይደለም 2 ነገሥት 2፥3 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የነቢያት ስብስብ››

በእጅህ

‹‹በእጅህ›› የሚለው ሐረግ ማሰሮውን ይዞ የሚሄደው እርሱ መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይዘህ››

ሬማት ዘገለዓድ

ይህን የከተማ ስም፣ 2 ነገሥት 8፥28 ላይ ያለውን በተረጐምህበት መንገድ ተርጒመው።

የናምሲ የልጅ ልጅ የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢዩ

ይህ ማለት ኢዮሣፍጥ የኢዩ አባት ነበረ፤ ናምሲ የኢዮሣፍጥ አባት ነበረ ማለት ነው።

ከጓደኞቹ

ይህ ከኢዩ ጋር የተቀመጡ ሰዎችን ያመለክታል።

አስገባው

‹‹ከእርሱ ጋር ሂድ›› ወይም፣ ‹‹ውሰደው››

ወደ እልፍኝ

‹‹ወደ ጓዳ››

2 Kings 9:4

እነሆ

ጸሐፊው፣ ‹‹እነሆ›› በተሰኘው ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ላለው ትኩረት ለመሳብ ነው። ይህን ለማለት በቋንቋህ ሌላ መንገድ ካለ ተጠቀምበት።

የሰራዊቱ ጦር መኰንኖች በአንድነት ተቀምጠው ነበር

ኢዩ ከጦር መኰንኖቹ ጋር ተቀምጦ ነበር። በቋንቋህ እንደዚያ ማድረግ አስፈላጊ ከሆነ የታሪኩ ፍሰት ውስጥ ኢዩን ማስተዋወቅ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዩና ሌሎች የጦር መኰንኖች አብረው ተቀምጠው ነበር››

2 Kings 9:7

አጠቃላይ መረጃ

ወጣቱ ነቢይ የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን ከቀባው ኢዩ ጋር እየተነጋገረ ነው።

የአገልጋዮቼን የነቢያትን ደም እንዲሁም የያህዌን አገልጋዮች ደም እበቀል ዘንድ

እዚህ ላይ፣ የነቢያትና የአገልጋዮች፣ ‹‹ደም›› ሞታቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአገልጋዮቼ የነቢያትንና የያህዌን አገልጋዮች መገደል ለመበቀል›› ወይም፣ ‹‹ስለ አገልጋዮቼ ነቢያትና ስለ ያህዌ አገልጋዮች ሞት እንድቀጣቸው››

ደም

ውስጠ ታዋቂ የሆነውን ግሥ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ደማቸውን እንድበቀል››

በኤልዛቤል እጅ የተገደሉትን

ይህን በሌላ መልክ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኤልዛቤል አገልጋዮቿን በማዘዝ ያስገደለቻቸውን›› ወይም፣ ‹‹በኤልዛቤል ትእዛዝ የተገደሉትን››

በኤልዛቤል እጅ

ይህ ማለት በኤልዛቤል ትእዛዝ የተገደሉ ሰዎች ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በኤዛቤል ትእዛዝ›› ወይም፣ ‹‹ኤልዛቤል ስላዘዘች››

የአክዓብ ቤት በሙሉ ይጠፋል፤ ማንኛውንም የአክዓብ ወንድ ልጅ አቆርጣለሁ።

‹‹እቆርጣለሁ›› እገድላለሁ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአክዓብ ቤት ሁሉ ይጠፋል፤ በቤተ ሰቡ ያለ ማንኛውም ወንድ ልጅ እንዲገደል አደርጋለሁ›› ወይም፣ ‹‹ማንኛውንም ወንድ ልጅ ጨምሮ የአክዓብ ቤተ ሰብ ሁሉ ይጠፋል››

ማንኛውም ወንድ ልጅ

ሐረጉ ጥቅም ላይ የዋለው ማንኛውንም ወንድ ለማመልከት ነው፤ ‹‹ልጅ›› የሚለው ግን ልጆችንም እንደሚጨምር ግልጽ አድርጐታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ማንኛውም ወንድ››

2 Kings 9:9

አጠቃላይ መረጃ

ወጣቱ ነቢይ የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን ለቀባው ለኢዩ የያህዌን ቃል መናገሩን ቀጥሏል።

የአክዓብን ቤት እንደ… አደርጋለሁ

ይህ ማለት ኢዮሮብዓምን ባአስንና ቤተ ሰቡን እንዳጠፉ ሁሉ ያህዌ አክዓብንና ቤተ ሰቡን ያጠፋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹… እንዳስወገድሁ የአክዓብንም ቤት አስወግዳለሁ››

ቤት

ይህ ቃል ሦስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል። በእያንዳንዱ ጊዜ፣ ‹‹ቤት የሚለው ስሙ የተጠቀሰው ሰው፣ ‹‹ቤተሰብ›› ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የ… ቤተ ሰብ››

ናባጥ… አኪያም

እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው። ናባጥ የሚለውን ስም 2 ነገሥት 3፥3 ላይ ያለውን እንደ ተረጐምህ ተርጒመው።

ኤልዛቤልን… ውሾች ይበሏታል።

ይህ ማለት የሞተ አካሏን ውሾች ይበሉታል ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የኤልዛቤልን ሬሳ ውሾች ይበሉታል››

2 Kings 9:11

የጌታው አገልጋዮች

ይህ ንጉሥ አክዓብን የሚያገለግሉ ሌሎች ባለ ሥልጣኖች ያመለክታል።

ይህ እብድ

‹‹ወፈፌ ሰው››

ሰውየውንም ሆነ የሚናገረውን ታውቃላችሁ

ኢዩ እርሱ ወጣት ነቢይ እንደ ሆነና ወጣት ነቢያት ደግሞ በአጠቃላይ ስለሚናገሩት ነገር ሁሉም እንደሚያውቁ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንደ እርሱ ያሉ ወጣት ነቢያት የሚናገሩትን ታውቃላችሁ››

ንገረን

‹‹እርሱ ያለውን ንገረን››

እንዲህና እንዲህ አለኝ

‹‹ስለ ተለያዩ ነገሮች ነገረኝ››

ልብሳቸውን እያወለቁ በሚራመድበት ደረጃ ላይ አነጠፉ

በዚህ ባሕል መሠረት እግሮቹ ቆሻሻውን መሬት እንዳይረግጡ ልብሶችን አውልቆ እግር ሥር ማንጠፍ ለንጉሡ ያላቸውን ክብር መግለጫ መንገድ ነበር። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከላይ ያለውን ልብሳቸውን እያወለቁ እንዲራመድበት ኢዩ ፊት አኖሩ››

መለከትም ነፍተው እንዲህ አሉ

ሁሉም ሰው መለከት አይነፋም። መለከት የሚነፋው አንድ ሰው ብቻ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከእነርሱ አንዱ መለከት ነፍቶ እንዲህ አለ››

2 Kings 9:14

ናሜሲ

የዚህን ሰው ስም 2 ነገሥት 9፥2 እንደ ተረጐምህ ተርጒመው።

አሁን ኢዮራም

ይህ ቃል እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው የዋናውን ታሪክ ፍሰት ገታ ለማድረግ ነው። ኢዮራም እንዴት እንደ ቆሰለና ለማገገም ወደ ኢይዝራኤል እንደ ሄደ ጸሐፊው የታሪኩን ዳራ መረጃ ያቀርባል።

እስራኤል ሁሉ

ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰራዊት ብቻ እንጂ፣ በእስራኤል የሚኖረውን ሁሉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱና ሰራዊቱ›› ወይም፣ ‹‹እርሱና የእስራኤል ሰራዊት››
ለማገገም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቁስሉ እንዲሻለው››
ሶርያውያን ካደረሱበት ቁስል
ይህ ማለት የቆሰለው ከሶርያውያን ጋር ሲዋጋ ነበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሶርያ ሰራዊት ጋር ሲዋጋ ኢዮራም ከደረሰበት ቁስል››
በሶርያ ንጉሥ አዛሄል ላይ
ይህ የሚያመለክተው አዛሄልና ሰራዊቱን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሶርያ ንጉሥ በአዛሄልና በሰራዊቱ››
አዛሄል
የዚህን ሰው ስም 2 ነገሥት 8፥8 ላይ እንደ ተረጐምኸው ተርጉመው።
ኢዩ ለኢዮራም አገልጋዮች እንዲህ ከሆነ
ይህ የሚናገረው ከኢዮራም ጋር በሬማት ዘገለዓድ ስለ ነበሩት ባለ ሥልጣኖች ነው።
እንግዲህ ሐሳባችሁ እንዲህ ሆነ
‹‹ከእኔ ጋር የምትስማሙ ከሆነ›› ኢዩ ይህን ያለው ንጉሥ ለመሆንና ያለውን ሐሳብ ሕዝቡ ይደግፉ እንደ ሆነ ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእውነት ንጉሣችሁ እንድሆን የምትፈልጉ ከሆነ››
ይህን ነገር ወደ ኢይዝራኤል ሄዶ እንዳይናገር
ይህ የሚያመለክተው የኢዩን ዕቅድ ለኢዮራምና ለሰራዊት መናገርን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኢይዝራኤል ያለውን ንጉሥ ኢዮራምና ሰራዊቱን ለማስጠንቀቅ››
አሁን አካዝያስ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አሁን›› የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የዋናውን ታሪክ ፍሰት ገታ ለማድረግ ነው። እዚህ ላይ ጸሐፊው አካዝያስ ኢዮራምን ስለ ጐበኘበት ምክንያት ዳራ የሚሆን መረጃ ይሰጣል።
2 Kings 9:17
ማማ ላይ ያቆመው ጠባቂ
ዘበኛ
የኢዩ ወታደሮች መቅረባቸውን ከሩቅ አይቶ
‹‹ኢዮና ወታደሮቹ ገና ሩቅ እያሉ››
ከሰላም ጋር ምን ጉዳይ አለህ?
ኢዩ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ለሰላም ቢሆን ወይም ባይሆን፣ የእርሱ ጉዳይ እንዳይደለ ለመልእክተኛው ለመናገር ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሰላም መምጣት አለመምጣቴ የአንተ ጉዳይ አይደለም›› ወይም፣ ‹‹ለሰላም መምጣት አለመምጣቴን ማወቅ የአንተ ጉዳይ አይደለም››
መልእክተኛው ከእነርሱ ዘንድ ደርሶአል፤ ነገር ግን ተመልሶ አልመጣም
ንጉሡ ላቀረበው ጥያቄ መልስ ይዞ መልእክተኛው ተመልሶ አለመምጣቱን ለንጉሥ ኢዮራም ተናገረ።
2 Kings 9:19
ስለዚህ ንጉሡ ሌላ ፈረሰኛ ላከ
‹‹ስለዚህ ንጉሥ ኢዮራም ከኢዩና ከሰራዊቱ ጋር እንዲገናኝ ሁለተኛ ፈረሰኛ ላከ።››
ሁለተኛ ሰው
ቀደም ሲል ኢዮራም አንድ ሰው ልኮ ነበር። ይኸኛው ቀጣዩ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌላ ሰው››
ከሰላም ጋር ምን ጉዳይ አለህ?
ኢዩ ይህን ጥያቄ ያቀረበው የመጣው ለሰላም ቢሆን ወይም ባይሆን፣ ያ የእርሱ ጉዳይ አለመሆኑን ለመልእክተኛው ለመንገር ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሰላም መምጣት አለመምጣቴ የአንተ ጉዳይ አይደለም››
ሠረገላ አነዳዱ ልክ እንደ ናሜሲ ልጅ እንደ ኢዩ አነዳድ ነው
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሠረገላው ነጂ አነዳድ የኖሜሲ ልጅ የኢዩን አነዳድ ይመስላል››
2 Kings 9:21
እያንዳንዱ በሠረገላው
‹‹እያንዳንዱ በገዛ ራሱ ሠረገላ››
... አገኙት
‹‹ኢዩ የነበረበት ቦታ ሲደርሱ››
ናቡቴ
ይህ የሰው ስም ነው።
ኢይዝራኤላዊው
ይህ ከኢይዝራኤል የሆነ ሰው ማለት ነው።
የእናትህ የኤልዛቤል የጣዖት አምልኮና መተት እንዲህ በዝቶ እያለ ምን ሰላም አለ?
ኢዩን ይህን የጠየቀው የመጣው ለሰላም እንዳይደለ ለማመልከት ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናትህ ኤልዛቤል መተትና ግል ሙትናዋ እንዲሁም ጣዖት አምልኮ በዝቶ እያለ ሰላም ሊኖር አይችልም››
2 Kings 9:23
ሰረገላውን አዙሮ ሸሸ
‹‹ሰረገላውን ወደ ኋላ አዙሮ ሸሸ››
ክዳት
ማታለል ወይም ማሳሳት
በሙሉ ኀይሉ
‹‹በኀይሉ ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በብርታቱ ሁሉ››
ሠረገላው ውስጥ ዘፍ ብሎ ወደቀ
ኢዮራም በቀስት ተወግቶ ሞተ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮራም ሠረገላው ውስጥ ሞቶ ወደቀ››
2 Kings 9:25
ቢድቃር
ይህ የሰው ስም ነው።
አንሣውና ጣለው
‹‹ሬሳውን አንሥተህ ጣል›› ወይም፣ ‹‹በድኑን አንሣና ጣል››
አስታውስ
‹‹አትርሳ››
አባቱን አክዓብን
ይህ ማለት የጋለቡት ከአክዓብ ሰረገላ ተከትለው ነበር ማለት ነው።
የናቡቴንና የልጆቹን ደም
እዚህ ላይ፣ ‹‹ደም›› የሚያመለክተው ግድያን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የናቡቴንና የልጆቹን መገደል››
እንድትከፍል አደርግሃለሁ
ይህ ማለት ለፈጸመው ክፉ ነገር ለአክዓብ ተገቢ ቅጣት ይሰጣል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ላደረግኸው ክፉ ነገር የሚገባህን እሰጥሃለሁ››
አንሣውና በዚሁ እርሻ ውስጥ ጣለው
‹‹ሬሳውን አንሥተህ ናቡቴ እርሻ ውስጥ ጣለው››
በያህዌ ቃል መሠረት
‹‹የተነገረን ትንቢት እንዲፈጸም››
2 Kings 9:27
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ኢዩ ኢዮራምን ከገደለ በኋላ የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ ላይ የሆነ ነው።
ይህን ሲያይ
‹‹ኢዮራም ላይ የሆነውን ሲያይ››
ቤት ሀጋን... ጉር... ይብለዓም... መጊዶ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።
በጉር ዐቀበት
‹‹ዐቀበት›› ወደ ጉር ሲሄዱ የሚወጡት ኮረብታ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ ጉር በሚወስደው መንገድ››
ከአባቶቹ
‹‹ከጥንት ወላጆቹ››
2 Kings 9:29
የአክዓብ ልጅ ኢዮራም በነገሠ በዐሥራ አንደኛው ዓመት
የአሁኑ የእስራኤል ንጉሥ ስንት ዓመት እንደ ገዛ በማመልከት አካዝያስ መግዛት የጀመረበትን ጊዜ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአክዓብ ልጅ ኢዮራም የእስራኤል ንጉሥ በሆነ በዐሥራ አንደኛው ዓመት››
ዐሥራ አንደኛ ዓመት
‹‹ከጥንት ወላጆቹ››
2 Kings 9:30
ዐይኗን ተኳኩላ፤ ጠጉራንም አሰማምራ
‹‹ዐይኗን ተኳኩላ፣ ጠጉርዋን ተሠርታ››
ጌታህን የገደልህ አንተ ዘምሪ የመጣኸው በሰላም ነውን?

ኤልዛቤል ይህን የጠየቀችው ኢዩ የመጣው በሰላም እንዳልሆነ ለማመልከት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ጌታህን የገደልህ ዘምሪ፣ የመጣኸው ለሰላም አይደለም››
ጌታህን የገደልህ አንተ ዘምሪ
እዚህ ላይ ኤልዛቤል፣ ‹‹ዘምሪ›› ያለችው ነፍሰ ገዳይ መሆኑን ለማመልከት ነው። ዘምሪ ንጉሥ መሆን ስለ ፈለገ፣ የእስራኤልን ንጉሥ የገደለ የጦር አዛዥ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዘምሪ ጌታውን እንደ ገደለ አንተም ጌታህን የገደልህ››
ዘምሪ
ይህ የሰው ስም ነው።
አብሮኝ ያለ ማነው?
‹‹አብሮ መሆን›› ታማኝና ተባባሪ መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእኔ ታማኝ የሆነ››
2 Kings 9:33
ወደ ታች ወርውሩአት
ኢዩ ኤልዛቤልን በመስኮት እንዲወረውሩአት ለጃንደረቦቹ እየነገረ ነው።
ኢዩ ረገጣት
ይህ ማለት ፈረሶቹ ረጋገጡአት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰረገላውን ይስቡ የነበሩ የኢዩ ፈረሶች በኮቴአቸው ረጋገጡአት››
አሁን ተመልከቱ
‹‹አሁን ተመልከቱ›› ማለት ቦታው ተለይቶ ሚነገረው ልብ በሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁን ሂዱ››
ምንም ቢሆን የንጉሥ ልጅ ናትና
x
2 Kings 9:35
ሌላ ያገኙት አልነበረም
‹‹ከአካሏ የቀረ አልነበረም›› ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያገኙት ከአካሏ የተረፈ››
ከእጇ መዳፍ በቀር
መዳፍ የእጅ ውስጥ ክፍል ነው።
ቴስቢያዊው
ይህ ከቴስቢ የሆነ ሰው ማለት ነው። 2 ነገሥት 1፥3 ላይ ይህን እንዴት እንደተረጐምኸው ተመልከት።
የኤልዛቤል ሥጋ እርሻ ውስጥ እንደ ፍግ ስለሚሆን ማንም ይህች ኤልዛቤል ናት አይልም
ይህ ፍግ እርሻ ውስጥ እንደሚበታተን የኤልዛቤልም ሥጋ ቁርጥራጭ እርሻ ውስጥ መበታተኑን ይናገራል። ሥጋዋ በጣም ስለሚበጣጠስ ማንም ሰብስቦ መቅበር አይችልም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኤልዛቤል ሥጋ እንደ ፍግ እርሻ ውስጥ ይበታተናል… ስለዚህ እርሷ መሆንዋን ማንም ማወቅ አይችልም››
ፍግ
ለማዳበሪያ የሚውል ነገር
ማንም፣ ‹‹ይህች ኤልዛቤል ናት›› ሊል አይችልም
‹‹ማንም እርሷ መሆንዋን አያውቅም›› ወይም፣ ‹‹ማንም ኤልዛቤል ናት ብሎ መናገር አይችልም››

---

# Chapter 10

2 Kings 10:1
ሰባ ወንዶች ልጆች
‹‹70 ወንዶች ልጆች››
ኢዩ ደብዳቤ ጽፎ… ወደ ሰማርያ ላከ
ይህ ማለት ኢዩ ደብዳቤ የሚያደርስ መላእክተኛ ላከ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዩ ደብዳቤ ጻፈ፤ ወደ ሰማርያ እንዲያደርሰውም መልእክተኛ ላከ››
እንዲህ የሚል ነበር… ‹‹የጌታችሁ››
‹‹ደብዳቤው፣ ‹‹የጌታችሁ›› የሚል ነበር
በአባቱ ዙፋን አስቀምጡት
ዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአባቱ ቦታ ንጉሥ አድርጉት››
ስለ ጌታችሁ ቤት
‹‹ስለ ጌታችሁ ዘሮች›› - ንጉሥ እንዲሆን የመረጡት ሰው የአክዓብ ወራሽ ተብሏል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለጌታችሁ ዘር ተዋጉ›› ወይም፣ ‹‹ተዋጉለት››
2 Kings 10:4
እነርሱ ግን እጅግ ፈርተው ነበር
‹‹በጣም ፈሩ››
ሁለት ነገሥታት
‹‹ሁለት ነገሥታት፣ ኢዮራምና አካዝያስ››
ኢዩ ፊት መቆም አልቻሉም
እዚህ ላይ፣ ‹‹መቆም›› ችግሩን መቋቋም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዩን መቋቋም አይችሉም›› ወይም፣ ‹‹ኢዩን መዋጋት አይችሉም››
እኛ እንዴት ልንቋቋመው እንችላለን?
ሰዎቹ ይህን ያሉት ኢዩን እንደማይችሉት ለመናገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኛም ብንሆን እርሱን መቋቋም አንችልም›› ወይም፣ ‹‹እኛም አንችለውም››
የከተማዪቱ ገዥ
‹‹የከተማዪቱ ከንቲባ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ገዥ›› ሥልጣንና ኀላፊነት ያለው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በከተማዋ ላይ ኀላፊ የነበረው ሰው››
የልጆቹ ሞግዚቶች
ይህ ማለት የንጉሡን ልጆች ያሳደጉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የንጉሡን ልጆች ያሳደጉ››
በዐይንህ ፊት ደስ የሚያሰኝህን አድርግ
እዚህ ላይ፣ የኢዩ፣ ‹‹ዐይን›› የእርሱን፣ ‹‹ፊት›› ያመለክታል፤ የእርሱ ፊት እርሱ የሚያስበውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ትክክል የመሰለህን አድርግ›› ወይም፣ ‹‹መልካም መስሎ የታየህን አድርግ››
2 Kings 10:6
ደግሞ ጻፈላቸው
ኢዩራም አንድ ደብዳቤ ጽፎ ነበር፤ ይህ ሁለተኛው ነው አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ገና ደብዳቤ ጻፈላቸው›› ወይም፣ ‹‹ሌላ ደብዳቤ ጻፈላቸው››
የእኔ ወገን ከሆናችሁ
‹‹የአንድ ሰው ወገን መሆን›› ለእርሱ ታማኝ መሆንና ደጋፊው መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእኔ ታማኝ ከሆናችሁ››
ስሙ
ሰምታቸሁ ታዘዙ
ለቃሌ
የኢዩ፣ ‹‹ቃል›› እርሱ የተናገረውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምነግራችሁን››
ራሳቸውን ቆርጣችሁ… ወደ እኔ ኑ
የአክዓብን ልጆች ራሶች ቆርጠው ለኢዩ እንዲያመጡ ነው የተነገረው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራሳቸውን ቆርጣችሁ አምጡልኝ››
የጌታችሁን ልጆች ራስ ቆርጣችሁ
ይህ የሚያመለክተው እነርሱን ገድሎ ራሳቸውን መቁረጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጌታችሁን ልጆች ግደሉ፤ ራሳቸውንም ቁረጡ››
በቁጥር ሰባ… ሰባ ሰዎች
‹‹በቁጥር 70… 70 ሰዎች››
አሳዳጊዎቻቸው
ሲንከባከቧቸውና ሲያስተምሯቸው የነበሩ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሲያሳድጓቸው የነበሩ›› ወይም፣ ‹‹ሲንከባከቧቸው የነበሩ››
ወደ ኢዩ ላኳቸው
ይህ ማለት ቅርጫቶቹን ለኢዩ የሚያደርሱ ሰዎች ላኩ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ ኢዩ የሚያደርሱ ሰዎች ላኩ››
2 Kings 10:8
ከንጉሡ ልጆች
‹‹የአክዓብ ልጆች››
ኢዩ ወጥቶ ቆመ
‹‹ኢዩ ወደ ከተማው በር ወጥቶ ሰዎቹ ፊት ቆመ››
እናንተ ንጹሐን ናችሁ
ንጹህ የሆኑት ከምን እንደ ነበር መግለጽ ይቻላል። ምናልባትም 1)‹‹ኢዮራም ላይ በሆነው ንጹሐን ናችሁ›› ማለት ሊሆን ይችላል። ወይም 2) በኢዮራምና በቤተ ሰቡ ሞት ኃላፊነት የለባችሁም።›› ‹‹ኢዮራምና ቤተ ሰቡ ላይ ከደረሰው እናንተ ንጹሐን ናችሁ›› ማለት ሊሆን ይችላል።
እነሆ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ኢዩ ይህን ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ወደሚናገረው የሰዎቹን ትኩረት ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አድምጡ›› ወይም፣ ‹‹ቃሌን ስሙ››

እነዚህን ሁሉ ግን የፈጃቸው ማን ነው?

ኢዩ ይህን የጠየቀው ስለ ሁኔታው ሕዝቡ በጥልቀት እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉሞቹም 1) ‹‹ለ70ዎቹ የአክዓብ ልጆች ሞት ተጠያቂዎቹ የሰማርያ ሰዎች ናቸው›› 2) ‹‹እነዚህ ሰዎች እንዲሞቱ የያህዌ ፈቃድ ነበር››

## 2 Kings 10:10

በእርግጥ ዕወቁ

‹‹ተረዱ›› ወይም፣ ‹‹ይህን ሐቅ ልብ በሉ››

ከያህዌ ቃል አንዲቱ እንኳ ወድቃ እንደማትቀር

ይህ የሚናገረው ያህዌ ይሆናል ያለው ሁሉ እንደሚሆን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከያህዌ ቃል አንዲቱም አትወድቅም›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ የተናገረው ሁሉ ይሆናል››

ያህዌ የተናገረውን ፈጽሞአል

ይህ የሚናገረው እርሱ ራሱ የገደላቸው ይመስል፤ ያህዌ የአክዓብ ልጆች እንዲሞቱ ማድረጉን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንደዚያ እንዲሆን አደረገ››

ኢዩ ሁሉንም ገደለ… ካህናቱን

ኢዩ እንዲገደሉ አዘዘ እንጂ፣ እርሱ በግሉ እነዚህን ሰዎች ሁሉ አልገደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዩ ሁሉም እንዲገደሉ አዘዘ›› ወይም፣ ‹‹ኢዩ ሁሉ እንዲገደሉ አዘዘ››

የተረፉትን ሁሉ

‹‹በሕይወት ያሉትን ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹የቀሩትን ሁሉ››

አንድ እንኳ እስከማይተርፍ ድረስ

ይህ ሁሉም ተገደሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሉም እስኪሞቱ ድረስ›› ወይም፣ ‹‹ሁሉም እስኪያልቁ ድረስ››

## 2 Kings 10:12

ቤት ኤከድ ወደ ተባለው የበግ ጠባቂዎች ቤት

ይህ በጐች የሚሸለቱበት ቦታ ስም ነው።

ለሰላምታ ወደዚህ ወርደን

‹‹ሰላም ለማለት መጥተናል››

የንጉሡ ልጆች

‹‹የንጉሥ ኢዮራም ልጆች››

ከነሕይወታቸው ያዛቸው

ይህ ሳይገድሉ መያዝ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያዛቸው›› ወይም፣ ‹‹አሰራቸው››

ከነሕይወታቸው ወስደው

‹‹ያዛቸው››

አርባ ሁለቱን ሰዎች

‹‹42 ሰዎች››

አንድ እንኳ አላስቀረም

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሉንም ገደላቸው››

## 2 Kings 10:15

የሬካብ ልጅ ኢዮናዳብ

ይህ የሰው ስም ነው።

ልቤ ከአንተ ጋር እንደ ሆነ ልብህ ከእኔ ጋር ነውን?

እዚህ ላይ የሰው፣ ‹‹ልብ›› ታማኝነቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ለአንተ ታማኝ እንደ ሆንሁ ታማኝ ትሆንልኛለህን?››

እንግዲያውስ እጅህን ስጠኝ

‹‹እንደዚያ ከሆነ እጅህን እጄ ላይ አስቀምጥ›› ወይም፣ ‹‹እንደዚያ ከሆነ፣ እንጨባበጥ›› በብዙ አገሮች ሁለት ሰዎች ከተጨባበጡ ስምምነታቸውን ያረጋግጣል።

ያለኝን ቅናት እይልኝ

‹‹ቅናት›› የሚለው ቃል ቅጽልን ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቀናተኛ መሆኔን እይልኝ››

ንጉሣዊ ዘር

‹‹ንጉሣዊ ቤተ ሰብን ሁሉ››

ለነቢዩ ለኤልያስ በተነገረው የያህዌ ቃል መሠረት

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የሰጠው ኤልያስ የተናገረው ትንቢት እንዲፈጸም››

## 2 Kings 10:18

ሕዝቡን ሁሉ በአንድነት ሰበሰበ

‹‹ሕዝብ ሁሉ ወደዚያ እንዲመጡ ጠራ››

ሕዝቡ ሁሉ ተሰበሰቡ

‹‹የሰማርያ ሕዝብ ሁሉ››

በጣም አገለገሉ

‹‹ከአክዓብ የበለጠ አገለገሉ››

አንድ እንኳ እንዳይቀር

‹‹አንድ እንኳ እንዳይተርፍ››

የማይመጣ ቢኖር ግን በሕይወት አይኖርም

ይህ ማለት ካልመጡ ይገደላሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የማይመጣ ካለ እንገድለዋለን››

ጉባኤ ጥሩ

ይህ ማለት አንድ ነገር ለማድረግ ጊዜ መወሰን ማለት ነው። እዚህ ላይ ግን ለበአል ጉባኤ ለማድረግ እየተዘጋጁ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተዘጋጁ››

## 2 Kings 10:21

ከዚያም ኢዩ መልእክት ላከ

ይህን መልእክቱ ወደ አገሩ ሁሉ የሚያደርሱ መልእክተኞች ላከ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚያም ኢዩ መልእክተኞ ላከ›› ወይም፣ ‹‹ከዚያ ኢዩ መልእክት ላከ››

ስለዚህ ሳይመጣ የቀረ አልነበረም

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአልን የሚያመልኩ ሁሉ እዚያ ነበሩ›› ወይም፣ ‹‹ሁሉም መጡ››

ዳር እስከ ዳር ሞላ

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤቱን ሞሉት››

የልብስ ቤቱ ኀላፊ

እዚህ ላይ፤ ‹‹ኀላፊ›› የሚጠብቅ፣ የሚቆጣጠር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የካህናቱ ልብስ ኀላፊ›› ወይም፣ ‹‹የካህናቱን ልብስ የሚጠብቅ››

## 2 Kings 10:23

ለበአል አገልጋዮች እንዲህ አለ

‹‹ኢዩ በአልን ለማምለክ በቤተ ጣዖቱ ለነበሩ ሰዎች እንዲህ አለ››

የበአል አገልጋዮች ብቻ

‹‹እዚህ መገኘት ያለባቸው የበአል አገልጋዮች ብቻ ናቸው››

በእጃችሁ ከሰጠኃችሁ ሰዎች አንድ እንኳ እንዲያመልጥ ያደረገ

እዚህ ላይ የሰዎቹ፣ ‹‹እጅ›› በእነርሱ ‹‹ቁጥጥር›› ያለ ማለት ነው። በቤተ ጣዖቱ ዙሪያ በመሆናቸው፣ ሁኔታው በቁጥጥራቸው ሥር ነበር፤ ሰዎች ቢያመልጡ ኀላፊነቱ የእነርሱ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እጃችሁ ላይ ካሉት ሰዎች አንዱ እንኳ ቢያመልጥ›› ወይም፣ ‹‹ውስጥ ካሉት ሰዎች አንድ እንኳ ሲያመልጥ››

አንድ እንኳ እንዲያመልጥ ያደረገ በገመዱ ይገባባታል

‹‹እንዲያመልጥ ያደረገ ይገደላል››

በገመዱ ይገባበታል

ይህ በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። ይህ መገደል በጨዋ ቃል ሲገለጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕይወቱን እናጠፋለን›› ወይም፣ ‹‹እንገድለዋለን››

በጠፋው ሰው ቦታ

‹‹በጠፋው ሰው ሕይወት ለውጥ›› እንደማይሞት አጽንዖት ለመስጠት እዚህ ላይ ሰውየው፣ ‹‹ሕይወት›› ተብሏል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለ ሰውየው››

## 2 Kings 10:25

ለጠባቂዎቹና ለጦር አለቆቹ እንዲህ አለ

ምናልባት ኢዩ ለጠባቂዎቹ ከመናገሩ በፊት ከቤተ ጣዖቱ መውጣቱን መግለጽ ያስፈልገህ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከበአል ቤተ ጣዖት ወጥቶ ለጠባቂዎቹና ለጦር አለቆቹ እንዲህ አላቸው››

በሰይፍ

ሰዎቹ የበአልን አገልጋዮች የገደሉት በሰይፍ ነበር። ይህ ሐረግ የራሳቸውን ሰይፍ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሰይፋቸው››

ወደ ውጭ አውጥታችሁ ጣሏቸው

ይህ ማለት የሞቱትን ሰዎች ከቤተ ጣዖቱ አውጥቶ መጣል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሬሳቸውን ከቤተ ጣዖቱ አውጥታችሁ ጣሉ››

የኩስ መጣያ አደረገው

‹‹የሕዝብ ሽንት ቤት አደረገው››

እስከ ዛሬ ድረስ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ማለት ያ ነገር እስከ አሁን ድረስ አለ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከዚያ ወዲህ ሁሌም እንዲሁ ነው››

2 Kings 10:29

የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓምን ኀጢአት አልተወም

ይህ ማለት ኢዩ ኢዮርብዓም ያደርግ የነበረውን ኀጢአት እያደረገ ነበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ያደረገውን ኀጢአት ማድረጉን አልተወም››

ናባጥ

ከ2 ነገሥት 3፥3 የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

የእስራኤል ኀጢአት

‹‹እስራኤል›› እዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ኀጢአት››

ስላደረግህ

‹‹ስለ ፈጸምህ›› ወይም፣ ‹‹በማድረግህ››

በዐይኔ ፊት መልካም

ዐይን ማየትን፣ ማየት ደግሞ ሐሳብንና ፍርድን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መልካም ነው ያልሁትን›› ወይም፣ ‹‹መልካም እንደ ሆነ ያሰብሁትን››

የአክዓብ ቤት

የአክዓብ፣ ‹‹ቤት›› የእርሱ፣ ‹‹ቤተ ሰብ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የአክዓብ ቤተ ሰብ››

በልቤ ያለውን ሁሉ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ልቤ›› - ‹‹ምኞትን›› ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንድታደርግ የምመኘው ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹እንድታደርግ የምፈልገውን ሁሉ››

ዙፋን ላይ ይቀመጣል

ዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይነግሣል››

እስከ አራት ትውልድ

ይህ ልጁን፣ የልጅ ልጁን፣ አያቱንና ቅድመ አያቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹4ኛ ትውልድ›› ወይም፣ ‹‹አራተኛ ትውልድ››

ኢዩ የያህዌን ሕግ ለመጠበቅ ጥንቃቄ አላደረገም

እዚህ ላይ፣ ‹‹መጠበቅ›› የሚያመለክተው፣ ‹‹መኖርን›› ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዩ በያህዌ ሕግ መሠረት ለመኖር አልተጠነቀቀም››

በፍጹም ልቡ

እዚህ ላይ ‹‹ልብ›› የሰውን ፈቃድና ምኞት ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሚያደርገው ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በሙሉ ፈቃደኝነት››

ከኢዮርብዓም ኀጢአት አልራቀም

ከአንድ ነገር ‹‹መራቅ›› ያንን ማድረግ ማቆም ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዮርብዓም ባደረገበት መንገድ ኀጢአት ማድረጉን አልተወም››

2 Kings 10:32

የእስራኤልን ምድር መቀናነስ ጀመረ

‹‹በእስራኤል ቁጥጥር ሥር የነበረው መሬት እያነሰ እንዲሄድ አደረገ››

ክልል

አንድ አካባቢ

አዛሄል ድል መታ

‹‹አዛሄል›› የሚያመለክተው ሰውየውንና ሰራዊቱን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አዛሄልና ሰራዊቱ›› ወይም፣ ‹‹የንጉሥ አዛሄል ሶርያዊ ሰራዊት››

አዛሄል

2 ነገሥት 8፥8 ይህን ስም እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ

‹‹ከዮርዳኖስ ምሥራቅ ካለ ምድር››

አሮዔር... ባሳን

እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።

አርኖን

‹‹የአርኖን ወንዝ›› ይህ የወንዝ ስም ነው።

2 Kings 10:34

በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?

ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። 2 ነገሥት 1፥18 ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎአል››

ኢዩ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ በሰማርያም ቀበሩት

ይህ ኢዩ ሞተ ማለት ነው። ከእነርሱ ጋር የተኛ ይመስል አባቶቹ በተቀበሩበት በታ መቀበሩን ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዩ ሞተ፤ አባቶቹም በተቀበሩበት ቦታ በሰማርያ ተቀበረ››

ኢዮአካዝ

ይህ የሰው ስም ነው።

ኢዩ በሰማርያ ተቀምጦ በእስራኤል ላይ የነገሠው ሃያ ስምንት ዓመት ነበር

‹‹ኢዩ ሰማርያ ሆኖ በእስራኤል ሃያ ስምንት ዓመት ነገሠ››

ሃያ ስምንት ዓመት

‹‹28 ዓመት››

---

Chapter 11

2 Kings 11:1

ጎቶልያ... ዮሳቤት... ኢዮአስ

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው

ልጇ መሞቱን በሰማች ጊዜ

‹‹ልጇ መሞቱን ባወቀች ጊዜ››

ተነሥታ የንጉሣዊ ቤተ ሰብ ልጆች ገደለች

ጎቶልያ ራሷ ልጆቹን አልገደለችም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጎቶልያ ንጉሥ የሚሆኑ የአካዝያስ ቤተ ሰብ አባሎች እንዲገደሉ አገልጋዮቿን አዘዘች››

የአካዝያስን ልጅ ኢዮአስን ሊገድሉ ከነበሩት ልዑላን መካከል ሰርቃ ወሰደችው። እንዳይገድሉትም ከጎቶልያ በመደበቅ እርሱንና ሞግዚቱን በአንድ አልፍኝ ሸሸገቻቸው

‹‹የአካዝያስ ትንሹን ልጅ ኢዮአስን ወስዳ እርሱንና ሞግዚቱን ቤተ መቅደስ ባለው መኝታ ቤት ደበቀቻቸው ስለዚህ ሳይገደሉ ቀሩ››

ጎቶልያ አገሩ በምትገዛበት ጊዜም በያህዌ ቤት ተሸሸገ

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኢዮአስና ዮሳቤት ጎቶልያ አገሩን በምትገዛበት ዘመን ስድስት ዓመት በያህዌ ቤት ተደበቁ››

ምድር

ይህ በምድር የሚኖሩ ሰዎች ተለዋጭ ስም ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የይሁዳ ሕዝብ››

2 Kings 11:4

አያያዥ ዐረፍተ ነገር

የንጉሥ አካዝያስ ልጆች ከተገደሉ በኋላ የንጉሥ አካዝያስ ልጅ ኢዮአስ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ከተደበቀ በኋላ የተፈጸመውን ታሪክ ይቀጥላል።

በሰባተኛውም ዓመት

‹‹በጎቶልያ አገዛዝ ሰባተኛው ዓመት›› ወይም፣ ‹‹ጎቶልያ ትገዛ በነበረበት 7ኛው ዓመት››

ዮዳሄ

ሊቀ ካህኑ

የመቶ አለቆች

ይህ የባለ ሥልጣኖች መጠሪያ ነው። አማራጭ ትርጒሙ፣ 1) ‹‹መቶ›› የሚለው እነዚህ ባለ ሥልጣኖች ምን ያህል ወታደር ከእነርሱ ሥር እንደ ነበር በትክክል ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የ100 ወታደሮች አዛዦች›› ወይም 2) ‹‹መቶ›› የሚለው ቃል በትክክል ቁጥርን የሚገልጽ ሳይሆን፣ የሚያመለክተው ሰራዊቱ ውስጥ ያለውን ምድብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የወታደራዊ ምድብ አዛዦች››

ካራውያን

እነዚህ የተወሰኑ የቤተ መንግሥት ጠባቂዎች ቡድን ናቸው።

ወደ ራሱ አመጣቸው

‹‹መጥተው እርሱን እንዲያገኙ አደረገ›› - እነዚህ ወታደሮች የሆነውን ነገር ቤተ መቅደስ ውስጥ ለሊቀ ካህኑ ለዮዳሄ ነገሩት።

የንጉሡን ልጅ አሳያቸው

የንጉሥ አካዝያስ ልጅ ኢዮአስ በሕይወት መኖሩን ዮዳሄ ነገራቸው።

2 Kings 11:7

አጠቃላይ መረጃ

ዮዳሄ ንጉሥ ኢዮአስን ለሚጠብቁ ወታደሮች መመሪያ እየሰጠ ነው።

ንጉሡን

ነቅተው ከማንኛውም አደጋ ንጉሡን መጠበቅ ነበረባቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንጉሥ ኢዮአስን ለመጠበቅ››

እናንተን የሚቀርባችሁ ቢኖር

‹‹ንጉሡ ኢዮአስን እየጠበቃችሁ እያለ እናንተን የሚቀርባችሁ ቢኖር ይገደል›› ረድፍ ማለት መደዳውን ያሉ ወታደሮች ማለት ነው።

ይገደል

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግደሉት››

ንጉሡ በሚወጣበትም ሆነ በሚገባበት ጊዜ ሁሉ አትለዩት

እነዚህ የሚቃረኑ የሚመስሉ ሁለት ነገሮች ንጉሡ የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁልጊዜ ከአጠገቡ አትለዩ››

2 Kings 11:9

የመቶ አለቆች

‹‹የመቶ አለቆች›› የሚለው ሐረግ ምናልባት ወታደራዊ ሥልጣን ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉሞቹ፤ 1) ‹‹መቶ›› የሚለው ቃል እነዚህ አዛዦች ሥር ያሉ ሰዎችን ቁጥር የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የ100 ወታደሮች አዛዥ›› ወይም 2) መቶ ተብሎ የተተረጐመው የወታደራዊ ምድብ ስም እንጂ፣ በትክክል ቁጥርን የሚያመለክት አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የወታደራዊ ምድብ አዛዥ›› 2 ነገሥት 11፥4 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እያንዳንዱ

‹‹እያንዳንዱ አዛዥ››

ያህዌ ቤት ውስጥ ነበሩ

‹‹ቤተ መቅደስ ውስጥ ተቀምጠው ነበር››

2 Kings 11:11

ከቤተ መቅደሱ ግራና ቀኝ፤ መሠዊያውና ቤተ መቅደስ አጠገብ።

አንዳንድ ትርጉሞች ‹‹ቤተ መቅደስ›› የሚለውን፣ ‹‹ቤተ መንግሥት›› በማለት ተርጉመዋል። እነዚህ ትርጉሞች፣ ‹‹ከቤተ መንግሥቱ ግራና ቀኝ፤ መሠዊያውና ቤተ መቅደሱ አጠገብ›› ይላሉ።

የንጉሡን ልጅ ኢዮአስን አውጥቶ

x

2 Kings 11:13

የጠባቂዎቹ ጩኸት

ይህ የሚያመለክተው የሁሉንም ወታደሮች ድምፅ ነው።

ሕዝቡ ወዳለበት ወደ ቤተ መቅደሱ ሄደች

‹‹ሕዝቡ ተሰብስቦ ወደ ነበረበት ወደ ቤተ መቅደሱ ሄደች››

ስትመለከት እነሆ ንጉሡ እዚያ ቆሞ ነበር

‹‹እዚያ ስትደርስ ንጉሥ ኢዮአስ ቆሞ ስታይ ተገረመች››

በዐምዱ አጠገብ

‹‹ቤተ መቅደስ ውስጥ ከነበሩ ዐምዶች በአንዱ››

በወጉ መሠረት

‹‹ሁሌም ንጉሡ ይቆምበት የነበረው ቦታ››

መለከት ነፊዎች

‹‹መለከት የሚነፉ ሰዎች››

ጐቶልያም ልብሷን ቀዳ

በጣም መቆጣቷንና መናደዷን ለማሳየት ልብሷን ቀደደች።

ክዳት ነው! ክዳት ነው!

‹‹ከሐዲዎች ነችሁ! አታለላችሁኝ!››

2 Kings 11:15

የመቶ አለቆች

‹‹የመቶ አለቆች›› የሚለው ሐረግ ምናልባት ወታደራዊ ሹመት ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ 1) ‹‹መቶ›› የሚለው ቃል በእነዚህ አዛዦች ሥር ያሉ ወታደሮችን ብዛት ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የ100 ወታደሮች አዛዥ›› ወይም 2) መቶ ተብሎ የተተረጐመው ቃል የሚያመለክተው የወታደራዊ ምድብ ስም እንጂ፣ ቁጥርን አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የወታደራዊ ምድብ አዛዥ›› 2 ነገሥት 11፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

በረድፍ በተሰለፉ ጭፍሮች መካከል አውጧት

‹‹ተርታውን ከተሰለፉ ጠባቂች መካከል አውጧት›› ወይም፣ ‹‹ግራና ቀኙን ከተሰለፉ ወታደሮች ውሰዷት›› ረድፍ መደዳውን የተሰለፉ ወታደሮች ሰልፍ ነው።

2 Kings 11:17

በንጉሡና በሕዝቡም መካከል

‹‹በንጉሡና በሕዝቡ መካከል ኪዳን ተደረገ››

የአገሩም ሕዝብ ሁሉ

ይህ በጣም ብዙ ሕዝብ የበአልን ቤት ጣዖት ማፍረሱን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአገሩ ሕዝብ አብዛኛው››

የበአል ቤት

‹‹የበአል ቤተ ጣዖት››

ማታን

ይህ የወንድ ካህን ስም ነው።

2 Kings 11:19

አጠቃላይ መረጃ

አዲሱን ንጉሥ ኢዮአስን ከቤተ መቅደስ ወደ ቤተ መንግሥት ወሰዱት

የመቶ አለቆች

‹‹መቶ አለቆች›› የሚለው ሀረግ ምናልባት ወታደራዊ ሹመት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉሞች፣ 1) ‹‹መቶ›› የሚለው ቃል በእነዚህ ሹሞች ሥር ያለውን ወታደር ብዛት ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የ100 ወታደሮች አዛዥ›› ወይም 2) ‹‹መቶ›› ተብሎ የተተረጐመው ቃል ወታደራዊ ምድብን እንጂ፣ ትክክለኛ ቁጥር የሚያመለክት አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወታደራዊ ምድብ አዛዥ›› 2 ነገሥት 11፥4 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ካራውያን

ይህ የቤተ መንግሥቱ ጠባቂዎች አንድ የተለየ ምድብ ነው።

ንጉሡን ከያህዌ ቤተ መቅደስ አውጥተው ወደ ቤተ መንግሥት ሄዱ

‹‹ንጉሡን ከቤተ መቅደስ ወደ ቤተ መንግሥት አመጡት››

የአገሩም ሕዝብ ሁሉ ደስ አለው

ይህ አብዛኛው ለማለት ነው፣ ደስ ያላላቸው ሰዎችም እንደሚኖሩ ግልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአገሩ ያሉ ብዙ ሰዎች››

ከተማዪቱ ጸጥ አለች

‹‹ከተማዪቱ ተረጋጋች›› ወይም፣ ‹‹ከተማዪቱ ሰላማዊ ሆነች››

2 Kings 11:21

ኢዮአስ በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሰባት ዓመት ነበር

ኢዮአስ 7 ዓመቱ ነበር

---

Chapter 12

2 Kings 12:1

ኢዩ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት

‹‹ኢዩ በእስራኤል ላይ በነገሠ 7 ዓመት ሲሆነው››

ኢዮአስ መንገሥ ጀመረ

‹‹ኢዮአስ በይሁዳ ነገሠ››

ሳቢያ

‹‹ሳቢያ የተባለች የቤርሳቤህ ከተማ ተወላጅ››

በያህዌ ፊት መልካም ነገር አደረገ

ዐይን ማየትን፣ ማየት ደግሞ ሐሳብንና ፍርድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልካም ነው የሚለውን›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ መልካም ነው ብሎ የሚያስበውን››

ያስተምረው ነበር

‹‹ይመራው ነበር››

ከፍታ ቦታዎቹ ግን አልተወገዱም

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፤ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡ ግን ከፍታ ቦታዎቹን አላፈረሰም››

ሕዝቡ በከፍታዎቹ መሥዋዕት ያቀርብና ዕጣን ያጥን ነበር

በእነዚህ ቦታዎች እንዳያመልኩ ያህዌ ሕዝቡን ከልክሎ ነበር። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መሥዋዕት ለማቅረብና ዕጣን ለማጠን ሕዝቡ ያህዌ ወደማይፈልጋቸው ቦታዎች እየሄደ ነበር››

2 Kings 12:4

በስእለት ወደ ያህዌ ቤት የገባው ገንዘብ

ይህ ቤተ መቅደሱን ለመርዳት ሕዝቡ የሰጠውን ገንዘብ ያመለክታል። በተቀረው የዐረፍተ ነገር ክፍል ግልጽ እንዲሆነው ይህ ገንዘብ በሦስት መልኩ ነበር የሚመጣው።

ያህዌ ልባቸውን ስላነሣሣው የሚሰጥ ገንዘብ

ይህ ሕዝቡ በነጻነት ለያህዌ የሚሰጡትን ገንዘብ ያመለክታል።
2 Kings 12:6
በሃያ ሦስተኛው የኢዮአስ ዘመነ መንግሥት
‹‹ኢዮአስ በነገሠ በሃያ ሦስተኛው ዓመት››
በቤተ መቅደሱ ውስጥ የፈረሰውን ያላደሳችሁት ለምንድነው?
ኢዮአስ ይህን ያለው ካህናቱን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤተ መቅደሱን ማደስ ነበረባችሁ››
የፈረሰውን ለማደስ ይዋል
‹‹የፈረሰውን ለሚያድሱ ሠራተኞች ክፈሉት››
2 Kings 12:9
ይልቁን ዮዳሄ
‹‹ካህናቱ ገንዘብ ከመሰብሰብ ይልቅ ዮዳሄ››
ወደ ያህዌ ቤት በሚያስገባው በስተ ቀኝ በኩል
‹‹ወደ ቤተ መቅደስ በሚገባበት በቀኝ በኩል››
ያስገቡ ነበር
‹‹ሳጥኑ ውስጥ ያስገቡ ነበር›› ወይም፣ ‹‹ገንዘብ መያዣው ውስጥ ያስገቡ ነበር››
የመጣው ገንዘብ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡ ያመጣው ገንዘብ››
ገንዘቡን በየከረጢቱ ውስጥ በማስገባት ቆጠሩ
ብዙ ትርጉሞች ይህን የበለጠ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ተረጉመውታል፤ ‹‹ገንዘቡን ቆጥረው በየከረጢቱ ውስጥ አኖሩት››
ገንዘቡን በየከረጢቱ ማኖር
ለዚህ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ገንዘቡን በከረጢት ማኖር›› ወይም፣ ‹‹ገንዘቡን በከረጢት መቋጠር››
የተገኘው ገንዘብ
‹‹ሳጥን ውስጥ የተገኘው ገንዘብ››
2 Kings 12:11
ተመዝኖ
‹‹ተቆጥሮ››
በሰዎቹ እጅ
‹‹እጅ›› የሚወክለው ሰዎችን ነው፤ ‹‹ለሰዎቹ››
የቤተ መቅደሱን ሥራ በኀላፊነት
‹‹ቤተ መቅደሱን ለሚያደሱት››
ለድንጋይ ጠራቢዎች
ድንጋይ ትክክለኛ ቅርጽ እንዲይዝ የሚጠርቡ ሰዎች
ዕንጨትና ጥርብ ድንጋይ መግዣ
‹‹ዕንጨት ለመግዛት፣ ድንጋይ ለማስጠረብ››
ለማደስ መከፈል ላለበት ሁሉ
‹‹አስፈላጊ ለሆነው ዕድሳት ሁሉ የሚከፈል››
2 Kings 12:13
ለዚያ ግን ምንም አልተከፈለም
‹‹ለቤተ መቅደሱ ሥራ ለመክፈል አልዋለም››
የብር ጽዋዎች መኰስተሪያዎች፣ ድስቶች፣ መለከቶች ወይም ለሌላው የወርቅም ሆነ የብር ሥራ
እነዚህ መሥዋዕት ማቅረብን ወይም በዓላት ማክበርትን ለመሳሰሉ የተለያዩ የቤተ መቅደስ ሥራዎች ካህናቱ የሚጠቀሙባቸው ዕቃዎች ናቸው።
2 Kings 12:15
ለሠራተኞቹ እንዲከፍሉ ገንዘቡ የተሰጣቸው ላይ ተቆጣጣሪ ማድረግ አላስፈለጋቸውም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ገንዘቡን ተቀብለው ለዕድሳቱ ሠራተኞች የሚከፍሉ ሰዎች ላይ ተቆጣጣሪ ማድረግ አላስፈለገም››
ተጠያቂ መሆን
ምን ያህል ገንዘብ እንደ ተሰጠና እንደ ተከፈለ መዝገብ መያዝ
ስለ በደል መሥዋዕት ስለ ኀጢአት መሥዋዕት የሚቀርበው ገንዘብ ወደ ያህዌ ቤተ መቅደስ አይገባም ነበር
ገንዘቡ ለጥገናው ሥራ አይውልም ነበር። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከበደል መሥዋዕትና ከኀጢአት መሥዋዕት የሚገኘው ገንዘብ ለያህዌ ቤተ መቅደስ ዕድሳት ሥራ ለሚደረግ ክፍያ አይውልም ነበር››
2 Kings 12:17
የሶርያ ንጉሥ አዛሄል አጠቃ… አዛሄል ፊቱን አዞረ
ይህ አዛሄልና የሶርያን ሰራዊት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሥ አዛሄልና ሰራዊቱ አጠቁ… ለማጥቃት ፊታቸውን አዞሩ››
አዛሄል
ይህ የሶርያ አገር ንጉሥ ስም ነው።
ያዛት
‹‹አሸንፎ ተቆጣጠራት››
ኢዮሳፍጥና ኢዮሆራም አካዝያስ፣ አባቱ
እነዚህ ቀድሞ የነበሩ የይሁዳ ነገሥታት ናቸው።
ቀደሱ
‹‹ለዩ››
በዕቃ ቤቶቹ የተገኘው ወርቅ
‹‹ግምጃ ቤት ውስጥ ተቀምጦ የነበረ ወርቅ››
አዛሄልም ከኢየሩሳሌም ተመለሰ
ኢዮአስ ለአዛሄል የሰጠው ስጦታ ኢየሩሳሌምን እንዳያጠቃ አደረገው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ አዛሄል ኢየሩሳሌምን ማጥቃቱን ትቶ ተመለሰ››
2 Kings 12:19
ይህ ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለም?
ጥያቄው የቀረበው እነዚህ ነገሮች በጽሑፍ የሰፈሩ መሆናቸውን ለአንባቢው ለማስገንዘብ ነው። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፈዋል››
ሲላ
ይህ ቦታ የት እንደ ሆነ አይታወቅም
ሰምዓት… የዛካር… ዮዛባት… ሽሜር… አሜስያስ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው
ከአባቶቹ ጋር
‹‹አባቶቹ በተቀበሩበት ቦታ››
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹ቀጣዩ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ››

## Chapter 13

2 Kings 13:1
የይሁዳ ንጉሥ የአካዝያስ ልጅ ኢዮአስ በነገሠ በሃያ ሦስተኛው ዓመት
‹‹ኢዮአስ ይሁዳን ለ23 ዓመት ያህል ከገዛ በኋላ
በሰማርያ ከተማ በእስራኤል ላይ ነገሠ
‹‹በሰማርያ በሚገኘው የእስራኤል መንግሥት ገዛ››
ዐሥራ ሰባት ዓመት ገዛ
‹‹ኢዮአካዝ ለ17 ዓመት ንጉሥ ነበረ››
በያህዌ ፊት ክፉ ሥራ ሠራ
የያህዌ ፊት የያህዌን ፍርድና ሚዛን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን››
የኢዮርብዓምን ኀጢአት ተከተለ
‹‹ኢዮርብዓም የሚያደርገውን ኀጢአት አደረገ››
ኢዮአካዝ ከዚሁ ድርጊት አልተመለሰም
ኀጢአትን ማድረግ መተው ከእነርሱ መመለስ እንደ ሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮአካዝ የኢዮርብዓምን ኀጢአት ማድረጉን አልተወም›› ወይም፣ ‹‹ኢዮአካዝ የኢዮርብዓምን ኀጢአት ማድረጉን ቀጠለ››
2 Kings 13:3
የያህዌ ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ
ያህዌ እስራኤልን መቆጣቱ ቁጣው የሚነድ እሳት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ በእስራኤል ላይ በጣም ተቆጣ››
የሶርያው ንጉሥ አዛሄልና ልጁ ቤንሐዳድ በነበሩበት ዘመን ሁሉ አሳልፎ በእጃቸው ሰጣቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው እስራኤልን ነው፤ ‹‹እጅ›› የሚለው እነርሱን የተቆጣጠረውን ኀይል ሥልጣን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሶርያ

ንጉሥ አዛሄልና ልጁ ቤንሐዳድ በተደጋጋሚ እስራኤላውያንን በጦርነት ድል አደረጉ››
ያህዌን ለመነ
‹‹ወደ ያህዌ ጸለየ››
የሶርያ ንጉሥ እስራኤልን እንዴት አድርጐ እንዳስጨነቀ አይቶአል
እነዚህ ሁለት ሐረጐች የሚናገሩት ስለ አንድ ጉዳይ ሲሆን፣ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ እስራኤልን በጣም ማስጨነቁን አዬ››
የሚታደጋቸው ሰው
‹‹የሚያድናቸው ሰው››
ከሶርያውያን ጭቁና (እጅ) ተላቀቁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› እነርሱን የተቆጣጠረ ኀይልና ሥልጣን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሶርያውያን ነጻ አወጣቸው››
2 Kings 13:6
ከኢዮርብዓም ቤት ኀጢአት አልተመለሱም
ኀጢአትን ማቆም ከኀጢአት መመለስ እንደ ሆነ ተናግሯል። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፤ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስራኤል ኢዮርብዓም ሲያደርግ የነበረውን ኀጢአት ማድረግ አልተወም›› ወይም፣ ‹‹እስራኤል ኢዮርብዓም ሲፈጽም የነበረውን ኀጢአት መፈጸም ቀጠለ››
የኢዮርብዓም ቤት
‹‹የኢዮርብዓም ቤተ ሰብ››
አጠፋቸው
‹‹የኢዮአካዝን ሰራዊት ድል አደረገ››
እንደ ዐውድማ ብናኝ አደረገው
የሶርያ ሰራዊት የእስራኤልን ሰራዊት ክፉኛ ድል አደረገ፤ የቀረውም በመከር ጊዜ ዐውድማ ላይ እንደሚረገጥ ብናኝ ጥቅም የለሽ ሆነ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በመከር ጊዜ ሠራተኞች በእግራቸው እንደሚያደቁት ገለባ ረገጣቸው››
2 Kings 13:8
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ጥያቄው የቀረበው የኢዮአካዝ ሥራ በሌላ መጽሐፍ ተጽፎ የሚገኝ መሆኑን ለአንባቢው ለማሳሰብ ነው። 2 ነገሥት 1፥18 ላይ ይህ እንዴት እንደ ተተረጐመ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ በተጻፈበት መጽሐፍ ተጽፎአል።››
ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ ማለት ሞተ ማለት ነው።
2 Kings 13:10
በይሁዳ ንጉሥ በኢዮአስ ሰላሣ ሰባተኛው ዓመት
‹‹ዮአስ ይሁዳን ለ37 ዓመት ከገዛ በኋላ››
የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ በሰማርያ ከተማ እስራኤል ላይ መንገሥ ጀመረ
‹‹የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ በሰማርያ ሆኖ እስራኤልን መግዛት ጀመረ››
ዮአስ
ይህ የኢዮአካስ ልጅ የእስራኤል ንጉሥ ስም ነው።
በያህዌ ፊት ክፉ ሥራ ሠራ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ፊት›› የእግዚአብሔርን ሐሳብና ፍርድ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ ነው የሚለውን አደረገ››
የኢዮርብዓምን ኀጢአት ማድረግ አልተወም
ኀጢአትን ማቆም ኀጢአትን መተው እንደ ሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዮአስ ኢዮርብዓም ሲያደርገው የነበረውን ኀጢአት ማድረጉን አልተወም›› ወይም፣ ‹‹ዮአስ የኢዮርብዓምን ኀጢአት ማድረጉን ቀጠለ››
እስራኤልን ካሳተበት ኀጢአት
‹‹ኢዮርብዓም እስራኤል እንዲበደል ካደረገበት››
በዚያው ገፋበት
ኀጢአት በኀጢአት መንገድ መሄድ እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዮአስ ይህንኑ ኀጢአት ማድረጉን ቀጠለ››
2 Kings 13:12
በይሁዳ ንጉሥ በአሜስያስ ላይ ያካሄደው ጦርነት
እዚህ ላይ፣ የዮአስ፣ ብርታት የእርሱ ጉልበት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ ሰራዊት ጋር ሲዋጋ የእርሱ ሠራዊት ያሳየው ኀይል››
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ጥያቄው የቀረበው ኢዮአስ ያደረገው ሁሉ በሌላ የታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ የሚገኝ መሆኑን ለአንባቢው ማሳሰቢያ ለመስጠት ነው። 2 ነገሥት 1፥18 ይህ እንዴት እንደ ተተረጐመ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ በሚጻፍበት መጽሐፍ ተጽፎአል።››
ዮአስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ ሞተ ማለት ነው።
ኢዮርብዓም በዙፋኑ ተቀመጠ
እዚህ ላይ፣ ‹‹በዙፋን፣ መቀመጥ›› መንገሥ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእርሱ በኋላ ኢዮርብዓም ነገሠ›› ወይም፣ ‹‹ቀጥሎ ኢዮርብዓም ነገሠ››
2 Kings 13:14
አለቀሰላት
‹‹ኤልሳዕ ታሞ ስለ ነበር አለቀሰ››
አባቴ! አባቴ!
ኤልሳዕ በሥጋ የንጉሡ አባት አልነበረም። ንጉሥ ዮአስ እንዲህ ያለው ለአክብሮት ነው።
የእስራኤል ሠረገሎችና ፈረሰኞች ሊወስዱህ ነው
ይህ 2 ነገሥት 2፥11-12 ላይ ያለውን የኤልያስን ወደ ሰማይ መወሰድ ያመለክታል። ዮአስ ይህን ያለው ኤልሳዕ እንደሚሞት ለመናገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ሠረገሎችና ፈረሰኞች ወደ ሰማይ ሊወስዱህ ነው››
ፈረሰኞች
እነዚህ ሠረገሎችን የሚነዱ ሰዎች ናቸው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሠረገሎች ነጂ››
2 Kings 13:17
አጠቃላይ መረጃ
ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ለዮአስ እየተናገረ ነው።
የምሥራቁን መስኮት ክፈት
‹‹በስተ ምሥራቅ በኩል ያለውን መስኮት ክፈት›› ወይም ‹‹ወደ ምሥራቅ ያለውን መስኮት ክፈት››
ከፈተውም
ይህ የሆነው ዮአስ ቀስቱንና ፍላጻዎቹን ከወሰደ በኋላ ስለ ነበር፤ መስኮቱን የከፈተው አገልጋዩ ሳይሆን አይቀርም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አገልጋዩም ከፈተው››
አስፈነጠረ
‹‹ዮአስ ፍላጻውን አስፈነጠረ››
ይህ የያህዌ የድል ቀስት! ሶርያ ድል የምትሆንበት ቀስት ነው!
በፍላጻውና በድል መካከል ያለውን ግንኙነት በጣም ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሶርያውያን ላይ ድል እንደሚሰጥህ ይህ ቀስት ከያህዌ የሆነ ምልክት ነው›› ወይም ‹‹ይህ ቀስት ያህዌ በሶርያውያን ላይ የሚሰጥህን ድል ያመለክታል››
አፌቅ
ይህ በእስራኤል ያለ ከተማ ነው።
የእግዚአብሔር ሰው ተቆጣው
‹‹ኤልሳዕ በንጉሥ ዮአስ በጣም ተቆጣ››
እስክታጠፋቸው ድረስ
‹‹ጨርሶ እስክታወድማቸው ድረስ›› ወይም፣ ‹‹እስክትደመስሳቸው ድረስ››
2 Kings 13:20
እነሆ
ይህ የዋናውን ታሪክ ፍሰት ገታ ለማድረግ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። ይህ ክፍል ቀጥሎ ላለው ታሪክ ዳራ የሚሆን መረጃ ይሰጣል።
በየዓመቱ መጀመሪያ
‹‹በመፀው ወቅት በየዓመቱ››
አንድ ሰው ሲቀብሩ
‹‹አንዳንድ እስራኤላውያን ሰው ሲቀብሩ››
የሞዓባውያንን ቡድን አዩ
ሞዓባውያንን መፍራታቸውን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሞዓባውያን አደጋ ጣዮች ወደ እነርሱ ሲመጡ አይተው ፈሩ።
የኤልሳዕ መቃብር
‹‹ኤልሳዕ የተቀበረበት ቦታ››

ሰውየው የኤልሳዕን ዐፅም እንደ ነካ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ሰውየው›› የሚያመለክተው የሰውየውን ሬሳ ነው፡፡ ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰውየው ሬሳ የኤልሳዕን ዐፅም እንደ ነካ››

ድኖ በእግሩ ቆመ

‹‹የሞተው ሕይወት አገኘ፤ ተነሥቶም ቆመ››

2 Kings 13:22

ያህዌ ግን ራራላቸው፤ አዘነላቸው

ይህን ታሪክ በትንንሹ መከፋፈል ይጠቅማል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ ስላዘነ ረዳቸው››

ስለዚህም ያህዌ አላጠፋቸውም

ያህዌ እስራኤልን ያላጠፋው ከኪዳኑ የተነሣ ነው፡፡ ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ያላጠፋቸው በዚህ ምክንያት ነው›› ወይም፣ ‹‹ከኪዳኑ የተነሣ ያህዌ አላጠፋቸውም››

ከፊቱም አላስወገዳቸውም

የያህዌ ችላ ማለት እርሱ ካለበት ቦታ እስራኤልን በግልጽ ከመተው ጋር ተመሳስሎአል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልተዋቸውም››

አዛሄል... ቤንሐዳድ... ዮአስ... ኢዮአካዝ

እነዚህ የነገሥታት ስሞች ናቸው

ዮአስ ሦስት ጊዜ ድል አደረገው

እዚህ ላይ ስለ ‹‹ዮአስ›› እና፣ ‹‹እርሱ የሚለው የሚያመለክተው ስለ ነገሥታቱና ስለ ሰራዊቱ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዮአስ ሰራዊት የቤንሐዳድን ሰራዊት ሦስት ጊዜ ድል አደረገ››

የእስራኤልንም ከተሞች መልሶ ያዘ

‹‹ዮአስ ቤንሐዳድ ይዞአቸው የነበሩትን የእስራኤል ከተሞች ተቆጣጠረ››

---

# Chapter 14

2 Kings 14:1

የእስራኤል ንጉሥ የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት

‹‹የኢዮአካዝ ልጅ ዮአስ የእስራኤል ንጉሥ በሆነ በሁለተኛው ዓመት››

የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ በይሁዳ መንገሥ ጀመረ

‹‹የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ››

መንገሥ ሲጀምር ሃያ አምስት ዓመቱ ነበር፡፡

‹‹ንጉሥ ሲሆን 25 ዓመት ሆኖት ነበር››

በኢየሩሳሌም ተቀምጦ ሃያ ዘጠኝ ዓመት ገዛ

‹‹ለ29 ዓመት በኢየሩሌም ነግሦ ነበር››

ዮዓዳን

(ስሞች እንዴት እንደሚረጐሙ ተመልከት)

በያህዌ ፊት መልካም ነገር አደረገ፤ ግን እንደ አባቱ እንደ ዳዊት አልነበረም፡፡

‹‹የያህዌ ፊት›› የእርሱን ዐይን፣ የእርሱ ዐይን ደግሞ ፍርዱን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሜስያስ በያህዌ ፊት ብዙ መልካም ነገሮች አደረገ፤ ሆኖም አባቱ ዳዊት ያደረገውን ያህል መልካም ነገሮች አላደረገም››

የአባቱን የዮአስን ፈለግ ተከተለ

ዮአስ ለያህዌ ታዘዙ መልካም ነገርንም አደረገ፤ ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አባቱ ዮአስ ያደረገውን መልካም ነገር አደረገ››

2 Kings 14:4

አጠቃላይ መረጃ

አሜስያስ የይሁዳ ንጉሥ ሆኖ የመግዛቱ ታሪክ ቀጥሏል፡፡

ከፍታ ቦታዎቹን ግን አላስወገደም

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ከፍታ ቦታዎች ለአረማውያን አምልኮ የሚውሉ ነበሩ፡፡ ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከፍታ ቦታዎቹን አላስወገደም››

መሥዋዕት ማቅረቡንና ዕጣን ማጨሱን

ከፍታ ቦታዎቹ ለአረማውያን አምልኮ የሚውሉ ናቸው፡፡ ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በከፍታ ቦታዎቹ ለአረማውያን አማልክት መሥዋዕት አቀረበ፤ ዕጣን አጠነ››

በዚሁ ጊዜ

ይህ ጥቅም ላይ የዋለው አዲስ ሁኔታ ለማስተዋወቅ ነው፡፡

መንግሥቱ እንደ ጸናለት

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሜስያስ ሲደላደልና መንግሥታዊ ሥልጣኑና አገዛዙ ሲረጋጋ››

አገልጋዮቹን ገደለ

አሜስያስ ባለ ሥልጣኖቹን እንዲገድሉ ያደረገውሌሎች ሹማምንት በማዘዝ ሊሆን ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አገልጋዮቹ ባለ ሥልጣኖቹን እንዲገደሉ አዘዘ››

2 Kings 14:6

አጠቃላይ መረጃ

አባቱ ንጉሥ ዮአስ ከሞተ በኃላ ንጉሥ አሜስያስ ምን እንዳደረገ ተራከው ይናገራል››

የነፍስ ገዳዩን ልጆች አልገደላቸውም

ንጉሥ አሜስያስ አባቱን የገደሉ ሰዎችን ልጆች እንዲገድሉ አገልጋዮቹን አለዘዘም፡፡ እንዲገደሉ ቢፈልግ ኖሮ፣ አገልጋዮቹን ያዝዝ ነበር እንጂ፣ ያንን እርሱ ራሱ ማድረግ የለበትም፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አገልጋዮቹ የእነዚያን ባለሥልጣን ልጆች እንዲገደሉ አላዘዘም››

አባቶች በልጆቻቸው፣ ልጆችም በአባቶቻቸው ኀጢአት መገደል የለባቸወም

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች አባቶችን ለልጆቻቸው ኀጢአት፣ ልጆችንም በአባቶቻቸው ኀጢአት መግደል የለባቸውም››

እያንዳንዱ በራሱ ኀጢአት ይገደል

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እያንዳንዱ ሰው በኀጢአቱ መሞት አለበት››

እርሱ ገደለ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› የሚያመለክተው ሰራዊቱን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሜስያስ ሰራዊት ገደለ›› ወይም፣ ‹‹የአሜ ስያስ ወታደሮች ገደሉ››

ዐሥር ሺህ ወታደሮች

‹‹10,000 ወታደሮች››

የጨው ሸለቆ

ይህ ከሙት ባሕር በስተ ደቡብ የሚገኝ ቦታ ስም ነው፡፡

ሴላን በጦርነት የያዘና

የሚናገረው ስለ ንጉሥ አሜስያስ ሲሆን፣ እርሱንና ሰራዊቱን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የንጉሥ አሜስያስ ሰራዊት የሴላን ከተማ ያዘ››

ሴላ... ዮቅትኤል

ለሴላ ከተማ ሌላ ስም አወጡላት፡፡ አዲሱ ስሟ ዮቅትኤል ነበር፡፡

2 Kings 14:8

አሜስያስ የኢዩ ልጅ፣ የኢዮአካዝ ልጅ ወደ ሆነው ወደ እስራኤል ንጉሥ ወደ ኢዮአስ፣ ‹‹ናና ፊት ለፊት ይዋጣልን›› ብሎ መልእክተኞች ላከበት

እዚህ ላይ፣ ‹‹ይዋጣልን›› የሚለው ሰራዊቱንም ይጨምራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚያም አሜስያስ፣ ‹‹መጥተህ ሰራዊቶቻችን ጦርነት ይግጠሙ›› በማለት ወደ ንጉሥ ኢዮአስ መልእክተኞች ላኩ››

የሊባኖስ ኩርንችት... ኩርንችቱን በእግሩ ረገጠው

ይህ የቃላት ስዕልና ዕንቆቅልሽ ነው፡፡ የሊባኖስ ዝግባ ትልቅ ሲሆን፣ ኩርንችት ደግሞ ትንሽና የማይረባ ነው፡፡ ኢዮአስ ራሱን ከሊባኖስ ዝግባ፣ አሜስያስን ከኩርንችት ጋር በማመሳሰል ጥቃት እንዳይሰነዝር አሜስያስን እያስጠነቀቀ ነው፡፡ በቋንቋህ ተመሳሳይ ንጽጽር ካለህ ልትጠቀምበት ትችላለህ፡፡

ኩርንቺት

እሾኻማ ቁጥቋጦ

ሴት ልጅህን ለልጄ በሚስትነት ስጠው

ይህን ቀጥተኛ ጥቅስ ቀጥተኛ ወዳልሆነ ጥቅስ መለወጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዝግባው ሴት ልጁን ለኩርንቺቱ ወንድ ልጅ እንዲድርለት ጠየቀው››

በእርግጥ ኤዶምን ድል አድርገሃል

ይህ ኢዮአስ ለአሜስያስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ክፍል ነው፡፡ ‹‹አሜስያስ አንተ በእርግጥ ኤዶምን ድል አድርገሃል››

ልብህ አለመጠን አይኩራራ

ይህ ትዕቢትን የሚያመለክት የፈሊጥ አነጋገር ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባደረግኸው ነገር በጣም ታብየሃል››

ድል በማድረግህ አትንጠራራ

‹‹ባገኘኸው ድል አትርካ››

የራስህን ውድቀት ለምን ትሻለህ?

ኢዮአስ ይህን የጠየቀው እርሱን እንዳያጠቃ አሜስያስን ለማስጠንቀቅ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራስህ ላይ ሽንፈት የሚያመጣብህን ጠብ መጫር የለብህም››

2 Kings 14:11

አሜስያስ ግን አልሰማም

እዚህ ላይ፣ ‹‹አልሰማም›› ማለት ማስጠንቀቂያውን አልተቀበለም ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይሁን እንጂ፣ አሜስያስ የኢዮአስን ማስጠንቀቂያ አልተቀበለም››

ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአስ አጠቃ… ከይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ ጋር ገጠሙ››

የእነዚህ ነገሥታት ሰራዊት አብረው ወደ ጦርነት ሄዱ፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮአስና ሰራዊቱ አሜስያስና ሰራዊቱን ለመግጠም ወደ ውጊያ ሄዱ››

ቤትሳሚስ

ይህ እስራኤል ድንበር አጠገብ ያለ የይሁዳ ከተማ ነው፡፡

ይሁዳ በእስኤል ድል ሆነ

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስራኤል ይሁዳን አሸነፈ››

እያንዳንዱም ሸሸ

‹‹ይሁዳ ሰራዊት ውስጥ የነበረ ሰው ሁሉ ወደ ቤቱ ሸሸ››

2 Kings 14:13

አጠቃላይ መረጃ

የእስራኤል ሰራዊት በቤትሳሚስ የይሁዳን ሰራዊት ድል ካደረገ በኃላ የሆነ ነው፡፡

እርሱ መጣ… እርሱ ወሰደ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› የተባለው የኢዮአስ ሰራዊት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮአስና ሰራዊቱ መጡ… የኢዮአስ ሰራዊት ወሰዱ››

የኤፍሬም ቅጥር በር… የማእዘን ቅጥር በር

እነዚህ በኢየሩሳሌም ቅጥር ላይ የነበሩ በሮች ናቸው፡፡

አራት መቶ ክንድ

‹‹180 ሜትር ያህል››

ክንድ

አንድ ክንድ 46 ሴንቲሜትር ያህል ነው፡፡

ምርኮኞችን ይዞ ወደ ሰማርያ ተመለሰ

ይህ የሚያመለክተው አሜስያስ እንደ ገና እንዳያጠቃ ለመከላከል ኢዮአስ እነዚህን ምርኮኞች መውሰድ መፈለጉን ነው፡፡ ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ አሜስያስ ችግር እንዳይፈጥርባቸው ለማድረግ እስረኞችን ወደ ሰማርያ ወሰዱ››

2 Kings 14:15

ይህ ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?

ይህ ጥያቄ የቀረበው የኢዮአካዝ ሥራ በሌላ መጽሐፍ ተጽፎ የሚገኝ መሆኑን አንባቢውን ለማሳሰብ ነው፡፡ 2 ነገሥት 1፥18 ላይ ይህ ሐረግ እንዴት እንደ ተተረጐመ ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ በተጻፈበት መጽሐፍ ተጽፎአል››

ከዚያም ኢዮአስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ

ይህ ሞተ የማለት ሌላ ቃል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚያም ኢዮአስ ሞተ››

በእግሩ ተተክቶ ነገሠ

‹‹ከእርሱ በኃላ ነገሠ››

2 Kings 14:17

በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?

ይህ ጥያቄ የቀረበው እነዚህ ሁሉ ተጽፈው ያሉ መሆኑን አንባቢውን ለማሳሰብ ነው፡፡ 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህ ሐረግ እንዴት እንደ ተተረጐመ ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የይሁዳ ነገሥታት ታሪክ በተጻፈበት መጽሐፍ ተጽፈዋል››

አሜስያስ ላይ በኢየሩሳሌም አሤሩበት

ሤራ አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር ላይ ጉዳት ለማድረስ በሚስጢር ማቀድ ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኢየሩሳሌም አንዳንድ ሰዎች አሜስያስ ላይ ተማከሩበት››

ለኪሶ

ይህ በደቡብ ምዕራብ ይሁዳ ያለ ከተማ ነው፡፡

እነርሱ ግን የሚከታተሉት ሰዎች ወደ ለኪሶ ላኩ

‹‹ሤራውን የጠነሰሱ ዎች አሜስያስን እንዲከታተሉ ሌሎች ሰዎች ወደ ለኪሶ ላኩ››

2 Kings 14:20

አጠቃላይ መረጃ

ይህ የሆነው አሜስያስ ከሞተ በኃላ ነው፡፡

በፈረስ ተጭኖ አመጡት

‹‹የአሜስያስን ሬሳ በፈረስ ጭነው አመጡት››

የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ ዕድሜው ዐሥራ ስድስት ዓመት የሆነውን ዓዛርያስን በአባቱ በአሜስያስ ፈንታ አነገሡት

ይህ አጠቃላይ አነጋገር ነው፡፡ አንዳንድ ንጉሥ መሆኑን የማይወዱ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የይሁዳ ሕዝብ ዐሥራ ስድስት ዓመት የሆነውን ዓዛርያስን በአባቱ በአሜስያስ ቦታ አነገሡት››

ኤላትን እንደ ገና የሠራ ዓዛርያስ ነበር

ዓዛርያስ ይህን ያደረገው ብቻውን አይደለም፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኤላት እንድትሠራ ያዘዘ ዓዛርያስ ነበር›› ወይም፣ የኤላትን እንደ ገና መሠራት ሲቆጣጠር የነበሩ ዓዛርያስ ነበር››

ዓዛርያስ

በዚህ ዘመን ይህ ንጉሥ ይበልጥ የሚታወቀው፣ ‹‹ዖዝያን›› በተሰኘ ስሙ ነው፡፡

ኤላት

የይሁዳ ከተማ

ወደ ይሁዳ መለሳት

‹‹እንደ ገና ወደ ይሁዳ አመጣት››

ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ

ይህ ሞተ ለማለት ነው፡፡

2 Kings 14:23

አጠቃላይ መረጃ

ይህ ንጉሥ ከሆነ በኃላ ንጉሥ ዖዝያን ያደረገውን ይናገራል፡፡

አሜስያስ በነገሠ በዐሥራ አምስተኛው ዓመት

‹‹አሜስያስ ንጉሥ በሆነ 15ኛው ዓመት››

አርባ አንድ ዓመት

‹‹41 ዓመት››

በያህዌ ፊት ክፉ

‹‹ፊት›› የፍርድ ወይም የግንዛቤ ምሳሌ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ሐሳብ ክፉ የሆነ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን››

ከኢዮርብዓም ኀጢአት አልተመለሰም

ኀጢአትን መተው መንገድን መተው እንደሆነ ተነግሯል፡፡ ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮርብዓም ሲያደርግ የነበረውን ኀጢአት ማድረጉን አልተወም›› ወይም፣ ‹‹ኢዮርብዓም ሲያደርግ የነበረውን ኀጢአት ማድጉን ቀጠለ››

ድንበር አስመለሰ

ይህ ሰራዊቱ ድንበሩን ወደ ምድሩ መለሰ ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰራዊቱ ከዚያ በፊት የእስራኤል የነበሩ ግዛቶችን እንደ ገና ድል አደረገ››

ሌቦሐማት

ይህ ሐማት ተብሎም ይጠራል፡፡

የአረባ ባሕር

‹‹ሙት ባሕር››

2 Kings 14:26

በጣም መራራ ነበር

በጣም ከባድ የሆነ ስቃይ፣ መራራ ጣዕም እንዳለው ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ከባድ ነበር››

እስራኤልን የሚታደግ አልነበሩም

‹‹እስራኤልን ማዳን የሚችል አልነበረም››

ጠረገ

እስራኤልን ጨርሶ ማጥፋት ያህዌ ጠረጋቸው ማለት መሆኑ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሙሉ በሙሉ አጠፋቸው››

የእስራኤል ስም

‹‹የእስራኤል ስም›› እስራኤልንና ነዋሪዎቹን ሁሉ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ››

ከሰማይ በታች

‹‹በምድር››

በኢዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም እጅ ታደጋቸው

‹‹እጅ›› የኀይል ሌላ ስም ነው፡፡ ‹‹ኢዮአስ›› ኢዮአስንና ሰራዊቱን ሁሉ ይወክላል፡፡

አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድል እንዲያደርግ ንጉሥ ኢዮርብዓምንና ሰራዊቱን ረዳ››
2 Kings 14:28
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ጥያቄው የቀረበው የኢዮአካዝ ተግባር በሌላ የታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ እንደሚገኝ ለአንባቢ ለማሳሰብ ነው። 2 ነገሥት 1፥18 ላይ ይህ ሐረግ እንዴት እንደ ተተረጐመ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ በተጻፈበት መጽሐፍ ተጽፎአል››
ኢዮርብዓም ከአባቶቹ ከእስራኤል ነገሥታት ጋር አንቀላፋ
x

---

Chapter 15
2 Kings 15:1
ኢዮርብዓም በነገሠ በሃያ ሰባተኛው ዓመት
ይህ የአገዛዝ ዘመኑ ሃያ ሰባተኛ ዓመት መሆኑን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮርብዓም በነገሠ በ27 ዓመት››
ዓዛርያስ
በዚህ ዘመን ይህ ንጉሥ ይበልጥ የሚወቀው፣ ‹‹ያዝያን በተሰኘው ስም ነው።
ይከልያ
ይህ የዓዛርያስ እናት ስም ነው
መልካም ነገር አደረገ
‹‹ዓዛርያስ መልካም ነገር አደረገ››
በያህዌ ዐይን ፊት መልካም ነገር
ዐይን ማየትን ይወክላል፤ ማየት ደግሞ ሐሳብና ፍርድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ መልካም ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ መልካም የሚለውን››
2 Kings 15:4
በየኮረብታው ላይ ያሉት የማምለኪያ ስፍራዎች አልተወገዱም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኮረብቶቹን ማንም አላስወገደም›› ወይም፣ ‹‹ዓዛርያስ ኮረብቶቹ እንዲወገዱ አላደረገም››
አልተወገደም
መወገድ ጨርሶ መደምሰስ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልተደመሰሱም ነበር››
እስከሚሞትባት ቀን ደረሰ
አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስከ ዕለተ ሞቱ ደረሰ››
ቤተ ሰቡን የሚያስተዳድረው የንጉሡ ልጅ ኢዮአታም ነበር
‹‹ቤተ ሰቡን›› የሚለውን በቤተ መንግሥቱ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። ዓዛርያስ ለምጻም ስለ ነበር በተለየ ቤት መኖር ነበረበት። ልጁ ኢዮአታም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።
በቤቱ ሁሉ ኀላፊ ሆነ
በቤቱ ሁሉ ኀላፊ መሆን በቤቱ ላይ ባለ ሥልጣን መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በቤቱ ሁሉ ባለ ሥልጣን ሆነ›› ወይም፣ ‹‹በዓዛርያስ ቤተ መንግሥት ባለ ሥልጣን ሆነ››
2 Kings 15:6
በይሁዳ… የተጻፈ አይደለምን?
ይህ ጥያቄ የቀረበው ዓዛርያስን የሚመለከት መረጃ በዚህ ሌላ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን ለአንባቢው ለማሳሰብ ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳ… ተጽፎአል›› ወይም፣ ‹‹በይሁዳ… ማንበብ ትችላላችሁ››
ዓዛርያስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
አንቅልፍ ሞትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዓዛርያስ እንደ አባቶቹ ሞተ›› ወይም፣ ‹‹እንደ አባቶቹ ዓዛርያስም ሞተ››
ከአባቶቹ ጋር ቀበሩት
‹‹ቤተ ሰቡ አባቶቹ በተቀበሩበት ቀበሩት››
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› የሚለው ሐረግ፣ ‹‹በእርሱ ቦታ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዓዛርያስ ቦታ ንጉሥ ሆነ››
2 Kings 15:8
ዓዛርያስ በነገሠ በሠላሳ ስምንተኛው ዓመት
ይህ የአገዛዙ ሠላሳ ስምንተኛው ዓመት መሆኑን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ 38ኛው ዓመት››
የኢዮርብዓም ልጅ ዘካርያስ
ይህ ኢዮርብዓም በዚህ ስም የሚጠራ ሁለተኛው የእስራኤል ንጉሥ ነው። የንጉሥ ዮአስ ልጅ ነው።
በሰማርያ ከተማ በእስራኤል ላይ ስድስት ወር ነገሠ
ሰማርያ የእስራኤል ንጉሥ በሆነ ጊዜ ንጉሥ ዘካርያስ የሚኖርባት ከተማ ነበረች። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሰማርያ ሆኖ፣ በእስራኤል ላይ ስድስት ወር ነገሠ››
ክፉ አደረገ
‹‹ዘካርያስ ክፉ አደረገ››
በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ አደረገ
የያህዌ ዐይን የሚወክለው የያህዌን ፍርድ ነው። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመለከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነውን›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን››
ከናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ኀጢአት አልተመለሰም
ከኀጢአት መመለስ ያንን አለማድረግን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዘካርያስ የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓምን ኀጢአት ማድረግን እንቢ አላለም›› ወይም፣ ‹‹የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ያደረገውን ኀጢአት አደረገ››
የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም
ይህ ኢዮርብዓም የእስራኤልን መንግሥት ከመሠረቱ ዐሥሩ ሰሜናዊ ነገዶች የመጀመሪያው ንጉሥ ነበር።
እስራኤልን ካሳተበት ኀጢአት
እዚህ ላይ ‹‹እስራኤል›› በእስራኤል መንግሥት ያለውን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤልን ሕዝብ ካሳተበት ኀጢአት››
2 Kings 15:10
ሰሎም… ያቤስ
እነዚህ የሁለት ሰዎች ስም ናቸው።
በዘካርያስ ላይ
‹‹በንጉሥ ዘካርያስ ላይ››
ኢብልዓም
ይህ የከተማ ስም ነው።
በእግሩም ተተክቶ ነገሠ
ሰሎም በዘካርያስ ቦታ ንጉሥ ሆነ
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተመዝግቦአል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተመዝግቦ ካለበት መጽሐፍ ማንበብ ትችላላችሁ።››
ይህ የያህዌ ቃል ነበር
ቁጥር 10 ላይ የተነገሩት ሁኔዎታዎች የያህዌ ቃል ፍጻሜዎች ነበሩ ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዘካርያስ ላይ የደረሰው በያህዌ ቃል መሠረት ነበር›› ወይም፣ ‹‹ዘካርያስ ላይ በደረሰው የያህዌ ቃል ተፈጸመ››
ልጆችህ እስከ አራት ትውልድ ደረስ በእስራኤል ዙፋን ላይ ይቀመጣሉ።
ዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልጆችህ እስከ አራት ትውልድ ደረስ የእስራኤል ነገሥታት ይሆናሉ››
2 Kings 15:13
የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በሠላሳ ዘጠነኛው ዓመት
ይህ የእርሱ አገዛዝ ሠላሳ ዘጠነኛው ዓመት እንደ ነበር በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዓዛርያስ የይሁዳ ንጉሥ በሆነ 39 ዓመቱ››
ሰሎም… ኢያቤስ
እነዚህ የሁለት ሰዎች ስም ናቸው። 2 ነገሥት 15፥10 ላይ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
ምናሔም… ጋዲ
እነዚህ የሁለት ሰዎች ስሞች ናቸው።
በሰማርያ ተቀምጦ አንድ ወር ብቻ ገዛ
የእስራኤል ንጉሥ በሆነ ጊዜ የሚቀመጠው በሰማርያ ከተማ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰሎም በሰማርያ ተቀመጠ፤ በእስራኤል ላይ አንድ ወር ብቻ ነገሠ››
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› ማለት፣ ‹‹በእርሱ ቦታ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

‹‹በሰሎም ፈንታ ነገሠ››
2 Kings 15:15
የጠነሰሰውም ሤራ
‹‹ሤራ›› የተሰኘውን ቃል፣ ‹‹ዕቅድ›› ብሎ መተርጐም ይቻላል። ይህ ሤራ ምን እንደ ነበር በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ንጉሥ ዘካርያስን ለመግደል ያወጣው ዕቅድ›› ወይም፣ ‹‹ንጉሥ ዘካርያስን መግደሉ››
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎአል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ከተጻፈበት መጽሐፍ ማንበብ ትችላላችሁ።››
ቲፍሳ
ይህ የከተማ ስም ነው። አንዳንድ ቅጂዎች፣ ‹‹ታፑ›› ይላሉ። ይህ የሌላ ከተማ ስም ነው።
2 Kings 15:17
የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በሠላሳ ዘጠነኛው ዓመት
ይህ የአገዛዙ ሠላሳ ዘጠነኛው ዓመት እንደ ሆነ በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ዓዛርያስ የይሁዳ ንጉሥ በሆነ በ39 ዓመት››
በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር
የያህዌ፣ ዐይን የያህዌን ፍርድ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን››
ዘመኑንም ሁሉ
‹‹ዘመን›› የሚለው፣ ‹‹በኖረበት›› ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በሕይወት በኖረበት ጊዜ ሁሉ››
ከናባጥ ልጅ ከኢዮርብዓም ኀጢአት አልተመለሰም
ከኀጢአት መራቅ ያንን ኀጢአት አለማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ዘካርያስ የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ኀጢአት ማድረግን እንቢ አላለም›› ወይም፣ ‹‹የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ያደረገውን ኀጢአት አደረገ››
እስራኤልን ካሳተበት ኀጢአት
እዚህ ላይ ‹‹እስራኤል›› የሚለው ቃል፣ የእስራኤልን መንግሥት ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ኀጢአት እንዲሠሩ ካደረገው››
2 Kings 15:19
የአሦር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌልሶር ምድሪቱን ወረረ
‹‹የአሦር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌልሶር›› የሚለው ቴልጌልቴልፌልሶርንና ሰራዊቱን ይወክላል
በምድሪቱ መጣ
‹‹በምድሪቱ መጣ›› የሚለው ምድሪቱን ለመውረር ለማለት ነው። ‹‹ምድሪቱ›› የእስራኤልን ምድር ሲሆን እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤልን ሕዝብ ለመውረር ከሰራዊቱ ጋር መጣ››
አንድ ሺህ መክሊት ብር
‹‹1000 መክሊት ብር›› ይህን ወደ ዘመኑ ምንዛሬ መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሠላሳ ሦስት ኪሎ ግራም ብር›› ወይም፣ ‹‹ሠላሳ ሦስት ሜትሪክ ቶን ብር››
የቴልጌልቴልፌልሶር ርዳታ ለማግኘት
‹‹ርዳታ›› የሚለውን፣ ‹‹ድጋፍ›› በማለት መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቴልጌልቴልፌልሶር እንዲደግፈው››
የእስራኤልን መንግሥት በእጁ ለማጽናት
የእስኤልን መንግሥት በእጁ ማጽናት መንግሥቱን መግዛት ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በእስራኤል መንግሥት ላይ አገዛዙን ለማጠናከር››
ይህን ገንዘብ ከእስራኤል ሰበሰበ
‹‹ይህን ገንዘብ ከእስራኤል ወሰደ››
አምሳ ሰቅል ብር
ይህን ወደ ዘመኑ ምንዛሬ መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ስድስት መቶ ግራም ብር›› ወይም፣ ‹‹የኪሎ ግራም ሦስት አምስተኛ ብር››
በዚያች ምድር አልቆየም
‹‹በእስራኤል ምድር አልቆየም››
2 Kings 15:21
በእስራኤል... ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን
ይህ ጥያቄ የቀረበው ምናሔን የተመለከተ መረጃ በሌላው መጽሐፍ የሚገኝ መሆኑን አንባቢን ለማሳሰብ ነው። 2 ነገሥት 1፥18 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ በተጻፈበት መጽሐፍ ተጽፎአል››
ምናሔም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
አንቀላፋ ሞተ ማለት ነው። 2 ነገሥት 10፥35 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምናሔም እንደ አባቶቹ ሞተ›› ወይም፣ ‹‹እንደ አባቶቹ ምናሔም ሞተ››
ፋቂስያስ
ይህ የሰው ስም ነው።
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› የሚለው ሐረግ፣ ‹‹በቦታው›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በምናሔም ቦታ ነገሠ››
2 Kings 15:23
የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በአምሳኛው ዓመት
ይህ የአገዛዙ አምሳኛው ዓመት መሆኑን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ 50ኛ ዓመት››
ፋቂስያስ
ይህ የሰው ስም ነው።
በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር
የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን ነገር››
ከናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ኀጢአት አልተመለሰም ኀጢአትን መተው ያንን አለማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ፋቂስያስ የናባጥ ልጅ የኢዮርብዓምን ኀጢአት
ማድረግን እንቢ አላለም›› ወይም፣ ‹‹የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ያደረገውን ኀጢአት አደረገ››
እስራኤልን ካሳተበት ኀጢአት
እዚህ ላይ፣ ‹‹እስራኤል›› በእስራኤል መንግሥት ያለውን ሕዝብ ይወክላል።
2 Kings 15:25
ፋቁሔ... ሮሜልዩ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው
አሤረበት
‹‹ሊገድለው በስውር መከረ››
አምሳ ሰዎች
‹‹50 ሰዎች››
አርጎብ... አርያ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው
የቤተ መንግሥት ምሽግ
‹‹የተመሸገ የቤተ መንግሥቱ አካል›› ወይም፣ ‹‹የቤተ መንግሥቱ መከለያ ቦታ››
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› የሚለው፣ ‹‹በእርሱ ቦታ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በፋቁሔ ቦታ ነገሠ››
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎአል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ይህን በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ማንበብ ይቻላል››
2 Kings 15:27
የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ በነገሠ በአምሳኛው ሁለተኛው ዓመት
ይህ በእርሱ አገዛዝ አምሳ ሁለተኛው ዓመት መሆኑን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ 52ኛ ዓመት››
በያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር አደረገ
የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ ነው የሚለውን››
ከናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ኀጢአት አልተመለሰም
ከኀጢአት መመለስ ያንን አለማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ዘካርያስ የናባጥ ልጅ የኢዮርብዓምን ኀጢአት ለማድረግ እንቢ አላለም›› ወይም፣ ‹‹የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓምን ኀጢአት አደረገ››
2 Kings 15:29
በእስራኤል ንጉሥ በፋቁሔ ዘመን
ይህ የሚያመለክተው የፋቁሔን የግዛት ዘመን መሆኑን በግልጽ ማስቀመጥ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሥ ፋቁሔ የእስራኤል ንጉሥ በነበረበት ዘመን›› ወይም፣ ‹‹በእስራኤል ንጉሥ በፋቁሔ ዘመን››
ቴልጌል-ቴልፌልሶር
2 ነገሥት 15፥19 ላይ ይህ ሰው፣ ‹‹ፑል›› ተብሎአል።
ዒዮን… አቤልቤትመዓካን… ያኖን… ቃዴስ… ሐጾር… ገለዓድ… ገሊላ…
እነዚህ የከተሞች ወይም የክልሎች ስሞች ናቸው።
ሕዝቡን ወደ አሦር ወሰደው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› የሚያመለክተው ቴልጌል-ቴልፌልሶርን ሲሆን፣ እርሱንና ሰራዊቱን ይወክላል። ሕዝቡን ወደ አሦር መውሰድ ወደ አሦር እንዲሄዱ ማስገደድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱና ሰራዊቱ ወደ አሦር እንዲሄድ ሕዝቡን አስገደዱ››
ሕዝቡ
የትኛው ሕዝብ እንደ ሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእነዚህ ቦታዎች የነበረ ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ››
ሆሴዕ… ኤላ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው።
አሤረበት
ሤራ ሰው ወይም አንዳች ነገር ላይ ጉዳት ለማድረስ ድብቅ ዕቅድ ማለት ነው።
አደጋ ጥሎ ገደለው
‹‹ሆሴዕ ፋቁሔ ላይ አደጋ ጥሎ ገደለው››
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› የሚለው ሐረግ፣ ‹‹በእርሱ ቦታ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፋቁሔ ቦታ ነገሠ››
የዖዝያን ልጅ ኢዮአታም በነገሠ በሃያኛው ዓመት
ይህ የአገዛዙ ሃያኛው ዓመት መሆኑን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዖዝያን ልጅ ኢዮአታም በነገሠ በ20ኛው ዓመት››
በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህን በተመለከተ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ማንበብ ትችላላችሁ››
2 Kings 15:32
የእስራኤል ንጉሥ የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት።
ይህ የአገዛዙ ሁለተኛ ዓመት መሆኑን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሮሜልሐ ልጅ ፋቁሔ የእስራኤል ንጉሥ በሆነ በ2ኛው ዓመት››
የዓዛርያስ ልጅ ኢዮአታም በይሁዳ መንገሥ ጀመረ
‹‹የዓዛርያስ ልጅ ኢዮአታም የይሁዳ ንጉሥ ሆነ››
ዕድሜ ሃያ አምስት ዓመት ነበር… ዐሥራ ስድስት ዓመት
‹‹ዕድሜው 25 ዓመት ነበር… 16 ዓመት››
ኢየሩሳ
ይህ የሴት ስም ነው።
2 Kings 15:34
በያህዌ ዐይን ፊት መልካም ነገር
ዐይን ዕይታን ይወክላል፤ ዕይታ ደግሞ ሐሳብን ወይም ፍርድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ መልካም ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ መልካም የሚለውን ነገር››
ኮረብቶች ላይ ያሉ ማምለኪያዎችን አላስወገደም
ይህን በሌላ መል ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም የኮረብቶቹን ማምለኪያዎች አላስወገደም›› ወይም፣ ‹‹ኢዮአታም የኮረብቶቹን ማምለኪያዎች ማንም እንዲያስወግድ አላደረገም››
አልተወገዱም
መወገድ መደምሰስን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልተደመሰሱም››
ኢዮአታም የላይኛውን በር መልሶ ሠራ
‹‹ኢዮአታም ሠራ›› የሚለው የኢዮአታም ሠራተኞች መሥራታቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮአታም ሠራተኞቹ የላይኛውን በር እንዲሠሩ አደረገ››
በይሁዳ… ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ጥያቄው የቀረበው ኢዮአታምን በተመለከተ መረጃ በዚህ ሌላ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚገኝ ለአንባቢው ለማሳሰብ ነው። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎአል››
በዚያ ዘመን
ይህ አንድ ወቅትን ያመለክታል። ይህ ወቅት የትኛው እንደ ነበር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹ኢዮአታም የይሁዳ ንጉሥ በነበረ ጊዜ››
ረአሶን
ይህ የሰው ስም ነው።
ፋቁሔ… ሮሜልዩ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው። ፋቁሔ የእስራኤል ንጉሥ ነበር። 2 ነገሥት 15፥37 ላይ ይህን እንዴት እንደተረጐምኸው ተመልከት።
ኢዮአታም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
አንቀላፋ ሞተ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢዮአታም እንደ አባቶቹ ሞተ›› ወይም፣ ‹‹አባቶቹ እንደ ሞቱ ኢዮአታምም ሞተ››
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› የሚለው ሐረግ፣ ‹‹በእርሱ ቦታ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኢዮአታም ቦታ ነገሠ››

---

Chapter 16
2 Kings 16:1
የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ በነገሠ በዐሥራ ሰባተኛው ዓመት
ይህ የአገዛዙ ዐሥራ ሰባተኛ ዓመት መሆኑን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ ንጉሥ በሆነ 17ኛ ዓመት››
ፋቁሔ… ሮሜልዩ
ይህ የሰዎች ስም ነው። ፋቁሔል የእስራኤል ንጉሥ ነበር። 2 ነገሥት 15፥25 ላይ ይህን እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
በያህዌ ዐይን ፊት መልካም ነገር
የያህዌ ዐይን ዕይታን ይወክላል፤ ዕይታ ደግሞ ሐሳብ ወይም ፍርድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ መልካም የሆነውን ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ መልካም ነው የሚለውን ነገር››
አባቱ ዳዊት ያደረገውን
ዳዊት መልካም ነገር አድርጐ ነበር
2 Kings 16:3
እርሱም የእስራኤልን ነገሥታት መንገድ ተከተለ
መመላለስ ፀባይንና ድርጊትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሥ አካዝ የእስራኤል ነገሥታት ያደረጉትን አደረገ›› ወይም፣ ‹‹እርሱ የእስራኤል ነገሥታት ያደረጉትን አደረገ››
የአሕዛብን ርኩሰት ተከትሎ
‹‹መከተል›› ሌሎች ያደረጉትን ማድረግ ማለት ነው። እዚህ ላይ የሚናገረው በዚያ ምድር የሚኖሩ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሌላ አገር ሕዝብ››
ያህዌ ያሳደዳቸውን
‹‹ማሳደድ›› — ‹‹ማስገደድ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚያ እንዲሄዱ ያህዌ ያስገደዳቸውን››
ከእስራኤል ሕዝብ ፊት
የእስራኤል ሕዝብ ወደ ምድሪቱ ሲመጡ፣ የእነዚያ መንግሥታት ሕዝቦች ሸሹ። ይህ ምን ማለት መሆኑን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ ምድሪቱ በመጡ የእስራኤል ሕዝብ ፊት›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ወደ ምድሪቱ ሲመጡ››
ኮረብታ ላይ ባሉ ማምለኪያ ስፍራዎች ቅጠሉ በተንሰራፋው ዛፍ ሥር
ሌሎች ሕዝቦች አማልክቶቻቸውን የሚያመልኩት በእንዲህ ያሉ ቦታዎች ነበር
ቅጠሉ በተንሰራፋው ዛፍ ሥር ሁሉ
እግዚአብሔር የፈለገው ሕዝቡ በኢየሩሳሌም መሥዋዕት እንዲያቀርቡለት ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ሁሉ›› የሚለው ቃል! ንጉሥ አካዝ በሌሎች ብዙ ቦታዎች መሥዋዕት በማቅረብ ምን ያህል ለእግዚአብሔር ባለ መታዘዝ የጸና ሰው መሆኑን የሚያመለክት ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቅጠሉ በተንሰራፋ ብዙ ዛፍ ሥር ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በአገሩ ባለ ቅጠሉ በተንሰራፋው ዛፍ ሥር ሁሉ››
2 Kings 16:5
ረአሶን… ፋቁሔ… ሮሜልዩ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው። 2 ነገሥት 15፥37 ላይ እንዴት እንደ ተረጐምሃቸው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተመልከት።
አካዝን ለመክበብ
አካዝ በኢየሩሳሌም ነበር። እዚህ ላይ፣ ‹‹አካዝ›› እርሱንና ከእርሱ ጋር በኢየሩሳሌም የነበሩ ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አካዝ የነበረበትን ከተማ ለመክበብ›› ወይም፣ ‹‹አካዝንና በከተማው የነበሩ ሌሎችንም ለመክበብ››
ኤላትን ወደ ሶርያ መለሰ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሶርያ›› እዚያ የሚኖሩ ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኤላት ከተማን ለሶርያ ሕዝብ መለሰ››
ኤላት
ይህ የከተማ ስም ነው። 2 ነገሥት 14፥22 እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
የይሁዳን ሰዎች ከኤላት አሳደደ
‹‹ኤላትን ለቀው እንዲወጡ የይሁዳን ሰዎች አስገደደ››
እስከ ዛሬ
ይህ ማለት ይህ መጽሐፍ እስከ ተጻፈ ድረስ ማለት ነው።
2 Kings 16:7
ቴልጌል-ቴልፌልሶር
2 ነገሥት 15፥19 ላይ ይህ ሰው፣ ‹‹ፑል›› ተብሎ ተጠርቷል። 2 ነገሥት 15፥29 ስሙን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
እኔ አገልጋይህም ልጅህም ነኝ
አገልጋይና ልጅ መሆን ለሥልጣን መገዛትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ አገልጋይህና እንደ ልጅህ እታዘዝሃለሁ››
ከሶርያ ንጉሥ እጅና ከእስራኤል ንጉሥ እጅ
‹‹እጅ›› - ‹‹ኀይልን›› ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሶርያ ንጉሥ ኀይልና ከእስራኤል ንጉሥ ኀይል››
ከሚወጉኝ
አካዝን የሚወጉ ነገሥታት፣ አካዝንና ሕዝቡን የሚወጉ ነገሥታት ሰራዊት ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሠራዊታቸው ከሚወጉኝ›› ወይም፣ ‹‹ሰራዊታቸው እኔን ከሚወጋኝ››
የአሦር ንጉሥ ደማስቆን አጠቃ
‹‹ንጉሥ›› የሚለው ቃል ንጉሡንና ሰራዊቱን ይወክላል። ደማስቆ እዚያ የሚኖረውን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥና ሰራዊቱ የደማስቆን ሕዝብ አጠቁ››
ሕዝቧን ማርኮ ወደ ቂር አፈለሳቸው
ሕዝብን ‹‹ማፍለስ›› ወደ አንድ ቦታ እንዲሄዱ ማስገደድ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡን እስረኛ አድርጐ ወደ ቂር እንዲሄድ አስገደደ››
ቂር
አማራጭ ትርጉሞች 1) የከተማ ስም ነው፤ ወይም 2) ቃሉ፣ ‹‹ከተማ›› ማለት ሲሆን የአሦርን ዋና ከተማ ያመለክታል።
2 Kings 16:10
ከዝርዝር ጥናቱ ጋር
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፤ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለግንባታው ሥራ ሠራተኞቹ የሚያስፈልጋቸውን መመሪያ ሁሉ››
2 Kings 16:13
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ከደማስቆ ከተመለሰና ካህኑ ኦርያ የሠራለትን መሠዊያ ከጐበኘ በኋላ ንጉሥ አካዝ ያደረገው ነው።
የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ
‹‹ንጉሥ አካዝ የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ››
መሠዊያው ላይ
ይህ ኦርያ እንዲሠራለት ንጉሥ አካዝ የነገረው መሠዊያ ነው።
ያህዌ ፊት የነበረው የናስ መሠዊያ
ይህ መሠዊያ በእግዚአብሔር መመሪያ መሠረት የእስራኤል ሕዝብ ከብዙ ጊዜ በፊት ሠርተውት የነበረ ነው።
ያህዌ ፊት የነበረው የናስ መሠዊያ
‹‹ያህዌ ፊት›› የሚለው ሐረግ ባለፈው ጊዜ ያህዌ ክብሩን ያሳየበትን ቦታ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤተ መቅደሱ ፊት የነበረው የናስ መሠዊያ››
ቤተ መቅደሱ ፊት... በመሠዊያውና በያህዌ ቤተ መቅደስ መካከል
እነዚህ ሐረጐች የናሱ መሠዊያ የነበረበትን ቦታ ይናገራሉ። ሁለቱም ስለ አንድ ቦታ ይናገራሉ።
2 Kings 16:15
ትልቁ መሠዊያ
ይህ እንዲሠራለት አካዝ ለኦርያ የነገረው አዲሱን መሠዊያ ያመለክታል።
የንጉሡ የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህል ቁርባን
አካዝ፣ ‹‹ንጉሡ›› እና፣ ‹‹የእርሱ›› ሲል ስለ ራሱ መናገሩ ነው። ንጉሡ መሥዋዕቱን በጥንቃቄ ነበር የሚመለከተው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚቃጠል መሥዋዕቴና የእህል መሥዋዕቴ›› ወይም፣ ‹‹ንጉሣዊ የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህል መሥዋዕት››
2 Kings 16:17
ተንቀሳቃሹ መቆሚያ
‹‹ተንቀሳቃሽ መቆሚያ›› ወይም፣ ‹‹ሰረገላ›› እነዚህ መቆሚያዎች ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ተሽከርካሪዎች ነበሩት።
የመታጠቢያ ሳሕኖች አስወገደ
‹‹ጐድጓዳውን ሳሕን አስወገደ›› ይህ ከናስ የተሠራ ገንዳ ወይም የውሃ መያዣ ነው።
በአሦር ንጉሥ ምክንያት
ለምን ይህን እንዳደረጉ የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦርን ንጉሥ ደስ ለማሰኘት››
2 Kings 16:19
በይሁዳ... ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
ጥያቄው የቀረበው አካዝን የሚመለከት መረጃ በዚህ ሌላ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚገኝ አንባቢውን ለማሳሰብ ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎአል›› ወይም፣ ‹‹አንድ ሰው በይሁዳ... መጽሐፍ ጽፎታል››
አካዝም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
አንቀላፋ ሞተ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አካዝ እንደ አባቶቹ ሞተ›› ወይም፣ ‹‹እንደ አባቶቹ አካዝም ሞተ››
ከአባቶቹ ጋር ተቀበረ
ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ከአባቶቹ ጋር ቀበሩት››
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ
‹‹በእግሩ ተተክቶ›› የሚለው ሐረግ፣ ‹‹በቦታው›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአካዝ ቦታ ነገሠ››

---

Chapter 17
2 Kings 17:1
የኤላ ልጅ ሆሴዕ
ሆሴዕ የሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥት ንጉሥ ሆነ።
ኤላ
ይህ የሰው ስም ነው።
በሰማርያ ከተማ ነገሠ
ሰማርያ የእስራኤል ዋና ከተማ ነበረች።
በያህዌ ፊት ክፉ
ለሙሴ ለተሰጠው የያህዌ ሕግ አልታዘዘም። ‹‹ፊት›› ፍርድንና ሐሳብን ያመለክታል። ‹‹ለያህዌ ክፉ ነገር››
ሰልምናሶር
ይህ የሰው ስም ነው።
ሆሴዕ ተገዛለት፤ ገበረለትም
ሆሴዕ የአሦር ንጉሥ ያዘዘውን አደረገ፤ ንጉሡ እስራኤልን እንዳያጠፋ ገንዘብ ይሰጠው ነበር።
2 Kings 17:4
ሲጐር
ይህ የሰው ስም ነው።
በየዓመቱ
‹‹በዓመት በዓመቱ››
ይህ ወህኒ ቤት አስገባው
‹‹አሰረው››

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከበባት
እጅ እንድትሰጥ ለማስገደድ በከተማው ዙሪያ ወታደሮች አሰፈረ
እስራኤልን በምርኮ ወደ አሦር አፈለሰ
‹‹እስራኤል›› እዚያ የሚኖር ሕዝብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤልን ሕዝብ ወደ አሦር ወሰደ››
አላሔ… አቦር ወንዝ… ጐዛን
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው
ሜዶን
ይህ የሕዝብ ስም ነው
2 Kings 17:7
አጠቃላይ መረጃ
በእስራኤል ላይ የያህዌን ፍርድ አሳጥሮ ለማቅረብ ታሪኩ ቆም ብሏል።
ይህ ምርኮ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤላውንን በአሦራውያን መወረር ነው።
እጅ
‹‹እጅ›› የመቆጣጠር፣ የሥልጣን ወይም የኀይል ሌላ መጠሪያ ነው።
ልማድ ስለ ተከተሉ
‹‹ተከተሉ›› የሚለው የሰዎች አኗኗር ሁኔታ ወይም መንገድ ማለት ነው።
2 Kings 17:9
አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ የያህዌን እስራኤል ላይ ፍርድ በአጭሩ ማቅረብ ቀጥሏል።
በእያንዳንዱ ኮረብታ ላይና በእያንዳንዱም የተንሰራፋ ዛፍ
ይህ በብዛት ሐሰተኛ አማልክት ይመለኩ እንደ ነበር ለማሳየት የቀረበ ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኮረብታውና በተንሰራፋው ዛፍ››
2 Kings 17:11
አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ የያህዌን እስራኤል ላይ ፍርድ በአጭሩ ማቅረብ ቀጥሏል።
ያህዌን የሚያስቆጣ ክፉ ነገር አደረጉ
ይህን የማቅረብ አማራጭ ትርጉሞች 1)‹‹ያህዌን የሚያስቆጣ ብዙ ክፉ ነገሮች አደረጉ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌን የሚያስቆጣ ብዙ ኀጢአት አደረጉ››
ይህን ማድረግ አይገባችሁም ቢላቸውም
‹‹ያህዌ ቢያስጠነቅቃቸውም››
2 Kings 17:13
አጠቃላይ መረጃ
ታሪኩ የያህዌን እስራኤል ላይ ፍርድ በአጭሩ ማቅረብ ቀጥሏል።
ያህዌ በነቢያት በኩል መሰከረባቸው
ያህዌ በነቢያት በኩል ተናገረ
ከክፉ መንገዶች ተመለሱ
‹‹የምታደርጉን ክፉ ነገር አቁሙ››
አገልጋዮቼ ነቢያትን ወደ እናንተ ላክሁ
የእግዚአብሔር ሕግ እንዲያሳስቡና እንዲታዘዙ ሕዝቡን ለማሳሰብ ያህዌ ነቢያትን ልኮ ነበር።
2 Kings 17:14
አጠቃላይ መረጃ
የያህዌን እስራኤል ላይ ፍርድ በአጭሩ ይቀጥላል
ዐንገታቸውን አደነደኑ
የእግዚአብሔርን ሕግ ለመከተልና በአምላካቸው በያህዌ ለመታመን ፈቃደኛ አልሆኑም
ሥርዐቱን ናቁ
ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዝ እንቢ አሉ
ከንቱ ነገር ተከተሉ
በዙሪያቸው ያሉ ሰዎችን ልማድ ተከተሉ
አትምሰሏቸው
‹‹እንደ እነርሱ አትሁኑ››
2 Kings 17:16
አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ እስራኤል ላይ ፍርድ በአጭሩ ቀጥሏል።
ምስል ሠሩ
ይህ ብረት አቅልጠው ቅርጽ ማስያዣ ላይ አፈሰሱ ማለት ነው።
ጥንቆላና መተት አደረጉ
ወደ ፊት የሚሆነውን ለመናገር አስማት አደረጉ
ክፉ ነገር ለማድረግ ራሳቸውን ሸጡ
‹‹ራስን መሸጥ›› ክፉ የሆነውን ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ራስን መስጠት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ ነው ያለውን ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ሰጡ››
ከፊቱ አስወገዳቸው
‹‹ፊት›› ከእንግዲህ ያህዌ ስለ እነርሱ እንዲያስብ ትኩረት መንፈግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ትኩረቱን ከእነርሱ አነሣ››
2 Kings 17:19
አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ እስራኤል ላይ ፍርድ ይሁዳም ወደ ጣዖት አምልኮ መውደቁን ያመለክታል።
ይሁዳ
ይሁዳ የሚለው ቦታ እዚያ የሚኖርን ሕዝብ ያመለክታል። ‹‹የይሁዳ ሕዝብ››
አስጨነቃቸው
‹‹ያህዌ እስራኤላውያንን ቀጣ››
በማራኪዎቻቸው እጅ አሳልፎ ሰጣቸው
‹‹እጅ›› የመቆጣጠር፣ የኀይል ወይም የሥልጣን ሌላ መጠሪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንብረታቸውን ለሚዘርፉ አሳልፎ ሰጣቸው››
ከፊቱ እስኪያስወግዳቸው ድረስ
‹‹ፊቱ›› የእርሱን ትኩረትና ለእነርሱ ማሰብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨርሶ እስኪተዋቸው ድረስ›› ወይም፣ ‹‹ከእንግዲህ በፊቱ እስከማይሆኑ ድረስ››
2 Kings 17:21
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ እስራኤል ላይ የፈረደበት ምክንያት ከጀርባው ያለውን ታሪክ በማቅረብ ቀጥሏል።
እስራኤልን ቀደደ
‹‹ቀደደ›› በከባድ ሁኔታ መለየት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የእስራኤልን ሕዝብ አስወገደ››
ከዳዊት ንጉሣዊ ዘር
‹‹ከዳዊት ዘር መንግሥት››
እስራኤላውያንን ያህዌን ከመከተል አራቀ
‹‹እስራኤላውያንን ያህዌን ከመከተል መለሰ››
ከእነርሱ አልራቁም
እስራኤላውያን እነዚያን ኀጢአት ማድረግ አልተዉም›› ወይም፣ ‹‹ከእነዚያ ኀጢአቶች አልራቁም››
ስለዚህ ያህዌ ከፊቱ አስወገዳቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ፊት›› ትኩረትንና ለእነርሱ ማሰብን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህም ያህዌ የእርሱን ትኩረት ከማግኘት አራቃቸው››
2 Kings 17:24
አጠቃላይ መረጃ
አረማዊ ሃይማኖታቸውን ይለማመዱ በነበሩ አዲሶቹ የአሦር ሰፋሪዎች የያህዌ ፍርድ መምጣቱን ቀጥሏል።
ኩታ… አዋና… ሐማት… ሴፈርዋይ
እነዚህ የአሦር መንግሥት ከተሞች ናቸው።
በዚያ መኖር እንደ ጀመሩም
‹‹እነዚህ ሰዎች መጀመሪያ እዚያ ሲኖሩ››
ወስዳችሁ በሰማርያ ከተሞች ያኖራችኋቸው ሕዝቦች
‹‹ከሌሎች አገሮች አንሥታችሁ በሰማርያ ከተሞች እንዲኖሩ የላካችኋቸው ሕዝቦች››
የዚያ አገር አምላክ ምን እንደሚፈልግ አላወቁም
‹‹እስራኤላውያን በዚያ ምድር የሚያመልኳቸውን አማልክት አላወቁም››
2 Kings 17:27
ከሰማርያ ማርካችሁ ካመጣችኋቸው ካህናት አንዱን ውሰዱ›› ያስተምር
‹‹ሳምራዊው ካህን አሁን እዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያስተምር››
2 Kings 17:29
ሱኮትበኖት… ኔርጋል… አሰማት… አልባዝር… ተርታቅ… አድራሜሌክ… አናሜሌክ
እነዚህ ወንዶችና ሴቶች አማልክት ስሞች ናቸው።
ኩታ… ሐማት
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።

ኢዋውያን… ሴፌርዋም
እነዚህ የሕዝብ ስሞች ናቸው፡፡
ልጆቻቸውን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ
‹‹የገዛ ልጆቻቸውን ሠው›› ወይም፣ ‹‹መሥዋዕት እንዲሆኑ ልጆቻቸውን በእሳት አቃጠሉ
2 Kings 17:32
እነርሱ
የአሦር ንጉሥ በሰማርያ ከተሞች እንዲኖሩ ያመጣቸውን አረማውያን ሕዝብ ይመለከታል፡፡
2 Kings 17:34
የመጡበትን ሕዝብ ልማድ ተከተሉ
‹‹የቀድሞ ልማዳቸውን ማድረግ ቀጠሉ››
ያህዌንም በአግባቡ አያመልኩም
እነዚህ ሰዎች የሚፈልጉት የያህዌን ቁጣ ለማብረድ ነበር፡፡ ያህዌ የሚፈልገውን ለማወቅ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ለማድረግ አይፈልጉም፡፡
2 Kings 17:36
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ክፍል ያህዌን ለማምለክ በቀረበ ጥሪ ወደ መጠናቀቅ ተቃርቧል፡፡
በታላቅ ኀይልና በተዘረጋች ክንድ
x
2 Kings 17:39
አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ መልእክቱ የሚጠናቀቀው ያህዌን ብቻ እንዲያመልኩ ጥሪ በማቅረብ ነው፡፡
አልሰሙም
‹‹መስማት›› ልብ ማለትና የሰሙትን መፈጸም ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልታዘዙም››
እነዚህ ሕዝቦች ያህዌን ፈሩ
እነዚህ ሰዎች ያህዌን የሚፈሩት አማልክቶቻቸውን ላለማስቆጣት እንደሚያደርጉት እርሱንም ላለማስቆጣት ብቻ ነበር፡፡
ዛሬም እንደ ቀጠሉበት ነው
‹‹እስከ ዛሬ ድረስ ያንኑ እያደረጉ ነው›› - ‹‹ዛሬም›› የሚለው ሐረግ ጸሐፊው የነበረበትን ዘመን ያመለክታል፡፡

---

Chapter 18
2 Kings 18:1
አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቅያስ በአባቱ በአካዝ ቦታ በይሁዳ ነገሠ
ሆሴዕ… ኤላ… ዘካርያስ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው፡፡
አብያ
ይህ የሴት ስም ነው፡፡
በያህዌ ዐይን ፊት መልካም ነገር አደረገ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐይን›› የያህዌን ትኩረትና ሐሳብ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሥ ሕዝቅያስ ለያህዌ መልካም ነገር አደረገ›› ወይም፣ ‹‹ሕዝቅያስ ያህዌ መልካም የሚለውን አደረገ››
2 Kings 18:4
አጠቃላይ መረጃ
የንጉሥ ሕዝቅያስ ታሪክ ቀጥሏል፡፡
በየኮረብታው ላይ ያሉትን ማምለኪያዎች አስወገደ፤ አዕማደ ጣዖታትን ሰባበረ
‹‹ሕዝቅያስ ከፍታው ቦ የነበረውን ማምለኪያ አስወገደ፤ የመታሰቢያ ድንጋዮችን ሰባበረ፤ የአሼራን እንጨት አዕማዶች ቆረጠ››
ነሑሽታን
ስሙ፣ ‹‹የናስ እባብ ጣዖት›› ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፡፡
2 Kings 18:6
አጠቃላይ መረጃ
የንጉሥ ሕዝቅያስ ታሪክ ቀጥሏል፡፡
ከያህዌ ጋር ተጣበቀ
‹‹ተጣበቀ›› ከእርሱ ታማኝ በመሆን ጸና ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቅያስ ለያህዌ ታማኝ ሆነ›› ወይም፣ ‹‹ሕዝቅያስ ለያህዌ ታማኝ በመሆን ጸና››
በሚሄድበት ሁሉ ተከናወነለት
‹‹ሕዝቅያስ በሄደበት ሁሉ ስኬታማ ነበር››
የተመሸገች ከተማ
ዙሪያውን በግንብ የተከበበች ከተማ
2 Kings 18:9
ሆሴዕ… ኤላ… ስልምናሶር
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው
2 Kings 18:11
አላሔ… አቦር ወንዝ… ጐዛን
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው
ሜዶን
ይህ የሕዝብ ስም ነው
የአሦር ንጉሥ እስራኤልን ማርኮ ወደ አሦር አፈለሳቸው
‹‹የአሦር ንጉሥ እስራኤላውያንን ከአገራቸው ወስደው በአሦር እንዲያኖሩዋቸው ሰራዊቱን አዘዘ››
የያህዌ ድምፅ
‹‹ድምፅ›› የያህዌ ትእዛዝ መልእክት ማለት ነው አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያህዌ ትእዛዝ››
2 Kings 18:13
ሰናክሬም
ይህ የሰው ስም ነው፡፡
ለኪሶ
ይህ የከተማ ስም ነው
የተመሸጉ ከተሞች
ለጥበቃ እንዲሆን ዙሪያውን በግንብ የተከበቡ ከተሞች፡፡ 2 ነገሥት 18፥8 ላይ፣ ‹‹የተመሸጉ ከተሞች›› እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት፡፡
ከእኔ ተመለሰ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ከእኔ›› የሚለው የሕዝቅያስን መንግሥት ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰራዊትህን ከግዛቴ መልስልኝ››
የምትጠይቀኝን ሁሉ እከፍላለሁ
‹‹ክፈል የምትለኝን ሁሉ እሰጣለሁ››
መክሊት
ይህ ገንዘብ ለመመዘን ጥቅም ላይ የሚውል ነገር ስም ነው፡፡ አንድ መክሊት 33 ኪሎ ግራም ይመዝናል፡፡
ግምጃ ቤቶች
ይህ ገንዘብና የከበሩ ነገሮች የሚቀመጡበት ቤተ መንግሥት ውስጥ ያለ ቦታ ነው፡፡
2 Kings 18:16
የአሦር ንጉሥ ታላቅ ሰራዊትን በማንቀሳቀስ ታርታንና ዋናውን አዛዥ ራብሳሪሰን ላከ፡፡
ሰናክሬም ንጉሥ ሕዝቅያስ ጋር እንዲገናኙ ከሰራዊቱ ውስጥ ታርታንና ራብሳሪስን የሚባሉ አዛዦች ጨምሮ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም ላከ፡፡
ታራታን… ሰብሳሪስ
አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እነዚህን እንደ ተፅውዖ ስም ያስቀምጣሉ፡፡ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች እንደ ሹመት ያስቀምጣሉ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታርታሮች… ሰብሰሪሶች›› ወይም፣ ‹‹የወታደሮች መሪ… የቤተ መንግሥት ሹም››
ለኪሶ
ይህ የከተማ ስም ነው፡፡
የላይኛው ኩሬ መስኖ
‹‹ላይኛው ኩሬ›› ውሃ የሚጠራቀምበትና ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ የሚፈሰው ቦይ
መጥተው ቆሙ
‹‹ንጉሥ ሕዝቅያስ መጥቶ እንዲያገኛቸው እዚያ ጠበቁት››
ኤልያቄም… ኬልቅያስ… ሰምናስ… ዮአስ… አሳፍ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው፡፡
2 Kings 18:19
አጠቃላይ መረጃ
ራፋስቂስ የአሦርን ንጉሥ መልእክት ለንጉሥ ሕዝቅያስ ሰዎች እየተናገረ ነው፡፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የትምክህትህ ምክንያት ምንድነው? ...በእኔ ላይ እንዲህ ያመፅኸውስ በማን ተማምነህ ነው?
የአሦር ንጉሥ (በመልእክተኛው በራፋስቂስ በኩል) እነዚህን ጥያቄዎች ያቀረበው ንጉሥ ሕዝቅያስ ራሱንና የግብፅን ርዳታ እንዲጠራጠር እንጂ፣ መልስ በመፈለግ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በማንም አትተማመን። በእኔ ላይ በማመፅህ ጅል ሆነሃል››
በዚህ በተቀጠቀጠ ሸምበቆ
የአሦር ንጉሥ ደካማ ሸንበቆ ነው፤ አንተን የሚደግፍህ ይመስልሃል፤ ስትደገፍበት ግን ተሰብሮ ይወጋሃል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የግብፅ ደካማ ርዳታ››
ሰው ቢደገፍበት... ወግቶ የሚያቆስል
ሸንበቆን ምርኩዝ የሚያደርግ ሰው ምን እንደሚሆን በመግለጽ ተናጋሪው በተለዋጭ ዘይቤ ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው በዚህ ቢደገፍ ጉዳት ይደርስበታል››
2 Kings 18:22
አጠቃላይ መረጃ
ራፋስቂስ የአሦርን ንጉሥ መልእክት ለንጉሥ ሕዝቅያስ ሰዎች እየተናገረ ነው።
እርሱ ከፍታ ቦታ በኢየሩሳሌም አይደለምን?
ጠያቂው አድማጮቹ መልሱን እንደሚያውቁ ይገነዘባል፤ የሚጠይቀው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእርሱ ከፍታ ቦታ ያለው በኢየሩሳሌም መሆኑን ማስታወስ አለባችሁ!››
2 Kings 18:24
አጠቃላይ መረጃ
ራፋስቂስ የአሦርን ንጉሥ መልእክት ለንጉሥ ሕዝቅያስ ሰዎች እየነገረ ነው።
ከጌታዬ የበታች ሹማምንት እንኳ አንዱን እንዴት መመለስ ትችላለህ?
ይህን ጥያቄ የሚያቀርበው የሕዝቅያስ ጦር የመዋጋት ዐቅም እንደሌለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። የሕዝቅያስ ሰራዊት ላይ ለማፌዝ ግነት ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፣ 1) ‹‹ከንጉሡ ወታደሮች ታናሽ የሆነውን እንኳ ማሸነፍ አትችልም›› ወይም 2) ‹‹የበታች ሹሙ የሚያዝዛቸውን ወታደሮች እንኳ ማሸነፍ አትችልም››
አደጋ ጥዬ ይህችን ስፍራ ለማጥፋት የመጣሁት ያለ ያህዌ ፈቃድ ይመስልሃልን?
ይህን ጥያቄ ያቀረበው እስራኤልን እንዲያጠፋ ስኬት የሰጠው ያህዌ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደዚህ መጥተን ምድሪቱን እንድናጠፋ የነገረን ያህዌ ራሱ ነው!››
2 Kings 18:26
ኤልያቄም... ኬልቅያስ... ሰምናስ... ዮአስ
የእነዚህን ሰዎች ስም 2 ነገሥት 18፥18 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው።
ቅጥሩ ላይ ባሉ ሰዎች ጆሮ
‹‹ጆሮ›› የመስማት ችሎታን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በቅጥሩ ላይ ያሉ ሰዎች ሰምተው እንዳይፈሩ››
ጌታዬ ይህን እንድናገር የላከኝ ለጌታችሁና ለእናንተ ብቻ ነውን? እነርሱም እንደ እናንተው ገና ኩሳቸውን ይበሉ ዘንድ፣ ሽንታቸውንም ይጠጡ ዘንድ በቅጥሩ ላይ ለተቀመጡት ጭምር አይደለምን?
ይህን የጠየቀው አድማጮቹ መልሱን እንዲሚያውቁ በማሰብ ሲሆን፣ ፍላጐቱ የኢየሩሌምን ሕዝብና መሪዎች ማዋረድና ድል ማድረግ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታዬ የላከኝ ወደ እናንተና ወደ ጌታችሁ ብቻ ሳይሆን፣ በሕይወት ለመኖር የገዛ ኩሳቸውን ለሚበሉና የገዛ ሽንታቸውን ለሚጠጡት ለዚህ ከተማ ሰዎች ጭምር ነው››
2 Kings 18:28
ከኀይሌ
‹‹ኀይሌ›› የንጉሡን ችሎታ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእኔ›› ወይም፣ ‹‹የሰራዊቴ ኀይል››
ይህች ከተማ ለአሦር ንጉሥ አልፋ አትሰጥም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥ ሰራዊት ይህችን ከተማ እንዲይዝ ያህዌ በፍጹም አይፈቅድም››
እጅ
‹‹እጅ›› መቆጣጠርን፣ ሥልጣንና ኀይልን ያመለክታል።
2 Kings 18:31
ከእኔ ጋር ሰላም መሥርቱ፤ እጃችሁን ስጡ
‹‹ከከተማው ወጥታችሁ እጃችሁን ስጡኝ›› ወይም፣ ‹‹እጃችሁን ለመስጠት ከእኔ ጋር ተስማሙ፤ ከከተማ ወጥታችሁ ወደ እኔ ኑ››
ከገዛ ወይኑ.. ከገዛ በለሱ... ከገዛ ጉድጓዱም ውሃ
እነዚህ የምግብና ውሃ መገኛዎች ሰላምንና መተረፍረፍን ይወክላሉ። ይህ ይህን ሐሳብ ለመግለጽ የተለመደ አባባል ነው።
እህልና አዲስ የወይን ጠጅ... እንጀራና የወይን እርሻ... የወይራ ፍሬና ማር
ይህ የመልካምና በየዕለቱ ሕይወት የበዛ ነገር የማግኘት ምሳሌ ነው።
2 Kings 18:33
አጠቃላይ መረጃ
ራፋስቂስ የአሦርን ንጉሥ መልእክት ለንጉሥ ሕዝቅያስ ሰዎች እየተናገረ ነው።
ከአሕዛብ አማልክት... ከአሦር?
ይህን የጠየቀው መልሱን ስለሚያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአሕዛብ አማልክት አንዱ እንኳ ከአሦር አላዳኑዋቸውም››
የአርፋድ አማልክት የት ደረሱ?
ይህን የጠየቀው መልሱን ስለሚያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአርፋድን አማልክት አጥፍቻለሁ››
ሐማት... አርፋድ... ሴፌርዋይም... ሄና... ዒዋም... ሰማርያ
እነዚህ እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን የሚወክሉ የቦታ ስሞች ናቸው።
ከእጄ
‹‹እጅ›› መቆጣጠርን፣ ኀይልንና ሥልጣንን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእኔ ቁጥጥር››
አገሩን ከእኔ ለማዳን የቻለ አምላክ አለን?
ይህን የጠየቀው መልሱን ስለሚያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንኛውም አምላክ ምድሩን ከእኔ ኀይል አላዳነም››
ከኀይሌ
‹‹ኀይሌ›› ያ ኀይል ያለውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእኔ››
ያህዌ ኢየሩሳሌምን እንዴት ከእጄ ማዳን ይችላል?
ይህን የጠየቀው መልሱን ስለሚያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ኢየሩሳሌምን ከእኔ ማዳን የሚችልበት አንድም መንገድ የለም››
2 Kings 18:36
ኤልያቄም... ሰምናስ... ዮአስ... አሳፍ...
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።
የቤተ መንግሥቱ አዛዥ
‹‹ቤተ መንግሥቱን የሚያስተዳድር››
ጸሐፊው
‹‹ታሪክ መዝጋቢ››
ዋና አዛዥ
x

---

Chapter 19
2 Kings 19:1
የያህዌ ቤት
ይህ፣ ‹‹የያህዌ ቤተ መቅደስ›› ሌላ መጠሪያ ነው።
ኤልያቄም... ሰምናስ... ኢሳይያስ... አሞጽ
እነዚህ ሁሉ የሰው ስሞች ናቸው።
ኤልያቄምን ላከ
‹‹ሕዝቅያስ ኤልያቄምን ላከ››
ሁሉም ማቅ ለብሰው ነበር
‹‹የሐዘን ልብስ ለብሰው ነበር››
2 Kings 19:3
ይህች ዕለት የጭንቀት ቀን ናት
‹‹ይህች የጭንቀት ጊዜ ናት››
ልጆች ሊወለዱ ምጥ እንዳፋፋመች፣ ነገር ግን ለመገላገል ዐቅም እንደ ታጠባት ሰዓት ናት።
ይህ ጠላትን ለመዋጋት ሕዝቡና መሪዎቹ ዐቅም ያጡበትን ሁኔታ የሚያመለክት ምሳሌ ነው።
የአዛዡ ቃል ሁሉ
‹‹ዋናው አዛዥ የተናገረው ሁሉ››
ጸሎት አቅርብ
ጸሎት ማቅረብ ከእኛ በላይ ላለው ለያህዌ አጥብቆ መጸለይን የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አጥብቀህ ጸልይ››
2 Kings 19:5
አንድ ዐይነት መንፈስ አሳድርበታለሁ፤ የሆነ ወሬም ሲሰማ ወደ አገሩ ይመለሳል

የአሦርን ንጉሥ ዝንባሌ እቆጣጠራለሁ፤ ስለዚህም አንድ ወሬ ሲደርሰው ወደ አገሩ ይመለሳል።
አንድ ዐይነት መንፈስ አሳድርበታለሁ
‹‹ሐሳቡን እቆጣጠራለሁ›› ወይም፣ ‹‹የተለየ ሐሳብ እንዲያስብ አደርገዋለሁ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹መንፈስ›› መንፈሳዊ ማንነትን ሳይሆን፣ የሚያመለክተው ዝንባሌና ሐሳብን ነው።
በሰይፍ እንዲወድቅ አደርገዋለሁ
‹‹በሰይፍ መውደቅ›› መገደል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሰይፍ እንዲሞት አደርገዋለሁ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች በሰይፍ እንዲገድሉት አደርጋለሁ››
2 Kings 19:8
የጦር አዛዡ
‹‹በንጉሡ ሥር ያለ የአሦር ባለ ሥልጣን››
ልብና... ለኪሶ
እነዚህ ይሁዳ መንግሥት ውስጥ ያሉ ከተሞች ናቸው።
ሰናክሬም... ቲርሐቅ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።
ሊወጋው በመገሥገሥ ላይ መሆኑን
‹‹አሦርን ለመውጋት ሰራዊቱን አዘጋጀ››
ስለዚህ ላከ
‹‹ስለዚህ ሰናክሬም ላከ››
መልእክት
መልእክቱ በጽሑፍ ነበር።
2 Kings 19:10
አጠቃላይ መረጃ
ይህ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ለንጉሥ ሕዝቅያስ የላከው መልእክት ነው።
በምትመካበት አምላክ እንዳያታልልህ
‹‹የምታምኑትን አምላክ አትተማመኑ፤ እርሱ እየዋሻችሁ ነው››
የአሦር ንጉሥ እጅ
‹‹እጅ›› መቆጣጠርን፣ ሥልጣንና ኀይልን ያመለክታል።
እነሆ ምን እንዳደረጉ ሰምተሃል
‹‹መስማትህን ልብ በል›› ወይም፣ ‹‹በእርግጥ ሰምተሃል›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል።
ታዲያ፣ አንተስ ከዚህ የምታመልጥ ይመስልሃልን?
ሰናክሬም እንዲህ ያለው እግዚአብሔር እንደማያድናቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አምላክህ አያድንህም›› ወይም፣ ‹‹አንተም ብትሆን ማምለጥ አትችሉም››
2 Kings 19:12
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰናክሬም ለንጉሥ ሕዝቅያስ እየተናገረ ነው።
የአሕዛብ አማልክት አድነዋቸዋልን... አርፋድ?
ጥያቄው ሕዝቅያስ መልሱን እንደሚያውቅ ያስባል፤ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሕዛብ አማልክት በእርግጥ ሕዝቡን ማዳን አልቻሉም... አርፋድ››
አባቶቼ
‹‹የቀድሞ የአሦር ነገሥታት›› ወይም፣ ‹‹የቀድሞ የአሦር ነገሥታት ሰራዊት››
ጐዛን... ካራን... ራፊስ... ኤደን... ተላሰር... ሐማት... አርፋድ... ሴፈርዋይን... ሄና... ዒዋ
እነዚህ ሁሉ የቦታ ስሞች ናቸው።
2 Kings 19:14
ደብዳቤው
ይህ ደብዳቤ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ለሕዝቅያስ የላከው ነው።
በኪሩቤል ላይ የተቀመጥህ
ኪሩቤል በቃል ኪዳኑ ታቦት መክደኛ ላይ ያሉ መሆኑን በመግለጽ ይህን ማብራራት ያስፈልግህ ይሆናል። የቃል ኪዳኑ ታቦት በላይ በሰማይ ዙፋኑ የሚቀመጥ የያህዌ እግር ማረፊያ መሆኑን የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ብዙ ጊዜ ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የቃል ኪዳኑ ታቦት ባለበት ከኪሩቤል በላይ በዙፋንህ የምትቀመጥ››
2 Kings 19:16
አጠቃላይ መረጃ
ከአሦር ንጉሥ ከሰናክሬም ደብዳቤውን ካገኘ በኋላ ንጉሥ ሕዝቅያስ ወደ ያህዌ እየጸለየ ነው።
ጆሮህን አዘንብልና ስማ፤ ያህዌ ሆይ፣ ዐይንህን ክፈትና እይ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ሰናክሬም የሚለውን ልብ እንዲል ለያህዌ የቀረቡ ልመናዎች ናቸው።
ጆሮህን አዘንብልና ስማ
‹‹አዘንብል›› እና፣ ‹‹ስማ›› የተሰኙ ቃሎች አንድ ዐይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ፣ ለልመናው አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ሆይ፣ እባክህ እርሱ የሚለውን ስማ››
ያህዌ ሆይ፣ ዐይንህን ክፈትና እይ
‹‹ዐይንህን ክፈት›› እና፣ ‹‹እይ›› የተሰኙት ቃላት አንድ ዐይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ፣ ለልመናው አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ሆይ፣ እባክህ እየሆነ ያለውን ልብ በል››
አማልክቶቻቸውን በእሳት አቃጥለዋል
‹‹የአሦር ነገሥታት የአሕዛብን አማልክት በእሳት አቃጥለዋል››
አሦራውያን በእርግጥ አጥፍተዋቸዋል
‹‹አሦራውያን ሕዝቡንና አማልክቶቻቸውን አጥፍተዋል››
2 Kings 19:19
አጠቃላይ መረጃ
ከአሦር ንጉሥ ከሰናክሬም ደብዳቤን ከተቀበለ በኋላ ንጉሥ ሕዝቅያስ እየጸለየ ነው።
እማጸንሃለሁ
‹‹እለምንሃለሁ››
ከኀይሉ
‹‹ከአሦር ንጉሥ ኀይል›› ወይም፣ ‹‹ከአሦር ንጉሥ ሰራዊት››
2 Kings 19:20
ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ
‹‹ድንግል ልጅ›› የተባሉት ወጣትነትን፣ ንቃትንና ውበትን በሚያመለክት መልኩ የኢየሩሳሌም ሰዎች ናቸው። ‹‹ልጅ›› የሚለውን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የከተሞችን ግላዊ ባሕርይ ለመግለጽ ተቅመውበታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምታምሩ የኢየሩሳሌም ሕዝቦች››
ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ ትንቅሃለች፤ ታቃልልሃለችም፤ የኢየሩሳሌም ልጅ ራስዋን ትነቀንቅብሃለች
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች አንድ ዐይነት ነገር ነው የሚናገሩት
የኢየሩሳሌም ልጅ
‹‹ልጅ›› የኢየሩሌም ሕዝብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኢየሩሌም ከተማ ሕዝብ››
ራሷን ትነቀንቅብሃለች
ይህ ድርጊት በአሦራውያን ትዕቢት ማፌዝን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታፌዝብሃለች››
የሰደብኸውና ያቃለልኸው ማንን ነው? ድምፅህንስ ከፍ ያደርግኸው? ዐይንህንስ በኩራት ያነሣኸው በማን ላይ ነው? በእስራኤል ቅዱስ ላይ ነው እንዴ?
ሰናክሬምን ለመገሠጽ ያህዌ እነዚህን ጥያቄዎች አቅርቧል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔን ሰድበኸኛል፤ አዋርደኸኛል! በእኔ በእስራኤል ቅዱስ ላይ ለመታበይ ድምፅህን ከፍ አድርገሃል ዐይንህን አንሥተሃል!››
ዐይንህን በኩራት አንሥተሃል
‹‹ዐይንህ ማንሣት›› ፊት ላይ የሚታይ ትዕቢትና እብሪት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም በትዕቢት ተመለከትህ››
የእስራኤል ቅዱስ
የእስራኤል አምላክ ያህዌ ማለት ነው።
2 Kings 19:23
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰናክሬምን በተመለከተ ለነቢዩ ኢሳይያስና ለንጉሥ ሕዝቅያስ ያህዌ የሰጠው መልእክት እንደ ቀጠለ ነው። ተጓዳኝ አቀራረብ ይጠቀማል።
ጌታን አቃልለሃል
‹‹ማቃለል›› በግልጽ መቃወም ወይም ማፌዝ ነው።
ወጥቻለሁ... ቆርጫለሁ... ገብቻለሁ
ይህ የሰናክሬም ፉከራ የሚፈጸመው በሰራዊቱ ነው። ‹‹እኔ›› የሚለው ተውላጠ ስም እርሱንና ሰራዊቱን ይወክላል።
በእግሬ ጫማዎችም የግብፅን ምንጮች ሁሉ ረግጬ አድርቄአለሁ
ይህ ፉከራ ሰናክሬም በጣም ብዙ ወታደሮች ስለ ነበሩት ወንዞን በሚሻገሩበት ጊዜ ውሃውን እንደሚያደርቁ ያመለክታል። ይህ የወታደሮቹን ብዛት የሚያሳይ ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በግብፅ ምንጮች ውስጥ በማለፍ አደረቅነው!››
2 Kings 19:25

አጠቃላይ መረጃ
የአሦር ንጉሥ ሰናክሬምን በተመለከተ ለነቢዩ ኢሳይያስና ለንጉሥ ሕዝቅያስ ያህዌ የሰጠው መልእክት እንደ ቀጠለ ነው። ተጓዳኝ አቀራረብ ይጠቀማል።
ከብዙ ጊዜ በፊት… ያደረግሁትን አልሰማህምን
መናገር የፈለገውን አጽንዖት በመስጠት ሰሚው መልሱን እንደሚያውቅ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በእርግጥ ከብዙ ጊዜ በፊት… ያደረግሁትን ታውቃለህ››
የተመሸጉትን ከተሞች
‹‹መያዝ የማይቻሉ ከተሞች›› ወይም፣ ‹‹በረጅሙ ግንብ የተከበቡ ከተሞች››
ሜዳ ላይ እንደ በቀለ ተክል… እንደ ጠወለገ ሣር
የአሦራውያንን ግሥጋሤ ሜዳ ላይ ካለና ከጠወለገ ሣር ጋር ያነጻጽሩዋል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሜዳ ላይ እንዳለ ተክልና ሣር›› ወይም፣ ‹‹እንደሚገባ ያልተተከለ ደካማ ተክል››
በቤት ጣራ ላይ በቅሎ፣ ገና ሳያድግ እንደ ጠወለገ ሣርም ሆነዋል
የአሦራውያንን ግሥጋሤ እንደሚገባ ለማደግ ከማይችሉ ደካማ ተክሎች ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጕም፣ ከማደጉ በፊት እንደ ሣር›› ወይም፣ ‹‹ከመርዘሙ በፊት እንደ ነበረ ሣር››
2 Kings 19:27
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሥ ሰናክሬምን በተመለከተ ለነቢዩ ኢሳይያስና ለንጉሥ ሕዝቅያስ ያህዌ የሰጠው መልእክት እንደ ቀጠለ ነው። ተጓዳኝ አቀራረብ ይጠቀማል።
በእኔ መቆጣትህ
‹‹እኔ ላይ በቁጣ መጮኽህ››
እብሪትህ ወደ ጆሮዬ ደርሶአል
‹‹ጆሮ›› መስማትና ማድመጥን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የትዕቢት ንግግርህን ሰምቻለሁ››
ስናጋዬን በአፍንጫህ አደርጋለሁ፤ ልጓሜን በአፍህ አገባለሁ
‹‹ስናጋ›› እና፣ ‹‹ልጓም›› (ፈረሶች መቆጣጠሪያ) ያህዌ ሰናክሬምን እንደሚቆጣጠር ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንደ እንስሳ እመራሃለሁ››
በመጣህበትም መንገድ እንድትመለስ አደርጋለሁ
ኢየሩሳሌምን ከመውረሩ በፊት ሰናክሬም ወደ አገሩ መመለሱን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ኢየሩሳሌምን ከመውረርህ በፊት በመጣህበት መንገድ ወደ አገርህ እንድትመለስ አደርጋለሁ››
2 Kings 19:29
አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ ኢሳይያስ ለንጉሥ ሕዝቅያስ እየተናገረ ነው። ተጓዳኝ አቀራረብ ይጠቀማል።
የገቦ እህል
‹‹ሳይዘራ የበቀለ እህል››
በሕይወት የተረፈው የይሁዳ ቤት ሥሩን ሰዶ ፍሬ ያፈራል።
የትሩፋኑን መመለስ ሳይዘራ ከበቀለና ፍሬ ከሚሰጥ ተክል ጋር ያነጻጸረዋል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በሕይወት የተረፈው የይሁዳ ሕዝብ ወደ ሕይወትና ወደ ብልጽግና ይመለሳል›› ወይም፣ ‹‹በይሁዳ የሚቀሩት ያበለጽጋሉ፤ ብዙ ልጆችም ይወልዳሉ››
የያህዌ ቅናት ይህን ታደርጋለች
‹‹ያህዌ የሚወስደው ከባድ ርምጃ ይህን ያደርጋል››
2 Kings 19:32
አጠቃላይ መረጃ
ነቢዩ ኢሳይያስ ለንጉሥ ሕዝቅያስ የተናገረው የያህዌ መልእክት እዚህ ላይ ያበቃል። ተጓዳኝ አቀራረብ ይጠቀማል።
አንዲት ፍላጻ አይወረውርባትም
‹‹ፍላጻ›› ማንኛውንም የውጊያና የጥፋት መሣሪያዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እዚህ ውጊያ አያደርግም››
በዐፈር ቁልል አይከባትም
‹‹ከተማዋን ለመያዝ እንዲያመቻቸው ዙሪያዋን የዐፈር ቁልል አያደርጉም››
ይላል ያህዌ
እርሱ የተናገረው እውነት መሆኑን ለማሳየት ያህዌ ስሙን ጠርቶ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ እንዲህ ይላል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ብያለሁ››
ስለ ራሴና ስለ ባርያዬም ስለ ዳዊት
‹‹ስለ ራሴ ክብርና በሚገባ እኔን ላገለገለው ንጉሥ ዳዊት ስለ ገባሁት ቃል››
2 Kings 19:35
እንዲህ ሆነ
‹‹ተደረገ››
185,000 ወታደሮች
‹‹አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ወታደሮች››
ሰዎቹ ሲነቁ
‹‹በሕይወት የተረፉ ሲነሡ››
አድራሜሌክ… ሰርሳር… አስራዶን
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

---

# Chapter 20

2 Kings 20:1
ቤትህን አስተካክል
‹‹ቤት›› በንጉሥ ሕዝቅያስ ሥር ያለውን ነገር ሁሉ ይመለከታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለቤተ ሰብህና ለመንግሥትህ የመጨረሻ መመሪያ ስጥ››
አስብ
ይህ ያህዌን አስታውስ ለማለት የተለመደ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አስታውስ››
ሄድሁ
ይህ፣ ‹‹ሕይወቴን እንደ ኖርሁ›› ለማለት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።
በዐይንህ ፊት መልካም የሆነውን
እዚህ ላይ ዐይን ፍርድንና ግንዛቤን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በፍርድህ መሠረት››
2 Kings 20:4
የያህዌ ቃል መጣ
‹‹ቃል›› ያህዌ ለኢሳይያስ የገለጠውን መልእክት ይወክላል። ይህ የተለመደ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ቃል ተናገረ››
ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ እንባህንም አይቻለሁ
ተጓዳኝ አስተሳሰብን በመጠቀም አንድ መልእክት ለማቅረብ ሁለተኛው የመጀመሪያውን ያጠናክራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጸሎትህን ሰማሁ፤ እንባህንም አየሁ››
በሦስተኛው ቀን
‹‹ከአሁን ጀምሮ ሁለት ቀን›› ኢሳይያስ ይህን የተናገረበት ቀን የመጀመሪያ ቀን ነው፤ ስለዚህም፣ ‹‹ሦስተኛው ቀን›› - ‹‹ከአሁን ጀምሮ ሁለት ቀን›› እንደ ማለት ነው።
2 Kings 20:6
አጠቃላይ መረጃ
በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል ለንጉሥ ሕዝቅያስ መልእክት ከያህዌ እየመጣ ነው።
ዐሥራ አምስት ዓመት
15 ዓመት
ከአሦር ንጉሥ እጅ
‹‹እጅ›› ኀይል፣ ሥልጣንና መቆጣጠር ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከአሦር ንጉሥ ቁጥጥር››
ትኩስ የበለስ ጥፍጥፍ
‹‹የሞቀ ወይን ጥፍጥፍ መለጠፍ››
እነርሱም አዘጋጅተው ዕባጩ ላይ አደረጉለት
‹‹የሕዝቅያስ አገልጋዮች ይህን አደረጉ፤ ሕዝቅያስ ቁስል ላይ አኖሩ››
2 Kings 20:8
ዐሥር ደረጃ ወደ ፊት ይቅደም ወይስ ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ ይመለስ?
‹‹ጥላው›› የተገኘው እንዴት እንደ ነበር ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ የፀሐይ ብርሃን ደረጃው ላይ የሚፈጥረውን ብርሃን ያህዌ ዐሥር ርምጃ ወይም ዐሥር ርምጃ ወደ ኋላ እንዲያደርገው ትፈልጋለህን?››
ዐሥር ደረጃ
ይህ አገላለጽ የሚያመለክተው 2 ነገሥት 20፥11 ላይ የተጠቀሰውን፣ ‹‹የአካዝን ደረጃዎች›› ነው። ምናልባትም ይህ ደረጃ የፀሐይ ጨረር ወደ ፊት ሲሄድ ቀኑ ምን ያህል እንደ ሆነ እንዲቆጥርበት ለንጉሥ አካዝ የተሠራ የተለየ ደረጃ ሊሆን ይችላል። በዚህ ሁኔታ ቀን ሲሆን ጊዜውን ለማወቅ ያገለግላል።
2 Kings 20:10


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ጥላው ዐሥር ደረጃ ወደ ፊት መሄዱ ቀላል ነው

ለምን ቀላል እንደ ሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። ‹‹ይህ ተፈጥሮአዊ ሂደት ስለ ሆነ ጥላው ዐሥር ደረጃ ወደ ፊት እንዲሄድ ማድረግ ቀላል ነው››

የአካዝ ደረጃ

ይህ የቀኑን ጊዜ እንዲያውቅበት ለንጉሥ አካዝ የተሠራ የተለየ ደረጃ ሊሆን ይችላል። ደረጃዎቹ ጊዜ የሚቆጥሩት በቀኑ ጊዜ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለንጉሥ አካዝ የተሠራ ደረጃ››

2 Kings 20:12

መርዱክ — ባልዳን… ባልዳን

እነዚህ የባቢሎን ንጉሥና ወንድ ልጆቹ ስሞች ናቸው።

ደብዳቤውን ሰማ

‹‹ደብዳቤዎቹን በጥንቃቄ አሰበባቸው›› ወይም 2) ‹‹የባቢሎንን ንጉሥ ደብዳቤ ሰማ››

በቤቴ መንግሥቱም ሆነ በመላው ግዛቱ ሕዝቅያስ ሳያሳያቸው የቀረ ምንም ነገር አልነበረም

‹‹ያላሳያቸው… ምንም አልቀረም›› አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋለ ግነት ነው። ሕዝቅያስ ማንኛውንም ጠቃሚ ነገር አሳያቸው ማለት ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቅያስ በቤቱም ሆነ በመንግሥቱ ያለውን ማንኛውንም ጠቃሚ ነገር አሳየው››

2 Kings 20:14

እነዚህ ሰዎች

ይህ የሚያመለክተው ከመርዱክ — ባልዳን መልእክትና ስጦታ ያመጡትን ሰዎች ነው።

በቤቴ ያለውን ሁሉ ዐይተዋል፤ ጠቃሚ ከሆኑት ነገሮቼ ያላሳየኋቸው ምንም የለም

ይህን ነጥብ አጽንዖት ለመስጠት ሕዝቅያስ አንዱን ሐሳብ ሁለት ጊዜ ደጋግሞአል።

ጠቃሚ ከሆኑት ነገሮቼ ያላሳየኋቸው ምንም የለም

‹‹ምንም›› እና ‹‹የለም›› ሐሳቡን አዎንታዊ ለማድረግ አንደኛው ሌላውን ይሽረዋል። ግነቱ ጥቅም ላይ የዋለው ለአጽንዖት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠቃሚ ነገሮቼን ሁሉ አሳየኋቸው››

2 Kings 20:16

ከዚያም ኢሳይያስ ሕዝቅያስን እንዲህ አለው

ኢሳይያስ ለምን እንደ ተናገረ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሰዎቹ ማንኛውንም ጠቃሚ ነገሮቹን በማሳየት ሕዝቅያስ ሞኝነት ማድረጉን ኢሳይያስ ስላወቀ እንዲህ አለው››

የያህዌ ቃል

‹‹የያህዌ መልእክት››

እነሆ… ጊዜ በእርግጥ ይመጣል

‹‹ስማ፣ አንድ ቀን ጊዜ ይመጣል››፤ ‹‹እነሆ›› ጥቅም ላይ የዋለው ኢሳይያስ ለሕዝቅያስ ለሚናገረው ትኩረት ለመሳብ ነው።

ጊዜ

‹‹ጊዜ›› ያልተወሰነ ጊዜን ያመለክታል።

2 Kings 20:19

አስቦአልና

‹‹ሕዝቅያስ ስላሰበ››

እኔ እስካለሁ ድረስ ሰላምና ጸጥታ ከተገኘ የሆነው ቢሆን ምን ቸገረኝ?

መልሱን ቢያውቅ እንኳ ሕዝቅያስ ይህን የጠየቀው ለአጽንዖት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዘመኔ ሰላምና ጸጥታ እንደሚኖር እርግጠኛ መሆን እችላለሁ››

ኩሬ

ውሃ የተጠራቀመበት ትንሽ ቦታ

ቦይ

ውሃ የሚተላለፍበት መስመር

በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?

ጥያቄው የቀረበው እነዚህ ነገሮች ተጽፈው እንደሚገኙ ለአንባቢው ለማሳሳብ ነው። 2 ነገሥት 8፥23 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎአል››

Chapter 21

2 Kings 21:1

ሐፍሴባ

የንጉሥ ምናሴ እናት።

የያህዌ ዐይን ፊት ክፉ ነገር

የያህዌ ዐይን የያህዌን ፍርድና ግንዛቤ ይወክላል። 2 ነገሥት 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ፍርድ ክፉ የሆነ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ክፉ የሚለውን ነገር››

አስጸያፊ ልማድ

የኮረብታውን ማምለኪያ ስፍራ ሠራ… ለበአል መሠዊያዎችን አቆመ፤ የአሼራንም ምስል ዐምድ ሠራ

የኮረብታውን ማምለኪያ ስፍራ ሠራ… ለበአል መሠዊያዎችን አቆመ፤ የአሼራንም ምስል ዐምድ ሠራ

ይህን እንዲሠሩለት ምናሴ አገልጋዮቹን ማዘዝ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኮረብታው ማምለኪያ እንዲሠራ አደረገ.. የበአልን መሠዊያዎች አስገነባ፤ የአሼራን ዐምድ አሠራ›› ወይም፣ ‹‹ሠራተኞቹ የኮረብታውን ማምለኪያ እንዲሠሩለት አደረገ፤ …የበአልንም መሠዊያዎች አሠራቸው፤ የአሼራን ዐምድ አሠራ››

2 Kings 21:4

አጠቃላይ መረጃ

የንጉሥ ምናሴ አገዛዝ ታሪክ ቀጥሏል።

ስሜን በኢየሩሳሌም ለዘላለም አኖራለሁ

ስም የሰው መጠሪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢየሩሳሌም የእኔ ማንነት ለዘላለም በሚታወቅበት ቦታ ትሆናለች››

በሁለቱም በያህዌ ቤት አደባባዮች ለሰማይ ከዋክብት ሰራዊት ሁሉ መሠዊያዎች ሠራ

እነዚህን መሠዊያዎች ያሠራው ሕዝቡ መሥዋዕት እንዲያቀርቡባቸውና እንዲያመልኩባቸው መሆኑ ግልጽ ነው። እነዚህን መሠዊያዎች ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አዘዘ እንጂ፣ እርሱ ራሱ አልሠራቸውም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡ ከዋክብትን እንዲያመልክና መሥዋዕት እንዲያቀርብላቸው በሁለቱ የያህዌ ቤት አደባባዮች መሠዊያዎች ሠራ››

ልጁን በእሳት ውስጥ አሳለፈ

ልጁን ለምን በእሳት ውስጥ እንዳሳለፈና ከዚያ በኋላ ምን እንደ ሆነ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለአማልክት መሥዋዕት እንዲሆን እስኪሞት ድረስ ልጁን በእሳት አቃጠለ››

ምክር ጠየቀ

‹‹መረጃ ጠየቀ››

በያህዌ ዐይን ፊት ብዙ ክፉ ነገር አደረገ

ምናልባትም ሠይፉ በሰውነቱ ውስጥ እንዲገባ እጀታውን መሬት ላይ በማጣበቅ ሲወድቅ ይወጋዋል፡፡ ድርጊቱ ውጤቱ ሞት የሆነውን ነገር ገላጭ ነው፡፡ ይህን 1 ዜና 10:4 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ፡፡ አት: - “ራሱን በሰይፉ ገደለ”
ሦስቱ ልጆቹ
“ሞተ” የሚለው ቃል በቀዳሚው ሐረግ መረዳት ይቻላል፡፡ ሊደገም ይችላል፡፡ አት. “ሦስት ልጆቹም ሞቱ”
1 Chronicles 10:7
የእስራኤል ሰዎች ሁሉ
ይህ ምናልባት ጠቅላይ መግለጫ ነው፡፡ አት: - “የእስራኤል ሰዎች”
ሸሹ
“የእስራኤል ወታደሮች ሸሹ”
ፍልስጥኤማውያንም መጥተው ተቀመጡባቸው
“ፍልስጥኤማውያን መጥተው እስራኤላውያን ጥለዋቸው በሄዱት ከተሞች ይኖሩ ነበር፡፡” ይህ ምናልባት የተከሰተው በቁጥር 8-12 ውስጥ ከተከናወኑት ክስተቶች በኋላ ሊሆን ይችላል፡፡
እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አንድን አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ቋንቋዎ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡
የሞቱትን ለመግፈፍ
“ዋጋ ያለው ነገር ሁሉ ከሰውነቱ ማስወገድ”
1 Chronicles 10:9
ገፈፉትም፥
ፍልስጤማውያን ሁሉንም ከሳኦል አካል አስወገዱ”
ለጣኦቶቻቸውና ለሕዝቡ የምሥራች ይወስዱ ዘንድ
የሆነውን ነገር ለሕዝቡ ነገሩ ፤ ጣኦቶቻቸውንም በጸሎት አወደሱ፡፡
የምሥራች ይወስዱ ዘንድ
አንድ ሰው ስለተፈጠረው ነገር ለሌሎች የሚናገር ሰው ግለሰቡ ጠንከር ያለ ነገር ተሸክሞ ለሌሎች ሰዎች እንደሰጠ ተደርጎ ይገለጻል ፡፡ አት: - “የሆነውን ነገር መንገር”
መሣሪያውንም አኑሥተው
“ፍልስጥኤማውያን የሳኦልን ጋሻ አደረጉ”
በዳጎን
ይህ የሐሰት አምላክ ስም ነው፡፡

1 Chronicles 10:11
የኢያቢስ ገለዓድም ሰዎች ሁሉ ፍልስጥኤማውያን ... በሰሙ ጊዜ
ሁለቱም “ሁሉም” የሚሉት ቃላት አጠቃላይ መግለጫዎች ናቸው፡፡ የከተማዋ ስም በከተማው ውስጥ ለሚኖሩት ሰዎች ትክክለኛ ስም ነው ፣ እናም የሰዎች ቡድን ስም የዚያ ህዝብ ቡድን ወታደሮች ስያሜ ነው። AT: “የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች የፍልስጥኤማውያን ጭፍራ ወታደሮች በሰሙ ጊዜ”
የኢያቢስ ገለዓድም
ይህ በጊልያድ ውስጥ የሚገኝ ከተማ ስም ነው ።
አጥንቶቻቸውን
አጥንቶች የሞተን ሰውነት ይወክላሉ። አት: - “ሰውነታቸውን”
ሰባት ቀንም
“7 ቀናት”
1 Chronicles 10:13
አያያዥ መግለጫ
እነዚህ ቁጥሮች ሳውል ለምን እንደሞተ ጠቅለል ያደርጉናል፡፡ ቋንቋዎ ይህ የታሪኩ መስመር አካል አለመሆኑን ለማሳየት መንገድ ካለው፣ እዚህ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡
እግዚአብሔርንም ስላልጠየቀ
“እግዚአብሔር እንዲመራው አልጠየቅም”
መንግሥቱንም ወደ እሴይ ልጅ ወደ ዳዊት አሳለፈው
እዚህ “መንግሥትን ሠጠው” ማለት ለአንድ ሰው በመንግሥቱ ላይ ስልጣንን መስጠትን የሚያሳይ ፈሊጥ ነው። አት.: - “የእሴይ ልጅ ፣ ዳዊትን ማንገስ

Chapter 11
1 Chronicles 11:1
እስራኤልም ሁሉ ወደ ዳዊት ተሰብስበው
ይህ ጠቅላይ መግለጫ በእስራኤል ውስጥ ካሉ ነገዶች ሁሉ ወደ ዳዊት እንደመጡ እንጂ፣ እያንዳንዱ ግለሰብ ማለት አይደለም። አት: “ከመላው እስራኤል ሰዎች ወደ ዳዊት መጡ” ወይም “ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ ሰዎች ወደ ዳዊት መጡ”
እኛ የአጥንትህ ፍላጭ የሥጋህ ቍራጭ ነን
ይህ ፈሊጥ ዘመድ ናቸው ማለት ነው። አት: - “እኛ የአንተ ዘመድ ነን” ወይም “እኛ አንድ ዘር አለን”
አስቀድሞ
ይህ ታሪካዊ መረጃ ነው። ሳኦል ከዳዊት በፊት ንጉሣቸው ነበር።
ሕዝቤን እስራኤልን አንተ ትጠብቃለህ፤ በሕዝቤም በእስራኤል ላይ አለቃ ትሆናለህ ብሎህ ነበር አሉት
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊ ነገሩ አንድ ናቸው የሚያመለክቱት ያህዌህ ዳዊትን ንጉሥ እንዲሆን የመረጠው መሆኑን ነው ። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)
ሕዝቤን እስራኤልን አንተ ትጠብቃለህ
እዚህ ላይ በሕዝቦች ላይ መግዛቱ እንደ እረኛ ሆኖ ተገልጻል። አት: - “ሕዝቤን እስራኤልን ትጠብቃለህ” ወይም “ሕዝቤን እስራኤልን ትመራለህ”
በእስራኤል ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ ዳዊትን ቀቡት
“መቀባት” እግዚአብሄር ዳዊትን እንደ ንጉሥ አድርጎ የመረጠው መሆኑን ለማሳየት ምሳሌያዊ ድርጊት ነው።
በሳሙኤልም እጅ እንደ ተናገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ሳሙኤል የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል”
1 Chronicles 11:4
ዳዊትም እስራኤልም ሁሉ
እዚህ ላይ “እስራኤል ሁሉ” የሚለው ሐረግ መላውን የእስራኤል ሠራዊት ይወክላል። አት: “ዳዊትና የእስራኤልም ሠራዊት ሁሉ”
ዳዊትም እስራኤልም ሁሉ
“አሁን” የሚለው ቃል በዋናው የታሪክ መስመር ውስጥ ዕረፍትን ለማመልከት ያገለግላል። እዚህ ተራኪው ስለ ኢየሩሳሌም ዳራ መረጃን ይናገራል፡፡
ዳዊት ግን አምባይቱን ጽዮንን ያዘ
እዚህ ላይ “ያዘ” የሚለው ቃል “የተያዘው” ወይም “ድል የተደረገ” ማለት ነው። ዳዊት ሠራዊቱን ስለመራ ፣ ስሙ በከተማዋ ላይ ለተጠቁት ሠራዊት ሁሉ ታላቅ ስም ነው። አት: - “ዳዊት የጽዮንን ምሽግ ተቆጣጠረ” ወይም “ዳዊትና የእስራኤል ሠራዊት የጽዮንን ምሽግ ያዙ”
አምባይቱን ጽዮንን ... የዳዊት ከተማ
እነዚህ ሁለቱም ስሞች የሚያመለክቱት ኢየሩሳሌምን ነው ።
አለቃም ሆነ
x
1 Chronicles 11:7
በዙሪያው ከተማ ሠራ... ኢዮአብም የቀረውን ከተማ አበጀ
“እሱ” የሚለው ቃል ዳዊትን ያመለክታል። አንባቢው ዳዊት እና ኢዮአብ ምናልባት በሌሎች ሰዎች ላይ የሠለጠኑ ሳይሆኑ እንደማይቀሩ መገንዘብ አለበት፡፡
ከሚሎም
ይህ ምናልባት ግድግዳዎቹን ከበስተጀርባ አቧራ በማስያዝ የተገነባውን የመሬት ገጽታ መዋቅር የሚያመለክት ሊሆን ይችላል ።
1 Chronicles 11:10
ለዳዊትም የነበሩት የኃያላን አለቆች እነዚህ ናቸው
“እነዚህ የዳዊት ኃያላን መሪዎች ነበሩ”
ስለ እስራኤል እንደ ተናገረው የእግዚአብሔር ቃል ያነግሡት ዘንድ ከእስራኤል ሁሉ ጋር በመንግሥቱ ላይ አጸኑት
ይህ ሐረግ ሁለቱም የዳዊት ሠራዊት መሪዎች እና መላው ሠራዊት ዳዊት ራሱን በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዲያደርግ አግዞታል ማለት ነው ። አት: - “እርሱን ንጉሥ ያደርገው ዘንድ የዳዊትን መንግሥት አጥብቆ የደገፈው”
ያሾብአም
ይህ የወንድ ስም ነው፡፡
የአክሞናዊው
ይህ ከሃክሞን ጎሳ የመጣውን ሰው ያመለክታል ።
በአንድ ጊዜ
“በአንድ ውጊያ”
1 Chronicles 11:12
ከእርሱም በኋላ
“ከያሶብዓም በኋላ”
አልዓዛር... የዱዲ
x
1 Chronicles 11:15
ከሠላሳውም አለቆች ሦስቱ
“ከ 30 ዎቹ 3”
ዓዶላም ዋሻ
በአዱላም ከተማ አቅራቢያ የሚገኘውን ዋሻ። ”ዓዱላም በቤተልሔም አቅራቢያ ይገኛል።
በራፋይም ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው ።
በዚያም ጊዜ ዳዊት በምሽጉ ውስጥ ነበረ፥
“አስተማማኝ በሆነው ዋሻው ውስጥ”
በዚያም ጊዜ ዳዊት በምሽጉ ውስጥ ነበረ፥
“ፍልስጤማውያን በቤተልሔም ወታደሮችን አሰፈሩ”
በበሩ አጠገብ ካለችው ከቤተ ልሔም ምንጭ ውሃ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት ተመሳሳይውን የውሃ ምንጭ ነው ። ሁለተኛው በቤተልሔም ውስጥ የትኛው የውሃ ምንጭ እንደሆነ ያሳያል ።
1 Chronicles 11:18
ሦስቱ ኃያላን
“3 ኃያላን ሰዎች”
የፍልስጥኤማውያንን ሠራዊት ቀድደው ሄዱ
'በፍልስጥኤማውያን ሠራዊት መካከል በመዋጋት አለፉት'
በበሩም አጠገብ ካለችው ከቤተ ልሔም ምንጭ ውሃ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት ተመሳሳይውን የውሃ ምንጭ ነው ። ሁለተኛው በቤተልሔም ውስጥ የትኛው የውሃ ምንጭ እንደሆነ ያሳያል ።
ለእግዚአብሔር አፍስሶ
ይህ ማለት ውሃውን ለያህዌ መባ አድርጎ አፈሰሰ ማለት ነው፡፡
ይህን አደርግ ዘንድ ... ይከልክለኝ
“እንደዚህ ያለ ነገር በጭራሽ አላደርግም!” ወይም “ይህን ፈጽሞ ማድረግ የለብኝም!”

በነፍሳቸው የደፈሩትም እነዚህ ሰዎች ደም እጠጣለሁን?
ሰዎቹ ውሃውን ወደ እርሱ ለማምጣት ሕይወታቸውን አደጋ ላይ ጥለው ስለነበር ዳዊት ውሃውን እንደ ደም አድርጎ ተናገረው። ይህንን ለማጉላት ጥያቄን ይጠቀማል ። ይህ አጻጻፍ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ሕይወታቸውን አደጋ ላይ የጣሉ የእነዚህን ሰዎች ደም እንደ ሚጠጡ ይህ ውሃ መጠጣት የለብኝም።”
1 Chronicles 11:20
የኢዮአብም
የዚህን ወንድ ስም በ1 ዜና 2:16 እንዴት እንደተረጎሙ ይመልከቱ።
የሦስቱ አለቃ
ይህም ማለት አቢሳ ለዳዊት ውኃ ያመጣ የሦስቱ መሪ ነበር።
በሦስት መቶ
“300 ሰዎች” ወይም “300 ተዋጊዎች”
በሦስቱም መካከል ስሙ የተጠራ ነበረ
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አት: “ሰዎች ስለ ሦስቱ ሲናገሩ ብዙ ጊዜ እሱን ይጠቅሱ ነበር” (ጋባሪ እና ተገባሪ: ይመልከቱ)
በሦስቱ መካከል የከበረ ነበረ አለቃቸውም ሆነ
ይህ በገባሪ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሦስቱ የተወበሉትን ክብር እጥፍ በእጥፍ የተቀበለ ነው። አት: “ሰዎች ለሦስቱ ከሰጡት እጥፍ እጥፍ ክብር ሰጡት እናም እርሱ ሆነ” ወይም 2) ሦስቱ ሌሎችን ከሚያከብሩት በላይ አክብረውታል። አት: “ሦስቱ ሌሎችን ከሚያከብሩት በላይ አክብረውታል ፤ እንዲሁም ሆኗል”
1 Chronicles 11:22
በናያስ ... የዮዳሄ... የአሪኤል
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።
አምስት ክንድ
“ክንድ” ከ 46 ሴንቲሜትር ጋር እኩል የሆነ የመለኪያ አሃድ ነው። አት: - “2.3 ሜትር”
የሸማኔ መጠቅለያ የመሰለ ጦር
ይህ የጦሩን መጠን ከሸማኔው ሞገድ መጠን ጋር ያነፃፅራል። አት: - “የሸመናው ሞገድ መጠን ያለው ጦር”
ወደ እርሱ ወረደ
“በናያስ ወደ ግብፃው ወረደ ።” ይህ ፈሊጥ በጦርነት ውስጥ እሱን አገኘ ማለት ነው ። አት: - “ወረደበት"
1 Chronicles 11:24
ወደ እርሱ ወረደ
“እነዚህን ታላላቅ ሥራዎች አደረጉ”
ወደ እርሱ ወረደ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: “ሦስቱን ኃያላን ሰዎች እንዳመሰገኑት ሰዎች ያወድሱት ነበር”
ከሠላሳው ይልቅ የከበረ ነበረ፥ ነገር ግን ወደ ፊተኞቹ ወደ ሦስቱ አልደረሰም
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: ከ 30ዎቹ ወታደሮች የበለጠ ህዝቡ ያከብረው ነበር ፣ ግን እንደ ሶስቱ ታዋቂ ወታደሮች አይደለም
በዘበኞቹ
ዳዊትን ከጥቃት የመጠበቅ ሃላፊነት ያለው የሰዎች ቡድን ነው
1 Chronicles 11:26
አጠቃላይ መረጃ
ይህ የዳዊት ሠላሳ በጣም ወሳኝ ተዋጊዎችን ዝርዝር ይጀምራል። ዝርዝሩ የእነዚያን የነበሩትን የወንዶችና የጎሳዎችን ስም ይቀጥላል። ዝርዝሩ እስከሚቀጥለው ድረስ ይቀጥላል 1 ዜና 11፡47።
1 Chronicles 11:30
አያያዥ መግለጫ
ይህ የዳዊት ሠላሳ በጣም ወሳኝ ተዋጊዎችን ዝርዝር ይቀጥላል።
1 Chronicles 11:34
አያያዥ መግለጫ
ይህ የዳዊት ሠላሳ በጣም ወሳኝ ተዋጊዎችን ዝርዝር ይቀጥላል።
1 Chronicles 11:38
አያያዥ መግለጫ
ይህ የዳዊት ሠላሳ በጣም ወሳኝ ተዋጊዎችን ዝርዝር ይቀጥላል።
1 Chronicles 11:42
አያያዥ መግለጫ
ይህ የዳዊት ሠላሳ በጣም ወሳኝ ተዋጊዎችን ዝርዝር ይቀጥላል።
ከእርሱም ጋር ሠላሳ
x
1 Chronicles 11:45
አያያዥ መግለጫ
ይህ የዳዊትን ሠላሳ በጣም ወሳኝ ተዋጊዎችን ዝርዝር ያጠናቅቃል።

---

Chapter 12
1 Chronicles 12:1
በተሸሸገ ጊዜ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: “በፊቱ መገኘት በማይችልበት ዘመን” (ገበሪና ተገባሪ: ይመልከቱ)
በቀኝና በግራም እጃቸው ድንጋይ ሊወነጭፉ ፍላጻም ሊወረውሩ ይችሉ ነበር
“በቀኝ እጆቻቸው ወይም በግራ እጆቻቸው በድንጋይ ለመወንጨፍና ፍላጻ ለመወርወር ይችሉ ነበር”
ድንጋይ ሊወነጭፉ
ወንጭፍ አንድ ሰው ረጅም ርቀት ድንጋይ ለመወርወር የሚጠቀምበት የቆዳ መደረቢያ ነው።
1 Chronicles 12:3
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ዚቅላቅ ዳዊትን የተቀላቀሉትን የብንያም ነገድ ሰዎች ዝርዝር የሚጀምር ነው።
በሠላሳው
“30ዎቹ ወታደሮች”
1 Chronicles 12:5
አያያዥ መግለጫ
ይህ ዚቅላቅ ዳዊትን የተቀላቀሉትን የብንያም ነገድ ሰዎች ዝርዝር የሚቀጥል ነው።
1 Chronicles 12:8
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ከዳዊን ጋር የተቀላቀሉትን የጋድ ነገድ የሆኑ ሰዎች ዝርዝር ይጀምራል።
ፊታቸውም እንደ አንበሳ ፊት ነበረ
እዚህ “ፊት” የሚለው ቃል ወንዶቹንና አንበሶቹን ይወክላል።ፊቶቻቸው በውጊያ ሀይለኞች መሆናቸውን ይገልጻል። አት: “አንበሶች በአደን ሀይለኞች እንደሆኑ እነርሱም በውጊያ ነበሩ”
በተራራም ላይ እንደሚዘልል ሚዳቋ ፈጣኖች ነበሩ
ይህ ቃል አጋኖ አጋዘኖች በኮረብታማ ተራራ ላይ በፍጥነት እንደሚጡት እንዲሁ እነዚህ ሰዎች በንፅፅር ተገልጸዋል።
ሚዳቋ
በኮረብቶች እና በከባድ መሬት ላይ በፍጥነት የሚሮጡ እንደ አጋዘን ያሉ እንስሳት
1 Chronicles 12:9
አያያዥ መግለጫ
ይህ ከዳዊን ጋር የተቀላቀሉትን የጋድ ነገድ ሰዎች ዝርዝር ይቀጥላል።
አለቃው ዔዜር፥ ሁለተኛው አብድዩ፥ ሦስተኛው ኤልያብ፥ አራተኛው፥... አምስተኛው... ስድስተኛው ... ሰባተኛው ... ስምንተኛው ... ዘጠነኛው ... አሥረኛው ... አሥራ አንደኛው
ይህ የሰራዊቱ መሪዎች እንደ አስፈላጊነታቸው በቅደም ተከተል ነው።
1 Chronicles 12:14
ታናሹ ከመቶ፥ .. ይመዛዙ ነበር
ይህ ማለት አንድ መሪ የሚመራው አነስተኛ የሰራዊቱ ቡድን 100 ሰዎች ነበሩ ማለት ነው።
ታላቁ ከሺህ ይመዛዙ ነበር
ይህ ማለት አንድ መሪ የሚመራው ከፍተኛው የሰራዊት ቡድን 1,000 ወንዶች ነበር ማለት ነው።
በመጀመሪያው ወር
ይህ በዕብራውያን የቀን አቆጣጠር የመጀመሪያ ወር ነው። ጊዜው በምዕራባዊ የቀን መቁጠሪያዎች የመጋቢት የመጨረሻ ክፍል እና በኤፕሪል የመጀመሪያ ክፍል ላይ ነው። የመጨረሻው ዝናብ ሲመጣ በፀደይ ወቅት መጀመሪያ ላይ ነው። (ዕብራውያን ወራት እና ሕግኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ዮርዳኖስ ከዳር እስከ ዳር ሞልቶ በነበረ ጊዜ
“ዮርዳኖሱ ዳርቻው ባለፈ ጊዜ”
በሸለቆውም ውስጥ … የተቀመጡትን ሁሉ አባረሩ
“በሸለቆዎች ውስጥ ያሉትን ሁሉ አሳደዱ”
1 Chronicles 12:16
ከብንያምና ከይሁዳ ወገን ሰዎች
“ከብንያምና ከይሁዳ ነገድ የሆኑ ሰዎች”
የአባቶቻችን አምላክ ይመልከተው
እግዚአብሔር የሚያየው በትርጉም ሊቀርብ ይችላል። አት: - “ማድረግ የምትፈልጉትን የአባቶቻችን አምላክ ይመለከት” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)
1 Chronicles 12:18
መንፈስም … በአማሳይ ላይ መጣ
መንፈስም አማሳይን መጣበት ሲል መንፈስ ሀይል እንደሰጠው ተደርጎ ተገልጾል። አት: “መንፈስ አማሳይን ሀይል ሰጠው” (ዜይቤ: ይመልከቱ)
አማሳይ
ይህ የወንድ ስም ነው።
1 Chronicles 12:19
ከዱ
“ለመቀላቀል መሪዎቻቸውን ተዉ”
ወደ ጌታው ወደ ሳኦል ይመለሳል ሲሉ
“ከእና ጋር መዋጋቱን ትቶ ለጌታው ለሳኦል ይዋጋል”
ዓድና, ዮዛባት, ይዲኤል, ሚካኤል, ዮዛባት, ኤሊሁ, እና ጺልታይ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።
የምናሴ ሻለቆች
ይህ እንዳንዳቸው እነዚህ ወንዶች ሺህ ወታደሮች ያሉት ቡድን ከምናሴ ነገድ ይመሩ ነበር ማለት ነው። አት “እያንዳንዱ 1,000 ወንዶችን በምሴ ነገድ ውስጥ ይመራሉ” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)
1 Chronicles 12:21
አደጋ ጣዮቹ
“የዘራፊዎች ቡድን።” ይህ በአገራቱ ጫፍ የሚንቀሳቀሱትን ሰዎች የሚዘርፉ የሰዎች ቡድኖችን ይወክላል።
ዕለት ዕለት
“ሁሉንም ቀን”
እንደ እግዚአብሔርም ሠራዊት ታላቅ ሠራዊት
አማራጭ ትርጉሞች 1) ሀረጉ “እንደ እግዚአብሄር ሠራዊት” ማለት “እግዚአብሄር እንደ ሰበሰበው ሠራዊት” ወይም 2) ቃሉ “እግዚአብሄር” የሠራዊቱን ትልቅነት ለማሳየት እንደ ፈሊጥ ያገለግላል። አት: “በጣም ትቅል ሠራዊት”
1 Chronicles 12:23
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ከእያንዳንዱ ነገድ ዳዊትን የተቀላቀሉትን ወንዶች የቁጥር ዝርዝር ይጀምራል።
የሳኦልን መንግሥት ወደ እርሱ ይመልሱ ዘንድ
በሳኦል ፈንታ ዳዊትን ንጉስ ያደረጉት ሰዎች ልክ የሳኦልን መንግስት ይዞታ ለዳዊት እንደመስጠት ይገላፃል። አት: “ዳዊትን በሳኦል ቦታ ማንገስ”
እንደ እግዚአብሔርም ቃል
“የያህዌን ቃል እውነት አደረጉ” ወይም “የያህዌን ቃል ፈጸሙ”
6,800, ለጦርነት የታጠቁ
“ለጦችነት የታጠቁ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ”
የስምዖን ልጆች
“ከስምዖን” ወይም “ከስምዖን ነገድ”
7,100 ተዋጊ ወንዶች
“ሰባት ሺህ አንድ መቶ ተዋጊ ወንዶች”
1 Chronicles 12:26
አያያዥ መግለጫ
ይህ ከእያንዳንዱ ነገድ ዳዊትን የተቀላቀሉ ወንዶች ቁጥር ዝርዝር ይጀምራል።
4,600 ተዋጊ ወንዶች
“አራት ሺህ ስድስት መቶ ተዋጊ ወንዶች”
ዮዳሄ
ይህ የወንድ ስም ነው።
ከእርሱ ጋር 3,700 ነበሩ
“ከእርሱ ጋር ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ነበሩ”
1 Chronicles 12:32
አያያዥ መግለጫ
ይህ ከእያንዳንዱ ነገድ ዳዊትን የተቀላቀሉ ወንዶች ቁጥር ዝርዝር ይቀጥላል። (ቁጥሮች: ይመልከቱ)
ሁለት መቶ … ሀምሳ ሺህ
“200 … 50,000”
ዘመኑን የሚያውቁ
አማራጭ ትርጉሞች 1) እነዚህ ወንዶች እርምጃ ለመውሰድ ትክክለኛውን ጊዜ ያውቃሉ ወይም 2) እነዚህ ወንዶች በእስራኤል ውስጥ ያለውን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ በጥሩ የሚረዱ።
የማያመነቱ
ለዳዊት ታማኝ እንደሚሆኑ በውስጥ ታዋቂ ነው። አት: “ያልተከፋፈለ ታማኝነት ለዳዊት ለመስጠት የተዘጋጁ”
1 Chronicles 12:34
አያያዥ መግለጫ
ይህ ከእያንዳንዱ ነገድ ዳዊትን የተቀላቀሉ ወንዶች ቁጥር ዝርዝር ይቀጥላል።
አንድ ሺህ … ሠላስ ሰባት ሺህ
“1,000 … 37,000” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)
ከዳን
“ከዳን” ወይም “ከዳን ነገድ”
28,600 ወንዶች
“ሀያ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ወንዶች”
1 Chronicles 12:36
አያያዥ መግለጫ
ይህ ከእያንዳንዱ ነገድ ዳዊትን የተቀላቀሉ ወንዶች ቁጥር ዝርዝር ይቀጥላል። (ቁጥሮች: ይመልከቱ)
1 Chronicles 12:38
ዳዊትን በእስራኤል ሁሉ ላይ ያነግሡት ዘንድ … በፍጹም ልባቸው
“ዳዊትን ንጉስ ለማድረግ ቆረጡ”
በዚያ ከዳዊት ጋር … ተቀመጡ
“እነዚህ ወታደሮች በዚይ ከዳዊት ጋር ነበሩ”
ሦስት ቀን
“3 ቀናት” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)
በእስራኤል ዘንድ ደስታ ሆኖአል
The word “እስራኤል” የሚለው ቃል አገሪቱን የመሠረቱትን ሕዝቦች ይወክላል። አት: “የእስራኤል ሕዝብ እያከበሩ ነበር” (Synecdoche: ይመልከቱ)

---

Chapter 13
1 Chronicles 13:1
ከሻለቆችና ከመቶ አለቆች
አማራጭ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቁጥሮች እነዚህ መሪዎች የመሯቸውን ወታደሮች ትክክለኛ ብዛት ያሳያል። አት: “1,000 ወታደሮች መሪዎች እና 100 ወታደሮች መሪዎች” ወይም 2) “ሺዎች” እና “መቶዎች” ተብለው የተተረጎሙት ቃላት ትክክለኛ ቁጥሮችን አያሳዩም፤ ነገር ግን የትልቅ እና የአነስተኛ የሰራዊት አከፋፈሎች ስም ናቸው። አት: “የትልቅ የሰራዊት ክፍሎች መሪዎች እና የትንሽ ሰራዊት ክፍሎች መሪዎች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)
የእስራኤልን ጉባኤ ሁሉ
ይህ በዚህ ቦታ የተሰበሰቡትን ሁሉንም እስራኤላውያን ይመለከታል። አት: - “እዚያ የተሰበሰቡት እስራኤላውያን ሁሉ” (ይመልከቱ:- ታሳቢ የሆነ ዕውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ)
ከአምላካችን ከእግዚአብሔርም ወጥቶ እንደ ሆነ
ይህ ፈሊጥ ይህ እርምጃ ያህዌ የሚቀበለው ድርጊት ነው ማለት ነው። አት: - “አምላካችን እግዚአብሔር የሚቀበለው ይህ ከሆነ” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)
ወደ እኛ ይሰበሰቡ ዘንድ እንላክ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ በቀጥተኛ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “መልእክተኞች እንዲቀላቀሉን ይንገሯቸው” ወይም “እነሱ ከእኛ ጋር ይሳተፉ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)
በሕዝቡ ሁሉ ዓይን ዘንድ ቅን ነበረና
እዚህ “ዐይን” የሚለው ቃል ማየትን ይወክላል ፣ ማየትም ሀሳቦችን ወይም ፍርድን ይወክላል። አት: - “ሕዝቡ ሁሉ እነዚህ ነገሮች ትክክል እንደሆኑ አድርገው ይመለከቱ ነበር” (ዘይቤ፡ ተመልከት)
1 Chronicles 13:5
ዳዊት እስራኤልን ሁሉ ሰበሰበ
እዚህ ላይ “ሁሉም” የሚለው ቃል አጠቃላይ ነው። ሐረጉ ዳዊት ከመላው እስራኤል ሰዎችን ሰብስቧል ማለት እንጂ፣ በእስራኤል እያንዳንዱን ሰብስቧል ማለት አይደለም። አት: - “ዳዊት ከእስራኤል ሁሉ ሰዎችን ሰበሰበ” (ቃል አጋኖ እና ማጠቃለል: ይመልከቱ)
ሴቦ ሐማት... ቂርያትይዓሪም... በኣላ
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው። “በኣላ” ለቂርያትይዓሪም ሌላ ስም ነው። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ) እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው ። ‹በኣላ› ለቂርያትይዓሪም ሌላ ስም ነው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጎሙ ይመልከቱ)
በይሁዳ ወዳለችው
በይሁዳ ያለው
የእግዚአብሔርንም ታቦት ያመጡ ዘንድ
ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚወስዱት ያመለክታል። AT: “የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ለመውሰድ” (ታሳቢ የተደረገ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)
ያመጡ ዘንድ
ኢየሩሳሌምን በእስራኤል ከሚገኙ ከማንኛውም ስፍራ ከፍ ያለ ነው ፣ ስለሆነም እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም ማወጣት እና ከእርሷ መውረድ በማለት መናገራቸው የተለመደ ነገር ነበር ።
በያህዌ ስም የሚጠራ
ይህ በቀጥተኛ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በስም የተጠሩ” የሚለው ፈሊጥ የሚያመለክተው የነገሩ ባለቤት የሆነውን ነው። አት: - “የእግዚአብሔር የሆነው” ወይም 2) ታቦቱ የእግዚአብሔር ስም በላዩ ላይ አለ። አት: - “የያህዌን ስም የተሸከመ” (ፈሊጥን፡ ተመልከት)
በኪሩቤል ላይ የተቀመጠውን
ኪሩቤል ማለት በቃል ኪዳኑ ታቦት መክደኛ ላይ ያሉት መሆናቸውን ግልፅ ማድረግ ያስፈልጋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የቃል ኪዳኑን ታቦት እንደ የእግዚአብሔር መቀመጫ ከላይ ሆኖ በሰማይ በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጠበት አግረኛ ይመስሉት ነበር። አት: “በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ከኪሩቤል በላይ በዙፋኑ ላይ የሚቀመጠው” (ታሳቢ የተደረገ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)
1 Chronicles 13:7
አሚናዳብ... ዖዛና አሒዮም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።
ዳዊትና እስራኤል ሁሉ
እዚህ ላይ “ሁሉም” የሚለው ቃል አጠቃላይ ነው። አት: “ዳዊትና በዚያ የነበሩት እስራኤል ሁሉ” (ቃል አጋኖ እና ማጠቃለል: ይመልከቱ)
አውታር ባለው መሣሪያ መጫወት
“ባለ አውታር መሣሪያዎች እየተጫወቱ መዘመር”
ከበሮ
መሳሪያው ሲወዘወዝ ድምፅ የሚሰጥ በዙሪያው ብረት ያለው የእጅ ከበሮ (የማይታወቁትን መተርጎም: ይመልከቱ)
ፀናፅል
ከፍተኛ ድምጽ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭን እና ክብ የብረት ሳህኖች (የማይታወቁትን ይተርጉሙይመልከቱ)
1 Chronicles 13:9
ኪዶን፣ ዖዛ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።
የእግዚአብሔርም ቍጣ በዖዛ ላይ ነደደ
የእግዚአብሔር ቁጣ እግዚአብሔር የተቆጣበትን ሰው እንደሚያቃጥለው ተደርጎ ተገልፆል። አት: “ያህዌ በዖዛ በጣም ተቆጥቶ ነበር” (ዘይቤ: ይመልከቱ)
በእግዚአብሄር ፊት
“በእግዚአብሔር ፊት”
በዚያም
ይህ ገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ሰዎች ያን ስፍራ ይጠሩታል” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)
የዖዛ ስብራት
ይህ የቦታ ስም ነው። ተርጎሚዎች እንዲህ ሲሉ የግርጌ ማስታወቻ መጨመር ይችላሉ፣ “‘የዖዛ ስብራት’ ማለት ‘የዖዛ ቅጥት.’ ” (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጎሙ፡ ይመልከቱ)
እስከ ዛሬም
በ 1 ዜና 4፡43 ውስጥ ይህንን ሐረግ እንዴት እንደሚተረጉሙ ይመልከቱ።
1 Chronicles 13:12
የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ እኔ እንዴት አመጣለሁ?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት እንደሚፈራ ለማጉላት ነው። ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “የእግዚአብሔርን ታቦት ከእኔ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት በጣም ፈራለሁ።” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)
ጌት ሰው ወደ አቢዳራይህ
የወንድ ስም ነው። “የጌት ሰው” ከጌት ከተማ የሆነ ግለሰብ ነው። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)
ወደ ጌት ሰው ወደ አቢዳራ ቤት አሳለፈው
“ከዖብአዴን ቤተሰብ ቤት ውስጥ”
ሦስት ወራት
“3 ወራት”
ይህዌ ቤቱን ባረከ
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል ለቤተሰቡ የባህሪ ስም ነው። አት: “እግዚአብሔርም ቤተሰቡን ባርኮታል” (የባህሪ ስም: ይመልከቱ)

---

Chapter 14
1 Chronicles 14:1
ኪራም
ይህ የወንድ ስም ነው።
አናጢዎችንም
ከእንጨት ነገሮችን የሚሰሩ ሰዎች
ጠራቢዎችንም
ከድንጋይ ወይም ከሸክላ ሰዎች ነገሮችን ይሰራሉ
ቤት ይሠሩለት ዘንድ
አናጢዎችና ግንበኞቹ ለዳዊት ቤት ሠሩ ”
እንዳጸናው
“ሰሩለት”
መንግሥቱ ከፍ ብሎአልና
“ከፍ ከፍ” የሚለው ፈሊጥ ያህዌ ለዳዊት መንግሥት ታላቅ ክብርን ሰጠው ማለት ነው። ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “እግዚአብሔር የዳዊትን መንግሥት ከፍ ከፍ አደረገው” ወይም “እግዚአብሔር ለዳዊት መንግሥት ታላቅ ክብር ሰጠው” (ፈሊጥ እና ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመልከቱ)
ስለ ሕዝቡም ስለ እስራኤል
እዚህ “የእሱ” የሚለው ቃል ያህዌን ያመለክታል።
1 Chronicles 14:3
የወለዳቸው የልጆቹ
“ሚስቶቹ ለእርሱ የወለዱአቸው ልጆች”
ሳሙስ፥ ሶባብ፥ ናታን፥
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። በ 1 ዜና 3፡5 ውስጥ እነዚህን እንዴት እንደተረጉሟቸው ይመልከቱ። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)
ኢያቤሐር፥ ኤሊሱዔ፥ ኤሊፋላት፥ ኖጋ፥ ናፌቅ፥ ያፍያ፥ ኤሊሳማ፥ ኤሊዳሄ፥ ኤሊፋላት
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። እነዚህ ስሞች በ1 ዜና 3፡6-8 ይገኛሉ፣ በዚያ “ኤልፋላት” የተጻፈው “ኤልፊሌት” እና ቢሊያዳ ደግሞ is spelled “ኢሊያዳ ቢሆንም እንኳን።” (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)
1 Chronicles 14:8
አሁን

ጸሐፊው ይህን ቃል በ1 ዜና 14:3-7 ያለውን የዳራ መረጃ መስጠት መጨረሱንና አዲሱን የታሪኩን ክፍል መጀመሩን ያሳያል። ቋንቋዎ ይህንን የሚያከናውንበት የተለየ መንገድ ሊኖረው ይችላል ።
ዳዊት ንጉሥ ሆኖ እንደተቀባ
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - "የእስራኤል ሽማግሌዎች ዳዊትን ንጉሥ አድርገው ቀቡት" (ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመልከቱ)
ሊጋጠማቸው ወጣ
ዳዊት ጦሩን እንዲዋጓቸው እንላከ ታሳቢ ያደርጋል። አት: "ጦሩን እንዲዋጓቸው ላካቸው" (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)
በራፋይም ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው።
1 Chronicles 14:10
በእጅህ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁና
ይህ ፈሊጥ ያህዌ ዳዊት በእነሱ ላይ ድል እንዲቀዳጅ ያስችለዋል ማለት ነው። አት: - "በእነሱ ላይ ድል ይሰጥህ" (ፈሊጥ ተመልከት)
በአልፐራሲም
ይህ የቦታ ስም ነው። እንዲህ የሚል የግርጌ ማስታዎሻ መጨመር ይችላሉ፣ "'በአልፐራሲም' የሚለው ቃል 'የመጠርመስ ጌታ' ማለት ነው" (የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)
ውኃ እንዲያፈርስ እግዚአብሔር ጠላቶቼን በእጄ አፈረሳቸው
ጎርፍ የሚያልፍበትን ሁሉ እንደሚያረነዳ እንዲሁ ዳዊት እግዚአብሄር የዳዊትን ጠላቶች በቀላሉ ማሸነሩን ይናገራል። አት: "ጎርፍ በሁሉ ነገር በቀላሉ እንደሚፈነዳ … እግዚአብሄር ጠላቶቼን በቀላሉ አሸነፈ" (ተመሳሳይነት: ይመልከቱ)
በእጄ
ይህ የዳዊትን ምንጮች ያሳያል። አት: - "ሠራዊቴን በመጠቀም" (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
በእሳትም አቃጠሏቸው
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - "የሐሰት አማልክቶቻቸውን ለማቃጠል" (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)
1 Chronicles 14:13
በሸለቆው
"የራፋይም ሸለቆ"
አደጋ ጣሉ
"ከፊት ጥቃት"
ከእነርሱ ዞረህ በሾላው ዛፍ ፊት ለፊት ግጠማቸው
"በሾላው ዛፎች ባለው ጫካ አልፈህ ከበስተኃላ አጥቃቸው"
በሾላው ዛፍ
እዚህ ላይ "ሾላ" የዛፍ አይነት ሲሆን ጫካዎች በአንድነት የሚያድጉ ብዙ የሾላ ዛፎችን ይገልጻል። (የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)
1 Chronicles 14:15
አያያዥ መግለጫ፡
እግዚአብሔር ለዳዊት ጥያቄ መልስ መስጠቱን የቀጥላል።
በሾላውም ዛፍ አራስ ውስጥ የሽውሽውታ ድምፅ ስትሰማ
ይህ የሚያወራው በንፋሱ ቅጠሎቹ ሲወዛወዙ ስለሚያሰሙት የተራማጅ ሰራዊት ስለመሰለው ድምፅ ነው። አት: "ንፋስ በሾላ ዛፎች ጫፍ ሲነፍስ የሚራመዱ ሰዎች እንደሚመስለው ድምፅ" (ዜይቤ: ይመልከቱ)
ጌዝር
ይህ የከተማ ስም ነው።
የዳዊትም ዝና በየአገሩ ሁሉ ወጣ
የዳዊትን ዝና በየአገሩ ሁሉ የሰሙ ሰዎች የዳዊት ዝና ወደነዚያ አገሮች እንደ ተጓዘ ይነገራል። አት: - "በሩቅ ያሉ ሰዎች ስለ ዳዊት ዝና ሰሙ" (ሰብአዊ: ይመልከቱ)

---

Chapter 15
1 Chronicles 15:1
ዳዊትም በከተማው ላይ ለራሱ ቤቶችን ሠራ
ይህን ዳዊት ይህን የሚሰሩለት ሌሎች ሰዎች እንደነበሩተረ አንባቢው መረዳት እንዲችል ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። አት: "ዳዊት ቤት የሚሰሩለት ሰራተኞች ነበሩተ … እንዲያዘጋጁ አደረጋቸው" (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ከመረጣቸው
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - "እግዚአብሔር መረጣቸው" (ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመልከቱ)
ዳቂት …. እስራኤልን ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም ሰበሰበ
እዚህ ላይ "ሁሉም" የሚለው ቃል አጠቃላይ ነው። "እስራኤል ሁሉ" የሚለው ሐረግ ዳዊት ከመላው እስራኤል ሰውዎችን መሰብሰቡን እንጂ እስራኤልን እያንዳንዱን ግለሰብ ሰብስቦ አይደለም። አት. "ዳዊት ከመላው እስራኤል በኢየሩሳሌም ሰዎችን ሰበሰበ" (ቃል አጋኖ እና ማጠቃለል: ይመልከቱ)
1 Chronicles 15:4
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ዳዊት ከእያንዳንዱ ከሌዋውያን ጎሳ ያሰባሰባቸውን ሰዎች ዝርዝር ይጀምራል። (የስሞችን እና ቁጥሮችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)
120 ወንዶች
"አንድ መቶ ሀያ ሰዎች" (ቁጥሮችን፡ ይመልከቱ)
220 ወንዶች
"ሁለት መቶ ሀያ ሰዎች" (ቁጥሮችን፡ ይመልከቱ)
1 Chronicles 15:7
አያያዥ መግለጫ፡
ይህ ዳዊት ከእያንዳንዱ ከሌዋውያን ጎሳ ያሰባሰባቸውን ሰዎች ዝርዝር ይቀጥላል። (የስሞችን እና ቁጥሮችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)
1 Chronicles 15:11
ኡርኤልን፥ ዓሣያን፥ ኢዮኤልን፥ ሸማያን፥ ኤሊኤልን፥ አሚናዳብንም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። በ 1ኛ ዜና 5-6 እና በ1 ዜና 7-10 እንዴት እንደተረጉሟቸው ይመልከቱ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
1 Chronicles 15:13
አልተሸከማችሁምና
"መርከቡን አልተሸከምክም"
በመካከላችን ስብራት አደረገ
"ለመዋጋት" የሚለው ፈሊጥ በአንድ ሰው ላይ የኃይል እርምጃ መውሰድ ማለት ነው። አት: - "ጥቃት ተሰነዘረብን" ወይም "ጥቃት ሰነዘረብን" (ፈሊጥ፡ ተመልከት)
አልፈለግነውምና
እዚህ እግዚአብሔርን መፈለግ ማለት ምክሩን መፈለግ ማለት ነው። አት: - "መመሪያ እንዲሰጠን አልጠየቅነውም" (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
እንዳዘዘው እንደ እግዚአብሔር ቃል
"ቃል" የሚለው ቃል በግስ ሊተረጎም ይችላል። ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - "የያህዌ ቃል የሰጣቸው ሕጎች" ወይም "ያህዌ የተናገራቸው ሕጎች" (ገባሪ ወይም ተገባሪ እና ረኪክ ስሞች፡ ይመልከቱ)
1 Chronicles 15:16
አያያዥ መግለጫ፡
ይህ ሕዝቡ ታቦቱን ወደ ኢየሱሳሌም ሲያመጡ ሌዋውያኑ እንዲዘምሩና ሙዚቃ እንዲጫወቱ የሾሟቸው ሰዎች ዝርዝር ይጀምራል። ( የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)
በጸናጽልም
ከፍተኛ ድምጽ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭን እና ክብ የብረት ሳህኖች። ይህን 1 ዜና 13:8 እንዴት እንደተረጎሙት ይዩ (የማይታወቁ ይተርጉሙ፡ ይመልከቱ)
ድምፃቸውንም … ከፍ እንዲያደርጉ
ይህ ፈሊጥ ማለት ጮክ ብሎ መዘመር ማለት ነው ። አት: - "በታላቅ ድምፅ መዘመር" (ፈሊጥን፡ ይመልከቱ)
ከእነርሱም ጋር በሁለተኛው ተራ የሆኑትን ወንድሞቻቸውን
ይህ ምናልባት እነዚህ ሰዎች በዝቅተኛ ቦታዎች ያገለገሉ በነር እነርሱም ለኤማን ፣ ለአሳፍ እና ለኢታን ረዳቶች ነበሩ ማለት ሊሆን ይችላል። አት: - "በዝቅተኛ ቦታ ላይ ያሉ ዘመዶቻቸው ከእነርሱ ጋር ነበሩ" ወይም "የሚከተሏቸው ዘመዶች ይረዷቸው ነበር" (ተራ ቁጥር ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)
ሚቅንያን, በረኞችንም ዖቤድኤዶምንና ይዒኤልን
"በር ጠባቂዎች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሮች ወይም መግቢያዎችን የሚጠብቁ ሰዎችን ነው ። እዚህ ላይ የቃል ኪዳኑን ታቦት የመጠበቅን መብት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚያመለክት ሲሆን ለኦቤድኤዶም እና ለያ .ል ይመለከታል ። አት: - “ሚካናህ፣ እና በረኞች፣ ኦቤድ ኤዶም እና ያይል” (የተገመተ ዕውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

1 Chronicles 15:19

አያያዥ መግለጫ፡

ሕዝቡ ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ሲያመጡ ሌዋውያኑ እንዲዘምሩና ሙዚቃ እንዲጫወቱ የሾሟቸውን ወንዶች ዝርዝር ይቀጥላል። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ይመልከቱ:)

መዘምራንም ኤማንና አሳፍ ኤታንም … ነበር

ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ሌዋውያን ኤማን፣ አሳፍ እና ኢታን ሙዚቀኞችን ሾሙ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመልከቱ)

ጸናጽል

ከፍተኛ ድምጽ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭን እና ክብ የብረት ሳህኖች። ይህንን በ1ኛ ዜና 13፡8 ውስጥ እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ። (የማይታወቁትን ይተርጉሙ፡ ይመልከቱ)

አላሞት … ሺሚኒት

የእነዚህ ቃላት ትርጉም ግልፅ አይደለም ግን የሙዚቃ ዘይቤን ሊያመለክት ይችላል ። (የማይታወቁትን ይተርጉሙ፡ይመልከቱ)

መንገዱን መሩ

“ሌሎቹን ሙዚቀኞች መራ” ወይም “ሰልፈኛውን መራ”

1 Chronicles 15:22

አያያዥ መግለጫ፡

ይህ ሕዝቡ ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ሲያመጡ ሌዋውያኑ እንዲዘምሩና ሙዚቃ እንዲጫወቱ የሾሟቸውን ወንዶች ዝርዝር ይቀጥላል። (የስሞችን አተረጓጎም፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 15:25

የሻለቆችም

አማራጭ ትርጉሞች 1) the word “ሺዎች” የሚለው ቃል እያንዳንዱ መሪ የመራቸውን ወታደሮች ሊገላ ይገልጻል። አት: - “የ 1,000 ወታደሮች አዛዥ” ወይም 2) “በሺዎች” ተብሎ የተተረጎመው ቃል ትክክለኛ ቁጥሮችን አይወክልም ፣ ነገር ግን ትልቅ የጦር ሰራዊት ስም ነው። አት: - “ትልቅ የጦር ሰራዊት ክፍል አዛዥ” (ቁጥሮችን፡ ይመልከቱ)

ያቤድኤዶም

ይህ የወንድ ስም ነው።

1 Chronicles 15:27

ዳዊትም፥ ታቦቱንም የተሸከሙ ሌዋውያን ሁሉ፥ መዘምራኑም፥ የመዘምራኑም አለቃ ከናንያ የጥሩ በፍታ ቀሚስ ለብሰው ነበር

ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ዳዊት፣ ታቦቱን የተሸከሙት ሌዋውያን ፣ ዘማሪዎቹ እና ከዘማሪዎቹ ጋር የዘማሪዎቹ አለቃ ሁሉ ጥሩ የበፍታ ቀሚስ ለብሰዋል” (ገባሪ ወይም ተገባሪ ተመልከት)

የበፍታ

ከፍላክስ አትክልት የተሰራ ልብስ

ከናንያ

ይህ የወንድ ስም ነው።

እስራኤል ሁሉ … የቃል ኪዳን ታቦት አመጡ

እዚህ ላይ “ሁሉም” የሚለው ቃል አጠቃላይ ነው። አት: “ስለዚህ እጅግ ብዙ ሰዎች ታቦቱን አመጡ” (ቃል አጋኖ እና መጠቅለል: ይመልከቱ)

ጸናጽልና

ከፍተኛ ድምጽ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭን እና ክብ የብረት ሳህኖች። ይህንን በ1ኛ ዜና 13፡8 ውስጥ እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ። (የማይታወቁትን ይተርጉሙ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 15:29

የእግዚአብሔርም ቃል ኪዳን ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ በደረሰ

“ሕዝቡ የያህዌን የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ ሲያመጡ”

ሜልኮል

ይህ የዳዊት ሚስት ስም ነው። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

በልቧ ናቀችው

እዚህ “ልብ” ሀሳቦችን ወይም ስሜቶችን ይወክላል። አት: - “ናቀችው” ወይም “ጠላችው”

Chapter 16

1 Chronicles 16:1

አጠቃላይ መረጃ:

በእነዚህ ቁጥሮች ላይ “እነሱ” የሚለው ቃል ካህናትንና ሌዋውያንን ያመለክታል።

በእግዚአብሔር ፊት

“ወደ እግዚአብሔር”

ዳዊትም የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የደኅንነቱን መሥዋዕት ማቅረብ በፈጸመ ጊዜ

ይህ መስዋዕት የማቅረብ ዋነኛውን ስራ ሲሰሩ ካህናቱን ሲመራቸው ለዳዊት የባህሪ ስም ነው። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ዳዊትም የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የደኅንነቱን መሥዋዕት ማቅረብ በፈጸመ ጊዜ

“በያህዌ ስም” መባረክ ማለት በያህዌ ኃይል እና ስልጣን ወይም እንደ ተወካይ መባረክ ማለት ነው። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ለእስራኤልም ሁሉ አካፈለ

ይህ የተከናወነው በዳዊት ስልጣን እና አመራር ነበር። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

የዘቢብ ጥፍጥፍ

ከደረቀ ወይን ጋር የተጋገረ ጣፋጭ እንጀራ

1 Chronicles 16:4

ዘካርያስ፣ ይዒኤል፣ ሰሚራሞት፥ ይሒኤል፥ መቲትያ፥ ኤልያብ፥ በናያስ፥ ያቤድኤዶምና፥ ይዒኤል… በናያስና የሕዚኤል

እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።

ከእርሱም በኋላ

ይህ ማለት በሥልጣን እና በቦታ ከእሱ ቀጥሎ ማለት ነው። (ሕገኛ ቁጥሮች: ይመልከቱ)

በጸናጽል

እነዚህ ድምፅ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭንና ክብ የብረት ሰሌዳዎች ናቸው። ይህንን በ 1ኛ ዜና13፡ 8 ውስጥ እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ። (የማይታወቁትን ይተርጉሙ፡ ይመልከቱ)

1 Chronicles 16:7

በዚያ ቀን

እዚህ “ያ ቀን” እዚህ ላይ የሚያመለክተው የቃል ኪዳኑ ታቦት ከኦቤድኤዶም ቤት ወደ ኢየሩሳሌም የተላለፈበትን ቀን ነው።

የምስጋና መዝሙር

“የምስጋና መዝሙር”

ስሙን ጥሩ

እዚህ “ስሙ” ያህዌን ይወክላል። አት: - “ያህዌን ይጥሩ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

ለአሕዛብ

ይህ በአገሩቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ያመለክታል። አት: - “የአገራቱ ሕዝቦች” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

1 Chronicles 16:10

በቅዱስ ስሙ ተጓደዱ

እዚህ “ቅዱስ ስሙ” ያህዌን ይወክላል። አት: - “በያህዌ ማንነት መመካት” ወይም “በያህዌ መመካት” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ደስ ይበለው

እዚህ “ልብ” ያህዌን የሚፈልግን ሰው ይወክላል። አት: “ያዌን የሚሹ ሰዎች ደስ ይበላቸው” (Synecdoche: ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ፈልጉት፥ ትጸናላችሁም

“የይሕዌን ብርታት መፈለግ” እርሱ እንዲያጠነክርህ መጠየቅ ማለት ነው። አት: “እግዚአብሔርን ፈልጉ እና ኃይሉንም እንዲሰጥ ጠይቁት” (ፈሊጥ፡ ይመልከቱ)

ሁልጊዜ ፊቱን ፈልጉ

“ሁልጊዜ ወደ እሱ ለመቅረብ ፈልጉ”

1 Chronicles 16:12

የሠራትን ድንቅ አስቡ “አስደናቂዎቹን ነገሮች አስታውሱ” ተአምራቱንም

የተረዱትን ግስ ማስገባት ይችላል። አት: - “ተዓምራቱን አስታውሱ” (ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)

የአፉንም ፍርድ
እዚህ “አፍ” ያህዌ የተናገረውን ያመለክታል። አት: - “እሱ የተናገረው ድንጋጌዎች” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
ባሪያዎቹ የእስራኤል ዘር፥ ለእርሱም የተመረጣችሁ የያዕቆብ ልጆች ሆይ
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉሞችን የሚያጋሩ ሲሆን ለማጉላት ጥቅም ላይ ይውላሉ። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)
ፍርዱ በምድር ሁሉ ነው
እዚህ ላይ “ምድር ሁሉ” የሚያመለክተው የምድር ሰዎችን ሁሉ ነው። አት: - “ሕጎቹ ለምድር ሕዝቦች ሁሉ” ናቸው (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
1 Chronicles 16:15
ቃል ኪዳኑን ለዘላለም፥ እስከ ሺህ ትውልድ ... አሰበ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉሞችን የሚያጋሩ ሲሆን ለማጉላት በጋራ ያገለግላሉ። እዚህ “ቃል” ቃል ኪዳኑን ያመለክታል። እዚህ “ቃል” ቃል ኪዳኑን ያመለክታል። (ትይዩአዊ እና የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
ቃል ኪዳኑን ... አሰበ
ይህ ማለት ስለ ኪዳኑ ማስታወስ እና ማሰብ ማለት ነው። አት: “ቃል ኪዳኑን አስቡ” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)
ሺህ ትውልድ
“1,000 ትውልዶች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)
አሰበ
“ወደ አእምሮ መጥራት” የሚለው ሐረግ አንድን ነገር ማስታወስ ማለት ነው። አት: - “ያስታውሳል” (ፈሊጥ: ይመልከቱ)
ለአብርሃም ያደረገውን፥ ለይስሐቅም የማለውን
ሁለቱም “ቃል ኪዳኑ” እና “መሐላ” የሚያመለክቱት ያህዌ ለሕዝቡ የገባውን ተመሳሳይ ተስፋ ነው ። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)
ለይስሐቅም የማለውን
ይህ ቀደም ሲል ለይስሐቅ የገባውን መሐላ ያመለክታል። AT: “ለይስሐቅ በገባው መሐላ” (ግድፈተ ቃላት: ይመልከቱ)
የርስታችሁን
“እንደ ራስህ አካል
1 Chronicles 16:19
አያያዥ መግለጫ
በእነዚህ ቁጥሮች ላይ “እርስዎ ፣” “እነሱ ፣” “እነሱ ፣” እና “የእነሱ” የሚሉት ቃላት እስራኤልን ያመለክታሉ።
ስደተኞች
“ምድሪቱ” የሚለው ከነዓንን እንደሚያመለክት ታሳቢ ሆኗል። አት: - “በከነዓን ምድር እንግዶች” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)
ሕዝብ ወደ ሕዝብ፥ ከመንግሥትም ወደ ሌላ ሕዝብ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው እና ለማጉላት በጋራ ጥቅም ላይ ይውላሉ። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)
ስለ እነርሱም
“ለእራሳቸው ደህንነት”
ቀባኋቸውን አትዳስሱ
እዚህ “መንካት” ማለት መጉዳት ማለት ነው። ይህ ህዝቡን ላለመጉዳት ያህዌ ማስጠንቀቂያን ያጠናከረበት የተጋነነ አገላለፅ ነው። አት: - “የቀባኋቸውን ሰዎች አትጎዱ” (ቃል አጋኖ እና መጠቅለል: ይመልከቱ)
1 Chronicles 16:23
አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩነት በዕብራይስጥ ቅኔ ውስጥ የተለመደ ነው ። (ቅኔ እና ትይዩአዊ: ይመልከቱ)
ምድር ሁሉ
ይህ የምድሪቱን ሰዎች ያመለክታል። አት: “በምድሪቱ ላይ የምትኖሩ ሁሉ”
ዳኑን አውሩ
“መዳን” የሚለው ስም “መዳን” በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “እርሱ ማዳኑን አውጁ” ወይም “የሚያድነው እርሱ መሆኑን ለሰዎች ንገሩ” (ረቂክ ስሞች: ይመልከቱ)
ዕለት ዕለት
"በየቀኑ"
ክብሩን ለአሕዛብ ... ንገሩ
“በሁሉም አገር ለሕዝብ ሁሉ ስለ ታላቅ ክብሩ ተናገሩ ”
1 Chronicles 16:25
እግዚአብሔር ታላቅ፥ ምስጋናውም ብዙ ነውና
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ይህዌ ታላቅ ነው። እጅግ በጣም አወድሱት ”ወይም“ ያህዌ ታላቅ ነው፤ ሰዎችም እጅግ ሊያወድሱት ይገባል” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)
አማልክትም ሁሉ ላይ የተፈራ ነው
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ከሌሎች አማልክት ሁሉ በላይ እሱን ፍሩ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)
ክብርና ግርማ በፊቱ ... ናቸው
ደራሲው ግርማ እና ታላቅነት በንጉሥ ፊት ሊቆም የሚችሉ ሰዎች ናቸው ብሎ ይናገራል። (ሰብአዊ: ይመልከቱ)
በፊቱ
“ዙሪያውን” ወይም “እሱ ያለበትን ቦታ”
ኃይልና ደስታ በስፍራው ውስጥ ናቸው
ደራሲው ሀይል እና ደስታ በያህዌ መቅደስ ውስጥ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ ይናገራል። (ሰብአዊ: ይመልከቱ)
በስፍራው
“በቤተ መቅደሱ” ወይም “በቤተ መቅደሱ ውስጥ”
1 Chronicles 16:28
ለእግዚአብሔር አምጡ
“ለያህዌ ውዳሴ ስጡት” ወይም “ያህዌን አወድሱ”
ክብርንና ኃይልን ለእግዚአብሔር አምጡ
ረቂክ የሆኑት “ክብር” እና “ሐይል” የተባሉት ስሞች እንደ ቅፅል ሊገለጹ ይችላሉ። አት.: - “ክቡርና ሀያል ስለሆነ እግዚአብሔርን አመስግኑ” (ረቂክ ስሞች: ይመልከቱ)
ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር አምጡ
ረቂክ የሆነው “ክብር” የሚለው ስም እንደ ግስ ወይም እንደ ቅፅል ሊገለፅ ይችላል። አት: “ለስሙ እንደሚገባ ያህዌን አክብሩት” ወይም “ያህዌ ልክ እንደስሙ የከበረ መሆኑን አውጁ” (አት: - “በቤቴል ተይዘው ይኖራሉ... መንደሮች” ወይም “በቤቴል ውስጥ ተይዘው ይኖራሉ ።: ይመልከቱ)
ለስሙ የሚገባ ... አምጡ
እዚህ ላይ “ስሙ” የእግዚአብሔርን ማንነት ያመለክታል። አት: “በእርሱ ምክንያት” ወይም “እሱ ይገባዋል” ወይም “ሊቀበለው የሚገባው ነው” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
ለእግዚአብሔር ስገዱ
በተዘዋዋሪ የቀረበው መረጃ ህዝቡ ለአምልኮ መስገድ እንዳለበት ነው። አት: - “ያህዌን ለማምለክ ስገድ” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ እና ምሳሌያዊ ድርጊት: ይመልከቱ)
በቅድስናው ስፍራ
ግልጽ ያልሆኑት ስሞች “ግርማ” እና “ቅድስና” እንደ ቅፅል ሊተረጎሙ ይችላሉ። አት: - “እርሱ እጅግ ውብና ቅዱስ ስለሆነ” (ረቂክ ስሞች: ይመልከቱ)
1 Chronicles 16:30
ትነዋወጥ
በፍርሃት ተንቀጠቀጡ
ምድር ሁሉ
ይህ በምድር ላይ ለሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ዘይቤ ነው። አት: “የምድር ሕዝብ ሁሉ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
ሰማያት ደስ ይበላቸው፥ ምድርም ሐሴትን ታድርግ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰማያትና ምድር የሰዎች ስሜት እንዳላቸው ተደርገው ተገልጠዋል። አት: “ሰማያት ደስ እንዳላቸው ምድርም ሀሴት እንዳደረገች ይሁን” ወይም 2) “ሰማያት” እና “ምድር” በእነዚህ ቦታዎች ለሚኖሩ የባህሪ ስም ነው። አት: “በሰማያት የሚኖሩ ደስ ይበላቸው እናም በምድር የሚኖሩ ሀሴትን ያድርጉ” (ሰብአዊ እና የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
1 Chronicles 16:32
ባሕርና ሞላዋ
የተዘገበው መረጃ ይህ በባህሩ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ፍጥረታት የሚያመለክት ነው። ሰዎች እንደሚያደርጉት በደስታ እንሲጮኹ ይናገሩ ነበር። አት: - “የባሕር ፍጥረታት በደስታ እልል ይላሉ” (ታሳቢ የሆነ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ እና ሰብአዊ: ይመልከቱ)

በእርሷም ያሉ ሁሉ ሐሤትን ያድርጉ
“ሜዳዎቹና በውስጣቸው ያሉቱ ሁሉ ደስ ይበላቸው” ፀሀፊው ሜዳዎቹና የሚኖሩባቸው እንስሳቱ ልክ እነደ ሰዎች ስሜት እንዳላቸው አድርጎ ይናገራል። አት: “ሜዳዎቹ ራሳቸው እና የሚኖሩባቸው እንስሳቱ ደስ እንዳለቸው ተደርጎ ይቆጠር” (ሰብአዊ: ይመልከቱ)
የዱር ዛፎች በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይላቸዋል
ይህ የሚናገረው በደስታ እንደ ሰዎች ስለሚጮሁ ዛፎች ነው። (ሰብአዊ: ይመልከቱ)
1 Chronicles 16:34
ምህረቱም ለዘላለም ነው
ረኪክ ይሆነው “ታማኝነት የሚለው ስም” “በታናኝነት” ወይም “ታማኝ” ተብሎ መገለፅ ይችላል። አት: “እርሱ በታማኝነት ለዘላለም ይወደናልና” ወይም “ለዘላለም ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው” (ረኪክ ስም: ይመልከቱ)
ከአሕዛብ
እዚህ ጋር “ሌሎቹ ሕዝቦች” በእዚሁ አገራት ውስጥ ያሉትን ሕዝቦች ይወክላል። አት: - “ከሌሎች ሕዝቦች ሰዎች” ወይም “ከሌሎች ሕዝቦች ሠራዊት” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
ስምህን እናመሰግን ዘንድ
እዚህ ያህዌ “በቅዱስ ስሙ” ተጠቅሷል። አት: - “አመሰግናለሁ” ወይም “ያህዌን አመስግን” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)1 ዜና መዋዕል 16:36 የትርጉም ማስታዎሻዎች
1 Chronicles 16:36
ከዘላለም እስከ ዘላለም
ይህ ሁለት ጽንፎችን እና መንገዶችን ለሁሉም ጊዜ የሚያመለክት ነው። አት: - “ለዘለዓለም” (ሜሪዝም: ይመልከቱ)
ሕዝቡም ሁሉ
ይህ ያህዌን ለማምለክ የተሰበሰቡትን ሰዎች ስብስብ የሚያመላክት አጠቃላይ መግለጫ ነው። “ሕዝቡ” ወይም “እዚያ የነበረው ሰው ሁሉ” (ቃል አጋኖ እና መጠቅለል: ይመልከቱ)
1 Chronicles 16:37
ወንድሞቹን
“ዘመዶቹ”
በየቀኑ እንደሚገባቸው
ታሳቢ የተደረገው መረጃ በያህዌ ሕግ ውስጥ የተሰጠውን ዕለታዊ ሥራ ማከናወን እንደነበረባቸው ያሳያል። አት: - “በየዕለቱ በሕጉ እንደሚፈለግ” (ታሳቢ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)
የኤዶታምም፣ ያቤድኤዶምና ሖሳ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ነበሩ።
ስድሳ ስምንቱንም ወንድሞቻቸውን
“68 ዘመዶች” (ቁጥሮች: ይመልከቱ)
ቃል ኪዳን ታቦት ፊት ተዋቸው
“በመገናኛው ድንኳን ለማገልገል”
1 Chronicles 16:40
አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ቁጥሮች ላይ “እነሱ” እና “እነሱ” የሚሉት ቃላት ካህናትን ያመለክታሉ።
ሁል ጊዜ ጥዋትና ማታ
“በየቀኑ ጠዋት”
ኤማንንና ኤዶታምን
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።
1 Chronicles 16:42
ጸናጽል
እነዚህ ድምፅ ለመፍጠር አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭንና ክብ የብረት ሰሌዳዎች ናቸው። ይህንን በ 1ኛ ዜና 13:8 ውስጥ እንዴት እንደተረጉሙ ይመልከቱ ። (የማይታወቁትን መተርጎም: ይመልከቱ)
በረኞች ነበሩ
ታሳቢ የሆነው መረጃ የመገናኛውን ድንኳን ደጃፍ መጠበቅ እንደነበረባቸው የሚያሳይ ነው። አት: - “የማደሪያ ድንኳኑን በር ጠበቁ” (ታሳቢ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)

---

Chapter 17
1 Chronicles 17:1
እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅምር ለመጠቆም እዚህ የሚያገለገል ነው። ቋንቋዎ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። (የአዲስ ክስተት መግቢያ: ይመልከቱ)
በተቀመጠ ጊዜ
የመንቀሳቀስ ወይም የመቀየር ፍላጎት ሳይኖር ምቾት እና ደስተኛ
እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤት ተቀምጫለሁ
ዝግባ በጥንካሬው የሚታወቅ ዓይነት ዛፍ ነው። በባህልዎ ውስጥ ተመጣጣኝ የሆነ የዛፍ አይነት ካለዎት ያንን ስም መጠቀም ይችላሉ፣ ካልሆነ ግን ይህን ስም እንደገና መጠቀም ይችላሉ። አት: - “እኔ ጠንካራ እና በቋሚ ቤት ውስጥ እኖራለሁ” (ታሳቢ እወቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ ይመልከቱ)
የእግዚአብሔርም ቃል ኪዳን ታቦት በመጋረጃዎች ውስጥ ተቀምጦአል
ድንኳኖች ጊዜያዊ መኖሪያ ናቸው። በባህልዎ ውስጥ ድንኳን ከሌለዎት ይህንን በተለየ ቃል መጥራት ይችላሉ። አት: - “የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ጊዜያዊ ቦታ ውስጥ ይቆያል” (ታሳቢ እወቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ ይመልከቱ)
በልብህ ያለውን ሁሉ አድርግ
እዚህ “ልብ” አእምሮን ይወክላል። አት: - “ማድረግ ያለብህን አድርግ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው
እዚህ “ካንተ ጋር” ማለት እግዚአብሔር ዳዊትን እየረዳ እና እየባረከው ነው ማለት ነው። (ፈሊጥ:ይመልከቱ)
1 Chronicles 17:3
የእግዚአብሔር ቃል ወደ ናታን መጣ እንዲህም አለው
“የእግዚአብሄር ቃል መጣለት” የሚለው ፈሊጥ ከእግዚአብሄር ልዩ መልዕክት መምጣቱን ለማሳየት የሚረዳ ነው። አት: “እግዚአብሄር ለናታን መልዕክት ሰጠው። ’ሂድ” ወይም “እግዚአብሄር ይህን መልዕክት ለናታን ተናገረው: ’ሂድ” አለ (ፈሊጥ ፡ ይመልከቱ)
ሂድ፥ ለባሪያዬ ለዳዊት ንገረው። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ ... የምኖርበትን ቤት አትሠራልኝም
ይህ ከጥቅሶቹ ውስጥ ጥቅሶች አሉት ። እነሱን በተዘዋዋሪ ጥቅሶች ለመተርጎም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል ። አት: - “ሂድ ፣ እኔ የምኖርበትን ቤት የሚገነባው እርሱ እንደማይሆን ለአገልጋይዬ ለዳዊት ንገረው” (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ጥቅስ: ይመልከቱ)
ቤት መስራት
እዚህ “ቤት” ማለት መቅደስ ማለት ነው ። በ 1 ዜና 17፡10 ላይ ያህዌ ለዳዊት ቤት ይሠራል ይላል። እዚያ “ቤት” ማለት ቤተሰብ ማለት ነው። ቋንቋዎ ሁለቱንም ሀሳቦች መግለፅ የሚችል ቃል ካለው እዚህ እና በ 17፡10 ውስጥ ይጠቀሙበት።
እስራኤልን ካወጣሁበት
ታሳቢ የሆነው መረጃ የሚያመለክተው እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ምድር እንዳወጣ ነው። አት: - “እስራኤልን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከግብፅ ምድር አመጣሁ” (ታሳቢ የተደረገ እውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃን ይመልከቱ)
ድንኳን, ማደሪያ
“ድንኳን” እና “ማደሪያው ድንኳን” የሚሉት ቃላት አንድ ነገር የሚያመለክቱ ሲሆን ዘላቂ የሆነ ሕንፃ ባልነበረበት ስፍራ እንደኖረ ያጎላሉ። (ድግግሞሽ: ይመልከቱ)
ስለ ምን ቤትን ከዝግባ እንጨት አልሠራችሁልኝም? ብዬ ሕዝቤን ይጠብቅ ዘንድ ከእስራኤል ፈራጆች ላዘዝሁት ለአንዱ በውኑ ተናግሬአለሁን?
ይህ በጥቅሱ ውስጥ ጥቅስ አለው። ቀጥተኛው ጥቅስ እንደተዘዋዋሪ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል። አት: “የዝግባ ቤት ለምን አልሰራችሁልኝም ብዬ ለሕዝቤ እረኛ እንዲሆኑ ከሾምኳችው የእስራኤል መሪዎችን ጠይቄያለሁን?” (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ጥቅስ: ይመልከቱ)
ከእስራኤል ፈራጆች ላዘዝሁት ለአንዱ በውኑ ተናግሬአለሁን?
ያህዌ ማንንም የእስራኤል መሪዎች ቤት እንዲሠሩለት በጭራሽ እንዳልጠየቃቸው ለማጉላት ጥያቄ ይጠቀማል። አት: - “ማንንም የእስራኤል መሪዎች አንዳች ነገር በጭራሽ አላልኩም” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)
ሕዝቤን ይጠብቅ ዘንድ
የእስራኤል ሕዝብ መሪዎች እንደ እረኞች ፣ ህዝቡም በግ እንደሆኑ ተደርጎ

ተገልፃል። (ዘይቤ: ይመልከቱ)
ስለ ምን ቤትን ከዝግባ እንጨት አልሠራችሁልኝም?
ይህዌ ይህን ጥያቄ መሪዎችን ጠይቆ ቢሆን፣ ጥያቄው የዝግባ ቤት ስላልሰሩለት መተንኮሻ ነበር። ነገር ግን ፣ ያህዌ ከዚህ ቀደም ይህን ጥያቄ እንዳልጠየቃቸው ተናግሯል። አት: - “የዝግባ ቤት ልትሠሩልኝ ይገባ ነበር።” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)
1 Chronicles 17:7
አጠቃላይ መረጃ
ይህዌ ለንጉሥ ዳዊት የገባውን ቃል በነቢዩ ናታን በኩል ይገልፃል።
አሁንም
ይህ “በአሁኑ ጊዜ” ማለት አይደለም ፣ ነገር ግን ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ነጥብ ሃሳብን ለመሳብ ይጠቅማል።
ባሪያዬን ዳዊትን እንዲህ በለው
እግዚአብሔር ለዳዊት ምን እንደሚናገር ለነቢዩ ናታን አሁንም ይነግረዋል።
አንተ መንጋውን ስትከተል … ከበግ ጥበቃ ወሰድሁህ።
እንደ እረኛ የተገለፀው የዳዊት ስራ በጎቹም ይጠብቅ ከነበረበት ቦታ አንጻር ተገልጾል። አት: “ከእረኝነት ስራህ ወሰድሁህ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
መንጋውን
እንስሳት ሣር የሚግጡበት መሬት። በ1 ዜና 4፡39 እና 4፡40 ይህንን ቃል እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
ከአንተ ጋር ነበርሁ
እዚህ “ካንተ ጋር” ማለት እግዚአብሔር ዳዊትን ረድቶታል እንዲሁም ባርኮታል ማለት ነው ። (ፈሊጥ: ይመልከቱ)
ጠላቶችህንም ሁሉ ከፊትህ አጠፋሁ
ይህዌ የዳዊትን ጠላቶች ማትፋቱ ልክ ያህዌ ከጨርቅ ላይ ብጣቂ እንደሚቆርጥ ወይም ከዛፍ ቅርንጫፍ እንደሚቆርጥ ተደርጎ ተገልጻል። (ዘይቤ: ይመልከቱ)
ለአንተ ስም አደርጋለሁ
እዚህ “ስም” የአንድን ሰው ዝና ያመለክታል። አት: - “ስምህ ታላቅና የታወቀ እንዲሆን አደርጋለሁ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
እንደታላላቆች
“ታላላቆች” የሚለው ሐረግ ታዋቂ ሰዎች ማለት ነው።
1 Chronicles 17:9
አያያዥ መግለጫ
እግዚአብሄር ለንጉሥ ዳዊት የገባውን ቃል በነቢዩ ናታን በኩል መግለጹን ቀጠለ።
አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ቁጥሮች ላይ “የአንተ” እና “አንተ” የሚሉት ቃላት ዳዊትን ያመለክታሉ ።
ስፍራ አደርግለታለሁ
“ቦታ እመርጣለሁ”
እተክለውማለሁ
እግዚአብሔር ህዝቡን በምድሪቱ ላይ በቋሚነት ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲኖሩ በማድረግ በምድሪቱ ላይ እንደሚተክላቸው ያህል ተገልጻል። አት: - “እዚያ አስቀምጣቸዋለሁ” (ሜታፈር: ይመልከቱ)
ከዚያም በኋላ አይናወጥም
ይህ ገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ማንም በጭራሽ አያስጨንቃቸውም” (ገባሪ ወይም ተገባሪ: ይመልከቱ)
እንደቀድሞው ዘመንና
እዚህ “ቀናት” ረዘም ያለ ጊዜን ይወክላል። አት: - “ከጊዜው”(የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
ፈራጆች እንዳስነሣሁበት
የእስራኤል ሰዎች ወደ ከነዓን ምድር ከገቡ እና በኋላ ሚመሯቸው ነገሥታት ከመኖራቸው በፊት ፣ እግዚአብሔር በችግር ጊዜ እንዲመሯቸው “ፈራጆች” የተባሉ መሪዎችን ሾመ።
በሕዝቤ በእስራኤል ላይ እንዲሆን
በሥልጣን መሆን ማለት በአንድ ሰው ላይ የበላይ መሆን ተብሎ ይጠራል። አት: - “ሕዝቤን እስራኤልን ይገዛል” (ፈሊጥ ይመልከቱ)
አያስጨንቁትም
አንድን ሰው ወይም እንስሳ ማጥቃት የማይችል ማድረግ
ቤት እንዲሠራልህ
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው አገላለጽ የሚያመለክተው የዳዊት ዘሮች እንደ እስራኤል ገዢዎች ሆነው መቀጠላቸውን ነው። በ 1ኛ ዜና 17፡4 ውስጥ እግዚአብሔር ለዳዊት ለያህዌ ቤት የሚሠራው እርሱ እንዳልሆነ ነገረው። እዚያም “ቤት” ቤተ መቅደስን ይወክላል። ቋንቋዎ ሁለቱንም ሀሳቦች መግለፅ የሚችል ቃል ካለው እዚህ እና በ17፡4 ውስጥ ይጠቀሙበት። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
1 Chronicles 17:13
አያያዥ መግለጫ
ያህዌ ለንጉሥ ዳዊት የገባውን ቃል በነቢዩ ናታን በኩል መግለጹን ቀጠለ።
እኔም አባት እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል
በ 17 11-14 ውስጥ ያለው ትንቢት የሚያመለክተው የዳዊትን ልጅ ሰለሞንን ነው ። ነገር ግን የትንቢቱ አንዳንድ ገጽታዎች በኢየሱስ ይፈፀማሉ። ስለዚህ እዚህ “አባት” እና “ልጅ” የሚሉትን ቃላት ለመደበኛ አባት እና ልጅ በሚያገለግሉ ቃላት ይተርጎም።
ከሳኦል እንደወሰድኩት የቃል ኪዳን ታማኝነቴን ከእርሱ አላርቅም
የቃላት ስሙ “ታማኝነት” የሚለው ቃል “በታማኝነት” ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ሳኦልን መውደዴን እንዳቆምኩ፣ እርሱን እስከ መጨረሻው እሱን መውደድ አላቆምም” (ረኪክ ስሞች: ይመልከቱ)
በቤቴና በመንግሥቴም ለዘላለም አቆመዋለሁ፤ ዙፋኑም ለዘላለም ይጸናል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የዳዊት ሥርወ መንግሥት ለዘላለም እንደሚቆይ አፅንኦት ይሰጣሉ። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)
ዙፋኑም ለዘላለም ይጸናል
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ዙፋኑን ለዘላለም አጸናለሁ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ :ይመልከቱ)
ዙፋኑም
የንጉሥ የመግዛት መብት የሚጠቀሰው አንድ ንጉሥ በሚቀመጥበት ቦታ ነው። አት: - “የመግዛት መብቱ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
ነገረው
“ነገረው”
እንደዚህ ነገር ሁሉ
እዚህ “ቃላት” ያህዌህ ያለውን ይወክላል። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
1 Chronicles 17:16
አለ
“ዳዊት አለ”
አቤቱ አምላክ ሆይ፥ እስከዚህ ያደረስኸኝ እኔ ማን ነኝ? ቤቴስ ምንድር ነው?
ዳዊት ይህን ጥያቄ የጠየቀው ያህዌን አዋጅ ሲሰማ የተሰማውን ጥልቅ ስሜት ለመግለጽ ነው። ይህ መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “ያህዌ አምላክ ሆይ፣ እኔና ቤተሰቤ ፣ ለዚህ ክብር ብቁ አይደለንም። (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)
ይህ … ጥቂት ነበረ
አስፈላጊ ያልሆነ ነገር ትንሽ እንደሆነ ተገልጻል። (ፈሊጥ: ይመልከቱ)
በፊትህ
እዚህ ማየት ፍርድን ወይም ግምገማን ይወክላል። አት: - “በፍርድህ” (ዘይቤ: ይመልከቱ)
ስለ ባሪያህ ቤት
እዚህ ላይ ዳዊት ራሱን “አገልጋይህ” ሲል ጠርቶታል ። ይህ በመጀመሪያ መደብ መጠሪያ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ቤተሰቤ”(ይመልከቱ የመጀመሪያ ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ)
ለሩቅ ዘመን
ይህ የሚናገረው ስለ ጊዜ ሲሆን፣ አንድ ነገር የሚጓዝ እና የሆነ ቦታ እንደሚደርስ ሆኖ ቀርቧአል። አት: - “እናም ወደፊት ምን ይሆናል” (ዘይቤ: ይመልከቱ)
ዳዊት ጨምሮ የሚለው ምንድር ነው?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ ለያህዌህ የሚለው አንዳች እንደሌለው ለማጉላት ተጠቅሞበታል። አት: - “ከዚህ በላይ የምናገርህ ነገር የለም።” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)
ባሪያህ
እዚህ ላይ ዳዊት ራሱን “አገልጋይህ” ሲል ጠርቶታል። ይህ በመጀመሪያ መደብ መጠሪያ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “እኔ” (የመጀመሪያ ፣ ሁለተኛ ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ መጠሪያ ይመልከቱ)
አንተ ባሪያህን ታውቀዋለህና ለባሪያህ ስለ ተደረገ ክብር
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው እና ለማጉላት የተደጋገሙ ናቸው። (ይመልከቱ: ትይዩአዊ)

ለባሪያህ ስለ ተደረገ ክብር
“እውቅና” የሚለው ስም “ዕውቅና” በሚለው ቃል መተርጎም ይችላል። አት: - “አገልጋይህን በልዩ ሁኔታ አውቀኸዋል” (ረኪክ ስሞች: ይመልከቱ)
1 Chronicles 17:19
አያያዥ መግለጫ
ዳዊት ያህዌን መናገሩን ቀጠለ።
ስለ ባሪያህ
እዚህ ላይ ዳዊት ራሱን “አገልጋይህ” ሲል ጠርቶታል። ይህ በመጀመሪያ መደብ መጠሪያ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ለእኔ ጥቅም” ወይም “ለእኔ ጥቅሜ” (የመጀመሪያ ፣ ሁለተኛ ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ ይመልከቱ)
እንደ ልብህም አድርገሃል
“ያሰብከውን ለማሳካት”
እንዳንተ ያለ የለም፣ ከአንተ በቀር አምላክ የለም
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው እና ለማጉላት የተደጋገሙ ናቸው። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)
በጆሮአችንም እንደሰማን ሁሉ
እዚህ “እኛ” የሚለው ቃል ዳዊትን እና የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል። (አግላይ እና አካታች “እኛ”: ይመልከቱ)
ለአንተም ሕዝብ ... እንዳንተ ሕዝብ እንደ እስራኤል ያለ በምድር ላይ ሌላ ሕዝብ አለን?
ይህ ጥያቄ እንደ እስራኤል ያለ ሌላ ሕዝብ እንደሌለ የሚያስተውል አሉታዊ መልስ ይጠብቃል። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አት: - “በምድር ላይ እንደዚህ ሕዝብ የለም ... በታላቅ እና በሚያስደንቅ ሥራዎች” (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ: ይመልከቱ)
ግብጽ ካወጣኸው
ታሳቢ የሆነው መረጃ እነሱ ከባርነት እንደዳኑ ነው። አት: - “ከግብፅ ባርነት አዳናችሁ” (ታሳቢ የሆነ ዕውቀት እና ውስጠ ታዋቂ መረጃ: ይመልከቱ)
ለአንተ ስም ታደርግ ዘንድ
እዚህ “ስም” የያህዌን ስም ይወክላል። አት: - “ለሰዎች ሁሉ ማን እንደሆንክ ለማሳወቅ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
አሕዛብን በማሳደድ
እዚህ “ሕዝቦች” በከነዓን ይኖሩ የነበሩትን ህዝቦችን ይወክላል ። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
1 Chronicles 17:22
አያያዥ መግለጫ
ዳዊት ያህዌን ማናገሩን ቀጠለ።
አሁንም
እዚህ “አሁን” ማለት “በአሁኑ ጊዜ” አይደለም ፣ ነገር ግን ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ነጥብ ትኩረትን ለማዞር ይጠቅማል።
ስለ ባሪያህና ስለ ቤቱ የተናገርኸው ለዘላለም የጸና ይሁን
፡ አት: - “ለእኔ እና ለቤቴ ቃል የገባኋውን አድርግ፣ እናም ቃል በጭራሽ አይለወጥ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመልከቱ)
ስለ ባሪያህና ስለ ቤቱ
ዳዊት ስለ ራሱ በሦስተኛው መደብ መጠሪያ እየተናገረ ነው። ይህ በመጀመሪያ መደብ መጠሪያ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “እኔ እና ቤተሰቤ” (የመጀመሪያ ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ ይመልከቱ)
ዘንድ ስምህ
እዚህ “ስም” የያህዌን ዝና ይወክላል። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
የባሪያህም የዳዊት ቤት
እዚህ “ቤት” ቤተሰብን ይወክላል። አት: - “ቤተሰቤ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
በፊትህ ጸንቶአል
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “በአንተ ምክንያት የተጠበቀ” ወይም “ከአንተ የተነሳ ይቀጥላል” (ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመልከቱ)
1 Chronicles 17:25
አያያዥ መግለጫ
ዳዊት ያህዌን ማናገር ይቀጥላል።
ባሪያህ
ዳዊት ራሱን “አገልጋይህ” ብሎ ይጠራል። ይህ በመጀመሪያ መደብ መጠሪያ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “እኔ” (የመጀመሪያ ፣ ሁለተኛ ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ፡ ይመልከቱ)
ቤት እንድሠራለት
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው አገላለጽ የሚያመለክተው የዳዊት ዘር እንደ እስራኤል ገዥዎች ሆነው እንደሚቀጥሉ ነው። በ1ኛ ዜና 17:4 እግዚአብሔር ለዳዊት ቤት የሚሠራለት እርሱ እንዳልሆነ ይነገረዋል። እዚያም “ቤት” ቤተ መቅደስን ይወክላል። ቋንቋዎ ሁለቱንም ሀሳቦች መግለፅ የሚችል ቃል ካለው እዚህ እና በ17፡4 ይጠቀሙብ ። (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
እኔ ባሪያህ ...በልቡ ደፈረ
እዚህ ላይ የተጠቀሰው “ድፍረት” የሚለው ስም “መበረታታት” በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- “እኔ አገልጋይህ ተበረታቻለሁ”
አሁንም
ይህ “በአሁኑ ጊዜ” ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ነጥብ ለመሳብ ይጠቅማል።
የባሪያህን ቤት
ዳዊት በሦስተኛው መደብ መጠሪያ ስለ ራሱ ይናገራል። ይህ በመጀመሪያ መደብ መጠሪያ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ቤቴ” ወይም “ቤተሰቤ” (የመጀመሪያ ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ ይመልከቱ)
አቤቱ፥ ባርከኸዋል፥ ለዘላለምም ቡሩክ ይሆናል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ስላላቸው ለማጉላት እዚህ ተደግመዋል። (ትይዩአዊ: ይመልከቱ)
ለዘላለምም ቡሩክ ይሆናል
ይህ በገባሪ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ለዘላለም በመባረክ ትቀጥላለህ” (ገበሪ ወይም ተገባሪ፡ ይመልከቱ)

Chapter 18
1 Chronicles 18:1
ከዚህም በኋላ
“እግዚአብሔር ዳዊትን እንደሚባርክ ከገባለት ቃል አኳያ”
እንዲህ ሆነ
ይህ ሀረግ እዚህ የሚያገለግለው አዲሱን የታሪኩን ክፍል ለመጀመር ነው። ቋንቋዎ ይህ ማድረግ የሚችልበት መንገድ ካለው እዚህ ሊጠቀሙት ይቻላሉ። .
1 Chronicles 18:3
ዳዊትም ... አድርአዛርን ... መታ
እዚህ ዳዊት እና አድርአዛር ብቻቸውን እንደሆኑ ተደርጎ የተነገረ ሲሆን፣ ነገር ግን እነዚህ ነገስታት አብረዋቸው የነበሩተን ሰራዊት እንደሚወክሉ አንባቢው ሊረዳው ማድረግ ያስፈልጋል። አት: “ዳዊት እና ሰራዊቱ የአድርአዛርን ሰራዊት ድል ነሱ” (የባሕሪ ስም: ይመልከቱ)
አድርአዛርን
ይህ የወንድ ስም ነው። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
የሱባን
ይህ የአገር ስም ነው።
በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ የነበረውን ግዛት ለመያዝ በሄደ ጊዜ
“ሕዝቦች በዚያ ለመያዝ ወደ ኤፍራታ ወንዝ እየሄደ ነበር”
አንድ ሺህ ሰረገሎች
“1,000 ሰረገሎች” (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)
ሰባት ሺህም ፈረሰኞች
እነዚህ ፈረስ ይጋልቡ የነበሩ ወራደሮች ናቸው። “7,000 ፈለሰኞች” (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)
ሀያ ሺህም እግረኞች
እነዚህ ይራመዱ የነበሩ ወራደሮች ናቸው። “20,000 እግረኞች” (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)
የሰረገሎቹን ፈረሶች ቋንጃ ቆረጠ
ከዛም በኋላ መሮጥ እንዳችሉ ዳዊት እና ወታደሮቹ ከፈረሶቹ ጀርባ ያለውን ቋንጃ ቀረጡ።
አስቀርቶ
ለልዩ አገልግሎት ማስቀረት
ለመቶ ሰረገሎች


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“100 ሰረገሎች” (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)
1 Chronicles 18:5
ሀያ ሁለት ሺህ ሰዎችን ገደለ
“22,000 ገደለ” (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)
ጭፍሮች
ለተለየ አካባቢ የተመደቡ ወታደሮች
እግዚአብሔርም ዳዊት በሄደበት ሁሉ ድል ይሰጠው ነበር
“ያህዌ ለዳዊት ድልን ሰጠው”
1 Chronicles 18:7
ለአድርአዛር
ይህ የዞባ ንጉስ ነበር። ስሙን በ1 ዜና 18:3 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
ለአድርአዛር ባሪያዎች የነበሩትን
“የአድርአዛር ባሮች የሚሸከሙት”
ከጢብሐትና … ከኩን
እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
ብዙ ናስ
“ከፍተኛ መጠን ያለው ናህስ”
ከዚህም ሰሎሞን የናሱን ኩሬና ዓምዶች የናሱንም ዕቃ ሠራ
ጸሀፊው ይህ ነህስ በቀጣይ ጊዜ ምን እንደሆነ ለማሳየት የዳራ መረጃ ይጭምራል። (የዳራ መረጃ :ይመልከቱ)
የናሱን ኩሬና የተባለውን
ይህ 5 ሜትር ርዝማመት ያለው ትልቅ የነሀስ ሳህን ሲሆን በቤተ መቅደሱ ለስርአቶች መታጠቢያነት ይቀመጥ ነበር።
1 Chronicles 18:9
ቶዑ … አዶራምን
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
ይዋጋ ነበርና
“በጦርነት ውስጥ መሆን”
እነዚህን ደግሞ ለእግዚአብሔር ቀደሰ
“እንዚህ እቃዎች ያህዌን ለማምለክ ብቻ እንዲያገለግሉ ወሰነ”ከአሕዛብ ሁሉ … ወሰደ
1 Chronicles 18:12
አቢሳ … ጽሩያ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
ከኤዶማውያን … አሥራ ስምንት ሺህ
“18,000 ኤዲማውያን” (ቁጥሮች፡ ይመልከቱ)
በጨው ሸለቆ
ይህ በኤዶምና ይሁዳ መካከል ለጦርነት ያገለግል የነበረ ሸለቆ ስያሜ ነው።
1 Chronicles 18:14
በእስራኤል ሁሉ
“በእስራኤላውያን ሁሉ ላይ”
ለሕዝቡም ሁሉ ፍርድንና ጽድቅም አደረገላቸው
ረቂክ የሆኑት “ፍትህ” እና “ጽድቅ” የሆኑት ስሞች እንደቅጽል መጸርጎም ይችላሉ። አት: “ለሕዝቡ ሁሉ ፍትህ እና ትክክል የሆነውን አደረገ” (ረቂክ ስሞች: ይመልከቱ)
ጽሩያ … አሒሉድም … አኪጦብም … አብያታር … ሱሳ … በናያስ … ዮዳሄ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
ጸሐፊ
የወሳኝ ኩነቶችን ዝርዝር የሚፅፍ ሰው
አቤሜሌክም
ይህ የፊደል አንዳንድ ቅጂዎች የሚከተሉትን ‹አቢሜሌክ› መታረሙን ይወክላል። የታረመው ፊደል ይህን ቁጥር 2 ሳሙኤል 8:17 እንዲስማማ ያደርገዋል።
የአኪጦብም ልጅ ሳዶቅ፥ የአቤሜሌክም ልጅ አብያታር ካህናት ነበሩ
አንዳንድ ቅጂዎች ይህን አኪጦብ እና አቤሜሌክ ሊቀ ካህናት ነበሩ በማለት ያስተካክሉታል።
ከሊታውያንና … ፈሊታውያን
እነዚህ የሌላ የሕዝቦች ስም ሲሆን የዳዊት ጠባቂዎች ሆነዋል።

---

Chapter 19
1 Chronicles 19:1
ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ለመጠቆም ያገለግላል ። ቋንቋዎ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ይችላሉ ።
ናዖስ… ለሐኖን
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
ደግነት አሳያለሁ… ደግነትን አሳይቷል
ደግነት የሚለው የረቂቅ ስም እንደ ድርጊት ሊገለጽ ይችላል ። ኣት: - “እኔ ደግ እሆናለሁ… ደግ ነበርኩ” (የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)
ማጽናናት
የሚያጽናኑህ ሰዎች ስለላከ ዳዊት አባትህን የሚያከብር ይመስልሃል? ልዑላኑ ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ንጉሡን ከዳዊት ጋር ለማጋጨት ፈልገው ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: “ዳዊት የሚያጽናኑህ ሰዎች ስለላከ አባትህን የሚያከብር አይምሰልህ።” ( አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ) አገልጋዮቹ ወደ አንተ የመጡጥ ምድሪቱን ሊሰልሏት እና ሊያጠፏት አይደለምን? ልዑላኑ ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ንጉሡን ከዳዊት ጋር ለማጋጨት ፈልገው ነው። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “በእርግጥ አገልጋዮቹ ምድሪቱን ያጠፉአት ዘንድ ለመመርመር ወደ አንተ ይመጣሉ።” (አወያይ ጥያቄን :ተመልከት)
1 Chronicles 19:4
ስለዚህ ሐኖን ያዛቸው
ሃኖን በግሉ ይህንን አላደረገም ፣ ነገር ግን ሐኖን የእርሱ ሰዎች እንዲያደርጉት አዘዘ ። ኣት: - “ስለሆነም የሐኖን ሰዎች ያዙአቸው” (የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)
ልብሳቸውን
ልብሳቸውን”
ከእነርሱ ጋር ለመገናኘት ልኮ ነበር “ዳዊት እነርሱን ለማበረታታት ጥቂት መልእክተኞችን ላከ”
ሃፍረታቸው ጥልቅ ነበረ
በዚህ ዘይቤ ውስጥ ሃፍረት በከፍተኛ ሁኔታ እንደጎዳቸው ለማሳየት እፍረታቸው ጥልቅ ነበር ተብሎ ተገልጾአል ። ኣት: - “በጣም አፈሩ” (ፈሊጥን፡ ይመልከቱ)
ንጉሡ
ይህ ዳዊትን ያመለክታል ።
ከዚያ ተመለሱ
“ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ”
1 Chronicles 19:6
በዳዊት ዘንድ እንደተጠሉ ተመለከተ
“ተጠሉ” የሚለው ቃል መጥፎ ሽታን ያመለክታል። ይህ አሞናውያን የተጠሉ እና የማይፈለጉ እንደሆኑ ይገልፃል ። ኣት: - “ለዳዊት አመጸኞች እንደ ሆኑ ተገነዘቡ” ወይም “ዳዊትን እንዳስቆጣው ተገነዘቡ” (ዘይቤ፡ ይመልከቱ)
አንድ ሺህ መክሊት … ሠላሳ ሁለት ሺህ ሰረገሎች
“1,000 መክሊት… 32,000 መክሊት” (ቁጥሮችን ፡ ይመልከቱ)
መክሊቶች
በግምት 33 ኪሎግራም (የመጽሐፍ ቅዱስ ገንዘብን :ይመልከቱ)
አራም… ማዓካ… ሱባ… ሜድባ
የከተሞች ስሞች እነዚህ ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ፡ ይመልከቱ)
ሠላሳ ሁለት ሺህ ሰረገሎች
አሞናውያን አንድ ሺህ መክሊቱን በሙሉ ለማዓካ ንጉሥ ይክፈሉ ወይም የተወሰነውን ብቻ ከፍለው ቀሪዎቹን ሰረገሎችና ፈረሰኞች ለሚልኩ ሌሎች ከተሞች የሰጡት ግልፅ አይደለም ።
1 Chronicles 19:8
ስለሱ ሰማ
አሞናውያን ለጦርነት እየወጡ እንደነበሩ ሰማ ”
እነርሱን ለመገናኘት
“ከእነርሱ ጋር ሊዋጉ”
በከተማው በር ላይ
ይህ የአሞናውያንን ዋና ከተማ በር ያመለክታል።
የመጡት ነገሥታት
ይህ አሞናውያን እስራኤልን ለመውጋት እንዲረዱአቸው የቀጠሯቸውን የሶርያን ነገሥታት ይመለከታል።

በሜዳ ውስጥ በራሳቸው
ከከተማይቱ ውጭ ከዐሞን ልጆች የተለየ
1 Chronicles 19:10
የጦርነት መስመሮችን ... በጦር ግንባር ውስጥ አኖራቸው
“የጠላት ወታደሮች ለውጊያ ተሰለፉ… ወታደሮቹን ለጦርነት በሰልፍ አደራጁ”
አቢሳ
ይህ የኢዮአብ ወንድም ስም ነው። ( ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)
1 Chronicles 19:12
በርታ… ጠንካራ መሆናችንን እናሳይ
“ደፋር ሁን… ደፋር ሁን”
ለሕዝባችንና ለአምላካችን ከተሞች
“ለሕዝባችንና ለአምላካችን ከተሞች” ወይም “ሕዝባችንን እና የአምላካችንን ከተሞች ለመጠበቅ”
በፊቱ መልካም የሆነውን
እዚህ ማየት ፍርድን ወይም ምዘናን ይወክላል ። ኣት: - “እርሱ ጥሩ እንደሆነ የሚቆጥረው” (ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)
1 Chronicles 19:14
ወደ ውጊያው ገቡ
“ወደ ጦር ግንባር ገቡ” ወይም “በጦርነቱ ወደ ጠላት ወታደሮች ቀረቡ”
ኢዮአብም ተመልሶ .. … ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ
ኢዮአብና ወታደሮቹ በከተሞቻቸው ላይ አሞናውያንን ማጥቃታቸውን አላቋረጡም ። አሞናውያን ወደ ከተማቸው ሲገቡ ውጊያው ተጠናቀቀ እስራኤላዊያንም ወደ አገራቸው ተመለሱ ።
1 Chronicles 19:16
አጠቃላይ መረጃ
በ 1ኛ ዜና 19 :15 ላይ ከኢዮአብ ሸሽተው የመጡ ሶርያውያን በሌሎች ሶርያውያን ተጠናክረው እስራኤልን እንደገና እንደወጉ ቁጥር 16-19 ይናገራል ።
ሶርያውያንም አይተዋል
ሶርያውያኑ የተገነዘቡት እንዳዩት ይነገራል። ኣት: - “ሶርያውያን ተረድተው ነበር” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)
ለማጠናከሪያነት ተልኳል
“ተጨማሪ ወታደሮችን ጠይቀዋል”
ሾፋክ…አድርአዛር
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። ( ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ :ይመልከቱ)
ዳዊትም ይህ ሲነገረው
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: የዳዊት መልእክተኞች ብዙ የሶርያ ሠራዊት እየመጣ መሆኑን በነገሩት ጊዜ ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
እርሱ ሰብስቦ … አስተካከለ
ዳዊት እነዚህን ነገሮች ብቻውን አላደረገም። የእርሱም ሆነ የአገሬው ሰዎች ረድተውታል። ኣት: “ዳዊትና አገልጋዮቹ ተሰበሰቡ… ዳዊትና አገልጋዮቹም አደራጁ” (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን፡ ይመልከቱ)
እስራኤል ሁሉ
ይህ አጠቃላይ ነው ። የእስራኤል ህዝብ በሙሉ ወደ ውጊያው አልመጡም ። ኣት: - “እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው እስራኤላውያን” (ግነትን እና አጠቃላይን : ይመልከቱ)
ዝግጅት አደረገ
“አደራጀ”
ተዋጉ
እዚህ “እርሱ” የሚለው ቃል ከዳዊት በተጨማሪ የዳዊትን ወታደሮች ያመለክታል ። ኣት: - “ሶርያውያን ዳዊትንና ወታደሮቹን ተዋጉ” ( ሁሉን በአንዱ መወከልን : ይመልከቱ)
1 Chronicles 19:18
ሰባት ሺህ … አርባ ሺህ ገደለ
”7,000… 40,000” ተገደሉ (ቁጥሮች :ይመልከቱ)
እነርሱ በእስራኤል ድል ተመቱ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እስራኤል ድል አደረጓቸው” (ገቢራዊን ወይም ተቢሮአዊን : ይመልከቱ)
ከዳዊት ጋር ታረቁ አገለገሏቸውም
ከዳዊት ጋር የሰላም ስምምነትን በማድረጉ እስራኤልን ያገለግሉ ነበር ።

---

Chapter 20
1 Chronicles 20:1
ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመር ለመጠቆም እዚህ ያገለግላል ። ቋንቋዎ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ይችላሉ ። ነገሥታት በተለምዶ ወደ ጦርነት የሚሄዱበት ጊዜ ነው። ይህ ከደራሲው የተሰጠ የመነሻ መረጃ ነው ። በቀዝቃዛው ክረምት ጦርነቶችን መድረግ ከባድ ነበረ ፣ ስለሆነም ነገሥታት በተለምዶ ጠላቶቻቸውን ለማጥቃት የፀደይ ወቅትን ይጠብቁ ነበር ። (ዳራዊ መረጃን :ይመልከቱ)
ነገሥታት በተለምዶ ወደ ጦርነት ይሄዳሉ… ኢዮአብም ሠራዊቱን ወደ ጦር ግንባሩ ይመራ ነበር እዚህ “ነገሥታት” ማለት ነገሥታቶቻ ሰራዊታቸውን ወደ ጦርነት ላኩ ማለት ነው ። ኢዮአብ የዳዊት ሠራዊት አለቃ ነበር። ኣት: “ነገሥታት በመደበኛነት ሠራዊታቸውን ወደ ጦርነት ይልካሉ… ኢዮአብ የዳዊትን ሰራዊት ወደ ጦርነት ይመራ ነበር” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
ምድሪቱን አወደመች
“ምድሪቱን አጥፍተዋታል።” ይህ የሚያመለክተው ጠላቶቻቸው ምግብ የሚያበቅሉበትን ምድር የሚያጠፋበት ወቅት ነው ።
እርሱም ሄዶ ረባትን ከበባት
“እርሱ” ወታደሮችንና ኢዮአብንም ያመለክታል ። ኣት: “ኢዮዓብና ወታደሮቹ በራባት ዙሪያ ሆኑ” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)
1 Chronicles 20:2
ችሎታ
33 ኪሎግራም ገደማ (ስለመጽሐፍ ቅዱስን ገንዘብ :ይመልከቱ)
ዘውዱ በዳዊት ራስ ላይ ተደረገ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ዳዊት ዘውዱን በራሱ ላይ አደረገ ወይም 2) የዳዊት ሰዎች ዘውዱን በራሱ ላይ አደረጉ ። ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
አውጥቷል… አውጥቷል
እነዚህ “እርሱ” ሁለት አጋጣሚዎች ዳዊትን ያመለክታሉ ፣ ደግሞም ዳዊት እነዚህን ነገሮች እንዲያደርግ የረዱትን የዳዊትን ወታደሮች ያመለክታሉ ። (ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን : ይመልከቱ) ዘረፋ በጦርነት ውስጥ የተወሰዱ ውድ ዕቃዎች
በሾላዎች እና በብረት መጫዎቻዎች እና መጥረቢያዎች እንዲሠሩ አስገደዳቸው
እነዚህ ውሎች የተሸነፉ ሰዎች እንዲሠሩ የተገደዱትን የጉልበት ሥራን ይገልፃሉ ።
ዳዊት የሕዝቡን ከተሞች ሁሉ ይፈልጋል
ሰዎቹ የሚናገሩት በከተማቸው ነው ። ኣት: “ዳዊት የከተሞቹን ሕዝብ ሁሉ ይፈልጋል” (አንቶኒን ይመልከቱ)
1 Chronicles 20:4
ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅምር ለመጠቆም እዚህ ያገለገለ ነው ። ቋንቋዎ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ለመጠቀም ሊጠቀሙበት ይችላሉ ።
በጌዜር ላይ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሰልፍ ነበር
“እስራኤላውያን ፍልስጥኤማውያንን በጌዜር ተዋጉ”
ጌዘር… ጎባ
የከተሞች ስሞች እነዚህ ናቸው። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ፡ ይመልከቱ)
ሲቤቤኪ… ሲፓፓ… ኤሊያናን… ያኢር… ላሚ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ፡ ይመልከቱ)
ሑሻዊው … ረፋይም… ቤተልሔም… ጋቲታዊ
እነዚህ የሰዎች ቡድኖች ስሞች ናቸው ።
ፍልስጥኤማውያንም ተዋረዱ
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ፍልስጥኤማውያንን አዋረዱ” (ገባሪ ወይም ተገባሪ፡ ተመልከት)
ፍልስጥኤማውያንም ተዋረዱ
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “እስራኤላውያን ፍልስጥኤማውያንን ድል ማድረግ ችለዋል” ወይም “ፍልስጥኤማውያን በእስራኤላውያን ቁጥጥር ሥር ወድቀዋል”
ሠራተኞች

ረዥም እና ቀጭን ምሰሶ።
የጦራቸውም እንደ የሸመና ሞገድ ነው
የሹራብ ክር በዙሪያቸው ስለሚተሳሰሩ የሸመና ሞገድ ገመድ የሚዘረጋበት በጣም ትልቅ እንጨት ነበር። ይህ ማለት የሌህሚ ጦር ጦር በጣም ትልቅ ነበር ማለት ነው።
1 Chronicles 20:6
ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ለመጠቆም እዚህ ያገለግላል ። ቋንቋዎ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ሊጠቀሙበት ይችላሉ ።
ራፋይም
ይህ ስም በጣም ረዥም እና ጠንካራ ለሆኑ ሰዎች የተሰጠ ስም ነው ። ( ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ : ይመልከቱ)
ዮናታን... ሳምዓ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ።
እነዚህ የጌት የራፋይም ልጆች ነበሩ
እዚህ “እነዚህ” በ 1 ኛ ዜና 20 :4 ውስጥ ሲፋይን ፣ በ 1ኛ ዜና ምዕራፍ 20 ፡ 5 ውስጥ ለሕሚን እና በቁጥር 6 ውስጥ ግዙፍ የሆነውን ያመለክታሉ ።
በዳዊት እጅ በሠራዊቱም እጅ ተገደሉ
ዳዊትና ወታደሮቹ ሰይፍ በሚይዙበት የሰውነት ክፍሎቻቸው ተጠቅሰዋል ። ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ዳዊትና ወታደሮቹ የራፋይም ዘሮችን ገደሉ” (አንዱን በሁሉ ወይም ሁሉን በአንዱ መወከልን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን : ይመልከቱ)

---

Chapter 21
1 Chronicles 21:1
በእስራኤል ላይ አንድ ጠላት ተነሳ
“ባላጋራ” ለሚለው ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞችን 1) ይህ የሚያመለክተው ለእስራኤል ችግር ለማምጣት የወሰነውን ሰይጣንን ነው ወይም 2) ይህ እስራኤልን ማስፈራራት የጀመረው የጠላት ጦር ነው ።
ዳዊት እስራኤልን እንዲቆጥር አነሳሳው
ዳዊትን አሳተው፣ ቋንቋዎ አንድን ሰው በማስቆጣት ስህተት እንደሆነ የሚያውቀውን ነገር እንዲያደርግ በማድረግ ማሳሳትን የሚገልጽ ነገር ካለ ፣ እዚህ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።
ቁጥራቸውንም እንዳውቅ የእስራኤልን ሕዝብ ቁጠሩ
ከ 1ኛ ዜና 21፡ 5 በግልጽ ማየት እንደሚቻለው ዳዊት ውጊያ የሚችሉትን ሰዎች ለመቁጠር ፈልጎ ነበር ።
ከቤርሳቤህ እስከ ዳን ድረስ
እስራኤላውያን እነዚህን ሁለት ከተሞች እንደ ብዙ ደቡባዊ እና ሰሜናዊ ከተሞች አድርገው ይመለከቱ ነበር። ዳዊት እነዚህን ከተሞች እስራኤልን በሙሉ ለማመልከት ይጠቀምባቸዋል ። (ሜሪዝምን : ይመልከቱ)
መቶ እጥፍ ይበልጣል
ኢዮአብ ሠራዊቱ መቶ እጥፍ እንዲሆንለት እናየበለጠ ኃያል እንዲሆኑ እንደሚመኝ በመናገር ገለጸ። (ግነት እና ማጠቃለል : ይመልከቱ)
ግን ጌታዬ ንጉሥ ፣ ሁሉም ጌታዬን አያገለግሉምን? ጌታዬ ይህን ለምን ይፈልጋል? በእስራኤል ላይ ለምን ጥፋትን ያመጣል?
ኢዮብ የሕዝብ ቆጠራው ሃሳብ መልካም እንዳልሆነ ለዳዊት ለመግለጽ እነዚህን ሦስት አወያይ ጥያቄዎችን ተጠቅሟል ። ዳዊት እግዚአብሔርን ከመታመን ይልቅ በሠራዊቱ መጠን የሚታመን ይመስላል እናም እስራኤልን ኃጢአተኛ ያደረገ ይመስላል ። እነዚህ አወያይ ጥያቄዎች እንደ መግለጫዎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። ኣት: ግን ጌታዬ ፣ ቀድሞ ሁሉም ያገልግሉሃል ። ጌታዬ ይህን መጠየቅ የለበትም ። ወታደራዊ ኃይልዎን ብቻ በመተማመን በእስራኤል ሕዝብ ላይ ጥፋት ያመጣሉ ።” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)
ጌታዬ ይህን ለምን ይፈልጋል?
“ይህ” የሚለው ቃል የዳዊትን የእስራኤልን ወንዶችን ለመቁጠር ያቀደውን ዕቅድ ያመለክታል ።
1 Chronicles 21:4
የንጉሡ ቃል በኢዮአብ ላይ ተፈፀመ
“የኢዮአብ ተቃውሞ ቢኖርም የንጉሡ ትእዛዝ አሸነፈ”
ኢዮአብም ወጥቶ ወደ እስራኤል ሁሉ ሄደ
በ 1 ኛ ዜና ምዕራፍ 21 :2 ውስጥ ኢዮአብ የእስራኤልን ህዝብ ለመቁጠር እንደሄደ ከዳዊት ትእዛዝ ተረድቷል ። ይህ በግልጽ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ኢዮአብም ሕዝቡን ለመቁጠር ወደ እስራኤል ሁሉ ሄደ” (የሚጠበቅ ዕውቀት እና ያልተገለጸ መረጃን፡ ይመልከቱ)
1,100,000 ወንዶች
“አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ወንዶች” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎች ነበሩ
የእስራኤል ወታደሮች ሰይፉን በመምዘዝ ተግባር ተገልጸአል ። ኣት: - “ወታደር ሆነው ያገለግሉ የነበሩ ወንዶች” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
470,000 ወታደሮች
“አራት መቶ ሰባ ሺህ ወታደሮች” (ቁጥሮችን:ይመልከቱ)
1 Chronicles 21:6
ከእነርሱ መካከል ሌዊና ቢንያም አልተጠሩም
ሌዋውያኑ አምልኮ መምራት ነበረባቸው እንጂ መዋጋት አይደለም ። ኢዮአብ ቢንያምን ለምን እንዳልቆጠረው ግልፅ አይደለም ። ይህ በገቢራዊ ቅርጽ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ነገር ግን ኢዮአብ የሌዊና የቢንያም ነገድ ሰዎችን አልቆጠረም” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን : ይመልከቱ)
የንጉሡ ትእዛዝ ኢዮአብን ጠላው
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ኢዮአብ ዳዊት ባዘዘው ነገር ተበሳጭቶ ነበር” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን : ይመልከቱ)
በዚህ እርምጃ
እዚህ “ይህ እርምጃ” የሚለው ኃረግ ውጊያ የሚችሉትን የእስራኤል ወንዶች ሁሉ ለመቁጠር ያለመውን የዳዊትን ዕቅድ ያመለክታል ።
በእስራኤልም ላይ ጥቃት ሰነዘረ
የዚህ ጥቃት ባህሪ ግልፅ አይደለም ። ዳዊትን ሕዝቡን በመቁጠር እግዚአብሔር በእርሱ ላይ እንደተቆጣ ማሳወቁ በቂ ነበር ።
የአገልጋይህን በደል አስወግዱ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ይቅርታ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ጥፋተኝነትን ማስወገድ ተብሎ ነው ። ኣት: - “ይቅር በሉኝ” (ፈሊጥን፡ ይመልከቱ)
የአገልጋይህ በደል
ዳዊት ራሱን የእግዚአብሔር አገልጋይ ሲል ገልጾአል ። ኣት: - “በደሌ” ( አንደኛ ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ ሰብዓዊን :ይመልከቱ)
1 Chronicles 21:11
በሰይፋቸው መያዝ
እዚህ “ጎራዴዎቻቸው” በጦርነት ውስጥ ሞትን ያመለክታሉ ። ኣት: - “በጦርነት በእነርሱ መገደላቸው” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ሰይፍ በምድሪቱ ላይ መቅሰፍት ነው
እዚህ ላይ መቅሰፍቱ “ሰይፍ” ተብሎ ተገልጾአል ምክንያቱም “ሰይፉ” የሞት መግለጫ ስለሆነ ነው። ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ )
በምድሪቱ ሁሉ ላይ በጥፋት
“በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች የሚኖሩትን ሰዎች መግደል”
ወደ ላከኝ መውሰድ አለብኝ
የላከው ጌታ እግዚአብሔር ነው ። ይህ በግልጽ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ወደ ላከኝ ወደ ጌታዬ እወስዳለሁ” (የተገመተ ዕውቀት እና ጥልቅ መረጃን : ይመልከቱ)
1 Chronicles 21:13
ከሰው እጅ ይልቅ በእግዚአብሔር እጅ ልውደቅ
እዚህ “እጅ” የሚለው እስራኤልን የሚጎዳ ወይም የሚቀጣ ኃይልን ይወክላል ። ኣት: - “በሰዎች ከመቀጣት ይልቅ እግዚአብሔር ይቅጣኝ” ( የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)
ልውደቅ
በመቅሰፍቱ የሚሞቱት የእስራኤል ሕዝብ ናቸው ፣ ነገር ግን ዳዊት እርሱ ራሱ እንደሚገደልና ፍርዱን እንደሚቀበል ገልጾአል።
የሰው እጅ
እዚህ “ሰው” የሚለው ቃል “ሰዎች” የሚለውን አጠቃላይ ስም ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል።
ምሕረቱም እጅግ ታላቅ ነው
“እግዚአብሔር እጅግ መሐሪ ነው”

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በእስራኤል ላይ
እዚህ እስራኤል የሚለው የባህሪ ስም ሲሆን የእስራኤል ሕዝብን ይወክላል። ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
ሰባ ሺህ ሰዎች ሞተዋል
“70,000 ሰዎች ሞቱ” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
ስለጉዳቱ አእምሮውን ለወጠ
እዚህ “አእምሮ” የሚለው ቃል የእርሱን ውሳኔ ይወክላል ። ኣት: - “ኢየሩሳሌምን ላለማጥፋት ወስኗል” ( የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)
ይበቃል!
ይህ ቃል አጋኖ “በቂ ሰዎችን ገድሏል!” ማለት ነው ( ታአምራዊን : ይመልከቱ)
እጅህን ወደኋላ መልስ
ይህ አንድ ነገር መሥራትን ማቆም ማለት ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “የኢየሩሳሌምን ሰዎች አትግደል” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ )
ኦርናን
ይህ የሰው ስም ነው ። (ስሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ : ይመልከቱ)
1 Chronicles 21:16
በምድርና በሰማይ መካከል ቆሞ
ይህ መላዕኩ በምድር ላይ ባሉት ሰዎች ላይ ለመፍረድ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ መሆኑን የሚያመለክት ምሳሌያዊ ቋንቋ ነው ። ( የምልክት ቋንቋን : ይመልከቱ)
የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ ይዞ ወደ ላይ ወጣ
በእጁ ሰይፍ የያዘው መልአክ ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት ዝግጁ መሆኑን የሚያሳይ ምሳሌያዊ ተግባር ነው ። ፍርዱ ህመም ስለነበረ ይህ ምሳሌያዊ ነው ። ኣት: - “ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት ሰይፍ በእጁ ይዞ እንደተዘጋጀ ተገልጾአል ” ( ምሳሌያዊ ድርጊትን :ይመልከቱ)
ማቅ ለብሰው መሬት ላይ ተደፉ
እነዚህ ድርጊቶች የንስሐ ምልክት ነበሩ ። ( ምሳሌያዊ ድርጊትን :ይመልከቱ)
ሠራዊቱ እንዲቆጠር ያዘዝኩት እኔ አይደለሁምን?
ዳዊት ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡን በመቁጠር ጥፋት የፈጸመው እርሱ እንደሆነ ለማጉላት ነው ። ኣት: - “ሠራዊቱ እንዲቆጠር ያዘዝኩት እኔ ነኝ።” (አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)
ግን እነዚህ በጎች
ዳዊት የእስራኤልን ህዝብ በመሪዎቻቸው ላይ እምነት በመጣል እና በመከተል በሚታወቁት በበጎች መስሏቸዋል። (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ )
ምን አደረጉ?
ዳዊት ይህንን ጥያቄ እግዚአብሔር ሰዎችን እንዳይቀጣ እግዚአብሔርን ይጠይቃል ። ይህ የአጻጻፍ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “እነሱ በትክክል ቅጣት የሚገባውን ነገር አላደረጉም ።” ( አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)
እጅህ እኔን እና ቤተሰቤን ይምታ
እዚህ “እጅ” የሚለው የእግዚአብሔርን ቅጣት ይወክላል ። ኣት: - “እኔን እና ቤተሰቤን ቅጣ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
1 Chronicles 21:18
ዳዊት መውጣት አለበት... ወደላይ ወጣ
ይህ የከፍታ ማመሳከሪያ ነው። ለወደፊት የቤተመቅደሱ ስፍራ የሆነው ይህ አውድማ በኢየሩሳሌም ውስጥ ከፍ ያለ ቦታ ነበር ።
ኦርና
በ 1 ኛ ዜና ምዕራፍ 21፡15 ውስጥ የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደተረጉሙት ይመልከቱ ።
ጋድም በእግዚአብሔር ስም እንዲያደርግ እንዳዘዘው
“በእግዚአብሔር ስም” መናገር ማለት ከኃይሉና ከስልጣኑ ወይም እንደ ተወካይ መናገር ማለት ነው ። ኣት: - “ጋድ በእግዚአብሔር ፈንታ እንደሚናገር ዳዊትም እንዲናገር አዘዘው” ( የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)
እራሳቸውን ደብቀዋል
እነርሱ መልአኩን ፈሩ ። ይህ የበለጠ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ኣት: “መላእክትን ስለ ፈሩ ተደበቁ” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን : ይመልከቱ)
1 Chronicles 21:21
በመሬት ላይ ተደፋ
ይህ ሐረግ ኦርናን በዳዊት ፊት እንደሰገደ ይገልጻል ። በአንድ ሰው ፊት መስገድ ትሕትናን እና አክብሮትን መግለጫ መንገድ ነው። በጣም ዝቅ ማለጥ የበለጠ ትህትናን እና አክብሮትን ያሳያል። ኣት: - “መሬት ላይ እጅግ ዝቅ አለ” ( ምሳሌያዊ ድርጊትን : ይመልከቱ)
ሙሉ ዋጋ
“ይህ አውድማ የሚያወጣውን ሙሉ ዋጋ እከፍላለሁ”
1 Chronicles 21:23
እንደ ራስህ አርገህ ውሰደው
ይህ የሚያመለክተው ዳዊት ለመሬቱ ምንም ክፍያ ሳይፈጽም መሬቱን መውሰድ እንደሚችል ነው ። ኣት: - “እንደ ስጦታ ውሰዱት” ( የሚጠበቅ ዕውቀት እና ያልተገለጸን መረጃ :ይመልከቱ)
በፊትህ መልካም የሆነውን
የዳዊት ግንዛቤ እንደ እይታ ተገልጾአል ። ኣት: - “ለማድረግ የፈለግከውን ሁሉ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ) ተመልከት
አውድማ
እነዚህ ከእንጨት የተሠሩ ዓለቶች ወይም ከእንጨት የተሠሩ የብረት መከለያዎች ሲሆኑ እህልን ከገለበው ለመለየት በእህል አውድማው ላይ በበሬዎች የሚጎተቱ መውቂያዎች ናቸው። ( የማይታወቁትን መተርጎምን :ይመልከቱ)
ሙሉ ዋጋ
ይህንን በ 1 ኛ ዜና መዋዕል 21 ፡ 22 ውስጥ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ ።
1 Chronicles 21:25
ስድስት መቶ ሰቅል ወርቅ
“600 ሰቅል ወርቅ” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
ሰቅል
ከ 11 ግራም ጋር እኩል የሆነ የክብደት መለኪያ (የመጽሐፍ ቅዱስን ገንዘብ : ይመልከቱ)
ለቦታው
“አውድማውን ለመግዛት”
ወደ እግዚአብሔር ጮኸ
“ እግዚአብሔር እንዲረዳው ጸለየ”
በሚቃጠል መሥዋዕቱ መሠዊያ ላይ ከሰማይ በእሳት መልስ ሰጠው
ዳዊት የሚቃጠለውን መሥዋዕት በሚያቀርብበት ቦታ ከሰማይ ወደ እርሱ እሳት በመላክ መልስ የሰጠው ”
መልአኩም ሰይፉን ወደ ሰገባው ውስጥ አስገባ
ሰይፉን ወደ ሰገባው ውስጥ ያስገባው መልአክ ሰዎችን መግደል እንደማይቀጥል የሚያሳይ ምሳሌያዊ ተግባር ነው ። ኣት: - መልአኩ ሕዝቡን መግደል እንደሚያቆም ለማሳየት ሰይፉን በሰገባው ውስጥ አደረገው ”( ምሳሌያዊ ድርጊትን :ይመልከቱ)
ሰገባ
ለጎራዴ ወይም ቢላ መሸፈኛ
1 Chronicles 21:28
ኦርናን
በ 1 ኛ ዜና ምዕራፍ 21 ቁጥር 15 እንደ ሆነ ስሙን ተርጉም ።
በዚያን ጊዜ ... የእግዚአብሔር መልአክ
ከቁጥር 29 - 30 ያሉት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በመሠዊያው ላይ ዳዊት ይህን መሥዋዕት ያቀረበው ለምን እንደሆነ የሚያስረዳ ዳራዊ መረጃ ነው ። ( ዳራዊ መረጃን :ይመልከቱ )
የእግዚአብሔርን መመሪያ ለመጠየቅ
“ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲነግረው እግዚአብሔርን መጠየቅ”
የእግዚአብሔር መልአክ ሰይፍ ፍራ
እዚህ “ሰይፍ” በእግዚአብሔርን መልአክ መገደልን ያመለክታል ። ኣት: - “በእግዚአብሔር መልአክ እንዳይገደል ፈሩ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

---

Chapter 22
1 Chronicles 22:1
እዚህ ነው
“ቦታው ይህ አውድማ ነው ”
ድንጋይ ጠራቢዎች
ግንበኞች የግንብ ግድግዳዎችን እና ሕንጻዎችን ለመሥራት እንዲጠቀሙባቸው ትላልቅ ድንጋዮችን ሰብስበው በትክክለኛው መጠን በመጥረብ የሚያዘጋጁ ሰዎች


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ናቸው።
1 Chronicles 22:3
መጠረቂያ
ሁለት ነገሮችን የሚያገናኙ ዕቃዎች ፡፡ “ክላች” ወይም “ማጠፊያዎች”
መመዘን ከሚችለው በላይ ናስ
ይህ እጅግ ብዙ ነሐስ እንደነበር የሚያሳይ ግነት ነው ፡፡ ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ፡፡ ኣት: - “ማንም ሰው ሊመዝነው የማይችል እጅግ ብዙ ናስ” (ገቢራዊን ወይም ተቢሮአዊን እና ግነትን እና አጠቃላይን ፡ ይመልከቱ)
ሊቆጠር ከሚችለው በላይ የሊባኖስ ዝግባዎች
ብዛት ያላቸው የሊባኖስ ዝግባዎች መኖራቸውን የሚያሳይ ግነት ነው። ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ፡፡ ኣት: - “ማንም ሊቆጥራቸው የማይችሉት በርካታ የዝግባ ዛፎች” (ገቢራዊን ወይም ተቢሮአዊን እና ግነትን እና አጠቃላይን ፡ ይመልከቱ)
ሲዶናውያን እና የጢሮስ ሰዎች ለመቁጠር የሚታክተውን እጅግ ብዙ የዝግባ እንጨት አመጡ
ይህ ብዙ እንጨት ማን እንደሰጠ ለማብራራት የሚረዳ ዳራዊ መረጃ ነው ፡፡ ( ዳራዊ መረጃን ፡ይመልከቱ)
ለእግዚአብሔር የሚሠራው ቤት
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ፡፡ ኣት: - “እርሱ ለእግዚአብሔር የሚሠራው ቤት” ( ገቢራዊን ወይም ተቢሮአዊን ፡ ይመልከቱ)
በሌሎች አገሮች ሁሉ ዝነኛ እና የከበረ ይሆናል
እዚህ “አገሮች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በዚያ ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ነው ፡፡ ኣት: - “ስለዚህ በየትኛውም ሌላ አገር ያሉ ሰዎች ስለዚህ ጉዳይ እንዲያውቁና የከበረ እንደሆነ እንዲገነዘቡ” (የባህሪ ስምን፡ ይመልከቱ)
ለህንፃው መዘጋጀት
“ለመገንባት ተዘጋጁ”
1 Chronicles 22:6
ጠራ
“ዳዊት ጠራ”
እንዲገነባ አዘዘው…ቤት እሠራ ዘንድ አስቤ ነበር
አንባቢዎች ዳዊት ሥራውን ሠራተኞቹ እንዲሠሩ አስቦ መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል ፡፡ ኣት: - “ለእግዚአብሔር ቤት እንዲያሠራ አዘዘው… እኔ ራሴ የቤቱን ግንባታ በበላይነት የመቆጣጠር እቅዴ” ( የባህሪ ስምን፡ ይመልከቱ)
የእኔ ፍላጎት ነበር
“ዓላማዬ”
እኔ ራሴ ቤት ለመሥራት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚገልጽ ተኪ ስም ነው ። በዚህ ሁኔታ እሱ የአክአብን ዘሮች ያመለክታል ። በ 2 ኛ ዜና 21፡ 6 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “የአክዓብ ዘሮች እንዳደረጉ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

እነርሱ አማካሪዎቹ ነበሩ

“የአክዓብ ዘሮች ምክር ሰጡት”

ለጥፋቱ

“ይህም ጥፋት አመጣ”

የእነርሱን ምክርም ተከትሏል ። ሄደ

“እርሱ ደግሞ የእነርሱን ምክር ተከትሎ ፣ ሄደ” ወይም “እርሱ ደግሞ የእነርሱን ምክር ተከተለ”

በአራምን ንጉሥ በአዛሄል ላይ

አዛሄል ብቻውን እንዳልተዋጋ ፣ ነገር ግን ሠራዊቱን ከእርሱ ጋር እንደወሰደ አንባቢው መገንዘብ አለበት ። ኣት: “የአራምን ንጉሥ አዛኤልን እና ሠራዊቱን ሊወጋ ሄደ” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

አዛኤል

ይህ የሰው ስም ነው። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

2 Chronicles 22:6

ከሰጡት ቁስል ሁሉ

“በውጊያው ከደረሰበት ቁስል”

ወደ ኢይዝራኤል ወረደ

ኢይዝራኤል ከኢየሩሳሌም ይልቅ ዝቅ ያለ ነበር ።

2 Chronicles 22:7

የአካዝያስ ጥፋት በእግዚአብሔር ዘንድ ሆነ

የ “ጥፋት” የሚለው ጽሑፍ ስም እንደ ድርጊት ሊገለጽ ይችላል። ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር አካዝያስን እንዲሞት አደረገው” ( የረቂቅ ስሞችን እና ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

ወደ ኢዮራም ሄደ... ከኢዮራም ጋር ሄደ

“ኢዮራም” እና “ኢዮራም” ለአንድ ሰው የተሰጡ ሁለት ስሞች ናቸው ።

ናሜሲ

ይህ የሰው ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ

ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አንድን አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።

በአክዓብ ቤት ላይ የአምላክን ፍርድ ይፈጽም ነበር

ይህ የአክአብን ዘሮች መግደል ያመለክታል ። ኣት: - “እግዚአብሔር እንዳዘዘው የአክአብን ዘሮች ሁሉ መግደል”

የአክዓብ ቤት

“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን የሚገልጽ ተኪ ስም ነው ። በዚህ ሁኔታ ቤት የሚለው ቃል የአክአብን ዘሮች ያመለክታል ። በ 2 ኛ ዜና21፡ 6 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “የአክዓብ ዘሮች” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

የአካዝያስ ወንድሞች ልጆች

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የአካዝያስ ወንድሞች ወይም 2) የአካዝያስ ዘመዶች ወንዶች ልጆች ።

2 Chronicles 22:9

ያዙት... ገደሉትም

አካዝያስን ያዙት... አካዝያስን ገደሉትም ”

“እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ የፈለገ የኢዮሣፍጥ ልጅ ነው” እያሉ ቀበሩት።

ጥሩ ንጉሥ የነበረው የኢዮሣፍጥ ዘር ስለሆነ አስክሬኑን በመቅበር ረገድ አክብረውታል ። ይህ የበለጠ ግልጽ ሊደረግ ይችላል ። ኣት: -እግዚአብሔርን ለማስደሰት ከፍተኛ ጥረት ያደረገው የኢዮሣፍጥ ዘር ስለሆነ ሊቀብር ይገባዋል ስላሉ አስክሬኑን ቀበሩት ።(የሚጠበቅ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ :ይመልከቱ)

የአካዝያስ ቤት መንግሥቱን የማስገኘት ኃይል አልነበረውም

እዚህ “የአካዝያስ ቤት” የሚለው የአካዝያስን ዘሮች የሚወክል ስም ነው ። እዚህ ላይ “የመግዛት ኃይል” የሚለው ንጉሡን የሚወክል ነው ። የአካዝያስ ትልልቆች አዋቂዎች ሁሉ ስለሞቱ ይሁዳን የሚገዛ አንድም ሰው አልነበረም። (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 22:10

ተነሥታ የንጉሡን ልጆች ሁሉ ገደለች

እዚህ ደራሲው ጎቶልያ ራሷ ልጆቹን እንደገደለች አስመስሎ ተናግሮአል ፣ ነገር ግን በአገልጋዮቿን እንዳስገደለቻቸው አንባቢው መገንዘብ ይኖርበታል ። ኣት: - “ንጉሣዊ ልጆችን ሁሉ እንዲገድሉ አገልጋዮቿን አዘዘች” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ሁሉም ንጉሣዊ ልጆች

ይህ የሚያመለክተው ወንዶቹን ብቻ ነው ፣ ምክንያቱም ንጉሥ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው ። ቁጥር 11 ወንዶቹ ልጆች እንደተገደሉ ያረጋግጣል ። (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት

“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩት ቤተሰቦች የሚወክል ስም ነው ። በዚህ ረገድ እሱ የሚያመለክተው የይሁዳን መንግሥት ነው ። ኣት: - “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ መንግሥት” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

የንጉሥ ሴት ልጅ ዮሳቤት ፣ የንጉሥ ኢዮራም ልጅ ናት

እዚህ “ንጉሡ” ”የአካዝያስን አባት ኢዮራምን ያመለክታል ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ሞግዚት

ይህ የሚያመለክተው ልጅን የሚንከባከበውን ግለሰብ እንጂ ሐኪምን አይደለም ።

ወደ መኝታ ክፍል ገባ

ቁጥር 12 ይህ መኝታ ቤት በቤተመቅደስ ውስጥ እንደነበረ ግልፅ ያደርግልናል ። ዮሴባ ካህን የሆነውን ዮዳሄን አግብታ ስለነበር ወደዚያ ክፍል መግባት ትችል ነበር።

ዮዳሄ

ይህ የወንድ ስም ነው። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)

እርሱ ከእነርሱ ጋር ነበር

“ዮአስ ከኢዮሳባ እና ዮዳሄም ጋር ነበረ”



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 23
2 Chronicles 23:1
አጠቃላይ መረጃ
በምዕራፍ 23 ውስጥ ሁሉ ፣ ኢዮአስ “ንጉስ” ተብሎ ተጠርቷል ። አልፎ አልፎ ማንነቱን ለአንባቢዎች በትክክል ለማሳየት “ንጉሥ ዮአስ” ወይም “ንጉሱ ኢዮአስ” ተብሎ ቢጻፍ ጥሩ ሊሆን ይችላል ። ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ ይመልከቱ)
ዮዳሄ
በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያገለግልና ለእግዚአብሔር የታመነ ሊቀ ካህን ነው። የኢዮአስ አማካሪ ነበር። (የስሞች አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)
ጥንካሬውን አሳይቷል
የጎቶሊያን አገዛዝ ለመቃወም ጊዜው እንደሆነ ወስኖ ኢዮአስ በሕይወት መኖሩን እና ንጉሥ ለመሆን ዝግጁ መሆኑን ገለጸ ። አት: - “እርምጃ ለመውሰድ ወሰነ”
የመቶዎች አዛዦች
“የመቶዎች አዛዦች” የሚለው ሐረግ ምናልባት ወታደራዊ ማዕረግ ሊሆን ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “መቶዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እነዚህ አለቆች የሚመሩትን ወታደሮች ትክክለኛ መጠን ነው። ኣት: - “የ 100 ወታደሮች አዛዦች” ወይም 2) “መቶዎች” ተብሎ የተተረጎመው ቃል ወታደራዊ ክፍልን እንጂ ትክክለኛውን ቁጥር አይወክልም ።ኣት: - “የወታደራዊ ክፍል አዛዦች” ( ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
ወደ ቃል ኪዳኑ ገባ
“ስምምነት አደረገ”
አዛርያስ... ይስማኤልን... ዓዛርያስ... መዕሤያ... ኤሊሳፋጥ
እነዚህ ሰዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች አዛዦች ነበሩ። ( የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)
ይሮሐም... ይሆሓናን... ዖቤድ... ዓዳያ... ዝክሪ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)
የእስራኤል አባቶች ቤቶች ራሶች
እዚህ “ራሶች” በጣም አስፈላጊ የሆነ አካል ምሳሌ ነው ። “ቤቶች” ቤተሰቦችን ይወክላሉ ። ኣት: - “የእስራኤል መሥራች ቤተሰቦች መሪዎች” ( ዘይቤያዊን እና የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)
የንጉሥ ልጅ
እዚህ “ንጉሥ” የሚለው የኢዮአስ አባትን ያመለክታል ። “የንጉሥ ልጅ ዮአስ”
2 Chronicles 23:4
አንድ ሦስተኛ... ሌላ አንድ ሦስተኛ... ሌላኛው ሦስተኛ
“አንድ ሶስተኛ... ሌላ አንድ ሶስተኛ... ሌላኛው አንድ ሦስተኛው” ( ሕገኛ ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
በበሩ ላይ ጠባቂዎች ይሆናሉ
'በቤተ መቅደስ በሮች ላይ ጠባቂዎች ይሆናሉ'
መካከለኛው በር
ይህ በር “መካከለኛው በር” ወይም “ሱር በር” ተብሎም ተጠርቶ ሊሆን ይችላል ። እሱ በንጉሥ ቤተ መንግሥት አቅራቢያ የሚገኝ ውስጣዊ በር ነበር ።
ህዝብ ሁሉ
ይህ የተገኙትን ሁሉ የሚያመለክት አጠቃላይ መረጃ ነው ። አት: - “የተገኙት ሌሎች ሰዎች ሁሉ” ( ግነትን እና አጠቃላይን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 23:6
ማንም ወደ እግዚአብሔር ቤት አይግባ
“ማንም ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዲገባ አትፍቀድ”
ሌሎቹም ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ማክበር አለባቸው
ያንን ትእዛዝ መግለፅ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። ኣት: “ሌሎቹ ሁሉ እግዚአብሄር ያዘዘውን በመታዘዝ በግቢው ውስጥ መቆየት አለባቸው” ( የሚጠበቁ እውቀቶችን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)
ሌዋውያኑ ንጉሡን በሁሉም ጎኖች ዙሪያውን መክበብ አለባቸው
“ሌዋውያኑ ንጉሡን ለመጠበቅ በእርሱ ዙሪያ በሁሉም አቅጣጫ መክበብ አለባቸው።”
በሁሉም በኩል እያንዳንዱ ሰው የጦር መሣሪያውን በእጁ ይዞ
“ሁሉም ጎኖች ፣ እና እያንዳንዱ የቤተመቅደሱ ጠባቂ መሳሪያዎቹን መያዝ እና ለውጊያ መዘጋጀት አለበት ”
ወደ ቤት የሚገባ ሁሉ ይገደል
ይህ የቤተ መቅደሱን ጠባቂዎች እና ካህናትን አላካተተም ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል። አት: - “ከመቅደሱ ጠባቂዎች እና ወደ ቤተመቅደስ ከሚገቡት ካህናቱ በስተቀር ማንንም መግደል አለብህ” ( የሚጠበቁ እውቀቶችን እና ያልተገለጸ መረጃን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)
ሲገባ እና ሲወጣ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በማንኛውም ጊዜ” ወይም 2) “በሄደበት ሁሉ” ናቸው ። (ፈሊጥን፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 23:8
መላው ይሁዳ
በዚያን ቀን በግቢው ውስጥ የነበሩትን የይሁዳን ሕዝብ በሙሉ የሚያመለክት ማጠቃለያ ነው ። (ግነትን እና አጠቃላይን ፡ይመልከቱ)
ካህኑ ዮዳሄ እንዳዘዘው በሁሉም መንገድ አገልግሏል
“ካህኑ ዮዳሄ ያዘዘውን ሁሉ አደረጉ” ወይም “ካህኑ ዮዳሄ ያዘዘውን ሁሉ ታዘዙ”
እያንዳንዳቸውም ሰዎች ወሰዱ ... ማንኛቸውም ክፍሎቻቸውን ወሰዱ
ካህናቱና ዘበኞቹ በየክፍላቸው ያገለግሉ ነበር ፤ እያንዳንዱ ቡድን ለሁለት ሳምንት ይሠራል። ይህ ሁለት ምድቦች የተገኙበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው - አገልግሎታቸውን የሚጨርሱ እና አገልግሎታቸውን የሚጀመሩ። ስለዚህ እንደተለመደው ወንዶች ሁለት እጥፍ ነበሩ።
የሰንበት አገልግሎታቸውን እየጨረሱ
በዚያኑ የሰንበት ቀን ሥራቸውን እየጨረሱ ነበር ”
2 Chronicles 23:10
አጠቃላይ መረጃ
በምዕራፍ 23 ውስጥ ሁሉ ፣ ኢዮአስ “ንጉስ” ተብሎ ተጠርቷል ። አልፎ አልፎ ማንነቱን ለአንባቢዎችዎ በትክክል ለማሳየት “ንጉሥ ኢዮአስ” ወይም “ንጉሡ ኢዮአስ” ማለት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልጸገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)
መሣሪያውን በእጁ ይዞ
ይህ ማለት ለውጊያ ዝግጁ ነበሩ ማለት ነው። በ 2 ዜና 23 :7 ውስጥ ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የንጉሥ ልጅ
እዚህ “ንጉሥ” የሚለው ቃል የኢዮአስን አባት ያመለክታል ። “የንጉሥ ልጅ ኢዮአስ”
ዘውድን በእርሱ ላይ አኖሩ
ይህ እርሱን ንጉሥ እያደረጉት እንዳለ የሚያመለክት ተግባር ነው ። ( ምሳሌያዊ ድርጊትን ፡ይመልከቱ)
የቃል ኪዳኑን ድንጋጌዎች ሰጡት
ትእዛዞቹን የያዘ ጥቅልል መስጠቱ እነርሱን መታዘዝ እንዳለበት የሚያሳይ ምሳሌያዊ ተግባር ። እነዚህ ድንጋጌዎች የሙሴ ሕግ አንድ አካል ይሁኑ ወይም ነገሥታቶች ሊታዘዙባቸው የሚገቡ የተለዩ ሕጎች ይሁኑ ግልጽ አይደለም ። ኣት: “እንዲታዘዝ የቃል ኪዳኑን ድንጋጌዎች ሰጡት” ( ምሳሌያዊ ድርጊትን ፡ይመልከቱ)
ቀባው
ይህ ንጉሥ እንዲሆን በእግዚአብሔር እንደተመረጠ የሚያመለክት ምሳሌያዊ ድርጊት ነበር ። (ተመልከት/ች: ምሳሌያዊ ድርጊት)
ንጉ the ለዘላለም ይኑር
“ንጉሥ ረጅም ዕድሜ ይኑር”
2 Chronicles 23:12
እነሆ
የሚከተለው መረጃ በጣም አስፈላጊ መሆኑን አንባቢውን ያነቃል ።
በመግቢያው ላይ ባለው ዓምድ ቆሞ ነበር
በንጉሡ እና በቤተመቅደሱ መግቢያ በለው ልዩ ዓምድ መካከል ያለው ግንኙነት ግልፅ አይደለም ።
የአገሬው ሕዝብ ሁሉ
ይህ በዝግጅቱ ውስጥ ብዙ ሰዎች እንደተሳተፉ ለማሳየት የቀረበ አጠቃላይ መረጃ ነው ። ኣት: - “እጅግ ብዙ የአገሩ ሕዝብ” ( ግነትን እና አጠቃላይን ፡ይመልከቱ)
ጎቶሊያ ልብሷን ቀደደች
ይህ ትልቅ ጭንቀትዋን የሚያመለክት ምሳሌያዊ ድርጊት ነበር ። ( ምሳሌያዊ ድርጊትን፡ይመልከቱ)
ክህደት! ክህደት!
ክህደት ማለት መንግሥት ለመገልበጥ እርምጃ መውድ ነው ። ጎቶሊያ በ 2 ኛ ዜና


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

22 ፡10-11 ውስጥ የንጉሱን ህጋዊ ወራሾች ገድላ ራስዋን ገዢ አደረገች ። ዮአስ በእሷ ፋንታ ንጉሥ በመሆኗ ተናደደች ። ግነቱ የተደጋገመው ለማጉላት ነው ። አት: - “ክህደት እየፈጸመክ ነው!”
2 Chronicles 23:14
ዮዳሄ
በ 2 ኛ ዜና 22 ፡11 እንዳለው የዚህን ሰው ስም ተርጉም ። ( የስሞችን አተረጓጎም፡ ይመልከቱ)
የመቶዎች አዛዦች
“የመቶዎች አዛዥ” የሚለው ሐረግ ምናልባት ወታደራዊ ማዕረግ ሊሆን ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “መቶዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እነዚህ አዛዦች የሚመሩትን ወታደሮች ትክክለኛ ብዛት ነው። ኣት: - “የ 100 ወታደሮች አዛዦች ” ወይም 2) “መቶዎች” ተብሎ የተተረጎመው ቃል የሚያመለክተው ትክክለኛውን ቁጥር ሳይሆን ወታደራዊ ክፍልን ነው። በ 2 ኛ ዜና 23 ፡1 ውስጥ እንዴት እንደተረጉምከው ተመልከት ። ኣት: - “የወታደር አዛዦች” ( ቁጥሮችን ፡ ይመልከቱ)
እነርሱ በሠራዊቱ ላይ ነበሩ
“በሠራዊቱ ውስጥ መሪ የነበሩት”
በደሰልፉ መካከል አውጧት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ከባችሁ ከቤተ መቅደሱ አደባባይ አውጧት” ወይም 2) “በቤተመቅደሱ ግቢ ውስጥ ካሉት ሰዎች መካከል አስወግዷት”
እርሷን የሚከተል ሁሉ በሰይፍ ይገደል
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። እርሷን የሚከተሉ ሰዎች ሊረዷት እየሞከሩ ነው ማለት ነው ። ኣት: - “እርሷን ለመርዳት የሚመጣውን ማንኛውንም ሰው ለመግደል ሰይፍህን ተጠቀም” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን እና የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)
ካህኑ እንዲህ ብሏል
“ካህኑ ዮዳሄ እንዲህ ብሏል”
ወደ ንጉሥ ቤት ወደ ፈረስ በር ገባች
አንዳንድ ትርጉሞች “ በነገሥታት ቤት መግቢያ አጠገብ ወዳለው የፈረስ በር ወሰዷት” የሚል አላቸው ።
የንጉሥ ቤት
“ንጉሣዊው ቤተ መንግሥት”
2 Chronicles 23:16
አጠቃላይ መረጃ
በምዕራፍ 23 ውስጥ ሁሉ ፣ ኢዮአስ “ንጉስ” ተብሎ ተጠርቷል ። አልፎ አልፎ ማንነቱን በትክክል ለማሳየት “ንጉሥ ዮአስ” ወይም “ንጉሡ ዮአስ” የሚለውን ብትጨምር ለአንባቢዎችህ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)
ሕዝቡ ሁሉ ወደ በኣል ቤት ሄደ
ይህ አጠቃላይ ገለጻ ሲሆን ብዙ ሰዎች ይህንን አደረጉ ማለት ነው ። አት: - “እጅግ ብዙ ሰዎች ወደ በኣል ቤተ መቅደስ ሄዱ” ( ግነትን እና አጠቃላይን ፡ይመልከቱ)
ማታን
ይህ የሰው ስም ነው ። ( የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 23:18
ከካህናቱ እጅ
እዚህ “እጅ” መቆጣጠርን ይወክላል ። አት: - “በካህናቱ አመራር” (ተመልከት/ች: የባህሪ ስም)
ስለዚህ በማንኛውም መንገድ ርኩስ የሆነ ማንም እንዳይገባ
ለእግዚአብሔር ዓላማ ተቀባይነት የሌለው ሰው በአካል ርኩስ ተደርጎ ይገለጻል ። አት: - “ስለሆነም በማንኛውም መልኩ በአምላክ ዘንድ ተቀባይነት ያሌለው ማንም እንዳይገባ” ( ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)
ስለዚህ በየትኛውም መንገድ ርኩስ የሆነ ማንም እንዳይገባ
ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ንፁህ ሰዎች ብቻ እንዲገቡ ማድረግ” ወይም “በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ብቻ መግባታቸውን ማረጋገጥ” ( እጥፍ አሉታዊን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 23:20
የመቶ አለቆቹ አዛዦች
“የመቶዎች አዛዦች” የሚለው ሐረግ ምናልባት ለወታደራዊ ማዕረግ ሊሆን ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “መቶዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እነዚህ አዛዦች የሚመሩትን ወታደሮች ትክክለኛ ቁጥር ነው። ኣት: - “የ 100 ወታደሮች አዛዦች” ወይም 2) “መቶዎች” ተብሎ የተተረጎመው ቃል ትክክለኛውን ቁጥር የሚወክል ሳይሆን ወታደራዊ ክፍልን የሚወክል ነው። AT: “የወታደራዊ ክፍል አዛዦች” በ 2 ኛ ዜና 23፡ 1 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ( ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
የአገሬው ሕዝብ ሁሉ
ይህ ጠቅለል ያለ ገለጻ ነው ማለትም እርሱ ብዙ ሰዎችን ከእርሱ ጋር ወስዶ ነበር ። ኣት: - “እጅግ ብዙ የእስራኤል ሕዝብ” ( ግነትን እና አጠቃላይን ፡ይመልከቱ)
ንጉሡን ከእግዚአብሔር ቤት አመጣለት
ቤተ መቅደሱ የተገነባው በኢየሩሳሌም ከፍ ባለው ኮረብታ ላይ ነበር። አት. “ንጉ ሡን ከቤተ መቅደሱ ወደ ቤተ መንግሥቱ አወረደው”
የመንግሥት ዙፋን
“ንጉሣዊው ዙፋን”
ስለዚህ የምድሪቱ ሰዎች ሁሉ
ይህ ጠቅለል ያለ ገለጻ ነው። አብዛኛው ህዝብ ተደስቷል ለማለት ነው ። ( ግነት እና አጠቃላይን፡ይመልከቱ)
ከተማይቱ ፀጥ አለች
“ከተማይቱ” የከተማዋን ህዝብ ይወክላል ፣ “ዝምታ” ደግሞ ሰላምን ይወክላል። ኣት: - “ጎቶልያ ከሞተች በኋላ ኢዮአስን የሚቃወም ስላልነበረ የከተማይቱ ሕዝብ በሰላም ነበር” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

---

Chapter 24
2 Chronicles 24:1
መግዛት ጀመረ
“የይሁዳ ንጉሥ ሆነ”
አርባ ዓመት
“40 ዓመት” ( ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
ሳብያ
ይህ የሴት ስም ነው። ( የስሞችን አተረጓጎም፡ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር
እዚህ “ዐይኖች” የሚለው ቃል ማየትን ይወክላል፣ ማየት ደግሞ ፍርድን ይወክላል ። እግዚአብሔር የኢዮአስን ተግባር አየ እና አጸናው። በ 2 ኛ ዜና 14 ፡1 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል እንደ ሆነ የወሰነው” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል አድርጎ የወሰደው” ( ዘይቤያዊን ፡ ይመልከቱ)
በካህኑ በዮዳሄ ዘመን ሁሉ
ይህ አገላለጽ “ካህኑ ዮዳሄ በሕይወት እስካለ ድረስ” ማለት ነው። ( ፈሊጥን፡ ይመልከቱ)
ዮዳሄ ሁለት ሚስቶችን አገባለት
“ዮዳሄ ለኢዮአስ ሁለት ሚስቶችን መረጠ”
2 Chronicles 24:4
ከዚህ በኋላ እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል መጀመሪያ ለመጠቆም እዚህ ያሚያገለግል ነው ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።
ወዲያውኑ
"ወድያው"
በመጀመሪያዎቹ ሌዋውያን ምንም ነገር አላደረጉም
ሌዋውያኑ እንዳልታዘዙ ለማሳየት “ግን” የሚለውን ማከል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። አት: - “ሌዋውያኑ ግን ወዲያውኑ አላደረጉቱም”
2 Chronicles 24:6
ሌዋውያንን ለምን የቃል ኪዳኑን ሕግ አልጠየቅኸም?
ንጉሥ ዮአስ ዮዳሄ ኃላፊነቱን አልተወጣም ብሎ ለመክሰስ ይህን አወያይ መጠይቅ ጠየቀ ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “ግዴታህን ችላ ብለሃል። ሌዋውያንን የቃል ኪዳኑን ድንጋጌዎች እንድትጠይቅ ነግሬህ ነበር ... ፣ ግን አላፈፀምከውም ። ” ( አወያይ መጠይቅን ፡ይመልከቱ)
ስለቃል ኪዳኑ ድንኳን

ምንም እንኳን ሰሎሞን የገነባው መቅደስ ቢሆንም ፣ ይህ ግብር በሙሴ ጊዜ እና ‹የመገናኛ ድንኳን› ጊዜ ጀምሮ ሲሰበሰብ የነበረ መሆኑ የሚያሳስብ ነው ፡፡
የተቀደሱ ነገሮች
ይህ በቤተመቅደሱ ውስጥ ለአምልኮ የሚውሉትን ዕቃዎች ያመለክታል ፡፡
ለባኣሊም
“ሰዎች ለበኣሊም ጣዖታት አምልኮ እንዲገለገሉበት”
2 Chronicles 24:8
ሳጥን
አንድ ትልቅ የእንጨት ሳጥን
አወጁ
“እነርሱ አወጁ” ወይም “እነርሱ አስታወቁ”
ሁሉም መሪዎች እና ህዝብ ሁሉ
ይህ ጠቅለል ያለ ገለጻ ነው ፡፡ ምናልባት አንዳንድ ሰዎች በዚህ መንገድ ምላሽ አልሰጡ ይሆናል ፡፡ (ግነትን እና አጠቃላይን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 24:11
እንዲሁም በየቀኑ ያደርጉ ነበር
ይህ ሐረግ አዲስ ፣ ተደጋጋሚ ድርጊትን ያስተዋውቃል ፡፡ ቋንቋህ ይህንን የሚያመለክትበት መንገድ ካለው ፣ እዚህ ልትጠቀምበት ትችላለህ ፡፡
ውሰደው እና ወደ ስፍራው መልሰው
“ሳጥኑን ወስደህ ወደ ቦታው መልሰው”
ጠራቢዎች እና አናጢዎች
“የድንጋይ ሠራተኞች እና የእንጨት ሠራተኞች”
የብረት እና የናስ ሠራተኞች
“ከብረት እና ከናስ እቃዎችን የሚሠሩ ሰዎች”
2 Chronicles 24:13
በእጃቸው ወደፊት እየተጠገነ ሄደ
እዚህ ላይ “ወደፊት” የሚለው ቃል መሻሻልን ይወክላል ፣ “እጆች” የሚለው ቃል የእነርሱን ቁጥጥር ይወክላል ፡፡ ኣት: - “በእነሱ ቁጥጥር ስር ተሻሻለ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
የተቀረው ገንዘብ
ይህ ሳጥኑ ውስጥ የተሰበሰበ ገንዘብ ነው ግን ለጥገናው የማይፈለግ ነው።
የቤት ዕቃዎች
ይህ ቀጥሎ ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የተዘረዘሩትን “መገልገያዎች” እና “ማንኪያዎችን” ያመለክታል ፡፡
በዮዳሄም ዘመን ሁሉ
ይህ ፈሊጥ የዮዳሄን ዕድሜ ያመለክታል ፡፡ ኣት: - “ዮዳሄ በሕይወት እስካለ ድረስ” ወይም “በዮዳሄ ዕድሜ ዘመን ሁሉ” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 24:15
አርጅቶ ዕድሜም ጠግቦ ነበር
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን ለምን ያህል ጊዜ እንደኖረ አፅንዖት ይሰጣል ፡፡ ኣት: “በጣም አረጀ” ( ድግግሞሽን :ይመልከቱ)
ዕድሜ ጠገበ
ይህ ፈሊጥ ረጅም ዕድሜ እንደኖረ ያሚያመለክት ነው ፡፡ ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
ዕድሜው 130 ዓመት
“ዕድሜው አንድ መቶ ሠላሳ ዓመት” ( ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
በነገሥታቱ መካከል
“በነገሥታቱ መቃብር” ወይም “በነገሥታቱ መቃብር መካከል”
ከእስራኤልም ጋር ፣ ከእግዚአብሔርና ከቤቱም ጋር ቸርነትን ሠርቶአልና
“ጥሩ” የሚለው ስያሜያዊ መግለጫ እንደ ቅፅል ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ለእግዚአብሔር እና ለእግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ በይሁዳ መልካም ነገሮችን ስላደረገ” ( ስማዊ ቅጽልን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 24:17
ለንጉሡ እጅ ነሱ
“ለንጉሥ ኢዮአስ አከበሩ” ወይም “ንጉሡን አከበሩ”
የዚያን ጊዜም ንጉሡ ሰማቸው
የሚቀጥለው ጥቅስ ንጉሡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ጣዖታትን እንዲያገለግል እንደሚፈልጉ ያሳያል ፣ እርሱም ተስማማ ፡፡ ኣት: - “ንጉሡም የፈለጉትን እንዲያደርግ ኦገባቡት” (የሚጠበቅ እውትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ቁጣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ሆነ
የእግዚአብሔር ቁጣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ እንደሸፈነ ነገር ተደርጎ ተገልጻል ፡፡ እዚህ ላይ “ይሁዳ” እና “ኢየሩሳሌም” የሚሉት ቃላት በዚያ ለሚኖሩት ሰዎች ተኪ መግለጫዎች ናቸው ፡፡ ኣት: - “እግዚአብሔር በይሁዳና በኢየሩሳሌም ሰዎች ላይ እጅግ ተቆጥቶ ነበር” ( ዘይቤያዊን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
ይህ የእነሱ ኃጢአት
“ኃጢአታቸው”
አሁንም እርሱ ሰደደ
እዚህ ላይ “አሁንም” የሚለው ቃል በእግዚአብሔር ቁጣ እና ንስሐ እንዲገቡ እድል ለመስጠት እና ፍርድን ለማስቀረት ነቢያትን መላኩ መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል።
ወደ ራሱ፣ እግዚአብሔር
የአፀፋው ተውላጠ ስም መመለስ ያለባቸው ወደ እግዚአብሔር እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣል ፡፡ ( የአፀፋ ተውላጠ ስም :ይመልከቱ)
እነርሱ መስማት እምቢ አሉ
“ሕዝቡ ለመታዘዝ እምቢተኛ ሆኑ”
2 Chronicles 24:20
የእግዚአብሔር መንፈስ በዘካርያስ ላይ ወረደ
ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን የእግዚአብሔር መንፈስ በዘካርያስ ውስጥ ተገልጦ ትንቢት እንዲናገር አስችሎታል ማለት ነው ፡፡ በ 2 ኛ ዜና 15 ፡1 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ፡፡ ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
የዮዳሄ ልጅ ዘካርያስ
ይህ የዘካርያስን መጽሐፍ የጻፈው የበራክዩ ልጅ ዘካርያስ አይደለም ፡፡
እንዴትበለጽጉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለምን ትተላለፋላችሁ?
ዘካርያስ ይህንን አወያይ መጠይቅ ህዝቡን ለመገሠጽ ጠይቋል ፡፡ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ፡፡ ኣት: - “ልትበለጽጉ ያልቻላችሁት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እየተላለፋችሁ ፣ ስለሆነ ነው።” ( አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)
የዘካርያስ አባት ዮዳሄ ያደረገለትን ደግነት ቸል አለ
የዘካርያስ አባት ዮዳሄ ለኢዮአስ ያደረገውን ቸርነት አላስተዋለም።
ከአንተ ይፈልገው
ለሠራኸው ጥፋት ይቀጣሃል ”
2 Chronicles 24:23
ይህ ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል መጀመሪያ ለመጠቆም እዚህ ያገለግላል ፡፡ ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ይችላሉ ፡፡
ምርኮውን ሁሉ ከእነርሱ ላከ
“ምርኮውን ሁሉ ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም ላከ”
እጅግ ታላቅ በሆነ ሰራዊት ላይ ድል ተቀዳጅቷል
'እጅግ ብዙ በሆነው በይሁዳ ሠራዊት ላይ ድል ተቀዳጅቷል'
በዚህ መንገድ ሶርያውያን በዮአስ ላይ ፍርድን አመጡበት
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ፍርድ ነው ፡፡ ይህ እንደ ድርጊት ሊገለፅ ይችላል ፡፡ ኣት. “በዚህ መንገድ እግዚአብሔር በኢዮአስ ላይ ለመፍረድ ሶሪያዊያንን ተጠቀመባቸው” (የረቂቅ ስሞችን እና የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን : ይመልከቱ)
2 Chronicles 24:25
ዮአስ እጅግ ቆስሎ ነበር
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ፡፡ ኣት: - “ኢዮአስን እጅግ አቁስለውት ነበር” ( ገቢራዊን እና ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
በዮዳሄ ልጆች ሞት ምክንያት
“የዮዳሄን ልጆች ስለ ገደለ”
አልጋው ላይ ገደሉት
“አገልጋዮቹ ኢዮአስ በአልጋው ላይ ገደሉት”
ዛባድ… ዮዛባት
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ፡፡ (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ )
የአሞናዊቱ ሴት ሰምአት ... ሰማሪት ሞዓባዊት ሴት
“ሳሚት ፣ ከአሞን አገር… ሺምሪ ፣ ከሞዐብ ምድር።” የሁለት ሴቶች ስሞች ነቸው። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
2 Chronicles 24:27
ስለ ወንዶች ልጆች የሚናገረው ዘገባ
“ወንዶች ልጆቹ ስላደረጉት ነገር ተጽፎአል”
ስለ እርሱ የተነገሩ አስፈላጊ ትንቢቶች

“ነቢያት ስለ እርሱ የተናገሩት አስፈላጊ ነገር”
እነሆ እነርሱ ተጽፈዋል
እዚህ “እነሆ” ቀጥሎ ላለው መረጃ ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ አንባቢውን ያነቃል ።
የነገሥታቱ መጽሐፍ ማብራሪያ
ይህ የማይገኝ መጽሐፍ ነው ።

---

Chapter 25
2 Chronicles 25:1
ሀያ - ዓመታት… ሃያ ዘጠኝ ዓመት
“25 ዓመት… 29 ዓመታት” ( ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
የዓዳን
ይህ የሴት ስም ነው። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር
እዚህ “ዐይን” የሚለው ቃል ዕይታን ይወክላል ፣ እና ዕይታ ደግሞ የእግዚአብሔርን ፍርድ ወይም ግምገማ ያመለክታል ። በ 2ኛ ዜና መዋዕል 14:2 ውስጥ ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል እንዲሆን የወሰነው” ( ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)
ነገር ግን በሙሉ ልብ አይደለም
እዚህ ላይ “በሙሉ ልብ” የሚለው ሐረግ “ሙሉ በሙሉ” የሚል ትርጉም አለው ። ኣት: “ነገር ግን ሙሉ በሙሉ አይደለም” ( ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 25:3
እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩ አዲስ ክፍል እንደሚጀምር ለመጠቆም ያገለግላል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።
የሙሴ መጽሐፍ
ይህ የዘፍጥረትን ፣ የዘጸአትን ፣ የዘሌዋውያን ፣ የዘኁልቁን፣ እና የዘዳግምን መጻሕፍት የሚያመለክት ነው ።
2 Chronicles 25:5
ይሁዳን ሰበሰበ
እዚህ ላይ “ይሁዳ” የሚያመለክተው በይሁዳ የኖሩ ሰዎችን ነው ። ኣት: - “የይሁዳን ሕዝብ አንድ ላይ ሰበሰበ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)
መዘገባቸው… ቆጠራቸው
አንድ ሰው ስማቸውን በመዝገብ ላይ እንዲጽፍ አደረገ ።
በአባቶቻቸው ቤቶች
እዚህ “ቤቶች” የሚለው ቃል በውስጣቸው የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚገልጽ ተኪ ስም ነው ። ኣት: - “በአባቶቻቸው ቤተሰቦች” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)
ሻለቆች እና መቶ አለቆች
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እነዚህ ቁጥሮች አለቆቹ የሚመሩትን ወታደሮች ብዛት ያመለክታሉ ። ኣት: - “የ 1000 ወታደሮች አዛዦች እና የ100 ወታደሮች አዛዦች” ወይም 2) “ሺህ” እና “መቶ” ተብለው የተተረጎሙት ቃላት ትክክለኛ ቁጥሮችን አይወክሉም ፣ ግን ትላልቅና ትናንሽ ወታደራዊ ምድቦች ስሞች ናቸው። ኣት: - “የትላልቅ የጦር ምድቦች አዛዦች እና የትናንሽ የጦር ምድቦች አዛዦች ።በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 1፡ 2 የሚገኘውን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ( ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
ይሁዳንና ብንያምን ሁሉ
እዚህ “ይሁዳ” እና “ቢንያም” በሰፊው በይሁዳ መንግሥት ውስጥ የኖሩትን ሰዎች ያመለክታሉ ። ኣት: - “የይሁዳና የብንያም ሕዝብ ሁሉ” ( የባህሪ ስሞችን ፡ ይመልከቱ)
ዕድሜያቸው ሀያ ዓመት እና ከዚያ በላይ
እዚህ ከሃያዎቹ የሚበልጡ ቁጥሮች ከፍ ያሉ እንደሆኑ ይናገራል። ኣት: “ዕድሜው 20 ዓመትና ከዚያ በላይ” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)
አገኛቸው
“መኖራቸውን አወቀ”
300,000… 100,000
“ሦስት መቶ ሺህ… አንድ መቶ ሺህ” ( ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
የተመረጡ ወንዶች
“ብቃት ያላቸው ወታደሮች” ወይም “ችሎታ ያላቸው ጦረኞች”
አንድ መቶ መክሊት ብር
“100 መክሊት ብር።” ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መቀየር ትችላለህ። ኣት: - “ወደ ሦስት ሺ ሦስት መቶ ኪሎ ግራም ብር” ወይም “3,300 ኪሎ ግራም ብር” ( ቁጥሮችን የመጽሐፍ ቅዱስ ክብደቶችን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 25:7
የእግዚአብሔር ሰው
“የእግዚአብሔር ነቢይ”
እስራኤል… የኤፍሬም ህዝብ
እነዚህ ለተመሳሳይ ቡድን የተሰጡ ሁለት ስሞች ናቸው ።
ከጠላትህ ፊት ጣልህ… ጣለህ
እዚህ ስለወታደራዊ ሽንፈት ሲናገር ንጉሡ መሬት ላይ እንደሚወረውር አድርጎ ይናገራል ። ኣት: - “ጠላትህ እንዲያሸንፍህ ያስችለዋል… ሽንፈት” ( ዘይቤያዊን ፡ ይመልከቱ)
2 Chronicles 25:9
አንድ መቶ መክሊት ያህል
“100 መክሊት ብር።” ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መቀየር ትችላለህ። ኣት: - “ወደ ሦስት ሺ ሦስት መቶ ኪሎ ግራም ብር” ወይም “3,300 ኪሎ ግራም ብር” ( መጽኀፍ ቅዱሳዊ ክብደትን ፡ይመልከቱ)
የእስራኤል ሠራዊት … ከኤፍሬም ወደ እርሱ የመጡ ወታደሮች ናቸው
እነዚህ አንዱን ሠራዊት የሚገልጹ ሁለት መንገዶች ናቸው ።
ስለዚህ እጅግ ተቆጡ
እዚህ የቁጣቸው መጨመር በእነርሱ ውስጥ እንደሚነድ እሳት እንደሆነ ተገልጾአል። ኣት: - “ስለዚህ ቁጣቸው በውስጣቸው እንደ እሳት ነደደ” ( ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)
ጽኑ ቁጣ
“በጣም ተቆጡ”
2 Chronicles 25:11
ደፋር ሆነ
“ደፋር ሆነ”
የጨው ሸለቆ
ይህ በሙት ባሕር አቅራቢያ የሚገኝ ቦታ ነው ።
አስር ሺህ ሰዎች… ሌላ አሥር ሺህ
“10,000 ወንዶች… ሌላ 10,000 ወታደሮች” ( ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
ሁሉም ተፈጠፈጡ
ይህ ግነት ሲሆን የግድያውን ትክክለኛነት አፅንዖት የሚሰጥ ነው ። ኣት: - “ሁሉም እንዲጠፉ” ( ግነትን ወይም አጠቃላይን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 25:13
አሜስያስ መልሶ የላካቸው የጦሩ ሰዎች
አሜስያስ ወደ እስራኤል የላከው የእስራኤል ሰራዊት ሰዎች ”
ቤትሖሮን
ይህ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ በኤፍሬም የሚገኝ መንደር ነበር። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
መታቸው
እዚህ “መታቸው” ማለት እነርሱን መግደል ነው ። ኣት: “ተገደለ”( ፈሊጥን ፡ ይመልከቱ)
ሦስት ሺህ ሰዎች
“3,000 ሰዎች”
ብዙ ምርኮ ወሰደ
“እጅግ ብዙ ዋጋ ያላቸውን ነገሮች ወሰደ”
2 Chronicles 25:14
አሁን እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅምር ለመጠቆም እዚህ ያገለገለ ነው ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።
የኤዶማዊያን መግደል
“ኤዶማውያንን መግደል” ወይም “ኤዶማውያንን ማሸነፍ”
የሴይር ሰዎች አማልክት
“የሴይር ሰዎች ያሚያመልኳቸው አማልክት”
ሰገደ… አጠነ
እነዚህ አምልኮን የሚያመለክቱ ተግባራት ናቸው ። ( ምሳሌያዊ ድርጊትን ፡

ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ቁጣ በአሜስያስ ላይ ነደደ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ በሚነድ እሳት ተመስሎ ተገልጾኣል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቁጣ በአሜስያስ ላይ እንደ ሚነድድ እሳት ሆነ” (ዘይቤያዊን ፡ ይመልከቱ)
የገዛ ወገኖቻቸውን እንኳ ከእጅህ ያላዳኑትን የሌሎች ሕዝብ አማልክት ለምን ፈለግህ?
ነቢዩ አሜስያስን ድል ያደረጋቸውን ሕዝብ አቅም አልባ አማልክት ማምለኩን ለመገሠጽ ይህን አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ቃል ኃይል የሚለውን ተክቶ የገባ ቃል ነው ። ጥያቄው እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። አትቲ: - “የራሳቸውን ሕዝብ እንኳ ካንተ ኃይል የማያድኑትን ሕዝብ አማልክትን አመለካቸው።” (አወያይ መጠይቅን እና የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)
የገዛ ወገኖቻቸውን እንኳ የማያድኑ አማልክት...
ይህ ጦርነቶችን የሚያሸንፈውን አማልክት እንደሚወስኑ ማሰብ በዘመኑ የተለመደ አስተሳሰብ እንደነበረ ያሳያል ።
2 Chronicles 25:16
እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ ቀጣዩን አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት ይጠቅማል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።
ለንጉሡ አማካሪ አድርገንሃልን? ተው! መገደልን ለምን ትሻለህ ?
ንጉሡ እርሱን ተቃውሞ ስለተናገረ ነቢዩን ለመገሰጽ እነዚህን አወያይ መጠይቆችን ተጠቅሟል ። ጥያቄዎቹ እንደ መግለጫዎች ሊተረጎሙ ይችላሉ ። ኣት: - “ከአማካሪዎቼ መካከል አንድትሆን አልሾምኩህም። ስለዚህ ማውራት አቁም! ከእንግዲህ አንድ ነገር ብትናገር ወታደሮቼ እንዲገድሉህ እነግራቸዋለሁ! ” ( አወያይ መጠይቅን ፡ይመልከቱ)
ይህን ሥራ አደረግህ
ይህ በ 2 ኛ ዜና 25 ፡14 ውስጥ የኤዶማውያንን አማልክት ያመለኩትን አሜስያስን ይመለከታል ።
2 Chronicles 25:17
ኢዮአስ... ኢዮአካዝ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተረጓጎም፡ይመልከቱ)
ፊት ለፊት ተገናኙ
ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን በመልክተኛ ወይም በሌሎች ሰዎች አማካኝነት ከመግባባት ይልቅ ሁለቱም በአካል በዚያ ተገኝተዋል ማለት ነው ። ኣት: - “በአካል ተነጋገሩ” ( ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 25:18
በሊባኖስ የነበረው ኩርንችት... ኩርንችቱን ረገጠ
ይህ መልእክት ምሳሌያዊ መልክ ያለው ነው ። ከንቱ ኩርንችት አሜስያንን ይወክላል ፣ የሊባኖስ ዝግባው ደግሞ ኢዮስያስን ይወክላል።ኩርንችቱ በአውሬው መረገጡ መጥፎ ነገር እንደሚከሰትበት እና ይህን ለማስቆም ኃይል የሌለው መሆኑን ይገልጻል ። የምሳሌው ነጥብ አሜስያስ ኢዮአስን መገዳደር ሞኝነት መሆኑ ነው ። (ምሳሌን ፡ይመልከቱ)
ኩርንችት
ይህ ትንሽ ፣ ሹል እሾህ ያለው ተራ ተክል ነው።
ዝግባ
በጣም ትልቅ የዛፍ ዓይነት
ልብህ ከፍ ከፍ አደረገህ
ይህ ማለት ኩራተኛ ነው ማለት ነው ። ኣት: - “ኩራተኛ ሆነሃል” ( ፈሊጥን ፡ ይመልከቱ)
አንተ ከይሁዳ ጋር ትወድቅ ዘንድ ስለምን መከራ ትሻለህ?
ኢዮስያስ አሜስያስን ከእርሱ ጋር እንዳይዋጋ ለማስጠንቀቅ ይህን አወያይ መጠይቅ ተጠቅሟል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “አንተ ከይሁዳ ጋር ሁላችሁንም ችግር ላይ መጣል የለብህም።” ( አወያይ መጠይቅን ፡ይመልከቱ)
መውደቅ
እዚህ “መውደቅ” “መሞት” ማለት ነው ።
ይሁዳ
እዚህ ላይ “ይሁዳ” በይሁዳ የሚኖሩትን ህዝብ የተካ ስም ነው ። ኣት: - “የይሁዳ ሰዎች” ( ዘወርዋሪን፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 25:20
ይህ ክስተት ከእግዚአብሔር ነበር
“እግዚአብሔር ይህ ነገር እንዲከሰት ፈቅዷል”
በጠላቶቻቸው እጅ ውስጥ
እዚህ “እጅ” የማሸነፍ ኃይልን ያመለክታል ። ኣት: - “በጠላቶቻቸው እጅ” ወይም “ጠላቶቻቸው ሊያሸንፏቸው ይችላሉ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)
ፊት ለፊት ተገናኙ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ሌሎች ሰዎችን ብቻ ወደ ውጊያው ከመላክ ይልቅ ሁለቱም ግለሰቦች ውጊያው ላይ ተገኝተው ነበር ማለት ነው ። በ 2 ኛ ዜና 25 ፡17 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “በአካል ተገናኙ።” (ፈሊጥን ፡ ይመልከቱ)
የይሁዳ ንብረት የሆነችው ቤትሳሚስ
የቤትሳሚስ ከተማ በይሁዳ ይገኛል።
ይሁዳ በእስራኤል ፊት ተመታ
እዚህ “ይሁዳ” እና “እስራኤል” የይሁዳ እና የእስራኤልን ወታደሮች ለማለት ነው ፣ “ተመቱ” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን “ተሸነፉ” ማለት ነው ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “የእስራኤል ወታደሮች የይሁዳን ወታደሮች አሸነፉ” ( የባህሪ ስምን እና ፈሊጥን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን፡ይመልከቱ)
እያንዳንዱ ሰው
ይህ ከጦርነቱ የተረፉ የይሁዳን ወታደሮች በተመለከተ ጠቅለል ያለ መረጃ ነው ። ኣት: - “የተረፉት የይሁዳ ወታደሮች” ( ግነትን እና አጠቃላይን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 25:23
ርቀቱ አራት መቶ ክንድ ነው
አንድ ክንድ 46 ሴንቲሜትር ነው ። ኣት: - “ርቀቱ 400 ክንድ” ወይም “ርዝመቱ 180 ክ.ሜ የሆነ ” ( ቁጥሮችን እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀትን ፡ይመልከቱ )
ከዖቤድኤዶም ጋር
እዚህ “ዖቤድኤዶም” የሚለው የዚህን ሰው ዝርያ ያመለክታል ። ኣት: - “በዖቤድኤዶም ዘሮች ጥበቃ” ( የባህሪ ስምን እና የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)
የንጉሥ ቤት
“ንጉሣዊው ቤተ መንግሥት”
2 Chronicles 25:25
የቀሩትም ጉዳዮች ... በይሁዳና በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ የተጻፈ አይደለምን?
ይህንን አወያይ መጠይቅ በአሜስያስ ላይ የደረሰው ነገር በደንብ የታወቀ መሆኑን ለአንባቢው ለማስገንዘብ ይጠቅማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “አሜስያስን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ እነሆ ፣ በይሁዳና በእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ ተጽፈዋል።” ( አወያይ መጠይቅን ፡ይመልከቱ)
የፊተኛውና የኋለኛው የአሜስያስ ነገር
እዚህ “የፊተኛውና እና የኋለኛው” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው እነዚያን ጽንፎች እና በመካከላቸው ያሉትን ነገሮች ሁሉ ነው ። ኣት: - “አሜስያስን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ” ( ሜሪዝምን ፡ይመልከቱ)
እነሆ
ይህ አንባቢው ቀጥሎ ለሚነገረው እውነት ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ያነቃል።
የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ
ይህ የማይገኝ መጽሐፍ ነው።
2 Chronicles 25:27
ያህዌን ከመከተል ዞር አለ
እዚህ “ዞር አለ ” ማለት እግዚአብሔርን አልታዘዝም አለ ማለት ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔርን መታዘዝ አቆመ” ወይም “እግዚአብሔርን መታዘዝ ጀመረ” ( ፈሊጥን፡ይመልከቱ)
ሴራ ማሴር ጀመሩ... ላኩ... አመጡ
ጽሑፉ “ማንን” እንደሚያመለክቱ አይገልጽም። ከተቻለ በትርጉምዎ ላይ “እነርሱ” የተባሉትን አነጋገሮች አስታውሱ።
በእሱ ላይ ሴራ ያሴሩ
የቃላት ስሙ “ሴራ” እንደ ድርጊት ሊገለጽ ይችላል ። ኣት: - “በእሱ ላይ አሴሩ” ወይም “በእሱ ላይ አሴሩ” ( የረቂቅ ስሞችን ፡ይመልከቱ)
ለኪሶ
በይሁዳ ያለች ከተማ ( የስሞችን አተረጓጎም፡ይመልከቱ)
መልሰው አመጡት
“አስከሬኑን አመጡ”
የይሁዳ ከተማ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 26
2 Chronicles 26:1
የይሁዳ ሰዎች ሁሉ የአሥራ ስድስት ዓመት ልጅ የነበረውን ዖዝያንን ወስደው በአባቱ በአሜስያስ ፋንታ አነገሡት።
“ሁሉም” የሚለው ቃል ጠቅለል ያለ አገላለጽ ነው ። አንዳንድ ሰዎች እርሱ ንጉሥ እንዲሆን አይፈልጉ ይሆናል ። ኣት: “የይሁዳ ሕዝብ የ 16 ዓመቱን ዖዝያንን ወስዶ በአባቱ በአሜስያስ ፋንታ አነገሡት” ( ግነትን እና አጠቃላይን :ይመልከቱ)
አስራ ስድስት…ሃምሳ ሁለት
“16… 52” ( ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
ኤላትን የሠራው እርሱ ነበር
ዖዝያን ብቻውን አሠራውም። ኣት: - “ኤላት እንደገና እንድትሠራ ያዘዘው እርሱ ነበር” ወይም “ኤላት እንደገና የተሠራው በእርሱ ቁጥጥር ነበር” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)
ኤላት
በይሁዳ ያለች ከተማ ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
ወደ ይሁዳ መለሳት
ወደ ይሁዳ መለሰው። ”ይህ ማለት የእርሱ ሠራዊት ከተማዋን ስለተቆጣጠረ እንደገና የይሁዳ ሆነች ።
ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ መሞቱ የሚነገርበት መንገድ ነው ። ( ዘወርዋራ አነጋገርን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 26:4
በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር አደረገ
ዐይን ማየትን ይወክላል ፣ ማየት ደግሞ አመለካከትን ወይም ፍርድን ይወክላል። በ 2 ኛ ዜና 14፡ 2 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል ነው ብሎ የሚወስነው” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል ነው የሚለው” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
በሁሉ የአባቱን የአሜስያስን ምሳሌ መከተል
ይህ የሚያመለክተው አባቱ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር እንዳደረገ ነው ። ኣት: “አባቱ አሜስያስ እንዳደረገው” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)
በሁሉም ነገር
ይህ ግርድፍ ነው ። ኣት: - “በተመሳሳይ መንገድ” ( ግነትን እና አጠቃላይን :ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን ለመፈለግ ራሱን አዘጋጀ
እዚህ“ራሱን አዘጋጀ” አንድ ነገር ለማድረግ ቁርጥ ውሳኔ መወሰንን የሚያመለክት ነው ። እግዚአብሔርን መፈለግ እርሱን ለማወቅ ፣ ለማምለክ እና ለመታዘዝን መምረጥን ያመለክታል ። ኣት: - “እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ቆርጦ ነበር” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
በዘካርያስ ዘመን
እዚህ ላይ “የዘካርያስ ቀናት” ዘካርያስ ካህን የነበረበትን ዘመን የሚያመለክት አገላለጽ ነው ። ኣት: - “ዘካርያስ ካህን በነበረ ጊዜ” ( ዘይቤያዊን:ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን ይፈልግ በነበረ ጊዜ
“እግዚአብሔርን በፈለገበት ጊዜ ሁሉ”
እግዚአብሔርን ፈለገ
እግዚአብሔርን መፈለግ እርሱን ለማወቅ ፣ ለማምለክ እና ለመታዘዝ መምረጥን ያመለክታል ። ኣት: - “እግዚአብሔርን መታዘዝ መረጠ” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 26:6
ዖዝያን ወጥቶ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተዋጋ
እዚህ ላይ “ዖዝያን” እራሱን እና የመረጠውን ሠራዊት ይወክላል ። ኣት: - “ዖዝያን ሠራዊቱን እየመራ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሊዋጋ ወጣ” ወይም “ዖዝያንና ሠራዊቱ ወጥተው ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተዋጉ” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል :ይመልከቱ)
አፈረሰ… ከተሞችን ሠራ… እግዚአብሔር ረዳው
እዚህ “እርሱ” እና “እርሱን” የሚሉት ተውላጠ ስሞች ዖዝያንንና ሠራዊቱን ይወክላሉ። ኣት: “ዖዝያንና ሠራዊቱ አፈረሱ… ከተሞችን ገነቡ… እግዚአብሔርም ረዳቸው” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)
የበናን
ይህ በሰሜናዊቷ ይሁዳ የነበረ ከተማ ነው። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
የአሽዶድ አገር
“በአሽዶድ ዙሪያ ያለች አገር” ወይም “በአሽዶድ አቅራቢያ”
ጉርበኣል
ይህ በአረባዊያን ምድር የሚገኝ ከተማ ነበር ። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
በምዑናውያን
ይህ በሴይር አቅራቢያ ካለው ከማኦን መንግሥት ወደዚያ አካባቢ የተጓዙት ሰዎች ሳይሆኑ አይቀሩም ። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
እስከ ግብጽ መግቢያ ደረሰ ዝናው ተዛመተ
የእርሱ ዝና መስፋፋት በተለያዩ ቦታዎች ስለ እርሱ ማወቃቸውን የሚያመለክት ነው ። ኣት: ““ እስከ ግብፅ ዳርቻ ድረስ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች እሱ ስለሚያደርገው ነገር አወቁ ”
2 Chronicles 26:9
ዖዝያን ማማዎቹን ሠሩ
እዚህ “ዖዝያን” ማማዎቹን እንዲሠሩ ያዘዛቸውን ሠራተኞች ይወክላል ። ኣት: - “ዖዝያን ሠራተኞቹ ማማዎቹን እንዲሠሩ አደረገ” ወይም “የዖዝያን ሠራተኞች ማማዎቹን ሠሩ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
እርሱ ማማዎቹን ሠራ… ብዙ ጉድጓዶችን ቆፈረ
ዖዝያን ሠራተኞቹን አዞ ፤ እነርሱም እንዲህ አደረጉ። ኣት: - “ሠራተኞቹ ማማዎቹን እንዲገነቡ አደረገ… ብዙ ጉድጓዶችን እንዲቆፍሩ” ወይም “መጠበቂያ ማማዎችን ሠሩ… ብዙ ጉድጓዶችንም ቆፈሩ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
ብዙ ከብቶች ነበሩት… ገበሬዎች ነበሩት… እርሻን ይወድ ነበር
“እርሱ” የሚለው ቃል ዖዝያንን ያመለክታል ።
2 Chronicles 26:11
ይዒኤል… መዕሤያ ፣ አለቃው… ሐናንያ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
ኃያላኑ መሪዎች የነገድ አለቆች መሪዎችን
“ኃያላኑን የመሩት የቤተሰብ መሪዎች”
2,600… 307,500
“ሁለት ሺህ ስድስት መቶ… ሦስት መቶ ሰባት ሺህ አምስት መቶ” ( ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
በእነርሱ ሥር ሠራዊት ነበር
እዚህ “እጃቸው” ሥልጣናቸውን ይወክላል። ኣት: - “በእነርሱ ሥር ሠራዊት ነበር” ወይም “ሠራዊትን ያዙ ነበር” (የባህሪ ስምን:ይመልከቱ)
2 Chronicles 26:14
ዖዝያን አዘጋጀላቸው
'ዖዝያን ምግብ ሰጣቸው'
የራስ ቁር
የራስ ቁር የራስ መከላከያ ሽፋን ነው ።
ጥሩር
ይህ ከብረት ሰንሰለቶች የተሠራ የአካል መሸፈኛ ነው ።
በብልሃተኞች እጅ የተነደፉ ማሽኖችን ሠራ
እዚህ “ማሽኖችን ሠራ” የሚለው ዖዝያን ሠራተኞቹ እንዲገነቡ ያዘዘውን ይወክላል ። ኣት: - “ሠራተኞቹ በሰለጠኑ ሰዎች የተነደፉ ማሽኖችን ሠሩ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
ቅጥር
የከተማው ግድግዳዎች ማዕዘናት ሲሆኑ ወታደሮቹ ለውጊያ የሚመሽጉባቸው ቦታዎች ናቸው።
እርሱ በጣም ተበረታቶ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር እጅግ ረድቶታል” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 26:16
ልቡ ከፍ ከፍ አለ
እዚህ ልብ ከፍ ከፍ ማለት ኩራትን ያመለክታል ። ኣት: - “ኩራተኛ ሆነ”( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ከእርሱም ጋር ጽኑዓን የነበሩ ሰማንያ የእግዚአብሔር ካህናት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከቀዳሚው ሐረግ "ገቡ" የሚለው ግስ ተወስዷል ። ኣት: “ከእርሱ ጋር ጽኑዓን የሆኑ ሰማንያ የእግዚአብሔር ካህናት” ወይም “ደፋር ሰዎች የነበሩት ስምንት የእግዚአብሔር ካህናት ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ” ( የቃላት ግድፈትን :ይመልከቱ)
ዖዝያን ሆይ ፣ ዕጣን ለእግዚአብሔር ታጥን ዘንድ ለአንተ አይገባም
“ዖዝያን ሆይ ዕጣን ማጨስ ለአንተ አይደለም” ወይም “ዖዝያን ሆይ ፣ ለእግዚአብሔር ዕጣን የማጠን መብት የለህም”
የአሮን ልጆች
እዚህ “ወንዶች ልጆች” ዘሮችን ይወክላሉ ። ኣት: - “የአሮን ዘሮች” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
ዕጣን ለማጠን የተቀደሱ ናቸው
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር ዕጣን ያጨስ ዘንድ የቀደሰው” ወይም “እግዚአብሔር ዕጣን ያጥን ዘንድ የመረጠው”
2 Chronicles 26:19
ጥና
ይህ ዕጣን ለማቃጠል የሚያገለግል ልዩ ድስት ወይም ጎድጓዳ ሳህን ነው።
እነሆ ፣ ለምጻም ሆነ
እዚህ “እነሆ” የሚለው ቃል ካህናቱ ባዩት ነገር ተደንቀው እንደነበር ያሳያል ።
እነሱ በፍጥነት ከዚያ አባረሩት
“በፍጥነት ከዚያ እንዲወጠ አስገደዱት” ወይም “በፍጥነት አባረሩት”
እግዚአብሔር ቀሰፈው
ይህ እግዚአብሔር በሽተኛ እንዳደረገው ሲናገር ልክ እግዚአብሔር እንደመታው በማስመሰል ተናግሯል ። ኣት: “እግዚአብሔር በሽተኛ አደረገው” ( ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)
2 Chronicles 26:21
እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ
“እስከሞተበት ጊዜ ድረስ” ወይም “በቀሪው የሕይወት ዘመኑ ሁሉ”
በተለየ ቤት ውስጥ ኖረ
ይህ የሚያመለክተው ከሌሎች ቤቶችና ከሌሎች ሰዎች ርቆ መኖሩን ነው ።
ከእግዚአብሔር ቤት ተቆረጠ
እዚህ ከእግዚአብሔር ቤት “ተቆርጠ” ከቤተመቅደስ መነጠልን ይወክላል። ኣት: - “ከእግዚአብሔር ቤት ተገለለ” ወይም “ወደ ቤተመቅደስ እንዲሄድ አልተፈቀደለትም” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ልጁ ኢዮዓታም በንጉሡ ቤት ላይ ተሹሞ ነበር
እዚህ ላይ ከአንድ ነገር በላይ መሆን ለእሱ ኃላፊነት ወይም ስልጣን እንዳለው ያሳያል። ኣት: - “ልጁ ኢዮአታም ለንጉ king ቤት ሀላፊ ነበር” ወይም “ልጁ ኢዮአታም በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ሹም ነበር” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
የንጉሡ ቤት
ይህ የንጉሡ ቤተ መንግስት የነበረውን ያመለክታል ።
2 Chronicles 26:22
ከመጀመሪያው እንስቶ እስከ መጨረሻው ዖዝያንን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች በአሞጽ ልጅ በነቢዩ ኢሳይያስ ተጽፈዋል።
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “የዖዝያንን ሌሎች ጉዳዮች ከቀድሞው እስከ መጨረሻው ድረስ ፣ የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ መዝግቧቸዋል” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው
( ሜሪዝምን :ይመልከቱ)
አሞጽ
ይህ የሰው ስም ነው ። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
ዖዝያንም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ መሞቱ የተነገረበት ጨዋነት ያለው መንገድ ነው ። ኣት-“እንዲሁ ዖዝያን ሞተ” ( ዘወርዋራን :ይመልከቱ)
ከአባቶቹ ጋር ቀበሩት
“ሰዎቹ በአባቶቹ አቅራቢያ ቀበሩት” ወይም “አባቶቹ በተቀበሩበት ቀበሩት ።”
በእርሱም ፋንታ ልጁ ኢዮአታም ነገሠ
“ልጁ ኢዮአታም ከዖዝያን በኋላ ነገሠ”

---

Chapter 27
2 Chronicles 27:1
ዕድሜ ሃያ-አምስት ... አሥራ ስድስት ዓመት
“ዕድሜው 25 ዓመት ... የ 16 ዓመት” ( ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
ኢየሩሳ
ይህ የሴት ስም ነው ። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
በእግዚአብሔርም ፊት ቅን ነገር አደረገ
እዚህ ያሉት ዓይኖች ማየትን ይወክላሉ ፣ ማየት ደግሞ ፍርድን ይወክላል ። እግዚአብሔር የኢዮአታም ድርጊቶችን አይቶ አጸደቀ። ይህንን በ 2ኛ ዜና 14 :2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል ነው ያለውን ነገር አደረገ” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል እንደሆነ የቆጠረውን ያደርግ ነበር” ( ዘይቤያዊን:ይመልከቱ)
በሁሉም ነገር
“እርሱ በሠራው ሁሉ”
2 Chronicles 27:3
የላይኛውን በር ሠራ... ብዙ ሠራ ፣... ከተሞችን ሠራ... ግንቦችንና ማማዎችን ሠራ
ኢዮአታም በነገሠ ጊዜ ሠራተኞቹ እነዚህን ነገሮች እንዲሠሩ አድርጎ ይሆናል። ኣት: “ሠራተኞቹ የላይኛውን በር እንዲሠሩ... ሠራተኞቹ ብዙ ነገሮችን እንዲሠሩ ፣ ሰራተኞቹ ከተማዎችን እንዲገነቡ ፣ ሰራተኞቻቸው ግንቦችንና ማማዎችን እንዲገነቡ አድርጓቸዋል” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
የዖፌል ኮረብታ
ይህ በኢየሩሳሌም የሚገኝ ኮረብታ ነው። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
2 Chronicles 27:5
እንዲሁም ከአሞን ህዝብ ንጉሥ ጋር ተዋጋ
ኢዮአታም ሠራዊቱን ወደ ውጊያ እንደመራ አንባቢው እንዲረዳው አድርጎ መተርጎም ሊኖርብህ ይችላል ። ኣት: “እርሱ ሠራዊቱን ከአሞን ሕዝብ ንጉሥ ጋር እንዲዋጋ መራ” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)
ከአሞን ህዝብ ንጉሥ ጋር
የአሞን ንጉሥ ሰራዊቱን ወደ ጌት እንደመራ አንባቢው እንዲረዳው መተርጎም የኖርብህ ይሆናል። ኣት: - “ከአሞን ንጉሥና ከሠራዊቱ ጋር” ( ሁሉን በአንሱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)
አንድ መቶ መክሊት ብር
ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መለወጥ ትችላለህ። “መክሊት” ከ 33 ኪሎግራም ጋር እኩል ነው ። ኣት: - “100 መክሊት ብር” ወይም “3,300 ኪሎ ግራም ብር” ( መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክብደትን እና ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
አሥር ሺህ መስፈሪያ ስንዴ
ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መለወጥ ትችላለህ። እዚህ “መስፈሪያ” ተብሎ የተተረጎመው ቃል “ኮር” ሲሆን እና ከ 220 ሊትር ጋር እኩል ነው ። ኣት: - “10,000 መስፈሪያ ስንዴ ” ወይም “2,200 ኪሎ ግራም ስንዴ” ( የመጽሐፍ ቅዱስ ይዘትን እና ቁጥሮችን:ይመልከቱ)
አሥር ሺህ መስፈሪያ ገብስ
ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት መለወጥ ትችላለህ ። እዚህ “መስፈሪያ” ተብሎ የተተረጎመው ቃል “ኮር” ሲሆን ከ 220 ሊትር ጋር እኩል ነው ። ኣት: - “10,000 መስፈሪያ ገብስ” ወይም “2,200 ኪሎ ሊትር ገብስ” ( መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘትን እና ቁጥሮችን:ይመልከቱ)
በሁለተኛው እና በሦስተኛው ዓመት ውስጥ
“እነርሱን ባሸነፈ በሁለተኛውና በሦስተኛው ዓመት”
2 Chronicles 27:8
ዕድሜው ሃያ-አመት ... አሥራ ስድስት ዓመት
“ዕድሜው 25 ዓመት... የ 16 ዓመት” ( ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
ኢዮአታም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
የኢዮአታም ሞት እንቅልፍ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። ኣት: - “ኢዮአታም ሞተ” ( ዘይቤያዊን እና ዘወርዋራን :ይመልከቱ)
ቀበሩት
“ሰዎች ቀበሩት”
በእርሱ ምትክ ነገሠ
“በእርሱ ምትክ” የሚለው ሐረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው ፣ “በእርሱ ፋንታ” የሚል ትርጉም አለው። ኣት: “በኢዮአታም ፋንታ ነገሠ” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 28
2 Chronicles 28:1
ዕድሜ ሃያ ዓመት… አሥራ ስድስት ዓመት
“ዕድሜ 20 ዓመት… 16 ዓመት” ( ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር አደረገ
እዚህ ዓይኖች ማየትን ይወክላሉ ፣ እና ማየት ደግሞ ፍርድን ይወክላል ። እግዚአብሔር የአካዝን ሥራ አየ ፣ አልተቀበለውምም ። ይህንን በ 2ኛ ዜና 14 :2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል እንደ ሆነ የወሰነው” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል እንደሆነ የቆጠረው” ( ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)
በእስራኤል ነገሥታት መንገድ ሄደ
መሄድ ባህሪን እና ድርጊትን ይወክላል። ኣት: - “የእስራኤል ነገሥታት እንዳደረጉት ሁሉ እርሱ አደረገ ” ወይም “የእስራኤል ነገሥታት እንዳደረጉት እርሱ አደረገ” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 28:3
የቤን ሄኖም ሸለቆ
ይህ በኢየሩሳሌም ያለ ሸለቆ ነው። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
በእስራኤል ልጆች ፊት
እስራኤላውያን ወደ ምድሩ ሲገቡ የተሰደዱት የነዚያ አገራት ሕዝቦች ። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልፅ ሊደረግ ይችላል ። ኣት: - “ከእስራኤል ሕዝብ ቀድመው ወደ ምድሪቱ የገቡት” ወይም “የእስራኤል ሰዎች ወደ ምድሩ ሲጓዙ” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)
በኮረብቶች ላይ ባሉት መስገጃዎች ፣ በኮረብቶች ላይና በእያንዳንዱ አረንጓዴ ዛፍ ሥር
እነዚህ የሌሎች አገራት ሕዝቦች የሐሰት አማልክቶቻቸውን ያመለኩባቸው ቦታዎች ናቸው።
በእያንዳንዱ አረንጓዴ ዛፍ ሥር
እግዚአብሔር ህዝቡ በኢየሩሳሌም ቅዱስ መስዋዕትን እንዲያቀርቡ ይፈልግ ነበር ። እዚህ “እያንዳንዱ” የሚለው ቃል ግነት ሲሆን ንጉሥ አካዝ በምትኩ በሌሎች ቦታዎች መስዋዕቶችን በማቅረብ እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ ምን ያህል ቆርጦ እንደነበረ የሚያሳይ ነው ። ኣት: - “በብዙ አረንጓዴ ዛፎች ዙሪያ ” ወይም “በአገሪቱ ባሉ ብዙ አረንጓዴ ዛፎች ሥር” ( ግነትን እና አጠቃላይን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 28:5
የአካዝ አምላክ እግዚአብሔር በሶሪያ ንጉሥ እጅ አሳልፎ ሰጠው
እዚህ “እጅ” የሚለው ዘይቤ ኃይልን ይወክላል። የሶርያ ንጉሥ ሠራዊት አካዝንና ሠራዊቱን እንዲያሸንፉ እግዚአብሔር አካዝን በሶርያ ንጉሥ እጅ እንዳስገባው ተደርጎ ተገልጾአል ። ኣት: - “የአካዝ አምላክ እግዚአብሔር የአራም ንጉሥ አካዝን እንዲያሸንፍ አስቻለው” ( የባህሪ ስምን እና ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ከእርሱ ወሰዱ
እዚህ ላይ “እርሱ” የአካንን ሰራዊት ይወክላል ። ኣት: - “ከአካዝ ሰራዊት ተወሰደ ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
አካዝ እርሱን ድል ባደረገው በእስራኤል ንጉሥ እጅ ታልፎ ተሰጠ
እዚህ “እጅ” የሚለው ዘይቤ ኃይልን ይወክላል። እግዚአብሔር የእስራኤል ንጉሥ እና ሠራዊት አካዝንና ሠራዊቱን እንዲያሸንፍ ስለማስቻሉ እግዚአብሔር አካዝን በእስራኤል ንጉሥ እጅ እንዳስቀመጠው ተደርጎ ተገልጾአል ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “እግዚአብሔርም የእስራኤል ንጉሥ አካዝን እንዲያሸንፍ አስችሎታል” (የባህሪ ስምን፣ ዘይቤያዊን፣ ገቢራዊን እና ተብሮኣዊን : ይመልከቱ)
የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ
ይህ የእስራኤል ንጉሥ ነበር ። ሁለቱም ‹ፋቁሔ› እና ‹‹ ‹‹ ‹› ›ሮሜልዩ› የሰዎች ስሞች ናቸው ። (የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
120,000 ወታደሮች
“አንድ መቶ ሀያ ሺህ ወታደሮች” ( ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
ዝክሪ… መዕሤያን… ዓዝሪቃም … ሕልቃና
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
ኃያል ሰው
ይህ ጀግናን የሚያመላክት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው ። ኣት: - “ኃያል ተዋጊ” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
ከንጉሡ ቀጥሎ የነበረው
ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ይህ ሰው የንጉሡ ረዳት ነበር ማለት ሲሆን ከንጉሱ ቀጥሎ ስልጣን ያለው ሰው ነው። ኣት: - “በማዕረግ ከንጉሡ ቀጥሎ ነበር” ( ፈሊጥን: ይመልከቱ)
የእስራኤል ጦር ከዘመዶቻቸው ምርኮኛ ወሰደ
“ከወገኖቻቸውም መካከል የእስራኤል ሠራዊት ምርኮኛ ወስደዋል።” “የእነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ሠራዊት ነው ። ተራኪው የይሁዳ ህዝብ የእስራኤል ሰዎች ዘመዶች እንደሆኑ ይናገራል ።
200,000 ሚስቶች ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆች
“ሁለት መቶ ሺህ ሚስቶች ወንዶችና ሴቶች ልጆች” ( ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 28:9
ዖዴድ
ይህ የሰው ስም ነው ። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
በእጃችሁ አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ “እጅ” የሚለው ቃል ኃይልን ይወክላል ። የእስራኤልን ሠራዊት የይሁዳን ሠራዊት ድል እንዲያደርግ እግዚአብሔር ስለማስቻሉ እግዚአብሔር የይሁዳን ሠራዊት በእስራኤል ሰራዊት እጅ እንዳስገኘ ተደርጎ ተገልጻል ። ኣት: - “እግዚአብሔር እንድታሸንፋቸው አስቻለህ” ( የባህሪ ስምን እና ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)
ወደ ሰማይ በሚደርስ ቁጣ ገደላችኋቸው።
የእስራኤል ሠራዊት የይሁዳን ሠራዊት የገደለበት ቁጣ እጅግ ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ እስከ ሰማይ ድረስ ደርሷል ሲል ዖዴድ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል ። ያደረጉትን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚያውቅ ያውቃል እርሱም ምላሽ ይሰጣል ማለት ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔር ራሱ አይቶ ይበቀላችሁ ዘንድ በታላቅ ቁጣ ገደላችኋቸው” ( ዘይቤያዊን እና የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን : ይመልከቱ)
ነገር ግን አምላካችሁን እግዚአብሔርን የበደላችሁት በደል በእናንተ ዘንድ የለምን?
ዖዴድ የእስራኤልን ሰራዊት ለመገሠጽ እና ጥያቄው የሚጠብቀውን አዎንታዊ መልስ ለማጉላት ይህንን አወያይ መጠይቅ ይጠይቃል ። ኣት: - “ነገር ግን እናንተ ራሳችሁ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ላይ በሠራችሁት ኃጢአት ጥፋተኞች ናችሁ።” ( አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ቁጣ በእናንተ ላይ ነድዶአል
ዖዴድ ስለእግዚአብሔር ከባድ ቁጣ ሲናገር ቁጣው ልክ እንደ አንድ ቁስ በላያቸው ላይ እንደ ሆነ አስመስሎ ተናግሯል። ኣት: - “በአንተ ላይ እግዚአብሔር እጅግ ተቆጥቷል” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 28:12
፤ የዮሐናን ልጅ ዓዛርያስ ፣ የምሺሌሞት ልጅ በራክያ ፤ የሰሎምም ልጅ ይሒዝቅያ እና የሓድላይ ልጅ ዓሜሳይ።
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
ከጦርነት በተመለሱት ላይ ተነሱባቸው
“ተነሱባቸው” የሚለው ሐረግ መቃወምን ወይም ፊት ለፊት መጋፈጥን የሚገልጽ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “ከጦርነት የተመለሱትን መጋፈጥ” ወይም “ከጦርነት የተመለሱትን መቃወም” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
ኃጢአት በእኛ ላይ የሚያመጣ ነገር ነው
መሪዎቹ እነርሱን ጭምር ጥፋተኛ እና ኃጢአተኛ የሚያደርጋቸውን ተግባር ስለመፈጸማቸው ሲናገሩ ኃጢአት እንደ አንድ ቁስ በላያቸው ላይ እንደሚመጣ ይናገራሉ ። ኣት: - “ኃጢአተኛ እና በደለኛ የሚያደርገን ነገር ” ተመልከት ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
በእስራኤል ላይ አስፈሪ ቁጣ ሆነ
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር አስፈሪ ቁጣ በእስራኤል ላይ መሆኑን ነው ። “አስፈሪ ቁጣ ” የሚሉት ቃላት በቃል ሐረግ ሊተረጎሙ ይችላሉ ። ኣት: - “እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ላይ እጅግ ተቆጣ” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 28:14
በስም የተመደቡት ወንዶች
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “መሪዎቹ በስማቸው የመደቧቸውን ሰዎች” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮኣዊን :ይመልከቱ)
ጫማ
ይህ የጫማ አይነት ነው ።
ደካማዎችን በአህዮች ላይ አስቀመጧቸው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“መራመድ የማይችሉትን በጣም ደካማ የነበሩትን በአህዮች ላይ ተቀምጠው እንዲጓዙ አደረጓቸው”
2 Chronicles 28:16
እነርሱ ቤትሳሚስንና ወሰዱ
ከተማን መውሰድ የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ማለት ከተማዋን ማሸነፍ ወይም መያዝ ማለት ነው ። ኣት: - “ፍልስጥኤማውያን የቤትሳሚስን ያዙ” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
ቤትሳሚስ ፣ ኤሎንን ፣ ግዴሮትን ፣ ሦኮን… ተምናን… ጊምዞን
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
2 Chronicles 28:19
በአካዝ ምክንያት እግዚአብሔር ይሁዳን አዋረደ
“ይሁዳ” የሚለው አገላለጽ የይሁዳን ሕዝብ ይወክላል ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ማዋረዱ በሆነ መንገድ ይሁዳን በአካል ወደ ታች ዝቅ እንዳደረገ ተደርጎ ተገልጻል ። ኣት: “እግዚአብሔር በአካዝ ምክንያት የይሁዳን ሕዝብ አዋረደ” (የባህሪ ስምን እና ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን እጅግ ሰርቶአልና
አካዝ እጅግ ኃጢአትን ስለማድረጉ ሲነገር ኃጢአት በጣም ከባድ ቁስ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጻል ። ኣት: - “በእግዚአብሔር ላይ ብዙ ኃጢአትን አደረገ” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ቴልጌልቴልፌልሶር
ይህ ቴልጌልቴልፌልሶር 3ኛ ሲሆን ፣ ደግሞ ፑል በመባል ይታወቃል። (ተመልከት/ች: የስሞች አተረጓጎም)
እርሱን ከማበረታታት ይልቅ አስጨነቀው
አካዝ ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ ማገዝ አካዝን መበረታታት እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል። ኣት: - “እርሱን ከመርዳት ይልቅ ችግር አመጣበት ( ዘይቤያዊን: ይመልከቱ)
2 Chronicles 28:22
በመከራው ጊዜ
“መከራ ሲደርስበት”
የደማስቆ አማልክት
እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም እንደሚያደርግ ሁሉ፣ ሶርያውያን ደማስቆ የአማልክቶቻቸው መኖሪያ ከተማ እንደ ሆነች ያምናሉ። ኣት: - “ሶርያውያን በደማስቆ ያሚያመልኳቸው አማልክት” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን : ይመልከቱ)
ያሸነፉጽ አማልክት
ይህ የአካዝን ሀሳብ ያሳያል ። ሶርያውያን እርሱ እና ሠራዊቱን ስላሸነፉ አካዝ ሽንፈቱን ሶርያውያን ለሚያመልኳቸው አማልክት ሰጥቷል ። ኣት: “የሶርያ ሠራዊት የሚያመልኳቸው አማልክት እርሱን እንዲያሸንፉ አስችለዋል” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)
እነርሱ ለእርሱና ለእስራኤል ሁሉ ጥፋት ነበሩ
“ጥፋት” የሚለው ቃል በግስ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “እነዚያ አማልክት እርሱንም ሆነ እስራኤልን ሁሉ አወደሙ” (የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)
እስራኤል ሁሉ
እዚህ ላይ “እስራኤል” ደቡባዊውን የይሁዳን መንግሥት ይወክላል ።
2 Chronicles 28:24
የእግዚአብሔር ቤት… የያህዌህ ቤት…
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ… የያህዌህ ቤተ መቅደስ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
በኢየሩሳሌም በእያንዳንዱ ማዕዘን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ማዕዘን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጎዳና ማዕዘኖችን ወይም ጎዳናዎች የሚገናኙባቸውን ቦታዎች ነው ። ኣት: - “በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች ሁሉ ላይ” ወይም 2) የተለያዩ የኢየሩሳሌም አካባቢዎች የከተማዋ ማዕዘኖች እንደሆኑ ተደርገው ተገልጻል ። ኣት: - “በመላው የኢየሩሳሌም ክፍል” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
መሠዊያዎችን ለራሱ ሠራ … መሥዋዕቶችን ያጥን ዘንድ የኮረብታ መስገጃዎችን ሠራ
አካዝ ንጉሥ ስለነበረ ሠራተኞቹ እነዚህን ከፍ ያሉ ስፍራዎች እንዲሠሩ አድርጎ ይሆናል። ኣት: - “ሠራተኞቹ መሠዊያ እንዲሠሩለት አደረገ… ሠራተኞቹ መሥዋዕቶችን ለማቃጠል ኮረብታዎችን እንዲሠሩ አደረጋቸው” ( የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)
2 Chronicles 28:26
የፊተኛውና የኋለኛው መንገዶቹ
የአካዝ ድርጊቶች የተጓዘበት መንገድ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል ። “የፊተኛውና እና የኋለኛው” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው እነዚያን ጽንፎች እና በመካከላቸው ያሉትን ነገሮች ሁሉ ነው። ኣት: - “ከንግሥናው መጀመሪያ አንስቶ እስከ ንግሥናው መጨረሻ ድረስ ያደረገውን ሁሉ” ( ዘይቤያዊን እና ሜሪዝምን:ይመልከቱ)
እነሆ ፣ በመጽሐፉ ተጽፈዋል … እስራኤል
“ማንም ሰው መጽሐፉ ላይ ማየት ይችላል… እስራኤልን እና እዚያ እንደተጻፈ ማየት ይቻላል”
እነርሱ በመጽሐፉ ተጽፈዋል
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “አንድ ሰው በመጽሐፉ ውስጥ ጻፋቸው” ወይም “በመጽሐፉ ውስጥ ስነእርሱ ማንበብ ትችላለህ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ
ይህ ከእንግዲህ የማይገኝ መጽሐፍ ነው።
አካዝ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
የአካዝ መሞት ማንቀላፋት እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል ። ኣት: “አካዝ ሞተ” ( ዘይቤያዊን እና ዘወርዋራን :ይመልከቱ)
ቀበሩት
“ሰዎች ቀበሩት”
በእርሱ ቦታ ነገሠ
“በእርሱ ቦታ” የሚለው ሐረግ ዘይቤያዊ አገላለጽ “በእርሱ ፋንታ” የሚል ትርጉም አለው ። “በአካዝ ፋንታ ነገሠ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

---

Chapter 29
2 Chronicles 29:1
ዕድሜ ሃያ - አምስት ዓመት … ሃያ ዘጠኝ ዓመት
“ዕድሜ 25 ዓመት… 29 ዓመት” ( ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
አቡ
ይህ የሴት ስም ነው። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር አደረገ
እዚህ “ዐይን” የሚለው ቃል ማየትን የሚወክል ሲሆን ማየት ደግሞ ፍርድን ይወክላል ። እግዚአብሔር የሕዝቅያስን ተግባር አየ አጸደቀውም። በ 2 ኛ ዜና 14 :1 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል እንደ ሆነ የወሰነው” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል እንደሆነ ያሰበው” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:3
በመጀመሪያው ወር
ይህ በዕብራይስጥ የቀን አቆጣጠር የመጀመሪያ ወር ነው። እንደ ምዕራባዊያን የቀን አቆጣጠር ወቅቱ የመጋቢት የመጨረሻ ክፍል እና የሚያዚያ የመጀመሪያ ክፍል ነው። ( የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ቤት
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “ያእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
ሕዝቅያስ በሮቹን ከፈታቸው አደሳቸውም
ሕዝቅያስ ንጉሥ ስለነበረ ሠራተኞቹ እነዚህን ነገሮች እንዲሠሩ አድርጎ ይሆናል። ኣት: “ሕዝቅያስ ሠራተኞቹን በሮቹን እንዲከፍቱ እና እንዲጠግኗቸው አዘዘ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
በምሥራቅ በኩል
ይህ የቤተ መቅደሱን ምስራቅ ያመለክታል ። ኣት: - “በቤተ መቅደሱ በስተ ምሥራቅ” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)
ርኩሱን ነገር ሁሉ ከቅዱሱ ቦታ አስወግዱ
“ርኩሰት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ህዝቡ ሌሎች አማልክትን ሲያመልኩ የጠቀሙባቸውን የነበሩትን ነገሮች ነው ። ተራኪው ስለ እነዚህ ነገሮች ሲናገር መቅደሱ ከመቆሸሹ የተነሳ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው ይናገራል። ኣት: - “የተቀደሰውን ሥፍራ የሚያረክሱትን ነገሮችን አስወግዱ” ወይም “የተቀደሰው ስፍራ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያጣ የሚያደርጉትን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነገሮች አስወግዱ” ( ዘይቤያዊን፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:6
በአምላካችን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ነገር
እዚህ “ፊት” የሚለው ቃል ፍርድን ይወክላል ። እግዚአብሔር የአባቶቻቸውን ተግባር አይቷል እናም አልተቀበለውም። ኣት: - “አምላካችን እግዚአብሔር ክፉ እንደሆነ የወሰነው” ወይም “አምላካችን እግዚአብሔር ክፉ እንደሆነ የቆጠረው” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ከሚኖርበት ስፍራ ፊታቸውን አዞሩ፣ ወደ እርሷም ጀርባቸውን አዙረዋል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ። “ፊቶች” እና “ጀርባዎች” የሚሉት ቃላት ፊቶቻቸው ከቤተ መቅደሱ ያርቁ እና ጀርባዎቻቸውን ወደዚያ ያዞሩ የነበሩትን ሰዎች ይወክላሉ ። ኣት: - “እግዚአብሔር ከሚኖርበት ስፍራ መራቅ” ( ምስስልን እና ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ከሚኖርበት ስፍራ ፊታቸውን አዞሩ፣ ወደእርሷም ጀርባቸውን አዞሩ
የሕዝቡ እግዚአብሔርን ማምለክ መተው ከቤተመቅደስ መራቅ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጻል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተዉ እርሱንም ማምለክ አቆመ” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
እግዚአብሔር የሚኖርበት ስፍራ
ይህ ቤተመቅደሱን ያመለክታል ። ኣት: - “እግዚአብሔር የሚኖርበት ቤተ መቅደስ” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:8
የእግዚአብሔርም ቁጣ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ ወደቀ
እዚህ “ይሁዳ እና ኢየሩሳሌም” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በዚያ ለሚኖሩት ሰዎች ነው ። በሕዝቅያስ እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለመቆጣቱ ሲናገር ቁጣው በላያቸው እንደ አንድ ነገር እንደ ወረደ አድርጎ ተናግሯል። ኣት: - “እግዚአብሔር ስለተቆጣ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ይቀጣ ነበር” ( የባህሪ ስምን እና ዘይቤያዊን፡ይመልከቱ)
ለድንጋጤ፣ ለማስፈራሪያ እና ለመዘበቻ
ይህ በቃል ሐረጎች ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ሰዎችን የሚያሳቅቅ እና የሚያስፈራ ፣ እና ሰዎች የሚያፌዙበት ነገር” (የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)
በገዛ ዓይንህ እንደምታይ
“በገዛ ዐይንህ” የሚለው ሐረግ ሰዎች ነጋሪ ሳያስፈልጋቸው ይህንን ለራሳቸው ማየት የሚችሉ መሆኑን ያሳያል ። ኣት: - “ለራስህ እንደምታየው”
አባቶቻችን በሰይፍ ወድቀዋል
“በሰይፍ ወድቋል” የሚለው አገላለጽ በጦርነት ውስጥ መሞት ማለት ነው። “ሠይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን ዋና መሣሪያቸው አድርገው ይጠቀሙባቸው የነበሩትን ወታደሮች ይወክላል ። ኣት: - “አባቶቻችን በጦርነት ሞተዋል” (ፈሊጥን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:10
ይህ በልቤ ውስጥ ነው
እዚህ “ልብ” የሚለው ቃል ሀሳቦችን እና ዝንባሌዎችን ይወክላል ። ሕዝቅያስ ውሳኔ ስለ መወሰን ተናግሯል ያ ነገር በልቡ ውስጥ ያለ ይመስል ነበር። ኣት: - “ዓላማዬ ነው” ወይም “እኔ ወስኛለሁ” ( የባህሪ ስምን እና ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
የቁጣ ጽናት ከእኛ ይርቃል
ሕዝቅያስም እግዚአብሔር ከእንግዲህ ወዲያ እንደማይቆጣቸው ሲናገር የእግዚአብሔር ቁጣ ከእነርሱ ዞር እንደሚመለስ ሰው አስመስሎ ተናግሯል ፣ ‹ከእንግዲህ በእኛ ላይ አይቆጣም› ( ዘይቤያዊን እና ተስብኦትን :ይመልከቱ)
በፊቱ መቆም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በመገኘቱ መቆም” ወይም 2) ይህ ፈሊጥ ሲሆን ፣ ከፍተኛ ስልጣን ያለውን ሰው ማገልገል ማለት ነው። ኣት: - “እርሱን ማገልገል” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:12
አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች ሕዝቅያስ ያዘዘውን ሥራ መሥራት የጀመሩ የሌዋውያንን ስሞች ይዘረዝራሉ ። እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው። ( የስሞችን አተረጓጎም፡ ይመልከቱ)
ሌዋውያኑ ተነሱ
እዚህ “ተነስቷል” የሚለው ቃል ፈሊጥ ሲሆን ሌዋውያን እርምጃ መውሰድ ጀመሩ ማለት ነው ። ኣት: - “ሌዋውያኑ መሥራት ጀመሩ” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:15
የእግዚአብሔርን ቃል በመከተል
ይህ ሐረግ ንጉሡ የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ ተዕዛዝ እንደሰጠ ያሳያል ። ኣት: - “ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ” ወይም “እግዚአብሔር ስለተናገረ”
የእግዚአብሔርን ቤት ያነጻ ዘንድ
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተስማሚ ስለሆን ቦታ በአካል ንፁህ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል ። (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ቤት ... የቤቱ አደባባይ
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ……የቤተ መቅደሱ አደባባይ (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር መቅደስ ያገኙትን እርኩስ ነገር ሁሉ አወጡ
“ርኩስ” የሚለው ቃል ህዝቡ ሌሎች አማልክትን ለማምለክ ይጠቀሟቸው የነበሩትን እቃዎች የመለከታል ። ተራኪው ስለ እነዚህ ሲናገር ቤተመቅደሱን እንዳቆሸሹት እና ለእግዚአብሔር ተገቢ እንዳይሆን እንዳደረጉት ይናገራል ። ኣት: “በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ያገኙትን ርኩስ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ አወጡ” ወይም “ቤተ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ተስማሚ እንዳይሆን ያደረጉትን ነገሮች ሁሉ አወጡ” ( ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)
ቁድሮን ወንዝ
ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ አቅጣጫ የሚፈስ ትንሽ የውሃ አካል ነው። አንዳንድ ጊዜ እንደ ቆሻሻ መጣያ ያገለግላል። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
በመጀመሪያው ወር በመጀመሪያው ቀን
ይህ የዕብራይስጥ የቀን አቆጣጠር የመጀመሪያ ወር ነው። የመጀመሪያው ቀን እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ያወጣበት ቀን ነው። ይህ በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያ ላይ በመጋቢት አጋማሽ አካባቢ ነው። ( የዕብራዊያን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
በዚያም ወር በስምንተኛው ቀን
ይህ በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያዎች ላይ በመጋቢት መጨረሻ አካባቢ ነው። ( የዕብራዊያን ወራትን እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
ወደ እግዚአብሔር ቤት ወለል ደረሱ
“የእግዚአብሔር ቤት ወለል” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው የቤተ መቅደሱን በረንዳ ነው። “ደረሱ” ማለት ይህንን ክፍል ማጽዳት ጀመሩ ማለት ነው ። ኣት: - “የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በረንዳ ማንጻት ጀምረው ነበር” ( የባህሪ ስምን እና ፈሊጥን :ይመልከቱ)
በመጀመሪያው ወር በአሥራ ስድስተኛው ቀን
ይህ በምእራባዊያን የቀን መቁጠሪያዎች ላይ በሚያዝያ ወር መጀመሪያ አካባቢ ነው። ( የዕብራዊያን ወራትን እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:18
የገጹንም ኅብስት
ይህ በመሠዊያው ፊት ለፊት ስለተቀመጡት 12 ዳቦዎች የሚያሳይ ነው ። በ 2 ኛ ዜና 2 :4 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ።
እነሆም ፣ ሆነዋል
ተመልከታቸው። ማየት ትችላለህ እነዚሁና”
2 Chronicles 29:20
የእግዚአብሔር ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:22
በሬዎቹንም አርደው ካህናቱ ደሙን ተቀበሉ
“ካህናቱ ወይፈኖችን አርደው ደሙን ወሰዱ”
እጃቸውን ጫኑባቸው
“ንጉሡና ማኅበሩ ሁሉ እጃቸውን ጫኑባቸው”
የሚቃጠል መሥዋዕት የኃጢአት መሥዋዕት ለእስራኤል ሁሉ እንዲደረግ
ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ካህናቱ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የኃጢአትን መሥዋዕት ለእስራኤል ሁሉ ያድርጉ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:25
የእግዚአብሔር ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
ጸናጽል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከፍተኛ ድምጽ ለመስራት አንድ ላይ የሚመቱ ሁለት ቀጭን እና ክብ የብረት ሳህኖች። በ 2 ኛ ዜና 5 :12 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጉምከው ተመልከት ። ( የማይታወቁትን :ይተርጉሙ)
በዳዊት ትእዛዝ ፣በንጉሡ ባለራእይ እንደ ጋድ፣ በነቢዩ በናታን ትእዛዝ አደራጇ
“ትዕዛዙ” የሚለው ቃል በቃላት ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ዳዊት ፣ የንጉሡ ባለ ራእይና ፣ነብዩ ናታን እንዳዘዙት ሌዋውያንን ማደራጀት” ( የረቂቅ ስሞችን : ይመልከቱ)
ትእዛዙ ከእግዚአብሔር ዘንድ በነቢያቱ አማካኝነት
“ትዕዛዙ” የሚለው ቃል በቃላት ሐረግ ሊተረጎም ይችላል።ኣት: - “እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካኝነት ይህን አእዛዝ ኣዞ ነበርና” ( የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:27
የእግዚአብሔር መዝሙር ደግሞ ተጀመረ
“የእግዚአብሔር መዝሙ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ለእግዚአብሔር መዝሙር የሚዘምሩ ሰዎችን ነው ። ኣት: - “ሕዝቡም ለእግዚአብሔር ያዜሙ ጀመር”
የሚቃጠለው መስዋዕት እስኪፈጸም ድረስ
ይህ በገቢራዊ አረፍተነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ካህናቱ የሚቃጠለውን መስዋዕት እስኪፈጽሙ ድረስ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:29
መባዎቹን በፈጸሙ ጊዜ
“ካህናቱ መባዎቹን ማቅረብ በጨረሱ ጊዜ”
አጎነበሱ ሰገዱም
የአምልኮ ሃሳብ በትርጉሙ ታክሎ ሊቀርብ ይችላል ። ኣት: “በስግደት እግዚአብሔርን አመለኩ” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:31
የምስጋናውን መሥዋዕት
እነዚህ የምስጋና መባዎች ነበሩ ።
የእግዚአብሔር ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
ፈቃደኛ ልብ ያለው
እዚህ “ልብ” የሚለው ቃል ፈቃደኛ የሆነን ሰው ይወክላል ። ኣት: - “ፈቃደኛ የሆኑት” ወይም “የፈለጉት”( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን : ይመልከቱ)
2 Chronicles 29:32
ሰባ ወይፈን አንድ መቶ አውራ በጎች እና ሁለት መቶ ወንድ ጠቦቶች ... ስድስት መቶ በሬዎች ሦስት ሺህ በጎች
“70 ወይፈን ፣ 100 አውራ በጎች ፣ 200 ወንድ የበግ ጠቦቶች… 600 በሬዎችና ፣3000 በጎች” (ተመልከት/ች: ቁጥሮች)
2 Chronicles 29:34
የሚቃጠለውን መባ ሁሉ ለመግፈፍ
“የሚቃጠለውን መስዋዕት ለመግፈፍ”
ስራው እስኪከናወን ድረስ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሥራውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
ካህናቱ ራሳቸውን እስኪቀድሱ ድረስ
ቀደም ብለው የተቀደሱ ካህናት ስለነበሩ ይህ የሚያመለክተው ተጨማሪ ካህናትን ራሳቸውን እንደቀደሱ ። ኣት: - “በርካታ ካህናቱ ራሳቸውን እስኪቀድሱ ደረስ” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)
እራሳቸውን ለመቀደስ የበለጠ ይጠነቀቁ ነበሩ
ራሳቸውን ለመቀደስ ጠንቃቃ ስለነበሩ ይህንን ሥራ የሚሠሩ በቂ ሌዋውያን ነበሩ ። ይህ የሚያመለክተው በቂ ካህናት ያልነበሩት ካህናቱ ራሳቸውን ለመቀደስ ጥንቃቄ ስለማያደርጉ ነበር ።
2 Chronicles 29:35
ከኅብረት መስዋዕት ስብ ጋር ተሠርተው ቀረቡ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ካህናቱ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ከኅብረት መስዋዕት ስብ ጋር አቀረቡ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን፡ ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ተዘጋጀ
ይህ በገቢራዊ አረፈተ ነገር ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: “ሕዝቅያስ የእግዚአብሔርን ቤት አገልግሎት አዘጋጀ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን፡ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” (የባህሪ ስምን፡ይመልከቱ)
በሥርዓት ተዘጋጅቷል
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ተደራጅቶ የተዘጋጀ ነገር ማለት ነው ። እዚህ በቤተመቅደስ ውስጥ እንደገና የሚጀምረውን የክህነት አገልግሎት ያመለክታል ። ኣት: - “ተመልሷል” ወይም “እንደገና ተጀመረ” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
ሥራው በፍጥነት ተሠራ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሕዝቡ በፍጥነት ሥራውን አከናውነዋል” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን፡ይመልከቱ)

## Chapter 30

2 Chronicles 30:1
እስራኤልና ይሁዳ ሁሉ
ይህ በአጠቃላይ የእስራኤልን ህዝብ ይወክላል ። ቀደም ሲል ህዝቡ በእነዚህ ስሞች በተጠሩ ሁለት መንግስታት ተከፍሎ ነበር ።
ኤፍሬምና ምናሴ
ኤፍሬምና ምናሴ በእስራኤል ሰሜናዊ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ሁለት ነገዶች ነበሩ። እዚህ ላይ “ኤፍሬም እና ምናሴ” የሚለው ሐረግ የሰሜናዊው እስራኤል አሥሩ ነገዶች አባላት የሆኑትን ሰዎች ሁሉ ያመለክታል ። ኣት: - “ሰሜናዊ የእስራኤል ነገዶች” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን፡ይመልከቱ)
በሁለተኛው ወር ፋሲካን ለማክበር መወሰኑ
እስራኤላውያን በተለምዶ በዕብራይስጥ የቀን አቆጣጠር በመጀመሪያው ወር ፋሲካን ያከብሩ ነበር ። የመጀመሪያው ወር በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያዎች ላይ የመጋቢት የመጨረሻ ክፍል እና የሚያዚያ ወር የመጀመሪያው ክፍል ነው።
ሁለተኛ ወር
ይህ በዕብራይስጥ የቀን መቁጠሪያ ሁለተኛ ወር ነው። ጊዜው በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያዎች ላይ በሚያዚያ መጨረሻ እና በግንቦት መጀመሪያ መካከል ነው። ( የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 30:4
ይህ ሀሳብ
ይህ ፋሲካን በመጀመሪያው ወር ፋንታ በሁለተኛው ወር ለማክበር የቀረበለትን ሀሳብ ያመለክታል ።
በንጉሡና በጉባኤው ሁሉ ፊት
ዐይን ማየትን የሚወክል ሲሆን ማየት ደግሞ አመለካከትን ወይም ውሳኔን ይወክላል። ኣት: - “በንጉሡና በጉባኤው ሁሉ እይታ” ወይም “ለንጉሡና ለማኅበሩ ሁሉ” ( ዘይቤያዊን፡ይመልከቱ)
ከቤርሳቤህ እስከ ዳን ድረስ
እነዚህ የእስራኤል ደቡባዊ ጫፍ እና ሰሜናዊ ጫፍ ናቸው ። ጸሐፊው በዚህ መንገድ በመጥቀስ እስራኤል ሁሉ የተካተተ መሆኑን ጎላ አድርጎ አመልክቷል ። ኣት: - “በደቡብ በኩል ከቤርሳቤህ አንስቶ እስከ ሰሜን ዳን ድረስ” (ፈሊጥ : ይመልከቱ)
እንደ ተጻፈ
“እንዲያደርጉት ተብሎ እንደተጻፈ።” ብዙ ሕዝብ ሆነው ፋሲካን ማክበር እንዳለባቸው መፃፉን ተጠቁሟል ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሙሴ እንዲጠብቁት እንደጻፈው” ( የሚጠበቅ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ :ይመልከቱ)
2 Chronicles 30:6
መልእክተኞች
መልዕክት የሚያደርሱ ሰዎች
እስራኤል ሁሉ እና ይሁዳ
የይሁዳ ነገድ ከእስራኤል ነገዶች ትልቁ ሲሆን በደቡባዊ የእስራኤል ክፍል ነበር። እዚህ ላይ “እስራኤል እና ይሁዳ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው የደቡብ እስራኤል ነገዶች የነበሩትን ነው ። በ 2 ኛ ዜና 30 :1 ውስጥ እንዴት

እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “የእስራኤል ደቡባዊ ነገዶች” ( ሂንዲዲያስን ፡ ይመልከቱ)
ወደ እግዚአብሔር ተመለስ
እዚህ “ወደ እግዚአብሔር ተመለስ” እንደገና ለእርሱ መገዛትን ይወክላል ። ኣት: - “እንደገና ለእግዚአብሔር ተገዙ” (ዘይቤያዊን:ይመልከቱ)
ወደ ቅሬታችሁ እንዲመለስ
እዚህ “ወደ ቅሬታዎች መመለስ” ቀሪዎቹን ደግሞ መጠበቅን ያመለክታል። ኣት: “ስለዚህ ቅሬታችሁን እንደ ገና ያድናቸዋል” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ከአሦር ነገሥታት እጅ ወዳመለጡት
“እጅ” የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ ኃይልን ወይም ስልጣንን ይወክላል ። እዚህ ሰዎችን ወደ ሌሎች አገሮች እንዲሄዱ የሚያስገድድበትን የንጉሡን የጭካኔ ሥልጣን ይወክላል ። ኣት: - “ከአሦር ነገሥታት ኃይል ያመለጡትን” ( የባህሪ ስምን፡ ይመልከቱ)
2 Chronicles 30:7
አያያዥ መግለጫ
ይህ ለእስራኤል ሕዝብ የንጉሥ ሕዝቅያስ ቀጣይ መልእክት ነው ።
ወንድሞችህ
እዚህ ላይ “ወንድሞችህ” ሌሎች የእስራኤል ሰዎችን ይወክላል ። ኣት: - “ሕዝብህ”( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ድንጋጤ አደረጋቸው
“ድንጋጤ” የሚለው ረቂቅ ስም በ “አስፈሪ” ወይም “አሰቃቂ” በሚሉት ቃላት ሊገለፅ ይችላል ። ደራሲው እግዚአብሔር በአያቶቻቸው ላይ ስላደረገው ነገር ሲጽፍ ሌሎች ሰዎች እግዚአብሔር ምን እንዳደረገ ሲያዩ የሚሰማቸውን ስሜት በሚገልጽ ቋንቋ ጽፏል ። ኣት: - “ሰዎች ለማየት የሚፈሩት ነገር ነው ያደርጋቸው ” ( የረቂቅ ስሞችን እና የባህሪ ስምን:ይመልከቱ)
ለእግዚአብሔር ራሳችሁን ስጡ
ይህ ለእግዚአብሔር መገዛትን ይወክላል ። ኣት: - “ለእግዚአብሔር ተገዙ” ወይም “ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ስጡ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ወደ ቅዱስ ስፍራውም ግቡ
“የተቀደሰ ስፍራ” የሚለው በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ያመለክታል ። ኣት: “ ቅዱስ ነውና በኢየሩሳሌም ወዳለው ወደ ቤተ መቅደሱ ኑ”ወይም“ በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ቤተ መቅደሱ ኑ ” ( የባህሪ ስምን፡ ይመልከቱ)
ጽኑ ቁጣው ከእናንተ ይመለስ ዘንድ
ደራሲው ስለ ቁጣ ሲጽፍ ፣ እንደ ሰብአዊ አካል ከሰዎች የሚርቅ አስመስሎ ነው። የእግዚአብሔር ቁጣ ከእነሱ መመለሱ ከእንግዲህ በእነርሱ ላይ ቁጣው እንዳልቀጠለ ያሳያል ። ኣት: - “ከእንግዲህ በእናንተ ላይ እንዳይቆጣ” (ተሰብኦትን ፡ ይመልከቱ)
ወደ እግዚአብሔር ብትመለሱ
እዚህ “ወደ እግዚአብሔር ተመለስ” የሚለው እንደገና ለእርሱ መገዛትን ይወክላል ። ኣት: - “ለእግዚአብሔር እንደገና ብትሰጡ ” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ወንድሞቻችሁና ልጆቻችሁ ማርከው በሚወስዷቸው ፊት ምህረትን ያገኛሉ
እዚህ ላይ “ምህረትን ያገኛሉ” የሚለው ዘይቤአዊ አገላለጽ ሲሆን ምህረትን ይለማመዳሉ ማለት ነው ። እነርሱን “ማርከው በሚወስዷቸው ፊት .. ያገኛሉ” የሚለው ማርከው የሚወስዷቸው ምህረትን ያሳየዋቸዋል ማለት ነው። ኣት: - “ወንድሞችህና ልጆችህ በግዞት ከወሰዷቸው ሰዎች ርኅራሆ ያገኛሉ” ወይም “ወንድሞችህንና ሕፃናትን ግዞተኛ አድርገው የወሰዷቸው ሰዎች ርኅራሄ ያሳዩአቸዋል” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ፊቱን ከእንተ አይርቅም
እዚህ “ፊቱን ከእናንተ ማራቅ” የሚለው አባባል እነርሱን አለመቀበልንና እነርሱን ለመጠበቅ ፈቃደኛ አለመሆንን ያሳያል። ኣት: - “አይጥልህም”( ዘይቤያዊን ፡ ይመልከቱ)
ወደ እርሱ ብትመለሱ
እዚህ “ወደ እርሱ ተመለስ” የሚለው ለእግዚአብሔር መገዛትን ያሳያል ። ኣት: - “እንደገና ለእርሱ ብትገዙ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 30:10
የኤፍሬምና የምናሴ ክልሎች
ኤፍሬምና ምናሴ በእስራኤል ሰሜናዊ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ሁለት ነገዶች ነበሩ። እዚህ ላይ “ኤፍሬም እና ምናሴ” የሚለው ሐረግ የሰሜናዊው እስራኤል አሥሩ ነገዶች አባላት የሆኑትን ሰዎች ሁሉ ያመለክታል። በ 2ኛ ዜና 30: 30 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “የሰሜናዊ የእስራኤል ነገዶች ግዛቶች” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)
እስከ ዛብሎን ድረስ
ዛብሎን በእስራኤል ሰሜን ጫፍ ውስጥ ከሚገኙት ነገዶች መካከል አንዱ ነበር ፣ ነገር ግን ከእነርሱ አልፈው ወደ ሰሜን ጥግ የሚደርሱ ሌሎች ሦስት ነገዶች ነበሩ።
የእግዚአብሔርም እጅ በይሁዳ ላይ ወረደ
እዚህ“የእግዚአብሔር እጅ” የሚለው የእርሱን አመራር የሚወክል ሲሆን ልክ በእጁ እየመራቸው ያለ ይመስላል። ኣት:- “እግዚአብሔር የይሁዳን ሕዝብ መራ።” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
አንድ ልብ ለመስጠት
“አንድ ልብ” መኖሩ አንድነትን እና መስማማትን ያመለክታል ። ኣት: - “እንዲስማሙ ማድረግ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ትዕዛዙን እንዲያደርጉ
እዚህ “ትዕዛዙን ማድረግ” የሚለው አባባል የታዘዘውን ማድረግ የሚል ትርጉም አለው። ኣት: - “ትዕዛዙን መታዘዝ” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር ቃል የሆነውን የንጉሡንና የአለቆቹን ትዕዛዝ
“በእግዚአብሔር ቃል” የሚለው ሐረግ የሚያሳየው ንጉሡና መሪዎቹ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ትዕዛዙን እንደሰጡ ያሳያል ። ኣት: - “ንጉሡና መሪያዎቹ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ የሰጧቸው ትእዛዝ” ወይም “እግዚአብሔር ከተናገረው ነገር የተነሳ ንጉሡና መኳንንቱ ያዘዙት”
2 Chronicles 30:13
በሁለተኛው ወር
ይህ በዕብራይስጥ የቀን መቁጠሪያ ሁለተኛ ወር ነው። ጊዜው በምዕራባዊያን ቀን መቁጠሪያዎች ላይ የሚያዚያ መጨረሻ እና የግንቦት የመጀመሪያ ክፍል ነው። ( የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
ተነሱና መሠዊያዎቹን አስወገዱ
እዚህ “ተነሱ” ማለት መሠዊያዎቹን ለማስወገድ መሥራት ጀመሩ ማለት ነው ። ኣት: - “መሥራት ጀመሩ ፣ መሠዊያዎቹንም አስወገዱ” ወይም “መሠዊያውን አራቁ”
በኢየሩሳሌም የነበሩትን መሠዊያዎችና ለጣዖታት የሚያጥኑበትን ዕቃ ሁሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት ሰዎች ለሐሰት አማልክት የሠሯቸውን መሠዊያዎችን ነው ።
በቄድሮን ወንዝ
ይህ በቄድሮን ሸለቆ ውስጥ የነበረ ትንሽ የውሃ ጅረት ነው ። ( የስሞችን አተረጓጎም ፡ ይመልከቱ)
በሁለተኛው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን
ይህ በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያዎች ላይ የግንቦት መጀመሪያ አካባቢ ነው። (የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 30:16
በየቦታቸው በየክፍላቸው ቆሙ
በተመደቡባቸው ቦታዎች ቆሙ ”
ከሌዋውያን እጅ የተቀበሉትን ደም
ይህ ሌዋውያን ያረዷቸውን የበግ ጠቦቶች ደም ያመለክታል። እዚህ ላይ “ከሌዋውያን እጅ የተቀበሉትን” የሚለው ሌዋውያኑ ደም ለካህናቱ መስጠታቸውን ለመግለጽ ነው ። ኣት: - “ከሌዋውያን የተቀበሉት ደም” ወይም “ሌዋውያኑ የሰጧቸው የበግ ጠቦት ደም” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
የፋሲካ-ጠቦት
“የፋሲካ የበግ ጠቦቶች”
2 Chronicles 30:18
ኤፍሬም ፣ ምናሴ ፣ ይሳኮር እና ዛብሎን
እነዚህ በሰሜናዊው የእስራኤል ክፍል ይኖሩ የነበሩ የአንዳንድ ነገዶች ስሞች ናቸው። በ 2ኛ ዜና 30 :10 ውስጥ “ዛቡሎን” የሚለውን እንዴት እንደተረጉምከው ተመልከት ። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
የተጻፈውን ትዕዛዝ በመተላለፍ
መመሪያዎችን የሚቃወም ነገር ማድረግ ማለት ለመመሪያዎቹ ባለመታዘዝ አንድን ነገር ማድረግ ማለት ነው ። አስፈላጊ ከሆነ መመሪያዎቹ ግልጽ ሊደረጉ ይችላሉ ። ኣት: - “ምንም እንኳን የተፃፉት መመሪያዎች መጀመሪያ ራሳቸውን እንዲያነጹ ቢናገሩም” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸን መረጃ :ይመልከቱ)
ቸሩ እግዚአብሔር

እዚህ “ቸር” የሚለው ቃል እግዚአብሔር ቸር መሆኑን ለህዝቡ የ ሚያሳስብ ነው ። ኣት: - “ቸር የሆነው እግዚአብሔር” ( መለየትን ከማስታወቅ ወይም ከማስታወስ ጋር :ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን ለመፈለግ ልቡን የሚያቀናውን
እዚህ“ልቡን የሚያቀናው” የሚለው አንድን ነገር ለማከናወን ጽኑ ውሳኔ መኖርን የሚወክል ሲሆን ፣ “እግዚአብሔርን መፈለግ” የሚለው ደግሞ እርሱን ማወቅን ፣ ማምለክን እና መታዘዝን የሚያመለክት ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የወሰነ ማንኛውም ሰው” ወይም “በእውነት እግዚአብሔርን ለማክበር የሚፈልግ ሁሉ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
እግዚአብሔርም ሕዝቅያስን ሰማው
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለሕዝቅያስ በጎ ምላሽ እንደሰጠ ያሳያል ። ኣት: - “እግዚአብሔርም ለሕዝቅያስ መልካም ምላሽ ሰጠው” ወይም “እግዚአብሔር ሕዝቅያስ የጠየቀውን አደረገ” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)
ሕዝቡን ፈወሰ
እዚህ “ህዝቡን ፈወሰ” የሚለው ሰዎችን ይቅር ለማለቱ እና እነርሱን የማይቀጣ ለመሆኑ ምልክት ነው ። ኣት: - “ህዝቡን ይቅር አለ” ወይም “ሕዝቡን አልቀጣም” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 30:21
የቂጣውን በዓል ጠበቀ
እዚህ “በዓሉን ጠበቁ” የሚለው ፈሊጥ በበዓሉ ላይ ተሳተፉ ወይም በዓሉን አከበሩ የሚል ትርጉም አለው። ኣት: - “በዓሉን አከበሩ” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)
ታላቅ ድምጽ ባላቸው የሙዚቃ መሣሪያዎች ለእግዚአብሔር መዘመር
“ለእግዚአብሔር ከፍተኛ ድምጽ ያላቸውን የሙዚቃ መሣሪያዎች መጫወት እና መዘመር”
የእግዚአብሔርን አገልግሎት የተረዳ
ያበረታታቸውም ለዚህ ነበር ። ኣት: - “የእግዚአብሔርን አገልግሎት ስለተረዱ” ወይም “ያህዌን በብቃት ስላገለገሉ” (መለየትን ከማስታወቅና ከማስታዎስ ጋር :ይመልከቱ)
ስለዚህ እነርሱ በበዓሉ ላይ ሁሉ በሉ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው ።
ለእግዚአብሔር እየተናዘዙ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እየተናዘዙ” የሚለው እዚህ ላይ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ታላቅ መሆኑን ማወጅን ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔርን ማወደስ” ወይም 2) “መናዘዝ” እዚህ ላይ ኃጢአታቸውን መናዘዝን ያመለክታል። ኣት: - “ኃጢአታቸውን ወደ እግዚአብሔር መናዘዝ”
2 Chronicles 30:23
ሕዝቅያስም ማኅበሩን ... ወይፈኖችን በጎችን ደግሞ ስለ ቁርባን ሰጣቸው
ሕዝቅያስ ከብቶቹን ህዝቡ ይበሉ ዘንድ ለእግዚአብሔር እንደ መባ አድርጎ ሰጠ። አንድ ሺህ ወይፈኖች… ሰባት ሺህ በጎች… አንድ ሺህ ወይፈኖችና… አሥር ሺህ በጎችና ፍየሎች “1,000 ወይፈኖች… 7,000 በጎች… 1,000 ወይፈኖች… 10,000 በጎችና ፍየሎች” ( ቁጥርን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 30:25
የይሁዳ ጉባኤ ሁሉ
እዚህ ላይ “ይሁዳ” ምናልባት የደቡቡን የእስራኤል ነገዶች ያመለክታል ።
ከእስራኤል የተሰበሰበ ሕዝብ ሁሉ
እዚህ “እስራኤል” የሚለው ምናልባት የሚያመለክተው ሰሜናዊያኑን የእስራኤል ነገዶች ነው ። ሰዎቹ የነዚያ ነገዶች አባላት ናቸው ። በይሁዳም ወደነበረው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ ። ኣት: - “ከሰሜን እስራኤል በአንድነት የተሰበሰበ ሕዝብ ሁሉ” ( የሚጠበቁ እውቀት ካልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)
ከእስራኤል ምድር የመጡ የባዕድ አገር ሰዎች
እዚህ “የእስራኤል ምድር” የሚለው ምናልባት በሰሜናዊ የእስራኤል ነገዶች የተያዙትን መሬት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል ። ኣት: “ከሰሜን እስራኤል ምድር የመጡት የባዕድ አገር ሰዎች” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)
በይሁዳ የኖሩት
እዚህ“ይሁዳ” የሚለው ምናልባት በደቡባዊው የእስራኤል ነገዶች የተያዙትን መሬት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል ። ኣት: - “በይሁዳ የኖሩ የባዕድ አገር ሰዎች” ( የሚጠበቁ እውቀቶችን እና ያልተገለጹ መረጃዎችን :ይመልከቱ)
ከእስራኤል ንጉሥ ከዳዊት ልጅ ከሰሎሞን ዘመን ጀምሮ
“የዳዊት ልጅ ሰሎሞን በእስራኤል ላይ ከነገሠበት ጊዜ አንስቶ” ወይም “የዳዊት ልጅ ሰሎሞን የእስራኤል ንጉሥ ንጉሥ ሳለ ህዝቡ ካከበሩት ከፋሲካ በዓል ጀምሮ”
በኢየሩሳሌምም እንደዚህ ያለ ነገር አልነበረም
“በኢየሩሳሌም በዚህ መልኩ የተከበረ የፋሲካ በዓል አልነበረም”
ድምፃቸው ተሰማ… ጸሎታቸውም እግዚአብሔር ወደሚኖርበት ወደ ቅድስት ሰማይ ወጣ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን የሚያመለክቱት እግዚአብሔር ለጸሎታቸው በጎ ምላሽ እንደሰጣ ነው ። ኣት: “እግዚአብሔር በሰማይ በተቀደሰ ማደሪያው ሆኖ ጸሎታቸው ሰማ በበጎም መለሰላቸው” ወይም “በቅዱሱ ሰማይ ውስጥ የሚኖር አምላክ ጸሎታቸውን ሰማ” ( ምስስልን :ይመልከቱ)
ድምፃቸው ተሰማ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “እግዚአብሔር ድምፃቸውን ሰማ” ወይም “እግዚአብሔር የለመኑትን ሰማ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን: ይመልከቱ)
ጸሎታቸው ወደ ሰማይ ወጣ
ጸሎታቸው ወደ ሰማይ መሄዱ በሰማይ ያለ እግዚአብሔር በምድር ላይ ለሚጸልዩ ለእነሱ ትኩረት እንደሚሰጥ የሚያመለክት ነው ። ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

---

Chapter 31
2 Chronicles 31:1
እዚያ ነበሩ
“በኢየሩሳሌም የነበሩት”
ለገዛ ንብረቱ
እዚህ “ንብረት” የሚለው በድፍኑ ንብረቶች ማለት ነው ። ኣት: - “ለገዛ ንብረቱ” ወይም “በገዛ ቤቱ” ( አጠቃላይ ስማዊ ግስን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 31:2
ሕዝቅያስም የካህናትንና የሌዋውያኑን በየክፍላቸውና በየአገልግሎታቸው አደራጀ ፤ እያንዳንዱም ሰው በሥራው ተመደበ ፣ካህናቱም ለሌዋውያኑም ።
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ሕዝቅያስ ካህናቱንና ሌዋውያኑን በቡድን በቡድን አደራጀ። እያንዳንዱን ካህን እና ሌዋዊ በስራው መደበ። ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን:ይመልከቱ)
ከገዛ ንብረቱ ለሚቃጠለው መስዋዕት የንጉሡን ድርሻ ሰጠ
ሕዝቅያስ ለሚቃጠሉ መባዎች የሚጠቀምበትን ሥጋና እህል ከራሱ ንብረቱ ወሰደ።
መባቻ
ይህ ከጨረቃ እንቅስቃሴ ጋር የተጣመረ በዓል ነበር ።
በዓላት
ይህ ለበዓል በተለዩ ቀናት ላይ የሚደረጉ በዓላትን ይመለከታል።
በእግዚአብሔር ሕግ እንደ ተጻፈ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሙሴ በእግዚአብሔር ሕግ እንደ ጻፈው” ወይም “እግዚአብሔር በሕጉ እንዳዘዘው” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 31:4
ትዕዛዙ እንደላከ ወዲያውኑ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል ። ኣት: - “ህዝቡ ትዕዛዙን እንደሰማ ወዲያው” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
የሁሉም ነገር አሥራት ነው
“ከእሕሎቻቸው ሁሉ አንድ አሥረኛ”
2 Chronicles 31:6
ሦስተኛ ወር
ይህ በዕብራይስጥ የቀን መቁጠሪያ ሦስተኛ ወር ነው። ይህ በመከር ወቅት መጨረሻና በበጋ ወቅት መጀመሪያ ላይ ነው ። ይህ በምዕራባዊያን የቀን መቁጠሪያዎች ላይ የግንቦት የመጨረሻ እና የሰኔ የመጀመሪያ ክፍል ነው። (የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
ሰባተኛ ወር
ይህ በዕብራይስጥ የቀን አቆጣጠር ሰባተኛ ወር ነው። ይህ ቀዳሚው የዝናብ ወቅት ሲሆን መሬቱ የሚዘራበት እንዲሆን ያለሰልሰዋል። ጊዜው በምዕራባዊያን ቀን መቁጠሪያዎች ላይ በመስከረም ወር መጨረሻ እና በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነው ። ( የዕብራዊያንን ወራትንና ሕገኛ ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 31:9
የሳዶቅ ቤት
እዚህ “ቤት” የሚለው ቤተሰብን ወይም ዘሮችን ይወክላል ። ኣት: - “የሳዶቅ ዘሮች” ( የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)
የተረፈው ይህ ክምር ትልቅ ነው
ሊቀ ካህኑ ወደ ትላልቅ ክምሮች እየጠቆመ ነበር።
ሕዝቅያስ መጋዘኖች እንዲዘጋጁ አዘዘ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ሕዝቅያስ ካህናቱና ሌዋውያኑ መጋዘኖችን እንዲያዘጋጁ አዘዙ” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ ፡ይመልከቱ)
ኮናንያ... ሰሜኢ... ይሒዒል ፣ ዓዛዝያ ፣ ናሖት ፣ አሣሄል ፣ ይሪሞት ፣ ዮዛባት ፣ ኤሊኤል ፣ ሰማኪያ ፣ መሓት ፣ እና በናያስ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። ( ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ ፡ይመልከቱ)
በኮናንያና በወንድሙ በሰሜዒ እጅ በታች አስተዳዳሪዎች ነበሩ
እዚህ “እጅ” ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ይወክላል ። “ከእጅ ስር” የሚለው ሐረግ ማለት በአንድ ሰው ስልጣን ስር መሆን ማለት ነው ። ኣት: “ኮናንያ እና ወንድሙ ሰሜኢ በበላይነት የሚቆጣጠሯቸው አስተዳዳሪዎች ነበሩ” (የባህሪ ስምን እና ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ቤት ላይ ተሾመ
እዚህ “ላይ” የሚለው አባባል ሲሆን ኃላፊ ማለት ነው ። ኣት: - “በእግዚአብሔር ቤት የሚያገለግሉ ሰዎች ሁሉ አለቃ” ( ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 31:14
የይምና ልጅ ቆሬ... ዔድን ፣ ሚንያሚን ፣ ኢያሱ ፣ ሸማያ ፣ አማርያ እና ሴኬኒያ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)
የምሥራቅ በር ጠባቂ
በቤተ መቅደሱ የምሥራቅ በር “በር ጠባቂ”
በካህናቱም ከተሞች ውስጥ ከእርሱ ሥር ዔድን ነበር
እዚህ “ስር” የሚለው ቃል በአንድ ሰው ስልጣን ስር መሆን ማለት ነው ። ኣት: - “ዔድን... በካህናቱ ከተሞች ውስጥ ቆሬን ረድቶታል” ( ፈሊጥን፡ይመልከቱ)
ለመስጠት እንዲችሉ በፈቃድ ባቀረቡት ላይ ተሾመ
ተግባራቸው መስጠት ወይም ”በታማኝነት መስጠት” ነበር
ለወንድሞቻቸው
እዚህ “ወንድሞች” የሚለው ምሳሌ “ሌሎች ካህናትን ” የሚያመለክት ነው ። ኣት: - “ባልደረቦቻቸው ለሆኑ ካህናት” (ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)
ክፍል በክፍል
“በቡድን በቡድን”
ለታላላቆችና ለታናናሾች
እዚህ “ታላላቆች” እና “ታናናሾች” አንድ ላይ “ሁሉም ሰው ” ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል ። “ኣት” “ ለሁሉም ሰው ታላላቆችን እና ታናናሾችን ጨምሮ” (ሜሪዝምን ፡ይመልከቱ)
ታላላቆችና እና ታናናሾች
ይህ ያረጀውንና እና ወጣቱን የሚያመለክት ይመስላል። ይህ አላስፈላጊ ተቀጽላዎችን በማስወገድ በሌላ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። ኣት: - “በዕድሜ የገፉ እና ወጣቶች” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን እና ስማዊ ቅጽሎችን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 31:16
በተጨማሪም ሰጡ
የነፃ ፈቃድ መባዎችን እንደሰጡ ይታወቃል። ኣት: - “ደግሞም በፈቃዳቸው መባዎችን አቀረቡ” ( የፊደል ግድፈትን ፡ይመልከቱ)
ዕድሜያቸው ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ
“ዕድሜያቸው ሦስት ዓመት የሆናቸውና ከዚያ በላይ የሆኑ”
በመዝገብ ውስጥ የተጻፉት
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ስማቸው በመዝገቦቹ ውስጥ ተመዝግቦ የለ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)
በእለታዊ መርሃግብሩ እንደተጠየቁት ሥራቸውን በምድባቸውና በክፍሎቻቸው ለማከናወን
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሊሠሩ የሚገባቸውን የዕለት ተዕለት ሥራ ለመሥራት” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 31:17
አሰራጭተዋል
የነፃ ፈቃድ መባን ማሰራጨታቸው ይታወቃል። ኣት: - “የነፃ ፈቃድ ስጦታዎችን አከፋፈሉ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)
ጭድሜው ሃያ ዓመት እና ከዚያ በላይ
“ዕድሜው 20 ዓመትና ከዛ በላይ” (ቁጥሮችን፡ይመልከቱ)
ድርሻቸውን ለመስጠት በስም የተመደቡ ሰዎች ነበሩ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ድርሻዎችን የመስጠት ኃላፊነት ያላቸው ሰዎች ነበሩ” ( ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ ፡ይመልከቱ)
በመዝገቡ ውስጥ ለተዘረዘሩት ሁሉ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በመዝገቦቹ ውስጥ ስማቸው ለነበረ ሁሉ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 31:20
አምላኩን ለመፈለግ
እግዚአብሔርን መፈለግ እርሱን ለማወቅ ፣ ለማምለክ እና ለመታዘዝ መምረጥን ያመለክታል ። ኣት: - “አምላኩን መታዘዝ” ( ዘይቤያዊን ፡ይመልከቱ)
ይህን ያደረገው በሙሉ ልቡ ነው
እዚህ “ልብ” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ፍላጎት እና ፈቃድ ያመለክታል ። ኣት: - “እርሱ ይህን ያደረገው በፍጹም ፈቃድ ነው ” ወይም “ እርሱ ለሥራው ሙሉ በሙሉ የተሠጠ ነበር” ( የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)

Chapter 32
2 Chronicles 32:1
ከነዚህ ነገሮች እና ከእነዚህ የታማኝነት ሥራዎች በኋላ
የረቂቅ ስሙ “ታማኝነት” የሚለው “በታማኝነት” ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። ኣት: “ ሕዝቅያስ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ በታማኝነት ከፈጸመ በኋላ ” ( የረቂቅ ስሞችን፡ይመልከቱ)
የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም መጣ ፣ እርሱም ሰፈረ
እዚህ ሰናክሬም ሠራዊቱን ይወክላል ። ኣት: - “የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም እና ሠራዊቱ መጡ... ሰፈሩ” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል)
ወደ ይሁዳም ገባ
እዚህ “መጥቷል” ማለት “እንደ ሄደ” ሊገለፅ ይችላል። ኣት: “ሄዶ ወደ ይሁዳ ገባ” ( ሂዱ እና ኑን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 32:2
ሰናክሬም መጥቷል ብሎ አሰበ
እዚህ ሰናክሬም ሠራዊቱን ይወክላል ። ኣት: - “ሰናክሬም እና ሠራዊቱ መጥተው አሰቡ” ( ሁሉን በአንዱ አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ይመልከቱ)
ኢየሩሳሌም ለመውጋት
እዚህ “ኢየሩሳሌም” የሚለው እዚያ ያሉትን ሰዎች ይወክላል ። ኣት: - “የኢየሩሳሌምን ሰዎች ለመውጋት” ወይም “በኢየሩሳሌምን ሠራዊት ለመውጋት” ( የባህሪ ስሞችን ፡ይመልከቱ)
ከከተማይቱ ውጭ የነበሩትን የውሃ ምንጮችን ለማቆም
የከተማይቱ ሰዎች ጉድጓዶችንና ምንጮቹን በአፈርና በድንጋይ በመሸፈን ውሃውን ከአሦራውያን ይደብቃሉ ፣ ነገር ግን ህዝቡ ውሃውን በስውር መንገዶች ወደ ከተማው ያስገባሉ ። ( አወያይ መጠይቅን ፡ይመልከቱ)
የአሦር ነገሥታት መጥተው ብዙ ውሃ ስለ ምን ያገኛሉ?
ሰዎቹ የአሦር ነገሥታት ውሃቸውን እንዲያገኙ እንዳልፈለጉ ለማጉላት አወያይ መጠይቅ ይጠቀማሉ ። ጥያቄው እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “የአሦር ነገሥታት ወደዚህ እንዲመጡ እና ብዙ ውሃ እንዲያገኙ እንፈልግም።” (አወያይ መጠይቅን ፡ይመልከቱ)
የአሦር ነገሥታት
ለ “ነገሥታት” ለሚለው ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን አንዱን የአሦር ንጉሥ የሚያመለክት ነው ። ኣት: “የአሦር ንጉሥ” ወይም 2) ይህ ምናልባት ንጉሡንና ሌሎች መሪዎቹን ሊያመለክት ይችላል ። ኣት: - “ንጉሡ እና ሌሎቹ የአሦር መሪዎች” ( ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 32:5
ሕዝቅያስም በድፍረት ሠራ . . . ሠራ ... ሠራ ... ደግሞም ሠራ
አንባቢያን ሕዝቅያስ ምናልባት ሌሎች ሰዎች ሥራውን እንዲሰሩ አዘ ሊሆን

እንደሚችል አንባቢዎች ሊገነዘቡ ይገባል ። ኣት: "ሕዝቅያስ በድፍረት ፣ ሕዝቡም እንዲገነቡ አዘዘ ፣ ሠሩ… ደግሞም ሠሩት" ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)
ሕዝቅያስ ደፋር ሆነ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሕዝቅያስ ህዝቡ የከተማይቱን ግንቦች እንዲጠግኑ በማዘዝ አቋሙን አጠናከረ ። አያያዥ የሆነውን "በ" በመጠቀም ይህንን ትርጉም የበለጠ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ ። "ኣት" "ሕዝቅያስ ከተማይቱን በመጠገን አጠናከረ" ወይም 2) እርሱ ተበረታታ ። ኣት.: - "ሕዝቅያስ ተበረታቶ ጠገነ " ( አያያዥ ቃላትን :ይመልከቱ)
ሚሎን
ይህ ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን በኩል የሚገኘው ግድግዳ ክፍል ነው።
2 Chronicles 32:6
በሕዝቡ ላይ የጦር አዛዦችን አስቀመጠ
"ላይ አስቀመጠ" የሚለው ፈሊጥ እርሱ በኃላፊነት ሾመ ማለት ነው። "በሕዝቦች ላይ የጦር አዛዦችን አለቃ አድርጎ ሾመ" ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
ከእኛም ጋር ያለው ከእርሱ ጋር ካለው ይበልጣል
"አምላካችን ከእኛ ጋር ስለሆነ ከአሦር ንጉሥ ጋር ካሉት የበለጠ ኃያል ነው"
የሥጋ ክንድ ብቻ ነው
እዚህ "ክንድ" ጥንካሬን ይወክላል ፣ "ሥጋ" ደግሞ ሰብአዊነትን ይወክላል ። ኣት: - "ሰብአዊ ኃይል ያላቸው ብቻ ናቸው" ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 32:9
አሁን እርሱ … ከእርሱ ጋር ነበር
"አሁን" የሚለው ቃል በዋናው የታሪክ መስመር መቋረጡን ለማመልከት እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል ። እዚህ ላይ ተራኪው ስለሰናክሬም እና ሠራዊቱ ያሉበትን ቦታ ዳራዊ መረጃ ይነግረናል ። ( ዳራዊ መረጃን :ይመልከቱ)
በለኪስ
ይህ በይሁዳ የሚገኝ ከተማ ነበር። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ )
በኢየሩሳሌም ላይ የተከበበውን ከበባ ለመቋቋም ምን ያህል ትተማመናለህ?
ሰናክሬም ህዝቡ ስለሁኔታቸው እንዲያስቡ ለማድረግ አወያይ ጥያቄ ይጠቀማል ። ጥያቄው እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - "የኢየሩሳሌምን ከበባ መቋቋም አልቻልክም።" ( አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 32:11
የሚያስታችሁ ሕዝቅያስ አይደለምን .. . የአሦርን ንጉሥ?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ስላሉበት ሁኔታ እንዲያስቡ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - "ሕዝቅያስ እያሳታችሁ ነው….የአሦር ንጉሥ ።" ( አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)
በራብ እና በጥም እንድትሞቱ ያድርግህ ዘንድ
"በምግብና በውሃ እጥረት ትሞታለህ"
ከአሦር ንጉሥ እጅ
እዚህ "እጅ" ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ይወክላል ። ኣት: - "ከአሦር ንጉሥ ኃይል" ወይም "ከአሦር ንጉሥ" ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
መሠዊያዎችን ያስወገደ ይሄው ሕዝቅያስ አይደለምን… መሠዊያ?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ እንዲያስቡ ለማድረግ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ።ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - "መሠዊያዎቹን የፈረሰ ይሄው ሕዝቅያስ ነው።" "ወይም " ሕዝቅያስ መሠዊያዎቹን አስወገደ…."
ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን አዘዘ
እዚህ "ይሁዳ" እና "ኢየሩሳሌም" የሚሉት ቃላት የሚቀመጡትን የሚያመለክቱ ናቸው ። ኣት: - "የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ሕዝብ አዘዘ" ( የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)
2 Chronicles 32:13
አገሮች….ምን እንደሆኑ አታውቁምን?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ስላላቸው ሁኔታ እንዲያስቡ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - "አገሮች ….ምን እንደሆኑ በደንብ ታውቃላችሁ!" ( አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)
አማልክቱ… ኃይል?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ስለ ንግግራቸው እንዲያስቡ ለማድረግ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - "ከአማልክት ሁሉ አምላክ የለም… ማን … ከኃይሌ!" ( አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)
ከአማልክት ሁሉ መካከል… አምላክ አለን…እጅ?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ስለሁኔታቸው እንዲያስቡ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - "በአማልክት ሁሉ መካከል አምላክ የለም… የሚገዛ… በእጅ…!" ( አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)
ከእጄ
እዚህ "እጅ" ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ይወክላል ። ኣት: - "ከኃይሌ" ወይም "ከእኔ"( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
አምላካችሁ እንዴት ይችላል ….ኃይል ?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ስለ ንግግራቸው እንዲያስቡ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - "አምላካችሁ የሚቻልበት ምንም ምክንያት የለም… ኃይል !" ( አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)
አሁን
እዚህ "አሁን" የሚለው ቃል ወደሚቀጥለው አስፈላጊ ነጥብ ትኩረትን ለመሳብ ይጠቅማል ።
አምላክሽ ከእጄ የማዳኑ እድል እጅግ ያነሰ ነው?
ሰናክሬም የኢየሩሳሌም ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ እንዲያስቡ ለማድረግ አወያይ መጠይቅ ይጠቀማል ። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - "አምላክህ በእርግጥ ከእጄ ሊያድንህ አይችልም!" ( አወያይ መጠይቅን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 32:16
ከእጄ ውጪ
እዚህ "እጅ" ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ይወክላል ። ኣት: - "ከኃይሌ" ወይም "ከእኔ"( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 32:18
ጮኹ
"የሰናክሬም አገልጋዮች ጮክ ብለው ጮኹ"
እነርሱን ለማስፈራራት እና እነርሱን ለማስጨነቅ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ የፍርሃትን ጥልቀት አፅንዖት ይሰጣሉ ። ኣት: - "እነርሱን በጣም እንዲፈሩ ለማድረግ" ( ድግግሞሽን :ይመልከቱ)
ሊይዙ ይችላሉ
"የአሦራውያን ሠራዊት ሊይዝ ይችላል"
በምድር አሕዛብ አማልክት ላይ እንደሚናገሩ መጠን በኢየሩሳሌም አምላክ ላይ ተናገሩ
"በሌሎች አገር ሕዝቦች አማልክት ላይ እንዳተሳለቁት የኢየሩሳሌምን አምላክ አፌዙበት"
የሰዎች እጅ ሥራ ብቻ ናቸው
ይህ የሰዎች እነዚህን ጣዖታት በገዛ እጃቻቸው እንደሠሩ እና በዚህም ምክንያት ዋጋ ቢስ እንደሆኑ አጽንዖት ይሰጣል ። ኣት: - "ሰዎች የሰሯቸው ጣዖታት ናቸው" ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 32:20
ወደ ሰማይ ጮኸ
እዚህ "ሰማይ" የሚለው እግዚአብሔርን ይወክላል ። ኣት: - "እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ" ወይም "ወደ እግዚአብሔር ተማጸኑ" ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
በፊቱ ላይ በሃፍረት
"አፈሩ" ወይም "ተሳቀቁ"
የአምላኩ ቤት
'የአምላኩ ቤተ መቅደስ'
2 Chronicles 32:22
ከሰናክሬም እጅ … ከሌሎች ሁሉ እጅ
እዚህ "እጅ" ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ይወክላል ። ኣት: - "ከሰናክሬም ኃይል… ከሌሎቹ ሁሉ ኃይል" ወይም "ከሰናክሬም… ከሌሎቹ ሁሉ" ( የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)
በሁሉም ወገን እረፍት ሰጣቸው
"እረፍት" የሚለው ረቂቅ ስም "ሰላም" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ኣት "በዙሪያቸው ካሉ አገራት ሁሉ ጋር በሰላም እንዲኖሩ አድርጓቸዋል" ( የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)
በሁሉም አገራት ፊት ከፍ ከፍ አለ
እዚህ "ከፍ ከፍ" የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ክብር ማለት ነው ። ደግሞም "ፊት" ፍርድን ወይም ምዘናን የሚወክል ዘይቤ ነው ። ኣት: - "የሁሉም አገራት ሰዎች አከበሩት" ( ፈሊጥን እና ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 32:24

እንዲድን

ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሕዝቅያስን እንዲፈውሰው” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

ሕዝቅያስ ግን እንደ ተቀበለው ቸርነት መጠን ለእግዚአብሔር አላደረገም

ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት : “ግን ሕዝቅያስ እግዚአብሔር ከረዳው በኋላ እንደ አመስጋኝ ሰው አልኖረም” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

ልቡ ከፍ ከፍ አለ

እዚህ “ልብ” የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን የሰውን ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክት ነው ። እዚህ “ልብ ከፍ ከፍ ብሏል” ማለት ኩራት ማለት ነው ። ኣት: “ትዕቢተኛ ሆነ” ( የባህሪ ስምን እና ፈሊጥን:ይመልከቱ)

ስለዚህ በእርሱ ላይ እና በይሁዳና በእየሩሳሌም ላይ ቁጣ ሆነባቸው

እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሕዝቡን መቅጣቱ “ቁጣ እንደወረደባቸው” ተደርጎ ተነግሯል። “ይሁዳ” እና “ኢየሩሳሌም” በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች የሚወክሉ መግለጫዎች ናቸው ። ኣት፡ ስለዚህ “እግዚአብሔርም ተቆጣ እርሱንም የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ቀጣ” ( ዘይቤያዊን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

በሕዝቅያስ ዘመን

“በሕዝቅያስ የሕይወት ዘመን” ወይም “ሕዝቅያስ በገዛበት ዘመን”

2 Chronicles 32:27

ጋጣ

ይህ ፈረሶችን ማሳደሪያ አስተኛ ቦታ ነው ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 9 ፡25 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በረት ሠራ

አስተኛ እንስሳትን ማሳደሪያ ቦታ ነው።

2 Chronicles 32:30

ሕዝቅያስ ደግሞ ደፈነ .....እርሱ አቅንቶ አወረደው

ምናልባት ሕዝቅያስ ሌሎች ሰዎች ሥራውን እንዲሰሩ አዞ ሊሆን እንደሚችል አንባቢዎቹ ሊገነዘቡ ይገባል ። ኣት: - “ሕዝቅያስ ሠራተኞቹ ውሃውን እንዲደፍኑ እና … ውሃው እንዲወርድ ቱቦ እንዲሰሩ አዘዘ ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

የጊዮንን ውሃ

ይህ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ያለ ዥረት ስም ነው። ( የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)

በምድሪቱ የተከናወነው ተአምራዊ ምልክት

ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ ያደረገውን ተአምር” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

በልቡ ውስጥ ያለውን ሁሉ ለማወቅ

እዚህ “ልብ” የሰውን ውስጣዊ ማንነት ያሳያል ። ኣት: - “የሕዝቅያስን እውነተኛ ባሕርይ ለመግለጥ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 32:32

ሕዝቅያስ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ

ይህ ስለ ሞቱ የሚነገርበት ትህትና ያለው መንገድ ነበር ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 9፡ 31 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: “ሕዝቅያስ ሞተ” ( ዘወርዋራን :ይመልከቱ)

---

Chapter 33

2 Chronicles 33:1

በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ የሆነውን ነገር

እዚህ የእግዚአብሔር “እይታ” የሚያመለክተው የእርሱን ፍርድ እና ምዘና ነው። በ 2 ኛ ዜና 14 ፡ 2 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ክፉ ነው ያለው ነገር” ወይም “እግዚአብሔር ክፋት እንደሆኑ የቆጠራቸው ነገሮች” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

እንደ አስጸያፊ ነገሮች

ሌላ አማራጭ ትርጉም “አስጸያፊ ነገሮችን” ጨምሮ ።

በኮረብታ ላይ የነበሩትን መስገጃዎች ሠራ ፤ መሠዊያዎችን ሠራ ፤ መሠዊያዎችን ሠራ ፤ የማምለኪያ ዐፀዶችንም ተከለ

ምናሴ ሠራተኞቹን ግንባታውን እንዲሠራለት አዞ ይሆናል ። ኣት: - “የኮረብታውን መስገጃዎች መልሶ አሠራ ፣ መሠዊያዎችን አወራ… የማምለኪያ አጸዶቹንም አሠራ” ወይም “ሠራተኞቹ የኮረብታውን መስገጃዎች እንዲሠሩ ፣ መሠዊያውንም እንዲሠሩለት አደረገ … የማምለኪያ አጸዶቹንም እንዲሠሩለት አደረገ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 33:4

ስሜ ለዘላለም በኢየሩሳሌም ይኖራል

ስሙ ግለሰቡን የሚተካ ነው። ኣት: - “በኢየሩሳሌም ለዘላለም ማን እንደ ሆንኩ እገልጣለሁ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ቤት በሁለቱ አደባባዮች ላይ ለሰማይ ኮከቦች ሁሉ መሠዊያዎችን ሠራ

ሰዎች ከዋክብትን እንዲያመልኳቸውና እና እንዲሰውላቸው እእነዚህን መሠዊያዎች ማሠራቱ ተጠቁሟል። ደግሞም ፣ እነዚህን መሠዊያዎች ራሱ አልሠራም ፣ ይልቁንም ሠራተኞቹን እንዲሠሩ አዘዞ ነበር ። ኣት: “ሰዎቹ ከዋክብትን ማምለክ እንዲችሉና መስዋዕት እንዲያቀርቡላቸው በእግዚአብሔር ቤት በሁለቱ ግቢዎች ውስጥ ሠራተኞቹ መሠዊያ እንዲሠሩ አደረገ” ( የሚጠበቅ እውቀትን ፣ ያልተገለጸ መረጃን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

በሄኖምም ሸለቆ

ይህ በገሃነም ተብሎም የሚታወቅ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ የሚገኝ ቦታ ነው። ( የስሞች አተረጓጎም :ይመልከቱ)

ልጆቹን በእሳት እንዲያልፉ አደረገ

ልጁን ለምን ወደ እሳት እንዳስገባ እና ይህን ካደረገ በኋላ ምን እንደ ሆነ ግልፅ ማድረግ ሊኖርብህ ይችላል ። ኣት: “ልጆቹን ለአምላኩ መሥዋዕት አድርጎ ልጆቹን በእሳት አቃጠላቸው” ( የሚጠበቅ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ:ይመልከቱ)

አማካሪ

መረጃ ጠይቋል

ሙታን

ይህ የሞቱ ሰዎችን ያመለክታል ። ኣት: - “የሞቱ ሰዎች” ወይም “ሙታን”( ስማዊ ቅጽልን :ይመልከቱ)

ምናሴ በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ክፉ ነገር አደረገ

እዚህ የእግዚአብሔር “እይታ” የሚለው የሚያመለክተው እርሱ አንድን ነገር እንዴት እንደሚመዝን ነው። በ 2 ኛ ዜና 14፡ 2 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “ምናሴ እግዚአብሔር ክፉ ነው ብሎ የተናገራቸውን ብዙ ነገሮች አደረገ” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ እንደሆኑ የወሰናቸውን ነገሮች አደረገ” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

አስቆጣው

“ምናሴ እግዚአብሔርን እጅግ አሳዘነ”

2 Chronicles 33:7

እርሱ ሠራው

ምናሴ ሥራውን አልሠራ ይሆናል። አገልጋዮቹ ሥራውን ሠርተው ይሆናል። ኣት: - “ምናሴ ሠራተኞቹን እንዲሠሩ አዘዘ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ስሜን ለዘላለም አኖራለሁ

እዚህ እግዚአብሔር “በስሙ” ተወክሏል። ኣት: “ሰዎች ለዘላለም እንዲያመልኩኝ በፈለግኩበት ቦታ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ለአባቶቻቸው ሰጠኋቸው

ለአባቶቻቸው የሰጠኋቸው ”

ይሁዳ እና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች

እዚህ “ኢየሩሳሌም”የ “ይሁዳ” አንድ አካል ነው። ኣት: “የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በእስራኤል ፊት ካጠፋቸው ከአሕዛብ ይልቅ

እዚህ “አገራት” የሚለው ቃል እስራኤል ከመምጣቱ በፊት በከነዓን ምድር ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ያመለክታል ። ኣት: “እግዚአብሔር የእስራኤልን ህዝብ ወደ ምድሪቱ ሲገባ እና እየተስፋፉ ሲሄዱ ካጠፋቸው እጅግ የበለጡ ሰዎች” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)

2 Chronicles 33:10

በእነሱ ላይ አመጣ

እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን እንዲያጠቃ ሰራዊቱን ላከ ። ኣት: “በእነርሱ ላይ ጥቃት አመጣባቸው” ( የሚጠበቅ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

የአሦር ንጉሥ ሰራዊት አዛዦች

አዛዦች ከወታደሮቻቸው ጋር ነበሩ ። ኣት: - “የአሦር ንጉሥ ሠራዊት አዛዦችና ወታደሮቻቸው” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል:ይመልከቱ)

ምናሴን በሰንሰለት አስረው ወደ ባቢሎን ወሰዱት
እዚህ ላይ ምናሴ ወደ ግዞት የተወሰደው እግሩ ታስሮ ነበር።ሰንሰለቶች በእግሮቹ ዙሪያ የተቀመጡ ማሰሪያዎች ነበሩ። ኣት: “ምናሴን ያዘው ፣ በሰንሰለት አስረው ወደ ባቢሎን እስረኛ አድርገው ወሰዱት።" ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 33:12
ተማጸነ
እርዳታ መለመን
ወደ እርሱም ጸለየ ። እግዚአብሔርም ተለመነው
ሁለተኛው ሐረግ የመጀመሪያው ሐረግ በማጠናከር የምናሴን ጸሎት እውነተኛነት ያስረግጣል ። ይህ በገቢራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል ። ኣት: - “ወደ እግዚአብሔር ጸለየ እርሱም ተለመነው” ( ድግግሞሽን ፣ ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን:ይመልከቱ)
ወደ ንግሥናው ገባ
“እንደ ንጉሥ እንደገና ለመግዛት”
2 Chronicles 33:14
አጠቃላይ መረጃ
የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ
ምናሴ ሠራ ... ከበበው ... ወሰደው .... በተራራ ላይ ሠራ
ምናሴ ሕንጻውንና ግንባታውን አልሠራም ፣ይልቅ ሠራተኞቹን እንዲሠሩት አዘዛቸው ። ኣት: “ምናሴ ሠራተኞቹን እንዲሠሩ ... ዙሪያውን ከበቡ... ሠራተኞቹንም እንዲያስወግዱ .....ከዚህ በፊት በተራራው ላይ የሠሩትን ።( የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)
ግዮን
ይህ ምንጭና እና የጅረት ስም ነበር ። በ 2ኛ ዜና 32 :30 ውስጥ ‹የጊዮን ውኃዎች› የሚለውን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ኣት: - “የጊዮን ውኃዎች” ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
የኦፌል ኮረብታ
በ 2 ኛ ዜና 27:3 እንዳለው የዚህን ኮረብታ ስም ይተረጉሙ ። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
ግድግዳውን ከፍ አደረጉ
“ግድግዳውን ከፍ አድርጎ ገነባ ”
የተመሸጉ ከተሞች
ይህ በዙሪያቸው ግንብ ያሉባቸውን ከተሞች ያመለክታል ።
ባዕዳን አማልክቱ
'ከሌሎች አገሮች የመጡ የሐሰት አማልክት'
2 Chronicles 33:16
እንደገና ገነባ
ምናሴ ሕንጻውንና ግንባታው አልሠራም ፣ ይልቅ ሠራተኞቹን እንዲሠሩት አዘዘ ። ኣት: - “እንደገና እንዲገነቡ አዘዛቸው” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
ይሁዳን አዘዘ
እዚህ ላይ “ይሁዳ” የሚያመለክተው በዚያ አገር የሚኖሩትን ሰዎች ነው ። ኣት: - “የይሁዳን ሕዝብ አዘዘ” ( የባህሪ ስሞችን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 33:18
እነሆ ፣ በእስራኤል ሥራዎች ... ተጽፈው ነበር
“ማንኛውም ሰው ሥራዎቹን ማየት ይችላል ... እስራኤልን እዚያ እንደተጻፈ ማየት ይችላል”
ተጽፈዋል... ተጽፈውባቸዋል
እነዚህ ሐረጎች በገቢራዊ አረፍተነገሮች ሊገለጹ ይችላሉ። ኣት: - “ሰዎች ጻፏቸው ... ሰዎች ስለእነርሱ ጻፉ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
የእስራኤል ነገሥታት ሥራ
ይህ በእስራኤል የታሪክ መዝገብ ውስጥ አሁን የማይገኝ ነው ።
በኮረብታው ላይ የነበሩትን መስገጃዎች የሠራበት ፣ የማምለኪያ አጸዶችን እና የተቀረጹ ምስሎችን ያቆመበት ቦታ
ምናሴ ሕንጻውንና ግንባታውን አልሠራም ፣ ይልቅ ሠራተኞቹን እንዲሠሩ አዟል ። ኣት: - “የኮረብታው መስገጃዎች ያሠራበት ፣ እና የማምለኪያ አጸዶቹን እና የተቀረጹ ምስሎችን ያስቆመበት ሥፍራ ፤” ወይም “ሠራተኞቹን የኮረብታ መስገጃዎቹን እንዲገነቡና የማምለኪያ አጸዶቹን እና የተቀረጹ ምስሎችን እንዲያቆሙ ” (የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
በባለ ራእዩ ታሪክ መጽሐፍ
ይህ የማይገኝ መጽሐፍ ነው።
ምናሴ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ
ይህ አክብሮት ያለው አገላለጽ ነው። ኣት: - “ምናሴ ሞተ” ( ዘወርዋራን :ይመልከቱ)
በገዛ ቤቱ
“በቤተ መንግሥቱ”
አሞጽ
ይህ የሰው ስም ነው ። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
በእርሱ ቦታ ነገሠ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “ቀጣዩ ንጉሥ ሆነ” ወይም “የይሁዳ ንጉሥ ሆነ” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 33:21
ዕድሜ ሃያ ሁለት ዓመት
“ዕድሜው 22 ዓመት” ( ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ የሆነውን ነገር አደረገ
እዚህ የእግዚአብሔር “እይታ” የሚያመለክተው አንድን ነገር እንዴት እንደሚመዝን ነው። በ 2 ኛ ዜና 14 ፡ 2 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ክፉ ናቸው ያላቸው ነገሮች” ወይም “እግዚአብሔር ክፋ እንደሆኑ የቆጠራቸው ነገሮች” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ይህ አምኖን እጅግ ብዙ ተላለፈ
“አሞን ደጋግሞ ኃጢአት ሠራ” ወይም “አሞጽ ኃጢአት በመሥራት ቀጠለ ”
2 Chronicles 33:24
ለሞት አበቁት
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: “እርሱን ገደለው” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
በእርሱ ላይ አመፁ
እሱን ለመግደል በስውር ታቅዶ ነበር ”
በእርሱ ቦታ ነገሠ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “ቀጣዩ ንጉሥ ሆነ” ወይም “የይሁዳ ንጉሥ ሆነ” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)

Chapter 34
2 Chronicles 34:1
ሠላሳ አንድ ዓመት
“31 ዓመት” ( ቁጥሮች :ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር
እዚህ የእግዚአብሔር “እይታ” የሚያመለክተው በአንድ ነገር ምንነት ላይ እንዴት እንደሚፈርድ ወይም እንደሚወስን ነው። በ 2 ኛ ዜና 14 ፡ 2 ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ። ኣት: - “እግዚአብሔር ትክክል ያላቸው ነገሮች” ወይም “እግዚአብሔር ትክክል እንደሆኑ የቆጠራቸው ነገሮች” ( ዘይቤያዊን : ይመልከቱ)
በአባቱም በዳዊት መንገድ ሄደ
ኢዮስያስ የዳዊትን ባሕርይ ማሳየቱ እንደ ዳዊት በአንድ ዓይነት መንገድ ወይም አካሄድ እንደሄደ ተደርጎ ተገልጾአል ። ኣት: - “አኗኗሩን እንደ አባቱ እንደ ዳዊት አደረገ” ወይም “የአባቱን የዳዊትን ምሳሌ ተከተለ” (ተመልከት/ች: ዘይቤአዊን :ይመልከቱ)
ወደ ቀኝም ሆነ ወደ ግራ አልተመለሰም
እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ መታዘዝ አንድ ሰው በትክክለኛው መንገድ ላይ እንደነበረና ፈጽሞ ከእርሷ እንደማያፈነግጥ ሆኖ ተገልጾአል ። ኣት: - “እግዚአብሔርን የማያስደስተውን ነገር አላደረገም” ወይም “የእግዚአብሔርን ሕግጋት ሙሉ በሙሉ ታዘዙ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ስምንተኛው ዓመት ... አሥራ ሁለተኛው ዓመት
በ 2 ኛ ዜና 14:2 ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ። ( ሕገኛ ቁጥሮችን : ይመልከቱ)
እስራኤልንና እየሩሳሌምን ከተቀረጹትና ከብረት ቀልጠው ከተሠሩት ማጽዳት ጀመረ
ይህ የሚናገረው ኢዮስያስ በይሁዳና በኢየሩሳሌም የሐሰት አማልክትን ለማምለክ ያገለገሉትን ስለማስወገዱ ሲሆን ቦታዎቹን በአካል እንዳፀዳ ተደርጎ ተነግሯል። ኢዮስያስ ሠራተኞቹን እነዚህን ነገሮች እንዲያስወግዱ አዞ ነበር ። ኣት: - “ሠራተኞቹ ከፍ ያሉ የማምለኪያ ሥፍራዎችን ፣የማምለኪያ አጻዶችን፣ የተቀረጹትን እና ቀልጠው የተሠሩትን ምስሎች በማስወገድ ይሁዳንና እየሩሳሌምን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደገና ተቀባይነት እንዲያገኙ አደረገ” (ዘይቤያዊን እና የባሕሪ ስምን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:4
በፊቱ
“በኢዮስያስ ፊት”
ቆራረጠው... ሰባበረ... በታተነ... አቃጠለ
ኢዮስያስ ሠራተኞቹን እነዚህን ነገሮች እንዲያደርግ አዞ ነበር ። ኣት: - “እንዲቆራርጡ አደረጋቸው... እንዲሰባብሩ አዘዛቸው... እንዲበታትኑ አደርጋቸው... እንዲያቃጥሉ አዘዛቸው” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
አቧራ
በነፋሱ ሊወሰዱ የሚችሉ በጣም ትንሽ ቁርጥራጮች
የካህናታቸውን አጥንቶች በመሠዊያዎቻቸው ላይ አቃጠላቸው
ይህ ማለት በመሠዊያው ላይ ለሐሰት አማልክት መሠዊያ የሚሠዉ ካህናት አጥንቶቻቸው ከዚህ በፊት በሠሯቸው መሠዊያዎች ላይ ይቃጠላሉ ማለት ነው ።
ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን አነጻ
ይህ የሚናገረው ኢዮስያስ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ስለማድረጉ ሲሆን በአካላዊ ሁኔታ እንዳነጻቸው ተደርጎ ተነግሯል። ኣት: - “ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን እንደገና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ አደረገ” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 34:6
መሠዊያዎችን አፍርሷል ... በታተነ....ቆራረጠ
ኢዮስያስ ሠራተኞቹን እነዚህን ነገሮች እንዲያደርግ አዞ ነበር ። ኣት: - “ሠራተኞቹን መሠዊያዎች እንዲሰባብሩ ፣ እንዲበታትኑ... እንዲቆራርጡ አዘዘ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
ወደ ዱቄት
“ወደ አፈር” ማለትም ዱቄት እስኪሆኑ ድረስ መከስከስ ማለት ነው ።
2 Chronicles 34:8
አሥራ ስምንተኛው ዓመት
“18ኛ ዓመት” ( ህገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
ኢዮስያስ ምድሪቱንና ቤተ መቅደሱን አነፃ
ይህ የሚናገረው ኢዮስያስ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ስለማድረጉ ሲሆን በአካላዊ ሁኔታ እንዳነጻቸው ተደርጎ ተነግሯል። ኣት: - “ኢዮስያስ ምድሪቱንና ቤተ መቅደሱን እንደገና በጌታ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ አደረገ” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
የኤዜልያስ ልጅ ሳፋን ፣ መዕሤያ ... የኢዮአካዝ ልጅ ኢዮአክ ... ኬልቅያስ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
በአደራ ተሰጥቶታል
“ገንዘቡን እንዲጠቀምበት ኃላፊነት ሰጠው”
በበሩ ጠባቂዎች በሌዋውያን ተሰብስቦ ወደ እግዚአብሔር ቤት ይገባ ነበር
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በሮቹን የሚጠብቁት ሌዋውያን ያከማቹትን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ቤት ያመጡ ነበር” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 34:10
በአደራ ሰጡ
“እነርሱ” የሚለው ቃል ኢዮስያስ ወደ ሊቀ ካህኑ ወደ ኬልቅያስ የላከላቸውን ሰዎች ያመለክታል ። በመጀመሪያ ገንዘቡን ሰጡት ከዚያም ሕንፃውን ለሚቆጣጠሩት ሰዎች አከፋፈለ ። ኣት: - “ከኬልቅያስ በአደራ የተሰጠ” (የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)
ገንዘቡ
ይህ ለኬልቅያስ በአደራ በተሰጠ ገንዘብ ላይ የተወሰነውን ይመለከታል ። ኣት: - “የተወሰነ ገንዘብ” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)
አናጢዎች
እንጨት የሚሰሩ ሠራተኞች
ሰረገሎች
ትላልቅ በሞችን ለማገናኘት ያገለግላሉ
ተበላሽቶ ነበር
“እንዲበሰብስ አድርገውት ነበር”
2 Chronicles 34:12
ኢኤት... ሜሱላም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
ከሜራሪ
በ 2 ኛ ዜና 29 :12 እንዳለው የዚህን ሰው ስም ተርጉም ። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)
ቀዓትም
በ 2 ኛ ዜና 20 :19 እንዳለው የጎሳውን ስም ተርጉም ። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)
አብድዩ... ዘካርያስ
በ 2 ኛ ዜና 17 : 7 ውስጥ የእነዚህን ሰዎች ስሞች ለሌሎች ሰዎች እንደተረጎምከው ተመሳሳይ ስም አድርገህ ተርጉም ። (የስሞችን አተረጓጎም : ይመልከቱ)
እነዚህ ሌዋውያን የግንባታ ቁሳቁሶችን የሚሸከሙትን እንዲሁም በማንኛውም መንገድ የሚሰሩትን ሰዎች ሁሉ ይቆጣጠሩ ነበር
ይህ ማለት ማንኛውንም ዓይነት የግንባታ ሥራ ለሚያደርጉ ወንዶች ሁሉ ኃላፊ ነበሩ ማለት ነው ። ኣት: - “እነዚህ ሌዋውያን ማንኛውንም ዓይነት የግንባታ ሥራ በሚሠሩ ሰዎች ሁሉ ላይ ተሾመው ነበር” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን : ይመልከቱ)
2 Chronicles 34:14
አጠቃላይ መረጃ
የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ
እነርሱ ወደ እግዚአብሔርም ቤት የቀረበውን ገንዘብ ባመጡ ጊዜ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኬልቅያስንና እሱን የሚረዳውን ሰው ነው ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ለተቆጣጣሪዎቹ ገንዘብ ባወጡ ጊዜ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ )
በሙሴ በኩል የተሰጠው
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለሕዝቡ በሰጣቸው ጊዜ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
ሳፋን
ይህ የሰው ስም ነው ። ( የስሞችን አተረጓጎም :ይመልከቱ)
የሕጉ መጽሐፍ
እነዚህ ሕጎች በአንድ ጥቅልል የመጻፍ እድላቸው ከፍተኛ ነው። ጥቅልል የመጽሐፍ ዓይነት ሲሆን ከአንድ ጊዜ የተጠቀለለ ፓፒረስ ወይም ቆዳ የሚሠራ ነበር።
በአደራ የተሰጣቸውን ነገር ሁሉ
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “አንተ እንዲያደርጉት በአደራ የሰጠሃቸውን ነገሮች ሁሉ” ወይም “እንዲሠሩ ኃላፊነት የሰጠሃቸውን ነገሮች ሁሉ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 34:17
ባዶ አደረጉ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “ሁሉንም ሰብስበዋል” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
በአለቆችና በሠራተኞቹ እጅ
የእነርሱን ንብረት አፅንዖት ለመስጠት ተቆጣጣሪዎችና ሠራተኞች በ “እጅ” ተወክለዋል ። ኣት: - “ለአለቆችና ለሠራተኞቹ” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን ሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)
ይህ በሆነ ጊዜ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አንድን አስፈላጊ ክስተት ለማመልከት እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል ። ቋንቋህ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ መጠቀም ትችላለህ ።
ልብሱን ቀደደ
ይህ የከባድ ሀዘን ወይም መከፋት አመልካች ድርጊት ነው። ኣት: “በጣም ስለተበሳጨ ልብሱን ቀደደ” ( ምሳሌያዊ ድርጊት :ይመልከቱ)
2 Chronicles 34:20
የሳፋን ልጅ አኪቃም ፣ የሚክያስ ልጅ አብዶን ፣ ሳፋንን ... አሳያ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። ( የስሞች አተረጓጎም :ይመልከቱ)
የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለእኔ ጠይቁ
“ፈቃድ” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል ። ደግሞም ፣ በ 2 ኛ ዜና 34 : 22 በግልፅ እንደተጠቀሰው ንጉሡ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ነብያት ሄደው የጌታን ፈቃድ ለይተው እንዲያውቁ ረዱቷቸዋል ። ኣት: - “ምን እንዳደርግ እንደሚፈልግ እግዚአብሔርን ጠይቁ” ( የረቂቅ ስሞችን :ይመልከቱ)
ስለተገኘው ቃል
“ስለተገኘው ቃል ”
የተገኘው የመጽሐፉ ቃል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እዚህ “ቃል” ህግጋትን ይወክላል ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ኬልቅያስ በገኘው መጽሐፉ ውስጥ ያሉ ሕግጋት” ( የረቂቅ ስሞችን እና ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

በእኛ ላይ የፈሰሰው የእግዚአብሔር ቁጣ ታላቅ ነውና። ታላቅ ነው

እንደ ቁጣ ያሉ ስሜቶች ብዙውን ጊዜ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንደ ፈሳሽ ይናገራሉ ። ኣት: - “ የእግዚአብሔር ቁጣ በእኛ ላይ ታላቅ ነው፣ እንደ ውኃ ጠራርጎ ሊወስደን ይችል ነበር። በእኛ ላይ ታላቅ ነው ፣ እንደ ውሃ ሙሉ በሙሉ አጥቦ ሊወስደን ይችላል”ወይም“ እግዚአብሔር እኛን ይቀጣበት ቁጣው ታላቅ ነውና ” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

የተጻፈውም ሁሉ በእርሱ ነው

ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በእርሱ ላይ የተጻፈው ሁሉ” ወይም “በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለው ሁሉ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:22

ሕልዳና

ይህ የሴት ስም ነው ። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

ሴሉም... ቲቁዋ... ሓስራ

እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)

የልብስ ጠባቂ

ይህ ሴሌምን ይመለከታል ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በቤተመቅደስ ውስጥ ካህናት የሚለብሱትን ልብስ የሚጠብቅ ሰው ወይም 2) የንጉሡን ልብስ በአግባቡ የሚጠብቅ ።

ሁለተኛው አውራጃ

ይህ የኢየሩሳሌም ክፍል ነው። ምናልባት አዲስ ክፍል ሊሆን ይችላል። ኣት: “ሁለተኛው ክፍል” ( ሕገኛ ቁጥሮችን :ይመልከቱ)

በዚህ መንገድ አነጋሯት

“የሚከተለውን ውይይት ከእርሷ ጋር አደረጉ”

2 Chronicles 34:23

ወደ እኔ የላከውን ሰው

እዚህ ላይ “ሰው” የሚለው የሚያመለክተው ንጉሥ ኢዮስያስን ነው።

እነሆ

እዚህ ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው እንደ አነጋገር ዘይቤ ሆኖ ሲሆን የአድማጮቹን ትኩረት ቀጥሎ ወደ ተናገረው ለመሳብ አገልግሏል ። ኣት: - “አዳምጥ” ( ፈሊጥን ፡ ይመልከቱ)

በዚህ ስፍራና በነዋሪዎቿ ላይ ጥፋት አመጣለሁ

እግዚአብሔር አስከፊ ነገሮችን እንዲከሰት ስለማድረጉ ሲነገር ጥፋት ወደ አንድ ቦታ ሊያመጣው የሚችል ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል ። ኣት: - “በቅርቡ በዚህ ቦታ እና በነዋሪዎቹ ላይ አስከፊ ነገሮች እንዲደርሱ አደርጋለሁ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

እዚህ ቦታ ላይ

“በኢየሩሳሌም” ይህ የይሁዳን ምድር በሙሉ የምትወክለውን የኢየሩሳሌምን ከተማ ያመለክታል ። ኣት: - “በይሁዳ ላይ” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን :ይመልከቱ)

የተጻፉትን እርግማኖች ሁሉ

ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “የተጻፉን እርግማኖች ሁሉ” ወይም “እርግማኖችን ሁሉ ” (ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ :ይመልከቱ)

እንድቆጣ አድርገውኛል

“አስቆጡኝ”

ስለዚህ ቁጣዬን በዚህ ስፍራ ላይ ይፈሳል ፣ ደግሞም አይጠፋም

እንደ ቁጣ ያሉ ስሜቶች ብዙውን ጊዜ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንደ ፈሳሽ ይናገራሉ ። ኣት: - “ስለዚህ በዚህ ስፍራ ላይ ቁጣዬ እንደ እሳት ነው ፣ ምንም ነገር አያቆመውም” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

ቁጣዬ ይፈስሳል

ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ቁጣዬን አወርዳለሁ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን:ይመልከቱ)

እዚህ ቦታ ላይ

እዚህ “እዚህ ቦታ” የሚያመለክተው እዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ነው ። ኣት: - “በእነዚህ ሰዎች ላይ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:26

ስለ ሰማኸው ቃል

“ስለ ሰማኸው መልእክት”

ልብህ ገር ሆኗልና

እዚህ “ልብ” የሰውን ውስጣዊ ማንነት ይወክላል ። የሚያዝን ልብ ገር ተብሏል ። ኣት: - “ስለተጸጸትክ” ወይም “ንስኃ ስለገባህ”( የባህሪ ስምን እና ዘይቤያዊን ፡ ይመልከቱ)

ልብሶቻችሁን ቀደዳችሁ

ይህ ከባድ ሀዘንን ወይም መከፋትን የሚያመለክቱ ምሳሌያዊ ድርጊቶች ነው። ( ምሳሌያዊ ድርጊትን :ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው

እርሱ ስለሚናገረው ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ እግዚአብሔር ስለ ራሱ በስሙ ይናገራል ። ኣት: - “እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርኩት የህ ነው” ( አንደኛ ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ መደብ ሰብዓዊን :ይመልከቱ)

እነሆ ወደ አባቶችህ እሰበስብሃለሁ። በሰላም ወደ መቃብርህ ትሰበሰባለህ

ሁለቱም መግለጫዎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ናቸው ። ይሞታል የሚለውን በአክብሮት የሚገልጹ ናቸው ። ኣት: - “ስለሆነም እንድትሞት እና በሰላም እንድትቀበር እፈቅድልኃለው” ( ምስስልን እና ዘወርዋራን :ይመልከቱ)

ወደ መቃብርህ ትሰበሰባለህ

ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ወደ መቃብርህ እሰበስብሃለሁ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

ዓይኖችህ አያዩም

እዚህ “ዐይን” ሙሉ ሰውን ይወክላል ። ደግሞም “አያዩም” የሚለው ሐረግ የሆነን ነገር አለመለማመድን ያሳያል ። ኣት: - “አይደርስብህም”( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

በዚህ ስፍራ የማመጣው ጥፋት

እግዚአብሔር አስከፊ ነገሮችን እንዲከሰቱ የሚያደርግ መሆኑ ጥፋት እግዚአብሔር ወደ አንድ ቦታ የሚያመጣ ቁስ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጸል ። ኣት: - “በዚህ ስፍራ ላይ አስከፊ ነገሮችን እንዲከሰቱ አደርጋለሁ” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:29

የይሁዳ ሰዎች ሁሉ እና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁሉ

ይህ አጠቃላይ ነው ። ኣት: - “ሌሎች ብዙ ሰዎች” ( ግነትን እና አጠቃላይን ፡ ይመልከቱ)

ከታላቅ እስከ ትንሽ

ይህ በመካከላቸው ያሉትን ሁሉ የሚያካትት አገላለጽ ነው። ኣት: - “ከታላላቆች እስከ ታናናሾች ድረስ” (ሜሪዝምን :ይመልከቱ)

ከዚያም በችሎታቸው አነበበ

“ከዚያም ንጉሡ መስማት እንዲችሉ ጮክ ብሎ ያነባል”

የተገኘውን

ይህበገቢራዊቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ኬልቅያስ እንዳገኘው” ወይም “ያገኘውን”( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)

2 Chronicles 34:31

በእርሱ ቦታ ቆመ

ይህ ንጉሡ በቤተ መቅደሱ የቆመበትን ቦታ ያመለክታል ። ኣት: - “በቤተ መቅደሱ መግቢያ በር ሊቆም በተገባው ቦታ ቆመ” ( የሚጠበቅ እውቀትን ወይም ያልተገለጸ መረጃን :ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ተከተል

የአንድ ሰው አኗኗር የሚጓዝበት መንገድ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል አንድን ሰው “እየተከተሉ መጓዝ” ያ ሰው የሚያደርገውን ነገር ለማድረግ መፈለግን ወይም ሌሎች እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ነገር የሚያሳይ ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔርን በመታዘዝ ኑሩ” ( ዘይቤያዊን ወይም የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)

ትእዛዛቱን ፣ ሥርዓቱንና ደንቦቹን

እነዚህ ቃላት ሁሉም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ። በአንድነት እግዚአብሔር በሕጉ ውስጥ ያዘዛቸውን ነገሮች ሁሉ ያጎላሉ ። ( ድግግሞሽን :ይመልከቱ)

በፍጹም ልቡ እና በሙሉ ነፍሱ

የቃሉ ፈሊጥ “በፍጹም ልቡ” ማለት “ሙሉ በሙሉ” ማለት ሲሆን “በሙሉ ነፍሱ” ማለት ደግሞ “በሁለንተናው” ማለት ነው ። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ። ኣት: - “በሁለንተናው” ወይም “በሙሉ ኃይሉ” (ፈሊጥን እና ድግግሞሽን :ይመልከቱ)

በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን

ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ይህ መጽሐፍ እንደያዘ” ( ገቢራዊን

ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)
በኢየሩሳሌምም ሆነ በብንያም የተገኙት ሁሉ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “በኢየሩሳሌምና በቢንያም የሚኖሩ ሁሉ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)
በቃል ኪዳኑ ቆሙ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “የቃል ኪዳኑን ውል ተቀበሉ” ወይም “ቃል ኪዳኑን ለመታዘዝ ቃል ገቡ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ )
2 Chronicles 34:33
ኢዮስያስ ሁሉንም አስወገደ
ኢዮስያስ ሠራተኞቹን ይህን እንዲያደርጉ አዞ ነበር ። ኣት : - “ኢዮስያስ ሠራተኞቹን ሁሉ እንዲያስወግዱ አዘዘ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)
አስጸያፊ ነገሮች
ለእግዚአብሔር አጸያፊ የነበሩት ጣዖታት እነዚህ ናቸው ። ኣት: - “አስጸያፊዎቹ ጣዖታት” ( የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)
ለዘመኑ ሁሉ
የኢዮስያስ ሕይወት በ “ቀኖቹ” ተወክሏል። ኣት: “በሕይወቱ ዘመን ሁሉ” ወይም “ኢዮስያስ በሕይወት እስካለ ድረስ” (ሁለን በአንድ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ይመልከቱ)

---

Chapter 35
2 Chronicles 35:1
ኢዮስያስም ለእግዚአብሔር ፋሲካ አደረገ
ኢዮስያስ ህዝቡ እግዚአብሔር አባቶቻቸው እንዲያከብሩት ያዘዘውን ፋሲካ እንዲያከብሩ ሕዝቡን አዘዘ ።
በኢየሩሳሌም
የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ፋሲካን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም እንዲወጡ እግዚአብሔር ለሙሴ አዝዞት ነበር።
በመጀመሪያው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን
ይህ በዕብራይስጥ የቀን አቆጣጠር የመጀመሪያ ወር ነው። አሥራ አራተኛው ቀን በምዕራባዊ የቀን መቁጠሪያዎች የመጋቢት ወር መጀመሪያ ነው። ( የዕብራዊያንን ወራት እና ሕገኛ ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
ካህናቱን በየምድባቸው አኖራቸው
ካህናቱን በየምድባቸው ማስቀመጡ ለካህናቱ ምን ዓይነት ሥራ መሥራት እንዳለባቸው ለመንገር ምሳሌ ነው ። አንባቢው ኢዮስያስ ለካህናቱ መመሪያ እንዲሰጥ ሰራተኞቹን ትእዛዝ እንደሰጠ አንባቢው መረዳት አለበት ። ኣት: - “ሰዎች ለካህናቱ የትኛውን ሥራ እንደሚሰሩ እንዲነግራቸው አደረገ (ዘይቤያዊን እና የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)
አገልግሎት ላይ
“አገልግሎት” የሚለው የረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “በያአገልግሎታቸው” ወይም “በጥሩ ሁኔታ ለማገልገል” (የረቂቅ ስሞችን ፡ ይመልከቱ)
2 Chronicles 35:3
የእስራኤል ንጉሥ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ሠራ
ሰሎሞን ምናልባት ሌሎች ሰዎች ት ሥራውን እንዲሰሩ እንዳዘዘ አንባቢዎቹ ሊገነዘቡት ይገባል ። ኣት - “የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን ህዝቡ እንዲሠሩ አዝዞ ነበር” (የሚጠበቅ እውቀትን እና ያልተገለጸ መረጃን ፡ይመልከቱ)
በአባቶቻችሁ ቤቶችና በየክፍላችሁ
“ስም” የሚለው ቃል እያንዳንዳንዱን የዘር ሐረግ እያንዳንዱን ቤት እና እያንዳንዱን ምድብ የሚያመለክት የጋራ ስም ነው። ቋንቋህ “እንደ አባቶቻችሁ ቤቶች ስሞችና እንደ ክፍሎቻችሁ ሁሉ” ማለት ያስፈልገው ይሆናል ።
የዘርህ ቤቶች
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች የሚወክል ስም ነው ። ኣት: - “የአባትህ ዘሮች ቤተሰቦች” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)
ክፍሎች
ህዝቡ ካህናትንና ሌዋውያንን የተከፋፈሉባቸው ቡድኖች
የዳዊትን ሕግ እና የልጁ የሰሎሞንን ቃሎች
“ዳዊትና ልጁ ሰሎሞን የጻፏቸው መመሪያዎች”
2 Chronicles 35:5
ቦታችሁን ይዛችሁ በቅዱሱ ስፍራው ቆሙ
“በቤተ መቅደሱ ውስጥ ቦታችሁን ጠብቁ”
በክፍሎቻችሁ
ይህ ህዝቡ እያንዳንዱን ሌዋዊ የሾመበትን የሥራ ቡድንን ይመለከታል ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና መዋዕል 35 ፡ 4 እንዴት እንደተረጉሙት ይመልከቱ ።
የዘር ሐረግ ቤቶች
ይህ በሌዋውያን መካከል ያሉትን የተለያዩ ነገዶች ይመለከታል ። ለእያንዳንዱ ነገድ ወይም ቅድመ አያት ቤት በተሰየመው ዓይነት ሥራ መሠረት ሌዋውያን ለተለያዩ የሥራ ቡድኖች የተመደቡ ይመስላል ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና 35፡4 እንዴት እንደተረጎምከ ተመልከት ።
ራሳችሁን ቀድሱ
ይህ ምናልባት ካህናቱና ሌዋውያኑ በቤተመቅደሱ ውስጥ ከመሥራታቸው በፊት ራሳቸውን የሚያጥቡትን ሊያመለክት ይችላል።
በሙሴ እጅ እንደ ተሰጠው እንደ እግዚአብሔር ቃል ይደረግ ዘንድ
እዚህ “እጅ” የሚለው ቃል ራሱ ሙሴን ያመለክታል። ትዕዛዙን ለመስጠት እግዚአብሔር እንደ ወኪሉ ሙሴን ተጠቅሟል ። ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለሕዝቡ የሰጣቸውን ትእዛዛት ሁሉ ለመታዘዝ” ወይም “እግዚአብሔር ሙሴን ለሕዝቡ እንዲናገር ያዘዘውን ሁሉ ለመፈጸም” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ )
2 Chronicles 35:7
አጠቃላይ መረጃ
ቁጥሮችን እና የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ
ሠላሳ ሺህ ጠቦቶች ነበሩ
“30,000 በጎች” ( ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
ልጆች
የፍየል ግልገሎች
ሦስት ሺህ ወይፈኖች
“3,000 ወይፈኖች” ( ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
እነዚህ ከንጉሡ ንብረቶች ነበሩ
“እነዚህ ሁሉ የበግ እና የፍየል ግልገሎች ፣ እና በሬዎች የሰጣቸው እርሱ ነበር”
2,600 በጎችና ፍየሎች
“ሁለት ሺህ ስድስት መቶ በጎችና ፍየሎች” ( ቁጥሮችን፡ይመልከቱ)
ሦስት መቶ በሬዎች
“300 በሬዎች” ( ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
ኬልቅያስ... ዘካርያስ... ይሒኤል... ለፋሲካው... ሸማያ... ናትናኤል... ሐሻቢያ... ይዒኤል ...ዮዛባት
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተረጓጎም ፡ይመልከቱ)
አምስት ሺህ በጎችና ፍየሎች
“5,000 ፍየሎችና በጎች” ( ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
አምስት መቶ በሬዎች
“500 በሬዎች” ( ቁጥሮችን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 35:10
አገልግሎቱ ተዘጋጅቶ ነበር
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “ፋሲካውን ለማከናወን የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ አዘጋጁ” (ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)
ክፍሎቻቸው
ሕዝቡ ካህናቱንና ሌዋውያኑን የከፋፈሉባቸው ቡድኖች ነበሩ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና 35 ፡ 4 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ።
ከሌዋውያን እጅ የተቀበሉትን ደም
እዚህ “እጅ” የሚለው ቃል ሌዋውያንን ያመለክታል። ኣት: - “ሌዋውያኑ የሰጧቸው ደም” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከልን ፡ይመልከቱ)
በየአባቶቻቸው ቤቶች
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚወክል ስም ነው ። ኣት: - “የአባቶቻቸው ዘሮች ቤተሰቦች” ( የባህሪ ስምን ፡ ይመልከቱ)
2 Chronicles 35:13
አጠቃላይ መረጃ
“እነርሱ” እና “ራሳቸው” የሚሉት ምሳሌዎች በሙሉ ሌዋውያንን ያመለክታሉ (2ኛ ዜና መዋዕል 35:10)።

የፋሲካውን የበግ ግልገል በእሳት ጠበሱት
“የፋሲካውን የበግ ግልገል በእሳት አበሰሉት”
እነርሱም በምንቸት ፣ በሰታቴ እና በድስትም ቀቀሉ
“የተለያየ መጠን ባለው ዕቃዎች ውስጥ በውኃ አበሰሏቸው”
ለእራሳቸው እና ለካህናቱ የተቀደሰውን ቁርባን ያዘጋጁ ነበር
“ የሚበሉትንም የተቀደሰውን ቁርባን ለራሳቸውና ለካህናቱ አዘጋጁ”
2 Chronicles 35:15
በዳዊት ፣ በአሳፍ ፣ ኤማን እና በንጉሡም ባለ ራእይ ኤዶታም መመሪያ መሠረት
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - እንደ “ዳዊት ፣ አሳፍ ፣ ኤማን እና የንጉሡ ባለ ራእዩ ኤዶታም እንደመራቸው” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ ይመልከቱ)
ኤማን…ኤዶታም
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። ( የስሞች አተረጓጎምን፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 35:16
የእግዚአብሔር አገልግሎት ሁሉ ተፈጸመ
ይህ በፋሲካ በዓል ዝግጅት ፣ ከቅዱሳኑ እና ከእግዚአብሔር አምልኮ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ሁሉ ይመለከታል ። “አገልግሎት” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል እና ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል ኣት: - “እግዚአብሔርን ለማገልገል መከናወን የነበረበትን ነገር ሁሉ አከናወኑ” ( የረቂቅ ስሞችን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)
ፋሲካውን ጠበቁ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: - “ፋሲካውን አደረጉ” ወይም “ፋሲካውን አከበሩ” ( ፈሊጥን ፡ይመልከቱ)
የቂጣ በዓል
ይህ በዓሉን ማክበርን ያመለክታል ።ኣት - “ከዚያም ያቂጣ በዓልን ጠበቁ” ወይም “ከዚያ በኋላ ያቂጣ በዓልን አከበሩ” ( የቃላት ግድፈትን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 35:18
እንዲህ ዓይነቱ የፋሲካ በዓል በእስራኤል ፈጽሞ ታይቶ አይታወቅም
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ኣት: - “በእስራኤል ውስጥ እንዲህ ያለ የፋሲካ በዓል አከባበር ኖሮ አያውቅም” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)
በእስራኤል ተካሄደ
ይህ ያልተከፈለቺውን እስራኤልን ይመለከታል፣ ይህ የሰሜናዊው መንግሥት እና የደቡባዊው መንግሥት ተበብሎ ከመከፋፈሉ በፊት የነበረውን እስራኤል ያመለክታል ።
ከቀናቱ
“ከጊዜው”
ሌሎቹ የእስራኤል ነገሥታት
እዚህ“እስራኤል” የሚያመለክተው የሚያመለክተው የሰሜናዊውን የእስራኤልን መንግሥት ነው ።
ይህ ፋሲካ ተጠበቀ
ይህ በገቢራዊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ይህን ፋሲካ አከበሩ” ( ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ ፡ይመልከቱ)
ተጠበቀ
ይህ ፈሊጥ ነው ። ኣት: “ጠደረገ” ወይም “ተከበረ” ( ፈሊጥ፡ይመልከቱ)
አሥራ ስምንተኛው ዓመት
“18ኛው ዓመት” ( ሕገኛ ቁጥሮች ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 35:20
ቤተ መቅደሱን አሰናዳ
ይህ ማለት በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበረውን አምልኮ በማደስ እንደ እግዚአብሔር ኃሳብ እንዲሆን አድርጎታል ። ኣት: “የቤተመቅደሱን አምልኮ ወደ ተገቢው መንገድ መልሶታል” (የሚጠበቁ እውቀቶችን ወይም ያልተገለጹ መረጃዎችን ፡ይመልከቱ)
የግብፅ ንጉሥ ኒካዑ ወጣ
ይህ የግብፅ ንጉሥ ስም ነው ። እዚህ ንጉሡ ራሱን እና ሠራዊቱን ይወክላል ። ኣት: “የግብፅ ንጉሥ ኒካዑ ከሠራዊቱ ጋር ወጣ” ( የስሞች አተረጓጎምን እና ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱሰን በሁሉ መወከልን ፡ይመልከቱ)
በከርከሚሽ ላይ
ይህ የከተማ ስም ነው ። እዚህ ከተማዋ የሚኖሩትን ሰዎች ትወክላለች ። ኣት: - “በከርከሚሽ ሰዎች ላይ” ( የስሞችን አተረጓጎም እና የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)
ኢዮስያስ እርሱን ሊዋጋ ሄደ
እዚህ ሁለቱም ኢዮስያስ እና ኒካዑ ራሳቸውን እና የጀባቸውን ሠራዊቶቻቸውን ይወክላሉ ። ኣት: “ኢዮስያስና ሠራዊቱ ኒካዑ እና በሠራዊቱን ሊዋጉ ሄዱ” ( ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ይመልከቱ)
የይሁዳ ንጉሥ ሆይ ፣ ከአንተ ጋር ምን አለኝ?
ኒካዑ ይህን አወያይ መጠይቅ ተጠቅሞ ለኢዮስያስ ከእሱ ጋር ግጭት እንደሌለው እና ኢዮስያስም እርሱን ማጥቃት እንደሌለበት ይነግረዋል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል ።ኣት: “የይሁዳ ንጉሥ ሆይ ፣ እኔን ለማጥቃት ምክንያት የለህም።” ( አወያይ መጠይቅን ፡ይመልከቱ)
በአንቺ ላይ አልመጣሁም
እዚህ ንጉሡ ኢዮስያስ መንግሥቱን ይወክላል ። ኣት: - “የንተን መንግሥት እየተዋጋሁ አይደለም” ( ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ይመልከቱ)
ከቤቱ ጋር
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የባቢሎንን ቤት ሲሆን “ቤት” ማለት መንግስቱን የሚወክል ነው ። መንግሥቱ የሚለው የባቢሎናውያንን ሰራዊት የሚያወሳ ዐውደ-ጽሑፍ ነው ። ኣት: - “ከባቢሎን ቤት ጋር ” (የባህሪ ስም እና ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 35:22
እራሱን ሌላ አስመሰለ
ሌሎቹ ወታደሮች እንዳያስተውሉት ኢዮስያስ ሌላ ሰው መስሎ ራሱን ገለጠ ።
ከእርሱ ጋር ለዋጋ
“እርሱ” የሚለው ቃል ራሱን እና ሰራዊቱን የሚወክለውን ኒካዑን ያመለክታል ። ኣት: - “ከግብጽ የጦር ሠራዊት ጋር ለዋጋ” ( ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ይመልከቱ)
ከእግዚአብሔር አፍ የመጣውን
እዚህ የእግዚአብሔርን ንግግር አፅንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር በ “አፉ” ተወክሏል ። ኣት: “ከእግዚአብሔር የመጣውን” ወይም “እግዚአብሔር የተናገረውን” ( ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ይመልከቱ)
ስለዚህ እርሱ ሄደ
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢዮስያስን እና ሠራዊቱን ነው ። ኣት: - “እርሱና ሠራዊቱ ሄዱ” (ሁሉን በአንዱ መወከልን ፡ይመልከቱ)
የመጊዶ ሸለቆ
ይህ የቦታ ስም ነው ። (የስሞችን አተረጓጎም፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 35:23
መላው ይሁዳና ኢየሩሳሌም
“ይሁዳ” እና “ኢየሩሳሌም” በዚያ የሚኖሩትን የሚያመለክቱ ናቸው ። ኣት: - “የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች ሁሉ” (የባህሪ ስምን ፡ይመልከቱ)
2 Chronicles 35:25
እስከዛሬ
ይህ ማለት ጸሐፊው የጻፈበትን ቀን ነው ። ይህንን በ 2 ኛ ዜና ምዕራፍ 5 9 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት ።
እነሆ ፣ እነርሱ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች-1) “እነርሱ ያሉት እዚህ ነው፡ እነርሱ” ወይም 2) “እነርሱ አሁንም አሉ ፣ እነርሱ” ።
የልቅሶ ግጥም
ይህ የጥንት የቀብር መዝሙሮች ጥቅል ነው ።
የደረጋቸው መልካም ሥራዎቹ
ይህ በንቃት ቅርፀ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ያከናወናቸውን መልካም ሥራዎች” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)
የተጻፈው
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: “ቃላቶቹ”( ገቢራዊን ወይም ተቢሮአዊን ፡ይመልከቱ)
ሥራውም ... በመጽሐፉ ተጽፎአል
ይህ በገቢራዊ ቅርፀ ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሰዎችም ስለ ሥራዎቹ ሁሉ… በመጽሐፉ ላይ ጻፉ” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን ፡ይመልከቱ)
የፊተኛውና የኋለኛውም ሥራው
ይህ የሚያመለክተው ከንግሥና ጀምሮ እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ድረስ ያከናወናቸውን ታላላቅ ነገሮችን ሁሉ ነው ። ኣት: - “ያደረገው ነገር ሁሉ” ወይም “ከንግሥናው መጀመሪያ አንስቶ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ያከናወናቸውን ነገሮች ሁሉ” ( ሜሪዝምን፡ይመልከቱ)
የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍት

Chapter 36
2 Chronicles 36:1
ኢዮአክስ
ይህ የወንድ ስም ነው። ( የስሞችን አተረጓጎም:ይመልከቱ)
በአባቱ ቦታ
“በእርሱ ቦታ” የሚለው ሐረግ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው ፣ትርጉሙ “በእርሱ ፋንታ” ማለት ነው።
ዕድሜው ሃያ ሦስት ዓመት… ሦስት ወር
“ዕድሜው 23 ዓመት… 3 ወር” ( ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 36:3
የግብፅ ንጉሥ በኢየሩሳሌም አወጣው
የሚለው አገላለጽ “በኢየሩሳሌም አስወግዶታል” ማለት በኢየሩሳሌም ላይ ንጉሥ እንዳይሆን አደረገው ማለት ነው። ኣት: - “የግብፅ ንጉሥ በኢየሩሳሌም ንጉሥ እንዳይሆን አግዶታል” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
ምድሪቱን ዕዳ ጣለባት
እዚህ “መሬት” የሚለው ቃል በዚያ የሚኖሩትን ያመለክታል ። ኣት: - “የአገሩን ሰዎች ዕዳ ጣለባቸው” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
አንድ መቶ መክሊት ብርና አንድ መክሊት ወርቅ
ይህንን ወደ ዘመናዊ ልኬት ሊለውጡት ይችላሉ። አንድ መክሊት 33 ኪሎ ግራም ያህል ነበር። ኣት: - “ሠላሳ ሦስት መቶ ኪሎ ግራም ብር ፣ ሠላሳ ሦስት ኪሎግራም ወርቅ” ወይም “3,300 ኪሎ ግራም ብር እና 33 ኪሎ ግራም ወርቅ” ( መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገንዘብን እና ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
ኤልያቄም… ኢዮአክስ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው ። ( የስሞችን አተርጓጎም :ይመልከቱ)
2 Chronicles 36:5
ዕድሜው ሃያ አምስት ዓመት… አሥራ አንድ ዓመት
“25 ዓመት… የ 11 ዓመት ልጅ” (ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት መጥፎ የሆነውን ነገር አየ
እዚህ “እይታ” የሚለው ቃል ፍርድን ያመለክታል ። እግዚአብሔር የኢዮአቄምን ድርጊት አየ ፣ አልተቀበለውም። ኣት: - “እግዚአብሔር እንደሆነ የወሰነው” ወይም “እግዚአብሔር እንደ ክፉ አድርጎ የሚቆጠረው” ( የባህሪ ስምን:ይመልከቱ)
እርሱን መታው
“እርሱ” የሚለው ቃል ኢዮአክስም ያመለክታል ። ኢዮአክስም ኢየሩሳሌምን ወይንም የይሁዳን ህዝብ ይወክላል ። ኣት: - “ኢየሩሳሌምን አጠቃ” ወይም “ ይሁዳን አጠቃ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
እንዲሁ ናቡከደነፆር ወሰደ
ናቡከደነ ፆር ንጉሥ ስለነበረ ወታደሮቹ ይህን እንዲፈጽሙ አድርጎ ይሆናል። ኣት: - “ናቡከደነፆር ወታደሮቹን ተሸክመው እንዲወስዱ አደረገ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ቤት
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር መቅደስ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 36:8
ያደረጋቸው ርኩስ ነገሮች
ይህ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር የሚጠላውን የሐሰት አማልክትን ማምለክን ያመለክታል ።
በእርሱም የተገኘው ሁሉ
ይህ ፈሊጥ የሚያመለክተው ሰዎች ጥፋተኛ ብለው እርሱን ሊከሱት ስለሚችሉት ድርጊቶቹ ነው ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል ። ኣት: - “ሰዎች በእርሱ ላይ ያገኙትን” ወይም “በሰዎች ሊያስከስሰው የሚችል ድርጊት” (ፈሊጥን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
እነሱ የተጻፉ ናቸው
“ማንም ሰው በመጽሐፉ ውስጥ … እስራኤልን ማየትና እዚያ እንደተጻፈ ማየት ይችላል” ( ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
እነርሱ በመጽሐፉ ተጽፈዋል
ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ኣት: “አንድ ሰው በመጽሐፉ ውስጥ ጻፋቸው” ወይም “ስለ እነርሱ በመጽሐፉ ውስጥ ማግኘት ትችላላህ” ( ገቢራዊ ወይም ተብሮአዊ:ይመልከቱ)
የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ
ይህ የማይገኝ መጽሐፍ ነው። በ 2 ኛ ዜና 35፡ 27 ውስጥ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት ።
በእርሱ ቦታ ነገሠ
“በእርሱ ቦታ” የሚለው ሐረግ ስእላዊ አገላለጽ ሲሆን “በእርሱ ፋንታ” የሚል ትርጉም አለው ። “በኢዮአቄም ፋንታ ነገሠ” ( ዘይቤያዊን:ይመልከቱ)
2 Chronicles 36:9
የስምንት ዓመት ልጅ… ሦስት ወር እና አስር ቀናት
“ዕድሜው 8 ዓመት… 3 ወር እና 10 ቀን” (ቁጥሮችን:ይመልከቱ)
በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ የሆነውን ነገር
እዚህ “እይታ”የሚለው ፍርድን ይወክላል ። እግዚአብሔር የዮአኪን ድርጊት አይቷል እናም አልተቀበለውም ። ኣት:- “እግዚአብሔር ክፉ እንደሆነ የወሰነው” ወይም “እግዚአብሔር ክፉ እንደሆነ የቆጠረው” (ዘይቤያዊን:ይመልከቱ)
ወደ ባቢሎን አመጣው
ዮአኪንን ወደ ባቢሎን አመጣ ”
የእግዚአብሔር ቤት
እዚህ “ቤት” የሚለው ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” ( የባህሪ ስምን:ይመልከቱ)
ዘመዱ
“ዮአኪንን ዘመድ”
2 Chronicles 36:11
ሃያ አንድ አመት… አሥራ አንድ ዓመት
“ዕድሜው 21 ዓመት… 11 ዓመት” ( ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት መጥፎ የሆነውን ነገር
እዚህ “ፊት” የሚለው ፍርድን ያመለክታል ። እግዚአብሔር የሴዴቅያስን ሥራ አየ ፤ አልተቀበለውምም። ኣት: “አምላኩ እግዚአብሔር ክፉ እንደ ሆነ የወሰነው ወይም “አምላኩ እግዚአብሔር ክፉ እንደሆነ የቆጠረው” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ከእግዚአብሔር አፍ የተናገረ
እዚህ “አፍ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ይወክላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር ለእርሱ የተናገረውን ቃል የተናገረው ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 36:13
ሴዴቅያስም ወደ እግዚአብሔር እንዳይመለስ አንገቱን አደነደነ ልቡንም አደነደነ
“አንገቱን አደነደነ” እና “ልቡን አደነደነ” የሚሉት ኃረጎች ሁለቱም እምቢተኝነትን የሚወክሉ ንግግሮች ናቸው ። ሴዴቅያስ እግዚአብሔርን ለማምለክ ፈቃደኛ አለመሆኑ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ለማለት እንቢ ማለት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል ። ኣት: - “ሴዴቅያስ እግዚአብሔርን ለማምለክ እምቢ አለ” ( ድግግሞሽን እና ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
የአሕዛብን ርኩስ ልምምዶች ተከትለዋል
“ልምምዶች መከተል” የሚለው ፈሊጥ እነዚህን ነገሮች ማድረግ ማለት ነው። ኣት: - “አሕዛብ ያደረጉትን አስጸያፊ ተግባር አደረጉ” ( ፈሊጥን :ይመልከቱ)
አስጸያፊ ልምዶች
ይህ ሐረግ ሌሎች አማልክትን ማምለክን ያመለክታል ።
የእግዚአብሔርንም ቤት አረከሱ
ለእግዚአብሔር አገልግሎት ጥቅም ላይ የማይውል ቦታ ቆሻሻ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል ። “ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አረከሱ” ( ዘይቤያዊን እና የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 36:15
ደግመው ደጋግመው
"ብዙ ጊዜ"
የሚኖርበት ቦታ
ይህ ቤተመቅደሱን ያመለክታል ።
የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ ተነሳ
እዚህ “ተነሳ” የሚለው ቃል የድርጊትን መጀመር ያመለክታል ። እግዚአብሔር ሕዝቡን በቁጣው መቅጣቱ ቁጣው በእነርሱ ላይ እርምጃ እንደሚወስድ ሰው ሆኖ ተቆጥረዋል። ኣት: - “እግዚአብሔር በቁጣው ሕዝቡን መቅጣት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ጀመረ” (ዘይቤያዊን :ይመልከቱ)
ፈውስም አልተገኘለትም
ይህ ፈሊጥ ሲሆን የተከሰተውን ለመከላከል ማንም ምንም ነገር ማድረግ አይችልም ማለት ነው ። ኣት: - “እርሱን ማስቀረት የሚቻልበት ምንም መንገድ አልነበረም” (ፈሊጥን:ይመልከቱ)
2 Chronicles 36:17
እግዚአብሔር የከለዳውያንን ንጉሥ በእነሱ ላይ አመጣባቸው
“በእነሱ ላይ አመጣባቸው”የሚለው ፈሊጥ ማለት ከሠራዊቱ ጋር ጥቃት እንዲሰነዝር ማድረግ ማለት ነው ። ኣት: - “እግዚአብሔር የከለዳውያንን ንጉሥ ጥቃት እንዲፈጽምባቸው አመጣባቸው እርሱም” (ፈሊጥን :ይመልከቱ)
ወጣቶቻቸውን በሰይፍ ገደለ
ምናልባት ንጉሡ ወጣቶቹን በግል አልገደላቸውም ይሆናል። ይልቁንም ሠራዊቱ ገድሏቸዋል ። ኣት: - “ሠራዊቱ ወጣቶቻቸውን በሰይፍ ገድለዋቸዋል” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ሁሉንም በእጁ አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ “እጅ” እነርሱን ለማሸነፍ የሚያስችል የኃይል መገለጫ ነው ። ኣት: - “የከለዳውያን ሠራዊት ድል እንዲያደርግ እግዚአብሔር ፈቅዷል” ( የባህሪ ስምን : ይመልከቱ)
2 Chronicles 36:18
የእግዚአብሔር ቤት... የእግዚአብሔር ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተመቅደሱን ይወክላል ። ኣት: - “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ... የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
እነርሱ አቃጠሉ
“እነርሱ” የሚያመለክተው የባቢሎናውያንን ወታደሮች ነው።
2 Chronicles 36:20
ንጉሡ ወደ ባቢሎን ተወሰደ
እዚህ “ንጉሡ” የሚለው ሥራውን እንዲሠሩ ያዘዛቸውን ይርሱን ወታደሮቹ ያመለክታል ። “ተወስዷል ” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን እነርሱን በኃይል ወደ ባቢሎን ማምጣት ማለት ነው ። ኣት: - “ንጉሡ ሠራዊቱን በኃይል ወደ ባቢሎን ወሰደው” ( የባህሪ ስምን እና ፈሊጥን :ይመልከቱ)
እስከ ፋርስ መንግሥት አገዛዝ ድረስ
“የፋርስ መንግሥት ወደ ሥልጣን እስኪመጣ ድረስ”
የእግዚአብሔር ቃል በኤርምያስ አፍ
እዚህ “ቃል” የሚለው ስም “ተናገር” ከሚለው ግስ ጋር መተርጎም ይችላል ። “አፍ” የሚለው ቃል ኤርሚያስን ይወክላል ። ኣት: - “እግዚአብሔር በኤርምያስ በኩል የተናገረው” ወይም “ኤርምያስ የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወከል :ይመልከቱ)
ምድሪቱ ሰንበትን በማድረግዋ እስክታርፍ ድረስ
ሰዎቹ በየሰባት ዓመቱ መሬቱን ባለማረስ የሰንበትን ሕግ መታዘዝ ነበረባቸው። ይህ ሐረግ ስለዚህ ሲናገር ምድርን እንደሰው የሰንበትን ሕግ የምትታዘዝ እና የምታርፍ አስመስሏታል ። ኣት: - “ምድሪቱ በሰንበት ሕግ እስክታርፍ ድረስ” ወይም “በሰንበት ሕግ በተደነገገው መሠረት ምድሪቱን ማንም ገና እስከማያርስ ድረስ” ( የባህሪ ስም: ተስብኦትን :ይመልከቱ)
በተተወችበት ዘመን ሁሉ ሰንበትን አከበረች
“እርሷ” የሚለው ቃል መሬትን ያመለክታል ። ምድሪቱ ሰንበትን የምታከብር ሰው እንደ ሆነች ተደርጋ ተገልጻለች ። ኣት: - “ምድሪቱ እስከተፈታች ድረስ የሰንበት ሕግ መስፈርቶች ተፈጽመዋል ማለት ነው ” ( የባህሪ ስምን: ተስብኦትን :ይመልከቱ)
በዚህ መንገድ ሰባ ዓመት ለማለፍ ነው
ምድሪቱ ባድማ ሆና ለ 70 ዓመት ቆየች ( ቁጥሮችን :ይመልከቱ)
2 Chronicles 36:22
በመጀመሪያው ዓመት
ይህ የንጉሥ ቂሮስ የአገዛዝ ዘመን መጀመሪያን ያመለክታል ። ( ሕገኛ ቁጥሮችን : ይመልከቱ)
በኤርምያስ አፍ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው
እዚህ “ቃል” የሚለው ስም “ተናገር” ከሚለው ግስ ጋር መተርጎም ይችላል ። “አፍ” የሚለው ቃል ኤርሚያስን ይወክላል ። ይህ በገቢራዊ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል ። ኣት: - “እግዚአብሔርም በኤርምያስ የተናገረው ነገር እንዲፈጸም” ወይም “ኤርምያስ የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ” ( ሁሉን በአንዱ ወይም አንዱን በሁሉ መወክልን እና ገቢራዊን ወይም ተብሮአዊን :ይመልከቱ)
እግዚአብሔር የፋርስ ንጉሥ የሆነውን የቂሮስን መንፈስ አነሳሳ
መንፈስን ማነሳሳት አንድን ሰው እርምጃ መውሰድ እንዲፈልግ ማድረግ ነው። ኣት: - “እግዚአብሔር የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ እርምጃ ለውሰድ እንዲፈልግ አደረገው” ( አንዱን በሁሉ ወይም ሁሉን በአንዱ መወከልን :ይመልከቱ)
የምድር መንግሥታት ሁሉ
ቂሮስ የማይገዛባቸው መንግስታት ስለነበሩ ይህ ግነት ነው ። ( ግነትን እና አጠቃላይን :ይመልከቱ)
ለእርሱ ቤት ይሠሩ ዘንድ
እዚህ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተ መቅደስን ይወክላል ። ኣት: - “ለእርሱ ቤተ መቅደስ ለመሥራት” ( የባህሪ ስምን :ይመልከቱ)
የእርሱ ህዝብ
“የእግዚአብሔር ሕዝብ”
ወደ ምድሪቱ ይሂድ
“ያ ሰው ወደ ይሁዳ ምድር ይሂድ”

---

Chapter 1
Ezra 1:1
የመጀመሪያ ዓመት
ይህ የሚያሳየው የቂሮስን የመጀመሪያ የንግሥ ዓመት ነው።
በኤርምያስ አፍ የተነገረውን ቃሉን እግዚአብሔር ፈጸመው
እዚህ ላይ ‹‹አፍ›› የሚለው የተነገረውን ለማለት ነው። ‹‹ ኤርምያስ እግዚአብሔር ያደርገዋል ብሎ የተነበየውን እግዚአብሔር አደረገው።፡››
ያሕዌ
ይህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ ራሱን የገለጠበት የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህንን ስለመተርጎም በትራንስሌሽን ወርድ ፔጅ ላይ የተጻፈውን ተመልከት።
እግዚአብሔር---የቂሮስን መንፈስ አስነሣ
እዚህ ላይ ቂሮስ የተገለጸው በመንፈሱ ነው። ይህም የሚናገረው እግዚአብሔር ቂሮስን መንፈሱን ‹‹በማስነሣት›› ፈቃዱን እንዲያደርግ መፈለጉን ነው። ‹‹እግዚአብሔር --- ቂሮስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ እንዲወድ አደረገው››
የቂሮስ አዋጅ በግዛቱ ሁሉ ላይ ተነገረ
አዋጁ የሚነገረውን መልእክት ምንነት የሚወክል ሲሆን ፣ በግዛቱ ሁሉ ላይ የሚለው ደግሞ በሚገዛው ምድር ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ይወክላል። ‹‹ ቂሮስ በመንግሥቱ ሁሉ ላይ አዋጅ አስነገረ።››
የተጻፈውና የተነገረው ምንድን ነው
ይህ በአድራጊ ግስነት ሊተረጎም ይችላል። ቂሮስ ያወጀውን አዋጅ በሚገዛው ግዛት ሁሉ ላ ሰዎች እንዲደርስ ሌሎች ሰዎች እንደረዱት ተደርጎ ቢተረጎም የተሻለ ነው።
‹‹ቂሮስ የጻፈውን መልእክተኞቹ ሲያነቡ ሕዝቡ ሰሙአቸው››
የምድርን መንግሥታት ሁሉ
እዚህ ላይ ‹‹ሁሉ›› የሚለው ቃል የተጋነነ ነው፤ ቂሮስ የማይገዛቸውን ግዛቶች ሁሉ ያጠቃለለ ይመስላል።
በይሁዳ --- ቤት ለእርሱ
ይህ ቤት ሕዝቡ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ቤት እንደሆነ ግልፅ ማድረግ ያስፈልጋል። ‹‹ በይሁዳ --- ሕዝቡ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ቤት ››
Ezra 1:3
የእርሱ ሕዝብ
የእግዚአብሔር ሕዝብ
በሚኖርበትም ስፍራ ሁሉ ለቀረው ሰው --- ይርዱት
ባሉበት ለመቅረት የመረጡት እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የመረጡትን በገንዘብና በቁሳቁስ ይርዱአቸው።
Ezra 1:5
ሥራቸው
ቀደም ባለው ቁጥር እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር ያነሣሣቸው ሰዎችን ሥራ ያመለክታል።
እግዚአብሔር እንዲሄድ መንፈሱን ያነሣሣው እያንዳንዱ
ያነሣሣው የሚለው ቃል አንድን ሰው የሥራው ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግን ያመለክታል። ዕዝራ 1:1 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። ‹‹እግዚአብሔር

እንዲሄድ ያደረገው እያንዳንዱ››
Ezra 1:7
ሚትሪዳጡ --- ሰሳብሳር
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው
በመዝገብ ቤት ኃላፊው በሚትሪዳጡ እጅ አወጣቸው
ዕቃዎቹን በአንድ ሰው እጅ አስቀመጡአቸው የሚለው አባባል ያ ሰው በእጁ የገባውን ዕቃ እንደወደደው ለማድረግ ይፈቀድለታል ማለት ነው። ‹‹ሚትሪዳጡን በንብረቶቹ ላይ ኃላፊ አደረገው›› ወይም ‹‹ ሚትሪዳጡን በዕቃዎቹ ላይ ኀላፊነት ሰጠው..
ሂሳብ ሹም
በገንዘብ ላይ የተሾመ ባለሥልጣን
Ezra 1:9
አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ቁጥር የተሰጣቸው የዕቃዎች ዝርዝር ናቸው።
ሰላሣ--- አንድ ሺህ --- ሃያ - ዘጠኝ --- 410
‹‹30 --- 1,000 --- 29 --- አራት መቶ አሥር››
ሰሐኖች --- ጎድጓዳ ሰሐኖች
ለእግር መታጠቢያ የሚያገለግሉ ውኃ የሚይዙ ዕቃዎች
5,400 --- ጠቅላላ
‹‹ አምስት ሺህ አራት መቶ --- ጠቅላ።›› እነዚህ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ፣ ከዚህ በላይ በተናጠል የተዘረዘሩ ጠቅላላ ዕቃዎች ቁጥር ነው

---

Chapter 2
Ezra 2:1
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ክፍል ከስደት የተመለሱትን ሰዎች ስም ዝርዝር በመግለጽ ይጀምራል።
ወጡ
ይህ ወደ ኢየሩሳሌም መጓዛቸውን የሚያመለክት ነው። ‹‹ተመለሱ›› ወይም ‹‹ተመልሰው መጡ››
ሠራያ፣ ረዕላያ፣ መረዶክዮስ፣ በላሳን፣ መሴፋር፣ በጉዋይ፣ ሬሁም፣ እና በዓና
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።
ቁጥራቸውም ይህ ነው
ይህ የሚያሳየው የሰዎቹን የስም ዝርዝር ነው 2፡3-35
Ezra 2:3
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቀጣይ የስም ዝርዝር እና እያንዳንዱን ቡድን ከነቁጥራቸው የሚያቀርብመረጃ ነው።
Ezra 2:7
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቀጣይ የስም ዝርዝር እና እያንዳንዱን ቡድን ከነቁጥራቸው የሚያቀርብመረጃ ነው።
ዛቱዕ --- ዘካይ --- ባኒ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።
Ezra 2:11
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቀጣይ የስም ዝርዝር እና እያንዳንዱን ቡድን ከነቁጥራቸው የሚያቀርብመረጃ ነው።
ቤባይ --- ዓዝጋድ --- አዶኒቃም
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።
በጉዋይ
ይህ የሰው ስም ነው። ዕዝራ 2፡02ን እንደተ እንደተረጎምከው ተመልከት
Ezra 2:15
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቀጣይ የስም ዝርዝር እና እያንዳንዱን ቡድን ከነቁጥራቸው የሚያቀርብ መረጃ ነው።
ዓዲን --- አጤር --- ቤሳይ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።
ዘጠና-ስምንት
‹‹98››
Ezra 2:19
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቀጣይ የስም ዝርዝር እና እያንዳንዱን ቡድን ከነቁጥራቸው የሚያቀርብ መረጃ ነው። ከምዕራፍ 2፡21 ጀምሮ የተጠቀሱት ከመጀመሪያው ከመጡበት ስፍራ ጋር የተዘረዘሩ ስሞች ናቸው።
ሐሱም --- ጋቤር
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።
ዘጠና-አምስት --- ሃምሳ-ስድስት
‹‹95 --- 56››
የቤተልሔም ልጆች
ዘሮቻቸው በይሁዳ ከተሞች ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ስም ዝርዝር እና ቁጥራቸው ከዚህ ይጀምራል።
ነጦፋ
ይህ በይሁዳ ያለ ከተማ ስም ነው።
Ezra 2:23
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ዘሮቻቸው ይኖሩበት ከነበረው ስፍራ ጋር የተጠቀሱ የእያንዳንዱ ቡድን ስም ዝርዝር ቀጣይ ክፍል ነው።
ዓናቶት --- ዓዝሞት --- ቂርያትይዓሪም --- ከፊራ --- ብኤሮትም --- ጌባ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።
አርባ-ሁለት
‹‹42››
Ezra 2:27
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ዘሮቻቸው ይኖሩበት ከነበረው ስፍራ ጋር የተጠቀሱ የእያንዳንዱ ቡድን ስም ዝርዝር ቀጣይ ክፍል ነው።
ማክማስ --- ናባው --- መጌብስ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።
ሃምሳ-ሁለት
‹‹52››
Ezra 2:31
አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ዘሮቻቸው ይኖሩበት ከነበረው ስፍራ ጋር የተጠቀሱ የእያንዳንዱ ቡድን ስም ዝርዝር ቀጣይ ክፍል ነው።
ካሪም --- ሎድ --- ሐዲድ ---- ኦኖ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።
Ezra 2:34
አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ዘሮቻቸው ይኖሩበት ከነበረው ስፍራ ጋር የተጠቀሱ የእያንዳንዱ ቡድን ስም ዝርዝር ቀጣይ ክፍል ነው።
ሴናዓ
ይህ የቦታ ስም ነው።
Ezra 2:36
አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ካህናት ዘሮቻቸው ይኖሩበት ከነበረው ስፍራ ጋር የተጠቀሱ የእያንዳንዱ ቡድን ስም ዝርዝር ቀጣይ ክፍል ነው።
ዮዳኤ --- ኢሜር --- ፋስኮር --- ካሪም
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው።
ኢያሱ
ይህ የሰው ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2፡06 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ካሪም
በዕዝራ 2፡32 የተጠቀሰው ‹‹ካሪም›› የቦታ ስም ነው፣ ነገር ግን እዚህ የተጠቀሰው ‹‹ካሪም ›› የሰው ስም ነው።
Ezra 2:40
አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሌዋውያን ዘሮቻቸው ይኖሩበት ከነበረው ስፍራ ጋር


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የተጠቀሱ የእያንዳንዱ ቡድን ስም ዝርዝር ቀጣይ ክፍል ነው።

ቀድምኤል --- ሆዳይዋ --- ሰሎም --- ጤልሞን፣ ዓቁብ፣ ሐጢጣ፣ እና ሶባይ

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው።

ሰባ-አራት

‹‹74››

በር ጠባቂዎች

እነዚህ በቤተ መቅደሱ በሮች ለመግባት ኃላፊነት የተሰጣቸው ናቸው።

አጤር

ይህ የሰው ስም ነው። ይህን ስም በዕዝራ 2:16 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 2:43

አጠቃላይ መረጃ:-

ይህ ክፍል ዘሮቻቸው ከምርኮ የተመለሱትን የሌዋውያን ስም ዝርዝር በቀጣይነት የያዘ ነው።

ሲሐ፣ ሐሱፋ፣ ጠብዖት፣ ኬራስ፣ ሲዓ፣ ፋዶን፣ ልባና፣ አጋባ፣ --- አጋብ፣ ሰምላይ፣ እና ሐና

እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።

ዓቁብ

ይህን በዕዝራ 2:42 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Ezra 2:47

አጠቃላይ መረጃ:-

ይህ ክፍል ዘሮቻቸው ከምርኮ የተመለሱትን የሌዋውያን ስም ዝርዝር በቀጣይነት የያዘ ነው። እነዚህ ሁሉ የሰዎች ስሞች ናቸው።

Ezra 2:51

አጠቃላይ መረጃ:-

ይህ ክፍል ዘሮቻቸው ከምርኮ የተመለሱትን የሌዋውያን ስም ዝርዝር በቀጣይነት የያዘ ነው። እነዚህ ሁሉ የሰዎች ስሞች ናቸው።

Ezra 2:55

አጠቃላይ መረጃ:-

ይህ ክፍል ዘሮቻቸው ከምርኮ የተመለሱትን የሌዋውያን ስም ዝርዝር በቀጣይነት የያዘ ነው።

392 ጠቅላላ ዝርያዎች

‹‹ ሦስት መቶ ዘጠና-ሁለት ጠቅላላ ዝርያዎች።›› ይህ በዚህ ቡድን ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቁጥር ነው።

Ezra 2:59

አጠቃላይ መረጃ:-

ይህ ከልዩ ልዩ የባቢሎን ከተማዎች ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ ነገር ግን ዝርያቸውን ማረጋገጥ ያልቻሉ ሰዎች ዝርዝር ነው።

ቴልሜላ፣ ቴላሬሳ፣ ክሩብ፣ አዳን፣ እና ኢሜር

እነዚህ በባቢሎን የነበሩ አሁን ግን የማይገኙ ከተሞች ስሞች ናቸው።

652 ዝርያዎች

‹‹ስድስት መቶ ሃምሳ-ሁለት ዝርያዎች››

ዳላያ፣ ጦብያ፣ ኔቆዳ

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው።

Ezra 2:61

ኤብያ --- አቆስ --- ቤርዜሊ

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው።

የዘር ሐረጋቸው ዘገባ

ዘገባው ዘሮቻቸው እነማን እንደነበሩ የሚናገር ነው

ሊያገኙ አልቻሉም

‹‹በካህናቱ የስም ዝርዝር ውስጥ ስማቸውን ሊያገኙ አልቻሉ››

እንዳልተቀደሱ ከክህነት ተከለከሉ

ይህ እንደ ተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ ክህነት ›› የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ‹‹ እንደ ካህን መሥራት›› በሚል ግስ ሊተረጎም ይቻላል። ‹‹ ሌሎቹ ካህናት እንደረከሱ ስለቆጠሩአቸው እንደ ካህናት እንዲሠሩ አልፈቀዱላቸውም››

ያልተቀደሰ

ለክህነት ብቁ ያልሆነ

ኡሪም ኣና ቱሚም

ካህናት እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የሚፈቅደውን ለመለየት የሚጠቀሙበት ሁለት ትናንሽ ኩብ የሚመስሉ ነገሮቸ ናቸው

Ezra 2:64

ጠቅላላ ቡድን

ይህ ማለት ከምርኮ ወደ ይሁዳ የተመለሱት ጠቅላላ ቡድን ማለት ነው።

42,360

‹‹አርባ-ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ስድሳ››

የእነርሱ የቤት ሠራተኞች

‹‹ የእነርሱ ሴት ሠራተኞቻቸው››

እነዚህ 7,337 ነበሩ

‹‹እነዚህ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሳ-ሰባት ነበሩ››

ሁለት መቶ

‹‹200››

Ezra 2:66

አጠቃላይ መረጃ:-

እነዚህ የእንስሳቱ ዝርዝር ከአይነታቸው ቁጥር ጋር እንዲሁም አብረዋቸው ከስደት ከተመለሱት ሰዎች ጋር የቀረበ ነው።

Ezra 2:68

ስድሳ-አንድ ሺህ --- አምስት ሺህ --- አንድ መቶ

‹‹ 61,000 ... 5,000 ... 100”

የወርቅ ዳሪክ

‹‹ ዳሪክ ›› በፋርስ ግዛት ውስጥ ጥቅም ላይ ይውል የነበረ ትንሽ የወርቅ ሳንቲም ነው።

ምናን

ምናን የአንድ ነገር መስፈሪያ ወይን መመዘኛ ነው። አንድ ምናን 550 ግራም ይሆናል። ምናን በተለምዶ ብርን ለመለካት ጥቅም ላይ የሚውል ነበር።

ቱኒክስ

የውስጥ አልባሳት

Ezra 2:70

በእስራኤል ያሉ ሰዎች ሁሉ በከተማዎቻቸው ነበሩ

እያንዳንዱ በይሁዳ ወዳለው ወደየቤቱ ተመለሰ። እንዳንዱ በየሩሳሌም መኖሪያውን አላደረገም።

---

Chapter 3

Ezra 3:1

ሰባተኛው ወር

በዕብራውያን የዘመን አቆጣጠር ይህ ሰባተኛው ወር ነው። ይህ የደረቁ ወቅት መጠናቀቂያ እና የዝናቡ ወቅት መጀመሪያ ነው። ይህ በምራባውያን የዘመን አቆጣጠር የመስከረም ወር መጨረሻ እና የጥቅምት ወር መጀመሪያ ነው።

እንደ አንድ ሰው

አንድ ሰው በአንድ ቦታ ብቻ ሲሆን አንድ አላማ ብቻ አለው። ‹‹ ለአንድ ዓላማ››

ኢያሱ

ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። ይህን ስም በዕዝራ 2:36 እንደተተረጎመው ይሁን።

ሰላትያል

ይህ የአንድ ሰው ስም ነው።

ተነሡ እና ገነቡ

ተነሡ የሚለው ሥራን ለመጀመር መነሣትን የሚያመለክት ነው። ‹‹ሊሠሩ ጀመሩ››

በሙሴ ሕግ እንደተጻፈው

ይህ እንደ ተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። እግዚአብሔር ያዘዘውን በመጥቀስ የበለጠ ግልፅ ማድረግ ትችላለህ። ‹‹እግዚአብሔር በሙሴ ሕግ እንዲሠሩ እንዳዘዛቸው››

Ezra 3:3

መሰዊያውን በሥፍራው ላይ አስቀመጡት

‹‹ መሰዊያውን በመቆሚያው ላይ ከፍ አደረጉት›› ወይም ‹‹ መሰዊያውን በመቆሚያው ሥፍራ አስቀመጡት››

ፍርሃት ነበረባቸው

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ‹‹በጣም ፈርተው ነበር››

በምድሪቱ ሰዎች ምክንያት



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አይሁድ የፈሩበትን ምክንያት ግልፅ ለማድረግ ስለ ሰዎቹ የተነገረውን መግለጽ ያስፈልግህ ይሆናል። ‹‹ የምድሪቱ ሰዎች ሊያጠቁአቸው እንደሚፈልጉ ስላሰቡ››
በጥዋትና በማታም የሚቃጠለውን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረቡበት
ሰዎቹ ማድረግ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅርብ ነበር። ይህ ቤተ መቅደሱ ከመሠራቱ አስቀድሞ ነበር።
የዳስ በዓል
በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር በሰባተኛው ወር ይህ የዳስ በዓል ለስምንት ቀናት ይከበራል። በዘፀአት ጊዜ እስራኤላውያን በዳስ ይኖሩ የነበረበትን ወቅት የሚያስታውስ በዓል ነው።
Ezra 3:6
የሰባተኛው ወር የመጀመሪያው ቀን
ይህ በዕብራውያን የዘመን መቁጠሪያ ሰባተኛው ወር ነው። የመጀመሪያው ቀን በምዕራባውያን ዘመን አቆጣጠር የመስከረም ወር አጋማሽ ላይ ይውላል።
ቤተ መቅደሱ ገና አልተመሠረተም
አይሁድ ቤተ መቅደሱ ከመመሥረቱ አስቀድሞ የአምልኮ ሥርዓቱን ጀምረው ነበር። ‹‹ቤተ መቅደሱ ገና አልተመሠረተም››
በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት
ከቂሮስ የተሰጣቸው ደብዳቤ አይሁድ የሚያስፈልጋቸውን ዕቃ እንዲገዙና ቤተ መቅደሱን መገንባት እንዲችሉ ፈቃድ የሚጣቸው ነው።
Ezra 3:8
ሁለተኛ ወር
ይህ በዕብራውያን ዘመን መቁጠሪያ ሁለተኛው ወር ነው። ይህ ሰዎች ሰብላቸውን የሚሰበስቡበት ሞቃታማ ወቅት ነው። ይህም በምዕራባውያን ዘመን አቆጣጠር የሚያዝያ ወር መጨረሻው ጊዜ እና የግንቦት ወር የመጀመሪያው ክፍል ነው።
ሁለተኛው ዓመት
ይህ ከተመለሱበት ዓመት ቀጥሎ ያለው ዓመት ነው።
ለእግዚአብሔር ቤት
እነርሱ በደረሱ ጊዜ የእግዚአብሔ ቤት እንዳልነበረ ግልጽ ማድረግ አለብህ። ‹‹የእግዚአብሔር ቤት በነበረበት ሥፍራ ›› ወይም የእግዚአብሔር ቤትን ሊሰሩበት ወደአሰቡት ስፍራ››
ኢያሱ --- ኢዮሴዴቅ --- ኤንሐዳድ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።
ሃያ ዐመቱ
‹‹20 ዓመቱ››
ቀድምኤል
ይህ የሰው ስም ነው። ይህንን ዕዝራ 2፡40 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Ezra 3:10
መሠረት መጣል
‹‹መሠረት›› ይህ ቤተ መቅደሱን የሚሸከሞ የድንጋይ መሠረት ከማስቀመጥ የላቀ ነው። የቤተ መቅደሱን ጠቅላላ ወለል በድንጋይ መገንባትን ይጨምራል። ይህም በቤተመቅደሱ ገብተው የሚያመልኩት ሁሉ ልብሳቸውን ለመልበስ እና ንጽሕናቸወን ለመጠበቅ የሚያስችላቸው ነው።
ልብሳቸውን
‹‹የእነርሱ ልዩ አልባሳት››
ከነሐስ የተሠሩ ሁለት ሰሐን መሰል የሙዚቃ መሣሪያዎች
ሁለት ቀጭን፣ ክብ የሆኑ የብረት ሰሐኖች እርስ በርሳቸውን በማጋጨት ከፍተኛ ድምፅ የሚያወጡባቸው የሙዚቃ መሣሪያዎች።
የዳዊት እጅ --- እንዳዘዘው
የንጉሥ እጅ ትእዛዝን ለመስጠት ያለውን ሥልጣን ለማሳየት ጥቅም ላይ የሚውል ምሳሌአዊ አነጋገር ነው።
ማመስገን
ሌሎች ላሳዩን መልካምነት አድናቆታችንን እና ምስጋናችንን የምንገልጥበት ስሜት ነው።
የእርሱ የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለእስራኤል የጸና ነው
‹‹ታማኝነት›› የሚለው ረቂቅ ስም ‹‹በታማኝነት›› ወይም ‹‹ ታማኝ›› በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። ‹‹እርሱ እስራኤልን በታማኝነት ለዘላለም ወድዶአል›› ወይም ‹‹ እርሱ ሁልጊዜ ለእስራኤል ለገባው ቃል ኪዳን ታማኝ ነው››
Ezra 3:12
የመጀመሪያ ቤት
ይህ ሰሎሞን ያሰራውን የመጀመሪያውን የእግዚአብሔር ቤት ያመለክታል።
በአይናቸው ፊት
ሰዎቹ የተገለጹት ‹‹በዓይናቸው›› መሆኑ ያዩት ላይ ትኩረት ለማድረግ ነው። ‹‹በዓይናቸው ፊት›› ወይም ‹‹እና አዩት››
በታላቅ ድምፅ አለቀሱ
ይህ ሐዘንን በእንባና በጩኸት መግለጽን ያመለክታል።

---

Chapter 4
Ezra 4:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
አይሁድ-ያልሆኑ ሰዎች በቤተ መቅደሱ ግንባታ ላይ ለመሳተፍ ጠየቁ።
ተሰድደው የነበሩ
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹ባቢሎናውያን በምርኮ የወሰዱአቸው››
ዘሩባቤል
የሰው ስም። ይህንን በዕዝራ 2፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
አስራዶን፣ የአሦር ንጉሥ
ቂሮስ በፋርስ ከመግዛቱ በፊት አስራዶን በአሦር ይገዛ ነበር።
Ezra 4:3
ኢያሱ
የሰው ስም። ይህን በዕዝራ 2፡06 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
እናንተ አይደላችሁም፣ ነገር ግን እኛ እንሠራዋለን
የሚከተሉት ተገቢ ትርጉሞች ናቸው፡- 1. የአይሁድ አለቆች ቂሮስ እንዳዘዛቸው እነርሱ ብቻ መገንባት እንዳለባቸው ተሰማቸው ወይም 2. ቤተ መቅደሱን መገንባት ሙሉ ለሙሉ የአይሁድ ተግባር ነው እንጂ አይሁድ ያልሆኑትን ሰዎች ማሳተፍ አይፈቀድም።
Ezra 4:4
የምድሩ ሰዎች
‹‹ በዚያን ዘመን በምድሩ ላይ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች፣›› አየሁድ ያልሆኑና ባቢሎናውያን በምርኮ ያልወሰዱአቸው አይሁዶች ጭምር››
የየይሁዳን ሕዝብ እጅ ያደክሙ ነበር
ይህ የሚገልጸው በምድሩ ላይ ይኖሩ የነበሩት ሰዎች የይሁዳን ሕዝብ እጃቸውን ያደክሙ እንደነበር ነው። ‹‹ አይሁድን ተስፋ ያስቆርጡ ነበር››
አይሁዶች
ከባቢሎን የተመለሱ እና በይሁዳ ምድር የሰፈሩ ሕዝቦች
እቅዳቸውን ለማጣጣል
‹‹ አይሁዶች እንዳቀዱት ቤተ መቅደሱን ሊሰሩ እንዳይችሉ ማድረግ››
በይሁዳ እና በኢየሩሳሌም በሚኖሩት ሰዎች ላይ የክስ ጽሕፈት ጻፉ
‹‹ክስ›› የሚለው ረቂቅ ስም ‹‹ከሰሰ›› እንደሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። እዚህ ላይ ጠላቶች አይሁድን ምን ሠሩ ብለው እንደከሰሱአቸው ግልፅ ማድረግ ያስፈልግሃል። ‹‹ በይሁዳ እና በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ንጉሡን እንደማይታዘዙ ጠቅሰው የክስ ጽሕፈት ጻፉባቸው።››
Ezra 4:7
ቢሽላም --- ሚትሪዳጡ --- ጣብኤል --- ሲምሳይ
የሰው ስሞች
ደብዳቤው
ይህ ደብዳቤ በዕዝራ 4፡6 የተነገረው ነው።
አረማይክ
ለይፋ የንግድ ሥራ በዚያን ዘመን ጥቅም ላይ ይውል የነበረ ቋንቋ
ተተረጎመ
ወደ ፋርስ ቋንቋ
ሬሁም
የሰው ስም። ይህንን በዕዝራ 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Ezra 4:9
አርካ --- ሱሳ
የከተሞች ስሞች
አስናፈር

ይህ የአንድ ሰው ስም ነው።
ከወንዙ ማዶ ላለው ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ከተማ መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው።
Ezra 4:11
ይህ ግልባጭ ነው
ዕዝራ በጽሑፉ ለንጉሥ አርጤክስስ የተጻፈውን ደብዳቤ ይዘት አስፍሮአል።
ከወንዙ ማዶ ላለው ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ከተማ መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንንበዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሃይማታዊ ከተማ
ይህ ከተማ በውስጧ የሚኖሩትን ሰዎች ማንነት በፈሊጣዊ አነጋገር የሚገልጽ ነው። ‹‹ ሊኖሩበት ያቀዱት ከተማ ነገር ግን በአንተ ላይ የምታምጽ ናት››
መሠረቱን አደሱ
‹‹መሠረቱን አስተካከሉ›› ወይም ‹‹ መሠረቱን ጠገኑ››
Ezra 4:13
ይህች ከተማ ከተገነባች ቅጥሮቿም ተሠርተው ካለቁ
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ ከተማዋን ከገነቡ ቅጥሯንም ሠርተው ከፈጸሙ››
ነገር ግን ንጉሡን ይጎዳሉ
‹‹ይጎዳሉ›› የሚለው ቃል አይሁድ ለንጉሡ ገንዘብ መስጠታቸውን እንደሚያቆሙ የሚያመለክት ነው።
Ezra 4:14
የቤተ መንግሥቱን ጨው እንበላለንና
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፡- 1. ጸሐፊዎቹ ለንጉሡ ታማኞች ናቸው ወይም 2. ንጉሡ ለጸሐፊዎቹ የተለየ ክብር ሰጥቶአቸዋል። ‹‹እኛ ለአንተ ታማኞች ነን ›› ወይም ‹‹ እኛን የአንተ ባለሟሎች በማድረግህ አክብረኸናል››
አመጸኛ ከተማ
ከተማዋ በውስጧ የሚኖሩትን ሰዎች ማንነት ትወክላለች፡- ‹‹ በዚህች ከተማ የሚኖሩ ሰዎች በአባትህም ላይ ያመጹ ነበሩ››
ከተማዋ ጠፍታ ነበር
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል፣ ከተማዋን ምን እንዳጠፋት ግልጽ ማድረግ ያስፈልግሃል። ‹‹ከተማዋ›› በውስጧ የሚኖሩትን ሰዎች ትወክላለች። ‹‹ ባቢሎናውያን ከተማዋን አጥፍተዋታል››
ይህች ከተማ ቅጥሮቿም ከተሠሩ
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ይህን በዕዝራ 4፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ‹‹ከተማዋንና ቅጥሮቿን ከገነቡ››
ለአንተ ምንም አይቀርልህም
እዚህ ላይ ‹‹ምንም›› የሚለው ቃል አይሁድ በንጉሡ ላይ ካመጹ ንጉሡ ብዙ የታክስ ገንዘብ እንደሚቀርበት የሚያሳይ የሚያጋንን ቃል ነው።
ከወንዙ ማዶ ላለው ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ከተማ መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንንበዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Ezra 4:17
ከወንዙ ማዶ ላለው ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ክፍለ ሀገር መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንንበዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ወደ እኔ የላካችሁት ደብዳቤ ተተርጉሞ ተነቦአል
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል፣ በመሆኑም ደብዳቤውን ማን እንደተረጎመውና ለንጉሡ እንደነበበለት ማብራራት ያስፈልግህ ይሆናል። ‹‹ ወደ እኔ የላካችሁትን ደብዳቤ አገልጋዮቼ ተርጉመው አንብበውልኛል››
ሬሁም
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 2፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሲምሳይ
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 4፡8 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ወንዙ
የኤፍራጥስ ወንዝ
Ezra 4:20
ከወንዝ ማዶ ያለው ክፍለ ሀገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ክፍለ ሀገር መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንን በዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ቀረጥ እና ግብር ይከፈላቸው ነበር
ይህ ተግባራዊ በሆነ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹በኢየሩሳሌም የነበሩ ሰዎች በዚያ ለነበሩ ነገሥታት ቀረጥ እና ግብር ይከፍላሉ። ወይም ‹‹ እነዚያ ነገሥታት ቀረጥና ግብር ማስከፈል ይችሉ ነበር››
አዋጅ አወጀ
‹‹ ሕግ አወጣ››
ይህን ቸል እንዳትሉ ተጠንቀቁ
‹‹ቸል እንዳትሉ›› የሚለው አባባል ፀሐፊዎቹ ንጉሥ አርጤክስስ የነገሩትን እንዲያደርግ የሚፈልጉትን ነገር የሚያሳስብ ነው። ‹‹ቸልም እንዳትሉ ተጠንቀቁ››
ለነገሥታቱ ጉዳትና ጥፋት እየበዛ ስለምን ይሄዳል?
አርጤክስስ ይህን ጥያቄ በመጠየቁ ቀረጥና ክብር ቢቀርበት ምን ያህል ጉዳት እንደሚሆን መገንዘቡን ነገራቸው። ‹‹ለነገስታቱ ቀረጥና ክብር በመቅረቱ ጉዳት እንዳይሆን ጉዳዩን በጥብቅ መከታተላቸሁን እርግጠኞች መሆን አለባችሁ።››
የጉዳት መብዛት
አደጋው ልክ እንደ እጽዋት እድገት እያሰፋ እና እያደገ እንደሚሄድ ተገልፆአል። ‹‹አደጋ እየከፋ ይሄዳል››
ጉዳቱ በነገሥታቱ ገቢ ላይ የበለጠ ይከፋል
‹‹የነገሥታቱ ገቢ›› የሚለው አባባል የሚያመለክተው የንጉሡን ገቢ ነው። ‹‹ለነገሥታቱ ጉዳትና ጥፋት እየበዛ ስለ ምን ይሄዳል››
Ezra 4:23
የንጉሥ አርጤክስስ አዋጅ ተነበበ
ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል፣ በዚህም መሠረት አዋጁን ከንጉሡ ተቀብሎ ለባለ ሥልጣኖቹ ማን እንዳነበበው ግልጽ ማድረግ ያስፈልግሃል። ‹‹የንጉሥ አርጤክስስ መልእክተኞች የእርሱን አዋጅ አነበቡ››
ሬሁም
ይህንን ዕዝራ 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሲምሳይ
ይህንን በዕዝራ 4፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በኢየሩሳሌም ያለው የእግዚአብሔር ቤት ሥር እስከ ዳርዮስ ዘመነ መንግስት ሁለተኛ ዓመት ድረስ ተቋረጠ
ይህ መስተጓጎል 16 ዓመታት ያህል ቆይቶአል።

Chapter 5
Ezra 5:1
አዶ --- ኢያሱ --- ኢዮሴዴቅ
የሰዎች ስም
ሰላትያል
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት
ይህ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነበረ
Ezra 5:3
ተንትናይ --- ሰተርቡዝናይ
የሰዎች ስሞች
ከወንዙ ማዶ ያለ ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ክፍለ ሀገር መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንን በዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
የእግዚአብሔር ዓይን በላዩ
ዓይን የሚለው የሚያሳየው አንድን ሰው የሚጠብቅ ሌላ ሰው እንዳለ ነው። ‹‹ እግዚአብሔር ይጠብቅ ነበር››
አንድ ደብዳቤ ወደ ንጉሡ እንዲላክ እና አዋጁ ወደ እነርሱ እንዲመለስ

ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ‹‹ አንድ ባለ ሥልጣን ደብዳቤ ወደ ንጉሡ እንዲልክ ንጉሡም ደብዳቤውን መልሶ ከአዋጅ ጋር ወደ እነርሱ እንዲልክ››

Ezra 5:6

ይህ የደብዳቤው ግልባጥ ነው

ዕዝራ በቤተ መቅደሱ ስላለው የእነርሱ ሥራ ለንጉሡ ለዳርዮስ በተጻፈው ደብዳቤ ውስጥ ያለውን ይዘት ጠቅሶአል፡፡

ከወንዙ ማዶ ያለ ክፍለ ሐገር

ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ክፍለ ሀገር መጠሪያ ነው፡፡ ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው፡፡ ይህንን በዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡

Ezra 5:8

አጠቃላይ መረጃ

ከተንትናይ የተጻፈ ደብዳቤ ከዕዝራ 5፡7 ጀምሮ ለተጠቀሰው ንጉሡ ይቀጥላል

ግንዶች

ለግንባታ የሚሆኑ እንጨቶች

ማን አወጀላችሁ

‹‹ማን ፈቀደላችሁ››

Ezra 5:11

አጠቃላይ መረጃ፡

ከተንትናይ የተጻፈ ደብዳቤ ከዕዝራ 5፡7 ጀምሮ ለተጠቀሰው ንጉሡ ይቀጥላል፡፡

የአንዱ አገልጋዮች ነን

ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1. የአይሁድን ሰዎች የእግዚአብሔር ባሪያዎች ብለው ይጠሩአቸዋል ወይም 2. መልስ የሰጡአቸው ለቤተ መውደሱ የአምልኮ እና የመስዋዕት አገልግሎት ኃላፊዎች ከሌዊ እና ከአሮን ወገን ስለሆኑ ነው፡፡

ከብዙ ዘመናት በፊት ታላቁ የእስራኤል ንጉሥ ሠርቶ የጨረሰው ነው

ይህ ተግባራዊ በሆነ ቅርጽ ሊተረጎም የሚችል ነው፡፡ ‹‹ የእስራኤል ታላቁ ንጉሥ ሊገነባው የሚያስፈልገውን ዕቃ ሁሉ ሰጠ››

ሠርቶ ፈጸመው

‹‹የሚያስፈልገውን ዕቃ ሁሉ ሰጠ››

Ezra 5:12

አጠቃላይ መረጃ፡-

ከተንትናይ ለንጉሡ የተጻፈ ደብዳቤ ይቀጥላል፡፡ ከዕዝራ 5፡11 ጀምሮ ተንትናይ አይሁድ የነገሩትን ሁሉ ለንጉሡ መንገሩን ቀጥሎአል፡፡

የሰማይን አምላክ አስቆጡ

‹‹ የሰማይ አምላክ በእኛ እጅግ እንዲቆጣ አደረገው››

በባቢሎን ንጉሥ በከለዳዊው በናቡከደነፆር እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፣ እርሱም ይህን ቤት አወደመው ሕዙንም ወሰዳቸው

እጅ የሚለው ቃል ኃይልንና ሥልጣንን የሚያመለክት አባባል ነው፣ እንዲሁም፣

‹‹ናቡከደነፆር›› ሠራዊቱን ይወክላል፡፡ ‹‹የከለዳዊው የባበሊሎን ንጉሥ የናቡከደነፆር ሠራዊት ይህንን ቤት እንዲያወድም እና ሕዝቡን እንዲወስድ ፈቀደለት››

ይህን ቤት እንዲያወድም

‹‹ይህን ቤት እንዲያፈርሰው››

ቂሮስ የእግዚአብሔር ቤት እንደገና እንዲሠራ ፈቃድ ሰጠ

ቂሮስ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንደገና እንዲሰሩ አዘዘ፡፡

Ezra 5:14

አጠቃላይ መረጃ

ከተንትናይ በዕዝራ 5፡7 ጀምሮ ለተገለጸው ንጉሡ የተጻፈ ደብዳቤ ይቀጥላል፡፡ ከዕዝራ 5፡11 ጀምሮ ተንትናይ አይሁድ የነገሩትን ሁሉ ለንጉሡ መንገሩን ቀጥሎአል፡፡

ሰሳብሳር

ይህንን በዕዝራ 1፡7 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

እርሱ መለሳቸው

ንጉሥ ቂሮስ የቤተ መቅደሱን ዕቃዎች መለሳቸው

የእግዚአብሔር ቤት እንደገና ይሠራ

ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ‹‹ አይሁዶች የእግዚአብሔርን ቤት እንደገና እንዲሠሩ እፈልጋለሁ..

Ezra 5:16

አጠቃላይ መረጃ፡-

ከተንትናይ በዕዝራ 5፡7 ጀምሮ ለተገለጸው ንጉሡ የተጻፈ ደብዳቤ ይቀጥላል፡፡ ከዕዝራ 5፡11 ጀምሮ ተንትናይ አይሁድ የነገሩትን ሁሉ ለንጉሡ መንገሩን ቀጥሎአል፡፡

እየተገነባ ነው፣ ነገር ግን አልተጠናቀቀም

ይህ እንደ ተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ‹‹ሕዝቡ እየገነባው ነው፣ ነገር ግን ሥራውን ፈጽመው አላጠናቀቁትም››

ተገንብቷል

ታንጾአል

Ezra 5:17

አጠቃላይ መረጃ፡-

ተንትናይ ከዕዝራ 5፡7 ጀምሮ ለተጠቀሰው ንጉሥ የጻፈው ደብዳቤ ቀጥሏል፡፡ ተንትናይ አየሁዶች የነገሩትን ለንጉሡ መንገሩን ጨርሶአል አሁን ንጉሡን የሚጠይቀው አይሁዶች የነገሩት ሁሉ ትክክል መሆኑን እንዲያጣራ ነው፡፡

ነገሩ ይመርመር

ይህ እንደ ተግባራዊ ቅርጽ ሊተረጎመ ይችላል፡፡ ‹‹አንድ ሰው አዝዘህ ይህን ጉዳይ እንድታስመረምር እፈልጋለሁ››

የንጉሥ ቂሮስ ፍርድ በዚያ ለመኖሩ

‹‹ንጉሥ ቂሮስ ይህን አዋጅ ስለማውጣቱ የተመዘገበ ነበር ካለ››

---

## Chapter 6

### Ezra 6:1

ምርመራው እንዲደረግ ታዘዘ

‹‹ምርመራ›› የሚለው ረቂቅ ስም ‹‹መመርመር›› ወይም ‹‹መፈለግ›› በሚሉት ቃላት ሊገለጽ ይችላል፡፡ ‹‹በለሟሎቹ ነገሩን እንዲመረምሩ አዘዘ›› ወይም ‹‹ባለሟሎቹ ጉዳዩን እንዲፈልጉ አዘዘ››

ምርመራ እንዲደረግ አዘዘ

ምን ይመረምሩ እንደነበር በግልጽ ሊብራራ ይችላል፡፡ ‹‹መዛግብቱን እንዲመረምሩ ባለሟሎቹን አዘዛቸው›› ወይም ‹‹ንጉስ ቂሮስ አይሁድ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤት እንዲሠሩ አዘዞአቸው እንደሆነ መርምረው እንዲያገኙ ባለሟሎቹን አዘዛቸው››

ቤተ መዛግብት

ይህ ሕንፃ የንጉሡ አስፈላጊ የሆኑ የመንግሥት መዛግበት የሚቀመጡበት ሕንፃ ነው፡፡

አሕምታ

ይህ የከተማ ስም ነው፡፡

አንድ ጥቅል መጽሐፍ ተገኝቷል

ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ‹‹አንድ ጥቅል መጽሐፍ አገኙ›› ወይም ‹‹ስለ ዳርዮስ እና ኢየሩሳሌም የሚናገር አንድ ጥቅል መጽሐፍ አገኙ››

### Ezra 6:3

አጠቃላይ መረጃ

ይህ ንጉሥ ቂሮስ አይሁድ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዲሠሩ ያዘዘበት መዝገብ ጅማሬ ነው፡፡.

በንጉሥ ቂሮስ የመጀመሪያው ዓመት

ይህ ዓመት ንገሡ የነገሠበት የመጀመሪያው ዓመት እንደሆነ ግልጽ መደረግ ይችላል፡፡ ‹‹ንጉሥ ቂሮስ በነገሠበት በመጀመሪያው ዓመት››

ቤቱ እንደገና ይገንባ

ይህ በተግባራዊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ‹‹አይሁዶች ቤቱን ይገንቡይት›› ወይም ‹‹አየሁዶች ቤቱን መገንባት አለባቸው››

ስድሳ ኩቢት

‹‹ስድሳ ኩቢት›› ይህንን ወደ ዘመናዊው መለኪያ መለወጥ ትችላለህ፡፡ ‹‹ሃያ ሰባት ሜትር››

ኩቢት፣ ሦስት ረድፍ ረጃጅም ድንጋዮች እና አንድ ረድፍ አዲስ ግንድ

ይህ እንደ አዲስ አረፍተ ነገር ሊቀርብ ይችላል፡፡ የሚከተሉት ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች ናቸው 1. ይህ የሚገልጸው መሠረቱ እንደሚጣል ነው ‹‹ኩቢት፡፡ መሠረቱን በሦስ ረድፍ ረጃጅም ድንጋዮችና በላዩም አንድ ረድፍ ግንድ በማድረግ ገንቡት›› ወይም 2. ይህ ግድግደዎቹ እንዴት እንደሚገነቡ ይገልጻል፡፡ ‹‹ኩቢት፡፡ የቤቱን ግድግዳዎች በሦስት ረድፍ ረጃጅም ድንጋዮች ከእያንዳንዱ ረገድፍ ቀጥሎ አንድ ረድፍ ግንድ በማድረግ ገንቡአቸው››



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ወጪው ከንጉሡ ቤት ይከፈል
‹‹ከንጉሡ ቤት›› የሚለው ሐረግ የሚወክለው በነገሥታቱ ንብረት የሚገኘውን የንጉሥ ቂሮስን የግል ሀብት ነው። ይህ በአድራጊ ቅርጽ ሊቀርብ ይችላል። ‹‹ከነገሥታቱ ንብረት ወጪውን እኔ እከፍላለሁ››
Ezra 6:6
አጠቃላይ መረጃ:-
ይህ ንጉሥ ቂሮስ አይሁድ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዲገነቡ ያዘዘበት በዕዝራ 6:3 ላይ የተገለጸው ዘገባ ቀጣይ ክፍል ነው።
ተንትናይ --- ሰተርቡዝናይ
ዳርዮስ በቀጥታ የጻፈው ለእነዚህ ሰዎች ነው። በዕዝራ 5:3 እንደተገለጸው ስማቸውን ተርጉም።
ከወንዙ ማዶ ያለው ክፍለ ሐገር
x
Ezra 6:8
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ንጉሥ ቂሮስ አይሁድ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዲገነቡ ያዘዘበት በዕዝራ 6:3 ላይ የተገለጸው ዘገባ ቀጣይ ክፍል ነው።
አስፈላጊው ገንዘብ በወንዙ ማዶ ከሚገኘው አገር ከንጉሡ የግብር ገቢ ለእነዚህ ሰዎች እንዲከፈል
ይህ እንደ አድራጊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹በወንዝ ማዶ ካለው አገር ከሚመጣው ግብር ከንጉሡ ገንዘብ ለእነዚህ ሰዎች ወጪውን በትጋት እንድትሰጡአቸው››
በወንዙ ማዶ ከሚገኘው አገር ከንጉሡ የግብር ገቢ
‹‹የንጉሡ የግብር ገቢ›› የሚያመለክተው ሰዎች ለንጉሡ የሚከፍሉትን ቀረጥ ነው። ‹‹ከወንዙ ማዶ ከለው አገር ከሚኖሩ ሰዎች ለንጉሡ በቀረጥ ከምትሰበስቡት ገንዘብ››
የሚያስፈልገውን
ይህ እንደ አድረጊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹የሚያስፈልጋቸውን››
Ezra 6:11
አጠቃላይ መረጃ:-
ይህ ንጉሥ ቂሮስ አይሁድ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዲገነቡ ያዘዘበት በዕዝራ 6:3 ላይ የተገለጸው ዘገባ ቀጣይ ክፍል ነው።
ምሰሶው ከቤቱ ተነቅሎ እርሱ ይሰቀልበት ቤቱም የጉድፍ መጣያ ይደረግ
ይህ በአድራጊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ምሰሶውን ከቤቱ ነቅለው እርሱን ይሰቀልበት ዘንድ ባለሥልጣኖቼን አዝዣለሁ። ቤቱንም የጉድፍ መጣያ ያደርጉታል››
ምሰሶ
ትልቅ እና ቀጥ ያለ የቤትን ጣሪያ የሚደግፍ እንጨት
ይሰቀልበት
ይጠረቅበት
ለመለወጥ እጃቸውን ያነሡትን --- ወይም ለማፍረስ
እጃቸውን ማንሳት የሚለው የሚወክለው አንድ ነገር ለማድረግ መሞከር። ‹‹ለመለወጥ የሚሞክር --- ወይም ለማጥፋት›› ወይም ‹‹እለውጣለሁ የሚል --- ወይም የሚያጠፋ››
ይህን ድንጋጌ ሊለውጥ
‹‹ድንጋጌ›› የሚለው የስውር ስም ‹‹እኔ የደነገግሁትን›› በሚለው ሐረግ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹ እኔ የደነገግሁትን ለመለወጥ›› ወይም ‹‹እኔ ከደነገግሁት የተለየ የሚናገር››
Ezra 6:13
ተንትናይ --- ሰተርቡዝናይ
በዕዝራ 5:03 ላይ እነዚህን ስሞች እንደተረጎምከው አስቀምጣቸው
ቤቱ ተጠናቀቀ
ይህ በአድራጊ ቅርጹ ሊተረጎም ይችላል። የትኛውን ቤት ሠርተው እንዳጠናቀቁ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። ‹‹የእግዚአብሔርን ቤት ሠርተው አጠናቀቁ›› ወይም ‹‹ቤተ መቅደሱን መገንባት አጠናቀቁ››
በአዳር ወር በሦስተኛው ቀን
‹‹አዳር›› በዕብራውያን የዘመን አቆጠቃጠር የአሥራ ሁለተኛውና የመጨረሻው ወር መጠሪያ ነው። ይህ ቀዝቃዛው ወቅት ነው። በምርአባውያን የዘመን አቆጣጠር ሦስተኛው ቀን ወደ ፌብሩዋሪ መካከለኛው ቀን ይጠጋል።
ስድስተኛ ዓመት
ንጉሥ ዳርዮስ የነገሠው ለአምስት አመታት ነበር፣ አሁን ስድሰተኛ አመቱን ይዞአል።
Ezra 6:16
የቀሩት ምርኮኞች
እነዚህ ሰዎች የተማረኩና ወደ ባቢሎን ተወስደው የነበሩ፣ ነገር ግን ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ ናቸው። ‹‹የቀሩት ምርኮኞች ወደ በምርኮ ተወስደው የነበሩ ሲሆኑ በኋላ ግን ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ ናቸው›› ወይም ‹‹የተቀሩት ሰዎች ከምርኮ የተመለሱ ናቸው››
መቶ ወይፈኖች --- አራት መቶ ጠቦቶች
‹‹100 ወይፈኖች --- 400 ጠቦቶች›› በንግግር ሐረግ መገለጽ ይቻላል።
የሥራ ክፍፍል
ስውር ስም የሆነው ‹‹የሥራ ክፍፍል›› በንግግር ሐረግ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹በቡድን እንዲሠሩ››
የሥራ ክፍፍል
‹‹በጋራ የሚሠሩ ቡድኖች››
Ezra 6:19
የመጀመሪያው ወር አስራ አራተኛ ቀን
ይህ በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። አስራአራተኛው ቀን በምዕራባውያን ዘመን አቆጣጠር ለኤፕሪል ወር መጀመሪያ ይቀርባል።
ራሳቸውን አነጹ
‹‹ራሳቸውን ንጹህ አደረጉ።›› ራስን ንጹህ ማድረግ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትን ያመለክታል። ‹‹ራሳቸውን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ አደረጉ››
Ezra 6:21
በምድሩ ላይ ከሚኖሩ ካልነጹ ሰዎች ራሳቸውን ለዩ
ራስን ከርኩሰት መለየት የሚያሳየው የሚያረክሱ ነገሮችን አለማድረግን ነው። ‹‹እነርሱ በምድሩ ላይ የሚኖሩት ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ግን የሚያረክሳቸውን ነገር ማድረግ እምቢ አሉ››
የምድሩ ሰዎች ርኩሰት
እዚህ ላይ ‹‹ርኩሰት›› የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አለማግኘትን ነው። ‹‹ በምድሩ ላይ የሚኖሩት ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳያገኙ ያደረጋቸው የሚያደርጉት ርኩሰት የሞላበት ሥራ ነው
እግዚአብሔርን መፈለግ
እግዚአብሔርን መፈለግ የሚያመለክተው እርሱን ለማወቅ፣ ለማምለክ፣ እና ለመታዘዝ መምረጥ ነው። ‹‹ እግዚአብሔርን መታዘዝ መምረጥ››
የአሦርን ንጉሥ ልብ መመለስ
የንጉሡን ልብ መመለስማለት ስለ ቤተ መቅደሱ ሥራ ሲያስብ ከነበረው የተለየ እንዲያስብ ማድረግ ነው። ‹‹የአሦር ንጉስ የነበረውን ዝንባሌ መለወጥ›› ወይም ‹‹የአሦርን ንጉሥ ፈቃደኛ ማድረግ››
ለቤቱ ሥራ እጃቸውን ያበረታ ዘንድ
ለሥራው እጃቸውን ያበረታ ዘንድ የሚለው የሚያመለክተው እንዲሠሩ መርዳትን ነው። የአሦር ንጉሥ ይህን ያደረገው እንዲሠሩ በመናገር እና ለሥራውም የሚያስፈልገውን ገንዘብ በመድጠት ነው። ‹‹ ቤቱን እንዲሠሩ ለመርዳት›› ወይም ቤቱን እንዲሠሩ ለማስቻል››
የቤቱ ሥራ
ይህ የሚያመለክተው የቤተ መቅደሱን ሥራ ነው።

---

Chapter 7
Ezra 7:1
አጠቃላይ መረጃ:-
የዕዝራ የዘር ግንድ፣ ወደ ኋላ ሲቆጠር የመጀመሪያ ሊቀ ካህን ከሆነው ከአሮን ጋር ይገናኘዋል።
ዕዝራ ከባቢሎን መጣ
ዕዝራ ከየት እንደመጣ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ‹‹ዕዝራ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌን መጣ››
ሠራያ
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2:2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ሰሎም
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2:42 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
አዛርያ፣ ኬልቅያስ፣ --- ሳዶቅ፣ አኪጦብ፣ አማርያ፣ ዓዛርያስ፣ መራዮት፣ ዘራእያ፣ ኦዚ፣ ቡቂ፣ አቢሱ፣

ፊንሐስ፣ አልዓዛር
እነዚህ ሁሉ የወንዶች ስም ዝርዝር ነው።
Ezra 7:6
ንጉሡ የጠየቀውን ሁሉ ሰጠው
‹‹ንጉሡ የጠየቀውን ሁሉ ለዕዝራ ሰጠው››
የእግዚአብሔር እጅ ከእርሱ ጋር ነበረች
የእግዚአብሔር ‹‹እጅ›› የሚያሳየው የእግዚአብሔርን በረከት ወይም እርዳታ ነው። ‹‹ የእግኢአብሔር በረከት ከዕዝራ ጋር ነበር›› ወይም ‹‹እግዚአብሔር ዕዝራን ይባርከው ነበር››
በንጉሥ አርጤክስስ ሰባተኛው ዓመት።
ይህ የሚያሳየው የንጉሡን ሰባተኛ ዓመት ንግስ ነው። ‹‹ ንጉሥ አርጤክስስ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት››
Ezra 7:8
አምስተኛው ወር
ይህ በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር አምስተኛው ወር ነው። ይህም በምዕራባውያነ ዘመን አቆጣጠር የጁላይ መጨረሻው ክፍልን እና የኦገስት የመጀመሪያውን ክፍል የሚያሳይ ነው።
የመጀመሪያው ወር የመጀመሪያው ቀን
ይህ በምዕራባውያን ዘመን አቆጣጠር የማርችን/መጋቢትን ወር መካከለኛ ጊዜ የሚያመለክት ነው።
የአምስተኛው ወር የመጀመሪያ ቀን
ይህ በምዕራባውያን ዘመን አቆጣጠር የጁላይ/ሐምሌ ወርን አካፋይ የሚያመለክት ነው።
የእግዚአብሔር መልከሚቱ እጅ
‹‹እጅ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለመልካም ውጤት ሥልጣኑን እና ቁጥጥሩን መጠቀሙን ነው።
ዕዝራ ልቡ ለማጥናት አዘጋጅቶ ነበር
ማዘጋጀት የሚያመለክተው ቁርጠኛ መሆንን ወይም አንድን ነገር ለማድረግ ራሱን መስጠቱን ነው። ‹‹ ዕዝራ ሕይወቱን ለጭናት ሰጥቶ ነበር››
ማድረግ
‹‹መታዘዝ››
የእግዚአብሔር ሥርዓት፣ ፍርድና ሕግ
እነዚህ እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለእስራኤል ያስተላለፈላቸው ሕጎች ናቸው
Ezra 7:11
ድንጋጌው ይህ ነበር
ከዚህ ዓረፍተ ነገር ቀጥሎ የሚገኘው ምንባብ በንጉሥ አርጤክስስ የተሰጠ ድንጋጌ ነው።
የነገሥታት ንጉሥ አርጤክስስ
‹‹ የነገሥታት ንጉሥ›› የሚለው ማዕረግ እርሱ ከነገሥታት ሁሉ ታላቅ መሆኑን የሚያሳይ ነው፣ ንጉሡ ሌሎች ነገሥታት ይታዘዙታል። ‹‹ታላቁ ንጉሥ አርጤክስስ›› ወይም ‹‹አርጩክስስ፣ ከሁሉም ታላቅ የሆነ ንጉሥ››
ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የሚወድ ሁሉ --- እኔ አዝዤአለሁ
በዚያን ዘመን ሰዎች በሌሎች መንግሥታት በተወረሩና በወደሙ ምድሮች ላይ እንደገና ለመኖር ከንጉሡ ፈቃድ መጠየቅ ይጠበቅባቸዋል።
ከአንተ ጋር ለመሄድ ይችላሉ
‹‹ከአንተ›› የሚለው የሚያመለክተው ዕዝራን ነው።
Ezra 7:14
አናኝ መግለጫ፡-
ይህ ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ድንጋጌ ቀጣይ ክፍል ነው።
እኔ፣ ንጉሡ፣ እና ሰባቱ አማካሪዎቼ
‹‹ኤኔ›› የሚለው ቃል እና ‹‹ንጉሡ›› የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው አንድን ሰው ነው። ንጉሡ ሕዝቡን ሊያስታውሳቸው የሚፈልገው የዚህ ደብዳቤ ጸሐፊ እርሱ መሆኑን ነው።
ስለ ይሁዳ እና ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት መጠየቅ
ስለ ምን እንደሚጠይቁ የበለጠ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ‹‹በይሁዳ እና በኢየሩሳሌም ያለውን ሁኔታ ለመመርመር የፈለጉት እርሱ የእግዚአብሔርን ሕግ ታዝዘው እንደሆነና እንዳልሆነ ለማወቅ ነው››
ብሩንና ወርቁን ታመጣ ዘንድ
ወዴት እንደሚያመጡ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። ‹‹ ብሩንና ወርቁን ወደ ኢየሩሳሌም ታመጣ ዘንድ››
በፈቃዳቸው የሚያቀርቡትን ብሩንና ወርቁን
‹‹በፈቃዳቸው›› ማለት ገንዘቡን እንዲሰጡ አልተገደዱም ማለት ነው። የሰጡት መስጠት ስለፈለጉ ነው።
በሕዝቡና በካህናቱ በፈቃዳቸው የተበረከተው
ይህ በድርጊታዊ ቅረጹ ሊብራራ ይችላል። ‹‹ ሕዝቡና ካህናቱ በፈቃዳቸው የሰጡት››
Ezra 7:17
አናኝ መግለጫ
ይህ ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ድንጋጌ ቀጣይ ክፍል ነው።
ቁርባኑን --- በተሟላ ሁኔታ ግዛ
‹‹በተሟላ ሁኔታ›› ማለት ኃላፊነቱን ለመወጣት መግዛት የቻለውን ያህል ማለት ነው። ብሩንና ወርቁን በቤተ መቅደሱ እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለመግዛት ጥቅም ላይ ያውሉታል። ‹‹ ስለዚህ በዚህ ገንዘብ ወይፈኖችንና አውራ በጎችን ጠቦቶችንም እህላቸውንና የመጠጣቸውን ቁርባን ተግተህ ግዛ››
አንተና የአንተ ወንድሞች
‹‹የአንተ ወንድሞች›› የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ከዕዝራ ጋር ይህን ሥራ የሚሠሩትን ሰዎች ነው። ‹‹ከአንተ ጋር የሚሠሩ›› ወይም ‹‹የሥራ ባልደረቦችህ››
Ezra 7:19
አናኝ መግለጫ
ይህ ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ድንጋጌ ቀጣይ ክፍል ነው።
ለአንተ በነፃ የተሰጡህን ዕቃዎች
ይህ በተግባራዊ ቅርጹ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹ ለአንተ በነፃ የሰጠንህን ዕቃዎች ሁሉ››
ዕቃዎቹን --- በፊቱ አስቀምጣቸው
‹‹በፊቱ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።
ለአምላክህ ቤት አገልግሎት ይሆን ዘንድ
የስውር ስም የሆነው ‹‹አገልግሎት›› ‹‹አገልግል›› ወይም ‹‹ተጠቀም›› ‹‹ በአምላክህ ቤት አገልግሎት ላይ ጥቅም ላይ እንዲውል›› ወይም ‹‹በአምላክህ ቤት አገልግሎት ላይ እንዲያገለግሉ››
ግምጃ ቤት
ገንዘብ የሚቀመጥበት የተጠበቀ ሥፍራ
Ezra 7:21
አናኝ መግለጫ
ይህ ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ድንጋጌ ቀጣይ ክፍል ነው።
ከወንዙ ማዶ ያለው ክፍለ ሐገር
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ክፍለ ሀገር መጠሪያ ነው። ከሱሳ ከተማ አንፃር ከወንዙ ማዶ የሚገኝ ነው። ይህንን በዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ካህኑ ዕዝራ ከእናንተ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ በሙሉ ስጡት
ይህ በተግባራዊ ቅርጹ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹ካህኑ ዕዝራ ከእናንተ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ በሙሉ ስጡት››
በሙሉ ሊሰጠው ይገባል
‹‹በሙሉ›› የሚለው ሐረግ የሚወክለው ሥራውን ለመሥራት የሚያስፈልገውን መጠን ያህል የሚለውን ነው ‹‹የሚያስፈልገውን ያህል ሊሰጠው ይገባል።››
አንድ መቶ መክሊት ብር
‹‹100 መክሊት ብር›› ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ትችላለህ። ‹‹ 3,300 ኪሎ ግራም ሲልቨር ››
መቶ የቆሮስ መስፈሪያ ስንዴ
ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ትችላለህ። ‹‹22,000 ሊትር ስንዴ›› ወይም ‹‹ሃያ ሁለት ሊትር ስንዴ››
አንድ መቶ የባዶስ መስፈሪያ ዘይት
ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ትችላለህ። ‹‹2,200 ሊትር ዘይት›› ወይም ሁለይ ሺህ ሊትር ዘይት››
የእርሱ ቤት
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ነው።
የእርሱ ቁጣ በመንግሥቴና በልጆቼ ላይ ስለምን ይመጣል?
ንጉሡ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ላይ እንዲመጣ ስለማይፈልግ ነው። ይሽም የሚያመለክተው ለዕዝራ የሚያስፈልገውን ካልሰጡ እግዚአብሔር መንግሥቱን እንደሚቀጣ ነው። ‹‹ የእግዚአብሔር ቁጣ በመንግሥቴ እና በልጆቼ ላይ እንዲመጣ አንፈልግም

የእርሱ ቁጣ በመንግሥቱና በልጆቹ ላይ ስለምን ይመጣል?
የእግዚአብሔር ቁጣ የሚያመለክተው እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው ነው። ‹‹የእግዚአብሔር ቁጣ በመንግሥቱና በልጆቹ ላይ ስለምን ይመጣል?›› ወይም እነዚህን ነገሮች የማታደርጉ ከሆነ እግዚአብሔር መንግሥቱንና ልጆቹን ይቀጣ፡፡››

Ezra 7:24

አገናኝ መግለጫ
ይህ ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ድንጋጌ ቀጣይ ክፍል ነው።

ማንኛውንም ግብር ወይም ታክስ በእንተ ላይ እንደይጥሉ አስታውቀናቸዋል
‹‹ማንኛውንም ግብር ወይም ታክስ በእንተ ላይ እንደይጥሉ ነግረናቸዋል››

ሙዚቀኞች
የሙዚቃ መሣሪያዎችን የሚጫወቱ ሰዎች

Ezra 7:25

አገናኝ መግለጫ
ይህ ንጉሥ አርጤክስስ ለዕዝራ የሰጠው ድንጋጌ ፍጻሜ ነው።

እግዚአብሔር እንደሰጠህ ጥበብ መጠን ዳኞችንና ፈራጆችን ሹም
ስውር ስም የሆነው ‹‹ጥበብ›› በንግግር ሐረግ ሊገለጥ ይችላል። ‹‹እግዚአብሔር ጥበበኛ አድርጎሃል፣ ስለዚህ በጥበብ ዳኞችንና ፈራጆችን መሾም አለብህ››

በሞት ወይም በስደት ወይም ገንዘብን በመውረስ ወይም በግዞት
ረቂቅ ስሞቹ በግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ። ‹‹ እርሱን በመግደል፣ በማሳደድ፣ ገንዘባቸውን በመውረስ፣ ወይም ወደ እስር ቤት በማስገባት›› ወይም ‹‹ልትገድሉአቸው ፣ ልታሳድዱአቸው፣ ያላቸውን ንብረት ሁሉ ልትወስዱባቸው፣ ወይም ወደ እስር ቤት ልታስገቡአቸው ትችላላችሁ››

Ezra 7:27

አገናኝ መግለጫ
ዕዝራ ንጉሥ አርጤክስስ በሰጠው ድንጋጌ ምክንያት እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔርን ቤት ያሳምር ዘንድ ይህን ሁሉ በንጉሡ ልብ አስቀመጠ
በንጉሡ ልብ ነገሮችን ማስቀመጥ የሚለው አነጋገር የሚያመለክተው አንድን አሳብ ወይም ፍላጎት እንዲኖረው ማድረግን ነው ‹‹በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔርን ቤት እንዲያከብር አደረገው››

የእግዚአብሔር ቤት
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ነው

ለእኔ የቃል ኪዳኑን ታማኝነት አድርጎልኛል
‹‹ታማኝነት›› የሚለው ረቂቀ ስም ‹‹ታማኝ›› ወይም ‹‹የታመነ›› በሚል ሊገለጽ ይችላል። ‹‹ለእኔ ታማኝ የሆነው›› ወይም ‹‹ለእኔ የታመነው›› /ምሥጢራዊ ስሞችን ተመልከት/

እኔም በረታሁ
በረታሁ የሚለው ቃል የሚያመለክተው መበረታታትን ነው።

በአምላኬ በእግዚአብሔር እጅ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር እጅ የሚያመለክተው ለዕዝራ ያደረገውን እርዳታ ነው። ‹‹ እግዚአብሔር ስለረዳኝ››

---

# Chapter 8

## Ezra 8:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ከዚህ ምዕራፍ ጀምሮ ግልጽ የሆነ የደረሲ ልዩነት እንመለከታለን። ከምዕራፍ 1-7 ጸሐፊው ስለ ዕዝራ የጻፈው ነው። ምዕራፍ 8 ግን ጸሐፊው ራሱ ዕዝራ እንደሆነ ያመለክታል።

አጠቃላይ መረጃ፡
ከቁጥር 2-14 የመሪዎችና የአባቶቻቸው ስም ዝርዝር ነው። ሁሉም ወንዶች ናቸው።

ከፊንሐስ ልጆች፣ ጌርሶን
በዝርዝሩ ውስጥ ይህ የመጀመሪያው ነው። ‹‹ነበር›› በሚለው ግስ መጻፍ ይቻላል። ‹‹ የፊንሐስ ዝርያ መሪ ጌርሶን ነበር›› ወይም ‹‹ ጌርሶን የፊንሐስ ዝርያ መሪ ነበር››

ከኢታምር ልጆች ዳንኤል
ይህ በስም ዝርዝር ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሰ ነው። ይህም ‹‹ነበር›› በሚለው ግስ ሊጻፍ ይችላል። ‹‹ የኢታምር ዝርያዎች መሪ ዳንኤል ነበር›› ወይም ‹‹ ዳንኤል የኢታምር ዝርያዎች መሪነበር››

ፋሮስ
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከዳዊት ልጆች ሐጡስ --- ፋሮስ እና ዘካርያስ
ይህ በዝርዝሩ ውስጥ ሦስተኛው ነው። ይህም ‹‹ነበሩ›› በሚለው ግስ ሊጻፍ ይችላል። ‹‹የዳዊት ልጆች መሪዎች ሐጡስ እርሱም --- ፋሮስ እና ዘካርያስ ነበሩ›› ወይም ‹‹ የዳዊት ልጆች መሪዎች ሐጡስ እና ዘካርያስ ነበሩ--- ሐጡስ ከፋሮስ --- ወገን ነበረ››

ሐጡስ፣ የሴኬንያ ዘር የነበረ፣ ከፋሮስ ነገድም የነበረ ነው።
ይህ ‹‹ከዘካርያስ›› በኋላ ለብቻው ሊጻፍ የሚችል ዐረፍተ ነገር ነው። ‹‹ሐጡስ የሴኬንያ ዝርያ ነበረ። እርሱም የፋሮስ ዝርያ ነው››

ከእርሱ ጋር በእርሱ የዘር ሐረግ የተመዘገቡ 150 ወንዶች ነበሩ።
‹‹ ከዘካርያስ ጋር በእርሱ የዘር ሐረግ የተመዘገቡ 150 ወንዶች ነበሩ››

150 ወንዶች
‹‹ አንድ መቶ ሃምሳ ወንዶች››

## Ezra 8:4

አጠቃላይ መረጃ
የወንዶቹ ስም ዝርዝር ይቀጥላል።

ከፋሐት ሞዓብ ልጆች የዘራእያ ልጅ፣ ኤሊሆዔናይ
ይህ በስም ዝርዝር ውስጥ ቀጣዩ ክፍል ነው። ‹‹ነበ›› በሚል ግስ ሊጻፍ ይችላል፡ ‹‹የፋሐት ሞዓብ ዝርያዎች መሪ የዘራእያ ልጅ አሊሆዔናይ ነበር›› ወይም ‹‹ የዘራእያ ልጅ ኤሊሆዔናይ የፋሐት ሞዓብ ዝርያዎች መሪ ነበረ››

ከእርሱ ጋር ሁለት መቶ ወንዶች ነበሩ
‹‹ከኤሊሆዔናይ ጋር ሁለት መቶ ወንዶች ነበሩ››

ዘራእያ
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 7፡4 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ዓዲን
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2፡15 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ሁለት መቶ --- ሦስት መቶ --- ሃምሳ -- ሰባ
‹‹ 200 --- 300 --- 50 --- 70››

## Ezra 8:8

አጠቃላይ መረጃ፡-
የወንዶቹ ስሞች ዝርዝር ይቀጥላል።

የሰፋጥያስ ልጆች የሚካኤል ልጅ ዝባድያ
ይህ በዝርዝሩ ውስጥ የሚቀጥለው ክፍል ነው። ‹‹ነበር›› በሚል ግስ ሊጻፍ የሚችል ነው። ‹‹ የሰፋጥያስ ዝርያዎች መሪ የሚካኤል ለጅ ዝባድያ ነበረ›› ወይም የሚካኤል ለጅ ዝባድያ የሰፋጥያስ ዝርያዎች መሪ ነበር

ሰፋጥያስ
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት

ሚካኤል
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው።

ከእርሱ ጋር የሰማንያ ወንዶች ስም ተጠቅሶአል።
‹‹ ከዝባድያ ጋር ሰማንያ ወንዶች ተጠቅሰዋል››

218 ወንዶች
‹‹ ሁለት መቶ አሥራ ስምንት ወንዶች››

160 ወንዶች
‹‹አንድ መቶ ስድሳ ወንዶች››

ቤባይ
ይህንን በዕዝራ 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሰማንያ --- ሃያ-ስምንት
‹‹80 --- 28››

## Ezra 8:12

አጠቃላይ መረጃ
ይህ የወንዶቹ የስም ዝርዝር መጨረሻ ነው።

ከዓዝጋድ ልጆች የሃቃጣን ልጅ የሐናን
ይህ በስም ዝርዝር ውስጥ የሚቀጥለው ክፍል ነው። ‹‹ነበር›› በሚለው ግስ ሊጻፍ ይችላል። ‹‹ ይህ የአዝጋድ ልጆች መሪ የሃቃጣን ልጅ የሐናን ነበር›› ወይም ‹‹ የሃቃጣን ልጅ የሐናን የዓዝጋድ ልጆች መሪ ነበር››

ከእርሱም ጋር 110 ወንዶች ተመዝዝግበዋል
‹‹ ከዮናታን ጋር የተመዘገቡ 110 ወንዶች ነበሩ››

110 ወዶች

‹‹ አንድ መቶ አሥር ወንዶች››
እነርሱ የአዶኒቃም ልጆች ናቸው
‹‹እነርሱ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው አለቆችን ነው። ‹‹ የአዶኒቃኽ ልጆች መሪዎች››
አዝጋድ
ይህንን ስም በዕዝራ 2፡12 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
አዶኒቃም
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በጉዋይ
የዚህን ሰው ስም በዝራ 2፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ስድሳ --- ሰባ
‹‹60 --- 70››
Ezra 8:15
አጠቃላይ መረጃ
በምዕራፉ ውስጥ ‹‹እኔ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዕዝራን ነው።
አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 16 የወንዶችን ስም ዝርዝር ይዞአል።
ወደ ካሲፍያ የሚወስደው ቦይ
‹‹ቦይ›› ለሚለው ቃል የሚከተሉት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው 1. ሰዎች የሠሩት የውኃ ቦይ ወይም 2. አንድ ተራ ወንዝ። በአጠቃላይ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ወደ አኅዋ ወንዝ የሚወርድ የውኃ መንገድ››
አኅዋ
ይህ የቦታ ስም ነው
ሸማያ
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 8፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ኤልናታን --- ኤልናታን --- ኤልናታን
በተመሳሳይ ስም የሚጠሩ ሥስት ሰዎች እንደነበሩ ግልጽ ነው
Ezra 8:17
አዶ
ይህ የአንድ ወንድ ስም ነው
በመቀጠል እነርሱን ወደ አዶ ላክኋቸው
‹‹እነርሱን›› የሚለው ቃል በዕዝራ 8፡16 ስለ እነርሱ የተጻፈላቸው ዘጠኝ መሪዎችና ሁለት አስተማሪዎች ናቸው። ‹‹በመቀጠል እነዚያን ሰዎች ወደ አዶ ላክኋቸው”
ካሲፍያ
ይህ የአንድ የቦታ ስም ነው
ለአዶ ምን ማለት እንዳለባቸው ነገርኳቸው --- ይኸውም፣ ለአምላካችን ቤት አገልጋዮችን እንዲልክልን ነው
‹‹ይኸውም›› የሚለው ቃል ምን እንዲናገሩ እንዳስታወቃቸው ያመለክታል። ‹‹ ለአዶ --- ለአምላካችን ቤት አገልጋዮችን እንዲልክልን እንዲነግሩት ነገርኳቸው።
Ezra 8:18
ሰራብያ --- ሞሖሊ --- ሐሸብያን --- የሻያን --- ሜራሪ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።
ስለዚህ በአምላካችን መልካም እጅ አንድ ሰው ላኩልን
የአምላካችን ‹‹መልካም እጅ›› የሚለው የሚያመለክተው ኪሰጣቸው ቸር መሆናቸውን ነው። ‹‹ አምላካችን ለእኛ መልካም ስለሆነ፣ አንድ ሰው ላኩልን››
አንድ ጠንቃቃ ሰው
ይህ የእውቀት እና የጥበብ ሰው ነው።
የሌዊ ልጅ የእስራኤል ልጅ
እዚህ ላይ ‹‹እስራኤል‹‹ የሰው ስም ነው። እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሰጠው ስም ነው።
አስራ ስምንት --- ሃያ
18 -- 20
የሻያን
የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 8፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ባለስልጣኖች
በመንግሥት አሠራር ውስጥ የተወሰነ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች።
Ezra 8:21
የአኅዋ ሸለቆ
ይህ አኅዋ ተብሎ ወደ ሚጠራው ወንዝ የሚፈስሰው የሸለቆ ስም ነው። አኅዋነና ሸለቆውን በዕዝራ8፡15 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ከእርሱም የቀናውን መንገድ ለእኛና ለልጆቻችን ለንብረታችንም ሁሉ እንለምን ዘንድ
‹‹መለመን›› የሚለው ቃል መልካም ነገር እንዲያደርግላቸው እግዚአብሔርን መጠየቅን የሚያመለክት ነው። ‹‹የቀናውን መንገድ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሚጓዙበት ጊዜ ከክፉ እንዲጠበቁ ነው። ‹‹ በምንጓዝበት ጊዜ እኛ እና ልጆቻችን ንብረታችንም ሁሉ ከክፉ እንድንጠበቅ እግዚአብሔርን ጠይቀን ነበር››
የአምላካችን እጅ እርሱን በሚፈልጉ ሁሉ ላይ ነች
የእግዚአብሔር እጅ በሕዝቡ ላይ ናት የሚለው አባባል በሕዝቡ ላይ ያለውን የእግዚአብሔር እርዳታ ያመለክታል፣፣ እግዚአብሔርን መፈለግ እርሱን የማገልገል ምሳሌአዊ አነጋገር ነው። ‹‹እግዚአብሔር እርሱን የሚያገለግሉትን ሁሉ ይረዳቸዋል››
ነገር ግን ኃይሉና ቁጣው እርሱን በሚተዉ ሁሉ ላይ ነው
የእግዚአብሔር ኃይልና ቁጣው በሕዝቡ ላይ ይሆናል የሚለው አባባል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚቀጣ ነው። እግዚአብሔርን መርሳት እግዚአብሔርን ለማገልገል እምቢ ማለትን የሚያመለክት አባባል ነው።
ስለዚህ ጾምን እግዚአብሔርንም ፈለግን
እዚህ ላይ እግዚአብሔርን ፈለግን ማለት አንድ ነገር እንዲያደርግልን እግዚአብሔርን ጠየቅን ማለት ነው። ‹‹ስለዚህ ጾምን እግዚአብሔር እንዲረዳንም ጠየቅነው››
Ezra 8:24
ሰራብያ፣ ሐሸቢያ
የእነዚህ ሰዎችን ስም በዕዝራ 8፡19 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
Ezra 8:26
650 መክሊት ብር
‹‹ ስድስት መቶ ሃምሳ መክሊት ብር›› አንድ መክሊት ሠላሳ ሦስት ኪሎ ግራም ይመዝናል ይህንን ወደ ዘመናዊው የክብደት መለኪያ መለወጥ ትችላለህ። ‹‹ 22,000 ኪሎ ግራም ብር››
አንድ መቶ መክሊት የብር ዕቃዎች
‹‹ 100 መክሊት የብር ዕቃዎች›› ይህንን ወደ ዘመናዊው የክብደት መለኪያ መቀየር ትችላለህ። ‹‹3,300 ኪሎግራም የብር ዕቃዎች››
አንድ መቶ መክሊት ወርቅ
‹‹100 መክሊት ወርቅ›› ይህንን ወደ ዘመናዊ የክብደት መለኪያ መለወጥ ትችላለህ። ‹‹3,300 ኪሎ ግራም ወርቅ››
አንድ ሺህ ዳሪክ
‹‹1,000 ዳሪክ›› ‹‹ዳሪክ›› በፋርስ ግዛት ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ይጠቀሙበት የነበረ ትንሽ የወርቅ ሳንቲም ነው። ይህንን በሳንቲሞቹ ብዛት ወይም በሚመዝኑት ክብደት ልክ መተርጎም ትችላለህ። ‹‹ አንድ ሺህ የፋርስ የወርቅ ሳንቲሞች›› ወይም ‹‹ ስምንት ነጥ አምስት ኪሎ ግራም ወርቅ››
የናስ ዕቃዎች
ናስ ከመዳብ እና ከሌላ ብረት ቅልቅል የሚገኝ ብረት ነው። ከንጹህ መዳብ ይልቅ ጠንካራ ነው።
Ezra 8:28
በመቀጠልም እንዲህ አልኳቸው
‹‹ በመቀጠልም ለአሥራ ሁለቱ የካህናት አለቆች እንዲህ አልኳቸው››
በሌዋውያን አለቆች እና በሕዝቡ መሪዎች ፊት እስክትቆጥሩአቸው ድረስ
ወደ ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ፣ ብሩንና ወርቁን ናሱንም መቁጠራቸው ከእነዚህ ዕቃዎች ምንም እንዳላጎደሉ ያሳያል።
ካህናቱና ሌዋውያን
በሙሴ ሕግ መሠረት፣ የሌዊ ነገዶች የቤተ መቅደሱን ሥራ ንበረቱንና መባዉን በማስተባበር ያገለግላሉ።
Ezra 8:31
ወደ ኢየሩሳሌም እንሄድ ዘንድ ከአኅዋ ወንዝ ተነሣን
‹‹የአኅዋ ወንዝን ትተን ተጓዝን›› ወይም‹‹ከአኅዋ ወንዝ ጀምረን ተጓዝን››
የአኅዋ ወንዝ
ይህ አኅዋ ወደሚባል ቦታ የሚፈስ ወንዝ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የመጀመሪያው ወር አሥራ ሁለተኛው ቀን
ይህ በዕብራውያን የዘመን መቁጠሪያ የመጀመሪያው ወር ነው። አሥራ ሁለተኛው ቀን በምዕራባውያን አቆጣጠር ወደ መጋት መጨረሻ የሚቃረብ ነው።
የአምላካችን እጅ በላያችን ነበረች
የአምላክ እጅ በሕዝቡ ላይ ነው ማለት የእግዚአብሔር እርዳታ ከእነርሱ ጋር ነው

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚል ማሳሌአዊ አነጋገር ነው፡፡ ‹‹ እግዚአብሔር እየረዳን ነበር››

በመንገድም ላይ ከጠላት እና ከ---- ሰው እጅ አዳነን

እጅ የሚለው እነዚያ ሰዎች ሊያደርጉ የሚችሉትን የሚያመለክት ነው፡፡ እነርሱም የሚኀዙትን ቡድኖች የሚያጠቁትን በቀጥታ የሚመለከት ነው፡፡ ‹‹ ከጠላታችን ጥቃት እና በመንገድ ላይ ከሚሸምቅብን አዳነን›› ወይም ‹‹ ጠላቶችና ዘራፊዎች በመንገድ ላይ እንዳያጠቁን ከእኛ አራቃቸው››

ሊያጠቁን ከሚሸምቁብን

ይህ የሚያመለክተው ተጓዦቹ የያዙትን ዕቃዎች ለመዝረፍ በመመኘት ሊያጠቁአቸው የሚፈልጉትን ሌቦችንና ዘራፊዎችን ነው፡፡

Ezra 8:33

ብሩ፣ ወርቁ ሌሎችም ዕቃዎች ተመዘኑ

ይህ በተግባራቂ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ‹‹ አሥራ ሁለቱ የካህናት አለቆች ብሩንና ወርቁን ሌሎችንም ዕቃዎች መዘኑአቸው››

ብሩ፣ ወርቁ ሌሎችም ዕቃዎች በሜሪሞት እጅ ተመዘኑ

እዚህ ላይ ‹‹ በሜሪሞት እጅ›› የሚለው የሚያመለክተው ብሩና ወርቁ ሌሎችም ዕቃዎች በእርሱ ቁጥጥር ሥር መቆጠራቸውን ነው፡፡ ሰዎቹ ዕቃዎቹን ከቆጠሩ በኋላ በእርሱ ቁጥጥር ሥር እንዲጠበቁ ለሜሪሞት ሰጡት፡፡

ሜሪመፐት ---- ኦሪዮ --- አልዓዛር --- ፊንሐስ ---ዮዛባት ---ኢያሱ ---ኖዓድያ ---ቢንዊ

እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው፡፡

ኢያሱ

የዚህን ሰው ስም በዕዝራ 2፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡

Ezra 8:35

ከምርኮ የወጡት ምርኮኞች --- የተሰደዱ ሰዎች

እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በባቢሎን ይኖሩ የነበሩ እና ባቢሎንን ትተው የወጡትን፣ ወደ ይሁዳ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱትን የአይሁድ ምርኮኞችን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ‹‹ከባቢሎን ምርኮኛነት ወደ ይሁዳ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት ስደተኛ ሕዝቦች››

አሥራ ሁለት --- ዘጠና ስድስት --- ሰባ ሰባት --- አሥራ ሁለት

‹‹12 --- 96 --- 77 --- 12››

በወንዙ ማዶ ላሉት ለንጉሡ ሹማምንቶች

እነዚህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምዕራብ የሚገኙትን ሰዎች የሚያስተዳድሩ ባለ ሥልጣኖች ናቸው፡፡ በይሁዳ የሚኖሩትን ሰዎች ይጨምራል፡፡

ከወንዙ ማዶ ያለ ክፍለ ሐገር

ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምዕራብ የሚገኘው ክፍለ ሐገር ስም ነው፡፡ ሱሳ ከምትባለው ከተማ ባሻገር ወንዙን ተሻግሮ ያለው ከተማ ነው፡፡ ይኽም ይሁዳን ይጨምራል፡፡ ይህንን በዕዝራ 4፡10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡

---

## Chapter 9

Ezra 9:1

ራሳቸውን አልለዩም ነበር

ከባዕድ ምድር ሴቶችን አግብተዋል የእነርሱንም ሃይማኖት የራሳቸው አድርገዋል፡፡

Ezra 9:3

እኔም ይህን በሰማሁ ጊዜ

አያሌ እስራኤላውያን የባዕድ ሴቶችን እንዳገቡ፣ የእነርሱንም አማልክት እንደሚያመልኩ ዕዝራበሰማ ጊዜ

ልብሴንና መጎናጸፊያዬን ቀደድሁ፣ የራሴንና የጺሜን ጠጉር ነጨሁ

ዕዝራ ሰዎቹ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ተግባር በመፈጸማቸው እጅግ ማዘኑን ለሁሉም አሳየ

እስከ ሠርክ መሥዋዕት

ካህናቱ ፀሐይ በገባች ጊዜ የሚያቀርቡት መሥዋዕት

Ezra 9:5

የተዋረደበት ሁኔታ

በሌላ አባባል ‹‹በሐፍረት ተቀመጦ›› ነበር (ዕዝራ 9፡4)፡፡ ‹‹ ምን ያህል እንዳዘንኩ ለማሳየት በመሬት ላይ ተቀመጥኩኝ››

ተንበርክኬም እጆቼን ዘረጋሁ

‹‹በጉልበቴ ተንበርክኬ እጆቼን ወደ ሰማይ ዘረጋሁ››

Ezra 9:7

የአባቶቻችን ቀናት

‹‹አባቶቻችን ይኖሩበት ከነበረ ዘመን ጀምሮ››

በከፍተኛ በደል ---- በኃጢአታችን ምክንያት

‹‹ በደል›› እና ‹‹ኃጢአት›› የሚሉት ምስጢራዊ ስሞች እንድ ቅጽል ስም እና ግስ በተከታታይ ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ ‹‹ በጣም በደለኛ --- ከሠራነው ከፉ ሥራችን የተነሣ››

ለ---- ለነገሥታት እጅ አሳልፈን ተሰጠን

ይህ በተግባራዊ ቅርጹ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ‹‹ ለነገሥታት እጅ --- አሳልፈህ ሰጠኸን››

ለዚህ ዓለም ነገሥታት አልፈን ተሰጠን

እዚህ ላይ ‹‹እጅ›› የሚለው ሥልጣንን ወይም ቁጥጥርን ያመለክታል፡፡ ‹‹ ለዚህ ዓለም ነገሥታት ቁጥጥር አልፈን ተሰጠን›› ወይም ‹‹ ለዚህ ዓለም ነገሥታት አልፈን ተሰጠን››

ለሰይፍና ለምርኮ ለብዝበዛ እና ለእፍረት

ሰይፍ ሰዎች ሌሎች ሰዎችን አንደሚገድሉ የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ ‹‹ ምርኮ›› እና ‹‹ብዝበዛ›› የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ግስ ሐረጎች ሊገለጹ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ‹‹በእፍረት ፊት›› የሰውን ሁለንተና የሚያመለክት ሁኔታ ነው፡፡ ‹‹ለጠላቶቻችን ይገድሉን ዘንድ፣ ይይዙን ዘንድ፣ ይዘርፉን ዘንድ እና ያሳፍሩን ዘንድ››

Ezra 9:8

ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ምሕረት መጣልን

እግዚአብሔር ምሕረት ለማድረግ መወሰኑ የሚያመለክተው ያ ምሕረት የተደረገለት መንቀሳቀስና መጓዝ የሚል መሆኑን ነው፡፡ ‹‹ አምላካችን እግዚአብሔር በእኛ ላይ ምሕረቱን ያደርግ ዘንድ ወሰነ››

የቃል ኪዳኑን ታማኝነት በእኛ ላይ አበረታ

‹‹ታማኝነት›› የሚለው ረቂቅ ስም ‹‹ታማኝ›› ወይም ‹‹የታመነ›› በማለት ሊገለጽ ይችላል፡፡ የዚህን ተመሳሳይ ሐረግ በዕዝራ 7፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡ ‹‹እርሱ ግን ለእኛ ታማኝ ነበር›› ወይም ‹‹እርሱ ለእኛ የታመነ ነበረ››

በፋርስ ነጉሥ ፊት

ንጉሡ በቀጥታ ቤተ መቅደሱን ሊያይ አይችልም፣ ነገር ግን በኢየሩሳሌም ምን እየተሠራ እንዳለ ያውቃል፡፡ እዚህ ላይ ‹‹ፊት›› የሚለው ቃል በእርሱ እውቀት ፊት ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ አባባል ነው፡፡ ‹‹ ስለዚህ የፋርስ ንጉሥ ይህንን ያውቃል፡፡

የእግዚአብሔር ቤት

ቤተ መቅደሱ

የምንጠበቅበት ቅጥር ይሰጠናል

ሕዝቡ የሚጠበቅበት ቅጥር እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚጠብቅ ስለመሆኑ ምሳሌአዊ አነጋገር ነው፡፡ ‹‹ሊጠብቀን ይችላል››

Ezra 9:10

ለዘላለም

‹‹እስከ ዘመናት መጨረሻ››

Ezra 9:13

ለክፉ ሥራችንና ለበደላችን

‹‹ሥራችን›› እና ‹‹በደላችን›› የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ስም እና ቅጽል በቅደም ተከተላቸው ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ ‹‹ስላደረግናቸው መጥፎ ተግባሮች በደለኞችም ስለሆንን››

ለበደላችን የሚገባው ሊደረግብን ሲገባ አኛን አተረፍከን

‹‹ልትገድለን ሲገባ፣ አልቀጣኸንም ይልቁንም አንዳዶቻችንነ በሕይወት እንኖር ዘንድ ተውከን››

ትእዛዛትህን እንደገና መተላለፍ ነበረብን እናም ---- ከአሕዛብ ጋር እንጋባ ዘንድ ይገባናልን?

ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ‹‹ ትእዛዛትህን መተላለፋችን ፈሞ ስህተት ነው ከአሕዛብም ጋር እንጋባ ዘንድ አይገባም››

አትቆጣንምን--- እናመልጣለንን?

ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ‹‹ ትቆጣናለህ --- ዘናመልጥም ብዬ እፈራለሁ፡፡››

Ezra 9:15

ተመልከት

‹‹የምናገረውን በአንክሮ ተመልከት››

በበደላችን በፊትህ አለን

‹‹ እኛ ሁላችን በደለኞች መሆናችንን ታያለህ››

በፊትህ ሊቆም የሚችል አንድም ሰው የለም



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 10
Ezra 10:1
ዕዝራ ሲጸልይ እና ሲናዘዝ --- ራሱን ዝቅ አድርጎ ነበር
ዕዝራ ስለራሱ ሲናገር ራሱን እንደ ተራ ሰው በመቁጠር ነበር
ራሱን እየጣለ እየወደቀ
እየተነሣ እና በግምባሩ እየወደቀ
በእግዚአብሔር ቤት ፊት
በቤተ መቅደሱ ትይዩ
ሴኬንያ
ይህንን በዕዝራ 8፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ይሒኤል
ይህንን በዕዝራ 8፡9 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ለአምላካችን ታማኞች አልሆንንም
ይህ ለጉራ ሳይሆን፣ በሕዝብ ፊት የተደረገ ኑዛዜ ነው።
Ezra 10:3
ከአንተ ጋር ነን
‹‹እንረዳሃለን››
Ezra 10:5
የሐናን --- ኤልያሴብ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው።
Ezra 10:7
ማንም የማይመጣ --- ንብረቱ ሁሉ እንዲወረስ እርሱም ከምርኮው ጉባዔ እንዲለይ
‹‹ምርኮኞቹም ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሰበሰቡ እንደ አለቆቹና እንደ ሽማግሌዎቹ ምክር --- ምብረቱ እንዲወረስ›› ወይም ‹‹የይሁዳ እና የኢየሩሳሌም ሰዎች የማይመጣውን ሰው ንብረት እንዲወስዱ--- ከጉባዔም እንዲለዩት››
ሦስት ቀናት
3ቀናት
Ezra 10:9
በሦስት ቀናት ውስጥ
‹‹ከሦስት ቀናት በኋላ››
ዘጠነኛው ወር የወሩም አሥራ ሁለተኛው ቀን
ይህ በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር ዘጠነኛው ወር ነው። አሥራ ሁለተኛው ቀን በምዕራባውያብ ዘመን አቆጣጠር የታህሳስ አጋማሽ ነው።
በአደባባዩ
በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት የሚፈኝ ሰፊ ቦታ
ሕግህን ተላለፍን
‹‹መተላለፍ›› የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ የሕዝብህን ጠላቶች ረዳን››
የእስራኤልን በደል ከፍ ለማድረግ
‹‹ካሁን ቀድም ካደረግነው በደል የከፋ በደል ማድረጋችንን እግዚአብሔር ቆጠረው››
Ezra 10:11
ከ--- መለየት
ከ---ራቀ፣ ከ--- የተለየ ሆነ
Ezra 10:12
ይህ የአንድ እና ሁለት ቀናት ሥራ ብቻ አይደለም።
ይህ ውስጠ ምስጢር አነጋገር በሆነ መንገድ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ይህንን ሥራ ሁሉ ለማከናወን ብዙ ጊዜ ያስፈልገናል››
Ezra 10:14
የከተማው አለቆችና ሽማግሌዎች በቀጠሩት ጊዜ
ይህ በተግባራዊ ቅርጹ ሊተረጎም እንዲሁም በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ሊቀመጡ ይችላሉ። ‹‹እናንተ በወሰናችሁት ጊዜ። ከከተማው አለቆችና ሽማግሌዎች ጋር ይምጡ››
ዮናታን --- አሣሄል --- የሕዝያ --- ቴቁዋ --- ሜሱላም --- ሳባታይ
የወንዶች ስሞች
የአሣሄል ልጅ ዮናታን እና የቴቁዋ ልጅ የሕዝያ ይህንን ተቃወሙ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1. እነዚህ ሰዎች የከተማው ባለስልጣኖች ጥፋቱን እንዲመረምሩ አልፈለጉም ይም 2. የሰዎቹን ጋብቻ ማንም እንዲመረምር አልፈለጉም።
Ezra 10:16
ይህን አደረጉ
አይሁድ ያልሆኑትን ሴቶች ያገቡትን ሕዝቡ መረመራቸው።
የአሥረኛው ወር የመጀመሪያው ቀን
ይህ በዕብራውያን የዘመን አቆጣጠር አሥረኛው ወር ነው። በምዕራባውያን የዘመን አቆጣጠር የመጀመሪያው ቀን ወደ ታህሳስ አጋማሽ ይጠጋል።
የመጀመሪያው ወር የመጀመሪያ ቀን
ይህ በምዕራባውያን የዘመን አቆጣር ወደ መጋቢት አጋማሽ የሚቀርብ ነው።
Ezra 10:18
ኢያሱ
ይህንን በዕዝራ 2፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ኢዮሴዴቅ
ይህንን በዕዝራ 3፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
መልሤያ --- ጎዶልያስ
የወንዶች ስም
አልዓዛር --- ያሪብ
ይህንን በዕዝራ 8፡16 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
Ezra 10:20
አጠቃላይ መረጃ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ይቀጥላል።
ኢሜር --- ፋስኮር
የወንዶች ስሞች። ይህንን በዕዝራ 2፡37 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
አናኒ --- ኤልዮዔናይ --- ናትናኤል --- ኤልዓሣ
የወንዶች ስሞች
ዝባድያ
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 8 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ካሪም
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 2፡32 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
መዕሤያ
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 10፡18 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሸማያ --- ይሒኤል
የወንዶች ስሞች። ይህንን እንዴት በዕዝራ 8፡13 እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዮዛባት
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 8፡33 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Ezra 10:23
አጠቃላይ መረጃ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ይቀጥላል።
ዮዛባት
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 8፡33 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ኤልያሴብ
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 10፡6 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሰሎም
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 2፡42 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ፋሮስ
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 2፡03 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
አልዓዛር
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 2፡03 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Ezra 10:26
አጠቃላይ መረጃ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ይቀጥላል።
ኤላም --- ዛቱስ --- ባኒ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። ይህንን በዕዝራ 2፡7 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ይሒኤል
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8፡09 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ዔሊዮዔናይ
የወንድ ስም። ይህንን በዕዝራ 10:22 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ኤልያሴብ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:06 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ቤባይ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:11 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ይሆሐናን
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:06 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሜሱላም
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:16 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Ezra 10:30
አጠቃላይ መረጃ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ይቀጥላል።
ፈሐት ሞዓብ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:04 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በናያስ --- መልኪያ
የወንዶች ስሞች። ይህንን በዕዝራ 10:25 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
መዕሤያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:18 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሙታንያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:26 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ቢንዊ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:33 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ካሪም
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:32 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
አልዓዛር
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:16 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
መሉክ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:29 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Ezra 10:33
አጠቃላይ መግለጫ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ይቀጥላል።
ሐሱም
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:19 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዛባድ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:27 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ኤሊፋላት
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:13 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ምናሴ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:30 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሰሜኢ --- በናያስ
የወንዶች ስሞች።ይህንን በዕዝራ 10:23 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ባኒ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:10 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሜሬሞት
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:33 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ኤልያሴብ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:06 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Ezra 10:37
አጠቃላይ መረጃ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ይቀጥላል።
መታንያ --- ዓዳያ
የወንዶች ስሞች። ይህንን በዕዝራ 10:26 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
መታንያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:33 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ቢንዊ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:06 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሰሌምያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:23 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Ezra 10:41
አጠቃላይ መረጃ
ዕዝራ አይሁድ ያልሆኑ ሴቶች ያገቡትን ወንዶች በዝርዝር መግለጹን ጨረሰ
ሰሌመያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:39 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሰማሪያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:32 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሰሎም
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:42 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
አማርያ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 7:03 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ናባው
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 2:29 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ይዒኤል
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 8:13 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዛባድ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:27 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዘቢና -- ያዳይ --ኢዮኤል
የወንዶች ስሞች።
በናያስ
ይህ የወንድ ስም ነው። ይህንን በዕዝራ 10:25 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
እነዚህ ሁሉ
እነዚህ ከዕዝራ 10:20 ጀምሮ በዝርዝሩ ውስጥ ያሉት ናቸው።

---

Chapter 1
Nehemiah 1:1
ነህምያ ... ሐካልያ ... አናኒ
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ተመልከት)
በካሴሉ ወር
“ካሴሉ” በዕብራውያን የቀን መቁጠርያ ዘጠነኛው ወር ነው። ይህ ወር በምዕራባውያኑ የቀን መቁጠርያ በህዳር ወር መጨረሻ እና በታህሳስ ወር መጀመርያ ላይ የሚገኝ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚሉትን ተመልከት)
በሀያኛው ዓመት
ነህምያ የሚያመለክተው አርጤክስስ ንጉስ ሆኖ የገዛበትን የዓመታት ቁጥር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የፋርስ ንጉስ የሆነው አርጤክስስ ይገዛ በነበረበት በሃያኛው ዓመት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ደረጃ የሚያሳዩ ቁጥሮች የሚሉትን ተመልከት)
ሱሳ ግንብ
ይህ በኤላም አገር የሚገኝ የፋርስ ነገስታት ንጉሳዊ ከተሞች ከሆኑት አንዱ ነበር። ይህ ስፍራ እጅግ በጣም ትልቅና ከፍ ባለ ጠንካራ ግንብ ዙርያውን የታጠረ ከተማ ነበር።
ከወንድሞቼ አንዱ አናኒ
አናኒ የነህምያ የስጋ ወንድሙ ነበር።
አናኒ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ከይሁዳ መጣ።
“አናኒ ከሌሎች ጥቂት ሰዎች ጋር ከይሁዳ መጣ”
ከምርኮ የተረፉት አይሁድ፣ በዚያ የነበሩት የአይሁድ ቅሬታዎች
እነዚህ ሁለት ሀረጎች የሚናገሩት ስለ ተለያዩ ሰዎች ሳይሆን ስለ ተመሳሳይ ሰዎች ነው። የሚከተሉት አማራጭ ትርጉም ሊሆኑ ይችላሉ፡- 1) ምሮኮኞች ሆነው ወደ ባቢሎን የተወሰዱ ነገር ግን ከዚያ አምልጠው በኢየሩሳሌም ለመኖር የተመለሱ ጥቂት አይሁዳውያን ወይም 2) ወደ ባቢሎን ምርኮኛ አድርገው ሊወስዱአቸው ከሞከሩ ሰዎች አምልጠው በኢየሩሳሌም የቀሩት ጥቂት አይሁዳውያን። እነዚህ ሰዎች ከየት እንዳመለጡ ግልጽ ስላይደለ በትርጉም ላይ በግልጽ ለይቶ አለማስቀመጡu የተሻለ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከምርኮ ያመለጡትና በኢየሩሳሌም የቀሩት አይሁዳውያን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

Nehemiah 1:3

እነርሱም እንዲህ አሉኝ

በዚህ “እነርሱም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አናኒ እና ከይሁዳ የመጡትን ሌሎች ጥቂት ሰዎችን ነው፡፡

ክፍለ ሀገር

በዚህ “ክፍለ ሀገር” የሚለው ቃል ይሁዳ በፋርስ ግዛት ስር የምትገኝ አንዲት የአውራጃ አስተዳደራዊ መዋቅር እደሆነች ለማሳየት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የይሁዳ ክፍለ ሀገር” ወይም “ይሁዳ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

የኢየሩሳሌምም ቅጥር ፈርሶአል፥ በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋል

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰራዊቱ የኢየሩሳሌምን ቅጥር አፈራርሰውታል፣ በሮቿን ደግሞ አቃጥለውታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ተመልከት)

Nehemiah 1:4

ከዚያም እንዲህ አልሁ

ነህምያ የተናገረው የጸለየውን ነገር ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከዚያም ለያህዌ እንዲህ አልሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ያህዌ

ይህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ራሱን ለሕዝቡ የገለጠበት የእግዚአብሔር ስም ነው፡፡ ስለ ያህዌ እና ይህን ቃል እንዴት መተርጎም እንደሚገባ ትራንስሌሽን ወርድ የሚለውን ድህረ ገጽ ተመልከት፡፡

እርሱን ለሚወድዱትና የእርሱን ትእዛዝ ለሚጠብቁ

ነህምያ የሚናገረው ለያህዌ ስለሆነ “እርሱ” እና “የእርሱ” የሚሉት ተውላጠ ስሞች “አንተ” እና “የአንተ” ተብለው ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን ለሚወዱና የአንተን ትእዛዝ ለሚጠብቁ” (አንደኛ መደብ፣ ሁለተኛ መደብ እና ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

Nehemiah 1:6

ዓይኖችህ ይከፈቱ

“ተመልከተኝ፡፡” በዚህ ክፍል “ዓይኖችህ ይከፈቱ” የሚለው ሀሳብ በዘይቤአዊ መንገድ የተገለጸ ሲሆን ለአንድ ሰው ትኩረት መስጠትን የሚወክል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ትኩረትህን በኔ ላይ አድርግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የባሪያህን ጸሎት ትሰማ ዘንድ

“እኔ ባሪያህ፣ የምጸልየውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ፡፡” “ባሪያ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ነህምያን ነው፡፡ አንድ ሰው ትህትና እና አክብሮት ለማሳየት ሲል ከአለቃው ጋር የሚነጋገረው እንዲህ ነበር፡፡

ቀንና ለሊት

ይህን በማለቱ ቀንም ሌሊትም ይጸልያል፤ ነህምያ የጸሎቱን ድግግሞሽ አጉልቶ ያሳያል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ” (ወካይ ዘይቤ ይመልከቱ)

እኔና የአባቴ ቤት

በዚህ ክፍል “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቤተሰብን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እኔና ቤተሰቤ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 1:8

አገናኝ አርፍተ ነገር

ነህምያ ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን ቀጠለ፡፡

እባክህ አስብ

“ማሰብ” የሚለው ፈሊጥ ማስታወስ የሚለውን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እባክህ አስታውስ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ለባሪያህ ሙሴ ያዘዝከውን ቃልህን

“ያዘዝከውን” እና “ቃልህን” በሚሉት ቃላት ውስጥ ያሉት ተውላጠ ስሞች እግዚአብሔርን ያመለክታሉ፡፡

ታማኝ ባትሆኑ … እበትናችኋለሁ … ብትመለሱ … የእናንተን ሕዝብ

“እበትናችኋለሁ” እና “የእናንተ” የሚሉት ቃላት ተውላጠ ስሞች የብዙ ቁጥር መግለጫ ሲሆኑ የሚያመለክቱት ደግሞ እስራኤላውያንን ነው፡፡

በአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ

ያሕዌ ሰው ዘርን ሲዘራ እንደሚበትን እንዲሁ እስራኤላውያንን በአሕዛብ መካከል እንዲኖሩ እንደሚበትናቸው ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በአሕዛብ መካከል እንድትኖሩ አደርጋችኋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእናንተ ሕዝብ ተበትነው ቢሆኑም እንኳ

ይህ ዓርፍተ ነገር በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም እንኳ የእናንተ ሕዝብ ብበትናቸውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ሰማይ ዳርቻ ደረሰ

ያሕዌ በምድር ላይ በጣም ሩቅ ያሉትን ቦታዎች “እስከ ሰማይ ዳርቻ” ብሎ ይጠራቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም ሩቅ ወደሆኑ ቦታዎች” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ይኖርበት ዘንድ ወደ መረጥኩት ቦታ

ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ቤተ መቅደሱ የሚገኝበትን ኢየሩሳሌምን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “… ይኖርበት ዘንድ ወደ መረጥኩት ወደ ኢየሩሳሌም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስሜ ይኖርበት ዘንድ ወደ መረጥኩት ቦታ

በዚህ ክፍል “ስሜ” የሚለው ቃል የሚያሳየው ራሱን ያሕዌን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እኖርበት ዘንድ የመረጥኩት ቦታ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 1:10

አጠቃላይ መረጃ፡-

ነህምያ ጸሎቱን ቀጠለ፡፡

አሁን

ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ነህምያ ወደ ሌላ የጸሎት ሃሳብ መሸጋገሩን ለማሳየት ነው፡፡ እዚህ ላይ ነህምያ በያሕዌ ተስፋ ቃል ላይ ተመስርቶ ጥያቄውን ያቀርባል፡፡

እነርሱ ባሪያዎችህ ናቸው

“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እስራኤላውያንን ነው፡፡

በታላቅ ሃይልህና በብርቱ እጅህ

እዚህ ላይ “እጅህ” የሚለው ቃል ጥንካሬንና ሃይልን ያመለክታል፡፡ እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ላይ በመሆን የያሕዌን ሃይል ታላቅነት ለማጉላት ጥንድ ሃሳቦችን መሰርተዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በታላቅ ኃይልህ እና ከፍ ባለው ብርታትህ” ወይም “በጣም ኃያል በሆነው ብርታትህ” (ምትክ ስም እና ተመሳሳይ ጥንድ ሃሳብ የሚለውን ይመልከቱ)

የባሪያህ ጸሎት

እዚህ ላይ “ባሪያህ” የሚለው የሚያመለክተው ነህምያን ነው፡፡ አንድ ሰው ትህትና እና አክብሮት ለማሳየት ሲል ከአለቃው ጋር የሚነጋገረው እንዲህ ነበር፡፡ ነህምያ 1፡6ን እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ፡፡

የባሪያዎችህ ጸሎት

እዚህ ላይ “ባሪያዎችህ” የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ ስለ ሕዝቡ እና ስለ ኢየሩሳሌም እንዲነሳ ይጸልዩ የነበሩትን የቀሩትን የእስራኤል ሕዝቦች በሙሉ ነው፡፡

ስምህን በማክበር ደስ የሚሰኙትን

እዚህ ላይ “ስም” የሚለው የሚያሳየው ያሕዌን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን ለማክበር ደስ የሚሰኙትን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ ሰው ፊት ምህረትን ስጠው

“ስጠው” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ነህምያን ሲሆን በእግዚአብሔር ፊት ያለውን ትህትና ለመግለጽ ራሱን በሶስተኛ መደብ ያመለከተበት ነው፤ “በዚህ ሰው” የሚለው የሚያመለክተው የፋርስን ንጉስ አርጤክስስን ነው፡፡

በዚህ ሰው ፊት

ነህምያ የሚናገረው ንጉሱ በሚያይበት እይታ ላይ ተመስርቶ ስለ ንጉሱ ዝንባሌ ወይም አመለካከት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉሱ በእኔ ላይ ምህረቱን ያሳይ ዘንድ አድርግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሱ ጠጅ አሳላፊ ሆኜ አገለግለው ነበር

ይህ ነህምያ በንጉሱ ቤተ መንግስት ምን ይሰራ እንደነበር የሚያሳይ የዳራ መረጃ ነው፡፡ የአንተ ቋንቋ የዳራ መረጃ የሚያሳዩበት የራሳቸው የተለየ መንገድ ሊኖረው ይችላል፡፡ (የዳራ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 2

Nehemiah 2:1

በኒሳን ወር

“ኒሳን” በዕብራይስጥ የቀን መቁጠርያ የመጀመርያው ወር ስም ነው፡፡ (የዕብራይስጥ ወራቶች የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉስ አርጤክስስ በሃያኛው አመት

“አርጤክስስ ንጉስ በሆነበት በ20ኛው አመት (ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን

ይመልከቱ)
አሁን
ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ከዋናው የታሪክ ፍሰት ወጣ ብሎ ሌላ ነገር መጀመሩን ለማሳየት ነው። እዚህ ላይ ነህምያ በንጉሱ ፊት ስለነበረው መልክ የዳራ መረጃ ይሰጣል። (የዳራ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሱ ግን
“ስለዚህም ንጉሱ”
ፊትህ ለምን አዘነ
እዚህ ላይ ነህምያ የተገለጸው በፊቱ ነው ምክንያቱም ፊት የሰውን ስሜት ሰለሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለምን አዘንህ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ተመልከት) (ወካይ ዘይቤ ይመልከቱ)
ይህ የልብ ሐዘን መሆን አለበት
ይህ ነህምያ ልቡ እንዳዘነ እርሱም እንደዛው እንዳዘነ ያሳያል፣ ምክንያቱም ልብ የስሜቶች ሁሉ ማዕከል እንደሆነ ተደርጎ ስለሚታሰብ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም አዝነሃል” (ወካይ ዘይቤ ይመልከቱ)
ከዚያም እጅግ በጣም ፈራሁ
ነህምያ ንጉሱ ለጠየቀው ነገር መልስ ለመስጠት ሲዘጋጅ በጣም ፈራ ምክንያቱም ንጉሱ እንዴት እንደሚመልስለት አያውቅም ነበር።
Nehemiah 2:3
ንጉሱ ለዘላለም ይኑር
ነህምያ ለንጉስ አርጤክስስ ክብርን እያሳየ ነው። እዚህ ላይ “ለዘላለም” የሚለው ቃል ረዥም እድሜን የሚያሳይ የግነት ቃል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉሱ ረዥም አመት ይኑር” (ግነት እና ጅምላ ምልከታ የሚለውን ተመልከት)
ለምን ፊቴ አይዘን?
እዚህ ላይ ነህምያ የሚያዝንበት ምክንያት እንዳለው ለንጉሱ ለመንገር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ተጠቀመ። ይህን በዓርፍተ ነገር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዳዝን የሚያደርጉኝ በቂ ምክንያቶች አሉኝ።” (መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የአባቶቼ መቃብር ያለበት ቦታ
“አባቶቼ የተቀበሩበት ቦታ”
በሮቹ በእሳት ተቃጥለዋል
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እሳት በሮችዋን አፈራርሶታል” ወይም “ጠላቶቻችን በሮችዋን አቃጥለውታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ተመልከት)
Nehemiah 2:4
ለንጉሱም ... አልሁት
“ከዚያም ለንጉሱ .... መለስኩለት”
ባርያህ
ነህምያ ለንጉሱ ያለውን አክብሮት ለመግለጽ ራሱን በዚህ መንገድ ገለጸ።
በፊትህ
እዚህ ላይ በፊትህ ሲል ፍርድን ወይም ግምገማን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በአንተ ፍርድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የአባቶቼ መቃብር ከተማ
“አባቶቼ የተቀበሩበት ከተማ”
እንደገና እሰራው ዘንድ
ነህምያ ግንባታውን በሙሉ ራሱ ለመስራት አላሰበም፣ ነገር ግን የስራው መሪ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔና ሕዝቤ እንሰራው ዘንድ” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 2:7
ደብዳቤ ይሰጠኝ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ደብዳቤ ስጠኝ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ከወንዙ ማዶ ያለው ግዛት
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምዕራብ በኩል የነበረው ግዛት ስም ነው። በሱሳ ከተማ ከነበረው ወንዝ ባሻገር ያለ ቦታ ነበር።
አሳፍ
ይህ የአንድ ወንድ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር መልካሚቱ እጅ በእኔ ላይ ነበረች
የእግዚአብሔር “መልካሚቱ እጅ” የሚያሳየው የእግዚአብሔርን “ሞገስ” ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔር ሞገስ በእኔ ላይ ነበር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 2:9
ሖሮናዊው ሰንባላጥ
ሰንባላጥ የአንድ ወንድ ስም ነው፣ ሖሮናውያን ደግሞ የአንድ ሕዝብ ወገን ነበሩ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ተመልከት)
አገልጋዩ አሞናዊው ጦቢያ
ይህ ሰው ባርያ የነበረ ነገር ግን ነጻ ወጥቶ በአሞን ከተማ ሹም ሆኖ እያገለገለ የነበረ ሰው እንደሆን ይታመናል። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ይህን ሰሙ
“መድረሴን ሰሙ”
Nehemiah 2:11
በልቤ አኖረው
እዚህ ላይ የነህምያ “ልብ” የሚያመለክተው ሃሳቡንና ፈቃዱን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አነሳሳኝ” ወይም “መራኝ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ምንም እንስሳ አብሮኝ አልነበረም
“ከኔ ጋር ምንም እንስሶች አልነበሩም”
Nehemiah 2:13
አጠቃላይ መረጃ፡-
በዚህ ጉብኝቱ ጥቂት ሰዎች ከነህምያ ጋር አብረው ነበሩ፣ ነገር ግን ነህምያ የሚናገረው በአንደኛ መደብ ነው ምክንያቱም ቀዳሚው ሰው እርሱ ሰለነበር ነው። (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
በምሽትም በሸለቆ በር ወጣሁ
“ሲመሽ፣ በሸለቆ በር በኩል ወጣሁ”
ቀበሮ
የበረሃ ውሻ
ቆሻሻ መጣያ በር
ይህ በር ቆሻሻ ከከተማው የሚወገድበት እንደነበር ይገመታል
ፈርሰው ክፍት የነበሩትን፣ የእንጨት በሮቹ ደግሞ በእሳት ተቃጥለው ነበር
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤል ጠላቶች ሰብረው የከፈቱትን፣ ጠላቶቻቸው በእሳት አቃጥለው ያፈረሷቸውን የእንጨት በሮች። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 2:15
... ስለዚህ ወጥቼ ... እንዲሁም ተመለስሁ
ከነህምያ ጋር የነበሩት ሰዎችም ተከትለውት ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ ወጥተን ... እንዲሁም ተመለስን” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
በሸለቆው በር
“በሸለቆ በር በኩል”
ስራውን ይሰሩ የነበሩት ሌሎች
ይህ የሚያመለክተው በኋላ ላይ ቅጥሩን በማደስ ሰራ ላይ የሚሳተፉትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በኋላ ቅጥሩን የማደስ ስራ የሚሰሩት ሌሎች” (ግምታዊ እውቀትና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 2:17
ችግሩን ታያላችሁ
እዚህ ላይ “ታያላችሁ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን ጥቅም ላይ የዋለው በነህምያ 2:16 ላይ የተገለጹትን ሰዎች በሙሉ ለማመልከት ነው። (የሁለተኛ መደብ ቅርጾች የሚለውን ይመልከቱ)
በሮችዋ በእሳት ተቃጥለዋል
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻችን በሮችዋን በእሳት እንዴት እንዳቃጠሉት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእንግዲህ ወዲያ መሳለቂያ እንዳንሆን
“ከእንግዲህ ወዲያ እንዳናፍር”
የአምላኬ መልካሚቱ እጅ በእኔ ላይ ነበረች
የእግዚአብሔር “መልካሚቱ እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን “ሞገስ” ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔር ሞገስ በእኔ ላይ ነበር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እንነሳና እንስራ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “መገንባት እንጀምር” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህ ለመልካም ስራ እጃቸውን አጠነከሩ
“እጃቸውን አጠነከሩ” የሚለው ሐረግ አንድን ስራ ለመስራት ተዘጋጁ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህን መልካም ስራ ለመስራት ተዘጋጁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 2:19
ሰንባላጥ … ጦብያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። እነዚህን በነህምያ 2፡9-10 ላይ እንዴት እንደተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ጌሳም
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ምን እያደረጋችሁ ነው? ንጉሱ ላይ እያመጻችሁ ነውን?
እነዚህ መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች ጥቅም ላይ የዋት ነህምያ ላይ ለመሳለቅ ነው። ይህ በዓርፍተ ነገር ቅርጽ ሊጻፉ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሞኝነት ስራ እየሰራችሁ ነው! በንጉሱ ላይ ልታምጹ አይገባም! (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሱ
ይህ የሚያመለክተው የፋርስ ንጉስ አርጤክስስን ነው።
ተነስተን እንሰራለን
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም “እንደገና መገንባት እንጀምራለን” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ ግን በኢየሩሳሌም ድርሻ፣ መብትና የኛ የምትሉት የታሪክ መታሰቢያም የላችሁም
“እናንተ ግን በኢየሩሳሌም ምንም ድርሻ፣ ሕጋዊ መብት ወይም ሃይማኖታዊ ባለቤትነት የላችሁም“

---

Chapter 3
Nehemiah 3:1
ታላቁም ካህን ኤልያሴብ ከካህናት ወንድሞቹ ጋር ተነሳ
“ከዚያም ታላቁ ካህን ኤልያሴብ ከካህናት ወንድሞቹ ጋር መጣ”
ኤልያሴብ … የአምሪ ልጅ ዙኩር
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
የመቶ ግንብ ግንብ
“የመቶ ግንብ ግንብ” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የሐናንኤል ግንብ
ይህ የግንብ ስም ነው። አንድ “ሐናንኤል” በሚባል ሰው ስም ስያሜ እንደተሰጠው መገመት ይቻላል። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
የኢያሪኮ ሰዎች
ይህ ማለት እነዚህ ሰዎች ከኢያሪኮ የመጡ ናቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ከኢያሪኮ የመጡ ሰዎች” (የንብረት ባለቤትነት የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 3:3
ሃስናአ … ሜሪሞት … ኦርዮ … አቆስ … ሜሱላም … በራክያ … ሜሴዜቤል … ሳዶቅ … በዓና
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
በሮችን አቆሙ
“በሮችዋን አስገቡ” ወይም “በሮችዋን በቦታው አስቀመጡ”
መቀርቀርያዎቹንና መወርወርያዎቹን
“ቁልፎቹንና መቀርቀሪያዎቹን።” እነዚህ በሮቹን በአስተግንብኝ ሁኔታ እንዲቆለፉ ያደርጉ ነበር።
የሚቀጥለውን ክፍል ሜሪሞት አደሰ …. ሜሱላም አደሰ … ሳዶቅ አደሰ … ቴቁሐውያን አደሱ …
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ቅጥሩን ስለ መገንባት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሜሪሞት የሚቀጥለውን ክፍል አደሰ … ሜሱላምም ቅጥሩን አደሰ … ሳዶቅ ቅጥሩን አደሰ … ቴቁሐውያን ቅጥሩን አደሱ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ቴቁሐውያን
እነዚህ ቴቁሐ ከሚባል ከተማ የመጡ ሰዎች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
በአለቆቻቸው የታዘዙትን
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አለቆቻቸው አድርጉ ብለው ያዘዟቸውን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 3:6
ዮዳሔ … ፋሴሐ እና ሜሱላም … በሶድያ … መልጥያ … ያዶን
እነዚህ ሁሉም የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
በሮችዋን አቆሙ
“በሮቹን አስገቡ” ወይም “በሮቹን በቦታቸው አስቀመጡ”
መቀርቀርያዎቹንና መወርወርያዎቹን
“ቁልፎቹንና መቀርቀሪያዎቹን።” እነዚህ በሮቹን በአስተግንብኝ ሁኔታ እንዲቆለፉ ያደርጉ ነበር።
ገባዖናዊ … ሜሮኖታዊ
ገባዖናውያንና ሜሮኖታውያን ሕዝቦች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ገባዖንና ምጽጳ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ከወንዙ ማዶ ያለው ግዛት
ይህ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምዕራብ በኩል የነበረው ግዛት ስም ነው። በሱሳ ከተማ ከነበረው ወንዝ ባሻገር ያለ ቦታ ነበር። ይህ በነህምያ 2፡7 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 3:8
ዑዝኤል … ሐርሃያ … ሐናንያ … ረፋያ … ሆር … ይዳያ … ኤርማፍ … ሐጡስ … ሐሰበንያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ወርቅ አንጥረኛ
ወርቅ አንጥረኛ ማለት የወርቅ ጌጣጌጥና ሌሎች የወርቅ እቃዎችን የሚሰራ ሰው ነው።
ወርቅ አንጥረኛው አደሰ … ሆር አደሰ … ኤርማፍ አደሰ … ሐሰበንያ አደሰ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ቅጥሩን ስለማደስ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ወርቅ አንጥረኞች ቅጥሩን አደሱ … ኤርማፍ ቅጥሩን አደሰ … ሐሰበንያ ቅጥሩን አደሰ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
በአጠገቡም የሽቶ ቀማሚ የነበረው ሐናንያ ነበር
ሐናንያም ቅጥሩን አደሰ። አማራጭ ትርጉም፦ “በአጠገቡም የሽቶ ቀማሚ የነበረው ሐናንያ ቅጥሩን አደሰ።” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ሽቶ
ሰዎች ጥሩ መዓዛ እንዲኖራቸው በሰውነታቸው ላይ በትንሽ መጠን የሚያደርጉት ፈሳሽ ቅመሞች ናቸው።
አለቃ
መሪ ወይም ዋና ገዢ
የግዛት እኩሌታ
“እኩሌታ” ማለት ከሁለት እኩል መጠን ያላቸው ነገሮች አንዱ ማለት ነው። (ክፍልፋዮች የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 3:11
መልክያ … ካሪም … አሱብ … ፈሐት ሞዓብ … ሰሎም … ኤሎኤስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 3:13
ሐኖን
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
የዛኖዋ ነዋሪዎች
“ከዛኖዋ የመጡ ሰዎች”
ዛኖዋ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
የሸለቆ በር
“የሸለቆ በር” ወይም “ወደ ሸለቆ የሚወስደው በር።” ይህን እንደ ማብራሪያ ሳይሆን እንደ ስም ለመተርጎም ይሞከር።
በሮችዋን አስገቡ
“በሮችዋን አስገቡ” ወይም “በሮችን በቦታቸው አደረጉ”
መቀርቀሪያዎቹና መወርወሪያዎቹ
“ቁልፎቹንና መቀርቀሪያዎቹን።” እነዚህ በሮቹ በአስተግንብኝ ሁኔታ ተዘግተው እንዲቆዩ ያደርጉ ነበር።
እስከ ቆሻሻ መጣያ በሩ ድረስ አንድ ሺህ ክንድ የሚሆን ቅጥር አደሱ
ከሸለቆ በር እስከ ቆሻሻ መጣያ በር መካከል ያለውን የቅጥር ክፍል አደሱት። አማራጭ ትርጉም፦ “ከሸለቆ በር እስከ ቆሻሻ መጣያ በር አንድ ሺህ ክንድ ርዝመት ያለው የቅጥር ክፍል አደሱ” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሺህ ክንድ ርዝመት ያለው አደሱ
የኢየሩሳሌምን ቅጥር እያደሱ እንደነበር ግልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሺህ ክንድ ርዝመት ያለው የቅጥር ክፍል አደሱ” ወይም “ከሸለቆ በር ባሻገር ሌላ አንድ ሺህ ክንድ የቅጥሩን ክፍል አደሱ” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሺህ ክንድ
“አንድ ሺህ ክንድ።” ይህ በዘመናዊ የርዝመት መለኪያ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “460 ሜትር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀት እና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ቆሻሻ መጣያ በር
ቆሻሻ ከከተማይቱ ይወገድ የነበረው በዚህ በር በኩል እንደነበር መገመት ይቻላል። ይህንን መግለጫ እንደ እንደ ማብራርያ ከመተርጎም ይልቅ እንደ ስም ለመተርጎም ይሞከር።
Nehemiah 3:14
መልክያ ... ሬካብ ... ሰሎም .... ኮልሖዜ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
አለቃው፣ የሬካብ ልጅ መልክያ
የግዛቱ አለቃ መልክያ ነበር፣ ሬካብ አልነበረም።
አለቃ
መሪ ወይም ዋና ገዢ። ይህንን በነህምያ 3፡9 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።
ቤትሐካሪም
ይህ የአንድ ቦታ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ... በሮቹን ሰራ
“በሮቹን አስገባ” ወይም “በሮቹን በቦታቸው አደረጋቸው”
መቀርቀሪያዎቹና መወርወሪያዎቹ
“ቁልፎችንና መቀርቀሪያዎች።” እነዚህ በሮቹ በአስተግንብኝ ሁኔታ እንዲዘጉ ያደርጋሉ።
የግዛቱ አለቃ የኮልሖዜ ልጅ ሰሎም
የግዛቱ አለቃ የነበረው ሰሎም ነው፣ ኮልሖዜ አልነበረም።
የሼላን መዋኛ ቅጥር
ይህ ማለት ቅጥሩ ከሼላን መዋኛ አጠገብ ነበር የሚገኘው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የሼላን መዋኛን የከበበው ቅጥር” (የንብረት ባለቤትነት የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 3:16
ነህምያ ... ዓዝቡቅ ... ሬሁም ... ባኒ ... ሐሸብያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
አለቃው፣ የዓዝቡቅ ልጅ ነህምያ
አለቃ የነበረው ነህምያ ነው፣ አዝቡቅ አልነበረም።
ነህምያ
እዚህ የተጠቀሰው ነህምያ ይህን መጽሐፍ ከጻፈው ሰው የተለየ ነው።
አለቃ
መሪ ወይም ዋና ገዢ። ይህንን በነህምያ 3፡9 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።
የግዛቱ እኩሌታ
“እኩሌታ” ማለት ከሁለት እኩል መጠን ያላቸው ነገሮች አንዱ ማለት ነው። (ክፍልፋዮች የሚለውን ይመልከቱ)
ቤት-ጹር
እነዚህ የቦታ ስያሜዎች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
... እስካለው ስፍራ አደሱ ... ሌዋውያን አደሱ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ስለ ቅጥሩ እድሳት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “... እስካለው ስፍራ ቅጥሩን አደሱ ... ሌዋውያን ቅጥሩን አደሱ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ኃያላን ሰዎች
“ተዋጊዎች”
ለግዛቱ
“ግዛቱን ወክሎ” ወይም “ግዛቱን በመወከል”
Nehemiah 3:18
ከእርሱም በኋላ የአገሩ ሰዎች አደሱ ... ሌላ ክፍልም አደሱ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ቅጥሩን ስለማደስ ነው ። አማራጭ ትርጉም፦ “ከእርሱም በኋላ የሃገራቸው ሰዎች ቅጥሩን አደሱ ... የቅጥሩን ሌላ ክፍልም አደሱ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእርሱ በኋላ
“ከእርሱ ቀጥሎ”
በዋይ ... ኤንሐዳድ ... ኤጽር ... እያሱ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
አለቃው፣ የኤንሐዳድ ልጅ በዋይ
የግዛቱ አለቃ የነበረው በዋይ ነው፣ ኤንሐዳድ አልነበረም።
ቅዒላ ... ምጽጳ
እነዚህ የቦታ ስያሜዎች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
አለቃው፣ የኢያሱ ልጅ ኤጽር
አለቃ የነበረው ኤጽር ነው፣ ኢያሱ አልነበረም።
በጦር መሳርያ ቤት አንጻር
“ወደ ጦር መሳርያ ቤት ከሚያመሩት ደረጃዎች ፊት ለፊት የሚገኘው”
የጦር መሳርያ ቤት
የጦር መሳርያዎች የሚቀመጡበት ስፍራ
Nehemiah 3:20
ከእርሱ በኋላ
“ከእርሱ ቀጥሎ”
ባሮክ ... ዘባይ ... ኤልያሴብ ... ሜሪሞት ... ኦርዮ ... አቆስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ሌላውን ክፍል አደሰ
ይህ የሚያመለክተው ቅጥሩን ሰለማደስ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የቅጥሩን ሌላ ክፍል አደሰ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 3:22
ኢየሩሳሌም ዙሪያ፣ አደሱ ... ብንያምና አሱብ አደሱ ... ዓዛርያስ .. አደሰ ... ቢንዊ ... አደሰ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት የቅጥሩን መታደስ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በኢየሩሳሌም ዙሪያ ቅጥሩን አደሱ፣ ብንያምና አሱብ ቅጥሩን አደሱ ... ዓዛርያስ ቅጥሩን አደሰ ... ቢንዊ ቅጥሩን አደሰ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ብንያም ... አሱብ ... ዓዛርያስ ... መዕሤያ ... ሐናንያ ... ቢንዊ ... ኤንሐዳድ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ከእነርሱ በኋላ ... ከእርሱ በኋላ
“ከእነርሱ ቀጥሎ ... ከእርሱ ቀጥሎ”
በቤታቸው አንጻር
“ከቤታቸው ፊት ለፊት”
Nehemiah 3:25
ፋላል ... አደሰ ... ፋሮስ ... አደሰ ... ባርያዎቹ አደሱ ... ሌላውን ክፍል አደሱ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት የቅጥሩን መታደስ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ፋላል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

... ቅጥሩን አደሰ ... ፋሮስ ቅጥሩን አደሰ ... ባርያዎቹ ... ቅጥሩን አደሱ ... የቅጥሩን ሌላኛ ክፍሎች አደሱ።
ፋላል ... ኡዛይ ... ፈዳያ ... ፋሮስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ወደላይ ከፍ ያለውን ግንብ
“ወደላይ የሚወጣውን ግንብ”
የላይኛው የንጉስ ቤት
“የእስራኤል መሪ ታላቁ ቤተመንግስት”
የዘበኞች አደባባይ
ይህ ጠባቂዎቹ ይኖሩበት የነበረው ቦታ ነው።
ከእርሱ በኋላ
“ከእርሱ ቀጥሎ”
ጾፌል
ይህ የቦታ ስያሜ ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
በውሃው በር አንጻር
“ከውሃው በር ፊት ለፊት”
ታላቁ ግንብ ... የቆመው ታላቅ ግንብ
“ታላቁ ግንብ ... ታላቁ ግንብ።” “የቆመው ግንብ” የሚለው ሐረግ ከቅጥሩ ወጣ በሎ የሚታየው ረጅሙ ግንብ ነው። ሁለቱም ሐረጎች ስለ አንድ ግንብ እንደሚያወሩ ይገመታል።
ቴቁሐውያን
እነዚህ ቴቁሐ ከሚባል ከተማ የመጡ ሕዝቦች ናቸው። ይህ በነህምያ 3:5 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 3:28
ካህናት አደሱ ... በቤታቸው አንጻር አደሱ ... የምስራቁን በር .. አደሰ ... ሌላውን ክፍል አደሱ ... ትይዩውን አደሱ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ስለ ቅጥሩ መታደስ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ካህናት ቅጥሩን አደሱ ... የቅጥሩን ክፍል አደሱ ... የቅጥሩን የምስራቅ በር ክፍል አደሱ ... የቅጥሩን ሌላ ክፍል አደሱ ... የቅጥሩን ተቃራኒ ክፍል አደሱ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ከፈረሱ በር በላይ
“በላይ” የሚለው ቃል እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው የካህናቱ ቤት በከፍታ ከፈሱ በር በላይ ከፍ በሎ ይገኝ ሰለነበር ይመስላል።
ከራሱ ቤት አንጻር
“ከራሱ ቤት ፊት ለፊት”
ከእነርሱ በኋላ ... ከእርሱ በኋላ
“ከእነርሱ ቀጥሎ ... ከእርሱ ቀጥሎ”
ሳዶቅ ... ኢሜር ... ሸማያ ... ሴኬንያ ... ሐናንያ ... ሰሌምያ ... ሐኖን ... ሴሌፍ ... ሜሱላም ... በራክያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
የምስራቁ በር ጠባቂ የሴኬንያ ልጅ ሸማያ
የምስራቁ በር ጠባቂ የነበረው ሸማያ ነው፣ ሴኬንያ አልነበረም።
የምስራቁ በር ጠባቂ
“የምስራቁን በር ይጠብቅ የነበረው ሰው” ወይም “የምስራቁን በር ይከፍትና ይዘጋ የነበረው ሰው”
ስድስተኛው ወንድ ልጅ
“ስድስተኛ የወንድ ልጅ” ወይም “በቁጥር ስድስተኛ የነበረው ወንድ ልጅ” (ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
በጓዳው አንጻር
“እርሱ ይኖርበት ከነበረበት ክፍሎች ፊት ለፊት።” “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሜሱላምን ነው።
Nehemiah 3:31
ከእርሱ በኋላ
“ከእርሱ ቀጥሎ”
መልክያ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ወርቅ አንጥረኛ
ወርቅ አንጥረኛ ማለት የወርቅ ጌጣጌጥና ሌሎች የወርቅ እቃዎችን የሚሰራ ሰው ነው።
እስከ ... ቤት ድረስ አደሰ ... ነጋዴዎች አደሱ
እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት ቅጥሩን ስለማደስ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እስከ ነጋዴዎቹ ቤት ድረስ ያለውን ቅጥሩን አደሰ ... ነጋዴዎች ቅጥሩን አደሱ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ነጋዴዎች
“ሻጮች” ወይም “ነጋዴዎች”

---

Chapter 4
Nehemiah 4:1
አሁን ሰንባላጥ
እዚህ ላይ ነህምያ አዲስ የታሪኩን አዲስ ክፍል መጀመሩን ለማመልት ሲል “አሁን” የሚለውን ቃል ይጠቀማል።
ሰንባላጥ ... ጦብያ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። ይህ በነህምያ 2:10 ላይ እንዴት እንደተተረጎሙ ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
በውስጡም እጅግ ነደደ፣ እጅግም ተበሳጨ
እዚህ ላይ “ነደደ” ተብሎ የተገለጸው አይሁዳውያን የፈረሰውን ቅጥር እያደሱ መሆኑን ሰንባላጥ መገንዘቡ ነው። ይህ ደግሞ የሰንባላጥ ንዴት እንደሚንድድ እሳት እንደሆነነ በጣም እንደተበሳጨ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እጅግ በኃይል ተናደደ” ወይም “በጣም ተናደደ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በወንድሞቹ ፊት
“በዘመዶቹ ፊት” ወይም “በወገኖቹ ፊት”
እነዚህ ደካሞች መምድን ናቸው ... ያድኑታልን ... ይሰዋሉን ... ስራውን በአንድ ቀን ይጨርሳሉን
ሰንባላጥ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቀው በአይሁዳውያን ላይ ለመሳለቅ ነው። እነዚህ በዓርፍተ ነገር መልክ ሊጻፉ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- “እነዚህ ደካማ አይሁዳውያን ምንም ነገር ሊያሳኩ አይችሉም። ከተማቸውን ከጥፋት አድነው ለራሳቸው ሊያደርጉ አይችሉም። መስዋዕት አያቀርቡም። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ደካማ አይሁዶች
“አቅመ ቢስ አይሁዶች”
በአንድ ቀን
በአንድ ቀን ስራው ሊያልቅ አይችልም ሲል አንድን ነገር ቶሎ ሰርቶ መጨረስ አለመቻልን ለማሳየት ነው።” አማራጭ ትርጉም:- “በቶሎ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ድንጋዮቹ ከተቃጠሉ በኋላ ከፍርስራሽ ክምር መካከል ነፍስ ይዘሩባቸው ይሆን?
ሰንባላጥ ይህንንም ጥያቄ የሚጠይቀው በአይሁዳውያን ላይ ለመሳለቅ ነው። ይህ በዓርፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ከተቃጠለው የፍርስራሽ ክምር መካከል ለድንጋዮቹ እንደገና ነፍስ ሊዘሩባቸው አይችሉም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ድንጋዮቹ ከተቃጠሉ በኋላ ከፍርስራሽ ክምር መካከል ነፍስ ይዘሩባቸዋል
ይህ ሰዎቹ ከተማውን ነፍስ እንደዘሩበት ያህለ ደግመው ስለመስራታቸውና ስለመገንባታቸው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “ከተቃጠሉትና ወደ ፍርስራሽነት ከተለወጡት የማይጠቅሙ ድንጋዮች ከተማይቱን ያድሳሉ ደግሞም ቅጥሩን እንደገና ይሰራሉ።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከተቃጠሉ በኋላ የፍርስራሽ ክምር ከሆኑት
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሰዎች አቃጥለው የፍርስራሽ ክምር ካደረጉት ድንጋይ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በሚገነቡት ላይ ቀበሮ ቢወጣበት የድንጋይ ቅጥራቸውን ያፈርሰዋል
ሰንባላጥ የሚሰራው ቅጥር ደካማ እንደሆነ ለማሳየትና በእነርሱ ላይ ለመሳለቅ ቀበሮ ቢወጣበት እንደሚያፈርሰው ግነት በተሞላበት ንግግር ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “የሚገነቡት ቅጥር በጣም ደካማ ከመሆኑ የተነሳ ትንሽ ቀበሮ እንኳን ቅጥሩ ላይ ቢወጣ የድንጋዩ ቅጥራቸው ይፈራርሳል።” (ግነትና ጅምላ መግለጫየሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አምላካችን ሆይ ስማ … ሰራተኞቹን አበሳጭተዋልና

እዚህ ላይ ነህምያ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል። ይህ በግልጽ ሊብራራና በትምህርተ ጥቅስ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ ከዚያም ጸለይሁ፣ “አምላካችን ስማ … ሰራተኞችን አስቆጥተዋቸዋልና። ስለዚህም …” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ተንቀናልና አምላካችን ስማ

እዚህ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አይሁዳውያንን ነው። ይህ በዓረፍተ ነገር ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻችን ንቀውናልና አምላካችን ስማ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለብዝበዛ አሳልፈህ ስጣቸው

ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻቸው እንዲበዘብዙአቸው አድርግ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ስድባቸውን በራሳቸው ላይ መልስባቸው

“ስድባቸውን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰንባላጥና የጦብያን ስድብ ነው። “በራሳቸው ላይ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ጠቅላላ ሕዝቡን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስድባቸው በራሳቸው ላይ ይሁንባቸው” ወይም “ስድባቸው በራሳቸው ላይ መሳለቂያ እንዲሆኑ ያድርጋው።” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

አትክደን

ይህ በአካል ሊከደኑ እንደሚችሉ እቃዎች እንዲሁ የአንድ ሰው ኃጢአት እንደሚከደንና ይቅር እንደሚባል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይቅር አትበል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በደላቸውም በፊትህ አትደምሰስ

ይህ ሊሰረዝ እንደሚችል አንድ ጽሑፍ የአንድን ሰው ኃጢአት እንደሚወገድና እንደሚረሳ የሚያሳይ ው። አማራጭ ትርጉም፡- “በደላቸውን አትርሳ”

የሚገነቡትን ሰዎች አበሳጭተዋልና

“ገንቢዎቹን አናድደዋቸዋል”

ቅጥሩንም ሰራን

“ቅጥሩን ደግመን ገነባን”

ቅጥሩም በሙሉ እስከ ቁመቱ አጋማሽ ደረስ ተጋጠመ

ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቅጥሩን አንድ ላይ አጋጠምነው፤ ከጠቅላላ ቁመቱም ግማሹን ያህል ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ግማሽ ቁመት የሚያክል

“እኩሌታ” ማለት ከሁለት ሁለት እኩያ መጠን ካላቸው ነገሮች አንዱ ማለት ነው። (ክፍልፋዮች የሚለውን ይመልከቱ)

## Nehemiah 4:4

አምላካችን ሆይ ስማ … ሰራተኞቹን አበሳጭተዋልና

እዚህ ላይ ነህምያ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል። ይህ በግልጽ ሊብራራና በትምህርተ ጥቅስ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ ከዚያም ጸለይሁ፣ “አምላካችን ስማ … ሰራተኞችን አስቆጥተዋቸዋልና። ስለዚህም …” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ተንቀናልና አምላካችን ስማ

እዚህ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አይሁዳውያንን ነው። ይህ በዓረፍተ ነገር ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻችን ንቀውናልና አምላካችን ስማ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለብዝበዛ አሳልፈህ ስጣቸው

ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻቸው እንዲበዘብዙአቸው አድርግ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ስድባቸውን በራሳቸው ላይ መልስባቸው

“ስድባቸውን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰንባላጥና የጦብያን ስድብ ነው። “በራሳቸው ላይ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ጠቅላላ ሕዝቡን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስድባቸው በራሳቸው ላይ ይሁንባቸው” ወይም “ስድባቸው በራሳቸው ላይ መሳለቂያ እንዲሆኑ ያድርጋው።” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

አትክደን

ይህ በአካል ሊከደኑ እንደሚችሉ እቃዎች እንዲሁ የአንድ ሰው ኃጢአት እንደሚከደንና ይቅር እንደሚባል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይቅር አትበል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በደላቸውም በፊትህ አትደምሰስ

ይህ ሊሰረዝ እንደሚችል አንድ ጽሑፍ የአንድን ሰው ኃጢአት እንደሚወገድና እንደሚረሳ የሚያሳይ ው። አማራጭ ትርጉም፡- “በደላቸውን አትርሳ”

የሚገነቡትን ሰዎች አበሳጭተዋልና

“ገንቢዎቹን አናድደዋቸዋል”

ቅጥሩንም ሰራን

“ቅጥሩን ደግመን ገነባን”

ቅጥሩም በሙሉ እስከ ቁመቱ አጋማሽ ደረስ ተጋጠመ

ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቅጥሩን አንድ ላይ አጋጠምነው፤ ከጠቅላላ ቁመቱም ግማሹን ያህል ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ግማሽ ቁመት የሚያክል

“እኩሌታ” ማለት ከሁለት ሁለት እኩያ መጠን ካላቸው ነገሮች አንዱ ማለት ነው። (ክፍልፋዮች የሚለውን ይመልከቱ)

## Nehemiah 4:7

ታላቅም ንዴት በውስጣቸው ነደደ

ይህ ሕዝቡ ንዴታቸው አንድ ነገር በውስጣቸው የሚነድድ እስከሚመስል ድረስ በጣም ተናድደው እንደነበር የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም ተናደዱ” ወይም “ሃይለኛ ንዴት ተፈጠረባቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌምን ይወጉ ዘንድ

እዚህ ላይ “ኢየሩሳሌም” የሚለው በዚያ የሚኖሩ ሕዝብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሕዝብን ይወጉና ያሸብሩ …” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለጥበቃ ዘቦችን አደረግን

“ከተማው ለመጠበቅ በቅጥሩ ዙሪያ ዘቦችን አቆምን”

## Nehemiah 4:10

ብዙ ፍርስራሽ አለ

ፍርስራሽ “የተቃጠለ ድንጋይ” ወይም “የተሰባበረ ድንጋይ” ወይም “የማይጠቅም ድንጋይ” ነው።

በመካከላቸው እስክንመጣ ድረስ አያውቁም ወይም አያዩምም

“አጠገባቸው እስክንደርስ ድረስ ስንመጣ አያዩንም”

ኤልያሴብ … ዮአዳ፣ ዮሐናን … ያዱአ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

በዳርዮስ መንግስት ዘመን

"እስከ ዳርዮስ የመንግስት ዘመን" የሚለው ሌላ ትርጉም መሆን ይችላል።

በታሪክ መጻሕፍት ተጻፉ

ይህ የዜና መዋዕልን ያመለክታል። ጸሐፊዎች ከላይ ባሉት ቁጥሮች ውስጥ እነዚህን ቃላት በየዕለቱ ምን እንደተፈጠረ በሚጽፉበት መጽሐፍ ላይ ጽፈዋቸው ነበር።

እስከ … ቀናት ድረስ ለዳዊት ትዕዛዝ በመታዘዝ

ንጉስ ዳዊት ሌዋውያንን አምልኮን እንዴት እንደሚመሩና እንደሚያስተባብሩ አዝዞአቸው ነበር።

በዮአቂም … ኤዮሴዴቅ ዘመን … እና በአለቃው በነህምያና በጸሐፊውም በዕዝራ ዘመን

ይህ ቀን የተወሰነው በጊዜው አይሁዳውያንን እየመራ የነበረው ማን ነበር የሚለውን በመመልከት ነው። "ዮአቂም … ኢዮሴዴቅ ሊቀ ካህን በነበረ ጊዜ፣ ነህምያ አለቃ በነበረ ጊዜ እና ዕዝራ ጸሐፊ በነበረ ጊዜ"

Nehemiah 12:27

የኢየሩሳሌም ቅጥር በተመረቀ ጊዜ

አማራጭ ትርጉም ሊሆን የሚችሉ፦ 1) "እነርሱ የኢየሩሳሌምን ቅጥር በመረቁ ጊዜ" ወይም 2) "የኢየሩሳሌም ቅጥር ምረቃ ይከናወን ዘንድ።"

ጽናጽል

ሁለት ቀጭን ክብ ብረት ያለው፣ አብሮ ሲመታ ጮክ ያለ ድምጽ የሚያወጣ መሳሪያ። (የማይታወቁ ነገሮች ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 12:29

ቤት ጌልገላ … ጌባ እና ዓዝሞት

እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 12:31

የይሁዳ አለቆች

በይሁዳ ይኖሩ የነበሩትን ሕዝቦች ይመሩ የነበሩ ሰዎች

Nehemiah 12:32

ሆሻያ … ዓዛርያስ ፣ ዕዝራ፣ ሜሱላም፣ ይሁዳ፣ ብንያም፣ ሸማያ፣ ኤርምያስ፣ ዘካርያስ፣ ዮናታን፣ ሸማያ፣ መታንያ … ሚካያ … ዙኩር … አሳፍ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነርሱ ኋላ ሄዱ

"ከእነርሱ በኋላ ተከተሉ"

አንዳንድ መለከት የያዙ የካህናት ወንዶች ልጆችና፣ ዘካርያስም some of the priests'

አንዳንድ ትርጉሞች "መለከት ይዘው ከነበሩት የካህናት ልጆች ውስጥ ዘካርያስ" ብለው ይተረጉሙታል።

የአሳፍ ልጅ የዘኩር ልጅ የሚካያ ልጅ የመታንያ ልጅ የሸማያ ልጅ የዮናታን ልጅ ዘካርያስ

"ዘካርያስ" ከሚለው ስም በፊት የተጻፉት በሙሉ የዘካርያስ ዘሮች ናቸው። ይህ ዝርዝር ዘካርያስን ታዋቂ ዘማሪ ከነበረው ከአሳፍ ጋር ያለውን ዝምድና ያሳያል። "የዮናታን ልጅ የነበረው፣ የሸማያ ልጅ የነበረው፣ የመታንያ ልጅ የነበረው፣ የሚካያ ልጅ የነበረው፣ የዘኩር ልጅ የነበረው የአሳፍ ልጅ ዘካርያስ"

Nehemiah 12:36

እነዚህም ነበሩ

"ከእነርሱ ጋርም እነዚህ ነበሩ"

ዘካርያስ … ሸማያ፣ ኤዝርኤል፣ ሚላላይ፣ ጊላላይ፣ መዓይ፣ ናትናኤል፣ ይሁዳ፣ አናኒ .. ዳዊት … ዕዝራ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ጸሐፊው ዕዝራ በፊታቸው ነበር

"ጸሐፊው ዕዝራ እየመራቸው ነበር"

በምንጭ በር … በውኃ በር

እነዚህ በቅጥሩ ላይ የነበሩ በሮች ስም ናቸው።

Nehemiah 12:38

መዘምራን

የዘማሪዎች ስብስብ

ተከተልኳቸው

ነህምያ ተከትሏቸው ሄደ

የእቶኑ ግንብ … የሐናኤል ግንብ … የመቶ ግንብ

እነዚህ ሰዎች አደጋ ካለ መከታተል እንዲያመቻቸው ወጥተው የሚመለከቱባቸው ግንብዎች ናቸው።። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሰፊው ቅጥር

ይህ የቅጥሩ የአንዱ ክፍል ስም ነው።

በኤፍሬም በር … በአሮጌው በር … በዓሣ በር … በበግ በር … በዘበኞች በር

እነዚህ በቅጥሩ ላይ የነበሩ በሮች ስም ናቸው።

Nehemiah 12:40

እኔም በቦታዬ ላይ ቆምኩኝ

እዚህ የሚናገረው ነህምያ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "እኔ ነህምያ በቦታዬ ላይ ቆምኩ"

ኤልያቄም … መዕሤያ … ሚንያሚን … ሚካያ … ኤልዮዔናይ … ዘካርያስ … ሐናንያ … መዕሤያ … ሸማያ … አልዓዛር … ኦዚ … ይሆሐናን … መልክያ … ኤላም … ኤጽር

እነዚህ በጊዜው ካህናት የነበሩ ወንዶች ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ይዝረሕያ

ይህ የዘማሪዎች መሪ የነበረ የወንድ ሰው ስም ነው።

በመለከቶች

አማራጭ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) ከኤልያቄም እስከ ሐናንያ ድረስ የተዘረዘሩት ሰባት ካህህናት መለከቶችን ተሸክመዋል ወይም 2) ከኤልያቄም እስከ ኤጽር ድረስ የተዘረዘሩት 15 ካህናት በሙሉ መለከቶችን ተሸክመዋል።

ድምጻቸው እንዲሰማ አደረጉ

"በጩኸት ዘመሩ"

Nehemiah 12:43

በታላቅ ደስታ ደስ መሰኘት

"እጅግ በጣም መደሰት" ከዚህ የተነሳ የኢየሩሳሌም ደስታ ከሩቅ መሰማት ይችል ነበር በዚህ ክፍል "የኢየሩሳሌም ደስታ" የሚለው "በኢየሩሳሌም ያሉ ሕዝቦች ያሰሙትን ድምጽ" የሚወክል ነው። ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ከኢየሩሳሌም በጣም ርቀው የሚኖሩ ሕዝቦች የእስራኤል ሕዝብ በዓሉን በሚያከብሩበት ጊዜ ያሰሙትን ድምጽ መስማት ይችሉ ነበር" (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 12:44

ተቆጣጣሪ እንዲሆኑ ሰዎች ተሸሙ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል፡፡ ሰዎቹን ማን እንደሾማቸው ግን የተገለጸ ነገር የለም፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ተቆጣጣሪ ይሆኑ ዘንድ ሰዎችን ሾሙ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

መዋጮ

ሕዝቡ ለካህናት የሰጡት ነገሮች

ይሁዳ በካህናቱና በሌዋውያን ተደስቶ ነበርና

ሕዝቡ እነዚህን ሰዎች የሾሙአቸው የይሁዳ ሕዝብ ያገለግሉ በነበሩት በካህናቱና በሌዋውያኑ በመደሰታቸው ነው፡፡

በፊታቸው ቆመው የነበሩት

ሌዋውያንኑና ካህናቱ ቆመው ብቻ አልነበረም፣ በተሰጣቸው ኃላፊነት እያገለገሉ ነበር፡፡ የዚህ ትርጉም ግልጽ ተደርጎ መቀመጥ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በፊታቸው ቆመው እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ የነበሩት” (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የበር ጠባቂዎች

ወደ ከተማውና ወደ መቅደሱ የሚገባውን ሰው ለመቆጣጠርና ገዢው በወሰነው ሰዓትና ምክንያት በሩን እንዲከፍቱና እንዲዘጉ ኃላፊነት የተሰጣቸው በእያንዳንዱ በር ላይ የተመደቡ ሰዎች፡፡ ይህ በነህምያ 7፡1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ፡፡

Nehemiah 12:46

የመዘምራን አለቆች ነበሩ

ይህ ዓርፍተ ነገር በነህምያ 12፡45 ላይ ሰዎቹ ያደረጉትን ነገር ያደረጉበትን ምክንያት ይናገራል፣ ከዚህ በተጨማሪ ዳዊት በመቅደስ ውስጥ እንዴት አምልኮ መደረግ እንዳለበት ለሕዝቡ ስለ ተናገረበት ጊዜ መረጃ የይሰጠናል፡፡

በዘሩባቤል ዘመን

ዘሩባቤል የንጉስ ዳዊት ዘር ሲሆን በይሁዳ ክልል ውስጥ ከገዢዎቹ ውስጥ አንዱ ነው፡፡

ፋንታቸውን ይሰጡ ነበር

“እስራኤል ሁሉ ድርሻውን ያስቀምጡ ነበር”

የአሮን ዘሮች

ከሙሴ ወንድም ከአሮን ዘር የመጡ በእስራኤል የነበሩ ካህናት

Chapter 13

Nehemiah 13:1

ለሕዝቡ አነበቡ

“ሕዝቡ እንደሚሰሙት ሆኖ”

ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ ለዘላለም እንዳይገቡ

“ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ ፈጽሞ እንዳይገቡ”

ይህም ምክንያቱ

“ወደ እግዚአብሔር ጉባዔ በፍጹም እንዳይገቡ የሆነበት ምክንያቱ”

Nehemiah 13:4

ካህኑ ኤልያሴብ ተሾሞ ነበር

ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ካህኑ ኤልያሴብን ሾሙት” ወይም “መሪዎቹ ካህኑ ኤልያሴብን ሾሙት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጦብያ ጋር ተወዳጅቶ ነበር

“ኤልያሴብና ጦብያ በቅርበት አብረው ይሰሩ ነበር”

ኤልያሴብ ... ጦብያ

እዚህ የወንድ ስሞች ናቸው

ኤልያሴብ ለጦብያ ትልቅ ማከማቻ ክፍል አዘጋጅቶለት ነበር

“ኤልያሴብ ጦብያ እንዲጠቀምበት ትልቅ የእቃ ማከማቻ ክፍል አዘጋጅቶለት ነበር”

የበር ጠባቂዎች

ወደ ከተማውና ወደ መቅደሱ የሚገባውን ሰው ለመቆጣጠርና ገዢው በወሰነው ሰዓትና ምክንያት በሩን እንዲከፍቱና እንዲዘጉ ኃላፊነት የተሰጣቸው በእያንዳንዱ በር ላይ የተመደቡ ሰዎች፡፡ ይህ በነህምያ 7፡1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ፡፡

Nehemiah 13:6

ነገር ግን በዚህ ጊዜ ሁሉ እኔ ኢየሩሳሌም አልነበርኩም

“ይህ በተከሰተ ጊዜ እኔ ከኢየሩሳሌም ውጪ ነበርኩ”

እኔ አልነበርኩም

እዚህ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል ነህምያን ያመለክታል፡፡

በእግዚአብሔር ቤት አደባባይ የእቃ ማከማቻውን

ይህ ክፍል ለቤተ መቅደስ ቁርባን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማስቀመጥ የተቀደሰ ክፍል ነበር፡፡ (ነህምያ 13፡5)

Nehemiah 13:10

የሌዋውያን ድርሻቸው አልተሰጣቸውም ነበር

የዚህ ዓርፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝቡ አስራታቸውንና ለቤተ መቅዱሱ ካህናት ለቁርባን የሚሆነውን የምግብ መስዋዕት ወደ ግምጃ ቤቱ አያስገቡም ነበር፡፡” (ግምታዊ እውቀትና ያልተገለጸ መረጃ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ስራውን ይሰሩ የነበሩት ሌዋውያንና ዘማሪያን እያንዳንዳቸው ወደ እርሻቸው ሄዱ

“ስራውን ይሰሩ የነበሩ ሌዋውያንና ዘማርያን መቅደሱን ጥለው እያንዳንዳቸcው ወደ እርሻቸው ሄዱ

የእግዚአብሔር ቤት ለምን ተተወ?

ነህምያ ስራቸውን ያልሰሩትን አለቆች ለመሞገትና በእነርሱ ላይ ለመሳለቅ ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ተጠቀመ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔር ቤት ትታችሁታል?” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 13:12

ይሁም ሁሉ

የሃገሩ ስም በሃገሩ ለሚኖሩ ሕዝቦች ወካይ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይህ ማስፋፊያ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በይሁዳ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች በሙሉ” (ምትክ ስም እና ግነትና ማስፋፊያ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰሌምያ ... ሳዶቅ ... ፈዳያ ... ሐናን ... ዘኩር ... መታንያ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው፡፡ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የታመኑ ሆነው ተገኙ

ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል፡፡ “የታመነ” የሚለው ረቂቅ ቃል በግስ መልክ መጻፍ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እምነቴን ልጥልባቸው የምችል ሰዎች አውቅ ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህን አስመልክቶ አምላኬ አስበኝ

“አምላኬ ይህን በተመለከተ አስበኝ”

Nehemiah 13:15

የወይን መጥመቂያ የሚረግጡትን

“የወይን መጥመቂያዎች” የሚለው ቃል በመጥመቂያዎች ውስጥ ለነበሩት የወይን ፍሬዎችን ወካይ ነው፡፡ ሕዝቡ ጭማቂ እንዲያወጡ በወይን ፍሬዎቹ ላይ በላያቸው ይራመዱባቸው ነበር፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በወይን መጥመቂያዎች ላይ የነበሩትን የወይን ፍሬዎችን ይረግጣሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይረግጡ

አንድን ነገር ለመጨፍለቅ ወይም ለመጭመቅ በላዩ ላይ መራመድ

Nehemiah 13:16

ጢሮስ

ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የምታደርጉት ክፉ ነገር ምንድን ነው፣ ሰንበትንስ ታረክሳላችሁን?

ነህምያ ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የይሁዳን አለቆች ለመገሰጽ ተጠመበት፡፡ ይህ በዓርፍተ ነገር መልክ መተርጎም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የሰንበትን ቀን በማርከስ ክፉ ስራን እየሰራችሁ ነው” ወይም “የሰንበትን ቀን በማርከስ ለሰራችሁት ክፉ ስራ እግዚአብሔር ይቀጣችኋል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አባቶቻችሁ ይህን አድርገው አልነበረም? እግዚአብሔር በእኛና በከተማዋ ላይ ክፉ ነገርን ሁሉ አላመጣም?

ነህምያ እነዚህን መልስ የማይሰጥባቸውን ጥያቄዎች የይሁዳን አለቆች ለመገሰጽ ተጠቀመባቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በአንድ ላይ በማያያዝና በመተርጎም በአንድ ዓረፍተ ነገር መጻፍ እንችላለን፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አባቶቻችሁ ይህን እንዳደረጉ ታውቃላችሁ፣ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ክፉ ነገር በእኛና በዚህች ከተማ ላይ ያመጣው ለዚህ ነው” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Nehemiah 13:19
በመሸ ጊዜ … ከሰንበት በፊት
“ፀሐይ በገባች ጊዜ … ሰንበት ሊሊምር ሰዓቱ ደርሶ ነበር”
በሮችዋ እንዲዘጉና እንዳይከፈቱ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ጠባቂዎቹ በሮቹን እንዲዘጉና እንዳይከፍቱአቸውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ሸክም ወደ ውስጥ እንዳይገባ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ማንም መሸጥ የሚፈልገውን ነገር ይዞ መግባት አይችልም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የሁሉም ዓይነት እቃ ሻጮች
“መሸጥ የፈለጉአቸውን ብዙ የተለያዩ እቃዎችን ይዘው የመጡ ሰዎች”
Nehemiah 13:21
ከቅጥሩ ውጪ ለምን ታድራላችሁ?
ነህምያ ነጋዴዎችን ለመገሰጽና ትዕዛዙን አጠንክሮ ለመናገር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ይጠቀማል፡፡ ይህ በዓርፍተ ነገር መልክ መተርጎም ይቻላል፡፡ የዚህ ዓርፍተ ነገር ሙሉ ትርጉምም ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ካዘዝኩት ነገር በተቃራኒ ከቅጥሩ ውጪ እያደራችሁ ነው” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እጄን በእናተ ላይ አደርጋለሁ!
“እጅ” የሚለው ቃል በሃይል የተሞላ እርምጃን የሚወክል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በኃይል አስነስቼ አባርራችኋለሁ!” ወይም “በኃይል አስወግዳችኋለሁ!” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
አምላኬ ሆይ ስለዚህ ደግሞ አስበኝ
“አምላኬ ሆይ፣ ይህንን አስመልክቶ እኔን አስበኝ” እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ሐረግ በነህምያ 13፡14 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ፡፡
Nehemiah 13:23
አያያዥ ዓርፍተ ነገር፡-
እነዚህ ቁጥሮች ተከትለው ለሚመጡት ድርጊቶች እንደ መግቢያ ያገለግላሉ፡፡
የአዛጦን፣ የአሞንና የሞዓብ ሴቶችን ያገቡት አይሁዳውያን
“አይሁውያን ያልሆኑ ሴቶችን ያገቡ አይሁዳውያን” እግዚአብሔር ከዘራቸው ውጪ መጋባትን ከልክሎ ነበር፡፡ የዚህ ዓረፍተ ነገር ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል፡፡ (ግምታዊ እውቀትና ያለተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አዛጦን
ይህ የከተማ ስም ነው፡፡ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
አሞን … ሞዓብ
እነዚህ የሕዝብ ስሞች ናቸው፡፡ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ከልጆቻቸውም ግማሾቹ
“ከዚህም የተነሳ ከልጆቻቸው ግማሾቹ”
Nehemiah 13:25
ተከራከርኳቸው
“ስለሰሩት ነገርም በቀጥታ ተናገርኳቸው”
አንዳንዶቹን መታኋቸው
ነህምያ አንዳንዶቹን በእጁ መታቸው፡፡
በእግዚአብሔር አስማልኳቸው
“በእግዚአብሔር ፊት ቃል አስገባኋቸው”
የእስራኤል ንጉስ ሰሎሞን በእነዚህ ሴቶች ምክንያት አልሳተምን?
ነህምያ ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ሰዎቹን ለመገሰጽ ተጠቀመ፡፡ ይህ በዓርፍተ ነገር ቅርጽ መጻፍ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤል ንጉስ ሰሎሞን በእነዚህ ሴቶች ምክንያት ኃጢአትን ማድረጉን ታውቃላችሁ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ታዲያ እናንተን ሰምተን ይህንን ታላቅ ኃጢአት እናድርግ፣ እነዚህን እንግዳ ሴቶች በማግባትም አምላካችን ላይ በደል እናድርግ?
ነህምያ ሰዎቹን ለመገሰጽ ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ተጠቀመ፡፡ ይህ በዓርፍተ ነገር መልክ መጻፍ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተን አንሰማም ወይም ይህን ታላቅ ኃጢአት አናደርግም ወይም እነዚህን እንግዳ ሴቶችም በማግባት አምላካችንን አንበድልም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 13:28
ዮአዳ … ኤልያሴብ … ሰንባላጥ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው፡፡ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ሖሮናዊው
ይህ የሚያመለክተው ከቤት ሖሮን ከተማ የመጣ ሰውን ነው፡፡ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
እኔም ከእጠገቤ አባረርኩት
“አባረርኩት” ወይም “ኢየሩሳሌምን እንዲለቅቅ አደረግኩት”
አስባቸው
“ስለ እነርሱ አስብ” ወይም “ያደረጉትን አስታውስ፡፡” እንደዚ አይነት ተመሳሳይ ሐረግ በነህምያ 13፡14 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ
ክህነትን ስላረከሱ የካህናትንና የሌዋውያንን ቃልኪዳንም ስላፈረሱ
ክህነትን ማርከስ እና ቃልኪዳኑን ማፍረስ ክህነቱንና ቃልኪዳኑን በአካል እንዳረከሱት ተደርጎ ቀርቧል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የክህነቱን ክብር አጉድለዋል፣ ከካህናቱና ከሌዋውያኑ ጋር ያደረግኸውን ቃልኪዳን አፍርሰዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Nehemiah 13:30
ስለዚህ አነጻኋቸው
“በዚህም መንገድ አነጻኋቸው”
የካህናትና የሌዋውያንን ሥርዓት አደረግሁ
“ካህናቱና ሌዋውያኑን ምን ማድረግ እንደነበረባቸው ነገርኳቸው”
የእንጨት ቁርባንን አደረግኩኝ
“የእንጨት ቁርባን የቀርብበትን እንጨት አዘጋጀሁ”
ለበኩራቱም
“በመኸር ጊዜ የሚቀርበው የመጀመርያው ምርት”
አስበኝ፣ አምላኬ፣ በመልካም አስበኝ
“አምላኬ፣ የሰራሁትን ነገር ሁሉ አስብ ደግሞ ስላደረግሁት መልካም ነገር ባርከኝ” ይህ በነህምያ 13፡14 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ፡፡

---

Chapter 1
Esther 1:1
በጠረክሲስ ዘመን
"ጠረክሲስ በሚገዛበት ዘመን" ወይም "ጠረክሲስ ንጉሥ ሆኖ ይገዛ በነበረበት ጊዜ"
ይህ ጠረክሲስ ከህንድ አንስቶ እስከ ኩሽ/ ኢትዮጵያ ድረስ ከ127 ግዛቶች በላይ ይገዛ ነበር፡፡
ይህ የመረጃ ዳራ የቀረበው አንባቢ ጠረክሲስን ለማወቅ ይረዳው ዘንድ ነው፡፡ (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)
ግዛቶች
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው፡፡
በንጉሣዊ ዙፋኑ ላይ ተቀመጠ
እዚህ ስፍራ "ንጉሣዊ ዙፋን" የሚለው በግዛቱ ላይ ያለውን አገዛዝ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፡፡ "መንግሥቱን አስተዳደረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡
(ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)
ምሽግ/ግንብ
ይህ የቤተመንግሥት ግንብን፣ ጠንካራ ይዞታን ወይም የተመሸገ ከተማን ያመለክታል፡፡
ሱሳ
ይህ የፋርስ ነገስታት መናገሻ ከተማ ነበር (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ፤ የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 1:3
በግዛቱ ሶስተኛ አመት
"ለ2 አመታት ከገዛ በኋላ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰራዊቱ

ይህ ምናልባት የሰራዊቱን መሪዎች ሊያመለክት የሚችል ነው። " የሰራዊቱ መኳንንት " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሲኔክቲኪ/ ዘይቤያዊ አነጋጋር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ የሚለውን ይመልከቱ)
የግዛቱ ብልጽግና ታላቅነት
እነዚህ ቃላቶች ግዛቱ ምን ያህል ታላቅ እንደነበር አጉልተው የሚገልጹ እና ተመሳሳይ ትርጉም የያዙ ናቸው። (ደብሌት/ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
የታላቅነቱ ግርማ ክብር
እነዚህ ቃላት ምን ያህል ታላቅ እንደነበር የሚያጎሉ እና ተመሳሳይ ትርጉም የያዙ ናቸው። "የታላቅነቱ ክብር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
180 ቀናት
"አንድ መቶ ሰማንያ ቀናት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 1:5
እነዚህ ቀናቶች በተፈጸሙ ጊዜ
"በዚያ ክብረ በዓል ማብቂያ"
ሰባት ቀናት የወሰደ በዓል
በሱሳ ለነበሩ መኳንንት ብቻ የተደረገ ሁለተኛው ክብረ በዓል ነበረር። "ሰባት ቀናት የፈጀ ሌላ ክብረ በዓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ምሽግ/ግንብ
ይህ የቤተመንግሥት ግንብን፣ ጠንካራ ይዞታን ወይም የተመሸገ ከተማን ያመለክታል። በአስቴር 1:1 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት ተመልሰው ይመልከቱ።
ሱሳ
በአስቴር 1:2 ላይ የዚህን ስፍራ ስያሜ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ፤ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)
በሞዛይክ (በጠጠር) የሚሰራ የአግረኛ መንገድ/ወለል
"ሞዛይክ" - ለዐይን ማራኪ በሆነ የአሰራር መንገድ የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ድንጋዮች በመጠቀም ይቀርባል
ፓርፌሪ/ ለጌጥ መስሪያ የሚያገለግል ቀይ/ሐምራዊ አለት
ይህ ቀይ እና ሐምራዊ መልክ ያለው አለት ሲሆን መስታወት የመሰለ ድንጋይ/ የክርስታል ቁርጥራጮች አሉት።
Esther 1:7
መጠጥ በወርቅ ዋንጫ ይቀርብ ነበር።
በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እንግዶች ከወርቁዋንጫ ወይን ጠጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ገቢር/ተገቢሮ ወይም አድራጊ/ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከንጉሡ ልግስና የተነሳ ብዙ የንጉሣዊ ክብር መገለጫ የሆነ ወይን ይቀርብ ነበር።
"ንጉሡ በንጉሳዊ ክብር መግለጫ ረገድ እጅግ ለጋስ ነበር"
ለጋስነት
"ለመስጠት ታላቅ ፈቃደኝነት"
እንዳች ግዴታ አይጣልም ነበር
"ማንም ወይን ለመጠጣት አይገደድም ነበር"
ንጉሡ ለቤተ መንግስቱ መኳንንት በሙሉ ለእያንዳንዱ ሰው የፈለገውን ያህል እንዲያቀርቡለት ትዕዛዝ አስተላለፈ።
ይህ ሃሳብ፤ ንጉሡ ለባለሟሎቹ ለሁሉም ታዳሚየሚፈልገውን ያህል ወይን እንዲሰጠው ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር ማለት ነው።
Esther 1:9
በሰባተኛው ቀን
"ከ6 ቀናት በኋላ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የንጉሡ ልብ ከወይን ጠጅ የተነሳ ደስ ተሰኝቶ ነበር።
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው ቃል ንጉሡን ያመለክታል፣ "ደስታ ተሞልቶ" የሚለው ደግሞ በፈሊጣዊ አገላለጽ ሰክሮ ነበር የሚል ትርጉም አለው። "ንጉሡ ወይን ጠጥቶ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሴኔክቲክ/ ዘይቤያዊ አነጋገር እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ምሁማን፣ ባዛን፣ ሐርቦና፣ ገበታ፣ ዘቶሊያ፣ ዜታር እና ከርከስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ፤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚያገለግሉት ሰባቱ ሹማማንት
ይህ እነዚህ ሰዎች እነማን እንደነበሩ ለመግለጽ የቀረበ የመረጃ ዳራ ነው። (መረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)
ተክለ ሰውነቷና ውበቷ አስደናቂ ነበር
"በጣም ውብ ነበረች"
Esther 1:12
በመኳንንቱ በደረሳት የንጉሡ ቃል መሰረት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የንጉሡ ሹማምንት ስለ ንጉሡ ትዕዛዝ በነገሯት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ-ገቢር/ተገቢሮ የሚለውን ይመልከቱ)
በቃሉ
"በትዕዛዙ"
ቁጣው በውስጡ ነደደ
ይህ ጠንካራ የንጉሡ ቁጣ የተገለጸው በውስጡ እንደሚነድ እሳት ነው። "ቁጣው በውስጡ እንዳለ እሳት የበረታ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 1:13
ወቅቱን የተረዱ
"በህይወታቸው ውስጥ የሚፈጸመውን ነገር የሚረዱ" ንጉሡ በህግና በፍርድ ዐዋቂ ከሆኑ ጋር የመመካከር ልማድ ነበረው። ይህ የመረጃ ዳራ ንጉሡ እነዚህን ሰዎች ለምን እንደጠራ ያብራራል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)
አርቄስዮስ፣ ሼታር፣ አድማታ፣ ተርሺሽ፣ ማሬስ፣ ማሌሴዓር እና ምሙካ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ፤ የሚለውን ይመልከቱ
ህጉ እንዲከበር...በሹማንነቱ ምን ቅሬታ ቀረበ?
ይህንን ጥያቄ ማን እንዳቀረበ መግለጹ ሊጠቅም ይችላል። ንጉሡ እንዲህ አላቸው፣ "ህጉ በመጣሱ ... በመኳንንት?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ህጉ እንዲከበር
"ህጉን በማጤን" ወይም "ህጉን በመታዘዝ"
Esther 1:16
ምሙካ
በአስቴር 1:14 በሚገኘው መሰረት ስሙን ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ፤የሚለውን ይመልከቱ)
መላው መኳንንት እና መላው ህዝብ... መላው ግዛት... ሴቶቹ ሁሉ
እነዚህ ሁሉ ግነቶች የተደረጉት የንግስቲቱ አለመታዘዝ የሚያስከትለውን ነገር ለማጉላት ነው። (ግነት እና ድምዳሜ የሚለውን ይመልከቱ)
ግዛቶች
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
ብዙ ንቀትና ቁጣ ይሆንል
"ባሎቻቸውን የማይታዘዙ ይሆናሉ፤ በንቀትም ያይዋቸዋል።
Esther 1:19
አያያዥ ሃሳብ፡
ምሙካ ለንጉሡ ጥያቄ ምላሽ መስጠቱን ቀጠለ
ንጉሡን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ ...ወደ ንጉሡ... በፊቱ....ንጉሡ... የንጉሡ አዋጅ... ታላቅ ግዛቱ
ምሙካ በሶስተኛ መደብ የተናገረው ንጉሡን በማክበር ነው። "ንጉሡን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ... ከእርሱ...በፊቱ... ካስደተ... አዋጁ... በሰፊ ግዛቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
የማይሻር ሆኖ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ሊሽረው የማይችል ሆኖ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የንጉሡ አዋጅ ሲታወጅ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የንጉሡን አዋጅ በሰሙ ጊዜ" ወይም "ንጉሡ ያዘዘውን በሰሙ ጊዜ" በሚለው ውሰስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ታላቅ
በጣም ሰፊ
ከታላቁ እስከ ታናሹ
ይህ ሁለቱንም ጽንፎች እና በመሃል የሚገኘውን ሁሉ ከዳር ስስከ ዳር የሚገልጽ ነው። ይህ ምናልባትም ባሎችን ሊመለከት ይችላል፣ ነገር ግን ሚስቶችን ማመላከት ይችላል። (ጽንፍ/ሜሪዝም የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 1:21
ምሙካ
ስሙን በአስቴር 1:14 ውስጥ በሚገኘው መሰረት ይተርጉሙ። (ስሞች እንዴት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይተረጎማሉ፤ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛት

ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

እያንዳንዱ ሰው የቤቱ ገዢ መሆን አለበት

" ሁሉም ወንዶች በሚስቶቻቸው እና በልጆቻቸው ላይ ሙሉ ስልጣን ሊኖራቸው ይገባል"

ይህ አዋጅ ተሰጥቶ የነበረው

ይህ በአድራጊ ጊዜ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። " እነርሱ ይህንን አዋጅ ጻፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ- ገቢር/ተገቢሮ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 2

Esther 2:1

ከእነዚህ ነገሮች በኋላ

ይህ ጥቂት ቆየት ብሎ የሚሆንን አዲስ ትዕይንት ያስተዋውቃል። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሥ ጠረክሲስ ቁጣ በረደ

" ንጉሡ ቁጣው ቀነሰ"

አዋጁ

ይህ በአስቴር 1:19-20 ያለውን አዋጅ ያመለክታል

ፍለጋ ይደረግ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አገልጋዮችህ እንዲፈልጉ እዘዛቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ- ገቢር/ተገቢሮ የሚለውን ይመልከቱ)

በንጉሡ ፊንታ

ሰዎቹ ንጉሡን በሶስተኛ መደብ የሚናገሩት ለአክብሮት መግለጫ ነው። "በአንተ ፈንታ" (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 2:3

አያያዥ ሃሳብ፡

ወጣቶቹ አገልጋዮች ለንጉሡ ገለጻቸውን ቀጠሉ

ንጉሡ... የንጉሡ ሹማምንት... ንጉሡ ቢፈቅድ

አገልጋዮቹ ንጉሡን በሶስተኛ መደብ የሚያናግሩት አክብሮታቸውን ለመግለጽ ነው። "ማድረግ ያለበት... ሹማምንቱ... ንጉሡ ቢፈቅድ" (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቶች

ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

የሴቶች ቤት/ ሃሬም

የአንድ ወንድ ሚስቶች ከብዙ ሚስቶቹ ጋር የሚኖሩበት ቤት

ግንቡ/ምሽጉ

ይህ የቤተመንግሥት ግንብን፣ ጠንካራ ይዞታን ወይም የተመሸገ ከተማን ያመለክታል። በአስቴር 1:2 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት ተመልሰው ይመልከቱ።

ሱሳ

በአስቴር 1:2 ላይ የዚህን ስፍራ ስያሜ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

የሴቶች የበላይ ሃላፊ በሆነው በንጉሡ አገልጋይ በሄጌ እንክብካቤ ስር ይሁኑ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል። " የሴቶች ሃላፊ የሆነው፣ የንጉሡ ሹም ሄጌ፣ እነርሱን ይንከባከባል" (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሄጌ

ይህ የወንድ ስም ነው።(ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ፤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሴቶች መኳኳያ

"መኳኳያ"- እንደ የፊት ዱቄት/ፓውደር፣ ፊትን ለማውዛት የሚረዳ ቅባት/ሎሽን፣ ክሬም/ጭቃ ቅባት የመሰለ ሲሆን ብዙውን ጊዜ ሴቶች ውበታቸውን ለማውጣት በፊታቸው ወይም በአካላቸው ላይ የሚቀቡትነው።

Esther 2:5

አንድ አይሁዳዊ ነበር

ይህ መርዶክዮስን እንደ አዲስ ገጸባህሪይ ያስተዋውቃል። (አዲስ እና አሮጌ ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ሱሳ

የዚህን ከተማ ስም በአስቴር 1:2 ላይ በተረጎሙት መሰረት ይተርጉሙት። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

የኢያዕር ልጅ የሰሜኢ ልጅ የቂስ ልጅ

"ኢያዕር፣ "ሰሜኢ፣" እና "ቂስ" እነዚህ ወንዶች ሲሆኑ እነርሱም የ"መርዶክዮስ" አባቶች ናቸው። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ፤ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

ብንያማዊ

"የብንያም ነገድ"

እርሱ ተወስዶ ነበር... የባቢሎን ንጉሥ ማረኮት ነበር

ይህ የመረጃ ዳራ መርዶክዮ ወደ ሱሳ ለመኖር እንዴት እንደመጣ ያብራራል። ይህ በአደራጊ ዐረፍተ- ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር እርሱን እና ሌሎች ምርኮኞችን ከይሁዳ ነጉሥ ከኢኮንያን ጋር ማረኮ ወሰዳቸው" (የመረጃ ዳራ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከኢየሩሳሌም ተማርኮ ነበር

የዕብራይስጡ ትርጉም እዚህ ስፍራ ስለማን እንደሚነገር ግልጽ አላደረገውም። ምናልባት የመርዶክዮስ ቅድም አያት የሆነው ቂስ ሊሆን ይችላል። ራሱ መርዶክዮስ ከሆነ ግን አስቴርን በተመለከተ የሆነው ትዕይንቶች ሲፈጸሙ እጅግ አርጅቶ ነበር ማለት ነው። በርካታ አዳዲስ ትርጉሞች ይህንን ጉዳይ ግልጽ አያደርጉትም። ጥቂት ትርጉሞች ፣ ዩዲቢን (አንሎክ ዳይናሚክ ባይብል) ጨምሮ ከኢየሩሳሌም የተማረከው መርደኪዮስ እንደሆነ አድርገው ማቅረብን ይመርጣሉ።

ኢኮንያን፣ የይሁዳ ንጉሥ

(ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

Esther 2:7

አያያዥ ሃሳብ፡

ይህ ስለ መርዶክዮስ የመረጃ ዳራ ማቅረብን ይቀጥላል እንደዚሁም ከአስቴር ጋር ያለውን ግንኙነት ያብራራል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ሀደሳ

ይህ የአስቴር የእብራዊ ስሟ ነው። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

የአጎቱ ሴት ልጅ

"ለእርሱ የአጎቱ ልጅ ናት"

እናትም ሆነ አባት አልነበራትም

"እናቷ እና አባቷ ሞተው ነበር"

እንደ ራሱ ልጅ አድርጎ ወስዷት ነበር

የራሱ ልጅ የሆነች ያህል ይንከባከባት ነበር"

Esther 2:8

የንጉሡ ትዕዛዝ እና አዋጅ በታወጀ ጊዜ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል። " ንጉሡ ውብ የሆነች ሴት እንዲፈልጉ ካዘዘ በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ታወጀ

"ተነገረ"

ብዙ ወጣት ሴቶች ቀረቡ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ብዙ ወጣት ሴቶችን አቀረቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሄጌ እንክብካቤ ስር ሆኑ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል።"ሄጌ እነርሱን መንከባከብ ጀመረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አስቴርም ጭምር ሴቶችን በሚንከባከበው በሄጌ እንክብካቤ ለመሆን ወደ ንጉሡ ቤተመንግት ተወሰደች

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሄጌ፣ የሴቶቹ ተንከባካቢ ወደ ንጉሡ ቤተመንግሥት ባመጧት ጊዜ አስቴርንም መንከባከብ ጀመረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤተመንግት

ይህንን በአስቴር 1:5 ውስጥ እንዴት እንተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ

ወጣቷ ልጃገረድ አስደሰተችው፣ ደግሞም በእርሱ ዘንድ ሞገስን አገኘች

እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ነገር ይናገራሉ፤ ደግሞም ምን ያህል ንጉሡን ደስ እንዳሰኘች ትኩረት ያደርጋሉ። "ወጣቷ ልጃገረድ እጅግ ደስ አሰኘችው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ወጣቷ ልጃገረድ

"አስቴር"

Esther 2:10

ስለ አስቴር ደህንነት

"አስቴር እንዴት እንደሆነች" ወይም "ስለ አስቴር በመልካም ሁኔታ መገኘት"

Esther 2:12

አጠቃላይ መረጃ፡

ከቁጥር 12-14 ያለው፣ የንጉሡ ሚስቶች ስለሚሆኑ ሴቶች ያሉ ልምዶችን የሚገልጹ የመረጃ ዳራዎች ናቸው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሴቶቹ የሚደረጉ ደንቦች ከተፈጸሙ

"ለሴቶቹ መደረግ ያለበት በስርዓቱ መሰረት ከተከናወነ"

የውበት እንክብካቤ

ልጃገረዶቹ ውብ ሆነው እንዲታዩ እና መልካም መዓዛ እንዲኖራቸው የሚደረጉ ነገሮች።

መኳኳያ

በአስቴር 2፡3 ውስጥ የተጠቀሙበትን ያንኑ ቃል ወይም ሀረግ ይጠቀሙ

የምትፈልገው ሁሉ ይሰጣት ነበር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ-ነገር ሊገለጽ ይችላል።"የምትፈልገውን ሁሉ መውሰድ ትችል ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤተመንግሥት

በአስቴር 1፡5 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ።

Esther 2:14

አያያዥ ሃሳብ፡

ይህ በአስቴር 2፡12 የተጀመረውን የንጉሡ ሚስቶች በሚሆኑ ሴቶች ላይ ስላለው ስርአት የመረጃ ዳራ ማቅረብን ይቀጥላል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠዋት

ይህ በማግስቱ ያለውን ማለዳ ያመላክታል። ይህ መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "በማግስቱ ጠዋት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ( ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለተኛ ቤት

"የተለየ ቤት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ) ወደ ሻሺጋዝ ጥበቃ… ዕቁባቶች "ሻሺጋዝ ወዳለበት… ቁባቶች ይንከባከቧት ነበር"

ተንከባካቢ

"ጉብኝት" ወይም "ጥበቃ"

ሻሺጋዝ

ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

Esther 2:15

አሁን ጊዜው ሲደርስ

ይህ የታሪኩን አዲስ ክፍል ያስተዋውቃል። (አዲስ ትዕይንት ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

የመርዶክዮስን አጎት የሆነውን፣ የአቢካኢልን ሴት ልጅ፣ ሴት ልጅ፣ እንደ ራሱ ልጅ አድርጎ የወሰዳት

ይህ የመረጃ ዳራ ለአንባቢው አስቴር ከመርዶክዮስ ጋር ያላትን ዝምድና ያስታውሰዋል። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

አቢካኢል

የአስቴር አባት እና የመርዶክዮስ አጎት (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ) አንዳች ነገር አልጠየቀችም ነገር ግን ምንን ጠየቀች ይህ በአዎነታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ምንን ብቻ ጠየቀች"

ሄጌ

በአስቴር 2፡3 ውስጥ ይህ የወንድ ስም እንዴት እንደት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)

በሁሉም ዘንድ ሞገስ አገኘች

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ሁሉንም ደስ አሰኘች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አስረኛው ወር፣ ይህም የቴቤት ወር ነው

"ቴቤት" በዕብራዊያን ወር አቆጣጠር አስረኛው ወር ነው። በምዕራባዊያን ወር አቆጣጠር የታህሳስ መጨረሻ የጥር መጀመሪያ ነው። (የዕብራዊያን ወሮች እና ተከታታይነትን የሚያሳይ ቁጥር እንዲሁም ስሞች እንዴት ይረረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባተኛው ወር

"7 ተኛው አመት" (ተከታታይነትን የሚያሳይ ቁጥር)

Esther 2:17

ንጉሡ ወደዳት

ይህ "ፍቅር" የሚለው ቃል አስደሳች/ሮማቲክ አጠቃቀም ነው።

ተቀባይነትን አገኘች፣ በፊቱም ሞገስን አገኘች

እነዚህ ፈሊጦች ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ፣ ደግሞም አስቴር ምን ያህል ንጉሡን ደስ እንዳሰኘች ትኩረት ይሰጣሉ።"እጅግ ደስ አሰኘችው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ እና ጥንድ ትርጉም የሚሉተን ይመልከቱ)

የእቴጌነት ዘውድ በራሷ ላይ ጫነላት

ንጉሡ ይህንን ያደረገው እርሷን ንግሥት ማድረጉን ለማሳየት ነው።(ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

"የአስቴር ክብረ በዓል፣"

ይህ የክብረ በዓሉ ስያሜ መሆኑን መግለጹ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "የአስቴር ክብረ በዓል ብሎ ጠራው፣" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ( ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለግዛቶች ከግብር እፎይታን ሰጠ

"ከዚያ አቀድሞ ከግዛቶች ይሰበስብ ከነበረው እነስ ያለ ግብር ሰበሰበ"

ግዛቶች

ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

ንጉሣዊ ልግስና

" ንጉሥ ብቻ ሊያደርገው የሚችለው ልግስና"

Esther 2:19

ደናግልቱ ለሁለተኛ ጊዜ በአንድነት ተሰብበው በነበረ ወቅት

ይህ ሁለተኛው መሰባሰብ መቼ እና ለምን እንደተደረገ ግልጽ አይደለም። ለዚህም አንዳንድ ትርጉሞች ክፍሉን ለወጥ አድርገው ያቀርቡታል። ምናልባትም ባለበት ሁኔታ መተርጎም እጅግ የተሻለ ሳይሆን አይቀርም።

ለሁለተኛ ጊዜ

"ለአንድ ተጨማሪ ጊዜ" ወይም "ለተጨማሪ ጊዜ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

መርዶክዮስ በንጉሡ በር ይቀመጥ ነበር

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መርደክዮስ በዚያ የሚቀመጠው አስቴር ምን እያደረገች እንደሆነ በበሩ በኩል ከሚያልፉ ብዙ ሰዎች መስማት ይችል ዘንድ ነው በሚል ሊተረጎም ይችላል ወይም 2) " በንጉሡ በር መቀመጥ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን መርዶክዮስ በንጉሡ ስልጣን ተሰጥቶት ነበር ማለት ሊሆን ይችላል።

የንጉሡ በር

"ወደ ንጉሡ ቤተመንግሥት መግቢያ በር"

መርዶክዮስ እንዳዘዛት

መርዶክዮስ ስለ ቤተሰቧ ለማንም እንዳትናገር ነግሯት ነበር

በእነዚያ ቀናት

ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ትዕይነትን ያስተዋውቃል። (አዲስ ትዕይነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ገበታ እና ታራ

እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 2:22

ነገሩ ለመርዶክዮስ በተገለጸ ጊዜ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መርዶክዮስ ምን እንዳሴሩ ባወቀ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በመርዶክዮስ ስም

ይህ ፈሊጥ ነው። "በመርዶክዮስ ምትክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘገባው ተመርምሮ ተረጋገጠ፣ በመሆኑም ሁለቱም ሰዎች በስቅላት ተቀጡ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ንጉሡ መርምሮ ዘገባውን አረጋገጠ፣ ደግሞም አገልጋዮቹ ሁለቱን ሰዎች እንዲሰቅሏቸው ትዕዛዝ ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው መስቀያ እንጨት

ይህ ሰዎችን ለመስቀል ያገለግል የነበረ አሰራር ሲሆን፣ የገመዱ አንዱ ጫፍ

በመስቀያው እንጨት ላይ ሲታሰር ሌላኛው የገመዱ ጫፍ በሚሰቀሉት ሰዎች አንገት ዙሪያ በማድረግ ይንጠለጠላሉ። "ሰዎችን ለመስቀል የሚዋቀር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የማይታወቁትን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ጉዳይ ተመዝግቦ ነበር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እነርሱ ይህንን ጉዳይ መዘገቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 3

Esther 3:1

ከእነዚህ ነገሮች በኋላ

ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ትዕይነትን ያስተዋውቃል። (አዲስ ትዕይነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

የአጋጋዊው የሐማዳቱ ልጅ ሐማ

ይህ ከንጉሡ መኳንንት አንዱ የሆነው የሐማ ስም እና ገለጻ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የስልጣኑን ስፍራ ከእርሱ ጋር ከነበሩ መኳንንት ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ አደረገ

እዚህ ስፍራ "የባለስልጣናት ስፍራ" የሚለው የሚገልጸው በመንግስት ውስጥ ያለውን ስፍራ ወይም ደረጃ ነው። "ከሌሎች መኳንንት በላይ ከፍ አደረገው" ወይም "ከሌሎች መኳንንት ሁሉ በላይ ይበልጥ ስልጣን ሰጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

መንበርከክ... መስገድ

እነዚህ ድርጊቶች ለሐማ ስልጣን መገዛትን ይገልጻሉ። (ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ለሐማ ሰገዱ

"ራሳቸውን ዝቅ አድርገው በሐማ ፊት ለጥ ብለው ሰገዱ"

Esther 3:3

ስለ መርዶክዮስ ያለው ጉዳይ እንደዚያ ሆኖ መቅረቱን ለማየት

"ሐማ ስለ መርዶክዮስ ድርጊቶች ምን እንደሚያደርግ ለማየት"

Esther 3:5

አልተንበረከከም ወድቆም አልሰገደም

መርዶክዮስ እነዚህን ድርጊቶች ባለማድረግ ሐማ በመንግስት ውስጥ ላለው ደረጃ ክብር አለመስጠቱን አሳየ።(ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ሐማ በቁጣ ተሞልቶ ነበር

እዚህ ሰፍራ የሐማ ቁጣ እጅግ እንደሚሞላው ነገር ተደርጎ ተነግሯል። "ሐማ እጅግ ተቆጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መርዶክዮስን ብቻ የመግደልን ሃሳብ ትንሽ ነገር አድርጎ አየው

"መርዶክዮስን ብቻ የመግደልን ሃሳብ አልተቀበለም።" ይህ በአዎንታዊ መልክም ሊገለጽ ይችላል። "መርዶክዮስን ብቻ ከመግደል ያለፈ ለማድረግ ወሰነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

መላውን አይሁድ ማጥፋት

"ሁሉንም አይሁድ ማስወገድ" ወይም "መላውን አይሁድ መግደል"

Esther 3:7

በመጀመሪያው ወር

" በአንደኛው ወር" (ተከታታይነትን የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ኒሳን የተኛው ወር ነው

"ኒሳን" በዕብራዊያን ወር አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ስያሜ ነው። በምዕራባዊያን ቀን መቁጠሪያ የመጋቢት መጨረሻ እና የሚያዚያ መጀመሪያ ላይ ነው። (የዕብራዊያን ወራት እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሥ ጠረክሲስ በነገሠ አስራ ሁለተኛ አመት

"በንጉሥ ጠረክሲስ በ12ኛ አመት" ወይም "ንጉሥ ጠረክሲስ ወደ አስራ ሁለት አመት ያህል ከገዛ በኋላ" (ተከታታይነትን የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ፉር - ያም ዕጣ ነው- ይጣላል

"ፉሩን ያወጣሉ - ያም ዕጣ ነው - " (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ ሁለተኛው ወር

"አስራ ሁለተኛ ወር" (ተከታታይነት ን የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የአዳር ወር

"አዳር" በዕብራዊያን የወር አቆጣጠር አስራ ሁለተኛው እና የመጨው ወር ነው። በምዕራባዊያኑ አቆጣጠር የየካቲት ወር መጨረሻ እና የመጋቢት መጀመሪያ ነው። (የዕብራዊያን ወራት እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 3:8

አንድ ህዝብ

" አንድ የህዝብ ወገን" ይህ አይሁድን እንደ አንድ ነገድ ያመላክታል።

ተበትኖ የሚኖር

"በብዙ የተለያዩ ስፍራዎች የሚኖር"

ግዛቶች

ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

የንጉሡ ... ንጉሡ

ሐማ ለአክብሮት መግለጫ ምልክትነት ንጉሡን በሶስተኛ መደብ ይናገረዋል። "የእርሱ ... እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን መተዉ ለንጉሡ ጠቃሚ አይደለም

"ንጉሡ እነርሱ እንዲተርፉ መፍቀድ የለበትም።" ይህ በአዎንታዊ መልክም ሊገለጽ ይችላል። "ንጉሡ ሊያስወግዳቸው ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በእነርሱ እጅ... እኔ እመዝናለሁ

እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው ወንዶች የሚለውን ይወክላል። "መመዘን" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ለእነርሱ መክፈል ማለት ነው። " ለሰዎቹ ...እኔ እከፍላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሲኔክቲኪ/ ዘይቤያዊ አነጋገር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ እና ፈሊጣዊ አነጋገር/ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አስር ሺህ መክሊት ብር

"330 ሜትሪክ ቶን ብር" መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገንዘብ እና ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 3:10

የቀለበት ማህተም

በአዋጅ ላይ የንጉሡን ይፋ ማህተም ለማሳረፍ የሚያገለግል የተለየ ቀለበት

ገንዘቡ ተመልሶ ለአንተ ሲሆንልህ አያለሁ

የዚህ ሐረግ ትርጉም ግልጽ አይደለም። ትርጉሙ 1) "እኔ ለአንተ ገንዘቡን እመልስልሃለሁ" ወይም 2) " ልክ እንደተናገርከው ገንዘቡን ወስደህ ለሰዎቹ ስጣቸው።" ማለት ሊሆን ይችላል። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 3:12

የንጉሡ ጸሐፍት ተሰበሰቡ... ሐማ ያዘዘውን ሁሉ የያዘ አዋጅ ተጻፈ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡ ጸሐፍቱን ሰበሰበ ... እነርሱ ሐማ ያዘዘውን ሁሉ የያዘ አዋጅ ጻፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የመጀመሪያው ወር አስራ ሶስተኛው ቀን

ይህ በዕብራዊያን አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። አስራ ሶስተኛው ቀን በምዕራባዊያኑ አቆጣጠር ወደ ሚያዝያ መጀመሪያ ላይ ነው። (የዕብራዊያን ወሮች እና ደረጃን የሚያሳዩ ቁጥሮች)

የንጉሡ ግዛቶች ገዢዎች

"የግዛቶች ገዢዎች።" በአስቴር 1፡1 ውስጥ በተረጎሙት መሰረት ይተርጉሙ። የተጻፈው በንጉሡ ጠረክሲስ ስም ነበር ደግሞም በእርሱ ማህተም ታትሞ ነበር ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እነርሱ አዋጁን በንጉሡ ጠረክሲስ ስም ጻፉ ሐማም በንጉሡ ቀለበት አተመው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በ...ስም

እዚህ ስፍራ "ስም" የንጉሡን ስልጣን ይወክላል። "በ... ስልጣን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

ሰነዶቹ በመልዕክተኞች እጅ ተላኩ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " መልዕክተኞች ሰነዶቹን በእጅ አደረሱ" ወይም "መልዕክተኞች ሰነዶቹን በቀጥታ አደረሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲጠፉ፣ እንዲገደሉ፣ እና እንዲደመሰሱ

እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ጥፋቱ በሙላት እንዲደረግ ትኩረት

የሚሰጡ ናቸው። "ሙሉ ለሙሉ መደምሰስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም/ደብሌት የሚለውን ይመልከቱ)
የአስራ ሁለተኛው ወር አስራ ሶተኛ ቀን
"የአስራ ሁለተኛው ወር አስራ ሶስተኛ ቀን" (ተከታታይነትን የሚያሳዩ ቁጥሮች)
አዳር የትኛው ወር ነው
አዳር" በዕብራዊያን የወር አቆጣጠር አስራ ሁለተኛው እና የመጨው ወር ነው። በምዕራባዊያኑ አቆጣጠር የየካቲት ወር መጨረሻ እና የመጋቢት መጀመሪያ ነው። (የዕብራዊያን ወራት እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ዝርፊያ
በሃይል መቀማት
Esther 3:14
የደብዳቤው ቅጂ በእያንዳንዱ ግዛት ህግ ተደርጎ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በእያንዳንዱ ግዛት የሚገኙ መኳንንት የደብዳቤውን ቅጅ ህግ አድርገው ተቀብለውት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ግዛት
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
በእያንዳንዱ ግዛት ለሁሉም ህዝብ እንዲታወቅ ተደርጎ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በእያንዳንዱ ግዛት ለሚኖረው ህዝብ አሳውቀው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ቀን
"ያ ቀን"
አዋጇም ተልኮ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እነርሱም አዋጁን ልከው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ግንብ/ምሽግ
ይህ የቤተመንግሥት ግንብን፣ ጠንካራ ይዞታን ወይም የተመሸገ ከተማን ያመለክታል። በአስቴር 1:2 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት ተመልሰው ይመልከቱ።
ሱሳ
የዚህን ስፍራ ስም በአስቴር 1:2 ላይ እንዴት እንደ ተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ተንጣ ነበር
"በታላቅ ግራ መጋባት ውስጥ ነበረች"

---

Chapter 4
Esther 4:1
የተደረገውን ሁሉ አውቆ ነበር
"ስለነዚያ ደብዳቤዎች ደርሶበት ነበር" ልብሱን ቀደደ ደግሞም ማቅ ለብሶ በራሱ ላይ አመድ ነሰነሰ እነዚህ ድርጊቶች የታላቅ ሃዘን ምልክቶች ናቸው። " ሃዘኑን ለመግለጽ ልብሶቹን ቀደደ ደግሞም ማቅ ለብ አመድ ነሰነሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ግዛት
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
በአይሁዳዊያን መካከል ታላቅ ለቅሶ ነበር
"አይሁዳዊያን እጅግ አለቀሱ"
ብዙዎቹ ማቅ ለበሱ በላያቸውም አመድ ነሰነሱ
"ብዙዎቹ መሬት ላይ ተቀምጠው ነበር፣ ማቅ ለብሰው አመድ ላይም ተቀምጠው ነበር"
Esther 4:4
ወጣት ሴቶች እና ወንድ አገልጋዮች
"ሴት አገልጋዮች እና ወንድ አገልጋዮች"
መርዶክዮስን ለማልበስ
"መርዶክዮስ እንዲለብሰው"
ሀታክ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሷን እንዲያገለግሏት ከተመደቡት የንጉሡ ባለሟሎች አንዱ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡ እርሷን እንዲያገለግሉ ከመደባቸው ባለሟሎች አንዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 4:6
ሀታክ
በአስቴር 4:5 ውስጥ ይህንን የወንድ ስም እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የከተማው አደባባይ
"በከተማው መሃል"
ሐማ
በአስቴር 3:1 ውስጥ ይህንን የወንድ ስም እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱም ሰጠው
" መርዶክዮስም ለሀታክ ሰጠው"
ከእርሱ ዘንድ ምህረትን እንድትለምን
"የንጉሡን ምህረት እንድትለምን"
Esther 4:9
ማንም ወንድ ወይም ሴት ወደ ንጉሡ ቢሄድ… ንጉሡ የወርቅ ዘንጉን/በትረ መንግሥቱን ይዘረጋል
ይህ ሁኔታዊ አባባል ሙሉ ሃሳብ/መግለጫ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። ይህንን አገላለጽ በሁለት ዐረፍተ ነገሮች መክፈሉም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "ንጉሡ ካልጠራቸው በስተቀር ማንም ወንድ ወይም ሴት ወደ ውስጠኛው አደባባይ ወደ ንጉሡ መግባት አይፈቀድለትም። ይህንን ህግ የጣሰ ሰው ንጉሡ ወደዚያ ሰው የወርቅ ዘንጉን/በትረ መንግሥቱን ካልዘረጋለት በስተቀር ይገደላል።"
ሰላሳ ቀናት
"30 ቀናት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 4:13
ደህንነት እና መዳን ለአይሁድ ከሌላ ስፍራ ይሆናል
እዚህ ላይ "ደህንነት" እና "መዳን" ማንሳት እንደሚችሉ ህያዋን ነገሮች ሆነው ተነግረዋል። "አንድ ሌላ ሰው ከሌላ ስፍራ ተነስቶ አይሁድን ያድናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ/ፐርሶኒፊኬሽን የሚለውን ይመልከቱ)
እንዲህ ላለው ጊዜ ወደዚህ የንግስትነት ደረጃ መጥተሽ እንደሆነስ ማን ያውቃል?
የዚህ ጥያቄ አላማው አስቴር በዚህ ሁኔታ ልትጫወት ስለምትችለው ሚና በጥልቀት እንድታስብ ማድረግ ነው። "ማን ያውቃል፣ ንግስት የሆንሽው ምናልባትም ልክ እንዲህ ላለው ጊዜ ሊሆን ይችላል።" (ንግግራዊ/ሬቶሪካል ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 4:15
ሱሳ
የዚህን ስፍራ ስም በአስቴር 1:2 ላይ እንዴት እንደ ተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእኔ ጹሙ… እንጾማለን
ጾም አይሁዳዊያን በጥብቅ ሲጸልዩ የሚያደርጉት ተምሳሌታዊ ድርጊት ነው። ይህ ይበልጥ ግለጽ ሊደረግ ይችላል። "ለእኔ ጹሙ ጸልዩ.. እንጾማለን እንጸልያለን" (ተምሳሌታዊ ድርጊት)
ሶስት ቀናት
"3 ቀነናት" (ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት እውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ)

---

Chapter 5
Esther 5:1
ወደ ቤቱ መግቢያ ፊቷን መልሳ
"ከቤቱ መግቢያ ትይዩ " ወይም "ወደ ቤቱ መግቢያ አንጻር"
በዐይኖቹ ተቀባይነት አገኘች
"ዐይኖች" የሚለው የሚያመለክተው የእርሱን መመለከት ሲሆን እርሱ ለእሷ ያለውን ሚዛን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " በእርሷ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተደስቶ ነበር" ወይም "እርሷን ተቀበላት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በእጁ ያለውን የወርቅ ዘንግ/በትረ መንግሥት ዘረጋላት
ይህንን ያደረገው በእርሷ ደስ መሰኘቱን ለማሳየት ነው።
የዘንጉን/ በትረ መንግሥቱን ጫፍ ነካች
ምናልበትም ይህንን ያደረገችው ስልጣኑን ማክበሯን እና ለእርሷ ላሳየው በጎነት ምስጋና ለማቅረብ ሳይሆን አይቀርም
Esther 5:3
እስከ መንግቱ እኩሌታ ድረስ ቢሆን እንኳን ይሰጥሻል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የመንግሥቴን እኩሌታ እንኳን ብትጠይቂ፣ እሰጥሻለሁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው ከሆነ፣ ንጉሡ እና ሐማ ይምጡ.. ለእርሱ
ለንጉሥ ክብር ለማሳየት፣ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ እርሱን "አንተ" ብለው አይጠሩም። ይህ "አንተ" የሚለው ቃል ከሌሎች ቃላት ጋር አክብሮትን ለማሳየት ሊተረጎም ይችላል። "ንጉሥ ሆይ፣ ይህ ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው ከሆነ፣ ንጉሡ … ከሐማ ጋር" (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ሐማ
በአስቴር 3፡1 ውስጥ ይህንን የወንድ ስም እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 5:5
ጥያቄሽ ምንድን ነው
"ጥያቄ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠየቀ" ወይም "ፈለግ" በሚሉ ግሶች ሊገለጽ ይችላል። "ምን ትጠይቂያለሽ" ወይም "ምን ትፈልጊያለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ለአንቺ ይሰጥሻል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የምትጠይቂውን እሰጥሻለሁ" ወይም "የምትጠይቂውን ለአንቺ አደርገዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የምትፈልጊው ምንድን ነው
"መፈለግ" የሚለው ረቂቅ ስም "መጠየቅ" ወይም "መሻት" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ምን ትጠይቂያለሽ" ወይም "ምን ትፈልጊያለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እስከ መንግስቴ እኩሌታ፣ ይሰጥሻል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እስከ መንግሥቴ እኩሌታ እንኳን ቢሆን ብትጠይቂ፣ እሰጥሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 5:7
የእኔ አቤቱታ/ልመና እና ጥያቄዬ/መሻት
"አቤቱታ/ልመና" እና "ጥያቄ/መሻት" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ይዘዋል። እነዚህን ቃላት በአንድነት የተጠቀመችባቸው ምናልባት ለንጉሡ በጣም ስርዓት በጠበቀ እና ክብር በሞላበት መንገድ ለመናገር ይሆናል። (ጥንድ ትረጉም የሚለውን ይመልከቱ)
በንጉሡ ዐይኖች ሞገስ አግኝቼ ከሆነ እና ንጉሡን ደስ ካሰኘሁ
ለአንድ ንጉሥ ክብር ለማሳየት፣ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ "አንተ" ብለው አይጠሩትም። ይህ "አንተ" ከሚለው ቃል ጋር ሌሎች ማክበርን የሚገልጹ ቃላት ተጨምረውበት ሊተረጎም ይችላል። "ንጉሡ በእኔ ደስ ተሰኝቶ ከሆነ፣ ንጉሥ ሆይ፣ ደግሞም ንጉሡን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
በንጉሡ ዐይኖች ሞገስ አግኝቼ ከሆነ
"ሞገስ ማግኘት" የዚህ ትርጉም በፈሊጥ ተቀባይነት ማግኘት ወይም ንጉሡ በእርሷ ደስ መሰኘቱን የሚገልጽ ነው። "በንጉሡ ዐይን " የሚለው የእርሱን ሚዛን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። "በንጉሡ ፊት ተቀባይነት ካገኘሁ" ወይም "ንጉሡ በእኔ ደስ ከተሰኘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ እና ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ንጉሡ እና ሐማ ይምጡ
ይህ "አንተ" ከሚለው ቃል እና ክብርን ከሚገልጹ ሌሎች ቃላት ጋር አብሮ ሊተረጎም ይችላል። "ንጉሡ ይገኝ ደግሞም ሐማንም ይዞት ይገኝ" ወይም " ንጉሡ ይምጣ ሐማም ከንጉሱ ጋር ይምጣ" (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
የንጉሡን ጥያቄ እመልሳለሁ
ይህ "አንተ" ከሚለው ቃል እና ክብርን ከሚገልጹ ሌሎች ቃላት ጋር አብሮ ሊተረጎም ይችላል። "የንጉሡን ጥያቄ እመልሳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 5:9
መርዶክዮስ አይነሳለትም ነበር
መነሳት ክብርን የመግለጫ ምልክት ነበር። መርዶክዮስ ለሐማ የተለየ ክብር አይሰጠውም ነበር። (ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
በቁጣ ይሞላ ነበር
"በቁጣ መሞላት" እጅግ በጣም መናደድን ያመለክታል። "እጅግ ተቆጥቶ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሆነ ሆኖ/ምንም እንኳን
ይህ በሐረግ ሊተረጎም ይችላል። "ምንም እንኳን እጅግ ቢበሳጭም
ሐማ ራሱን ተቆጣጠረ
ራሱን ተቆጣጠረ የሚለው የሚገልጸው ሊያደርግ እጅግ ፈልጎ ያለውን ነገር ከማድረግ መገታቱን ነው። ሐማ እጅግ መናደዱን ለመርደክዮስ ማሳየት ፈልጎ ነበር። "ሐማ ምን ያህል እንደ ተናደደ ላለማሳየት ራሱን ተቆጣጠረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዞሳራ
ይህ የሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሐማ የሃብቱን ታላቅነት እያጋነነ ዘረዘረላቸው
"እያጋነነ" እና "ሃብቱን" የሚሉት ቃላት ሁለቱም ረቂቅ ስሞች ናቸው። "ሐማ ሃብቱ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ነገረቸው" ወይም "ሐማ ስላሉት ብዙ ታላላቅ ነገሮች ነገራቸው" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሡ ሊያከብረው የሰጠው እድገቶች ሁሉ
"እድገት" የሚለው ረቂቅ ስም "አደገ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። ንጉሡ ይበልጥ ከፍ ያለ ደረጃ ሰጠው ማለት ሊሆን ይችላል። "ንጉሡ እንዴት ብዙ ጊዜ ከፍ እንዳደረገው እና እንዳከበረው" ወይም "ንጉሡ እንዴት ብዙ ጊዜ ይበልጥ ከፍ ያለ ደረጃ በመስጠት እንዴት እንዳከበረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እንዴት ከሁሉም መኳንንት እና ከንጉሡ አገልጋዮች በላይ ከፍ ከፍ እንዳለ
ከሰዎች በላይ ከፍ ከፍ ማለት የሚለው የሚገልጸው ከሌሎቹ በላይ ጠቃሚ መሆኑን ነው። "ከሁሉም መኳንንት እና ከንጉሡ አገልጋዮች በላይ እንዴት ጠቃሚ እንደሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 5:12
ሌላ ማንም ሳይሆን እኔን
ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ብቻ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ለእኔ እንዳች አይጠቅመኝም
"እኔን ደስ አያሰኘኝም" ወይም "እኔን አያረካኝም"
Esther 5:14
የሰው መስቀያ እንጨት
ይህ አንድን ሰው ለመስቀል የገመዱ አንዱ ጫፍ በመስቀያው እንጨት ላይ ሲታሰር ሌላኛው የገመዱ ጫፍ በሚሰቀለው ሰው አንገት ዙሪያ በማድረግ ሰውየው ይሰቀላል። በአስቴር 2፡3 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (የማይታወቁትን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)
ሃምሳ ክንድ ቁመት
"50 ክንድ ቁመት።" ይህንን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ይችላሉ። ወደ" ሃያ ሶስት ሜትር ከፍታ" (ቁጥሮች እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ መስቀያውን አሰራ
"ሰዎች መስቀያውን እንዲያበጁ አዘዘ"
ይህ ሐማን ደስ አሰኘው
"ይህ ሃሳብ ሐማን ደስ አሰኘው"

Chapter 6

Esther 6:1

ገበታ እና ታራ

እነዚህ የሁለት ወንዶች ስሞች ናቸው። ስሞቻቸውን በአስቴር 2:21 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመዝግቦ ተገኘ

እዚህ ስፍራ "ተገኘ" የሚለው ማወቅ ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ተገኘ" እና "ተመዝግቦ" የሚሉት ሁለቱም በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጹ ይችላሉ። "ጸሐፍቱ በዚያ እንደመዘገቡት አገኙ" ወይም "ጸሐፍቱ እንደጻፉ አወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ክብር ለመስጠት ምን ተደረገ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ክብር ለመስጠት ምን አደረግኩ" ወይም "ክብር ለመስጠት ምን አደረግን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ምንም አልተደረገለትም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። የሆነ ሆኖ አገልጋዮች ንጉሡን እየከሰሱ እንደሆነ የማያስመስል መንገድ መፈለጉ መልካም ሊሆን ይችላል። "ማንም ለመርደክዮስ ምንም አላደረገም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 6:4

ሐማ

ይህንን የወንድ ስም በአስቴር3፡1 ውስጥ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ

ውጫዊው አደባባይ

"ከውጭ የመጀመሪያው አደባባይ"

መርዶክዮስን ለመስቀል

እርሱን ለመስቀል ተፈልጎ የነበረበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ይቻላል። "መርዶክዮስን በመስቀል ለመግደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የሚገመት ዕውት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ያዘጋጀው መስቀያ

መስቀያ እንጨት ሰዎችን በዚያ ላይ ለመግደል የሚዘጋጅ ነበር። በአስቴር 5፡14 ላይ "መስቀያ እንጨት" የሚለውን እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "ሐማ መርዶክዮስን ለመስቀል ያዘጋጀው ግንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

አዘጋጀ

"ሰራ"

ንጉሡ ሊያከብረው ለወደደው ሰው ምን መደረግ አለበት

እዚህ ስፍራ ላይ ንጉሡ በሶስተኛ መደብ ራሱ እየተናገረ ነው። ይህ በአንደኛ መደብ እና በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ ለወደድኩት እና ላከብረው ለምፈልገው ሰው ምን ማድረግ ይኖርብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ሊያከብረው ለወደደ

አንዳች ነገር በማድረግ ደስ መሰኘት፤ አንድ ነገር በመደረጉ ምክንያት አንድ ነገር ለማድረግ ደስ መሰኘትን ወይም አንድ ነገር ለማድረግ መፈለግን የሚገልጽ ፈሊጥ ነው። "ንጉሡ ሊያከብረው ደስ ተሰኝቷል" ወይም "ንጉሡ ሊያከብረው ፈልጓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በልቡ እንዲህ አለ

ልቡ የሚለው አስተሳሰብን እና ዝንባሌን ይወክላል። "ሃሳብ" ወይም "ለራሱ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ከእኔ ይልቅ ሊያከብረው የሚወደው ማን አለ?

ይህ እንደ ሙሉ አሳብ/መግለጫ ሊገለጽ ይችላል። "በእርግጥ ንጉሡ ከእኔ ይልቅ ሊያከብረው የሚወደው ማንም የለም!" (ሬቶሪካል/ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 6:7

ንጉሡ የሚጎናጸፈው ልብስ ይምጣ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው ንጉሣዊ መጎናጸፊያዎችን ያምጣ" ወይም "አገልጋዮችህ ንጉሣዊ መጎናጸፊያዎችን እንዲያመጡ እዘዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ) ንጉሣዊው ባርኔጣ/ክራስት በማን ራስ ላይ ነው "በማን" የሚለው ቃል ፈረሱን ያመለክታል። ንጉሣዊው ባርኔጣ የንጉሡን ቤተሰብ የሚወክል ልዩ ምልክት ነው።

ከዚያም የንጉሡልብሶ እና ፈረስ ይሰጠው

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከዚያም ልብሶቹን እና ፈረሱን ይስጡት" ወይም "ከዚያም ልብሶቹን እና ፈረሱን እንዲሰጡት እዘዝ" ጨ

ያልብሱት… በማክበር፣ ደግሞም ከፊቱ እየሄዱ ይምሩ

"እንዲያለብሱ እዘዝ… በማክበር ደግሞም እየመሩ"

ያውጁ

"የከበሩ መኳንንት እና አገልጋዮች እንዲያውጁ እዘዝ"

Esther 6:10

ከተናገርከው አንዳች ነገር አይጉደል

"አንዳች ነገር" የሚለው ሐረግ የተናገረውን ሁሉ አንዳች ሳያስቀር እንዲያደግ ትኩረት የሚሰጥ ነው። በአዎንታዊ ሊጻፍ ይችላል። "የተናገርከውን ሁሉ ሙሉለሙሉ ማድረግህን እርግጠኛ ሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Esther 6:12

ራሱን ተከናንቦ

ሰዎች ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን የሚሸፍኑት እጅግ ማዘናቸውን ወይም ማፈራቸውን ለመግለጽ ነበር። (ተምሳሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ዞሳራ

ይህን የሴት ስም በእስቴር 5፡10 ውስጥ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ መውደቅ የጀመርክለት… በእርግጥ በፊቱ ትወድቃለህ

የሚናገሩት ሐማ እና መርዶክዮስ ልክ በጦርነት ውስጥ እንደሚገኙ አድርገው ነው፣ ደግሞም ሐማ በጦርነቱ ተሸናፊ መሆን ጀምሮ ነበር። እዚህ ስፍራ "መውደቅ" የሚለው ቃል የሚወክለው ክብርን ማጣትን እና መሸነፍን ነው። "በፊቱ መውደቅ የጀመርክለት… በእርግጥ ያሸንፍሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አታሸንፈውም

"ልትቋቋመው አትችልም።" የሚናገሩት ሐማ እና መርዶክዮስ ልክ በጦርነት ውስጥ እንደሚገኙ አድርገው ነው። እዚህ ስፍራ ላይ አንድን ሰው ማሸነፍ የሚለው የሚገልጸው ከዚያ ሰው ይልቅ የበለጠ ክብር ማግኘትን ነው። "እርሱ ካለው ክብር በላይ ትልቅ ክብር አይኖርህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 7

Esther 7:1

ሐማ

ይህንን የወንድ ስም በአስቴር3፡1 ውስጥ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ በሁለተኛው ቀን

"በዚህ በበዓሉ ሁለተኛ ቀን"

ወይን ጠጅ እያቀረቡ ሳለ

"አገልጋዮች ወይን እየቀዱ እና እነርሱን እያስተናገዷቸው ሳለ"

ልመናሽ ምንድን ነው

"ልመና" የሚለው ረቂቅ ስም "መጠየቅ" ወይም "መፈለግ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ምን ትጠይቂያለሽ" ወይም "ምን ትፈልጊያለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንቺ ይሰጥሻል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የጠየቅሽውን እሰጥሻለሁ" ወይም "የምትጠይቂውን አደርግልሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ መንግሥቴ እኩሌታም ቢሆን ይሰጥሻል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የመንግሥቴን እኩሌታ እንኳን ቢሆን ብትጠይቂ፣ እሰጥሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 7:3

ንጉሥ ሆይ፣ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"ሞገስ ማግኘት" ይህ ፈሊጥ ሲሆን ተቀባይነት ማግኘት ወይም ንጉሡ በእርሷ ደስ መሰኘቱን የሚገልጽ ነው። "በዐይኖችህ" የእርሱን ሚዛን የሚገልጽ ዘይቤያው አነጋገር ነው። "መዝነህ ከተቀበልከኝ" ወይም "በእኔ ደስ ከተሰኘህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ህይወቴ ትትረፍ
"ህይወት መስጠት" የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር የሚገለልጸው አንድን ሰው ከመገደል ማዳንን ነው። ይህ አባባል በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ህይወቴን አድን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ልመናዬ ይህ ነው
"ልመና" የሚለው ረቂቅ ስም "መጠየቅ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "የምጠይቀው ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ተሸጠን ቢሆን ኖሮ
"ተሸጠን ቢሆን" የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር መካድን ይገልጻል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኛን የካደን አለ" ወይም "ለጠላቶቻችን ለአደጋ አሳልፍ የሰጠን አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እንድንጠፋ፣ እንዲንገደል፣ እና እንድንደመሰስ
እዚህ ስፍራ እነዚህ ሶስት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲይዙ አገልግሎት ላይ የዋሉት ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጠላቶቻችን እንዲያጠፉን፣ እንዲገድሉን፣ እና እንዲደመስሱን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትረጉም እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እንዲህ ያለውን ነገር ለማድረግ ልቡን የሞላው ይህ ሰው ወዴት አለ
አንድ ነገር ለማድረግ ልብን መሙላት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው ትረጉሙም አንዳች ነገር ለማድረግ መፈለግ ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እንዲህ ያለ ነገር ለመስራት የደፈረው ሰው ወዴት አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 7:6
በፍርሃት ተዋጠ
"እጅግ ፈራ"
ንጉሡ በቁጣ ብድግ አለ
በቁጣ መሆን የሚለው እጅግ መቆጣትን ለመግለጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ንጉሡ እጅግ ተቆጥቶ ነበር እናም በቁጣ ብድግ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ ህይወቱ ንግስት አስቴርን ለመማጸን
"ህይወቱን እንድታድንለት ንግሥት አስቴርን ለመማጸን"
ጥፋት እንደተወሰነበት አየ
እዚህ ስፍራ ማየት የሚገልጸው ማወቅን ወይም መረዳትን ነው። "ጥፋት እንደተወሰነበት አወቀ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ላይ ከንጉሡ ዘንድ ጥፋት ተወስኖበት ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጥፋት" የሚለው ረቂቅ ስም ይበልጥ ተጨባጭ በሆነ "ጠፋ" ወይም "ተገደለ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። " ንጉሱ በእርሱ ላይ ጥፋት እንዲፈጸም ወስኖ ነበር" ወይም "ንጉሡ ሊያጠፋው ወስኖ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 7:8
ወይን ጠጅ በሚታደልበት ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አገልጋዮች ወይን ጠጅ በሚያቀርቡበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ድንክ አልጋ
ሰው ሊቀመጥበት ወይም ሊጋደምበት የሚችል ተለቅ ያለ የቤት ዕቃ
እኔ እያለሁ በገዛ ቤቴ ንግሥቲቱን ያስነውራልን?
ንጉሡ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ሐማ ያደርግ በነበረው ነገር መረበሹን እና መቆጣቱን ለማሳየት ነው። ይህ ጥያቄ ሙሉ ሃሳብ/መግለጫ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። " እኔ ባለሁበት እና በገዛ ቤቴ ንግሥቲቱን ሊያስነውር ጭምር ያስባል!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ንግሥቲቱን ያስነውራል
"ንግሥቲቱን ያጠቃል።" ይህ ሐረግ በጨዋ አገላለጽ ጾታዊ መድፈርን መግለጫ ነው። (አስነዋሪ/ጸያፍ ቃልን ሻል ባለ ቃል መጠቀም/ዩፊምዝም የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ዐረፍተ ነገር ከንጉሡ አፍ እንደ ወጣ ወዲያውኑ
ንግግሩ ከአፉ እንደ ወጣ የሚለው ንግግርን የሚወክል ሜቶኖሚ (ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት ነው)። "ንጉሡ ይህንን እንደተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)
አገልጋዮች የሐማን ፊት ሸፈኑ
ይህንን ያደረጉት ሐማ እንዲገደል ንጉሡ መፈለጉን ስለተረዱ መሆኑ ግልጽ ነው። "አገልጋዮቹ የሐማን ፊት መሸፈናቸው እንደሚገደል ምልክት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ተምሌታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 7:9
ሐርቦና
ይህ የወንድ ስም ነው።(ስሞችን እንዴት ይተረጉማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሃምሳ ክንድ ርዝመት ያለው መስቀያ
"ሃምሳ ክንድ ቁመት፡፡" የሚለውን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ይችላሉ። በአስቴር 5፡14 ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። ወደ፡ "አንድ የሰው መስቀያ ሃያ ሶስት ሜትር ከፍታ" (ቁጥሮች እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀት የሚለውን ይመልከቱ)
የንጉሡ ቁጣ በረደ
የንጉሡ ቁጣ የተገለጸው ታላቅ እሳት እንደነበረ እና እየቀነሰ እንደመጣ ነው። "የንጉሡ ቁጣ በረደ" ወይም "ከዚያ ንጉሡ እጅግ አልተቆጣም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 8
Esther 8:1
ሐማ
በአስቴር 3፡1 ላይ ይህን የወንድ ስም እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ
የቀለበት ማህተም
ይህ ቀለበት የንጉሡ ስም ወይም ምልክት በላዩ አለበት። ጠቃሚ በሆኑ ሰነዶች ላይ የሰም ማህተም ሲያሳርፍ፣ በማህተሙ ላይ ምልክቱን ያኖር ነበር። አንድ ሰነድ በማህተሙ ላይ ይህ ምልክት ካለበት፣ ሰዎች በወረቀቱ ላይ የተጻፈው ነገር በንጉሡ ስልጣን የተጻፈ መሆኑን ይረዱና ለዚያም መታዘዝ ይኖርባቸው ነበር። ይህንን በአስቴር 3፡10 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ። (የማይታወቁትን ስለ መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
ለመርዶክዮስ ሰጠው
ለመርዶክዮስ የማህተም ቀለበቱን በመስጠት፣ ንጉሡ ለመርዶክዮስ ህዝቡ የሚታዘዘው ሰነድ መጻፍ የሚያስችለውን ስልጣንን ሰጠው
የሐማን ቤት ንብረት
ይህ የሚያመለክተው የሐማ የነበሩና ንጉሡ ለአስቴር የሰጣቸውን ሃብት ንብረቶችን ነው።
Esther 8:3
ከተማጽኖ ጋር
"ለመነች"
የአጋጋዊውን የሐማን ክፉ እቅድ ለማስወገድ
"ማብቂያው እንዲሆን" ይህ ፈሊጣው አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ አንድን ነገር ማስቆም ማለት ነው። " የአጋጋዊውን የሐማን ክፉ እቅድ ለማስቆም" ወይም " አጋጋዊውን ሐማ ያቀደውን ክፉ እቅድ ለመከላከል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አጋጋዊው
ይህንን በአስቴር 3፡1 ውስጥ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ።
ያዘጋጀው ሴራ
"የፈጠረው ተንኮል" ወይም "ሐማ የፈጠረው ሴራ"
ንጉሡ ለአስቴር በትረ መንግሥቱን/የወርቅ ዘንጉን ዘረጋላት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህንን ያደረገው በእርሷ ደስ መሰኘቱን ለማሳየት ነው። በአስቴር 5:2 ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ።

Esther 8:5

ንጉሡን ደስ ካሰኘው

"እኔ የምጠይቀው ንጉሡን ደስ ካሰኘው"

በንጉሡ በዐይኖች ሞገስ አግኝቼ ከሆነ

እዚህ ስፍራ "ሞገስ ማግኘት" የሚለው ፈሊጣው አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ ተቀባይነት ማግኘት ወይም በእርሷ ደስ መሰኘቱ የሚል ነው። "ዐይኖች " የሚለው ማየት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት ሲሆን እይታ የሚለው የንጉሱን ሚዛን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። "መዝነኸኝ ተቀባይነትን አግኝቼ ከሆነ" ወይም "በእኔ ደስ ተሰኝተህ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጥ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እንዲሁም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በንጉሡ ፊት ነገሩ ትክክል ሆኖ ከታየ

"በንጉሡ ፊት" ይህ የእርሱን ምዘና የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "የጠየቅኩት በንጉሡ ሚዛን ትክክል መስሎ ከታየ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በዐይኖችህ ፊት ደስ አሰኝቼ ከሆነ

እዚህ ስፍራ "በዐይኖችህ ፊት " የሚለው ማየት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት ሲሆን/ እይታ የሚለው የንጉሱን ሚዛን የሚገልጽ ዘይቤ ነው።"መዝነኸኝ ተቀባይነትን አግኝቼ ከሆነ" ወይም "በእኔ ደስ ተሰኝተህ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የሚሽር

ወደ ኋላ መመለስ እና የማይሰራ ማድረግ

ሐማዳት

ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቶች

ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

በህዝቤ ላይ የሚደርሰውን ጥፋት እያየሁ እንዴት ልታገስ እችላለሁ? የቤተ ዘመዶቼን ጥፋት እንዴት እያየሁ እንዴት መቋቋም እችላለሁ?

አስቴር እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመችባቸው ህዝቧ የሚጠፋ ከሆነ እጅግ እንደምታዝን ለማሳየት ነው። "በአይሁድ ላይ የሚደርሰውን ጥፋት እያየሁ እንዴት መቋቋም እችላለሁ። ቤተዘመዶቼ ሲገደሉ እንዴት ልታገስ እችላለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 8:7

የሐማ ቤት

ይህ የሚገልጸው ሐማ የነበረውን ሁሉ ነው። "የሐማ የነበረው ሁሉ" ወይም "መላው የሐማ ንብረት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሲኔክቲኪ/ ዘይቤያዊ አነጋገር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው መስቀያ እንጨት

ይህንን በአስቴር 6:4 እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመለከቱ

በንጉሡ ስም... የተጻፈ

አንድን ነገር በንጉሥ ስም መጻፍ በእርሱ ስልጣን መጻፍን ያመላክታል፣ ወይም የእርሱ ወኪል ሆኖ መጻፍን ያሳያል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

በማህተም... የወጣ አዋጅ ሊሻር አይችልም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በንጉሱ ቀለበት ...ማንም አዋጁን ሊሽር ስለማይችል" ወይም " በቀለበት የታተመውን...ማንም አዋጁን ሊሰርዝ ስለማይችል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በማህተም... የወጣ አዋጅ ሊሻር አይችልም

"አዋጅ" እና "አይቻልም" በሚሉት ቃላት መሃል የተሰጠው መረጃ ንጉሡ የሐማን አዋጅ መሻር ያልቻለበትን ምክንየት ያሳያል። "ምክንያቱም" በሚለው ቃል በግልጽ የማይችልበት ምክንያት ሊታይ ይችላል። "ቀደም ሲል የተጻፈውን አዋጅ ልሽር አልችልም፣ ምክንያቱም በንጉሡ ስምና ማህተም ከንጉሡ ቀለበት የታተመ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አስቀድሞ በንጉሡ ስም የወጣ አዋጅ

አንድን ነገር በንጉሥ ስም መጻፍ በእርሱ ስልጣን መጻፍን ያመላክታል፣ ወይም የእርሱ ወኪል ሆኖ መጻፍን ያሳያል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 8:9

የንጉሡ ጸሐፊዎች ተጠርተው ነበር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሡ የእርሱን ጸሐፊት ጠራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። አንባቢ መረዳት የሚገባው ንጉሡ ምናልባት ለአንዱ ሹም ሰነዱን እንዲያመጣ ያዘዘው መሆኑን ነው። ንጉሡ ሰነዱን እንዲያመጡለት ምናልናት ጮክ ብሎ አልተጣራም ይሆናል። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሶስተኛው ወር፣ በኒሳን ወር፣ በወሩ ሃያ ሶስተኛ ቀን በዕብራዊያን ቀን አቆጣጠር "ኒሳን" በተባለው

"ኒሳን" በዕብራዊያን ቀን አቆጣጠር የሶስተኛው ወር ስም ነው። ሃያ ሶስተኛው ቀን በምዕራባዊያኑ ወር አቆጣጠር ወደ ሰኔ አጋማሽ ላይ ነው። (የዕብራዊያን ወራት እና ተከታታይነትን የሚያሳዩ ቁጥሮች እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚሉትን ይመልከቱ)

አዋጅ ተጻፈ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አዋጅ ጻፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

127 ግዛቶች

"አንድ መቶ ሃያ ሰባት ግዛቶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቶች

ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

በራሳቸው ጽህፈት ተጻፈ

"በራሳቸው ፊደል ተጻፈ።" በዓለም ዙሪያ የተለያዩ የአጻጻፍ ስርአቶች አሉ።

Esther 8:10

በንጉሥ ጠረክሲስ ስም ተጻፈ

አንድን ነገር በንጉሥ ስም መጻፍ በእርሱ ስልጣን መጻፍን ያመላክታል፣ ወይም የእርሱ ወኪል ሆኖ መጻፍን ያሳያል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

የቀለበት ማህተም

ይህንን ሀረግ በአስቴር 8:2 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ

መልዕክተኞች

መልዕክትየሚያደርሱ ሰዎች

ከንጉሡ ፈረሶች ዝርያ

የንጉሡ ምርጥ ወንድ ፈረሶች ዝርያ። ለንጉሡ አገልግሎት የሚውሉት ምርጥ ዝርያዎች ነበሩ። "የንጉሡ ምርጥ ፈረሶች ዝርያዎች። "የንጉሡ ምርጥ ፈረሶች ዝርያዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአይሁድ እንዲሰበሰቡ... ፈቃድ ሰጣቸው

"እንዲሰበሰቡ እንደፈቀደላቸው...ለአይሁድ ነገራቸው"

ዝግጁ እንደሆኑ

ይህ መልሰው እንዲያጠቁ እንጂ እንዳይሸሹ የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ራሳቸውን ከጥቃት እንዲከላከሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአስራ ሁለተኛው ወር አስራ ሶስተኛ ቀን፣ ይህም የአዳር ወር ነው

ይህንን በአስቴር 3:13 እንዴት እንደተረጎሙት መለስ ብለው ይመልከቱ።

Esther 8:13

ጠላቶቻቸውን እንዲበቀሉ

"ጠላቶቻቸውን እንዲበቀሉ" የዚህ ፈሊጥ ትርጉሙ የጎዳን ሰው መልሶ መጉዳት የሚል ነው። "ጠላቶቻቸውን መልሰው እንዲበቀሉ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሳይዘገዩ ወጡ

"ሳይዘገዩ" የዚህ ፈሊጥ ትርጉም አልዘገዩም ወይም አልጠበቁም ማለት ነው። "ወዲያውኑ ወጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሱሳ

የንጉሡ ቤተመንግስት የነበረባት ከተማ ናት። በአስቴር 1:2 ይህንን እንዴት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 8:15
የሱሳ ከተማ ተደሰተች ሀሴት አደረገችም
"ከተማይቱ" የሚለው በከተማዋ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ይገልጻል። "የሱሳ ከተማ ሰዎች በደስታ ጮሁ ሃሴትም አደረጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)
በደስታ ጮሁ፣ ሃሴትም አደረጉ
"ሃሴት አደረጉ" የሚለው ቃል እንዴት እንደጮሁ ይገልጻል። "በደስታ ጮሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ብርሃን እና ደስታ ሆነላቸው
አማራጭ ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት 1) ብርሃን የሚለው ደስተኛ ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "በደስታ እና ሃሴት ተሞሉ" ወይም 2) ብረሃን ወጣላቸው የሚለው እንደ በለጸጉ እና ደህንነት እንደተሰማቸው የሚገልጽ ፈሊጥ ነው። "ደህንነት ተሰማቸው ደግሞም ድተኞች ሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ክብር
አማራጭ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) ሌሎች ህዝቦች አይሁዶችን አከበሯቸው። "ሌሎች ህዝቦች እነርሱን አከበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) አይሁዶች እንደተከበሩ ተሰማቸው "እንደ ተከበሩ ተሰማቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ግዛት
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
የንጉሡ አዋጅ በየደረሰበት ስፍራ
የደረሰበት ቦታ የሚለው የሚገልጸው ወደየ ስፍራው መድረስን ነው። " የንጉሡ ሰዎች አዋጁን ይዘው ወጡ" ወይም "የንጉሡ አዋጅ በተነበበት ስፍራ ሁሉ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ክብረ በዓል
ሰዎች ልዩ ትዕይንቶችን የሚያከብሩበት ቀን
አይሁዶችን መፍራት ወደቀባቸው
በሰዎች ላይ ፍርሃት ወደቀ የሚለው የሚገልጸው ሰዎች በጣም እየፈሯቸው መምጣቱን ነው። "አይሁዶችን በጣም ፈሯቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 9
Esther 9:1
አዳር በተባለው በአስራ ሁለተኛው ወር፣ በአስራ ሶስተኛ ቀን
በአስቴር 3:13 ተመሳሳይ የሆነውን ሀረግ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ
የንጉሡ ህግ እና አዋጅ ሊፈጸም ባለበት ወቅት
"ሊፈጸም" የዚህ ፈሊጥ ትርጉም የታዘዘን ወይም የታቀደን ነገር ማድረግ ማለት ነው።ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች የንጉሡን ህግና አዋጅ የሚፈጽሙበት ጊዜ ሲደርስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በእነርሱ ላይ ስልጣን ለማግኘት
በሰዎች ላይ ሃይል ማግኘት እነርሱን ለማሸነፋቸው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "አይሁዶችን ለማሸነፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ተቀለበሰ
"ሁኔታው ተቀለብሶ ነበር።" ሁኔታው ተቀልብሶ የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ትርጉሙ ሊሆን ከሚጠበቀው ተቃራኒው ሲሆን ማለት ነው። "ተቃራኒው ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ግዛቶች
ግዛት አንዳንድ አገራት ለአስተዳደር ሲባል የሚከልሉት ሰፊ አካባቢ/ስፍራ ነው። ይህንን በአስቴር 1:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
የእነርሱን ጥፋት በሚፈልጉ ወገኖች ላይ አደጋ ለመጣል
በሰዎች ላይ አደጋ መጣል የሚለው ከእነርሱ ጋር መዋጋት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። "ጠላቶቻቸውን ለመዋጋት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)
በእነርሱ ላይ ጥፋት ለማምጣት የሞከረው ማን ነው
በሰዎች ላይ ጥፋት ማምጣት የሚለው ፈሊጥ ትርጉሙ በእነርሱ ላይ ጥፋት እንዲደርስ ምክንያት መሆን ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ እነርሱን ማጥፋት የሚለውን ያመላክታል። "እነርሱን ለማጥፋት የሞከረው ማን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ማንም ሊቋቋማቸው አልቻለም
ሰዎችን ተቃውሞ መቆም የሚለው የሚወክለው ጥቃታቸውን መቋቋምን ነው። "ማንም የአይሁዳዊያንን ጥቃት መቋቋም አይችልም" ወይም "ማንም በስኬት ከአይሁዶች ጋር መዋጋት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱን መፍራት በሁሉም ላይ ህዝቦች ላይ ወደቀ
ፍርሃት በሰዎች ላይ ወደቀ የሚለው የሚወክለው ሰዎች እጅግ ፈሩ የሚለውን ነው። "ሁሉም ህዝብ አይሁዶችን እጅግ ፈራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 9:3
የአውራጃ ገዢዎች
"የአውራጃዎች ገዢዎች"
መርዶክዮስን መፍራት በእነርሱ ላይ ወደቀ
ፍርሃት በሰዎች ላይ ወደቀ የሚለው የሚገልጸው ሰዎች እጅግ ፈሩ የሚለውን ነው። "መርዶክዮስን ፈርተው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በንጉሡ ቤት ታላቅ ሰው ነበር
"በንጉሡ ቤተ መንግስት እጅግ ጠቃሚ ሰው ነበር"
ዝናው በሁሉም አውራጃዎች ተሰራጨ
በየስፍራው ዝናው ተሰራጨ የሚለው የሚገጸው፣ በእነዚያ ስፍራዎች የሚገኙ ሰዎች ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ አወቁ የሚለውን ነው። "በየአውራጃዎቹ ሰዎች እርሱ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ አወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 9:6
ምሽጎች
ምሽግ የቤተመንግሥት ግንብን፣ ጠንካራ ይዞታን ወይም የተመሸገ ከተማን ያመለክታል። በአስቴር 1:2 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት ተመልሰው ይመልከቱ።
ሱሳ
ይህ ከተማ የፋርስ ነገሥታት መናገሻ ከተማ ነበር። በአስቴር1:2 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አምስት መቶ ወንዶች
"500 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ፓርሻንዳታ፣ ደልፎን፣ አስፓታ፣ ፓራታ፣ አዳልያ፣ አሪዳታ፣ፓርማታ፣ አሪሳይ፣ አሪዳይ፣ ዋይዛታ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አስር ወንድ ልጆች
"10 ወንድ ልጆች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ሐማ
ይህ የንጉሡ ባለሟል የሆነው የሐማ ስም እና ለ እርሱ ገለጻ ነው። ይህንን በአስቴር 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሐመዳቱ
የዚህን ሰው ስም በአስቴር 3:1 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የአይሁዶች ጠላት
ይህ ሀረግ ስለ ሐማ ይነግረናል
Esther 9:11
አምስት መቶ ወንዶች
"500 ወንዶች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ፓርሻንዳታ፣ ደልፎን፣ አስፓታ፣ ፓራታ፣ አዳልያ፣ አሪዳታ፣ፓርማታ፣ አሪሳይ፣ አሪዳይ፣ ዋይዛታ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አስር ወንድ ልጆች


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"10 ወንድ ልጆች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያ እነርሱ በተቀረው በንጉሡ አውራጃዎች ምን አደረጉ?
ንጉሡ ይህንን ጥያቄ ያነሳው አይሁድ በሌሎች አውራጃዎችም የሚገኙ ጠላቶቻቸውን መግደል እንደለባቸው ማመኑን ለማሳየት ነው። "በሌሎቹ በንጉሡ ግዛቶች ማድረግ ያለባቸው" ወይም "በተቀሩትም የንጉሡ ግዛቶች ተጨማሪ ብዙ ጠላቶቻቸውን እንዲገድሉ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሬቶሪካል/ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
አቤቱታሽ/ልመናሽ ምንድን ነው?
"አቤቱታ/ልመና" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠየቀ" ወይም "ለመነ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "የምትለምኚው ምንድን ነው?" ወይም "ምን ትፈልጊያለሽ?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ይሰጥሻል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የምትለምኚውን እኔ እሰጥሻለሁ" ወይም "የምጠይቂውን እኔ ለአንቺ አደርገዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የምትጠይቂው ምንድን ነው?
"ጥያቄ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠየቀ" ወይም "ፈለገ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። " ምን ትጠይቂያለሽ?" ወይም "ምን ትፈልጊያለሽ?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 9:13
የዚህ ቀን አዋጅ ነገም ጭምር እንዲቀጥል
"እንዲቀጥል" የዚህ ፈሊጥ ትርጉም አስቀድሞ የተፈቀደ ወይም የታቀደ ነገርን ማድረግ የሚል ነው። "የዛሬም አዋጅ ነገም ደግሞ እንዲቀጥል" ወይም "ዛሬ እንዲፈጽሙት ታውጆ የነበረውን ነገም ደግሞ እንዲያደርጉት። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አስር ወንድ ልጆች
"10 ወንድ ልጆች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው መስቀያ እንጨት
ይህ ሰዎችን ለመስቀል ያገለግል የነበረ አሰራር ሲሆን፣ የገመዱ አንዱ ጫፍ በመስቀያው እንጨት ላይ ሲታሰር ሌላኛው የገመዱ ጫፍ በሚሰቀሉት ሰዎች አንገት ዙሪያ በማድረግ ይንጠለጠላሉ። በአስቴር 2:23 ይህንን እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "ሰዎችን ለመስቀል የሚዋቀር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የማይታወቁትን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 9:15
በአዳር ወር በአስራ አራተኛው ቀን
በአስቴር 3:13 ተመሳሳዩን ሀረግ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
በምርኮው ላይ እጃቸውን አልጫኑም
በነገሮች ላይ እጆቻቸውን መጫን የሚለው የሚያመለክተው ነገሮቹን መውሰድን ነው። "ከምርኮው አንዳች አልወሰዱም" ወይም "ከምርኮው አንዳች እንኳን አልወሰዱም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)
ሰባ አምስት ሺህ
"75፣000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
እጆቻቸውን በገደሏቸው ሰዎች ንብረት ላይ አልጫኑም
በነገሮች ላይ እጆቻቸውን መጫን የሚለው የሚገልጸው ነገሮቹን መውሰድን ነው። " ከገደሏቸው ሰዎች አንዳች ንብረት አልወሰዱም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)
ዋጋ ያላቸው
"ዋጋ ያላቸው ነገሮች" ወይም "ንብረቶች"
Esther 9:17
በአዳር ወር በአስራ ሶስተኛው ቀን
በአስቴር 3:13 ተመሳሳዩን ሀረግ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
በአስራ አራተኛው ቀን አረፉ
"በአዳር ወር በአስራ አራተኛው ቀን በየአውራጃዎቹ የሚኖሩ አይሁዶች አረፉ
በሱሳ የሚኖሩ አይሁዶች ተሰበሰቡ
የተሰበሰቡበት ምክንያት በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። " በሱሳ የሚኖሩ አይሁዶች ከጠላቶቻቸው ጋር ለመውጋት በአንድነት ተሰበሰቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 9:20
በየአመቱ የአዳርን ወር አስራ ሁለተኛ እና አስራ ሶስተኛ ቀን ለመጠበቅ
ቀንን መጠበቅ የሚለው ፈሊጣው አነጋገር ቀኑን ማክበር ማለት ነው። "በየአመቱ የአዳርን ወር አስራ አራተኛ እና አስራ አምስተኛ ቀን ለማክበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሀዘናች ወደ ደስታ ዞረ
ዞረ የሚለው መለወጥን ያመለክታል። ሀዘን እና ደስታ የሚሉት ረቂቅ ስሞች "መከፋት" እና "በደስታ መሞላት" በሚል ሊገለጹ ይችላሉ። " እጅግ ሀዘንተኛ ከመሆን ወደ ደስተኛነት ተለወጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 9:23
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ምንባብ ለፉሪም በዓል መከበር ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ለማብራራት የአስቴርን አመዛኙን ታሪክ በአጭሩ ያቀርባል።
የአጋጋዊው የሐመዳቱ ልጅ ሐማ
ይህ ከንጉሡ ሹማምንት አንዱ የሆነው የሐማ ስም እና ገለጻ ነው። ይህን በአስቴር 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ፉር አወጣ/ጣለ (ይህ ማለት፣ ዕጣ አወጣ ማለት ነው)
"ፉር" በፋርስ ቋንቋ "ዕጣ" የሚል ቃል ነው። "ጣለ/አወጣ" የሚለው ሀረግ "ፉር ጣለ/አወጣ" የሚለው ምን ማለት እንደሆነ ያብራራል።
ፉር አወጣ/ጣለ (ይህ ማለት፣ ዕጣ አወጣ ማለት ነው)
ለምን ፉር፣ ወይም ዕጣ ጣለ የሚለው በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "አይሁድን ለማጥቃት የተሻለው ቀን የትኛው እንደሆነ ለማወቅ እጣ ጣለ (ዕጣ አወጣ)" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን ጉዳዩ ወደ ንጉሡ ፊት ስትቀርብ
የዕብራይስጡ ጽሁፍ "አስቴር ግን ንጉሡ ፊት ስትቀርብ" ተብሎም ሊተረጎም ይችላል። አንዳድ ዘመናዊ ቅጂዎች ይህንን ትርጉም ይመርጡታል።
ሐማ በአይሁዶች ላይ ያወጣው ክፉ እቅድ በገዛ ራሱ ላይ ተመለሰበት
"በራሱ እናት ላይ ተመለሰ" ማለት በሐማ ላይ ይፈጸም ማለት ነው። "ሐማ በአይሁድ ላይ ያዘጋጀው ክፉ እቅድ በራሱ ላይ መፈጸም አለበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Esther 9:26
እነዚህን ቀናት፣ ፉር ከሚለው ስም በመነሳት ፉሪም ብለው ጠሯቸው
አንድን ነገር ከሌላ አንድ ለነገር በመነሳት መሰየም ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ ያም ማለት አንድ አይነት ስም መስጠት ወይም ተመሳሳይ ስም መስጠት ነው። "እነዚህን ቀናት፣ ፉር ከሚለው ቃል በመነሳት ፉሪም ብለው ጠሯቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ፉሪም
ይህ የአይሁድ ህዝብ በጥንቱ ፋርስ በሐማ ሴራ በአንዲት ቀን ውስጥ ከመደምሰስ እና ከእልቂት የተረፈበት መታሰቢያ በዓል ስያሜ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የፉር ስያሜ
"ፉር" ማለት ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ፉር የሚለው ቃል፣ 'ዕጣ' ማለት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆና ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህ ቀናት ሊከበሩ እና ሊታሰቡ ይገባል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አይሁዶች እነዚህን ቀናት ያከብራሉ ያስቧቸዋልም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በታማኝነት ከማክበር በፍጹም አያቋርጡም
ይህ በአዎንታዊ ሊጻፍ ይችላል። "ሁሌም በታማኝነት ያከብሩታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
Esther 9:29
ይህንን ሁለተኛውን ደብዳቤ .... የአቢካኢል ሴት ልጅ ንግሥት አስቴር እና አይሁዳዊው መርዶክዮስ ጻፉ
አስቴር የአቢካኢል ሴት ልጅ ናት። አስቴር እና መርዶክዮስ ደብደቤውን ጻፉ።
አቢካኢል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የአስቴር አባት እና የመርዶክዮስ አጎት። ይህንን በአስቴር 2:15 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለተኛ ደብዳቤ

"ተጨማሪ ደብዳቤ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 9:30

ደብዳቤዎች ወደ ሁሉም አይሁዶች ተላኩ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወደ ሁሉም አይሁዳዊያን ደብዳቤዎች ላኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

127 አውራጃዎች

"አንድ መቶ ሃያ ሰባት አውራጃዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ) ለአይሁድ ደህንነት እና እውነት መመኘት ረቂቅ ስሞች የሆኑት "ደህንነት" እና "እውነት በሀረግ ሊገለጽ ይችላል። "አይሁድ ሰላም እንዲሆኑ እና ሌላው ህዝብ ለአይሁድ ታማኝ እንዲሆን መመኘት" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አይሁዳዊያን ይህንን ግዴታ ለራሳቸው እና ለትውልዳቸው ተቀበሉ

ግዴታን መቀበል ከተሰጡትን ግዴታዎች ጋር መስማማትን ለመግለጽ የሚውል ፈሊጥ ነው። "ግዴታ የሚለው ረቂቅ ስም "ታዘዘ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "አይሁዶች ተስማምተው እነርሱ እና የእነርሱ ትውልዶች የፉሪምን ቀናት ለማክበር ግዴታ እንዳለባቸው ተነገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የጾም እና የሰቆቃ ጊዜያነትን ተቀበሉ

የጾም እና የሰቆቃ ጊዜያነትን መቀበል የሚለው ለተወሰነ ጊዜ ለመጾም እና ለማልቀስ መስማማትን የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ለተወሰነ ጊዜ ለመጾም እና በለቅሶ ለመጸለይ ተስማሙ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 10

Esther 10:1

እስከ ባህር ዳርቻ በሚዘልቀው ግዛቱ ግብር ጣለ

ግብር መጣል ማለት ህዝቡ ግብር እንዲከፍል ማድረግ ማለት ነው። ምድሩ እና የባህር ዳርቻ የሚለው የሚገልጸው በዚያ የሚኖረውን ህዝብ ነው። "በምድሩ እና በባህር ዳርቻ የሚኖረው ህዝብ ግብር እንዲከፍል አደረገ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት- የሚለውን ይመልከቱ)

የሃይሉ እና የብርታቱ ስኬቶች ሁሉ

"ስኬቶች" የሚለው ረቂቅ ስም "ተሳካ" በሚል ግስ ወይም "ታላላቅ ነገሮችን ማድረግ" በሚል ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። "ሃይል" እና "ብርታት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በቅጽል ሊገለጹ ይችላሉ። "ያደረገው ሁሉ ታላቅ እና ብርቱ ስለነበረ ነው። ወይም "ያደረጋቸው ታላላቅ ነገሮች ሁሉ ከሀይሉና ከታላቅነቱ የተነሳ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡ ከፍ ከፍ ያደረው የመርደክዮስ ታላቅነት ሙሉ ታሪክ

የንጉሡ መርዶክዮስን ማክበር የተገለጸው ንጉሡ በአካል ያነሳው ያህል ተደርጎ ነው። "ንጉሡ እንዴት መርዶክዮስ ታላቅ መሆኑ እንዲታወቅ እንዳደረገ ያለው ሙሉ ታሪክ" ወይም "መርዶክዮስ ላደረጋቸው ነገሮች ንጉሡ እንዴት እንዳከበረው ሙሉው ታሪክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Esther 10:3

ከንጉሡ ከጠረክሲስ ቀጥሎ በደረጃ ሁለተኛ

"ከንጉሥ ጠረክሲስ ቀጥሎ እጅግ ጠቃሚው ሰው"

አይሁዳዊ ወንድሞች

ወንድሞች የሚለው ቃል እንደ እርሱ ያሉ ሰዎችን ይወክላል። "አይሁዳዊ ወገኖች" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የህዝቡን ደህንነት ፈለገ

አንድን ነገር መፈለግ ለአንድ ነገር በጥንካሬ መስራትን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ደህንነት" የሚለው ረቂቅ ስም "በለጸገ" በሚለው ግስ ወይም "ደህንተነት" በሚል ቅጽል ሊተረጎም "ህዝቡ ይበለጽግ ዘንድ በጥንካሬ ሰራ" ወይም "የህዝቡ ደህንነት ይጠበቅ ዘንድ በጥንካሬ ሰራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ለመላው ህዝቡ ሰላም ተናገረ

" ሰላም ይኖራቸው ዘንድ፣ እርሱ ህዝቡን ይወክላል

---

Chapter 1

Job 1:1

በዖጽ ምድር

ይህ ስፍራ ሊገኝ የሚችለው 1) በአሁኗ ዮርዳኖስ፣ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምስራቅ ጥንት ኤዶም በምትባል ስፍራ ወይም 2) በአሁኗ ኢራን ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምስራቅ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ነቀፋ የሌለበት እና ትክክለኛ

"ነቀፋ የሌለበት" እና "ትክክለኛ" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም ቃላቱ ኢዮብ ጻድቅ ሰው መሆኑን ትኩረት ይሰጣሉ። "በእግዚአንሔር ፊት ትክክል የሆነውን የሚያደርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን የሚፈራ

"እግዚአብሔርን የሚያከብር"

ከክፉ የራቀ

እዚህ ስፍራ ክፉ የተገለጸው ሰው ወደዚያ ስፍራ ሄዶ ክፉ ከማድረግ ይልቅ ወደዚያ ከመሄድ ራሱን እንደሚያቅብበት ስፍራ ተደርጎ ነው። "ክፉ ማድረግን አሻፈረኝ ማለት/ከክፋት የራቀ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባት ወንዶች ልጆች እና ሶስት ሴቶች ልጆች

"7 ወንዶች ልጆች እና 3 ሴቶች ልጆች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰባት ሺህ በጎች ነበሩት

"7,000 በጎች ነበሩት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሶስት ሺህ ግመሎች

"3,000 ግመሎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አምስት መቶ ጥማድ/ጥንድ በሬዎች

"500 ጥማድ/ጥንድ በሬዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እጅግ ታላቅ

"ከሁሉም ባለጸጋ"

በምስራቅ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ

ከከነዓን በስተ ምስራቅ የሚገኝን ስፍራ ያመለክታል። "ከከነዓን በስተ ምስራቅ በሚገኝ ምድር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 1:4

በእያንዳንዱ ልጅ ተራ፣ እርሱ ያቀርብ ነበር

"ቀን" የሚለው ቃል ምናልባት የአንዱን ልጅ ልደት የሚያከብሩበት ቀን ማለት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ቢያንስ ልጆቹ በየተራ ድግስ እንደሚያደርጉ ያመለክታል። "በእያንዳንዱ ልጅ የልደት ቀን፣ ልጁ ያቀርብ ነበር" ወይም "እያንዳንዱ ልጅ በተራው ያቀርብ ነበር"

እርሱ ያቀርብ ነበር... እነርሱ ልከው... ይጠሩ ነበር... ኢዮብ ይልክ ነበር... እርሱ ይሳል ነበር...

በጥዋት ማልዶ ተነስቶ መስዋዕት ያቀርብ ነበር... እንዲህ ይል ነበር

"ሁሌም ያቀርብ ነበር...እነርሱ ሁሌም... ልከው ይጠሩ ነበር... ኢዮብ ሁሌም ይልክ... ሁሌም ይሳል... እርሱ ሁሌም ማልዶ ይነሳ እና ይሰዋ... እርሱ ሁሌም እንዲህ ይል ነበር"

ከእነርሱ ጋር

"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰባቱን ወንዶች ልጆች እና ሶስቱን ሴት ልጆች ሲሆን ኢዮብን ግን አይጨምርም።

የድግሱ ዕለት ሲያልፍ

"ድግሱ ሲጠናቀቅ" ወይም "ከድግሱ በኋላ"

ኢዮብ ወደ እነርሱ ይልክና

"ኢዮብ ዘወትር እነርሱ ወደ እርሱ እንዲመጡ አንድ ሰው ይልክ ነበር"

እነርሱን ያነጻ ነበር

እዚህ ስፍራ "ማንጻት" ማለት የኢዮብ ልጆች በደስታ በአንድነት ተሰብስበው ግብዣ ሲያደርጉ የፈጸሙት የምልኮ ነቀፊታ ቢኖር ጥፋት እንዳይደርስባቸው እግዚአብሔርን ይቅርታ መለመን ማለት ነው። ኢዮብ ስለ እነርሱ መስዋዕት በማቅረብ ይህን ያደርግ ነበር።

በልባቸው እግዚአብሔርን ረግመው ቢሆን
"በልባቸው" የሚለው የሚወክለው ሃሳባቸውን ነው። ብዙውን ጊዜ እንዲህ ያሉ ሃሳቦች አንድ ሰው ነገሩን ሊያስበው ሳይፈልግ ከፈቃዱ ውጭ ሊመጡ ይችላሉ። "በሃሳባቸው እግዚአብሔርን ረግመው ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 1:6
ከዚያም ... የሚደረግበት ቀን ነበር
"በ...በሚሆንበት ጊዜ" ወይም "አንድ ዕለት... በ...ጊዜ።" ይህ በአንድ የተለየ ቀን ብቻ የተደረገ አይደለም፣ ይልቁንም ስብሰባው ብዙውን ጊዜ እንደሚደረግ ግልጽ ነው።
የእግዚአብሔር ልጆች
ይህ ሰማያዊ ፍጥረታትን፣ መላዕክትን ያመለክታል።
ራሳቸውን በያህዌ ፊት ለማቅረብ
"ያደርጉት ዘንድ እርሱ እንዳዘዛቸው በያህዌ ፊት በአንድነት ለመቆም"
ያህዌ
ይህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ራሱን ለህዝቡ የገለጸበት ስም ነው። ስለ ያህዌ ይህ እንዴት እንደሚተረጎም የቃል ትርጉም ገጽን ይመልከቱ።
በምድር ከመዞር፣ በላይዋ ከመመላለስ
"መዞር" እና "መመላለስ" የሚሉት ሀረጋት በምድር ሁሉ የመጓዝን ድርጊት በሙላት ለማጉላት የዋለ ነው። "በምድር ላይ በሁሉም ስፍራ መዞር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ጽንፍ የሚሉትን ይመልከቱ)
ባሪያዬን ኢዮብን አይተኸዋልን?
"ስለ ባሪያዬ ኢዮብ አውቀሃልን?" እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ስለ ኢዮብ ከሰይጣን ጋር መነጋገር ይጀምራል። "ባሪያዬን ኢዮብን አይተኸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ነቀፋ የሌለበት እና ቅን ሰው
"ነቀፋ የሌለበት" እና "ቅን" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉሞችን ሲይዙ ኢዮብ ጻድቅ ሰው መሆኑን አጉልተው ያሳያሉ። ይህ በኢዮብ 1፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነውን የሚያደርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን የሚፈራ
"እግዚአብሔርን የሚያከብር።" ይህ በኢዮብ 1፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
Job 1:9
ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራው ያለ ምክንያት ነውን?
"ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚያከብረው ያለ ምክንያት ነውን?" ሰይጣን ለእግዚአብሔር ጥያቄ አቅርቦ ራሱ መልስ ይሰጣል። ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚታዘዘው እግዚአብሔር ስለባረከው ብቻ ነው ይላል። "ኢዮብ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ምክንያት አለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በዙሪያው፣ በቤቱ ዙሪያ እና ባለው ነገር ሁሉ ዙሪያ ቅጥር አላኖርክለትምን?
ሰይጣን ክርክሩን ለማጠናከር የሚረዱትን መረጃዎች ሁሉ ይናገራል። "አንተ እርሱን፣ ቤተሰቡን እና ያለውን ነገር ሁሉ ጠብቀሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በዙሪያው፣ በቤቱ ዙሪያ እና ባለው ነገር ሁሉ ዙሪያ ቅጥር አድርገህለታል
እንደ ግርግዳ ወይም አጥር ያለ መከላከያ የአንድን ሰው ይዞታ ዙሪያውን እንደሚከብ እና እንደሚጠብቅ፣ እግዚአብሔር ኢዮብን በጥበቃው ከቦታል። "እርሱን እና ቤቱን እንዲሁም የእርሱ የሆነውን ሁሉ ጠብቀሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእጆቹን ስራዎች
"የሚሰራውን ነገር ሁሉ"
በምድር ላይ ከብቱ በዝቶለታል
"በምድር ላይ ከብቱ ተትረፍርፏል"
ነገር ግን አሁን እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሁሉ ንካበት፣ በዚያን ጊዜ ፊት ለፊት እንደማይረግምህ ታያለህ
ሰይጣን ይህንን ማለቱ እግዚአብሔር ኢዮብን ቢነካው፣ የኢዮብ ምላሽ ምን እንደሚሆን ይመለከታል ማለቱ ነው። "ነገር ግን አሁን፣ እጅህን ብትዘረጋ እና ያለውን ሁሉ ብትነካ ፊት ለፊት እንደሚረግምህ ታያለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ነገር ግን አሁን፣ እጅህን ዘረጋ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው የእግዚአብሔርን የማድረግ አቅም ነው። "ነገር ግን አሁን ሀይልህን ተጠቀም" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ያለውን ሁሉ ንካ
እዚህ ስፍራ "መንካት" የሚወክለው ጉዳት የማድረስ ወይም የማጥፋት ድርጊትን ነው። "ያለውን ሁሉ አጥፋ" ወይም "ያለውን ሁሉ ደምስስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በፊትህ
"እየሰማኸው።" ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ትኩረት የሚሰጥበትን ጊዜ ነው።
እነሆ
"እነሆ" ወይም "የምናገረውን ትኩረት ሰጥተህ ብትሰማኝ"
እርሱ ያለው ሁሉ በእጅህ ነው
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው አንድ ሰው አንድን ነገር ለመቆጣጠር ያለውን አቅም/ሀይል ነው። "እርሱ ባለው ነገር ላይ ሁሉ አቅም ተሰጥቶሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ በራሱ ላይ
"በህይወቱ ላይ"
ያህዌ ከሚገኝበት ወጥቶ ሄደ
"ከያህዌ ፊት ወጥቶ ሄደ" ወይም "ያህዌ ካለበት ለቆ ሄደ"
Job 1:13
ሳባውያን
ይህ በዛሬ ዘመን በየመን አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። እዚህ ስፍራ ይህ የሚወክለው የፈረሰኞችን ቡድን ወይም ሽፍቶችን ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
በእነርሱ ላይ ወደቁባቸው
እዚህ ስፍራ "መውደቅ" የሚለው የሚገልጸው ማጥቃትን ነው። "እነርሱን አጠቋቸው/አደጋ ጣሉባቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መቷቸው
እዚህ ስፍራ ማጥቃት የሚለው የሚገልጸው መግደልን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የሰይፍ ስለት
እዚህ ስፍራ "የሰይፍ ስለት" የሚለው የሚወክለው ሰው ለመግደያነት የሚውለውን የሰይፉን ክፍል ነው፤ ይህም ማለት አንድም የሰይፉን ጫፍ ወይም የተሳለውን ጠርዝ ማለት ነው። እንደዚሁም ደግሞ፣ የሳባውያን ሰይፎች ሁሉ እንደ አንድ ሰይፍ ብቻ ተደርጎ ተገጽዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና የስማዊ ሀረጋት ክፍል የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 1:16
እርሱ ገና እየተናገረ ሳለ
"እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የመጀመሪያውን መልዕክተኛ ነው።
ሌላው ደግሞ መጣ
ይህ የሚያመለክተው ሌላውን መልዕክተኛ ነው። "ሌላው መልዕክተኛ ደግሞ መጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ብቻዬን አመልሁ፤ ልነግረህም መጣሁ
ይህ በኢዮብ 1፡15 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
አገልጋዮችህንም በሰይፍ ስለት መቷቸው። እኔ ብቻ ልነግርህ አመለጥሁ
እዚህ ስፍራ "የሰይፍ ስለት" የሚለው የሚወክለው ሰው ለመግደያነት የሚውለውን የሰይፉን ክፍል ነው፤ ይህም ማለት አንድም የሰይፉን ጫፍ ወይም የተሳለውን ጠርዝ ማለት ነው። እንደዚሁም ደግሞ፣ የከለዳውያን ሰይፎች ሁሉ እንደ አንድ ሰይፍ ብቻ ተደርጎ ተገጽዋል። ይህ በኢዮብ 1፡15 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና የስማዊ ሀረጋት ክፍል የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 1:18
ወንዶች እና ሴቶች ልጆችህ በታላቅ ወንድማቸው ቤት ይበሉና ወይን ይጠጡ ነበር
ይህ በኢዮብ 1፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
አውሎ ነፋስ

"አውራቂስ/ቶርኔዶ" ወይም "የበረሃ ማዕበል"
የቤቱ አራት ማዕዘኖች
"ቤቱን ያቆመው መዋቅር/ቤቱ የተዋቀረበት ድጋፍ"
በወጣቶቹ ላይ ወደቀ
"ቤቱ በወንዶች እና ሴቶች ልጆችህ ላይ ወደቀ"
እኔ ብቻዬን አመልሁ፤ ልነግረህም መጣሁ
ይህ በኢዮብ 1:15 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
Job 1:20
ልብሱን ቀደደ፣ ራሱን ተላጨ
እነዚህ ሀዘንን የመግለጫ ስርዓቶች ነበሩ፤ ጥልቅ ሀዘንን መድረሱን ያመለክታሉ። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊቶች የሚለውን ይመልከቱ)
ከእኔቴ ማህጸን ስወጣ እርቃኔን ነበር፣ ደግሞም እርቃኔን እመለሳለሁ
"ስወለድ፣ ወደዚህ ዓለም አንዳች ይዤ አልመጣሁም፤ ስሞትም ምንም ሳልይዝ ወደ ምድር እመለሳሉ"
በዚህ ሁሉ ነገር
"በሆነው ነገር ሁሉ"
እግዚአብሔርን አጥፍተሃል ብለህ ክሰስ
"እግዚአብሔርን ተሳስተሃል በለው"

---

Chapter 2
Job 2:1
አጠቃላይ መረጃ:
እነዚህ ሀረጋት በኢዮብ 1:1-6 ውስጥ ካለው ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ናቸው፤ እናም ምናልባትም በተመሳሳይ መንገድ ሊተረጎሙ ይችላሉ።
ከዚያም ዕለቱ ያ ነበር
ይህ በኢዮብ 1:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ
አንድ ዕለት
ይህ አንድ ውሱን ቀን አይደለም። መሰባሰቡ ብዙ ጊዜ ይደረጋል። "በ…ጊዜ" ወይም "በ…አንድ ዕለት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
የእግዚአብሔር ልጆች
ይህ በኢዮብ 1:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ
ራሳቸውን በያህዌ ፊት አቀረቡ/በእግዚአብሔር ፊት መጡ
ይህ በኢዮብ 1:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ
በምድር ላይ ከመዞር፣ በላይዋ ወዲያና ወዲህ ከመመላለስ
ይህ በኢዮብ 1:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ
Job 2:3
አጠቃላይ መረጃ:
ይህ ሀረግ "አንተ ያለ ምክንያት እንዳጠፋው በእርሱ ላይ ብታነሳሳኝም እርሱ ታማኝነቱን እንዳጸና ነው" የሚለው ከመጨመሩ በስተቀር ከኢዮብ 1:8 ጋር ተመሳሳይ ነው።
አገልጋዬን ኢዮብን ተመለከትከውን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በእርግጥ ዐረፍተ ነገርን ይመሰርታል። ይህ በኢዮብ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "አገልጋዬን ኢዮብን ተመለከትከው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ነቀፋ የሌለበት እና ቅን ሰው
"ነቀፋ የሌለበት" እና "ቅን" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉሞችን ሲይዙ ኢዮብ ጻድቅ ሰው መሆኑን አጉልተው ያሳያሉ። ይህ በኢዮብ 1:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነውን የሚያደርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን የሚፈራ እና ከክፋት የራቀ
ይህ በኢዮብ 1:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እስከ አሁን ታማኝነቱን ጠብቋል
"መልካም እና ትክክል የሆነውን ለማድረግ እስከ አሁን ሙሉ ለሙሉ ራሱን ሰጥቷል"
በእርሱ ላይ በክፉ ብትገፋፋኝም
"ያለ ምክንያት እርሱን እንዳጠፋው ብትገፋፋኝም"
እርሱን እንዳጠፋው
እዚህ ስፍራ "ማጥፋት" የሚለው የሚገልጸው "ማደህየት" የሚለውን ነው። "ደሃ ሰው እንዳደርገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
Job 2:4
በእርግጥ ቆዳ ስለ ቆዳ ነው
እዚህ ስፍራ "ቆዳ" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚገልጸው የኢዮብን ህይወት ነው። "ሰው ህይወቱን ለማዳን ሀብቱን እና የሚወዳቸውን ሰዎች ማጣትን መቀበልን ጨምሮ ማናቸውንም ዐይነት ነገር ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን አሁን እጅህን ዘርግተህ አጥንት እና ስጋውን ብትነካ፣ በፊትህ በእርግጥ የማይራገም ስለመሆኑ እስኪ ተመልከት
ሰይጣን ይህን ማለቱ፣ እግዚአብሔር ኢዮብን ቢጎዳው ኢዮብ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ ይመለከታል ማለቱ ነው። "ነገር ግን አሁን፣ እጅህን ብትዘረጋ እና አጥንቱን እና ስጋውን ብትነካ በፊትህ እንደሚረግምህ ትመለከታለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
እጅህን ዘርጋ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን የማድረግ ሀይል ነው። "ነገር ግን አሁን ሀይልህን ተጠቀም" ይህ በኢዮብ 1:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
መንካት
እዚህ ስፍራ "መንካት" የሚያመለክተው መጉዳትን ነው። "አጥቃው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አጥንቱ እና ስጋው
ይህ አገላለጽ የሚወክለው የኦዮብን አካል ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በፊትህ ይረግምሃል
ይህ በኢዮብ 1:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
በፊትህ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በትኩረት ነገሩን የሚመለከትበትን ጊዜ ነው። "እየሰማህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 2:7
ከዚያም ሰይጣን ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ ሄደ
ይህ በኢዮብ 1:12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እርሱ ኢዮብን በቁስል መታው
"በከባድ ቁስል አሰቃየው"
የስቃይ ቁስል
ትልቅ፣ የሚያሳክክ እና ስቃይ የሞላበት የቆዳ ቁስል
ገላውን የሚያክበት ገል/የሸክላ ስባሪ
ማከኪያው ስቃዩን ለመቀነስ ቆዳውን የሚያክበት ነው
በአመድ መሃል ተቀመጠ
ይህ ምናልባት አመድና ቆሻሻ ተጥሎ የሚቃጠልበትን ስፍራ ሊያመለክት ይችላል። እንዲህ ባለው ስፍራ መቀመጥ ጥልቅ ሀዘን መድረሱን የሚያመለክት ነበር። "በቆሻሻ ክምር ላይ ተቀመጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊቶች የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 2:9
እስከ አሁን ታማኝነትህን ጠብቀሃል?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ዐረፍተ ነገርን ይገልጻል። "እስከ አሁን ታማኝነትህን መጠበቅ አልነበረብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን ተራገም
"እግዚአብሔርን ተው"
አንቺ እንደ ሞኝ ሴት ተናገርሽ
"የማይረቡ ሴቶች እንደሚናገሩት ተናገርሽ"
መልካሙን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ተቀበልን ክፉውንስ አንቀበልምን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ዐረፍተ ነበርን ይገልጻል። "መልካሙን ከእግዚአብሔር እንደተቀበልን ሁሉ ክፉውንም በእርግጥ መቀበል ይገባናል" በሚለው ውስጥ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
መልካሙን መቀበል
"መልካም ከሆኑ ነገሮች ሁሉ ተጠቃሚ መሆን"
መልካም የሆነው
ይህ የሚወክለው እግዚአብሔር የሰጠንን መልካም ነገሮች ሁሉ ነው። (የስማዊ ሀረጋት ክፍሎች)
ክፉ የሆነውን መቀበል
"ሳያማርሩ ክፉ የሆነውን ሁሉ መቀበል"
ክፉ የሆነው
ይህ የሚወክለው እግዚአብሔር እንድናልፍበት የፈቀደቀውን ወይም ያደረገውን ክፉ ነገሮች ሁሉ ነው። (የስማዊ ሀረጋት ክፍሎች)
ከከንፈሮቹ በደል
እዚህ ስፍራ "ከንፈሮች" የሚወክለው የንግግርን ነው። "በንግግር እግዚአብሔርን መበደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 2:11
ቴማናዊው ኤልፋዝ፣ ሹሐዊው በልዳስ፣ እና ናዕማታዊው ሶፋር
ኤልፋዝ፣ በልዶስ እና ሶፋር የወንድ ስሞች ናቸው። ቴማን በኤዶም ውስጥ የምትገኝ ከተማ ናት። ሹሐዊያን የአብርሃም እና የኬጡራ ትውልዶች ናቸው። ናዕማ በከነዓን ውስጥ የምትገኝ ከተማ ናት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ጊዜ ወሰኑ
"በጊዜው ላይ ስምምነት ላይ ደረሱ)
ከእርሱ ጋር ለማልቀስ እና እርሱን ለማጽናናት
እዚህ ስፍራ "አብሮ ለማልቀስ" እና "ለማጽናናት" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ወዳጆቹ ኢዮብን ለማጽናናት የሞከሩት ከእርሱ ጋር በማዘን ነው። "መከራውን እንዲረሳ" ከኢዮብ ጋር አዘኑ በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
Job 2:12
ዐይኖቻቸውን አነሱ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም "በትኩረት ተመለከቱ" ወይም "በጥንቃቄ አዩ" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አላወቁትም
ይህ ምናልባት የኢዮብ ጠያቂዎች ከሩቅ ሲመለከቱት በመጀመሪያ በቶሎ አላወቁትም ማለት ሊሆን ይችላል። ኢዮብ ከሀዘኑ እና ገላውን ከወረሰው ህመም የተነሳ ከወትሮው በጣም የተለየ ሆኖ ይታይ ነበር። "ለይተው ሊያውቁት አልቻሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ድምጻቸውን አንስተው አለቀሱ
እዚህ ስፍራ "ድምጻቸውን አንስተው" የሚለው ጮኸው ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ጮኸው አለቀሱ" ወይም "ድምጻቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ልብሱን ቀደደ
ይህ የሀዘን ምልክት ነው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ትቢያ ወደ ላይ እየበተነ እና በራሱ ላይ እየነሰነሰ
እነዚህ የሀዘን መግለጫዎች ነበሩ። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 3
Job 3:1
አፉን ከፈተ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ንግግርን መጀመር ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የተወለድኩባት ቀን እና ምሽት ይጥፉ/መታሰቢያ ይጡ
ኢዮብ ስለዚያ ቀን እና ምሽት የሚናገረው ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ነው። "ምነው ባልተወለድኩ ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
'ወንድ ልጅ ተጸነሰ' የተባለበት ምሽት
ይህ አገላለጽ የኢዮብን ሀዘን ከተወለደበት እስከ ተጸነሰበት ቀን ድረስ ወደ ኋላ በመመለስ አጠንክሮ ይገልጻል። 'ወንድ ልጅ ተጸነሰ የተባለበት ዕለት ይጥፋ' በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
የተባለበት ምሽት
እዚህ ስፍራ ምሽት የተገለጸው መናገር የሚችል ሰው ተደርጎ ነው። ሆኖም ተርጎሚው ከዚህ ዝቅ ባለ ዘይቤያዊ አገላለጽ ሊተረጉመው ይችላል። "ሰዎች … ያሉበት ምሽት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወንድ ልጅ ተጸንሷል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እናቱ ወንድ ልጅ ጸንሳለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
Job 3:4
አጠቃላይ መረጃ፡
በዚህነዚህ ሀረጋት ውስጥ የሚገኙት አገላለጾች ኢዮብ የተወለደበት ቀን ከእንግዲህ እንዳይኖር ያለን ምኞች የሚገልጹ ናቸው። ይህ ምናልባት የቀደመው ቀን በአንድ መንገድ የሚቀጥል መሆኑን የሚጠቁም ሊሆን ይችላል። ዩዲቢ ቀኑ ምን ይመስል እንደነበር የሀዘን መግለጫ አድርጎ ይተረጉማቸዋል።
ያ ቀን ጨለማ ይሁን… ፀሐይም አይውጣበት።
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ኢዮብን ጸጸት በመደጋገም የተወለደበትን ቀን ጨለማነቱ ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ያ ቀን ጨለማ ይሁን
ይህ ያዚያችን ቀን ከእንግዲህ ያለመኖር የሚገልጽ ምኞት ነው። "ያቺ እለት ትጥፋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ( ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጨለማ እና የሞት ጥላ እርሱን ይውረሱት
እዚህ ስፍራ ጨለማ እና የሞት ጥላ የተገለጹት አንድን ሰው ወይም አንድን ነገር የራሱ እንደሚያደርግ ሰው ተደርገው ነው። "እርሱን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢዮብን የልደት ቀን ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሞት ጥላ
እዚህ ስፍራ ጥላ የሚወክለው ሞትን ነው። "ሞት እንደ ጥላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ደመና በላዩ ይኑር
እዚህ ስፍራ ደመና የተገለጸው በኢዮብ የልደት ቀን ላይ መኖር እንደሚችል ሰው ተደርጎ ነው። "ማንም ሊመለከተው እንዳይችል ደመና ይሸፍነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቀኑን ጨለማ የሚያደርግ ነገር ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው የፀሐይን ብርሃን የሚጋርድን እና መለማ የሚፈጥርን ነገር ሁሉ ነው። እዚህ ስፍራ "ጥቁር" የሚወክለው ጨለማን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ያስፈራሩት
"ያንን ቀን ያስፈራሩት።" ቀኑ የተገለጸው በጨለማ ፍርሃት እንደሚውጠው ሰው ተደርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 3:6
ድቅድቅ ጨለማ ይያዘው
ይህ ጨለማ የተገለጸው ምሽቱን እንደሚይዝና እንደሚጨብጥ አንድ ሰው ተደርጎ ነው። "ከባድ ጨለማ ጨርሶ ያጥፋው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጥቅጥቅ ጨለማ
"ጥልቅ ጨለማ" ወይም "ድፍን ጨለማ"
እርሱን ደስ አይበለው
"እርሱን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢዮብ የተወለደበትን ወይም የተጸነሰበትን ምሽት ነው። ኢዮብ የተጸነሰበት ምሽት የተገለጸው ደስታ ማግኘት እንደማይገባው ሰው ተደርጎ ነው። "ያ ምሽት ከቀኖች መሀል ተለይቶ ይጥፋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አይቆጠር/ወደ ቁጥር አይምጣ
ምሽቱ የተገለጸው መራመድ የሚችል ሰው ተደርጎ ነው። "ማንም በቁጥር ውስጥ አስገብቶ አይቁጠረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ያ ቀን መሃን ይሁን
ኢዮብ የተወለደበት ምሽት እንዲት ሴት ሆኖ ተገልጸዋል። "በዚያ ምሽት አንድም

ልጅ አይወለድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የደስታ ድምጽ ወደ እርሱ አይምጣ/አይሰማበት

እዚህ ስፍራ ኢዮብ የተወለደበት ምሽት የተገለጸው በዚያ ዕለት ወንድ ልጅ በመወለዱ ደስ የተሰኘ ሰው እንደነበር ተደርጎ ነው። "ወንድ ልጅ ሲወለድ የተሰማውን የደስታ ጩኸት ድምጽ/እልልታ ማንም አይስማው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የደስታ ጩኸት ደረሰ

እዚህ ስፍራ ድምጽ የሚለው ሚገልጸው ደስተኛ የሆነን ሰው ነው። "በእርሱ ማንም ደስተኛ አይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 3:8

ሌዋታንን መቀስቀስ የሚችሉ

እዚህ ስፍራ ኢዮብ ጥፋትን በማስፋፋት ሌዋታንን ሳይቀር ለመቀስቀስ ይችሉ ይሆናል የሚላቸውን ጠንቆዮችን እና አስማተኞችን እያመላከተ ሊሆን ይችላል። ሌዋታን ሁሉንም አይነት ጥፋት፣ ስርአት ማጣትና ምስቅልቅል ያደርሳል ተብሎ የሚታሰብ በቅርብ ምስራቅ አገራት አፈታሪክ ውስጥ የሚታወቅ እንስሳ ነበር።

የዚያን ዕለት የንጋት ከዋከወበት ይጨልሙ

ይህ የሚያመለክተው ብዙውን ጊዜ ንጋት ላይ የሚታዩትን ፕላኔቶች ነው። "ከዚያን ቀን ከሚፈነጥቀው ብርሃን አስቀድሞ የሚታዩ ከዋክብት ይጨልሙ"

ያ ቀን ብርሃን ቢፈልግን አንዳች አያግኝ

የኢዮብ ልደት ቀን የተገለጸው አንዳች ነገር እንደሚፈልግ ሰው ተደርጎ ነው። "ያ ቀን ብሃንን ተስፋ ቢያደርግም፣ ነገር ግን አንዳች አያግኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጋት ሽፋሽፍቶች አይመልከቱ

ንጋቱ የተገለጸው እንደ ሰው ሁሉ ሽፋሽፍቶች እንዳሉት ተደርጎ ነው። "የንጋቱን የብርሃን ፍንጣቂ አይመልከት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምክንያቱም የእናቴን ማህጸን አልዘጋምና

ማህጸን የተገለጸው በሮች እንዳሉት መያዣ ተደርጎ ነው። "ምክንያቱም ያ ቀን የእናቴን ማህጸን አልዘጋምና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምክንያቱም ከዐይኖቼ ችግርን አላራቀምና

እዚህ ስፍራ የኢዮብ ልደት ቀን የተገለጸው አንድን ነገር ሊደብቅ እንደሚችል ሰው ተደርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዐይኖቼ

እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው የሚወክለው የሚመለከትባቸውን ሰው ነው። "ከእኔ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 3:11

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ የንባብ ክፍል ኢዮብ የተለያዩ ተከታታይ ሃሳቦችን ለማቅረብ የሚጠይቃቸውን አራት ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎችን ይይዛል

ከማህጸን ሳልወጣ ሞቼ በቀረሁ?

"ለምን በምወለድበት ጊዜ ሳልሞት ቀረሁ?" ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው የተወለደበትን ቀን ለመርገን እና ጭንቀቱን ለመግለጽ ነው። "ምነው በተወለድኩበት ቀን በሞትኩ ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ምነው እናቴ በወለደችኝ ቀን ነፍሴን ሳልሰጥ ቀረሁ?

ኢዮብ ይህንን የሚለው በህይወት መወለድ አልነበረብኝም ለማለት ነው። "ምነው ከማህጸን በመጣሁበት ሰአት በሞትኩ ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ነፍሴን ብሰጥ

ይህ ሞትን ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ጉልበቶቿ ታቀፉኝ

ይህ ምናልባት የኢዮብን እናት ጭኖች ሊያመለክት ይችላል። የእናቱ ጉልበቶች የተገለጹት አዲስ የተወለደን ህጻን እንደሚቀበሉ ሰዎች ተደርጎ ነው። "እኔን የሚታቀፉ የእናት ጭኖች/ጉልበቶች ባይኖሩ በመደድኩ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አጠባቸው ዘንድ ስለምን የእናቴ ጡቶች ተቀበሉኝ?

የኢዮብ እናት ጡቶች የተገለጹት አዲስ የተወለደን ህጻን እንደሚቀበሉ ሰዎች ተደርጎ ነው። "የምጠባቸው ጡቶች ባይኖሩ በወደድኩ " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 3:13

አሁን በጸጥታ ባረፍኩ ነበር። በዚህን ጊዜ ተኝቼ በእረፍት ላይ በሆንኩ ነበር።

ኢዮብ ሁለቱን ዐረፍተ ነገሮች የተጠቀመው ከነጭርሱ ሳይወለድ ቢቀር ኖሮ ወይም በሚወለድበት ሰአት ሞቶ ቢሆን ኖሮ ምን ይሆን እንደነበር ለማሰብ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ የሚሉትን ይመልከቱ)

በሰላም እንቀላፋ ነበር

ኢዮብ ከላይ እንደተጠቀሰው ሳይሆን ስለቀረው ነገር ግን ባለፈው ዘመን ሊሆን ይችል ስለነበረው ነገር ያሰላስላል። "በፀጥታ በተኛሁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በፀጥታ መተኛት

"መተኛት፣ ማረፍ፣ በሰላም"

በዕረፍት መሆን

እዚህ ስፍራ "ዕረፍት" ማለት በሰላም መተኛት ማለት ሲሆን ነገር ግን ኢዮብ የገጠመውን ስቃይ አይኖረውም ነበር ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከምድር ነገሥታት እና አማካሪዎች ጋር

"ከነገሥታት እና አማካሪዎቻቸው ጋር"

Job 3:15

አጠቃላይ መረጃ

ኢዮብ ከመወለዱ አስቀደሞ ስለመሞቱ ያለውን ሀሳብ ይቀጥላል።

ወይ አተኛ ነበር...ብርሃን በፍጹም እንዳላየ

ይህ ሊሆን የሚችል ነገር ግን ያልሆነ ነገርን ይገልጻልለለ (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከልዑላን ጋር አርፍ ነበር

" ከልዑላን ጋር አርፍ ነበር" በዚህ ሀረግ፣ "መተኛት" እና "ማረፍ" የሚሉት ቃላት በትሁት/በተሻለ አገላለጽ "ከዚያ ወዲያ በህይወት አለመኖር" የሚሉ ናቸው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

በአንድ ወቅት ወርቅ የነበራቸው፣ ቤቶቻቸውንም በብር የሞሉ

ኢዮብ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን የተጠቀመው እየተናገረ የሚገኘውን ነገር ለማጉላት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወይም ምናልባት ብርሃን ፈጽሞ አይቶ እንደማያውቅ፣ ሞቶ የተወለደ ጭንጋፍ እሆን ነበር

ኢዮብ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን የተጠቀመው እየተናገረ የሚገኘውን ነገር ለማጉላት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞቼ በተወለድሁ

"በእናቴ ማህጸን ሳለሁ በሞትኩ"

ብርሃን ፈጽሞ እንዳላየ ጨቅላ

"እንዳልተወለዱ ህጻናት"

ጨቅላ ህጻናት

"ህጻናት" ወይም "በጣም ትንንሽ ልጆች"

Job 3:17

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢዮብ ንግግሩን ከሞት ወደ ከሞት በኋላ ያለ ህይወት ይለውጠዋል።

በዚያ ክፉዎች ማስቸገር ያቆማሉ፤ በዚያ የደከሙ በዕረፍት ላይ ይሆናሉ።

ኢዮብ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የተጠቀመው የተጨቆኑ ከመከራ እንደሚያርፉ አጉልቶ ለማሳየት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያ የክፉዎች ማወክ ያበቃል

ኢዮብ እየተናገረ የሚገኘው ሰዎች በምድር መኖር ካቆሙ በኋላ ስለሚሄዱበት ስፍራ ነው። "ክፉ ሰዎች ችግር ማድረሳቸው በሚያበቃበት በዚያ ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የባሪያ አሳዳሪዎች/ገዢዎች ድምጽ

እዚህ ስፍራ "ድምጽ" የሚለው የባሪያ ጌቶች በባሪያዎቻቸው ላይ ያላቸውን ሀይል የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ከእንግዲህ ወዲያ በባሪያ ገዢዎች ቁጥጥር ስር አይሆኑም" በሚለው ውስጥ

እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ታናናሾች እና ታላላቆች
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን "ሁሉም ሰው፣ ደሃውም ሆነ ባለጸጋው" የሚል ትርጉም አለው። (ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)
አገልጋይ ከጌታው ነጻ ነው
ከዚያ በኋላ አንድ አገልጋይ ጌታውን ለማገልግል አይገደድም
Job 3:20
በመከራ ውስጥ የሚኖር ለምን ብርሃን ያያል? ነፍሱ የተመረረች ለምን ህይወት ይሰጠዋል?
ሁለቱ የኢዮብ ጥያቄዎች በመሰረቱ አንድ አይነት ናቸው። በመከራ ውስጥ የሚገኙ ለምን በህይወት እንደሚቀጥሉ ይገረማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በመከራ ውስጥ የሚኖር ለምን ብርሃን ይሰጠዋል?
እዚህ ስፍራ ኢዮብ ሰዎች ለምን በህይወት ቆይተው እንደሚሰቃዩ በመገረም ይጠይቃል። "እግዚአብሔር ስለምን በመከራ ውስጥ ለሚኖረው ህይወት እንደሚሰጠው ሊገባኝ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ብርሃን
እዚህ ስፍራ ብርሃን የሚወክለው ህይወትን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የተደበቀ ሀብት....በነፍሱ ለተመረረ ለምን ህይወት ይሰጠዋል የተደበቀ ሀብት?
"እግዚአብሔር ለመከረኛው ሰው ለምን ህይወት ይሰጠዋል?" "እግዚአብሔር እጅግ ሀዘንተኛ ለሆነ ሰው ለምን ህይወት እንደሚሰጠው አይገባኝም… የተደበቀ ሀብት…" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ሞትን እየተመኘ ለማያገኘው ሰው
እዚህ ስፍራ ሞት የተገለጸው ወደ አንድ ሰው እየመጣ እንሚገኝ ቁስ ነው። "ለመኖር ለማይፈልግ ሰው፣ ነገር ግን አሁንም በህይወት ለሚገኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የከበረ ሀብትን በቁፋሮ ከሚፈልግ ሰው ይልቅ ሞትን ለሚፈልግ ሰው
ሞትን ተስፋ የሚያደርግ ሰው የተገለጸው የተቀበረ ውድ ሀብትን ለማግኘት እንደሚቆፍር ሰው ተደርጎ ነው። "የተደበቀ ውድ ሀብትን ከሚፈልግ ሰው ይልቅ መሞትን በብርቱ የሚፈልግ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መቃብርን ሲያገኝ እጅግ ደስ ለሚሰኝ ለምን ብርሃን ይሰጠዋል
እዚህ ስፍራ ኢዮብ ጥያቄ የሚጠይቀው ዐረፍተ ነገር ለማብጀት ነው። "ሰውየው ሞቶ መቀበር እጅግ ደስ የሚያሰኘው ከሆነ እግዚአብሔር ለዚያ ሰው መኖርን ለምን እንደሚፈቅድ አይገባኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በጣም ደስ የሚሰኝ እና ደስተኛ የሆነ
"በጣም ደስ የሚሰኝ" የሚለው ሀረግ "ደስተኛ የሆነ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለቱ አገላለጾች በአንድነት ሆነው የደስተኝነትን መጠን ያጎላሉ። "እጅግ ደስ የተሰኘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
መቃብርን ሲያገኝ
ይህ ሞትን ሻል ባለ መንገድ መግለጫ ነው። "በሚሞትበት እና ሊቀበር በሚችልበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
መቃብር
እዚህ ስፍራ መቃብር የሚወክለው ሞትን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 3:23
መንገዱ ለተደበቀችበት እግዚአብሔር ላጠረበት ሰው፣ ለምን ብርሃን ተሰጠው?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ዐረፍተ ነገር ለማብጀት ነው። "እግዚአብሔር ለሰው ህይወት ከሰጠው በኋላ የወደፊቱን ነጥቆ ሊያጥርበት አይገባም" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ለሰው ለምን ብርሃን ተሰጠው
እዚህ ስፍራ ብርሃን የሚወክለው ህይወትን ነው። "እግዚአብሔር ለምን አንድን ሰው በህይወት ያኖረዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መንገዱ ለተደበቀችበት
እዚህ ስፍራ ኢዮብ አስቀድሞ ስለማያውቀው ስለ ወደፊቱ እግዚአብሔር እንደሰወረበት አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር መንገዱን ያጠረበት
እዚህ ስፍራ በችግር ውስጥ መሆን እና አደጋዎች የተገለጹት በጠባብ ስፍራ እንደመወሰን ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ትካዜ ምግብ ሆኖኛል፣ የስቃይ ጩኸቴ/መቃተቴ እንደ ውሃ ይፈሳል
ኢዮብ ጭንቀቱን በሁለት መንገዶች ይገልጻል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ትካዜ ምግብ ሆኖኛል
"ከመመገብ ይልቅ፣ ሀዘንተኛ ሆኛለሁ"
የስቃይ ጩኸቴ/መቃተቴ እንደ ውሃ ይፈሳል
እንደ ሀዘን የመሰሉ የስነምግባር ባህሪያት እና ስሜቶች ብዙውን ጊዜ በውሃ ይገለጻሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 3:25
የፈራኋቸው ነገሮች በላዬ መጡብኝ፣ የፈራሁት ደረሰብኝ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "በጣም ሰግቻለሁ" ወይም "እጅግ የፈራሁት ነገር ደረሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ተዘልዬ የተቀመጥኩ አይደለሁም፣ አላረፍኩም፣ ደግሞም እረፍት የለኝም
ኢዮብ ጭንቀቱን በሶስት የተለያዩ ሀረጋት ይገልጻል። "በጣም ሰግቻለሁ" ወይም "በስሜትም በአካልም ተሰቃይቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

# Chapter 4
## Job 4:1
ኤልፋዝ
ኤልፋዝ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ቴማናዊ
ቴማናዊ ከተምና ነገድ የሆነ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ትታገሳለህን?
ኤልፋዝ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው በዐረፍተ ነገር ሃሳቡን ለመግለጽ ነው። "በእርግጥ ልትታገስ ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ትታገሳለህን?
"ይህ ነገር ያስከፋሃልን?"
ነገር ግን ማን ከመናገር ራሱን ሊገታ ይችላል?
ኤልፋዝ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው የወዳጁን መጨነቅ እየተመለከተ ማንም ዝም ማለት አይችልም ለማለት ነው። "ወዳጄ አንተ በምትገኝበት ሁኔታ ሆኖ ማንም ከመናገር ራሱን መግታት አይችልም" ወይም "አንተ በጭንቀት ውስጥ ሆነህ እኔ ከመናገር ዝም ማለት አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ብዙዎቹን አስተምረሃል፣ የላሉ እጆችን አጽንተሃል
ይህ ስንኝ አንድን ሃሳብ በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይገልጻል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ የላሉ እጆችን አጽንተሃል
እዚህ ስፍራ "የላሉ/ደካማ እጆች" የሚለው የሚወክለው እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎችን ነው። "ሌሎች እርዳታ በሚፈልጉ ጊዜ አንተ ረድተሃቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
## Job 4:4
አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው ሁለት ሃሳቦችን በመጠቀም አንድ ሃሳብ ለመመስረት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን በእያንዳንዱ ሀረግ ውስጥ የሚጠቀመው 1) በቀደመው ጊዜ ኢዮብ ለሌሎች የሰጠውን ድጋፍ፣ 2) በአሁኑ ችግሩ ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ፣ እና 3) በእግዚአብሔር ፊት የእርሱን ንጽህና ለማጉላት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ትደግፍ
የተበረታታ አንድ ሰው የተገለጸው ወደ ታች ከመውደቅ እንደተጠበቀ ተደርጎ ነው
መውደቅ
እዚህ ስፍራ ተስፋ መቁረጥ የተገለጸው ወደ ታች መውደቅ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የተብረከረኩ ጉልበታችን ታጠነክር ነበር
እዚህ ስፍራ ተስፋ መቁረጥ የተገለጸው ደካማ ጉልበቱ ተሸክሞ ሊያቆመው እንዳልቻለ አንድ ሰው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አሁን ግን መከራ ወደ አንተ መጥቷል
እዚህ ስፍራ መከራ የተገለጸው ወደ አንድ ሰው እንደሚመጣ ቁስ ተደርጎ ነው። "ነገር ግን አንተ አሁን ከውድቀት የተነሳ ትጨነቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ዝለሃል
"አንተ ተስፋ ቆርጠሃል"
የምትፈራው
"አንተ እግዚአብሔርን ማክበርህ"
ፍርሃትህ ልበ ሙሉነትህ አይደለምን፣ ደግሞስ የመንገዶችህ ጽናት ተስፋህ አይደለምን?
ኤልፋዝ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቀው ኢዮብን የምትሰቃየው ከኃጢአትህ የተነሳ ነው ሊለው ፈልጎ ነው። "ሁሉም ሰው አንተ እግዚአብሔርን እንደምታከብር ያስባል፣ ሁሉም ሰው አንተ እውነተኛ ሰው እንደሆንክ ያስባል። እነዚህ ነገሮች ግን እውነት ሊሆኑ አይችሉም፣ ምክንያቱም አንተ እግአብሔርን ተስፋ ማድረግ አቁመሃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ፍርሃትህ
ኤልፋዝ የኢዮብን እግዚአብን መፍራት ማለቱ ነው። "የአንተ እግዚአብሔርን መፍራት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መንገዶችህ
እዚህ ስፍራ "መንገዶችህ" የሚለው የሚወክለው "ባህሪህ፣" "አደራረግህ፣" የሚለውን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 4:7
ንጹህ ሆኖ ሳለ የጠፋ ማን ነው?
ኤልፋዝ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ ህይወቱን ከኃጢአት እንዲመረምር፣ የእግዚአብሔርን ጻድቅ ፈራጅነት እንደዚሁም ሁሉን ሊያጣ የቻለበትን ምክንያት እንዲ ሊያነሳሳው ነው። "ንጹህ ሆኖ ሳለ የጠፋ ማንም የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ትክክለኛ ሰዎች መች ተቆርጠው ጠፍተው ያውቃሉ?
ይህም ጥያቄ ሃሳብን ለማቅረብ የተሰነዘረ ነው፤ በአድራጊ ዐረፍት ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ትክክለኛ ሰው ሆኖ ሳለ ተቆርጦ የቀረ ሰው የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ተቆርጦ የጠፋ
እዚህ ስፍራ ተቆርጦ መጥፋት የሚለው የሚገልጸው መደምሰስን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኩልነት ማጣትን ያርሳል... ችግርን ይዘራል... ያጭዳል
እዚህ ስፍራ የማረስ እና መዝራት ድርጊቶች የመወከሉት ለሌላው ሰው ለችግር ምክንያት መሆንን ነው። የማጨድ ድርጊት የሚወክለው አንድ ሰው ራሱ ባመጣው ችግር ምክንያት በመከራ መሰቃየትን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር እስትንፋስ ይጠፋሉ፣ በቁጣው መአት ይበላሉ
ጸሐፊው አንድን ሀሳብ ሁለት አይነት አገላለጽ በመጠቀም ያብራራል። ይህ በዕብራውያን ስነግጥም ትኩረት ለመስጠት፣ ሀሳብን ግልጽ ለማድረግ፣ ለማስተማር ወይም ለእነዚህ ለሶስቱም ጉዳዮች የሚውል ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር እስትንፋስ
ይህ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የመስጠት ድርጊት የሚወክል ሊሆን ይችላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የቁጣው መአት
ይህ አገላለጽ የሚጠቁመው አንዳንድ ጊዜ ሰው በጣም ሲቆጣ በአፍንጫው በከባዱ የሚተነፍሰውን አተነፋፈስ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የቁጣ... አተነፋፈስ
አንደኛው ቃል በሌላኛው ላይ ይመሰረታል። ውጤቱን ከፍ የሚያደርግ ትርጉሞችን በመጠቀም አንድን ነጥብ ይገልጻሉ። "ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ትንፋሽ ይሞታሉ፤ የቁጣው አውሎ ነፋስ ያጠፋቸዋል።" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይጠፋሉ... ይበላሉ
ሁለተኛው ሀረግ በመጀመሪያው ላይ የተመሰረተ ነው። ሁለቱም ተመሳሳይ ነጥብን ይገልጻሉ። "ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ትንፋሽ ይሞታሉ፤ የቁጣው አውሎ ነፋስ ያጠፋቸዋል።" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ይበላሉ
እዚህ ስፍራ መፈጀት ወይም መበላት የሚለው የሚወክለው መገደልን ነው።
Job 4:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው በእነዚህ ስንኞች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን የሚጠቀመው፣ በተለያየ አገላለጽ እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን የሚያጠፋ መሆኑን አጉልቶ ለማሳየት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንበሳ ግሳት፣ የተቆጣ አንበሳ ድምጽ፣ የአንበሳው ጥርሶች ¬- ተሰብረዋል።
እዚህ ስፍራ የአንበሳ ግሳት፣ ድምጹ፣ እና የጥርሱ መሰበር ክፉዎች እንደሚጠፉ መገለጫ ሆኖ አገልግሏል። ( ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ተሰብረዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ነገር ሰብሮቸዋል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ያረጀ አንበሳ የሚያድነው በማጣቱ ይጠፋል፣ የአንበሳ ደቦሎች በየስፍራው ይበተናሉ
ኤልፋዝ ያረጀ አንበሳን በረሃብ መሞት እና የአንበሳ ቤተሰብ የመበተንን ዘይቤያዊ አገላለጾች የተጠቀመው ክፉዎች የሚጠፉ መሆኑን ለመግለጽ ነው።
የአንበሳ ደቦሎች ተበተኑ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የአንበሳ ደቦሎችን አንድ ነገር በተናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 4:12
አሁን አንድ ነገር በድብቅ ወደ እኔ መጥቷል... ስለዚያም ነገር ጆሮዎቼ ሹክሹክታ ሰምተዋል
እነዚህ ሀረጋት አንድን ሀሳብ በተለያየ መንገድ ይገልጻሉ። ኤልፋዝ በሹክሹክታ መልእክት የመቀበሉን ሀሳብ ያስተላልፋሉ። የዚህ አይነቱ መደጋገም በዕብራውያን ሰነ ግጥም ውስጥ ትኩረት ለመስጠት፣ ለማስተማር ወይም ሃሳብን ግልጽ ለማድረግ አዘውትሮ በተግባር ላይ ይውላሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሌት በራዕይ
"ህልም"
በሰዎች ላይ ከባድ እንቅልፍ ሲወድቅ
"ሰዎች ከባድ እንቅልፍ ሲተኙ"
Job 4:14
አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው በእነዚህ ቁጥሮች የኤልፋዝን ስጋት ለማጉላት አንድን ሀሳብ የተለያዩ አገላለጾች በመጠቀም ለማስተላለፍ ንጽጽራዊ ዘይቤን ይጠቀማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ በላዬ መጡ
እዚህ ስፍራ ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ የተገለጹት ወደ አንድ ሰው እንደሚመጡ ቁሶች ተደርገው ነው። "መፍራት እና መንቀጥቀጥ ጀመርኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰውነቴ ፀጉር ቆመ
ይህ ታላቅ ፍርሃትን ያመለክታል
የሰውነቴ ፀጉር
"በሰውነቴ ላይ የሚገኝ ፀጉር"
Job 4:16
አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው በቁጥር 17 ላይ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን የተጠቀመው አንድን ሀሳብ በሁለት የተለያዩ አገላለጾች በእግዚአብሔር ፊት የሰውን ንጹህ አለመሆን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ቅርጽ/መልክ በፊቴ ነበረ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"አንድ ነገር በዐይኔ ፊት ነበር፣" "አንድ ነገር ተመለከትኩ"

ደግሞም ሰማሁ

"ከዚያም ሰማሁ"

ሟች የሆነ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ይልቅ ጻድቅ ይሆናልን?

ኤልፋዝ ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው ኢዮብ "ራሴን ከእግዚአብሔር ይልቅ ጻድቅ አድርጌ ቆጥሬያለሁን?" ብሎ እንዲጠይቅ ለማድረግ ወይም "ሟች የሆነ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ይልቅ ጻድቅ ሊሆን አይችልም" እንዲል ለማድረግ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰርሱን ያበጀው

"የእርሱ ፈጣሪ"

Job 4:18

በሸክላ ቤት ውስጥ የሚኖሩ፣ መሰረታቸው አፈር የሆነ

ይህ ከምድር አፈር የተፈጠሩና አካላቸው እንደቤቶች የሆነ፣ ከሸክላ የተሰሩ መሰረታቸው ትቢያ የሆነ ሰዎችን በዘይቤያዊ መንገድ መግለጫ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከብል ይልቅ ፈጥነው የሚጨፈለቁ

የዚህ ዘይቤያዊ አነጋገር ትረጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት 1) "እግዚአብሔር ብልን ሊጨፈልቅ የሚችለውን ያህል በቀላሉ የሚያጠፋቸው" ወይም 2) "ዘመናቸው የብልን እድሜ ያህል አጭር የሆነ።" (ዘይቤያዊ አገላለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 4:20

አጠቃላይ መረጃ:

እነዚህ ቁጥሮች ቀደም ሲል ያገለገሉት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ ቀጣዮች ናቸው፣ እነዚህ ስፍራ ሰዎች በድንገት ጥበብ ሳያገኙ እና ከሌሎችም ይሁንታ ሳይኖራቸው መሞታቸው በተለያየ መንገድ ትኩረት ተሰጥቶታል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀንና በምሽት መሃል ይጠፋሉ

ይህ የሚያመለክተው በፍጥነት የሚሆንን ነገር ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ጠፍተዋል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እነርሱ ሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የድንኳኖቻቸው ማሰሪያዎች/ገመድ ከመሃላቸው አልተነቀለምን?

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጠላቶቻቸው የድንኳኖቻቸውን ማሰሪያ ከመሃላቸው ስበው አልጣሉምን?" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የድንኳኖቻቸው ማሰሪያ/ገመድ

እዚህ ስፍራ የድንኳኖች ማሰሪያ የሚወክለው ድንኳኖችን ነው። አንዳንድ ጊዜ የአንድ ሰው ቤት እና ቤተሰብ እንደ ድንኳኑ ተደርጎ ይገለጻል፤ ይህ ሰውየው ያለውን ንብረት ሁሉ የሚወክል ሊሆንም ይችላል። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 5

Job 5:1

ወደትኛው ቅዱስ ፊትህን ትመልሳለህ?

ኤልፋዝ ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው ኢዮብ ለእርዳታ ፊቱን ሊያቀና የሚችልበት ማንም እንደሌለ ለመግለጽ ነው። "ፊትህን ወደ እርሱ ልትመልስ የምትችለው ቅዱስ አለን?" ወይም "እርዳታ ፍለጋ ወደ እርሱ ፊትህን ልታቀና የምትችልበት አንዳችም ቅዱስ የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅዱስ የሆነ

ይህ መልአክንም ሆነ ሌላ መንፈሶች፣ አንድ እጅግ ሉዓላዊ የሚባልን ማንነት ያመለክታል።

በቅናት እዚህ ግባ የማይባለውን/ሞኙን መግደል

"በሞኝነት እና በስሜት በመገፋፋት የሚያደርገውን ማናቸውንም በቅናት መግደል"

እዚህ ግባ የማይባል... ሞኝ ሰው

ይህ የሚያመለክተው ማናቸውንም የማይረባ ሰው እና ማናቸውንም ሞኝ ሰው ነው። (የስማዊ ሀረግ ክፍል የሚለውን ይመልከቱ)

ሞኝ ሰው በሞኝነቱ ስር ይሰዳል

እዚህ ስፍራ ሞኝ ሰው የተገለጸው እርሱ ራሱ ተክል እንደሆነ፣ ምናልባትም በጊዜ ውስጥ ይበልጥ ሞኝ እየሆነ እንደሚሄድ ነው። "ሞኝ ሰው በሞኝነት ስር እየሰደደ ይሄዳለል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቱ

ይህ የሰውየውን ቤተሰብ እና ንብረቱን ሁሉ ያመለክታል

Job 5:4

አጠቃላይ መረጃ

ይህ ቁጥር ቀደም ሲል ያገለገለ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ ቅጥያ ነው፣ እዚህ ስፍራ የሞኝ ሰው ልጆች በፍጹም ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዳልሆነ በተለያዩ መንገዶች በትኩረት ተገልጽዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ልጆች ደህንነትን/ጥበቃ ከማግኘት የራቁ ናቸው

"የእርሱ" የሚለው የሚያመለክተው በኢዮብ 5፡2 ላይ የሚገኘውን ሞኙን ሰው ወይም ሞኝ ሰዎችን ነው። "ልጆቻቸው ፈጽሞውን ደህንነታቸው የተጠበቀ አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ይፈጫሉ

እዚህ ስፍራ መፈጨት የሚለው የሚወክለው በፍትህ አደባባይ በጭቆና ስር መሆንን እና ጥቅምን መቀማትን ነው። ይህ ሀሳብ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው ያደቅቃቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የከተማ በር

የከተማ በር፣ ክርክሮች የሚፈቱበት እና ፍትህ የሚሰጥበት ስፍራ ሆኖ ያገለግል ነበር።

የሚታደጋቸው ማንም የለም

"የሞኝ ሰዎችን ልጆች ከመከራቸው ለማውጣት ሊረዳቸው የሚችል ማንም የለም"

ሌላው ቀርቶ ከእሾህ መሃል ይህን ይወስዳሉ

ምናልባት ይህ የሚያመለክተው የእሾህ ተክል ከመኖሩ የተነሳ የከፋው ተክል የሚበቅልበትን ስፍራ ነው

ሃብታቸውን ተጠምቶ የሚፈልግ

እዚህ ስፍራ ስግብግብ ሰዎች የተገለጹት እንደ ተጠሙ ሲሆን፣ የሞኝ ሰው ሃብት ደግሞ እነርሱ ሊጠጡት እንደሚችሉት ነገር ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 5:6

ችግር ከአፈር ውስጥ አይወጣም፣ አሊያም መከራ ከምድር አይበቅልም

እዚህ ስፍራ ችግር እና መከራ የተገለጹት ተክል እንደሆኑ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእሳት ፍንጣሪ ወደ ላይ እንደሚወጣው ሁሉ የሰው ልጅ የተወለደው ለመከራ ነው

ከእሳት ፍንጣሪው ወደላይ እንደሚወጣ ሁሉ ለሰው ልጆችም አንዴ ከተወለዱ በኋላ ችግር ማጋጠሙ ተፈጥሯዊ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 5:8

አጠቃላይ መረጃ:

በእነዚህ ቁጥሮች፣ ኤልፋዝ ንግግሩን ከኢዮብ 4፡1 ጀምሮ ይቀጥላል። ጸሐፊው ኢዮብ አስደናቂ ነገሮች የሚያደርገውን እግዚአብሔርን መለመን እንደሚገባው አጉልቶ ለማሳየት አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ አገላለጾች በመጠቀም ለማስተላለፍ በእያንዳንዱ ቁጥር ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቅ እና የማይመረመሩ ነገሮች፣ ቁጥር የሌላቸው አስደናቂ ነገሮች

"ከመረዳት ባሻገር የሆኑ ታላላቅ ነገሮች፣ ሊቆጠሩ የማይችሉ አስደናቂ ነገሮች"

የማይመረመሩ ነገሮች

ይህ የሚያመለክተው የሰው ልጅ ሊረዳቸው የማይችሉ ነገሮችን ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቅ እና የማይመረመሩ ነገሮች

እዚህ ስፍራ ጸሐፊው "እና" በሚል የተያያዙ ሁለት ራሳቸውን የቻሉ ቃላትን የሚጠቀመው የእግዚአብሔርን ስራ ታላቅነት ለማጉላት ነው። "በታላቅነት ጥልቅ/ መሰረታዊ የሆኑ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሄንዲያዲስ/ሁለት ቃላት 'እና' በሚል አያያዥ ቃል የሚገኛኙበትና አንድን ጥልቅ ሀሳብ ለመግለጽ የሚያገለግል ዘይቤያዊ አነጋገር)

አስደናቂ ነገሮች



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"አስገራሚ ነገሮች" ወይም "አስደናቂ ነገሮች"

Job 5:11

አጠቃላይ መረጃ፡

ጸሐፊው በእያንዳንዱ ቁጥር ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ መግለጫዎችን በመጠቀም የሚያስተላልፈው እግዚአብሔር የተጠቁትን ከወደቁበት እንደሚየነሳ እና ተንኮለኞችን እንደሚያወርድ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይህንን የሚያደርገው ዝቅ ባለ ስፍራ ያሉትን ከፍ ለማድረግ ነው

የትሁታን መጎዳት የተገለጸው በዝቅተኛ ስፍራ እንደ ተቀመጡ ተደርጎ ነው። እግዚአብሔር በሚታደጋቸው ጊዜ፣ ክብርን ይቀበላሉ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ከፍ ተደርገው በከበረ ስፍራ እንደተቀጡ ተደርጎ ይነገርላቸዋል። "እግዚአብሔር ይሰቃዩ የነበሩ ትሁታንን ለማዳን እና እነርሱን ለማክበር ይህንን ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እቅዳቸውን ይሰብራል

እዚህ ስፍራ የተንኮለኞችን እቅድ ማስቆም የተገለጸው እነርሱ በአካል እንክት ተደርገው እንደሚሰበሩ ነገሮች ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ተንኮለኛ ሰዎችን በራሳቸው ክፉ ስራ ያጠምዳቸዋል

እዚህ ስፍራ ተንኮለኞችን በራሳቸው ክፉ ስራ እንዲጨነቁ ማድረግ የተገለጸው እነርሱን በወጥመድ እንመያዝ ተደርጎ ነው። የራሳቸው ድርጊቶች የተነገሩት እነዚያ ወጥመዶች እንደሆኑ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠመዝማዛ ሰዎች

እዚህ ስፍራ በብልጣብልጥነት የሚደረግ ክፋት የተገለጸው ጠመዝማዛ መሆን ተደርጎ ነው። "ብልጣብልጥ የሆኑ" ወይም "ቅን ያለሆኑ" ወይም "ብልጦች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 5:14

አጠቃላይ መረጃ፡

ጸሐፊው በእያንዳንዱ ቁጥር ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ መግለጫዎችን በመጠቀም የሚያስተላልፈው እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን እንሚያዋርድ እና ድሆችን እንደሚያድን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀን ብርሃን ጨለማ ይገጥማቸዋል

እዚህ ስፍራ ለእግዚአብሔር የማይመቹ ክፉዎች እና ጨካኝ ሰዎች ፀሐይ በአናት ትክክል ሳለች፣ በቀን ብርሃን እነርሱ ግን በጨለማ ውስጥ እንደሚገኙ ይናገራል። ማድረግ የሚፈልጉትን አንዳች ነገር ማድረግ አይችሉም፣ ምክንያቱም ማየት አይችሉም። "ተንኮለኞች፣ በእኩለ ቀን እንኳን በጨለማ ውስጥ ናቸው" (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ዳበሳ

እንደ ዐይነ ስውር ዙሪያን መዳሰስ

እኩለ ቀን

የቀኑ እኩሌታ፣ ፀሐይ በአናት ትክክል የምትሆንበትና ከፍተኛ ብርሃኗን የምትሰጥበት ጊዜ

እርሱ ግን ደሃውን ከአንደበታቸው ካለ ሰይፍ ያድነዋል

እዚህ ስፍራ ሰዎች የሚናገሯቸው ስድቦች እና ማስፈራሪያዎች በአንደበታቸው ላይ የሚገኝ ሰይፍ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጸዋል። "እርሱ ግን ደሃውን ከታላላቆች ማስፈራራት ያድነዋል" ወይም "እርሱ ግን ደሃውን ታላላቆች ሲያስፈራሩት ወይም ሰድቡት ይታደገዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህ አልባነት አንደበቷን ትዘጋለች

ፍትህ አልባ ሰዎች የተገለጹት መናገርን ማቆም ያለባቸው ተደርገው እና ራሱን ፍትህ አልባነትን ሆነው ነው። "ይህ ፍትህ አልባነት የራሷን አንደበት እንደምትዘጋ ያህል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 5:17

አጠቃላይ መረጃ፡

ጸሐፊው በቁጥር 18 እና 19 ላይ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ መግለጫዎችን በመጠቀም የሚያስተላልፈው የእግዚአብሔርን ቅጣት እና ፈውስ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ያስተካክላል... ሁሉን ቻይ የሆነው ይቀጣል

እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የቀረበው እንደሚያርም ወላጅ ወይም ልጅን እንደሚመራ ወላጅ ሆኖ ነው። እግዚአብሔር የሚያርመው ሰው የተባረከ ነው "እግዚአብሔር እርሱ የሚያርመውን ሰው በእርግጥም ተቀብሎታል"

አታቃል

"አትቃወም" ወይም "ጥቅም እንደሌለው ነገር አድርገህ አትቁጠር"

መቅጣት

"መምራት" ወይም "ማረም" ወይም "ስርአት ማስያዝ"

እርሱ ያቆስላል እርሱ ይጠግናል፣ እርሱ ያቆስላል ደግሞም የእርሱ እጆች ይፈውሳሉ

"እርሱ ቢያቆስልም እርሱ ይጠግናል፣ እርሱ ያደቃል የእርሱ እጆች ይፈውሳሉ"

እጆቹ ይፈውሳሉ

እዚህ ስፍራ "የእርሱ እጆች" የሚለው የሚገልጸው እግዚአብሔርን ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከስድስት ችግሮች ያድንሃል፤ በእርግጥ በሰባተኛው ችግር የትኛውም ክፉ አያገኝህም

ቁጥሮችን ከፍ እያደረጉ "ስድስት" እና "ሰባት" እንደሚለው መጠቀም ብዙ ብዙ ጊዜ የሚለውን ሀሳብ ይወክላል። "እርሱ ደግሞ ደጋግሞ ከችግር ያወጣሃል፣ በእርግጥ፣ ከጊዜ ጊዜ አንዳች ክፉ አይነካህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 5:20

አጠቃላይ መረጃ፡

በኢዮብ 5:19 የሚጀምረው "እርሱ" ከሚለው "አንተ" ወደሚለው የተዋላጠ ስም/ የስም ምትክ ሽግግር ማድረግ እስከ ኢዮብ 5፡29 ማለትም የኤልፋዝ ንግግር እስከሚያልቅበት ደረስ ይቀጥላል። በረሃብ ጊዜ ይቤዡሃል እዚህ ስፍራ ማዳን የተገለጸው መቤዠት፣ መልሶ መግዛት እንደሆነ ተደርጎ ነው። "በርሃብ ጊዜ እግዚአብሔር ከአደጋ ያድንሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰይፍ እጆች

እዚህ ስፍራ "እጆች" ምናልባት የሚወክለው ሰይፎችን ጨምሮ በመሳሪያ ጥቃት የሚያደርሱ ሰዎችን ሊሆን ይችላል። "ጥቃት የሚያደርሱ ሰዎች" ወይም "አንተን የሚያጠቁ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጥፋት

እዚህ ስፍራ "ጥፋት" የሚለው የሚያመለክተው በጠላት መደምሰስን ነው። "ያገኘህ ማንኛውም ጠላት ያጠፋሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በጥፋት እና ረሃብ ላይ ትስቃለህ

እዚህ ስፍራ "ሳቅ" የሚለው የሚገልጸው አለመፍራትን ነው። "ማናቸውንም የጥፋት አደጋ ወይም ረሃብ አትፈራም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምልክታዊ/ ትዕምርታዊ ቋንቋ የሚለውን ይመልከቱ)

የምድር አራዊት

ይህ የሚያመለክተው የዱር አራዊት ነው።"የዱር እንስሳት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 5:23

አጠቃላይ መረጃ፡

ጸሐፊው በእያንዳንዱ ቁጥር ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ መግለጫዎችን በመጠቀም ማቅረቡን የሚቀጥለው ደህንነትን ከተፈጥሮ ዓለም፣ ከቤት እና ከአንድ ሰው ትውልዶች ጋር በማያያዝ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በማሳህ ከሚገኙ ድንጋዮች ጋር ትዋዋላለህ

እዚህ ስፍራ በገበሬ ማሳ ውስጥ የሚገኙ ድንጋዮች የተገለጹት አንድ ሰው አብሯቸው የሚዋዋላቸው ሰዎች ተደርገው ነው። "በእርሻህ ውስጥ የሚገኙ ድንጋዮች በአንተ ላይ አንዳችም ችግር ላያመጡ ቃል እንደገቡ ሰዎች ይሆናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የዱር አራዊት

ይህ አደገኛ የዱር አራዊትን ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ድንኳንህ በሰላም እንዳለ ታውቃለህ

እዚህ ስፍራ "ድንኳን" የሚወክለው የአንድን ሰው ቤተሰብ፣ ቤቱን፣ እና ያለውን ሀብት ሁሉ ነው። "ቤተሰብህ፣ አገልጋዮችህ፣ እና ያለህ ሁሉ በሰላም መጠበቁን ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በረትህን ስትቃኝ አንዳች አይጎድልም
"ምሽት በረትህን ስትመለከት፣ መንጋህን በሙሉ በዚያ ታገኛለህ"
ዘርህ ታላቅ ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ዘር" የሚለው የሚወክለው የአንድን ሰው ትውልዶች ነው። "ዘርህ ብዙ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ትውልድህ በምድር ላይ እንዳለ ሳር ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ትውልድ" የሚለው የተገለጸው ታጭዶ እንደተከመረ ሳር ብዙ ተደርጎ ነው፤ ምናልባትም በብዙ እንዳደገ ሳር ተደርጎ ተገልጽዋል። "ትውልድህ እንደ ሚያድግ ሳር ብዙ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 5:26
እድሜ ጠግበህ ወደ መቃብር ትመጣለህ
"እጅግ አርጅተህ ትሞታለህ"
በጊዜው እንደሚሰበሰብ የእህል ነዶ
በዚህ ተነጻጻሪ ዘይቤ ሰብል የሚለው በሚገባ ደርሶ መታጨዱን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። በእርጅና እድሜው ሲሞት በጣም ደካማ አይሆንም ወይም ደግሞ ያለ ጊዜውም እንደማይሞት። (ቅጽ 1 የትርጉም ማብራሪያ) እና (ቅጽ 1 የተነጻጻሪ ዘይቤ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)
እነሆ፣ ይህንን ጉዳይ እኛ መርምረነዋል፤ ነገሩ ይህን ይመስላል፣ አድምጥ መርምረህ ድረስበት
"እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢዮብን ወዳጆች እንጂ ኢዮብን አይደለም። "እነሆ፣ እኛ ስለዚህ ጉዳይ አስበንበታል። የምነግርህን አድምጥና ነገሩ እውነት መሆኑን ተረዳ" (የሚያጠቃልል እና የማያጠቃልል "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 6
Job 6:1
ምነው ጭንቀቴ ቢመዘን፣ ስጋቴ በሚዛን ላይ ቢቀመጥ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው አንድ ሃሳብን፣ ይኸውም የኢዮብን መከራ ሸክም ለመግለጽ ሁለት የተለያዩ አገላለጾችን ይጠቀማል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "መከራዬን መመዘን ብችል፣ ደግሞም ስጋቴን ሁሉ በሚዛን ላይ ባስቀምጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
በሚዛን ላይ
"በመለኪያ ላይ"
ከባህር አሸዋ የከበደ ይሆናል
ኢዮብ የመከራውን ክብደት ከአሸዋ ክብደት ጋር ያነጻጽራል፤ ሁለቱም አንድን ሰው ማድቀቅ የሚችሉ ናቸው። "ጭንቀቴ እና ስጋቴ በባህር ዳር ካለ አሸዋ ይከብዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ንግግሬ የማያስገርሙ ነበሩ
"በግዴለሽነት ተናገርኩ" ወይም "በችኮላ ተናገርኩ"
Job 6:4
አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው በእያንዳንዱ ቁጥር አንድን ሃሳብ ለማስተላለፍ ሁለት የተለያዩ አገላለጾችን በመጠቀም የኢዮብን ከባድ መከራ ለማማረሩ መነሻ ምክንያት አድርጎ ለማጉላት ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ቀስቶች በእኔ ስጋ ውስጥ ናቸው
ይህ የኢዮብን መከራ የሚገልጽ ዘይቤ ነው። ብዙ መከራውን እግዚአብሔር በቀስቱ ገላውን እንደ ወጋበት ቀስት አድርጎ ያነጻጽረዋል። "መከራዬ ሁሉን ቻይ የሆነው ቀስቶችን ወደ አካሌ እንደወረወረ ያህል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ነፍሴ መርዝ ተጎነጨች
"ነፍሴ የቀስቱን መርዝ ጠጣች።" ይህ መርዝ ያለባቸው መሆኑን በማመልከት እና ኢዮብ በመንፈሱ ስቃዩ የተሰማው መሆኑን በመግለጽ በቀስቱ የተነገረውን ዘይቤ ይቀጥላል። መከራውን ሲናገር መንፈሱ መርዝ እንደጠጣ አድርጎ ይገልጻል። "በውስጠኛው ሰውነቴ የመርዛቸው ስቃይ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር አስጨናቂነት በእኔ ላይ በተራ ተሰልፎብኛል
እግዚአብሔር ብዙ ነገሮች ኢዮብን እንዲያስጨንቅ ማድረጉ የተገለጸው፤ የእግዚአብሔር ማሰጨነቅ ኢዮብን ለማጥቃት እንደ ተሰለፉ ወታደሮች ተደርጎ ነው። "በሰራዊት ውስጥ እንደሚገኝ ወታደር የእግዚአብሔር ማስጨነቅ ራሱን አሰልፎብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
የሜዳ አህያ ሳር እያለው ያናፋል ወይስ በሬ ድርቆሽ እያለው እምቧ ይላል?
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚያቀርበው ለማመረር ምክንያት እንዳለው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። "የሜዳ አህያ ሳር እያለው ካለ ምክንያት እንደማያናፋ ወይም በሬ ድርቆሽ/ገለባ እያገኘ በረሃብ እምቧ እንደማይል እኔም ምክንያት ባይኖረኝ ኖሮ ባላጉረመረምኩ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ማናፋት
አህያ የሚያሰማው ድምጽ
እምቧ ማለት
በሬ የሚያሰማው ድምጽ
ድርቆሽ/ገለባ
የእንስሳ ምግብ
ጣዕም የሌለው ካለ ጨው ሊበላ ይችላልን? ወይስ የእንቁላል ውሃ ይጣፍጣልን?
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ ባለበት ሁኔታ ደስ አለመሰኘቱን የሚያነጻጽረው ሰዎች ጣዕም የሌለውን ምግብ ካለመውደዳቸው ጋር ነው ወይም 2) ኢዮብ በወዳጆቹ ምክር ደስ አለመሰኘቱን የሚያነጻጽረው ሰዎች ደስ የማያሰኝን ምግብ ካለመውደዳቸው ጋር ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ጣዕም የሌለው ካለ ጨው ሊበላ ይችላልን? ወይስ የእንቁላል ውሃ ይጣፍጣልን?
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠቀመው የራሱን ደስ አለመሰኘት ለማጉላት ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። "በእንቁላል ውሃ ውሰጥ ጣዕም እንደሌለ፣ ጣዕም የሌለው ምግብ ካለ ጨው ሊበላ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ጣዕም የሌለው ሊበላ ይችላልን?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጣዕም የሌለውን መብላት ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 6:7
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ስለ መከራው መናገሩን እና መሞት መፈለጉን በገለጸ መጠን በእነዚህ ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱን መንካት አልፈልግም
"እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው መጥፎ ጣዕም ያላቸውን ምግቦች ነው።
እኔን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ለማድቀቅ
ይህ ማለት እግዚአብሔር እርሱ/ኢዮብ እንዲሞት ቢፈቅድ ማለቱ ነው። "ቢያደቀኝ እና እንድሞት ቢተወኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
ምነው ፈጥኖ እጆቹን ቢያነሳ እና ከዚህ ህይወት ቢቆርጠኝ
"ፈጥኖ እጆቹን ቢያነሳ" የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን በፍጥነት ማድረግን ይገልጻል። እንደዚሁም፣ "ከዚህ ህይወት ቢቆርጠኝ" የሚለው ሀረግ መግደል ለሚለው ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። "ምነው ፈጥኖ ህይወቴን በአጭር ቢቆርጠው" ወይም "ፈጥኖ መጨረሻዬን ቢያደርገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 6:10
ይህ እንኳን መጽናናት በሆነኝ ነበር
"ይህ መጽናናት ያመጣልኝ።" "ይህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር እርሱ/ኢዮብ እንዲሞት መፍቀድን ነው። "ሞቴ መጽናናት በሆነኝ" ወይም "ሞቴ ያጽናናኝ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በመከራዬ ብፈነድቅ እንኳን ይህም ጭምር ስቃዬን አይቀንሰውም
"ማብቂያ በሌለው ስቃይ ደስታን ላገኝ እችኩላለሁ" ወይም "የማይጠፋ መከራ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በጽናት እታገሳለሁ"
መፈንደቅ
"መደሰት"
አይቀንስም
"አይጠፋም"
የቅዱሱን ትዕዛዝ አልተላለፍኩም
"እግዚአብሔርን አልካድኩምና።" ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሁልጊዜም ቅዱሱን ታዝዣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
እታገስ ዘንድ ብርታቴ ምንድን ነው? ህይወቴ ይረዝም ዘንድ መጨረሻዬ ምንድን ነው?/ህይወቴ ስለ ምን ይቀጥላል?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያነሳው መኖርን እንዲቀጥል የሚያደርግ ምንም ምክንያት እንደሌለው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። እነዚህ ጥያቄዎች ሁሉም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በገለጻ መልክ ሊጻፉ ይችላሉ። "በህይወት ለመቀጠል በቂ ጥንካሬ የለኝም፤ ህይወቴ የሚቀጥልበት ምንም ምክንያት የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 6:12
አጠቃላይ መረጃ:
ጸሐፊው በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ጥያቄዎችን የተጠቀመው ኢዮብ መከራውን ለመቋቋም አቅም ማጣቱን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ብርታቴ የድንጋይ ጥንካሬ ነውን? ወይንስ ስጋዬ የተሰራው ከነሀስ ነው?
ኢዮብ የሰውነቱን ደካማነት ለማጉላት እንደ አለት እና ነሀስ ጠንካራ አይደለሁም በማለት ይገልጻል። እነዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በገለጻ መልክ ሊቀርቡ ይችላሉ። "እንደ አለት ጠንካራ አይደለሁም። ስጋዬ እንደ ብረት ጠንካራ አይደለም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ.... በውስጤ እርዳታ የሚሆነኝ አለመኖሩ እውነት አይደለምን?
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠቀመው እውቀት እንዳጣ እና ደካምነቱን አጉልቶ ለማሳየት ነው። እንደዚሁም ደግሞ፣ "በውስጤ እርዳታ የሚሆነኝ የለም" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። " እኔ...የቀረ አቅም የሌለኝ መሆኑ እውነት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ጥበብ ከውስጤ ተሟጦ ወጥቷል
"ስኬቴ ከእኔ ተወስዷል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጥበቤ ከእኔ ርቋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 6:14
እያበቃለት/እየደከመ ላለ ሰው፣ ወዳጆቹ ታማኝነትን ሊያሳዩት ይገባል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አበቃልኝ/ደከምኩ ላለ ሰው ወዳጁ ታማኝ ሊሆንለት ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እየደከመ ያለ ማን ነው
ይህ የሚናገረው፣ በአካል እየደከመ የመጣ ስለሚመስል፣ ተስፋ ስለ ቆረጠ እና በችግሩ ስለተዋጥ ሰው ነው። "ተስፋ የቆረጠ ማን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉን ቻይ የሆነውን ፍርሃት ለሚፈልግ እንኳን
"ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ መፍራት ቢያቆም እንኳን።" ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የደከመ/ያበቃለት ሰው እግዚአብሔርን አይፈራም ወይም 2) የእርሱ ወዳጆች እግዚአብሔርን አይፈሩም
ወንድሞቼ ለእኔ የነበራቸው ታማኝነት እንደ በረሃ ጅረት ነበር
ኢዮብ ወዳጆቹ ለእርሱ ታማኝ አለመሆናቸውን የሚገልጸው በድንገት እንደሚደርቅ "በክረመት እንደሚሞላ ደረቅ ወንዝ" ነው። እንደዚሁም ኢዮብ እዚህ ስፍራ ወዳጆቹን በምጸት "ወንድሞች" እያለ ይገልጻቸዋል። "ወዳጆቼ ለእኔ ታማኝ አይደሉም። እነርሱ እንደ በረሃ ጅረት ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻፃሪ ዘይቤ እና ምጸት የሚሉትን ይመልከቱ)
ወደትም እንደማይደርስ የውሃ ቦይ
"እንደሚደርቅ ጅረት ውሃ።" ኢዮብ ስለ ወዳጆቹ እንደ ሚደርቅ ወራጅ ሊታመኑባቸው የማይቻል መሆኑን መናገሩን ይቀጥላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ደግሞም ራሱን በውስጣቸው ከሚደበቀው በረዶ የተነሳ...በላያቸው ካለው በረዶ የተነሳ የሚጠቁሩ/የሚደፈርሱ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ወራጁ ውሃ/ትንሽ ወምዝ በክረምት እንዴት በበረዶ እንደተሞላ ይገልጻሉ። "በክረምት በበረዶ በመሸፈናቸው ጠቁረው/ደፍርሰው ይታያሉ፤ ደግሞም በቀለጠው በረዶ/አመዳይ ይሞላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከበረዶው የተነሳ ራሱን በእነርሱ ውስጥ የሚደብቅ
ይህ የሚናገረው በረዶው እየቀለጠ ራሱን በወራጁ እንደሚደብቅ ውሃው ወደ ወንዙ እንደሚሄድ ነው። "ምክንያቱም በረዶው እየቀለጠ ወደ እነርሱ ይሄዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አየሩ ሲሞቅ/በጋ ሲመጣ፣ ይጠፋሉ... ሞቃት ሲሆን ከስፍራቸው ይቀልጣሉ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሰይ ትርጉም አላቸው። በበጋ/በሞቃቱ ወቅት ወራጁ ወንዝ እንዴት እንደሚደርቅ ይገልጻሉ። "በጋ ሲመጣ፣ በረዶ ይቀልጣል ወራጁም ወንዝ ይደርቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 6:18
አያያዥ ሀሳብ
ኢዮብ ወዳጆቹ እንደሚደርቅ ወራጅ ውሃ ሊታመኑባቸው የማይቻል መሆኑን መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሲራራ/ተጓዥ ነጋዴዎች ውሃ ፍለጋ መንገዳቸውን ይቀይራሉ
"ሲራራ ነጋዴዎች መንገዳቸውን የሚቀይሩት ውሃ ፍለጋ ነው" ወይም "ሲራራ ነጋዴዎች ውሃ ለማግኘት የሚጓዙበትን መንገድ ይቀይራሉ"
ሲራራ ነጋዴዎች
በረሃ አቋርጠው ግመል እየነዱ በርካታ የሆኑ ተጓዦች ናቸው
በረሃ
"ጠፍ መሬት" ወይም "ምንም የሌለበት መሬት"
ቴማን..ሳባ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። የእነዚህ ስፍራዎች ሰዎች በሌላ አገር ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ነገሮችን ለመነገድ ቅፍለት/ብዙ ግመሎች ይጠቀማሉ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የሳባ መንገደኞች
"ከሳባ የሚመጡ መንገደኞች"
በእነርሱ ተስፋ ያደረጉ
"በእነርሱ ላይ ተስፋ ያደረጉ" ወይም "ተስፋቸውን በእነርሱ ላይ የጣሉ"
ነገር ግን ተታለው ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ነገር ግን እነርሱ ተስፋ ቆርጠው ነበር" ወይም "ነገር ግን እነርሱ አልረኩም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 6:21
አጠቃላይ መረጃ:
በእነዚህ ቁጥሮች ኢዮብ ወዳጆቹን ለመገሰጽ እና ከእነርሱ አንዳች እርዳታ አለመጠየቁን ለማጉላት አራት ጥያቄዎችን ያነሳል። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
አሁንም
ኢዮብ ይህንን ሀረግ የሚጠቀመው እየተናገረ የሚገኘውን ነገር ዋና ክፍል ለመጀመር ነው
እናንተ ወዳጆቼ ለእኔ አንዳች አላደረጋችሁም
"የእናንተ ወዳጅነት ለእኔን ምንም አልባኝም"
ፈርታችኋል
ይህ ማለት ኢዮብ ያለበትን ችግር አይተዋል፤ እናም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ እንዳይገቡ ፈርተዋል። "እግዚአብሔር ተመሳሳይ ነገር ያደርስብናል ብላችሁ ፈርታችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተን ‘አንዳች ነገር አድርጉልኝ ብያችኋለሁ?' ወይስ፣ ‘ከሀብታችሁ ስጦታ ስጡኝ ብያችኋለሁ?' ወይስ፣ ‘ከጠላቴ እጅ አድኑኝ ብያችኋለሁ?' ወይስ ‘ከጨቋኞች እጅ ተቤዡኝ ብያችኋለሁ?'
ኢዮብ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው እርሱን ወዳዶቹ አንድም ነገር እንዲሰጡት ወይም እንዲያደርጉለት አለመጠየቁን ለማጉላት ነው። "ገንዘብ ወይም ስጦታ እንድትሰጡኑ ጠየቅኳችሁን። ወይንስ ከጠላቶቼ ወይም ከጨቋኞቼ እንድታድኑኝ ጠይቄያችኋለሁ።በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ

ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጠላቶቼ እጅ አንድኑኝ...ከጨቋኞቹ እጅ ተቤዡኝ

እነዚህ ሁለቱም አገላለጾች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እንደዚሁም፣ እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ሃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። "ከጠላቶቼ ወይም ከጨቋኞቼ አድኑኝ" ወይም "ከባላጋጣዎቼ አድኑኝ" በሚው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ተቤዡኝ

"አድኑኝ"

Job 6:24

አስተምሩኝ...አድርጉልኝ

እዚህ ስፍራ "አስተማረ" እና "አደረገ" የሚሉት ግሶች የተጻፉት በሁለተኛ መበድ ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚገልጹትም የእርሱን/ኢዮብ መዳጆች ነው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም ልዩ ልዩ መለኮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላሜን እይዛለሁ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ዝም እላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእውነት ቃላት ምን ያህል ይከብዳሉ! የእናንተ ንግግር ግን እንዴት አድርጎ በእርግጥ እኔን ሊቃወም/ሊወቅስ ይችላል?

የመገኛ ቋንቋው/ዋናው ቋንቋ ትክክለኛ ትርጉም በእርግጠኝነት አይታወቅም። አንዳንድ ቅጂዎች "እንዴት ያስጨንቃሉ" ብለው የሚተረጉሙት "እንዴት ደስ ያሰኛሉ" እንደማለት ነው። "አንድ ሰው እውነቱን ሲፈልግ፣ ይህ ማንንም አይጎዳም። የእናንተ ክርክር ግን ዕውነት አይደለም ስለዚህም እንዴት አድርጎ እኔን ሊገስጸኝ ይችላል?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ነገር ግን የእናንተ ክርክር፣ በእርግጥ እንዴት እኔን ሊገስጸኝ ይችላል?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ወዳዶቹን ለመገሰጽ እና እነርሱ የሚናገሩት ነገር በእርሱ ላይ እንደማይሰራ/ትክክለኛ እንዳልሆነ ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እናንተ እኔን ለመገሰጽ በምታቀርቧቸው ምክንያቶች ምንም እንኳን በጥብቅ ልታርሙኝ ብትሞክሩም በእኔ ላይ ግን አይሰሩም/እውነትነት የላቸውም።" ወይም "በእኔ ላይ የምታቀርቡት ክርክር ዕውነት አይደለም፣ ስለዚህም ነገራችሁ በእርግጥ ሊገስጸኝ አይችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የእናንተ ክርክር

"የምታቀርቧቸው ምክንያቶች" ወይም "እናንተ ነው የምትሉት"

Job 6:26

ቃሌን ቸል ልትሉ ታስባላችሁ፣ ተስፋ የቆረጠውን ሰው ቃል እንደ ነፋስ ታዩታላችሁን/ትቆጥራላችሁን?

ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ወዳጆቹን ለመገሰጽ ነው። የእርሱን ቃላት ከነፋስ ጋር የሚያነጻጽረው፣ የወዳጆቹን ድርጊት እንደ እርሱ ቃላት ባዶ እና ረብ የሌላቸው መሆኑን ለማብራራት ነው። "እናንተ ቃሌን ቸል ብላችኋል! እኔ ተስፋ የቆረጥኩ ሰው ነኝ፣ እናንተ ደግሞ ቃሎቼን እንደ ነፋስ እርባና ቢስ አድርጋችሁ ታያላችሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እናንተ

"እናንተ" ሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ነው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም ልዩ ልዩ መለኮች የሚለውን ይመልከቱ)

አባት በሌላቸው ልጆች ላይ ዕጣ ትጣጣላላችሁ

"ወላጅ አልባን ለማሸነፍ ቁማር እንኳን ትጫወታላችሁ"

እጣ ትጥላላችሁ... በወዳጆቻችሁ ላይ ትከራከራላችሁ

እዚህ ስፍራ "እናንተ" እና "የእናንተ" የሚሉት በሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር የተጻፉ ናቸው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም ልዩ ልዩ መለኮች የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሸቀጥ ንግድ በወዳጃችሁ ላይ ትከራከራላችሁ

ይህ አንድ ሰው ሸቀጥ እንደሚሸጥ እንዴት ወዳጁን እንደሚሸጠው ያነጻጽራል። "ወዳጆቻችሁን በገንዘብ ለመሸጥ ትከራከራላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 6:28

አሁን

ኢዮብ ይህንን ቃል የተጠቀመው አዲስ መረጃ ለመስጠት/ለማስተዋወቅ ነው።

እባካችሁ ተመልከቱ

"ተመለከተ" የሚለው ግስ በሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር የተጻፈ ነው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም ልዩ ልዩ መለኮች የሚለውን ይመልከቱ)

በፊታችሁ አልዋሽም

"እናንተ" የሚለው ቃል የኢዮብን ወዳጆች ያመለክታል። እዚህ ስፍራ የእርሱ ወዳጆች የተወከሉት በእነርሱ ፊት በሚለው ነው፤ ይህም ያገለገለው እርሱን እየተመለከቱት መሆኑን አጉልቶ ለመግለጽ ነው። "ፊት ለፊት እየተመለከትኳችሁ ልዋሻችሁ አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ይቅር እንድትሉኝ እለምናችኋለሁ

"እባካችሁ ይቅር በሉኝ" ወይም "እባካችሁ እኔ የምለምናችሁ፣ እንዲህ መናገራችሁን እንድታቆሙ ነው"

ፍርደ ገምድልነታችሁን ከእናንተ አስወግዱ

ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ቅን ፍረዱ" (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በእርግጥ ይቅር በሉኝ

x

---

Chapter 7

Job 7:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ጸሐፊው በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚጠቀመው አንድን ሀሳብ በሁለት የተለያዩ ገለጻዎች ለማስተላለፍ ሲሆን፣ የእርሱ ግላዊ መከራ ሁሉም ሰው የሚደርስበት የጋራ መከራ ክፍል መሆኑን ትኩረት ለመስጠትም ይጠቀምበታል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው በምድር ላይ ከባድ ስራ የለበትምን?

ኢዮብ ይህንን አሉታዊ ጥያቄ የሚያቀርበው፣ ሁሉም ሰው ከባድ ስራ እንደሚሰራ የእርሱን ግንዛቤ ለማጉላት ነው። ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "በምድር ላይ እያንዳንዱ ሰው የሚሰራው ከባድ ስራ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ላይ

ይህ ሰው በምድር ላይ በሚኖርበት ጊዜ ለሚለው አጠቃላይ አስተያየት ነው። "በምድር በሚኖርበት ዘመን" (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

ዘመኑ እንደ ምንደኛ/ለእለት ስራ ተቀጣሪ/ ዘመን አይደለምን?

ኢዮብ ይህንን አሉታዊ ጥያቄ የሚያቀርበው ሁሉም ሰው በህይወት ውስጥ ትግል እንዳለበት ያለውን ግንዛቤ በትኩረት ለማቅረብ ነው። "ቀናቸው እንደ የእለት ተቀጣሪ ሰው ቀናት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደ አንድ ባሪያ... ልክ እንደ የእለት ተቀጣሪ ሰው... እኔ እንደዚያ ነበርኩ...በመከራ የተሞሉ ምሽቶች የተሰጡኝ

ኢዮብ መከራውን እና ችግሩን ከባሪያና ከተቀጣሪ ሰው ጋር ያነጻጽራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የምሽት ጥላ

"ቀዝቃዛ ጥላ።" በስውር የተጠቆመው መረጃ የምሽት ጥላ ቅዝቃዜን ይሰጣል፣ ደግሞም ከፀሐይ ይከልላል የሚለው ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የተቀጠረ ሰው/ተቀጣሪ

"የቀን ሰራተኛ።" ይህ ለአንድ ቀን ስራ የተቀጠረ እና በእያንዳንዱ በሰራበት ቀን መጨረሻ ላይ የሚከፈለው ሰው ነው።

የሰራበትን እንደሚጠብቅ

"ክፍያውን እንደሚጠብቅ"

እኔም፣ መከራ የበዛባቸውን ምሽቶች አግኝተውኛል፣ የወራት መከራን እንድታገስ ተደርጌያለሁ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ስለዚህም የወራት መከራ ታግሻለሁ፤ መከራ የባዘባቸው ምሽቶች ገጥመውኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የመከራ ወራት/ጊዜያት

"መከራ" የሚለው ረቂቅ ስም "መከረኛ" በሚል ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "የመከራ ወራት/ጊዜያት" ወይም "ከንቱ ወራት/ጊዜያት" በሚለው ውስጥ

እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 7:4

ጋድም በምልበት ጊዜ

በውስጠ ታዋቂነት የቀረበው መረጃ ኢዮብ በምሽት ለመተኛት ጋድም በሚልበት ጊዜ ማለት ነው። "ለመተኛት ጋደም በምልበት ጊዜ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለራሴ እንዲህ አላለሁ

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ በተለይ ለሌላ ለማንም ሰው አያቀርብም። "እኔ እጠይቃለሁ" ወይም "እኔ እገረማለሁ" (ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መቼ ከመኝታዬ እነሳለሁ መቼ ለሊቱ ይነጋል?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው መተኛት ባለበት ሰአት ምን ያህል መከራው ጽኑ እንደሆነ አጉልቶ ለመግለጽ ነው። "ከመኝታዬ መነሳት ብችል እወዳለሁ፣ ነገር ግን ምሽቱ አይነጋም/ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ፊት እና ወደ ኋላ ስገላበጥ

"ወደ ኋላ እና ወደፊት ስዟዟር።" ይህ የሚያመለክተው ኢዮብ ካለ አንዳች እንቅልፍ ሌሊቱን በመኝታው ላይ ሲገላበጥ እንደሚያድር ነው።

ስጋዬ በትሎች እና በአቧራ ጓል ተሸፍኗል

ትሎቹ እና የአቧራው ጓል ብዛት የተገለጸው ልብስ ሆነው እንደ ሸፈኑት ተደርጎ ነው። "ስጋዬ በትሎች እና በአቧራ ተሸፍኗል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስጋዬ

ይህ መላ አካሉን ያመለክታል። "መላ አካሌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የአቧራ ጓል

ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ አማራጭ ትርጉሞች 1) የእድፍ ቅርፊት ወይም ጓል ወይም 2) በቆዳ ላይ ቅርፊት/ማፈክፈክ

አመርቅዟል

"ዳግም ቆስሏል"

Job 7:6

አጠቃላይ መረጃ፡

ጸሐፊው የኢዮብን የእድሜ ጥቂትነት ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ እንዲሁም አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ ገለጻዎችን በመጠቀም ለማስተላለፍ በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኖቼ/ዘመኔ ከሸማኔ መወርወሪያ ይልቅ ፈጣኖች ናቸው

ኢዮብ ህይወቱን ከሸማኔ መወርወሪያ ፈጣንነት ጋር ያነጻጽራል። "ህይወቴ በጣም በቶሎ ያልፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሸማኔ

ክር በማዳወር ልብስ የሚሰራ ሰው

የሸማኔ መወርወሪያ

ክሩን የሚይዘው ተንቀሳቃሽ ክፍል፣ ወይም ልብሱ ሲሰራ ከሸማኔው ዕቃ ውስጥ ክሩ ወደፊት እና ወደ ኋላ በፊጥነት እንዲንቀሳቀስ የሚያደርግ

አስብ

"አስታውስ።" "አስብ" የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር ይረሳል ማለት አይደለም። ኢዮብ የህይወቱ ዘመን ጥቂት መሆኑን እግዚአብሔር እንዲያይለት እየጠየቀ ነው።

ህይወቴ የእስትንፋስ ያህል ናት

ኢዮብ የህይወቱን ጥቂትነት ከእስትንፋስ አጭርነት ጋር ያነጻጽራል። "ህይወቴ የአንዲት እስትንፋስ ያህል አጭር ናት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ዐይኖቼ አንዳች መልካም ነገር አያዩም

እዚህ ስፍራ "ዐይኖቼ" የሚለው የሚወክለው የኢዮብን መላ ሰውነት እና ነገሮችን የማየት ወይም የማድረግ ችሎታ ነው። "ዳግም በፍጹም መልካም ነገር አላይም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 7:8

አጠቃላይ መረጃ፡

ጸሐፊው ኢዮብ ከሞት በኋላ እግዚአብሔርም ሆነ እርሱን የሚያውቁት ሰዎች ዳግም እንደማያዩት ያለውን ሀሳብ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ እንዲሁም አንድን ሀሳብ ሁለት የተለያዩ ገለጻዎችን በመጠቀም ለማስተላለፍ በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚመለከተኝ የእግዚአብሔር ዐይን ከእንግዲህ አያየኝም

በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን "የሚመለከቱኝ ዐይኖች ከእንግዲህ አያዩኝም" በሚል ተርጉመውታል። "የእግዚአብሔር" ቃሎች በዚህ ሀረግ ላይ የተጨመሩት በይዘቱ ውስጥ የተካተቱ/የተጠቆሙ በመሆኑ ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚመለከተኝ የእግዚአብሔር ዐይን... የእግዚአብሔር ዐይን በእኔ ላይ ይሆናል

እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ምን እንደሚመለከት ትኩረት ለመስጠት የተወከለው በእርሱ "ዐይን" ነው። "እኔን የሚመለከት እግዚአብሔር... እግዚአብሔር ይመለከተኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ደመና እንደሚበን እና እንደሚጠፋ፣ ወደ ሲኦል የሚወርድ ዳግም አይመለስም

ኢዮብ ሞትን የሚገልጸው በኖ እንደሚጠፋ ደመና ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚልን ይመልከቱ)

ደመና እንደሚበተን

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ደመና እንደሚበን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ሲኦል የሚወርድ ዳግም አይመለስም

"የሞተ ተመልሶ አይመጣም"

በእርሱ ስፍራ/በስፍራው

"በእርሱ ስፍራ" የሚሉት ቃላት በእርሱ ስፍራ የሚኖሩትን ይወክላል። "በእርሱ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች" ወይም "የእርሱ ቤተሰቦች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 7:11

በመንፈሴ ጭንቀት እናገራለሁ፣ በነፍሴን መራርነት አማርራለሁ

ኢዮብ ዝም የማይልበትን ምክንያት ለማጉላት ሁለት የተለያዩ ገለጻዎችን በመጠቀም አንድን ሃሳብ ያስተላልፋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አፌን አላቅብም

እዚህ ስፍራ አፍ የሚወክለው ንግግርን ነው። "ንግግሬን አልገድብም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በመንፈሴ ምሬት

"በመንፈሴ ሀዘንተኝነት" ወይም "በመከራዬ ስቃይ።" "ጭንቀት" የሚለውን ረቂቅ ስም "ስቃይ" የሚለውን ተውሳከ ግስ ተጠቅሞ መተርጎም ይቻላል። "መንፈሴ ተጨንቆ ሳለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በነፍሴን መራርነት

እዚህ ስፍራ ሀዘን የተገለጸው መራራ ጣዕም እንዳለው ተደርጎ ሲሆን፣ "ነፍስ" ደግሞ የሰውን ሁለንተና የሚያመለክት ሆና ተነግራለች። "በቁጣ እና ቅር በመሰኘት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

በእኔ ላይ ጠባቂ ታኖር ዘንድ እኔ ባህር ነኝ፣ ወይንስ የባህር አውሬ ነኝ?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው በእግዚአብሔር ላይ ማዘኑን ለመግለጽ ነው። ኢዮብ ራሱን ከባህር ወይም ከባህር አውሬ ጋር በማነጻጸር እግዚአብሔር እርሱን አሰቃቂ ፍጥረት አድርጎ እንደቆጠረው ይናገራል። ይህ በገለጻ ሊተረጎም ይችላል። "እኔ ጠባቂ የሚያስፈልገው የባህር አውሬ ወይም ባህሩን አይደለሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 7:13

አጠቃላይ መረጃ፡

ጸሐፊው የኢዮብን ጥልቅ መከራ ለማጉላት ሁለት የተለያዩ አገላለጾችን በመጠቀም አንድን ሃሳብ ለማስተላለፍ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መኝታዬ ያጽናናኛል፣ መከዳዬ ማጉረምረሜን ቀለል ያደርግልኛል

እዚህ ስፍራ "መኝታ/አልጋ" እና "መከዳ" የሚሉት "እንቅልፍ" ለሚለው ሜቶኖሚ/

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ኢዮብ ለመተኛት ጋደም ሲል አረፍ ለማለት ተስፋ ያደርጋል። ይህ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሰብአዊ ባህሪያትም ደግሞ አሉት፤ የማጽናናት እና ሰውን አረፍ የማድረግ አቅም አላቸው። "መኝታዬ እና መከዳዬ እንደ ሰው ያሉ ነገሮች ናቸው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አልጋዬ/መኝታዬ... መከዳዬ

እነዚህ ሀረጋት ተመሳሳይ ነገርን ያመለክታሉ፡ "አልጋዬ...መኝታዬ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

አንተ አስደነገጥከኝ/አስፈራኸኝ

እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው

ማነቅ

አንድን ሰው ጉሮሮውን ጨምቆ እና ትንፋሹን አቁሞ መግደል

እነዚህ የእኔ አጥንቶች/አጥንቶቼ

እዚህ ስፍራ ኢዮብ "አጥንቶች" የሚለውን ቃል የተጠቀመው አካሉን ለማመልከት ነው። "ይህ የእኔ አካል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሲኔክዶክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 7:16

አያያዥ ሃሳብ፡

ጸሐፊው የኢዮብ መከራ በእርሱ ማንነት እርባና ግንዛቤ ላይ ትኩረት ለመስጠት ሁለት የተለያዩ አገላለጾችን በመጠቀም አንድን ሃሳብ ለማስተላለፍ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴን ጠላሁ

"ህይወቴን ናቅኩት"

ሁሌም በህይወት ለመኖር

"ለዘለአለም ለመኖር"

ቀናቴ/ዘመኔ እርባና ቢስ ናቸው

"ዘመኔ አለ ፍሬ ነው" ወይም "የህይወቴ ቀናት ከንቱ/ባዶ ናቸው"

ትከታተለው ዘንድ .... ሰው ምንድን ነው?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔር ለሰው ለምን ትኩረት እንደሚሰጥ መደነቁን ለማጉላት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ትከታተለው ዘንድ...ሰው ምንድን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህን ታሳርፍበት ዘንድ

እዚህ ስፍራ ልብ/አእምሮ የመሚለው የሚወክለው ሃሳብን እና ትኩረት መስጠትን ነው። "ልብህን ታሳርፍበት ዘንድ" ማለት ትኩረት መስጠት ማለት ነው። "ትኩረትህን ወደ እርሱ ታደርግ ዘንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱን ተመልከተው

"እርሱን በጥንቃቄ መርምረው"

Job 7:19

ምራቄን ለመዋጥ...ይህ ለምን ያህል ጊዜ ይሆና?

እዚህ ስፍራ ኢዮብ ሁለት የተለያዩ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎችን በመጠቀም አንድን ሀሳብ የሚገልጸው እግዚአብሔር እርሱን መከታተሉን ቢያቆም ደስ እንደሚለው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "እኔን መከታተልህን አቁም! የራሴን ምራቅ የምውጥበትን ያህል ጊዜ እንኳን ፋታ ስጠኝ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ምራቅ

አፍ እርጥበቱን እንዲጠብቅ እና ምግብን ለመዋጥ የሚረዳ በሰዎች አፍ ውስጥ የሚፈጠር ፈሳሽ

ኃጢአት ብሰራ እንኳን ... ሸክም ሆንኩብህ?

ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያቀርበው እግዚአብሔር የማይገባ ነገር እንዳደረሰበት ከእርሱ ጋር ለመከራከር ነው። " ኃጢአት ብሰራ እንኳን፣ አንተ ሰዎችን ሁሉ ስለምታይ ያ በአንተ ላይ አንዳች አያደርግም። ሸክም እሆንብህ ዘንድ፣ ለምን አላማህ እንዳደረግከኝ ንገረኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 7:21

ስለ ምን መተላለፌን ይቅር ብለህ በደሌን ከእኔ አታርቅም?

እዚህ ስፍራ ኢዮብ ከቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ጋር ሃሳቡን ለማጉላት ሁለት ተመሳሳይ ሐረጎችን ይጠቀማል። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፡ 1) ኢዮብ ለምን እግዚአብሔር ይቅር እንደማይለው ይጠይቃል። "መተላለፌን ለምን ይቅር እንደማትለኝ እና ኃጢአቴን እንደማታርቅልኝ ንገረኝ።" ወይም 2) ኢዮብ እግዚአብሔርን ምናልባት በድዬ ቢሆን እንኳን ለምን ስህተቴን እንዳላየህ ሆነህ አታልፈኝም። "በደሌን እና መተላለፌን ለምን እንዳልተውክልኝ ንገረኝ።" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ውሰድ/አርቅ

"አስወግድ"

አሁን በአፈር ውስጥ እጋደማለሁን

"በአፈር ውስጥ መጋደም" የሚለው ሀረግ ሞትን የሚወክል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እኔ አሁን እሞታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በህይወት አልኖርም

"እዚህ አልሆንም" ወይም "እኔ እሄዳለሁ"

Chapter 8

Job 8:1

አያያዥ ሃሳብ

በዚህ ምዕራፍ፣ በልዳዶስ ስለ ኢዮብ ማማረር መናገር ይጀምራል።

አጠቃላይ መረጃ፡

ቁጥር 2 እና ቁጥር 3 እያንዳንዳቸው ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሁለት የተለያዩ ጥያቄዎችን ይይዛሉ። በልዳዶስ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያውላቸው/ የሚጠቀምባቸው ኢዮብን ለመገሰጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከዚያም ሹሐዊው በልዳዶስ እንዲህ ሲል መለሰ

"በልዳዶስ" የሹሐ ነገድ አባል የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ መቼ የአፍቃል እንደ ታላቅ ነፋስ ይሆናል

በልዳዶስ የኢዮብን ቃል የሚገልጸው ባዶ እና እንደ ነፋስ በውስጣቸው ምንም ፍሬ ነገር እንደሌላቸው አድርጎ ነው። ይህ በገለጻ አይነት ሊተረጎም ይችላል። "የአፍህ ቃላት እንደ ታላቅ ነፋስ ምንም ጥቅም የሌላቸው ናቸው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ፍትህን ይከለክላልን? ሁሉን ቻይ የሆነው ጽድቅን ያጣምማልን?

እዚህ ስፍራ "እግዚአብሔር" እና "ሁሉን ቻይ የሆነው" የሚሉት ሁለቱም ያህዌን የሚያመለክቱ ናቸው። እነዚህ ጥያቄዎች በመግለጫ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እግዚአብሔር ፍትህን አያጣምምም፤ ሁሉን ቻይ የሆነው ጽድቅን አያጣምም።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህን ያጣምማልን?... ጽድቅን ያጣምማልን?

"ትክክል ያለሆነውን ማረጋገጫ ሰጥቶ ያደርጋልን?.. ጽድቅ ያልሆነውን ማረጋገጫ ሰጥቶ ይፈጽማልን?"

Job 8:4

ለእጃቸው ኃጢአት አሳልፎ ሰጥቷቸው ከሆነ

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው የኃጢአትን ሀይል ወይም ውጤት ነው። በልዳዶስ እግዚአብሔር የኢዮብን ልጆች የገደላቸው በኃጢአታቸው ምክንያት እንደሆነ ያመለክታል። "የልጆችህ ኃጢአት እግዚአብሔር እንዲገድላቸው ምክንያት ሆኖታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ነገር ግን አንተ ምናልባት እግዚአብሔርን በትጋት ፈልገህ ጥያቄህንም ሁሉን ቻይ ለሆነው አቅርበህ ይሆናል

በልዳዶስ ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር በትክክል ቢስማማ ምን ሊሆን ይችል እንደ ነበረ እየተናገረ ነው፤ ነገር ግን በልዳዶስ ኢዮብ ይህንን ማድረጉን አያምንም። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በትጋት እግዚአብሔርን መፈለግ... ሁሉን ቻይ ለሆነው ጥያቄህን ማቅረብ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እነዚህ ሁለት ሀረጋት ኢዮብ እግዚአብሔርን እርዳታ ወይም ምህረት መጠየቁን ያመለክታሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
በትጋት እግዚአብሔርን መፈለግ
"ከልብ እግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅ"
Job 8:6
አጠቃላይ መረጃዎች፡
በልዳዶስ ኢዮብ ንጹህ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ይረዳው ነበር ይላል፣ ነገር ግን በልዳዶስ ኢዮብ ንጹህ መሆኑን አያምንም። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ንጹህ እና ትክክለኛ ብትሆን
"ንጹህ እና ጻድቅ ሰው ብትሆን ኖሮ" ወይም "እግዚአብሔርን ታዝዘህ ቢሆን እና ትክክለኛ የሆነውን ነገር የምታደርግ ቢሆን ኖሮ"
እርሱ ስለ አንተ ይነሳል
እዚህ ስፍራ ያህዌ የተገለጸው ኢዮብን ለመርዳት ከእንቅልፉ እንደተነሳ ተደርጎ ነው። "አንተን ሊረዳህ" ወይም "ለአንተ መልካም ነገሮችን ለማድረግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተን ወደ ትክክለኛ ስፍራ ይመልስሃል
ይህ የሚያመለክተው ኢዮብ ያጣቸውን ነገሮች፤ ቤተሰቡን ጨምሮ፣ ሀብቱን እና ክብሩን መልሶ እንደሚሰጠው ነው።
ምንም እንኳን ጅማሬህ እጅግ ታናሽ ቢሆንም፣ ፍጻሜህ ግን እጅግ ታላቅ ይሆናል
እዚህ ስፍራ ሀብትን ማጣት የተገለጸው "ታናሽ ጅማሬ" እንደሆነ ተደርጎ ነው። "በህይወትህ መነሻ ላይ ደሃ ብትሆንም፣ በዕድሜህ የኋልኛ ዘመን እግዚአብሔር እጅግ ባለጠጋ ያደርግሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 8:8
አጠቃላይ መረጃ፡
በልዳዶስ አባቶቻቸው እርሱ ለኢዮብ ከሚነግረው ሃሳቦች ጋር የሚስማሙ መሆኑን አጉልቶ ለመግለጽ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን በእነዚህ ቁጥሮች ሁሉ መጠቀሙን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልቱ)
አባቶቻችን ያስተምሯቸው ለነበሩ ነገሮች ዋጋ ስጥ
"አባቶቻችን ይናገሩ የነበረውን በጥንቃቄ ተረዳ" ወይም "አባቶቻችን የተዉልንን ትምህርቶች ስፍራ ስጣቸው"
በምድር ላይ የሰው ዘመን ጥላ ነው
የህይወት አጭርነት የተገለጸው በፍጥነት የሚጠፋ ጥላ እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ አያስተምሩህምን፣ ደግሞስ አይነግሩህምን? እነርሱ ከልባቸው ቃል አይነግሩህምን? በልዳዶስ እነዚህን ቃል
ምልልሳዊ ጥያቄዎች የሚጠቀመው ኢዮብን ከእርሱ እና ከአባቶቻቸው ጋር ባለመስማማቱ ሊወቅሰው ነው። ይህ በገለጻ ሊተረጎም ይችላል። "እነርሱ ያስተምሩሃል፣ ደግሞም ይነግሩሃል፤ በእውነት የሚያምኑበትንም ይነግሩሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ከልባቸው
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው ውስጣዊ እምነትን ነው። "እነርሱ በእውነተኝነት የሚያምኑበትን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 8:11
አጠቃላይ መረጃ፡
ከቁጥር 11-14 ያለው የበልዳዶስ ትምህርቶች ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም፣ ወይም በልዳዶስ ከኢዮብ 8፡8-10 ያለውን የአባቶች ትምህርት ጠቅሶ ሊሆን ይችላል።
ረግረግ በሌለበት ደንገል ይበቅላልን? ውሃ በሌለበት ቄጠማ ይደጋልን?
በልዳዶስ እነዚህን ትይዩ ንጽጽራዊ ጥያቄዎች የሚጠቀመው ሰዎች ያለ እግዚአብሔር መኖር እንደማይችሉ ይህን አንድ ሀሳብ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። እዚህ ስፍራ ተክሎች ሰውን ሲወክሉ፣ ውሃ ደግሞ እግዚአብሔርን ይወክላል። ጥያቄው በግልጽ ሊተረጎም ይችላል። "የደንገል ተክል ከረግረግ ርቆ ሊያድግ አይችልም። ቄጠማም ያለ ውሃ ሊያድግ አይችለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እንደዚሁም ዘይቤያው አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ደንገል
ጥልቀት በሌለው ውሃ ላይ የሚያድግ ረጅም ቄጠማ መሰል ተክል
ገና አረንጓዴ ሳሉ እና ሳይቆረጡ ከሌላው ተክል ፈጥነው ይደርቃሉ
ውሃ በሚያጥርበት ጊዜ እንደሚደርቁ ተጠቁሟል። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ማንም ባይቆርጣቸውም እንኳን እነዚህ ተክሎች ውሃ በሚያጥርበት ጊዜ ማደግ አይችሉም፤ ደግሞም ፈጥነው ይደርቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ይጠፋሉ
"ይደርቃሉ"
Job 8:13
አጠቃላይ መረጃ፡
ከቁጥር 11-14 ያለው የበልዳዶስ ትምህርት ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም፣ ወይም በልዳዶስ የአባቶችን ትምህርት ከኢዮብ 8፡8-10 ካለው ክፍል ጠቅሶ ሊሆን ይችላል።
አጠቃላይ መረጃ፡
ከቁጥር 14-18፣ "እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ተውላጠ ስሞች የሚያመለክቱት በአጠቃላይ እግዚአብሔር የለሽ ሰዎችን የሚወክል እግዚአብሔር የለሽ ሰውን ነው። "እነርሱ" እና "የእነርሱ" የሚሉትን የብዙ ቁጥር ተውላጠ ስሞች/የስም ምትኮች/ መጠቀም አንባቢያንን ሊያግዝ ይችላል። (የስማዊ ሀረግ ክፍሎች የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን የሚረሱ/የሚተዉ ሁሉ መንገዳቸው እንዲህ ነው
እዚህ ስፍራ "መንገድ" የሚወክለው የአንድን ሰው የወደፊት ጊዜ እና በእርሱ ላይ የሚደርሱ ነገሮቸን ነው። "እግዚአብሔርን በሚረሱ ሁሉ ላይ ተመሳሳይ ነገር ይደርሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር የለሾች ተስፋ ይጠፋል
"አምላክ የለሽ ሰው የሚሻቸው ነገሮች አይጸሙም"
የእርሱ ልበ ሙሉነት የንኮታኮታል/ይሰበራል... መታመኛው እንደ ሸረሪት ድር ደካማ ነው
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም አገላለጾቹ አምላክ የለሽ ሰው ሊያድነው በማይችል ነገር እንደሚታመን ትኩረት ይሰጣሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልቱ)
እምነቱ እንደ ሸረሪት ድር ደካማ ነው
እዚህ ስፍራ በልዳዶስ የአምላክ የለሽ ሰዎችን እምነት ከሸረሪት ድር ጋር ያነጻጽራል፤ ሁለቱንም ጥቂት ሀይል ያፈራርሳቸዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በቤቱ ላይ ይደገፋል፣ ነገር ግን ይህ አይደግፈውም፤ እርሱ ይህን ይይዛል፣ ነገር ግን የያዘው ጸንቶ አይቆምም።
ይህ ሀሳብ የሚያመለክተው ምናልባት ለደህንነቱ ንብረቱን እና ሀብቱን መታመኛ ያደረገን ሰው ሊሆን ይችላል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚወክለው የባለቤቱን ንብረት እና ሀብት ነው። "ሀብት ስላለው በደህንነት የሚጠበቅ እንደሆነ ያስባል፣ ነገር ግን ደህንነቱ አይጠበቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሀብቱ አይደግፈውም
ይህ አሉታዊ ሀሳብ ተቃራኒውን ነገር ያጎላል። ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ ይወድቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)
አይቆምም
ይህ አሉታዊ ሀሳብ ተቃራኒውን ነገር ያጎላል። ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ይህ ይወድቃል"
Job 8:16
አጠቃላይ መረጃ፡
እዚህ ስፍራ "እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ተወላጠ ስሞች የሚያመለክቱት በአጠቃላይ እግዚአብሔር የለሽ ሰዎችን የሚወክል እግዚአብሔር የለሽ ሰውን ነው። "እነርሱ" እና "የእነርሱ" የሚሉትን የብዙ ቁጥር ተውላጠ ስሞች/የስም ምትኮች/ መጠቀም አንባቢያንን ሊያግዝ ይችላል። (የስማዊ ሀረግ ክፍሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ከፀሐይ በታች አረንጓዴ ነው፣ ቅርንጫፉ ሁሉ በስፍራ ሁሉ ይሰፋፋል
እዚህ ስፍራ በልዳዶስ እግዚአብሔር የለሽ ሰውን ከጤናማ ተክል ጋር ያነጻጽራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከፀሐይ በታች አረንጓዴ ነው
የዕብራይስጡ ጽሁፍ ትርጉም ግልጽ አይደለም። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች

1) በቀን ጤናማ ነው ወይም 2) ፀሐይ ከመውጣቱ አስቀድሞ ውሃ ይጠጣል
ስሮቹ በድንጋይ ክምር ላይ ይጠመጠማሉ... በአለት መካከል መልካም ስፍራ ይፈልጋል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ሆኖም ትርጉማቸው ግልጽ አይደለም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እያንዳንዱን ቀዳዳ በሚገባ በመጠቀም በአለት ላይ ስር የሰደደ ይመስላል ወይም 2) ስሩ ለም መሬት ማግኘት ስላልቻለ በአለቶች መሃል አልሚ ምግብ ለማግኘት መሞከር አለበት። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ይህ ሰው ከስፍራው ከተደመሰሰ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው ከስፍራው አስለቅቆታል" ወይም "አትክልተኛው ከስፍራው ከነቀለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ስፍራው
"አለታማው መሬት" ወይም "የተተከለበት ስፍራ"
ስፍራው ሊክደው እና እንዲህ ሊለው ይችላል 'በፍጹም አይቼህ አላውቅም'
የአትክልቱ/የተተከለበት ስፍራ የተገለጸው የመናገር ችሎታ እንዳለው ተደርጎ ነው። ስፍራው ወዲያውኑ የእርሱን መኖር ረስቷል። (ሰውኛ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 8:19
ይህ እንዲህ ያለው ሰው የ"ደስታ" ባህሪይ ነው
በልዳዶስ እግዚአብሔር የለሽ ሰው አንዳች ደስታ እንደሌለው በምጸት እየተናገረ ነው። "እግዚአብሔር የለሽ ከሆነው ድርጊታቸው የሚያተርፉት ደስታ ቢኖር ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት የሚለውን ዘይቤያዊ አነጋገር ይመልከቱ።
በተመሳሳይ አፈር ላይ በስፍራው ሌሎች ተክሎች ይበቅላሉ
በልዳዶስ ከኢዮብ 8:16-18 ዘይቤውን ይቀጥላል። ሌሎች እግዚአብሔር የለሽ ሰዎች የተገለጹት የመጀመሪያው አምላክ የለሽ ሰው ሲሞት የስርሱን ስፍራ እንደወሰዱ ተክሎች ተደርገው ነው። "አንድ ክፉ ሰው ሲሞት፣ ሌላው የእርሱን ስፍራ ይወስዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይበቅላል
"ያድጋል"
በዚያው አፈር
"አለታማ ምድር" ወይም "ስፍራው/የአትክልቱ ቦታ"
በስፍራው
"አምላክ የለሽ በሆነው ሰው ቦታ"
እግዚአብሔር ንጹሁን ሰው አያጠፋም
ይህ በአዎንታዊ አረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ንጹሁን ሰው ይቀበላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
እርሱ የክፉ አድራጊዎችን እጅ አይዝም
እዚህ ስፍራ "እጅ መያዝ" የሚለው የሚያመለክተው መርዳት ወይም መደገፍ የሚለውን ነው። "እግዚአብሔር ክፉ የሚያደርጉ ሰዎችን አይደግፍም/አይረዳም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 8:21
እርሱ ገና የአንተን አፍ በሳቅ፣ ከንፈሮችህን በእልልታ/በደስታ ጩኸት ይሞላዋል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ኢዮብ ትሁት መሆን ቢችል እንደምን ተመልሶ ደስተኛ ሊሆን እንደሚችል ትኩረት ይሰጣሉ። "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ሲሆን "የአንተ" ሚለው ኢዮብን ያመለክታል። "ንጹህ ብትሆን እግዚአብሔር ዳግም በጣም ደስተኛ ያደርግሃል" (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
አፍህን በሳቅ ይሞላል
እግዚአብሔር ኢዮብን በሳቅ እንዲሞላ ደርጋል የሚለው ሀሳብ የተገለጸው እግዚአብሔር በኢዮብ አፍ ሳቅ እንደሚጨምር ተደርጎ ነው። "ሳታቋርጥ እንድትስቅ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከንፈሮችህን በእልልታ/በደስታ ጩኸት
"ይሞላል" የሚለው ግስ በውስጠ ታዋቂነት በቀደመው ሀረግ ውስጥ ይገኛል። እግዚአብሔር የደስታ ጩኸት/ እልልታ እንዲያሰማ ማድረጉ የተገለጸው እግዚአብሔር በኢዮብ አፍ ደስታን እንደሚጨምር ተደርጎ ነው። "እግዚአብሔር በደስታ እንድትጮህ/እልል እንድትል ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
አንተን የሚጠሉ ሀፍረት ይለብሳሉ
እዚህ "ሀፍረት" የሚለው ቃል የተገለጸው እግዚአብሔር የኢዮብ ጠላቶች እንዲለብሱት እንደሚያደርገው ልብስ ተደርጎ ነው። ይህ ማለት እነርሱ በጣም ያፍራሉ ማለት ነው። "እግዚአብሔር አንተን የሚጠሉትን በጣም እንዲያፍሩ ያደርጋቸዋል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከእንግዲህ የክፉዎች ድንኳን አይገኝም
እዚህ "ድንኳን" የሚያመለክተው የክፉዎችን ቤት ነው። "የክፉዎች ቤት ይደመሰሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ከእንግዲህ አይገኝም
"አይቀጥልም" ወይም "ይደመሰሳል"

Chapter 9
Job 9:1
ይህ እንዲህ እንደሆነ በእውነት አውቃለሁ
"አንተ እምትናገረው እውነት እንደሆነ ያንን አውቃለሁ"
ይህ እንዲህ ነው
እዚህ ስፍራ "ይህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በልዳዶስ የተናገረውን ነው።
ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ትክክል/ጻድቅ ሊሆን ይችላል?
"ማንስ ቢሆን እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ ሊሆን ይችላል?"
ክርክር
"ጠብ"
ከአንድ ሺህ ጊዜ አንዴም ሊመልስለት አይችልም
"ከሺህ አንዴ" የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም "በፍጹም" ማለት ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፡ 1) "ለእግዚአብሔር ምንም መልስ መስጠት አይችልም" ወይም 2) "እግዚአብሔር በፍጹም መልስ አይሰጠውም" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሺህ ጊዜ
"1,000 ጊዜ"
Job 9:4
በልቡ ጠቢብ
እዚህ ስፍራ ልብ የሚለው የሚወክለው ውስጣዊ ፍጥረትን ወይም ሀሳብን ነው። "በውሳኔው ጠቢብ የሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በጥንካሬው ታላቅ
"ጥንካሬ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠንካራ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "በጥንካሬው እንዴት ታላቅ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ላይ ደንድኖ ስኬት ያገኘ ማን ነው?
ይህ "ማንም" የሚል ምላሽ የሚጠበቅበት ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ነው። በገለጻ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። "ማንም በእርሱ ላይ ራሱን አደንድኖ ፍሬያማ የሆነ የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ላይ ራሱን አደንድኖ
ራስን ማደንደን ማለት ግትር መሆን ማለት ነው። "እርሱን ተቃውሞ" ወይም "እርሱን ሳያከብር" (ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም)
ተራሮችን ከስፍራቸው የሚያስወግድ
"እግዚአብሔር ተራሮችን ያስወግዳል"
በእርሱ ቁጣ
"ቁጣ" የሚለው ረቂቅ ስም "መቆጣት" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ ስለተቆጣ/እርሱ በመቆጣቱ ምክንያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ምድርን የሚያናውጠው እርሱ
"እግዚአብሔር ምድርን ያናውጣል"
ምሰሶዎቿን ያንቀጠቅጣል
"መሰረቶቿ እንዲንቀጠቀጡ ያደርጋል"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Job 9:7
ከዋክብትን የጋረደ ማን ነው?
"ከዋክብትን ከመታየት የሚከለክል ማን ነው"
በራሱ ችሎታ ሰማያትን የዘረጋ ማን ነው
እግዚአብሔር ሰማያትን ካለ ማንም እርዳት እንደፈጠረ፣ ሰማያት እርሱ የዘረጋቸው ስራዎቹ መሆኑ ተነግሯል። (ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
የባህር ማዕበልን የሚከለክል
እግዚአብሔር ባህርን ጸጥ እንደሚያደርግ ተገልጾዋል። "እግሮቹን በባህረ ማዕበል ላይ ያሳርፋል" ወይም "የባህር መዕበልን ጸጥ ያደርጋል በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ድብ፣ ኦሪዮን፣ ፕልያዲስ
እነዚህ በሰማይ ላይ የተለየ ቅርጽ የሚሰሩ የሚመስሉ የከዋክብት ስብስብ ስሞች ናቸው። (የማይታወቀውን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)
ኦሪዮን
በግሪኮች አፈታሪክ ውስጥ ዝነኛ የሆነ አዳኝ
ፕልያዲስ
በሰማይ የተቀራረቡ የሚመስሉ በርካታ ብሩህ ከዋክብት
የከዋክብት ስብስብ
በሰማይ ላይ የተለየ ቅርጽ የሚሰሩ የሚመስሉ የከዋክብት ስብስቦች
Job 9:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው በእነዚህ በእያንዳቸው ቁጥሮች ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤን በመገልገል ድርብ ሃሳቦችን ተጠቅሞ የእግዚአብሔርን ታላቅነት፣ የማይታይ መሆኑን እና ሉዓላዊነቱን በአንድ ሃሳብ ለማስተላለፍ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የማይደረስባቸው/የማይመረመሩ ነገሮች
"ለመረዳት የማይቻሉ ነገሮች"
እነሆ
"ተመልከት" ወይም "አድምጥ" ወይም "ልነግርህ የተዘጋጀሁትን ለመስማት ትኩረት ስጥ።"
እርሱ አለፈ
"እርሱ በዚያ አለፈ" ወይም "እርሱ ተንቀሳቀሰ"
እርሱ አንዳች ነገር ቢነጥቅ፣ ማን ሊያስቆመው ይችላል? እርሱን 'ምን እያደረግህ ነው' ብሎ ሊጠይቀው የሚችል ምን ነው?
እነዚህ "ማንም" የሚል ምላሽ ሚጠበቅባቸው ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች ናቸው። በገለጻ መልክ ሊጻፉ ይችላሉ። "እርሱ አንድ ነገር ቢወስድ፣ ማንም ሊያስቆመው አይችልም። ማንም 'ምን እያደረግህ ነው?' ሊለው አይችልም። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ አንዳች ነገር ቢነጥቅ
"እርሱ አንድ ነገር ቢወስድ" ወይም "እርሱ አንድ ነገር መንጠቅ ቢፈልግ"
Job 9:13
ረዓብን የሚረዱ ከእርሱ በታች ይሰግዳሉ
እዚህ ስፍራ "ከእርሱ በታች መስገድ" የሚለው መገዛትን ወይም መሸነፍን ይወክላል። "እርሱ የረዓብን ረዳቶች ያደቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመለከቱ)
ረዓብ
እዚህ ስፍራ "ረዓብ" የሚለው ቃል የባህር አውሬን ያመለክታል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ታዲያ ከእርሱ ጋር እሟገት ዘንድ ፣ ለእርሱስ ምክንያት ለማቅረብ ቃላት ማግኘት እችላለሁን?
ኢዮብ እግዚአብሔርን ለመግጠም አቅም እንደሌለው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ሁለት ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ያቀርባል። እነዚህ ጥያቄዎች በገለጻ መልክት እንደገና ሊጻፉ ይችላሉ። "ስለዚህ በእርግጥ እኔ ለእርሱ መልስ ልሰጥ አልችልም ወይም ለእርሱ ምክንያት ለማቅረብ/ከእርሱ ጋር ለመከራከር ቃላት ልመርጥ አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 9:16
በአውሎ ነፋስ ሰብሮኛልና
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣበትን መከራ ከአውሎ ነፋስ ተጽዕኖ ጋር ያነጻጸረዋል። "በአውሎ ነፋስ እንደተጎዳሁ ጎድቶኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አውሎ ነፋስ
ጥቃት የሚያደርስ ሀያለኛ ነፋስ
ቁስሌን አበዛው
"ብዙ ቁስሎች አደረገብኝ" ወይም "ደጋግሞ አቆሰለኝ"
ያለ ምክንያት
"ምንም እንኳን እንዲህ እንዲያደርግ የሚያበቃ ጥፋት ባልሰራም" ወይም "ምንም እንኳን ንጹህ ብሆንም"
ትንፋሽ እንዳገኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "ደግሜ መተንፈስ እንድችል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ በመራራነት ሞላኝ
ይህ ቁጥር እግዚአብሔር የኢዮብን ህይወት እንዲመረር በሚያደርጉ ነገሮች እንደሞላው ይናገራል። "መራርነት" የሚለው ረቂቅ ስም "መራራ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "በመራራ ነገሮች ሞላኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 9:19
ይህ የጥንካሬ ጉዳይ ቢሆንም
"የጥንካሬ መፎካከሪያ ቢኖርም"
እነሆ፣ እርሱ ታላቅ ነው
"ተመልከት እርሱ ታላቅ መሆኑን ትረዳለህ" ወይም "እኔ ልነግርህ ለተዘጋጀሁት ነገር ትኩረት ስጥ፡ እርሱ ታላቅ ነው"
እርሱ ታላቅ ነው
"እርሱ ከሁሉ ታላቅ ነው"
ለእርሱ ማን የክስ መጥሪያ ሊያቀርብለት ይችላል?
ይህ ጥያቄ "ከቶ ማንም" የሚል ምላሽ እግዚአብሔርን ወደ ፍርድ ቤት ሊያቀርበው አይችልም የሚል ምላሽ ያሰጣል። ይህ በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ለእርሱ መጥሪያ ሊያቀርብለት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ምንም እንኳን ጻድቅ/ትክክለኛ ብሆንም፣ የገዛ አንደበቴ ይፈርድብኛል፤ እንከን የለሽ ብሆንም ቃሎቼ ይኮንኑኛል።
ይህ ሀረግ ተመሳሳይ ሃብን ሁለት ጊዜ ደግሞ በማቅረብ አጽንኦት ይሰጣል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ትክክለኛ/ጻድቅ ብሆንም
እዚህ ስፍራ "እኔ ትክክለኛ ነኝ" የሚለው ትክክለኛ የሆነውን ያረግኩት እኔ ነኝ ማለት ነው። "ምንም እንኳን ትክክለኛ ነገሮችን ባደርግም" ወይም "ምንም እንኳን እኔ ንጹህ ብሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ስማዊ ቅጽሎች የሚሉትን ይመልከቱ)
የገዛ አንደበቴ ይኮንነኛል/በደለኛ ያደርገኛል
እዚህ ስፍራ "አንደበት" የሚለው የኢዮብን ቃላት ነው። "የራሴ ቃላት ይከሱኛል" ወይም " የተናገርኩት ይኮንነኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ነውር ባይኖርብኝም
"ጥፋት/እንከን ባይኖርብኝም"
የራሴ ቃሎች ጥፋተኛ መሆኔን ያሳያሉ
እዚህ ስፍራ "የራሴ ቃሎች" የሚለው የተገለጸው ቃላቶቹ ራሳቸው እርምጃ መውሰድ እንደሚችሉ ተደርጎ ነው። "እግዚአብሔር እኔ የተናገርኩትን የእኔኑ ጥፋተኝነት ለማረጋገጥ ይጠቀምበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጥፋተኛ
እዚህ ስፍራ ይህ ቃል "ገልበጥባጣ" ወይም "ጠማማ" የሚል ትርጉም አለው።
Job 9:21
እኔ ነውር አልባ ነኝ
"እኔ ጥፋት የለብኝም"
ስለ ራሴ
"በእኔ ላይ የደረሰው"
ምንም ልዩነት አያመጣም
"ልዩነት የለውም" ወይም "ምንም ማለት አይደለም"
ጥፋት የሌለበትን እና ንጹሁን ሰው በአንድነት ያጠፋል

እዚህ ስፍራ "ነውር/ጥፋት የሌለበት" እና "ክፉ" የሚሉት ቃላት በመሃል ያሉትን ሁሉ የሚያካትት ሁለት ጽንፍ ነው። "እንከን የሌለውን እና ክፉውንም ሁሉንም ወደ ፍጻሜ ያመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

መቅሰፍት በድንገት ሲገድል

እዚህ ስፍራ "መቅሰፍት" የሚለው ቃል ለማኛቸውም አይነት ጥፋት ዘይቤ ነው። "በእንገት ጥፋት ሲደርስ እና ሰዎች ሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (በ ተመልከቱ)

የንጹህ ሰው ተስፋ መቁረጥ

"ተስፋ መቁረጥ" የሚለው ቃል ረቂቅ ስም ሲሆን "ተስፋ ቆረጠ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። እዚህ ስፍራ ተስፋ እየቆረጠ ለሚገኝ ንጹህ ሰው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ተስፋ የቆረጡ ንጹሀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (በ ተመልከቱ)

ንጹህ

ይህ ስማዊ ቅጽል ነው። "ንጹህ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (በ ተመልከቱ)

ምድር ተሰጥታለች

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ምድርን ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድር

እዚህ ስፍራ "ምድር" የሚለው የሚወክለው በምድር ላይ የሚኖሩ ዎችን ነው። "የዓለም ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በ…እጅ ውስጥ

እዚህ ስፍራ "እጅ" "መቆጣጠር ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በ…ቁጥጥር ስራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር የፈራጆቿን ፊት ሸፍኗል

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር እግዚአብሔር የምድር ፈራጆችን/ዳኞችን እውነት እና ሀሰት በሆነው መሃል መለየት እንዳይችሉ ከልክሏቸዋል። "እግዚአብሔር ፈራጆቿን አሳውሯል" ወይም "እግዚአብሔር ፈራጆቿ/ዳኞቿ በትክክል እንዳይፈርዱ ከልክሏቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህንን ያደረገው እርሱ ካልሆነ፣ ታዲያ ይህንን ያደረገው ማን ነው?

"እነዚህን ነገሮች ያደረገው እግዚአብሔር ካልሆነ፣ ማን አደረጋቸው ይባላል?"

Job 9:25

ቀኖቼ ከሯጭ መልዕክተኛ ይልቅ ፈጣኖች ናቸው

ኢዮብ ቀኖቹ እንዴት በፍጥነት እያለፉ እንደሆነ የገለጸው ከፈጣን ሯጭ ጋር በማወዳደር ነው። "ቀኖቼ በፍጥነት ያልፋሉ" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሯጭ መልዕክተኛ

"ሯጭ" ወይም "የሚሮጥ ሰው"

ቀናቶቼ ይበራሉ

ይህ የኢዮብ የህይወቱ ቀናት እንደ ሰው መሮጥ እንደሚችል ተደርጎ ተስሏል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የትም ስፍራ መልካምን ማየት አልቻሉም

ይህ የኢዮብን የህይወቱን ቀናት እንደ ሰው የሚያዩ ሆነው ተስለዋል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንዳች መልካም

"አንዳች መልካም ነገር"

እንደ ደንገል ታንኳ ፈጣኖች ናቸው

ኢዮብ ቀኖቹ እንዴት በፍጥነት እያለፉ እንደሆነ ከፈጣን ታንኳ ፍጥነት ጋር ያነጻጽራል። "እንደ ደንገል ታንኳ በፍጥነት ያልፋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የቄጠማ ደንገል ታንኳ

"ከቄጤማ የተሰራ ታንኳ።" ደንገል ቄጠማ ውስጡ ክፍት የሆነ በወንዝ ዳርቻ የሚበቅል ሳር መሰል ተክል ነው።

ንስር ወደ ሚያድነው በፍጥነት ቁልቁል እንደሚወርድ

ኢዮብ ቀናቱ እንዴት በፍጥነት እንደሚያልፉ ትልቁ ወፍ ንስር ወደሚያድነው ነገር ቁልቁል እንዴት እንደሚወረወር በማነጻጸር ይናገራል። "ንስር ምግቡን ለማግኘት/ ለመያዝ ከላይ ቁልቁል በፍጥነት ወደ ታች እንደሚወርድ/እንደሚበር" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በፍጥነት ወደታች መውረድ

"በፍጥነት ቁልቁል መውረድ"

Job 9:27

ስለ ማማርርባቸው ነገሮች እረሳለሁ

"ምሬት" የሚለው ረቂቅ ስም "ማማረር" በሚለው ግስ መተርጎም ይችላል። "ማማረሬን አቆማለሁ" ወይም "በእግዚአብሔር ላይ ማማረሬን አቆማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ማማረሬን

ኢዮብ በማን ላይ እንደሚያማርር በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "በእግዚአብሔር ላይ ማማረሬን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃዘንተኛ ፊቴን መልሼ ደስተኛ እሆናለሁ

የኢዮብ ሀዘንተኛ ገጽ የተገለጸው አንድ ዞር ሊደረግ እንደሚችል ነገር ተደርጎ ነው። ሀዘንተኛ ሆኜ መታጠቴን አቁሜ ፈገግ እላለሁ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሀዘኖቼ ሁሉ ያስፈሩኛል

ኢዮብ በቁጥር 27 የተናገረውን ቢያደርግ ሊከተል የሚችለውን ውጤት ቁጥር 28 እና 29 ይገልጻሉ። ይህ "ከዚያ" የሚለውን ቃል በመጨመር ሊገለጽ ይችላል። "ከዚያም ከሀዘኖቼ ሁሉ የተነሳ እፈራለሁ" (አያያዥ ቃላት/መስተጻምር የሚለውን ይመልከቱ)

ከሀዘኔ ሁሉ የተነሳ

"ሀዘን" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። "ከጎዱኝ ነገሮች ሁሉ የተነሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እኮነናለሁ

"ተጠያቂ እሆናለሁ ደግሞም እቀጣለሁ።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ይፈርድብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይምተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ስለምን በከንቱ እደክማለሁ?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው የእግዚአብሔርን ፊት ለማግኘት የሚያደደርገው ሙከራ ምንም ጥቅም እንደማያስገኝለት ማሰቡን በትኩረት ለመግለጽ ነው። ኢዮብ ሊያደርግ እየሞከረ ስለሚገኘው ነገር በውስጠ ታዋቂነት የሚገኘው መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይቻላል። "የእግዚአብሔርን ፊት ለማግኘት መሞከሬ አንዳች ጥቅም የለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 9:30

ፊቴን በበረዶ ውሃ ብታጠብ እንኳን

"ሰውነቴን በንጹህ፣ የተራ ውሃ ብታጠብ"

የበረዶ ውሃ

ከሟሟ በረዶ የተገኘ ውሃ

በረዶ

ከደመና የሚወርድ የአየር ጸባዩ ቀዝቃዛ በሆነ ቦታ የሚወርድ ደቃቅ የቀዘቀዘ ውሃ

እጆቼን እጅግ ባነጻ

"እጆቼን ፍጹም ባነጻ።" አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች "በጣም ጠንካራ በሆነ ሳሙና እጆቼን ባነጻ" ብለው ይተረጉሙታል።

በዘአቅት ውስጥ ታስምጠኛለሁ

"ወደ ጉድጓድ ትወረውረኛለህ"

የገዛ ልብሶቼ ይጸየፉኛል

እግዚአብሔር ወደ ጉድጎድ ከጣለው በኋላ የኢዮብ ልብሶች የተገለጹት ለኢዮብ አሉታዊ ምላሽ እንዳላቸው ተደርጎ ነው። "ገዛ ልብሶቼ እጅግ ይጸየፉኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 9:32

እመልስለታለሁ

ኢዮብ እግዚአብሔር ስህተት ሰርተሃል ብሎ እንደከሰሰው ያመለክታል፣ እርሱም ለክሶቹ መልስ መስጠት እንደሚፈልግ ይናገራል። "ላቀረበብኝ ክስ ምላሽ እንድሰጥ" ወይም "እራሴን እንድከላከል" ወይም "ከእርሱ ጋር ስለ ንጹህነቴ እንድከራከር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አብረን ወደ ፍርድ/ችሎት እንግባ
"ወደ ፍርድ/ችሎት አብረን እንግባ።" እዚህ ስፍራ "ፍርድ ቤት" የሚለው ሰዎች ቀርበው ዳኛ ለክርክራቸው መፍት የሚሰጥበትን ቦታ ነው። "አብሮ ወደ ፍርድ ቤት መግባት" እርስ በእርስ ተካሶ ወደ ፍርድ ቤት መሄድን የሚያመለክት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እውነቱ እንዲወጣ በዳኛ ፊት አንዱ ከሌላው ጋር መከራከር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በመካከላችን ዳኛ የለም
ይህ ማለት በኢዮብ እና በእርሱ መሃል ከእግዚአብሔር የሚበልጥ ምን ትክክል እንደሆነ ሊወስን የሚችል ዳኛ የለም ማለት ነው።
በሁለታችንም ላይ እጁን የሚጭን
እዚህ ስፍራ "እጁን የሚጭን" ማለት የበለጠ ስልጣን ወይም ሃይል ያለው ማለት ነው። "እጁን በሁለታችንም ላይ የሚያኖር" ወይም "በሁለታችንም ላይ ስልጣን ያለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 9:34
አያያዥ ሃሳብ፡
እነዚህ ቁጥሮች በኢዮብ እና በእግዚአብሔር መካከል ገብቶ ሊዳኝ የሚችል ከእግዚአብሔር የሚበልጥ ማንም እንደሌለ ቀደም ሲል የቀረበውን ክርክር ይቀጥላሉ
የእግዚአብሔርን በትር ከእኔ ውሰድ
እዚህ ስፍራ "የእግዚአብሔር በትር" የሚለው እግዚአብሔር ኢዮብን መቅጣቱን ወይም ማረሙን የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እግዚአብሔር እኔን መቅጣቱ ይቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ማስፈራራቱ ከእኔ ይቁም
"ፍርሃት" የሚለው ረቂቅ ስም "አስፈራራ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ እኔን ማስፈራራቱን እና ማስፈራቱን ማን ባስቆመልኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያ እኔም እናገራለሁ
"ቀጥሎ እናገራለሁ"
ነገሮች አሁን ባሉበት
"ምክንያቱም አሁን ነገሮች እንዲህ ናቸውና"

---

Chapter 10
Job 10:1
ህይወቴ ዝላለች
"መኖር ሰልችቶኛል/ደክሜያለሁ"
የማማርርበትን ምክንያት በግልጽ እናገራለሁ
"መግለጽ" እና "ማማረር" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ገለጸ" እና "አማረረ" በሚሉ ግሶች ሊተረጎሙ ይችላሉ። "የማማርርበትን ነገር በግልጽ እናገራለሁ" ወይም "በግልጽ እከራከራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
በነፍሴ ምሬት እናገራለሁ
ኢዮብ እንዴት እንደተሰማው የተገለጸው የተነጻጸረው ከመራራ ጣዕም ጋር ነው። "መራርነት" የሚለው ረቂቅ ስም "በመራርነት" በሚለው ተውሳከ ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ውስጣዊ ማንነቴ በመራርነት ይናገራል" ወይም "እኔ በመራርነት እናገራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
እኔን መጨቆንህ ለአንተ መልካም ነገር ማድረግ ነውን፣ በክፉዎች እቅድ ፈገግ እያልክ የእጆችህን ስራዎች መናቅህስ መልካም ነውን?
ይህ ጥያቄ "አይደለም" የሚል ምላሽ ይጠበቅበታል፤ ደግሞም በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። "በክፉዎች ስራ ፈገግ እያልክ፣ እኔን መጨቆንህ መልካም አይደለም፤ የእጆችህን ስራ መናቅህ ትክክልአይደለም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይልከቱ)
የእጆችህ ስራዎች
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የተወከለው በእርሱ "እጆች" ነው። "አንተ የፈጠርከው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በክፉዎች እቅድ ይስቃል
እዚህ ስፍራ "ይስቃል" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር የሚወክለው የእግዚአብሔርን መስማማት። "የክፎዎችን እቅድ ያጸድቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 10:4
የስጋ ዐይን አለህን? ሰው እንደሚያይ ታያለህን?
እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ታራራቢ ትርጉም አላቸው። እነዚህ ጥያቄዎች እግዚአብሔር ሰው እንደማያይ ወይም ሰው በሚረዳበት መንገድ ነገሮችን እንደማይረዳ ትኩረት ለመስጠት አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃሉ። ጥያቄዎቹ በገለጻ መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። "አንተ የስጋ ዐይን የለህም፣ አንተ ሰው እንደሚያይ አታይም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
የአንተ ቀኖች እንደ ሰው ቀናት ናቸውን ወይስ የአንተ አመታት እንደ ሰው አመታት ናቸው… ደግሞም ከእጆችህ የሚያድነኝ ማንም የለም?
እነዚህ ጥያቄዎች እግዚአብሔር ዘለዓለማው መሆኑን እና የሰው ዘመን ጥቂት መሆኑን ትኩረት ለመስጠት አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃሉ። ይህ በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። "የአንተ ቀናት እንደ ሰው ቀናት አይደሉም የአንተ አመታት እንደ ሰው አመታት አይደሉም…ደግሞም ከአንተ እጅ የሚያድነኝ ማንም የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ቀናት እንደ ሰው ቀናት…የአንተ አመታት እንደ ሰው አመታት
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተቀራራቢ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ቀናት
"የአንተ ቀናት ቁጥር"
የአንተ አመታት
"የአንተ አመታት ቁጥር"
በእኔ ስህተት ላይ ጥያቄ ታነሳለህ… ኃጢአቴን ትከታተላለህ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተቀራራቢ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጥያቄ ታነሳለህ
"ትከታተለኛለህ"
ከእጆችህ
እዚህ ስፍራ "እጆችህ" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን ሀይል ነው። "ከአንተ ሃይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 10:8
የአንተ እጆች
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን እና የእርሱን የመፍጠር ድርጊት ነው። "አንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ እጆች አበጁኝ ሰሩኝም
ኢዮብ እግዚአብሔር እንዴት በጥንቃቄ እርሱን እንደፈጠረው ለመግለጽ ሸክላ ሰሪ ሸክላውን የሚያበጅበትን አሰራር በዘይቤ ይጠቀማል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አበጀኝ ሰራኝም
"ቅርጽ ሰጠኝ ሰራኝ" "ቅርጽ ሰጠኝ" እና "አበጀኝ" የሚሉት ቃላት በትርጉም ተመሳሳይ ናቸው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
ልብ በል
"አስታውስ"
ዳግም ወደ አፈር አምጣኝ
"እንደገና ወደ አፈር መልሰኝ"
Job 10:10
አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ሀረጋት፣ ኢዮብ እግዚአብሔር እንዴት በእናቱ ማህጸን ውስጥ እንዳበጀመው ለመግለጽ የሸክላ ሰሪተኛን ቋንቋ ይጠቀማል። (ስነ ግጥም የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ወተት አላፈሰስከኝምን፣ እንደ እርጎስ አላረጋኸኝምን?

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ አዎንታዊ ምላሽ የሚጠብቅ ጥያቄ ነው። "እንደ ወተት አፈሰስከኝ እንደ እርጎ አረጋኸኝ" ወይም "ፈሳሽ ወተት እርጎ እንደሚሆን በማህጸን አበጀኸኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
አንተ
እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው
እኔ
እዚህ ስፍራ "እኔ" የሚለው የሚያመለክተው ኢዮብን ነው።
ቆዳ እና ስጋ አለበስከኝ
እግዚአብሔር የኢዮብን አካል በቆዳ እና ስጋ መሸፈኑ የተገለጸው እግዚአብሔር ኢዮብን እንዳለበሰው ተደርጎ ነው። "ሰውነቴን በቆዳ እና ስጋ ሸፈንክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በአንድነት አጣጠምከኝ
"በአንድነት ሸመንከኝ።" እግዚአብሔር የኢዮብን አካል በማህጸን ማዋደዱ የተገለጸው እግዚአብሔር ጨርቅን እንደሸመነ ተደርጎ ነው። "አዋደድከኝ/በአንድነት አደረግከኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጅማቶች
ጡንቻን ከአጥንት ወይም ከሌላ የሰውነት ክፍል ጋር የሚያያይዝ እና ነጭ ጠንካራ ማስተሳሰሪያ
Job 10:12
ህይወት እና የቃል ኪዳን ታማኝነት ሰጠኸኝ
"ህይወት" እና "ታማኝነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ህያው" እና "ታማኝ" በሚል ሊገለጹ ይችላሉ። "አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ነበርክ ደግሞም ህያው እንድሆን ፈቅደሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ እርዳታ
"የአንተ እንክብካቤ"
መንፈሴን ጠበቀ
እዚህ ስፍራ ኢዮብ የተወከለው "በመንፈሱ" ነው። "ጠበቅከኝ" ወይም "እኔን በጥንቃቄ ተመለከትክ" ወይም "በደህንነት/በሰላም ጠበቅከኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህ አንተ በልብህ የሰወርካቸው ነገሮች
እዚህ ስፍራ "እነዚህ ነገሮች" የሚለው የሚያመለክተው ከተከታዩ ቁጥር ላይ የሚገኘውን ነገር ነው
እነዚህ አንተ በልብህ የሰወርካቸው ነገሮች
እዚህ ስፍራ "አንተ በልብህ የሰወርካቸው" ማለት እግዚአብሔር ምስጢር አድርጓቸዋል ወይም ደብቆታል ማለት ነው። "አንተ ምስጢር ያደረካቸው እነዚህ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ታውቀዋለህ
"አንተ ትጠብቀኛለህ"
Job 10:15
በክፋት አንድ ነገር ባደርግ
"ክፉ ነገሮችን ባደርግ"
ወዮው ለእኔ
"ለእኔ ይህ እደምን መጥፎ ይሆናል"
ራሴን ቀና ባደርግ
ይህ ፈሊጥ እርግጠኛ ወይም ልበ ሙሉ መሆን ማለት ነው። "ራስን ቀና ባደርግ" ወይም "ልበ ሙሉ መሆን" ወይም "ስለ ራሴ እርግጠኛ ብሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በሀፍረት ተሞላሁ - መከራዬን ተመልከት
ሌላው ሊሰጥ የሚችል ትርጉም፣ "ውርደት ተሞልቻለሁ በመከራዬ ተይዣለሁ"። ውርደቱ መጥፎ ሆነ ሳለ መከራው ደግሞ የከፋ ነው።
በውርደት ተሞልቻለሁ
"ሙሉ ለሙሉ አፍሬያለሁ" ወይም "ከዚህ በኋላ የሚያከብረኝ ማንም አይኖርም"
ውርደት
ሀፍረት
የደረሰብኝን ውርደት ተመልከቱ
"ተዋረደ" የሚለው ረቂቅ ስም "ውርደት" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል።
"እግዚአብሔር እንዴት እንዳዋረደኝ ተመልከቱ" (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ራሴን ቀና ባደርግ፣ አንተ እንደ አንበሳ ታደባብኛለህ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)ይህ ያልሆነ መላምታዊ ሁኔታ ነው ወይም 2) ይህ በተደጋጋ የተፈጸመ ሁኔታ መግለጫ ነው። "ራሴን ቀና ሳደርግ፣ እንደ አንበሳ ታደባብኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)
ራሴ ቀና ባደርግ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር በራስ መተማመን ወይም ኩራት ማለት ነው። "ብኮራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመለከቱ)
Job 10:17
አንተ በእኔ ላይ አዲስ ምስክር ታመጣለህ
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚደርስበት መከራ የተገለጸው በእርሱ ላይ ምስክር የሚሆኑ ሰዎች እንደሆኑ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእኔ ላይ ቁጣህ ይጨምራል
"ቁጣ" የሚለው ረቂቅ ስም "ቁጡነት" በሚል ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "በእኔ ላይ ቁጡነቱ እየጨመረ መጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በአዲስ ሰራዊት/ሀይል ታጠቃኛለህ
እግዚአብሔር ወደ ኢዮብ መከራ መላኩ የተገለጸው እግዚአብሔር ሳያቋርጥ በኢዮብ ላይ አዲስ ሰራዊት እንደሚልክ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 10:18
ከማህጸን አወጣኸኝ
እዚህ ስፍራ ከማህጸን ማውጣት የሚወክለው ወደዚህ ዓለም መምጣትን/ መወለድን ነው። "ከእናቴ ማህጸን አወጣኸኝ" ወይም "ወደዚህ ዓለም አመጣኸኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መንፈሴን እሰጣለሁ
አንድ ሰው መንፈሱን መስጠቱ የሚወክለው መሞትን ነው። "ሞተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዐይኖች ለዘለአለም አይመለከቱኝም
እዚህ ስፍራ ኢዮብ "ዐይን" የሚለውን የተጠቀመበት ሰውን ሁሉ ለመጥቀስ ነው። ማንም ሰው ከማየቱ አስቀድሞ በተወለደበት ጊዜ ቢሞት ይመኛል። " አስቀደሞ ማንም ሰው ሳይመለከተኝ" ወይም "ከመወለዴ አስቀድሞ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ያልተፈጠርኩ ያህል ነው
"በፍጹም አልኖርኩም"
በወሰዱኝ ኖሮ/ወደ መቃብር
"አካሌ ወደ መቃብር ይወሰድ ነበር"
Job 10:20
ቀኖቼ ጥቂት አይደሉምን?
እዚህ ስፍራ "ቀኖቼ" የሚለው የሚወክለው የኢዮብን የህይወት ዘመን መጠን ነው። ይህ ጥያቄ ኢዮብ ጥቂት የቀናት እድሜ ብቻ እንዳለው ለማጉላት አዎንታዊ ምላሽ ይጠብቃል። ይህ በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። "ከእንግዲህ በህይወት ለመቆየት የቀሩኝ ጥቂት ቀናት ብቻ ናቸው" ወይም "ህይወቴ በቅርቡ ያበቃለታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሩ
እዚህ ስፍራ የሞቱ ሰዎች መንፈስ የሚሄድበት ቦታ የተገለጸው ምድር እንደሆነ ተደርጎ ነው። "ስፍራው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጨለማው እና የሞት ጥላው
"የሞት ጥላ" የሚለው ሀረግ "ጨለማ" የሚለውን ሀሳብ ያጠናክራል። ሁለቱም ሀረጎች የሞቱ ሰዎች መንፈስ ወዴት እንደሚሄድ ይገልጻሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
የሞት ጥላ
ይህ በኢዮብ 3:5 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።
እንደ እኩለ ሌሊት የጨለመ
የሞቱ ሰዎች መንፈስ የሚሄድበት ስፍራ ጥቁረት የተነጻጸረው ከእኩለ ሌሊት ጨለማ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያለ አንዳች ስርአት

ይህ አሉታዊ ሀረግ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ግራ በመጋት የተሞላ" ወይም "ሁሉም ግራ የተጋባበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እኩለ ለሊት የጨለመ

የሞቱ ሰዎች ነፍስ የሚሄድበት ስፍራ መጨለም የተነጻጸረው ከእኩ ለሊት ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 11

Job 11:1

ነዕማታዊው ሶፋር

ይህ ስም በኢዮብ 2፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ከነዕማታ ግዛት የሆነው ሶፋር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደዚህ የበዙ ጥያቄዎች/ቃላት መልስ ሊያገኙ አይገባምን?

ሶፋር ጥያቄውን በአሉታ የሚያቀርበው የኢዮብ ቃላት/ንግግር መገታት አለበት የሚለውን ለማጉላት ነው። "ለእነዚህ ንግግሮች ሁሉ እኛ መልስ ልንሰጥ ይገባል!" ወይም "አንድ ሰው ለዚህ ሁሉ ንግግር መልስ መስጠት ይኖርበታል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ እንዲህ ንግግር የሚያበዛ ሰው ሊታመን ይገባዋልን?

ሶፋር ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ኢዮብ የሚናገረውን ማመን እንደማይኖርባቸው ትኩረት ለመስጠት ነው። "ይህ ሰው በንግግር የተሞላ ነው፣ ነገር ግን ሰዎች ሊያምኑት አይገባም!" ወይም "ብዙ ንግግርህ ብቻውን አንተ ንጹህ መሆንህን አያሳይም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ መዘላበድ ሌሎች ዝም እንዲሉ ያደርጋልን?

ሶፋር ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ኢዮብን ለመገሰጽ ነው። "አንተ ብዙ ስለተናገርክ ብቻ፣ ሌሎች ዝም ማለት አለባቸው ማለት አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ስትቀልድ፣ እንድታፍር የሚያደርግህ ሰው የለምን?

ሶፋር ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ኢዮብን ለመገሰጽ ነው። ኢዮብ ቀለደ የተባለውን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። "እኛ በተናገርነው ላይ አንተ ትቀልዳለህ/ ታሾፋለህ። አሁን እኛ አንተን እናሳፍርሀለን!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን እና (በ ተመልከቱ)

Job 11:4

እምነቴ ንጹህ ነው

"መረዳቴ ትክክል ነው"

በአንተ ዐይኖች ንጹህ ነኝ

ዐይኖች አመለካከትን ይወክላል፣ ይህም እግዚአብሔርን የሚመዝንበት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ እግዚአብሔር ነውር አልባ አድርጎ እንደሚያየው መናገሩ። "አንተ ነውር እንደሌለብኝ ትናገራለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው ወይም 2) ኢዮብ ነውር እንደሌለበት እግዚአብሔር እንደሚፈርድላት እንደሚያምን። "እኔ ነውር/ እንከን እንደሌለብኝ እውቅና መስጠት ይገባሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር እንዲህ ይናገራል... ከንፈሩን ከፍቶ በአናንተ ላይ ይናገራል

"ከንፈሩን ይከፍታል" የሚሉት ቃላት ንግግር ለሚለው ሜቶኖሚ /ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድነት ሆነው ሶፋር እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ በሀይል ይናገራል የሚለውን ፍላጎቱን ያጎላሉ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ የሚያሳየው... የጥበብ ምስጢር

"የጥበብ ምስጢር" የሚለው በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "በኃጢያትህ ምክንያት መከራን እንደምትቀበል ያስረዳሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከአንተ የሚጠብቀው/ለአንተ የከፈለው/ ለኃጢአትህ ከሚገባህ ያነሰውን ነው

ከኢዮብ የሚጠበቀው የሚለው የሚወክለው የኢዮብን መቅጣትን ነው። "እግዚአብሔር እየቀጣህ ያለው ልትቀጣ ከሚገባህ ያነሰውን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 11:7

እግዚአብሔርን በመፈለግ ልትረዳው ትችላለህ/መርምረህ ትደርስበታለህ? ሁሉን ቻይ የሆነውን ሙሉ ለሙሉ ልታውቀው ትችላለህ?

እነዚህ ሁለት ትይዩ ጥያቄዎች ተመሳሳይ ነገርን ይጠይቃሉ። ጸሐፊው የጥያቄ መልክን የተጠቀመው ትኩረት ለመስጠት ነው። "እግዚአብሔርን በመመርመር/ በመፈለግ እርሱን መረዳት አትችልም፣ ሁሉን ቻይ የሆነውን ሙሉ ለሙሉ ልትረዳው አትችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጉዳዩ

ይህ እግዚአብሔርን ማወቅ/ መረዳትን ያመለክታል። "እግዚአብሔርን ማወቅ/ መረዳት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ መንግስተ ሰማይ ሩቅ ነው...ከሲኦል ይጠልቃል

እግዚአብሔርን መረዳት አለመቻል ወደ እነዚህ እጅግ ሩቅ ወደሆኑ ስፍራዎች መሄድ እንደማይቻለው አይነት ተደርጎ ተነግሯል። "በሰማይ ወዳለው ከፍ ያለ ስፍራ እንደማይደረስ... በሲኦል ካዳለው ጥልቅ ስፍራ ይልቅ የማይደረስበት ነው" (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ምን ማድረግ ትችላለህ?

ሶፋር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው አንድ ሰው እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት አንዳች ነገር ማድረግ አይችልም የሚለውን ለማሳየት ነው። "አንዳች ነገር ማድረግ አትችልም" ወይም "በዚያ መታወቅ ያለበትን ሁሉ ማወቅ አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መጠኑ

ይህ ሊያመለክት የሚችለው አማራጭ ትርጉሞች 1) የእጋዚአብሔርን ታላቅነት 2) የእግዚአብሔርን ጥበብ ታላቅነት

ከምድር ይረዝማል... ከባህር ይሰፋል

የእግዚአብሔር ታላቅነት ወይም ጥበብ የተገለጸው በርቀት እንደሚለካ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 11:10

እርሱ.. በማንንም ላይ ቢዘጋ

"እግዚአብሔር... ማንንም በእስርቤት አስገብቶ ቢዘጋበት"

ማንንም ወደ ፍርድ ቢጠራ/ቢሰበስብ

"ፍርድ" የሚለው ረቂቅ ስም "ዳኘ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "እግዚአብሔር ሊፈርድበት ፈልጎ ማንንም ወደ እርሱ ቢጠራ/ቢሰበስብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ማን ሊያስቆመው ይችላል?

ይህ ጥያቄ ማንም እግዚአብሔርን ማስቆም እንደማይችል ትኩረት ይሰጣል። "ማንም ሊያስቆመው አይችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይህን አያስተውልምን?

ይህ እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚያይ ትኩረት ይሰጣል። "እርሱ በእርግጥ ይህንን ያያል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞኝ ሰዎች ግን ማስተዋል/መረዳት የላቸውም

"መረዳት" የሚለው ረቂቅ ስም "ተረዳ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ሞኝ ሰው ግን ይህንን አይረዳም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሜዳ አህያ ሰው ሲወልድ እነርሱ ይህን መረዳት ይችላሉ

የሜዳ አህያ በፍጹም ሰው መውለድ እንደማይችል ሁሉ ሞኝ ሰውም ይህን መረዳት ማግኘት አይችልም። "የሜዳ አህያ ሰው ከወለደ ብቻ ያን ጊዜ ሞኝ ሰው መረዳትን/ ጥበብን ያገኛል" ወይም "አህያ ሰው ሊወልድ እንደማይችል ሁሉ ሞኝ ሰውም መረዳት/ጥበብን ማግኘት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 11:13

ምናልባት ልብህን ቀና ብታደርግ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ልብ የሚወክለው አስተሳሰብን እና ዝንባሌን ነው። ልብን ማስተካከል የሚለው የሚወክለው ልብን ማረምን ነው። "ዝንባሌህን ብታስተካክል እንኳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እጅህን ወደ እግዚአብሔር ብትዘረጋ

ይህ እግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅን የሚወክል ድርጊት ነው። "ወደ እግዚአብሔር ጸልይ ወደ እርሱ ልመናህን አቅርብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ምናልባት ያ ኃጢአት በእጅህ ይገኛል

እጅ የሚወክለው አንድ ሰው የሚያደርገውን ነገር ነው። "ባለፈው ዘመን ክፉ ነገር አድርገህ ቢሆን እንኳን" ሚለው ውሰጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ከዚያ በኋላ ይህንን ከአንተ ታርቃለህ

ኃጢአትን ከኋላ መተው የሚወክለው ኃጢአትን መስራትን ማቆምን ነው። "ነገር ግን ከዚያ በኋላ ክፉ ነገሮችን ማድረግ ታቆማለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርክሰት በድንኳንህ እንዲኖር አትፍቀድ

እርክሰት እንዲኖር የሚለው የሚወክለው ጽድቅ ያልሆነ ነገር የሚያደርጉ ሰዎችን ነው። "በቤትህ የሚኖሩ የረከሱ ነገሮችን እንዲያደርጉ አትፍቀድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 11:15

ያለ ሀፍረት ምልክት ፊትህን ወደ ላይ አንሳ

"ፊትህን ወደ ላይ አንሳ" የሚለው የሚወክለው ልበ ሙሉ እና ጀግና የሆነ ሰውን ዝንባሌ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እንዳለፈ ውሃ ብቻ ታስታውሰዋለህ

ሶፋር መከራን አልፎ ከሄደ ወራጅ ውሃ ጋር ያነጻጽረዋል። "ታስታውሰዋለህ፣ ነገር ግን መከራው አልፎ እንደሄደ ውሃ ይረሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወትህ እንደ ማለዳ...ይሆናል

ሶፋር ትኩረት ለመስጠት ተመሳሳይ የሆነን ሃሳብ ይደግማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወትህ ከቀትር ብርሃን ይልቅ ብሩህ ይሆናል

ብሩህነት የሚወክለው ባለጸጋ እና ደስተኛ መሆንን ነው። "ህይወትህ ልክ እንደ እኩለ ቀን የብልጽግና እና የደስታ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳን ጨለማ ቢኖርም

ጨለማ እግርን እና ሃዘንን ይወክላል። "ምንም እንኳን ከባድ ችግር እን ሀዘን ቢኖርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ማለዳ ይሆናል

ማለዳ የሚወክለው ብርሃን፣ ብልጽግናን እና ደስታን ይወክላል። "እንደ ማለዳ ብልጽግና እና ደስታ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 11:18

ደህንነትህ የተጠበቀ ይሆናል...በሰላምም ታርፋለህ

ሶፋር ተመሳሳይ ሃሳብን ትኩረት ለመስጠት እና የሚቻል መሆኑን ለመግለጽ ሲል ይደግማል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

በሰላም ታርፋለህ

እዚህ ስፍራ "በሰላም ማረፍ" የሚለው "ዕረፍት" ማለት ነው። "በሰላም" የሚለው ሀረግ "በደህና/በአስተማማኝ" በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። "በሰላም ማረፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስም የሚሉትን ይመልከቱ)

የአንተ ስጦታ...ደግሞም በሰላም ትተኛለህ

ሶፋር ተመሳሳይ የሆነ ሃሳብ የሚደግመው ትኩረት ለመስጠት እና የሚቻል መሆኑን ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

በሰላም ትተኛለህ

"ረፍት" የሚለው ረቂቅ ስም "አረፈ" ከሚለው ግስ ጋር ሊገለጽ ይችላል። "ጋድም ትላለህ ደግሞም ታርፋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Job 11:20

የክፉ ሰዎች ዐይኖች ይጨልማሉ

የእነርሱ ዐይኖች የሚወክሉት መረዳታቸውን ነው። "የክፉ ሰዎች መረዳት ይጨልማል" ወይም "ክፉ ሰዎች መረዳት/እውቀት ማግኘት አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 12

Job 12:1

እናንተ እንደነዚህ አይነት ሰዎች መሆናች አያጠያይቅም፣ ጥበብ በእናንተ ዘንድ ትሞታለች

ኢዮብ በድርጊታቸው ይሳለቃል፣ ሀሳባቸው ምን ያህል የማይረባ እንደሆነ ያሳያቸዋል። "በእርግጥ እናንተ እንዲህ ያላችሁ ቁምነገረኞች ናችሁ፣ እውቀት ካለ እናንተ መኖር አትችልም" ወይም "እናንተ ብቸኛ ጥበብ ያላችሁ ሰዎች አድርጋችሁ ራሳችሁን ታሳያላችሁ፣ እናንተ በሞታችሁ ጊዜ ጥበብ ትጠፋለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት የሚለውን ዘይቤ ይመልከቱ)

አያጠራጥርም

"በእርግጥ"

እናንተ

በቁጥር 2 እና 3 ይህ ብዙ ቁጥር ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

እናንተ እነዚያ ሰዎች ናችሁ

"እናንተ ሁሉንም ነገር የምታውቁ ጠቃሚ ሰዎች ናችሁ"

በእርግጥ፣ እንደ እነዚህ ያሉ ነገሮችን የማያውቅ ማን ነው?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ለአድማጮቹ ግልጽ መሆን ያለበትን እውነት ለመግለጽ ነው። ይህ በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል። " በእርግጥ እንደ እነዚህ ያሉ ነገሮችን የማያውቅ ሰው የለም" ወይም "በእርግጥ እያንዳንዱ ሰው እነዚህን ነገሮች ያውቃል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 12:4

ለወዳጆቼ መሳለቂያ ሆኛለሁ - እግዚአብሔርን የምጠራ እና እርሱም ምላሽ ይሰጠኝ የነበረ እኔ፣

በእነዚህ ሀረጎች መሃል ያለው ግንኙነት "ምንም እንኳን" በሚሉት ቃላት ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ምንም እንኳን እግዚአብሔርን ጠርቼ የመለሰልኝ ብሆንም፣ አሁን ግን የወዳጆቼ መሳለቂያ ሆኛለሁ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አያያዥ ቃላት የሚለውን ይመልከቱ)

ትክክለኛ እና ያለ ነቀፋ የሆንኩት እኔ - አሁን መሳለቂያ ሆኛለሁ

በእነዚህ ሀረጋት መሃል ያለው ግንኙነት "ምንም እንኳን" በሚሉት ቃላት ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ምንም ያለ ነቀፋ እና ትክክለኛ ሰው ብሆንም፣ አሁን ግን የሰው መሳለቂያ ሆኛለሁ" (አያያዥ ቃላት የሚለውን ይመልከቱ)

በተመቸው ሰው አስተሳሰብ፣ መከራ የደረሰበት ሰው ይናቃል

"ሃሳብ"፣ "ምቾት"፣ "ንቀት"፣ "መከራ የደረሰበት/ዕደለ ቢስ" የሚሉት በሌሎች ሀረጋት ሊገለጹ ይችላሉ። "ቀላል ህይወት የሚመራ ሰው መከራ የሚቀበለውን ሰው ይንቀዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ መከራ ያመጣል

መከራ ማምጣት የሚወክለው ነገሩ እንዲሆን ምክንያት መሆንን ነው። "ብዙ መጥፎ ነገሮች እንዲፈጸሙ ምክንየት መሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግራቸው ለሚንሸራተት

የእግር መንሸራተት የሚወክለው በአደጋ ወይም ችግር ውስጥ መሆንን ነው። "አሁንም በችግር ውስጥ ለሚገኙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የዘራፊዎች ድንኳን ይበለጽጋል

የእነርሱ ድንኳን ይበለጽጋል የሚለው የሚወክለው ዘራፊዎች በድንኳናቸው ባለጸጋ እንደሚሆኑ ነው። "ዘራፊዎች በራሳቸው ድንኳን ውስጥ በብልጽግና ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የገዛ እጃቸው አማልክቶቻቸው ናቸው

"የገዛ እጃቸው" የሚለው ለጥንካሬ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን፤ "አማልክቶቻቸው" የሚለው ለኩራታቸው ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "በችሎታቸው እጅግ ይመካሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 12:7

ነገር ግን አሁን ጠይቁ…ለእናንተ ያሳውቋችኋል

እነዚህ 4 ሃሳቦች፤ አውሬዎች፣ ወፎች፣ ምድር እና አሶች ሁሉም ከኢዮብ ወዳጎች ይልቅ እግዚአብሔርን መረዳት እንደሚችሉ ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)

እናንተ

ይህ በኢዮብ ቁጥር 7 እና 8 ላይ ብዙ ቁጥር ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ነገር ግን አሁን አውሬዎችን ጠይቁ እነርሱም ያስተምሯችኋል

በዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ላይ የሚገኘው ትዕዛዝ እንደ መላምታዊ ሁኔታ ሆኖ ያገለግላል። "አውሬዎችን ብትጠይቁ ኖሮ፣ እነርሱ ባስተማሩዋችሁ ነበር።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስልጣን እና ሃላፊነቶች - ሌሎች ጥቅሞች እንዲሁም መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

የሰማይ ወፎችን ጠይቁ፣ እነርሱም ይነግሯችኋል

በዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ላይ የሚገኘው ትዕዛዝ እንደ መላምታዊ ሁኔታ ሆኖ ያገለግላል። የሰማይ ወፎችን ብትጠይቁ ኖሮ፣ እነርሱ ባስተማሩዋችሁ ነበር።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስልጣን እና ሃላፊነቶች - ሌሎች ጥቅሞች እንዲሁም መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

ወይም ከምድር ጋር ተነጋገሩ፣ እርሷ ታስተምራችኋለች

በዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ላይ የሚገኘው ትዕዛዝ እንደ መላምታዊ ሁኔታ ሆኖ ያገለግላል። "ወይም ከምድር ጋር ብትነጋገሩ ኖሮ፣ ባስተማረቻችሁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስልጣን እና ሃላፊነቶች - ሌሎች ጥቅሞች እንዲሁም መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

የባህር አሶች ያሳውቋችኋል

"የባህር አሶችን ጠይቁ" የሚለው ትዕዛዝ ከቀደሙት ዐረፍተ ነገሮች ለማለት የተፈለገው ይታወቃል። እንደ መላምታዊ ሁኔታ ሆኖ ይሰራል። "የባህር አሶችን ብትጠይቁ ኖሮ፣ ለእናንተ ያሳውቋችሁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና ስልጣንና ሃላፊነቶች - ሌሎች ጥቅሞች እንዲሁም መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 12:9

ይህንን… ከእነዚህ ሁሉ እንስሳት የማያውቅ የትኛው ነው?

ይህ ጥያቄ ሁሉም እንስሳት ያህዌ ይህን እንዳደረገ ያውቃሉ የሚለውን ያጎላል። ይህ ጥያቄ በገለጻ መለክ ሊጻፍ ይችላል። " ይህን… ከእነዚህ ሁሉ መሃል እያንዳንዱ እንስሳ ያውቃል።"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ እጆች ይህን አድርጓል

የያህዌ እጅ የሚወክለው የእርሱን ሀይል ነው። "ያህዌ ይህንን በሀይሉ አድርጓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በእርሱ እጅ ህይወት… እና የሰው ሁሉ እስትንፋስ አለ

የያህዌ እጅ የሚወክለው የእርሱን ሀይል ወይም መቆጣጠር/መግዛት ነው። "እግዚአብሔር እስትንፋስ ያለውን ነገር ሁሉ ህይወት ይቆጣጠራል፤ ደግሞም ለሰው ሁሉ እስትንፋስን ይሰጣል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የሰው ሁሉ እስትንፋስ

እዚህ ስፍራ "እስትንፋስ" የሚወክለው ህይወትን ወይም ለመኖር ያለ አቅምን/ችሎታ ነው።

Job 12:11

ላንቃ ጣዕምን እንደሚለይ ጆሮስ ቃላትን አይለይምን?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ሰዎች ሌሎች የሚናገሩትን በስማት ነገሩ መልካም መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንደሚመዝኑ/እንደሚፈርዱ ትኩረት ለመስጠት ነው። ጆሮ እና ላንቃ ለመስማት እና ጣዕም ለመለየት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "ሰዎች የሚናገሩትን እንሰማለን ደግሞም ምግብን እንደምቀምስ እንቀምሰዋለን ደግሞም እናጣጥመዋለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር እንደዚሁም ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጥበብ ከእድሜ ባለጸጎች ጋር ናት

"የእድሜ ባለጸጎች ጥበብ አላቸው።" "ጥበብ" የሚለው ረቂቅ ስም "ብልህ" በሚለው ሊገለጽ ይችላል። "ወንዶች" የሚለው ቃል በአጠቃላይ ሰዎች የሚለውን ያመለክታል። "አዛውንቶች ብልህ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ጥንካሬን የሚገልጹ ቃላት ሴቶችን ሲያካትቱ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀናት ሲጨምሩ መረዳት/ዕውቀት ይገኛል

ይህ የሚገልጸው ሰዎች ረጅም እድሜ በኖሩ መጠን እውቀት/መረዳትን እያገኙ ይሄዳሉ የሚለውን ነው። "መረዳት" የሚለው ረቂቅ ስም "ብዙ መረዳት" በሚለው ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ረጅም እድሜ ሲኖሩ መረዳት ይጨምራሉ/ያገኛሉ" ወይም "ብዙ ዘመን የኖሩ ሰዎች ብዙ መረዳት አላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Job 12:13

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢዮብ12፡13 እግዚአብሔር ጠቢብ እና ታላቅ ነው ይላል። የምዕራፉ ቀሪ ክፍል እግዚአብሔር ስለ ሰራቸው በጥበብ የተሞሉ እና ታላላቅ ስራዎች በመናገር ይህ እውነት መሆኑን ያሳያል።

ጥበብ እና ታላቅነት የእግዚአብሔር ናቸው

"ጥበብ" እና "ታላቅነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ጠቢብ" እና "ታላቅ" በሚሉ ቅጽሎች ሊገለጹ ይችላሉ። "እግዚአብሔር ጠቢብ እና ታላቅ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ/ተመልከት

"እይ" ወይም "አድምጥ" ወይም "ልነግርህ ስላለው ነገር ትኩረት ስጥ"

ይህ ዳግም ሊገነባ አይችልም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ይህን ማንም ዳግም ሊገነባው አይችልም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ያሰረውን፣ ሊፈታው የሚችል የለም

"መፍታት" የሚለው ረቂቅ ስም "ነጻ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ያሰረውን፣ ማንም ነጻ ሊያወጣው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ውሆችን ከገደበ፣ ይደርቃሉ

ውሃን መገደብ/መያዝ የሚለው ሊኖረው የሚችለው ትርጉሞች 1) ዝናብ እንዳይዘንብ ቢከለክል። "ዝናብ እንዳይዘንብ ቢከለክል ምድር ትደርቃለች" ወይም 2) ወራጅ ውሃን ከመፍሰስ ቢያስቆም። "ውሃ እንዳይወርድ ቢያግድ ምድር ትደርቃለች" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ቢለቃቸው፣ ምድሩን ያጥለቀልቃሉ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፤ እነርሱን መልቀቅ የሚለው ዘይቤ ነው ትርጉሙም 1) ዝናብ እንዲዘንብ ቢያደርግ/ዝናብን ቢያዘንብ። "ብዙ ዝናብ ቢያዘንብ፣ ምድሪቱ ትጥለቀለቃለች" ወይም 2) ውሃ እንዲወርድ/እንዲፈስ ቢያደርግ። "ብዙ ውሃ እንዲወርድ ቢያደርግ፣ ምድር ትጥለቀለቃለች" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 12:16

ብርታት/ሀይል እና ጥበብ የእርሱ ናቸው

"ብርታት" እና "ጥበብ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ብርቱ" እና "ጠቢብ" በሚሉ ቃላት ሊገለጹ ይችላሉ። "እግዚአብሔር ብርቱ እና ጠቢብ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የተታለሉ እና የሚያታልሉ ሰዎች ሁለቱም ከእርሱ ሀይል ስር ናቸው

በእግዚአብሔር ሀይል ስር የሚለው የሚገልጸው እግዚአብሔር በሁሉም ላይ ገዢ መሆኑን ነው። "በሀሰት የሚያምኑ እና ለሌሎች የሚዋሹ ሰዎች ሁለቱም በእርሱ ሀይል ስራ ናቸው" ወይም "እግዚአብሔር በሃሰት በሚያምኑ እና ለሌሎች ሃሰትን በሚናገሩ በሁለቱም አይነት ሰዎች ላይ ገዢ ነው" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው።

እርሱ አማካሪዎችን በባዶ እግራቸው ይሰዳቸዋል

አማካሪዎችን በባዶ እግር መላክ የእርሱን ጥበብና ስልጣን መቀማት ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሀዘን

"ሀዘን" የሚለው ረቂቅ ስም "መመረር" ወይም "ማዘን" በሚሉ ቃላት ሊገለጽ ይችላል። "ደግሞም በጣም ያዝናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ፈራጆችን ሞኞች ያደርጋቸዋል
"እርሱ ፈራጆች ሞኞች እንዲሆኑ ያደርገል"
እርሱ የነገሥታት በሰንሰለት የማሰር ስልጣን ይወስድባቸዋል
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ነገሥታት ከዚህ በኋላ ስልጣን እንዳይኖራቸው ያደርጋል ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የነገሥታትን ስልጣን ይቀማቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ሰዎችን ነገስታት ከጫኑባቸው ቀንበር ነጻ ማውጣት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። "እርሱ ነገሥታት በህዝቡ ላይ የጫኑትን ቀንበር ያነሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እስከ ወገባቸው ድረስ ያለብሳቸዋል/ከወገባቸው በላይ ይራቆታሉ
ይህ ልብስ ምናልባት ባርያ የሚለብሰው ልብስ ይሆናል። ይህንን ልብስ ንጉሦችን ማልበስ የሚገልጸው ንጉሦችን ባሮች ማድረግን ነው። "እርሱ ነገሥታት የባሮችን ልብስ እንዲለብሱ ያደርጋል" ወይም "እርሱ ባሮች ያደርጋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 12:19
ካህናቱን ባዶ እግራቸውን ይሰዳቸዋል
ካህናትን ባዶ እግራቸውን መስደድ ስልጣናቸውን መቀማትን ያመለክታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በሀዘን
"ሀዘን" የሚለው ረቂቅ ስም "መመረር" ወይም "ማዘን" በሚሉ ቃላት ሊገለጽ ይችላል። "ደግሞም በጣም ያዝናሉ" ወይም "ደግሞም ይመረራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ታላላቆችን ያዋርዳል
"ሀይለኞችን ያሸንፋል"
ይታመኑ የነበሩትን ንግግራቸውን ያቀላል/ያርቃል
ንግግራቸውን ያቀላል/ያርቃል የሚለው የሚገልጸው መናገር እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል ማለትን ነው። "ይታመኑ የነበሩትን መናገር የማይችሉ ያደርጋቸዋል" ወይም "ሌሎች ያምኗቸው የነበሩትን ጸጥ ያሰኛቸዋል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የሽማግሌዎችን እውቀት/መረዳት ይወስድባቸዋል
መረዳታቸውን ይወስዳል የሚለው የሚገልጸው መረዳት ወይም ጥሩ ውሳኔ መስጠት እንዳይችሉ ማድረግ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሽማግሌዎች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በእድሜ ትልቅ የሆኑ ሰዎች ወይም 2) መሪዎች የሚሉ ናቸው።
በልዑላን ላይ ንቀትን ያፈሳል
በልዑላን ንቀት ማፍሰስ ህዝቡ እንዲንቃቸው ማድረግ ለሚለው (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የሃያላንን ቀበቶ/ወገብ ይፈታል
ቀበቶ የጥንካሬ ምልክት ነው። የሀያልን ሰው ቀበቶ መፍታት የሚወክለው አቅሙን ከእርሱ መንጠቅ እና ሰውየውን ደካማ ማድረግን ነው። "ሃያልንን ደካማ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 12:22
የጨለማን ጥልቅ ነገሮች ይገልጣል
ነገሮችን መግለጽ የሚወክለው እነርሱን እንዲታወቁ ማድረግን ነው። "በጨለማ ያሉ ጥልቅ ነገሮች" የሚወክለው ሰዎች የማያውቋቸውን ነገሮች ነው። "እርሱ ሰዎች የማያውቋቸውን ምስጢሮች እንዲታወቁ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጥልቅ ጥላዎችን ወደ ብርሃን ያመጣል
ነገሮችን ወደ ብርሃን ማምጣት የሚወክለው እንዲታወቁ ማድረግን ሲሆን፣ እዚህ ስፍራ "ጥላዎች" በጥላ ውስጥ ለተደበቁ ነገሮች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። ይህም በተራው እግዚአብሔር ከሰዎች ለደበቀው እውነት ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "ማንም ሊመለከተው የማይችለውን ነገር እንዲታወቅ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
መንግሥታትን ታላቅ ያደርጋል
"እርሱ መንግሥታትን ትልቅ ያደርጋል" ወይም "እርሱ መንግሥታት ብዙ መሬት እንዲኖራቸው ያደርጋል"
እንደዚሁም እርሱ ከእስረኞች ጋር ይመራቸዋል
እግዚአብሔር አህዛብን ይመራል የሚለው የሚወክለው እግዚአብሔር ጠላቶቻቸው እንዲመሯቸው ያደርጋል የሚለውን ነው። "እርሱ" የሚለው ቃል የሚወክለው ህዝቦችን ነው፤ እዚህ ስፍራ እነዚያን አገራት ሰዎች ነው። "እንደዚሁም እርሱ ጠላቶቻቸው እንደ እስረኛ እንዲመሯቸው ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 12:24
ከምድር ህዝቦች መሪዎች ዘንድ ሁሉ እርሱ ማስተዋልን ይወስዳል
ማስተዋላቸውን መውሰድ የሚለው የሚወክለው እንዳያስተውሉ ማድረግን ነው። "እርሱ የምድር ህዝቦች መሪዎች እንዳያስተውሉ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መንገድ በሌለበት በረሃ መንከራተት
መንገድ በሌለበት በበረሃ መንከራተት የሚለው የሚወክለው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መሆንን እና መሄጃን አለማወቅን ነው። "መንገድ በሌለበት ጠፍ መሬት እንደሚንከራተት ምን ማድረግ እንዳለበት እንደማያውቅ ሰው እርግጠኛ አለመሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ብርሃን በሌለበት በጨለማ ይርመሰመሳሉ
ብርሃን በሌለበት በጨለማ መሆን የሚወክለው እውቀት ማጣትን ነው። "ሰዎች ያለ ብርሃን በጨለማ ለመራመድ እንደሚታገሉ እነርሱም ያለ እውቀት ውሳኔ ለመስጠት ይታገላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንደሰከረ ሰው እንዲንገዳገዱ ያደርጋቸዋል
እንደጠጣ/እንደሰከረ ሰው መንገዳገድ የሚለው የሚወክለው ያለ አላማ መኖርን ነው። "ሲራመድ እንደሚነገዳገድ የሰከረ ሰው ያለ አላማ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል" ወይም "ወደ ፊት እና ወደ ኋላ እንደሚንገዳገድ እንደ ሰከረ ሰው ያለ አላማ ይንከራተታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 13
Job 13:1
አያያዥ ሃሳብ
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ይቀጥላል።
እነሆ/እይ
"ተመልከት" ወይም "አድምጥ" ወይም "ለምናገረው ትኩረት ስጥ"
ዐይኔ ይህን ሁሉ ተመልክቷል
ኢዮብ እነዚህን ነገሮች በዐይኑ በማየቱ ራሱን የሚገልጸው ዐይኖቹን አድርጎ ነው። "ይህንን ሁሉ አይቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክዶክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ጆሮዎቼ ሰምተው ተረድተዋል
ኢዮብ እነዚህን ነገሮች በጆሮው በመስማቱ ራሱን የሚገልጸው ጆሮቹን አድርጎ ነው። "ይህን ሰምቼ ተረድቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክዶክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ የምታውቁትን፣ ያንኑ እኔም አውቃለሁ
"የምታውቁትን፣ እኔም አውቃለሁ" ወይም " እናንተ የምታውቁትን ያህል እኔም አውቃለሁ"
Job 13:3
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ይቀጥላል
ከእግዚአብሔር ጋር መከራከር እፈልጋለሁ
የኢዮብ ወዳጆች እየፈረዱበት ነው፣ ነገር ግን እውነት እየተናገሩ አይደለም። ይልቁንም ኢዮብ ቅሬታውን እያቀረበ ከእግዚአብሔር ጋር እየተከራከረ ነው።

እናንተ እውነትን በውሸት ኖራ ትሸፋፍናላችሁ
ኖራ መቀባት ወይም እውነትን መሸፈን የሚገልጸው እውነትን መተውን ነው። "እውነትን በሀሰት ትደብቃላችሁ" ወይም "ትዋሻላችሁ ደግሞም እውነትን ተዋላችሁ/ትጥላላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ ሁላችሁም ምንም የማትጠቅሙ ባለ መድሀኒቶች ናችሁ
ባለ መድሃኒት መሆን የሚወክለው ሌላውን የሚያጽናና ሰው መሆንን ነው። ምንም የማትጠቅሙ ማለት ማድረግ ያለባቸውን እንዴት እንደሚያደርጉ አያውቁም ማለት ነው። "ሰው እንዴት እንደሚፈውሱ እንደማያውቁ ባለመድሀኒቶች ናችሁ" ወይም "እናንተ ልታጽናኑኝ መጣችሁ፣ ነገር ግን ያልሰለጠነ መድሃኒተኛ እንዴት እንደሚፈውስ እንደማያውቅ ሁላችሁም እንዴት እንደምታጽናኑ አታውቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእናንተ ሰላም ለእናንተ ይሁን/ሰላማችሁን ያዙት
ይህ አገላለጽ "ዝም በሉ" ወይም "መናገራችሁን አቁሙ" ማለት ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ያንን ብታደርጉ ይህ ለእናንተ ጥበብ ይሆናል
እነርሱ ጥበብ የሞላበትን ነገር እየተናገሩ ይመስላቸዋል፣ ኢዮብ ግን መናገራቸውን አቁመው ዝም ቢሉ የበለጠ ጥበበኞች እንደሚሆኑ ይነግራቸዋል። "ጥበብ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠቢብ" በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። "ያንን ብታደርጉ ጠቢብ ትሆናላችሁ" ወይም "መናገራችሁን ብታቆሙ፣ ጠቢብ መስላችሁ ትታያላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Job 13:6
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ይቀጥላል
የከንፈሮቼን ልመና ስሙ
እዚህ ስፍራ "ከንፈሮች" የሚለው የሚወክለው ተናጋሪውን ሰው ነው። "እኔ ራሴ የምለውነውን ነገር አድምጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእርሱ በሽንገላ ... ያለ ጽድቅ/በክፉ ትናከራላችሁን?
ኢዮብ እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች የሚጠቀመው ወዳጆቹ ያለ ጽድቅ/በክፉ በመናገራቸው ሊወቅሳቸው ነው። "እናንተ ለእግዚአብሔር የምትናገሩ ይመስላችኋል፣ ነገር ግን በክፋት/ጽድቅ የሌለበትን ነገር እየተናገራችሁ ነው። በማታለል እየተናገራችሁ ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
በማታለል መናገር
"መዋሸት" ወይም "ውሸት መናገር"
ለእርሱ ወገንተኝነትን ታሳያላችሁን? ለእግዚአብሔር ትከራከራላችሁን?
ለእግዚአብሔር ደግነትን ማሳየት የሚወክለው እግዚአብሔርን መርዳትን ወይም እግዚአብሔርን ከኢዮብ ማማረር መከላከልን ነው። ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው ወዳጆቹ ለእግዚአብሔር እንቆምለታለን ብለው በማሰባቸው ሊወቅሳቸው ነው። "እግዚአብሔር እንድትከራከሩለት ይፈልጋል ብላችሁ ታስባላችሁን? ጠበቃ በፍርድ ቤት እንደሚካከር ለእግዚአብሔር እንደምትከራከሩለት ታስባላችሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እንዲሁም ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 13:9
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ይቀጥላል
እርሱ መርምሮ በደረሰባችሁ ጊዜ ይህ ለእናንተ መልካም ይሆንላችኋልን?
እዚህ ስፍራ "ከውጭ ሲያገኛችሁ" በዘይበያዊ አነጋገር "ሲመረምራችሁ" የሚል ትርጉም አለው። ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እግዚአብሔር ወዳጆቹን በመረመራቸው ጊዜ ስህተተኞች ሆነው ስለሚያገኛቸው ሊያስጠነቅቃቸው ፈልጎ ነው። "እግዚአብሔር በመረመራችሁ ጊዜ፣ ለእናንተ መልካም አይሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተን ይወቅሳል
"እናንተን ይገስጻል"
በድብቅ ወገናዊነትን/አድልዎ ብታሳዩ
"ለሌላው በድብቅ አድልዎ ብታደርጉ።" ወገናዊነትን ማሳየት የሚመለክተው፣ ዳኛው ያ ሰው መልካም ነው እንዲል ስለ አንድ ሰው መልካሙን ብቻ መናገርን ነው። ይህንን በድብቅ ማድረግ ማለት በትክክል የተናገሩ ማስመሰል ሲሆን፣ በእርግጥ ግን ሲታይ ከአንዱ ሰው ይልቅ ለሌላው ማድላት ነው።
Job 13:11
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ይቀጥላል
የእርሱ ግርማ አያስፈራችሁምን፣ ደግሞስ የእርሱ ፍራሃት አይወድቅባችሁምን?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ወዳጆቹን ለመገሰጽ ነው። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ እግዚአብሔርን መፍራት አለባችሁ እያላቸው ነው። "ግርማው ሊያስፈራችሁ፣ እርሱን መፍራት ሊወድቅባችሁ ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ኢዮብ ወዳጆቹን እግዚአብሔርን ፍሩት ይላቸዋል። "ግርማው ያስፈራችኋል፣ ደግሞም የእርሱ ማስደንገጥ በላያችሁ ይወድቃል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ ማስደንገጥ በላያችሁ ይወድቃል
ማስደንገጥ በሰዎች ላይ መውደቅ የሚለው የሚወክለው እነርሱ እጅግ ይፈራሉ የሚለውን ነው። "እናንተ እጅግ አትደነግጡምን" ወይም "ደግሞስ እጅግ አትፈሩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእናንተ ምርጥ ንግግሮች/ምሳሌዎች የሚባሉት ከአመድ የተበጁ ናቸው
አመድ የሚወክለው ጥቅም እና እድሜ የሌላቸውን ነገሮች ነው። "የእናንተ ምርጥ አባባሎች እንደ አመድ እርባና ቢሶች ናቸው" ወይም "የእናንተ ምርጥ አባባሎች/ምሳሌዎች ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስዳቸው አመድ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መከላከያዎቻችሁ
ይህ የሚያመለክተው ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም 1) ራሳቸውን ለመከላከል የሚናገሩት ወይም 2) ለእግዚአብሔር ጥብቅና ለመቆም የሚናገሩት
Job 13:13
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ይቀጥላል
የእናንተ ሰላም ለእናንተ ይሁን/ሰላማችሁን ያዙት
ይህ ፈሊጣው አገላለጽ ነው "ዝም በሉ" ወይም "መናገራችሁን አቁሙ" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔን ብቻዬን ተዉኝ
ይህ ፈሊጣው አገላለጽ ነው "እኔኝ መሳሰጨነቃችሁን አቁሙ" ወይም "እኔን ማስተጓጎላችሁን አቁም" ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእኔ ላይ የሚደርሰው ይድረስብኝ/ይምጣብኝ
በአንድ ሰው ላይ የሚመጡ ነገሮች የሚወክሉት በዚያ ሰው ላይ የሚሆኑ ነገሮችን ነው። ይህ አገላለጽ የሚጀምርበት "ይሁን" የሚለው አባባል በእርሱ ላይ ስለሚደርሰው ነገር ግድ የለውም ማለት ነው። "በእኔ ላይ ሊደርስ ያለው ማናቸውም ነገር ይድረስብኝ" ወይም "በእኔ ላይ ስለሚደርሰወ ነገር ግድ አይለኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስጋዬን ... በእጆቼ አይዛለሁ
እዚህ ስፍራ "ስጋ" የሚለው ለህይወት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ጥርስ" እና "እጆች" የሚሉት ራሱን ስለ መግዛቱ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። እነዚህ ሁለት ሀረጋት በአንድነት ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር በመከራከር ህይወቱን አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑን ያጎላሉ። "ህይወቴን አሳልፌ ለመስጠት ዝግጁ ነኝ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 13:16
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለወዳጆቹ መናገሩን ጨርሶ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር መናገር ይጀምራል።
ይህ ለእኔ ነጻ መውጣት ምክንያት ይሆናል
"ነጻ መውጣት" የሚለው ረቂቅ ስም "ነጻነት" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር እኔን ነጻ የሚያወጣበት ምክንያት ይህ ነው" ወይም "እግዚአብሔር እኔን ከችግሮቼ የሚያድነኝ ከዚህ የተነሳ ነው" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ሆይ፣ ስማኝ
ኢዮብ ንግግሩን የሚጀምረው በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር በመጮህ/በመናገር ነው።
ንግግሬን አድምጥ፣ የምናገረው ወደ ጆሮህ ይድረስ
እነዚህ ሁለት መስመሮች በመሰራታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም ኢዮብ እግዚአብሔር እንዲሰማው የሚያቀርበውን ጥያቄ አጉልተው ይገልጻሉ። (ትይዩ

ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የምናገረው ወደ ጆሯችሁ ይድረስ

"መናገር/ማወድ" የሚለው ረቂቅ ስም "ተናገረ/አወጀ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። ጆሯችሁ የሚለው የሚወክለው መስማትን ነው። "የምናገረውን ስሙ" ወይም "የምለውን ስሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 13:18

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ለእግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

እነሆ አሁን ተመልከት

ይህ ተከትሎ የሚነገረውን ያጎላል። "እነሆ አሁን ስማ" ወይም "እባክህ ስማኝ"

መከላከያዬን በስርአት አቀርባለሁ

መከላከያውን በስርአት ማቅረብ የሚወክለው ራሱን ለመከላከል የሚያቀርበውን መወሰንን ያመለክታል። "እርሴን እንዴት እንደምከላከል በሚገባ አስቤበታለሁ" ወይም "ያለኝን ሀሳብ እንዴት እንደምገልጽ ወስኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በፍርድ ቤት እኔን በደለኛ አድርጎ መከራከር የሚችል ማን ነው?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀምበት ትክክለኛ እስከሆነ ድረስ ከእርሱ ጋር ማንም ሊከራከር እንደማይችል ያለውን እምነት ለመግለጽ ነው። "በፍርድ ቤት ማንም ከእኔ ጋር ይከራከራል ብዬ አላምንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህንን ለማድረግ ብትመጡ

"ከእኔ ጋር ለመከራከር ብትመጡ"

አንተ ብትመጣ እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው እግዚአብሔርን ራሱን ነው

ስህተተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ስህተተኛ መሆኔን አንተ ካረጋገጥህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴን አሳልፌ እሰጣለሁ

አንድ ሰው ህይወቱን አሳልፎ መስጠቱ ለሞት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "እሞታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 13:20

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ለእግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

ከአንተ ፊት

"ፊት" የሚገለጸውን አካል ይወክላል። "ከአንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከባድ እጅህን ከእኔ ላይ አንሳ

ከባድ/የሚጫን እጅ አንድን ሰው የሚጫን ነገር ማድገረግን የሚገልጽ ሜቶኖሚ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። እጅን ማንሳት እነዚያ ነገሮችን ማድረግ ማቆምን የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "እኔን መጫንህን አቁም/እጅህን ከእኔ አንሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ማስጨነቅህ እንድፈራ አያድርገኝ

"ማስጨነቅህ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲፈሩ የሚያደርጋቸውን ምክንያት ነው። "እታስጨንቀኝ/አታስፈራኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 13:23

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ለእግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል

እንደ ጠላትህ ....ስለምን ከእኔ ትደበቃለህ?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔር እያደረሰበት ስላለው ነገር ለማማረር ነው። ምናልባትም መልስ ለማግኘት ተስፋ እያደረገ ይሆናል። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፊትህን ከእኔ ደበቅህ/ሰወርክ

ፊትን ከሌላው መደበቅ የሚወክለው ለመመልከት አለመፈለግን ወይም ለማየት መቃወምን ነው። "እኔን ማየት አልፈለግክም" ወይም "ተውከኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ታሰቃያለህን...የደረቀውንስ እብቅ ትከታተላለህን?

ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠቀምባቸው እርሱ እዚህ ግባ የማይባል እና ደካማ ሳለ እግዚአብሔር ኢዮብን መከታተሉና ማሳደዱ ዋጋ እንደሌለው ለእግዚአብሔር ለመናገር ነው። "ቅጠል" እና "የደረቀ እብቅ" የኢዮብን ደካማነት፣ አቅመቢስነት እና ተሰባሪነት የሚገልጹ ዘይቤዎች ናቸው። "አንተ ታሳድደኛለህ፣ እኔ ግን ነፋስ እንደሚጠርገው ቅጠል እና እንደ ደረቅ እብቅ ደካማነኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እንደዚሁም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 13:26

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢዮብ ጉዳዩን ለእግዚአብሔር ማቅረቡን ያበቃል

አንተ በእኔ ላይ መራራ ነገሮችን ታቀርባለህ/ትጽፋለህ

"መራራ ነገሮች" የሚለው የሚወክለው መክሰስን ነው። "አንተ በእኔ ላይ ክስን ታቀርባለህ/ትጽፋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም ያልሆኑትን የወጣትነቴን ታማኝነት ማጣት/ኃጢአት እንድወርስ አደረግህ

የወጣትነቱን ታማኝነት ማጣት መውረስ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፡ 1) በወጣትነቱ ታማኝነት ማጣት/ኃጢአት በደለኛ መሆን። "በወጣትነቴ ኃጢአት አሁንም ድረስ በደለኛ አደርገኸኛል" ወይም 2)በወጣትነት ኃጢአቱ እየተቀጣ ይገኛል። "በወጣትነቴ በሰራሁት ኃጢአት እየቀጣኸኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የወጣትነቴ ኃጢአት

"ወጣት" የሚለው ረቂቅ ስም "ታዳጊ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። "ታዳጊ ሳለሁ የሰራሁት ኃጢአት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እግሮቼንም ደግሞ በእግር ግንድ ታጣብቃለህ

ይህንን ማድረግ የሚወክለው ወንጀል የሰራ እና እስረኛ የሆነ ይመስል፣ ኢዮብን መቅጣትን እና በነጻነት እንዳይኖር መከልከልን ነው። "እግሮቼን በእግር ግንድ ያጣበቅከኝ ያህል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእግር ግንድ

ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፡ 1) የእስረኛን እግሮች በፍጹም መንቀሳቀስ እንዳይችል አድርጎ በአንድ ስፍራ የሚይዝ ማሰሪያ ወይም 2) መንቀሳቀሱን ከባድ የሚያደርግበት በእስረኛ እግሮች ዙሪያ የሚደረግ ሰንሰለት። እነዚህ እንደ ቅጣት መልክ የሚያገለግሉ ናቸው።

መንገዶቼ ሁሉ

"መንገዶች" የሚለው የሚወክለው ኢዮብ ያደረጋቸውን ነገሮች ነው። "ያደረግኳቸው ነገሮች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግሮቼ የረገጡትን ስፍራ/ዱካዬን ሁሉ መረመርህ/ተከታተልክ

የእግሩ ጫማ የሚወክለው የሚራመደውን ሰው ነው። "የተራመድኩባቸውን ስፍራዎች ሁሉ መረመርህ/ተከታተልህ" ወይም "አንድ ሰው የረገጣቸው ቦታዎች ሁሉ እንደሚታዩ የሰራኋቸውን ነገሮች ሁሉ ተከታተልክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደተበላሸ/ እንደበሰበሰ እና እንደተጣለ ነገር

ኢዮብ ህይወቱን ከበሰበሰ ነገር ጋር ያነጻጽራል። ቀስ በቀስ ወደ ሞት እየሄደ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እይጦች እንደበሉት ጨርቅ

ኢዮብ ራሱን አይጦች በልተው ከቀዳደዱት ጨርቅ ጋር ያመነጻጽራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 14

Job 14:1
አጠቃላይ መረጃ፡
በዚህ ምዕራፍ በኢዮብ 12፡1 የተጀመረው የኢዮብ ንግግር ይቀጥላል፣ ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገራል፡፡
ከሴት የተወለደ፣ ሰው
ይህ ወደዚህ ዓለም የተወለደውን ሁሉ፣ ወንድንም ሴትንም በአጠቃላይ ሰውን ያመለክታል፡፡ (ጉልበትን/ጠንቻማነትን የሚያመለክቱ ቃላት ሴቶችን ሲያካትቱ የሚለውን ይመልከቱ)
ለጥቂት ቀናት የሚኖር
ይህ ሰው አጭር እድሜ እንዳለው በማጋነን የቀረበ አገላለጽ ነው፡፡ "በጣም አጭር ጊዜ ብቻ የሚኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
በችግር የተሞላ
"በችግር የተሞላ" መሆን የሚወክለው ብዙ ችግር ማጋጠሙን ነው፡፡ "ብዙ ችግር አለው" ወይም "ብዙ ተሰቃየ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ አበባ ከምድር ይበቅላል፣ ደግሞም ይቆረጣል
የሰው እድሜ እንደ አበባ እድሜ አጭር ነው፣ ደግሞም በቀላሉ ይሞታል፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ጥላ ይሸሻል፣ ደግሞም አይቆይም
የሰው አጭር ህይወት በፍጥነት ከሚጠፋ ጥላ ጋር ተነጻጽሯል፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእነዚህ አንዱን ተመልክተሃል?
ኢዮብ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ እንዲህ እንዲያተኩር አለመፈለጉን ይጠቁማል፡፡ "ከእነዚህ አንዱን አልተመለከትክም" ወይም "ለእነዚህ ብዙ ትኩረት አልሰጠህም፡፡ እባክህ በእኔ ላይ ብዙ አታተኩር፡፡" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ተመልከት
እዚህ ስፍራ አንድን አካል መመልከት የሚወክለው በእርሱ ላይ ለመፍረድ ትኩረት መስጠትን ነው፡፡ "ትኩረት ስጥ" ወይም "ከዚያ ላይ ስህተትን መፈለግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡
እኔን ከአንተ ጋር ወደ ፍርድ ታመጣለህን?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ አበባ በቶሎ ጠፊ ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ መፍረዱ እንዳስደነቀው ለመግለጽ ነው፡፡ "ነገር ግን አንተ በእኔ ላይ ፈረድክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 14:4
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል፡፡
ማን ንጹህ ካልሆነ ነገር ንጹህ የሆነ ነገርን ማውጣት ይችላል? ማንም
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው እርሱ ንጹህ ስላልሆነ ነገር የሚያውቀውን እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ እንዲያደርግ ለመገፋፋት ነው፡፡ "ማንም ንጹህ ካልሆነ ነገር ንጹህ ነገርን ማምጣት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ቀኖች የተወሰኑ ናቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፡፡ "አንተ የሰውን ቀናት ትወስናለህ" ወይም "አንተ ሰው የሚኖርበትን ዘመን ትወስናለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የወራቱ ቁጥር በአንተ ዘንድ ነው
ሰው የሚኖርበት ወራት ቁጥር በእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑ የሚወክለው ሰው የሚኖርበትን ወራት ቁጥር የሚወስነው እግዚአብሔር መሆኑን ነው፡፡ "ምን ያህል ወራት እንደሚኖር አንተ ትወስናለህ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሊያልፍ የማይችልበትን ገደብ አንተ ወስነሀል
ገደብን ማለፍ የሚለው የሚወክለው አንድ ሰው እንዲኖር እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰነለት ዘመን መኖር ነው፡፡ "አንተ የሚሞትበትን ጊዜ ወስነሃል፣ እናም ሰው ያንን አልፎ መኖር አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የተቀጠረ ሰው/ቅጥረኛ
አንድን ስራ ለመስራት የተቀጠረ እና ከዚያ ወደ ቤቱ የሚሄድ ሰው
Job 14:7
ለዛፍ ተስፋ ሊኖረው ይችላል
"ተስፋ" የሚለው ረቂቅ ስም "ተስፋ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ተስፋ ከቁር 7-9 ባለው ውስጥ ተብራርቷል፡፡ "ዛፍ ዳግም እንደሚኖር ተስፋ ልናደርግ እንችላለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ዳግም ሊበቅል ይችላል
"እንደገና መብቀል ሊጀምር /ሊያቆጠቁጥ ይችላል"
ስለዚህም ቅርንጫፉ ሊጠፋ አይችልም
መጥፋ የሚወክለው መሞትን ነው፡፡ "ስለዚህም አዳዲሶቹ ቅርንጫፎች አይደርቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ምንም እንኳን
"ቢሆንም እንኳን"
ጉቶ
ዛፉ ከተቆረጠ በኋላ ታች ከመሬቱ ላይ ብቅ ብሎ የሚቀረው ክፍል
የውሃ ሽታ ቢያገኝ ብቻ
ይህ የሚገልጸው የሞተው ጉቶ ልክ ውሃ ማሽተት እንደሚችል እና ውሃ በአቅራቢያው እንደሚገኝ ተደርጎ ነው፡፡ "ጥቂት ውሃ እንኳን በአቅራቢያው ቢኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሰውኛ የሚለውን ዘይቤ ይመልከቱ)
ያቆጠቁጣል
"ማደግ/ማቆጥቆጥ ይጀምራል"
እንደ ተክል ቅርንጫፍ ያወጣል
ዛፍ ቅርንጫፍ ማውጣቱ የሚወክለው ቅርንጫፎች በዛፍ ላይ ማደጋቸውን ነው፡፡ "ቅርንጫፎች በጉቶው ላይ እንደ ተክል ማደግ ይጀምራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሰውኛ የሚለውን ዘይቤ ይመልከቱ)
Job 14:10
ከእንግዲህ የት ይገኛል?
ኢዮብ ይህንን ጥጣቄ የተጠቀመው ሰው በሞተ ጊዜ፣ እንደማይገኝ አጉልቶ ለማሳየት ነው፡፡ "የት እንደሆነ ማንም አያውቅም" ወይም "ላይመለስ ሄዷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ውሃ ከሐይቅ እንደሚተን... ደግሞም ዳግምም እንደማይነሳ
ሞት ዳግም የሚከናወን ነገር አለመሆኑ የተነጻጸረው አንዴ የተነነ ውሃ ዳግም ሊመለስ ካለመቻሉ ጋር ነው፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ውሃ እንደሚተን... ከወንዝ እንደሚነሳ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት አንድ አይነት ሀሳብን ይገልጻሉ፤ ይህም መደጋገም የተደረገው ሞት የመጨረሻ ነገር መሆኑን ለማጉላት ነው፡፡ (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደዚሁም ሰዎች ይጋደማሉ
መጋደም የሚለው የሚወክለው መሞትን ነው፡፡ "እንደዚሁም ሰዎች ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዳግም አይነሱም
ዳግም መነሳት የሚወክለው ዳግም መኖር የሚለውን ነው፡፡ "ዳግም አይኖርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዳግም አይነቁም አሊያም ከተኙበት አይነሱም
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድነት ያገለገሉት ሞት የመጨረሻ መሆኑን ለማጉላት ነው፡፡ መተኛት የሚለው የሚወክለው መሞትን ሲሆን መንቃት ደግሞ የሚወክለው ዳግም መኖርን ነው፡፡ "የሞቱ ሰዎች ዳግም አይኖሩም፣ እናም ከሞት አይነሱም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 14:13
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል፡፡
አቤቱ፣ እባክህ ሰውረኝ
ይህ ኢዮብ በጣም የሚፈልገውን ነገር ግን በእርግጥ ይሆናል ብሎ የማይጠብቀውን ነገር የሚያሳይ ቃለ አጋኖ ነው፡፡ "ብትሰውረኝ በወደድሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)
ለብቻዬ አግልለኝ

"በእኔ ላይ ቆልፍ" ወይም "ሰውረህ አስቀምጠኝ"
አትርሳኝ
አንድን ሰው አለመርሳት/ማስታወስ ስለዚያ ሰው ማሰብን የሚገልጽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ስለ እኔ አስብ" ወይም "እኔን አስታውስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሞተ ሰው ዳግም ይኖራልን?
በውስጠ ታዋቂነት የተሰጠ ምላሽ "አይ" የሚል ነው። "የሞተ ሰው፣ ዳግም በህይወት አይኖርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እንዲህ ከሆነ
"ከሆነ" የሚለው ምን እንደሚያመለክት ከቀደመው ሀረግ ይታወቃል። "እርሱ ዳግም ቢኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የድካም ጊዜያቶቼን ሁሉ በዚያ ለመቆየት
"ብደክም እንኳን ዘመኔን ሁሉ በዚያ ለመቆየት"
የመለቀቅ/የመታደስ ጊዜዬ እስኪደርስ
"መለቀቅ/መታደስ" የሚለው ረቂቅ ስም "ተለቀቀ/ታደሰ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እስከምለቀቅ ድረስ" ወይም "አንተ እስከምትለቀኝ/እስክታድሰኝ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Job 14:15
አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።
እኔ መልስ እሰጣለሁ
"እኔ ምላሽ እሰጣለሁ"
ትፈልገኛለህ/ትናፍቃለህ
"ፍላጎት" የሚለው ስም "ፈለገ" ወይም "ወደደ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ትፈልጋለህ/ትናፍቃለህ" ወይም "አንተ ትወዳለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የእጆችህ ስራ
እዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር እጆች የሚወክሉት እርሱ ነገሮችን መስራቱን ነው። ኢዮብ ራሱን የእግዘአብሔር የእጆቹ ስራ አድርጎ ይገልጻል። "እኔን ያበጀኸኝ አንተ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)
ቁጥር እና መቆጣጠር/መከታተል
እነዚህ ሁለት ግሶች ሁለቱ በአንድነት አንድን ድርጊት ይገልጻሉ። "በንቃት ትከታተላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሄንዲየዲስ/ሁለት ቃላት 'እና' በሚል አያያዥ ቃል የሚገኛኙበትና አንድን ጥልቅ ሀሳብ ለመግለጽ የሚያገለግል ዘይቤያዊ አነጋገር)
የእግሬ ኮቴ/እርምጃዬ
እርምጃ/ኮቴ የሚለው የሚወክለው ህይወቱን ወይም ያደረገውን ነው። "ህይወቴ" ወይም "ያደረግኳቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አትቆጥርብኝም… መተላለፌን ይቅር ትላለህ…አንተ ትሸፍንልኛለህ
እነዚህ ሶስት ሀረጎች ተመሳሳይ ሀሳብን ይገልጻሉ፣ በአንድነት የዋሉት እግዚአብሔር ይቅር እንደሚለው ያለውን እርግጠኝነት/ልበሙሉነት ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ኃጢአቴን አትቆጥርብኝም
የኢዮብን ኃጢአት አለመቁጠር የሚወክለው ስለ እርሱ ኃጢአት አለማሰብን ነው። "ኃጢያቴን አትመለከትም" ወይም "ስለ እኔ ኃጢአት አታስብም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መተላለፌን በከረጢት ውስጥ ታትምበታለህ
መተላለፍን በከረጢት ማተም የሚለው የሚገልጸው ኃጢአትን መሸፈን እና ስለ እርሱ ማሰብን አለመፍቀድ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድን ነገር በከረጢት ውስጥ እንደደበቀ ሰው መተላለፌን ማሰብ አትፈቅድም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በደሌን ትሸፍናለህ/ይቅር ታላለህ
እንዳይታይ የአንድን ሰው በደል መሸፈን የሚወክለው ስለዚያ ማሰብን አለመፍቀድን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በደሌን ትሸፍናለህ" ወይም "ኃጢአቴን ትተውልኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 14:18
አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።
ተራሮች ይወድቃሉ ከስፍራቸውም ይጠፋሉ
እዚህ ላይ "ከስፍራቸው ይጠፋሉ/መታሰቢያ ያጣሉ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ ሙሉ ለሙሉ ይደመሰሳሉ ማለት ነው። ይህ ሀረግ "መውደቅ" የሚለውን ቃል በማብራራት ጥፋቱ ሙሉ ለሙሉ መሆኑን ያጎላል። "ታራሮች ሙሉ ለሙሉ ይፈራርሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
አለቶች ከስፍራቸው ይወገዳሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አለቶች ከስፍራቸው ቁልቁለል ይንከባለላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ልክ እንደዚህ፣ የሰውን ተስፋ ትደመስሳለህ
በቋንቋችሁ ቀላል ከሆነ፣ ይህንን ሀረግ በቁጥር 18 መጀመሪያ ላይ መጻፍና ጽሁፉን በዚያው መሰረት ማስተካከል ትችላላችሁ። "ልክ እንደ ምድር አፈር፣… የሰውን ተስፋ ትደመስሳለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ ሚለውን ይመልከቱ)
አንተ የሰውን ተስፋ ትደመስሳለህ/ታጠፋለህ
ተስፋን መደምሰስ የሚወክለው/የሚገልጸው ሰዎች ተስፋ የሚያደረጓቸው ነገሮች እንዳይሆኑ ማድረግ ነው። "አንተ የሰው ተስፋ እውን እንዳይሆን ታግዳለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ተስፋ
"ተስፋዎች" የሚለው ረቂቅ ስም "ተስፋ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ሰው ተስፋ የሚያደርጋቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Job 14:20
አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።
አንተ ሁልጊዜም እርሱን ታሸንፋለህ
"እርሱ" የሚለው ቃል ማናቸውንም ሰው ያመልክታል። "አንተ ሁልጊዜም ሰውን ታሸንፋለህ" ወይም "አንተ ሁልጊዜም ሰዎችን ታሸንፋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
እርሱ ያልፋል
ማለፍ የሚለው የሚወከወለው/የሚገልጸው ሞትን ነው። "እርሱ ይሞታል" (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ፊቱን ትለውጣለህ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ከመሞቱ አስቀድሞ የሚገጥመው ስቃይ ፊቱ እንዲጨማደድ ያደርጋል ወይም 2) አንድ ሰው ሲሞት፣ እግዚአብሔር የሰውየውን ፊት የተለየ ያደርገዋል
እንዲሞት ይተወዋል/በሞት ይሸኘዋል
ይህ የሚገልጸው እንዲሞት ማድረግን/መፍቀድን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዝቅ ከተደረጉ/ከተዋረዱ
መዋረድ/ዝቅ መደረግ የሚለው የሚገልጸው ወይም የሚወክለው እንዲያፍር መደረግን ነው። "እንዲዋረዱ ከተደረገ" ወይም "ሰዎች ካሳፈሯቸው/ካዋረዷቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

## Chapter 15
Job 15:1
ቴማናዊው ኤልፋዝ
ይህ የወንድ ስም ነው። የቴማን ሰዎች ቴማናውያን ተብለው ይጠራሉ። ይህ ስም በኢዮብ 2:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ብልህ ሰው እርባና ቢስ መልስ ይሰጣልን፣ ደግሞስ ራሱን በምስራቅ ነፋስ ይሞላልን?

ኤልፋዝ ይህን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠቀመው ኢዮብን ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር/መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። "ብልህ ሰው እርባና ቢስ ምላሽ መስጠት የለበትም አሊያም ራሱን በምስራቅ ነፋስ መሙላት የለበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱን በምስራቅ ነፋስ መሙላት

ነፋስ የሚወክለው ባዶነትን ነው። ይህ ሀረግ የሚናገረው ያ ሰው በነፋስ እንደተሞላ ሁሉ ባዶ እና ትርጉም አልባ ቃላትን የሚናገርን ሰው ነው። "ራሱን በባዶ ቃላት የሞላ" ወይም "ትርጉም የለሽ ቃላት ብቻ ያሉት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የምስራቅ ነፋስ

"ሞቃት አየር" ወይም "የበረሃ ነፋስ"

ትርፍ በሌለው ወሬ ወይም አንዳች መልካም ማድረግ በማይችልበት ንግግሮች ምክንያት ማቅረብ/መከራከር ይኖርበታልን?

ኤልፋዝ ይህን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠቀመው ኢዮብን ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር/መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። "ትርፍ በሌለው ወሬ አሊያም አንዳች መልካ ማድረግ በማይችልበት ንግግር ምክንያት ማቅረብ/መከራከር የለበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 15:4

የእግዚአብሔርን ክብር ቀንሰሃል

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በተናገርከው እና ባደረግከው ምክንያት፣ ሌሎች ከእንግዲህ እግዚአብሔርን አያከብሩም" ወይም 2) "አንተ ከእንግዲህ እግዚአብሔርን አታከብርም"

መቀነስ

ማሳነስ/ትንሽ ማድረግ

ለእርሱ ያለን መሰጠት ዘግተሃል

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) " ሌሎች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዳይሰጡ ይህን አስቸጋሪ አድርገሃል" ወይም 2) "አንተ ከእንግዲህ ራስህን ለእግዚአብሔር አሳልፈህ አትሰጥም"

መዝጋት

የአንድን ሰው መንገድ ማገድ

መሰጠት

"በተመስጦ" ወይም "ግድ መሰኘት/ዋጋ መስጠት"

ኃጢአትህ አንደበትህን ታስተምራለች

ይህ የሚገልጸው "ኃጢአት" አስተማሪ እንደሆነ ተደርጎ እና የኢዮብ አንደበት/አፍ ደግሞ የተገለጸው ይህን እየተማረ እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ንግግሩ በኃጢአቱ እጅግ ተጽዕኖ አድሮበታል ማለት ነው። "ኃጢአትህ እንደ አስተማሪ ነው አፍህ ደግሞ እንደ ተማሪ ነው" ወይም "አሁን እንደምትምትናገረው እየተናገርክ የምትገኘው በኃጢአትህ ምክንያት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

አፍህ/አንደበትህ

ይህ ስለ ኢዮብ ይናገራል፣ ነገር ግን ለተናገረው ትኩረት ለመስጠት የሚያመለክተው ስለ "አንደበቱ/አፉ" ነው። "አንተ ተናገርክ" ወይም "የተናገርከውን የተናገርከው አንተ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የተንኮለኛ ሰው ምላስ መያዝ

ይህ የሚያመለክተው ተንኮለኛ ሰው እንደ "ምላሱ" የሚናገርበትን መንገድ ነው። "ተንኮለኛ ሰው በሚናገርበት መንገድ መናገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ተንኮለኛ ሰው

ለእነርሱ በመዋሸት ሌሎችን የሚጎዳ ሰው

የእኔ ሳይሆን፣ የገዛ አንደበትህ ይወቅስሃል

ይህ በተናገሩት ላይ ትኩረት ለመስጠት በ"አንደበታቸው/አፋቸው" አማካይነት ኢዮብን እና ኤልፋዝን ያመለክታል። "አንተ እኔ በተናገርኩት ሳይሆን ራስህ በተናገርከው በራስህ ላይ ትፈርዳለህ" ወይም "የምፈርድብህ እኔ ሳልሆን በተናገርከው በራስህ ላይ ትፈርዳለሁ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የራስህ ከንፈሮች ይመሰክራሉ

ይህ ስለ ኢዮብ ይናገራል፣ ነገር ግን በተናገረው ላይ ትኩረት ለመስጠት "ከንፈሮቹን" ያመለክታል። "የገዛ ቃላቶችህ" ወይም "አንተ ትመሰክራለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 15:7

አጠቃላይ መረጃ:

እያንዳንዱ ቁጥር ሁለት ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄን የያዘ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

በመጀመሪያ የተወለድከው/የተፈጠርከው ሰው አንተ ነህን?

እዚህ ስፍራ በውስጠ ታዋቂነት የተቀመጠው ምላሽ "አይደለም" የሚል ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር/በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "በመጀመሪያ የተወለድከው ሰው አንተ አይደለህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከኮረብቶች አስቀድሞ አንተ ወደ ህልውና መጥተሃልን/ኮረብቶች ሳይፈጠሩ ተፈጥረሃልን?

እዚህ ስፍራ በውስጠ ታዋቂነት የተቀመጠው ምላሽ "አይደለም" የሚል ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር/በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ከኮረብቶች አስቀድመህ አልተፈጠርክም/ከእነርሱ አስቀድመህ ወደ ህልውና አልመጣህም" ወይም "እግዚአብሔር ኮረብቶችን ወደ መኖር ከማምጣቱ አስቀድሞ አንተን ወደ መኖር አላመጣህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ነበርክን

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር አምጥቶህ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርን ምስጢራዊ እውቀት ሰምተሃል?

እዚህ ስፍራ በውስጠ ታዋቂነት የተቀመጠው ምላሽ "አይደለም" የሚል ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር/በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "አንተ የእግዚአብሔርን ምስጢራዊ እውቀት አልሰማህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብን በራስህ ትወስናታለህ?

ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እውቀትን በራሱ ሊወስናት እንደማይችል ትኩረት ይሰጣል። ይህ በዐረፍተ ነገር/በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እውቀትን በራስህ ልክ ልትወስናት አትችልም" ወይም "ብቸኛው ጠቢብ ሰው አንተ አይደለህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ የማናውቀው አንተ የምታውቀው ምን ነገር አለ?

እዚህ ስፍራ በውስጠ ታዋቂነት የተቀመጠው ምላሽ "ምንም የለም" የሚል ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር/በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እኛ የማናውቀው አንተ የምታውቀው ምንም ነገር የለም" ወይም "አንተ የምታውቀውን ነገር ሁሉ፣ እኛም ደግሞ እውቃለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በእኛ ውስጥ የሌለ አንተ የምትረዳው ምን ነገር አለ?

ይህ የሚናገረው ሰዎቹ ያላቸው መረዳት "በውስጣቸው" እንዳለ አንድ ነገር ሆኖ ነው። "አንተ የምትረዳውን ማናቸውንም ነገር እኛም ደግሞ እንረዳዋለን" ወይም "አንተ የምታውቀውን ነገር ሁሉ እኛም ደግሞ እናውቃለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 15:10

ከእኛ ጋር ፀጉራቸው ሸበት የሆነ እና በጣም ያረጁም ሰዎች ይገኛሉ

ኤልፋዝ ስለ ራሱ እና ከአዛውንቶች፣ እንደዚህም ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣውን ጥበብን ስላገኙ ሌሎች ሰዎችም ልክ እነዚህ ሽማግሌዎች በአካል ከእነርሱ ጋር እንደሚገኙ አድርጎ ይናገራል። "እኛ ከአዛውንቶች፣ ከአባትህ አስቀድሞ ከተወለዱ ሰዎች ጥበብ አግኝተናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ማጽናናት... በእርጋታ የተነገረህ ቃል አነሰብህን?

ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ክስን ያዘለ ነው፣ ለዚህ ጥያቄ በውስጠ ታዋቂነት የቀረበው ምላሽ "አዎን" የሚል ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር/በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "የእግዚአብሔር ማጽናናት ጥቂት ነገር ሆኖንሃል፣ በእርጋታ ወደ አንተ የመጣውን ምክር ንቀሃል"

ማጽናናት

"ማበረታት" ወይም "ርህራሄ/አዘኔታ"

Job 15:12

ስለምን ልብህ ያሸፍትሃል?

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የአንድን ሰው ስሜት ነው። "ለምን ስሜትህ ይዞህ ይሄዳል?" ወይም "ለምን ስሜትህ ውሳኔህን እንዲመራ ትፈቅዳለህ?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣው ነገጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ለምን ዐይኖችህ ይፈጣሉ

ይህ ማንላበት ኢዮብ መቆጣቱን ሊያመለክት ይችላል፤ በተለይም የዐይኖቹን ሁኔታ ሊያመለክት ይችላል። "ስለ ምን ዐይኖችህ የተቆጡ መሰሉ" ወይም "ለምን ተቆጣህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈስህን መልስ

እዚህ ስፍራ "መንፈስህ" የሚለው የሚያመለክተው መላውን ማናነትን ነው። "ራስህን መልስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ያሉ ቃላትን ከአንደበትህ አስወግድ

ይህ የሚገልጸው የእርሱን ንግግር ነው። "አንተ በእርሱ ላይ የማይገባ ነገሮችን ተናግረሃል" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የተወለደ እርሱ ...ሰው ምንድን ነው

እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች በመሰረቱ አንድ አይነት ናቸው፤ በአንድነት የቀረቡት ሰው ፍጹም መሆን እንደማይችል ለማጉላት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጹህ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድን ነው?

ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠየቀው ሰው ሙሉ ለሙሉ "ንጹህ" መሆን እንደማይችል ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር/በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ሰው ሙሉ ለሙሉ ንጹህ ሊሆን አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጹህ

እግዚአብሔር በመንፈሳዊነት ተቀባይነት አለው ብሎ የሚቆጥረው ሰው በአካሉ ንጹህ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጽዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከሴት የተወለደ ሰው ጻድቅ ይሆን ዘንድ እርሱ ማን ነው?

ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠየቀው ሰው ሙሉ ለሙሉ "ጻድቅ" መሆን እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር/በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ከሴት የተወለደ ሰው ሙሉ ለሙሉ ጻድቅ ሊሆን አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 15:15

እነሆ

ይህ ቃል እዚህ ስፍራ ያገለገለው የኢዮብን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚነገረው ነገር ለመሳብ ነው። "አድምጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የእርሱ ቅዱሳን

"የእርሱ መልአክት"

ንጹህ

እግዚአብሔር በመንፈሳዊነት ተቀባይነት አለው ብሎ የሚቆጥረው በአካል ንጹህ እንደሆነ ተደርጎ ተወስዷል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ዐይኖች/እይታ

እዚህ ስፍራ እይታ የሚወክለው ፍርድን ወይም ሚዛንን ነው። "በእርስ ፍርድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አስፀያፊ እና ብልሹ

እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም ሰው ምን ያህል ክፉ እንደሆነ ትኩረት ይሰጣሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአትን እንደ ውሃ የሚጠጣ

ይህ ኃጢአት እንደ ውሃ ልትጠጣው የምትችለው ነገር እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። ክፉ ሰው ኃጢአት መስራትን ምን ያህል እንደሚፈልግ ያነጻጸረው በፈቃዱ ቀዝቃዛ ውሃ ለመጠጣት ካለው ፍላጎት ጋር ነው። "ንጹህ ኩባያ ውሃ ለመጠጣት ያላቸውን ፍላጎት ያህል ኃጢአትን የሚወዱ" ወይም "ውሃ የሚጠጡትን ያህል ደጋግመው ክፉ ስራ የሚሰሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 15:17

እኔ አሳይሃለሁ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "እኔ አብራራልሃለሁ" ወይም "እኔ ግልጽ አደርግልሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አሳውቃለሁ

"እኔ አውጃለሁ"

አባቶቻቸው አልደበቁም

ኤልፋዝ አባቶቻቸው በአላማ እነዚህን ነገሮች እንዳስማሯቸው ትኩረት ይሰጣል። "አባቶቻቸው በግልጽ አስተምረዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 15:19

ምድሪቱ ለብቻቸው የተሰጣቸው

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ምድሪቱን ለብቻቸው የሰጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በመካከላቸው ማንም እንግዳ አላለፈም

ይህ ማለት ምንም ባዕድ በመካከላቸው አልኖረም፣ በተለይ በአህዛብ ሃይማኖት ተጽእኖ ስር እንዳይወድቁ ይህ ሆነ። "ከሌላ አገር ማንም ሰው መጥቶ ስለ እግዚአብሔር የተሳሳተ ሃሳብ እንዲኖራቸው ምክንያት አልሆነም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በህመም ይጥመለመላል

"ብዙ ስቃይ ማየት።" ይህ የአካል ወይም የስሜት ስቃይ ነው

የተመደቡ አመታት ቁጥር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግኢአብሔር የመደባቸው አመታት ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የተመደቡ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "የተዘጋጁ" ወይም "የተለዩ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በጆሮቹ የፍርሃት ድምጽ

"ሳያቋርጥ የሚያስፈራውን ድምጽ ይሰማል"

Job 15:22

አያያዥ ሀሳብ፡

ኤልፋዝ በኢዮብ 15:20 መግለጽ የጀመረውን ክፉ ሰው ማብራራቱን ይቀጥላል

ከጨለማ መመለስ

እዚህ ስፍራ "ጨለማ" ለችግር ወይም እድለቢስነት ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "መጥፎ እድልን ማምለጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ ይጠብቀዋል

እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" ክፉ ሰውን ለመግደል የሚጠብቅን ጠላት የሚወክል ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰው ይገድለኛል ብሎ ፈርቷል። "አንድ ሰው ይገድለኛል ብሎ ፈርቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) መገደሉ የተረጋገጠ ነው። "ሊገድለው የሚጠብቅ ሰው አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእንጀራ/ለዳቦ

እዚህ ስፍራ "እንጀራ/ዳቦ" የሚያመለክተው በአጠቃላይ ምግብን ነው። "ለ እንጀራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የቀን ጨለማ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "የጥፋት ቀን" ወይም "የሞቱ ሰአት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእጅ ላይ ያለ ነገር

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "በቶሎ የሚመጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጥፋት እና ጭንቀት አስፈራርተውታል፤ በእርሱ ላይ አይለዋል

"ጥፋት" እና "ጭንቀት" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ የስሜቱን ጥልቀት ያጎላሉ። እዚህ ስፍራ እነዚህ ስሜቶች ክፉውን ሰው የሚያጠቁ ጠላቶች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። (ጥንድ ትርጉም እና ሰውኛ የሚሉትን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይመልከቱ)
አይለውበታል
"ከአቅም በላይ" ወይም "ማሸነፍ"
ለጦርነት እንደ ተዘጋጀ ንጉሥ
ይህ ጥፋቱ እና ጭንቀቱ ለጦርነት እንደተዘጋጀ ንጉሥ እንዴት በእርሱ ላይ እንዳየሉበት ያነጻጽራል። "ልክ ለጦርነት እንደ ተዘጋጀ ንጉሥ በእርሱ ላይ ተነስተውበታል/አይለውበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 15:25
እጁን በእግዚአብሔር ላይ አንስቶ
"እጁን በእግዚአብሔር ላይ አወዛውሏል።" ይህ የጠብ ምልክት ነው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት)
በእግዚአብሔር ላይ መነሳት
ይህ ክፉ ሰው በእግዚአብሔር ላይ እርሱን ለማጥቃት ይመስል በጠብ የሚያደርገውን የሚገልጽ ነው። "እግዚአብሔርን ማጥቃት/መድፈር" ወይም "በእግዚአብሔር ላይ መነሳት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በበወፍራም ጋሻ
"በእርሱ ጠንካራ ጋሻ"
Job 15:27
ይህ እውነት ነው
"ይህ" የሚለው በቀደመው ቁጥር ክፉ ሰው በእግዚአብሔር ላይ መነሳቱን ያሳያል
ፊቱን በስቡ ሸፍኗል፣ ደግሞም በሽንጡ ስቡን አከማችቷል
ክፉ ሰው እንደ ሰባ እና ደካማ ሰው ተገልጾዋል፤ እርሱ ግን እግዚአብሔርን እስከሚያሸንፍ ድረስ ጠንካራ እንደሆነ እንደሚያምን ተደርጎ ቀርቧል። "እርሱ ፊቱ እና ሽንጡ በስብ የተሸፈነ ደካማ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
ማንም ሰው በማይኖርበት
"ወና በሆነ ስፍራ"
ክምር
እርባና ቢስ የሆኑ ነገሮች ቁልል
Job 15:29
ባለጸጋ አይሆንም፣ ሀብቱ አይቆይም
እነዚህ ሁለት ምፀታዊ አገላለጾች የብልጽግና ተቃራኒው እንደሚደርስበት፣ ማለትም ደሃ እንደሚሆን ይናገራሉ። "ይደኸያል፣ ገንዘቡ ሁሉ ይጠፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)
ከጨለማ ስፍራ
ጨለማ እዚህ ስፍራ ላይ ሞትን ይወክላል። "በሞት ጨለማ ውስጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ቅርንጫፎቹን እሳት ያደርቃቸዋል
እዚህ ስፍራ እሳት/ነበልባል የሚወክለው የእግዚአብሔርን ፍርድ ሲሆን፣ የቅርንጫፎች መድረቅ የሚወክለው አንድም የክፉ ሰው ሃብት መጥፋቱን፣ አሊያም የሚሞት መሆኑን ነው። "እሳት የእርጥብ እንጨትን እርጥበት እንደሚያደርቅ፣ እግዚአብሔር ያለውን ነገር ሁሉ ይወስድበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር አፍ እስትንፋስ
እዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር "እስትንፋስ" የሚለው የሚወክለው የእርሱን ፍርድ ነው። "የእግዚአብሔር እስትንፋስ" ወይም "የእግዚአብሔር ፍርድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ይሄዳል/ይሸሻል
ይህ የሚያመለክተው የእርሱን መሞት ነው። "እርሱ ይሞታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 15:31
ሸላማቱ ረብ የለሽነት ይሆናል
ይህ የሚያመለክተው በማይረቡ ነገሮች ከታመነ የሚደርስበት ነገር ነው። "በእነርሱ ላይ ከታመነ፣ ሽልማቱ የማይረቡ ነገሮች ይሆናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
ቅርንጫፎቹ አይለመልሙም
ይህ የሚገልጸው ከግንዱ ተገነጥሎ እንደ ደረቀ ቅርንጫፍ የሚገረጣ ወይም የሞተ የሚመስልን ሰው ነው። "የሞተ ዛፍ ቅርንጫፍ እንደማይለመልም እርሱም የሞተ ይመስላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ፍሬውን...ይጥላል፣ አበባውን ... ያረግፋል
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉን የሰጣሉ፤ የተደገሙት ነገሩ እንደሚሆን ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ወይን ተክል ያልበሰለ የወይን ፍሬውን ይጥላል
ይህ የሚናገረው ያልበሰለ የወይን ፍሬውን እደሚጥል የወይን ተክል ክፉ ሰው ይበልጥ እየደከመ እና እየሞተ የሚሄድ መሆኑን ነው። "የወይን ተክል ያልበሰለ ፍሬውን እንደሚጥል፣ ክፉ ሰው ጥንካሬው ይክደዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ወይራ ዛፍ አበባውን ያረግፋል
ይህ የሚናገረው የወይራ ዛፍ አበባውን እንደሚያረግፍ ክፉ ሰው እየደከመ እና እየሞተ እንደሚሄድ ነው። "የወይራ ዛፍ አበባውን እንደሚያረግፍ ክፉ ሰውም ጥንካሬው ይክደዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 15:34
እግዚአብሔር የለሽ የሆኑ ሰዎች ጉባኤ
"እግዚአብሔር የለሽ የሆኑ ሰዎች ስብስብ"
በጉቦ የተሰራውን ድንኳናቸውን እሳት ይበላዋል
"በጉቦ የተሰራ ድንኳን" የሚለው ሀረግ እነዚህ ክፉ ሰዎች ድንኳናቸው የገዙት በጉቦ ባገኙት ገንዘብ ነው ማለት ነው። "ከጉቦ ባገኙት ገንዘብ የገዙት ድንኳን በእሳት ይቃጠላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሀብት ንብረት የሚለውን ይመልከቱ)
ተንኮልን ጸንሰው ኃጢአትን ይወልዳሉ፤ማህጸናቸው ማታለልን ይጸንሳል
ተመሳሳይ ሀሳብ ሶስት ጊዜ የሚደጋገመው እነዚህ ሰዎች ምን ያህል ክፉ ነገር እንደሚያደርጉ ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ክፉ ነገሮችን ለማድረግ የሚያቅዱ እና ያንንም የሚያደርጉ ሰዎች፣ ሴት ጸንሳ እንደምትወልድ እነዚህም ክፉ ነገርን ጸንሰው እንደሚወልዱ ይገልጻል። "እነርሱ ተንኮልን ለማድረግ አቅደው ክፉ ነገሮችን ያደርጋሉ፤ ሁልጊዜም ሌሎችን ለማታለል ያቅዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ማህጸናቸው ይጸንሳል
እዚህ ስፍራ "ማህጸን" የዋለው ጸንስ የሚጸነሰው በማህጸን እንደሆነ ሁሉ ይህን ትኩረት ሰጥቶ ከሰው ጋር አያይዞ ለመግለጽ ነው። "ይጸንሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 16
Job 16:1
እናንተ ሁላችሁ የምታስጨንቁ አጽናኖች ናችሁ
"እኔን ከማጽናናት ይልቅ፣ ሁላችሁም ታስጨንቁኛላችሁ"
እስከ መቼ ማለቂያ የሌለው የማይረባ ቃል ትጠቀማላችሁ?
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠቀመው እርባና የሌላቸውን ቃላት መናገራቸውን እንዲያቆሙ መፈለጉን ለመግለጽ ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር/በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እርባና ቢስ የሆኑ ቃሎቻችሁ ማብቂያ ቢኖራቸው ምን ያህል ደስ ባለኝ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በዚህ አይነት መልስ የምትሰጡት ምን ሆናችሁ ነው?
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠቀመው ኤልፋዝን ለመገሰጽ ነው። እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም ከኢዮብ ጋር ንግግሩን የጨረሰውን ኤልፋዝን ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር/በገለጻ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ኤልፋዝ ሆይ፣ ለእኔ እንዲህ ያለ መልስ መስጠትህን ማቆም ይኖርብሃል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Job 16:4
እኔም ቃላትን አቀናብሬ ማሳመር እችላለሁ
ኢዮብ እርባና ስለሌላቸው ነገሮች ስለማሰብ የሚናገረው እርሱም ቃላትን አጠረቃቅሞ መናገር እንደማይቸግረው ለመግለጽ ነው። "እኔም ቃላትን አሳክቼ መናገር እችላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እራሴን እነቀንቃለሁ
አይሆንም የሚለውን ለማሳየት የሚደረግ ድርጊት። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
በመሳለቅ
"መሳለቅ" የሚለውን ቃል በግስ መልኩ መጠቀም ይቻላል። "በእናንተ ላይ መሳለቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
በአንደበቴ አበረታታችሁ ነበር፣ የከንፈሬ ቃል ለእናንተ ረፍት በሆናችሁ ነበር!
"አንደበት/አፍ" እና "ከንፈር" ሰው አንደበቱን እና ከንፈሩን በመጠቀም ለሚናገራቸው ቃላት ወይም መልዕክቶች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። እዚህ ስፍራ ኢዮብ በሽሙጥ እየተናገረ ሲሆን ከሚናገረው ተቃራኒውን ማለቱ ነው። "በእርግጥ ንግግሬ እናንተን አያበረታታም! በእርግጥ ሀዘናችሁን አያቀልም" ወይም "እናንተ አስቀድማችሁ እኔን በተናገራችሁበት መንገድ እናንተን በመናገር፣ እናንተን አላበረታታም ወይም ሀዘናችሁን አላቀልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)
በአንደበቴ/በአፌ
እዚህ ስፍራ የኢዮብ "አፍ" የሚወክለው እርሱ የተናገረውን ነው። "እኔ በምናገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በከንፈሬ ንግግር/በአፌ ቃል
እርሱ ለተናገራቸው ቃላት ወይም መልዕክቶች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የማጽናናት ቃሎቼ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)
እረፍት በሆናችሁ
ይህ ሀዘን አካላዊ ከባድ ሸክም እንደሆነ ይናገራል። "ሀዘናችሁን ያቀልላችኋል" ወይም "ሀዘናችሁ እንዲቀል ይረዳችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 16:6
ሀዘን
ኢዮብ ያልተጠበቀና በቃላት ለመግለጽ የሚያዳግት "ታላቅ ሀዘን እና የስሜት ስቃይ" ቤተሰቡን እና ጤናውን በማጣት አጋጥሞታል
እንዴት አጸናናለሁ?
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ዝም ማለቱ ስቃዩን ለማቃለል እንዳልረዳው ለመግለጽ ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ/ዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ይህ ምንም አልረዳኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን አሁን፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ
ኢዮብ አሁን ማጉረምረሙን ወደ እግዚአብሔር ዞር ያደርገዋል
ቤተሰቤን ሁሉ አጠፋህ
"ቤተሰቤን ሁሉ ደመሰስህ"
አንተ እኔን አደረቅኸኝ
ይህ ማለት የኢዮብ አካል ከሳ ቆዳው ተሸበሸበ ማለት ነው። "ከሰውነት ተራ ወጣሁ አካሌን አከሳኸው" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ራሱ ይመሰክርብኛል
ኢዮብ የሰውነቱን መክሳት በእርሱ ላይ ከሳሽ እንደሆነ አድርጎ ያቀርበዋል። "ደግሞም ይህ ሰዎች እኔን ኃጢአተኛ አድርገው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰውነቴ ክሳት በእኔ ላይ ተቃዋሚ ሆኖ ይነሳብኛል፣ ምስክርም ይሆንብኛል
ኢዮብ የአካሉን መክሳት በእርሱ ላይ ከሳሽ እንደሆነበት ይገልጻል። "ምን ያህል እንደከሳሁ ይመለከታሉ፣ ይህም ደግሞ እኔ ኃጢአተኛ እንደሆንኩ ያረጋግጣል ብለው ያስባሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ፊቴ ላይ
እዚህ ስፍራ ኢዮብ የተጠቀሰው በእርሱ "ፊቱ" ነው። "በእኔ ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 16:9
እግዚአብሔር በቁጣው በጫጨቀኝ፣ ደግሞም አሳደደኝ... ቀዳዶ ጣለኝ
ይህ የሚገልጸው እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ ስቃይ ያደረሰበት ያደነውን ገድሎ እንደሚመገብ እንስሳ አድርጎ ነው። "እግዚአብሔር በእኔ በጣም ስለተቆጣ የዱር አውሬ በጥርሱ እንደሚቦጫጭቅ አካሌን ጠላት ሆኖ በጣጥሶታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጠላቴ
ኢዮብ እግዚአብሔርን ትልቅ መከራ እንዳደረሰበት እንደ "ጠላቱ" አድርጎ ይገልጻል
ዐይኖቹን በእኔ ላይ አጣብቋል/ተክሏል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ዐይኑን ተከለብኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሰዎች በመገረም አፋቸውን ከፍተዋል
"አፍ መክፈት" የሚለው በመደነቅ አፍን ከፍቶ መመለከት ማለት ነው
Job 16:11
አምላክን ለማይወዱ ሰዎች አሳልፎ ሰጠኝ፣ በክፉ ሰዎች እጅ ላይ ጣለኝ
እነዚህ ሁለት መስመሮች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በአንድነት ሆነው የኢዮብን በእግዚአብሔር የመካድ ስሜት ያጎላሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አሳልፎ ሰጠኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "በቁጥጥራቸው ስር አደረገኝ"
በእጃቸው ላይ ጣለኝ
እዚህ ስፍራ የሰው "እጅ" የሚያመለክተው በ"ቁጥጥሩ ስር" ማድረግን ነው። "ከተጽዕኗቸው ነጻ አውጣኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ደግሞም እርሱ ሰባብሮኛል
ኢዮብ መከራውን እና ተስፋ መቁረጡን የሚገልጸው እርሱ ራ ወደ ትንንሽ ነገሮች እንደተሰባበረ አድርጎ ነው። "ነገር ግን የሚሰማኝ እርሱ እንደሰባበረኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቆራርጦ ጣለኝ
ኢዮብ የሚናገረው እግዚአብሔር ስቃይ እንዳደረሰበት እና ተስፋ እንዳስቆጠረው፣ እንደዚሁም ወደ ቁርጥራጭ ነገርነት እንዳደቀቀው ነው። "አንገቴን አንቆ ትንንሽ ነገር አድርጎ አድቅቆኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ደግሞም አላማው አድርጎ አስቀምጦኛል
ኢዮብ ራሱን የእግዚአብሔር ጥቃት ትኩረት እንደሆነና እግዚአብሔር ቀስቱን የሚያነጣጥርበት አላማው እንዳደረገው ይናገራል። "አላማው አድርጎኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 16:13
የእርሱ ቀስተኞች ዙሪያዬን ከበውኛል
ኢዮብ ስለ ራሱ የሚናገረው የእግዚአብሔር ጥቃት ትኩረት እንደሆነ፣ እግዚአብሔር እርሱን እንደ ጥቃት አላማ ከፍ አድርጎ እንዳስቀመጠው የእግዚአብሔር ቀስተኞች ሊያጠቁት እንደከበቡት አድርጎ ነው። "የእርሱ ቀስተኞች ዙሪያዬን ከበውኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ኩላሊቴን በስቶታል፣ ለአፍታም አልተወኝም፣ ሀሞቴን በምድር ላይ አፍስሶታል
ኢዮብ የደረሰበትን መከራ ስሜት የሚገልጸው እግዚአብሔር አካሉን በቀስቶች እንደበሳው በማነጻጸር ነው። እዚህ ስፍራ "እግዚአብሔር" የሚለው የሚወክለው እርሱ የሚወረውራቸውን ቀስቶች ነው። "ኩላሊቴን እና ጉበቴን የእግዚአብሔር ቀስቶች እንደወጉኝ፣ ሀሞቴ በምድር ላይ እንደፈሰሰ ይሰማኛል። እርሱ አልተወኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቅጥሬን አፈረሰው
ኢዮብ የተሰማውን ስቃይ የሚገልጸው ራሱን እግዚአብሔር ካፈረሰው ግንብ ጋር በማነጻጸር ነው። "እግዚአብሔር እንዳፈረሰው ግንብ እንደሆንኩ ይሰማኛል" ወይም "እግዚአብሔር እንዳደቀቀው ግንብ እንደሆንኩ ይሰማኛል። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ጦረኛ ወደ እኔ ይሮጣል
ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚገልጸው እርሱን እንደሚያጠቃ ወታደር ነው። "ሊያጠቃኝ ወደ እኔ እየሮጠ እንደሚመጣ ተዋጊ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 16:15
በቆዳዬ ላይ ማቅ ሰፍቻለሁ
ኢዮብ ከሰውነቱ ጋር እንደ ተያያዘ ሆኖ የተሰፋ ማቅ ስለ መልበስ ይናገራል። ሰዎች ብዙጊዜ ማቅ የሚለብሱት ሀዘናቸውን ወይም ታላቅ መከራ እንደደረሰባቸው ለመግለጽ ነው። "አዝኛለሁና ማቅ ሰፍቼ አለብሳለሁ" ወይም "ከማቅ የሰፋሁትን ልብስ እለብሳለሁ፣ ምክንያቱም አዝኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቀንዴን በአፈር ውስጥ እቀብራለሁ
የኢዮብ "ቀንድ" የሚወክለው ቀድሞ የነበረውን አሁን ግን ከእርሱ ጋር የሌለውን ሀይሉን እና ስልጣኑን ነው። "አሁን እዚህ በትካዜ/በጣም በድባቴ ሆኜ በትቢያ ላይ እቀመጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በዐይኖቼ ሽፋሽፍት የሞት ጥላ አለ
እዚህ ስፍራ የኢዮብ ዐይኖች የተወከሉት በ "ዐይኖቹ ሽፋሽፍት" ነው። ኢዮብ የዐይኖቹን መጨለም የሚገልጸው ዐይኖቹ የሞተ ሰው ዐይን እንደመሰሉ አድርጎ ነው። "በዐይኖቼ ዙሪያ ጥቁር ክቦች አሉ" ወይም "ዐይኖቼ እንደ ሞተ ሰው ዐይን ጥቁር ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
በእጆቼ ላይ አመጽ የለም
"እጆች" የሚለው የሚወክለው የአንድን ሰው ችሎታ እና ድርጊት ነው። "በግፍ አንዳች አላደረግኩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 16:18
ምድር ሆይ፣ ደሜን አትሸፍኚ
ኢዮብ ሃሳቡን ለማጉላት ባትሰማውም እንኳን በቀጥታ ለ"ምድር" ይናገራል። ምድር ከሞቱ በኋላ ደሙን አውቃ እንደምትሸፍን ተደርጋ በሰውኛ ተገልጻለች። "ደሜን ምድር ሳትመጠው ከላይ ተቀምጦ እንዴት እንደሞትኩ ምስክር ቢሆን እመኛለሁ" (አፖስትሮፊ/በተለይ በአጠገብ የማይገኝን ነገር አጋኖ ለማመልከት የሚነገር ዘይቤ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ምድር ሆይ፣ ደሜን አትሸፍኚ
ኢዮብ ስለ ራሱ ሞት የሚናገረው እንደሚገደል አድርጎ ነው። እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው የእርሱን መሞት የሚያመለክት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ምድር ሆይ፣ በምሞትበት ሰአት፣ አለአግባብ መሞቴን አትደብቂ" ወይም "አለ አግባብ መሞቴ አይደበቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ጩኸቴ የእረፍት ስፍራ አያግኝ
ኢዮብ የእርሱ "ጩኸት" ሰው ሆኖ የደረሰበትን እና በፍጹም እረፍት ያሳጣውን ነገር ለሁሉም ሰው እንዲያሳውቅለት በመፈለግ ይናገራል። "ሁሉም ሰው በእኔ ላይ የደረሰውን ይስማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ
ኢዮብ ይህንን ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ለሚናገረው ትኩረት ለመስጠት ነው። "አድምጡኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ይመሰክርልኛል
"ጻድቅ መሆኔን ይመሰክራል"
በላይ ያለው
ይፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "በሰማይ" ወይም "በላይ በሰማይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 16:20
በፌዝ
"ንቀት" ወይም "መሳለቅ"
ዐይኖቼ እንባ ያፈሳሉ
ኢዮብ ሀዘኑ ምን ያህል ብርቱ እንደሆነ ይገልጻል። ከዐይኖቼ እንባ ይጎርፋል በማለት ምን ያህል አዘውትሮ እንሚያለቅስ አጉልቶ ይናገራል። "በምጮህበት ጊዜ ዐይኖቼ በእንባ ይሞላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
ለዚህ ሰው
"ለእኔ።" እዚህ ስፍራ ኢዮብ ራሱን በሶስተኛ መደብ ይጠቅሳል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦስተኛ መደቦች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰው ከወዳጁ ጋር እንደሚያደርገው
"ሰው ለወዳጁ እንደሚያደርገው።" ኢዮብ በሰማይ የሚኖረው ለእርሱ ምላሽ እንዲሰጥለት እንደሚፈልግ ይገልጻል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ አንድ ስፍራ እሄዳለሁ
እዚህ ስፍራ ኢዮብ እንደሚሞት እያመለከተ ነው። "ስሞት ወደ አንድ ስፍራ እሄዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 17
Job 17:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጠለ
መንፈሴ ደክሞአል
ኢዮብ ስለ ራሱ በ"መንፈሱ" አማካይነት የሚያመለክተው ውስጣዊ ስሜቱን በትኩረት ለመግለጽ ነው። ሁለንተናው እንደደከመ እና አንዳች ጥንካሬ በውስጡ እንዳልቀረ ይናገራል። "እኔ ደክሜያለሁ" ወይም "አቅሜ ሁሉ ተሟጧል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ዘመኔ ተፈጽሟል
"የእኔ እድሜ አብቅቷል" ወይም "በቅርቡ እሞታለሁ"
መቃብር ተዘጋጅቶልኛል
ይህ ሀረግ "መቃብርን" የሚገልጸው ኢዮብን በእንግድነት እንደሚቀበል ሰው አድርጎ ነው። "በቅርብ እሞትና እቀበራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በእርግጥ በእኔ ዘንድ ፌዘኞች አሉ
"በዙሪያዬ የሚገኙት በእኔ ላይ እያፌዙ ነው"
በእርግጥ
"በእርግጠኝነት" ወይም "ስለዚያ ነገር ጥርጥር የለውም"
ዐይኖቼ ሁሌም ማየት ያለባቸው
ኢዮብ ባየው ነገር ላይ ትኩረት ለመስጠት ራሱን በ "ዐይኖቹ" አማካይነት ይገልጻል። "እኔ ሁልጊዜም ማየት ያለብኝ" ወይም "ሁሌም መስማት የሚገባኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
የእነርሱ ትንኮሳ
"የእነርሱ ስድብ።" "ትንኮሳ" የሚለው ቃል በግስ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። "እነርሱ ተነኮሱኝ" ወይም "እነርሱ ሊያናድዱኝ ሞከሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ቃል ግባልኝ፣ አንተ ዋስ ሁነኝ
ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ይጀምራል። እዚህ ስፍራ ስለሚገኝበት ሁኔታ በእስርቤት ውስጥ እንደሚገኝ አድርጎ ይናገራል። ነጻ ይሆን ዘንድ ቃል እንዲገባለት እግዚአብሔርን ይጠይቃል። "እግዚአብሔር ሆይ፣ ከዚህ እስር እፈታ ዘንድ ቃል ግባልኝ" ወይም "ከእስር እንድፈታ ዋጋ ክፈል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሚረዳኝ ሌላ ማን አለ?
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው እርሱን ለረዳው የሚችል ሌላ ማንም እንደሌለ ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ/ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሊረዳኝ የሚችል ሌላ ማንም የልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 17:4
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጠለ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የእነርሱን ልቦች ይዘሃል
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእርሱን ወዳጆች ነው። እነርሱ በ "ልቦቻቸው" የተገለጹት ስሜታቸው ላይ ትኩረት ለመስጠት ነው። "ይዘሃቸዋል" ወይም "ጓደኞቼን ይዘሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ እነርሱን በእኔ ላይ ከፍ ከፍ አታደርግም
"እንዲያሸንፉኝ አትፈቅድላቸውም"
ማንም እርሱ
"ማንም ቢሆን"
ለጥቅም ብሎ ወዳጁን የሚያወግዝ
"ጥቅም ለማግኘት ብሎ ወዳጆቹን በሃሰት የሚወነጅል" ወይም "ሽልማት ለማግኘት ብሎ ወዳጁን የሚክድ"
የልጆቹ ዐይኖች ይጨልማሉ
እዚህ ስፍራ የሰውየው ልጆች የተገለጹት በ"ዐይኖቻቸው" ነው። ይህ ሀረግ የሚገልጸው አባቶቻቸው ወይም እናቶቻቸው በሰሩት ስራ ምክንያት ስለሚሰቃዩ ልጆች ነው። "ልጆቹ መከራ ይቀበላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 17:6

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ መናገሩን ቀጠለ
ለሰው ሁሉ መተረቻ አደረገኝ
ይህ ማለት ሰዎች ስለ እረሱ በፌዝ ይናገራሉ፤ ስሙንም በነቀፌታ/ስድብ ያነሳሉ። "በእርሱ ምክንያት፣ ሰዎች የእኔን ስም እንደ ስድብ አደረጉት" ወይም "በእነርሱ ምክንያት፣ ሰዎች ስሜን መተረቻ አደረጉት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ፊቴ ላይ ተፉ
"ሰዎች ፊቴ ላይ ተፉ።" በዚህ ባህል በአንድ ሰው ፊት ላይ መትፋት ታላቅ ስድብ ነበር። ፊት ላይ መትፋት በባህላችሁ የተለየ ትርጉም ካለው ይህንን በተለየ መልክ መጻፍ ትችላላችሁ። "ሰዎች ፊቴ ላይ በመትፋት እጅግ አዋርደው ሰደቡኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ከሀዘን የተነሳ ዐይኔ ፈዘዘ
ኢዮብ እይታውን እንደ "ዐይኖቹ" አድርጎ ይናገራል። "እጅግ ከማዘኔ የተነሳ እይታዬ ደካማ ሆነ" ወይም "ከሀዘኔ የተነሳ የታወርኩ ያህል ሆንኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
መላው የሰውነቴ ክፍሎች እንደ ጥላ የሳሱ ናቸው
ጥላ ምንም ውፍረት የለውም ይህ ነው በማይባል መጠን የሳሳ ነው። ይህ የኢዮብ የሰውነት ክፍሎች ምን ያህል ቀጭን እንደሆኑ የሚያሳይ ግነት ነው። "የአካል ክፍሎች ሁሉ በጣም የከሱ/ቀጭን ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ኩሸት እንዲሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
መላው የሰውነቴ ክፍሎች
ይህ መላ አካሉ ቀጭን መሆኑን ለማጉላት የዋለ አጠቃላይ አስተያየት ነው፤ ሆኖም በተለይ እጆቹን እና እግሮቹን ያመለክታል። "እጆቼ እና እግሮቼ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
ይደነግጣሉ
"ይርበተበታሉ" ወይም "ይፈራሉ"
በዚህ
"በእኔ ላይ በደረሰው"
ራሱን በ…ተቃውሞ ያስነሳል
ይህ ፈሊጣው አነጋገር ነው። "በ…ምክንያት ይሰቃያል" ወይም "በ… በጣም ይቆጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 17:9

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ መናገሩን ቀጠለ
በመንገዱ ይጸናል
ይህ ፈሊጣው አነጋገር ነው። "በጽድቅ መንገድ መኖሩን ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ንጹህ እጆች ያሉት
ይህ የሚናገረው ትሁት የሆነውን ሰው ንጹህ እጆች እንዳሉት ሰው አድርጎ ነው። "ትክክል የሆነውን የሚያደርግ እርሱ" ወይም "ትሁት የሆነ እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እያደር እየበረታ ይሄዳል/እየበረታ እና እየበረታ ይሄዳል
ይህ ስለ አካላዊ ጥንካሬ ብቻ አይናገርም፤ ነገር ግን ስለ ሰው ፈቃድ እና ስሜት ጥንካሬም ጭምር ይናገራል።
እናንተ ሁላችሁ
ኢዮብ የሚናገረው ለኤልፋዝ፣ በልዳዶስ እና ሶፋር ነው።
አሁን ቅረቡ
ኢዮብ ወዳጆቹን እርሱ የተናገረውን እንዲሞግቱ/እንዲከራከሩ ይጋብዛቸዋል። " አሁን ቅረቡ፣ ዳግም ከእኔ ጋር ተከራከሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 17:11

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ መናገሩን ቀጠለ
ቀኖቼ አልፈዋል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ጊዜዬ አልፏል" ወይም "ህይወቴ አብቅቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እቅዶቼ ተንኮታኩተዋል፣ የልቤ መሻቶችም እንደዚሁ
እዚህ ስፍራ የኢዮብ "ልብ" የሚወክለው ውስጣዊ ማንነቱን ነው። "እቅዶቼ መቼም አይፈጸሙም፣ እጅግ የተመኘኋቸው ነገሮችም እውን አይሆኑም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህ ሰዎች፣ እነዚህ ፌዘኞች
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ሰዎችን ያመለክታሉ፣ እነርሱም የኢዮብ ወዳጆች የሆኑት ኤልፋዝ፣ በልዳዶስ እና ሶፋር ናቸው። ሁለተኛው ሀረግ ወዳጅነት የጎደለውን ዝንባሌያቸውን ያጎላል። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
ምሽቱን ወደ ቀን ይለውጣሉ
ይህ የሚናገረው ሰዎቹ በእርግጥም ምሽቱን ወደ ቀን የለውጡ ይመስል ምሽቱን ቀን ነው እንደሚሉ ነው። "ምሽት ሆኖ ሳለ ቀን ነው ይላሉ" ወይም "ምሽት የቀን ተቃራኒ የሆነውን ያህል እውነት ከሆነው በተቃራኒ ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ብርሃን ለጨለማ ቅርብ ነው
እዚህ ስፍራ የተጠቆመው ፌዘኞች ጨለማ ቀርቦ ሳለ ብርሃን ነው ማለታቸው ነው። "ብርሃን ለጨለማ ቅርብ ነው ይላሉ" ወይም " ጨለማው እየመጣ፣ እየነጋ ነው ይላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 17:13

አጠቃላይ መረጃ:
ኢዮብ መናገሩን ቀጠለ
ብቸኛው ቤት ቢሆን እንኳን… ደግሞም እኔ ባነጥፍ …. ብዬ ብናገር እንኳን
እዚህ ስፍራ "ቢሆን" የሚሉት ሁኔታዎች ሁሉ "እስከ/ድረስ" የሚል ትርጉም አላቸው፡ ኢዮብ ሁሉም ነገሮች እውነት እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። "ብቸኛው ቤት ቢሆን … እስካነጥፍ ድረስ….ደግሞም እስከተናገርኩ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)
በጨለማ አልጋዬን አነጥፋለሁ
እዚህ ስፍራ ኢዮብ የሚናገረው፣ በጨለማ አልጋውን እያነጠፈ ባለበት ለሞት እየተዘጋጀ መሆኑን ነው። "በሞቱት መካከል ሄጄ ለመተኛት ራሴን አዘጋጅቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አልጋዬን አነጥፋለሁ
"አልጋዬን አዘጋጃለሁ"
ለጉድጓድ እንዲህ እለዋለሁ… ለትልም ደግሞ
እነዚህ ሁለት መስመሮች አንዱ ለሌላው አማራጭ ሲሆን በአንድ ላይ የኢዮብን ተስፋ መቁረጥ ጥልቀት ያጎላሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጉድጓዱ
"መቃብሩ"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አንተ አባቴ ነህ

ኢዮብ በቅርቡ ወደ መቃብሩ የሚኖረውን ቅርበት የሚገልጸው ሰው ከአባቱ ጋር ከሚኖረው ቅርበት ጋር በማነጻጸር ነው። "አንተ የአባቴን ያህል ለእኔ ቅርብ ነህ" ወይም "ስቀበር፣ አንተ የአባቴን ያህል ትቀርበኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ትልን

"ትል/የስጋ ወይም የእበት ትል።" ትሎች የሞተ አካልን የሚበሉ ትንንሽ ፍጥረት ናቸው።

አንቺ እናቴ ነሽ ወይም አንቺ እህቴ ነሽ

ኢዮብ አንድ ሰው ከእናቱ ወይም ከእህቶቹ ጋር ከሚኖረው ቅርበት ጋር በማነጻጸር በቶሎ በመቃብር ውስጥ ከትል ጋር የሚኖረውን ቅርበት ይናገራል። "አንተ የእናቴ ወይም የእህቴን ያህል ለእኔ ቅርብ ነህ" ወይም "አንተ ለእኔ የእናትን ወይም የእህትን ያህል ቅርቤ ትሆናለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ተስፋዬ ወዴት አለ?

በውስጠ ታዋቂነት የተሰጠው መልስ "የትም የለም" የሚል ነው፤ ምክንያቱም ተስፋ ቆርጧል። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በገለጻ/ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ ምንም ተስፋ የለኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው)

ተስፋዬን የሚያይልኝስ ማን ነው?

ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ማንም ሰው እርሱ አንዳች ተስፋ ይኖረዋል ብሎ እንደማያስብ ለማጉላት ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ/ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ሰው ስለ እኔ ተስፋ አይታየውም" ወይም "ማንም ሰው ከእንግዲህ እኔ ምንም ተስፋ እንደሚኖረኝ አይጠብቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው)

ወደ ትቢያ ...ተስፋ ከእኔ ጋር ይሄዳልን?

በውስጠ ታዋቂነት የተሰጠው ምልስ "የለም" የሚል ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ/ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወደ ትቢያ...ተስፋ ከእኔ ጋር አይወርድም" ወይም "ወደ ትቢያ... ስወርድ ከዚያ ወዲያ ተስፋ አላደርግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው)

የሲኦል በሮች

ሲኦል በእርግጥ በር የለውም፣ ነገር ግን ኢዮብ ወደ መቃብር ለመግባቱ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ወደ መቃብር ስወርድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ በ...ጊዜ

"እኔ እና ተስፋ ያደረኳቸው ነገሮች በ...ጊዜ" ወይም "እኔ እና ተስፋ ያደረኩት በ...ጊዜ" "እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢዮብን እና ተስፋውን ነው።

ወደ አፈር ስገባ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ሞቼ ስቀበር" ወይም "ወደ መቃብር ስወርድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

## Chapter 18

### Job 18:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ሦነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ

አጠቃላይ መረጃ፡

ሹሐዊው በልዳዶስ ከኢዮብ ጋር ይነጋገራል

ከዚያም ሹሐዊው በልዳዶስ እንዲህ ሲል መለሰ

"በልዳዶስ" የሹሐ ነገድ የሆነ ሰው የወንድ ስም ነው። ይህ በኢዮብ 8፡1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

ንግግርህን የምታቆመው መቼ ነው?

ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ኢዮብ ለረጅም ጊዜ ሲናገር ነበር ማለት ነው። ይህ በገለጻ/ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ንግግርህን አቁም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አስተውል፣ ደግሞም

"ምክንያታዊ ሁን፣ ደግሞም" ወይም "ስለእነዚህ ነገሮች አስብ፣ ደግሞም"

### Job 18:3

አጠቃላይ መረጃ፡

በልዳዶስ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

ለምን እኛ በአንተ ፊት እንደ አውሬ/አረመኔ እና የማይረቡ ሆነን ተቆጠርን?

በልዳዶስ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ ወዳጆቹን እንደ እንስሳ እና ማሰብ ወይም መናገር እንደማይችሉ አድርጎ መውሰድ እንደሌለበት አጉልቶ ለማሳየት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር በገለጻ ሊጻፍ ይችላል። "እኛን እንደ አውሬ ወይም ማሰብ እንደማይችሉ መቁጠር የለብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ለምን

"እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምናልባት በልዳዶስን እና ሌሎቹን የኢዮብ ወዳጆች በመሆኑ አካታች አይደለም። (አካታች እና የማያካትት "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)

ተመልከት

እዚህ ስፍራ መመልከት፣ ማየት የሚሉት በሚገባ ማሰብ ወይም በሚገባ አለማሰብ ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ እይታ/ዐይን

እዚህ ስፍራ እይታ የሚወክለው ፍርድን ወይም ሚዛንን ነው። "በአንተ ሚዛን" ወይም "በአንተ አስተሳሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአናንተ እይታ

እዚህ ስፍራ "የእናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። በልዳዶስ ሽሙጥ በመጠቀም ኢዮብ ራሱን ታላቅ ሰው አድርጎ ማሰብ እንደሌለበት ይነግረዋል። "በአንተ ዐይን፣ በስህተት ትልቅ እንደሆንክ የምታስበው አንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሲስተኛ መደብ እንዲሁም ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)

በቁጣህ በራስህ ላይ የምታለቅሰው አንተ

እዚህ ስፍራ በልዳዶስ የሚናገረው ኢዮብ በጉዳት ልይ የሚገኘው ከራሱ ቁጣ እና አለመታዘዝ የተነሳ እንጂ ቀደም ሲል ኢዮብ ሲናገር እንደቆየው ከእግዚአብሔር የተነሳ አለመሆኑን ነው። እዚህ ስፍራ "እንባ"የሚለው ቃል "ጉዳት" ማለት ነው። "ከቁጣህ የተነሳ በራስህ ላይ ጉዳት ያመጣኸው አንተ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ምክንያት ምድር ከስፍራዋ ትጠፋለችን ወይስ አለቶች ስፍራቸውን ይለቃሉ?

ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠቁመው እርሱ ጥፋተኛ አድርገው የሚቆጥሩትን ኢዮብን ዝም ማለት እና መተው መላውን ዓለም እንደመለወጥ ይቆጠራል። በልዳዶስ እዚህ ስፍራ እንዲህ ያለውን ታላቅ ማጋነን የሚጠቀመው ይህ ምን ያህል አስደንጋጭ እና አስፈሪ እንደሆነ እንደሚያስብ ለማጉላት ነው። በዐረፍተ ነገር/ በገለጻ ሊጻፍ ይችላል። "በደለኛ የሆንከውን፣ እግዚአብሔር ዝም እንዲልህ እና እንዲተውህ መለመን እግዚአብሔር ለአንተ ሲል ምድርን ቸል እንዲላት የመጠየቅን ያህል ወይም አንተን ለማስደሰት ሲል አለቶችን ከስፍራቸው እንዲያስወግድ የመጠየቅ ያህል የማይረባ ነገር ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ኩሸት እንደዚሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

ምድር ለአንተ ሲባል መተው/ባዶ መሆን አለባት

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሁሉም ሰው ምድርን መተው/መልቀቅ አለበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አለቶችን ከስፍራቸው መወገድ አለባቸው

x

### Job 18:5

አጠቃላይ መረጃ፡

በልዳዶስ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

በእርግጥ፣ የክፉ ሰው መብራት ትጠፋለች፤ የብርሃኑ ብልጭታ አያበራም

በላዳዶስ የክፉ ሰው አማሟት ሻማው ድርግም ብሎ እንደሚጠፋ አይነት መሆኑን ይናገራል። "የሚሆነው እንዲህ ነው፣ አንተ እንደሚያበቃልህ የክፉ ሰዎች ህይወት ሻማ ወይም የእሳት ነበላባል እንደሚጠፋ በፍጥነት ይጠፋል" በሚለው ውስጥ

እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይጠፋል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ይወገዳል/ያበቃለታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በጎጆው ውስጥ ብርሃን ይጨልማል፣ ከበላዩ ያለው መብራት ይጠፋል

በልዳዶስ ስለ ክፉ ሰው አመሟት መናገሩን ይቀጥላል። ስለ ክፉ ሰው ህይወት በድንኳኑ እንዳለ ብርሃን አድርጎ ይናገራል። "በቤቱ ያለ ብርሃን ወደ ጨለማነት እንደሚለወጥ፣ ከበላዩ ያለ ብርሃን እንደሚጠፋ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 18:7

አጠቃላይ መረጃ፡

በልዳዶስ ክፉውን ሰው መግለጹን ይቀጥላል

የጥንካሬው እርምጃዎች አጭር ይሆናል

ይህ የሚናገረው ክፉ ሰው ለመራመድ አቅም እንደሚያጣ ሆኖ በድንገት ጥፋት እንደሚገጥመው ነው። "ለመራመድ አቅም እንደሚያጣ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የራሱ እቅድ ጠልፎ ይጥለዋል

"የራሱ ምክር እንዲወድቅ ያደርገዋል።" ይህ ክፉ ሰው ልክ እንደሚወድቅ አይነት ጥፋት እንደሚደርስበት ይናገራል። "የራሱ እቅድ ወደ ጥፋት ይመራዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በገዛ እግሮቹ ወደ መረብ ይጣላል፣ ወደ ወጥመድ ይራመዳል

"የራሱ እግሮች ወደ መጥመድ/መረብ ይመሩታል።" በልዳዶስ ይህንን ምስል የሚጠቀመው ክፉ ሰው ህይወቱን የሚኖርበት መንገድ ወደ ድንገተኛ ጥፋት ይመራዋል ለማት ነው። "በቀጥታ ወደ ወጥመድ እንደሚራመድ እራሱን ወደ መረብ የሚመራ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መረብ

ሲባጎ ወይም ገመድ በአንድነት በመሸመን ለወጥነድነት የሚሰራ ወንፊት/መረብ። ሰዎች እንስሳ ለማጥመድ መረብ ይተቀማሉ

ወጥመድ

እንስሳት በላዩ ሲረማመዱ ወደ ውስጥ እንደወድቁ ቅርንጫፎች እና ቅጠል በላዩ የተረበረበበት ጉድጓድ

Job 18:9

አጠቃላይ መረጃ፡

በልዳዶስ ሶስት ትይዩ ንጽጽራዊ ምስሎችን በመጠቀም ክፉ ሰው እንዴት በድንገት ጥፋት እንደሚገጥመው መግለጹን ይቀጥላል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወጥመድ ይይዘዋል… መሰናክል ይገጥመዋል… ሽምቀቆ…. ደግሞም በመንገዱ እንቅፋት

እነዚህ አራት ሀረጎች ክፉ ሰው ጥፋት የሚደርስበት በወጥመድ እንደሚያዝ ሆኖ እንደሆነ ይናገራሉ። "ወጥመድ እንደሚይዘው ይሆናል… መሰናክል ይገጥመዋል… ሽምቀቆ .. ደግሞም በመንገዱ እንቅፋት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማጥመጃ

ሰዎች እንዲህ አይነት ማጥመጃ ወፎችን ለመያዝ ይጠቀማሉ። ማጥመጃ ተሸምቅቆ የወፍን እግር ይይዛል።

ተረከዙን ይይዛል

እዚህ ስፍራ "ተረከዝ" የሚያመለክተው በአቅላላው እግርን ነው። "እግሩን ይይዘዋል/ያጠምዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ሽምቀቆ በምድር ላይ ተደብቆ ተቀምጦለታል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " ይያዝበት/ይጠመድበት ዘንድ አንድ ሰው ሽምቀቆ በምድር ላይ በስውር አጥምዷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሽምቀቆ

እንስሳው በቋተሮም መሃል ሲረማመድ እግሩን ለማጥመድ ቋጠሮ ያለው ገመድ መጠቀም

ለእርሱ ወጥመድ

"ተደብቋል" የሚለው የሚታወቀው ቃላዊ ሀረግ ሊጨመር ይችላል። "እርሱን ለመያዝ ወጥመድ በመንገዱ ላይ ተደብቆ ተቀምጧል" ወይም "እርሱን በመንገዱ ላይ ለማጥመድ አንድ ሰው ወጥመድ ይደብቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/ የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

በየአለቱ ሽብር ያስደነግጠዋል

"በዙሪያው ሽብር ያስፈራዋል"

ከስር ከስሩ/ከተረከዙ በታች ያሳድዱታል

ይህ የሚናገረው ክፉ ሰውን አስፈሪ ነገሮች ጠላት ሆነው እንደሚያሳድዱት ነው። "በሁሉም ስፍራ ሽብር እንደሚያሳድደው ሰው ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 18:12

አጠቃላይ መረጃ፡

በልዳዶስ ክፉውን ሰው መግለጹን ይቀጥላል

ሃብቱ ወደ ረሃብ ይለወጣል

ይህ የሚናገረው ክፉ ሰው ሃብቱ ወዳልሆነ ሌላ ነገር እንደሚለወጥና ደሃ እና ረሀብተኛ እንደሚሆን ነው። "ባለጠጋነቱ ጠፍቶ፣ ድሃ እና ረሃብተኛ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መቅሰፍት በጎኑ የተዘጋጀ ይሆናል

"በጎኑ የተዘጋጀ" የሚለው ሀረግ አንዳች ክፉ ነገር ሁሉም ከአጠገቡ አይታጣም ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ሁሌም ጥፋት ይገጥመዋል" ወይም "መቅሰፍትን ማስቀረት የማይችል ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰውነቱ ክፍሎች ይበላሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። እንደዚሁም፣ ይህ ሰውነቱን የጎዳው ጥፋት እንስሳ እንዳጠቃው እና እንደበላው ተደርጎ ተነግሯል። "በሽታ ቆዳውን በልቶ ጨርሶታል" ወይም "በሽታ ቆዳውን አጥፍቶታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ዘይቤያው አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የሞት የበኩር ልጅ አካሉን ይበላዋል

እዚህ ስፍራ ብዙ ሰዎችን የገደለው በሽታ "የሞት የበኩር ልጅ" ተብሎ ተገልጽዋል። ይህ የተነገረው ሰውነቱን ያጠፋው በሽታ እርሱን እንዳጠቃና እንደበላው እንስሳ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "ክፉ በሽታ የሰውነቱን የተለያዩ ክፍሎች ያጠፉታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 18:14

አጠቃላይ መረጃ፡

በልዳዶስ ክፉውን ሰው መግለጹን ይቀጥላል

በሰላም ከተቀመጠበት ድንኳኑ ይነቀላል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ጥፋት በሰላም ከተቀመጠበት ከድንኳኑ ያባርረዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይነዳል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ነድቶ ያስወጣዋል" ወይም "ወጥቶ እንዲሄድ ያስገድደዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሽብር ንጉሥ

ይህ በሞት ላይ ስልጣን አለው የሚባለው የአህዛብ አማልእክት ለሆነው "ንጉሥ ሞት" ለሚባለው መግለጫ ነው። "በሙታን ላይ የሚገዛው" ወይም " የሞት ንጉሥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ያልሆኑ ሰዎች

"የእርሱ ቤተሰብ ያልሆኑ ሰዎች"

በቤቱ ውስጥ ድኝ እንደተረጨ ከተመለከቱ በኋላ

ሰዎች በሽታን እየሞተ ከሚገኝ/በጽኑ ከታመመ ሰው ላይ ለማባረር ድኝን ይጠቀሙ ነበር። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በቤቱ ላይ ሁሉ ድኝ ከበተኑ በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 18:16

አጠቃላይ መረጃ፡

በልዳዶስ ክፉውን ሰው መግለጹን ይቀጥላል

ስሩ ይደርቃል…ቅርንጫፉ ይቆረጣል

ይህ የሚናገረው ክፉ ሰው ሲሞት፣ ስሩ እንደ ደረቀ እና ቅርንጫፎቹ ጠውልገው እንዳች ፍሬ እንደማያፈራ ዛፍ ሁሉ ተከታይ ትውልድ እንደሚይኖረው ነው። "እርሱ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይሞታል ተከታይ ትውልድም አይኖረውም፣ ስሩ እንደ ደረቀ እና ቅርንጫፉ እንደ ጠወለገ ዛፍ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቅርንጫፉ ይቆረጣል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ቅርንጫፎቹ ይጠወልጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
መታሰቢያው ከምድር ይጠፋል፤ በጎዳና ምንም ስም አይኖረውም
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም ከሞተ በኋላ ማንም የሚያስታውሰው እንደማይኖር ለማጉላት በአንድ ላይ ቀርበዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መታሰቢያው ከምድር ይጠፋል
ይህ የክፉ ሰውን "መታሰቢያ" እንደ ሞተው ሰው አድርጎ ይናገራል። "በምድር ላይ ማንም ሰው አያስታውሰውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በመንገድ/ጎዳና ላይ ምንም ስም አይኖረውም
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "በመንገድ የሚራመድ ማንም ሰው ስሙን እንኳን አያስታውሰውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 18:18
አጠቃላይ መረጃ፡
በልዳዶስ ክፉውን ሰው መግለጹን ይቀጥላል
ከብርሃን ተወግዶ ወደ ጨለማ ይነዳል...ከዚህ ዓለም ይባረራል
እነዚህ ሀረጎች በአንድነት ክፉ ሰው፣ የሙታን መኖሪያ ወደ ሆነው ወደ ሲኦል እንደሚወርድ አጉልተው ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከብርሃን ተወግዶ ወደ ጨለማ ይነዳል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ክፉን ሰው ከብርሃን ወደ ጨለማ ይነዳዋል/ይወስደዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከብርሃን ወደ ጨለማ
"ብርሃን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ህይወትን ሲሆን፣ "ጨለማ" ደግሞ ሞትን ያመለክታል። "ከህይወት ብርሃን ወደ ሞት ጨለማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚህ አለም ይባረራል
ይህ እግዚአብሔር ክፉውን ሰው ምድርን ትቶ ሙታን ወደሚሄዱበት እንደሚያባርረው ይናገራል። "እግዚአብሔር ይህንን ምድር እንዲለቅ/እንዲተው ያደርገዋል" ወይም "እግዚአብሔር ሙታን ወደሚሄዱበት ይልከዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይባረራል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ያሳድደዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ልጅ አይኖረውም... አሊያም የሚቆይበት ቤተዘመድ አይኖረውም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በአንድነት የሚያጎሉት ቤተሰብ ወይም ቀሪ ትውልድ እንደማይኖረው ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የልጅ ልጅ
"የልጅ ልጅ"
ቤተ ዘመድ
"ዘመድ"
በምዕራብ የሚኖሩ...በምስራቅ የሚኖሩ በዚህ ነገር ይደነግጣሉ
"በምዕራብ" እና "በምስራቅ" የሚሉት ሀረጎች በየትኛውም ስፍራ ለሚኖሩ ሰዎች ጽንፍን የሚያመለክቱ ናቸው። ይህ ስለ ክፉ ሰዎች በምድር ላይ የሚኖር ሁሉ እንደሚሰማ በማጋነን የተነገረ ነው። "በመላው ዓለም የሚኖሩ በክፉ ሰው ላይ የደረሰውን ሲሰሙ ይደነግጣሉ ደግሞም በፍርሃት ይሞላሉ" ወይም "በምስራቅ እና በምዕራብ የሚኖሩ ብዙ ሰዎች በክፉ ሰው ላይ የደረሰውን ሲሰሙ ይደነግጣሉ ደግሞም በፍርሃት ይሞላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጽንፍ እና ኩሸት እንዲሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
አንድ ቀን
"በሆነ ቀን"
Job 18:21
አጠቃላይ መረጃ፡
በልዳዶስ ክፉውን ሰው መግለጹን ይቀጥላል
የኃጢአተኛ/ጻድቅ ያልሆኑ ሰዎች ቤቶች፣ እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች ስፍራ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የሚያመለክቱትም ተመሳሳይ ሰዎችን ነው። እዚህ ስፍራ እነዚህ ሰዎች የተጠቀሱት በሚኖሩበት ስፍራ ነው። "ኃጢአተኛ/ጻድቅ ያልሆኑ ሰዎች፣ እግዚአብሔርን የማያውቁ እነርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

Chapter 19
Job 19:1
አያያዥ ሀሳብ፡
ኢዮብ ከሶስቱወዳጆቹ ጋር ይነጋገራል።
አጠቃላይ መረጃ፡
ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ
እስከመቼ ታስጨንቁኛላችሁ፤ እስከ መቼስ በቃላት ታደቁኛላችሁ?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ወዳጆቹ እንዴት እያዩት እንደሆነ ለማማረር ነው። "እንድሰቃይ ማድረጋችሁን እና በቃላት እኔን ማድቀቃችሁን አቁሙ/ ይብቃችሁ" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በቃላት የምታደቁኝ
ኢዮብ ይህንን ምስል የሚጠቀመው ቃላቶቻቸው በጣም እንዲያዝን እና ተስፋ እንዲቆርጥ እንዳደረጉት ለመናገር ነው። "በቃላቶቻችሁ ከፍተኛ ስቃይ አድርሳችሁብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 19:3
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
በእነዚህ አስር ጊዜያት ዘለፋችሁኛል
"በእነዚህ አስር ጊዜያት" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ወዳጆቹ ኢዮብን ሙሉ ለሙሉ/እጅግ እንደገሰጹት ነው። "እጅግ ዘለፋችሁኝ" ወይም "ብዙ ጊዜ ዘለፋችሁኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በጭካኔ ስትመለከቱኝ አላፈራችሁም
ኢዮብ ለዚህ ይገስጻቸዋል። ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እጅግ በጭካኔ ስታዩኝ/ስትቀርቡኝ ልታፍሩ በተገባችሁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
በጭካኔ ስታዩኝ/ስትቀርቡኝ
"ንቃችሁኛል" ወይም "በአደባባይ አዋርዳችሁኛል"
ተሳስታችኋል
"በድንገት መበደል" ወይም "ተሳስቶ ኃጢአት መስራት"
የእኔ ጥፋት የኔው ጉዳይ ሆኖ ይቆያል
ኢዮብ እርሱ ጥፋቱን እስከ ሰራ ድረስ ወዳጆቹ እነርሱ ሃላፊነት በማይወስዱበት ጥፋት ሳያቋርጡ እርሱን መውቀስ እንደሌለባቸው ይነግራቸዋል። "የእኔ ጥፋት የራሴ ተጠያቂነት ነው፣ ስለዚህ እኔን መገሰጻችሁን መቀጠል የለባችሁም" ወይም "የእኔ ጥፋት እናንተን አይጎዳም፣ ስለዚህ እኔን መገሰጻችሁን መቀጠል የለባችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የእኔ ጥፋት
"የእኔ ኃጢአት" ወይም "የእኔ ስህተት"
Job 19:5
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
በእርግጥ ራሳችሁን በእኔ ላይ ከፍ ከፍ ብታደርጉ
"ከእኔ ይልቅ እንደተሻላችሁ አድርጋችሁ ስለ ራሳችሁ ብታስቡ" ወይም "ከእኔ እንደተሻላችሁ አስካስመሰላችሁ ድረስ"
መዋረዴን አይታችሁ በእኔ ላይ ከፍ ብትሉ
ወዳጆቹ ይህንን እንዴት እንሚያደርጉ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "መዋረዴ በእኔ ላይ ማስረጃ እንደሆነ ብትናገሩ" ወይም "መዋረዴን እኔ በደለኛ ለማድረግ ማስረጃ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አድርጋችሁ ብትጠቀሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መዋረዴን እኔ በደለኛ ለማድረግ ማስረጃ አድርጋችሁ ብትጠቀሙ
"ውርደት" የሚለው ረቂቅ ስም "ተዋረደ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "የሆነውን ነገር በመናገር እኔን በማዋረድ ጥፋተኛ መሆኔን ለማረጋገጥ ተጠቀሙበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በመረቡ/ወጥመዱ ያዘኝ
ኢዮብ እግዚአብሔር እርሱን በመጥመዱ የሚይዝ አዳኝ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ይህ ዘይቤ የሚወክለው እግዚአብሔር ኢዮብን ተቆጣጥሮ የሚይዝ መሆኑን እና የኢዮብን የተስፋ ቢስነት ስሜት ነው። "አጠመደኸኝ" ወይም "እኔን ተቆጣጥረህ ያዝከኝ/አላላውስ አልከኝ" ወይም "እኔ ተስፋ ቢስ እሆን ዘንድ፣ በእኔ ላይ የሚሆነውን ሁሉ ተቆጣጠርክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 19:7
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
እነሆ፣ እኔ እነባለሁ
"እኔ እጮሀለሁ፣ ትኩረት ስጡኝ/ልብ በሉ፣ ምክንያቱም ልናገረው ያልኩት ነገር እውነት ነው ደግሞም ጠቃሚ ነው።"
ተበደልሁ!
ይህ የእርዳታ ጩኸት ነው። በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ተበደልኩ! ድረሱልኝ!" ወይም "እርዱኝ! ጥቃት እየደረሰብኝ ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእርዳታ ተጣራሁ
"ለእርዳታ ጮኹኩ" ወይም "እሪ አልኩ"
ነገር ግን ፍትህ የለም
"ፍትህ" የሚለው ረቂቅ ስም ትርጉሙን ግለጽ በሚያደርግ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "በእኔ ላይ ስህተት ከሚፈጽሙ ሰዎች ማንም ሊከላከልልኝ አልቻለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
እርሱ መንገዴን አጥሮታል…መንገዴን አጨልሞታል
ኢዮብ እነዚህን ምስሎች የሚጠቀመው እግዚአብሔር እንዴት ረዳት የለሽ እና ተስፋ ቢስ እንዳደረገው ለመግለጽ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ማለፍ እንዳልችል መንገዴን ቀጥሮታል
"እግዚአብሔር በምሄድበት መንገድ ላይ ግንብ አጥሮበታል" ወይም "መሄድ እንዳልችል መንገዴን ዘግቶታል"
ዘውዱን ከራሴ ላይ… እርሱ አንስቶታል
ኢዮብ እነዚህን ምስሎች የሚጠቀመው እግዚአብሔር ከእርሱ ላይ መልካሙን ማዕረጉን፣ ሀብቱን፣ ክብሩን እንደወሰደበት ለመናገር ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ክብሬን ከእኔ ከፏል
ኢዮብ ስለ ክብሩ የሚናገረው እግዚአብሔር ከእርሱ እንደ ገፈፈው ልብሱ አድርጎ ነው። "እርሱ ከእኔ ክብሬን ወሰደው/ገፈፈው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከራሴ ላይ ዘውዴን ወሰደው
ዘውድ የሚወክለው የኢዮብን ማዕረግ ወይም ክብር ነው። "እርሱ የእኔን ማዕረግ እና ክብር ገፈፈው" ወይም "ከራሴ ላይ ዘውዴን እንደወሰደብኝ ያህል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 19:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
በሁሉም አቅጣጫ እርሱ ሰብሮኛል
ኢዮብ እግዚአብሔር እርሱን እያጠፋው ያለው እግዚአብሔር እደመሰሰ የሚገኘውን እርሱ እየገነባ እንደሚገኝ ባለ ሁኔታ ነው። "እርሱ በሁሉም መንገድ አጥፍቶኛል" ወይም "እርሱ በሁሉም መንገድ አጥቅቶኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ሄዳለሁ/አብቅቶልኛል
"መሄድ" የሚለው ዘይቤ የሚወክለው ሙሉ ለሙሌ መጥፋትን ነው። "እኔ ሙሉ ለሙሉ ጠፍቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ተስፋዬን እንደ ዛፍ ነቅሎታል
ኢዮብ የሚናገረው እግዚአብሔር እርሱን ከስሩ እንደተነቀለ ዛፍ ተስፋ እንዳይኖረው አድርጎ እንደነቀለው ነው። "እርሱ ሙሉ ለሙሉ ተስፋዬን አጥፍቶታል" ወይም "እርሱ ካደረገው ነገር የተነሳ፣ አንዳች መልካም ተስፋ መጠበቅ አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤያዊ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ዛፍ
ይህ ተነጻጻሪ ዘይቤ የተተወ/የተዘለለ ጭምርም ነው። የተዘለሉትን ቃላትም መጨመር ይኖርባችኋል። "አንድ ሰው ዛፍን ከስሩ በሚነቅልበት መንገድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና የተተወ/የተዘለለ ሚሉትን ይመልከቱ)
ደግሞም እርሱ ቁጣውን በእኔ ላይ አንድዷል
ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር ቁጣ የሚናገረው እሳት እንደሆነ አድርጎ ነው። "እግዚአብሔር በእኔ ላይ የቁጣ እሳቱ እንዲነድ ፈቅዷል" ወይም "እግዚአብሔር በእኔ እጅግ ተቆጥቷልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ከጠላቶቹ እንደ አንዱ አይቶኛል
"እርሱ እኔን እንደ ጠላቱ አስቦኛል"
የእርሱ ጦር በአንድነት መጣብኝ
ኢዮብ የሚናገረው እግዚአብሔር እርሱን ያጠቃው እርሱ ከተማ እንደሆነ እና እግዚአብሔር እርሱን እንዲያጠቁት ሰራዊት እንደላከ አድርጎ ነው። "እኔን እንዲያጠቁኝ እግዚአብሔር ሰራዊቱን በእኔ ላከ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእኔ ላይ ከበባ ለማድረግ ድንጋይ ቆልለው ምሽግ ሰሩ
ኢዮብ የሚናገረው እግዚአብሔር እርሱን ያጠቃው እርሱ ከተማ እንደሆነ እና የእግዚአብሔር ሰራዊት በከተማይቱ ቅጥር ዙሪያ ቁልል ሰርተው ቅጥሩን ለመውጣት እና ከተማይቱን እንደሚያጠቁ አድርጎ ነው። "ወታደሮቹ በእኔ ግንብ ላይ ለመውጣት ቁልል ከመሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በድንኳኔ ዙሪያ ሰፈሩ
ኢዮብ እግዚአብሔር እርሱን እንዴት እንዳጠቃው የሚናገረው ኢዮብ በድንኳኑ ውስጥ እንደሆነ እና የእግዚአብሔር ሰራዊት በእርሱ ዙሪያ ሰፍሮ ሊያጠቃው እንደሚዘጋጅ አድርጎ ነው። "በድንኳኔ ዙሪያ ሰፍረው ሊያጠቁኝ እየተዘጋጁ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 19:13
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
ወንድሞቼን ከእኔ አራቀ
"ከአንድ ሰው መራቅ" የሚለው የሚወክለው ወደዚያ ሰው ለመቅረብ ወይም ያንን ሰው ለመርዳት ፈቃደኛ አለመሆንን ነው። "እግዚአብሔር ወንድሞቼ ከእኔ እንዲርቁ አደረገ" ወይም "እግዚአብሔር ወንድሞቼ እኔን መርዳት እንዳይፈልጉ/እንዲጠሉ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የቅርቤ የሆኑ በሙሉ ከእኔ ተለዩ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የቅርቤ የሆኑ በሙሉ ራሳቸውን ከእኔ ለዩ" ወይም "ወዳጆቼ እንደ እንግዳ ተመለከቱኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ዘመዶቼ ተዉኝ
"ቤተዘመዶቼ ካለ አንዳች እርዳታ ተዉኝ"
የቅርብ ወዳጆቼ
"የእኔ ናቸው የምላቸው ጓደኞቼ"
እኔን ረሱኝ
"እኔን ተዉኝ" ወይም "ቸል አሉኝ።" ይህ ማለት እርስ በእርሳቸው ቀድሞ በነበራቸው ግንኙነት መሰረት ሊመለከቱት አልፈቀዱም። ይህ እርሱን እንተዉት ያመለክታል።
Job 19:15
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
ተመለወከቱኝ/ትኩረት ስጡኝ
"ስፍራ ስጡኝ/ቦታ ስጡኝ"
በእነርሱ አይታ እኔ ባእድ/እንግዳ ነኝ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ኢዮብ ሰዎች አሁን እንዴት እንደ ውጭ ሰው እንደሚያዩት/እንደሚቆጥሩት ይገልጻል። እዚህ ስፍራ እይታ የሚለው ሚወክለው ፍርድን ወይም ሚዛንን ነው። "እኔን እንደ ባዕድ ይቆጥሩኛል/ያስቡኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን እርሱ ለእኔ አንዳች ምላሽ አልሰጠኝም
"ነገር ግን እርሱ ለእኔ አልመለሰልኝም" ወይም "ነገር ግን እርሱ ወደ እኔ አልመጣም" መልሱ ለኢዮብ ጥሪ ምላሽ ነው።
ምንም እንኳን በአፌ ብለምነውም
"በአፌ" የሚለው ሀረግ የኢዮብን ንግግር የሚያለክት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ምንም እንኳን ከእርሱ ጋር ብናገር እና ብለምነውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱን መለመን
"ለእርሱ ልመና ማቅረብ"
Job 19:17
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
ትንፋሼ ለሚስቴ የሚያስጸይፍ ሆነባት
እዚህ ስፍራ "ትንፋሽ" የሚወክለው የእስትንፈሳሱን ሽታ ነው። አንድ ነገር ለአንድ ሰው የሚያስጸይፍ/ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ተቀባዩ ጠልቶታል ማለት ነው። "ሚስቴ የትንፋሼን ሽታ ጠላችው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እኔን ናቀችኝ
"ጠላችኝ" ወይም "አልወደደችኝም"
በጠላትነት ተነሱብኝ
"መሳቂያ አደረጉኝ" ወይም "በእኔ ላይ ተሳለቁ"
የቅርብ ወዳጆቼ ሁሉ
"የቅርቤ/የራሴ የምላቸው ጓደኞቼ" ወይም "ምስጢሬን ያካፈልኳቸው ጓደኞቼ ሁሉ።" ይህ የቅርብ ጓደኞቹን ያመለክታል።
ጠሉኝ
"አስፀያፊ አድርገው ቆጠሩኝ"
በእኔ ላይ ተነሱ
"ካዱኝ"
Job 19:20
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
አጥንቶቼ ከቆዳዬ እና ከስጋዬ ጋር ተጣበቁ
"ቆዳ እና አጥንቴ ብቻ ቀረ" ወይም "ቆዳዬ ከአጥንቴ ጋር ተጣበቀ።" ኢዮብ ስለ አጥንቶቹ፣ ቆዳው እና ስጋው የሚናገረው ምን እንደሚያምል ለመግለጽ ነው። እጅግ ከስቶ ነበር፤ ሰዎች የአጥንቱን አቀማመጥ /አጥንቱ መውጣቱን/ በቀላሉ ይመለከቱ ነበር። አንዳንድ ቋንቋዎች ለዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር አላቸው።
በአጥንቴ ቆዳ ብቻ ቀረሁ/ድዴ ብቻ ቀረ
ይህ ፈሊጣው አነጋገር የቀረው ሞቴ ብቻ ነው ማለት ነው። "በሞት አፋፍ ላይ ነኝ" ወይም "በህይወትና በሞት መሃል ላይ እገኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ለእኔ ሀዘኔታ ይኑራችሁ
"ለእኔ ርህራሄ ይኑራችሁ"
የእግዚአብሔር እጅ ነክታኛለችና
እዚህ ስፍራ "ነክታኛለች" የሚለው "መትቶኛል" ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እጅ" የሚለው ደግሞ የሚወክለው የእግዚአብሔርን ሀይል ነው። ኢዮብ መሰቃየቱ የተገለጸው ያህዌ በአካል በእጁ እንደመታው ተደርጎ ነው። "ምክንያቱም እግዚአብሔር መትቶኛል። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር አሳዶኛል ... ለምን ታሳድዱኛላችሁ?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ወዳጆቹ እርሱን እንዴት እንደሚይዙት/ እንደሚያዩት በምሬት ለመግለጽ ነው። " እናንተ አታሳዱኝ ... እግዚአብሔር አሳዶኛል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እስከ መቼ በቁስሌ ደስ ትሰኛላችሁ?
ኢዮብ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠቀመው ወዳጆቹ እርሱን ሰለሚያስተናግዱበት መንገድ ምሬቱን ለመግለጽ ነው። "ስጋዬን እስከሚበቃ ድረስ ፈጅታችኋል/ በልታችኋል!" ወይም "ስጋዬን መብላታችሁን አቁሙ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በስጋዬ ስቃይ መቼ እርካታ ታገኛላችሁ?
ኢዮብ የጓደኞቹን ጭካኔ የተሞላበት ንግግር የገለጸው የዱር አውሬ ሌላ እንስሳን እንደሚበላ ባለ መልክ ነው። "በሀይል ስሜን ማጥፋታችሁን አቁሙ።" ወይም "በቃላቶቻችሁ እኔን ማጥቃታችሁን አቁሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 19:23
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
አወይ፣ ምነው ቃሎቼ በተጻፉ
ይህ አጋኖ የሚናገረው ኢዮብ ምን እንደሚፈልግ ነው። በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው ቃሎቼን ቢጽፍ በወደድኩ" (ቃለ አጋኖ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
የእኔ ቃሎች/ቃሎቼ
"እኔ የምናገረው"
አወየው፣ ምነው በመጽሐፍ በተጻፉ
ይህ አጋኖ የሚናገረው ኢዮብ ምን እንደሚፈልግ ነው። በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው በመጽሐፍ ቢጽፋቸው በወደድኩ" (ቃለ አጋኖ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
አወይ፣ በብረት ብዕር እና እርሳስ ለዘለዓለም በአለት ላይ በተቀረጹ
ይህ አጋኖ የሚናገረው ኢዮብ ምን እንደሚፈልግ ነው። በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንድ ሰው የብረት ብዕር እና እርሳስ ተጠቅሞ ለዘለዓለም በአለት ላይ ቢቀርጻቸው በወደድኩ" (ቃለ አጋኖ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
የብረት ብዕር
"ጠብረት መሮ።" ይህ ለመጻፊያ ያገለግል ነበር። ሰዎች ቃላቶችን በአለት ላይ እንዲቀርጹ ከብረት የተሰራ ነበር።
እርሳስ
እርሳስ ለስላሳ ብረት ነው። ሰዎች አለት ሲጠርቡ እንዴት እርሳን ይጠቀሙ እንደነበር አናውቅም። ምናልባት ጽሁፉ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ የጽሁፉን ፊደላት በእርሳስ ይሞሉት ይሆናል
Job 19:25
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
እኔን ነጻ የሚያወጣኝ
"እኔን የሚከላከል።" እዚህ ስፍራ "ነጻ አውጪ" የሚለው የሚያመለክተው የኢዮብን ንጹህነት በማረጋገጥ ነጻ የሚያወጣውን፣ ክብሩን የሚመልስለትን፣ እና ፍትህ የሚሰጠው አካል ማለት ማለት ነው።
በመጨረሻ እርሱ በምድር ላይ ይቆማል
ይህ የሚያመለክተው በፍርድ ቤት ለመናገር መቆምን ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)ነጻ አውጪው በፍርድ ቤት ቆሞ ለመናገር የመጨረሻው ሰው ይሆናል። "እርሱ እኔ ጥፋተኛ መሆን አለመሆኔን ይፈርዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ነጻ አውጪው ኢዮብን ለመከላከል በዚህ በመጨረሻው ፍርድ ቤት ይቆማል። "በመጨረሻ እርሱ በፍርድ ቤት ቆሞ ለእኔ ይከላከላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ስጋዬ... ከጠፋ በኋላ
ይህ ሊያመለክት የሚችለው ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የእርሱ አካል በበሽታ መጥፋትን/መጎዳቱን ወይም 2) ከሞተ በኋላ አካሉ መበስበሱን
በስጋዬ እግዚአብሔርን አያለሁ
ስጋው የሚወክለው አካሉን ነው፣ ደግሞም "በስጋዬ" የሚለው በህይወት መኖርን ይወክላል። "በስጋዬ ውስጥ እየኖርኩ ሳለ፣ እግዚአብሔርን እየዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የገዛ ዐይኖቼ/የራሴ ዐይኖች - እኔ፣ ራሴ ሌላ ሰው ሳይሆን
"የገዛ ዐይኖቼ/የራሴ" የሚለው ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ

መላውን ነገር መግለጽ/ የሚያመለክተው ኢዮብን ነው። "የገዛ ዐይኖቼ" እና "ሌላ ማንም ሳይሆን" የሚሉት ሀረጎች የሚያጎሉት በእርግጥ ኢዮብ ራሱ እግዚአብሔርን እንደሚመለከት ነው። እግዚአብሔርን የሚመለከተው እና ስለ እር የሚነግረው ሌላ ማንም አይደለም። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ በመናፈቅ ዝሏላ

ሰዎች ስሜታቸው ባለበት በዚያ ልባቸው እንዳለ ያስባሉ። ስለዚህ የልብ መውደቅ የሚወክለው/የሚገልጸው እርሱ የተለያዩ ስሜቶች እንዳሉት ነው። "ስለዚህ ጉዳይ በጣም ስሜታዊ ነኝ" ወይም "ስለዚህ ሁኔታ ሳስብ ስሜቴ ሁለንተናዬን ይወርሰዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ በመናፈቅ ዝሏል

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ በተስፋ፣ በምስጋና ተሞልቷል ደግሞም ተድቷል ወይም 2) ኢዮብ አዳኙን በመጠበቅ ደክሟል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 19:28

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢዮብ ከሶስቱ ወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

እንዴት እናሳድደዋለን

ይህ ቃለ አጋኖ ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እነርሱ በእርግጥ ኢዮብን ያሳድዱታል ወይም 2) በከፋ ሁኔታ እነርሱ ያሳድዱታል። (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

የችግሩ ስር በእርሱ ላይ አለ

"ስር" የሚወክለው መነሻን/መገኛን ነው። "እርሱ የችግሮቹ ሁሉ መገኛ/ምክንያት ነው" ወይም "ይህ ሁሉ ችግር ያጋጠመው ከሰራው ስራ/ካደረገው ነገር የተነሳ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንግዲህ ሰይፍን ፍሩ

ሰይፍ ሊወክለው የሚችላቸው ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ይፈርዳል "እንግዲህ እግዚአብሔር ይፈርድብናል ብላችሁ ፍሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) እግዚአብሔር እነርሱን ይገድላቸዋል። "እንግዲህ እግዚአብሔር ይገድለናል ብላችሁ ፍሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ምክንያቱም ቁጣ በሰይፍ መቅጣትን ያመጣል

"ቁጣ" እና "ቅጣት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ተቆጣ" እና "ተቀጣ" በሚሉ ግሶች ሊገለጹ ይችላሉ። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የእግዚአብሔር ቁጣ ቅጣት ያስከትላል። "ምክንያቱም እግዚአብሔር በእናንተ ሊቆጣ እና ሊቀጣችሁ ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) የኢዮብ ወዳጆች ቁጣ ቅጣትን ያስከትላል።" ምክንያቱም እናንተ በእኔ ላይ እጅግ ብትቆጡ፣ እግዚአብሔር እናንተን ይቀጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ያመጣል

"ምክንያት ይሆናል" ወይም "ያስከትላል"

ፍርድ አለ

"ፍርድ" የሚለው ረቂቅ ስም "ፈረደ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር በሰዎች ላይ ይፈርዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 20

Job 20:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ሶፋር ለኢዮብ እንዲህ ሲልመለሰ።

ናዕማታዊው ሶፋር

ይህንን ወንድ ስም በኢዮብ 2፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። ይህ ሶፋር የሚናገርበት ሁለተኛ ጊዜ እንደመሆኑ፣ አንዳንድ ቅጂዎች/ትርጉሞች እዚህ ስፍራ "ናዕማታዊው" የሚለውን ይተዉታል።

ሃሳቤ በፍጥነት እንድመልስ ያደርገኛል

የሶፋር ሃሳብ የሚለው አስተሳሰብ አንዳች ነገር ለማድረግ ያለውን ጠንካራ ፍላጎት ይወክላል። "በፍጥነት ልመልስልህ እጅግ እፈልጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጤ ባለው ጭንቀት ምክንያት

"ጭንቀት" የሚለው ረቂቅ ስም "ተጨነቀ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። ለመጨነቅ ምክንያት የሆነው ነገር በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ምክንያቱም እኔ ስለአንተ በጣም ተጨንቄያለሁ" ወይም "ምክንያቱም አንተ በተናገርከው ነገር እኔ በጣም ከመጨነቄ የተነሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔን የሚያዋርድ ግሳጼ ሰምቻለሁ

"ግሳጼ" የሚለው ረቂቅ ስም "ገሰጸ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ስትገስጹኝ እና እኔን በማቃለል ስትናገሩ ሰማኋችሁ" ወይም "በስድብ አቃለላችሁኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

መረዳት/ግንዛብ የሚሰጠኝ መንፈስ መልስ ይሰጠኛል

እዚህ ስፍራ "መንፈስ" የሚለው ምናልባት ሃሳብን ወይም አስተሳሰብን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። "መረዳት የሚሰጠኝ አስተሳሰብ መልስ ይሰጠኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

መረዳት/ግንዛብ የሚሰጠኝ መንፈስ መልስ ይሰጠኛል

እዚህ ስፍራ "መንፈስ" ወይም አስተሳሰብ የሚለው ቃል የተነገረው ለሶፋር መልስ ሊሰጥ እንደሚችል ሰው ተደርጎ ነው። ከመረዳቴ የሚመነጭ ሀሳብ አለኝ፤ እናም አሁን ማወቅ የምፈልገው ምን እንደሆነ አውቃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መረዳት/ግንዛብ የሚሰጠኝ መንፈስ መልስ ይሰጠኛል

የመረዳቱ ይዘት በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ከመረዳቴ የሚመነጨው አስተሳሰብ ለአንተ እንዴት መልስ እንደምሰጥ ያሳውቀኛል" ወይም "ከመረዳቴ የሚመነጭ አስተሳሰብ አለኝ፣ እናም አሁን ለአንተ እንዴት ምላሽ እንደምሰጥ አውቃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መረዳት/ግንዛብ የሚሰጠኝ መንፈስ መልስ ይሰጠኛል

"መንፈስ" እና "መረዳት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "አሰበ" እና "ተረዳ" በሚሉ ግሶች ሊገለጹ ይችላሉ። "ነገሮችን ስለምረዳ፣ ሃሳብ አለኝ እናም አሁን እንዴት ለአንተ እንደምመልስ አውቃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Job 20:4

አጠቃላይ መረጃ፡

ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

ለቅጽበት…ይህንን እውነት ከጥንት ጀምሮ ታውቅ ነበርን?

ሶፋር ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ አሁን የሚናገረውን ነገር ኢዮብ በጥልቀት እንዲያስብበት ለማድረግ ነው። ይህ በገለጻ ሊተረጎም ይችላል። "ለአፍታ…አንተ በእርግጥ ከጥንት ጀምሮ ያለውን ታውቃለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉ ሰው ድል ለአጭር ጊዜ ነው

"ድል" የሚለው ረቂቅ ስም "ድል አደረገ" ወይም "ግብዣ አደረገ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ክፉ ሰው የሚያሸንፈው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው" ወይም "ክፉ ሰው ግብዣ የሚያደርገው ለአጭር ጊዜ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አምላክ የለሽ የሆነ ሰው ደስታ የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው

"ደስታ" የሚለው ረቂቅ ስም "ሀሴት" ወይም "ደስታ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "አፍታ/ቅጽበት" የሚለው ቃል ጊዜው በጣም አጭር መሆኑን ለማጉላት የዋለ ግነት ነው። "አምላክ የለሽ ሰው ደስታው ለቅጽበት ነው" ወይም "አምላክ የለሽ ሰው ደስ የሚሰኘው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ኩሸት እንደዚሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 20:6

አጠቃላይ መረጃ፡

ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

እስከ ሰማይ ከፍ ቢል እንኳን

"የክፉ ሰው ከፍታ እስከ ሰማይ ቢደርስ እንኳን" "ከፍታ" የሚለው ረቂቅ ስም "ትልቅ/ረጅም" በሚል ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "ምንም እንኳን እርሱ እስከ ሰማይ ቢረዝም/ቢተልቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ሰማይ ከፍ ቢል እንኳን

 

የክፉ ሰው ከፍታ የሚለው የሚወክለው ክብሩን ወይም ኩራቱን ነው። እንደዚሁም እዚህ ስፍራ እስከ ሰማይ መድረስ" የሚወክለው በጣም ትልቅ መሆንን ነው። "ምንም እንኳን ክብሩ ታላቅ ቢሆንም" ወይም "ምንም እንኳን ኩራቱ ታላቅ ቢሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱ እስከ ደመና ይደርሳል

"ደግሞም ምንም እንኳን ራሱ እስከ ደመና ከፍ ቢልም" ይህም የሚወክለው ክብሩን ወይም ትልቅ በመሆኑ መኩራቱን ነው። ይህ ማለት ከቀደመው ሀረግ ጋር ተመሳሳይ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደ ራሱ እዳሪ ለዘለዓለም ይጠፋል

እዳሪ ከመሬት ጋር ተደባልቆ ይጠፋል። ክፉ ሰው ከእዳሪ ጋር መነጻጸሩ እርባና ቢስ/ ጥቅም የለሽ መሆኑን የሚጠቁም ነው። "በአፈር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ እንደሚጠፋ እንደ ራሱ እዳሪ በዘላቂነት ይጠፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ራሱ እዳሪ ለዘለዓለም ይጠፋል

ሰዎች እዳሪ በሚለው ቃል ደስ የማይሰኙ/የሚያሳፍር ከሆነ ሙሉ ለሙሉ ከሚጠፋ ሌላ ነገር ጋር ማመሳሰል ይቻላል። "ንፋስ እንደ በተነው አቧራ ለዘለዓለም ይጠፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 20:8

አጠቃላይ መረጃ፡

ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

እርሱ

"ክፉ ሰው"

እንደ ህልም ይጠፋል... እንደ ምሽት ህልም ተሰዶ ይጠፋል

እዚህ ስፍራ "መጥፋት" እና "መባረር/መሰደድ" የሚሉት ቃላት የሚወክሉት መጥፋትነ ነው። ህልሞች እና ራዕዮች በረስዋቸው ጊዜ እንደሚጠፉ ሁሉ፣ እነዚህም ክፉዎች እንደሚረሱ ያመለክታል። "እንደ ህልም ይረሳሉ... በምሽት እንደ ታየ ህልም ይረሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አይገኝም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ሊያገኘው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የተመለከቱት ዐይኖች

ዐይን ሰውየውን ይወክላል። "እርሱን የተመለከተ ማንም ሰው" ወይም "እርሱን የተመለከቱ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ስፍራው

"ስፍራው/የእርሱ ስፍራ" የሚለው ሀረግ የሚወክለው በእርሱ ስፍራ የሚኖሩትን ነው። "በእርሱ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች" ወይም "ቤተሰቦቹ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 20:10

አጠቃላይ መረጃ፡

ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

ልጆቹ

"የክፉ ሰው ልጆች"

እጆቹ ብልጽግናውን መልሰው ያመጡለታል

እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚወክለው የክፉ ሰው ልጆችን ነው። እርሱ በሚሞትበት ጊዜ፣ ልጆቹ እርሱ ከሌሎች ሰዎች የወሰደውን ለመመለስ ይገደዳሉ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አጥንቶቹ በጥንካሬ የተሞሉ ናቸው

"አጥንቶቹ" የሚለው የሚወክለው አካሉን/ሰውነቱን ነው። "ጠቃሚ በሆነ ጥንካሬ ሙሉ መሆን" የሚለው የሚወክለው እንደ ወጣት ሰው ጠንካራ መሆንን ነው። "ሰውነቱ እንደ ወጣት ሰውነት ጠንካራ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ነገር ግን ይህ ከእርሱ ጋር አፈር ውስጥ ይገባል

"ይህ" የሚለው የሚያመለክተው የእርሱን ጠቃሚ ጥንካሬ ነው። "አፈር ውስጥ… ይጋደማል" የሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚወክለው ሞትን ነው። የሞት ጥንካሬ የሚለው መጥፋት ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ነገር ግን ጠቃሚ ጥንካሬው ከእርሱ ጋር አብሮ ይሞታል" ወይም "ነገር ግን የእርሱ ጠቃሚ ጥንካሬ/የሚመካበት እርሱ ሲሞት አብሮት ያከትማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 20:12

አጠቃላይ መረጃ፡

ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

ምንም እንኳን ክፋት በአፉ ላይ ጣፋጭ ቢሆንለትም

እዚህ ስፍራ "ክፋት ጣፋጭ ቢሆንለትም" የሚለው የሚወክለው ክፉ ነገር በማድረግ ደስ የሚሰኝ ሰውን ነው። " ምንም እንኳን ክፉ ነገሮችን ማድረግ ጣፋጭ ምግብን እንደ መቅመስ ደስ የሚያሰኘው ቢሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳን ቢደብቅም ... እንዲሄድ አይፈቅድም

አንድ ሰው ጣፋጭ ምግብን በመቅመስ ደስ መሰኘቱን መቀጠል እንደሚፈልግ ክፉ ሰው ክፉ በማድረግ ደስታ ለማግኘት መፈለጉን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንጀቱ ውስጥ ያለ ምግብ መራራ ይሆንበታል

ምግብ በአንጀት ውስጥ ወደ መራራነት ሲቀየር፣ ስቃይን ያስከትላል ደግሞም መራራ ጣዕም ያመጣል። ይህ ክፉ በማድረጉ ምክንያት መጥፎ ለሚገጥመው የዋለ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "እነዚያ ክፉ ነገሮች በሆድ ውስጥ ወደ መራራነት እንደ ተለወጠ ምግብ ይሆናሉ" ወይም "የእነዚያ ክፉ ነገሮች ውጤታቸው በሆድ ውስጥ ጎምዛዛ እንደሆነ ምግብ ስቃይ የሚፈጥሩ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጡ እንደ እባብ መርዝ ይሆናል

ምግብ በሆድ ውስጥ ወደ መራራነት ሲቀየር፣ ስቃይን ይፈጥራል ደግሞም መራራ ጣዕምን ያመጣል። ይህ ክፉ ነገሮችን በማድረግ መከራ ለሚቀበል ሰው የዋለ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "እነዚያን ክፉ ነገሮች ማድረግ ውጤቱ በውስጡ የእባብ መርዝ የገባ ያህል መሰቃየት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መርዘኛ

"መርዛማ እባቦች

Job 20:15

አጠቃላይ መረጃ፡

ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።

ባለጸግነትን ይውጣል... መልሶ ከሆዱ ያስወግዳቸዋል

ሶፋር ሀብት ማግኘትን እና ማጣትን የሚገልጸው አንድ ሰው በልቶ መልሶ እንደሚያስመስለው ምግብ አድርጎ ነው። "ክፉ ሰው ባለጸጋ ይሆናል፣ ነገር ግን የበላውን እንደሚያስመልስ ሰው ሀብቱን ያጣዋል። እግዚአብሔር ሃብቱን በሙሉ እንዲያጣ ያደርገዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሃብትን ይውጣል

"ሃብትን ይውጣል" ለሚለው ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሀብት ያሰበስባል፣ ደግሞም በስስት ያከማቻል። "ክፉ ሰው ብዙ ሃብት ያገኛል፣ ደግሞም ሁሉንም ለራሱ ያደርገዋል" ወይም 2) ከክፋት መንገዶች ሀብት ማከማቸት። "ክፉ ሰው ብዙ ሀብት ይሰርቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከሆዱ ያስተፋዋል

"ከሆዱ ያስተፋዋል" የሚለው ሰውየው ያገኘውን በማስመለስ ያወጣዋል ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ ክፉ ሰው ሃብቱን ለሚያጣበት ምክንያት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ያስወግዳል

ያስወጣል

እዚህ ስፍራ "የእባብ መርዝ ይጠባል"

የሚለው የሚወክለው ክፉ ነገር ማድረግን ነው። ሁለቱም በጣም አደገኛ ናቸው። "ክፉ ነገሮችን ማድረግ የእባብ መርዝን እንደ መጥባት ነው" ወይም "ክፉ ነገሮችን ያደርጋል ደግሞም የእባብ መርዝን እንደሚጠባ ሰው ህይወቱን አደጋ ላይ ይጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መርዛም እባብ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መርዘኛ እባብ
የእፍኝት ምላስ ይገድለዋል
እፍኝት መርዛም እባብ ነው። ምላሱ የሚወክለው መርዛም ንክሻውን ነው። "የእፍኝት መርዛማ ንክሻ እርሱን ይገድለዋል" ወይም "እፍኝት ይነክሰዋል ከዚያም ይሞታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የእፍኝት ምላስ ይገድለዋል
እፍኝት የሚወክለው የሰውየውን ክፉነት ነው። "ክፋቱ እንደ እፍኝት ንክሻ ይገድለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 20:17
አጠቃላይ መረጃ፡
ሶፋር ለኢዮብ መልስ መስጠቱን ቀጠለ።
ጅረቶች፣ የቅቤ እና ማር ጎርፍ
"ጅረቶች" እና "ጎርፍ" ብዛትን የሚወክሉ ዘይቤያዊ አነጋገሮች ናቸው። "ማር" እና "ቅቤ" እግዚአብሔር ለሰዎች የሚሰጠውን መልካም ነገሮች የሚወክሉ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "እግዚአብሔር ለህዝቡ የሚሰጠው መልካም ነገሮች ብዛት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
የስራው ፍሬ
በተለመደው አነጋገር "የስራው ፍሬ" በቀጥታ የሚያመለክተው የስራውን ውጤት ነው። በዚህ ሁኔታ ግን ክፉ ሰው የሰረቃቸውን ነገሮች ያመለክታል። "ለማግኘት የሰራቸው ነገሮች" ወይም "የሰረቃቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ሊመገበው አይችልም
እዚህ ስፍራ የስራውን ፍሬ "ሊመገብ" የሚለው የሚወክለው በሰረቀው ነገር ደስ መሰኘቱን ይወክላል። "በእነርሱ ደስ ሊሰኝ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 20:20
ሳይበላ የሚያስተርፈው ምንም ነገር የለም
ይህ ከአሉታዎቹ አንዱ ብቻ ተቀይሮ ሊጻፍ ይችላል። "ሁሉንም ነገር ፈጅቷል፣ ያስቀረው እንድም የለም" ወይም "የቀረ ምንም ነገር የለም ምክንያቱም እርሱ ሁሉንም በልቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ አሉታ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ያልበላው የቀረ ምንም ነገር የለም
እዚህ ስፍራ "መብላት" የሚለው የሚወክለው ነገሮችን ለራሱ መውሰድን ነው። "ለራሱ ያልወሰደው፣ ምንም የቀረ ነገር የለም" ወይም "እርሱ ሁሉንም ለራሱ ወስዷል፣ እናም ምንም ነገር አልቀረም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ችግር ላይ ይወድቃል
"በድንገት ችግር ያጋጥመዋል"
በችግር ላይ ያለ እጅ ሁሉ በእርሱ ላይ ይነሳሉ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ሀይልን ነው፣ ደግሞም "እጅ… በእርሱ ላይ ይነሳል" የሚለው የሚወክለው እርሱን የሚያጠቁ ሰዎችን ነው። "ድህነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ድሀ" በሚለው ቅጽል ይገለጻል። "በድህነት ውስጥ ያለ ሁሉ እርሱን ያጠቃዋል" ወይም "ደሀ የሆነ ሁሉ እርሱን ያጠቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 20:23
አጠቃላይ መረጃ፡
ሶፋር ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ።
ሆዱን ለመሙላት
እዚህ ስፍራ "ሆዱን መሙላት" የሚለው ብዙ መብላት የሚል ትርጉም የሚሰጥ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የቁጣውን መአት ያወርድበታል
"የቁጣው መአት" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን ቁጣ እና ቅጣት ነው። ቁጣውን ያወርድበታል የሚለው በከፍተኛ ደረጃ ይቀጣዋል ማለት ነው። "እግዚአብሔር ይቆጣል ደግሞም ቁጣውን ያወርድበታል" ወይም "እግዚአብሔር ይቆጣል ደግሞም እጅግ ይቀጣዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ይህን ያዘንብበታል
"እግዚአብሔር ይህን በእርሱ ላይ እንዲዘንብ ያደርጋል።" እዚህ ስፍራ "ይህን በእርሱ ላይ ያዘንባል" የሚለው የሚገልጸው በሰውየው ላይ ብዙ ጥፋት እንደሚደርስ ነው። "እግዚአብሔር እጅግ ይቀጣዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከብረት መሳሪያ ያመልጣል
የብረት መሳሪያ የሚለው የሚወክለው መሳሪያውን የያዘውን ሰው ነው። "የብረት መሳሪያ ከያዘ ሰው ያመልጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የነሀስ ደጋን ይወጋዋል
ደጋኑ የሚወክለው በእርሱ ቀስት የሚወረውረውን ሰው ነው። "የነሀስ ደጋን የያዘ ሰው እርሱን ይወጋዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ጉበት
ይህ ትልቅ እና ጠቃሚ የሆነ የሰውነት ክፍል ነው። አንድ ሰው በቀስት ይህን የሰውነት ክፍል ቢወጋ፣ የተወጋው ሰው ይሞታል።
ፍርሃት ይወርድበታል
በድንገት በጣም ይፈራል። "በፍርሃት ተዋጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 20:26
ሀብቱ ለድቅድቅ ጨለማ ተዳርጓል
እዚህ ስፍራ "ድቅድቅ ጨለማ" የሚለው ለጥፋት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ሀብቱ ለጥፋት ተዳርጓል " ወይም "ሀብቱ ይጠፋል/ይደመሰሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ያልተራገበ እሳት ይበላዋል
እዚህ ስፍራ "መብላት/መፍጀት" የሚለው ዘይቤ ትርጉሙ መጥፋት/መደምሰስ ማለት ነው። "የልተራገበ እሳት ያጠፋዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ያልተራገበ እሳት ይበላዋል
"ያልተራገበ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ማንም ሰው እሳቱን እንደማይጀምር ነው። ይልቁንም፣ እግዚአብሔር እሳቱን ይፈጥራል። "በሰው ያልተጀመረ እሳት እርሱን ይበላዋል" ወይም "እግዚአብሔር እርሱን የሚበላ እሳት ያመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ይበላዋል/ይፈጀዋል
እዚህ ስፍራ "መብላት/መፍጀት" የሚለው ዘይቤያዊ ትርጉም መጥፋት/መደምሰስ ነው። "እሳቱ ይደመስሰዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሰማያቱ… ምድሪቱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በሰማያት እና በምድር የሚኖሩት ወይም 2) ሶፋር ሰማያትን እና ምድርን የሚገልጻቸው በፍርድ ቤት ቀርበው በክፉዎች ላይ ምስክር እንደሚሆኑ ሰዎች አድርጎ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 20:28
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ሶፋር ከኢዮብ ጋር የሚያደርገውን ንግግር ያጠቃልላል።
ጠፋ
ተደመሰሰ
ንብረቶቹ ተጠራርገው ይሄዳሉ
እዚህ ስፍራ "ተጠራርገው ይሄዳሉ" የሚለው የሚወክለው ከእርሱ ይወሰዳሉ የሚለውን ነው። "ንብረቶቹ፣ በጎርፍ ላይ እየተንሳፈፉ እንደሚወሰዱ ነገሮች ከእርሱ ይወሰዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ንብረቶቹ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"ያለው ሃብት"

የእግዚአብሔር የቁጣ ቀን

እዚህ ስፍራ "ቁጣ" የሚለው የሚወክለው ቅጣትን ነው። "ቁጣ" የሚለው ረቂቅ ስም "ቀጣ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ሰዎችን በሚቀጣበት ቀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ የክፉ ሰው እድል ፈንታው/ድርሻው ነው

እዚህ ስፍራ "ከእግዚአብሔር ዘንድ እድል ፈንታው/ድርሻው" የሚለው የሚወክለው እግዚአብሔር የወሰነው በሰውየው ላይ መድረሱ አይቀርም የሚል ነው። ይህ ተገለጸው እግዚአብሔር ለሰውየው እንደሚሰጠው ነገር ተደርጎ ነው። "እግዚአብሔር በክፉ ሰው ላይ እንዲደርስ የወሰነው ነገር ይህ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ለእርሱ የተጠበቀለት ቅርስ

ይህ እግዚአብሔር ለአንድ ሰው እንዲሆንለት የወሰነውን ይወክላል/ይገልጻል። ይህ የተነገረው እግዚአብሔር እንደ ውርስ አድርጎ የሚሰጠው ነገር ተደርጎ ነው። "እግዚአብሔር ለእርሱ ሊሰጠው ያቀደው" ወይም "እግዚአብሔር ለእርሱ ይሁን ብሎ ያቀደው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 21

Job 21:1

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ለሶፋር ክስ ምላሽ መስጠት ይጀምራል።

ታገሱኝ

"ፍቀዱልኝ" ወይም "ትዕግስት ይኑራችሁ"

መሳለቅ

"በእኔ ላይ መሳለቃችሁን መቀጠል ትችላላችሁ።" ኢዮብ ምጸት የተጠቀመው ጓደኞቹ የሚናገረውን ቸል በማለታቸው እና በእርሱ ላይ መሳለቅ በመቀጠላቸው ነው። (ምጸት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 21:4

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

ቅሬታዬ በሰው ላይ ነውን? ትዕግስት ማጣት አይገባኝምን?

ኢዮብ ጥያቄዎችን የሚጠቀመው ቅር መሰኘቱን ለእግዚአብሔር መናገሩ ተገቢ መሆኑን ለማጉላት ነው። "ቅሬታዬን የማቀርበው ለሰው አይደለም። ትዕግስት ለማጣት መብቱ አለኝ/ትዕግስት ባጣም ይገባኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

እጃችሁን በአፋችሁ ላይ አድርጉ

"አፋችሁን በእጃችሁ ሸፍኑ።" ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ለመገረም ምላሽ ነው። "አፋችሁን በእጃችሁ ሸፍኑ" እንደሚለው ወይም 2) ይህ አንድ ሰው እንደማይናገር ምልክት ነው። "አንዳች ነገር አትናገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

አካሌን መንቀጥቀጥ ያዘው

"ፍርሃት ሰውነቴን አራደው/አንቀጠቀጠው" ወይም "በፍርሃት ተንቀጠቀጥኩ"

Job 21:7

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

ክፉ ሰዎች ለምን ህልውናቸው ይቀጥላል፣ ለምን እስከ እርጅናቸው ይኖራሉ፣ ለምንስ ሀይላቸው እየጨመረ ይሄዳል?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ወዳጆቹ ክፉ ሰዎች ሁሌም ስቃይ ይደርስባቸዋል ብለው ማሰባቸው ስህተት መሆኑን ሊያሳያቸው ነው። "በእርግጥ ክፉ ሰዎች መኖራቸውን ይቀጥላሉ፣ ያረጃሉ፣ ይበልጥ ባለጸጋም እየሆኑ ይሄዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

በአይናቸው እየተመለከቱ ከእነርሱ ጋር ትውልዳቸው ይታነጻል… ትውልዳቸው በዐይናቸው ፊት ጸንቶ ይኖል

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ይህ እውነት መሆኑንም ያጎላሉ ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እየተመለከቱ… በዐይናቸው ፊት

እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ምክንያቱም "ዐይኖች" እይታን ያመለክታሉ። ክፉ ሰዎች ትውልዳቸው እያየለ እና እየበለጸገ ሲሄድ ያያሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ቤቶቻቸው

እዚህ ስፍራ "ቤቶች" በእነርሱ ውስጥ የሚኖሩ የቤተሰብ አባላትን ያመለክታሉ። "ቤተሰቦቻቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር በትር

ይህ የእግዚአብሔርን ቅጣት ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 21:10

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

ላማቸው አትጨነግፍም

"ላማቸው አትጨነግፍም" ወይም "ጥጃዋ ጤናማ እና ጠንካራ ሆኖ ይወለዳል"

ህጻናቶቻቸው እንደ መንጋ ናቸው

ኢዮብ እነዚህን ህጻናት ከጥጆች ጋር የሚያነጻጽረው ህጻናቶቻቸው እንደሚቦርቁ፣ እንደሚጫወቱ እና ደስተኞች እንደሆኑ ለማጉላት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከበሮ መሰል የሙዚቃ መሳሪያ/ታምብሪን

ላዩ ከበሮ የሚመስል በብረት ቁራጭ የሚመታ እና በዙሪያው ያሉ ቁርጥራጭ ብረቶች ሲርገፈገፉ ድምጽ የሚሰጥ የሙዚቃ መሳሪያ። (ማይተወቀውን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Job 21:13

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

ቀናቸው

"የህይወት ዘመናቸው"

በሰላም ወደ መቃብር/ሲኦል ይወርዳሉ

ይህ ትሁት በሆነ መንገድ ሞታቸውን መግለጽ ነው። "በሰላም ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ መንገዶች/መንገድህን

ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንደሚፈልግ ነው

እናመልከው ዘንድ፣ ሁሉን ቻይ የሆነው ምንድን ነው? ወደ እርሱ ብንጸልይ ምን ጥቅም እናገኛለን?

ክፉ ሰዎች እነዚህ ጥያቄዎች የሚጠይቁት በእግዚአብሔር ላይ ለመዘበት ነው። "ይህ ሁሉን ቻይ አምላክ የእኛ አምልኮ ይገባዋል ብለን አናምንም። እርሱ ለእኛ ምንም ሊያደርግ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

Job 21:16

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

እነሆ፣ ብልጽግናቸው በገዛ እጃቸው ላይ አይደለምን?

እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚያመለክተው ሀይላቸውን ወይም አቅማቸውን ነው። ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ወዳጆቹን ለመገዳደር ነው። "እነሆ፣ እነዚህ ክፉ ሰዎች ራሳቸውን ባለጸጋ እንዳደረጉ ይናገራሉ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

መቅሰፍት በላያቸው የሚመጣው… እስከ መቼ ነው?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ክፉዎችን አይቀጣም ብሎ የሚያስበውን ለማጉላት ነው። "ብዙ ጊዜ መቅሰፍት… አያጋጥማቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የክፉ ሰዎች መብራት ይጠፋል

ኢዮብ መብራት ማትፋትን ከሰው ሞት ጋር ያነጻጽራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር በድንገት ይገድላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የክፉ ሰዎች መብራት

ኢዮብ የክፉ ሰዎችን ህይወት እየነደደ ከሚገኝ መብራት ጋር ያነጻጽራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በቁጣው... ይህ ለምን ያህል ጊዜ ይሆናል?

ኢዮብ ይህን ሁለተኛ ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔር ክፉዎችን ብዙ ጊዜ አይቀጣም ብሎ ስለሚያስብ ይህንን ለማጉላት ነው። "በቁጣው... ይህ ብዙ ጊዜ አይሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ማዕበል የሚወስዳቸው ...ይህ ለምን ያህል ጊዜ ነው?

ኢዮብ ይህን ሦስተኛ ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔር ክፉዎችን ብዙ ጊዜ አይቀጣም ብሎ ስለሚያስብ ይህንን ለማጉላት ነው። "ማዕበል የሚወስዳቸው... ይህ ብዙ ጊዜ አይሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

በነፋስ ፊት እንደሚጠረግ ገለባ ይሆናሉ ወይም ዐውሎ ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው አብቅ ይሆናሉ

የክፉ ሰው ሞት የተነገረው ከገለባ ይልቅ እርባና ቢስ እንደሆኑ እና በቀላሉ ተጠርጎ እንደሚወሰድ እብቅ ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ነፋስ ገለባን ጠርጎ እንደሚወስድ እግዚአብሔር ይወስዳቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 21:22

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

እርሱ ከፍ ባሉት ላይም ፈረጅ ስለሆነ እግዚአብሔርን የሚያስተምረው አለን?

ኢዮብ ይህንን የሚጠይቀው እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚያውቅ ለማጉላት ነው። "እርሱ በሰማያት ባሉት ላይ እንኳን የሚፈርድ ስለሆነ፣ በእርግጥ ማንም እግዚአብሔርን ማስተማር አይችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከፍ ያሉት

ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በሰማያት ያሉት" ወይም 2) "ሀያላን ሰዎች"

አንዱ በሙሉ ሀይሉ ሳለ ይሞታል

ኢዮብ በጤና እና በሰላም ኖሮ የሞተውን ይህንን ሰው በሀዘን እና በስቃይ ከሞተው በበኢዮብ 21፡25 ከተጠቀሰው ሰው ጋረ ያነጻጽራል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውነቱ ወተት ጠግቧል ... የአጥነቱ መቅኔ እርጥብ ነው

እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ሰውየው በጣም ጤነኛ ነው የሚል ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውነቱ ወተት ጠግቧል

"ወተት" የሚለው ቃል "ስብ" ለማለት ይሆናል። ተሸፍኗል/የተሞላ ማለት በሚገባ ተመግቧል ማለት ነው። "ሰውነቱ በስብ የተሞላ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአጥንቶቹ መቅኔ እርጥብ ነው

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሰውነቱ ብርቱ እና ጤናማ ነው ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 21:25

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

ሌላው ሰው ይሞታል

ኢዮብ ይህንን ሰው በኢዮብ 21፡23 ላይ ከተጠቀሰው በሰላም ከሞተው ሰው ጋር ያነጻጽራል

በነፍስ መራራነት

እዚህ ስፍራ ሀዘን የተገለጸው መራራ ጣዕም እንዳለው ነገር ተደርጎ ነው፣ "ነፍስ" ደግሞ መላ የሰውን ማንነት ታመለክታለች። "በቁጣ እና በንዴት" ወይም "አሳዛኝ ህይወት ከመኖር በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንዳች መልካም ነገር ሳያገኝ/ሳያይ

ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "መጥፎ ነገሮችን ብቻ አይቶ" እንደሚለው።

እነርሱም እንደዚው በአፍር ውስጥ ተጋደሙ

ይህ እነርሱም ሞቱ የሚለው በትህትና መግለጫ መንገድ ነው። "እነዚህ ሁለቱም ሞተው ሰዎች ይቀብሯቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለቱንም ትል ይሸፍናቸዋል

ትሎች የተያያዙት ከሞተ ሰውነት መበስበስ ጋር ነው። "በአፍር ውስጥ የሚገኙ ትሎች የሞቱ አካሎቻቸውን ይመገባሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 21:27

አያያዥ ሃሳብ፡

x

Job 21:29

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

መንገደኞችን አልጠየቃችሁምን? በቁጣው ቀን...እነርሱ የመሚናገሩትን አታውቁምን?

ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያነሳው ወዳጆቹ ከመንገደኞች መማር ባለመቻላቸው ሊወቅሳቸው ነው። "ወደ ሩቅ አገር የተጓዙትን ልታደምጧቸው ይገባል። በቁጣው ቀን ... የሆነውን ጭምር ይነግሯችሁኋል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ሰው ከቁጣ ቀን ይጠበቃል... በቁጣ ቀን ከጥፋት ይርቃል

እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር በአንድ ስፍራ ጥፋት ሲያደርስ ክፉውን ሰው ይጠብቀዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 21:31

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ከወዳጆቹ ጋር መነጋገሩን ይቀጥላል።

የክፉውን ሰው መንገድ በፊቱ የሚወቅስ ማን ነው?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው ክፉዎች ሁልጊዜም እንደሚፈረድባቸው የወዳጆቹን አስተሳሰብ ለመቃወም ነው። "ማንም ሰው ክፉ ሰውን በፊቱ አይኮንነውም/ አይወቅሰውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ

ይህ ማለት ማንም ሰው በቀጥታ ወደ ክፉ ሰው ሄዶ ፊት ለፊት አይወቅሰውም። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለሰራው ስራ መልሶ የሰራውን የሚከፍለው ማን ነው?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ከፉ ሰዎች ይፈረድባቸዋል የሚለውን የወዳጆቹን እምነት ለመቃወም ነው። "ለሰራቸው መጠፎ ነገሮች ማንም ሰው መልሶ አይከፍለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ድጋፍ ያገኛል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ይደግፉታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሸለቆ ጓል ለእርሱ ጣፋጭ ይሆንለታል

ኢዮብ የሞተው ክፉ ሰው በላዩ የተጫነው አፈር እንኳን ደስ እንደሚያሰኘው ይገምታል። ይህ ማለት ክፉ ሰው ሞቱ እንኳን መልካም እንደሚሆንለት እና ዘመኑ ሲያበቃ መልካም ቀብር ይደረግለታል ይላል። "ጓል" የሚያመለክተው መቃብር የሚሸፍን አፈርን ነው። "በሸለቆ አፈር መሸፈኑን ደስ ይሰኝበታል" ወይም "በሸለቆ አፈር መቀበሩ ደስ ያሰኘዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ በፊት አያሌ ሰዎች እንደነበሩ፣ ሰው ሁሉ እርሱን የከተለዋል

ኢዮብ ብዙ የህዝብ ስብስብ በክፉ ሰው ቀብር ላይ እርሱን ለማክበር እንደሚገኙ አጉልቶ ይናገራል። "ወደ ቀብሩ ስፍራ ብዙ ህዝብ ከፊሉ ከፊት፣ ከፊሉ ከኋላ አጅቦት ይሄዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Job 21:34

አያያዥ ሃሳብ፡

ይህ ኢዮብ ለወዳጆቹ የሚያደርገውን ንግግር ያጠቃልላል።

በመልሶቻችሁ ውስጥ ከሀሰት በስተቀር ሌላ ነገር ሳይኖር እንዴት በማይረባ ነገር ልታጽናኑኝ ትችላላችሁ?


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 22

Job 22:1

ቴማናዊው ኤልፋዝ

ይህ የወንድ ስም በኢዮብ 2:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው እግዚአብሔርን ሊጠቅመው ይችላልን? ብልህ ሰው ለእርሱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላልን?

ሁለቱ ጥያቄዎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ኤልፋዝ ጥያቄዎቹን የተጠቀመባቸው የሰው ድርጊት እና ጥበብ እግዚአብሔርን እንደማይጠቅመው ለማጉላት ነው። "ሰው እግዚአብሔርን ሊጠቅም አይችልም። ጥበበኛ ሰው እርሱን ሊጠቅመው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ ጻድቅ ብትሆን ሁሉን ቻይ ለሆነው አንዳች ደስታ ነውን? መንገድህን ያለ ነቀፋ ብታደርግ ለእርሱ ጥቅም ነውን?

ሁለቱ ሃሳቦች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ኤልፋዝ ጥያቄዎቹን የተጠቀመባቸው የኢዮብ ድርጊት እግዚአብሔርን እንደማይረዳው ለማጉላት ነው። "አንተ ጻድቅ ብትሆን ሁሉን ቻይ የሆነው አንዳች ደስታ አይቀበልም። አንተ መንገዶችህን ያለ ነቀፋ ብታደርግ እርሱ አንዳች ነገር አያገኝም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 22:4

አያያዥ ሃሳብ፡

ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

ወደ ፍርድ የሚያቀርብህ እና የሚገስጽህ አንተ ለእርሱ ካለህ አምልኮ የተነሳ ነውን? ኃጢአትህ/ክፋትህ ታላቅ

አይደለምን? ለበደልህ ዳርቻ የለውምን? ኤልፋዝ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ኢዮብን ለመገሰጽ እና አስከፊ ኃጢአት ስለመስራቱ ሊከሰው ነው። "በእርግጥ እግዚአብሔር አንተን የገሰጸህ እና ወደ ፍርድ ያቀረበህ ለእርሱ የተሰጠህ ስለነበርክ አይደለም! አይደለም፣ እንደምታውቀው፣ የፈረደብህ ክፋትህ/ኃጢአትህ ታላቅ ስለሆነ እና በኃጢአተኛነትህ ስለቀጠልክበት/ከኃጢአትህ ስላልተመለስክ ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:6

አያያዥ ሃሳብ፡

ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

ላበደርከው መያዣ ጠይቀሃል

ይህ የሚያመለክተው አበዳሪ ከተበዳሪው መልሶ መክፈል መቻሉን ለማረጋገጥ አንድ ነገር እንደሚወስድ ነው።

የተራቆቱትን/ድሆችን ልብሳቸውን ገፈሃል

ኤልፋዝ ኢዮብን የሚከሰው ከእርሱ ከተበደሩ ድሆች ላይ መያዣ አድርጎ ልብሳቸውን እንደወሰደ አድርጎ ነው።

እንጀራቸውን ከልክለሃል

እዚህ ስፍራ "እንጀራ" የሚያመለክተው በአጠቃላይ ምግብን ነው። " ምግብ ከልክለሃል" (ስኔክዲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

መሬታቸውን ወርሰሃል/ቀምተሃል… በላይዋ ኖረሃል

ኤልፋዝ ኢዮብን የሚከሰው ከድሃ ሰዎች መሬታቸውን እንደ ቀማ እና በመሬታቸው እንዳይኖሩ እንደከለከላቸው አድርጎ ነው። ይህንን ነጥብ የሚያጎላው ነገሩን ሁለት ጊዜ ደጋግሞ በመናገር ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መሬታቸውን ወርሰሃል/ቀምተሃል

ኤልፋዝ ኢዮብ የያዘውን መሬት መጠን የሚያጋንነው ኢዮብን ራስ ወዳድ አድርጎ ለማሳየት ነው። "እጅግ ሰፊ መሬት ይዘሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 22:9

አያያዥ ሃሳብ፡

ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

ባሎቻቸው የሞቱባቸውን መበለቶች ባዷቸውን ሰደሃል

"መበለቶች ባዷቸውን እንዲሄዱ አድርገሃል"

መበለቶች

ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች

አባት የሌላቸው ክንዳቸው ተሰብሯል

እዚህ ስፍራ "ክንዶች" የሚለው የሚያመለክተው ሀይልን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወላጅ የሌላቸውን ሳይቀር ጨቁነሃል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በዙሪያህ ወጥመድ አለ… ጨለማ ሆኗል… ብዙ ውሃ ሸፍኖሃል

እያንዳንዳቸው እነዚህ ዘይቤያዊ አነጋገሮች፣ ከኃጢአቱ የተነሳ ኢዮብን ችግር እና አደጋ ዙሪያውን እንደከበቡት ይገልጻሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ ውሃ

"ጎርፍ"

Job 22:12

አያያዥ ሃሳብ፡

ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

እግዚአብሔር በሰማያት ከፍታ አይደለምን?

ኤልፋዝ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እግዚአብሔር የኢዮብን ኃጢአት እንደሚመለከት እና እንደሚፈርድበት ለመናገር ነው። "እግዚአብሔር በሰማያት ከፍታ ነው፤ በምድር የሚሆነውን ሁሉ ይመለከታል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ወደ ከዋክብት ከፍታ ተመልከት፣ እንደምን ከፍ ያሉ ናቸው!

ኤልፋዝ እግዚአብሔር ከከዋክብትም በላይ ከፍ ብሎ እንደሚገኝ እያመለከተ ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ከዋክብት እንዴት ከፍ ብለው እንደሚገኙ ተመልከት። እግዚአብሔር ከከዋክብትም በላይ ከፍ ያለ ነው!"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ምን ያውቃል? እርሱ በድቅድቅ ጨለማ ሊፈርድ ይችላልን?

ኤልፋዝ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ኢዮብ በእግዚአብሔር ላይ እነዚህን ነገሮች ተናግሯል ለማለት ነው። "እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚሆነውን አያውቅም። እሱ በጥቁር ደመና ላይ ስለተቀመጠ በእኛ ላይ ለመፍረድ ሊመለከተን አይችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በሰማያት ከፍታ ይራመዳል

እዚህ ስፍራ "ከፍታ፣ጣሪያ" የሚለው የሚያመለክተው የጥንት ሰዎች ምድርን እና ሰማይን ይለያል ብለው የሚያስቡትን መለያ ነው። "እርሱ እዚህ የሚሆነውን እጅግ ሩቅ በሰማያት ሆኖ ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:15

አያያዥ ሃሳብ፡

ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

ኃጢአተኞች በሚሄዱበት አሮጌ መንገድ መሄድህን ትቀጥላለህ

ክፉ ስራ መስራት የተነጻጸረው በመንገድ ላይ ከመሄድ ጋር ነው። "ክፉ ሰዎች የሚያደርጉትን ማድረግህን ትቀጥልበታለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ተቀሙት እንደ እነርሱ

ሞት የተነጻጸረው እግዚአብሔር እነርሱን እንደ ቀማቸው ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የሞቱት እነርሱ" ወይም "እግዚአብሔር የወሰዳቸው እነርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

መሰረታቸው እንደ ወንዝ ተጠርጎ የተወሰደው

የክፉ ሰዎች ሞት የተነጻጸረው መሰረታቸው በጎርፍ ከተወሰደ ህንጻዎች ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ የሆነው በእኛ ላይ ምን ማድረስ ይችላል?

ኤልፋዝ የሚጠቅሰው ክፉዎች በእግዚአብሔር ላይ ለመሳለቅ የሚያነሱትን ጥያቄ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነው። "ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ በእኛ ላይ አንዳች ማድረግ አይችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:18

አያያዥ ሃሳብ፡

ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

ሆኖም እርሱ ይሞላዋል

"ሆኖም እግዚአብሔር ይሞላዋል"

የክፉ ሰዎች እቅድ ከእኔ የራቀ ነው

"ከእኔ የራቀ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉሙ ኤልፋዝ እነርሱን ይቃወማል ማለት ነው። "እኔ ግን ክፉ እቅዳቸውን አልሰማም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እድል ፈንታቸውን ያያሉ

"በክፉዎች ላይ የሚደርሰውን ያውቃሉ"

በንቀት ይስቁባቸዋል

"በክፉዎች ላይ ይሳለቃሉ"

እነርሱ እንዲህ ይላሉ

"ጻድቃን እንዲህ ይላሉ"

በእርግጥ በእኛ ላይ ሚነሱ ይቆረጣሉ/ይጠፋሉ

እዚህ ስፍራ "እነርሱ የሚነሱብን" የሚለው የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው።ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በእርግጥ እግዚአብሔር እኛን የጎዱትን ክፉ ሰዎች ያጠፋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:21

አያያዥ ሃሳብ፡

ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

እነሆ

ኤልፋዝ ይህንን ቃል የተጠቀመው ሊናገር የፈለገውን ጠቃሚ ነገር ለማስተዋወቅ ነው።

ከአፉ የወጣው ትዕዛዝ

እዚህ ስፍራ "ከአፉ የወጣው" የሚለው የሚወክለው እግዚአብሔር የተናገረውን ነው። "እግዚአብሔር የሰጠው/የተናገረው ትዕዛዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሉን አከማችቷል

የእግዚአብሔር ቃሎች የተነጻጸሩት ኢዮብ በግምጃ ቤት ሊያጠራቅመው ከሚችለው ሀብት ጋር ነው። "ትዕዛዛቱን ማከማቸት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህ

እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚያመለክተው የኢዮብን አስተሳሰብ ነው። "የአንተ አእምሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:23

አያያዥ ሃሳብ፡

ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

አንተ ትጸናለህ

ኤልፋዝ የኢዮብን መታደስ የሚያነጻጽረው ከወደቀ ቤት መልሶ መገንባት ጋር ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ ይፈውስሀል፣ ደግሞም መልሶ ባለጠጋ ያደርግሀል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከጎጆች ጽድቅ ያልሆውን ብታርቅ

ጽድቅ ያልሆነ የሚለው የተገለጸው ሊርቅ እንደሚገባው በኢዮብ ጎጆ እንደሚኖር ሰው ተደርጎ ነው። "አንተ እና በቤትህ የሚኖሩ ሁሉ ኃጢአት መስራትን ብታቆሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሀብትህን በአፈር ውስጥ ቅበር

ሀብትን በአፈር ውስጥ መቅበር፣ ሀብትን ጥቅም እንደሌለው ማድረግ ነው። "ብልጽግናህን እንደ አፈር ጥቅም የሌለው አድርገህ ቁጠረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የኦፊርን ወርቅ በጅረቶች ድንጋይ መሃል

ወርቅን በወራጅ ውስጥ መጣል ከደንጋይ የተሻለ ምንም ጥቅም እንደሌለው አድርጎ መቁጠር ነው። "የኦፊር ወርቅ በወራጅ ውስጥ እንደሚገኝ ድንጋይ ጥቅም የሌለው ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኦፊር

ይህ በወርቁ የታወቀ ቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ የሆነው ብልጽግና፣ እና ውድ ብር ይሆንልሃል

ይህ ማለት እግዚአብሔር ለኢዮብ ከማንኛውም ሀብት ይልቅ ዋጋ ያለው ይሆንለታል ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:26

አያያዥ ሃሳብ፡

ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ

ፊትህን ወደ እግዚአብሔር ታነሳለህ

ይህ ማለት ኢዮብ ከእንግዲህ አያፍርም፣ ይልቁንም በእግዚአብሔር ይታመናል። "በሙሉ ልብ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሆንልሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ለአንተ ይረጋገጥልሃል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ፍሬያማ ያደርግሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በመንገዶችህ ብርሃን ይሆናል/ይበራል

የእግዚአብሔር በረከት የተነጻጸረው በኢዮብ መንገድ ላይ ሁሉ እንደሚሆን ብርሃን ነው። "በፊትህ በሚገኝ መንገድ ላይ እንደሚበራ ብርሃን ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 22:29

አያያዥ ሃሳብ፡

ይህ ኤልፋዝ ከኢዮብ ጋር ያለውን ንግግር ያጠቃልላል

ዝቅ ያሉ/የተዋረዱ ዐይኖች ያሉት

እዚህ ስፍራ "ዝቅ ያሉ ዐይኖች" የሚለው የሚያመለክተው ትህትናን ነው። "ትሁቱ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ትህት ያልሆነውን ሰው እንኳን ያድናል፤ በአንተ እጅ ንጽህና ግን የሚድነው ማን ነው

የኢዮብ ንጹህ መሆን የተነገረው አካላዊ እጁ ንጹህ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "ማን ይድናል" የሚለው ሀረግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ትክክል የሆነውን ስታደርግ ያኔ ያህዌ ንጹህ ያልሆውን ሰው እንኳን ያድናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ ትህት ያልሆነውን ሰው እንኳን ያድናል፤ በአንተ እጅ ንጽህና ግን የሚድነው ማን ነው

አንዳንድ ቅጂዎች እንዲህ ይላሉ፣ "እርሱ ትሁቱን ሰው ያድናል፤ ስለዚህ የአንተ እጆች ንጹህ በሆኑ ጊዜ አንተን ያድንሃል"

---

Chapter 23

Job 23:1

ዛሬም እንኳን ሀዘኔ መራራ ነው

እዚህ ስፍራ "ዛሬም እንኳን" የሚለው የወዳጆቹ ክርክር የኢዮብን ሁኔታ ምንም እንዳለወጠው የሚያጎላ ነው። "እንንተ ከተናገራችሁት ሁሉ ባሻገር፣ የእኔ ሀዘን ዛሬም መራራ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ሀዘኔ መራራ ነው

ኢዮብ ስላልተመለሱ ጥያቄዎቹ በአፉ ውስጥ እንዳለ መራራ ጣዕም አድርጎ እግዚአብሔርን ተቃውሞ ይናገራል። "ያልተመለሱ ጥያቄዎቼ በአፌ ውስጥ እንደሚገኝ መራራ ምግብ ሆኖብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእኔ እጅ ... ከማቃሰቴ የተነሳ ከብዷል

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ከማቃሰቴ የተነሳ እጄን ማንሳት እንኳን አልቻልኩም" ወይመም 2) "ከማቃሰቴ ባሻገር የእግዚአብሔር እጅ እኔን ማሰቃየቱን ቀጥሏል" እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለመቅጣት ያለውን ሀይል ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 23:3

አያያዥ ሃሳብ፡



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
አወይ፣ ያ የት እንደሆነ አውቃለሁ... አወይ፣ እኔ ወደዚያ እመጣለሁ
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የሚያጎሉትም ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ያለውን ፍላጎት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አገኘው ይሆናል
"እግዚአብሔርን አገኘው ይሆናል"
ጉዳዬን በፊቱ አቀርብ... አፌን በሞላው
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የሚያጎሉትም ኢዮብ ለእግዚአብሔር ሁኔታውን ለማስረዳት ያለውን ፍላጎት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አፌን በክርክር ሞላው
እዚህ ስፍራ "አፌን ሞላው" የሚለው የሚያመለክተው ንግግርን ነው። "ክርክሬን ሁሉ አቀርባለሁ/እናገራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ቃሎቹን እማራለሁ... እረዳቸዋለሁ
እነዚህ ሁለት መስመሮች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትረጉም አላቸው፤ የሚያተኩሩትም ኢዮብ የእግዚአብሔርን መልስ ለመስማት ባለው ፍላጎት ላይ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእኔ የሚሰጠኝን መልስ
"እርሱ ለእኔ የሚሰጠውን መልስ"

Job 23:6

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
እርሱ ...ይሆን
"እግዚአብሔር...ይሆን"
በዚያ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሚገኝበትን ስፍራ ነው
ፈራጄ/ዳኛዬ ለዘለዓለም ነጻ ያወጣኛል
ይህ በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የእኔ ዳኛ ለዘለአለም ነጻ ያወጣኛል" ወይም "የእኔ ዳኛ የሆነው እግዚአብሔር፣ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ንጹህ መሆኔን ይናገራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 23:8

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
ወደ ምስራቅ... ወደ ምዕራብ... ሰሜን....ደቡብ
እነዚህን አራት አቅጣጫዎች በመጥራት፣ ኢዮብ ወደ ሁሉም ስፍራ መመልከቱን ያተኩራል
ራሱን የት እንደ ሰወረ
ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር ራሱን እንደ ሰወረ ሰው አድርጎ ይናገራል

Job 23:10

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
እርሱ እኔ የምወስደውን መንገድ ያውቃል
የኢዮብ ድርጊቶች የተገለጹት በመንገድ እንደሚሄድ ተደርገው ነው። "እግዚአብሔር የማደርገው ምን እንደሆነ ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ወርቅ ነጥሬ እወጣለሁ
ኢዮብ መከራው እርሱ እንደ ነጠረ ወርቅ መሆኑን እንደሚያረጋግጥ ያምናል። "ማናቸውም ንጹህ ያልሆነ ነገር በእሳት ተፈትኖ ሲወገድ፣ እኔ እንደ ወርቅ ንጹህ መሆኔን ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እግሮቼ የእርሱን መንገድ ጠብቀዋል
እዚህ ስፍራ "እግሬ" የሚለው የሚያመለክተው ኢዮብን ነው። "እርሱ ያሳየኝን መንገድ ተከትያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱን መንገድ ጠብቄያለሁ
የኢዮብ ታዛዥነት የተገለጸው እግዚአብሔር ባሳየው መንገድ እንደሄደ ተደርጎ ነው። "እርሱ አደርገው ዘንድ የነገረኝን አድርጌያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያ ፈቀቅ አላልኩም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "በትክክል ተከትያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ከዚያ ወደ ኋላ አልልኩም/አላፈገፈግኩም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ሁልጊዜም ታዝዣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
የእርሱ ከንፈሮች
ይህ ሀረግ የሚያመለክተው እግዚአብሔር የተናገረውን መልዕክት ነው። "እርሱ የተናገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የአፉ ቃል
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የተገለጸው በ "አፉ" ነው። "እርሱ የተናገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 23:13

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
እርሱ ብቻውን ነው፣ ማን ሊመልሰው ይችላል?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም እንደሌለ እና እርሱን ይለውጠው ዘንድ የሚችል ማንም እንደሌለ ትኩረት ሰጥቶ ለመናገር ነው። "ነገር ግን እንደ እርሱ ያለ ማንም የለም፣ ማንም ሀሳቡን ሊያስለውጠው አይችልም።" ወይም " ነገር ግን እርሱ ብቻ አምላክ ነው፣ ማንም ተጽኖ ሊያሳድርበት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ የወደደውን ያደርጋል
"እርሱ ማድረግ የፈለገውን ሁሉ ያደርጋል"
በእኔ ላይ ትዕዛዙን አወጣ
"በእኔ ላይ አደርጋለሁ ያለውን አደረገ"
እንደነዚህ ያሉ ሌሎች ብዙዎች አሉ
"እርሱ ለእኔ ሌሎች ብዙ ተመሳሳይ እቅዶች አሉት"

Job 23:15

አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ እያንዳንዳቸው ሀረጋት ኢዮብ በዚያ ያደረጋቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ለማጉላት የትይዩ ንጽጽር ዘይቤ መልኮች አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ ሚለውን ይመልከቱ)
ልቤን ደካማ አደረገው
ልቡ የደከመ ሰው ድንጉጥ ወይም በፍርሃት የተሞላ ነው። "እንድፈራ አደረገኝኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በጨለማ ወደ ፍጻሜ አልመጣሁም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ከፊቴ ያለው ድቅድቁ ጨለማ ዝም አላሰኘኝም" ወይም 2) "ጨለማ አላስቆመኝም" ወይም " እግዚአብሔር እንጂ ጨለማ አላስቆመኝም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የፊቴ ትካዜ
እዚህ ስፍራ ኢዮብ ራሱን የሚገልጸው በ"ፊቱ/ገጹ" ነው። "ትካዜዬ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 24

Job 24:1
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
ሁሉን ቻይ በሆነው አምላክ የክፉ ሰዎች የፍርድ ጊዜ ለምን አይወሰንም
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ አይፈርድም የሚለውን መረበሹን ለመግለጽ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፡፡ "እግዚአብሔር በክፉ ሰዎች ላይ ሚፈርድበትን ጊዜ ለምን እንደማይወስን አይገባኝም" ወይም "ሁሉን ቻይ የሆነው በክፉ ሰዎች ላይ መቼ እንደሚፈርድ መወሰን አለበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ለእግዚአብሔር ተማኝ የሆኑ ለምን የፍርዱ ቀን ሲመጣ/ ሲደርስ አይመለከቱም?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ጻድቃን እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ላይ ሲፈርድ ባለመመልከታቸው የሚሰማቸውን መረበሽ ለመግለጽ ነው። "እርሱን የሚታዘዙ እርሱ በኃጢአተኞች ላይ ሲፈርድ የሚመለከቱ አይመስልም" ወይም "እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ላይ ሲፈርድ እርሱን የሚያውቁ ይህንን የሚመለከቱበትን ቀን ማሳየት/ ማምጣት አለበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 24:2
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
ዳርቻን አመልካቾች
እነዚህ በተለያዩ ሰዎች የተያዙ መሬቶችን ድንበር የሚለዩ ድንጋዮች ወይም ሌሎች ቁሳቁሶች ናቸው።
የግጦሽ መሬት
እንስሳት ለግጦሽ የሚሰማሩበት መሬት
ይነዷቸዋል
"ይሰርቃሉ"
አባቶች የሌሏቸውን
"የሙት ልጆች" ወይም "ወላጆቻቸው የሞቱባቸው ልጆች"
የመበለቶችን በሬዎች መያዣ አድርገው ይወስዳሉ
"የመበለቶችን በሬዎች ለተበደሩት ገንዘብ መያዣ አድርገው ይወስዳሉ"
መበለት
ባሏ የሞተባት ሴት
መያዣ አድርገው
አበዳሪው ከተበዳሪው መልሶ መክፈሉን ለማረጋገጥ አንድ ነገር ይወስዳል።
ከመንገዳቸው ወጥተው
"ከመንገዳቸው ውጭ" ወይም "ከመንገዱ ውጭ"
የምድር ድሆች ሁሉም ራሳቸውን ይደብቃሉ
"ሁሉም" የሚለው ቃል ብዙ ድሆች እነዚህን ክፉ ሰዎች እንደሚፈሯቸው የሚያሳይ ግነት ነው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 24:5
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
የሜዳ አህዮች ወደ በረሃ ምግብ ፍለጋ በጥንቃቄ እንደሚወጡ፣ እነዚያ ድሃ ሰዎች ወደ ስራቸው ይወጣሉ
እነዚህ ድሃ ሰዎች የተገለጹት ምግባቸውን ከየት ማግኘት እንደሚችሉ እንደማያውቁ የሜዳ አህዮች ነው። "እነዚህ ድሃ ሰዎች ምግብ ፍለጋ የሚወጡት በበረሃ እንደሚኖሩ የሜዳ አህዮች ባለ ሁኔታ ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሜዳ አህዮች
"ባለቤት ወይም ተንከባካቢ የሌላቸው አህዮች"
ድሆች በምሽት ያጭዳሉ…ወይን ይለቅማሉ
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ፤ በአንድነት የዋሉት እነዚህ ሰዎች እጅግ የተራቡ እና በምሽት ምግብ ለመስረቅ የተገደዱ መሆናቸውን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ ሚለውን ይመልከቱ)
እርቃናቸውን ተጋድመዋል… የሚለብሱት የላቸውም
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ፤ በአንድነት የዋሉት እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን ከብርድ ለመከላከል ምንም ልብስ እንደሌላቸው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ ሚለውን ይመልከቱ)
Job 24:8
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
ከተራሮች በሚወርድ ዝናብ ርሰዋል
"በተራሮች ሲዘንብ ርሰዋል"
የሙት ልጆችን ከእናታቸው ጡት ያስጥላሉ
እዚህ ስፍራ "ጡት" የሚያመለክተው እናትን ነው። ይህ የሚያመለክተው እነዚህ ወላጅ የሞተባቸው ገና ልጆች መሆናቸውን ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል፡፡ "ወላጆች የሞቱባቸው ልጆች ከእናቶቻቸው እቅፍ ሲወጡ" ወይም "አባቶቻቸው የሞቱባቸው ጨቅላ ልጆች ከእናቶቻቸው ተነጠሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ወላጅ የሞተባቸው
ይህ በአጠቃላይ ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ያመለክታል። ሆኖም እዚህ ስፍራ በተለይ እናት ያላቸውን ነገር ግን አባት የሌላቸውን ልጆች ያመለክታል።
ከድሆች ልጆቻቸውን በመያዣነት ይወስዳሉ
"የድሆችን ልጆች ድሆቹ ከክፉ ሰዎች የተበደሩትን መልሰው እንዲከፍሉ በመያዣነት ይወስዳሉ"
በመያዣነት
አበዳሪው ተበዳሪው መልሶ መክፈል መቻሉን ለማረጋገጥ ከተበዳሪው አንድ ነገር ይወስዳ/ ይይዛል። ይህ በኢዮብ 24:3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ወደዚያ ሄደ
"ተዘዋወረ"
ያለ ልብስ የተራቆተ
"ያለ ልብስ" የሚለው ሀረግ "እርቃን" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። "ሙሉ ለሙሉ እርቃን" ወይም "አንዳች ልብስ ስላልነበራቸው እርቃናቸውን ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
የሌሎችን ነዶ ይሸከማሉ
ይህ ማለት ድካማቸው/ስራች የሚጠቅመው/ምግብ የሚያስገኘው ለእነርሱ ሳይሆን ለሌሎች ነው
Job 24:11
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
ድሆች ዘይት ያዘጋጃሉ
ከወይራ ዘይት ለእነርሱ ዘይት ይጨምቃሉ
በክፉ ሰዎች አጥር ውስጥ
እዚህ ስፍራ "አጥር" የሚለው የሚወክለው በአጠቃላይ ቤቱን ነው። "በእነዚያ ክፉ ሰዎች ቤት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በክፉዎች ወይን መጭመቂያ ይረግጣሉ
ወይን ለማዘጋጀት ይህንን እንደሚያደርጉ መግለጽ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ "ወይን ለማዘጋጀት የወይን ፍሬ ይረግጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ራሳቸው በጥም ይሰቃያሉ
"ከጥማት የተነሳ ይሰቃያሉ" ወይም "ተጠምተዋል"
Job 24:13
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
ብርሃን ላይ ማመጽ
ለ"ብርሃን" ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የሚታይ ብርሃን ወይም 2) መንፈሳዊ ብርሃን፣ ይህ እግዚአብሔርን ሊያመለክት ወይም በጽድቅ መኖርን ሊያመለክት ይችላል፡፡ "የቀን ብርሃንን ጠላ" ወይም "ነገሮችን በገሃድ ለማድርግ አለመፈልግ" ወይም "በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ መንገዱን አላወቁም፣ አሊያም በመንገድ አልቆዩም
እነዚህ ሁለት ምመሮች ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ፣ በአንድነት የዋሉት የብርሃንን መንገድ ለመከተል አለመፈለጋቸውን አጉልቶ ለመግለጽ ነው። "ስነ ምግባር ያለው

ህይወት እንዴት እንደሚኖሩ አያውቁም፤ የጽድቅ ህይወት ከመኖር የራቁ ናቸው" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ድሆች እና ጎስቋላ ሰዎች
"ድሃ" እና "ጎስቋላ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክተው ተመሳሳይ ሰዎችን ነው፤ አጉልቶ የሚገልጸውም እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን መርዳት አለመቻላቸውን ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ እንደ ሌባ ነው
ሌባ ማንም ሳያየው እንደሚሰርቅ ሁሉ ነብሰ ገዳዩም በድብቅ ይገድላል። "ሌባ በድብቅ እንደሚሰርቅ ሁሉ እርሱ/ነብሰ ገዳዩ ሰዎችን በድብቅ ይገድላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 24:15
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
የዘማዊ ዐይን
እዚህ ስፍራ "ዐይን" የሚለው የሚያመለክተው በጠቅላላ ሰውየውን ነው። "ዘማዊው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ጀንበር ስትጠልቅ
"ፀሐይ ስትጠልቅ"
የማንም ዐይን አያየኝም
እዚህ ስፍራ "ዐይን" የሚለው የሚያመለክተው በጠቅላላ ሰውየውን ነው። "ማንም አያየኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉ ሰዎች ቆፍረው ወደ ቤት ይገባሉ
ወደ ቤቶች ቆፍረው የሚገቡት ከእነርሱ ለመስረቅ ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ክፉ ሰዎች ወደቤቶች ቆፍረው የሚገቡት ከእነርሱ ለመስረቅ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በራሳቸው ላይ ይዘጋሉ
"እነርሱ በውስጥ ይደበቃሉ"
ለእነርሱ ለሁሉም፣ ድቅድቅ ጨለማ እንደ ንጋት ነው
ለጤናማ ሰው የንጋት ብርሃን ምቹ እንደሚሆንለት ለክፉዎች ድቅድቅ ጨለማ ምቹ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የድቅድቅ ጨለማ ፍርሃት
"በጨለማ የሚሆኑ አስፈሪ ነገሮች"
Job 24:18
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
በውሃ ላይ እንዳለ አረፋ
አረፋ የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው። ይህ እግዚአብሔር ክፉዎችን እንደምን በቶሎ እንደሚያጠፋ አጉልቶ ያሳያል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ምድራቸው የተረገመ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ምድራቸውን ይረግማታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ድርቅ እና በረሃማነት/ሙቀት እንደሚያጠፉ… ኃጢአት የሰሩ
ኢዮብ፣ በሙቀት ጊዜ በረዶ እንደሚቀልጥ እና እንደሚጠፋ ኃጢአተኞች በሲኦል ይጠፋሉ ይላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ድርቅ እና በረሃማነት/ሙቀት
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ የአየር ንብረትን ይገልጻሉ፤ በአንድነት የቀረቡት ነገሩን በሙላት ለመግለጽ ነው። (ሄንዲያዲስ/ሁለት ቃላት 'እና' በሚል አያያዥ ቃል የሚገኛኙበትና አንድን ጥልቅ ሀሳብ ለመግለጽ የሚያገለግል ዘይቤያዊ አነጋገር)
Job 24:20
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
ማህጸን
ይህ የሚያመለክተው እናትን ነው። "እናት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ትሎች በደስታ ይመገቡታል
ይህ ማለት ይሞትና ትሎች በድኑን ይበሉታል ማለት ነው። "ትሎች በድኑን በመብላት ይረካሉ" ወይም "እርሱ ይሞታል ደግሞም በድኑ በትል ይበላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚህ ወዲያ መታሰቢያ አይኖረውም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከዚህ በኋላ ማንም አያስታውውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፋት እንደ ዛፍ ይቆረጣል
እግዚአብሔር በክፉ ሰው ላይ የሚያደርሰው ጥፋት የተገለጸው ዛፍን ቆርጦ እንደሚጥል ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ክፉ ሰውን የሚያጠፋው/ቆርጦ የሚጥለው ዛፍ እንደነበር አድርጎ ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ክፉዎች ይበላሉ
ይህ ዘይቤ ክፉ ሰው ምን ያህል ስር የለሽ እንደሆነ ያሳያል። "የዱር አውሬ የሚያድነውን እንደሚገድል፣ ክፉ ሰውም እንደዚያው ጉዳት ይደርስበታል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መሃኒቱ ወለደች
የዚያን ዘመን ሰዎች መሀን ሴት በእግዚአብሔር እንደ ተረገመች አድርገው ይቆጥሩ ነበር። ስለዚህም ይህ እጅግ እድለቢስ የሆነችን ሴት ይወክላል።
መበለት/ጋለሞታ
ባሏ የሞተባት ሴት
Job 24:22
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል
በእርሱ ሀይል
"ሀይሉን በመጠቀም" ወይም "ሀይለኛ በመሆኑ ምክንያት"
እርሱ ይነሳል ደግሞም በህይወት አያበረታቸውም
"በህይወት አያበረታቸውም" ማለት እግዚአብሔር በህይወት አያኖራቸውም/ህይወት አይሰጣቸውም ማለት ነው። "እግዚአብሔር ይነሳል፣ ክፉዎች በህይወት እንዲኖሩ አቅም አይሰጣቸውም" ወይም "እግዚአብሔር ይነሳል ደግሞም በህይወት እንዳይኖሩ ይገድላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን ዐይኖቹ በመንገዳቸው ላይ ነው
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። "ነገር ግን ሁልጊዜም የሚያደርጉትን ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 24:24
አያያዥ ሃሳብ፡
ይህ የኢዮብን ንግግር ያጠቃልላል
ወደ ህግ ይቀርባሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ወደ ህግ ያቀርባቸዋል" ወይም "እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደሌሎቹ ሁሉ ይሰበሰባሉ
አንዳንድ ትርጉሞች በተለየ ጥንታዊ ጽሁፍ/ጥቅስ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፣ "እንደ እረም ጠውልገው ይጠፋሉ" እንደሚለው። (የጽሁፍ/ጥቅስ ልዩነቶች የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱም እንደ ሌሎቹ ሁሉ ይሰበሰባሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሌሎች" የሚለው ምን እንደሚያመለክት በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ሌሎች ክፉ ሰዎችን እንደሰበሰበ እነዚህንም ይሰበስባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
በምድር ገጽ ላይ እንደሚገኝ ቅንጣት እነርሱም ይቀረጣሉ
እነዚህ ክፉ ሰዎች በአዝመራ ወቅት እንደሚታጨድ ሰብል በተመሳሳይ መንገድ ይቆረጣሉ። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ገበሬ የእህልን አገዳ እናት

እደሚቆርጥ እግዚአብሔር እነርሱን ይቆርጣቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
እንደዚህ ካልሆነ፣ የእኔን ሀሰተኝነት ማን ማረጋገጥ ይችላል፣ ማነድ ንግግሬን እርባና ቢስ ያደርገዋል?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት የክርክሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ ነው። በውስጠ ታዋቂነት የቀረበው መልስ፡ "ማንም የለም" የሚል ነው። "ይህ እውነት ነው፣ ደግሞም ማንም እኔ ሀሰተኛ ሊያደርገኝ አይችልም፤ ማንም እኔ ስህተተኛ መሆኔን ማረጋገጥ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ንግግሬን እርባና ቢስ የሚያደርግ
"የተናገርኩት ስህተት መሆኑን ማረጋገጥ የሚችል"

Chapter 25

Job 25:1

ሹሐዊው በልዳስ
ይህ የወንድ ስም በኢዮብ 2:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ
ገናናነት እና መፈራት የእርሱ ናቸው
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። "ገናና/የበላይ" እና "ፍርሃት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በግስ መልክ ሊጻፉ ይችላሉ። "እግዚአብሔር በሁሉም ላይ ይገዛል፣ እናም ሰዎች እርሱን ብቻ ይፍሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ በሚገኝበት በከፍታ ስፍራ በላይ በሰማይ ስርአትን አበጅቷል
"በላይ በሰማይ ሰላምን አድርጓል"
ለሰራዊቱ ቁጥር ልክ/መጠን አለውን?
በልዳዶስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እግዚአብሔር ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ አጉልቶ ለመግለጽ ነው። በውስጠ ታዋቂነት ለጥያቄው የተሰጠው ምላሽ "የለውም" የሚል ነው። ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ሰራዊት የሆኑትን መልአክትን ነው። "በእርሱ ሰራዊት ውስጥ የመላዕክቱ ቁጥር መጠን የለውም።" ወይም "የእርሱ ሰራዊቶች ማንምሊቆጥራቸው የማይቻለው እጅግ ብዙ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
የእርሱ ብርሃን የማያበራው በማን ላይ ነው?
በልዳዶስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው ብርሃን እንደሚሰጥ አጉልቶ ለመግለጽ ነው። "የእርሱ ብርሃን በላዩ የማያበራለት ማንም የለም" ወይም "እግዚአብሔር ብርሃኑ በሁሉም ላይ እንዲበራ አድርጓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 25:4

አያያዥ ሃሳብ፡
በልዳዶ መናገሩን ቀጥሏል
ታዲያ ሰው እንዴት... በእግዚአብሔር ፊት...? ከ...የተወለደ ሰው እርሱ እንዴት?
እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች በአንድነት የዋሉት ሰው በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ሊሆን እንደማይችል አጉልቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
ሰው እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ ሊገኝ ይችላል?
በውስጠ ታዋቂነት የሚሰጠው ምላሽ አይችልም የሚል ነው። "አንድ ሰው በፍጹም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሊሆን አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ከ.. የተወለደ ... በእርሱ ፊት እንዴት ተቀባይነት ያገኛል?
በውስጠ ታዋቂነት የጥያቄው ምላሽ አይችልም የሚል ነው። "ከሴት የተወለደ ሰው በእግዚአብሔር ፊት በፍጹም ንጹህ ሊሆን ወይም ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሴት የተወለደ እርሱ/ሰው
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሁሉንም ሰው ያካትታል። "ማንኛውም ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ተከትሎ በሚመጣው ላይ ትኩረት ይጨምራል። "በእርግጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
በእርሱ ፊት ጨረቃ ብሩህነት የላትም
"ብሩህ" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊገለጽ ይችላል። "በእግዚአብሔር ፊት ጨረቃ በቂ ብሩህነት የላትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ አይታ ከዋክብት ንጹሃን አይደሉም
እዚህ ስፍራ "ንጹህ" ማለት ፍጹም ማለት ነው። "እርሱ ከዋክብትን እንኳን ፍጹም አድርጎ አያያቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ትል የሆነ፣ የሰው ልጅ ... ሰው ምን ያህል ያንሳል
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ነገር ይናገራሉ፤ በአንድነት ሆነው የሚያጎሉትም ሰው ፍጹም አለመሆኑን ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ትል ማን ነው
በልዳዶስ የሰው ልጆች እንደትሎች እርባና ቢስ መሆናቸውን ይገልጻል። "እንደ ትል እርባና ቢስ የሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ልጅ
ይህ ሰው የተገለጸበት ሌላ መንገድ ነው። "አንድ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 26

Job 26:1

አቅም የሌለውን ክንድ ... እርሱን እንዴት ረዳኸው
በዚህ ዐረፍተ ሀሳብ፣ ኢዮብ በልዳዶስን እየነቀፈው/እየከሰሰው ነው። "እርሱን" የሚለው የሚያመለክተው ኢዮብን ነው። "ክንድ" የሚለው ቃል ደግሞ የሚወክለው በአጠቃላይ ሰውየውን ነው። "እኔ አቅም የለኝም፤ ደግሞም አንዳች ጥንካሬ የለኝም፣ ነገር ግን አንተ እንደረዳኸኝ ያህል ትሆናለህ፣ ነገር ግን በእርግጥ አንተ ምንም አልረዳኸኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
ጥበብ የሌለውን እንዴት መከርከው፤ እንዴት ጠቃሚነት ያለው እውቀት ሰጠው
ኢዮብ በልዳዶስ መልካም ምክር እና እውቀት እንዳልሰጠው እየተናገረ ነው። "አንተ የሚምልህ እኔ አንዳች ጥበብ እንሌለኝ እና አንተ እንደመከርከኝ፤ ደግሞም ጥሩ ምክር እንደሰጠኸኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
ለእርሱ ተሰሚነት ያለው እውቀት ሰጠው
"ጥሩ ምክር ሰጠው"
እነዚህን ቃላት በማን እርዳታ ተናገርክ? አንተ...ይህ የማን መንፈስ ነበር?
በእነዚህ ጥያቄዎች ኢዮብ በበልዳዶስ ላይ መሳለቁን ይቀጥላል። ሁለቱም ጥያቄዎች ቃለ ምልልሳዊ ናቸው፤ ትርጉማቸውም በመሰረታዊነት አንድ ነው። በአንድነት የቀረቡት አንዱ ሀሳብ ሌላውን ለማጠንከር ነው። "እነዚህን ቃላት እንድትናገር እርዳታ ሳታገኝ አልቀረህም። ምናልባት እነዚህን ነገሮች እንድትናገር አንድ መንፈስ ሳይረዳህ አልቀረም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 26:5

የሞቱት
ይህ የሚያመለክተው የሞቱ ሰዎችን ነው። "እነዚያ የሞቱት" ወይም "የሞቱት መንፈስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
መንቀጥቀጥ
እግዚአብሔርን ስለፈሩ ተንቀጠቀጡ። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "በፍርሃት ተንቀጠቀጡ" ወይም "እግዚአብሔርን በመፍራት ተንቀጠቀጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከውሆች በታች የሚኖሩ
ይህ በፍርሃት የተንቀጠቀጡትን ሙታን ያመለክታል
በእነርሱ የሚኖሩ ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው በውሆች ውስጥ የሚኖሩ የሞቱ ሰዎችን ነው
በእግዚአብሔር ፊት ሲኦል እርቃኑን ነው፤ ጥፋት ራሱ ምንም መሸፈኛ የለውም
ሲኦል የተገለጸው ሰው እንደሆነ ተደርጎ ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ራቁት" መሆን ወይም "መሸፈኛ" ማጣት አንዳች ነገር ለመደበቅ

አለመቻል እና ሙሉ ለሙሉ መጋለጥ ማለት ነው። "ሲኦል በእግዚአብሔር ፊት የተራቆተ እንደሆነ ሁሉ፣ በሲኦል አንዳች ነገር እንደሌለ፣ የጥፋት ስፍራ እንደሆነ፣ ከእግዚአብሔር ፊት የራቀ/የተደበቀ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይልከቱ)

ጥፋት

ይህ የሲኦል ሌላው ስሙ ነው። "የጥፋት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Job 26:7

እርሱ ሰሜናዊውን ሰማይ በህዋው ላይ ዘረጋው

ሰሜናዊ ሰማይ የሚለው የሚወክለው፣ እግዚአብሔር እርሱ ከፈጠራቸው ፍጥረታት ጋር የሚኖርበትን ስፍራ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በእነዚህ ከባድ ደመናዎች ውሆችን ቋጥሯል

ደመናዎች የተነጻጸሩት እግዚአብሔር የዝናብን ውሃ ከጠቀለለበት ትልቅ ብርድ ልብስ ጋር ነው። "እርሱ ውሆችን በከባድ ደመናዎች ጠቅልሏል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 26:9

ደግሞም በእርሷ ላይ ደመናዎችን ዘርግቷል

ይህ ሀረግ የጨረቃን ገጽ እንዴት እንደሸፈነ ይገልጻል። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። "ደመናዎቹን በእርሷ ፊት በመዘርጋት"

እርሱ በውሆች ገጽ ዙሪያ ክብ ዳርቻዎችን አበጅቷል

ይህ እግዚአብሔር በውቅያኖስ ላይ የዳርቻ ምልክት ያደረገ የሚመስልበትን ምድር ከሰማይ ጋር የገጠመ ሆኖ ስለሚታይበት ስለ አድማስ ይናገራል

Job 26:11

የሰማይ አምዶች ተናወጡ፣ በቁጣውም ራዱ

ሰዎች ሰማያት ወይም ሰማይ በአምዶች ላይ እንደቆሙ ያስባሉ። ኢዮብ ሰዎች እግዚአብሔር ሲቆጣ የሚርዱ አምዶች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። "ሰማይን የተሸከሙ አምዶች እግዚአብሔር ሲቆጣቸው በፍርሃት ይናወጣሉ" ወይም "ሰማይን የተሸከሙ አምዶች እግዚአብሔር ሲገስጻቸው እንደሚርዱ ሰዎች ይናወጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ረአብን ይቆራርጣል/ይሰባብራል

"ረአብን ያጠፋል"

ረአብ

ይህ በውሃ ውስጥ የሚኖር አስፈሪ የሆነ አውሬ ስም ነው። ይህ በኢዮብ 9፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 26:13

በእስትንፋሱ ሰማያትን ያነጻል

"እስትንፋስ" የሚለው ስም "ተነፈሰ" ወይም "እፍ አለ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። ይህ ምሳሌ የሚወክለው እግዚአብሔር ደመናትን ለመበተን እግዚአብሔር ነፋሳትን እንደሚያነፍስ ነው። "እግዚአብሔር ሰማያት ንጹህ ይሆኑ ዘንድ ደመናዎችን ይበትናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቹ በራሪውን አውሬ ወጋ

ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በእጆቹ ሰይፍ እንደ ያዘ እና እዚህ ስፍራ "የእርሱ እጅ" የሚለው ደግሞ የሚያመለክተው ያንን ሰይፍ ነው። "በሳው" መግደልን ያሳያል። "በሰይፉ በራሪ አውሬውን ወጋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

በራሪው አውሬ

"አውሬው ከእርሱ ለማምለጥ በሞከረ ጊዜ።" ይህ በውሃ ውስጥ የሚኖረውን ረአብን ያሳያል። ኢዮብ 26፡12 ይመልከቱ።

እነሆ፣ ይህ የመንገዱ ዘርፍ ነው

እዚህ ስፍራ "ዘርፍ" የሚወክለው ትልቅ ከሆነ ነገር ውስጥ አነስተኛ የሆነውን ክፈል ነው። "እነሆ፣ እነዚህ እግዚአብሔር የሰራቸው ነገሮች የሚያመለክቱት ከታላቅ ሀይሉ ውስጥ ጥቂቱን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ምንኛ ታናሽ ሹክሹክታውን እንሰደማለን!

ይህ እኛ ስለመኖሩ እንኳን ከነጭርሱ የማናውቀው የኢዮብን አድናቆት አጋኖ የሚገልጽ እግዚአብሔር ከሰራቸው ታላላቅ ነገሮች አንዱ ነው። እግዚአብሔር ያደረገውን ማየት የተገለጸው የእግዚአብሔርን ድምጽ እንደመስማት ተደርጎ ነው። "ይህ የእርሱን ጸጥ ያለ ማንሾካሾክ እንደመስማት ነው!" (ቃለ አጋኖ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 27

Job 27:1

እንደ እግዚአብሔር ህልውና እርግጠኝነት ያለው

ይህ ሀረግ የሚያመለክተው ኢዮብ ማሃላ ማድረጉን ነው። ኢዮብ የእግዚአብሔርን ህልውና እርግጠኝነት የሚያነጻጽረው እርሱ ከተናገረው ነገር እርግጠኝነት ጋር ነው። ይህ በመሃላ ነገርን የማረጋገጥ መንገድ ነው። "ህያው እግዚአብሔርን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ፍትህን ከእኔ አራቀው

ፍትህ የተገለጸው ሊወሰድ ወይም ሊሰጥ እንደሚችል አካል/ቁስ ነው። መውሰድ የሚለው የሚገልጸው ለኢዮብ ተገቢውን ፍትህ መንፈግን ነው። "ለእኔ ፍትህ መስጠትን አልወደደም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴን መራራ አደረገ

የኢዮብ "ህይወት" መራራ መሆን የሚወክለው ኢዮብ ለእግዚአብሔር ያለውን በቅሬታ የተሞላ ስሜት ነው። "ህይወቴ በቅሬታ የተሞላ እንዲሆን አደረገ" ወይም "በአግባብ ስላልተመለከተኝ በሀዘን ሞላኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቴ ገና በውስጤ እስካለች ድረስ

ይህ የሚያመለክተው በህይወት ለመኖር የቀረውን እድሜ ነው። "ህይወቴ በውስጤ በምትኖርበት በቀሪው ዘመን ሁሉ" ወይም "ህይወቴ በእኔ ውስጥ እስካለች ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ህይወቴ ገና በውስጤ እስካለች ድረስ

"ህይወት" የሚለው ረቂቅ ስም "መኖር" በሚል ቅጽል ወይም "ኖረ" በሚል ግስ ሊገለጽ ይችላል። "በህይወት እስካለሁ ድረስ" ወይም "በህይወት እስከ ኖርኩ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር እስትንፋስ በአፍንጫዬ ውስጥ አለ

"እስትንፋስ... በአፍንጫዬ አለ" የሚለው የሚወክለው መተንፈስ መቻልን ነው። "እስትንፋስ ከእግዚአብሔር ዘንድ" የሚለው የሚገልጸው እግዚአብሔር እርሱን መተንፈስ ማስቻሉን ነው። "እግዚአብሔር እስትንፋስ ሰጠኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አፍንጫዎች

"አፍንጫ"

Job 27:4

ከንፈሮቼ ክፋትን አይናገሩም፣ ምላሶቼም ሽንገላን አያወሩም

እነዚህ ሁለት ሀረጋት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድነት የቀረቡት በዚህ አይነት መንገዶች እንደሚናገር በትኩረት ለመግለጽ ነው። "ከንፈሮቼ" እና "ምላሴ" የሚሉት የሚወክሉት ራሱን ኢዮብን ነው። "ክፋትን አልናገርም ወይም አላታልልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ክፋትን መናገር... ማታለል/ሀሰትን መናገር

"ክፋት" እና "ማታለል" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "በክፋት" እና "በማታለል" በሚሉት ቃላት ሊገለጹ ይችላል። "በክፋት መናገር... በማታለል መናገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

መቼም ቢሆን እናንተ ሶስታችሁ ትክክል ናቸው ብዬ መናገር አልችልም

"መቼም ቢሆን ሶስታችሁ ትክክል ናችሁ ስል ከእናንተ ጋር አልስማማም"

እናንተ ሶስታችሁ ትክክል ናችሁ

"እናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። የሚያመለክተውም የኢዮብን ወዳጆች ነው። (አንተ የሚለው ቃል ልዩ ልዩ መልኮች)

ቅንነቴን አልጥልም

"በፍጹም ትሁት መሆኔን ልክድ አልችልም" ወይም "ሁልጊዜም ቢሆን ትሁት መሆኔን እናገራለሁ"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Job 27:6

ጽድቄን አጥብቄ እይዛለሁ

እዚህ ስፍራ "አጥብቄ እይዛለሁ" የሚለው አንድን ነገር አጥብቆ ይዞ መቀጠል ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ጽድቅ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጻድቅ" በሚለው ሊገለጽ ይችላል። "ጻድቅ ነኝ የሚለውን አጥብቄ ይዤ ለመቀጠል ወስኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

እንዲሄድ አልፈቅድም

እዚህ ስፍራ "እንዲሄድ አልፈቅድም" የሚለው አንድን ነገር ለመተው/ለማቆም አለመፍቀድን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። "ጻድቅ መሆኔን መናገርን አላቆምም" ወይም "እንደዚያ ማለቴን አላቆምም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሀሳቤ አይዘልፈኝም

እዚህ ስፍራ "ሀሳቤ/አስተሳሰቤ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብን ነው። "በሃሳቤ እንኳን፣ ራሴን አልዘልፍም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላቶቼ እንዲህ ይሁኑ... በእኔ ላይ የሚነሱ እንዲህ ይሁኑ

በእነዚህ ቃላት የሚጀምሩት እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በአንድነት የቀረቡት ይህ እንዲሆን ኢዮብ ያለውን ጠንካራ ፍላጎት በትኩረት ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላቶቼ እንደ ኃጢአተኛ ሰው ይሁኑ

እርሱ ጠላቶቹ እንዴት እንደ ኃጢአተኛ ሰው እንዲሆኑ እንደሚፈልግ ግልጽ ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። "ጠላቶቼ እንደ ኃጢአተኛ ሰው ይቀጡ" ወይም "እግዚአብሔር ኃጢአተኛ ሰዎችን እንደሚቀጣ ጠላቶቼን ይቅጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ላይ የሚነሳ እንደ ኃጢአተኛ ሰው ይሁን

ኢዮብ ይህ ሰው/ጠላቱ/ እንዴት እንደ ኃጢአተኛ ሰው ሊሆን እንደሚፈልግ ግልጽ ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። "በእኔ ላይ የሚነሳብኝ እርሱ ኃጢአተኛ ሰው እንደሚቀጣ ይቀጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ላይ የሚነሳብኝ እርሱ

እዚህ ስፍራ "በእኔ ላይ የሚነሳብኝ" የሚለው ዘይቤያዊ አገላለጽ ሲሆን ትርጉሙ "የሚቃወመኝ" ማለት ነው። መላው ሀረግ የሚያመለክተው የኢዮብን ተቃዋሚዎች ነው። "እኔን የሚቃወመኝ እርሱ" ወይም "የእኔ ተቃዋሚ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 27:8

እግዚአብሔር ህይወቱን በሚሰበስባት/በሚወስድ ጊዜ... እግዚአብሔር የለሽ የሆነ ሰው ተስፋው ምንድን ነው?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እንዲህ ያለው ሰው ምንም ተስፋ የለውም ለማለት ነው። ይህ ጥያቄ በቀላል ሀሳብ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ነፍሱን ሲወስዳት... እግዚአብሔር የለሽ ለሆነ ሰው አንዳች ተስፋ የለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሲቆርጠው፣ እግዚአብሔር ህይወቱን ሲወስዳት

ሁለቱ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "እግዚአብሔር እርሱን በሚቆርጠው እና ህይወቱን በሚወስድ ጊዜ" ወይም "እግዚአብሔር እርሱን ሲገድለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ሲቆርጠው

የዚህ ዘይቤያዊ አነጋገር ትርጉም "እርሱን ሲገድለው" ወይም "እንዲሞት ሲያደርግ" ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወቱን ሲወስድ

የዚህ ዘይቤያዊ አነጋገር ትርጉም "እርሱን ሲገድለው" ወይም "መኖሩ እንዲያበቃ ሲያደርግ" ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ችግር ደርሶበት ሲጮህ እግዚአብሔር ይሰማው ይሆን?

x

Job 27:11

እኔ አስተምርሃለሁ

በእነዚህ ሀረጎች "እናንተ" የሚለው በተገለጸ ጊዜ ሁሉ ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም የኢዮብን ሶስት ጎደኞች ነው።

የእግዚአብሔር እጅ

የእግዚአብሔር "እጅ" የሚያመለክተው ሀይሉን ነው። "የእግዚአብሔር ሀይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ የሆነውን ሀሳብ አልሸሽግም

"ሀሳብ" የሚለው ረቂቅ ስም "አሰበ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ሁሉን ቻይ የሆነውን ሀሳብ ከእናንተ አልደብቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ለምን ይህንን የማይረባ ነገር ሁሉ ትናገራላችሁ?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ወዳጆቹ እንደዚህ ያሉ የማይረቡ ነገሮችን ስለተናገሩ ሊገስጻቸው ነው። ይህ ጥያቄ በቀላል ሀሳብ ሊተረጎም ይችላል። "እንዲህ ያለ የማይረባ ነገር መናገር አልነበረባችሁም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 27:13

ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ የኃጢአተኛ ሰው እድል ፈንታው/ድርሻ ነው።

"ይህ እግዚአብሔር ለኃጢአተኛ ሰው ያቀደለት ነው"

ሁሉን ቻይ ከሆነው ዘንድ የሚቀበለው የጨቆኝ ሰው/ሰውን የሚያሳዝን ሰው ድርሻው

እዚህ ስፍራ "የጨቆኝ/ ሰውን የሚያሳዝን ሰው ድርሻው" የሚለው በጨቆኝ ሰው/ ሰውን በሚያሳዝን ሰው ላይ የሚደርሰውን ነገር የሚገልጽ ዘይቤ ነው። በዚህ ሰው ላይ እግዚአብሔር የሚያደርገው ነበር የተገለጸው እግዚአብሔር ለእርሱ የሚሰጠው ነገር ተደርጎ ነው። "ሁሉን ቻይ የሆነው በጨቆኝ ሰው/ሰውን በሚያሳዝን ሰው ላይ የሚያደርገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለሰይፍ ይሆናል

እዚህ ስፍራ "ለሰይፍ" የሚወክለው በጦርነት መሞትን ነው። "በጦርነት ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 27:15

ከእርሱ ልጆች በህይወት የሚኖሩት ይህ የኃጢአተኛውን ሰው ልጆች ያመለክታል። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ክፉ የሆኑት

አባቶቻቸው ከሞቱ በኋላ የሞኖሩት ልጆቻቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በመቅሰፍት ይቀበራሉ

እዚህ ስፍራ "ይቀበራሉ" የሚለው የሚወክለው ሞትን ነው። "በመቅሰፍት ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱ መበለቶች...እነርሱ

"የእነርሱ" እና "እነርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክተው "ከእርሱ በኋላ የሚኖሩትን" ይኸውም የክፉ ሰውን ልጆች ነው።

ብር እንደ አፈር መከመር

እዚህ ስፍራ "መከመር" የሚለው "ብዙ መሰብሰብ" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ኢዮብ ብር ማግኘት አፈር የማግኘት ያህል እንደሚቀላቸው ይናገራል። "የብር ቁልል ይሰበስባሉ" ወይም "አፈር መሰብሰብ የሚችሉትን ያህል በቀላሉ ብር ይሰበስባሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብስ እንደ ሸክላ ይከምራሉ

እዚህ ስፍራ "መከመር" የሚለው "ብዙ መሰብሰብ" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ኢዮብ ልብስ ማግኘት አፈር የማግኘት ያህል እንደሚቀላቸው ይናገራል። "የልብስ ቁልል ይሰበስባሉ" ወይም "አፈር መሰብሰብ የሚችሉትን ያህል በቀላሉ ልብስ ይሰበስባሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 27:18

ቤቱን እንደ ሸረሪት ይሰራል/ይገነባል

"ከሸረሪት" በኋላ "ድሯን ማድራት" የሚለው ሀረግ በግልጽ የሚታወቅ ነገር ነው። ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ሸረሪት ድሯን እንደምታደራ ኃጢአተኛው ቤቱን ይሰራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቱን እንደ ሸረሪት ይሰራል

የሸረሪት ድር በቀላሉ ይበጣጠሳል፣ ደግሞም በቀላሉ ይጠፋል። "ሸረሪት ድሯን

እንደምትሰራ ቤቱን ይገነባል" ወይም "የሸረሪት ድር በቀላሉ እንደሚበጣጠስ፣ ቤቱን እንደዚያው ይገነባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ጎጆ
ጎጆ በጣም ጠንካራ ያልሆነ ጊዜያዊ ቤት ነው። "እንደ ጊዜያዊ ጎጆ/ድንኳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በባለጸጋ አልጋ ይተኛል
"በመኝታው ሲጋደም ባለጸጋ ነው።" ይህ የሚያመለክተው በምሽት በአልጋው ላይ መጋደሙን እና መተኛቱን ነው።
ነገር ግን ይህንን ማድረጉን አይቀጥልም
"ነገር ግን በባለጸጋ አልጋ ላይ መተኛቱን አይቀጥልም" ወይም "በአልጋው ላይ በሚተኛበት ጊዜ ባለጸጋነቱ አይቀጥልም/ከመኝታው ሳይወርድ ባለጸጋነቱ ያበቃል"
ዐይኖቹን ሲከፍት
ዐይኖቹን ሲከፍት የሚለው የሚወክለው በጠዋት ሲነሳ የሚለውን ነው። "ከእንቅልፉ ሲነቃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ያለውን ሁሉ አጥቶታል/ያለው ሁሉ ሄዷል
"ሀብቱ ሁሉ ጠፍቷል" ወይም "ሁሉም ነገር ከእርሱ ርቋል"
Job 27:20
ፍርሃት ውጦታል
እዚህ ስፍራ "እርሱን ውጦታል" የሚለው የሚወክለው በድንገት የሚደርስበትን ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች "ጭንቀት/መሸበር" ለተከታዮቹ ሀሳቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። 1) ሰዎች እንዲፈሩ የሚያደርጉ ነገሮች። "በድንገት በኃጢአተኛው ላይ የሚደርሱ ነገሮች" ወይም 2) ፍርሃት። "በድንገት ፍርሃት ዋጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
እንደ ውኆች
"ውኆች" የሚለው ቃል ጎርፍን ያመለክታል። ጎርፍ ሰዎች ሳይጠብቁት በድንገት ሊደርስ ይችላል፤ ደግሞም አደገኛ እና አስፈሪም ነው። "እንደ ጎርፍ" ወይም "በድንገት እንደሚሞላ ደራሽ ውሃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አውሎ ነፋስ ይወስደዋል
"ሃይለኛ ነፋስ ጠርጎ ይወስደዋል"
ከስፍራው ይጠርገዋል
ኢዮብ ኃጢአተኛውን ሰው ከቤቱ ጠርጎ የሚወስደውን ነፋስ የገለጸው፣ ነፋስን እንደ ሰው በመግለጽ እና አቧራን ከቤት ከሚያስወግድ መጥረጊያ ጋር በማነጻጸር ነው። "ሴት ቆሻሻን በመጥረጊያ ጠርጋ እንደምታስወጣ ነፋስ ከስፍራው ይጠርገዋል" ወይም "ነፋስ በቀላሉ ከስፍራው ይጠርገዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ስፍራው
"ቤቱ"
Job 27:22
አጠቃላይ መረጃ፡
በኢዮብ 27: 22-23 ላይ ኢዮብ ስለ ነፋስ የሚናገረው ክፉዎችን እንደሚያጠቃ ሰው አድርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በኃጢአተኛው ላይ ይወድቅበታል
" በኃጢአተኛው ላይ ይወድቅበታል" የሚለው ሀረግ የሚወክለው ነፋሱ በኃጢአተኛው ላይ አደጋ እንደሚጥል ሰው ሆኖ በሃይል ይነፍስበታል ማለትን ነው። "አደጋ እንደሚጥል ሰው በእርሱ ላይ በሃይል ይነፍስበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእጁ አምልጦ ለመብረር ይሞክራል
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ነፋስ በክፉ ሰው ላይ ያለውን ሀይል ወይም አቅም ነው። "ከእርሱ ቁጥጥር ለማምለጥ ይሞክራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
በፌዝ እጆቹን ያጨበጭብበታል
እጆችን ማጨብጨብ በሌላ ሰው ላይ የማፌዝ መንገድ ነው። እዚህ ስፍራ ይህ የሚወክለው ነፋስ ከፍ ያለ ድምጽ ማሰማቱን/መስጠቱን ነው። "በእርሱ ላይ ለማፌዝ አንድ ሰው እጆቹን እንደሚያጨበጭብ ከፍ ያለ ድምጽ ያወጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 28
Job 28:1
የማዕድን ስፍራ
ይህ ሰዎች ከመሬት የተለያዩ አለቶችን የሚያወጡበት ስፍራ ነው። አለቶች በውስጣቸው ብረት አላቸው።
ማጣራት
ይህ በብረት ውስጥ የሚገኘውን አፈር ለማጣራት ብረትን የማቅለጥ ሂደት ነው
ብረት ከአፈር ውስጥ ይወጣል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ብረትን ከመሬት ያወጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
መዳብ ከማዕድን ድንጋይ ቀልጦ ይወጣል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች መዳብን ከመሬት ያወጣሉ" ወይም "ሰዎች መዳብን ለማውጣት ድንጋይ ያቃጥላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
መዳብ
ጠቃሚ የሆነ ቀይ ቡኒ ቀለም ያለው ብረት
ማቅለጥ
ይህ በአለቶች ውስጥ የሚገኘውን ብረት ለማግኘት ሲባል አለቶችን የማቃጠል ሂደት ነው
Job 28:3
ሰው ለጨለማ ዳርቻ ያበጅለታል
እዚህ ስፍራ "ለጨለማ ዳርቻ ማበጀት/ጨለማ ማስወገድ" የሚለው የሚወክለው በጨለማ ማብራትን ነው። ሰዎች ብርሃን ለማግኘት ፋኖስን ወይም ችቦን ይጠቀማሉ። "ሰው ወደ ጨለማ ስፍራ ብርሃን ይዞ ይሄዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሩቅ ወደሆነው ስፍራ
"ወደ ማዕድን ቁፋሮው ሩቅ ስፍራ"
ድብቅነት…ድቅድቅ ጨለማ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በአንድነት አገልግሎት ላይ የዋሉት ማዕድን የሚገኝበት ስፍራ እጅግ ጨለማ መሆኑን ለመግለጽ ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
የጉድጓድ መግቢያ/አፍ
ወደ መሬት ወደ አለት ውስጥ የተቆፈረ ጠባብ ጥልቅ ጉድጓድ። ሰዎች ማዕድን ለማውጣት ወደ ጉድጓዱ ውስጠኛ ክፍል ይገባሉ።
በማንም እግር ያልታወሱ ስፍራዎች
እግር የተገለጸው ማስታወስ እንደሚችል ሰው ተደርጎ ነው። "ሰዎች ያልሄዱባቸው ስፍራዎች" ወይም "ማንም ተራምዶባቸው የማያውቁ ስፍራዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ከሰዎች ርቆ ይቆያል
እንዴት እና የት እንደ ራቀበግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "በጉድጓዱ ውስጥ በገመድ ታስሮ ከሰዎች ርቆ ያቆያል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 28:5
ከመሬት እንጀራ ይወጣል
እዚህ ስፍራ "እንጀራ" የሚወክለው በአጠቃላይ ምግብን ነው። እንጀራ ከመሬት ይወጣል የሚለው እንጀራ ከመሬት ይበቅላል የሚል ዘይቤ ነው። "እንጀራ የሚወጣበት መሬት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክዶክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
በእሳት እንደሆነ ነገር ከስር ተገልብጧል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አለቶችን ለመሰባበር ሰዎች ከምድር በታች እሳት አንድደዋል። "መአድን ቆፋሪዎች ባነደዱት እሳት ከምድር በታች ያለው ተንኮታኩቷል" ወይም 2) "ተገልብጧል" የሚለው ተለውጧል ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ከስር በእሳት የጠፋ ያህል በከፍተኛ ደረጃ ተንኮታኩቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እርሷ ተገልብጧለች.. የእርሷ አለቶች/ደንጋይ ... የእርሷ አብዋራ/አፈር
"እርሷ" የሚለው የሚያመለክተው መሬትን ነው።
ሰንፔር
በጥቂቱ ብቻ የሚገኝ ዋጋው የከበረ ሰማያዊ ቀለም ያለው ድንጋይ
Job 28:7
የትኛውም አዳኝ ወፍ ወደዚያ የሚወስደውን መንገድ አያውቅም... አሊያም የጭልፊት ዐይንም አላየውም
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "የትኛውም አዳኝ ወፍ ወይም ጭልፊት ወደ ማዕድን ስፍራ የሚወስደውን መንገድ አይቶት አያውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አዳኝ ወፍ
"ሌሎች እንስሳትን የሚበላ ወፍ"
ጭልፊት
ይህ "አሞራ" ተብሎም ሊተረጎም ይችላል። እነዚህ ሁለቱም የሚያድኑ እና ሌሎች እንስሳት የሚመገቡ ወፎች ናቸው። ይህንን በባህላችሁ ውስጥ በሚገኝ አነስተኛ ወፍ ተክታችሁ መተረጎም ትችላላችሁ።
ኩሩዎቹ እንስሳት በዚህ መንገድ አልሄዱም... አሊያም ሀይለኞቹ አንበሶች በዚያ አላለፉም
እነዚህ ሀረጎችም ደግሞ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ኩሩዎቹ እንስሳት
ይህ የሚያመለክተው በጣም ጠንካራ የሆኑ የዱር አራዊትን ነው
Job 28:9
በባልጩት/ጠንካራ አለቶች ላይ እጆቹን ያሳርፋል
ይህ የሚወክለው አለቶችን መሰባበርን ነው። "ጠንካራ አለት መቆፈር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ጠንካራ አለት
"ጠጣር አለት"
እርሱ ተራሮችን ከስራቸው ይገለብጣል
ተራሮችን እና ከስራቸው የሚገኘውን መሬት መቆፈር የሚለው አረምን ወይም ዛፎችን ከስራቸው መንቀል ለሚለው ዘይቤያዊ አገላለጽ ሲሆን ማዕድኖችን ከመሬት ቆፍሮ ማውጣትን አጋኖ ለመግለጽ የዋለ ነው። "እርሱ ስራቸውን ቆፍሮ በማውጣት ተራሮችን ከስራቸው ገለበጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት እንዲሁም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
የእርሱ ዐይኖች
እዚህ ስፍራ "የእርሱ ዐይኖች" የሚለው የሚወክለው እርሱን ነው። "እርሱ ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ጅረቶች እንዳይፈሱ/እንዳይወርዱ ያግድ ነበር
እዚህ ስፍራ " ጅረቶች እንዳይወርዱ" የሚለው ጅረቶችን ማገድ ወይም እንዳይፈሱ መከልከል ማለት ነው። "እርሱ ጅረቶች እንዳይወርዱ ያግዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በዚያ የተደበቀው
ይህ የሚያመለክተው ሰዎች ከምድር በታች ወይም ከውሃ ስር በመሆናቸው ምክንያት ሊመለከቱ የማይችሉትን ነገር ነው።
Job 28:12
አጠቃላይ መረጃ፡
በኢዮብ 28:12-28 እውቀት እና ግንዛቤ ማግኘት በአንድ ስፍራ የሚገኙ እና ሰዎች የሚፈልጓቸው ውድ ሀብቶች እንደሆኑ ተደርጎ ተገልጽዋል። እውቀት እና ግንዛቤ ማግኘት የሚወክሉት ብልህ መሆንንና ነገሮችን በሚገባ መረዳትን መማርን ነው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጥበብ ከወዴት ይገኛል? የመረዳትስ ስፍራው የት ነው?
እነዚህ ጥያቄዎች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ የዋሉትም ጥበብን እና መረዳትን ማግኘት በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ለማሳየት ነው። "ጥበብን እና መረዳትን ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
ጥበብ ከወዴት ይገኛል?የመረዳትስ ስፍራው የት ነው?
ብልህ መሆን እና ግንዛቤ ማግኘት የተገለጹት ጥበብን እና መረዳትን እንደ ማግኘት ተደርጎ ነው። "ሰዎች ብልህ የሚሆኑት እንዴት ነው? ሰዎች ነገሮችን በሚገባ መረዳት የሚችሉት እንዴት ነው?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሰው ዋጋዋን አያውቅም
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጥበብ የተገለጸችው ሰዎች ሊገዟት እንደሚችሉት ነገር ተደርጋ ነው። "ሰዎች የሚረባው ምን እንደሆነ አያውቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) "ዋጋ" ተብሎ የተተረጎመው ቃል "ስፍራ" ማለት ነው። "ሰዎች የት እንደምትገኝ አያውቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በህያዋን ምድር አትገኝም
"እናም በህያዋን ምድር አትገኝም።" የህያዋን ምድር" የሚለው የሚያመለክተው ሰዎች የሚኖሩበትን ይህንን ምድር ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እናም ማንም በዚህ ምድር ጥበብን ሊያገኝ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ጥልቅ ውኆች... 'በእኔ ውስጥ አትገኝም' ይላሉ፤ ባህር 'በእኔ ውስጥ አትገኝም' ይላል።
ጥልቅ ውኆች እና ባህር የቀረቡት መናገር እንደሚችል ሰው ተደርገው ነው። "ጥበብ ከምድር በታች ባለው በጥልቅ ውኆች ውስጥ አትገኝም፣ አሊያም በባህር ውስጥ አይደለችም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 28:15
በወርቅ አትገኝም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ይህ የሚያመለክተው ጥበብ ከወርቅ ይልቅ ጠቃሚ እንደሆነ ነው። "ሰዎች እውቀትን በወርቅ መግዛት አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ብር ዋጋዋ ተደርጎ ሊመዘንላት አይችልም
ይህ የሚያመለክተው ጥበብ ከብር ይልቅ ጠቃሚነት እንዳላት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ለእውቀት በቂየሆነ ብር መክፈል/መመዘን አይቻላቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ዋጋዋ በሰንፔር... ሊመዘን/ሊለካ አይችልም
ይህ የሚያመለክተው ጥበብ ከኦፊር ወርቅ፣ ከከበረ መረግድና ሰንፔርና የበለጠ ዋጋ እንዳላት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ኦፊር
ይህ የተጣራ ወርቅ የሚገኝበት ምድር ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
መረግድ የከበረ ድንጋይ
ጥቁር የከበረ ድንጋይ
ሰንፔር
ሰማያዊ የከበረ ድንጋይ
ወርቅ እና አብረቅራቂ መአድን/ብርሌ የእርሷን ያህል ዋጋ የላቸውም
ይህ የሚያመለክተው ጥበብ ከወርቅ እና ከከበረ ድንጋይ/አብረቅራቂ መአድን እጅግ እንደምትበልጥ ነው
የከበረ ድንጋይአብረቅራቂ መአድን/ብርሌ
ዋጋ ያለው የከበረ እንደ ብርጭቆ ንጹህ ቀለም ያለው ድንጋይ
በጠራ ወርቅ በተሰራ ጌጥም ቢሆን ልትለወጥ አትችልም
"እናም በጠራ ወርቅ በተሰራ ጌጥ አትለወጥም።" ይህ የሚያመለክተው ጥበብ በጠራ ወርቅ ከተሰራ ጌጥ የሚበልጥ ዋጋ ያላት መሆኑን ነው።
መለወጥ/መቀየር
"መነገድ"
Job 28:18
ዛጎል፣ ኢያስፔር እና አልማዝ ከእርሷ ጋር አይስተካከሉም
"እርሷን ከዛጎል እና ሰንፔር ጋር ማነጻጸር አይቻልም" ይህ የሚያመለክተው ጥበብ ከዛጎል እና ኢያስፔር እጅግ እንደምትበልጥ ነው፤ ስለዚህም ኢዮብ ስለነዚህ ነገሮች መናገር አላስፈለገውም። "ስለ ዛጎል ወይም ኢያስፔር መናገር አያስፈልገኝም" ወይም "ዛጎል፣ ኢያስፔር እና አልማዝ ከጥበብ ጋር ሲነጻጸሩ እርባና እንደሌለው ነገር ይቆጠራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ዛጎል

ይህ ውብ የሆነ፣ ጠንካራ እና በውቅያኖስ ዳርቻ የሚገኝ ቁስ ነው።

ኦፊር…ቀይ እንቁ…ቶጳዝዮን

እነዚህ የከበሩ ድንጋዮች/ማዕድናት ናቸው

የኩሽ ቶጳዝዮን አይስተካከሏትም

ይህሚያመለክተው ጥበብ ምርጥ ከተባለው ቶጳዝዮን እንደምትሻል ነው

ከንጹህ ወርቅ ጋርም ልትመዘን/ዋጋዋ ሊተመን አይችልም

"እናም ጥበብ በንጹህ ወርቅ ዋጋዋ ሊለካ አይችልም።" ይህ ጥበብ ከንጹህ ወርቅ እጅግ እንደምትበልጥ ያሳያል።

Job 28:20

ታዲያ ጥበብ ከወዴት ትገኛለች? የእውቀትስ ስፍራዋ የት ነው?

ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠቀመው ሰዎች ጥበብን እና እውቀትን ሰዎች ከየት እንደሚያገኙ ለመናገር ነው። "ጥበብ ከየት እንደምትገኝ እነግራችኋለሁ ደግሞም እውቀት ከወዴት እንደሆነች አስታውቃችኋል።" ወይም "እንዴት ጥበበኛ መሆን እንደሚቻል እንደዚሁም ደግሞ እንዴት ነገሮችን መረዳት እንደሚቻል እነግራችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ጥበብ ከወዴት ትገኛለች

ጥበብ የተገለጸችው በአንድ ስፍራ እንደሆነችና ወደ ሰዎች እንደምትመጣ ተደርጎ ነው። የእርሷ መምጣት የሚወክለው ሰዎች ብልህ ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የመረዳት/እውቀት ስፍራዋ የት ነው

መረዳት/እውቀት የተገለጸችው በአንድ ስፍራ እንደምትገኝ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጥብብ ከህያዋን ዐይኖች ሁሉ ተሰውራለች

ይህ ማለት ህያዋን ነገሮች ጥበብን ማየት አልቻሉም ማለት። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማናቸውም ህያው ነገር ጥበብን ማየት/ማግኘት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከሰማይ ወፎች ተደብቃ ተቀምጣለች

ይህ ማለት ወፎች ጥበብን ማየት አይችሉም ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በሰማያት የሚበሩ ወፎች እንኳን ጥበብን ማየት አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥፋት እና ሞት እንዲህ ይላሉ

እዚህ ስፍራ "ጥፋት" እና "ሞት" መናገር የሚችሉ ነገሮች ተደርገው ቀርበዋል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 28:23

እግዚአብሔር የእርሷን መንገድ ያውቃል፤ እርሱ ስፍራዋን ያውቃል

ጥበብ የተገለጸችው በአንድ ስፍራ እንደምትገኝ ተደርጎ ነው። "እግዚአብሔር ጥበብ እንዴት እንደምትገኝ ያውቃል። እርሱ ጥበብ የት እንዳለች ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የምድራ ዳርቻ

"የምድር የመጨረሻው ሩቅ ስፍራ"

ውኆችን ይሰፍራል

ይህ የሚገልጸው እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ስፍራ መገኘት ያለበትን የውሃ መጠን የወሰነ መሆኑን ነው። ይህ ለመወሰን የሚያመለክተው አማራጭ ትርጉም 1) በእያንዳንዱ ደመና ምን ያህል ዝናብ መገኘት እንዳለበት ወይም 2) በእያንዳንዱ ባህር የሚገኘውን ውሃ መጠን። "በእያንዳንዱ ስፍራ የሚኖረውን ውሃ ወስኗል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 28:26

ለመብረቅ መንገድን

"እርሱ መብረቅ እንዴት መሰማት እንዳለበት ውስኗል" ወይም "እርሱ የመብረቅን መሄዳ ወስኗል"

እነሆ፣ እግዚአብሔርን መፍራት - ይህ ጥበብ ነው።

"ፍርሃት" የሚለው ረቂቅ ስም "ፈራ" ወይም "አከበረ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ጥበብ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠቢብ" በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። "አድምጡ፣ ጌታን ብትፈሩ ጥበበኛ ትሆናላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከክፉ መራቅ ጥበብ/መረዳት ነው

እዚህ ስፍራ "ከክፉ መለየት" ክፉ ነገሮችን ለማድረግ እሻፈረኝ ማለት ነው። "መረዳት" የሚለው ረቂቅ ስም "ተረዳ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ክፉ ማድረግን ባትፈቅድ፣ ከዚያ በኋላ ብዙ ነገሮችን ትገነዘባለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 29

Job 29:1

አወይ፣ ምነው ባለፉት ወራት እንደነበርኩት በሆንኩ ኖሮ

ኢዮብ ይህንን አጋኖ የተጠቀመው ምኞትን ለመግለጽ ነው። "በቀደሙት ወራት እንደነበርኩት ብሆን በወደድኩ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ብርሃን በእኔ ራስ ላይ ሲበራ

የእግዚአብሔር ብርሃን በኢዮብ ላይ ማብራቱ የሚወክለው እግዚአብሔር ኢዮብን ያለውን መባረኩን ነው። "የእግዚአብሔር በረከት እንደ መብራት በላዬ በሚያበራበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ብርሃን በጨለማ ውስጥ በማልፍበት ጊዜ

በጨለማ ውስጥ ማለፍ የሚወክለው አስቸጋሪ ሁኔታን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:4

በመልካም ቀናቶቼ/በአጨዳ ቀናቶቼ

ኢዮብ ጠንካራ እና ወጣት ስለነበረበት ጊዜ የተናገረው እነዚያን ጊዜያት አዝመራ እንደሚታጨድበት ጊዜ አድርጎ ነው። "ወጣትና ጠንካራ በነበርኩበት ወቅት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ወዳጅነት በጎጆዬ በነበሩበት ወቅት

"ወዳጅነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ወዳጅ" በሚለው ስም ሊገለጽ ይችላል። "ጎጆ" የሚለው ቃል የኢዮብን ቤት ይወክላል። "እግዚአብሔር የእኔ ወዳጅ በነበረበት እና እኔን በሚጠብቅበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

መንገዴ በቅባት/ወተት እና የወተት ተዋጽኦ በተሸፈነበት ጊዜ

"መንገዴ በቅባት በተጥለቀለቀ ጊዜ" ኢዮብ ይህንን አጋኖ የተጠቀመው ብዙ ላሞች እንደመበሩት እና ላሞቹ ለእርሱ እና ለቤተሰቡ ከሚያስፈልገው ያለፈ ብዙ ቅባት ይሰጡት እንደነበረ ለመግለጽ ነው። "ላሞቼ እጅግ የበዛ ቅባት ይሰጡኝ በነበረ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሽት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚለውን ይመልከቱ)

ደግሞም አለቱ የዘይት ፈሳሽ ይሰጠኝ ነበር

"ደግሞም አለቱ የዘይት ፈሳሽ ይሰጠኝ ነበር።" ኢዮብ ይህንን አጋኖ የተጠቀመው ብዙ የወይራ ተክል እንደነበረው እና ብዙ የወይራ ዘይት ያመርት እንደነበር ለመግለጽ ነው። አለቱ አገልጋዮቹ ከወይራ ፍሬ ዘይት ይጨምቁበት የነበረበት ስፍራ ነው። "አገልጋዮቼ እጅግ ብዙ የወይራ ዘይት ይጨምቁ በነበረበት ጊዜ" ወይም "ዘይት እንደ ወንዝ ዘይት ከሚጨመቅበት አለት ይፈስ በነበረበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሽት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:7

የከተማ አደባባይ

ይህ በመንደር ወይም በከተማ ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ የበለጡ መንገዶች የሚገናኙበት ስፍራ ነው።

ለእኔ ተነስተው ይቆሙ ነበር

ይህ የአክብሮት ምልክት ነው። ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ለእኔ በአክብሮት ተነስተው ይቆሙ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:9

ልዑላን እኔ ስመጣ ንግግራቸውን ያቋርጡ ነበር

ይህ የአክብሮት ምልክት ነበር። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

እጃቸውን በአፋቸው ላይ ይጭኑ ነበር

ይህን የሚያደርጉት እንደማይናገሩ ለማሳየት ነው። ይህ ለኢዮብ ያላቸውን አክብሮት የሚያሳዩበት ምልክት ነበር። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የተከበሩ ሰዎች ድምጽ ጭጭ ይል ነበር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የተከበሩ ሰዎች ጸጥ ይሉ ነበር" ወይም

"የተከበሩ ሰዎች መናገራቸውን ያቆሙ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምላሳቸው ከትናጋቸው ጋር ይጣበቅ ነበር

ይህ እነርሱ ለኢዮብ ካላቸው እጅግ ከፍ ያለ አክብሮት የተነሳ አንዳች የሚናገሩት ነገር እንዳልነበረ ያሳያል፡፡ "መናገር የማይችሉ ሆኖ ይሰማቸው ነበር" ወይም "አንዳች የሚሉት አልነበራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:11

ጆሯቸው እኔን ካደመጠ በኋላ ... ዐይናቸው እኔን ካደመጠ በኋላ

ጆሮዎች የሚለው የሚወክለው እርሱን የሰሙትን ሰዎች ሲሆን፣ ዐይኖች የሚለው ደግሞ የሚወክለው እርሱን ያዩተን ሰዎች ነው፡፡ "የነገርኳቸውን ከሰሙ በኋላ... እኔን ከተመለከቱ በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ ምስክርነት ይሰጡ፤ ደግሞም ያልኩትን ይቀበሉ ነበር

"የተናገርኩት ትክክል ነው በማለት ይመሰክሩ ነበር"

ድሃው ሲጮህ ካለበት ሁኔታ አወጣው ነበር

እዚህ ስፍራ "ድሃ የሆነው/ድሃው" የሚለው የሚያመለክተው ማንኛውንም ድሃ ሰው ነው፡፡ "ድሆች ሲጮሁ ደርሼ ካሉበት ችግር አወጣቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (የስማዊ ሀረግ ክፍል የሚለውን ይመልከቱ)

በሞት አፋፍ ላይ የደረሰው መርቆኛል

የአንድ ሰው ምርቃት/በረከት ወደ ሌላው መድረሱ የሚወክለው ያ ሰው ሌላውን መባረኩን ነው፡፡ "ሞት አፋፍ ላይ ደርሶ ነበረው ስረዳው ይባርከኝ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሞት አፋፍ ላይ የደረሰው/ለመጥፋት የተቃረበው

ይህ የሚወክለው ለሞት የተቃረበውን ማናቸውንም ሰው ነው፡፡ "ለሞቱ የተቃረቡ/ በሞት አፋፍ ላይ ያሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (የስማዊ ሀረግ ክፍል የሚለውን ይመልከቱ)

የመበለቶች ልብ በሀሴት እንዲዘምር አድርጌያለሁ

እዚህ ስፍራ "የመበለቶች ልብ" የሚለው የሚወክለው ማንኛይቱንም መበለት ነው፡፡ "መበለቶች በደስታ እንዲዘምሩ ምክንያት ሆኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና የስማዊ ሀረግ ክፍል የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 29:14

ጽድቄን አበዛለሁ፤እንደልብስ ይሸፍነኛል

ብዙውን ጊዜ ሰዎች ጽድቅን እንደ ልብስ አድርገው ይገልጽዋታል፡፡ "ጽድቅ የሆነውን አደርግ ነበር፣ እርሷም ለእኔ እንደ ምለብሰው ልብስ ነበረች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርዴ እንደ ልብስ እና እንደ ጥምጥም ነበረች

ብዙውን ጊዜ ሰዎች ጽድቅን እንደ ልብስ አድርገው ይገልጽዋታል፡፡ "ትክክል የሆነውን አደርግ ነበር፣ ፍትህ በእኔ ላይ እንደ ልብስ እና እንደ ጥምጥም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤያዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥምጥም

ወንዶች በራሳቸው ላይ የሚጠመጥሙት እና እንደ ኮፍያ የሚያደርጉት ረጅም ጨርቅ

ለዐይነ ስውራን ዐይን ነበርኩ

ይህ የሚወክለው ዐይነ ስውር የሆኑ ሰዎችን መርዳትን ነው፡፡ "ለዐይነ ስውራን ዐይን ነበርኩ" ወይም "ዐይነ ስውራንን እመራ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንካሶች እግር ነበርኩ

ይህ አካል ጉዳተኞችን መርዳትን ያመለክታል፡፡ "ለአንካሶች እግር ነበርኩ" ወይም "አንካሶችን እደግፍ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለችግረኞች አባት ነበርኩ

እዚህ ስፍራ "አባት ነበርኩ" የሚለው የሚወክለው ለሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ማቅረብን ነው፡፡ "አባት ለልጆቹ የሚያስፈልጋቸውን እንደሚያቀርብ ለችግረኞች አቀርብላቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:17

አጠቃላይ መረጃ:

ከቁጥር/ስንኝ 18-20 ባለው ክፍል ኢዮብ በእርሱ ላይ መከራ ከመድረሱ በፊት ይናገራቸው ስለነበሩ ነገሮች ይገልጻል፡፡

የ... መንጋጋ እሰብር ነበር፣ ...ምርኮኞችን ነጻ አወጣ ነበር

ኢዮብ ኃጢአተኞችን በጥርሳቸው ያደኑትን እንደሚነክሱ የዱር አራዊት ይገልጻቸዋል፡፡ "አንድ ሰው የዱር አውሬን መንጋጋ ሰብሮ ያደነውን ከጥርሶቹ መሃል እንደሚያስጥለው፣ እኔም ኃጢአተኞች ሰዎችን እንዳያሳድዱ እከለክላቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በጎጆዬ ውስጥ እሞታለሁ

እዚህ ስፍራ "ጎጆ" የሚወክለው የኢዮብን ቤት እና ቤተሰብ ነው፡፡ ኢዮብ እርሱን እንደ ወፍ ልጆቹን ደግሞ እንደ ወፍ ጫጩቶች አድርጎ ይናገራል፡፡ "ከቤተሰቦቼ ጋር በቤቴ ውስጥ እሞታለሁ" ወይም "በቤቴ በሰላም እሞታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እድሜዬን እንደ ምድር አሸዋ አበዛለሁ

በወንዝ ዳርቻ ማንም ሊቆጥረው የማይችለው አሸዋ አለ፡፡ ማንም ሊቆጥረው ከሚችለው በላይ እድሜ እኖራለሁ ማለቱ ረጅም እድሜ እንደሚኖር አጋኖ መናገሩ ነው፡፡ "በጣም ዘመን እኖራለሁ" ወይም "ብዙ አመታት እኖራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት እንዲሁም ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእኔ ስር... የእና ቅርንጫፍ

ኢዮብ ስለ ጥንካሬው በሚገባ ውሃ እንዳገኘ ዛፍ አድርጎ ይናገር ነበር፡፡ በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:20

በውስጤ ያለው ክብር ሁሌም አዲስ ነው

" ክብር" የሚለው ረቂቅ ስም "ከበረ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ እዚህ ስፍራ "አዲስ/ትኩስ" የሚለው የሚወክለው ያለማቋረጥ የሚሰጥን ክብር ነው፡፡ "ሰዎች ሁሌም/ሳያቋርጡ ክብር ይሰጡኝ ነበር" ወይም "ሰዎች ሁሌም ያከብሩኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእጄ ያለው ቀስት ሁሌም በእጄ ላይ አዲስ ነው

አዲስ ቀስት በጣም ጠንካራ ነው፡፡ የኢዮብ በእጁ የሚገኘው ቀስት ጥንካሬ የሚወክለው የእርሱን አካላዊ ብርታት ነው፡፡ "እኔ ሁልጊዜም እንደ አዲስ ቀስት ጠንካራ ነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ንግግሬ እንደ ውሃ በላያቸው ይንጠባጠባል

እዚህ ስፍራ "እንደ ውሃ በላያቸው ይንጠባጠባል" የሚለው የሚወክለው እርሱን የሚሰሙ ሰዎች መታደሳቸውን ነው፡፡ "ንግግር" የሚለው ረቂቅ ስም "ተናገረ" ወይም "አለ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ውሃ ሲፈስበት የሰዎች አካል እንደሚታደስ ንግግሬ ልባቸውን ደስ ያሰኝ ነበር" ወይም "እኔ እምናገራቸው ነገር በአካላቸው እንደሚፈስ ውሃ ያድሳቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 29:23

ዝናብን እንደሚጠባበቅ ንግግሬን ይጠባበቁ ነበር

ሰዎች ኢዮብን በትግስት ይጠባበቁት ነበር፤ ደግሞም ከእርሱ መልካም ነገርን ለመስማት ይጠባበቁ ነበር፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእኔ ቃላት ለመጠጣት አፋቸውን በሰፊው ይከፍታሉ

ይህ የሚወክለው ኢዮብ ከሚናገረው ተጠቃሚ ለመሆን በጉጉት መጠባበቅን ነው፡፡ "ከምናገረው ለመጠቀም እኔ እስከምናገር ድረስ በጉጉት ይጠባበቁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የኋለኛውን ዝናብ እንደሚጠባበቁ

"ገበሬዎች የኋለኛውን ዝናብ በጉጉት እንደሚጠባበቁ"

የኋለኛው ዝናብ

ይህ ዝናብ የሌለበት/ደረቅ ወቅት ከመግባቱ አስቀድሞ የሚዘንበውን ብዙ መጠን ያለውን ዝናብ ያመለክታል፡፡

ፈገግ እልላቸው/እስቅላቸው ነበር

ፈገግ የሚልበት ምክንያት እነርሱን ለማበረታታት በመሆኑ፣ ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል፡፡ "እነርሱን ለማበረታታት ፈገግ እልላቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የፊቴ ብርሃን

ይህ የሚወክለው በኢዮብ ገጽ ላይ የሚመለከቱትን ደግነት ነው፡፡ በሚለው ውስጥ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 29:25

መንገዳቸውን እመርጥላቸው ነበር

እዚህ ስፍራ "መንገዳቸውን እመርጥላቸው" የሚለው የሚገልጸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው መወሰንን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አለቃቸው ሆኜ እቀመጥ ነበር

እዚህ ስፍራ "መቀመጥ" የሚወክለው መግዛትን ወይም መምራትን ነው። አለቆች ከፍ ያለ ውስኔ የሚሰጡት ተቀምጠው ነው። "አለቃቸው ሆኜ እመራቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አለቃቸው ሆኜ እቀመጥ ነበር

ኢዮብ የእነርሱ አለቃ ነበር። "አለቃቸው ስለነበርኩ እመራቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰራዊቱ መሃል እንደሚገኝ ንጉሥ አኖር ነበር

ኢዮብ ሰዎቹን እንዴት ይመራ እንደነበር፤ ራሳቸውን እንደ ሰራዊቱ፣ እርሱንም እንዴት እንደ ንጉሳቸው ያህል ቆጥረው ይታዘዙት እንደነበር ይናገራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤያዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ያዘኑትን አጽናና ነበር

ይህ ሀረግ ኢዮብ በእርግጥ ሰዎችን ያጽናና ነበር ማለት ነው። "ባዘኑ ጊዜ አጽናናቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 30

Job 30:1

በእኔ ላይ ይሳለቃሉ

"መሳለቅ" የሚለው ረቂቅ ስም "ተሳለቁ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "በእኔ ላይ ተሳለቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አባቶቻቸው መንጋዎቼን ከሚጠብቁ ውሾች ጋር እንዲቀመጠ/እንዲሰሩ እንኳን ያላፈቀድኩላቸው

ይህ የሚያመለክተው እነዚያን አባቶች ምን ያህል ይንቃቸው እንደነበረ ነው። መንጎቼን ከሚጠብቁ ከውሾቹ ጋር ለመሆን እንኳን የሚበቁ አልነበሩም። "እኔ የናቅኳቸው አባቶቻቸው፤ ከመንጎቼ ውሾቼ ጋር እንዲሆኑ ያልፈቀድኩላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የመንጎቼ ውሾች

ውሾቹ ከመንጎቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "መንጎቼን የሚጠብቁ ውሾች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርግጥ፣ የአባቶቻቸው እጆች ጥንካሬ፣ እንዴት እኔን ሊያግዝ ይችላል... አልጠፋምን?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት በእነዚያ ሰዎች ጥንካሬ ላይ ለማፌዝ ነው። "የአባቶቻቸው ክንዶች ጥንካሬ ሊረዳኝ አልቻለም... ጠፍቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የብስለት እድሜ ሃይላቸው የጠፋባቸው ሰዎች

የሃይላቸው መጥፋት ከእንግዲህ እየደከሙ እንጂ እየበረቱ እንደማይሄዱ የመሚገልጽ ዘይቤ ነው። "የብስለት እድሜ" የሚለው ማርጀታቸውን ያመለክታል። "ያረጁ እና ሀይላቸው የደከመ ሰዎች" ወይም "ያረጁ እና የደከሙ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከድህነት እና ከረሀብ የተነሳ ከስተዋል

"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሚያላግጡ/የሚቀልዱ ወጣቶችን አባቶች ነው።

ከድህነት እና ከረሀብ የተነሳ ከስተዋል

"ረሃብ" የሚለው ረቂቅ ስም "ድሃ" በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። "ረሃብ" የሚለው ረቂቅ ስም "መራብ" ወይም "ችጋር" በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። "በጣም ከሲታ የነበሩት ድሆች እና የተራቡ ስለነበሩ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በደረቁ ምድር ላይ ያገኙትን ይቆረጣጥማሉ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ደረቅ ምድር" በደረቅ ምድር ላይ የሚበቅሉ ደረቅ ስሮች ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። "ከምድር ያገኙትን ደረቅ ስራስሮችን ይቆረጣጥማሉ" ወይም2) "ከደረቁ መሬት ላይ ያገኙትን ይቆረጣጥማሉ/ይበላሉ" የሚለው በደረቁ ምድር ያገኙትን ለመመገባቸው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 30:4

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ስለሚሳለቁበት ሰዎች አባቶች መናገሩን ቀጥሏል በረሃብ ጊዜ ብቻ የሚበላ ጨው ጨው የሚል ተክል... የቁጥቋጦ ቅጠል... የክትክታ ዛፍ/ችፍርግ እነዚህ ሰዎች ሌላ የሚበላ ነገር ባጡ ጊዜ የሚበሏቸው ቅጠላቅጠሎች ናቸው።

የክትክታ ስር ምግባቸው ነበር

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰዎች የክትክታ ቅጠል/ችፍርግ ይበሉ ነበር ወይም 2) ሰዎች የክትክታ ስራ ስሮችን በማንደድ ይሞቁ/ሙቀት ያገኙ ነበር

እንደ ሌባ... እየተከታተሉ ከሚጮሁባቸው ሰዎች ይሸሹ ነበር

"ይሸሹ ነበር" የሚለው ሀረግ "ለመሸሽ ይገደዱ ነበር" ማለት ነው። ይህ ሀረግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች እንደ ሌባ እያባረሩ ይጮሁባቸው ነበር... ደግሞም ለቀው እንዲሄዱ ያስገድዷቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው ሌባን እንደሚያበርር እየጮሁ ያሳድዷቸው ነበር

"ሌባ የሆኑ ያህል ይጮሁባቸው ነበር"

Job 30:7

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ ስለሚሳለቁበት ሰዎች አባቶች መናገሩን ቀጥሏል

እንደ አህዮች ያናፉ ነበር

ኢዮብ በረሃብ ይጮሁ የነበሩ ሰዎችን ከፍ ያለ ድምጽ እንደሚያሰሙ የሜዳ አህዮች ይገልጻቸዋል። "ከረሃባቸው የተነሳ እንደ ሜዳ አህያ ይጮሁ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤያዊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሳማ ስር በአንድነት ይሰባሰቡ ነበር

"ሳማ" ሹል እሾህ ያለው እጅብ ብሎ የሚበቅል ተክል ነው። ይህ የሚያመለክተው ቤት እንደሌላቸው ነው።

የማይረቡ ሰዎች ልጆች ናቸው

እዚህ ስፍራ "የማርረቡ ሰዎች ልጆች" የሚለው የሚገልጸው የማይረባ/ጅል ባህሪይ እንዳላቸው ነው። "እንደ ጅሎች ነበሩ" ወይም "ሞኞች ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእርግጥ፣ ስም የለሽ ሰዎች ልጆች ነበሩ

"በእርግጥ" የሚለው ቃል ቀጥሎ የሚመጣውን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው። እዚህ ስፍራ " የስም የለሽ ሰዎች ልጆች" የሚለው የሚገልጸው ስም እዚህ ግባ የሚባል ባህሪ እንዳሌላቸው ነው። "በእርግጥ፣ የሚረቡ ሰዎች አልነበሩም" ወይም "በእርግጥ፣ እርባና ቢስ ሰዎች ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስም የለሽ ሰዎች

እዚህ ስፍራ "ስም የለሽ" የሚለው የሚገልጸው አንዳች ክብር ወይም ከበሬታ የሌለው ማለት ነው። ይህ ማለት እርባና ቢስ ነበሩ ማለት ነው። "እርባና ቢስ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአለንጋ እየተገረፉ ከምድሪቱ ይባረሩ ነበር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አለንጋ የሚለው እንደ ወንጀለኛ ይቀጡ እንደነበር ያመለክታል። "ሰዎች እንደ ወንጀለኞች ይመለከቷቸው እና ከአገራቸው በግድ ያስወጧቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ሰዎች በአለንጋ እየገረፉ በግድ ያስወጧቸው ነበር። "ሰዎች ይገርፏቸው እና ምድሪቱን ለቀው እንዲወጡ ያስገድዷቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከምድሪቱ ይባረሩ ነበር

እዚህ ስፍራ "ምድሪቱ" የሚለው የሚያመለክተው ወደ በረሃ ከመሰደዳቸው አስቀድሞ የሚኖሩበትን ምድር ነው።

Job 30:9

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ እንደገና ስለሚሳለቁበት ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል ነገር ግን አሁን ለሚያንጓጥጥ ዘፈናቸው ሆኛለሁ "ዘፈን" የሚለው ረቂቅ ስም "ዘፈነ" በሚል ግስ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሊገለጽ ይችላል። "በእኔ ላይ ለማንጓጠጥ ይዘፍናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ መተረቻ ሆኛለሁ

እዚህ ስፍራ "መተረቻ" የሚለው ሰዎች በጭከና ለማፌዛቸው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። "አሁን እነርሱ በጭካኔ የሚዘባበቱብኝ ሆኛለሁ" ወይም "ስለ እኔ በፌዝ ጭካኔ የተሞላበት ነገር ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቴ ላይ ምራቃቸውን ጢቅ ለማለት ወደኋላ አይሉም

ይህ በአዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በፊቴ ላይ እንኳን ይተፉብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምጸት የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ከእኔ ቀስቴን ሰብሮታል

የተሰበረ ቀስት ጥቅም የለውም። "ቀስቴን ሰብሮታል" የሚለው ሀረግ ኢዮብን አቅመቢስ ስለ ማድረግ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "እግዚአብሔር እራሴን እንዳልከላከል አቅሜን ከእኔ ወስዶታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ላይ የሚያላግጡት

"በእኔ የሚቀልዱ"

በፊቴ ያለገደብ ክፉ ያደርጋሉ

ገደብ አንድ ሰው በነጻነት እንዳይንቀሳቀስ እና የሚፈልገውን እንዳያደርግ ያግዳል። እዚህ ስፍራ "መቆጠብ" የሚለው የሚገልጸው አንድ ነገር ከማድረግ መገታተትን፣ ሲሆን "ገደብን መስበር" የሚለው ደግሞ አንድ ነገር ከማድረግ አለመከልከልን ነው። በዚህ ሁኔታ ፌዘኞቹ በኢዮብ ላይ ክፉ ነገርን ከማድረግ አልተቆጠቡም። "ለእኔ ክፉ ከመሆን አልተገቱም" ወይም "በእኔ ላይ ማድረግ የሚፈልጉትን የጭካኔ ተግባር ሁሉ ያደርጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 30:12

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ እንደገና ስለሚሳለቁበት ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢዮብ ክፉ የሚያደርጉበትን ፌዘኞች በቡድን እንደሆኑ እና እንደ ሰራዊት በአንድላይ ሆነው እንደሚያጠቁት አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በቀኜ ጆሌዎች ተነሱብኝ

"በቀኜ ጆሌዎች ተነሱብኝ" የሚለው በሚከተሉት መንገዶች ሊተረጎም ይችላል 1) በኢዮብ ቀኝ እጅ ላይ መነሳት በእርሱ ጥንካሬ ላይ መነሳትን ሊወክል ይችላል። "ወሮበሎች አቅሜን መቱት/አጠቁኝ" ወይም በኢዮብ ቀኝ እጅ ላይ መነሳት የእርሱን ክብር ማጥቃትን ይወክላል። "ጆሌው ክብሬን አጠፋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

አሳደዱኝ

"እንድሸሽ አስገደዱኝ"

የዐፈር ድልድል አዘጋጁብኝ

ሰራዊት አንዲትን ከተማ በቅጥሯ ላይ ተንጠላጥሎ ወጥቶ ለማጥቃት በቅጥሩ ስር አፈር ይከምራል። ኢዮብ በእርሱ ላይ የሚያፌዙት እንዲህ ያለ ነገር እንዳደረጉ ይናገራል። "ሰራዊት አንዲትን ከተማ ለማጥቃት እንደሚዘጋጅ እነርሱ እኔን ለማጥቃት ተዘጋጁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዴን ደመሰሱ

ይህ የሚገልጸው ኢዮብ ከጥቃታቸው እንዳያመልጥ ማድረጋቸውን ነው። "ከእነርሱ እንዳላመልጥ ከለከሉኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጥፋትን ወደ እኔ አመጡ

እዚህ ስፍራ "ክፋትን ማምጣት" የሚለው የሚገልጸው ጥፋት እንደሆን ማድረግን ነው። "በእኔ ላይ ጥፋት እንዲደርስ ተጣጣሩ" ወይም "እኔን ለማጥፋት ሞከሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም ሊያግዳቸው/ወደ ኋላ ሊመልሳቸው የማይችላቸው ሰዎች

እዚህ ስፍራ "ወደ ኋላ መመለስ/ማገድ" የሚለው የሚገልጸው አንድ ነገር እንዳያደርጉ እነርሱን መከልከልን/ማስቆምን ነው። "እኔን ከማጥቃት ማንም የማያስቆማቸው ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 30:14

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢዮብ እንደገና ስለሚሳለቁበት ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢዮብ ክፉ የሚያደርጉበትን ፌዘኞች በቡድን እንደሆኑ እና እንደ ሰራዊት በአንድላይ ሆነው እንደሚያጠቁት አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንዲት ከተማ ትልቅ የቅጥር ፍራሽ/ብስ አልፎ እንደሚገባ ሰራዊት በእኔ ላይ መጡብኝ

ይህ የሚገልጸው ኢዮብን በሃይል ማጥቃታቸውን ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በላዬ በሃይል መጡብኝ

ይህ የሚገልጸው ታላቅ የውቅያኖስ ማዕበል በእርሱ ላይ እንደመጣበት ብዙ ሆነው በአንድነት መጥተው እንዳጠቁት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርሃት በላዬ ወረደ/መጣ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ እጅግ ፈራ ወይም 2) ኢዮብ እንዲፈራ የሚያደርጉ ነገሮች እየሆኑ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በነፋስ ተጠርጎ እንሚወሰድ ክብሬ ተወሰደ

ኢዮብ ነፋስ በድንገት ጠርጎ እንደወሰደው ነገር ክብሩ ከእርሱ መወሰዱን ይናገራል። "ማንም እኔን አያከብርም" ወይም "እኔ አሁን ማንም የማያከብረው ሰው ሆኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብልጽግናዬ/ሀብቴ እንደ ደመና አለፈ

ኢዮብ የሃብቱን መጥፋት በነፋስ እንደተጠረገ ደመና ይገልጻል። እዚህ ስፍራ "ሀብት/ብልጽግና" ደህንነትን ወይም ጥበቃን ሊያመለክት ይችላል። "ከእንግዲህ አንዳች የለኝም" ወይም "ከእንግዲህ ሰላም አይደለሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 30:16

አሁን ህይወቴ ከውስጤ ይፈሳል

ኢዮብ ህይወቱ ፈሳሽ እንደሆነ እና አካሉን ህይወቱን እንደያዘ እቃ/መያዣ አድርጎ ይገልጻል። መሞቻው እንደደረሰ ይሰማዋል። "አሁን እሞትኩ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ የመከራ ቀናት ይዘውኛል

ኢዮብ የማያቆርጥ መከራውን የሚገልጸው የመከራ ቀናቱ እርሱን አንቀው እንደያዙት አድርጎ ነው። "ለብዙ ቀናት ተሰቃየሁ፣ መከራው ግን አላበቃም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጤ አጥንቴ ይወጋኛል

ኢዮብ በአጥንቱ ውስጥ የሚሰማውን ስቃይ የሚገልጸው አጥንቶቱ እየተበሱ እንደሚገኙ አድርጎ ነው። "አጥንቶቼን እጅግ ይቆረጥመኛል" ወይም "በአጥንቶቼ ውስጥ እጅግ አስጨናቂ ስቃይ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ካለ ማቋረጥ ይቆረጥመኛል

ኢዮብ የማያቋርጥ ስቃዩን ህይወት እንዳለው እና እንደሚነክሰው ደግሞም ለማቆም እምቢ እንዳለ ነገር አድርጎ ይገልጸዋል። "የሚያሰቃየኝ መከራ አያቋርጥም" ወይም "በማያቋርጥ ስቃይ ውስጥ ነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 30:18

የእግዚአብሔር ታላቅ ሀይል በልብሴ አንቆ ይዞኛል

ኢዮብ፣ የእግዚአብሔር ሀይል አንዳች ነገር እያደረገ እንደሆነ እና እግዚአብሔር ሀይሉን እየተጠቀመ እንደሆነ ይናገራል። እዚህ ስፍራ "የእግዚአብሔር…ሀይል" የሚለው የቆመው/የሚገልጸው "እግዚአብሔርን" ነው። "እግዚአብሔር በታላቅ ሀይሉ በልብሴ አንቆ ይዞኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መከራው እንደ ሸሚዜ ኮሌታ ዙሪያዬን አንቆታል

የእግዚአብሔር ሀይል በኢዮብ ዙሪያ መጠምጠሙ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የኢዮብን መከራ ይወክላል/ይገልጻል። "ስቃዬ እግዚአብሔር በሸሚዜ ኮሌታ አንቆ የያዘኝን ያህል ነው" ወይም 2) ይህ የሚገልጸው እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ ብዙ መከራ እንዳደረሰበት ነው። "የሚሰማኝ እግዚአብሔር በታላቁ ሀይሉ በልብሴ አንቆ የያዘኝን ያህል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ወደ ጭቃ ውስጥ ወረወረኝ
ኢዮብ እግዚአብሔር አዋርዶኛል እያለ ነው። "ያደረገኝ ልክ ጭቃ ውስጥ የመጣልን ያህል ነው" ወይም "እርሱ፣ ጭቃ ውስጥ የተጣለን ሰው ያህል አዋርዶኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ አዋራ እና አመድ ሆንኩ
ይህ የሚገልጸው ኢዮብ የተሰማውን እርባና ቢስነት ነው። "እንደ አብዋራ እና አመድ ጥቅም የማይሰጥ ሰው ሆንኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 30:20
ጨካኝ
ይህ ቃል ደግነት የሌለው ማለት ነው
በክንድህ ጥንካሬ አሳደድከኝ
"እጅ" የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ሀይል ይገልጻል/ይወክላል። "በሀይልህ አሳደድከኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 30:22
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለእግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።
በነፋስ አነሳኸኝ... በማዕበል አናወጥከኝ
እነዚህ አገላለጾች የሚወክሉት እግዚአብሔር ኢዮብ ጸንቶ እንዲያልፍበት ያደረገውን እጅግ ከፍ ያለ መከራ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንዲያንገላታኝ አደረግህ
"ነፋሱ/ማዕበሉ እንዲገፋኝ አደረግህ"
ወደ ሞት ታደርሰኛለህ/ትገድለኛለህ
እዚህ ስፍራ "ወደ ሞት ታደርሰኛለህ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብ እንዲሞት ማድረጉን ነው። "እንድሞት ታደርጋለህ/ትገድለኛለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ህያው ለሆነው ሁሉ የተዘጋጀለት ቤት
ኢዮብ ይህ እግዚአብሔር ለህያዋን ነገሮች ሁሉ ይሄዱበት ዘንድ ያዘጋጀው ቤት ይህ እንደሆነ ስለ ሙታን ዓለም እየተናገረ ነው። "በህይወት የኖረ ሁሉ የሚሄድበት የሙታን ዓለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ህይወት ያለው ነገር ሁሉ
ይህ፣ አንድ ቀን የሚሞት ነገር ግን አሁን በህይወት ያለ ነገር ሁሉ።
Job 30:24
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢዮብ ለእግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።
ሲወድቅ እጆቹን አንስቶ የማይለምን አለን? በችግር የወደቀ ሰው ለእርዳታ አይጣራምን?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያነሳው/የሚጠቀመው ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር መጮሁ ተገቢ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። "ማንም ሰው በችግር ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር እጆቹን ያነሳል። በችግር ውስጥ የሚገኝ ሁሉ እርዳታ ለማግኘት ይጣራል።" ወይም "እኔ ወድቄያለሁ፣ ስለዚህ እርዳታውን ስለምነው እግዚአብሔር እንደተሳሳትኩ ሊመለከተኝ አይገባውም። እኔ በመከራ ውስጥ እገኛለሁ፣ ስለዚህም በእርግጥ እርዳታ ለማግኘት እጣራለሁ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በችግር ...እኔ አላለቅስምን? ሰው... አያዝንምን?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ለሌሎች ጥሩ ነገሮችን ያደርግ እንደነበረ ለመናገር ነው። "እኔ እንደማለቅስ አንተ ታውቃለህ... የተቸገረ እና ያዘነ...ሰው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
መልካምን ነገር ተስፋ ሳደርግ፣ ክፉ ደረሰብኝ
መልካምን መጠባበቅ የሚገልጸው መልካም ነገሮችን ተስፋ ማድረግን ነው፣ ደግሞም የክፉ መድረስ/መምጣት የሚወክለው ክፉ ነገሮች እንደሚሆኑ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ብርሃንን ተጠባበቅኩ... ጨለማ መጣብኝ/ሆነ
እዚህ ስፍራ "ብርሃን" የሚወክለው የእግዚአብሔርን በረከት እና ሞገስ ሲሆን "ጨለማ" ደግሞ የሚወክለው ችግርን እና መከራን ነው። "የእግዚአብሔርን ብርሃን በረከት ተጠባበቅሁ፣ ነገር ግን በምትኩ የጨለማ መከራ ደረሰብኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 30:27
ልቤ ተጨነቀ እረፍት አላገኘም
ኢዮብ ልቡ ሰው እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። "በልቤ ታወክሁ/ተጨነቅሁ፣ ደግሞም መከራው ማብቂያ የለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የመከራ ቀን መጣብኝ
የመከራ ቀን በኢዮብ ላይ መምጣቱ የሚወክለው ኢዮብ ለብዙ ቀናት በመከራ ውስጥ መቆየቱን ነው። "ለእያሌ ቀናት በመከራ ውስጥ ኖርኩ" ወይም "በየቀኑ መከራ ወረደብኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ኖርኩ/ቆየሁ
እዚህ ስፍራ "ኖርኩ/ቆየሁ" የሚለቀው የሚገልጸው በህይወት መቆየቱን ነው። "ኖርኩ" ወይም "አለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ፀሐይ ሳይመለከት፣ በጨለማ ውስጥ እንደሚኖር ሰው
እዚህ ስፍራ "በጨለማ ውስጥ መኖር" የሚለው አገላለጽ እጅግ ማዘንን የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ነገር ግን ፀሐይን ሳይመለከት" የሚለው ሀረግ "በጨለማ ውስጥ መኖር" የሚለውን ፀሐይ ባለመውጣቷ ምክንያት ጨለማው አለመፈጠሩን የሚያብራራ ዘይቤ ነው። "እጅግ እንዳዘነ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የቀበሮዎች ወንድም፣ የሰጎን ወዳጅ
የእነዚህ እንስሳት ወንድም መሆን እንደ እነርሱ አይነት መሆን ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "በበረሃ እንደሚጮሁ ቀበሮዎች እና ሰጎኖች ሆንኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 30:30
አጥንቶቼ በሙቀት ተቃጠሉ
እዚህ ስፍራ "አጥንቶች" የሚያመለክተው በትኩሳት የሚሰቃየውን መላ አካልን ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በገናዬ ወደ ሀዘን እንጉርጉሮ ተለወጠ
እዚህ ስፍራ "በገናዬ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብን ራሱን ነው፣ እንደዚሁም ደግሞ የሀዘን እንጉርጉሮ ብቻ መዘመር መፈለጉን ይወክላል። "በበገናዬ የሀዘን እንጉርጉሮ ብቻ እጫወታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ዋሽንቱ ለሙሾ ማውረጃ ሆነ
እዚህ ስፍራ "ዋሽንቴ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብን ራሱን ነው፣ እንደዚሁም ደግሞ የሀዘን እንጉርጉሮ ብቻ መዘመር መፈለጉን ይወክላል። "በዋሽንቴ የሀዘን እንጉርጉሮ ብቻ እጫወታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ዋይታ/ለቅሶ
ዋይታ ከፍ ካለ ሀዘን ወይም ስቃይ የተነሳ ድምጽን በጣም ከፍ አድርጎ ማልቀስ ነው

Chapter 31
Job 31:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል።
ከዐይኖቼ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ
ኢዮብ ዐይኖቹ ሰው የሆኑ ይመስል ስለሚመለከተው ነገር ከዐይኖቹ ጋር ቃል መግባቱን ይናገራል። "ስለምመለከተው ነገር ከዐይኖቼ ጋር ጽኑ ቃል ገባሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከዐይኖቼ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ
ኢዮብ ምን ቃል ኪዳን እንደገባ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ድንግሊቱን በአምንዝራ አይን እንዳልመለከት የጸና ኪዳን ገባሁ" ወይም "ወደ አንዲት ድንግል በአመንዝራነት ላለመመልከት ቃል ገባሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ታዲያ እንዴት ወደ አንዲት ድንግል በአመንዝራነት ፍላጎት እመለከታለሁ?

ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀምበት ቃልኪዳኑን በምንም ምክንያት እንደማያፈርስ ትኩረት ለመስጠት ነው። "ስለዚህ በእርግጥ ወደ አንዲት ድንግል በአመንዝራነት ዐይን አልመለከትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ድርሻዬ፣ በከፍታ ካለው ሁሉን ቻይ ከሆነው ርስቴ ምንድን ነው?

ኢዮብ እግዚአብሔር ለሰዎች ባህሪ ያለውን ምላሽ የሚገልጸው እግዚአብሔር ለሰዎች የሚሰጠው ርስት ክፍል አድርጎ ነው። "በሰማይ የሚኖር አምላክ ለእኔ የሚመልሰው እንዴት ነው? በላይ የሚኖረው ሁሉን ቻይ አምላክ ምን ይፈጽማል? በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ድርሻዬ፣ በከፍታ ካለው ሁሉን ቻይ ከሆነው ርስቴ ምንድን ነው?

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፤ ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው ተከታዬቹን ነጥቦች ለማጉላት ነው 1) እግዚአብሔር መጥፎ ባህሪ ያለውን አይባርከውም። "ወደ አንዲት ሴት በአመንዝራነት ዐይን ብመለከት፣ በላይ በሰማይ የሚኖር ሁሉን ቻይ አምላክ አይባርከኝም።" ወይም 2) እግዚአብሔር መጥፎ ባህርይን ይቀጣል። "ወደ ሴት በአመንዝራነት ብመለከት፣ በሰማይ የሚኖር ሁሉን ቻይ አምላክ በእርግጥ ይቀጣኛል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:3

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል።

እግዚአብሔር መንገዴን አይመለከትምን ደግሞስ እርምጃዬን አይቆጥርምን?

እዚህ ስፍራ "መንገዶቼ" እና "እርምጃዎቼ" የሚሉት ለኢዮብ ባህርይ መግለጫነት የቀረቡ ዘይቤዎች ናቸው። እዚህ ስፍራ "መንገዶቼን ተመልከት" እና "እርምጃዎቼን ሁሉ ቁጠር" የሚሉት ኢዮብ የሚያደርገውን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚያው ለመግለጽ የቀረቡ ዘይቤዎች ናቸው። ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት እግዚአብሔር እርሱ ያደረገውን ሁሉ እንደሚያውቅ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "በእርግጥ እግዚአብሔር ይመለከተኛል፣ ደግሞም ያደረግሁትን ነገር በሙሉ ያውቃል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር መንገዶቼን አይመለከትምን ደግሞስ እርምጃዎቼን ሁሉ አይቆጥርምን?

ኢዮብ ምናልባትም እግዚአብሔር የእርሱን ጻድቅነት ማወቅ እንደሚገባው እና መቅሰፍት እና ጥፋት ለእርሱ እንደማይገባው እያመላከተ ሊሆን ይችላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:5

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል።

እንዲህ አድርጌ ቢሆን

በኢዮብ 31፡ 5-40 ውስጥ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደሚይገባው የተለያዩ ሁኔታዎችን ይገልጻል። ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በሀሰት መንገድ ተመላልሼ እንደሆነ፣ እግሮቼ ወደ ማታለል ፈጥነው እንደሆነ

እዚህ ስፍራ "መመላለስ" እና "መፍጠን" የሚሉት ኢዮብ እንዴት እንደኖረ የሚገልጹ ዘይቤዎች ናቸው። "አንዳች ሀሰት የሆነ ነገር አድርጌያለሁን ወይስ ይሁን ብዬ የፈጸምኩት ማታለል አለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በትክክለኛ ሚዛን ልመዘን

ሰዎች ነገሮችን ለመለካት እና ዋጋቸውን ለመወሰን ሚዛን ይጠቀማሉ። ይህ ምስል በንጹህነት መበየንን ይወክላል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በንጹህነት ልመዘን" ወይም "እግዚአብሔር እንደ ንጽህናዬ ይፍረድብኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 31:7

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እርምጃዎቼ ከመንገድ ፈቀቅ ብለው ቢሆን

እዚህ ስፍራ "እርምጃዎቼ" የሚለው የኢዮብን ባህርይ የሚገልጽ ዘይቤ ሲሆን "ከመንገድ ፈቀቅ ብለው ቢሆን" የሚለው ከትክክለኛ አኗኗር መውጣትን የሚያሳይ ዘይቤ ነው። "ከጽድቅ ህይወት ዘወር ብዬ ቢሆን" ወይም "ትክክለኛ የሆነውን ማድረግ አቁሜ ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ ዐይኖቼን ተከትሎ ሄዶ ቢሆን

እዚህ ስፍራ "ልቤ" እና "ዐይኖቼ" የሚሉት ኢዮብ ለሚፈልጋቸው እና ለሚያያቸው ነገሮች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። ልብ ዐይንን ተከትሎ መሄድ የሚለው የተመለከተውን ለማድረግ መፈለግን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። ይህ ኢዮብ የተመለከተውን በኃጢአት የተሞሉ ነገሮች ያመለክታል። "ከተመለከትኳቸው ክፉ ነገሮች አንዱን ለማድረግ ፈልጌ ቢሆን ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በእጄ ላይ አንዳች በደል ተገኝቶ ቢሆን

ይህ ጥፋተኝነትን ለማመልከት የሚውል ዘይቤ ነው። "በአንዳች በደል ውስጥ ብገኝ ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ቢሆን፣ እኔ የዘራሁትን ሌላው ይብላው፣ ደግሞም የተከልኩት ከስሩ ይነቀል

ኢዮብ በእርግጥ በደል ፈጽሞ ቢሆን እነዚህ ክፉ ነገሮች ይድረሱብኝ እያለ ነው። በደል ፈጽሞ ቢሆን ከባድ የሆነውን የመዝራት ተግባር በእርሻው ላይ ያከናውናል ነገር ግን ከዚያ አንዳች መቅመስ አይችልም።

የተከልኩት ከስሩ ተነቅሎ ይጥፋ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሌላ ሰው መጥቶ ከእርሻዬ አዝመራዬን ይውሰድ። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:9

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ በሴት ተታሎ ቢሆን

እዚህ ስፍራ "ልቤ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብን ነው። "ተታሎ" የሚለው ቃል "ማማለልን/የዐይን ዐምሮትን" የሚገልጽ ሃሳብ ነው። "ሴት" የሚለው ቃል "የሌላ ሰው ሚስት የሆነችን ሴት" ይገልጻል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የሌላ ሰው ሚስት ብትስበኝ" ወይም "የሌላ ሰውን ሚስት ብመኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በወዳጄ በር አድብቼ ብጠባበቅ

በወዳጄ በር ለምን አድብቶ እንደሚጠባበቅ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ከሚስቱ ጋር ለመተኛት በወዳጄ በር አድብቼ ብጠባበቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ቢሆን የእኔ ሚስት ለሌላው ወፍጮ ትፍጭ

ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ ሚስቴ ከሌላ ሰው ጋር ትተኛ የሚለውን በዩፊምዝም/ በማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ እየተናገረ ነው። 2) ይህ ማለት ሚስቱ ባሪያ ሆና ለሌላ ሰው ታገለግላለች። (ዩፊምዝም/ የማያስደስት ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:11

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ክፉ ወንጀል በሆነብኝ ነበር

"ይህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢዮብ ከሌላ ሴት ጋር የመተኛትን ክፉ በደል ነው።

ይህ በዳኞች ቅጣት የሚያስጥል ወንጀል ይሆናል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ይህ ዳኞች በእኔ ላይ ቅጣት ቢጥሉ/ ቢፈጽሙ ትክክለኛ ናቸው የሚያሰኝ ወንጀል ይሆናል" በሚለው ውስጥ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ እሳት ያለውን ሁሉ ይፍጀው፣ አዝመራዬንም ከስሩ ጭምር ያቃጥለው
ኢዮብ ከሌላ ሰው ሚስት ጋር መተኛት የሚያስከትለውን ጥፋት እሳት ሁሉንም ነገር ከማጥፋቱ ጋር ያነጻጽረዋል። "ይህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከሌላ ሰው ሚስት ጋር መተኛትን ነው። "ማመንዘር ሁሉንም ነገር ከጫፍ ጫፍ እንደሚያጠፋ እና አዝመራን ሁሉ እንደሚያቃጥል እሳት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከዳር እዳር ይፍጅ/ያቃጥል
እነዚህ ቃላት ምናልባት "ለቀሪው ዘመኔ አንዳች ሳያስቀር ሁሉንም ነገር ያጥፋ" ለሚለው ሀሳብ ዘይቤያዊ አገላለጽ ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ደግሞ ይህንን ቃል በቃል መተረጎም ያስፈልጋል። ተከታዩን ይመልከቱ ([[:en: ta: vol1: translate: figs:-metaphor]])
አዝመራዬን ከስሩ ያቃጥል
እዚህ ስፍራ "ይህ" የሚለው ቃል ከሌላ ሰው ጋር የመተኛትን ድርጊት ያመለክታል። ይህ ድርጊት ኢዮብ ነገሩን አድርጎት ቢሆን ሊቀበለው ስለሚገባው ቅጣት በዘይቤ የቀረበ ነው። አዝመራውን የሚያቃጥል እሳት የደከመበትን ሁሉ ማጣት ለሚለው ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "እኔን የሚቀጡ የደከምኩበትን ሁሉ ይውሰዱት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ተከታዩን ይመልከቱ ([[:en: ta: vol2: translate: figs:-metonomy]]) እና([[:en: ta: vol2: translate: figs:-synecdoche]])
Job 31:13
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያነሳው እግዚአብሔር በእርሱ ላይ እንዲፈርድ የሚያደርግ በደል ሰርቶ ራሱን ንጹህ
አድርጎ እንደማያቀርብ በትኩረት ለመግለጽ ነው። "እንዲህ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ሊፈርድብኝ ሲመጣ ራሴን ለመከላከል የማቀርበው አንዳች ነገር አይኖርም ነበር።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በማህጸን ያበጀኝ እነርሱንስ አላበጀምን? ሁላችንንም በማህጸን የሰራን እርሱ አይደለምን?
ኢዮብ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያነሳው ከእርሱም አገልጋዮቹ እንደማይለይ በትኩረት ለመግለጽ ነው። አገልጋዮቹን ከራሱ ዝቅ አድርጎ ቢመለከት እግዚአብሔር እንደሚቆጣ ይናገራል። "በማህጸን የሰራኝ እርሱ፣ እነርሱንም ፈጥሯል። እርሱ ሁላችንንም በማህጸን ሰርቶናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 31:16
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። ሀሳቡን በቁጥር 16 እና 17 ላይ አይጨርስም። ይልቁንም በቁጥር 18 ላይ እነዚህ ለምን ጥፋተኛ እንዳልሆነ ያብራራል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ለድሆች የሚያስፈልጋቸውን ከልክዬ ከሆነ
"ድሆች የሚፈልጉትን እንዳያገኙ ከልክዬ ከሆነ"
የመበለቲቱ ዐይኖች በለቅሶ እንዲፈዙ አድርጌ ከሆነ
እዚህ ስፍራ "እየፈዘዙ እንዲሄዱ/እንዲፈዙ" የሚለው የሚያመለክተው መበለት ብዙ በማንባት ዐይኖቿ ሊፈዙ መቻላቸውን ነው። "አንዲት መበለት በታላቅ ሀዘን እንድታለቅስ ምክንያት ሆኜ ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቁራሼን
"ምግቤን"
ምክንያቱም ከልጅነቴ አንስቶ አባት ለሌላቸው እንደ አባት ሆኜ አሳድጌያለሁ
እዚህ ስፍራ "ወላጅ የሌላቸው" የሚለው የሚያመለክተው በአጠቃላይ ወላጆቻቸው ሞቱባቸውን ነው። ኢዮብ ወላጅ የሌላቸውን እንዴት ይረዳ እንደነበር ይናገራል። "ምክንያቱም ገና ወጣት ሳለሁ እንኳን ወላጅ የሌላቸውን እንደ አባት ሆኜ እንከባከባቸው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የስማዊ ሀረግ ክፍል የሚለውን ይመልከቱ)
በወጣትነቴ ምክንያት
"ከእነዚህ ነገሮች ውስጥ አንዱንም አልፈጸምኩም" የሚለው ሀረግ ትርጉም ከአውዱ/አገባቡ ግልጽ ነው። "ነገር ግን ከእነዚህ ነገሮች ውስጥ አንዱንም አልፈጸምኩም፣ ምክንያቱም ከወጣትነቴ አንስቶ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእናቴ ማህጸን አንስቶ መበለቲቱን ደግፌያለሁ
ኢዮብ መበለቶችን በእውነት እንዴት እንደ ደገፈ ይናገራል። "ከእናቴ ማህጸን አንስቶ" የሚለው ይህንን በህይወት ዘመኑ ሁሉ ማድረጉን በማጋነን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ዘመኔን በሙሉ አባት የሌላቸውን ልጆች እናቶች ደግፌያለሁ" ወይም "ዘመኔን በሙሉ መበለቶችን ደግፌያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 31:19
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ልቡ ባርኮኝ ካልሆነ
"ልቡ/የእርሱ ልብ" የሚለው ሀረግ የሚወክለው ልብስ የሚፈልገውን የተራቆተ ድሃ ነው። "እርሱ አመስግኖኝ/ባርኮኝ ካልሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ከበጎቼ ፀጉር ከተሸለተው ለብሶ ሞቆት ካልሆነ
እዚህ ስፍራ "የበጎቼ ፀጉር" የሚለው የሚገልጸው ከኢዮብ በጎች ፀጉር የተሰራን ብርድ ልብስ ወይም ልብስ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከበጎቼ ሱፍ የተሰራው ልብስ ሳያሞቀው ቀርቶ ቢሆን" ወይም "ከበጎቼ ሲፍ የተሰራ ልብስ ሳልሰጠው ቀርቼ ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
አባት በሌላቸው ላይ እጆቼን አንስቼ ቢሆን
በአንድ ሰው ላይ እጅን ማንሳት ማለት ያንን ሰው መጉዳትን ይገልጻል። "አባት የሌላቸውን አግባብ የሌለው ሁኔታ አድርሼባቸው ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ድጋፌን በከተማ መግቢያ አይቻለሁ
እዚህ ስፍራ "ማየት" የሚለው "ማወቅ፣" ለሚለው ዘይቤ ሲሆን "ድጋፍ" የሚለው "ማረጋገጫ" ለሚለው ዘይቤ ነው። "የከተማ መግቢያ/በር" የሚለው ደግሞ በከተማዋ በር ለሚቀመጡ መሪዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ/ ነው። "በከተማዋ በር የሚቀመጡ መሪዎች ስለ እኔ እንደሚመሰክሩ አውቃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
በከተማይቱ በር
ይህ የከተማይቱ ታላላቅ ሰዎች ውሳኔ ለመስጠት የሚቀመጡበት ስፍራ ነው
በእኔ ላይ ክሳችሁን አቅርቡ
ይህ ሀረግ በመጀመሪያው ጽሁፉ በቀረበበት ቋንቋ ወይም በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ውስጥ የለም። እዚህ የተጨመረው በኢዮብ ረዘም ያለ ንግግር ውስጥ ያለውን ሀሳብ ላለማጉደል ነው።
Job 31:22
አጠቃላይ መረጃ፡
እንዲህ ከሆነ ትከሻዬ ከመጋጠሚያው ይነቀል፣ ክንዴም ደግሞ ከመታጠፊያው ይሰበር ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እንዲህ ከሆነ አንድ ሰው ትከሻዬን ከመጋጠሚያው ይንቀለው ደግሞም ክንዴን ከመታጠፊያው ይስበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱን ግርማ ... ፈርቻለሁና
ኢዮብ ከቁጥር 7 አንስቶ እስከ 21 ድረስ ከተናገረው ውስጥ በአንዱም እንዳልበደለ የተናገረበት ምክንያት ይህ/የእርሱን ግርማ/ መፍራቱ ነው
Job 31:24
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ወርቅን ተስፋ አድርጌ ቢሆን

"ተስፋ" የሚለው ረቂቅ ስም "ታመነ" ወይም "ተስፋ አደረገ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "በወርቅ ታምኜ ቢሆን" ወይም "የብዙ ወርቅ ባለቤት መሆን ይጠብቀኛል ብዬ ተስፋዬን ጥዬበት ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ምርጥ የሆነውን ወርቅ 'የታመንኩት በአንተ ነው' ብዬው ቢሆን

ይህ ስንኝ/ቁጥር ከላይኛው ቁጥር ጋር ተመሳሳይ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እጄ ብዙ ሀብት ነበረው

እዚህ ስፍራ "እጄ" የሚለው የሚገልጸው የኢዮብን ነገሮችን የማከናወን አቅም ነው። "በችሎታዬ ብዙ ሀብት አከማችቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ከሆነ በእኔ ላይ ክስ አቅርቡ

ይህ ሀረግ በመጀመሪያው ጽሁፉ በቀረበበት ቋንቋ ወይም በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ውስጥ የለም። እዚህ የተጨመረው በኢዮብ ረዘም ያለ ንግግር ውስጥ ያለውን ሀሳብ ላለማጉደል ነው።

Job 31:26

አጠቃላይ መረጃ:

ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የጨረቃ አካሄድ

እዚህ ስፍራ "አካሄድ" የሚወክለው ቀስ ብሎ መንቀሳቀስን ነው። "ጨረቃ ሰማይን እያቋረጠች ስትንቀሳቀስ"

ጨረቃ በድምቀቷ ስትራመድ

"ድምቀት" የሚለው ረቂቅ ስም "ብሩህ" ወይም "በብሩህነት" በሚሉ ቃላት ሊገለጽ ይችላል። "ብሩኋ ጨረቃ ሰማይን እያቋረጠች ስትንቀሳቀስ" ወይም "ጨረቃ ብሩህ ሆና በሰማይ ስትንቀሳቀስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ በስውር ተስቦ ቢሆን

እዚህ ስፍራ "ልቤ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብን ነው። ይህ ሀረግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በድብቅ ወደ እነርሱ ተስቤ ቢሆን" ወይም "በድብቅ እነርሱን ለማምለክ ፈልጌ ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በዚህም ምክንያት አፌ እጄን ስሞ ቢሆን

እዚህ ስፍራ "አፌ" የሚለው የሚወክለው ኢዮብን ነው። ይህ የፍቅር እና የተመስጦ ምልክት ነው። "ስለዚህም እጄን ስሜ ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱን ለማምለክ

"ፀሐይን እና ጨረቃን ለማምለክ"

በዳኞች መቀጣት

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የትኛዎቹ ዳኞች እኔን ቢቀጡኝ ትክክለኛ ይሆናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰማይ ያለውን አምላክ ክጄ ቢሆን

"በላይ ላለው እግዚአብሔር አምላክ ታማኝ ሳልሆን ቀርቼ ቢሆን"

Job 31:29

አጠቃላይ መረጃ:

ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን የሚጠሉ ሁሉ በሚጠፉበት ጊዜ

"ጥፋት" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠፋ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "እኔን የሚጠላ ማንም ቢሆን በሚጠፋበት ጊዜ" ወይም "እኔን በሚጠላ ማንም ሰው ክፉ ነገር በሚደርስበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ጥፋት በሚውጠው ጊዜ

"ጥፋት ሲደርስበት"

እንዲህ ከሆነ/በዚይን ጊዜ በእኔ ላይ ክስ አቅርቡ

ይህ ሀረግ በመጀመሪያው ጽሁፉ በቀረበበት ቋንቋ ወይም በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ውስጥ የለም። እዚህ የተጨመረው በኢዮብ ረዘም ያለ ንግግር ውስጥ ያለውን ሀሳብ ላለማጉደል ነው።

በእርግጥ፣ አፌ እንኳን ኃጢአት እንዲናገር አልፈቀድኩም

እዚህ ስፍራ "አፌ/እንደበቴ" የሚለው የሚወክለው የኢዮብን ንግግር ነው። "በእውነት ራሴን ለኃጢአት አሳልፌ አልሰጠሁም" ወይም "በእውነት፣ ኃጢአት አልሰራሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ህይወት እንዲረገም በመጠየቅ

እዚህ ስፍራ "የእርሱ ህይወት እንዲረገም በመጠየቅ" የሚለው የሚገልጸው አንድ ሰው እንዲሞት መራገምን ነው። "ይሞት ዘንድ እርሱን በመርገም" ወይም "ህይወቱን በመርገም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:31

አጠቃላይ መረጃ:

ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የጎጆዬ/የቤቴ ሰዎች

ጎጆው የሚወክለው የኢዮብን ቤት ነው። የጎጆው ሰዎች የሚያጠቃልለው የቤተሰቡን አባላት እና አገልጋዮቹን ነው። እነዚህ ሁሉ ኢዮብን በሚገባ ያውቁታል። "የቤቴ ሰዎች" ወይም "የቤተሰቤ አባላት እና አገልጋዮቼ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማን ከኢዮብ ገበታ ያልጠገበን ሰው ማግኘት ይችላል?

የኢዮብ ሰዎች ይህንን ጥያቄ ኢዮብ ለጋስ ሰው እንደሆነ በትኩረት ለመግለጽ ሊያነሱ ይችላሉ። "ሁሉም ከኢዮብ ገበታ በልቶ ጠግቧል!" ወይም "እኛ የምናውቀው ሁሉ የፈለገውን ያህል ከኢዮብ ምግብ ተመግቧል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ባዕድ እንኳን በከተማ አደባባይ አይረሳም ነበር

ኢዮብ እንግዶችን እንዴት ይንከባከብ እንደነበር ተገልጽዋል። እዚህ ስፍራ "በከተማ አደባባይ መቀመጥ" የሚለው የሚገልጸው በከተማ አደባባይ ምሽቱን ማደርን ነው። "እንግዶች ፈጽሞውኑ በከተማይቱ አደባባይ በሜዳ ላይ አያድሩም ነበር" ወይም "እንግዶች/ባዕዳን ውጭ አያድሩም ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሌም በሮቼን ለመንገደኞች ክፍት አደርግ ነበር

እዚህ ስፍራ "ለመንገደኞች በሬን እከፍት ነበር" የሚለው የሚወክለው ወደ ቤቱ መንገደኞችን መቀበሉን ነው። "ሁሌም መንገደኞችን በቤቴ እቀበል ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እናም ነገሩ ይህ ባይሆን፣ በዚያን ጊዜ በእኔ ላይ ክስ አቅርቡ

ይህ ሀረግ በመጀመሪያው ጽሁፉ በቀረበበት ቋንቋ ወይም በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ውስጥ የለም። እዚህ የተጨመረው በኢዮብ ረዘም ያለ ንግግር ውስጥ ያለውን ሀሳብ ላለማጉደል ነው።

Job 31:33

አጠቃላይ መረጃ:

ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ቀጥሏል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአቴን... ደብቄ/ሰውሬ ቢሆን

እዚህ ስፍራ "ኃጢአቴን ሰውሬ ቢሆን" የሚለው የሚወክለው እርሱ ኃጢአት መስራቱን ሰዎች እንዳያውቁበት ለመደበቅ ሞክሮ ያውቅ እንደሆነ ነው። "ኃጢአቴን... ሰዎች እንዳያውቁ ለመደበቅ ሞክሬ እንደሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአቴን በካቦርቴ ውስጥ በመሰወር

ይህ የሚወክለው እርሱ በደለኛ መሆኑን ሰዎች እንዳያውቁ ለመደበቅ መሞከርን ነው። "የበደሎቼን ማስረጃዎች በካቦርቴ ውስጥ በመሸሸግ" ወይም "በካቦርቱ ውስጥ የበደሉን ማስረጃዎች እንደሚሸሽግ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ ህዝብ በመፍራት፣ ከቤተሰብ የሚመጣን ንቀት በመፍራት

ኃጢአቱን ለመደበቅ ምክንያት ሊሆን የሚችለው ይህ ነው። እነዚህ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ትኩረት የሚሰጡት አንድ ሰው ኃጢአቱን የሚሸሽገው ሰዎች ስለ እርሱ የሚኖራቸውን አስተሳሰብ በመፍራት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያን ጊዜ በእኔ ላይ ክስ አቅርቡ

ይህ ሀረግ በመጀመሪያው ጽሁፉ በቀረበበት ቋንቋ ወይም በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ውስጥ የለም። እዚህ የተጨመረው በኢዮብ ረዘም ያለ ንግግር ውስጥ ያለውን ሀሳብ ላለማጉደል ነው።

Job 31:35

አወይ፣ ምነው የሚሰማኝ ባገኘሁ!

ይህ አጋኖ የኢዮብን ፍላጎት/የሚመኘውን ይገልጻል። "የሚሰማኝ ባገኝ በመደድሁ" ወይም "የሚሰማን ሰው ባገኝ እወዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ አጋኖዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ፊርማዬ እነሆ

እዚህ ስፍራ "ፊርማዬ" የሚለው የሚገልጸው፣ ኢዮብ የተናገረው ነገር ሁሉ እውነት መሆኑን ቃል መግባቱን ነው። ስለ ደረሰበት ነገር ህጋዊ ሰነድ እንደጻፈ አድርጎ ይናገራል። "የተናገርኩት እውነት መሆኑን በእርግጥ ቃል እገባለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ የሆነው እርሱ ይመልስልኝ!

እዚህ ላይ ምላሽ የሚለው የሚያመለክተው ምናልባት ኢዮብ ምን ስህተት እንደፈጸመ የሚከሰስበትን የሚነግረውን መፈለጉን ይሆናል። "ሁሉን ቻይ የሆነው እርሱ የሰራሁትን በደል ይንገረኝ" ወይም "ሁሉን ቻይ የሆነው የሰራሁት በደል ምን እንደሆነ ቢነግረኝ እወዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተቃዋሚዎቼ በእኔ ላይ የጻፉትን የክስ ማስረጃ ባውቅ በወደድኩ!

ይህ የኢዮብን ፍላጎት ይገልጻል። ኢዮብ አንድ ሰው እርሱን ኃጢአተኛ አድርጎ ለመክሰሱ ማስረጃ አድርጎ የሚያቀርበው የደረሰበትን ችግር ነው። "የትኛውም ተቃዋሚ የሚያቀርብብኝ ክስ ቢኖር በወደድኩ" ወይም "ምነው ተቃዋሚዬ የሚያቀርብብኝን ክስ ማንበብ በቻልኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ተቃዋሚዬ/ባለጋራዬ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ እግዚአብሔርን ሊያመለክት ይችላል ወይም 2) ሌላ አካልን ሊያመለክት ይችላል

በእርግጥ ክሱን በግልጽ በትክሻዬ እሸከመዋለሁ፤ እንደ ዘውድ በራሴ ላይ እጭነዋለሁ

ይህ የሚወክለው ክሱን ማንም ሊያነበው በሚችለው ስፍራ ማስቀመጥን/ማድረግን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ልበ ሙሉ ልዑል ወደ እርሱ ዘንድ እሄዳለሁ

ይህ ማለት ኢዮብ ኃጢአት ባለመስራት አንዳች ፍራቻ ወደ እግዚአብሔር እንደሚቀርብ ይናገራል። ኢዮብ ይህን ማድረግ እንደሚችል የሚናገረው ጥፋተኛ ስላልሆነ ነው። "በድፍረት ወደ እርሱ እቀርባለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 31:38

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢዮብ የእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይገባው ሁኔታዎችን መግለጹን ያጠቃልላል፣ ይልቁንም፣ ጥፋት እንደሌለበት እና ንጹህ እንደሆነ ያውቃል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሬ በእኔ ላይ ቢያለቅስብኝ፣ እርሻዩ በአንድነት ቢያለቅስ

ኢዮብ ጥፋተኛ ስላለመሆኑ የሚናገረው ምድሩ ሰው እንደሆነ እና እርሻውን በመበደሉ ምክንያት በእርሱ ላይ እንደሚያለቅስበት አድርጎ ነው። "እርሻዬን በሚመለከት አንዳች ስህተት ሰርቼ ቢሆን" ወይም "እርሻዬን/ መሬት ከሌላ ሰው ሰርቄ ቢሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወታቸው እንዲያልፍ

ይህ ሞትን ያመለክታል። "እንዲሞት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በገብስ ፈንታ አረም

"ይሁን" እና "ይብቀል" የሚሉት ከቀደመው ሀረግ ይታወቃሉ። "በገብስ ፈንታ አረም ይብቀል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 32

Job 32:1

እርሱ በራሱ ዐይኖች ፊት ጻድቅ ነበር

ዐይኖች የሚመክሉት ማየትን ስሆን፣ ማየት የሚወክለው ሃሳብን ወይም ፍርድን ነው። "ራሱን ጻድቅ አድርጎ ቆጥሯል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም የራም ቤተሰብ የሆነው የቡዛዊው የባሮክ ልጅ የኤሊሁ ቁጣ ነደደ፤ ቁጣው የነደደው በኢዮብ ላይ ነበር

ይህ የሚያነጻጽረው የኤሊሁን ቁጣ አንድ ሰው እሳት ከመለኮሱ ጋር ነው። እንደዚሁም፣ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከዚያም የራም ቤተሰብ የሆነው የቡዛዊው የባሮክ ልጅ የኤሊሁ ቁጣ በኢዮብ ላይ እጅግ ነደደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ኤሊሁ… ባሮክ…ራም

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቡዛዊ

ይህ የህዝብ የወል/የቡድን ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ሳይለው ራሱን ጻድቅ አድርጓል

ይህ ማለት፣ ራሱን ንጹህ አድርጎ፤ እርሱን በመቅጣቱ እግዚአብሔር ጥፋተኛ እንደሆነ አምኗል። "ራሱን አጽድቆ እርሱን ስለቀጣው እግዚአብሔርን ጥፋተኛ ነው ብሏል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 32:3

የኤሊሁ ቁጣ የነደደው በሶስቱ ወዳጆቹም ላይ ጭምር ነበር

ይህ የኤሊሁን ቁጣ እሳትን ከመለኮስ ጋር ያነጻጽራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እንደዚሁም ደግሞ ኤሊሁ በሶስቱ ወዳጆቹ ላይ እጅግ ተቆጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነሆ/አሁን

ይህ ቃል በዚህ ስፍራ የዋለው በዋናው ታሪክ ላይ ማረፊያ ለማበጀት ነው። ይህ ስለ ኤሊሁ የመረጃ ዳራ/የቀደመ ማስረጃ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ/የቀደመ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእነዚህ ሶስት ሰዎች አፍ አንዳች መልስ አልተገኘም

ይህ ማለት ሰዎቹ ከኢዮብ ጋር መነጋገራቸውን ጨርሰው/አብቅተው ነበር። ይህ፣ መልስ በሰዎቹ አፍ ላይ የሚገኝ ነገር ቢሆን ኖሮ ምናልባት መልስ ያገኙ እንደ ነበር ይገልጻል። "እነዚህ ሶስት ሰዎች ሌላ የሚናገሩት ነገር የላቸውም" ወይም "እነዚህ ሶስት ሰዎች ለኢዮብ የሚሰጡት ሌላ ምንም ተጨማሪ መልስ የላቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣው ነደደ ነበር

ይህ የኤሊሁን ቁጣ እሳትን ከመለኮስ ጋር ያነጻጽራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በጣም ተቆጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 32:6

እናንተ አዛውንቶች ናችሁ/በጣም ሽማግሌዎች ናችሁ

እዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም ኢዮብን እና ሶስቱን ወዳጆቹን ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመለከቱ)

የቀናት እርዝመት መናገር መቻል አለበት፣ የአመታት ብዛት እውቀትን መስጠት አለበት

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ኤሊሁ ትኩረት የሰጠው ከወጣቶች ይልቅ አዛውንቶች ጥበብ የቀሰሙ በመሆናቸው የሚያውቁትን አስቀድሞ መናገር እንደሚገባቸው ነው። "ብዙ ዘመናትን የኖረ እርሱ መናገር አለበት፤ አዛውንት የሆነው እርሱ ጥበብን ማስተማር ይገባዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 32:8

አጠቃላይ መረጃ፡

ኤሊሁ ለኢዮብ እና ለእርሱ ወዳጆች መናገሩን ቀጥሏል

ሁሉን ቻይ የሆነው እስትንፋስ፤ በሰው ውስጥ መንፈስ አለ

ሁለቱ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አቸላቸው። ኤሊሁ የሰው ጥበብ ከእግዚአብሔር



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደሚመጣ ትኩረት ይሰጣል። "በሰው ውስጥ መንፈስ አለ፣ ይህም፣ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ እስትንፋስ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ እስትንፋስ
እዚህ መንፈስ የሚለው የተወከለው በ"እስትንፋስ" ነው። "ሁሉን ቻይ የሆነው የእርሱ መንፈስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 32:11
እነሆ
ኤሊሁ እዚህ ስፍራ ይህንን ቃል የተጠቀመው የሰዎቹን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚናገረው ነገር ለመሳብ ነው። "አድምጡኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ቃላችሁን አደመጥኩ
"የተናገራችሁትን ስሰማ ቆየሁ።" "እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የኢዮብን ወዳጆች ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)
ለእርሱ ቃላት ማን ምላሽ ሊሰጥ ይችላል
እዚህ ስፍራ "ምላሽ" የሚለው ቃል መልስ ማለት ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ጠቃሚ የሆነ ምላሽ መስጠት ነው።
Job 32:13
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ለኢዮብ ወዳጆች መናገሩን ቀጥሏል
እኛ እውቀት አግኝተናልን/አለን
ይህ ማለት ጠቢብ ምን እንደሆነ ለይተው እንደሚያውቁ ያምናሉ ማለት ነው። "ጠቢብ ምን እንደሆነ እኛ አውቀናል/ደርሰንበታል"
ኢዮብን ለማሸነፍ
ይህ የሚገልጸው እግዚአብሔር ለኢዮብ ምላሽ እንደሚሰጥ እና እርሱን በጦርነት እንዳሸነፈ አድርጎ እንደሚያስተካክለው ነው። "ኢዮብን ለመቃወም" ወይም "ለኢዮብ መልስ ለመስጠት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በበአፍህ ቃል
"ያልከውን በማለትህ"
Job 32:15
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ መናገሩን ቀጥሏል
እጅግ መገረም
መደነቅ፣ መናገር አለመቻል
እነርሱ ስላልተናገሩ፣ በዚያ በጸጥታ ስለቆሙ እና መልስ መስጠት ስላቆሙ እኔ ዝም ማለት ይኖርብኛል?
ኤሊሁ ጥያቄውን የሚጠቀምበት ከእንግዲህ በኋላ ዝም ብሎ እንደማይቆይ ትኩረት ለመስጠት ነው። ኤሊሁ በቀጣዩ ቁጥር ለጥያቄው ራሱ መልስ ይሰጣል። "ነገር ግን እናንተ ዝም ስላላችሁ፣ እኔ በእርግጥ ከእንግዲህ ዝም አልልም፤ እናንተ ዝም ብላችሁ ቆማችኋል ምላሽ መስጠትም አቁማችኋል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 32:17
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤን በመጠቀም መናገሩን ቀጥሏል።
እኔም የበኩሌን መልስ እሰጣለሁ
"እኔ አሁን በተራዬ መልስ እሰጣለሁ"
በቃላት ተሞልቻለሁ
ኤሊሁ በቃላት እንደመሞላቱ መጠን የሚናገረው ብዙ እንዳለው ይገልጻል። "ብዙ የምናገረው አለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በውስጤ ያለው መንፈስ ግድ ይለኛል
"መንፈሴ እንድናገር ያስገድደኛል"
ደረቴ መተንፈሻ እንዳጣ እንደ ፈላ ወይን፣ እንደ አዲስ የወይን አቁማዳ፣ ለመፈንዳት ተዘጋጅቷል
ወይን በሚፈለበት ጊዜ፣ በመያዣው ውስጥ አየር ይታመቃል። አየሩ መውጫ ካላገኘ አቁማዳው ይፈነዳል። ኤሊሁ ይህንን ሲል ብዙ የሚናገረው እንዳለው እና ይህንን ካልተናገረ የሚፈነዳ ሆኖ እንደተሰማው መግለጹ ነው፤ ምንም እንኳን እነዚህ ሁለት ሃሳቦች ትይዩ ቢሆኑና ትርጉማቸው ግን ተመሳሳይ ቢሆንም። "የሚተመፍስበት እንዳጣ የፈላ ወይን ጠጅ እንደያዘ አቁማዳ ደረቴ የሚፈነዳ ሆኖ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ደረቴ ... ነው
ይህ የሚገልጸው ኤሊሁን ሲሆን፣ በተለይም መንፈሱን ነው። "መንፈሴ...ነው" ወይም "እኔ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 32:20
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ትኩረት ለመስጠት ትይዩ ተነጻጻሪ ዘይቤን በመጠቀም መናገሩን ቀጥሏል።
እታደስ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የተሻለ /እፎይታ ሊሰማኝ ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከንፈሮቼን እንቀሳቅሳለሁ
እዚህ ስፍራ "ከንፈሮች" የሚለው የሚወክለው አፍን/አንደበትን ነው። "አፌን እከፍታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ለማንም ሰው የከበረ መጠሪያ አልሰጥም
"ማንንም አላወድስም ወይም ለማንም የክብር ስም አልሰጥም"
ያበጀኝ/የሰራኝ
ይህ እግዚአብሔርን የሚያመለክት ስም ነው። "ያበጀኝ እርሱ እግዚአብሔር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ይወስደኛል
ይህ ማለት እርሱ ያጠፋዋል ማለት ነው። "ያጠፋኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 33
Job 33:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ መናገሩን ቀጥሏል።
ንግግሬን አድምጡ፤ ቃሎቼን ሁሉ ስሙ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርም አላቸው። ኤሊሁ ኢዮብ በጥንቃቄ ሊያደምጥ እንደሚገባው ትኩረት ሰጥቶ ይናገራል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ አፌን እከፍታለሁ... ምላሶቼ የአንደበቴን ቃል ይናገራሉ
እነዚህ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ኤሊሁ አሁን ለመናገር ዝግጁ መሆኑን በትኩረት ይገልጻል። የእርሱ "ምላስ" ንግግር የሚወክለው የራሱን ንግግር ነው። "አፌን ከፍቼ መናገር ጀምሬያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
ቃሎቼ ከልቤ ቅንነት ይፈልቃሉ
እዚህ ስፍራ ኤሊሁ ትክክል መሆኑን የሚገልጸው በ"ልቡ" ቅንነት ነው። "በጽድቅ እናገራለሁ" ወይም "በሙሉ ቅንነት እናገራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ከንፈሮቼ መልካም እውቀት ይናገራሉ
እዚህ ስፍራ ኤሊሁ በ"ከንፈሮቹ" ራሱን የሚወክለው ለንግግሩ ትኩረት ለመስጠት ነው። "በትክክለኛ አቋም እናገራለሁ" ወይም "በፍጹም ቅንነት እናገራለሁ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 33:4
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ለኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል።
የእግዚአብሔር መንፈስ ... ህይወት ሰጠኝ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ኤሊሁ እግዚአብሔር እርሱን እንደሰራው እና ለሚናገረው ሀላፊነትን እንደሰጠው ትኩረት ይሰጣል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ቃሎችን አሰናድተህ በፊቴ ለመቆም ተዘጋጅ
ይህ የሚገልጸው ኢዮብ የሚናገረውን አካላዊ ቁሶችን እንደሚደረድር እንዲያሰናዳ ነው። "የምትናገረውን አሰናዳ፣ ከዚያም ቆመህ/ታጥቀህ መልስልኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 33:6
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ለኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል።
እነሆ
ኤሊሁ እዚህ ስፍራ ይህንን ቃል የተጠቀመው የኢዮብን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚናገረው ነገር ለመሳብ ነው። "አድምጠኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
በእግዚአብሔር እይታ እኔም ልክ እንደ አንተ ነኝ
እዚህ ስፍራ እይታ የሚወክለው ፍርድን ወይም ሚዛንን ነው። "በእግዚአብሔር ፍርድ እኔም ልክ እንደ አንተ ነኝ" ወይም "እግዚአብሔር በአንተ ላይ በሚፈርድበት ተመሳሳይ መንገድ በእኔም ላይ ይፈርዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔም ደግሞ የተበጀሁት ከሸክላ ነው
ምንም እንኳን ሰዎች ከሸክላ ባይሰሩም፣ ሸክላ ሰራተኛ ነገሮችን በጥንቃቄ ከሸክላ እንደሚያበጅ እግዚአብሔር ሁሉንም አበጅቷል። "ሸክላ ሰራተኛ ነገሮችን ከሸክላ እንደሚሰራ እግዚአብሔር ሁለታችንንም ሰርቶናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔም ደግሞ ተሰርቻለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር እኔንም ደግሞ አበጅቶኛል" ወይም "እግዚአብሔር ሁለታችንንም አበጅቶናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የእኔ ማስደንገጥ አንተን አያስፈራህም
"እኔን ልትፈራ አያስፈልግም"
የእኔ ጫና በአንተ ላይ ሊከብድ አያስፈልግም
ይህ ማለት እርሱ ኢዮብን አያግደውም ወይም ሸክም አይጭንበትም። እርሱ ስሜታዊውን ሸክም የሚናገረው እንደ ከባድ አካላዊ ሸክም አድርጎ ነው። "እኔ በአንተ ላይ ሸክም አልጭንም" ወይም "በምናገረው ነገር ጫና አላሳድርብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 33:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ለኢዮብ መናገሩን ቀጥሏል።
እኔ ስሰማህ
"እኔ ልሰማህ በምችልበት"
እንደበትህ ሲናገር የሰማሁት
"ስትናገር የሰማሁህ"
ንጹህ
እግዚአብሔር በመንፈስ ተቀባይነት አለው ያለው ሰው፤ በአካል ንጹህ እንደነበረ ሰው ተደርጎ ይገለጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ኃጢአት የለብኝም
"ኃጢአት አልሰራሁም"
Job 33:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ኢዮብ የተናገረውን መጥቀሱን ቀጥሏል።
እነሆ
ተናጋሪው እዚህ ስፍራ ይህንን ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ወደሚናገረው ትኩረት ለመሳብ ነው። "አድምጠኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። እግሮቼን በግንድ አጣበቀ "ከግንድ ጋር ማሰሪያ" ይህ ከግንድ ጋር ተጣብቆ ማሰሪያ ሲሆን አሳሪው በእስረኛው እግር ዙሪያ እንቅስቃሴውን ለመገደብ የሚያደርገው ነው። ኢዮብ እስረኛ እንደሆነ የሚሰማው በግንድ ተጣብቆ እንደታሰረ በመናገር ነው። "እስረኛ እንዳደረገኝ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእኔ መንገዶች
እነዚህ ቃላት ወዴት እንደሚሄድ ያመለክታሉ። እዚህ ስፍራ ወዴት እንደሚሄድ የሚለው የሚገልጸው ምን እንደሚያደርግ ነው። "የማደርገው ነገር ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ እመልስልሃለሁ
ኤሊሁ ለኢዮብ እየተናገረ ነው
Job 33:13
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
ለምን እርሱን በመቃወም ትታገላለህ?
ኤሊሁ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀምበት ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር መታገል እንደሌለበት ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ከእግዚአብሔር ጋር መታገል የለብህም" ወይም "ከእግዚአብሔር ጋር ለመከራከር መሞከር የለብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይልከቱ)
እርሱ በሚያደርገው ሁሉ አይጠየቅም
"እርሱ የሚያደርገውን ማናቸውንም ነገር ለእኛ ማብራራት አይኖርበትም"
እግዚአብሔር በአንድም- በሌላም መንገድ ይናገራል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ደግሞ ደጋግሞ ይናገራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በህልም... በምሽት በራዕይ
እነዚህ ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በሰዎች ላይ ከባድ እንቅልፍ ሲወድቅ፣ በአልጋ ላይ አንቀላፍተው ሳሉ
ይህ ሰዎች በከባድ እንቅልፍ ላይ ሳሉ፣ እንቅልፍ በእነርሱ ላይ እንደ ወደቀባቸው ወይም እነርሱን እንዳሸነፈ አድርጎ ይናገራል። "ሰዎች በአልጋቸው ላይ ተኝተው ሙሉ እንቅልፍ ወስዷቸው ሳለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 33:16
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር የሰዎችን ጆሮ ይከፍታል
ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር ይሰሙ ዘንድ ጆሯቸውን በመክፈት ሰዎች ስለ ነገሮች እንዲረዱ ማድረጉን ነው። "በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ነገሮችን ለሰዎች ይገልጻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሰውን ከሄደበት ለመመለስ
ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር አንድ ሰው ክፉ ነገር እንዳይሰራ በአካል ወደ ኋላ የመጎተትን ያህል እየከለከለ ከክፉ ተግባሩ እንደሚጠብቀው ነው። "እርሱን ከ... ይጠብቅ ዘንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር የሰውን ህይወት ከጉድጓድ ይጠብቃል... ህይወቱ ወደ ሞት እንዳይሻገር ይጠብቀዋል
እነዚህ ሁለቱም ሃሳቦች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "እግዚአብሔር ሰዎችን ከመቃብር እና ከሞት ያድናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጉድጓድ
ሰዎች ሲሞቱ የሚሄዱበት ስፍራ እዚህ ላይ "ጉድጓድ" ተብሎ ተጠቅሷል። "የሞቱ ሰዎች የሚገኙበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ህይወት ይመለሳል...የእርሱ ህይወት
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ሰው ከመሞት እና...እርሱ ይጠብቀዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ሞት ከመሻገር
እዚህ ስፍራ "ሞት" የሚወክለው ሰዎች ሲሞቱ የሚሄዱበትን ስፍራ፣ ይኸውም፣ ሲኦልን ነው። "ወደ ሲኦል ከመሄድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 33:19
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
እንደዚሁም ደግሞ ሰው ይቀጣል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ደግሞ ሰውን ይቀጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በአልጋው ላይ ሳለ በህመም
ይህ ማለት ሰው በአልጋው ላይ ታሞ ይተኛ ዘንድ እንዲህ ያለው መከራ ይደርስበታል። "በአልጋው ላይ በስቃይ ይተኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህም ህይወቱ ምግብ ትጸየፋለች፣ ደግሞም ነፍሱ ምቾትን ትጠላለች
በመሰረቱ እነዚህ ሁለቱ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይኸውም ሰውየው መመገብ እንኳን እስከሚያቅተው ደረስ በታላቅ ስቃይ ውስጥ ነው ማለት ነው። ሰውየው የተገለጸው በ"ህይወቱ" እና በ"ነፍሱ" ነው። "ውጤቱ አንዳች የሚበላ አይፈልግም፣ እጅግ ምርጥ የሆነውን ምግብ እንኳን አይፈልግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
ምቾትን መጸየፍ
"እጅግ ምርጥ የሆነውን ምግብ እንኳን መጥላት"
Job 33:21
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
ስጋው በአካሉ ላይ እስከማይታይ ደረስ ይሟሽሻል፣ በአንድ ወቅት የማይታዩ የነበሩ አጥንቶቹ አሁን ወጥተው ይታያሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ስጋው" የሚለው የሚያመለክተው ውፍራቱን እና ጡንቻዎቹን እንጂ የውጭ ሰውነቱን ቆዳ አይደለም። "በሽታ አጥንቶቹ እስኪታዩ ደረስ ሰውነቱን ደካማ እና ከሲታ አድርጎታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ነፍሱ ወደ ጉድጓድ ተቃርባለች
እዚህ ስፍራ ሰውየው የተገለጸው በ"ነፍሱ" ነው። "ወደ መቃብር ሊወርድ ተቃርቧል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ጉድጓድ
ሰዎች ሲሞቱ የሚሄዱበት ስፍራ እዚህ ላይ "ጉድጓድ" ተብሎ ተጠቅሷል። "የሞቱ ሰዎች የሚገኙበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ህይወቱ ሊያጠፏት ለሚፈልጉ
እዚህ ስፍራ ሰውየው የተገለጸው በ"ነፍሱ" ነው። "ህይወቱ ሊያጠፏት ለሚፈልጉ" የሚለው ሀረግ ሰዎች ከሞቱ በኋላ የሚሄዱበትን ስፍራ ያመለክታል። "እናም የሞቱ ሰዎች ወደሚሄዱበት ስፍራ ለመሄድ ቅርብ ነው" ወይም "እናም በቅርቡ ወደ ሙታን ስፍራ ይሄዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 33:23
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
ለእርሱ
ይህ አንድን የተለየ ሰው አያመለክትም። ኤሊሁ ስለማንኛውም ሰው በአጠቃላይ መናገሩን ይቀጥላል።
ከሺህ መላዕክት መሃል
በአንዳንድ ቋንቋዎች "በብዙ ሺህ" ከማለት ይልቅ "ብዙ/አእላፋት" ማለቱ ይበልጥ ተገቢ ይሆናል። "ከብዙ መላዕክት መሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ጉድጓድ
ሰዎች ሲሞቱ የሚሄዱበት ስፍራ እዚህ ላይ "ጉድጓድ" ተብሎ ተጠቅሷል። "የሞቱ ሰዎች የሚገኙት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ለእርሱ መቤዣ አገኛለሁ
ይህ ማለት መላዕክት ሰውየው እንዳይሞት ለኃጢአቱ ክፍያ የሚያደርጉበት መንገድ ያገኛሉ ማለት ነው። "እርሱ እንዳይሞት የምታደርግበትን መንገድ እኔ ለአንተ አግኝቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 33:25
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
ከዚያም
"ከዚይም" የሚለው ቃል እዚህ ስፍራ የዋለው እግዚአብሔር ለመላዕክቱ ጥያቄ ምላሽ ቢሰጥ ምን እንደሚሆን ለማመልከት ነው። "ከዚያም በውጤቱ" ወይም "መላዕክቱ ለእግዚአብሔር ከሚያቀርቡት ጥያቄ የተነሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ስጋው ከትንሽ ልጅ ገላ ይልቅ አዲስ ይሆናል
ይህ የሚናገረው የተፈወሰው ሰው አካሉ እንደ ህጻን አካል ታድሰሶ ዳግም እንደሚታደስ ነው። "የታመመው ሰው አካል ዳግም እንደ ወጣት ሰው አካል ይታደሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከልጅ ይልቅ ታድሶ
በዚህ ንጽጽር፣ "አዲስ" የሚለው ቃል ግነት ነው። "እንደ ልጅ አዲስ ገላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
የልጅ
ይህ የሚያመለክተው የልጅን ገላ ነው። "የልጅ ገላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ወጣትነቱ ቀናት ጥንካሬ ይመለሳል
ይህ የሚናገረው ሰውየው ዳግም ወጣት እንደነበረበት ዘመኑ ጥንካሬ ያንኑ የወጣትነት ዘመኑን ብርታት እንደሚይዝ ነው። "ወጣት እንደነበረበት ዘመን ዳግም ብርቱ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔርን ፊት በደስታ ይመለከታል
ይህ ፈሊጥ ነው። "በደስታ እግዚአብሔርን ያመልካል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ፊት
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የተገለጸው በ "ፊቱ" ነው። "እግዚአብሔር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ለሰው ድል ይሰጣል
"እግዚአብሔር ሰውን ያድናል" ወይም "እግዚአብሔር ለሰው ነገሮችን ዳግም ያስተካክላል"
Job 33:27
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
ነገር ግን ኃጢአቴ አልተቀጣም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ነገር ግን እግዚአብሔር ለሰራሁት ኃጢአት አልቀጣኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ነፍሴን ወደ ጉድጓድ ከመውረድ አዳናት
እዚህ ስፍራ ሰውየው የተገለጸው በ"ነፍሱ" ነው። "ከሞት እና ወደ ጉድጓድ ከመውረድ አዳነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ጉድጓድ
ሰዎች ሲሞቱ የሚሄዱበት ስፍራ እዚህ ላይ "ጉድጓድ" ተብሎ ተጠቅሷል። "የሞቱ ሰዎች የሚገኙት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ህይወቴ ብርሃን ማየቱን ይቀጥላል
እዚህ ስፍራ ሰውየው የተገለጸው በ"ህይወቱ" ነው። መኖር ደግሞ የተነገረው ብርሃንን ማየት ተደርጎ ነው። "መኖሬን እና የቀን ብርሃን ማየቴን እቀጥላለሁ" ወይም "መኖሬ ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 33:29
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
እነሆ
ኤሊሁ እዚህ ስፍራ ይህንን ቃል የሚጠቀመው ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር ኢዮብ ትኩረት እንዲሰጠው ለማድረግ ነው። "አድምጠኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ሁለቴ፣ አዎን፣ ሶስቴ እንኳን

ይህ ፈሊጥ ነው። "ደግሞ ደጋግሞ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ ነፍስ
ሰውየው የተገለጸው በ"ነፍሱ" ነው። "እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ነፍሱን ዳግም ከጉድጓድ ለመመለስ
ይህ የሚናገረው አንድ ሰው ሞቶ እንደ ነበረ እና ዳግም ከሞት አድኖ ወደ ህይወት እንደመመለስ አድርጎ ነው። "እርሱን ከሞት እና ወደ ጉድጓድ ከመውረድ መጠበቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጉድጓድ
ሰዎች ሲሞቱ የሚሄዱበት ስፍራ እዚህ ላይ "ጉድጓድ" ተብሎ ተጠቅሷል። "የሞቱ ሰዎች የሚገኙት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ምናልባት እርሱ የህይወት ብርሃን ይበራለት ይሆናል
ይህ ፈሊጥ ነው፤ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽም ይችላል። "ምናልባት አስካሁን በህይወት በመቆየቱ ደስተኛ ሊሆን ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 33:31
አጠቃላይ መረጃ:
ኤሊሁ ከኢዮብ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።
ኢዮብ ሆይ ልብ በል፣ ደግሞም አድምጠኝ
እነዚህ ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ኢዮብ ሆይ፣ በጥንቃቄ አድምጠኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ትክክል እንደሆንክ
ይህ ፈሊጥ ነው። "አንተ ቅን ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 34
Job 34:1
ኤሊሁም ቀጠለ
"ከዚያም፣ ኤሊሁ"
ኤሊሁ
ይህ የወንድ ስም በኢዮብ 32:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ቃሌን አድምጥ
"የምናገረውን ስማ"
እናንተ ጠቢባን ... እናንተ አዋቂዎች
ኤሊሁ ኢዮብን እና ወዳጆቹን እየተቸ ነው። በእርግጥ ጠቢባን ናቸው ብሎ አያስብም። (ምጸት የሚለውን ይመልከቱ)
ላንቃ/ምላስ የምግብ ጣዕም እንደሚለይበት ጆሮም ነገርን ይለያል
ኤሊሁ ይህንን ማለቱ ሰዎች የምግብን ጣዕም ለመለየት ምግቡን እንደሚቀምሱ ሁሉ ትክክል የሆነውን ከስህተት ለመለየት በጥንቃቄ ያደምጣሉ ማለቱ ነው። እዚህ ስፍራ ሰዎች የተጠቀሱት በ"ጆሯቸው" እና በ"ላንቃቸው/ምላሳቸው" የሆነው ሰዎች እንደሚያጣጥሙ እና እንደሚያደምጡ ትኩረት ለመስጠት ነው። "መልካም የሆነውን ምግብ ለመለየት እንደምንቀምስ ሁሉ፣ መልካም የሆነውን ቃል ከክፉው ለመለየት እናደምጣለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 34:4
አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።
እኛ
እዚህ ስፍራ "እኛ" የሚለው የሚያመለክተው ኤሊሁን፣ ኢዮብን፣ እና ሶስቱን ወዳጆቻቸውን ነው። (አካታች "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ መብቴን ገፎኛል/ቀምቶኛል
"ፍትህ ሊሰጠኝ አልፈቀደም"
ሀሰተኛ ተደርጌ ተቆጠርኩ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ሀሰተኛ አድርጎ ቆጥሮኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ቁስሌ የማይድን ነው
እዚህ ስፍራ የኢዮብ ህመም እና መከራ የተወሰደው እንደ "ቁስል" ተደርጎ ነው። "እኔ ታምሜያለሁ ማንም ሊፈውሰኝ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 34:7
አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።
እንደ ኢዮብ ያለ ሰው ማን ነው
ኤሊሁ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚያነሳው ኢዮብን ለመገሰጽ ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊቀርብ ይችላል። "እንደ ኢዮብ ያለ ሌላ ማንም ሰው የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ፌዝን እንደ ውሃ የሚጨልጥ/የሚጠጣ ማን ነው
ኤሊሁም ሰው ውሃ እንደሚጠጣ ያህል ኢዮብን በፌዝ እየከሰሰው ነው። "ውሃ እንደሚጠጣ ሰው ያህል እንደ ኢዮብ ማን አዘውትሮ በሌሎች ላይ ያፌዛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማን ከኃጢአተኛ ሰው ጋር ይሄዳል/ይራመዳል
እዚህ ስፍራ "መራመድ" የሚለው አንድ ሰው ለሚያደርገው ነገር ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ማን እንደ ኃጢአተኛ ሰው ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 34:10
አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ። እነዚህ እያንዳንዳቸው ቁጥሮች ትይዩ ሀረጎችን ይዘዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ አዋቂዎች
ኤሊሁ ኢዮብን እና ወዳጆቹን እየነቀፈ ነው። በእርግጥ ጠቢባን ናቸው ብሎ አያስብም። (ምፀት የሚለውን ዘይቤ ይመልከቱ)
ይህ ከእግዚአብሔር የራቀ ይሁን... ሁሉን ቻይ ከሆነው በደል የራቀ ይሁን
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ደግሞም በአንድ ላይ የቀረቡት እግዚአብሔር እንደማይሳሳት ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ከእርሱ የራቀ ይሁን" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር ስህተት ወይም ክፉ የሆነ ነገር አያደርግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)
እርሱ ለሰው ዋጋውን መልሶ ይከፍለዋል
ይህ ማለት እርሱ ለአንድ ሰው ለሰራው ስራ የሚገባውን ይከፍለዋል ማለት ነው። እዚህ ስፍራ "ስራ" የሚለው ቃል አንድ ሰው ለሰራው ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "እርሱ ለአንድ ሰው ለሰራው ስራ የሚገባውን መልሶ ይከፍለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ እያንዳንዱ ሰው የራሱን መንገዶች ላይ ያለውን ዋጋ እንዲያገኝ ያደርጋል
"በራሱ መንገዶች" የሚለው ሀረግ አንድ ሰው ህይወቱን እንዴት እንደሚኖር ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኤሊሁ ያንን እግዚአብሔር ለሰዎች የሚገባቸውን እንደሚሰጥ በትኩረት ይናገራል። "እርሱ እያንዳንዱ በኖረበት መሰረት ዋጋውን እንዲቀበል ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 34:13
አጠቃላ መረጃ:
ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።
በምድር ላይ እርሱን የሚከስ ማን አለ? ማን መላዋን ምድር በእርሱ ስር አደረገ?
እነዚህ ሁለቱም ቃለምልልሳዊ ጥያቄዎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ እናም፣ ቀድሞኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ማንም የእግዚአብሔርን ስልጣን እንደማያረጋግጥለት ትኩረት ሰጥተው ይገልጻሉ። እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፉ ይችላሉ። "በመላው ምድር ላይ ያሻውን እንዲያደርግ ማንም ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሊሰጠው አያስፈልግም። እርሱ ምድርን ለመግዛት ሙሉ ስልጣን አለው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መቼም ቢሆን

ኤሊሁ እርሱ የማያምንበት ሁኔታ በፍጹም ሊሆን እንደማይችል ይገልጻል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ መንፈስ እና እስትንፋሱ

ሁሉንም ህያዋን ነገሮች በህይወት የሚያኖረው የእግዚአብሔር "መንፈስ" እና "እስትንፋስ" ነው። "ለእኛ ህይወት የሰጠን የእርሱ መንፈስ እና እስትንፋስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስጋ ለባሽ ሁሉ

እዚህ ስፍራ ህይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ የተወከሉት በ"ስጋቸው" ነው። "ህይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክዶክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰው የሆነ ሁሉ/ የሰው ልጅ ወደ አፈር ይመለሳል

ይህ ማለት ሁሉም ሰው ይሞታል፤ አካሉም በስብሶ አፈር ይሆናል። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ከአፈር ነው። "የሰው ልጅ አካል በቶሎ ተመልሶ አፈር ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:16

አጠቃላ መረጃ:

ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እነሆ

ኤሊሁ ይህንን ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ወደሚናገረው ጠቃሚ ነገር ትኩረት ለመሳብ ነው።

አንተ አለህ

እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው ተውላጠ ስም ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው ኢዮብን ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

የቃሌን ድምጾች ስማ

"የምናገረውን ስማ" ይህ ማለት ከዐረፍተ ነገሩ የመጀሪያ ክፍል ጋር ተመሳሳይ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህን የሚጠላ ያስተዳድራልን? አንተ ጻድቅ እና ታላቅ የሆነውን እግዚአብሔርን ትከሳለህን?

ኤሊሁ ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው እግዚአብሔር ፍትህን ይጠላል ብለሃል በማለት ኢዮብን ለመገሰጽ ነው። "ፍትህን የሚጠላ በሰዎች ላይ ይገዛል ተብሎ ሊጠበቅ አይችልም። ስለዚህም አንተ ጻድቅ እና ሃያል የሆነውን እግዚአብሔርን በእርግጥ ልትወቅስ አትችልም፤ ደግሞም እርሱ የሚያደርገውን ስህተት ነው ልትል አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህን የሚጠላ ያስተዳድራልን?

ለዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በውስጠታዋቂነት የተሰጠው ምላሽ "አይችልም" የሚል ነው። ይህ ጥያቄ የሚያሳየው እግዚአብሔር ፍትህን ቢጠላ ኖሮ አለምን ሊገዛ አይችልም ነበር የሚል ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ፍትህን የሚጠላ ዓለምን ሊገዛ አይችልም" ወይም "በእርግጥ እግዚአብሔር በፍጹም ትክክል የሆነውን ሊጠላ እና ዓለምን ሊገዛ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጻድቅ እና ታላቅ የሆነውን እግዚአብሔርን ትወቅሳለህን?

ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው ኢዮብ እግዚአብሔርን ለመውቀስ ስልጣን ወይም ምክንያት እንደሌለው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ጻድቅ እና ታላቅ የሆነውን እግዚአብሔርን ልትወቅስ አትችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:18

አጠቃላ መረጃ:

ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እንደ እግዚአብሔር ንጉሡን 'አንተ የማትረባ ነህ' ወይም ከበርቴውን 'አንተ ደካማ ነህ' የሚል ማን ነው?

ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ ኢዮብ እግዚአብሔርን ሊወቅስ እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ከቀደመው ጥቅስ ይቀጥላል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ ንጉሡን 'አንተ የማትረባ ነህ' ይላል ከበርቴውንም 'አንተ ደካማ ነህ' ይለዋል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉሡን የሚናገር፣ እግዚአብሔር

ይህ የቀደመው ጥያቄ ክፍል ነው። ከቀደመው ክፍል መረዳት እንደሚቻለው "አንተ እግዚአብሔርን ትውቀሳለህን" የሚለው ሊጨመር ይችላል። "አንተ ንጉሡን የሚናገረውን እግዚአብሔርን ትወቅሳለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

የማይረባ

"ክፉ" ወይም "ዋጋ የሌለው"

እነርሱ የእጆቹ ስራዎች ናቸውና

እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚወክለው ሀይልን ነው። "እግዚአብሔር ሁሉንም አበጅቷልና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእኩለ ሌሊት

እኩለ ሌሊት አንዱ ቀን የሚያበቃበት እና ሌላው ቀን የሚጀምርበት ጊዜ ነው። እዚህ ስፍራ "እኩለ ሌሊት" የሚለው ያገለገለው እንደ ፈሊጣዊ አነጋገር ሆኖ ነው። "በምሽት" ወይም "ድንገት በምሽት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎች ይርዳሉ/ይንቀጠቀጣሉ ደግሞም ያልፋሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ይንቀጠቀጣሉ" የሚለው ሀረግ "ይሞታሉ" ለሚለው ፈሊጣዊ አገላለጽ ነው። "እግዚአብሔር ይመታቸዋል ይሞታሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ታላላቅ ሰዎች ይወሰዳሉ፣ ነገር ግን በሰዎች እጆች አይደለም

ይህ ማለት ሰዎች የሚሞቱት በእግዚአብሔር እንጂ በሰዎች አይደለም ማለት ነው። ይህም ደግሞ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ብዙ ሰዎች እንዲሞቱ ምክንያቱ እግዚአብሔር እንጂ ሰዎች አይደሉም" (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በሰዎች እጅ አይደለም

እዚህ ስፍራ ሰዎች የተወከሉት በ"እጆቻቸው" ነው። "በሰውልጅ አይደለም" ወይም "በሰዎች አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክዶክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:21

የእግዚአብሔር ዐይኖች በሰው መንገዶች ላይ ነው

የእግዚአብሔር "ዐይኖች" የሚወክለው የእርሱን እይታ ነው። "የሰው መንገዶች" የሚለው ሀረግ ለሚያደርገው እና ለአኗኗሩ ፈሊጥ ነው። "እግዚአብሔር ሰው የሚያደርገውን ነገር ሁሉ ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ እርምጃዎቹን ሁሉ ይመለከታል

ይህ ማለት እርሱ ሁሌም አንድ ሰው የት እንደሚገኝ እና ወዴት እንደሚሄድ ያውቃል። "እርሱ ሰው ወዴት እንደሚሄድ ይመለከታል/የሰውን መንገድ ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ጨለማ የለም፣ ጥልቅ ጨለማም የለም

"ጥልቅ ጨለማ" የሚሉት ቃላት "ጨለማ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ለጨለማው ጥልቀት ሰጥቶ ለመግለጽ የዋለ ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በፍርድ

"ስለዚህ እርሱ ይፈርድበታል" ወይም "ፍርድ ለመቀበል"

Job 34:24

አጠቃላ መረጃ:

ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እርሱ ታላላቅ ሰዎችን ይሰባብራቸዋል

ይህ የሚገልጸው እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች አጥንታቸውን እንደሚሰባብር አድርጎ እንደሚያጠፋቸው ነው። "እርሱ ታላላቅ ሰዎችን ይደመስሳል" ወይም "እርሱ ከፍ ያሉትን ይደመስሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለመንገዳቸው ተጨማሪ ምርመራ አያስፈልገውም

እርሱ ያደረጉትን ጨምሮ መመርመር አያስፈልገውም ምክንያቱም ስለ እነርሱ ሁሉንም አስቀድሞ ያውቃል። "መንገዳቸውን አስቀድሞ ስለሚያውቅ፣ ተጨማሪ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ምርመራ ማድረግ ሳያስፈልግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዶቻቸውን

ይህ ፈሊጥ ነው። "እነርሱ ያደረጓቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ሌሎችን በእነርሱ ስፍራ ያስቀምጣል

ይህ ማለት ሌሎች ሰዎች በእነርሱ ስፍራ ተቀምጠው እንዲመሩ ይሾማል። "እናም ሌሎች ሰዎች በእነርሱ ስፍራ እንዲመሩ ይመርጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በምሽት

ይህ ፈሊጥ ነው። "እነርሱ ነገሩን በማይጠብቁበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይጠፋሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እናም ያጠፋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:26

አጠቃላ መረጃ፡

ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

ሌሎች በግልጽ እየተመለከቱ፣ እንደ ወንጀለኛ ስለ ክፉ ስራቸው እርሱ ይገድላቸዋል

ይህ ሀረግ እነዚህ ሰዎች የሚሞቱበትን መንገድ ወንጀለኞች ከሚሞቱበት ሁኔታ ጋር ያነጻጽራል። "ወንጀለኞች የሆኑ ያህል በሰዎች ፊት እነርሱን ስለ ክፉ ስራቸው ይገድላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሌሎች በግልጽ እየተመለከቱ

ይህ ፈሊጥ ነው። "ሁሉም ሰው ሊመለከተው በሚችለው ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይገድላቸዋል

ይህ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ራሱ በሰይፍ ባይመታቸውም፣ እነዚህን ሰዎች እርሱ እንደሚገድላቸው ይገልጻል። ሌሎች ሰዎች እንዲገድሏቸው ሊያደርግ ወይም ጥፋት በላያቸው እንዲመጣባቸው ይችላል። "እንዲሞቱ ያደርጋል" ይህ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ራሱ በሰይፍ ባይመታቸውም፣ እነዚህን ሰዎች እርሱ እንደሚገድላቸው ይገልጻል። ሌሎች ሰዎች እንዲገድሏቸው ሊያደርግ ወይም ጥፋት በላያቸው እንዲመጣባቸው ይችላል። "እንዲሞቱ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ መንገዶች

ይህ ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛ ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ የድሆች ጩኸት ወደ እርሱ እንዲመጣ አድርገዋል

"ጩኸት" የሚለው ቃል በግስ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር ጩኸታቸውን የሚሰማው ጩኸቱ ራሱ ሰው ሆኖ ወደ እርሱ እንደመጣ አድርጎ ነው። "እነርሱ ድሆችን አስለቅሰዋል፣ እግዚአብሔርም የድሆችን ጩኸት ሰምቷል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Job 34:29

አጠቃላ መረጃ፡

ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እርሱ ዝም ሲል፣ ማን ሊወቅሰው ይችላል?

ኤሊሁ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብን ለማስተማር ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ ዝም ለማለት ከወሰነ ማንም እግዚአብሔርን ሊተቸው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ፊት

እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የተገለጸው በ"ፊቱ" ነው። "እርሱ ራሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም ሰዎችን እያጠምድም

ይህ አዳኝ እንስሳ እንደሚያድን ሁሉ አምላክ የለሽ መሪ ሰዎችን ከመጉዳቱ ጋር ያነጻጽራል። "ማንም ሰዎችን እንዳይጎዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 34:31

አጠቃላ መረጃ፡

ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

ማየት የማልችለውን አስተምረኝ

እዚህ ስፍራ "ማየት" ማለት ማወቅ ማለት ነው። "ሳላውቅ የሰራሁትን ስህተት አሳየኝ/አስተምረኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ እግዚአብሔር የሚያደርገውን እስከጠላህ ድረስ እርሱ የዚያን ሰው ኃጢአት ይቀጣል ብለህ ታስባለህን?

"እግዚአብሔር የሚያደርገውን እስከጠላህ ድረስ፣ እግዚአብሔር የዚህን ሰው ኃጢአት መቅጣት ይገባዋል ብለህ ታስባለህን?" ኤሊሁ ይህን ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው እግዚአብሔር ይህንን ሰው አይቀጣውም ብሎ ማሰብ አይኖርበትም የሚለውን ለማጉላት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ምንም እንኳን እግዚአብሔር ያደረገውን አንተ ባትወደውም፣ በእርግጥ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ይህንን ሰው ይቀጣዋል ብለህ ባታስብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የዚያ ሰው ኃጢአት

እዚህ ስፍራ ሰውን በኃጢአቱ ምክንያት መቅጣት የተጠቀሰው "የሰውየውን ኃጢአት" መቅጣት ተደርጎ ነው። "ያ ሰው በኃጢአቱ ምክንያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ እስካልወደድክ ድረስ

"አንተ ባለመውደድህ ምክንያት"

ይህ አንተ የምታውቀው ምንድን ነው

"ስለዚህ አንተ የምታስበው"

Job 34:34

አጠቃላ መረጃ፡

ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እኔን የሚሰሙኝ

"ስናገር የሚሰሙኝ እነርሱ"

Job 34:36

ኢዮብ በፈተና ቢቀመጥ ኖሮ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኛ ኢዮብን በፈተና ሊናስቀምጠው ብንችል ኖሮ" ወይም "ኢዮብን ወደ ፍርድቤት ልናቀርበው ብንችል እና ዳኛ ሊያደምጠው ቢችል ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በትናንሽ ዝርዝር ጉዳዮቹ

ይህ ፈሊጥ ነው። "ጉዳዮቹን በጥልቀት ለመስማት" ወይም "የእርሱን ጉዳዮች በሙሉ በዝርዝር ለመስማት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ ንግግር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ክፉ ሰዎች የሆነውን ንግግሩን

"እንዴት እንደ ክፉ ሰው እንደተናገረ"

አመጽን ጨምሯል

ይህ በእግዚአብሔር ላይ ማመጽን ያመለክታል። "እርሱ በእግዚአብሔር ላይ አመጽ ጨምሯል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በመሃከላችን ሆኖ በፌዝ እጆቹን አጨብጭቧል

በዚህ ክስ፣ ኢዮብ አጨበጨበ የተባለው በእግዚአብሔር ላይ አፊዟል የሚባለውን ለማጠናከር ነው። "በመካከላችን ሆኖ በእግዚአብሔር ሲያፌዝ እጆቹን አጨብጭቧል" ወይም "በፊት ለፊታችን በእግዚአብሔር ላይ አፊዟል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እንዲሁም ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚሉትን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ላይ ብዙ ተናግሯል

ኤሊሁ ስለ "ቃላት" ሲናገር ቁሶች እንደሆኑ አድርጎ ነው፤ ብዙ ቃላትን ስለመናገር ሲናገርም እነዚያን ቁሶች አንዱን በሌላው ላይ እንደመከምር አድርጎ ነው። "እርሱ በእግዚአብሔር ላይ ብዙ ቃላትን ተናግሯል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 35

Job 35:1

ይህ ፍትህ ነው… 'በእግዚአብሔር ፊት ያለኝ መብት ነው' ብለህ ታስባለህ?

ኤሊሁ ኢዮብን ለመገዳደር ጥያቄዎችን ያነሳል። "አንተ ትክክል እንደሆንክ ታስባለህ… 'በእግዚአብሔር ፊት መብቴ ነው'" ትላለህ ወይም "ይህ ልክ አይደለም…'በእግዚአብሔር ፊት መብቴ ነው'" ትላለህ። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህን በማለትህ ልክ የሆንክ ይመስልሃል

"አንተ ይህን ማለትህ ልክ ይመስልሃል"

ይመስልሃል/እንዲህ ታስባለህ

እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም ኢዮብን ነው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም መልኮች የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ፊት ያለኝ መብት

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢዮብ በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ መሆኑን እየተናገረ ነው። ወይም 2) ኢዮብ ከእግዚአብሔር ይልቅ እኔ ትክክል ነኝ እያለ ነው።

አንተ 'ይህ ለእኔ ምን ጥቅም አለው?' ብለህ ጠይቀሃል። ደግሞም፣ 'ኃጢአት ባለመስራቴ ምን አተረፍኩ?' ብለሃል።

ኤሊሁ ኢዮብ እነዚህን ሁለት ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች እንዳነሳ ይጠቅሳል። "አንተ እንዲህ ብለሃል፣ 'ይህ እኔን አልጠቀመኝም' ደግሞም፣ 'ኃጢአት ብሰራ ከሚደርስብኝ ምንም የተሻለ አልሆነልኝም/ኃጢአት ባለመስራቴ አልተጠቀምኩም'" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 35:4

አጠቃላ መረጃ፡

ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

Job 35:6

አጠቃላ መረጃ፡

ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

ኃጢአት ብትሰራ… በእርሱ ላይ ምን ታደርጋለህ/ትጨምራለህ?

እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። ሁተኛው መስመር የመጀመሪያውን መስመር ትርጉም ያጠናክራል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኃጢአት ብትሰራ፣ እግዚአብሔርን ምን ተጎዳዋለህ?

ኤሊሁ ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው የኢዮብ ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ አንዳች ነገር እንደማያመጣ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ኃጢአት ብትሰራ፣ እግዚአብሔርን አንዳች አትጎዳውም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መተላለፍህ ወደ ላይ ቢከመር፣ እርሱን ምን ታደርገዋለህ?

ኤሊሁ ስለ "መተላለፎች" የሚናገረው ቁሶች እንደሆኑ አድርጎ ነው፤ ብዙ መተላለፎችን ማድረግ ደግሞ እነዚህን ቁሶች አንዱን በሌላው ጫፍ ወደ ላይ መከመር እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮብ በመተላለፉ በእግዚአብሔር ላይ አንዳች ማምጣት ማድረግ እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው። "አንተ ብዙ ታላላቅ መተላለፎችን ብትፈጽም፣ በእርሱ ላይ አንዳች ማድረግ አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጻድቅ ብትሆን፣ ለእርሱ ምን ልትሰጠው ትችላለህ? እርሱ ከአንተ እጅ ምን ይቀበላል?

ሁለቱ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ናቸው፤ ሁለቱም የሚገልጹት የኢዮብ ጽድቅ ለእግዚአብሔር አንዳች ነገር እንደማይጨምር ነው። "አንተ ጻድቅ ብትሆን፣ ይህ አንተ ለእርሱ አንዳች ነገር እንድትሰጠው አያበቃህም፤ ደግሞም እርሱ ከአንተ እጅ የሚቀበለው አንዳች ነገር የለም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከአንተ እጅ መቀበል

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚወክለው ኢዮብን ነው። "ከአንተ እጅ መቀበል"

ሌላ የሰው ልጅ

"ሌላ የሰው ልጅ" ወይም "ሌላ ሰው"

Job 35:9

አጠቃላ መረጃ፡

ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

በብዙ የተጽዕኖ ድርጊቶች ምክንያት

"ተጽዕኖ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች ሌሎችን ለመጨቆን በሚያደርጓቸው በርካታ ነገሮች ምክንያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከታላላቅ ሰዎች ክንዶች እርዳታን ይፈልጋሉ

እዚህ ስፍራ "ክንዶች" የሚለው የሚያመለክተው ሀይልን ወይም ጥንካሬን ነው። "ከታላላቅ ሰዎች ሀይል ለማግኘት ጥሪ ያደርጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በምሽት ዝማሬዎችን የሚሰጥ ማን ነው

ኤሊሁ እግዚአብሔር ለሰዎች በችግር ጊዜ፣ በምሽት ሰአት የሚዘምሩት ዝማሬ አድርጎ ተስፋን እንደሚሰጥ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Job 35:12

አጠቃላ መረጃ፡

ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

እነርሱ ይጮሃሉ

"የተጨቆኑ ሰዎች ይጮሃሉ"

አንተ እርሱን ከምትጠባበቅበት… ምን ያህል ያነሰ ነገር ይመልስልሃል!

እግዚአብሔር የትዕቢተኞችን እና የክፉዎችን ጸሎት ስለማይሰማ፣ ይልቁንም ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር ላይ የተነሳውን የኢዮብን ጸሎት ይሰማል አይባልም። "ስለዚህ አንተ በትጠባበቀውም…እርሱ በእርግጥ ምላሽ አይሰጥህም!" (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ጉዳይ በፊቱ ነው

"አንተ ጉዳይህን ለእርሱ አቅርበሃል"

አንተ እርሱን እየጠበቅህ ነው

" አንተ እርሱን እንዲመልስልህ እየጠበቅህ ነው"

Job 35:15

አጠቃላ መረጃ፡

ኤሊሁ ንግግሩን ቀጠለ።

አሁን አንተ የእርሱ ቁጣ ቅጣት አያደርስም ብለሃል፣ ስለ መተላለፍ ጥቂት እርምጃ እንኳን አይወስድም ብለሃል

ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር እውነት ያልሆኑ እነዚህን ነገሮች በመናገሩ ምክንያት፤ እግዚአብሔር ለኢዮብ ጸሎት ምላሽ አይሰጥም።

የእርሱ ቁጣ ቅጣት አያስከትልም

እዚህ ስፍራ "የእርሱ ቁጣ" የሚለው "እርሱ" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እርሱ በመቆጣቱ ምክንያት በፍጹም ማንንም አይቀጣም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ( ይመልከቱ)

ያለ ዕውቀት ቃሎችን ደርድሯል/ብዙ ቃሎችን ተናግሯል

ኤሊሁ ስለ "ቃላት" ሲናገር ቁሶች እንደሆኑ አድርጎ ነው፤ ብዙ ቃላትን ስለመናገር ሲናገርም እነዚያን ቁሶች አንዱን በሌላው ላይ እንደመከምር አድርጎ ነው። "እውቀት" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ስለ ምን እንደሚናገር ሳያውቅ ብዙ ቃላትን ተናግሯል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 36

Job 36:1

ጥቂት ነገሮችን አሳይሃለሁ

ኤሊሁ ለኢዮብ ነገሮችን ማስረዳትን የሚገልጸው እነዚያን ነገሮች ለኢዮብ እንደሚያሳየው አድርጎ ነው። "ጥቂት/አንዳንድ ነገሮችን አሳይሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እውቀት ከሩቅ ስፍራ አገኛለሁ

ኤሊሁ ስለ ተለያዩ ነገሮች እውቀትን ከሩቅ ስፍራ እንዳገኘ አድርጎ ይገልጻል። "ታላቁን እውቀቴን አሳይሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጽድቅ የሰራኝ/የፈጠረኝ የእርሱ መሆኑን

እዚህ ስፍራ "ጽድቅ" የሚለው በቅጽል መልኩ ሊተረጎም ይችላል። "ፈጣሪዬ/የሰራኝ ጻድቅ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Job 36:4
ቃሎቼ ሀሰት አይሆኑም
"እኔ የምናገረው ሀሰት አይሆንም"
በእውቀት የበሰለ አንድ ሰው ከአንተ ጋር አለ
"አንድ ሰው" የሚለው ቃል ኤሊሁ ራሱን ያመለክታል። በእውቀት የበሰለ በጣም አዋቂ ስለ መሆኑ ይናገራል። "እኔ፣ ከአንተ ጋር ያለሁት፣ በጣም በእውቀት የላቅሁ ነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ
"ተመልከት" ወይም "ስማ" ወይም "ልነግርህ ላለው ነገር ትኩረት ስጥ"
እርሱ በመረዳት ባለጸጋነቱ ሃያል ነው።
"በጥንካሬ ሃያል" የሚለው ሀረግ ጥንድ ትርጉም ይሰጣል፤ ይህም "በጣም ጠንካራ" ማለት ነው። ኤሊሁ ስለ እግዚአብሔር መረዳት/እውቀት ሁሉንም ነገር በፍጹምነት የሚናገረው የእርሱ መረዳት በጣም ጠንካራ እንደሆነ አድርጎ ነው። "እርሱ በመረዳቱ በጣም ጠንካራ ነው" ወይም "እርሱ ሁሉንም ነገር ሙሉ ለሙሉ ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 36:6
እርሱ ዐይኖቹን ከጻድቅ ሰው ላይ አያነሳም
ኤሊሁ እግዚአብሔር ለጻድቅ ሰው ሚያደርገውን ጥበቃ የመገልጸው እግዘአብሔር በዐይን እንደሚከታተላቸው አድርጎ ሲሆን እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የሚያደርገውን ጥበቃ ማቆሙን ደግሞ ዐይኖቹን ከላያቸው ማንሳት አድርጎ ይገልጸዋል። "እርሱ ጻድቃን ሰዎችን መጠበቁን አያቆምም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ንጉሥ በዙፋን ላይ ያስቀምጣቸዋል
ኤሊሁ እግዚአብሔር ለጻድቃን የሚሰጠውን ክብር የሚገልጸው እንደ ንጉሥ በዙፋን ላይ እንደሚያስቀምጣቸው አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ከፍ ይላሉ
ኤሊሁ እግዚአብሔር ጻድቃንን የሚያከብራቸው ከፍ ወዳለ ስፍራ እንደሚያወጣቸው አድርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍት ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ ወደ ላይ ከፍ ያደርጋቸዋል" ወይም "እርሱ ያከብራቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 36:8
እነርሱ በሰንሰለት ቢታሰሩ እንኳን
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ኃጢአት ቢሰሩ እግዚአብሔር ለእርማት የሚቀጣቸውን ጻድቃን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍት ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንዱ በሰንሰለት ቢያስራቸው" ወይም "አንዱ እስረኛ ቢያደርጋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በመከራ ገመድ ቢያጠምዳቸው
ኤሊሁ በስቃይ ውስጥ እንዲገባ የተደረገን ሰው የሚገልጸው፤ ያ ሰው በገመድ እንደተያዘ እና እንዲሰቃይ እንደተደረገ ነው። "አንዱ ሰው እነርሱ እንዲሰቃዩ አድርጓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
የእነርሱ መተላለፍ እና የእነርሱ ኩራት
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ሊገኝ ይችላል። "መተላለፋቸውን እና ኩራታቸውን ለእነርሱ ይገልጥላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 36:10
እርሱ ጆሯቸውንም ደግሞ ይከፍታል
ኤሊሁ የሚናገረው የአንድን ሰው ጆሮ መክፈት ሰውየው እንዲሰማ ማድረግ መሆኑን ነው። "እርሱ እንዲሰሙም አድርጓል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ትዕዛዝ
"ትዕዛዝ" የሚለው ስም በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ ለሚያዛቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ከክፋት መመለስ
ኤሊሁ አንድን ድርጊት ማቆም ከዚያ መመለስ አድርጎ ይናገራል። "ክፉ ከማድረግ መመለስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቀኖቻቸውን በብልጽግና ይፈጽማሉ፣ አመቶቻቸውንም በእርካታ
"ቀናት" እና "አመታት" የሚሉት ቃላት ሁለቱም የሚያመለክቱት የአንድን ሰው የህይወት ዘመን ነው። "ዘመናቸውን/እድሜያቸውን በብልጽግና እና በእርካታ ይፈጽማሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ በሰይፍ ይጠፋሉ
ኤሊሁም የሚናገረው በሀይል በሰይፍ ስለሚጠፋ ሰው፣ በሰይፍ አንድ ሰው ስለገደላቸው ሰዎች ነው። "በአመጽ ይገደላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 36:13
በልባቸው አምላክ የለሽ የሆኑ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው የሚያመለክተው ሃሳብን እና ስሜትን ነው። ይህ ሀረግ ሰውየው እግዚአብሔርን ማመንን በግትርነት መቃወመውን ነው።"በእግዚአብሔር ማመንን ማን ይቃወማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር በእንድ ላይ በሚያስራቸው ጊዜ እንኳን
ኤሊሁ እግዚአብሔር ሰዎችን መቅጣቱን በገመድ እንደሚያስራቸው አድርጎ ይገልጸዋል። "እግዚአብሔር በሚቀጣች ጊዜ እንኳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ህይወታቸው በቤተ ጣኦት አመንዝሮች መሃል ያከትማል
እዚህ ስፍራ "የቤተ ጣኦት አመንዝሮች" የሚለው የሚያመለክተው በጣኦት አምልኮ ቤተመቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉ ወጣት ወንዶች የአምልኳቸው ክፍል አድርገው የሚፈጽሙትን ስነምግባር የሌለው ወሲባዊ ድርጊት ነው። ለዚህ ሀረግ ሊሰጡ የሚችሉ አማራጭ ትርጉሞች 1) አምላክ የለሾች ስነምግባር በሌለው ባህሪያቸው መሞታቸውን ወይም 2) አምላክ የለሾች በሀፍረት እና በውርደት ይሞታሉ።
Job 36:15
እርሱ ጆሮዎቻቸውን ከፍቷል
ኤሊሁ ያለ ችግር በሰፊ መከራ በሌለበት በሰፊ መኖርን ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ገበታህ ስብ በበዛበት ማዕድ ይሞላል
ኤሊሁ የሚናገረው ገበታ በምርጥ ምግቦች ተሞልቶ በብልጽግና ስለመኖር ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ገበታህ ይዘጋጃል
ይህ በአድራጊ ዐረፍት ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አገልጋዮችህ ገበታህን ያዘጋጃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በስብ የተሞላ ምግብ
ብዙ ስብ ያለው ስጋ የብልጽግና ምልክት ነበር፣ ምክንያቱም እንስሳቱ ጤናማ እና በሚገባ የተመገቡ እንደነበሩ ያሳያል። "እጅግ ምርጥ የሆነ ምግብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 36:17
አንተ እንደ ክፉ ሰዎች በፍርድ ስር ነህ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እግዚአብሔር ክፉዎችን እንደሚቀጣ አንተንም እየቀጣ ነው" ወይም 2) "ክፉዎች በሚቀጡበት ቅጣት እየተቀጣህ ነው"
ፍርድ እና ብይን ይዘውሃል
ኤሊሁ እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ እየፈረደበት እንደሆነ እና ፍርድ እና ብይን ኢዮብን እንደያዙት ሰዎች አድርጎ ይናገራል። "እግዚአብሔር ወደ ፍርድ አምጥቶሃል ደግሞም ብይን ሰጥቶሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቁጣህ ወደ ፌዝ አይምራህ
አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ይህንን "በሀብት አለመማለልህን ተጠንቀቅ" ይላሉ።
Job 36:19
እንዳትጎዳ ሀብትህ ሊረዳህ ይችላልን፣ ወይም የጥንካሬህ ሀይል ሁሉ ሊያግዝህ ይችላል?
ኤሊሁ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቀው ገንዘብ እና ሀይል በትክክለኛ መንገድ እስካልሄደ ድረስ ኢዮብን ሊረዱት እንደማይችሉ ለመግለጽ ነው። "ሀብት ከመከራ ሊያወጣህ አይችልም፣ ደግሞም የትኛውም ሀይልና ጥንካሬ በሙሉ ሊረዳህ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄየሚለውን ይመልከቱ)
የአቅምህ ጥንካሬ በሙሉ
"የታላቅ አቅምህ ጥንካሬ በሙሉ" ወይም "ታላቅ ጥረትህ በሙሉ"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሰዎች ከስፍራቸው ሲወገዱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ "ሰዎች" የሚለው በአጠቃላይ ሰዎችን ያመለክታል፣ "ከስፍራቸው ይቆረጣሉ" የሚለው ደግሞ ሌሎችን ከቤታቸው በሀይል ማስወገድን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። "ሰዎች ሌሎችን ከቤታቸው ጎትተው ሲያስወጡ" ወይም 2) ይህ "ሰዎች" የሚለው የሚገልጸው አገርን ሲሆን "ከስፍራቸው ይቆረጣሉ" የሚለው ህዝቦች እንዲጠፉ መደረጋቸውን ይገልጻል። "አገራት ሲጠፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ በመከራ እየተፈተንክ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "መከራ እንድትቀበል በማድረግ እግዚአብሔር እየፈተነህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 36:22
እነሆ፣ እግዚአብሔር
"ይህንን አስቀድሞውኑ ታውቃለህ፡ እግዚአብሔር"
እግዚአብሔር በሀይሉ ከፍ ያለ ነው
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እግዚአብሔር እጅግ ሀያል ነው" ወይም 2) "ሰዎች እግዚአብሔርን ከፍ ያደርጋሉ ምክንያቱም እርሱ ሀያል ነው"
እንደ እርሱ አስተማሪ ማን ነው?
ኤሊሁ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው እንደ እግዚአብሔር ያለ አስተማሪ የለም የሚለውን ለማጉላት ነው። "እንደ እርሱ ያለ አስተማሪ የለም" ወይም "እርሱ እንደሚያስተምር የሚያስተምር ማንም የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄየሚለውን ይመልከቱ)
Job 36:25
እነርሱ እነዚያን ድርጊቶች የተመለከቱት ከርቀት ብቻ ነው
ኤሊሁም የእግዚአብሔርን ስራዎች ከርቀት ብቻ በመመልከታቸው፣ ስራዎቹን በሙላት ሊረዱ ስላልቻሉ ሰዎች ይናገራል። "እነርሱ ስራዎቹን በሙላት አልተረዱም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ
"ተመልከት" ወይም "ስማ" ወይም "ልነግርህ ለተዘጋጀሁት ነገር ትኩረት ስጥ"
የእርሱ ዘመናት ቁጥር አይሰላም
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ከመቼ አንስቶ እንደነበር ነው። "ሰዎች እርሱ ለምን ያህል ጊዜ እንደኖረ ማወቅ አይችሉም" ወይም "ሰዎች የእርሱን እድሜ ሊያውቁ አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 36:27
እርሱ ከእንፋሎቱ ዝናብ ያዘንባል/ያነጥራል
"ማንጠር" የሚለው ቃል "ማጥራት" ወይም "ማጣራት" ማለትም ሊሆን ይችላል። ኤሊሁ እግዚአብሔር እንዴት የውሃ ጠብታን፣ ወይም ተንን እንዴት ወደ ዝናብነት እንደሚለውጥ ይገልጻል። "እርሱ ተኑን ወደ ዝናብ ይለውጠዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የደመናዎችን ታላቅ መበተንት፣ ከእርሱ ጎጆ የሚወጣውን መብረቅ የሚረዳ አለን?
ኤሊሁ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ማንም እነዚህን ነገሮች ማድረግ እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው። "ማንም የደመናን መበተን እና ከእርሱ ጎጆ የሚወጣውን መብረቅ ሊረዳ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄየሚለውን ይመልከቱ)
የደመናዎችን ታላቅ መበተንት
"ታላቅ መበተንት" የሚለው ሀረግ በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "በሰማይ ሁሉ ላይ ደመና እንዴት እንደሚበተን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ከእርሱ ጎጆ
ኤሊሁ ሰማይን እግዚአብሔር እንደሚኖርበት "ጎጆ" አድርጎ ይገልጸዋል። "እግዚአብሔር ከሚኖርበት፣ ከሰማይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 36:30
እነሆ፣ እርሱ ይበትናቸዋል
"በጥንቃቄ ተመልከት፣ ደግሞም እንዴት እንደሚበትናቸው እይ"
እናም የባህርን ስሮች ይሸፍናል
ኤሊሁ ባህር ተክል እንደሆነ እና ጥልቅ ስፍራው ስሩ እንደሆነ አድርጎ ስለባህር ጥልቅ ክፍል ይናገራል። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ምንም እንኳን መብረቅ በሰማይ ብርሃን እንዲታይ ቢያደርግም፣ የባህር ጥልቅ ክፍሎች ግን ጨለማ እንደሆኑ ይቀራሉ። "ነገር ግን የባህር ጥልቅ ክፍል ጨለማ ሆኖ ይቀራል" ወይም 2) የሰማይ መብረቅ የባህር ጥልቅ ስፍራ ጭምር ብርሃን እንዲያገን ያደርጋል። "እናም ብርሃናት የባህርን ጥልቅ ስፍራ ያበራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 36:32
እጆቹን በመብረቅ ይሞላል
ኤሊሁ ነጎድጓድ ስለሚያመጣው መብረቅ እግዚአብሔር መብረቅን በእጆቹ እንደያዛቸው እና እርሱ ወደ ፈለገው አቅጣጫ እንደሚጥላቸው ይናገራል። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር የመብረቅን ሀይል ሊወረውራቸው በእጆቹ ይዟል፣ ወይም 2) እግዚአብሔር የመብረቅን ሀይል እስከሚጠቀምባቸው ድረስ በእጆቹ ደብቆ ይዟል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መብረቆቹ
"በብልጭታ የሚፈጠረው መብረቅ" ወይም "መብረቁ"
አድምጥ እየመጣ ነው
"ሞገዱ እየመጣ መሆኑን ስማ"

---

Chapter 37
Job 37:1
ልቤ ተንቀጠቀጠ... ከስፍራው ሸሸ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም የፍርሃቱን ክብደት ያጎላሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በዚህ ነገር ልቤ ራደ/ተንቀጠቀጠ
"ይህ" የሚለው የሚያመለክተው በኢዮብ 36:33 ላይ የሚገኘውን ነጎድጓ ነው
ከስፍራው ሸሸቷል
ኤሊሁ ስለ ልቡ የሚናገረው ከደረቱ የሚወጣ እስኪመስል በሃይል እንደሚመታ ነው። "ከስፍራው ለቀቀ" ወይም "በሃይል ይመታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
የድምጹ ነጎድጓድ፣ ከአፉ የሚወጣው ድምጽ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ነገሮችን ይናገራሉ። ኤሊሁ መብረቅን የእግዚአብሔር ድምጽ እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር እናትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
እስከ ምድር ዳርቻ ደረሰ
ኤሊሁ በምድር ሩቅ ስፍራ የሚገኘውን ቦታ የምድር ዳርቻ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። "በምድር በሁሉም ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 37:4
ከዚህ በኋላ ከፍ ያለ ድምጽ ይሰማል... የግርማው ድምጽ ይሰማል
ኤሊሁ ስለ ነጎድጓዱን እንደ እግዚአብሔር ድምጽ አድርጎ መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚህ በኋላ ያጉረመርማል
"ከብልጭታው በኋላ ያጉረመርማል"
የግርማዊነቱ ድምጽ
"የእርሱ ግርማዊነት ድምጽ"
ድምጹ በሚሰማበት ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ድምጹን በሚሰሙበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ልክ እንደዚሁ ለዶፍ ዝናብ
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። "ልክ እንደዚሁ፣ ለዶፍ ዝናብ ይናገረዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ ሚለውን ይመልከቱ)
Job 37:7
እርሱ የሁሉንም ሰው እጅ ያቆማል
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚወክለው መላውን ሰውነት ነው። "እርሱ ሁሉንም ሰው ያስቆማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር

ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ሀይለኛው ዝናብ በደቡብ ካለው ማደሪያው ይወጣል፣ በረዶም/ቅዝቃዜ በሰሜን ካለው የተበታተነ ነፋስ ይወጣል
በእስራኤል፣ ጠንካራ የነፋስ ማዕበል ከደቡብ ይነፍሳል፤ ቀዝቃዛ አየር ደግሞ ከሰሜን ይመጣል፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ማዕበል በደቡብ ካለው ማደሪያው ይመጣል
ኤሊሁ አውሎ ነፋሱ እስኪመጣ ድረስ ማደሪያ ስፍራ እንዳለው አድርጎ እና ከደቡብ እንደሚነፍስ ይናገራል፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 37:10
በእግዚአብሔር እስትንፋስ በረዶ ይሆናል
ኤሊሁ ቀዝቃዛው የሰሜን ነፋስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ እንደሆነ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ "የእግዚአብሔር እስትንፋስ በረዶ ይሰጣል/ ይፈጥራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
እንደ ብረት ይጋገራል
ኤሊሁ የበረዶን ጥንካሬ ከብረት ጥንካሬ ጋር ያነጻጽራል፡፡ "እንደ ብረት ይጋገራል" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ክምሩን ደመና እርጥበት ያሸክመዋል
ኤሊሁ እግዚአብሔር የደመናው ማዕበል እርጥበቱ ከብዶ በውሃ እንዲሞላ ማድረጉን ይናገራል፡፡ "እርሱ ከባዱ ደመና በእርጥበት እንዲሞላ ያደርጋል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 37:12
አንዳንድ ጊዜ ይህ ለእርማት ይሆናል
"እርማት/ቅጣት" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "የሚያርመው" አካል ሰዎች ናቸው። "አንዳንድ ጊዜ ህዝቡን ለመቅጣት ይህ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
አንዳንድ ጊዜ ለምድሩ
ይህ ማለት ዝናብ ምድሩን አጠጥቶ ሰብል እንዲበቅል ያደርጋል፡፡ "አንዳንድ ጊዜ ምድሩን ለማጠጣት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አንዳንድ ጊዜ እንደ ቃል ኪዳን ታማኝነት ተግባር
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ታማኝ"ነ ወይም "በታማኝነት" ተብሎ ሊጻፍ ይችላል፡፡ "አንዳንድ ጊዜ በታማኝነት ለቃል ኪዳኑ ለማድረግ" ወይም "አንዳንድ ጊዜ ለህዝቡ ታማኝ ለመሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Job 37:14
እግዚአብሔር ደመናትን እንዴት እንደሰራ ደግሞም የመብረቆችን ብልጭታ እንዳበጀ ታውቃለህን?
ኤሊሁ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮብ ይህን ማወቅ እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡ "እግዚአብሔር እንዴት ደመናትን እንደሚያበጅ እና እንዴት መብረቅን እንደሚያበርቅ ልታውቅ አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
ደመናትን መስራት
"ደመናትን መቆጣጠር" ወይም "ደመናት እርሱን እንዲታዘዙለት እንደሚያደርግ"
Job 37:16
በእውቀቱ ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ስራዎች፣ የደመናትን መንሳፈፍ ማወቅ ትችላለህ?
ኤሊሁ ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮብ እነዚህን ነገሮች ማወቅ እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡ "በእውቀት ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ስራዎች፣ የደመናትን መንሳፈፍ፣ መረዳት አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
የደማናትን መንሳፈፍ
"ደመናት እንዴት እንደሚንሳፈፉ"
የእግዚአብሔርን አስደናቂ ስራዎች
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ሊገኝ ይችላል፡፡ "ወይስ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ስራዎች ትረዳለህን?" ወይም "ደግሞም የእግዚአብሔርን አስደናቂ ስራዎች ልተረዳ አትችልም" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
ከደቡብ በሚመጣ... እንዴት ልብስህ እንደሚወብቅህ/እንደሚሞቅህ ትረዳለህ?
ኤሊሁ ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮብ እነዚህን ነገሮች እንደማያውቅ ትኩረት ለመስጠት ነው። "ከደቡብ በሚመጣ...ልብሶችን እንዴት እንደሚወብቁህ አታውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
ልብሶችህ እንዴት እንደሚወብቁህ/እንደሚሞቁህ
"የለበስከው እንዴት ወበቅ እንደሚፈጥርብህ" ወይም "በልብስህ ውስጥ እንዴት እንደሚያልብህ"
ነፋሱ ከደቡብ አቀጣጫ ከመምጣቱ/ከመንፈሱ የተነሳ
በእስራኤል፣ ሞቃት ነፋስ የሚፍሰው ከደቡብ በረሃ ሲሆን ይህም ሞቃት የሙቀት መጠን ይፈጥራል፡፡ "ከሙቀቱ የተነሳ፣ ከደቡብ ደረቅ ነፋስ ይነፍሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 37:18
ከብረት እንደተሰራ መስታወት...ሰማይን ልትዘረጋ ትችላለህ?
ኤሊሁ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮብ ይህን ማድረግ እንደማይችል ትኩረት ሰጥቶ ለመናገር ነው፡፡ ከብረት የተሰራ መስታወት የሚመስለውን ሰማይ...አንተ ሰማይን ልትረረጋ አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
ከብረት እንደ ተደተሰራ መስታወት ጥንካሬ ያለው
መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈባቸው ዘመናት፣ መስታወት የሚሰራው ከብረት ነበር፡፡ ኤሊሁ ሰማዩ እንደ ብረት ከመጠንከሩ የተነሳ ዝናብ አለመስጠቱን ይናገራል፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የነጠረ ብረት
ይህ የሚያመለክተው፣ በማቅለጫ ውስጥ ተጨምሮ የቀለጠ እና ከዚያም ሲቀዘቅዝ የጠነከረ ብረትን ነው፡፡
እኛን ለእርሱ መናገር የሚገባንን ለእኛ አስተምረን
እዚህ ስፍራ "እኛን" እና "እኛ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ኤሊሁን፣ ኤልፋዝን፣ በልዳዶስን እና ሶፋርን ሲሆን ኢዮብን አይጨምርም። ኤሊሁ ይህን ሀረግ የተጠቀመው በምጸት ነው፡፡ (አካታች የሆነ እና አካታች ያልሆነ "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)
ከአእምሯችን መጨለም የተነሳ
ኤሊሁ መረዳት አለመቻልን በአንድ ሰው አይምሮ ውስጥ እንደሚገኝ ጨለማ አድርጎ ይገልጻል፡፡ "እኛ ስለማንረዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከእርሱ ጋር መናገር እንደምፈልግ ለእርሱ ሊነገረው ይገባልን?
ኤሊሁ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ማንም ይህን ማድረግ እንደማይችል ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው፡፡ "ከእርሱ ጋር መነጋገር እንደምፈልግ ለእርሱ የሚነግረው ሰው ማግኘት አልችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
ለእርሱ ሊነገረው ያስፈልጋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ "ለእርሱ የሚነግረው ሰው ሊኖረኝ ያስፈልጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሰው መዋጥ ሊፈልግ ያስፈልገዋልን?
ኤሊሁ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ማንም ሰው ይህ እንዲደርስ እንደማይፈልግ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው፡፡ "ማንም ሰው ሊዋጥ አይፈልግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
ለመዋጥ
ኤሊሁ አንድ እየጠፋ ያለን ሰው እየተዋጠ እንደሚገኝ ሰው ይገልጸዋል፡፡ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡"እግዚአብሔር እርሱን ስለሚያጠፋው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 37:21
ከሰሜን ወርቃማ ድምቀት ይመጣል
"ወርቃማ ድምቀት" የሚለው ሀረግ የሚገልጸው የወርቅን ክብር/ድምቀት ነው፡፡ ይህ በትርጉም ውስጥ ይበልጥ ግልጽ መደረግ ይችላል፡፡ "እግዚአብሔር ከሰሜን በመርቃማ ክብር/ድምቀት ይመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ላይ አስፈሪ ግርማ አለ
"አስፈሪ" የሚለው ቃል ትርጉሙ ፍርሃት ይፈጥራል ማለት ነው። ኤሊሁ ስለ እግዚአብሔር ግርማ የሚገልጸው በእግዚአብሔር ላይ እንዳረፈ ነገር አድርጎ ነው። "የእግዚአብሔር ግርማ ሰዎች እንዲፈሩ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 37:23
እኛ እርሱን ልናገኘው አንችልም
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ወደ እርሱ ልንቀርብ አንችልም" ወይም 2) ይህ ዘይቤ ኤሊሁ ሰው እግዚአብሔርን ማግኘት እንደማይችል አድርጎ ቢያቀርብም ሰው እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ሊረዳ እንደማይችል የገለጸበት ነው። "ሙሉ ለሙሉ ልናውቀው አንችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በራሳቸው አዕምሮ ጠቢባን ነን የሚሉ
እዚህ ስፍራ "አዕምሮ" የሚወክለው የሰውን ሀሳብ ነው። "በራሳቸው አስተሳሰብ ጠቢባን የሆኑ" ወይም "ራሳቸውን ጠቢባን አድርገው የቆጠሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶናሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 38
Job 38:1
ከዚያም ያህዌ መናገር ጀመረ
እዚህ ስፍራ "ከዚያም" የሚለው ቃል የመጽሐፉን አዲስ ክፍል መጀመር ያሳያል። በእናንተ ቋንቋ አዲስ ትዕይንትን ለመጀመር ተመሳሳይ ቃል ካለ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ። "ያ ሁሉ ከሆነ በኋላ፣ ያህዌ መናገር ጀመረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ለኢዮብ ተናገረ
"ለኢዮብ መለሰለት" ወይም "ለኢዮብ ምላሽ ሰጠው"
ያለ እውቀት በቃላት ጨለማን ወደ እቅድ የሚመለስ/የሚያመጣ እርሱ ማን ነው?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ኢዮብ ስለማያውቀው ነገር መናገሩን ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ጨለማን ያለ እውቀት በቃላት አማካይነት ወደ እቅዴ አስገብተሃል/አምጥተሃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
ይህን የሚያመጣ እርሱ ማን ነው
"ይህ ለማምጣት አንተ ማን ነህ"
ወደ እቅዶች ጨለማ የሚያመጣ
"እቅዴን የሚያበላሽ" ወይም "ተግባሬን ግራ የሚያጋባ።" ኢዮብ የእግዚአብሔርን እቅድ እንዴት እንዳበላሸ የተገለጸው የእግዚአብሔርን እቅድ ለማየት ይበልጥ ከባድ እንዳደረገ ተደርጎ ነው። "ጨለማ" የሚለው ረቂቅ ስም "አጨለመ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "እቅዶችን አጨለመ" ወይም "እቅዶች መታየት እንዳይችሉ ከባድ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
ያለ እውቀት በቃላት አማካይነት
"ስለማታውቃቸው ነገሮች በመናገር"
ያለ እውቀት በመናገር
"እውቀት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልኩ ሊገለጽ ይችላል። "የማይታወቁ ቃላት" ወይም "እውቀት የሌለባቸው ቃላት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ወንድ ወገብህን ታጠቅ
"ቀበቶህን እንደ ወንድ በወገብህ ዙሪያ እሰር።" ወንዶች ከባድ ስራ ሲሰሩ በነጻነት እግራቸውን ማንቀሳቀስ እንዲችሉ በወገባቸው ዙሪያ ቀበቷቸውን ይታጠቃሉ። "እንደ ወንድ ወገብህን ታጠቅ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር እንደ ስራ፣ ውድድር፣ ወይም ጦርነትን የመሰለ አንድ ነገር ለማድረግ ተዘጋጅ የሚል ትርጉም አለው። ኢዮብ ለእግዚአብሔር መልስ መስጠትን ለመሰለ ከባድ ስራ መዘጋጀት ነበረበት። "ለከባድ ስራ ራስህን አዘጋጅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 38:4
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እርሱ እንጂ ኢዮብ ምድርን አለመፍጠሩን ትኩረት ሰጥተው በሚገልጹ በርካታ ጥያቄዎች ኢዮብን መገዳደር ጀመረ። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
እኔ የምድርን መሰረቶች መሰረትኩ
ያህዌ መሬትን መፍጠሩን የሚገልጸው መዋቅሮችን ይገነባ እንደነበረ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንግዲህ አንተ እጅግ ብዙ መረዳት ካለህ
"መረዳት" የሚለው ረቂቅ ስም "ተረዳ/አወቀ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "እጅግ ብዙ አውቀህ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
መጠኗን የወሰነው ማን ነው? ይህ ታውቅ እንደሆነ ንገረኝ
ይህንን በዐረፍተ ነገር መልክ መግለጽ ይቻለል። "የምታውቅ ከሆነ፣ መጠኗን ማን እንደወሰነ ንገረኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
መጠን
"ልክ"
በላይዋ የመለኪያ ገመዷን የዘረጋ ማን ነው?
ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ መግለጽ ይቻላል። "በላይዋ የመለኪያ ገመድ ማን እንደዘረጋ ንገረኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
የመለኪያ ገመድ
ሰዎች የአንድን ነገር ትክክለኛ መጠን እና ቅርጽ ለመለካት የሚጠቀሙበት ገመድ ወይም ሲባጎ
Job 38:6
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
አጠቃላይ መረጃ፡
"የእርሷን" የሚለው ቃል መሬተን ያመለክታል፡፤
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ታላቅነቱን ለማጉላት ብዙ ጥያቄዎችን ይጠቀማል። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
መሰረቷ የተጣለው በምን ላይ ነበር?
ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "መሰረቷ በምን ላይ እንደተጣለ ንገረኝ" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
መሰረቷ የተጣለው በምን ላይ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ መሰረቷን በምን ላይ መሰረትኩ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ልጆች በደስታ ሲጮኹ… በዚያን ጊዜ ማን ማዕዘኖቿን መሰረተ?
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " የእግዚአብሔር ልጆች በደስታ ሲጮኹ… ያን ጊዜ ማን ማዕዘኖቿን እንደመሰረተ ንገረኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
የማለዳ ከዋክብት በአንድነት ሲዘምሩ ደግሞም የእግዚአብሔር ልጆች በደስታ ሲጮሁ
እነዚህ ሁለት መስመሮች በትርጉም ተመሳሳይ ናቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የማለዳ ከዋክብት በአንድነት ሲዘምሩ
የማለዳ ከዋክብት የተገለጹት ሰዎች እንደሚዘምሩ የሚዘምሩ ተደርገው ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በቀጣዩ መስመር እንደተገለጸው "የማለዳ ከዋክብት" ከ "እግዚአብሐር ልጆች" ጋር ተመሳሳይ ናቸው ወይም 2) "የማለዳ ከዋክብት" የሚለው የሚያመለክተው በሰማይ የሚገኙ ከዋክብትን ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የማለዳ ከዋክብት
"በማለዳ የሚያበሩ ደማቅ ከዋክብት"
የእግዚአብሔር ልጆች
ይህ የሚያመለክተው ሰማያዊ ፍጥረታት የሆኑተን መላዕክትን ነው። ይህ በኢዮብ 1፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
በደስታ ሰጮኹ
"ደስታ" የሚለው ረቂቅ ስም "ደስተኛነት" በሚል ተውሳከ ግስ ሊተረጎም ይችላል። "በደስተኝነት ጮኹ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በደስታ
"በደስታ ተሞልተው ስለነበር"
Job 38:8
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ሌላ ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ እንጂ ኢዮብ ምድርን አለመፍጠሩን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
በባህር ላይ በር የዘጋ ማን ነው… ደግሞስ ከባድ ጨለማን መጠቅለያው ያደረገለት ማን ነው?
ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ማን በባህ ላይ በሮችን እንደዘጋበት ንገረኝ…ከባድ ጨለማንስ ማን መጠቅለያው እንዳደረገ ንገረኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
በባህር ላይ በሮችን የዘጋ
ያህዌ ባህር መላውን ምድር እንዳይሸፍን የከለከለበት መንገድ በባህሩ ላይ በር ከመዝጋት ጋር ተነጻጽሯል። "ውሃ ምድርን እንዳያጥለቀልቅ ከልክሏል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከማህጸን የወጣ ይመስል
ያህዌ ባህርን የፈጠረበትን ሁኔታ ከልጅ መወለድ ጋር ያነጻጽረዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ልብሱ
"ለባህር ልብስ ሆኖ"
ጥልቅ ጨለማ መጠቅለያው ሆኖ
"ጨለማ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጨለመ" በሚል ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "ከባድ ጨለማን መጠቅለያው አደረግሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
መጠቅለያ ጨርቅ/መጠምጠሚያ
ልጆች እንደተወለዱ የሚጠቀለሉበት ረጅም ቁራጭ ጨርቅ
Job 38:10
ለባህር የእኔን ዳርቻን በጀሁለት
"ለባህር ዳርቻ አበጀሁለት"
ዳርቻ
ያህዌ ባህር እንዲያልፍ ያልተፈቀደለትን ድንበር አበጀለት"
መቀርቀሪያዎቹን እና በሮቹን አደረግሁለት
ያህዌ ለባህር ዳርቻ ያበጀበትን መንገድ የሚያነጻጽረው መቀርቀሪያ እና በሮች እንዲኖር ከማድረግ ጋር ነው። "መቀርቀሪያ አበጀሁለት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መቀርቀሪያዎች
በር ለመዝጊያ የሚያገለግል ረጅም የአንጨት ቁራጭ ወይም ብረት
እኔ ስናገረው/ሳዝዘው
"እኔ ባህሩን ስናገረው።" ያህዌ ባህሩን የሚናገረው/የሚያዘው ሰው እንደሆነ አድርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህን ያህል መቅረብ ትችላለህ፣ ከዚህ ወዲያ ግን አታልፍም
"ይህን ያህል" የሚለው ቃል ያህዌ እስከፈቀደለት ስፍራ ድረስ ማለት ነው። "እስከዚህ ድንበር ድረስ ልትመጣ ትችላለህ፣ ነገር ግን ከዚህ አታልፍም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የማዕበልህ ኩራት
"ለማዕበልህ ሀይል።"ማዕበል የተገለጸው ኩራት እንዳለው ተደርጎ ነው። "ኩራት" የሚለው ረቂቅ ስም "ኩሩ" በሚል ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "ለኩሩ ማዕበልህ" ወይም "ለሀይለኛው ማዕበልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 38:12
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ እንጂ ኢዮብ ብርሃንን አለመፍጠሩን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
ክፉው ከእርሱ እንዲወገድ … አንተ ነቅንቀኸዋልን?
ይህ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ ይጠበቅበታል። ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ፈጽሞውኑ ክፉውን … ከእርሱ ነቅንቀህ አላስወገድክም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ለማለዳ ትዕዛዝ መስጠት
ያህዌ ማለዳ ትዕዛዝን መቀበል እንደሚችል እና እንደ ሰው ነገሮችን ማወቅ እንደሚችል ይናገራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይልከቱ)
ንጋት ስፍራውን እንዲያውቅ ማድረግ
"ንጋት ስፍራው የት እንደሆነ እንዲያውቅ ማድረግ"
ንጋት
በማለዳ ሰማይ ላይ ፀሐይ ከመውጣቷ አስቀድሞ የቀኑ ብርሃን መታየት
የምድርን ዳርቻ መያዝ
የንጋት ብርሃን የተገለጸው የምድርን አድማስ እንደያዘ ተደርጎ ነው። "የምድርን ዳርቻዎች መያዝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ክፉውን ከውስጧ ነቅንቆ ማስወገድ
የቀን ብርሃን የተገለጸው የማያስፈልጉ ነገሮች በመነቅነቅ እንደሚወገዱ ክፉ ሰዎችን እንደሚያስወግድ ተደርጎ ነው። "ክፉ ሰዎችን ከምድር ነቅንቆ ማስወገድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 38:14
ከማህተም በታች እንዳለ ጭቃ/ሸክላ የምድር መልኳ ይለወጣል
በምሽት፣ ሰዎች በግልጽ መመልከቱ አይችሉም፣ ማለዳ ግን ማህተም በሸክላ ላይ ግልጽ ምስልን እንደሚፈጥር ብርሃን የሁሉንም ነገር ቅርጽ በግልጽ መለየት ያስችላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ቁራጭ ጨርቅ እጥፋት በእርሷ ላይ የሚገኙ ነገሮች ሁሉ በግልጽ ይታያል
እዚህ ስፍራ "እርሷ" የሚለው የሚያመለክተው ምድርን ነው። ይህ ሀረግ በዚህ ስንኝ ከሚገኘው የመጀመሪያው ሀረግ ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከክፉ ሰዎች "ብርሃናቸው" ይወሰዳል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማለዳ የክፉ ሰዎችን 'ብርሃን' ይወሰዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የእነርሱን 'ብርሃን'
ክፉዎች ጨለማን ብርሃናቸው አድርገው ይቆጥራሉ፣ ምክንያቱም ክፉ ስራቸውን ሚሰሩት በጨለማ ሲሆን ደግሞም ከጨለማ ጋር ቅርርብ አላቸው። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
የተነሳው ክንዳቸው ይሰበራል
የተነሳው የክፉዎች እጅ የሚለው የሚወክለው ሀይላቸውን እና ክፉ ለማድረግ ያላቸውን ፍላጎት ነው። ነገር ግን የማለዳው ብርሃን ስወጣ ክፉዎች እነዚያን ክፉ ነገሮች ማድረጋቸውን ያቆማሉ። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Job 38:16
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ አምስት ጥያቄዎችን የተጠቀመው እርሱ እንጂ ኢዮብ ምድርን እና ባህርን አለመፍጠሩን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ፡
ቁጥር 16 እና 17 እያንዳንዳቸው ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሀረጎችን ይዘዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በስፋቷ… ሄደህባታል?
እነዚህ ጥያቄዎች አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃሉ። ጥያቄዎቹ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። "ወደ ባህር ውሃ መሰረት አልሁድክም፣ ወይም በጥልቁ ታችኛ ክፈል አልተራመድክም። የሞት ደጆች ለአንተ አልተገለጹም፤ ደግሞም የሞት ጥላ ደጆችን አላየህም። ምድርን በስፋቷ አላወቅካትም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
የውኆች መሰረትን/መገኛ
"ምንጮች"
ጥልቅ
ይህ ጥልቅ ውሃ የሚገኝበትን ባህርን ወይም ውቅያኖስን ያመለክታል። "ጥልቁ ባህር" ወይም "የውቅያኖስ ጥልቀት" ወይም "ጥልቁ ውሀ" በሚለው ውስጥ

እንደሚገኘው። (ሰማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)
የሞት ደጆች ለአንተ ተገልጸውልሃል
x
Job 38:19
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ሶስት ጥያቄዎችን የተጠቀመው እርሱ እንጂ ኢዮብ ብርሃንን እና ጨለማን እንደማይረዳ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ሁለቱ ሀረጎች እያንዳንዳቸው ሁለት ትይዩ ሀረጎች አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ብርሃን ማረፊያ ስፍራ ደግሞም ወደ ጨለማ የሚወስደው መንገድ የት ነው?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ወደ ብርሃን ወይም ወደ ጨለማ ስፍራ የሚወስደውን መንገድ አታውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
የብርሃን ማረፊያ ስፍራ
"የብርሃን መኖሪያ።" ብርሃን የተገለጸው ለእያንዳንዱ ቀን ተነስቶ የሚመጣበት ማረፊያ ስፍራ እንዳለው ተደርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ብርሃን
"የቀን ብርሃን" ወይም "የፀሐይ ብርሃን"
ብርሃንን እና ጨለማን ወደ ስራ ስፍራቸው ልትመራቸው ትችላለህን? ለእነርሱ ወደ ሆነው ቤታቸው መልሶ
የሚወስዳቸውን መንገድ ልታገኝ ትችላለህ? እነዚህ ጥያቄዎች አሉታዊ ምላሽ እንዲሰጥባቸው ይጠበቃል። እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። "ብርሃንን እና ጨለማን ወደ ስራ ስፍራቸው ልትመራቸው አትችልም ወይም ደግሞ የእነርሱ ወደ ሆነ ቤታቸው የሚመለሱበትን መንገድ ልታገኝ አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
ወደ ስራ ስፍራቸው
"ወደ አካባቢያቸው/መኖሪያቸው።" ብርሃን እና ጨለማ የተነገሩት በእየዕለቱ የያህዌን ተግባር ለማከናወን እንደሚወጡና እንደሚገቡ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ያለ ጥርጥር... እጅግ ትልቅ
ያህዌ ምፀታዊ ቀልድ የተጠቀመው ኢዮብ ብርሃንን እና ጨለማን እንደማይረዳ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "አንተ እንደማታውቅ ግልጽ ነው፣ ምክንያቱም እነርሱን ስፈጥራቸው አንተ ገና አልተወለድክም ነበር፣ ደግሞም አንተ በጣም አላረጀህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
በዚያን ጊዜ ተወልደህ እንደሆነ
"በዚያን ጊዜ አንተ ትኖር ነበር።" "በዚያን ጊዜ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ብርሃን የተፈጠረበትን እና ከጨለማ የተለየበትን ጊዜ ነው። "እነርሱን በፈጠርኩበት ጊዜ አንተ ተወልደህ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
የቀኖችህ ቁጥር እጅግ ትልቅ ነው
"እጅግ ረጅም አመታት ኖረሃል"
Job 38:22
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ይህን ጥያቄዎችን የተጠቀመው እርሱ እንጂ ኢዮብ በተፈጥሮ ላይ እንደማይገዛ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
ወደ በረዶ ቤተመዛግብት/መጋዘን ገብተሃል፣ ወይም የበረዶ ውሽንፍሩን ቤተመዛግብት አይተሃል... ደግሞስ ለጦርነት ቀን?
እነዚህ ጥያቄዎች አሉታዊ ምላሽ እንዲሰጥባቸው ይጠበቃል። እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። "አንተ በፍጹም ወደ በረዶ ቤተመዛግብት አልገባህም፣ ወይም የበረዶ ውሽንፍሩን ቤተመዛግብት... እና ለጦርነት ቀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
የበረዶ ግምጃ ቤት ገብተሃል... የበረዶውን ውሽንፍርን ቤተመዛግብት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በትርጉም ተመሳሳይ ናቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የበረዶ ቤት ማዛግብት... የበረዶ ውሽንፍር ቤተመዛግብት
በረዶ እና የበረዶ ወሽንፍሩ ያህዌ የእርሱን ፈቃድ ሊፈጽምባቸው ያጠራቀማቸው ተደርገው ተገልጸዋል። (ዘይቤያው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የበረዶ ውሽንፍር
የበረዶ ኳስ (ብዙ ጊዜ ትንንሽ ናቸው) አንዳንድ ጊዜ በሃይለኛ ዝናብ ወቅት ከሰማይ ይወርዳል።
የመብረቅ ብልጭታ መንገዱ ወዴት ነው ወይም ከምስራቅ በምድር ላይ ሁሉ የነፋስ መሄጃው ወዴት ነው?
እነዚህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፉ ይችላሉ። "የመብረቅን ብልጭታ የምልክበት መንገድ ወዴት ነው ወይም ከምስራቅ በምድር ላይ ሁሉ ነፋሳትን የምበትነው ወዴት ነው?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ነፋሳት ይበተናሉ
"ነፋሳት ይነፍሳሉ"
Job 38:25
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ይህን ጥያቄ ኢዮብን የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ ዝናብ እንዲዘንብ እና መብረቅ እንዲበርቅ እንደማያደርግ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
ለዝናብ መውረጃውን የሚፈጥርለት ወይም...ሳር እንዲበቅል የሚያደርገው ማን ነው?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፈ ይችላል። "ለዝናብ መውረጃውን የማበጅለት፣ ሳር እንዲበቅል የማደርግ እኔ ብቻ ነኝ፣... እኔ ብቻ ይህንን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
የዝናብ መውረጃ
"የዝናብ ጎርፍ"
የመብረቅ መንገድ
"የመብረቅ ጉርምርምታ የሚሰማበት መንገድ"
ማንም ሰው በማይኖርበት መሬት፣ ማንም በማይኖርበት ምድረበዳ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተቀራራቢ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማንም ሰው በማይኖርበት
"ሰዎች በሌሉበት"
ለማርካት
በውስጠ ታዋቂነት የቀረበው መረጃ ምድር ሳር እንድታበቅል የሚያደርገው ዝናብ ነው። "ስለዚህ ዝናብ ምድር እንድታበቅል ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አጠፋ ደግሞም አወደመ
"የፈራረሰ እና የተበላሸ።" እነዚህ ሁለት ቃላት ተቀራራቢ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም የእነዚህን አካባቢዎች የፈራረሰ እና ባዶ ተፈጥሮ ትኩረት ይሰጣሉ። (ሄንዲየዲስ/ሁለት ቃላት 'እና' በሚል አያያዥ ቃል የሚገኛኙበትና አንድን ጥልቅ ሀሳብ ለመግለጽ የሚያገለግል ዘይቤያዊ አነጋገር)
በሣር
"እየበቀለ ያለ ሣር" ወይም "በመብቀል ላይ የሚገኝ ሣር።" ማደግ የጀመረ ይህ ሣር።
ምድርን በአዲስ ሣር የሚሞላ
"ምድር አዲስ ሳር እንድታበቅል የሚያደርግ"
Job 38:28
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ኢዮብን አራት ጥያቄዎችን የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ ዝንብን እንደማያዘንብ፣ ጤዛና እና በረዶን እንደማይፈጥር እንደዚሁም አመዳይን እንደማያበጅ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በእነዚህ ሶስት ስንኞች ውስጥ የሚገኙ እያንዳንዳቸው መስመሮች ተመሳሳይ ነገሮችን ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡

ዝናብ፣ ጤዛ፣ በረዶ፣ እና አመዳይ የተገለጹት እንደ ሰዎች እንደሚወለዱ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝናብ አባት አለውን፣ ወይስ፣ የጤዛ ጠብታ አባቱ ማን ነው? በረዶ ከማን ማህጸን መጣ? የሰማይን ነጭ አመዳይ ማን ወለደው?

እነዚህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ዝናብ አባት እንዳለው፣ የዝናብ ጠብታዎችን ማን እንዳስገኘ ንገረኝ። በረዶ ከማን ማህጸን እንደወጣ፣ ደግሞም የሰማይን ነጭ አመዳይ ማን እንደወለደው ንገረኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ለጤዛ ጠብታ አባቱ

ለጤዛ አባቱ የሆነው የሚለው ለመፈጠሩ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "የጤዛ ጠብታ እንዲኖር ምክንያት የሆነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በረዶ

"ቀዝቅዞ ጠጣር የሆነ/የረጋ ውሃ"

መውለድ

"ልጅ መስጠት"

ነጭ አመዳይ

በቅዝቃዜ መሬት ላይ በረዶ/ጠጣር የሆነ ጤዛ፣ ደማና በሌለበት ምሽቶች

ራሳቸውን የደበቁ እና እንደ ድንጋይ ጠጣር የሆኑ ውኆች

ውኆች የተገለጹት መደበቅ እንደሚችሉ ተደርጎ ነው። በክረምት በረዶ ከስሩ ውሃ ይደብቃል። (ሰውኛ እና ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደ ድንጋይ ሆነ

የበረዶው ጠጣርነት የተገለጸው ድንጋይ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "እንደ ድንጋይ ጠጣር/ጠንካራ ሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥልቁ

ይህ የሚያመለክተው ውሃው በጣም ጥልቅ የሆነን፣ ባህርን ወይም ውቅያኖስን ነው። "ጥልቁ ባህር" ወይም "የውቅያኖስ ጥልቀት" ወይም "ጥልቁ ውሃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይምለከቱ)

Job 38:31

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ኢዮብን አምስት ጥያቄዎችን የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ ሰማያትን እንደማይገዛ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡

በእነዚህ ሶስት ስንኞች ውስጥ የሚገኙ እያንዳንዳቸው ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ነገሮችን ይገልጻሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ላይ ሁሉ...በሰንሰለቶች መቆለፍ ትችላለህ

እነዚህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ፕልያዲስ የተባለውን ኮከብ በሰንሰለት ማሰር ትችል እንደሆነ፣ ወይም ኦርዮን የተባለውን ኮከብ ገመድ መበጠስ ትችል እንደሆነ ንገረኝ። የከዋክብት ክምችትን በተገቢው ጊዜያቸው እንዲታዩ መምራት ትችል እንደሆነ ነገረኝ፤ ወይም ድብ የተባለውን ኮከብ ከልጆቹ ጋር መምራት ትችላለህ። የሰማይን ስርአት የምታውቅ ከሆነ፣ ወይም የሰማይን ህግ በምድር ላይ ማድረግ ትችል እንደሆነ ንገረኝ። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ሰንሰለት መፍታት

"የሰንሰለት እስራት ልጥበጥስ" ወይም "ሰንሰለት መበጠስ"

ፕልያዲስ...ኦርዮን... ድብ

እነዚህ የከዋክበት ክምችቶች ስሞች ናቸው። እነዚህ በኢዮብ 9፡9 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

የኦርዮንን ገመዶች ልትበጥስ

"ኦርዮን የተባለውን ኮከብ ያሰሩትን ገመዶች ልትፈታ"

የከዋክብት ክምችት

በሰማይ ላይ አንድ የተለየ ቅርጽ ሚፈጥሩ የከዋክብት ክምችት

በተገቢ ጊዜያቸው መታየት

"በትክክለኛ ጊዜያቸው ይታዩ ዘንድ"

ልጆቹ

"ግልገሎቹ"

Job 38:34

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ኢዮብን ሁለት ጥያቄዎችን የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ የዝናብ ደመናዎችን እና መብረቅን እንደማይገዛ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

'እኛ በዚህ አለን' ...እንተ ልትነሳ ትችላለህ?

እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ብዙ የዝናብ ውሃ ይሸፍንህ ዘንድ ድምጽህን እስከ ደመናት ድረስ ማሰማት ትችል እንደሆነ ንገረኝ። የመብረቅ ብልጭታን ይወጣ ዘንድ ልታዘው ትችል እንደሆነ ንገረኝ፤ እነርሱም 'እዚህ አለን!' ይሉህ እንደሆነ ተናገር።" በሚለው ውስጥ እንሚገኝ። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ብዙ የዝናብ ውሃ

"ብዙ/የተትረፈረፈ" የሚለው ረቂቅ ስም "የበዛ" በሚል ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "ብዙ የዝናብ ውሃ" ወይም "የውኆች ጎርፍ" በሚለው ውስጥ እንሚገኝ። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን መልከቱ)

እዚህ አለን

ይህ የሚያሳየው የመብረቅ ብልጭታዎች እንደ አገልጋይ ትዕዛዝ ለመቀበል ዝግጁ ነን ማለታቸውን ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 38:36

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ኢዮብን ሶስት ጥያቄዎችን የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ ደመናዎችን እና ዝናብን እንደማይገዛ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ጥበብን በአንድነት አጥብቆ የያዘ...ማን ነው?

እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ጥበብን በደመናዎች ያኖረ ማን እንደሆነ ደግሞም ለብዝታ መረዳትን የሰጠ ማን ነው። ማን በችሎታው ደመናትን ሊቆጥር እንደሚችል ንገረኝ። አፈር ወደ ጠጣርነት ሲለወጥ እንዲሁም የምድር ጓል በአንድነት ሲጣበቅ የሰማይ የውሃ አቁማዳን ማን ማንቆርቆር እንደሚችል ንገረኝ።" በሚለው ውስጥ እንሚገኝ። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ጥበብን በደመናት ውስጥ ያስቀመጠ ማን ነው ወይም ለብዝታ መረዳትን የሰጠ ማን ነው?

እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ደመናት እና ብዝታን ማስወገድ ያህዌ ለሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ይረዱ ዘንድ የሰጣቸው ጥበብ እና መረዳት ተደርገው ተገልጸዋል። "ጥበብ" እና "መረዳት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ጠቢብ" በሚል ቅጽል እና "ተረዳ" በሚል ግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ደማናትን ጠቢብ ያደረገ ማን ነው ወይም ብዥታን ግልጽ ያደረገ ማን ነው?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሰውኛ ዘይቤ እንዲሁም ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

በደማናት ውስጥ ጥብን ያኖረ

"ለደማናት ጥበብን የሰጠ"

በራሱ ጥበብ ደማናት መቁጠር የሚችል ማን ነው?

"ደማናትን መቁጠር የሚችል ማን ነው?"

የውሃ አቁማዳዎች

እነዚህ ሰዎች በአንድነት የሚሰፏቸው ሲሆኑ ውሃ ለመያዝ የሚያገለግሉ ናቸው። ያህዌ ከባድ ደማናዎችን ከ"ውሃ አቁማዳ" ጋር ያስተያያቸዋል፣ ምክንያቱም እንደ ውሃ አቁማዳ ብዙ ውሃ መያዝ ይችላሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አፈር ወደ ጠጣርነት ሲለወጥ እና የምድር ጓል በአንድነት ሲጣበቅ

እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አፈር ወደ ጠጣርነት ሲለወጥ

ዝናብ የላመውን ደረቅ አፈር በአንድነት ያጣብቀዋል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዝናብ አፈሩን በአንድ ላይ አጣብቆ ሲያድበለብለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የምድር ጓል በአንድነት ሲጣበቅ

"የአፈር ጓል በአንድነት ሲጣበቅ"

Job 38:39

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ኢዮብን ይህን ጥያቄ የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ አንበሶችን እንዴት እንደሚመግብ አለማወቁን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

አንተ አድብተህ ጠብቀህ… ማደን ትችላለህ?

ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "አድብተህ ጠብቀህ…ማደን ትችል እንደሆን ንገረኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

የሚታደን

"ታዳኝ።" ይህ አንድ አንበሳ አድኖ የሚበላው እንስሳ ነው።

ሴት አንበሳ

ይህች ሴት አንበሳ ናት

የምግብ ፍላጎት

ረሃብ

የእርሷ የአንበሳ ግልገል

"የአንበሳ ግልግል/ደቦል" ለራሳቸው አድነው መመገብ የጀመሩ ደቦል አንበሶች

ዋሻ

"ዋሻ" አንበሳ የሚጠለልበት መኖሪያ/የአውሬ ዋሻ/ ነው

በሚደበቅበት ጊዜ የሚጠለልበት

"በቁጥቋጦ ውስጥ መደበቅ።" አንበሶች ሲያድኑ ጥቅጥቅ ባለ ሳር ቅጠል ውስጥ ይደበቃሉ

አድብቶ መጠበቅ

በውስጠ ታዋቂነት የሚገኘው መረጃ አንበሶች ተደብቀው የሚያድኑት እንስሳ እስኪቀርብ ይጠብቃሉ። "ታዳኙን ተጋድሞ/አድፍጦ መጠበቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 38:41

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ኢዮብን ይህን ጥያቄ የጠየቀው እርሱ እንጂ ኢዮብ ለአሞሮች ምግብ እንደማይሰጣቸው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ምግብ ላጡ… ምግባቸውን የሚሰጣቸው ማን ነው?

ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ምግብ ላጡ… ለተጠቁት ማን ምግባቸውን እንደሚሰጣቸው ንገረኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ለተራቡት ምግብ የሚሰጥ

"ምግብ የሚሰጥ።" ይህ የሚያመለክተው ቁራዎች ለምግብነት የሚፈልጓቸውን እንስሳት ነው።

ቁራዎች/ቁራ መሰል አሞራ

የሞቱ እንስሳትን የሚመገቡ የሚያብረቀርቅ ጥቁር ላባ ያላቸው ትላልቅ ወፎች

ወደ እግዚአብሔር መጮህ

በውስጠ ታዋቂነት የሚገኘው መረጃ ቁራዎች ምግብ ለማግኘት ይጮሃሉ የሚል ነው። "ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር መጮህ" ወይም "ምግብ እንዲሰጣቸው ወደ እግዚአብሔር ይጮሃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዳገድ

ይህ ማለት ወዲያ ወዲህ በመንገዳገድ መራመድ

ምግብ በማጣት

"በምግብ በማጣት ምክንያት" ወይም "የሚበሉት በማጣታቸው ምክንያት"

---

Chapter 39

Job 39:1

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ኢዮብን አራት ጥያቄዎች የጠየቀው እርሱ ከኢዮብ ታላቅ እንደሆነ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ምክንያቱም ለእነዚህ የተራራ ዱር ፍየሎች እና አጋዘኖች እንክብካቤ የሚያደርገው እርሱ እንጂ ኢዮብ አይደለም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ልጆቻቸውን ምን ጊዜ እንደሚወልዱ…. አንተ ታውቃለህን?

ይህ በዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንተ በእርግጥ መቼ ነገሮች ምቹ እንደሚሆኑ …አጋዘኖች መቼ ግልገሎቻቸውን እንደሚወልዱ ማወቅ አትችልም!"

አጋዘኖች መቼ ልጆቻቸውን እንደሚወልዱ መጠባበቅ ትችላለህ?

ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አጋዘኖች ግልገሎቻቸውን የሚወልዱበትን ሁሉም ነገር ምቹ የሚሆንበትን ገዜ በእርግጠኝነት መጠባበቅ አትችልም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ግልገሎች የሚኖራቸው

"ግልገሎቻቸውን የመወልዱበት"

የእርግዝና ወራቶቻቸውን መቁጠር ትችላለህ?

ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርገዝ የሚሆኑበትን ወራት መቁጠር አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

እርጉዝ የሚሆኑበት

"እርግዝናቸው የሚያበቃበት"

እነርሱ

"እነርሱ" የሚለው ቃል ፍየሎችን እና አጋዘኖችን ያመለክታል

እርጉዞች

"እርጉዝ የሆኑ"

ግልገሎቻቸውን መቼ እንደሚወልዱ ጊዜውን ታውቃለህ?

ይህ በዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "በእርግጥ መቼ ግልገሎቻቸውን እንደሚወልዱ አታውቅም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

Job 39:3

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

እነርሱ ወደ ታች ቁጢጥ ይላሉ

"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሜዳ ፍየሎችን እና አጋዘኖችን ነው።

ግልገሎቻቸውን ይወልዳሉ

"ዘራቸውን ይሰጣሉ"

ከዚያም የምጣቸው ስቃይ ያጨርሳሉ

የሚሰጡ ትርጉሞች 1) ወልደው ሲጨርሱ የምጣቸው ስቃይ ያልፋል ወይም 2) "የምጥ ስቃይ" የሜዳ ፍየሎች እና የአጋዘኖች ግልገሎችን የሚያመለክት ሜቶኖሚ/ ነው። ምክንያቱም እነርሱ የእናቶቻቸው ምጥ እና ስቃይ ውጤቶች ናቸው። "ከማህጸናቸው ግልገሎቻቸውን ይወልዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ባዶ ሜዳዎች

"ገጠራማ አካባቢ" ወይም "ጫካ"

ተመልሰው አይመጡም

"ወደ እነርሱ አይመለሱም" ወይም "ወደ እናቶቻቸው አይመለሱም"

Job 39:5

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል

የጨው ምድሩን…ማን ሰጠው?

ያህዌ ከኢዮብ ይልቅ ታላቅ መሆኑን በትኩረት ለመግለጽ ሁለት ጥጣቄዎችን ይጠቀማል፤ ምክንያቱም ያህዌ ለሜዳ አህዮች እንክብካቤ የሚያደርገው ያህዌ

እንጂ ኢዮብ አይደለም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
የሜዳ አህያን በነጻነት እንዲፈነጭ ያደረገው ማን ነው?
ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "የሜዳ አህያን በነጻነት እንዲፈነጭ ያደረግኩት እኔ ነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
የሜዳ አህያ…የዱር አህያ
ይህ ተመሳሳይ ለሆነ የአህያ አይነት የተሰጠ ስም ነው
በጨው ምድር …እስራቱን የፈታ ማን ነው?
ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "በጨው ምድር…እስራቱን የፈታሁለት እኔ ነኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
ማሰሪያዎች
እንስሳት ሮጠው እንዳይሄዱ የሚታሰሩባቸው ገመዶች፣ ሰንሰለቶች፣ ወይም ማሰሪያዎች
በምድረበዳ የማንን ቤት ሰራሁ
ያህዌ አህያ ቤት እንዳለው ሰው አድርጎ ይገልጻል። "ምድረበዳን መኖሪያ አድርጌ ሰጠሁት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የጨው ምድር
በጨው ባህር አካባቢ ያለው ምድር ብዙ ጨው ይገኝበታል
Job 39:7
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
እርሱ
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሜዳ አህያን ነው
በንቀት ይስቃል
ያህዌ አህያን እንደ ሰው ይስቃል በማለት ይገልጻል። አህያው የሚስቀው በከተማ የሚኖሩ ከፍ ያለ ድምጹን እንዲሰሙ ሲሆን፣ እርሱ ግን በጸጥታ ስፍራ ይኖራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ነጂዎች
እንስሳው እንዲሰራ የሚያስገድድ
መሰማሪያ
እንስሳት በሜዳ የበቀለውን የሚግጡበት ስፍራ
Job 39:9
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
አጠቃላይ መረጃ፡
እዚህ ስፍራ ያህዌ አራት ጥያቄዎች የጠየቀው ኢዮብ እንደ ያህዌ እንዳልሆነ ትኩረት ለመስጠት ነው፤ ምክንየቱም ኢዮብ ጎሽን ሊቆጣጠር አይችልም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ጎሽ
ሊሰጡ የሚችለሁ ምክንያቶች 1) በጫካ የሚኖር የበሬ ዝርያ/አይነት ወይም 2) በሬ የሚመስል የጎሽ አይነት
ደስተኛ መሆን
"ፈቃደኛ መሆን"
በግርግምህ ሊቆይ ይፈቅዳልን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "በግርግምህ ሊቆይ አይፈቅድም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በግርግምህ ሊቆይ ይፈቅዳል
"ምሽቱን በበረትህ ለማደር"
ግርግም
እንስሳት መመገብ እንዲችሉ ምግባቸውን መያዣ
በእርሻ ስፍራ ጎሽን ለማሰር ገመድ መጠቀም ትችላለህ?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ጎሽ የእርሻህን ትልም እንዲያርስ በገመድ ጠምደህ ልትቆጣጠረው አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ገመድ
ገበሬዎች እንስሳትን ለመምራት በጭንቅላታቸው ወይም ጫንቃቸው/አንገት ላይ ገመድ ያስራሉ
ትልሞች
እነዚህ በእርሻ ላይ ያሉ ረጃጅም ቦዮች ናቸው። ትልም የሚለው በኢዮብ 31:38 እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ሸለቆውን አንተን እየተከተለ ይከሰክስልሃል?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "በፍጹም አንተን እየተከተለ ሸለቆውን አይከሰክስልህም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
መከስከስ
አፈርን ማለስለስ
Job 39:11
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
አጠቃላይ መረጃ፡
እዚህ ስፍራ ያህዌ ሶስት ጥያቄዎች የጠየቀው ኢዮብ እንደ ያህዌ እንዳልሆነ ክርክሩን ለመቀጠል ነው፤ ምክንየቱም ኢዮብ ጎሽን ሊቆጣጠር አይችልም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ሀይሉ ታላቅ ስለሆነ እርሱን ትተማመናለህን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ሀይሉ ታላቅ ስለሆነ በእርሱ ልትተማመን አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱን ታምናለህ
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "ጎሽ"ን ነው።
ይሰራው ዘንድ ስራህን በእርሱ ላይ ትጥላለህ/ትተዋለህ?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ለአንተ ይሰራልህ ዘንድ ስራህን ለእርሱ መተው አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ይሰራልህ ዘንድ ስራህን ለእርሱ መተው
"ከባዱን ስራህን ይሰራልህ ዘንድ"
እህልህን ይወቃልህ/ያበራይልህ ዘንድ…በእርሱ ትታመናለህ?
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ይይዛሉ። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እህልህን እንዲወቃልህ …በእርሱ ላይ ልትታመን አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 39:13
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
የሰጎን ክንፎች…የፍቅር ላባዎች እና ክንፎች ናቸው?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ኢዮብ ሰጎኖች የሚያደርጉትን ለምን እንደሚያደርጉ ኢዮብ እንደማያውቅ ትኩረት ለመስጠት ነው። "የሰጎን ክንፎች እና ላባዎች በኩራት ሲቀዝፉ ይህን የሚያደርጉት በፍቅር ይሁን አይሁን አንተ አታውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰጎን
በጣም በፍጥነት መሮጥ የምትችል ነገር ግን የማትበር በጣም ትልቅ ወፍ
በኩራት ማርገብገብ
"በደስታ መንቀሳቀስ"
ክንፍ
በወፍ ክንፍ ላይ የሚገኝ በጣም ረጃጅም ላባዎች
ላባ
የወፍ አካልን የሚሸፍኑ አነስተኛ ላባዎች
የፍቅር
የዕብራይስጡ ቃል እርግጠኛ አይደለም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "የታማኝነት" ወይም 2) "የሺመላ።" ማለት ሊሆን ይችላል። የሽመላ ስም ትርጉሙ "ታማኝ የሆነው" ወይም "አፍቃሪ የሆነ" ማለት ነው፤ ምክንያቱም ሰዎች ሽመላ ለጫጩቶቻቸው በጣም መልካም ተንከባካቢ እንደሆኑ ያውቃሉ።
በመሬት ላይ
"በምድር"
እነርሱን ያደቋቸዋል/ይቸጯቸዋል
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እንቁላሎችን ነው
ይረጋግጧቸዋል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"በላያቸው ይቆማሉ/ይራመዱባቸዋል"
Job 39:16
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
እርሷ በጭካኔ ትተዋቸዋለች
"እርሷ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሴቷን ሰጎን ነው
የእርሷ ምጥ
እንቁላሏን ስትጥል የምትሰራው ስራ
በከንቱ ሊሆን ይችላል
ጫጩቶቹ ከሞቱ፣ ስራዋ ሁሉ ዋጋ ቢስ ነበር። "ጫጩቶቹ የሚሞቱ ከሆነ ልፋቷ ከንቱ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከጥበብ ተነጥላለች
"ጥበብን እንድትዘነጋ ተደርጋለች" ወይም "ጥበብ አልተሰጣትም"
የጥበብ ምስጢር
ይህ ቃል በኢዮብ 11፡ ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እርሷ ስትሮጥ
ይህ ስንኝ ጫጩቶቿን ከመንከባከብ ከድካሟ ጋር በንጽጽር ይታያል። "ሆኖም፣ በምትሮጥበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
እርሷ በጋላቢው…ትስቃለች
በጋላቢው የምትስቀው ከፈረስ ፈጣን በመሆኖ እንደሆነ ተጠቁሟል። "በጋላቢው የምትስቀው… ከፈረስ ይልቅ ፈጣን በመሆኗ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 39:19
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
አጠቃላይ መረጃ፡
እዚህ ስፍራ ያህዌ ሶስት ጥያቄዎች የጠየቀው ኢዮብ እንደ ያህዌ እንዳልሆነ ትኩረት ለመስጠት ነው፤ ምክንየቱም ኢዮብ የዱር/ያልተገራ ፈረስን ሊቆጣጠር አይችልም። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
አንገቱን በጋማ ትሸፍናለህን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "አንገቱን በጋማ ልትሸፍን አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
አንገቱን በጋማ ልትሸፍን
የፈረስ "ጋማ" የተገለጸው የፈረስን አንገት እንደሚሸፍን ልብስ ተደርጎ ነው። "ጋማው አንገቱን እንደ ልብስ ይሸፍናል" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በአንገቱ ላይ የወረደው ጋማ
በፈረሱ አንገት ላይ የሚገኘው ረጅም ፀጉር
በእውኑ አንተ እንደ አንበጣ እንዲፈናጠር ልታደርገው ትችላለህን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "አንተ እንደ አንበጣ እንዲዘል ልታደርገው አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ትልቅ አንበጣ
በጣም በፍጥነት እና በጣም ሩቅ ሊዘል የሚችል ትልቅ የአንበጣ አይነት
ማሽካካት/ማንኮራፋት
ፈረሶች በአፍንጫቸው የሚያወጡት በጣም ጉልህ ድምጽ
Job 39:21
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
እርሱ ይጎደፍራል/መሬቱን ይመታል
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፈረስን ነው። ፈረሱ ምድርን በእግሩ ይመታል/ይጎደፍራል ምክንያቱም ምግያው እንዲጀምር በጣም ቸኩሏል። "በጉጉት መሬቱን ይመታል ደግሞም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መጎድፈር
"በኮቴው መሬቱን መቆፈር/መምታት"
መሳሪያውን ለማግኘት
እዚህ ስፍራ "መሳሪያ" የሚለው የሚወክለው ለጦርነቱ የሚጠቀሙበትን ነው።
"ወደ ጦርነት ለመግባት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በፍርሃት ላይ ያፌዛል
"በፍጹም አይፈራም"
ያፌዛል
"ይስቃል"
መጨነቅ
"ተስፋ መቁረጥ"
ወደ ኃላ አይመለስም
"አይሸሽም"
ኮሮጆ
ፍላጻዎችን መያዣ
ማስፈራራት
መርገፍገፍ እና ድምጽ ማሰማት
ሽንጥ
የፈረሱ ጎን
ጦር
ሰዎች በጠላቶቻቸው ላይ የሚወረውሩት ጫፉ ሹል የሆነ ብረት ያለው ረጅም በትር
Job 39:24
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
እርሱ
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፈረስን ነው።
ምድርን ይውጣል
የፈረሱ በምድር ላይ በፍጥነት መሮጥ ሰው ውሃን ሲጠጣ በፍነት ጭልጥ እንደሚያደርግ ፍጥነቱ ተገልጾዋል። "በምድር ላይ በፍጥነት ይሮጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመለከቱ)
በሃይል እና በቁጣ
ፈረሱ ስለጓጓ በፍጥነት እና በጥንካሬ ይንቀሳቀሳል
በመለከት ድምጽ
አንድ ሰው መለከት እንደሚነፋ ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። "ጦርነት መጀመሩን ለማወጅ አንድ ሰው መለከት ሲነፋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በአንድ ስፍራ መቆም አይችልም
"በአንድ ስፍራ ተረጋግቶ መቆም አይችልም/ይቅበጠበጣል"
አሃ፣ ይላል
"አሃ" የሚለው ቃል ሰዎች አንድ ነገር ሲያገኙ የሚያወጡት ድምጽ ነው። ፈረስ ድምጽ የሚያወጣው ጦርነት መኖሩን በማወቁ ምክያት ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ነጎድጓዳዊ ጩኸት
ይህ የሚያመለክተው ፈረሱ እነዚህን ነገሮች መስማቱን ነው። "እርሱ ነጎድጓዳዊ ጩኸቱን ሰምቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ፉከራ
"የጦርነት ጩኸት።" ሰዎች በጦርነት ጊዜ ጀግንነታቸውን እና ብርታታቸውን ለማሳየት እንዲሁም ጠላቶቻቸውን ለማስፈራራት የሚያሰሙት የተለየ ጩኸት አለ
Job 39:26
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
ወደ ደቡብ… ይህ በአንተ ጥበብ ነውን?
ያህዌ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ያህዌ ታላቅ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ነው። ለዚህ ጥያቄ በውስጠ ታዋቂነት የሚሰጠው ምላሽ "አይደለም" የሚል ነው። "ወደ ደቡብ…ይህ በአንተ ጥበብ አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ክንፎቹን ወደ ደቡብ የሚዘረጋው
እዚህ ስፍራ ክንፎችን መዘርጋት የሚያመለክተው መብረርን ነው። "ወደ ደቡብ

መብረር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ደቡብ
በመጽሐፍ ቅዱሳዊው መልከአምድር ወፎች በክረምት በሞቃታማ የአየር ንብረት ለመኖር ወደ ደቡብ ይበራሉ።
Job 39:27
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
ጎጆቸውን በከፍታ ስፍራ የሚሰሩት ... በአንተ ትዕዛዝ ነውን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ ንስሮችን ለማዘዝ አቅም እንደሌለው ለማረጋገጥ ነው። ለዚህ ጥያቄ በውስጠ ታዋቂነት የሚሰጠው ምላሽ "አይደለም" የሚል ነው። "አንተ ንስር በከፍታ ስፍራ ቤቱን እንዲሰራ ልታዝዘው አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በአንተ ትዕዛዝ
"ትዕዛዝ" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልኩ ሊጻፍ ይችላል። "እንዲህ እንዲያደርግ አንተ ስለ ነገርከው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ከፍ ብሎ እንዲወጣ
ይህ ማለት ወደ ላይ ይበራል ማለት ነው። "ወደ ሰማይ ይበራል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጠንካራ ምሽግ
ታላቁ ገደል ለንስር ጠንካራ ምሽጉ ነው፤ ምክንያቱም ሊበላው የሚፈልገው እንስሳ ወደዚያ ስፍራ ሊደርስ አይችልም።

Job 39:29
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
እርሱ የሚያድነውን ይፈልጋል
እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ንስርን ነው።
የሚያድነው
"ገድሎ የሚመገበው እንስሰ"
የእርሱ ዐይኖች ይመለከቷቸዋል
እዚህ ስፍራ "የእርሱ ዐይኖች" የሚለው የሚያመለክተው ንስሩን ነው። "እርሱ ይመለከታቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ጫጩቶቹ
"ትንንሽ ንስሮች።" ይህ የሚሆነው ንስር አድኖ ከገደለ በኋላ መሆኑን መግለጹ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "ንስሩ አድኖ ከገደለ በኋላ፣ ጫጩቶቹ ንስሮች"
ደም ይጠጣል
"የገደለውን እንስሳ ደም ይጠጣል"
በድን ባለበት
"የሞቱ ሰዎች ባሉበት።" ይህ ሀረግ የሚያመለክተው ምድር ውስጥ የተቀበሩትን ሳይሆን በሜዳ ላይ የወደቁትን በድኖች ነው።
በዚያ እርሱ ይገኛል
ይህ በድን ለመብላት እንደሚመጣ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "እነርሱን ለመብላት በዚያ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 40
Job 40:1
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
ሁሉን ቻይ የሆነውን እንዲህ አድርግ ለማለት መድፈር የሚችል አለን?
ያህዌ ኢዮብን እየገሰጸው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ቢሆን እኔን ለመንቀፍ ወይም ከእኔ ጋር ለመከራከር መሞከር የለበትም፣ እኔ ሁሉን ቻይ አምላክ ነኝና።" ወይም "አንተ ሰው ሆነህ ሳለ፣ ሁሉን ቻይ አምላክ የሆንኩትን እኔን ለመንቀፍ ትፈልጋለህ፤ ደግሞም እኔን ለማረም መሞከር የለብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእግዚአብሔር ጋር የሚከራከር፣ እርሱ ምላሽ ይስጥ
ያህዌ ስለ ራሱ እና ስለ ኢዮብ ሌሎች ሁለት ሰዎች እንደሆኑ እና በየትኛውም ስፍራ የሚገኝ ማንኛም ሰው ከእግዚአብሔር ጋር መከራከር እንደሌለበት አድርጎ ይናገራል። "ከእኔ ጋር ትከራከራለህን፣ እንግዲያውስ መልስልኝ" (ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Job 40:3
እነሆ እኔን ተመልከት
"እኔ መሆኔን ስትናገር አልተሳሳትክም" ወይም "እኔን ተመልከት እኔ መሆኔን ታያለህ"
እኔ ዋጋ የለኝም
"እኔ ጠቃሚ አይደለሁም"
እንዴት መልስ ልሰጥህ እችላለሁ?
ኢዮብ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው እግዚአብሔርን በመሟገቱ/በመጠየቁ ምህረት ለመለመን ነው። "እኔ መልስ ልሰጥህ አልችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 40:6
እንደ ወንድ ወገብህን ታጥቀህ ተዘጋጅ
ቀበቶውን የታጠቀ ወንድ ለብርቱ ስራ የተዘጋጀ ነው፤ ኢዮብ ለእግዚአብሔር መልስ መስጠትን ለመሰለ ከባድ ስራ መዘጋጀት ነበረበት። ይህ በኢዮብ 38:3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልከቱ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 40:8
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገዳደሩን/መጠየቁን ቀጥሏል
በእርግጥ እኔን ትክክል አይደለህም ትላለህን?
"በእርግጥ" የሚለው ቃል ኢዮብ እርሱን ትክክል አይደለህም በማለቱ መደነቁን እና በእርግጥም ይህን ለማለት መፈለጉን እንዲያረጋግጥ እየጠየቀው መሆኑን ያመለክታል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እኔን ትክክል አይደለህም በማለትህ ተገርሜያለሁ" ወይም "እኔን ትክክል አይደለህም ለማለት መፈለግህን እርግጠኛ መሆን አለብህ፣ ምክንያቱም እያልክ ያለኸው ያንን ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ራስህን ትክክለኛ አድርገህ እኔን ትኮንናለህን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ራስህን ንጹህ አድርገህ በመቁጠር እኔን መኮነን ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔርን ክንድ የመሰለ
ክንድ የሚለው በክንድ ውስጥ ለሚገኝ ጥንካሬ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እንደ እግዚአብሔር ጥንካሬ ብርቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚውን ይመልከቱ)
እንደ እርሱ በድምጽ መብረቅ ታወጣለህ?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እግዚአብሔር በድምጹ እንደሚያደርገው አንተ በእርግጥ በድምጽህ መብረቅ ማብረቅ አትችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
እንደ እርሱ ድምጽ ያለ
"እርሱ በሚያደርግበት መንገድ እንዳለ ድምጽ" ወይም "እንደ እርሱ ድምጽ ያለ ድምጽ"
Job 40:10
ሰው እንደሚለብሰው ልብስ አድርገህ ራስህን በክብር እና በማዕረግ አጎናጽፍ፤ በሞገስ እና ግርማ አዘጋጅ
"ክብር፣" "ማዕረግ፣" "ሞገስ፣" እና "ግርማ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች የተነገሩት ሰው እንደሚጎናጸፈው ልብስ ተደርገው ነው። እንደ ቅጽሎች እና ግሶች ሆነው ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ራስህን ክቡር አድርግ፤ ሰዎች ያከብሩህ እና ከፍ ከፍ ያደርጉህ ዘንድ አንዳች ታላቅ ነገር አድርግ፤ ደግሞም ሰዎች እንደ ታላቅ ንጉስ እንዲመለከቱህ አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
የበዛውን ቁጣህን አፍስስ
"ቁጣ" የሚለው ረቂቅ ስም ብዙጊዜ የሚገለጸው በአንዳች መያዣ ነገር እንደሚያዝ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተደርጎ ነው፣ በዚህ ሁኔታ ግን አብሮ ሊሄድ የማይችለው በዙሪያ የሚፈስ ብዙ ነገር እንዳለው ተደርጎ። ይህ ሲበሳጭ ለሚወስደው እርምጃ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ለምን እንደሚቆጣ ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። "ሰዎች ስለሚኮሩ እና ስለሚቀጣቸው በዚህ ምክንያት ይቆጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች እንዲሁም ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

አዋርደው

"የሚኮራበትን ነገር ሁሉ ውሰድበት"

Job 40:12

የእነርሱን ፊቶች

"ፊት" የሚለው የሚወክለው ሰውየውን ነው። "እነርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ስውር ስፍራ

ሰዎች ሲሞቱ መንፈሳቸው ስለሚሄድበት ስፍራ በዩፊሚዝም/የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ የቀረበ አገላለጽ። (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

Job 40:15

ብሄሞት

ትልቅ ውሃ ውስጥ የሚኖር እንስሳ፣ ምናልባት ጉማሬ ሊሆን ይችላል

እርሱ ይበላል

ብሄሞት ይበላል

እንደ በሬ ሳር ይበላል

ብሄሞትም በሬም ሁለቱም ሳር ይበላሉ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የወገብ... የሽንጥ/ሆድ ጡንቻዎች

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ የሰውነት ክፍልን ይገልጻሉ

Job 40:17

እንደ ጥድ

ጥድ በጣም ጠንካራ እንጨት ነው፣ እናም የጉማሬው ጭራ እንደ ጥድ በጣም ጠንካራ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ናስ ቱቦዎች

እዚህ ስፍራ፣ የእንስሳውን ጥንካሬ ለመግለጽ አጥንቶቹ የተነጻጸሩት ከናስ ከተሰራ ቱቦ ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ብረት መቀርቀሪያዎች

ይህ የመጨረሻው ማነጻጸሪያ የሚገልጸው የዚህን ትልቅ እንስሳ ጥንካሬ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 40:19

የፍጥረት አለቃ/ዋና

"ከፍጥረታት ሁሉ ዋናው" ወይም "ከፍጥረታት በጣም ጠንካራው"

የፍጥረታት አምላክ። እግዚአብሔር ብቻ

ያህዌ ራሱን እንደ ሌላ አካል አድርጎ ይናገራል። "የእኔ ፍጥረቶች። እኔ ብቻ፣ እግዚአብሔር" (ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ኮረብቶች ምግብ ያበቅሉለታል

ኮረብቶች የተገለጹት ምግብ መስጠት እንደሚችሉ ሰዎች ተደርገው ነው። "ለእርሱ በኮረብቶች ምግብ ይበቅላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አስደሳች ተክሎች

በረግረጋማ አካባቢዎች በውሃ ላይ የሚበቅሉ አበባማ ተክሎች

ቄጠማ

በረግረጋማ ወይም አረንቋማ ስፍራ የሚገኝ ረጅም ሳር

Job 40:22

አስደሳች ተክሎች

በረግረጋማ አካባቢዎች በውሃ ላይ የሚበቅሉ አበባማ ተክሎች። ይህ በኢዮብ 40፡ 19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የወንዝ ዳርቻ ዛፍ

የወንዝ ዳርቻ ዛፎች በረግረጋማ ስፍራ የሚበቅሉ ትላልቅ ዛፎች ናቸው። በእናንተ ባህል ውስጥ የማይታወቁ ከሆኑ፤ በውሃ ዳር የሚበቅል ዛፍን ስም መጠቀም ትችላላችሁ።

የወንዝ ዳርቻ

በወንዝ ዳርና ዳር

ዮርዳኖስ ከአፍ እስከ ገደፉ ቢሞላም

"ምንም እንኳን የዮርዳኖስ ወንዝ እስከ አፉ ቢሞላም"

አጥምዶ...በመንጠቆ ሊይዘው የሚችል አለን?

ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ማንም በመንጠቆ ወይም በወጥመድ አፍንጫውን ሊይዝ አይችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 41

Job 41:1

አጠቃላ መረጃ፡

እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል። ኢዮብን ለመገዳደር ብዙ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎችን ይጠቀማል

አሳ በሚያዝበት መንጠቆ ሌዋታንን አጥምደህ ልታወጣው ትችላለህ?

እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ሌዋታን ጠንካራ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "አሳ በሚጠመድበት መንጠቆ ሌዋታንን ማጥመድ እንደማትችል ታውቃለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አጥምደህ ልታወጣው

ከውሃ ውስጥ ልታወጣው

የእርሱ...እርሱ

"የእርሱ" እና "እርሱ" የሚሉት ቃላት ሌዋታንን ያመለክታሉ።

ወይስ በገመድ/ሲባጎ መንጋጋውን ታስራለህ?

"አንተ ትችላለህን?" የሚሉት ቃላት ከቀደመው ጥያቄ በመነሳት ሊታወቁ የሚችሉ ናቸው። እዚህ ስፍራ ሊደገሙ ይችላሉ። እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ ኢዮብ እንደ ሌዋታን ጠንካራ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ተጠቅሞበታል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ወይንስ መንጋጋውን በሲባጎ ልታስር ትችላለህን?" ወይም "ደግሞም መንጋጋውን በሲባጎ ማሰር እንደማትችል ታውቃለህ።" (የተዘለለ/ የተተወ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

በአፍንጫው ውስጥ ገመድ ማስገባት... በመንጠቆ ልታጠምደው ትችላለህን?

እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ሌዋታን ሀይለኛ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "በመንጠቆ እንደማትይዘው...በሌዋታን አፍንጫ ገመድ ማስገባት እንደማትችል ታውቃለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንተ ብዙ ልመና ያቀርባልን?

እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ሌዋታን ሀይለኛ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። " ለአንተ ልመና እንደማያቀርብልህ ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንተ ለስላሳ ቃላትን ይናገራል?

እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ሌዋታን ሀይለኛ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ለአንተ ለስላሳ ቃላትን እንደማይናገር ታውቃለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Job 41:4

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ኢዮብን መገሰጹን ቀጥሏል። እርሱ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ሌዋታን ጠንካራ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ነው።

ለዘለዓለም አገልጋዩ እንድታደርገው እርሱ ከአንተ ጋር ቃለኪዳን ይገባል?

ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ለዘለአለም አገልጋይህ እንድታደርገው ከአንተ ጋር ቃለኪዳን እንደማይገባ ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ... የእርሱ

"እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት ሌዋታንን ያመለክታሉ።



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከወፍ ጋር እንደሚጫወት ከእርሱ ጋር ትጫወታለህን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ከወፍ ጋር እንደምትጫወት ከእርሱ ጋር መጫወት እንደማትችል ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ለአገልጋይ ልጃገረዶችህ እርሱን ማሰር ትችላለህን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ለአገልጋይ ልጃገረዶችህ እርሱን ማሰር እንደማትችል ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
አሳ አጥማጆች ከእርሱ ጋር መደራደር ይችላሉን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "አሳ አጥማጆች ከእርሱ ጋር ሊደረደሩ እንደማይችሉ ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በነጋዴዎች መሃል ሊነግዱበት እርሱን ይከፋፈሉሉን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "እርሱን ሊነግዱት በማህላቸው እንደማይከፋፈሉት ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ይከፋፈሉታል
"አሳ አጥማጅ ቡድኖች ይከፋፈሉታል"

Job 41:7

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ኢዮብን መገሰጹን ቀጥሏል፡፡ እርሱ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ኢዮብ እንደ ሌዋታን ጠንካራ አለመሆኑን ሊያስታውሰው ነው፡፡
ቆዳውን በአንካሴ ወይም ጭንቅላቱን በአሳማጥመጃ ጦር ልትወጋው ትችላለህ?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ቆዳውን በአንተ ማደኛ መሳሪያ ልትበሳው አትችልም፣ አሊያም ጭንቅላቱን በአሳ ማጥመጃ ጦር ልትበሳው አትችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ… የእርሱ
"እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት ሌዋታንን ያመለክታሉ፡፡
አንካሴዎች
ሰዎች ትላልቅ የውሃ ውስጥ ፍጥረታትን ለማደን የሚጠቀሙባቸው ሹል ጫፍ ያላቸው ረጃጅም ጦሮች
እነሆ
"ተመልከት" ወይም "ስማ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ"
በአይታው ብቻ ማንም ቢሆን ምድር ላይ አይወድቅምን?
ይህ ማጠቃለያ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ወደ እርሱ የሚመለከት ምድር ላይ እስኪወድቅ ድረስ እጅግ በፍርሃት ይዋጣል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
እርሱን ማየት
"ወደ እርሱ በመመልከት" ወይም "እርሱን በማየት"

Job 41:10

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በመጠየቅ ኢዮብን መገሰጹን ቀጥሏል፡፡ እርሱ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ያህዌ ከሌዋታንም ሆነ ከኢዮብ ይልቅ እጅግ ጠንካራ መሆኑን ሊያስታውሰው ነው፡፡
ማን ሌዋታንን ሊደፍር ይችላል፣ ታዲያ ይልቁን በእኔ ፊት ማን ሊቆም ይችላል?
በያህዌ ፊት ከመቆም ሌዋታንን መንካት ቀላል ይሆናል፡፡ ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ማንም ሌዋታንን ሌዋታንን ለመንካት እንደማይደፍር ታውቃለህ፣ ይልቁንም ማንም በፊቴ ሊቆም እንደማይደፍር በእርግጠኝነት ማወቅ ይኖርብሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእርሱ እመልስለት ዘንድ አስቀድሞ አንዳች ነገር ለእኔ የሰጠኝ ማን ነው?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ማንም ለእኔ አስቀድሞ አንዳች ነገር እንዳልሰጠኝ ታውቃለህ፣ ስለዚህም እኔ መልሼ ልከፍለው የሚገባኝ ማንም የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ… የእርሱ
"እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት አንድን ሰው ያመለክታሉ፡፡
… በተመለከተ ዝም አልልም…አሊያም ስለ… አሊያም ስለ
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "በእርግጥ እኔ ስለ…በእርግጠኝነት እናገራለሁ… እና ስለ…እና ስለ…" (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
የሌዋትንን እግሮች በተመለከተ፣ አሊያም ስለ እርሱ ጥንካሬ፣ አሊያም ስለ አስፈሪ መልኩ
እነዚህ እግዚአብሔር ዝም የማይልባቸው ነገሮች ናቸው
የእርሱ
"የእርሱ" የሚለው ቃል ሌዋታንን ያመለክታል

Job 41:13

አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በመጠየቅ ኢዮብን መገሰጹን ቀጥሏል፡፡
ውጫዊ ሽፋኑን ማን ሊያስወልቀው ይችላል?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ማንም ውጫዊ ልብሱን ሊያስወልቀው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ
"የእርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋታንን ነው፡፡
ድርብ የጦር ልብሱን ማን ሊበሳው ይችላል?
"የጦር ልብስ" የሚለው ጠንካራ ቅርፊት ወይም የጀርባው ቆዳ ለሚለው ዘይቤ ነው፡፡ ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ማንም ቢሆን በጣም ወፍራም ቆዳውን ሊበሳ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
አስፈሪ የሆነውን…ማን የአፉን ደጅ ሊከፍት ይችላል?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ማንም አስፈሪ… መንጋጋውን መክፈት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ጋሻዎች
"ጋሻዎች" የሚለው ቃል ለሌዋታን ጠንካራ ቆዳ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው፡፡ ጋሻዎች እና የሌዋታን ቆዳ የሚሉት ሁለቱም ቀስቶችን የሚመክቱ እና ከሌሎችም መሳሪያዎች የሚከላከሉ ናቸው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ተገጣጥመው እርስ በእርስ የተቀራረቡ ናቸው
ይህ ማለት "ጋሻዎቹ" እርስ በእርሳቸው የተቀራረቡ በመሆናቸው በመሃላቸው ምንም ነገር ሊገባ አይችልም፡፡

Job 41:16

አንዱ ወደ ሌላው እጅግ የቀረበ ነው
በአንዱ ረድፍ ሚገኙት ጋሻዎች ከሌላው ጋር እጅግ ቅርብ ነው፡፡ (ኢዮብ 41፡15)
የእነርሱ…እነርሱ
"የእነርሱ" እና "እነርሱ" የሚሉት ቃላት በመስመር የተደረደሩ ጋሻዎችን ያመለክታሉ፡፡ (ኢዮብ 41፡15)
ለየብቻ ሊለያዩ አይችሉም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ "ማንም ሊገነጣጥላቸው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከመደንፋቱ/ከማሽካካቱ
"ሲደነፈፉ/ሲያሽካካ፡፡" በመኝታ ከሚሰማ አጭር ማንኮራፋት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ሊሰጥ የሚችለው ሌላ ትርጉም "ከማስነጠሱ ጋር" ወይም "ሲያስነጥስ" የሚል ነው፡፡
ዐይኖቹ የንጋት ሽፋሽፍትን ይመስላሉ
ይህ ማለት ዐይኖቹ የማለዳ ሰማይ እንደሚቀላ የቀሉ ናቸው፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ
"የእርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋታንን ነው፡፡

Job 41:19

ከአፉ የሚነድ ችቦ ይወጣል፣ የእሳት ብልጭታ ይፈናጠራል
እግዚአብሔር በሌዋታን አስፈሪ መልክ ላይ ትኩረት ለመስጠት ተመሳሳይ ሀሳብን በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይገልጻል፡፡ ይህንን የተተወውን ቃል በመጨመር ግልጽ ማድረግ ትችላላችሁ፡፡ "ከአፉ የሚነድ ችቦ ይወጣል እና የእሳት ብልጭታ ይወጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና የተዘለለ/የተተወ የሚሉትን ይመልከቱ)
የእርሱ
"የእርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋታንን ነው፡፡
አፍንጫዎቹ

የአፍንጫው ሁለቱ ቀዳዶች
እንደሚፈላ ገንቦ የሚጤስ
ጢስ እና የሚፈላ ገንቦ ሁለቱም በጣም ሞቃት ናቸው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሰል ወደ ፍምነት ይቀጣጠላል
"ከሰል ፍም እንዲሆን"
Job 41:22
የእርሱ...እርሱ
"የእርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌዋታንን ነው።
ፍርሃት በፊቱ ያሸበሽባል
"ፍርሃት" የሚለው ረቂቅ ስም "ፈራ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች እርሱ ሲመጣ ሲመለከቱ፣ በጣም ይፈራሉ" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ሊንቀሳቀሱ አይችሉም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ሊያንቀሳቅሳቸው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ልቡ እንደ ድንጋይ ጠንካራ ነው
አለት ወይም ድንጋይ ተለውጦ ለስላሳ አይሆንም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)የሌዋታን ደረቱ እና በውስጡ ያሉ አካላት ጠንካራዎች ናቸው ወይም 2)ሌዋታን አንዳች ነገር አይፈራም ወይም 3) ሌዋታን የተገለጸው ያለ አንዳች ርህራሄ እንደሚገድል ሰው ተደርጎ ነው። (ተነጻጻሪ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
የታችኛው ድርብርብ አለት
"ከአለቶች ሁሉ ይበልጥ ጠንካራ የሆነው።" የታችኛው አለት ትልቅ እና ለእህል ወፍጮነት የሚያገለግል ከሁለቱ የላይኞቹ አለቶች ጠንካራ የሆነው ነው። ሰዎች ሊያገኙ ከሚችሏቸው አለቶች እጅግ ጠንካራዊ ነው።
Job 41:25
እርሱ... እርሱ ራሱ...የእርሱ
"እርሱ፣" "እርሱ ራሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ሌዋታንን ነው።
አማልዕክቱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ታላላቅ ሰዎች" ወይም 2) "በጣም ጠንካራ ሰዎች"
ብረትን እንደ ገለባ ይቆጥራል
"ከብረት የተሰሩ መሳሪያዎችን ከገለባ እንደተሰሩ ይቆጥራቸዋል።" ገለባ ቆዳውን አልፎ ሊገባ እንደማይችል ያህል፣ የብረት መሳሪያዎች ቆዳውን ሊበሱት አይችሉም/ ብረትን እንደ ገለባ ይቆጥራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ነሐስን ብል እንደበላው እንጨት ይቆጥራል
ይህንን የተተዉ ቃላትን በመጨመር ግልጽ ማድረግ ይቻላል። "ከነሐስ የተሰሩ መሳሪያዎችን ብል በበላው እንጨት እንደተሰሩ ይቆጥራቸዋል" (የተዘለለ/የተተወ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
Job 41:28
ለእርሱ የወንጭፍ ድንጋይ ገለባ ይሆንለታል
ገለባ ሌዋታንን ሊጎዳው አይችልም፣ እንደዚሁም የወንጭፍ ድንጋይ ልክ እንደ ገለባ ሁሉ የማይጎዳው ይሆናል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ... እርሱ ራሱ...የእርሱ
"እርሱ፣" "እርሱ ራሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ሌዋታንን ነው።
በትርን እንደ ገለባ ይቆጠራል
ከገለባ የተሰራ መምቻ እርሱን ሊጎዳው እንደማይችል ሁሉ ከእንጨት የተሰራም በትር አይጎዳውም። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ዱላን እንደ ገለባ ይቆጥራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በተሰበቀ ጦር ላይ ይስቃል
ጦር የወረወረ ሰው ጦሩ ሌዋታንን እንደሚገድል ተስፋ ያደርጋል፣ ነገር ግን ጸሐፊው የሚገልጸው ሌዋታን ጦሩ እንደማይገድለው እንደሚያውቅ እና በተወረወረው ጦር እንደሚስቅ አድርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ መውቂያ መሳሪያ በጭቃ ውስጥ ምልክት ጥሎ ያልፋል
የመውቂያ መሳሪያ የሚወቃውን እህል እንደሚያደቅ፣ ሌዋታ ጭራውን እያወዛወዘ ሲራመድ በጭቃ ላይ ምልክት እያደረግ ያልፋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 41:31
ጥልቁን በማሰሮ እንደሚፈላ ውሃ አረፋ ያደርገዋል
"በውሃ ውስጥ ሲያልፍ፣ ከኋላው በማሰሮ እንደሚፈላ ውሃ አረፋ እየተው ይሄዳል"
እርሱ
"እርሱ" የሚለው ቃል ሌዋታንን ያመለክታል።
ባህሩን በገንቦ እንዳለ ቅባት ያደርገዋል
በገንቦ ውስጥ ያለ ቅባት አንድ ሰው ቢበተብጠው ይደፈርሳል፣ እንደዚሁ ሌዋታን ሲዋኝበት ባህሩ ይደፈርሳል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሰው ጥልቁ ሽበት እንዳለው አድርጎ ሊያስብ ይችላል
ይህ የሚሆንበት ምክንያት ያንቀሳቀሰው ውሃ አረፋ ስለሚነጣ ነው
Job 41:33
ለእርሱ አቻ የለውም
"የትኛውም ፍጥረት እንደ ሌዋታን አይደለም"
እርሱ ኩራተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ ይመለከታል
"እርሱ በጣም፣ በጣም ኩራተኛ ነው"
የእርሱ... እርሱ
"የእርሱ" እና "እርሱ" የሚሉት ቃላት ሌዋታንን ያመለክታሉ።
እርሱ በኩራት ልጆች ላይ ሁሉ ንጉሥ ነው
ሌዋታን የተገለጸው ንጉሥ ሊሆን እና ሊኮራ እንደሚችል ሰው ተደርጎ ነው። "ሌዋታን በምድር ላይ ከማንም ይልቅ ሊኮራ የሚችልበት የበለጠ ምክንያት አለው" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 42
Job 42:1
አንተ ሁሉንም ነገሮች መስራት እንደምትችል አውቃለሁ፣ ከስራዎችህ አንዱም ሊገታ አይችልም
"እኔ አውቃለሁ" የሚሉትን ቃላት መድገም ልትፈልግ ትችላለህ። "ሁሉንም ነገሮች መስራት እንደምትችል አውቃለሁ። የትኛውም ተግባርህ ሊገታ እንደማይችል አውቃለሁ" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
የትኛውም ተግባርህ ሊገታ አይችልም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ከእቅዶችህ አንዱንም ማስቆም አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ማን ነው
ዩኤልቢ እና በርካታ ዘመናዊ ቅጅዎች ኢዮብ ከ መጽሐፈ ኢዮብ 38፡2 ላይ እንደጠቀሰ ይስማማሉ። እናንተም ሃሳቡን ግልጽ ለማድረግ በዩዲቢ እንደቀረበው እግዚአብሔር ኢዮብን ይህንን ጥያቄ እንደ ጠየቀው እና ኢዮብ አሁን ይህንን እንደሚያስታውስ መወሰን ትችላላችሁ። "አንተ ለእኔ፣ 'ይህ ማን ነው' ብለሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 42:4
ነገር ግን አሁን ዐይኖቼ አንተን አይተዋል
ዐይኖች ማየትን ይወክላሉ፣ ማየት ደግሞ መረዳትን ይወከወላል። "ነገር ግን አሁን እኔ በእርግጥ አንተን እረዳለሁ/አውቃለሁ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይምልከቱ)
ራሴን እንቃለሁ
የኢዮብ እኔነት/ራሱ ለተናገረው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ / ነው። "የተናገርኳቸውን ነገሮች እንቃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
መናቅ
ጥልቅ የሆነ መጥላት
በአፈር እና በአመድ ላይ ተቀምጬ ንስሃ እገባለሁ
በአፈር እና በአመድ ላይ መቀመጥ ሰውየው ማዘኑን የሚገልጽ ምልክታዊ ድርጊት ነው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 42:7
እንዲህም ሆነ
ይህ ሀረግ እዚህ ስፍራ የዋለው ጠቃሚ የሆነ ትዕይንት ወደ ታሪኩ ውስጥ መግባቱን ለማመልከት ነው። በእናንተ ቋንቋ ይህን መግለጽ የምትችሉበት መንገድ ካለ ይህን እዚህ ላይ መጠቀም ትችላላችሁ።
ቴማናዊው ኤልፋዝ
ይህ የወንድ ስም በኢዮብ 2፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ቁጣዬ በእናንተ ላይ ነድዷል

እሳት ቁጣን ለመግለጽ የዋለ ዘይቤ ነው። እሳት መለኮስ ለመቆጣት ዘይቤ ነው። "እኔ በእናንተ ላይ እጅግ ተቆጥቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይምልከቱ)
ሰባት ኮርማዎች
"7 ኮርማዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የሰራችሁትን አሳፋሪ ጥፋት እምር ዘንድ
"አሳፋሪ ጥፋት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ምንም እንኳን ያደረጋችሁት ሞኝነት ቢሆንም፣ የሚገባችሁን ቅጣት አልቀጣችሁም" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ሹሐዊው በልዳዶስ
ይህ የወንድ ስም በኢዮብ 2፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ናዕማታዊው ሶፋር
ይህ የወንድ ስም በኢዮብ 2፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ያህዌ ኢዮብን ተቀበለው
ሰውየው ለጸለየው ጸሎት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እግዚአብሔር ኢዮብ ለሶስቱ ወዳጆቹ የጸለየውን ጸሎት ተቀበለ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Job 42:10
ያህዌ እድል ፈንታውን አደሰለት
"ያህዌ ሀብቱን መለሰለት" ወይም "ያህዌ ሀብቱን አደሰለት"
አስቀድመው ያውቁት የነበሩ ሁሉ
"አስቀድሞ ያውቃቸው የነበሩ ሰዎች"
Job 42:12
ከመጀመሪያው ይልቅ
"እርሱ ባረከው" እና "የኢዮብ ህይወት" የሚሉት ቃላት ከቀደመው ሀረግ የሚታወቁ ናቸው። እዚህ ስፍራ ሊደገሙ ይችላሉ። "የመጀመሪያውን የኢዮብ የህይወት ምዕራፍ ከባረከው ይልቅ" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
አስራ አራት ሺህ በጎች
14,000 በጎች (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ስድስት ሺህ ግመሎች
6,000 ግመሎች (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሺህ ጥማድ በሬዎች
1,000 ጥማድ በሬዎች (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰባት ወንዶች ልጆች እና ሶስት ሴቶች ልጆች
7ወንዶች እና 3 ሴቶች (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ይማሚ... ቃሥያ... አማልቶያስ ቂራስ
የሴቶች ስሞች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Job 42:15
እንደ ኢዮብ ሴቶች ልጆች ያሉ ውብ ሴቶች አልነበሩም
"የኢዮብ ሴቶች ልጆች ከሌሎች ሴቶች ሁሉ የተዋቡ ነበሩ"
140 አመታተት ኖረ
"140 አመታት ኖረ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
እድሜ ጠገበ ደግሞም አርጅቶ
"እድሜ ጠግቦ" የሚሉት ቃላት "አረጀ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለቱ ሀረጎች የጋራ ፈሊጥ አላቸው። "በጣም ያረጀ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 1
Psalms 1:1
አጠቃላይ ሃሳብ፡
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)
በክፉዎች ምክር ያልሄደ
የ“ክፉዎች ምክር” የቀረበው እንደ መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፤ “በክፉዎች ምክር ያልሄደ” ወይም “የክፉዎችን ምክር ያልተገበረ” (ዘይቤን ይመልከቱ)
በኃጢአተኞች መንገድ የልቆመ
እዚህ ጋር “መንገድ” የሚለው ቃል የሚወክለው የሰዎችን የአኗኗር ዘይቤ ነው። “መቆም” የሚለው ቃል ደግሞ “መራመድ” ከሚለው ቃል ጋር ትይዩ ነው። አማራጭ ትርጉም፤ “የኃጢአተኞችን ባህሪ ማስመሰል”። (ዘይቤን ይመልከቱ)
ወይም በዋዘኞች መንገድ ያልተቀመጠ
በእግዚአብሔር ላይ ከሚያፌዙ (ዋዘኞች) ጋር መቀመጥ የሚያመለክተው ከዋዘኞች ጋር ማበርን ነው። አማራጭ ትርጉም፤ “ከዋዘኞች ጋር ማበር” ወይም “ከሌሎች ፌዘኞች ጋር እግዚአብሔር ላይ ማፌዝ”። (ድጋሚ መሰየም (Metonymy)ን ይመልከቱ)
በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል
“መደሰት” የሚለው ቃል ከረቂቅ ስም የወጣ ግስ ነው። አንድ ግለሰብ በሕግ ሊደሰት ይችላል ማለትም ሕጉ መልካም ስለሆነ እና ስለሚታዘዘው ደስተኛ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፤ “የእውነት የሚያስደስተው የእግዚአብሔር ሕግ ነው” ወይም “የእውነት የሚያስደስተው የእግዚአብሔርን ሕግ አየታዘዘ እንደሆነ ማወቁ ነው” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)
Psalms 1:3
አጠቃላይ ሃሳብ
ይህ ክፍል አንድ ጻድቅ ሰው ምን እንደሚመስል አንድ በአበበ ዛፍ ምስል ያብራራል።
እርሱም ... ፍሬዋን በየጊዜው እንደምትሰጥ ዛፍ ነው
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ አንድ ጊዜ ሰዎች እንደ ዛፍ ይመሰላሉ። በእግዚአብሔር ሕግ ደስ የሚሰኙ ሰዎች እግዚአብሔር እንዲሰሩ የሚፈልውን ሁሉ በውሃ ዳር የተተከለ ዛፍ መልካም ፍሬን እንደሚያፈራ መስራት ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፤ “ዛፍ በየወቅቱ እንደሚያራ የበለጸገ ይሆናል” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)
በውሃ ዳር እንደተተከለ
ከውሃ ዳር የተተከለ ዛፍ ጤነኛ ሆኖ እንዲቆይ የሚያደርገውን የውሃ መጠን ያገኛል።
ፍሬውን በየጊዜው እንደሚሰጥ
ጤነኛ ዛፎች መልካም ፍሬን በወቅቱ ያፈራሉ።
ቅጠልዋም እንደማይረግፍ
በቂ ውሃ የሚያገኝ ዛፍ ቅጠሎቹ ደርቀው አይሞቱም።
የሚሰራው ሁሉ ይከናወንለታል
“በሚሰራው ሁሉ ስኬታማ ይሆናል”
Psalms 1:4
ክፉዎች እንዲህ አይደሉም
እንዴት እንዳልሆኑ በግልጽ መጥቀስ ይቻላል። “ክፉዎች እንዲህ አይበለጥጉም” ወይም “ክፍዎች አይበለጽጉም” (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)
ነገር ግን እንደ ትብያ ናቸው
እንደ ትብያ የሆኑበትን መንገድ በግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፤ “እንደ ትብያ ጥቅም የለሾች ናቸው” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)
በፍርድ ፊት አይቆሙም
ያሉት አማራጭ ፍችዎች፡ 1) በፍርድ አለመቆም በእግዚአብሔር መፈረድን እና ከመገኘቱ መውጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፤ “እግዚአብሔር በሚፈርድባቸው ጊዜ በፊቱ አይቆዩም`` ወይም ጥፋተኛ እንደሆኑ እግዚአብሔር እንደወሰነባቸው ከመገኘቱ ዞር ማለት አለባቸው ወይም 2) በፍርድ ፊት አለመቆም በፍርዱ የሚፈረድበት መሆንን የሚያመለክት አባባል ነው. አማራጭ ትርጉም በፍርድ ይፈረድባቸዋል ወይም እግዚአብሔር በሚፈርድበት ጊዜ ይፈረድባቸዋል (ምሳሌያዊ አባባን ይመልከቱ)
በፍርድ
ፍርድ የሚለው ስም እንደ ግስም ሊሆን ይችላል። ይህ የሚያመለክተው የመጨረሻውን ፍርድ እግዚአብሔር በሁሉም ላይ የሚፈርድበትን ነው። አማራጭ ትርጉም፡ እግዚአብሔር በሁሉም በሚፈርድበት ጊዜ
ኃጣንም በፃድቃን ማህበር
‘መቆም’ የሚለውን ግስ ተርጓሚው ሊጨምር ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ኃጣን በጻድቃን ማህበር አይቆሙም” ወይም “እግዚአብሔር ኃጣን ከጻድቃን ጋር እንዲቆሙ አይፈቅድም”
ኃጥአንም በፃድቃን ማህበር
ተርጓሚዎች አይዎሙም የሚለውን ግስ ሊጨምሩበት ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም እግዚአብሔርም ኃጥአንን ከፃድቃን ጋር አብሮ አይቀበልም (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Psalms 1:6

እግዚአብሔር የፃድቃንን መንገድ ያውቃልና፤ የኃጥአን መንገድ ግን ትጠፋለች

እነዚህ ሁለት ስንኞች የሚያወዳድሩት በፃድቁ እና በኃጥአኑ ላይ የሚደርሰውን ነው። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

የፃድቁ መንገድ

የሰዎች ሕይወት እንደ ምንሄድበት መንገድ ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: የፃድቁ ሕይወት (ዘይቤን ይመልከቱ)

የኃጥአን መንገድ ግን ትጠፋለች

የሰዎች ሕይወት እንደ ምንሄድበት መንገድ ይገለጻል። አማራጭ ፍችዎች 1)የሚጠፋው መንገድ የሚያመለክተው ከአኗኗሩ የተነሣ የፃድቁን መጥፋት ነው። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ኃጥአን ከአኗኗራቸው የተነሣ ይጠፋሉ›› ወይም 2) የመንገድ መጥፋት መኖር ማቆምን የሚያሳይ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትጉም: ‹‹ኃጥአን የሚኖሩት አኗኗር መኖር መቀጠል አየችሉም›› (ዘይቤን እና ድጋሚ መሰየምን ይመልቱ)

---

Chapter 2

Psalms 2:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡

ትይዩነት በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

አሕዛብ ለምን አጉረመረሙ፣ ሕዝቦችስ ለምን ከንቱ ሴራ ያሴራሉ?

እነዚህ ጥያቄዎች የተጠየቁት ሕዝቡ ምን ያህል የተሳሳተ እና የሞኝ ነገሮች እንደሚያደርጉ ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም: ‹‹አሕዛብ ግራ ተጋብተዋል ሕዝቦችም ከንቱ ሴራ ያሴራሉ›› (መልስ አዘል ጥያቄዎችን ይልከቱ)

አሕዛብ ለምን ያጉረመርማ

ይህ የሚያመለክተው ምንአልባት አሕዛብ የንዴት ጩኸት እያሰሙ እንደነበር ነው።

አሕዛብ

ይህ የሚወክለው መሪዎቹን ወይም ሕዝቦቹን ነው። (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ከንቱ ሴራ

ምን አልባት በእግዚአብሔር እና በሕዝቡ ላይ የተሴረ ሴራ ነው።

የምድር ነገሥታት ተነሱ፤ አለቆችም … እንዲህ ሲሉ ተማከሩ

እነኚህ ሁለት ስንኞች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

ተነሱ … ተማከሩ

እነዚህ ቃላት አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው። የሚያመለክቱም፤ መሪዎች በአንድ ላይ እግዚአብሔርን እና መሲሁን ለመዋጋት እንደ ተነሱ። ይህ በግልጽ ሊፃፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፤ ‹‹ለመዋጋት መሰባሰብ … ለማመጽ በጋራ ማቀድ›› (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

መሳሪያቸውን እንበጥስ… ገመዳቸውንም እንጣል

ሌሎች ሕዝቦች ስለ የያህዌን እና የመሲሁን በእነርሱ ላይ መንገስ እንደ መሳርያ እና ሰንሰለት ይገልጹታል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ከእነርሱ ቁጥጥር ራሳችንን ነፃ ማውጣት አለብን፤ በእኛ ላይ እንዲሰለጥኑ ልንፈቅድላቸው አይገባም›› (ዘይቤን ይመልከቱ)

Psalms 2:4

እርሱ… ጌታ

እነዚህ ቃላት ያህዌን ያመለክታሉ። ያህዌ ብዙውን ጊዜ ‹‹ጌታ›› ተብሎ ይገለጻል። ነገር ግን ያህዌ እኛ ጌታ የተለያዩ ቃላ ናቸው።

በሰማይ የሚኖር

በዚህ ስፍራ መኖር የሚያመለክተው መግዛትን ነው። የሚኖቦት በግልጽ ሊጠቀስ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፤ ‹‹በሰማይ ይገዛል›› ወይም ‹‹በሰማይ በዙፋኑ ይኖራል›› (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

ጌታም ይሳለቅባቸዋል

‹‹እንደነዚህ ባሉት ጌታ ይሳለቅባቸዋል።›› ለምን እንደሚሳለቅባቸው በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ጌታ ከሞኝ እቅዳቸው የተነሣ ይሳለቅባቸዋል። (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

በመአቱ ያውካቸዋል

‹‹መአት›› ረቂቅ ስም ነው ‹‹በቁጣ›› ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፤ ‹‹ይቆጣና ያውካቸዋል›› (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

መታወክ

ታላቅ ፍርሃት

Psalms 2:6

እኔ ግን

የህዌ የሚያተኩረው ሌላ ሳይሆን እርሱ ራሱ ንጉሡን እንደሚሾም ነው።

ንጉሤን ሾምሁ

‹‹ንጉሤ እንዲነግስ አደረግሁ››

ትእዛዙን እናገራለሁ

ይህን የሚናገረው ንጉሡ ነው። ይህ በግልጽ ቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ንጉሡም እንዲህ አለ፣ ‹‹የያህዌን ትእዛዝ እናገራለሁ›› (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

እንዲህ አለኝ

‹‹ያህዌ እንዲህ አለኝ››

አንተ ልጄ ነህ፤ ዛሬ እኔ ወለድሁህ

በዚያን ዘመን እና የዓለም ክፍል ከብዙ ሰዎች መካከል ሰዎች ወራሽ የሚሆናቸውን በሕግ በጉዲፈቻነት ለመውሰድ ይወስኑ ነበር። እዚህ ጋር ያህዌ አንድ ሰው በጉዲፈቻ ይወስድ እኛ በእስራኤል ላይ ንጉሥ ያደርገዋል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ልጄ አደረግሁህ። ዛሬ አባት ሆኜሃለሁ›› ወይም ‹‹አሁን አንተ ልጄ ነህ እኔም አባትህ››

Psalms 2:8

አያያዥ ዓረፍተ-ነገር፡

ያህዌ ለአዲሱ የእስራኤል ንጉሥ መናገሩን ይቀጥላ።

ሕዝቡን ለርስትህ፣ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ

እነዚህ ሁለት ስንኞች አንድ አይነት ሃሳብን ያመለክታሉ። (ትይዩነትን ይመልቱ)

የምድርም ዳርቻ

‹‹እሩቅ የሚገኙ ቦታዎች››

በብረት በትር ትሰባብራቸዋለህ፤ እንደ ሸክላ ሰሪ ዕቃዎች ትቀጠቅጣቸዋለህ

እነዚህ ሁለት ስንኞች አንድ አይነት ሃሳብን ያመለክታሉ። (ትይዩነትን ይመልቱ)

በብረት በትር ትሰባብራቸዋለህ

ሕዝቡን ማሸነፍ እንደ መሰበበር ተገልጧል የንጉሡም ኃይል እንደ ብረት ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፤ ‹‹በኃይልህ ሙሉ ለሙሉ ታሸንፋቸዋለህ።›› (ዘይቤን ይመልከቱ)

ትቀጠቅጣቸዋለህ

ሕዝቦችን መሸነፍ እንደ ሸክላ ዕቃ መሰባበር ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ሙሉ ለሙሉ እንደ ሸክላ ዕቃ ታጠፋቸዋለህ›› (ዘይቤን እና አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልክቱ)

እንደ ሸክላ ሰሪ ዕቃዎች

የሸክላ ሰሪ ዕቃዎች በቀላሉ ተሰባሪ ዕቃዎች ናቸው። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ሸክላ›› ወይም ‹‹የሸክላ ዕቃ›› (የማይታወቁን መተርጎምን ይመልከቱ)

Psalms 2:10

ስለዚህ እናንተ ነገሥታት ልብ በሉ፤ እናንተ የምንር ገዥዎችም፤ ተጠንቀቁ።

እነዚህ ሁለት ስንኞች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ስለዚህ እናንተ ነገሥታት እና የዓለም መሪዎች ልብ በሉ እና ታረሙ›› (ትይዩነትን ይመልከቱ)

ልብ በሉ

በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ይህን ማስጠንቀቂያ አድምጡ›› ወይም ‹‹ጥበበኞች ሁኑ›› (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)

ተጠንቀቁ

በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ይህን ማስጠንቀቅያ አድምጡ›› ወይም ‹‹ጥበበኞች ሁኑ›› (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)

Psalms 2:12

ልጁን ሳሙት

ሰዎች ታማኝነታቸውን ለመግለጽ ንጉሡን ይስሙታል ምን አልባትም እግሩን። አማራጭ ትርጉም: ‹‹የእውነት መገዛታችሁን ለልጁ አሳዩት›› ወይም ‹‹ በልጁ ፊት ዝቅ ብላችሁ ስገዱ›› (አመልካች ድርጊትን ይመልከቱ)

በመንገዱ እንዳትጠፉ

አንድ ሰው ከመንገዱ ዞር ማለት ሳይችል እዚያው እና ወድያው መሞትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም ‹‹ወድያው ትሞታላችሁ››

ቁጣው ፈጥኖ ይነዳል እና

የንጉሡ ቁጣ እንደ እሳት ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም: ‹‹ድንገት በተናደደ ጊዜ›› (ዘይቤን ይመልከቱ)

እርሱን መጠጊያ የሚያደርጉ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ክለላን ከንጉሡን መፈለግ መጠጊያ እንደመፈለግ ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም:
‹‹ንጉሡ እንዲጠብቃቸው የሚጠይቁ›› (ዘይቤን ይመልከቱ)

## Chapter 3

### Psalms 3:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡

x

### Psalms 3:3

አንተ ግን ያህዌ ጋሻዬ ነህ

ጋሻ ተዋጊን ይከላከላል። ዳዊት እግዚአብሔርን እንደ ገሻው ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም: አንተ ግን ያህዌ እንደ ጋሻ ትከልከኛለህ›› (ዘይቤን ይመልከቱ)

ክብሬ

እግዚአብሔርን ክብሬ ብሎ በመጥራት ዳዊት ክብር የሚሰጠው እግዚአብሔር እንደሆነ ይናገራል። ዳዊት ስለጠላቶቹ ስለተናገረ እና እግዚአብሔርን ጋሻዬ ስላለ፣ ክብሬ ሲል ደግሞ ምን አልባት በጠላቶቹ ላይ እንዲያሸንፍ በማድረግ ክብር እንደሚሰጠው ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም: “ክብር የምትሰጠኝ አንተ ነህ” ወይም “ድልን የምትሰጠኝ አንተ ነህ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ራሴን ከፍ ከፍ የምታደርገው አንተ ነህ

“ራሴን ከፍ ክፍ የምታደርገው አንተ ነህ” አንድን ሰው ማበረታታት ራስን ከፍ እንደ ማድረግ ይገለጣል። አማራጭ ትርጉም “የምታበረታታኝ” (ዘይቤን ይመልከቱ)

ድምፄን ከፍ አደርጋለሁ

ለመጮህ ድምፅን መጠቀም ድምፅን ከፍ እንደማድረግ ይገለፃል። አማራጭ ጥርጉም: “እጮሃለሁ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

ሴላ

ይህ ምንአልባት ሰዎች እንዴት መዘመር ወይም የሙዚቃ መሳርያ እንዴት መጫወት እንደሚገባቸው የሚያሳይ የሙዚቃ ቃል ነው። አንድ አንድ ትርጉሞች የዕብራይስጥ ቃሉን ሲጽፉት ሌሎች ደግሞ በትርጉም ውስጥ እንደውም አያካትቱትም። በመዝ 3፡1 ይህን እንዴት እደተረጎሙት ይመልከቱ። (ቃላት መዋስን ይመልከቱ)

### Psalms 3:5

የሚከቡኝን

“ከየአቅጣጫው የከበበኝን”

### Psalms 3:7

ተነሥ

ዳዊት አንድን ነገር ለማድረግ መጀመር መነሳት ብሎ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም: “እርምጃ ውሰድ” ወይም “አንድ ነገር አድርግ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

የጠላቶቼን መንጋጋ መትተሃልና የክፉዎችንም ጥርስ ሰብረሃል

እነዚህ ሁለት አገላለጾች ተመሳሳይ ናቸው። “ጠላቶቼ” እና “ክፉዎች” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ሰዎችን ይወክላሉ። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

የጠላቶቼን መንጋጋ መትተሃልና

ይህ ሰዎችን የመሳደብ መንገድ ነው። ዳዊት እየተናገረ ያለው ያህዌ እራሱ መጥቶ ጠላቶቹን እንደሚመታ ነው አማራጭ ትርጉም: “መንጋጋችን እንደሚመታ ጠላቶቼን ታዋርዳቸዋለህ” (ምስላዊ እንቅስቃሴን እና ዘይቤን ይመልከቱ)

## Chapter 4

### Psalms 4:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ትይዩነት በዕብራይስጥ የቅኔ ጽሑፍ የተለመደ ነው። (ቅኔና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ

“ይህ ለመዘምራን አለቃ በአምልኮ ለመምራት ነው”

በበገናዎች የሚዜም

“ከመዝሙሮች ጋር ሰዎች በመሳርያዎችን/በገናዎችን ሊጫወቱ ይገባል”

የዳዊት መዝሙር

አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው

በጠራሁህ ጊዜ መልስልኝ

“ስጠራህ መልስልኝ” ወይም “ስጠራህ እርዳኝ”

የጽድቁ አምላክ

“ጻድቅ እንደሆንሁ የሚያሳይ አምላክ”

በጭንቀቴ አሰፋልኝ

በችግር ውስጥ መሆን በጠባብ ስፍራ እንደመሆን ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “በችግር ጊዜ አድነኝ” (ዘይቤን ይመልከቱ)

### Psalms 4:2

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህን የመዝሙር ክፍል ዳዊት ለጠላቶቹ እንደሚያወራ ይዘምረዋል።

እናንተ ሰዎች ሆይ እስከ መቼ ድረስ ክብሬን ዝቅ ታደርጋላችሁ?

ዳዊት ይህን ጥያቄ ጠላቶቹን ለመገሰጽ ይጠቀምበታል። አማራጭ ትርጉም: “እናንተ ሰዎች ባለማቋረጥ ክብሬን ወደ ውርደት ትለውጣላችሁ!” (መልስ አዘል ጥያቄዎችን ይልከቱ)

ክብሬን ወደ ውርደት

በማክበር ፈንታ እርሱን ማዋረድ ክብርን ወደ ውርደት እንደመቀየር ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም: “በማክበር ፈንታ ታዋርዱኛላችሁ” ወይም “ክብርን በመስጠት ፈንታ ውርደት ትሰጡኛላችሁ”

እስከ መቼ ድረስ ከንቱ ነገርን ትወዳላችሁ? ሐሰትንስ ትሻላችሁ?

ዳዊት ይህን ጥያቄ ጠላቶቹን ለመገሰጽ ይጠቀምበታል። አማራጭ ትርጉም: “ከንቱ ነገር በመውደድ ትቀጥላላችሁ ውሸትንም ትሻላችሁ” (መልስ አዘል ጥያቄዎችን ይልከቱ)

ከንቱ ነገርን ትወዳላችሁ? ሐሰትነስ ትሻላችሁ?

እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ትርጉም አዝለዋል። ሐሰት ከንቱ ነገር ነው። አማራጭ ትርጉም: “ከንቱ ሐሰትን ትወዳላችሁ” (ትይዩነትን ይመልከቱ)

ያህዌ ለራሱ ጻድቁን እንደለየ ዕወቁ

“ያህዌ እግዚአብሔራዊ ሰዎችን ለራሱ ይመርጣል”

### Psalms 4:4

በፍርሃት መርበትበት

የ”ፍርሃት” እና የ”መርበትበት” ግንኙነት እና ሰዎች ማንን መፍራት እንዳለባቸው በግልጽ መጠቀስ ይችላል።አማራጭ ትርጉም: “ያህዌን እስክትርበተበቱ ድረስ ፍሩት” ወይም “በያህዌ በመደነቅ ቁሙ” (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

መርበትበት

በፍርሃት መንቀጥቀጥ

በልብ አሰላስል

ልብ የሰውን ሃሳብ ይወክላል። በጥንቃቄ ማሰብ እንደ ማሰላለሰል ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “በጥንቃቄ አስብ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

የጽድቅን መስዋዕት ሰዉ

“ጻድቅ መስዋዕትን ሰዉ”

እግዚአብሔርን ታመኑ

እዚህ ጋር እምነት አንድ ቦታ ማስቀመጥ እደምንምችለው ቁስ አቃል ተገልጧል። “መታመን” የሚለው ስምም በግስ መልክ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “በያህዌ ታመን” ወይም “ያህዌን ታመን” (ዘይቤን እና ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

### Psalms 4:6

በጎውን ማን ያሳየናል?

አማራጭ ፍችዎች 1) መልካም ነገር ማሳየት መልካም ነገር ማምጣትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “መልካም ነገር ማን ያመጣልናል?” ወይም 2) ምልካም ነገር ማሳየት መልካም ነገር እንደሆነ መናገር። አማራጭ ትርጉም: “መልካም ነገር ሆንዋል ብሎ ምን ይነገረናል?” (ድጋሚ መሰየምን ይመለክቱ)

የፊትህ ብርሃን በላያችን ያብራ

ጸሐፊው ያህዌ በአድሎ ወደነሱ ሲመለከት ፊቱን እንደ ማብራት ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም: “ለኛ በአድሎ እርምጃ ውሰድ” (ዘይቤን ይመልከቱ)

በልቤ ደስታን ጨመርህ

ልብ ግለሰቡን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “የበለጠ ደስታን ሰተኸኛል” (በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየም Synecdocheን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከሌሎች ይልቅ ደስታን አብዝተህ ሰጠኸኝ

እዚህ ጋር “ደስታ” ሊሰጥ እንደሚችል ቁስ አካል ተገልቷል፡፡ “ደስታ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ “መደሰት” ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “ከሌሎች ይልቅ ደስተኛ አድርገኸኛል” (ዘይቤን እና ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

ስንዴና አዲስ ወይን ይልቅ

“አዲስ ወይን” የወይን ፍሪን ሊያመለክት ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም “የስንዴ እና የወይን መኸሩ ብዙ በሆነ ጊዜ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

በሰላም እተኛለሁ አንቀላፋለሁም

ሰላም የተገለፀው እንደ ስፍራ ነው፡፡ ይህ ወደ ረቂቅ ስም ወደ መሆን ይቀይረዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “ስተኛ እና ሳንቀላፋ ሰላማዊ እሆናለሁ” ወይ “ስተኛ እና ሳንቀላፋ አደጋን አልፈራም” (ዘይቤን እና ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

በሰላም እና ያለስጋት

እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው በመደገማቸው ፍጹም ደህንነትን ያመለክታሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “ፍጹም ደህና እንድሆን ያደርገኛል”

---

Chapter 5

Psalms 5:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡

በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው፡፡ (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ

“ይህ ለመዘምራን አለቃ ለአምልኮ እንዲጠቀምበት ነው”

በዋሽንት

“ይህ መዝሙር በዋሽንት በሚጠቀሙ መታጀብ አለበት”

የዳዊት መዝሙር

አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው፡፡

ቃሌን አድምጥ

ይህ እርዳታን ፍለጋ የሚደረግ ጥሪ ነው፡፡ አማራጭ ትጉም፡ “ለእርዳታ ወደ አንተ ስጣራ ስማኝ”(ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)

መቃተቴን

ሰዎች በስቃይ ጊዜ የሚያሰሙት ዝግ ያለ ድምጽ

በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ፤ በማለዳ ልመናዬን በፊትህ አቀርባለሁ

እነኚህ ሁለት ስንኞች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፡፡ (ትይዩነትን ይመልከቱ)

ልመናዬን በፊትህ አቀርባለሁ

“ጥያቄዬን አቀርባለሁ” ወይም “የሚያስፈልገኝን እጠይቅሃለሁ”

በጥሞና እጠባበቃለሁ

“የጠየኩትን እንደምታደርግልኝ እጠብቃለሁ”

Psalms 5:4

ያህዌ ክፉ እና ሐሰተኛ ሰዎችን ይቃወማል

በዚህ መዝሙር ዳዊት ወደ እግዚአብሔር እየተናገረ ስለሆነ፣ ይህ ስንኝ አንተ በሚል መተካ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም “ያህዌ፣ አንተ ክፉ እና ሐሰተኛ ሰዎችን ትቃወማለህ” ወይም “ያህዌ፣ አንተ ክፉ የሚሰሩ ሰዎችን እና የሚዋሹ ሰዎችን ትጠላለህ” (አንደኛ፥ ሁለተኛ እና ሦስተኛ መደብን ይመልከቱ)

Psalms 5:7

በምሕረትህ (በታማኝነትህ) ብዛት

“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ገላጭ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፤ “ለቃልኪዳንህ ታማኝ ስለሆንክ” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

ቤትህ

ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “ቤተ
መቅደስህ”

በጽድቅህ ምራኝ

ዳዊት ጽድቅን እንደ መንገድ ማስተማርንም እንደ መምራት ይገልጻል፡፡ “ጽድቅህ” የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑን ያመለክታል አማራጭ ትርጉም፡ “ትክክል የሆነውን ማድረግ እንድችል አስችለኝ” (ምሳሌያዊ አባባልን ይመልከቱ)

መንገድህን በፊቴ አቅና

ዳዊት ጽድቅን እንደ መንገድ ይገልጸዋል፡፡ የቀና መንገድ ለማየትም ለመራመድም ቀላል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “በትክክለኛ መንገድ መኖርን አሳየኝ” ወይም “ትክክለ የሆነውን ማድረግ ቀላል አድርግልኝ” (ምሳሌያዊ አባባልን ይመልከቱ)

Psalms 5:9

አጠቃላይ ሃሳብ፡

ዳዊት ስለ ጣቶቹ ይናገራል፡፡

በአንደበታቸው ምንም እውነት ስለሌለ

እውነት በአንደበት መኖር እውነትን መናገር ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “እውነት የሆነውን መቼም ስለማይናገሩ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

Psalms 5:11

አንተን መጠግያ ያደረጉ ሁሉ ደስ ይበላቸው

እግዚአብሔር እንደ መጠግያ ተገልጸዋል፣ ሰዎች ከጥፋት ሊጠበቁበት የሚችሉበት ቦታ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “ከክፋት ለመጠለል ወደ አንተ የሚመጡ ሁሉ ደስ ይበላቸው” (ምሳሌያዊ አባባልን የመልከቱ)

... ደስ ይበላቸው፤ ዘላለም በደስታ ይዘምሩ፤

እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ሃሳብ አላቸው. (ትይዩነትን ይመልከቱ)

አንተን መጠግያ ያደረጉ

ለመጠለያነት ወደ ያህዌ መሄድ እርሱን መጠግያ እንደማድረግ ይገለፃል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “ወደ አንተ መለጠለያነት የሚሄዱ” (ምሳሌያዊ አባባልን የመልከቱ)

ስምህን የሚወዱ

የእግዚአብሔር ስም እራሱን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም “አንተን የሚወዱ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

እንደ ጋሻ በጸጋህ ትከልላቸዋለህ

የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ጋሻ ተመስሏል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “ወታደር አራሱን እንደሚጠብቀው በ ጸጋህ ትጠብቃቸዋለህ፣ ትከልላቸዋለህ” ወይም “አንተ ለእነርሱ መልካም ስለሆንህ ትጠብቃቸዋለህ” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)

---

Chapter 6

Psalms 6:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡

በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው፡፡ (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ

“ይህ ለመዘምራን አለቃ ለአምልኮ እንዲጠቀምበት ነው”

በዋሽንት

“ይህ መዝሙር በዋሽንት በሚጠቀሙ መታጀብ አለበት”

በሺሚኒት

ይህ የሙዚቃውን ስልት ሊያመለክት ይችላል

የዳዊት መዝሙር

አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው፡፡

አጥንቶቼ ታውከዋል/ይንቀጠቀጣሉ

x

Psalms 6:3

እጅግ ታወከች

“ፍራች” ወይም “ተጨነቀች”

እስከ መቼ ይቀጥላሉ?

ዳዊት ይህን ጥያቄ መበጠቀም እየፈራ እና እየተጨነቀ መቀጠል እንደማይፈልግ ይገልፃል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “እባክህ እንዲቀጥሉ አትፍቀድ!” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

ተመለስ ያህዌ

እግዚአብሔር ወደ እርሱ ሲመለስ ለእርሱ መልካም እንደሆነ ይገልፃል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “ያህዌ ወደኔ ተመለስ” ወይም “ያህዌ፥ምሕረት አድርግልኝ” (ምሳሌያዊ አባባልን የመልከቱ)

ስለኪዳን ታማኝነትህ ስትል አድነኝ

“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ገላጭ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “ለኪዳንህ ታማኝ ስለሆንህ አድነኝ” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

በሞት መታሰብያ የለህምና፥ በሲዖልም የሚያመሰግን ማን ነው?

እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ሃሳብ አላቸው፡፡ (ትይዩነትን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በሞት መታሰብያ የለህምና
“መታሰብያ” የሚለው ረቂቅ ስም ምስጋናን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም “ምክንያቱም ሰዎች በሚሞቱበት ጊዜ፥ ሊያመሰግኑህ አይችሉም።” (ድጋሚ መሰየም እና ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)
በሲዖል ማን ያመሰግንሃል?
ዳዊት ይህን ጥያቄ በመጠየቅ ትኩረት እየሰጠ ያለው በሲዖል እግዚአብሔርን የሚያመሰግን እንደሌለ ነው። አማራጭ ትርጉም: “በሲዖል ማንም አያመሰግንህም” ወይም “ሙታን ሊያመሰግኑህ ይችሉም” (መልስ አዝል ጥያቄን ይመልከቱ)
Psalms 6:6
በሰቆቃዬ ደክሚያለሁ
ይህ ሰቆቃ የሚያመለክተው የሚሰማውን ህመምን እና ጭንቀት ነው። አማራጭ ትርጉም: “ከህመም የተነሣ ደክምያለሁ” (ድጋሚ መሰየም ይመልከቱ)
አልጋዬን በእንባ አረጠብኩ፥ ትራሴን በእንባ አጠብኩ
እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያስተላልፋሉ(ትይዩነትን ይመልከቱ)
አልጋዬን በእንባ አረጠብኩ፥
“አልጋዬን በእንባዬ አረጠብኩት” ወይም “አልጋዬ ከእንባዬ የተነሣ ረጠበ”
ትራሴን በእንባ አጠብኩ
“ትራሴን ከእንባዬ የተነሣ አረጠብኩት”
ዓይኖቼ ፈዘዙ
የማየት አቅም በዓይኖች ይወሰላል። አማራጭ ትርጉም “እይታዬ ፈዘዘ” ወይም “በግልጥ ማየት አልቻልኩም” (ድጋሚ መሰየም ይመልከቱ)
ከሃዘን
እዚህ ጋር ሃዘን ለቅሶን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “ከለቅሶ” ወይም “ከለቅሶ ብዛት” (ድጋሚ መሰየም ይመልከቱ)
Psalms 6:8
ያህዌ የምሕረት ልመናዬን ሰምቷል.... ያህዌ ፀሎቴን ተቀብሏል
እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያስተላልፋሉ(ትይዩነትን ይመልከቱ)
ያህዌ ፀሎቴን ተቀብሏል
ዳዊት የፀለየውን ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን ፀሎትን እንደ መቀበል ተለግጧል። አማራጭ ትርጉም: “ያህዌ ፀሎቴን ይመልሳል” (ድጋሚ መሰየም ይመልከቱ)

---

Chapter 7

Psalms 7:1
አጠቃላይ መረጃ
ትይዩነት በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)
ዳዊት የዘመረው መዝሙር
“ይህ ዳዊት የጻፈው መዝሙር ነው”
ስለ ብንያማዊ ሰው ስለ ኩሽ ቃል
“ብንያማዊው ኩሽ ስለተናገረው” ወይም “ኩስ፤ የቢንያም ሰው ስለተናገረው”
በአንተ እታመናለሁ
ለጥበቃ ወደ ያህዌ መሄድ በእርሱ እንደመታመን ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ለጥበቃ ወደአንተ እመጣለሁ” (ቅኔን ይመልከቱ)
ነፍሴን እንደ አንበሳ ነጥቀው እነዳይሰብሩዋት
ዳዊት ስለ ጠላቶቹ ሲናገር ሰውነቱን እንደሚገለጣጥሉ እናብስት ይገልፃቸዋል። አማራጭ ትርጉም “አንበሳ የሚያጠቃውን እንስሳ እንደሚነጣጥል በጭካኔ ይገድሉኛል” ወይም “በጭካኔ ይገድሉኛል” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)
ማንም የሚያድነኝ በሌለበት
“ማንም ሊያድነኝ አይችልም”
Psalms 7:3
አመፃ በእጁ ቢኖር
እጅ ሰው የሚያደርገውን ይወክላሉ። አመፃ በእጅ መኖር የተሳሳተ ነገርን ማድረግ ይወክላል. አማራጭ ትርጉም “የተሳሳተ ነገር በማድረግ አጥፍቻለሁ” ወይም “ኃጢአትን ሰርቻለሁ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
Psalms 7:5
ሕይወቴ
ሕይወት ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም “እራሴ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ይይዙኛል
መማረክን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “ይማርኩኛል” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ሕይወቴን ከምድር ይቀላቅላል
እዚህ ጋ ‘ሕይወቴ’ የሚወክለው ጸሐፊውን ነው። አማራጭ ትርጉም: “ሊያጠፋኝ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ክብሬን ከዐፈር ይደባልቃል
ይህ የሚያለክተው መሞትን እኛ በክብር አለመቀበርን ነው።
Psalms 7:6
እግዚአብሔር ሆይ በቁጣህ ተነስ
መነሳት እንድን ነገር ማድረግ ወይም እርምጃ መውሰድን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “በቁጣህ አንድ ነገር አድርግ” ወይም “በጠላቶቼ ላይ ተቆጣ እና እርምጃ ውሰድ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
በቁጣ በተነሱብኝ ላይ ተነስ
ከሰዎች ጋር መጣላት ወይም መዋጋት በእነርሱ ላይ እንደ መነሳት ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “በቁጣ የሚዋጉኝን ተዋጋቸው” ወይም “የተቆጡኝ ጠላቶች አጥቃቸው” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
የጠላቶቼ ቁጣ
የጠላቶች ቁጣ ማጥቃታቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “የጠላቶቼ ጥቃት” ወይም “የሚያጠቁኝ ጠላቶቼ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ተነስ
መነሳት አንድ ነገር ማድረግ መጀመር ወይም እርምጃ መውሰድ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “እርምጃ ውሰድ ” ወይም “አንድ ነገር አድርግ” (ቅኔን ይመልከቱ)
ስለ እኔ ስትል
“ለእኔ” ወይም “እኔን ለመርዳት”
አገሮች ተሰባሰቡ
አገር የሚለው ቃል የሚወክለው ለማጥቃት የተሰባሰቡትን ጦሮችን ነው
በእነርሱ ላይ ለአንድ ጊዜ የሚገባህን ስፍራ ውሰድ
ሰዎችን መግዛት በእነርሱ ላይ እንደመሆን ይገለጻል። የያህዌ የሚገባ ስፍራ ሰማያትን ወይም በአጠቃላይ መግዛትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “ከሰማይ በእነርሱ ላይ ግዛ” ወይም “በእነርሱ ላይ ግዛ” (ቅኔን ይመልከቱ)
Psalms 7:8
አክብረኝ
“ጥፋተኛ እንዳልሆንኩ አሳያቸው”
ጻድቃንን አጽና
“ጻድቅ የሆኑ ሰዎችን አጠንክር” ወይም “ጻድቅ የሆኑ ሰዎችን እንዲበለጽጉ አድርግ”
አንተ ልብን እና አእምሮን የምትመረምር
ልብ እና እእምሮ የሰውን ፍላጎት እና ሃሳብን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም: “አንተ የውስጥ ሃሳባችንን የምታውቅ” (ቅኔን ይመልከቱ)
Psalms 7:10
ጋሻዬ ከእግዚአብሔር ይመጣል
‘ጋሻ’ የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ጥበቃ ያመለክታል። (ቅኔን ይመልከቱ)
በየቀኑ ንዴቱ ይነዳል
ይህን ሃሳብ በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም: “ኃጢአተኛውን በየቀኑ የሚቆጣ” (ድብቅ ሃሳብ ወይም ግምታዊ እውቀትን ይመልከቱ)
Psalms 7:12
እግዚአብሔር ሰይፉን ይስላል ቀስቱንም ይገትራል
በቁጥ 12 እና 13፣ ዳዊት እግዚአብሔር ክፉዎችን እንደ ተዋጊ በጦር መሳርያ ሊቀጣ እንደ ተዘጋጀ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም: “እግዚአብሔር ሰይፉን እንደ ሳለ ቀስቱንም እንደ ገተረ ጦረኛ እርምጃ ይወስዳል።” (ቅኔን ይመልከቱ)
Psalms 7:14
ክፋትን ጸንሷል ቅጥፈትን አርግዟል ሐሰትን ይወልዳል
x

---

Chapter 8


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Psalms 8:1
አጠቃላይ ሃሳብ
ትይዩነት በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)
ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራን አለቃ ለአምልኮ እንዲጠቀምበት ነው”
በዋሽንት
“ይህ መዝሙር በዋሽንት በሚጠቀሙ መታጀብ አለበት”
የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፏታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።
ስምህ በምድር ላይ እንዴት ታላቅ ነው
የእግዚአብሔር ስም ማንነቱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡ “በምድር ያሉ ሰዎች ሁሉ ታላቅነትህን ያውቃሉ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ከሕጻናት እና ከሚጠቡ አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ
አማራጭ ፍችዎች 1) ምስጋና እንደ ቁስ አካል ተገልጧል። እግዚአብሔር ከህጻናት እና ከሚጠቡ አፍ ያወጣው እና እንደ መከላከያ ግንብ ያኖረዋል ወይም 2) እግዚአብሔር አለምን የፈጠረው ምስጋና ህጻናት አንደበት እንዲወጣ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ለህጻናት እና ለሚጠቡ አንተን የማመስገን ብቃት ሰጥተሃቸዋል” ወይም “በእውነት የሚያመሰግኑህ ህጻናት እና የሚጠቡት ናቸው” (ቅኔን ይመልከቱ)
Psalms 8:3
ጣቶችህ ያመጁት ሰማያትህ
የእግዚአብሔር ጣቶች እርሱን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፡ “አንተ የሰራሃቸው ሰማያት”
በሐሳብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ትጠነቀቅለትም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው?
እነዚህ ሃሳቦች ትኩረትን ለመስጠት በጥያቄ መልክ ተቀምጠዋል። አማራጭ ትርጉም፡ “ሰለሰዎች ማሰብህ እና መጠንቀቅህ አስገራሚ ነው!” (መልስ አዝል ጥያቄን ይመልከቱ)
የሰው ዘር…. የሰው ልጅ
ሁለቱም ሃረጎች በአጠቃላይ ሰዎችን ይወክላሉ።
የክብር እና የሞገስ ዘውድ ደፋህላቸው
ክብር እና ሞገስ እንደ ዘውድ ተገልጾዋል። ‘ክብር’ እና ‘ሞገስ’ የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ አላቸው። አማራጭ ትርጉም፡ “ክብር እና ሞገስ ሰጥተሃቸዋል” ወይም “እንደ ንጉሥ እንዲሆኑ አድርገሃቸዋል” (ቅኔ እና መድገምን ይመልከቱ)
Psalms 8:6
ሾምህው… ሁሉንም ከእግሩ በታች አደረግህ
ሁለቱ ሃረጎች ተመሳሳይ ፍቺ አላቸው። (ትይዩነትን ይመልከቱ)
የእጆችህን ስራ
እጆች እግዚአብሔርን የሰራውን ይወክላሉ። አማራጭ ጥርጉም፡ “አንተ የሰራሃቸው ነገሮች” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛህለት
ነገሮች መግዛት እና መቆጣጠር ከእግር በታች እንደማድረግ ይገለጣል። ይህም ማለት እግዚአብሔር ለሰዎች በፍጥረት ሁሉ ላይ እንዲገዙ ስልጣን ሰጣቸው። አማራጭ ትርጉም “በሁሉ ነገሮች ላይ ስልጣንን ሰተሀዋል” (ቅኔን ይመልከቱ)
Psalms 8:9
ስምህ በምድር ሁሉ ምንኛ ግርማዊ ነው
በነዚህ የአጋኖ ቃላት፣ ዳዊት በእግዚአብሔር ታላቅነት መደሰቱን እና መደነቁን ይገልጣል። አማራጭ ትርጉም፡ “ስምህ በሚያስደንቅ መልኩ በአለም ሁሉ ታላቅ ነው” ወይም “በምድር ያሉ ሰዎች ሁሉ ምንያህል ታላቅ እንደሆንህ ያውቃሉ” (አጋንኖን ይመልከቱ)
ስምህ
የእግዚአብሔር ስም አራሱን ወይም ስለሱ የሚባለውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ስለአንተ የሚባለው” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ግርማዊ
ታላቅ፣ ፍጹም

---

# Chapter 9

Psalms 9:1
አጠቃላይ መረጃ፡
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ዘይቤ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)
ለመዘምራን አለቃ
“የመዘምራን አለቃ በጋራ አምልኮ ጊዜ የሚጠቀምበት”
በሙትላቤን ቅኝት
ይህ ምንአልባት የቅኝትን አይነት ያመለክታል
የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፏታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።
በሙሉ ልቤ ያህዌን አመሰግናለሁ
ይህ መዝሙር ለያህዌ የተደረሰ ስለሆነ፣ ያህዌ ‘አንተ’ ሊባል ይችላል። አማራጭ ትርጉም “ያህዌ፥ በሙሉ ልቤ አንተን አመሰግንሃለሁ” (አንደኛ ሁለተኛ እና ሦስተኛ መደብን ይመልከቱ)
ድንቅ ስራዎችህ
ስራ የሚለው ስም በግስ መልክ ሊተካ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ያደረካቸው አስደናቂ ነገሮች ሁሉ” ወይም “የሰራሃቸው አስደናቂ ነገሮች ሁሉ” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)
ለስምህ ምስጋናን እዘምራለሁ
የእግዚአብሔር ስም እራሱን እግዚአብሔርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡ “ለአንተ ምስጋናን አዘምራለሁ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
Psalms 9:3
ወደ ኋላ መመለስ
“ማፈግፈግ” ወይም “በፍርሃት መመለስ”
አንተ ጻድቅ ፈራጅ በዙፋንህ ተቀምጠሃል
ንጉሦች በሰዎች ላይ የመፍረድ ሥልጣን ነበራቸው፣ ሲፈርዱም በዙፋናቸው ይቀመጣሉ። ዳዊት ስለ እግዚአብሔር በምድር እንዳለ ንጉሥ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡ “በዙፋኑ እንደቀመጠ ንጉሥ ትፈርዳለህ፥ ጻድቅም ነህ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
Psalms 9:5
ስማቸውን እስከ ወዲያኛው ደመሰስህ
ሰዎች እንዲረሱ ማድረግ ስማቸውን እንደ መደምሰስ ይገለጣል። አማራጭ ትርጉም፡ “ስማቸው እንደተደመሰሰ እንዲረሱ አደረግህ” ወይም “ማንም መቼም አያስታውሳቸውም” (ቅኔን ይመልከቱ)
ደመሰስህ
“ሰረዝህ”
ጠላቶች እንደ ፍርስራሽ ወደቁ
ጠላት ልክ እንደ ፈራረሰ ህንጻ እንዳለው ከተማ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡ “ጠላቶቻችን ተደምስሰዋል” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)
ከተማዎቻቸውን ገለበጥሃቸው
“ከተማዎቻቸውን ደመሰስህ”
ዝክራቸውም በአንድነት ጠፋ
“ዝክር” በህይወት እንዳለ ነገር እና ሊሞት እንደሚችል ነገር ነው የተገለጸው። አማራጭ ትርጉም፡ “እነርሱም የሚያስታስ ነገር ሁሉ ቆሟል” ወይም “ምንም እነርሱን ማስታወስ የለም” (ምሳሌያዊ አነጋገርን ይመለክቱ)
መታሰቢያዎቻቸውም ተደምስሰዋል
“መታሰቢያዎቻቸው” የሚለው ቃል በሕይወት እንደለ ነገር ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡ “እነርሱን ማስታወስ ቆምዋል” ወይም “እነርሱን የሚያስታውስ ምንም ነገር የመልም” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)
Psalms 9:7
ያህዌ ለዘላለም ይኖራል
“ይኖራል” የሚለው ቃል የሚወክለው በዙፋኑ እንደ ንጉሥ መኖርን ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “ያህዌ ለዘላለም በዙፋኑ ይቀመጣል” ወይም “ያህዌ ለዘላለም ይገዛል” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
መንበሩንም ለፍርድ አፍንቶአል
“መንበሩ” የሚለው ቃል ዙፋኑን ወይም አገዛዙን ይወክላል። አማራጭ ፍቺ 1) “በሰዎች ለመፍረድ ይገዛል” ወይም “በጽድቅ በሰዎች ላይ ይገዛል” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

በዓለም በጽድቅ ይፈርዳል … በፍትህ በሕዝቦች ላይ ይፈርዳል
እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ሃሳብ አላቸው (ትይዩነትን ይመልከቱ)
በጽድቅ በዓለም ላይ ይፈርዳል
“ዓለም” የሚለው ቃል እዚህ ጋር የሚወክለው በዓለም ያሉትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም: “በጽድቅ በዓለም ያሉትን ሰዎች ሁሉ ላይ ይፈርዳል” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
Psalms 9:9
ያህዌ ለተጨነቁ ዐምባ ነው
እግዚአብሔር ሰዎች ለማለጥ የሚሸሸጉበት አንድ ስፍራ እንደሆነ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም: “ያህዌ የተጨነቁትን የጠብቃል” ወይም “ያህዌ ለተጨነቁ መሸሸግያ ይሆናል” (ቅኔን ይመልከቱ)
ስምህን የሚያውቁ
ስምህ የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “አንተን የሚያውቁ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
አትተዋቸውም
“ብቻቸውን አትተዋቸውም” ወይም “ያለ ረዳት አትተዋቸውም”
Psalms 9:11
በጽዮን የሚገዛ
“በኢየሩሳሌም የሚኖር”
ለሕዝቦች አውሩ
“ሕዝቦች” የሚለው ቃል ከተለያዩ ቦታ የሆኑ ሰዎችን ያመለክታል። (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ደም ተበቃዮ አስታውሶዋቸዋል እና
አስታውሷል የሚለው ቃል በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: ”የተገደሉትን ደም የሚበቀለው እግዚአብሔር አስታውሷቸዋል” ወይም “የተገደሉትን እግዚአብሔር አስታውሷቸዋል ገዳዮችንም ይቀጣል” (ግምታዊ እውቀትን እና ድብቅ ሃሳብ ይመልከቱ)
ለቅሶዋቸውን አይረሳም
“ለቅሶዋቸውን አይዘነጋም”
Psalms 9:13
በሚጠሉኝ እንዴት እንደተጨቆንኩ ተመልከት
በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “የሚጠሉኝ እንዴት እንደጨቆኑኝ ተመልከት” ወይም “የሚጠሉኝ እንዴት በመጥፎ ሁኔታ እንደሚያንገላቱኝ ተመልከት” (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)
አንተ ከሞት ደጃፍ ልትነጥቀኝ የምትችል
ሞት ሰዎች ለሊገቡበት እንደሚችሉ ደጃፍ እንዳለው ከተማ ተገልጧል። አንድ ሰው ከደጃፉ ቅርብ ከሆነ ለሞት ቀርቧል ማለት ነው። ሰውን ከሞት መጠበቅ ከሞት ደጆች እንደ መመለስ ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ከሞት ልትታደገኝ የምትችል አንተ” ወይም “ከመሞት የምትጠብቀኝ አንተ” (ቅኔን ይመልከቱ)
Psalms 9:15
አሕዛብ በቆፈሩት ጉድጓድ ገቡ
ሰዎች እንስሳትን ለማጥመድ ጉድጓድ ይቆፍራሉ። እዚህ ጋር ጉድጓድ መቆፈር ሰዎችን ለማጥፋት ማቀድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “አሕዛብ ለሌሎች ጉድጓድን ይቆፍራሉ እራሳችው ይገቡበታል” (ቅኔን ይመልከቱ)
እግቸውም እራሳቸው በስውር ባስቀመጡት ወጥመድ ተያዘ
ሰዎች እንስሳትን ለማጥመድ ወጥመድ ይዘረጋሉ። እዚህ ጋር ወጥመድ በስውር ባስቀመጥ ሰዎችን ለማጥፋት ማቀድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “በደበቁት ወጥመድ እንደሚያዙ ሰዎች ናቸው” (ቅኔን ይመልከቱ)
ክፉዎች በእራሳቸው ስራ ተጠመዱ
እዚህ ጋ ክፉዎች የሚለው ቃል ማንኛውም ኃጢአተኛ ሰውን ይወክላል። አንድ ክፉ ሰው ሌላ ሰውን ለመጉዳት የሚሰራ ስራ ሌሎች እንዲያዙበት ወጥመድ እንደማዘጋጀት ተገልጧል። ይህ በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “አንድ ክፉ ሰው ሌሎች ሰዎችን ለመጉዳት ሲሞክር፥ የእራሱ ስራ መልሶ ይጎዳዋል”
ተጠመዱ
“ወጥመድ ውስጥ ገቡ”
Psalms 9:19
ተነሣ
መነሣት የሚያመለክተው አንድ ነገር ለማድረግ መጀመርን ነው። አማራጭ ትርጉም: “አንድ ነገር አድርግ” ወይም “እርምጃ ውሰድ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ሰው
ሰዎች
ይፍረድ
መፍረድ መቅጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “ይቅጣ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
በፊትህ
መገኘትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “በመገኘትህ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
አሕዛብ በፊትህ ይፈረድባቸው
በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “በፊትህ አሕዛብ ፍረድባቸው” ወይም “አህዝብን ወደ ፊትህ አምጣቸው እና ፍረድባቸው” (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)

---

Chapter 10
Psalms 10:4
ክፉው ሰው
ይህ ሁሉንም ክፉ ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “ክፉ ሰዎች” (አጠቃላይ ስያሜን ይመልከቱ)
የተነሣ ፊት
የተነሣ ፊት ትዕቢትን ይወክላል። አማራጭ እርጉም: “የንቀት ሃሳብ አለው” ወይም “ጉረኛ ነው” (ቅኔን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን አይፈልግም
እግዚአብሔርን መፈለግ 1) እግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅ ወይም 2) እግዚአብሔርን ማሰብ እና መታዘዝ። አማራጭ ትርጉም: “እግዚአብሔርን ዕርዳታ አይጠይቅም” ወይም “ስለ እግዚአብሔር አያስብም” (ቅኔን ይመልከቱ)
መንገዱ የተሳካ ነው
“ሁልጊዜ የተጠበቀ ነው”። በእውነትም የተጠበቀ አይደለም ነገር ግን የተጠበቀ እንደሆነ ይመስለዋል።
ከጻድቅ ሕግህ የራቀ ነው
ለመረዳት የሚከብድ ነገር ለመድረስ የራቀ እንደሆነ ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ጻድቅ ሕግህን ለመረዳት አይችልም።” (ቅኔን ይመልከቱ)
በጠላቶቹ ላይ ያፊዛል
ይህን የሚያደርገው ጠላቶቹ ደካማ እና አላስፈላጊ እንደሆኑ ስለሚያስብ ነው። አማራጭ ትርጉም: “ጠላቶቹ ሁሉ ደካማ እና ጥቅም የለሽ እንደሆኑ ያስባል” ወይም “በጠላቶቹ ሁሉ ላይ ያሾፋል” (አመልካች ድርጊትን ይመልከቱ)
ያፊዛል
x
Psalms 10:6
ይላል
“ክፉው ሰው እንዲህ ይላል”
ከትውልድ እስከ ትውልድ
ምናልባትም ለዘላለም ማለት ሊሆን ይችላል።
መከራ አያገኘኝም
መከራ በሕይወት መለማመድ እንደ መገናኘት ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ምንም አይነት ችግር አይኖርብኝም” (ቅኔን ይመልከቱ)
አፉ መርገምን፣ ቅጥፍትንእ ግፉን የተሞላ ነው
ሰዎች የሚናገሩት ነገር በአፋቸው እንዳለ ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ሁልጊዜ ሰዎችን ይረግማል እና የሚጎዳ ውሸት ይናገራል” ወይም “ሰዎችን ሁልጊዜ ይረግማል፣ ይዋሻል እና እንደሚጎዳቸው በማስፈራራት ይናገራል” (ቅኔን ይመልከቱ)
ሸንገላ እና ክፋት ከምላሱ ስር ይገኛሉ
ምላስ መናገርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “የሚናገረው ሰዎችን የሚያጠፋ እና የሚጎዳ ነው” ወይም “ሰዎችን የሚያስፈራራ እና የሚጎዳ ነገር ይናገራል” (ቅኔን ይመልከቱ)
Psalms 10:8
ያደፍጣል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ድርጊት በክፉው ሰው ይደረጋል።
ዐይኖቹ በምስኪኖች ላይ ያነጣጥራል
ዐይኖቹ እርሱን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም: “ረዳት የሌላቸው ምስኪኖችን ይመለከታል” (በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)
በደኑ ውስጥ እንዳለ አንበሳ በስውር ያደባል
ይህ ሃሳብ ክፉው ሰው ልክ እንደ አንበሳ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም: “ደካሞች እስኪቀርቡት ድረስ አንበሳ እንስሳን ለማጥቃት በዝምታ እንደሚያደባ ይደበቃል” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)
ያደባል
ለመጉዳት ወይም ለመግደል ተደብቆ መቆየት ማለት ነው።
Psalms 10:11
ይላል
የሚናገር ክፉው ሰው ነው። ክፉው ክፉ ሰዎችን የሚወክል ስም ነው። (አጠቃላይ ስያሜን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ረስቷል
ለማሰብ አለመፍቀድ እንደመርሳት ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም: “እግዚአብሔር ሰዎችን አያስብም” ወይም “እግዚአበሔር ስለ እኔ ግድ አይለውም” (ቅኔን ይመልከቱ)
ፊቱን ይሸፍናል
አንድ ሰው ምን እያደረገ እንዳለ ለመመልከት አለመፍቀድ ፊትን እንደመሸፈን ይገለጻል። አማራጭ ትርጉምን “እየሆነ ያለውን ለመመልከት እግዚአብሔር አይፈልግም” (ቅኔን ይመልከቱ)
ፈጽሞም አያይም
አንድን ነገር ማሰብ እንደ ማየት ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “እግዚአብሔር እየሆነ ያለውን ለማየት ፈቃደኛ አይደለም።” (ቅኔን ይመልከቱ)
ተነሣ
መነሣት የሚያመለክተው አንድ ነገር ለማድረግ መጀመርን ነው። አማራጭ ትርጉም: “አንድ ነገር አድርግ” ወይም “እርምጃ ውሰድ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
እጅህን አንሣ
አንድን ሰው ለመምታት እጅን ማንሣት መቅጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “በሃይል መምታት” ወይም “ክፉውን ሰው መቅጣት” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
Psalms 10:13
ክፉ ሰው በእግዚአብሔር ላይ ለምን ክፉ ይናገራል? “ስለ ስራዬ አይጠይቀኝም” ለምን ይላል?
ተናጋሪው እነዚህ ጥያቄዎች በመጠየቅ ክፉ ሰዎች በሚያደርጉት ነገር ማዘኑን ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም: “ክፉ ሰዎች ሁልጊዜ ‘በስራቻን ተጠያቂ አይደለንም’ በማለት እግዚአብሔርን እየተቃወሙ ነው” (መልስ አዘል ጥያቄዎችን ይመልከቱ)
ስለ ስራዬ ተጠያቂ አይደለሁም
“የማደርገውን ለምን እንደማደርግ አትጠይቀኝም” አንድ ሰው ተጠያቂ ማድረግ መቅጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “አትቀጣኝም” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
Psalms 10:17
የተጨቆኑትን ፍላጎት ሰምተሃል
የተጨቆኑ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መጮሃቸው የልተገለጸ ሃሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም: “የተጨቆኑ ሰዎች ወደ አንተ ሲጮሁ እና ፍላጎታቸውን ሲነግሩህ ሰምተሃቸዋል” (ግምታዊ እውቀትን እና ድብቅ ሃሳብ ይመልከቱ)
ልባቸውን ታጠነክራለህ
ጠንካራ ልብ ድፍረትን ያመለክታለ የሰዎችን ልብ ማጠንከር ደግሞ ሰዎችን ማበረታታት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “ታበረታታቸዋለህ” ወይም “ደፋር ታረጋቸዋለህ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ማንም ሰው ከእንግዲህ አያስጨንቃቸውም
“ማንም ሰው ከእንግዲህ እንዲፈሩ አያደርጋቸውም”

Chapter 11

Psalms 11:1
አጠቃላይ ሃሳብ:
ትይዩነት በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ )
ለመዘምራን አለቃ
“የመዘምራን አለቃ በጋራ አምልኮ ጊዜ የሚጠቀምበት”
የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች: 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።
በያህዌ ታምኛለሁ
ለእርዳታ ወደ ያህዌ መሄድ በእርሱ እንደ መታመን ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ለጥበቃ ወደ ያህዌ ሄጃለሁ” (ቀኔን ይመለክቱ)
“እንደ ወፍ ወደ ተራራ ብረሪ” ለምን ትላላችሁ?
ይህ ጥያቄ የተጠቀው ትኩረትን ለመሳብ ነው። እንደ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ተርጉም: “እንዳመልጥ ትጠይቁኛላችሁ!” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ )
እነሆ፣ ክፉዎች ቀስታቸውን ገትረዋል፣ የቅኑን ሰው ልብ በጨለማ ለመንደፍ ፍላጻቸውን በአውታሩ ላይ ደግነዋል
“ተመልከት! ክፉዎች ቅኖችን ለማጥቃት ተዘጋጅተዋል”
ቅን ልብ
ቅን ልብ የሚወክለው ጻድቅ ወይም እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎችን ነው።
Psalms 11:3
መሰረቱ ከተናደ ጻድቅ ምን ማድረግ ይችላል?
“መሰረት” የሚወክለው ሕግ እና ስርዓትን ነው። መልስ አዘል ጥያቄው የተጠየቀው ትኩረት ለመጨመር ነው። ዓረፍተ ነገር ማናድረግ መተርጎም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም: “ክፉ ሰዎች ሕጉን ባለመታዘዛቸው ምክንያት ሳይቀጡ ሲቀሩ ጻድቃን ምንም ማድረግ አይችሉም።” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ )
Psalms 11:5
ያህዌ ይፈትናል
“ያህዌ በጥንቃቄ ይመለከታል”
ዐመጻ የሚያደርጉ
“ሌሎችን የሚጎዱ”
እርሱ በክፉዎች ላይ የእሳት ፍምና ዲን ያዘንባል፥ የጽዋቸውም ዕጣ ፈንታ የሚለበልብ ዐውሎ ነፋስ ነው
የእግዚአብሔር ቅጣት እንደሚነድ ፍም እና እንደ እሳተ ጎመራ ዲን ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም: “ክፉውን ይቀጣል፥ ምንም እረፍት አይሆንላቸውም።” (ቅኔን ይመልከቱ)
ዲን
ሰልፈር
ፊቱን ያያሉ
“በመገኘቱ ይሆናሉ”

Chapter 12

Psalms 12:1
አጠቃላይ ሃሳብ:
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)
ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራን አለቃ ለአምልኮ እንዲጠቀምበት ነው”
በሺሚኒት
ይህ የሙዚቃውን ስልት ሊያመለክት ይችላል
የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች: 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።
ያህዌ ሆይ ድረስልኝ
“ያህዌ ለችግሬ ድረስልኝ”
ታማኝ ሰው የለም
“ታማኝ ሰዎች ሁሉ ጠፍተዋል”
Psalms 12:2
ያወራሉ ይነጋገራሉ
በተደጋጋሚ ይህ ሃሳብ መጠቀሱ ግነትን ያመለክታል፥ ለብዙ ሰዎችም እውነት መሆኑን ያሳያል። (አጠቃላይነትን እና ግነትን ይመልከቱ)

በሽንገላ ከንፈር እና በሁለት ልብ ይናገራሉ

‘ከንፈር’ ለሰዎች ንግግር ቅያሪ ስያሜ ነው። ‘ሁለት ልብ’ ለሃሰተኝነት ቅኔያዊ ገለጻ ነው። አማራጭ ትርጉም: “ሁሉም ሰው በሃሰት እና በአታለይ ከንፈር ይናገራል” ወይም “ሁሉም ሰው በውሸት ሰዎችን እያመሰገነ ይዋሻል።” (ድጋሚ መሰየም እና ቅኔን ይመልከቱ)

ሸንጋዩን ከንፈር እግዚአብሔር ቆርጣል

x

Psalms 12:5

ጩኸት

በህመም ጊዜ በታላቅ ስሜት ሰዎች የሚያሰሙትን ስቃ ያመለክታል።

ያህዌ “እነሳለሁ” ይላል

ያህዌ ሰዎቹን ለመርዳት አንድ ነገር ያደርጋል ማለት ነው።

Psalms 12:6

በምድር ላይ እነደ ተፈተነ ሰባት ጊዜ እነደ ተጣራ ብር

የያህዌ ቃላት ከተጣራ ብር ጋር ተወዳድሯል። አማራጭ ትርጉም: “ያለምንም እንከን ናቸው” (አነጻጻሪ ዘይቤን ይመልከቱ)

አንተ ትጠብቃቸዋለህ

“ጻድቃንን ትጠብቃቸዋለህ”

በየአቅጣጫው ይሄዳሉ

“ይዞራሉ”

ዐመጻ በሰዎች ዘንድ ከፍ ከፍ ባለ ጊዜ

በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ሰዎች ሀሉም ቦታ ዐመጻን ከፍ ከፍ ባደረጉ ጊዜ” (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)

የሰው ልጆች

“ሰዎች”

Chapter 13

Psalms 13:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡

በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ

“ይህ ለመዘምራን አለቃ ለአምልኮ እንዲጠቀምበት ነው”

የዳዊት መዝሙር

አማራጭ ፍችዎች: 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።

እስከ መቼ፣ ያህዌ ትረሳኛለህ?

ይህ ጥያቄ የተጠየቀው የአንባብያንን ትኩረት ለመሳብ እና ለመጨመር ነው። እንደ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ያህዌ፣ ስለ እኔ የረሳህ ይመስላል!” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

ፊትህንም ከእኔ የምትመልሰው እስከ መቼ ድረስ ነው?

“ፊትህ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ሁለመና ያመለክታል። መልስ አዝል ጥያቄ የተጠየቀው ትቁረት ለመስጠት ነው። እንደ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ከእኔ እየተደበክ ይመስላል” (በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን እና መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

ጠላቴስ በእኔ ላይ የሚያይለው እስከ መቼ ድረስ ነው?

መልስ አዝል ጥያቄ የተጠየቀው ትቁረት ለመስጠት ነው። እንደ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “በእርግጥ ጠላቶቼ ሁልጊዜ አያሸንፉኝም” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

Psalms 13:3

ተመልከተኝ ስማኝም

“ትኩረትህን ስጠኝ እና ስማኝ”

ዐይኖቼን አብራ

ይህ ኃይልን የመጠየቅያ መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም: “በድጋሚ ኃይለኛ አድርገኝ” (ፈሊጥን ይመለከቱ)

የሞት እንቅልፍ እንዳልተኛ

“የሞት እንቅልፍ” ማለት መሞት ማለት ነው።

ጠላቶቼ እንዳይሉ … ጠላቶቼ እንዳይሉ

“ጠላቶቼ ስለ እኔ እንዲህ እንዲሉ አትፍቀድላቸው … ጠላቶቼ በእኔ ላይ እንዳይሉ”

ወደ ታች በወረድሁ ጊዜ

“ስወድቅ” ወይም “ሲያሸንፉኝ”

Psalms 13:5

በቃል ኪዳን ታማኝነትህ እታመናለሁ

“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ገላጭ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ለቃል ኪዳንህ ታማኝ እንደሆንህ አምናለሁ” ወይም “ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ስለሆንህ በአንተ እታመናለሁ” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

በማዳንህ ልቤ ደስ ይለዋል

“ልቤ” የሚለው ቃል መላ ሰውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “ስላዳንከኝ ደስ ይለኛል” (በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

Chapter 14

Psalms 14:1

አጠቃላይ ሃሳብ፡

በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ

“ይህ ለመዘምራን አለቃ ለአምልኮ እንዲጠቀምበት ነው”

የዳዊት መዝሙር

አማራጭ ፍችዎች: 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።

ሞኝ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል

ይህ ፈሊጥ ለራስ መናገር ወይም ማሰብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “ሞኝ ሰው ለራሱ ይናገራል” (ፈሊጥን ይመለከቱ)

ብልሹዎች ናቸው

“ናቸው” የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔር የለም የሚሊትን ሞኝ ሰዎችን ነው።

Psalms 14:2

የሰው ልጆች

ይህ ሃረግ ሰዎችን ሁሉ ይወክላል

እርሱን የሚፈልግ

ይህ የሚገልጠው እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚፈልጉትን በመንገድ እንደሚከተሉት የሚፈልጉትን ነው። አማራጭ ትርጉም: “እርሱን ለማወቅ የሚፈልጉ” (ቅኔን ይመልከቱ)

ሁሉም ከመንገድ ወጥተዋል

እግዚአብሔርን የሚቃወሙ ሰዎችን በትክክለኛ መንገድ መሄድ አቁመው በተሳሳተ አቅጣጫ እንደሚሄዱ የሚገልጥ ነው። አማራጭ ትርጉም: “ሁሉም ከያህዌ ዞር ብለዋል” (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 14:4

የእግዚአብሔርን ስም የማይጠሩት ዕውቀት የላቸውምን?

መልስ አዝል ጥያቄ የተጠየቀው ትቁረት ለመስጠት ነው። እንደ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ያህዌን የማይጠሩ ምንም እንደማያውቁ ይሆናሉ። የሚያደርጉትን ግን ያውቃሉ” (መልስ አዘል ጥያቄን ይመልከቱ)

ክፉት አድራጊዎች

“ክፉት” የሚለው ረቂቅ ስም “ክፉ አድራጊዎች” በማለት ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ክፉ የሚያደርጉ” (ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)

ሕዝቤን እንደ እንጀራ የሚበሉ

የሚያመለክተው ክፉ አድራጊዎችን እና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ምግብ እንደሚበሉ የሚያጠፉትን ነው። (ቅኔን ይመልከቱ)

Psalms 14:5

ይደነግጣሉ

ክፉ የሚያደርጉትን ያመለክታል።

እግዚአብሔር በጻድቃን ጉባኤ ይገኛል

እግዚአብሔር ከጻድቃን ጋር ነው ማለት ይረዳቸዋል ማለት ነው። ይህ ሃሳብ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “በጽድቅ የሚኖሩትን እግዚአብሔር



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይረዳል” ወይም “ትክክለኛ ነገር የሚያደርጉትን እግዚአብሔር ይረዳል” (ግምታዊ እውቀትን እና ድብቅ ሃሳብ ይመልከቱ)
ትሻለህ
የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው።
ድሃውን ለማዋረድ
“ድሃ የሆነው ሰው ውርደት እንዲሰማው ለማድረግ”
ያህዌ መጠግያው ነው
ያህዌ የሚሰጠውን ጥበቃ ያመለክታል። እንደ ሰው ከማዕበል እንደሚጠለልበት መጠግያ። አማራጭ ትርጉም: “ያህዌ እንደሚጠብቀው ጋሻ ነው” (ቅኔን ይመልከቱ)
Psalms 14:7
ምን ነው እስራኤልን መዳን ከጺዮን በመጣ!
ይህ ማጋነን ነው። ጸሐፊው እግዚአብሔር እንዲያደርገው የሚፈልገውን አየገለጸ ነው። አማራጭ ተርጉም: “የእስራኤል መዳን ከጺዮን እንዲመጣ እመኛለሁ!” (አጋኖን ይመልከቱ)
ምን ነው እስራኤልን መዳን ከጺዮን በመጣ!
“እስራኤልን መዳን” የሚለው የያህዌ ሌላ ስም ነው። እስራኤልን የሚያድን እርሱ። አማራጭ ትርጉም: “ያህዌ ከጺዮን መጥቶ እስራኤልን ያድናል።” ወይም “ያህዌ ከጺዮን መጥቶ የእስራኤልን ህዝብ እንዲያድን እመኛለሁ።” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ያዕቆብም ደስ ይበለው፥ እስራኤልም ሐሴት ያድርግ
እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። “ያዕቆብም” “እስራኤልም” የሚወክሉት የእስራኤልን ሕዝብ ነው። በትርጉም ወቅት ሁለቱን ሃረጎች ማጣመር ይቻላል። አማራጭ ትርጉም: “ሁሉም የእስራኤል ሕዝቦች ሐሴት ያድርጉ” (ትይዩነትን እና በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

---

Chapter 15
Psalms 15:1
አጠቃላይ ሃሳብ፡
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)
የዳዊት መዝሙር
አማራጭ ፍችዎች፡ 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፎታል ወይም 2) ዝማሬው ስለዳዊት ነው ወይም 3) ዝማሬው የተዘመረው በዳዊት የአዘማመር ስልት ነው።
በተቀደሰው ተራራህ ማን መኖር ይችላል?
የእግዚአብሔር “ተራራ” የሚወክለው በጺዮን ተራራ የነበረውን የእግዚአብሄር መቅደስን ነው። አማራጭ ተርጉም: “በተቀደሰው ስፍራህ ማን ሊኖር ይችላል?” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ከልቡ እውነትን የሚናገር
“በታማኝነት የሚናገር”
Psalms 15:3
በምላሱ የማይሸነግል
“ምላስ” የሚወክለው ሰውን ነው። የማይሸነግለው ሰው “ጻድቁ ሰው” ነው (መዝሙር 15፡02)። አማራጭ ትርጉም: “በንግግሩ አይሸነግልም” ወይም “ስለ መልካም ሰዎች ክፉ አይናገርም” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ጉዳት
“መጉዳት”
Psalms 15:4
ነውረኛ በፊቱ የተናቀ፥ እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ግን የሚያከብር
“ጻድቅ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚቃወሙትን ይጠላሉ፥ ነገር ግን እግዚአብሔርን የሚያከብሩትን ያከብራሉ”
የተናቀ
“ክፉ ሰው” ወይም “ያህዌን የሚቃወም ሰው”
“ከቶ አይናወጥም”
“ከቶ አይናወጥም” የሚለው ሃረግ በሰላም ረዥም እድሜ መኖርን ያመለክታል። በሌላ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “በሰላይ ይኖራል” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)

---

Chapter 16
Psalms 16:1
አጠቃላይ ሃሳብ፡
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)
የዳዊት ቅኔ
ቅኔ በሚለው ፋንታ ያለው የዕብራይስጡ ቃል ትርጉም በእርግጠኝነት አይታወቅም። በምትኩ “መዝሙር” ወይም “ቅኔ” የሚለውን ቃል መጠቀም ይቻላል። እንዲህ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል: “ይህ መዝሙር ዳዊት የጻፈው ነው”
መጠጊያዬ ነህ
ለመሸሸግ ወደ ያህዌ መሄድ እርሱን መጠግያ እንደ ማድረግ ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ለመሸሸግ ወደ አንተ እመጣለሁ” (ቅኔን ይመልከቱ)
በምድር ያሉ ቅዱሳን ሁሉ
“ቅዱሳን” የሚወክለው በእርሱ የሚታመኑትን የእግዚአብሔር ሕዝብን ነው። አማራጭ ትርጉም: “በዚህ ምድር የሚኖሩ ሕዝብህ” (ግምታዊ እውቀትን እና ድብቅ ሃሳብ ይመልከቱ)
Psalms 16:4
ሌሎች አማልክት የሚከተሉ ሀዘናቸው ይበዛል
በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ሌሎች አማልክት የሚያመለኩ ሰዎች ሀዘን እበዛ ይሄዳል” (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)
ደም ለአማልክቶቻቸው ያፈሳሉ
“ደም እንደ ቁርባን ለአማልክቶቻቸው ያቀርባሉ”
ስማቸውን በአፌ አልጠራም
ስማቸውን መጥራት የሚያመለክተው እነርሱን ማወደስ ነው። “በአፊ” ሰው የሚናገርውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “በቃላቴ አላወድሳቸውም” ወይም “አማልክቶቻቸውን አላወድስም” (የተጋነነ ቅኔ እና ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
Psalms 16:5
የርስቴ ድርሻዬ
ዳዊት ስለ ያህዌ እንደ ተሰጠው የመሬት ድርሻ ይናገራል። (ቀኔን ይመልከቱ)
ጽዋዬ
ዳዊት ስለ ያህዌ ብዙ በረከትን እንደያዘ ጽዋ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም: “የሚባርከኝ” (ቀኔን ይመልከቱ)
ዕጣዬ በእጅህ ናት
“የወደፊቴን የምትወስን አንተ ነህ” ወይም “በእኔ የሚሆነውን ትቆጣተራለህ”
ገመድ ባማረ ስፍራ
ገመድ መጣል መሬትን ለመለካት እና ለሰው ለመስጠት ሌላ ስያሜ ነው። ዳዊት ከእግዚአብሔር በተለዩ ታላላቅ መንገዶች ስላገኘው በረከት ቅኔያዊ መግለጫ ነው። በቀጥታ ሊገለጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “በመልካም ስፍራ መሬት ወስነህልኛል” ወይም “በመልካም ስፍራ መሬት ሰተኸኛል” ወይም “በመልካም ስፍራ መሬት እንደሚሰጥ ባርከኸኛል” (ድጋሚ መሰየም፥ ቅኔ፥ ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)
ገመድ
ገመድ በዚያን ጊዜ መሬትን ለመለካት እና ድንበር ለመከለል ይጠቀሙበት ነበር።
በርግጥም የተዋበች ርስት አግኝቻለሁ
ዳዊት የያህዌን በረከት እንደተቀበለው ርስት አድርጎ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም: “በሰጠኝ ነገር ሁሉ ደስተኛ ነኝ” (ቀኔን ይመልከቱ)
Psalms 16:7
ያህዌ ሁልጊዜ በፊቴ ነው
“ያህዌ ከእኔ ጋር እንዳለ ሁል ጊዜ አስታውሳለሁ”
እርሱ በቀኜ ስላለ አልናወጥም
በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “ከአጠገቡ ምንም ሊወስደኝ የሚችል ነገር የለም” (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪን ይመልከቱ)
Psalms 16:9
አጠቃላይ ሃሳብ
ዳዊት ስለ እግዚአብሔር መናገር ይቀጥላል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ልቤ ሐሴት ያደርጋል
“ልብ” የሚወክለው የተናጋሪውን ሀሳብ እና ስሜትን ነው። አማራጭ ትርጉም: “ስለዚህ ደስተኛ ነኝ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ክብሬ ይደሰታል
አማራጭ ፍቺዎች 1) “ክብር” የሚለው ቃል የሚወክለው አንድ ሰው የሚሰማውን ክብር። አማራጭ ትርጉም: “በእግዚአብሔር በመደሰቱ ክብር ይሰማኛል” ወይም 2) “ከብር” ለሚለው ቃል የተጠቀመው የዕብራይስጥ ቃል “ጉበት” ማለት ነው፥ ይህም የሰውን ስሜት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “ደስተኛ ነኝ”

Psalms 16:11
የደስታ ሙላት
“ታላቅ ደስታ” ወይም “እጅግ ብዙ የሆነ ደስታ”
በአንተ ዘንደ ደስታ
ጸሐፊው “ደስታን” እንደ ግለሰብ ይገልጻታል። (ሰውኛ ዘይቤ ይመልከቱ)
በቀኝህ
“በቀኝህ” የሚለው ቃል የሚወክለው በእግዚአብሔር ዘንድ የተለየ ስፍራን ነው። አማራጭ ትርጉም: “በቅርብህ ስሆን” (ፈሊጥን ይመልከቱ)

---

## Chapter 17

### Psalms 17:1
አጠቃላይ ሃሳብ፡
በዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት የተለመደ ነው። (ቅኔ እና ትይዩነትን ይመልከቱ)
የዳዊት ጸሎት
“ይህ ዳዊት የጻፈው ጸሎት ነው”
ከአታላይ ከንፈር ያልወጣውን ጸሎቴን አድምጥ
“ጆሮ ስጥ” ስማ ለሚለው ቅኔ ነው። “ከአታላይ ከንፈር ያልወጣ” ከማይዋሽ ሰው ለሚለው ወካይ ነው። አማራጭ ትርጉም: “ያለሽንገላ የሆነ ጸሎቴን አድምጥ” (ቅኔን እና በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)
ጽድቄ ከአንተ ዘንድ ይምጣ
ጽድቅ ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣት የሚያመለክተው እግዚአብሔር ፈርዶ አንድን ሰው ጻድቅ ሲለው ነው። የእግዚአብሔር መገኘት ለእግዚአብሔር ለራሱ ገላጭ ነው። አማራጭ ተርጉም: “ጽድቄ ከአንተ ዘንድ ይምጣ” ወይመ “ንጹህ እንደሆነሁ ተናገር” (ቅኔ እና ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
ዐይኖችህም ፍትህን ይዩ
ዐይኖችህ የሚወክለው እራሱ እግዚአብሔርን ነው። “ይዩ” የሚለው ሃሳብ ትኩረትን መስጠት እና አንድ ነገር ለማድረግ መወሰን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “አባክህ ትክክል የሆነውን ተመልከት” ወይም “ትክክል የሆነው አድርግ” (ቅኔን እና በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

### Psalms 17:3
ልቤን መረመርኸው በሌሊት ጠጋ ብለህ ፈትነኸኝ
“ልቤን መረመርኸው” ማለት ሀሳቤን እና ስሜቴን መርምር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም: “ሀሳቤን በሌሊት ብትመረምር” (ፈሊጥን ይመልክቱ)
አንደበቴ አላፊ አይሄድም
እዚህ ጋር አንደበት በራሱ መንቀሳቀስ እንደሚችል ነው የተገለጸው። የሚወክለውም ሰው የሚናገረውን ቃላት ነው። አማራጭ ትርጉም: “ውሸትን አልናገርም ወይም በቃላቴ ኃጢአትን አልሰራም” (ሰውኛ ዘይቤ እና በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

### Psalms 17:4
በከንፈርህ ቃል ከዐመጸኞች መንገድ ራሴን ጠብቄአለሁ
“በከንፈርህ ቃል” የሚለው ሃረግ ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሌላ ስያሜ ነው። “የዐመጸኞች መንገድ” ዐመጸኞች የሚያደርጉትን የሚያመለክት ቅኔ ነው። አማራጭ ትርጉም: “ትዕዛዛትህን በመታዘዝ እራሴን ዐመጸኞች የሚያደርጉትን ከማድረግ ጠበቅሁ” ወይም “ትዕዛዛትህ ክፉ ነገር ማድረግን እንዳሶግድ አድርገውኛል” (ድጋሚ መሰየምን እና ቅኔን ይመልከቱ)
አረማመዴ በመንገድህ ጸንቶአል፥ እግሮቼም አልተንሸራተቱም
ሁለቱም ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጓሜ አላቸው። መደገማቸው ትኩረትን ይጨምራል። (ትይዩነትን ይመልከቱ)

### Psalms 17:6
ስለምታደምጠኝ አንተን እጣራለሁ
እነዚህ ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጓሜ አላቸው። “ስለምታደምተኝ” የሚለው ሃሳብ የእግዚአብሔርን ጸሎተ ለመስማት እና ለመመለስ ፈቃደኝነት ይገልጻት። አማራጭ ትርጉም: “ስናገር ትሰማለህ፤ ትኩረትን ትሰጠኛለህ” (ትይዩነትን እና ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
የቃል ኪዳን ታማኝነትህን በአስደናቂ ሁኔታ ግለጽ
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ገላጭ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም: “በአስደናቂ መንገድ ለቃልኪዳንህ ታማኝ መሆንህን ግለጥ።”(ረቂቅ ስምን ይመልከቱ)
ቀኝህ
ቀኝ እጅ የእግዚአብሔርን ኃይል ታመለክታለች። አማራጭ ትርጉም: “ኃይልህ” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
መተገኛ
ለጥበቃ ወደ ያህዌ መሄድ በእርሱ እንደ መጠለል ይገለጻል። አማራጭ ትርጉም: “ለመከለል ወደ አንተ መምጣት” (ቅኔን ይመልከቱ)

### Psalms 17:8
እንደ ዐይንህ ብሌን ጠብቀኝ
“የዐይን ብሌን” የከበረን ነገር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “ውድ እና የከበረን ነገር እንደምትጠብቅ ትጠብቀኛለህ” (አነጻጻሪ ዘይቤ ይመልከቱ)
በክንፎችህ ጥላ ሰውረኝ
ዳዊት ስለ እግዚአብሔር ጥበቃ ሲናገር ወፍ ጫጩቶቿን በክንፎቿ ስር እንደምትጋርድ ነው። አማራጭ ትርጉም: “እናት ወፍ ጫጩቶቿን በክንፏ ስር እንደምትጋርድ ጠብቀኝ።” (ቅኔን ይመልከቱ)
በአፋቸው ትዕቢትን ይናገራሉ
“በአፋቸው” የሚለው ቃል የሚወክለው የጠላቶችን ንግግር ነው። አማራጭ ትርጉም: “በትዕቢት ይናገራሉ” ወይም “ሁልጊዜ ይታበያሉ” (በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

### Psalms 17:11
ከበቡኝ
“ከበቡኝ” የሚለው ቃል ዳዊት ጠላቶቹ እንዴት በሁሉም ስፍራ ሊይዙት እንደተከታተሉት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “ጠላቶቼ ከበውኛል” (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
እነርሱ ለንጥቂያ እንደሚጓጓ አንበሳ በስውርም እደሚያደባ ደቦል አንበሳ ናቸው
ሁለቱም ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጓሜ አላቸው። መደገማቸው ትኩረትን ይጨምራል። (ትይዩነትን ይመልከቱ)
አንበሳ … ደቦል
ጸሐፊው አንበሳ የሚበላውን እነደሚያሳድድ እየተሰደደ እንደሆነ ተሰምቶታል። (አነጻጻሪ ዘይቤ ይመልከቱ)

### Psalms 17:13
ያህዌ በሰይፍም ከክፉዎች ታደገኝ … እንዲህ ካሉት ሰዎች በክንድህ አድነኝ
ሁለቱም ሃረጎች ተመሳሳይ ትርጓሜ አላቸው። መደገማቸው ትኩረትን ይጨምራል። (ትይዩነትን ይመልከቱ)
በሰይፍህ … በክንድህ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል እና “ክንድ” የሚለው ቃል የያህዌን ኃይል ያመለክታሉ። (ድጋሚ መሰየምን ይመልከቱ)
የመዝገቦችህን ሆዳቸውን ሙላ
የጥንቱ ጽሑፍ ለመረዳት አስቸጋሪ ነው። አማራጭ ፍቺዎች 1) “መዝገብ” ለፍቅር ቅኔያዊ መግለጫ ነው፥ ስለዚህ “መዝገብ” በእግዚአብሔር የተወደዱትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: “የምትወዳቸውን ሰዎች ሆድ በፍቅርህ ተሞላለህ” ወይም 2) “የመዝገቦችህ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለዚህ ዓለም ህዝብ የሚሰጠውን መዝገብ ነው፥ አማራጭ ትርጉም: “ሆዳቸውን በሀብት መዝገብ ትሞላለህ” (ቅኔን ይመልከቱ)
የመዝገቦችህን ሆዳቸውን ሙላ
“የመዝገቦችህን ሆዳቸውን ሙላ” የሚያመለክተው ብዙ ውድ ነገሮችን መስጠትን ነው። አማራች ፍቺዎች 1) “ለምትወዳቸው ሰዎች ብዙ ሀብትን ትሰጣቸዋለህ” ወይም 2)”ለዚህ ዓለም ሰዎች ብዙ ሀብትን ትሰጣቸዋለህ” (ቅኔን ይመልከቱ)

### Psalms 17:15
እኔ ግን በጽድቅ ፊትህን አያለሁ
“ፊት” የሚወክለው የያህዌን ሁለመና ነው። ዳዊት ያህዌን እንደሚያይ እርግጠኛ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነው። አማራጭ ትርጉም: “በትክክለኛ መንገድ ስለምሄድ፥ አንድ ቀን ፊትህን አያለሁ” (በአንድ ክፍል ሙሉ አካልን መሰየምን ይመልከቱ)

ስነቃም ክብርህን አይቼ እረካለሁ

ዳዊት ከሞተ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚሆን እርግጠኛ ነው። ይህ ሃሳብ በትርጉም ውስጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም: “ከሞትኩ በኋላ በመገኘትህ ውስጥ በመንቃት ደስ ይለኛል” (ግምታዊ እውቀትን እና ድብቅ ሃሳብ ይመልከቱ)

Chapter 18

Psalms 18:1

አጠቃላይ መረጃ

ተጓዳኝ ሐሳቦች በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመዱ ናቸው።

ለመዘምራን አለቃ

‹‹ይህ የመዘምራን መሪው በአምልኮ ጊዜ የሚጠቀምበት ነው››

የዳዊት መዝሙር

እንዲህም ማለት፤ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው፤ ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው፤ ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።

ለያህዌ እንዲህ ሲል የዘመረው ነው

‹‹ይህን መዝሙር ለያህዌ ዘመረ››

ያህዌ በታደገው ቀን

‹‹ያህዌ ከታደገው በኃላ››

ከሳዖል እጅ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሳዖልን ኀይል ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሳዖል ኀይል››

Psalms 18:2

ያህዌ ዐለቴ ነው

ዳዊት ያህዌ ዐለት እንደሆነ ይናገራል። ‹‹ዐለት›› የምቹ ቦታ ምሳሌ ነው።

ዐለቴ መሸሸጊያዬ

እዚህ ላይ ‹‹ዐለት›› እና፣ ‹‹መሸሸጊያ›› ተመሳሳይ ነገሮች ቢሆኑም፣ ያህዌ ከጠላት ማምለጫ ቦታ እንደሚያዘጋጅ አጽንዖት ይሰጣል።

የምሸሸግበት

መከላከያ ለማግኘት ወደ ያህዌ መሄድ በእርሱ ውስጥ መሸሸግ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንድከለል ወደ እርሱ እሄዳለሁ››

ጋሻዬ፣ የድነቴ ቀንድና ዐምባዬ ነው

ያህዌ፣ ‹‹ጋሻው›› የድነቱ፣ ‹‹ቀንድ›› እና፣ ‹‹ዐምባው›› እንደሆነ ዳዊት ይናገራል። ከጉዳት የሚጠብቀው ያህዌ ነው። እዚህ ላይ አጽንዖት ለመስጠት ተመሳሳይ ሐሳቦች በሦስት የተለያዩ መንገዶች ቀርበዋል።

ከጠላቶቼ እድናለሁ

‹‹ከጠላቶቼ አመልጣለሁ››

Psalms 18:4

የሞት ገመድ ከበበኝ

ዳዊት ሞት በገመድ ከያዘ በኃላ የሚያስር ሰው እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልገደል ነበር››

የጥፋት ጐርፍ አጥለቀለቀኝ

ዳዊት ጐርፍ እንደሚወስደው ሰው ዐቅም አጥቶ እንደ ነበር ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍጹም ዐቅመ ቢስነት ተሰማኝ››

የሲኦል ገመድ ከበበኝ፤ የሞት ወጥመድ ያዘኝ››

እዚህ ላይ የሙታን ቦታ የሆነው፣ ‹‹ሲኦል›› እና፣ ‹‹ሞት›› እንደ ሰው እንደ ከበቡትና እንዳጠመዱት ተነግሯል። ሁለቱም ቃሎች ተመሳሳይ ነገር ቢሆኑም፣ የተደገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በወጥመድ እንደ ተያዝሁ ተሰማኝ፤ ልሞት ነው በማለት አሰብሁ››

Psalms 18:6

በጨነቀኝ ጊዜ

‹‹በቸገረኝ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹ተስፋ ስቆርጥ››

የርዳታ ጥሪዬ ወደ ፊቱ ሄደ

እዚህ ላይ ዳዊት፣ ‹‹የርዳታ ጥሪው›› ሰው ይመስል ወደ ያህዌ ፊት እንደ ሄደ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እርሱ ጸለይሁ››

ወደ ጆሮው ገባ

ዳዊት የርዳታውን ጩኸት ያህዌ እንደ ሰማው ይናገራል። ሐሳቡ የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልመናዬን ሰማ››

Psalms 18:7

ያህዌ ስለ ተቆጣ… ምድር ተናወጠ

የእግዚአብሔር ቁጣ ከባድ የመሬት መናወጥ እንዳመጣ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር በጣም ስለ ተቆጣ… ምድር ተናወጠ››

ምድር ተንቀጠቀጠ ተናወጠም

‹‹መንቀጥቀጥ›› እና፣ ‹‹መናወጥ›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ቢሆኑም፣ አጽንዖት የተሰጠው ምድር በኀይል እንደ ተንቀጠቀጠ ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምድር ወደ ፊት ወደ ኃላ ተንቀሳቀሰ›› ወይም፣ ‹‹ምድር ወደ ላይ ወደ ታች ተንቀሳቀሰ›› ወይም፣ ‹‹ከባድ የምድር መናወጥ ሆነ››

የተራሮች መሠረትም ተንቀጠቀጠ፤ ተናወጠ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተራሮች መሠረትም ተንቀጠቀጠ ተናወጠ››

ከአፍንጫው ጢስ ወጣ… ፍም ከእርሱ ወጣ

ዳዊት ያህዌ እሳት እየተነፈሰ እንደሆነ ይናገራል። ይህም እግዚአብሔር ምን ያህል እንደ ተቆጣ ያሳያል።

ከአፉ የሚባላ እሳት ወጣ፤ ከእርሱም እሳት ነደደ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚባላ እሳት ከአፉ ወጣ፤ ከዚያም እሳት ነደደ››

Psalms 18:9

ከፈተ

እርሱ የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

ከእግሮቹም በታች ድቅድቅ ጨለማ ነበረ

ምንም እንኳ እግሮች ባይኖሩትም፣ ዘማሪው የሰው ባሕርይ ሰጥቶታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከበታቹ ድቅድቅ ጨለማ ነበረ››

የነፋስ ክንፎች

እዚህ ላይ ዘማሪው ነፋስ እንደ መልአክ ዐይነት ክንፎች እንዳሉት ይናገራል

Psalms 18:11

ጨለማን ሠራ… የእርሱ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› እና፣ ‹‹የእርሱ›› ያህዌን ያመለክታል።

ጨለማን ድንኳን አደረገ

ጨለማ እንደ ድንኳን እንደሆነ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨለማን መሸፈና አደረገ›› ወይም፣ ‹‹ጨለማን መደበቂያ ቦታ አደረገ››

ጥቁር ደመና

‹‹ዝናብ የከበደው ደመና›› ወይም፣ ‹‹ጥቅጥቅ፣ ጥቁር ጨለማ››

የበረዶ ድንጋይ

ከበረዶ የተሠራ ድንጋይ

Psalms 18:13

ያህዌ በሰማያት አንጐዳጐደ

የያህዌ ድምፅ እንደ መብረቅ ተሰማ

ልዑል

‹‹ልዑል›› የተባለው ያህዌ ነው።

ፍላጻውን አስፈንጥሮ ጠላቶቹን በተናቸው… መብረቅ አዥጐድጉዶ አሳደዳቸው

ሁለቱም ዐረፍተ ነገር ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው።

ፍላጻውን አስፈንጥሮ ጠላቶቹን በተናቸው

እዚህ ላይ መብረቅ እንደ ፍላጻ ተነግሮአል።

በተናቸው

‹‹በተለያየ አቅጣጫ አባረራቸው››

Psalms 18:15

አጠቃላይ መረጃ

ጸሐፊው ስለ ያህዌ ታላቅ ኀይል መናገር ቀጥሏል።

ከዚያም የባሕር ወለል ተገለጠ፤ የዓለምም መሠረት ራቁቱን ቀረ

ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚያም የባሕሩ ታችኛው ክፍል ተገለጠ፤ አንተም የዓለምን መሠረት እርቃኑን አስቀረህ።››

ከአፍንጫው ታላቅ እስትንፋስ የተነሣ

እዚህ በተነገረው መሠረት እግዚአብሔር ሰብዓዊ ባሕርያት ባይኖሩትም፣ ይህ ታላቅ ኀይሉን ያመለክታል። ነፋስ ከእግዚአብሔር ትንፋሽ የሚወጣ ታላቅ እስትንፋስ እንደሆነ ተነግሯል።

Psalms 18:16

እጁን ወደ ታች ሰደደ… እኔን ያዘኝ… ጐትቶ አወጣኝ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

የሚናወጥ ውሃ

እዚህ ላይ ዘማሪው ጠላቶቹ እንደ ግዙፍና ኀይለኛ ውሃ እንደሆኑ ይናገራል፤ ያህዌ ያዳነው ከዚያ ውስጥ ነበር።

Psalms 18:18

መጡብኝ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ቁጥር 17 ላይ የተጠቀሱትን ጠላቶቹን ነው።

በመከራዬ ቀን መጡብኝ፤ ያህዌ ግን ድጋፍ ሆነልኝ

‹‹መከራ›› የሚለውን የነገር ስም ቅጽል ማድረግ ይቻላል፤ ‹‹ድጋፍ›› የሚለውን ስም ‹‹ከለላ›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብርቱዎቹ ጠላቶቼ ጭንቀት ውስጥ ባለሁበት ቀን መጡብኝ፤ ያህዌ ግን ከለላ ሆነኝ››

Psalms 18:20

እጆቼ ንጹሕ ነበሩ

የእጅ ንጽሕና የሚያመለክተው በደል አለማድረግን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በደል አልነበረብኝም›› ወይም፣ ‹‹ያደረግሁት ትክክል ነበር››

የያህዌን መንገዶች ጠብቄአለሁ

የያህዌ ሕጐች ሰው ሊመላለስባቸው የሚገባ መንገዶች እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለያህዌ ሕጐች ታዝዣለሁ››

በዐመፅ ከያህዌ አልራቅሁም

እዚህ ላይ ዐመፅ ትክክለኛውን መንገድ በመተው ትክክል ባልሆነው መንገድ መሄድ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአምላኬ በመራቅ ዐላመፅሁም››

Psalms 18:22

ጻድቅ ሕጐች ሁሉ… ከእነርሱ አልራቅሁም

ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ጸሐፊው የደጋገማቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው።

በፊቴ ነበሩ

‹‹መርተውኛል›› ወይም፣ ‹‹አስታውሻለሁ››

ነቀፋ አልነበረብኝም… ራሴን ከኀጢአት ጠብቄአለሁ

ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው የደጋገማቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው።

በፊቱ ነቀፋ አልነበረብኝም

‹‹በእርሱ ዘንድ ንጹሕ››

ራሴን ከኀጢአት ጠብቄአለሁ

‹‹ኀጢአት አላደረግሁም››

እጆቼ ንጹሕ ነበሩ

‹‹ንጹሕ እጆች›› ምንም በደል አለማድረግ ማለት ነው። መዝሙር 18፥20 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በደል አልነበረብኝም›› ወይም፣ ‹‹ሥራዬ ትክክል ነበር››

በዐይኖቹ ፊት

ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር መገኘት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፊቱ›› ወይም፣ ‹‹በእርሱ ዘንድ››

Psalms 18:25

አጠቃላይ መረጃ

ጸሐፊው ለያህዌ ይናገራል

ታማኝ ለሆነ ሁሉ

‹‹ታማኝ›› መሆን እግዚአብሔር ያዘዘውን ማድረግ ማለት ነው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በታማኝነት ትእዛዞችህን የሚጠብቁ›› ወይም፣ ‹‹በታማኝነት ኪዳንህን ለሚያደርጉ››

ከንጹሑ ጋር… አንተም ንጹሕ ትሆናለህ

ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው የደጋገማቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው።

ለጠማማው ጠማማ ትሆንበታለህ

‹‹ቅን›› ላልሆነው አንተም አትሆንለትም››

Psalms 18:27

አወረድሃቸው

‹‹ዝቅ አደረግሃቸው››

የትዕቢተኛውን፣ የንቀት ዐይን

ፈሊጣዊው አነጋገር ትዕቢተኛ ሰውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የታበዬ››

ለመብራቴ ብርሃን ሰጠኸኝ፤ ያህዌ አምላኬ ጨለማዬን ያበራል

ጸሐፊው የያህዌ መገኘት ብርሃን እንደሆነ ይናገራል። እነዚህ አነጋገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው።

በአንተ ቅጥሩን እዘላለሁ

‹‹በአንተ ርዳታ እንቅፋትን እሻገራለሁ››

Psalms 18:30

ለሚጠጉት ሁሉ ጋሻ ነው

ጋሻ ወታደሩን ይከልላል። ዳዊት ያህዌ የሚከልለው ጋሻ እንደሆነ ይናገራል። መዝሙር 3፥3 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ሆይ፣ ወደ አንተ የሚጠጉትን እንደ ጋሻ ትከልላቸዋለህ››

ከያህዌ በቀር አምላክ ማነው? ከአምላካችን በቀር ዐለት ማን ነው?

የሚጠበቀው መልስ ማንም የለም የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ብቻ አምላክ ነው፤ አምላካችን ብቻ ዐለት ነው››

ዐለት

ያህዌ ከጠላቶቹ ለማምለጥ የሚወጣበት ዐለት እንደ ሆነ ዳዊት ይናገራል። መዝሙር 18፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ኀይልን አስታጠቅኸኝ

እግዚአብሔር ለዳዊት ትጥቅ የሚሆነው ኀይል ሰጠው

ቀናውን ሰው በመንገዱ አደረገ

እዚህ ላይ ዳዊት በትክክለኛው መንገድ በመሄድ ያህዌን ደስ ሚያሰኝ ሕይወት እየኖረ እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቀናውን ሰው የጽድቅ ሕይወት እንዲኖር አደረገ››

Psalms 18:33

እግሮቼን አፈጠነ

ይህ የሚያመለክተው በፍጥነት መሮጥን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፍጥነት እንድሮጥ አደረገ››

እንደ ብሖር ከፍታ ላይ አደረገኝ

ብሖር ፈጣን ነው፤ ተራሮችም ላይ ጸንቶ ይቆማል።

እጆቼን ያሠለጥናል

‹‹እጆቼ›› ሰውየውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያሠለጥነኛል››

ክንዶቼን

ይህ ሰውየውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔን››

Psalms 18:35

የድነት ጋሻ

እዚህ ላይ ጸሐፊው የእግዚአብሔር ጥበቃ እንደ ጋሻ እንደሆነ ይናገራል። ‹‹ድነት›› የሚለውን፣ ‹‹መዳን›› በማለት መተርጐ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥበቃህ አዳነኝ››

ቀኝ እጅህ ደገፈኝ

የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ኀይሉን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀይልህ ደገፈኝ›› ወይም፣ ‹‹አንተ በኀይልህ ደገፍኸኝ››

ሞገስህ ታላቅ አደረገኝ

እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ሞገስ እንደ እርሱ ሞገስ ያደረገውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ሞገስህ ታላቅ አደረግኸኝ›› ወይም፣ ‹‹በቸርነትህ ታላቅ አደረግኸኝ››

ከእግሮቼ በታች ያለውን ቦታ አሰፋህልኝ

እግዚአብሔር ያደረገለት ጥበቃ የሚቆምበት ሰፊ ቦታ እንደ መስጠት መሆኑን ጸሐፊው ይናገራል። እዚህ ላይ፣ ‹‹እግሮቼ›› ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእኔ ደህና ቦታ››

እግሮቼ አልተንሸራተቱም

‹‹እግሮቼ›› ሰውየውን ይወክላል። እግዚአብሔር ያደረገለት ጥበቃ ተንሸራትቶ እንዳይወድቅ ደህና ቦታ መቆም ማለት እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልተንሸራተትሁም›› ወይም፣ ‹‹በደንብ ቆሜአለሁ››

Psalms 18:37

አደቀቅኋቸው

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

‹‹ፈጨኃቸው›› ወይም፣ ‹‹ሰባበርኋቸው››
መነሣት አይችሉም
‹‹መቆም አይችሉም››
በእግሮቼ ሥር ወደቁ
አነጋገሩ ዘማሪው ጠላቶቹን አሸነፈ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሉንም አሸነፍኋቸው››
ኀይልን አስታጠቅኸኝ
ዘማሪው እርሱን ለመደገፍ ወገቡ ላይ እንደሚታጠቀው ቀበቶ ያህዌ ኀይል እንደ ሰጠው ይናገራል።
ከእግሬ ሥር አደረግህልኝ
እዚህ ላይ ዘማሪ የጠላቶቹ መሸነፍ እነርሱ ላይ መቆም ማለት እንደሆነ ይናገራል፤ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ አሸነፍህልኝ››
በእኔ ላይ የተነሡትን
ይህ የሚያመለክተው ዘማሪውን የሚቃወሙትን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቼን››
Psalms 18:40
የጠላቶቼን ማጅራት ሰጠኸኝ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለዳዊት ጠላቶቹ ላይ ድል እንደ ሰጠው ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጠላቶቼ ላይ ድል ሰጠኸኝ››
የጠላቶቼን ማጅራት ሰጠኸኝ
ይህም የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለዳዊት ጠላቶቹ ላይ ድል እንደ ሰጠው ነው። 1) ዳዊት የጠላቶቹን ራስ ከአንገታቸው መቁረጥ ይችላል፣ ወይም 2) ዳዊት እግሩን ጠላቶቹ ላይ ማድረግ ይችላል፤ ወይም 3) ዳዊት ከእርሱ ሲሸሹ የጠላቶቹን ጀርባ ማየት ይችላል።
የሚጠሉንን አጠፋኃቸው
‹‹የሚጠሉንን አሸነፍሁ›› ወይም፣ ‹‹የሚጠሉኝን ፈጽሞ ደመሰስሁ››
እርሱ ግን አልመለሰላቸውም
ይህ ማለት ያህዌ አልረዳቸውም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ግን አልረዳቸውም››
ነፋስ ፊት እንዳለ ትቢያ አደቀቅኃቸው
ምን ያህል እንደ ተሸነፉ ለማሳየት የዘማሪው ጠላቶች ከትቢያ ጋር ተመሳስለዋል።
እንደ መንገድ ላይ ጭቃ ረገጥኃቸው
ምን ያህል እንደ ተሸነፉ ለማሳየት የዘማሪው ጠላቶች በመንገድ ላይ ጭቃ ተመስለዋል።
Psalms 18:43
ፀብ
አለመግባባት፤ ግጭት
በሕዝቦች ላይ ራስ አደረገኝ
‹‹ራሱ›› የሚወክለው መሪን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የብዙ ሕዝብ መሪ አደረግኸኝ››
ባዕዳን በፊቴ ዝቅ አሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ባዕዳን በፊቴ ዝቅ እንዲሉ አደረገ››
የሌላ አገር ሰዎች እየተንቀጠቀጡ መጡ
‹‹መንቀጥቀጥ›› የሚያመለክተው መፍራታቸውን ነው። ትርጉሙ ውስጥ ይህን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሌላ አገር ሰዎች ፍርሃታቸውን ለማሳየት እየተንቀጠቀጡ መጡ››
Psalms 18:46
ዐለቴ ይመስገን
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ዐለቴ ነው፤ መመስገን ይገባዋል›› ወይም፣ ‹‹ሕዝቦች ዐለቴን ያመስግኑት››
ዐለቴ
እዚህ ላይ ጸሐፊው ጠላቶቹ እንዳያገኙት ያህዌ መከላከያ ዐለት እንደሆነለት ይናገራል። መዝሙር 18፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
የድነቴ አምላክ ከፍ ይበል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች የድነቴን አምላክ ከፍ ያድርጉት››
የድነቴ አምላክ
‹‹ድነት›› የሚለው ስም፣ ‹‹መዳን›› ወይም፣ ‹‹መታደግ›› ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የታደገኝ አምላክ››
የሚበቀልልኝ አምላክ
‹‹የሚበቀልልኝ›› ማለት ሰዎችን በክፉ ሥራቸው የሚቀጣ ማለት ነው። ‹‹በቀል›› የሚለውን ቃል ማውጣት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ላይ ባደረጉት ክፉ ሥራ ሰዎችን የሚቀጣ አምላክ››
Psalms 18:48
ነጻ ወጣሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ነጻ አደረገኝ››
ወደ ላይ ከፍ አደረግኸኝ
x
Psalms 18:50
ድል ለንጉሡ
ዳዊት፣ ‹‹ለንጉሡ›› የሚለው ራሱን ነው።
እርሱ ለቀባው የኪዳኑን ታማኝነት ያሳየዋል… ለዘሩም ለዘላለም
‹‹በኪዳኑ ባገባው ቃል መሠረት በታማኝነት ወደደኝ፤ ዘሮቼንም ለዘላለም ወደደ››

---

Chapter 19
Psalms 19:1
አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።
ለመዘምራን አለቃ
‹‹ይህ በአምልኮ የመዘምራን መሪ የሚጠቀምበት ነው››
የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈው ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው፤ ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት መሠረት ነው።
ሰማያት ይናገራሉ
ሰማያት እንደ ሰው እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰማያት ያሳያሉ›› ወይም፣ ‹‹ሰማያት ያውጃሉ››
የሰማያትም ጠፈር የእጁን ሥራ ያሳውቃሉ
ሰማያት አስተማሪ እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰማያት የእግዚአብሔርን እጅ ሥራ ያስታውቁናል››
የእጁ ሥራ
‹‹ፍጥረቱ›› ወይም፣ ‹‹እርሱ የሠራው ዓለም››
ድምፃቸው ወጣ
የፍጥረት ውበት ፍጥረት የሚናገር ሰው እንደሆነ ያመለክታል። እነዚሁ ቃሎች በየቦታው ከሚፈስስ ውሃ ጋር ተመሳስለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍጥረት ለሁሉም እንደሚናገር ሰው ነው››
ንግግር የለም፤ ቃል የለም፤ ድምፃቸውም አልተሰማም
እነዚህ ሐረጐች የመጀመሪያዎቹ ሁለት ቁጥሮች ምሳሌያዊ አነጋገር መሆናቸውን በግልጽ ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድምፅ ወይም ቃል የለም፤ በጆሮው ድምፅ የሰማ ሰው የለም››
ድምፃቸው አልተሰማም
ሌሎች ትርጒሞች፣ ‹‹ድምፃቸው ባልተሰማበት›› ይላሉ፤ ይህም የፍጥረት፣ ‹‹ድምፅ›› በየቦታው እንደሚሰማ አጽንዖት ይሰጣል።
Psalms 19:4
አጠቃላይ መረጃ
ዳዊት ፍጥረት የእግዚአብሔርን ክብር እንደሚያሳይ ያመለክታል።
ቃላቸው… ድምፃቸው
ይህ የሚያመለክተው ‹‹በቃላት›› የማይነገረውን የእግዚአብሔርን ክብር የሚያሳየውን ፍጥረት ነው።
ቃላቸው ወጣ
ቃላቸው መልእክት ይዞ እንደ ወጣ ሰው መሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍጥረት የሚናገረው ቃል ይዞ እንደ ወጣ ሰው ነው››
ንግግራቸው እስከ ዓለም ዳርቻ
ይህ ትርጉም ውስጥ ቃሎች መግባት እንዳለበት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣

‹‹ንግግራቸው እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ››
ለፀሐይ ድንኳን ተከለ
ያህዌ ለፀሐይ ያዘጋጀለት ስፍራ እንደ ድንኳን መሆኑን ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለፀሐይ ስፍራ አዘጋጀ››
በመካከላቸው
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ምናልባት ሰማያትን ነው።
ፀሐይ ከእልፍኙ እንደሚወጣ ሙሽራ ነው።
የፀሐይ መውጣት እንደ ሙሽራ እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ፀሐይ ደስ እያለው ወደ ሙሽራዪቱ እንደሚሄድ ሙሽራ ነው››
ወደ ግቡ እንደሚሮጥ ብርቱ ሰው ደስ ይለዋል
ብርታትና ድምቀቱን ለማሳየት ጸሐፊው ፀሐይን ከሯጭ ጋር ያመሳስለዋል።
ብርቱ ሰው
‹‹ፈጣን ሯጭ››
አድማስ
ምድርና ሰማይ የሚገናኙበት መስመር
ወደ ሌላው
ወደ ‹‹ሌላው›› የሚያመለክተው ሌላውን አድማስ ነው። ትርጒሙ ውስጥ ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ሌላው አድማስ››
ከሙቀቱ የሚያመልጥ የለም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሙቀቱ ለሁሉም ይደርሳል››
Psalms 19:7
ነፍስ… ልብ… ዐይኖች
ሦስቱም የሚያመለክቱት መላውን ሰው ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰው››
አላዋቂ
‹‹ልምድ የሌለው›› ወይም፣ ‹‹ያልተማረ››
ትክክል
‹‹እውነት›› ወይም፣ ‹‹ተገቢ››
ብሩህ
‹‹ማስተዋል የሚሰጥ››
Psalms 19:9
የታመነ
‹‹ፍጹም ትክክል››
ከወርቅ ይልቅ ዋጋው የከበረ… ከማር ይልቅ የጣፈጠ
የያህዌ ሕግ የሚገዛና የሚቀመስ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከገዛኸው ከወርቅ ይበልጣል… ከቀመስኸው ከማር ይበልጥ ይጣፍጣል››
ከጠራ ወርቅ እንኳ ይበልጣል
‹‹ዋጋው›› የሚለው ቃል ካለፈው ሐረግ ውስጠ ታዋቂ ነው፤ መደገምም ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከብዙ የጠራ ወርቅ ዋጋው ይበልጣል››
የጠራ ወርቅ
‹‹ንጹሕ ወርቅ›› ወይም፣ ‹‹ውድ ወርቅ››
Psalms 19:11
አዎን
ይህ ቃል ከተነገረው በላይ እውነት መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የበለጠ››
በእነርሱ ባርያህ ጥንቃቄ ያደርጋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ባርያህን ያስጠነቅቁታል›› ወይም፣ ‹‹ለባርያህ ማስጠንቀቂያ ናቸው››
ለእነርሱ… በመታዘዝ
‹‹በእነርሱ›› የሚለው የያህዌን ቅዱስ ትእዛዞች ያመለክታል።
ባርያህ ይጠነቀቃል
አክብሮቱን ለማሳየት ዳዊት ለእግዚአብሔር ሲናገር ራሱን ባርያ በማለት ይጠራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እጠነቀቃለሁ››
ስሕተቱን ማን ሊያስተውል ይችላሉ?
በጥያቄ ያቀረበው አጽንዖት ለመስጠት ነው፤ ጠንከር ተደርጐ በዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የራሱን ስሕተት ማስተዋል የሚችል የለም››
ከተሰወረ በደል
‹‹ካደረግሁት ስውር በደል››
Psalms 19:13
ባርያህን ጠብቀው
ፈሊጣዊው አነጋገር ባርያው ማድረግ ከማይፈልገው ኀጢአት መራቅ እንደሚፈልግ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ባርያህን ከማድረግ ጠብቀው›› ወይም፣ ‹‹እንዳላደርግ ርዳኝ››
ባርያህ
አክብሮቱን ለማሳየት ለእግዚአብሔር ሲናገር ዳዊት ራሱን ባርያ በማለት ይጠራል። መዝሙር 19፥11 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
አይግዙኝ
ኀጢአት ሰውን የሚገዛ ንጉሥ እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኀጢአቶቼ እንደ ንጉሥ አይግዙኝ››
ከብዙ መተላለፍ እንጻኝ
‹‹አንተ ላይ እንዳላምፅ አድነኝ›› ወይም፣ ‹‹ብዙ ኀጢአት ከማድረግ››
የአፌ ቃልና የልቤ ሐሳብ
እነዚህ ቃሎች በአንድነት ሲወሰዱ አንድ ሰው የሚናገረውና የሚያስበው ሁሉ ማለት ናቸው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የምናገረውና የማስበው ሁሉ››
በፊትህ የተወደደ ይሁን
‹‹በፊትህ ተቀባይነት ያለው›› ወይም ‹‹ደስ የሚያሰኝህ››
በፊትህ
ፊት ፍርድና ሚዛንን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በአንተ ፍርድ››
ያህዌ ዐለቴ
ጸሐፊው ያህዌ ከጠላቶቹ የሚሸሸግበት ዐለት እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ፣ አንተ ለእኔ እንደ ዐለት ነህ››

---

Chapter 20
Psalms 20:1
አጠቃላይ መረጃ
ይህ መዝሙር የሚጀምረው ሰዎች ለእስራኤል ንጉሥ እየተናገሩ ነው።
አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።
ለመዘምራን አለቃ
‹‹ይህ በአምልኮ ጊዜ ለመዘምራን መሪ የሚሆን ነው››
የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው፤ ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው፤ ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው።
ይረዳሃል
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተን›› የሚለው ንጉሡን ነው።
በመከራ ቀን
‹‹በችግር ቀን›› ወይም፣ ‹‹ችግር ሲገጥምህ››
የያዕቆብ አምላክ ስም ይጠብቅህ
ይህም ማለት፣ 1) እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የያህዌን ኀይል ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የያዕቆብ አምላክ ኀይል ይጠብቅህ›› ወይም፣ ‹‹የያዕቆብ አምላክ በኃይሉ ይጠብቅህ›› ወይም 2) እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› እግዚአብሔርን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የያዕቆብ አምላክ ይጠብቅህ››
ከመቅደሱ ረድኤት ይላክልህ
እግዚአብሔር በመቅደሱ ሆኖ መርዳቱ ርዳታ መላክ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ከመቅደሱ ረድኤት ይላክልህ››
መቅደሱ… ጽዮን
ሁለቱም ቃሎች የሚያመለክቱት በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው።
Psalms 20:3
ያስብህ
‹‹ያስብህ›› የተባለው እግዚአብሔር ስለሚረሳ አይደለም። ያስታውስህ ወይም ያስብልህ ለማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ ያስታውስህ››
እርሱ
ይህ ቃል የሚያመለክተው ያህዌን ነው።
ሴላ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ቃል እንዴት እንደሚዘምሩ ወይም የሙዚቃ መሣሪያቸውን እንደሚጫወቱ ለሕዝብ የሚናገር የሙዚቃ አገላለጽ ነው፡፡ አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል ይጽፋሉ፤ አንዳንድ ትርጉሞች ያንን አያደርጉም፡፡ መዝሙር 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት፡፡
ይስጥህ
‹‹ይለግሥህ››
የልብህን መሻት
‹‹ልብ›› የሰውን ሁለንተና ይወክላል፡፡ ‹‹መሻት›› የሚለውን ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምትሻውን›› ወይም፣ ‹‹የምትፈልገውን››
ዕቅድህን ሁሉ ያሳካልህ
‹‹ዕቅድ›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያቀድኸውን ሁሉ ለማሳካት ይርዳህ››
Psalms 20:5
በአንተ ድል ደስ ይለናል
‹‹እኛ›› የሚለው ሕዝቡን ነው፡፡ በንጉሡ ድል ደስ ይላቸዋል፡፡
በአምላካችን ስም
እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› ክብርንና ዝናን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለአምላካችን ክብር›› ወይም፣ ‹ለአምላካችን ዝና››
ዐርማ እናነሣለን
‹‹የድል ባንዲራ እናነሣለን›› እንዲህ የሚያደርጉት በጠላቶቻቸው ላይ ድል ስለሰጣቸው እግዚአብሔርን ለማመስገን ነው፡፡
ልመናህን ሁሉ ይፈጽምልህ
‹‹የለመንኸውን ሁሉ ይስጥህ››
አሁ
ቃሉ እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው መዝሙሩ ቆም የሚልበትን ቦታ ለማመልከት ነው፡፡ ንግግሩ ከሕዝቡ ወደ ንጉሡ እንዲሸጋገር፡፡
አውቃለሁ
‹‹እኔ›› የሚለው ምናልባት በዚህ ክፍል እየተናገረ ያለውን ንጉሡን ያመለክት ይሆናል፡፡
የቀባውን… ይመልስለታል… ይታደገዋል
ንጉሡ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ስለ ራሱ ይናገራል፡፡ ይህን በመጀመሪያ ሰው ደረጃ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የቀባውን እኔን… ይመልስልኛል… ይታደገኛል››
ከሰማይ መቅደሱ
በኢየሩሳሌም እንዳለው ቤተ መቅደስ ሁሉ፣ እግዚአብሔር በሰማይም ይኖራል (መዝሙር 20፥2 ይመ.)፡፡
በቀኝ እጁ ብርታት ይታደገዋል
የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ኀይሉን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በታላቅ ብርታቱ ይታደገዋል››
Psalms 20:7
አንዳንዶች በሰረገላ ሌሎች በፈረስ ይታመናሉ
‹‹ሰረገላ›› እና፣ ‹‹ፈረስ›› የንጉሡን ሰራዊት ይወክላሉ፡፡
ሌሎች በፈረሶች
‹‹ይታመናሉ›› ውስጠ ታዋቂ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌሎች በፈረስ ይታመናሉ››
እንጠራለን… እንነሣለን
‹‹እኛ›› የሚያመለክተው ጸሐፊውንና አንባቢዎቹን ነው፡፡
እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው በሰረገሎችና በፈረሶች የሚተማመኑትን ሰዎች ነው፡፡ ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ያሰነካከላቸዋል፤ ይጥላቸዋል››
ተሰነካክለው ወደቁ
ሁለቱም ግሦች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ሁለቱም የሚያመለክቱት በጦርነት መሸነፍን ነው፡፡
እኛ ተነሣን ጸንተንም ቆምን
‹‹እኛ ተነሥተን ቀጥ ብለን እንቆማለን›› ሁለቱን ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ሁለቱም የሚያመለክቱት በጦርነት ድል ማድረግን ነው፡፡
Psalms 20:9
ያህዌ ንጉሡን ያድነዋል
ይህም ማለት፣ 1) ንጉሡን እንዲጠብቀው ሕዝቡ እግዚአብሔርን እየለመኑ ነው፡፡ ወይም 2) ንጉሡ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ስለ ራሱ መናገር ቀጥሏል፡፡
ንጉሡ፣ እኛም ስንጠራህ ስማን
አንዳንድ ትርጉሞች ዕብራይስጡን በተለየ ሁኔታ ይተረጉሙታል፡፡ አንዳንዶች ሕዝቡ ለንጉሣቸው ለያህዌ እየተናገሩ እንደሆነ ተርጉመውታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሥ፣ ስንጠራህ ሰማን››

---

Chapter 21
Psalms 21:1
አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው፡፡
ለመዘምራን አለቃ
‹‹ይህ በአምልኮ እንዲጠቀምበት ለመዝሙር መሪው ነው››
የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈው ዳዊት ነው፤ ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው፤ ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው፡፡
ያህዌ ሆይ፣ በኀይልህ
ይህ ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ ያህዌ ለንጉሡ የሰጠው ኀይል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ሆይ፣ ጠላቶቹን እንዲያሸንፍ አንተ ኀይል ስለ ሰጠኸው››
ምንኛ ደስ አለው
‹‹በጣም ደስ አለው››
በምትሰጠው መዳን
እግዚአብሔር ንጉሡን ከጠላቶቹ እንዳዳነው ግልጽ ነው፡፡ ‹‹መዳን›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከጠላቶቹ ስላዳንኸው››
ልቡ ደስ ይለዋል
‹‹የልቡ መሻት›› እዚህ ላይ ‹‹ልብ›› የሰውን ሁለንተና ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የልቡ መሻት›› ወይም፣ ‹‹እርሱ የተመኘው››
አልከለከልኸውም
‹‹እንቢ አላልኸውም›› ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰጠኸው››
የከንፈሮቹን ልመና
‹‹ከንፈሮች›› የሰውን ሁለንተና ይወክላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የለመነህን›› ወይም፣ ‹‹የጠየቀህን››
ሴላ
ይህ እንዴት እንደሚዘምሩ ወይም የሙዚቃ መሣሪያ እንደሚጫወቱ ለማሳሰብ የተሰጠ የሙዚቃ አገላለጽ ነው፡፡ አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል ጽፈዋል፡፡ ሌሎች ግን ያንን አላደረጉም፡፡ መዝሙር 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት፡፡
Psalms 21:3
ብዙ በረከት አመጣህለት
‹‹በረከት›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹በበረከት›› ወይም፣ ‹‹መልካም ነገር›› ማለት ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በብዛት ባረክኸው›› ወይም፣ ‹‹ብዙ መልካም ነገር ሰጠኸው››
ራሱ ላይ የንጹሕ ወርቅ ዘውድ ደፋህለት
አንድ ሰው ራስ ላይ ዘውድ መድፋት፣ እርሱን ንጉሥ ማድረግ ማለት ነው፡፡
የንጹሕ ወርቅ ዘውድ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ንጹሕ ወርቅ›› ለንጉሡ የተሰጠውን ታላቅ ክብር ይወክላል፡፡
ሕይወትን ለመነህ አንተም ሰጠኸው
‹‹ሕይወት›› የሚለውን ግሥ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ረጅም ዘመን እንዲኖር ለመነህ አንተም ያንኑ አደረግህለት››
ከዘላለም እስከ ዘላለም ረጅም ዘመን
ይህም ማለት፣ 1) በጣም ረጅም ዘመን፤ ወይም 2) የዘላለም ሕይወት፤ ወይም 3) ረጅም የትውልድ ሐረግ ማለት ሊሆን ይችላል፡፡
Psalms 21:5
ክብሩ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

‹‹የንጉሡ ክብር›› ወይም፣ ‹‹የንጉሡ ዝና››
ክብርና ሞገስን አኍናጸፍኸው
‹‹እርሱ ላይ ክብርና ሞገስ አደረግህ፡፡›› ንጉሡን ሀብታምና ኀያል ማድረግ፣ እርሱ ላይ ክብርና ሞገስ ማድረግ ማለት እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሀብታምና ኀያል አደረግኸው››
ሰጠኸው
‹‹ፈቀድህለት›› ወይም፣ ‹‹ልትሰጠው ፈቀድህ››
ዘላቂ በረከት
‹‹የማይጠፉ በረከት›› ወይም፣ ‹‹ሁሌም የሚኖር በረከት››
የፊትህ ደስታ
‹‹በፊትህ የመሆን ደስታ›› ወይም፣ ‹‹ወደ አንተ በመቅረብ የሚገኝ ደስታ››
Psalms 21:7
ከልዑል ታማኝነት ኪዳን የተነሣ
‹‹ታማኝነት›› የሚለውን መለወጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልዑል ለኪዳኑ ታማኝ በመሆኑ››
አይናወጥም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከንጉሥነቱ ማንም አይነቀንቀውም››
እጅህ ትይዛለች
‹‹እጅ›› ኃይልን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀይልህ ትይዛለች›› ወይም፣ ‹‹በኀይል ትይዛለህ››
እጅህ... የሚጠሉህን
‹‹የአንተ›› እና፣ ‹‹አንተ›› ሲል፣ 1) ንጉሡን ነው ወይም 2) እግዚአብሔርን ነው፡፡
ቀኝ እጅህ የሚጠሉህን ፈልጋ ትይዛለች
ይህ ከዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ እግዚአብሔር ጠላቶቹን የሚቋቋምበት ኀይል ለንጉሡ እንደሚሰጠው አጠንክሮ ይናገራል፡፡
Psalms 21:9
በተቆጣህ ጊዜ
‹‹በቁጣህ ስትገለጥ››
በቁጣህ... ታጠፋለህ
‹‹የአንተ›› እና፣ ‹‹አንተ›› ሲል፣ 1) እግዚአብሔርን ነው ወይም 2) ንጉሡን ማለቱ ነው፡፡
እንደ ምድጃ እሳት ታቃጥላቸዋለህ
ያህዌ ወይም ንጉሡ ጠላቶቻቸውን መደምሰሳቸው ጠላቶቻቸው ያህዌ ወይም ንጉሡ ምድጃ ውስጥ የሚጥሏቸው እንጨት እንደሆኑ ተነግሮአል፡፡
ያህዌ በመዓቱ ያቃጥላቸዋል፤ እሳት ይበላቸዋል
ሁለቱም ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ያህዌ ጠላቶቹን ጨርሶ መደምሰሱ የእርሱ መዓት እነርሱን ፈጽሞ የሚያጠፋ እሳት እንደሆነ ተነግሯል፡፡
ከምድር... ከሰው ዘር መካከል
ሁለቱም ሐረጎች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ከጠላቶቻቸው አንድ እንኳ እንደማይቀር ነው አጽንዖት የሚሰጡት፡፡
Psalms 21:11
ያውጠነጥናሉ
‹‹ያቅዳሉ›› - ‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው የእግዚአብሔርንና የንጉሡን ጠላቶች ነው፡፡
በአንተ ላይ ክፉ
‹‹አንተ ላይ ክፉ ነገር ለማድረግ››
ተንኰል አውጠነጠኑ
‹‹ዕቅድ አወጡ›› ወይም፣ ‹‹አሤሩ››
Psalms 21:13
ያህዌ ሆይ፣ በብርታትህ ከፍ በል
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ያህዌ ብርታትህን አሳየን›› ወይም 2) ‹‹ያህዌ አንተ ብርቱ በመሆንህ እኛም ከፍ እንላለን›› ማለት ሊሆን ይችላል፡፡
እንዘምራለን ኀይልህን እናመሰግናለን
‹‹መዘመር›› እና፣ ‹‹ማመስገን›› ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፡፡ ‹‹ኀይል›› የሚለው እግዚአብሔርንና ኀይሉን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ኀይል ስለሆንህ በዝማሬ እናመሰግንሃለን››

Chapter 22
Psalms 22:1
አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው፡፡
ለመዘምራን አለቃ
‹‹ይህ የመዘምራን መሪ በአምልኮ ጊዜ የሚጠቀምበት ነው››
የንጋት አጋዘን
ይህ የሚያመለክተው የዜማውን ስልት ሊሆን ይችላል፡፡
የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈው ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል፡፡
አምላኬ፣ አምላኬ
ጸሐፊው፣ ‹‹አምላኬ›› የሚለውን የደገመው እግዚአብሔር እንዲሰማው አጥብቆ መፈለጉን አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡
አምላኬ ለምን ተውኸኝ?
ጸሐፊው ጥያቄውን ያነሣው እግዚአብሔር እንደ ተወው ስለ ተሰማው ነው፡፡ ይህን ጥያቄ እንደሆነ መተው ይቻላል፡፡ እንደ ዐረፍተ ነገር መተርጐምም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አምላኬ ሆይ፣ አንተ እንደ ተውኸኝ ይሰማኛል!››
ተውኸኝ
‹‹ብቻዬን ተውኸኝ››
እኔን ከማዳን፣ ከመቃተቴ ቃል ለምን ራቅህ?
ጸሐፊው ጥያቄውን ያነሣው እግዚአብሔር ከእርሱ በጣም እንደ ራቀ ስለ ተሰማው ነው፡፡ ይህን ጥያቄ እንደሆነ መተው ይሻላል፡፡ በዐረፍተ ነገር መተርጐምም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ እኔን ከማዳንና ከመቃተቴ ቃል ርቀሃል››
ከመቃተቴ ቃል ርቀሃል
እግዚአብሔር እንዳልሰማው ጸሐፊው የነበረው ስሜት እግዚአብሔር ከመቃተቱ ቃል በጣም የራቀ ያህል መሆኑን ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለሚሰማኝ ጭንቀት ስናገር የማትሰማኝ ለምንድነው?›› ወይም ‹‹ስለ መከራዬ ነገርሁህ አንተ ግን ወደ እኔ አልመጣህም››
በቀን... በሌሊት
ጸሐፊው፣ ‹‹ቀን›› እና፣ ‹‹ሌሊት›› በተሰኙ ቃሎች የተጠቀመው ዘወትር ወደ እግዚአብሔር እንደሚጸልይ ለማመልከት ነው፡፡
ዝም አላልሁም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁንም እየተናገርሁ ነው››
Psalms 22:3
በእስራኤል ምስጋና እንደ ንጉሥ ተቀመጥህ
‹‹የእስራኤል ምስጋና አንተ እንደ ንጉሥ የምትቀመጥበት ዙፋን ነው›› የእስራኤል ምስጋና እግዚአብሔር ተቀምጦ የሚገዛበት ዙፋን ወይም እግዚአብሔር የሚኖርበት ቤት እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ንጉሥ ነህ፤ የእስራኤል ሕዝብ ያመሰግንሃል››
የእስራኤል
እዚህ ላይ፣ ‹‹የእስራኤል›› የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል፡፡
አላፈሩም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አላሳፈርሃቸውም›› ወይም ‹‹አልጣልሃቸውም››
አላፈሩም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አዳንሃቸው›› ወይም ‹‹የለመኑህን አደረግህላቸው››
Psalms 22:6
እኔ ትል ነኝ፤ ሰው አይደለሁም
ጸሐፊው እርሱ ትል እንደሆነ ይናገራል፡፡ ይህም እርሱ ከንቱ እንደሆነ ወይም ሰዎች እንደ ከንቱ ነገር እንደሚቆጥሩት አጽንዖት ይሰጣል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ እንደ ትል ነኝ እንጂ፣ ሰው አይደለሁም››
ሰው ያላገጠብኝ፤ ሕዝብም የናቀኝ ነኝ
ሁለቱም ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ‹‹ሕዝብም የናቀኝ›› የሚለውን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ሁሉ ዋጋ እንደሌለኝ

በመቁጠር ይጠሉኛል››
ያላግጡብኛል፤ ይሣለቁብኛል፤ ራሳቸውንም ይነቀንቁብኛል
እነዚህ ሦስት ሐረጐች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ሰዎች ምን ያህል እንዳዋረዱት አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡
ራሳቸውንም ይነቀንቁብኛል
ይህ ሰውን የመናቅ ምልክት ነው፡፡
በያህዌ ተማምኖአል… በእርሱ ደስ የተሰኘበትን
ሰዎች እንዲህ ያሉት በጸሐፊው ለማፌዝ ነው፡፡ ያህዌ እንደሚታደገው በእርግጥ አያምኑም፡፡
እስቲ ይታደገው
‹‹እስቲ ያህዌ ይታደገው››
በእርሱ ደስ የተሰኘበትን
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ያህዌ በእርሱ ደስ ተሰኝቶአልና›› ወይም 2) ‹‹እርሱ በያህዌ ደስ ተሰኝቶአልና››
Psalms 22:9
አንተ ግን
ጸሐፊው፣ ‹‹ግን›› በሚል ቃል የተጠቀመው ለምን እርሱን ለመርዳት እንደማይመጣ ግራ መጋባቱን ለማሳየትና እግዚአብሔር ለመጠየቅ ነው፡፡
ከማሕፀን አወጣኸኝ
ይህ ‹‹እንድወለድ አደረግህ›› ማለት ነው፡፡
በእናቴ ጡት ሳለሁ
ይህ ማለት ገና ሕፃን እያለ በያህዌ ይተማመን ነበር ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእናቴ ጡት እጠባ በነበረበት ጊዜ እንኳ››
ከእናቴ ማሕፃን ስወጣም በአንተ ተጣልሁ
‹‹ተጣልሁ›› የሚለው ቃል ያህዌ እንደራሱ ልጅ ተቀብሎ ተጠነቀቀለት ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው፡፡ ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ተወለድሁ አንተ ተቀበልኸኝ››
አንተ አምላኬ ነህ
ይህ የሚያመለክተው ያህዌ ዘወትር ለጸሐፊው ይጠነቀቅለት እንደ ነበር ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ተጠነቀቅህልኝ››
በእናቴ ማሕፀን ሳለሁ
‹‹ከመወለዴ በፊት››
Psalms 22:11
ከእኔ አትራቅ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እኔ ቅረብ››
መከራ እየተቃረበ ነውና
ጸሐፊው፣ ‹‹መከራ ወደ እርሱ እየቀረበ ያለ ነገር እንደሆነ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቼ ወደ እኔ እየቀረቡ ነውና››
የሚረዳ የለም
‹‹ረዳት የለም››
ብዙ ኮርማዎች ከበቡኝ፣ ኀይለኛ የባሳን በሬዎችም በዙሪያየ ቆሙ
ጸሐፊው ጠላቶቹ እንደ ኮርማ እንደሆኑ ይናገራል፡፡ ይህ የሚያሳየው ጠላቶቹ ምን ያህል አደገኛና ብርቱ መሆናቸውን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ኮርማዎች የከበቡኝ ብዙ ጠላቶች አሉኝ እነርሱ ዙሪያዬን እንደ ቆሙ ኀይለኛ የባሳን በሬዎች ናቸው››
አፋቸውን አስፍተው ከፈቱብኝ
ጸሐፊው ጠላቶቹ እርሱን ለመብላት አፋቸውን እንደ ከፈቱ አንበሶች እንደሆኑ ይናገራል፡፡ ጠላቶቹ እርሱን ለማዋረድ ሐሰት እየተናገሩ ይሆናል፡፡ ወይም እንደሚያጠቁት እየዛቱበት ይሆናል፡፡
እንደሚነጥቅና እንደሚያገሣ አንበሳ
ጸሐፊው ጠላቶቹ እንደ አንበሳ እንደሆኑ ይናገራል፡፡ ይህም ጠላቶቹ ምን ያህል ኀይለኞችና አደገኞች መሆናቸውን አጽንዖት ይሰጣል፡፡
Psalms 22:14
እንደ ውሃ ፈሰስሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ውሃ የፈሰሰሁ መሰለኝ››
እንደ ውሃ ፈሰስሁ
ከእንስራ ወደ ውጭ እንደ ፈሰሰ ውሃ ያበቃለትና ፍጹም ደካማነት እንደ ተሰማው ጸሐፊው ይናገራል፡፡
ዐጥንቶቼ ሁሉ ከመጋጠሚያቸው ወለቁ
‹‹ዐጥንቶቼ ሁሉ ተናጉ›› ጸሐፊው አንድ ዐይነት የአካል ሕመም ደርሶበት ይሆናል፡፡ ወይም ስሜታዊውን ሕመም እንደ አካላዊ ሕመም እያመለከተ ይሆናል፡፡
ልቤ እንደ ሰም… ውስጤ
ልቡ እንደ ሰም እንደ ቀለጠ ሰው፣ ጸሐፊው ከእንግዲህ ምንም ወኔ እንደሌለው ይናገራል፡፡ እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› የሚያመለክተው፣ ‹‹ወኔን›› ነው፡፡
ሰም
በአንጻራዊ በጣም ዝቅ ባለ ሙቀት እንኳ የሚቀልጥ ነገር
በውስጤ
‹‹እኔ ውስጥ››
ብርታቴ እንደ ገል ደረቀ
ጸሐፊው በቀላሉ እንደሚሰበር የደረቀ ሸክላ ስባሪ ዐቅመ ቢስነት እንደ ተሰማው ይናገራል፡፡
የሸክላ ስባሪ
እቤት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ከሸክላ የተሠራ ነገር
ምላሴ ከላንቃዬ ጋር ተጣበቀ
‹‹ምላሴ ከትናጋዬ ጋር ተጣበቀ›› ምናልባትም ጸሐፊው በጣም ጠምቶት እንደ ነበር እየተናገረ ይሆናል፡፡ ወይም መድከሙ የመድረቅ ያህል እንደሆነበት እየተናገረ ይሆናል፡፡
በሞት ዐፈር አጋደምኸኝ
‹‹የሞት ዐፈር›› ማለት 1) ከሞተ በኋላ ወደ ዐፈር የተለወጠ ሰው ማለት ይሆናል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንድሞትና ዐፈር እንድሆን አደረግኸኝ›› ወይም 2) ስለ መቃብርና በዚያም አማካይነት እግዚአብሔር ጸሐፊው እንዲሞት እንዳደረገ መናገሩ ይሆናል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በመቃብሬ አጋደምኸኝ››
አጋደምኸኝ
‹‹አንተ›› የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው፡፡
Psalms 22:16
ውሾች ከበቡኝ
ጸሐፊው ጠላቶቹ እንደ ውሾች እንደሆኑ ይናገራል፡፡ ጠላቶቹ የሞተ እንስሳ እንደሚበሉ የዱር ውሾች ወደ እርሱ እየቀረቡ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቼ እንደ ውሾች ከበቡኝ››
የክፉዎች ሸንጐ
‹‹የክፉዎች ጉባኤ›› ወይም፣ ‹‹የክፉዎች ቡድን››
በዙሪያዬ
ክብ ሠርተው ቆሙ
እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩ
ይህም ስለ ውሾቹ ነው የሚናገረው ጸሐፊው ጠላቶቹ እንደሚናከሱና በጥርሳቸው እጆችና እግሮቹን እንደ ቸነከሩ ይናገራል፡፡
ቸነከሩኝ
ስል በሆነ ነገር ወጉኝ
ዐጥንቶቼን መቁጠር እችላለሁ
ይህም ማለት፣ 1) ጸሐፊው በጣም ከሲታ ስለ ነበር ዐጥንቶቹን ማየት ይችላል ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐጥንቶቼን ሁሉ ማየት እችላለሁ›› ወይም፣ ‹‹ዐጥንቶቼን መንካት እችላለሁ›› ወይም 2) ይህ የሚናገረው ስለ ውሾቹ ሲሆን፣ ሥጋውን ከገነጣጠሉ በኋላ ዐጥንቶቹን ማየት ቻሉ ማለት ሊሆን ይችላል፡፡
አፍጥጠው ያዩኛል፤ ይመለከቱኛል
‹‹ያዩኛል›› እና፣ ‹‹ይመለከቱኛል›› በመሠረቱ አንድ ቢሆኑም፣ ሰዎች በፍርሃት እንደሚያዩትና እንደሚቀልዱበት አጽንዖት ይሰጣል፡፡
Psalms 22:18
በእጀ ጠባቤ
‹‹በልብሴ››
አትራቅ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እኔ ቅረብ››
ብርታቴ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ብርታት›› የሚያመለክተው ብርታት የሚሰጠውን ያህዌን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብርታት ሰጠኸኝ››
Psalms 22:20
ነፍሴን ታደጋት
‹‹ነፍስ›› የሰውን ሁለንተና ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታደገኝ››

ከሰይፍ
ሰይፍ ለአደገኛ ጠላት የሚሰጥ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሊገድሉኝ የሚፈልጉ›› ወይም፣ ‹‹ጠላቶቼ››
ውድ ሕይወቴን
‹‹የከበረች ሕይወቴን›› ወይም፣ ‹‹ያለችኝን ብቸኛ ሕይወቴን››
ከዱር ውሾች ጥፍር... ከአንበሶች አፍ... ከዱር በሬዎች ቀንድ
ጸሐፊው ጠላቶቹ ምን ያህል አደገኞች መሆናቸውን አጽንዖት ለመስጠት የዱር ውሾች፣ አንበሶችና የዱር በሬዎች እንደሆኑ ይናገራል። በተጨማሪም ጥፍር፣ አፍና ቀንድ በምሳሌያዊ አነጋገር እንስሳትን ሁሉ ያመለክታል። ጸሐፊው ለእነዚህ ነገሮች አጽንዖት የሰጠው እንስሶች ሌላውን ለመግደል የሚጠቀሙት በእነዚህ ነገሮች በመሆኑ ነው።
የዱር ውሾች... የዱር በሬዎች
እዚህ ላይ ‹‹ዱር›› የሚለው ቃል እንስሶቹን ማንም ይዞአቸው ወይም አልምዶአቸው። እንደማያውቅ ለማመልከት ነው።
Psalms 22:22
ስምህን እናገራለሁ
‹‹ስምህን አሳውቃለሁ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የእግዚአብሔርን ባሕርይና ማንነት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለ ባሕርይህ እናገራለሁ››
ለወንድሞቼ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ወንድሞቼ›› ማለት፣ ‹‹እስራኤላውያን ወገኖቼ›› ወይም፣ ‹‹እንደ እኔ ያህዌን ለሚያመልኩ›› ማለት ነው።
በጉባኤ መካከል
‹‹እኔና እስራኤላውያን ወገኖቼ በአንድነት ስንሰባሰብ›› ወይም ‹‹ያህዌን በሚያመልኩ ሰዎች ስከበብ››
የምትፈሩት
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› በነጠላ ቁጥር ሳይሆን የተነገረው በብዙ ቁጥር ነው።
እናንተ የያዕቆብ ዘር... የእስራኤልም ዘር
ሁለቱም የሚያመለክቱት አንድን ሕዝብ ነው።
እርሱን ፍሩት
‹‹እርሱን በጣም ፍሩት›› ወይም፣ ‹‹የእግዚአብሔር ኀይል ያስደንቃችሁ››
Psalms 22:24
የተጨነቀውን ሰው ጭንቀት አልናቀም፤ ቸልም አላለምና
ይህም ማለት፣ 1) መከራ ላይ ስለሆነ የተጨነቀውን ሰው አልናቀም ወይም 2) የተጨነቀውን ሰው መከራ አቅልሎ አላየም ማለት ሊሆን ይችላል።
አልናቀም ወይም አልተጸየፈም
በመሠረቱ ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸው፤ የተጨነቀውንና በመከራ ያለውን እግዚአብሔር አለመርሳቱን አጽንዖት ይሰጣሉ።
አልናቀም
አጥብቆ አልጠላም
የተጨነቀውን ሰው መከራ... አልተጸየፈም
እዚህ ላይ፣ መከራ የሚያመለክተው ሰውየውን ነው። አንድን ነገር መጸየፍ አጥብቆ መጥላት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተጨነቀውን ሰው መከራ አጥብቆ አልጠላም››
የተጨነቀው ሰው መከራ... ከእርሱ... የተጨነቀው ጮኸ
ይህም ማለት፣ 1) ጸሐፊው እግዚአብሔር መከራ ውስጥ ያሉትን እንዴት እንደሚያይ እየተናገረ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መከራ ውስጥ ያሉት... ከእነርሱ... መከራ ውስጥ ያሉት ጮኹ›› ወይም 2) ጸሐፊው በተለይ እርሱን እንዴት እንደሚያይ እየተናገረ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከመከራዬ የደረሰብኝ ጭንቀት... ከእኔ... ጮኽሁ››
ፊቱን ከእርሱ አልሰወረም
ከሰው ፊትን መሰወር እርሱን ችላ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ትኩረቱን ከእርሱ አላነሣም›› ወይም፣ ‹‹ችላ አላለውም››
ሰማ
‹‹አደመጠ›› ጩኸታቸውን ሲሰማ ምላሽ መስጠቱ ግልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መለሰ›› ወይም፣ ‹‹ረዳ››
በአንተ
‹‹አንተ›› የሚለው ያህዌን ነው።
ስዕለቴን እፈጽማለሁ
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፊው ለእግዚአብሔር እንደሚያቀርብ ቃል የገባውን ነው።
እርሱን በሚፈሩት ፊት
‹‹እርሱ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው። ‹‹አንተ›› ሊባልም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተን በሚፈሩ ፊት››
Psalms 22:26
ችግረኞች ይበላሉ ይጠግባሉ
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፊው ቃል የገባውን መሥዋዕት ካቀረበ በኋላ የሚኖረውን የኅብረት ምግብ ነው። እርሱ ለመሥዋዕት ያቀረበውን እንስሳ ክፍል እንዲበሉ ችግረኞችን ይጋብዛል።
ያህዌን የሚፈልጉት
ያህዌን ማወቅና እርሱን ደስ ማሰኘት የሚፈልጉ እርሱን ራሱን ለማግኘት እንደሚፈልጉ ተነግሯል።
ልባችሁ ለዘላለም ሕያው ይሁን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› የሰውን ሁለንተና ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለዘላለም ሕያው ሁኑ››
ልባችሁ ለዘላለም
እዚህ ላይ፣ ‹‹የእናንተ›› የሚለው ችግረኞቹን ነው።
ያስታውሳሉ ወደ ያህዌ ይመለሳሉ
ለያህዌ መታዘዝ የሰዎች ወደ ያህዌ መመለስ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን ያስታውሱታል ይታዘዙለታል››
የሕዝቦች ወገኖች ሁሉ በፊትህ ወድቀው ይሰግዳሉ
ይህ ከመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ክፍል ጋር ተመሳሳይ ነገር ነው የሚናገረው። ጸሐፊው በየቦታው ያሉ ሰዎች ሁሉ ያህዌን እንደሚያመልኩና እንደሚታዘዙለት አጽንዖት ይሰጣል።
በፊትህ ወድቀው ይሰግዳሉ
ይህ የሚያመለክተው ክብርንና ምስጋናን መስጠትን ነው።
በፊትህ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው። ከመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ክፍል ጋር እንዲጣጣም በሦስተኛ ሰው ደረጃ መተርጎም አለበት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፊቱ››
Psalms 22:28
መንግሥት የያህዌ ነው
‹‹መንግሥት የሚገባው ለያህዌ ነው›› እዚህ ላይ፣ ‹‹መንግሥት›› የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን እንደ ንጉሥ መግዛት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ንጉሥ ነውና››
ሕዝቦችንም የሚገዛ እርሱ ነው
‹‹ሕዝቦች›› የሚያመለክተው ሰዎችን ሁሉ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በየአገሩ ያሉ ሰዎች››
ይበላሉ
ሰዎቹ በአንድነት በደስታ ይበላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አብረው ይበላሉ›› ወይም፣ ‹‹የደስታ ምግብ አብረው ይበላሉ››
ወደ ዐፈር የሚወርዱ ሁሉ... ራሳቸውን ማዳን የማይችሉ
ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት ስለ አንድ ወገን ነው። ሰዎች ሁሉ ሟች ስለ ሆኑ ሁለቱም የሚናገሩት ስለ ሰዎች ሁሉ ነው።
ወደ ዐፈር የሚወርዱ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐፈር›› የሚያመለክተው መቃብርን ነው። ‹‹ወደ ዐፈር የሚወርዱ›› የሚለው የሚያመለክተው የሚሞቱ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እየሞቱ ያሉ›› ወይም፣ ‹‹የሚሞቱ››
ራሳቸውን ማዳን የማይችሉ
‹‹ሕይወታቸውን ማዳን የማይችሉ›› ወይም፣ ‹‹ራሳቸውን ከሞት የማያድኑ››
Psalms 22:30
የሚመጣ ትውልድ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ትውልድ›› የሚያመለክተው ትውልዱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ነው። ‹‹የሚመጣ›› የሚያመለክተው የወደ ፊቱን ጊዜ ሲሆን እንደሚሄድና አንድ ቦታ እንደሚደርስ ነገር አድርጎ ይናገራል።
የሚቀጥል ትውልድ
‹‹ትውልድ›› የሚያመለክተው ትውልዱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚቀጥለው ትውልድ ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ልጆቻቸው››
ስለ ጌታ
‹‹ጌታን በተመለከተ›› ወይም፣ ‹‹ጌታ ስላደረገው››

ጽድቁን ይነግራሉ
‹‹ጽድቁ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ቅጽል ማድረግ ይቻላል። ‹‹እርሱ ያደረገውን
የጽድቅ ሥራ ይነግራሉ››

## Chapter 23

### Psalms 23:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።
አጠቃላይ መረጃ
በአብዛኛው በዚህ መዝሙር ክፍል ራሱን እንደ በግ ጌታን ደግሞ እንደ እረኛ አድርጐ ዳዊት ይጽፋል።
የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።
ያህዌ እረኛዬ ነው
ጸሐፊው ያህዌ እንደ እረኛ እንደሆነ ይናገራል። ይህም እረኛ ለበጐቹ እንደሚያስብ ያህዌም ለሰዎች እንደሚያስብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንደ እረኛዬ ነው›› ወይም፣ ‹‹እረኛ ለበጐቹ እንደሚያስብ ያህዌ ለእኔ ያስብልኛል››
አንዳች አይጐድልብኝም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚያስፈልገኝ ሁሉ አለኝ››
በለመለመ መስክ ያሳርፈኛል
ጸሐፊው ራሱን እንደ በግ ያህዌን እንደ እረኛ ያቀርባል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጉን በለመለመ መስክ እንደሚያሳርፍ እረኛ ዕረፍት ይሰጠኛል››
በዕረፍት ውሃ ዘንድ ይመራኛል
ጸሐፊው ራሱን እንደ በግ ያህዌን እንደ እረኛ ያቀርባል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጉን በዕረፍት ውሃ ዘንድ እንደሚመራ እረኛ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ያቀርብልኛል።››
የዕረፍት ውሃ
‹‹ረጋ ያለ ውሃ›› ወይም፣ ‹‹ረጋ ብሎ የሚወርድ ውሃ›› ይህ ውሃ ለመጠጥ ተስማሚ ነው።

### Psalms 23:3

አጠቃላይ መረጃ
ይህ መዝሙር እረኛ ለበጐቹ እንደሚያስብ እግዚአብሔርም ለእኛ እንደሚያስብ መናገር ቀጥሏል።
ነፍሴን መለሳት
ይህ ማለት ደካማውን ሰው እግዚአብሔር ብሩቱ ያደርገዋል ያሳርፈዋል ማለት ነው።
በትክክለኛው መንገድ መራኝ
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት መኖርን ለአንድ ሰው ማሳየት በጉን በትክክለኛ መንገድ እንደሚመራ እረኛ መሆን እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በትክክል መኖርን ያሳየኛል››
ስለ ስሙ ሲል
‹‹ስለ ስሙ›› የሚለው ሐረግ የእርሱን ማንነት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለ ማንነቱ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች እንዲያከብሩት››

### Psalms 23:4

አጠቃላይ መረጃ
ይህ መዝሙር እረኛ ለበጐቹ እንደሚያስብ እግዚአብሔርም ለእኛ እንደሚያስብልን መናገር ቀጥሏል።
በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ ብሄድ እንኳ
ከባድ መከራ የደረሰበት ሰው በጨለማና አደገኛ ሸለቆ ውስጥ እንደሚሄድ ሰው መሆኑን ጸሐፊው ይናገራል። በዚያ በጐች ይጠፋሉ፤ በአደገኛ አውሬ ይጠቃሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕይወቴ በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ እንደሚሄድ ቢሆን እንኳ››
ጉዳት ይደርስብኛል ብዬ አልፈራም
‹‹ጉዳት›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንዳች ነገር ይጐዳኛል ብዬ አልፈራም››
አንተ ከእኔ ጋር ስለሆንህ
‹‹አንተ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው።
በትርህና ምርኩዝህ ያጽናኑኛል
በትርና ምርኩዝ እረኞች በጐቻቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ የሚጠቀሙባቸው ስለሆነ ጥበቃን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በበትርና በምርኩዙ በጐቹ እንደሚጠብቅ እረኛ እኔንም ስለምትጠብቀኝ አልፈራም››

### Psalms 23:5

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር በቤቱ እንግድነት ተቀብሎ እንደሚጠብቀው ሰው እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል።
ገበታ አዘጋጀህልኝ
ገበታ ግብዣን ያመለክታል፤ ሰዎች ምግቦችን ሁሉ ገበታው ላይ ይኖራሉ።
በጠላቶቼ ፊት
የዚህ ትርጉም ጸሐፊው እርሱ የተከበረ የጌታ እንግዳ እንደሆነና እርሱም ከአደጋ ስለሚጠብቀው እንደማይሰጋ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ጠላቶቼ እያዩ››
ራሴን በዘይት ቀባህ
ሰዎች ለእንግዳው ክብር ራሱን በዘይት ይቀቡት ነበር።
ጽዋዬም ሞልቶ ይፈስሳል
ወይን ሞልቶ የሚፈስስ ጽዋ ብዙ በረከትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሞልቶ እስኪፈስ ድረስ ጽዋዬን ሞላኸው›› ወይም፣ ‹‹ብዙ በረከት ሰጠኸኝ››

### Psalms 23:6

በጐነትና ኪዳናዊ ታማኝነት በእርግጥ ይከተሉኛል
ያህዌ ለሰው ደግና ታማኝ መሆኑ በጐነትና ኪዳናዊ ታማኝነት ያንን ሰው እንደሚከተሉት ተደርጐ ተነግሯል። ‹‹በጐነት›› እና፣ ‹‹ታማኝነት›› የተሰኙ የነገር ስሞች እንደ ቅጽል መተርጐም ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእኔ አንተ በእርግጥ መልካምና ታማኝ ነህ››
በሕይወቴ ዘመን ሁሉ
‹‹ሕይወት›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሕይወት እስካለሁ ድረስ››
በያህዌ ቤት
ይህም ማለት፣ 1) የያህዌን ዘላለማዊ ቤት ያመለክታል ወይም 2) በኢየሩሳሌም ያለውን የያህዌን ቤቴ መቅደስ ያመለክታል። ከተቻለ ሁለቱንም ሐሳቦች በሚያካትት ሁኔታ ተርጉመው።
ለረጅም ዘመን
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ለዘላለም›› ወይም 2) ‹‹በሕይወት እስካለሁ ድረስ››

## Chapter 24

### Psalms 24:1

አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።
የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈው ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው።
ሞላዋ
‹‹ሞላዋ›› የሚለው የነገር ስም፣ ‹‹የሞላት›› በሚል ግሥ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሷን የሞላ ሁሉ››
እርሱ በባሕር ላይ መሥርቶአታልና በውሆችም ላይ አጽንቶአታል
እዚህ ላይ፣ ‹‹በባሕር ላይ መሠረታት›› እና፣ ‹‹ውሆች ላይ አጸናት›› ማለት በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው በዚያ ዘመን የነበሩ ዕብራውያን ምድራቸው በባሕር እንደ ተመሠረተችና በጥልቅ ውሆች ላይ እንደ ጸናች ያምኑ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መሠረቷን ባሕር ላይ አደረገ፤ ጥልቅ ውሆችም ላይ አጸናት››
ባሕር… ውሆች
እነዚህ ሐረጐች በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት ከምድር በታች ያለውን ግዙፍና ጥልቅ ውቅያኖስ ለማመልከት ነው።
በውሆች ላይ
‹‹ከታች ጥልቅ ውስጥ ያለው ውሃ››

### Psalms 24:3


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ወደ ተራራው ማን ይወጣል… በተቀደሰ ስፍራውስ?
ሁለቱም ጥያቄዎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። ጸሐፊው ወደዚያ ሄዶ ያህዌን የሚያመልክ ማን ሊሆን እንደሚችል እየጠየቀ ነው።
ማን ሊወጣ ይችላል
‹‹ማን ወደ ላይ ይሄዳል›› ወይም፣ ‹‹ማን መውጣት››
የያህዌ ተራራ
ይህ የሚያመለክተው ኢየሩሳሌም ያለው የጽዮን ተራራ ነው።
የተቀደሰ ስፍራ
ይህ የሚያመለክተው የያህዌን ቤተ መቅደስ ነው። ቤተመቅደሱ ያለው በኢየሩሳሌም በጽዮን ተራራ ላይ ነው።
ያለው… የማያስገዛ… የማይምል
‹‹እርሱ›› ሲል አንድ ግለ ሰብ ማመልከቱ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያላቸው… የማያስገዙ… የማይምሉ››
Psalms 24:5
እርሱ ከያህዌ ዘንድ በረከት ይቀበላል
‹‹እርሱ›› ሲል አንድ ግለ ሰብ ማመልከቱ አይደለም። ባለፈው ቁጥር የተጠቀሱትን ንጹሕ ልብ ያላቸውን እያመለከተ ነው። ‹‹በረከት›› የሚለውን የነገር ስም፣ ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ይባርካቸዋል››
ጽድቅን ከአዳኝ አምላኩ
‹‹ጽድቅ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹በጽድቅ›› በማለት መግለጽ ይቻላል። ‹‹አዳኝ›› የሚለውን፣ ‹‹መዳን›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር በጽድቅ ይፈርድለታል ደግሞም ያድነዋል››
እርሱን የሚፈልግ ትውልድ እንዲህ ነው።
‹‹ትውልድ›› ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱን የሚፈልጉ ሰዎች እንዲህ ናቸው››
እርሱን የሚፈልጉ፣ የያዕቆብን አምላክ ፊት የሚፈልጉ
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች የሚያመለክቱት ተመሳሳይ ነገር ነው። ሁለቱም የሚናገሩት እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ቤተ መቅደስ የሚሄዱትን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡ የእስራኤልን አምላክ የሚያመልኩ ናቸው››
እርሱን የሚፈልጉ
ያህዌን ለማምለክ ወደ ቤተ መቅደስ መሄድ እርሱን መፈለግ እንደሆነ ተነግሯል።
የያዕቆብ አምላክ ፊት
‹‹ፊት›› ሙሉውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያዕቆብን አምላክ››
Psalms 24:7
እናንተ ደጆቸ ቀና በሉ፤ እናንተም የዘላለም በሮች ብድግ በሉ
የሁለቱም ሐረጎች ትርጉም በጣም ተቀራራቢ ነው። ‹‹ደጆች›› እና፣ ‹‹በሮች›› የሚያመለክቱት የቤተ መቅደሱን ደጆች ነው። ጸሐፊው ደጆቹ ሰው እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። ደጆቹን የሚከፍት ጠባቂው ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንት የጥንት ደጆች ተከፈቱ›› ወይም፣ ‹‹እነዚህን የጥንት ደጆች ክፈቱ››
ራሳችሁን ቀና አድርጉ
እንደ፣ ‹‹ራስ›› ቀና የሚል የደጃፉ ክፍል ግልጽ አይደለም። ግን የሚወክለው ደጁን ሁሉ ነው።
ያህዌ ብርቱና ኀያል፣ ያህዌ በጦር ኀያል
ጸሐፊው ያህዌ ጦርነት የሚዋጋ ብርቱ ጦረኛ እንደሆነ ይናገራል።
Psalms 24:9
እናንት ደጆች ቀና በሉ፤ የዘላለም በሮች ብድግ በሉ
የሁለቱም ሐረጎች ትርጉም ተመሳሳይ ነው። ‹‹ደጆች›› እና፣ ‹‹በሮች›› የሚያመለክቱት የቤተ መቅደሱን ደጆች ነው። ጸሐፊው ደጆቹ ሰው እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። ደጆቹን የሚከፍት ጠባቂው ነው። መዝሙር 24፥7 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንት የዘላለም ደጆች ተከፈቱ›› ወይም፣ ‹‹እነዚህ የዘላለም ደጆችን ክፈቱ››
ራሳችሁን ቀና አድርጉ
ቀና የሚለው የደጃፉ ‹‹ራስ›› ግልጽ አይደለም። ሆኖም ደጃፉን ሁሉ ይወክላል።
ሴላ
እንዴት እንደሚዘምሩ ወይም ሙዚቃ እንደሚጫወቱ ለሰዎች የሚያመለክት ሙዚቃዊ አገላለጽ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል ይጽፋሉ፤ ሌሎች ግን ይተውታል። መዝሙር 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

---

Chapter 25
Psalms 25:1
አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።
ሕይወቴን አነሣለሁ
‹‹ሕይወቴን አነሣለሁ›› ምሳሌያዊ አባባል ነው። ይህም ማለት፣ 1) ጸሐፊው ራሱን ለያህዌ እየሰጠ ነው፤ ማለት ሙሉ በሙሉ በያህዌ ይታመናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራሴን ለአንተ እሰጣለሁ›› ወይም 2) የምስጋና ጸሎት ለያህዌ ማቅረቡ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አመልክሃለሁ፤ ከፍ አደርግሃለሁ››
አታሳፍረኝ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቼ እንዲያሳፍሩኝ አትተዋቸው››
በድል አድራጊነት በእኔ ላይ ደስ አይበላቸው
‹‹እኔን በማሸነፍ ደስ አይበላቸው›› - ‹‹በእኔ ላይ›› የሚለው ሐረግ ጠላቶቹ እንዳሸነፉትና በድል እንደ ቆሙ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔን በማሸነፍ ደስ አይበላቸው››
አንተን ተስፋ የሚያደርጉ አያፍሩም
‹‹አንተን ተስፋ የሚያደርጉ አይፈሩ›› በጠላት መሸነፍ እፍረት ያመጣል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተን ተስፋ የሚያደርጉን ጠላት አያሸንፋቸው››
አንተን ተስፋ የሚያደርጉ
‹‹የሚታመኑብህ››
ከሐዲዎች የሆኑ
‹‹አታላዮች›› ወይም፣ ‹‹የሚያጭበረብሩ››
ያለ ምክንያት
‹‹ምንም ምክንያት ሳይኖር››
Psalms 25:4
ያህዌ ሆይ፣ አካሄድህን አሳወቀኝ መንገድህንም አስተምረኝ
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ናቸው። እንዴት እንደሚኖር እግዚአብሔርን ሰውን ማስተማሩ እርሱን በትክክለኛው መንገድ መምራት ማለት እንደሆነ ተነግሯል።
አንተን ተስፋ አድርጌአለሁ
‹‹በአንተ ታምኛለሁ›› ወይም ‹‹አንተን በትዕግሥት እጠብቃለሁ››
በእውነትህ ምራኝ አስተምረኝም
መመራትና ማስተማር ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ መመሪያ መስጠት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለአንተ እውነት በመታዘዝ ሕይወቴን እንዴት እንደምመራ አስተምረኝ››
የመዳኔ አምላክ
‹‹መዳኔ›› የሚለውን ‹‹የምታድነኝ›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምታድነኝ››
Psalms 25:6
አስበኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እግዚአብሔር ይረሳል ማለት አይደለም። ጸሐፊው እግዚአብሔርን እየጠየቀ ያለው የርኅራኄና የታማኝነት ሥራውን እንዲያስብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አስታውስ›› ወይም፣ ‹‹አስብ››
የርኅራኄና የኪዳናዊ ታማኝነት ሥራህን
‹‹ርኅራኄ›› እና፣ ‹‹ታማኝነት›› የተሰኙትን የነገር ስሞች ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለኪዳንህ ርኅሩኅና ታማኝ መሆንህን››
እነርሱ ከጥንት የነበሩ ናቸውና
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› በማለት ሰውኛ የሚያደርገው የእግዚአብሔርን ርኅራኄና ኪዳናዊ ታማኝነት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ሁሌም እንደዚያ ነበርህ››
የልጅነቴን ኀጢአት አታስብብኝ
‹‹ኀጢአት›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ኀጢአቴን›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በልጅነቴ ጊዜ አንተ ላይ የፈጸምሁትን በደል››
መተላለፌንም
‹‹መተላለፌንም›› የሚለውን፣ ‹‹ዐመፃየንም›› ማለት ይቻላል። ‹‹አንተ ላይ የፈጸምሁትን ዐመፅ››
አስበኝ
ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እግዚአብሔር ይረሳል ማለት አይደለም። ጸሐፊው

እግዚአብሔርን እየጠየቀ ያለው እንዲያስበው ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አስበኝ›› ወይም፣ ‹‹አስብ››

እንደ ቸርነትህ ብዛት በኪዳናዊ ታማኝነትህ

‹‹ታማኝነት›› እና፣ ‹‹ቸርነት›› የሚለውን ትጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ አንተ ቸር ስለሆንህ በኪዳንህ ታማኝ ሁንልኝ››

Psalms 25:8

መንገድ… መንገዱ

እግዚአብሔር ከሰው የሚፈልገው አኗኗር እርሱ እንዲሄድ የሚፈልገው መንገድ እንደሆነ ተነግሯል።

ትሑት

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ትሑት ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ትሑት የሆኑ››

Psalms 25:10

የያህዌ መንገድ ሁሉ ቸርነትና እውነት ነው።

‹‹መንገድ›› የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከኪዳኑና ከታማኝነቱ የተነሣ ያህዌ ሁሌም ይወደናል››

በስምህ ምክንያት

‹‹በስምህ›› የሚለው የያህዌን ማንነት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በማንነትህ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች እንዲያከብሩህ››

ኀጢአቴ ታላቅ ነውና ይቅር በለኝ

‹‹ኀጢአት›› የሚለውን፣ ‹‹ያደረግሁት ኀጢአት›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያደረግሁት ኀጢአት ብዙ ስለሆነ ይቅር በለኝ››

Psalms 25:12

ያህዌን የሚፈራ ሰው ማን ነው?

ይህ ጥያቄ፣ ‹‹ያህዌን የሚፈራውን ሰው›› እንደ አዲስ ርዕሰ ጉዳይ ያስተዋውቃል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን ስለሚፈራ ሰው እነግራችኋለሁ››

የሚፈራ ሰው… ያስተምረዋል… በመረጠለት… ሕይወቱ… ዘሮቹ

ይህ የሚናገረው ስለ አንድ ሰው አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚፈሩ… ያስተምራቸዋል… በመረጠላቸው… ሕይወታቸው… ዘሮቻቸው››

በመረጠው መንገድ ጌታ ያስተምረዋል

እንዴት መኖር እንዳለበት ያህዌ ሰውን ማስተማሩ መሄድ የሚገባውን መንገድ ለእርሱ መምረጡ እንደሆነ ተነግሯል።

ሕይወቱን በተድላ በደስታ ያሳልፋል

‹‹እግዚአብሔር ያበለጽገዋል›› ወይም፣ ‹‹ጌታ ያበለጽጋቸዋል››

Psalms 25:14

የያህዌ ወዳጆች

‹‹ያህዌ… ወዳጅ ነው›› አንዳንዶች፣ ‹‹ያህዌ ምስጢሩን›› በማለት ተርጉመውታል። ምስጢሩን ለእነርሱ መናገሩ ምን ያህል የጠበቀ ወዳጃቸው መሆኑን ያመለክታል።

ዐይኖቼ ዘወትር ያህዌ ላይ ናቸው

‹‹ዐይኖች›› ማየትን ይወክላሉ። እንዲረዳው ያህዌን እንደሚያይ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲረዳኝ ሁሌም ያህዌን እመለከታለሁ›› ወይም ‹‹እንዲረዳኝ ሁሌም በያህዌ እታመናለሁ››

እግሮቼን ከመረብ ነጻ ያደርጋልና

መረብ ወጥመድ ነው። አደጋ ላይ ያሉ ሰዎች እግሮቻቸው በመረብ እንደ ተጠላለፉ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአደጋ ያወጣኛል››

ወደ እኔ ተመለስ

ያህዌ ትኩረቱን ሰው ላይ ማድረጉ ወደ እርሱ መመለስ እንደሆነ ተነግሯል።

Psalms 25:17

የልቤ መከራ በዝቶአል

‹‹ልብ›› የሰውን ስሜት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ከባድ ችግር ደርሶብኛል››

ከጭንቀቴ አውጣኝ

‹‹ከጭንቀቴ አድነኝ›› ይህ ጭንቀት ሰው ከውስጡ የሚወጣበት ነገር እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከጭንቀቴ ታደገን›› ወይም፣ ‹‹ከጭንቀቴ ፋታ ስጠኝ››

ጭንቀቴ

‹‹ጭንቀት›› የሚለው ቃል የነገር ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚያስጨንቁኝ ነገሮች›› ወይም፣ ‹‹የሚያስፈሩኝ ነገሮች››

መከራዬን ተመልከት

‹‹መከራዬን ልብ በል››

መከራዬ

‹‹መከራ›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያስጨነቀኝ ነገር›› ወይም፣ ‹‹ምን ያህል እንደ ተጐዳሁ››

ስቃዬ

‹‹ስቃይ›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያስቸገሩኝ ነገሮች››

አምርረው ጠሉኝ

‹‹በጣም ጠሉኝ›› ወይም፣ ‹‹አጥብቀው ጠሉኝ››

Psalms 25:20

አታሳፍረኝ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቼ እንዲያሳፍሩኝ አትተዋቸው››

ወደ አንተ እጠጋለሁ!

ለጥበቃ ወደ ያህዌ መሄድ ወደ እርሱ መጠጋት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥበቃ እንድታደርግልኝ ወደ አንተ እጠጋለሁ››

ታማኝነትና ቅንነት ይጠብቁኝ

‹‹ታማኝነት›› እና፣ ‹‹ቅንነት›› እንደ ሰው የሚጠብቁ ነገሮች እንደሆኑ ተነግሯል። እነዚህን የነገር ስሞች ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታማኝ መሆኔና ቅን የሆነውን ነገር ማድረጌ ይጠብቁኝ›› ወይም፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ ታማኝና ቅን ስለሆንሁ ጠብቀኝ››

ጠብቀኝ

‹‹አድነኝ››

Psalms 25:22

እስራኤልን ታደገው

‹‹እስራኤልን አድነው›› ‹‹ወይም እስራኤልን ዋጀው››

እስራኤልን… ከመከራዎቹ

እዚህ ላይ ‹‹እስራኤል›› የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤልን ሕዝብ… ከመከራዎቻችን››

---

Chapter 26

Psalms 26:1

አጠቃላይ መረጃ

ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

የዳዊት መዝሙር

ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው።

ተመላለስሁ

‹‹መመላለስ›› አኗኗርን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ኖርሁ››

በያህዌ

‹‹ያህዌን›› በተመለከተ በሦስተኛ ሰው ደረጃ የተነገረውን በሁለተኛ ሰው ደረጃ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአንተ››

ያለ መናወጥ

መጠራጠር ሚዛን መሳትና ወዲያ ወዲህ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያለ መጠራጠር››

ፈትነኝ

‹‹መርምረኝ››

ልቤንና የውስጤን ንጽሕና መርምር

እዚህ ላይ፣ ‹‹የውስጤ›› እና፣ ‹‹ልቤ›› ዝንባሌን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዝንባሌዬ መልካም መሆን አለመሆኑን መርምር››

ኪዳናዊ ታማኝነትህ በዐይኔ ፊት ነውና

እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐይን›› የሰውን ሐሳብና አንድን ነገር ዐይን ፊት ማድረግ ስለዚያ ነገር መገንዘብን ያመለክታል። ‹‹ታማኝነት›› የተሰኘውን የነገር ስም እንደ ቅጽል መተጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ሁልጊዜም ኪዳናዊ ታማኝነትህን አነዘባለሁ›› ወይም፣ ‹‹አንተ ለኪዳንህ ታማኝ መሆንህን ሁሌም አነዘባለሁ››

በታማኝነትህ ተመላለስሁ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

‹‹መመላለስ›› አኗኗርን ይወክላል። ‹‹ታማኝነት›› የተሰኘውን የነገር ስም እንደ ቅጽል መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕይወቴን እንደ አንተ ታማኝነት እኖራለሁ›› ወይም፣ ‹‹አሁን እንደምኖረው የምኖረው አንተ ታማኝ ስለሆንህ ነው››

Psalms 26:4

ከ… አልተባበርም

‹‹…ወዳጅ አልሆንም›› ወይም፣ ‹‹ከ… አልቀመጥም››

ከአታላይ ሰዎች

‹‹ሌሎችን ከሚያታልሉ››

ከክፉዎች ሸንጐ ጋር አልተባበርሁም

ይህም ማለት ከዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ጋር ተመሳሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሐሰተኞች ጋር አልተባበርሁም››

ሐሰተኞች ሰዎች

‹‹ግብዞች›› ወይም፣ ‹‹የሚዋሹ››

የክፉዎች ሸንጐ

‹‹ክፉ ለማድረግ የሚሰበሰቡ››

ዐመፀኞች

ይህ ቅጽል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐመፀኛ ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ዐመፅ የሚያደርጉ››

Psalms 26:6

እጆቼን በየዋህነት እታጠባለሁ

ይህ ምንም ኀጢአት ወይም በደል አለማድረግን ለማመልከት እጅ የመታጠብን ሥርዐት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

መሠዊያህን እዞራለሁ

ይህ እስራኤላውያን የለመዱት አምልኮ ነው።

የምትኖርበትን ቤት

ይህም ማለት፣ 1) ይህ የተጻፈው ከዳዊት ዘመን በኃላ ቢሆን ኖሮ፣ በኢየሩሳሌም ያለውን ቤተ መቅደስ ያመለክት ነበር። ወይም 2) ይህን የጻፈው ዳዊት ከሆነ እርሱን የሚያመልኩበትን ቦታ እንዲሠሩለት ለሕዝቡ የተናገረው ድንኳን ነው ማለት ነው።

ክብርህ የሚኖርበትን

‹‹ክብር›› የሚወክለው የእግዚአብሔርን ሐልዎትና ኀይል ሲሆን፣ በጣም ደማቅ ብርሃን ጋር ይመሳሰላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝብህ የሓልዎትህን ክቡር ብርሃን የሚያዩበትን ቦታ››

Psalms 26:9

ከኀጢአተኞች ጋር አታስወግደኝ

‹‹ማስወገድ›› መደምሰስ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከኀጢአተኞች ጋር አታጥፋኝ››

ወይም ሕይወቴን

‹‹አታስወግድ›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወይም ሕይወቴን አታስወግድ››

ደም ከጠማቸው ጋር

‹‹ደም የጠማቸው›› ሰው መግደል የሚፈልጉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሌሎችን ደም ማፍሰስ ደስ የሚላቸው›› ወይም፣ ‹‹ነፍሰ ገዳዮች››

በእጃቸው

‹‹እጅ›› መላውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የደም ሰዎች››

ሤራ

‹‹ክፉ ዕቅድ››

Psalms 26:11

እኔ ግን

ይህ ሐረግ ጸሐፊው ስለ ክፉ ሰዎች ከመናገር ስለ ራሱ ወደ መናገር መመለሱን ያመለክታል።

በተአማኒ ሕይወት እመላለሳለሁ

‹‹መመላለስ›› አኗኗርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በተአማኒ ሕይወት እኖራለሁ››

እግሮቼ ቆመዋል

‹‹እግሮች›› መላውን ሰው ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እቆማለሁ››

ደልዳላ ስፍራ

‹‹እግሮች›› መላውን ሰው ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እቆማለሁ››

ደልዳላ ስፍራ

‹‹ደልዳላ ስፍራ፣ 1) ደህና ቦታ ማለት ሊሆን ይችላል ወይም 2) መልካም ፀባይ ማለት ሊሆን ይችላል።

በጉባኤ ውስጥ ያህዌን እባርካለሁ

‹‹ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ስሰበሰብ አመሰግንሃለሁ››

---

Chapter 27

Psalms 27:1

አጠቃላይ መረጃ

ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

የዳዊት መዝሙር

ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው።

ያህዌ ብርሃኔ ነው

እዚህ ላይ ‹‹ብርሃን›› ሕይወትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የሕይወቴ ምንጭ ነው››

ማንን እፈራለሁ?

ጥያቄው ዳዊት የሚፈራው አለመኖሩን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንንም አልፈራም››

ያህዌ የሕይወቴ መጠጊያ ነው

ይህ ያህዌ ሰዎች የሚጠጉበት ቦታ እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሰላም እንድኖር የሚጠብቀኝ ያህዌ ነው››

የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?

ጥያቄው ዳዊትን የሚያስደነግጠው ነገር አለመኖሩን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚያስደነግጠኝ የለም››

Psalms 27:2

ሥጋዬን ለመብላት

አንድን ሰው ጨርሶ ማጥፋት የእርሱን ሥጋ መብላት እንደሆነ ተነግሯል። ቃል በቃል ሥጋውን ይበላሉ ማለት አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሊያጠፉኝ››

ባላጋራዎቼና ጠላቶቼ

ሁለቱም ቃሎች ተመሳሳይ ናቸው። እነዚህ ወደ እርሱ የቀረቡ ክፉ አድራጊዎች ናቸው።

ተሰናክለው ወደቁ

ይህ የሚያመለክተው የጸሐፊው ጠላቶች እርሱን የማጥፋት ዕቅዳቸው አለመሳካቱን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልተሳካላቸውም›› ወይም፣ ‹‹ፈረሰባቸው››

ሰራዊት ቢሰፍርብኝ እንኳ

‹‹ሰራዊት ቢከበኝ እንኳ›› ወይም ‹‹ሰራዊት ድንኳኑን በዙሪያየ ቢያደርግ እንኳ››

ልቤ አይፈራም

‹‹ልብ›› መላውን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልፈራም››

ጦርነት ቢነሣብኝ እንኳ

የጸሐፊው ጠላቶች ራሳቸው ጦርነት እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቼ ሊወጉኝ ቢመጡ እንኳ››

ልበ ሙሉ ነኝ

‹‹እግዚአብሔር እንደሚረዳኝ እተማመናለሁ››

Psalms 27:4

ያህዌን እጠይቀዋለሁ

‹‹ያንን እንዳገኝ ያህዌን እጠይቀዋለሁ››

እርሷን እሻለሁ

አጥብቆ አንድን ነገር የሚፈልግና ያንን እንዲሰጠው ዘወትር ያህዌን የሚለምን ሰው አንድን ነገር ማግኘት እንደሚፈልግ ሰው እንደሆነ ተነግሯል።

የያህዌን ውበት ለማየት

አስደናቂው የእግዚአብሔር ባሕርይ ውበት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እጅግ ድንቅ መሆኑን እንዳይ››

መቅደሱ ውስጥ እንዳሰላስል

ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ያህዌ ከእኔ የሚፈልገውን ለመጠየቅ›› ወይም 2) ‹‹መቅደሱ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ረጋ ብዬ እንዳስብ››

Psalms 27:5

በመከራ ቀን

‹‹በመከራ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹መከራ ሲደርስብኝ››



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንዲሰውረኝ
‹‹እንዲደብቀኝ››
መሸሸጊያው… ድንኳኑ
ሁለቱም የሚያመለክቱት ጸሐፊው እግዚአብሔርን የሚያመልክበትን መገናኛ ድንኳን ነው።
በድንኳኑ መሸፈኛ
‹‹መሸፈኛ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው መደበቂያና መሸሸጊያ ቦታ ነው።
በዐለት ላይ ያነሣኛል
እግዚአብሔር ጸሐፊውን ከጠላቶቹ ማዳኑ ጠላቶቹ የማይደርሱበት ከፍ ያለ ዐለት ላይ እንዳደረገው መሆኑ ተነግሯል።
ራሴ ከጠላቶቼ በላይ ከፍ ይላል
ይህ የሚያመለክተው ጠላቶቹን ሲያሸንፍ ጸሐፊው ያገኘውን ኩራት ወይም ክብር ነው። በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላቶቼን ሳሸንፍ ሰዎች ያከብሩኛል›› ወይም፣ ‹‹ጠላቶቼን እንዳሸንፍ በማድረግ እግዚአብሔር ያከብረኛል።››
Psalms 27:7
ያህዌ፣ ድምፄን ስማ
‹‹ድምፅ›› የሚናገር ወይም የሚጣራ ሰውን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ሰማኝ››
መልስልኝ
ይህ የሚያመለክተው ያህዌ የጸሐፊውን ጸሎት እንደሚሰማና የለመነውን እንደሚያደርግለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጸሎቴን መልስ›› ወይም፣ ‹‹የለመንሁህን አድርግልኝ››
ልቤ ይላል
‹‹ልብ›› የሰውን አእምሮና ሐሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በልቤ አልሁ›› ወይም፣ ‹‹ለራሴ አልሁ››
ፊቱን ፈልግሁ
ወደ ያህዌ ለመጸለይ ወደ ቤተ መቅደስ የሚሄድ ሰው ያህዌን ለመፈለግ እንደሚሄድ ሰው እንደሆነ ተነግሯል። እዚህ ላይ፣ ‹‹ፊት›› የእግዚአብሔርን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስህ እመጣለሁ››
ያህዌ ሆይ ፊትህን እሻለሁ
ወደ ያህዌ ለመጸለይ ወደ ቤተ መቅደስ የሚሄድ ሰው ያህዌን እንደሚፈልግ ተነግሯል። እዚህ ላይ ‹‹ፊት›› የእግዚአብሔርን ሁለንታ ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ወደ አንተ ለመጸለይ ወደ ቤተ መቅደስህ እመጣለሁ››
Psalms 27:9
ፊትህን ከእኔ አትሰውር
እዚህ ላይ፣ ‹‹ፊት›› የያህዌን ትኩረት ይወክላል፤ ፊትን መሰወር ችላ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ችላ አትበለኝ›› ወይም፣ ‹‹ለእኔ ማሰብህን አትተው››
ተቆጥተህ ከባርያህ ዘወር አትበል
ዳዊት ትሕትናውን ለማሳየት ራሱን፣ ‹‹ባርያህ›› ይላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አትቆጣኝ››
አትጣለኝ፤ አትተወኝ
‹‹መጣል›› እና፣ ‹‹መተው›› ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸው። ጸሐፊው እግዚአብሔር እንዲተወው እንደማይፈልግ አጥብቆ ይናገራል።
ወይም አትተወኝ
‹‹እኔን›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔን አትተወኝ››
ወይም፣ ‹‹እኔን አትጣለኝ››
የመዳኔ አምላክ
‹‹መዳኔ›› የሚለውን፣ ‹‹የምታድነኝ›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የምታድነኝ አምላክ›› ወይም፣ ‹‹የምታድነኝ አንተ ስለሆንህ››
አባትና እናቴ ቢተውኝ እንኳ
‹‹አባትና እናቴ የሚተውኝ ቢሆን እንኳ››፤ እንዲህ አድርገዋል ወይም ያደርጋሉ ማለቱ አይደለም። ዋናው ነጥብ ያንን ቢያደርጉ እንኳ እግዚአብሔር እንደማይተወው መናገሩ ነው።
ያህዌ ይቀበለኛል
‹‹ያህዌ ይጠብቀኛል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይጠነቀቅልኛል››
Psalms 27:11
መንገድህን አስተምረኝ
የሰው አኗኗር የሚሄድበት መንገድ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንድኖር የምትፈልገውን አስተምረኝ›› ወይም፣ ‹‹እንዳደርግ የምትፈልገውን አስተምረኝ››
በደልዳላ መንገድ ምራኝ
ያህዌ ጸሐፊውን ከጠላቶቹ መጠበቁ መሰናከል ወይም መውደቅ በማይችልበት መንገድ እርሱን መምራት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠብቀኝ››
ለጠላቶቼ ፍላጐት አሳልፈህ አትስጠኝ
ፍላጐት የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጠላቶቼ የሚፈልጉትን እንዲያደርጉብኝ አሳልፈህ አትስጠኝ››
ተነሥተውብኛል
እዚህ ላይ ‹‹መነሣት›› ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ከሳሾች ክስ ለማቅረብ ፍርድ ቤት ውስጥ ቆመዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ ላይ ክፉ ለመናገር ቆመዋል››
ዐመፅን ይረጫሉ
ዐመፅ የሚረጭ ነገር እንደሆነ እዚህ ላይ ተነግሯል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እኔ ላይ ክፉ ነገር እንደሚያደርጉ ይናገራሉ››
Psalms 27:13
እኔ ላይ ምን ይሆናል
ጥያቄውን በሌላ መልኩ ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንድ ክፉ ነገር ይደርስብኛል››
የያህዌን ቸርነት
‹‹ቸርነት›› የሚለውን እንደ ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ የሚያደርገው መልካም ነገር››
በሕያዋን ምድር
ይህ የሚያመለክተው በሕይወት መኖርን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በሕይወት እያለሁ››
ያህዌን ጠብቅ… ያህዌን ጠብቅ!
በዚህ ጥቅስ፣ 1) ጸሐፊው ለራሱ እየተናገረ ነው ወይም 2) ጸሐፊው ለሌሎች እየተናገረ ነው ወይም 3) ሌላ ሰው ለጸሐፊው እየተናገረ ሊሆን ይችላል።
ልብህ ይበርታ
‹‹ልብ›› መላውን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በርታ››
ያህዌን ጠብቀው!
የመዝሙሩ መደምደሚያ እንዲሆን ይህ ቃል መጨረሻ ላይ ተነግሯል።

---

Chapter 28
Psalms 28:3
አታርቀኝ
እግዚአብሔር ሰዎችን መቅጣቱ እነርሱን ማራቅ እንደሆነ ተነግሯል። በዚህ ምሳሌያዊ ቋንቋ ያህዌ ወደ እስር ቤት፣ ምርኮ ወይም ሞት እያራቃቸው እንደሆነ ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አታስወግደኝ››
ከባልንጀሮቻቸው ጋር ሰላም ከሚናገሩ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ባልንጀራ›› ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከሰዎች ጋር ሰላም ከሚናገሩ››
በልባቸው ተንኰል እያለ
‹‹ልብ›› የሰውን አእምሮና ሐሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ግን ስለ እነርሱ ክፉ ከሚያስቡ››
እንደ ተግባራቸው ስጣቸው… እንደ ክፋታቸው መጠን ክፈላቸው
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። በአንድነት የተነገሩት እግዚአብሔር ለቀጣቸው እንደሚገባ አጽንዖት ለመስጠት ነው።
እንደ እጃቸው ሥራ
‹‹እጅ›› ሰው የሚያደርገውን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እንዳደረጉት ነገር››
አጸፋውን መልስላቸው
‹‹የሚገባቸውን ስጣቸው››
አልተረዱምና… አይገነባቸውም
ይህም ማለት፣ 1) እግዚአብሔር ክፉዎች ላይ ስለሚያደርገው ነገር ዳዊት እርግጠኛ ነው ወይም 2) ዳዊት እግዚአብሔር ክፉዎችን እንዲያጠፋ እየለመነ ነው።
የያህዌን ሥራ አልተረዱምና


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

‹‹አልተረዱምና›› ሲል ችላ ብለዋል ወይም የያህዌን ሥራ ማክበር አልፈለጉም ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ያደረገውን በክብር አላዩምና››

የእጆቹን ሥራ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እጆች›› ያህዌ ያደረገውን ወይም የፈጠረውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ የፈጠረውን››

ያፈርሳቸዋል፤ መልሶም አይገነባቸውም

የክፉ ሰዎች መቀጣት እርሱ እግዚአብሔር የሚያፈርሰው ሕንፃ ወይም ከተማ እንደሆኑ ተነግሯል።

Psalms 28:6

የልመናዬን ድምፅ ሰምቷል

እዚህ ላይ፣ ‹‹ድምፅ›› ጸሐፊው የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱን ስለምን የተናገርሁትን ሰማ››

ያህዌ ብርታቴ ነው

‹‹ብርታት›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ብርቱ›› በማለት መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ብርቱ ያደርገኛል››

ጋሻዬ

ይህ የሚያመለክተው ያህዌ ጸሐፊውን ይጠብቀው እንደ ነበር ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ ይጠብቀኛል››

ልቤ ይታመናል

‹‹ልብ›› መላውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እታመናለሁ››

ተረዳሁ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ ረዳኝ››

ልቤ ሐሤት አደረገ

‹‹ልብ›› መላውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጣም ደስ አለኝ››

ያህዌ ለሕዝቡ ብርታታቸው ነው

‹‹ብርታት›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ብርቱ›› በማለት መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ሕዝቡን ብርቱ ያደርጋል››

ለቀባውም የመዳን ዐምባ ነው

ያህዌ ንጉሡን በሰላም መጠበቁ ያህዌ ንጉሡ ሄዶ የሚሸሸግበት ቦታ እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ ንጉሥ እንዲሆን የቀባውን በደህና ይጠብቀዋል››

ለቀባው

ይህ የሚያመለክተው ንጉሡን ነው።

Psalms 28:9

ርስትህ

ይህ የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔር ርስት እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንብረትህ›› ወይም፣ ‹‹የአንተ የሆኑት››

እረኛ ሁናቸው ለዘላለሙም ዐቅፈህ ያዛቸው

ጸሐፊው ያህዌ እረኛቸው ሕዝቡ ደግሞ በጐቹ እንደሆኑ ይናገራል። በጉ ርዳታ ወይም ጥበቃ ከፈለገ እረኛው ይሸከመዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንደ እረኛ ሆነህ ለዘላለሙ ጠብቃቸው››

---

Chapter 29

Psalms 29:1

አጠቃላይ መረጃ

ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።

የዳዊት መዝሙር

ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።

እናንት የእግዚአብሔር ልጆች

‹‹ልጆች›› የሚለው፣ ‹‹ባሕርዩ ያላችሁ›› እንደ ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እናንት ኀያላን››

ለያህዌ ክብርንና ብርታትን ስጡ

‹‹ክብር›› እና፣ ‹‹ብርታት›› የተሰኙትን የነገር ስሞች እንደ ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ የከበረና ብርቱ ስለሆነ ያህዌን አመስግኑ››

ለስሙ የሚገባውን ክብር ለያህዌ አምጡ

‹‹ክብር›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ወይም ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለስሙ እንደሚገባው ያህዌን አክብሩ›› ወይም፣ ‹‹ለስሙ እንደሚገባው ያህዌ ክቡር መሆኑን ተናገሩ››

ለስሙ የሚገባውን

‹‹ለስሙ›› የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ያህዌን ወይም ማንነቱን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለማንነቱ ተገቢ የሆነው››

ለያህዌ ዝቅ በሉ

ይህ ሕዝቡ ለአምልኮ ዝቅ ማለት እንዳለባቸው ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌን ለማምለክ ዝቅ በሉ››

በቅድስናው ግርማ

‹‹ቅድስና›› እና፣ ‹‹ግርማ›› የተሰኙትን የነገር ስሞች እንደ ቅጽል መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እርሱ የከበረ ውብና ቅዱስ በመሆኑ››

Psalms 29:3

አጠቃላይ መረጃ

መዝሙሩ የያህዌን ኀይልና ክብር ያሳያል።

የያህዌ ድምፅ በውሆች ላይ ይሰማል

የእግዚአብሔር ድምፅ ከሌሎች ጫጫታዎች ሁሉ ይልቅ ጮኽ ያለና ጥርት ያለ ነው። የውሆችን ድምፅ ከመሳሰሉ ሌሎች ድምፆች በላይ ከፍ ብሎ ይሰማል። ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ በሚናገርበት ጊዜ ድምፁ ከባሕር ድምፅ ይልቅ ጮኽ ብሎ ይሰማል››

በውሆች ላይ

ይህ ባሕሮችን ወይም ውቅያኖሶችን ያመለክታል። ማዕበሉ ሲነሣና ሲወድቅ እነዚህ ውሆች በጣም ከፍ ያለ ድምፅ ይኖራቸዋል።

የያህዌ ድምፅ

እዚህ ላይ ያለ፣ ‹‹ድምፅ›› ሁሉ የያህዌን ንግግር ይወክላል። ያህዌ ሲናገር ድምፁ ከፍ ያለ በመሆኑ በውሆች ላይ እንደሚሰማና ኀያል በመሆኑም ታላላቅ ዛፎችን እንደሚሰብር ጸሐፊው አጽንዖት ሰጥቶ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ሲናገር ድምፁ››

የክብር አምላክ አንጐዳጐደ

ይህ እግዚአብሔር ሲናገር ድምፁ እንደ መብረቅ ድምፅ እንደሆነ ያመለክታል። እንደ መብረቅ ድምፅ የያህዌም ድምፅ በጣም ከሩቅ ይሰማል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የክብር አምላክ ድምፅ እንደ መብረቅ ድምፅ ከፍ ያለ ነው›› ወይም፣ ‹‹ክቡር አምላኬ ሲናገር እንደ መብረቅ ያንጐዳጉዳል››

በብዙ ውሆች ላይ

‹‹በሰፊ ውሆች አካል ላይ››

Psalms 29:6

አያያዥ ዐረፍተ ነገር

ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ድምፅ ኀይል መናገር ቀጥሏል።

ሊባኖስን እንደ ጥጃ ያዘልለዋል

የሊባኖስ ምድር መናወጥ እንደሚዘልል ጥጃ ተደርጐ ተነግሯል። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ያህዌ ሲናገር የድምፁ ኀይል ምድሩን እንደሚያናውጥ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሊባኖስን ምድር እንደ ጥጃ ያዘልለዋል››

መዝለል

ወደ ፊትና ወደ ኃላ ቀለል ያለ ዝላይ

ሰርዮንንም እንደ ኮርማ

‹‹ያደርገዋል›› እና፣ ‹‹ያዘልለዋል›› የሚለው ከመጀመሪያው ሐረግ ውስጠ ታዋቂ ነው። እዚህ ላይ መደገም ይችላሉ። የሰርዮን ምድር መናወጥ እንደሚዘልል ኮርማ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰርዮንን እንደ ኮርማ ያዘልለዋል››

ሰርዮን

ይህ ሊባኖስ ውስጥ ያለ ተራራ ነው። የሄርሞን ተራራ ተብሎም ይጠራል።

የያህዌ ድምፅ የእሳት ነበልባል ይረጫል

እዚህ ያለ ‹‹ድምፅ›› ሁሉ የያህዌን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ሲናገር ሰማዩ ላይ መብረቅ እንደሚያበራ ያደርጋል››

የእሳት ነበልባል

ይህ የሚያመለክተው መብረቅን ነው።

Psalms 29:9

የያህዌ ድምፅ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ድምፅ›› የያህዌን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ሲናገር ድምፁ››



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ወርካዎችን ይወዘውዛል
‹‹ትልልቅ ዛፎች ይናወጣሉ››
ጫካዎችን ያራቁታል
የዛፎቹ ቅጠሎች መወገድ እነርሱን መመንጠር ወይም ልብስ ማስወለቅ እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቅጠሎቹ ከዛፎቹ ላይ እንዲረግፉ ያደርጋል።››
ያህዌ እንደ ንጉሥ ተቀምጧል
ይህ ያህዌ ይገዛል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ይገዛል›› ወይም፣
‹‹ያህዌ ንጉሥ ነው››
በጐርፍ ላይ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ጐርፍ›› ምድርን የሚሸፍን ውሃ ነው።
Psalms 29:11
ያህዌ ሕዝቡን በሰላም ይባርካል
‹‹ሰላም›› የሚለው ቃል የነገር ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱን በማበልጸግና በሰላም እንዲኖሩ በማድረግ ያህዌ ሕዝቡን ይባርካል››

---

Chapter 30
Psalms 30:1
አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው
በቤተ መቅደሱ ምረቃ ጊዜ የተዘመረ
‹‹ይህ መዝሙር የተዘመረው ቤተ መቅደሱ የተመረቀ ጊዜ ነበር››
የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት 1) መዝሙን የጻፈ ዳዊት ነበር፣ ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው።
አንሥተኸኛልና
እግዚአብሔር እርሱን መታደጉና ከሞት ማዳኑ እርሱን ከጥልቅ ጉድጓድ ማውጣት እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ታደግኸኝ››
ነፍሴን ከሲኦል አወጣት
‹‹ሲኦል›› የሞቱ ሰዎች የሚሄዱበት ስፍራ ስለሆነ ሞትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሞት አዳነኝ››
ነፍሴን አወጣት
‹‹ነፍሴ›› የሚለው የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አወጣኝ››
ወደ መቃብር ከመውረድ
‹‹መቃብር›› ሞትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከመሞት››
Psalms 30:4
ቅድስናውን ስታስታውሱ አመስግኑ
‹‹ቅድስና›› እና፣ ‹‹ማመስገን›› የተሰኙትን የነገር ስሞች፣ ‹‹ምስጋና›› እና፣ ‹‹ቅዱስ›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን አስታውሱ ስለዚህ አመስግኑ›› ወይም፣ ‹‹ቅዱስ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር ያደረገውን አስታውሱ፤ ስለዚህ አመስግኑት››
ቁጣው ለአጭር ጊዜ ነው
‹‹ቁጣው የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ነው›› ‹‹ቁጣ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹መቆጣት›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚቆጣው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው››
ለአጭር ጊዜ
‹‹ለአጭር ጊዜ›› ለጊዜው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለጊዜው››
ሞገሱ ግን ለሕይወት ዘመን ነው
‹‹ሞገስ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ቸርነት›› በሚል ቅጽል መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሕይወት ዘመናችን ሁሉ እርሱ ቸር ነው››
ለቅሶ ማታ ይመጣል፤ ደስታ ግን ጠዋት ይመጣል
ይህ፣ ‹‹ለቅሶ›› እና ‹‹ደስታ›› በተወሰነ ጊዜ የሚመጡ ነገሮች እንደሆነ ተነግሯል›› አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማታ እናለቅስ ይሆናል ጠዋት ግን ደስ ይለናል››
Psalms 30:6
ተረጋጋሁ
‹‹መረጋጋት›› የሚለው ቃል የነገር ስም ነው። ጸሐፊው የበለጸገበትንና ሁሌም መልካም የነበረበትን ጊዜ ያስታውሳል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በተረጋጋሁ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹የተረጋጋሁ በመሰለኝ ጊዜ››
አልናወጥም
‹‹መናወጥ›› መሸነፍን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም አያሸንፈኝም››
በሞገስህ
‹‹በሞገስህ›› የተሰኘውን የነገር ስም፣ ‹‹ሞገስ›› ወይም፣ ‹‹ቸርነት›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሞገስ ስለሆንኸኝ›› ወይም፣ ‹‹ለእኔ ቸር ስትሆን››
እንደ ብርቱ ተራራ አጸናኸኝ
ጸሐፊው የሚሰማውን ደህንነት ከብርቱ ተራራ ጋር አመሳስሎታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከፍ እንዳለ ተራራ ደህንነት እንዲሰማኝ አደረግህ››
ፊትህን በሰወርህ ጊዜ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔን መርዳት በተውህ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹ችላ ያልኸኝ ጊዜ››
ታወክሁ
‹‹ፈራሁ›› ወይም፣ ‹‹ተጨነቅሁ››
ከጌታዬ ሞገስ ፈለግሁ
‹‹ሞገስ ፈለግሁ›› የሚለው ርዳታ ለመንሁ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንድትረዳኝ ለመንሁ››
ከጌታዬ
ጸሐፊው ያህዌን በሦስተኛ ሰው ደረጃ ያመለክታል። በሁለተኛ ሰው ደረጃ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታዬ ሆይ፣ ከአንተ››
Psalms 30:9
በመሞቴና ወደ መቃብር በመውረዴ ምን ጥቅም ይገኛል?
ጸሐፊ ይህን ጥያቄ ያቀረበው የእርሱ መሞት ለእግዚአብሔር ጥቅም እንደሌለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብሞትና ወደ መቃብር ብወርድ ምንም ጥቅም የለም››
ዐፈር ያመሰግንሃልን? ታማኝነትህንስ ይናገራልን?
ጸሐፊው ይህን ጥያቄ ያቀረበው የእርሱ መሞትና መበስበስ እግዚአብሔርን እንደማያመሰግን አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐፈር በእርግጥ አያመሰግንህም፤ ታማኝ መሆንህንም ለሌሎች አይናገርም››
ዐፈር
ይህ የሚያመለክተው ሲሞት ዐፈር የሚሆነውን የጸሐፊውን ሰውነት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚበሰብስ አካሌ››
Psalms 30:11
ዋይታዬን ወደ ሽብሸባ ለወጥህልኝ
በጣም ደስ ሲላቸው ማሸብሸብ በአይሁድ ባሕል የተለመደ ነበር። ‹‹ዋይታ›› እና ‹‹ማሸብሸብ›› እንደ ግሥ ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዋይታዬን ትቼ ደስ ብሎኝ እንዳሸበሽብ አደረግህ››
ማቄን አስወገድህ
ማቅ ከዋይታና ከሐዘን ጋር የተያያዘ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ እንዳላዝን አደረግህ››
ደስታን አለበስኸኝ
ደስታ እንደ ልብስ የሚለበስ ነገር እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ደስ አሰኘኸኝ››
ክብሬ ምስጋናህን ይዘምራል
‹‹ክብሬ›› የሚለው የጸሐፊውን ነፍስ፣ ልብ ወይም ውስጣዊ ሰውነት ያመለክታል። ይህ ደስ ስላሰኘው እግዚአብሔርን እያመለከ ያለውን የጸሐፊውን ሙሉ ሰውነት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምስጋና እዘምርልሃለሁ››

---

Chapter 31
Psalms 31:1
አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።
ለመዘምራን አለቃ
‹‹ይህ በአምልኮ ጊዜ ለመዘምራን መሪ ነው››
የዳዊት መዝሙር


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው፡፡
ያህዌ ሆይ፣ በአንተ እሸሸጋለሁ
ጥበቃ እንዲደረግለት ወደ ያህዌ መሄድ እርሱ ውስጥ መሸሸግ እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንድትጠብቀኝ ያህዌ ሆይ፣ ወደ አንተ እሄዳለሁ››
አታሳፍረኝ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሌሎች እንዲያሳፍሩኝ አታድርግ››
መጠጊያ ዐለቴና የምታድነኝ ምሽግ ሁነኝ
‹‹መጠጊያ ዐለቴ›› ማለት ጥበቃ እንዲያገኝ መለመን ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው ሐረግ የመጀመሪያውን ሐረግ ያጠናክራል፡፡
መጠጊያ ዐለቴ
የሚያድን ታላቅ ዐለት እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔን እንደሚያድን ግዙፍ ዐለት››
የምታድነኝ ምሽግ
ያህዌ ጸሐፊው ከጠላቶቹ የሚድንበት ጠንካራ ምሽግ እንደሆነ ተነግሯል፡፡
Psalms 31:3
ዐለቴ
ያህዌ ጸሐፊውን ከጥቃት የሚያድን ግዙፍ ዐለት እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የምድንበት ግዙፍ ዐለት››
ምሽጌ
ያህዌ ጸሐፊው ከጠላቶቹ የሚድንበት ጠንካራ ምሽግ እንደሆነ ተነግሯል፡፡
ስለ ስምህ ስትል
‹‹ስም›› የሚወክለው ያህዌን ነው፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስምህ እንዲከበር›› ወይም፣ ‹‹እኔ እንዳመልክህ››
ምራኝ መንገዱን አመልክተኝ
‹‹ምራኝ›› እና፣ ‹‹አመልክተኝ›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ቢሆኑም፣ ያህዌ እንዲረዳው ያቀረበውን ልመና ያጠነክራል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንድሄድ ወደምትፈልገው ምራኝ››
ከሰወሩብኝ መረብ አወጣኝ
ጸሐፊው በተሰወረ መረብ እንደ ተያዘ ወፍ እንደሆነና ያህዌ ከወጥመዱ ነጻ እንዲያደርገው እንደሚጠብቅ ይናገራል፡፡
አንተ መጠጊያዬ ነህ
ያህዌ ሰዎች ጸሐፊውን እንዳያጠቁ የሚደበቅበት ቦታ እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተ ሁሌም ትጠብቀኛለህ›› ወይም፣ ‹‹ዘወትር ጥበቃ ታደርግልኛለህ››
Psalms 31:5
በእጆችህ
እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ እዚህ ላይ ግን እጅ እንዳሉት ተነግሯል፡፡ ‹‹እጆችህ›› የሚለው የያህዌን ጥበቃ ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹ለጥበቃህ››
መንፈሴን አሰጣለሁ
‹‹መንፈሴ›› የሚለው የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ራሴን አኖራለሁ››
የሚታመን አምላክ
‹‹አንተ የምታመንብህ አምላክ ነህ››
ከንቱ ጣዖቶች የሚያገለግሉትን ጠላሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ከንቱ›› የሚለው ጣዖቶችን ሁሉ ይመለከታል፡፡ ይህን በትርጒም ማብራራት ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጣዖቶች ከንቱ ናቸው፤ እነርሱን የሚያገለግሉትን ጠላሁ››
በኪዳናዊ ታማኝነትህ ደስ ይለኛል፤ ሐሤት አደርጋለሁ
‹‹ደስታ›› እና፣ ‹‹ሐሤት›› የተሰኙት ቃሎች ተመሳሳይ ትርጒም ቢኖራቸውም፣ የደስታውን ታላቅነት አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም እንደ ቅጽል መተርጐም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንተ ለኪዳንህ ታማኝ ስለሆንህ በጣም ደስ ይለኛል››
መከራዬን አይተሃል... የነፍሴንም ጭንቀት አውቀሃል
ሁለቱም ሐረጐች እግዚአብሔር የጸሐፊውን መከራ እንደሚያውቅ ያመለክታሉ፡፡
የነፍሴን ጭንቀት
‹‹ነፍሴ›› ጸሐፊውን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹‹‹ጭንቀቴን››
Psalms 31:8
እግሮቼን አቆምሃቸው
‹‹እግሮቼ›› ጸሐፊውን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አቆምኸኝ››
በሰፊ ቦታ
በዕብራይስጥ ሰፊ ቦታ ደህንነትንና ነጻነትን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ነጻ ወደምሆንበት ቦታ››
ጭንቀት ውስጥ ነኝ
‹‹ትልቅ መከራ ደርሶብኛል››
ነፍሴ እና ሥጋዬ
‹‹ነፍስ›› እና፣ ‹‹ሥጋ›› ሙሉውን ሰው ያመለክታሉ፡፡
Psalms 31:10
ሕይወቴ በመጨነቅ
‹‹ሕይወቴ›› ጸሐፊውን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጣም ደከምሁ››
በሐዘን... በመቃተት
‹‹በሐዘኔ ምክንያት... በመቃተቴ ምክንያት››
ዕድሜዬ በመቃተት
‹‹አለቀ›› የሚለው ቃል ባይጠቀስም በውስጠ ታዋቂነት ይታወቃል፡፡ ‹‹ዕድሜዬ በመቃተት አለቀ››
ጉልበቴ ከዳኝ
‹‹ጉልበቴ›› ጸሐፊውን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በጣም ደከምሁ››
ዐጥንቴ በውስጤ ሟሟ
‹‹ዐጥንት›› የጸሐፊን አካል ጤንነት ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጤና አጣሁ››
ሰዎች ይንቁኛል
‹‹ሰዎች ይሰድቡኛል››
የሚያገኙኝም ይሸሹኛል
‹‹በሁኔታዬ ይደነግጠቃሉ››
Psalms 31:12
እንደ ሞተ ሰው ተረሳሁ
ሰዎች ለሞተ ሰው አያስቡም፡፡ ጸሐፊው ሰዎች ስለ እርሱ እንደሚያስቡ አያስብም
እንደ ተሰበረ የሸክላ ዕቃ
ጸሐፊው ጨርሶ ከጥቅም ውጪ እንደሆነ ያስባል፡፡ ‹‹እንደ ተሰበረ የሸክላ ዕቃ ጥቅም የለሽ››
የብዙዎችን ሹክሹክታ
‹‹ብዙ›› የሚለው ሰዎችን ነው፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ብዙዎች ስለ እኔ ያወራሉ››
በዙሪያዬ አስፈሪ ወሬ
‹‹ከብዙ አቅጣጫዎች አስፈሪ ወሬ››
ሕይወቴን ለመውሰድ
ይህ ማለት መግደል ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሊገድሉኝ››
Psalms 31:14
ዘመኔ ያለው በእጅህ ነው
‹‹በእጅህ›› የያህዌን ኀይል ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የወደ ፊት ሕይወቴን ለመወሰን ኀይል አለህ››
ለሚያሳድዱኝ
‹‹ሊይዙኝ ለሚሞክሩ››
ባርያህ ላይ ፊትህን አብራ
ያህዌ ለእርሱ መልካም ነገር ማድረጉ እርሱ ላይ ፊቱን ማብራት እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለባርያህ መልካም አድርግ››
በኪዳናዊ ታማኝነትህ አድነኝ
‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም እንደ ቅጽል መተርጐም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለኪዳንህ ታማኝ በመሆንህ አድነኝ››
Psalms 31:17
አልፈር
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሌሎች እንዲያሳፍሩኝ አታድርግ››
ክፉዎች ይፈሩ
‹‹ክፉ ሰዎችን እግዚአብሔር እንዲያሳፍራቸው እፈልጋለሁ››
ክፉዎች
ይህ የሚመለከተው፣ ‹‹ክፉ ሰዎችን›› ነው፡፡
Psalms 31:19
በጐነትህ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህን ግሥ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ የምታደርገው መልካም ነው››
ያስቀመጥሃት
የያህዌ በጐነት እንደ አንዳች ነገር የሚቀመጥ እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ለሚያስፈልግ ጊዜ ያስቀመጥኸው››
ለሚፈሩህ
‹‹አንተን በጣም ለሚያከብሩ››
ወደ አንተ ለሚጠጉ
ጥበቃ ለማግኘት ወደ ያህዌ መሄድ ወደ እርሱ መጠጋት እንደሆነ ተነግሯል፡፡ መዝሙር 31፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥበቃ እንድታደርግላቸው ወደ አንተ ለሚመጡ››
በማደሪያህ ውስጥ ትሸሽጋቸዋለህ… በመጠለያህ ውስጥ ትደብቃቸዋለህ
ሁለቱም ሐረጐች እግዚአብሔር ይጠብቃቸዋል ማለት ናቸው፡፡
በመጠለያህ
የያህዌ ማደሪያ ጸሐፊው ደህንነት የሚያገኝበት ትልቅ ግንብ እንደሆነ ተነግሯል
በመጠለያህ ትደብቃቸዋለህ
እዚህ ላይ፣ ‹‹መጠለያ›› አደጋ የሌለበት ቦታ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አደጋ የሌለበት ቦታ ታዘጋጅላቸዋለህ››
ከአንደበት ጭቅጭቅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንደበት›› ጸሐፊው ላይ ክፉ የሚናገሩ ሰዎችን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቻቸው ክፉ መናገር የማይችሉበት››
Psalms 31:21
የሚያስደንቅ ኪዳናዊ ታማኝነቱን አሳየኝ
‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም እንደ ቅጽል መተርጐም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ለኪዳኑ ታማኝ መሆኑን በአስደናቂ ሁኔታ አሳየኝ››
ከዐይንህ ፊት ተወገግጃለሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከፊትህ አስወገድከኝ››
ከዐይንህ
ያህዌ፣ ‹‹በዐይኖቹ›› ተወክሏል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ››
የርዳታ ልመናዬን ሰማህ
‹‹ልመና›› የሚለውን ግሥ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለርዳታ ስለምን ሰማኸኝ››
Psalms 31:23
ታማኞች
ይህ የሚያመለክተው ታማኝ ሰዎችን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታማኝ የሆኑ ሰዎች››
ለእብሪተኞች የሚገባውን ይከፍላቸዋል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ይከፍላቸዋል›› ቅጣትን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለትዕቢተኞች የሚገባቸውን ቅጣት ሁሉ ይሰጣቸዋል››

---

Chapter 32
Psalms 32:1
አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው፡፡
የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው፡፡ ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል፡፡
ማስኪል
ይህ የአዘማመርን ስልት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፡፡
መተላለፉ ይቅር የተባለለት፣ ኀጢአቱም የተሸፈነለት
እነዚህ ሐረጐች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፡፡ በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር መተላለፉን ይቅር ያለው፣ ኀጢአቱንም የሸፈነለት››
ኀጢአቱ የተሸፈነለት
ይቅር የተባለ ኀጢአት ከእንግዲህ ማንም እንዳያየው የተሸፈነ እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀጢአቱ የታለፈለት›› ወይም፣ ‹‹ሆን ተብሎ ኀጢአቱ የተረሳለት››
ያህዌ በደሉን የማይቆጥርበት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንደ ንጹሕ የሚያየው›› ወይም፣ ‹‹በያህዌ ፊት በደለኛ ያልሆነ››
በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት
‹‹መንፈስ›› የሚያመለክተው ሰውየውን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሽንገላ የሌለበት›› ወይም፣ ‹‹ፍጹም ቅን የሆነ››
Psalms 32:3
ዐጥንቶቼ ተበላሹ
‹‹ዐጥንቶቼ›› የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እየተጐዳሁ ነው›› ወይም፣ ‹‹የበለጠ እየደከምሁ ነው››
ቀኑን ሙሉ
ይህም ማለት ‹‹ዘወትር›› ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁልጊዜ››
ቀንና ሌሊት
እነዚህ ሁለት ጽንፎች በመካከል ያለውን ሁሉ ይጨምራሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁልጊዜ››
እጅህ ከብዳኛለችና
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው፡፡ ይህ ሐረግ በሙሉ፣ ‹‹ጐዳኸኝ›› ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም አሰቃየኸኝ››
ኀይሌም የበጋ ድርቅ እንዳገኘው ተሟጠጠ
የዳዊት ኀይል በድርቅ ጊዜ እንደሚጠወልግ ትንሽ ለምለም ተክል ጋር ተመሳስሎአል፡፡
ሴላ
ይህ እዚህ ላይ እንዴት እንደሚዘምሩ ወይም የሙዚቃ መሣሪያ እንደሚጫወቱ የሚያመለክት ሙዚቃዊ አገላለጽ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል ይጽፋሉ ሌሎች ትርጉሞች ግን ትተውታል፡፡ መዝሙር 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት፡፡
በታላቅ ጭንቅ ጊዜ
‹‹በጣም በተጨነቁ ጊዜ››
ኀይለኛ ጐርፍ አካባቢውን ቢያጥለቀልቅም፣ እነርሱ አጠገብ አይደርስም
አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንደ ጐርፍ እንደሆኑ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ችግሮች እንደ ጐርፍ ሲመጡ እነዚህ ሰዎች ምንም አይሆኑም››
Psalms 32:7
አንተ መሸሸጊያዬ ነህ
ጸሐፊው ከጠላቶቹ ከደረሰበት ጥቃት ያህዌ መሸሸጊያ እንደሆነው ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ከጠላቶቼ የምደበቅበት ቦታ ነህ››
በድል ዝማሬ ትከበኛለህ
ምሳሌው የሚያመለክተው ያህዌ ለጸሐፊው ጥበቃ ማድረጉ የድል ዝማሬ እንዲያቀርብ ምክንያት እንደሆነው ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአንተ የተነሣ የድል ዝማሬ አቀርባለሁ››
ሴላ
ይህ እዚህ ላይ እንዴት እንደሚዘምሩ ወይም የሙዚቃ መሣሪያቸውን እንደሚጫወቱ ለሰዎች የሚናገር ሙዚቃዊ አገላለጽ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል ይጽፋሉ፤ ሌሎች ግን ይተውታል፡፡ መዝሙር 3፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት፡፡
አስተምርሃለሁ በምትሄድበት መንገድ አመራሃለሁ
‹‹ማስተማር›› እና፣ ‹‹መምራት›› ተመሳሳይ ነገሮች ቢሆኑም፣ ጠበቅ ያለ ትምህርትን ለማመልከት አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መንገዱን በተመለከተ ማንኛውንም ነገር አስተምርሃለሁ››
አስተምርለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› ሲል ያህዌ በቀጥታ ለዳዊት እየተናገረ ሊሆን ይችላል፡፡
በምትሄድበት መንገድ
በትክክለኛው መንገድ መኖር ጸሐፊው የሚሄድበት መንገድ እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕይወትህን እንዴት እንደምትኖር››
በዐይኔ እከታተልሃለሁ
‹‹ዐይኔ›› የሚለው የያህዌ ትኩረት ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ትኩረቴን አንተ ላይ አደርጋለሁ›› ወይም፣ ‹‹እጠብቅሃለሁ››
Psalms 32:9
ማስተዋል እንደሌላቸው… እንደ ፈረስ አትሁኑ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ጸሐፊው ማስተዋል የሌላቸውን ሰዎች ከፈረስና ከበቅሎ ጋር ያመሳስላቸዋል። ይህም ማለት፣ 1) ጸሐፊው ለአንባቢዎቹ የያህዌን ቃል እየተናገረ ነው፤ ‹‹ሁላችሁም ማስተዋል እንደሌላቸው… እንደ ፈረስ አትሁኑ›› ወይም 2) ለብዙዎች እንደሚናገር ያህዌ ለጸሐፊው እየተናገረ ነው።
በልጓብና በልጓም
ሁለቱም ነገሮች ፈረሶችና በቅሎዎች እንዲሄዱ ወደሚፈልጉት ቦታ ለመምራት የሚጠቀሙባቸው ናቸው።
እንዲሄዱ የምትፈልገው
‹‹ሰው ሁሉ እንዲሄዱ የሚፈልገው›› እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› ነጠላ ቁጥር ቢሆንም፣ አንድን ሰው ነጥሎ እየተናገረ አይደለም።
የያህዌ ኪዳናዊ ታማኝነት የሚታመነበትን ይከብበዋል
ያህዌ ለሰው ታማኝ መሆኑና እርሱንም መጠበቁ የያህዌ ኪዳናዊ ታማኝነት ያንን ሰው እየከበበው እንደሆነ ተነግሯል። ‹‹ታማኝነት›› የሚለው የነገር ስም እንደ ቅጽል ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ለኪዳኑ ታማኝ በመሆኑ፣ በእርሱ የታመነውን ይጠብቀዋል››
Psalms 32:11
በያህዌ ደስ ይበላችሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹በያህዌ›› ያህዌ ያደረገውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ባደረገው ደስ ይበላችሁ››
ጻድቃን ሆይ
ይህ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናንት ጻድቃን ሰዎች››
በደስታ እልል በሉ
‹‹ደስ እያላችሁ ጨኹ›› ወይም፣ ‹‹ከደስታ የተነሣ ጨኹ››
ቅን ልብ ያላችሁ
‹‹ልብ›› ሰውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቅን ልብ ያላችሁ ሰዎች››

---

Chapter 33
Psalms 33:1
አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።
በያህዌ ደስ ይበላችሁ
‹‹በያህዌ›› የሚለው ያህዌ ለእነርሱ ያደረገውን ያመለክታል። ‹‹ያህዌ ባደረገላችሁ ደስ ይበላችሁ››
ቅኖች ሊያመሰግኑት ይገባል
‹‹ያህዌን ማመስገን ለቅኖች የተገባ ነው››
Psalms 33:4
አጠቃላይ መረጃ
እያንዳንዱ ቁጥር በጣም ተመሳሳይ ትርጕም ያላቸው ሁለት መስመሮች አሉት።
የያህዌ ቃል የቀና ነው
‹‹የቀና›› የሚለው እውነተኛ የሆነ ነገርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ ሁሌም አደርጋለሁ ያለውን ያደርጋል››
ጽድቅንና ፍትሕን ይወድዳል
እነዚህን የነገር ስሞች በተግባር መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጽድቅና እውነት የሆነውን ነገር ማድረግ ይወድዳል›› ወይም፣ ‹‹ጽድቅና እውነት የሆነውን ነገር የሚያደርጉትን ይወድዳል››
ምድር በያህዌ ኪዳናዊ ታማኝነት ተሞልታለች
በዓለም ማንኛውም ቦታ ያሉ ሰዎች የያህዌን ኪዳናዊ ታማኝነት ማስረጃ ማየት መቻላቸው ኪዳናዊ ታማኝነቱ ምድርን እንደ ሞላ ተነግሯል። ‹‹ኪዳናዊ ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም እንደ ቅጽል መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በምድር የትኛውም ቦታ ያሉ ሰዎች ያህዌ ለኪዳኑ ታማኝ መሆኑን ማየት ይችላሉ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ለኪዳኑ ታማኝ ስለ መሆኑ በምድር ሁሉ ማስረጃ አለ››
በያህዌ ቃል ሰማያት ተሠሩ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በቃሉ አማካይነት ያህዌ ሰማያትን ሠራ››
በአፉ እስትንፋስ
ይህ የሚያመለክተው የያህዌን ቃል ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በቃሉ››
Psalms 33:7
አጠቃላይ መረጃ
እያንዳንዱ ቁጥር በጣም ተመሳሳይ ትርጕም ያላቸው ሁለት መስመሮች ይዘአል።
እንደ ክምር
‹‹ግድብ ውስጥ እንዳለ›› ጸሐፊው ስለ ባሕር መፈጠር ሲናገር ያህዌ ውሆችን በክምር እንዳደረገ ይናገራል።
ውቅያኖሱን በአንድ ስፍራ ያከማቻል
ጸሐፊው ስለ ውቅያኖስ መፈጠር ሲናገር እግዚአብሔር በአንድ ስፍራ እንዳከማቸው ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰው እህልን በጐተራ እንደሚያከማች እርሱም ውቅያኖስን በአንድ ስፍራ አከማቸ››
ምድር ሁሉ
ይህ መላው ምድርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በምድር ያለ ሁሉ››
በፊቱ በፍርሃት ይቁም
‹‹በፍርሃት ይቁም›› ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያክብሩት››
በቦታቸው ሆኑ
‹‹በቦታቸው ሆኑ›› ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ‹‹ተፈጠሩ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹መሆን ጀመሩ››
Psalms 33:10
አጠቃላይ መረጃ
እያንዳንዱ ቁጥር በጣም የሚመሳሰሉ ትርጕሞች ያሏቸው ሁለት መስመሮች ይዞአል።
ያህዌ ያጨናግፋል
‹‹ያህዌ ያጠፋል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይሰብራል››
የሕዝቦች ወገን
‹‹ሕዝቦች›› የእነዚህ አገሮችን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የተለያዩ ሕዝቦች ወገን››
ኅብረት
ኅብረት በጦርነት ጊዜ አብረው የጋራ ጠላት እንዲወጉ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው።
የሕዝቦች ምክክር
‹‹የሰዎች ፍላጐት›› አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሰዎች ክፉ ምክክር››
ለዘላለም ይጸናል
‹‹ይጸናል›› ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ‹‹ይኖራል›› ማለት ነው።
ለትውልዶች ሁሉ የልቡ ሐሳብ
‹‹ይጸናል›› የሚለው ቃል ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የልቡም ሐሳብ ለትውልዶች ሁሉ ይጸናል››
የልቡም ሐሳብ
‹‹ልብ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የእርሱ ሐሳብ››
ለትውልዶች ሁሉ
‹‹ወደ ፊት ለሚኖሩ ትውልዶች ሁሉ›› ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ‹‹ለዘላለም›› ማለት ነው።
ሕዝብ የተባረከ ነው
‹‹ሕዝብ›› ሲል ሰዎችን ሁሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰዎች የተባረኩ ናቸው››
ያህዌ አምላኩ የሆነ
‹‹ያህዌን የሚያመልክ››
እንደ ራሱ ርስት
እዚህ በተገለጸው መሠረት የእርሱ ርስት የሆኑ ይመስል ሕዝቡ ያህዌን እንዲያመልኩ ተመርጠዋል።
Psalms 33:13
ወደ ታች ይመለከታል
ያህዌ የሚኖርበት ቦታ ከሰዎች መኖሪያ በላይ እንደሆነ ተነግሯል።
የሁሉንም ልብ የሠራ
‹‹ልብ›› የእነዚህን ሰዎች አስተሳሰብ ያመለክታል። እርሱ የሸክላውን ዕቃ ቅርጽ የሚያስይዝ ሸክላ ሠሪ ይመስል ያህዌ የሕዝቡን አስተሳሰብ እንደሚመራ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሸክላ ሠሪ ዕቃውን ቅርጽ እንደሚያስይዝ አስተሳሰባቸውን የሚመራ››
Psalms 33:16


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ንጉሥ በሰራዊቱ ብዛት አይድንም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሥን የሚያድነው የሰራዊቱ ብዛት አይደለም››
በፈረስ ጉልበት ድል አደርጋለሁ ማለት አይቻልም
‹‹ፈረስ›› የአንድን ሰራዊት ብርቱ ክፍል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠንካራ ፈረሰኞች ያሉት ሰራዊት ባለቤት መሆን ደህንነት ለመኖሩ ማረጋገጫ አይደለም››
Psalms 33:18
እነሆ
ይህ ቃል የሚያመለክተው በዚህ መዝሙር አዲስ ዐቢይ ሐሳብ መጀመሩን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹ስሙ›› ወይም፣ ‹‹የምነግራችሁን ልብ በሉ››
የያህዌ ዐይኖች
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐይኖች›› የያህዌን ትኩረት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያህዌ ትኩረት››
በኪዳኑ ታማኝነት የሚተማመኑ
‹‹የሚተማመኑ›› የሚለው ቃል፣ ‹‹የሚጠብቁ›› ወይም ‹‹ተስፋ የሚያደርጉ›› ማለት ነው። ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ከኪዳኑ የተነሣ በታማኝነት እንዲያደርግላቸው የሚጠብቁት››
ሕይወታቸውን ከሞት ለማዳን
‹‹ሕይወታቸውን›› የሚለው የሚያመለክተው ሕዝቡን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሞት እንዲያድናቸው››
Psalms 33:20
ያህዌን እንጠባበቃለን
‹‹መጠባበቅ›› መተማመን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ እንታመናለን›› ወይም፣ ‹‹ያህዌን ተስፋ እናደርጋለን››
እርሱ ረዳታችን፣ ጋሻችንም ነው
እዚህ ላይ ያህዌ ሰራዊትን ከጥቃት የሚከልል ጋሻ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ረዳታችንና እንደ ጋሻ የሚከልለን ነው››
ልባችን ደስ ይለዋል
‹‹ልብ›› የሚያመለክተው ሕዝቡን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ደስ ይለናል››
በቅዱስ ስሙ
‹‹ቅዱስ ስሙ›› የያህዌን ቅዱስ ባሕርይ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቅዱስ ባሕርዩ›› ወይም፣ ‹‹እርሱ ቅዱስ ስለሆነ በእርሱ››
Psalms 33:22
ያህዌ ሆይ፣ የኪዳን ታማኝነትህ ከእኛ ጋር ይሁን
ያህዌ ለሕዝቡ ታማኝ መሆኑ የኪዳኑ ታማኝነት ከእነርሱ ጋር እንደ ሆነ ተናግሯል። ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ሆይ፣ ከኪዳንህ የተነሣ አንተ ሁሌም ታማኝ ሁንልን››
ተስፋችንን በአንተ ላይ አድርገናል
‹‹አንተ እንደምትረዳን ተስፋ አለን››

---

Chapter 34
Psalms 34:1
አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።
የዳዊት መዝሙር
ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።
እንደ እብድ ሆኖ
‹‹እብድ በመምሰል››
አቢሜሌክ ፊት
ይህ የሚናገረው አይሁዳውያን በሚገባ የሚያውቁትን ታሪክ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አቢሜሌክ ቤት በነበረ ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹የአቢሜሌክ እስረኛ ሳለ››
ተባርሮ በወጣ ጊዜ
‹‹በግድ የወጣ ጊዜ››
ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው
እዚህ ላይ፣ ‹‹በአፌ›› የሚለው ዳዊት ለያህዌ ሲናገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዘወትር አመሰግነዋለሁ››
Psalms 34:2
የተጨቆኑ
ይህ የሚያመለክተው የተጨቆኑ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተጨቆኑ ሰዎች››
ያህዌን ከእኔ ጋር አመስግኑ
‹‹አመስግኑ›› የሚለው ግሥ ሕዝቡን ማዘዝ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው ሁሉ ከእኔ ጋር ያህዌን ያመስግን››
ስሙን ከፍ አድርጉ
‹‹ከፍ አድርጉ›› ማለት ያህዌን አክብሩት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታላቅነቱን ለሰዎች ተናገሩ››
ስሙ
‹‹ስሙ›› የያህዌን ባሕርይ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባሕርዩ››
Psalms 34:4
ያህዌን ፈለግሁት
‹‹ፈለግሁት›› የሚለው ዳዊት ያህዌ እንዲረዳው መለመኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ ያህዌ ጸለይሁ›› ወይም፣ ‹‹እንዲረዳኝ ያህዌን ለመንሁ››
ወደ እርሱ የሚመለከቱ
‹‹መመልከት›› ከእርሱ ርዳታ መለመንን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲረዳቸው ወደ እርሱ የሚመለከቱ›› ወይም፣ ‹‹ከእርሱ ብቻ ርዳታ የሚጠብቁ››
ያበራሉ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ደስ ይላቸዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ደስ ይላቸዋል››
ፊታቸውም አያፍርም
‹‹ፊታቸው›› ወደ ያህዌ የሚመለከቱ ሰዎችን ያመለክታል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አያፍሩም›› ወይም፣ ‹‹ይኮራሉ››
ይህ ችግረኛ
ዳዊት ራሱን እንደ ችግረኛ ይቆጥራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተቸግሬ ነበር››
ያህዌ ሰማው
‹‹ሰማኝ›› ያህዌ ረዳኝ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ረዳው››
Psalms 34:7
በዙሪያቸው ይሰፍራል
የእግዚአብሔር መልአክ ሰዎችን ለመጠበቅ በዙሪያቸው እንደሚሰፍር በዳዊት ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሊጠብቃቸው››
ያህዌ መልካም መሆኑን ቀምሳችሁ እዩ
የያህዌ መልካምነት ተቀምሶ እንደሚታይ ነገር እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልካም መሆኑን በሕይወታችሁ እዩ››
ወደ እርሱ በሚጠጉ
ያህዌ ሕዝቡ ከጠላቶቻቸው ለመዳን የሚደበቁበት ቦታ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲጠብቃችሁ በእርሱ የሚተማመኑ››
የሚፈሩ አንዳች አያጡም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚፈሩት የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ይኖራቸዋል››
Psalms 34:10
ምንም አያጡም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚያስፈልጋቸው መልካም ነገር ሁሉ ይኖራቸዋል››
ልጆቼ
እዚህ ላይ የጸሐፊውን ልጆች ሳይሆን፣ ስለ ያህዌ የሚያስተምራቸውን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተማሪዎቼ››
Psalms 34:12
መልካምን እንዲያይ ሕይወትን የሚፈልግና ረጅም ዘመን መኖር የሚፈልግ ማን ነው?
ለዚህ ጥያቄ መልሱ፣ ‹‹ሰው ሁሉ›› የሚል ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው ሁሉ ሕይወትንና ረጅም ዕድሜ መኖርን እንዲሁም መልካምን ነገር ማየትን ይፈልጋል››
አንደበትህን ከክፉ ጠብቅ… ከንፈሮችህን ሐሰት ከመናገር ከልክል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ነገር ማለት ቢሆኑም ለአስፈላጊነቱ አጽንዖት ለመስጠት በሁለት የተለያዩ መንገዶች ቀርቧል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አንደበትህን ከክፉ ጠብቅ
‹‹አንደበት›› መላውን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ አትናገር››
ከንፈሮችህን ሐሰት ከመናገር ከልክል
‹‹ከንፈር›› የሚናገረውን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሐሰት አትናገር››
ከክፉ ሽሽ
‹‹ሽሽ›› ከክፉ ራቅ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ አታድርግ››
ሰላምን እሻ
‹‹እሻ›› ስለ ሰላም አስብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሰዎች ጋር በሰላም ለመኖር አጥብቀህ ፈልግ››
Psalms 34:15
የያህዌ ዐይኖች ወደ ጻድቃን ናቸው
‹‹የያህዌ ዐይኖች›› በጥንቃቄ መጠበቁን ያመለክታል። ‹‹ጻድቃን›› ጻድቅ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ጻድቅ ሰዎችን በጥንቃቄ ይጠብቃል››
ጆሮዎቹም ለጩኸታቸው ክፍት ናቸው
ያህዌ፣ ‹‹በጆሮዎቹ›› ተወክሏል። ለአንድ ነገር ክፍት መሆን ለዚያ ነገር ትኩረት መስጠትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለጩኸታቸው ትኩረት ይሰጣል›› ወይም፣ ‹‹ለጩኸታቸው መልስ ይሰጣል››
መታሰቢያቸውን ከምድር ይቆርጣል
ልክ በቢላ ተቆርጦ የተጣለ ይመስል እነርሱ ሲሞቱ ያህዌ መታሰቢያቸውን ጨርሶ ያጠፋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሲሞቱ ሰዎች ጨርሶ ይረሷቸዋል››
ያህዌ ይሰማል
‹‹ይሰማል›› ማለት ምላሽ ይሰጣቸዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ትኩረት ይሰጣቸዋል››
Psalms 34:18
ያህዌ ቅርብ ነው
‹‹ቅርብ›› ማለት ‹‹ለመርዳት ዝግጁ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ዘወትር ለመርዳት ዝግጁ ነው››
ልባቸው የተሰበረ
ይህ ልባቸው የተሰበረ ሰዎችን የማያመለክት አነጋገር ነው። ጥልቅ ሐዘን የሰውን ልብ መሰበር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ያዘኑ ሰዎች››
መንፈሳቸው የደቀቀ
በጣም ተስፋ የቆረጡ ሰዎች መንፈሳቸው የደቀቀ ሰዎች እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ተስፋ የቆረጡ ሰዎች››
ጻድቃን
ይህ የሚያመለክተው ጻድቅ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጻድቅ ሰዎች››
ዐጥንቱን ሁሉ ይጠብቃል፤ ከእነርሱ አንዱ እንኳ አይሰበርም
‹‹ዐጥንቱ ሁሉ›› ቃል በቃል ቢሆንም፣ ያህዌ መላውን ሰው እንደሚጠብቅም ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ፈጽሞ ይጠብቀዋል፤ በምንም መንገድ ጉዳት አያገኘውም››
Psalms 34:21
ክፋት ክፉውን ይገድላል
ክፋት ሰውን መግደል የሚችል ሰው እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የክፉ ሰዎች ሥራ እነርሱን ይገድላቸዋል››
ክፉዎች
ይህ የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው።
ጻድቃንን የሚጠሉ ይፈረድባቸዋል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጻድቃንን በሚጠሉ ላይ ያህዌ ይፈርድባቸዋል››
ጻድቃን
ይህ የሚያመለክተው ጻድቅ ሰዎችን ነው።
ወደ እርሱ የሚጠጉ አይፈረድባቸውም
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። ቀጥተኛ በሆነ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እርሱ የሚጠጉትን ሁሉ ያህዌ ይቅር ይላቸዋል››
ወደ እርሱ የሚጠጉ
ጥበቃ ለማግኘት ወደ ያህዌ መሄድ ወደ እርሱ መጠጋት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥበቃ ለማግኘት ወደ እርሱ መሄድ››

---

Chapter 35
Psalms 35:1
አጠቃላይ መረጃ
ተጓዳኝ ሐሳብ በዕብራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው።
የዳዊት መዝሙር
ይህም 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።
ትንሹንና ትልቁን ጋሻህን ያዝ... ጦርህንና ጭሬህን ምዘዝ
ይህ ሐረግ እግዚአብሔር ለጦርነት የተዘጋጀ ጦረኛ እንደሆነ ያመለክታል
Psalms 35:4
ሕይወቴን የሚሹ ይፈሩ ይዋረዱ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔን ለመጉዳት የሚያቅዱትን ያህዌ ይመልሳቸው ግራ ያጋባቸው››
ወደ ኃላ ይመለሱ
‹‹ወደ ኃላ መመለስ›› ዕቅድን ለመፈጸም አለመቻልን የሚያሳይ ምሳሌ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አይሳካላቸው››
ግራ ይጋቡ
‹‹የሚያደርጉ ይጥፋቸው››
በነፋስ ፊት እንዳለ እብቅ
የጸሐፊው ጠላቶች በቀላሉ እንደሚበንን ነፋስ ፊት እንዳለ እብቅ እንደ ሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ እብቅ ነፋስ ያብንናቸው››
በመንገዳቸው
‹‹መንገዳቸው›› ሕይወታቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕይወታቸው››
ጨለማና ድጥ
ይህ ድብቅና አደገኛ መንገድን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድብቅና አደጋ የሞላበት››
ያሳድዳቸው
ይህ የሚያመለክተው የያህዌ መልአክ የጸሐፊው ጠላቶችን መቃወም ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱ ላይ ይነሣ›› ወይም፣ ‹‹እነርሱን ይቃወም››
Psalms 35:7
መረብ አኑረውብኛል
የክፉዎች አድማ ጸሐፊውን ለማጥመድ መረብ መጣል እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ትንሽ እንስሳ በመረብ ሊይዙኝ ፈልገዋል››
ለሕይወቴ ጉድጓድ ቆፍረዋል
የክፉዎች አድማ ጸሐፊውን ለማጥመድ ጉድጓድ መቆፈር እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ትልቅ እንስሳ ሊይዙኝ ጉድጓድ ቆፍረዋል።
ሕይወቴን
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔን››
ጥፋት በድንገት ይምጣባቸው
ጥፋት በድንገት የሚያጠቃ አደገኛ አውሬ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በድንገት ይጥፉ›› ወይም፣ ‹‹በድንገት ስታጠፋቸው ይደነቁ››
ያስቀመጡት መረብ
የክፉዎች ሤራ ጸሐፊውን ለመያዝ ያስቀመጡት መረብ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ እንስሳ እኔን ለመያዝና ለመጉዳት ያስቀመጡት መረብ››
በውስጡ ይውደቁ
ይህ ቁጥር 7 ላይ እንዳለው ምሳሌያው አነጋገር ነው። መረቡ ጸሐፊውን ለመያዝ የታሰበ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእኔ የቆፈሩት ጉድጓድ ውስጥ ይውደቁ››
ውስጡ ይውደቁ
ይህም ማለት፣ 1) ቁጥር 7 ላይ ያለው ጉድጓድ ውስጥ ይውደቁ ወይም 2) ጥፋት ውስጥ ይወደቁ
ለጥፋታቸው
‹‹ጥፋት›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲጠፉ›› ወይም፣ ‹‹አንተ የምታጠፋቸው እንደዚያ ነው››
Psalms 35:9
በማዳኑ
‹‹ማዳን›› የሚለውን የነገር ስም እንደ ግሥ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ስላዳንኸኝ››
ዐጥንቶቼ ሁሉ
‹‹ዐጥንት›› የሰውየውን ጥልቅ ውስጣዊ ማንነት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

‹‹ጠቅላላ ውስጣዊ ማንነቴ››
ያህዌ እንደ አንተ ማን አለ… ሊቀሟቸው ከሚሞክሩ?
የዚህ ጥያቄ መልስ እንደ ያህዌ ማንም የለም የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንደ አንተ ማንም የለም ሊቀሟቸው ከሚሞክሩ››
ድኾችና ችግረኞች
‹‹ድኾች›› እና፣ ‹‹ችግረኞች›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ቢሆኑም፣ አጽንዖት የተሰጠው ርዳታውን የሚፈልጉትን ብዙዎች ያህዌ እንደሚያድናቸው ነው።
Psalms 35:11
ተነሡ
ይህ ፍርድ ቤት መመስከርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለመመስከር ፈቃደኛ የሆነ››
ለመልካም ክፉ ከፈሉኝ
ይህ ማለት ለተቀበሉት መልካም ነገር ለውጥ ክፉ የሚመልሱ ሰዎችን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ላደረግሁላቸው መልካም ክፉ አደረጉብኝ››
ክፉ… መልካም
እነዚህን የነገር ስሞች በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ነገሮች… መልካም ነገሮች››
አዝኛለሁ
‹‹በጣም አዝኛለሁ››
Psalms 35:13
እነርሱን ባመማቸው ጊዜ
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው፣ ‹‹ክፉ ምስክሮችን ነው›› (መዝሙር 35፥11)
ማቅ ለበስሁ
‹‹ማዘኔን አሳየሁ››
ራሴን ዝቅ አደረግሁ
ይህ የጸሎት ምሳሌ ነው። ‹‹ራሴን ለጸሎት ዝቅ አደረግሁ››
ለወንድሜ እንደማዝን ሆንሁ
ጸሐፊው የራሱ ወንድም የሞተ ያህል አዝኗል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የገዛ ወንድሜ የታመመ ያህል አዘንሁ››
ለእናቴ እንደማለቅስ አንገቴን ደፋሁ
ጸሐፊው የራሱ እናት የሞተች ያህል አልቅሷል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናቴ የሞተች ያህል አለቀሰሁ››
አንገቴን ደፋሁ
ይህ የሕመምና የመከራ ምልክት ነው።
Psalms 35:15
ተሰበሰቡ
‹‹በአንድነት ተሰባሰቡ›› ወይም ‹‹ተገናኙ››
እኔ ላይ
ይህ ማለት ጸሐፊውን ለማጥቃት በአንድነት ተሰባሰቡ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ላይ ተማከሩ›› ወይም፣ ‹‹ሊያጠፉኝ ለመማከር››
ቦጫጨቁኝ
ጸሐፊው ጨርቅ ይመስል ቆራርጠው ቦጫጨቁት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉዎች አጠቁኝ››
እንደ ምናምንቴዎች አፌዙብኝ
‹‹ከከንቱ ሰዎች ጋር አብረው አፌዙብኝ›› ወይም 2) ‹‹ያለ አንዳች አክብሮት ቀለደብኝ››
ጥርሳቸውን በቁጣ አፏጩብኝ
ይህ የቁጣና የጥላቻ ምልክት ነው። ‹‹እኔ ላይ ጥርሳቸውን የማፏጨት ድምፅ አሰሙ››
Psalms 35:17
እስከ መቼ ዝም ብለህ ታያለህ?
ይህ ጥያቄ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ዝም ብሎ ማየቱን ትቶ እርሱን መርዳት እንዲጀምር መፈለጉን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲህ ሲያደርጉ ዝም ብለህ የምታያቸው እስከ መቼ ነው?›› ወይም፣ ‹‹የምትረዳኝ መቼ ነው?
ነፍሴን ታደጋት
‹‹ነፍስ›› ጸሐፊውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታደገኝ››
ሕይወቴን ከአንበሶች
‹‹አድን›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕይወቴን ከአንበሶች አድን››
ሕይወቴን
ይህ ጸሐፊውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔን››
ከአንበሶች
ጸሐፊው ጠላቶቹ አደገኛ አንበሶች እንደሆኑ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ዱር አራዊት ከሚያጠቁኝ ጠላቶቼ››
Psalms 35:19
ከውሸታም ጠላቶቼ
‹‹እኔ ላይ ሐሰት እንዲናገሩ ጠላቶቼን አትተዋቸው››
ክፉ ሤራቸው
‹‹ክፉ ዕቅዳቸው››
ሰላም አይናገሩም
‹‹ሰላም›› የሚለውን ቃል ‹‹ሰላማዊ›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሰዎች ሰላማዊ ቃል አይናገሩም››
ክፉ ቃሎች ይሸርባሉ
‹‹ሐሰት መናገር ይፈልጋሉ››
በሰላም በሚኖሩት
‹‹ሰላም›› የሚለውን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሌሎች ጋር ሰላማዊ ሆኖ መኖር›› ወይም፣ ‹‹ማንንም ሳይጐዱ››
Psalms 35:21
አፋቸውን አስፍተው የከፈቱት ጸሐፊውን ለመክሰስ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣
‹‹እኔን ለመክሰስ ጮኹብኝ››
አሃ፣ አሃ
ይህ አንድነ ነገር በድንገት ሲታይ ወይም ግልጽ ሲሆን የሚባል ቃለ አጋኖ ነው፤ ለሚከተለው ዐረፍተ ነገር አጽንዖት ይሰጣል።
በዐይናችን ዐየነው
‹‹ዐይናችን›› የሚያመለክተው የጠላቶቹን ዐይን ነው። እንዲህ ያሉት ጸሐፊው አንዳች መጥፎ ነገር ሲያደርግ ስላዩ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐየነው›› ወይም ያደረግኸውን መጥፎ ነገር ዐየን››
አንተ አይተሃልና
‹‹ያየው›› የጸሐፊው ጠላቶችን ሐሰተኛ ክስ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሐሰት እየከሰሱኝ እንደሆነ ዐየህ››
ዝም አትበል
‹‹ያደረጉትን ቸል አትበል›› ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባደረጉት መሠረት ፍረድባቸው››
ከእኔ አትራቅ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እኔ ቅረብ››
ተነሥ፣ ንቃ
እንዲህ ማለት እግዚአብሔር ተኝቶአል ማለት አይደለም። ጸሐፊው እግዚአብሔር ጣልቃ እንዲገባ ይፈልጋል። ሁለቱም ቃሎች ተመሳሳይ ቢሆኑም የልመናውን አጣዳፊነት አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ያንቀላፋህ ይመስለኛል! ንቃ››
ልትከራከርልኝ
‹‹መከራከር›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ተከራከር›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእኔ ተከራከር››
ነገሬን
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእኔ››
Psalms 35:24
በእኔ ላይ ደስ አይበላቸው
‹‹በእኔ መከራ ደስ አይበላቸው››
በልባቸውም አይበሉ
ይህ ለራስ መናገርን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለራሳቸው አይበሉ››
አሃ
ይህ አንድ ነገር በድንገት ሲደረግ ወይም መግለጽ ሲያቅት የሚባል ቃለ አጋኖ ነው። ለሚከተለው ነገር አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አዎን››
የፈለግነውን አገኘን
ይህ የሚያመለክተው የጸሐፊው ጠላቶች በደለኛ እንዲባል ፈልገው እንደ ነበር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ፈለግነው በደለኛ ተባለ››
ዋጥነው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የጸሐፊው ጠላቶች የእርሱን ውድቀት እንደ ዱር እንስሳት እርሱን እንደበሉት ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨርሶ ዋጥነው›› ወይም፣ ‹‹አጠፋነው››

በጭንቀቴ ደስ የሚላቸው ይፈሩ፣ ግራም ይጋቡ

‹‹የእኔ መጨነቅ ደስ የሚላቸው ይፈሩ ግራ ይጋቡ››

ይፈሩ

‹‹እፍረት ይከናነቡ››

ግራ ይጋቡ

‹‹የሚያደርጉት ይጥፋቸው›› ወይም፣ ‹‹ይዋረዱ››

ራሳቸውን ከፍ የሚያደርጉብኝ እፍረትና ውርደት ይከናነቡ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ላይ ከፍ ማለት የሚፈለጉትን አንተ እፍረትና ውርደት አከናንባቸው››

እኔ ላይ ከፍ ማለት የሚፈልጉ

‹‹ከእኔ የበለጠ እንደሆኑ የሚቆጥሩ›› ወይም፣ ‹‹እኔ ላይ ክፉ የማድረግ መብት እንዳላቸው የሚያስቡ››

እፍረትና ውርደት ይከናነቡ

እፍረትና ውርደት እንደ ልብስ እንደሆኑ ተነግሯል፡፡ እነዚህን የነገር ስሞች እንደ ግሥ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይፈሩ ይዋረዱ››

እፍረት ውርደት

እነዚህ ቃሎች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ቢሆንም፣ ጥቅም ላይ የዋሉት ወርደታቸው የከፋ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡

Psalms 35:27

ፍረድልኝ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ፍረድ›› ሲል ዘማሪው ንጹሕ መሆኑን ያህዌ እንዲፈርድለት መፈለጉን ያመለክታል፡፡

ዘወትር እንዲህ ይበሉ

‹‹ሁሌም እንዲህ ይበሉ››

ያህዌ ይመስገን

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን እናመስግን››

በእርሱ ደስ ይበላቸው

‹‹ደስ የሚላቸው›› ወይም፣ ‹‹ደስ ያላቸው››

ሰላም

ደህንነት፣ ደስታ

ጽድቅህን ይናገራል

‹‹ጽድቅ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ትክክል›› ማለት ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሥራህ ትክክል መሆኑን ይናገሩ››

---

Chapter 36

Psalms 36:1

አጠቃላይ መረጃ

ተጓዳኝ ሐሳብ በዕራይስጥ ቅኔ የተለመደ ነው፡፡

ለመዘምራን አለቃ

‹‹ይህ የመዝሙር መሪው በአምልኮ የሚጠቀምበት ነው››

የያህዌ ባርያ የዳዊት መዝሙር

ይህም ማለት፣ 1) መዝሙሩን የጻፈ ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት አዘማመር ስልት ነው ማለት ሊሆን ይችላል፡፡

ክፉ ሰው

ይህ በአጠቃላይ ስለ ክፉ ሰዎች እንጂ፣ ስለ አንድ ሰው የተነገረ አይደለም፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ሰዎች››

በጥልቅ ልቡ

‹‹ልብ›› የሰውን ጥልቅ ማንነት ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከጥልቅ ልቦናው››

በዐይኑ ፊት

‹‹ዐይኑ›› ክፉውን ሰው ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእርሱ ዘንድ››

እንዲህ በማሰብ ራሱን ያጽናናል

‹‹ይህን ማመን ይመርጣል›› ወይም፣ ‹‹እንዲህ ማሰብ ይፈልጋል››

ኀጢአቱ የሚታወቅና የሚጠላ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ኀጢአቱን የሚያውቅና የሚጠላ››

Psalms 36:3

ቃሎቹ

‹‹እርሱ የሚለው››

በጎ ማድረግ

‹‹መልካም ነገር ማድረግ››

በክፉ መንገድ ይሄዳል

የሰው ክፉ ሥራ በክፉ መንገድ መሄድ እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ነገር ያደርጋል››

ክፋትን አያርቅም

‹‹ክፋት›› የሚለውን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ተግባርን አይንቅም››

Psalms 36:5

የኪዳን ታማኝነትህ… ወደ ሰማያት ይደርሳል

የእግዚአብሔር ኪዳን ታማኝነት ወደ ሰማይ የሚደርስ አንዳች ነገር እንደሆነ ተነግሯል፡፡ ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኪዳን ታማኝነትህ… በጣም ትልቅ ነው›› ወይም፣ ‹‹ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል አንተም… ለኪዳንህ ታማኝ ነህ››

ወደ ደመናት ይደርሳል

የእግዚአብሔር ታማኝነት ትልቅነት በጣም ከፍ ያለ እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ደመናት ከፍ ያለ ነው›› ወይም፣ ‹‹እጅግ ታላቅ ነው››

እንደ የእግዚአብሔር ተራሮች… እንደ ታላቁ ጥልቅ

የእግዚአብሔር ጽድቅና ፍርድ ታላቅነት በጣም ከፍ ያለና የጠለቀ መሆኑን ይህ ሐረግ ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ተራሮች ከፍ ያለ… እንደ ባሕር የጠለቀ››

የጠበቅኸው

‹‹የረዳኸው›› ወይም፣ ‹‹ያዳንኸው››

Psalms 36:7

የኪዳን ታማኘነትህ ምንኛ የከበረ ነው

‹‹የከበረ›› የሚለው ጸሐፊው የያህዌን ኪዳን ታማኝነት ምን ያህል ታላቅ ዋጋ እንደሚሰጠው ያመለክታል›› ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን የነገር ስም በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለኪዳንህ ታማኝ መሆንህን ታላቅ ዋጋ እሰጣለሁ››

በቤትህ ሙላት ደስ ይላቸዋል፡፡

ቤት ውስጥ በእንግድነት መመገብ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን ሁሉ መስጠት እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ስለምትሰጣቸው ሁሉም አላቸው›› ወይም፣ ‹‹ብዙ የምትሰጠው አለህ፤ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ታዘጋጅላቸዋለህ››

ከደስታህ ወንዝ እንዲጠጡ አደረግህ

እዚህ ላይ ሁለት ምሳሌያዊ ገለጻዎች ቀርበዋል፡፡ የእግዚአብሔር በረከት ሙላት ወንዝ ውስጥ እንደሚፈስስ ውሃ እንደሆነ ተነግሯል፡፡ እነዚህን በረከቶች የሚቀበሉ እንደ ውሃ እየጠጧቸው እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የከበሩ በረከቶችህ እንደሚጠጡት የወንዝ ውሃ ነው››

የሕይወት ምንጭ

‹‹የሕይወት መገኛ››

በብርሃንህ ብርሃን እናያለን

‹‹ብርሃን›› የእውነተኛ ዕውቀት ምሳሌ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ስታበራልን እውነትን እናውቃለን›› ወይም፣ ‹‹ስለ አንተ እውነቱን ማወቅ የሚስችለን የአንተ ብርሃን ነው››

Psalms 36:10

አንተን ለሚያውቁ የኪዳንህን ታማኝነት በሙላት ይድረሳቸው

ያህዌ ዘወትር ለሕዝቡ ታማኝ መሆኑን ወደ እነርሱ እስኪደርስ የሚረዝም ነገር እንደሆነ ጸሐፊው ይናገራል፡፡ ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሚያውቁህ በታማኝነት ፍረድላቸው››

ልባቸው ለቀና መከታ ሁንላቸው

‹‹መከታ›› የሚለውን እንደ ግሥ ማድረግ ይቻላል፡፡ ካለፈው ሐረግ፣ ‹‹ዘወትር›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልባቸው የቀናውን ዘወትር መከታ ሁንላቸው››



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ልባቸው የቀና
‹‹ልብ›› ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቅኖች›› ወይም፣ ‹‹በጽድቅ የሚኖሩ ሰዎች››
የእብሪተኛ እግር… የክፉ ሰው እጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እግር›› እና፣ ‹‹እጅ›› ክፉ ሰዎችን ያመለክታሉ። እነዚህ ክፉ ሰዎችን በአጠቃላይ እንጂ፣ የተወሰኑ ሰዎችን ብቻ የሚመለከቱ አይደሉም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እብሪተኛ ሰዎች… ክፉ ሰዎች››
አያሳድደኝ
‹‹አያባርረኝ›› ወይም፣ ‹‹ስፍራዬን እንድተው አያድርገኝ››
ክፉ አድራጊዎች ወድቀዋል፤ ተፈጥፍጠዋል መነሣትም አይችሉም
ሦስቱም ሐረጐች የሚያመለክቱት የተሸነፉትን ክፉ አድራጊዎች ነው
ተፈጥፍጠዋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፈጥፍጠሃቸዋል›› ወይም፣ ‹‹አጥፍተሃቸዋል››
መነሣትም አይችሉም
‹‹ከእንግዲህ አይነሡም››

Chapter 37
Psalms 37:1
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚመለከተው ዳዊትን ነው ወይም 3) መዝሙሩ የዳዊትን መዝሙሮች ዘይቤ የተከተለ ነው የሚሉት ናቸው።
በክፉ አድራጊዎች ምክንያት አትበሳጭ
“አመፀኞች ሰዎች እንዲያናድዱህ አትፍቀድላቸው” ወይም “አመፀኞች ሰዎች በሚያደርጉት ነገር አሳብ አይግባህ”
እንደ ሣር ይደርቃሉ … እንደ አረንጓዴ ተክሎች ይጠወልጋሉ
ክፉ አድራጊዎች በሞቃት የአየር ጠባይ እንደሚደርቅና እንደሚሞት ሣርና ተክል ተደርገው ተነግረዋል። የእነዚህ የሁለቱም ማነጻጸሪያዎች ትርጉም ይሞታሉ የሚል ነው። አ.ት: “ይሞታሉ” ወይም “ፍጻሜአቸው ይሆናል” (See: Simile and Parallelism)
Psalms 37:3
በታማኝነት ተሰማራ
ታማኝነት በመልካም መሰማሪያ የሚያሳድጉት እንስሳ በሚመስል መልኩ ተነግሮለታል። አ.ት: “ታማኝነትን ተመገብ” ወይም “ታማኝነትህን አብዛ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የልብህን ፍላጎት
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው የሰውየውን ውስጣዊ ማንነትና አሳብ ነው። አ.ት: “ጥልቅ የሆነ ውስጣዊ ፍላጎትህን” ወይም “እጅግ የምትፈልጋቸውን ነገሮች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 37:5
መንገድህን ለእግዚአብሔር ስጥ
እዚህ ጋ “መንገድህን ስጥ” የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን እግዚአብሔር ሕይወትህን እንዲቆጣጠር ጠይቀው ማለት ነው። አ.ት: “እግዚአብሔር አኗኗርህን እንዲመራ ጠይቀው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ስለ አንተ ሆኖ ያደርጋል
ይህ በሕግ ጉዳዮች ሌላውን ሰው መወከል ነው። እዚህ ጋ፣ አንድ ሰው በእግዚአብሔር በሚታመንበት ጊዜ እርሱ ለዚያ ሰው ተከላካይ ይሆናል፣ ፍትሕ እንዲያገኝም ያደርጋል። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እንደ ቀን ብርሃን … ቀትሩም እንደ ቀን
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚሉት ስለ አንድ ነገር ነው። (See: Parallelism)
እንደ ቀን ብርሃን
ይህ “ሁሉም በሚያየው ሁኔታ” ማለት ነው። አ.ት: “እንደ ቀን ብርሃን በግልጽ የሚታይ” (See: Simile)
ቀትሩም እንደ ቀን
ይህ “የቀትር ፀሐይ እንደሚታይ” ማለት ነው። አ.ት: “በቀን ውስጥ ብርሃኑ ብሩህ ሆኖ እንደሚታይ” (See: Simile)
Psalms 37:7
ጸጥ በል
“ዝም በል”
Psalms 37:8
ይቆረጣሉ
የአመፀኛው መጥፋት ተቆርጦ እንደሚጣል የተክል ቅርንጫፍ ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን
“በእግዚአብሔር የሚታመኑ ግን”
ምድሪቱን ይወርሳሉ
ምድሪቱን መውረስ ርስትን እንደ መቀበል ሆኖ ተነግሯል። አ.ት: “ምድሪቱን እንደ ራሳቸው ንብረት አድርገው ይቀበላሉ” ወይም “በምድሪቱ ላይ በሰላም እንዲኖሩ ይፈቀድላቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይጠፋሉ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ የክፉውን ሰው ሞት ያመለክታል። አ.ት: “ይሞታል፣ ዳግመኛም አታየውም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 37:11
የዋሁ
ይህ የሚያመለክተው የዋህ የሆኑትን ሰዎች ነው። አ.ት: “የዋህ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ምድሪቱን ይወርሳል
ምድሪቱን መውረስ ርስትን እንደ መቀበል ሆኖ ተነግሯል። ይህንን በመዝሙር 37፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አ.ት: “ምድሪቱን እንደ ራሳቸው ንብረት አድርገው ይቀበላሉ” ወይም “በምድሪቱ ላይ በሰላም እንዲኖሩ ይፈቀድላቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ክፉው ሰው
ይህ አንድን የተለየን ሰው አያመለክትም። የሚያመለክተው በአጠቃላይ ክፉ ሰዎችን ነው። አ.ት: “ክፉው ሰውዬ” (See: Generic Noun Phrases)
ጻድቃን
ይህ አንድን የተለየን ሕዝብ አያመለክትም። የሚያመለክተው ጻድቅ የሆኑ ሕዝቦችን ነው። አ.ት: “ጻድቁ ሰውዬ” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ጥርሱን ያፋጫል
ክፉው ሰው ጻድቁን እጅግ ይጠላዋል፣ ንዴቱን ለማሳየትም ጥርሶቹን ያፋጫል። (See: Symbolic Language)
ቀኑ ቀርቧል
“ቀኑ” የፍርድ ቀን እንደሚሆን ያመለክታል። አ.ት: “እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የሚፈርድበትና የሚቀጣበት ቀን ቀርቧል” ወይም “እግዚአብሔር በክፉው ሰው ላይ የሚፈርድበትና የሚቀጣበት ቀን ቀርቧል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Psalms 37:14
ክፉው
ይህ ክፉዎቹን ሰዎች ያመለክታል። አ.ት: “ክፉዎቹ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ሰይፋቸውን መዘዋል … ቀስታቸውን ገትረዋል
“ሰይፍ” እና “ቀስት” ሁለቱም ሰዎችን ለማጥቃት ጥቅም ላይ የሚውሉ የጦር መሣሪያዎች ናቸው። “መዘዋል” እና “ገትረዋል” የሚሉት የእርግጠኝነት ቃላት ውጊያውን ለመጀመር ዝግጁ ናቸው ማለት ነው። (See: Synecdoche)
ለመጣል
የእነዚህ ችግረኞች ጥፋት፣ መሬት ላይ ሲጣል ስብርብሩ እንደሚወጣ ሸክላ ማሰሮ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት: “ለማጥፋት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የተጨቆኑና የተቸገሩ
እነዚህ ሁለቱም ቃላት የሚያመለክቱት ራሳቸውን ለመከላከል አቅም የሌላቸውን ሰዎች ነው። አ.ት: “ሊቋቋሟቸው የማይችሏቸው ሰዎች” (See: Doublet)
ሰይፋቸው የገዛ ልባቸውን ይወጋል
ሰይፍ የጦር መሣሪያዎች ምሳሌ ሲሆን “ልብ” የሚወክለው ሕዝቡን ነው። “ልብን መውጋት” በአነጋገር ዘይቤ “መግደል” የሚል ትርጉም አለው። አ.ት: “ሰይፋቸው በራሳቸው ላይ ይመለሳል፣ ራሳቸውንም ይገድላሉ” (Synecdoche እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 37:16


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከብዙ ክፉ ሰዎች ሀብት ይልቅ ለጻድቁ ያለው ትንሹ ይሻላል
“ከብዙ ብልጽግና ጋር ክፉ ከመሆን ጻድቅ ሆኖ ድኻ መሆን ይሻላል”
ለጻድቁ ያለው ትንሹ ይሻላል
“ትንሹ” የሚለው ስማዊ ቅጽል የሚያመለክተው ጥቂት ሀብትን ነው። “ጻድቁ” የሚለው ስማዊ ቅጽል የሚያመለክተው ደግሞ ጻድቁን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “ጻድቅ ሰው ያለው ጥቂት ሀብት ይሻላል” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ብዙ
ይህ የሚያመለክተው የክፉ ሰዎችን ብልጽግና ነው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
የክፉ ሰዎች ክንድ ይሰበራል
እዚህ ጋ “ክንድ” የሚወክለው የክፉ ሰዎችን ኃይል ነው። ክንዳቸውን መሰበር ሥልጣናቸውን መውሰድን ይወክላል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር የክፉ ሰዎችን ብርታት ያስወግዳል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 37:18
ነቀፋ የሌለባቸውን ይመለከታል
“መመልከት” አንድን ሰው መጠበቅ ማለት ነው። እዚህ ጋ “ነቀፋ የሌለባቸው” የሚያመለክተው የማይነቀፉትን ሰዎች ነው። ኢ.ት፡ “ነቀፋ የሌለባቸውን ሰዎች ይጠብቃል” (የአነጋገር ዘይቤ እና ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ዕለት በዕለት
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም “ባለማቋረጥ” የሚል ነው። ኢ.ት፡ “በየቀኑ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ቀኖቹ ክፉዎች በሚሆኑበት ጊዜ
ይህ ሐረግ እንደ ረሃብ ያለውን ጥፋት ያመለክታል። ኢ.ት፡ “መቅሰፍት በሚሆንበት ጊዜ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 37:20
የእግዚአብሔር ጠላቶች እንደ ሳር ክብር ይሆናሉ
ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ጠላቶች መስክ ላይ ከሚያብቡ አበባዎች ጋር ያነጻጽራቸዋል። (See: Simile)
በእሳት ይቃጠላሉ፣ በነኑውም ይጠፋሉ
ጸሐፊው የክፉዎችን መጥፋት ከመከር በኋላ በሚቃጠል አረም ወይም መስክ ላይ ጠውልገው ባሉ አበቦች መስሎ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እሳት የመስኩን አረም ወደ ብናኝነት እንደሚቀይረው እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ለጋስ ነው፣ ይሰጣልም
የሁለቱም ትርጉም አንድ ሲሆን አጽንዖት የሚሰጡት ስለ ጻድቁ ልግስና ነው። (See: Doublet)
Psalms 37:22
እነዚያ በእግዚአብሔር የተባረኩ ምድርን ይወርሳሉ፤ በእርሱ የተረገሙት እነዚያ ይቆረጣሉ
ይህ የሁለት ተመሳሳይ አሳቦች ንጽጽር ነው። እነዚያ በእግዚአብሔር የተባረኩት በእግዚአብሔር ከተረገሙት ጋር ተነጻጽረዋል። (See: Parallelism)
እነዚያ በእግዚአብሔር የተባረኩ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እነዚያ እግዚአብሔር የሚባርካቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ምድርን ይወርሳሉ
ምድርን መውረስ ርስትን እንደ መቀበል ሆኖ ተነግሯል። ይህንን በመዝሙር 37፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ምድሪቱን እንደ ግል ንብረታቸው አድርገው ይቀበላሉ” ወይም “ምድሪቱ ላይ በሰላም እንዲኖሩ ይፈቀድላቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እነዚያ በእርሱ የተረገሙት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እነዚያ እግዚአብሔር የሚረግማቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ይቆረጣሉ
የአመፀኛው መጥፋት ተቆርጦ እንደሚጣል የተክል ቅርንጫፍ ሆኖ ተነግሯል። ይህንን በመዝሙር 37፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የሰው አካሄድ የሚጸናው በእግዚአብሔር ነው ... በእግዚአብሔር ፊት ይመሰገናል
እነዚህ የአስተሳሰቡን ተገቢነት በሚያሳዩበትና ተደራጊ አንቀጹን በሚያብራሩበት ሁኔታ ሊነገሩ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት በሚመሰገንበት ሁኔታ ከኖረ እግዚአብሔር አካሄዱን ያጸናለታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የሰው አካሄድ የሚጸናው በእግዚአብሔር ነው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ስኬታማ እንዲሆን የሚያስችለው እግዚአብሔር ነው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
አንድ ሰው ... ሰውየው
ይህ ሰዎችን በአጠቃላይ እንጂ አንድን የተለየን ሰው አያመለክትም። (See: Generic Noun Phrases)
የሰው አካሄድ
አካሄድ የሚወክለው የአንድን ሰው አኗኗር ነው። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው የሚኖርበት አኗኗር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቢደናቀፍም አይወድቅም
እዚህ ጋ “መደናቀፍ” እና “መውደቅ” የሚያመለክቱት ሰውየው በአስቸጋሪ ጊዜ የሚኖረውን ምላሽ ነው። ኢ.ት፡ “አስቸጋሪ ጊዜዎች ቢገጥሙትም ፈጽሞ አይወድቅም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእጁ ይይዘዋል
እዚህ ጋ “በእጁ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ሲሆን “ይይዘዋል” የሚያመለክተው የሚያደርግለትን ጥበቃ ነው። ኢ.ት፡ “በኃይሉ ይጠብቀዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 37:25
ጻድቁ ሰው ተረስቷል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ጻድቁን ሰው ረስቶታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ጻድቁ ሰው
ይህ አጠቃላይ ንግግር እንጂ አንድን የተለየን ሰው አያመለክትም። (See: Generic Noun Phrases)
እንጀራ ሲለምን
እዚህ ጋ “እንጀራ” የሚለው ቃል በአጠቃላይ ምግብን ይወክላል። ኢ.ት፡ “ምግብ ሲለምን” (See: Synecdoche)
ዕድሜውን ሙሉ
በዚህ የአነጋገር ዘይቤ ይህ አድራጎት የሕይወት ዘመን ልምምዱ ነው የሚል ትርጉም አለው። ኢ.ት፡ “እርሱ ሁሌም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ልጆቹ በረከት ይሆናሉ
“ልጆቹ ሌሎችን ለመባረክ ያድጋሉ”
ከ -- ራቅ
አንድ ነገር ማድረግን መተው ሰውየው ከድርጊቱ እንደ ራቀ ተደርጎ ተናግሯል። ኢ.ት፡ “ማድረግን ተው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 37:28
ለዘላለም ይኖራሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ለዘላለም ይጠብቃቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ይቆረጣሉ
የአመፀኛው መጥፋት ተቆርጦ እንደሚጣል የተክል ቅርንጫፍ ሆኖ ተነግሯል። ይህንን በመዝሙር 37፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)።
ጻድቁ
ይህ ጻድቅ የሆኑትን ሰዎች ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ጻድቅ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ምድሪቱን ይወርሳሉ
ምድሪቱን መውረስ ርስትን እንደ መቀበል ሆኖ ተነግሯል። ይህንን በመዝሙር 37፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ምድሪቱን እንደ ራሳቸው ንብረት አድርገው ይቀበላሉ” ወይም “በምድሪቱ ላይ በሰላም እንዲኖሩ ይፈቀድላቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የጻድቅ ሰው አፍ
እዚህ ጋ “አፍ” የሚወክለው የተናጋሪውን ሰው ሁለንተና ነው። ኢ.ት፡ “ጻድቁ ሰው” (See: Synec- doche)
ጥበብን ይናገራል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የነገር ስም የሆነው “ጥበብ” “ጠቢብ” ተብሎ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ለሌሎች ጥበብ ያለበትን ምክር ይሰጣል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ፍትሕን ያበዛል
የነገር ስም የሆነው “ፍትሕ” እንደ ድርጊት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሌሎች ሰዎች በጽድቅ እንዲኖሩ ያበረታታል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Psalms 37:31
የእግዚአብሔር ሕግ በልቡ አለ
እዚህ ጋ “በልቡ ውስጥ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ጥልቅ የሆነውን ውስጣዊ ማንነቱን ነው። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በውስጣዊ ማንነቱ ውስጥ ያስቀምጠዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግሮቹም አይንሸራተቱም
እዚህ ጋ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ከትክከለኛው መንገድ መንሸራተትና መውደቅ እንደሆነ ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር እንዲሄድበት በሚፈልገው መንገድ በሰላም ይሄዳል” ወይም “እግዚአብሔር እንዲያደርግ የፈለጋቸውን ነገሮች በሰላም ያደርጋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አመጸኛው ሰው … ጻድቁን ሰው … ክፉው ሰው
እነዚህ ተለይተው የታወቁ ሰዎች አይደሉም። በጥቅሉ እንዲህ ዓይነቶቹን ሰዎች የሚያመለክቱ ናቸው። (See: Generic Noun Phrases)
ጻድቁን ሰው ይመለከተዋል
እዚህ ጋ መመልከት ጻድቅ የሆኑትን ሰዎች ለመጉዳት መከታተልን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ጻድቁን ሰው አድፍጦ ይጠብቀዋል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Psalms 37:34
ምድሪቱን እንድትወርስ ያነሣሃል
እዚህ ጋ “ያነሣሃል” የሚያመለክተው እግዚአብሔር እርሱን ተስፋ ለሚያደርጉት ክብርን እንደሚሰጣቸው ነው። ኢ.ት፡ “ምድሪቱን ለአንተ በመስጠት ያከብርሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ክፉዎች
ይህ ክፉ ሰዎችን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ክፉዎች ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ይቆረጣሉ
የአመፀኛው መጥፋት ተቆርጦ እንደሚጣል የተክል ቅርንጫፍ ሆኖ ተነግሯል። ተመሳሳዩን ሐረግ በመዝሙር 37፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 37:35
ክፉውንና ጨካኙን ሰው
ይህ አንድን የተለየን ሰው አያመለክትም። ይህ ጥቅል አነጋገር ነው። (See: Generic Noun Phrases)
በራሱ ዐፈር ላይ እንደ ለመለመ ዛፍ ተስፋፍቶ
እዚህ ጋ የክፉው ሰው መበልጸግ በጥሩ ዐፈር ላይ በሚበቅል ጤናማ ዛፍ ተመስሎ ተነግሮለታል። (See: Simile)
ሊገኝ አይችልም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ላገኘው አልቻልኩም” ወይም “እግዚአብሔር እርሱን አስወግዶታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 37:37
ቅኑን ሰው
ይህ አንድን የተለየን ሰው አያመለክትም። ይህ ጥቅል አነጋገር ነው። (See: Generic Noun Phrases)
ትክክለኞቹን ልብ በላቸው
“ደግ ሰዎችን በጥንቃቄ አስተውላቸው” ወይም “ደግ ሰዎችን አስተውላቸው”
የክፉ ሰው ተስፋው ይቆረጣል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር የትውልድ ሐረጉ እንዳይቀጥል ያደርጋል” ወይም “አንድም ዘር አይኖረውም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ተስፋው
ይህ የሚያመለክተው ዘሩን ነው። ኢ.ት፡ “ዘሩ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ክፉው ሰው
ይህ አንድን የተለየን ሰው አያመለክትም። ይህ ጥቅል አነጋገር ነው። (See: Generic Noun Phrases)
ይቆረጣል
የአመፀኛው መጥፋት ተቆርጦ እንደሚጣል የተክል ቅርንጫፍ ሆኖ ተነግሯል። ተመሳሳዩን ሐረግ በመዝሙር 37፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 37:39
የጻድቃን ድነት የሚመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው
የነገር ስም የሆነው “ድነት” እንደ ድርጊት ለገለጽ ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ጻድቅ የሆነውን ሕዝብ ይታደገዋል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ጻድቃን
ይህ የሚያመለክተው ጻድቅ የሆኑትን ሰዎች ነው። ኢ.ት፡ “ጻድቃን” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ይረዳል … ይታደጋል … ያድናል
ይህ ተመሳሳይ አሳብ እግዚአብሔር የሚታመኑበትና ለመርዳት የሚችል መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት በብዙ የተለያዩ መንገዶች ተደጋግሟል። (See: Parallelism)
እርሱን መጠጊያ አድርገዋል
ጥበቃ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር መሄድ በእርሱ መጠጊያ ማግኘት እንደሆነ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ጥበቃ ለማግኘት ወደ እርሱ ሄደዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Chapter 38
Psalms 38:1
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚናገረው ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) የመዝሙሩ ስልት የዳዊትን መዝሙር ይመስላል የሚሉት ናቸው።
በቁጣህ አትገስጸኝ … በመዓትህ አትቅጣኝ
በመሠረቱ የእነዚህ ሐረጎች ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን አሳቡ የተደጋገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። (See: Paral- lelism)
ፍላጻዎችህ ወግተውኛል
በጸሐፊው ላይ የእግዚአብሔር ቅጣት ከባድነት ልክ እግዚአብሔር በጸሐፊው ላይ ቀስት የወረወረበት ያህል ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ቅጣትህ በቀስት የወጋኸኝ ያህል አሳምሞኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እጅህ ወደ ታች ይጫነኛል
እግዚአብሔር ጸሐፊውን የቀጣበት መንገድ ልክ በእጁ የመታው ያህል ተቆጥሮ ተነግሯል። እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። ኢ.ት፡ “ኃይልህ መትቶ ይጥለኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 38:3
በኃጢአቴ ምክንያት አጥንቶቼ ምንም ጤና የላቸውም
እዚህ ጋ “አጥንቶቼ” የሚወክለው የጸሐፊውን አካል ነው። ኢ.ት፡ “በኃጢአቴ ምክንያት መላው አካላቴ ታሞአል” (See: Synecdoche)
በደሌ አጥለቅልቆኛል
የጸሐፊው በደል በሚሸፍነው ጎርፍ ተመስሎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “በደሌ እንደ ጎርፍ ሸፍኖኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እንደ ከባድ ሸክም ሆነውብኛል
የጸሐፊው በደል ሊያነሣው በማይችል ከባድ ሸክም ተመስሎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እርሱ ላነሣው እጅግ እንደሚከብድ ሸክም ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 38:5
ቁስሎቼ አመረቀዙ፣ ሸተቱም
እዚህ ጋ፣ “ሸተቱ” የሚለው ቃል ከሥጋው መበስበስ የተነሣ ቁስሎቹ መጥፎ ጠረን እንዲወጡ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ቁስሌቼ አመርቅዘዋል፣ በመበስበሳቸውም ይገማሉ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ኀበጥሁ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በቁስሎቹ ምክንያት የጸሐፊው ሕመም እንደ ሽመገለ ደካማ ሰው እንዲጎብጥ አድርጎታል። ኢ.ት፡ “በሕመም ጎብጫለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 38:7
በቃጠሎ ተሞልቻለሁ
ጸሐፊው ውስጡ የሚቃጠል እስኪመስለው ድረስ በትኩሳት ታሟል። ኢ.ት፡ “ሰውነቴ በትኩሳት ነዶአል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሥጋዬ ጤና የለውም
እዚህ ጋ “ሥጋዬ” የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። ኢ.ት፡ “ሙሉ በሙሉ ታምሜአለሁ” (See: Synecdoche)
ፈጽሞ ደቅቄአለሁ
ከባድ ሸክም የተጫነው ያህል የጸሐፊው ሕመም እጅግ ብርቱ ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የልቤ ጭንቀት
እዚህ ጋ “ልቤ” የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። ኢ.ት፡ “ጭንቀቴ” (See: Synecdoche)
Psalms 38:9
የልቤ ጥልቅ ናፍቆት
እዚህ ጋ “ልቤ” የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። ጸሐፊው ጤንነቱ እንዲስተካከልለት መመኘቱን መናገር ሊጠቅም ይችላል። ኢ.ት፡ “ታላቁ ምኞቴ” ወይም “እንድትፈውሰኝ እመኝሃለሁ” (Synecdoche and Assumed Knowl- edge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
ማቃሰቴ ከአንተ አልተሰወረም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የሐዘን እንጉርጉሮዬንም ሁሉ ማየት ትችላለህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ልቤ ይመታል
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም ልቡ በፍጥነት ይመታል የሚል ነው። ኢ.ት፡ “ልቤ በኃይል ይመታል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ጉልበቴ ይከዳኛል
“በጣም ደካማ ሆንኩ”
ዕይታዬ ጨልሞአል
“ከእንግዲህ በአግባቡ ማየት አልችልም”
Psalms 38:11
ወጥመድ አጠመዱብኝ
የጸሐፊው ጠላቶች ሤራ እንደ እንስሳ በእርሱ ላይ ወጥመድ እንደዘረጉበት ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እኔን ለመያዝ ወጥመድ አጠመዱ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የሚያፈርስ ቃል ያወራሉ፣ የሚያታልል ቃልም ይናገራሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን እነዚህ ሰዎች የሚናገሩት የመጉዳት ባህርይ እንዳለው አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Parallelism)
Psalms 38:13
እኔ መስማት እንደ ተሣነው ሰው ነኝ … ምንም እንደማይሰማ … አይሰማም
የቁጥር 13 እና 14 የመጀመሪያ ስንኞች ተመሳሳዩን መስማት የተሣነውን ሰው ምስል ለማቅረብ ንጽጽርን ይጠቀማሉ። ጸሐፊው መስማት እስከማይችል ድረስ በጣም ታሟል። (See: Parallelism and Simile)
እኔ እንደ ዲዳ ሰው ነኝ … ምንም እንደማይናገር … ምንም እንደማይመልስ
የቁጥር 13 እና 14 ሁለተኛ ስንኞች የዲዳን ሰው ምስል ለማቅረብ ንጽጽርን ይጠቀማሉ። ጸሐፊው መናገር እስከማይችል ድረስ በጣም ታሟል። (See: Parallelism and Simile)
ዲዳ ሰው
መናገር የማይችል ሰው
Psalms 38:15
አንተ ትመልሳለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ትመልስልኛለህ” ወይም 2) “ለጠላቶቼ ትመልስላቸዋለህ” የሚሉት ናቸው።
በእኔ ላይ አይፈነድቁም
“በመከራዬ አይደሰቱም”
እግሬ ቢንሸራተት
እዚህ ጋ “እግሬ” የሚወክለው ጸሐፊውን ነው። የእግሩ መንሸራተት የጸሐፊውን መከራና መጥፎ አጋጣሚ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ስሕተትን ብሠራ መከራን ያመጣብኛል” (Synecdoche እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 38:17
ለመሰናከል ተቃርቤአለሁ
ለዚህ ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ለመሞት እስክቃረብ ድረስ በጣም ታምሜአለሁ” ወይም 2) “በቶሎ የተረሳሁ እሆናለሁ” የሚሉት ናቸው። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያለው ዘይቤአዊ አነጋገር ባይተረጎም ተመራጭ ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በማያቋርጥ ሕመም ውስጥ ነኝ
“ሁሌም በሕመም ውስጥ ነኝ”
Psalms 38:19
ነገር ግን ጠላቶቼ እጅግ ብዙ ናቸው … በጣም ብዙ ናቸው
እነዚህ ሁለትም ሐረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት ተመሳሳይ ነገር ነው። (See: Parallelism)
መልካም ባደረግሁ ክፉ ይመልሱልኛል
የጸሐፊው ጠላቶች ድርጊት፣ እንደ ገንዘብ ግብይት፣ ባደረገው መልካም ነገሮች ምትክ ክፉ ነገሮችን እንደመለሱለት ተደርጎ ተነግሯል። የነገር ስም የሆነው “ክፉ” እና “መልካም” እንደ ቅጽል ሊነገሩ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “መልካም ከሆንኩላቸው በኋላ ክፉን ነገር ያደርጉብኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ክሶችን ይወረውሩብኛል
የጸሐፊው ጠላቶች እርሱን የሚከሱበት መንገድ ክሶቹ ድንጋዮች የሆኑ ይመስል በእርሱ ላይ እንደወረወሩበት ሆኖ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
መልካሙን ተከተልሁ
ጸሐፊው መልካምን ነገር መመኘቱ ከመልካም ነገሮች በስተኋላ እንደሮጠ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 38:21
አትተወኝ … ከእኔ አትራቅ
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች በጣም ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም አላቸው። (See: Parallelism)
ከእኔ አትራቅ
እግዚአብሔር ለጸሐፊው ጥያቄ ምላሽ ሳይሰጥ በመቆየቱ ምክንያት እግዚአብሔርን ከእርሱ እንደራቀ አድርጎ ጸሐፊው ይናገራል (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እኔን ለመርዳት ፈጥነህ ና
እግዚአብሔር ጸሐፊውን ለመርዳት እንደሚሮጥ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ድነቴ
የነገር ስም የሆነው “ድነት” እንደ ድርጊት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እኔን የምታድነኝ አንተ ነህ” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 39
Psalms 39:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
ኤዶታም
ከዳዊት የሙዚቃ አለቆች ለአንዱ ይህ ተመሳሳይ ስም ነበረው። ይህ ምናልባት እርሱን ያመለክት ይሆናል። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚናገረው ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) የመዝሙሩ ስልት የዳዊትን መዝሙር ይመስላል የሚሉት ናቸው።
የምናገረውን አያለሁ
እዚህ ጋ “ማየት” የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን “ልብ ማለት” የሚል ትርጉም አለው። ኢ.ት፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ለምናገራቸው ነገሮች ትኩረት እሰጣለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በምላሴ ኃጢአትን እንዳልሠራ
እዚህ ጋ “ምላስ” የሚያመለክተው የጸሐፊውን ንግግር ነው። ኢ.ት: “እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ ነገር እንዳልናገር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ልጓም
“መለጎም” ማለት አፍን መዝጋት ነው። ዳዊት እዚህ ጋ የሚናገረው ከክፉ ሰው ጋር ሲሆን እንደማይናገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 39:2
ዝም አልኩ፤ ቃሌን መለስኩ
የእነዚህ የሁለቱም ሐረጎች ትርጉም አንድ ሲሆን ጸሐፊው ፈጽሞ እንደማይናገር አጽንዖት ይሰጣል። ኢ.ት: “ፈጽሞ ጸጥ ብዬ ነበር” (See: Doublet)
ቃሌን መለስኩ
“አልተናገርኩም”
ልቤ ሞቀ ... እንደ እሳትም ነደደ
እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው የሰውን ሁለንተናውን ነው። የጸሐፊው አስጨናቂ አሳብ በውስጡ እንደሚነድ እሳት ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት: “ስለ እነዚህ ነገሮች ባሰብኩ ጊዜ በጣም ተጨነቅኩኝ” (See: Synecdoche እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 39:4
የሕይወቴ ማብቂያ ... የቀኖቼ ርዝመት
በመሠረቱ እነዚህ ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ነው። (See: Parallelism)
አላፊ ጠፊ መሆኔን አሳየኝ
“ሕይወቴ ምን ያህል አጭር እንደሆነ አሳየኝ” ወይም “በቶሎ የምሞትበትን ጊዜ አሳየኝ”
የእጄን እርዝመት ያህል ብቻ
ጸሐፊው የሕይወት ዘመኑ በእጁ እርዝመት ሊለካ እንደሚችል አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “በጣም አጭር ጊዜ ብቻ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የሕይወት ዘመኔ በፊትህ እንደ ኢምንት ነው
ይህ ንጽጽር የሚናገረው የጸሐፊው የሕይወት ዘመን እርዝማኔ የማይሰነብት፣ አጭር መሆኑን ነው። ይህ ዕድሜው ምን ያህል አጭር እንደሚሆን አጽንዖት ለመስጠት የተነገረ ግነት ነው። ኢ.ት: “የሕይወቴ እርዝመት በየትኛውም ጊዜ ሊያበቃ የሚችል ነው” (Simile፣ ግነትና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
በእርግጥ እያንዳንዱ ሰው እስትንፋስ ብቻ ነው
ሕይወት አጭር ነው፤ ዘማሪው በዚህ ስፍራ ዕጥረቱ አንድ ሰው ትንፋሹን አንድ ጊዜ የሚተነፍስበትን ያህል እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “የሰዎች የሕይወት ዘመን ልክ አንድ ሰው ከሚተነፍሰው አጭር እስትንፋስ ጋር አንድ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 39:6
በእርግጥ እያንዳንዱ ሰው እንደ ጥላ ይመላለሳል
የሰዎች ሕይወት ምንም ያህል እንደማይቆይ ጥላ ተደርጎ ተነግራል። ኢ.ት: “ጥላ እንደሚጠፋ እያንዳንዱ ይጠፋል” (See: Simile)
ማን እንደሚቀበላቸው ባያውቁም
እዚህ ጋ እነርሱ ከሞቱ በኋላ ሀብታቸው ምን እንደሚሆን እንደማያውቁ ያመለክታል። የዚህ አነጋገር ሙሉ ትርጉም ሊብራራ ይችላል። (See: Assumed Knowledge and Implicit Informa- tion)
ጌታ ሆይ፣ አሁን እኔ የምጠብቀው ምንድነው?
ጸሐፊው ይህንን የሚጠይቀው ሰዎች ሊረዱት እንደማይችሉ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እንደ ንግግር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “እንግዲህ እግዚአብሔር ሆይ፣ ከማንም ምንም ነገር አልጠብቅም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 39:8
ዝም አላለሁ ... አፌን አልከፍትም
በመሠረቱ እነዚህ ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ነው። (See: Parallelism)
ይህንን ያደረግኸው አንተ ነህና
“ቅጣቴ የሚመጣው ከአንተ ነውና”
Psalms 39:10
እኔን ማቁሰልህን ተው
እግዚአብሔር ጸሐፊውን መቅጣቱ ልክ በጦር መሣሪያ እግዚአብሔር እንዳቆሰለው ተደርጎ ተነግራል። ኢ.ት: “እባክህን እኔን መቅጣትህን ተው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እኔ ዝዬአለሁ
“ፈጽሞ ተሸንፌአለሁ”
የእጅህ ምት
እግዚአብሔር ጸሐፊውን መቅጣቱ ልክ እግዚአብሔር በቡጢ እንደመታው ተደርጎ ተነግራል። እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ፍርድ ነው። ኢ.ት: “ፍርድህ በእኔ ላይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እንደ ብል የተመኟቸውን ነገሮች በላህ
ብል የጨርቅን ቁራጭ እንደሚበላው እግዚአብሔር የከበረ የሚሉትን ነገራቸውን ይወስድባቸዋል። ኢ.ት: “ብል ጨርቅን እንደሚበላ የሚመኟቸውን ነገሮች ይበላል” (See: Simile)
ሰዎች ሁሉ እንደ ተን ብቻ ናቸው
ጸሐፊው የሰዎችን ደካማነት ፈጥኖ ከሚጠፋ ጭጋግ ጋር በማመሳሰል ይናገራል። ኢ.ት: “ሁሉም ፈጽሞ ተሰባሪ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 39:12
ጸሎቴን ስማ ... አድምጠኝ ... ለቅሶዬን አድምጥ
የእነዚህ ሦስት ሐረጎች ትርጉማቸው በመሠረቱ ተመሳሳይ ሲሆን እግዚአብሔር ምላሽ እንዲሰጠው እንዴት አጥብቆ እንደሚፈልግ ያሳያል። (See: Parallelism)
ደንቆሮ አትሁንብኝ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእርሱ ምላሽ አለመስጠቱን እንደ ደነቆረ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “ልትሰማኝ የማትችል ይመስል ዝም አትበለኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እኔ ከአንተ ጋር እንደ እንግዳና ስደተኛ ነኝ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእርሱ ምላሽ አለመስጠቱን እግዚአብሔር ለእርሱ ፈጽሞ እንግዳ እንደሆነበት አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “እኔ ፈጽሞ እንደ እንግዳ ሆኜብሃለሁ” (See: Simile)
ዐይንህን ከእኔ ላይ አንሣ
እዚህ ጋ “ዐይንህን” የሚወክለው የእግዚአብሔርን ቅጣት ነው። ኢ.ት: “እባክህን እኔን መቅጣትህን ተው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እንደገና እንድስቅ
እዚህ ጋ “መሳቅ” ደስተኛ ከመሆን ጋር ተያይዟል። ኢ.ት: “እንደገና ደስተኛ መሆን እንድችል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 40
Psalms 40:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚናገረው ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) የመዝሙሩ ስልት የዳዊትን መዝሙር ይመስላል የሚሉት ናቸው።
እግዚአብሔርን በትዕግስት ጠበቅሁት
ይህ ማለት ጸሐፊው እግዚአብሔር እንዲረዳው ሲጠብቀው ነበር።
እርሱ ሰማኝ ... ጩኸቴንም አደመጠ
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድ ዐረፍተ ነገር ሊጣመሩም ይችላሉ። ኢ.ት: “በጠራኹት ጊዜ ሰማኝ” (See: Doublet)
ከአስከፊ ጉድጓድ፣ ከረግረጉም ጭቃ
እነዚህ ሁለት ዘይቤአዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው የነበረበት አደገኛ ሁኔታ ጭቃ በተሞላና ለሞት በሚያበቃ ጉድጓድ ተመስሎ ተነግሯል። ይህ አደገኛነቱ ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ኢ.ት: “የሚያጣብቅ ጭቃ በሞላበት አስከፊ ጉድጓድ ከመጠመድ” (Parallelism እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግሮቼን በዐለት ላይ አቆማቸው
እዚህ ጋ “እግሮቼን” የሚያመለክተው የጸሐፊውን ሲሆን “ዐለት” የሚያመለክተው ሰላማዊ ስፍራን ነው። ኢ.ት: “ሰላማዊ ስፍራን አዘጋጀልኝ” (Synecdoche and ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Psalms 40:3
አዲስን መዝሙር በአፌ ጨመረ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ለአዲስ መዝሙር የሚሆን ቃል አስተማረኝ” ወይም 2) “ለመዘመር አዲስ ምክንያትን ሰጠኝ” የሚሉት ናቸው።
በአፌ
እዚህ ጋ “አፌ” የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። ኢ.ት፡ “በውስጤ” (See: Synecdoche)
ለአምላካችን ምስጋና
“ምስጋና” የሚለው ስም እንደ ግሥ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አምላካችንን የምናመሰግንበትን ዝማሬ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ብዙዎች ያዩታል
እዚህ ጋ “ያዩታል” እግዚአብሔር ስላደረገለት ነገር ጸሐፊው ሲዘምር እንደሚሰሙት ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር ያደረገልኝን ስናገር ይሰሙኛል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔርን መታመኛው የሚያደርግ ሰው የተባረከ ነው
“በእግዚአብሔር የሚታመን ሰው የተባረከ ነው” ወይም “በእግዚአብሔር የሚታመኑ እነርሱ የተባረኩ ናቸው’
ኩሩው
ይህ ኩሩ የሆኑትን ሰዎች ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ኩሩ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ለውሸት
የዕብራይስጡ ቃል ግልጽ አይደለም። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ውሸት” ወይም 2) “ሐሰተኞች አማልክት” የሚሉት ናቸው።
Psalms 40:5
ስለ እኛ የምታስባቸው አሳቦች ሊቆጠሩ አይችሉም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ለእኛ የምታስባቸውን ነገሮች በሙሉ ማንም ሊቆጥራቸው አይችልም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሊቆጠሩ አይችሉም … ሊቆጠሩ ከሚችሉ በላይ ናቸው
በመሠረቱ የእነዚህ ሐረጎች ትርጉም አንድ ነው። የመጀመሪያው በአሉታዊነት ሲነገር ሁለተኛው በአዎንታዊነት ተነግሯል። (See: Parallelism and Litotes)
በመሥዋዕት ወይም በቁርባን ደስ አይልህም
ይህ ሌሎች ነገሮች ለእግዚአብሔር በይበልጥ አስፈላጊ ስለመሆናቸው በግነት የተነገረበት ነው። ኢ.ት፡ “አንተን እጅግ የሚያስደስትህ መሥዋዕቶችና ሌሎች ቁርባኖች አይደሉም” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
ጆሮዎቼን ከፍተሃቸዋል
እዚህ ጋ “ጆሮዎቼ” የሚያመለክተው የመስማትን ችሎታ ነው። ኢ.ት፡ “ትዕዛዝህን ለመስማት አስችለኸኛል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የሚቃጠሉ ቁርባኖችን ወይም የኃጢአት ቁርባኖችን አልፈለግህም
ይህ፣ እነዚህ ነገሮች ለእግዚአብሔር እጅግ አስፈላጊዎች እንዳልሆኑ ለማሳየት የተነገረ ግነት ነው። ኢ.ት፡ “አንተ አብልጠህ የምትፈልጋቸው በመሰዊያ ላይ የሚቃጠሉ እንስሶችንና ሌሎች ስለ ኃጢአታችን የሚቀርቡ ቁርባኖችን አይደለም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 40:7
የመጽሐፍ ጥቅልል
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈበትን ጥቅልል ነው። ኢ.ት፡ “የተጻፈበት ጥቅልል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ሕግጋቶችህ በልቤ ውስጥ ናቸው
እዚህ ጋ “ልቤ” የሚያመለክተው የጸሐፊውን ውስጣዊ ማንነት ነው። ኢ.ት፡ “በውስጣዊ ማንነቴ ሁልጊዜ ስለ ሕግህ አስባለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የጽድቅህን የምስራች በታላቅ ጉባዔ ተናግሬአለሁ
“ስለ ጽድቅህ የምስራች በታላቅ ጉባዔ ለነበሩ ሰዎች ተናግሬአለሁ”
የጽድቅህን የምስራች
ይህ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚታደጋቸው የሚነገረውን የምሥራች ያመለክታል። ኢ.ት፡ “አንተ ጻድቅ ስለሆንክ ሕዝብህን ስለማዳንህ የምሥራችን” (See: Ellipsis)
ከንፈሮቼ ይህንን ከማድረግ አላተቆጠቡም
እዚህ ጋ “ከንፈሮቼ” ንግግሩ ላይ አጽንዖት በመስጠት ጸሐፊውን ይወክላሉ። ኢ.ት፡ “እነዚህን ነገሮች ከማብሰር ራሴን አልገታሁም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 40:10
ጽድቅህን በልቤ አልደበቅሁም
“ጽድቅህን ምስጢር አድርጌ አልያዝሁትም”። ይህ ደግሞ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ስለ ጽድቅህ ለሁሉም በግልጽ ተናግሬአለሁ” (See: Litotes)
በልቤ
እዚህ ጋ ይህ የሚያመለክተው የጸሐፊውን ውስጣዊ ማንነት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የቃል ኪዳን ታማኝነትህንና አለኝታነትህን ከታላቁ ጉባዔ አልደበቅሁም
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በታላቁ ጉባዔ ውስጥ ለነበሩት ሁሉ ስለ ቃል ኪዳን ታማኝነትህ ወይም ስለ አለኝታነትህ ነግሬአቸዋለሁ” (See: Litotes)
የቃል ኪዳን ታማኝነትህ
የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” የሚለው ቃል “ታማኝ” ተብሎ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ነህ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
አለኝታነትህ
ይህ የነገር ስም የሆነው “አለኝታነት” እንደ “አለኝታ” ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንተ አለኝታ ነህ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
የቃል ኪዳን ታማኝነትህና አለኝታነትህ ሁልጊዜ ይጠብቁኝ
እዚህ ጋ “የቃል ኪዳን ታማኝነት” እና “አለኝታነት” ጸሐፊውን ሊጠብቁት እንደሚችሉ ሕያዋን ሰዎች ተደርገው ተነግረዋል። ኢ.ት፡ “የቃል ኪዳን ታማኝነትህ እና አለኝታነትህ ሁልጊዜ እንዲጠብቁኝ እፈልጋለሁ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 40:12
ሊቆጠር የማይቻል መከራ ከቦኛል
እዚህ ጋ መከራ ተናጋሪውን ከቦ እንደሚያጠምደው ቁስ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ልቆጥረው ከምችለው በላይ የበዛ መከራ በዙሪያዬ አለ” ወይም “ልቆጥረው የማልችለው መከራ መጣብኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሊቆጠር የማይቻል
ይህ ቁጥሩን ለማጉላት በአሉታዊነት ተነግሯል። ይህንን በመዝሙር 40:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “በቁጥር ብዙ ናቸው” (See: Litotes)
ኃጢአቴ
ይህ የኃጢአቱን ውጤት ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የኃጢአቴ ውጤት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይዞኛል
የጸሐፊው ኃጢአት እንደሚያጠቃው ጠላት ተደርጎ ተነግሯል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
ከእንግዲህ ምንም ነገር ማየት አልችልም
የተለያዩ ትርጉሞች በዚህ አስቸጋሪ ምንባብ ላይ ይለያያሉ። ምናልባት ተናጋሪው እጅግ ከመጮኹ የተነሣ በዕንባው ምክንያት ምንም ነገር ለማየት አልቻለም ይሆናል።
ልቤ ከድቶኛል
እዚህ ጋ “ልብ” የሚያመለክተው የጸሐፊውን ውስጣዊ መተማመን ነው። ኢ.ት፡ “በጣም ተስፋ ቆርጫለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 40:14
ነፍሴን ለመውሰድ የሚከታተሉኝ እነርሱ … ይሁኑ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊጻፍና ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እነዚያን ሊገድሉኝ የሚሞክሩትን እንዲያፍሩና እንዲዋረዱ አድርጋቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ነፍሴን ለመውሰድ የሚከታተሉኝ
እዚህ ጋ “ነፍሴን ለመውሰድ የሚከታተሉኝ” ማለት ጸሐፊውን ለመግደል ይመኛሉ ማለት ነው። ጸሐፊው “በነፍሱ” ተወክሏል። ኢ.ት፡ “ሊገድሉኝ የሚሞክሩ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እኔን በመጉዳት የሚደሰቱ እነርሱ … ይሁኑ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊጻፍና ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እኔን በመጉዳት የሚደሰቱትን ከልክላቸው፣ አዋርዳቸውም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ወደ ኋላ ይመለሱ
መከልከላቸው ወይም መታገዳቸው ከማጥቃታቸው ወደ ኋላ እንዲመለሱ እንደተደረጉ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ተከልክለዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተመልከት)

በእኔ ላይ “እንኳን፣ እንኳን!” የሚሉ እነርሱ … ይሁኑ

“በእኔ ላይ ‘እንኳን፣ እንኳን!’ የሚሉ በእፍረታቸው ምክንያት ይንቀጥቀጡ”

በእፍረታቸው ምክንያት ይደንግጡ

“በምታሳፍራቸው ጊዜ እንደሚደነግጡ ተስፋ አደርጋለሁ”

በእኔ ላይ “እንኳን፣ እንኳን!” የሚሉ

“እንኳን፣ እንኳን!” ሰዎች በሌላው ላይ በሚስቁበት ጊዜ የሚሉት ነገር ነው። የአንተ ቋንቋ ሰዎች በሌላው ላይ ሲስቁ የሚናገሩት የተለየ ቃል ካለው እዚህ ጋ መጠቀም ይቻላል። ይህ ታዲያ “መሳቅ” ከሚል ግሥ ጋር ሊተረጎም ይችላል።

Psalms 40:16

ደስ ይበላቸው፣ ሐሴትም ያድርጉ

የእነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን የደስታው ጥልቀት ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “በጣም ደስ ይበላችሁ” (See: Doublet)

ማዳንህን ይወዳል

የነገር ስም የሆነው “ማዳን” እንደ ድርጊት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ስላዳንካቸው ይወዱሃል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ድኻና ችግረኛ

እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ጸሐፊው ምን ያህል ምስኪን እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣሉ። አ.ት፡ “በጣም ችግረኛ” (See: Doublet)

ጌታ ስለ እኔ ያስባል

“ጌታ ስለ እኔ ይገደዋል”

አንተ ረዳቴ ነህ … ልትታደገኝ መጣህ

እነዚህ ሐረጎች የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ነው። (See: Parallelism)

አንተ ረዳቴ ነህ

“እኔን የምትረዳኝ አንተ ነህ”

ልትታደገኝ መጣህ

“ልታድነኝ መጣህ”

አትዘግይ

ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ፈጥነህ መልስ” (See: Litotes)

---

Chapter 41

Psalms 41:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ

“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”

የዳዊት መዝሙር

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚናገረው ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) የመዝሙሩ ስልት የዳዊትን መዝሙር ይመስላል የሚሉት ናቸው።

እርሱ … እርሱን … የእርሱ

እነዚህ ቃላት ስለ ደካሞች የሚገደውን ማንኛውንም ሰው ያመለክታሉ።

ደካማው

“ደካሞች ሰዎች” ወይም “ድኾች ሰዎች”

በመከራው አልጋ ላይ እግዚአብሔር ይደግፈዋል

“የመከራ አልጋ” የሚለው ሐረግ አንድ ሰው ታሞ በአልጋው ላይ የሚተኛበትን ጊዜ ያመለክታል። አ.ት፡ “ታሞ አልጋው ላይ በሚሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር ይደግፈዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሕመም አልጋውን የፈውስ አልጋ ታደርግለታለህ

“የፈውስ አልጋ” የሚለው ሐረግ አንድ ሰው በአልጋው ላይ በማረፍ ከሕመሙ የሚያገግምበትን ጊዜ ያመለክታል። አ.ት፡ “አንተ እግዚአብሔር፣ ከሕመሙ ትፈውሰዋለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 41:4

ስሙ የሚደመሰሰው

የአንድ ሰው ስም ሞተ ማለት ሰዎች በሕይወት ኖሮ እንደነበር ይረሱታል ማለት ነው። አ.ት፡ “ስሙ የሚደመሰሰው መቼ ነው” ወይም “ሰዎች ስለ እርሱ የሚረሱት መቼ ነው” (Ellipsis እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ጠላቴ ሊያየኝ ከመጣ

“ጠላቴ” የሚለው ቃል አንድን የታወቀውን ጠላት ማለት ሳይሆን በጥቅሉ የትኛውንም ጠላት ያመለክታል።

እርሱ ከንቱ ነገሮችን ይናገራል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ትርጉም የለሽ ነገሮችን ይናገራል” ወይም 2) ጠላቶቹ ወዳጆቹ ሳይሆኑ እንደሆኑ እንዲያስብ የሚያስደርገውን ነገር ይናገራሉ የሚሉት ናቸው። አ.ት፡ “የሚያሳስቱ ነገሮችን ይናገራል” ወይም “ስለ እኔ የሚገዳቸው ያስመስላሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ልቡ ለጥፋቴ የሚሆነውን ለራሱ ያከማቻል

ጠላቶቹ የእርሱን ክፉ ነገሮች ሁሉ ለማጥናት ይሞክራሉ። እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። መጥፎ ሁኔታዎች ሊከማቹ እንደሚችሉ ቁሶች ተደርገው ተነግሮላቸዋል። አ.ት፡ “ለጥፋቴ የሚሆነውን ሁሉ ለማጥናት ይሞክራሉ” (Synecdoche እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 41:7

መጎዳቴን ተስፋ ያደርጋሉ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “በጣም መጥፎ የሆኑ ነገሮች እንደሚደርሱብኝ ተስፋ ያደርጋሉ” ወይም 2) “እኔን ለመጉዳት እያቀዱ ነው” የሚሉት ናቸው።

በእርሱ ላይ ክፉ በሽታ …

ጠላቶቹን እርሱን በሚይዘው ሰው በመመሰል ስለ “በሽታ” ይናገራሉ። አ.ት፡ “በአደገኛ በሽታ ታሞአል” (ሰውኛ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፉ በሽታ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “አደገኛ በሽታ” ወይም 2) “ክፉ የሆነ ነገር” የሚሉት ናቸው።

አሁን ወድቋል፣ ከእንግዲህ አይነሣም

እዚህ ጋ “ወድቋል” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ከሕመም የተነሣ አልጋ ላይ መተኛትን ነው። “አይነሣም” ማለት መተኛቱን ይቀጥላል ማለት ሲሆን ይሞታል የሚለውን በጨዋነት የመግለጽ አሳብ ነው። አ.ት፡ “አሁን ታሞ አልጋ ላይ ነው፣ በዚያ ይሞታል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information and Euphemism)

ተረከዙን በእኔ ላይ አንሥቶአል

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ባልንጀራው አሳልፎ ሰጥቶታል ማለት ነው። አ.ት፡ “አሳልፎ ሰጠኝ” ወይም “በእኔ ላይ ተቃዋሚ ሆነ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 41:10

እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ግን ማረኝ፣ አንሣኝም

ይህ ልመና ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ እባክህን ማረኝና አንሣኝ” (See: Statements - Other Uses)

አንሣኝ

ይህ ማለት ከአልጋው ላይ እንዲያነሣው ወይም ከበሽታው እንዲያገግም እንዲያደርገው ነው። አ.ት፡ “ጤነኛ አድርገኝ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

መልሼ እንድከፍላቸው

ጸሐፊው የሚናገራው የተበዳራቸውን ይመልስላቸው ይመስል ጠላቶቹን ስለ መበቀል ነው። አ.ት፡ “እንድበቀላቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጠላቴ ድል አላደረገኝምና በእኔ ደስ እንደተሰኘህ በዚህ አውቃለሁ

“በዚህ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጸሐፊው ቀጥሎ የሚናገረውን ነው። ለግልጽነት እንዲረዳ ሐረጉ ቦታው ሊቀያየር ይችላል። አ.ት፡ “ጠላቴ ድል ስለማያደርገኝ በእኔ ደስ እንደሚልህ አውቃለሁ” (የሁነቶች ቅደም ተከተል የሚለውን ተመልከት)

ጠላቴ ድል አላደረገኝምና በእኔ ደስ እንደተሰኘህ በዚህ አውቃለሁ

እግዚአብሔር ገና ስላልፈወሰው ይህ የወደፊቱን በሚያመለክት ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ጠላቶቼ ድል እንዳያደርጉኝ ካስቻልከኝ በእኔ እንደተደሰትክ አውቃለሁ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

በቅንነቴ ትደግፈኛለህ

“በቅንነቴ ምክንያት ትደግፈኛለህ”

በፊትህ ትጠብቀኛለህ

ጸሐፊው እግዚአብሔር እርሱን ማየት በሚችልበትና እርሱም የእግዚአብሔርን ፊት ለማየት በሚችልበት ስፍራ እንደተገኘ ያህል በእግዚአብሔር ሀልዎት ውስጥ ስለመሆን ይናገራል። አ.ት፡ “ከአንተ ጋር ታቆየኛለህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተመልከት)
Psalms 41:13
መዝሙር 1 መዝሙር 41 ላይ ያበቃል።
መዝሙር 1 መዝሙር 41 ላይ ያበቃል።
ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም
ይህ ሁለቱን ጽንፍ የሚያመለክት ሲሆን ትርጉሙ ሁልጊዜ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ለዘለዓለም” (See: Merism)
አሜን፣ አሜን
“አሜን” የሚለው ቃል የተነገረውን ከማጽደቅ አንጻር አጽንዖት ለመስጠት ተደግሟል። ኢ.ት፡ “እንደዚሁ ይሁን” (See: Doublet)

---

Chapter 42
Psalms 42:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
ማስቺል
ይህ ምናልባት የሙዚቃን ስልት ያመለክት ይሆናል። ይህንን በመዝሙር 32፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዋላ ወደ ውሃ ምንጮች እንደምታለከልክ፣ አምላክ ሆይ አንተን እጠማለሁ
ደራሲው ለእግዚአብሔር ያለውን ናፍቆት የተጠማች ዋላ ለውሃ ካላት ናፍቆት ጋር ያነጻጽረዋል።
ማለክለክ
ሰው ወይም እንስሳ በጣም ደክሞ ወይም ተጠምቶ በከባዱ ሲተነፍስ
እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተን ተጠማሁ … እግዚአብሔርን መጠማት
ደራሲው ለእግዚአብሔር ያለውን ብርቱ ናፍቆት ውሃን በብርቱ ከመጠማት ጋር አመሳስሎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
መጥቼ በእግዚአብሔር ፊት የምቀርበው መቼ ነው?
ደራሲው ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው በእግዚአብሔር ፊት ለመሆን ያለውን ብርቱ ናፍቆት ለማሳየት እንጂ ምላሽ ፈልጎ አይደለም። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 42:3
ዕንባዬ ምግብ ሆነኝ
የሚመገበው ምግብ ይመስል ደራሲው ወደ ዕንባው ያመለክታል። ይህ ማለት መብላት እስከማይችል ድረስ አዝኗል። ኢ.ት፡ “ዕንባዬ እንደ ምግብ ስለሆነኝ ሌላ ምንም ነገር አልበላም” (ዘይቤአዊ አነጋገር፣ Assumed Knowledge እና Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
ቀንና ሌሊት
ይህ ሐረግ ጅማሬውንና መጨረሻውን በመጠቆሙ የሚያመለክተው ሙሉውን ቀን ነው። ኢ.ት፡ “ቀኑን ሙሉ” (See: Merism)
ጠላቶቼ ሁልጊዜ እንዲህ ይሉኛል
ይህ ግነት ነው። ጠላቶቹ ይህንን የሚሉት አልፎ አልፎ እንጂ ሁልጊዜ አይደለም። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አምላክህ የት አለ?
x
Psalms 42:5
ነፍሴ ሆይ፣ ለምን አቀረቀርሽ? ለምንስ በውስጤ ተረበሸሽ?
ደራሲው ራሱን ወደሚወክልበት “ነፍሱ” ይኸውም ውስጣዊ ማንነቱ ያመለክታል። ራሱን ለመውቀስ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቃል። ኢ.ት፡ “ማቀርቀር አልነበረብኝም። መጨነቅ አልነበረብኝም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)
ማቀርቀር
ጸሐፊው ነፍሱ የጎበጠች ይመስል የሚናገረው ስለ መጫጫን ወይም ተስፋ መቁረጥ ነው። ኢ.ት፡ “ተስፋ ቆርጫለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእግዚአብሔር ተስፋ አድርጊ
ጸሐፊው ለነፍሱ መናገሩንና በእግዚአብሔር እንድትታመን ማዘዙን ቀጥሏል። (See: Imperatives - Other Uses)
አምላኬ ሆይ፣ ነፍሴ
ጸሐፊው ስለ ነፍሱ ለእግዚአብሔር መናገር ይጀምራል።
አስብሃለሁ
የዚህ ሐረግ ትርጉም ማስታወስ ወይም ስለ አንድ ነገር ማሰብ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ስለ አንተ አስባለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የዮርዳኖስ ምድር
ይህ ምናልባት የዮርዳኖስ ወንዝ መነሻ የሆነውን ሰሜናዊ እስራኤል ያመለክት ይሆናል። ኢ.ት፡ “የዮርዳኖስ ወንዝ መነሻ ምድር” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ጫፍ
የተራራ ጫፍ
የሚዛር ኮረብታ
ይህ በአርሞንኤም ተራራ ስር ያለ የኮረብታ ስም ነው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 42:7
በፏፏቴህ ድምፅ አንዱ ጥልቅ ሌላውን ጥልቅ ይጣራል
“ጥልቅ” የሚለው ቃል ጥልቅ የሆነውን የውሃ አካል የሚያመለክት ሲሆን እዚህ ጋ ሊሆን የሚችለው ከአርሞንኤም ተራራ ወደ ታች የሚወርደውን ምንጭ ነው። ሰዎች ከተራራው ላይ ሲወርዱ የሚያሰሙትን እንቅስቃሴ ለእርስ በእርስ እንደሚያወሩ አድርጎ ጸሐፊው ስለ ውሃው አወራረድ ይናገራል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
ሞገድህና … ሁሉ በላዬ ላይ አልፏል
ደራሲው እጅግ አስከፊ የሆነበትን አጋጣሚና ሐዘኑን አንዱ ሞገድ ከሌላው ሞገድ ጋር እያላጋው ጥልቅ ውሃ እንዳሰጠመው ያህል አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሞገድህና ማዕበልህ
“ማዕበል” የሚለው ቃል “ሞገድ” ለሚለው ተለዋጭ ቃል ነው። ሁለቱ ቃላት በአንድነት በሞገዱ ታላቅነት ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት፡ “ታላላቅ ሞገዶችህ ሁሉ” (See: Doublet)
እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነቱን በቀን ያዛል
ከእርሱ ጋር እንዲኖር የሚያዝው ሰው የሆነ ይመስል ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት ይናገራል። የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነቱን በቀን ያሳየኛል” ወይም “እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ምን ያህል ታማኝ እንደሆነ በቀን ያሳየኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
መዝሙሩን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “የሚሰጠኝ መዝሙር” ወይም “ስለ እርሱ የሆነውን መዝሙር” የሚሉት ናቸው።
የሕይወቴ አምላክ
“ሕይወት የሚሰጠኝ አምላክ”
Psalms 42:9
ለእግዚአብሔር፣ ለዐለቱ እናገራለሁ
ጸሐፊው ከጠላት ጥቃት ሊከላከል በሚችል በትልቅ ዐለት መስሎ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለምን እያለቀስኩ እሄዳለሁ
“እያለቀሱ መሄድ” በጣም ከማዘን ጋር የተያያዘ ሥርዓት መፈጸም ነው።
በአጥንቴ ውስጥ እንደገባ ሰይፍ
ጸሐፊው የባላጋራዎቹን ወቀሳ በብርቱ እንዳቆሰሉት ይህል አድርጎ ይናገራል። (See: Simile)
ሁልጊዜ እንዲህ ይሉኛል
ይህ ግነት ነው፤ ጠላቶቹ አልፎ አልፎ እንጂ ሁልጊዜ እንዲህ አይሉትም። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አምላክህ የት አለ?
የደራሲው ጠላቶች እንዲህ በማለት የሚጠይቁት ሊሳለቁበትና እግዚአብሔር ሲረዳው እንዳላዩ ለመግለጽ ነው። ኢ.ት፡ “የሚረዳህ አምላክህ በዚህ የለም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 42:11
ነፍሴ ሆይ፣ ለምን አቀረቀርሽ? ለምንስ በውስጤ ተረበሸሽ?
ደራሲው ራሱን ወደሚወክልበት “ነፍሱ” ይኸውም ውስጣዊ ማንነቱ ያመለክታል። ራሱን ለመውቀስ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቃል። ይህንን በመዝሙር 42፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ማቀርቀር አልነበረብኝም። መጨነቅ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አልነበረብኝም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)
ማቀርቀር
ጸሐፊው ነፍሱ የጎበጠች ይመስል የሚናገረው ስለ መጫጫን ወይም ተስፋ መቁረጥ ነው። ይህንን በመዝሙር 42:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “ተስፋ ቆርጫለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእግዚአብሔር ተስፋ አድርጊ
ጸሐፊው ለነፍሱ መናገሩንና በእግዚአብሔር እንድትታመን ማዘዙን ቀጥሏል። ይህንን በመዝሙር 42:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (See: Imperatives - Other Uses)

Chapter 43
Psalms 43:1
የብርታቴ አምላክ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “የሚጠብቀኝ አምላክ” ወይም 2) “ብርታት የሚሰጠኝ አምላክ” የሚሉት ናቸው።
ለምን ተውከኝ? በጠላት ጭቆና ምክንያት ለምን እያለቀስኩ እሄዳለሁ?
ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቀው ምላሽ ለማግኘት ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ቅሬታና ስሜቱን ለመግለጽ ነው። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ለምን እያለቀስኩ እሄዳለሁ
“እያለቀሱ መሄድ” በጣም ከማዘን ጋር የተያያዘ ሥርዓት መፈጸም ነው።
በጠላት ጭቆና ምክንያት
“ጭቆና” የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ጠላቴ ስለሚጨቁነኝ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Psalms 43:3
ብርሃንህን እና እውነትህን ላክ
ብርሃን ሆኖ መንገዱን ያሳየው፣ እውነት ሆኖም እንዴት መኖር እንዳለበት ያስተምረው ይመስል ጸሐፊው የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር ታዳጊነት ነው። ኢ.ት: “በብርሃንህ እና በእውነትህ ምራኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቅዱስ ኮረብታ
ይህ መቅደሱ የሚገኝበትን የኢየሩሳሌም ኮረብታና መቅደሱን ራሱን ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ወደ ማደሪያህ
“አንተ ወደምትኖርበት ስፍራ”
ፍጹም ደስታዬ እግዚአብሔር
“ታላቅ ደስታዬ የሆነው እግዚአብሔር” ወይም “ታላቅ ደስታን የሚሰጠኝ እግዚአብሔር”
Psalms 43:5
ነፍሴ ሆይ፣ ለምን አቀረቀርሽ? ለምንስ በውስጤ ተረበሽሽ?
ደራሲው ራሱን ወደሚወክልበት “ነፍሱ” ይኸውም ውስጣዊ ማንነቱ ያመለክታል። ራሱን ለመውቀስ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቃል። ይህንን በመዝሙር 42:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “ማቀርቀር አልነበረብኝም። መጨነቅ አልነበረብኝም” (See: Imperatives - Other Uses)
ማቀርቀር
ጸሐፊው ነፍሱ የጎበጠች ይመስል የሚናገረው ስለ መጫጫን ወይም ተስፋ መቁረጥ ነው። ይህንን በመዝሙር 42:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “ተስፋ ቆርጫለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእግዚአብሔር ተስፋ አድርጊ
ጸሐፊው ለነፍሱ መናገሩንና በእግዚአብሔር እንድትታመን ማዘዙን ቀጥሏል። ይህንን በመዝሙር 42:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
አምላኬና ድነቴ
“ድነቴ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። አስፈላጊ ከሆነ ሁለቱ ሐረጎች ሊጣመሩ ይችላሉ። ኢ.ት: “የሚያድነኝ አምላኬ” (See: Doublet)

Chapter 44
Psalms 44:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
የቆሬ ልጆች መዝሙር
x
Psalms 44:3
በገዛ ሰይፋቸው
“ሰይፍ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ወታደራዊ ኃይልን ነው። ኢ.ት: “በገዛ ሰይፋቸው በመዋጋት” ወይም “በገዛ ሰራዊታቸው ጉልበት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የገዛ ክንዳቸው
እዚህ ጋ “ክንድ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኃይልን ነው። ኢ.ት: “የገዛ ኃይላቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የፊትህ ብርሃን
ለዚህ ሐረግ ግሥ ልትጨምርበት ትችላለህ። ኢ.ት: “የፊትህ ብርሃን ምድሪቱን የእነርሱ እንድትሆን አደረገ” (See: Ellipsis)
ቀኝ እጅህ፣ ክንድህ
እዚህ ጋ “እጅ” እና “ክንድ” የሚሉት ቃላት ሁለቱም የእግዚአብሔርን ኃይል ያመለክታሉ። ተጣምረው ለእግዚአብሔር ኃይል ታላቅነት አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት: “ታላቅ ኃይልህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Doublet የሚለውን ተመልከት)
የፊትህ ብርሃን
የእግዚአብሔር ፊት በእነርሱ ላይ ያበራ ይመስል ጸሐፊው እግዚአብሔር በሞገስ እንዳያቸውና ቸር እንደሆነላቸው ይናገራል። ኢ.ት: “ደግነትህ” ወይም “ሞገስህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለያዕቆብ ድልን
የእስራኤል ሕዝብ በአባታቸው በ “ያዕቆብ” ስም ተጠርቷል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 44:5
በአንተ አማካይነት … የአንተ በሆነው አማካይነት
“በአንተ… የአንተ በሆነው”
ይወድቃሉ … ይረገጣሉ … አይነሡም
ጸሐፊው ጠላቶቹ “የወደቁ” እና ለጦርነት ለመዘጋጀት “የተነሡ” ይመስል የሚናገረው ስለመሸነፋቸው ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በስምህ
እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይልና ሥልጣን ነው። ኢ.ት: “በኃይልህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይረገጣሉ
“በእግሮቻችን ይረገጣሉ” ወይም “በላያቸው ላይ እንረማመዳለን”
Psalms 44:7
ፎክረናል
“መፎከር” የሚለው ቃል ከግሥ ጋር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ፎክረናል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ለስምህ ምስጋናን እናቀርባለን
እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል ራሱን እግዚአብሔርን ያመለክታል። ኢ.ት: “ለአንተ ምስጋናን እናቀርባለን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 44:9
ጥለኸናል
ጸሐፊው እግዚአብሔር የማይፈለግን ቁራጭ ጨርቅ እንደሚጥል እስራኤልን እንደ ተወው ይናገራል። ኢ.ት: “ትቶናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዘረፉ
ሰራዊት ጦርነቱን ካሸነፈ በኋላ የሚሰበስበው ሀብትና ንብረት
እንደሚታረዱ በጎች አድርገኸናል
ጸሐፊው እስራኤላውያኑን ሰዎች አርደው ከሚበሏቸው በጎች ጋር ያነጻጽራቸዋል። በጎች በአራጆቻቸው ፊት ተስፋ እንደሌላቸው እስራኤላውያንም በጠላቶቻቸው ፊት ተስፋ የላቸውም። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “በጎችን አርደው እንደሚበሉ ጠላቶቻችን እንዲገድሉን ፈቅደህላቸዋል” (Simile እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በሕዝቦች መካከል በተንከን

“በተለያዩ ሕዝቦች መካከል እንድንኖር አደረግኸን”

Psalms 44:12

ሕዝብህን በከንቱ ሸጥከው

እግዚአብሔር፣ የእስራኤል ጠላቶች እነርሱን እንዲያሸንፏቸው ማድረጉን ምንም ክፍያ ሳይጠይቃቸው የእስራኤልን ሕዝብ ለጠላቶቻቸው እንደሸጣቸው አድርጎ ጸሐፊው ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ለጎረቤቶቻችን ተግሳጽ፣ በዙሪያችን ላሉትም መሳቂያና መሳለቂያ ታደርገናለህ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመካከላቸው የሚኖሩባቸው ሕዝቦች እንዴት እንደሚሳለቁባቸው አጽንዖት የሚሰጡ ተመሳሳዮች ናቸው። (See: Parallelism)

ለጎረቤቶቻችን ተግሳጽ ታደርገናለህ

“ተግሳጽ” የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ጎረቤቶቻችን እንደሚገስጹት አንዳች ነገር ታደርገናለህ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በዙሪያችን ላሉትም መሳቂያና መሳለቂያ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በዙሪያችን ያሉ ይስቁብናል፣ ይሳለቁብናልም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በመካከላቸው ስድብ ... የራስ መነቅነቅ

እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳዮች ሲሆኑ በዙሪያቸው ያሉ ሕዝቦች ምን ያህል አብዝተው እንደ ተሳለቁባቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Parallelism)

በሕዝቦች መካከል ስድብ ታደርገናለህ

“ስድብ” የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “በዙሪያችን ያሉ ሕዝቦች እንዲሰድቡን አደረግሃቸው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በሰዎች መካከል ለራስ መነቅነቂያ

“ራስን መነቅነቅ” የሚለው ሐረግ በግሥነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች ራሳቸውን የሚነቀንቁበት አንዳች ነገር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ለራስ መነቅነቂያ

ሰዎች ሌሎች ላይ ያላቸውን ንቀት ለማሳየት የሚጠቀሙበት የሰውነት እንቅስቃሴ ነው።

Psalms 44:15

ውርደቴ በፊቴ ነው

ጸሐፊው እንደ ቁስ ፊት ለፊቱ ይታየው ይመስል ስለ ውርደቱ ይናገራል። የሐረጉ ትርጉም፣ ‘ሁልጊዜ ስለ ውርደቱ ያስባል’ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ስለ ውርደቴ አስባለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእፍረት ፊቴ ጋርዶኛል

ጸሐፊው እንደ ብርድ ልብስ የሚሸፍነው ቁስ ይመስል የሚናገረው ስለ እፍረቱ ነው። ኢ.ት፡ “የፊቴ እፍረት ውጦኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የፊቴ እፍረት

“በፊቴ ላይ የሚታየው እፍረት”። ይህ እፍረቱ በፊት ገጽታው ላይ እንዴት እንደሚንጸባረቅ ያመለክታል።

ከዘላፊውና ከተሳዳቢው ድምፅ የተነሣ

እዚህ ጋ “ድምፅ” የሚለው ቃል እርሱን የሚሰድበውን ሰው ይወክላል። ኢ.ት፡ “እኔን ከሚዘልፈኝና ከሚሰድበኝ ሰውዬ ንግግር የተነሣ” (See: Synecdoche)

የሚዘልፍና የሚሳደብ

እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ይህ ሰው ባለው ብልሹ ጸባይ ላይ አጽንዖት ያደርጋሉ። (See: Doublet)

Psalms 44:18

ልባችን ወደ ኋላ አልተመለሰም ... ከመንገድህ አልራቀም

እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳዮች ናቸው። ጸሐፊው እግዚአብሔርን መከተልን እንደ ታማኝነት፣ ከእርሱ መለየትን ደግሞ ታማኝነትን እንደ ማጉደል በመቁጥር ይናገራል። (Parallelism እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ልባችን ወደ ኋላ አልተመለሰም

እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል ስሜትን፣ በተለይም ደግሞ ታማኝነትን እና ፍቅርን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ለአንተ ያለንን ታማኝነት አላቋረጥንም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፉኛ ሰብረኸናል

ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ቅጣት የሚናገረው ተሰባሪውን ዕቃ እንደሚሰብር አድርጎ ነው። ኢ.ት፡ “ክፉኛ ቀጣኸን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በቀበሮዎች ስፍራ

ጸሐፊው እግዚአብሔር ከቀጣቸው በኋላ ሰዎች እንደማይኖሩበት እንደ ኦና ስፍራ በመቁጠር ስለ እስራኤል ይናገራል። ኢ.ት፡ “ምድራችንን እንደ ቀበሮዎች መኖሪያ አደረገ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቀበሮዎች

የዱር ውሾችን የሚመስሉ

በሞት ጥላ ሸፈንከን

ጸሐፊው ለሞቱ ባሉት ላይ ጥላውን እንደ ዘረጋ ቁስ አካል አድርጎ የሚናገረው ስለ ሞት ነው። ኢ.ት፡ “እንድንሞት አደረገን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የአምላካችንን ስም ረስተን ከሆነ

እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱን እግዚአብሔርን ነው። እግዚአብሔርን መርሳት ማለት እርሱን ማምለክ ማቆም ማለት ነው። ይህ ያልሆነ ነገር ነው። ኢ.ት፡ “አምላካችንን ረስተን ከነበረ” ወይም “አምላካችንን ማምለክ ትተን ከነበረ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Hypothetical Situations የሚለውን ተመልከት)

ወደ ባዕድ አማልክት እጆቻችንን ዘርግተን

እጆችን መዘርጋት ሰዎች ወደ አምላክ በሚጸልዩበት ጊዜ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው። ኢ.ት፡ “ባዕድን አምላክ አምልከን” ወይም “ወደ ባዕድ አምላክ ጸልየን” (See: Symbolic Action)

እግዚአብሔር ይህንን አያየውም?

ጸሐፊው ሌላ አምላክ አምልከው ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ያውቀው እንደነበር ለመግለጽ ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። ኢ.ት፡ “በእርግጥ እግዚአብሔር ያውቀዋል” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እርሱ የልብን ምስጢር ያውቃል

እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል አዕምሮንና አሳብን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው በምስጢር የሚያስበውን እርሱ ያውቃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቀኑን ሁሉ እንገደላለን

“ቀኑን ሁሉ” የሚለው ሐረግ ሕዝባቸው ባለማቋረጥ መገደላቸውን አጽንዖት ለመስጠት የተደረገ ግነት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከሚገድሉን ሰዎች የተነሣ ሁሌም አደጋ ውስጥ ነን” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እንደሚታረዱ በጎች ተቆጥረናል

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች እንደሚታረዱ በጎች ይቆጥሩናል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

የሚታረዱ በጎች

ጸሐፊው እስራኤላውያኑን ሰዎች አርደው ከሚበሏቸው በጎች ጋር ያነጻጽራቸዋል። በጎች በአራጆቻቸው ፊት ተስፋ እንደሌላቸው ሁሉ እስራኤላውያኑም በጠላቶቻቸው ፊት ተስፋ የላቸውም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 44:23

ጌታ ሆይ ንቃ፣ ለምንስ ትተኛለህ?

እግዚአብሔር በእርግጥ ተኝቷል ማለት አይደለም። ጸሐፊው እግዚአብሔር ፈጥኖ አለመመለሱን እንደ ተኛ ቆጥሮት ይናገራል። እግዚአብሔር ስለ መከራቸው ግድ ያለው መስሎ ስላልታየው እርሱን ለመውቀስ ጥያቄውን ይጠይቃል። ኢ.ት፡ “ጌታ ሆይ! የተኛህ መስሎ ይሰማኛልና ንቃ!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አትጣለን

ጸሐፊው እግዚአብሔር የማይፈለግን ቁራጭ ጨርቅ እንደሚጥል እስራኤልን እንደተወው ይናገራል። ተመሳሳዩን ሐረግ በመዝሙር 44፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “አትተወን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከመጠቃታችን ፊትህን ለምን ትሰውራለህ?

እግዚአብሔር ዝም ያላቸው መስሎ ስለታየው ቅሬታውን ለማቅረብ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት፡ “ከመጠቃታችን ፊትህን አትሰውር” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ፊትህን ሰወርክ

ጸሐፊው እግዚአብሔር እነርሱን መተዉን እንዳያያቸው ፊቱን እንደሰወረባቸው አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ተውከን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስቃያችንን እና መጠቃታችንን ረሳህ

በመሠረቱ “ስቃይ” እና “መጠቃት” የሚሉት ቃላት ትርጉማቸው አንድ ሲሆን የስቃያቸው ክብደት ላይ አጽንዖት ይሰጣል። እነዚህ ቃላት እንደ ግሥ ሊተረጎሙም ይችላሉ። ኢ.ት፡ “ሰዎች እንደሚያሰቃዩንና እንደሚያጠቁን ረሳህ” ወይም “ሰዎች እጅግ እንዳሰቃዩን ረሳህ” (የነገር ስም እና Doublet የሚለውን ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Psalms 44:25

ዐፈር ውስጥ ቀልጠናል፤ ሥጋችን ከምድር ጋር ተጣብቋል

እነዚህ ተመሳሳይ ሐረጎች ተመሳሳዩን ትርጉም ይጋራሉ። ጸሐፊው የራሱን ሕዝብ በተሸናፊነትና በውርደት መሬት ላይ እንደ ተጋደመ ይገልጸዋል። (See: Parallelism)

ዐፈር ውስጥ ቀልጠናል

ጸሐፊው በረዶ ቀልጦ ወደ ዐፈር ውስጥ እንደሚሰርግ አካላቸው ቁስ የሆነ ይመስል ስለ መዋረዳቸው ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሥጋችን ከምድር ጋር ተጣብቋል

ጸሐፊው ራሳቸውን ወደ ላይ ማንሣት እስከማይቻላቸው ድረስ ሥጋቸው ከመሬት ጋር እንደተጣበቀ አድርጎ ስለ መዋረዳቸው ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ተነሥ

ይህ እንዲነሣ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ይህ ሐረግ በአንድ ነገር ላይ እርምጃ ለመውሰድ መጀመርን ያመለክታል። ኢ.ት፡ "እርምጃ ውሰድ" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ስለ ቃል ኪዳን ታማኝነትህ ስትል

የነገር ስም የሆነው "ታማኝነት" እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ "ለቃል ኪዳንህ ታማኝ መሆንህን ለማሳየት" (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Chapter 45

Psalms 45:1

ለሙዚቀኞቹ አለቃ

"ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው"

ለሾሻኒም የተዘጋጀ

ለሾሻኒም የተዘጋጀ

የቆሬ ልጆች መዝሙር

"ይህ የቆሬ ልጆች የጻፉት መዝሙር ነው" ይህ አንድን ሙዚቃ ስልት ወይም ቅኝት ሳያመለክት አይቀርም። አንዳንድ ጊዜ "ለ'ጽጌረዳ' ቅኝት የተዘጋጀ" ተብሎ ተተርጉሟል። ይህንን በመዝሙር 32:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የፍቅር መዝሙር

"የፍቅር መዝሙር"

ልቤ መልካም አሳብ ሞልቶት ያፈስሳል

ጸሐፊው ፈሳሽ ሞልቶት እንደሚያፈስ ዕቃ ስለ ልቡ ይናገራል። "ልብ" የሚለው ቃል በሚዘምረው መዝሙር የተደሰተ ስሜቱን ይወክላል። ኢ.ት፡ "ስለ መልካሙ አሳብ ደስታ ተሰምቶኛል" (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መልካም አሳብ

"የከበረ ርዕሰ ጉዳይ" ወይም "ያማረ ቃል"። ይህ የሚያመለክተው እርሱ የጻፈውን መዝሙር ነው።

የተቀናበረ

የተጻፈ ወይም የተደረሰ መዝሙር

ምላሴ የዝግጁ ጸሐፊ እስክሪብቶ ነው

ጸሐፊው እስክሪብቶ ብሎ የሚናገረው ስለ ምላሱ ነው። ልምድ ያለው ጸሐፊ ቃላትን እንደሚጽፍ እርሱ ቃላትን በብልሃት ይናገራል። ኢ.ት፡ "ምላሴ በደንብ እንደሚጽፍ ሰው እስክሪብቶ ነው" ወይም "ልምድ ያለው ጸሐፊ ቃላትን መጻፍ እንደሚችል ሁሉ እኔም ቃላትን በብልሃት እናገራለሁ" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከሰው ልጆች ይልቅ ውብ ነህ

ይህ ሐረግ ንጉሡ ከማንም ይልቅ ማራኪ ስለመሆኑ አጽንዖት ለመስጠት የተነገረ ግነት ነው። "የሰው ልጆች" የሚለው ሐረግ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል። ኢ.ት፡ "አንተ ከየትኛውም ወንድ ይልቅ መልከ መልካም ነህ" (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በከንፈሮችህ ላይ ጸጋ ይፈስሳል

አንድ ሰው የንጉሡን ከንፈሮች ለመቀባት የተጠቀመበትን ዘይት በሚመስል መልኩ ጸሐፊው የሚናገረው ስለ ጸጋ ነው። "ከንፈሮች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የንጉሡን ንግግር ነው። የሐረጉ ትርጉም፣ ንጉሡ አንደበተ ርቱዕ ነው የሚል ነው። ኢ.ት፡ "አንድ ሰው ከንፈሮችህን በዘይት የቀባቸው ይመስላል" ወይም "አንደበተ ርቱዕ ነህ" (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 45:3

ሰይፍህን በጎንህ ታጠቀው

ተዋጊዎች ሰይፋቸውን በወገባቸው ዙሪያ ባለው ቀበቶ በሚንጠለጠለው ሰገባ ውስጥ ይታጠቁት ነበር። ሰይፉ በጎናቸው በኩል ይቀመጣል። ይህ ሐረግ አንድ ሰው ለጦርነት የሚያደርገውን ዝግጅት ይገልጻል። ኢ.ት፡ "ራስህን ለጦርነት አዘጋጅ" (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

በድል አድራጊነት ገስግስ

ጸሐፊው ንጉሡ በፈረሱ ወይም በሰረገላው ላይ ተቀምጦ ወደ ድል እንዲገሰግስ ይነግረዋል

በእውነተኝነትህ፣ በየዋህነትህና በጽድቅህ ምክንያት

የነገር ስም የሆኑት "እውነተኝነት"፣ "የዋህነት" እና "ጽድቅ" እንደ ቅጽል ሊነገሩ ይችላሉ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) እነዚህ የኃያል ሰው መለያ ናቸው። ኢ.ት፡ "አንተ እውነተኛ፣ የዋህና ጻድቅ ስለሆንክ" ወይም 2) እነዚህ ለሚያስተዳድረው ሕዝብ ሊያቆይላቸው የሚዋጋላቸው መልካም ባህርያት ናቸው። ኢ.ት፡ "ለእውነተኝነት፣ ለየዋህነትና ለትክክለኝነት ለመዋጋት" የሚሉት ናቸው። (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ቀኝ እጅህ አስፈሪ ነገሮችን ያስተምርሃል

አብዛኞቹ ወታደሮች በሚዋጉበት ጊዜ ሰይፋቸውን በቀኝ እጃቻቸው ይይዙ ነበር። እዚህ ጋ "ቀኝ እጅ" የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ጸሐፊው ስለ አንድ፣ ከጦርነት ያገኘውን ልምድ ለንጉሡ ሊያስተምር ስለ ቻለ ሰው፣ የተናገረውን ነው። ኢ.ት፡ "በብዙ ጦርነቶች በመዋጋት ታላላቅ ወታደራዊ ጀብዱዎችን ለመፈጸም ትማራለህ" (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

አስፈሪ ነገሮች

"አስደናቂ ሥራዎችን"። ይህ ጠላቶቹ እንዲፈሩትና ተባባሪዎቹ እንዲያከብሩት የሚያስደርጋቸውን ወታደራዊ ድሎች ያመለክታል።

Psalms 45:5

ሕዝቦች ከበታችህ ይወድቃሉ

ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ንጉሡ ጠላቶቹን ማሸነፉን ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) "ሕዝቦች ተማርከው እግርህ ላይ ይወድቃሉ" ወይም 2) "ሕዝቦች እግርህ ስር ይሞታሉ" የሚሉት ናቸው።

ቀስቶችህ በንጉሡ ጠላቶች ልብ ውስጥ ናቸው

"ቀስቶችህ የጠላቶችህን ልብ ወግተዋል"። ጸሐፊው ንጉሡን በማመልከት በሦስተኛ መደብ የሚናገረው ለንጉሡ ነው።

. . . ዙፋንህ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ነው

"ዙፋን" የሚለው ቃል የንጉሡን መንግሥትና አገዛዝ ይወክላል። ኢ.ት፡ "መንግሥትህ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ነው" ወይም "ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ትነግሣለህ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ሆይ ዙፋንህ

ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ "እግዚአብሔር" የሚለው ቃል 1) የእግዚአብሔር ወኪል የሆነው የንጉሡ መጠሪያ ነው ወይም 2) "ዙፋን" የሚለውን ቃል "እግዚአብሔር የሰጠህ መንግሥት" ለሚለው ተስማሚ ያደርገዋል የሚሉት ናቸው።

በትረ - መንግሥትህ የፍትሕ በትረ - መንግሥት ነው

"በትረ - መንግሥት" የሚለው ቃል መንግሥቱን ለማስተዳደር ያለውን የንጉሡን ሥልጣን ይወክላል። ኢ.ት፡ "መንግሥትህን በፍትሓዊነት ታስተዳድራለህ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላክህ እግዚአብሔር በደስታ ዘይት ቀብቶሃል

ጸሐፊው ስለ ደስታ ሲናገር እግዚአብሔር ንጉሡን ለመቀባት እንደተጠቀመበት ዘይት አድርጎ ይገልጸዋል። እግዚአብሔር እርሱን መቀባቱ ንጉሥ እንዲሆን እንደ መረጠው ምልክታዊ ድርጊት ነው። ኢ.ት፡ "እግዚአብሔር ንጉሥ አድርጎ በሾመህ ጊዜ በጣም ደስ አሰኘህ" (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Symbolic Action የሚለውን ተመልከት)

Psalms 45:8

ከርቤ፣ አደስ፣ እና ጥንጁት

እነዚህ ሰዎች ሽቶ ለመሥራት የሚጠቀሙባቸው መዓዛ ያላቸው እጽዋት ናቸው። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

በዝሆን ጥርስ የተዋቡ ቤተ መንግሥቶች

የዝሆን ጥርስ ከእንስሳ የሚገኝ ነጭና ጠንካራ ነገር ነው። ይህ ሐረግ የሚገልጸው ሰዎች ግድግዳዎቹንና ቁሳቁሶቹን በዝሆን ጥርስ ስላስዋቡት ቤተ መንግሥት ነው።

ባለ አውታር የሙዚቃ መሣሪያዎች ደስ አሰኝተውሃል



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ባለ አውታር የሙዚቃ መሣሪያዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች ባለ አውታር የሙዚቃ መሣሪያ በመጠቀም የሚጫወቱትን ሙዚቃ ነው። ኢ.ት፡ “የባለ አውታሩ ሙዚቃ ደስ አሰኝቶሃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የተከበሩ ሴቶች
እነዚህ ሴቶች የንጉሡን ፈቃድ የሚቀበሉ ሚስቶቹ ናቸው።
ንግሥቲቱ
ይህ ንግሥት ልትሆን ያለችውን ሴት ማመላከቻ ነው። ኢ.ት፡ “ንግሥቲቱ ሙሽራህ” ወይም “ንግሥት የምትሆነው ሙሽራህ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ኦፊር
ይህ በጥሩ ወርቁ የተመሰከረለት የቦታ ስም ነው። ስፍራው አይታወቅም። (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 45:10
ልጄ ሆይ፣ ስሚ
ንግሥቲቱ ወጣት ሴት በመሆኗ ምክንያት ጸሐፊው “ልጄ” በማለት ሊያነጋግራት ይጀምራል።
ጆሮሽን አዘንብዪ
ጸሐፊው አንድን ነገር በጥንቃቄ መስማቱን ለመግለጽ በተናጋሪው ሰው አቅጣጫ ጎንበስ ከማለት ጋር ያገናኘዋል። ኢ.ት፡ “በጥንቃቄ አድምጪ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የገዛ ሕዝብሽን እርሺ
ንግሥቲቱ ልክ ልትረሳቸው በምትችልበት መልኩ ከእንግዲህ የወገኖቿን እምነትና ልማድ መከተል እንደማይኖርባት ጸሐፊው ይናገራል። ኢ.ት፡ “ከእንግዲህ የሕዝብሽን ልማድ መከተል አይኖርብሽም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የአባትሽን ቤት
እዚህ ጋ “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቤተሰብን ነው። ኢ.ት፡ “ዘመዶችሽን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በዚህ መልኩ
“እና” ወይም “እንደዚህ”
ንጉሡ ውበትሽን ይመኛል
ይህ ንጉሡ ሚስቱ አድርጓት ከንግሥቲቱ ጋር ለመተኛት መፈለጉ በጨዋነት የተነገረበት ነው። (See: Eu- phemism)
Psalms 45:12
የጢሮስ ሴት ልጅ
ጸሐፊው በጢሮስ ስለሚኖሩ ሰዎች ሲናገር እንደ ጢሮስ ልጆች ይቆጥራቸዋል። ኢ.ት፡ “የጢሮስ ሕዝብ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የንጉሥ ሴት ልጅ
ይህ ንጉሡ የሚያገባትን ሴት ማንነት የሚያመላክት ነው። ኢ.ት፡ “የንጉሡ ሙሽራ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ሁለንተናዋ ያሸበረቀ
“በጣም ውብ”። ይህ የሴቲቱን ገጽታ ያመለክታል።
ልብሷ በወርቅ የተሠራ ነው
ልብሷ በወርቅ ያጌጠ ወይም የተጠለፈ ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እንደ ሰው በወርቃማ ክር የጠለፈውን ልብስ ትለብሳለች” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 45:14
የተጠለፈበትን ልብስ ለብሳ ወደ ንጉሡ ትወሰዳለች
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የተጠለፈበትን ልብስ እንደ ለበሰች ሰዎች ወደ ንጉሡ ይወስዷታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ጥልፍ
የተለያየ ቀለም ያሏቸውን ክሮች ወደ ጨርቅነት ለመስፋት የተዘጋጀ ንድፍ
አጅበው የሚከተሏትን ደናግል ወደ አንተ ያመጣሉ
እዚህ ጋ፣ “አንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ንጉሡን ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች እርሷን አጅበው የሚከተሏትን ደናግል ያመጡልሃል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ደስታና ሐሴት ይመሯቸዋል
ይህ ሐረግ “ደስታና ሐሴት”ን ሌሎች እንዲደሰቱ የሚመራቸው ዓይነት ሰው ተደርጎ ተገልጿል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ደስታና ሐሴት እነርሱን ይመሯቸዋል” ወይም “በደስታና በሐሴት ወደፊት ይሄዳሉ” (ሰውኛ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ደስታና ሐሴት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ትርጉማቸው አንድ ሆኖ ሳለ የደስታው ጥልቅነት ላይ አጽንዖት የሚሰጡ ናቸው። ኢ.ት፡ “በታላቅ ደስታ” (See: Doublet)
Psalms 45:16
በአባቶቻችሁ ቦታ ልጆቻችሁ ይሆናሉ
ይህ ማለት እርሱ ነገሥታት የነበሩ አባቶቹን እንደተካቸው የንጉሡ ወንዶች ልጆች ንጉሥ በመሆን ይተኩታል ማለት ነው።
በምድር ሁሉ ላይ ገዦችን ታደርጋለህ
“በምድር ሁሉ ላይ” የሚለው በብዙ ሀገሮች እንደሚያስተዳድሩ አጽንዖት ለመስጠት እንጂ ግነት ነው። ኢ.ት፡ “በብዙ ሀገሮች ላይ ገዢዎች እንዲሆኑ ታደርጋቸዋለህ” (ግነት እና ጥቅል አስተያየት የሚለውን ተመልከት)
ትውልድ ሁሉ ስምህን እንዲያስታውስ አደርጋለሁ
እዚህ ጋ በውስጠ ታዋቂነት “እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጸሐፊውን ነው። “ስም” የሚለው ቃል የንጉሡን ጸባይና ምስክርነት ያመለክታል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በየትውልዱ የሚኖሩ ሰዎች ስለ ታላቅነትህ እንዲያውቁ አደርጋቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 46
Psalms 46:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
የቆሬ ልጆች መዝሙር
“ይህ የቆሬ ልጆች የጻፉት መዝሙር ነው”
ለአላሞስ የተዘጋጀ
ይህ ምናልባት አንድን ዓይነት የሙዚቃ ስልት ያመለክት ይሆናል። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር መጠጊያችንና ኃይላችን ነው
ጸሐፊው ሰዎች ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ እንደሚሄዱበት ስፍራ አድርጎ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ደህንነትንና ኃይልን ይሰጠናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ተራሮች ተንቀጥቅጠው ወደ ባህር ልብ ቢሰጥሙ
ጸሐፊው የባህሩን ጥልቅ ክፍል እንደ ባህሩ ልብ ቆጥሮት ይናገራል። እዚህ ጋ፣ ተራሮችን ገለባብጦ ባህር ውስጥ ስለሚጥላቸው የመሬት መንቀጥቀጥ ያብራራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ተራሮች ወደ ባህሩ ጥልቀት እስኪወድቁ ድረስ በኃይል ይንቀጠቀጣሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ውኆቹ ቢቆጡና ቢጮኹም
“የባህሩ ውሃ ቢቆጣና ቢጮህም”። “ቁጣ” እና “ጩኸት” የሚሉት ቃላት በብርቱ ማዕበል ወቅት ባህሩ የሚኖረውን ኃይለኛ እንቅስቃሴ ይገልጻሉ።
ተራሮች ከነእብጠታቸው ይንቀጠቀጣሉ
“እብጠታቸው” የሚለው ቃል ከባህሩ ላይ እየተነሣ ከተራሮች ጋር የሚጋጨውን ውሃ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ያበጡ ውኆች ተራሮቹ እንዲንቀጠቀጡ ያደርጓቸዋል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Psalms 46:4
በምንጮቹ የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ የሚያሰኝ ወንዝ አለ
የወራጅ ወንዝ ሥዕል የእግዚአብሔርን ከተማ ሰላምና ብልጽግና ያሳያል። (See: Symbolic Language)
የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ የሚያሰኝ
“የእግዚአብሔር ከተማ” የሚለው ሐረግ ኢየሩሳሌምን ሲያመለክት በከተማይቱ የሚኖሩትን ሰዎችም ይወክላል። ኢ.ት፡ “በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ሰዎች ደስ ያሰኛቸዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ልዑሉ የሚያድርበት ቅዱሱ ስፍራ
ይህ ሐረግ “የእግዚአብሔር ከተማ”ን ያብራራል። ኢ.ት፡ “ልዑሉ የሚኖርበት ቅዱሱ ስፍራ” (See: As- sumed Knowledge and Implicit Information)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በመካከሏ፤ … ይረዳታል፣ አትናወጥም
“እርሷን” እና “እርሷ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት “የእግዚአብሔር ከተማ”ን ነው።
አትናወጥም
እዚህ ጋ፣ “አትናወጥም” የሚለው ቃል በመዝሙሩ ቁጥር 2 ላይ “አትነቀነቅም” ተብሎ ከተተረጎመው ቃል ጋር አንድ ነው። ጸሐፊው፣ ኢየሩሳሌም በወታደሮች መፍረሷን የመሬት መንቀጥቀጥ እንዳጠፋት አድርጎ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ምንም ነገር እርሷን ሊያጠፋት አይችልም” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 46:6
ሕዝቦች ተቆጡ
እዚህ ጋ፣ “ተቆጡ” የሚለው ቃል ጸሐፊው በመዝሙሩ ቁጥር 3 ላይ የባህሩን ውሃ ከገለጸበት ቃል ጋር አንድ ነው። ታላቅ ማዕበል በሚሆንበት ጊዜ የባህሩ ውሃ በኃይል እንደሚንቀሳቀስ ስለ ሕዝቦች ፍርሐት ይናገራል። ኢ.ት: “ሕዝቦች ፈረተዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
መንግሥታቱ ተነቀጥቅጠዋል
እዚህ ጋ፣ “ተንቀጥቅጠዋል” የሚለው ቃል ጸሐፊው በመዝሙሩ ቁጥር 2 ላይ የመሬት መንቀጥቀጡ በተራሮቹ ላይ ያስከተለውን ለመግለጽ ከተጠቀመበት ቃል ጋር አንድ ነው። ጸሐፊው በሰራዊት አማካይነት የሚወድቀውን መንግሥት ልክ የመሬት መንቀጥቀጥ እንዳጠፋው አድርጎ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ሰራዊቱ መንግሥቱን ገለበጠው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ድምፁን አነሣ
“እግዚአብሔር ድምፁን አነሣ”። ጸሐፊው “ድምፅ”ን አንድ ሰው ከመሬት አንሥቶ ወደ ሰማይ ከፍ እንደሚያደርገው ቁስ አድርጎ ይናገራል። ይህ ድምፁ ከፍ ያለ ይሆናል ማለት ነው። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ጮኸ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ምድሪቱ ቀለጠች
ጸሐፊው መሬትን እንደ አንዳች ነገር፣ ለምሳሌ ሊቀልጥ እንደሚችል በረዶ አድርጎ ይናገራል። እዚህ ጋ፣ “ምድሪቱ” የሰው ዘርን ስትወክል፣ መቅለጥ ደግሞ ፍርሐትን ይወክላል። ኢ.ት: “በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች በፍርሃት ይንቀጠቀጣሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር ሰዎች ደህንነት ፍለጋ እንደሚሄዱበት ስፍራ አድርጎ ይገልጸዋል። ኢ.ት: “የያዕቆብ አምላክ ደህንነትን ይሰጠናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የያዕቆብ አምላክ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ያዕቆብ ያመለከው አምላክ” ወይም 2) “ያዕቆብ” የእስራኤል ሕዝብ የሚገለጽበት ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ “የእስራኤል አምላክ” ማለት ነው የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 46:8
ጦርነቶችን ያስቀራል
“ሀገራት እንዳይዋጉ ያግዳቸዋል”
እስከ ምድር ዳርቻ ደረስ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን በዓለም ላይ በሁሉም ስፍራ ማለት ነው። ኢ.ት: “በዓለም ላይ በሁሉም ስፍራ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ቀስትን ይሰብራል … ጋሻዎችን ያቃጥላል
እግዚአብሔር ጦርነቶችን ሁሉ ከሚያስቀርባቸው መንገዶች አንዱ ወታደሮች እርስ በርሳቸው የሚዋጉባቸውን የጦር መሣሪያዎች በማጥፋት ነው።
Psalms 46:10
ዝም በሉና እኔ አምላክ መሆኔን ዕወቁ
እዚህ ጋ እግዚአብሔር መናገር ይጀምራል።
ዝም በሉ
በዚህ ዐውድ፣ እነዚህ ቃላት ሀገራት ጦርነቶቻቸውን እንዲያቆሙ የተሰጣቸው ትዕዛዝ ሊሆን ይችላል። ኢ.ት: “መዋጋት አቁሙ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
እኔ አምላክ መሆኔን ዕወቁ
እዚህ ጋ፣ “ዕወቁ” የሚለው ቃል ትርጉም እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ መሆኑን መረዳትና መመስከር ነው።
በሕዝቦች መካከል እከብራለሁ፤ በምድር ላይ እከብራለሁ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ በዓለም ላይ ያሉ ሀገራት ሕዝቦች ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያከብሩት አጽንዖት ይሰጣሉ። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ከሀገራት ሁሉ ሰዎች ያከብሩኛል፤ በምድር ሁሉ ላይ የሚኖሩ ሰዎች ያከብሩኛል” (Parallelism እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የሰራዊት አምላክ ከእኛ ጋር ነው፤ የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር ሰዎች ደህንነት ፍለጋ እንደሚሄዱበት ስፍራ አድርጎ ይገልጸዋል። እነዚህን በመዝሙር 46:7 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

## Chapter 47

Psalms 47:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
የቆሬ ልጆች መዝሙር
“ይህ የቆሬ ልጆች የጻፉት መዝሙር ነው”
እጆቻችሁን አጨብጭቡ
“እጆቻችሁን አጨብጭቡ” ከደስታ ጋር ተዛምዷል። ኢ.ት: “በደስታ እጆቻችሁን አጨብጭቡ” (Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
በድል አድራጊነት ድምፅ ወደ እግዚአብሔር ጩኹ
“በደስታ ድምፅ ወደ እግዚአብሔር ጩኹ”። እዚህ ጋ፣ “በድል አድራጊነት” የሚለው ቃል ከድል ጋር የተዛመደውን ደስታ ያመለክታል።
Psalms 47:3
ሕዝቦችን ከበታቻችን፣ ሀገራትንም ከእግሮቻችን በታች ያስገዛል
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች ተመሳሳዮች ናቸው፤ ትርጉሙም፣ እስራኤል ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ እግዚአብሔር አስችሏቸዋል ማለት ነው። (See: Parallelism)
ያስገዛል
ድል ማድረግና በሌላው ሥልጣን ሥር እንዲሆኑ ማድረግ
ከበታቻችን … ከእግሮቻችን በታች
ጸሐፊው ሌሎች ሕዝቦችን ስለ ማሸነፍ ሲናገር እነዚያ ሕዝቦች ከእግሮቻቸው ሥር እንደተደረጉ ያህል አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ርስታችንን ይመርጥልናል
ጸሐፊው የእስራኤልን ምድር ቋሚ ንብረት እንዲሆናቸው እግዚአብሔር ለሕዝቡ በርስትነት እንደሰጣቸው አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “ይህችን ምድር ርስት እንዲሆነን ይመርጥልናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የያዕቆብ ክብር
እዚህ ጋ፣ “ክብር” የሚለው ቃል የኩራትን ምንጭ ያመለክታል፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ርስት አድርጎ የሰጣቸውን ምድርም ይወክላል። ኢ.ት: “ያዕቆብ የሚኮራበት ምድር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የወደደውን ያዕቆብን
“ያዕቆብ” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አምላክ በዕልልታ ዐረገ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ሕዝቦችን ድል ስለማድረጉ ሲናገር እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ በቤተ መቅደስ በሚገኘው ዙፋን ላይ እንደሚቀመጥ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “ሕዝቡ ዕልል እያሉ እግዚአብሔር ወደ መቅደሱ ዐረገ” ወይም “ሕዝቡ ዕልል እያሉ እግዚአብሔር ዙፋኑ ላይ ተቀመጠ” (ዘይቤአዊ አነጋገር፣ እና Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ
ይህ ሐረግ ቀደም ሲል ከነበረው ሐረግ ጋር ተመሳሳይ ነው። ለግልጽነቱ ግሥ ሊጨመርበት ይችላል። ኢ.ት: “ሕዝቡ መለከቶቹን እየነፉ እግዚአብሔር ዐረገ” (See: Parallelism and Ellipsis)
Psalms 47:6
ምስጋናን ለእግዚአብሔር ዘምሩ፣ ምስጋናን ዘምሩ፤ ምስጋናን ለንጉሣችን ዘምሩ፣ ምስጋናን ዘምሩ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ምስጋናን ዘምሩ” የሚለው ሐረግ አጽንዖት ለመስጠት ተደግሟል። ድግግሞሹ በአንተ ቋንቋ የማይመች ከሆነ ልትተወው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ዘምሩ፣ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ዘምሩ፤ ዘምሩ፣ ለንጉሣችን ምስጋናን ዘምሩ” (See: Parallelism)
Psalms 47:8
የሕዝቦች ልዑላን
“የሕዝቦች ሁሉ ገዢዎች”
ከሕዝቡ ጋር በአንድነት ተሰበሰቡ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ የሕዝቦቹ ገዢዎች 1) “በሕዝቡ ፊት ለፊት ተሰበሰቡ” ወይም 2) ሁሉም እግዚአብሔርን እንደ ንጉሥ ሊያመልኩት “ከሕዝቡ ጋር በአንድነት ተሰበሰቡ” የሚሉት ናቸው።
የምድር ጋሻዎች የእግዚአብሔር ናቸው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ “ጋሻዎች” 1) የጦር መሣሪያዎችን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “በምድር ካሉ ነገሥታት የጦር መሣሪያዎቻቸው ይልቅ እግዚአብሔር የበለጠ ኃይል አለው” ወይም 2) ሕዝባቸውን ለመጠበቅ እንደ ጋሻ የተነገረላቸውን የሕዝቦቹን ገዢዎች ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የምድር ነገሥታት ለእግዚአብሔር ተገዢዎች ናቸው” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Chapter 48
Psalms 48:1
የቆሬ ልጆች መዝሙር
“የቆሬ ልጆች የጻፉት መዝሙር ይህ ነው”
ከፍ ያለ ምስጋና ይገባዋል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች ከፍ ያለ ምስጋና ያቅርቡለት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የአምላካችን ከተማ በተቀደሰው ተራራው ላይ
ይህ በጽዮን ተራራ ላይ የተሠራችውን ኢየሩሳሌምን ያመለክታል።
የአምላካችን ከተማ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “አምላካችን የሚኖርበት ከተማ” ወይም 2) “የአምላካችን የሆነው ከተማ” የሚሉት ናቸው።
በከፍታው ላይ የተዋበው
“የተዋበና ከፍ ያለ”። “ከፍታ” የሚለው ቃል የጽዮን ተራራ ምን ያህል ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል።
የምድር ሁሉ ደስታ ጽዮን ናት
እዚህ ጋ፣ “ምድር” የሚለው ቃል በምድር ላይ የሚኖሩትን ሁሉ ያመለክታል። “ደስታ” የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የጽዮን ተራራ በምድር ለሚኖሩ ሁሉ ደስታን ይሰጣል” ወይም “በጽዮን ተራራ ምክንያት በምድር የሚኖሩ ሁሉ ይደሰታሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
በሰሜን በኩል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ ይህ ሐረግ 1) የሰሜንን አቅጣጫ ያመለክታል ወይም 2) “የእግዚአብሔር ተራራ” የሚል ትርጉም ላለው የጽዮን ተራራ ሌላኛው ስሙ ነው የሚሉት ናቸው።
እንደ መሸሸጊያ በሆኑት ቤተ መንግሥቶቿ እግዚአብሔር ራሱን ገልጧል
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር ሰዎች ለደህንነታቸው እንደሚደበቁበት ስፍራ አድርጎ ይገልጸዋል። ኢ.ት፡ “በጽዮን ተራራ ቤተ መንግሥቶች ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ደህንነትን የሚሰጥ ሆኖ ራሱን ገልጧል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 48:4
ተመልከቱ
እዚህ ጋ፣ “ተመልከቱ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስደናቂ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።
ራሳቸውን አከማቹ
እዚህ ጋ፣ ነገሥታቱ ሰራዊታቸውን ይወክላሉ። ኢ.ት፡ “ሰራዊታቸውን አከማቹ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በአንድነት አለፉ
“በኢየሩሳሌም በኩል በአንድነት አለፉ”
አዩአት
“ኢየሩሳሌምን አዩአት”
ሰጉ
እጅግ ተረበሹ
በዚያ መንቀጥቀጥ ያዛቸው
x
Psalms 48:7
በምስራቁ ንፋስ የተርሴስን መርከቦች ትሰብራለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) እግዚአብሔር በታላቅ ንፋስ ስለሚያጠፋቸው እንደሚናወጡ መርከቦች፣ ይህ ጸሐፊው የንጉሡን መፍራት የሚገልጽበት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በምስራቁ ንፋስ በሰባበርካቸው ጊዜ የተርሴስ መርከቦች እንደተናወጡ እነርሱ በፍርሐት ተናወጡ” ወይም 2) ይህ ደራሲው የእግዚአብሔርን ታላቅ ኃይል የሚገልጽበት ምልክት ነው የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Apostrophe የሚለውን ተመልከት)
የምስራቅ ንፋስ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ከምስራቅ የሚነፍሰው ንፋስ” ወይም 2) “ከባድ ንፋስ” የሚሉት ናቸው።
የተርሴስ መርከቦች
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ ይህ የሚያመለክተው 1) ወደዚያ የሚጓዙ ወይም በተርሴስ የሚሠሩ መርከቦችን ወይም 2) የትኛውንም በውቅያኖስ ላይ መጓዝ የሚችል ትልቅ መርከብን ነው የሚሉት ናቸው።
እንደ ሰማነው
እግዚአብሔር ባለፉት ዘመናት ያደረጋቸውን ታላላቅ ነገሮች መስማታቸውን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ስላደረጋቸው ታላላቅ ነገሮች እንደሰማነው” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
እኛም ደግሞ አይተናል
ይህ ማለት የሰሟቸው ነገሮች እውነት ስለመሆናቸው ማረጋገጫውን አይተዋል። ኢ.ት፡ “አሁንም እግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን ሲሠራ አይተናል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
በሰራዊት ጌታ ከተማ፣ በአምላካችን ከተማ
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት ኢየሩሳሌምን ነው። ኢ.ት፡ “በሰራዊት ጌታ፣ በአምላካችን ከተማ” (See: Paral- lelism)
ያጸናታል
“የተጠበቀች ያደርጋታል”። እዚህ ጋ፣ “ማጽናት” የሚለው ቃል ትርጉም አንድን ነገር ማቆየት እና መጠበቅ ማለት ነው።
Psalms 48:9
የቃል ኪዳን ታማኝነትህ
የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ለቃል ኪዳንህ ምን ያህል ታማኝ እንደሆንክ” ወይም “ከቃል ኪዳንህ የተነሣ ለእኛ ምን ያህል ታማኝ እንደሆንክ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
በመቅደስህ መካከል
“በመቅደስህ ውስጥ እያለን”
እንደ ስምህ ሁሉ ... ምስጋናህም እስከ ምድር ዳርቻ ደረሰ ነው
እዚህ ጋ፣ “ስም” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ባህርይና ዝና ይወክላል። ሁለቱ ሐረጎች የእግዚአብሔርን የታላቅነቱን ዝና ሰዎች እርሱን እንዴት ከፍ ባለ ሁኔታ ያመሰግኑት እንደሆነ ያነጻጽራሉ። ኢ.ት፡ “ስምህ እጅግ ታላቅ ነው ... በዓለም የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርቡልሃል” ወይም “በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ስለ አንተ ሰምተዋል ... ስለዚህ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ያመሰግኑሃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እስከ ምድር ዳርቻ ደረሰ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን በዓለም ላይ በሁሉም ስፍራ ማለት ነው። ይህንን በመዝሙር 46:9 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ቀኝ እጅህ በጽድቅ ተሞልቷል
ጸሐፊው ጽድቅን እግዚአብሔር በእጁ ሊይዘው እንደሚችለው ቁስ አድርጎ ይናገራል። እዚህ ጋ፣ “እጅ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ኃይልና የመግዛት ሥልጣኑን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “በጽድቅ ትገዛለህ” ወይም “አንተ ስትገዛም ጻድቅ ነህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 48:11
የጽዮን ተራራ ደስ ይበለው

ጸሐፊው የጽዮንን ተራራ ሊደሰት እንደሚችል ሰው አድርጎ ይናገርለታል። ሐረጉ በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። ኢ.ት: “በጽዮን ተራራ የሚኖሩ ደስ ይበላቸው” (ሰውኛ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የይሁዳ ሴቶች ልጆች ደስ ይበላቸው
ጸሐፊው በይሁዳ የሚገኙትን ከተሞች እንደ ይሁዳ ልጆች አድርጎ ይናገራል። ሐረጉ በእነዚያ ከተሞች የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። ኢ.ት: “በይሁዳ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች ደስ ይበላቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 48:12
በጽዮን ተራራ አካባቢ ተመላለሱ፣ በዙሪያዋም ሂዱ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ናቸው። ኢ.ት: “በጽዮን ተራራ ዙሪያ ሁሉ ተመላለሱ” (See: Parallelism)
በሚገባ ተመልከቱ
“በዝርዝር ተመልከቱ”
Psalms 48:14
እርሱ መሪያችን ይሆናል
“መሪ” የሚለው ቃል እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “እርሱ ይመራናል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
እስከ ሞት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “እስክንሞት ድረስ” ወይም 2) “ለዘላለም” የሚሉት ናቸው።

---

Chapter 49
Psalms 49:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
የቆሬ ልጆች መዝሙር
“ይህ የቆሬ ልጆች የጻፉት መዝሙር ነው”
ሕዝቦች ሁሉ ይህንን ስሙ፤ የምትኖሩባትም ሁሉ ጆሮአችሁን ስጡ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳዮች ናቸው። በአንድ ላይ ሰዎች ሁሉ እንዲሰሙ የተሰጠውን ትዕዛዝ ያጠናክራሉ። (See: Parallelism)
ጆሮአችሁን ስጡ
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም አንድ ሰው ለመስማት ጆሮውን ማዘጋጀቱ ነው። ኢ.ት: “ስሙ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ዝቅተኞችና ከፍተኞች
ጸሐፊው ደካሞች ወይም በማኅበረሰቡ ውስጥ ቦታ የማይሰጣቸውን ሰዎች እንደ ዝቅተኞች፣ አስፈላጊዎችና ብርቱዎቹን ሰዎች እንደ ከፍተኞች በመቁጠር ይናገራል። “ዝቅተኛ” እና “ከፍተኛ” የሚሉት ቃላት በአንድነት ሰዎችን ሁሉ ይወክላሉ። ኢ.ት: “አስፈላጊ የሆኑና ያልሆኑ ሰዎች ሁሉ” ወይም “በየትኛውም የማኅበራዊ ደረጃ ያሉ ሰዎች” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Merism የሚለውን ተመልከት)
ሀብታሙና ድኻው በአንድነት
“ሀብታም” እና “ድኻ” የሚሉት ቃላት በአንድነት የብልጽግናቸውን ልክ ሳይሆን ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል። ኢ.ት: “ሰዎች ሁሉ” (See: Merism)
Psalms 49:3
አፌ ጥበብን ይናገራል
እዚህ ጋ፣ “አፍ” የሚለው ቃል የሚናገረውን ሰው ሁለንተና ያመለክታል። ኢ.ት: “የጥበብን ቃል እናገራለሁ” (See: Synecdoche)
የልቤም ጥልቅ አሳብ ማስተዋልን
እዚህ ጋ፣ “ልብ” የሚለው ቃል አዕምሮንና አሳብን ይወክላል። የነገር ስም የሆነው “ጥልቅ አሳብ” እና “ማስተዋል” እንደ ግሥ ሊተረጎሙ ይችላሉ። ኢ.ት: “በጥልቀት የማስበው አሳብ እንድታስተውል ይረዳሃል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ጆሮዬን አዘነብላለሁ
ጸሐፊው በጥንቃቄ መስማትን አጎንብሶ፣ ጆሮን ወደሚናገረው ሰው እንደ ማቅረብ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “በጥንቃቄ ስማ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በበገና
“በገና ስደረድር”
ተረከዜን … ለምን እፈራለሁ?
ጸሐፊው ክፉ ነገር በሚመጣበት ጊዜ የሚፈራበት ምክንያት ሊኖር እንደማይገባ አጽንዖት ለመስጠት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት: “ተረከዜን … የምፈራበት ምክንያት የለኝም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ክፉ ቀናትን
“ክፉ ነገሮች በሚመጡበት ጊዜ”። እዚህ ጋ “ቀናት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጥቅሉን የጊዜ ክፍልፋይ ነው።
ኃጢአት ተረከዜን በከበበኝ ጊዜ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ጸሐፊው የጠላቶቹን ክፉ ምኞት ሊቀማው እንደተዘጋጀ ዘራፊ በመቁጠር ይናገራል። ኢ.ት: “የኃጢአተኞች ኃጢአት ሊያሸንፈኝ በሚዘጋጅበት ጊዜ” ወይም 2) የጸሐፊው ጠላቶች ኃጢአት በመሥራት ላይ እያሉ እርሱን ከበውታል” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 49:6
በብልጽግናቸው የሚታመኑ
እነዚህ ሰዎች ብልጽግናቸው መከራ እንዳይደርስባቸው እንደሚያደርግ ይታመናሉ። (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ስለ ሀብታቸውም ብዛት
የአንድ ነገር በብዛት መኖር
አንድም እንደሌለ የታወቀ ነው
“ማናቸውም የሚችሉበት መንገድ የለም” ወይም” ወይም ኢ.ት: “ማንም አይችልም”
ማንም ወንድሙን ማዳን አይችልም ወይም ስለ እርሱ ለእግዚአብሔር ዋጋ አይሰጥም
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚገልጹት አንድ ሰው ሞትን ለማስቀረት ለእግዚአብሔር በቂ ገንዘብ መስጠት እንደማይችል ነው። ኢ.ት: “ወንድሞቻቸው እንዳይሞቱ ለእግዚአብሔር ገንዘብ መክፈል የሚችል ማንም የለም” (See: Assumed Knowl- edge and Implicit Information and Parallelism)
የአንድን ሰው ሕይወት መቤዠት ዋጋው ውድ ነው
“መቤዠት” የሚለው ቃል ከግሥ ጋ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “የአንድን ሰው ሕይወት መቤዠት ከፍ ያለ ዋጋ ያስከፍላል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Psalms 49:9
ሰውነቱ እንዳይበሰብስ
ይህ በመቃብር ውስጥ የሚበሰብሰውን ሰውነት ያመለክታል።
መበስበስን ያያል
ጸሐፊው አንድን ነገር መለማመድ ያንን ነገር እንደማየት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “ይሞትና ሰውነቱ ይበሰብሳል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጠቢባን ይሞታሉ፤ ሰነፎችና ጨካኞችም እንደዚሁ ይጠፋሉ
ጸሐፊው እጅግ ጠቢብ የሆኑትና ከዚያም የሚያንሱትን በመጥቀሱ ሰዎችን ሁሉ ያመላክታል። (See: Merism)
ጨካኝ
ይህ ማለት የማይረባና ብልሃት የጎደለው ሰው ማለት ነው።
Psalms 49:11
የውስጥ አሳባቸው
“እምነታቸው”
ከትውልድ እስከ ትውልድ የሚኖሩባቸው ስፍራዎች
ቀደም ብሎ ካለው ሐረግ ግሡ ሊጨመርበት ይችላል። ኢ.ት: “የሚኖሩባቸው ስፍራዎች ለትውልዶች ሁሉ ይተላለፋሉ” (See: Ellipsis)
ምድራቸውን በስሞቻቸው ይጠራሉ
“በስሞቻቸው ይጠራሉ”። ይህ ሐረግ ባለቤትነትን ይገልጻል። ኢ.ት: “ምድራቸውን የራሳቸው ያደርጋሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 49:12
ሰው ግን ሀብት ያለው
“ሰው ግን፣ ሀብት እንኳን ቢኖረው”
ይህ መንገዳቸው የጅልነታቸው ነው
ጸሐፊው የሞኞችን ዕጣ ፈንታ የሚራመዱበት የመንገዳቸው መጨረሻ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “በጅልነት የሚኖሩ ዕጣ ፈንታቸው ይህ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሆኖም ከእነርሱ በኋላ
“ሆኖም ከሞቱ በኋላ”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Psalms 49:14

እንደ በጎች

ጸሐፊው የሚሞቱትን ሰዎች ሁሉ ከበግ መንጋ ጋር ያነጻጽራቸዋል። ልክ አራጁ ሊያርዳቸው በሚወስንበት ጊዜ በጎች ማምለጥ እንደማይችሉ ሰዎችም የሚሞቱበት ጊዜ ሲደርስ አያመልጡም። (See: Simile)

ተወስነዋል

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "እግዚአብሔር ወስኗቸዋል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሞት እረኛቸው ይሆናል

ጸሐፊው ሞትን ወደ መቃብር እንደሚመራቸው ሰው በመቁጠር ስለሚሞቱ ሰዎች ይናገራል። ኢ.ት: "እረኛ በጎችን ወደሚታረዱበት እንደሚወስዳቸው ሞት ይወስዳቸዋል" (ሰውኛ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በጠዋት

እዚህ ጋ "ጠዋት" የሚለው ቃል ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን እግዚአብሔር ጻድቃንን ነጻ የሚያወጣበትንና ከክፉ ሰዎች የሚያድንበትን ጊዜ ያመለክታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሰውነታቸው በሲዖል ይቃጠላል

ሲዖል ሰው ወይም እንስሳ የሆነ ይመስል ጸሐፊው የሙታን ስፍራ ስለሆነው ስለ እርሱ ይናገራል። ስለ ሬሳ መበስበስ ሲናገርም ሲዖል እነርሱን እንደሚበላቸው አድርጎ ይናገራል። (ሰውኛ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ሕይወቴን ከሲዖል ኃይል ያድናታል

ጸሐፊው ስለ ሲዖል ሲናገር በሚሞቱት ላይ ኃይል እንዳለው ሰው አድርጎ ይገልጸዋል። ከዐውዱ አንጻር ይህ ኃይል የሙታንን አካል እንደሚበላ ያመለክታል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ሕይወቴን ያድናታል

እዚህ ጋ "ሕይወት" የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና ያመለክታል። ኢ.ት: "እግዚአብሔር ያድነኛል" (See: Synecdoche)

Psalms 49:16

የቤቱ ክብር ይጨምራል

እዚህ ጋ፣ "ክብር" የሚለው ቃል ሀብትን ወይም ብልጽግናን ያመለክታል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) "በቤቱ የበለጠ ሀብት በሚያገኝበት ጊዜ" ወይም 2) "ቤተሰቡ በሚበለጽጉበት ጊዜ" የሚሉት ናቸው።

ምንም ነገር አይወስድም

"ምንም ነገር ከራሱ ጋር ወደ መቃብር አይወስድም"

ክብሩ ተከትሎት አይወርድም

"መውረድ" የሚለው ቃል ሰው የሚሞትበትን ጊዜ ያመለክታል። ኢ.ት: "እርሱ በሚሞትበት ጊዜ ክብሩ ከእርሱ ጋር አይሄድም" ወይም "በሚሞትበት ጊዜ ዝናውን አያቆይም" (See: Euphemism)

Psalms 49:18

ነፍሱን ባርኳል

እዚህ ጋ "ነፍስ" የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና ያመለክታል። የዚህ ሐረግ ትርጉም፣ በሀብቱ ምክንያት ራሱን ደስተኛና ስኬታማ አድርጎ ይቆጥራል የሚል ነው። ኢ.ት: "ራሱን 'እንኳን ደስ ያለህ' ብሏል" (See: Synecdoche እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ለራስህ በምትኖርበት ጊዜ ሰዎች ያመሰግኑሃል

እዚህ ጋ፣ ጸሐፊው ሰዎች በዓለማዊው መስፈርት ስኬታማ ስለሆኑ ስለ ሌሎች ሰዎች እንዴት እንደሚናገሩ ጠቅለል ያለ አባባል አቅርቧል።

ለራስህ ስትኖር

ይህ ሐረግ በዓለማዊው መስፈርት በስኬታማነት መኖርን ያመለክታል። ኢ.ት: "ለራስህ መልካሙን አድርግ" ወይም "በስኬት ኑር" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ወደ አባቶቹ ትውልድ ይሄዳል

"የአባቶቹ ትውልድ ወዳለበት ይሄዳል"። ይህ የተሻለ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ሀብታሙ ሰው ይሞትና በመቃብር ውስጥ ከአባቶቹ ጋር ይገናኛል የሚል ነው። ኢ.ት: "መቃብር ውስጥ ከአባቶቹ ጋር ይገናኛል" (See: Euphemism)

ዳግመኛ ብርሃንን ከቶ አያዩም

በውስጠ ታዋቂ ያለው "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሀብታሞችንና አባቶቻቸውን ነው። "ብርሃን" የሚለው ቃል ፀሐይን ያመለክት ይሆናል ወይም በዘይቤአዊ አነጋገር ሕይወት ሊሆን ይችላል። ኢ.ት: "ዳግመኛ ፀሐይን ከቶ አያዩም" ወይም "ዳግመኛ ከቶ በሕይወት አይኖሩም" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Chapter 50

Psalms 50:1

የአሳፍ መዝሙር

"ይህ አሳፍ የጻፈው መዝሙር ነው"

ኃያሉ አምላክ፣ እግዚአብሔር

ደራሲው ስለ እግዚአብሔር ለመናገር የተለያዩ ሦስት ስሞችን ይጠቀማል።

ምድርን ጠርቷል

እዚህ ጋ፣ "መሬት" የሚለው ቃል በምድር ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። ኢ.ት: "ሰዎችን ሁሉ ጠርቷል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያው ድረስ

ይህ ሐረግ ፀሐይ የምትወጣበትን የምስራቅ አቅጣጫና የምትገባበትን የምዕራብ አቅጣጫ ያመለክታል። ጸሐፊው በምድር ላይ ሁሉን ስፍራ እንዲወክል እነዚህን ሁለት ጽንፎች ይጠቀማል። ኢ.ት: "በምድር ላይ በሁሉም ስፍራ" (See: Merism)

የውበት መደምደሚያ ጽዮን

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) "ውበቷ ፍጹም የሆነ ጽዮን" ወይም 2) "እጅግ የተዋበችው ከተማ ጽዮን" የሚሉት ናቸው።

እግዚአብሔር አበራ

ጸሐፊው እግዚአብሔርን እንደሚያበራ ብርሃን አድርጎ ይናገራል። ይህ ሰዎች ስለ ክብሩ እንዲያውቁ እግዚአብሔር እንደሚያደርግ ያመለክታል። ኢ.ት: "የእግዚአብሔር ክብር እንደ ብርሃን ያበራል" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:3

ዝም አይልም

ጸሐፊው አዎንታዊው ንግግር ላይ አጽንዖት ለመስጠት አሉታዊውን ይጠቀማል። ኢ.ት: "ሁሉም ሊሰማው እንዲችል አድርጎ ይናገራል" (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

በፊቱ እሳት ይበላል

ይበላቸው ይመስል ጸሐፊው የሚናገረው ነገሮችን ስለሚያቃጥል እሳት ነው። ኢ.ት: "በፊት ለፊቱ እሳት ይቃጠላል" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ብርቱ ዐውሎ ነፋስም በዙሪያው ነው

"ታላቅ ዐውሎ ነፋስ በዙሪያው አለ"

በላይ ያሉ ሰማያትንና ምድርን ይጠራል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ በሚፈርድበት ጊዜ በሰማይና በምድር ላይ የሚኖሩትን ሁሉ ምስክሮች እንዲሆኑ ይጠራቸዋል ወይም 2) እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ በሚፈርድበት ጊዜ ልክ እንደ ሰዎች ምስክር እንዲሆኑ ለሰማይና ለምድር ይናገራል የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:6

ሰማያት ያውጃሉ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ጸሐፊው "ሰማያት" በሚለው ቃል በዚያ የሚኖሩትን መላእክት ለማመልከት ይጠቀማል ወይም 2) ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ እንደሚመሰክር ሰው በመቁጠር ስለ "ሰማያት" ይናገራል የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 50:7

ስለ መሥዋዕቶችህ አልነቅፍህም

"እነቅፍሃለሁ፣ ስለ መሥዋዕቶችህ ግን አይደለም"። እግዚአብሔር የሚወቅሳቸው በመሥዋዕቶቻቸው ምክንያት እንዳልሆነ ያስታውቃቸዋል።

መንቀፍ

አንድ ሰው የማይገባውን ነገር እንዳደረገ ለእርሱ መንገር

የሚቃጠሉ መሥዋዕቶችህ ሁልጊዜ በፊቴ ናቸው

እግዚአብሔር ስለ መሥዋዕታቸው ለምን እንደማይወቅሳቸው ይኼ ያብራራል። "ሁልጊዜ በፊቴ ናቸው" የሚለው ሐረግ በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ መሆንን የሚያመለክት ሲሆን ትርጉሙም የእርሱ የሆነው ሕዝብ የሚቃጠሉ መሥዋዕቶችን ሁልጊዜ እያቀረቡለት ነው የሚል ይሆናል። ኢ.ት: "እናንተ ሁልጊዜ የሚቃጠል

መሥዋዕት እያቀረባችሁልኝ ነው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 50:9
በረት
በጎችና ፍየሎች የሚጠበቁበት፣ ዙሪያው የታጠረ አካባቢ
በሺህ ኮረብታ ላይ ያሉ የቀንድ ከብቶች
“በሺህ ኮረብታዎች ላይ” የሚለው ሐረግ በአጠቃላይ የእግዚአብሔር የሆኑትን የቀንድ ከብቶች ቁጥር አይወክልም። ቁጥሩ የተጋነነ ሲሆን በዓለም ላይ ያሉት የቀንድ ከብቶች ሁሉ የእግዚአብሔር ስለመሆናቸው አጽንዖት ይሰጣል። ቀደም ብሎ ካለው ቁጥር ግሥ ሊጨመርበት ይችላል። ኢ.ት፡ “በዓለም ላይ ያሉት የቀንድ ከብቶች ሁሉ የእኔ ናቸው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና Ellipsis የሚለውን ተመልከት)
አንድ ሺህ ኮረብታዎች
“1000 ኮረብታዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ወፎችን ሁሉ አውቃቸዋለሁ
እዚህ ጋ “አውቃለሁ” የሚለው ቃል ባለቤትነትን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ወፎች ሁሉ የእኔ ናቸው” (የአነጋገር ዘይቤ፣ Assumed Knowledge እና Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
Psalms 50:12
ቢርበኝም እንኳን
ይህ እግዚአብሔር ስለማይቆጣ ሊሆን ያልቻለን አንድን ነገር ያብራራል። (See: Hypothetical Situations)
የኮርማዎችን ሥጋ እበላለሁ ወይስ የፍየሎችን ደም እጠጣለሁ?
እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች እንደማያደርግ፣ በመሆኑም መሥዋዕታቸው እንደማያስፈልገው አጽንዖት ለመስጠት ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት፡ “የኮርማዎችን ሥጋ አልበላም ወይም የፍየሎችን ደም አልጠጣም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 50:14
ለእግዚአብሔር አቅርብ
እዚህ ጋ እግዚአብሔር የሚያመለክተው ወደ ራሱ ነው። ኢ.ት፡ “አቅርብልኝ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
ስእለትህን ለልዑሉ ክፈል
ጸሐፊው አንድ ሰው ለእግዚአብሔር የሚከፍለው ገንዘብ በሚመስል መልኩ ስለ “ስእለት” ይናገራል። ኢ.ት፡ “ለልዑሉ ስእለትህን ፈጽም” ወይም “ለልዑሉ ለማድረግ ቃል የገባኸውን አድርግ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በመከራ ቀን
እዚህ ጋ፣ “ቀን” የሚለው ቃል የትኛውንም የጊዜ ክፍል የሚያመለክት ነው። ኢ.ት፡ “መከራ በሚገጥምህ ጊዜ ሁሉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 50:16
ለክፉው ሰው ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይለዋል
እዚህ ጋ፣ እግዚአብሔር ገና እየተናገረ ነው፣ ስለ ራሱ የሚናገረውም በሦስተኛ መደብ አድርጎ ነው። ኢ.ት፡ “ለክፉው ግን እንዲህ እላለሁ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
ለክፉው ሰው
“ክፉ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክፉ የሆኑትን ሰዎች በአጠቃላይ ነው። ኢ.ት፡ “ለክፉ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
ቃሌን ወዲያ ትጥላለህና . . . ሕጌን ለማወጅ ምን መብት አለህ?
እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ለመውቀስ ይህንን ጥያቄ ይጠቀምበታል። ይህ ጥያቄ ወደ ንግግር ሊቀየር ይችላል። ኢ.ት፡ “ትምህርቴን ስለምትጠላና ቃሌን ወዲያ ስለምትጥል ሕጌንና ቃል ኪዳኔን ማወጅህ ትርጉም አይኖረውም” ወይም “ሕጌን ማወጅ ለአንተ ተገቢህ አይደለም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
በአፍህ ቃል ኪዳኔን መውሰድህ
ክፉ ሰዎች የቃል ኪዳን ቃሉን ማነብነባቸውን እግዚአብሔር ኪዳኑን በአፋቸው እንዳስቀመጡት አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ስለ ቃል ኪዳኔ መናገርህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቃሌን ወዲያ ጥለሃል
ክፉ ሰዎች ቆሻሻን እንደሚጥሉ እርሱ የሚናገረውን መጣላቸውን እግዚአብሔር ይናገራል። ኢ.ት፡ “እኔ የምናገረውን ጥለሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 50:18
ከእርሱ ጋር ትስማማለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) የሌባውን ተግባር ያጸድቃሉ። ኢ.ት፡ “ታጸድቁታላችሁ” ወይም 2) በተግባራቸው ሌባውን ይተባበሩታል። ኢ.ት፡ “ትተባበሩታላችሁ” የሚሉት ናቸው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
አፍህን ለክፋት ሰጠህ
ክፉ ነገርን ስለሚናገር ሰው፣ የዚያ ሰው አፍ፣ ክፉ ነገርን እንዲያደርግ ለሚልከው ለእርሱ መልዕክተኛ እንደሚሆን እግዚአብሔር ይናገራል። ኢ.ት፡ “አንተ ሁሌም የምትናገረው ክፉ ነገርን ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Synec- doche የሚለውን ተመልከት)
ምላስህ ማታለልን ይገልጣል
“ምላስ” የሚለው ቃል የሚወክለው ተናጋሪውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “አንተ ሁልጊዜ ትዋሻለህ” (See: Synecdoche)
ተቀምጠህ ወንድምህን አማኸው፤ የገዛ እናትህን ልጅ ስም አጠፋህ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የተለያየ ቃል ቢጠቀሙም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በቤተሰብ አባሎቻቸው ላይ በሐሰት ስለመናገራቸው እግዚአብሔር ይወቅሳቸዋል። (See: Parallelism)
ተቀምጠህ ተናገርክ
በአንድ ሰው ላይ “ተቀምጠህ ተናገርክ” ማለት ይህ ሰው ስለሌላው ሰው ሆነ ብሎ ክፉ ነገሮችን ያወራል ማለትን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ሁሌም ስለምትናገርባቸው መንገዶች ታስባለህ” (የአነጋገር ዘይቤ፣ Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
Psalms 50:21
እኔም ልክ እንዳንተው እንደሆንኩ አሰብክ
እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ሳይገስጻቸው ዝም በማለቱ ምክንያት እያደረጉት ያሉትን እግዚአብሔር እንዳጸደቀላቸው አሰቡ። ኢ.ት፡ “ልክ አንተ እንደምታደርገው እኔም እንደማደርግ አሰብክ” (See: Assumed Knowledge እና Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
መውቀስ
ለአንድ ሰው የማይገባውን በማድረጉ በደለኛ ስለ መሆኑ መንገር
ያደረግከውን ነገር ሁሉ … አምጣ
ያደረጉትን ክፉ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚዘረዝራቸው ይናገራል። ኢ.ት፡ “ያደረግከውን ነገር ሁሉ … ዘርዝር” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በዐይኖችህ ፊት መልካም
እዚህ ጋ “በዐይኖችህ ፊት” መሆን ማለት ሊያዩት በሚችሉበት ቦታ ማለት ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ የሚያቀርበውን ክስ ለመካድ አይችሉም ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ልክ በፊት ለፊታችሁ” ወይም “ልትክዷቸው በማትችሉባቸው ሁኔታዎች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እናንተ እግዚአብሔርን የምትረሱ
እግዚአብሔርን የተዉትን ክፉዎች እርሱን እንደረሱት አድርጎ ይናገራል። ስለ ራሱ በሦስተኛ መደብ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እኔን የምትተዉኝ እናንተ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
እሰባብራችኋለሁ
ያደነውን እንደሚበላ አንበሳ እግዚአብሔር ክፉዎችን እንደሚያጠፋቸው ይናገራል። ኢ.ት፡ “አጠፋችኋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 50:23
መንገዱን ቀና ለማድረግ ያቅዳል
እግዚአብሔር አንድ ሰው የሚኖርበትን የሕይወት አኳኋን ሰውዬው እንደሚጓዝበት መንገድ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ሕይወቱን በትክክለኛው መንገድ ይመራል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔርን ድነት አሳየዋለሁ
የነገር ስም የሆነው “ድነት” እንደ “ማዳን” ተደርጎ ሊነገር ይችላል። እግዚአብሔር በሦስተኛ መደብ ወደ ራሱ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “አድነዋለሁ” (የነገር ስም እና አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

Chapter 51


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Psalms 51:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚመለከተው ዳዊትን ነው ወይም 3) መዝሙሩ የዳዊትን መዝሙሮች ዘይቤ የተከተለ ነው የሚሉት ናቸው።
ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ
ናታን ወደ ዳዊት በመጣ ጊዜ ያደረገው ነገር በግልጽ ሊነገር ይችላል፣ ምክንያቱም ይህ መዝሙር ለዚያ ምላሽ ነውና። ኢ.ት፡ “ነቢዩ ናታን ወደ ዳዊት መጥቶ በገሰጸው ጊዜ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
ከቤርሳቤህ ጋር ከተኛ በኋላ
“ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ከተኛ በኋላ”
ስለ ቃል ኪዳን ታማኝነትህ
የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “አንተ ለኪዳንህ ታማኝ ስለሆንክ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
እጅግ ብዙ ስለሆኑት ምሕረትን የተሞሉ ሥራዎች
“እጅግ ብዙ የምሕረት ሥራዎችን ታደርጋለህና”
መተላለፌን ደምስሰው
ኃጢአትን ይቅር ማለት 1) እንደ መደምሰስ ወይም 2) በጽሑፍ የተመዘገበውን ኃጢአት እንደ መሰረዝ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው አንድን ነገር ጠርጎ እንደሚያስወግደው ኃጢአቴን ይቅር በለኝ” ወይም “አንድ ሰው የተመዘገበውን ኃጢአት እንደሚሰርዝ ኃጢአቴን እርሳው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከበደሌ ፈጽመህ አጠበኝ … ከኃጢአቴ አንጻኝ
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚሉት አንድ ነገር ነው። (See: Parallelism)
ከበደሌ ፈጽሞ አጠበኝ
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ንጹሕ እንደ መሆን ተደርጎ ተነግሯል። እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት ይቅር በማለት ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያደርጋል። ኢ.ት፡ “ኃጢአቴን ሁሉ አጠብልኝ” ወይም “በአንተ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረኝ ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ፈጽሞ
ሙሉ በሙሉ፣ ጨርሶ
ከኃጢአቴ አንጻኝ
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ንጹሕ እንደ መሆን ተደርጎ ተነግሯል። እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት ይቅር በማለት ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያደርጋል። ኢ.ት፡ “ከኃጢአቴ አንጻኝ” ወይም “ንጹሕ እንድሆን ኃጢአቴን ይቅር በለኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 51:3
ኃጢአቴ ሁልጊዜ በፊቴ ነው
ኃጢአቱን ለመርሳት አለመቻሉ ሁልጊዜ ሊያየው በሚችልበት በፊት ለፊቱ እንዳለ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ስለ ኃጢአቴ ሁልጊዜ አውቃለሁ” ወይም “ኃጢአቴን ልረሳው አልችልም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በፊትህ ክፉ የሆነውን
እዚህ ጋ “ፊት” የሚለው ቃል የሚወክለው ፍርድን ነው። እግዚአብሔር የዳዊትን ድርጊት ተመልክቶ አልተቀበለውም። ኢ.ት፡ “አንተ ክፉ ነው ያልከውን” ወይም “አንተ ክፉ እንደሆነ የቆጠርከውን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 51:5
እይ፣ የተወለድኩት በአመፅ ነው … እይ፣ አንተ ታማኝነትን ትፈልጋለህ
እዚህ ጋ፣ ሁለቱ የ “እይ” አጠቃቀሞች ትኩረታችንን በሁለቱ ሁኔታዎች መካከል ወዳለው ንጽጽር ይስቡታል። ኢ.ት፡ “በእውነት እኔ የተወለድኩት በአመፅ ነው … አንተ ግን ታማኝነትን ትፈልጋለህ”
እይ፣ የተወለድኩት በአመፅ ነው … እናቴ እንደ ፀነሰችኝ በኃጢአት ውስጥ ነበርኩኝ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚሉት አንድ ነገር ሲሆን በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት አጽንዖት ለመስጠት ነው። (See: Paral- lelism)
የተወለድኩት በአመፅ ነው
ኃጢአተኛ መሆን በደለኛ እንደመሆን ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “በተወለድኩ ጊዜ ወዲያው ኃጢአተኛ ሆንኩኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እናቴ እንደ ፀነሰችኝ በኃጢአት ውስጥ ነበርኩኝ
ኃጢአተኛ መሆን በኃጢአት ውስጥ እንደመሆን ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እናቴ በፀነሰችኝ ጊዜ እንኳን እኔ ኃጢአተኛ ነበርኩ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በውስጡ ማንነቴ ታማኝ እንድሆን ትፈልጋለህ
“ውስጣዊ ማንነት” የሚወክለው 1) የሰውየውን ፍላጎት ወይም 2) ሙሉዉን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “ታማኝነትን እንድመኝ ትፈልጋለህ” ወይም “ታማኝ እንድሆን ትፈልጋለህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)
Psalms 51:7
አንጻኝ … እጸላሁ … አጠበኝ … ከበረዶ ይልቅ ነጭ እሆናለሁ
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ንጹሕ ወይም ነጭ እንደመሆን ተቆጥሮ ተነግሯል። እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት ይቅር በማለት ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በሂሶጵ አንጻኝ
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር፣ እርሱን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ውሃ እንደሚረጭበት ካህን አድርጎ ይገልጸዋል። ኢ.ት፡ “ውሃውን በሂሶጵ ነክረህ በእኔ ላይ በመርጨት ተቀባይነት እንዲኖረኝ አድርገኝ” ወይም “በአንተ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረኝ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሂሶጵ
ይህ ካህናት ለማንጻት ሥርዓት፣ ይኸውም ለእግዚአብሔር ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ በሰዎች ወይም በሌሎች ነገሮች ላይ ውሃ ወይም ደም ለመርጨት የሚጠቀሙበት ተክል ነው። (See: የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
ከበረዶ ይልቅ ነጭ
ኃጢአት የሌለበት መሆን ነጭ እንደ መሆን ተቆጥሯል። ኢ.ት፡ “እጅግ፣ በጣም ነጭ” (See: Simile)
ደስታና ሐሴት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት የሚሉት አንድ ነገር ሆኖ አስደሳች ነገሮችን ለመስማት ባለው ምኞት ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። (See: Doublet)
የሰበርካቸው አጥንቶቼ ደስ ይሰኙ ዘንድ
ስለ ተሰማው እስከፊ ሐዘን ሲገልጽ አጥንቶቹ እንደተሰበሩ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “በውሳጣዊው ማንነቴ ላይ የከፋ ሐዘን እንዲደርስብኝ አድርገሃልና። እንደገና ደስ ይበለኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ
ስለ አንድ ሰው ኃጢአት ማሰብ ኃጢአቱን እንደ ማየት ሆኖ ተነግሯል። ይቅር ማለት ወይም ኃጢአቱን ለማሰብ አለመፍቀድ ለማየትም እንዳለመፍቀድ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ኃጢአቴን አትመለከት” ወይም “ኃጢአቴን አታስታውሰው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ኃጢአቴን ሁሉ ደምስስልኝ
የአንድን ሰው ኃጢአት ይቅር ማለት ወይም ለማሰብ አለመፍቀድ 1) እንደ መደምሰስ ወይም 2) በጽሑፍ የተመዘገበውን ኃጢአት እንደ መሰረዝ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ 1) “አንድ ሰው አንድን ነገር ጠርጎ እንደሚያስወግደው ኃጢአቴን ይቅር በለኝ” ወይም “አንድ ሰው የተመዘገበውን ኃጢአት እንደሚሰርዝ ኃጢአቴን እርሳው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 51:10
በውስጤ ንጹህ ልብን ፍጠርልኝ
እዚህ ጋ፣ “ልብ” ምኞትንና ስሜትን ይወክላል። ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መሰጠትና መታዘዝ ንጹሕ ልብ እንዳለው ሰው ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ሙሉ በሙሉ ለአንተ የተሰጠ ሰው አድርገኝ” ወይም “ሁልጊዜ አንተን ለመታዘዝ እንድፈልግ አድርገኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ትክክለኛውን መንፈስ በውስጤ አድስ
እዚህ ጋ “መንፈስ” የሚወክለው የዳዊትን ጠባይና ምኞት ነው። ኢ.ት፡ “ጠባዬን ትክክለኛ አድርገው” ወይም “ሁልጊዜ ትክክል የሆነውን እንዳደርግ አድርገኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከህልዎትህ አታርቀኝ
“ከአንተ ተለይቼ እንድሄድ አታስገድደኝ”። በእግዚአብሔር የተተወ መሆን ከእርሱ ተለይቶ እንዲሄድ እንደመገደድ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ከሕዝብህ እንደ አንዱ አትተወኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 51:12
ደግፈኝ
“ከፍ አድርገኝ” ወይም “አግዘኝ”

መንገድህን
“ሰዎች እንዲኖሩት የምትፈልገውን መንገድ” ወይም “ሰዎች እንዲያደርጉት የምትፈልገውን”
ተላላፊዎች ... ኃጢአተኞች
እዚህ ጋ፣ እነዚህ ሁለት ቃላት የሚያመለክቱት አንዱን ዓይነት ሰዎች ነው።
Psalms 51:14
ደም ከማፍሰስ
ይህ ሐረግ ሌላውን ሰው መግደልን ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጌታ ሆይ፣ ከንፈሮቼን ክፈታቸው፣ አፌም ምስጋናህን ይናገራል
እዚህ ጋ፣ ሰውዬው በ”አፍ” ተወክሏል። መናገር መቻል እንደ ከንፈሮች መከፈት ተነግሯል። እዚህ ጋ መናገር አለመቻል በኃጢአት ምክንያት በደለኛና መከላከል የማይችል የመሆን ምልክት ነው። ኢ.ት፡ “ጌታ ሆይ፣ መናገር እንድችል አድርገኝ፣ እኔም አመሰግንሃለሁ” (See: Synecdoche)
በመሥዋዕት ደስ አትሰኝም ... የሚቃጠል መሥዋዕትም አያስደስትህም
ይህ ማለት እግዚአብሔር ከእነዚህ ነገሮች ይልቅ በይበልጥ የሚፈልገው ነገር አለ። ኢ.ት፡ “አንተን ለማስደሰት መሥዋዕት በቂ አይደለም... አንተ ከሚቃጠል መሥዋዕት ይልቅ አብልጠህ የምትፈልገው ነገር አለ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

Psalms 51:17
የእግዚአብሔር መሥዋዕት
“እግዚአብሔርን የሚያስደስት መሥዋዕት”
የተሰበረ መንፈስ
የተሰበረ መንፈስ ትሁት ጠባይን ይወክላል። ኢ.ት፡ “ትህትና” ወይም “ትሁት የሆነ ሰው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የተሰበረና የተጸጸተ ልብ
ትሁት መሆንና ስለ ኃጢአት ማዘን የተሰበረና የተጸጸተ ልብ እንዳለው ሰው መሆን ተደርጎ ተነግሯል። ልብ ስሜትንና ፈቃድን ይወክላል። ኢ.ት፡ “ሀዘንና ትህትና” ወይም “ስለ ኃጢአቱ የሚያዝንና ትሁት የሆነ ሰው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የኢየሩሳሌምን ግንቦች አድስ
የአንድ ከተማ ግንቦች ከተማይቱንና በውስጧ የሚኖሩትን ሰዎች ይጠብቃሉ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የኢየሩሳሌምን ግንቦች እንድናድስ አስችለን” ወይም 2) “ኢየሩሳሌምን ጠብቃትና አበርታት” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሕዝባችን በመሰዊያህ ላይ ኮርማዎችን ያቀርባሉ
ኮርማ ወደ በሬነት እያደገ ያለ ነው። እግዚአብሔር በሰጠው መመሪያ መሠረት ኮርማዎች አብዛኛውን ጊዜ ለመሥዋዕት የሚቀርቡ እንስሶች ናቸው።

---

Chapter 52
Psalms 52:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
ማሺል
ይህ ምናልባት አንድን ዓይነት የሙዚቃ ስልት ያመለክት ይሆናል። ይህንን በመዝሙር 32:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዶይቅ ... አቢሜሌክ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
አንተ ኃያል ሰው፣ ችግር በመፍጠርህ ለምን ትኩራራለህ?
ይህ ጥያቄ ዳዊት ችግር በፈጠረው ላይ እንዴት እንደተቆጣ ያሳያል። ኢ.ት፡ “አንተ ኃያል ሰው፣ ችግር በመፍጠርህ መኩራራት አልነበረብህም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አንተ ኃያል ሰው
ዳዊት ዶይቅን እንዲህ ብሎ በሚጠራበት ጊዜ ምጸትን ሳይጠቀም አይቀርም። ኢ.ት፡ “ኃያል እንደሆንክ የምታስብ ሰው ሆይ” (See: Irony)
የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት በየቀኑ ይመጣል
ዳዊት፣ ሊመጣ እንደሚችል አንዳች ነገር አድርጎ የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት ነው። የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” እንደ ቅጽል ወይም ተውሳከ ግሥ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር የሰጠውን የቃል ኪዳን ተስፋ ለመጠበቅ በየዕለቱ ታማኝ ነው” ወይም “እግዚአብሔር በየዕለቱ ሕዝቡን እንዳንተ ካሉ ክፉ ሰዎች ይጠብቃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር፣ Assumed Knowledge፣ Implicit Information እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ስል መቁረጫ
ስል ምላጭ
እንደ ስል መቁረጫ ምላስህ በማታለል እየሠራ ጥፋትን ያቅዳል
እዚህ ጋ ምላስ ትልቅ ጉዳት ሊያስከትል ከሚችል ስል መቁረጫ ጋር ተነጻጽሯል። ኢ.ት፡ “ጥፋትን በምታቅድበትና ሌሎችን በምታታልልበት ጊዜ ምላስህ እንደ ስል መቁረጫ ሰዎችን ይጎዳል” (See: Simile)
ምላስህ
እዚህ ጋ “ምላስህ” ዳዊት እየተናገረው ያለውን ሰው ያመለክታል። ኢ.ት፡ “አንተ” (See: Synecdoche)
Psalms 52:3
ጽድቅን ከመናገር ይልቅ መዋሸትን
“ትክክል የሆነውን ከመናገር የበለጠ መዋሸትን ትወዳለህ”
Psalms 52:4
ሌሎችን የሚበሉ ቃላቶችን

እዚህ ጋ ሌሎችን የሚጎዱ ቃላት ሰዎችን እንደሚበሉ የዱር እንስሶች ተደርገው ተነግረዋል። ኢ.ት፡ “ሌሎችን የሚጎዱ ቃላት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አንተ አታላይ ምላስ ሆይ
ይህ ደራሲው የሚናገረውን ሰውዬ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የማታለልን ቃል የምትናገር አንተ” ወይም “አንተ ውሸታም” (See: Synecdoche)
መንጥቆ ያወጣሃል ... ይጎትትሃል ... ይነቅልሃል
እነዚህ ሦስቱም ሐረጎች በተለያየ መንገድ “ያስወግድሃል” የሚል ትርጉም አላቸው። (See: Parallelism)
ከሕያዋን ምድር ይነቅልሃል
በምድር ላይ ሕያው ሆኖ መኖር፣ ሥራቸውን በመሬት ውስጥ በሚያደርጉ ተክሎች ተመስለው ስለ ሰዎች ተነግሯል። እግዚአብሔር አንድን ሰው መግደሉ ልክ የተክልን ሥር ከመሬት ውስጥ እንደ መንቀል ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ከሕያዋን ምድር ይወስድሃል” ወይም “ከሕያዋን ሰዎች ጋር በምድር ላይ እንዳትኖር ይገድልሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሴላ
ይህ ሰዎች እንዴት መዘመር ወይም የሙዚቃ መሣሪያ መጫወት እንዳለባቸው የተነገራቸው ሙዚቃዊ ቃል ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል ሲጽፉ አንዳንድ ትርጉሞች ደግሞ ይህንን አያካትቱም። (ቃላትን ቅዳ ወይም ተዋስ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 52:6
ጻድቃን ይህንን አይተው ይፈራሉ
“ጻድቃን ደግሞ እግዚአብሔር እርሱን ሲያስወግደው ያዩና ይፈራሉ”
እነሆ
“እዩ” ወይም “ስሙ” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ”
እግዚአብሔርን መጠጊያው ያላደረገ
እዚህ ጋ “መጠጊያ” የሚወክለው ተከላካይን ነው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔርን ተከላካዩ ያላደረገ” ወይም “እግዚአብሔር እንዲከላከልለት ያልጠየቀ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 52:8
የለመለመ የወይራ ዛፍ
የለመለመ የወይራ ዛፍ ጠንካራና አስተማማኝ ነው፤ ተሰብሮ አይወድቅም።
እኔ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እንደ ለመለመ የወይራ ዛፍ ነኝ
ጉዳት በማያገኘውና በአስተማማኝ ሁኔታ ውስጥ መሆን ጠንካራ ዛፍ እንደ መሆን ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እኔ እንደ ለመለመ የወይራ ዛፍ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ጠንካራ ነኝ” ወይም “በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ስለማመልክ እንደ ለመለመ የወይራ ዛፍ አስተማማኝ ጥበቃ አለኝ” (See: Simile)
በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ

ይህ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ያመለክታል።
ከዘላለም እስከ ዘላለም በእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት ላይ እታመናለሁ
የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” ከቅጽል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እርሱ ለኪዳኑ ታማኝ ስለሆነ ከዘላለም እስከ ዘላለም በእግዚአብሔር እታመናለሁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
በስምህ ተስፋ አደርጋለሁ፣ እርሱ መልካም ነውና
የእግዚአብሔር ስም ራሱን እግዚአብሔርን ይወክላል። እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ የሚወክለው እግዚአብሔር እንዲረዳው እርሱን ተስፋ ማድረግን ነው። ኢ.ት፡ “አንተ መልካም ስለሆንክ ተስፋ አደርግሃለሁ” ወይም “አንተ መልካም ስለሆንክ እንድትረዳን ተስፋ አደርግሃለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 53
Psalms 53:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
ለማሃላዝ የተዘጋጀ
ይህ ምናልባት አንድን የሙዚቃ ስልት ዓይነት ያመለክት ይሆናል። (ቃላትን ቅዳ ወይም ተዋስ የሚለውን ተመልከት)
ማሺል
ይህ ምናልባት አንድን የሙዚቃ ስልት ዓይነት ያመለክት ይሆናል። ይህንን በመዝሙር 32፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የሰው ልጆች
ይህ ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል።
እርሱን የሚፈልግ
እግዚአብሔርን እንደ ሰው መፈለግ እርሱን እንደ “መፈለግ” ሆኖ ተነግሯል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) እግዚአብሔርን ለማወቅ መፈለግ። ኢ.ት፡ “እርሱን ለማወቅ የሚፈልግ” ወይም 2) እግዚአብሔርን ማምለክ። ኢ.ት፡ “እርሱን የሚያመለክ” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሁሉም ወደ ኋላ ተመልሰዋል
እግዚአብሔርንና ትክክል የሆነውን መተው ወደ ኋላ እንደ መመለስ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ሁሉም ትክክል የሆነውን ከማድረግ ወደ ኋላ ተመልሰዋል” ወይም “ሁሉም እግዚአብሔርን ትተውታል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 53:4
እግዚአብሔር … ለእነዚያ … ኃጢአትን ለሚሠሩ ማስተዋል የላቸውም?
ሕዝቡ እጅግ ኃጢአተኞች በመሆናቸው ጸሐፊው የተሰማውን ድንጋጤ ለማሳየት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ ሁለት ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። “እነዚያ ኃጢአትን የሚሠሩ ሰዎች ምንም ነገር እንደማያውቁ ያህል ያደርጋሉ። እንጀራን እንደሚበሉ ሕዝቤን ይበላሉ፣ እግዚአብሔርንም አይጠሩም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
እንጀራን እንደሚበሉ ሕዝቤን የሚበሉ እነዚያ
ሕዝብን ማጥፋት እነርሱን እንደመብላት ተደርጎ ተነግሯል። እንጀራን በሚበሉበት መልኩ ማድረጋቸው የሚያመለክተው ያንን ያደረጉት በቀላሉ ወይም በደለኝነት ሳይሰማቸው መሆኑን ነው። ኢ.ት፡ “እንጀራን የሚበሉ ያህል በነጻነት ሕዝቤን የሚያጠፉ እነዚያ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Simile የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር፣ ማንንም በአንተ ላይ የሚሰፍረውን አጥንቱን ይበታትነዋል
የሰዎችን አጥንት መበታተን የሚወክለው እነርሱን መግደልንና በአግባቡ እንዳይቀበሩ አጥንቶቻቸው በሞቱበት ስፍራ ሁሉ እንዲቀመጥ መተውን ነው። “እግዚአብሔር ማንንም በአንተ ላይ የሚሰፍረውን ፈጽሞ ያጠፋዋል፣ አጥንቶቻቸውም በምድር ላይ ተበታትነው ይቀራሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ማንንም በአንተ ላይ የሚሰፍረውን
በሰዎች ላይ መስፈር እነርሱን መውጋትን ይወክላል። የጠላት ሰራዊት ሊወጋው ወደሚፈልገው ሕዝብ በመጓዝ በአቅራቢያው በጊዜያዊነት የሚኖርበትን የጦር ሰፈር ይሠራል። ኢ.ት፡ “አንተን የሚወጋህ ማንም ቢሆን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 53:6
ምነው የእስራኤል ድነት በመጣ!
እዚህ ጋ “ምነው” የሚለው ቃል ተስፋን ወይም ጸሎትን የሚገልጽ ቃለ አጋኖን ያስተዋውቃል። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ድነት እንደሚመጣ ተስፋ አደርጋለሁ” ወይም “ድነት እንዲመጣ እጸልያለሁ” (ቃለ አጋኖ የሚለውን ተመልከት)
የእስራኤል ድነት ከጽዮን ይመጣል
ድነት መቅደሱ በጽዮን የሆነውን፣ አዳኙን እግዚአብሔርን ይወክላል። ኢ.ት፡ “የእስራኤል አዳኝ ከጽዮን ይመጣል” ወይም “እግዚአብሔር ከጽዮን ይመጣና እስራኤልን ያድናል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ሕዝቡን ከምርኮ በሚመልስበት ጊዜ
“እግዚአብሔር የተማረከ ሕዝቡን በሚያድንበት ጊዜ”
ያዕቆብ ደስ ይለዋል፣ እስራኤልም ሐሴትን ያደርጋል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው። (See: Parallelism)
ያዕቆብ
እዚህ ጋ “ያዕቆብ” የሚያመለክተው የያዕቆብ ዘር የሆኑትን እስራኤላውያንን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 54
Psalms 54:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
አውታር ባላቸው የሙዚቃ መሣሪያዎች
“ሰዎች ከዚህ መዝሙር ጋር አውታር ያላቸውን የሙዚቃ መሣሪያዎች መጫወት አለባቸው”
ማሺል
ይህ አንድ የሙዚቃ ስልት ዓይነትን ያመለክት ይሆናል። ይህንን በመዝሙር 32፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዜፋውያን
ከኬብሮን ደቡባዊ ምስራቅ፣ በይሁዳ ተራሮች ላይ ያለው የዚፍ ከተማ ሰዎች። (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ዳዊት በእኛ ዘንድ ተደብቆ የለምን?
ሳዖል ሊያውቀው የሚገባው አስፈላጊ ነገር መሆኑን ለማሳየት ይህ ዓይነቱ ጥያቄ ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት፡ “ዳዊት በእኛ ዘንድ ተደብቋል”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ሆይ፣ በስምህ አድነኝ
እዚህ ጋ፣ የእግዚአብሔር ስም ባህርዩን ይወክላል። በተለይም ኃይሉንና ፍትሐዊነቱን ሊወክል ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ በኃይልህ አድነኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በብርታትህ ፍረድልኝ
እዚህ ጋ ለዳዊት መፍረድ፣ እርሱ በደለኛ አለመሆኑን ለሕዝብ ማሳየትን ይወክላል። እግዚአብሔር ዳዊትን ለማዳን ብርታቱን በሚጠቀምበት ጊዜ ዳዊትን በደለኛ አድርጎ እንዳልፈረደበት ሰዎች ያውቃሉ። ኢ.ት፡ “በደለኛ አለመሆኔን በብርታትህ ለሕዝቡ አሳያቸው” ወይም “እኔን ለመታደግ ኃይልህን በመጠቀም በደለኛ አለመሆኔን ለሕዝቡ አሳያቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለቃሌ ጆሮህን ስጥ
የአንድ ሰው ጆሮ መስጠት መስማትን ይወክላል። ኢ.ት፡ “ቃሌን ስማ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የአፌን ቃል
እዚህ ጋ ተናጋሪው በአፉ ተወክሏል። ኢ.ት፡ “ቃሎቼን” ወይም “እኔ የምነግርህን” (See: Synecdoche)
በእኔ ላይ ተነሥተዋል
በአንድ ሰው ላይ መነሣት እርሱን ለማጥቃት መዘጋጀትን ወይም ማጥቃትን ይወክላል። ኢ.ት፡ “እኔን ለማጥቃት ተዘጋጅተዋል” ወይም “እያጠቁኝ ነው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጨካኞች ሰዎች
“ምንም ርኅራኄ የሌላቸው ሰዎች”
ሕይወቴን ፈልገዋታል
የአንድን ሰው ሕይወት መፈለግ እርሱን ለመግደል መሞከርን ይወክላል። ኢ.ት፡

“ሊገድሉኝ ሞክረዋል” ወይም “ሊገድሉኝ ይፈልጋሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔርን በፊታቸው አላስቀመጡትም
እግዚአብሔርን በፊታቸው ማስቀመጥ ለእግዚአብሔር ትኩረት መስጠትን ይወክላል። ኢ.ት፡ “ለእግዚአብሔር ትኩረት አይሰጡም” ወይም “እግዚአብሔርን ቸል ብለዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 54:4
ደግፎ የሚይዘኝ
ለዳዊት መከላከልና ጥበቃ ማድረግ ደግፎ እንደ መያዝ ወይም እርሱን እንደ ማገዝ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “የሚከላከልልኝ” ወይም “ጥበቃ የሚያደርግልኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለጠላቶቼ በክፋት ይከፍላቸዋል
ቅጣት እንደ ክፍያ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ጠላቶቼ ክፋትን ስላደረጉብኝ እርሱም ክፉን ያደርግባቸዋል” ወይም “ጠላቶቼ በእኔ ላይ ያደረጉትን ክፋት በእነርሱም ላይ እንዲደረግ ያደርጋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በታማኝነትህ አጥፋቸው
እዚህ ጋ፣ ዳዊት ስለ እግዚአብሔር ከመናገር ለእግዚአብሔር ወደ መናገር ይቀይረዋል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ለእኔ ታማኝ ነህና አጥፋቸው”
Psalms 54:6
እግዚአብሔር ሆይ፣ መልካም ነውና ለስምህ ምስጋናን አቀርባለሁ
የእግዚአብሔር ስም እርሱን ይወክለዋል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ መልካም ነህና ምስጋናን አቀርብልሃለሁ” (See: Synecdoche)
ዐይኔ ተመልክቷል
ዐይን ሰውዬውን ይወክላል። ኢ.ት፡ “ተመልክቻለሁ” (See: Synecdoche)
ዐይኔ በጠላቶቼ ላይ በድል አድራጊነት ተመልክቷል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጠላቶቹ ድል ሲደረጉ መመልከትን። ኢ.ት፡ “ጠላቶቼ ድል ሲደረጉ ተመልክቻለሁ” ወይም 2) ጠላቶቹን ድል ማድረጉን። ኢ.ት፡ “ጠላቶቼን ድል አድርጌአቸዋለሁ” የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 55
Psalms 55:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
አውታር ባላቸው የሙዚቃ መሣሪያዎች
“ሰዎች ከዚህ መዝሙር ጋር አውታር ያላቸውን የሙዚቃ መሣሪያዎች መጫወት አለባቸው”
ማሺል
ይህ አንድ የሙዚቃ ስልት ዓይነትን ያመለክት ይሆናል። ይህንን በመዝሙር 32፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ለጸሎቴ ጆሮህን ስጥ
የአንድ ሰው ጆሮ መስጠት የሚወክለው መስማትን ነው። ኢ.ት፡ “ጸሎቴን ስማ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከልመናዬ ራስህን አትሰውር
ለልመናው ትኩረትን አለመስጠት ራሱን እንደ ሰወረ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ልመናዬን ቸል አትበል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከጠላቶቼ ድምፅ የተነሣ
እዚህ ጋ፣ “ድምፅ” የሚወክለው እነርሱ የሚናገሩትን ነው። ኢ.ት፡ “ጠላቶቼ ከሚናገሩት ነገር የተነሣ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
መከራን ያመጡብኛል
መከራ እንዲሆን ማድረግ መከራን እንደማምጣት ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ታላቅ መከራ እንዲደርስብኝ ያደርጋሉ” ወይም “እኔ እንድሰቃይ ክፉ ነገሮችን ያደርጉብኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 55:4
ልቤ በውስጤ ይንቀጠቀጣል
እዚህ ጋ፣ “ልብ ይንቀጠቀጣል” ስቃዩንና የሕመም ስሜቱን ያመለክታል። ይህ ስቃይ የሆነበት ከፍርሐት የተነሣ ነው። ኢ.ት፡ “እጅግ ስለ ፈራሁ እየተሰቃየሁ ነው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የሞት ድንጋጤ በላዬ ወደቀብኝ
በጣም መፍራትን ወይም መሸበርን ለመግለጽ ድንጋጤን በአንድ ሰው ላይ እንደሚወድቅበት አንዳች ነገር ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እሞታለሁ ብዬ በጣም ፈርቻለሁ” ወይም “እሞታለሁ ብዬ ተሸብሬአለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ፍርሃትና መንቀጥቀጥ መጥተውብኛል
ፈሪ መሆንና መንቀጥቀጥ ልክ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ በሰው ላይ እንደሚመጣ እንደ አንዳች ነገር ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “በጣም ፈርቼ እንቀጠቀጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሽብር ዋጠኝ
የመሸበር ስሜት ሰዎችን እንደሚሸፍናቸው እንደ አንዳች ነገር ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ከባድ ሽብር ይሰማኛል” ወይም “እጅግ ፈርቻለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 55:6
ምነው እንደ እርግብ ክንፍ ብቻ በኖረኝ!
ይህ ጩኸት ጸሐፊው በጣም የተመኘውን ነገር ይገልጻል። ኢ.ት፡ “እንደ እርግብ ክንፍ እንዲኖረኝ በጣም እመኛለሁ” (See: Exclamations)
በርሬ እሄድ ነበር
“ክንፍ ቢኖረኝ ኖሮ በርሬ እሄድ ነበር”
እነሆ፣ ከዚያ እቅበዘበዝ ነበር
“ይህንን እና ሌላም አደርግ ነበር፤ እቅበዘበዝ ነበር”
ሴላ
ይህ ሰዎች እንዴት መዘመር ወይም የሙዚቃ መሣሪያ መጫወት እንዳለባቸው የተነገራቸው ሙዚቃዊ ቃል ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል ሲጽፉ አንዳንድ ትርጉሞች ደግሞ ይህንን አያካትቱም። (ቃላትን ቅዳ ወይም ተዋስ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 55:8
አውሎ ንፋስ
ብርቱ አውሎ ንፋስ
ዋጣቸው
አንድን ነገር ማጥፋት ጨርሶ እንደ መብላት ተደርጎ ተነግሯል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ “የጠላቶቼን ዕቅድ አጥፋው” ወይም “ጠላቶቼን አጥፋቸው” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቋንቋቸውን ደበላልቀው
እዚህ ጋ፣ “ቋንቋ” የሚወክለው ሰዎች እርስ በርሳቸው ይነጋገሩት የነበረውንና በተለይም ክፉ ስለማድረግ ዕቅድ ይነጋገሩ የነበሩትን ያመለክት ይሆናል። ያንን መደበላለቅ የሚወክለው እርስ በርሳቸው እንዳይግባቡ ማድረግን ነው። ኢ.ት፡ “እርስ በርስ በሚነጋገሩበት ጊዜ አደናግራቸው” ወይም “ዕቅዳቸውን አደናግረው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 55:10
በግምቦቹ ላይ ይወጣሉ
“ግፍና ሁከት በግምቦቿ ላይ ይወጣሉ”። (መዝሙር 55፡9ን ተመልከት) ግፍና ሁከት እንደ ሰዎች ተቆጥረው ተነግሮላቸዋል። ግፍና ሁከትን ስለሚፈጥሩ ሰዎች ይህንን በመናገር መግለጽ ይቻላል። ኢ.ት፡ “በከተማይቱ ግምቦች ላይ ሰዎች እየተዋጉና እያወኩ ይመላለሳሉ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
በግምቦቿ ላይ
“በከተማይቱ ግምቦች አናት ላይ”። ከተሞች ከጠላቶቻቸው የሚጠበቁባቸው ጠንካራ ግምቦች በዙሪያቸው ይኖራቸው ነበር። የትኛውም ጠላት ወደ ከተማይቱ በመምጣት ላይ መሆኑን ለማየት ሰዎች በግምቦቹ አናት ላይ መመላለስ ይችሉ ነበር።
ኃጢአትና ተንኮል በመካከሏ ነው
ኃጢአትና ተንኮል እንደ ሰዎች ተቆጥረው ተነግሮላቸዋል። ይህንን፣ ኃጢአትንና ተንኮልን ስለሚያደርጉ ሰዎች በመናገር መግለጽ ይቻላል። ኢ.ት፡ “በከተማይቱ መካከል ሰዎች ኃጢአትን ይሠራሉ፣ ተንኮልንም ያደርጋሉ” ወይም “በውስጧ ሰዎች በኃጢአት የተሞሉ ነገሮችን ይሠራሉ፣ ችግርም ይፈጥራሉ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
ተንኮል
ችግር
ክፋት በመካከሏ ነው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ክፋት እንደ ሰው ተቆጥሮ ተነግሮለታል። ይህንን፣ ክፉ ነገሮችን ስላደረጉ ሰዎች በመናገር መግለጽ ይቻላል። ኢ.ት: “በከተማይቱ መካከል ሰዎች ክፉ ነገሮችን ያደርጋሉ” ወይም “ሰዎች በከተማይቱ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ያጠፋሉ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
ግፍና ማታለል ከጎዳናዎቿ አይርቁም
ግፍና ማታለል እንደ ሰዎች ተቆጥረዋል። ይህንን በሌሎች ላይ ግፍ ስለሚያደርጉና ስለሚያታልሉ ሰዎች በመናገር መግለጽ ይቻላል። ኢ.ት: “በከተማይቱ ጎዳናዎች ሰዎች በሌሎች ላይ ግፍና ማታለልን ይፈጽማሉ፣ ከዚያም አይርቁም” ወይም “በከተማይቱ ጎዳናዎች ላይ ሰዎች ሁልጊዜ በሌሎች ላይ ግፍ ይፈጽማሉ፣ ያታልላሉ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
በጎዳናዎቿ ላይ
ይህ ምናልባት በከተማይቱ ውስጥ ያለውን የገበያ ስፍራ ያመለክት ይሆናል።
Psalms 55:12
ልሸከመው እችል ነበር
ተግሳጽን መታገስና መጽናት እርሱን ይዞ እንደመቆየትና እንደ መሸከም ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት: “ተግሳጹን መታገስ በቻልኩ ነበር” ወይም “ስለ ተግሳጹ እምብዛም አላዝንም ነበር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ራሱን በእኔ ላይ ቀና አደረገ
ኩሩ መሆንና ሌላውን መሳደብ ራስን በሌላው ላይ ቀና እንደማድረግ ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት: “ሰደበኝ” ወይም “ናቀኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ነገር ግን አድራጊው አንተ ነህ
እርሱን የሚገስጸውና የሚያንጓጥጠው ሰውዬ በዚያ ሆኖ ይሰማው ይመስል ዘማሪው ይናገረዋል። (See: Apostrophe)
እኔ ራሴ፣ ባልንጀራዬና የቅርብ ጓደኛዬ
ይህ ተከፋፍሎ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊጀመር ይችላል። ኢ.ት: “እኔ ራሴ። አንተ ባልንጀራዬና የቅርብ ጓደኛዬ ነበርክ”
እኛ
“እኛ” የሚለው ቃል ዘማሪውንና ጓደኛውን ያመለክታል።
ከተሰበሰበው ጋር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “በአንድነት” ወይም 2) “ከሕዝቡ ጋር” የሚሉት ናቸው።
Psalms 55:15
ሞት በድንገት ይምጣባቸው
ሞት ሰዎችን ሊያጠቃ እንደሚችል ሰው ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት: “ጠላቶቼ በድንገት ይሙቱ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
ሕያዋን ሳሉ ወደ ሲዖል ይውረዱ
በድንገት መሞት ሰዎች መሞታቸው እንኳን በአግባቡ ሳይረጋገጥ በፍጥነት ወደ ሲዖል እንደሚሄዱ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት: “በድንገት ወደ ሲዖል ይሂዱ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ክፋት መኖሪያቸው ነው
ክፋት በሆነ ቦታ ላይ ሊቀመጥ እንደሚችል ነገር ተደርጎ ተነግሯል። የጠላቶቹ የተለመደው ክፋት ከእነርሱ ጋር ወይም አጠገባቸው እንደሚኖር ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት: “በሚኖሩበት ስፍራ ሁልጊዜ ክፉ ነገሮችን ያደርጋሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እዚያው በመካካላቸው
ይህ ሐረግ፣ ክፋት በጣም በቅርባቸው አለ የሚለውን አሳብ ያጠናክራኣል። እዚህ ጋ፣ ክፋት በቤቶቻቸው ብቻ ሳይሆን ባሉበት ቦታ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት: “ባሉበት ቦታ ሁሉ ክፉ ነገሮችን ሁልጊዜ ያደርጋሉ” ወይም “ባሉበት ቦታ ሁሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 55:16
ለእኔ ግን
ይህ ሐረግ የሚያሳየው ጸሐፊው ስለ አንድ ነገር መናገሩን አቁሞ ስለ ራሱ ሊናገር መሆኑን ነው። ኢ.ት: “እኔ ግን”
ማቃሰት
ሰዎች ወይም እንስሳት በህመማቸው ጊዜ የሚያሰሙት ድምፅ
እርሱ ድምፄን ይሰማኛል
እዚህ ጋ፣ “ድምፅ” የሚወክለው 1) ዘማሪውን ወይም 2) የዘማሪውን ቅሬታና ማቃሰት ይሆናል። ኢ.ት: “እርሱ ይሰማኛል” ወይም “እርሱ ማቃሰቴን ይሰማል” (See: Synecdoche እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሕይወቴ
እዚህ ጋ፣ “ሕይወቴ” የሚወክለው ዘማሪውን ነው። ኢ.ት: “እኔን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የሚዋጉኝ ብዙዎች ነበሩ
“ብዙ ሰዎች ተዋግተውኛል”
Psalms 55:19
ይሰማቸዋል
“ጠላቶቼን ይሰማቸዋል” ወይም “ጠላቶቼ የሚሉትን ይሰማል”። አንዳንድ ትርጉሞች “ይሰማኛል” ይላሉ።
አዋርዳቸው
እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያዋርዳቸው በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ያሸንፋቸዋል፣ ያዋርዳቸዋልም” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
Psalms 55:20
በእነዚያ ላይ እጆቹን አንሥቷል
በሰዎች ላይ እጅን ማንሣት እነርሱን ማጥቃትን ይወክላል። ይህ ሰዎችን አደጋ ላይ ስለ መጣል ወይም እንዲቸገሩ ስለ ማድረግ ለሚነገሩ ነገሮች ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆኑ ይችላሉ። ኢ.ት: “እነዚያን አጥቅቷል” ወይም “እነዚያን ክዷል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 55:22
ሸክምህን አስቀምጥ
እዚህ ጋ ዘማሪው የሚናገረው ለሌሎች እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ሰዎች ነው።
ሸክማችሁን በእግዚአብሔር ላይ አስቀምጡት
እዚህ ጋ፣ ችግሮች ሰዎች እንደሚሸከሟቸው ሸክሞች ተደርገው ተነግረዋል። በችግራችን ጊዜ እግዚአብሔር እንዲረዳን በእርሱ መታመናችን እርሱ ስለ እኛ እንዲሸከማቸው ሸክሞቻችንን በእርሱ ላይ እንደ መጣል ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት: “ችግሮችህን ለእግዚአብሕር ስጠው” ወይም “አንዱ፣ ብርቱ የሆነውን ሰው ‘ሸክሜን ሊሸከምልኝ ይችላል’ ብሎ እንደሚታመነው፣ አንተም በችግሮችህ ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚረዳህ ታመነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እርሱ ይደግፍሃል
አንድ ሰው ችግር በሚገጥመው ጊዜ እርሱን መንከባከብ ወይም መርዳት እርሱን እንደ መርዳት ተቆጥሮ ተነግሮለታል። ኢ.ት: “እርሱ ይጠነቀቅልሃል” ወይም “እርሱ ይረዳሃል”
ጻድቁ እንዲንገዳገድ እርሱ በፍጹም አይፈቅድም
አንድ በሆነ ዓይነት አደጋ ክፉኛ የተጎዳ ሰው ለመውደቅ እንደሚንገዳገድ ወይም እንደሚወዛወዝ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት: “ጻድቁን ሰው ተንገዳግዶ እንዲወድቅ አይተውውም” ወይም “ጻድቁ ሰው እንዲጠፋ አይተውውም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ግን
አሁን ደራሲው የሚናገረው ለእግዚአብሔር ነው።
የጥፋት ጉድጓድ
ይህ ምናልባት መቃብርን ወይም ሲዖልን ያመለክታል።
ክፉዉን ወደ ጥፋት ጉድጓድ ውስጥ ያወርደዋል
ይህ ሰዎች እንዲሞቱ ማድረግን ይወክላል። ኢ.ት: “ክፉው እንዲሞት ያደርጋል” ወይም “ክፉ ሰዎች እንዲሞቱና ሙታን ወዳሉበት ስፍራ እንዲሄዱ ያደርጋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ደም የተጠሙና የሚያታልሉ ሰዎች
“የሚዋሹና ሌሎችን ለመግደል የሚፈልጉ ሰዎች” ወይም “አታላይ ነፍሰ ገዳዮች”
የሌሎቹን ግማሽ እንኳን
“ሌሎች ሰዎች ከሚኖሩት ግማሹን እንኳን”

---

Chapter 56
Psalms 56:1
ለሙዚቃኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
ለዮናስ ኤሌም ሬሆኪም የተዘጋጀ

ይህ ምናልባት መዝሙሩን በሚዘምሩበት ጊዜ ምን ዓይነት የሙዚቃ ስልት ወይም ቅኝት መጠቀም እንዳለባቸው ሳይነግራቸው አይቀርም። ኢ.ት፡ “’የዮናስ ኤሌም ሬሆኪም’ን ቅኝት በመጠቀም ይህንን መዝሙር ዘምሩ” ወይም “የዮናስ ኤሌም ሬሆኪምን ስልት በመጠቀም ይህንን ዘምሩ”

የናስ ኤሌም ሬሆኪም

ይህ ምናልባት “በሩቅ የወርካ ዛፎች ላይ ያለች እርግብ” ማለት ሊሆን ይችላል። ተርጓሚዎች ትርጉሙን መጻፍ ወይም የዕብራይስጡን ቃላት መቅዳት ይኖርባቸው ይሆናል። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው እና ቃላትን ቅዳ ወይም ተዋስ የሚለውን ተመልከት)

የዳዊት መዝሙር

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚመለከተው ዳዊትን ነው ወይም 3) መዝሙሩ የዳዊትን መዝሙሮች ዘይቤ የተከተለ ነው የሚሉት ናቸው።

ሚችታም

“ሚችታም” የሚለው ቃል ትርጉሙ በእርግጠኝነት አይታወቅም። በምትኩ “መዝሙር” የሚለውን ቃል መጠቀም ይኖርብህ ይሆናል። “ዳዊት የጻፈው መዝሙር ይህ ነው” ተብሎ ሊጻፍ ይችላል። ይህንን በመዝሙር 16፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ፍልስጤማውያን በጌት በያዙት ጊዜ

“ፍልስጤማውያን በጌት በማረኩት ጊዜ”

ከበባቸውን አጠናክረዋል

“ሊወጉኝ በጣም ተጠግተዋል”

ጠላቶቼ ረጋግጠውኛል

የጠላት ብርቱ ጥቃት በእርሱ ላይ በመሄድ ሰውነቱን የሰባበሩት በሚመስል መልኩ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ጠላቶቼ ክፉኛ እያጠቁኝ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 56:3

አንተ

“አንተ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።

ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?

እዚህ ጋ ዘማሪው፣ ሰዎች በከፋ ሁኔታ ሊጎዱት ስለማይችሉ እንዳልፈራቸው ለማሳየት ጥያቄው ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰው ብቻ የሆነ እርሱ ምንም ሊያደርገኝ አይችልም!” ወይም “ሰው ብቻ የሆነ እርሱ ከባድ ጉዳት ሊያደርስብኝ አይችልም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ሰው ብቻ የሆነ

“ሰብአዊ ፍጡር” ወይም “ሰዎች”። ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር እንጂ ሰዎች ብርቱዎች አለመሆናቸውን ነው።

Psalms 56:5

ቀኑን ሁሉ

“ሁልጊዜ”

ቃሌን ያጣምማሉ

አንድ ሰው የሚናገረውን ደግሞ መናገር፣ ነገር ግን ትንሽ ለውጥ በማድረግ ሌላ ትርጉም እንዲኖረው ማድረግ ቃላቸውን እንደማጣመም ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ያልተናገርኩትን እንደተናገርኩ አድርገው ይናገራሉ” ወይም “ነገሮቼን እኔ እንደ ተናገርኩ ይናገራሉ፣ ነገር ግን ይዋሻሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእኔ ላይ የሚያስቡት ሁሉ ለክፋት ነው

“በእኔ ላይ ሁልጊዜ ክፉ አሳብ አላቸው” ወይም “ክፉ ነገር ሊያደርጉብኝ ሁልጊዜ ያስባሉ”

እርምጃዬን ይከታተላሉ

ልክ አንድን ሰው ለመያዝ የሚፈልግ፣ ያ ሰው ወዴት እንደሚሄድ እንደሚመለካከት ሁሉ፣ አንድን ሰው ችግር ላይ ለመጣል እርሱ የሚያደርገውን መመልከት ርምጃውን እንደመመልከት ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “የማደርገውን ሁሉ ይመለከታሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ልክ ሕይወቴን እንደሚጠባበቁት

አንድን ሰው ለመግደል መጠባበቅ ሕይወቱን እንደ መጠባበቅ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እኔን ለመግደል ሲጠብቁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Psalms 56:7

ኃጢአትን ሠርተው እንዲያመልጡ አትተዋቸው

ካመለጡ በግልጽ ይከሰሳሉ። ኢ.ት፡ “ስለ ኃጢአታቸው በአንተ ከመቀጣት እንዲያመልጡ አትተዋቸው” ወይም “ስለሚያደርጉት ክፉ ነገር አንተ በምትቀጣቸው ጊዜ እንዲያመልጡ አትተዋቸው” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ሕዝቡን ጣላቸው

ጠላቶችን ማሸነፍ እነርሱን እንደ መጣል ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ሕዝቡን ድል አድርጋቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መንከራተቴን ትመዘግባለህ

እግዚአብሔር ስለ ዘማሪው ግድ መሰኘቱ፣ ዘማሪው ለመጽናናት የሚሄድበት ስፍራ ሳይኖረው በስጋት የተመላለሰበትን እያንዳንዱን ጊዜ እግዚአብሔር እንደቆጠረለት ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ብቻዬን ስለ ተንከራተትኩባቸው ጊዜያት ሁሉ አንተ ይገድሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዕንባዬን በጠርሙስህ አስቀምጠው

እግዚአብሔር ለዘማሪው ግድ መሰኘቱ፣ እግዚአብሔር የዘማሪውን ዕንባ በጠርሙስ ውስጥ እንዳስቀመጠ ተደርጎ ተነግሯል። ዕንባ ለቅሶን ይወክላል። ኢ.ት፡ “ምን ያህል እንዳለቀስኩ ታውቃለህ፣ ስለ እኔም ይገድሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመጽሐፍህ ውስጥ ያሉ አይደሉም?

እግዚአብሔር ለዘማሪው ግድ መሰኘቱ፣ እግዚአብሔር የዘማሪውን የዕንባ ቁጥር በመጽሐፉ ውስጥ እንደጻፈ ተደርጎ ተነግሯል። እግዚአብሔር ለዘማሪው እጅግ እንደሚጠነቀቅለት ለማሳሰብ ጥያቄው ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት፡ “ስለ እነርሱ በመጽሐፍህ ውስጥ ጽፈሃል!” ወይም “ለቅሶዬን ታስታውሳለህ!” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 56:9

ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ

“ያፈገፍጋሉ” ወይም “ተመልሰው ይሸሻሉ”

እግዚአብሔር ለእኔ ነው

ትርጉሙ እግዚአብሔር ለእርሱ ያደላል ማለት ነው። በዚህ ዐውድ፣ ዘማሪውን ለመጠበቅ እግዚአብሔር ከዘማሪው ጠላቶች ጋር እንደሚዋጋ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ስለ እኔ ይዋጋል” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)

ማን ምን ሊያደርግብኝ ይችላል?

እዚህ ጋ ጥያቄው ጥቅም ላይ የዋለው ዘማሪው ብዙም ሊጎዱት ስለማይችሉ ሰዎችን እንደማይፈራቸው ለማሳየት ነው። ይህ ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ ‘ሰዎች ምንም ሊያደርጉብኝ አይችሉም!” ወይም “ሰዎች በከፋ ሁኔታ ሊጎዱኝ አይችሉም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Psalms 56:12

ስእለቴን የመፈጸም ኃላፊነት አለብኝ

አንድ ነገር ለማድረግ ግዴታ ውስጥ መሆን፣ መደረግ ያለበት ነገር በሰውየው ላይ እንደ ተቀመጠ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ለአንተ የገባሁትን ስእለት መፈጸም አለብኝ” ወይም “ላደርገው ቃል የገባሁልህን ማድረግ አለብኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግሮቼን ከመውደቅ አድነኻቸዋል

እዚህ ጋ እግር የሚወክለው ሰውዬውን ነው። መውደቁ ደግሞ በጠላቶቹ መገደልን ሊወክል ይችላል። ኢ.ት፡ “ከመውደቅ አድነኸኛል” ወይም “በጠላቶቼ እጅ ከመሞት አድነኸኛል” (Synecdoche የሚለውን ተመልከት)

በእግዚአብሔር ፊት እንድመላለስ

መኖርና በእግዚአብሔር መታየት በእግዚአብሔር ፊት እንደ መመላለስ ተወስዶ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “በእግዚአብሔር ሀልዎት ውስጥ እንድኖር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሕያዋን ብርሃን ውስጥ

እዚህ ጋ “የሕያዋን ብርሃን” የሚወክለው ምናልባት ሰዎች በሕይወት እንዲኖሩ እግዚአብሔር የሚያስችላቸው መሆኑን ነው። ኢ.ት፡ “አንተ በምትሰጠው ሕይወት” ወይም “በሕይወት እንድኖር ስለምታስችለኝ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 57

Psalms 57:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
ለአል ታሼዝ የተዘጋጀ
ይህ ምናልባት መዝሙሩን በሚዘምሩበት ጊዜ ምን ዓይነት የሙዚቃ ስልት ወይም ቅኝት መጠቀም እንዳለባቸው ሳይነግራቸው አይቀርም። ኢ.ት፡ “'የአል ታሼዝን ቅኝት በመጠቀም ይህንን መዝሙር ዘምሩ” ወይም “የአል ታሼዝን ስልት በመጠቀም ይህንን ዘምሩ”
አል ታሼዝ
ይህ “አታጥፋ” ማለት ነው። ተርጓሚዎች ትርጉሙን መጻፍ ወይም የዕብራይስጡን ቃል መቅዳት ይኖርባቸዋል። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው እና ቃላትን ቅዳ ወይም ተዋስ የሚለውን ተመልከት)
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚመለከተው ዳዊትን ነው ወይም 3) መዝሙሩ የዳዊትን መዝሙሮች ዘይቤ የተከተለ ነው የሚሉት ናቸው።
ሚችታም
“ሚችታም” የሚለው ቃል ትርጉሙ በእርግጠኝነት አይታወቅም። በምትኩ “መዝሙር” የሚለውን ቃል መጠቀም ይኖርብህ ይሆናል። “ዳዊት የጻፈው መዝሙር ይህ ነው” ተብሎ ሊጻፍ ይችላል። ይህንን በመዝሙር 16፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ከሳዖል ሸሽቶ በዋሻ ውስጥ በነበረ ጊዜ
የዚህ ሐረግ ዓላማ ሁኔታውን በዝርዝር ከሚያስረዱ አንዳንድ መሠረታዊ ነገሮች ጋር በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ይህ ዳዊት ዋሻ ውስጥ ከሳዖል ስለተደበቀበት ጊዜ ነው” ወይም “ይህ ንጉሥ ሳዖል ዳዊትን ባሳደደው ጊዜ ዳዊት ዋሻ ውስጥ ስለተደበቀበት ወቅት ነው” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
አንተን መጠጊያዬ አድርጌአለሁ
ጥበቃ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር መሄድ በእርሱ መጠጊያ ማግኘት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ጥበቃ ለማግኘት ወደ አንተ እመጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከለላ ለማግኘት በክንፎችህ ስር እቆያለሁ
ዘማሪው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር ጫጩቶቿን በክንፎቿ ስር ከምትሰበስባቸው ወፍ ጋር ያነጻጽረዋል። ኢ.ት፡ “እንደምትጠብቀኝ እታመንሃለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይህ ጥፋት እስኪያልፍ ደረስ
የነገር ስም የሆነው “ጥፋት” እንደ “አጥፊ” ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ይህ አጥፊ ማዕበል እስኪያልፍ ደረስ” (የነገር ስም እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 57:2
ሁሉን ነገር የሚያደርግልኝ
ወደ እግዚአብሔር የሚጮኸው ለምን እንደሆነ ይህ ያብራራዋል። “ምክንያቱም” ከሚል ቃል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ምክንያቱም እርሱ ሁሉን ነገር ያደርግልኛል”
እነዚያን የረጋገጡኝን
የጠላቶቹ ብርቱ ጥቃት በላዩ ላይ በመረማመድ ሰውነቱን እንደ ረጋገጡት ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “በከፋ ሁኔታ ያጠቁኝ እነዚያ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ምህረቱንና ታማኝነቱን ይልክልኛል
የእግዚአብሔር መሐሪነትና ታማኝነት ምህረቱንና ታማኝነቱን እንደሚልክ ተደርጎ ተነግሯል። የነገር ስም የሆነው “ምህረት” እና “ታማኝነት” እንደ “መሐሪ” እና “ታማኝ” ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ለእኔ መሐሪና ታማኝ ይሆናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Psalms 57:4
ሕይወቴ በአንበሶች መካከል ነው
ዘማሪው ስለ ጠላቶቹ ሲናገር እንደ አንበሶች ይቆጥራቸዋል። ኢ.ት፡ “የምኖረው በጨካኝ ጠላቶች መካከል ነው” ወይም “ጨካኝ ጠላቶች እንደ አንበሳ ከብበውኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እነዚያ ሊውጡኝ የተዘጋጁት
ማጥፋት አንድን ነገር እንደ መዋጥ ወይም ጨርሶ እንደ መብላት ሆኖ ተነግሯል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡ ቃል “ጨካኝ አውሬዎች” ማለት እንደሆነ ይገነዘባሉ። ሁለቱም ሥዕሎች ጠላቶቹን እንደ ዱር አውሬ አድርገው ይገልጻሉ። ኢ.ት፡ “እነዚያ ሊያጠፉኝ የተዘጋጁት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጥርሶቻቸው ጦርና ቀስት የሆኑ ሕዝብ
የጠላት ቀስትና ጦር እንደ አንበሳ ጥርስ ተደርጎ ተነግሯል። ዘማሪው ጠላቶቹ እንደ አንበሳ እንደሆኑ መናገሩን ቀጥሏል። ኢ.ት፡ “አንበሳ በሹል ጥርሶቹ እንደሚገድል በቀስትና በጦር ሌሎችን ሰዎች የሚገድሉ ሕዝቦች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጦርና ቀስት
የእነዚህ የሁለቱም ስያሜ የጦር መሣሪያ እስከሆነ ድረስ የአንተ ባህል አንዱን ብቻ የሚያውቅ ከሆነ እርሱን ብቻ ብትጠቀም ተቀባይነት አለው። (See: Doublet)
ምላሳቸው የተሳለ ሰይፍ ነው
ምላስ አንድ ሰው የሚናገረውን ይወክላል፣ ጭካኔን የተሞሉት የጠላቶች ቃላት እንደ ሰይፍ ተቆጥረው ተነግረዋል። ኢ.ት፡ “ጭካኔን የተሞሉት ቃሎቻቸው እንደ ተሳሉ ሰይፎች ናቸው” ወይም “በሚናገሩት ቃል የከፋ ችግር የሚያስከትሉብኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ በል
እግዚአብሔር መክበሩን እንዲያሳይ ዘማሪው እየጠየቀው ነው። ከሰማያት በላይ ከፍ ማለት ታላቅ መሆንን ይወክላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ ማለትህን አሳይ” ወይም “እግዚአብሔር ሆይ፣ በሰማያት ላይ ታላቅ መሆንህን አሳይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ክብርህ በምድር ሁሉ ላይ ይሁን
እግዚአብሔር ክብሩን እንዲያሳይ ዘማሪው እየጠየቀው ነው። ኢ.ት፡ “በምድር ሁሉ ላይ ክብርህን አሳይ”
Psalms 57:6
ለእግሮቼ መረብን ዘረጉ
ጠላቶቹ እርሱን ለመያዝ ማቀዳቸው እርሱን ለማጥመድ መሬት ላይ ወጥመድ እንደ ዘረጉ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ነገሩ ጠላቶቼ እኔን ለማጥመድ መረብ የዘረጉ ይመስላል” ወይም “ሰዎች የዱር እንስሳ ለማጥመድ መረብ እንደሚዘረጉ እኔን ለመያዝ አቅደዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በፊት ለፊቴ ጉድጓድን ቆፍረዋል
ጠላቶቹ እርሱን ለመያዝ ማቀዳቸው ይወድቅበት ዘንድ ጉድጓድ እንደ ቆፈሩለት ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እንድወድቅበት ጉድጓድ የቆፈሩልኝ ያህል ይመስላል” ወይም “ልክ ሰዎች የዱር እንስሳ ለማጥመድ ጉድጓድ እንደሚቆፍሩ እኔን ለመያዝ አቅደዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እነርሱ ራሳቸው በመካከሉ ወደቁ
ጠላቶቹ እርሱን ለመያዝ በሚሞክሩበት ጊዜ በእነርሱ ላይ የደረሰባቸው ጉዳት ለእርሱ ባጠመዱት ወጥመድ ውስጥ እንደ ወደቁ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “በቆፈሩልኝ ጉድጓድ ውስጥ እነርሱ ራሳቸው ወደቁ” ወይም “ነገር ግን በእኔ ላይ ለማድረግ ባቀዱት በዚያ እነርሱ ራሳቸው ተጎዱበት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 57:7
ልቤ ጽኑ ነው፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ልቤ ጽኑ ነው
ስለ መተማመን፣ የአንድ ሰው ልብ ከመንቀጥቀጥ ወይም በቀላሉ ከመነቅነቅ ይልቅ የጸና እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። በእግዚአብሔር ላይ ፍጹም መታመን እንዳለውና እንደማይለወጥ ለማሳየት ሐረጉ ተደግሟል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ ሙሉ በሙሉ በአንተ እተማመናለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ምስጋናን እዘምራለሁ
የሚዘምረው ማን እንደሆነ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ ምስጋናን እዘምርልሃለሁ” (Assumed Knowl- edge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
ዕድለኛው ልቤ ተነሥ
የመነሣቱ ዓላማ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ለመዘመር መሆኑ በግልጽ ሊነገር ይችላል። መነሣት አንድን ነገር ለማድረግ የመጀመር ወይም የመዘጋጀት ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። ልብ ዘማሪውን ወይም የእርሱን ስሜት ይወክላል። ኢ.ት፡ “ዕድለኛው ልቤ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ለመዘመር ተነሥ” ወይም “ለእግዚአብሔር የምስጋናን መዝሙር እንዲዘምር ዕድለኛውን ልቤን አዘጋጀዋለሁ” ወይም “ለመነሣትና ለእግዚአብሔር ምስጋናን ለመዘመር ታድያለሁ” (Assumed Knowledge and Implicit Information፣ዘይቤአዊ አነጋገር እና

Synecdoche የሚለውን ተመልከት)
በገና እና መሰንቆም ተነሡ
የመነሣቱ ዓላማ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ለመዘመር መሆኑ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ዘማሪው በገናና መሰንቆ ለእግዚአብሔር ምስጋናን የሚዘምሩ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “በገናና መሰንቆ ተነሡ፣ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ዘምሩ” ወይም “ለእግዚአብሔር ምስጋናን በምዘምርበት ጊዜ በበገናና በመሰንቆ እጫወታለሁ” (Assumed Knowledge and Implicit Information፣ ሰውኛ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ንጋትን አቀሰቅሰዋለሁ
ንጋት በራሱ ሕያው እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮለታል፣ ከመንጋቱ በፊት መነሣትም እርሱን እንደ መቀስቀስ ተደርጎ ተነግሯል። ከመንጋቱ በፊት የመነሣት ዓላማው እግዚአብሔርን ለማመስገን ነው። ኢ.ት፡ “ከመንጋቱ በፊት እነሣለሁ” ወይም “ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት እነሣለሁ” (ሰውኛ፣ ዘይቤአዊ አነጋገር እና Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
Psalms 57:9
እስከ ሰማያት ድረስ፣ ምህረትህ ታላቅ ነውና … ታማኝነትህ እስከ ደመና ድረስ
የእነዚህ የሁለቱም ሐረጎች ትርጉም በጣም ተመሳሳይ ነው። የእግዚአብሔር ምህረትና ታማኝነት ታላቅነት መለካት በሚችል ርቀት ተመስሎ ተነግሯል። (Parallelism እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እስከ ሰማያት ድረስ፣ ምህረትህ ታላቅ ነውና
የእግዚአብሔር ምህረት ታላቅነት መለካት በሚችል ርቀት ተመስሎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ከመሬት እስከ ሰማያት ድረስ ያለውን ርቀት ያህል ምህረትህ ታላቅ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ታማኝነትህ እስከ ደመና ድረስ
“ታላቅ ነው” እና “ድረስ” የሚሉትን ቃላት ቀደም ብሎ ካሉት ቁጥሮች መገንዘብ ይቻላል። ኢ.ት፡ “እስከ ደመናት የሚደርስ ታማኝነትህ ታላቅ ነው” ወይም “ታማኝነትህ ከመሬት እስከ ደመናት ድረስ ያለውን ርቀት ያህል ታላቅ ነው” (Ellipsis እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ በል
እግዚአብሔር መክበሩን እንዲያሳይ ዘማሪው እየጠየቀው ነው። ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ ማለት ታላቅ መሆንን ይወክላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ ማለትህን አሳይ” ወይም “እግዚአብሔር ሆይ፣ በሰማያት ላይ ታላቅ መሆንህን አሳይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ክብርህ በምድር ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ይበል
እግዚአብሔር ክብሩን እንዲያሳይ ዘማሪው እየጠየቀው ነው። ኢ.ት፡ “በምድር ሁሉ ላይ ክብርህን አሳይ”

---

Chapter 58
Psalms 58:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
“ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው”
ለአል ታሼዝ የተዘጋጀ
ይህ ምናልባት መዝሙሩን በሚዘምሩበት ጊዜ ምን ዓይነት የሙዚቃ ስልት ወይም ቅኝት መጠቀም እንዳለባቸው ሳይነግራቸው አይቀርም። ይህንን በመዝሙር 57:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
አል ታሼዝ
ይህ “አታጥፋ” ማለት ነው። ተርጓሚዎች ትርጉሙን መጻፍ ወይም የዕብራይስጡን ቃል መቅዳት ይኖርባቸዋል። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው እና ቃላትን ቅዳ ወይም ተዋስ የሚለውን ተመልከት)
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚመለከተው ዳዊትን ነው ወይም 3) መዝሙሩ የዳዊትን መዝሙሮች ዘይቤ የተከተለ ነው የሚሉት ናቸው።
ሚችታም
“ሚችታም” የሚለው ቃል ትርጉሙ በእርግጠኝነት አይታወቅም። በምትኩ “መዝሙር” የሚለውን ቃል መጠቀም ይኖርብህ ይሆናል። “ዳዊት የጻፈው መዝሙር ይህ ነው” ተብሎ ሊጻፍ ይችላል። ይህንን በመዝሙር 16:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
እናንተ ገዢዎች ጽድቅን ትናገራላችሁ?
ደራሲው በጽድቅ ስለማይናገሩ ገዢዎቹን ለመገሰጽ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት፡ “እናንተ ገዢዎች ትክክለኛውን ነገር አትናገሩም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
እናንተ … የእናንተ
“እናንተ” እና “የእናንተ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ፈራጆች የሆኑ ኃያላን ሰዎችን ነው። እዚህ ጋ የእንግሊዝኛው “ዩ” ብዙ ቁጥር ነው። (Forms of You የሚለውን ተመልከት)
እናንተ ሰዎች፣ እናንተ በጽድቅ ትፈርዳላችሁ?
ደራሲው በጽድቅ የማይፈርዱትን ፈራጆች ለመገሰጽ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት፡ “እናንተ ሰዎች፣ በሕዝቡ ላይ በጽድቅ አትፈርዱም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አይደለም
ደራሲው ጠይቋቸው የነበሩትን ሁለቱንም ጥያቄዎች ይመልሳል።
በልባችሁ ክፋትን ታደርጋላችሁ
ልብ የሕዝቡን አሳብ ወይም ዕቅድ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “በአሳባችሁ ክፋትን ታደርጋላችሁ’ ወይም “ክፉ ነገሮችን ስለማድረግ ታስባላችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በምድሪቱ ሁሉ ላይ በእጆቻችሁ ሁከትን ታከፋፍላላችሁ
በምድሪቱ ላይ በተለያየ ስፍራ ማወክ ልክ ሁከት ዕቃ ይመስል በምድሪቱ ሁሉ ላይ እንደ ማከፋፈል ወይም እንደ ማስፋፋት ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እናንተ ራሳችሁ በምድሪቱ ሁሉ ላይ የሁከት ተግባር ትፈጽማላችሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 58:3
ክፉዎች በማህፀን እያሉ እንኳን መንገድ የሳቱ ናቸው … ከመወለዳቸው ጀምሮ መንገድ ይስታሉ
ይህ በሁለት የተለያየ መንገድ የተገለጸ ተመሳሳይ አሳብ ነው። (Parallelism የሚለውን ተመልከት)
መንገድ መሳት
የተሳሳቱ ነገሮችን ማድረግ ልክ ሰዎች በመንገድ ላይ እየሄዱ እያሉ ታጥፈው በተሳሳተ መንገድ እንደሚሄዱ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “የተሳሳተ ነገሮችን ያደርጋሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
መርዛቸው ልክ እንደ እባብ መርዝ ነው
ሰዎች የሚናገሯቸው ክፉ ነገሮች መርዝ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “የእባብ መርዝ ሰውን እንደሚጎዳ ሁሉ ክፉ ቃላቸውም ችግር ይፈጥራል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Simile የሚለውን ተመልከት)
እነርሱ ልክ ጆሮዎችን እንደሚያቆም ደንቆሮ እባብ ናቸው
ምክርን ወይም ተግሳጽን የማይሰሙ ክፉ ሰዎች ለደጋሚው ሙዚቃ ምላሽ እንደማይሰጡ እባቦች ተደርገው ተነግሮላቸዋል። ኢ.ት፡ “ጆሮዎቹን እንደሚያቆም ደንቆሮ እባብ ለመስማት አይፈልጉም” (Simile የሚለውን ተመልከት)
ጆሮዎቹን የሚያቆም ደንቆሮ እባብ
ለደጋሚው ሙዚቃ ምላሽ የማይሰጠው እባብ እንዳይሰማ ጆሮው ውስጥ የሆነ ነገር እንደ ከተተ ተደርጎ ተነግሮለታል። ኢ.ት፡ “የማይሰማ እባብ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
እባብ
የመርዘኛ እባብ ዝርያ
ደጋሚዎች
እባቡን ለመቆጣጠር በሙዚቃ የሚጫወቱ ወይም የሚዘፍኑ ሰዎች
ምንም ያህል ብልሆች መሆናቸው ልዩነት የለውም
በእባብ ላይ ድግምት የሚያደርጉት ብልህ የሆኑት በምን እንደሆነ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እባቦቹን በመቆጣጠር ጉዳይ ደጋሚዎቹ ምንም ያህል ብልኖች ቢሆኑም እንኳን” (Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
Psalms 58:6
ጥርሶቻቸውን ስበር … የአንበሳ ደቦሎቹን ታላላቅ ጥርስ ስበር
በእነዚህ በሁለቱም ሐረጎች ውስጥ ክፉ ሰዎች አንበሳ እንደሆኑ ተደርጎ የተነገረላቸው ሲሆን ሰዎችን እንዳይገድሉ እነርሱን አቅም ማሳጣት ደግሞ ጥርሶቻቸውን እንደ መስበር ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “የሚገድሉበትን ኃይል ውሰድባቸው። ጥርሶቻቸው ተሰብሮ እንደ ወደቀባቸው ደቦል አንበሶች አቅመ ቢስ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አድርጋቸው" (Paral- lelism እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ፈጥኖ እንደሚያልፍ ወራጅ ውሃ ቀልጠው እንዲጠፉ አድርጋቸው
ክፉ ሰዎች እንደ በረዶ ወይም ውሃ ተመስለው ተነግሮላቸዋል። ዳግመኛ አለመኖር እንደ መቅለጥ ወይም ወደ መሬት ውስጥ እንደመስረግ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ "እንደ ወራጅ ውሃ እንዲጠፉ አድርጋቸው" ወይም "ልክ ቀልጦ ወደ መሬት ውስጥ እንደሚሰርግ በረዶ እንዲተኑ አድርጋቸው" (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Simile የሚለውን ተመልከት)
ምንም ዒላማ እንደሌላቸው ይሁኑ
"ቀስቶቻቸው ዒላማዎቻቸውን እንደሚስቱ ይሁኑ"
ቀልጦ እንደሚጠፋ ቀንድ አውጣ ይሁኑ
ዳግመኛ አለመኖር እንደ መቅለጥ ወይም መጥፋት ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ "ክፉዎች እንደሚቀልጥና ዳግመኛ እንደማይኖር ቀንድ አውጣ ተነው ይጥፉ" (Simile የሚለውን ተመልከት)
ቀንድ አውጣ
እስራኤላውያን እንደ እርኩስ የሚቆጥሩትና በሚያመነጨው ልጋግ መሰል ነገር ላይ ሲሄድ የሚቀልጥ የሚመስል ነፍሳት
ከሴት ተወልዶ የፀሐይን ብርሃን እንደማያይ ጭንጋፍ
አለመኖር ሞቶ የተወለደ ሕፃን መምሰል እንደሆነ ተነግሯል። ኢ.ት፡ "በሕይወት ለመኖርና የፀሐይን ብርሃን ለማየት እንዳይችል በጣም ቀድሞ እንደ ተወለደ ሕፃን" ወይም "ሞቶ እንደ ተወለደ ሕፃን" (Simile የሚለውን ተመልከት)
Psalms 58:9
የሚነደው እሾህ ድስታችሁን ሳያሰማው ... እርጥቡን እሾህና የሚነደውን እሾህ
ክፉዎች በእሾህ ቅርንጫፎች ተመስለዋል፤ በእነርሱ ላይ የእግዚአብሔር ፈጣን ቅጣትም ፈጥኖ እንደሚያነዳቸው ወይም ጠራርጎ እንደሚያስወግዳቸው ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ "ከማብሰያው ድስት ስር በእሳት የተለኮሰውን የእሾህ ቅርንጫፍ ጠራርጎ ሊወስድ ከሚችል ዐውሎ ነፋስ ይልቅ እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን በፍጥነት ያጠፋቸዋል" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእናንተ
ዳዊት የሚናገረው ለእግዚአብሔር ሕዝብ ስለሆነ ይህ ብዙ ቁጥር ነው። (Forms of You የሚለውን ተመልከት)
የሚቃጠለው እሾህ ሳያሰማው ... እርጥቡን እሾህና የሚነደውን እሾህ
"የሚነድደው የእሾህ ቅርንጫፍ ሙቀት ... የእርጥቡ እሾህ ቅርንጫፍና የሚነደው እሾህ ቅርንጫፍ
ጻድቁ በሚያይበት ጊዜ ደስ ይለዋል
"ጻድቁ" የሚለው ቃል በጥቅሉ ጻድቅ የሆኑ ሰዎችን ያመለክታል። ኢ.ት፡ "ጻድቅ የሆኑ ሰዎች በሚያዩበት ጊዜ ደስ ይላቸዋል" (Generic Noun Phrases የሚለውን ተመልከት)
በክፉዎቹ ደም እግሮቹን ይታጠባል
በደም ላይ በመራመዱ የአንድ ሰው እግር መርጠቡ እግሩን በደም እንደ ታጠበ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ "ጻድቃን እግሮቻቸውን በክፉዎች ደም ያረጥባሉ" ወይም "ጻድቃን በክፉዎች ደም ላይ ይረማመዳሉ" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በክፉዎች ደም እግሮቹን ይታጠባል
ይህ ግነት ብዙ ቁጥር ያላቸው ክፉ ሰዎች እንደሚሞቱ ይገልጻል። ኢ.ት፡ "እጅግ ብዙ ሰዎች በመሞታቸው ጻድቃን በደማቸው ላይ በሚረማመዱበት ጊዜ እግሮቻቸውን በደም ያጠቡ እስኪመስሉ ድረስ ይደርሳሉ" (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Hyperbole and Generalization የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 59
Psalms 59:1
ለሙዚቀኞቹ አለቃ
"ይህ በዝማሬ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ለሙዚቃ መሪው የተጻፈ ነው"
ለአል ታሼዝ የተዘጋጀ
ይህ ምናልባት መዝሙሩን በሚዘምሩበት ጊዜ ምን ዓይነት የሙዚቃ ስልት ወይም ቅኝት መጠቀም እንዳለባቸው ሳይነግራቸው አይቀርም። ኢ.ት፡ "'የአል ታሼዝን ቅኝት በመጠቀም ይህንን መዝሙር ዘምሩ" ወይም "የአል ታሼዝን ስልት በመጠቀም ይህንን ዘምሩ"
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መዝሙሩን ዳዊት ጽፎታል ወይም 2) መዝሙሩ የሚመለከተው ዳዊትን ነው ወይም 3) መዝሙሩ የዳዊትን መዝሙሮች ዘይቤ የተከተለ ነው የሚሉት ናቸው።
ሚችታም
"ሚችታም" የሚለው ቃል ትርጉሙ በእርግጠኝነት አይታወቅም። በምትኩ "መዝሙር" የሚለውን ቃል መጠቀም ይኖርብህ ይሆናል። "ዳዊት የጻፈው መዝሙር ይህ ነው" ተብሎ ሊጻፍ ይችላል። ይህንን በመዝሙር 16፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሳዖል በላካቸውና ሊገድሉት ቤቱን በከበቡት ጊዜ
"የሚገድሉበትን አጋጣሚ ለማግኘት የዳዊትን ቤት እንዲጠብቁ ሳዖል ወታደሮቹን በላካቸው ጊዜ"
በከፍታ አስቀምጠኝ
የከፍታ ስፍራ ጠላቶቹ ሊደርሱበት የማይችሉበትን አስተማማኝ ስፍራ ይወክላል። ኢ.ት፡ "በአስተማማኝ ስፍራ አስቀምጠኝ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእኔ ላይ ተነሥተዋል
በአንድ ሰው ላይ መነሣት እርሱን ማጥቃትን ይወክላል። ኢ.ት፡ "ሊያጠቁኝ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ደም የተጠሙ ሰዎች
"ደም የተጠሙ" የሚለው ቃል መግደልን የሚያመለክተውን "ደም" እና "ምኞትን የሚያመለክተውን "መጠማት" ይዟል። ኢ.ት፡ "ለመግደል የሚመኙ ሰዎች" ወይም "ሰዎችን መግደል ደስ የሚያሰኛቸው ሰዎች" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 59:3
ሕይወቴን ለመውሰድ አድብተው ይጠብቃሉ
የዳዊት ጠላቶች ተደብቀዋል፣ እርሱን የሚያጠቁበትን አጋጣሚም በመጠባበቅ ላይ ናቸው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ንቃ
አንድ ነገር ለማድረግ መወሰንና እርሱኑ ለማድረግ መጀመር እንደ መንቃት ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት፡ "አንድ ነገር አድርግ" ወይም "እርምጃ ውሰድ" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እና ተመልከት
እግዚአብሔር ምን እንዲያይለት እንደ ፈለገ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ "ምን እየደረሰብኝ እንዳለ ተመልከት" ወይም "ምን እያደረጉብኝ እንዳሉም ተመልከት" (Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
Psalms 59:5
ተነሥ
አንድ ነገር ለማድረግ መወሰንና እርሱኑ ለማድረግ መጀመር እንደ መነሣት ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት፡ "አንድ ነገር አድርግ" ወይም "እርምጃ ውሰድ" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ሕዝቦች ሁሉ
እዚህ ጋ፣ "ሕዝቦች" የሚለው ቃል እግዚአብሔርን የማያከብሩትን የሀገራቱን ሕዝቦች ይወክላል። ኢ.ት፡ "የየሀገሩ ሕዝብ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 59:6
በምሽት ይመለሳሉ
በውስጠ ታዋቂነት ያለው "እነርሱ" የሚለው ቃል ክፉዎች ተላላፊዎችን ያመለክታል።
እንደ ውሻ ያላዝናሉ
ዘማሪው ለማጥቃት ስለሚያስፈራሩት ጠላቶቹ ሲናገር በሰዎች ላይ እንደሚያላዝኑ ወይም እንደሚጮኹ ውሾች አድርጎ ይገልጻቸዋል። ኢ.ት፡ "ሰዎችን ለማጥቃት ያስፈራራሉ" (Simile የሚለውን ተመልከት)
በከተማይቱ ዙሪያ ይሄዳሉ
በከተማይቱ ዙሪያ የሚሄዱበት ምክንያት በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ "የሚያገኙትን የትኛውንም ሰው ለማጥቃት በከተማው ዙሪያ ይሄዳሉ" (Assumed Knowledge and Implicit Information የሚለውን ተመልከት)
እነሆ
እዚህ ጋ፡ "እነሆ" የሚለው ቃል ትኩረትን ወደ አንድ ነገር ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት፡ "ስማ"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በአፋቸው ያገሳሉ
መጥፎ ነገር መናገር እንደ ማግሳት ተቆጥሮ ተነግሯል። እነዚህ መጥፎ ነገሮች ስድብ ወይም ማስፈራራት ሊሆኑ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “መጥፎ ነገሮችን ይናገራሉ” ወይም “መጥፎ ቃላት እየተናገሩ ይጮኻሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ማግሳት
ከፍ ባለ ድምፅ ማግሳት፤ የተቃጠለ አየር ከሆድ በአፍ በኩል ከፍ ባለና በሚረብሽ ድምፅ እንዲወጣ ማድረግ
በከንፈራቸው ውስጥ ሰይፍ አለ
ክፉ ሰዎች የሚናገሯቸው የጭከና ቃላት እንደ ሰይፍ ሆነው ተነግረዋል። ኢ.ት፡ “ሰይፍ ሰዎችን የሚያጠፋቸውን ያህል በሰዎች ላይ ችግር የሚፈጥሩ የጭካኔ ቃላት ይናገራሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ማን ይሰማናል?
እግዚአብሔር እንደማይሰማቸውና እንደማይቀጣቸው ማመናቸውን ለማሳየት ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት፡ “ማንም ሊሰማን አይችልም!” ወይም “አምላክህ አይሰማንም!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Psalms 59:8
ትስቅባቸዋለህ
“በንቀት ትስቅባቸዋለህ” ወይም “ትሳለቅባቸዋለህ”። የማይረቡና አቅመ ቢሶች ስለሆኑ እግዚአብሔር ይስቅባቸዋል።
ሕዝቦችን ሁሉ በንቀት ታያቸዋለህ
“ሕዝቦችን ሁሉ ታሞኛቸዋለህ” ወይም “የየሀገሩ ሕዝብ ሞኝ እንደሆኑ ታውቃለህ”
ንቀት
ማሞኘት
ጉልበቴ
እግዚአብሔር የዘማሪው ጉልበት መሆኑ የእግዚአብሔርን ጥበቃ ይወክላል። ኢ.ት፡ “አንተ ጉልበቴ ነህ” ወይም “አንተ ጠባቂዬ ነህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አንተ ረጅም ማማዬ ነህ
ረጅም ማማ ሰዎች ከጠላቶቻቸው ለመከለል የሚሄዱበት ስፍራ ነው። ዘማሪው እግዚአብሔር እርሱን እንደሚጠብቀው ሲናገር እግዚአብሔር ብርቱና አስተማማኝ ከለላ እንደሆነው ይመሰክራል። ኢ.ት፡ “እንደ ረጅም ማማ ትከልለኛለህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 59:10
እግዚአብሔር በቃል ኪዳን ታማኝነቱ ይገናኘኛል
ይህ ሐረግ እግዚአብሔር ሊያድነው እንደሚመጣ ያመለክታል። የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” ከቅጽል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ለቃል ኪዳኑ ታማኝ የሆነው አምላኬ ሊያድነኝ ይመጣል” ወይም “ለኪዳኑ ታማን ስለሆነ አምላኬ ሊያድነኝ ይመጣል” (Assumed Knowledge and Implicit Information እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
በጠላቶቼ ላይ የእኔ ምኞት
የነገር ስም የሆነው “ምኞት” ከግሥ ጋር “ፍላጎት” ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኢ.ት፡ “በጠላቶቼ ላይ እንዲደርስባቸው የምፈልገው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
በትናቸው
“እንዲቅበዘበዙ አድርጋቸው”
ጋሻችን
የእግዚአብሔር ጻድቁን መጠበቅ፣ እግዚአብሔርን ጋሻ እንደሆነ ተደርጎ እንዲነገር አድርጓል። ኢ.ት፡ “የእኛ ጠባቂ” ወይም “እንደ ጋሻ የሚከላከልልን እርሱ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 59:12
ከአፋቸው ስለሚወጣው ኃጢአትና ስለ ከንፈሮቻቸው ቃል
አፍና ከንፈር ሰዎች የሚናገሩትን ነገር ይወክላል። ኢ.ት፡ “በሚናገሩት ኃጢአትን ስለሚያደርጉ” ወይም “በሚናገሩት የኃጢአት ንግግር ምክንያት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በትዕቢታቸው ይያዙ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በትዕቢታቸው ምክንያት ሰዎች ይያዟቸው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ስለሚገልጹት
“ስለሚሉት”
በቁጣ አቃጥላቸው፣ ከእንግዲህ እንዳይገኙ አቃጥላቸው
እነርሱን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት እንደ ማቃጠል ወይም መብላት ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ተቆጣቸው፣ አንዳቸውም እንዳይቀሩ አድርገህ አጥፋቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በያዕቆብ
እዚህ ጋ፣ ያዕቆብ የሚያመለክተው እስራኤልን ነው። ኢ.ት፡ “በእስራኤል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እስከ ምድር ዳርቻ
“በምድር ላይ እጅግ ሩቅ እስከሆነው ቦታ እንኳን”። ይህ በምድር ላይ ሁሉን ስፍራ ይወክላል። ኢ.ት፡ “በምድር ላይ በሁሉም ቦታ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Psalms 59:14
እንደ ውሻ ማላዘን
ዘማሪው ሰዎችን ለማጥቃት ስለሚያስፈራሩ ጠላቶቹ ሲናገር በሰዎች ላይ እንደሚያላዝኑ፣ እንደሚያጉረመርሙ ወይም እንደሚጮኹ ውሾች አድርጎ ይገልጻቸዋል። ኢ.ት፡ “ሊያጠቁን ያስፈራራሉ” ወይም “እንደ ዱር ውሾች ሊያጠቁን ያስፈራሩናል” (Simile የሚለውን ተመልከት)
ርክተዋል
የሚፈልጉት ሁሉ ስላላቸው በቃኝ ማለት
Psalms 59:16
አንተ ለእኔ ረጅም ማማና መጠጊያ ነህና
ረጃጅም ማማዎችና መጠጊያዎች ሰዎች ከጠላቶቻቸው ለመከለል የሚሄዱባቸው ቦታዎች ናቸው። ዘማሪው ለእርሱ የሚያደርግለትን ጥበቃ እግዚአብሔር ብርቱና አስተማማኝ መጠለያ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እንደ ረጅም ማማና መጠጊያ ጠብቀኸኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በጭንቀቴ ቀን
“በችግሬ ጊዜ ሁሉ”
ጉልበቴ ሆይ፣ ለአንተ ምስጋናን እዘምርልሃለሁ
“ጉልበቴ ሆይ፣ ለአንተ” እንደ አንድ አንቀጽ ሊጣመር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንተ ጉልበቴ ነህ፤ ስለዚህ ምስጋናን እዘምርልሃለሁ” (Sentence Structure የሚለውን ተመልከት)
ጉልበቴ
እግዚአብሔር የዘማሪው ጉልበት መሆኑ እግዚአብሔር እርሱን መጠበቁን ይወክላል። ኢ.ት፡ “ጠባቂዬ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ረጅም ማማዬ ነውና
ረጃጅም ማማዎች ሰዎች ከጠላቶቻቸው ለመከለል የሚሄዱባቸው ቦታዎች ናቸው። ዘማሪው፣ እግዚአብሔር ለእርሱ የሚያደርግለትን ጥበቃ እግዚአብሔር ብርቱና አስተማማኝ መጠለያ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እንደ ረጅም ማማ ጠብቀኸኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የቃል ኪዳን ታማኝነት አምላክ
የነገር ስም የሆነው “ታማኝነት” ከቅጽል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ይህ ለብቻው በሚቆም ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ኢ.ት፡ “ለቃል ኪዳኑ ታማኝ የሆነው እርሱ እግዚአብሔር ነው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Chapter 60
Psalms 60:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።”
የኪዳን ጽጌ ረዳ በምሚለው ቅኝት የሚዘመር
ይህ ምናልባትም መዝሙሩን ስንዘምር ምን አይነት የዜማ ቅኝት ወይም ዘይቤ መጠቀም እንዳለብን ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህንን መዝሙር “የኪዳን ፅጌሬዳ” ቅኝትን በመጠቀም ዘምር” ወይም “ይህንን መዝሙር የኪዳን ፅጌሬዳን ዘይቤ በመጠቀም ዘምር”
የኪዳን ጽጌሬዳ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ “የኪዳን ፅጌሬዳ” ማለት ነው። ተርጓሚው ትርጉሙን መፃፍ ወይም ደግሞ የዕብራይስጡን ቃል መገልበጥ ይችላል። (የማይታወቁትን ተርጉም እና ቃላትን ገልብጥ ወይም ከሌላ ውሰድ የሚለውን ይመልከቱ)

ሚክታም

ሚክታም የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ትርጉም በእርግጠኝነት አይታወቅም። በምትኩ “መዝሙር” የሚለውን ቃል መጠቀም ይቻላል። ይህ እንዲህ ተብሎ ሊፃፍ ይችላል፡- “ይህ ዳዊት የፃፈው መዝሙር ነው።” ይህንን በመዝሙረ ዳዊት 16:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

አራም ናሃራይም . . . አራም ዞባህ

“በሁለቱ ወንዞች መካከል የሚገኘው አራም . . . በዞባህ የሚገኘው አራማውያን ሕዝብ።” እነዚህ ቦታዎች ናቸው።(ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ኢዮአብ

ይህ ኢዮአብን እና እርሱ የሚመራውን የጦር ሰራዊት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኢዮአብ እና የእርሱ የጦር ሰራዊት” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ ሁለት ሺህ ኤዶማውያን

“12,000 ኤዶማውያን” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ጣልኸን

እግዚአብሔር ሰዎችን አለመቀበሉ እነእርሱን እንደጣላቸው ተደርጎ ተረግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ አልተቀበልከንም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ምሽጋችንን ጥሰህ ገባህ

እግዚአብሔር የእስራኤል ጠላቶች ምሽጋቸውን ጥሰው እንዲገቡ መፍቀዱ እርሱ ራሱ እንደፈፀመው ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ጠላቶቻችን ምሽጋችንን ጥሰው እንዲገቡ ፈቅደሀል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 60:2

አያያዥ ሀሳብ፡-

ዘማሪው ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል።

አንተ ምድሪቱ እንድትናወጥ አደረግህ፤ፍርክስክስም አደረግሀት

ዘማሪው በሀገሩ ውስጥ ያለውን አደጋ የመሬት መንቀጥቀጥ እንደሆነ እንደዚያ አድርጎ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስብራትዋን ጠግን

ህዝቡን እንደገና ጠንካራ ማድረግ የመሬትን ወይም የግድግዳን ውስጥ ስብራት መጠገን እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስብራቶች

የመሬት ወይም የግድግዳ ውስጥ ሰፊ ስንጥቅ

ህዝብህ አስቸጋሪ ነገሮችን እንዲያይ አድርገሀል

እዚህ ላይ “እንዲያይ” የሚለው ቃል “እንዲደርስበት” ወይም “እንዲሰቃይ” የሚለውን ይወክላል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሚያንገዳግድ የወይን ጠጅ መጠጣት

ረዳት ማጣት በዙሪያ እንደመንገዳገድ ተደርጎ ተነግሯል፣ እንደምንም ቀጥ ብሎ መቆም እንደመቻል። “መንገዳገድ” የሚለው ረቂቅ ስምን እንደግስ መግለፅ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንድንገዳገድ የሚያደርግ የወይን ጠጅ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 60:4

አንተ ምልክትን አቆምህ

እግዚአብሔር ህዝቡን በጦርነት ውስጥ መምራቱ እግዚአብሔር ለጦር ሰራዊቱ ምልክትን ያቆመ ስጋለባሽ ንጉስ ወይም የጦር ዋና አዛዥ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ምልክትን እንዳቆመ ንጉስ እንደዚያ ነህ” ወይም “ምልክትን ወደላይ ከፍ እንደአደረገ ንጉስ እንደዚያው አንተ በጦርነት ውስጥ ትዕዛዝ ትሰጠናለህ።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምልክት

“የጦርነት ሰንደቅ አላማ።” ይህ ንጉስ ወይም የጦር ዋና አዛዥ ሰራዊቱ መሰብሰብ እንዳለበት ለማሳየት በዋልታ ላይ ከፍ የሚያደርገው ሰንደቅ አላማ ነው።

ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ

ይህ በገቢር/አድራጊ ሀረግ መግለፅ ይቻላል። ነገር ግን አንዳንድ እትሞች ስለዚህ ሀረግ የተለያየ ፍቺ አላቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “ “ቀስትን ከተሸከሙ ሰዎች ፊት ያመልጡ ዘንድ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀስትን ከተሸከሙ ሰዎች ፊት ያመልጡ ዘንድ

“ቀስትን የተሸከሙ ሰዎች” የሚለው ሀረግ በጦርነት ውስጥ ያሉትን የጠላት ወታደሮችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ በጠላቶቻችሁ ላይ ወታደሮቹን ወደ ጦርነት ሲያሰማራ ያመልጡ ዘንድ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ቀኝ እጅ

የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ የእርሱን ስልጣን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በስልጣንህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መልስን ስጠኝ answer me

እዚህ ላይ መመለስ ለእርሱ ጥያቄ ምላሽ መስጠትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔን ጥያቄ መመለስ” ወይም “ፀሎቴን መመለስ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 60:6

ኤፍሬም ደግሞ የእኔ የብረት ባርኔጣ ነው

እግዚአብሔር የኤፍሬም ነገድን የእርሱ ሰራዊት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። የብረት ባርኔጣ የጦርነት መሳሪያን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኤፍሬም እንደመረጥኩት የብረት ባርኔጣ እንደዚያው ነው” ወይም “የኤፍሬም ነገድ የእኔ ሰራዊት ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የብረት ባርኔጣ

ወታደሮች ራሳቸውን ከጉዳት ለመከላከል የሚያደርጉት ጠንካራ ኮፍያ

ይሁዳ በትረ መንግስቴ ነው

እግዚአብሔር ከይሁዳ ነገድ ለእርሱ ህዝብ ንጉስ እንዲሆኑ ወንዶችን መርጧል እናም ያ ነገድ የእርሱ በትረ መንግስት እንደሆነ እንደዚያ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “የይሁዳ ነገድ እንደ በትረ መንግስቴ እንደዚያው ነው” ወይም “ይሁዳ በእርሱ አማካኝነት ህዝቤን የምመራበት ነገድ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 60:8

ሞዐብ የመታጠቢያ ገንዳዬ ነው

እግዚአብሔር ሞዐብ ጠቃሚ አለመሆኑን ሞዐብ የመታጠቢያ ገንዳ ወይም ተራ አገልጋይ እንደሆነ እንደዚያ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞዐብ ለመታጠቢያ እንደምጠቀምበት ጎድጓዳ ሰሀን ልክ እንደዚያው ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በኤዶምያስ ላይ ጫማዬን አወረውራለሁ

እግዚአብሔር ምናልባትም የኤዶምያስ ባለቤትነትን መውሰዱ እርሱ ባለቤት እንደሆነ ለማሳየት በተምሳሌነት ጫማውን ወደ ምድሪቱ እንደወረወረ እንደዚያ አድርጎ እየተናገረ ነበረ። ነገር ግን አንዳንድ እትሞች ሌላ ትርጉሞች አሏቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “የኤዶምያስ ምድር ባለቤትነትን እኔ ወስጃለሁ” ወይም “የኤዶምያስ ምድር የእኔ እንደሆነ ለማሳየት ጫማዬን ወደ እርሱ ወረወርሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 60:10

እግዚአብሔር ግን፣ የጣልከን አንተ አይደለህምን?

መዝሙረኛው ይህንን ጥያቄ እግዚአብሔር የጣላቸው ስለሚመስል ስለዚያ ሀዘኑን ለመግለፅ ተጠቅሞበታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ግን እግዚአብሔር ሆይ አንተ እንደጣልከን እንደዚያ ይመስላል” ወይም “እግዚአብሔር አንተ የተውከን ይመስላል።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከሰራዊታችን ጋር ወደ ጦርነት አትወጣህም

መዝሙረኛው እግዚአብሔር የእነርሱን ሰራዊት መርዳቱ እግዚአብሔር ሄዶ ከእነርሱ ጋር እንደሚዋጋ እንደዚያ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ ጦርነት ስንሄድ ሰራዊታችንን አንተ አትረዳም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከንቱ ነው

“ዋጋቢስ ነው”

ድል ማድረግ ይሆናል

ጠላታችንን እናሸንፋለን

እርሱ ጠላቶቻችንን ይረጋግጣል

መዝሙረኛው እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ የእነርሱን ሰራዊት መርዳቱ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እንደሚረጋግጥ እንደዚያ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ጠላቶቻችንን እንድንረጋግጥ ያስችለናል” ወይም “እርሱ ጠላቶቻችንን ለማሸነፍ ብቁ ያደርገናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 61

Psalms 61:1

አጠቃላይ መረጃ፡-

ትይዩነት/ተመሳሳይነት በዕብራውያን ግጥም የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡-

ይህ መዝሙር ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት ነው።

ለመዘምራን አለቃ

"ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።"

ክር ባለው የሙዚቃ መሳሪያ

"ሰዎች ይህንን መዝሙር ክር ባለው የሙዚቃ መሳሪያ መጫወት አለባቸው"

የዳዊት መዝሙር

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ዳዊት መዝሙሩን ፅፎታል ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት ዘይቤ ነው

ጩኸቴን ስማ እግዚአብሔር ሆይ፣ ፀሎቴንም አድምጥ

እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። አማራጭ ትርጉም፡- "እግዚአብሔር ሆይ አድምጠኝ ፀሎቴንም መልስ" (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእኔ ይልቅ ከፊ ወዳለው አለት ምራኝ

እዚህ ላይ ጸሐፊው እግዚአብሔር እርሱ ለመጠለል ወደላይ ሊወጣ የሚችልበት ከፍ ያለ አለት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠላት ፊት ፅኑ ግንብ

እዚህ ላይ ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር እርሱ ከጠላቶቹ መከለያን የሚያቀርብ "ፅኑ ግንብ" እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- "ከጠላቶቼ የሚከልለኝ ፅኑ ግንብ" ወይም "ከጠላቶቼ ጠብቆ እንደሚያቆየኝ ፅኑ ግንብ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 61:4

በክንፎችህ ጥላ ስር መሸሸግ

ለጥበቃ ወደ እግዚአብሔር መሄድ በእርሱ ውስጥ መሸሸግ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ጥበቃ እርሱ ህፃን ጫጩቷን በክንፎችዋ ስር እየጠበቀች እንዳለች ዶሮ እንደሆነ አድርጎ የሚናገር ሁለተኛ ተለዋጭ ዘይቤ አለ። አማራጭ ትርጉም፡- "የዶሮ ጫጩት በእናቱ ክንፎች ስር የተጠበቀ እንደሆነ እንደዚይ ወደ አንተ ለጥበቃ መሄድ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ርስትን ለእኔ ሰጠህ

ጸሐፊው የእግዚአብሔር በረከቶች እርሱ የተቀበላቸው ርስቶች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- "በረከቶችን አንተ ሰጥተኸኛል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስምህን የሚያከብር

እዚህ ላይ "ስምህ" ማለት እግዚአብሔር ራሱ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "አንተን የሚያከብር" ወይም "ለአንተ አስደናቂ አክብሮት ያለው" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 61:6

ታረዝማለህ..........ብዙ ትውልዶችን

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሀሳቡ የተደጋገመው ለአፅንኦት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሱን እድሜ ታረዝማለህ

"የንጉሱን ህይወት ትቀጥላለህ" ወይም "የንጉሱ ህይወት ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ታደርጋለህ"

የእርሱ አመታትም እንደ ብዙ ትውልዶች ይሆናሉ

እዚህ ላይ "አመታት" ምን ያህል ንጉሱ እንደሚኖር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- "እርሱ ለብዙ ትውልዶች ይኖራል" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ለዘልአለም በእግዚአብሔር ፊት ይኖራል

እዚህ ላይ "በእግዚአብሔር ፊት መኖር" በእግዚአብሔር ህልውና ውስጥ መሆን ወይም ከእግዚአብሔር ጋር መሆን ማለት ነው። ይህ በትርጉሙ ውስጥ በግልፅ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- "እግዚአብሔር ለዘልአለም ከእርሱ ጋር ይሆናል" ወይም "እግዚአብሔር ለዘልአለም ከንጉሱ ጋር ይሆናል" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 61:8

ለዘለአለም ለስምህ ምስጋናን እዘምራለሁ

እዚህ ላይ "ስምህ" እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- "ሁልጊዜ ለአንተ ምስጋናን እዘምራለሁ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ስእለቴ

ይህ ዘወትር ለእግዚአብሔር መስእዋት የመስጠት ቃልኪዳንን ያመለክታል።

---

Chapter 62

Psalms 62:1

አጠቃላይ መረጃ፡-

ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡-

ይህ መዝሙር ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት ነው።

ለመዘምራን አለቃ

"ይህ ለመዘምራኑ መሪ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ነው።"

ኤዶታም

አንዱ የዳዊት የመዘምራን አለቃ የዚህ አይነት ስም ነበረው። ይህ ምናልባት እርሱን ያመለክታል። ይህንን በመዝሙረ ዳዊት 39:1 እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የዳዊት መዝሙር

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ዳዊት መዝሙሩን ፅፎታል ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት ዘይቤ ነው

መድሀኒቴ ከእርሱ ዘንድ ይመጣል

"የሚታደገኝ እርሱ ነው" ወይም "የሚያድነኝ እርሱ ነው"

አለቴ እና መድሀኒቴ እርሱ ብቻ ነው

ጸሐፊው የእግዚአብሔር እርሱን የመከላከል ችሎታን እግዚአብሔር አለት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- "እኔን ሊከላከልልኝ እና ሊያድነኝ የሚችለው እርሱ ብቻ ነው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ከፍ ያለ ግንቤ ነው

ጸሐፊው የእግዚአብሔር እርሱን የመከላከል ችሎታን እግዚአብሔር ከፍ ያለ ግንብ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- "እርሱ ከጠላቶቼ እጅ ያስመልጠኛል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እጅግ አልናወጥም

ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- "ምንምነገር ከቶ ሊያናውጠኝ አይችልም" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 62:3

እናንተ ሁላችሁ

"የእኔ ጠላቶች" ወይም "ሁሉም የእኔ ጠላቶች"

እስከ መቼ......ሰውን ታጠቃላችሁ.......ወይም የተንጋደደ አጥርን

ዳዊት መደናገጡን ለመግለፅ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄን ይጠቀማል። መልስ አይጠበቅም። አማራጭ ትርጉም፡- "ጠላቶቼ እኔን ማጥቃት መቼም ቢሆን የሚያቆሙ አይመስልም። በአንተ ፊት ልክ እንደ አዘነበለ ግንብ ወይም እንደ ተሰበረ አጥር ደካማ እንደሆንሁ ይሰማኛል። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውን ማጥቃት

"እኔን ማጥቃት"

ከእርሱ ጋር መክረዋል

"እነርሱ አስበዋል" ወይም "እነርሱ አቅደዋል"

ከእርሱ ጋር መምከር ... እርሱን ማምጣት.......እርሱን መባረክ.... እርሱን መርገም

በእነኚህ ጥቅሶች ውስጥ ዳዊት ራሱን "እርሱ" እያለ ይጠቅሳል።

በአፋቸው

ይህ ንግግራቸውን ወይም ቃላታቸውን ያመለክታል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በልባቸው ውስጥ

ይህ ሀሳባቸውን ያመለክታል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 62:5

ተስፋዬ በአንተ ላይ ተቀምጧል

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ተስፋዬን በእርሱ ውስጥ ስለ አስቀመጥሁ”
አለቴ እና መድሀኒቴ እርሱ ብቻ ነው፤ እርሱ ከፍተኛ ግንቤ ነው
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር እርሱ አለት እና ከፍተኛ ግንብ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። እነኚህ ሁለቱም ተለዋጭ ዘይቤዎች እግዚአብሔር ከአንድ ሰው ጠላቶች እንዴት ጥበቃን እንደሚሰጥ ያሳያሉ። እዚህ ላይ “መድሀኒት” እግዚአብሔር ጸሐፊውን አዳነው ማለት ነው። ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 62:2 ላይ እንዴት ተተርጉሞ እንደሆነ ይመልከቱ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አልናወጥም
ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም ነገር ሊያናውጠኝ አይችልም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 62:7
ብርቱ አለቴ እና መሸሸጊያዬ በእግዚአብሔር ነው
ጸሐፊው እግዚአብሔር አንድን ሰው ከጠላቶቹ በደህንነት እንደሚጠብቅ አለት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል።ደግሞ እግዚአብሔር መከለያን የሚሰጥ መጠለያ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ እግዚአብሔር ብርታትን እና መሸሸጊያን ይሰጠኛል”(ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ልባችሁን አፍስሱ
ይህ ፈሳሽን ወደ ውጪ እያፈሰሱ እንደሆነ እንደዚያ ለእግዚአብሔር ውስጣዊ ስሜትን መንገር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥልቃዊ ሀሳብህን ለእግዚአብሄር መስጠት” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእኛ መሸሸጊይ
“እኛ” የሚለው ቃል ዳዊትን እና የሚናገራቸውን ሰዎች ያመለክታል። (አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 62:9
በዝቅተኛ ደረጃ ያለ ሰዎች ... በከፍተኛ ደረጃ ያለ ሰዎች ሁሉ ውሸት ናቸው
ይህ የሁሉም የሀብት እና ጠቃሚነት ደረጃ ሰዎችን ያመለክታል። ሀረጎቹ “ከንቱ ናቸው” እና “ውሸት ናቸው” አንድ ትርጉም አላቸው። አንድ ሰው በማንም ሰው ላይ በእርግጠኝነት እምነት መጣል አይችልም። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም ያህል አንድ ሰው ብርቱ ቢሆንም እንኳን እምነትህን በእነርሱ ላይ መጣል አትችልም” (ትይዩነት እና ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
ባንድነት ሲመዘኑ፣ ከምንም ነገር የቀለሉ ናቸው
ሁሉንም እንደዚህ አይነት ሰዎች ባንድነት ሚዛን ላይ ብታስቀምጥ ምንም ክብደት አይኖራቸውም። ይህ ምንም ተጨባጭ ዋጋ የላቸውም ማለት ነው።
በጭቆና ወይም በዝርፊያ
እነኚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። ከሌላ ሰዎች በመውሰድ ባገኛችሁት ገንዘብ ውስጥ እምነት መጣል አትችሉም። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ምንም ፍሬ አያፈሩምና
ጸሐፊው ሀብታሞች ፍሬ ማፍራት እንደሚችሉ ዛፎች ወይም ሀረግ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንተ ምንም መልካም ነገር አይሰጡህም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ልብህ በእነርሱ ላይ አያተኩር
እዚህ ላይ “ልብ ማተኮር” አንድን ነገር በእጅጉ መመኘት የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱን አትመኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 62:11
እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ተናገረ፤ እኔም ሁለት ጊዜ ይህን ሰማሁ
ይህ እግዚአብሔር ይህንን ከአንድ ጊዜ በላይ ተናግሯል ማለት ነው።
ሀይል የእግዚአብሔር ነው
እግዚአብሔር በሀይል መገለፁ ሀይል የእርሱ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። “ሀይል” የሚለው ረቂቅ ስም በቅፅል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሀያል ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልቱ)
ደግሞም ጌታ ሆይ የቃልኪዳን ታማኝነት የአንተ ነው
እግዚአብሔር በቃልኪዳን ታማኝነት መገለፁ የቃልኪዳን ታማኝነት የእርሱ እንደሆነ ተደርጎ ተረግሯል። “ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም በቅፅል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ጌታ ሆይ ለቃልኪዳንህም ደግሞ ታማኝ ነህ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልቱ)
አንተ ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ስራው ስለምትከፍል
ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ወሮታ መክፈል ለስራ ደሞዝ እንደመክፈል አድርጎ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 63
Psalms 63:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት/ተመሳሳይነት በዕብራውያን ግጥም የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ዳዊት መዝሙሩን ፅፎታል ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት ዘይቤ ነው
በቅንነት
በእውነተኛነት
ነፍሴ አንተን ተጠማች፤ ስጋዬም አንተን ናፈቀች
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ አንድ አይነት ትርጉም አላቸው እንዴት ጸሐፊው ያለቅጥ ከእግዚአብሔር ጋር መሆን እንደሚሻ አፅንዶት ለመስጠትም ባንድነት ይጠቀማሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሙሉ ሰውነቴ ያለቅጥ ከአንተ ጋር መሆንን ይሻል” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
በደረቅ እና አድካሚ ምድር
“ሞቃት፣ ደረቅ በረሀ”
Psalms 63:3
የአንተ ቃልኪዳን ታማኝነት ከህይወት የተሻለ ስለሆነ ከንፈሮቼ
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም በተውሳከ ግስ ሊተረጎም ይችላል እና “ህይወት” የሚለው ረቂቅ ስም በግስ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ለቃልኪዳንህ ታማኝ መሆንህን በህይወት መኖርን ከምሰጠው በላይ ከፍ ያለ ቦታ እሰጠዋለሁ ስለዚህ ከንፈሮቼ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ከንፈሮቼ ያመሰግኑሀል
እዚህ ላይ “ከንፈሮቼ” ሙሉ ግለሰቡን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን አመሰግንሀለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
በአንተ ስም እጆቼን ወደላይ አነሳለሁ
እዚህ ላይ “በአንተ ስም” “ለአንተ” ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን አመልካለሁ ለአንተም እፀልያለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 63:5
የመቅኒ እና ስብ ማዕድ እንደተመገብኩ እንደዚያ ይሆናል
እዚህ ላይ ጸሐፊው እግዚአብሔርን ማወቅ እና ማምለክ መልካም ማዕድን ከመብላት ይበልጥ የሚያረካ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስብ እና የተመረጠ ምግብን ከበላ ሰው ይበልጥ ደስተኛ እሆናለሁ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በደስታ በተሞሉ ከንፈሮቼ አፌ አንተን ያመሰግናል
እዚህ ላይ “በደስታ የተሞሉ ከንፈሮቼ ኣአፌ” የሚለው እግዚአብሔርን በደስታ የሚያመሰግኑትን ግለሰቦች በሙሉ ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “በደስታ አመሰግንሀለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
በመኝታዬ ላይ ስለ አንደ ባሰብሁ ጊዜ....በለሊቱ ጊዜ ውስጥ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። ሀሳቦቹ ጸሐፊው ምን ያህል ስለ እግዚአብሔር እንደሚያስብ አፅንዖት ለመስጠት ነው የተደጋገሙት። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 63:7
በክንፎችህ ጥላ ስር ደስ ይለኛል
ጸሐፊው እግዚአብሔር ልጁን በክንፎቹ ስር የሚከላከል ወፍ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ስለምትጠብቀኝ እደሰታለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተን አጥብቄ እይዛለሁ
“እፈልግሀለሁ” ወይም “አንተ ላይ እተማመናለሁ”
ቀኝ እጅህ ይደግፈኛል
እዚህ ላይ ቀኝ እጅ ለብርታት እና ሀይል ተምሳሌትነት ይጠቅማል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ትደግፈኛለህ” ወይም “አንተ ወደላይ ታነሳኛለህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 63:9

ወደ ምድር ጥልቅ ክፍል ውስጥ ይወርዳሉ
ይህ ማለት ይሞቱ እና ወደ ሙታን መኖሪያ ይሄዳሉ። ይህ በትርጉም ውስጥ በግልፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞተው ወደ ሙታን መኖሪያ ይወርዳሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እጃቸው ሰይፍን ለሚጠቀሙ ለእነርሱ ታልፈው ይሰጣሉ
እዚህ ላይ “ሰይፍ” በጦርነት ውስጥ ሞትን ይወክላል እና “እጃቸው ሰይፍን ለሚጠቀሙ ለእነርሱ” በጦርነት ውስጥ የሚገሏቸውን ጠላቶቻቸውን ይወክላል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር በጦርነት ውስጥ እንዲሞቱ ያደርጋል” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ለቀበሮዎች ምግብ ይሆናሉ
እዚህ ላይ “እነርሱ” በጦርነት የሞቱትን የእነርሱን ሬሳ ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ቀበሮዎች ሙት ሰውነታቸውን ይበሉታል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀበሮዎቹ the

እዚህ ላይ “ቀበሮዎች” ረጅም እግር ያላቸው የዱር ውሻ አይነት ናቸው። የበሰበሰ ስጋ፣ የአደን እንስሳትን እና ፍራፍሬ ይመገባሉ።
Psalms 63:11
ንጉሱ . . . ይለዋል
ዳዊት ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። ይህ በትርጉሙ ውስጥ በግልፅ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የእስራኤል ንጉስ ይለኛል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ መማል.....በእርሱ መኩራት
“እርሱ” የሚለው ቃል “እግዚአብሔር”ን ያመለክታል።
ሀሰትን የሚናገሩ ሰዎች አፍ ግን ይዘጋል
እዚህ ላይ “አፍ” የሰውን ሁለንተና ይወክላል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ግን ውሸታሞቹን ዝም ያሰኛል” ወይም “እግዚአብሔር ግን የሚዋሹትን ሰዎች ዝም ያሰኛል” (ወካይ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 64
Psalms 64:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ መዝሙር ለእርዳታ ፀሎት ነው።
ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራኑ መሪ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ነው።”
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ዳዊት መዝሙሩን ፅፎታል ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት ዘይቤ ነው
ማቆየት
ማዳን
ከክፉዎች ሚስጢራዊ ሴራ ሰውረኝ
እዚህ ላይ “መሰወር” ጥበቃን ይወክላል እናም “የክፉዎች ሚስጥራዊ ሴራ” ክፉዎች በሚስጥር ዳዊት ላይ ሊያደርጉበት ያቀዱትን ጉዳት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉዎች በሚስጥር እኔ ላይ ሊያደርጉ ከአቀዱት ጉዳት ጠብቀኝ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ከአመፅ
“ሰውረኝ” የሚለው ቃል በፊተኛው ሀረግ ግልፅ ሆኗል እናም እዚህ መድገም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከአመፅ ሰውረኝ” ወይም “ከአመፅ ጠብቀኝ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
የጭካኔ አድራጊዎች አመፅ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- “አመፅ” የሚያመለክተው 1) በጩኸት የተሞላ ረብሻ አማራጭ ትርጉም፡- “ጭካኔ አድራጊዎች የሚያደርጉት በጩኸት የተሞላ ረብሻ” ወይም 2) በጩኸት የተሞላን ረብሻ የሚያደርግ ህዝብ ስብስብ። አማራጭ ትርጉም፡- “በጩኸት የተሞላ የጭካኔ አድራጊዎች ህዝብ ስብስብ”
Psalms 64:3
ምላሳቸውን እንደ ሰይፍ ስለዋል
ጸሐፊው የጠላቶቹ ምላስ እንደ ሰይፍ ሹል እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። እዚህ ላይ “ምላስ” ጠላቶች የሚናገሩትን መጥፎ ቃላት ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ የሚናገሩአቸው መጥፎ ነገሮች እንደ ሾለ ሰይፍ ያሳምሙኛል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ቀስት፣ መራራ ቃላት
ጸሐፊው የጠላቶቹ መራራ ቃላት እርሱ ላይ እየተተኮሱ እንዳሉ ቀስት አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ቀስት እኔን የሚወጉ መራራ ቃላት”(ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 64:5
እኛን ማን ያየናል?

ክፉዎች ማንም እንደማያያቸው ስለሚያስቡ ለጥያቄያቸው መልስ አልጠበቁም። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ ምን እንደምናደርግ ማንም አያይም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው የውስጥ ሀሳቡና ልቡ ጥልቅ ናቸው
ጸሐፊው የሰው “የውስጥ ሀሳብ” እና “የሰው ልብ” ማንም እስከ መላ መነሻ መንገዱ ሊመረምር እንደማይችለው ጥልቅ የውሀ አካል እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ውስጣዊ ሀሳብ.... የሰው ልብ
እነኚህ ሁለቱም ሀረጎች የሰው የግል ወይም ውስጣዊ ሀሳቦችን ያመለክታሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 64:7
አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው ለ”ክፉዎች” መናገሩን ቀጥሏል መዝሙረ ዳዊት 64:01።
እግዚአብሔር ግን ይመታቸዋል.... በእርሱ ቀስቶች
ጸሐፊው የእግዚአብሔር የክፉዎች ቅጣት እግዚአብሔር እነርሱ ላይ ቀስቶችን እየመታ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ እንዲሰናከሉ ይደረጋሉ
ጸሐፊው እግዚአብሔር የክፉዎችን እቅድ እንዲከሽፍ ማድረጉ እግዚአብሔር በጎዳናቸው ላይ እንዲሰናከሉ እንዳደረጋቸው አድርጎ ይናገራል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እነርሱ እንዲሰናከሉ ያደርጋል” ወይም “እግዚአብሔር የእነርሱ እቅድ እንዲከሽፍ ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የገዛ ምላሳቸው እነርሱን ስለሚቃወም
እዚህ ላይ “ምላስ” እነርሱ የሚናገሩትን ቃላት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ የሚናገሩት ቃላቶች ራሳቸውን የሚቃወሙ ስለሆኑ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ምን እንዳደረገ
“እግዚአብሔር ምን እንዳደረገ”
Psalms 64:10
በእርሱ ውስጥ መሸሸግ
ለጥበቃ ወደ እግዚአብሔር መሄድ በእርሱ ውስጥ መሸሸግ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ እርሱ ለጥበቃ መሄድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ልበ ቅኖችም ሁሉ በእርሱ ይኮራሉ
እዚህ ላይ “ልበ ቅኖች” የእግዚአብሔር ወይም ፃድቅ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔር የሆኑ ሰዎች ሁሉ እርሱን ያመሰግናሉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 65


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Psalms 65:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ መዝሙር የምስጋና መዝሙር ነው።
ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራኑ መሪ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ነው።”
መዝሙር። የዳዊት መዝሙር
“ይህ ዳዊት የፃፈው መዝሙር ነው”
ለአንተ፣ በፅዮን ላለህ እግዚአብሔር፣ ምስጋናችን ይገባሀል
ይህ ምስጋና በገዛ ራሱ መተግበር የሚችል ግለሰብ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንተ ብቻ በፅዮን ላለህ እግዚአብሔር ምስጋናችንን እናቀርባለን” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ስዕለታችንን ለአንተ እናደርሳለን
ይህ በገቢር/አደራጊ መልኩ መገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እናደርጋለን ብለን ለአንተቃል የገባነውን እናደርጋለን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ኀጢአት በእኛ ላይ በረታብን
ዳዊች ስለ ሀጢአት ሊያሸንፍ ወይም ሊጨቁን የሚችል ግለሰብ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “የገዛ ራሳችን ሀጢአት እንደሚያሸንፈን ልክ እንደዚያ ነው” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱን ይቅር ትላቸዋለህ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የእኛ “ሀጢአትን” ያመለክታል።
Psalms 65:4
አንተ የመረጥከው… የአንተ ሕዝብ
አንተ እና የአንተ የሚሉት ቃላት በዚህ ጥቅስ ውስጥ እግዚአብሔርን ያመለክታሉ።
በአንተ ቤተ መንግስቶች ውስጥ መኖር
ይህ ግነት ያ ሰው እግዚአብሔርን ለማምለክ በጣም አዘውትሮ ቤተ መቅደስ ውስጥ እንደሚሆን ይገልፃል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ጊዜ በአንተ ቤተ መንግስትህ ውስጥ ማምለክ” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከቤትህ በረከት እንረካለን፣ ከተቀደሰው ቤተ መቅደስህም
ይህ በገቢር/አደራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የቤትህ በረከት፣ የተቀደሰውም ቤተ መቅደስህ እኛን ያረካናል” (ገቢር/አደራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እኛ እንሆናለን
እዚህ ላይ እኛ የሚለው ቃል ዳዊት እና የእስራኤል ህዝብን ያመለክታል፣ እርሱ የሚያናግረውን እግዚአብሔርን ግን አይደለም። (አግላይ እና አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ቤት፣ የአንተ ቅዱስ ቤተ መቅደስ
“የተቀደሰ ቤተ መቅደስህ የሆነው የአንተ ቤት”
Psalms 65:5
በፅድቅ
“ምክንያቱም አንደ ፃድቅ ስለሆንህ”
አንተ . . . የሆንከው
“አንተ ነህ”
በምድረ ዳርቻ ሁሉ… ባህር ዳር እስከ ዳር
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “ምድር ሙሉ በሙሉ እና ባህር ዳር እስከ ዳር ከሚኖር ሰዎች ሁሉ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
በምድር ዳርቻ ሁሉ
ይህ በምድር ላይ ሁሉ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 65:6
ብርታትን የታጠቅኸው አንተ
ጸሐፊው እግዚአብሔር እርሱ ብርታቱን ልክ እንደ ቀበቶ እንደለበሰው አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ በጣም ጉልበተኛ እንደሆንህ ማሳየት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የባህሮችን ማጓራት፣ የእነርሱ ሞገድ ማጓራት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው እናም አድማጩ ወይም አንባቢው ላይ ጉልህ አሻራ ለመፍጠር ባንድነት እንጠቀማቸዋለን። አማራጭ ትርጉም፡- “የማያቋርጥ የባህሮች ማጓራት” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ማጓራት
በነፋስ እና በሞገድ የሚፈጠር ሀይለኛ ጩኸት
የህዝቦቹ አመፅ
ይህም ደግሞ እግዚአብሔር ፀጥ የሚያደርገው ነገር ነው።
አመፅ
ሀይለኛ ጩኸት
Psalms 65:8
ማስረጃ
ማረጋገጫ ወይም ሌላ ነገር ትክክል እንደሆነ የሚያሳይ ነገር
አንተ ምስራቅ እና ምዕራብ እንዲደሰቱ ታደርጋለህ
“ምስራቁ እና ምዕራቡ” የሚለው ሀረግ በአለም ዙሪያ ሁሉ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ሁሉም ቦታ ያሉ ሰዎች በደስታ እንዲጮሁ ታደርጋለህ” (ምትክ ስም እና ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
ምድርን መርዳት
ይህ የምድርን አፈር ያመለክታል።
አንተ በጣም አበለፀግኸው
“አንተ መልካም ነገሮች እርሱ ላይ እንዲበቅሉ አፈሩን በጣም መልካም አደረግኸው”
የእግዚአብሔር ወንዝ በውሀ የተሞላ ነው
ይህ በሰማይ ውስጥ ያለን እግዚአብሔር ምድርን ለማጠጣት እና ጅረትን ለመሙላት የሚልከውን የውሀ አቅርቦት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጅረቶችን በውሀ ሞላህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 65:10
አንተ… የአንተ
x
Psalms 65:13
መስኮቹ መንጎችን ለብሰዋል
ጸሐፊው መስኮቹ በጣም በመንጋ መሸፈናቸው መስኮቹ ልብስ የለበሱ የሚመስል እንደሆነ ይናገራል።
መስኮቹ
እንስሳቶች ሳር ላይ የሚመገቡበት ሰፊ ማሳ
መንጋዎች
የእንስሳት ቡድን፣ በግ እና ፍየል የመሳሰሉት
እነርሱ በደስታ ይጮሀሉ፣ እናም ይዘምራሉ
መስኮቹ፣ ኮረብታዎቹ እና ሸለቆዎቹ እነርሱ በደስታ እየዘመሩ እና እየጮሁ እንደሚመስሉ ሁሉ በጣም ለጋስ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ እንደ ደስተኛ የሚዘምሩ ሰዎች ናቸው” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ይጮሀሉ
እነርሱ የሚለው ቃል መስኮቹን እና ሸለቆዎቹን ያመለክታል።

---

Chapter 66
Psalms 66:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ መዝሙር የምስጋና መዝሙር ነው።
ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለመዘምራኑ መሪ አምልኮ ውስጥ ለመጠቀም ነው።”
Psalms 66:3
ስራህ እንዴት አስደናቂ ነው
የእግዚአብሔር ስራዎች እኛ በአክብሮት እና በፍርሀት ውስጥ እንድንሆን ያደርጉናል ምክንያቱም እርሱ ሀይለኛ እና ቅዱስ እንደሆነ እናውቃለን።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በሀይልህ ታላቅነት
“ምክንያቱም አንተ ትልቅ ሀይል አለህ”
ምድሩ ሁሉ አንተን ያመልካሉ
ይህ በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በምድር ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ አንተን ያመልካሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ለአንተ ስም ይዘምራሉ
እዚህ ላይ “የአንተ ስም” እግዚአብሔር ራሱን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ አንተን ያመልካሉ ያከብራሉም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 66:5
እርሱ... የእርሱ... እርሱ
እዚህ ላይ እነኚህ ቃሎች ሁሉ እግዚአብሔርን ያመለክታሉ፡፡
እርሱ ለሰው ልጆች ያደረገው ስራው አስፈሪ ነው
“እርሱ ሰዎች የእርሱን ስራ ሲያዩ ፍርሀት እና መደነቅ እንዲሰማቸው ያደርጋል”
የሰው ልጆች
“ሰብአዊነት”
እርሱ ባህሩን ወደ ደረቅ ምድር ቀየረ፤ እነርሱ በባሩሩ ውስጥ በእግር ሄዱ
ይህ ቀይ ባህርን መሻገርን ያመለከታል፡፡ (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 66:8
ለእግዚአብሔር በረከት መስጠት... የእርሱ ምስጋና ድምፅ ይሰማ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሰይ ትርጉም አላቸው፡፡ ሀሳቡ እግዚአብሔርን የማመስገን ጠቃሚነትን ለማጉላት ነው የተደገመው፡፡ (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
እኛ... የእኛ
እነዚህ ቃላቶች ዳዊትን እና እርሱ የሚያናግራቸው ሰዎችን ያመለክታሉ፡፡ (አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ እግራችን እንዲንሸራተት አልፈቀደም
ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ጥበቃ ሲገልጽ ሕዝቡ ሲጓዙ ወይም ከገደል አፋፍ ሊወድቁ ሲሉ እርሱ እንዳይንሸራቱ ሕዝቡን እንደሚጠብቅ አድርጎ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ወደ አደጋ እንድንወድቅ አልፈቀደም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 66:10
አንተ ወደ መረብ አመጣኸን
ጸሐፊው የእግዚአብሄር ቅጣትን እግዚአብሔር ህዝቡን በመረብ እንደያዘ አድርጎ ይናገረዋል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መረብ
ለወፍ ወይም ለእንስሳ ወጥመድ
አንተ በጀርባችን ላይ ከባድ ሸክምን አስቀመጥህ
ጸሐፊው ህዝቡ የተቋቋመውን በእነርሱ ጀርባ ላይ ከባድ ጭነት መሸከም እንዳለባቸው አድርጎ ይናገረዋል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ሰዎች በራሳችን ላይ እንዲጋልቡ አደረግህ
ይህ በጦርነት ውስጥ ክፉኛ የመሸነፍ ምስል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ የእኛ ጠላቶች በጦርነት አሸንፈውን እና ከዛም በወደቀው ሰውነታችን ላይ ሰረገላቸውን እንደነዱብን እንደዛ ነው፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በእሳት እና በውሀ ውስጥ ማለፍ
እግዚአብሄር እነርሱን እንደ እሳት እና ጎርፍ ባሉ ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ፈተናቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በእሳት እና ጎርፍ እንደሚሰቃዩ ሰዎች እኛም ተሰቃየን” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰፊ ቦታ
ጸሐፊው የእስራኤል ህዝብ አሁን ስላለው በረከት ሲናገር አስተማማኝ ድነት በሚኖራቸው በሰፊና ክፍት ስፍራ እንዲመጡ እንደተደረገ አድርጎ ገልፆታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በደህንነት በምንኖርበት በክፍት ስፍራ”(ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 66:13
ከንፈሮቼ ቃል የገቡትንና አፌ የተናገረውን
እዚህ ላይ “ከንፈሮቼ” እና “አፍ” የተነገሩትን የተስፋ ቃላት የሚያመለክት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የሰጠሁትን ተስፋ ቃል” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚቃጠል መስዋዕት
“ለመስዕዋት የቀረቡ በጎች ሲቃጠሉ የሚኖረው ሽታ”
Psalms 66:16
ለነፍሴ ያደረገላትን ነገር እናገራለሁ
“ነፍስ” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ለእኔ የሰራውን ስራ እኔ እነግራችኋል” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ በአፌ ወደ እርሱ ጮኽኩኝ
“አፍ” የሚለው ቃል ወደ እግዚአብሔር የሚጮኹትን ሰዎች ሁለንተና የሚወክል ነው፡፡ (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ በአንደበቴ ተመሰገነ
እዚህ ላይ “አንደበት” ንግግርን ይወክላል፡፡ ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱን በአንደበቴ አመሰገንሁት” ወይም “እርሱን አመሰገንሁት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ሀጢአትን አይቼ
“ሀጢአትን ወድጄ” ወይም “በደልን ይዤ”
እኔን አይሰማኝም ነበር
እዚህ ላይ “አይሰማኝም ነበረ” የሚለው እግዚአብሔር ፀሎቱን አይመልስለትም ነበር የሚል ሀሳብ አለው፡፡ ይህ በትርጉሙ ውስጥ ግልፅ ሊደረግ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ እርሱ ስጣራ አይሰማኝም ነበር ” ወይም “ፀሎቴን አይመልስልኝም ነበር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 66:19
ነገር ግን እግዚአብሔር በእውነት ሰምቶኛል፤ ትኩረት ሰጥቶኛል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት እግዚአብሔር ፀሎቱን እንዲሰማለት አፅንኦት ለመስጠት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን እግዚአብሔር በእውነት ፀሎቴን ሰምቷል” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
የፀሎቴን ድምፅ
እዚህ ላይ የጸሐፊው ፀሎት የድምፅ ግላዊ ማንነት ተሰጥቶታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ፀሎቴ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ፀሎቴን ያልከለከለኝ
እዚህ ላይ “ያልከለከለኝ” የሚለው ፀሎቱን ችላ ማለትን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- ”ፀሎቴን ችላ ያላለ”
ወይም የቃል ኪዳን ታማኝነቱን ከእኔ
“ከእኔ አልከለከለም” የሚለው ሀረግ ከዚህ በፊት ከነበረው ሀረግ መረዳት ይቻላል፣ እዚህ ደግሞ ሊደገም ይችላል፡፡ “የቃል ኪዳን ታማኝነት” የሚለው ሀሳብ “ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው” በሚለው ሀረግ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የቃል ኪዳኑን ታማኝነት ከእኔ አልመለሰም” ወይም” ከእኔ ጋር ለነበረው ቃል ኪዳን ታማኝ መሆኑን አላቆመም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 67
Psalms 67:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው፡፡ (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው፡፡”
በበገናዎች
“ሰዎች በገናዎችን ከዚህ መዝሙር ጋር ሊጫወቱ ይገባቸዋል”
ፊቱን በላያችን ያብራ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእነርሱ በቸርነት እንዲደረገላቸው ሲናገር የእግዚአብሔር ፊት በእነርሱ ላይ ብርሀን እንዳበራ አድርጎ ገልፆታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለእኛ በቸርነት አድርጎልናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መንገዶችህ በምድር ሁሉ ይታወቁ ዘንድ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች መንገዶችህን በምድር ላይ ያውቁ ዘንድ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ማዳንህን በአህዛብ ሁሉ መካከል
ጸሀፊው እግዚአብሔር እነርሱን ለማዳን ሀይል እንዳለው እያንዳንዱ ሰው እንዲያውቅ ይፈልጋል። ይህ በትርጉሙ ግልፅ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ እነርሱን ለማዳን ሀይል እንዳለህ የሀሉም መንግስታት ህዝቦች በሙሉ ያውቁ ዘንድ” (አስጨምሬ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 67:3
አቤቱ አህዛብ ያመስግኑህ… አህዛብ ሁሉ ያመስግኑህ
እግዚአብሔርን የማመስገን አስፈላጊነት አፅንኦት ለመስጠት ሁለተኛው ሀረግ የመጀመርያውን ሀረግ ትርጉም ያጠነክራል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
አህዛብ… አህዛብን ትመራለህ
እዚህ ላይ “አህዛብ” በምድር ላይ ባሉ መንግስታት በሙሉ የሚኖሩ ሰዎችን የሚወክል ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በፍትህ
“በቅንነት” ወይም “በፍትሀዊነት”
Psalms 67:5
አህዛብ ያመስግኑህ… አህዛብ በሙሉ ያመስግኑህ
እግዚአብሔርን የማመስገን አስፈላጊነትን አፅንኦት ለመስጠት ሁለተኛው ሀረግ የመጀመርያውን ሀረግ ትርጉም ያጠናክራል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ምድር ፍሬዋን ሰጠች
እዚህ ላይ ጸሐፊው ስለ “ምድር” ሲናገር ለህዝቡ ምርትን ለመስጠት እንደመረጠ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ ከሰብላችን ብዙ ምርት ሰብስበናል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 67:7
የምድር ዳርቻ ሁሉ ያከብሩታል
ይህ በየትኛውም ስፍራ የሚገኙ ሰዎች በሙሉ ከእርሱ በረከት የተነሳ እግዚአብሔርን ሊያከብሩት ይገባል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በየትኛውም የምድር ገፅ የሚገኙ ሰዎች በሙሉ ለእርሱ ታላቅ አክብሮት እንዲኖራቸው እፈልጋለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 68
Psalms 68:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።”
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) መዝሙሩን የፃፈው ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት ዘይቤ የተፃፈ ነው
እግዚአብሔር ይነሳ
እግዚአብሔር መስራት መጀመሩ እርሱ እንደተነሳ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር መስራት ይጀምር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠላቶቹ ይበተኑ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ጠላቶቹን ይበታትናቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ጢስ እንደሚበንን እንዲሁ ይብነኑ
የእግዚአብሔር ጠላቶች በነፋስ በቀላሉ እንደሚበንኑ ጢስ እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነፋስ ጢስን እንደሚያበንን እንደዚሁ በትናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ
የእግዚአብሔር ጠላቶች በእሳት በቀላሉ እንደሚቀልጥ ሰም ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ እንዲጠፉ አድርጋቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉዎች
ይህ በአጠቃላይ ክፉ ሰዎችን የሚያመለክተ ነው። (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ፃድቅ
ይህ በአጠቃላይ ፃድቃን ሰዎችን የሚያመለክት ነው። (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ሀሴት ያድርጉ ደስም ይበላቸው
እነዚህ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን እነርሱ የሚሰማቸውን የደስታ መጠን አፅንኦት ይሰጣሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 68:4
ለስሙ
ይህ እግዚአብሔርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእርሱ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በደመናት ላይ የሚሄደውን
የእግዚአብሔር ህልውና በህዝብ መካከል እርሱ በፈረስ ወይም በሰረገላ ላይ ሆኖ ወደ ምድር እንደሚሄድ ሆኖ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አባት ለሌላቸው አባት ነው
እግዚአብሔር ለወላጅ አልባዎች እንደ አባት የሚሆን ሩህሩህ አምላክ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወላጆች ለሌላቸው ልጆች እንደ አባት የሚሆን አምላክ”” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለባልቴቶች ዳኛ
እግዚአብሔር ባልቴቶችን የሚጠብቅ ምህረት የተሞላ አምላክ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የባልቴቶች ጠባቂ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ብቸኞችን በቤተሰብ መካከል ያኖራቸዋል
እግዚአብሔር ብቸኞችን በቤተሰብ መካከል እንደሚያኖራቸው ተደርጎ ተነግሯል። “እግዚአብሔር ቤተሰብ ለሌላቸው ቤተሰብ ይሰጣቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ እስረኞችን ከታሰሩበት እየዘመሩ እንዲወጡ ያደርጋቸዋል
እግዚአብሔር እስረኞችን ከታሰሩበት እንዲወጡ የሚመራቸው እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እስረኞችን ነፃ ያወጣል፤ በደስታም እንዲዘምሩ ያደርጋቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አመፀኞች
ይህ የስም ቅፅል አመፀኛ ሰዎችን የሚያመለክት ሲሆን በቅፅል ወይም በስም ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አመፀኛ ሰዎች” ወይም” በእርሱ ላይ የሚያምፁ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ምድረ በዳ
እግዚአብሔር አመፀኞችን ስለ መቅጣቱ ሲናገር እርሱ እጅግ በጣም ሞቃት የሆነ ምድረ በዳ እንዲኖሩ እንዳስገደዳቸው ተደርጎ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም ሞቃት እና ደረቅ ምድር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 68:7
አጠቃላይ መረጃ፡-
ዳዊት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በምድረ በዳ ወደ ሲና ተራራ የመራበትን ታሪክ መናገር ጀመረ።
እናንተ በወጣችሁ ጊዜ… እናንተ በዚያ ባለፋችሁ ጊዜ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ክስተት ያመለክታሉ። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ በህዝብህ ፊት ሄድህ
“አንተ ህዝብህን መራህ”
እናንተ በምድረ በዳ ባለፋችሁ ጊዜ
እግዚአብሔር በእስራኤል ህዝብ ቀድሞ የወጣ ወታደር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰማያት ዝናብን አንጠባጠቡ… የእግዚአብሔር ህልውና
“እግዚአብሔር እንዲዘንብ አደረገ”
በእግዚአብሔር ህልውና ውስጥ
እዚህ ያለው ፈሊጥ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ፊት መገለጡን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በተገለጠ ጊዜ” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 68:9


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ርስትህ በደከመ ጊዜ አንተ አበረታኸው
የእስራኤል ምድር ሊደክም የሚችል ወይም ብርታት ሊያገኝ የሚችል ሰው እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምድሪቱ መልካም እህል እድታመርት አድርገሀታል።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ርስትህ
እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣት ምድር አባት ለልጆቹ ያወረሳቸው ርስት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእስራኤላውያን የሰጠሀት ምድር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ደሀው
ይህ በአጠቃላይ ደሀ የሆኑ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ደሃ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 68:11
አጠቃላይ መረጃ፡-
ዳዊት እስራኤላውያን በምድረ በዳ የተጓዙት የጉዞ ታሪክ መናገር ቀጥሏል። በዚህ የታሪክ ክፍል ውስጥ እስራኤላውያን በጦርነት በጠላቶቻቸው ላይ ድል አድርገዋል።
ትእዛዙን የሚያውጁት ... ሰራዊት
እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን መልእክት ለሌሎች ተናገሩ። እነርሱ እጅግ ታላቅ ሰራዊት እንደ ነበሩ ተደርጎ ተነግሯል። ሀረጉ በሴት ፆታ ስለተገለፀ አንዳንድ ትርጉሞች “ትእዛዙን ያወጁት ሴቶች... ሰራዊት” ብለው ተርጉመውታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰራዊቶች ንጉስ... ለምን ይህን ታደርጋለህ?
በ መዝሙረ ዳዊት 68:12-13 ያለው መረጃ ትርጉሙን የበለጠ በቀላሉ መረዳት እንዲቻል ለማድረግ ቅደም ተከተሉ ተስተካክሏል። (የጥቅስ ድልድዮች የሚለውን ይመልከቱ)
የሰራዊት ነገስታት ፈጥነው ይሸሻሉ፣ እነርሱ ይሸሻሉ
ነገስታቱ ራሳቸውንና ሰራዊታቸውን በሙሉ ይወክላሉ። እነርሱ የሸሹት በእስራኤል ሰራዊት በመሸነፋቸው ምክንያት እንደሆነ ግልፅ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገስታቱና ሰራዊታቸው በሙሉ በመሸነፋቸው ምክንያት ከእኛ ሸሹ” (ወካይ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ምርኮ
ከተሸነፈው ሰራዊት የተወሰዱና ድል ወዳደረገው ሰራዊት ቤተ የተወሰዱ ነገሮች።
በብር የተሸፈኑ ርግቦች... ወርቅ
የዚህ ትርጉም አንዳንድ ምርኮዎች በከበሩ ብረቶች የተሸፈኑ ስለሆኑ በጣም ውድ ናቸው ማለት ነው።
እናንተ አንዳንድ ሰዎች በበጎች በረት መካከል ብትገኙ እንኳ፣ ይህንን ለምን ታደርጋላችሁ?
ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው በጦርነት ውስጥ ያልተሳተፉትን ሰዎች ለመገሰፅ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በበጎች በረት መካከል የቆዩት ሰዎች በዚያ ሊቆዩ አይገባቸውም ነበር፤ ወደ ጦርነቱ መሄድ ነበረባቸው” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 68:14
በዚያ ያሉት የተበታተኑ ነገስታት ... በሰልሞን ላይ በረዶ ዘነበ
በተራራው ላይ በጣም ቡዙ የሞቱ ነገስታትና ወታደሮች ነበሩ፤ እነዚህ ተራራውን የሸፈኑ በረዶ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በዚያ በጣም ቡዙ የጠላት ነገስታትና ወታደሮች ተሸንፈው ስለነበር እንደ በረዶ ሰልሞን ተራራን ሸፍነውት ነበር” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የተበታተኑ ነገስታት
እዚህ ላይ “ነገስታት” የሚያመለክተው ሰራዊታቸውንም ጭምር ነው።አማራጭ ትርጉም፡- “የጠላት ነገስታትና ሰራዊቶቻቸው ተበታተኑ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰልሞን
ይህ የተራራ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ብርቱ ተራራ... ከፍ ያለ ተራራ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት አንዱ ሌላውን ለማጠንከር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ብርቱና ከፍ ያለው ተራራ የኮረብታማው አገር ባሰን ነው” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ለምን በምቀኝነተ አይን ታያላችሁ... እርሱ ለዘላለም የሚኖርበትን ስፍራ?
ጥያቄው እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊፃፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የባሳን ከፍ ያለው ኮረብታማ አገር እግዚአብሔር ሊኖርበት የሚፈልገው ስፍራ በሆነው በተራራው ላይ በምቀኝነት አይን ሊያየው አይገባም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 68:17
ሃያ ሺህ፣ ሺዎች እና ሺዎች
ይህ ምናልባት ትክክለኛው እቅጩን የሆነ ቁጥር ማለቱ ላይሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ሺዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ከፍ አለ
“ከፍ ማለት” ወደ ላይ መንቀሳቀስ ነው፣ ወደ ሰማይ መሄድ ነው።
Psalms 68:19
ሸክማችንን በየእለቱ ይሸከማል
“የእኛን ከባድ ሸክም በየቀኑ ይሸከማል።” ጌታ ለህዝቡ የሚያደርገው እንክብካቤ እርሱ በአካል ችግሮቻቸውን እንደ ሸክም እንደሚሸከም ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ደህንነታችን የሆነው እግዚአብሔር... አምላካችን የሚያድን አምላክ ነው
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እዚህ ላይ “ደህንነታችን” የሚለው “አዳነ” በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚያድን አምላክ... አምላካችን እኛን የሚያድነን አምላክ ነው።” (ትይዩነት እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የጠላቶቹን ራስ ይቀጠቅጣል
እግዚአብሔር ጠላቶቹን ለመግደል ዓላማ በማድረግ የእነርሱን ራስ በመቀጥቀጥ የሚገድል ጦረኛ ተዋጊ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ራሳቸውን በመፈንከት ጠላቶቹን ይገድላል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ፀጉራም አናት
በጦርነት ጊዜ ወታደሮች ፀጉራቸውን አለመቆረጣቸው የሚዘወተር ልማድ የነበረ ይመስላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ረጅም ፀጉር ያለው አናት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ላይ በሀጢአት የሚሄዱትን
እግዚአብሔርን ማሳዘን በሀጢአት መካከል መሄድ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በተለምዶ በእርሱ ላይ ሀጢአት ያደርጋሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 68:22
እነርሱን እመልሳቸዋለሁ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ጠላቶች ያመለክታል።
የባህር ጥልቆች
ይህ የሚናገረው የባህር ጥልቅ እንደሆነ ያህል በማሰብ ሰዎች ከእግዚአብሔር ለማምለጥ የሚሞክሩበት እጅግ በጣም ሩቅ የሆነ የምድር ክፍል ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ትጨፈልቃቸዋለህ
የእስራኤል ጠላቶች ሙሉ በሙሉ የሆነ ጥፋት እስራኤላውያን እነርሱን ከእግራቸው በታች እንደሚጨፈልቋቸው ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻችሁን ሙሉ በሙሉ ታሸንፏቸዋላችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እግርህ በደም ውስጥ እንዲጠልቅ
ከጠላቶች ጥፋት የሚነሳው ብጥብጥ በጣም ስእላዊ በሆነ መልኩ ተነግሯል፣ እስራኤላውያን በሞቱት ጠላቶቻቸው ደም ውስጥ እንደቆሙ ተደርጎ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- “በደማቸው ውስጥ መረማመድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የውሻህም ምላስ ከጠላትህ ድርሻውን ያገኛል
በእስራኤል ጠላቶች ላይ በተረገው ጦርነት ምክንያት የፈሰሰው ደም ውሾች በምላሳቸው የሚፈስሰውን ደም እስኪልሱ ድረስ እጅግ የከፋ እንደነበር ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 68:24
ሰልፍ
ሰልፍ የክብረ በአል መገለጫ ሆኖ ብዙ ሰዎች ስርአት ባለው ሁኔታ የሚራመዱበት ነው።
መዘምራን
የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚጫወቱ ሰዎች።
Psalms 68:26
እግዚአብሔርን በጉባኤ አመስግኑት፣ ከእስራኤል ምንጭ የተገኛችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑ።
የእነዚህን ሀረጎች ቅደም ተከተል መለወጥ ሊረዳ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡-

“ከእስራኤል ምንጭ የተገኛችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑት፣ እግዚአብሔርን በጉባኤ አመስግኑት”
ከእስራኤል ምንጭ
ምንጭ የሚለው ቃል እስራኤል የሚለው ሰው የብዙ ሰዎች አባት የመሆን ችሎታ የሚገልፅ ተለዋጭ ዜይቤ ነው፤ ከምንጭ ብዙ ውሀ እንደሚወጣ እስራኤልም ደግሞ የብዙ ሰዎች አባት ነው። ይህ በተጨማሪ የሚያሳየው እስራኤል የሚባለው ሰው እንዳደረገው እዚህ እየተደረገ ያለው ጥሪ እግዚአብሔርን ለሚያገግሉ ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤል እውነተኛ ልጆች” ወይም “ከእስራኤል የተገኛችሁ ልጆች ሁላችሁም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የእነርሱ በብዙ የሚቆጠሩ ህዝብ
“የእነርሱ ቡድን።” የእነርሱ የሚለው ቃል የይሁዳ መሪዎችን ያመለክታል።
Psalms 68:28
እስራኤል ሆይ አምላክህ ሀይልህን አዝዞአል
አንዳንድ ትርጉሞች የእብራይስጡን ትርጉም በተለየ መንገድ ይረዱታል፡- “እግዚአብሔር ሆይ፣ ሀይልህን እዘዝ” ወይም “እግዚአብሔር ሆይ ሀይልህን ተጠቀም”
እስራኤል ሆይ፣ አምላክህ አዝዞአል
“የእስራኤል ህዝብ ሆይ፣ አምላክህ አዝዞአል”
ለእኛ... ለእኛ
“እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጸሐፊውንና የእስራኤልን ህዝብ ነው ነገር ግን ጸሐፊው የሚናገረው እግዚአብሔርን አይደለም። (አግላይ እና አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)
በኢየሩሳሌም ካለው ከቤተ መቅደስህ ብርታትህን ግለጥ
“በኢየሩሳሌም ባለው በቤተ መቅደስህ በምትገኝበት ጊዜ ሀይልህን አሳየን”
ሀይልህን ግለጥ
“ሀይል” የሚለው ረቂቅ ስም “ብርቱ” ተብሎ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ብርቱ እንደሆንህ አሳየን” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 68:30
በሸንበቆ መካከል ያሉት አራዊቶች
ብዙ የስነ መለኮት ምሁራን እነዚህ አራዊቶች የግብፅን ህዝብ የሚያመለክቱ ተለዋጭ ዘይቤዎች እንደሆኑ ያምናሉ። ይህ ግልፅ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሸንበቆ መካከል እንዳሉት አራዊቶች የመሰሉት የግብፅ ህዝብ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ህዝብ፣ የኮርማዎችና የወይፈኖች መንጋ
የሌሎች መንግስታት ሕዝቦች የከብቶች ትልቅ መንጋ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ኮርማዎች መንጋ የሆኑ ኃያላን ሕዝቦች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በትናቸው
አንድ ነገር እንዲበታተን ወይም ደግሞ በተለያየ አቅጣጫ በፍጥነት እንዲሰራጭ ማድረግ
መኳንንት ከግብፅ ይመጣሉ
ይህ የሚያመለክተው እነዚህ መኳንንቶች በኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር ስጦታ ለማቅረብ ከግብፅ እንደሚመጡ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከዚያም የግብፅ መሪዎች ለአንተ ስጦታ ያመጣሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ኩሽ
ይህ የኩሽን ህዝብ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ኩሻውያን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች
ይህ እግዚአብሔርን ማምለክ የሚወክል ምሳሌያዊ ድርጊት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔርን ለማመስገን እጆቿን ወደ ላይ ትዘረጋለች” (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 68:32
እናንተ የምድር መንግስታት ሆይ
እዚህ ላይ “መንግስታት” የሚለው የመንግስታቱን ዜጎች የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በአለም ዙሪያ ያላችሁ እናንተ የመንግስታቱ ዜጎች የሆናችሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ሰማየ ሰማያት ለወጣ ለእርሱ ዘምሩ
“ዘምሩ” የሚለው ቃል የዚህ ጥቅስ መጀመሪያ እንደሆነ ይታሰባል። እዚህ ላይ እግዚአብሔር በሰማይ ላይ በሰረገላ እንደሚነዳ ተደርጎ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሰረገላው ላይ ሆኖ ወደ ሰማይ ለሚወጣው ለእግዚአብሔር ዘምሩ” (አስጨምሬ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ድምፁን በሀይል ከፍ ያደርጋል
ይህ ፈሊጥ እርሱ በሀይል ይናገራል የሚል ትርጉም አለው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ በሀይል ይጮሀል” ወይም “እርሱ ከፍ ባለ ድምፅ ይናገራል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 68:34
ለእግዚአብሔር ክብርን አቅርቡ
“አቅርቡ” ለአንድ ሰው ተገቢውን ዝና ስጡ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ክብር የእግዚአብሔር ነው”
ሀይሉ በሰማያት ላይ ነው
“ሀይል” የሚለው ረቂቅ ስም “ሀይለኛ” ተብሎ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ሀይለኛ እንደሆነ በሰማያት ላይ ያሳያል” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ በተቀደሰ ስፍራህ የተፈራህ ነህ
እዚህ ላይ ጸሐፊው ለእግዚአብሔር በቀጥታ ይናገራል። (እንቶኔ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ብርታትና ሀይል
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እግዚአብሔር ለህዝቡ ምን ያህል ብርታት እንደሚሰጥ አፅንኦት ይሰጣሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 69
Psalms 69:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ መዝሙር ለእርዳታ የሚደረግ መዝሙር ነው።
ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።”
በፅጌረዳ ዜማ
ይህ ምናልባትም የሚያመለክተው የሙዚቃ አይነትን ነው። ይህንን በ መዝሙረ ዳዊት 45:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) መዝሙሩን የፃፈው ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት የመዝሙር ስልት የተቃኘ ነው።
አቤቱ ውሀ፣ ህይወቴን ለአደጋ ተጋላጭ አድርጎታል
ጸሐፊው በህይወቱ የገጠመውን ችግር በውሀ ጎርፍ እየሰመጠ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በውሆች እየሰጠምሁ እንደሆነ ይሰማኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በጥልቅ ረግረግ ጠለቅሁ
ጸሐፊው በህይወቱ የገጠመውን ችግር በጥልቅ ረግረግ እየሰጠመ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥልቅ ረግረግ እየሰጠምሁ እንደሆንና እንደምሞት ሆኖ ይሰማኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ረግረግ
ወፍራም ጭቃ
መቆምያ ስፍራ የለኝም
ጸሐፊው ያለበት ሁኔታ እንዴት ያልተረጋጋና እርግጠኝነተ የሌለበት እንደሆነ አፅንኦት ለመስጠት አሉታዊ አረፍተ ሀሳቦችን ይጠቀማል። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
ጎርፍ በእኔ ላይ በሚፈስስበት ወደ ጥልቅ ወርጃለሁ
ጸሐፊው ችግሩን በጥልቅና አስፈሪ ወንዝ እየሰጠመ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አማራጭ ትርጉም:- “በጥልቅ ውሀ እንደሆንሁና የውሀ ጎርፍ በላዬ ላይ እየፈሰሰ እንደሆነ ይሰማኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:3

ደከምሁ

በጣም መዛል

አይኖቼ ፈዘዙ

ይህ ፈሊጥ ጸሐፊው እጅግ በጣም እንዳለቀሰና ከአሁን በኋላ አይኖቹ በሚገባ ማየት እንደማይችሉ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም:- “አይኖቼ ከእንባ የተነሳ አብጠዋል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በራሴ ካሉት ፀጉሮች የበለጠ

ይህ ጸሐፊው ምን ያህል ጠላቶች እንዳሉት ለመግለፅ የተጠቀመበት ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “በራሴ ላይ እንዳሉት ፀጉሮች እኔ ልቆጥራቸው ከምችላቸው በላይ ናቸው” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቆረጡኝ

ይህ ፈሊጥ “ገደሉኝ” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:5

ሞኝነቴ

“ሞኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም “ሞኝ” ተብሎ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ የሰራኋቸው ሞኝ ነገሮች” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሀጢአቶቼ ከአንተ የተሰወሩ አይደሉም

ይህ በአዎንታዊ አረፍተ ሀሳብ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሀጢአቶቼን በሙሉ ታውቃቸዋለህ” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ አይፈሩ.. እነዚህ አይዋረዱ

“እነዚህን አታሳፍራቸው… እነዚህን አታዋርዳቸው”

በአንተ ተስፋ የሚያደርጉ ከእኔ የተነሳ አይፈሩ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እነዚህ አንተን የሚጠባበቁ ሰዎች ከእኔ የተነሳ አንዳቸውም ለሀፍረት ታልፈው እንዲሰጡ እባክህ አትፍቀድ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተን የሚፈልጉ ከእኔ የተነሳ አይዋረዱ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እነዚህ አንተን የሚፈልጉ ሰዎች ከእኔ የተነሳ አንዳቸውም ለውርደት ታልፈው እንዲሰጡ እባክህ አትፍቀድ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ አንተን የሚፈልጉ

እግዚአብሔርን መፈለግ የሚከተሉትን ሊወክል ይችላል:- 1) እግዚአብሔርን ለእርዳታ መጠየቅ ወይም 2) ስለ እግዚአብሔር ማሰብና እርሱን መታዘዝ። አማራጭ ትርጉም:- 1) “እነዚህ አንተን ለእርዳታ የመሚጠይቁህ ሰዎች” ወይም 2) “እነዚህ አንተን የሚያመልኩህና የሚታዘዙህ ሰዎች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:7

ስለ አንተ

“ለአንተ ስል” ወይም “ለአንተ”

ስድብን ታግሻለሁ

የጸሐፊው ጠላቶች ስድቦች ሊሸከማቸው የሚገባው እጅግ በጣም ከባድ ሸክም እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል።አማራጭ ትርጉም:- “የጠላቶቼን ስድቦች ተሸክሜአለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፊቴን እፍረት ሸፍኖታል

ጸሐፊው የተሰማው እፍረት ማንኛውም ሰው በግልፅ ሊያየው የሚችለው በፊቱ ላይ የሚታይ መጥፎ ነገር እንደሆነ አድርጎ ተናግሮታል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ ሙሉ በሙሉ ተዋርጃለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለወንድሞቼ እንደ እንግዳ ሆንኩኝ

ጸሐፊው ስለ ራሱ ሲናገር የቤተሰቡ አባል እንዳልሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም:- “ወንድሞቼ ከእንግዲህ ወዲህ ፈፅሞ አያውቁኝም ወይም አይቀበሉኝም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለወንድሞቼ እንደ እንግዳ… ለእናቴ ልጆች ደግሞ እንደ ባእድ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። የተደጋገሙት ከራሱ ቤተሰብ መለያየቱን አፅንኦት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ለእናቴ ልጆች እንደ ባእድ

እዚህ ላይ “ሆንሁኝ” የሚለው ሀሳብ ልንረዳው እንደሚገባ ታሳቢ ኖሯል። ጸሐፊው ስለ ራሱ ሲናገር የራሱ ቤተሰብ አባል እንዳልሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም:- “ወንድሞቼ ከእንግዲህ ወዲህ ፈፅሞ አያውቁቁኝም ወይም አያምኑኝም” (አስጨምሬ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የቤትህ ቅናት በላኝ

ጸሐፊው ለእዚአብሔር ቤተ መቅደስ ስላለው ቅናት ሲናገር ቅናቱ ጸሐፊውን የሚበላ አራዊት እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም:- “ለአንተ ቤት ያለኝ ቅናት በላኝ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በላኝ

ይህ ፈሊጥ ጸሐፊው ለቤተ መቅደሱ ያለው ቅናት ሀሳቡንና ድጊቱን በሙሉ ተቆጣጥሮታል ማለቱ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የማስበውንና የምሰራውን ነገር ሁሉ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሯል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚሰድቡህ ስድብ… በላዬ ወድቋል

ጸሐፊው የእግዚአብሔር ጠላቶች ስድቦች በጸሀፊው ላይ እንደተጣሉ ድንጋዮች እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል።አማራጭ ትርጉም:- “አንተን የሚሰድቡህ ስድባቸውን በእኔም ላይ ጥለዋቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 69:10

አለቀስሁ ምግብም አልበላሁም

ጸሐፊው የወፆሙ እውነታ ህዝቡ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በአግባቡ ካለመያዙ የተነሳ በጣም አዝኖ እንደነበር ያመለክታል። (ምሳሌያዊ ድርጊት እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰደቡኝ

x

Psalms 69:13

አንተ በምትቀበልበት ጊዜ

“አንተ በምትወድደው ጊዜ” ወይም “አንተ ፈቃደኛ ስትሆን”

በማዳንህ እርግጠኝነት መልስልኝ

“እርግጠኝነት” እና “ማዳንህ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “በታማኝነት” እና “አድነኝ” በሚሉት ሊብራሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- “አንተ በታማኝነትህ ስለምትወድደኝ፣ ለእኔ ቃል እንደገባኸው፣ አድነኝ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አውጣኝ… እስጥም ዘንድ አትተወኝ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ከረግረግ አውጣኝ እሰጥም ዘንድ አትተወኝ

ጸሐፊው ከጠላቶቹ ስለሚገጥመው አደጋ ሲናገር ወደ ጭቃ ጉድጓድ እየሰጠመ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም:- “ከእንግዲህ ጭቃ ውስጥ እንድሰጥም አትፍቀድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንድወጣ አድርገኝ

እዚህ ላይ “አውጣኝ” የሚለው ከአደጋ ስለማምለጥ ያመለክታል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “አውጣኝ” ወይም “አድነኝ” (ፈሊጥ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ታደገኝ

እዚህ ላይ “እኔን” የሚለው ሀሳብ ግልፅ እንደሆነ ታሳቢ ተደርጎ ነው። ይህ በገቢር ቅርፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እባክህ አድነኝ” (አስጨምሬ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥልቅ ውሀ… የውሀ ጎርፍ… ጥልቅ

እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ከጥልቅ ውሀ አድነኝ

ጸሐፊው ከጠላቶቹ ስለሚደርስበት አደጋ ሲናገር በጥልቅ ውሀ እየሰጠመ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የውሀው ጎርፍ አስፈራኝ

ጸሐፊው ከጠላቶቹ ስለሚደርስበት አደጋ ሲናገር የውሀ ጎርፍ ሙሉ በሙሉ እንደሚሸፍነው አድርጎ ገልፆታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥልቅ ይውጠኛል

ጸሐፊው ስለ ጥልቁ ሲናገር ጉድጓዱ እርሱን ሊበላው የተዘጋጀ ጨካኝ አውሬ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም:- “ጥልቅ ውሀዎቹ እንደ አደገኛ አውሬ ዋጡኝ” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድጓዱ አፉ በእኔ ላይ እንዲዘጋ አታድርግ

እዚህ ላይ “ጉድጓድ” እንደ ሰው አፍ እንዳለውና ጸሐፊውን መብላት እንደሚችል ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “ጉድጓዱ እንዲበላኝ አታድርግ” ወይም “የሞት ጉድጓድ በእኔ ላይ እንዲዘጋ አታድርግ” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 69:16
የኪዳንህ ታማኝነት መልካም ነው
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅፅል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ለኪዳንህ መልካምና ታማኝ ነህ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ለእኔ ያለህ ምህረት ብዙ ነው
“አንተ ለእኔ በጣም መሀሪ ነህ”
ወደ እኔ ተመለስ
ወደ አንድ ሰው የመመለስ ሀሳብ ለእነርሱ ተገቢ ትኩረት መስጠት ወይም እነርሱን መርዳት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርዳኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከባሪያህ ፊትህን አትሰውር
የአንድ ሰው ፊት መሰወር ሌላ ሰውን ለመስማት ወይም ለመርዳት ፈቃደኛ አለመሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እባክህ ባሪያህን እርዳ” ወይም “እባክህ እርዳኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ጭንቅ ውስጥ
“በታላቅ መከራ ውስጥ”
Psalms 69:18
ታደገኝ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ሊታደገውና ነፃነቱን ሊመልስለት እንደሚችል ባሪያ እንደሆነ ራሱን በማሰብ እግዚአብሔርን እንዲታደገው ይጠይቀዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነፃ አውጣኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ተቤዠኝ
ጸሐፊው ነፃ ለመውጣት እዳው ሊከፈልለት የሚቻል እስረኛ እንደሆነ ራሱን በማሰብ እግዚአብሔርን እንዲቤዠው ይጠይቀዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “አድነኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ስድቤን፣ እፍረቴን እና ውርደቴን
እነዚህ ረቂቅ ስሞች እንደ ድርጊት ሊብራሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች እንዴት እንደሰደቡኝ፣ እንዳሳፈሩኝ እና እንዳዋረዱኝ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ጠላቶቼ ሁሉ በፊትህ ናቸው
እዚህ ላይ “በፊትህ” የሚለው እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ሁሉን ያያል ደግሞም ያውቃል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቼ ሁሉ እነማን እንደሆኑ አንተ ታውቃቸዋለህ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 69:20
ልቤን ሰበረው
ይህ ፈሊጥ ሰውየው እጅግ በጣም እንዳዘነ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥልቀት ውስጤን አሳዘነኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ልቤ እጅግ በጣም ከብዶታል
የጸሐፊው ታላቅ ሀዘን እርሱ ትልቅ ክብደት እንደተሸከመ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ሀዘን ከብዶኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አስተዛዛኝ
ሀዘንና ስብራት መጋራት
ለምግቤ መርዝ ሰጡኝ
ይህ ምናልባትም ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ሰዎች ለጸሐፊው ይሰጡት የነበረው ምግብ እንደ መርዝ ጣእም ያለው በጣም መጥፎ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ መርዝ ጣእም ያለው ምግብ ሰጡኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 69:22
በፊታቸው የቀረበው ማእዳቸው ወጥመድ ይሁንባቸው… እንቅፋት ይሁንባቸው
ጸሐፊው ጠላቶቹ በወጥመድ ወይም በመረብ እንደሚያዙ ትንንሽ እንስሳቶች የጠላቶቹ ምግብ ሙሉ በሙሉ እንዲያጠፋቸው ይፈልጋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምግባቸው እንደ ወጥመድ ያጥፋቸው… እንደ መረብ ታውድማቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማእዳቸው
ይህ ምናልባትም በግብዣ ላይ በማእድ የሚቀርበውን ምግብ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የራሳቸው ምግብ ወይም ለመስዋእት የቀረበ ግብዣ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
አይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ
ጸሐፊው በሚገባ ስለማያዩ አይኖች ሲናገር እንደጨለሙ አድርጎ ገልፆታል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እባክህ አንድም ነገር ማየት እንዳይችሉ አድርጋቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ጀርባቸው እንዲጎብጥ አድርግ
ደካማ ጀርባዎች በድካም እንደሚንቀጠቀጡ ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጀርባቸው አንድም ነገር መስራት እንዳይችሉ እጅግ ደካማ አድርጋቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጀርባቸው
“ጎናቸው” ወይም “ወገባቸው”
Psalms 69:24
መአትህ በእነርሱ ላይ ይፍሰስ
የእግዚአብሔር ቁጣውን መግለፅ እርሱ በጠላቶቹ ላይ እንደ ዉሀ እንደሚያፈስስ ተደርጎ ተገልጧል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መአት
ፍትህ ያጣ ሰው ቁጣ
የቁጣህ መቅሰፍት
“የሚነድ ቁጣህ” ወይም “ጠንካራ ቁጣህ”
ይደረስባቸው
በጠላቶቹ ላይ የሚገለጠው የእግዚአብሔር ቁጣ እነርሱን እየተከተለ እንደሚሮጥና እንደሚይዛቸው ተደርጎ ተገልጧል።(ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ባድማ ይሁን
ይህ ረቂቅ ስም “የተተዉ ይሁኑ” በሚለው ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የተተዉ ይሁኑ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 69:26
እርሱን አሳድደውታልና
“ሰውየውን አሳድደውታልና”
መታኻቸው
እዚህ ላይ “መመታት” ቅጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ቀጣሀቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ያቆሰልካቸው
እዚህ ላይ “ማቁሰል” እርሱ እንዲሰቃዩ ማድረግን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዲሰቃዩ ያደረግኻቸው ሰዎች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በሀጢአታቸው ላይ ሀጢአት ጨመርክባቸው
“የሀጢአታቸውን በሙሉ መዝገብ ያዝክባቸው”
በሀጢአት ላይ ሀጢአት
“በጣም ብዙ ሀጢአት”
ወደ ፅድቅህ ድል አይግቡ
ወደ እግዚአብሔር ድል መምጣት ከእርሱ ዘንድ ሽልማት መቀበልን የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የአንተን የፅድቅ ሽልማት እንዲቀበሉ አታድርጋቸው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 69:28
እርሱ ይደምሰሱ
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው የጠላቶቹን ስሞች ያመለክታል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስማቸውን ደምስስ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
አይጻፉ
“እነርሱ” የሚለው ሀሳብ ግልፅ እንደሆነ ታሳቢ ተደርጓል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስማቸውን አትፃፋቸው” (አስጨምሬ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ሆይ፤ የአንተ መድሀኒት በከፍታ ላይ ያድርገኝ
“መድሀኒት” የሚለው ረቂቅ ስም “አድነኝ” በሚለው ግስ ሊብራራ ይችላል። እዚህ ላይ “በከፍታ ላይ” የሚለው የደህንነት ስፍራን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሆይ፤ አድነኝ ደግሞም በደህንነት ስፍራ አስቀምጠኝ” (ረቂቅ ስሞች እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 69:30
የእግዚአብሔር ስም
እዚህ ላይ “ስም” እግዚአብሔርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዝአብሔር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በምስጋና
ይህ ረቂቅ ስም ማመስገን በሚለው ግስ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱን በማመስገን” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ከበሬና ከኮርማ ይልቅ የበለጠ
በሬና ኮርማ ለእግዚአብሔር እንደ መስዋእት ሊቀርቡ እንደሚገቡ ግልፅ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሬ ከመሰዋትና ኮርማ ከመሰዋት ይበልጣል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀንድና ጥፍር ካለው ኮርማ
ይህ ሀረግ ሙሉ ለሙሉ ያደገ ኮርማና ሌሎች ያልደረሱ ላሞችን በአግባቡ ይለያል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቀንድና ጥፍር ያለው ሙሉ በሙሉ ያደገ ኮርማ”
Psalms 69:32
የዋሆች
ይህ በአጠቃላይ “የዋህ” ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የዋህ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ እግዚአብሔርን የምትፈልጉ
እግዝአብሔርን መፈለግ የሚወክለው የሚከተሉትን ነው፡- 1) እግዚአብሔርን ለእርዳታ መጠየቅ ወይም 2) ስለ እግዚአብሔር ማሰብና እርሱን መታዘዝ። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ እግዚአብሔርን ለእርዳታ የምትጠየቁት” ወይም “እናንተ ስለ እግዚአብሔር የምታስቡ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ልባችሁ ህያው ይሁን
እዚህ ላይ “ልባችሁ” የሚለው የሚያመለክተው ሰዎቹን ነው። እዚህ ላይ “ህያው” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን መበረታታት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የበረታችሁ ሁኑ” (ወካይ እና ግምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ይሰማል
እዚህ ላይ “ይሰማል” ማለት ይሰጣል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ይመልሳል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ችግረኞች
ይህ በአጠቃላይ ችግረኛ ሰዎችን ይመለከታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ችግረኛ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ እስረኞች
“ለእርሱ መከራ የተቀበሉት”
Psalms 69:34
ሰማይና ምድር፣ ባህርም… ያመሰግኑት
እዚህ ላይ ሰማይ፣ ምድርና ባህር እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚችሉ ሰዎች ተደርገው ተነግረዋል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ባህርና በውስጣቸው የሚንቀሳቀሱ ሁሉ
“ያመስግኑት” የሚለው ሀሳብ በውስጡ እንዳለ ግልፅ ሊሆን ይገባዋለው። አማራጭ ትርጉም፡- “ባህሮችና በውስጣቸውም የሚንቀሳቀሱ ማንኛውም ነገሮች ሀሉ ያመስግኑት” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ፅዮንን ያድናታል
እዚህ ላይ “ፅዮን” የሚለው በፅዮን የሚኖሩትን ህዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የፅዮንን ህዝብ ያድናል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እርሷን ይወርሳታል
“እርሷን” የሚለው ቃል የይሁዳን ምድር ያመለክታል።
ስሙን የሚወድዱ
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔርን የሚወድዱ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 70
Psalms 70:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራይስጥ ግጥም በጣም የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ለመዘምራን አለቃ
“ይህ በአምልኮ ጥቅም ላይ እንዲውል ለመዘምራን አለቃ ነው”
የዳዊት መዝሙር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) መዝሙሩን የፃፈው ዳዊት ነው ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) የዳዊት አይነት መዝሙር ነው
ለመታሰቢያ
“ይህ መዝሙር የተፃፈው ሰዎች እንዲያስታውሱ ነው”
እነዚያ
“እነዚያ ሰዎች”
ነፍሴን ለመውሰድ
ይህ ፈሊጥ “ሊገድሉኝ” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ይፈሩ ይዋረዱም
ይህ በገቢር ቅርፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “”እግዚአብሔር ያሳፍራቸው፣ በእነርሱም ላይ ውርደት ያምጣባቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ኋላቸው ይመለሱ፣ ይፈሩም
ይህ በገቢር ቅርፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ወደ ኋላቸው ይመልሳቸው፣ ስለ ሰሩት ስራ እንዲያፍሩ ይድጋቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ኋላቸው ይመሰሉ
እንዲቆሙ ወይም እንዳይንቀሳቀሱ መደረግ ከጥቃታቸው ወደኋላ እንዲመለሱ እንደማድረግ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዲቆሙ ማድረግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንኳ፣ እንኳ የሚሉኝ
ይህ የስላቅ ሳቅ መግለጫ ነው። “እንኳ እንኳ” የሚለውን በአንተ ቋንቋ በምትጠቀምበት በየትኛውም የሳቅ ድምፅ ልትተካው ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚያ በእኔ ላይ የሚቀልዱና የሚስቁ”
Psalms 70:4
የሚፈልጉህ
እግዚአብሔርን መፈለግ የሚከተሉትን ሊወክል ይችላል፡- 1) እግዚአብሔርን ለእርዳታ መጠየቅ ወይም 2) ስለ እግዚአብሔር ማሰብና እርሱን መታዘዝ። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን ለእርዳታ እጠይቃለሁ” ወይም “ስለ አንተ አስባለሁ እታዘዛለሁም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሀሴት ማድረግና ደስ መሰኘት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የደስታውን ጥልቀት አፅንኦት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “በታላቅ ሁኔታ ሀሴት ማድረግ” ወይም “በጣም ደስ መሰኘት” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
መዳንህን የሚወድዱ
“መዳን” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ተግባር ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱን ስላዳንካቸው እወድሀለሁ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ሁልጊዜ ይበሉ
ይህ ግነት አፅንኦት የሚሰጠው እግዚአብሔርን ሁልጊዜ ማድነቅ አስፈላጊ እንደሆነ ነው። (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ታላቅ ነው ይበሉ
ይህ በገቢር መልክ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉም ሰው እግዚአብሔር ታላቅ ነው ይበል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ችግረኛና ምስኪን
እዚህ ላይ ችግረኛ እና ምስኪን የሚሉት ቃላቶች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ራሱን መርዳት እንደማይችል አፅንኦት የሚሰጡ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም ምስኪን” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ለእኔ ፍጠን
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር እርሱን ለመርዳት ወደ ጸሐፊው እንደሚሮጥ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔን ለመርዳት ፈጥነህ ና” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ረዳቴ ነህ፣ እኔን ታድገኸኛል
እዚህ ላይ “እኔን ታድገኸኛል” የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር እንዴት የእርሱ “ረዳት” እንደሆነ አፅንኦት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔን በመታደግ ትረዳኛለህ” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
አትዘግይ
ይህ በገቢር ቅርፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እባክህ በፍጥነት ና” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 71
Psalms 71:1
አጠቃላይ መረጃ:-
ትይዩነት በዕብራይስጥ ግጥም በጣም የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ:-
ይህ መዝሙር ለእርዳታ የተደረገ ፀሎት ነው።
እግዚአብሔር ሆይ፣ እኔ በአንተ እሸሸጋለሁ
ለጥበቃ ወደ እግዚአብሔር መሄድ በእርሱ እንደመሸሸግ ተደርጎ ተረግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር ሆይ፣ ለጥበቃ ወደ አንተ መጣሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለዘላለም አልፈር
ይህ በገቢር ቅርፅ ሊብራራ ይችላል። “ለዘላለም አልፈር” የሚለው በ መዝሙረ ዳዊት 25:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “ጠላቶች ፈፅሞ ለሀፍረት አይዳርጉኝ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በፅድቅህ አድነኝ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉዎች 1) አድነኝ ምክንያቱም አንተ ሁልጊዜ የምትሰራው ትክክለኝ የሆነውን ነገር ነው” ወይም 2) አድነኝ እኔ የምሰራው አንተ ልሰራ የምትፈልገውን ነገር ነውና (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ጆሮህን ወደ እኔ መልስ
እዚህ ላይ ጆሮህ የሚለው የሚያመለክተው ወደ እርሱ የሚፀልየውን ሰው ለመስማት የእግዚአብሔርን ፈቃደኝነት ነው። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 17:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “ለእኔ ትኩረት ስጥ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ለእኔ የመሸሸጊያ አለት ሁነኝ
ዘማሪው ጠላቶች ሊያገኙት በማይችሉበት በትልቅ አለት ገደል ውስጥ ተደብቆ ደህና ሊሆን እንደሚችል ሁሉ እንደዚሁ በደህንነት እንዲጠብቀው እግዚአብሔርን ይጠይቃል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አለት... አለት
እነዚህ አንድ ሰው እጁን በሌላው ይዞ አስገብቶ የሚይዝባቸው ኮረብቶችና ተራሮች ናቸው፣ አለቶች አይደሉም።
አንተ ትእዛዝ ሰጥተሀል
“አንተ ለመላእክትህ ትእዛዝ ሰጥተሀል”
አድነኝ
“በደህንነት ጠብቀኝ”
አንተ አለቴ እና መጠጊያዬ ነህ
ዘማሪው እግዚአብሔር እንደሚጠብቀውና በትልቁ ተራራ ጫፍ ላይ እንደተደበቀና በሰው ሰራሽ መጠጊያ እንደተደበቀ ያህል እግዚአብሔር እንዲጠብቀውና ደህና እንዲያደርገው ያምናል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 71:4
ከክፉ እጅ፣ ከአመፀኛው እጅ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) “እጅ” የሚለው ቃል ለሀይል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ከሀያላን እጅ፣ ከአመፀኞች እጅ” ወይም 2) “እጅ” ለራሱ ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ከክፉ ሰዎች፣ ከአመፀኞች ሰዎች” ወይም “ክፉ ሰዎች ወይም አመፀኞች ሰዎች እኔን መጉዳት እንዳይችሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉ፣ ከአመፀኛ እጅ
“ክፉ፣ ከአመፀኛ እጅ አድነኝ።” አማራጭ ትርጉም:- “መረዳት የሚቻለውን መረጃ ግልፅ ልታደርገው ትችላለህ።” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉ... አመፀኛ... ጨካኝ
እነዚህ ቅፅሎች እንደ የስም ሀረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- “ክፉ ሰዎች... አመፀኛ ሰውች... ጨካኝ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ተስፋዬ ነህ
እዚህ ላይ “ተስፋ” መዝሙረኛው ተስፋ ለሚያደርግበት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ በእርግጠኝነት እንደምትረዳኝ የምጠብቀው አንተ ነህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 71:6
ከማህፀን ጀምሮ በአንተ ተደገፍሁ
ይህ በገቢር ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ከማህፀን ጀምሮ አንተ እኔን ደገፍከኝ” ወይም “ከእናቴ ማህፀን ከወጣሁበት ጊዜ ጀምሮ አንተ እኔን ተንከባከብከኝ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ አንተ ነህ
“አንተ ነህ”
እኔ ለብዙ ሰዎች ምሳሌ ነኝ
“ብዙ ሰዎች እንዴት እንደምኖር ይመለከታሉ እኔም እንደምኖረው መኖር ይፈልጋሉ”
Psalms 71:8
አፌ ሁልጊዜ በምስጋናህ ይሞላል... በክብርህ
ዘማሪው በሚናገረው ቃላቶች እግዚአብሔርን ለማመስገንና ለማክበር ያለውን ፍላጎት ሲናገር አፉ በምግብ እንደሚሞላ እንደዚሁ በቃላቶች እንደተሞላ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም:- “አፌ አንተን በሚያመሰግኑና በሚያከብሩ ቃላቶች ይሞላል” ወይም “እኔ ሁልጊዜ አመሰግንሀለሁ... እኔ ሁልጊዜ አከብርሀለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ምስጋና
እዚህ ላይ “ምስጋና” የሚለው እግዚአብሔርን ለማመስገን የሚጠቀምባቸውን ቃላቶች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “አንተ ምን ያህል ታላቅ እንደሆንህ ለሰዎች የሚናገሩ ቃላቶች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ክብር
እዚህ ላይ ክብር የሚለው እግዚአብሔርን ለማክበር የሚጠቀምባቸውን ቃላቶች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሰዎች አንተን እንዲያከብሩ የሚያደርጉ ቃላቶች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ቀኑን በሙሉ
“ቀኑን ሁሉ” ወይም “ሁልጊዜ”
አትጣለኝ... አትተወኝ
እነዚህ ሁለት ቃላቶች በመሰረታዊነተ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ጥቅም ላይ የዋሉት ለአፅንኦት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
አትጣለኝ
“ከአንተ ርቄ እንድሄድ አታድርገኝ።” እግዚአብሔርን እርሱን መተዉ ከእርሱ ርቆ እንዲሄድ እግዚአብሔር እንዳስገደደው ተደርጎ ተነግሯል። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 51:11 እንዴት እደተረጎምከው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “አታስወግደኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አትተወኝ
“ሁልጊዜ አትልቀቀኝ”
Psalms 71:10
ህይወቴን ይፈልጓታል
እነርሱ ህይወቱን ለመውሰድ አጋጣሚ እየጠበቁ እንደሆነ ያመለክታል። ህይወት መውሰድ የሚለው ለስላሴ መግደል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ህይወቴን ለመውሰድ አጋጣሚ ይፈልጋሉ” ወይም “እኔን ለመግደል አጋጣሚ ይፈልጋሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አሉ
ይህ እነርሱ ስለ እርሱ እያወሩ እንደሆነ ግልፅ ለማድረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ስለ እኔ ተናገሩ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ተከተሉና ያዙት
“ሲሮጥ ተከተሉትና ግደሉት”
Psalms 71:12
ከእኔ አትራቅ
እግዚአብሔር የጸሐፊውን ጥያቄ ገና ስላልመለሰለት እርሱ ስለ እግዚአብሔር ከጸሐፊው ርቆ እንደቆመ አድርጎ ተናግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 71:14
እጨምራለሁ
“ሁልጊዜ የበለጠ” ወይም “ሁልጊዜ ከዚህ በፊት ሳደርገው ከነበረው የበለጠ”
አፌ ፅድቅህ ይናገራ፣ ማዳንህን ደግሞ ቀኑን ሙሉ፣ ምንም እንኳ ሊገባኝ ባይችልም
“ፅድቅህን እና ማዳንህን ሙሉ በሙሉ አልተረዳሁትም፣ ነገር ግን አፌ ቀኑን ሙሉ ስለ እነርሱ ያወራል”
አፌ ይናገራል

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አፍ ለሰው ሁለንተና ወካይ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እናገራለሁ” ወይም “በአፌ አወራለሁ እናገርማለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
ፅድቅህ
“ፅድቅ” የሚለውን ረቂቅ ስም ለማስወገድ ይህ እንደገና ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “አንተ እንዴት ፃድቅ ነህ” ወይም “የሰራሀቸው መልካም ነገሮች በሙሉ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ማዳንህ
“ማዳን” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ተግባር ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “አንተ እኔን እንዴት አዳንከኝ” ወይም “ሰዎችን እንዴት አዳንህ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እመጣለሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) “ሰዎች እግዚአብሔርን ወደሚያመልኩበት ስፍራ እሄዳለሁ” ወይም 2) “ወደ ጠላቶቼ እሄዳለሁ (ሂድ እና ና የሚለውን ይመልከቱ)
በጌታ በእግዚአብሔር ታላቅ ስራ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) “ጌታ እግዚአብሔር የሰራቸውን ታላላቅ ስራዎች ለእነርሱ እነግራቸዋለሁ” ወይም 2) ጌታ እግዚአብሔር ታላላቅ ስራዎችን ለመስራት ብርታት ስለሰጠኝ”
አስባለሁ
“ስለዚያ አወራለሁ”
Psalms 71:17
አስተማርኸኝ
ሊያመለክት የፈለገው መረጃ በግልፅ ሊብራራ ይችላል። “ብዙ ነገሮችን አስተማረኝ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ሆይ አትተወኝ
“እግዚአብሔር ሆይ እባክህ አትተወኝ”
ሀይልህን እየተናገርሁ ነበር
“ሀይል” የሚለው ረቂቅ ስም በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “አንተ እንዴት ብርቱ እንደሆንህ ስናገር ነበር” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ለሚመጣ ትውልድ
“ዛሬ ልጆች ለሆኑት”
ለሚመጣ ትውልድ ሁሉ ሀይልህን
የተዘለለው መረጃ በግልፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ለሚመጣው ለማንኛውም ሰው ሀይልህን በምናገርበት ጊዜ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ለሚመጣው ትውልድ ሁሉ
ይህ ግነት የሚያመለክተው ጸሐፊው ሊነግራቸው ለሚችላቸው ሰዎች በሙሉ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ ልነግራቸው የምችላቸው ብዛት ያላቸው ሰዎች በሙሉ ያውቃሉ” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 71:19
እግዚአብሔር ሆይ ፅድቅህ ደግሞ እጅግ ታላቅ ነው
ዘማሪው እግዚአብሔር ስለሰራቸው መልካም ነገሮች ሲናገር እነዚያ ስራዎች አንድ ላይ ተሰባስበው እንደ ትልቅ ህንፃ ወይም ከፍ ያለ ተራራ እንደሆኑ ተደርጎ ተገልጧል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ አንተ ያለ ማን ነው?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊተረጎም ይችላል።አማራጭ ትርጉም:- “እንደ አንተ ያለ አንድም የለም!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ህያው አደረግኸኝ
አበረታኸኝ ወይም እንደገና እንድኖር አደረግኸኝ
ከምድር ጥልቆች
እዚህ ላይ የምድር ጥልቆች የሚለው ሰዎች ሲሞቱ ለሚሄዱበት ስፍራ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ዘማሪው በስጋ አልሞተም ነገር ግን ይህ እርሱ የሚናገረው ግነት እንደ ሞተ አድርጎ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ወደ ሞት በምንቀርብበት ጊዜ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 71:21
ትጨምራለህ... ተመልሰህ ታፅናናኛለህ
“እንድትጨምር እፈልጋለሁ... እንድትመለስና እንድታፅናና እፈልጋለሁ።”
ተመለስና አፅናናኝ
ይህ አንድን ተግባር በሁለት ሀረጎች ይገልፃል። አማራጭ ትርጉም:- “እንደገና አፅናናኝ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ለአንተ በበገና አመሰግንሀለሁ፣ የእስራኤል ቅዱስ ሆይ
“የእስራኤል ቅዱስ ለሆንህ ለአንተ በገና እየተጫወትሁ ምስጋና እዘምርልሀለሁ”
Psalms 71:23
ከንፈሮቼ በደስታ ይጮሀሉ
“ከንፈሮች” የሰውን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “በደስታ እጮሀለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ የተቤዠሀት ነፍሴ
ዘማሪው የዘለላቸው ቃላቶች በግልፅ ሊብራሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- “አንተ የተቤዠሀት ነፍሴ ምስጋናን ትዘምርልሀለች” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ነፍሴ
እዚህ ላይ “ነፍስ” የሰውን ሁለንተና ይወክላል። (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
አንደበቴ ያወራል
እዚህ ላይ አንደበት የሰውን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔም አወራለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
የእኔን መጎዳት የሚፈልጉ አፍረዋል፣ ግራም ተጋብተዋል
“የእኔን ጉዳት የፈለጉ ሰዎች ተዋርደዋል፤ ግራም ተጋብተዋል”
አፍረዋል፣ ግራም ተጋብተዋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር አዋረዳቸው ደግሞም ግራ አጋባቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የእኔን መጎዳት የሚፈልጉ
ይህ የጸሐፊውን ጠላቶች ያመለክታል። (መዝሙረ ዳዊት 71:10)። “የእኔን መጎዳት የሚፈልጉ” በ መዝሙረ ዳዊት 71:13. ላይ እንዴት እደተረጎምከው ተመልከት።

---

Chapter 72
Psalms 72:1
አጠቃላይ መረጃ:-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ:-
የሰለሞን መዝሙር ለሚለው ርእስ አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው:- 1) ዳዊት ይህንን መዝሙር ስለ ሰለሞን ፃፈው (“የንጉሱ ወንድ ልጅ”) ወይም 2) ሰለሞን (እንደ ዳዊት ወንድ ልጅ “የንጉሱ ወንድ ልጅ” ነበር) ይህንን መዝሙር ስለ ራሱ እንደ ፀሎት ፃፈው ወይም 3) ሌላ ንጉስ በሰለሞን የአፃፃፍ ስልት ስለ ወንድ ልጁ ይህን መዝሙር ፃፈው። በእነዚህ ቀናቶች ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ብዙ ጊዜ ስለ ራሳቸው ሲናገሩ ሌላ ሰው እንደሆኑ አድርገው ይናገሩ ነበር። ይሁን እንጂ ዘማሪው ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ ሌላ ሰው ይናገር እንደነበረ አድርጎ መተርጎም የበለጠ ተመራጭ ይሆናል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ሆይ፣ የጽድቅ ስርአቶችህን ለንጉስ ስጥ፣ ፅድቅህን ለንጉስ ልጅ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው:- 1) “እግዚአብሔር ሆይ፣ ለእኔ ለንጉስ የፅድቅህን ስርአቶችህን ስጠኝ፣ ፅድቅህን ለልጄ” ወይም 2) “እግዚአብሔር ሆይ፣ ለእኔ ለንጉስ የፅድቅ ስርአቶችህን ስጠኝ፣ ፅድቅህን ለእኔ ለንጉስ ልጅ።” በእነዚህ ቀናቶች ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ብዙ ጊዜ ስለ ራሳቸው ሲናገሩ ሌላ ሰው እንደሆኑ አድርገው ይናገሩ ነበር። ይሁን እንጂ ዘማሪው ስለራሱ ሳይሆን ስለ ሌላ ሰው ይናገር እንደነበር አድርጎ መተርጎም የበለጠ ተማራጭ ይሆናል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
የፅድቅ ስርአቶችህን ለንጉስ ስጥ
“ንጉስ በትክክል መፍረድ እንዲችል አድርገው”
ፅድቅህን ለንጉስ ልጅ
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። እዚህ ላይ ፅድቅ የሚለው ቃል ፅድቅ ያለበት ውሳኔ ማድረግን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “ፅድቅህን ለንጉስ ልጅ ስጥ ወይም የንጉስ ልጅ በፅድቅ መምራት እንዲችል አድርገው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ይፈርድ ዘንድ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህን የፃፈው ዳዊት ከሆነ የሚናገረው ስለ ልጁ ነው፣ “የንጉስ ልጅ” ፣ ልጁ ንጉስ የሚሆንበትን ጊዜ እየተናገረ ነው። ይህን የፃፈው ሰለሞን ከሆነ ምንም እንኳ የሚናገረው ስለ ራሱ ቢሆንም እርሱ ስለ ሌላ ሰው ይፅፍ እንደነበር አድርጎ መተርጎሙ የበለጠ ተማራጭ ነው። በየትኛውም መንገድ ቢሆን “ንጉስ ይፈርድ ዘንድ” የሚለው የተሻለ ትርጉም ነው።

ህዝብህን... ችግረኞችህን

ዘማሪው ለእግዚአብሔር እየተናገረ ነው።

ችግረኞችህ

ግሱ ከበፊተኛው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። “ችግረኞች” የሚለው ቅፅል የሚያመለክተው ድሆችን ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እርሱ ችግረኞች ህዝብህን ይዳኝ ዘንድ” (አስጨምሬ እና የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ተራሮች የሰላምን ፍሬ ይስጡ... ኮረብቶች የፅድቅን ፍሬ ይስጡ

ዘማሪው ስለ የእስራኤል ህዝብ ሲናገር እርሱ የሚኖሩባቸው ተራሮችና ኮረብቶች እንደሆኑ አድርጎ ገልጧቸዋል። ተራሮቹና ኮረብቶቹ የእስራኤል መላው ምድር እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል፣ ይህ ምድር ደግሞ ፍሬ የሚያፈራ የአትክልት ስፍራ እንደሆነ አድርጎ በመናገር ፍሬው ደግሞ ሰላምና ፅድቅ እንደሆኑ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም:- “የምድሪቱ ህዝብ በሰላም ይኖሩ ዘንድ... ሁሉን ነገር በፅድቅ መንገድ ያደርጉ ዘንድ” (ምትክ ስም፣ ወካይ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 72:4

እርሱ... እርሱ

እነዚህ የሚያመለክቱት “የሚፈርደውን” ነው። (መዝሙረ ዳዊት 72:2)።

ጨቋኙን ያደቅቀዋል

ጸሀፊው ሌሎችን የሚጨቁኑ ህዝቦችን ስላሸነፈውና ስለቀጣው ንጉስ ሲናገር እነዚህ ህዝቦች ንጉሱ የሚያደንቃቸው ግኡዛን ነገሮች እንደሆኑ አድርጎ ገልጧቸዋል። አማራጭ ትርጉም:- “ሌሎችን የሚጨቁን ሰው ቅጣ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፀሀይ እስካለች ድረስ፣ ጨረቃም በምትኖርበት ዘመን ሁሉ

ፀሀይና ጨረቃ በአንድ ላይ ሆነው ሁሉንም ጊዜ ስለሚወክሉት ቀንና ሌሊት ምትክ ስም ናቸው። አማራጭ ትርጉም:- “ለዘላለም፣ መጨረሻ የሌለው” (ምትክ ስም እና ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 72:6

እርሱ በታጨደ መስክ ላይ እንደሚወርድ ዝናብ ይምጣ

ንጉሱ መልካም ይሆናል፣ ደግሞም እርሱ አዲስ በታጨደ መስክ ላይ እንደሚዘንብ ዝናብ እንደሆነ በማሰብ ለህዝቡ መልካም የሆኑትን ነገሮች ያደርጋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይመጣ ዘንድ

“እርሱ እንዲመጣ እፈልጋለሁ”

እንደሚያረሰርስ ውሀ

“እንደሚያረሰርስ ውሀ ወደታች ይምጣ።” ንጉሱ መልካም ይሆናል፣ ደግሞም እርሱ አዲስ በታጨደ መስክ ላይ እንደሚዘንብ ዝናብ እንደሆነ በማሰብ ለህዝቡ መልካም የሆኑትን ነገሮች ያደርጋል። (አስጨምሬ እና ተንጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፃድቅ

“ፃድቅ” የሚለው ቅጽል እንደ ስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ፃድቅ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

በዘመኑ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው:- 1) “ንጉሱ በሚመራበት ዘመን” ወይም 2) “ፃድቅ ሰው እስከኖረ ድረስ” ወይም “ፃድቃን ሰዎች እስከኖሩ ድረስ”

Psalms 72:8

እርሱ ይግዛ

“ንጉሱ ይግዛ”

ከባህር እሰከ ባህር ድረስ፣ ከታላቁም ወንዝ እስከ ምድር ዳርቻ

እነዚህ መግለጫዎች በሙሉ ወካዮቹ ሲሆኑ መላውን ምድር ያመለክታሉ። (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ከባህር እስከ ባህር

ከሙት ባህር ጀምሮ በምስራቅ ከኪኔሬት ባህር ድረስ በምእራብ ደግሞ እስከ ሜዲቴራኒያን ባህር ድረስ።

ወንዝ

“የኤፍራጥስ ወንዝ”፣ ይህ እስራኤላውያን ወደ ሰሜን አቅጣጫ በምድር የሚጓዙበት ነው።

የምድር ዳርቻ

ይህ የሚያመለክተው ሰዎች ወደ ደቡብ አቅጣጫ በምድር ሊሄዱ የሚችሉበትን ርቀት በሙሉ ነው። እስራኤላውያን ምድር ዳርቻ ያላትና ዝርግ ገፅታ የያዘች እንደሆነች አድርገው ይናገራሉ። (ተለዋጭ ዘይቤ እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አፈር ይልሳሉ

ይህ አባባል ተለዋጭ ዘይቤ ሲሆን ታላቅ ውርደትን የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እንዲኖሩ ይፈቅድላቸው ዘንድ ማድረግ የሚችሉትን ማንኛውንም ነገር ያደርጋሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ታርሴስ

የቦታ ስም ነው (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ይሰጣሉ

ይከፍላሉ

ስጦታ ያቀርባሉ

“ስጦታ ይሰጣሉ”

ሳባ

ይህ የአገር ስም ነው። ይህ ከአረብ አገር ጋር ተመሳሳይ አይደለም። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 72:11

በፊቱ ይሰግዳሉ

“በፊቱ ወድቀው ይሰግዳሉ” ወይም “እንደ ንጉሳቸው ያከብሩታል”

ህዝቦች ሁሉ

እዚህ ላይ “ህዝቦች” የሚለው በመንግስታቱ ውስጥ የሚኖሩትን ህዝቦች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “በሁሉም መንግስታት ውስጥ የሚኖሩት ህዝቦች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሌላ ረዳት የለም

“እርሱን ለመርዳት ሌላ አንድም የለም”

Psalms 72:13

ለድኾችና ለችግረኛው ይራራል

“እርሱ ድሆችና ችግረኞች ስቃያቸውን ለማስቆም ይፈልጋል”

ድኾችና ችግረኞች

እዚህ ላይ “ድኾች” እና “`ችግረኞች” የሚሉት የስም ቅፅሎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ራሳቸውን መርዳት እንዳልቻሉ አፅንኦት የሚሰጡ ናቸው። አማራጭ ትርጉም:- “እነዚህ ድኾችና እነዚህ ችግረኞች የሆኑ ሰዎች” (ጥምር ቃል እና የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ህይወታቸውን ያድናል

እዚህ ላይ “ህይወት” የሚለው የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተና ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እነርሱን አዳናቸው” ወይም “አዳናቸው” ወይም “ታደጋቸው” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ጭቆናና ግፍ

እነዚህ ሁለት ቃላቶች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ችግረኞች ምን ያህል እንደሚሰቃዩ አፅንኦት የሚሰጡ ናቸው። እነዚህ ረቂቅ ስሞች እንደ ግስ ሊብራሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- “እነዚህ እነርሱን የሚጨቁኑና እነርሱን የሚጎዱ ሰዎች” (ጥምር ቃል እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ ፊት ደማቸው ክቡር ነው

እዚህ ላይ “ደማቸው” የሚለው ለደህንነታቸው ምትክ ስም ነው። የእግዚአብሔር ፊት ደግሞ የእርሱን ፍርድ ወይም ግምገማ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “የእነርሱ ደህንነት ለእርሱ በጣም ዋነኛ ነገር ነው” ወይም “እነርሱ በደህንነት እንዲኖሩ ይፈልጋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ

ይህ ቃል በ መዝሙረ ዳዊት 19:14 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

Psalms 72:15

እድሜው ይርዘም!

ይህ አባባል ንጉሱ በጣም ረጅም ጊዜ እንዲኖር ምኞታቸውን በመግለጥ እርሱን ለማክበር ጥቅም ላይ ይውል ነበር። አማራጭ ትርጉም:- “ንጉሱ ረጅም ዘመን ይኑር!” ወይም “ንጉሱ ረጅም ዘመን እንዲኖር እመኛለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የአረብ አገር ወርቅ ይምጣለት

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እነርሱ የአረብ አገር ወርቅ

ይስጡት” ወይም” እርሱ የአረብ አገር ወርቅ ይቀበል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኑን ሙሉ

ይህ ፈሊጥ “ያለማቋረጥ” ማለት ሲሆን አንድ ቀን ብቻ የሚያመለክት አይደለም። አማራጭ ትርጉም፡- “ያለማቋረጥ” ወይም “ሁልጊዜ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የእህል ብዛት

“ብዛት” የአንድ ነገር መትረፍረፍ ነው። ይህ ረቂቅ ስም “ብዙ” ወይም “የተትረፈረፈ” በሚሉት ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ እህል” ወይም “የተትረፈረፈ እህል” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰብል

ሰዎች ለምግብነት የሚየበቅሏቸው ተክሎች።

ተወዛወዘ

ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ረጅም ሳር ረጋ ያለ ነፋስ በላዩ ላይ ሲነፍስ የሚያሳየውን እንቅስቃሴ ለማሳየት ነው፤ በቀስታ ወደፊትና ወደኋላ ይንቀሳቀሳል።

እንደ ሊባኖስ

“እንደ ሊባኖስ የጥድ ዛፍ።” እነዚህ ዛፎች ውብና ለህንጻ በጣም ጥሩ ነበሩ። የዚህ አባባል ትርጉም ግልፅ ሊደረግ ይችላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቡ በከተማ ውስጥ እንደ ሜዳ ሳር ይለምልም

በከተማ ስለሚኖረው ህዝብ ብልፅግና ሲናገር ህዝቡ በሜዳ ላይ በብዛት እንደሚበቅል ሳር ተደርገው ተገልፀዋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 72:17

ስሙ ለዘላለም ፀንቶ ይኑር

ይህ አባባል ህዝቡ ሁልጊዜ እርሱን ለማሰብ ያላቸውን ፍላጎት በመግለፅ እግዚአብሔርን ለማክበር ጥቅም ላይ ውሏል።አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ሁልጊዜ ስለ እርሱ ይወቁ” ወይም “ሰዎች እርሱ ማን እንደሆነ ፈፅሞ አይርሱ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ስም

እዚህ ላይ “የእርሱ ስም” የሚለው የእግዚአብሔርን መልካም ስም የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የንጉሱ ስም” ወይም “የንጉሱ መልካም ስም” ወይም “የንጉሱ ዝና” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፀሀይ የምትኖረውን ዘመን ያህል

ግሱ ከዚህ በፊት ከነበረው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፀሀይ ፀንታ የምትኖረውን ያህል” ወይም “ፀሀይ እስከበራች ድረስ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቦች ሁሉ በእርሱ ይባረኩ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እርሱ ለህዝብ መልካም ነገርን እንዲፈፅም ያድርገው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ብሩክ ነህ ይበለው

“እግዚአብሔር እንደባረከው ይወቅ”

Psalms 72:18

አጠቃላይ መረጃ፡-

እነዚህ ጥቅሶች የዚህ መዝሙር መጨረሻ ከመሆንም በላይ ጠቀሜታ አላቸው። የመዝሙረ ዳዊት ሁለተኛ መፅሀፍ የሆነው ከመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 42 እስከ መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 72 ድረስ ያለው መፅሀፍ የመዝጊያ ሀሳብ ነው።

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ህዝብ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ይባርክ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ክቡር ስሙ ለዘላለም ይባረክ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ህዝብ የተከበረ ስሙን ለዘላለም ይባርክ” ወይም “ስም” የሚለውን ለራሱ ለእግዚአብሔር ምትክ ስም እንደሆነ በማሰብ፣ “ህዝብ እርሱ እንዴት የከበረ እንደሆነ ለዘላለም ይወቅ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የተከበረ ስሙ ይባረክ

“ክቡር የሆነው እርሱ ይባረክ”

ምድር ሁሉ በክብሩ ይሞላ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክብሩ ምድርን ሁሉ ይሙላ” ወይም “እርሱ ምድርን ሁሉ በክብሩ ይሙላ ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አሜን፤ አሜን

አሜን የሚለው ቃል የተደጋገመው ለተነገረው ነገር ማረጋገጫመስጠቱን አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህንን በመዝሙረ ዳዊት 41:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “በእርግጥም እንዲህ ይሁን”

የእሴይ ልጅ የዳዊት ፀሎት እዚህ ላይ ተፈፀመ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ዳዊት የእሴይ ልጅ ፀሎቱን ፈፀመ” ወይም “ይህ የእሴይ ልጅ የዳዊት የመጨረሻው ፀሎት ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 73

Psalms 73:1

አጠቃላይ መረጃ፡-

ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የአሳፍ መዝሙር

“ይህ አሳፍ የጻፈው መዝሙር ነው።” ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 53:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

እኔ ግን እግሬ ሊሰናከል፣ አዳልጦኝም ልወድቅ ጥቂት ቀረኝ

ዘማሪው የሚናገረው እግዚአብሔርን መታመን አንዳልቻለና በሚያዳልጥ መንገድ ሲራመድ ሊወድቅ እንደደረሰ አድርጎ ራሱን በማሰብ ሀጢአት ለመስራት እንደፈለገ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ በእግዚአብሔር መታመን ለማቆም ደርሼ ነበር፤ በእርሱ ላይ ትልቅ ሀጢአት ለመስራትና በደለኛ ለመሆን ደርሼ ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአመፀኞች ቀንቼ ነበር

“አመፀኞች ቀናሁባቸው” ወይም “አመፀኞች ሰዎች የነበራቸው መልካም ነገር እንዲኖራቸው አልፈልግም”

አመፀኞች

“አመጸኞች” የሚለወ ቅፅል እንደ ስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አመፀኞች ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉዎች ባለጠግነት

“ባለጠግነት” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉዎች በጣም ብዙ መልካም ነገር እንዳላቸው አይቼ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉዎች

“ክፉዎች” የሚለው ቅፅል እንደ የስም ሀረግ ሊተረጎም ይቸላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎች” (የስም ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 73:4

አጠቃላይ መረጃ፡-

አሳፍ “አመፀኞች” እና “ክፉዎች” ስለሆኑ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንዴት እንደሚፈልግ መግለፅ ይጀምራል። (መዝሙረ ዳዊት 73:3)።

የሌሎች ሰዎች ሸክም

ሸክም የሚለው ቃል ለእለት ከእለት የህይወት ትግል ምትክ ስም ነው(የምግብ፣ መጠለያ፣ ልብስ እና ጤና ፍላጎት) (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሌሎች ሰዎች መከራ አይደርስባቸውም

“ሌሎች ሰዎች እንደሚሰቃዩት እነርሱ አይሰቃዩም”

Psalms 73:6

አጠቃላይ መረጃ፡-

አሳፍ “አመፀኞች” እና “ክፉዎች” ስለሆኑ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንዴት እንደሚፈልግ መግለፅን ቀጥሏል። (መዝሙረ ዳዊት 73:3)።

ስለዚህ ትዕቢት የአንገት ጌጣቸው ነው፤ አመፅንም እንደ ልብስ ተጎናፅፈዋል

ክፉዎች የአንገት ጌጥ እንዳደረጉና ውበት ያለው ልብስ እንደለበሱ ያህል ለእያንዳንዱ ሰው ምን ያህል ትእቢተኞችና አመፀኞች እንደሆኑ ያሳያሉ። (ተነፃፃሪ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንገት ጌጥ... ልብስ
ይህ የሚያመለክተው ባለጠጋና ትልቅ ስፍራ ያላቸው ሰዎች የሚያጌጡበትና የሚለብሷቸው ነገሮች ናቸው።
የአንገት ጌጥ
ብዙ ጊዜ ከወርቅ የሚሰራ ሰንሰለት ወይም በአንገት ዙሪያ የሚደረግ ጌጣጌጥ ነው።
ከእንዲህ አይነት እውርነት ሀጢአት ይመጣል
የሚሄዱበትን ስፍራ ማየት እንደማይችሉ እንደ አይነ ስውራን ከመሆነቸው የተነሳ ሳያውቁት ሀጢአት ያደርጋሉ። እውር መሆን ምን ያህል ክፉ እንደሆነ ማየት ያልቻለ ሰውን የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ልባቸው በክፉ ሀሳብ ተሞልቷል
እዚህ ላይ ዘማሪው የሰዎችን ሀሳብ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ይገልፅላቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ የክፉ ሰዎችን ውስጣዊ ማንነት ሲገልፅ ሰዎች ሊራመዱ የሚችሉበት ህንጻዎች እንደሆኑ አድርጎ አቅርቦታል። አማራጭ ትርጉም፦ “በውስጣዊ ማንነታቸው ስለሚሰሯቸው ተጨማሪ ክፉ ነገሮች ሁልጊዜ ያስባሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 73:8
አጠቃላይ መረጃ፦
አሳፍ “አመፀኞች” እና “ክፉዎች” ስለሆኑ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንዴት እንደሚፈልግ መግለፁን ቀጥሏል (መዝሙረ ዳዊት 73:3)።
አፌዙ
በማን ላይ እንዳፌዙ በግልጥ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱ በእግዚአብሔርና በህዝቡ ላይ አፌዙ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አፋቸውን በሰማይ ላይ ያላቅቃሉ
እዚህ ላይ አፋቸው “የሚለው” ለንግግራቸው ምትክ ስም ነው፣ “ሰማይ” የሚለው ደግሞ በሰማያት ላይ ለሚኖረው ለእግዚአብሔር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በሰማያት ላይ በሚኖረው በእግዚአብሔር ላይ ተናገሩ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እንደበታቸውም በምድር ላይ ተመላለሰ
“እንደበት” የሚለው ቃል ህዝቡን ይወክላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) ስለ እግዚአብሔር ክፉ ነገሮችን እየተናገሩ በምድር ዙሪያ ተመላለሱ” ወይም “ስለ ራሳቸው እየታበዩ በሁሉም ስፍራ ተመላለሱ“ (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 73:10
አጠቃላይ መረጃ፦
አሳፍ “አመፀኞች” እና “ክፉዎች” ስለሆኑ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንዴት እንደሚፈልግ መግለፁን ቀጥሏል (መዝሙረ ዳዊት 73:3)።
ህዝቡ ወደ እነርሱ ይመለሳሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) “የእግዚአብሔር ህዝብ ክፉ ሰዎችን ወደደ” ወይም “ክፉ ሰዎች ወደዚህ ስፍራ ተመለሱ”
ብዙ ውሀ ፈሰሰ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) “የእግዚአብሔር ህዝብ የክፉ ሰዎችን ቃላት በደስታ ያዳምጣሉ ወይም 2) “ክፉ ሰዎች የሚበሉት ብዙ ምግብና የሚጠጡት ብዙ ወይን ጠጅ አላቸው”
እንዲህ አሉ
ክፉ ሰዎች እንዲህ አሉ
እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል? በልዑልስ ዘንድ እውቀት አለ?
እነዚህ መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች ለእግዚአብሔር ያለውን ንቀት ያሳያሉ። እነዚህ ጥያቄዎች እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር እኛ የምንሰራውን ስራ በእርግጠኝነት አያውቅም። ልዑል ስለዚህ ነገር እውቀት የለውም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 73:13
አጠቃላይ መረጃ፦
በቁጥር 13 እና 14 አሳፍ “አመፀኞች” እና “ክፉዎች” ስለሆኑ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንዴት እንደሚፈልግ መግለፁን ቀጥሏል (መዝሙረ ዳዊት 73:3)። በቁጥር 15 በእርግጥ ስለሚያስበው ነገር መናገር ጀምሯል።
እኔ አለኝ
“እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አሳፍን ነው።
ልቤን ጠበቅሁ
አሳፍ ልቡን ስለ መጠበቁ ሲናገር ከተማ ወይም ህንፃን ከጠላቶች እንደሚጠብቁት አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “አሳቦቼን በንፅህና ጠበቅሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እጆቼን በየዋህነት ታጠብሁ
ጸሐፊው ስለ ንፅህናው ሲናገር እጆቹን በውሀ ከመታጠብ ይልቅ በየዋህነት እንደታጠበ አድርጎ ገልፆታል። ይህንን በ መዝሙረ ዳዊት 26:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “ድርጊቴ ንፁህ ነው” ወይም “እኔ እውነተኛ እንደሆንሁ ለማሳየት እጆቼን ታጠብሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀኑን ሙሉ
“ሁልጊዜ” ወይም “በየቀኑ”
ተቀሰፍሁ
“እኔ እንድሰቃይ አደረግኸኝ።”በ መዝሙረ ዳዊት 73:5 ላይ “እነርሱ መከራ አይደርስባቸውም” የሚለው እንዴት እነደተተረጎመ ተመልከት።
እኔ... ተቀጣሁ
“እኔ... ተገረፍሁ”
“እኔ እንደዚህ እናገራለሁ” ብልማ ኖሮ፤ የልጆችህን ትውልድ በከዳሁ ነበር
ይህ ግምታዊ ሁኔታ በተግባር አልተከሰተም። አማራጭ ትርጉም፦ “እነዚህን ነገሮች እናገራለሁ” ፈፅሞ አላልኩም፣” ስለዚህ የልጆችህን ትውልድ አልካድሁም” (ግምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 73:16
እነዚህ ነገሮች
በክፉዎች ላይ የተፈፀሙ መልካም ነገሮች (መዝሙረ ዳዊት 73:4-መዝሙረ ዳዊት 12)።
እጣ ፈንታቸው
“ክፉ ሰዎች ሲሞቱ የሚሆንባቸው ነገር” ወይም “ክፉ ሰዎች እንዴት እንደሚሞቱ”
Psalms 73:18
እነርሱን አስቀመጥካቸው
“እነርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው።
በሚያዳልጥ ስፍራ
“የማይመች ወይም የማይፀና መሬት። ”ማዳለጥ” በ መዝሙረ ዳዊት 73:2 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።
እንዴት በቅፅበት ምድረበዳ ሆኑ
“ምድረ በዳ” የሚለው ቃል መልካም የሆነውን ነገሩን ሁሉ ያጣ ሰው ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እንዴት በፍጥነት ጠፉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰው ከህልሙ ሲነቃ እንደሚሆነው
ክፉዎች አንድ ሰው በህልም ከሚያየው የረዘመ ጊዜ አይቆዩም። ያ ሰው በነቃበት ቅፅበት ይጠፋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 73:21
ልቤ አዘነች
“ልብ” የሚለው ቃል የሚወክለው ሰውየውን ሲሆን ሀሳባቸውንና ስሜታቸውን አፅንኦት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ በጣም አዝኜ ነበር” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ በጣም ቆስያለሁ
ዘማሪው ስለ ስሜታዊ ህመም ሲናገር በቢላዋ ወይም በቀስት እደተወጋና አካላዊ ህመም እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው እንዳቆሰለኝ ያህል ተሰማኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አላዋቂና ስሜት የሌለው
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የሚያውቀው ምን ያህል ጥቂት እንደሆነ አፅንኦት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፦ “በጣም አላዋቂ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ስሜት የሌለው
“ምንም የማይገባው”
አንተ
ይህ “አንተ” እግዚአብሔርን ያመለክታል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Psalms 73:23
እኔ ሁልጊዜ ከአንተ ጋር ነኝ
እዚህ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሚወክለው አሳፍን ነው፡፡ እዚህ ላይ “አንተ” የሚለው ቃል ደግሞ የሚወክለው እግዚአብሔርን ነው፡፡
አንተ ቀኝ እጄን ያዝከኝ
የሰው “ቀኝ እጅ” የሰውን ሁለንተና ያመለክታል፡፡ ይህ ፅናትና ዋስትና የሚሰጠውን ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ፅኑ አብሮነት የሚያሳይ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ አጥብቀህ ያዝከኝ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ክብርህ ተቀበለኝ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) “ሰዎች በሚያከብሩኝ ስፍራ አስቀምጠኝ” ወይም 2) “አንተ ወዳለህበት እኔን በመውሰድ አክብረኝ፡፡” “ተቀበለኝ” የሚለው በ መዝሙረ ዳዊት 49:15 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት፡፡
Psalms 73:25
በሰማይ ከአንተ በቀር ማን አለኝ?
ይህንን እንደ አረፍተ ሀሳብ መተርጎም ትችላለህ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በሰማይ ላይ ለእኔ ማንም የለኝም፣ አንተ ብቻ ነህ!” ወይም “በሰማይ ያለኸኝ አንተ ብቻ ነህ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በሰማይ
“በአማልክት መካከል ወይም በልዕለ ተፈጥሮአዊ በሆኑ አካላት መካከል”
ስጋዬና ልቤ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ፡፡ በአንድ ላይ እነዚህ ሀረጎች የሰውን ሀለንተና ይወክላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ አካልና የእኔ አእምሮ” (ጥምር ቃል እና ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 73:27
አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር መናገር ቀጥሏል፡፡
ከአንተ የሚርቁ
እዚህ ላይ ከእግዚአብሔር ርቆ መቆየት እርሱን ለመታዘዝ ፈቃደኝ ካለመሆን ጋር ተነፃፅሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን ለመታዘዝ የማይፈልጉ ሰዎች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መጠጊያዬ
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር እርሱ ሰው ለደህንነቱ ሸሽቶ የሚያመልጥበት ስፍራ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 74
Psalms 74:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው፡፡ (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
የአሳፍ ትምህርት
“ይህ አሳፍ የፃፈው ትምህርት ነው”
ትምህርት
ይህ የሙዚቃ ስልትን ያመለክት ይሆናል፡፡ ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 32:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት፡፡
እግዚአብሔር ሆይ፣ ለዘላለም የጣልኸን ለምንድን ነው?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሆይ፤ እኛ የፈጸምነው ጥፋት የለም ነገር ግን አንተ ለዘላለም ጣልኸን!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በማሰማሪያህ ባሉ በጎችህስ ላይ ቁጣህ ለምን ነደደ?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ አንተ ልትጠብቀን ቃል ኪዳን የገባህልን ሰዎች ነን፣ የፈፀምነው ጥፋት ደግሞ የለም ነገር ግን አንተ ግን በእኛ ላይ ተቆጥተሀል!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በማሰማሪያህ ላይ ያሉ በጎች
አሳፍ ስለ እስራኤል ህዝብ ሲናገር እነርሱ በጎች እንደሆኑ አድርጎ ይገልፃቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ በጎች የሆኑትንና በማሰማሪያ በምትመግባቸው በእስራኤል ላይ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አስብ
“ለእነርሱ ትኩረት ስጥ…” እግዚአብሔር ህዝቡን አልረሳም ነገር ግን ስለ እነርሱ የሚያስብ አይመስልም፡፡
ገንዘብህ የሆነውን
“ለዘላለም የአንተ የሆነውን”
Psalms 74:3
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም በሚገኘው በእስራኤል ቤተ መቅደስ ህንፃ ላይ የተፈፀመውን እውነተኛ ክስተት ይገልፃሉ፡፡
ና ተመልከት
አሳፍ ለእግዚአብሔር በመናገር እርሱ እንዲመጣና ጥፋቱን እንዲመለከት ይጠይቀዋል፡፡
ደነፋ
ጠላቶቹ በታላቅ የድል ጩኸት በጣም ይጮሁ ነበር፡፡
የተቀረፁ ምልክቶች
ይህ የሚያመለክተው በቤተ መንግስት ውስጥ በእንጨት ፣ ብረት እና ድንጋይ የተቀረፁ ምስሎችን ነው፡፡
Psalms 74:7
አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ የቤተ መቅደሱን መፈራረስ መግለፅ ቀጥሏል፡፡
እነርሱ… እነርሱ… እነርሱ… እነርሱ
እዚህ ላይ እነርሱ የሚለው የሚያመለክተው በ መዝሙረ ዳዊት 74:4 ላይ የተጠቀሱትን ጠላቶች ነው፡፡
በልባቸው እንዲህ አሉ
ይህ ፈሊጥ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለራሳቸው እንዲህ አሉ” ወይም “ለራሳቸው አሰቡ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 74:9
አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ ስለተመለከተው ጥፋት ለእግዚአብሔር ይናገራል፡፡
ምልክታችንን ከእንግዲህ ወዲህ አናይም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) “ከእንግዲህ ወዲህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተአምራታዊ የሆኑ ምልክቶችን አናይም” ወይም 2) “የተቀደሱ ምልክቶቻችን በሙሉ ሄደዋል” ወይም 3) “ምልክቶቹ” ራሱን ሰራዊቱን የሚወክሉ የሰራዊት ሰንደቅ አላማዎችና ምልክቶች ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የእኛን ጦር ሰራዊት ሙሉ በሙሉ አጥፍተውታል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እግዝአብሔር ሆይ፣ ጠላት በአንተ ላይ የሚሳደበው እስከ መቼ ነው?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሆይ፣ ጠላት በአንተ ላይ ለረጅም ጊዜ ስድብን እየወረወረ ነበር !” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ጠላት ለዘላለም በስምህ ላይ ያላግጣልን?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላት የአንተን ስም ከመሳደብ ፈፅሞ የምታስቆም አይመስልም!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ስምህን ይሳደባሉ
“ስም” የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር ለራሱ ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ መጥፎ እንደሆንህ ይናገራሉ” ወይም “ይሰድቡሀል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እጅህን ለምን ትሰበስባለህ? ቀኝ እጅህን ለምን ትመልሳለህ?
ዘማሪው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር ስጋዊ አካል እንዳለው አድርጎ ይገልፅዋል፡፡ ይህ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እጅህን፣ ቀኝ እጅህን አትሰብስብ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)
እጅህን ሰብስብ
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ቃል ለሀይል ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሀይልህን አትግለጥ” ወይም “ጠላቶችህን ለማጥፋት ሀይልህን አትጠቀም”(ምትክ ስም እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀኝ እጅህ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ጠንካራ እጅህ”
ቀኝ እጅህን ከልብስህ አውጣ
ይህ ዘማሪ ስለ ዘማሪው ሲናገር ስጋዊ አካል እንዳለው አድርጎ ይገልፀዋል። “ሀይልህን ከመሰወር አቁምና እርምጃ ውሰድ” (ምትክ ስም እና ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 74:12
አጠቃላይ መረጃ፡-
ይህ አዲስ ርዕስ ይምራል፡- አሳፍ እግዚአብሔር በህዝቡ ታሪክ ውስጥ የሰራውን ታላቅ ስራዎች ያውጃል።
እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ ንጉሴ ነው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) አሳፍ እንደ እስራኤል ወኪል ሆኖ ይናገራል፣ “እኛ እስራኤላውያን ህዝብ ከሆንንበት ከመጀመሪያ ጀምሮ ንጉሳችን ነበር” ወይም 2) “እግዚአብሔር አምላኬ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ህያው ነው”
ድነትን አመጣህ
“ድነት” የሚለው ረቂቅ ስም “ማዳን” በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ሰዎችን ማዳን ሲገለፅ ድነት ከእርሱ ጋር ይዞት የሚመጣው እቃ እንደሆነ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ህዝብን ማዳን” (ረቂቅ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከፈልህ… በውሀ ውስጥ
አሳፍ እዚህ ላይ ምናልባት የሚናገረው እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ማውጣቱን፣ ቀይ ባህርን መክፈሉን፣ እስራኤልን በደረቅ ምድር መምራቱን ከዚያም የፈርኦን ሰራዊትን በውሀ አሰጠማቸው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ በሀይልህ ባህሩን ከፈልህ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር እርሱ ስጋዊ አካል እንዳለው አድርጎ ገልፆታል። “አንተ እጅግ በጣም ጠንካራ ነህ፣ በባህር መካከል ደረቅ መሬት ማድረግ ችለሀል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ባህር
“ታላቁ ዉሀ”
የባህሩን አውሬ ራሶች በውሀ ውስጥ ቀጠቀጥህ
አሳፍ ምናልባት ስለ ፈርኦንና ሰራዊቱ የባህር አውሬዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። የሚቻል ከሆነ እነዚህን ቃላቶች በቁሙ ተርጉማቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “የፈርኦንን ሰራዊት በገደልሀቸው ጊዜ የባህርን አውሬ ራሶች በውሀ ውስጥ እንደቀጠቀጥሀቸው ያህል ነው።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 74:14
አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ እግዚአብሔር ከረጅም ጊዜ በፊት የሰራውን ስራ መናገሩን ቀጥሏል። እርሱ ምናልባት እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ምድር ያወጣበትንና የፈርኦንን ሰራዊት በቀይ ባህር ያሰጠመበትን ጊዜ እየተናገረ ነው። የሚቻል ከሆነ እነዚህ ቃላቶች በቁሙ መተርጎም ይኖርባቸዋል።
ሌዋታን
ሌዋታን የባህር አውሬ ነው። ይህ ጨካኝ የሆነውን ጠላት ይወክላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ምንጮችንና ፈሳሾችን ያፈለቅህ አንተ ነህ
እግዚአብሔር ምንጮችንና ፈሳሾችን ከምድር እንዲፈስሱ ማድረጉ እርሱ መሬትን ሰንጥቆ እንደመክፈትና ፈሳሾች እንዲፈስሱ እንደማድረግ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ምንጮችና ፈሳሾች ከምድር ፈልቀው እንዲፈስሱ አድርገሀል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 74:16
አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ የእግዚአብሔርን የመፍጠር ሀይል እንደገና ማሳሰቡን ቀጥሏል።
የምድር ዳርቻዎች
“የመሬትና የባህር ዳርቻዎች”
Psalms 74:18
አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ የእግዚአብሔርን እርዳታ እየጠየቀ ነው።
አስብ
“ትኩረት ስጥ።” ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 74:2 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠላት በአንተ ላይ ስድብን አወረደ
አሳፍ ስለ ስድብ ቃላቶች ሲናገር ጠላት በእግዚአብሔር እንደሚወረውረው እንደ ድንጋይ ቁሳዊ ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላት አንተን ብዙ ጊዜ ሰደበህ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የርግብህን ህይወት
አሳፍ ስለ ራሱ ማንም ረዳት እንደሌላት ወፍ እንደ ርግብ አድርጎ ተናግሯል። ይህ ሀረግ ለእስራኤል ህዝብ ምናልባት ተለዋጭ ዘይቤ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ፣ የአንተ ርግብ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ርግብ
ራስዋን መከላከል የማትችልና እንደ ለማዳ እንስሳ የምትጠበቅ ትንሽ ወፍ ናት።
የዱር እንስሳ
ይህ ምናልባት ለእስራኤል ጠላት ተለዋጭ ዘይቤ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ዱር እንስሳ የመሰለ ጨካኝ ጠላት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የችግረኞች ህዝብህን ህይወት ለዘላለሙ አትርሳ
“የተቸገሩ ህዝብህን ለመርዳት ምንም ነገር ካለማድረግ ለዘላለል አትቀጥል።” ይህ በአዎንታዊ ቅርፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የተቸገሩ ህዝብህን ለመርዳት በፍጥነት ና” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 74:20
አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ ለእግዚአብሔር የሚያደርገውን ልመና ቀጥሏል።
የምድሪቱ የጨለማ አካባቢዎች የአመፅ ስፍራ ተሞልተዋል
አሳፍ ስለ አካባቢዎች ሲናገር አንድ ሰው የአመፅ ስፍራዎች ሊያስቀምጥበት እንደሚችለው ማስቀመጫ እቃ እንደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አመፀኞች ሰዎች በምድር ዙሪያ በሚችሉት ቦታ ሁሉ በጨለማ ስፍራ ክፉ ድርጊት ይሰራሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የምድሪቱ የጨለማ አካባቢዎች
“ጨለማ” የሚለው ቃል ምናልባት መጥፎ ነገሮች ለሚፈፅሙት ስፍራ ወይም እስራኤላውያን ለግዞት ተልከው ለነበሩበት ምድር ተለዋጭ ዘይቤ ነው ነገር ግን እነዚህ ቃላቶች የሚቻል ከሆነ በቁሙ ሊተረጎሙ ይገባል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የተጨቆኑት አፍረው አይመለሱ
“ክፉ ሰዎች የተጨቆኑትን እንዲያሸንፉና እንዲያሳፍሯቸው አታድርጋቸው”
የተጨቆኑት
እነዚህ በሀይለኛ ሰዎች በጭካኔ የሚሰቃዩ ሰዎች ናቸው።
ድሆችና የተጨቆኑ
“ድሆች” እና “የተጨቆኑ” የሚሉት ቃላቶቸ በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን እግዚአብሔር የእርሱን እርዳታ የሚፈልጉትን ሰዎች እንደሚያድን አፅንኦት ይሰጣሉ። እነዚህ ቃላቶች በ መዝሙረ ዳዊት 35:10.ላይ እንዴት እንደተተረጎሙ ተመልከት። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 74:22
ለክብርህ ተሟገት
“አንተ ፃድቅ እንደሆንህ ለሁሉም አሳይ”
አስብ
“ትኩረት ስጥ።” እግዚአብሔር ሞኞች እርሱን እንደሚሰድቡት አልረሳም ነገር ግን ስለዚህ ነገር እርሱ የሚያስብ አይመስልም። ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 2 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።
የባላጋራዎችህ ድምፅ
ድምፅ የሚለው ቃል ሰዎች ሲናገሩ ለሚጠቀሙባቸው ቃላቶች ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የአንተ ጠላቶች የሚናገሩት ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ወይም በማያቋርጥ ሁኔታ የሚቃወሙህ ሰዎች ሁካታ
ዘማሪው እግዚአብሔርን ስለሚቃወሙት ሰዎች ቃላቶች ሲናገር ከእንስሳት ወይም እንደ ውሃና ነፋስ ከመሳሰሉ ሕይወት የሌላችው ቁሳቁሶች የሚወጣ ከባድ ጩኸት እንደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ያለማቋረጥ በአንተ ላይ የሚቃወሙ ሰዎች ጩኸትና ትርጉም አልባ ቃላቶችን ትኩረት ስጥ” (አስጨምሬ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ተቃውሞ
በድፍረት መቃወም

Chapter 75

Psalms 75:1

አጠቃላይ መረጃ:-

ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው፡፡ (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ:-

የእግዚአብሔር ህዝብ በ 75:1 ላይ ይናገራሉ፣ እና እግዚአብሔር ደግሞ በ 75:2-3 ውስጥ ይናገራል፡፡

ለመዘምራን አለቃ

"ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው፡፡"

"አታጥፋ" በሚለው ቅኝት የሚዜም

ይህ የሚያመለክተው የዜማ ስልትን ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 57:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡

የአሳፍ መዝሙር

x

Psalms 75:4

አመፀኞችንና ክፉዎችን... እላቸዋለሁ

አመፀኞች እና ክፉዎች የሚሉት ቃላቶች የስም ቅፅሎች ሲሆኑ በስም ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ ለሁለተኛው ሀረግ የሚያስፈልገው ግስ ከመጀመሪያው ሀረግ ሊወስድ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "ለአመፀኞች ሰዎች... አልኋቸው... ለክፉዎች ሰዎች... አልኋቸው" (የስም ቅፅሎች እና አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

አልሁ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) እግዚአብሔር እየተናገረ ነው ወይም 2) አሳፍ እየተናገረ ነው፡፡

አመፀኞች አትሁኑ... አታንሱ... የአንተን ወደ ላይ አታንሳ... አትናገር

ተናጋሪው ለብዙ ክፉ ሰዎች እተናገረ ነው ስለዚህ እነዚህ ቅርፆች ሁሉም ብዙ ቁጥር ናቸው፡፡ (ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንድህን ወደ ላይ አታንሳ

አሳፍ ስለ ክፉ ሰዎች ሲናገር በራሳቸው ላይ ቀንድ እንዳላቸው፣ አንገታቸውን እንደሚመዝዙና ሌሎች እንስሳትን ለማስፈራራት ራሳቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው እንደሚያነሱ እንስሳት አድርጎ ገልጧቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "በራሳችሁ አትተማመኑ" ወይም "እንዴት ብርቱ ነኝ እያላችሁ በራሳችሁ አትመኩ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንድህን ወደ ከፍታዎች አታንሳ

አሳፍ ስለ ክፉ ሰዎች ሲናገር ነራሳቸው ላይ ቀንድ እንዳላቸው፣ አንገታቸውን እንደሚመዝዙና ሎለሎች እንስሳትን ለማስፈራረራት ቻሉትን ያህል ራሳቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው እንደሚያነሱ እንስሳት አድርጎ ገልጧቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "እናንተ በተለይም ደግሞ ከእግዚአብሔር በላይ ትልቅ እንደሆናችሁ በማሰብ ራሳችሁን ከፍ እንዳታደርጉ እርግጠኞች ሁኑ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በትዕቢተ በተሞላ አንገት

አሳፍ እግዚአብሔርን ስለሚቃወሙና ስለሚገዳደሩ ክፉ ሰዎች ሲናገር በራሳቸው ላይ ቀንድ እንዳላቸው፣ አንገታቸውን እንደሚመዝዙና ሌሎች እንስሳትን ለማስፈራራት ራሳቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርው እንደሚያነሱ እንስሳት አድርጎ ገልጧቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "በትዕቢት" (ፈሊጥ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክብር ከምስራቅ... አይመጣም

አሳፍ ራሱን ከፍ ስለሚደርግ ሰው ሲናገግ ራሱ ሰውየው ከፍ የማድረግ ተግባር እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል፡፡ በተጨማሪ እርሱ እግዚአብሔር ለሰው ብርታትና ክብር ስለመስጠቱ ሲናገር እግዚአብሔር ሰውየውን በአካል ወደ ላይ ከፍ እንዳደረገው አድርጎ ገልፆታል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "አንተን ወደ ላይ ከፍ የሚያደርግህ ከምስራቅ የሚመጣ ሰው አይደለም" ወይም "አንተን ብርቱ የሚያደርግህና ሰዎች እዲያከብሩህ የሚያደርግህ ከምስራቅ የሚመጣ ሰው አይደለም" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 75:7

አጠቃላይ መረጃ:-

አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል፡፡

እርሱ ያዋርዳል፣ እርሱ ያከብራል

የግሱ ተሳቢ በግልፅ ሊብራራ ይችላል፦ "እርሱ አንዳንድ ሰዎችን ያዋርዳል፣ ሌሎች ሰዎችን ደግሞ ያከብራል፡፡ "ያዋርዳል" እና "ያከብራል የሚሉት ቃላቶች እግዚአብሔር ሰዎችን ባለስልጣን ስለማድረግና የሰዎችን ስልጣን ስለመውሰዱ ተለዋጭ ዘይቤዎች ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "እርሱ አንዱን ሰው በሌላ ሰው ምትክ ንጉስ ያደርገዋል" ወይም "እርሱ የአንዱን ሰው ስልጣን ይወስድና ለሌላው ሰው ስልጣን ይሰጠዋል " (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዐረፋ የሚወጣው የወይን ጠጅ የሞላበት ፅዋ... በቅመማ ቅመም የተቀመመ

እግዚአብሔር ሰዎችን ሲቀጣ ሰዎቹ ጠንካራ ወይን ጠጅ እንደጠጡና እንደታመሙ ሰዎች ይሆናሉ፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዐረፋ የሚወጣው የወይን ጠጅ

ዐረፋ ሰዎች እንዲሰክሩ ለሚያደርገው የወይን ጠጅ ጥንካሬ ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "ጠንካራ የወይን ጠጅ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅመማ ቅመም

የደረቁ ቅጠላ ቅጠሎች ወይም መሬት ውስጥ የሚገኙ ዘሮች

ገለበጠው

ከትልቅ ፈሳሽ መያዣ ሰዎቹ ወደሚጠጡበት ፅዋዎች ገለበጠው

እስከ መጨረሻው ጠብታ ድረስ ጠጡት

"እያንዳንዱን የወይን ጠጅ ጠብታ ጠጧት"

Psalms 75:9

እርሱ ተናገረ

እግዚአብሔር ተናገረ

ቀንዶችን ሁሉ እሰብራለሁ

የእንስሳ ቀንዶች ለሰው ስልጣን ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "ስልጣናቸውን ሁሉ ከእነርሱ እወስዳለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የፃድቃን ቀንድ ግን ከፍ ከፍ ይላል

የእንስሳት ቀንዶቸ ለሰው ስልጣን ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ ይህ በገቢር ቅርፅ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "የፃድቃንን ቀንዶች ከፍ ከፍ አደርጋለሁ ወይም ፃድቃንን ባለ ስልጣን አደርጋቸዋለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 76

Psalms 76:1

አጠቃላይ መረጃ:-

ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው፡፡ (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ

"ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው፡፡"

በበገናዎች

"ሰዎች ይህንን መዝሙር በበገና ሊጫወት ይገባል"

የአሳፍ መዝሙር

"አሳፍ የፃፈው ይህ መዝሙር" ይህ በመዝሙር በ መዝሙረ ዳዊት 53:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት፡፡

ራሱን በይሁዳ እንዲታወቅ አደረገ

"እርሱ ማን እንደሆነ የይሁዳ ህዝብ እንዲያውቁት አደረገ"

ስሙ በእስራኤል ታላቅ ነው

"ስሙ" የሚለው ቃል ለመልካም ስሙ ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "የእስራኤል ህዝብ እርሱን መልካምና ሀያል እንደሆነ ይቆጥሩታል" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የማደሪያው ስፍራ

"እርሱ ሊኖርበት የመረጠው ስፍራ"

በዚያም ተወርዋሪውን ፍላፃ፣ ጋሻ፣ ሰይፉና ሌሎች የጦር መሳሪያዎችን ሰበረ

እነዚህ ቃላቶች ምናልባት የይሁዳ ህዝብ ጠላቶቻቸው በእነርሱ ላይ ጦርነት ይደፍቱብናል የሚል ፍርሀት ሳይኖራቸው በሰላም እንዲኖሩ ለማድረጉ ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው ነገር ግን እነዚህ ቃላቶች በቁሙ ሊተረጎሙ ይገባል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሴላ
ይህ ምናልባትም ሰዎች እንዴት መዘመር እንዳለባቸው ወይም ከዚህ ላይ የሙዚቃ መሳርያዎቻቸውን እንዴት መጫወት እንዳለባቸው የሚናገር የሙዚቃ ቃል ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል በቀጥታ ይፅፋሉ፣ አንዳንድ ትርጉሞች ደግሞ ይህን አያካትቱም። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከተት። (ቃላቶችን ቅዳ ወይም ከሌላ ውሰድ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 76:4
አጠቃላይ መረጃ፡-
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር እግዚአብሔር ታላቅ ጦርነትን ካሸነፈ በኋላ ከተራራ እንደሚመለስ አድርጎ ገልፆታል።
አንተ ብርሀን ተላብሰህ ክብርህን ገልጠሀል
ሁለተኛው ሀረግ አንደኛውን ሀረግ ያጠናክራል ምክንያቱም የእግዚአብሔር ክብር ከእግዚአብሔር ብርሀን መላበስ ጋር ተያያዥነት ስላለው ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ በድምቀት ታበራለህ
በድምቀት ታበራለህ የሚሉት ቃላት ታላቅ ለመሆን ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ እጅግ ታላቅ እንደሆንህ አሳይተሀል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ልበ ሙሉ የሆኑት ተዘረርፈዋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የአንተ ህዝብ የጠላቶቻቸውን ደፋር ወታደሮች ገደሉና ንብረታቸውን በሙሉ ወሰዱባቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
አንቀላፍተው ተኝተዋል
እዚህ ላይ “አንቀላፍተው ተኝተዋል” የሚለው ሞተዋል ለማለት ለስላሴ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞተዋል” ወይም “ሞተው ወደቁ” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 76:6
ከተግሳፅህ የተነሳ
“ተግሳፅ” የሚለው ረቂቅ ስም የሚያመለክተው በቁጣ ወይም በጥልቅ መንገድ አንድ ነገር መናገርን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ በገሰፅሀቸው ጊዜ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
አንቀላፍተው ተኝተዋል
ይህ ሀረግ እነርሱ ሞተዋል ብሎ ለመናገር ትህትና የተሞላበት መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞተዋል” ወይም “ሞተው ወደቁ” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በተቆጣህ ጊዜ ማን በፊትህ መቆም ይችላል?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ በተቆጣህ ጊዜ አንድም ሰው በፊትህ ሊቆም አይችልም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 76:8
አንተ ፍርድህ እንዲሰማ አደረግህ
“አንተ ፍርድን አስተላለፍህ” ወይም “አንተ ክፉ ሰዎችን እንዴት እንደምትቀጣ አወጅህ”
ምድር ነበረች
እዚህ ላይ “ምድር” በምድር ለሚኖሩ ሰዎች ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የምድር ሰዎች… ነበሩ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ፍርድን ፈፀምህ
“ፍርድን አስተላለፍህ” ወይም “ክፉ ሰዎችን ቀጣህ”
ሴላ
ይህ ምናልባት ሰዎች እንዴት መዘመር እንዳለባቸው ወይም እዚህ ላይ የሙዚቃ መሳርያዎቻቸውን እንዴት መጫወት እንዳለባቸው የሚናገር የሙዚቃ ቃል ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል በቀጥታ ይፅፋሉ፣ አንዳንድ ትርጉሞች ደግሞ ይህን አያካትቱም። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ቃላቶችን ቅዳ ወይም ከሌላ ውሰድ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 76:10
በእርግጥ የአንተ የቁጣ ፍርድ
“የአንተ የቁጣ ፍርድ እርግጠኛ ነው”
በሰው ልጆች ላይ የሚገለጠው የአንተ የቁጣ ፍርድ ለአንተ ክብርን ያመጣል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) “ሰዎች አንተን ያመሰግኑሀል ምክንያቱም አንተ በክፉዎች ላይ ስለተቆጣህና በእነርሱ ላይ ስለፈረድህ ነው” ወይም 2) “ከአንተ ጋር የተቆጡ ሰዎች አንተን እንዲያመሰግኑ የሚያደርጉ ነገሮችን ያደርጋሉ።”
ከቁጣህ በተረፉት ራስህን ትታጠቃለህ
የእግዚአብሔር ቁጣ እርሱ በዙሪያው እንደ ቀበቶ ሊታጠቀው የሚችለው ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የተረፈውን ቁጣህን እንደ ቀበቶ በዙሪያህ ትታጠቃለህ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 76:11
ሊፈራ ለሚገባው ለእርሱ
“ሊፈሩት የሚገባው እግዚአብሔር”
እርሱ የገዢዎችን መንፈስ ይሰብራል
“እርሱ… መንፈስ ይሰብራል” የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ሲሆን እርሱ መንፈስን ይሰብራል ወይም ያዋርዳል ማለት ነው።አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ገዢዎችን ያዋርዳል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
በምድር ነገስታት ዘንድ የተፈራ ነው
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የምድር ነገስታት እርሱን ይፈሩታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

---

# Chapter 77
## Psalms 77:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ለመዘምራን አለቃ
“ይህ አምልኮ ላይ እንዲጠቀምበት ለመዘምራኑ አለቃ ነው።”
ኤዶታም
ከዳዊት ዋነኛ ሙዚቃ ተጫዋቾች መካከል አንዱ ይህ ተመሳሳይ ስም ነበረው። ይህ እሱነ ሊያመለክት ይችላል። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 39:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
የአሳፍ መዝሙር
“ይህ አሳፍ የፃፈው መዝሙር ነው።” ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 53:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።
## Psalms 77:2
እጆቼን ዘረጋሁ
“እጆቼን በመዘርጋት ፀለይኩኝ”
ነፍሴ አልፅናና አለች
ነፍስ ሰውየውን ትወክላለች። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ አንድም ሰው እኔን ለማፅናናት እንዲሞክር አልፈቅድለትም” (ወካይ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በጭኸሁ ጊዜ እግዚአብሔርን አሰብሁት፤ ነፍሴን በሳትሁ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር አሰብሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ፣ በአንድ ላይ የተጣመሩት ለአፅንኦት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ነፍሴን ሳትሁ
“መንፈሴ በፈዘዘ ጊዜ” ወይም “መንፈሴ በደከመ ጊዜ“
ሴላ
ይህ ምናልባት ሰዎች እንዴት መዘመር እንዳለባቸው ወይም እዚህ ላይ የሙዚቃ መሳሪያዎቻቸውን እንዴት መጫወት እንዳለባቸው የሚናገር የሙዚቃ ቃል ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል በቀጥታ ይፅፋሉ፣ አንዳንድ ትርጉሞች ደግሞ ይህን አያካትቱም። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 3:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ቃላቶችን ቅዳ ወይም ከሌላ ውሰድ የሚለውን ይመልከቱ)
## Psalms 77:4
አጠቃላይ መረጃ፡-
ስለ እግዚአብሔር ከተናገረ በኋላ አሳፍ በቁጥር 4 ላይ ለእግዚአብሔር ተናገረና


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደገና ተመልሶ ስለ እግዚአብሔር መናገር ቀጠለ።
አይኖቼ እንዳይከደኑ ያዝኸቸው
“ለእግዚአብሔር እንዲህ አልኩት፣ “አይኖቼ እዳይከደኑ ያዝኸቸው”
አይኖቼ እንዳይከደኑ ያዘ
ያልተከደነ አይን ለመተኛት አለመቻልን የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እንዳልተኛ ከለከለኝ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የድሮውን ቀናት… የጥንቶቹን ጊዜያት
አስፈላጊ ከሆነ “የድሮ ቀናት” እና “የጥንት ጊዜያት” የሚሉት ሊጣመሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “በጣም ረጅም ጊዜ በፊት ስለተከናወኑ ነገሮች” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 77:6
ወደ አእምሮዬ ተመለሰሁ
ይህ ማስታወስን የሚገልጽ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አስታወስሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የሆነው ምን እንደሆነ
ሌላ አማራጭ ትርጉም፦ “ምን እየሆነ እንደነበረ” ነው።
ጌታ ለዘላለም ይጥለኛል? እርሱ እንደገና በጎነትን አያሳየኝም?
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በጌታ ዘንድ የተጣለ የመሆን ስሜትን የሚገልፁ ናቸው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
በጎነት ያሳየኛል
“በእኔ እንደተደሰተ የሚያሳዩ ነገሮችን ያደርጋል”
Psalms 77:8
አጠቃላይ መረጃ፦
አሳፍ ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ ምን እንደሆነ እርግጠኛ ስላልነበረ ምናልባት በቀጥታ የተጠየቁ ጥያቄዎች ሊሆኑ ይችላሉ ስለዚህ በቀጥታ ሊተረጎሙ ይገባል።
የኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጠፋ ወይ?
አሳፍ እግዚአብሔር ለኪዳኑ በታማኝነት ከእንግዲህ ወዲህ ስላለመስራቱ ሲናገር የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታማኝነት እንደጠፋ አድርጎ ገልፆታል። ታማኝነት የሚለው ረቂቅ ስም በቅፅል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ለኪዳኑ ታማኝ መሆን ለዘላለም አቆመን?” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ቸርነቱን ረሳን? ከቁጣው የተነሳ ርህራሄውን ነፈገ?
እነዚህ እግዚአብሔር ርህራሄ አለማሳየቱን ተመሳሳይ ሀሳብ የሚያብራሩ ሁለት መግለጫዎች ናቸው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ከቁጣው የተነሳ ርህራሄውን ነፈገ?
አሳፍ ስለ ቁጣ ሲናገር ቁጣ ሌላ ሰው፣ ርህራሄ የሚባል፣ ወደ ውጭ እንዳይወጣ ለመጠበቅ በር የሚዘጋ ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር በእኛ ላይ ከመቆጣቱ የተነሳ ርህራሄ ለእኛ ማሳየቱን አቆመን?” (ሰውኛ ዘይቤ እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 77:10
አልሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) ዘማሪው የሚናገረው ለራሱ ይናገር ነበር ወይም 2) ዘማሪው ለእግዚአብሔር ይናገር ነበር።
የልዑል የቀኝ እጅ ለእኛ እንደተለወጠ
“ቀኝ እጅ” ለሀይል፣ ስልጣንና ብርታት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ልዑል እኛን ለመርዳት ከእንግዲህ ወዲህ ሀይሉን አይተቀምም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 77:11
አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው ለእግዚአብሔር መናገር ጀምሯል።
ወደ አእምሮዬ ተመለስኩ
“አስታወስሁ” ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 74:2 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የጥንት አስደናቂ ስራዎችህን
“ከረጅም ጊዜ በፊት የሰራሀቸውን አስደናቂ ነገሮች”
ስራህን ሁሉ አሰላስላለሁ፣ በእነርሱ ላይ አውጠነጥናለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች እግዚአብሔር በሰራው ስራ ላይ የማሰላሰልን ሀሳብ የሚገልፁ ናቸው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
አሰላስላለሁ
በጥልቀት ስለ አንድ ነገር ማሰብ
በእነርሱ ላይ አውጠነጥናለሁ
“እነርሱ ምን ማለት እንደሆኑ ማሰብ”
Psalms 77:13
አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው ለእግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።
እንደ አምላካችን ያለ ታላቅ አምላክ ማን ነው?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከእኛ ታላቅ አምላክ ጋር የሚወዳደር ማንም አምላክ የለም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በህዝቦች መካከል ሀይልህን ትገልጣለህ
“ሀይል” የሚለው ረቂቅ ስም በቅፅል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከብዙ የህዝብ ወገኖች ለህዝብ ምን ያህል እንደሆንህ አሳየህ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ለህዝብህ ድል ሰጠሀቸው… ለልጆች
“ለእኛ ለህዝብህ ድል ሰጠኸን… ለእኛ ለልጆች”
ለህዝብህ ድል ሰጠሀቸው
“ድል” የሚለው ረቂቅ ስም በቅፅል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ህዝብህ አሸናፊ እንዲሆኑ አደረግሀቸው” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የያዕቆብና የዮሴፍ ልጆች
ይህ መላው የእስራኤልን ህዝብ የሚያመለክት ነው።
Psalms 77:16
ውሆች አንተን አዩህ… ፈሩ… ጥልቆች ተነዋወጡ
አሳፍ ስለ ውሀ ሲናገር ውሀው እርሱን የሚያስፈራው ነገር እንዳየ ሰው አድርጎ ገልፆታል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ውሆች አንተን አዩህ፣ እነርሱም ፈሩ፤ ጥልቆችም ተነዋወጡ
“ውሀ” እና “ጥልቅ” ባህር እና ውቅያኖስ የመሳሰሉትን ትልቅ የውሀ አካል ያመለክታሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ጥልቆች
ጥልቅ ውሀዎች
ደመናት ውሀን አንጠባጠቡ
አሳፋ ስለ ደመናት ሲናገር ውሀን ከማጠራቀሚያ እያወጡ የሚያፈስሱ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ገልፆአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ብዙ ዝናብ ወረደ” ወይም “በጣም ጠንካራ ዝናብ ዘነበ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ፍላፆችህ ዙሪያውን አብለጨለጩ
ይህ የእግዚአብሔር ፍላጾች ማብለጭለጫቸውን የሚገልፅ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ከአንተ የወጣው መብረቅ እንደ ፍላጻዎች ያበራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አብለጨለጨ
አንድ ሰው ፍላፃን ከወረወረ በኋላ ፍላፃው ምን እንደሚያደርግ የሚገልጽ በራስህ ቋንቋ ተጠቀም።
Psalms 77:18
የነጎድጓድ ድምፅ
ይህ ሰውኛ ዘይቤ ሲሆን ነጎድጓዱን እንደ እግዚአብሔር ድምፅ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እንደ ነጎድጓድ የሚጮህ ድምጽ” ወይም “በጣም ታላቅ ድምፅ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መብረቅህ አለምን አበራው
ይህ መብረቅ ጸሀፊው ሊያየው የሚችለውን ማንኛውንም ነገር እንዳበራው አፅንኦት ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋለ ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “መብረቅህ ልታየው የምትችለውን ያህል ያለ ማንኛውንም ነገር አበራው” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መንገድህ… መሄጃህ
እነዚህ ሁለት ቃላቶች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አንድ ላይ የተጣመሩት ለአፅንኦት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ዱካ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር እግዚአብሔር እግር ያለው ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። ይህ ሰውኛ ሆኖ ሳለ የሚቻል ከሆነ በቀጥታ ሊተረጎም ይገባል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ዱካዎች አይታዩም

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የአንተን ዱካ ማንም ሰው አላየም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝብህን እንደ በግ መንጋ መራኸው

ይህ ተነፃፃሪ የእግዚአብሔርን ህዝብ ከእንስሳት መንጋ ጋር ያወዳድረዋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእጅ

እዚህ ላይ “በእጅ” የሚለው ቃል “በድርጊታቸው” ወይም “በድርጊታቸው በኩል” ማለት ነው።

እጅ

እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ለሰው ሁለንተና ወካይ ዘይቤ ነው። (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 78

Psalms 78:1

አጠቃላይ መረጃ፦

ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የአሳፍ ትምህርት

“ይህ አሳፍ የፃፈው ትምህርት ነው።” “የአሳፍ ትምህርት” የሚለውን መዝሙረ ዳዊት 50:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

ትምህርት

ይህ የሙዚቃ ስልትን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 32:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ትምህርቴን ስማ

“ትምህርት” የሚለው ስም በግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ የማስተምርህን ስማ” ወይም “ሳስተምርህ ስማ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የአፌን ቃላቶች

“አፍ” የሚለው ቃል ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ቃሌን” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ

“አፌን እከፍታለሁ” የሚለው ፈሊጥ መናገር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በምሳሌ እናገራለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ... ዘምሩ

“ተናገሩ።” “ትናገራለች” የሚለውን በ መዝሙረ ዳዊት 19:2 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

የተሰወሩ ነገሮችን

የአንተ ቋንቋ ሆን ተብሎ ለመረዳት አስቸጋሪ እንዲሆን የተደረጉትን አባባሎች የሚገልፅ ቃል ካለው እዚህ ላይ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

Psalms 78:3

አጠቃላይ መረጃ፦

ቁጥር 3 በቁጥር 2 ላይ የተጀመረውን አረፍተ ነገር ይቀጥላል።

እነዚህን ከልጆቻቸው አንሰውርም

ይህን በአዎንታዊ መልክ ልንፅፈው እንችላለን። አማራጭ ትርጉም፦ “ስለ እነርሱ ለልጆቻችን በእርግጠኝነት እንነግራቸዋለን”

የእግዚአብሔርን ምስጋናውንና ያደረገውን ድንቅ ነገር

“እግዚአብሔርን የምናመሰግንባቸውን ነገሮች”

Psalms 78:5

መሰረተ

“እግዚአብሔር መሰረተ”

የቃል ኪዳን ስርአቶች

ሌሎች ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ “ምስክሮች” ወይም “ህጎች።”

Psalms 78:7

አጠቃላይ መረጃ፦

ጸሐፊው የሚናገረው በ መዝሙረ ዳዊት 78:5-6 ስላሉት ልጆች ነው።

Psalms 78:9

የኤፍሬም ልጆች... የጦርነት ቀን

ይህ ምናልባት ቃል ኪዳኑን (ቁጥር 10) ላለመጠበቅ ተለዋጭ ዘይቤ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ይህን በቀጥታ መተርጎም ይሻላል።

የኤፍሬም ልጆች

“የኤፍሬም ልጆች ወታደሮች”

ቀስት ታጥቀው ነበር

ወታደሮቹ ምናልባት ቀስት ጭምር ነበራቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለጦርነት የሚሆኑ ቀስትና ጦር ነበራቸው።” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:12

የጣኔዎስ ምድር

ይህ በግብፅ ምድር የነበረውን በጣኔዎስ ከተማ አካባቢ የነበረውን ስፍራ ያመለክታል። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:15

እርሱ ሰነጠቀ

“እግዚአብሔር ሰነጠቀ”

የባህሩን ጥልቅ ለመሙላት የሚበቃ

ይህ ምናልባት ግነት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሊጠጡት ከሚችሉት በላይ የሆነ ተጨማሪ ዉሀ” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ምንጮች

ትንንሽ ወንዞች

Psalms 78:17

እነርሱ እግዚአብሔርን ተፈታተኑት

እግዚአብሔር አደርገዋለሁ ብሎ የተናገረውን ነገር ማድረግ እንደሚችል እርሱን ከማመናቸው በፊት እንዲያረጋግጥላቸው ፈለጉ።

በልባቸው

“በሙሉ ልባቸው”

የምግብ ፍላጎታቸውን ለማርካት

“የተመኙትን ያህል መብላት እንዲችሉ”

Psalms 78:19

ተናገሩ

እስራኤላውያን ተናገሩ

በእውነት እግዚአብሔር በምድረ በዳ ማዕድ ለእኛ ማዘጋጀት ይችላልን?

ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኛ በእውነት እግዚአብሔር በምድረ በዳ ለእኛ ማእድ ሊያዘጋጅ ይችላል ብለን አናምንም!” ወይም “እግዚአብሔር፣ አንተ በእውነትም በምድረ በዳ ለእኛ ማእድ ማዘጋጀት የምትችል መሆንህን አረጋግጥልን!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ማእድ ማዘጋጀት

“ማእድ ማዘጋጀት” የሚለው ፈሊጥ ምግብ ለመብላት ማእድ ማዘጋጀት ማለት ነው። እዚህ ላይ “ማእድ” የሚለው ለሚበላው ምግብ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ምግብ አዘጋጀልን” (ፈሊጥ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ውሃ ተንዶለዶለ

ብዙ ውሀ በፍጥነት ወጣ

ነገር ግን እንጀራ መስጠት ይችላልን? ለህዝቡስ ስጋን ሊያቀርብ ይችላልን?

ህዝቡ በእነዚህ ጥያቄዎች እርሱን እየሰደቡ በእግዚአብሔር ላይ ይስቃሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ነገር ግን እንጀራ እንደሚሰጠንና ለህዝቡ ስጋ ማቅረብ እንደሚችል ይህን ሰርቶ እስከሚያሳይ ድረስ አናምንም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እንጀራ... ስጋ

ከእፅዋት የሚገኝ ምግብ፣ ከእንስሳት የሚገኝ ምግብ። ምንም እንኳ ይህ ለሁሉም አይነት ምግብ ወካይ ቢሆንም የሚቻል ከሆነ በቀጥታ መተርጎም የተሻለ ነው። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 78:21

በያዕቆብ ላይ እሳቱ ነደደ

ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ቁጣ ሲናገር ቁጣው እሳት እንደሆነና እሳቱ ያዕቆብን እንዳቃጠለው ያህል እግዚአብሔር በያዕቆብ ላይ በቁጣ እርምጃ እንደወሰደበት አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ቁጣው ያዕቆብን እንደ እሳት



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አቃጠለው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ያዕቆብ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው።
ቁጣው እስራኤልን አጠቃ
ጸሐፊው እግዚአብሔር በተቆጣ ጊዜ እስራኤልን ስለመቅጣቱ ሲናገር ቁጣው እስራኤልን ያጠቃ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ስለተቆጣ እስራኤልን አጠቃው” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ማዳን አልታመኑም
“እነርሱን እንደሚያድናቸው አላመኑትም”
Psalms 78:23
እርሱ ሰማያትን አዘዘ
አሳፍ ስለ ሰማያት ሲናገር ሊሰማ የሚችልና የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚያደርግ ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ለሰማይ ተናገረ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰማያት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፦ 1) “ሰማይ” ወይም 2) “ደመናት።”
የሰማይንም ደጆች ከፈተ
አሳፍ ስለ ሰማይ ሲናገር በር ያለው መጋዘን እንደሆነ አድርጎ አቅርቦታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰማይን እንደ መጋዘን ከፈተው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይበሉም ዘንድ መና አዘነበላቸው፤ ከሰማይም መብልን ሰጣቸው
እነዚህ ሁለት መስመሮች ስለ ተመሳሳይ ክስተት ያወራሉ።
መና አዘነበላቸው
“መና ከሰማይ እንደ ዝናብ እንዲፈስስላቸው አደረገ”
የመላዕክት እንጀራ
ይህ እግዚአብሔር ለህዝቡ የሰጠውን መና የሚያመለክት ነው። “እንጀራ” የሚለው ቃል በአጠቃላይ ምግብን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “መላዕክት የሚበሉት አይነት ተመሳሳይ ምግብ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
የተትረፈረፈ ምግብ
“የተትረፈረፈ” የሚለው ረቂቅ ስም በቅፅል ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ብዙ ምግብ” ወይም “ትልቅ መጠን ያለው ምግብ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:26
አመጣ
“እግዚአብሔር አመጣ”
ስጋን እንደ አፈር አዘነበላቸው
ጸሐፊው እግዚአብሔር ወፎችን ከሰማይ እንዲወርዱ ስለማድረጉ ሲናገር ወፎቹ እግዚአብሔር ከሰማይ እንዲወርዱ ያደረጋቸው ዝናብ እንደሆኑ አድርጎ ገልፆአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ስጋ እንደ ዝናብ ከሰማይ እንዲወርድ አደረገ፣ ይህም እጅግ በጣም ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ምድርን እንደ አፈር ሸፈነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተነጻጻሪ የሚለውን ይመልከቱ)
ስጋ
ወፎች
እንደ ባህር አሸዋ እጅግ ብዙ ናቸው
የባህርን አሸዋ መቁጠር የሚችል አንድም ሰው የለም። አንድም ሰው ሊቆጥራቸው ከሚችለው በላይ የሆኑ እጅግ ብዙ ወፎች ነበሩ፣ ነገር ግን ይህ መግለጫ ግነት ነው፦ ምናልባት ከባህር አሸዋ የሚበልጥ ቁጥር ያላቸው ወፎች ቃል በቃል አልነበሩም ይሆናል። (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:29
ጎመጁ
በብርቱ ፈለጉ
Psalms 78:31
በዚያን ጊዜ
ምግቡ በአፋቸው እያለ (መዝሙረ ዳዊት 78:31)
የእግዚአብሔር ቁጣ በላያቸው ላይ መጣ
“እግዚአብሔር ተቆጣና በላያቸው መጣ።” “የእርሱ ቁጣ በእስራኤል ላይ መጣ “ የሚለውን በ መዝሙረ ዳዊት 78:21 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በላያቸው ላይ መጣ
ይህ ለስላሴ ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም እንዲሞቱ አደረጋቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ገደላቸው” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አስደናቂ ስራውን አላመኑም
“ስራ” የሚለው ቃል ስራዎቹን ለሰራው ለእግዚአብሔር ምትክ ስም ነው። ያላመኑት ምን እንደሆነ በግልፅ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ምንም እንኳ እንዲህ አይነት አስደናቂ ስራ ቢሰራም እነርሱን እንደሚንከባከባቸውና እንደሚጠብቃቸው አላመኑም።” (ምትክ ስም እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:33
አጠቃላይ መረጃ፦
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መናገሩን ቀጥሏል።
ቀኖቻቸውን አሳጠረው
እዚህ ላይ “ቀኖች” የሚለው ቃል የህይወት ዘመናቸውን ያመለክታል። “ቀኖቻቸውን አሳጠረ” የሚለው ፈሊጥ ረጅም ዘመን ከመኖራቸው በፊት እንዲሞቱ አደረጋቸው የሚል ትርጉም አለው። አማራጭ ትርጉም፦ “ገና ወጣቶች ሳሉ ገደላቸው” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አመቶቻቸው በድንጋጤ የተሞሉ ነበሩ
አሳፍ ስለ “አመቶች” ሲናገር ማጠራቀሚያ እንደሆኑ አድርጎ ገልጧቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከአመት ወደ አመት ሁልጊዜ በፍርሀት ይኖሩ ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱን ለመፈለግ
ይጠብቃቸው ዘንድ ሊያደርግላቸው የሚፈልጉትን ነገር ለመጠየቅ (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:35
አጠቃላይ መረጃ፦
እስራኤላውያን ስለ ሰሯቸው ስራዎች የሚናገሩ ንግርቶች።
አስብ
“አስታውስ።” ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 20:3 ላይ እንዴት እደተተረጎመ ተመልከት።
እግዚአብሔር አለታቸው ነበር
ጸሀፊው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር እርሱ ሰዎች ከጠላቶቻቸው እንዲድኑ ሄደው የሚጠጉበት ኮረብታ ወይም ተራራ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱ የሚጠብቃቸው እግዚአብሔር ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አዳኛቸው
“እነርሱን የሚያድናቸው”
ሸነገሉት
“በልባቸው ሳያምኑበት እርሱ አስደናቂ አምላክ እንደሆነ ነገሩት”
በአፋቸው
“አፍ” የሚለው ቃል አፋቸውን በመጠቀም እነርሱ ለሚናገሯቸው ቃላቶች ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የተናገሩትን በመናገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ልባቸው በእርሱ የፀና አልነበረም
እዚህ ላይ ”ልባቸው” ለሀሳባቸው ምትክ ስም ነው። ለእርሱ ታማኝ መሆን ከእርሱ ጋር በአፅንኦት መጠበቅ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሀሳባቸው በእርሱ ላይ ያተኮረ አልነበረም” ወይም “ለእርሱ ታማኞች አልነበሩም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:38
በደላቸውን ይቅር አላቸው
“ምንም እንኳ ክፉ ስራ ቢሰሩም ይቅር አላቸው”
ቁጣውን ገታ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ቁጣ ሲናገር ቁጣው የተቆጣ ሰው እንደሆነና እግዚአብሔር እርሱን ያስቆጡትን ሰዎች እንዳያጠቃቸው እርሱን እንዲከለክለው ሀላፊነት የሰጠው ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም: “ምንም እንኳ በእነርሱ ላይ የተቆጣ ቢሆንም አልቀጣቸውም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መአቱንም ሁሉ አላወረደም
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር መአት ሲናገር መአቱ እግዚአብሔር እንዲተኛ የፈቀደለትና ከዚያ በኋላ ሳይነቃ የቀረ እንቅልፍ የወሰደው ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሙሉ በሙሉ በእነርሱ ላይ ቁጡ እንዳይሆን ራሱን ከለከለ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:39


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አስብ
“አስታውስ።” “አስብ” የሚለውን በ መዝሙረ ዳዊት 20:3 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ስጋ ለባሾች ናቸው
“ስጋ” የሚለው ቃል፣ ደካማና ሟች የሆነው፣ ለሰው ልጅ ደካማነትና ሟችነት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እስራኤላውያን ደካሞችና አንድ ቀን የሚሞቱ ናቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ምድረ በዳ
“አንድም ነገር የማይበቅልበት ስፍራ”
እግዚአብሔርን ተፈታተኑት
እግዚአብሔር አደርገዋለሁ ብሎ የተናገረውን ነገር ማድረግ እንደሚችል እርሱን ከማመናቸው በፊት እንዲያረጋግጥላቸው ፈለጉ። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 78:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
Psalms 78:42
አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዴት እንዳዳናቸው ይናገራል።
ጣኔዎስ
በግብፅ የሚገኝ ከተማ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:44
አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው እግዚአብሔር የሰራውን ስራ ይገልጻል።
የዝንብ ሰራዊት
እንደ ደመና የሚመስል እጅግ ብዙ ዝንቦች።
እነርሱን ነደፏቸው
ዝንቦቹ ግብፃውያንን ቢበሏቸው ኖሮ ሊሰማቸው ይችል እንደነበር እንደዚሁ ግብፃውያንን እንዲያዝኑ አድርገዋቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አዝመራቸውን ለኩብኩባ፣ ሰብላቸውን ለአንበጣ ሰጠባቸው
“ኩብኩባ አዝመራቸውን በሙሉ እንዲበሉ አንበጣ ደግሞ ለማምረት ሲሉ እጅግ በጣም ደክመው የሰሩትን ማንኛውንም ነገር እንዲበሉ ፈቀደላቸው”
ምድራቸውን ወረሩት
“በምድራቸው በየትኛውም አቅጣጫ ሄዱ”
ኩብኩባ
ለመዝለል የሚረዱ ረጃጅም እግሮች ያሉት ዕፅዋት የሚበላ ነፍሳት
አዝመራቸውን ለኩብኩባ ሰጠ
አሳፍ ስለ አዝመራው ሲናገር እግዚአብሔር ለኩብኩባው የሰጠው ስጦታ እንደሆነ አደርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አዝመራቸውን እንዲበላባቸው እርሱ ለኩብኩባው ፈቀደለት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የደከሙበትን ሁሉ ለአንበጣ ሰጠ
“እርሱ የደከሙበትን ማንኛውም ነገር ለአንበጣ ሰጠ።” አሳፍ ሰዎቹ የደከሙበትን ነገር እግዚአብሔር ለአንበጣዎች የሰጠው ስጦታ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል።” “የደከሙበት ነገር” የሚለው ሀረግ በድካማቸው ለማምረት በተዘጋጀው እህል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እጅግ በጣም ደክመው ለምርት የበቃውን እህል አንበጣዎች እንዲበሉት ፈቀደላቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:47
አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለግብጻውያን የሰራውን ስራ መግልጽ ቀጥሏል።
ወይን
ፍሬ የሚሰጥ ዛፍ
የመብረቅ እሳት
ትልቅ ነጎድጓድ የሚያስከትል መብረቅ
እርሱ በረዶ አዘነበባቸው
“እርሱ በረዶ አወረደ” ወይም “በረዶ እንዲወርድ አደረገ”
ፅኑ ቁጣውን በእነርሱ ላይ ሰደደ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር መቅሰፍት ሲናገር መቅሰፍቱ ሌላ ሰውን እንደሚያጠቃ ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ በእነርሱ ላይ ተቆጣ፣ ከዚህ የተነሳ በድንገት በመአቱ አጠቃቸው” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ፅኑ ቁጣ
“የእርሱ ፅኑ ቁጣ”
በእነርሱ ላይ ሰደደ
“በእነርሱ ላይ አንድም ነገር ይሆናል ብለው ሳያስቡት አጠቃቸው”
መከራ እንደሚያመጡ ወኪሎች ቁጣ፣ መአትና መቅሰፍት ላከባቸው
አሳፍ ስለ ቁጣ፣ መአትና መቅሰፍት ሲናገር እግዚአብሔር ስራውን ለእርሱ ለመስራት ሊልካቸው እንደሚችላቸው ሰዎች አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ በጣም ከመቆጣቱ የተነሳ ግብፃውያንን መጉዳት ፈለገ፣ ከዚህ የተነሳ በእነርሱ ላይ መከራ ላከባቸው፣ መቅሰፍት ደግሞ አመጣባቸው” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መአት
አንድ ሰው ሌሎችን ለመጉዳት የሚያነሳሳ ቁጣ
Psalms 78:50
አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለግብጻውያን የሰራውን ስራ መግልጽ ቀጥሏል።
ለቁጣው መንገድ ጠረገ
ዘማሪው ስለ ቁጣ ሲናገር እግዚአብሔር ህዝቡን እንዲቀጣ ለማመቻቸት ቀድሞ የሚወጣ ሰው እንደሆነና ሰዎች እንዲራመዱበት መንገዱን ደልዳላ የሚያደርግ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ በጣም ስለተቆጣ እነርሱን ለመጉዳት ማድረግ የሚችለውን ማንኛውንም ነገር አደረገ” ወይም “ቁጣው ታላቅ ጦር ሰራዊት እነደሆነ ያህል ለጦርነት ለመዝመት ደልዳላ መንገድ ሰራ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱን ከሞት አላዳነም
“እርሱ ግብፃውያንን ከሞት አልጠበቃቸውም” ወይም “ግብፃውያን በህይወት እንዲኖሩ አልፈቀደላቸውም”
ህይወታቸውን ለመቅሰፍት አሳልፎ ሰጠ
አሳፍ ስለ መቅሰፍት ሲናገር ግብፃውያንን ለመጉዳት የሚሄድ ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉም በመቅሰፍት በጣም እንዲታመሙ አደረጋቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)
የአፍላ ጉልበታቸው በኩር
ይህ ሀረግ የእያንዳንዱን ቤተሰብ ወንድ ልጅ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የመጀመሪያ ወንዶች ልጆች” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
በካም ድንኳኖች
እዚህ ላይ “ድንኳን” የሚለው ቃል ለቤተሰብ ምትክ ስም ነው። “ካም” የሚለው ቃል ደግሞ በቅድመ አያታቸው ስም ግብፃውያንን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በግብጽ ቤተሰቦች መካከል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:52
አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግልጽ ቀጥሏል።
እንደ በግ... እንደ መንጋ
ጸሐፊው እስራኤላውያን እንደ በግ እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር እረኛ ለበጎቹ እንደሚያደርገው ህዝቡን እንደሚንከባከብና እንደሚጠብቅ ነው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዋጣቸው
ሙሉ በሙሉ ሸፈናቸው
Psalms 78:54
አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግልጽ ቀጥሏል።
ቀኝ እጁ አባረረ
“ቀኝ እጅ” የሚሉት ቃላቶች ለሀይል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ በራሱ ሀይል ለራሱ አሸነፈ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ርስታቸውን አከፋፈላቸው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በአንድ ወቅት ሌሎች ህዝቦች ይኖሩበት በነበረው ምድር ርስታቸውን አከፋፈላቸው ወይም 2) እግዚአብሔር በአንድ ወቅት ከርስታቸው ወደ ሌላ አውጥቶ ለሰደዳቸው አህዛብ ርስታቸውን አካፈላቸው። “ሁልጊዜ ለእነርሱ የሚሆን ምድር ሰጣቸው”
በድንኳናቸው ውስጥ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) እርሱ እስራኤላውያንን በምድሪቱ በራሳቸው ድንኳኖች አኖራቸው ወይም 2) እርሱ እስራኤላውያንን ሌሎች ህዝቦችን አባርሮ ባወጣበት ድንኳኖች አኖራቸው። እነዚህ “ድንኳኖች” አብዛኛዎቹ እውነተኛ

ቤቶች ነበሩ፣ እነዚህ ቤቶች ደግሞ ሌሎች ህዝቦች በውስጣቸው የኖሩባቸውና እስራኤላውያኑ ራሳቸው የኖሩባቸው ናቸው። አማራጭ ትርጉም:- “በራሳቸው ቤት” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:56
አጠቃላይ መረጃ:-
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግልጽ ቀጥሏል።
ተፈታተኑት፣ አመፁ
እነዚህ ቃላቶች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው እነዚህን የተጠቀመው እግዚአብሔር ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸውን እንደሚያዘጋጅላቸው ወይም እንደተናገረው ክፉውን እንደሚቀጣ እስራኤላውያን ፈፅመው እንደማያምኑ አፅንኦት ለመስጠት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ተፈታተኑት
እግዚአብሔር አደርገዋለሁ ብሎ የተናገረውን ነገር ማድረግ እንደሚችል እርሱን ከማመናቸው በፊት እንዲያረጋግጥላቸው ፈለጉ። ይህን በ መዝሙረ ዳዊት 78:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
አመጹ
ለመታዘዝ እንቢ አሉ
ከዳተኞች ነበሩ፣ ክፋትንም አደረጉ
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው ሁለቱንም ሀረጎች የተጠቀመባቸው እስራኤላውያን እናደርጋለን ብለው የተናገሩትን ነገር ለእግዚአብሔር እንዳላደረጉ አፅንኦት ለመስጠት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:58
አጠቃላይ መረጃ:-
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግልጽ ቀጥሏል።
በኮረብታ ማምለኪያዎቻቸው አስቆጡት፤ ተቀርፀው በተሰሩ ጣኦቶቻቸው አስቀኑት
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ትይዩነት ያላቸው ሲሆን ሁለቱም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:60
አጠቃላይ መረጃ:-
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግልጽ ቀጥሏል።
የሀይሉን ምልክት አስማረካት፤ ክብሩንም ለጠላቶቹ እጅ አሳልፎ ሰጠ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ሀይልና ክብር ሲናገር እነዚህ ሁለቱ ሰዎች ሊይዟቸውና ሊሸከሟቸው የሚችሉ ቁሳዊ እቃዎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጧቸዋል። “ሀይል” እና “ክብር” የሚሉት ቃላቶች ምናልባት ለቃል ኪዳኑ ታቦት ምትክ ስሞች ሊሆኑ ይችላሉ። “እጅ” የሚለው ቃል ለጠላት ሀይል ምትክ ስም ነው። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ጠላቶቹ የከበረውን የቃል ኪዳኑን ታቦት እንዲማርኩት ፈቀደ፤ ታቦቱን የፈለጉትን ማንኛውንም ነገር ሊያደርጉበት እንዲችሉ ለእነርሱ አሳልፎ ሰጣቸው” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:62
አጠቃላይ መረጃ:-
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግልጽ ቀጥሏል።
ህዝቡን ለሰይፍ አሳልፎ ሰጠ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር ህዝብ ሲናገር እግዚአብሔር እንደ ስጦታ ለሌሎች የሚሰጣቸው ትንሽ እቃ እንደሆኑ፣ በጦርነት ለሚከሰት ሞት ምትክ ስም የሆነውን ሰይፍ ደግሞ ስጦታውን ሊቀበል የሚችል ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልጧቸዋል። አማራጭ ትርጉም:- “እርሱ ሌሎች ሰዎች ህዝቡን በጦርነት ውስጥ እንዲገድሏቸው ፈቀደ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ሰውኛ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በርስቱ ላይ እጅግ ተቆጣ
“ለዘላለም የራሱ ይሆናል ብሎ የተናገረላቸው ህዝቡ ላይ ተቆጣ”
ጎልማሶቻቸውን እሳት በላቸው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው:- 1) “ጎልማሶቻቸውን በሙሉ ለመግደል ጠላት እሳት ተጠቀመ” ወይም 2) “ጎልማሶቻቸው በጦርነት ውስጥ እሳት ደረቅ ሳርን እንደሚያቃጥል እንደዚሁ በፍጥነት ሞቱ።” እነዚህ ሰዎች የጦር መሳሪያ እንደተጠቀሙ የሚያሳይ መልእክት አታስተላልፍ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በላቸው
“መብላት” ማንኛውንም ነገር በጣም በፍጥነት መብላት ነው።
ሰርግ
ሰዎች ሲያገቡ የሚፈፀም ስርአት
Psalms 78:64
ካህናቶቻቸው በሰይፍ ወደቁ
እዚህ ላይ “ሰይፍ” የሚለው ቃል በሰይፍ የሚዋጉ ወታደሮችን የሚወክል ነው። “በሰይፍ ወደቁ” የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ሲሆን በጦርነት መካከል መሞት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ካህናቶቻቸው በጦርነት መካከል ሞቱ” ወይም “ጠላት ካህናቶቻቸውን በሰይፍ ገደላቸው” (ምትክ ስም እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
መበለቶቻቸው ማልቀስ ተሳናቸው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው:- 1) አንድ ሰው መበለቶች እንዳያለቅሱ አስገደዳቸው ወይም 2) ብዙ ካህናቶች ከመሞታቸው የተነሳ አግባብነት ያለው የቀብር ስርአት ለመፈፀም ጊዜ አልነበረም።
መበለቶች
ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች
ጌታም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሳ
ጌታ ለተወሰነ ጊዜ ስራ ስለ አለመስራቱ ሲናገር እርሱ ተኝቶ እንደነበረ ተደርጎ ሲገለፅ፣ ስራ መጀመሩ ደግሞ ከእንቅልፍ መነሳቱ ተደርጎ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደነቃ ያህል ስራ መስራት ጀመረ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የወይን ጠጅ ስካር እንደ በረደለት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው:- 1) ብዙ የወይን ጠጅ እንደጠጣና እንደሰከረ ከስካሩም በመንቃቱ ምክንያት ለመዋጋት እንደፈለገ በቁጣም እንደተሞላ ተዋጊ ወይም 2) ብዙ የወይን ጠጅ እንደጠጣ ነገር ግን አሁን ማሰብ እንደቻለና ከመተኛቱ የተነሳ በሚገባ እንደተዋጋ ተዋጊ።
Psalms 78:67
አጠቃላይ መረጃ:-
ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰራውን ስራ መግልጽ ቀጥሏል።
የዮሴፍ ድንኳን
እዚህ ላይ “ድንኳን” የሚለው ቃል ለቤተሰብ ምትክ ስም ነው። በዚህ ሀረግ ድንኳን የዮሴፍን ልጆች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “የዮሴፍ ልጆች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ዮሴፍ... ኤፍሬም
ኤፍሬም የዮሴፍ ልጅ ነበር።
ይሁዳ... የፅዮን ተራራ
የጽዮን ተራራ የሚገኘው የይሁዳ ነገድ ይኖርበት በነበረው ምድር ነው።
መቅደሱን እንደ ሰማያት ሰራት
የዚህ ንፅፅር ዘይቤ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው:- 1) እግዚአብሔር መቅደሱን እንደ ሰማያት ከፍ አድርጎ ሰራት። አማራጭ ትርጉም:- “መቅደሱን እንደ ሰማያት ከፍ አድርጎ ሰራት” ወይም 2) እግዚአብሔር መቅደሱን እንደ ሰማያት የማይናወጥ አድርጎ ሰራት። አማራጭ ትርጉም:- “ሰማያት ለዘላለም ፀንተው እንደሚኖሩ እንደዚሁ መቅደሱን ለዘላለም ፀንታ እንድቅቆም አድርጎ ሰራት” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ምድር
ይህ ግስ የተሰጠው ከቀደመው መስመር ሊሆን ይችላል። ጸሐፊው የእግዚአብሔርን መቅደስ ቋሚነት ከምድር ቋሚነት ጋር አነፃፅሮታል። አማራጭ ትርጉም:- “ምድር በቋሚነት እንደሚኖር እንዲሁ እርሱ መቅደሱን በቋሚነት እንዲኖር አድጎ ሰራት።” (አስጨምሬ እና ተንጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 78:70
አጠቃላይ መረጃ:-
ጸሐፊው እግዚአብሔር የሰራውን ስራ መግልጽ ቀጥሏል።
የበጎች ጉረኖ
“በጎች በደህንነት እንዲጠበቁ የሚያደርግ በዙርያው ግድግዳ ያለው ስፍራ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለህዝቡ ለያዕቆብ፣ ለርስቱም ለእስራኤል እረኛ ይሆን ዘንድ
“እረኛ” የሚለው ቃል ሌሎች ሰዎችን ለሚመራና ለሚጠብቅ ሰው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ህዝቡን የያዕቆብን ልጆች፣ ርስቱንም እስራኤልን ይመራና ይጠብቅ ዘንድ ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ርስቱን
“ለዘላለም የራሱ ይሆኑ ዘንድ የመረጣቸው ህዝብ” ይህን በ መዝሙረ ዳዊት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

78:62 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።
እነርሱን ዳዊት ጠበቃቸው
“ጠበቃቸው” የሚለው ቃል ለመምራትና ለመጠበቅ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ዳዊት እነርሱን መራቸው፣ እነርሱን ጠበቃቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 79
Psalms 79:1
አጠቃላይ መረጃ፦
ትይዩነት በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ግጥም እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
የአሳፍ መዝሙር
“ይህ አሳፍ የፃፈው መዝሙር ነው።” ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 50:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።
ርስትህ
“ለአንተ ለዘላለም የሚሆን ምድር” ይህ በ መዝሙረ ዳዊት 68:9 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።
ደማቸውን እንደ ውሀ አፈሰሱ
“ደም” የሚለው ቃል ለንፁሀን ሰዎች ህይወት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ደም ማፍሰስ ንፁሀን ሰዎችን መግደል ነው። አብዛኛው ሰዎች ዉሀ በየቀኑ ያያሉ፣ ስለዚህ ደም እንደ ውሀ የተለመደ ነገር እንዲሆን ብዙ ንፁሀን ሰዎች መሞት ነበረባቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “እጅግ በጣም ብዙ ንፁሀን ሰዎች ከመግደላቸው የተነሳ ደማቸው ዝናብ ከዘነበ በኋላ እንደሚፈስስ ውሀ ደማቸው በየቦታው ፈሰሰ” (ምትክ ስም እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 79:4
እኛም ለጎረቤቶቻችን መዘባበቻ፤ በዙሪያችንም ላሉት መሳቂያና መሳለቂያ ሆንን
“መዘባበቻ እና መሳቂያ የሚሉት ቃላቶች ሌሎች ለሚዘባበቱባቸው፣ ለሚስቁባቸውና ለሚሳለቁባቸው ምትክ ስሞች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “እኛ ጎረቤቶቻቸው የሚስቁባቸውን የሚሳለቁቸው ሰዎች ሆነናል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ሆነናል
“እኛ” የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ህዝብ ነው።
መሳለቂያ
አንድን ሰው ለማዋረድ የሚደረግ ብርቱ ሳቅ ነው።
የቅናትህ ቁጣ እንደ እሳት የሚነደው እስከ መቼ ነው?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የቅናት ቁጣህ እንደ እሳት መንደዱን ፈፅሞ የሚቆም አይመስልም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
የቅናትህ ቁጣ ይነድዳልን
“ቁጣ” የሚለው ረቂቅ ስም ቁጡ ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ቀናተኛና ቁጡ ትሆናለህን” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ እሳት ይነድዳል
ይህ ተነፃፃሪ ዘይቤ የእግዚአብሔር ቁጣ መገለጠ ነገሮች ከሚያጠፋ እሳት ጋር ያነፃፅረዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “አጠፋን” (ተነጻጻሪ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 79:6
አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ሁለት ጥንድ ሀረጎች እያንዳንዳቸው ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በአንድ ላይ የተጣመሩት አፅንኦት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
በህዝቦች ላይ መአትህን አፍስስ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር መአት ሲናገር ፈሳሽ እንደሆነ አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ ስለተቆጣህ ህዝቦችን ቅጣቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ስምህን በማይጠሩ
“ስም” የሚለው ቃል ለሰውየው ሀይልና ስልጣን ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የአንተ ያልሆኑት ወይም እንድትረዳቸው ለማይጠይቁህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ያዕቆብን በልተውታልና
“ያዕቆብ” የሚለው ቃል ልጆቹ ለሆኑት ለእስራኤል ህዝብ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስራኤልን ህዝብ ሙሉ በሙሉ አጠፏቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 79:8
የአባቶቻችንን ሀጢአት በእኛ ላይ አትቁጠርብን
“የአባቶቻችንን ሀጢአት ማሰብህን አቁም፣ ስለ እነርሱም እኛን አትቅጣን” ወይም “ስለ አባቶቻችን ሀጢአት እኛን ይቅር በለን”
እኛ በጣም ተቸግረናል
ጸሐፊው ስለ ህዝቡ ደካማነትና ሀዘንተኛ መሆን ሲናገር በዝቅተኛ ስፍራ እንዳሉ አድርጎ ገልጧቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኛ በጣም ደካሞች ነን” ወይም “እኛ በጣም አዝነናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የደህንነታችን አምላክ
“ደህንነት” የሚለው ቃል “አዳነ” በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል፦ “ያዳነን አምላክ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ ስምህ ክብር ብለህ
“ስም” የሚለው ቃል ለመልካም ስሙ፣ ስለእርሱ ሰዎች ለሚያውቁት ነገር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች ስለ አንተ ክብር ያውቁ ዘንድ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ ስምህ ብለህ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ስም ሁለንተናዊ ማንነቱንና የሚገባውን ክብር የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች አንተን ያከብሩ ዘንድ” ወይም “ስለ ራስህ ስም ብለህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 79:10
ህዝቦች “አምላካቸው የት አለ?” ለምን ይበሉ?
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ህዝቦች “አምላካቸው የት አለ?” ብለው መናገር መቻል የለባቸውም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
አምላካቸው የት አለ?
ይህ ማንጓጠጥ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አምላካቸው ምንም ሊያደርግ አይችልም!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
የፈሰሰውን የአገልጋዮችህን ደም በቀል፣ አይናችን እያየ ህዝቦች ይወቁት
ደም ማፍሰስ ንፁሀን ሰዎችን ለመግደል ምትክ ስም ነው። ይህ በገቢር ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ህዝቦች የገደሏቸውን የንፁሀን አገልጋዮችህን በቀል አንተ ስታደርገው በአይናችን ፊት መመልከት መንገድ ተበቀልላቸው” (ምትክ ስም እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በአይናችን ፊት
“በአይናችን” ወይም “በአካል በተገኘንበት”
የእስረኞች ሰቆቃ በፊትህ ይድረስ
አሳፍ በመከራና በሀዘን ውስጥ የነበሩት እስረኞች ስላሰሙት ሰቆቃ ሲናገር በንጉስ ፊት እንደሚቀርብ ሰው አድርጎ ገልፆታል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስረኞችን ሰቆቃ በጥንቃቄ አድምጥና እርዳቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የሞት ልጆች
ይህ ሞት የተፈረደባቸውን ሰዎች የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እንዲሞቱ የተፈረደባቸው ሰዎች” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 79:12
ጌታ ሆይ፤... የተዘባበቱበት መዘባበት... አንተ መልስላቸው
አሳፍ የጎረቤት አገሮች በእስራኤል ላይ የሰሩት ክፉ ስራ እንደ “መዘባበት” እንደሆነና እነዚህ ስድቦች እንደ ቁሳቁሶች እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። እነዚህን ድርጊቶች እንዲቆጥርባቸው ጌታን ይጠይቃል፣ የጎረቤት አገሮች ስላደረጉት ሰለ እያንዳንዱ ድርጊት በእነዚህ የጎረቤት አገሮች ላይ ሌላ አካል አስነስቶ ሰባት እጥፍ ክፉ ስራ በእነርሱ ላይ እዲያደርግባቸው ጌታን ይጠይቃል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፈላቸው
“መልስላቸው” ወይም “መልሰህ ስጣቸው”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በጭናቸው ላይ
በተቀመጡበት በጉልበታቸውና በታፋቸው። ይህ “በቀጥታና በግለሰብ ደረጃ” ለመፈፀሙ ተለዋጭ ቀይቤ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እኛ ህዝብህ፣ የማሰማሪያ በጎችህ፣ ለዘላለም ምስጋና እናቀርብልሀለን
“በጎች” የሚለው ቃል እረኛ ለሚጠብቃቸውና ለሚመራቸው ረዳት አልባ ሰዎች ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ የምትጠብቀንና የምትመራን እኛ ህዝብህ ለዘላለም እናመሰግንሀለን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ምስጋናህን ለትውልድ ሁሉ እንናገራለን
“የሚመጣው ትውልድ በሙሉ የሰራኸውን መልካም ነገሮች በሙሉ እንዲያውቁ በእርግጠኝነት እናደርጋለን”
ምስጋናህን
ይህ ሰዎች ጌታን የሚያመሰግኑባቸው እርሱ የሰራቸው ነገሮችን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ስለ ሰራሀቸው ነገሮች አንተን ማመስገን እንዲቀጥሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 80

Psalms 80:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነ ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
የመዘምራን አለቃ
"ይህ የመዘምራን አለቃ ሆኖ አምልኮ የሚመራውን ያመለክታል። ይህ በመዝሙር 4፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
"የኪዳን ጽጌሬዳ" በሚለው ቅኝት የሚዜም
ይህ የዝማሬን ዐይነት ሊያመለክት ይችላል። ይህ በመዝሙር 45፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
የአሳፍ መዝሙር
"ይህ አሳፍ የጻፈው መዝሙር ነው።"ይህ በመዝሙር 50፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
የእስራኤል እረኛ
አሳፍ እግዚአብሔር እርሱ እስራኤልን እንደሚመራና እንደሚጠብቅ አድርጎ ይጠቅሳል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ዮሴፍን እንደ መንጋ የምትመራ
"ዮሴፍ" የሚለው ቃል የእስራኤልን ያመለክታል። አሳፍ ስለ ህዝቡ እነርሱ በጎቹ እንደሆኑ እና እረኛቸው የሆነው ያህዌ ደግሞ እንደሚጠብቃቸው አድርጎ ይናገራል። "እንደ በግ መንጋ የዮሴፍን ትውልድ የምትመራ ሆይ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዮሴፍ
እዚህ ስፍራ ዮሴፍ እስራኤልን ይወክላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በኪሩብ ላይ የምትቀመጥ ሆይ
ኪሩቤል በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት ብዙውን ጊዜ የቃል ኪዳኑ ታቦት፣ በላይ በሰማይ በዙፋኑ የተቀመጠው የያህዌ የእግሩ መቆሚያ እንደሆነ አድርገው ይናገራሉ። "በቃል ኪዳኑ ታቦት ከኩሩቤል በላይ በዙፋንህ የተቀመጥህ ሆይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
በላያችን አብራ
አሳፍ ስለ እግዚአብሔር እርሱ ብርሃንን የሚሰጣቸው ፀሐይ እንደሆነ እና ለመልካምነት ዘይቤ አድርጎ ይናገራል። "ብርሃን ስጠን" ወይም "የምንኖርበትን ትክክለኛ ህይወት አሳየን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ኃይልህን አንቀሳቅስ
"አንቀሳቅስ" የሚለው ሀረግ "ወደ ድርጊት አምጣው" የሚል ትርጉም አለው።
ፊትህን በእኛ ላይ አብራ
ጸሐፊው ያህዌ ለእነርሱ የሚያሳየውን ሞገስ ያህዌ በላያቸው ብርሃን እንዳበራ አድርጎ ይገልጸዋል። "ለእኛ ሞገስ ስጠን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኛም እንድናለን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። " እባክህ አድነን" ወይም "ስለሆነም ልታድነን ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 80:4

የአንተ ህዝብ
እስራኤል
የእንባ እንጀራ መገብካቸው፣ ብዙ እንባ ይጠጡ ዘንድ ሰጠሃቸው
"የእንባ እንጀራ" እና "ይጠጡ ዘንድ እንባ" የሚሉት ቃላት ለማያቋርጥ ሀዘን ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "ሁሉም በመከራ ውስጥ እንዲኖሩ አደረግህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Psalms 80:7

አጠቃላይ መረጃ፡
አሳፍ በእስራኤል ህዝብ ምትክ ተናገረ። በቁጥር 8 እግዚአብሔር፣ ሰው ምድርን መንጥሮ የወይን ተክልን እንደሚተክልባት ሁሉ እስራኤልን በምድራቸው የመሰረተበትን መንገድ መናገር ይጀምራል። የወይን ተክሉ ምሳሌ እስከ ቁጥር 16 ደረስ ይቀጥላል።
በላያችን አብራ
ጸሐፊው እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ሞገሱን እንዳደረገ የሚገልጸው ያህዌ በላያች እንዳበራ አድርጎ ነው። ይህ በመዝሙር 80፡3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በእኛ ላይ ሞገስህን አደረግህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኛም እንድናለን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ታድነናለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ የግብጽን ወይን ታመጣለህ
አሳፍ የእስራኤልን ህዝብ ወደ ሌላ ስፍራ ተወስዶ ሊተከል ከተዘጋጀ ወይን ጋር ያነጻጽራል። "አንተ እኛን፣ እንደ ወይን ከግብጽ አወጣኸን" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
አንተ ህዝብን አውጥተህ በሌላ ስፍራ ተከልክ
ዘማሪው ስለ ህዝቡ ያህዌ በሌላ ስፍራ ወስዶ እንደ ተከለው ተክል አድርጎ ይናገራል። "አንተ ህዝብን፣ ከምድራቸው አውጥተህ ለእኛ ሰጠኸን እናም ወይንህን በዚያ ተከልክን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ህዝብን አወጣህ
"አንተ ህዝብ ለቆ እንዲወጣ አስገደድክ"

Psalms 80:9

አጠቃላይ መረጃ፡
አሳፍ ስለ እስራኤል በምድራቸው የወይን እርሻ ውስጥ እንዳለ የወይን ተክል አድርጎ እስራኤልን መናገሩን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሩን መነጠርክለት
"ምድሩን ለወይን መነጠርክ"
ስር ሰደደ
"ወይኑ ስር ሰደደ" ወይም "የወይን ለክሉ ማደግ ጀመረ"
ምድሩን ሞላ
"ቅርንጫፉ ምድሩን ሸፈነ
ተራሮች በጥላዎቿ የእግዚአብሔር ዝግባ በቅርንጫፎቿ ተሸፍነው ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጥላዎቿ ተራሮችን፣ ቅርንጫፎቿ የእግዚአብሔርን ዝግባ ሸፈኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔርን ዝግባዎች በቅርንጫፎቿ
"እግዚአብሔር ዝግባዎች በቅርንጫፎቿ ተሸፍነው ነበር፣" ግሱ የተወሰደው ከቀደመው ዐረፍተ- ነገር ነው።ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ቅርንጫፎቿ የእግዚአብሔርን ዝግባ ሸፈነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ዝግባ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ረጃጅሙ የዝግባ ዛፎች፣" ከእስራኤል በስተሰሜን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በሊባኖስ ምድር "በተራሮች" ላይ ያደጉ የዝግባ ዛፎች፣ ወይም 2) "የእግዚአብሔር የራሱ የዝግባ ዛፎች"
ባህሩ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ረጃጅሙ የዝግባ ዛፎች፣" ከእስራኤል በስተሰሜን በሊባኖስ ምድር "በተራሮች" ላይ ያደጉ የዝግባ ዛፎች፣ ወይም 2) "የእግዚአብሔር የራሱ የዝግባ ዛፎች"
ባህሩ
ከእስራኤል ምዕራብ የሜድትራንያን ባህር
ቡቃያ
ከምድር መብቀል የጀመረ የአዲስ የተክል ክፍል
Psalms 80:12
አጠቃላይ መረጃ፡
አሳፍ ስለ እስራኤል በምድራቸው የወይን እርሻ ውስጥ እንዳለ የወይን ተክል አድርጎ እስራኤልን መናገሩን ቀጥሏል።
ቅጥሯ
የድንጋይ ቅጥር፣ የእንጨት አይደለም
ከርከሮዎች
x
Psalms 80:14
አጠቃላይ መረጃ፡
አሳፍ ስለ እስራኤል በምድራቸው የወይን እርሻ ውስጥ እንዳለ የወይን ተክል አድርጎ እስራኤልን መናገሩን ጨረሰ።
ወደኋላ ዙር/ተመለስ
ጸሐፊው እግዚአብሔር ይረዳው ዘንድ ዘወር እንዲልለት ይፈልጋል። ይህ ይበልጥ ግለጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ወደ እኛ ዘወር በል" ወይም "ዳግም ወደ እኛ መጥተህ እርዳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እይ
"ተመልከት"
ይህ ወይን
ጸሐፊው እስራኤልን ከወይን ተክል ጋር ማነጻጸሩን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቀኝ እጅህ የተከላት ስር ይህች ናት
ቀኝ እጅ የሚወክለው የያህዌን ሀይል እና መቆጣጠር ነው። "ይህች አንተ ያህዌ የተከልካት ስር ናት" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ቡቃያ
ከምድር መብቀል የጀመረ የአዲስ የተክል ክፍል። ይህ በመዝሙር 80፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ወደቁ፤ ከግሳጼህ የተነሳ ጠፉ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ወደቁ፤ ከግሳጼህ የተነሳ ህዝብህ ጠፉ።" ወይም 2) "ወደቁ። ከግሳጼህ የተነሳ ጠላቶችህ ይጥፉ!"
Psalms 80:17
የአንተ እጅ
ይህ የያህዌን ሀይል እና መቆጣጠር ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የቀኝ እጅህ ሰው
ያህዌ የራሱ አድርጎ የመረጠው፣ የእስራኤል ህዝብ። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀኝ እጅ
በእስራኤል አንድ ሰው ሌላውን ማክበር ሲፈልግ፣ ያሰው ወደ ቀኝ እጁ ተጠግቶ በቀኙ በኩል እንዲቆም ያደርጋል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከአንተ ዘወር አንልም
እዚህ ስፍራ "ዞር ማለት" የሚለው አንድን ሰው ላለመቀበል ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ይህ በአዎንታዊ መልክም ሊገለጽ ይችላል። "አንተን መታዘዝ እና ማምለክ አናቆምም" ወይም "እኛ ሁልጊዜም አንተን እናመልካለን እንታዘዛለንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 80:19
በላያችን አብራ
ጸሐፊው ያህዌ ለእነርሱ ሞገስ መስጠቱን የሚገልጸው የያህዌ ፊት በላያቸው ብርሃን እንዳበራ አድርጎ ነው። ይህ በመዝሙር 80፡3 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በእኛ ላይ ሞገስህ አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኛም እንድናለን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ታድነናለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 81
Psalms 81:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነ ግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ፡
የአሳፍ መዝሙር።
ለመዘምራን አለቃ
"ይህ በመዘምራን አለቃ ለአምልኮ የሚዜም ነው"
ጊተት በሚባል (ዋሽንተ መሰል) የሙዚቃ መሳሪያ የሚቀርብ
ይህ ምናልባት የሙዚቃን/ዝማሬን አይነት ያመለክት ይሆናል። በመዝሙር 8፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
የአሳፍ መዝሙር
"ይህ አሳፍ የጻፈው ዝማሬ ነው"
እግዚአብሔር ሀይላችን
"ሀይል/ጥንካሬ" የሚለው ረቂቅ ስም "ጠንካራ" በሚል ሊገለጽ ይችላል። "እንድንጠነክር የሚያስችለን እግዚአብሔር/ እግዚአብሔር ሀይላችን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የያዕቆብ አምላክ
እዚህ ስፍራ "ያዕቆብ" የሚወክለው ትውልዶቹን ሁሉ ነው። "የእስራኤል አምላክ፣ የያዕቆብ ትውልድ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ደስ የሚያሰኘውን ድምጽ በበገና እና በታምቡሪኒ/ከበሮ መሰል መሳሪያ/ አሰሙ
በገና እና ከበሮ መሰል የሙዚቃ መሳሪያ/ታምቡሪኒ/ የሙዚቃ መሳሪያ ናቸው
ታምቡሪኒ/ከበሮ መሰል የሙዚቃ መሳሪያ
እናቱ ከበሮ የሚመስል የምት መሳሪያሲሆን በዚሪያው ያሉ ቁርጥራጭ ብረቶች እየተርገፈገፉ ድምጽ የሚሰጥ የሙዚቃ መሳሪያ። (የማይታወቀውን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
አዲስ ጨረቃ
ይህ የጨረቃ ወር መጀመሪያ ነው
የሙሉ ጨረቃ ቀን
ይህ የጨረቃ ወር አጋማሽ ነው
የክብረ በዓላችን ዕለት ሲጀምር
"ክብረ በዓላችን በመጀምርበት ቀን"
Psalms 81:4
ለዚህ
እዚህ ስፍራ "ይህ" የሚለው የሚያመለክተው የክብረ በዓሉን ቀን ነው።
በያዕቆብ አምላክ የተሰጠ ሥርዐት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የያዕቆብ አምላክ ይህን ሥርዐት ሰጠ" ወይም "የያዕቆብ አምላክ ይህን አዘዘ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የያዕቆብ አምላክ
እዚህ ስፍራ "ያዕቆብ የሚወክለው ትውልዱን ሁሉ ነው። "የእስራኤል አምላክ፣ የያዕቆብ ትውልድ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ከግብጽ ምድር ለቆ በወጣ ጊዜ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤል ህዝብ ባሪያ ከነበሩበት ከግብጽ ምድር እግዚአብሔር ነጻ ያወጣቸውን ታሪካዊ ወቅት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የግብጽ ምድር
እዚህ ስፍራ "ምድር"የሚወክለው ህዝቡን ነው። "የግብጽ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 81:6
አጠቃላይ መረጃ፡
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር መናገር ይጀምራል።
ከጫንቃው ሸክሙን አስወገደ
እዚህ ስፍራ "ከጫንቃው ሸክሙን" የሚለው የሚወክለው አስራኤላውያን በግብጽ ውስጥ በባርነት በነበሩበት ጊዜ ይሰሩት የነበረውን የግዴታ ስራ ነው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
እጆቹ ቅርጫት ከመሸከም ነጻ ወጡ
እዚህ ስፍራ "ቅርጫት መሸከም" የሚለው የሚወክለው አስራኤላውያን በግብጽ ውስጥ በባርነት በነበሩበት ጊዜ ይሰሩት የነበረውን የግዴታ ስራ ነው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በጭንቀትህ
"በታላቁ መከራህ"
በጨለማና ነጎድጓዳማ ደመና ውስጥ ለጥያቄህ መልስ ሰጠሁህ
እግዚአብሔር ወደ እስራኤላውያን ሲመጣ፣ ሙሉ መገኘቱን እና ክብሩን፣ በጨለማ እና አስፈሪ ደመና ውስጥ ይሰውራል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በመሪባ ውኆች ፈተንኩህ
እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች በመሪባ በረሃ ውሃ እንደሚሰጣቸው ያምኑ እንደሆነ ለማየት ፈተናቸው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 81:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ህዝቡን በበረሃ በነበሩ ጊዜ የተናገራቸውን አስታወሳቸው።
እኔ የማስጠነቀቅህ
"ማስጠንቀቂያ የምሰጥህ"
እስራኤል
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው የሚወክለው የእስራኤልን ህዝብ ነው። "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እኔን ብቻ ብትሰማኝ!
"እኔን ብትሰማኝ እንዴት በወደድኩ" ወይም "ነገር ግን እኔን መስማት መጀመር ይኖርብሃል!"
አፍህን በሰፊው ክፈት፣ እኔም እሞላዋለሁ
እግዚአብሔር የህዝቡን ፍላጎት ሁሉ እንደሚያሟላ የተገለጸው እንዴት እናት ወፍ ጫጩቶቿን በምትመግብበት ሁኔታ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 81:11
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ህዝቡን ካስጠነቀቀ በኋላ በእርግጥ የሆነውን ተናገረ
በእኔ ቃሎች
"እኔ እንደ ተናገርኩት" ወይም "በእኔ"
ለራሳቸው ግትር መንገድ/ደንዳናነት አሳልፎ ሰጠኋቸው
እግዚአብሔር ህዝቡን ለደንዳናነቱ እንዲቆይ መፍቀዱ የተገለጸው ጠላት እነርሱን እንዲጎዳቸው አሳልፎ እንደመስጠት ተደርጎ ነው። "ስለዚህ፣ ለደንዳናው ልባቸው አሳላፌ ሰጠኋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 81:13
አወይ፣ ምነው ይህ ህዝቤ በመንገዶቼ ቢሄድ
እግዚአብሔር ህዝቡ እርሱን እንዲታዘዘው መፈለጉ የተገለጸው፣ ህዝቡ በእርሱ መንገድ ወይም ጎዳና እንዲሄድ እርሱ እንደሚፈልግ ተደርጎ ነው። "እነርሱ ለህጎቼን እንዲጠብቁ እሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እጄን በእነርሱ ላይ እነሳሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው የያህዌን ሀይል ነው። "እኔ እጠፋለሁ" ወይም "እኔ አሸንፋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 81:15
ያህዌን የሚጠሉ... ከእኔ አስቀድሞ
ያህዌ ስለ እረሱ በሶስተኛ መደብ ይናገራል። "እኔን የሚጠሉ...ከእኔ አስቀድሞ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
በፍርሃት መሸማቀቅ
"በፍርሃት መጎንበስ" ወይም "በፍርሃት መውደቅ"
ለዘለዓለም የተዋረዱ ይሁኑ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ እነርሱን ለዘለዓለም አዋርዳቸዋለሁ" ወይም "እኔ እነርሱን ለዘለዓለም እቀጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ እስራኤልን ምርጥ የሆነውን ስንዴ እመግበዋለሁ
እግዚአብሔር ምርጥ የሆነው ስንዴ በእስራኤል እንዲበቅል ማድረጉ የተገለጸው እርሱ ስንዴውን በቀጥታ ለህዝቡ እንደሚያበላ ተደርጎ ነው። "እኔ እስራኤላውያን ምርጥ የሆነውን ስንዴ እንዲመገቡ አደርጋለሁ"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እስራኤልን መመገብ...እናንተን ማርካት
"እስራኤል" እና "እናንተ" የሚሉት ሁለቱም የሚያመለክቱት እስራኤላውያንን ነው።
ከዓለቱ ውስጥ ማር
ይህ የጫካ ማርን ያመለክታል። ንቦች በዓለት ውስጥ በሚገኙ ቀዳዶች ቀፎ ሰርተው በዚያ ስፍራ ማር ያበጃሉ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 82
Psalms 82:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው
የአሳፍ መዝሙር
"ይህ አሳፍ የጻፈው ዝማሬ ነው"
መለኮታዊ ጉባኤ
"ሰማያዊው ምክር ቤት" ወይም "በሰማይ የተደረገ ስብሰባ"
እርሱ ፍርድ አደረገ
"እርሱ ፍርድ ሰጠ።" "ፍርድ" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ ፈረደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
አማልዕክት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እነዚህ በሰማይ የሚኖሩ ሌሎች መንፈሳዊ አካላት ናቸው። "መለኮታዊ አካላት" ወይም "ሰማያዊ ፈራጆች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፤ ወይም 2) እነዚህ እግዚአብሔር ለዳኝነት የሾማቸው ሰዎች ናቸው። በማንኛውም መንገድ ቢሆን፣ ያህዌ አምላክ እንደሆነው ያሉ አማልዕክት ናቸው ማለት አይደለም። የዚህ ትርጉም እግዚአብሔር ታላቅ ስልጣን እና ሀይል ሰጥቷቸዋል ማለት ነው። "መሪዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
እስከ መቼ ያለ ቅንነት ትፈርዳላችሁ፣ እስከ መቼስ ለክፉዎች ታደላላችሁ?
ያህዌ ጥያቄውን የተጠቀመበት ዳኞች ለህዝቡ በቅንነት ባለመፍረዳቸው ለመውቀስ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 82:3
ድሆች እና አባት የሌላቸው
እዚህ ስፍራ "ድሃ" እና "አባት የሌለው" የሚሉት ስማዊ ቅጽሎች ናቸው። በቅጽል መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። "ድሆች የሆኑ እና ወላጅ የሌላቸው" በሚለው ውስጥ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
የ…መብት ጠብቁ
"ለ…ትክክል የሆነውን አድር/ ለ…በጽድቅ ፍረዱ
የተጠቁ እና ምስኪኖች
እዚህ ስፍራ "የተጠቁ" እና "ምስኪኖች" የሚሉት ስማዊ ቅጽሎች ናቸው። በቅጽል ሊገለጹ ይችላሉ። "መከራ የሚቀበሉ እና አንዳች ነገር የሌላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ድሆች እና እረዳታ የሚሹ… ክፉዎች
እነዚህ ስማዊ ቅጽሎች ናቸው። እንደ ቅጽል ሊገለጹ ይችላሉ። "ድሆች እና እርዳታ ፈላጊ የሆኑ… ክፉ የሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱን ከክፉዎች እጅ አድኗቸው
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ወይም መቆጣጠርን ይወክወላል። "ክፉ ሰዎች እነርሱን ማጥቃታቸውን ከልክሉ/አስቁሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 82:5
እነርሱም የላቸውም
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እነርሱ" የሚለው አማልዕክትን ያመለክታል፤ ወይም 2) "እነርሱ" የሚለው ክፉ ሰዎችን ያመለክታል።
በጨለማ ውስጥ ይመላለሳሉ
ክፉ ነገር ማድረግ የተገለጸው በጣም ጨለማ በሆነ ስፍራ እንደሚመላለሱ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የምድር መሰረቶች ሁሉ ተናወጡ
ያህዌ የመሰረተውን የሞራል ስርዓትን የጣሱ ዳኞች የተገለጹት አማልዕክት ምድርን እንዳናወጡ እና ምድር እንደፈራረሰች ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ተናወጠ
ፈራረሰ
Psalms 82:6
እናንተ አማልዕክት ናችሁ፣ እናንተ ሁላችሁም የልዑሉ ወንዶች ልጆች ናችሁ
እዚህ ስፍራ "አማልዕክት" የሚለው የሚያመለክተው በመዝሙር 82፡1 ላይ የሚገኙትን እነዚያኑ ወገኖች ነው። ይህ የሚያመለክተው መንፈሳዊ ፍጥረቶችንም ሆነ ሰዎችን፣ ያህዌ እንደሆነ ያሉ አምላክ አይደሉም። ቃል በቃል የእርሱ ወንዶች ልጆች ናቸው ማለትም አይደለም። "አማልዕክት" እና "የልዑሉ ወንዶች ልጆች" ብሎ በመጥራት ያህዌ ለእነርሱ ትልቅ ሀይል እና ስልጣን መስጠቱን ያረጋግጣል።
የልዑሉ ወንዶች ልጆች
ያህዌ ስለ እራሱ "ልዑሉ/ እጅግ ከፍ ያለው" በማለት ይገልጻል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
የሆነ ሆኖ እናንተ
"ሆኖም እናንተም"
ትወድቃላችሁ
ይህ ሰው የሚሞት መሆኑ የሚገለጽበት መንገድ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 82:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው ዳግም ይናገራል
በምድሪቱ ላይ መፍረድ
እዚህ ስፍራ "ምድር" ህዝቡን ይወክላል። "በምድሪቱ ህዝብ ላይ ፍረድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ በምድር ወገኖች ላይ ሁሉ ርስት አለህና
"የምድር ወገኖች ሁሉ የአንተ ርስት ናቸውና።" ያህዌ ህዝብን በሙሉ የራሱ አድርጎ ይወስዳል ደግሞም በእነርሱ ላይ መግዛት የተገለጸው ህዝቦች ሁሉ የእርሱ የሚገዛቸው ሀብቱ ተደርገው ነው። "አንተ በአገራት ሁሉ ህዝብ ላይ ትገዛለህና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አገራት ሁሉ
እዚህ ስፍራ "አገራት" የሚለው የሚወክለው የአገራትን ህዝብ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 83
Psalms 83:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ዝማሬ። የአሳፍ ዝማሬ
"ይህ አሳፍ የጻፈው ዝማሬ ነው"
ጸንቶ/በዝምታ መቆየት
"እኛን ለመርዳት አንዳች አለማድረግ"
እነሆ፣ ጠላቶችህ ሁከት እየፈጠሩ ነው
እዚህ ስፍራ "ሁከት መፍጠር" ማለት እነርሱ አመጽ እያስነሱ እና በእግዚአብሔር ላይ እያመጹ ነው ማለት ነው። "እነሆ፣ ጠላቶችህ በአንተ ላይ አምጸዋል"
አንተን የሚጠሉ ራሳቸውን ቀና እያደረጉ ነው
"እራሳቸውን ቀና እያደረጉ" የሚለው ሀረግ በእግዚአብሔር ላይ እያመጹ ነው የሚለው መገለጫ ነው። "አንተን የሚጠሉ አንተን እየተቃወሙ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 83:3
በአንተ የተጠበቁ
"አንተ የጠበቅካቸው" ይህ እስራኤላውያንን ያመለክታል።
ከአንግዲህ የእስራኤላውያን ስም አይታወስም
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው የአንድን ሰው ክብር ወይም መታሰቢያ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም ከእንግዲህ የእስራኤላውያንን የቀድሞ ህልውና አያስታውስም" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
እነርሱ በአንድ ላይ በአንድ ሀሳብ አመጹ
"ጠላቶችህ በአንድ እቅድ ተስማሙ"
በአንተ ላይ በአንድነት ተስማምተው ተነሱ
"አንተን ለመቃወም ህብረት አደረጉ"
Psalms 83:6
አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው እስራኤልን ለማጥፋት የሚፈልጉ ወገኖችን መዘርዘሩን ይቀጥላል።
የኤዶም ድንኳኖች
ይህ የሚያመለክተው በድንኳን የሚኖሩ የኤዶም ሰዎችን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አጋራውያን
ይህ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምስራቅ የሚኖሩ የህዝብ ወገኖች ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ጌባል፣ አሞን፣ አማሌቅ…ፍልስጥኤም
እነዚህ ሁሉ የሚወክሉት የእያንዳንዱን አካባቢ ሰዎች ወይም ነገድ ነው። "የጌባል ሰዎች፣ አሞናውያን፣ አማሌቃውያን…ፍልስጥኤማውያን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ጌባል
ይህ ከሙት ባህር በስተ ደቡብ የሚገኝ አካባቢ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 83:8
አሦር
ይህ የአሦር ህዝብን ይወክላል። "የአሦር ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የሎጥ ትውልድ
ይህ የሞዓብንና የአሞንን አገር ሰዎች ያመለክታል። መረጃውን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ትችላላችሁ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 83:9

በእነርሱ ላይ አድርግ…በምድሪቱ

ጸሐፊው እግዚአብሔርን የእስራኤልን ጠላቶች በቀድሞ ጊዜ እንዳደረገው ድል እንዲያደርጋቸው ይጠይቃል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድያማውያን ላይ እንዳደረግኸው

እዚህ ስፍራ "ምድያም" የሚለው የሚወክለው የምድያምን ሰዎች ነው። "በምድያም ላይ እንዳደረግከም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሲሳራ…ኢያቢስ

እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። ኢያቢስ የሔሬብ ንጉሥ ነው። ሲሳራ የኢያቢስ ጦር አዛዥ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የቂሶን ወንዝ

ይህ በሰሜን እስራኤል የሚገኝ ወንዝ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዐይንዶር

ይህ በሰሜን እስራኤል የሚገኝ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምድር እንደ ፍግ ይሆናሉ

ይህ ማለት የሲሳራ እና ኢያቢስ በድኖች ሳይቀበሩ በሜዳ ወድቀው ይቀራሉ ማለት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 83:11

አጠቃላይ መረጃ:

ጸሐፊው ወደ እግዚአብሔር ባለፉት እርሱ ድል ያደረጋቸውን ሌሎች ጠላቶቻቸውን ማስታወሱን ይቀጥላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሔሬብ…ዜብ…ዛብሄል…ስልማና

እነዚህ ሁሉ የነገሥታት ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እንዲህ አሉ

እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ሔሬብ፣ ዜብ፣ ዛብሄል እና ስልማን ነው።

የእግዚአብሔር የግጦሽ ስፍራ

ይህ የሚናገረው የእስራኤል ምድር በጎች የሚሰማሩበት የግጦሽ ስፍራ በማድረግ እና እግዚአብሔር በዚያ ላይ እረኛ እንደሆነ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 83:13

አጠቃላይ መረጃ:

ጸሐፊው እግዚአብሔር የእስራኤልን ጠላቶች በጠቅላላ ማጥፋቱን ለመግለጽ ተነጻጻሪ ዘይቤን ይጠቀማል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዐውሎ ነፋስ እንደሚነዳ ትቢያ፣ በነፋስ ፊት እንዳለ ገለባ አድርጋቸው

ሁለቱም ሀሳቦች ስለ እግዚአብሔር ጠላቶቹን እርሱ አውሎ ነፋስ እንደሆነ እና እነርሱን በቀላሉ እንደሚጠርጋቸው ይገልጻሉ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጫካን እንደሚያቃጥል እሳት፣ እና ተራሮችን እንደሚያነድ እሳት

ሁለቱም ሀሳቦች የእግዚአብሔር ቅጣት እሳት እንደሆነ እና የእግዚአብሔርን ጠላቶች ደግሞ በእሳቱ እንደሚቃጠሉ ነገሮች አድርገው ይናገራሉ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

በዐውሎ ነፋስህ አባራቸው፣ በማዕበልህ አስደንግጣቸው

ሁለቱም ሀሳቦች እግዚአብሔር ጠላቶቹን በማዕበሎች እንዲያጠፋቸው ይጠጥቃሉ።(ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Psalms 83:16

ፊታቸውን በሀፍረት ሙላው

እዚህ ስፍራ "ፊት" የሚወክለው ማለውን ማንነት/ሰው ነው።"በጣም አሳፍራቸው" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ስምህን ይፈልጉ ይሆናል

እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው የእግዚአብሔርን ሀይል ነው። የእግዚአብሔር ጠላቶች እግዚአብሔር ሀያል ለመሆኑ እውቅና እንደሚሰጡ የተገለጸው ያህዌን ለማግኘት እንደሚፈልጉ ተደርጎ ነው። "አንተ ሀያል መሆንህን እውቅና ይሰጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ስምህን ይፈልጉ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የእግዚአብሔር ጠላቶች እግዚአብሔር ሀያል መሆኑን አምነው ተቀበሉ፤ ወይም 2) የእግዚአብሔር ጠላቶች እግዚአብሔርን እርዳታ ይለምናሉ፤ ወይም 3) የእግዚአብሔር ጠላቶች እርሱን ማምለክ እና መታዘዝ ይጀምራሉ።

እነርሱ ይፈሩ ለዘለዓለምም ይንቀጥቀጡ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እንዲያፍሩ እና ለዘለዓለም እንዲፈሩ አድርጋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሀፍረትም ይጥፉ

"በሀፍረታቸው ይወገዱ/ይሙቱ)

Psalms 83:18

ከዚያም እነርሱ ያውቃሉ

ይህ ጸሐፊው ለእግዚአብሔር ልመና በሚያቀርብበት ጊዜም ሊገለጽ ይችላል። "እንዲረዱ አድርጋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እጅግ ከፍ ያለው በምድር ላይ ነው

እግዚአብሔር በምድር ላይ የሁሉም ገዢ መሆኑ የተገለጸው እርሱ ከማንኛውም ነገር በላይ ከፍ ብሎ እንደሚገኝ ተደርጎ ነው። " ከፍ ያልክ፣በምድር ላይ የሚገኙ ነገሮችን ሁሉ የምትገዛ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 84

Psalms 84:1

አጠቃላይ መረጃ:

ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለመዘምራን አለቃ

"ይህ ለመዘምራን መሪ በአምልኮ ጊዜ የሚውል ነው"

ጊተት በሚባል (ዋሽንት መሰል) የሙዚቃ መሳሪያ የሚቀርብ

ይህ ምናልባት የሙዚቃን/ዝማሬን አይነት ያመለክት ይሆናል። በመዝሙር 8:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

የቆሬ ልጆች መዝሙር

"ይህ የቆሬ ልጆች የጻፏቸው መዝሙሮች ናቸው"

እንዴት የተወደደ

"እንዴት ውብ"

የያህዌን አደባባይ እጠብቃለሁ

"በያህዌ አደባባይ መሆን እፈልጋለሁ"

የያህዌ አደባባይ

እዚህ ስፍራ "አደባባይ" የሚወክለው ቤተ መቅደስን ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ለዚህ ያለኝ ጥበቃ አጓጉቶኛል

"በጉጉት ዝያለሁ" ወይም "ይህን እጅግ ከመፈለጌ የተነሳ ደክሜያለሁ"

ልቤ እና ጠቅላላው ማንነቴ ይጣራሉ

እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው ጠቅላላ ስብዕናን ነው። "በመላው ማንነቴ ፈለግሁ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ህያው አምላክ

ይህ ማለት እግዚአብሔር ህያው ነው፣ ደግሞም እርሱ ሌሎች ነገሮች ሁሉ እንዲኖሩ የማድረግ ሀይል አለው።

Psalms 84:3

ድንቢጥ…ዋኖስ

እነዚህ የወፍ አይነቶች ናቸው። (የማይታወቀውን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እርሷ ማረፊያ/ማኖሪያ አገኘች

"ቤት አገኘች" ወይም "ቤት ሰራች"

የድንቢጥ ቤት

እዚህ ስፍራ "አገኘች" ወይም "ሰራች" የሚሉት ቃላት ባይጠቀሱም የታወቁ ናቸው። "ድንቢጥ እንኳን ቤቷን አገኘች" ወይም "ድንቢጥ እንኳን ቤቷን ሰራች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

ጫጩቶቿን የምኖርበት

"እንቁላልዋን የምትጥልበት እና ጫጩቶቿን የምትንከባከብበት"

እነርሱ በአንተ ቤት የሚኖሩ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እነርሱ" የሚለው ቤተመቅደሱን በቋሚነት የሚያገለግሉ ካህናትን ያመለክታል፤ ወይም 2) "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው በቤተ መቀደሱ መጥተው የሚያመልኩ ሰዎችን በአጠቃላይ ነው።

ሳያቋርጡ አንተን ያወድሳሉ

"አንተን ደግመው ደጋግመው ማወደሳቸውን ይቀጥላሉ"

Psalms 84:5

የተባረከ ሰው ነው

እዚህ ስፍራ "ሰው" የሚያመለክተው በአጠቃላይ ሰዎችን ነው። (የስማዊ ሀረግ ክፍል እና ወንዴ መጠሪያ/ቃላት ሴቶችን ሲያካለትት የሚለውን መልከቱ)

አንተ ብርታታቸው የሆንክ

ስለ እግዚአብሔር የተነገረው ሀይል በእርሱ እንደሚገኝ ተደርጎ ነው። "አንተ ያበረታሃቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የጽዮን መንገዶች በማን ልብ ይገኛል

ይህ አገላለጽ ልባዊ ምኞትን ያመለክታል። "እስከ ጽዮን መድረስ የሚወዱ" ወይም "በእውነት እስከ ጽዮን መድረስ የሚፈልጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጎዳና

በዙሪያው ከሚገኘው መሬት ከፍ ብለው የተገነቡ መንገዶች

እስከ ጽዮን ድረስ

ቤተመቅደሱ የሚገኘው ጽዮን ተብሎ በሚጠራው በእየሩሳሌም በሚገኘው ከሁሉም ከፍ ባለው ኮረብታ ላይ ነበር

የእንባ ሸለቆ

ይህ የሚያመለክተው ደረቅ እና የማይታረስ ስፍራን ነው። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅጂዎች "የባካ ሸለቆ" የሚል ይጨምራሉ። "ባካ" ማለት "ለቅሶ" ማለት ነው።

የመጀመሪያ/ቀዳሚ ዝናብ

ይህ ማለት ከክረምቱ አስቀድሞ በበልግ የሚዘንበው ዝናብ ማለት ነው። ይህም በምዕራባውያን የወር አቆጣጠር በጥቅምት እና ህዳር ወራት ማለት ነው።

በረከቶች

እዚህ ስፍራ "በረከቶች" የሚለው ቃል በደረቅ ምድር የሚኖሩ ሰዎችን ደስተኛ ለሚያደርግ የኩሬ ውሃ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እነርሱን ደስ የሚያሰኝ የኩሬ ውሃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ([[rc://*/ta/vo12/translate/figs-metonomy]]) ይመልከቱ።

Psalms 84:7

ከሀይል ወደ ሀይል ይሄዳሉ

ይህ እየበረቱ ይሄዳሉ የሚለው የሚገለጽበት መንገድ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይሄዳሉ

እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ቤተመቅደስ ለመሄድ ብርቱ ፍላጎት ያላቸውን ነው።

ሴላ

ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር፣ ከጋሻችን በላይ ይመለከታል

ህዝቡን የሚጠብቀው ንጉሥ የተገለጸው ጋሻ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "እግዚአብሔር ከንጉሣችን በላይ ይመለከታል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ አደባባዮች ለአንድ ቀን መሆንበሌላ ስፍራ ሺህ ቀን ከመኖር ይሻላል

ይህ በሚታወቅ መረጃ ሊገጽ ይችላል። "በሌላ ስፍራ ለሺህ ቀናት ከመሆን በአንተ አደባባዮች ለአንድ ቀን መሆን ይሻለኛል" (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሺህ

"1,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ዘብ ጠባቂ መሆን

"በበር ላይ ጠባቂ መሆን" ወይም "በር ላይ መቆም"

ክፉዎች

ይህ ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "ክፉ ሰዎች" ወይም "ክፉ የሆኑ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 84:11

ያህዌ አምላክ ፀሐያችን እና ጋሻችን ነው

ህዝቡን የሚጠብቀው እና የሚመራው ያህዌ የተገለጸው ፀሐይ እና ጋሻ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "ያህዌ አምላክ ከፀሐይ እንደሚወጣ ብርሃን ይመራናል፣ ደግሞም እንደ ጋሻ ሆኖ ይጠብቀናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ጸጋ እና ክብር ይሰጣል

"ጸጋ" እና "ክብር" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በግሥ ሊገለጹ ይችላሉ። "ያህዌ ለእኛ መልካም ይሆንልናል ደግሞም ያከብረናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በቅንነት የሚራመድ

አንድ ሰው ህይወቱን የሚመራበት መንገድ ወይም ድርጊቱ የተገለጸው ያ ሰው እንደሚራመድ ተደርጎ ነው። "በሀቀኝነት የሚኖር" ወይም "ሀቀኛ የሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የተባረከ ሰው ነው

እዚህ ስፍራ "ሰው" የሚያመለክተው በአጠቃላይ ሰዎችን ነው። (የስማዊ ሀረግ ክፍል እና ወንዴ መጠሪያ/ቃላት ሴቶችን ሲያካለትት የሚለውን መልከቱ)

---

Chapter 85

Psalms 85:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የመዘምራን አለቃ

"ይህ የመዘምራን አለቃ ሆኖ አምልኮ የሚመራውን ያመለክታል።

የቆሬ ልጆች መዝሙር

"ይህ የቆሬ ልጆች የጻፏቸው መዝሙሮች ናቸው"

አንተ ለምድርህ ሞገስ ሰጠህ

እዚህ ስፍራ "ምድር" የሚወክለው የእስራኤልን አገር እና ህዝብ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ደህንነት

ይህ የሚያመለክተው የአንድን ሰው ደስተኛ መሆን፣ ጤንነት እና ብልጽግና ነው።

የያዕቆብ

እዚህ ስፍራ "ያዕቆብ" የሚወክለው የያዕቆብን ትውልድ፣ እስራኤላውያንን ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ኃጢአታቸውን ሁሉ ከደንክ

እዚህ ስፍራ የኃጢአት ይቅርታ የተነገረው እንዳይታይ የተሸፈነ ተደርጎ ነው። "አንተ እያወቅህ ኃጢአታቸውን ረሳህላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱን ኃጢአት

ይህ ጸሐፊ ስለ ራሱ የእግዚአብሔር ህዝብ ወገን አድርጎ ያስባል። "የእኛ ኃጢአት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ሴላ

ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 85:3
ቁጣህን ሁሉ አስቀረህ
ከእንግዲህ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ቁጣው እንደማይቀጥል የተገለጸው፣ ቁጣ እሳት እንደሆነ እናእግዚአብሔር ከዚያ ፊቱን እንደመለ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የደህንነታችን አምላክ
"ደህንነት" የሚለው ረቂቅ ስም በግሥ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ያዳነን እግዚአብሔር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
በእኛ ደስ አለመሰኘትህ ያብቃ
እግዚአብሔር በእስራኤላውያን መቆጣቱ እንዲያበቃ መለመኑ የተገለጸው፣ ጸሐፊው ደስ አለመሰኘትን እግዚአብሔር እንዲወስደው የሚፈልገው ቁስ አካል እንደሆነ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ በእኛ ላይ ለዘለዓለም ትቆጣለህን? ቁጣህ በሚቀጥለውም ትውለድ ዘመን ውስጥ ሁሉ ይቀጥላልን?
ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ መቆጣቱ እንዲያበቃ እየለመነ መሆኑን ለማጉላት ነው። እነዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጉሙ ይችላሉ። "እባክህ በእኛ ላይ ለዘለዓለም አትቆጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 85:6
ዳግም አታድሰንምን?
ጸሐፊው ጥያቄውን ያዋለው የእስራኤልን ህዝብ ለማበልጸግ እና ዳግም ደስተኛ ለማድረግ ወደ እግዚአብሔር ለሚያቀርበውን ጥያቄ ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እባክህ ዳግም ባለጸጎች አድርገን።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የቃል ኪዳንህን ታማኝነት አሳየን
ዐረፍተ ነገሩ እንደገና ቢጻፍ፣ "የቃል ኪዳን ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም ሀሳብ "ለአንተ ቃል ኪዳን ታማኝ መሆን" በሚለው ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተን ማዳን አረጋግጥልን
ይህ ጸሐፊው እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለውን ታማኝነት እንዲያሳይ የፈለገው እንደዚህ ነው። ዐረፍተ ነገሩ እንደገና ቢጻፍ፣ "ደህንነት" በሚለው ረቂቅ ስም ውስጥ የሚገኘው ሀሳብ "ዳነ" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እናም አድነን" ወይም "እኛን በማዳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 85:8
እርሱ ከህዝቡ ጋር ሰላም አደረገ
"ከህዝቡ ጋር ሰላማዊ ግንኙነት ይኑር" ወይም "ለህዝቡ ሰላም አመጣ"
ሆኖም ወደ ጥፋት መንገዳቸው ዳግም መዞር የለባቸውም
የአንድ ሰው የቀድሞ መንገዱን መቀየር የተገለጸው ሰውየው በአካል ወደ ሌላ አቅጣጫ እንደዞረ ተደርጎ ነው። "ሆኖም እነርሱ ዳግም ጥፋት መስራት መጀመር የለባቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእርግጥ የእርሱ ማዳን ለእነርሱ ቅርብ ነው
እግዚአብሔር ለማዳን ዝግጁ መሆኑ የተገለጸው ደህንነት እግዚአብሔር በአንደ ሰው አጠገብ ያስቀመጠው ቁስ አካል እንደሆነ ተደርጎ ነው። "በእርግጥ እግዚአብሔር እነርሱን ለማዳን ዝግጁ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያም ክብር በምድራችን ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ክብር" የሚወክለው የእግዚአብሔርን መገኘት ነው። "ከዚያም የክብሩ መገኘት በምድራችን ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 85:10
የቃል ኪዳን ታማኝነት እና እምነት የሚጣልበት የመሆን አስፈላጊነት በአንድነት ተገናኙ
"ታማኝነት" እና "እምነት የሚጣልበት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች የተገለጹት በአንድነት እንደተገኙ ሰዎች ተደርጎ ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው፤ እናም እርሱ ለማድረግ ቃል የገባወን ያደርገዋል። "እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው፤ ሰዎች እርሱን ሊያምኑት እንደሚገባ አረጋግጦላቸዋል" ወይም 2) ከቃል ከዳኑ የተነሳ እና ሰዎች ለእርሱ ታማኝነት መሆናቸውን ምልሽ በመስጠታቸው የእግዚአብሔር ታማኝነት ታይቷል። "እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነበር፣ ሰዎችም እርሱን በመታመን ምላሽ ሰጥተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
በአንድነት ተገኙ...እርስ በእርሳቸው ተሳሳሙ
ምናልባት ተናጋሪው እግዚአብሔር ህዝቡን ወደፊት ዳግም ባለጸጋ የሚያደርግበትን ጊዜ እየገለጸ ሊሆን ይችላል። "በአንድነት ይገናኛሉ... እርስ በእርስ ይሳሳማሉ"
ጽድቅ እና ሰላም እርስ በእርሳቸው ተሳሳሙ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ህዝቡ ትክክለኛ የሆነውን ያደርጋል፣ እግዚአብሔርም ህዝቡ በሰላም እንዲኖር ያደርጋል፤ ወይም 2) እግዚአብሔር ትክክል የሆነውን ያደርጋል፣ ህዝቡም በሰላም እንዲኖር ያደርጋል። በየትኛውም መንገድ ቢሆን ጽድቅ እና ሰላም ረቂቅ ስሞች ናቸው፤ የተገለጹትም እርስ በእርሳቸው እንደሚሳሳሙ ሰዎች ተደርገው ነው። (ረቂቅ ስሞች እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
እርስ በእርስ ተሳሳሙ
ይህ ጓደኞሞች እርስ በእርስ ሰላምታ የሚለዋወጡበት የተለመደ መንገድ ነበር።
ታማኝነት ከምድር በቀለ
በምድር የሚገኙ ሰዎች ለእግዚአብሔር ያላቸው ታማኝነት የተገለጸው ታማኝነት ከምድር የሚበቅል ተክል ተደርጎ ነው። "ታማኝነት" የሚለው ቃል "ታዛዥ" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "እዚህ በምድር ላይ፣ ለእግዚአብሔር ታዛዥ እንሆናለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
ጽድቅ ከሰማ ሆኖ ወደታች ተመለከተ
"ጽድቅ" የሚለው ቃል ረቂቅ ስም ነው፣ የተገለጸውም እግዚአብሔር እንደሚያደርገው ከላይ ሆኖ ወደታች እንደሚመለከት ነው። "እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ እኛ ይመለከታል፣ ደግሞም በእኛ ላይ በትክክል ይፈጽማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
Psalms 85:12
ጽድቅ በፊቱ ይሄዳል፣ ለእግሩም እርምጃዎች መንገድን ያዘጋጃል
እግዚአብሔር እርሱ በሚሄድበት ስፍራ ሁሉ ትክክል እንደሚያደርግ የተገለጸው ጽድቅ ከእግዚአብሔር ፊት የሚሄድ እና እግዚአብሔር የሚራመድበትን መንገድ እንደሚያዘጋጅ ሰው ተደርጎ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ የእግሩ እርምጃዎች/ኮቴ
እዚህ ስፍራ "የእግር ኮቴ" የሚወክለው የእግዚአብሔርን እርምጃዎች ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

---

# Chapter 86
Psalms 86:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ድሃ እና የተጨቆነ
"ደካማ እና እርዳታ ፈላጊ"
አገልጋይህን አድን
ዳዊት ራሱን "የአንተ አገልጋይ" በማለት ይጠቅሳል፣ ይህም ማለት የእግዚአብሔር አገልጋይ ማለት ነው። "እኔን አገልጋይህን አድነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 86:3
ቀኑን በሙሉ
ይህ ማጋነን ነው። ዳዊት ያለማቋረጥ አልቅሷል፣ ነገር ግን ቃል በቃል ነግቶ እስኪመሽ ሁሉንም ሰአት ማለት አይደለም። "አለማቋረጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ አጋኖ እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
አገልጋይህን ደስ አሰኝ
ዳዊት ራሱን "የአንተ አገልጋይ" በማለት ይጠቅሳል፣ ይህም ማለት የእግዚአብሔር አገልጋይ ማለት ነው። "እኔን የአንተ አገልጋይ አድርገኝ" ወይም "አድርገኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 86:5


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በመከራዬ ቀናት
"በችግሬ ጊዜ"
ወደ አንተ እጣራለሁ
"ወደ አንተ እጸልያለሁ"
Psalms 86:8
በአማልክት መሃል
ጸሐፊው የእነዚህ ሌሎች አማልክት ህልውና እውቅና እየሰጠ አይደለም። ሌሎች አገራት የሚያመልኳቸውን ሀሰተኛ አማልክት እያመለከተ ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አገራት ሁሉ
እዚህ ስፍራ "አገራት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "ከሁሉም አገራት ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ስምህን ያከብራሉ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው መላ ማንነትን ነው። "እነርሱ አንተን ያከብራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 86:10
አስደናቂ ነገሮች
"እኔን የሚያስደንቁ በጣም ጥሩ ነገሮች"
አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ
"ብቸኛው አምላክ አንተ ነህ"
ያህዌ ሆይ፣ መንገዶችህን አስተምረኝ። ያን ጊዜ በእውነትህ እራመዳለሁ
እግዚአብሔር የሚፈልገውን የሚታዘዝ ሰው የተገለጸው በእግዚአብሔር መንገድ ወይም ጎዳና እንደሚራመድ ተደርጎ ነው። "ያህዌ ሆይ፣ እውነትህን አስተምረኝ። ይህ ሲሆን የተናገርከውን እታዘዛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተን አከብር ዘንድ ልቤን አንድ አድርገው/ያልተከፋፈለ ልብ ስጠኝ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የአንድን ሰው ሀሳብ፣ ስሜት እና ሰበበ ምክንያት ነው። አንድ ሰው እርሱን በሙሉ ልቡ እንዲያከብር እግዚአብሔርን መጠየቅ የተገለጸው፣ የዚያ ሰው ልብ የተከፋፈለ እንደነበረ እና እግዚአብሔር እነዚያን ክፍልፋዮች እንደሚገጣጥማቸው ተደርጎ ነው። "በሙሉ ልቤ በቅንነት አንተን እንዳከብር አድርገኝ" ወይም "በቅንነት አንተን እንዳከብር አድርግ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ))
እኔ ስምህን አከብራለሁ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው መላ ማንነትን ነው። "እኔ አከብርሃለሁ" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 86:13
አንተ ለእኔ ያለህ የቃልኪዳን ታማኝነት ታላቅ ስለሆነ
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ከቃል ኪዳንህ የተነሳ አንተ ለእኔ በጣም ታማኝ ነህና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ለፍሴን ከሲኦል ጥልቅ አዳንካት
ይህ ማለት እርሱ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር ዳግም ወደ ህይወት መለሰው ማለት አይደለም። ለሞት ከተቃረበበት እግዚአብሔር እርሱን አዳነው ማለት ነው።
እብሪተኛ
ይህ ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሆኖ ሊገለጽ ይችላል። "እብሪተኛ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)
በእኔ ላይ ተነስተውብኛል
"እኔን ለመጉዳት በአንድነት እየመጡ ነው"
ነፍሴን ፈለጓት
ሊገድሉኝ ፈለጉ የሚለው የተገለጸበት መንገድ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 86:15
በቃል ኪዳን ታማኝነት እና በታማኝነት የተትረፈረፈ
የእግዚአብሔር የማያቋርጥ ታማኝነት እና መታመን የተገለጸው ታማኝነት እና መታመን እግዚአብሔር በብዙ መጠን ያለው ቁሳዊ ነገር ተደርጎ ነው። ሁለቱ ረቂቅ ስሞች እንደ ቅጽል ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ሁሌም ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ደግሞም ሰዎች አንተን ለመታመን በጣም የተገባህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
ወደ እኔ ዘወር በል
እርሱን እንዲመለከት እግዚአብሔርን መጠየቅ የተገለጸው እግዚአብሔር ወደ እርሱ ዘወር ብሎ ሊመለከተው እንደሚፈልግ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ብርታትህን ለአገልጋይህ ስጥ
"ብርታት" የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ወይም እንደ ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "አገልጋይህን አበርታው" ወይም "አገልጋይህን ጠንካራ አድርገው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ አገልጋይ....የሴት አጋልጋይህ ወንድ ልጅ
ጸሐፊው በሶስተኛ መደብ የሚናገረው ስለ እራሱ ነው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ይፈሩ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እነርሱ ይፈሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 87
Psalms 87:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
የቆሬ ልጆች ዝማሬ፣ ዝማሬ
"ይህ የቆሬ ልጆች የጻፉት ዝማሬ ነው"
የጽዮን በሮች
እዚህ ስፍራ "የጽዮን በሮች" የሚለው የሚወክለው መላዋን የእየሩሳሌም ከተማ ነው። "የኢየሩሳሌም ከተማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
መላው የያዕቆብ ድንኳኖች
በበረሃ በሚንከራተቱበት ወቅት በድንኳኖች የኖሩ ሰዎች። እዚህ ስፍራ ጸሐፊው "የያዕቆብ ድንኳኖች" የሚለውን የተጠቀመበት እስራኤላውያን አሁን የሚኖሩነትን ለመግለጽ ነው። "ማናቸውም አሁን እስራኤላውያን የሚገኙባቸው ሌሎች የመኖሪያ ስፍራዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፣ ስለ አንቺ አስደናቂ ነገሮች ተነግረዋል
ጸሐፊው ለእየሩሳሌም ከተማ እርሱን እንደምትሰማው አድርጎ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እናንተ በእየሩሳሌም የምትኖሩ ሰዎች ሆይ፣ ሌሎች ሰዎች ስለ እናንተ ከተማ አስደናቂ ነገሮችን ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አጋኖ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 87:4
እኔ እጠቅሳለሁ
"እኔ ስለዚህ ተናገርኩ።" እዚህ ስፍራ "እኔ" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌን ነው።
ረዓብ እና ባቢሎን
እዚህ ስፍራ "ረዓብ" ግብጽ የተጠቀሰችበት ስነግጥማዊ መንገድ ነው። "ረዓብ" እና "ባቢሎን" ሁለቱም ህዝቡን ይወክላሉ፤ "የግብጽ እና የባቢሎን ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚሉትን ይመልከቱ)
ለእኔ ተከታዮች
"እኔን ለሚያመልኩኝ"
ፍልስጤም፣ እና ጢሮስ፣ ከኩሽ ጋር


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የእነዚህ አገራት ሰዎች ህዝብን ይወክላል። ከፍልስጤም እና ጢሮስ እንዲሁም ከኩሽ ከመጣው ህዝብ ጋር"

ይህኛው የተወለደው በዚያ ነበር

"ይህኛው" የሚለው የሚያመለክተው ጸሐፊው ከጠቀሳቸው አገሮች የሆኑ ሰዎችን ነው። ምንም እንኳ እነርሱ በአካል በጽዮን ባይወለዱም፣ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ በመንፈስ የእየሩሳሌም ተወላጆች ናቸው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 87:5

የጽዮን የሆኑ ይባላል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ስለ ጽዮን ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ እያንዳንዳቸው የተወለዱት በዚህ ነበር

ያህዌን የሚያመልኩ ከሌሎች አገራት የመጡ ሰዎች በእየሩሳሌም እንደ ተወለዱ ተደርጎ ይነገራል። "ይህም እነዚህ ሁሉ ሰዎች በእየሩሳሌም እንደተወለዱ ይቆጠራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በ እርሷ

ከተሞችን "እርሷ" ብሎ መጥራት የተለመደ ነበር። "በእየሩሳሌም" ወይም "በጽዮን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ከሁሉም ከፍ ያለው /ልዑሉ ራሱ

ጸሐፊው "እርሱ ራሱ" የሚለውን ደጋጋሚ ተውላጠ ስም የተጠቀመው ይህንን ያደረገው ልዑሉ ራሱ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷን ያጸናታል

"እየሩሳሌምን ጠንካራ ያደርጋታል"

ያህዌ በአገራት የህዝብ ቆጠራ መጽሐፍ ላይ ሲጽፍ

ያህዌ የሌላ አገር ሰዎችም የእርሱ እንደሆኑ እውቅና መስጠቱ የተገለጸው፣ በእርሱ ከተማ የሚኖሩ ሰዎችን ስሞች እንደጻፈ ንጉሥ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህኛው የተወለደው እዚህ ነበር

"ይህኛው" የሚለው የሚያመለክተው ጸሐፊው ከጠቀሳቸው አገራት የሆኑ ሰዎችን ነው። ምንም እንኳን በአካል በጽዮን ባይወለዱም፣ እግዚአብሔርን የሚከተሉ/የሚያመልኩ በመንፈስ የእየሩሳሌም ተወላጆች ናቸው። ይህ በመዝሙር 87:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 87:7

ፏፏቴዎቼ ሁሉ በአንቺ ውስጥ ይገኛሉ

እየሩሳሌም ሰዎች በረከቶቻቸውን ሁሉ የሚቀበሉባት ስፍራ መሆኗ የተገለጸው፣ እየሩሳሌም ለህዝቡ ውሃ የምታቀርብ ምንጭ እንደሆነች ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

## Chapter 88

### Psalms 88:1

አጠቃላይ መረጃ፦

ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ዝማሬ፣ የቆሬ ልጆች ዝማሬ

"ይህ የቆሬ ልጆች የጻፉት ዝማሬ ነው"

ለመዘምራን አለቃ

"ይህ በመዘምራን አለቃ ለአምልኮ የሚዜም ነው"

በማሕሌት የሚዘመር

ይህ የዝማሬ አይነትን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

ማኸላት

ይህ የዝማሬ አይነትን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ይህ በመዝሙር 32:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ኤማን

ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ይዝራኤላዊ

ይህ የህዝብ ወገን ስም ነው። የዛራን ወንድ ልጅ ወይም ትውልድ ያመለክታል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የደህንነቴ አምላክ

"ደህንነት" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ያዳንከኝ አንተ ነህ/ አንተ አዳንከኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንና ሌሊት

ጸሐፊው እነዚህን ተቃራኒ ትርጉሞች ያላቸው ቃላት የተጠቀመው ያለማቋረጥ እንደሚጮህ ለመናገር ነው። (ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

### Psalms 88:3

እኔ በመከራ ተሞልቻለሁና

ጸሐፊው ስለ እራሱ፣ እርሱ ዕቃ መያዣ እንደሆነ እና ችግር ደግሞ መያዣውን እንደሞላ ይዘት አድርጎ ይናገራል። "እኔ በጣም ተጨንቄያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእኔ ህይወት ሲኦል ደረሰች

እዚህ ስፍራ "ህይወት" የሚወክለው ጸሐፊውን ነው። "ሲኦል" ደግሞ ሞትን ይወክላል። ጸሐፊው ስለ እራሱ ምናልባትም በቶሎ እንደሚሞት እና ሲኦል መድረሻ ስፍራው ሆኖ በዚያ እንደሚደርስ ይናገራል። "ልሞት ተቃርቤያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ሰዎች እኔን የቆጠሩት ወደ ጉድጓድ እንደወረዱት አድርገው ነው

"ጉድጓድ" የሚለው ቃል "ሲኦል" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። "ወደ ሲኦል መውረድ" የሚለው ሀረግ የሚወክለው መሞትን ነው። "ሰዎች የሞትኩ አድርገው ቆጠሩኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

### Psalms 88:5

በሞቱት መሃል ተተውኩ

ሰዎች ጸሐፊውን የሞተ አድርገው እንደቆጠሩት የተገለጸው ሳይቀበር እንደተጣለ በድን ነው። "የሞትኩ ያህል ብቻዬን ተተውኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በመቃብር እንደተጋደመ ሬሳ ነኝ

ጸሐፊው ሰዎች እና እግዚአብሔርም እንደተዉት የተሰማው ስሜት የተገለጸበት ሁኔታ ልክ ሞቶ በመቃብር እንደ ተጋደመ ሰው ነው።

ሞተው የተጋደሙ

"ሙታን" የሚለው ስማዊ ቅጽል እንደ ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "ሞቶ የተጋደመ ሰው" ወይም "ሞተው የተጋደሙ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከአንተ ሀይል ተቆርጠዋል/ጠፍተዋል

የእግዚአብሔር ሀይል ከእንግዲህ የሞቱ ሰዎችን እንደ ማይረዳቸው የተገለጸው፣ እግዚአብሔር እርሱን ቆርጦ እንደጣለው ወይም ከእርሱ ሀይል እንዳስወገደው ተደርጎ ነው። "ከእንግዲህ እነርሱን ለመርዳት ሀይልህን አትጠቀምም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በጉድጓዱ ታችኛው ስፍራ፣ በጨለማውን እና በጥልቁ አስቀመጥከኝ

ጸሐፊው እግዚአብሔር እርሱን እንደ ተወው የተሰማውን ስሜት የገለጸው፣ እግዚአብሔር እርሱን በጥልቅ እና ጨለማ መቃብር ውስጥ እንዳስቀመጠው አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

### Psalms 88:7

ቁጣህ በላዬ በእጅጉ ወደቀ

ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር በጸሐፊው ላይ በጣም እንደተቆጣ ሲሆን፣ የእግዚአብሔር ቁጣ ልክ እንደ ከባድ ቁስ ሆኖ በላዩ ላይ እንደወደቀበት አድርጎ ይገልጻል። "ታላቁ ቁጣህ ተሰማኝ" ወይም "አንተ በእኔ ላይ እንዴት በጣም እንደተቆጣህ ተሰማኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማዕበልህ ሁሉ ሰባብሮኛል

ይህ እግዚአብሔር በጸሐፊው በጣም መቆጣቱን የሚገልጸው የእግዚአብሔር ቁጣ ከባህር የሚነሳ ትልቅ ማዕበል ሆኖ በእርሱ ላይ እንዳረፈበት አድርጎ ነው።

ሴላ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 88:8

የቅርብ ወዳጆቼ

"እኔን የሚያውቁኝ እነርሱ"

ለእነርሱ ማስፈራሪያ አደረግከኝ

"ለዐይናቸው የሚጸየፉኝ አደረግከኝ" ወይም "ከአንተ ከደረሰብኝ ነገር የተነሳ፣ ሲመለከቱኝ ድንጋጤ ወደቀባቸው"

እኔ ተከብቤያለሁ

ጸሐፊው በጓደኞቹ ዘንድ ተቀባይነት ያሳጣው አካላዊ ሁኔታ የተገለጸው በተጣበበ ስፍራ እንደተቆለፈበት ሆኖ ነው። "በእስር ቤት ውስጥ እንዳለ ሰው ሆንኩ" ወይም "በወጥመድ ተያዝኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 88:9

ዐይኖቼ ከመከራ የተነሳ ደከሙ

እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው የሚወክለው የሰውን የማየት አቅም ነው። ዐይኖቹ ከመከራ የተነሳ መድከማቸው፣ የደረሰበት መከራ ብዙ እንዲያነባ እንዳደረገውና ከዚህም የተነሳ ማየት እንደከበደው የተገለጸበት መንገድ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እጆቼን ወደ አንተ ዘረጋሁ

"እጆቼን ወደ አንተ አነሳሁ።" ይህ እርሱ ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር ላይ መደገፉን የሚያሳይ ድርጊት ነው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት)

አንተ ለሙታን አስደናቂ ነገርን ታደርጋለህን?

ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት፣ እግዚአብሔር እርሱን ይሞት ዘንድ ቢተወው ከዚያ በኋላ ለእርሱ አስደናቂ ነገሮችን ለማድረግ እንደማይችል ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ለሙታን አስደናቂ ነገሮችን አታደርግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞቱ ተነስተው ያመሰግኑሃልን?

ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት፣ እግዚአብሔር እርሱን ይሞት ዘንድ ቢተወው ከዚያ በኋላ ተነስቶ ሊያመሰግነው እንደማይችል ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 88:11

የቃል ኪዳንህ ታማኝነት በመቃብር ፣ ወይንስ ታማኝነትህ በሙታን ስፍራ ይታወጃል?

ሁለቱም ጥያቄዎች ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻሉ። ጸሐፊው ጥያቄዎቹን የተጠቀመባቸው የሞተ ሰው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ማወደስ እንደማይችል ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ታማኝነት" እና "ትክክለኛነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በቅጽል መልካቸው ሊተረጎሙ ይችላሉ። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም የቃል ኪዳንህን ታማኝነት እና ትክክለኛነት ከመቃብር ሊያውጅ/ ሊናገር አይችልም።" ወይም "ማንም ከመቃብር ሆኖ አንተ ለቃል ኪዳንህ ወይም ለትክክለኛነትህ ታማኝ መሆንህን ለህዝብህ መናገር አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለምልልሳዊ ጥያቄ እንዳሁም አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

መቃብር... የሙታን ስፍራ...በጨለማ...የመረሻ ስፍራ

እነዚህ ሁሉ ሰዎች ከሞቱ በኋላ የሚሄዱበትን ስፍራ ይወክላሉ።

በሙታን ስፍራ የአንተ ታማኝነት አለን?

ይህ የተለየ ዐረፍተ ነገር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። "ታማኝነትህ በሙታን ስፍራ ሊታወጅ ይችላልን?" ወይም "ሙታን የአንተን ታማኝነት ሊናገሩ አይችሉም።" (የተተወ/የተዘለለ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

አስደናቂ ስራዎችህ በጨለማ ፣ ወይስ ጽድቅህ በመረሳት ስፍራ ይታወቀልን?

ሁለቱም ጥያቄዎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው ጥያቄዎቹን የተጠቀመባቸው ሙታን የእግዚአብሔርን ስራ ታላቅነት ለመግለጽ ወይም ለማወጅ እንደማይችሉ ትኩረት ሰጥቶ ለመናገር ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ስለ አንተ አስደናቂ ስራዎች እና ጽድቅ፣ በተረሱ/በተዘነጉት ሙታን መሃል አይናገሩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች እንዲሁም አድራጊ ወይም ተደራጊ በሚሉት ውስጥ ይመልከቱ)

ወይስ ጽድቅህን በዝንጉነት ስፍራ ይናገራሉን?

ይህ የተለየ ዐረፍተ ነገር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። "ጽድቅህ በዝንጉነት ስፍራ ይታወቃልን?" ወይም "በመረሳት ስፍራ የሚገኙ አንተ ስላደረግካቸው የጽድቅ ስራዎች አያውቁም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በሚሉት ውስጥ ይመልከቱ)

Psalms 88:13

ጸሎቴ በፊትህ ይምጣ

ጸሐፊው ወደ ያህዌ የሚያደርሰው ጸሎት የተገለጸው ጸሎቱ ራሱ ከያህዌ ጋር ለመነጋገር እንደሚሄድ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ፊትህን ከእኔ ትደብቃለህ?

ይህ የሚናገረው ጸሐፊው እግዚአብሔር እንደተወው ወይም እንዳልተቀበለው የተሰማውን ስሜት ሲሆን፣ እግዚአብሔር ፊቱን እንደደበቀበት ወይም ከጸሐፊው በአካል ፊቱን እንዳዞረ ተደርጎ ተገልጽዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 88:15

የአንተ የቁጣ ድርጊቶች በላዬ አለፉ

ይህ እግዚአብሔር ጸሐፊውን መቅጣቱን፣ የእግዚአብሔር ቅጣት ከባህር እንደሚነሳ እና በጸሐፊው ላይ ወድቆ እንደሚያፈራርስ ታላቅ ማዕበል ተደርጎ ተገልጽዋል። "ይህ የአንተ የቁጣ ድርጊቶች እኔን እንዳጠፉኝ ያህል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ አስፈሪ ድርጊቶች ራሴን አሳተኝ/አጠፋኝ

ይህ ግነት የሚናገረው እግዚአብሔር ጸሐፊውን የቀጣው ሙሉ ለሙሉ እንደሆነ አድርሰጎ ነው። "አንተ ያደረግካቸው አስፈሪ ነገሮች እኔን አጠፉኝ" ወይም "አንተ ያደረግካቸው አስፈሪ ድርጊቶች እኔን አጠፉኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ግነት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

Psalms 88:17

ቀኑን በሙሉ እንደ ውሃ ከበቡኝ

ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ቁጣ ከውሃ ፈሳሽ/ጎርፍ "የቁጣ ድርጊት" እና "አስፈሪ ድርጊቶች" ጋር ያነጻጽራል። "እነርሱ ቀኑን በሙሉ ጎርፍ እንደሚያጠፋ ሊያጠፉኝ ያስፈራሩኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ

"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከቀደመው ቁጥር የእግዚአብሔርን "የቁጣ ድርጊቶች" እና "አስደንጋጭ ስራዎች" ነው።

እነርሱ ሁሉ እኔን ከበቡኝ

ጸሐፊው የእግዚአብሔርን "የቁጣ ድርጊቶች" እና "አስፈሪ ተግባራት" የሚገልጸው እርሱን ለመያዝ እና ለመግደል እንደሚሞክሩ ጠላቶች አድርጎ ነው። "እነርሱ እንደ ጠላት ወታደሮች ከበቡኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ወዳጅ እና የቅርብ ሰው

"እያንዳንዱ እኔ የምወደው እና የማውቀው ሰው"

ብቸኛው ወዳጂ ጨለማ ነው

ይህ ስለ ጨለማ የሚናገረው፣ ጨለማ ሰው እንደሆነ እና ከሌላ ሰው ጋር ጓደኛ ሊሆን እንደሚችል ነገር አድርጎ ነው። ጸሐፊው ሙሉ ለሙሉ ብቸኝነት እንደተሰማው ትኩረት ይሰጣል። "በደረስኩበት ሁሉ ጨለማ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 89

Psalms 89:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነግጥም እና ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ማሽል

ይህ የዝማሬ ስልትን ሊያመለክት ይችላል። ይህ በመዝሙር 32:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ኤታን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ የጸሐፊው ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ይዝራኤላዊው
ይህ የአንድ ወገን ህዝብ ስያሜ ነው። ይህ አንድን ወንድ ልጅ ወይም የየዛራን ትውልድ ሊያመለክት ይችላል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የቃል ኪዳን ታማኝነት ድርጊቶች
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ታማኝ ድርጊቶች" ወይም "ተወዳጅ ድርጊቶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የቃል ኪዳን ታማኝነት ለዘለዓለም ተመስርቷል
እግዚአብሔር ሁሌጊዜም ሊያደርግ ቃል የገባውን ማድረጉ የተገለጸው ታማኝነቱ እርሱ የገነባው እና ያጠነከረው/ያቆመው ህንጻ ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን የተነሳ አንተ ሁልጊዜም ታማኝ ትሆናለህ" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
አንተ እውነተኛነትህን በሰማያት መሰረትህ
እግዚአብሔር ሁሌጊዜም ሊያደርግ ቃል የገባውን ማድረጉ የተገለጸው ታማኝነቱ እርሱ የገነባው እና ያጠነከረው/ያቆመው ህንጻ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በሰማት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ የእግዚአብሔርን መኖሪያ ስፍራ ያመለክታል። ይህ ማለት እግዚአብሔር በሰማይ ሆኖ ይገዛል፣ ደግሞም እርሱ ሁልጊዜም ቃል የገባውን ያደርጋል፤ ወይም 2) ይህ ሰማይን ያመለክታል። ይህም ማለት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንደ ሰማይ የጸና እና ቋሚ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 89:3
እኔ ከመረጥኩት ጋር ቃል ሊዳኔን አድርጌያለሁ
"የመረጥኩት " የሚለው ዳዊትን እንደሚያመለክት ግልጽ ማድረግ ይቻላል። "እኔ ለመረጥኩተ ለዳዊት ቃል ኪዳን ገብቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ አድርጌያለሁ
ያህዌ በመዝሙር 89፡3-4 ባለው ውስጥ ይናገራል።
እኔ ተውልድህን ለዘለዓለም አጸናለሁ
ያህዌ ሁልጊዜ ከዳዊት ተውልዶች አንዱን እንደሚያነግስ የተገለጸው የዳዊት ትውልዶች የሚያንጸው እና አጠንክሮ የሚያቆመው ህንጻ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በትውልዶች ሁሉ ዙፋንህን አጸናለሁ
እዚህ ስፍራ "ዙፋን" የሚወክለው እንደ ንጉሥ የመምራትን ሀይል ነው። መዝሙረኛው ከዳዊት ትውልዶች ውስጥ አንዱ ሁልጊዜ ንጉሥ እንደሚሆን እና እንደሚመራ የሚናገረው እግዚአብሔር የዳዊትን ዙፋን እንደሚመሰርት እና እንደሚያጸና አድርጎ ነው። "ከትውልዶች ውስጥ አንዱ በህዝቤ ላይ በየትውልዱ ንጉሥ ሆኖ እንደሚመራ አረጋግጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3፡2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 89:5
ሰማያት ያወድሳሉ
እዚህ ስፍራ "ሰማየት" የሚወክሉት በሰማይ ያሉትን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ ሆይ፣ አስደናቂ ስራዎችህን አወድሳለሁ
"ያህዌ ሆይ፣ ከሰራሃቸው አስደናቂ ስራዎች የተነሳ አወድስሃሁ"
ታማኝነትህ በቅዱሳን ጉባኤ ይወደሳል
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "አንተ ሁሌጊዜም ለማድረግ ቃል የገባኸውን ታደርጋለህ።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገርም ሊጻፍ ይችላል። "የቅዱሳኑ ጉባኤ አንተን ያወዱስሃል ምክንያቱም አንተ ሁልጊዜም ለማድረግ ቃል የገባኸውን ታደርጋለህ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ሚለውን ይመልከቱ)
የቅዱሳኑ ጉባኤ
ይህ በሰማይ ያሉትን መላዕክት ያመለክታል።
በሰማይ ማን ከያህዌ ጋር ሊነጻጸር ይችላል? ከአማልክት ልጆች ያህዌን ይመስላል?
ሁለቱም ጥያቄዎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው በሰማይ እንደ ያህዌ ያለ ማንም እንደሌለ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
የአማልክት
እዚህ ስፍራ "የልጆች" ማለት የ...ባህሪይ ያለው ማለት ነው። ይህ በሰማይ የሚኖሩ ሌሎች መንፈሳዊ ፍጥረታትን የማመላከቻ መንገድ ነው። "መላዕክት" ወይም "መለኮታዊ ፍጥረታት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 89:7
እርሱ በቅዱሳኑ ምክርቤት እጅግ የተከበረ አምላክ ነው።
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የቅዱሳኑ ምክርቤት እግዚአብሔርን እጅግ ያከብራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የቅዱሳኑ ምክር ቤት
"የሰማያዊ ፍጥረታት ስብሰባ" ወይም "የመላዕክት ስብሰባ"
ያህዌ ሆይ፣ እንደ አንተ ሀያል ማን ነው?
ጸሐፊው ጥያቄውን ያነሳው እንደ ያህዌ ያለ ሀያል እንደሌለ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ታማኝነትህ ከቦሃል
ያህዌ ሁልጊዜም ለማድረግ ቃል የገባውን ማድረጉ የተገለጸው የእርሱ ታማኝነት ዙሪያውን እንደ ጠቀለለው ልብስ ወይም እንደ ካባው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 89:9
አንተ የባህሩን ቁጣ ትገዛለህ
"አንተ የባህሩን ቁጣ ትቆጣጠራለህ"
ረዐብን እንደ ተገደለ ያህል ታደቀዋለህ
እዚህ ስፍራ "ረዐብ" የሚለው ቃል የባህርን አውሬ ያመለክታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚሉትን ይመልከቱ)
በብረቱ ክንዶችህ
እዚህ ስፍራ "ክንድ" የሚወክለው ሀይልን ነው። "በታላቁ ሀይልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 89:11
ሰሜኑ እና ደቡቡ
ጸሐፊው "ሰሜን" እና "ደቡብ" የሚሉትን ቃላት በአንድነት የተጠቀመባቸው፣ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የሚገኙትን ሁሉንም ነገሮች ፈጥሯል ለማለት ነው። (ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)
ታቦር እና አርሞንዔም በስምህ ደስ ይሰኛሉ
ታቦር ከገሊላ በስተ ደቡብ ምዕራብ የሚገኝ ተራራ ሲሆን አርሞንዔም ከገሊላ ባህር በሰሜን ምስራቅ የሚገኝ ተራራ ነው። ጸሐፊው እነዚህን ተራሮች የሚገልጸው ደስ መሰኘት እንደሚችሉ ሰዎች አድርጎ ነው። "ይህ የታቦር ተራራ እና የአርሞንዔም ተራራ በስምህ ደስ እንደተሰኙ ሆኖ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚሉትን ይመልከቱ)
በስምህ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው ጠቅላላ ሰውነትን ነው። " በአንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 89:13
አንተ ታላቅ ክንድ እና ጠንካራ እጅ አለህ፣ ደግሞም ቀኝ እጅህ ከፍ ያለ ነው
"ታላቅ ክንድ፣" "ጠንካር እጅ፣" እና "ቀኝ እጅ" የሚሉት ሁሉም የእግዚአብሔርን ሀይል ይወክላሉ። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ቀኝ እጅህ ከፍ ያለ ነው
ቀኝ እጅን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ ማንሳት፣ ሀይልን የሚያሳይ ምልክት ። (ትዕምርታዊ/


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ምልክታዊ ድርጊት)

ጽድቅ እና ፍትህ የዙፋንህ መሰረቶች ናቸው

የእግዚአብሔር በንግሥናው መግዛት እና ትክክልና ተገቢ የሆነውን ማድረግ የተገለጸው፣ የእግዚአብሔር ዙፋን ግንብ እንደሆነ እና ጽድቅና ፍትህ መሰረቶቹ እንደሆኑ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዙፋንህ

ዙፋኑ የእግዚአብሔርን እንደ ንጉሥ መግዛት ይወክላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የቃል ኪዳን ታማኝነት እና ታማኝነት ከፊትህ ይወጣሉ

እግዚአብሔር ሁልጊዜም ታማኝ መሆኑ እና ቃል የገባውን መፈጸሙ የተገለጸው የቃል ኪዳን ታማኝነት እና ታማኝነቱ መጥተው ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚገኙኙ ተደርጎ ነው። ረቂቅ የሆኑት ስሞች በቅጽል መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "አንተ ሁልጊዜም ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ነህ ደግሞም አንተን ላመኑህ ትበጀቸዋለህ" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:15

አንተን የሚያመልኩ

እዚህ ስፍራ "አምልኮ" የሚለው የሚያመለክተው መጮህን እና መለከት/ቀንዶችን መንፋትን ነው። ይህ በእስራኤላውያን ክብረ በዓል የተለመደ ድርጊት ነበር። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሄዳሉ/ይራመዳሉ

እዚህ ስፍራ የሰዎች ኑሮ የተገለጸው እንደሚሄዱ/እንደሚራመዱ ተደርጎ ነው። "ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በፊትህ ብርሃን

ጸሐፊው ያህዌ ለእነርሱ ሞገስን እንደሚሰጥ የገለጸው፣ የያህዌ ፊት በእነርሱ ላይ ብርሃንን እንደሚያበራ አድርጎ ነው። "በእነርሱ ላይ ሞገስህን እንደምታደርግ ይወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በስምህ

እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው ጠቅላላ ሰውነትን ነው። " በአንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በጽድቅህ አንተን ከፈ ከፍ ያደርጋሉ

"ጽድቅ" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ሁልጊዜም ትክክል የሆነውን ስለምታደርግ እነርዱ ከፈ ከፍ ያየርጉሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። "ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:17

አንተ የእነርሱ ባለ ግርማ ሞገስ ብርታታቸው ነህ

"ብርታት/ጥንካሬ" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊገለጽ ይችላል። "እጅግ ብርቱ ታደርጋቸዋልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የእነሱ ነህ

እዚህ ስፍራ "የእነሱ" የሚለው የሚያመለክተው እስራኤላውያንን ነው። ጸሐፊው የእስራኤላውያን አባል አድርጎ አካቷል። "አንተ የእኛ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ድል አድራጊ ነን

እዚህ ስፍራ "እኛ" የሚለው የሚያመለክተው ጸሐፊውን እና እስራኤላውያንን ነው፤ ጸሐፊው የሚያናግረውን ያህዌን አይጨምርም። (የማያካትት እና አካታች "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ የሆነ የእኛ ጋሻ

ህዝቡን የሚጠብቀው እና ያህዌ የመረጠው ንጉሥ የተገለጸው የያህዌ ጋሻ እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:19

አጠቃላይ መረጃ፡

ጸሐፊው፣ አንባቢው እንዴት ዳዊት የተመረጠው ንጉሥ እንደሆነ ታሪኩን እንደሚያውቅ ይገምታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ሀያል በሆነው ላይ ዘውድ አደርጌያለሁ/ጭኛለሁ

በአንድ ሰው ራስ ላይ ዘውድ መጫን ሰውየውን ንጉሥ የማድረግ ምልክት ነው። "ታላቁን ሰው አነግሰዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በቅዱሱ ቅባቴ እርሱን ቀባሁት

እዚህ ስፍራ በአንድ ሰው ራስ ላይ ዘይት ማፍሰስ እግዚአብሔር ያንን ሰው ንጉሥ እንዲሆን መሾሙን የሚያሳይ ምልክት ነው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የእኔ እጅ እርሱን ይደግፈዋል፣ ክንዴም ያበረታዋል

እዚህ ስፍራ "እጅ" እና "ክንድ" የሚሉት ሁለቱም የያህዌ ሀይል እና ቁጥጥር ማለት ነው። "እኔ እደግፈዋለሁ ደግሞም አበረታዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የክፋት ወንድ ልጅ

ጸሐፊው የክፋት ተፈጥሮ ወይም ባህሪይ ያላቸውን "የክፋት ወንዶች ልጆች" በማለት ይገልጻቸዋል። "ክፉ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:24

አያያዥ ሃሳብ፡

ያህዌ ስለ ዳዊት መናገሩን ቀጥሏል።የእግዚአብሔር የዘላለም ታማኝነት እና ለዳዊት የገባውን እንደሚፈጽምለት የተገለጸው፣ እውነት እና ታማኝነት ከዳዊት ጋር እንደሚሆኙ አካላት ተደርገው ነው። "እውነት" እና "ታማኝነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በቅጽል መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እኔ ለእርሱ ሁልጊዜም ታማኝ እሆናለሁ ደግሞም ለእርሱ ሁሌም በታማኝነት እፈጽምለታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

በስሜ ድል ይጎናጸፋል

እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን ሀይል ነው። "እኔ፣ እግዚአብሔር፣ድል አጎናጽፈዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እጆችን ከባህሮች በላይ፣ ቀኝ እጁንም ከወንዞች በላይ አደርጋለሁ

እዚህ ስፍራ "እጅ" እና "ቀኝ እጅ" የሚሉት የሚወክሉት ሀይልን እና ስልጣንን ነው። "ባህሩ" ከእስራኤል በስተ ምዕራብ የሜድትራኒያን ባህርን የሚያመለክት ይመስላል፤ "ወንዞች" የሚለው በስተ ምስራቅ የሚገኘውን የኤፍራጥስ ወንዝ ያመለክታል። ይህ ማለት ዳዊት ከባህሩ እስከ ወንዙ ድረስ ባለው ማናቸውንም ነገር ላይ ስልጣን ይኖረዋል ማለት ነው። "እኔ ለእርሱ ከሜድትራኒያን ባህር እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ባለው ማናቸውም ነገር ላይ ስልጣን እሰጠዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ከጽንፍ ጽንፍ /ከዳር ስስከ ዳር/ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ፣ 'አምላኬ ሆይ፣ አንተ አባቴ ፣ የደህንነቴ አለት ነህ' ብሎ ወደ እኔ ይጣራል።

ይህ በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ ይዟል። ቀጥተኛ ባልሆነ ጥቅስ ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ እኔን፤ አባቱ፣ አምላኩ፣ እና የደህንነቱ አለት እንደሆንኩ ይናገራል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እንደዚሁም ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያለሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

የደህንነቴ አለት

ያህዌ ዳዊትን መጠበቁ እና ማዳኑ የተገለጸው፤ ያህዌ፣ ዳዊት ከጠላቶቹ ለመዳን በላዩ ሊቆምበት እንደሚችል ከፍ ያለ አለት ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:27

አያያዥ ሃሳብ፡

ያህዌ ስለ ዳዊት መናገሩን ቀጥሏል።

እንደ በኩር ልጄ አድርጌ አስቀምጠዋለሁ

ያህዌ ለዳዊት ልዩ ማዕረግ መስጠቱ እና ኬሌሎች ሰዎች በላይ ለእርሱ ጥበቃ ማድረጉ የተገለጸው፣ ዳዊት የያህዌ የበኩር ልጅ እንደሚሆን ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አገላለጽ ሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለእርሱ የቃል ኪዳኔን ታማኝነት ለዘለዓለም እቀጥላለሁ

የያህዌ የቃል ኪዳን ታማኝነቱን ለዳዊት እንደሚቀጥል የገለጸው የያህዌ ቃል ኪዳን ታማኝነት እርሱ እንደሚያሰፋው ወይም እንደሚያራዝመው አካል ተደርጎ ነው። "ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በተውሳከ ግስ መለኩ ሊተረጎም ይችላል። "እኔ ለእርሱ ያለኝን ታማኝነት ለዘለዓለም እቀጥላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

(ዘይቤያዊ አገላለጽ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
የእርሱ ዙፋን በላይ እንደሚገኘው ሰማይ የጸና ነው
ከዳዊት ቤት ንጉሥ እንደማይታጣ የተገለጸው የእርሱ ዙፋን ሰማይ ለዘለዓለም የጸና እንደሆነ ዙፋኑ ለዘለዓለም እንደሚኖር ተደርጎ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ ዙፋን
እዚህ ስፍረ "ዙፋን" የሚወክለው እንደ ንጉሥ የመግዛት ሀይልን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 89:30
የእርሱ ልጆች
"የዳዊት ልጆች"
አመጻቸውን በበትር አቀጣለሁ
እግዚአብሔር የዳዊትን ልጆች መቅጣቱ የተገለጸው እግዚአብሔር በቀጥታ እነርሱን በበትር እንደሚመታ ተደርጎ ነው። "አመጽ" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "በእኔ ላይ በማመጻቸው እቀጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
በደላቸውን በጅራፍ
እግዚአብሔር የዳዊትን ትውልዶች መቅጣቱ የተገለጸው እግዚአብሔር እነርሱን በቀጥታ እንደሚመታ ተደርጎ ነው። ይህ በሙሉ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔን በድለዋልና እቀጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና የተዘለለ/የተተወ በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው)
Psalms 89:33
ጽኑ ፍቅሬን ከእርሱ አላርቅም ወይም የቃል ኪዳኔን ታማኝነቴን አላርቅም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ዳዊትን ለዘለዓለም እወደዋለሁ፣ ደግሞም ለእርሱ ቃል የገባሁትን እፈጽማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምጸት የሚለውን ይመልከቱ)
የከንፈሬ ቃሎች
እዚህ ስፍራ "ከንፈሮች/ከናፍርት" የሚለው የሚወክለው በጠቅላላው አፍን እና ንግግር ነው። "እኔ የተናገርኩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 89:35
በቅዱስናዬ ማልኩ
ያህዌ ቅድስናውን ለመሃላው መሰረት አድርጎ ተጠቅሞበታል። ይህ እርሱ ለማድረግ ቃል የገባውን በእርግጥ እንደሚያደርግ የሚያረጋግጥበት መንገድ ነው።
የእርሱ ዙፋን እንደ ፀሐይ በፊቴ ለዘለዓለም ይሆናል/ይቀጥላል
"ይቀጥላል" የሚለው ቃል በውስጠ ታዋቂነት መኖሩ ይታወቃልለ። "የእርሱ ዙፋን ፀሐይ በፊቴ እስካለች ድረስ ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለየሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ለዘለዓለም የጸና ይሆናል
እዚህ ስፍራ "ይህ" የሚለው የሚያመለክተው የዳዊትን ዙፋን ወይም እንደ ንጉሥ የመግዛት ሀይሉን ነው። በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ለዘለዓለም የጸና እንዲሆን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ጨረቃ ለዘለዓለም
እግዚአብሔር የዳዊትን ንጉሣዊ አገዛዝ ከጨረቃ ጋር ያነጻጸረው ከዳዊት ትውልዶች ውስጥ ሁልጊዜም የሚነግስ ሰው እንደሚኖር ትኩረት ለመስጠት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጨረቃይቱ፣ በሰማይ ታማኝ ምስክር
ጨረቃይቱ የተገለጸችው ያህዌ ለዳዊት ቃልኪዳን ሲገባለት ምስክር ሆኖ እንደተገኘ ሰው ተደርጋ ነው። "ጨረቃይቱ፣ በሰማይ እንደ ታማኝ ምስክር የሆነች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሴላ
ይህ ሰዎች የሙዚቃ መሳሪያቸውን እዚህ እንዴት እንደሚያዜሙበት ወይም እንደሚጫወቱበት የሚያሳይ ሙዚቃዊ ስያሜ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ቃል እንዳለ ይጠቀሙበታል፣ አንዳንድ ትርጉሞች ይተዉታል። ይህ በመዝሙር 3፡2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ቅጂ/እንዳለ መገልበጥ/ወይም ቃላትን መዋስ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 89:38
አንተ ተቃወምከው ተውከውም
"ንጉሡ" የሚለው ቃል በውስጠ ታዋቂነት አለ። "አንተ ንጉሡን ተቃወምከው ወይም ተውከውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለየሚለውን ይመልከቱ)
የቀባኸው ንጉሥ
"አንተ የመረጥከው ንጉሥ"
አንተ ቃል ኪዳኑን ተውክ
"አንተ ቃል ኪዳኑን ጣልክ"
አንተ የእርሱን ዘውድ በመሬት ላይ አረከስክ
ወደ መድር ወይም አፈር ላይ መጣል በታላቅ ሁኔታ ማዋረድን ያመለክታል። "አንተ የእርሱን ዘውድ ምድር ላይ ጥለህ አቆሸሸክ" ወይም "አንተ የእርሱ ዘውድ ቆሻሻ ላይ እንዲወድቅ አደረግህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ ዘውድ
ይህ የሚወክለው እንደ ንጉሥ የንጉሡን ሀይል እና የመግዛት መብት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ የእርሱን ቅጥሮች ሁሉ አፈረስክ። ጠንካራ ምሽጎቹን ሁሉ አወደምክ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ጠላቶች የእየሩሳሌም መከላከያ ሁሉ እንዲወድም መፍቀዱን ነው። "ጠላቶች የእርሱን ቅጥር እንዲያፈርሱ እና ጠንካራ ምሽጎቹን እንዲደመስሱ ፈቀድክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 89:41
ለጎረቤቶቹ
እዚህ ስፍራ "ጎረቤቶች" ማለት በአቅራቢያ አገራት የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው።
የጠላቶቹን ቀኝ እጅ አስነሳሁበት
እዚህ ስፍራ "ቀኝ እጅ" የሚለው የሚወከወለው ሀይልን ነው። "ቀኝ እጅን ማንሳት" ማለት ያህዌ እርሱ ራሱ የመረጠውን ንጉሥ ጠላቶቹ እንዲያሸንፉት አቅም ሰጣቸው ማለት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚሉትን ይመልከቱ)
የሰይፉን ስለት አጠፍኩ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚወክለው ንጉሡ በጦርነት ያለውን ሀይል ነው። ሰይፍን መመለስ/ማጠፍ የሚወክለው ንጉሡን በጦርነት ማሸነፍ እንዳይችል ማድረግን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
የሰይፉ ስለት/ጠርዝ
እዚህ ስፍራ "ስለት/ጠርዝ" የሚወክለው ጠቅላላ ሰይፉን ነው። "የእርሱ ሰይፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በጦርነት መሃል መቆም እንዳይችል ማድረግ
እዚህ ስፍራ "መቆም" የሚወክለው በጦርነት ወቅት አሸናፊ መሆንን ነው። "በጦርነት አሸናፊ እንዲሆን አንተ አልረዳኸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 89:44
ዙፋኑን ወደ ምድር ጣልክ
እዚህ ስፍራ "ዙፋን" የሚወክለው እንደ ንጉሥ የመግዛትን ሀይል ነው። "አንተ፣ ያህዌ፣ እንደ ንጉሥ ሆኖ የሚገዛበትን ዘመን አበቃህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የወጣትነት ቀናቱን አሳጠርክ
ይህ እግዚአብሔር ንጉሡ ወጣት ሆኖ ሳለ ሽማግሌ እንዲመስል አደረገ ማለት ነው። "ገና ወጣት ሳለ አንተ እርሱን እንደ ሽማግሌ ሰው ደካማ አደረግኸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእፍረት ሸፈንከው/ከደንከው
ያህዌ ንጉሡን ሙሉ ለሙሉ ማሳፈሩ የተገለጸው፤ እፍረት እግዚአብሔር ንጉሡን ለመሸፈን እንደ ተጠቀመበት ልብስ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 89:46
ያህዌ ሆይ፣ እስከመቼ ድረስ? ለዘለዓለም ራስህን ትሰውራለህን?
ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው እግዚአብሔርን ንጉሡን አለመቀበሉን

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንዲቀጥልበት አለመፈለጉን ትኩረት ለመስጠት ነው። "ያህዌ ሆይ፣ እባክህ ንጉሡን ለዘለዓለም አትጣለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ራስን ትደብቃለህን

እግዚአብሔር ንጉሡን አለመርዳቱ የተገለጸው እግዚአብሔር ራሱን ከእርሱ እንደሰወረ/እንደ ደበቀ ተደርጎ ነው። "ንጉሡን አትረዳውምን?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣህ እስከ መቼ እንደ እሳት ይነዳል?

ጸሐፍው ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት እግዚአብሔር እንደ ተቆጣ እንዲቆይ እንደማይፈልግ ትኩረት ለመስጠት ነው። "እባክህ ቁጣህ ይብረድ/ ቁጣህ አይቀጥል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣህ እንደ እሳት ይነዳል

እግዚአብሔር በጣም መቆጣቱ የተገለጸው ቁጣዉ የሚነድ እሳት ተደርጎ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለምን ረብ ለሌለው ነገር የሰው ልጆችን ሁሉ ፈጠርካቸው

"ረብ/ጥቅም የሌለው" የሚለው ረቂቅ ስም "ያለ ጥቅም" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎችን ሁሉ ያለ ጥቅም ይሞቱ ዘንድ ፈጠርካቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጆች

ይህ ሰዎችን ሁሉ በጠቅላላ ያመለክታል። "የሰው ልጆች" ወይም "ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጡንቻማነትን የሚገልጹ ቃላት ሴትን ሲያካትቱ የሚለውን ይመልከቱ)

ላይሞት ነዋሪ የሚሆን ማን ነው፣ ወይም ራሱን ከሲኦል እጅ የሚያድን ማን ነው?

ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ሰዎች ሟች እንደሆኑ ትኩረት ለመስጠት ነው። "ማንም ለዘለዓለም መኖር አይችልም ወይም ማንም ራሱን ከሞት በኋላ ወደ ህይወት መመለስ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:49

ጌታ ሆይ፣ በእውነተኛነትህ ለዳዊት የማልክለት የቀድሞው የቃል ኪዳንህ ታማኝነት ወዴት አለ?

ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ጌታ ከዳዊት ጋር የገባውን ኪዳን እንዲጠብቅ ለመጠየቅ ነው።"ጌታ ሆይ፣ በቀድሞው ጊዜ እንደ ነበርህ ከዳዊት ጋር የገባኸውን ኪዳን ጠብቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የቀደመው የቃል ኪዳን ታማኝነትህ ድርጊቶች

"ድርጊቶች" እና "ታማኝነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በግስ እና ተውሳከ ግስ መልካቸው ሊረተጎሙ ይችላሉ። "አስቀድሞ ያደረግሃቸው ነገሮች አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ መሆንህን ያሳያሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

አስታውስ

ጸሐፊው ያህዌን ይህንን እንዲያስትውስ ይጠይቃል። "አስታውስ" ወይም "ስፍራ ስጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አገልጋችህ መቀለጃ ሆነናል

እዚህ ስፍራ "አገልጋዮችህ" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰዎች ነው። "እንደምን በእኛ በአገልጋዮችህ ላይ እንዳፌዙብን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እንደምን በልቤ ከአገራት ሁሉ እጅግ ብዙ ስድብን ተሸከምኩ

እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የሰውን ስሜቶች ነው። "ከአገራት ህዝቦች ብዙ ስድብን ተቋቋምኩ" ወይም "ከየአገራቱ ሰዎች በደረሰብኝ ስድብ ምክንያት ተሰቃየሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከየአገራቱ

እዚህ ስፍራ "አገራት" የሚለው የሚወክለው የተለያዩ አገራት ሰዎችን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ጠላቶች ስድብ አወረዱብኝ

ጠላቶች በንጉሱ ላይ በጩኸት መሳደባቸው የተገለጸው ስድብ ጠላቶች በንጉሡ ላይ በሀይል እንደሚወረውሩት ነገር/ቀስ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በቀባኸው እርምጃዎች ላይ አፌዙ

እዚህ ስፍራ "እርምጃዎች" የሚለው የሚወክለው ንጉሡ የሄደበትን ነው። "የቀባኸውን በሄደበት እየተከተሉ አፌዙበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 89:52

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ ቁጥር ከዚህ ዝማሬ መጨረሻነት/ማብቂያነት የላቀ ነው። በመዝሙር 73 ለሚጀምረው እና በመዝሙር 89 ለሚጨርሰው ለመጽሐፈ መዝሙር 3 የመዝጊያ ሀሳብ ነው።

ያህዌ ለዘለዓለም የተባረከ ይሁን

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ህዝቦች ያህዌን ለዘለዓለም ያወድሱት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አዎን እና አዎን /አሜን፤ አሜን

"አሜን" የሚለው ቃል የተወከለው እርሱ የተናገረውን ለማረጋገት ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ በመዝሙር 41፡13 እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

---

Chapter 90

Psalms 90:1

አጠቃላ መረጃ፡

ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ሰው የሙሴ ጸሎት

"ይህ የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ የጸፈው ጸሎት ነው"

ጌታ ሆይ፣ አንተ መጠጊያችን ነህ

እግዚአብሔር ለህዝቡ ያደረገው ጥበቃ የተገለጸው እግዚአብሔር መጠጊያ ወይም መጠለያ ተደርጎ ነው። "ጌታ ሆይ፣ አንተ ለእኛ መጠለያችን ሆንክልን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በትውልዶች ሁሉ ውስጥ

"ሁልጊዜም"

ተራሮች ከመመስረታቸው አስቀድሞ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገርሊገለጽ ይችላል።"አንተ ተራሮችን ከመፍጠርህ/ ከማበጀትህ አስቀድሞ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመስርተው ነበር/ተበጅተው ነበር

"ተፈጥረው ነበር" ወይም "ቅርጽ ተሰጥቷቸው ነበር"

ዓለም

ይህ በዓለም ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ ይወክላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም

ይህ ሀረግ የሚወክለው ያለፈውን፣ የአሁኑን እና መጪውን ዘመን ሁሉ ነው።

Psalms 90:3

አንተ ሰውን ወደ አፈር ትመልሰዋለህ

ይህ የሚያመለክተው፣ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው፣ አዳምን፣ ከአፈር እንደፈጠረው፤ ሰዎች ከሞቱ በኋላ እግዚአብሔር የሰው አካል ወደ አፈር እንዲመለስ እንደሚያደርግ ነው። "አንተ ሰዎችን ሲሞቱ ወደ ትቢያነት ትመልሳቸዋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውን ትመልሰዋለህ

እዚህ ስፍራ "ሰው" የሚለው በአጠቃላይ የሰው ልጅን ነው። (ጡንቻማነትን የሚገልጹ ቃላት ሴትን ሲያካትቱ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ትውልዶች/የሰው ልጆች ትመለሳላችሁ

"ወደ ትቢያ" ወይም "ወደ አፈር" የሚሉት ቃላት በውስጠ ታዋቂነት ይገኛሉ። "እናንተ ትውልዶች ወደ ትቢያ ትመለሳላችሁ" ወይም "እናንተ ትውልዶች ወደ አፈር ትመልሳላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ የሰው ልጆች

ይህ በአጠቃላይ የሰው ልጆችን መጥቀሻ መንገድ ነው። "እናንተ የሰው ልጆች" ወይም "እናንተ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ዘንድ ሺህ አመት እንደ ትላንት፣ በምሽት እንዳለፈ አንድ ሰዓት ነው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ጸሐፊው ረጅም ጊዜ ለእግዚአብሔር እንደ አጭር ጊዜ ይቆጠራል ማለቱ ነው። "አንተ ሺህ አመትን እንዳለፈ አንድ ቀን ወይም በምሽት እንዳለፈ አጭር ጊዜ ትቆጥራለህ" ወይም "ለአንተ ሺህ አመት እንኳን ረጅም ጊዜ አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሺህ አመታት
"1,000 አመታት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በአንተ ዐይኖች/አይታ
እዚህ ስፍራ እይታ የሚወክለው አስተያየትን ወይም ምዘናን ነው። "ለ አንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 90:5
በጎርፍ ትጠርጋቸለህ እነርሱም ይጠረጋሉ
እግዚአብሔር ሰዎችን በድንገት መግደሉ የተገለጸው እነርን በመጥረጊያ እንደመጥረግ ተደርጎ ነው። ይህ መጥረግ የተነገረው ሰዎችን ጠርጎ እንደሚወስድ ጎርፍ ተደርጎ ነው። "ጌታ ሆይ፣ አንተ ሰዎችን በጎርፍ እንደሚጠፉ አጠፋህ እነርሱም ሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
እነርሱ ተኙ
ይህ የሰዎች መሞት ሻል ባለ ቃል የተገለጸበት መንገድ ነው። (ዩፊምዝም/ሻል ያለ ቃል መጠቀም የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ በማለዳ እንደ ሳር ናቸው…በምሽት ይጠወልጋል ይደርቃልም
ሰዎቹ ከሳር ጋር የተነጻጸሩት ረጅም ጊዜ እንደማይኖሩ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይፈካል ያድግማል
እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ሳር እንዴት እንደሚያድግ ያመለክታሉ። "ማደግ እና መበልጸግ ይጀምራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
ይጠወልጋል ይደርቅማል
እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ሳር እንዴት እንደሚያሞት/እንደሚደርቅ ያመለክታሉ። "ይጠወልጋል፣ ይደርቅማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 90:7
እኛ በቁጣህ አልቀናል
የሰዎች በእግዚአብሔር ቁጣ ማለቅ የተገለጸው፣ የእግዚአብሔር ቁጣ ሰዎችን ሙሉ ለሙሉ የሚያጠፋ እሳት እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ በቁጣህ አጠፋኸን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
እኛ ከቁጣህ የተነሳ ተሸብረናል
"አንተ በምትቆጣ ጊዜ እኛ እጅግ እንፈራለን"
በደላችንን በፊትህ፣ የተሰወሩ ኃጢአቶቻችን በመገኘትህ ብርሃንህ ውስጥ አኖርክ
እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት መመልከቱ የተገለጸው፣ ኃጢአት በራሱ ፊት እንደሚያስቀምጠው ቁስ እና እንደሚመለከተው ነገር ተደርጎ ነው። "አንተ እኛ የምናደርጋቸውን ክፉ ነገሮች ሁሉ፣ በስውር ያደረግናቸውን እንኳን ሳይቀር ታያለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 90:9
ህይወታችን በቁጣህ ስር አለፈ
"ምክንያቱም" የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ቁጣ የሰው ህይወት እንዲያበቃለት እንደሚያደርግ ግልጽ ለማድረግ ሊውል ይችላል። "ከቁጣህ የተነሳ ህይወታችን አበቃለት/ሞትን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አያያዥ የሚለውን ቃላት የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ አንድ ትንፋሽ/ሳግ
ጸሐፊው የሰውን ህይወት ከአንድ ትንፋ ጋር የሚያነጻጽረው ህይወት በጣም አጭር መሆኗን ትኩረት ለመስጠት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰባ
"70" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰማንያ
"80" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ምርጥ የተባሉ ዘመናቻችን እንኳን ችግር እና ሀዘን ነበረባቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እጅግ የተሻሉ ዘመኖቻችን እንኳን በችግር እና ሀዘን ያለባቸው ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እንወሰዳለን
ይህ የሰዎች መሞት ሻል ባለ ቃል የሚገለጽበት መንገድ ነው። "ሞትን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊምዝም/ሻል ያለ ቃል መጠቀም የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 90:11
የቁጣህን ክብደት ፣ አንተን መፍራትን ያሚተካለለውን መአትህንስ ማን ያውቃል?
ጸሐፊው ጥያቄውን የተጠቀመበት ማንም የእግዚአብሔርን ቁጣ መቋቋም እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው። ስለዚህ ማንም እግዚአብሔር ከሚያደረገው ሊመልሰው አይችልም፣ ደግሞም ሰዎች ኃጢአት ባደረጉ ጊዜ ቁጣውን አልፈሩም። "ማንም የቁጣህን ክብደት አያውቀውም። ስለዚህ ኃጢአት ሲፈጽሙ አንዳቸውም የአንተን ቁጣ አልፈሩም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ ሆይ፣ ተመለስ! ይህ እስከ መቼ ይሆናል?
ያህዌን ቁጣው እንዳይቀጥል መለመን የተገለጸው ጸሐፊው እግዚአብሔር በአካል ከቁጣው ዞር እንዲል እንደፈለገ ተደርጎ ነው። "ያህዌ ሆይ፣ እባክህ ከእንግዲህ ቁጣህ አይቀጥል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ እስከ መቼ ይሆናል?
ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት እግዚአብሔር ቁጣውን እንዲያቆም መፈለጉን ለመግለጽ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ለአገልጋዮችህ ምህረት አድርግ
እዚህ ስፍራ "የአንተ አገልጋዮች" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰዎች ነው። "ለእኛ ለአገልጋዮችህ ምህረት አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
Psalms 90:14
በማለዳ ደስ አሰኘን
"እኛን በየማለዳው/በየጠዋቱ ደስ አሰኘን"
በቃልኪዳንህ ታማኝነት
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልኩ ሊገለጽ ይችላል። "ከእኛ ጋር ካለህ ቃል ኪዳን የተነሳ ታማኝ በመሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
መከራ ባሳየኸን ቀናት ችግር ባየንበት አመታት ፈንታ
እነዚህ ሁለቱም ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጸሐፊው ያህዌን የሚጠይቀው እነርሱን በቁጣቸው ጊዜ መጠን ደስተኞች እንዲያደርጋቸው ነው። "መከራ ባሳየኸን እና ችግር ባየንባቸው ጊዜያት መጠን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተን አገልጋዮች
እዚህ ስፍራ "የአንተ አገልጋዮች" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰዎች ነው። "እኛ አገልጋዮችህ" ወይም "እኛን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የእኛ ልጆች
እዚህ ስፍራ "ልጆች" ማለት ልጆች እና ትውልዶች ማለት ነው።
ክብርህን እናያለን
"ክብር" የሚለው ረቂቅ ስም "ታላላቅ ነገሮች" በሚለው ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ያደረግሃቸውን ታላላቅ ነገሮች እንመለከታለን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 90:17
የእግዚአብሔር የአምላካችን ሞገስ በላያችን ይሁን
"ሞገስ" የሚለው ረቂቅ ስም "መልካም መሆን" በሚለው ውስጥ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር አምላካችን ለእኛ መልካም ይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 91
Psalms 91:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻይ በሆነው ...ዘንድ የሚኖር እርሱ...ያድራል

"መጠጊያ/መጠለያ" እና "ጥላ" እንደሚሉት ለጥበቃ ዘይቤያዊ አገላለጽ እንዳላቸው ቃላት ሁሉ "መኖር" እና "ማደር" የሚሉት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ስለዚህም ሁለቱን ስንኞች በአንድ ላይ ማጣመር ይቻላል። "እጅግ ከፍ ያለው እና ሁሉን ቻይ የሆነው በእርሱ ጥበቃ ውስጥ ለሚኖሩ ጥንቃቄ ያደርግላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

እጅግ ከፍ ባለው መጠለያ/ በልዑል መጠጊያ የሚኖር

"መጠለያ" የሚለው ቃል ያህዌን የሚያመለክት ዘይቤ ነው።"ልዑሉ ለእርሱ ጥበቃ በሚያደርግበት የሚኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እጅግ ከፍ ያለው /ልዑሉ

"ልዑል/እጅግ ከፍ ያለ" የሚለው ቃል ያህዌን ያመለክታል። ይህ በመዝሙር 18:13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ሁሉን ቻይ በሆነው ጥላ ስር ይቆያል/ያድራል

እዚህ ስፍራ "ጥላ" የሚለው ቃል ጥበቃ ለሚለው ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "ሁሉን ቻይ የሆነው ሊጠብቀው በሚችልበት ስፍራ ይቆያል/ያድራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉን ቻዩ

ሀይል ያለው እና ሁሉን ነገር ሊቆጣጠር/ሊገዛ የሚችል። ይህ በመዝሙር 68:14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ያህዌን እንዲህ እለዋለሁ

"ስለ ያህዌ እንዲህ እላለሁ"

መሸሸጊያዬ እና ምሽጌ

"መሸሸጊያ" አንድ ሰው ሊሄድ የሚችልበት እና የሚሸሸገው ሰው ወይም ነገር የሚያገኝበት ስፍራ ነው። "ምሽግ" ሰዎች ራሳቸውን እና ያላቸውን ንብረት ለመጠበቅ የሚያበጁት ስፍራ ነው። እዚህ ስፍራ አሳፍ እነዚህን ለጥበቃ እንደ ዘይቤ ተጠቅሞባቸዋል። "እኔ ልሄድ የምችልበት እና እርሱም እኔን የሚጠብቅበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚውን ይመልከቱ)

Psalms 91:3

እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ ደግሞም ከክፉ መቅሰፍት ያድንሃል

የተተዉት ቃላት ሊጨመሩ/ሊገቡ ይችላሉ። "እግዚአብሔር አንተን ከአዳኝ ወጥመድ እና ሊገድል ከሚችል መቅሰፍት ያድንሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

የአዳኝ ወጥመድ

"አዳኝ አንተን ለመያዝ ካስቀመጠው ወጥመድ"

በክንፎቹ ይጋርድሃል/ይሸፍንሃል፣ ከክንፎቹም በታች መሸሸጊያ ታገኛለህ

እዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ጥበቃ የተገለጸው ወፍ ጫጩቶቿን ከአደጋ እንደ ምትጋርድበት "ክንፎች" ተደርጎ ነው። "በክንፎቹ ይሸፍንሃል" እና "ከክንፎቹ በታች" የሚሉት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "እርሱ በሰላም ይጠብቅሃል፣ ይጋርድህማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእርሱ ታማኝነት ጋሻ እና ጥበቃ ነው

እዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ታማኝነት የሚለው የተገለጸው በእርሱ የሚታመኑ ሰዎችን መጠበቅ እንደሚችል "ጋሻ" ተደርጎ ነው። "ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "መታመን" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ እንደሚጠብቅህ ልትታመንበት ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

መከላከያ

የዚህ ቃል ትርጉም በእርግጠኝነት አይታወቅም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ወታደሮች ራሳቸውን ከጠላት ቀስቶች እና ሰይፍ ለመከላከል በክንዳቸው የሚያዙት ትንሽ ጋሻ፤ ወይም 2) ወታደሮች በውስጡ ተሸሽገው ቀስት የሚወረውሩበት በክብ የተሰራ የድንጋይ ግርግዳ

Psalms 91:5

በምሽት ሽብር

ዘማሪው ስለ "ሽብር" የሚናገረው በምሽት ጥቃት እንደሚያደርስ መንፈስ ወይም አስፈሪ እንስሳ እና እጅግ አስፈሪ ሰዎች አድርጎ ነው። "በምሽት ከሚያጠቁህ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በምሽት...በቀን

እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ ላይ የተወሰዱት ማናቸውንም የምሽት ወይም የቀን ክፍለ ጊዜ ለማመልከት ነው። (ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀን የሚበር/የሚፈናጠር ፍላጻ

እዚህ ስፍራ "ፍላጻ/ቀስት" ቀስት ለሚወረውሩ ሰዎች የዋለ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በቀን በቀስት ጥቃት ከሚያደርሱብህ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ወይም ከሚከብህ መቅሰፍት

ዘማሪው ስለ ህመም የሚናገረው በሽታ ሰው ሆኖ ሰዎችን ለመግደል በምሽት እንደሚሄድ ሰው አድርጎ ነው። "በበሽታ የሚመጣ ሞት አያስፈራህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንከራተት/መሄድ

በማናቸውም ጊዜ ወደሚፈልግበት ስፍራ ሁሉ መሄድ

በጨለማ...በቀትር ወቅት

እነዚህ ሁለት ሀረጎች በአንድነት ሆነው የሚያመለክቱት ሁሉንም የምሽት እና ቀን ጊዜያት ነው። (ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)

በሽታ

በተመሳሳይ ጊዜ ብዙ ሰዎችን ህመም ላይ የሚጥል

በሺህ የሚቆጠሩ በጎንህ፣ በአስር ሺህ የሚቆጠሩ በቀኝህ ሊወድወቁ ይችላሉ

"ብዙ ሰዎች በዙሪያህ ሊወድቁ ይችላሉ።" ትክክለኛውን ቁጥር መተርጎሙ አንባቢዎችን ግራ የሚያጋባ ከሆነ፣ እርሱን መተው ይቻላል።

ይህ አይደርስብህም/አያገኝህም

"ክፉው አይጎዳህም"

Psalms 91:8

አንተ በዐይኖችህ ትመለከታለህ፣ ታያለህም

"አንተ ራስህ መከራ አትቀበልም፣ ነገር ግን በጥንቃቄ ታያለህ፣ ደግሞም ትመለከታለህ"

የክፉዎች መቀጣት

"ቅጣት" የሚለው ረቂቅ ስም በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "እግዚአብሔር ክፉዎችን እንዴት እንደሚቀጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ መሸሸጊያዬ ነው

ጸሐፊው፣ ከጠላቶቹ ጥበቃ ለማግኘት ያህዌ ለእርሱ አስተማማኝ ስፍራ እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። "አንድ ሰው በመሸሸጊያ ስፍራ ጥበቃ እንደሚያገኝ ያህዌ እኔን ይጠብቀኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልዑሉንም መሸሸጊያህ አድርግ

"ልዑሉንም መሸሸጊያህ ማድረግ አለብህ ።" ዘማሪው ለእግዚአብሔር መናገሩን አቁሞ ለአንባቢው ይናገራል።

Psalms 91:10

የትኛውም ክፉ ነገር አያገኝህም

ጸሐፊው መጥፎ ወይም ክፉ ነገርን የሚለማመድን ሰው የሚገልጸው ክፉ ሰው እንደሆነና በሌላ ሰው ላይ መጥፎ ነገር እንደሚያደርስ አድርጎ ነው። "አንዳችም ክፉ በአንተ ላይ አይደርስም" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሰውኛ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንዳች መቅሰፍት ወደ ቤትህ አይቀርብም

ዘማሪው ሌላውን ሰው የሚበክሉ ራሳቸውን የሚያደርሱትን ጉዳት ራሱን አድርጎ ያቀርባቸዋል። "ማንም ቤተሰብህን ሊጎዳ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ ያዛል

"ያህዌ ያዛል"

በመንገድህ ሁሉ

ዘማሪው አንድ ሰው ህይወቱን የሚኖርበትን መንገድ ሰውየው እንደሚራመድበት ጎዳና አድርጎ ይገልጻል። "በምታደርገው ነገር ሁሉ" ወይም "በሁሉም ጊዜያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 91:12

እነርሱ ያነሱሃል

"የያህዌ መላዕክት ያነሱሃል"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እግርህ በድንጋይ አይሰናከልም
መላዕክት የሚጠብቁት የአንባቢውን እግር ብቻ ሳይሆን ሌላውንም የሰውነቱን ክፍል ሁሉ ነው። "እግርህ በድንጋይ ...አይሰናከልም" የሚለው አንዳች ጉዳት አይደርስብህም የሚለው በግነት የተገለጸበት ሜቶኖሚ/ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ ምናልባት አንዳች ክፉ ነገር ዳግም በፍጹም አይደረስም ለሚለው እንደ ቃል ኪዳን አይወሰድም። "እግርህን እንቅፋት አይመታውም" ወይም "ጥቂት ክፉ ነገር እንኳን በአንተ ላይ አይደርስም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት፣ አጠቃላይ አስተያየት እንዲሁም ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

አንበሳዎችን ሰባብረህ ከእግርህ በታች ታደርጋለህ፤ በደቦል አንቦች እና በእባቦች ላይ ትጫማለህ/ ትረጋግጣቸዋለህ
"እግርህ በድንጋይ ይጋጫል/እንቅፋት እግርህን ይመታል" የሚለው አስተኛ ችግርን ሲያሳይ፤ አንበሶች እና እባቦች የታላላቅ አደጋዎች ምልክቶች ናቸው። ዘማሪው ስለ አንበሶች እና እባቦች የሚናገረው በሰው እግር እንደሚረጋገጡ ትንንሽ እንስሳት አድርጎ ነው። "አንበሶችን እና ዘንዶውን እንደ ትናንሽ እንስሳት ከእግርህ በታች ትፈጫቸዋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዘንዶ/መርዘኛ እባብ
መርዘኛ የእባብ አይነት

መረጋገጥ
በሀይል በላዩ ላይ በመራመድ መፍጨት/መጨፍለቅ

Psalms 91:14

እርሱ ራሱን ለእኔ ሰጥቷልና
"ወዶኛልና"

በመከራው ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ
ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "በችግሩ ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ድል አሰጠዋለሁ
"ድል" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ድል ነሺ አደርገዋለሁ" ወይም "ጠላቶቹን ማሸነፍ እንዲችል አበቃዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ረጅም እድሜ አጠግበዋለሁ
ዘማሪው ስለ ህይወት የሚናገረው አንድ ሰው ሊመገበው እንደሚችለው ነገር አድርጎ ነው። "ረጅም እና ደስተኛ ህይወት እንዲኖር እፈቅድለታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማዳኔን አሳየዋለሁ
"ማዳኔንም አሳየዋለሁ።" ዘማሪው እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን ያደረገውን ስራ የሚናገረው እንደ ቁሳዊ አካል አድርጎ ነው። "ያዳንኩት እኔ መሆኔን ያውቅ ዘንድ እታደገዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 92

Psalms 92:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለስምህ ውዳሴ/ምስጋና ማቅረብ
"የአንተ ስም" የሚሉት ቃላት "አንተ" ለሚለው ሜቶኖሚ /ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ለአንተ በውዳሴ መዘመር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በማለዳ የቃል ኪዳንህን ታማኝነት እናገራለሁ/አውጃለሁ
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ታማኝ" በሚለው ቅጽል ሊተረጎም ይችላል።"አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ እንደሆንክ በማለዳ አውጃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በየምሽቱ የአንተን እውነተኝነት
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። "እውነተኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "እውነት" በሚለው ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "አንተ የምትናገረው ነገር ሁሉ እውነት መሆኑን በየምሽቱ እናገራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

Psalms 92:4

አስደሳች
ደስታ

በስራዎችህ
"የአንተ ስራዎች" የሚለው ረቂቅ ስማዊ ሀረግ "አንተ የሰራኸው" በሚለው ተዛማጅ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "አንተ በሰራኸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የእጆችህ ስራዎች
"የእጆችህ ስራዎች" የሚለው ረቂቅ ስማዊ ሀረግ "የአንተ እጆች የሰሩት" በሚለው ተዛማጅ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "እጆች" የሚለው ቃል ለጠቅላላው ማንነት ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "አንተ የሰራኸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

የአንተ ስራዎች
"የአንተ ስራዎች" የሚለው ረቂቅ ስማዊ ሀረግ በተዛማጅ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "አንተ የሰራኸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሀሳቦችህ በጣም ጥልቅ ናቸው
"አንተ እስከ ምታደርገው ድረስ ለማድረግ ያቀድከውን መረዳት አንችልም"

የአንተ ሀሳቦች
"የአንተ ሀሳቦች" የሚለው ረቂቅ ስማዊ ሀረግ በተዛማጅ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "አንተ የምታስበው" ወይም "አንተ የምታቅደው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 92:6

ደነዝ
እንደ እንስሳ

ክፉዎች እንደ ሳር ሲበቅሉ
ይህ ክፉ ሰዎችን በፍጥነት ብዙ ስፍራ ከሚበቅል ሳር ጋር ያነጻጽራል። "ክፉ ሰዎች እንደ ሳር፣ በፍጥነት ሲታዩ እና በየስፍራው የሚገኙ ሲመስሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዘለዓለም ጥፋት ይፈረድባቸዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እግዚአብሔር እነርሱን ሙሉ ለሙሉ ለማጥፋት ወስኗል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 92:8

ያህዌ ሆይ፣ በእርግጥ ጠላቶችህን ተመልከት
ብዙ ቅጂዎች እነዚህን ቃላት አያካትቱም

እነርሱ ይጠፋሉ
"እነርሱ ይሞታሉ" ወይም "አንተ ትገድላቸዋለህ"

ክፉ የሚያደርጉ ሁሉ ይበተናሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "አንተ ክፉ የሚያደርጉትን ሁሉ ትበትናቸዋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይበተናሉ
ብዙ ቅጂዎች "ተበትነዋል" ይላሉ

ይበተኑ
"ይወሰዱ"

Psalms 92:10

ቀንዴን እንደ ዱር በሬ/አውራሪስ ቀንድ ከፍ ከፍ አደረግህ
ዘማሪው እግዚአብሔር እንደ ዱር እንስሳ ጠንካራ እንዳደረገው ይናገራል። እዚህ ስፍራ የእርሱ "ቀንድ" የሚወክለው ጥንካሬውን ነው። "እንደ ዱር በሬ/አውራሪስ ጠንካራ አደረግኸኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በለጋ ዘይት ተቀብቻለሁ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች እግዚአብሔር በዘማሪው ላይ ያስቀመጠው ቅባት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለመሆኑ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው 1) እርሱን ደስ ማሰኘቱ "አንተ እኔን በጣም ደስ አሰኘኸኝ" ወይም 2) እርሱን ጠንካራ አደረገው "አንተ እኔን ጠንካራ አደረግኸኝ" ወይም 3) ጠናቶችን እንዲያሸንፍ አስቻለው፣ "አንተ ጠላቶቼን እንዳሸንፍ አስቻልከኝ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዐይኖቼ የጠላቶቼን ውድቀት ተመለከቱ፤ ጆሮዎቼ የጠላቶቼን ክፉ ቀን ሰሙ
"ዐይኖች" እና "ጆሮዎች" የሚሉት ቃላት ለተመልካቹ እና ሰሚው ሰው ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። ስንኞቹ ሊጣመሩ ይችላሉ። "የክፉ ጠላቶቼን ሽንፈት አየሁ ደግሞም ሰማሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 92:12
ጻድቅ እንደ ዘንባባ ዛፍ ያብባል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፤ ጻድቅ ሰዎች እንደ ጤናማ የዘንባባ ዛፍ ናቸው ምክንያቱም እነርሱ 1) ጠንካራ ይሆናሉ/ይበረታሉ ወይም 2) ሰዎች ያከብሯቸዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የተተከሉ ናቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ ተክሏቸዋል" ወይም "ያህዌ እርሱ እንደ ተከላቸው ዛፎች ለእነርሱ እንክብካቤ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
በያህዌ ቤት…በአምላካችን በእግዚአብሔር አደባባዮች
ዘማሪው በእውነት እግዚአብሔርን ስለሚያመልኩ ሰዎች በያህዌ ቤት እንደሚያድጉ ዛፎች አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ያብባሉ
ዘማሪው ስለ ጻድቅ ሰዎች ጤናማ ዛፎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። "በጥሩ ሁኔታ ያድጋሉ" ወይም "በጣም ጠንካራ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በአምላካችን አደባባይ
በእየሩሳሌም ቤተመቅደስ በሚገኘው አደባባይ
Psalms 92:14
ፍሬ ያፈራሉ
ዘማሪው ጻድቅ ሰዎችን የሚበላ ፍሬ እንደሚያፈሩ ዛፎች አድርጎ ይገልጻቸዋል። "እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ለምለም እና አረንጓዴ ሆነው ይቆያሉ
ዘማሪው ጻድቅ ሰዎችን ዛፎች እንደሆኑ አድርጎ ይገልጻቸዋል። "ጠንካራ እና ጤናማ ሆነው ይቆያሉ" ወይም "ሁልጊዜም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ያደርጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አረንጓዴ/ለምለም፣ ያንን ለመናገር
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "አረንጓዴ/ለምለም፣ እነርሱ ያንን መናገር ይችላሉ" ወይም 2) "አረንጓዴ/ለምለም። ይህ ያንን ያሳያል"
እርሱ አለቴ ነው
"እኔን የሚጠብቀኝ ያህዌ ነው።" ዘማሪው ስለ ያህዌ የሚናገረው እርሱን እንደሚጠብቀው አለት አድርጎ ነው። ይህ በመዝሙር 18:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 93
Psalms 93:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ክብርን ተጎናጽፏል፤ ያህዌ ክብርን ለብሷል ብርታትንም ታጥቋል
ዘማሪው ስለ ያህዌ ጥንካሬ እና ክብር የሚናገረው ያህዌ እነዚህን ነገሮች እንደለበሳቸው አድርጎ ነው። "እርሱ ለእያንዳንዱ ሀያል ንጉሥ መሆኑን ያሳያል" ወይም "ግርማዊነቱን፣ ንጉሥ እንደሚገናጸፈው ካባ ሁሉም ይመለከተዋል፤ ሁሉም ነገር የያህዌን ብርታት እና እርሱ ታላቅ ስራ ለመስራት መዘጋጀቱን ያሳያል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ግርማዊ
የንጉሥ ሀይል እና የንጉሥ አደራረግ
ራሱን አስታጠቀ
ቀበቶ መታጠቅ- አንድ ሰው ለስራ ወይም ለጦርነት ለመዘጋጀት በወገቡ ዙሪያ የሚታጠቀው ከቆዳ ወይም ሌላ ቁስ የተሰራ ማሰሪያ/መታጠቂያ
ዓለም በጽኑ ተመስርታለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ዓለምን በጽኑ መሰረትክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ሊንቀሳቀስ/ሊናወጥ አትችልም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም መቼም ሊያንሳቅሳት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ከዘለዓለም ደረስ ነህ
"አንተ ለዘለዓለም አለህ"
Psalms 93:3
ውቅያኖሶች…የውቅያኖስ
አንዳንድ ቅጂዎች "ጎርፍ…የጎርፍ" ይላሉ። ቃሉ ብዙውን ጊዜ ወንዝን ያመለክታል (በመዝሙር 72:8 ላይ "ወንዝ" የሚለውን ይመልከቱ) ፣ ነገር ግን እዚህ ስፍራ የተመረጠው "ውቅያኖሶች…የውቅያኖሶች" የሚለው እንጂ ወንዞች የሚለው አይደለም፤ ምክንያቱም "የሚላተም እና የሚያጎራ" "ማዕበል" ያለው ውቅያኖስ እንጂ ወንዝ አይደለም
የውቅያኖስ ማዕበል እና ማጎራት፣ ድምጻቸውን አነሱ
ዘማሪው ማዕበልን የሚገልጸው መናገር እንደሚችል ሰው አድርጎ ነው። "ማዕበላቸው ሲጋጭ እን ሲያጓራ ታላቅ ድምጽ አሰሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማጓራት
ረጅም እና ከፍተኛ ድምጽ ማሰማት
ከብዙ ማዕበል መጋጨት በላይ፣ የባህር ታላቅ ነውጥ
"የባህር ታላቅ ነውጥ" የሚለው ሀረግ "ብዙ ማዕበል" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖረው እነዚህ ማዕበሎች እንዴት ታላቅ እንደሆኑ ትኩረት ይሰጣል። "ከባህሩ ታላቅ ነውጦች ሁሉ በላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትጉም የሚለውን ይመልከቱ)
ሞገድ
ከባህሩ ወደ ዳርቻ የሚመጣ ትልቅ ማዕበል
በላይ
ዘማሪው እግዚአብሔር የሚኖርበትን ከምድር በላይ ከፍ ብሎ እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። "በሰማያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 93:5
የተከበረ
በጣም የተረጋጋ
በጣም የታመኑ ናቸው
"ተለዋዋጭ ያልሆነ" ወይም "በፍጹም የማይለወጥ"
ቅድስና ቤትህን ያስጌጠዋል
ዘማሪው ስለ ያህዌ ቤት ውብ ልብስ እንደለበሰች ወይም እንዳጌጠች ሴት ሲገልጸው የያህዌን ቅድስና እንደማረ ልብስ ወይም ጌጥ አድርጎ ያናገራል። "አንተ ቅዱስ ነህና ቤትህ የተዋበ ነው" ወይም "እንዲትን ሴት ውብ ልብሶችና ጌጥ ይበልጥ ውብ እንደሚያደርጓት ቅድስናህ ቤትህን አስውቦታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቤትህ/የአንተ ቤት
በእየሩሳሌም የሚገኘው ቤተመቅደስ
ይዋባል
ውብ ይደረጋል

Chapter 94
Psalms 94:1
አቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
በላያችን አብራ
እዚህ ስፍራ "አብራ" የሚለው እግዚአብሔር ራሱን ለመግለጹ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ራስህን አሳይ" ወይም "ክብርህን ግለጽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የምድር ዳኛ ሆይ ተነስ፣ ለኩሩዎች የሚገባቸውን ስጣቸው
"የምድር ዳኛ ሆይ ና፣ ኩሩዎችን ቅጣቸው"
ተነስ
ዘማሪው አንድ ነገር ማድረግ መጀመርን እንደ መነሳት አድርጎ ይገልጸዋል። የእናንተ ቋንቋ አንድን ድርጊት ለመጀመር የሚጠቀምበት ቃል ካለው እዚህ ስፍራ ተጠቀሙበት። "እርምጃ ውሰድ" ወይም "አንድ ነገር አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 94:3
ያህዌ ሆይ ክፉዎች እስከ መቼ፣ እስከ መቼ ክፉዎች ደስ ይሰኛሉ?
ዘማሪው ጥያቄውን የሚደግመው፣ ክፉዎች ደስ ይላቸው ዘንድ ያህዌ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚፈቅድላቸው በመጠየቅ ደስ አለመሰኘቱን ለማሳየት ነው። ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ሊቀርብ ይችላል። "ያህዌ ሆይ በጣም ለረጅም ጊዜ ዝም አልካቸው፤ ክፉዎች በጣም ደስ እየተሰኙ እነርሱን ከመከልከል እጅግ ዘገየህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ለምን ክፉዎች ደስ ይሰኛሉ
ለምን የክፉዎች ደሰ መሰኘት በግልጽ ይታያል። "ክፉዎች ባደረጉት አንተ ፍጹም ስላልቀጣሃቸው እነርሱ ደስ ይሰኛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ያንቀረቁራሉ/ያፈሳሉ
"ክፉ የሚያደርጉ ሁሉ ያንቀረቁራሉ"
የትዕቢት ቃሎቻቸውን ያንቀረቁራሉ
ዘማሪው የክፉዎችን ንግግር እንደሚፈስ ፈሳሽ አድርጎ ይጽፋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉ የሚያደርጉ ሁሉ ይኩራራሉ
እነዚህ ሰዎች በክፉ ድርጊቶቻቸው እንደሚኩራሩ ትርጉሙ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ክፉ የሚያደርጉ ሁሉ በክፉ ድርጊታቸው ይኩራራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 94:5
አገሪቱን ጎዱ
እዚህ ስፍራ "አገር" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የአገሪቱን ህዝብ ያመለክታል። "የአገሪቱን ህዝብ አደቀቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አደቀቁ
ዘማሪው ሀይል ያላቸው ሰዎች ደካሞችን እንዳጠቁ የሚናገረው እነርሱን እንደ ማድቀቅ ወይም እንደ መሰባበር አድርጎ ነው። "መሰባበር" የሚለው በመዝሙር 72፡4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሙሉ ለሙሉ አጠፉ" ወይም "በታላቅ ሁኔታ ጎዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መበለቲቱን
"ባሏ የሞተባት ሴት
አባት የሌላቸው
"አባቶቻቸው የሞቱባቸው ልጆች"
የያዕቆብ አምላክ ይህንን አላየም
"የእስራኤል አምላክ ያደረግነውን አላየም"
Psalms 94:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው አሁን ክፉ ሰዎችን ያስተምራቸዋል።
እናንተ መቼ ትምህርት ታገኛላችሁ?
ቃለ ምልልሳዊው ጥያቄ ትኩረት የሚሰጠው ጸሐፊው በክፉ ሰዎች ላይ መቆጣቱን ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ!" ወይም "ከስህተቶቻችሁ ተማሩ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ጆሮን ያበጀው እርሱ አይሰማምን? ዐይንን የፈጠረው እርሱ አይመለከትምን?
እነዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር ወይም በትዕዛዝ መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ጆሮን የፈጠረው እግዚአብሔር እርሱ ይሰማል። ዐይንን የፈጠረው እግዚአብሔር እርሱ ይመለከታል" ወይም "እግዚአብሔር ጆሮን አበጅቷል፣ ስለዚህ እርሱ እንደማይሰማ አድርጋችሁ የምትቆጥሩትን ነገር አቁሙ። እግዚአብሔር ዐይኖችን ፈጥሯል፣ ስለዚህ እርሱ እንደማያይ ይምትሆኑትን አቁሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 94:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ጸሐፊው ክፉ ሰዎችን ማስተማሩን ቀጥሏል።
አገራትን የሚገስጽ እርሱ አያስተካክልምን?
ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። ያህዌ ህዝቡን እንደሚቀጣ ተጠቁሟል። "ያህዌ ህዝቡን እንደሚገስጽ ታውቃላችሁ፣ ስለዚህ ህዝቡን እንደሚያስተካክል እርግጠኞች መሆን ትችላላችሁ!" ወይም "እርሱ ህዝቡን ይቀጣል!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
እርሱ አይገስጽምን
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር ይገስጻል። "እርሱ ይገስጻል/ያርማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። 2) እግዚአብሔር ይቀጣል። "እርሱ ይቀጣል" (ምጸት የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ተን ናቸው
እዚህ ስፍራ የሰዎች አስተሳሰብ የተነጻጸረው በአየር ላይ ከሚጠፋው ከተን ወይም እንፋሎት ጋር ነው። ይህ ዘይቤ የሚያመለክተው እነርሱ ምን ያህል የማይጠቅሙ እና የማይረቡ መሆናቸውን ለማሳየት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ተን
"ጭጋግ።" ይህ ቃል በመዝሙር 39፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
Psalms 94:12
አጠቃላይ መረጃ፡
አሁን ጸሐፊው ዳግም ከያህዌ ጋር ይነጋገራል።
ለክፉዎች ጉድጓድ እስኪቆፈር ድረስ
ዘማሪው ያህዌ ክፉዎችን መቅጣቱን የሚነሰገረው እንስሳን በወጥመድ እንደሚይዝ አድርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ለክፉዎች ጉድጓድ እስክትቆፍር ድረስ" ወይም "ክፉዎችን እስክታጠፋ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Psalms 94:14
የእርሱ ርስት
"ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም እንዲሆኑ የመረጣቸው"
ፍርድ ዳግም ጽድቅ ይሆናል
ዘማሪው ፈራጆችን እንደሚሰጡት ውሳኔ አድርጎ ይገልጻቸዋል። "ፍርድ" የሚለው ረቂቅ ስም "ፈረደ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ዳኞች ዳግም በጽድቅ ይፈርዳሉ" ወይም "ዳኞች ዳግም ትክክለኛ ውሳኔ ይሰጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
በልባቸው ትክክለኛ የሆኑ
" በልባቸው ትክክለኛ የሆኑ" የሚለው ቅጽላዊ ሀረግ በስማዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ልባቸው ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል የሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)
ይህን ይከተላል
" ዳኞች በጽድቅ እንዲፈርዱ ይፈልጋል"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ክፉ አድራጊዎቸን ማን ይቋቋምልኛል? በክፉ አድራጊዎች ላይ ስለ እኔ የሚከላከል ማን ነው?
ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ማንም ለእኔ ክፉ አድራጊዎችን የሚከላከልልኝ የለም፡፡ ክፉዎችን በመዋጋት እኔን የሚረዳኝ የለም፡፡" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉዎች
"ክፉዎች" የሚለው ቅጽል በስማዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ክፉ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 94:17
ያህዌ ረዳቴ ባይሆን ኖሮ…ዝምታ
ይህ መላምታዊ ሁኔታ ነው፡፡ ያህዌ እርሱን ረድቶታል፣ ስለዚህም እርሱ በዝምታ ስፍራ አልተጋደመም፡፡ (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ ረዳቴ ባይሆን ኖሮ
"እርዳታ" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡፡ "ያህዌ ባይረዳኝ ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
በቶሎ በዝምታ ስፍራ እጋደማለሁ
እዚህ ስፍራ "እጋደማለሁ" የሚለው የሚያመለክተው "ሞትን" ሲሆን "በዝምታ ስፍራ" የሚለው የሚያመለክተው መቃብርን ነው፡፡ "በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ ሞቼ በዝምታ ስፍራ እጋደማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዩፊምዝም/ሻል ያለ ቃል መጠቀም የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ ሆይ፣ የአንተ የቃል ኪዳን ታማኝነት አቁሞኛል
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልኩ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ያህዌ ሆይ፣ አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ነህና እርዳኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
በውስጤ ያለው ሀዘን ሲበዛ፣ የአንተ ማጽናናት ደስተኛ ያደርገኛል
ዘማሪው ስለ ሀዘን የሚናገረው መከራዎቹን እንደሚቆጥራቸው አድርጎ ነው፡፡ "ማጽናናት" የሚለው ረቂቅ ስም "ማስተዛዘን" ወይም "ማጽናናት" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ስለ ብዙ ነገሮች በምጨነቅበት ጊዜ፣ አንተ ታጽናናኛለህ ደግሞም ደስተኛም ታደርገኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 94:20
አመጻን ህጋዊ የሚያደርግ የጥፋት ዙፋን ከአንተ ጋር ሊተባበር ይችላልን?
ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የዋለው አንድን ጉዳይ ግልጽ ለማድረግ ነው፡፡ ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ኢፍትሃዊ ህግ የሚያወጣ ክፉ መሪ የአንተ ወዳጅ አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የጥፋት ዙፋን
እዚህ ስፍራ "ዙፋን" የሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ንጉሥን ወይም መሪን ያመለክታል፡፡ "ክፉ መሪ" ወይም "ብልሹ ዳኛ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አድማ/ሴራ
x
Psalms 94:22
ያህዌ ከፍ ያለ ማማዬ ነው
እዚህ ስፍራ "ማማ" ጥበቃ ለሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው፡፡ "ያህዌ ከጠላቶቼ ጠበቀኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር የመሸሸጊያ አለቴ ሆነኝ
ዘማሪው እግዚአብሔር እርሱን መጠበቁን የገለጸው፣ ደህንነት ለማግኘት እንደሚሄድበት ስፍራ አድርጎ ነው፡፡ "አለት" እና "መሸሸጊያ" የሚሉት ቃላት በመዝሙር 62:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ፡፡ "እግዚአብሔርን እንዲጠብቀኝ ለመንኩት፣ እርሱም በሀይሉ ጠበቀኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የገዛ ክፋታቸውን በራሳቸው ላይ ያመጣባቸዋል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በሌሎች ላይ ክፉ እንዳደረጉት በእነርሱ ላይ ያደርግባቸዋል" ወይም 2) "በሌሎች ላይ ባደረጉት ክፉ ነገሮች ሁሉ ይቀጣቸዋል፡፡"
ይቆርጣቸዋል
ይህ "ይገድላቸዋል" ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በራሳቸው ክፋት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ክፉ ነገሮችን ሲያደርጉ" ወይም 2) "ክፉ ነገሮች በማድረጋቸው ምክንያት፡፡"

---

Chapter 95
Psalms 95:1
አጠቃላይ መረጃ:
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው፡፡ (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
የደህንነታችን አለት
ዘማሪው ስለ ያህዌ የሚናገረው፣ ያህዌን ሰዎች ለደህንነታቸው እንደሚወጡት ተራራ አድርጎ ነው፡፡ "አለት" እና "የእኔ ደህንነት" የሚሉት በመዝሙር 18:46 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ፡፡ "እኛ ልንሄድ የምንችልበት አለት እና እግዚአብሔር እኛን የሚያድንበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ እርሱ መገኛ ግቡ
ዘማሪው አንባቢ ወደ አንድ ንጉሥ ክፍል እንዲገባ እንደሚናገር አድርጎ ይገልጻል፡፡ "እርሱ ወደሚገኝበት ሂዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከምስጋና ጋር
"ወደ እርሱ መገኘት ስንገባ እናመስግነው"
ከአማልዕክት ሁሉ ይልቃል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች፣ ያህዌ ታላቅ ንጉሥ ነው የሚል ነው፡፡ 1) "በሌሎች አማልዕክቶች ላይ ሁሉ የሚገዛ፣" ወይም 2) "ከሌሎች አማልዕክት ሁሉ በጣም የተሻለ፡፡"
Psalms 95:4
በእርሱ እጅ
"በእርሱ ቁጥጥር" ወይም "እርሱ ሃላፊ ይሆናል" ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጥልቆች
x
Psalms 95:6
መንበርከክ
ብዙውን ጊዜ መሸነፍን ለማሳየት ሁለቱንም ጉልበቶች በመሬት ላይ ማድረግ፡፡ (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ የመሰማሪያው ህዝብ
"መሰማሪያ" የሚለው ቃል እንስሳት በሚሰማሩበት ስፍራ ስለሚያገኙት ምግብ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን ይህም ደግሞ በተራው ያህዌ ለህዝቡ ለሚያደርገው አቅርቦት ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው፡፡ "እኛ የሚያስፈልገንን የሚያሟላን ህዝቡ ነን" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
መሰማሪያ
እንስሳት ለመጋጥ ሳር የሚያገኙበት አካባቢ
የእጁ በጎች
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እረኛ በጎችን እንደሚጠብቅበት መንገድ ያህዌ እንዴት ህዝቡን እንደሚጠብቅ ነው፡፡ "እረኛ በጎቹን እንደሚጠብቅ እርሱ የሚጠብቃቸው ህዝቦች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዛሬ እነሆ፣ የእርሱን ድምጽ ትሰማላችሁ!
"እነሆ፣ ዛሬ ድምጹን ትሰማላችሁ!" ዘማሪው ይሁነኝ ብሎ የሚናገረውን ይተረጉመዋል፡፡
የእርሱን ድምጽ ስሙ
እዚህ ስፍራ "የእርሱ ድምጽ" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን ንግግር ወይም እርሱ የተናገረውን ነው፡፡ "እግዚአብሔር ሲናገር አድምጡ" ወይም "እግዚአብሔር የሚናገረውን ስሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 95:8
አጠቃላይ መረጃ፡
እዚህ ላይ ጸሐፊው ያህዌ የተናገራቸውን ቃላት ይጽፋል
ልባችሁን አደነደናችሁ
"ግትር ሆናችሁ"
መሪባ፣...ማሳህ
እነዚህ እስራኤላውያን በማመጻቸው ምክንያት ሙሴ የሰየማቸው በበረሃ የሚገኙ ስፍራዎች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
እኔን ፈተኑኝ...ተፈታተኑኝ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ያህዌ እነረሱን ከመቅጣቱ አስቀድሞ ህዝቡ ምን ያህል ክፉ ነገር በያህዌ ፊት ሊያደርጉ እንደሚችሉ የሚገልጹ ዘይቤዎች ናቸው። በመሰረቱ ሀረጎቹ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ በአንድ ላይ ሊቀናጁ ይችላሉ። "እኔን ፈተኑኝ" ወይም "እኔ ቅጣት ሳላደርስባቸው ክፉ ነገሮችን ማድረግ ይችሉ እንደሆነ ማየት ፈለጉ...እነርሱን መታገሴ ይቀጥል እንደሆነ ለማየት ተፈታተኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)
የእኔ ስራዎች
"እኔ ያደረግኳቸው አስደናቂ ነገሮች

---

Chapter 96
Psalms 96:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
አዲስ ዝማሬ
ማንም አስቀድሞ ያልዘመረው ዝማሬ
መላው ምድር
ይህ የምድር ሰዎችን በሙሉ ያመለክታል። "በምድር የሚኖሩ ሰዎች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ስሙን ባርኩ
"ስም" የሚለው ቃል ለያህዌ ለራሱ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ያህዌን ባርኩ" ወይም "ያህዌን ደስ የሚያሰኘውን አድርጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። "ክቡር ስሙ ይባረክ" የሚለው በመዝሙር 72፡ 19 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ማዳኑን ተናገሩ/አውጁ
"ደህንነት" የሚለው ረቂቅ ስም "አዳነ" የሚለውን ግስ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። "እርሱ እኛን እንደ አዳነን ተናገሩ" ወይም "እኛን ያዳነን እርሱ እንደሆነ ለሰዎች ተናገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 96:3
በአገራት መሃል ክብሩን አውጁ
"ስለ እርሱ ታላቅ ክብር በየአገራቱ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ተናገሩ"
ያህዌ ታላቅ ነው እጅግ ሊከበር ይገባዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ ታላቅ ነው። እጅግ አድርጋችሁ አወድሱት" ወይም "ያህዌ ታላቅ ነው፣ እናም ሰዎች እጅግ ሊያወድሱት ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሌሎች አማልዕክት ሁሉ በላይ ሊፈራ ይገባዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ከሌሎች አማልዕክት በላይ ፍሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 96:5
እርሱ በሚገኝበት
"እርሱ ባለበት"
ውበት እና ግርማ በእርሱ ዘንድ ናቸው
ዘማሪው ውበትን እና ግርማን በንጉሥ ፊት እንደሚቆሙ ሰዎች አድርጎ ያቀርባቸዋል። "እያንዳንዱ የእርሱን ውበት እና ግርማ ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጥንካሬ/ብርታት እና ውበት በቅድስናው ስፍራ ናቸው
"ጥንካሬ/ብርታት" እና "ውበት" የሚሉት ቃላት በተቀደሰው ስፍራ ለሚገኘው ለቃል ኪዳኑ ምስክር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "የቃል ኪዳኑን ታቦት ህግ/ድንጋጌ የያዘው የእርሱ ቅዱስ ስፍራ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 96:7
ያህዌን እንዲህ በሉት...ስለ እርሱ ክብር እና ብርታት ያህዌን እንዲህ በሉት
"ውዳሴ፣" "ክብር፣" እና "ብርታት" የሚሉትን ረቂቅ ስሞች እንደገና መግለጽ ይቻላል። እነዚህ ቃላት በመዝሙር 29፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። "ያህዌን አወድሱት...ያህዌን አወድሱት ምክንያቱም እርሱ ክቡር እና ብርቱ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ለያህዌ ስም የሚገባውን ክብር ስጡ
"ክብር" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ ወይም ቅጽል መልክ ሊገለጽ ይችላል። እነዚህ ቃላት በመዝሙር 29፡2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። "ስሙ እንደሚገባው ልክ ያህዌን አክብሩ" ወይም "እንደ ስሙ ታላቅነት ያህዌ ክቡር መሆኑን አውጁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ ስም የተገባው ነው
እዚህ ስፍራ "ስም" የእግዚአብሔርን ማንነት ያመለክታል። "እርሱ ይገባዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ አደባባይ
ካህናት ለያህዌ እንስሳትን የሚሰዉበት የቤተ መቅደሱ አደባባይ
Psalms 96:9
ለያህዌ ስገዱ
በውስጠ ታዋቂነት የተነገረው መረጃ ሰዎች በአምልኮ ጊዜ ጎነበስ በለው እንደሚሰግዱ ነው። "ያህዌን ለማምለክ ጎንበስ ብላችሁ ስገዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በቅድስና ውበት
"ውበት" እና "ቅድስና" የሚሉት በቅጽል መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እርሱ በክብር ውብ እና ቅዱስ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ተናወጡች
ከፍርሃት የተነሳ መንቀጥቀጥ
ምድር ሁሉ
እዚህ ስፍራ "ምድር" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የምድር ህዝብ በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ምድርም ደግሞ ተመሰረተች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርሱ ደግሞ ዓለምን መሰረታት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሷ ልትናወጥ አትችልም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ምንም ነገር ሊያናውጣት አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 96:11
ሰማያት ሀሴት ያድርጉ፣ ምድርም ደስ ይበላት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰማያት እና ምድር የተገለጹት እንደ ሰዎች ሁሉ ስሜት እንዳላቸው ተደርጎ ነው። "ሰማያት ሀሴትን እንዳደረጉ ምድርም ደስ እንዳላት ይሁን" ወይም 2) "ሰማያት" እና "ምድር" በእነዚያ ስፍራዎች ለሚኖሩ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "በሰማያት የሚኖሩ ሀሴት ያድርጉ በምድር የሚኖሩም ደስ ይበላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚሉትን ይመልከቱ)
በደስታ ጩኸት የተሞላ
በውስጠ ታዋቂነት የተነገረው መረጃ በባህር ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታትን ያመለክታል። እነርሱ የተገለጹት እንደ ሰዎች በደስታ መጮህ እንዳለባቸው ተደርጎ ነው። "የባህር ፍጥረታት በደስታ ጮሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መስኮች እና በውስጣቸው የሚገኙ ሁሉ ደስ ይበላቸው
"መስኮች እና በውስጣቸው የሚገኙ ሁሉ ደስ ይበላቸው።" ዘማሪው የሚናገረው "መስኮች" እና በውስጣቸው የሚኖሩ እንስሳት እንደ ሰዎች ስሜት እንዳላቸው አድርጎ ነው። "መስኮች ራሳቸው እና በውስጣቸው የሚኖሩ እንስሳት ሁሉ ደስ እንደሚላቸው ይሁኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በዱር የሚገኙ ዛፎች በደስታ ይጨሁ
ይህ ስለ ዛፎች የሚናገረው በደስታ እንደሚጮሁ ሰዎች አድርጎ ነው። "በጫካ የሚገኙ ዛፎች ሁሉ በደስታ እንደሚጮሁ ይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ በምድር ለመፍረድ ይመጣል። እርሱ በምድር ... እና በሰዎች ይፈርዳል
ሶስቱም ሀረጋት ተመሳሳይ ትጉም አላቸው፤ የመጨረሻዎቹ ሁለት ሀረጋት የመጀመሪያውን ለማጠናከር ውለዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለመፍረድ... ይፈርዳል
ሌላው ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም "ለመግዛት...ይገዛል" የሚል ነው።
እርሱ በምድር ላይ በጽድቅ ይፈርዳል
እዚህ ስፍራ "ምድር" የሚለው በምድር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። እነዚህ ቃላት በመዝሙር 9፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። "እርሱ በምድር ሰዎች ላይ ሁሉ በጽድቅ ይፈርዳል። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሰዎች በእርሱ ታማኝነት
"እርሱ ይፈርዳል" የሚሉት ቃላት በውስጠ ታዋቂነት አሉ። "እርሱ በሰዎች ላይ በእርሱ ታማኝነት ይፈርዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ታማኝነት
"ታማኝነት" የሚለውን ረቂቅ ስም ለመተካት እንደገና ሊጻፍ ይችላል። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በትክክል፣ እርሱ የሚያውቀው እውነት በመሆኑ" ወይም 2) "ለሁሉም ሰዎች ያለ አድልኦ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 97

Psalms 97:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ምድር ደስ ይበላት፤ የባህር ዳርቻዎችም ሀሴት ያድርጉ
ምድር እና የባህር ዳርቻ እንደ ሰው ስሜት እንዲኖራቸው ተነግሯል። "በምድር ላይ እና በባህር ዳርቻ ያላችሁ ሰዎች ሁሉ ሀሴት አድርጉ ደስም ይበላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የባህር ዳርቻዎች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በባህር ዳርቻ የሚገኝ መሬት" ወይም 2) "ደሴቶች።"
ደመናዎች እና ጨለማ እርሱን ከቦታል
"በዙሪያው ደመና ከቦት በጨለማ እንደተቀመጠ ሁሉ፣ እርሱን ልንመለከተው አንችልም"
ጽድቅ እና ፍትህ የዙፋኑ መሰረቶች ናቸው
"ዙፋን" የሚለው ቃል በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ተግባራት እና ቃላት ሜቶኖሚ/ ነው። ዘማሪው ጽድቅ እና ፍትህ ዙፋኑን የሚጠብቁ ቁሳዊ አካሎች እንደሆኑ አድርጎ ይገልጻል። "እርሱ በስራዎቹ ሁሉ ጻድቅ እና ትክክለኛ ነው" ወይም "እርሱ መግዛት ይችላል ምክንያቱም እርሱ በጽድቅ እና በፍትሃዊነት ይመራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
የዙፋኑ መሰረቶች
እዚህ ስፍራ "የዙፋኑ መሰረቶች" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ መንግሥቱን እንዴት እንደሚገዛ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 97:3

እሳት በፊቱ ይሄዳል
ዘማሪው እሳትን ከንጉሡ ያህዌ ፊት እንደሚሄድ ሰው እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል፤ ደግሞም ለሰዎች ንጉሡ እየመጣ እንደሆነ ይናገራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ተቃዋሚዎቹን ይበላል
"ጠላቶቹን ያቃጥላል"
ምድር ተመለከተች ተንቀጠቀጠችም
ጸሐፊው ስለ ምድር ያህዌ የሚያደርገውን የምትመለከት ሰው እንደሆነች እና በፍርሃት እንደምትንቀጠቀጥ አድርጎ ይገልጻታል። "ምድር እንደ ሰው ትመለከታለች ደግሞም ትንቀጠቀጣለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ተናወጠች
ከፍርሃት የተነሳ መንቀጥቀጥ
ተራሮች በያህዌ ፊት እንደ ሰም ይቀልጣሉ
ጸሐፊው ተራሮች በያህዌ ፊት እሳት ፊት እንዳለ ሰም እንደሚቀልጡ ይናገራል። "ተራሮች ያህዌ ሲቀርባቸው በፊቱ ሊቆሙ አይችሉም" ወይም "ተራሮች በያህዌ መገኘት ይወድቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 97:6

ሰማያት የእርሱን ፍርድ ያውጃሉ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ዘማሪው ሰማያት የያህዌን ትክክለኛነት የሚናገሩ መልዕክተኞች አድርጎ ይገልጻል። "ሁሉም ሰማይን ቀና ብሎ ማየት የሚችለውን ያህል እግዚአብሔር ትክክለኛ መሆኑን ማየት ይችላል" ወይም 2) ሰማያት የሚለው የሚገልጸው በሰማይ የሚኖሩ ፍጥረታትን ነው። "በሰማይ የሚኖሩ ሁሉ ያህዌ ትክክለኛ መሆኑን ያውጃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
የተቀረጹ ምስሎችን እና እርባ ቢስ የሆኑ ጣኦታትን የሚያመለኩ ሁሉ ያፍራሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እግዚአብሔር በእርባና ቢስ ጣኦቶች የሚመኩትን እና የተቀረጹ ምስሎችን የሚያመለኩት ያሳፍራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ጽዮን ሰማች...የይሁዳ ከተሞች
ይህ የሚያመለክተው በእነዚህ ምድሮች የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "የጽዮን ሰዎች ሰሙ...የይሁዳ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 97:9

ከሁሉ በላይ ከፍ ያሉ ናቸው
ዘማሪው ለመግዛት በጣም ጠንካራ የሆኑት በአካል ኬሎቹ ከፍ ያሉ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። "በዚያ ከሚኖሩ ሰዎች በላይ ሆነው የሚገዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
አንተ እስከ ሩቅ ከፍ ብለሃል
ዘማሪው ለመግዛት በጣም ጠንካራ የሆኑት በአካል ኬሎቹ ከፍ ያሉ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። "አንተ እስከ ሩቅ ከፍ ያልክ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ከክፉዎች እጅ ያስጥላቸዋል
"እጅ" የሚለው ቃል የሚወክለው ሀይልን ነው። ያህዌ ሰዎችን ከክፉዎች ሀይል ማዳኑ የተገለጸው ከእጃቸው እንደሚወስዳቸው/እንደሚያስጥላቸው ተደርጎ ነው። "እርሱ ከክፉዎች ሀይል ያድናቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ብርሃን ለ...ይዘራል፣ ደስታ ደግሞ ለ...

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ትኩረት ለመስጠት በአንድነት ቀርበዋል። "ያህዌ ትክክለኛ ስራ ለሚሰሩ ብርሃን ያወጣላቸዋል/ይዘራል፤ እውነተኛ ልብ ላላቸው ደስታን ይጨምርላቸዋል/ይዘራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ እንደዚሁም የተተወ/የተዘለለ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለጻድቃን ብርሃን ይወጣላቸዋል/ይዘራል

"መውጣት/መዝራት" የሚለው ቃል ወደፊት ውጤቱ ለሚታወቅ ነገር ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ብርሃን" ለመልካም ነገር ዘይቤ ነው። "ያህዌ ለጻድቃን መልካም እንደሚሆን ያስባል/ያቅዳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጻድቃን

"ጻድቅ" የሚለው ቅጽል በስማዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ጻድቅ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ሀቀኛ/ትክክለኛ ልብ ላላቸው ደስታ ይሆናል

"ይዘራል/ይሆናል" የሚለው ቃል በውስጠ ታዋቂነት አለ። "መዝራት" የሚለው ቃል ወደፊት ውጤቱ ለሚታወቅ ነገር ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ደስተኛነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ደስታ" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ደስተኝነት ሀቀኛ ልብ ላላቸው ይዘራል" ወይም "ያህዌ ሀቀኛ ልብ ያላቸው ወደፊት ደስተኛ ይሁኑ ዘንድ ያቅዳል/ያስብላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ እና ዘይቤያዊ አነጋገር እንደዚሁም ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ሀቀኛ ልብ ያላቸው

ልብ ለሰው ጠቅላላ ማንነት ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "ሀቀኛ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 97:12

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ ሀረግ ለትዕዛዙ ምክንያት የሆነውን ትዕዛዝ ይዟል። የእናንተ ቋንቋ ትዕዛዙን የሚከተል ምክንያት የሚፈልግ ከሆነ፡ "ያህዌ ለእናንተ ካደረገው ነገር የተነሳ፣ እናንተ ጻድቃን ሆይ፣ ቅድስናውን ስታስታውሱ ደስ ይበላችሁ ምስጋናም አቅርቡ"

በያህዌ ደስ ይበላችሁ

የዚህ ፈሊጥ ትርጉም ያህዌ ካደረገው ነገር የተነሳ ደስ መሰኘት ማለት ነው። "ያህዌ ካደረገው ነገር የተነሳ ደስ ይበላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቅድስናውን ስታስታውሱ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እርሱ ምን ያህል ቅዱስ እንደሆነ በምታስታውሱበት ጊዜ" ወይም 2) "ለቅዱሱ ስሙ፣" ይህም "ለእርሱ" ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 98

Psalms 98:3

አሰበ

"አስታወሰ።" በመዝሙር 20:3 ላይ "አሰበ" የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎመ ይልከቱ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የምድር ዳርቻ ሁሉ...መላው ምድር

እነዚህ ለምድር ሰዎች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "ከመላው ምድር የሆኑ ሰዎች...በምድር ያሉ ሰዎች ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የአምላካችንን ድል ማድረግ ይመለከታሉ

"ድል" የሚለው ረቂቅ ስም "አሸነፈ" የሚለውን ግስ በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። "አምላካችን ጠላቶቹን ሲያሸንፍ ይመለከታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በዝማሬ ይሞላሉ/እልል ይላሉ

"በድንገት በደስታ መዘመር ይጀምራሉ"

በደስታ ትዘምራላችሁ

"ከደስታ የተነሳ ትዘምራላችሁ"

በውዳሴ መዘመር

"ለእግዚአብሔር በውዳሴ መዘመር"

Psalms 98:5

ጣዕመ ዝማሬ

በደስታ የተሞላ ወይም ደስ የሚያሰኝ የሙዚቃ ድምጽ

የቀንድ መለከት

እንደ ሙዚቃ መሳሪያ የሚያገለግል የእንስሳ ቀንድ

ደስ የሚያሰኝ ድምጽ ማሰማት/ማውጣት

"ከፍ ያለ ድምጽ ማሰማት/እልል ማለት።" በመዝሙር 47፡1 ላይ "ጩኸት" የሚለው ድምጽ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Psalms 98:7

ባህር እና በውስጡ የሚገኘው ሁሉ እልል ይበል

ዘማሪው ባህርን ወደ እግዚአብሔር እንደ ሚጮህ ሰው አድርጎ ይገልጸዋል። "ባህር እና በውስጡ የሚገኘው ሁሉ እልል ይበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓለም እና በውስጧ የሚኖሩ ሁሉ

ዘማሪው የሚነገረው ዓለም ሰው እንደሆነች አድርጎ ነው። "እናም ዓለም እና በውስጧ የሚኖሩ ሁሉ እልል ይበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/ የተዘለለ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ወንዞች በእጆቻቸው ያጨብጭቡ፣ ደግሞም ተራሮች በደስታ እልል ይበሉ

ዘማሪው ወንዞች እና ተራሮች ማጨብጨብ እና እልል ማለት እንደሚችሉ አድርጎ ይናገራል። "ወንዞች ማጨብጨብ እንደሚችሉ እና ተራሮች በደስታ እልል ማለት እንደሚችሉ ይሁኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓለም... አገራት

እነዚህ ሀረጎች "በዓለም ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች" እና "በአገራት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች" ሜቶኖሚ ናቸው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አገራት በትክክለኝነት

ግሱ ከቀደመው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። "እርሱ አገራትን በትክክል ይዳኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/ የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

በትክክለኝነት

"በእውነተኝነት" ወይም "ያለ አድልኦ"

---

Chapter 99

Psalms 99:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

አገራት

ይህ የሁሉንም አገራት ሰዎች ያመለክታል። "የሁሉም አገራት ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መናወጥ

በፍርሃት መንቀጥቀጥ

እርሱ ከኪሩቤል በላይ በዙፋኑ ተቀምጧል

ኪሩቤል በቃል ኪዳኑ ታቦት መክደኛ ላይ የሚገኙ መሆኑን ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት ብዙውን ጊዜ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት፣ የያህዌ በላይ በሰማይ ተቀምጦ የቃል ኪዳኑ ታቦት የእግሩ ማረፊያ እንደሆነ አድርገው ይገልጻሉ። "እርሱ በዙፋኑ ላይ ከኪሩቤል በላይ በቃል ኪዳኑ ታቦት ተቀምጧል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተናወጠ

ተንቀጠቀጠ

ያህዌ በጽዮን ታላቅ ነው፤ እርሱ ከአገራት ሁሉ በላይ ከፍ ብሏል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"ያህዌ ታላቅነቱ በጽዮን ብቻ አይደለም፣ በአገራት ሁሉ ላይ እርሱ ከፍ ያለ ነው" ወይም "ያህዌ የሚገዛው በጽዮን ላይ ብቻ አይደለም፣ እርሱ በአገራት ሁሉ ላይ ይገዛል"
እርሱ በአገራት ሁሉ ላይ ከፍ ያለ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በሁሉም አገራት የሚኖሩ ሰዎች እርሱን ከፍ ያደርጉታል" ወይም "የአገራት ሁሉ ህዝቦች በታላቅ ሁኔታ ያወድሱታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ እንደዚሁም ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
ታላቁን እና አስደናቂ ስምህን ያወድሱ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር ከመናገር፣ ለእግዚአብሔር ወደ መናገር ዘወር ይላል። በእርግጥ ከዚህ ሀረግ በኋላ ዳግም ተመልሶ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል።
Psalms 99:4
እርሱ ፍትህን ይወዳል
"ፍትህ" የሚለው ረቂቅ ስም ትክክለኛ ለሆኑ ህጎች ሜቶኖሚ/ ነው። "አንተ የመሰረትካቸው ህጎች ትክክለኞች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
በእግሩ መቀመጫ ስር አምልኩት
"የእግር መቀመጫ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው፤ ብዙውን ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የያህዌ በላይ በሰማይ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፣ ያህዌ እግሩን የሚያሳርፍበት አድርገው የሚገልጹትን የቃል ኪዳኑን ታቦት ይሆናል። ሰዎች ያህዌን ሊያመልኩ እንደሚገባ ትርጉሙ ግልጽ ሊያደርግ ይችላል። "በእግሩ ማስቀመጫ ስር ሆናችሁ ያህዌን አምልኩት" ወይም "ያህዌን በመቅደሱ በዙፋኑ ፊት አምልኩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 99:6
የከበረ
"ጠቃሚ፣ ትኩረት የተሰጠው"
Psalms 99:8
አንተ መለስክላቸው
"አንተ ለህዝብህ ምላሽ ሰጠህ"
የእርሱ ቅዱሱ ተራራ
"የጽዮን ተራራ"

---

# Chapter 100

## Psalms 100:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
በደስታ ለያህዌ እልል በሉ
"ወደ ያህዌ እልልታ አሰሙ።" "እልልታ/የደስታ ጩኸት" የሚለው በመዝሙር 47:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
መላው ምድር
ይህ መላውን የምድር ህዝብ ያመለክታል። "በምድር ያለ ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
ወደ መገኘቱ ቅረቡ/ኑ
ዘማሪው አንባቢያን የንጉሡ ዙፋን ወደሚገኝበት ክፍል እንዲሄዱ እንደሚናገር አድርጎ ይገልጻል። "እርሱ በደስታ ዝማሬ ወደሚገኝበት ሂዱ" ወይም "እርሱ ይሰማችኋልና በደስታ ዘምሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

## Psalms 100:3

የመሰማሪያው በጎች
የእግዚአብሔር ህዝብ እንደ እርሱ በጎች ነው። "እግዚአብሔር አቅርቦት የሚያደርግለት እና የሚጠብቀው ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መሰማሪያ
እንስሳት የሚግጡበት/የሚሰማሩበት ሳራማ አካባቢ

---

# Chapter 101

## Psalms 101:1

አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
የቃል ኪዳን ታማኝነትን እና ፍትህን እዘምራለሁ
"ታማኝነት" እና "ፍትህ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በቅጽል መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ እንደሆንክ እና ፍትሃዊ እንደሆንክ እዘምራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

## Psalms 101:2

በአንድነት መንገድ እሄዳለሁ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ስለ "መኖር" የሚናገረው "መራመድ" እንደሆነ አድርጎ ነው። "እውነተኛ እና ትክክለኛ በሆነ መንገድ እኖራለሁ" ወይም "አንድነት/ሀቀኝነት የተሞላ ህይወትን እኖራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በቤቴ ውስጥ በአንድነት/ሀቀኝነት እራመዳለሁ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ስለ "መኖር" የሚናገረው መኖር "መራመድ" እንደሆነ አድርጎ ነው። ዳዊት አንድነትን በቤቱ ውስጥ ተወስኖ እንደሚኖር አካላዊ ቁስ አድርጎ ቢመለከትም፣ ቤቱን በአንድነት እንደሚቆጣጠር ይናገራል። "ቤቴን በአንድነት/ በሀቀኝነት እቆጣጠራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በዐይኖቼ ፊት ትክክለኛ ያልሆኑ ስራዎችን አላኖርም
"ትክክለኛ ያልሆኑ" የሚለውን ረቂቅ ስም ዳግም ማስተካከል ይቻላል። "ክፉ የሆነውን በዐይኖቼ ፊት ማኖር፣" የሚለው ፈሊጥ ትርጉም ይህ ማረጋገጥ ማለት ነው። "እኔ ባለሁበት ለማናቸውም ትክክለኛ ያልሆነ ድርጊት ለሚፈጽም ይሁንታ አልሰጥም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
በእኔ ላይ አይጣበቅም
ዳዊት "ክፉውን" በእርሱ ላይ ሊጣበቅ እንደማይችል ነገር አድርጎ ይናገራል። ይህም ማለት ክፉ ነገሮች እና ሰዎች ክፉ እንዳያደርጉ ይከለክላቸዋል ማለት ነው። "ክፉውን ፍጹም አስወግደዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መጣበቅ
ከአንድ ነገር ወይም ከአንድ ሰው ጋር በጣም በጥብቅ መያያዝ

## Psalms 101:4

ለክፉ
"ክፉ ለሆነ ማናቸውም ነገር"
በትዕቢት የሚያዋርድ እና እብሪተኛ ዝንባሌ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው እንዲህ አይነት ሰዎች እንዴት እንደሚታበዩ ትኩረት ይሰጣሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
በትዕቢት የሚያዋርዱ
"በግልጽ የሚታይ ትዕቢት።" ይህ ትዕቢቱን ማንም በግልጽ ሊመለከተው ስለሚችለው ሰው ይናገራል።
ትሁቱ ከጎኔ እንዲቀመጥ አደርጋለሁ
ይህ ማለት ዳዊት እንዲህ ያሉ ሰዎች በእርሱ ዙሪያ እንዲሆኑ እና ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ ይፈቅዳል። "በምድሪቱ የሚገኙ ታማኝ ሰዎች ከእኔ ጋር እንዲኖሩ እፈቅዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ታማኞች
ይህ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ሰዎችን ያመለክታል። "ታማኝ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
በአንድነት መንገድ የሚራመዱ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ስለ "መኖር" የሚናገረው "መራመድ" እንደሆነ አድርጎ ነው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"ሀቀኛ እና ትክክለኛ በሆነ መንገድ መኖር" ወይም "በሀቅ የተሞላ ህይወትን መኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 101:7

አስመሳይ ሰዎች...ሀሰተኛ ሰዎች

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ሀሳብ ሲኖራቸው በአንድነት የዋሉት ዳዊት አስመሳዮችን እንደማይታገስ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሀሰተኞች ተቀባይነት የላቸውም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሀሰተኞችን አልቀበላቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በዐይኖቼ ፊት

እዚህ ስፍራ "የእኔ ዐይኖች" የሚለው የሚያመለክተው ራሱን ዳዊትን ነው። "በእኔ ፊት" ወይም "እኔ በምገኝበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በየማለዳው

"በየዕለቱ)

ክፉዎች

ይህ የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው። "ክፉ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከያህዌ ከተማ

ዳዊት እርሱ የሚገኝበትን ከተማ "የያህዌ ከተማ" በማለት ይጠራታል።ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "የያህዌ ከተማ ከሆነችው፣ ከዚህች ከተማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 102

Psalms 102:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የተጎዳ

ይህ ጉዳት የደረሰበትን ሰው ያመለክታል። "ጉዳት የደረሰበት ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰቆቃውን በያህዌ ፊት አፈሰሰ

ጸሐፊው ሰቆቃውን የገለጸበት መንገድ ፈሳሽን ከማንቆርቆር ጋር ተነጻጽሯል። "ሀዘኑን ለያህዌ በነጻነት/በሙሉ ልቡ ገለጸ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 102:3

ቀኖቼ እንደ ጪስ አለፉ

እዚህ ስፍራ "ቀኖቼ" የሚለው የሚያመለክተው የጸሐፊውን ህይወት ሲሆን "ጪስ" የሚለው ሀሳብ በፍጥነት የሚጠፋን ነገር የሚገለጽ ነው። "ህይወቴ በቶሎ ያልፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አጥንቶቼ እንደ እሳት ይቃጠላሉ

እዚህ ስፍራ ጸሐፊው "አካሉን" እንደ "አጥንቶቹ" አድርጎ ይጠቅሳል። "ሰውነቴ እንደሚነድ ሆኖ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ልቤ ደቀቀ

እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ራሱን እንደ ራሱ "ልብ" አድርጎ ይገልጻል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ተስፋ ቆርጫለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ እንደ ጠወለገ ሳር ነኝ

ይህ ተስፋ መቁረጡን የገለጸበት ሌላው መንገድ ነው። "እንደ ጠወለገ ሳር እየደረቅኩ እንደሆነ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 102:5

እንደ በረሃ ቆልማሚት መሰልኩ

ብቸኝነቱን የሚያነጻጽረው ከቆልማሚት ጋር ነው፤ ቆልማሚት ከሌሎች ወፎች ጋር ከመሆን ይልቅ ብዙውን ጊዜ ብቻውን ይሆናል። "በበረሃ እንደሚገኝ ቆልማሚት ብቻዬን እና ተስፋ ቆርጬ እገኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቆልማሚት

ትልቅ አሳ የሚመገብ ወፍ

በፍርስራሽ ውስጥ እንደሚኖር ጉጉት ሆንኩ

ጸሐፊው ብቸኝነትን ራሱን በፍርስራሾች ውስጥ ከሚኖር ጉጉት ጋር በማነጻጸር መግለጹን ቀጥሏል። "በፍርስራሾች ውስጥ ተጥሎ እንደሚኖር ጉጉት ወፍ ብቻዬን ሆንኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉጉት ወፍ

ይህ በምሽት ከተኛበት የሚነሳ ወፍ ነው። "የምሽት ወፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Psalms 102:7

እንደ ብቸኛ ወፍ ብቻዬን ሆንኩ

ጸሐፊው የብቸኝነት ስሜቱን በትኩረት ለመግለጽ ራሱን ከወፍ ጋር ያነጻጽራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 102:9

አመድን እንደ ዳቦ ተመገብኩ

ዳዊት እንደ ሀዘን መግለጫ በአመድ ላይ ይቀመጣል፣ ስለዚህም አመድ በምግቡ ላይ ይወድቃል። "ዳቦ እንደምመገብ አመድ እመገባለሁ" ወይም "በሀዘኔ በምመገበው ዳቦ ላይ አመድ ይወድቅበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መጠጤን ከእንባ ጋር ቀላቀልኩ

ዳዊት ይሁነኝ ብሎ መጠጡን ከእንባው ጋር አልቀላቀለም፤ ይልቁንም እርሱ ሲያዝን እና ሲያለቅስ እንባው በሚጠጣበት ብርጭቆ ውስጥ ይገባል። "እንባዬ በምጠጣበት ብርጭቆ/ጽዋ ውስጥ ይንጠባጠባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደታች ልትጥለኝ ወደላይ ከፍ አደረግከኝ

እግዚአብሔር በቀጥታ የዳዊትን አካል ወደ ላይ ከፍ አላደረገውም ደግሞም ወደ ታች አልጣለውም፤ ይልቁንም ዳዊት ይህንን የተናገረው ምን እንደተሰማው እና እንደገጠመው ለመግለጽ ነው። "ወደላይ ያነሳኸኝ ቁልቁል ልትወረውረኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Psalms 102:11

ቀናቶቼ እንደ ደበዘዘ ጥላ ናቸው

ዳዊት በምድር ላይ ለመኖር የቀሩትን ጊዜያት የሚያነጻጽረው እየደበዘዘ ከሚሄድ ጥላ ጋር ነው። "በህይወት ለመኖር የቀረኝ እድሜ ምሽት ላይ በቶሎ እንደሚጠፋ ጥላ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሳር ጠውልጌያለሁ

የዳዊት አካል እየደከመ ሲሄድ እና ወደ ህይወቱ ማብቂያ ሲቃረብ፣ ራሱን ከሚጠወልግ ሳር ጋር ያነጻጽራል። "እንደ ሚጠወልግ ሳር ሰውነቴ ደከመ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መጠውለግ

መድረቅ እና መጨማደድ

ዝናህ ለትውልዶች ሁሉ ነው

"በሚመጡት ትውልዶች ሁሉ ትታወቃለህ"

ዝና

በብዙ ሰዎች መታወቅ

Psalms 102:13

በጽዮን ላይ ምህረት አድርግ

እዚህ ስፍራ "ጽዮን" የሚያመለክተው በጽዮን የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "በጽዮን ሰዎች ላይ ምህረት አድርግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሷ ላይ

"እርሷ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጽዮንን ነው።

ድንጋዮቿን/ቅጥሮቿን በውዴታ ያዛቸው

"ድንጋዮች" የሚለው የሚያመለክተው ከመደምሰሷ አስቀድሞ የከተማይቱ ቅጥር ክፍል የሆኑን ድንጋዮች ነው። "አሁንም አስቀድሞ የከተማይቱ ቅጥር የነበሩትን

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ድንጋዮች ውደዳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ስምህ
እዚህ ስፍራ "ስምህ" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌን ነው። "አንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ክብርህና ከፍ ከፍ ያደርጋሉ
ሰዎች ያህዌን ከክብሩ የተነሳ ከፍ ከፍ ያደርጋሉ። እዚህ ስፍራ ያህዌ የተገለጸው በክብሩ ነው። "አንተን ያከብራሉ፣ ምክንየቱም አንተ ክቡር ነህ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በክብሩ ይታያል
"በክብሩ ይታያል" ወይም "ሰዎች ክብሩን ያያሉ"
Psalms 102:17
ምሲኪኖች/ችግረኞች
ይህ ሚስኪናንን ያመለክታል። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ጸሎታቸውን አይንቅም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ ጸሎታቸውን ይቀበላል/ይሰማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም አሉታዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ለመጪው ትውልድ ይተላለፋል/ይጻፋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ይህንን ለመጪው ትውልድ አስተላልፈዋለሁ/እጽፈዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 102:19
እርሱ ከተቀደሰው ከፍ ካለው ስፍራው ሆኖ ወደ ታች ተመልክቷል፤ ያህዌ ከሰማይ ተመልክቷል
እነዚህ ሁለቱ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድነት የዋሉት እግዚአብሔር እንዴት ከሰማይ ወደ ታች እንደ ተመለከተ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የተቀደሱት ከፍታዎች
"ከምድር በላይ ከፍ ያለ የእርሱ ቅዱስ ስፍራ"
ሞት የተፈረደባቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ባለስልጣናት ሞት የፈረዱባቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
Psalms 102:21
በጽዮን ያለውን ስሙን፣ ደግሞም በእየሩሳሌም የሚወደሰውን የያህዌን ስም አውጁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም የያህዌ ስም መወደሱን ትኩረት ይሰጣሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 102:23
ብርታቴን ወሰደ
ዳዊት እግዚአብሔር ደካማ እንዳደረገው የሚገልጸው የእርሱ ጥንካሬዎች ከእርሱ ሊወሰዱ እንደሚችሉ አካላዊ ቁስ አድርጎ ነው። "ደካማ አደረገኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቀኖቼ
እዚህ ስፍራ "ቀኖች" የሚለው ቃል የእርሱን ህይወት ያመለክታል። "የእኔ ህይወት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔን አትውሰደኝ
ዳዊት እግዚአብሔርን የሚጠይቀው እንደሞት እንዳይፈቅድ/እንዳይገድለው ነው። "ከምድር አትውሰደኝ" ወይም "አትግደለኝ/እንደሞት አትፍቀድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ በትውልዶች ውስጥ ሁሉ በዚህ አለህ
"አንተ በትውልዶች ሁሉ መሃል አለህ"
Psalms 102:25
እርሱ ሁሉም ያረጃሉ
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "መሬትን" እና "ሰማያትን" ነው
አመታትህ መጨረሻ አይኖራቸውም
እዚህ ስፍራ ዳዊት እግዚአብሔር ህያው የሚሆንበት የጊዜ ርዝመት እንደ እርሱ "አመታት" ይገልጻል። ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ለዘለዓለም ትኖራለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ጥንድ አሉታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)
Psalms 102:28
ይኖራል
"መኖሩ ይቀጥላል"
በአንተ መገኘት መኖር
እዚህ ስፍራ ዳዊት የሚገልጸው፣ ትውልዶች በያህዌ ተጠብቀው የሚኖሩት በመገኘቱ መሆኑን ነው። "በአንተ መገኘት ውስጥ ሲኖሩ ይጠበቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 103
Psalms 103:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
የዳዊት መዝሙር
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ዳዊት ዝማሬውን ጽፏል፤ ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው፤ ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት መዝሙር ስልት የተጻፈ ነው።
በህይወቴ ሁሉ ለያህዌ ውዳሴ አቀርባለሁ፣ ደግሞም በውስጤ ባለው ሁሉ ለቅዱስ ስሙ ውዳሴ አቀርባለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ ያህዌን እርሱ ምን ያህል እንደሚያወድስ ትኩረት ይሰጣሉ። "በውስጥ ሰውነቴ ሁሉ ያህዌን አወድሰዋለሁ"ን በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለቅዱስ ስሙ ውዳሴ ስጡ
ይህ የሚያመለክተው ያህዌን ስም እንደ ያህዌነቱ ማወደስን ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በውስጥ ሰውነቴ ሁሉ/ባለኝ ሀይል ሁሉ
"በመላው ማንነቴ" ወይም "በሆንኩት ሁሉ።" ዳዊት ይህን ሀረግ የተጠቀመው ወደ ራሱ ለማመልከት እና ለያህዌ ያለውን መሰጠት ለማጉላት ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 103:3
የእናንተ…የአንተ
ዳዊት ስለ ራሱ ይናገራል፣ ስለዚህም "የአንቺ" እና "አንቺ" የሚሉትን ቃለት ራሱን ለማመልከት ይጠቀምባቸዋል። ብዙ ቅጂዎች/ትርጉሞች ይህንን በዩዲቢ ውስጥ እንደሚገኘው "የእኔ" እና "እኔ" በሚል ይገልጽዋቸዋል።
እርሱ የአንቺን ህይወት ከጥፋት ተቤዥቷል
ይህ ማለት ያህዌ እርሱን በህይወት ጠብቆታል። "እርሱ ከሞት ታድጎሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ በቃል ኪዳን ታማኝነት ዘውድ ጭኖብሻል ደግሞም ታላቅ ምህረት አድርጎልሻል
እዚህ ስፍራ አንድን ሰው መባረክ እና ታላቅ ክብር መስጠት የተገለጸው በሰው ራስ ላይ ዘውድ እንደ መድፋት ተደርጎ ነው። "ታማኝነት" እና "ምህረት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በተውሳከ ግስ መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እርሱ አንቺን በታማኝነት እና በምህረቱ ይባርክሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
ህይወትሽን በመልካም ነገር ያረካል
"ህይወትሽን" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው "አንቺ" የሚለውን ሲሆን፣ ነገር ግን ይህ በህይወት ዘመን ሁሉ ባርኮትን እንደሚሰጥ ትኩረት ያደርጋል። "እርሱ በመልካም ነገሮች በዘመንሽ ሁሉ ያረካሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ወጣትነትሽ እንደ ንስር ይታደሳል
"ወጣትነት ማደስ" የሚለው ዳግም ወጣት የመሆን ስሜት ማግኘት ማለት ነው። እዚህ ስፍራ ዳዊት ይህንን የወጣትነት ስሜት የሚያነጻጽረው ከንስር ፍጥነት እና ጥንካሬ ጋር ነው። "ወጣትነት ይሰማሻል ደግሞም እንደ ንስር ጠንካራ ትሆኛለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወጣትነትሽን
"ወጣትነት" የሚለው ቃል ጥንካሬን አንድ ሰው በጎልማሳነቱ የሚሰማውን ጥንካሬ ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Psalms 103:6
ፍትህን ያደርጋል
"ፍትህን እውን ያደርጋል"
የተጨቆኑ ሁሉ
ጭቆናን የሚፈጽሙ በግልጽ ሊጠቀሱ ይችላሉ። "በሰዎች ጭቆና የሚደርስባቸው ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ለእስራኤል ትውልዶች ያደረገው
"እንዲታወቅ ያደርጋል" የሚሉት ቃላት ከቀደመው ሀረግ ይታወቃሉ። እዚህ ስፍራ ሊደገሙ ይችላሉ። "እርሱ ስራዎቹ ለእስራኤል ትውልዶች እንዲታወቁ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
ታላቅ የቃል ኪዳን ታማኝነት አለው
"በምህረት እና ፍቅር የተሞላ"
Psalms 103:9
እርሱ ሁልጊዜ አይቀጣም፣ ሁልጊዜም አይቆጣም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለተኛው የመጀመሪያውን ሃሳብ ያጠናክራል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ እኛን አይከታተልም…ወይም እንደ በደላችን አይከፍለንም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ትይዩ ናቸው ደግሞም እግዚአብሔር እኛ መቀጣት የሚገባንን ያህል እንደማይቀጣን ትኩረት ይሰጣሉ። "በኃጢአታችን መቀጣት የሚገባንን ያህል አይቀጣንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ በደላችን አይከታተለንም
"አይቀጣንም"
Psalms 103:11
ሰማያት ሩቅ እንደሆኑ…እርሱን ለሚያከብሩት
ንጽጽሩ የሚያወዳድረው እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለውን ታላቅ ፍቅር፤ በሰማይና በምድር መሃል ካለው ትልቅ ርቀት ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የቃል ኪዳኑ ታማኝነት እጅግ ታላቅ ነው
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ስለዚህ እርሱ ለኪዳኑ በጣም ታማኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እስከ ምስራቅ ድረስ…በደላችንን ከእኛ አራቀው
በምስራቅ እና ምዕራብ መሃል ያለው ርቀት መለካት እስከማይቻል ድረስ እጅግ ሩቅ ነው። በዚህ ተነጻጻሪ ውስጥ፣ ርቀቱ የተወዳደረው እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ከእኛ ምን ያህል እንዳራቀው ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አባት እንደሚራራው… እርሱ በሚያከብሩት ላይ
እዚህ ስፍራ ጸሐፊው አባትለልጆቹ ያለውን ርህራሄ፣ ያህዌ እርሱን ለሚያከብሩ ካለው ርህራሄ ጋር ያነጻጽራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 103:14
እኛ እንዴት እንደተሰራን/እንደተበጀን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የእኛ አካል የሚመስለው" ወይም "እርሱ አካላችንን ያበጀው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
እርሱ አፈር መሆናችንን ያውቃል
ያህዌ የመጀመሪያውን ሰው አዳምን ሲፈጥር፣ የፈጠረው ከአፈር ነው። "እርሱ ከአፈር እንደ ፈጠረን ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰው ቀናቱ እንደ ሳር ነው
በዚህ ንጽጽር፣ የሰው ህይወት ዘመን መጠኑ የተወዳደረው ሳር ከመጠውለጉ አስቀድሞ ከሚኖራት አጭር ጊዜ ጋር ነው። "የሰው የህይወት ዘመን እንደ ሳር እድሜ አጭር ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ሜዳ አበባ ያብባል
በዚህ ንጽጽር፣ ሰው እንዴት በጊዜ ውስጥ እንደሚያድግ የተወዳደረው ከአበባ እድገት ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ያብባል
"ማበብ" በሚገባ ወይም ውብ ሆኖ ማደግ ነው።
ነፋስ በላዩ ይነፍሳል፣ ከዚያም ይጠፋል…በቅሎበት ከነበረው ስፍራ
እነዚህ ሀረጋት ስለ አበቦች እና ሳር መናገራቸውን ይቀጥላሉ። አበቦች እና ሳር እንዴት እንደሚሞቱ ከሰው አሟሟት ጋር ያነጻጽራሉ። "ነፋስ በአበቦች እና ሳሮች ላይ ይነፍሳል፣ እነርሱም ይጠፋሉ፤ ማንም የት ስፍራ በቅለው እንደነበር መናገር አይችልም - የሰው ልጅም እንደዚሁ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 103:17
የያህዌ የቃል ኪዳኑ ታማኝነት
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልኩ ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ነው
ይህ ማለት ያህዌ የያህዌ ፈቅር ለዘለዓለም ይቀጥላል ማለት ነው። "ለዘለዓለም ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)
የእነርሱ ትውልዶች
"እርሱን የሚያከብሩ ትውልዶች"
እነርሱ የእርሱን ኪዳን ይጠብቃሉ፣ ደግሞም ትዕዛዛቱን መጠበቅን አይዘነጉም
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ ዙፋኑን በሰማያት ላይ መስርቷል
እዚህ ስፍራ የያህዌ እንደ ንጉሥ መግዛት የተገለጸው እንደ "ዙፋኑ" ተደርጎ ነው። "ያህዌ በሰማይ እንደ ንጉሥ በሚገዛበት በወንበሩ ላይ ተቀመጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
መስርቷል
"አበጅቷል"
መንግስቱ ይገዛል
እዚህ ስፍራ እንደ ንጉሥ ስልጣኑ ላይ ለማተኮር፣ ያህዌ የተጠቀሰው "በእርሱ መንግሥት" ነው። "እርሱ ይገዛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 103:20
ፈቃዱን ይፈጽማል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ "ፈቃዱን ያደርጋል" ማለት ነው። "ፈቃዱን ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ በሚገዛባቸው ስፍራዎች ሁሉ
"እርሱ በሚገዛባቸው ስፍራዎች ሁሉ አመስግኑት"
በሙሉ ህይወቴ
የዚህ ሀረግ ትርጉም ያህዌን በሙሉ ልቡ ያወድሰዋል ደግሞም ለእርሱ ላለው መሰጠት ትኩረት ይሰጣል ማለት ነው። "በሙሉ ማንነቴ" ወይም "በሙሉ ነፍሴ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 104
Psalms 104:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ የተለመደ ነው። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ዝማሬ የውዳሴ መዝሙር ነው
በሙሉ ህይወቴ
የዚህ ሀረግ ትርጉም ያህዌን በሙሉ ልቡ ያወድሰዋል ደግሞም ለእርሱ ላለው መሰጠት ትኩረት ይሰጣል ማለት ነው። "በሙሉ ማንነቴ" ወይም "በሙሉ ነፍሴ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ውበትን እና ግርማዊነትን ለብሰሃል
"ውበት" እና "ግርማ" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ለያህዌ ክብር ትኩረት ይሰጣሉ። የተገለጹትም ያህዌ እንደ ልብስ እንደተጎናጸፋቸው ተደርጎ ነው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"በአንተ ዙሪያ ውበት እና ግርማ አለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
አንተ ራስህን እንደ ልብስ በብርሃ ሸፍነሃል
ያህዌ የተገለጸው ብርሃን እንደ ልብስ በዙሪያው እንደሸፈነው ተደርጎ ነው። "አንተ በብርሃን ተሸፍነሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ሰማያትን እንደ ድንኳን መጋረጃ ዘርግተሃል
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የተገለጸው ሰው በውስጡ የሚቀመጥበት መጋረጃ እንደሚዘረጋ፣ ያህዌ ሰማያትን እንደ ዘረጋ ተደርጎ ነው። "ሰው ድንኳን እንደሚዘረጋ አንተ ሰማያትን ዘረጋህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የአዳራሽህን አግዳሚ በደመናት ላይ ዘረጋህ
"አንተ ላይኛውን ክፍልህን በሰማያት ገነባህ።" ይህ የሚያመለክተው የእርሱ ቤት የላይኛው ወለል እጅግ ረጅም ከመሆኑ የተነሳ እስከ ደመናት እንደሚደርስ ነው።
አንተ ደመናትን ሰረገላህ አደረግህ
እዚህ ስፍራ ደመናት የተገለጹት ሰረገላ ሆነው ያህዌን እንደተሸከሙ ተደርጎ ነው። "አንተ ደመናት እንደ ሰረገላ እንዲሸከሙህ አደረግህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ በነፋሳት ክንፎች ላይ ትራመዳለህ
እዚህ ስፍራ የነፋስ መንፈስ የተገለጸው ያህዌ እንደሚራመድባቸው ክንፎች ተደርጎ ነው። "አንተ በነፋስ ላይ ትራመዳለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 104:4
እርሱ ነፋሳትን መልዕክተኞቹ አደረገ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እርሱ ነፋስ እንደ መልዕክተኛ መልዕክት እንዲያደርስ አደረገ፣ "እርሱ ነፋሳትን መልዕክተኞቹ አደረገ" ወይም 2) "እርሱ መልዕክተኞቹን እንደ ነፋስ ፈጣን አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
የእሳት ነበልባልን አገልጋዮቹ
ይህ በቀደመው ዐረፍተ ነገር ውስጥ በውስጠ ታዋቂነት ከቀረበው መረጃ ጋር ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ የእሳት ነበልባልን አገልጋዮቹ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ የምድር መሰረቶችን መሰረተ
እዚህ ስፍራ "መሰረቶችን መሰረተ" የሚለው ሀረግ "ፈጠረ" ማለት ነው። "እርሱ መላዋን ምድር ፈጠረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 104:6
አንተ ምድርን እንደ ልብስ በውሃ ሸፈንክ
እዚህ ስፍራ ምድርን የሸፈነው ውሃ የተነጻጸረው ትልቅ ልብስ አንድን ነገር እንዴት ሙሉ ለሙሉ እንደሚሸፍን ከዚያ ጋር ነው። "አንተ ምድርን ሙሉ ለሙሉ በውሃ ሸፈንክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ግሳጼ ውሆችን...እነርሱም ይሸሻሉ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ደግሞም በአንድነት የዋሉት እግዚአብሔር እንዴት እንደተናገረ እና ውሆች እንደሸሹ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይመለሳሉ
ወደ ኋላ መመለስ፣ ዝቅ ማለት
ይሸሻሉ
እዚህ ስፍራ ዘማሪው ስለ ውሆች መመለስ የሚናገረው የያህዌን ድምጽ ከሰሙ በኋላ ልክ እንደ እንስሳ እንደሚሸሹ አድርጎ ነው። "መሸሽ" የሚለው ቃል በፍጥነት መሮጥ ማለት ነው። "በችኮላ መሸሽ/ፈጥኖ መሄድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 104:8
ተራሮች ከፍ ይላሉ፣ ሸለቆችም ይሰፋፋሉ
እዚህ ስፍራ ዘማሪው የሚናገረው፤ ተራሮች እና ሸለቆዎች ራሳቸውን ለማንቀሳቀስ የፈቀዱ ይመስል እግዚአብሔር እንዲንቀሳቀሱ እና እንዲለወጡ ማድረጉን ነው። እነርሱ በዚህ መንገድ የተገለጹት በእግዚአብሔር ሀይል ላይ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንዳያልፉ ድንበር አበጀላቸው
እዚህ ስፍራ ዘማሪው እግዚአብሔር ውሆች እርሱ የፈጠረላቸውን ድንበራቸውን እንዳያልፉ ማድረጉን የገለጸው ውሆች ራሳቸው ድንበራቸውን ላለማለፍ እንደመረጡ አድርጎ ነው። እነርሱ በዚህ መንገድ የተገለጹት እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ያለውን ስልጣን ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ሊያልፉት/ሊያቋርጡት የማይችሉት ድንበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ድንበር
ዳርቻ
ለእነርሱ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ውሆችን ነው።
Psalms 104:10
ወራጆች
አነስተኛ ወንዞች
የሜዳ አህዮች ጥማቸውን ቆረጡ
ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። እነርሱ ውሃ በመጠጣት ትማቸውን ቆረጡ/ጠጥተው ረኩ። "የዱር አህዮች ውሃ ጠጥተው ከጥማቸው ረኩ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የወንዝ ዳርቻዎች
በወንዝ ዳርቻ የሚገኝ መሬት
በቅርንጫዎች መሃል ይዘምራሉ
እዚህ ስፍራ ዳዊት የወፎችን ጭውጭውታ እንደ ሚዘምሩ አድርጎ ይገልጸዋል። "በዛፍ ቅርንጫፎች መሃል ጭውጭው ይላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 104:13
በሰማይ ካለው የውሃ እልፍኙ ተራሮችን ውሃ ያጠጣል
ይህ ማለት እግዚአብሔር ዝናብ ያዘንባል ማለት ነው። ውሆች የተገለጹት በሰማይ ባለው እልፍኝ እንደሚኖሩ ተደርጎ ነው። "እርሱ ዝናብ ከሰማይ እንዲዘንብ በማድረግ ተራሮችን ውሃ ያጠጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ የስራ ፍሬ
"አንተ የፈጠርካቸው ብዙ መልካም ነገሮች"
ሰው እንዲንከባከባቸው ዕፅዋትን ታበቅላለህ
"እርሱ አደረገ" እና "በቀሉ" የሚሉት ቃላት በቀደመው ሀረግ ወስጥ በውስጠ ታዋቂነት ይገኛሉ፣ እናም እዚህ ስፍራ ሊደገሙ ይችላሉ። "እርሱ ሰው እንዲንከባከባቸው ተክሎች እንዲበቅሉ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 104:16
የያህዌ ዛፎች ብዙ ውሃ ያገኛሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ያህዌ ለእርሱ ዛፎች ብዙ ውሃ ይሰጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በዚያ ወፎች ጎጇቸውን ይሰራሉ
እነርሱ ጎጇቸውን በጥድ ላይ ይሰራሉ። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ወፎች ጎጆዎቻቸውን በጥድ ላይ ይሰራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሸመላ
ይህ የወፍ ዐይነት ነው። "ወፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ሽኮኮ
ሽኮኮ የአይጥ መልክ ያለው ትንሽ እንስሳ ነው። "በቋጥኝ የሚሸሸግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
Psalms 104:19
ወቅቶች
ይህ ቃል የሚያመለክተው በአመት ውስጥ ስለሚለዋወጡት የተለያዩ የአየር ንብረት ነው። አንዳንድ ቦታዎች ዝናባማ ወቅት እና ደረቅ ወቅት ሲኖራቸው፣ ሌሎች ፀደይ፣ በጋ፣ በልግ እንዲሁም ክረምት አላቸው።
ፀሐይ ወቅቷን ታውቃለች
እዚህ ስፍራ ዳዊት ፀሐይን የሚገልጻት የቀኑን ሰዓት እንደምታውቅ አድርጎ ነው። "እርሱ በሰዓቱ ፀሐይ እንድትጠልቅ ያደርጋል" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ታደርጋለህ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"ያህዌ ሆይ፣ አንተ ይህን ታደርጋለህ።" እዚህ ስፍራ ጸሐፊው ስለ ያህዌ ከመናገር ለያህዌ ወደ መናገር ዘወር ይላል።
Psalms 104:21
ታዳኝ/ታድኖ ለምግብ የሚውል እንስሳ
ለሌላው እንስሳ ምግብ የሚሆን እንስሳ
ምግባቸውን ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኛሉ
"ምግባቸውን ለማግኘት እግዚአብሔርን ተስፋ ያደርጋሉ"
ማፈግፈግ
ወደ ጎሬ/ ዋሻቸው ይመለሳሉ
ጎሬ/ዋሻ
የትናንሽ ጡት አጥቢዎች እና ትንንሽ እንስሳት ቤቶች
Psalms 104:23
በስራዎችህ ታጥለቀልቃቸዋለህ
እዚህ ስፍራ ዳዊት ዳዊት የፈጠራቸውን ነገሮች ብዛት ከመያዣቸው እየወጡ እንደ ሚያጥለቀልቁ ፈሳሾች አድርጎ ይገልጻል። "በስራህ ተሞልቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 104:25
ጥልቅ እና ሰፊ
"በጣም ጠልቅ እና ሰፊ ነው።" የባህር ጥልቀት እና ስፋት ይህ ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ ትኩረት ይሰጣል። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
ከቁጥር በላይ በሆኑ ፍጥረታት መሞላት
"ማንም ሊቆጥራቸው ከሚችለው በላይ የሆኑ ፍጥረታትን መያዝ"
የማይቆጠር
ማንም ሊቆጥረው ከሚችለው በላይ
ትናንሽ እና ታላላቅ የሆኑትን ሁሉ
ይህ ማለት ሁሉንም አይነት መጠን ያላቸው ፍጥረታት። (ከጽንፍ ጽንፍ የሚለውን ይመልከቱ)
መርከቦች በዚያ ይጓዛሉ/ይመላለሳሉ
"መርከቦች በባህር ላይ ይጓዛሉ/ይመላለሳሉ"
Psalms 104:27
እነዚህ ሁሉ
"እነዚህ ፍጥረታት ሁሉ"
በጊዜው ምግባቸውን ትሰጣቸዋለህ
"በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ምግባቸውን ትሰጣቸዋለህ"
በምትሰጣቸው ጊዜ፣ እነርሱ ይሰበስባሉ
የሚሰጣቸው ምግብ መሆኑን መግለጽ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "ምግብ በምትሰጣቸው ጊዜ፣ እነርሱ ይሰበስቡታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መሰብሰብ
ማከማቸት
እጆችህን ስትከፍት
ይህ ለፍጥረታቱ ምግብ ለመስጠት ያህዌ እጆቹን እንደሚከፍት ይገልጻል። "እነርሱን ለመመገብ እጆችህን በምትከፍትበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 104:29
ፊትህን ስትደብቅ
ይህ ማለት ያህዌ እነርሱን አይመለከትም ወይም ለእነርሱ ትኩረት አይሰጥም። "እነርሱን በማትመለከትበት ጊዜ" ወይም "ቸል ባልካቸው/በተውካቸው ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ አፈር ይመለሳሉ
ይህ ማለት አካላቸው ይበሰብሳል፤ ወደ አፈራቸውም ይመለሳሉ/ ተመልሰውም አፈር ይሆናሉ። "አካላቸው ይበሰብሳል፣ ወደ ምድር ይመለሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መንፈስህን ስትወስድ
ይህ የሚያመለክተው የእርሱ መንፈስ ለፍጥረታት ህይወት ለመስጠት እንደሚላክ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ይፈጠራሉ
እነርሱን የፈጠረው የያህዌ መንፈስ ነው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ የአገር ዳርቻን ታድሳለህ
"አንተ ምድር በአዲስ ህይወት እንዲሞላ ታደርጋለህ"
Psalms 104:33
ሀሳቦቼ አስደሳች ይሁኑ
ሀሳቡን የሚያነጻጽረው ጣፋጭ ጣዕም ካለው ነገር ጋር ነው። "ሃሳቦቼ ደስ የሚያሰኙ ይሁኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Psalms 104:35
ይወገዱ
ይጥፉ
ክፉዎች ከእንግዲህ አይገኙ
"ክፉዎች" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው። "ክፉ ሰዎች ይጥፉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 105
Psalms 105:1
አጠቃላይ መረጃ
x
Psalms 105:4
እግዚአብሔርን እና ኃይሉን ፈልጉ
“የእግዚአብሔርን ኃይል ፈልጉ” ማለት እንዲያጸናችሁ ጠይቁ ማለት ነው። “እግዚአብሔርን ፈልጉ፤ ኃይሉንም እንዲሰጣችሁ ጠይቁ”
አስታሱ
አስታውሱ እና አስቡ
ተአምራቱንና
“አስቡ” የሚለው ቃል ቀድሞ ከነበረው ሐረግ ጋር በማያያዝ የምንረዳው ነው። “ተአምራቱን አስቡ እና”
ከአፉ የወጣውን ፍርድ
እዚህ ላይ “አፍ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር የተናገረውን ነው። “የተናገረውን ፍርድ”
እናንተ የአብርሃም ዘሮች ... እናንተ የያዕቆብ ልጆች
ጸሐፊው ለእስራኤላውያን እነዚህን ስሞች በመጥራት ይናገራል።
የእርሱ አገልጋይ አብርሃም
“የእግዚአብሔር አገልጋይ አብርሃም”
Psalms 105:7
ያዘዘውን ቃሉን ... ያስባል
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ስለሆነም አጽንኦት ለመስጠት አንድ ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል። “ቃሉ” የሚለው የሚያመለክተው ቃል ኪዳኑን ነው። “ለባሪያው የገባውን ቃል ኪዳን ለዘላለም ያስባል”
ያስባል
ይህ ማለት ስለ አንድ ነገር ማስታወስ እና ማሰብ ማለት ነው። “ያስታውሳል”
ለሺህ ትውልዶች
“1,000 ትውልዶች”
Psalms 105:9
አሰበ
“አሰበ” ማለት አንድን ነገር አስታወሰ ማለት ነው። “ያስታውሳል”
ከአብርሃም ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን ... ለይስሐቅም የማለውን
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች “ቃል ኪዳኑ” እና “መሐላው” የሚያመለክቱት እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባውን ተመሳሳይ ቃል ኪዳኑን ነው።
ለይስሐቅ የማለውን
"ያደረገው" የሚለው ቃል በቀደመው ሐረግ ውስጥ ግንዛቤ ተወስዶበታል። እዚህ ላይም ሊደገም ይችላል። “ለይስሐቅ ያደረገው መሐላ” ወይም “ለይስሐቅ የሰጠው መሐላ”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Psalms 105:12
አገናኝ መግለጫ
መዝሙረኛው ስለ እስራኤል ይጽፋል።
እነርሱ በቁጥር ጥቂቶች በነበሩ ጊዜ
“እነርሱ” የሚለው ቃል እስራኤላውያንን ያመለክታል።
በምድሪቱ ላይ ስደተኞች ነበሩ
“ምድሪቱ” የከነዓንን ምድር ያመለክታል። “በከነዓን ምድር ስደተኞች ነበሩ”
ከ ሄዱ
“መቅበዝበዛቸውን ቀጠሉ”
ከሕዝብ ወደ ሕዝብ እንዲሁም ከመንግሥትም ወደ ሌላው
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ስለሆነም አጽንኦት ለመስጠት አንድ ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል።
Psalms 105:14
አገናኝ መግለጫ
መዝሙረኛው ስለ እስራኤል ይጽፋል።
ስለ እነርሱ ሲል
“ለእነርሱ መልካም እንዲሆን።” ይህም እስራኤልን የሚያመለክት ነው።
የቀባኋቸውን አትንኩ
እዚህ ላይ “አትንኩ” ማለት አትጉዷቸው ማለት ሲሆን፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዳይነኩ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት የተጠቀመበት የተጋነነ ቃል ነው።
“የቀባኋቸውን ሰዎች አትጉዱ”
Psalms 105:16
ጠራ
“ላከ።” ይህ ማለት በምድሪቱ ላይ ረሃብ እንዲሆን አደረገ።
የእህልን አቅርቦት ሁሉ
x
Psalms 105:18
የእግር ብረት
የእስረኛ እግሮች የሚታሰሩበት የብረት ሰንሰለት
እግሮቹ በእግር ብረት ታሰሩ፣ አንገቱም በብረት ታሰረ
እነዚህ መግለጫዎች እንደ ድርጊት ሊገለጹ ይችላሉ። “ግብፃውያን እግሮቹን በእግር ብረት አሰሯቸው፤ በአንገቱም ላይ የብረት ሰንሰለት አደረጉ።
የእግዚአብሔር ቃል ፈተነው
“የእግዚአብሔር መልእክት ፈተነው”
Psalms 105:20
ንጉሡም ይፈቱት ዘንድ ባሪያዎችን ላከ፤ የሕዝቡም ገዢ ከእስር ነፃ አደረገው
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ስለሆነም ንጉሡ ዮሴፍን ነፃ እንዳደረገው አጽንኦት ለመስጠት በአንድ ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል።
ከዚያም እስራኤል ወደ ግብፅ መጣ
እዚህ ላይ “እስራኤል” የተባለው ያዕቆብን ያመለክታል። ያዕቆብ ቤተሰቡን ከእርሱ ጋር ይዞ መጣ። “እስራኤልና ቤተሰቡም ወደ ግብፅ መጡ”
Psalms 105:24
እግዚአብሔር ሕዝቡን ፍሬያማ አደረጋቸው
ጸሐፊው የእስራኤልን መብዛት ብዙ ፍሬ እንዳፈራ ተክል አድርጎ ገልጾታል።
“እግዚአብሔር የሕዝቡን ቁጥር እጅግ አበዛው”
ሕዝቡን ለመጥላት፣ አገልጋዮቹንም ለመበደል
“ሕዝቡን ለመጥላት እና አገልጋዮቹን ለመበደል”
ምልክቶቹን በግብፃውያን መካከል አደረጉ ... ተአምራቱንም በካም ምድር
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። “ሙሴና አሮን የእግዚአብሔርን ተአምራት በግብፅ ውስጥ በካም ዝርያዎች መካከል አደረጉ”
ድንቆቹን በካም ምድር
“አደረጉ” የሚለው ቃል ቀደም ሲል በነበረው ሐረግ ውስጥ ግንዛቤ ተገኝቶበታል። እዚህም ላይ በድጋሚ ሊገለጹ ይችላሉ። “ድንቆቹንም በካም ምድር አደረጉ”
Psalms 105:28
ያንን ምድር ጨለማ አደረገው
“ሰማዩን አጨለመ”
እንቁራሪቶች
ትናንሽ የሚዘሉ እንስሳት
በገዢዎቻቸው ክፍሎች ውስጥ እንኳ
“በገዢዎቻቸው ክፍሎች ውስጥ ነበሩ”
Psalms 105:31
አገናኝ መግለጫ
መዝሙረኛው በግብፅ ላይ የነበረውን የእግዚአብሔርን ፍርድ መግለጹን ቀጥሏል።
መንጋ
የዝንብ መንጋ
ትንኞች
ትናንሽ የሚበሩ ነፍሳት
በረዶ
እንደ ዝናብ ከሰማይ የሚወርድ በረዶ
አጠፋ . . . ሰበረ
እግዚአብሔር በረዶን፣ ዝናብን እና መብረቅን አድርጎ ወይኑንና ዛፎችን አወደማቸው።
“አጠፋው እና ሰበረውም”
Psalms 105:34
እጅግ ብዙ አንበጣዎች
“እጅግ ብዙ አንበጣዎች”
አንበጣዎቹም እፅዋቱን ሁሉ በሉ . . . በመሬት ላይ ያለውን ሰብል ሁሉ በሉ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ስለሆነም አጽንኦት ለመስጠት በአንድነት ጥቅም ላይ ውለዋል። “አንበጣዎቹ እፅዋቱንና በምድሩ ላያ ያለውን ሰብል ሁሉ በሉ።
በምድራቸውም እያንዳንዱን በኩር ገደለ፣ የጉልበታቸው መጀመሪያ የሆነውን ፍሬ ሁሉ መታ
እዚህ ላይ በሁለተኛው ሐረግ ስለ “መጀመሪያ ፍሬ” የሚናገረው በመጀመሪያው ሐረግ ስለ መጀመሪያ ልጅ ወይም ስለ በኩር የተጠቀሰውን ለመግለጽ ነው። “በምድራቸውም በመጀመሪያ የተወለደውን ሁሉ ገደለ፣ ያም የጉልበታቸው የመጀመሪያ ፍሬ ነው” ወይም “ከዚያም እግዚአብሔር በግብፃውያን ቤት ውስጥ ያለውን የመጀመሪያ ልጅ ወይም ታላቅ ልጅ ገደለ”
Psalms 105:37
እስራኤላውያንን ከብርና ከወርቅ ጋር አወጣቸው
እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡ ጊዜ ብርና ወርቅ ይዘው ወጡ። “እስራኤላውያንን ከግብፅ ባወጣቸው ጊዜ ብርና ወርቅን ከንብረቶቻቸው ጋር ይዘው እንዲወጡ አደረጋቸው”
ከወገኖቹም አንዳቸውም በመንገድ ላይ አልተሰናከለም
ወደ ኋላ የቀረ አንድም አልነበረም። ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል።
“ወገኖቹ ሁሉ ጉዞውን ማድረግ ችለዋል”
Psalms 105:40
ድርጭትን አመጣ
እዚህ ላይ ይህንን ግልጽ ማድረግ ጠቃሚ ነው። ድርጭቶች ማለት ትናንሽ ወፎች ሲሆኑ እግዚአብሔር ይበሉ ዘንድ የላከላቸው ናቸው። “እግዚአብሔር ትናንሽ ወፎችን ይበሉ ዘንድ ላከላቸው”
ምግብ ከሰማይ
እግዚአብሔር መናን፣ የምግብ ዓይነት፣ ከሰማይ እንዲወርድ አድረገ። “ከሰማይ የወረደ ምግብ”
ፈሰሱ
“ውሃዎች ፈሰሱ”
አሰበ
ይህ ማለት አስታወሰ ማለት ነው። “አስተዋሰ”
Psalms 105:43
ሕዝቡን መራቸው . . . የመረጣቸውንም በድል አድራጊነት ድምፅ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ አውጥቶ በመራቸው ጊዜ ደስተኞች እንደ ነበሩ አጽንኦት ለመስጠት በአንድነት ጥቅም ላይ ውለዋል። ሕዝቡ በደስታ ይጮኹ ነበር።
“የተመረጡትን ሕዝቦቹን በደስታ እና በድል አድራጊነት ድምፅ መራቸው”
የመረጣቸው
እዚህ ላይ “የመረጣቸው” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን የተመረጠ ሕዝብ ነው። “የእርሱ የተመረጠ ሕዝብ”
የድል አድራጊነት ድምፅ
ጠላቶቻቸውን ስላሸነፉ ሕዝቡ በደስታ የሚያሰሙት የድል አድራጊነት ድምፅ ነው
ሥርዓቱን ጠብቁ ሕጎቹን ታዘዙ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው፣ አጽንኦት ለመስጠት

ግን በአንድነት ጥቅም ላይ ውለዋል። ሥርዓቱን "መጠበቅ" ማለት እነርሱን መታዘዝ ማለት ነው። "ሕጉንና ሥርዓቱን መታዘዝ"

---

Chapter 106

Psalms 106:1

አጠቃላይ መረጃ

በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል

ስውር ስሙ "ታማኝነት" ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። "ለቃል ኪዳኑ ለዘላለም ታማኝ ነውና"

የእግዚአብሔርን ኃያል ድርጊቶች . . . ሥራውንስ ማን ይናገራል?

ደራሲው ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔርን ለማመስገን ነው እንጂ መልስ ፈልጎ አይደለም። "ማንም የእግዚአብሔር ኃያላን ድርጊቶች . . . ሥራውንም መናገር አይችልም።"

የሚያስመሰግኑ ሥራዎች

"ምስጋና የሚገባቸው ሥራዎች"

Psalms 106:3

አስበኝ

"አስበኝ" የሚለው ሐረግ አንድን ነገር ማስታወስ ማለት ነው። "አስበኝ"

የመረጥከውን

"የመረጥከው" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በእግዚአብሔር የተመረጠውን ሕዝብ ነው። "የመረጥከውን ሕዝብህን"

በደስታ ደስ መሰኘት . . . እናም መክበር

እነዚህ ነገሮች ዳዊት "የመረጥካቸውን ብልጽግና በማየት" ከሚለው ጋር ስለሚያደርገው የሚናገረው ነው። "አደርጋለሁ" የሚለው ቃል እዚህ ጋ ሊደገም ይችላል። "በደስታ ደስ ይለኛል . . . እከብራለሁም"

መደሰት

ደስታ፣ ደስ መሰኘት

ከአንተ ርስት ጋር መክበር

እዚህ ላይ "የአንተ ርስት" የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች የሆኑትን እስራኤላውያንን ነው። "መክበር" ማለት "በአንድ ነገር መመካት" ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ በእግዚአብሔር ይመካሉ። "በታላቅነትህ ከሕዝብህ ጋር እመካለን" ወይም "ከሕዝብህ ጋ ስለ አንተ እንመካለን"

Psalms 106:6

አስገራሚ ሥራዎችህን አላደነቁም

"ለሠራሃቸው አስደናቂ ሥራዎች አላመሰገኑም"

በቃል ኪዳን ታማኝነትህ የሠራሃቸውን ብዙ ሥራዎች ቸል አሉ

"ታማኝነት" የሚለው ስውር ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። "አንተ ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ሆነህ ያደረግከውን ብዙ ሥራ ቸል አሉ"

በባህር ውስጥ . . . የመቃ ባህር

እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት አንዱን ባህር ነው። ሁለተኛው የባህሩ ስም ነው።

Psalms 106:8

የሆነ ሆኖ፣ እርሱ

"ምንም እንኳን አሁን የተናገርኩት እውነት ቢሆንም፣ እርሱ"

ስለ ስሙ

እዚህ ላይ "ስለ ስሙ" የሚይለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። "ስለ ራሱ መልካም ስም ሲል"

በጥልቅ በምድረ በዳ ውስጥ

እዚህ ላይ ዳዊት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በመቃ ባህር ውስጥ በደረቅ ምድረ በዳ እንደ መራቸው ይናገራል። "ጥልቁ" የሚያመለክተው የባህሩን ታችኛው ክፍል ሲሆን እግዚአብሔር ውሃውን በከፈለ ጊዜ የታየው ነው። "በመቃ ባህር ውስጥ በደረቅ ምድር"

Psalms 106:10

ከእጁ አዳናቸው ... እናም ከእጁ ታደጋቸው

እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ናቸው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው እንዳዳናቸው አጽንኦት ለመስጠት በአንድ ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል።

ከሚጠሏቸው እጅ

እዚህ ላይ "እጅ" የሚያመለክተው ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ነው። "ከሚጠሏቸውም ኃይል" ወይም "ከሚጠሏቸው ቁጥጥር"

ጠላቶቻቸውን ሸፈናቸው

ይህ ስለ ጠላቶቻቸው መስጠም ጨዋ በሆነ መንገድ መግለጽ ነው። "ጠላቶቻቸውን አሰጠመ"

ከዚያም እነርሱ የእርሱን ቃሎች አመኑ

እዚህ ላይ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "ዘሮቻቸውን" እና "የእርሱ" የሚለው ቃል ደግሞ "እግዚአብሔርን" ነው።

Psalms 106:13

ምክሩን አልታገሱም

እግዚአብሔር እንዲሄዱበት የሚፈልገውን ከመጠበቅ ይቅል እርሱን ሳይጠብቁ ነገሮችን ሁሉ አደረጉ። "የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጀመሪያ ሳይጠብቁ ነገሮችን አደረጉ"

የማይረኩ ምኞቶች

"እርካታ ሊሰጡ የማይችሉ ምኞቶች"

እግዚአብሔርን ተፈታተኑ

"በእግዚአብሔር ላይ አመጹ"

ነገር ግን እርሱ አጅግ አስከፊ በሽታ ላከ

እዚህ ላይ ዳዊት እግዚአብሔር ሰዎቹ ይጎዱ ዘንድ ልክ አንድ ሰው ሌላን ሰው ወይም መልእክተኛን እንደሚልክ በሽታን እንደ ላከባቸው ይናገራል። "ነገር ግን እርሱ በአስከፊ በሽታ እንዲሠቃዩ አደረጋቸው።

አስከፊ በሽታ

ሰዎች ቀስ በቀስ እንዲዳከሙ እና የተወሰኑት እንዲሞቱ የሚያደርግ በሽታ ነው

Psalms 106:16

በሰፈር ውስጥ

ይህ በምድረ በዳ የሚገኘውን የእስራኤል ሰፈር ያመለክታል። "በምድረ በዳ ሰፈር ውስጥ"

ምድር ተከፍታ ዋጠቻቸው

እዚህ ላይ ምድር ተከፍታ ሰዎችን መቅበሯ ፍጥረት አንድ ነገር ከመዋጡ ጋር ይነጻጸራል። "ምድር ተከፈተች ቀበረቻቸውም"

ዳታን

ይህ በሙሴ ላይ ያመፀ የታወቀ ሰው ነበር።

የአቢሮን ተከታዮች ተሸፈኑ

የአቢሮን ተከታዮችም መሬቷ ተከፍታ ዳታንን ስትቀብረው አብረው ተቀብረዋል። "የአቢሮን ተከታዮች ተሸፍነዋል" ወይም "የአቢሮን ተከታዮች ተቀብረዋል"

አቢሮን

ይህ በሙሴ ላይ ያመፀ የታወቀ ሰው ነበር።

እሳት በመካከላቸው ተነሣ፤ ክፉዎችን በላች

እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን፣ ክፉ ሰዎች በእሳት እንዴት እንደ ተገደሉ አጽንኦት ለመስጠት በአንድነት ተጽፈዋል።

Psalms 106:19

በኮሬብ የጥጃ ምስል ሠሩ ቀልጦ ለተሠራ ምስልም ሰገዱ

የጥጃው ምስል ከብረት ቀልጦ የተሠራ እንደ ነበር ይህ መረጃ ሊመዘገብ ይችላል። "በኮሬብ ቀልጦ የተሠራ የጥጃ ምስል አደረጉ ሰገዱለትም"

የእግዚአብሔርን ክብር በጥጃ አምሳያ ለወጡ

ይህ ማለት እግዚአብሔርን ከማምለክ ይልቅ የጥጃውን ምስል አመለኩ። "የእግዚአብሔርን ክብር ከማምለክ ይልቅ የጥጃውን ምስል አመለኩ"

የእግዚአብሔር ክብር

እዚህ ላይ እግዚአብሔር የተገለጠው በክብሩ ነው። "የተከበረው አምላካቸው" ወይም "የተከበረው አምላክ"

Psalms 106:22

የካም ምድር

ይህ የሚያመለክተው የካም ዝርያዎች የኖሩበትን ምድር ነው። "የካም ዝርያዎች የኖሩበት ምድር"

ታላላቅ ድርጊቶች

"አስደናቂ ነገሮች"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በቁጣው መቅሰፍት እንዳያጠፋቸው በመካከል ገብቶ በፊቱ ቆመ
እዚህ ላይ ዳዊት የሚናገረው ሙሴ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዳያጠፋቸው በመካከል ገብቶ ስለ መቆሙ ነው፡፡ “እግዚአብሔር እንዳያጠፋቸው በእስራኤላውያንና በእግዚአብሔር መካከል ቆመ”
Psalms 106:24
አጕረመረሙ
ተነጫነጩ
ቃል ኪዳኑ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር እንደ ርስታቸው እንዲወስዱ የገባላቸውን ቃል ኪዳን ነው፡፡
Psalms 106:26
የእርሱን እጅ ዘረጋ
“የእርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው፡፡ መሐላ በሚማልበት ጊዜ እጅን ማንሣት ደግሞ የተለመደ ነገር ነበር፡፡
ዘሮቻቸውን . . . በባዕድ ምድር በተናቸው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው ነገር ግን ትኩረት ለመስጠት በአንድነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ “እናም ዘሮቻቸው በባዕድ ምድር እንዲኖሩ አደረጋቸው”
በተነ
ይህ ማለት መበታተን ወይም አንድን ነገር ማሰራጨት ማለት ነው፡፡
Psalms 106:28
ለሙታን የሚደረግ መሥዋዕት
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል፡፡ “ለሙታን ያቀረቡት መሥዋዕት”
ለሙታን
“ሙታን” የተባሉት እስራኤላውያን ያመልኳቸው የነበሩት ጣዖታትና ባዕድ አማልክት ናቸው፡፡ “ለሞቱ አማልክት” ወይም “ሕይወት ለሌላቸው አማልክት”
መቅሰፍት መጣ
“መቅሰፍቱ ተሰራጨ”
እንዲናደድ አደረጉት
“አስቆጡት”
Psalms 106:30
ፊንሐስ ጣልቃ ለመግባት ተነሣ
x
Psalms 106:32
መሪባ
ይህ የቦታ ስም ነው፡፡
ከእነርሱ የተነሣ ተሰቃየ
ሙሴ ከሕዝቡ ኃጢአት የተነሣ ተሰቃየ፡፡ እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል ሕዝቡን የሚያመለክት ተውላጠ ስም ሲሆን ኃጢአታቸውንም ያመለክታል፡፡ “በድርጊታቸውም ምክንያት ተሰቃየ”
ከአሕዛብ ጋር ተቀላቀሉ
እዚህ ላይ ዳዊት የሚናገረው ሕዝቡ የአሕዛብን ሴቶች በማግባት ስለ “መቀላቀላቸው” ነው፡፡ “ነገር ግን ከአሕዛብ ጋር በጋብቻ ተደባለቁ”
ያም ለእነርሱ ወጥመድ ሆነባቸው
ጣዖቶቹ ወጥመድ ሆኑባቸው፡፡
Psalms 106:37
የወንዶችና የሴቶች ልጆቻቸውን ደም፣ የንጹሐንን ደም አፈሰሱ
“ደም ማፍሰስ” የሚለው ሐረግ “መግደልን” ለመግለጽ ጥቅም ላይ የሚውል ገላጭ የአነጋገር ዘይቤ ነው፡፡ “ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን በገደሉበት ጊዜ የንጹሐንን ደም አፍስሰዋል”
በሥራቸው ረከሰዋል
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል፡፡ “ሥራቸው አርክሶአቸዋል”
በድርጊታቸውም እንደ አመንዝሮች ሆኑ
እዚህ ላይ ዳዊት ለእግዚአብሔር ታማኝ አለመሆናቸውን ከማይታመኑትን አመንዝሮች ጋር ያነጻጽረዋል፡፡ “እነርሱም እንደ አመንዝሮች ለእግዚአብሔር ታማኞች አልሆኑም”
Psalms 106:40
ስለዚህ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ተቆጣ . . . የራሱን ሕዝብ ናቃቸው
“ስለዚህ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ተቆጣ ናቃቸውም”
በአሕዛብ እጅ አሳልፎ ሰጣቸው
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው፡፡ “እግዚአብሔር ሕዝቡን ይቆጣጠሩ ዘንድ ለአሕዛብ ፈቀደላቸው”
የጠሏቸው
“የጠሏቸው ሰዎች”
Psalms 106:42
ለባለ ሥልጣኖቻቸው ተገዢዎች ሆኑ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል፡፡ “ጠላቶቻቸው ለባለሥልጣኖቻቸው እንዲገዙ አደረጓቸው”
በራሳቸው ኃጢአት ሕግን አመጡ
እዚህ ላይ “ሕግን አመጡ” የሚለው ሐረግ በራሳቸው ላይ ጥፋትን አመጡ ማለት ነው፡፡ እንዲሁም፣ ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል፡፡ “ኃጢአታቸው አጠፋቸው”
Psalms 106:44
የሆነ ሆኖ፣ እርሱ
“ምንም እንኳን አሁን የተናገርኩት እውነት ቢሆንም፣ እርሱ” ይህንን በመዝሙር 106:8 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት፡፡
ጭንቀታቸው
“ስቃያቸው” ወይም “መከራቸው”
አሰበ
“አሰበ” የሚለው ቃል አንድን ነገር አስታወሰ ማለት ነው፡፡ “አስታወሰ”
እርሱ . . . ከጽኑ ፍቅሩ የተነሣ ተጸጸተ
“እርሱ . . . እስከ አሁን አጥብቆ ስለሚወዳቸው እንዲቀጣቸው አልወሰነም”
ያሸነፏቸው
“የማረኳቸው” ይህ የሚያመለክተው ምርኮኛ አድርገው የወሰዷቸውን የእስራኤላውያንን ጠላቶች ነው፡፡
ምሕረት አደረገላቸው
“ራራላቸው”
Psalms 106:47
አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ 106:48 ከዚህ መዝሙር መጨረሻ የሚበልጥ ነው፡፡ ከመዝሙር 90 እስከ መዝሙር 106 መጨረሻ ላሉት 4 መጽሐፍት በሙሉ የመዝጊያ መግለጫ ነው፡፡
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡ “ሕዝቡ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ያመስግኑ”
ለቅዱሱ ስምህ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር “በቅዱስ ስሙ” ተጠቅሷል፡፡ “ለአንተ”
ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ
ይህ የሚያመለክተው ሁለት ጽንፎችን ሲሆን ትርጉሙም ለዘለዓለም ማለት ነው፡፡ ይህንን በመዝሙር 41:13 እንዴት እንደ ተረጎምኸው ተመልከት፡፡ “ለዘለዓለም”

---

Chapter 107
Psalms 107:1
አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው፡፡
የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል፡፡ “ለቃል ኪዳኑ ለዘላለም ታማኝ ነው”
እግዚአብሔር የተቤዣቸው
“የተቤዣቸው” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ያዳናቸውን ሰዎች ነው፡፡ “እነርሱ እግዚአብሔር ያዳናቸው”
መናገር
ይህ ማለት ስለ አንድ ነገር ለሌሎች መናገር ማለት ነው፡፡ “እግዚአብሔር ስላደረገው ነገር ተናገሩ”
ከጠላት እጅ
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው የሚያመለክተው ኃይልን ነው፡፡ “ከጠላት ኃይል”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከምሥራቅ . . . እና ከደቡብ
እዚህ ላይ አራቱ አቅጣጫዎች ትኩረት የተሰጣቸው ከሁሉም ስፍራ እንደ ሰበሰባቸው ለማመልከት ነው። “ከሁሉም አቅጣጫ” ወይም “ከሁሉም የዓለም ክፍል”
ከምሥራቅና ከምዕራብ፣ ከሰሜን እና ከደቡብ
ይህ የሚገልጸው እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚሰበስበባቸውን ስፍራዎች ነው። “እርሱ ከምሥራቅና ከምዕራብ፣ ከሰሜን እና ከደቡብ ሰበሰባቸው”
Psalms 107:4
ተቅበዘበዙ
“አንዳንድ ሰዎች ተቅበዝብዘዋል”
በምድረ በዳ መንገድ ላይ
“በምድረ በዳ በነበረው መንገድ ላይ”
በኖሩበት
“መኖር በቻሉበት”
በመከራቸው ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ወደ እርሱ መጸለያቸውን ነው። “በመከራቸው እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ”
ጭንቀታቸው
“ችግራቸው” ወይም “ሥቃያቸው”
Psalms 107:8
ኦ እነዚያ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታማኝነቱ ሊያመሰግኑት ይገባል
እዚህ ላይ “ኦ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ መስጠትን ነው። “ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለ ሆነ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ያመስግኑ” ወይም “ሕዝቡ እግዚአብሔርን ማመስገን ያለባቸው እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለሆነ ነው”
ለሰብአዊነት
“ለሁሉም ሰዎች”
እርሱ የተጠሙትን ሰዎች ፍላጎት አርክቶአል
“ለሚፈልጉት ውሃን ሰጣቸው፣ ለተጠሙትም”
የተራቡትን ሰዎች ፍላጎት በመልካም ነገሮች አጥግቦአል
“እጅግ ለተራቡ እና ምግብ ላስፈለጋቸው፣ ይበሉ ዘንድ መልካምን ነገር ሰጣቸው”
አንዳንዶች ተቀመጡ
ይህ የሚያመለክተው እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር ያዳናቸው መሆናቸውን ነው። “እግዚአብሔር የተቀመጡትን ሰዎች አድኖአቸዋል”
በጨለማ እና በድንግዝግዝ ውስጥ
“ጨለማ” እና “ድንግዝግዝ” በመሠረቱ አንድ አይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ የነበሩበት ስፍራ ምን ያህል ጨለማ እንደነበረ ትኩረት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውለዋል። “በፍጹም ጨለማ ውስጥ”
Psalms 107:11
በእግዚአብሔር ቃል ላይ አመፁ . . . የልዑሉንም ትእዛዝ አንቀበልም አሉ
እነዚህ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አሏቸው ትኩረት የሚሰጡትም ምን ያህል በእግዚአብሔር ላይ እንዳመፁ ነው፤ ለዚህም ነው በእስር ቤት የተጣሉት።
በመከራ ጊዜ ልባቸውን ትሑት አደረገ
እዚህ ላይ ልብ የሚለው አንድን ሰው ይወክላል፣ ነገር ግን በተወሰነ ሁኔታ ፈቃዱን የሚያመለክት ነው። “መከራ እንዲቀበሉ በማድረግ ትሑት እንዲሆኑ አደረጋቸው”
ችግር
“መከራ” ወይም 2) “ከባድ ሥራ” የሚሉት ትርጉሞችም ተቀባይነት አላቸው።
ተሰናከሉ፤ የሚረዳቸውም አልነበረም
“ተሰናከሉ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እነዚህ ሰዎች እጅግ አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ የነበሩባቸውን ጊዜያት ነው። “መከራ ውስጥ ገቡ ማንም ከመከራ ውስጥ እንዲወጡ የሚረዳቸው አልነበረም”
በመከራቸውም ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህም ማለት እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ወደ እርሱ ጸለዩ ማለት ነው። ይህንን በመዝሙር 107፡6 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “በመከራቸው እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ”
ጭንቀታቸው
“ችግር” ወይም “ሥቃይ።” ይህንን በመዝሙር 107፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
አመጣ
እዚህ ላይ ዳዊት እግዚአብሔር ከጭንቀታቸው እንዳዳናቸው ጭንቀታቸውንም እርሱ እነርሱን አድኖ እንዳመጣበት ተጨባጭ ስፍራ አድርጎ ይገልጸዋል።
Psalms 107:14
አመጣቸው
“እግዚአብሔር በእስር ቤት ያሉትን አመጣ”
ጨለማ እና ድንግዝግዝ
“ጨለማ” እና “ድንግዝግዝ” በመሠረቱ አንድ አይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ የነበሩበት ስፍራ ምን ያህል ጨለማ እንደነበረ ትኩረት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውለዋል። ይህንን በመዝሙር 107፡10 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “ፍጹም ጨለማ”
ኦ እነዚያ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታማኝነቱ ሊያመሰግኑት ይገባል
እዚህ ላይ “ኦ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ መስጠትን ነው። “ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ይህንን በመዝሙር 107፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለ ሆነ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ያመስግኑ” ወይም “ሕዝቡ እግዚአብሔርን ማመስገን ያለባቸው እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለሆነ ነው”
እርሱ
“ምክንያቱም እርሱ”
የነሐሱን በሮች ሰበረ፤ የብረቱንም ምሰሶዎች ቆረጠ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች የሚያመለክቱት እግዚአብሔር ሕዝቡን ከእስር ነጻ ማውጣቱን ሲሆን አጽንኦት የሚሰጡትም እግዚአብሔር በእውነት ነጻ እንዳወጣቸው ነው። “ሕዝቡን ከእስር ነጻ አደረገ”
Psalms 107:17
በአመጻ መንገዳቸው ሞኞች ነበሩ
“በእግዚአብሔር ላይ በማመጻቸው ሞኞች ነበሩ”
እናም ተሰቃዩ
“እናም መከራ ተቀበሉ።” በልዩ ሁኔታ ስለ ታመሙ ተሰቃዩ። “እናም ሕመምተኞች ሆኑ”
ወደ ሞት በሮች ተጠጉ
ይህ “የመሞት” ተግባር እንደ “ሞት በሮች” ተገልጾአል። “የሞቱ ያህል ሆኑ”
በመከራቸውም ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህ ማለት እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ወደ እርሱ ጸለዩ ማለት ነው። ይህንን በመዝሙር 107፡6 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። “በመከራቸው እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ”
Psalms 107:20
ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም
እዚህ ላይ ዳዊት የሚገልጸው እግዚአብሔር ቃሎቹን እንደ መልእክተኛ ልኮ እንደሚናገር ነው። ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “እንዲፈወሱ አዘዘ እነርሱም ተፈወሱ” ወይም 2) “አበረታታቸው ፈወሳቸውም”
ኦ እነዚያ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታማኝነቱ ሊያመሰግኑት ይገባል
እዚህ ላይ “ኦ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ መስጠትን ነው። “ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ይህንን በመዝሙር 107፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለ ሆነ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ያመስግኑ” ወይም “ሕዝቡ እግዚአብሔርን ማመስገን ያለባቸው እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለሆነ ነው”
Psalms 107:23
እና በውጭ አገር ንግድ በማካሄድ
በዚያ ካሉ ሰዎች ጋር እቃዎችን ለመግዛትና ለመሸጥ በመርከብ ይሄዳሉ። “በሩቅ ካሉ ከተሞች ጋር ሸቀጦችን ይሸጣሉ”
Psalms 107:25
ባሕሩንም የሚያናውጥ አውሎ ነፋስ አዘዘ አስነሳባቸውም
“ነፋሱን አዘዘ፣ ባሕሩንም የሚያንቀሳቅስ ታላቅ ዐውሎ ነፋስ ሆነ”
አውሎ ንፋስ
ኃይለኛ ንፋስ፣ ውሽንፍር የሚያስከትል ኃይለኛ ንፋስ
ባሕሮችን የሚያንቀሳቅስ
እዚህ ላይ ዳዊት የሚገልጸው ነፋሱ ማዕበልን በማስነሣት ልክ አንድን ነገር

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደሚመታ ዕቃ ይሆናል ይላል። “የባሕሩን ማዕበል እጅግ ከፍ እንዲል አደረገው”
ወደ ሰማይ ከፍ አሉ፤ ወደ ታችም ወደ ጥልቁ ወረዱ
ይህ የሚያሳየው መርከቦቹ በማዕበሉ ወደ ላይ እና ወደ ታች ማለታቸውን ነው። ወደ ሰማይ ወጡ እንዲሁም ወደ ታች ወደ ጥልቁ ወረዱ የሚለው ማዕበሉ ምን ያህል ከፍተኛ እንደ ነበር የሚገልጽ የተጋነነ አባባል ነው። “መርከቦቻቸው በማዕበሎቹ ወደ ላይ እጅግ ከፍ አሉ እንዲሁም በማዕበሎቹ መካከል ወደ ታች ወረዱ።
ሕይወታቸው በጭንቀታቸው ምክንያት ቀልጦአል
x
Psalms 107:28
በመከራቸውም ወደ እግዚአብሔር ጮኹ
ይህ ማለት እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ወደ እርሱ ጸለዩ ማለት ነው። ይህንን በመዝሙር 107፡6 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። “በመከራቸው እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ”
ከዚያም እነርሱ
“እነርሱ” የሚለው ቃል መርከበኞቹን ያመለክታል።
ማዕበሉን ጸጥ አደረገው
“ነፋሱን እንዲቆም አደረገው”
ማዕበሉ ጸጥ አለ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ማዕበሎቹን ጸጥ አደረጋቸው”
አመጣቸው
“መራቸው”
የሚፈልጉት ወደብ
“መሄድ ወደሚፈልጉበት ወደብ”
Psalms 107:31
ኦ እነዚያ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታማኝነቱ ሊያመሰግኑት ይገባል
እዚህ ላይ “ኦ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ጠንከር ያለ ማሳሰቢያ መስጠትን ነው። “ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ይህንን በመዝሙር 107፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለ ሆነ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ያመስግኑ” ወይም “ሕዝቡ እግዚአብሔርን ማመስገን ያለባቸው እርሱ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለሆነ ነው”
በሽማግሌዎች ሸንጎ ይወድሱት
“ሽማግሌዎች በአንድ ላይ ሲቀመጡ።” ሽማግሌዎች በኅብረተሰቡ መካከል ያለውን ጉዳይ ለመነጋገርና ውሳኔዎችን ለመስጠት በአንድነት ተቀምጠዋል።
Psalms 107:33
ለወጠ
እግዚአብሔር አደረገ
ስለ ሕዝቡ ክፋት የተነሣ
“በዚያ የሚኖሩት ሰዎች ክፉዎች ስለ ናቸው”
ምድረ በዳውን ወደ ውሃ ገንዳ፣ ደረቁን መሬት ወደ ውሃ ምንጮች ይለውጣል
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አጽንኦት የሚሰጡት እግዚአብሔር በምድረ በዳ ውሃ እንዲገኝ ማድረግ እንደሚችል ነው። “በረሃ በነበረው ምድር ላይ ምንጮችና ሐይቆችን ያደርጋል”
Psalms 107:36
የተራቡትን በእዚያ ያሰፍራቸዋል
“እዚያ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር ምንጮችን እና ሐይቆችን ያደረገበትን ስፍራ ያመለክታል። ደግሞም “የተራቡት” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው የተራቡትብን ሰዎች ነው። “እግዚአብሔር የተራቡትን ሰዎች እዚያ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል”
የወይን እርሻዎችን ለመትከል
“የወይን እርሻዎችን በዚያ ለመትከል”
በዚያ የተትረፈረፈ ምርት ለመሰብሰብ
“በዚያ ብዙ እህል ማምረት ይችላሉ”
ስለዚህ እጅግ ብዙ ናቸው
“ሕዝባቸውም እጅግ ብዙ ነው”
ከብቶቻቸው በቁጥር እንዲቀንሱ አያደርግም
ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። “ከብቶቻቸውን እጅግ ያበዛላቸዋል”
Psalms 107:39
እነርሱ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር በምድሪቱ ያሰፈራቸውን የተራቡትን ሰዎች ነው። ይህ ዐረፍተ ነገር የሚያመለክተው ሰዎቹ እግዚአብሔር በምድሪቱ ሳያሰፍራቸው በፊት የነበሩበትን ሁኔታ ነው።
እነርሱ እየቀነሱ እና እያነሱ ነበር
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “መሪዎቻቸው ቁጥራቸውን ቀንሱ አነስተኛም አደረጓቸው”
ቀንሰዋል
“በቁጥር አነስተኛ ሆኑ”
አነስተኛ
ይህ መዋረድ ማለት ነው። “ተዋረዱ”
መናቅን አዘነበባቸው
እዚህ ላይ ዳዊት የሚናገረው እግዚአብሔር በመሪዎች ላይ ንቀትን እንደ ዝናብ እንዳወረደባቸው ነው። “መናቅን አሳያቸው”
መሪዎቹ
“መሪዎቹ።” ይህ የሚያመለክተው ሕዝቡን የጨቆኑትን መሪዎች ነው። “የጨቆኗቸው መሪዎች”
መንገዶች በሌሉበት
“ሰዎች በጭራሽ የማይሄዱበት”
Psalms 107:41
ግን እርሱ
“እግዚአብሔር ግን”
ችግረኞች
ይህ ችግረኞችን ይመለከታል። “ችግረኞች” ወይም “ድኾች”
ቤተሰቡን እንደ መንጋ ይንከባከባል
እዚህ ላይ ዳዊት እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዴት እንደሚንከባከብ ሲገልጽ እረኛ ለበጎቹ ከሚያደርገው ጥንቃቄ ጋር ያወዳድራል። ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “በእያንዳንዱ ቤተሰብ ያሉትን ሰዎች እንደ መንጋ ቁጥራቸውን ያበዛል ወይም 2) “እረኛ ለበጎቹ እንክብካቤ እንደሚያደርግ ይጠነቀቅላቸዋል”
ቅኖች
ይህ የሚያመለክተው በትክክለኛ መንገድ የሚመላለሱትን ሰዎች ነው። “ቅን ሰዎች” ወይም “ትክክል የሆነውን የሚያደርጉ ሰዎች”
ክፋት ሁሉ
እዚህ ላይ ክፉ ሰዎች እንደ “ክፋት” ተጠቅሰዋል። “ክፉ ሰዎች ሁሉ”
አፉን ይዘጋ
ይህ ማለት ምንም ምላሽ መስጠት አይችልም ማለት ነው። “በምላሹ እግዚአብሔርን በመቃወም መልስ መስጠት አይችልም”
እነዚህን ነገሮች ልብ በሉ
ይህ ማለት ስለ እነዚህ ነገሮች ማሰብ ማለት ነው። “ስለ እነዚህ ነገሮች አስቡ” ወይም “እነዚህን ነገሮች አስታውሱ”
ስለ እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት አሰላስሉ
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝ መሆኑን ማሳየቱን አሰላስሉ”

---

Chapter 108
Psalms 108:3
የቃል ኪዳንህ ታማኝነት ከሰማያት በላይ ታላቅ ነው፤ ታማኝነትህ እስከ ሰማይ ይደርሳል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። የሚናገሩት የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት እና አስተማማኝነት ልክ እንደ አንድ ቁመቱ እስከ ሰማይ እንደሚደርስ ረጅም ነገር ታላቅ መሆኑን በመጥቀስ ነው። “ታማኝነት” እና “አስተማማኝነት” የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ቅፅል ሊተረጎሙ ይችላሉ። “የቃል ኪዳን ታማኝነትህ እና አስተማማኝነትህ ከመሬት እስከ ሰማይ እንዳለ ርቀት ታላቅ ነው” ወይም “አንተ ለቃል ኪዳንህ የበለጠ ታማኝ ነህ፣ እንዲሁም ሰዎች ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል በአንተ ሊታመኑብህ የሚገባ ነህ”
Psalms 108:5
አምላክ ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ በል
መዝሙረኛው እግዚአብሔር ከፍ ያለ መሆኑን እንዲያሳየው ይጠይቃል። ከሰማያት በላይ ከፍ ማለት የሚያመለክተው ታላቅ መሆኑን ነው። “እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሰማያት በላይ ከፍ ያልክ መሆንህን አሳይ” ወይም “እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በሰማያት ታላቅ እንደ ሆንክ አሳይ” (ሜታፎርን ተመልከት)
ክብርህ ከፍ ይበል
እዚህ ላይ እግዚአብሔር በ“ክብሩ” ተጠቅሷል። “አንተ ከፍ በል”
ስለዚህ የሚወድዱህ ይዳና
ይህ በአድራጊ ቅርፅ መገለጽ ይችላል። “ምክንያቱም የሚወድዱህ መታደግ ያስፈልጋቸዋል” ወይም “የወደዱህን ታደግ”
በቀኝ እጅህ
ይህ የእግዚአብሔር “ቀኝ እጅ” የሚያመለክተው ኃይሉን ነው። “በኃይልህ”
መልስልኝ
መመለስ የሚያመለክተው ለጥያቄው ምላሽ መስጠትን ነው። “ለጥያቄዬ መልስ ስጠኝ” ወይም “ጸሎቴን መልስ”

Psalms 108:7

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች በመዝሙር 60፡6-7 ካሉት ጋር ተመሳሳይ ናቸው።
እግዚአብሔር በቅድስናው ተናግሯል
እዚህ ላይ ዳዊት የሚገልጸው እግዚአብሔር እርሱ ቅዱስ ስለሆነ በ“ቅድስናው” እንደሚናገር ነው፤ ልክ ቅድስናውን እርሱ በውስጡ እንዳለ ነገር አድርጎ ይገልጸዋል። “እግዚአብሔር እርሱ ቅዱስ ስለሆነ ተናግሯል”
ሴኬምን እከፍላለሁ እንዲሁም የሱኮትን ሸለቆ አካፍላለሁ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሴኬምን ምድር ስለ መከፋፈል እንዲሁም የሱኮትን ሸለቆ ስለ ማካፈል ይናገራል።
ማካፈል
በክፍሎች መከፋፈል
ኤፍሬም ደግሞ የራስ ቁሬ ነው
እግዚአብሔር የኤፍሬምን ነገድ የእርሱ ሰራዊት እንደ ሆነ አድርጎ ይናገራል። የራስ ቁር የጦር መሣሪያን ይወክላል። “ኤፍሬምን እንደ ራስ ቁር መርጬዋለሁ” ወይም “የኤፍሬም ነገድ ሠራዊቴ ነው”
የራስ ቁር
ወታደሮች ጭንቅላታቸውን ከጉዳት ለመጠበቅ የሚያደርጓቸው ጠንካራ ባርኔጣ
ይሁዳ በትሬ ነው
እግዚአብሔር ከይሁዳ ነገድ ወንዶችን በሕዝቡ ላይ ነገሥታት ይሆኑ ዘንድ መርጦአል፤ የሚናገረውም ስለእዚያ ነገድ እርሱም በትሩ እንደ ሆነ አድርጎ ነው። “የይሁዳ ነገድ እንደ በትሬ ነው” ወይም “ይሁዳ በእርሱ በኩል ሕዝቤን የምገዛበት በትር ነው”

Psalms 108:9

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች በመዝሙር 60፡8-9 ካሉት ጋር ተመሳሳይ ናቸው።
ሞዓብ መታጠቢያ ገንዳዬ ነው
እግዚአብሔር ስለ ሞዓብ አስፈላጊ እንዳልሆነ እንደ የመታጠቢያ ገንዳ ወይም ዝቅተኛ አገልጋይ እንደ ሆነ አድርጎ ይናገራል። “ሞዓብ ለመታጠቢያ እንደሚጠቀሙበት ሳህን ነው”
በኤዶምያስ ላይ ጫማዬን እወረውራለሁ
እግዚአብሔር ምናልባት የኤዶምያስ ላይ ያለውን ባለቤትነት በምሳሌነት ለመግለጽ ጫማውን ወደ ምድሩ በመወርወር የራሱ መሆኑን ያሳያል። የሆነ ሆኖ አንዳንድ ትርጉሞች ሌላ አይነት ትርጓሜ አሏቸው። “የኤዶምያስ ምድር ባለቤት ነኝ” ወይም “በኤዶምያስ ምድር የእኔ መሆኑን ለማሳየት ጫማዬን እጥላለሁ፣”

Psalms 108:11

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች በመዝሙር 60፡10-12 ካሉት ጥቅሶች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፣ ነገር ግን እንደ 60፡10 ጀማሬ መዝሙር 108:11 “ግን አንተ” የሚል ሐረግ እንደሌለው ልብ በሉ።
እግዚአብሔር ሆይ፣ የጣልኸን አንተ አይደለህምን?
መዝሙረኛው ልክ እግዚአብሔር እንደ ጣላቸው ለመግለጽ ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። “ልክ እንደ ጣልኸን ይመስላል!” ወይም “እግዚአብሔር ሆይ ፣ አንተ የተውኸን ይመስላል!”
ከሠራዊታችን ጋር ወደ ውጊያ አትወጣም
መዝሙረኛው፣ እግዚአብሔር የእነርሱን ሠራዊት እንዲረዳ የሚናገረው እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ሆኖ እንዲዋጋ ነው። “ወደ ጦርነት በሄድን ጊዜ ሠራዊታችንን አላገዝክም”
ከንቱ ነው
“ዋጋ ቢስ ነው”
ያሸንፋል
“ጠላቶቻችንን ያሸንፋል”
ጠላቶቻችንን ይረግጣል
መዝሙረኛው፣ እግዚአብሔር ሠራዊታቸውን እንደሚረዳ ጠላቶቻቸውንም እንደሚያሸንፍ ወደ ታችም እንደሚረግጣቸው ይናገራል። “ጠላቶቻችንን እንድንረግጥ ይረዳናል” ወይም “ጠላቶቻችንን ማሸነፍ እንድንችል ያደርገናል።

---

Chapter 109

Psalms 109:1

አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።
ለመዘምራን አለቃ
“ይህ ለአምልኮ የሚጠቀሙበት የሙዚቃ አለቃ ነው።”
የዳዊት መዝሙር
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) ዳዊት መዝሙሩን ጽፎአል ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት የመዝሙር አጻጻፍ ዘይቤ ነው።
ለክፉዎች እና አታላዮች
“ክፉ” እና “አታላይ” የሚሉት ቃላት ሰዎችን ያመለክታሉ። ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አጽንኦት የሚሰጡትም ሰዎቹ ምን ያህል መጥፎ እንደሆኑ ነው። “ለክፉ እና አታላይ ሰዎች”

Psalms 109:4

ለመውደዴ ምላሽ
“ምንም እንኳ ብወዳቸው”
ፍቅሬ
“ለእነርሱ ያለኝ ፍቅር”
እነርሱ ይከሱኛል
“እነርሱ” የሚለው ቃል ክፉ እና አታላይ የሆኑትን ሰዎች ያመለክታል። መዝሙረኛውን የሚከስሱ ሰዎች በሐሰት እንደሚሠሩ በግልጽ ማስረዳት ያስፈልግ ይሆናል። “በሐሰት ከሰሱኝ” ወይም “ሰደቡኝ”

Psalms 109:6

ክፉውን ሰው ሾሙ . . . ከሳሹን ሾሙ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ትይዩ ናቸው “ክፉ ሰው” እና “ከሳሽ” የሚሉት ሐረጎች የሚያመለክቱት አንድን ሰው ነው።
በቀኝ እጁ በኩል
“በጠላቴ ቀኝ እጅ በኩል”
በሚፈረድበት ጊዜ ጥፋተኛ ሆኖ ይገኝ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ለፍርድ በሚቀርብበት ጊዜ ዳኛው ጥፋተኛ ያድርገው”

Psalms 109:8

ዕድሜውም ይጠር
“ዕድሜው” የሚለው ሐረግ የሕይወቱን ርዝመት ያመለክታል። “ረጅም ዕድሜ አይኑር”
ሹመቱ
“የሥልጣን ደረጃው”
በእጅ የሚሰጥ
ለድኾች የሚሰጥ ምግብ ወይም ገንዘብ
የፈረሰው ቤታቸው
“የወደሙ ቤታቸው”

Psalms 109:11

አበዳሪው
ለሌላ ሰው ገንዘብ የሚያበደር ነገር ግን ያ ሰው ገንዘቡ እንዲመልስለት የሚጠብቅ

Psalms 109:14

የአባቶቹ በደል በእግዚአብሔር ፊት ይታሰብ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “እግዚአብሔር ሆይ የአባቶቹን ኀጢአት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አስታውስ”
የእናቱም ኀጢአት አይደምሰስ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “እናቱም ያደረገችውን ኀጢአት አትረሳ”
ኀጢአታቸው ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ይኑር
እዚህ ላይ ዳዊት የሚናገረው እግዚአብሔር ስለ ኀጢአታቸው እንዲያስብ እንደ አንድ ቁስ አካል በፊቱ እንዲሆን ነው። “እግዚአብሔር ስለ ኀጢአታቸው ዘወትር ያስብ”
እግዚአብሔር መታሰቢያቸውን ከምድር ያጥፋ
ዳዊት በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎችን ሁሉ ለማመልከት “ምድር” የሚለውን ቃል ተጠቅሟል ። ደግሞም፣ “መታሰቢያቸው” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ከሞቱ በኋላ ሰዎች የሚያደርጉትን ማስታወሻ ነው። “እግዚአብሔር በምድር ላይ ማንም ሰው ስለ እነርሱ እንዳያስብ ያድርግ”
ይህ ሰው ምንም አይነት የቃል ኪዳን ታማኝነትን ለማድረግ ፈጽሞ አላሳበም
ይህ የሚያመለክተው ለሰዎች ሊደረግ የሚገባውን የቃል ኪዳን ታማኝነት ነው። “ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “ይህ ሰው ለሰዎች የቃል ኪዳን ታማኝነት ለማሳየት ፈጽሞም አላሰበም” ወይም “ይህ ሰው ለቃል ኪዳኑ ታማኝ መሆኑን ለማሳየት ምንም ያደረገው ነገር የለም”
የተጨቆኑትን፣ ችግረኞችንም
ይህ የተጨቆኑትንና የተቸገሩ ሰዎችን ይመለከታል። “የተጨቆኑ ሰዎች፣ ችግረኛ ሰዎች”
ልባቸው የቆሰለ
ይህ የሚያመለክተው ልባቸው የቆሰለ ሰዎችን ነው። “ልባቸው የቆሰለ ሰዎች” ወይም “ተስፋ የቆረጡ ሰዎች”
እስከ ሞት
“እስኪሞቱ ድረስ።” ይህ ማለት እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ አሰቃይቷቸዋል ማለት ነው።
Psalms 109:17
በእርሱ ላይ ይምጣበት
“እርግማኑ በእርሱ ላይ ይምጣበት”
መርገምን እንደ ልብስ ለብሶታል
ዳዊት ስለ ክፉ ሰው ባህሪ ሲናገር ክፋቱ እንደ ልብሱ እንደ ሆነ አድርጎ ነው። “ልብስን እንደሚለብስ ሌሎች ሰዎችን ይራገማል” ወይም “ሁልጊዜ ሰዎችን ይራገማል”
እንደ ልብሱ
“ልብሶቹ እንደ ሆኑ”
እርግማኑ ወደ ውስጡ እንደ ውሃ ይመጣል እንደ ዘይትም ወደ አጥንቱ ይገባል
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) ሁል ጊዜ እርግማንን ከመናገሩ የተነሣ የእርሱ ማንነት ክፍል ሆኖአል። “የናገራቸው እርግማኖች የእርሱ አካል ናቸው” ወይም 2) የተናገረው እርግማን በእርሱ ላይ ደርሷል። “በተናገረው እርግማን የእርሱ መላ ማንነቱ ተረገመ”
እንደ ውሃ
ይህ አንድ ሰው ውሃን እንዴት እንደሚጠጣ ያሳያል። “ሰው እንደሚጠጣው ውሃ”
እንደ ዘይት ወደ አጥንቶቹ
ይህ የሚያመለክተው ዘይት በቆዳው ላይ በሚደረግበት ጊዜ ወደ አጥንቶች የሚገባ መሆኑን ነው። “በሰው ቆዳ ላይ በሚቀባበት ጊዜ ወደ አጥንቶቹ ዘልቆ እንደሚገባ የወይራ ዘይት ነው”
Psalms 109:19
ራሱን ለመሸፈን እንደሚለብሰው ልብስ እርግማኑ በእርሱ ላይ ይሁን
ሰዎች ልብሳቸውን በየቀኑ ይለብሳሉ። ዳዊት ስለ ክፉ ሰው ሲናገር ሁል ጊዜ እንደሚለብሰው ልብስ እርግማኑ በእርሱ ላይ ይሁን ይላል። “እርግማኑ እንደሚለብሰው ልብስ በየቀኑ በእርሱ ላይ ይሁን”
ሁል ጊዜ እንደሚታጠቀው ቀበቶ
“እርግማኑ ለእርሱ ይሁን” የሚሉት ቃላት ከቀዳሚው ሐረግ ጋር የምንረዳቸው ናቸው። እዚህ ላይ ሊደገሙ ይችላሉ። “እርግማኑ ሁል ጊዜ እንደሚታጠቀው ቀበቶ ለእርሱ ይሁን” ወይም “እርግማኑ ሁል ጊዜ እንደሚታጠቀው ቀበቶ በእርሱ ላይ ይሁን”
ይህ ሽልማቱ ይሁን
“እነዚህ እርግማኖች ሽልማቱ ይሁኑ”
Psalms 109:21
በበጎ ተመልከተኝ
ይህ እግዚአብሔር በበጎነት እንዲመለከተው የቀረበ ልመና ነው። “በበጎነት አስበኝ”
ስለ ስምህ
“ስለ በጎ ስምህ”
የቃል ኪዳንህ ታማኝነት መልካም ነውና
“ታማኝነት”የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “አንተ መልካምና ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ስለሆንክ”
የተጨቆነና የተቸገረ
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የሚያተኩሩትም እርሱ እራሱን መርዳት አለመቻሉ ላይ ነው።
ልቤ በውስጤ ቆሰለ
እዚህ ላይ ዳዊት ልቡ ስለ መቁሰሉና በከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ስለ መሆኑ ይናገራል። “በሐዘንና በተስፋ መቁረጥ ተሞልቻለሁ”
እኔ እንደ ጥላ እየጠፋሁ ነው . . . እንደ አንበጣም
እዚህ ላይ ዳዊት በቶሎ እንደሚሞት ሲገልጽ እየጠፋ እንደሚሄድ ጥላ እና በነፋስ እንደሚወሰድ አንበጣ በምሳሌነት በመጠቀም ነው። “እንደ ምሽት ጥላ በቶሎ እንደሚወገድ፣ እንዲሁም በቀላሉ በነፋስ እንደሚጠረግ አንበጣ፣ እኔም እንዲሁ እንደምሞት ይሰማኛል”
Psalms 109:24
ጉልበቶቼ ደከሙ
ይህ ማለት እርሱ በጣም ደክሞአል ለመቆምም አልቻለም ማለት ነው። “ለመቆም ተቸገርኩ” ወይም “ሰውነቴ ደክሞአል”
ከጾም
“ምንም ምግብ ስላልበላሁ”
ቆዳ እና አጥንት ብቻ ቀረኝ
ይህ ማለት ክብደቱን በጣም ቀንሶአል ማለት ነው። “ሰውነቴ በጣም ቀጭን ሆነ”
በከሳሾቼ ተንቁአለሁ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ከሳሾቼ ተሳለቁብኝ”
ራሳቸውን ነቀነቁ
ይህ ያለመስማማት ምልክት ነው።
Psalms 109:26
በቃል ኪዳንህ ታማኝነት አድነኝ
“ታማኝነት” የሚረው ረቂስ ስም በቅፅል ሊተረጎም ይችላል። “ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ስለሆንህ አድነኝ”
እነርሱ ያውቁ ዘንድ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የዳዊትን ከሳሾች እና ስለ እርሱ መጥፎ ነገር የሚናገሩ ሰዎችን ያመለክታል።
ይህን አድርገሃል
“አድነኝ”
Psalms 109:28
እነርሱ ቢረግሙኝም
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዳዊትን የከሰሱ እና መጥፎ ነገር የሚናገሩ ሰዎችን ነው ።
እነርሱ ይፈሩ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “እነርሱ ያፍሩ ይሆናል” ወይም “እነርሱ ይፈሩ”
ባሪያህ ግን ሐሴት ያድርግ
“ነገር ግን እኔ የአንተ አገልጋይ ሐሴት ላድርግ” ወይም “እኔ የአንተ አገልጋይ ነኝ፣ ሐሴት ላድርግ።” ዳዊት “የአንተ ባሪያ” የሚለውን ሐረግ የሚጠቀመው ስለ ራሱ ነው።
ባላጋራዎቼ ይከናነቡ . . . ይልበሱ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት እርሱ ጠላቶቹ ምን ያህል ማፈር እንዳለባቸው እንደሚመኝ አጽንኦት ለመስጠት ነው።
እፍረትን ይልበሱ
እዚህ ላይ ዳዊት ስለ እነርሱ የሚናገረው ልብስን እንደሚለብሱ እፍረትን እንዲለብሱ ነው። “በጣም ይፈሩ”
እፍረታቸውን እንደ ልብስ ይልበሱ
ዳዊት ስለ እነርሱ የሚናገረው እንደሚለብሱት ልብስ እፍረትን እንዲለብሱ ነው። “ልብሳቸው በዙሪያቸው እንደ ተሸፈነ፣ እፍረታቸው ይሸፍናቸው”
Psalms 109:30
በአንደበቴ

ይህ ማለት እርሱ ይናገራል ማለት ነው። “እናገራለሁ እሰጣለሁ”
በችግረኛው በቀኝ እጁ በኩል ይቆማል

ይህ ማለት ድኾችን ይረዳል እና ይጠብቃል ማለት ነው። “ለችግረኛው ይከላከላል”

Chapter 110

Psalms 110:1

አጠቃላይ መረጃ

በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

የዳዊት መዝሙር

ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) ዳዊት መዝሙሩን ጽፎአል ወይም 2) መዝሙሩ ስለ ዳዊት ነው ወይም 3) መዝሙሩ በዳዊት የመዝሙሮች አጻፋፍ ዘይቤ ነው።

በቀኝ እጄ በኩል ተቀመጥ

“በቀኝ እጄ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው የክብር ቦታን ነው። “ለአንተ ባለኝ የክብር ስፍራ ተቀመጥ”

ጠላቶችህን የእግርህ መርገጫ እስከማደርግልህ

እዚህ ላይ ዳዊት የሚገልጸው እግዚአብሔር የጌታን ጠላቶች በኃይሉ ቁጥጥር ስር አድርጎ ለእግሩ ልክ እንደ እግር መርገጫ እንደሚያደርግለት ነው። “ጠላቶችህን ከኃይልህ በታች አድርግ”

Psalms 110:2

አጠቃላይ መረጃ

ዳዊት ለንጉሡ መናገሩን ቀጠለ።

እግዚአብሔር የኃይልህን በትር ይይዛል

ዳዊት እዚህ ላይ የሚናገረው እግዚአብሔር የንጉሡን የገዢነት በትሩን በመያዝ ግዛቱን እንደሚያሰፋለት ነው። “እግዚአብሔር በኃይል የምትገዛውን ስፍራ ያሰፋልሃል”

በጠላቶችህ መካከል ግዛ

“ንጉሥ፣ በጠላቶችህ መካከል ግዛ።” ይህ ለንጉሡ የተነገረው እንደ ትእዛዝ ነው።

በራሳቸው ነፃ ፈቃድ

“በራሳቸው ምርጫ።” ይህ ማለት ንጉሡን ለመከተል ይመርጣሉ ማለት ነው።

በኃይልህ ቀን

ይህ የሚያመለክተው ንጉሡ ሠራዊቱን ወደ ጦር ግንባር የሚመራበትን ቀን ነው። ይህ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። “ሠራዊትህን ወደ ጦርነት በምትመራበት ቀን”

ከንጋት ማኅፀን . . . እንደ ጠል

ዳዊት ጠልን ንጋት እንደሚወልደው ሕፃን ይገልጸዋል። “በማለዳ . . . እንደ ጠል”

ከንጋት ማኅፀን፣ ጎልማሳነትህ እንደ ጠል ልምላሜ ይሆንልሃል

ዳዊት ንጉሡን የሚናገረው በየጠዋቱ የሚኖረውን የወጣትነት ጥንካሬ በየቀኑ ማለዳ ከሚታየው ጠል ጋር በማነፃፀር ነው። “በየማለዳው ምድርን ለማለምለም የጠዋት ጤዛ እንደሚታይ አንተም ለመጽናት በወጣትነት ኃይል በየማለዳው ትሞላለህ”

Psalms 110:5

ጌታ በቀኝህ ነው

ጌታ ወደ ጦርነት በሚሄድበት ጊዜ እግዚአብሔር ሊረዳው በቀኙ ይቆማል።

“እግዚአብሔር በጦርነት ውስጥ ይረዳሃል”

ጌታ

“ጌታ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።

እርሱ ይገድላል

“እርሱ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። ነገሥታቱ እንዲሸነፉና እንዲሞቱ ያደርጋል፣ ነገር ግን የንጉሡን ሠራዊት የጠላት ነገሥታትን እንዲገድሉ ይፈቅድላቸዋል። “ነገሥታቱን እንዲሞቱ ያደርጋል” ወይም “ሠራዊትህ ነገሥታትን እንዲገድሉ ይፈቅድላቸዋል”

ነገሥታት

ይህ ጠላቶቹን ይመለከታል። “ጠላቶች ነገሥታት”

በቍጣው ቀን

እዚህ ላይ ዳዊት እግዚአብሔር በሚቆጣበት ጊዜ ነገሥታትን በ“ቍጣው ቀን” እንደሚያሸንፋቸው ይናገራል። “ትዕግሥቱ ወደ ቍጣ በሚለወጥበት የፍርድ ቀን”

የጦርነት ሜዳዎችን በሬሳዎች ይሞላል

ይህ ማለት እግዚአብሔር ይህ እንዲሆን ያደርጋል፣ በጦር ሜዳ የሞቱትን ሰዎች ሁሉ እርሱ በግል ገድሏቸዋል ማለት አይደለም። “የጦር ሜዳዎቹን በሬሳዎች እንዲሞላ ያደርጋል”

እርሱ በብዙ አገሮች ውስጥ መሪዎችን ይገድላል

ይህ ማለት እግዚአብሔር ይህ እንዲሆን ያደርጋል፣ መሪዎቹን በግል ይገድላል ማለት አይደለም። “በብዙ አገሮች ውስጥ መሪዎችን እንዲገደሉ ያደርጋል” ወይም “በብዙ አገሮች ውስጥ መሪዎች እንዲሞቱ ይፈቅዳል”

Psalms 110:7

መንገድ ዳር ካለች ፈሳሽ ውሃ ይጠጣል

ንጉሡ ለጥቂት ጊዜ ውሃ ለመጠጣት በመንገድ ላይ ይቆማል ከዚያም ጠላቶቹን ማሳደዱን ይቀጥላል። “ጠላቶቹን በማሳደድ ላይ እያለ ለጥቂት ጊዜ ከፈሳሽ ውሃ በፍጥነት ለመጠጣት ይቆማል”

ከፈሳሽ ውሃ

ይህ ማለት እርሱ ከመንገድ ዳር ፈሳሽ ውሃ ይጠጣል ማለት ነው። የመንገድ ዳር ፈሳሽ አነስተኛ ወንዝ ነው። “ከወንዙ ውሃ ይጠጣል”

እና ከዚያ

“እና እንደዚያ” ወይም “ስለዚህ”

እርሱ ራሱን ቀና ያደርጋል

ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) ንጉሡ የራሱን ጭንቅላት ቀና ያደርጋል ወይም 2) እግዚአብሔር የንጉሡን ራስ ከፍ ያደርጋል።

ከድል በኋላ ራሱን ወደ ላይ ቀና ያደርጋል

x

Chapter 111

Psalms 111:1

አጠቃላይ መረጃ

በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

በሙሉ ልቤ

“ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአንድ ሰው ውስጣዊ ማንነትና ስሜቱን ነው። አት: - “ከመላ ማንነቴ ጋር”

በቅኖች ሸንጎ፣ በጉባኤአቸውም

እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በአንድ ላይ ሊሆኑ ይችላሉ። “በቅኖች ስብስባ ውስጥ”

በሁሉ ዘንድ የሚፈለጉት እነርሱ በናፍቆት ይጠበቃሉ

“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “የእግዚአብሔርን” ሥራዎች ነው። ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “የእግዚአብሔርን ሥራዎች የሚፈልጉ ሁሉ በጉጉት ይጠባበቋቸዋል”

በጉጉት መጠበቅ

ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “የሚፈለጉ” ወይም 2) “የሚጠኑ” ናቸው።

Psalms 111:4

ይታወሳል

ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ሰዎች ሁል ጊዜ የሚያስታውሱት”

አስታውስ

ይህ አስበኝ ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ አባባል ነው። “አስታውስ”

ኃያል ሥራዎቹ

“ኃይሉን የሚገልጹ ሥራዎቹ”

የአሕዛብ ርስት

ጸሐፊው የሚናገረው በከነአን የሚኖሩ አሕዛብ ምድር የእነርሱ ርስት እንደሆነ አድርጎ ነው። “የሌሎች አሕዛብ ንብረት የሆነ ምድር”

Psalms 111:7

የእጆቹ ሥራዎች

እዚህ ላይ “እጆች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። አት: “እርሱ የሠራቸው ሥራዎች”

Psalms 111:10

የጥበብ መጀመሪያ

“ጥበብ” የሚለው ቃል “ጠቢብ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። “ጠቢብ ለመሆን የመጀመሪያው እርምጃ” ወይም “ጥበበኛ ለመሆን በጣም አስፈላጊው ነገር”

የእርሱን ትእዛዛት የሚፈጽሙ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"የእርሱን ትእዛዛት የሚታዘዙ"
ምስጋውም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
"ምስጋና" የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ሰዎች ለዘላለም ያመሰግኑታል"

Chapter 112
Psalms 112:1
አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው፡፡
እጅግ ደስ ይለኛል
"እጅግ ደስ ይለዋል"
እግዚአብሔርን የሚፈራ የተባረከ ነው
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡ "እግዚአብሔር እርሱን የሚፈራውን ሰው ዘሮች ይባርካል"
Psalms 112:3
አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር የሚዘምረው ሰው እግዚአብሔርን ስለሚያከብረው ሰው መግለጹን ይቀጥላል፡፡
ሀብትና ብልጽግና በቤቱ ነው
x
Psalms 112:8
አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር የሚዘምረው ሰው እግዚአብሔርን ስለሚያከብረው ሰው መግለጹን ይቀጥላል፡፡
ልቡ ጽኑ ነው
"ልቡ ተደግፎአል፡፡" እዚህ ላይ "ልብ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ግለሰቡን ነው፡፡ ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) "እርሱ ሰላም ነው" ወይም 2) "እርሱ የተማመነ ነው"
ጽድቁ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
"የጽድቅ ሥራው ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፡፡" ይህንን በመዝሙር 112፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡
በክብር ከፍ ከፍ ይላል
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡ "እግዚአብሔር ክብርን በመስጠት ከፍ ያደርገዋል"
Psalms 112:10
ይሄንን ያያል
"እግዚአብሔርን ለሚፈራ ሰው ነገሮች በመልካም እንደሚደረጉ ያያል፡፡" "ይህን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጸሐፊው እግዚአብሔርን ስለሚፈራ ሰው ቀደም ባሉት ጥቅሶች ላይ የገለጻቸውን መልካም ነገሮችን ሁሉ ነው፡፡
እርሱ በቁጣ ጥርሱን ያፋጫል
የጥርስ መፋጨት የከባድ ቁጣ መግለጫ ነው፡፡ ይህንን በመዝሙር 35:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡
ይቀልጣል
ጸሐፊው ስለ ክፉው ሰው ቀጣይ ሞት ሲናገር እንደ አንድ የሚቀልጥ ነገር ወይም በረዶ አድርጎ በመግለጽ ነው፡፡ "በመጨረሻም ይሞታል"
የክፉ ሰዎች ምኞት ይጠፋል
"ምኞት" ለሚለው ቃል ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፡- 1) ክፉ ሰዎች ያላቸውን ስሜታዊ ፍላጎት፡፡ "ክፉ ሰዎች ሊያደርጉት የሚፈልጉት ነገር ፈጽሞ ሊሆን አይችልም" ወይም 2) እርሱ ክፉ ሰዎች ለሚፈልጉት ምሳሌያዊ መግለጫ ነው፡፡ "ክፉ ሰዎች የፈለጉትን ያጣሉ"

Chapter 113
Psalms 113:1
አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው፡፡
የእግዚአብሔር ስም
እዚህ ላይ "ስም" የሚለው ቃል የሚወክለው እግዚአብሔርን እራሱን ነው፡፡ AT: "እግዚአብሔር"
Psalms 113:3
ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያው ድረስ
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ፀሐይ ወደምትወጣበት ምሥራቅ እና ወደምትጠልቅበት ምዕራብ ነው፡፡ ጸሐፊው እነዚህን ሁለት ጽንፎች የተጠቀመው በምድር ላይ የትኛውንም ስፍራ ለመወከል ነው፡፡ በመዝሙር 50፡1 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡ "በምድር ሁሉ ላይ"
የእግዚአብሔር ስም ሊመሰገን ይገባዋል
እዚህ ላይ "ስም" የሚለው ቃል እግዚአብሔር ራሱን ይወክላል፡፡ ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡ "ሰዎች እግዚአብሔርን ያመስግኑ"
ክብሩ ከሰማያት በላይ ይደርሳል
የእግዚአብሔር ክብር እጅግ ከፍ ያለ እንደ ሆነ ይነገራል፡፡ "ክብሩ ከሰማያት በላይ ነው" ወይም "ክብሩ እጅግ ታላቅ ነው"
Psalms 113:5
እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ያለ . . . በምድር ላይ ማን ነው?
ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም እንደሌለ አጽንኦት ለመስጠት ነው፡፡ ይህ የአጻጻፍ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል፡፡ "እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ያለ . . . በምድር ላይ የለም፡፡"
መቀመጫው በከፍታ ላይ የሆነ ማነው
"በከፍታ ላይ የነገሠው ማነው" ወይም "በከፍተኛው ሥልጣን ላይ የሚገዛው ማነው"
Psalms 113:9
መካን ለሆነች ሴት ቤተሰብን ይሰጣታል
እዚህ ላይ "ቤተሰብ" የሚያመለክተው በቤት ውስጥ የሚኖሩትን ልጆች ነው፡፡ "ምንም ለሌላት ሴት ልጆችን ይሰጣታል"

Chapter 114
Psalms 114:1
አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው፡፡
እስራኤል ከግብፅ ሲወጣ ያዕቆብም ባዕድ ቋንቋ ከሚናገሩ ሰዎች መካከል
እነዚህ ሁለቱ መስመሮች "እስራኤል" እና "የያዕቆብ ቤት" አንድ አይነት ትርጉም ያላቸው ናቸው፤ "ግብፅ" እና "የባዕድ አገር ሰዎች" የሚያመለክተው ስለ አንድ ሕዝብ ነው፡፡
የያዕቆብ ቤት ባዕድ ቋንቋ ከሚናገሩ ሰዎች
እዚህ ላይ "ቤት" የሚለው ቃል ቤተሰብን ወይም ዘሮችን ይወክላል፡፡ ግሱ ለዚህ ሐረግ ሊሆን ይችላል፡፡ "የያዕቆብ ዘሮች የማያውቁትን ቋንቋ ከሚናገሩ ሰዎች ትተው ወጡ"
ይሁዳ የተቀደሰ ስፍራው፣ እስራኤልም መንግሥቱ ሆነ
"ለይሁዳ" እና "እስራኤል" ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፡- 1) መሬቱን ያመለክታሉ፡፡ "የይሁዳ ምድር የእግዚአብሔር የተቀደሰ ስፍራ ሆነ፣ የእስራኤልም ምድር የእርሱ መንግሥት ሆነ" ወይም (2) እነርሱ ለይሁዳ እና ለእስራኤል ሕዝብ መገለጫዎች ናቸው፡፡ "የይሁዳ ሕዝብ እግዚአብሔር በመካከላቸው የሚኖር ሕዝብ ሆኑ፣ የእስራኤልም ሕዝብ ደግሞ የሚገዛበት ሆኑ"
Psalms 114:3
ባሕሩ አየች ሸሸችም
ጸሐፊው የሚናገረው ባሕር ልክ እንደ ሰው ከእግዚአብሔር ፊት እንደ ሸሸች እና እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ በደረቅ ምድር እንደ መራው ነው፡፡ "ባሕር ልክ እንዳየችና እንደሸሸች ነበር"
ዮርዳኖስ ተመለሰ
ጸሐፊው የሚናገረው የዮርዳኖስ ወንዝ ልክ ሰው ወደ ኋላው እንደ ተመለሰና እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ በውስጡ በደረቅ ምድር እንደ መራው ነው፡፡ "ይህ ልክ ዮርዳኖስ ወደ ኋላው እንዲፈገፈግ ያህል ነበር"
ተራሮች እንደ ኮርማዎች፣ ኮረብቶችም እንደ ጠቦቶች ዘለሉ
ጸሐፊው ስለ ተራሮች እና ስለ ኮረብቶች ሕይወት እንዳላቸው አድርጎ ይናገራል፡፡ ምናልባትም የሚናገረው ስለ መሬት መንቀጥቀጥ ሆኖ የገለጸው ተራሮችና ኮረብቶች በእግዚአብሔር ፊት ፈርተው እንደ ኮርማዎችና ጠቦቶች እንደ ዘለሉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አድርጎ ነው። “ተራሮች ኮርማዎች እንደሚዘልሉ እንደ ተንቀጠቀጡ እና ኮረብታዎች ጠቦቶች እንደሚዘልሉ እንደንተንቀጠቀጡ ያህል ነበር”

Psalms 114:5

አጠቃላይ መረጃ

ከ5-6 ቁጥሮች አራት የአጻጻፍ ጥያቄዎችን ይይዛሉ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚጠበቀው መልስ “ከጌታ መገኘት የተነሣ” በቁጥር 7 ላይ ይገኛል።

እንደ ኮርማዎች ዘለሉ . . . እንደ ጠቦቶች ዘለሉ

ጸሐፊው ስለ ተራሮች እና ስለ ኮረብቶች ሕይወት እንዳላቸው አድርጎ ይናገራል። ምናልባትም የሚናገረው ስለ መሬት መንቀጥቀጥ ሆኖ የገለጸው ተራሮችና ኮረብቶች በእግዚአብሔር ፊት ፈርተው እንደ ኮርማዎችና ጠቦቶች እንደ ዘለሉ አድርጎ ነው። በመዝሙር 114፡3-4 ላይ ተመሳሳይ ሐረጎችን እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት። “እንደ ኮርማዎች ዝላይ መንቀጥቀጥ . . . እንደ ጠቦቶች ዝላይ መንቀጥቀጥ”

ምድር በጌታ ፊት፣ በያዕቆብ አምላክ ፊት ተንቀጠቀጠች

x

Psalms 114:8

እርሱ ድንጋዩን ወደ ውሃ ፣ ዓለቱንም ወደ ውሃ ምንጭ ለወጠው

እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ትይዩ ናቸው። ጸሐፊው እግዚአብሔርን የሚገልጸው ውሃውን ከድንጋይ ውስጥ እንዲፈስ ያደረገው ልክ ዓለቱን ወደ ውሃ እንደ ቀየረው አድርጎ ነው።

ዓለቱን ወደ ውሃ ምንጭ

ግሱ ከቀዳሚው ሐረግ ሊገኝ ይችላል። “ዓለታማውን ድንጋይ ወደ ውሃ ምንጭ ቀየረው

---

Chapter 115

Psalms 115:3

የሰዎች የእጆች ሥራ

እዚህ ላይ “እጆች” የሚለው ቃል ጣኦታትን የሠሩትን ሰዎች ይወክላል። “ሰዎች የሠሯቸው ነገሮች”

Psalms 115:5

እነዚያ ጣኦታት አፍ አላቸው

ጣኦታት እውነተኛ አፍ፣ ዐይን፣ ጆሮ ወይም አፍንጫ የላቸውም። ይልቁንም ሰዎች የአፍ፣ የአይኖች፣ የጆሮዎች እና የአፍንጫዎች አምሳያ አድርገው ይሠሩላቸዋል። ጸሐፊው አጽንኦት የሚሰጠው እነዚህ ጣኦታት በእውነት ሕያዋን አለመሆናቸውን ነው። የተሰጠውን መግለጫ ግልፅ ማድረግ ትችላለህ። “ሰዎች ለእነዚያ ጣኦታት አፎችን ሰጥተዋቸዋል”

Psalms 115:7

እነዚያ ጣኦታት እጅ አላቸው

ጣኦታት እውነተኛ እጆች፣ እግሮች ወይም አፎች የላቸውም። ይልቁንም ሰዎች የእጆች፣ የእግሮች እና የአፎች አምሳያ ይሠሩላቸዋል። ጸሐፊው አጽንኦት የሚሰጠው እነዚህ ጣኦታት በእውነት ሕያዋን አለመሆናቸውን ነው። ይህንን ስውር መረጃ ግልፅ ማድረግ ትችላለህ። “ሰዎች ለእነዚያ ጣኦታት እጆችን ሰጥተዋቸዋል”

ነገር ግን አይሰማቸውም

“እነዚያ እጆች ግን አይሰማቸውም”

Psalms 115:9

እስራኤል ሆይ፣ በእግዚአብሔር ታመን

“እስራኤል” የሚለው ቃል የእስራኤልን ህዝብ ይወክላል። “የእስራኤል ሕዝቦች፣ በእግዚአብሔር ታመኑ”

የእናንተ እርዳታ እና ጋሻ

ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው እርሱ ለእስራኤል እንደ ጋሻ ሆኖ ሕዝቡን ከጉዳት እንደሚጠብቃቸው ነው። “የሚረዳችሁና የሚጠብቃችህ”

የአሮን ቤት

እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል ቤተሰብን ወይም ዘሮችን ይወክላል። ይህ ሐረግ የአሮን ዘሮች የነበሩትን ካህናትን ያመለክታል። “የአሮን ዘሮች” ወይም “ካህናት”

Psalms 115:12

አሰበን

“ትኩረት ሰጠን”

የእስራኤል ቤተ ሰብ

ይህ የሚያመለክተው የያዕቆብ ዘሮች የሆኑትን እስራኤል ብሎ የሚጠራቸውን ሕዝብ ነው። “የእስራኤል ሕዝብ”

የአሮን ቤተ ሰብ

ይህ የሚያመለክተው የአሮን ዘሮች የሆኑትን ካህናትን ነው። “የአሮን ዘሮች” ወይም “ካህናቱ”

ወጣቶችና አዛውንት

“ታናሾችና ታላቆች።” ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ ይህ የሚያመለክተው 1) የኅብረተሰብ ደረጃ ወይም 2) ዕድሜን። በየትኛውም ሁኔታ፣ ሁለቱም ጽንፎች የሚያመለክቱት እያንዳንዱን፣ ዕድሜን ወይም የኅብረተሰብ ደረጃን ሳይመለከት ነው።

እግዚአብሔር አብዝቶ አብዝቶ ቁጥራችሁን ይጨምር

ጸሐፊው የሚናገረው የእስራኤል ሕዝብ ስለሚኖራቸው ልጆች ቁጥር ነው። “እግዚአብሔር የልጆቻችሁን ቁጥር አብዝቶ አብዝቶ ይጨምር”

የእናንተ እና የዘሮቻችሁ

የእናንተ ልጆች እና የዘሮቻችሁ ልጆች። ጸሐፊው እዚህ ላይ ግልጽ የሚያደርገው ይህ ጥያቄ ለአሁኑ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለዘሮቻቸውም ጭምር መሆኑን ነው።

Psalms 115:15

ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ተባረኩ

ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ሰማይንና ምድርን የሠራ እግዚአብሔር ይባርካችሁ”

ምድርን ለሰው ልጆች ሰጣት

ይህ ማለት ምድር የእግዚአብሔር አይደለችም ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ምድርን ለሰው ልጆች የሰጣት መኖሪያቸው ትሆን ዘንድ ነው።

Psalms 115:17

ሙታን

“ሙታን” የሚለው ቅፅል ከስም ጋር ሊተረጎም ይችላል። “የሞቱ ሰዎች”

ወደ ሲኦል የሚወርዱ ምንም አያደርጉም

ይህ ትይዩ ሐረግ ቀደም ሲል ከነበረው ሐረግ ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። ፍቺውን ግልፅ ለማድረግ ግሱ ከቀደመው ሐረግ ጋር ሊተያይ ይችላል። “ወደ ሲኦል የሚወርዱ እግዚአብሔርን ማመስገን አይችሉም”

---

Chapter 116

Psalms 116:1

አጠቃላይ መረጃ

በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።

ለምሕረት ያደረግኩትን የልመናዬን ድምፅ ሰምቷል

እዚህ ላይ “ድምፅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሚናገረውን ሰው ነው። “ልመና” እና “ምሕረት” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “መለመን” እና “መሐሪ” ተብለው ሊገለጹ ይችላሉ። “ለእኔ መሐሪ እንዲሆንልኝ ወደ እርሱ ስለምን ይሰማኛል”

Psalms 116:3

አጠቃላይ መረጃ

ይህን መዝሙር ያቀናበረው ሰው መናገሩን ይቀጥላል።

የሞት ገመዶች ከበቡኝ

ጸሐፊው ስለ ሞት የሚናገረው አንድን ሰው እንደ ያዘና በገመድ እንዳሰረው አድርጎ ነው። መዝሙር 18፡4ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “ልክ እንደምሞት ሆኖ ተሰማኝ”

የሲኦል ወጥመድ አገኘኝ

ጸሐፊው ስለ “ሲኦል” የሚናገረው የሙታን ስፍራ መሆኑን እና ልክ በወጥመድ እንደ ታያዘ ሰው አድርጎ ነው። “ልክ ወደ መቃብር ለመግባት ዝግጁ እንደሆንኩ ተሰማኝ”

የእግዚአብሔርንም ስም ጠራሁ

እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል የሚወክለው እግዚአብሔርን ራሱን ነው። “ወደ እግዚአብሔር ተጣራሁ”

ሕይወቴን አድናት

እዚህ ላይ “ሕይወት” የሚለው ቃል የሚወክለው ግለሰቡን ነው። “አድነኝ” ወይም



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ከመሞት አድነኝ”
Psalms 116:7
አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር ያቀናበረው ሰው መናገሩን ይቀጥላል።
ነፍሴ ወደ እረፍት ስፍራዋ መመለስ ትችላለች
ጸሐፊው ሰላምንና መተማመንን ማግኘት ልክ ነፍሱ የምታርፍበትን ስፍራ እንዳገኘች አድርጎ ይናገራል። “ነፍስ” የሚለው ቃል ግለሰቡን ይወክላል። “እንደገና በሰላም ማረፍ እችላለሁ”
አንተ ሕይወቴን ከሞት አዳንካት
እዚህ ላይ “አንተ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። “ሕይወት” የሚለው ቃል ግለሰቡን ይወክላል። “ከሞት አድነኸኛል” ወይም “ከመሞት ጠብቀኸኛል”
ዓይኖቼን ከእንባ
ትርጉሙን ግልፅ ለማድረግ የቃል ሐረግ ከቀዳሚው ሐረግ ሊወሰድ ይችላል። “ዓይኖቼን ከእንባ አዳንካቸው” ወይም “ከማልቀስ ጠብቀኸኛል”
እግሮቼን ከመሰናከል
ትርጉሙን ግልፅ ለማድረግ የቃል ሐረግ ከቀዳሚው ሐረግ ሊወሰድ ይችላል። እዚህ ላይ እግሮች ግለሰቡን ይወክላሉ። መሰናክል የሚለው ምናልባት በጠላቶቹ መገደልን ይወክላል። “ከመሰናክል አድነኸኛል” ወይም “በጠላቶቼ ከመገደል ጠብቀኸኛል”
Psalms 116:9
አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር ያቀናበረው ሰው መናገሩን ይቀጥላል።
በሕያዋን ምድር
“ሰዎች በሚኖሩበት በዚህ ዓለም ውስጥ።” ይህ ከሙታን ስፍራ በተቃራኒ ነው።
እኔ በጣም ተሠቃይቼአለሁ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “በጣም ተሠቃየሁ” ወይም “ሰዎች በጣም አሠቃዩኝ”
ግራ በመጋባት ውስጥ ተናገርሁ
“በፍጥነት እንዲህ አልሁ” ወይም “ሳላስብበት ተናገርሁ”
ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው
“ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው” ወይም “ሰዎች ሁሉ ሐሰተኞች ናቸው”
Psalms 116:12
አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር ያቀናበረው ሰው መናገሩን ይቀጥላል።
ስላደረገልኝ ሁሉ ... ለእግዚአብሔር ምን እመልሳለሁ?
ጸሐፊው ይህንን መሪ ጥያቄ የጠየቀው እግዚአብሔር ላደረገው ነገር እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ ለማስተዋወቅ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። “ላደረገልኝ ሁሉ ... ለእግዚአብሔር የምመልሰው እንዲህ ነው”
እኔ የመድኃኒትን ጽዋ አነሣለሁ
ይህ ምናልባት የሚያመለክተው ስለ መጠጥ ቁርባን ሲሆን ይህም ወይንን በመሠዊያው ላይ ማፍሰስን ይጠይቃል፤ ጸሐፊው ይህንን ቁርባን የሚያደርገው እግዚአብሔር ላደረገለት ማዳን ምላሽ እንዲሆን ነው። የዚህ መግለጫ ሙሉ ትርጉም ግልፅ ሊደረግ ይችላል። “እርሱ ስላዳነኝ ለእግዚአብሔር የመጠጥ ቁርባንን አቀርባለሁ”
የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል። “እግዚአብሔርን እጠራለሁ”
Psalms 116:16
አጠቃላይ መረጃ
ይህን መዝሙር ያቀናበረው ሰው መናገሩን ይቀጥላል።
የሴት ባሪያህ ልጅ
ይህ ምናልባት የሚያመለክተው የጸሐፊውን እናት ሲሆን እርሷም እግዚአብሔርን በታማኝነት የምታመልክ እንደ ሆነች ይጠቁማል። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። “እናቴ እንደ ነበረች”
ሠንሠለቴን አስወገድህ
ጸሐፊው በእስር ቤት የታሰረ ያህል የመሞት አደጋ ላይ እንደነበረ ይናገራል። “ከሞት አድነኸኛል”
የምስጋና መሥዋዕት
“ምስጋናዬን የሚገልጽ መሥዋዕት”
የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል። “የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ”

---

Chapter 117
Psalms 117:1
አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።
ለእርሱ
“በእርሱ ምክንያት”
የቃል ኪዳኑ ታማኝነት በእኛ ዘንድ ታላቅ ነው
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ስለ ሆነ ለእኛ ታላቅ ነገር ያደርጋል”
የእግዚአብሔር አስተማማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“አስተማማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ወይም ከቃል ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። “እግዚአብሔር ለዘላለም የታመነ ነው” ወይም “እግዚአብሔር በእርሱ ለሚታመኑ ሰዎች ለዘላለም የታመነ ነው”

---

Chapter 118
Psalms 118:1
አጠቃላይ መረጃ
በዕብራውያን የቅኔ አጻጻፍ ውስጥ ተመሳሳይነት የተለመደ አገላለጽ ነው።
እግዚአብሔር መልካም ስለሆነ አመስግኑ
“እርሱ ከሚያደርጋቸው መልካም ነገሮች የተነሣ እግዚአብሔርን አመስግኑ”
የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። “ለቃል ኪዳኑ ለዘላለም ታማኝ ነው”
እስራኤል እንዲህ ይበል
x
Psalms 118:3
የአሮን ቤት እንዲህ ይበል
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ቤተሰብ እና ዘሮቹን ይወክላል። ይህ ሐረግ የአሮን ዘሮች የነበሩትን ካህናትን ያመለክታል። “የአሮን ዘሮች እንዲህ ይበሉ” ወይም “ካህናቱ እንዲህ ይበሉ”
የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። በመዝሙር 118፡1-2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “ለቃል ኪዳኑ ለዘላለም ታማኝ ነው”
የእግዚአብሔር ታማኝ ተከታዮች
“እግዚአብሔርን የሚፈሩ” ወይም “እግዚአብሔርን የሚያመልኩ”
Psalms 118:5
ነጻ አድርገኝ
ጸሐፊው ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው ከአንድ ጠባብ እስር ቤት አውጥቶ በነፃነት መንቀሳቀስ ወደሚችልበት ሰፊ ስፍራ እንደ ወሰደው ልክ እንደዚሁ ከጭንቀት እንዳዳነው ነው።
ሰው ምን ያደርገኛል?
ጸሐፊው ይህንን የአጻጻፍ ጥያቄ የሚጠይቀው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለሆነ ማንም ሰው ሊጎዳው እንደማይችል አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። “ሰዎች እኔን ለመጉዳት ምንም ማድረግ አይችሉም።”
እግዚአብሔር ረዳቴ ሆኖ ከአጠገቤ ነው
በአንድ ሰው አጠገብ መቆም ያንን ሰው ለመርዳት መወሰኑን የሚያመልክት ፈሊጣዊ አገላለፅ ነው። “እግዚአብሔር እኔን ለመርዳት ወስኖአል”
በሚጠሉኝ ሰዎች ላይ በድል አድራጊነት እመለከታለሁ
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፊው እየተመለከተ ሳለ እግዚአብሔር ጠላቶቹን የሚያሸንፍለት እርሱ መሆኑን ነው። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊሆን ይችላል። “እግዚአብሔር የሚጠሉኝን ሁሉ ሲያሸንፋቸው አይቻለሁ”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Psalms 118:10
አሕዛብ ሁሉ
እዚህ ላይ “አሕዛብ” የሚለው ቃል የእነዚህን አሕዛብ ሠራዊት ይወክላል። ጸሐፊው በዙሪያው የከበቧቸውን እጅግ ብዙ የሆኑ ሠራዊቶችን ለማጉላት ይህን መግለጫ ተጠቅሞአል። “የብዙ አሕዛብ ሠራዊቶች”
በእግዚአብሔር ስም
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል። “በእግዚአብሔር ኃይል”
ቆረጥኳቸው
ጸሐፊው የሚናገረው የጠላቱን ሠራዊት ልክ አንድ ሰው የእፅዋትን ቅርንጫፎች እንደሚቆርጥ መቁረጡንና ማሸነፉን በመግለጽ ነው። “አሸንፍኳቸው”
እንደ ንቦች ከበቡኝ
ጸሐፊው የጠላትን ሠራዊት ከንብ ከበባ ጋር ያወዳድረዋል። “ንቦች አንድን ሰው እንደሚከብቡ እኔን ከበቡኝ”
በእሾህ መካከል እንደሚነድድ እሳት በፍጥነት ጠፉ
ልክ ደረቅ እሾህ በፍጥነት እንደሚቃጠል፣ የጠላት ሠራዊት ጥቃትም በፍጥነት ይጠፋል። “እሾህን የሚያቃጥለው እሳት ቶሎ አቃጥሎት እንደሚጠፋ የእነርሱም ጥቃት ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው”
Psalms 118:13
ወደ ታች ልትጥለኝ
ጸሐፊው የሚናገረው የጠላት ጦር እርሱን ለማሸነፍ በምድር ላይ ለመጣል ወደ ታች ሊገፉት እንደሞከሩ ነው። “እኔን ለማሸነፍ”
እግዚአብሔር ኃይሌና ደስታዬ ነው
“እግዚአብሔር ብርታትና ደስታ ሰጠኝ”
Psalms 118:15
የእልልታና የደስታ ድምፅ በጻድቃን ድንኳን ተሰማ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ሰዎች የደስታና የድል ድምፅ በጻድቃን ድንኳኖች ውስጥ ሰሙ” ወይም “ጻድቃን በድንኳኖቻቸው ውስጥ ስላገኙት ድል እልል አሉ”
የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ድል አደረገች
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል። “እግዚአብሔር በታላቅ ኃይሉ አሸነፈ”
የእግዚአብሔር ቀኝ እጁ ከበረ
እዚህ ላይ፣ እጅን ማንሣት የድል ምልክት ነው። ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “እግዚአብሔር ቀኝ እጁን አከበረ” ወይም “እግዚአብሔር ቀኝ እጁን በድል አነሣ”
Psalms 118:17
አልሞትም፣ በሕይወት እኖራለሁ
ጸሐፊው እርሱ በእርግጥ ሕያው መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት አንድ ዓይነት ሀሳብ በአሉታዊም በአዎንታዊ መልኩ ገልጾታል።
እግዚአብሔር ቀጣኝ
“እግዚአብሔር ሥርዓት አስያዘኝ”
ለሞት አሳልፎ አልሰጠኝም
ጸሐፊው ስለ ሞት የተናገረው ልክ እንደ ሰው ሥልጣን እግዚአብሔር ጸሐፊውን ለእርሱ አሳልፎ እንደሚሰጠው አድርጎ ነው። “እንድሞት አልፈቀደም” ወይም “ጠላቶቼ እንዲገድሉኝ አልፈቀደላቸውም”
Psalms 118:19
የጽድቅ ደጆች ክፈቱልኝ
“ጻድቃን የሚገቡበትን በሮች ክፈቱልኝ።” ይህ የቤተ መቅደሱን በሮች የሚያመለክት ሲሆን ጸሐፊው የበር ጠባቂዎቹን እየተናገረ ነው። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊሆን ይችላል። “የቤተ መቅደሱን በሮች ክፈቱልኝ”
የእግዚአብሔር በር
ወደ “እግዚአብሔር ሕልውና የሚያደርስ በር” ወይም “የእግዚአብሔር በር”
ምስጋናን ለአንተ እሰጣለሁ
እዚህ ላይ ጸሐፊው ለእግዚአብሔር መናገርን ይጀምራል።
አንተ ድነቴ ሆንህልኝ
“ድነት” የሚለው ቃል በቃል ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። “አዳንኸኝ”
Psalms 118:22
ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ድንጋይ ሆነ
ይህ ጸሐፊው የተጠቀመበት ምሳሌ ንጉሡን ወይም የእስራኤልን መንግሥት የሚገልጽ ነው። ሌሎች እንደማይጠቅም የሚቆጥሩት እግዚአብሔር እጅግ የሚጠቅም አደረገው።
ይህ በዓይናችን ፊት ድንቅ ነው
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) “ለእኛ ይህንን ማየት ድንቅ ነው” ወይም 2) “እኛ እንደ ድንቅ ነገር እንቆጥረዋለን።”
Psalms 118:26
በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው
እዚህ ላይ ካህናቱ ለንጉሡ መናገር ይጀምራሉ።
በእግዚአብሔር ስም የሚመጣው
እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ኃይል የሚወክል ነው። “በእግዚአብሔር ኃይል የሚመጣው”
እኛ ከእግዚአብሔር ቤት ባረክናችሁ
እዚህ ላይ ካህናቱ ለሕዝቡ ይናገራሉ።
የእግዚአብሔር ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተ መቅደሱን ያመለክታል። “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ”
እርሱ ብርሃን ሰጥቶናል
ጸሐፊው እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለ መባረኩ ሲናገር ልክ እግዚአብሔር ብርሃንን በላያቸው እንዳበራ አድርጎ ነው። “ባርኮናል”
መሥዋዕቱን በገመድ እሰሩ
“መሥዋዕቱን በገመድ እሰሩ”
አንተ አምላኬ ነህ
እዚህ ላይ ጸሐፊው እግዚአብሔርን በቀጥታ መናገር ይጀምራል።
Psalms 118:29
ኦ
ይህ የቃለ አጋኖ ምልክት ሲሆን በቋንቋ ውስጥ በሚገኝ በየትኛውም የቃለ አጋኖ ትኩረት ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ልትጠቀምበት ትችላለህ።
እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ እርሱ ቸር ነውና
“ስላደረገው መልካም ነገር እግዚአብሔርን አመስግኑ።” ይህንን መዝሙር 118፡1ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የቃል ኪዳኑ ታማኝነት ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል
“ታማኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም ከቅፅል ጋር ሊተረጎም ይችላል። ይህንን መዝሙር 118፡1-2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። “ለቃል ኪዳኑ ለዘላለም ታማኝ ነው”

Chapter 119
Psalms 119:1
አጠቃላይ መረጃ
ትይዩነት በዕብራይስጥ ቅኔ ውስጥ የተለመደ ነው።
አሌፍ
ይህ በዕብራይስጥ ፊደላት የመጀመሪያው ፊደል ስም ነው።
እነዚያ የተባረኩ
“ለእነዚያ እንዴት መልካም ነው”
መንገዳቸው ነቀፋ የሌለበት
የአንድ ሰው ባሕርያት “መንገዶች” ወይም “ጎዳናዎች” ይባላሉ። “እነዚያ ባሕርያቸው ነቀፋ የሌለባቸው” ወይም “ስሕተት በማድረግ ማንም የማይወቅሳቸው”
በእግዚአብሔር ሕግ የሚመላለሱ
አንድ ሰው አካሔዱ ወይም ባሕርይው እንደ መመላለስ ተደርጎ ይነገራል። “እንደ እግዚአብሔር ሕግ የሚኖር” ወይም “የእግዚአብሔርን ሕግ የሚታዘዙ”። ይህ ሐረግ “መንዳቸው ነቀፋ የሌለበት” የሚለውን ትርጉሙ ግልፅ ያደርጋል።
በፍጹም ልባቸው እርሱን የሚፈልጉት
እግዚአብሔርን “መፈለግ” ማለት እርሱን ለማወቅ መፈለግ ማለት ነው።
በፍጹም ልባቸው
ይህ በጣም ወይም በእውነት ለማለት የምንጠቀምበት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “በሁለንተናቸው” ወይም “በውስጣቸው ባለው ነገር ሁሉ” ወይም “በእውነት”
Psalms 119:3


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አጠቃላይ መረጃ
የዚህ መዝሙር አብዛኛው ክፍል ለእግዚአብሔር የሚናገር ሲሆን “አንተ” እና “የአንተ” የሚሉት ቃላት ሁል ጊዜ የሚያመለክቱት እርሱን ነው።
እነርሱ ስሕተትን አያደርጉም
እግዚአብሔርን እንታዘዝም አይሉም።
በመንገዶቹ ይሄዳሉ
“በእግዚአብሔር መንገዶች ይሄዳሉ።” እዚህ ላይ ባሕርያቸው “መራመድ” ተብሎ ተጠርቷል፣ እንዲሁም እግዚአብሔር እንዲያሳዩ የሚፈልገውን ባሕርይ “መንገዶቹ” ተብሎ ተነግሯል። “እግዚአብሔር የሚፈልገውን ባሕርይ ያሳያሉ”
ትእዛዛትህን ይጠብቃሉ
“እንድናደርገው የደነገግኸውን ትእዛዛትህን ሁሉ እንታዘዛለን”
በጥንቃቄ ይጠብቃሉ
ይህ በጥንቃቄ ትዕዛዛቱን ማወቅ እና መረዳት እንደዚሁም መታዘዝ ነው።
Psalms 119:5
እኔ በፅኑ ተመስርቻለሁ
ጸሐፊው የሚናገረው ልክ በአካል ማንም ሰው ሊያነቃንቀው እንደማይችል ሁሉ በእግዚአብሔር ትእዛዛት መመስረቱን ነው።
ትእዛዛትህን አከብራለሁ
“ትእዛዛትህን እታዘዛለሁ”
እኔ አላፍርም
ጸሐፊው በእግዚአብሔር ፊት ሲቀርብ ማፈር አይፈልግም።
ትእዛዛትህ ሁሉ
“ያዘዝከንን ሁሉ”
Psalms 119:7
ቅን ልብ
“እውነተኛ ልብ።” ቅን የሆነ ሰው ትክክለኛውን ነገር ያደርጋል። ልብ በአንድ ሰው ውስጥ የስሜቱ ማዕከል መሆኑን ያመለክታል። በመዝሙር 25:21 ላይ “ቅንነት” የሚለውን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ትእዛዛትህ
“ትእዛዛት” የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ሕጎችን ወይም ትእዛዞችን ነው።
Psalms 119:9
ቤት
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት ሁለተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 9 እስከ 16 ያለው እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።
ጎልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል?
ይህ ጥያቄ ለእግዚአብሔር ቃል አዲስን እሴት ለማስተዋወቅ ይጠቅማል። ይህ የአጻጻፍ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። “ጎልማሳ መንገዱን የሚያነጻው እንዲህ ነው”
መንገዱን ንፁሕ ማድረግ
ጸሐፊው እንደ እግዚአብሔር ሕግ መኖርን ከወጥመድ ነጻ ከሆነ መንገድ ጋር ያነጻፅረዋል።
በሙሉ ልቤ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጥ ነው። ልብ ሁሉንም የአንድን ሰው ስሜቶች፣ ፍላጎቶች እና ፍቃድ ያሳያል። “በሁለንተናዬ” ወይም “ውስጤ ባለው ነገር ሁሉ” ወይም “በእውነት”
ከትእዛዛትህ አታርቀኝ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት አለመታዘዝ ከመንገድ እንደ መውጣት ተገልጾአል። “ትእዛዛትህን የማልታዘዝ አታድርገኝ”
Psalms 119:11
ቃልህን በልቤ ውስጥ አሰውራለሁ
“ቃልህን በልቤ ውስጥ አኖርሁ።” "ቃልህን አሰላስላለሁ" ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ልብ ሰዎች የሚያስቡትን መያዝ የሚችል መያዣ ነገር ነው።
Psalms 119:13
ከባለጠግነት በላይ ነው
“ከሀብት ሁሉ በላይ”
Psalms 119:15
አሰላስላለሁ . . . እናም ትኩረት እሰጣለሁ
እነዚህ አጽንኦት ለመስጠት የሚደገሙ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ትይዩ ሀሳቦች ናቸው።
ትእዛዛትህን አሰላስላለሁ
“ያዘዝከንን በጥንቃቄ አስባለሁ”
ትኩረት እሰጣለሁ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው እየተወያየበት ስላለው ነገር በግልጽ ማሰብን ነው። “በጥንቃቄ አስብ”
ደስ ይለኛል
ለመደሰት
Psalms 119:17
ጋሜል
ይህ በዕብራይስጥ ፊደል ሦስተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 17 እስከ 24 ያለው እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።
ባሪያ
ጸሐፊው ትሑት መሆኑን ለማሳየት ራሱን “ባሪያህ” ብሎ ጠርቷል።
ማየት እንድችል ዐይኖቼን ክፈት
ደራሲው መረዳትን፣ እውቀትንና ጥበብን ማግኘት ማየት እንደ መቻል ነው ብሎ ይናገራል። እንዳስተውል እርዳኝ
በሕግህ ውስጥ አስደናቂ ነገሮች
ደራሲው በሕጉ ውስጥ መረዳትን ማግኘት የሚያስደንቅ ነገር ነው ይላል።
በሕግህ ውስጥ
“በትእዛዛትህ” ወይም “በትእዛዛትህ”
Psalms 119:19
እኔ በምድሪቱ ላይ መጻእተኛ ነኝ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) ጸሐፊው የሚናገረው በምድር ላይ ያለው ዘመኑ አጭር መሆኑን ለመግለጽ ሲሆን፣ በምድር ላይ እንደ መጻእተኛ ለአጭር ጊዜ እንደሚቆይ ይናገራል። “እኔ እንደ መጻእተኛ በምድር ላይ ለአጭር ጊዜ እንደሚኖር ነኝ” ወይም 2) ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ቃል አለማወቁን ሲገልጽ የሚኖርበትን ምድር ሕግ እንደማያውቅ መጻእተኛ መሆኑን ይገልጻል። “እኔ በምድር ላይ እንዳለ መጻእተኛ አላዋቂ ነኝ”
ምኞቶቼ በመናፈቅ ተሰብረዋል
ጸሐፊው ስለ ምኞቶቹ ሲናገር ፍላጎቶቹ በሥቃይ ውስጥ ያሉ ያህል በጣም ጠንካራ እንደሆኑ ተናግሯል። “የውስጥ ማንነቴ ለማወቅ በጣም ይጓጓል” ወይም “ነፍሴ ሕመም እስከሚሰማት በጣም ለማወቅ ጓጓች”
Psalms 119:21
የተረገሙ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር ይረግማቸዋል ወይም 2) የእግዚአብሔር ቅጣት ይገባቸዋል። “የአንተ ቅጣት የሚገባው”
ከትእዛዛትህ የራቁ
ጸሐፊው የሚናገረው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት አለመታዘዝ ከመንገድ ወጥቶ እንደ መባዘን ነው። “ከአንተ የትእዛዝ መንገድ ርቀው የሄዱ” ወይም “የአንተን ትእዛዛት የማይታዘዙ”
አራቅኸኝ
“ጠበቅኸኝ” ወይም “ታደግኸኝ”
Psalms 119:23
ገዥዎች ቢያሴሩብኝና ቢሰድቡኝም
“ገዥዎች እኔን ለመጉዳት እና ስለ እኔ መጥፎ ነገር ለመናገር ቢያቅዱም”
የቃል ኪዳን ድንጋጌዎችህ ደስታዬ ናቸው
“የቃል ኪዳን ድንጋጌዎችህ በጣም ደስተኛ አደረጉኝ።”
እነርሱ አማካሪዎቼ ናቸው
የእግዚአብሔር ድንጋጌዎች ልክ ሰዎች እንደሆኑ ተነግሯል። “እነርሱ ለእኔ እንደ ጠቢባን አማካሪዎች ናቸው” ወይም “ጥሩ ምክር ለእኔ ይሰጡኛል”
Psalms 119:25
ዳሌጥ
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አራተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 25 እስከ 32 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።
ሕይወቴ ከአፈር ጋር ተጣብቃለች
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) በቶሎ እንደሚሞት አሰበ፣ ወይም 2) በጣም ስላዘነ በአፈር ላይ ተኛ፣ ወይም 3) በምድር ላይ ያሉ ከንቱ ነገሮች እንደ ተመኘ ተገነዘበ።
በቃልህ ሕይወት ስጠኝ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እዚህ ላይ “ሕይወት” ማለት ተፈጥሮአዊ ሕይወት ሳይሆን ዓላማ ያለው እና አስፈላጊ የሆነ ሕይወትን የሚያመለክት ነው።
በቃልህ
“እንደ ተስፋ ቃልህ”
የእኔ መንገዶች
አንድ ሰው የሚያደርገው ወይም ባህሪው እንደ ጎዳና ወይም እንደ መንገድ ተደርጎ ተነግሮአል። “ያደረግኩት”
Psalms 119:27
አስደናቂ ትምህርቶች
“አስገራሚ ትምህርቶች”
በሐዘን
“በጣም ስለ አዘንሁ”
አበርታኝ
“አበረታታኝ።” ይህ አካላዊ ጥንካሬን ወይም መንፈሳዊ ጥንካሬን ሊያመለክት ይችላል።
Psalms 119:29
የማታለልን መንገድ ከእኔ አርቅ
እዚህ ላይ “መንገድ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ባህሪን ነው። “የአታላይነትን መንገድ ከመከተል ጠብቀኝ” ወይም “ከመታለል ጠብቀኝ”
ማታለል
x
Psalms 119:31
ከቃል ኪዳን ድንጋጌዎችህ ጋር ተጣብቄአለሁ
እነርሱን አጥብቆ መያዝ የሚያመለክተው እነርሱን ለመታዘዝ ቁርጠኛ መሆንን ነው። “የቃል ኪዳንህን ድንጋጌ አጥብቄ እይዛለሁ” ወይም “የቃል ኪዳን ድንጋጌዎችህን ለመታዘዝ ቁርጠኛ ነኝ”
የቃል ኪዳን ድንጋጌዎች
ይህ የሙሴን ሕግ ያመለክታል።
በትእዛዝህ መንገድ እሮጣለሁ
ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለመታዘዝ ማተኮርና ቁርጠኛ መሆንን ልክ አንድ ሯጭ በመሮጫያው ላይ አተኩሮ እንደሚሮጥ ነው። “ትዕዛዛትህን ለመታዘዝ ቁርጠኛ ነኝ”
ልቤን አስፋው
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “ስለ ትእዛዛትህ የበለጠ ግንዛቤ እንዳገኝ እርዳኝ” ወይም 2) “ትእዛዛትህን ለመታዘዝ ትልቅ ፍላጎት ስጠኝ”
Psalms 119:33
ሔ
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት አምስተኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 33-40 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።
ሕጎችህ
ይህ የሙሴ ሕግ የሚገለጽበት ሌላው መንገድ ነው።
እስከ መጨረሻ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “ሙሉ በሙሉ” ወይም 2) “እስከ ሕይወቴ መጨረሻ” ወይም 3) “እስከ ዘመን መጨረሻ።”
ሕግህን መጠበቅ
“ሕግህን መታዘዝ”
በሙሉ ልቤ እመለከተዋለሁ
“ሕግህን በእርግጥ አከብራለሁ” ወይም “ሕግህ የሚለውን ሙሉ በሙሉ ለማድረግ ቁርጠኛ ነኝ”
በሙሉ ልቤ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “በሙሉ ማንነቴ” ወይም “በውስጤ ባለው ነገር ሁሉ” ወይም “በቅን ልቦና”
Psalms 119:35
በትእዛዝህ መንገድ ምራኝ
“እንደ ትእዛዛትህ ምራኝ” ወይም “ትእዛዛትህን እንድታዘዝ አስተምረኝ።” የእግዚአብሔር ትእዛዛት አንድ ሰው እግዚአብሔርን በመታዘዝ ከሚራመድበት መንገድ ጋር ይነጻጸራሉ።
ልቤን አዘንብል
ይህ ፈሊጣዊ አባባል ነው። “ልብ” የሚያመለክተው የአንድን ሰው ሕይወት የሚመሩ ፍላጎቶችን፣ ምኞቶችን እና ምርጫዎችን ነው። “እንድፈልግ አድርገኝ”
የቃል ኪዳንህ ድንጋጌዎች
“የቃል ኪዳንህን ድንጋጌዎች እንድታዘዝ።” ይህ የሙሴን ሕግ መታዘዝን ያመለክታል።
በጽድቅ ያልሆነ ትርፍ
“የብልጽግና ምኞት።” ይህ የሚያመለክተው ሕገ-ወጥ በሆኑ መንገዶች ወይም በሌሎች ላይ በደልን በማድረግ የሚገኝ ሀብትን ነው።
Psalms 119:37
ዓይኖቼን ከንቱ ነገሮችን ከማየት መልስ
ይህ ዘላለማዊ ዋጋ የሌላቸውን ነገሮች መመኘትን የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው።
በመንገዶችህ አነቃቃኝ
“አንተ እንድኖር እንደምትፈልገው መኖር እንድችል አድርገኝ”
አነቃቃኝ
“ሕይወቴን አበርታት” ወይም “ብርታት ስጠኝ”
አንተን ላከበሩህ የገባኸውን ቃል ኪዳን ለባሪያህም አድርግለት
“ለሚያከብሩህ ሁሉ ለማድረግ የገባኸውን ቃል ኪዳን ለባሪያህም አድርግለት”
ባሪያህ
ጸሐፊው ትህትናውን ለማሳየት ራሱን የእግዚአብሔር ባሪያ እንደ ሆነ ያመለክታል። “እኔ የአንተ ባሪያ”
Psalms 119:39
እፈራለሁ
“እኔ በጣም ፈርቻለሁ”
የጽድቅ ፍርዶችህ መልካም ናቸው
እግዚአብሔር በትክክል ይፈርዳል ውሳኔዎቹም መልካም ናቸው። “ፍርዶችህ ጽድቅና መልካም ናቸው”
ተመልከት
ይህ ሁኔታን መገንዘብን ያሳያል። ትኩረቱ ከመመልከት ይልቅ በእውቀት ወይም በማስተዋል ላይ ነው።
ትእዛዛትህን እናፍቃለሁ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “የአንተን ትእዛዛት ለማወቅ በጣም እፈልጋለሁ” ወይም 2) “ያስተማረከንን ለመታዘዝ በጣም እፈልጋለሁ።”
በጽድቅህ ሕያው አድርገኝ
“ጽድቅ” የሚለው ቃል ቀጥተኛ ያልሆነ ትርጉም ያለው ሲሆን ጻድቅ መሆንን ያመለክታል። “ጻድቅ ስለ ሆንህ ሕያው አድርገኝ”
አነቃቃኝ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “ሕያው አድርገኝ” ወይም 2) “አበርታኝ።”
Psalms 119:43
የእውነትን ቃል ከአፌ አትውሰድ
እዚህ ላይ ጸሐፊው “በአፉ” ተወክሏል። ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፦ 1) “ስለ እውነት መልእክትን ከመናገር ፈጽሞ አታርቀኝ” ወይም 2) “እውነተኛውን መልእክት ከመናገር ፈጽመህ አታርቀኝ።”፡
አከብራለሁ
“እታዘዛለሁ”
Psalms 119:45
እኔ በደህንነት እሄዳለሁ
በደህንነት መመላለስ የአንድን ሰው ሕይወት በደህንነት መኖር ነው። “በእግዚአብሔር በደህንነት እኖራለሁ”
ትእዛዛትህን እፈልጋለሁ
“መፈለግ” ማለት አንድ ሰው ሊያያቸው እንደሚችል የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ማስተዋል ወይም መረዳት ነው።
በነገሥታት ፊት የጠበቀ ትእዛዝ
“ለነገሥታት ከባድ ትእዛዛት” ወይም “ለነገሥታት የሚሰጡ መመሪያዎች”
Psalms 119:47
በትእዛዛትህ ደስ ይለኛል
x
Psalms 119:49
ዛይ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት ሰባተኛ የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 49-56 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።
ቃል ኪዳንህን አስታውስ
ቃል ኪዳንህን አስታውስ። በመዝሙር 20:3 ውስጥ ይህንን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
በስቃዬ ጊዜ መጽናኛዬ ይህ ነው - ቃል ኪዳንህ ሕያው አድርጎኛል
ይህ ክፍል እንደገና ቀለል ባለ ሁኔታ ሊጻፍ ይችላል። "ለመጽናናቴ ምክንያት የሆነው ቃል ኪዳንህ በስቃዬ ውስጥ ሕያው ስላደረገኝ ነው"
Psalms 119:51
ኩራተኞች
ይህ የስሜታዊ መግለጫ ጽሑፍ እንደ አንድ ቅፅል ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። "ኩሩ ሰዎች"
ማፌዝ
በአንድ ሰው ላይ ማፌዝ ወይም ዝቅ አድርጎ መመልከት፣ መጠራጠር ወይም አለማክበር
ከጥንት ጊዜያት ጀምሮ
ይህ ድንጋጌዎቹና ሕጉ ለሙሴ ከብዙ ዓመታት በፊት መሰጠታቸውን የሚያመለክት ነው።
Psalms 119:53
ከፍተኛ ንዴት ያዘኝ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እዚህ ላይ ቁጣ አንድን ግለሰብ እንደ ያዘ ሰው ተደርጎ ተገልጾአል። "በጣም ተናደድኩ"
ትእዛዛትህ መዝሙሮቼ ናቸው
"ትእዛዛትህን ለመዝሙሮቼ እንደ ግጥም ትጠቅሜአለሁ" ወይም "ከመግለጫዎችህ መዝሙሮችን ደርሻለሁ"
Psalms 119:57
ሔት
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት ስምንተኛ የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከቁጥር 57-64 ያሉት እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።
እግዚአብሔር እድል ፈንታዬ ነው
ይህ ማለት ዋናው የሚፈልገው እግዚአብሔርን ነው ማለት ነው። ሌዋውያኑ ለጌታ ሰፊ መሬት ርስት እንዳልተቀበሉ፣ ጸሐፊውም ለሚያስፈልገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር እርካታው እንደሆነ ይናገራል።
Psalms 119:59
እግሮቼን መለሰ
እዚህ ላይ "እግሮች" መላውን ሰው ይወክላሉ። ንስሐ መግባት እና የእግዚአብሔርን ሕግ ለመታዘዝ መምረጥ እግርን ወደ ሌላ አቅጣጫ ከመሄድ መመለስ ነው። "አቅጣጫዬን ቀይሬያለሁ"
አፈጥናለሁ አልዘገይምም
እግዚአብሔር የሰጠውን ትእዛዝ የመታዘዝን አስፈላጊነት ለማጉላት ጸሐፊው ተመሳሳይ ሀሳብ በአዎንታዊ እና በአሉታዊ መልኩ ገልጾታል።
Psalms 119:61
የክፉዎች ገመድ ተበተበኝ
በዚህ ምሳሌያዊ አባባል፣ ኃጢአተኞች ወይም ክፉ ሰዎች አደን የሚያድን ሰው አንድን እንስሳ በወጥመድ ለመያዝ እንደሚፈልግ ጸሐፊውን ኃጢአት እንዲሠራ ለማድረግ ሞክረዋል። "ጠላቶቼ እኔን ለመያዝ ሞክረዋል"
Psalms 119:63
እኔ ለሚያከብሩህ ሁሉ ባልንጀራ ነኝ
"ለሚያከብሩህ ሁሉ ጓደኛ ነኝ"
Psalms 119:65
ጤት
ይህ የዕብራይስጥ ፊደላት ዘጠነኛው የፊደል ስም ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ ከ65-72 ያሉት ቁጥሮች እያንዳንዱ መስመር በዚህ ፊደል ይጀምራል።
ለባሪያህ
ጸሐፊው ራሱን "የአንተ ባሪያ" ብሎ ጠርቶታል። "ለእኔ ለባሪያህ" ወይም "ለእኔ"
በቃልህ አማካይነት
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ቃልህ" እግዚአብሔር ለጸሐፊው የገባውን ቃል ኪዳን ያመለክታል። "ቃል እንደገባኸው"
በትእዛዝህ ታምኛለሁና ትክክለኛ መረዳትንና ማስተዋልን አስተምረኝ
አንዳንድ ቋንቋዎች አመክንዮአዊ እድገት ለውጥ ይጠይቁ ይሆናል። "በትእዛዛትህ ስለ አመንሁኝ፣ ትክክለኛ መረዳትንና ማስተዋልን አስተምረኝ"
Psalms 119:67
እኔ ከመሰቃየቴ በፊት
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። "ሳታሰቃየኝ በፊት" ወይም "ሳትቀጣኝ በፊት"
በስሕተት መንገድ ሄጃለሁ
እግዚአብሔር አለመታዘዝ ግለሰቡ በተሳሳተ ጎዳና ላይ እንደሄደ ተደርጎ ተገልጿል። "አንተን አልታዘዝኩም"
ቃልህን አከብራለሁ
እዚህ ላይ "ቃል" የሚለው ትእዛዛትን ይወክላል። "ትእዛዛትህን እታዘዛለሁ"
Psalms 119:69
እብሪተኞች
ይህ የስሜታዊ መግለጫ ጽሑፍ እንደ አንድ ገላጭ ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። "እብሪተኛ ሰዎች"
በሐሰት የተሞሉ
እግዚአብሔር በረዶውን እንደሚያወርድ ልክ እንደ ሰው በቀላሉ ዳቦ እንደሚፈረፍር ይመስለዋል። “በረዶውን በቀላሉ ያወርዳል ልክ እንደ ፍርፋሪ”
ያወርዳል
ይልካል
በረዶ
ትናንሽ በረዶ ከሰማይ የሚዘንብ
በበረዶውስ ፊት ማን ይቆማል
ጸሐፊው ይህንን ጥያቄ ምንያህል እግዚአብሔር የላከው በረዶ ከባድ እንደሆነ እግንኖ ያሳያል። “ማንም ቢሆን በላከው በረዶ ሚኖር አይኖርም”
ቃሉን ልኮ ያቀልጠዋል።
ጸሐፊው የእግዚአብሔር ቃል እንደ መልእክተኛ መስሎ ይናገራዋል። “በረዶ እንዲቀልጥ በቃሉ ያዛል”

Psalms 147:19
ቃሉን ለያዕቆብ፣ ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእሥራኤል ይናገራል
እነዚህ ሁለት አረፍተ ነገሮች አንድ አይነት ሀሳብ ሲኖራቸው ይህም እግዚአብሔር ህጎቹን ለእሥራኤል ብቻ እንደሰጠ ይናገራል፡፡
ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእሥራኤል ይናገራል
"ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእሥራኤል ይናገራል"
ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእሥራኤል ይናገራል
"ስርአቱንና ፍርዱን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሙሴ ህጎችን ነው፡፡
ፍርዱንም አልገለጠላቸውም
ሌሎች ከተሞች የእግዚአብሔርን ስርአት እና ፍርዱን አያቁትም፡፡

## Chapter 148

Psalms 148:1
አጠቃላይ ሀሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው
እግዚአብሔርን ከሰማያት አመስግኑት በአርያም አመስግኑት
"እግዚአብሔርን ከሰማያት አመስግኑት በአርያም አመስግኑት" እነዚህ ሁለቱ "አርያም" እና "ከሰማያት" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ከበፊቱ መስመር ጋር አንድ አይነት ሃሳብ አላቸው፡፡
Psalms 148:3
ፀሀይና ጨረቃ አመስግኑት
ጸሐፊው ፀሃይና ጨረቃ ልክ እንደ ሰው መስሎ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑት ያዛል፡፡ "እግዚአብሔርን ሰዎች እንደሚያመሰግኑት ፀሃይና ጨረቃ አመስግኑት"
ከዋክብት እና ብርሃን ሁሉ አመስግኑት
ጸሐፊው ከዋክብት እና ብርሃን ልክ እንደ ሰው መስሎ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑት ያዛል፡፡ "እግዚአብሔርን ሰዎች እንደሚያመሰግኑት ከዋክብት እና ብርሃን አመስግኑት"
Psalms 148:5
የእግዚአብሔርን ስም ያመስግኑት
"ስም" የሚለው ቃል ራሱን እግዚአብሔርን ያመለክታል፡፡ "እግዚአብሔርን ያመስግኑት"
ተፈጠሩም
"እርሱ ፈጠራቸው"
ለዘላለም ዓለም አቆማቸው ትእዛዝን ሰጠ፣ አያልፉምም
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1) "የማይለዋወጥ ትዛዝን ሰጠ" 2) "መታዘዝ ያለባቸውን ትዕዛዛትን ሰጣቸው"
ሰጠ
"ሰጠ"
Psalms 148:7
ጥልቆችም ሁሉ
ይህ ሃረግ ጥልቀት ካላቸው ባህሮች ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታትን ያመለክታል፡፡
"በጥልቁ ባህር ውስጥ ያሉ ፍጥረታት ሁሉ"
እሳትና በረዶ አመዳይና ውርጭ
ጸሐፊው እነዚህን የተፈጥሮ ተአምራቶችን እንደ ሰው መስሎ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ያዛቸዋል፡፡
ቃሉን የሚያደርግ ዓውሎ ነፋስም
ቃሉን የሚያዘውን የሚያደርግ ዓውሎ ነፋስ
Psalms 148:9
አያያዥ ሀሳብ
ጸሐፊው ሰው ያልሆኑ ነገሮችን ሰዎች እንደሆኑ ያህል እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ማዘዙን ይቀጥላል፡፡
አራዊት እንስሳትም ሁሉ ተንቀሳቃሾች
እነዚህ ቃላቶች የተለያዩ ሲሆኑ በአንድ ላይ ሁሉንም እንስሳቶችን ይወክላሉ፡፡
"እንስሳት ሁሉ"
Psalms 148:11
አያያዥ ሀሳብ
ጸሐፊው ሁሉም ሰው እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ያዛል፡፡
የምድር ነገሥታት
ይህ ቃል የሚያመለክተው በውስጡ የሚኖሩትን ሕዝቦችን ነው፡፡ "በምድር ላይ ሕዝቦች ሁሉ"
ጎልማሶችና ቆነጃጅቶች ሽማግሌዎችና ልጆች
ጎልማሶችና ቆነጃጅቶች ሽማግሌዎችና ልጆች ጸሐፊው ሁለት ማነፀፀሪያ ሲጠቀም አንደኛው በፆታ ሲሆን አንደኛው ደግሞ በእድሜ ነው ይህም ሁሉንም ሰው ለማመልከት ነው፡፡
Psalms 148:13
የእግዚአብሔርን ስም ያመስግኑ ስሙ ብቻውን
እዚህ ጋር "ስም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ራሱን ነው፡፡
"እግዚአብሔር ራሱ ብቻውን"

## Chapter 149

Psalms 149:1
አጠቃላይ ሀሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው
አጠቃላይ ሃሳብ
መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ሕዝቦች እየተናገረ ነው
አዲሱን ቅኔ
የሚሆነው ትርጉም 1) ከዚህ ቀደም ተቀኝተኸው ማታቀውን ቅኔ 2) ከዚህ ቀደም ማንም ተቀኝቶት ማያውቀውን ቅኔ
ተቀኙለት ምስጋናው...
"በምስጋና ዘምሩለት"
Psalms 149:2
በፈጣሪው ደስ ይበለው
የሚሆነው ትርጉም 1) ስለፈጠራቸው ደስ ይበላችሁ 2) የፈጠራቸው መልካም ስለሆነ ደስ ይበላችሁ
በንጉሣቸው ሐሤትን ያድርጉ
"በንጉሳቸው" የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል፡፡ የሚሆነው ትርጉም 1) እርሱ ንጉሳቸው ስለሆነ ደስ ይበላቸው 2) ንጉሳቸው መልካም ስለሆነ ሀሴት ያድርጉ
ስሙን በዘፈን ያመስግኑ
"ስሙን" የሚለው ቃል ራሱን እግዚአብሔርን ያመለክታል፡፡ "እሱን አመስግኑ" ወይም "ታላቅነቱን ለሕዝቦች ተናገሩ"
በከበሮ
የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ከላይ በኩል የሚመታ እንደ ከበሮ ሲመስል በጎኖቹ ደግሞ ብረት ዙሪያውን ሲኖረው ሲነቃነቅ የሚያሰማው ድምፅ ነው፡፡
Psalms 149:4
የዋሃንንም በማዳኑ ከፍ ከፍ ያደርጋልና
"የዋሆችን በማዳን ከፍ ከፍ ያደርጋቸዋል"
የዋሆች
"የዋህ የሆኑትን"
በምንጣፋቸውም ላይ
ይህ የሚያመለክተው በማታ ወደ መኝታው አልጋ የሚተኛውን ሰው ነው፡፡ "በምሽት ወደ አልጋቸው የሚተኙትን"
Psalms 149:6
የእግዚአብሔር ምስጋና በጉሮሮአቸው ነው
"ጉሮሮአቸው" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሉ ሰውን ነው፡፡ "እግዚአብሔርን ለማመስገን ሁልጊዜ የተዘጋጁ ይሁኑ"
ሁለት አፍ ያለውም ሰይፍ በእጃቸው ነው
"ሰይፍ" የሚለው ቃል ለጦርነት እና ለውጊያ መዘጋጀትን ያመለክታል፡፡ "ለእርሱ ጦርነት ለመዋጋት ሁልጊዜ ዝግጁ ይሁኑ"
አሕዛብ ላይ
"አሕዛብ ላይ" የሚለው ቃል በዛች ከተማ የሚኖሩትን ሕዝብ ያመለክታል፡፡
"የከተማዋ ሕዝቦች"
Psalms 149:8
በሰንሰለት

እስረኛዎች እንዳይንቀሳቀሱ ተብሎ ከከባድ ብረታብረት የሚሰራ ነው።
በእግር ብረት
በእግር ወይም በእጅ ላይ የሚደረጉ ሰንሰለት ሲሆን እንቅስቃሴን ይቀንሳል።
የተጻፈውን ፍርድ ያደርጉባቸው ዘንድ
“ፍርድ” የሚለው ቃል “መፍረድ” ወደሚለው መቀየር ይቻላል። “እግዚአብሔር እንዲሆን እንደፃፈው ሕዝቡ ላይ ይፈርዳሉ እናም ይቀጧቸዋል”

Chapter 150
Psalms 150:1
አጠቃላይ ሀሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው
አጠቃላይ ሀሳብ
ተመሳሳይነት በዕብራውያን ስነግጥም የተለመደ ነው
አጠቃላይ ሀሳብ
በመቅደሱ የሚሆኑትን አምልኮ እና ምስጋና ላይ ያተኩራል
እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት
ይህ ቦታ ለአምልኮ የሚኬድበት ቦታ ነው።
በሀይሉ ጠፈር
x
Psalms 150:3
አጠቃላይ ሀሳብ
ይህ የሚያተኩረው በሙዚቃ መሳሪያ እና በጭፈራ ማመስገን እና ማምለክ ላይ ነው።
በከበሮ
የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ከላይ በኩል የሚመታ እንደ ከበሮ ሲመስል በጎኖቹ ደግሞ ብረት ዙሪያውን ሲኖረው ሲነቃነቅ የሚያሰማው ድምፅ ነው።
ፅናፅል
ሁለት ቀጫጭን ብረቶች አብረው በመሆን እንድላይ ሲመቱ ከፍተኛ ድምፅ ያሰማሉ።
Psalms 150:6
አጠቃላይ ሀሳብ
ይህ ቁጥር የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ መጨረሻ ከመሆን ያለፈ ለሁሉም 5 የመዝሙር መጽሐፎች የመደምደሚያ ሀሳብ ነው። በመዝሙር 107 ጀምሮ በመዝሙር 150 ይጨርሳል።
እስትንፋስ ያለው ሁሉ
ይህ አገንኖ የሚናገረው በሕይወት ሆነው እግዚአብሔር እንዲያመልኩ የሚጠራ መልእክት ነው።

Chapter 1
Proverbs 1:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
ቁጥር 2-33 ግጥም ነው። (ግጥም የሚለውን ይመልከቱ)
ጥበብን እና ተግሳፅን ለማስተማር
ይህን ለውጦ “ጥበብ” እና “ተግሳፅ” የተባሉት ረቂቅ ስሞችን እንደ ገላጭ ወይም ግስ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- እንዴት ጥበበኛ መሆን እንደሚቻል እናንተን ለማስተማር እና እንዴት ግብረገባዊ ህይወት መኖር እንደሚቻል አቅጣጫ ለማሳየት ነው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
አርቆ ለማስተዋል የሚያስችሉ ቃላትን ለማስተማር
“ጥበበኛ አስተምህሮዎችን እንድትረዱ ለማገዝ”
ስለዚህ እናንተ እንድትቀበሉ
እዚህ ላይ “እናንተ” የሚመለከተው አንባቢዎችን ነው። በእናንተ ቋንቋ የተለመደ ከሆነ “እኛ” በሚለው አካታች ቃል መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ እኛ እንድንቀበል” (የሁለተኛ መደብ ቅርጾችን እና አካታች “እኛ” ይመልከቱ)
ለመኖር የሚያስችል መመሪያ ለመቀበል
ይህን ለውጦ “መመሪያ” የሚለው ረቂቅ ስምን እንደ ግስ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዴት መኖር እንደሚገባህ ታውቅ ዘንድ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 1:4
በተጨማሪ ለአላዋቂዎች ጥበብ ለመስጠት ነው
ይህን ለውጦ “ጥበብ” የሚለውን ረቂቅ ስም እንደ ቅፅል “ጠቢብ” ብሎ ማቅረብ ይቻላል። ይህ ደግሞ እንደ ገቢር/አድራጊ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ደግሞ ለአላዋቂዎች እንዴት ጠቢብ መሆን እንደሚቻል ለማስተማር ነው” (ረቂቅ ስሞች እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገቢሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
አላዋቂ
ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው
እውቀት እና ጥንቃቄን ለወጣቶች ለመስጠት
“እውቀት” እና “ጥንቃቄ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ግስ መቅረብ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- ወጣቶች ማወቅ የሚገባቸውን እና ማድረግ የሚገባቸውን ትክክለኛውን ነገር እንዴት መወሰን እንዳለባቸው ለማስተማር ነው (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ጥንቃቄ
በእያንዳንዱ ሁኔታ ምን መደረግ እንዳለበት ለማወቅ
ጥበበኛ ሰዎች ያድምጡ፣ እውቀትንም ይጨምሩ
“ጠቢቦች ያስተውሉ፣ ተጨማሪ እውቀትን ያግኙ”
አስተዋዮች ምሪት ያግኙ
“አስተዋይ ሰዎች ከእነኚህ ምሳሌዎች እንዴት ጥሩ ውሳኔ መወሰን እንዳለባቸው ይማሩ”
እንቆቅልሾች
አንድ ሰው ስለ እርሱ ካሰላሰለ በኋላ ብቻ ሊረዳቸው የሚችላቸው አባባሎች
Proverbs 1:7
አጠቃላይ መረጃ፡-
አባት ልጁን ያስተምራል።
የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው
“ፍርሀት”፣ “መጀመሪያ” እና “ጥበብ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ግስ መቅረብ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ ምን እንደሆነ ማወቅ ከመጀመርህ በፊት እግዚአብሔርን መፍራት አለብህ” ወይም “ጥበብ ምን እንደሆነ ለመማር መጀመሪያ እግዚአብሔርን ማክበር እና መታዘዝ አለብህ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ
ይህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለህዝቡ የገለጠላቸው ስሙ ነው። ይህንን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ ለመረዳት ስለ ያህዌ የሚናገረውን የትርጉም ቃል ገፅ ላይ ይመልከቱ።
ሞኞች ጥበብን እና ተግሳፅን ይንቃሉ
ለጥበብ እና ለምክር ዋጋ የማይሰጡ ሞኞች ናቸው።
አትተወው
ይህ ፈሊጥ “ችላ አትበለው” ወይም “አትናቀው” ማለት ነው (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ለራስህም የሞገስ ዘውድ ለአንገትህም ውበት የሚሰጥ ጌጥ ይሆንሃልና
ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያስተምሩት መመሪያ እና ተግሳፅ በጣም ጠቃሚ እና ትልቅ ዋጋ ያለው ስለሆነ እንደ ቆንጆ አንገት ላይ የሚደረግ ጌጥ ወይም የአበባ ጉንጉን ተደርገው ተገልፀዋል። አማራጭ ትርጉም፡- የአበባ ጉንጉን በራስ ላይ ወይም ድሪ በአንገት ላይ ማድረግ ውበትን እንደሚሰጥ እንደዚሁ እነርሱ ጠቢብ ያደርጉሀል (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አክሊል
ከአበባ ወይም ከቅጠል ተሰካክቶ የተሰራ ክብ ቅርፅ ያለው ዘውድ
ድሪ
በአንገት ዙሪያ የሚደረግ ጌጥ
Proverbs 1:10
በሀጢያታቸው እንድትሳተፍ ሊያባብሉህ ሞከሩ
“እነርሱ እንደሚያደርጉት ሀጢያትን እንድትሰራ ሊያሳምኑህ ሞከሩ”
አትከተላቸው
“እሺ አትበላቸው” ወይም “አትስማቸው”
ቢያባብሉህ

እዚህ ላይ ተናጋሪው ሀጢያተኞች አንድን ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት ለማባበል ለሞክሩ የሚችሉትን ምሳሌ ይሰጣል፡፡ (ግምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
እናድባ
“ተሸሸጎ ትክክለኛውን ጊዜ መጠበቅ”
Proverbs 1:12
አጠቃላይ መረጃ:-
ቁጥር 12-14 ሌሎች ሰዎች ሀጢያት እንዲሰሩ ለማባበል የሚሞክሩ የሀጢያተኞችን የሀሳብ ቃል ይጠቀልለዋል፡፡
ሲኦል ጤናማ ሰዎችን እንደሚውጣቸው እንዲሁ በህይወታቸው ሳሉ እንዋጣቸው
ሀጢያተኞች ልክ እንደ ሲኦል ንፁሀንን ስለ መግደል ያወራሉ፣ ህያው እና ጤነኛ ሰዎችን የሞቱ ሰዎች ወደሚሄዱበት ቦታ ይወስዳሉ፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንዋጣቸው. . . . ሲኦል እንደሚውጥ
እዚህ ላይ መቃብር ሰዎችን እንደሚውጥና ወደ ሙታን ቦታ እንደሚወስድ ሰው ተመስሎ ይነገራል፡፡ (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሲኦል ጤናማ ሰዎችን እንደሚውጣቸው
የሙታን መኖሪያ የሆነው ሲኦል ጤናማ ሰዎችን እንኳን እንደሚውጥ እንዲሁ ክፉዎች ሰለባዎቻቸውን ለማጥፋት ተስፋ ያደርጋሉ፡፡
ወደ ጉድጓድ እንደሚወርዱ እናርጋቸው
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች እነዚህ ናቸው፡- 1) ማንም ሊያገኘው የማይችል፣ ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ የገቡ መንገደኞችን ያመለክታል ወይም 2) እዚህ ላይ “ጉድጓድ” የሚለው ቃል ሲኦል ወይም የሞቱ ሰዎች የሚገቡበት ቦታ ማለት ነው፡፡
ከእኛ ጋር ዕጣህን ጣል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ተቀላቀለን” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ሁላችንም አንድ የጋራ ቦርሳ ይኖረናል
እዚህ ላይ “ቦርሳ” የሚወክለው የሰረቁትን ነገር በሙሉ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “የሰረቅነውን በሙሉ እኩል እንካፈለለን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ቦርሳ
ገንዘብ ለመያዝ የሚሆን ከረጢት
Proverbs 1:15
ከእነርሱ ጋር በዚያ መንገድ አትሂድ፤ እነርሱ በሚሄዱበት መንገድ እግርህ አይርገጥ
የሀጢያተኞችን ድርጊት እና ባህርይ አለመከተል ልጁ ሀጢያተኞች በሚሄዱበት መንገድ አለመሄዱ እና ፈፅሞም አለመንካቱ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ከሀጢያተኞች ጋር አትሂድ ወይም የሚያደርጉትን አታድርግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እግሮቻቸው ወደ ክፋት ይሮጣሉ
ሀጥያተኞች ክፉ ነገሮችን ለማድረግ ያላቸው ጉጉት ወደ ክፋት እየሮጡ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ክፉ ነገሮችን ለማድረግ የተጠሙ ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እግሮቻቸው ይሮጣሉ
እዚህ ላይ “እግር” የሚለው የሚወክለው ሙሉ ግለሰቡን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ይሮጣሉ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ደም ለማፍሰስ
እዚህ ላይ “ደም” የሚወክለው የሰውን ህይወት ነው፡፡ “ደም ለማፍሰስ” ማለት አንድ ሰውን መግደል ማለት ነው፡፡ (ምትክ ስም የሚለውን የመልከቱ)
ወፍ ፊት ለፊት እያየች እርስዋን ለመያዝ ወጥመድ መዘርጋት ጥቅም የለውም
ይሄ ተለዋጭ ዘይቤ ፊት ለፊት እያየች ያለውን ወጥመድ ያመለጠች ወፍን ጥበብ እና ለራሳቸው በሰሩት ወጥመድ ስር የወደቁ ሀጥያተኞችን ሞኝነት ያወዳድራል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 1:18
እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን ደም ለማፍሰስ ተደብቀው ይጠብቃሉ - በራሳቸው ላይ ወጥመድን ይዘረጋሉ
ይህ በምሳሌ 1:17 የጀመረውን ንፅፅር ያጠናቅቀዋል፡፡ ኃጢአትን በመለማመድ ራሳቸውን እያጠፉ ያሉት ሰዎች ለራሳቸው ወጥመድ አጥምደው ራሳቸውን እንደ ገደሉ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “እነኚህ ሰዎች ግን ከወፎቹም የበለጠ ሞኝ ናቸው፡፡ ራሳቸውን በገዛ ወጥመዳቸው ገደሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን ደም ለማፍሰስ ተደብቀው ይጠብቃሉ
ተደብቆ መጠበቅ መሸሸግ ነው፣ ጭካኔን ለማድረግ መዘጋጀት፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ራሳቸውን ለመግደል ምቹ ጊዜ እንደ መጠባበቅ ነው” ወይም “ሌሎችን ለመግደል እየሞከሩ ስለሆነ እነርሱ ራሳቸው ይገደላሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የራሳቸውን ደም
እዚህ ላይ ደም ለአስከፊ ሞት ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- ራሳቸውን በአስከፊ ሁኔታ ለመግደል (ምትክ ስም የሚለውን የመልከቱ)
በራሳቸው ህይወት ላይ ወጥመድን ይዘረጋሉ
እዚህ ላይ “የራሳቸው ህይወት” የሚለው ራሳቸው ለሚለው ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- ራሳቸው የገዛ ራሳቸውን በድንገት አጥቅቶ ለመግደል በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ የሚቆጠር ነው (ምትክ ስም የሚለውን የመልከቱ)
የሁሉም መንገዳቸው እንደዚህ ነው
የአንድ ሰው መድረሻ ወይም እጣ ፋንታ ልክ አንድ ሰው እንደሚራመድበት መንገድ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ይህ ነው ሁሉም ሰው ላይ የሚደርሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ፍትሀዊ ባልሆነ መንገድ የተከማቸ ሀብት የባለቤቱን ህይወት ያጠፋል
ሀብትን በሀይል፣ በስርቆት እና በማታለል ለማግኘት በመሞከር ራሳቸውን እያጠፉ ያሉ ሰዎች ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ የተገኘው ሀብት ራሳቸውን እንደሚገላቸው ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- ፍትሀዊ ባልሆነ መንገድ የተገኘው ሀብት የባለቤቶቹን ህይወት እንደሚያጠፋ እንደዚያ ነው፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 1:20
አጠቃላይ መረጃ:-
በ 1:20-1:33 ላይ ጥበብ ለህዝቡ እንደምትናገር ሴት ተደርጎ ተነግሯል፡፡ (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጥበብ ትጮሀለች
ቋንቋህ ጥበብን በከተማው ውስጥ ለህዝቡ እንደምትጮህ ሴት ለመጠቀም ካልፈቀደልህ እንደዚህ ብለህ መሞከር ትችላለህ፡- “እምዬ ጥበብ ትጮሀለች” ወይም “ክብርት ጥበብ ትጮሀለች” ወይም “ጥበብ እንደምትጮህ ሴት ናት” ( ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን የመልከቱ)
ድምፅዋን ከፍ ታደርጋለች
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- በጉልህ ደምፅ ትናገራለች (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
በአደባባይ
ይህ ቡዙ ሰዎች የሚገኙበት ቦታ ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “በገበያ ቦታዎች” ወይም “በከተማዋ ዋና አደባባዮች” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ጩኸት በበዛባቸው ዋና ጎዳናዎች ላይ
እነዚህ አማጭ ትርጉሞች ናቸው፡- 1) “ዋና” የሚለው የተጨናነቁ ጎዳናዎች የሚገናኙበት ቦታ ያመለክታል ወይም 2) “ዋና” ጩኸት በበዛበት ጎዳና ላይ ያሉ ሰዎች ጥበብን ሊመለከቱ እና ሊሰሙ የሚችሉበት የግንብ ጫፍን ያመለክታል፡፡
እናንተ አላዋቂዎች እስከመቼ አላዋቂነትን ትወዳላችሁ?
ጥበብ ይህንን ጥያቄ ጠቢብ ያልሆኑትን ለመገሰፅ ትጠቀምበታለች፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “እናንተ አላዋቂዎች አላዋቂ መሆንን መውደድ ማቆም አለባችሁ፡፡” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
አላዋቂ
ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው
እናንተ ፌዘኞች እስከመቼ በፌዝ ትደሰታላችሁ፣ እናንተ ሰነፎች እስከመቼ እውቀትን ትጠላላችሁ?
ጥበብ ፌዘኞችን እና ሰነፎችን ለመገሰፅ ይህንን ጥያቄ ትጠቀማለች፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “እናንተ የምታፌዙ በፌዝ መደሰታችሁን ማቆም አለባችሁ፣ እና እናንተ ሰነፎች እውቀትን መጥላት ማቆም አለባችሁ፡፡” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 1:23
አጠቃላይ መረጃ:-
ጥበብ መናገሯን ቀጥላለች፡፡ (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ትኩረት ስጡ
“በጥንቃቄ አዳምጡ”
ሀሳቤን ለእናንተ አፈስሳለሁ
ጥበብ ስለ ህዝቡ የምታስበውን በሙሉ ለእነርሱ መንገሯ ሀሳቧ እንደ ፈሳሽ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የምታፈሰው እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን የመልከቱ)
ቃሎቼን አሳውቃችኋለሁ
“የማስበውን እነግራችኋለሁ”
እጄን ዘረጋሁ
x
Proverbs 1:26
አጠቃላይ መረጃ:-
ጥበብ በናቋት ላይ ምን እንደሚደርስ በማብራራት መናገሯን ቀጥላለች።
እስቃለሁ
ጥበብ የምትባለው ሴት እርስዋን በማቃለላቸው ምክንያት በናቋት ላይ የምትስቅባቸው እንደሆነ ለማሳየት “ስለዚህ” የሚለውን ቃል በመጠቀም መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስለዚህ እስቃለሁ” (አያያዥ ቃላት የሚለውን ይመልከቱ)
በመከራችሁ ላይ
“መጥፎ ነገር ሲደርስባችሁ”
ሽብር በመጣ ጊዜ
“ሽብር” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅፅል መገለፅ ይችላል። “በተሸበራችሁ ጊዜ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
አስፈሪ ድንጋጤ እንደ ማዕበል በመጣባችሁ ጊዜ …… እንደ ዐውሎ ነፋስ ……. በመጣባችሁ ጊዜ
(ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ) በሕዝቡ ላይ የደረሰው አስከፊ ነገር እነርሱን እንደመታቸው ማዕበል፣ ፍርሃትና መከራ ጋር ተነጻጽሯል።
ዐውሎ ነፋስ
በጣም ሀይለኛ ጉዳትን የሚያስከትል የነፋስ ማዕበል
Proverbs 1:28
አያያዥ ሀሳብ:-
ጥበብ መናገሯን ቀጥላለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የዚያን ጊዜ ይጠሩኛል
“የዚያን ጊዜ የናቁኝ ለእርዳታ ወደ እኔ ይጮሀሉ”
እውቀትን ስለ ጠሉ
“እውቀት” የሚለውን ረቂቅ ስም “ተማረ” እንደሚለው ግስ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ ጠቢብ ለመሆን መማርን ስላልፈቀዱ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን መፍራት አልመረጡም
“ፍርሀት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔርን አልፈሩም” ወይም “እግዚአብሔርን አላከበሩትም ደግሞም አልታዘዙትም” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ምክሬን አልተከተሉም
“ትዕዛዜን አልተቀበሉም” ወይም “ምክሬን አልተቀበሉም”
Proverbs 1:31
አጠቃላይ መረጃ:-
ቀጥር 33 በምሳሌ 1:22 ላይ የጀመረውን የጥበብ መግለጫ ይደመድማል።
የመንገዳቸውን ፍሬ ይበላሉ
እዚህ ላይ የአንድ ግለሰብ ባህርይ መንገድ ወይም አቅጣጫ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። በተጨማሪም አንድ ሰው የባህሪውን ውጤት መቀበሉ ግለሰቡ የባህሪውን ፍሬ እየበላ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ ድርጊታቸው የሚያመጣውን መዘዝ መለማመድ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በእቅዳቸውም ፍሬ ይጠግባሉ
“የእቅዳቸውን ፍሬ እስከሚጠግቡ ድረስ ይመገባሉ።” የተንኮለኛ ሴራውን ውጤት የሚቀበል ግለሰብ የእቅዱን ፍሬ እንደሚበላ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “በተንኮለኛ ሴራቸው መዘዝ ይሰቃያሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አላዋቂ
ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው
መራቃቸው ይገድላቸዋል
ጥበብን የማይቀበል ግለሰብ በአካል ከጥበብ እንደ ራቀ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊነገር ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለመማር ስላልፈቀዱ ሞቱ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰነፎችን ቸልተኛነታቸው ያጠፋቸዋል
“ቸልተኛ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሞኞች ምን መደረግ እንደሚገባ ግድ ስለማይሰጣቸው ይሞታሉ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ቸልተኛነት
ስለ አንድ ነገር ፍላጎት ማጣት

---

Chapter 2
Proverbs 2:1
አጠቃላይ መረጃ:-
አባት ልጁን ግጥም በመጠቀም ያስተምራል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ቃሎቼን ብትቀበል
“የማስተምርህን ብትሰማ”
ትዕዛዛቴን በአንተ ዘንድ ብታኖር
ለታዘዙት ነገር ዋጋ መስጠት ትዕዛዛቶቹ ሀብት እንደሆኑ እና ግለሰቡ ሀብቱን ለማስቀመጥ አስተማማኝ ቦታ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ትዕዛዞቼ እንደ ሀብት ዋጋ እንዳላቸው አስብ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጆሮዎችህ እንዲያተኩሩ አድርግ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በጥንቃቄ ለማዳመጥ ራስህን አስገድድ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ጥበብን
ይህ ረቂቅ ስም እንደ ቅፅል ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እያስተማርኋችሁ ወዳለሁት ወደ ጥበብ ነገሮች” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ልብህን ወደ ማስተዋል አዘንብል
እዚህ ላይ “ልብ” የሰውን አእምሮ ይወክላል። “ልብህን አዘንብል” የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን አእምሮን ለአንድ ተግባር ሙሉ ለሙሉ መስጠት ወይም ማዘጋጀት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ጥበብ የሆነውን ለመረዳት ጠንክረህ ሞክር” ወይም “ጠቢብ አስተምሮዎችን ለመረዳት ራስህን ሙሉ በሙሉ ስጥ” (ምትክ ስም እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 2:3
ማስተዋልን ለማግኘት ብትጣራ እና ድምፅህን ከፍ አድርገህ ብትጮህ
እነኚህ ሁለት ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። ግለሰቡ እግዚአብሔርን አጥብቆ ማስተዋልን እየለመነ እንደሆነ ያመላክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “በአስቸኳይ እግዚአብሔርን ከጠየቅህ እና ማስተዋልን ከለመንክ” (ትይዩነት እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ድምፅህን ከፍ አድርገህ ብትጮህ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጮክ ብሎ መናገር ወይም መጮህ ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እርስዋን ብር እንደምትፈልግ ብትሻት እና ማስተዋልን የተቀበረ ገንዘብን እንደምትፈልግ ብትፈልጋት
ሁለቱም ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። እነዚህ ተነፃፃሪ ዘይቤዎች አንድ ሰው ጠቢብ የሆነውን ለመረዳት ማድረግ የሚገባውን ፅኑ ጥረት ያሳስባሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ዋጋ ያለው ነገርን ለማግኘት ጥረት በምታደርጉበት መጠን ማስተዋልን ብትፈልጉ” (ትይዩነት እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ብትሻት……… ማስተዋልን ብትፈልጋት
ጥበብ የሆነውን ለመረዳት በጣም በፀና መሞከር አንድ ሰው መፈለግ ያለበት እቃ በሚገባ እንደመረዳት ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔርን እውቀት ታገኛለህ
እግዚአብሔርን በማወቅ ስኬታማ መሆን የእግዚአብሔር እውቀት አንድ ሰው ከፍለጋ በኋላ የሚያገኘው ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 2:6
ከአንደበቱም እውቀት እና ማስተዋል ይወጣሉ
እዚህ ላይ “አንደበት” እግዚአብሔር ራሱን ወይም የሚናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከእግዚአብሔር እውቀት እና ማስተዋል ይወጣሉ” ወይም “እግዚአብሔር ማወቅ እና ማስተዋል ያለብንን ይነግረናል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ደስ ለሚያሰኙት ጥልቅ ጥበብን ያከማቻል
እግዚአብሔር ለሰዎች ጥበብ ማስተማሩ ጥበብ እግዚአብሔር የሚያከማቻቸው እና ለሰዎች የሚሰጠው ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "ለሚያስደስቱት ለእነርሱ በእውነት ጠቢብ የሆነውን ያስተምራል።" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መልካም
"የሚያስተማምን"
ለእነርሱ ጋሻ ነው
እግዚአብሔር ህዝቡን መከላከል መቻሉ እርሱ ጋሻ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "እግዚአብሔር እነርሱን ይከላከላል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ያለነቀፋ ለሚሄዱ
ያለነቀፋ የሚሄድ ሰው ያለነቀፋ እንደሚራመድ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "ነቀፋ የሌለበት ሕይወት የሚኖር" ወይም "መኖር የሚገባቸውን ሕይወት የሚኖሩ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የፍትህን መንገድ ይጠብቃል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ፍትህ ራሱ መንገድ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "እግዚአብሔር ሰዎች በፍትህ መመላለሳቸውን ያረጋግጣል" ወይም 2) የሰው ህይወት መንገድ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "በፍትህ የሚመላለሱትን እግዚአብሔር ይጠብቃል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእነርሱን መንገድ ያፀናል
የአንድ ሰው ህይወት መንገድ ወይም አቅጣጫ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "እነዚያን ይከላከላል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 2:9
ፍትሃዊነት
ትክክለኛነት
መልካም መንገድን ሁሉ
x
Proverbs 2:11
ጥንቃቄ ይጠብቅሀል፣ ማስተዋልም ይጋርድሀል
"ጥንቃቄ" እና "ማስተዋል" አንድ ሌላ ሰውን መጠበቅ የሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። እነዚህ ሁለት ሀሳቦች በመሰረቱ አንድ አይነት ትርጉም አላቸው። አማራጭ ትርጉም፡- "አንተ በጥንቃቄ ስለምታስብ እና ትክክል እና ስህተት የሆነውን ስለምትረዳ የተጠበቅህ ትሆናለህ" (ሰውኛ ዘይቤ እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ጥንቃቄ
በድርጊት እና ንግግር ጥንቁቅ የመሆን ችሎታ
ይጠብቅሀል
አንድን ሰው ወይም አንድን ነገር ለመጠበቅ፣ ለመከላከል ወይም ለመንከባከብ
እነርሱ ከክፋት መንገድ ያድኑሃል
"እነርሱ" የሚለው አንድን ሰው መጠበቅ የሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ ተደርጎ የተነገረላቸው ጥንቃቄ እና ማስተዋልን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- "ክፉ ከሆነው መራቅን ታውቃለህ" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከክፋት መንገድ
ክፉ ባህሪ ክፋት አንድ ሰው የሚራመድበት መንገድ ወይም አቅጣጫ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ትክክለኛውን መንገድ የተወ እና በጨለማ መንገድ የሚጓዝ
ትክክለኛ የሆነውን የማያደርግ ነገር ግን ክፉ የሆነውን ለማድረግ የወሰነ ግለሰብ በትክክለኛው መንገድ መጓዝ እንዳቆመ እና በጨለማው መንገድ መጓዝ እንደመረጠ ሰው ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የተወ
"እርሱ" የሚለው ጠማማውን ነገር የሚናገሩትን ሰዎች ይወክላል።
መተው
ወደ አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር ፈጽሞ ላይመለሱ ትቶ መሄድ
Proverbs 2:14
ደስ ይሰኛሉ
እነርሱ የሚለው ምሳሌ 2:12 ላይ ያሉትን ሰዎች ይወክላል
በክፉ ጠማማነት ሀሴት ማድረግ
ይህ ከመጀመሪያው የዐረፍተ ነገር ክፍል ጋር በመሰረቱ አንድ አይነት ትርጉም አለው። አማራጭ ትርጉም፡- "ክፉ እንደሆነ የሚያውቁትን በማድረግ ሀሴት ያደርጋሉ" (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ጠማማ መንገድን ይከተላሉ
ሌሎችን የሚዋሹ ሰዎች የተጣመመ ወይም የተጠመዘዘ መንገድ ላይ እንደሚጓዙ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "ሌላ ሰዎችን ያታልላሉ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አካሄዳቸውን በአታላይነታቸው ይደብቃሉ
ሌሎች ሰዎች ምን እንዳደረጉ እንዳያውቁባቸው የሚዋሹ ሰዎች ማንም ሰው መንገድ ላይ እንዳያይከተላቸው አካሄዳቸውን እንደሸፈኑ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "ማንም ሰው ያደረጉትን እንዳያውቅ ይዋሻሉ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 2:16
አጠቃላይ መረጃ፡-
አባት ልጁን ጥበብ እንዴት እንደምትጠብቀው ማስተማር ቀጥሏል።
ጥበብ እና ጥንቃቄ ያድኑሀል
ፀሀፊው ጥበብ እና ጥንቃቄን የተቆጣጠራቸውን ግለሰብ የሚያድኑ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- "ጥበብ እና ጥንቃቄ ካለህ ራስህን ታድናለህ" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የወጣትነት ወዳጅዋን
ይህ ልጅ እያለች ያገባችውን ባለቤትዋን የሚያመለክት ነው።
የአምላክዋን ቃል ኪዳን
ይህ ሊወክል የሚችለው በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ከባለቤትዋ ጋር ስለፈፀመችው የጋብቻ ቃል ኪዳን ነው።
Proverbs 2:18
ቤትዋ ወደ ሞት ይመራል
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) "ወደ ቤትዋ መሄድ ወደ ሞት ይወስዳል" ወይም 2) "ወደ ቤትዋ የሚወስደው መንገድ ወደ ሞት የሚወስድ መንገድ ነው።"
አካሄዷ ይመራሀል
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) "ወደ ቤትዋ ያለው መንገድ ይመራሀል" ይህ ወደ ቤትዋ የሚያመራውን መንገድ ወይም ዱካ ይወክላል 2) ይህ ተለዋጭ ዘይቤ አኗኗርዋን እንደምትጓዝበት መንገድ አድርጎ የሚናገር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "የአኗኗር መንገዷ ይመራሀል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በመቃብር ወዳሉት
ይህ የሙታንን መንፈስ ይወክላል ደግሞም ለሙታን መኖሪያም ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "ወደ መቃብር" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ እርስዋ መግባት
ይህ አንድ ሰው ከሴተኛ አዳሪ ጋር እንደሚያደርገው ከእርስዋ ጋር ለመተኛት ወደ ቤትዋ መሄድ ማለት ነው። (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የህይወትን መንገድ አያገኙም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ወደ ህያዋን ምድር አይመለሱም" ወይም 2) "መቼም ቢሆን እንደገና ደስተኛ ህይወትን አይኖሩም።"
Proverbs 2:20
ታዲያ
ፀሀፊው ማስተዋል እና ጥንቃቄን የማግኘት ውጤትን ይናገራል።
በመንገድ ትሄዳለህ ......... ጎዳና ትከተላለህ
የአንድ ሰው ጠባይ በመንገድ ላይ እየተጓዘ እንዳለ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "በመንገዱ ትኖራለህ........ምሳሌውን ተከተል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉዎች ከምድሪቱ ይቆረጣሉ
ፀሀፊው እግዚአብሔር ሰዎችን ከምድሪቱ ማስወገዱን አንድ ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ ላይ እንደሚቆርጥ እግዚአብሔር ሰዎቹን እየቆረጠ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ መገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- "እግዚአብሔር ክፉዎችን ከምድሪቱ ያስወግዳል" (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉዎች ......... ታማኝነት የጎደላቸው
እነኚህ የስም ቅፅሎች እንደ ቅፅል ሊገለፁ የሚችሉ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- እነዚያ ክፉ የሆኑት...... እነዚያ ታማኝነት የጎደላቸው ወይም ክፉ ሰዎች........ ታማኝነት የጎደላቸው ሰዎች (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ታማኝነት የሌላቸው ከእርስዋ ይቆረጣሉ

ፀሀፊው እግዚአብሔር ሰዎችን ከምድሪቱ ማስወገዱን አንድ ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ ላይ እንደሚቆርጥ እግዚአብሔር ሰዎቹን እየቆረጠ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ መገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ታማኝነት የሌላቸውን ከእርስዋ ያስወግዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 3

Proverbs 3:1

አጠቃላይ መረጃ፡-

ፀሀፊው ግጥምን በመጠቀም ልጁን እንደሚያስተምር አባት ይናገራል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ትእዛዛቴን አትርሳ

“ትእዛዛት” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ያዘዝኩህን እንዳትረሳ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ትምህርቴንም በልብህ ጠብቅ

የፊተኛው ሀረግ በአሉታዊ አነጋገር ያለውን ይሄ ሀረግ በአዎንታዊ አነጋገር ይናገረዋል። እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል አእምሮን ይወክላል። “ትምህርቴን” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ ያስተማርኳችሁን አስታውሱ” (ትይዩነት እና ምትክ ስም እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ረጅም ቀኖችን እና የሕይወት ዘመናትን

እነዚህ ሁለት ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉምን ይጋራሉ ደግሞ ረጅም ህይወት መኖርንም ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፡- ረጅም እድሜ (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:3

በኪዳን የተመሰረተ ታማኝነት እና እውነተኛነት አይለዩህ

ፀሀፊው ስለ “የኪዳን ታማኝነት” እና “እውነተኛነት” አንድን ሰው ትተው መሄድ የሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። “ታማኝነት” እና “እውነተኛነት” የተባሉት ረቂቅ ስሞች “ታማኝ” እና “እውነተኛ” ተብለው ሊገለፁ ይችላሉ። እናም አሉታዊው ትእዛዝ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ እውነተኛ እና ለኪዳኑ ታማኝ ሁን” ( ሰውኛ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በአንገትህ ዙሪያ እሰራቸው

ፀሃፊው ስለ ታማኝነት እና እውነተኛነት አንድ ሰው እንደ አንገት ጌጥ በአንገቱ ዙሪያ የሚያስራቸው ነገሮች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አምሳያው እነዚህ አንድ ሰው ወደ ውጪ የሚያሳያቸው ዋጋቸው የከበረ ነገሮች እንደሆኑ ይጠቁማል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው የአንገት ጌጥ እንደሚያስረው እነርሱን በኩራት አሳያቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በልብህ ፅላት ላይ ፃፋቸው

እዚህ ላይ ልብ የአንድ ሰውን አእምሮ ይወክላል። አእምሮ አንድ ሰው መልእክት እና ትእዛዛትን መፃፍ የሚችልበት ፅላት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- በፅላት ላይ በቋሚነት እንደፃፍሃቸው እንደዚሁ ሁልጊዜ አስታውሳቸው (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔረ እና በሰው ፊት

እዚህ ላይ ፊት ፍርድን ወይም ምዘናን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- በእግዚአብሔር እና በሰው ዳኝነት (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:5

ፍፁም ልብህ

“ልብ” የሚለው ቃል ውስጣዊ ማንነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሙሉ ማንነትህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በራስህ ማስተዋል አትደገፍ

ፀሀፊው በራስ ማስተዋል መደገፍን “ማስተዋል” አንድ ሰው ሊደገፍበት የሚችል ነገር እንደሆነ አድርጎ

በመንገድህ ሁሉ

ፀሀፊው የአንድ ሰው ድርጊትን ግለሰቡ የሚጓዝበት መንገድ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “በምታደርገው ሁሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገድህን ቀና ያደርገዋል

እግዚአብሔር የአንድ ሰው ተግባርን ማበልፀጉ የዚያ ሰው ተግባር እርሱ የሚጓዝበት እና እግዚአብሔር ከእንቅፋት ነፃ የሚያደርገው መንገድ እንደሆነ አድርጎ ፀሀፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ መሳካትን ይሰጥሀል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:7

በራስህ አስተያየት ጥበበኛ አትሁን

ፀሀፊው የአንድ ሰውን አስተሳሰብ ያ ሰው በአይኑ አንድ ነገር እያየ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- በራስህ አስተሳሰብ ጥበበኛ አትሁን (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከክፉ ራቅ

ፀሃፊው ክፉ ተግባር አለመፈፀምን ከክፋት እየራቀ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፋትን አትፈፅም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ለስጋህ ፈውስ ይሆንልሀል

“እርሱ” የሚለው ቃል በቀደመው ቁጥር ላይ ፀሀፊው የሰጠውን ትእዛዛት ያመለክታል። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልፅ መደረግ ይችላል። “ስጋ” የሚለው ቃል ሙሉ አካልን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህንን ካደረግህ ለአካልህ ፈውስ ይሆንልሀል” ( ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:9

በምርትህ ሁሉ

“በሰበሰብከው ምግብ ሁሉ”

ጎተራህ ሙሉ ይሆናል

ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጎተራህ ሙሉ ይሆናል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ጎተራ

ምግብ የሚከማችበት ህንፃ ወይም ክፍል

ገንዳህም ይትረፈረፋል

ማከማቻህም መክደን እስከማይቻል ድረስ እጅግ በጣም ይሞላል።

Proverbs 3:11

አጠቃላይ መረጃ፡-

ፀሀፊው ልጁን እንደሚያስተምር አባት ይፅፋል።

ደስታን የሚፈጥርለት ልጅ

“እርሱ ሀሴት የሚያደርግበት ወንድ ልጅ። ይህ አባትየውን ለወንድ ልጁ ያለውን ፍቅር ያመለክታል እንጂ የወንድ ልጁ ባህርይ በአባትየው ዘንድ ያለውን ቅቡልነት አይደለም። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ የሚወደው ወንድ ልጅ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 3:13

ጥበብን የሚያገኝ ሰው

ፀሀፊው “ጥበብ” አንድ ሰው የሚያገኘው ነገር እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብን ያገኝ ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብር በምላሹ የሚሰጠው

ይህ ሰው ብርን ስራ ላይ በማዋል ወይም በመሸጥ የሚያገኘውን ትርፍ ያመለክታል።

Proverbs 3:15

አጠቃላይ መረጃ፡-

ፀሀፊው ጥበብ ሴት እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይበልጥ የከበረ

“የላቀ ዋጋ ያለው”

በቀኝ እጇዋ ረጅም እድሜ ይዛለች፤ በግራ እጇዋ ባለጠግነት እና ክብር

x

Proverbs 3:17

መንገድዋ የደግነት መንገድ ነው፣ ጎዳናዋም ሁሉ ሰላም ነው

ፀሀፊው ጥበብ ሴት እንደሆነች እና ጥበብ ለሰው የምትሰጠው ጥቅም ያንን ሰው ጥበብ በመንገድ ላይ እየመራችው እንዳለች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ ሁልጊዜ በደግነት ትይዝሀለች እና ሰላም ትሰጥሀለች” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርስዋ አጥብቀው ለሚይዟት የህይወት ዛፍ ናት

ፀሀፊው ጥበብን ህይወት የሚሰጥ ፍሬ እንደሚያፈራ ዛፍ እና ከጥበብ የሚጠቀም ሰውን ያም ሰው ከፍሬዋ እንደበላ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከፍሬዋ የበሉትን ሰዎች በህይወት እንደምታቆይ ዛፍ ናት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የህይወት ዛፍ
“ህይወትን የሚሰጥ ዛፍ” ወይም “ፍሬው ህይወትን የሚያቆይ ዛፍ”
አጥብቀወ ለሚይዟት
“ፍሬውን አጥብቀው ለሚይዙ”
Proverbs 3:19
እግዚአብሔር ምድርን መሰረተ………. ሰማያትንም አፀና
ፀሀፊው እግዚአብሔር ምድርና ሰማያት መፍጠሩን የህንፃ መሰረትን እንደጣለ አድርጎ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ምድርን ፈጠረ……….. ሰማያትን ሰራ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጥልቆች ተሰንጥቀው ተከፈቱ
በጥንት አስተሳሰብ ውሀ ከመሬት በታች ይገኛል፡፡ ይህ ሀረግ እግዚአብሔር ይህንን ውሀ ከመሬት እንዲወጣ እንዳደረገና ውቅያኖሶችና ወንዞች እንዲገኙ እንዳደረገ ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ወንዞቹ እንዲፈሱ አደረገ” ወይም “ውቅያኖሶች እንዲፈጠሩ አደረገ” (ግምታው እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠል
ሌሊት በመሬት ላይ የሚሰበሰብ ውሀ
Proverbs 3:21
እነርሱ ከእይታህ አይራቁ
ፀሀፊው አንድ ነገር አለመርሳትን ሁልጊዜ እርሱን ማየት እንደመቻል አድርጎ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱን አትርሳ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለነፍስህ ህይወት ይሆናሉ
እዚህ ላይ “ነፍስ” ግለሰቡን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንተ ህይወት ይሆናሉ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
በአንገትህ ዙሪያ የምታስረው የሞገስ ጌጥ
ፀሀፊው “ትክክለኛ ፍርድ” እና “ማስተዋል” አንድ ሰው በአንገቱ ዙሪያ እንደ አንገት ጌጥ የሚያስራቸው ነገሮች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል፡፡ ይህ ምስል እነዚህ አንድ ሰው ወደ ውጪ የሚያሳያቸው ዋጋ ያላቸው እንደሆኑ ይጠቁማል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ራሱን በአንገት ጌጥ እንደሚያስጌጥ እንደዚያ የሞገስ ማሳያ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሞገስ ጌጥ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የሚስማማ ጌጥ” ወይም 2) “የእግዚአብሔርን ሞገስ የሚያሳይ ጌጥ፡፡”
Proverbs 3:23
በመንገድህ ላይ በደህንነት ትራመዳለህ
ፀሀፊው የአንድ ሰው ህይወትን መኖር ያ ሰው በመንገድ ላይ እየተራመደ እንዳለ አድርጎ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ህይወትህን በደህንነት ትኖራለህ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እግርህ አይሰናከልም
“እግር” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና ይወክላል፡፡ ፀሀፊው ስህተት ማድረግን ሰው በመንገድ ላይ በአንድ ነገር እንደተደናቀፈ አድርጎ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ስህተት የሆኑ ነገሮችን አታደርግም” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በተጋደምህ ጊዜ
ሰው የሚጋደመው ለመተኛት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ የዚህ ትርጉም ግልጽ መደረግ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለመተኛት ስትጋደም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እንቅልፍህ ጣፋጭ ይሆናል
ፀሀፊው ስለ ሰላማዊ እና አስደሳች እንቅልፍ ለሚተኛው ሰው ጣፋጭ ጣእም እንደሚያስገኝለት አድርጎ ይናገራል፡፡ “እንቅልፍ” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እንቅልፍህ አስደሳች ይሆናል” ወይም “በሰላም ትተኛለህ” (ተለዋጭ ዘይቤ ወይም ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 3:25
በክፉዎች አማካኝነት የሚደርስ ጥፋት፣ ሲመጣ
ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉዎች ጥፋትን ሲያመጡ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ከጎንህ ይሆናል
“እግዚአብሔር ከአጠገብህ ይሆናል፡፡” አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጎን መቆም የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር አንዱ ሰው ሌላኛውን ሰው ይረዳዋል እና ይደግፈዋል ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ይደግፍሀል እና ይከራከርልሀል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እግርህ በወጥመድ እንዳይያዝ ይጠብቃል
ፀሀፊው “በሽብር” እና “በጥፋት” የተጎዳውን ሰው በወጥመድ እንደተያዘ አድርጎ ይናገራል፡፡ “እግር” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን ለጎዱ ከሚፈልጉህ ሰዎች ይጠብቅሀል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 3:27
መልካሙን አትከልክል
“መልካም ነገርን አትከልክል” ወይም “መልካም ተግባርን አትከልክል”
ልታደርግ የሚቻልህ ሲሆን
“መርዳት የምትችል ሲሆን”
በእጅህ ላይ ገንዘብ ሲኖር
በእጅህ ላይ ገንዘብ ሲኖርህ፡፡ የዚህ ትርጉም ግለሰቡ ለመርዳት የሚሆን ገንዘብ በአሁኑ ጊዜ እያለው ነገር ግን ጎረቤቱን ነገ ተመልሶ እንዲመጣ ይነግረዋል የሚል ነው፡፡
Proverbs 3:31
መንገዱን ሁሉ አትምረጥ
የሁከተኛ ግለሰብ ተግባርን ማድረግ መምረጥ እንደሌለበት ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡ “መንገዱን ሁሉ ለማድረግ አትምረጥ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠማማ ሰው በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው
“እግዚአብሔር ጠማማን ሰው ይጠላል”
ጠማማ ሰው
የማይታመን ወይም አታላይ የሆነ ሰው
ለቅን ሰው ሚስጥሩን ይገልፅለታል
እግዚአብሔር ትክክለኛውን ነገር የሚያደርጉትን እንደ ቅርብ እና ታማኝ ጓደኛ ሀሳቡን ያካፍላቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለቅኖች ቅርብ ጓደኛ ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 3:33
የእግዚአብሔር እርግማን በክፉዎች ቤት ላይ ነው
ፀሀፊው የእግዚአብሔርን እርግማን በክፉ ሰው ቤት ጫፍ ላይ እግዚአብሔር እንዳስቀመጠው ነገር እንደሆነ አድርጎ ይናገራል፡፡ “ቤት” የሚለው ቃል የቤተሰብ ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የክፉ ሰውን ቤተሰብ ረግሟል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የፃድቃን ሰዎችን ቤት ይባርካል
“ቤት” የሚለው ቃል ቤተሰብን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የፃድቅ ሰዎችን ቤተሰብ ይባርካል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ለትሁታን ሞገሱን ይሰጣል
ፀሀፊው የእግዚአብሔርን ሞገስ እርሱ ለሰዎች የሚሰጠው ነገር እንደሆነ አድርጎ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሞገሱን ለትሁት ሰዎት ያሳያል” ወይም “ለትሁት ሰዎች ጸጋውን ይሰጣል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 3:35
ጠቢብ ሰዎች ክብርን ይወርሳሉ
ፀሀፊው ጠቢብ ሰዎች የክብር ስም ማግኘታቸውን ክብርን በቋሚ ባለቤትነት እንደወረሱ አድርጎ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ጠቢብ ሰዎች ክብርን ያገኛሉ” ወይም “ጠቢብ ሰዎች የተከበረ ስም ያገኛሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሞኞች ከፍታ ውርደታቸው ይሆናል
ፀሀፊው እግዚአብሔር የሞኞች ውርደትን ለሁሉም ሰው ግልፅ ማድረጉን እግዚአብሔር ሞኞችን ሁሉም ሰው እንዲያያቸው ወደላይ ከፍ እንዳደረጋቸው አድርጎ ይናገራል፡፡ ይህ በገቢር/አድራጊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የሞኞትን ውርደት ሁሉም ሰው እንዲያይ ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 4

Proverbs 4:1

አጠቃላይ መረጃ:-

ፀሀፊው ልጁን እንደሚያስተምር አባት ይናገራል።

ትኩረት ስጥ

“በጥንቃቄ አዳምጥ”

ማስተዋል ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ

“እንዴት ማስተዋል እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ” ወይም “ማስተዋልን ታገኛላችሁ”

እኔ መልካም ትምህርትን እሰጣችኋለሁ

“እኔ የማስተምራችሁ መልካም ነው”

Proverbs 4:3

የአባቴ ልጅ ሳለሁ

ይህ ፀሀፊው ገና በአባቱ እንክብካቤ ስር ያለ ልጅ የነበረበትን ጊዜ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “ገና ከአባቴ የምማር ወንድ ልጅ ሳለሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ተወዳጅ ራሱን ያልቻለ እና ብቸኛ ልጅ

እዚህ ላይ ተወዳጅ “ራሱን ያልቻለ” የሚለው ቃል አካላዊ ብቃት ገና የሌለው የታዳጊነት እድሜውን ያመለክታል። “ብቸኛ” ከሚለው ቃል ጋር ጥምር ቃልን ይፈጥራል። አማራጭ ትርጉም:- “ተወዳጅ ራሱን ያልቻለ ብቸኛ ልጅ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህ ቃሎቼን ይያዝ

እዚህ ላይ “ልብ” የሰውን አእምሮ ይወክላል። ፀሀፊው ቃሎች ማስታወስን ልብ እነርሱን አጥብቃ እንደያዘች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትጉርም:- “የማስተምርህን ሁልጊዜ አስታውስ” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:5

Possible

አባትየው የራሱ አባት ያስተማረውን ለልጆቹ ማስተማር ቀጥሏል።

ጥበብ ማግኝት

“ጥበብን ለራስህ ለማግኘት ጠንክረህ ስራ” ወይም “ጥበብ አግኝ”

አትርሳ

“አስታውስ”

አትተው

“ተቀበል”

የአፌን ቃላቶች

እዚህ ላይ “አፍ” የሚለው ቃል የሚናገረውን ግለሰብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “የምናገረውን” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብን አትተዋት እርስዋም ከለላ ትሆንሀለች፤ ውደዳት እርስዋም ትጠብቅሃለች

ፀሀፊው ጥበብ ታማኝ የሆነላትን ሰው የምትጠብቅ ሴት እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብን አትተዋት

ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ጥበብን አጥብቀህ ያዝ” ወይም “ለጥበብ ታማኝ ሁን”

ውደዳት

“ጥበብን ውደድ”

Proverbs 4:7

አጠቃላይ መረጃ:-

አባትየው የራሱ አባት ያስተማረውን ለልጆቹ ማስተማሩን አበቃ።

ማስተዋልን ማግኘት እንድትችል ያለህን ሁሉ ክፈል

“ካለህ ነገር ሁሉ በላይ ለማስተዋል ዋጋ ስጥ”

ለጥበብ ከፍተኛ ስፍራ ስጥ እርስዋም ከፍ ከፍ ታደርግሀለች

ፀሀፊው ጥበብ ሴት እንደሆነችና ለሰው ትልቅ ክብር መስጠቷን ያንንም ሰው ጥበብ ወደ ታላቅ ስፍራ እንዳወጣች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “ለጥበብ ከፍተኛ ስፍራን ከሰጠህ ትልቅ ክብርን ትሰጥሀለች” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከፍተኛ ስፍራን መስጠት

ለአንድ ነገር ወይም ለአንድ ሰው ታላቅ ፍቅር መሰማት ወይም ማሳየት

እርስዋን አጥብቀህ ስትይዛት ታከብርሀለች

ፀሀፊው ጥበብ ሴት እንደሆነች እና ለጥበብ ዋጋ የሚሰጥ ሰው ክንዱን በእርስዋ ዙሪያ እንዳሰቀመጠ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “ጥበብን በጣም ከወደድህ ጥበብ ሰዎች እንዲያከብሩህ ታደርጋለች” (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በራስህ ላይ የክብር አክሊልን ታስቀምጣለች

ፀሀፊው ሰው ጥበብን ከማግኘቱ የተነሳ የሚኖረውን ክብር ጥበብ በግለሰቡ ራስ ላይ አክሊልን እንዳስቀመጠችለት አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “ጥበብ የአንተን ታላቅ ክብር የምታሳይ በራስህ ላይ እንደተቀመጠ አክሊል ትሆንልሃለች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አክሊል

ከአበባ ወይም ከቅጠል ተሰካክቶ የተሰራ ክብ ቅርፅ ያለው ዘውድ

የተዋበ ዘውድን ትሰጥሀለች

ፀሀፊው ሰው ጥበብን ከማግኘቱ የተነሳ የሚኖረውን ክብር ጥበብ በግለሰቡ ራስ ላይ ዘውድን እንዳስቀመጠችለት አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- ጥበብ በራስህ ላይ እንደሚሆን የተዋበ ዘውድ ይሆናል (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመላከቱ)

Proverbs 4:10

ለቃሎቼ ትኩረት ስጥ

“የማስተምርህን በጥንቃቄ አዳምጥ”

በህይወትህ ዘመን ቡዙ አመታት ይኖሩሀል

“ቡዙ አመታትን ትኖራለህ”

በጥበብ ጎዳና አስተማርሁህ፤ በቀጥተኛ መንገዶች መራሁህ

ፀሀፊው ወንድ ልጁ በጥበብ እንዲኖር ማስተማሩ ወንድ ልጁን ሰው ጥበብ ሊያገኝ በሚችልበት መንገዶች እየመራው እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “በጥበብ መኖር እንዴት መኖ እንዳለብህ እያስተማርሁህ ነው፤ ለመኖር ትክክለኛውን መንገድ እያብራራሁ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምትራመድ ጊዜ ማንም በመንገድህ ላይ አይቆምም፣ በሮጥህ ጊዜም አትሰናከልም

እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። ፀሀፊው ሰው የሚያደርገውን ውሳኔ እና ተግባር ያ ሰው በመንገድ ላይ እየተራመደ ወይም እየሮጠ እንደሆነ እና ስኬታማ ስለሆነ ሰው ደግሞ መንገዱ ሰው እንዲሰናከል ከሚያደርግ መሰናክል ነፃ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “አንድ ነገር ስታቅድ፣ እርሱን በማድረግ ስኬታማ ትሆናለህ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:13

ተግሳፅን ያዝ፣ አትተወውም

ፀሀፊው የተማረውን የሚያስታውስ ሰውን “ተግሳፅ” ያ ሰው አጥብቆ ሊይዘው የሚችለው ነገር እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “ያስተማርሁህን መታዘዝ ቀጥል እና መቼም ቢሆን አትርሳው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ህይወትህ ነውና

ፀሀፊው ምክር የሰውን ህይወት መጠበቁ የዚያ ሰው ህይወት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “እርሱ ህይወትህን ይጠብቃልና” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉዎችን መንገድ አትከተል ደግሞም ክፋትን በሚያደርጉ ሰዎች መንገድም አትሂድ

ፀሀፊው የሰውን ተግባር ያ ሰው በመንገድ ላይ እየሄደ እንዳለ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “ክፉ ሰዎች የሚያደርጉትን አታድርግ፣ ክፉ በሚያደርጉ ሰዎች ድርጊትም አትተባር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሽሽው

“የክፉዎችን መንገድ ሽሽ”

Proverbs 4:16

ክፋትን እስኪፈፅሙ ድረስ መተኛት አይችሉም

ምናልባት ቃል በቃል ሊተኙ ይችላሉ፣ ፀሀፊው ግን እንዴት ክፉ ተግባርን ለመፈጸም በብርቱ እንደሚፈልጉ ለመግለፅ ግነትን ተጠቅሟል። (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንቅልፋቸው አይመጣም

ፀሀፊው እንቅልፍ መተኛት ያልቻሉ ሰዎችን እንቅልፍ አንድ ሰው ከእነርሱ እንደሰረቀባቸው አቃ አድርጎ ይናገራል። እነርሱ ምናልባትም ቃል በቃል እንቅልፍ ሊተኙ ይችላሉ ነገር ግን ፀሀፊው ክፉ ተግባርን ለመፈጸም ምን ያህል አጥብቀው እንደሚሹ ለማስረዳት ግነትን ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም:- “መተኛት አይችሉም” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው እስኪያሰናክሉ ድረስ

ፀሀፊው ሌላ ሰው ላይ ጉዳት ማድረስን ያን ሰው እንዲሰናከል ማድረግ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ አንድ ሰው እስኪጎዱ ድረስ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፋትን እንጀራ ይበላሉና የአመፃንም ወይን ጠጅ ይጠጣሉና

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ይህ ፀሀፊው እነዚህ ሰዎች ሳያቋርጡ ክፋትን እና አመፃን የሚያደርጉ ሰዎች አንድሰው እንጀራ እና ወይንጠጅ እንደሚጠጣ እንደዚያ እንደበሏቸው እና እንደጠጧቸው አድርጎ የሚናገርበት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ክፋት እንደሚመገቡት እንጀራ አመፅ ደግሞ እንደሚጠጡት ወይንጠጅ ነው። ወይም 2) እነዚህ ሰዎች ምግባቸውን እና መጠጣቸውን የሚያገኙት ክፋትን እና አመፃን በማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ክፉ ነገሮችን በማድረግ የሚያገኙትን እንጀራ ይበላሉ፣ በአመፅ ያገኙትንም ወይን ጠጅ ይጠጣሉ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:18

የፃድቅ ሰዎች መንገድ........ የክፉዎች መንገድ

ፀሀፊው የፃድቅ እና የክፉ ሰዎች ተግባር እና የአኗኗር ዘይቤ እነርሱ የሚራመዱበት “መንገድ” ወይም “አቅጣጫ” እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ የፃድቅ ሰዎች የአኗኗር ዘይቤ.......... የክፉዎች የአኗኗር ዘይቤ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የፃድቅ ሰዎቸ መንገድ እየፈካ እንደሚሄድ የንጋት ብርሀን ነው

ፀሀፊው የፃድቅ ሰዎችን መንገድ ከፀሀይ መውጣት ጋር ያወዳድረዋል፤ ትርጉሙም እነርሱ የተጠበቁ ናቸው ምክንያቱም በሚራመዱበት ጊዜ የሚሄዱበትን ቦታ ለማየት የሚሆን ብርሀን አላቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ ፃድቅ ሰዎች በመንገዳቸውን በአስተማማኝ ሁኔታ ይራመዳሉ ምክንያቱም የጠዋት ፀሀይ በመንገዳቸው ላይ ይበራል፣ እየፈካም ይሄዳል (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጋት ብርሀን

ይህ ንጋትን ወይም የፀሀይ መውጣትን ያመለክታል።

ሙሉ ቀን እስኪመጣም ድረስ

ይህ ፀሀይ ይበልጥ ደማቅ ሆና የምትወጣበት የቀኑን ጊዜ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ፀሀይ እጅግ ደምቃ እስክትወጣ ድረስ” ወይም “እስከ ሙሉ የቀን ብርሀን ድረስ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉዎች መንገድ እንደ ጨለማ ነው

ፀሀፊው የክፉዎች መንገድን ከጨለማ ጋር ያወዳድራል፣ ትርጉሙም እነርሱ ሁልጊዜ ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው ማለት ነው ምክንያቱም ወዴት እንደሚራመዱ ለማየት ብርሀን የላቸውም። አማራጭ ትርጉም፦ ክፉ ሰዎች በመንገዳቸው ላይ በአደገኛ ሁኔታ ይራመዳሉ ምክንያቱም ለማየት የሚያስችል ብርሀን የላቸውም (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በምን እንደሚሰናከሉ አያውቁም

ፀሀፊው መጎዳትን ሰው በሚጓዝበት መንገድ ላይ በሆነ ነገር መደናቀፍ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለምን እንደሚጎዱ እና መጥፎ አጋጣሚ እንደሚገጥማቸው አያውቁም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:20

ትኩረት ስጥ

“በጥንቃቄ አዳምጥ”

ወደ ንግግሮቼ ጆሮህን አዘንብል

እዚህ “ጆሮ” የሚለው ቃል የሚያደምጠውን ሰው ይወክላል። ፀሀፊው አንድ ሰውን በትኩረት ማዳመጥን ጆሮ ለተናጋሪው ቅርብ እንዲሆን ወደሚናገረው ሰው አንገትን ማዝመም እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። “ንግግሮች” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለምናጋራቸው ነገሮች ትኩረት በመስጠት አዳምጥ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከአይኖችህ እንዲርቁ አታድርግ

ፀሀፊው ስለ አንድ ነገር ሁልጊዜ ማሰብን አንድ ሰው ሊያይ በሚችልበት ቦታ መጠበቅ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። “ስለ እነርሱ ማሰብ አታቁም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በልብህ ውስጥ ጠብቃቸው

ፀሀፊው አንድን ነገር ማስታወስ በልብ ውስጥ ማስቀመጥ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሁልጊዜ አስታውሳቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:22

ቃሎቼ ህይወት ናቸው

ፀሀፊው የእርሱ ቃሎች የሰውን ህይወት መታደጋቸው እነዚያ ቃች የሰውየው ህይወት እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእኔ ቃሎች ህይወት ይሰጣሉ” ወይም “የተናገረኋቸው ነገሮች ህይወት ይሰጣሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለሚያገኟቸው ለእነዚያ

ፀሀፊው ሙሉ በሙሉ የእርሱን ቃል መረዳት ሰው እነርሱን ፈልጎ እንደደሚያገኛቸው አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለሚረዱአቸው እና ለሚተገብሯቸው ለእነርሱ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመላው የእነርሱ ሰውነት ፈውስ ነው

“የእነርሱ” የሚለው ቃል “ለሚያገኟቸው ለእነዚያ” የሚለውን ይወክላል። የዚህ ሀረግ ባለቤት ከፊተኛው ሀረግ ሊቀርብ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ቃሎቼ ለሚያገኟቸው ለሰውነታቸው በሙሉ ፈውስን ይሰጣሉ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህን በጥንቃቄ ጠብቅ ከልለውም

እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሰውን አእምሮ እና ሀሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አእምሮህን በጥንቃቄ ጠብቅ ሀሳብህንም ከልል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በመላው ትጋት

በማያቋርጥ እና በቅን ጥረት

የህይወት ምንጭ ከእርሱ ይፈልቃል

“እርሱ” የሚለው ቃል ለአእምሮ እና ለሀሳብ ምትክ ስም የሆነው ልብን ይወክላል። ፀሀፊው የሰውን ህይወት ከልብ የሚመነጭ ፈሳሽ ምንጭ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡ “የምትናገረው እና የምታደርገው ሁሉ ከሀሳብህ ይመጣል” ወይም “ሀሳቦችህ የህይወትህን መንገድ ይወስናሉ” (ምትክ ስም እና ተለዋጨ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:24

ጠማማ ንግግርን ከአንተ አስወግድ ብልሹ ወሬንም ከአንተ አርቅ

ፀሀፊው መዋሸት ወይም አታላይ ንግግርን ጠማማ እንደሆነ እና እንደዚህ አይነቱን ቋንቋ የማይጠቀም ሰውን ደግሞ ውሸትና አታላይነትን ከራሱ አርቆ ማስወገድ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “አትዋሽ በማታለልም አትናገር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አይኖችህ ወደ ፊት በቀጥታ ይመልከቱ ደግሞም በቀጥታ ፊት ለፊት አትኩረህ ተመልከት

እዚህ ላይ “አይኖች” የሚለው ቃል የሚመለከተውን ሰው ይወክላሉ። ፀሀፊው ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ የቆረጠ ሰውን ያ ሰው ወደ ሌላ አቅጣጫ ለማየት ጭንቅላቱን ሳያዞር ያለማቋረጥ ወደፊት የሚያይ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሁልጊዜ ወደፊት በቀጥታ ተመልከት በቀጥታ ፊትለፊትም አተኩረህ እይ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 4:26

ለእግርህን ደልዳላ መንገድ አዘጋጅ

እዚህ ላይ “እግር” የሚለው ቃል የሚራመደውን ሰው ይወክላል። ፀሀፊው የሰውን ተግባር ያ ሰው በመንገድ እየተጓዘ እንደሆነ እና ያንን ተግባር በጥንቃቄ ማቀድን ደግሞ ያንን መንገድ ደልዳላ ማድረግ እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለመራመድ ደልዳላ መንገድን አዘጋጅ” ወይም “ማድረግ የምትፈልገውን ደህና አድርገህ አዘጋጅ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ደልዳላ መንገድ

“ለስላሳ መንገድ” ወይም “የተስተካከለ መንገድ”

መንገድህ በሙሉ አስተማማኝ ይሆናል

ፀሀፊው የሰውን ተግባር ያ ሰው በመንገድ ላይ እየተጓዘ አንደሆነ እና እነዚያ ተግባሮች ስኬታማ መሆናቸውን መንገዱ አስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከዚያ የምታደርገው ሁሉ ትክክል ይሆናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ አትበል

“ቀኝ” እና “ግራ” የሚሉት አቅጣጫዎች ወካይ ይመሰርታሉ፣ ትርጉሙም ሰው ደልዳላውን መንገድ በየትኛውም አቅጣጫ ሊተው አይገባውም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በቀጥታ ወደፊት ተራመድ ደልዳላውን መንገድንም አትተው” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

እግርህን ከክፉ መልስ

እዚህ ላይ “እግር” የሚለው ቃል የሚራመደውን ሰው ይወክላል። ፀሀፊው ክፉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ድርጊት አለማድረግን ሰው ከክፉ ርቆ እየሄደ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከክፉ ሽሽ” ወይም “ከክፉ ራቅ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 5

Proverbs 5:1

አጠቃላይ መረጃ፦

ፀሀፊው ልጆቹን እንደሚያስተምር አባት ይናገራል።

ጆሮህን አዘንብል

እዚህ ላይ “ጆሮ” የሚለው ቃል የሚያዳምጠውን ሰው ይወክላል። ፀሀፊው አንድ ሰውን በትኩረት ማዳመጥን ጆሮ ለተናጋሪው ቅርብ እንዲሆን ወደሚናገረው ሰው አንገትን ማዝመም እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ይህንን በምሳሌ 4፡20 ላይ እንዴት እነደተረጎምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “በትኩረት አዳምጥ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥንቃቄ

ጥንቃቄ ድርጊት እና ንግግርን በተመለከተ ጥንቁቅ የመሆን ችሎታ ነው። ይህንን በምሳሌ 1፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ከንፈሮችህ እውቀትን ይጠብቁ

እዚህ ላይ “ከንፈሮች” የሚለው ቃል የሚናገረውን ሰው ይወክላል። ፀሀፊው እውነተኛ የሆነውን ነገር ብቻ ለመናገር ጥንቁቅ የሆነ ሰውን የዚያ ሰው ከንፈሮች እውቀትን እየጠበቁ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “እውነት የሆነውን ብቻ ትናገራለህ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 5:3

የአመንዝራ ሴት ከንፈሮች ማርን ያንጠባጥባል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ከንፈሮች” የሚለው ቃል የአመንዝራ ሴት ቃሎችን ይወክላል እናም ፀሀፊው ቃላቶችዋ የሚስቡ መሆናቸው ከንፈሯ ማር የሚያንጠባጥቡ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “የአመንዝራ ሴት ቃሎች ማር እንደሚያንጠባጥቡ ጣፋጭ ናቸው” ወይም 2) ፀሀፊው አመንዝራ ሴትን መሳም ስሜት መሳቡን የእርስዋ ከንፈሮች ማር እንደሚያንጠባጥቡ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “አመንዝራ ሴት መሳም ከንፈሯ ማር እንደሚያንጠባጥቡ ጣፋጭ ነው” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አፏ ከዘይት ይበልጥ የለሰለሰ ነው

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “አፍ” የሚለው ቃል የአመንዝራ ሴት ንግግርን ይወክላል ፀሀፊውም የንግግርዋን አሳማኝነት አፏ ከወይራ ዘይት የለሰለሰ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ንግግሯ አሳማኝ እና ከወይራ ዘይት የለሰለሰ ነው” ወይም 2) ፀሀፊው አመንዝራ ሴትን የመሳም ደስታ አፏ ከዘይት የለሰለሰ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእርስዋ መሳም ከወይራ ዘይት ይለሰልሳል” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በመጨረሻ ግን እንደ እሬት መራራ ናት

ፀሀፊው ከአመንዝራ ሴት ጋር ትስስር መጀመር የሚያመጣው ጉዳት እርስዋ እንደ እሬት የምትመር እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “በመጨረሻ ግን እርስዋ እንደሚመር እሬት ናት

እሬት

መራራ ጣእም ያለው ተክል

እንደ ስለታም ሰይፍ የሚቆርጥ

ፀሀፊው አመንዝራ ሴት ከእርስዋ ጋር ትስስር ያለው ሰው ላይ የምታስከትለውን ስቃይ እርስዋ ሰውየውን የሚቆርጥ ስለታም መሳሪያ እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስለታም መሳሪያ እንደሆነች ሰውን ታቆስላለች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 5:5

እግሮቿ ወደ ሞት ይወርዳሉ

እዚህ ላይ “እግሮቿ” አመንዝራ ሴት ስትራመድ ይወክላል። ፀሀፊው ተግባሯን በመንገድ ላይ እየተራመደች እንዳለች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ ሞት የሚያመራ መንገድ ላይ እየተራመደች ነው” ወይም “የአኗኗር ዘይቤዋ ወደ ሞት ያመራል” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርምጃዎችዋ ወደ ሲኦል ይሄዳሉ

ፀሀፊው ተግባሯን በመንገድ ላይ እየተራመደች እንዳለች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ ሲኦል ትራመዳለች” ወይም “ተግባሯ ወደ ሲኦል ይወስዳታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ህይወት መንገድ አታስብም

ፀሀፊው ለሰው ረጅም ህይወት የሚሰጥ ባህርይ ወደ ህይወት የሚመራ መንገድ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ ህይወት በሚመራው መንገድ ላይ መራመድን አታስብም” ወይም “ወደ ህይወት ስለሚመራ ተግባር አትጨነቅም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አረማመዷ የተቅበዘበዘ ነው

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እንደጠፋ ወዲህ እና ወዲያ ትቅበዘበዛለች” ወይም 2) “በተሳሳተ መንገድ ላይ ትጓዛለች”

Proverbs 5:7

አሁን

እዚህ ላይ አስተማሪው ስለ አመንዝራ ሴት ከማስጠንቀቅ ምክር ወደ መስጠት ተሸጋግሯል።

አድምጠኝ..... ከማዳመጥ ፈቀቅ አትበል

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተማሪው ትኩረት እንዲሰጥ ተመሳሳይ ሀሳብን ይገልፃሉ። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ከማዳመጥ ፈቀቅ አትበል

ፀሀፊው አንድ ድርጊት ማቆምን ያ ሰው በአካላዊ አቋም ከእርሱ ፈቀቅ ያለ እንደሆነ አስመስሎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ማዳመጥ አታቁም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአፌን ቃል

እዚህ ላይ “አፍ” የሚለው ቃል የሚናገረውን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእኔ ቃሎች” ወይም “የምናገረውን” ( ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምንገድህን ከእርስዋ አርቅ

እዚህ ላይ “መንገድ” የሚለው ቃል የሰውን የእለት ከእለት ተግባርንና ሁኔታን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ራስህን ከእርስዋ አርቀህ ጠብቅ” ወይም” ከእርስዋ ራቅ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ቤትዋ በር አቅራቢያ አትምጣ

እዚህ ላይ “የቤትዋ በር” ቤቱን ራሱን ይወክላል። “አትምጣ” በሚለው ቃል ፈንታ “አትሂድ” የሚለውን ቃል መጠቀም በይበልጥ ተስማሚ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም የመጀመሪያው ተናጋሪው የእርስዋ በር ላይ እንደሆነ ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ ቤትዋ በር አቅራቢያ አትሂድ” ወይም “ወደ ቤትዋ አቅራቢያ እንኳን ሳይቀር አትሂድ” (ተዛምዶአዊ እና የአትምጣ እና አትሂድ አጠቃቀም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 5:9

በዚያ መንገድ

“እንዲህ ካደረግህ።” ይህ ሀረግ በቀደመው ቁጥር ላይ የተናገረውን ያመለክታል።

ክብርህን ለሌሎች አሳልፈህ አትሰጥም

“ክብር” ለሚለው ቃል ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ፦ 1) ይህ የአንድን ሰው ዝና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በሌሎች ሰዎች መካከል ያለህን መልካም ዝና አታጣም” ወይም 2) ይህ የሰውን ሀብት እና ንብረት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሀብትህን ለሌሎች ሰዎች አሳልፈህ አትሰጥም” ወይም 3) ይህ ብርታትን ያመለክታል፣ የአንድን ሰው የሕይወት ግንባር ቀደም ዘመናት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የህይወትህን ምርጥ ጊዜያት ለሌሎች ሰዎች አሳልፈህ አትሰጥም”

ወይም የህይወት ዘመንህን ለጨካኝ ሰው

ፀሀፊው ያለጊዜው ምናልባትም በግድያ የሞተን ሰው የህይወቱን ዘመን ለሌላ ሰው አሳልፎ እንደሰጠው እቃ እንደሆነ ይናገራል። ግሱ በፊተኛው ሀረግ የቀረበ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወይም የህይወት ዘመንህን ለጨካኝ ሰው ስጥ” ወይም “ወይም ጨካኝ ሰው እንዲገድልህ አድርግ” (አስጨምሬ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጨካኝ ሰው

ይህ ከአመንዝራዋ ሴት ጋር የተኛውን ሰው በጭካኔ የሚቋቋመውን የአመንዝራዋን ሴት ባል ሊያመለክት ይችላል።

ባእድ ሰው በሀብትህ አይጠግቡም

ፀሀፊው የሌላ ሰውን ሀብት የወሰዱና የተጠቀሙበትን ሰዎች በሃብቱ እንደጨፈሩ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ባእድ ሰዎች ሀብትህን በሙሉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አይወስዱም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የደከምክበት ነገር ወደ ባእዳን ቤት አይሄድም
እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል የዚያን ሰው ቤተሰብ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ያገኘሀቸው ነገሮች መጨረሻቸው የባእድ ቤተሰብ ንብረት አይሆኑም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 5:11
ስጋህ እና ሰውነትህ መነመነ
“ስጋ” እና “ሰውነት” የሚሉት ቃሎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው እናም የሰውን ሁለንተና ይወክላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ሰውነትህ መነመነ” ወይም “አንተ መነመንህ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
መነመነ
“በሰውነት አካል መድከም” ወይም “ደካማ እና ጤና የጎደለው መሆን”
ተግሳፅን ጠላሁ…….. ልቤ እርማትን ናቀ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ሀሳብን ይገልፃሉ እናም ምን ያህል ይህ ሰው አስተማሪው የነገረውን ነገር እንደጠላ ያስገነዝባል፡፡ (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ተግሳፅን እንዴት ጠላሁ
“እንዴት” የሚለው ቃል የጥላቻውን ብርታት የሚያጎላ ቃለ አጋኖ ነው፡፡ ተግሳፅ የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “አንድ ሰው ሲገስፀኝ በጣም እጠላለሁ” (ቃለ አጋኖ እና ረቂቂ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ልቤ ተግሳጽን ጠላ
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ሰውየውንና ስሜቶቹን ይወክላል፡፡: “ተግሳጽ” የሚለው ቃል በግስ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ተርጉም:- “ሰዎች ሲገስጹኝ ጠላኋቸው” (ተዛምዶአዊ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልቱ)
Proverbs 5:13
ጆሮየን ወደ አስተማሪዎቼ አዘነበልሁ
እዚህ “ጆሮ” የሚለው ቃል የሚያደምጠውን ሰው ይወክላል፡፡ ፀሀፊው አንድ ሰውን በትኩረት ማዳመጥን ጆሮ ለተናጋሪው ቅርብ እንዲሆን ወደሚናገረው ሰው አንገትን ማዝመም እንደሆነ አድርጎ ይናገራል፡፡ በምሳሌ 4፡20 ላይ ይህን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመለክት፡፡ (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በጉባኤው መካከል፣ በሕዝቡ ስብሰባ መካከል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ደግሞም 1) እግዚአብሔርን ለማምለክ ወይም 2) ለፈጸመው ክፉ ድርጊት ፍርድ ሊሰጡት በአንድ ላይ የተሰበሰቡትን የሰውየውን የማሕበረሰብ አካላት ያመለክታል፡፡ (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 5:15
ውኃ ከጉድጓድህ … የሚፈልቅ ውኃ ከምንጭህ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊነት ትርጉማቸው አንድ ነው፡፡ ፀሐፊው ከሚስቱ ጋር ብቻ የሚተኛ ሰውን ከራሱ ጉድጓድና ምንጭ ብቻ ውኃ እንደሚጠጣ አድርጎ ተናግሯል፡፡ (ትይዩነት እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚፈልቅ ውኃ
ፀሐፊው አዲስ ወይም የሚፈልቅ ውኃን ውኃው እንደሚፈስ አድርጎ ተናግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “አዲስ ውኃ” ወይም “የሚፈስ ውኃ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ምንጮችህ … ወንዞችህ ወደ ሕዝብ አደባባይ ሊፈሱ ይገባልን?
ፀሐፊው እነዚህን መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የጠየቀው ልጁ እነዚህን ነገሮች ማድረግ እነደሌለበት አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ምንጮችህ … ወንዞችህ ወደ ሕዝብ አደባባይ ሊፈሱ አይገባም፡፡” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ምንጮችህ … ወንዞችህ ወደ ሕዝብ አደባባይ ሊፈሱ ይገባልን?
እነዚህ “ምንጮችህ” እና “ወንዞችህ” የሚሉት ቃላት የወንድ የዘር ፈሳሽን የሚወክሉ ለስላሴ ዘይቤ ይመስላሉ፡፡ ለእነዚህ ተለዋጭ ሐረጎች ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት የሚከተሉት ናቸው፡- 1) ሰው ከሚስቱ ውጭ ከሌሎች ሴቶች ጋር መተኛት የአንድን ሰው ውኃ በሕዝብ አደባባዮች እንዲፈስስ መፍቀድ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ ወይም 2) ሰው ከሚስቱ ውጭ ከሌሎች ሴቶች ልጆች መውለድ የአንድን ሰው ውኃ በሕዝብ አደባባዮች እንዲፈስስ መፍቀድ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ (ለስላሴ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሕዝብ አደባባዮች
እነዚህ በትልልቅ ወይም በትንንሽ ከተማዎች ሁለትና ከዚያም በላይ መንገዶች የሚገናኙበት ባዶ ቦታ ናቸው፡፡ ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚገናኙበትና የሚነጋገሩበት የተለመዱ ቦታዎች ናቸው፡፡
እነርሱ ይሁኑ
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “ምንጮችን” እና “ወንዞችን” እንደዚም ለቆሙለት ዓላማ ነው፡፡
ከአንተ ጋር ለሚገኙ እንግዶች አይሁኑ
“እነርሱን ከእንግዶች ጋር አትጋራ”
Proverbs 5:18
ምንጭህ ቡሩክ ይሁን
ፀሐፊው የወንዱ ልጅ ሚስት ምንጭ እንደሆነች አድርጎ ተናግሯል፡፡ በዚህ ስፍራ “ብሩክ” የሚለው ቃል አንድ ሰው በሚስቱ ያለውን የደስታ ስሜት የሚያመለክት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ሁልጊዜም ቢሆን ከሚስትህ ጋር ደስ ይበልህ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የጉብዝናህም ሚስት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ወጣት እያለህ ያገባሃት ሚስትህ” ወይም 2) “ወጣት ሚስትህ”
እንደ ተወደደች አጋዘን እንደ ተዋበችም ሚዳቋ
ፀሐፊው የወንድ ልጁን ሚስት “የተወደደች አጋዘን እና የተዋበች ሚዳቋ” እነደሆነች አድርጎ ይናገራል፡፡ በዚህ ክፍል “አጋዘን” እና “ሚዳቋ” ትርጉሙ ሴት አጋዘን ነው፡፡ እነዚህ በመልካቸውም ሆነ በእንቅስቃሴአቸው የውበት ምልክት ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “እርስዋ እንደ አጋዘን እና እንደ ሚዳቋ ውብና ሞገስ የተሞላች ናት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሞገስ የተሞላች
ይህ ቃል “ጸጋን የተሞላች” ማለት ኤደለም፣ “ስትንቀሳቀስ ውበት አላት” ለማለት ነው፡፡
ጡቶችዋ ሁልጊዜ ያርኩህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) የሚስት ጡቶች የባልን የወሲብ ፍላጎት ይቀሰቅሳል ይህም የሚስትን ሁለንተና አካልዋን የሚወክል ይሆናል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ጡቶችዋ ፍላጎትህን ያርኩ” ወይም “ ሰውነቷ ፍላጎትህን ያርካ” ወይም 2) ይህ ፀሐፊው የእናት ጡቶች የተራበ ልጅዋን እንደሚያረካ እንደዚሁ የሚስት ጡቶች የባልን ፍላጎት እንደሚያረኩ የተናገረበት ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በፍቅርዋም ሁልጊዜ ጥገብ
ከሚስት ጋር የሚደረግ ወሲባዊ ፍቅር ጥልቅ ስሜትና ደስታባል ከፍቅር እንደጠጣ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ ይህ በገቢር ግስ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “አልኮል የሰከረን ሰው እንደሚቆጣጠር እንደዚሁ የሚስትህ ፍቅር ይቆጣጠርህ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በፍቅርዋ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “አንተ ለእርስዋ ባለህ ፍቅር” ወይም “እርስዋ ለአንተ ባላት ፍቅር”
Proverbs 5:20
ልጄ ሆይ፣ ስለምን በጋለሞታ ሴት ትማረካለህ፤ ስርአት የሌላትንስ ሴት ጡቶች ለምን ታቅፋለህ?
ፀሐፊው እነዚህን መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የጠየቀው ወንድ ልጁ እነዚህን ነገሮች ማድረግ እንደሌለበት አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ልጄ ሆይ፣ በጋለሞታ ሴት አትማረክ! ስርአት የሌላትንስ ሴት ጡቶች አትቀፍ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በጋለሞታ ሴት ትማረካለህ
ለሴት በሚኖር ፍላጎት የሚመጣ ጥልቅ መነሳሳት ልጁ በዚያች ሴት እንደመማረክ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ጋለሞታ ሴት እንድትማርክህ ፍቀድ” ወይም “ጋለሞታ ሴት እንድታፈዝዝህ ፍቀድ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ስርአት የሌላትን ሴት ጡቶች ለምን ታቅፋለህ?
“እዚህ ላይ “ጡቶች” የሚለው ቃል ስርአት የሌላትን ሴትና ወሲባዊ ማራኪነትዋን የሚወክል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ስርአት የሌላትን ሴት ለምን ታቅፋለህ”
ስርአት የሌላትን ሴት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ሚስትህ ያልሆነች ሴት” ወይም “የሌላ ሰው ሚስት የሆነች ሴት”
ሁሉንም ነገር ያያል … የሚሄድበትንም መንገድ ሁሉ ይመለከታል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉማቸው ተመሳሳይ ነው፣ እግዚአብሔር ማንኛውም ሰው

የሚሰራውን ማኛውንም ነገር እንሚያውቅ አጽንዖት ይሰጣል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሚሄድበትንም መንገድ ሁሉ

ፀሐፊው የሰውን ድርጊት ወይም የሕይወት ዘይቤ አንድ ሰው የሚሄድበት መንገድ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ "የሚሄድበት ቦታ ሁሉ" ወይም "የሚያደርገውን ነገር ሁሉ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

### Proverbs 5:22

ክፉ ሰው ኃጢአቱ ታጠምደዋለች፥ በኃጢአቱም ገመድ ይታሰራልA

ፀሐፊው እነዚህ ኃጢአቶች ክፉውን ሰው የሚያጠምዱት ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ በመናገር "ክፉ ሰው" የኃጢአቱን መዘዝ ፈጽሞ ሊያመልጠው እንደማይችል ይናገራል። ይህ በገቢር ግስ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ክፉ ሰው የራሱ ኃጢአት ታጠምደዋለች" ወይም "ክፉ ሰው የኃጢአቱን መዘዝ ፈጽሞ ሊያመልጠው አይችልም" (ሰውኛ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የኃጢአቱ ገመድ አጥብቆ ያስረዋል

ፀሐፊው ኃጢአቱ ሰውየው የተጠመደበት በገመድ የተሰራ ወጥመድ እንደሆነ አድርጎ በመናገር ክፉ ሰው የኃጢአቱን መዘዝ ፈጽሞ ሊያመልጥ እንደማይችል ይናራል። አማራጭ ትርጉም፦ "በኃጢአቱ ምክንያት በወጥመድ እንሚጠመድ እንስሳ ይሆናል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሞኝነቱም ብዛት የተነሳ መንገድ ይስታል።

ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ይህ ታላቅ ሞኝነት ከትክክለኛው መንገድ ያስተዋል" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሞኝነቱም ብዛት

"በጣም ሞኝ ስለሆነ"

---

## Chapter 6

### Proverbs 6:1

ገንዘብህን ዋስ ሆነህ ብታስይዝ

እዚህ ላይ ቃል ኪዳንህና ሁኔታዎች ገንዘብህን እንድትቆጥብ አስገድደውሃል የሚል ሃሳብ አለው። አማራጭ ትርጉም፦ "የተወሰነ ገንዘብህን እንድትቆጥብ አድርጎሃል" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለጎረቤትህ ብድር ዋስ ብትሆን

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ጎረቤትህ ብድር ሊጠይቅህ ወደ አንተ መጥቶ ይሆናል" ወይም 2) ጎረቤትህ ከሌላ ሰው ብድር ለመውሰድ ፈልጎ ነገር ግን ጎረቤትህ ብድሩን መመለስ ባይችል በድሩን ለመክፈል ቃል ገብተህ ይሆናል"

ጎረቤት

ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለበት የዕብራይስጡ ቃል "ጓደኛ" የሚል ትርጉም አለው።

በአፍህም ቃል ተጠምደህ ተይዘሃል

ይህ ዘይቤአዊ ንግግር አንተ ራስህን ልታስጠምድ ነው ይላል። አማራጭ ትርጉም፦ "አንተ ራስህ የምጥጠመድበትን ወጥመድ ሰርተሃል" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በአፍህ ቃል

"በተናገርከው" ወይም "ቃል በገባኸው"

### Proverbs 6:3

ራስህን አድን

"ራስህነ ጠብቅ" ወይም "ከእነዚህ ችግሮች ለመውጣት ራስህን እርዳ"

በጎረቤትህ እጅ ወድቀሃልና

ይህ የንግግር ዘይቤ "እጅ" የሚለውን ቃል በመጠቀም "ጉዳት" የሚለውን ትርጉም ያስተላልፋል። አማራጭ ትርጉም፦ "ጎረቤትህ ከፈለገ ወደ አንተ ጉዳት ሊያመጣብህ ይችላል" ወይም "ጎረቤትህ በአንተ ላይ የሚፈልገውን ለማድረግ ሐይል አለው" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ጎረቤት

"ጓደኛ"

### Proverbs 6:4

ለአይንህ እንቅልፍን ለሽፋሽፍቶችህም እንጉልቻን አትስጥ።

"አይኖችህ አያንቀላፉ፤ ሽፋሽፍቶችህ አያንጎላጁ።" እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው እናም የተደጋገሙት ሰነፍ መሆን እንደማይገባ አጽንዖት ለመስጠት ነው። የበለጠ አጽንዖት ለመስጠት በአሉታዊ መንገድ ተገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ "ነቅተህ ጠብቅ፣ የምትችለውን ሁሉ አድርግ" (ትይዩነት እና ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

አይንህ ... ሽፋሽፍቶችህ

ይህ የፊትን አካላት በመጠቀም የሰውን ሙሉ ሰውነት የሚያሳይ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "አንተ ራስህ ... የአንተ ሰውነት" (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሜዳ ፍየል ከአዳኝ እጅ እንደምታመልጥ እንዲሁ ራስህን አድን።

"ከአዳኝ እንደምታመልጥ የሜዳ ፍየል ከጎረቤትህ አምልጥ"

የሜዳ ፍየል

ይህ ሳር የሚበላና ብዙ ጊዜ ሰዎች ለምግብነት የሚያድኑት በጣም ትልቅና ቀጭን እንስሳ ነው። ይህ እንስሳ በፍጥነት በመሮጥ ችሎታው የታወቀ ነው።

ከአዳኝ እጅ

የአዳኝ እጅ የአዳኙን በቁጥጥር ስር ማድረግ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ "ከአዳኝ ቁጥጥር" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከአጥማጅ እጅ እንደምታመልጥ ወፍ

"ከወፍ ወጥመድ በርራ እንደምታመልጥ ወፍ አምልጥ"

### Proverbs 6:6

ተመልከት ... አስተውል

"እጥና ... አስብ" ወይም "በጥንቃቄ አስተውል ... አሰላስል"

ጉንዳን

ጉንዳን ከምድር በታች ወይም ራሳቸው በሰሩት የአፈር ክምር የሚኖሩ ትንሽ ነፍሳት ናቸው። ብዙ ጊዜ በሺዎች የሚቆጠሩ በቡድን ተሰባስበው የሚኖሩና ከራሳቸው እጅግ የበለጡ ነገሮችን መሸከምና ማንሳት የሚሉ ናቸው።

መንገዷን አስተውል

ይህ የጉንዳንን "መንገድ" በመጠቀም የጉንዳንን ባህርይ የሚያሳይ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "ጉንዳን እንዴት እንደምትሰራ አስተውል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አለቃ፣ አዛዥ ወይም ገዢ

እነዚህ ሶስት ቃላቶች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ በአንድ ጉንዳን ላይ በመደበኛነት ስልጣን ያለው ማንም እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ምግቧን በበጋ ታዘጋጃለች ... የምትበላውን በመከር ትሰበስባለች

እነዚህ ሁለት ቃላቶች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ የተደጋሙት ጉንዳን ምን ያህል ኃላፊነት የምትሸከም መሆኗን ለማሳየት ነው።

በጋ

በጋ አንዳንድ ዛፎች ፍሬ የሚያፈሩበት የዓመቱ ወቅት ነው።

### Proverbs 6:9

እስከ መቼ ትተኛለህ ... ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሣለህ?

አስተማሪው እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠቀመው ብዙ እንቅልፍ የሚተኛውን ሰነፍ ሰው ለመገሰጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "አንተ ሰነፍ ሰው ንቃ! ከአልጋህ ውጣ!" (ትይዩነት እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ጥቂት ትተኛለህ ... ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ

እነዚህ ነገሮች ሰነፍ ሰው የሚናገራቸው ዓይነት ናቸው።

ጥቂት ትተኛለህ፥ ጥቂት ታንቀላፋለህ

እነዚህ ሃሳቦች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እንደ ሙሉ ዓረፍተ ነገር ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ "ትንሽ ረዘም ላለ ጊዜ እተኛለሁ። ረዘም ላለ ጊዜ ዘና ብየ ልተኛ።" (ትይዩነት እና አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ለማረፍ እጅህን ታጥፋለህ

ሰዎች ብዙ ጊዜ የበለጠ ተመቻችተው ለማረፍ ጋደም ሲሉ እጆቻቸውን ያጥፋሉ። አማራጭ ትርጉም፦ "ተመቻችቼ እጆቼን አጥጥፋለሁ ከዚያም ለትንሽ ጊዜ አርፋለሁ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ድህነትህ ይመጣብሃል

ይህ የስንፍና ውጤት እንደሆነ ግልጽ ለማድረግ እንደ አዲስ አረፍተ ነገር መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ሰነፍ መሆንህን ከቀጠልህ ድህነትህ ይመጣብሃል" ወይም "በተኛህበት ድህነት ይመጣብሃል" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ድህነትህ እንደ ወንበዴ ትመጣብሃለች
ሰነፍ ሰው በድንገት ድሃ የሚሆንበት መንገድ ልክ ወንበዴ በድንገት መጥቶ ሀብትን ሰርቆ የሚሄድበት ዓይነት መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ወንበዴ በድንገት መጥቶ ያለህን በሙሉ እንደሚሰርቅ እንደዚሁ በድንገት ድሃ ትሆናለህ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ችጋርህም ሰይፍ እንደ ታጠቀ ወታደር
ሰነፍ ሰው በድንገተኛ መንገድ ችጋሩ የሚመጣበት እንደ የታጠቀ ወታደር ከአንድ ሰው ያለውን ሁሉ በድንገተኛ መንገድ እንደሚወስድበት ነው። ይህ እንደ ሙሉ ዓረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላ። አማራጭ ትርጉም፦ “ችጋርህ እንደ ታጠቀ ወታደር ወደ አንተ ይመጣብሃል” ወይም “የታጠቀ ወታደር ወደ አንተ መጥቶ ያለህን ሁሉ እንደሚሰርቅብህ እንደዚሁ ችጋርህ ይመጣብሃል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
የታጠቀ ወታደር
“የጦር መሳርያ የያዘ ወታደር” ወይም “ የጦር መሳርያ የያዘ ሰው”
Proverbs 6:12
የማይረባ ሰው - ክፉ ሰው
እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው እናም ይህ ሰው ምን ያህል ክፉ እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ምንም ዓይነት ጥቅም የሌለው ሰው - ክፉ ሰው” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
በጠማማ ንግግሩ ይኖራል
በዚህ ስፍራ ውሸት እንደ ጠማማ ንግግር ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፦ ያለማቋረጥ ውሸት ይናራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በዓይኑ ይጠቅሳል፣ በእግሩም ምልክት ያስቀምጣል እና በጣቶቹም ይጠቁማል
እነዚህ ሶስት ሐረጎች ክፉ ሰው ሌሎች ሰዎችን ለማታለል መልእክት በምስጢር የሚያስተላልፍበትን መንገድ ያብራራሉ።
በዓይኑ ይጠቅሳል
አንድ ሰው በዓይኑ ከጠቀሰ፣ አንድ ዓይኑን በቅጽበት ጨፍኖ በመግለጥ ለሌላ ሰው ምስጢራዊ ምልክት ይሰጣል። ይህ እምነት የመጣል፣ የማረጋገጫ ወይም የሌላ ነገር ምልክት ሊሆን ይችላል።
Proverbs 6:14
ክፋትን ያስባል
“ክፋትን ያቅዳል” ወይም “ክፉ ድርጊቶችን ለመፈጸም ይዘጋጃል”
ሁልጊዜ ጠብን ያነሳሳል
“ሁልጊዜ የጠብ ምክንያት ነው” ወይም “ያለማቋረጥ ግጭትን ይፈልጋል ደግሞም ያባብሳል”
ስለዚህ
“በዚህ ምክንያት”
ጥፋቱ ድንገት ይደርስበታል
ይህ ጥፋቱ እንደ ሰው ወይም እንደ እንስሳ እንደሚያሳድደውና ወዲያውኑ እንደሚደርስበት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጥፋቱ ያገኘዋል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጥፋቱ
ይህ በእርሱ ላይ የሚደርስበትን ጥፋት ያሳያል ነገር ግን እርሱ ራሱ የሚያደርሰውንም ጥፋት ያመለክታል።
ድንገት፣ በቅጽበት
ሁለቱም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ አንዱ ወይም ሁለቱ “ሳይታሰብ” ወይም “በፍጥነት” በሚለው ሊተኩ ይችላሉ።
Proverbs 6:16
እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች፣ ሰባትንም
ይህ ሙሉ ጥቅስ እግዚአብሔር አንድ ነገር ብቻ ሳይሆን ብዙ ነገሮችን እንደሚጠላ አጽንዖት የሚሰጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች፤ ሰባት ነገሮች” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
የሚጠላቸው
x
Proverbs 6:17
አያያዥ ሃሳቦች፦
ይህ በምሳሌ 6:16 ላይ የተመለከቱ እግዚአብሔር የሚጠላቸው የተለያዩ ነገሮች ዝርዝር ነው።
ዓይኖች ... ምላስ ... እጅ ... ልብ ... እግር
እነዚህ የሰውነት አካላት በሙሉ የሰውን ሁለንተና ያመለክታሉ። እያንዳንዳቸውን “ሰዎች” ብለህ ልትተረጉማቸው ትችላለህ። (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ደም የምታፈስስ
“መግደል” ወይም “ነፍስ ማጥፋት”
ክፉ ሃሳብ
“ክፉ እቅድ”
ውሸትን ወደ ውጭ ይተነፍሳል
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር የማያቋርጥ ውሸትን ለማመልከት “ይተነፍሳል” የሚለውን ቃል ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፦ “ያለማቋረት ይዋሻል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠብ
ይህንን በምሳሌ 6:16 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልት።
ጠብን የሚዘራ
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር “የሚዘራ” የሚለውን ቃል በመጠቀም የጠብ ምክንያት መሆንንና ጠብ ማምጣትን ያመለክታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 6:20
የአባትህን ትዕዛዝ ጠብቅ ... የእናትህንም ትምህርት አትተው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በአንድ በኩል ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በሌላ በኩል ደግሞ “አባት” እና “እናት” በሚሉት ድግግሞሽ አጽንዖት ሴቶችን በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በግልጽ ያካትታል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
የእናትህንም ትምህርት አትተው
ይህ የንግግር ዘይቤ አዎንታዊውን “ጠብቅ” ለማለት አሉታዊውን “አትተው” የሚለውን ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእናትህን ትምህርት ጠብቅ” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
ሁልጊዜ በልብህ እሩራቸው፣ በአንገትህም ዙርያ አስራቸው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እነዚህ ሐረጎች አንተን ለማስታወስ በሰውነትህ ውስጥ ወይም በሰውነትህ ላይ ልታስቀምጣቸው እንድትችል ትእዛዘቱና ትምህርቶቹ እንደተጻፉ አድርገው ይገልጿቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በልብህ እሩራቸው
“ውደዳቸው” “ስለእነርሱ አስብ”
Proverbs 6:22
ስትሄድም ... ስትተኛ ... ስትነሣ
እነዚህ ሶስት ሐረጎች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት ትምህርቶቹ በየትኛውም ጊዜ ጠቃሚ እንደሆኑ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ይመሩሃል ... ይጠብቁሃል ... ያስተምሩሃል
የእነዚህ ሐረጎች መደጋገም ትምህርቶቹ ለሁሉም ዓይነት ጉዳዮች ጠቃሚዎች መሆናቸውን ለማሳየት ነው። በተጨማሪ እነዚህ ትምህርቶች ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናራል። (ትይዩነት እና ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)
በምክር የሚገኙት ትዕዛዛቱ ... ትምህርቶቹ ... ተግሳጾቹ
እነዚህ ሶስት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድ ላይ አባትና እናት የሚያስተምሩትን የተለያዩ ትምህርቶች ያሳያሉ። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
መብራት ... ብርሃን ... የሕይወት መንገድ
እነዚህ ሶስት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት ትምህርቶቹ ሕይወትን የተሻለና ቀላል የሚያደርጉ የመሆናቸውን እውነታ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እንደ መብራት ጠቃሚ ናቸው ... በጨለማ ውስጥ እንዳለ ብርሃን አጋዥ ናቸው ... እንደ ሕይወት መንገድ ልንከተላቸው የሚያስፈልጉ ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
የሕይወት መንገድ
“ወደ ሕይወት የሚመራ መንገድ” ወይም “እግዚአብሔር የተቀበለው የሕይወት መንገድ”
Proverbs 6:24
እርሱ ይጠብቅሃል
እዚህ ላይ “እርሱ” የሚለው ቃል በምሳሌ 6:20 ላይ በአባትና በእናት የተማራቸውን ትምህርቶች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ያድንሃል” ወይም “ይጠብቅሃል” (እንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ምግባረ ብልሹ ሴት ... አመንዝራ ሴት
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። “አመንዝራ ሴት”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚለውን በምሳሌ 5:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
በሽፋሽፍትዎቿ እንድታጠምድህ አትፍቀድላት
ፀሐፊው የሴትን ሽፋሽፍቶች ወጣት ወንድ ልጅ ሊሳስት የሚችልበት ወጥመድ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። እነዚህ ለውበቷ ተዛምዶአዊ ንግግር ዘይቤ ናቸው፣ በእርስዋ እንዲሳብና እርስዋን እንዲፈልጋት ለማድረግ ሴቷ ወጣት ወንድ ልጅን ለምታይበት መንገድ ደግሞ ምትክ ስም ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “በቁንጅናዋና አንተን በዓይኖቿ በምታይበት ሁኔታ በቁጥጥር ስር እንድታደርግህ አትፍቀድላት” (ተለዋጭ፣ ተዛምዷዊ እና ምትክ ስም የሚለውን ተመልከት)
ምግባረ ብልሹ
“ክፉ ምግባር”
በልብህ
“ልቧ” አእምሮዋን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም: “በሃሳብህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ውበቷ
“ስለ እርስዋ ያላት ውበት” ይህ ለሴቷ ምትክ ስም ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእርስዋ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
አያጥምድህ
“በቁጥጥር ስር አታድርግህ”
ሽፋሽፍትዎቿ
“ሽፋሽፍቶች” የወንድ ልጅ ቀልብ ለመሳብ የምትጠቀምበት በሰውነቷ ስለሚታዩ ማንኛውም ውበት የሚቆም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “መልከ መልካም ዓይኖቿ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 6:26
የአንድ ቁራሽ ዳቦ ዋጋ
ይህ የሚናገረው ስለ ቁስ ዋጋ እንጂ ስለ መንፈሳዊ ዋጋ ወይም ስለ ስነ ምግባር ዋጋ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፡- “ትንሽ ነው”
ሕይወትህን ሊያስከፍልህ ይችላል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) የሌላ ወንድ ሚስት ሕይወትህን ታጠፋዋለች ምክንያቱም እርስዋ ሁልጊዜ የምትፈልገው የላቀ ነገር ነው ወይም 2) የሌላ ሴት ባል አድኖ ይገድልሃል
አንድ ሰው ልብሶቹ ሳይቃጠል በደረቱ እሳት መያዝ ይችላልን?
ይህ ድርጊት በጣም አደገኛ ስለሚሆን ጉዳት ያስከትላል። ለዚህ ጥያቄ የሚቀርበው መልስ “አይችልም” የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በደረቱ ላይ እሳት የሚይዝ ወንድ ልብሱን ያቃጥላል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ሳይቃጠል
“ጥፋት ሳይደርስ” ወይም “ሳይወድም”
ልብሶቹ
ልብሶቹ የሚለው ቃል ለሰውየው ሙሉ ሁለንተና የሚቆም ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 6:28
ሰው እግሩ ሳይቃጠል በፍም ላይ መራመድ ይችላልን?
በፍም ላይ መራመድ የሰውየውን እግር ያቃጥላል፤ ለዚህ ጥያቄ ስለዚህ ተገቢው መልስ “አይችልም” ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በፍም ላይ የሚራመድ ማንኛውም ሰው እግሩ ይቃጠላል።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በፍም ላይ መራመድ
ይህ ለአመንዝራነት የቆመ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መራመድ
ይህ ያለ ማታለል እና ያለ አስማት ሩቅ ርቀት ቀስ ብሎ መጓዝ ነው።
መቃጠል
“መንደድ”
Proverbs 6:30
ሌባን አይንቁትም
“ሌባን በንቀት አትመልከት” ወይም “ሌባ ክፉ እንደሆነ አታስብ”
ቢያዝ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው እርሱን ቢይዘው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በቤቱ
ይህ የንግግር ዘይቤ በቤቱ ያለው ማንኛውም ነገር እርሱ በባለቤትነት የያዘው ነው ይላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእርሱ የሆነው ሁሉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 6:32
ሰው
“ሰውየው” ወይም “ያ ሰው”
የሚገባው
“ሌባ ለሰራው ድርጊት ተገቢው ቅጣት”
ውርደቱ
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር “ውርደት” የሚለውን ቃል የተጠቀመው ስላደረገው አሳፋሪ ተግባር የሚሰማውን ስሜት ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የአሳፋሪ ተግባሩ ትዝታ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
አይደመሰስም
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር “አይደመሰስም” የሚለውን አሉታዊ አገላለጽ የተጠቀመው ስድቡ ሁልጊዜ በዚያ እንደሚኖር ለማመልከት ነው። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 6:34
ቁጡ
በጣም መናደድ
እርሱ ምህረት አያደርግም
“እርሱ” የሚለው የሚያመለክተው ሚስቱ ከሌላ ወንድ ጋር ያመነዘረችው የአመንዝራይቱ ባል ወይም ጎረቤት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በአንተ ላይ የሚያመጣው ጉስቁልና ገደብ አይኖረውም” ወይም “የተቻለውን ያህል ይጎዳሃል” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
በሚበቀልበት ጊዜ
“በቀል በሚያደርስበት ጊዜ” ወይም “የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ጊዜው በሚቀርብበት ጊዜ”
ይበቀላል
ሰውየው ሲበቀል፣ ቀድሞ የጎዳውን ሰው ለመጉዳት ነው
ካሳ
ይህ በደል ያደረሰው ሰው ለተበዳዩ የሚከፍለው ክፍያ ነው
እሺ አይልም
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእርሱን አእምሮ ለመለወጥ የሚችል በቂ ገንዘብ ልትከፍለው አትችልም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እሺ አይልም፣ ብታቀርብለትም
“እሺ አይልም። ብታቀርብለትም ይህ እውነት ነው”

---

Chapter 7
Proverbs 7:1
ቃሎቼን ጠብቅ
እዚህ መጠበቅ መታዘዝን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቃሎቼን ታዘዝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ትእዛዜንም በአንተ ውስጥ አስቀምጥ
እዚህ የእግዚአብሔር ትእዛዛት አንድ ሰው በመጋዘን ውስጥ እንደሚያስቀምጣቸው ዕቃዎች ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትእዛዛቴን በቃልህ አጥና/ሸምድድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ትእዛዜን ጠብቅ
እዚህ መጠበቅ መታዘዝን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቃሎቼን ታዘዝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ዓይንህ ብሌን
የዓይን ብሌን ሰዎች ብዙ ጊዜ በፊታቸው የተለያየ ነገር ሲመጣባቸው በተለምዶ በደመነፍስ ጥበቃ የሚያደርጉለትና የሚከላከሉለት በዓይን ውስጥ ያለው ጥቁሩ የዓይን ክፍል ነው። እዚህ “የዓይን ብሌን” አንድ ሰው እጅግ ዋጋ የሚሰጠውና በሚገባ ጥበቃ የሚያደርግለት ማንኛውንም ነገር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እጅግ ውድ እንደሆነው ንብረትህ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
በጣቶችህ እሰራቸው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ፀሐፊው ወንድ ልጁ አንዳንድ የእግዚአብሔር ትእዛዛት በቀለበቱ ላይ ቀርፆ በጣቱ ላይ እንዲያደርገው ይፈልጋል ወይም 2)

ፀሐፊው ወንድ ልጁ ቀለበቱን ሳይረሳ ሁልጊዜ እንደሚያደርገው እንደዚሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁልጊዜ እንዲያስታውስ ይፈልጋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በልብህ ጽላት ጻፋቸው

እዚህ ልብ የሰውን አእምሮ ይወክላል፣ አንድን ነገር በሚገባ ማስታወስ ደግሞ ያ ሰው በድንጋይ ጽላት ላይ እንደጻፈው ተደርጎ ተነግሯል። ይህንን በምሳሌ 3:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- "በድንጋይ ላይ እንደጻፍካቸው እያሰብህ ትእዛዛቴን በሚገባ አስታውሳቸው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 7:4

ጥበብን አንቺ እኅቴ ነሽ በላት

እዚህ ላይ ጥበብ ሰው እንደሆነች ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "እህትህን እንደምትወድ እንደዚሁ ለጥበብ ተገቢ ዋጋ ስጣት" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተማውልንም ወዳጁ ብለህ ጥራት

እዚህ ላይ የማስተዋልን ባሕርይ እንደ ወዳጅ ወይም ዘመድ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም፡- "ወዳጅህን እንደምትንከባከብ እንደዚሁ ማስተዋልን ተንከባከባት" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወዳጅ

"ዘመድ" ወይም "የቤተሰብ አባል"

ጋለሞታ ሴት

ይህ አንድ ወንድ ጋብቻ ያልፈጸመላትን ማንኛዋንም ሴት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- "ከእርስዋ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ሊኖርህ የማትገባ ሴት"

ብልሹ ስነምግባር ያላት ሴት

ይህ አንድ ወንድ የማያውቃትን ማንኛዋም ሴት ያመለክታል።

በለዘበ ቃሏ

ለማታለል የሚነገሩ ቃላት ለስላሳ እቃዎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- "ደስ የሚያሰኙ ነገሮችን የምትናገር፣ ነገር ግን ልታታልልህ የምትፈልግ"

Proverbs 7:6

ርብራብ

እርስ በርሳቸው በተጠላለፉ ቀጭን እንጨቶች የተሰራ ያዘነበሉ አራት ማዕዘን ንድፍ ያላቸው ቀዳዳዎች ያሉት የመስኮት ክዳን።

አላዋቂ

ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው

Proverbs 7:8

የእርስዋ ማዕዘን

እዚህ ላይ "የእርስዋ" የሚለው ቃል በምሳሌ 7:5 ላይ እንደተጠቀሰው ማንኛዋንም እንግዳ ሴት የሚያመለክት ነው። እርስዋ በተወሰኑ ማዕዘኖች በአጠገቧ የሚያልፍ የሚስማማትን ወንድ እየጠበቀች ቆማ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- "እንግዳ ሴት ቆማበት የነበረው ማዕዘን"

ማዕዘን

ይህ ሁለት መንገዶች የሚገናኙበትነ ስፍራ ያመለክታል።

ማታ ሲመሽ

የሚጨልምበትና ሌሊቱ የሚመጣበት የቀኑ ጊዜ ነው

Proverbs 7:10

በሐሰተኛ ልብ

እዚህ ላይ "ልብ" የሚለው ሃሳብን ወይም እቅድን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- "እርስዋ አንድን ሰው ለማታለል አቅዳለች" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጯኺና አምባገተኛ ናት

"የምትናገረው በጩኸት ነው፣ የምታደርገው ደግሞ እሷ በምትፈልገው መንገድ ነው"

እግሮችዋም በቤትዋ አይቀመጡም

"እግሮቿ" የሚለው ሐረግ የሚወክለው ሴቷን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "በቤት ፈጽሞ አትቀመጥም" (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

አድፍጣ ትጠብቃለች

እዚህ ላይ ሴቷ በአካል አንድን ሰው ወይም እንስሳ ለመያዝ እንደተዘጋጀች አድርጎ ገልጧታል። በተጨማሪ እዚህ ላይ አንድን ሰው የማጥመዷ ሃሳብ ኃጢአት እንዲፈጽም አንድን ሰው መገፋፋትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- "ሰው ለማጥመድ ትጠብቃለች" ወይም "ኃጢአት እንዲሰራ ልትገፋፋው የምትችለውን ሰው ለማጥመድ ትጠብቃለች" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 7:13

እርስዋ

ይህች በምሳሌ 7:10 ላይ የተጠቀሰችው ሴት ናት።

ያዘችው

"አጥብቃ አፈፍ አደረገችው"

ፊትዋም ያለ እፍረት ሆኖ

እዚህ "ያለ እፍረት" የሚለው "ግትርነትን" ይወክላል። "ፊትዋ እፍረት ሳይታይበት" የሚለው በአንድ ሰው የሚታይ መንቻካ የፊት ገጽታ ማለት ነው። ይህ ሴትየዋ በከባድ መንገድ ስራዋን እንደምትሰራ፣ ትክክል እንዳልሆነ እያወቀች ሆን ብላ እንደምታደርገው የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "በፊትዋ ምንም ዓይነት የሀፍረት ገጽታ ሳይታይባት" (ፈሊጥ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ስእለቴንም ፈጽሜአለሁ

እዚህ ላይ "ስእለት" የሚለው ሰውየው ለእግዚአብሔር ለመሰዋት የገባውን ቃል ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- "ለእግዚአብሔር ቃል የገባሁትን መስዋዕት አቅርቤአለሁ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፊትህን አሻለሁ

እዚህ ላይ "ፊት" ሰውየውን በተለይም ደግሞ የሰውየውን ሕልውና የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "እፈልግሃለሁ" ወይም "ባለህበት እፈልግሃለሁ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 7:16

በአልጋየ ላይ መሸፈኛ ዘርግቼበታለሁ

"በአልጋየ ላይ አንጥፌአለሁ"

አልሙን

በጣም ቆንጆ ሽታ ካለው ዛፍ የሚገኝ የግንድ ዓይነት ነው።

በጥልቅ ፍቅር እንርካ

እዚህ ላይ የወሲባዊ ፍቅር ደስታ እንደሚጠጣ መልካም ነገር ተደርጎ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፡- "እርስ በርሳችን የፈለግነውን ያህል ፍቅርን እናድርግ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 7:19

በቤቱ የለም

"በቤት ውስጥ የለም"

ሙሉ ጨረቃ

ጨረቃ ሙሉ የምትባለው ሙሉ በሙሉ ክብ ቅርጽ ስትይዝና ከፍተኛ ብርሃንዋን ስታንጸባርቅ ነው።

እንዲስት ታደርገዋለች

አንድ ሰው በሆነ መንገድ አንድ ነገር እንዲያደርግ ማነሳሳት በመንገድ ይሄድ የነበረ ሰው አቅጣጫውን እንደቀየረ ተደርጎ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፡- "ገፋፋችው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርስዋ ... እርስዋ ... የእርሱ

ሴትዮዋ በትዳር ያለች ስትሆን ነገር ግን "ከእርሱ" ማለትም ከወጣት ወንድ ጋር መተኛት የምትፈልግ ሴት ናት።

ለስላሳ ከንፈር

እዚህ ላይ "ከንፈር" የሚወክለው የሰውን ንግግር ነው። አንድ ሰው እውነተኛ ያልሆነ ነገር በመናገር ሌላውን ሰው ከፍ ከፍ ሲደርገው እነዚህ በልዝብነት የተነገሩ ቃላቶች እንደ ለስላሳ እቃዎች ተደርገው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "ሽንገላ፣ የማታለያ ቃላት" (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲስት አደረገችው

"ክፉ ነገር እንዲሰራ አሳመነችው" አማራጭ ትርጉም፡- "ከእርስዋ ጋር ኃጢአት እንዲሰራ አሳመነችው"

Proverbs 7:22

በድንገት ተከትሏት ሄደ

ወጣት ወንድ ምን ማድረግ እንዳለበት ለማሰብ የሚወስደው ጊዜ በጣም አጭር እንደሆነ ይህ ሃሳብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- "እርስዋን ተከትሎ ለመሄድ በፍጥነት ወሰነ" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመታረድ እንደሚነዳ በሬ

ይህ ወጣት ወንድ በአላዋቂነትና ሳይጠረጥር አመንዝራይቱን ተከትሎ የሄደበት መንገድ ሶስቱ እንስሳት የገቡበትን አደጋ ባለማወቅ ከሄዱበት መንገድ ጋር ተነጻጽሯል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መታረድ
ይህ ስጋውን ለመብላት እንስሳን ማረድ ያመለክታል።
አጋዘን
ይህን ቃል በምሳሌ 5፡19 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
ፍላጻ ጉበቱን እስኪወጋው ድረስ
ይህ ክፍል አዳኙ አጋዘኑን በወጥመድ የያዘው በፍላጻ ለመውጋት እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አዳኝ በጣም ዋነኛ የሆነውን የሰውነቱን ክፍል እስኪወጋው ድረስ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ጉበት
እዚህ ላይ ይህ ብልት የአጋዘኑን በጣም ዋነኛ የሰውነት ክፍል ይወክላል።
ሕይወቱን ያሳጣዋል
ይህ ሰው ከዚህ የተነሳ ይሞታል ለማለት የአባባል ዜይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ይገድለዋል” ወይም “ወዲያውኑ ይሞታል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 7:24
አሁን
ይህ በዚህ ትምህርት ማጠቃለያ ላይ የተናጋሪው ወንድ ልጆች ትኩረት ላይ ለማነጣጠር የተነገረ ነው።
ልብህ ወደ መንገዶቿ አያዘንብል በጎዳናዋ አትሳት።
እዚህ ላይ “መንገዶች” ማለት ሰው ሊሄድበት የሚመርጠው መንገዶች ናቸው። ይህ የሰውን ባሕርይ ማለትም በሕይወቱ ሊፈጽማቸው የወሰናቸውን ነገሮች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ልብህ ከአመንዝራይቱ ሴት መንገዶች በጣም ርቆ እንዲቆይ አድርግ” ወይም “አመንዝራይቱ ሴት የምታደርጋቸውን ነገሮች እንዲያደርግ ልብህ እንዲሻ አትፍቀድለት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ልብህ
እዚህ ላይ “ልብ” ሰውን ይወክላል፣ ለፍላጎቱም አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ”(ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
በመንገዶቿ አትሳት
ይህ ከቀደመው ዓረፍተ ነገር ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። የመጀመርያውን ማስጠንቀቂያ የሚያጠናክር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በእርስዋ መንገድ ለመሄድ ስትል ትክክለኛውን መንገድ አትተው” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 7:26
ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸው
በፍላጻ ወይም በጦር መወጋት መገደልን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ሰዎች ተወግተው እንዲሞቱ አድርጋለች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ቤቷ ወደ ሲኦል በሚወስደው መንገድ ነው … ይወርዳሉ
እዚህ ላይ “መንገድ” ሞኞች ሰዎች የሚሳተፉበትን የባህርይ ዓይነት የሚወክል ነው። ሲኦል ሙታን ለሚኖሩበት ስፍራ የተሰጠ ስም ነበር።
ወደ ሲኦል በሚወስደው መንገድ … ጨለማ ወደሆነው ወደ ሞት ማደርያም የሚያወርድ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት የሴትየዋ ተጠቂዎች እንደሚተፉ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ቸለማ የሆነው የሞት ማደርያ
ይህ መግለጫ ሙታን በሲኦል ውስጥ በብዙ የተለያዩ ክፍሎች እንደሚተኙ የሚያሳይ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

## Chapter 8
### Proverbs 8:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
በምዕራፍ 8 ጥበብ ሰዎች እንዴት ጥበበኛ መሆን እንዳለባቸው እንደምታስተምር ሴት ተደርጋ ተነግራለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አጠቃላይ መረጃ፡-
በምዕራፍ 8 ውስጥ ብዙ ጥቅሶች ትይዩነት አላቸው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
በውኑ ጥበብ አትጮኽምን?
ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው አንባቢዎች ቀድመው የሚያውቁትን ነገር ለማስታወስ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ ትጣራለች” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በውኑ ጥበብ አትጮኽምን?
እዚህ ላይ ጥበብ እንደ ሴት ቀርባለች። አንድ ቋንቋ እንዲህ ዓይነት ተለዋጭ ዘይቤ መጠቀም የማይፈቅድ ከሆነ የሚከተሉት ሌሎች አማራጮች ናቸው፡- 1) “ጥበብ እንደ ሴት የምትጮኽ አይደለችምን?” 2) “ጥበብ የምትባል ሴት እየጮኸች አይደለምን?” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማስተዋልስ ድምፅዋን ከፍ አታደርግምን? Does not Understanding raise her voice?
እዚህ ላይ “ማስተዋል” ትርጉሙ ከ“ጥበብ” ጋር ተመሳሳይ ነው። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ድምፅዋን ከፍ አደረገች
“ተናገረች”
ወደ ከተማይቱ በሚያስገቡት በሮች አጠገብ
በጥንት ጊዜ ከተሞች ብዙ ጊዜ በር የተገጠመላቸው የውጭ የግንብ አጥር ነበራቸው።
ትጣራለች
ይህ እንደ ሴት የተመሰለችውን ጥበብን ያመለክታል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
### Proverbs 8:4
አጠቃላይ መረጃ፡-
በቁጥር 4-36 ጥበብ ለሕዝቡ ትናገራለች።
ድምፄም ወደ ሰዎች ልጆች ነው
እዚህ ላይ “ድምጽ” የሚወክለው የተነገሩትን ቃላት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ቃላቶቼ ወደ ሰዎች ልጆች ናቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የሰዎች ልጆች
ይህ ሁሉንም የሰው ልጆች የሚወክል ምትክ ስም ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
አላዋቂነት
ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው
ጥበብን ተማር
“ጥበብ” የሚለው ረቂቅ ቃል የሚያመለክተው ጥበበኛ ሰው የሚያምንበትንና ድርጊቱን የሚፈጽምበት መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ ሰው እንዴት እንደሚያደርግ ተማር” ወይም “ጥበበኛ መሆን ምን ማለት እንደሆነ ተማር” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የሚያስተውል ልብ ይኑራችሁ
“ነገሮችን በአእምሮአችሁ መረዳት መጀመር አለባችሁ”
### Proverbs 8:6
ከንፈሮቼ ሲከፈቱ
እዚህ ላይ “ከንፈሮች “ የሚወክለው የሚናገርበትን የሰውን አንደበት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለመናገር አንደበቴን ስከፍት” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ቅን
ተገቢ የሆነ ወይም ፍትሃዊ
አፌ ይናገራል
እዚህ ላይ “አፍ” የሚወክለው የሚናገረውን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እናገራለሁ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
እውነትን
“ሰዎች ሊያምኑት የሚችሉት”
ከንፈሮቼም ክፋትን ይጠላሉ
እዚህ ላይ “ከንፈሮች” የሚወክሉት የሚናገረውን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፋትን እጠላለሁ” ወይም “ክፉ ነገሮችን መናገር በእኔ ዘንድ የተጠላ ነው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፋት
እዚህ ላይ “ክፋት” የሚለው ረቂቅ ስም የሚወክለው ክፉ ንግግርን ነው። (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
### Proverbs 8:8
ከአፌ የሚወጡ ቃሎች
“አፍ” የሚወክለው የሚናገረውን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የማስተምራቸው ነገሮች” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠማማ አይደሉም
መልእክትን ማጣመም እውነተኛውን መልእክት ወደ ውሸት ለመለወጥ እንደ ተለዋጭ የተነገረ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ውሸት አይደለም” (ተለዋጭ ዘይቤ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚለውን ይመልከቱ)
ቀጥታ
እውነተኛ እና ግልጽ
ቃሎቼ እውቀትን ለሚያገኙ ጽድቅ ናቸው
ይህ አረፍተ ነገር እውቀትን የሚያገኙ ሰዎች የተናጋሪው ቃሎች ጽድቅ እንደሆኑ በቀላሉ ይረዳሉ የሚል ትርጉም አለው። እዚህ ላይ "ቃላቶች" የሚወክለው መልእክትን ወይም ትምህርትን ነው። አማራጭ ትርጉም:- "ጽድቅ ምን እንደሆነ እና ስህተት ምን እንደሆነ የሚያውቁ እኔ የማስተምረው ጽድቅ እንደሆነ ይረዳሉ።" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ቅን
እውነተኛ እና የሚታመን
Proverbs 8:10
ከብር ይልቅ ተግሳጼን ምረጡ
"ብርን ለማግኘት ከመድከም ይልቅ ተግሳጼን ለመረዳት በብዙ ልትደክሙ ይገባችኋል"
ጥበብ ከቀይ ዕንቊ ትበልጣለች፤ የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም
እዚህ ላይ የምትናገረው በሴት የተመሰለችው ጥበብ አይደለችም። ይሁን እንጂ በዚህ ስፍራ ጥበብ ተናጋሪዋ እንደሆነች ለማሰብም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም:- "እኔ ጥበብ ከቀይ እንቁ እሻላለሁ፤ ምንም ዓይነት ሃብት ከእኔ ጋር አይስተካከልም" (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 8:12
እኔ ጥበብ በብልሃት ተቀምጫለሁ
ብልሃት በዚህ ክፍል እንደ ሰው ተወክላለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ብልሃት
ጥንቃቄ ወይም መልካም ውሳኔ
እውቀትንም ጥንቃቄንም አግኝቻለሁ
"እውቀት" እና "ጥንቃቄ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በሌላ መንገድ ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- "እኔ እውቀት እና ጥንቃቄ ነኝ" ወይም "እኔ ብዙ ነገር አውቃለሁ፣ እኔ ጠንቃቃ ነኝ" (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጥንቃቄ
ለምንናገረውና ለምንሰራው ነገር ጥንቁቅ መሆን፤ ጉዳትን ላለመፍጠርና ሌሎችን ላለመጉዳት ጥንቁቅ መሆን
ጠማማ ንግግር
"ክፉ ንግግር"
ጠማማ
ትክክለኛ ያልሆነ
Proverbs 8:14
መልካም ምክር
"ጥበብ የተሞላ ሃሳብ"
ምክር
አንድን ሰው ለመርዳት የሚሰጥ ሃሳብ
መልካም
ጥሩ፣ ተዓማኒነት ያለው
እኔ ማስተዋል ነኝ
እዚህ ላይ ጥበብ ማስተዋል እንደሆነች ተደርጋ ቀርባለች። አማራጭ ትርጉም:- "እኔ ማስተዋል አለኝ" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሹማምንቶች
የከበሩ ሰዎች፣ በአንድ አገር ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ቤተሰቦችን የሚመሩ አባላት
Proverbs 8:17
ፍቅር
ይህ የሚያመለክተው ወንድማዊ ፍቅር ወይም ለጓደኛ ወይም ለቤተሰብ ያለንን ፍቅር ነው። ይህ በጓደኞችና በቤተዘመዶች መካከል ያለው ተፈጥሮአዊ ፍቅር ነው።
በትጋት
ጥንቃቄ የተሞላበትና የማያቋርጥ ጥረት
ብልጥግናና ክብር በእኔ ዘንድ ናቸው
"ብልጥግናና ክብር አለኝ"
ዘላቂነት ያለው ሃብትና ጽድቅ
ይህ "ሃብትና ክብር" ምን እንደሆነ ያብራራል። ይህ "ስለዚህ" በሚለው አያያዥ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "ስለዚህ እኔ ለሚፈልጉኝ ዘላቂነት ያለው ሃብትና ጽድቅ እሰጣለሁ" (አያያዥ ቃላቶች የሚለውን ይመልከቱ)
ጽድቅ
"በትክክለኛው መንገድ የመኖር ችሎታ"
Proverbs 8:19
ፍሬየ
ጥበብ የምታፈራውና የምታመጣው ነገር
ቡቃያየ
ጥበብ ካመጣችው ነገር የሚገኘው ትርፍ ወይም ጥቅም
እኔ በጽድቅ መንገድ እሄዳለሁ
በትክክለኛው መንገድ መኖር በትክክለኛው መንገድ እንደመራመድ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም:- "እኔ በትክክል እኖራለሁ" ወይም "ትክክል የሆነውን ነገር አደርጋለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ፍትህ በሚወስዱ ጎዳናዎች
ይህ "የጽድቅ መንገድ" የሚለውን ትርጉሙ ምን እንደሆነ የበለጠ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- "እኔ ፍጹም ፍትህ የሆነውን አደርጋለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መዛግብት
በታም ውድ የሆኑ ነገሮች የሚቀመጡበት። ጥበብ የተከታዮቿን መዛግብት በውድ ነገሮች የምትሞላ ሴት ተደርጋ ተገልጻለች። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 8:22
በቀድሞ ዘመን የስራው መጀመርያ
"እኔ እርሱ በቀድሞ ዘመን ከፈጠራቸው ነገሮች የመጀመርያው ነበርሁ
በቀድሞ ዘመን
"በጣም ከረጅም ጊዜ በፊት"
ዘመናት
"ዘመን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጥቅሉ በጣም ረጅም ጊዜን ነው።
ተሰራሁ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "እግዚአብሔር ሰራኝ"
ምድር ከመፈጠርዋ አስቀድሞ
"አስቀድሞ" የሚለው ቃል በጥቂቱ ረቂቅ በሆነ መንገድ ሊተረጎም ይችላ። አማራጭ ትርጉም:- "እግዚአብሔር ምድርን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ" (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 8:24
አጠቃላይ መረጃ:-
ጥበብ መናገር ቀጥላለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ተራሮች ገና ሳይመሠረቱ
"የተራሮች መሰረት በቦታው ላይ ገና ሣይቀመጥ" ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል።: አማራጭ ትርጉም:- "እግዚአብሔር የተራሮችን መሰረት ገና ሳይሰራና በተገቢው ቦታቸው ሳያስቀምጣቸው በፊት" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 8:26
ተወለድሁ ... ነበርሁ
ኢዚህ ላይ ጥበብ ስለራስዋ ትናገራለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ተወለድሁ
"እኖር ነበር"
ተመሰረተ
አንድን ነገር መመስረት ማለት በማይናወጥ መሰረት ላይ ወደ ሕልውና ማምጣት ነው። አማራጭ ትርጉም:- "ፈጠረ" ወይም "ሰራ"
በቀላያት ፊት ክበብን በደነገገ ጊዜ
ይህ የሚያመለክተው በባህር ላይ በመርከብ ውስጥ ያለ አንድ ሰው በሁሉም አቅጣጫ እንዴት ማየት እንደሚችል መነሻ ቦታ ማስቀመጥን ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀላይ
"ውቅያኖስ"
Proverbs 8:28
አጠቃላይ መረጃ:-
ጥበብ መናገርዋን ቀጥላለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ተመሰረተ
ወደ ቋሚ ማንነት ማምጣት

የቀላይን ምንጮች ባጸና ጊዜ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ምንጮችን በቀላይ ውስጥ ባጸና ጊዜ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የቀላይ ምንጮች
የጥንት ዕብራውያን ውቅያኖስ ውኃውን የሚያገኘው ከባህር ጣጭኛው ክፍል ውስጥ ካሉት ምንጮች ነው ብለው ያስተምሩ ነበር።
ለባሕርም ዳርቻን በወሰነ ጊዜ
ለውቅያኖሶች ዳርቻ በፈጠረላቸው ጊዜ። “የባህር ዳርቻ” ውቅያኖሶችን ከደረቅ መሬት ይለያቸዋል።
የምድርም መሰረት የት መሆን እንዳለበት በወሰነበት ጊዜ
“ምድር” የሚለው የዕብራይስጡ ቃል ብዙ ጊዜ “መሬት” የሚል ትርጉም አለው።
የምድርም መሰረት የት መሆን እንዳለበት በወሰነበት ጊዜ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ለምድር መሰረት ዳርቻ ባስቀመጠለት ጊዜ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 8:30
በአጠገቡ ነበርሁ
አሁንም ጥበብ እየተናገረች ነው። ጥበብ ከእግዚአብሔር አጠገብ እንደነበረች እየተናገረች ነው፣ ይህን ያለችው እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር የእርሱ ረዳት እንደነበረች ለማመልከት ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዋና ሰራተኛ
ይህ ጠቃሚ ነገሮችን ማለትም የቤት እቃዎችንና ቤቶችን በሚገባ ለመስራት ለአመታት የሰለጠነ ሰው ነው።
ደስ አሰኘው ነበር
“እርሱ እንዲደሰት የማደርገው እኔ ነበርሁ።” “ደስ” የሚለው ቃል እንደ ግስ መገለጽ የሚችል ረቂቅ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በእኔ ምክንያት ደስተኛ ነበር” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ዕለት በዕለትዕለት በዕለት
ይህ የልማዳዊ ድርጊት ሃሳብን ወይም ቀጣይነት ያለው ሁኔታን ለመግለጽ የምንጠቀምበት መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ያለማቋረጥ” ወይም “ሁልጊዜ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ በሆነው በመላው ዓለም
“እርሱ የፈጠረው መላው ዓለም” ወይም “እርሱ የፈጠረው በሙሉ”
የሰው ልጆች
ይህ የሚያመለክተው በአጠቃላይ የሰው ልጆችን በሙሉ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ ሕልውና ያመጣቸው ሕዝብ በሙሉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 8:32
አሁን
ይህ የልጆቹን ትኩረት ወደ ትምህርቱ መደምደሚያ እንዲያደርጉ ለማገዝ ነው።
አድምጡኝ
አሁንም ጥበብ ስለራስዋ እየተናገረች ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መንገዴን የሚጠብቁ
እዚህ ላይ “መንገዴን” የሚወክለው የጥበብን ባሕርይ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ የማስተምረውን የሚያደርጉ” ወይም “የእኔን ምሳሌ የሚከተሉ ሰዎች” (ተላዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቸል አትበል
“ግድየለሽ አትሁን” አማራጭ ትርጉም፦ “ትኩረት ለመስጠትህ እርግጠኛ ሁን” ወይም “ለመከተል እርግጠኛ ሁን” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
ዕለት ዕለት በቤቴ መግቢያ የሚተጋ፣ የደጄንም መድረክ የሚጠብቅ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጥበብ ቤት እንዳላት ተገል ጧል፤ “መትጋት” ለሚለው ቃል ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ፦ 1) ጥበበኛ ሰው እርስዋን ለማገልገል በማለዳ በጥበብ ቤት መግቢያ ሆኖ ይጠብቃል፣ ወይም 2) ጥበበኛ ሰው እርስዋ እንድትመጣና እንድታስተምረው በጥበብ ቤት መግቢያ ሆኖ ይጠብቃል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 8:35
ያገኘኛል ... ይጠላኛል
አሁንም ጥበብ ሰለራስዋ ትናገራለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔን ያጣ
ሙሉ ሃሳቡ እንዲህ የሚል ነው፦ “እኔን ሊያገኘኝ ያልቻለ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሕይወቱን
እዚህ ላይ “ሕይወት” የሚወክለው ሰውየውን ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 9
Proverbs 9:1
አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ጥቅሶች ጥበብ ለሰዎች መልካም ምክር የምትሰጥ ሴት ተደርጋ የተገለጸችበት ተምሳሌት ይጀምራሉ።(ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጥበብ ሠራች
ፀሐፊው ስለ ጥበብ የራስዋን ቤት እንደሰራች ሴት አድርጎ ያቀርባታል። ቤትዋን ሠራች
ፍሪዳዎቿን አረደች
ይህ ጥበብ እራት በምታቀርብበት ጊዜ ስጋቸው የሚበላውን እንስሳት የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለእራት የሚቀርበውን ስጋ ለማዘጋጀት ፍሪዳዎችን አረደች” (ምትክ ስም እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የወይን ጠጅዋን ደባለቀች
በጥንቷ እስራኤል ሰዎች ብዙ ጊዜ የወይን ጠጅን ከውኃ ጋር ይደባልቁ ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “የወይን ጠጇን ከውኃ ጋር በመደባለቅ አዘጋጀች” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ማዕድዋን አዘጋጀች
“እርስዋ ማዕድዋን አዘጋጀች”
Proverbs 9:3
አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ ቁጥሮች እንደ ሴት የቀረበችውን የጥበብን መልእክት ማቅረብ ይጀምራሉ። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰራተኞችዋን ላከች
እነዚህ ሰራተኞች ወደ ውጭ ሄደው ጥበብ ወዳዘጋጀችው ድግስ እንዲመጡ ሰዎችን ጋበዙአቸው።
ሰራተኞችዋ
ጥበብን የመሰሉ የተከበሩ ሴቶችን የሚያገለግሉ ወጣት ሴቶች ወይም ልጃገረዶች።
ጠራች
“እርስዋ አወጀች” ወይም “እርስዋ ጥሪ አደረገች” አማራጭ ትርጉም፦ “እርስዋ ደጋግማ በመጮህ ጥሪዋን አስተላለፈች”
በከተማይቱ ከፍተኛ ስፍራ ላይ
ግብዣው በሁሉም ሰዎች ዘንድ በሚገባ መደመጥ እንዲችል ከፍ ባለ ድምጽ የተላለፈው በከፍተኛ ስፍራ ላይ ነው።
አላዋቂ የሆነ ማን ነው? ... አእምሮ የጐደለውም ይምጣ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች የሚገልጹት በሕይወታቸው የበለጠ ጥበብ የሚያስፈልጋቸው ተመሳሳይ ዓይነት ሰዎችን ነው። በዚህ ስፍራ ጥያቄው የቀረበው እንዲህ ለመሰሉ ለሁሉም ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፦ አላዋቂ የሆነ ማንኛውም ሰው፣ አእምሮ የጎደለውም ሁሉ ይምጣ”
አላዋቂ
“ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው”
ወደዚህ ፈቀቅ ይበል
“መንገዱን ይተውና ወደ ቤቴ ይምጣ”
Proverbs 9:5
አጠቃላይ መረጃዎች፦
እነዚህ ቁጥሮች የጥበብን መልእክት ማስተላለፍ ቀጥለዋል።
ኑ ... ብሉ ... ጠጡ .... ተዉ ... ኑሩ ... ሂዱ
እነዚህ ትእዛዛት በሙሉ በብዙ ቁጥር የተገለጡ ናቸው፤ ጥበብ በአንድ ጊዜ ለብዙ ሰዎች ጥሪ እያደረገች ነው።
የደባለቅሁትንም የወይን ጠጅ
በጥንትዋ እስራኤል ሰዎች ብዙ ጊዜ የወይን ጠጅን ከውኃ ጋር ይደባልቁ ነበር።

አማራጭ ትርጉም:- የወይን ጠጅዋን ከውኃ ጋር በመደባለቅ አዘጋጀች” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አላዋቂ ድርጊቶቻችሁን ተዉ
እዚህ ላይ የአላዋቂ ድርጊቶች አንድ ሰው ትቶት ሊሄድ እንደሚገባ ስፍራ ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም:- “አላዋቂነት የተሞላ ባህርይህን ተው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የአላዋቂ ድርጊቶች
“ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው ሰው ድርጊቶች”
የማስተዋልም መንገድ
እዚህ ላይ ጥበብን የመረዳት ሂደት አነድ ሰው ሊከተለው የሚችለው መንገድ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጧል። አማራጭ ትርጉም:- “ጥበበኛ ሰው ያለው የሕይወት ዘይቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 9:7
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ቁጥሮች የጥበብን መልእክት ማስተላለፍ ቀጥለዋል።
የሚገስጽ ... የሚዘልፍ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት የሚናገሩት ተመሳሳይ ነገር ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ፌዘኛ
በልምድ ሰዎች ላይ የሚያፌዝ ሰው። አማራጭ ትርጉም:- “ስለ ሌሎች ሰዎች የስድብ ነገሮችን የሚናገር ሰው” ወይም “የሌሎች ሰዎችን ስም ማጥፋት የሚወድ ሰው”
ስድብን ይቀበላል
“መጥፎ ምላሽ ይቀበላል”
የሚዘልፍ
“የሚያስተካክል”
አትገስጽ
“አታርመው”
ለጠቢብ ሰው ... ስጠው፥ እርሱም ... ጻድቅን ሰው አስተምረው፣ እርሱም
እነዚህ ሁለት ትእዛዛት በእርግጥ የሚወክሉት ቅድመ ሁኔታ ያለበት ሃሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ለጠቢብ ሰው ብትሰጠው፣ እርሱም ... ለጻድቅ ሰው ብታስተምረው፣ እርሱም”
ለጠቢብ ሰው ስጠው ... ጻድቅን ሰው አስተምረው
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት የሚናገሩት ተመሳሳይ ነገር ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ለጠቢብ ሰው ስጠው
ይህ የሚያመለክተው ለጠቢብ ሰው ምክርን መስጠት ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 9:10
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ቁጥሮች የጥበብን መልእክት ይፈጽማሉ።
የእግዚአብሔር ፍርሃት
ይህንን በምሳሌ 1:7 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
ዘመንህ በእኔ ይበዛል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ዘመንህን እኔ አበዛዋለሁ” ወይም “እኔ ብዙ ዘመን እንድትኖር አደርግሃለሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በእኔ
ጥበብ እንደ ሴት ተመስላ እዚህ መናገር ቀጥላች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዘመንህ በእኔ ይበዛልና፥ የሕይወትህም ዕድሜ ይጨመርልሃል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ጥቅም ላይ የዋሉትም ጥበብ ያላትን ታላቅ ጥቅም አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
የሕይወትህም ዕድሜ ይጨመርልሃል
ጥበብ ስለ ሕይወት ዕድሜ ቁሳዊ ነገሮች እነደሆኑ አድርጋ ትናገራለች።ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ ለአንተ የሕይወት ዕድሜ እጨምርልሃለሁ” ወይም “ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አደርግሃለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠቢብ ብትሆን ... ፌዘኛም ብትሆን
እነዚህ ሁለት ሃሳቦች ሰዎች ከጥበባቸው የተነሳ ለራሳቸው ጥቅም እንደሚያገኙ ፌዘኞች ደግሞ ከባህርያቸው የተነሳ እንደሚሰቃዩ የሚናገሩ ይመስላሉ።
ለብቻህ ትሸከመዋለህ
ይህ ከመጥፎ ባሕርዩ የተነሳ ሰው የሚመጣበትን መዘዝ አንድ ሰው በጀርባው ሊሸከመው የሚገባው ከባድ ሸክም እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 9:13
ሞኝ ሴት
የሚቻል ከሆነ “ሞኝነት” የሚለውን “ሞኝ ሴት” እና በተመሳሳይ መግለጫዎች ተርጉመው። ይሁን እንጂ በዚህ ምዕራፍ የቀደሙ ክፍሎች ላይ እንደነበረው ቋንቋው ለጥበብ የሰው ባህርይ እንዲሰጣት የሚፈቅድ ከሆነ ለሞኝነትም የሰው ባህርይ እንዲሰጣት ሊፈቅድ ይችላል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አልተማረችም፣ አንዳችም አታውቅም
እነዚህ ሁለት መግለጫዎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የተደጋገሙት ሞኝ ሴት ምን ያህል የማትጠቅም እንደሆነች ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እርስዋ አንዳች ነገር እንኳ በጭራሽ አታውቅም” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ያልተማረች ናት
“ከልምድ አልተማረችም” ወይም “ወጣትና አላዋቂ ናት”
በመንገድ የሚያልፉትን
ይህ ፈሊጥ ሲሆን “የራሳቸውን ጉዳይ ብቻ የሚያስቡትን” ወይም “የራሳቸውን ስራ ብቻ የሚያስቡትን” ለማሳየት ይመስላል። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 9:16
አላዋቂ ነው
“ልምድ የሌለው ወይም የአእምሮ ብስለት የሌለው ነው”
ወደዚህ ፈቀቅ ይበል
“ይህንን መንገድ ይተውና ወደዚህ ይምጣ”
እንዲህ አለች
ይህች በምሳሌ 9:13 ላይ የተዋወቀችው ሞኝ ሴት ናት።
እነዚህ አእምሮ የጎደላቸው
“እነዚህ ጥበብ የሌላቸው” ወይም “እነዚህ ጠቢብን ያልሆኑ”
የተሰረቀ ውኃ ጣፋጭ ነው፣ በምስጢር የበሉት እንጀራም ደስ ያሰኛል
ይህች ሞኝ ሴት ከእርስዋ ጋር ከተኙ ደስተኛ እንደሚሆኑ ለወንዶች ለመናገር ስለ ተሰረቀ ውኃ እና በምስጢር ስለተበላ እንጀራ አስደሳችነት ትናገራለች። ይህ በተነጻጻሪ ዘይቤ በግልጽ ሊብራራ ይችላል:- “የሰረቅኸው ውኃ እና በምስጢር የበላኸው ደስ እንደሚያሰኝህ ሁሉ ከእኔ ጋር ብትተኛ በእኔ ደስ ትሰኛለህ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሙታን ከዚያ እንዳሉ
“ወደ እርስዋ የሄዱ ወንዶች አሁን ሞተዋል”
በሲኦል ጥልቀት
“ሲኦል” የሚያመለክተው የሙታን ዓለምን ነው።

---

Chapter 10
Proverbs 10:1
አጠቃላይ መረጃ:-
በምዕራፍ 10 የሚገኙ ብዙ ቁጥሮች ትይዩነትን ያነጻጽራሉ። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
የሰሎሞን ምሳሌዎች
ከምዕራፍ 1-9 ካለው መግቢያ በኋላ ምዕራፍ 10 የምሳሌዎችን ማለትም ጥበብን የሚያስተምሩ አጫጭር ትምህሮችን ስብስብ ማቅረብ ይጀምራል።
መዝገብ
በጊዜ ሂደት የተከማቸ
እግዚአብሔር የጻድቁን ነፍስ አያስርብም
እዚህ ላይ “ነፍስ” የሚለው ሰውየውን የሚያመለክት ነው። ይህ በአዎንታዊ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር ጽድቅ የሚያደርጉትን ሰዎች


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚበሉት እንጀራ እንዲኖራቸው ማረጋገጫ ይሰጣቸዋል” (ተዛምዶአዊ እና ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 10:4
የታካች እጅ
“እጅ” የሰውን ብርታትና ችሎታ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለመስራ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የትጉ እጅ
“እጅ” የሰውን ብርታትና ችሎታ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በትጋት የሚሰራ ሰው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 10:6
ራስ ላይ ነው
“ራስ” የሰውን ሁለንተና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለእነርሱ ይሰጣል” (ፈሊጥ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
የኀጥኣንን አፍ
“አፍ” ሰውየው የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ኃጢአተኛ የሚናገራቸው ቃላቶች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ይከድነዋል
እውነትን ይደብቃል
ስም
“ስም” የሚለው ቃል የሰውየውን ዝና ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም “ትውስታ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 10:8
ይወድቃል
“ይጠፋል” ወይም “ከጥቅም ውጭ ይሆናል”
ጠማማ
ቀጥተኛ ያልሆነ፤ የተንሻፈፈ፤ የማይታመን፤ አታላይ
Proverbs 10:10
በዓይኑ የሚጠቅስ
“በዓይን መጥቀስ” በሌላ ሰው ላይ ጭካኔ ለመፈጸም ምስጢራዊ ምልክትን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በሰውነት እንቅስቃሴ ምልክት የሚሰጥ” (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ታች ይጣላል
የወደቀ ሰው ወደ ታች እንደ ተጣለ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ ሌሎች ይጥሉታል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የጻድቅ አፍ
እዚህ ላይ “አፍ” ሰውየው የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የጻድቅ ሰው ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጻድቅ
ይህ በአጠቃላይ ጻድቅ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጻድቅ ሰዎች” (ብዙ ገላጭ ስም ሐረጎች የሚለውን ይመልቱ)
የሕይወት ውኃ ምንጭ ነው
የዚህ ሰው ንግግር የውኃ ምንጭ በደረቅ መሬት እንደሚያደርገው እንዲሁ ሕያዋን እንስሳትን ወይም ሰዎችን በሕይወት የሚያኖር ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የኃጥኣንን አፍ ግን ግፍ ይከድነዋል
ክፉ ሰው ጉዳት የማያደርሱ ነገሮችን ይናገራል ነገር ግን በሌሎች ሰዎች ላይ ግፍ ለማድረግ ያቅዳል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የኃጥእ አፍ
እዚህ ላይ “አፍ” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የክፉ ሰው ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉ ሰው
ይክ በአጠቃላይ ክፉ ሰዎችን በሙሉ ይወክላል። (ብዙ ገላጭ ስም ሐረጎች የሚለውን ይመልቱ)
Proverbs 10:12
ፍቅር ትከድናለች
ፍቅር ጠብን ከማባባስ ይልቅ በሰዎች መካከል ያለውን ችግር እንደሚያስታግስ ሰው እንዲሁ ታደርጋለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልቱ)
በብልሃተኛ ሰው ከንፈር
“ከንፈርየሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሚያስተውል ሰው በሚናገረው ውስጥ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በትር ለጀርባ ነው
“በትር” ጠንካራ የሆነ አካላዊ ቅጣት ይወክላል፣ “ጀርባ” ደግሞ ቅጣቱን የሚቀበለውን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አእምሮ የጎደለው ሰው ጠንካራ ቅጣት ያስፈልገዋል” (ተዛምዶአዊ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 10:14
የሰነፍ አፍ
“አፍ” ሰውየው የሚናገረውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከሞኝ ሰው የሚወጣ ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ የጸናች ከተማ
ይህ ሃብት እንደ አስተማማኝ ስፍራ የተወከለበት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእርሱ ደህንነት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 10:16
ደሞዝ ... ትርፍ
እነዚህ ቃላቶች ብዙውን ጊዜ የሚያመለክቱት ሰራተኛ የሚከፈለውን ገንዘብ ነው። እዚህ ላይ ትክክለኛውን ነገር የመስራት ወይም ደግሞ ትክክለኛ ያልሆነውን ነገር የመስራት ውጤት ይወክላሉ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ተግሣጽን የሚጠብቅ በሕይወት መንገድ
“ጥበብ ያለበትን ምክር የሚታዘዝ ሰው ረጅምና ደስተኛ ሕይወት ይኖረዋል”
ተግሳጽን የማይቀበል ሰው ግን ይስታል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጥበብ የተሞላበት ምክር የማይቀበል ሰው ግን ጥሩ ሕይወት አይኖረውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 10:18
ሐሰተኛ ከንፈር አለው
“ከንፈር” ሰውየው የሚናገረውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ውሸትን ይናገራል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ኃጢአት ሳይኖር አይቀርም
ይህ ሀረግ አዎንታዊ ሃሳብን አጽንዖት ለመስጠት አሉታዊ ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፦ “ብዙ ኃጢአት አለበት” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 10:20
የጻድቅ ምላስ
“ምላስ” ሰውየው የተናገረውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጻድቅ ሰው የተናገረው ማንኛውም ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ንጹህ ብር ነው
“ብር” ውድ ዋጋ ያላቸውን ነገሮች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እጅግ በጣም የከበረ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የጻድቅ መምላስ
“ምላስ” ሰውየው የሚናገረውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የጻድቅ ሰው ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ይመግባሉ
እንዲጎለብቱ ወይም ጠንክረው እንዲያድጉ
Proverbs 10:22
ክፉ ነገር ማድረግ ለሰነፍ ሰው ጨዋታ ነው
ጨዋታ ሰዎች ለመዝናናት የሚፈጽሙት ተግባር ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሞኞች ክፉ ነገር በማድረግ ይደሰታሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 10:24
በላዩ ይመጣበታል
አንድን ሰው ያሸንፋል
ክፉ ሰዎች እንደ ዐውሎ ነፋስ ናቸው
ዐውሎ ነፋስ እንደሚመጣና ማንኛውንም ነገር እንደሚያጠፋ ክፉ ሰዎችም እንዲሁ ይጠፋሉ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የዘላለም መሠረት ነው
“መሠረት” አርማታን ወይም ሰዎች የሚገነቡት የአንድ ነገር መጀመርያን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለረጅም ጊዜ ለሚቆይ ነገር መጀመርያው ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 10:26
በጥርስ ላይ ያለ ሆምጣጤ፣ በዓይንም ውስጥ ያለ ጢስ እንደሚጎዳ፣ ሰነፍ ሰው ለሚልኩት እንዲሁ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነው።
“ሆምጣጤ” እና “ጢስ” የሰውን ጥርስ እና ዓይን የሚጎዱ ነገሮችን የሚወክሉ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰነፍን ሰው አንድ ነገር እንዲያከናውን መላክ የሚቆጠቁጥና የሚያሳዝን ነው” (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሆምጣጤ
ምግብ ለማጣፈጥና ሳይበላሽ ለመጠበቅ የሚረዳ የሚኮመጥጥ ፈሳሽ ነው
የክፉ እድሜ
“እድሜ” አንድ ሰው የሚኖርበትን ጊዜ የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የክፉ ሰው የሕይወት ዘመን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 10:28
የክፉ ሰዎች እድሜ
እዚህ ላይ “እድሜ” የሚወክለው ሰው የሚኖርበት ዘመን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የክፉ ሰው የሕይወት ዘመን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አይናወጥም
ይህ በገቢር ግስና በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላ። አማራጭ ትርጉም፦ “ዋስትና አለው” (ምፀት እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 10:31
ከጻድቅ ሰው አፍ
“አፍ” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከጻድቅ ሰው ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጠማማ ምላስ ግን ትቈረጣለች
“ምላስ” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ውሸት የሚናገሩትን ሰዎች አንደበት ይዘጋል” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የጻድቅ ከንፈሮች ደስ የሚያሰኝ ነገርን ያውቃሉ
“ከንፈሮች” የሰውየውን ንግግር ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ጻድቅ ሰው ደስ የሚያሰኝ ነገር እንዴት እንደሚናገር የውቃል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የኀጥኣን አፍ
“አፍ” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ የክፉ ሰው ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 11
Proverbs 11:1
አጠቃላይ መረጃ፦
በምዕራፍ 11 ውስጥ ያሉ ብዙ ቁጥሮች ትይዩነትን ያነጻጽራሉ። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ትክክለኛ ያልሆነ ሚዛን ይጠላል
“ሚዛን” በስምምነት የሚደረግ ትክክለኛ መለኪያን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር አታላይነት ያለበትን መለኪያ ይጠላል” ወይም “እግዚአብሔር ሰዎች አታላዮች ሲሆኑ ይጠላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ትክክለኛ ሚዛን ግን ደስ ያሰኘዋል
“ትክክለኛ ሚዛን” በስምምነት የሚሆን ልክነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ነገር ግን እርሱ በሀቀኛ መንገድ ይደሰታል” ወይም “ነገር ግን እርሱ ሰዎች ሀቀኛ ሲሆኑ ይደሰታል”
Proverbs 11:3
ወስላቶች
የስም ቅጽል እንደ መደበኛው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወስላቶች ሰዎች” ወይም “እነዚያ ወስላቶች የሆኑ ሰዎች” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልቱ)
በቍጣ ቀን ሀብት አትረባም
“የቁጣ ቀን” እንደ “የእግዚአብሔር ቀን” ወይም “የፍርድ ቀን” ወይም “የመጨረሻው ቀኖች” የመሳሰሉት ወሳኝ ጊዜያትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ለፍርድ ሲመጣ ሰው ሀብቱ ምንም ሊያደርግለት አይችልም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 11:5
መንገዱን ያቀናለታል
“ግልጽ አቅጣጫ አለው”
ክፉው ... ወስላታው
እነዚህ የስም ቅጽሎች እንደ መደበኛው ቅጽል ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “እነዚህ ክፉዎች .... እነዚህ ወስላቶች” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልቱ)
ወስላቶች ግን በምኞታቸው ይጠመዳሉ
“እነዚህ ክፉ ስራ የሚሰሩ ሰዎች በምኞታቸው ይጠመዳሉ”
ወስላቶች
እምነት ለማጥፋት ዝግጁ የሆኑ፤ ከሃዲዎች፤ አታላዮች
Proverbs 11:7
በብርታቱ የተመካበት ተስፋ
“በራሱ ኃይል የነበረው ትምክህት”
ከንቱ ይሆናል
“ይጠፋል”
ጻድቅ ሰው ከመከራ ይድናል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጽድቅን የሚያደርግ ሰው እግዚአብሔር ከመከራ ይጠብቀዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ይመጣል
“መከራ ይመጣበታል”
Proverbs 11:9
አምላክ የለሽ ሰው በአንደበቱ
“አንደበት” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የአምላክ የለሽ ሰው ቃሎች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ከተማዋ ታላቅ ትሆናለች
“ከተማ” ማህበረሰቡን ወይም ሕዝቡን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕዝቡ ይበለጽጋል ዌም “ሕብረተሰቡ ባለጠጋ ይሆናል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በክፉዎች አንደበት
“አንደበት” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የክፉ ሰዎች ንግግር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 11:12
ነገሩን ይሰውራል
“ይሰውራል” በተቻለ መጠን ነገሮች እንዳይገለጡ መጠበቅን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አይናገርም” ወይም “ስለ ጉዳዩ አያወራም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 11:14
አማካሪዎች
ድርጊትን በምሪት ለማከናወን ሃሳብ የሚሰጡ ሰዎች፤ አማካሪዎች
Proverbs 11:15
መስጠት የሚጠላ ሰው
“መስጠት የማይፈልግ ሰው”
ጨካኝ ሰዎች
ሃዘኔታ ወይም ርህራሄ የሌላቸው ሰዎች፤ አረመኔ ሰዎች
ሀብትን የሚጨብጥ
“እነዚህ ለሃብት የሚሳሱ ናቸው”
Proverbs 11:17
እርሱ
“ያ ሰው”
ትክክለኛውን ነገር ይዘራል
“መዝራት” የበለጠ ለማግኘት መበተንን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ትክክል የሆነውን ነገር ይበትናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእውነትን ደመወዝ ይሰበስባል
“መሰብሰብ” ማግኘት ወይም መሸከፍን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በእርግጠኝነት ወሮታን ይቀበላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 11:19
እርሱ
“ያ ሰው”
ክፋትን የሚከተል
“ከክፋት በኋላ የሚከተል” ወይም “ክፋትን ለማድረግ የሚፈልግ”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ጠማማ ልብ ያላቸው
“ልብ” የሰውን ስሜት፣ አመለካት እና ተነሳስቶት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሃሳብ ያላቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 11:21
ሳይቀጣ አይቀርም
ይህ ሀረግ አዎንታዊውን አጽንዖት ለመስጠት አሉታዊውን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእርግጠኝነት ይቀጣል” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ወርቅ ቀለበት … ማስተዋል የሌላትም
Like a gold ring … without discretion ማስተዋል የሌላት ቆንጆ ሴት ከማይጠቅምና ከማይስማማ በዓሳማ አፍንጫ ካለ የወርቅ ቀለበት ጋር ተነጻጽሯል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማስተዋል የሌላት
x
Proverbs 11:23
ያለውን የሚበትን ሰው አለ፥ እርሱ የበለጠ ይሰበስባል
ይህ በቸርነት በመስጠት የበለጠ ባለጠጋ ለሆነ ሰው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንዳንድ ሰዎች ለሌሎች በነጻ ይሰጣሉ፣ እንዲህም ሆኖ ግን የበለጠ ባለጠጋ ይሆናሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚበትን
ይህ ሰው እህል እንዲበቅል ዘርን እንደሚበትን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግሃል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ዘር የሚበትን ሰው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ተተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የበለጠ ይሰበስባል
“የበለጠ ያገኛል”
መስጠት የሚገባውን ያለ ቅጥ የሚይዝ
ይህ ባለመስጠት ባለጠጋ መሆን እንደሚችል የሚያስብን ሰው ይወክላል።
Proverbs 11:25
ይበለጽጋል
“የበለጠ ያገኛል”
እርሱ
“ያ ቸር ሰው” ወይም “ማንኛውም ሰው”
ለመሸጥ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው
ይህ ድሆችን ከመርዳት ይልቅ ሀብትን የሚያከማች ሰውን ይገልጻል።
መልካም ስጦታዎች ግን በሚሸጠው ራስ ላይ እንደ አክሊል ይጎናጸፋል
“አክሊል” እህል ለመሸጥ ፈቃደኛ ለሆነው ሰው የሚሰጠውን ወሮታ ወይም ሽልማት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ስጦታዎች እንደ ክብር አክሊል ለሚሸጥ ሰው ይሰጠዋል” ወይም “የሚሸጥ ሰው በብዙ በረከቶች ይከበራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 11:27
ተግቶ የሚፈልግ ሰው
በጥንቃቄና በማያቋርጥ ጥረት የሚፈልግ ሰው
ይወድቃል
ይህ ፈሊጥ ነው። “ይወድቃል” ጥፋትን እና ውድቀትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይጠፋል” ወይም “ለወደፊት ክፉ ነገር ይጠብቀዋል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ጽድቅን የሚያደርጉ ግን እንደ ቅጠል ይለመልማሉ
“ቅጠል” እድገትንና ባለጠግነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ጤነኛ ቅጠል እንደሚያድግ እንደዚሁ ይበለጽጋሉ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጽድቅን የሚያደርጉ ይለመልማሉ
ይህ ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ያድጋሉ ወይም ይበለጽጋሉ ማለት ነው።
Proverbs 11:29
ነፋስን ይወርሳሉ
“ነፋስ” ለማይጨበጥ ነገር ወይም ዋጋ ለሌለው ነገር የቆመ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም አይወርስም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 11:30
ጽድቅን የሚያደርግ ሰው እንደ ሕይወት ዛፍ ይሆናል
ጽድቅን የሚያደርግ ሰው የሕይወት ፍሬን ከሚያፈራ ዛፍ ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ለራሳቸውና ለሌሎች ሰዎች ሕይወትን ያመጣሉ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሕይወት ዛፍ
ይህን በምሳሌ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልት።
ምን ያህል የላቀ
“ከዚያም የበለጠ”

---

Chapter 12
Proverbs 12:1
አጠቃላይ መረጃዎች፡-
ጸሐፊው በዚህ ምዕራፍ በሙሉ ትይነትን ይጠቀማል።
አጠቃላይ መረጃዎች፡-
ከቁጥር 5-15 ያለው ጥበብንና ሞኝነትን ያወዳድራል።
ማንም
“ማንም ሰው”
እርምትን የሚጠላ ግን ደነዝ ነው።
“ሊያደርግ የሚገባውን ነገር ሊነገረው የማይወድ ሰው”
ደንቆሮ ነው
“ሞኝ ነው” ወይም “ጥበብ የሌለው ነው”
Proverbs 12:3
ሰው በክፋት ላይ ተመስርቶ ጸንቶ ሊቆም አይችልም
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ነገር በማድረግ ማንም ሰው ዋስትናና ጥበቃ ሊኖረው አይችልም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
አይነቀልም
“አይነቀልም” እንደ ተክል ወይም ዛፍ ከምድር መነቀልን ይወክላል። ጽድቅ የሚያደርጉ ሰዎች ላይ ይህ አይሆንም። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥልቅ ስር እዳላቸው ተክሎች ጽኑ ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት
ዘውድ አንድ ሰው ሊቀበለው የሚችለውን ታላቅ ክብር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ሴት ለባሏ የታላቅ ክብር ምልክት ናት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አሳፋሪ ሴት ግን አጥንቱን እንደሚያበሰብስ በሽታ ናት
አጥንትን የሚያበሰብስ በሽታ የሰው ሕይወት መበለላሸትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚስት አሳፋሪ ተግባር የባሏን መልካም ተጽዕኖና ደስታ ያጠፋል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 12:5
የክፉ ሰዎች ቃል ድንገት ለመግደል አድፍጦ ያደባል
ሌሎችን ሰዎች ለመጉዳት ክፉ ሰዎች የሚናገሩት አታላይ ነገር ቃሎቻቸው አንድን ሰው በድንገት ለመግደል እንደሚጠብቁ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎች የሚናገሩት ቃል አንድን ሰው በድንገት ለመግደል እንደሚጠብቅ ሰው ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የቅኖች አፍ ግን ይታደጋቸዋል።
“ከቅን ሰው የሚገኝ ምክር ሰዎችን በደህንነት ይጠብቃቸዋል”
ቅን
“ጻድቅ ሰው” ወይም “ታማኝ ሰው” ወይም “ፍትህ የተሞላ ሰው”
Proverbs 12:7
ኀጥኣን ይገለበጣሉ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ክፉ ሰዎችን ይገለብጣሉ” ወይም “ሰዎች ክፉ ሰዎችን ከስልጣናቸው ያስወግዱአቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ በዘይቤአዊ አነጋር ቅድመ አያቶችን፤ የትውል ሀረግን ወይም ሌሎች ዘመዶችን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቤተሰብ” ወይም “የትውልድ ሀረግ” (ምትክ ስም


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚለውን ይመልከቱ)
ሰው በጥበቡ ብዛት ይመሰገናል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ጥበብ ያላቸውነ ሰዎች ያወድሳሉ (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠማማ ምርጫዎች የሚያደርግ ግን ይናቃል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ክፉ ሃሳብ ሁልጊዜ የሚያስብን ሰው ይጠላሉ” ወይም “ሰዎች መልካምን ነገር አጣምሞ በመጥፎ የሚለውጥን ሰው ይጠላሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 12:9
ራሱን ዝቅ አድርጎ አገልጋይ መሆን ይሻላል።
“ስልጣንና ዝና የሌው ሰው መሆን ይሻላል”
ጨካኝ ነው
“ለሌሎች መከራን ያስከትላል”
Proverbs 12:11
ዋጋ ቢስ ስራዎችን
“ዋጋ የሌለው እቅድ” ወይም “ዋጋ የሌላቸው ስራዎች”
ፍሬው
ይህ የሰውን ድርጊትና ሃሳብ ያመለክታል። በዛፍ ላይ ያለ ፍሬ ዛፉ ምን እንደሆነ እንደሚያሳይ ሁሉ እንደዚሁ በተመሳሳይ መንገድ የሰው ቃላቶችና ድርጊቶች የሰውየው ባሕርይ ምን እንደሚመስል ያሳያል።
Proverbs 12:13
ክፉ ሰው በክፉ ንግግሩ ይጠመዳል
“ይጠመዳል” በወጥመድ መያዝን ወይም ደግሞ መታለልን ይወክላል። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰው የሚናገራቸው ነገሮች ራሱን ያጠምዱታል” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ እጁ ስራም ዋጋውን ይቀበላል
“የእጁ ስራ” የሚለው ሀረግ የጉልበት ስራን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ስራው ዋጋ እንዲቀበል እንደሚያደርገው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 12:15
ይመስለዋል
ይህ ሀረግ በራሱ ግንዛቤ፣ አስተሳሰብ ወይም ትውስታ የሚለውን ሃሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በራሱ አመለካከት” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ምክር
ጥበብ ያለባቸው ሃሳቦች
ጠንቃቃ ነው
“ጥበበኛ ነው” ወይም “ጥሩ ግንዛቤ አለው”
Proverbs 12:17
የለፍላፊ ሰው ቃሎች እንደሚዋጋ ሰይፍ ነው።
“እንደሚዋጋ ሰይፍ” የሚለው ሀረግ ሌላ ሰው የሚጎዳ ጭካኔ የተሞሉ ቃላቶችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው እንደሚገባ ሳያስብ የሚናገረው ንግግር እንደ ስለታም ሰይፍ ሰውን ሊጎዱ ይችላሉ። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የጠቢባን ምላስ
“ምላስ” ሰውየው የሚናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ ሰዎች የሚናገሩት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ፈውስን ያመጣል
“ያጽናናል እና ይፈውሳል”
Proverbs 12:21
መከራ አያገኘውም
“አያገኘውም” የሚለው አሉታዊ ቅርጽ የመከራን (ሊመጡ የሚችሉ ክፉ ነገሮችን) ሃሳብ ይሰርዘዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ነገሮች ይመጣሉ (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
ውሸተኛ ከንፈርን እግዚአብሔር ይጠላል
“ከንፈር” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “Yahweh detests those who tell lies” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 12:23
እውቀትን ይሸሽጋል
“የሚያውቀውን ሁሉ አይናገርም”
የትጉ እጅ
“እጅ” ሰውየው የሚሰራውን ስራ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትጉ ሰዎች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ለጉልበት ስራተኝነት ታልፈው ይሰጣሉ
“የጉልበት ስራ” ሰውየው ሊሰራው የሚፈልገውን ነገር ለመስራት ነጻነት የሌለው መሆኑና በግዴታ ሊሰራው የሚገባውን የሚገልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ባርያ ይሆናል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 12:25
ጭንቀት
በጣም ከባድ የፍርሃት ወይም ስጋት፣ ትካዜ ስሜት
ያዋርደዋል
“ማዋረድ” አንድ ሰው በነጻነት እንደሚገባ እንዳይንቀሳቀስ ለማድረግ በጣም ከባድ ሸክም በሰውየው ላይ የመጫን ሃሳብን ይወክላል። ይህ ሀረግ አንድን ሰው እንዲያዝን ወይም እንዲጨነቅ ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዲያዝን ወይም እንዲጨነቅ ማድረግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መልካም ቃል ግን ደስ ያሰኘዋል
“ቃል” የሚለው ረቂቅ ስም “ተናገረ” በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ሌሎች ለእርሱ በደግነት ሲናገሩ እንደገና ደስተኛ ይሆናል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 12:27
ሰነፍ ሰዎች አድነው ያመጡትን እንስሳ እንኳ አይጠብሱም
“እንስሳ” በአደን ጊዜ የተያዘና የታረደ እንስሳ ማለት ነው። “መጥበስ” የሚለው ደግሞ ምግብን የማዘጋጀት መንገድ ነው።
የከበረ ሀብት
“ዋጋው የከበረ መዝገብ”

Chapter 13

Proverbs 13:1
ጥበበኛ ልጅ ይሰማል
እዚህ ላይ “ይሰማል” የሚለው በተግባር ለመፈጸም ማድመጥን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ ልጅ ይታዘዛል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ተግሣጽን አይሰማም
እዚህ ላይ “መስማት” የተነገረውን በተግባር ለመፈጸም ትኩረት መስጠትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከተግሳጽ አይማርም” ወይም “ቢገሰጽም እንኳአይታዘዝም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ከአፉ ፍሬ
እዚህ ላይ “ፍሬ” ሰውየው የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከአንደበቱ ቃላቶች” ወይም “ከተናገረው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ምኞት
የአንድ ነገር አምሮት ወይም ፍላጎት
ጠማማው
ይህ የስም ቅጽል እንደ መደበኛ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠማማ ሰው” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመለከቱ)
Proverbs 13:3
አፉ
እዚህ ላይ “አፍ” ሰውየው የሚናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የተናገረው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ከንፈሮቹን ያለ ልክ የሚከፍት
ከንፈሮችን መክፈት መናገርን ይወክላል፣ ከንፈሮችን ያለ ልክ መክፈት ደግሞ በተደጋጋሚ መናገር ወይም ብዙ መናገርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ይናገራል” ወይመ “በተደጋጋሚ ይናገራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ምኞት … ምኞት
ይህን በምሳሌ 13:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
ትመኛለች አንዳችም አታገኝም
“በብርቱ ይፈልጋል ነገር ግን ምንም አያገኝም”

የትጉ ሰው ምኞት ግን በሙላት ይረካል
እዚህ ላይ ምኞት" ፍላጎትን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ትጉ ሰዎች በሙላት የሚረካ ሕይወት ይኖራቸዋል" ወይም "ትጉ መሆን ሰወች በሙላት እንዲረኩ ያደርጋል" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ትጉ ሰዎች
በጥንቃቄ እና በማያቋርጥ ጥረት የሚሰሩ ሰዎች
Proverbs 13:5
ጥላቻ የሚፈጥር ሰው
ብርቱ የሆነ የጥላቻ ስሜት የሚፈጥር
ጽድቅ ይጠብቀዋል
"ጽድቅ" በእግዚአብሔር ተቀባይነት ያለው የሕይወት ዘይቤን ይወክላል፡፡ ይህ የሕይወት ጥራት እንደሚጠብቅ ሰው ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "በእግዚአብሔር ተቀባይነት ያለው የሕይወት ዘይቤ ይጠብቃል" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በመንገዱ ያለ ነውር የሚሄደውን
እዚህ ላይ "መንገድ" አንድ ሰው ሕይወቱን እንዴት እንደሚመራ የሂሚያሳይ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "በአናኗር ዘይቤአቸው ያለ ነውር የሚሄዱ" ወይም "ሀቀኝነት የተሞላ ሕይወት የሚኖሩ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ክፋት ግን ኃጢአተኞችን ትጥላቸዋለች
እዚህ ላይ "ኃጢአተኝነት" ክፋት የተሞላ የሕይወት ዘይቤን ይወክላል፡፡ ይህ የሕይወት ዘይቤ ኃጢአት የሚሰሩትን ሰዎች እንደሚጥል ሰው ተገልጧል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ክፋት ኃጢአተኞችን ከስኬታማ መንገድ ያርቃቸዋል" ወይም "ክፋት የኃጢአተኞችን ሕይወት ያከስራል" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 13:7
ራሱን ባለጠጋ የሚያስመስል
"ራሱን ባለጠጋ የሚያስመስል ሰው"
ተግሣጽን አይሰማም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ከእርሱ ለመስረቅ ማንም ሰው አያስፈራራውም ምክንያቱም ማንም ሰው ሊሰርቀው የሚችለው አንዳች ነገር የለውም 2) ሰዎች ሲያስተካክሉት ፈጽሞ አይሰማም ምክንያቱም ቢቀጡትም አንዳች የሚያጣው ነገር የለም፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ተግሳጽ ፈጽሞ አይሰማም"
Proverbs 13:9
ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ብርሃን ደምቆ ይበራል
እዚህ ላይ ብርሃን የጻድቅ ሰውን ሕይወት ወይም መልካ ባህርይ ይወክላል፤ "ደምቆ መብራት" ደግሞ ሰዎች ደስ እንዲሰኙ ማድረግን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "የጻድቅ ሰው ሕይወት ሰዎችን እንደሚያስደስት በብርሃን ነው፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የኀጥኣን መብራት ይጠፋል
እዚህ ላይ መብራት የክፉ ሰው ሕይወት ወይም ባህርይ ይወክላል፣ "ይጠፋል" ደግሞ እሳቱ ይቆማል ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጥ ነው፡፡ የሚጠፋው መብራት የሰውየውን መሞት ወይም የሰውየው ሕይወት ደስታ አልባ መሆኑን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "የክፉ ሰዎች ሕይወት እሳቱ መንደድ እንደሚያቆም መብራት ነው" (ተለዋጭ ዘይቤ እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ትዕቢት ጠብን ብቻ ያስፋፋል
"ትዕቢት ሁልጊዜ ጠብን ያመጣል"
ምክርን የሚቀበሉ
"ይሰውራሉ" ወይም "ይከተላሉ"
መልካም ምክር
የሚጠቅሙና የሚያግዙ ሃሳቦች
Proverbs 13:11
ሀብት ትኈድላለች
"ሀብት ይቀንሳል" ወይም "ሀብት ቀስ በቀስ እየጠፋ ይሄዳል"
በእጁ እየሰራ
"በእጁ እየሰራ" የሚለው ሀረግ ከአእምሮ ወይም ከሌሎች የስራ ዓይነቶች ይልቅ በጉልበት የሚሰራ ስራን ይወክላል፡፡ ብዙ ሰዎች የጉልበት ስራን አነስተኛ ዋጋ ይሰጡታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "በአካላዊ ብርታት መስራት" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ገንዘቡ እየጨመረ እንዲሄድ ያደርጋል
ገንዘብ ከሚያድግ ዛፍ ጋር ተነጻጽሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ገንዘቡ እንዲጨምር ያደርጋል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ተስፋ ሲዘገይ
እዚህ ላይ "ተስፋ" አንድ ሰው ለወደፊት የሚጠብቀውን ነገር ይወክላል፡፡ ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "አንድ ሰው አንድ ነገር ተስፋ እያደረገ ነገር ግን ያን ተስፋውን ለረጅም ጊዜ ሳይቀበል ሲቀር" (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ልብን ይሰብራል
የሰውን ልብ መስበር ያንን ሰው በሀዘን ስሜቱን መጉዳት ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ጥልቅ ሃዘን ያስከትላል" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የተሳካ ምኞት ግን የሕይወት ዛፍ ነው
ሰዎች ተስፋ ያደረጉትን ነገር ሲቀበሉና በጣም ደስተኛ ሲሆኑ የተስፋቸው መሳካት ሕይወት እንደሚሰጥ ዛፍ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "የተሳካ ተስፋ እንደ ሕይወት ዛፍ ነው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሕይወት ዛፍ
"ሕይወት የሚሰጥ ዛፍ" ወይም "ፍሬው ሕይወትን የሚያቆይ ዛፍ፡፡" ይህንን በምሳሌ 3:18 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡
Proverbs 13:13
ትእዛዝን የሚያከብር ግን ወሮታን ያገኛል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ትእዛዝ የሚያከብርን ሰው ወሮታ ይከፍሉታል" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የሕይወት ምንጭ
ምንጭ የተትረፈረፈ የውኃ ምንጭ ነው እናም በዚህ የሚወክለው የሕይወት ምንጭን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "የሕወይት የተትረፈረፈ ምንጭ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሞት ወጥመድ
እዚህ ላይ "ወጥመድ" የሚገድል አደጋን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ወደ ሞት የሚመራ ወጥመድ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 13:15
የከዳተኛ መንገድ ግን አያልቅም
እዚህ ላይ የሰው ባህርይ ወይም ጠባይ አንድ ሰው የሚጓዝበት መንገድ ወይም አቅጣጫ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ በራሳቸው ክፋት ውድቀት የሚደርስባቸው ሰዎች ዘመናቸውን ሁሉ ቢጓዙ የማያልቅ መንገድ ወይም ጉዞ ላይ እንደሆኑ ተደርጎ ተንግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ነገር ግን የከዳተኞች ባህርይ በራሳቸው ላይ ጥፋት ያመጣባቸዋል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከዳተኞች
ይህ የስም ቅጽል በመደበኛው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ከዳተኛ ሰው" (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ሞኝ ሞኝነቱን ይገልጣል
"መግለጥ" በማንኛውም ሰው ፊት ማሳየት ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ሞኝ ሞኝነቱን ለሁሉም ሰው ያሳያል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 13:17
በመከራ ውስጥ ይወድቃል
"አይታመንም" ወይም "ክፉ ነገር ያደርጋል"
የታመነ መልእክተኛ
"ታማኝ መልእክተኛ" ወይም "ታማኝ ወኪል"
ከእርምት ይማራል
ይህ "እርምት" የሚለው ረቂቅ ስም በድርጊት ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "አንድ ሰው ሲያርመው በሚገባ ይማራል" (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 13:19
ጣፋጭ ነው
"ደስ ያሰኛል" ወይም "ደስታን ያመጣል"
ምኞት
የአንድ ነገር ፍላጎት ወይም አምሮት
መከራን ይቀበላል
"መከራ ይገጥመዋል" ወይም "ጥፋት ይመጣበታል"
Proverbs 13:21
ክፉ ነገር ኃጢአተኞችን ይከታተላቸዋል
"ክፉ ነገር" እንደ ሩጫ ችሎታ የሰው ልጅ የሚከታተል መጥፎ ባህርይ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ኃጢአተኞች የትም ቢሄዱ መከራ ይገጥማቸዋል" (ሰውኛ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች መልካምን ነገር ይቀበላሉ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ጻድቅ ሰዎችን በመልካም ነገር ይባርካቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የልጅ ልጆቹ
“የወንድ ልጆቹ ወንድ ልጆች” ወይም “የልጆቹ ልጆች” ወይም “ዘሮቹ”
የኃጢአተኛ ሀብት ጽድቅን ለሚያደርጉ ይከማቻል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ኃጢአተኛ ያከማቸውን ሀብት ይቀበላል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 13:23
ያልታረሰ እርሻ
“ምግብ ለማምረት ያልተዘጋጀ እርሻ” ወይም “ዘር ለመዝራት ያልተዘጋጀ ባዶ እርሻ”
ነገር ግን በፍትህ መጓደል ምክንያት ተጠራርጎ ይወሰዳል
“ተጠራርጎ ይወሰዳል” የሚለው አንድን ነገር ሙሉ በሙሉ ማስወገድን ያመለክታል። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን የፍትህ መጓደል ያንን ምግብ ይወስደዋል” ወይም “ነገር ግን ፍትህ የማያደርጉ ሰዎች ምግቡን ይወስዱታል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በጥንቃቄ ይቀጣዋል
“እርሱን ለመገሰጽ ይተጋል”
Proverbs 13:25
ፍላጎቱን ያረካል
“ራሱን አጠገበ” ወይም “ፍላጎቱን አረካ”
የኀጥኣን ሆድ ሁልጊዜ እንደተራበ ነው
እዚህ ላይ “ሆድ” የሚለው የሰውየውን ፍላጎት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰው ሁልገዜ በጣም እንደተራበ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 14
Proverbs 14:1
ቤቷን ትሰራለች
“ቤቷን ትገነባለች” ወይም “ቤቷን የተሻለ አድርጋ ትሰራለች”
ቤት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ ቃል በቃል ቤቷን ማለትም የምትኖርበትን ሕንጻ ሊያመለክት ይችላል” ወይም 2) ቤተሰቧን ሊያመለክት ይችላል።
በራሷ እጅ
ይህች ሴት “በእጇ” ተወክላለች። አማራጭ ትርጉም፡- “በራሷ” ወይም “በባህርይዋ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ሴት … ሴት
“ብልሃተኛ ሴት … ሞኝ ሴት”
በጽድቅ ይሄዳል
“ይሄዳል” የሚለው የሰውየውን የአኗኗር ዘይቤ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕይወቱን በትክክለኛነት እና በታማኝነት ይመራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይንቀዋል
“አያከብረውም” ወይም “እንደሚጠላው ያመለክታል”
በመንገዱ ሁሉ ይንቀዋል
“በመንገዱ” የሚለው ታማኝ ያልሆነውን ሰው ያመለክታል፣ “ይንቀዋል” የሚለው ደግሞ እግዚአብሔርን ያመለክታል።
Proverbs 14:3
አፍ … ከንፈር
አፍና ከንፈር ሁለቱም ሰውየው የተናገረውን ነገር ያመለክታል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የትዕቢት ቅርንጫፍ
ቅርንጫፍ ከሌላ ነገር የሚወጣ ነገር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ትዕቢቱ የሚያመጣው ነገር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠቢባን
ይህ ቃል በእርግጥ ብዙ ቁጥር ነው። “ጥበበኛ ሰዎች” ወይም “ጥበበኛ ሕዝብ”
ትጠብቃቸዋለች
“ከጉዳት ትጠብቃቸዋለች” ወይም “በደህንነት ትጠብቃቸዋለች”
የመመገቢያ ገንዳ
“ገንዳ” ለእንስሳት መኖ የሚቀርብበት ትልቅ እቃ ነው
ብዙ ምርት
“ጥሩ ምርት”
በበሬ ጉልበት
“ጉልበት” በሬ ሊሰራ የሚችለውን ጠንካራ ስራ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሬ በሚሰራው ስራ ምክንያት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 14:5
ውሸት ይለፈልፋል
ይህ የንግግር ዘይቤ ያለማቋረጥ እንደሚዋሽ ለማሳየት “ይለፈልፋል” የሚለውን ቃል ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ ይዋሻል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ) ይህንን በምሳሌ 6:19 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
ምንም የለም
“ጥበብ በዚያ አትገኝም” ወይም “ነገር ግን ጥበብን አያገኝም”
በቀላሉ ትመጣለች
“በቀላሉ ትገኛለች” ወይም “ያለ ምንም ችግር ያገኛታል”
አስተዋይ ሰው
“ጥበበኛ የሆነ ሰው” ወይም “ግንዛቤ ያለው ሰው”
Proverbs 14:7
በከንፈሩ
“ከንፈር” የሚለው ቃል ሰውየው የተናገረውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከንግግሩ” ወይም “ከሃሳቡ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጠንቃቃ ሰው
ጥሩ ግንዛቤና አመለካከት ያለው
በመንገዱ
“መንገድ” የሚለው ቃል የሰውየውን የሕይወት ዘይቤ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ባህርዩ” ወይም “እንዴት እንደሚኖር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የሞኞች ሞኝነት ማታለል
የሞኞች ሞኝነት እነርሱ ሞኞች ሆነው ሳለ ጥበበኞች እንደሆኑ ያስባሉ።
Proverbs 14:9
የኃጢአት መስዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ
“በኃጢአት” ወይም “የኃጢአት መስዋዕት” በእነዚህ ሀረጎች በስተጀርባ ያለው ትርጉም እንዲህ የሚል ነው፡- ሞኞች ለበደሉት በደል እግዚአብሔርን ወይም ሰዎችን ይቅርታ አይጠይቁም።
በጻድቃን መካከል ግን ቸርነት ይገኛል።
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ጻድቃን ሁሉ ቸርነትን ይለማመዳሉ” ወይም “ነገር ግን የእግዚአብሔር ሞገስ በጻድቃን ሁሉ መካከል ይገለጣል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የራሱን ምሬት
“የራሱን ሃዘን” ወይም “የራሱን ጉስቁልና”
ሌላ ሰው
“እርሱን የማያውቁት”
Proverbs 14:11
ድንኳን
“ድንኳን” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ የሚከናወነውን ማንኛውንም ነገር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቤት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ያብባል
“ያብባል” የሚለው ቃል ኃይለኛ የሆነ የአበቦች መፍካት ማለት ነው፣ ስለዚህ በኃይል የሚያድጉትን ማንኛውንም ነገር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሚገባ የተሰራና ዘለቄታዊነት ያለው” ወይም “በጣም ስኬታማ መሆን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለሰው ትክክል የምትመስል መንገድ አለች
“መንገድ” የሚለው ቃል ሰው የሚከተለውን የሕይወት ዘይቤ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች የሚኖሩት የሕይወት ዘይቤ ትክክለኛው መንገድ እንደሆነ

ያስባሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 14:13
ልብ ሊስቅ ይችላል
“ልብ” የሚለው ቃል የሰውን ስሜት፣ አመለካከትና ተነሳስቶት ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የሰው ስሜት ሳቅን ሊያሳይ ይችላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በሐዘን ውስጥ መሆን
“ማዘን” ወይም “መጎዳት”
ሰው
“ያ ሰው”
ለመንገዱ የሚገባውን ዋጋ ያገኛል
“መንገድ” የሚለው ቃል የሰውን የሕይወት ዘይቤ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እንዴት እንደኖረ መሰረት በማድረግ የሚገባውን ያገኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የራሱ
“የእርሱ የሆነው” ወይም “ሊያዝዝበት የሚችለው ያለው ነገር”
Proverbs 14:15
አላዋቂ
ልምድ የሌለው ወይም ያልበሰለ አእምሮ ያለው
አካሄድ
እዚህ ላይ አካሄድ የሚለው ሃሳብ የሰውን ባህርይ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ድርጊቱ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከክፉም ይሸሻል
እዚህ ላይ ክፉ ቦታ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ አያደርግም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ራሱን ታምኖ ማስጠንቀቂያን ችላ ይላል
“በድፍረት ይንቃል”
Proverbs 14:17
ለቁጣ የሚቸኩል ነው
“በቶሎ ይቆጣል”
አላዋቂ
ልምድ የሌለው ወይም ያልበሰለ አእምሮ ያለው
ሞኝነትን ይወርሳል
እዚህ ላይ “ይወርሳል” የሚለው የአንድ ነገር ቋሚ ባለቤት መሆን ይወክላል፡፡ (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ሞኝነት
“ሞኝነት” የሚለው ቃል ሞኝ አስተሳሰብና ሞኝ ድርጊትን የሚወክል ረቂቅ ስም ነው፡፡
ጠንቃቃ ሰዎች
“ጥበበኛ ሰዎች”
እውቀትን እንደ ዘውድ ይጭናሉ
እዚህ ላይ እውቀት እንቁ እንዳለበት ጥምጥም በአንድ ሰው ጸጉር ላይ የሚደረግ ውብ ጌጥ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ጥምጥም እውቀትን ልበስ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 14:19
ይሰግዳል
ይህ በትህትና አክብሮትን ለመግለጽ መጎንበስ እና ለሌላ ሰው ራስን ማስገዛት ማለት ነው፡፡ (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
በጻድቃን በር
“በር” የሚለው ቃል ከሌላ ሰው ጋር ለመገናኘት መግቢያን ይወክላል፡፡ ይህ ማለት ክፉ ሰው ጻድቅ ወዳለበት ለመግባት እርሱን መጠበቅ እና መለመን እንዳለበት ያሳያል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከጻድቅ ሰው ጋር ለመገናኘት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ድሃ ሰው በራሱ ባልንጀሮችም ጭምር የተጠላ ነው
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ድሃ ሰው ጎረቤቶቹን ጨምሮ ሁሉም ሰው ይጠላዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 14:21
ሰው … ሰው
“ያ ሰው … ያ ሰው”
ድሃ
“ድሃ ሰው”
ክፋትን የሚያሴሩ አይስቱምን?
ለዚህ ጥያቄ የሚጠበቀው መልስ “አዎ” የሚል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፋትን የሚያሴሩ ሰዎች ይስታሉ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ክፋትን የሚያሴሩ
“ክፉ እቅድ የሚያቅዱ ሰዎች” ወይም “ክፋትን ለማድረግ የሚያቅዱ ሰዎች”
መልካምን ለማድረግ የሚያቅዱ ግን በኪዳን የተመሰረተ ታማኝነትና እውነተኛነት ይቀበላሉ
“ታማኝነት” እና “እውነተኛነት” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “ታማኝ” እና “እውነተኛ” ተብለው ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር መልካምን ለማድረግ ለሚያቅዱ ሰዎች ለከኪዳኑ ታማኝ እና እውነተኛ ለመሆኑ ራሱን ያሳያል፡፡ (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 14:23
ነገር ግን ወሬ ብቻ ሲኖር
“ነገር ግን የምታወራ ብቻ ከሆንህ” ወይም “ነገር ግን ሰው የሚሰራው ወሬ ብቻ ከሆነ”
የጠቢባን ዘውድ
“ዘውድ” የሚለው ቃል ሰው ሊደርስበት የሚችለው ከፍተኛውና ለሁሉም ሰው የሚታይ ስኬትን የሚወክል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የጠቢባን ሰዎች ወሮታ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሞኞች ሞኝነት
ይህንን እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ ምሳሌ 14:8.
Proverbs 14:25
ውሸት ይለፈልፋል
ይህ የንግግር ዘይቤ ያለማቋረጥ እንደሚዋሽ ለማሳየት “ይለፈልፋል” የሚለውን ቃል ይጠቀማል፡፡ ይህንን በምሳሌ 6:19 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ ይዋሻል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 14:26
የሕይወት ምንጭ
ምንጭ የተትረፈረፈ የውኃ ምንጭ ነው እናም በዚህ የሚወክለው የሕይወት ምንጭን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የሕወይት ምንጭ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሞት ወጥመድ
“ወጥመድ” እንስሳትን ለማደን የሚጠቅም ነገር ሲሆን የሚገድል አታላይና አደገኛ የሆነ ነገርን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከሚገድል ወጥመድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 14:28
ከሕዝቡ ብዛት
“የሚመራው ብዙ ሕዝብ”
ልዑል ይጠፋል
“ልዑል ምንም የለውም መንግስቱም ይወድቃል”
ለቁጣ የሚቸኩል
ለመቆጣት የሚፈጥን ሰው
Proverbs 14:30
ሰላም የተሞላ ልብ
“ሰላማዊ የሆነ አእምሮ” ወይም “ሰላም የሰፈነበት አመለካከት”
አጥንትን ያነቅዛል
“ያነቅዛል” የሚለው ቃል የሰውየውን መበስበስ ይወክላል “አጥንት” ደግሞ የሰውየውን ሁለንተና ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰውየውን በአካልና በመንፈስ በሽተኛ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰው … ሰው
“ያ ሰው … ያ ሰው”
መርገም
ይህ ክፉ ነገር በአንድ ሰው ላይ እንዲመጣበት ምኞትን መግለጽ ማለት ነው፡፡
ድሃ … ምንም የሌለው
“ድሃ ሰው … ምንም የሌለው ሰው”
ምህረትን የሚያደርግ

“ደግ ነው” ወይም “ይረዳል”

Proverbs 14:32

በክፉ ስራው ይወድቃል

ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ስራው ይጥለዋል” ወይም “ክፉ ስራው ያጠፋዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥበብ በልብ ትቀመጣለች

“ልብ” የሚለው ቃል የሰውን ስሜት፣ አመለካከትና ተነሳስቶት ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ በአመለካከት ውስጥ አለች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አስተዋይ

“አስተዋይ ሰው”

ራሷን ታሳውቃለች

ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች እንደሚያውቋት እርግጠኛ ትሆናለች” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እርስዋ

“እርስዋ” የሚለው ቃል ጥበብን ያመለክታል፡፡ (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 14:34

ውርደት ነው

“በማንኛውም ሰው እፍረትን ያመጣል” ወይም “ሰው ሁሉ እንዲዋረድ ታደርጋለች”

በማስተዋል የሚያደርግ

“በጥበብ የሚያደርግ” ወይም “ክፉ ነገር እንዳይመጣ እርግጠኛ የሚሆን”

ያ ሰው

“ያ አገልጋይ”

---

Chapter 15

Proverbs 15:1

የለዘበ መልስ ቁጣን ይመልሳል

አንድ ሰው ቁጣውን እንዲያቆም ማድረግ የዚያን ሰው ቁጣ መመለስ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንድ ሰው በጨዋነት መልስ መስጠት የዚያን ሰው ቁጣ ያበርዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መጥፎ ቃል ግን ቁጣን ያስነሳል

አንድ ሰው የበለጠ እንዲቆጣ ማድረግ ቁጣን ማነሳሳት ወይም ማቀጣጠል ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን መጥፎ ቃል መናገር ያንን ሰው የበለጠ እንዲቆጣ ያደርገዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጥበበኛ ሰዎች ምላስ እውቀትን ያሳምራል

እዚህ ላይ “ምላስ” የሚለው ቃል የሚናገረውን ሰው የሚያመለክት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ ሰዎች ሲናገሩ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

እውቀትን ያሳምራል

“እውቀትን ማራኪ ያደርጉታል” ወይም “እውቀትን በትክክል ይጠቀማሉ”

የሞኞች አፍ ግን ሞኝነትን ያፈልቃል

ጸሐፊው የሞኞችን አፍ የፈሳሽ መያዣ ዕቃ እንደሆነ፣ ሞኝነት ደግሞ እነርሱን የሞላቸው ፈሳሽ እንደሆነ አድርጎ ተናግሮታል፡፡ ሞኞች ሲናገሩ አፋቸው ፈሳሹን ያፈሳል፡፡ “አፍ” የሚለው ቃል የሚናገሩትን ሰዎች የሚወክል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኞች ሁልጊዜ ሞኝነትን ይናገራሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:3

የእግዚአብሔር ዓይኖች በሁሉ ስፍራ ናቸው

እዚህ ላይ “ዓይኖች” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ይወክላል ደግሞም የእርሱን ሁሉን ነገር የማየት ችሎታውን አጽንዖት ይሰጣል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ይመለከታል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉዎችንና ደጎችን

“ክፉ” እና “ደግ” የሚሉት ቃላት ሰዎችን ያመለክታሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎችና መልካም ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ፈዋሽ ምላስ የሕይወት ዛፍ ነው

“ምላስ” የሚለው ቃል ንግግርን ያመለክታል፡፡ ጸሐፊው ሌሎችን የሚያግዝና የሚያበረታታ ንግግር ስለተናገረው ሰው ሲናገር ንግግሮቹ ሕይወት የሚሰጥ ምግብ እንሚያቀርብ ዛፍ እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ቃላቶች ሕይወት እንደሚሰጥ ዛፍ ናቸው (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠማማ ምላስ ግን መንፈስን ይሰብራል

“ጠማማ ምላስ” የሚለው አታላይነት የተሞላና ጉዳት የሚያስከትል ንግግርን ያመለክታል፡፡ ጸሀፊው የተጎዳውን ወይም ተስፋ የቆረጠውን ሰው መንፈስ ቃላት እንደሰበሩት ዕቃ አድርጎ አቅርቦታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አታላይነት የተሞላ ንግግር ሰውን ተስፋ እንዲቆርጥ ያደርገዋል” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:5

ከእርምት የሚማር

“እርምት” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው ሲያስተካክለው የሚማር” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አስተዋይ ነው

“ጥበበኛ ነው”

ክፉ ሰዎች የሚያገኙት ገቢ

“ገቢ” የሚለው ቃል እንደ ግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰው የሚያካብተው ሀብት” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:7

የጠቢባን ከንፈር እውቀትን ትዘራለች

“ከንፈር” የሚለው ጠቢባን የሚናገሩትን ይወክላል፡፡ ጸሐፊው ስለ እውቀት ጠቢባን ሲናገሩ በየአካባቢው የሚዘሩት ዘር እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የጠቢባን ንግግር እውቀትን ያሰራጫል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሞኞች ልብ ግን እንዲህ አይደለም

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ልብ” የሚለው ቃል ለሞኞች ተዛምዶአዊ ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም እንደ ጠቢባን እውቀትን አይዘሩም ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኞች እውቀትን አይዘሩም” ወይም 2) ሞኞች በልባቸው ውስጥ እውቀት የላቸውም፣ እዚህ ላይ “ልብ” ለሃሳብ ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኞች እውቀትን አይረዱም” (ተዛምዶአዊ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቅን ሰዎች

“በጽድቅ የሚኖሩ ሰዎች”

በእርሱ ዘንድ የተወደደ ነው

“ያስደስተዋል”

Proverbs 15:9

እግዚአብሔር የኃጢአተኞችን መንገድ ይጠላል

የኃጢአተኞች የሕይወት ዘይቤ እነዚህ ሰዎች እንደሚሄዱባቸው መንገዶች እንደሆኑ ተደርገው ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ኃጢአተኞች የሚኖሩትን የሕይወት ዘይቤ ይጠላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጽድቅን የሚከታተለውን

ጽድቅን ለመኖር መትጋ ትክክለኛ ነገሮችን እንደመከታተል ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- በጽድቅ ለመኖር ጥረት የሚያደርግ ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገድን የሚተው ሰው

እዚህ ላይ “መንገድን” የሚለው የጽድቅ መንገድን ያመለክታል፡፡ ጽድቅን ማድረግ የተወ ሰው በትክክለኛው መንገድ መሄድን እንዳቆመ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ጽድቅን መኖር የተወ ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርምትን የሚጠላ

“እርምት” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሌሎች ሲያርሙት የሚጠላ ሰው” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:11

ሲኦልና ጥፋት በእግዚአብሔር ፊት የታወቁ ናቸው

“ሲኦልና ጥፋት” የሚሉት ቃላቶች ሁሉም የሚያመለክቱት የሙታንን መኖርያ ነው፡፡ እግዚአብሔር ስለ ሙታን መኖርያ ሁሉን ነገር ማወቁ በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሙታን ስለሚኖሩበት ስፍራ ሁሉን ነገር ያውቃል” (ጥምር ቃል እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይልቁንም የሰው ልጆች ልብማ ምንኛ የተገለጠ ይሆን?

ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እግዚአብሔር ስለ ሙታን መኖርያ ሁሉን ነገር ስለሚያውቅ፣ ስለ ሰዎች ልብ ሁሉን ነገር እንደሚያውቅ የበለጠ ግልጽ እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፦ "ስለዚህ የሰው ልጆችን ልብ በእርግጠኝነት ያውቃል!" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጆች ልብ

እዚህ ላይ "ልብ" የሚለው ቃል ሃሳብንና ተነሳስቶትን ይወክላል። "የሰው ልጆች" የሚለው ሀረግ ለሰው ዘር ሁሉ የቆመ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "የሰዎች ሃሳብ" (ምትክ ስም እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ፌዘኛ ሰው እርምትን አይወድድም

"እርምት" የሚለው ቃል በግስ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ፌዘኛ ሰው ሌሎች ሲያርሙት ይጠላል" (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ጠቢባንም አይሄድም።

የእነርሱን ምሪትና ምክር ለመፈለግ ወደ ጠቢባን እንደማይሄድ የሚያመላክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "ምክራቸውን ለመፈለግ ወደ ጠቢባን አይሄድም" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:13

ደስተኛ ልብ ፊትን ያፈካል

እዚህ ላይ "ልብ" የሚወክለው ሰውየውን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "አንድ ሰው ደስተኛ ሲሆን ፊቱ ይፈካል" (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈስን ይሰብራል

ጸሐፊው ልቡ ስለተሰበረ ሰው ሲናገር የዚያ ሰው መንፈስ እንደተሰበረ ዕቃ አድርጎ ገልጾታል። ይህንን በምሳሌ 15:4 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ "ሰውን ልቡ እንዲሰበር ያደርጋል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአስተዋይ ልብ

እዚህ ላይ "ልብ" የሚወክለው አእምሮንና ሃሳብን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "የአስተዋይ ሰው አእምሮ" ወይም "አስተዋይ ሰው" (ምትክ ስም እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞኞች አፍ ግን ሞኝነትን ይመገባል

እዚህ ላይ "አፍ" የሚወክለው ሰውየውን ነው። ጸሐፊው ሞኝ ነገሮች ስለሚፈልጉ ሞኞች ሲናገር ሞኝነትን እንደተመገቡ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ "ሞኞች ሰዎች የሚመገቡት ምግብ እንደሆነ ዓይነት ሞኝነትን ይፈልጋሉ" (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:15

የተጨቆኑ ሰዎች ቀናት በሙሉ አስቃቂ ናቸው

"የተጨቆኑ ሰዎች ቀኖቻቸው ሁሉ አስቃቂ ናቸው"

ደስተኛ ልብ ግን የማያልቅ ድግስ አለው

እዚህ ላይ "ልብ" የሚወክለው ሰውየውን ነው። ጸሐፊው ሕይወቱን በደስታ እየኖረ ሀሴት ስለሚያደርግ ሰው ሲናገር ሰውየው የማያቋርጥ ድግስ እያከበረ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ "ደስተኛ ሰው የማያልቅ ድግስ እንደደገሰ ያህል ሕይወትን በሚገባ ይኖራል" (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማያልቅ ድግስ

"የማያቋርጥ ድግስ"

ከሁከት ጋር

"ከጭንቀት ጋር"

Proverbs 15:17

የአትክልት ምግብ

አትክልት በጣም ትንሽ ምግብ ያለበትን ትንሽ ማዕድ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ትንሽ ማዕድ" ወይም "በጣም ትንሽ ምግብ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፍቅር ባለበት

"ፍቅር" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ሰዎች እርስ በርሳቸው በሚዋደዱበት" (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጥላቻ ባለበት የሰባ ጥጃ ከመብላት

ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ "አንድ ሰው በጥላቻ ከሚያቀርበው የሰባ ጥጃ ይልቅ" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰባ ጥጃ

ይህ የሚያመለክተው በሚገባ እንዲወፍር በጣም ብዙ ምግብ የተመገበ ጥጃን ይወክላል። ይ የሚወክለው በጣም ጣፋጭ ምግብ ወይም ድግስ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ "መንደላቀቅ ያለበት መዐድ" ወይም "ድግስ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከጥላቻ ጋር

"ጥላቻ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ሰዎች እርስ በርሳቸው በሚጣሉበት" (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጭቅጭቅን ያነሳሳል

ሰዎች የበለጠ እንዲጨቃጨቁ ማድረግ ጭቅጭቅን ማባባስ ወይም መቀስቀስ ተደርጎ ተነግሮአል። "ጭቅጭቅ" የሚለው ረቂቅ ስም "ተጨቃጨቀ" ተብሎ ሊገለጽ ይችላ። አማራጭ ትርጉም፦ "ሰዎች የበለጠ እንዲጨቃጨቁ ማድረግ" (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:19

የታካች ሰው መንገድ ... የቅን ሰው መንገድ

ጸሐፊው ስለ ሰው ሕይወት ሲናገር ሰውየው የሚጓዝበት መንገድ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ "የታካች ሰው ሕይወት ... የቅን ሰው ሕይወት" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የታካች ሰው መንገድ በእሾህ እንደ ታጠረ ስፍራ ነው

ጸሐፊው የታካች ሰው የሕይወት ዘይቤን በእሾህ በታጠረ ስፍራ ለመራመድ ከመሞከር ጋር ያነጻጽረዋል። ሁሉም ቢሆኑ ሰውየው እንዲሰቃይ ያደርጋሉ። አማራጭ ትርጉም፦ "የታካች ሰው ሕይወት በእሾህ በታጠረ ስፍራ ለመራመድ እንደሚሞክር ሰው ነው" (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የቅን መንገድ ግን በሚገባ የተገነባ አውራ ጎዳና ነው

ጸሐፊው ቅን ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው የሚለማመዱትን በረከት በተደላደለ መንገድ እንደሚራመዱ አድርጎ ገልጾታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሚገባ የተገነባ አውራ ጎዳና

ይህ በጣም ሰፊ፣ ለጥ ያለ እና ምንም እንቅፋት ወይም የተቦረቦረ ነገር የሌለው መንገድ ነው።

Proverbs 15:21

አስተዋይ ሰው ቀጥ ባለ መንገድ ይሄዳል

ጸሐፊው ትክክለኛውን ነገር ስለሚያደርግ ሰው ሲናገር በመንገድ ላይ ቀጥ ብሎ እንደሚሄድ ሰው አድርጎ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ "አስተዋይ ሰው ትክክለኛውን ነገር ያደርጋል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እቅድ ይበላሻል

"እቅድ አይከናወንም"

ምክር በሌለበት

"ምክር ለመስጠት አንድም ሰው በሌለበት"

አማካሪዎች

ድርጊትን በምሪት ለማከናወን ሃሳብ የሚሰጡ ሰዎች

ይከናወናል

"እቅድ ይከናወናል"

Proverbs 15:23

ተገቢ የሆነ መልስ

"የሚስማማ መልስ" ወይም "ተገቢ መልስ"

የጊዜው ቃል ምንኛ መልካም ነው

ይህ ቃለ አጋኖ በጊዜው የተነገረ ቃል በጣም መልካም እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፦ "ሰው በትክክለኛው ጊዜ የሚናገረው ቃል በጣም መልካም ነው"

የሕይወት መንገድ ወደ ላይ ይመራቸዋል ... በታች ካለው ከሲኦል

ጸሐፊው ወደ ሕይወት ስለሚወስደው የሕይወት ዘይቤን ወደላይ ወደ ሕይወት የሚሄድ መንገድ እንደሆነ፤ ወደ ሞት ስለሚወስደው የሕይወት ዘይቤን ደግሞ ወደታች ወደ ሙታን መኖርያ የሚመራ መንገድ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:25

ቤት

ይህ የሰውን ቤተሰብ፣ ንብረት እና ሀብት የሚወክል ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የደግነት ቃሎች ንጹህ ናቸው

“ደግ ቃሎች ንጹህ ናቸው” ወይም “ደስ የሚያሰኙ ቃሎች ንጹህ ናቸው”

Proverbs 15:27

ጽድቅን የሚያደርግ ሰው ልብ መልስ ከመስጠቱ በፊት አጥብቆ ያስባል

እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል ለአእምሮ እና ለሃሳብ ምትክ ስም ነው። ይህ የሚያስብን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጽድቅን የሚያደርግ ሰው መልስ ከመስጠቱ በፊት ምን መናገር እንዳለበት አጥብቆ ያስባል” (ምትክ ስም እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉ ሰዎች አፍ ክፋትን ሁሉ ያጎርፋል

ጸሐፊው ስለ ክፉ ሰዎች አፍ ሲናገር አፋቸው የፈሳሽ መያዣ ዕቃ እንደሆነና፣ ስለ ክፋት ሲናገር ደግሞ እነርሱን የሞላቸው ፈሳሽ እንደሆነ አድርጎ ተናግሮታል። “አፍ” የሚለው ቃል የሚናገሩትን ሰዎች የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ሰዎች ሁልጊዜ ክፉ ነገሮችን ይናገራሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉ ሰዎች አፍ ክፋትን ሁሉ ያጎርፋል

በአንተ ቋንቋ እነዚህን ቃላቶች ሁሉ በነጠላ ቁጥር ወይም በብዙ ቁጥር መተርጎም የበለጠ የተለመደ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የክፉ ሰው አፍ ክፋቱን ሁሉ ያጎርፋል” ወይም “የክፉ ሰዎች አፎች ክፋታቸውን ሁሉ ያጎርፋሉ”

Proverbs 15:29

እግዚአብሔር ከክፉ ሰዎች እጅግ ሩቅ ነው

ጸሀፊው ክፉ ሰዎች በአካል እግዚአብሔር ከእነርሱ እጅግ በጣም ሩቅ እንደሆነ ያህል እነርሱን እንደማይሰማቸው አድርጎ ይናራል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን አይሰማም” ወይም “እግዚአብሔር ለክፉ ሰዎች መልስ አይሰጥም“ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የዓይን ብርሃን

ጸሀፊው በአንድ ሰው ፊት የሚታየውን ደስታ ሲገልጽ የሰውየው ዓይኖች ብርሃን እንደሚፈነጥቁ አድርጎ ተናግሮታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ደስ የሚያሰኝ መግለጫ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለልብ ደስታን ያመጣል

“ልብ” የሚለው ቃል ሰውየውን ይወክላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ፍልቅልቅ ፊት ያለው ሰው ደስተኛ ይሆናል ወይም 2) ፍልቅልቅ ፊት ያለው ሰው ሲመለከቱ ሌሎች ሰዎች ደስተኛ ይሆናሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰውን ደስተኛ እንዲሆን ያደርጋል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም ወሬ ለሰውነት ጤና ነው

እዚህ ላይ “ሰውነት” የሚለው ቃል ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “መልካም ወሬ መስማት ሰውን ጥሩ ስሜት እንዲሰማው ያደርጋል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:31

በጥበበኛ ሰዎች መካከል ትቆያለህ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ሰዎች አንተ ጥበበኛ ሰው እንደሆንህ ያስቡሃል ወይም 2) ከጥበበኛ ሰዎች ጋር በመሆንህ ምክንያት ደስተኛ ትሆናለህ።

እርምትን ያደምጣል

“እርምት” የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሌሎች ሲያርሙት ያደምጣል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 15:33

የእግዚአብሔር ፍርሃት ጥበብን ያስተምራል

“ፍርሃት” እና “ጥበብ” የሚሉት ቃላቶች በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው እግዚአብሔርን ሲፈራ ጥበበኛ መሆንን ይማራል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን መፍራት

ይህንን በምሳሌ 1:7 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ትህትና ከክብር በፊት ትመጣለች

አንድ ሰው እግዚአብሔር እርሱን ከማክበሩ በፊት ያ ሰው በመጀመርያ ትህትናን መማር አለበት ማለት ነው።

---

Chapter 16

Proverbs 16:1

የልብ እቅድ የሰው ነው

እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሰውን አእምሮና ሃሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰው እቅዱን የሚያቅደው በአእምሮው ውስጥ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መልስ ከእግዚአብሔር አንደበት ይመጣል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) እግዚአብሔር ለሰው እቅድ መልስ ይናገራል፤ ይህ ተለዋጭ ዜይቤ ሲሆን የሰውን የእቅዱ ውጤት የሚወስነው እግዚአብሔር ነው የሚል ትርጉም አለው ወይም 2) ሰው ስላቀደው እቅድ ቃሎች እንዲናገር እግዚአብሔር ያስችለዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መልስ ከእግዚአብሔር አንደበት

ለንግግሩ አጽንዖት ለመስጠት ሰውየው በራሱ “አንደበት” ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ የሚናገረው መልስ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንድ ሰው መንገዶች በሙሉ በራሱ ዓይኖች ንጹህ ናቸው

ዓይኖች መመልከትን ይወክላሉ፤ መመልከት ደግሞ ሃሳብን ወይም ውሳኔን ይወክላል። ጸሐፊው ሰው ስለሚሰራው ስራ ሲናገር ያ ሰው በመንገድ ወደታች እየተጓዘ እደነበር አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰው የሚሰራው ስራ ሁሉ ንጹህ እንደሆነ ያስባል” ወይም “ሰው የሚሰራው ስራ ሁሉ ንጹህ እንደሆነ ይገምታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር መንፈስን ይመዝናል

እዚህ ላይ “መንፈስ” የሚለው ቃል የሰዎችን ምኞትና ተነሳስቶት ይወክላል። ጸሐፊው እግዚአብሔር የሰውን ምኞትና ተነሳስቶት እንደሚለይና እንደሚያውቅ ሲናገር እርሱ የዚያን ሰው መንፈስ እንደሚመዝን አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የሰውን ተነሳስቶት ይመዝናል” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:3

ሃጢአተኛውንም እንኳ ለክፉ ቀን

ይህ በሀረግ የተገለጸ የቃላት አገባብ የመጣው ምናልባት ከቀደመው ሀረግ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ኃጢአተኛውን እንኳ ለመከራ ቀን አዘጋጅቶታል” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:5

እምቢተኛ ልብ ያለውን ሁሉ

እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እምቢተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሳይቀጡ አይቀሩም

በዚህ ሀረግ ውስጥ ያሉት ሁለት አሉታዊ አገላለጾች አዎንታዊውን አጥብቀው አጽንዖት ይሰጣሉ። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር በእርግጠኝነት ይቀጣቸዋል” (ምፀት እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በኪዳን በተመሰረተ ታማኝነትና እውነተኛነት ኃጢአት ስርየት ያገኛል

“ታማኝነት” እና “እውነተኛነት” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “ታማኝ” እና “እውነተኛ” ተብለው ሊገለጹ ይችላሉ። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ለኪዳኑ ታማኝና እውነተኛ ስለሆነ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ይላል” ወይም 2) አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ለኪዳኑ ታማኝና እውነተኛ ለሆኑ ሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ይላል” (ረቂቅ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎች ከክፋት ይርቃሉ

ጸሐፊው ክፉ ነገሮችን መስራት ስላቆሙ ሰዎች ሲናር ከክፋት እንደራቁ አድርጎ ገልጾቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች ክፋትን መስራት አቁመዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:7

ያደርጋል

“እግዚአብሔር ያደርጋል”

ትልቅ ገቢ

“ብዙ ገንዘብ ማግኘት”

ፍትህ በጎደለው

“ክፉ ስራ በመስራት”

Proverbs 16:9

ሰው በልቡ መንገዱን ያቅዳል

እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሰውን አእምሮ እና ሀሳብ ይወክላል። ጸሐፊው

ሰውየው ስለሚሰራው ስራ ሲናገር ያ ሰው በመንገድ እየተጓዘ እደነበር አድርጎ ገልጾታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው የሚሰራውን ስራ በአእምሮው ውስጥ ያቅዳል” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር እርምጃውን ያቀናለታል
ጸሐፊው የሰውን የእቅዱ ውጤት የሚወስነው እግዚአብሔር እንደሆነ ሲገልጽ እግዚአብሔር ለዚያ ሰው ወዴት መሄድ እንዳለበት እየነገረው እንደነበር አድርጎ ገልጾታል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማስተዋል የተሞሉ ውሳኔዎች በንጉስ ከንፈሮች ላይ አሉ
እዚህ ላይ “ከንፈሮች” የሚለው ቃል ንጉስ ለተናገረው ንግግር ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉስ የሚናገረው ንግግር ማስተዋል የተሞላበት ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በፍርድም ጊዜ አፉ በማታለል አይናገርም፡፡
“አፍ” የሚለው ቃል ንጉሱን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ሲፈርድ በማታለል ሊናገር አይገባውም” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 16:11
እውነተኛ ሚዛን ከእግዚአብሔር ይመጣል
የንግድ ስራ ስንሰራ እግዚአብሔር ፍትህና ትክክለኛነት እንድናደርግ ይጠብቅብናል፡፡ አታላይ ሰዎች ከሚገባው በላይ ለማትረፍ ሲሉ ሲገዙና ሲሸጡ በሚዛናቸው ከባድ ወይም ቀላል ክብደት ይጠቀማሉ፡፡ (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በቦርሳ ውስጥ ያሉት መመዘኛዎች ሁሉ የእርሱ ስራዎች ናቸው
ነጋዴዎች መመዘኛዎቻቸውን በቦርሳ ውስጥ ይይዛሉ፡፡ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) እግዚአብሔር እያንዳንዱ ክብደት ምን ያህል ሊመዝን እንደሚገባ ወስኗል ወይም 2) እግዚአብሔር ነጋዴ በሚጠቀምበት እያንዳንዱ ክብደት ግድ ይለዋል፡፡
ጸያፍ ነገር ነው
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ሰዎች የሚጸየፉት ነገር ነው” ወይም “ይህ እግዚአብሔር የሚጸየፈው ነገር ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ዙፋን የሚጸናው ጽድቅን በማድረግ ነውና
እዚህ ላይ “ዙፋን” የሚለው ቃል የንጉሱን አመራር የሚወክል ነው፡፡ ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉስ አመራሩን የሚመሰርተው ጽድቅን በማድረግ ነው” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 16:13
እውነትን የሚናገሩ ከንፈሮች
እዚህ ላይ “ከንፈሮች” የሚወክሉት የሚናገረውን ሰው ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እውነትን የሚናገር ሰው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
የንጉስ ቁጣ የሞት መልእክተኛ ነው
ጸሐፊው አንድን ሰው እንዲገደል ያደረገ ንጉስን ሲገልጽ የንጉሱ ቁጣ አንድን ሰው ለመግደል የላከው መልእክተኛ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የተቆጣ ንጉስ ሰዎች እንዲገደሉ ማድረግ ይችላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 16:15
አጠቃላይ መረጃ፡-
ቁጥር 15 ከቁጥር 14 ጋር ያነጻጽራል፡፡
የንጉስ ፊት ሲያበራ ሕይወት አለ
ጸሐፊው በንጉሱ ፊት የሚገለጠውን የደስተኝት ስሜት ፊቱ ብርሃን እንደሚፈነጥቅ አድርጎ ተናግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉሱ ደስተኛ ሲሆን ሰዎች በሕይወት ይኖራሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መልካም ፈቃዱም የጸደይን ዝናብ እንደሚያመጣ ደመና ነው
ጸሐፊው ንጉሱ ለአንድ ሰው ሞገሱን ማሳየቱ የተዘራ እህል ማደግ እንዲችል ዝናብ እንዲመጣ ከሚያደርግ ደመና ጋር አነጻጽሮታል፡፡ ሁለቱም ለሚቀበላቸው በረከት ያስገኙላቸዋል፡፡ (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከወርቅ ይልቅ ጥበብን ማግኘት ምንኛ ይበልጣል
ይህ ቃለ አጋኖ ጥበብ ማግኘት ወርቅ ከማግኘት እጅግ በጣም እንደሚበልጥ አጽንዖት ይሰጣል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብን ማግኘት ወርቅ ከማግኘት እጅግ በጣም ይበልጣል” (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)
ማስተዋል ማግኘት ከብር ይልቅ ሊመረጥ ይገባዋል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው ማስተዋልን ማግኘት ብርን ከማግኘት ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊመርጥ ይገባዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 16:17
የጻድቃን መንገድ
ጸሐፊው የጻድቃንን የሕይወት ዘይቤ እንቅፋት የሌለበት በሚገባ የተገነባ መንገድ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ጻድቃን የሚኖሩት የጽድቅ መንገድ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከክፋት ትርቃለች
ጸሐፊው ክፋትን መተው ወይም ክፉ ነገሮችን አለማድረግን ከክፋት መራቅ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፋትን ከማድረግ ይጠብቃቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ኩሩ መንፈስም
እዚህ ላይ “መንፈስ” የሚለው ቃል የሰውየውን መለካትና ባህርይ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ግትር አመለካከት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ውድቀት
“ጥፋት” ወይም “አለመሳካት”
Proverbs 16:19
ምርኮ
በጦርነት ጊዜ የተወሰዱ እቃዎች
የተማሩት ነገር
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ያስተማራቸው ነገር” ወይም “የተማሩት ነገር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 16:21
በልቡ ጥበበኛ የሆነ ሰው አስተዋይ ይባላል
ይህ ሰው አስተዋይ ሰው የሚል መልካም ስም ይኖረዋል፡፡ ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች በልቡ ጥበበኛ የሆነውን ሰው አስተዋይ ይሉታል” ወይም “በልቡ ጥበበኛ የሆነ ሰው አስተዋይ ሰው የሚል መልካም ስም ይኖረዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በልቡ ጥበበኛ የሆነው ሰው
እዚህ ላይ ልብ አእምሮንና ሃሳብን የይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ የሆነ ሰው” ወይም “በአስተሳሰቡ ጥበበኛ የሆነ ሰው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጣፋጭ ንግግር
ጸሐፊው ስለ መልካም ወይም ደስ የሚያሰኝ ንግግር ሲናገር ጣፋጭ ጣዕም እንዳለው ነገር አድርጎ አቅርቦታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ንግግር” ወይም “ደስ የሚያሰኝ ንግግር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማስተዋል የሕይወት ምንጭ ነው
ጸሐፊው ስለ “ማስተዋል” ሲናር ያለማቋረጥ የሚፈስ ውኃ እንዳለውና ከእርሱ ለሚጠጡ ሰዎች በሕይወት እንዲኖሩ እንደሚያደርግ ምንጭ አድርጎ ገልጾታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ማስተዋል እንደሚፈስ የሕይወት ውኃ ምንጭ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 16:23
የጥበበኛ ሰው ልብ … ይሰጣል
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል አእምሮንና ሃሳብን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የጥበበኛ ሰው ሃሳብ … ይሰጣል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ለአፉ ትምህርትን ይሰጠዋል
እዚህ ላይ “አፍ” የሚለው ቃል ለንግግር ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ንግግሩን ጥበብ የተሞላ ያደርገዋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ለከንፈሮች
እዚህ ላይ “ከንፈሮች” የሚለው ቃል ለንግግር ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለሚናገረው ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ደስ የሚያሰኙ ቃላት የማር ወለላ ናቸው
ጸሐፊው ደስ የሚያሰኙ ቃላት ለሰሚዎች ደስታን ማምጣት የሚችሉ እንደሆኑ ሲናገር እነዚህ ቃላት አዲስ ማር የሚያንጠባጥቡ የማር እሸት እነደሆኑ አድርጎ ገልጾታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ደስ የሚያሰኙ ቃላት እንደ ማር እሸት ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለነፍስ የሚጣፍጡ
“ነፍስ” ለሚለው ቃል ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፡- 1) ይህ የሰውን ውስጣዊ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ምኞትና ደስታ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሰውን ደስ ለማሰኘት በጣም ጣፋጭ ናቸው” ወይም 2) “ጉሮሮ” ማለት ሊሆን ይችላል፣ ይህ ደግሞ የሰውን ምላስና ጣዕም የመለየት ችሎታውን የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ለሰው ጣፋጭ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለአጥንቶችም ፈውስ ናቸው

እዚህ ላይ “አጥንቶች” የሚለው ቃል የሰውን አካል የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ለሰውነትም ፈውስ ናቸው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:25

ለሰው ትክክል የሚመስል መንገድ አለ

ጸሐፊው ስለ ሰው ጠባይ ወይም ባህርይ ሲናገር ሰውየው የሚኳዝበት መንገድ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- “ሰው የሚኖርበት መንገድ ትክክል እንደሆነ ያስባል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፍጻሜው ግን ወደ ሞት የሚወስድ ነው

“ፍጻሜው” የሚለው ቃል የሚያያዘው በቀደመው መስመር ላይ ከተጠቀሰው “መንገድ” ከሚለው ጋር ነው።

የሰራተኛ ረሃብ ለእርሱ ይሰራል

ጸሐፊው ስለ ረሃብ ሲናገር የቀን ሰራተኛውን ወክሎ የሚሰራ ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። ይህም የሚሰራ ሰው ለመብላት ባለው ፍላጎት ይነሳሳል ለማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ሰራተኛ የምግብ ፍላጎቱን ለማርካት ይሰራል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ረሃቡም ያነሳሳዋል

ጸሐፊው ስለ “ረሃብ” ሲናገር ስራውን በሚገባ እንዲሰራ ሰራተኛውን የሚያነሳሳ ሰው እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- “እርሱ ስራውን ሳያቋርጥ ይሰራል ምክንያቱም ርቦታል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:27

የማይረባ ሰው ክፋትን ይቆፍራል

ጸሐፊው ሌሎች ሰዎችን ለመጉዳት መንገድ ለመፈለግ ስለሚሞክር ሰው ሲናገር ያ ሰው አንድ የተቀበረ ነገር ለመፈለግ መሬት እየቆፈረ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- “የማይረባ ሰው አንድ ነገር ለማግኘት መሬት እንደሚቆፍር እንደዚሁ ክፋትን ይፈልጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማይረባ

“የማይጠቅም” ወይም “ክፉ”

ክፋት

መከራ

ንግግሩ እንደሚያቃጥል እሳት ነው

ጸሐፊው የዚህ ሰው ቃላት ሌሎች ሰዎችን የሚጎዳበት መንገድ እሳት ቁሳቁሶችን ከሚያቃጥልበት መንገድ ጋር አነጻጽሮታል። አማራጭ ትርጉም:- “እሳት የሚነካውን ማንኛውንም ነገር እንደሚያቃጥል ሁሉ እንደዚሁ ይህ ሰው በቃሎቹ ሰዎችን ይጎዳል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሉባልተኛ

ሀሜት የሚናገር ወይም ወሬ የሚያሰራጭ ሰው

Proverbs 16:29

በጥባጭ ሰው ጎረቤቱን ይዋሻል

ይህ ሰው ብጥብጥ በመፍጠር ስራው ጎረቤቱ ከእርሱ ጋር እንዲተባበር ለማድረግ ጎረቤቱን ይዋሸዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “በጥባጭ ሰው ጎረቤቱን ያባብላል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የብጥብጥ ሰው

“በጥባጭ ሰው” ወይም “የሚረብሽ ሰው”

መልካም ወዳልሆነ መንገድ ይመራዋል

ጸሐፊው የሰውየውን ድርጊት ሰውየው የሚኳዝበት መንገድ እንደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- “መልካም ያልሆኑ ነገሮችን በማድረግ ያገኘዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም ያልሆነ መንገድ

ጸሐፊው ይህ መንገድ ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ዝቅ አድርጎ የሚያሳይ መግለጫ ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም:- “በጣም መጥፎ መንገድ” ወይም “አስከፊ መንገድ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በዓይኑ የሚጠቅስ ሰው … ከንፈሮቻቸውን የሚነክሱ

እነዚህ ሁለቱም ሰዎች ዕቅዳቸውን ለሌች በስውር ለማስተላለፍ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉአቸው የፊት እንቅስቃሴዎች ናቸው።

ክፋትን ይጎትታሉ

“ክፉ ነገሮችን ያደርጋሉ”

Proverbs 16:31

ሽበት የክብር ዘውድ ነው

ጸሐፊው ስለ ሽበት ሲናገር ዘውድ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። “ሽበት” ለእርጅና ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ሽበት ለማውጣት የደረሰና ለረጅም ዘመን የኖረ ሰው በራሱ ላይ የክብር ዘውድ እንደጫነ ሰው ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይገኛል

ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሰው ያገኘዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈሱን የሚገዛ ሰው

ጸሐፊው ግልፍተኝነቱንና ስሜቱን ስሚቆጣጠር ሰው ሲናገር ንጉስ ሕዝቡን እንደሚመራ እንደዚሁ መንፈሱን እንደሚመራ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- “ግልፍተኝነቱን የሚቆጣጠር ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 16:33

እጣ በጉያ ይጣላል

ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሰው እጣውን በጉያው ይጥላል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ውሳኔው ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) እጣ እንዴት እንደሚወድቅ የሚወስነው እግዚአብሔር ነው ወይም 2) ምን እንደሚሆን የሚወስነው እጣው ሳይሆን እግዚአብሔር ነው።

---

Chapter 17

Proverbs 17:1

ጸጥታ ያለበት

እዚህ ላይ ”ጸጥታ” የሚወክለው “ሰላም” ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ሰላም ያለበት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጥል ባለበት ግብዣ ከሞላበት ቤት ይልቅ

“ከሞላበት” የሚለው ቃል ከፊተኛው ሀረግ መረዳት ይቻላል። ሊደጋገሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- “ጥል ባለበት ትልቅ ድግስ ከሞላበት ቤት ይልቅ” ወይም “ጥል ባለበት ትልቅ ድግስ በሞላበት ቤት ከመገኘት ይልቅ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 17:3

ማቅለጫ ለብር ነው እቶንም ለወርቅ ነው

ይህ ወርቅና ብር እንዴት እንደሚነጥሩ የሚያሳይ ነው። ብረት መቅለጥ እንዲችልና በውስጡ ያለው ቆሻሻ እንዲወገድ የሚነጥረው እጅግ በጣም ሀይለኛ በሆነ የሙቀት ሃይል በማሞቅ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ማቅለጫ ብር ለማንጠር ይጠቅማል፣ እቶን ደግሞ ወርቅ ለማንጠር ይጠቅማል” ። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ማቅለጫ

በጣም ከፍተኛ በሆነ ሙቀት ብረት የሚቀልጥበት ማሰሮ ነው።

እግዚአብሔር ልብን ያነጥራል

ይህ የሰዎች ልብ ብረት እንደሆነ ያህል እነርሱ ክፉ እና ሞኝ መሆንን እንዲያቆሙ በሕይወታቸው ያለውን ማንኛውንም ቆሻሻ ለማስወገድ ሲል እግዚአብሔር ሰዎችን በማንጠር እንደሚፈትናቸው አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር የሰዎችን ልብ ይፈትናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ከንፈሮች

እዚህ ላይ “ከንፈሮች” የሚለው ቃል በሚከተሉት መንገድ ሊተረጎም ይችላል:- 1) ለሰው ተዛምዶአዊ ነው ወይም 2) ከእነዚህ ከንፈሮች ለሚወጡት ቃላት ደግሞ ምትክ ስም ነው አማራጭ ትርጉም:- “ክፉ ሰው” ወይም “ክፉ ንግግር” (ተዛምዶአዊ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጆሮውን ይሰጣል

ይህ ፈሊጥ ሲሆን “ማዳመጥ” የሚል ትርጉም አለው። (ፈሊጥ የሚለውን



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይመልከቱ)
ጥፋት የሚያደርስ ምላስ
“ምላስ” የሚለው ቃል እንደሚከተለው ሊተረጎም ይችላል፡- 1) ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው ወይም 2) ምላሱ ለሚፈጥረው ቃላት ደግሞ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አጥፊ ሰው” ወይም “አጥፊ ንግግር” (ተዛምዶአዊ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 17:5
ድሃr
ይህ ድሃ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሃ የሆኑ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ፈጣሪውን
ይህ እግዚአብሔርን የሚያመለክት ስም ነው። ይህ እንደ ግስ ሊጻፍ የሚችል ረቂቅ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የፈጠረው” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በጥፋት
ይህ የሌሎችን ጥፋት የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሌሎች ጥፋት” ወይም “በሌሎች ሰዎች መከራ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ዘውድ ናቸው
ይህ የትልልቅ ሰዎች የልጅ ልጆች ለእነርሱ የክብር ምልክት ስለመሆናቸው ሲናገር የልጅ ልጆቻቸው ዘውድ እንደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኩራትና ክብር ያመጡላቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሽማግሌዎች
ይህ ትልልቅ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትልልቅ የሆኑ ሰዎች” ወይም “ትልልቅ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 17:7
ልብ የሚነካ ንግግር
“መልካም ንግግር” ወይም “እጅግ በጣም ጥሩ ንግግር”
ውሸታም ከንፈሮች ለንጉሳውያን አይመቹም
ይህ የሚዋሹ ሰዎች ውሸትን የሚናገሩት የእነርሱ “ከንፈሮች” እንደሆኑ አድርጎ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለንጉሳውያን ቤተሰብ መዋሸት ይልቁንም ደግሞ መልካም ኤደለም” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ጉቦ ለሰጪው እንደ አስማት ድንጋይ ነው
ይህ ጉቦ መስጠትን ከአስማት ድንጋይ ወይም ከክታብ ጋር በማነጻጸር ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጉቦ ለሰጪው እንደ አስማት ድንጋይ ይሰራል” ወይም “ጉቦ ለሰጪው እንደ አስማት ይሰራል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በሄደበት ስፍራ ሁሉ
እዚህ ላይ “በሄደበት” የሚለው ሰው የሚሰራውን የተለያዩ ነገሮች ያመለክታል። በተለይ ደግሞ ይህ አንድ ሰው በጉቦ ምክንያት የሚሰራቸውን የተለያዩ ነገሮችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሚሰራው ስራ ሁሉ” ወይም “ጉቦ በመስጠት ለመስራት የሚሞክረውን ማንኛውንም ነገር“ (ፈሊጥ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 17:9
ጥቃት
እርሱን የሚጎዳው ድርጊት ወይም ቃል
ነገርን የሚደጋግም
ይህ አንድ ጓደኛ የተጎዳበትን ወይም የተናደደበትን ያለፈ ሁኔታን አሁን ጎትቶ ማምጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ያለፈ ጉዳትን የሚደግም ሰው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የቅርብ ወዳጆችን ይለያያል
“ሰዎች የቅርብ ጓደኞች መሆናቸውን እንዲያቆሙ” ወይም “የቅርብ ጓደኞች እርስ በርስ መዋደዳቸውን እንዲያቆሙ”
መቶ ግርፋት በሞኝ ጠልቆ ከሚገባ ይልቅ ተግሣጽ በአስተዋይ ሰው ጠልቆ ወደ ልቡ ይገባል።
ይህ ተግሳጽ በአስተዋይ ሰው ውስጥ እንዴት ውጤት እንደሚያመጣ እና ግርፋት ደግሞ በሞኝ ሰው ውስጥ እንዴት ውጤት እንደሚያመጣ ያነጻጽራል። ይህ በእነዚህ ሰዎች ውስጥ የሚመጣው ውጤት ወደ እነርሱ ውስጥ ጠልቆ በሚገባበት መጠን ሊለካ እንደሚችል አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “መቶ ግርፋት በሞኝ ውስጥ ከሚያመጣው ውጤት ይልቅ ተግሣጽ በአስተዋይ ሰው ውስጥ የበለጠ ውጤት አለው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አስተዋይ ሰው
“ጥሩ ግንዛቤ ያለው ሰው። “ማስተዋል” የሚለው ቃል በግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚያስተውል ሰው” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
መቶ ግርፋት ይገባል
“መቶ የግርፋት ምት ይገባል”
Proverbs 17:11
አመጽን ይፈልጋል
“አመጽ” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለማመጽ ይፈልጋል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጨካኝ መልዕክተኛም ወደ እርሱ ይላክበታል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጨካኝ መልዕክተኛም ወደ እርሱ ይመጣበታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ እርሱ ይላክበታል
ወደ አንድ ሰው “ይላክበታል” የሚለው እርሱን ለመጉዳት ይላካል ለማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱን ለመጉዳት ይላካል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ግልገሎቿ የተነጠቀች ድብ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ግልገሎቿ የጠፉባት ድብ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በሞኝነቱ
“ሞኝነት” የሚለው ቃል በቅጽል ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ተግባር የሚፈጽም” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 17:13
ክፋት ከቤቱ ፈጽሞ አይርቅም
እዚህ ላይ “ክፉ” የሰውየውን ቤት የማይለቅ ሰው እንደሆነ ተደርጎ ተገልጿል። “ቤት” የሚለው ቃል በቁሙ መኖርያ በሚለው ሊተረጎም ይችላል ነገር ግን ለቤተሰቡም ምትክ ስም ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእርሱና በቤተሰቡ ላይ መጥፎ ነገሮች መፈጸም ይቀጥላል” ወይም “መጥፎ ነገሮች በእርሱና በቤተሰቡ ላይ ከመፈጸም በፍጹም አይከለከልም” (ሰውኛ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የጠብ መጀመርያ በሁሉም ስፍራ ውኃ እንደሚለቅ ሰው ነው
ይህ ጠብ በቀላሉ እንዴት እንደሚሰራጭ እና የፈሰሰ ውኃ በሁሉም ስፍራ እንዴት እንደሚፈስ ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠብ መጀመር ውኃን እንደ መልቀቅና በሁሉም ስፍራ እንዲፈስ እንደማድረግ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይበረታል
“ይጀምራል” ወይም “ይነሳል”
Proverbs 17:15
ክፉ ሰዎችን ነጻ የሚለቅም ሆነ ጽድቅን የሚያደርጉትን ደግሞ የሚኮንን ማንኛውም ሰው
“ክፉ ሰዎችን ነጻ የሚለቅ ሰው እና ጽድቅን የሚያደርጉትን የሚኮንን ሰው”
በነጻ የለቀቀ
ተገቢ የሚያስመስል፣ ወንጀለኛ እንዳልሆነ የሚያውጅ
ሞኝ ጥበብን ለመማር የማይችል ሆኖ ሳለ፣ ጥበብን ለመማር ለምን ገንዘብ ይከፍላል?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ሞኝ ይህን ማድረግ እንደሌለበት አጽንዖት ይሰጣል። ይህ ጥያቄ እንደ አረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ስለ ጥበብ ለመማር ገንዘብ ሊከፍል አይገባውም ምክንያቱም ጥበብን ለመማር ችሎታ የለውም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 17:17
ወንድምም ለመከራ ቀን ይወለዳል
የወንድም አንዱ ዓላማ ወንድሙን ወይም እህቱን በመከራ ጊዜ ለመርዳት አብሮ ለመሆን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወንድም ለመከራ ጊዜ በዚያ ይገኛል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አእምሮ የጎደለው
“ጥሩ ግንዛቤ የሌለው”
ግዴታ የሚያስገባ ቃልኪዳን
ይህ መጠበቅ ያለባቸውና ቃል ለገባው ሰው ደግሞ ብዙ ጊዜ ሸክም የሚሆኑ ቃል ኪዳኖችን የሚያመለክት ነው።
Proverbs 17:19
አጥንቶች እንዲሰበሩ ያደርጋል
ይህ አንድ ሰው ወደ መግቢያ በር ይሄድና አጥንት ምናልባትም የእግር አጥንት ይሰብራል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- ““አንድ ሰው እንዲሄድና የእግራቸውን አጥንት እንዲሰብር በእርግጠኝነት ያደርጋል” ወይም “አንድ ሰው እንዲሄድና ራሱን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንዲጎዳ በእርግጠኝነት ያደርጋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠማማ ልብ ያለው ሰው
“ልብ” የሰውን ስሜት፣ አመለካከትና ተነሳስቶት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አታላይ ሰው” ወይም “የማይታመን ሰው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጠማማ ምላስ አለው
“ምላስ” የሰውየውን ንግግር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጠማማነት ይናገራል” ወይም “በክፋት ይናገራል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
አደጋ ውስጥ ይወድቃል
“መከራ ውስጥ ይወድቃል” ወደ አንድ ነገር “መውደቅ” ማለት ወደዚያ ሁኔታ ውስጥ መግባት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አደጋ ያገኘዋል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 17:21
ደስተኛ ልብ ጥሩ መድሃኒት ነው
ይህ ስለ ደስተኛ ልብ ሲናገር እንደ ጥሩ መድኃኒት እንደሆነ ገልጾታል ምክንያቱም እድትፈወስ ያደርግሃል። አማራጭ ትርጉም፡- “ደስተኛ ልብ እድትፈወስ እንደሚያደርግ እንደ ጥሩ መድኃኒት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ደስተኛ ልብ
“ልብ” የሰውን ስሜት፣ አመለካከትና ተነሳስቶት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ደስተኛ መሆን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የተሰበረ መንፈስ
እዚህ ላይ “መንፈስ” የሰውን ጥልቅ ስሜትና ስሜታዊ ሁኔታ ይወክላል። የተሰበረ መንፈስ ደካማ ስሜታዊ ሁኔታን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ድብርት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
አጥንትን ያደርቃል
የሰው አጥንት የሰውየውን አካላዊ ጤንነትና ጥንካሬ ይወክላል። የሰው አጥንት ከደረቀ በጣም የታመሙና ጤንነት የሌላቸው ናቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰውን በሽተኛና ደካማ ያደርጋሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 17:23
የፍትህን መንገድ ለማጣመም
“ፍትህ እንዳይተገበር ማጣመም” ወይም “ፍትህን ማጣመም”
ፊቱን ወደ ጥበብ ያዘነብላል
ይህ የሚናገረው ጥበብን ከማድረግ አቅጣጫ ስለ ሰውየው ትኩረት ሲሆን ያ ሰው ጥበብን ይመለከት እንደነበር አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥበብ ማከናወን ላይ ትኩረት ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሞኝ አይኖች … ናቸው
ይህ ሞኝን በዓይኖቹ አማካይነት የሚያመለክት ሲሆን በምን ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ አጽንዖት ለመስጠት የቀረበ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ … ነው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
የምድር መጨረሻ
ይህ ተግባራዊነት ስለሌላቸው የሞኝ ሕልሞች የሚናገር ሲሆን ተጨባጭነት እንደሌላቸው አጽንዖት ለመስጠት የምድር መጨረሻ ላይ እንደሆኑ አድርጎ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእርሱ ዘንድ የምድር መጨረሻ ያህል የራቁትን ነገሮች ለማግኘት ጥረት ያደርጋል” ወይም “በማይሆንና በማይቻል ነገር ላይ ትኩረት ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 17:25
ሞኝ ልጅ ለአባቱ ሐዘን ነው
ይህ ለአባቱ የሐዘን ምክንያት ስለሆነ ልጅ የሚናገር ሲሆን ልጁ ራሱ “ሐዘን” እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ልጅ ለአባቱ ሐዘን ያመጣል”
ሞኝ ልጅ … ለወለደችውም እናቱ ምሬትን ያመጣል
ይህ ለእናቱ የምሬት ምክንያት ስለሆነ ልጅ የሚናገር ሲሆን ልጁ ራሱ “ምሬት” እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ልጅ … ለእናቱ ምሬትን ያመጣል”
ለወለደችው
“እርሱን ለወለደችው”
ምሬት
ስሜታዊ ጉዳት፣ ሐዘን
በፍጹም መልካም አይደለም … መልካምም አይደለም
እነዚህ ሃሳቦች በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ሁልጊዜ ስህተት ነው …. ይህ ሁልጊዜም ክፉ ነው” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
ጻድቅ ሰው
የዚህ ሌላኛው ተቀባይነት ያለው ትርጉም የሚከተለው ነው፡- “ንጹህ ሰው” ባልሰራው ወንጀል ሌሎች እንደፈጸመ አድርገው የሚወነጅሉት ማንኛውም ሰው ነው።
መግረፍ
በአሰቃቂ ሁኔታ መምታት
በሐቀኝት የሚሄድ
“ሐቀኝነት” የሚለው ቃል “ታማኝ” በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ታማኝ የሆኑ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 17:27
ጥቂት ቃላትን ይናገራል
ይህ የሚናገርበትን መንገድ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥቂት ቃላት ይናገራል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሞኝ እንኳ እንደ ጥበበኛ ይቆጠራል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ሞኝ እንኳ ጥበበኛ እንደሆነ ያስባሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
አፉንም ዘግቶ ዝም ሲል
ይህ አይናገርም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አይናገርም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ምሁር እንደሆነ ይታሰባል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ምሁር እንደሆነ ያስቡታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 18
Proverbs 18:1
ራሱን ይለያል
“ከሌሎች ሰዎች ራሱን ይለያል”
ትክክለኛውንም ፍርድ ሁሉ ይቃወማል
ይህ ትክክለኛውን ፍርድ ስለሚቃወም ሰው የሚናገር ሲሆን “ትክክለኛ ፍርድ” ከእርሱ ጋር እንደሚዋጋ ሰው ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ከትክክለኛ ፍርድ ሁሉ ጋር አይስማማም” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ትክክለኛውን ፍርድ
“መልካም ፍርድ” ወይም “ጥበብ የተሞላበት ምርጫ”
ሞኝ ሰው በማስተዋል ደስታን አያገኝም፣ … እንጂ
“ሞኝ ሰው ስለ ማስተዋል ፈጽሞ አይገደውም፣ ነገር ግን ስለ … እንጂ” ይህ ሞኝ “ማስተዋልን” የደስታ ተቃራኒ እንደሆነ ያስባል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ማስተዋል ይጠላል እናም ደስታን ብቻ ይፈልጋል” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
በራሱ ልብ ውስጥ ያለውን ነገር በመግለጥ እንጂ
ይህ ማለት ሞኝ ሰው ደስታ የሚያገኘው ለሌሎች ሰዎች በልቡ ምን እንደሚሰማውና ምን እንደሚመኝ በመንገር ብቻ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ለሌሎች በልቡ ውስጥ ያለውን በመናገር ብቻ ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በልቡ ውስጥ ያለውን
በሰው ልብ ውስጥ ያለው ነገር የሰውየውን ሃሳብና ስሜት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚያስበውን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 18:3
ንቀት ከእፍረትና ከስድብ ጋር አብረውት ይመጣሉ
እዚህ ላይ “ንቀት፣” “እፍረት፣” እና “ስድብ” ክፉ ሰውን የሚያጅቡት ሰዎች እንደሆኑ ተደርገው ተገልጸዋል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ሰዎች ለክፉ ሰው ንቀት ያሳያሉ ከዚህ የተነሳ እፍረትና ስድብ እንዲሰማው ያደርጋሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ስለ እርሱ ከእፍረትና ከስድብ ጋር ንቀት ይሰማቸዋል” ወይም 2) ክፉ ሰው ለሌሎች ንቀት ያሳያል ከዚህ የተነሳ እፍረትና ስድብ እንዲሰማቸው ያደርጋል” አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ለሌሎች ሰዎች ያለውን ንቀቱን ያሳያል ከዚህ የተነሳ እፍረትና ስድብ እንዲሰማቸው ያደርጋል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እፍረትና ስድብ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ሁለቱም በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት ክፉው ሰው ወይም ደግሞ ሌሎች ሰዎች የተሰማቸውን "እፍረት" አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ከሰው አፍ የሚወጡ ቃላት ጥልቅ ውሃ ናቸው፤ የጥበብ ምንጭም የሚፈስ ወንዝ ነው
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሳሳይ ናቸው፣ በመጀመርያው መስመር ላይ ያለው ሰው ጥበበኛ እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- "ከጥበበኛ ሰው የሚወጡ ቃላት ጥልቅ ውኃ ናቸው፤ የጥበብ ምንጭም የሚፈስ ወንዝ ነው" (ትይዩነት እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሰው አፍ የሚወጡ ቃላት ጥልቅ ውሃ ናቸው
ይህ የሚናገረው የጥበበኛ ሰው ቃላት ጥልቅ እውቀት የሚገለጥባቸው እንደሆኑ ሲሆን በጣም ጥልቅና እንደ ጥልቅ ውኃ የጠለቁ እንደሆኑ ተደርገው ተገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- "ከሰው አፍ የሚወጡ ቃላት እንደ ጥልቅ ውኃ የጠለቁ ናቸው" ወይም "ከሰው አፍ የሚወጡ ቃላት ጥልቅና እውቀት ያለባቸው ናቸው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው አፍ
እዚህ ላይ ለተናገረው ነገር አጽንዖት ለመስጠት ሲባል ሰውየው በአፉ ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- "የሰው" (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
የጥበብ ምንጭም የሚፈስ ወንዝ ነው
ይህ የሚናገረው የጥበብ ምንጭ እንደሚፈልቅ ምንጭ የተትረፈረፈ እንደሆነ ነው። የምንጭ መፍለቅ እንደሚፈስ ወንዝ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "የጥበብ ምንጭ ከሚፈልቅ ምንጭ እንደሚፈስ ውኃ የተትረፈረፈ ነው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 18:5
ጽድቅን ለሚያደርጉ … መልካም አይደለም
እነዚህ ሀረጎች በአዎንታዊ ቅርጽ ሊጻፉ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- "ለክፉ ሰው የሚገባውን ዋጋ መክፈል፣ ለጻድቃን ደግሞ ፍትሃዊ መሆን መልካም ነው (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
የሞኝ ከንፈሮች ያመጣሉ
እዚህ ላይ ንግግሩ ላይ አጽንዖት ለመስጠት ሲባል ሞኝ "በከንፈሮቹ" ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- "ሞኝ የተናገረው ያመጣል" (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ያመጣል
"ምክንያት ይሆናል"
አፉም በትርን ትጠራለች
ይህ የሚናገረው ስለ ሞኝ ሲሆን ሰዎች እንዲመቱት የሚያደርግ ነገሮችን መናገሩ እርሱ ራሱ ሰዎቹ እንዲመቱት እንደጋበዛቸው ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፡- "አፉ ሰዎች እንዲመቱት ያደርጋል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አፉ
እዚህ ላይ "አፍ" የሞኝ ሰው ንግግርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- "የተናገረው ንግግር" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 18:7
የሞኝ አፍ … ከከንፈሮቹ ጋር
እነዚህ ሁለቱም ሞኝ የሚናገረውን ነገር ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- "ሞኝ የተናገረው …. በተናገረው ነገር" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
መጥፊያው ነው
"ያጠፋዋል"
ራሱን ወጥመድ ውስጥ ይጥላል
በራሱ ላይ ችግርና መከራ ስለሚያመጣ ሰው ሲናገር ሰው እንስሳን እንደሚያጠምድ እንዲሁ ይህ ሰው ራሱን እንዳጠመደ አድርጎ አቅርቦታል። አማራጭ ትርጉም፡- "በራሱ ላይ ችግር ያመጣል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሐሜት ቃላት እንደ ጣፋጭ ጉርሻ ናቸው
ይህ የሐሜት ቃላት ለማድመጥ በጣም ደስ የሚያሰኙ ስለመሆናቸው ሲናገር ለመብል የሚመች በጣም ጣፋጭ ምግብ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- "የሀሜት ቃላት ለመስማት ደስ የሚሉ ናቸው" (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሐሜት ቃላት
ይህ የሐሜተኛ ሰው ንግግርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- "ሐሜተኛ ሰው የተናገራቸው ቃላት" (ባለቤትነት የሚለውን ይመልከቱ)
ጉርሻ
ትንሽ የምግብ ጥቅልል
ወደ ሰውነት ውስጣዊ ክፍሎች ጠልቀው ይገባሉ
ይህ ወደ ሰው ውስጣዊ ክፍል ገብተው አስተሳሰቡን ስለሚያበላሹ የሐሜት ቃላት የሚናገር ሲሆን ወደ ሰውየው ሆድ ውስጥ እንደሚገባ ምግብ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- "ወደ ሰው አእምሮ ገብተው አስተሳሰቡን ያበላሻሉ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 18:9
በስራው ችላ የሚል የአጥፊ ሰው ወንድም ነው
በስራው ችላ የሚል ሰው ከአጥፊ ጋር ተመሳሳይ እንደሆኑና በእርግጠኝነት ሁለቱም የሚመሳሰሉ እንደሆኑ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- "በጣም ይገናኛሉ" ወይም "በጣም ተመሳሳይ ናቸው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ችላ ባይ ነው
"ሰነፍ ነው" ወይም "ፍላጎት የለውም"
በጣም አጥፊ የሆነ
"ሁሉንም ነገር የሚያጠፋ" ወይም "ሁልጊዜ አጥፊ የሆነ"
የእግዚአብሔር ስም ጽኑ ግንብ ነው
ይህ ሃሳብ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚጠብቅ የሚናገር ሲሆን የእርሱ ሕዝብ የሚጠለሉበት ጠንካራ ግንብ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- "እግዚአብሔር እንደ ጠንካራ ግንብ ይጠብቃል" ወይም "እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ ጠንካራ ግንብ ይጠብቃቸዋል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ስም
እዚህ ላይ እግዚአብሔር በስሙ ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- "እግዚአብሔር" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጻድቅ
ይህ ጽድቅ የሚያደርጉ ሰዎችን ይወክላል፡፡። አማራጭ ትርጉም፡- "ጻድቃን የሆኑ ሰዎች" ወይም "ጻድቅ ሰዎች" (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ይድናል
ይህ ከእግዚአብሔር ደህንነትን ስለሚፈልጉና እግዚአብሔር ስለሚጠብቃቸው ሰዎች የሚናገር ሲሆን እግዚአብሔርን እነዚህ ሰዎች ደህንነትን ለማግኘት ወደ እርሱ የሚሮጡበት ጠንካራ ግንብ እንደሆነ አድርጎ ገለጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- "ወደ እርሱ ይሮጣሉ ደግሞም ደህንነትን ያገኛሉ" ወይም "እርሱን ይፈልጉታል ደግሞም ደህንነትን ያገኛሉ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 18:11
የባለጸጋ ሐብት የእርሱ የተመሸገ ከተማ ነው
ይህ በብልጽግናው ስለሚታመን ሀብታም ሰው የሚናገር ሲሆን ሀብቱ እርሱን የሚጠብቀው የተመሸገ ግንብ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፡- "ከተማ በተመሸገ ግንብ ላይ እንደሚደገፍ ሁሉ ባለጸጋ ሰው ደግሞ በሀብቱ ላይ ይደገፋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ባለጸጋ
ይሀህ ሀብታም ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- "ሀብታም ሰው" (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
የተመሸገ ከተማ
በግድግዳና በግንብ የተከበበች ጠንካራ ከለላ ያላት ከተማ
ሃሳቡም እንደ ረዥም ግንብ ነው
ይህ የሚናገረው ከፍ ያለ ግንብ በከተማ ውስጥ ያሉትን በደህንነት እንዲጠበቁ እንደሚያደርግ ሁሉ ሀብቱ በደህንነት ይጠብቀኛል ብሎ ስለሚያምን ባለጸጋ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "ከፍ እንዳለ ግንብ ሀብቱ ይጠብቀኛል ብሎ ያስባል" (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከውድቀቱ በፊት የሰው ልብ ትዕቢተኛ ይሆናል
"በመጀመርያ የሰው ልብ በትዕቢት ይሞላል፣ ነገር ግን ወዲያውኑ ውድቀቱ ይመጣል"
ውድቀት
ይህ በሰው መልካም ስምና ጤንነት ላይ የሚመጣውን ውድቀት የሚያመለክት ነው።
የሰው ልብ
እዚህ ላይ ለሃሳቡና ለስሜቱ አጽንዖት ለመስጠት ሰው በልቡ ተtወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- "ሰው" (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ትህትና ግን ክብርን ቀድሞ ይመጣል
"ትህትና" የሚለው ቃል እንደ ቅጽል ሊገለጽ ይችላል፣ "ክብር" የሚለው ደግሞ እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- "ሰው ከመከበሩ በፊት ትሁት ሊሆን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይገባዋል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

## Proverbs 18:13

ሞኝነትና ዕፍረት ይሆንበታል

“ሞኝነት” እና “እፍረት” የሚሉት ረቂቅ ቃላት እንደ ቅጽል ሊገለጹ ይችላ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝነቱ ነው፣ ሊያፍር ይገባዋል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው መንፈስ ሕመምን ትታገሳለች

እዚህ ላይ ሰው ለአስተሳሰቡ አጽንዖት ለመስጠት በመንፈሱ ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “ተስፋ ያለው ሰው ሕመም ይታገሳል” ወይም “ሰው በውስጣዊ ማንነቱ ተስፋ የተሞላ ከሆነ ከመታመም ይድናል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

የተሰበረን መንፈስ ግን ማን ሊሸከም ይችላል?

ጥቂቶች ብቻ ሊሸከሙት ይችላ የሚል መልስ እንደሚሰጥ በማሰብ ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን የተሰበረ መንፈስ መሸከም በጣም ከባድ ነው” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የተሰበረ መንፈስ

ይህ በድብርት መውደቅን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በድብርት ውስጥ መሆን” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

## Proverbs 18:15

የአስተዋይ ሰው ልብ ያገኛል

እዚህ ላይ ለፍላጎቱ አጽንዖት ለመስጠት አስተዋይ ሰው በልቡ ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “አስተዋይ ሰው ለማግኘት ይፈልጋል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

አስተዋይ ሰው

ይህ አስተዋይ የሆኑ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አስተዋይ የሆኑ ሰዎች” ወይም “አስተዋይ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ያገኛል

“ያተርፋል” ወይም “ይጨምራል”

የጠቢብም ጆሮ ይፈልገዋል

እዚህ ላይ ጥበበኛ ሰው ለመስማት የሚፈልገውን ነገር አጽንዖት ለመስጠት ሲባል ጆሮ በሚለው ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠቢብ ስለዚያ ነገር ለመማር ይፈልጋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጠቢብ

ይህ ጠቢብ የሆኑ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠቢብ የሆኑ ሰዎች” ወይም “ጠቢብ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይፈልገዋል

እዚህ ላይ “ይፈልገዋል” የሚለው ቃል የሚወክለው “እውቀትን” ነው።

መንገዱን ትከፍትለታለች

እዚህ ላይ “መንገዱን ትከፍትለታለች” እድል ይፈጥርለታል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእርሱ እድል ይፈጥርለታል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ፊት ታቆመዋለች

ይህ አንድን ሰው ለማየት ይፈቀድለታል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ያግኘው” ወይም “ከእርሱ ጋር ይተዋወቅ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

## Proverbs 18:17

ጉዳዩን ለማሰማት የመጀመርያ ነው

ይህ ተቀናቃኙ ቀርቦ ጉዳዩን ከማሰማቱ በፊት ቀድሞ ጉዳዩን የሚያሰማውን ሰው የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጉዳዩን ለማሰማት የመጀመርያው ሰው” ወይም “ጉዳዩን ያሰማ የመጀመርያው ሰው” (ደረጃ የሚያሳይ እና የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

እጣውን ማውጣት

“እጣ ማውጣት”

ሃይለኛ ጠላቶችንም ትለያለች

ይህ በክርክር ምክንያት ክፉኛ የሚጣሉ ሰዎችን ያመለክታል። ሲለያዩ በክርክራቸው ምክንያት መጣላታቸውን ያቆማሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ተቀናቃኞች በክርክራቸው ምክንያት መጣላታቸውን እንዲያቆሙ ያደርጋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

## Proverbs 18:19

የተበደለ ወንድምን መርታት ጠንካራ ከተማን ከማሸነፍ ይልቅ በጣም የከበደ ነው

ይህ ጠንካራ ከተማን በጦርነት ማሸነፍ በጣም አስቸጋሪ ከመሆኑ ጋር በማነጻጸር ከበደልከው ወንድምህ ጋር ሰላም መፍጠር በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወንድምህን ከበደልከው እንደገና ከእርሱ ጋር ሰላምን ለመፍጠር መንገድ መፈለግ ከተማን ለማሸነፍ ጦርነት ከመግጠም በላይ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጠብ እንደ ግንብ ብረት ነው

ይህ የሚናገረው የግንብ ብረት መስበር በጣም አስቸጋረ ከመሆኑ ጋር በማነጻጸር ለጠብ መፍትሔ መስጠትም አስቸጋሪ መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠብን ማስቆም የግንብ ብረትን እንደመስበር በጣም አስቸጋሪ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ግንብ

የተመሸገ ስፍራ

የሰው ሆድ ከአፉ ፍሬ ይሞላል፤ ከንፈሩም ከሚያፈራው ይጠግባል

ሁለቱ መስመሮች አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው፤ ጥቅም ላይ የዋሉት ደግሞ ለተነገረው ነገር አጽንዖት ለመስጠት ነው። ሁለቱን በአንድ ላይ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው የሚናገረው መልካም ነገር ባመጣው ውጤት ይረካል” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የአፉ ፍሬ

ይህ ሰው ስለሚናገረው መልካም ነገሮች የሚናገር ሲሆን ከአፉ የሚወጣ ፍሬ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ የተሞላ ንግግሩ” ወይም “መልካም ቃላቶቹ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሆዱ ይሞላል

ይህ በተናገሩት ነገር ምክንያት በመጣው ውጤት ስለጠገቡ ወይም ስለረኩ ሰዎች የሚናገር ሲሆን እንደበሉና እንደጠገቡ አድርጉ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ረክቷል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የከንፈሮቹ ምርት

ይህ ሰው ስለሚናገረው መልካም ነገር የሚናገር ሲሆን ከዛፉ ላይ እንደሚሰበሰብ ፍሬ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእርሱ ጥበብ የተሞላ ንግግር” ወይም “የእርሱ መልካም ቃላት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይረካል

“እርሱ ይደሰታል”

## Proverbs 18:21

ሞትና ሕይወት በምላስ ላይ ናቸው

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምላስ ወደ ሕይወት ወይም ወደ ሞት ሊመራ ይችላል” ወይም “ሰዎች የሚናገሩት ንግግር ወደ ሕይወት ወይም ወደ ሞት ሊመራ ይችላል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በምላስ … ምላስ ይወዳሉ

እዚህ ላይ “ምላስ” ንግግርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች በሚናገሩት … መናገር ይወዳሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፍሬዋን ይበላሉ

ይህ የሚናገረው በተናገረው ንግግር ምክንያት ያስከተለውን ውጤት ስለተቀበለ ሰው ሲሆን ውጤቱን እንደሚቀበለው ፍሬ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ውጤቱን ይቀበላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

## Proverbs 18:23

ብዙ ጓደኞች ያለው ሰው በእነርሱ አማካኝነት ወደ ጥፋት ይመጣል

ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ጓደኞች ያሉት ሰው እነርሱ ጥፋት ያመጡበታል” ወይም “ብዙ ጓደኞች ያሉት ጓደኞቹ ያጠፉታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚጠጋጋ

“የበለጠ ታማኝ ነው” ወይም “ታማኝ ሆኖ ይቆያል”

---

# Chapter 19

## Proverbs 19:1

ድሃ ሰው ይሻላል

“ድሃ ሰው መሆን ይሻላል”

በሃቀኝነት የሚራመድ ሰው

ይህ ፈሊጥ ነው። እዚህ ላይ መራመድ መኖርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሐቀኝነቱ የሚኖር ሰው” ወይም “እውነተኛ ሕይወት የሚኖር ሰው” (ፈሊጥ

የሚለውን ይመልከቱ)
በንግግሩ ጠማማ ነው
“ንግግር” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጠማማነት ይናገራል” ወይም “በክፉ መንገድ ይናገራል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ያለ እውቀት አንድን ነገር መመኘት
ይህ የሚያመለክተው አንድን ነገር በትክክለኛ መንገድ እንዴት መስራት እንዳለባቸው እውቀት ሳይኖራቸው ለመስራት የሚሞክሩ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የምትሰራው ነገር ምን እንደሆነ ሳታውቅ በትጋት መስራት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ
በችኮላ የሚሮጥም መንገዱን ይስታል
ይህ የሚናገረው ነገሮችን በጣም በችኮላ ስለሚሰራና ስህተትን ስለሚፈጽም ሰው ሲሆን ይህን ሰው በችኮላ እንደሚሮጥና መንገዱን እንደሚስት ሰው አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም በችኮላ የሚሰራ ሰው ስህተት ይፈጽማል” ወይም “በጣም በችኮላ የሚሰራ ሰው የተሳሳተ ምርጫ ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 19:3
ልቡም ይቆጣል
እዚህ ላይ ስሜቱን አጽንዖት ለመስጠት ሲባል ሰው “በልቡ” ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይቆጣል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ሐብት ብዙ ጓደኞችን ይጨምራል
ይህ ሀብታም ሰው ብዙ ጓደኞች ይኖረዋል ምክንያቱም ሀብት ሰውን ይስባል ማለት ነው። የዚህ ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሀብታም ሰዎች በቀላሉ ብዙ ጓደኞች ያገኛሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ
ድሃ ሰው ግን ከወዳጆቹ የተለየ ነው
ድሃ ሰው በድህነቱ ምክንያት ከብዙ ጓደኞቹ ይለያል። የዚህ ሃሳብ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ድህነት ሰው ጓደኞቹን እንዲያጣ ያደርጋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 19:5
ሐሰተኛ ምስክር ሳይቀጣ አይታለፍም
ይህ በአዎንታዊና በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ሐሰተኛ ምስክርን በእርግጠኝነት ይቀጡታል” (ጥምር አሉታ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ውሸትንም የሚያሰራጭ ሰው አያመልጥም
እርሱ ይያዛል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ውሸት የሚያሰራጨውን ሰው ይይዙታል” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
ውሸት ያሰራጫል
ይህ ፈሊጥ ነው። እዚህ ላይ “ያሰራጫል” የሚለው ቃል የማያቋርጥ ውሸትን ያመለክታል። ይህንን በምሳሌ 6:19 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ያለማቋረጥ ይዋሻል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ቸር ሰው
ብዙ ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን ለሰው የሚሰጥ
ሁሉ ጓደኛ ይሆነዋል
“ሁሉ” የሚለው ቃል ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉ ጓደኛው የሆነ ይመስላል” ወይም “ሁሉም ሰው ጓደኛው ነው ማለት እንችላለን” (ግነትና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 19:7
ከእርሱ ብዙ ርቀው የሚገኙ ጓደኞቹማ ምንኛ ይጠሉት!
ከበፊቱ ሀረግ ይልቅ ይህ ሀረግ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ለማሳየት ቃለ አጋኖ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ ጓደኞቹ በእርግጠኝት ይጠሉታል ደግሞም ከእርሱ ርቀው ይሄዳሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሕይወቱን ይወዳል
እዚህ ላይ ሰውየው በሕይወት እየኖረ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት “ሕይወት” በሚለው ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “ራሱን ይወዳል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ማስተዋልን ገንዘቡ ያደርጋል
“ማስተዋል አለው”
Proverbs 19:9
ሐሰተኛ ምስክር ሳይቀጣ አይቀርም
ይህ በአዎንታዊና በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። ይህንን በምሳሌ 19:5 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ሐሰተኛ ምስክርን በእርግጠኝነት ይቀጡታል” (ጥምር አሉታ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ውሸት ያሰራጫል
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር “ያሰራጫል” የሚለውን ቃል ሳያቋርጡ መዋሸትን ለማመልከት ተጠቅሞበታል። ይህንን በምሳሌ 6:19 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ያለማቋረጥ ይዋሻል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
አይገባውም
“ትክክል አይደለም”
ቅንጦት
የባለጠግነትና የደስታ ሁኔታ
ለባርያ ደግሞ የከፋ ነው
“ይህ” እና “አይገባውም” የሚሉት ቃላት ከቀደመው ሀረግ ግልጽ ተደርገዋል። ሊደገሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ለባርያ ፈጽሞ አይገባውም” ወይም “ለባርያ ከዚህም የከፋ ነው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 19:11
ጠቢብ አእምሮ ሰውን ታጋሽ ያደርገዋል
“ጠቢብ አእምሮ ያለው ሰው ቁጡ ከመሆን ይታገሳል”
ማስተዋል
ይህ በአንድ ወሳኝ ሁኔታ ላይ ምን መደረግ እንዳለበት ማወቅ ማለት ነው። ይህንን በምሳሌ 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
መተው ክብር ይሆንለታል
“መተው ክብር ያመጣለታል” ወይም “እርሱ ከተወ ሌሎች ክብር እንደሆነ ያስባሉ”
መተው
በዓላማ መርሳት
የንጉስ ቁጣ እንደ ጎረምሳ አንበሳ ግሳት ነው
እዚህ ላይ የጎረምሳ አንበሳ ግሳት ማጥቃትን ያመለክታል። የንጉስ ቁጣ ካልተጠበቀና አደገኛ ከሆነ የአንበሳ ደቦል ጥቃት ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የንጉስ ቁጣ እንደ አንበሳ ደቦል ጥቃት አደገኛ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በፊቱ ሞገስ ማግኘት ግን ሳር ላይ እንዳለ ጤዛ ነው
በንጉስ ፊት ሞገስ ማግኘት በማለዳ በሳር ላይ ከሚታየው የሚያድስ ውኃ ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን በፊቱ ሞገስ ማግኘት በሳር እንዳለ ጤዛ ያድሳል” ወይም “ነገር ግን በፊቱ ሞገስ ማግኘት በማለዳ በመሬት ላይ እንደሚታየው ጤዛ የሚያድስ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 19:13
ለአባቱ መጥፊያ ነው
“አባቱን ያጠፋዋል”
ጨቅጫቃ ሚስትም እንደማያቋርጥ የውኃ ነጠብጣብ ናት
ይህ የሚናገረው ስለ ጨቅጫቃ ሚስት ሲሆን እርሷ የማታቋርጥ የውኃ ነጠብጣብ እንደሆነች አድርጎ ገልጿታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጨቅጫቃ ሚስት እንደማያቋርጥ የውኃ ነጠብጣብ ነዝናዛና በጥባጭ ናት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጨቅጫቃ ሚስት
“ተከራካሪ ሚስት” ወይም “ስምምነት የሌላት ሚስት”
ቤትና ሐብት ከወላጆች ይወረሳል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ልጆች ቤትና ሐብት ከወላጆች ይወርሳሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
አስተዋይ
ይህን ቃል በምሳሌ 12:23 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
አስተዋይ ሚስት ከእግዚአብሔር ናት
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር አስተዋይ ሚስት ይሰጣል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 19:15
ስንፍና ሰውን ወደ እንቅልፍ ይጥለዋል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ስንፍና ሰውን ብዙ እንዲተኛ እንደሚያደርገው የሚናገር ሲሆን ስንፍና ሰውን በጉልበት ወደ እንቅልፍ እንደሚጥለው ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስንፍና ሰው ብዙ እንዲተኛ ያደርገዋል” ወይም “ሰነፍ ሰው ብዙ ይተኛል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይራባል

ይህ አይበላም የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አይበላም” ወይም “ይራባል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ትእዛዛት

“እርሱ የተማረው ትእዛዛት”

ሕይወቱን ይጠብቃል

“ሕይወቱን ይጋርዳል”

መንገዱ

ይህ ሰውየው እንዴት እንደሚኖር የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ የሚኖርበት መንገድ” ወይም “እንዴት እንደሚኖር” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:17

ለድሃ ቸር የሆነ ሰው ለእግዚአብሔር ያበድራል

እግዚአብሔር ለድሃ የተደረገውን ቸርነት ለእርሱ እንደተደረገ ይቆጥራል። ሰዎች ለድሃ ደግነትን የሚገልጡበት አንዱ መንገድ በመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለድሃ የሚሰጥ ሰው ለእግዚአብሔር ይሰጣል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድሃ

ይህ ድሃ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ድሃ የሆኑ ሰዎች” ወይም “ድሃ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ተስፋ ሳለ

ይህ የሚያመለክተው ልጅ ገና በሕጻንነቱ ሳለና ቅጣትና ተግሳጽ ሊቀበል የሚችልበትን ጊዜ ነው። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ገና ልጅ ሳለ” ወይም “ለማር በሚችልበት ጊዜ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞቱንም እየተመኘህ ዝም ብለህ አትየው

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ይህ ሀረግ የሚገልጸው ልጅህን መቅጣት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ነገር ግን ልጅህ እንዳይሞት አስከፊ በሆነ ሁኔታ አትቅጣው” ወይም 2) ይህ ሀረግ የሚገልጸው ልጅህን ባትቀጣው ምን ሊሆን እንሚችል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ካልቀጣኸው ራሱን እንዲያጠፋ እያገዝኸው ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እየተመኘህ ዝም ብለህ አትየው

ይህ ፈሊጥ ሲሆን ትርጉሙም አንድ ነገር እንዲከናወን መጨከን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱን ዝም ብሎ ማየት” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:19

ንዴቱን መቆጣጠር የማይችል ሰው

ይህ ፈሊጥ ሲሆን በቀላሉ የሚበሳጭ ሰውን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ስሜቱን መቆጣጠር የማይችል ሰው” ወይም “በቶሎ የሚቆጣ ሰው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅጣቱን ማግኘት አለበት

ይህ የሚያመለክተው እርሱ ሲቆጣ የሚከተለውን አሉታዊ ውጤት የተሸከመውን ሰው ነው። የዚህ ዓረፍተ-ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የቁጣውን አሉታዊ ውጤት መሸከም አለበት” ወይም “በቁጣው የፈጸመው ድርጊት አሉታዊ ውጤት መሸከም አለበት” (ፈሊጥ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ብታድነው

“ብትታደገው።” ይህ የሚያመለክተው ከቁጣው የተነሳ ከሚወስደው እርምጃ እርሱ ማዳን ነው። የዚህ ዓረፍተ-ሃሳብ ትርጉም በቀላሉ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በቁጣ ከተሞላ በኋላ ብታድነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሁለተኛ ጊዜ

“ሌላ ጊዜ” ወይም “እንደገና” (ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ምክርን ስማ ተግሳጽንም ተቀበል

እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ናቸው፣ የተደጋገሙት ነገሩ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ምክርን ስማ

ይህ ፈሊጥ ነው። እዚህ ላይ “ስማ” የሚለው እንዲያው ዝም ብሎ በጆሮ መስማት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ከተሰጠህ ምክር መማርና ምክሩን መከተል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለምክር ትኩረት ስጥ” ወይም “ምክርን ተከተል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:21

በሰው ልብ ውስጥ

እዚህ ላይ “ልብ” ጥቅም ላይ የዋለው አእምሮን ለማመልከት ሲሆን ለሰው ምኞት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በሰው አእምሮ ውስጥ” ወይም “ሰው የሚመኘው ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ዓላማ

“የእግዚአብሔር ዓላማ” ወይም “የእግዚአብሔር እቅድ”

የሚጸናው

ይህ ፈሊጥ ሲሆን “መፈጸም” ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱ ይፈጸማል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:23

እግዚአብሔርን ማክበር ሰዎችን ወደ ሕይወት ይመራል፤ እንዲህ ያለውም ሰው ይረካል

ይህ ሰዎች እግዚአብሔርን ቢያከብሩ ረጅም እድሜ ይኖራሉ ማለት ነው። የዚህ ዓረፍተ-ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ሰዎች ረጅም እድሜ ይኖራሉ፤ እግዚአብሔርን የሚያከብር ማንኛውም ሰው ይረካል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ያለው ሰው

እዚህ ላይ “ያለው” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “እግዚአብሔርን ማክበር” ነው።

ይረካል በመከራም አይጎዳም

ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ይረካል፤ ምንም ነገር አይጎዳውም” ወይም “ይረካል፤ በደህንነት ይጠበቃል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰነፍ

ይህንን በምሳሌ 10፡26 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

እጁን በሳህን ውስጥ ያጠልቃል

“እጁን በሳህን ውስጥ ያስገባል” ወይም “እጁን በራሱ ሳህን ውስጥ ያስቀምጣል።” በዘመናችን በብዙ ባህሎች ውስጥ እንደሚሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ባህል ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚበሉት በእጃቸው ነበር።

ወደ አፉም እንኳ እንደገና መልሶ አያመጣውም

እጁን እንደገና ወደ አፉ መልሶ አያመጣውም ምክንያቱም እጅግ በጣም ሰነፍ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ነገር ግን በጣም ሰነፍ ከመሆኑ የተነሳ ራሱን ለመመገብ እጁን መልሶ ወደ አፉ ማምጣት አይችልም። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:25

ፌዘኛን ብትመታው፣ አላዋቂው

“ቀልደኛውን ብትመታው፣ አላዋቂው”

ቀልደኛውን ብትመታው

“ቀልደኛውን ቅጣው”

አላዋቂ ሰው

“ልምድ የሌለው” ወይም “ብስለት የሌለው ሰው”

አስተዋይ

ይህንን በምሳሌ 12፡23 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

አስተዋዩን አርመው

“አስተዋይ የሆነውን ሰው ብታርመው”

እውቀትን ያገኛል

ይህ “እውቀት” የሚለው ረቂቅ ስም “አወቀ” በሚለው ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የበለጠ ያውቃል” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 19:26

ዕፍረትና ውርደት ያመጣል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ለራሱ ዕፍረትና ውርደት ያመጣል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለራሱ ዕፍረትና ውርደት ያመጣል” ወይም 2) ለቤተሰቡ ያመጣል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለቤተሰቡ ዕፍረትና ውርደት ያመጣል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተግሳጽን መስማት እምቢ ብትል

እዚህ ላይ “ማድመጥና መታዘዝ” እንደ “መስማት” ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለተግሳጽ ትኩረት መስጠት ካቆምህ” ወይም “ተግሳጽን መታዘዝ እምቢ ብትል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ትስታለህ

“ትተዋለህ” ወይም “ጆርባህን ትስጣለህ”

የእውቀት ቃላት

“እውቀት”

Proverbs 19:28

የክፉ ሰው አፍ በደልን ይውጣል

ይህ የሚናገረው ክፉ ሰዎች እንዴት ክፋትን በማድረግ እንደሚደሰቱ ሲሆን ምግብ በቀላሉ እንደሚውጡ እንደዚሁ በደልን በቀላሉ እንደሚውጡ ገልጾታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉዎች ምግብን ሲበሉ እንደሚደሰቱ እንደዚሁ ክፋትን በማድረግ ይደሰታሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉ ሰው አፍ ይውጣል

“የክፉ ሰው አፍ” የሚለው ሀረግ ክፉ ሰዎችን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎች ይውጣሉ” ወይም “ክፉ ይውጣል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ

ይህ ክፉ ሰዎችን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰው” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ለፌዘኞች ፍርድ ተዘጋጅቶላቸዋል፣ ግርፋት ደግሞ

“ፍርድ” እና “ግርፋት” የሚሉት ቃላት እንደ ግስ ሊገለጹ ይችላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር በፌዘኞች ላይ ለመፍረድና ለመግረፍ ዝግጁ ነው” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለሞኞች ጀርባ ግርፋት

“ዝግጁ ነው” የሚሉት ቃላት ከቀደመው ሀረግ በግልጽ መረዳት ይቻላል፤ ሊደገሙም ይችላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ግርፋት ለሞኞች ጀርባ ተዘጋጅቷል” ወይም “እርሱ ጀርባቸውን ለመግረፍ ዝግጁ ነው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

መግረፍ

በጅራፍ ወይም በበትር መምታት

---

Chapter 20

Proverbs 20:1

ወይን ጠጅ ፌዘኛ፣ ብርቱ መጠጥም ጠበኛ ያደርጋል

እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድ ላይ የተጣመሩት ብዙ አልኮል የመጠጣት አደገኛትን አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ወይን ጠጅ ፌዘኛ

እዚህ ላይ “ወይን” የሚያመለክተው በወይን የሰከረን ሰው ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በወይን የሰከረ ሰው ፌዘኛ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ብርቱ መጠጥም ጠበኛ ያደርጋል

እዚህ ላይ “ብርቱ መጠጥ” የሚያመለክተው በጠንካራ ወይን የሰከረ ሰውን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በብርቱ መጠጥ የሰከረ ሰው ጠብ ይጀምራል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጠበኛ

ብዙ ጊዜ ሕዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ በጩኸት የሚጣላ ሰው

በመጠጥ የሳተ ሁሉ ጠቢብ አይደለም

ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በግልጽ ማሰብ እስከማይችሉ ድረስ የሚጠጡ ሰዎች ሁሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በመጠጥ

እዚህ ላይ “መጠጥ” የሚያመለክተው አልኮል መጠጦችን ነው፡፡

ጠቢብ አይደለም

ይህ የጥበበኛ ተቃራኒ ነው፣ “ሞኝ” ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሞን ነው” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉስ ቁጣ እንደሚያገሳ ደቦል አንበሳ ቁጣ ነው

እዚህ ላይ የንጉስ ቁጣ ሰዎች እንዴት እንደሚፈሩት እና የደቦል አንበሳ ቁጣ እንዴት እንደሚፈሩት ተነጻጽሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች የአንበሳ ደቦል ሲጣጣባቸው እንደሚፈሩ እንደዚሁ የንጉስ ቁጣ ያስፈራቸዋል፡፡ (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያስቆጣዋል

“ንጉሱን ያስቆጣዋል”

ሕይወቱን ይከፍላል

ይህ የሚያመለክተው መሞትን ነው፡፡ እዚህ ላይ “ሕይወት” የሚያመለክተው ስጋዊ ሕይወትን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ይሞታል” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:3

ክብር ነው

“የሚያስከብር ነው፡፡” ይህ ሰውየው ይከበራል ማለት ነው፡፡

ሞኝ ሰው ሁሉ ወደ ጭቅጭቅ ይገባል

ይህ ወደ ጭቅጭቅ ፈጥኖ ስለመግባት የሚናገር ሲሆን ጭቅጭቅ ሞኝ ሰው በአካል ዘልሎ የሚገባበት እንደሆነ ተደርጎ ተገልጿል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሞኝ ሁሉ ወደ ጭቅጭቅ ፈጥኖ ይገባል” ወይም “ሞኝ ሁሉ ወደ ጭቅጭቅ ለመግባት ፈጣን ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማረስ

ለመዝራት መሬትን ማዘጋጀት

በመከር

“እህል የሚዘራበት ወቅት”

ምንም አያገኝም

ይህ ሊሰበስበው የሚችለው በእርሻው ላይ የበቀለ ምንም ነገር አይኖርም ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን የሚሰበስበው ምንም ነገር አይኖረውም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:5

በሰው ልብ ውስጥ ያለ አሳብ እንደ ጥልቅ ውሃ ነው

ይህ የሰውን ድርጊት መነሻ ምክንያት መረዳት እንዴት አስቸጋሪ እንደሆነ በጥልቅ ጉድጓድ ያለውን ውኃ ለማግኘት አስቸጋሪ ከመሆኑ ጋር በማነጻጸር ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በጥልቅ ጉድጓድ ያለውን ውኃ ለማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነ እንደዚሁ በሰው ልብ ውስጥ ያለውን ሃሳብ መረዳት አስቸጋሪ ነው፡፡ (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አስተዋይ ሰው

“ማስተዋል ያለው ሰው”

ቀድቶ ያወጣዋል

ይህ በሰው ልብ ውስጥ ያለውን ሃሳብ ስለመለየት የሚናገር ሲሆን ከጥልቅ ጉድጓድ ተቀድቶ እንደሚወጣ ውኃ አድርጎ ገልጾታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሃሳቡ እንዲታወቅ ያደርጋል” ወይም “ሃሳቡን ይለየዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጣማኝ

“ታማኝ ነው” ወይም “አመኔታ የሚጣልበት ነው”

ታማኝ የሆነውን ግን ማን ሊያገኘው ይችላል?

ግልጽ የሆነው መልስ “እንደዚያ ያለ ሰው ማግኘት የሚችሉት ጥቂቶች ናቸው” የሚል ነው፡፡ ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እንደ ዓረፍተ-ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ጥቂት ሰዎች ታማኝ ሰው ሊያገኙ ይችላሉ” ወይም “ነገር ግን ታማኝ የሆነ ሰው ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:7

በሐቀኝነቱ ይራመዳል

እዚህ ላይ መራመድ መኖርን ያመለክታል፡፡ ይህንን በምሳሌ 19፡1 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በሐቀኝነቱ ይኖራል” ወይም “ታማኝ ሕይወት ይኖራል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍለጋውን የሚከተሉ ልጆቹም

ከእርሱ ይልቅ በእድሜ ለጋ ስለሆኑና ልጆቹም ስለሆኑ እርሱን “እርሱን ይከተሉታል” ለማለት ነው፡፡ ይህ ሀረግ በአንተ ቋንቋ ያልተለመደ ከሆነ እንዳለ መተው ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ልጆቹ ይከተሉታል “ ወይም “ልጆቹ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ ያለውን ክፋት ሁሉ በዓይኖቹ አበጥሮ ይለያል

ይህ ንጉስ በተለያዩ የክፋት ዓይነቶች መካከል የሚለይ ስለመሆኑ የሚናገር ሲሆን



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ የመለየቱን ተግባር ሰው እህል አበጥሮ እንደሚለይ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- “በእርሱ ፊት የሚመጡትን የተለያዩ የክፋት ዓይነቶች ይመለከታል ደግሞም ይለያል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 20:9
“ልቤን በንጽህና ጠብቄያለሁ፤ ከኃጢአቴ ንጹህ ነኝ” ብሎ መናገር የሚችል ማን ነው?
ለዚህ ጥያቄ ጠቋሚ መልስ ሊሆን የሚችለው:- “ማንም ሰው ይህን ሊናገር አይችልም” የሚል ነው። ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እንደ ዓረፍተ-ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- ““ልቡ ንጹህ እንደሆነና ኃጢአት የለብኝ ብሎ መናገር የሚችል አንድም ሰው የለም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ልቤ
እዚህ ላይ የሰው “ልብ” ሃሳቡንና ምኞቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “ሃሳቤ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ንጹህ
በመንፈሳዊነቱ እግዚአብሔር ተቀባይነት እንዳለው የቆጠረው ሰው በአካል ንጹህ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጿል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ከኃጢአቴ ንጹህ ነኝ
“ኃጢአት የለብኝም” ወይም “ኃጢአት አልሰራሁም”
Proverbs 20:11
ወጣት እንኳ በስራው ይታወቃል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሰዎች ወጣትን በስራው ያውቁታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ባህርዩ ንጹህና ቅን መሆኑ
“ባህርዩ ንጹህና ቅን መሆኑና አለመሆኑ”
ባህርዩ
“ተግባሩ” ወይም “የሚሰራው ስራ”
ንጹህና ቅን
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ናቸው፤ ይህ ወጣት ምን ያህል መልካም እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣል። አስፈላጊ ከሆነ ወደ አንድ ቃል መጣመር ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- “ንጹህ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የሚሰሙ ጆሮዎችና የሚያዩ ዓይኖች
እግዚአብሔር ስሜቶቻችንን በሙሉ እርሱ እንደፈጠራቸው አጽንዖት ለመስጠት ተመሳሳይ ሃሳቦች ተደጋግመዋል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 20:13
ወደ ድህነት ትመጣለህ
እዚህ ላይ “ትመጣለህ” የሚለው ቃል ወደ አዲስ ሁኔታ ትገባለህ፤ ትመጣለህ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ድሃ ትሆናለህ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ዓይንህን ክፈት
እዚህ ላይ “የአንድ ሰው ዓይን መክፈት” “መንቃት” እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “ንቁ ሁን” ወይም “ጥንቁቅ ሁን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ዕቃ የሚገዛ ሰው “መጥፎ ነው! መጥፎ ነው!” ይላል፣ በሄደ ጊዜ ግን ይኩራራል
እዚህ ላይ ገዢ ለራሱ የሚገዛውን በዝቅተኛ ዋጋ እንዲያገኝ አንድ ሰው የሚሸጠውን ነገር ያቃልላል። ከገዛ በኋላ ግን ሻጩ እንዲሸጥለት በማሳመን ስለገዛበት ጥሩ ዋጋ ይኩራራል። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ገዢ የሻጩን እቃ እያቃለለ ‘መጥፎ ነው! መጥፎ ነው!’ ይላል ነገር ግን እቃውን ከገዛ በኋላ ይሄዳል ከዚያም ስለከፈለው ዝቅተኛ ዋጋ ይኩራራል (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 20:15
የእውቀት ከንፈሮች የከበረ ጌጥ ናቸው
ይህ የሚናገረው ከከበረ ጌጥ ጋር በማወዳደር ስለ እውቀት ከንፈሮች ዋጋ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የእውቀት ከንፈሮች እንደ ውድ ጌጥ በጣም የከበሩ ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእውቀት ከንፈሮች
እዚህ ላይ “ቃላት” የሚሉት “ከንፈሮች” በሚሉት ተገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም:- “የጥበብ ቃላት” ወይም “የእውቀት ቃላት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ለማይታወቅ ሰው ብድር በዋስትና ገንዘብ ያስያዘውን ሰው ልብስ ውሰድበት
ገንዘብ ስትበደር አበዳሪው ከተበዳሪው እንደገና ለመከፈሉ ዋስትና ይሆን ዘንድ አንድ ነገር እንደ ልብስ የመሳሰሉ ይወስዳል። አበዳሪውም መያዣውን ገንዘቡ ከተከፈለው ቧላ ይመልሳል። ተበዳሪው በጣም ድሃ ከሆነ ደግሞ ለአበዳሪው ሌላ ሰው እንደ ዋስትና አንድ ነገር ሊሰጠው ይችላል። የዚህ ዓረፍተ-ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላ። አማራጭ ትርጉም:- “አንድ እንግዳ ሰው የተበደረውን ብድር መክፈል ለመቻሉ ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ እንደ ዋስትና ዋስ ከሆነው ሰው ልብሱን ውሰድ። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ማስያዣ አስይዝ
ይህ ፈሊጥ ነው። አንድ ሰው ብድር ከተበደረ በኋላ ዋስ የሆነው ሰው ብድሩ የሚከፈል መሆኑን ለማረጋገጥ ለአበዳሪው አንድ ነገር ይሰጠዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ብድሩ ተመልሶ የሚከፈል መሆኑን ለማረጋገጥ ዋስትና ስጠው” ወየም “ብድር ለመክፈል ቃል ግባ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
በዋስትና ያዘው
ይህ ፈሊጥ ነው። “አንድን ነገር ማስያዣ መያዝ” አንድ ሰው የወሰደውን ዕዳ እንደሚከፍል ለማረጋገጥ አንድ ሰው እንደ ማስያዣ የሰጠውን ነገር ወይም ቃል ኪዳን መያዝ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ዕዳው የሚከፈል ለመሆኑ ዋስትና እንዲሆን ኮቱን እንደ ማስያዣ ያዝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 20:17
በማጭበርበር የተገኘ ዳቦ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “አንድ ሰው በማጭበርበር ያገኘው ዳቦ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በማጭበርበር
“ማጭበርበር” የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሌሎችን በማጭበርበር” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ዳቦ
እዚህ ላይ “ዳቦ” በአጠቃላይ ምግብን ሁሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “ምግብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ይጣፍጣል
“ጥሩ ጣዕም አለው”
ነገር ግን ከዚያ በኋላ አፉ ጠጠር ይሞላል
ይህ ምግቡ የማይጣፍጥ ስለመሆኑ የሚናገር ሲሆን አፉ በእርግጥም ከምግብ ይልቅ በጠጠር እንደተሞላ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- “ነገር ግን ከዚያ በኋላ በአፉ ውስጥ እንደ ጠጠር ጣዕም ይሆንበታል” ወይም “ነገር ግን ወዲያውኑ በአፉ ውስጥ እንደ አፈር ጣዕም ይሆንበታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠጠር
ትንሽ ድንጋዮች
እቅዶች በምክር ይጸናሉ
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሰዎች እቅዳቸውን በምክር ላይ ተመስርተው ያቅዳ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 20:19
ሐሜት
ይህ በስተጀርባ ብዙ መናገር ነው።
ከእርሱ ጋር አንድነት አትፍጠር
“አንተ ከእርሱ ጋር ጓደኛ አትሁን”
አንድ ሰው ከሰደበ
አንድ ሰው ክፉ ነገር በሌላ ሰው ላይ እንዲሆን ምኞቱን ከገለጸ ማለት ነው።
መብራቱ በድቅድቅ ጨለማ መካከል ይጠፋል
ይህ የሚናገረው በድንገትና ባልተጠበቀ ሁኔታ ስለሚሞት ሰው ሲሆን የዚህን ሰው ሕይወት በድቅድቅ ጨለማ እንደጠፋ መብራት አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- “በድቅድቅ ጨለማ እንደጠፋ መብራት ሕይወቱ በድንገት ይቆማል” ወይም “በድንገት ይሞታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መብራቱ በድንገት ይጠፋል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “መብራቱ ይጠፋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
መብራቱ
ይህ የሚንበለበል ነበልባል ያለው መብራት ያመለክታል። እዚህ ላይ የመብራቱ ነበልባል እንደ መብራት ተተጠቅሷል። አማራጭ ትርጉም:- “የመብራቱ ነበልባል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ይጠፋል
ነበልባል እንዲጠፋ ማድረግ

Proverbs 20:21

በመጀመርያ

ይህ የሚያመለክተው ውርሱን ሊቀበል ከሚገባበት ጊዜ በፊት ቀድሞ የተቀበለን ሰው ነው። የዚህ ዓረፍተ-ሃሳብ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "ከትክክለኛው ጊዜ በፊት" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እመልስልሃለሁ

ይህ አንተ በሌሎች ሰዎች ላይ መጥፎ ነገር ስላደረግህ እነርሱም በአንተ ላይ የሚወስዱት በቀል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- "እቀጣሃለሁ" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔርን ጠብቅ

ይህ እግዚአብሔር የአንተን ጉዳይ እርሱ ይይዘዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- "በእግዚአብሔር ታመን" ወይም "በእግዚአብሔር ተስፋ አድርግ" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:23

እኩል ያልሆኑ ሚዛኖችን እግዚአብሔር ይጠላል፣ ሐሰተኛ መስፈሪያም መልካም አይደለም

እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ናቸው፣ በአንድ ላይ የተጣመሩት ይህ ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው አካሄድ በእግዚአብሔር ይመራል

ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "የሰውን አካሄድ እግዚአብሔር (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው አካሄድ

ይህ ሰው የሚያደርገውን የተለያዩ ነገሮች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- "የሰው ድርጊቶች" (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ታዲያ ሰው የራሱን መንገድ እንዴት ሊያስተውል ይችላል?

የዚህ አመልካች መልስ ሊያስተውለው አይችልም የሚል ነው። ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "ስለዚህ ሰው የራሱን መንገድ ሊያስተውለው አይችልም" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዱን አያስተውልም

ይህ ፈሊ ነው። "መንገዱን" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የሰውየውን ሕይወት ነው። አማራጭ ትርጉም:- "በሕይወቱ ለምን አንድ ነገር እንደሚሆን አያስተውልም" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:25

ወጥመድ ነው

ይህ የሚናገረው አደገኛ ስለሆነ ነገር ሲሆን እንደ ወጥመድ ወይም መንጠቆ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- "አደገኛ ነው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በችኮላ ቢናገር

ምን ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል በጥንቃቄ ሳያስተውሉ በችኮላ አንድ ነገር መናገር

ስእለት ቢሳል

ይህ ሰው አንድ ነገር ለእግዚአብሔር የተቀደሰና የተለየ ነው ብሎ ስእለት ገባ።

አማራጭ ትርጉም:- "ለእግዚአብሔር የተለየ አደረገ" ወይም "የተቀደሰ ነው አለ" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉውን ያበጥራል

ይህ የሚናገረው ንጉስ እህልን እንደሚያበጥር እንደዚሁ ክፉ ሰዎችን እንደሚለይ ነው። አማራጭ ትርጉም:- "ክፉዎችን ይለያል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ

ይህ የሚያመለክተው ክፉ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም:- "ክፉ የሆኑ ሰዎች" ወይም "ክፉ ሰዎች" (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም የመውቂያ ጋሪውን በላያቸው ላይ ይነዳል

ይህ ንጉስ የመውቂያ ጋሪውን በእነርሱ ላይ እንደሚነዳ አድርጎ በመግለጽ ክፉዎችን እንደሚቀጣ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- "እርሱ በአሰቃቂ ሁኔታ ይቀጣቸዋል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የመውቂያ ጋሪ

"የመውቂያ ጋሪ።" ይህ እህል ለመውቃትና ከገለባው ለመለየት የሚረዳ መሳርያ ነው።

Proverbs 20:27

የሰው መንፈስ የእግዚአብሔር መብራት ነው፣ ውስጣዊ ማንነቱንም ይመረምራል

ይህ የሚናገረው ስለ ሰው መንፈስ ሲሆን እንደ መብራት ገልጾታል። የሰው መንፈስ ውስጣዊ ማንነቱን እንደሚገባ እንዲረዳ ያግዘዋል። አማራጭ ትርጉም:- "መብራት በጨለማ እንድናይ እንደሚያግዘን እንደዚሁ ጥልቅ ማንነታችንን በሚገባ እንድንረዳ እግዚአብሔር መንፈስ ሰጥቶናል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በኪዳን የተመሰረተ ታማኝነትና እውነተኛነት ንጉስን ይጠብቁታል

"ታማኝነት" እና "እውነተኛነት" የተባሉት ረቂቅ ስሞች "ታማኝ" እና "እውነተኛ" ተብለው ሊገለፁ ይችላሉ። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- ንጉስ ለኪዳኑ "ታማኝ" እና "እውነተኛ" በመሆን ራሱን ሊጠብቅ ይችላል። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ንጉስን ይጠብቁታል

ንጉሱን በደህንነት ከጉዳት ይጠብቁታል

ዙፋኑም በፍቅር ይጸናል

እዚህ ላይ "ዙፋን" የንጉሱን የአገዛዝ ኃይል ይወክላል። "ፍቅር" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ ሊገለጽ ይችላል። በተጨማሪ ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "ንጉስ ለረጅም ጊዜ መምራቱን ሌሎችን በመውደድ ያረጋግጣል" (ምትክ ስም እና ረቂቅ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 20:29

የሚያቆስል ምት ክፋትን ያስወግዳል፣ ግርፋትም ውስጣዊ የሰውነት ክፍሎችን ያነጻል

ሁሉም ዓረፍተ ሃሳቦች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አንድን ሰው ለማረም አካላዊ ቅጣት ስለ መጠቀም ሲናገር ክፉ ነገር ቆሻሻ እንደሆነና ቅጣት ደግሞ እንደሚያነጻው ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም:- "ጥፋት የሰራን ሰው መግረፍ ከጥፋቱ እንዲታረም ያደርገዋል ደግሞም የተሻለ ሰው እንዲሆን ያደርገዋል። (ትይዩነት እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 21

Proverbs 21:1

የንጉስ ልብ በእግዚአብሔር እጅ እንዳለ የውኃ ፈሳሽ ነው

ጸሐፊው ስለ ንጉስ ልብ ሲናገር ሰዎች እርሻቸውን በአስፈለጊ ጊዜ ለማጠጣት ውኃውን እንደሚፈልጉ እንደሚመሩት እንደ መስኖ ቦይ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- "ሰው የመስኖ ውኃን እንደሚመራው ሁሉ እንደዚሁ እግዚአብሔር የንጉስን ልብ ይቆጣጠራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉስ ልብ

ልብ ሰው ለሚያስበውና ሊሰራ ለሚፈልገው ነገር ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም:- "የንጉስ ሃሳብና ተግባር" ወይም "ንጉስ የሚያስበውና ሊያደርገው የሚፈልገው" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ለሰው መንገዱ በራሱ ዓይን ፊት ቀና ሊመስለው ይችላል

ዓይን ማየትን ይወክላል፣ ማየት ደግሞ ሃሳብን ወይም ፍርድን ይወክላል። ጸሐፊው ሰው ስለሚያደርገው ነገር ሲናገር ያ ሰው በመንገድ እንደሚጓዝ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- "እያንዳንዱ ሰው የሚሰራው ስራ ሁሉ መልካም እንደሆነ ያስባል" ወይም "እያንዳንዱ ሰው የሚሰራው ስራ ሁሉ መልካም እንደሆነ ይደመድማል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብን የሚመዝን

ጸሐፊው ሰው ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ይፈልግ እንደሆነና እንዳልሆነ እግዚአብሔር ስለሚያደርገው ውሳኔ ሲናገር እግዚአብሔር ወደ እቃ እንደሚመለከትና መልካም ጥራት ያለው እንደሆነ መዝኖ ድምዳሜ እንደሚደርስ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- "የሰውን የውስጥ ሃሳብ የሚመዝን ማን ነው" (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 21:3

ቅን የሆነውን ነገር ማድረግ

"እግዚአብሔር ትክክል እንደሆነ የሚያስበውን ነገር ማድረግ"

ፍትህን ... ማድረግ

"እግዚአብሔር ሰዎች ሌሎች ሰዎችን ሊይዙ የሚፈልገውን ዓይነት አያያዝ ለሰዎች ማድረግ"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ለእግዚአብሔር ፍትህ የበለጠ ተቀባይነት አለው
“ፍትህ - እግዚአብሔር ይህን የበለጠ ይፈልገዋል”
ትቢተኛ ዓይንና ኩሩ ልብ
“ዓይን” እና “ልብ” የሚሉት ቃላት ራሱን ከሌሎች ሰዎች ይልቅ እንደሚሻል ለሚቆጥርና ሌሎች ሰዎች ይህን ሃሳቡን እንዲያወቁለት ለሚፈልግ ሰው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሌሎች ሰዎች ይልቅ እንደሚሻሉ ሰዎች እንዲያስቡ የሚፈልጉ ሰዎች” (ተዛምዶአዊ እና ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ትዕቢተኛ ዓይን
ይህ እርሱ ከእነርሱ ይልቅ እንደሚሻል እንደሚያስብ ሌሎች ሰዎች እንዲያውቁለት ለሚፈልግ ሰው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ኩሩ ልብ
ይህ እርሱ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ የተሻለ እንደሆነ ለሚያስብ ሰው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
የክፉ ሰውም መብራት
ክፉ ሰውን የሚያግዙ ነገሮች በሙሉ እንደ መብራት እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰውን እንደ መብራት የሚያግዙ ነገሮች በጨለማ እንዲያይ ይረዱታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 21:5
ትጉ ሰው
ይህ የስም ቅጽል እንደ ስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትጉ ሰው” ወይም “ጠንክሮ የሚሰራ ሰው” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ድህነት ይመጣል
“ድህነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሃ ይሆናል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ሃብትን ማግኘት
“ሃብትን ማከማቸት”
ውሸታም ምላስ
ምላስ እንደበቱ ይናገር ዘንድ ሰው ለሚጠቀምባቸው ቃላቶች ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ውሸት መናገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የሚጠፋ ተን
ጸሐፊው ሰው በውሸት የሚያገኘውን ሃብት በማለዳ በፍጥነት ከሚጠፋ ተን ጋር አመሳስሎታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚጠፋ ተን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚገድል ወጥመድ
ጸሐፊው ሰው በውሸት የሚያገኘውን ሃብት በአዳኝ ወጥመድ ላይ እንደሚደረገው የማታለያ ምግብ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 21:7
የክፉዎች አመጽ ራሳቸውን ይጠራርጋቸዋል፣
ጸሐፊው ስለ ክፉዎች አመጽ ሲናገር ሌሎችን እንደሚጠራርግ ሰው አድርጎ ገልጾታል። እግዚአብሔር ቅን የሆኑ ጎረበቤቶቻቸውን የሚጎዱትን ክፉ ሰዎች ይቀጣል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የክፉዎች አመጽ
“አመጽ” የሚለው ረቂቅ ስም የሚያመለክተው ሰዎች ቅን ጎረቤቶቻቸውን ለመጉዳት የሚሰሯቸውን ድርጊቶችን ወይም ሌሎች ነገሮችን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የክፉ ሰዎች አመጸኛ ድርጊት” (ረቂቅ ስም እና የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ራሳቸውን ይጠራርጋቸዋል
ይህ ሀረግ የሚያመለክተው በውኃ ውስጥ ዓሳ ለመያዝ መረብ መጎተትን ነው። በራሳቸው ድርጊት ስለሚጠፉ ክፉ ሰዎች ሲናገር አንድ ሰው ዓሳ እንደሚይዝ እንደዚሁ ድርጊታቸው በመረብ አጥምዶ እንደሚይዛቸው አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም: “እንደ ዓሳ አጥምዳቸው” ወይም “አንድ ሰው ዓሳ በመረብ እንደሚይዝ እንደዚሁ በቀላሉ አጥፋቸው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የበደለኛ ሰው መንገድ ጠማማ ነው
ይህ አንድ ሰው የሚኖርበትን መንገድ አንድ ሰው ከሚጓዝበት ጠማማ መንገድ ጋር ያነጻጽረዋል። ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በደለኛ ሰው የሚኖርበት መንገድ ጠማማ ነው” (ፈሊጥ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠማማ
እዚህ ላይ “ጠማማ” የሚለው የታጠፈ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ማለት ነው። ይህ በስነ ምግባር ለተሳሳተ ሰው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስህተት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 21:9
በጣራ ማእዘን
በዚያን ጊዜ የነበሩ ቤቶች ለጥ ያለ ጣራ ነበራቸው። የጥንት እስራኤላውያን ጣራቸውን ለመስራት ብዙ ጊዜ ይወስድባቸው ነበር። ጣራው ከቤቱ ውስጠኛው ክፍል ይልቅ ቀዝቃዛ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለመኝታ የሚሆን ትልቅ መጠለያ በጣራው በአንዱ ማእዘን ላይ ይሰሩ ነበር። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠበኛ ሚስት
“ብዙ ጊዜ የምትጨቃጨቅና የምታማርር ሚስት”
የክፉ ሰው ምኞት ክፋትን አጥብቆ ይመኛል
ጸሐፊው ስለ ሰው ምኞት ማለትም ለሚበላና ለሚጠጣ ነገር ስላለው ፍላጎት ሲናገር አንድን ነገር እንደሚፈልግ ሰው አድርጎ ገልጾታል። “ክፉ” የሚለው ቃል ክፉ ሰዎችን የሚያመለክት የስም ቅጽል ሲሆን “ክፋት” የሚለው ቃል ደግሞ ክፉ ድርጊቶችን የሚወክል የስም ቅጽል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎች ለመብላትና ለመጠጣት እንደሚመኙ እንደዚሁ ክፉ ድርጊቶችን ለመፈጸም ይመኛሉ” (ሰውኛ ዘይቤ እና የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
መመኘት
አጥብቆ መፈለግ
ጎረቤቱም በዓይኖቹ ውስጥ ምንም ደግነት አያይም
“ደግነት መፈለግ” የሚለው ፈሊጥ አንድ ሰው ደግነት ለሚፈልገው ሰው ማረጋገጫ ሲሰጠውና በደግነት ሲያደርግለት ማለት ነው። በተጨማሪ ዓይኖች ማየትን ይወክላል፣ ማየት ደበደግነት ግሞ ሰውየው ለሌሎች ሰዎች ያለውን ሃሳብና አመለካከት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጎረቤቱ ከእርሱ ምንም ዓይነት ደግነት አላገኘም” ወይም “ለጎረቤቱ ደግነትን አላሳየም” (ፈሊጥ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 21:11
ፌዘኛ ሲቀጣ
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ፌዘኛውን ሲቀጣ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
አላዋቂ
“ልምድ የሌላቸው” ወይም “ብስለት የሌላቸው”
ፈዘኛ
“በሌሎች ላይ የሚያፌዝ”
ጥበበኛ ሰው ሲገሰጽ
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ጥበበኛውን ሰው ሲገስጸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እውቀትን ይጨምራል
እዚህ ላይ እውቀት አንድ ሰው ሊጨብጠውና ለራሱ ሊወስደው የሚችለው እቃ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጽድቅን የሚያደርግ ሰው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ማንኛውም ጻድቅ ሰው ወይም 2) “ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር”
ቤት ልብ ብሎ ይመለከታል
“ለቤት ጥንቃቄ የተሞላበት ትኩረት ያደርጋል” “ቤቱ ላይ ምን ሊሆን እንደሚችል ለማየት ይጠብቃል”
እርሱ ክፉውን ወደ ጥፋት ያወርደዋል
እዚህ ላይ ጥፋት አንድ ሰው የሚወሰድበት ቦታ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ያጠፋቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 21:13
የድሆችን ለቅሶ የማይሰማ ሰው
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሆች ለእርዳታ ሲጮሁ የማይሰማ ሰው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱም ሲጮህ ማንም አይመልስለትም
“አይመልስለትም” የሚለው ቃል ሌላ ሰው ለእርዳታና ተግባራዊ እርምጃ ሲጠይቀው ለሚሰማ ሰው ምትክ ስም ነው። ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድም ሰው እርሱን ለመርዳት አንዳች አያደርግም” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣን ያበርዳል
“የተቆጣን ሰው በቁጣው እንዳይቀጥል ስሜቱን ያረጋጋል”
Proverbs 21:15
ፍትሕ በተደረገ ጊዜ
“ፍትሕ” የሚለው ረቂቅ ስም በስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል፡፡ እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ “መሪዎች ፍትሕ ሲያደርጉ” (ረቂቅ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ከማስተዋል መንገድ ይስታል
ይህ ፈሊጥ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ “ለወደፊት በጥበብ መኖር ፈጽሞ ኤችልም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
በሙታን ጉባኤ ውስጥ ያርፋል
“የሙታን መናፍስት ባሉበት ጉባኤ ይኖራል”
Proverbs 21:17
ቤዛ ይሆናል
“ቤዛ” የሚለው ቃል የሌላውን ሰው ስፍራ ለሚወስድ ሰው ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ እዚህ ላይ ጽድቅ ካደረገው ሰው ይልቅ ስህተት የፈጸመው ሰው ቅጣት ይቀበላል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከዳተኛ ሰው
በመዋሸትና ሌሎች ውሸት የተሞሉ ነገሮችን በማድረግ የሚያምኑትን ሰዎች የሚጎዳ ሰው
Proverbs 21:19
ጠቢብ
ይህ የስም ቅጽል በስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ “ጠቢብ ሰው” (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ያባክናቸዋል
x
Proverbs 21:21
ከተማ ይገባባታል
“በከተማዋ ዙርያ ያለውን የግንብ አጥር ዘልሎ ይገባል”
የኃያላን ከተማ
“ኃያላን ሰዎች የሚኖሩባት ከተማ” ወይም “ኃያላን ተዋጊዎች ያሉባት ከተማ”
ያፈርሳል
ይህ ፈሊጥ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ “ያጠፋዋል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የታመኑበትን ምሽግ
“ማንም ሰው ወደ ከተማው አልፎ ሊገባ ይችላል ብለው ያላሰቡትንና ከዚህም የተነሳ ደህንነት እንዲሰማቸው የሚያደርጉትን በከተማዋ ዙርያ ያሉትን ግንቦቹንና ማማዎችን”
Proverbs 21:23
አፉንና ምላሱን የሚጠብቅ ሰው
“አፍ” እና “ምላስ” ሰውየው የተናገረውን ነገር ያመለክታሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ “ለሚናገረው ነገር ጥንቃቄ የሚያደርግ ማንኛውም ሰው” (ጥምር ቃል እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ))
ኩሩና ትዕቢተኛ ሰው … በእብሪትና በትዕቢት ያደርጋል
“ኩሩና ትዕቢተኛ ሰዎች በእብሪትና በትዕቢት እንሚያደርጉ መጠበቅ ትችላለህ”
ኩሩና ትዕቢተኛ ሰው
እነዚህ ሁለተ ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ነገር ናቸው፣ ሰውየው ምን ያህል ትዕቢተኛ እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ስሙ “ፌዘኛ” ይባላል
“ስም” የሚለው ቃል ሰዎች ለሚጠሩት መጠሪያው ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ “ልትጠራው የሚገባህ ፌዘኛ ብለህ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 21:25
የሰነፍ ምኞት ራሱን ይገድለዋል
ጸሐፊው ሰውየው ስለሚፈልገው ነገር ሲናገር ምኞቱ ሰነፍ ሰው ሊገድል የሚችል ሰው አድርጎ ገልጾታል፡፡ እዚህ ላይ ሰነፍ ሰው ስራ ፈት እና የማይሰራ መሆን ይፈልጋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ “ሰነፍ ሰው ስራ መፍታት ይወዳል ከዚህ የተነሳ ይሞታል” ወይም “ሰነፍ ሰው ሊሰራ ካለመፈለጉ የተነሳ ይሞታል” (ሰውኛ ዘይቤ እና የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ) )
እጆቹ አይፈቅዱም
እጅ ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፦
“አይፈቅድም” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ይመኛል
በብርቱ ይፈልገዋል
ይሰጣል፤ አይሰስትም
“አይሰስትም” የሚለው ቃል በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፤ የሚሰጠው ነገር ደግሞ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ “ሊሰጥ የሚገባውን ሁሉ ይሰጣል” ወይም “በቸርነት ይሰጣል “ (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 21:27
የክፉዎች መስዋዕት አስጸያፊ ነው
ጸሐፊው በምሳሌ 15፡8 ላይ እንዳደረገው እዚህ ላይ እግዚአብሔርን አልጠቀሰም፣ ነገር ግን አንባቢው የክፉዎችን መስዋዕት የሚጸየፈው እግዚአብሔር እንደሆነ ሊያስተውል ይገባል፡፡
ክፉ
“ክፉ” የሚለው የስም ቅጽል በስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦
“ክፉ ሰው” ወይም “ክፉ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ደግሞ የበለጠ አስጸያፊ ነው
“እግዚአብሔር መስዋዕቱን የበለጠ ይጸየፈዋል”
ለሁልጊዜ የሚሆን ይናገራል
እንዲህ የሚሆነው ሰዎች እርሱ የሚናገረውን ስለማይረሱት ነው፡፡
Proverbs 21:29
ፊቱን ያጠነክራል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) “ጀግና እንደሆነ ያስመስላል” ወይም 2) “ተግሳጽን አይሰማም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ መንገዶቹ እርግጠኛ ነው
የሰው ድርጊት ሰው የሚሄድበት መንገድ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦
“ስለሚሰራው ነገር እርግጠኛ ነው” ወይም “ስለሚሰራው ነገር ልበ ሙሉ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 21:30
ጥበብ የለም፣ ማስተዋል የለም እና ምክር የለም
“የለም” የሚለው ቃል የተደጋገመው ረቂቅ ስም ለሆኑት “ጥበብ፣” “ማስተዋል” እና “ምክር” አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ እግዚአብሔር ማንኛውም ሰው ሊያውቅ ወይም ሊያስብ ወይም ሊናገር ከሚችለው ማንኛውም ነገር ይበልጣል፡፡ በአንተ ቋንቋ “የለም” የሚለው ቃል እንዲደጋገም አያስፈልገውም ይሆናል፡፡ ይህ ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ወይም ግስ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ “ጥበበኛ ሰው የለም፣ ነገሮችን የሚያስተውል አንድም ሰው የለም እና ለሌሎች ምን መስራት እንዳለባቸውና ማን መስራት እንደሚገባው የሚነግራቸው አንድም ሰው የለም” ወይም “ጥበብ፣ ማስተዋል ወይም ምክር የለም” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን ሊቋቋም የሚችል
“እግዚአብሔርን የሚያሸንፍ” ወይም “እግዚአብሔር ሊሰራ ከሚፈልገው በተቃራኒ የሚሰራ” ወይም “እርሱ ትክክል እግዚአብሔር ግን ስህተት እንደሆነ ሊያሳይ የሚችል”
ፈረስ ለጦርነት ቀን ይዘጋጃል
እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ “ወታደሮች ለጦርነት ቀን ያዘጋጁሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የጦርት ቀን
“ቀን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከቀን ለሚያጥር ወይም ለሚረዝም ጊዜ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ “ጦርነት በሚኖርበት ጊዜ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 22
Proverbs 22:1
ከብዙ ሐብት ይልቅ ጥሩ ስም ይመረጣል
እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ “ሰው ከብዙ ሀብት ይልቅ ጥሩ ስም ሊመርጥ ይገባዋል፡፡ (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ጥሩ ስም

“ሌሎች ሰዎች አንድ ሰው መልካም እንደሆነ እንዲያስቡ የሚያደርግ”
ሰዎች የሚጋሩት አንድ ነገር
“በአንድ መንገድ ተመሳሳይነት አላቸው” ወይም “በዚህ መልክ ተመሳሳይ ናቸው”

## Proverbs 22:3

ጠንቃቃ ሰው
“ጥበበኛ የሆነ ሰው” ወይም “ጥሩ የማመዛዘን ችሎታ ያለው ሰው” ይህንን በምሳሌ 12:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
አላዋቂ ሰው
“ልምድ የሌለው ወይም ብስለት የሌለው ሰው”

## Proverbs 22:7

ይበደራል … ያበድራል
ይህንን መበደር ወይም ማበደር ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፡- “ገንዘብ ይበደራል … ገንዘብ ያበድራል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አፍትሐዊነትን የሚዘራ መከራን ያጭዳል፣
ጸሐፊው ሀይል የሌላቸውን ሰዎች በአፍትሐዊነት ስለሚያሰቃዩ መሪዎች ወይም ሌሎች ሃያላን ሰዎች ሲናገር እነርሱ መከራ የሚያመጡ ዘፎችን የሚያበቅሉ ዘሮችን እንደዘሩ አድርጎ ገልጿቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው ከእርሱ ይልቅ ሃይል የሌላቸውን ሰዎች በአፍትሐዊነት ያሰቃያቸው እንደሆነ በኋላ መከራ ያመጡበታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የቁጣውም በትር ይጠፋል
“በትር” የሚለው ቃል በሌሎች ሰዎች ላይ ላለን ሃይል ምትክ ስም ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) አፍትሐዊ መሪ ሌሎች ሰዎችን እንዲያሰቃይ የፈቀደለትን ስልጣን ያጣዋል ወይም 2) እርሱ ለፈጸመው አፍትሐዊነት ሰዎች እርሱን በመጉዳት ምላሽ ሲሰጡ እነርሱን ለማስቆም የሚችልበት ምንም ዓይነት ሃይል አይኖረውም። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎችን ለመጉዳት የተጠቀመበት ሃይል ከእንግዲህ ወዲህ ፈጽሞ አይኖረውም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የቁጣው በትር
“በትር” የሚለው ቃል በሌሎች ሰዎች ላይ ላለን ስልጣን ምትክ ስም ነው። አፍትሐዊ ሰው በንጹሃን ሰዎች ላይ በጣም እንደተቆጣ ያህል እነርሱን ሲጎዳቸው ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎችን እንደሚቀጣ ይጠቀምበት የነበረ በትር” ወይም “ሌሎችን ለመጉዳት የተጠቀመበት ሃይል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ይጠፋል
“ይጠፋል” ተብሎ የተተረጎመው ቃል እጽዋት ሲደርቁም ጥቅም ላይ ይውላል።

## Proverbs 22:9

ቸር አይኖች ያሉት ሰው ይባረካል
እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ቸር ዓይን ያለውን ሰው እግዚአብሔር ይባርከዋል። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ቸር አይኖች ያሉት ሰው
ዓይን ሌሎች ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ለማየት ምትክ ስም ነው፣ “ቸር ዓይን” ደግሞ ማየት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሌሎች ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣል። ዓይን ለሰው ሁለንተና ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ቸር ሰው” ወይም “ለሌሎች ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ ሰው” (ምትክ ስም እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ዳቦ
በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ዳቦ ለብዙ ሰዎች ምግብ ስለነበር በአጠቃላይ ምግብን ለማመልከት ጥቅም ላይ ይውላል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ግጭትና ስድብም ይቆማሉ
“ግጭት” እና “ስድብ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች እርስ በርሳቸው ለወደፊት አይጨቃጨቁም ወይም እርስ በርሳቸው ለመጎዳዳት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችን አይናገሩም” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

## Proverbs 22:11

ንጹህ ልብ ይወዳል
ሰው ንጹህ እንዲሆን የሚፈልገው ልቡ ነው። ልብ ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጹህ ልብ ሲኖረው ይወዳል” ወይም “ንፁህ እንዲሆን ይፈልጋል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ቸር ነው
“ደግ ነው”
የእግዚአብሔር ዓይኖች ይከታተላሉ
ዓይን ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። ጸሐፊው እግዚአብሔር እንደ ሰው ስጋዊ ዓይን እንዳለው አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ይከታተላል” ወይም “እግዚአብሔር እውቀትን ይጠብቃል” (ተዛምዶአዊ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እውቀትን ይከታተላሉ
መከታተል ለጥበቃ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እውቀት ይይብቃል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ይገለብጣል
“ያጠፋል”
ከዳተኞች
ከዳተኞች የሚለው የስም ቅጽል እንደ ስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። “ከዳተኞች” የሚለውን በምሳሌ 11:3 ላይ እንዳለው ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከደተኛ ሰው” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

## Proverbs 22:13

ሰነፍ ሰው ይላል
ከዚህ የሚቀጥለው አባባል ውሸትና ላላመስራት ምክንያት መስጠት ነው። የአንተ ቋንቋ በተለየ መንገድ ሀሰተኛ አረፍተ ሃሳብ የሚያስተዋውቅ ከሆነ እዚህ ላይ እሱን መጠቀም ትችላለህ።
የአመንዝራ ሴት አፍ ጥልቅ ጉድጓድ ነው
“አፍ” የሚለው ከአፍ ለሚወጡ ቃላት ምትክ ስም ነው። ጸሐፊው ለሰራው ክፉ ስራ ሰዎች ሲቀጡት ሊያመልጥ ስላልቻለ ሰው ሲናገር አንድ ሰው በመሬት ላይ ከቆፈረው ሊያመልጠው ከማይችለው ጉድጓድ እንደወደቀ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በአመንዝራ ሴት የተነገሩ ቃላቶች ወደታች ያዘቅጥሃል፣ አንተ ወደ ጥልቅና አደገኛ ጉድጓድ እንደወደቅህ ያህል ነው” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አመንዝራ
ይህንን በምሳሌ 5:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
የእግዚአብሔር ቁጣ ይነሳሳል
እዚህ ላይ “ይነሳሳል” የሚለው ቁጣው ይጨምራል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ተቆጥቷል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
በዚያ ይወድቃል
አመንዝራነት ሰው ወደዚያ ሊወድቅበት የሚችልበት ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በአመንዝራ ምክንያት ኃጢአት ይሰራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

## Proverbs 22:15

ሞኝነት በሕጻን ልብ ላይ ታስሯል
“የሕጻን ልብ በሞኝነት የተሞላ ነው”
የስርዓት በትር
ጸሐፊው የቅጣት አማራጮችን ስለሚጠቀም ወላጅ ሲናገር ያ ወላጅ ልጁን በእንጨት በትር እንደሚመታ አድርጎ ገልጾታል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ከእርሱ ያርቀዋል
ጸሐፊው ሞኝነት ሰው እንደሆነና ሌላ ሰው እርሱን ለማራቅ በትር ሊጠቀም እንደሚችልና አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ልጅን ጥበበኛ ያደርገዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሃብቱን ለመጨመር
“የበለጠ ሀብታም ለመሆን” ወይም “የበለጠ ገንዘብ ለማግኘት”
ለሃብታሞች ይሰጣል
“ገንዘብ ለሃብታሞች ይሰጣል”
ወደ ድህነት ይመጣል
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሃ ይሆነል። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

## Proverbs 22:17

አጠቃላይ መረጃ፡-
ቁጥር 17 ለመጽሐፈ ምሳሌ አዲስ ክፍል መግቢያ ሆኖ ይጀምራል።
ጆሮህን አዘንብልና አድምጥ
እዚህ ላይ “ጆሮ” የሚለው ቃል የሚያደምጠውን ሰው ይወክላል። ጸሐፊው አንድን ሰው በጥሞና ስለማድመጥ ሲናገር ጆሮ ወደተናጋሪው መጠጋት እንዲችል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በሚናገረው ሰው ላይ እንደመደገፍ አድርጎ ገልጾታል፡፡ “ጆሮን ማዘንበል” የሚለውን በምሳሌ 4፡20 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ትኩረት በመስጠት አድምጥ” ወይም “በትኩረት አድምጥ” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጥበበኛ ቃላት

“ጥበበኛ ሰዎች የሚናገሩት”

ልብ በል

ይህ ፈሊጥ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በሚገባ ለመረዳትና ለማስታወስ የምትችለውን ሁሉ አድርግ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እውቀቴ

የሚናገረው ሰው ምናልባት በምሳሌ 1፡8 ላይ ካለው አባት ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላሉ፡፡ “እውቀቴ” በማለት የሚናገረው ስለ “ጥበበኛ ቃላት” ሊሆን ይችላል፡፡ “እውቀት” የሚለው ረቂቅ ስም “እወቅ” በሚለው ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከአንተ ጋር የምካፈለው እኔ ያለኝ እውቀት” ወይም “የማውቀውን” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም በከንፈሮችህ ላይ ዝግጁ ናቸው

ለመናገር ዝግጁ የሆነው ሰው ለመነገር ዝግጁ እንደሆኑት ቃላት ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ በማንኛውም ጊዜ ቃላቶቹን ለመናገር ትችላለህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ዛሬ ለአንተ

“ዛሬ፡፡ አዎ፣ እኔ እያስተማርኩህ ነው፣” ተናጋሪው የሚያስተምረው አድማጩን እንጂ ሌላ ሰውን እያስተማረ እንዳልሆነ አጽንዖት ይሰጣል፣ አድማጩን የሚያስተምረው ደግሞ አድማጩ መማር ስለሚያስፈልገው ነው፡፡ በዚህ መንገድ አጽንዖት መስጠት በቋንቋህ ተስማሚ ካልሆነ በሌላ መንገድ አጽንዖት ልትሰጠው ትችላህ ወይም “ለአንተ” የሚለውን ቃል ሳትተረጉመው ልታልፈው ትችላለህ፡፡

Proverbs 22:20

አጠቃላይ መረጃ፡-

እነዚህ ቁጥሮች የሚቀጥሉ ሲሆን በምሳሌ 22፡17 ላይ የተጀመረውን መግቢያ ይጨርሳሉ፡፡

ለአንተ አልጻፍኩልህምን

ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እንደ ዓረፍተ-ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንተ የጻፍኩልህን ልትረዳው ይገባሃል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች

አንዳንድ ትርጉሞች “እጅግ በጣም ጥሩ አባባሎች” ብለው ተርጉመውታል፡፡ (የጽሑፍ መልክ የሚለውን ይመልከቱ)

ለላኩህ

ይህ የሚያመለክተው አድማጩ መረጃ እንዲያገኝና ይዞ እንዲመለስ የተላከ ነው ወይም ደግሞ ከተላኩት ብዙዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

Proverbs 22:22

አጠቃላይ መረጃ፡-

እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይጀምራሉ (ምሳሌ 22፡20)፡፡

አትዝረፍ ... አታድቅቀው

የአንተ ቋንቋ አንድ ሰው ለሌላ ሰው ጠንከር ባለ መልኩ የሚናገርበት መንገድ ይህ እንደሆነ የሚያሳዩበትና ሰዎች ሊያከብሩት የሚገባቸው ከአጠቃላይ መመርያ የተለየ መንገድ ካለ እዚህ ላይ ልትጠቀምበት ትችላለህ፡፡

ድኃ

ይህ እንደ ስም ቅጽል ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ማንኛውም ድኃ ሰው” ወይም “ድኃ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ማድቀቅ

ዱቄት እንዲሆን መፍጨት፡፡ ይህ “እፍትንዊነት” ለሚለው ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ችግረኛ

ይህ የስም ቅጽል እንደ ስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ማንኛውም ችግረኛ ሰው” ወይም “ለመኖር የሚያስችለው ነገር የሌለው ማንኛውም ሰው” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

በደጅ ላይ

ይህ ስፍራ ሰዎች የተለያዩ ነገሮች የሚገዙበትና የሚሸጡበት ስፍራና ሕጋዊ ጉዳዮችና ክርክሮች የሚፈቱበት ሲሆን ለንግድና ሕጋዊ ጉዳዮች ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ፍርድ ቤት ውስጥ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ለእነርሱ ይፈርድላቸዋልና

ይህ ተለዋጭ ዘይቤ በዳኛው ፊት ለፊት ችግረኛውን ሰው የሚሟገትለት ዳኛ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለችግረኞች በጨቋኞቻቸው ፊት ይሟገትላቸዋል” ወይም “እግዚአብሔር ችግረኞች ፍትህ ሲያገኙ ይመለከታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የዘረፏቸውንም ሰዎች ሕይወት እርሱ ይነጥቃል

እግዚአብሔር ሌባ አይደለም፣ ነገር ግን ቸርነት ለማድረግና ለመስጠት ከማይፈልጉ ሰዎች እንደ ሌባ ሕይወታቸውን ይወስዳል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ድኃ ሰዎችን የሚጨቁኑ ሰዎች ያጠፋቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 22:24

አጠቃላይ መረጃ፡-

እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22፡20)፡፡

በቁጣ የሚነዳ ሰው

ቁጣውን መቆጣጠር የማይችል ሰው፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ግልፍተኝነት

በጣም ኃይለኛ የሆነ ቁጣ

ለነፍስህም ወጥመድ እንዳታገኝህ

እንደ ቁጡ ሰው መምሰል የሚፈልግ ሰው በወጥመድ ላይ የተቀመጠ ምግብን እንደሚወስድ እንስሳ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ወጥመድ እንዲስፈነጠር ለማድረግ ወጥመድ ላይ የተቀመጠ ምግብን እንደሚበላ እንስሳ ትሆናለህ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለነፍስህ ወጥመድ

ነፍስ ለሰውየው ሕይወት ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ይገድልህ ዘንድ አንድ ሰው የሚያስቀምጠው መሳቢያ ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 22:26

አጠቃላይ መረጃ፡-

እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22፡20)፡፡

እጅ ይመታል

አንድ ሰው ሊያደርግ የተስማማውን ነገር የሚያደርግ መሆኑን ቃል ለመግባት በእጁ የሌላውን ሰው እጅ ይመታል፡፡ እዚህ ላይ ተናጋሪው የሌላ ሰው ዕዳ እንዲከፍል ቃል በመግባት እጅ እንዳይመታ አድማጩን ያስጠነቅቀዋል፡፡

ውል መስስት

“አንድ ሰው ለሌላ ሰው ያለበትን ዕዳ እንዲከፍል መስማማት”

Proverbs 22:28

አጠቃላይ መረጃ፡-

እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22፡20)፡፡

ጥንት

በጣም ያረጀ

የድንበር ድንጋይ

የአንድ ሰው የመሬት ድንበር የት እንደሚያልቅና የሌላው ሰው መሬት የት እንደሚጀምር የሚያሳይ ትልቅ ድንጋይ ነው፡፡

አባቶች

ቅድመ አያቶች

በስራው ስልጡን የሆነውን ሰው አይተሃልን?

ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ በእርግጥ ትእዛዝ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በስራው ጥበበኛ የሆነ የሆነ የምታውቀውን ሰው አስብ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቱ ይቆማል

ይህ የወሳኝ ሰው አገልጋይ መሆንን ይወክላል፡፡ ነገስታትና ሌሎች ትልልቅ ሰዎች አገልግሎቱን በመመልከት ስለ እርሱ ከፍ አድርገው ያስባሉ፡፡ (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 23
Proverbs 23:1
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
በጉሮሮህ ላይ ካራ አድርግ
ለዚህ ግነት ፤ሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው:- 1) “ብዙ እንዳትበላ ጠጠንቀቅ” ወይም 2) “ምንም ነገር አትብላ” (ግነትና ጅምላ ፍረጃ እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
አትመኝ
“ክፉኛ አትጎምጅ።” ይህንን በምሳሌ 21:19 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
ጣፋጭ ምግቡ
“ልዩና ውድ ምግቦቹ”
ይህ በውሸት የተገኘ ምግብ ነው
ይህ ፈሊጥ ነው። “ያታልልህ ዘንድ ይሰጥሃል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 23:4
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ከመጠን በላይ አትልፋ
“ሁልጊዜ እንዳትደክም ከመጠን በላይ አትስራ”
በ ... ላይ አትጣል
በሐብት ላይ እንደ ወፍ አትረፍ (ቁጥር 4)። ይህ በሐብት ላይ ለአጭር ጊዜ ዓይንን መጣል ለሚለው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በድንገት ክንፍ ያወጣል እንደ ንስርም ወደ ሰማይ እየበረረ ይሄዳል
ሐብቱን ስላጣ ሰው ሲናገር ሐብቱ ወፍ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም:- “ንስር በፍጥነት እንደሚበርር እነደዚሁ ሐብት በፍጥነት ይጠፋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ንስር ክንፍ
እንደ ንስር ክንፍ የመሰለ ክንፍ
Proverbs 23:6
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ክፉ ዓይን ያለው ሰው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) ተናዳፊ ሰው፣ ለሌሎች ሰዎች ያለውን ነገር ለመስጠት የማይወድ ሰው ወይም 2) ክፉ ሰው።
አትመኝ
“አጥብቀህ አትጎምጅ።” ይህንን በምሳሌ 21:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
ጣፋጭ መብሎቹ
“ልዩና ውድ የሆኑ ምግቦቹ” ይህንን በምሳሌ 23:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
ልቡ ከአንተ ጋር አይደለም
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ምግቡን እንድትበላና እንድትደሰት በእርግጥም አይፈልግም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ትንሽ የበላኸው ያስታውክሃል
ይህ አንድ ሰው ምንም ነገር ባልበላሁ ብሎ ለተመኘው ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ምንም ነገር ባትበላ ትመኝ ነበር” (ግነትና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የምስጋና ቃልህንም ከንቱ ታደርጋለህ
ምስጋና እጅግ ውድና የከበሩ ነገሮች እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። “ምስጋና” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ስለ እርሱና ስላቀረበልህ ምግብ መልካም ነገር ብትነናገር እንኳ ደስተኛ አይሆንም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 23:9
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ሞኝ ሰው በሚሰማበት
ይህ “በሚሰማበት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሞኝ ሊሰማህ በሚችልበት ስፍራ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጥንት
በጣም ያረጀ። ይህንን በምሳሌ 22:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
የድንበር ድንጋይ
የአንድ ሰው የመሬት ድንበር የት እንደሚያልቅና የሌላው ሰው መሬት የት እንደሚጀምር የሚያሳይ ትልቅ ድንጋይ ነው። ይህንን በምሳሌ 22:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
ጥሶ ገባ
ይህ የሌላ ሰውን መሬት (ወይም ሌላ ነገር) ቀስ በቀስ መውሰድድ ወይም ለመጠቀም መጀመር ማለት ነው።
መላጅ አልባ
መወላጆቻቸው የሞቱባቸው ልጆች
ታዳጊያቸው
እግዚአብሔር
እርሱ ጉዳያቸውን ከአንተ ጋር ይፋረዳል
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ጠበቃ በዳኛ ፊት ችግረኞችን ሲከላከልላቸው የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ወላጅ አልባዎችን ከአንተ ይከላከልላቸዋል” ወይም “ወላጅ አልባዎች ፍትህ ሲቀበሉና አንተ ስትቀጣ ያያል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 23:12
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ልብህን ስጥ
ይህ ፈሊጥ ነው። ይህንን በምሳሌ 22:17 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “ለመረዳትና ለማስታወስ የምትችለውን ሁሉ አድርግ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ቅጣት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) “ትክክል እና ስህተት የሆነውን ነገር ምን እንደሆነ የሚያውቁ ሰዎች የሚነግሩህ” ወይም 2) “አንተን ሲያስተካክሉህ ሰዎች የሚናገሩትና የሚያደርጉት ነገር”
ጆሮችህ
ይህ አስጨምሬ ሊምላ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ጆጥንቃቄ አድምጥ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
የእውቀት ቃላት
“ለእኔ የማውቀውን ነገር ለአንተ ስነግርህ”
Proverbs 23:13
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ልጅን ከመቅጣት ወደ ኋላ አትበል
ይህ “ቅጣት” የሚለው እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ልጅን ከመቅጣት ቸል አትበል” ወይም “ልጅን ለመቅጣት እምቢይ አትበል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ያዘ
ሌላ ሰው እንደሚያስፈልገው እያወቀ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን
በትር
ከእንጨት የተሰራ ዱላ
በበትር ልትመታው የሚገባህ አንተ ነህ ... እና ነፍሱን ታድናለህ
“ልትመታው የሚገባህ አንተ ነህ ... እና ነፍሱን ታድናለህ” ከአንተ ሌላ ማንም ይህን አያደርገውም። አድማጩ የልጁን ነፍስ ከሲኦል ለማዳን ኃላፊነት አለው፣ ልጁን ለማዳን መንገዱ ደግሞ መምታት ነው።
ነፍሱን ከሲኦል ታድናለህ
አድማጩ ልጆቹን በበትር ቢመታቸው በሰሩት ሞኝነት ወይም ክፉ ነገር በልጅነታቸው አይሞቱም። “ነፍስ”` የሚለው ቃል ለሰውየው ምትክ ስም ነው። ሲኦል የሙታን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ዓለም ነው፤ ወደ ሙታን ዓለም መሄድ የሚለው ሀረግ ለመሞት ለስላሴ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ ሙታን ዓለም ከመሄድ ትጠብቀዋለህ” ወይም “ከመሞት ትጠብቀዋለህ” (ምትክ ስም እና ለስላሴ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 23:15
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
አፎችህ ሲናገሩ
“አፎች” ማት የሰው ሁለንተና ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስትናገር” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 23:17
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ልብህ በኃጢአተኞች እንዲቀና አትፍቀድ
“ልብ” የሚለው ቃል ለሰው ሁለንተና ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሀጢአተኞች ላይ እድትቀና አትፍቀድ” ወይም “በሀጢአጠኞች ላይ አለመቅናትህ እርግጠኛ ሁን” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ተስፋህ አይጠፋም
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ተስፋህን ማንም ሰው እንዲያጠፋው እግዚአብሔር አይፈቅድም” ወይም “እግዚአብሔር ለአንተ የገባልህን ቃል ኪዳን ይጠብቃል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 23:19
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ልጄ ሆይ፣ ስማኝ
“ልጄ ሆይ በጠንቃቄ ስማኝ።” ተናጋሪው አድማጩ በአግባቡ ትኩረት ሰጥቶ እንደሆነ እርግጠኛ ለመሆን ተጨማሪ ቃላት ይናራል።
ልብህንም በትክክለኛው መንገድ ላይ አዘንብል
ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ መወሰን አንድ ሰው ለሌላ ሰው ትክክለኛውን መንገድ እንዲከተለው እንደማሳየት ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበብ ያለበትን ነገር ለማድረግህ እርግጠፐኛ ሁን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በሆዳምነት ስጋ የሚበሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “መብላት ከሚያስፈልጋቸው በላይ ብዙ ስጋ የሚበሉ ሰዎች” ወይም 2) “ስጋ” በአጠቃላይ ምግብን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መብላት ከሚያስፈልጋቸው በላይ ብዙ ምግብ የሚበሉ ሰዎች (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
እንቅልፋምነት ቁራጭ ጨርቅ ያስለብሳቸዋል
“እንቅልፋምነት” የሚለው ቃል አስፈላጊ ስራ ሳይሰራ ምግብ በመብላትና መጠጥ በመጠጣት ብዙ ጊዜውን ለሚያሳልፍ ሰው በግነት የተጻፈ ነው። ይህ ድርጊት ወላጅ ለልጁ ልብስ እንደሚያለብሰው ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ በመብላትና በመጠጣት ብዙ ጊዜአቸውን ስለሚያጠፉ ምንም ስራ አይሰሩም፣ ከዚህ የተነሳ ድኃ ይሆናሉ” (ሰውኛ ዘይቤ እና ግነትና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 23:22
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
አትናቃት
ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለእርስዋ አክብሮት አሳይ” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
እውነትን የራስህ አድርጋት፣ አትሽጣትም፤ ጥበብን፣ ስርዓትንና ማስተዋልንም ገንዘብህ አድርግ።
ሌሎች አማራጭ ትርጉሞች፡- “እውነትን የራስህ አድርጋት፣ ጥበብን፣ ስርዓትንና ማስተዋልንም ገንዘብህ አድርግ።” “እውነት፣” “ጥበብ፣” “ስርዓትና” “ማስተዋል” የሚሉት ቃላት ረቂቅ ስሞች ሲሆኑ ቁሳዊ ነገሮች እንደሆኑና አንድ ሰው ወደ ገበያ ሄዶ የሚገዛውና የሚሸጠው እንደሆነ ተደርገው ተገልጸዋል። እነዚህ በገቢር ግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እውነት የሆነውን ማወቅ እንድትችል፣ ጥበበኛ እንድትሆን፣ አንድን ነገር እንዴት መስራት እንዳለብህ መማር እንድትችል እና ከመጥፎ ይልቅ መልካም ነገር መናገር እንድትችል ማድረግ የሚገባህን አድርግ፤ ከእነዚህ ነገሮች በላይ የበለጠ ጠቃሚ ነገር እንዳለ ፈጽሞ አታስብ” (ረቂቅ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 23:24
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
የጻድቅ ሰው አባት በደስታ ይሞላል፣ ጥበበኛ ልጅንም የወለደ በልጁ ይደሰታል።
ሌሎች አማራጭ ትርገሞች፡- “የወለደ” የሚለው “የጻድቅ ሰው አባት” ማን እንደሆነ ያብራራል። አማራጭ ትርጉም፡- “የጻድቅ ሰው አባት፣ ጥበበኛ ልጅንም የወለደ፣ በደስታ ይሞላል ደግሞም በልጁ ይደሰታል።”
በእርሱ ደስ ይሰኛል
“ከእርሱ የተነሳ ደስ ይለዋል”
Proverbs 23:26
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ልብህን ስጠኝ
“ልብ” የሚሚው ቃል ሰው ለሚያስበውና ለማድረግ ለሚወስነው ምትክ ስም ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ጥንቃቄ የተሞላበትe ትኩረት አድርግ” ወይም 2) “ሙሉ በሙሉ እኔን ታመን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ዓይኖችህ ያስተውሉ
“ዓይን” ለሰው ሁለንተና ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አስተውል” ወይም “በጥንቀቄ ተመልት” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ዝሙት አዳሪ ሴት ... ምግባረ ብልሹ ሴት
በወሲብ ሕይወታቸው ምግባረ ብልሹ የሆኑ ሁለት ዓይነት ሴቶች አሉ። “ዝሙት አዳሪ” ያላገባች ናት፣ “የሌላ ሰው ሚስት” ያገባች ናት። ሁለቱ በአንድ ላይ ለማንኛውም በወሲብ ምግባረ ብልሹ ለሆኑት ሴቶች ጥምረ ቃል ይፈጥራሉ። (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዝመት አዳሪ ሴት ጥልቅ ጉድጓድ ናት
“ጉድጓድ” የሚለው ቃል ከዝሙት አዳሪ ሴት ጋር የሚተኙ ወንዶች ላይ ምን እንሚሆባቸው የሚያሳይ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከዝሙት አዳሪ ሴት ጋር መተኛት በጥልቅ ጉድጓድ እንደመውደቅ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዝሙት አዳሪ ሴት
እዚህ ላይ ቃሉ የሚያመለክተው ይህንን ስራ ገንዘብ ለማግኘት ብለው ለሚሰሩ ብቻ ሳይሆን ወሲብ ለምትፈጽም ማንኛዋንም ያላገባችን ሴት ነው።
ጥልቅ ጉድጓድ ... የጠለቀች አዘቅት
“ጉድጓድ” በጣም “ጥልቅ” ስለሆነ “አዘቅት” ደግሞ “ጠባብ” ስለሆነ እነዚህ ወደ ውስጥ ለመውደቅ በጣም ቀላልና ለመውጣት ግን በጣም ከባድ የሆኑ ስፍራዎች ናቸው።
ምግባረ ብልሹ ሴት ጠባብ አዘቅት ናት
አንድ ሰው የሚቀጣበትን ክፉ ስራ መስራት ፈጽሞ ሊያመልጠው በማይችለው በጠባብ ስፍራ እንደ መውደቅ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሌላ ሰው ሚስት ጋር መተኛት በጠባብ አዘቅት እንደ መውደቅ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የውኃ ጉድጓድ
ሰዎች ውኃ ለማግኘት ሲሉ በመሬት ላይ የቆፈሩት ጉድጓድ
አድፍጣ ትጠብቃለች
ተጠቂ ሲመጣ ለማጥቃት በስውር ትጠብቃለች
ከዳተኛ ሰው
ይህ የስም ቅጽል እንደ ቅጽል ወይም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከዳተኛ ሰዎች”` ወይም “ሌሎች ሰዎችን በማታለል የሚጎዱ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 23:29
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ዋይታ የማን ነው? ሃዘን የማን ነው? ጠብስ የማን ነው? ማጉረምረም የማን ነው? ያለ ምክንያት

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መቁሰል የማን ነው? የዓይን መቅላት የማን ነው?
ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ስለ አንድ ሰው መናገር የፈለገውን ነጥብ አንባቢው መጨበጥ እንዲችል ለማዘጋጀት ነው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ እንዲመለስለት አይጠብቅም። የአንተ ቋንቋ አንድን ትምህርት ለማስተዋወቅ የተለየ መንገድ ይኖረው ይሆናል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ምን ዓይነት ሰው ዋይታ፣ ኃዘን፣ ትግል፣ ማጉረምረም፣ ያለ ምንም ምክንያት ቁስልና የዓይን ቅላት እንዳለበት ስነግርህ አድምጠኝ። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
የዓይን ቅላት
“እንደ ደም ቀለም ዓይን መቅላት”
ወይን ጠጅ በመጠጣት የሚቆዩ፣ ድብልቅ ወይን ጠጅ የሚቀምሱ ሰዎች ነው
እነዚህ ቃላቶች በቁጥር 29 ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡና ብዙ ወይን የሚጠጡ ሰዎችን የሚገልጹ ናቸው።
ወይን ጠጅ በመጠጣት የሚቆዩ
ወይን በመጠጣት ብዙ ጊዜ የሚያሳልፉና ከዚህ የተነሳ ብዙ ወይን የሚጠጡ (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ድብልቅ ወይን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) የተለያዩ ወይኖች በአንድ ላይ ተደባልቀው ወይም 2) ከወይን ይልቅ በጣም ጠንካራ የሆኑ መጠጦች
Proverbs 23:31
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
በመጨረሻ
“ወይኑን ከጠጣህ በኋላ”
እንደ እባብ ይናከሳል … እንደ እፉኝትም ይናደፋል
“ይናከሳል” እና “ይናደፋል” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት “ወይኑ ቀይ ሲሆን” ነው። “ንክሻ” እና “ንድፊያ” ብዙ ወይን ሰዎች እንዲሰማቸው ለሚያደርግበት መንገድ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እባብ እንደነከሰህና እፉኝት እንደነደፈህ እንደነደፈህ መጥፎ ስሜት እንዲሰማህ ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እፉኝት
መርዘኛ የእባብ ዓይነት
ልብህ ጠማማ ነገሮችን ይናገራል
“ልብ” የሚለው ቃል የሚወክለው ሰውየውን ሲሆን ለሚያስበውና ለማድረግ ለሚወስነው ነገር አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ነገር ታስባለህ ደግሞም ጠማማ ነገሮችን ለማድረግ ትወስናለህ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠማማ ነገሮች
እግዚአብሔር በስነ ምግባር የተበላሹና መጥፎ እንደሆኑ የተናገራቸው፤ ክፉ የሆኑ ነገሮች
Proverbs 23:34
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)። የሰካራም ሰው ገለጻ ቀጣይ ክፍሎች ናቸው።
ምሰሶ ጫፍ ላይ ይጋደማል
ሰውየው የተጋደመበት ምሰሶ ጫፍ ላይ ያለው ስፍራ በሚገባ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በምሰሶ ጫፍ አጠገብ በቅርጫት ውስጥ ተጋድሟል” (ፈሊጥ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ምሰሶ ጫፍ
ቀዛፊ መርከብ ላይ ያሉ የመርከብ ሸራዎችን የሚያያይዙ በጣም ረጅም የእንጨት ምሰሶዎች።
“መቱኝ!” “ነገር ግን አልተጎዳሁም። ደበደቡኝ፣ ነገር ግን አልተሰማኝም።
የሰከረ ሰው በሚገባ ማሰብ ስለማይችል ሰዎች እንደሚመቱትና እንደሚደበድቡት ያስባል፣ ነገር ግን ምንም ዓይነት ሕመም አይሰማውም ደግሞም ምንም ዓይነት ነገር አያስታውስም።
መቼ እነቃለሁ?
የሰከረ ሰው እንደገና የሚነቃበትን ጊዜ መቼ እንደሆነ ይጠይቃል፤ የወይን ስራ በውስጡ መስራት ባቆመ ጊዜ።

---

# Chapter 24
Proverbs 24:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ልባቸው
“ልባቸው” የሚለው ቃል የሰው ሁለንተና የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከንፈሮቻቸው
“ከንፈሮቻቸው” የሚለው ቃል የሰው ሁለንተና የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 24:3
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ቤት በጥበብ ይሰራል፣
“ጥበብ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። እነዚህ ቃላቶች በገቢር ግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ጥሩ ቤት መስራት የሚፈልጉ ከሆነ ጥበበኛ መሆን አለባቸው” (ረቂቅ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በማስተዋልም ይጸናል
ይህ “ማስተዋል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ቤት ለመስራት የሚፈልጉ ከሆነ መልካም ባህርይና መጥፎ ባህርይ ምን እንደሆነ መረዳት አለባቸው” (ረቂቅ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ይጸናል
“ይጸናል” የሚለው ቃል ጽኑ እና ጠንካራ መሆን ማለት ነው። “ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው፣ ጽኑ እና ጠንካራ ሆኖ የተሰራው ቤት ደግሞ በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ተለዋጭ ዘይቤ ነው። (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በእውቀትም ክፍሎቹ ይሞላሉ
“እውቀት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች መኖርያ ክፍሎቻቸው እንዲሞሉ የሚፈልጉ ከሆነ ውድና አስደሳች የሆነውን ነገር ማወቅ ያስፈልጋቸዋል” (ረቂቅ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 24:5
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ተዋጊና ጥበበኛ
ይህ “ጥበብ” የሚለው ረቂቅ ስም “ጥበበኛ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥበበኛ ተዋጊ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እውቀት ያለው ሰው ጥንካሬውን ይጨምራል
ይህ “እውቀት” እና “ጥንካሬ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “እወቅ” በሚለው ግስ እና “ጠንካራ” በሚለው ቅጽል ሊተረጎም ይችላል” አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ነገሮች የሚያውቅ ሰው ጠንካራ ነው ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች ያውቃል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በጥበበኛ ምክር
ይህ “ምክር” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረገም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምን ማድረግ እንዳለብህ የሚነግሩህ ጥበበኛ ሰዎች” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጦርነትህን መዋጋት ትችላለህ፣
“ጦርነት ተዋጋ”
አማካሪዎች
ለመንግስት አካላት ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚነግሩአቸው ሰዎች

Proverbs 24:7
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ለሞኝ ሰው እጅግ ትርቃለች
ይህ “ለሞኝ ሰው እጅግ ትርቃለች” የሚለው ፈሊጥ ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
አፉን አይከፍትም
አፍ የሚለው ቃል ከአፍ ለሚወጡ ቃላት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም:- “መናገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 24:8
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
የተንኮል አለቃ
ክፉ እቅድ የሚያቅድ ክህሎት ያለው ሰው። አማራጭ ትርጉም:- “አታላይ ሰው” ወይም “ችግር ፈጣሪ”
Proverbs 24:10
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
አቅምህ ትንሽ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “በጣም ትንሽ ኃይል አለህ” ወይም “በእርግጥም ደካማ ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 24:11
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
የሚነዱትን
እነዚህ ቃላት “እነርሱ” በሚለውና ማንኛውም ሰው የሚል ትርጉም ባለው ቃል በመጠቀም በገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል፣ ነገር ግን እነዚህ የመንግስት ባለስልጣኖች ሊሆኑ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- “እነርሱን የወሰዱአቸው ሰዎች” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የተወሰዱ
ሌላ አማራጭ ትርጉም “የተጎተቱ” የሚል ነው።
የሚንገዳገዱትን
እየተንቀጠቀጡ መራመድና ለመውደቅ መድረስ። ይህ ቃል አንድ ሰው ሲጎተት እንዴት እንደሚራመድ የሚገልጽ ነው።
ለመታረድ
“መታረድ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። ጸሐፊው ሲናገር የሚወስዱአቸው ሰዎች ከእንስሳሳ ያልተሸሉ እንደሆኑ ያስባል። የአንተ ቋንቋ እንስሳትን ለማረድ የሚገልጽበት ቃል ካለው እርሱ ተገቢ ሊሆን ይችላሉ፣ ይህንን መጠቀም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም:- “እንስሳ እንደሚገድሉ ሰዎችን ወደሚገድሉበት ሰፍራ” (ረቂቅ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተም “እዚያ! ስለዚህ ነገር ... ” ብትል
ጸሐፊው አንባቢው ምናልባት በስህተት ስላሰበው አንድ ነገር መልስ እየሰጠው ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እንዲህ ትላህ ‘እነሆ፣ ... ይህ፣’ ነገር ግን ሰራ”
እነሆ፣ እኛ
“እኛን አዳምጡ! እኛ” ወይም “ነገር ግን እኛ” ወይም “እኛ ምንም ሰህተት ነገር አልሰራንም፣ ምክንያቱም እኛ ... ”
ልብን የሚመረምረው እርሱ ንግግርህን አያስተውለውምን?
ጸሐፊው አንባቢዎቹ መልሱን ያውቃሉ ብሎ ያስባል፣ ከዚህ የተነሳ አጽንዖት ለመስጠት ሲል ይህን ጥያቄ ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም:- “ልብን የሚመረምረው እርሱ ንግግርህን በሚገባ ይረዳል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ
ጸሐፊው “እርሱ” የሚለው እግዚአብሔር እንደሆነ አንባቢው ያውቃል ብሎ ያስባል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር፣ እርሱ” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ልብን ይመረምራል
“ልብ” ሰው ለሚያስበውና ለሚመኘው ነገር ምትክ ስም ነው። ጸሐፊው ሰው የሚያስበውና የሚመኘው ነገር ቁስ የሆነ ያህል ሰው የሚመዝነው አድርጎ ተናግሮታል፤ አንድን ነገር መመዘን ምን ያህል ጥሩ እንደሆነ ለማወቅ አንድ ነገር ላይ አስተውሎ ለማየት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ሰዎች የሚያስቡትና የሚመኙት ነገር ምን ያህል ጥሩ እንደሆነ ያውቃል” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሕይወትህን የሚጠብቀው እርሱ አያውቅምን?
ጸሐፊው አንባቢዎቹ መልሱን እንደሚያውቁቱ ያስባል ከዚህ የተነሳ ይህንን አጽንዖት ለመስጠት ሲል ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም:- “ሕይወትህን የሚጠብቀው እርሱ ያውቀዋል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ለእያንዳንዱ እንደ ስራው መጠን እግዚአብሔር አይሰጠውምን?
ጸሐፊው አንባቢዎቹ መልሱን እንደሚያውቁቱ ያስባል ከዚህ የተነሳ ይህንን አጽንዖት ለመስጠት ሲል ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እንደ ስራው መጠን ይሰጠዋል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 24:13
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ተስፋህም አይጠፋም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) ይህ ተሳቢ ቅርጽ ሲሆን እንደ ገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ተስፋህን ማንም ሰው አይወስድብህም” ወይም 2) ይህ በአዎንታዊ ቅርጽ ሊተረጎም የሚችል ምፀት ነው። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 24:15
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
አድፍጠህ አትጠብቅ
“አድፍጠህ አትጠብቅ” የሚሉት ቃላት ፈሊጥ ነው። “አድፍጠህ አትጠብቅ” የሚለውን በምሳሌ 1:11 ላይ እንደተረጎምኸው ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም:- “አጋጣሚውን ለመጠቀም አድፍጠህ አትጠብቅ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ቤቱ
የጻድቅ ሰው ቤት
እንደገና ይነሳል
“በእግሩ እንደገና ይነሳል” ወይም “እንደገና ይቆማል”
ክፉ ሰዎች ግን በመቅሰፍት ላይ ይወድቃሉ
ጸሐፊው “መቅሰፍት” በሌሎች ሰዎች ላይ መጥፎ ነገሮችን የሚያደርግ ሰው እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። እነዚህ ቃላት እንደ ገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ለመጣል መቅሰፍት ይጠቀማል” (ሰውኛ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ይወድቃሉ
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ሲሆን የሚወክለው ቆሞ የነበረ ሰው ነገር ግን ሌላ ሰው ወደ መሬት ወደታች ጎትቶ ያመጣው ወይም እንዲወድቅ ያደረገው ሰው ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መቅሰፍት
በሰዎችና በንብረታቸው ላይ መጥፎ ነገር የተከናወነበት ጊዜ
Proverbs 24:17
አጠቃላይ መረጃ:-
እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።
ጠላትህ ይወድቃል
“መጥፎ ነገር በጠላትህ ላይ ይሆናል”
ደስ አይበልህ
ይህ ጠንካራ ትእዛዝ ነው። “ልብ” የሚለው ቃል ሰውየውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ደስተኛ ለመሆን ለራስህ አትፍቀድለት” ወይም “ደሰተኛ ከመሆን ራስህን ከልክል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ተመልሶም ቁጣውን ከእርሱ ይመልሳል

“ቁጣውን ከእርሱ ይመልሳል” የሚሉት ቃላቶች ለወደፊት ቁጡ ላለመሆን ፈሊጥ ናቸው። ከዚህ ይልቅ እግዚአብሔር ለወደፊት የሚሰራው ነገር ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእርሱ ላይ መቆጣትህን አቁምና ይልቁንም በራስህ ላይ ተቆጣ” (ፈሊጥ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 24:19

አጠቃላይ መረጃ፡-

እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

የክፉ ሰውም መብራት ይጠፋልና

መብራት ለሕይወት እንደ ተለዋጭ ዘይቤ ጥቅም ላይ ውሏል። መብራት ወዲያው እንደሚጠፋ እንደዚሁ የክፉ ሰዎች ሕይወት ይጠፋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 24:21

አጠቃላይ መረጃ፡-

እነዚህ ጥቅሶች “ሰላሳ የተግሳጽና የእውቀት ቃሎች” የተባሉትን ይቀጥላሉ (ምሳሌ 22:20)።

ፍርሃት

ጥልቅ አክብሮት እና በስልጣን ላይ ለሚገኝ ሰው የሚደረግ አክብሮታዊ ፍርሃት።

ከሁለቱም የሚመጣውን ጥፋት ምን ያህል እንደሆነ ማን ያውቃል?

ጸሐፊው የጥፋቱን ከፍተኛነት አጽንዖት ለመስጠት ይህን ጥያቄ ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከሁለቱም የሚመጣውን ጥፋት ምን ያህል እንደሆነ ማንም ሰው አያውቅም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከሁለቱም

እነዚህ ቃላቶች እግዚአብሔርን እና ንጉሱን ይወክላሉ

Proverbs 24:23

እነዚህ ደግሞ የጥበበኞ ሰው ንግግር ናቸው

ይህ ዓረፍተ ነገር የምሳሌ አዳዲስ ስብስቦችን ይጀምራል።

በዳኝነት

አንድ ሰው ሕግ በመተላለፉ ምክንያት ተከስሶ በዳኛ ፊት የቀረበ አንድ ሁኔታ

Proverbs 24:24

ወንጀለኛውን … የሚለው በሕዝብ ዘንድ ይረገማል፣ በመንግስታትም ዘንድ ይጠላል።

“መንግስታት” የሚለው ቃል በአገሮቹ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ምትክ ስም ነው። እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉውን ሰው … ለሚለው ሰዎች ይረግሙታል፣ የሌሎች አገሮች ሕዝቦች ደግሞ ይጠሉታል”

ክፉ ሰው … ጻድቅ ሰው

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ሰዎች ለክፉ ሰው ጻድቅ ሰው ብለው ሊጠሩት በፍጹም አይገባም ወይም 2) ሕግ በመተላለፉ ምክንያት ወንጀለኛ ለሆነ ሰው ማም ሰው ንጹሕ ነው ሊለው አይገባም። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕግ በመተላለፉ ምክንያት ወንጀለኛ የሆነ ሰው … ንጹሕ ሰው”

ደስ ይለዋል

“በጣም ደስተኛ ይሆናል”

የደግነት ስጦታዎችም ወደ እነርሱ ይመጣሉ

ስጦታዎች በራሳቸው መንቀሳቀስ የሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። “ደግነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ጥሩ ስጦታዎች ይሰጧቸዋል” (ሰውኛ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የደግነት ስጦታዎች

“ጥሩ ነገሮች” ወይም “በረከቶች”

Proverbs 24:28

በከንፈሮችህ

ከንፈሮች ሰውየው ለተናገራቸው ቃላቶች ምትክ ስም ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “በተናገርኸው ቃል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ዋጋውን እከፍለዋለሁ

ይህ ፈሊጥ ነው። “እርሱን እበቀለዋለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 24:30

እሾህ

ጥቅቅ የሌላቸው ሹል እሾህ ያለባቸው ተክሎች

ሳማ

በሚያቃጥል ቅጠሎችና ጸጉሮች የተሸፈነ ተክል

ፈርሶ ነበር

“ወድቆ ነበር”

Proverbs 24:32

ተግሳጽን ተቀበልሁ

“ትምህርት ተማርሁ”

ጥቂት እንቅልፍ … ጥቂት ለማረፍ … ድህነት ይመጣል

የተዘለሉትን ቃላት መሙላት ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለራስህ እንዲህ ትለው ይሆናል፣ ‘ጥቂት እንቅልፍ … ጥቂት ማረፍ’ - ነገር ግን ወዲያውኑ ድህነት ይመጣል” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ድህነት በአንተ ላይ ይመጣል

አንዳንድ ትርጉሞች እንዲህ ብለው ተርጉመውታል፣ “ድህነት እንደ ሌባ በአንተ ላይ ይመጣል።” ድህነት ሰነፍ ሰውን ሊያጠቃ የሚችል ሰው ወይም እንስሳ ተደርጎ ተነግሯል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ችግርህም መሳሪያ እንደታጠቀ ወታደር ይመጣብሃል

ችግር ሰነፍ ሰው ሊያጠቃ የሚችል ሰው እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ችግርህም መሳሪያ እንደታጠቀ ወታደር ሆኖ ወደ አንተ ይመጣብሃል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 25

Proverbs 25:1

ነገርን መሰወር

“አንዳንድ ነገሮችን በምስጢር መያዝ”

ነገር ግን ክብር

አስጨምሬ ለሞላ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ክብር ነው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

መርምረህ አውጣት

“ይህንን ጉዳይ መርምረህ አውጣው” ወይም “እግዚአብሔር የሰወረውን ነገር መርምር”

ሰማያት ከፍ ያሉ እንደሆኑ፣ ምድርም ጥልቅ እንደሆነች ሁሉ፣ የነገስታት ልብም አይመረመርም

የንጉስ ልቦች ከሰማያትና ከምድር ግዝፈት ጋር ተነጻጽረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰማያትን ከፍታና የምድርንም ጥልቀት አንድም ሰው ሊለካው እንደማይችል ሁሉ የነገስታትን ልብ አንድም ሰው ሊመረምረው አይችልም” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማያት

ይህ ጸሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ጨምሮ ከምድር በላይ የምናየውን ማኛውንም ነገር የሚያመለክት ነው።

Proverbs 25:4

ቆሻሻ

ሰዎች የማይፈልጉት በብረት ላይ ያለ ነገርና ብረቱን በማሞቅ የሚያሰስወግዱት

ዙፋኑ ጽድቅን በማድረግ ይጸናል

ዙፋን ለመምራት ለሚያስፈልገው ስልጣን ምትክ ስም ነው። እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉስ በማድረግ ዙፋኑን ያጸናል” ወይም “ለመምራት ስልጣን ይኖረዋል ምክንያቱም ይሰራል” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 25:7

ይልቅ፣ እርሱ “ወደዚህ ና” ቢልህ ይሻላል።

እዚህ ላይ “ና” የሚለው ለንጉሱ ቅርብ የሆነው ጠረጴዛ ወዳለበት ስፍራ ተነስቶ መጠጋት ማለት ነው። ከንጉሱ አጠገብ መቀመጥ ለአንድ ሰው ትልቅ ክብር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ከ … ይልቅ አንድ ሰው ከንጉሱ አጠገብ እንድትቀመጥ ቢጋብዝህ ይሻላል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በተከበሩ ሰዎች ፊት

“በተከበሩ ሰዎች ፊት ለፊት”

ጎረቤትህ ባሳፈረህ ጊዜ በመጨረሻ ምን ታርጋለህ?

ይህ ጥያቄ የተጠየቀው አንባቢው ሁኔታውን በተሳሳተ መንገድ የመረዳት እድል ሊገጥመው እንደሚችል ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ ነው። ጎረቤቱ አንባቢውን

ለሃፍረት ሊዳርገው የሚችልበት መንገድ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በመጨረሻ ጎረቤትህ ለሃፍረት ከዳረገህ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለብህ አታውቅም” ወይም “ጎረቤትህ ማብራሪያ ካለው፣ አንተን ለሃፍረት ይዳርግሃል፣ ከዚያ በኋላ ራስህን ለመከላከል ምንም የምትናገረው ነገር የለህም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 25:9
ጉዳይህ
“አለመስማማትህ”
የሌላ ሰው ምስጢር ግን አታውጣ
“የጎረቤትህን ምስጢር ለሌሎች ሰዎች አታውራ”
ስለ አንተም ልትመልሰው የማትችለው መጥፎ ወሬ ይወራብሃል
እዚህ ላይ “መጥፎ ወሬ” አንድ ሰው ለሌሎች ሰዎች የሚናገረው ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን ይወክላል። “ልትመልሰው የማትችለው” የሚለው ሀረግ በግስ ቅርጽ ሊገለጽ ይችላ። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ አንተ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን ከመናገር ልታስቆመው አትችልም” ወይም “ስለ አንተ ክፉ ነገሮችን ለሌሎች ሰዎች ይናገራል ከዚህ የተነሳ ጥሩ ስም አይኖርህም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 25:11
በብር ላይ እንደተቀረጸ የወርቅ ንድፍ፣ በትክክለኛ ሁኔታ የተነገረ ቃል እንዲሁ ነው
“በትክክለኛ ሁኔታ የተነገረ ቃል” መልካምነት በአካል እንደሚታይ “በብር ላይ እንደተቀረጸ የወርቅ ንድፍ” ውበት ተደርጎ ተነግሯል። ብዙ ትርጉሞች ይህንን ተለዋጭ ዘይቤ እንደ ተነፃፃሪ ዘይቤ በመተርጎም የሀረጎቹን ቅደም ተከተል ለውጠዋቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “በትክክለኛ ሁኔታ የተነገረ ቃል፣ በብር ላይ እንደተቀረጸ የወርቅ ንድፍ ውብ ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በብር ላይ እንደተቀረጸ የወርቅ ንድፍ
የጥንት እስራኤላውያን ዛሬ ብዙ ሰዎች የሚያውቁትን ንድፍ አያውቁም። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ንድፎች” የሚለው “ዲዛይን” ተብሎ ሊተረጎም ይገባል።” አማራጭ ትርጉም፡- “የወርቅ ዲዛይን በብር ሳህን ላይ የተቀረጸ” ወይም 2) “ፖም” አንድ ሰው በዝርግ ወይም በጎድጓዳ ሳህን ላይ ያስቀመጠው ወርቃማ ቀለም ያለው ሌላ ዓይነት ፍሬ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በብር ሳሳን ላይ የተቀመጠ ወርቃማ ቀለም ያለው ፍሬ”
የተነገረ ቃል ነው
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው የተናገረው መልእክት ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ለሚሰማ ጆሮ የጥበበኛ ተግሳጽ እንደ ወርቅ ቀለበት፣ ከንጹህ ወርቅም እንደተሰራ ጌጥ ነው
“የጥበበኛ ተግሳጽ” ዋጋና አስፈላጊነት የወርቅ ውበትና ዋጋ እንዳለው ተደርጎ ተነግሯል። ብዙ ትርጉሞች ይህንን ተለዋጭ ዘይቤእንደ ተነፃፃሪ ዘይቤ ተርጉመውታል እና የሀረጎቹ ቅደም ተከተል ቀይረውታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የጥበበኛ ተግሳጽ ለሚሰማ ጆሮ እንደ ወርቅ ቀለበት ወይም የወርቅ ጌጥ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለሚሰማ ጆሮ
ጆሮ ለሰው ሁለንተና ተዛምዶአዊ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለመስማት ፈቃደኛ የሆነ ሰው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 25:13
በምርት መሰብሰቢያ ወቅት እንዳለ የበረዶ ቅዝቃዜ ታማኝ መልዕክተኛ
እዚህ ላይ ታማኝ መልእክተኛ ከበረዶ ቅዝቃዜ ጋር ተነጻጽሯል ምክንያቱም ሁለቱም ደስ የሚያሰኙ ናቸው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የበረዶ ቅዝቃዜ
በረዶ የሚወርደው መተራራ ጫፎች ላይ ብቻ ነው፣ ምርት የሚሰበሰበው ደግሞ በሞቃት ወቅት የአየር ሁኔታ ነው፣ ስለዚህ ይህ ምናልባት ከንጹህ ምንጭ ለሚወጣ ቀዝቃዛ ውኃ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በረዶ
እንደ ዝናብ ከሰማይ የሚወርድ ነጭ የደቀቀ በረዶ
የጌቶቹን ሕይወት ይመልሳል
ደካማና አቅመ ቢስ የሆኑትን ጌቶቹን ጠንካራና በእረፍት የተሞሉ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።
የማይሰጠውን ስጦታ እሰጣለሁ ብሎ የሚመካ ሰው ዝናብ እንደሌለው ደመናና ንፋስ ነው
ብዙ ትርጉሞች ይህን ተለዋጭ ዘይቤ እንደ ተነፃፃሪ ዘይቤ ተርጉመውታል፣ የሀረጎቹንም ቅደም ተከተል ለውጠዋቸዋል። ዝናብ ለእስራኤላውያን በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም የሚዘንበው በጣም ትንሽ ዝናብ ነው፣ ስለዚህ ዝናብ የሌለው ደመና ጥቅም የሌለውና እስራኤላውያንን የሚያሳዝን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚመካ ነገር ግን የማይሰጥ ሰው ዝናብ እንደሌለው ደመናና ነፋስ ነው” ወይም “የማይሰጥ ነገር ግን የሚመካ ሰው ዝናብ እንደሌለው ደመናና ነፋስ ጥቅም የሌለውና ኀዘን የሚያመጣ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 25:15
በትዕግስት ገዢን እንዲለዝብ ማድረግ ይቻላል
እነዚህ ቃላት በገቢር ቅርጽ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ትእግስተኛ የሆነ ሰው ንጉስን እንዲለዝብ ማድረግ ይችላል” ወይም “ትእግስተኛ ሰው ከንጉስ ጋር መነጋገርና ሃሳቡን ማስለወጥ ይችላል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
መልካም ምላስ አጥንትን መስበር ትችላለች
“ምላስ” ሰው ምላሱን በመጠቀም ለሚናገረው ንግግር ምትክ ስም ነው። “አጥንት” የሚለው ቃል ለጠንካራ ተቃውሞ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም ንግግር ጠንካራ ተቃውሞን ማሸነፍ ይችላል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 25:16
አጠቃላይ መረጃ፡-
ቁጥር 16 አጠቃላይ መርህ የሚናገር ሲሆን ቁጥር 17 ደግሞ አንድ የተወሰነ ምሳሌ ይሰጣል። ብዙ ማር የመብላትና የመትፋት ሃሳብ ብዙ መልካም ነገር ለመውሰድና በኋላ ለመጸጸት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 25:18
በጎረቤቱ ላይ በሐሰት የሚመሰክር ሰው በጦርነት ላይ ጥቅም ላይ እንደሚውል ዱላ፣ ሰይፍ ወይም የተሳለ ቀስት ነው
ሐሰተኛ ምስክር ሰዎችን ከሚጎዱ ወይም ከሚገድሉ ከሶስት መሳርያዎች ጋር ተነጻጽሯል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በችግር ጊዜ የታመንከው ወስላታ ሰው እንደ ተበላሸ ጥርስ ወይም እንደሚያነክስ እግር ነው
ሞኝ ሰው ለሰው ችግር ከሚፈጥር የሰውነት ክፍል ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በችግር ጊዜ ወስላታ ሰውን መታመን እንደ ተበላሸ ጥርስ ወይም እንደሚያነክስ እግር ችግር ያመጣብሃል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 25:20
በሶዳ ላይ ኮምጣጤ
ይህ እንደ ኮምጣጤ ያሉ የአሲድ ፈሳሽ ጋር ሲገናኝ በኃይል የሚፍለቀለቅና ተሽ የሚል ድምጽ የሚያሰማ የማዕድን ዓይነት ነው። ብዙ ትርጉሞች ይህንን ሀረግ “ቁስል” ብለው ይተረጉምታል።
መዝሙር የሚዘምር
ዘማሪዎቹ የሚዘምሩት ምን ዓይነት መዝሙር እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጥ ያስፈልግ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፡- “ደስ የሚሉ መዝሙሮች ይዘምራሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ያዘነ ልብ
x
Proverbs 25:21
በራሱ ላይ ፍም ትከምራለህና
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የበደለኝነት አእምሮ እንዲፈጠርበትና የሰራው ስራ እንዲያሳፍረው ያደርጋል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 25:23
የሰሜን ነፋስ
በእስራኤል አገር ከሰሜን የሚመጣ ነፋስ ብዙ ጊዜ ዝናብ ይዞ ይመጣል። ተርጓሚዎች ተመሳሳይ ውጤት ለሚያሳይ ሁኔታ የተለያዩ ዓይነት ነፋሳትን ለመጠቀም ነጻነት አላቸው፣ ለምሳሌ፡- “ቀዝቃዛ ነፋስ።”
ምስጢር የሚያባክን ምላስ
አንዳንድ ትርጉሞቸ ይህን “ምስጢር የሚያባክን አንድ ሰው” ብለው ተርጉመውታል።
የሰዎችን ፊት ያስቆጣል
ፊት ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌሎች ሰዎችን በጣም ያስቆጣል፣ ይህንን ደግሞ በፊታቸው ማየት ትችላላህ” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

በጣራ ማእዘን
በዚያን ጊዜ የነበሩ ቤቶች ለጥ ያለ ጣራ ነበራቸው። የጥንት እስራኤላውያን ጣራቸውን ለመስራት ብዙ ጊዜ ይወስድባቸው ነበር። ጣራው ከቤቱ ውስጠኛው ክፍል ይልቅ ቀዝቃዛ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለመኝታ የሚሆን ትልቅ መጠለያ በጣራው በአንዱ ማእዘን ላይ ይሰሩ ነበር። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ጠበኛ ሚስት
“ብዙ ጊዜ የምትጨቃጨቅና የምታማርር ሚስት”
Proverbs 25:25
ለተጠማ ሰው ቀዝቃዛ ውሃ እንደሚያረካው ሁሉ፣ ከሩቅ አገር የመጣ የምስራችም እንዲሁ ነው
ቀዝቃዛ ውሃ ከሚያድስና ከሚያስደስት መልካም የምስራች ጋር ተነጻጽሯል፡፡ (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በክፉ ሰዎች ፊት የሚንበረከክ ጻድቅ ሰው፣ እንደ ተበከለ ወንዝና እንደተበላሸ ምንጭ ነው
አንድ ሰው ጻድቅ ለሚያምነት ነገር በጽናት እንዲቆም እንደሚጠብቅ ሁሉ እንዲሁ፣ አንድ ሰው ወንዝና ምንጭ ንጹህ ውኃ እንዲኖረው ይጠብቃል። የተበከለ ወንዝና የተበላሸ ምንጭ በአቋሙ ከወደቀ ጻድቅ ሰው ጋር ተነጻጽሯል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በክፉ ሰዎች ፊት የሚንበረከክ
መንበርከክ ለሚከተሉት ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡- 1) ክፉ ሰዎችን ለመጋፈጥ አለመፈለግ ወይም 2) በክፋታቸው መሳተፍ። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎች ክፋት እንዲያደርጉ መፍቀድ” ወይም “ክፉ ሰዎች የሚሰሩትን ስራ መስራት የሚጀምር ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መንበርከክ
መንበርከክ መልካም ስራ መስራት መቀጠል ለአለመቻል ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለመቆም አለመቻል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በክፉ ሰዎች ፊት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ክፉ ሰዎች ሲያጠቁት” ወይም 2) “ክፉ ሰዎች ክፉ ነገር እንዲሰሩ ሲገፉት፡፡” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 25:27
እጅግ በጣም ብዙ ማር መብላት ጥሩ አይደለም፤ በክብር ላይ ክብር እንደመፈለግ ነው
ሁሉም አንተን ሊያከብሩህ ሲፈለጉና ማር መብላት መልካም ነው፣ ነገር ግን ብዙ ማር መብላት ትችላለህ፣ ሰዎች አንተን ሊያከብሩህ መሞከር አስቸጋሪ ይሆንብሃል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መልካም አይደለም
ይህ በአዎንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የይህ መጥፎ ነገር ነው” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
በክብር ላይ ክብር እንደመፈለግ ነው
“ይህ ሌሎች አንተን እንዴት እንደሚያከብሩህ ሁልጊዜ እንደ ማሰብ ነው፡፡” የመጀመርያው ቋንቋ ትርጉም ግልጽ አይደለም። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን “ለሰዎች በጣም ብዙ አስተያየቶችን እንደ መናገር ነው” ብለው ተርጉመውታል።
ራሱን መግዛት የማይችል ሰው እንደፈረሰችና ቅጥር እንደሌላት ከተማ ነው
ራሱን መግዛት የማይችል ሰውና ቅጥር የሌላት ከተማ ደካማና ተጋላጭ ናቸው፡፡ (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የፈረሰና ቅጥር የሌላት
“የግንብ አጥሮቹን ወታደር ያጠቃውና ያፈረሰው”

---

Chapter 26
Proverbs 26:1
በበጋ ጊዜ እንደሚወርድ በረዶና በመከር ጊዜ እንደሚዘንብ ዝናብ
ብዙውን ጊዜ በረዶ በበጋ ጊዜ አይወርድም፣ ዝናብ ደግሞ በመከር ጊዜ አይዘንብም። ይህ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በረዶ በበጋ ጊዜ መውረድና ዝናብ ደግሞ በመከር ጊዜ መዝነብ እንግዳ ነገር እንደሆነ ሁሉ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ያልተገባ እርግማን ማንም ላይ አይደርስም
ሰውን የማይጎዳ እርግማን መሬት ላይ እንደማታርፍ ወፍ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ ያልተገባ እርግማን በታሰበው ሰው ላይ አይደርስም” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ያልተገባ እርግማን
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በማይገባው ሰው ላይ የሚደረግ እርግማን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
አረፈ
በአንድ ሰው ወይም ነገር ላይ ማረፍ
Proverbs 26:3
ጅራፍ ለፈረስ፣ ልጓምም ለአህያ እንደሆነ፣ በትርም ለሞኞች ጀርባ ነው፡፡
ጅራፍ፣ ልጓምና በትር ሰዎ ፈረስ፣ አህያና ሞኝ ሰው የፈለጉትን እንዲያደርጉ የሚጠቀሙባቸው ነገሮች ናቸው።
ልጓም ለአህያ ነው
ልጓም ከጠፍር የተሰራ ነው። ሰዎች ልጓሙን በአህያው ራስ ላይ ያስገቡትና አህያውን ወደሚፈልጉት ቦታ እንዲሔድ ለማድረግ ከጠፍሩ አንዱን ይይዙታል።
ጅራፍ ለሞኞች ጀርባ ነው
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች ልጆቻቸውን ወይም ባሪያዎቻቸውን ስርዓት ለማስያዝ በአንጨት በትር ይመቷቸው ነበር።
Proverbs 26:5
ሞኝን እንደ ሞኝነቱ መልስለት፣ በሞኝነቱም ተባበረው፣
ለሞኝ ስትመልስለት በሞኝነቱ መተባበር በሞኝነት መንገድ ለእርሱ መመለስን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለሞኝ እንደሞኝነቱ መልስለት” ወይም “ለሞኝ በሞኝነት መልስለት”
ስለዚህ በዓይኖቹ ጥበበኛ የሆነ እንዳይመስለው
ዓይን መመልከትን ይወክላል፣ መመልከት ደግሞ ሃሳብንና ግንዛቤን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ በእርሱ ግንዛቤ ጥበበኛ የሆነ እንዳይመስለው” ወይም “ስለዚህ ራሱን ጥበበኛ እንደሆነ እንደያስብ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በሞኝ ሰው እጅ መልዕክትን የሚልክ ሁሉ
እዚህ ላይ እጅ መልእክትን ለማድረስ ሞኝ ያለውን ኃላፊነት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልእክት እንዲያደርስለት ሞኝን የሚልክ ሁሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የራሱን እግር ይቆርጣል
የራስን እግር መቁረጥ ራስን ለመጉዳት የግነት መግለጫ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የራሱን እግር እንሚቆርጥና ሁከትን እንደሚጠጣ ሰው ራሱን ይጎዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሁከትንም ይጠጣል
ሁከት አንድ ሰው ሊጠጣው የሚችል መርዛም ፈሳሽ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሁከት ፈጣሪነት ራሱን ይጎዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 26:7
እንደ እግሮች … በሞኝ አፍ ያለ ምሳሌ እንዲሁ ነው
የእነዚህ ሀረጎች አቀማመጥ ቅደም ተከተሉ ሊለወጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሞኝ አፍ ያለ ምሳሌ እንደ ተንጠለጠሉ የሰለሉ የሽባ እግሮች ናቸው” ወይም “በሞኝ አፍ ያለ ምሳሌ እንደ ተንጠለጠሉ የሰለሉ የሽባ እግሮች የማይጠቅሙ ናቸው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሽባ
መንቀሳቀስ የማይችል ሰው ወይም ሁሉም ወይም ከፊል ሰውነቱ እንዲህ የሚሰማው
በሞኞች አፍ
“አፍ” ለመናገር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በሞኞች ንግግር” ወይም “ሞኞች የሚናገሩት ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ድንጋይን በወንጭፍ ማሰር
ወደ ረጅም ርቀት ድንጋይ ለመወርወር ሰዎች ድንጋይ በወንጭፍ ያስቀምጣሉ ከዚያም ግንጋዩ በጣም በፍጥነት ወደቦታው እንዲስፈነጠር ወንጭፉን ያዞሩታል። ድንጋይን በወንጭፍ የማሰር ውጤት በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዳይወረወር ድንጋይን በወንጭፍ ማሰር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለሞኝ ክብር መስጠት
“ሞኝን ማክበር”
Proverbs 26:9

እንደ እሾህ ... በሞኝ አፍ ውስጥ ያለ ምሳሌ እንዲሁ ነው
ሁለቱ እንዴት ተመሳሳይነት እንዳላቸው በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በሰካራም እጅ እንደገባ እሾህ በሞኝ አፍ ውስጥ ያለ ምሳሌ አደገኛ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በሰካራም እጅ እንደገባ እሾህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ሰካራም እሾህ ያለው ቁጠቋጦ በእጁ ከያዘ፣ እሾሁ እጁን ይወጋዋል፣ ወይም 2) ሰካራም ሰው ከተቆጣ፣ እሾህ ያለው ቁጠቋጦ ይዞ በሰዎች ላይ ይጥለዋል። ለሁለተኛው ትርጉም “እሾህ” የሚለው ቃል የእሾህ ቁጥቋጦን ይወክላል። (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
በሞኞች አፍ
እዚህ ላይ “አፍ” ለመናገር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በሞኞች ንግግር” ወይም “ሞኞች የተናገሩት ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ሞኝ ይቀጥራል
“ለሞኝ ስራ ይሰጣል”
Proverbs 26:11
ውሻ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ
“ውሻ የራሱን ትፋት እንደሚበላ”
በራሱ ዓይኖች ጥበበኛ እንደሆነ የሚያስብ ሰው አይተሃል?
ይህ ጥያቄ በራሱ ዓይኖች ጥበበኛ እንደሆነ ስለሚቆጥር አንድ ሰው እንዲያስብ አንባቢውን ለመምራት የሚጠቅም ነው። “በራሱ ዓይኖች ጥበበኛ የሆነ” የሚለው ሀረግ “ጥበበኛ እንደሆነ የሚያስብ” ማለት ነው፣ እዚህ ላይ ሰውየው በግልጽ ጠቢብ እንዳልሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጥበበኛ እንደሆነ የሚስያብን ነገር ግን ጥበበኛ ያልሆነውን ሰው ተመልከት” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእርሱ ይልቅ ለሞኝ የተሻለ ተስፋ አለው
“ከእርሱ ይልቅ ሞኝ በቀላሉ ጥበበኛ መሆን ይችላል።”
Proverbs 26:13
ሰነፍ ሰው እንዲህ ይላል፣ “አንበሳ በመንገድ አለ! በውጭ በአውራ ጎዳና አንበሳ አለ።”
ሰነፍ ሰው በውሸት በመንገድ ላይ ወይም በባዶ ሜዳዎች መካከል አንበሳ አለ ብሎ ምክንያት በመስጠት ወደ ውጭ መሄድና መስራት እንደማይችል ይናገራል።
በመንገድ ላይ አንበሳ አለ
ይህንን በምሳሌ 22:13 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
በባዶ ሜዳዎቹ
ይህ በከተማ መካካል ሰዎች የሚዘዋወሩበት ወይም የሚሰበሰቡበት ብዙ ስፍራዎችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የከተማ የገበያ ማዕከል” ወይም “መንገዶች”
ማጠፊያዎች
በርን ከሌላ ነገር ጋር የሚያያይዙና በሮቹ እንዲዘጉና እንዲከፈቱ የሚያደርጉ የብረት ቁራጮች
በር በማጠፊያው ላይ እንደሚዞር፣ ሰነፍም በአልጋው ላይ ይዟዟራል
ሰነፍ ሰውና በር ሁለቱም ይንቀሳቀሳሉ ነገር ግን ሁለቱም የትም አይሄዱም (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 26:15
ሰነፍ ሰው እጁን ወደ ሳህኑ ያስገባል
“ምግብ ለማግኘት እጁን ወደ ሳህኑ ያስገባል” ወይም “ለምግብ ይዘረጋል”
እጁን ወደ አፉ ለመመለስ ጉልበት የለውም
ይህ ሰውየው በግልጽ መልካም የሚያደርገውን አስፈላጊ ስራ ስለመስራት የሚያመለክት ግነት ነው። (ግነትና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰነፍ ሰው ማስተዋል ካላቸው ከሰባት ሰዎች የበለጠ ጥበበኛ እንደሆነ በራሱ ዓይን ያስባል
“በራሱ ዓይን” የሚለው ሀረግ የሰውየውን ሃሳብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰነፍ ሰው ከሰባት ሰዎች የበለጠ ጥበበኛ እንደሆነ ያስባል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 26:17
የውሻን ጆሮ እንደሚይዝ ሰው፣ የራሱ ባልሆነ ጥል የሚበሳጭ መንገድ አላፊ ሰውም እንዲሁ ነው
ይህ ቅደም ተከተሉ መለወጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የራሱ ባልሆነ ጥል ላይ የሚገባ መንገድ አላፊ ሰው የውሻን ጆሮ እንደሚይዝ ሰው ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የውሻን ጆሮ እንደሚይዝ ሰው
ይህ የሚያስተላልፈው መረጃ ውሻ ይቆጣና ሰውየውን ይነክሰዋል” የሚል ነው።
አማራጭ ትርጉም፦ “ጆሮውን በመጎተት ውሻን እንደሚያስቆጣ ሰው” ወይም “የውሻን ጆሮ እንደሚጎትትና በውሻ እንደሚነከስ ሰው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ
የራሱ ባልሆነ ጥል የሚበሳጭ መንገድ አላፊ ሰውም እንዲሁ ነው
ይህ የሚያስተላልፈው መረጃ መንገድ አላፊው መጨቃጨቅ ይጀምራል ከዚያም ሲጣሉ የነበሩት ሰዎች ከእርሱ ላይ ይቆጣሉ ደግሞም ይጎዱታል የሚል ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 26:18
እንደ እብድ ሰው ... የተናገርሁት እኮ ቀልዴን ነበር? ... በማለት የሚያታልል ሰው እንዲሁ ነው
እብድ ሰውና አታላዩ ሁለቱም ሰዎችን ይጎዳሉ ነገር ግን ለሰሩት ስራ ኃላፊነት አይወስዱም።
“የተናገርሁት እኮ ቀልዴን ነበር?”
አታላዩ የእርሱ ቀልድ ለማዝናናት ስለሆነ እርሱ ለፈጠረው ለማንኛውም ጉዳት ሊወቀስ እንደማይገባ ለማሳየት ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ እኮ እንዲሁ እየቀለድሁ ነበር” ወይም “እኔን አትውቀሱኝ። እኔ የተናገርሁት ቀልዴን ነበር።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 26:20
ሐሜተኛ
ብዙ ሐሜት የሚናገር ሰው
ከሰል ፍምን እንጨትም እሳትን እንደሚያቀጣጥል
ከሰል በፍም ላይ እንጨት ደግሞ በእሳት ላይ የሚያመጣው ውጤት በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከሰል ፍም እንዲቀጣጠል እንደሚያግዝና እንጨት እሳትን እንዲነድ እንደሚያግዝ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሁከትን ያቀጣጥላል
አንድን ነገር ማቀጣጠል በእሳት ማያያዝ ማለት ነው። ሁከትን በእሳት ማቀጣጠል ሰዎች እንዲጣሉ ወይም እንዲከራከሩ ለማድረግ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች እንዲጣሉ ማድረግ” ወይም “ሰዎች እንዲከራከሩ ማድረግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 26:22
የሐሜት ቃላቶች እንደ ጣፋጭ ጉርሻ ናቸው
ለመብላት ጣፋጭ እንደሆነ ምግብ ሐሜትም ለመስማት ደስ የሚያሰኝ ሰለመሆኑ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሐሜት ቃላቶች ለመስማት ደስ የሚያሰኙ ናቸው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ውስጣዊ የሰውነት ክፍሎችም ይወርዳሉ
ይህ ሐሜት የሚናገራቸው ቃላቶች ወደ ሰው አእምሮ ገብተው ሃሳቡን እንደሚያበላሹ የሚናገር ሲሆን ወደ ሆዱ እንደሚገባ ምግብ ተደርገው ተገልጸዋል። ይህ ዓረፍተ-ሃሳብ በምሳሌ 18:8 ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ወደ ሰው አእምሮ ይገቡና ሃሳቡን ያበላሻሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንሚያቃጥሉ ከንፈሮችና እንደ ክፉ ልብ በብር ፈሳሽ የተለበጠ የሸክላ ድስት እንዲሁ ነው
ይህ ተነፃፃሪ ዘይቤ ክፋትን በልባቸው ለመደበቅ የተለያዩ ነገሮችን የሚናገሩ ሰዎች ጥሩ እንዲመስል ለማድረግ በብር ፈሳሽ እንደተለበጠ የሸክላ ድስት ነው። እነዚህ ሀረጎች ቅደም ተከተላቸው ሊለዋወጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሚያቃጥሉ ከንፈሮች ያላቸው ሰዎችና ክፉ ልብ በብር ፈሳሽ እንደተለበጠ የሸክላ ድስት ነው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በብር ፈሳሽ የተለበጠ የሸክላ ድስት
“የሸክላ ድስትን የሚሸፍን የሚያብረቀርቅ ቅብ።” የሸክላ ድስት ርካሽና በሁሉም ስፍራ የሚገኝ ነው። ስለዚህ የሚያብረቀርቅ እንዲሆንና በጣም ውድ እንደሆነ ለማስመሰል ሰዎች በሚያብረቀርቅ ቅብ ይሸፍኑታል።
የሚያቃጥሉ ከንፈሮችና ክፉ ልብ እንደዚሁ ናቸው
ይህ የሚወክለው የሚያቃጥሉ ከንፈሮችና ክፉ ልብ ያለውን ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የሚያቃጥሉ ከንፈሮችና ክፉ ልብ ያለው ሰው እንደዚሁ ነው” ወይም “መልካም ንግግር የሚናገር ነገር ግን ልቡ ክፉ የሆነ ሰው እንደዚሁ ነው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚያቃጥሉ ከንፈሮች
“የሚያቃጥሉ” የሚለው ቃል “ከመጠን ያለፈ ስሜታዊ መሆን” ለማመልከት ተለዋጭ ዘይቤ ሲሆን “ከንፈሮች” የሚለው ቃል ደግሞ “ንግግር” ለማመልከት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ስሜታዊ ንግግር” ወይም “ጥሩ ነገሮች

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መናገር” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉ ልብ
ልብ የሰውን ሃሳብ፣ ዝንባሌ፣ ፍላጎት ወይም ስሜት ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሃሳብ” ወይም “ክፉ ምኞት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 26:24
ስሜቱን በከንፈሮቹ ይሸነግላል
ስሜትን መሸንገል ስሜቱን ሰዎች እንዳያውቁ መደበቅን ይወክላል፡፡ “ከንፈሮቹ” የሚለው ቃል ለተናገረው ንግግር ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በሚናገረው ንግግር ስሜቱን ይደብቃል” ወይም “እውነተኛ ስሜቱን ሰዎች ሊያውቁ በማይችሉበት ሁኔታ ይናገራል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ተንኮሉን ግን በውስጡ ያኖራል
ተንኮለኛ መሆን ሰውየው ተንኮል በውስጡ ያጠራቅም እንደነበር ተደርጎ ተነግሯል፡፡ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- “ተንኮል” ውሸትን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ውሸቱን ይወድደዋል” 2) ተንኮል ሰዎችን ለመጉዳት ምስጢራዊ እቅዶችን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎችን ለመጉዳት በምስጢር አቅዷል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን አትመነው
“ነገር ግን የሚናገረውን አትመነው”
በልቡ ውስጥ ሰባት ርኩሰቶች አሉ
ሰባት ቁጥር ፍጹምነትን ይወክላል፡፡ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ርኩሰት” እግዚአብሔር የሚጠላውን አመለካከት ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ልቡ ሙሉ በሙሉ በጥላቻ ነገሮች የተሞላ ነው” ወይም 2) “ርኩሰት” ለሰዎች ያለውን ጥላቻ ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- ““ልቡ ሙሉ በሙሉ በጥላቻ የተሞላ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ምንም እንኳ ጥላቻው በሽንገላ የተሸፈነ ቢሆንም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም እንኳ ሽንገላው ጥላቻውን ቢሸፍነውም” ወይም “ምንም እንኳ ጥላቻውን በሽንገላው ቢሸፍነውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ምንም እንኳ ጥላቻው በሽንገላ የተሸፈነ ቢሆንም
ሰዎች እነርሱን እንደሚጠላቸው እንዳያውቁ መደበቁ ጥላቸውን እንደሸፈነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ምንም እንኳ ሰዎች እነርሱን እንደሚጠላቸው እንዳያውቁ ለመደበቅ ቢዋሽም” ወይም “ምንም እንኳ ሰዎች እነርሱን እንደሚጠላቸው እንዳያውቁ ቢዋሽም” “Though he lies so that people will not know that he hates them” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፋቱ ግን በጉባኤ ይገለጣል
መገለጥ መለየት ወይም መታወቅ የሚለውን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፋቱ በጉባኤ ይታወቅበታል” ወይም “ጉባኤው ክፋቱን ይደርስበታል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ጉባኤው
“የእስራኤል ማህበረሰብ”
Proverbs 26:27
ጉድጓድን የሚቆፍር ሰው እርሱ ይገባበታል
ይህ ሰው ጉድጓድ የሚቆፍረው ሌላ ሰው በዚያ ጉድጓድ ላይ እንዲወድቅበት እንደ ወጥመድ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሌላ ሰው ለማጥመድ ጉድጓድን የሚቆፍር ማንኛውም ሰው እርሱ ይገባበታል” ወይም ““ሌላ ሰው ለማጥመድ በማሰብ አንድ ሰው ጉድጓድ ከቆፈረ፣ የቆፈረው ሰው ራሱ ይገባበታል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ድንጋይንም የሚያንከባልል ተመልሶ በላዩ ላይ ይገለበጥበታል
ይህ ሰው በኮረብታ ላይ ሆኖ ወደታች ትልቅ ድንጋይን የሚያንከባልለው ከታች ያለውን ሌላ ሰው ለመጨፍለቅ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ከታች ያለውን ሌላ ሰው ለመጨፍለቅ በኮረብታ ላይ ሆኖ ወደታች ትልቅ ድንጋይ የሚያንከባልል ከሆነ፣ ድንጋዩ በራሱ ላይ ተመልሶ ይንከባለልበታል” ወይም “አንድ ሰው ሌላ ሰው ለመጉዳት ድንጋይ የሚያንከባልል ከሆነ ድንጋዩ ተመልሶ ራሱን ይጨፈልቀዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ውሸታም ምላስ የጎዳቸውን ሰዎች ይጠላል
“ውሸታም ምላስ” የሚለው ሀረግ ውሸት የሚናገረውን ሰው ይወክላል፡፡ ሰዎችን መጉዳት በሰዎች ላይ ችግር መፍጠርን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ውሸታም ሰው በውሸቱ የጎዳቸውን ሰዎች ይጠላል” (ተዛምዶአዊ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሸንጋይ አፍም ጥፋትን ያመጣል
“ሸንጋይ አፍ” የሚለው ሀረግ ሰዎችን የሚሸነግለውን ሰው ይወክላል፡፡ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- ሌሎችን የሚሸነግል ሰው ችግር ይፈጥራል፡፡ ወይም 2) ሌሎችን የሚሸነግል ሰው ያጠፋቸዋል (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
መሸንገል
አንድን ሰው እውነተኛነት በሌለው ሁኔታ ማመስገን፣ ወይም አንድን ሰው እውነተኛ ላልሆኑ ነገሮች ማመስገን

Chapter 27
Proverbs 27:1
ነገ በሚሆነው አትመካ
ይህ ነገ ይሆናል ብለህ ስለምትጠብቀው ነገር ጉራ እንዳትነዛ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ ይህ በግልጽ ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለነገ ስላለህ እቅድ በኩራት አትናገር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀኑ የሚያመጣውን
በተወሰነ ቀን የሚከናወነው ነገር ያንን ክስተት ቀኑ እንደሚያመጣው ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በዚያ ቀን የሚሆነውን” ወይም “ነገ የሚሆነውን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በራስህ አፍ ሳይሆን … የራስህ ከንፈሮች ሳይሆኑ
“ያመስግኑህ” የሚለውን ቃል ከመጀመርያው ሀረግ በግልጽ መረዳት ይቻላል፡፡ ቃላቶቹ ሊደጋገሙ ይችላሉ፡፡ እዚህ ለላይ ሰውየው በ “አፉ” እና በ “ከንፈሮቹ” ተወክሏል ምክንያቱም እነዚህ ለመናገር የሚጠቅሙ የሰውነት አካላት ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የራስህ አፍ አያመስግንህ … የራስህ ከንፈሮች አያመስግኑህ” ወይም “ራስህን አታመስግን … ራስህን አታመስግን” (አስጨምሬ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
የማያውቅህ ሰው
“ያመስግኑህ” የሚለውን ቃል ከመጀመርያው ሀረግ በግልጽ መረዳት ይቻላል፡፡ እዚህ ላየ ቃላቶቹ ሊደጋገሙ ይችላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የማያውቅህ ሰው ያመስግንህ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 27:3
የሞኝ ሰው ትንኮሳ ግን ከሁለቱም እጅግ የከበደ ነው
ሞኝ ሰው ሲተነኩስህ የሚገጥምህ ትዕግስተኛ የመሆን ችግር ያ ችግር እጅግ የከበደ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የሞኝ ትንኮሳ መታገስ ከሁለቱም ይከብዳል” ወይም “ሞኝ ሲተነኩስህ መታገስ እነርሱን ለመሸከም ከመታገስ የበለጠ ይከብዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሞኝ ትንኮሳ
“በሞኝ አማካኝነት የሚመጣ ችግር፡፡” “ትንኮሳ” ቁጣ ወይም መራራነት የሚፈጥሩ ድርጊቶች ወይም ቃላት ናቸው፡፡
የንዴት ጭካኔና የቁጣ ጎርፍ አለ፣ በቅናት ፊት መቆም የሚችል ግን ማን ነው?
“ንዴት፣” “ጭካኔ” እና “ቁጣ” እንደ ቅጽል ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ተናዳጅ ሰው ጨካኝ ነው፣ ቁጡ ሰው ይጎዳል፣ ነገር ግን በቀናተኛ ሰው ፊት ማን መቆም ይችላል? (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጭካኔ
“ሀይለኛነት”
የቁጣ ጎርፍ
“የቁጣ አጥፊነት፡፡” እዚህ ላይ ቁጣ ሀይለኛ ጎርፍ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በቅናት ፊት መቆም የሚችል ግን ማን ነው?
ይህ ጥያቄ ማንም ሰው በቅናት ፊት መቆም እንደማይችል የሚያመለክት ነው፡፡ እንደ ዓረፍተ-ሃሳብ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን በቅናት ፊት መቆም የሚችል ማንም ሰው የለም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በቅናት ፊት መቆም

እዚህ ላይ መቆም የሚለው ቃል ጥቃት በሚፈጽም ቀናተኛ ሰው ላለመጎዳት ጠንካራ እና ጽኑ መሆንን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "ቀናተኛ ሰውን መከላከል" ወይም "ቀናተኛ ሰው ጥቃት ሲፈጽምበት በጥንካሬ መጽናት" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 27:5

የተገለጠ ተግሳጽ ይሻላል

ይህ "ተግሳጽ" የሚለው ረቂቅ ስም "መገሰጽ" በሚለው ግስ ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "በገልጽ መገሰጽ ይሻላል" (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከተሰወረ ፍቅር

"በግልጽ ከማይታይ ፍቅር ይልቅ፡፡" ይህ ""ፍቅር" የሚለው ረቂቅ ስም እንደ የግስ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "በምስጢር ከመወደድ ይልቅ" (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የጓደኛ ማቁሰል የታመኑ ናቸው

"ጓደኛ የሚያመጣው ጉዳቶች የታመኑ ናቸው፡፡" እዚህ ላይ "ቁስል" የሚለው ቃል ጓደኛ ሲገስጸውና ሲያስተካክለው ሰውየው የሚሰማው ሕመምና ሀዘንን ይወክላል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጓደኛ ማቁሰል የታመኑ ናቸው

የጓደኛ ተግሳጽ ታማኝነት ተግሳጹ የሚያመጣው ሀዘን ታማኝ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "ምንም እንኳ ሀዘን ቢያስከትልም፣ የጓደኛ ተግሳጽ የታመነ ነው" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጠላት ግን ከመጠን በላይ ይስማል

የጠላት መሳም ታማኝ እንዳልሆነ በግልጽ ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "ነገር ግን የጠላት ብዙ መሳም ታማኝ አይደሉም" ወይም "ነገር ግን ጠላት ከመጠን በላይ በመሳም ሊያታልልህ ይሞክር ይሆናል" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ

ከመጠን በላይ

"በብዛት" ወይም "ብዙ ጊዜ"

Proverbs 27:7

በጣም ጠግቦ የበላ ሰው

"የጠገበ ሰው" ወይም "በጣም ጠግቦ የበላ ሰው"

የማር ወለላንም አይቀበልም

የማር ወለላ ብዙ ጊዜ አስፈላጊ ነው፣ ነገር ግን በጣም ጠግቦ ለበላ ሰው ግን አይሆንም፡፡

ማንኛውም መራራ ነገር እንኳ ጣፋጭ ነው

"ማንኛውም መራራ ነገር ይጣፍጣል"

ከጎጆዋ ወጥታ እንደምትንከራተት ወፍ ከመኖሪያው አካባቢ ወጥቶ እንደሚባዝን ሰው እንደዚሁ ነው

በዚህ ጥቅስ "መንከራተት" እና መባዘን" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፡፡ (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 27:9

ሽቶ

እዚህ ላይ "ሽቶ" የሚለው ቃል ደስ የሚል ዘይት ወይም ቅባት ማለት ነው፡፡

ልብን ደስ ያሰኛል

እዚህ ላይ "ልብ" የሰውን ስሜት ወይም መንፈስ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "ሰውን የደስተኝነት ስሜት እንዲሰማው ማድረግ" ወይም "ሰውን ደስ እንዲለው ማድረግ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የጓደኛ ጣፋጭነት ግን ከምክሩ ይበልጣል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) "ጣፋጭነት" ደግነትን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "እኛ የጓደኞችንን ደግነት በምክሩ እውቀናል" ወይም 2) "ጣፋጭነት" ስለ ሰው የምናደንቀውን ነገር ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "ስለጓደኛ የምናደንቀውን ነገር ምክሩን ነው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የወንድምህ ቤት

እዚህ ላይ "ወንድም" የሚለው ቃል ለዘመዶች ማለትም ተመሳሳይ ጎሳ፣ ዘር ወይም ሕዝብ አባላት አጠቃላይ መግለጫ ነው፡፡

ችግር

ጽኑ የሆነ መከራና አጋጣሚ

Proverbs 27:11

ልቤንም ደስ አሰኛት

እዚህ ላይ "ልብ" የሰውን ስሜት ወይም መንፈስ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "ደስተኛ አድርገኝ" ወይም "ደስ አሰኝኝ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያን ጊዜ ለሚያፌዝብኝ ሰው እኔ መልስ እሰጣለሁ

እዚህ ላይ "መልስ" ለጥያቄ መልስ መስጠት ማለት አይደለም፡፡ ለሚያፌዝ ሰው ምላሽ መስጠት ወይም ተገቢውን መልስ መስጠት ማለት ነው፡፡ ይህ በፊቱ ካው ሀረግ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ግልጽ ሊደረግ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "እኔ በእኔ ላይ ለሚያፌዝብኝ ሰው ለእርሱ ስለ አንተ በመንገር ምላሽ እሰጠዋለሁ" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ማፌዝ

ለየተ ባለ መልኩ ጭካኔ በተሞላበት መንገድ በአንድ ሰው ላይ መቀለድ

ጥንቁቅ ሰው ችግር ሲያይ ራሱን ይሸሽጋል፣ አላዋቂዎች ግን ቀድመው ሄደው በችግሩ ምክንያት ይጎዳሉ

ይህንን በምሳሌ 22:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡

ጥንቁቅ ሰው

"ጥበበኛ የሆነ ሰው" ወይም "ጥሩ የማገናዘብ ችሎታ ያለው ሰው"

አላዋቂዎች

"ልምድና የሕይወት ብስለት የሌላቸው ሰዎች"

ይጎዳሉ

የሚያሳዝኑ ነገሮች ማለትም እንደ በሽታ፣ ሕመም ወይም ሌሎች መከራዎች በሕይወታቸው ይገጥማቸዋል

Proverbs 27:13

ለማይታወቅ ሰው ብድር በዋስትና ገንዘብ ያስያዘውን ሰው ልብስ ውሰድበት

ገንዘብ በማበደር ጊዜ አበዳሪ ከተበዳሪው ብድሩን መልሶ ለመክፈሉ እንደ ዋስትና የሚሆን ልብስ ወይም ሌላ ነገር ይወስዳል፡፡ ገንዘቡ ከተመለሰለት በኋላ የያዘውን መያዣ ይመልሳል፡፡ ተበዳሪው በጣም ድኃ ከሆነ ሌላ ሰው ስለ እርሱ እንደ ዋስትና ለአበዳሪው የሆነ ነገር ይሰጣል፡፡ ይህንን በምሳሌ 20:16 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "የማይታወቅ ሰው የተበደረው ብድር ተመልሶ እንዲከፈል ተያዥ ከሆነው ሰው እንደ ዋስትና እንዲሆን ልብስ ውሰድበት" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በዋስትና ገንዘብ ያስያዘውን ሰው

የተበደረው ብድር እንደገና ለመከፈሉ እንደ ዋስትና እንዲሆን አንድ ሰው አንድ ነገር ለአበዳሪው ይሰጣል ማለት ነው፡፡ ይህንን በምሳሌ 20:16 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "የተበደረው ብድር ተመልሶ እንዲከፈል ተያዥ የሆነው ሰው" ወይም "ብድርን ለመክፈል ቃል የገባው ሰው" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

መያዣ ውሰድበት

"አንድን ነገር በመያዣነት መውሰድ" ዕዳውን እንዲከፍል አንድ ሰው እንደ መያዣ ወይም ቃል ኪዳን የሰጠውን ነገር መያዝ ማለት ነው፡፡ ይህንን በምሳሌ 20:16 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "ብድሩ ለመከፈሉ እንደ ዋስትና ልብሱን ውሰድበት" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ጎረቤቱን የሚባርክ ሰው

"አንድ ሰው ለጎረቤቱ በረከት ቢሰጠው"

ባርኮቱ እንደ እርግማን ይቆጠራል

ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "ጎረቤቱ በረከቱን እንደ እርግማን ይቆጥረዋል" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 27:15

ጠበኛ

ይህ ሰዎች እርስ በርሳቸው እንዲበሳጩ ማድረግ ወይም በሰዎች መካከል ጠንካራ ጠብ እንዲፈጠር ማድረግ ማለት ነው፡፡

እንደማያቋርጥ ነጠብጣብ

ይህ የሚያስተላልፈው መልእክት በማያቋርጥ ሁኔታ የሚንጠባጠብ ዝናብ ነው የሚል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፦ "የማቋርጥ የዝናብ ነጠብጣብ" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የዝናብ ቀን

"የማያቋርጥ ዝናብ የሚዘንብበት ቀን"

እሷን ማቆም ንፋስን እንደማቆም ወይም ዘይትን በቀኝ እጅህ ለመጨበጥ እንደ መሞከር ነው፡

የዚህ መልእክት እርስዋን ለማስቆም መሞከር ነፋስን እንደ ማቆም ወይም በእጅህ ዘይትን እንደ መጨበጥ በጣም አስቸጋሪና ጥቅም አልባ ነው፡፡ (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርስዋን ማስቆም

"እርስዋን ወደኋላ መመለስ" ወይም "እርስዋን መቆጣጠር፡፡" የዚህ መልእክት

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እርስዋን ከመጣላት ለማስቆም መሞከር የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርስዋን ከመጣላት ማስቆም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ንፋስን ማስቆም
“ነፋስን መመለስ” ወይም “ነፈስን በቁጥጥር ስር ማዋል”
Proverbs 27:17
ብረት ብረትን ይስለዋል፤ በተመሳሳይ መንገድ ሰው ጓደኛውን ይስለዋል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ብረት እና ሰው እንዴት ሊለወጡ እንደሚችለ ያነጻጽራሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ብረት ሌላ ቁራጭ ብረትን እንደሚስል በተመሳሳይ መንገድ የሰው ባህርይ ከጓደኛው ጋር ባለው ግንኙነት ይለወጣል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚጠብቅ
“የሚንከባከብ”
ጌታውንም የሚጠብቅ ይከብራል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚጠብቀውን ጌታው የከብረዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 27:19
የሰው ልብ
እዚህ ላይ የሰው ሃሳብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው የሚያስበው ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የሙታን ዓለም
ይህ ስም “አጥፊ” ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አጥፊው” (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
አይጠግቡም
“አይሞሉም”
የሰው ዓይን
እዚህ ላይ “ዓይን” የሰውን ምኞት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰው ምኞት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 27:21
ማቅለጫ ለብር ከውርም ለወርቅ ነው
ይህ ወርቅና ብር እንዴት እንደሚነጥሩ የሚያሳይ ነው። ብረት መቅለጥ እንዲችልና በውስጡ ያለው ቆሻሻ እንዲወገድ የሚነጥረው እጅግ በጣም ሀይለኛ በሆነ የሙቀት ሃይል በማሞቅ ነው። ይህን በጣም ተመሳሳይ ሀረግ በምሳሌ 17:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- አማራጭ ትርጉም፡- “ማቅለጫ ብር ለማንጠር ይጠቅማል፣ ከውር ደግሞ ወርቅ ለማንጠር ይጠቅማል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ማቅለጫ
በጣም ከፍተኛ በሆነ ሙቀት ብረት የሚቀልጥበት ማሰሮ ነው። (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
ከውር
ከመጠን በላይ ማሞቅ የሚቻል ምድጃ (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
ሰውም በሚመሰገንበት ጊዜ ይፈተናል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ሌላ ሰው ሲያመሰግን ያንን ሰው እየፈተኑት ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ሞኝን ብትወቅጠውም … ሞኝነቱ ግን እርሱን አይለቀውም
ምንም እንኳ ሞኝ በብዙ መከራ ወይም ውጣ ውረድ ቢያልፍም (መወቀጥ በዕብራይስጥ ብዙ ጊዜ ለመከራ ተለዋጭ ዘይቤ ነው) ሞኝ እንደሆነ ይቀራል ማለት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዘነዘና
የተለያዩ ነገሮችን በሙቀጫ ለማድቀቅ የሚረዳ ክብ ጫፍ ያለው ጠንካራ መሳርያ ነው (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 27:23
የመንጋህን ሁኔታ በእርግጠኝነት እወቅ፣ ስለ እንስሳዎችህም ግድ ይበልህ፣
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድ ላይ የተቀመጡት አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
መንጋህ
“የበግ መንጋ”
እንስሳዎችህ
“የፍየል መንጋ”
ዘውድ ለትውልድ ሁሉ ይጸናልን?
ይህ ጥያቄ የምድር ገዢዎች የአገዛዝ ዘመን ለዘላለም እንደማይኖር ግንዛቤ ለማስጨበጥ አሉታዊ መልስ የሚሰጥበት እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህ እንደ ዓረፍተ-ሃሳብ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ዘውድ ለትውልድ ሁሉ አይጸናም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ዘውድ
እዚሂ ላይ “ዘውድ” የንጉሱን በመንግስቱ ላይ ያለውን አገዛዝ የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የንጉስ አገዛዝ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
አዲሱ ቡቃያ አድጎ ይታያል
“አዲስ ቡቃያ ይታያል” ወይም “አዲስ ሳር ማደግ ጀምሯል”
Proverbs 27:26
አያያዥ ዓረፍተ-ሃሳቦች
ቁጥር 26 እና 27 ከቁጥር 23 እና 25 ጋር እንደ አንድ ምሳሌ አብረው ይሄዳሉ።
እነዚህ በጎች ለልብስህ የሚሆን ይሰጡሃል
ከዚህ የምናገኘው አመልካች መረጃ ከበጎች የሚገኘው ሱፍ (ጸጉር) ልብስ ለመስራት ጥቅም ላይ ይውላል የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የበጎች ሱፍ ለልብስህ የሚሆን ይሰጥሃል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእርሻህ ዋጋ የሚሆን ደግሞ ከፍየሎችህ ታገኛለህ
ከዚህ የምናገኘው አመልካች መረጃ ፍየሎችን በመሸጥ የሚገኘው ገንዘብ እርሻ ለመግዛት በቂ ነው የሚል ነው። ከበጎች የሚገኘው ሱፍ (ጸጉር) ልብስ ለመስራት ጥቅም ላይ ይውላል የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ፍየሎችህን መሸጥ የእርሻህን ዋጋ ይሰጥሃል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለቤተሰብህ
“ለቤተሰብህ በሙሉ”
ሴት አገልጋዮችህንም ለመመገብ የሚበቃ
ከዚህ የምናገኘው አመልካች መረጃ ከዚህ በተጨማሪ ሴት አገልጋዮችንም ለመመገብ የሚበቃ በቂ የፍየሎች ወተት ይኖራል የሚል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሴት አገልጋዮችህን ለመመገብ የሚበቃ በቂ የፍየሎች ወተት ይኖራል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መመገብ
“ምግብ”

---

Chapter 28
Proverbs 28:1
በምድሪቱ በደል ምክንያት
“በደል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምድሪቱ በበደለችው በደል ምክንያት” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የምድሪቱ በደል
ይህ በምድሪቱ የሚኖረው ሕዝብ ኃጢአት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የምድሪቱ ሕዝብ በደል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ማስተዋልና እውቀት ባለው ሰው
ከዚህ የምናገኘው አመልካች መረጃ ይህ ሰው መሪ ወይም ገዢ መሆኑ ነው። “ማስተዋል” እና “እውቀት” የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ግስ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “በሚያስተውልና እንዴት መምራት እንዳለበት በሚያውቅ ሰው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 28:3
የሚጨቁን
“በጭካኔ የሚያስጨንቅ”
ሰብልን እንሚያጠፋ ዶፍ ዝናብ ነው
ድሆችን የሚጨቁን ድሃ ሰው በከባድ ሁኔታ ከሚወርድና ሰብልን ከሚያጠፋ ዶፍ ዝናብ ጋር ተነጻጽሯል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዶፍ ዝናብ
ይህ በከባድ ሁኔታ ለሚወርድና ሰብልንለሚያጠፋ ዝናብ ተለዋጭ ዘይቤ ነው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አማራጭ ትርጉም:- “አጥፊ ዝናብ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሕግን የሚተዉ
“የእግዚአብሔyርን ሕግ መተው”
ሕግን የሚጠብቁ
“ሕግን መጠበቅ” የእግዚአብሔር ሕግ የሚፈልገውን መፈጸም ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “የእግዚአብሔርን ሕግ የሚታዘዙ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእነርሱ ጋር ይዋጋሉ
“ከእነርሱ ጋር ይታገላሉ፡፡” ይህ እነርሱን አጥብቀው ይቃወሟቸዋል ወይም ይቋቋሟቸዋል ማለት ነው፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 28:5
ክፉ ሰዎች
እዚህ ላይ “ሰዎች” የሚለው በአጠቃላይ ሕዝብ ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ክፉ ነገሮችን የሚሰሩ ሕዝብ” (ለወንዶች የምንጠቀምባቸው ቃላቶች ሴቶችንም ሲያካትቱ የሚለውን ይመልከቱ)
ፍትህን አያውቁም
“ፍትህ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ፍትህ ምን እንደሆነ አታውቅም” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚብሔርን የሚፈልጉ ሰዎች
እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚፈልጉና እርሱን የሚያስደስቱ ሰዎች እግዚአብሔርን በአካል ለማግኘት እንደሚፈልጉ ተደርገው ተነግሯል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉን ነገር ያውቃሉ
ከዚህ የምናገኘው አመልካች መረጃ እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ሰዎች ስለ ፍትህ ሁሉን ነገር ያውቃሉ ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ፍትህ ምን እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ያውቃሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከባለጠጋ ይልቅ ... ድሃ ሰው ይሻላል
“ባለጠጋ ሰው ከመሆን ይልቅ ... ድሃ ሰው መሆን ይሻላል
በሐቀኝነት የሚራመድ
ይህ የሐቀኝትን ሕይወት የሚኖር ሰውን ይወክላል፡፡ ይህ “ሐቀኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ተውሳከ ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “በታማኝነት ይራመዳል” walks honestly” or “lives honestly” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በመንገዱ ጠማማ የሆነ
ታማኝ ያልሆኑ ባለጠጋ ሰዎች በጠማማ መንገድ ወይም በጠመዝማዛ መንገድ እንደሚሄዱ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “በሚያደርገው ነገር ታማኝ ያልሆነ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 28:7
ሕግን የሚጠብቅ
“ሕግን መጠበቅ” የእግዚአብሔር ሕግ የሚጠይቀውን ነገር ማድረግ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “የእግዚአብሐርን ሕግ የሚታዘዝ ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማስተዋል ያለው ልጅ
“ማስተዋል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “የሚያስተውል ልጅ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ሆዳሞች
“ከመጠን በላይ የሚበሉ ሰዎች፡፡” “ሆዳም” ሰው ብዙ ጊዜ ከመጠን በላይ የሚበላና የሚጠጣ ሰው ነው፡፡
አባቱን ያሳፍራል
“አባቱ እንዲያፍር ያደርጋል” ወይም “አባቱን ያዋርዳል”
ሀብት የሚያከማች
“ሀብቱን ይጨምራል”
ከፍተኛ ወለድ መሰብሰብ
“ለማበደር ተጨማሪ ገንዘብ መሰብሰብ”
ወለድ
የሌላ ሰው ገንዘብ በመጠቀሙ በተበዳሪው የሚከፈል ገንዘብ
ሀብቱን ይሰበስባል
“ገንዘቡን በአንድ ላይ ያመጣል”
ሌላ ሰው
“ለሌላ ሰው”
ማዘን
ለአንድ ሰው የማዘን ወይም የመራራት ጠንካራ ስሜት
Proverbs 28:9
አንድ ... ከሆነ
“አንድ ሰው ... ከሆነ”
ሕግን ከማድመጥ ጆሮውን የሚያዞር ከሆነ
ይህ ሰው በሁለንተናው የእግዚአብሔርን ሕግ ከማድመጥ ጆሮውን ማዞርና አለመቀበልን የሚወክል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “የእግዚአብሔርን ሕግ ከማድመጥና ከመታዘዝ ይዞራል” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ጸሎቱ እንኳ የተጠላ ነው
“ጸሎቱ እንኳ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው፡፡” ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር ጸሎቱን እንኳ ይጠላዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የጠጠላ
ይህንን በምሳሌ 3:32 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡
ቅኑን ሰው ወደ ክፋት መንገድ የሚመራ ሁሉ
ይህ ቅን ሰዎችን ወደ ክፋት መንገድ ለመምራት ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ቅኑን ሰው ወደ ክፋት መንገድ እንዲሔድ የሚያደርግ ሁሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ክፋት መንገድ የሚመራ ሁሉ ... ይወድቃል
“አንድ ሰው ወደ ክፋት መንገድ ከመራ ... ይወድቃል”
ቅን
ይህ በአጠቃላይ ቅን ሰዎችን የሚያመለክት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ቅን ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
በቆፈረው ጉድጓድ ይገባል
“ራሱ በቆፈረው ወጥመድ ውስጥ ይገባል፡፡” ፍጻሜው ሌሎችን ወደመራበት ተመሳሳይ መጥፎ ቦታ ስለመሆኑ የሚያመለክት ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “እርሱ ሌሎች ሰዎቸን ወደመራበት ክፉ ስፍራ የእርሱም ፈጻሜ እንደዚያው ይሆናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ንጹሐን ሰዎች
ይህ በአጠቃላይ ነቀፌታ የለለባቸውን ሰዎች የሚያመለክት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ነቀፌታ የሌለባቸው ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
መልካምን ነገር ይወርሳሉ
“መልካም የሆነውን ነገር ይወርሳሉ”
Proverbs 28:11
በራሱ ዓይኖች ጥበበኛ ሊሆን ይችላል
ዓይኖች መመልከትን ይወክላል፣ መመልከት ደግሞ ሃሳብንና ግንዛቤን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “በራሱ አስተሳሰብ ጥበበኛ ነው” ወይም “ጥበበኛ እንደሆነ ያስባል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማስተዋል ያለው
“ማስተዋል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “የሚያስተውል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱን ይመረምረዋል
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ድሃው ሰው ሀብታምን ሰው በእርግጥ ጥበበኛ እንደሆነና እንዳልሆነ መወሰን ይችላል ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “እውነተኛ ተፈጥሮውን ይመለከታል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ጽድቅን የሚያደርግ ድል በሚያገኙበት ጊዜ
“ጽድቅን የሚያደርግ በሚሳካለት ጊዜ”
ክፉዎች በሚነሱበት ጊዜ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ክፉ ሰዎች ስልጣን በሚይዙበት ጊዜ ወይም መምራት በሚጀምሩበት ጊዜ ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ክፉ ሰዎች ወደ ስልጣን በሚመጡበት ጊዜ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉ ሰው
ይህ በአጠቃላይ ክፉ ሰዎችን የሚያመለክት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ክፉ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰዎች ራሳቸውን ይሸሸጋሉ
እነዚህ “ራሳቸውን የሸሸጉ” ሰዎች ከክፉ ሰዎች ለማምለጥ ሲሉ ራሳቸውን መደበቃቸውን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግ ይሆናል፡፡ ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል፡፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አማራጭ ትርጉም:- “ሰዎችን ያገኙአቸዋል” ወይም “ከእነርሱ የተደበቁትን ሰዎች ያገኙአቸዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:13

ኃጢአቱን ይደብቃል

“ኃጢአቱን ይሰውራል።” ይህ ንስሃ የመግባትና ኃጢአትን የመተው ተቃራኒ ሲሆን ኃጢአትን ወደ ብርሃን ከማምጣት ይልቅ ኃጢአትን መሰወር ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አይበለጽግም

“አይሳካለትም” ወይም “አያድግም”

ኃጢአቱን የሚሰውር አይሳካለትም፣ የሚናዘዝና የሚተወው ግን ምህረትን ያገኛል

ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ለሚናዘዙና የሚተወው ምህረትን ይሰጣቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘወትር እግዚአብሔርን እየፈራ የሚኖር ሰው ደስተኛ ነው

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር ዘወትር እየፈራ የሚኖርን ሰው ይባርካል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እየፈራ የሚኖር ሰው

“መፍራት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “በፍርሃት የተሞላ ሕይወት ይኖራል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መፍራት

ይህ እግዚአብሔርን በጥልቀት ማክበርና ይህንን አክብሮት እርሱን በመታዘዝ ማሳየትን ያመለክታል።

ልቡን የሚያጠነክር ሰው

“ልቡን የሚያደነድን ሰው”

ልቡን አጠነከረ

ይህ ፈሊጥ ሲሆን ግትርና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆነ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ አይደለም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

መከራ ውስጥ ይወድቃል

ይህ በስቃይና በጉስቁልና ውስጥ መግባትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “በችግር ውስጥ ይገባል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:15

እንደሚያገሳ አንበሳ ወይም እንደ ተቆጣ ድብ በድሆች ላይ የሚገዛ ክፉ ገዥም እንዲሁ ነው

ከክፉ ገዥ ሊያድናቸው የሚችል ማንም የሌላቸው ድሃ ሰዎች አንበሳ በላያቸው ላይ ከሚያገሳባቸው ሰዎች ወይም ድብ ከሚያጠቃቸው ሰዎች ጋር ተነጻጽረዋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የተቆጣ ድብ

ድብ በአራት እግር የሚራመድ ስለታም ጥፍርና ጥርስ ያለው ትልቅ፣ አስፈሪና አደገኛ እንስሳ ነው። (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ማስተዋል የሌለው ገዥ

“ማስተዋል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “የማያስተውል ገዥ” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ጨቋኝ

ሰዎችን በማስጨነቅ የሚይዝና የሰዎችን ሕይወት አስቃቂ የያደርግ

ማታለልን የሚጠላ ሰው

“ማታለል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ታማኝ አለመሆንን የሚጠላ ሰው” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እድሜውን ያረዝማል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) ይህ ፈሊጥ ሲሆን ለበለጠ ጊዜ ይኖራል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ረጅም ጊዜ መኖር” ወይም 2) ይህ ፈሊጥ ሲሆን የመሪነት ጊዜውን ማስረዘም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ለረጅም ጊዜ ይመራል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:17

የሌላ ሰው ደም አፍስሷል

እዚህ ላይ “ደም” የሚለው የሰውን ሕይወት ይወክላል። “ደምን ማፍሰስ” አንድን ሰው መግደል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የሆነ ሰው ገድሏል” ወይም “የሆነ ሰውን ነፍስ አጥፍቷል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ኮብላይ

እንዳይያዝ ለማምለጥ የሚሸሽ ሰው

እስከ ሞት ድረስ

“እስከሚሞት ድረስ።” ለቀጣይ የሕይወቱ ዘመን ሁሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ሕይወቱን በሙሉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በሐቀኝነት የሚራመድ ሰው በደህና ይጠበቃል

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር በሐቀኝነት የሚሄድን ማንኛውንም ሰው በደህንነት ይጠብቀዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ማንም

“ማንኛውም ሰው”

በሐቀኝት የሚራመድ

ይህ የሐቀኝነት ሕይወት የሚኖር ሰው የሚወክል ነው። “ሐቀኝነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ተውሳከ ግስ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “በታማኝነት ይራመዳል” ወይም “በታማኝነት ይኖራል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዱ በጠማማነት የተሞላ

ታማኝ ያልሆኑ ባለጠጋ ሰዎች በጠማማ መንገድ ወይም በጠመዝማዛ መንገድ እንደሚሄዱ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “በታማኝነት የማይኖር ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በድንገት ይወድቃል

ታማኝ ባልሆነ ሰው የሚደርሰው ነገር በድንገት እንደሚወድቅ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “በድንገት ይጠፋል” ወይም “በድንገት ይከስራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:19

መሬቱን የሚያርስ

ይህ መሬቱን የሚያርስ፣ የሚዘራ እና ሰበሉን የሚንከባከብ ማለት ነው።

የሚከተል

“የሚከተል ማንኛውም ሰው”

የማይጠቅም ሞያ የሚከተል

“የማይጠቅም ሞያ ያሳድዳል።” ምንም ትርፍ የሌላቸውን ነገሮች በመስራት የሚደክምና ጊዜ አልባ የሚሆን ሰው የማይጠቅሙ ነገሮችን እንደሚያሳድድ ተደርጎ ተነግሯል። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በድህነት ይሞላል

የማይጠቅሙ ሞያዎችን የሚከተል ሰው የተትረፈረፈ ምግብ እንደማያገኝ ተደርጎ ተነግሯል። “ድህነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “will be very poor” (ምፀት እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ))

በጥድፊያ ሃብታም የሆነ ግን ሳይቀጣ አይቀርም

“ሳይቀጣ አይቀርም” የሚለው ሁለት አሉታዊ አገላለጽ ጥቅም ላይ የዋለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “በጥድፊያ ሃብታም የሚሆኑትን ሰዎች እግዚአብሔር በእርግጠኝት ይቀጣል” (ምፀት እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በጥድፊያ ሃብታም የሆነ

እዚህ ላይ ያለው አመልካች መረጃ ይህ ሰው ሀብት ያገኘው ታማኝነት በጎደለውና አታላይነት በተሞላበት መንገድ መሆኑን የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “በጠድፊያ ሀብታም ለመሆን የሚሞክር ሰው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 28:21

ለቁራጭ ዳቦ ሲል ሰው ስህተትን ይሰራል

እዚህ ላይ “ቁራጭ ዳቦ” የሚለው በጣም ትንሽ ጉቦ ወይም ስጦታ ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋለ ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ሰው ለትንሽ ጥቅም ሲል ኃጢአትን ይሰራል” (ግነትና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስህተት ይሰራል

“ኃጢአት”

ስስታም ሰው

“ራስ ወዳድ ሰው።” ይህ ያለውን ሀብት ለሌሎች ለማካፈልና ገንዘብ ለማውጣት የማይወድ ሰው ነው።

ሀብት ያሳድዳል

ስስታም ሰው ሀብት እንደሚያሳድድ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “ለሀብት

በጣም ስስታም ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ድህነት በእርሱ ላይ ይመጣል
የስስታምነት ውጤት ድህነት በስስታም ላይ በድንገት እንደሚደርስበት ተደርጎ ተነግሯል። “ድህነት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በድንገት ድሃ ይሆናል” (ፈሊጥ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 28:23
ሰውን በምላሱ ከሚያሞግስ ይልቅ የሚገስጽ ሰው በኋላ ውሎ አድሮ ከገሰጸው ሰው ብዙ ሞገስ ያገኛል
ይህ “ሞገስ” የሚለው ረቂቅ ስም በገቢር ቅርጽ በመግለጽ፣ እንደ ግስ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው በምላሱ የሚያሞግሰው ሰው በፊቱ ሞገስ ከሚያገኝ ይልቅ ይልቅ የሚገስጸው በፊቱ ሞገስ (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የሚገስጽ ሰው
“ሰው የሚገስጽ ከሆነ”
መገሰጽ
ሰዎች ለሞራላዊ ባህርይ የተለያዩ መመርያዎችን እንዲታዘዙ ማሰልጠን
በምላሱ ያሞግሰዋል
እዚህ ላይ ምላስ መናገርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በቃላት ይክበዋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ይክበዋል
አንድን ሰው እውነተኛ ባልሆነ መንገድ ማመስገን፣ ወይም እውነተኛ ስላልሆኑ ነገሮች አንድን ሰው ማመስገን
የሚሰርቅ
“የሚሰርቅ ሰው”
“ኃጢአት አይደለም” የሚል፣ እርሱ
ይህ ቀጥተኛ ባልሆነ ትመህርተ ጥቅስ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህ ኃጢአት አይደለም” የሚል፣ እርሱ” (ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልቱ)
ተባባሪ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦: 1) “የእርሱ ጓደኛ” ወይም 2) ይህ ፈሊጥ አንድ ዓይነት ባህሪይ ያላቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እንደ እርሱ ተመሳሳይ የሆነ ሰው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 28:25
ስግብግብ ሰው
ከሚያስፈልገው በላይ በራስ ወዳድነት ተጨማሪ ነገሮችን፣ ገንዘብ ወይም ምግብ የሚፈልግ ሰው።
ግጭትን ያነሳሳል
የስግብግበ ሰው ድርጊት ግጭትን እንደሚያስነሳ ወይም እንደሚቀሰቅስ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ግጭትን ያመጣል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በራሱ ልብ የሚደገፍ ሰው
በራስ ልብ መደገፍ በራስ ልብ እንደ መታመን ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “በራሱ የሚታመን ሰው” (ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚራመድ
“የሚራመድ ማንኛውም ሰው”
በጥበብ ይመላለሳል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ይህ ፈሊጥ ሲሆን በጥበብ መኖር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በጥበብ ይኖረል” ወይም 2) ይህ ፈሊጥ ሲሆን የጥበበኛ ሰዎች ትምህርትን መከተል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የጥበብ ትምህርቶችን ይከተላል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 28:27
ሰው
“ያ ሰው”
ድሀ
ይህ በአጠቃላይ ድሆችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ድሀ ሰዎች” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)
ምንም አያጡም
ይህ ድርብ አሉታዊ ቃላት ጥቅም ላይ የዋለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የሚያስፈልጋቸው ማንኛውም ነገር አላቸው” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
በእነርሱ ላይ ዓይኖቹን የሚከድን ሰው ብዙ እርግማን ይቀበላል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ከድሀው ብዙ እርግማ ይቀበላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ድሆች በእነርሱ ላይ ዓይናቸውን ለሚከድኑ ለማንኛውም ሰው ብዙ እርግማ ይሰጣሉ” ወይም 2) በአጠቃላይ ብዙ እርግማን ከሰዎች ይቀበላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች በድሆች ላይ ዓይናቸውን ለሚከድኑ ለማንኛውም ሰው ብዙ እርግማን ይሰጣሉ” ወይም 3) ከእግዚአብሔር ብዙ እርግማን ይቀበላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር በድሆች ላይ ዓይናቸውን ለሚከድኑ ለማንኛውም ሰው ብዙ እርግማን ይሰጣቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ዓይኖቹን የሚከድን
“ዓይኑን የሚገድን ማንኛውም ሰው”
ለ ... ዓይኖቹን የሚከድን
ዓይንን መክደን ለድሆች ፍላጎት ምላሽ አለመስጠትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ቸል የሚል” ወይም “ላለመርዳት መምረጥ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉ ሰዎች ሲነሱ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ክፉ ሰዎች ስልጣን ሲይዙ ወይም መግዛት ሲጀምሩ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ሰዎች ወደ ስልጣን ሲወጡ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰዎች ራሳቸውን ይሸሸጋሉ
ክፉ ሰዎች እነርሱን እንዳይጎዱአቸው ሊያደርጉ የሚችሉትን ሁሉ ለማድረጋቸው በግነት የቀረበ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች ወደ መሸሸጊያ ይሄዳሉ” (ግነትና ጅምላ ፍረጃ እና ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ አመልካች ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ))
ይጠፋሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) “ይሄዳሉ” ወይም 2) “ከስልጣን ይወርዳሉ” ወይም 3) “ይወድማሉ።”
ይጨምራሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) “ይበዛሉ” ወይም 2) “ወደ ስልጣን ይወጣሉ።”

---

Chapter 29
Proverbs 29:1
አንገቱን ያደነደነ ሰው
ግትር ሰው አንገቱን እንዳደነደነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ግትር የሆነ ሰው” ወይም “ለመስማት እምቢተኛ የሆነ ሰው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በቅጽበት ይሰበራል
ይህ በገቢር ግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር በቅጽበት ይሰብረዋል፡ (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደማይድን ሆኖ
“እንዲፈወስ ሊረዳው የሚችል አንድም ሰው የለም።” በሽታ ለማንኛውም ዓይነት መጥፎ ሁኔታ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሊረዳው የሚችል ማም የለም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰዎች በኃይል ይተነፍፍሉ
ሰዎች በጥልቀት በረጅሙ ይተነፍሳሉ፣ መድከማቸውንና ማዘናቸውን የሚያሳይ ጩኸ መተንፈስ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕዝቡ ይደክማሉ፣ ያዝናሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 29:3
በፍትህ
“ፍትህ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ስም ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ፍትህ ያለበትን ነገር በማድረግ” ወይም “ፍትሃዊ ሕግጋትን በማዘጋጀት” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 29:5
ጎረቤቱን የሚሸነግል ሰው
ተናጋሪው የሚፈልገውን ነገር እንዲያደርግለት በማወቅ ሆን ብሎ ለጎረቤቱ እውነት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ያልሆነውን ነገር መንገር።
ለገዛ እግሩ መረብ ይዘረጋል
ተናጋሪው የሰውን ጉራ ሰውየው እንዲያዝ ወጥመድ ከማዘጋጀት ጋር አነጻጽሮታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ያንን ሰው በወጥመድ ለመያዝ ወጥመድ ማዘጋጀት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉ ሰው በራሱ ኃጢአት በወጥመድ ይያዛል
ክፉ ሰው ኃጢአትን ሲሰራ ወደ ወጥመድ እየሄደ እንደሆነ ያህል ነው። በሌሎች ሰዎች ላይ ክፋትን ለማድረግ ይመኛል፤ ነገር ግን እርሱ የሰራውን ነገር ራሱን ለመቅጣት እግዚአብሔር ይጠቀምበታል። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 29:7
ከተማን ያቃጥላሉ
እዚህ ላይ “ከተማ” የሚለው ቃል በከተማይቱ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች የሚወክል ነው። ምናልባትም ኀይላቸውን ለማሳየት ሕዝብ በብጥብጥ ውስጥ እንዲገባ የሚያደርጉ ሰዎች ከተማይቱን በእሳት እንዳቃጠሉ ተደርገው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለከተማይቱ ሕዝብ ብጥብጠጥ ይፈጥራሉ” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቁጣን ይመልሳሉ
ይህ ፈሊጥ ቁጡ ሰዎችን ለወደፊት ተቆጭ እንዳይሆኑ ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የቁጡ ሰዎችን ቁጣ ያበርዳሉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 29:9
ከ … ጋር ክርክር አለው
ሌላ አማራጭ ትርጉም እንዲህ የሚል ነው፦ “ሊከስሰው ወደ ፍርድ ቤት ይሄዳል።”
ይቆጣል ይስቃልም
ሞኝ በጣም ይናደዳል ከዚያም ጥበበኛውን ሰው እንዳይናገር ወይም ዳኛው ፍርድ እንዳይሰጥ ሊከለክለው ይሞክራል።
ይቆጣል
ይህ እንደ ጠንካራ አውሎ ነፋስ በጣም መጮህና መደናገጥ ከዚያም ኃይል በተሞላበት ሁኔታ ንቅስቃሴ ማድረግ ማለት ነው። ይህ አሉታዊ ቃል ነው።
እረፍትም አይኖርም
“ችግሩን መፍታት ፈጽሞ አይችሉም”
ሕይወት ይፈልጋሉ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን “ሊገድሉ ይፈልጋሉ” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 29:11
ትኩረት ይሰጣል
“ያደምጣል።” ይህንን በምሳሌ 17:4 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
ሹማምንቶቹ ሁሉ ክፉ ይሆናሉ
የገዢው ተግባር የፈጸሙት ነገር የሚያመጣውን ውጤት በመዘርዘር ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሹማምንቶቹ ሁሉ ክፉ እንዲሆኑ እንደሚያስተምር ያህል ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 29:13
ጨቋኝ
ሰዎችን በማስጨነቅ የሚይዝና የሰዎችን ሕይወት አስቃቂ የያደርግ
እግዚአብሔር ለሁለቱም የዓይን ብርሃንን ሰጥቷቸዋል
ይህ ፈሊጥ ሲሆን “እግዚአብሔር ሁለቱም በሕይወት እንዲኖሩ አድርጓቸዋል” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
በዙፋኑ
ዙፋን በዙፋኑ ላይ ሆኖ ለሚመራው መንግስት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በመንግስቱ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 29:15
በትርና ተግሳጽ ጥበብን ይሰጣሉ
ጸሐፊው በትርና ተግሳጽ እንደ ቁሳዊ እቃ ጥበብን የሚሰጡ ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወላጅ ልጁን ለመቅጣት በትር ቢጠቀምና ቢገስጸው፣ ልጁ ጥበበኛ ይሆናል” ወይም “ወላጆች ልጃቸውን ቢቀጡና ጥፋት ሲሰራ ቢነግሩት ልጁ በጥበብ መኖርን ይማራል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በትር
በእስራኤል የነበሩ ወላጆች ልጆቻቸውን በመምታት ስነ ስርዓት ለማስያዝ የእንጨት በትር እንደ መሳሪያ ይጠቀሙ ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “ስነ ስርዓት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ተግሳጽ
አንድ ሰው ለሌላ ሰው ተግሳጽ ሲሰጥ ወይም ያንን ሰው ሰገስጽ እርሱ የሚሰራውን ስራ እንደማይቀበለው ለዚያ ሰው እየነገረው ነው።
አመጸኝነት ይጨምራል
ይህ “አመጸኝነት” የሚለው ረቂቅ ቃል እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ተጨማሪ ሰዎች አመጽን ያደርጋሉ ከዚያም ኃጢአታቸው እየበዛ ይመጣል” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የክፉ ሰዎች ውድቀት
“ውድቀት” የሚለው ረቂቅ ስም “ወደቀ” በሚለውና የመምራት ስልጣንን ለማጣት ተለዋጭ ዘይቤ በሆነው ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እነዚህ ክፉ ሰዎች ይወድቃሉ” ወይም “እነዚህ ክፉ ሰዎች የመሪነት ስልጣናቸውን ያጣሉ” (ረቂቅ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 29:17
ሕግን የሚጠብቅ ግን የተባረከ ነው
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ሕግን የሚጠብቁትን ሰዎች ይባርካል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 29:19
ባርያ በቃል አይታረምም
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። “ባሪያን ከእርሱ ጋር በመነጋገር ብቻ ልታስተካክለው አትችልም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በቃሎቹ የሚቸኩለውን ሰው ተመልከተሃል?
ጸሐፊው የአንባቢውን ትኩረት ለማግኘት ሲል ጥያቄ ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፦ “በቃሎቹ የሚቸኩል ሰው ላይ ምን እንደሚመጣ ልብ ብለህ ልታስተውል ይገባሃል። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 29:21
ባርያውን የሚያሞላቅቅ
“ባርያውን ስራ እንዳይሰራ የሚያደርግና ባርያውን ከሌሎቹ ባርያዎቹ የበለጠ የሚንከባከበው”
በመጨረሻ
“በባርያው የወጣትነት እድሜ መጨረሻ” ወይም “ባርያው ሲያድግ”
ችግር ይኖራል
እነዚህ ቃላት ማንም ፈጽሞ አያውቅም የሚል ትርጉም ካለው የዕብራይስጥ ቃል የተተረጎሙ ናቸው። አንዳንድ ሰዎች ባርያው ደካማ ይሆናል የሚል መረዳት አላቸው፣ ሌሎች ደግሞ ባርያው ቤተሰቡን ይመራል የሚል መረዳት አላቸው።
ሁከትን ያነሳሳል
ሰዎች የበለጠ እንዲከራከሩ ማድረግ ሁከትን እንደ መቀስቀስ ወይም እንደ ማነሳሳት ተደርጎ ተነግሯል። “ሁከት” የሚለው ረቂቅ ቃል “ክርክር” በሚል ሊብራራ ይችላል። ይህንን በምሳሌ 15:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች የበለጠ እንዲከራከሩ ያደርጋል” ወይም “ሰዎች የበለጠ እንዲከራከሩና እንዲጣሉ ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ቁጣ የሞላበትም ሰው
ይህ ፈሊጥ ሲሆን “በቀላሉ የሚቆጣ ሰው” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 29:23
ትሁት መንፈስ ያለው ሰው ክብር ይሰጠዋል
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ትሁት መንፈስ ላለው ሰው ሰዎች ክብር ይሰጡታል” ወይም “ትሁት መንፈስ ያለው ሰው ከሰዎች ክብር ይቀበላል” ወይም “ትሁት መንፈስ ላለው ሰው እግዚአብሔር ሰዎች እንዲያከብሩት ያደርጋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የራሱን ሕይወተት ይጠላል
“የራሱ ጠላት ይሆናል”
እርግማንን ይሰማል መልስ ግን አይሰጥም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) “ከሌባ ጋር የሚካፈል ሰው” ስለሚያውቀው ነገር ማለትም ሌባው ስለሰረቀው ነገር እውነቱን እንዲናገር ሰዎች በመኃላ ስር ይይዙታል፣ እርሱም እውነቱን ቢናገር እንደሚቀጣ ያውቃል። አማራጭ ትርጉም፦ “በመኃላ ለመመስከር ፈቃደኛ አይሆንም” ወይም 2) ሰዎች ሌባው ማን እንደሆነ አያውቁም

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነገር ግን ሌባው እንዲረገም ወደ እግዚአብሔር ይጮሃሉ፣ ከዚያም “ከሌባው ጋር የተካፈለው” ሰው ለመናዘዝ ይፈራል ስለዚህ ከእርግማኑ ይወጣል ምክንያቱም ሌባውን ስለሚፈራ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ከረገሙት በኋላ እንኳ መልስ አይሰጥም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:25

ሰውን መፍራት ወጥመድ ውስጥ ይከትታል

ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉትን በማሰብ መፍራት በወጥመድ ውስጥ እንደመግባት ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉትን በማሰብ የሚፈራ ሰው በወጥመድ ውስጥ እንደተየያዘ ሰው ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወጥመድ

እንስሳትን በገመድ አፍኖ የሚይዝ

በእግዚአብሔር የሚታመን ይጠበቃል

ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር በእርሱ የሚታመነውን ይጠብቀዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙዎች የገዢን ፊት ይፈልጋሉ

“ፊት” የሚለው ቃል ሕዝቡ እርሱ ሊያደርግላቸው የሚፈልጉት ነገር ምን እንደሆነ ሲነግሩት የሚሰማና ሰምቶም የሚፈጽም መሪን የሚወክል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ሕዝብ መሪያቸው ለእነርሱ ትኩረት እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህ ለሰው የሚመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው

ሰዎች አንድን ሰው በፍትህ ይዘው እንደሆነና እንዳልሆነ የሚመለከት እግዚአብሔር እንጂ የሰው መሪዎች አይደሉም። “ፍትህ” የሚለው ረቂቅ ስም “ፍትሀዊ” ተብሎ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለሰዎች እውነተኛ ፍትሀዊ የሆነ እግዚአብሔር ነው” (የስም ቅፅሎች የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 29:27

የተጠላ

ሊጠላ የሚገባው ሰው። ይህንን በምሳሌ 3:32 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

---

Chapter 30

Proverbs 30:1

አጉር ... ያቄ ... ኢቲኤል ... ኡካል

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አጉር የያቄ ልጅ

ይህ የያቄ ልጅ ነው፣ የልጅ ልጅ አይደለም።

ንግግር

“መልእክት”

ለኢቲኤል፣ ለኢቲኤልና ኡካል

“ለኢቲኤል - ኢቲኤል የተባለውና ኡካል”

በእርግጥ

“በእውነት” ወይም “ምንም ጥርጥር የለውም”

የሰው ልጅ ማስተዋልም የለኝም

“ማስተዋል” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ማንኛውንም ነገር ሰዎች ሊያስተውሉ በሚገባቸው መንገድ እኔ አላስተውልም” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ቅዱሱም እውቀት የለኝም

“እውቀት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ ቅዱሱ በእርግጥም ምንም ነገር አላውቅም” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 30:4

ማን ነው ... የተመለሰ? ማን ነው ... በእጁ የያዘ? ማን ነው ... በካባው የሰበሰበ? ማን ነው ... የምድር ዳርቻ የጸና?

ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች የጠየቀው አንባቢው እግዚአብሔር ከሰዎች ይልቅ ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ እንዲያስብ ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ማንም ሰው ወደላይ ደርሶ የተመለሰ የለም። ማንም ሰው በእጁ የያዘ የለም። ማንም ሰው በካባው የሰበሰበ የለም። ማንም ሰው ምድርን ያጸና የለም።” ወይም “ማን ነው ... የተመለሰ? ማን ነው ... በእጁ የያዘ? ማን ነው ... በካባው የሰበሰበ? ማን ነው ... የምድር ዳርቻ የጸና? እነዚህን ነገሮች የሰራ አንድም ሰው የለም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማይ

እግዚአብሔር የሚኖርበት

ነፋሳትን በእጁ መዳፍ ሰብስቦ ያዘ

ጸሐፊው ስለ ነፋስ ሲናገር ሰው በእጁ ሊይዘውና ሊጨብጠው የሚችለው ነገር እንደሆነ አድርጎ አቅርቦታል። ማራጭ ትርጉም፡- “ነፋስን በእጁ ውስጥ ይዟል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእጁ መዳፍ

የተለያዩ ነገሮችን ለምሳሌ ውኃ እና አሸዋ የመሳሰሉትን ሲሰፍር እጁ የተቀረጸበት ሁኔታ። “ጎድጓዳ መሰል እጁ”

ሰብስቦ ያዘ

የተበታተኑ ትንንሽ ነገሮችን መያዝ እንዲቻል ሰብስቦ ከምሮ አስቀመጣቸው

የምድርን ዳርቻ ሁሉ አጸና

“የምድርን መጨረሻ የት እንደሆነ ወሰነ” ወይም “የምድርን መጨረሻ ዳርቻውን ምልክት አደረገበት”

ስሙ ማን ነው፣ የልጁስ ስም ማን ነው?

አንባቢው መልስ እንዲሰጥ ለማስገደድ ጸሐፊው እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱን የምታውቃቸው ከሆነ የእርሱንና የልጁን ስም ንገረኝ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በእርግጠኝነት ታውቃለህ!

ጸሐፊው እርሱ ራሱም ሆነ አንባቢው “ማን” ተብሎ በጥያቄዎቹ የተጠቀሰው ማድረግ የሚችለውን የሚያደርግ አንድም ሰው እንደማያውቁ ለማሳየት ምፀት ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህን ነገሮች ማድረግ የሚችል አንድም ሰው ታውቃለህ ብየ በእርግጥ አላስብም” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 30:5

ተፈትኗል

ቃላት አንድ ሰው ቆሻሻቸውን ከውስጣቸው ሊያጸዳቸው የሚያስፈልጋቸው ብረታ ብረት እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው የማይጠቅሙ ቆሻሻ ነገሮቹን ሊያሰወግድልት እንደሚገባ እንደ ውድና የከበረ ብረት ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መሸሸጊያቸውን በእርሱ ውስጥ ለሚያደርጉ ጋሻ ነው

“ጋሻ” የሚለው ቃል ሰውን ለሚከላከል ነገር ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ወደ እርሱ ለሚመጡና ሊጠብቃቸው ለሚለምኑት ይጠብቃቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቃሉ ላይ መጨመር

እርሱ ከተናገረው በላይ መናር

ትመዘናለህ

ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ አንተ ... እንደሆንህ ይመዝንሃል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Proverbs 30:7

ከንቱነትንና ውሸትን ከእኔ አርቅ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ሰዎች ለእኔ ከንቱነትንና ውሸትን እንዲነግሩኝ አትፍቀድላቸው” ወይም 2) “ከንቱነትንና ውሸትን እንድናገር አትፍቀድልኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከንቱነት

ውሸት፣ የማይጠቅሙ ቃላት

ድህነትንም ብልጽግናንም አትስጠኝ

ጸሐፊው “ድህነት” እና “ብልጽግና” አንድ ሰው ለሌላ ሰው ሊሰጣቸው የሚችለው ግዑዝ ነገሮች እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ ቃላት ረቂቅ ስም ናቸው፣ “ድሀ” እና “ባለጸጋ” ተብለው ሊብራሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም ድሃ ወይም በጣም ባለጸጋ እንድሆን አትፍቀድልኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ ሃብት ካለኝ፣ አንተን ከድቼ ... አላለሁና

ይህ ያልሆነ ሃሳባዊ ሁኔታ የሚገልጽ ሲሆን ጸሐፊው ባለጠጋ ከሆነ ግን እውን ሊሆን

የሚችል ነው። (ግምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)
ድሃ ከሆንኩኝ ደግሞ እሰርቅ ይሆናል … አሰድባለሁ
ይህ የሚገልጸው ያልተፈጸመ ሃሳባዊ ሁኔታ ሲሆን ጸሐፊው ድሀ ከሆነ ግን እውን ሊሆን የሚችል ነው። (ግምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)
ድሃ ከሆንኩኝ ደግሞ እሰርቃለሁ፣ የአምላኬንም ስም አሰድባለሁና
“የተለያዩ ነገሮች እንደሰረቅሁ የሚያውቁ ሰዎች እግዚአብሔር የለም ብለው እንዲያስቡ ላደርግ እችላለሁ” ወይም “በመስረቄ የእግዚአብሔርን መልካም ስም አሰድብ ይሆናል”
Proverbs 30:10
ስም ማጥፋት
እርሱን ለመጉዳት በመፈለግ ስለ ሌላ ሰው በውሸት መናገር
ይረግምሃል
“ባርያው ይረግመዋል”
አንተም በደለኛ ትሆናለህ
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሰዎች በደለኛ ያደርጉሃል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 30:11
የሚረግም ትውልድ … የማይባርክ … ትውልድ
“የሚረግም የሕዝብ ትውልድ … የማይባርክ … ትውልድ ናቸው”
ትውልድ
የክፍል ወይም የቡድን ዓይነት
በራሳቸው ዓይን ንጹሐን ናቸው
ዓይን መመልከትን ይወክላል፣ መመልከት ደግሞ ሃሳብና ግንዛቤን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ራሳቸውን ንጹህ እንደሆኑ ይቆጥራሉ” ወይም “ንጹህ እንደሆኑ ያምናሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእድፋቸው ያልታጠቡ ናቸው
“ታጠቡ” እና “እድፍ” የሚሉት ቃላት የሚናገሩት እግዚአብሔር ኃጢአትን የሰሩ ሰዎችን ይቅርታ እንደሚያደርግላቸው ሲሆን እርሱ አካላዊ እድፈትን ከሰዎች እንደሚያጥብና እንደሚያነጻ ዓይነት አድርጎ አቅርቦታል። ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር አላላቸውም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እድፍ
ይህ የሰዎችንና የእንስሳትን ትውከትና ሰገራ ሚጨምር ትህትና በተሞላበት ቃል ሊተረጎም ይገባል።
Proverbs 30:13
ዓይናቸው ትዕቢተኛ ነው … ሽፋሽፍቶቻቸውም ወደ ላይ ከፍ ያሉ ናቸው
ይህ የሚገልጸው ከሌሎች ሰዎች ይልቅ እነርሱ እንደሚሻሉ ስለሚያስቡ ሰዎች ነው። ዓይኖቻቸው ትዕቢተኞች እንደሆኑ ያሳያሉ፣ ሌሎችን የሚያዩበት መንገድ ደግሞ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ እነርሱ የተሻሉ እንደሆኑ እንደሚያስቡ ያሳያል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጥርሳቸው ሰይፍ የሆነ፣ መንጋጋቸውም ቢላዋ የሆነ ትውልድ ናቸው፣ ድሆችን ከምድር፣ ችግረኞችንም ከሰው ልጆች መካከል ያጠፉ ዘንድ
በጣም የሚጎዳ ንግግር የሚናገሩ የእነዚህ ትውልድ ሕዝብ ጥርሳቸውና መንጋጋቸው ሰይፍና ቢላዋ ሆኖ የተሰራ እና ድሀ እና ችግረኛን የሚበሉ የዱር እንስሳት እንደሆኑ ተደርገው ተገልጸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መንጋጋ
ጥርስ የሚበቅልበት የፊት አጥንቶች
Proverbs 30:15
አልቅት ሁለት ሴቶች ልጆች አሉት
ይህ ሁልጊዜ ስጠኝ ለሚል ለማይጠግብ ነገር ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ስስት ሁለት ልጆች አሏት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አልቅት
በቆዳ ላይ በመጣበቅ ደም የሚመጥጥ የትል ዓይነት
“ስጡን፣ ስጡን” እያሉ የሚጮሁ
ለዚህ ሌላ ተቀባይነት ያለው ትርጉም እንዲህ የሚል ነው:- “ሁሉም ስጡን የሚል ስም ተሰጥቷቸዋል።”
ፈጽሞ የማይጠግቡ ሦስት ነገሮች አሉ፣ ፈጽሞ “በቃኝ” የማይሉ አራት፤
እዚህ ላይ “ሶስት” እና “አራት” የሚሉት ቁጥሮች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት እንደ ግጥም ዘዴ ሳይሆን አይቀርም። አማራጭ ትርጉም:- “ፈጽሞ ጠገብሁ የማይሉ አራት ነገሮች አሉ፣ ፈጽሞ ‘በቃኝ’ የማይሉ” (ግጥም የሚለውን ይመልከቱ)
በቃኝ አይሉም
ይህ በአዎንታዊ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሁልጊዜ የበለጠ ይፈልጋሉ” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
ውኃ ፈጽሞ የማትጠግብ ምድር
ዝናብ ስላልነበረ ምግብ የማታመርት ምድር ለመጠጣት በቂ ውኃ እንደሌለው ሰው እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእናት መታዘዝን የሚንቅ
“መታዘዝ” የሚለው ቃል ለራሷ ለእናት ምትክ ስም ነው። በተጨማሪ “ታዘዝ” ተብሎ ሊብራራ የሚችል ረቂቅ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እናቱ ምንም የማትጠቅም እንደሆነች የሚቆጥርና የማይታዘዛት” (ረቂቅ ስም እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ዓይኑ … አሞራዎች
ጸሐፊው በሕዝብ መካከል ከሚኖሩበት ስፍራ ተለይተው በሚሞቱ ሰዎች ላይ ምን እንደሚሆን ሁለት መግለጫዎችን በመስጠት ሰውየው ይሞታል ይላል።
ዓይኑ የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጉጡታል
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “የሸለቆ ቁራዎች ዓይኑን ይጎጠጉጡታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ቁራ
እጽዋትንና የሞቱ እንስሳትን የሚበላ ትልቅ፣ የሚያብረቀርቅ፣ ጥቁር ወፍ
በአሞራዎችም ይበላል
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “አሞራዎች ይበሉታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
አሞራዎች
የሞቱ እንስሳትን የሚበሉና ትንንሽ ላባ የሌለው ራስ ካላቸው ከብዙ ትልልቅ ወፎች መካከል አንዱ ነው
Proverbs 30:18
ሦስት ነገሮች አሉ … አራት ደግሞ ፈጽሞ የማላስተውለው፡-
እዚህ ላይ “ሶስት” እና “አራት” የሚሉት ቁጥሮች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት እንደ ግጥም ዘዴ ሳይሆን አይቀርም። አማራጭ ትርጉም:- “ለእኔ ፈጽሞ የማለስተውላቸው በጣም አስደናቂ የሆኑ አንዳንድ ነገሮች አሉ - አራቱ የሚከተሉት ናቸው፡-“
በባህር ልብ ውስጥ
“ልብ” የመሐል ክፍሉን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “በባህር መሐል” ወይም “በክፍት ባህር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 30:20
ትበላለች አፏንም ትጠርጋለች
ይህ ለማመንዘር ከዚያም ለመታጠብ ለስላሴና ተለዋጭ ዘይቤ ሊሆን ይችላል። (ለስላሴ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 30:21
በሶስት ነገሮች ምድር ትናወጣለች፣ አራተኛውንም መቋቋም አትችልም
እዚህ ላይ “ሶስት” እና “አራት” የሚሉት ቁጥሮች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት እንደ ግጥም ዘዴ ሳይሆን አይቀርም። “ምድር እንድትናወጥ የሚያደርጉ መቋቋም የማትችለው አንዳንድ ነገሮች አሉ። አራቱ የሚከተሉት ናቸው፡-“
ሞኝ በመብል በጠገበ ጊዜ
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “የሚበላው በጣም በቂ ምግብ ያለው ሞኝ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የተጠላች ሴት ትዳር ስትይዝ
ይህች ሴት ከማግባቷ በፊት ሰዎች በትክክል ይጠሏት ነበር፤ አንድ ጊዜ ካገባች በኋላ ከማግባቷ በፊት ከነበራት የበለጠ ተቀባይነት ይኖራታል። ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ጥሩ ሰዎች የጠሏት ሴት ስታገባ” ወይም “የተጠላች ሴት ስታገባ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የእመቤቷን ቦታ ስትወስድ
ቤቱን ስታስተዳድር
Proverbs 30:24
ሽኮኮዎች
ትንሽ፣ ክብ ጆሮ፣ አጭር እግርና ጭራ ያላቸው እንስሳት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Proverbs 30:27
እንሽላሊት
አራት እግር፣ ረጅም፣ ቀጭን ሰውነትና ጭራ ያለው በደረቱ የየሚሳብ ትንሽ እንስሳ
Proverbs 30:29
ሰት ነገሮች አሉ ... በአካሄዳቸው ግርማ ሞገስ ያላቸው አራት አሉ
እዚህ ላይ “ሶስት” እና “አራት” የሚሉት ቁጥሮች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት እንደ ግጥም ዘዴ ሳይሆን አይቀርም። አማራጭ ትርጉም፡- “በግርማ ሞገስ የሚራመዱ አንዳንድ ነገሮች አሉ። አራቱ የሚከተሉት ናቸው።”
ግርማ ሞገስ
በግርማ ወይም በክብር፣ እንደ ንጉስ
አውራ ዶሮ
በኩራት የሚራመድ ያደገ ትልቅ ወንድ ዶሮ
Proverbs 30:32
እየተንጎራደደ
በኃይል እየተናጠ
ቅቤ
ከእንስሳት ወተት በሰው ተንጦ የሚወጣው ወፍራም ነገር

---

Chapter 31
Proverbs 31:1
ንጉስ ልሙኤል
ይህ የንጉስ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ልጄ ሆይ፣ ምንድን ነው? የማሕጸኔ ልጅ ሆይ ምንድን ነው? የስእለቴ ልጅ ሆይ ምን ፈለግህ?
የዚህ “ምን” የሚለው መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ምን ትሰራለህ?” ወይም “የምትሰራውን ልትሰራው አይገባም” ወይም 2) “ምን ልንገርህ?” ወይም “የምነግርህን ስማኝ” ወይም 3) “እንዳታደርግ የማስጠነቅቅህን ነገሮች አትስራ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ልጄ ... የማሕጸኔ ልጅ ... የስእለቴ ልጅ
ጸሐፊው አድማጩ በጥንቃቄ እንዲያስተውልና ለሚናገረው ሰው አክብሮት እንዲሰጥ ይፈልጋል።
የማሕጸኔ ልጅ
ማህጸን ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው። ልጆች ከመወለዳቸው በፊት ለሚያድጉበት ለሰውነት ክፍል የበለጠ ትህትና ያለው ቃል መጠቀም ተመራጭ ነው።
የስእለቴ ልጅ
“ስእለት” የሚከተሉትን ሊሆን ይችላል፡- 1) የእናት የጋብቻ ቃል ኪዳን ወይም 2) ካገባች በኋላ እግዚአብሔር ልጅ እንዳተገኝ የፈቀደላት ከሆነ ልጇን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ቃል የገባችው።
ብርታትህን ለሴቶች አትስጥ
ከትዳር ውጭም ሆነ ከቁባቶች ጋር “ከሴቶች ጋር ወሲብ ለመፈጸም ብዙ አትድከም።
ነገስታትን ለሚያጠፉም መንገድህን
“ወይም ነገስታትን የሚያጠፉ ሰዎች እንዲመክሩህ ፍቀድላለቸው”
መንገድህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “ሕይወትህን የምትኖርበት መንገድ” ወይም 2) “የምትሰራው ስራ”
ነገስታትን ለሚያጠፉም
ምናልባት ብርታቱን ሊሰጣቸው የማይገቡ ስነ-ምግባር የሌላቸው “ሴቶች”
Proverbs 31:4
ልሙኤል
ይህ የወንድ ሰው ስም ነው። ይህንን በምሳሌ 31:1 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
የተደነገገው
ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) “እግዚአብሔር የደነገገው” ወይም 2) “ነገስታቱ ራሳቸው የደነገጉት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የተጨቆኑ ሰዎችንም መብት ያጣምማሉ
“ለተጨቆኑ ሰዎች ሕጋዊ መብታቸውን ይነፍጋሉ”
ያጣምማሉ
መልካምን በክፉ ይለውጣሉ
የተጨቆኑ ሰዎችንም በሙሉ
“ሌሎች ሰዎች ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ የጎዷቸው ሰዎች በሙሉ
Proverbs 31:6
ወይን
x
Proverbs 31:8
መናገር ለማይችሉ ተናገርላቸው
መናገር ንጹሐን ሰዎችን ለመከላከል ለምንጠቀምባቸው ቃላት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ራሳቸውን መከላከል ለማይችሉ አንተ ተከላከልላቸው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እየጠፉም ላሉት ሁሉ ስለ ጉዳያቸው ተናገር
ስለ ጉዳያቸው የሚለው ጉዳይ ያለበትን ሰው የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ ሰዎች በፍትህ ምክንያት እየጠፉ ያሉትን በአግባቡ እንዲይዙአቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ ጉዳያቸው
ይህ አስጨምሬ ሊሞላ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ ጉዳያቸው ተናገር” ወይም “ስለ እነርሱ ተናገር” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ድሆችና የተቸገሩ ሰዎች
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት ደግሞ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ድሃ የሆኑና የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማግኘት የማይችሉ ሰወች” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 31:10
ችሎታ ያላትን ሴት ማን ሊያገኛት ይችላል?
ጸሐፊው አዲስ ክፍል እየጀመረ እንደሆነ ለማሳየት ጥያቄ ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ወንዶች ችሎታ ያላትን ሴት ማግኘት አይችሉም” ወይም “ብዙ ወንዶች ብዙ ስራን በጥራት የመስራት ችሎታ ያላትን ሚስት ማግኘት አይችሉም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሷ ዋጋ ከእንቁ የበለጠ ነው
“እርሷ ከእንቁ ይልቅ ዋጋዋ የከበረ ነው”
ድሃም በፍጹም አይሆንም
ይህ ምፀት በአዎንታዊ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ሁልጊዜ የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ይኖረዋል” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
Proverbs 31:16
የእጆቿ ፍሬ
ከሱፍና ከተልባ እግር ከሰራችው ያገኘችው ገንዘብ (ምሳሌ 31:13) ከዛፍ የሚገኝ ፍሬ እንደሆነ ተደርጎ ተንሯል። እጆች ለዚያ ሰው ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ያገኘችው ገንዘብ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)
ራሷን በብርታት ታለብሳለች
ልብስ መልበስ ለስራ ለመዘጋጀት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ራስዋን ለከባድ አካላዊ ስራ ታዘጋጃለች” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ክንዶቿንም ታጠነክራለች
“ስራዋን በመስራት ክንዶቿን ታበረታለች”
Proverbs 31:18
ታውቃለች
በጥንቃቄ በማየት ትገነዘባለች
ሌሊቱንም ሙሉ መብራቷ አይጠፋም
ይህ ምናልባት ግነት ሊሆን ይችላል፡- ሌሊቱን ሁሉ ቆይታ ትሰራለች፣ ነገር ግን ጸሐይ ጠልቃ እስከምትወጣ ድረስ አይደለም” አማራጭ ትርጉም፡- “ስራዋን ስትሰራ ሌሊቱን ሁሉ መብራቷን ታበራለች” (ግነትና ጅምላ ፍረጃ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እንዝርት
ሹል ጫፍ ያለው ክር ለመፍተል የሚጠቅም በጣም ቀጭን እንጨት
Proverbs 31:20


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እጆቿን ለድሆች ትዘረጋለች

እጅ ሴትዮዋ በእጇ ተጠቅማ በመስጠት ለምታደርገው እርዳታ ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ድሀ ትረዳለች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቿን ትዘረጋለች

እነዚህ ቃላቶች በምሳሌ 31:19 ላይ “እጆቿን ለድሆች ትዘረጋለች” በሚለው እንደተተረጎመው በተመሳሳይ ቃላት ይተረጎማሉ፡፡

ቀይ ልብስ ለብሰዋልና

እዚህ ላይ “ቀይ ልብስ” የልብሱን ቀለም አያመለክትም፣ ነገር ግን የሚያሳየው ልብሱ በጣም ውድና የሚሞቅ መሆኑን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ውድና የሚሞቅ ልብስ አላቸው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ቀይ

ቀይ ቀለም፣ ነገር ግን ብርቱካናማ የተቀላቀለበት፡፡

Proverbs 31:22

ላይነን

በተልባ እግር ክር የተሰራ ልብስ

ባለቤቷ ይታወቃል

ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል፡፡ “ማወቅ” የሚለው ግስ ለአክብሮት ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ሰዎች ባለቤቷን ያከብሩታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ባለቤቷም ከአገሩ ሽማግሌዎች ጋር ሲቀመጥ

ሕግ ለመስጠትና ክርክሮችን ለመፍታት

Proverbs 31:24

ላይነን

x

Proverbs 31:26

አፏን በጥበብ ትከፍታለች

አፋችንን የመክፈት ተግባር ለመናገር ምትክ ስም ነው፡፡ ”ጥበብ” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ተውሳከ ግስ ወይም ቅጽልሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “በጥበብ ትናገራለች” ወይም “የጥበብ ቃላት ትናገራለች” (ምትክ ስም እና ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የደግነት ሕግም በምላሷ ላይ አለ

“በምላሷ ላይ” የሚለው ሀረግ ንግግሯን የሚያመለክት ነው፣ ምክንያቱም ምላስ የአፍ አንዱ አካል ነው፡፡ “የደግነት ሕግ” የሚለው ሀረግ ሰዎችን ደግ እንዲሆኑ ማስተማርን የሚወክል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ሰዎች ደግ እንዲሆኑ ታስተምራለች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የቤተሰቦቿን መንገዶች ትመለከታለች

“መንገዶች” የሚለው ቃል ሰዎች የሚኖሩበትን መንገድ የሚያመለክት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ቤተሰቦቿ በሙሉ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ እየኖሩ እንደሆነ ታረጋግጣለች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የስንፍናንም እንጀራ አትበላም

የአንድ ነገር “እንጀራ መብላት” አንድ ነገር መስራት ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ሰነፍ አይደለችም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ስንፍና

ምንም አለመስራት እና ሰነፍ መሆን

Proverbs 31:28

አድገው

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) ቃል በቃል “ተነስተው” ወይም 2) እንደ ምትክ ስም፣ “በቅልጥፍና:” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የተባረክሽ ነሽ ይሏታል

መልካም ነገሮች በሕይወቷ እንደተከናወኑ መናገር ምክንያቱም መልካም ነገሮችን ሰርታለች፡፡ ይህ በቀጥታ እንደ ተጠቀሰ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “እንኳን ደስ አለሽ ማለት” ወይም “‘እናቴ እንኳን ደስ አለሽ!’ ብሎ መናገር” (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

ትበልጫለሽ

“ከሁሉም የተሸለ ስራ ሰርተሸል”

Proverbs 31:30

ቁንጅና አሳሳች ነው

“ቁንጅና” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ቆንጆ ሴት ሰዎችን ልታታልል ትችላለች” ወይም “መልካም ውበት ያላት ሴት በእርግጠኝነት ክፉ ልትሆን ትችላለች፡፡” ይህንን በምሳሌ 11:16 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ውበትም ጠፊ ነው

“ውበት” የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “አሁን ውብ የሆነች ሴት ሁልጊዜ ውብ ልትሆን አትችልም” (ረቂቅ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ ትመሰገናለች

ይህ በገቢር ግስ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ሰዎች ያመሰግኗታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የእጆቿን ፍሬ

ከሱፍ እና ከተልባ እግር (ምሳሌ 31:13) ስራ ያገኘችው ገንዘብ ፍሬ ከሚሰጥ ዛፍ እነንደሚገኝ ፍሬ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ እጆች ለሰውየው ተዛምዶአዊ ዘይቤ ነው፡፡ ይህንን በምሳሌ 31:16 እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ያገኘችው ገንዘብ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተዛምዶአዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ስራዎቿም በአደባባዮች ያስመሰግኗት

ስለ ሰራችው ስራዎቿ ትመሰገናለች፣ በስራዎቿ አይደለም፡፡ “በአደባባይ” ያሉት ሰዎች ንግድና የሕግ ጉዳዮች በከተማይቱ መግቢያ አካባቢ የሚሰሩ የከተማይቱ ዋነኛ ሰዎች ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “በሰራችው ስራዎቿ ምክንያት የከተማይቱ ዋነኛ ሰዎች ያመስግኗት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

---

## Chapter 1

Ecclesiastes 1:1

እንደ ተን (ከንቱ) እንፋሎት እንደ ንፋስ ሽዉታ ሁሉም ነገር ጠፊ ነው

ይህ የሚናገረው እንዴት በሕይወት ወስጥ ሁሉም ነገር እንደ ተን ወይም ንፋስ ሽዉታ ጠፊ እንደሆነና ዘላቂ እሴት ወይም ጥቅም እንደሌለው ነው፡፡ ተርጓሚ "እንደ ተን (ከንቱ) እንፋሎት አላፊ እንደ ንፋስ ሽዉታ ጠፊ ሁሉም አላፊና ዘላቂ እሴት ወይም ጥቅም የለውም"

ከፀሐይ በታች ....... የሰው ትርፍ ምንድር ነው?

ፀሐፊው ይህን የግነት ጥያቄ የተጠቀመው የሰው ድካሙ ከንቱና ዘላቂ ትርፍ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት ነው፡፡ ጥያቄው በአረፍተ-ነገር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚ "ከፀሐይ በታች የሰው ልጅ ትርፍ የለውምን "(የግባት ጥያቄ ተመልከት)

ከፀሐይ በታች ........ የሰው ትርፍ ምንድነው ?

ፀሐፊው በተጋነነ መልኩ የጠየቀበት ምክንያት የሠው ሥራ እርባና ቢስና ዘለቄታዊ ፍፃሜ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት ነው፡፡ ይህ ጥያቄ አንድ በአረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል፡፡ ተርጓሚ "ከፀሐይ በታች የሰው ልጅ ትርፍ የለውም" ( የተጋነነ ጥያቄ ተመልከት )

ከፀሐይ በታች

ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ነገሮች ሁሉ የሚገልፅ ሐሳብ ነው፡፡

Ecclesiastes 1:4

አጠቃላይ መረጃ

ፀሐፊው በተረዳው መልኩ ተፈጥሮአዊ የሕይወት ሥረዓትን እያቀረበ ( እየገለፀ ) ነው፡፡

ወደምትወጣበትም ስፍራ ትቸኩላለች

ይህ ፀሐይን በሠው አስመስሎ ከገባችበት ወደምትጠልቅበት በፍጥነት ወጥታ እንድትሄድ እንዴት በቀኑ መጨረሻ እንደምትጠልቅና በፍጥነት ዳግም መልሳ እንደምትወጣ የሚናገር ሃሳብ ነው፡፡( በሰው ማስመሰል ተመልከት )

Ecclesiastes 1:7

አጠቃላይ መረጃ

ፀሐፊው ስለተፈጥሮ ስርዓት ግንዛቤውን ( ማስተዋልን ) ቀጥሏል፡፡ ነገር ሁሉ ያደክማል

"ሁሉም ነገር አድካሚ ይሆናል

የሰው ልጅ እነዚህን ነገሮች ለመግለፅ ስለማይችል መሞከሩ ዋጋ የለውም፡፡"

ዓይን ከማየት አይጠግብም

እዚህ ጋር ዓይን የሚወክለው ሙሉ ሰውን ነው፡፡ ተርጓሚ የሰው ልጅ በዓይን በሚያየው ነገር አይረካም

ጆሮም ከመስማት አይሞላም



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እዚህ ጋር "ጆሮ" የሚወክለው ሙሉ ሰው ነው። ተርጓሚ የሰው ልጅ በጆሮ በሚሰማውም አይደሰትም
Ecclesiastes 1:9
አጠቃላይ መረጃ
በጆሮ በሚሰማው ነገር ሁሉ እርሱ የሚሆን ነው ሰውና ድርጊቶቹን ተመልከት ምንም አዲስ ነገር የለውም ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ " ከዚህ በፊት የሆነው ነገር ሁሉ ተመልሶ ወደፊት ይሆናል "
ከፀሐይ በታች
ይህ ምድር ላይ የተደረጉትን ነገሮች ሁሉ ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "በምድር ላይ"
ማንም እነሆ ይህ ነገር አዲስ ነው ይል ዘንድ ይችላልን?
ይህ የግነት ጥያቄ የተጠየቀው የሰው ልጅ አዲስ ነገር አለ ማለት እንደማይችል አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ በአረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ይህ ነገር አዲስ ነው የሚባል ነገር የለም " ( የግነት ጥያቄ ተመልከት )
ይል ዘንድ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "የሆነ ሰው ሊናገር ያለው ነገር "
እርሱ የሚደረግ ነው
ጥገኛ ሊቀርብ ይችላል ተርጓሚ "ሰዎችም አያስተውሉአቸውም "
Ecclesiastes 1:12
ልቤን አተጋሁ
እዚህ ጋር ፀሐፊው "ልብ"ን የተጠቀመው ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "ቆራጥ ሆንኩ" ወይም እራሴን አፀናሁ።"
አመረምርና እፈልግ ዘንድ
እነዚህ ሁለቱ ቃላት ተመሳሳይ ሲሆኑ ተግቶ እንዳጣ አፅንኦት ለመስጠት ነው ።
ከሰማይ በታች
ይህ ምድር ላይ የተደረጉትን ነገሮች ሁሉ ይገልፃል። ተርጓሚ "ምድር ላይ"
ለሰው ልጅ
"የሰው ዘር" ( የሰው ልጅ )
የተወራውን ሥራ ሁሉ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል ። ተርጓሚ "ሰዎች የሚያደርጉት ሁሉ "
ከፀሐይ በታች
ይህ ምድር ላይ የተደረጉትን ነገሮች ሁሉ ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "በምድር ላይ" (ፈሊጣዊ ተመልከት)
እነሆ
ፀሐፊው ይህን ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ ለሚናገረው ንግግር ትኩረት ለመሳብ ነው። ተርጓሚ "በእርግጥ " "በእውነት " (ፈሊጣዊ ተመልከት )
ሁሉ ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ዘይቤአዊ ሲሆኑ ነገሮች ሁሉ ከንቱና የማይረቡ መሆናቸውን አፅንኦት ለመስጠት ነው።
ሁሉ ከንቱ ነው
"እንደተን ብቻ " ተርጓሚው ስለማይጠቅሙና ትርጉም ስለሌላቸው ነገሮች ንፋስን ለመቆጣጠር ለሞከሩ እንደፈለጉ ይናገራል። ተርጓሚ "ጥቅም የሌላቸው ነገሮች ንፋስን ለመቆጣጠር ሲሞክሩ" (ዘይቤአዊ ተመልከት )
ጠማማ ይቀና ዘንድ አይችልም ጎደሎም ይቆጠር ዘንድ አይችልም
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "የተጣመመን ነገር ሰዎች ሊያቀኑ አይችሉም የሌለን ነገር መቁጠር አይችሉም።"
Ecclesiastes 1:16
እኔ በልቤ .......... ተናገርሁ
እዚህ ጋር ተርጓሚው እራሱን በልቡ ይገልፃል። ይህም ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት ነው ተርጓሚ "እኔ ለራሴ ተናገርኩ"
ልቤን ሰጠሁ
እዚህ ጋር እራሱን በ"ልብ" ይገልፃል። ሲገልፅ ለተማረው ነገር አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "አገኘሁ ወይም ተማርኩ"
ልቤን ሰጠሁ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በልቡ ይገልፃል። ተርጓሚ "ቆረጥኩ" ወይም "እራሴን ሰጠው"
እብደትን ሞኝነትንም
"እብደትና " ሞኝነት " ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ሁለቱም ቃላት ስለሞኝነት አስተሳሰብና ባህሪይ ይናገራል ።
ነፋስንም እንደመከተል ነው።
ፀሐፊው፡ጥበብን፡ መማርና እብደትና ሞኝነት፡ ልክ ነፋስን ለመቆጣጣር የመሞከር ያክል፡ እርባና ቢስ ነው። ተርጓሚ ይህን በመክብብ፡ 1:14 ላይ ተተርጉሟል። ተርጓሚ "ልክ ነፋስን የመቆጣጣር ያክል እርባና ቢስ ነው።"(ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

---

Chapter 2
Ecclesiastes 2:1
እኔ በልቤ አልሁ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በልቡ ይገልፃል። ተርጓሚ"ለራሴ አልኩ "
በደስታም እፈትንሃለሁ
እዚህ ጋር እራሱን በሦስተኛ ወገን ይናገራል ። መልካም ደስታ የሚለው ቃልም እንደ ቅፅል ሊገለፅ ይችላል ። ተርጓሚ" እራሴን ደስታ በሚሰጡኝ ነገሮች እፈትናለሁ "(ረቀቅ ስሞች ተመልከት) መልካም የሚለው ቃል በግስ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ "በሚያስደስቱም ነገሮች ሐሴት አደርጋለሁ።"(ረቂቂ ስም ተመልከት)
ይህም ደግሞ እነሆ ከንቱ ነበር
ይህ ደስታ ልክ እንደ ተን ጊዜአዊ እንደሆነና ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንደሆነ ይናገራል። ተርጓሚ ይህም ልክ እንደ ተን ጊዜአዊና ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ሳቅን "ዕብድ ነህ" አልሁት
በትምህረተ ጥቅስ ውስጥ ያለው ሐሳብ ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ "በነገሮች ላይ መሣቅ እብደት ነው አልሁ"(ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅስ ተመልከት)
ምን ታደርጋለህ?
ፀሐፊው መልካም (እርካታ) እርባና ቢስ እንዲሆንና አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄን ይጠቀማል ። የግነት ጥያቄን ተመልከት)
Ecclesiastes 2:3
እስካይ ድረስ ልቤ
ይህ ሐሳብ (ንግግር ) የሚናገረው ላይታዪ ነገር በጣም ማሰብን ያሳያል። ስሜቱና ሐሳቡ ልቡ የሆኑ ያክልም ፀሐፊው ይናገራል።
ሰውነቴን በወይን ጠጅ ደስ ለማሰኘት
"ሰውነቴን" የሚለው ቃል በቀላል ሐረግ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ "እራሴን ደስ ለማሰኘት ወይን ጠጅ መውሰድ (መጠቀም) (ረቂቂ ስም ተመልከት)
ልቤ በጥበብ እየመራኝ
ፀሐፊው የተማረን ጥበብ በሰው አስመስሎ ልክ የሆነ ሰው እንደመራው እንዴት ሊመራው እንደነበረ ይናገራል። ተርጓሚ "ጥበበኞች ስላስተማሩኝ ነገሮች አሰብኩ" (ሕይወት ክል ነገሮችን በሰው ማስመሰል ተመልከት )
ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ ስለሆኑት ነገሮች ሁሉ ይገልፃል ። ተርጓሚ "በምድር ላይ"
በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ
"በሕይወት እያሉ"
Ecclesiastes 2:4
ቤቶችንም አደረግሁ ወይንም ተከልሁ አትክልትንና ገነትን አደረግሁ
ምናልባት ፀሐፊው ሌሎች ሥራውን እንዲሠሩ ተናግሮአል። ተርጓሚ ቤትን የሠሩልኝና ወይንም የተከሉ ሰዎች ነበሩኝ ። አስተከልኩአቸው አስደረኩአቸው ። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
አትክልትንና ገነትን
እነዚህ ሁለት ተመሣሣይ ትርጉም ሲኖራቸው የሚገልፁትም የሚያምር የፍራፍሬ እርሻ ተክል (ዛፍን)ነው።
ዘፎችን አጠጣበት ዘንድ
"ለዛፎች ውሃ አቀርብ ዘንድ"
በድር የተተከሉትንም ዛፎች
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል ። ተርጓሚ "ዛፎች ያሉበት (የሚያድጉበት) ዱር"
Ecclesiastes 2:7
የቤት ውልድ ባሪያዎችም ነበሩኝ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"በቤት ውስጥ የተወለዱ ባሪያዎች ነበሩኝ " ወይም "ባሪያዎች ልጆች ወልደው እነርሱም ባሪያዎች ነበሩ"
ከነበሩት ሁሉ ይልቅ
ግልፅ የሆነ ግሥ ሊቀርብ ይችላል ። ተርጓሚ "ማንም ከነበረው በላይ "ወይም ማንም የትኛውም ንጉሥ ከነበረው በላይ"
የከበረውንም የነገሥታትና የአውራጃዎችን መዝገብ
ይህ የሚገልፀው የጎረቤት ሀገሮች ለእሥራኤል ንጉሥ ተገደው ይከፍሉት የነበረውን ወርቅና ሀብት ነው። ተርጓሚ ከነገሥታትና ከአውራጃ ገዥዎች መዝገብ አገኘው።
አውራጃዎች
እዚህ ጋር "አውራጃዎች"የክፍለ-ሀገር ገዥዎችን ይወክላሉ ።ተርጓሚ "የክፍለ-ሀገር ገዥዎች"
የሰዎች ልጆችንም ተድላ ....... የብዙ ሴቶችም
ይህ ማለት አንድ ሰው ልክ ከሴቶች ጋር ሲተኛ የሚያገኘውን እርካታ ያክል ከብዙ ሴቶች ጋር በመተኛት ደስ ይለኝ ነበር። ተርጓሚ "ሰው ከሴት ጋር በመተኛት እንደሚደሰተው እንዲህ ከብዙ ሴቶች ጋር በመተኛት እጅግ እደሰት ነበር ።
Ecclesiastes 2:9
ከእኔ አስቀድመው በኢየሩሳሌም ከነበሩት ሁሉ ይልቅ
ይህ የቀደሙትን የኢየሩሳሌም ገዥዎች ይገልፃል። ተርጓሚ "ከእኔ በፊት በኢየሩሳሌም ውስጥ ገዥ ከነበሩት ይልቅ"
ጥበቤ ከእኔ ጋር ፀንታ ቀረች
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። "በጥበብ መመለስ ቀጠልኩ " (ፈሊጣዊ ተመልከት)
ዓይኖቼን ከፈለጉት ሁሉ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለተመለከተው ነገር አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በዓይኖቹ ይገልፃል።ተርጓሚ ያየሁትንና የተመኘሁትን ሁሉ .... ከራሴ "
... ሁሉ አላራቅሁትም
"ሁሉንም አገኘሁ"
ልቤን ከደስታ ሁሉ አላራቅሁትም
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለምኞቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በልቡ ይገልፃል ይህ በመልካም መልኩ ሊቀመጥ /ሊፃፍ የሚችል ሲሆን ደስታ የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገልፅ ይችላል። ተርጓሚ "እራሴን ከየትኛውም ደስታ አልከለከልኩም" ወይም "በሚያስደስተኝ ነገር ሁሉ ለመደሰት ለራሴ ፈቀድኩ"
ልቤም ...... ደስ ይለው ዘንድ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለምኞቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በልቡ ይገልፃል። ተርጓሚ "ደስ ተሰኘሁ"
Ecclesiastes 2:11
እጁ የሠራቻት ሥራዬን ሁሉ
እዚህ ጋር ፀሐፊው እራሱን በእጁ ይገልፃል። ተርጓሚ "ያከናወንኳቸውን ሁሉ"
ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነበር
እነዚህ ሁለት ቃላት ዘይቤአዊ ሲሆን እርባና ቢስ ስለሆኑት ነገሮች የሚገልፅ ሀሳብ ነው።
ከንቱ
ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም ስለሌላቸው ነገሮች ተን የሆኑ ያክል ይናገራል። መክብብ 1:14 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። ተርጓሚ "ልክ እንደ ተን እርባና ቢስ " ወይም "ትርጉም የለሽ (ዘይቤአዊ ተመልከት)
ንፋስን እንደመከተል
ፀሐፊው የሚለው ሰዎች የሚያደርጉት ሁሉ ንፋስን ለመቆጣጠር እንደ መሞከር እርባና ቢስ ነው ። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "ንፋስን እንደመቆጣጠር ያክል እርባና ቢስ ነው።" (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ከፀሐይ በታችም ትርፍ አልነበረም
"ነገር ግን ከፀሐይ በታች ትርፍ አልነበረም"
ከፀሐይ በታች
ይህ የሚገልፀው በምድር ላይ የተደረጉትን ሁሉ ነው። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "በምድር ላይ "(ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
እብደትንና ስንፍናን
ሁለቱ ቃላት ተመሣሣይ ትርጉም ሲኖራቸው የሞኝነት አስተሳሰብንና ባህሪይን በቅደም ተከተሉ ይገልፃል። የመክብብ 1:17 ትርጉምን ተመልከት።
በፊት ከተደረገው በቀር ከንጉሥ በኋላ የሚመጣው ሰው ምን ያደርጋል
ፀሐፊው የግነት ጥያቄን ንጉሡ በፊት ከሠራው የተሻለ ነገር የሚቀጥለው ንጉሥ ምንም ሊያደርግ እንደማይችል አፅንኦት ለመስጠት ነው ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ከንጉሡ ቀጥሎ የሚመጣው ንጉሥ የቀደመው ንጉሥ ያልሠራውን ሊሠራ እንደማይችል" (የግነት ጥያቄ ተመልከት)
ከንጉሥ በኋላ የሚመጣው ሰው (ንጉሥ)
አሁን ያለውን ንጉሥ የሚተካ ንጉሥ ወይም "ከእኔ ቀጥሎ የሚመጣው ንጉሥ"
Ecclesiastes 2:13
ብርሃን ከጨለማ እንደሚበልጥ እንዲሁ ጥበብ ከሥንፍና
ይህ ንግግር ብርሃን ከጨለማ እንደሚሻል በማነፃፀር ጥበብ ከሥንፍና እንደሚሻል ያሳያል። (ንግግር ተመልከት)
የጠቢብ ዓይኖች በራሱ ላይ ናቸው
ይህ ጠቢብ ሰው ለመንገዱ ወዴት እንደሚሄድ አትኩሮት በመስጠት በጥበብ እንዴት እንደሚሄድ የሚናገር ነው። ተርጓሚ ጠቢብ ሰው ወዴት እንደሚሄድ አይኖቹን እንደሚጠቀም አይነት ሰው ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ዓይኖቹ በራሱ ላይ ናቸው
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው ተርጓሚ ለማየትና ለመመልከት ትኩረት ይሰጣል
ሰነፉ ግን በጨለማ ይሄዳል
ይህ ሰነፉ የሚወስነውን ያልተገባ ውሳኔ በጨለማ ውስጥ ከሚሄድ ሰው ጋር ያነፃፅራል (ያወዳድራል) ተርጓሚ "ሰነፉ በጨለማ ወስጥ እንደሚሄድ አይነት ሰው ነው"(ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ተመሳሳይ ክስተት
ሞት
Ecclesiastes 2:15
በልቤ .........አለው
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን "በልቡ" ይገልፃል። ተርጓሚ "ለራሴ ተናገርኩ (አልኩ)
ለምን እጅግ ጠቢብ ሆንሁ?
ይህ ፀሐፊው የግነት ጥያቄን የሚጠቀመው ጠቢብ መሆን ትርፍ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "በጣም ጠቢብ ቢሆን ምንም ለወጥ አያመጣም" (የግነት ጥያቄን ተመልከት)
በልቤ ...... አልሁ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን "በልቡ" ይገልፃል። ተርጓሚ "ደመደምኩ"
ይህ ደግሞ ከንቱ ነው
ይህ ደግሞ "ተን" ነው ፀሐፊው ተን (ከንቱ) እንደሆኑ ያክል ስለማይረቡና ትርጉም ስለሌላቸው ነገሮች ያወራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ወይም ትርጉም የለሽ" (ዘይቤአዊ ተመልከት)
ለዘላለም የሚሆን የጠቢብና የሰነፍ መታሰቢያ አያገኝም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ሰነፍን ለዘላለም እንደማያስተውሉ ሁሉ ጠቢብንም እንደዚሁ ለዘላለም አያስታውሱም"
ነገር ሁሉ የተረሳ ይሆናልና
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ሁሉም ነገር በሰዎች ዘንድ የተረሳ ይሆናል።"
Ecclesiastes 2:17
የተሠራው ሥራ ሁሉ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል ። ተርጓሚ "ሠዎች የሚሰሩት ሥራ ሁሉ"
ከብዶኛልና
"አስቸግሮኛልና "
ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነው።
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ዘይቤአዊ ሲሆኑ እርባና እና ከንቱ ስለሆኑ ነገሮች አፅንኦት የሚሰጥ ሀሳብ ነው።
ከንቱ
"ተን "ፀሐፊው እርባና ቢስን ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ተን (ከንቱ) እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ 1:14፡ ትርጉምን የለሽ"(ዘይቤአዊ ተመልከት)
ነፋስን እንደመከተል
ፀሐፊው የሚናገረው ሰዎቸ የሚያደርጉት ሁሉ ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ ነው ። የመክብብ :1:14፡ ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "ነፋስን እንደመቆጣጠር ያክል እርባና ቢስ ነው" (ዘይቤአዊ ተመልከት)
ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉ ነገሮችን ሁሉ ይገልፃል። የመክብብ :1:3፡ ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "በምድር ላይ" (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ከእኔ በኋላ ለሚመጣው ሰው
"ከእኔ በኋላ ለሚወርሰው ሰው"
Ecclesiastes 2:19
ጠቢብ ወይም ሰነፍ እንዲሆን የሚያውቅ ሰው ማን ነው?
ፀሐፊ ይህን የግነት ጥያቄ ሀብቱን ስለሚወርሰው ሰው ባህርይ ማንም እንደማያወቅ አፅንኦት ለመስጠት ነው ። ተርጓሚ "ጠቢብ ወይም ሰነፍ ስለመሆኑ ማንም ስለማያውቅ" (የግነት ጥያቄን ተመልከት)
እንዲሆን
የፀሐፊውን ወራሽ ማንነት ይገልፃል።
ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉ ነገሮችን ሁሉ ይገልፃል የመክብብ ፡1፡3፡ትርጉምን ተመልከት ። ተርጓሚ "በምድር ላይ "(ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
በድካም ሀብትና ጠቢብ ብሆን ሀብት በድካሜ
እዚህ ጋር የፀሐፊው "ድካም "እና ጥበብ እራሱንና በጥበብ የሠራቸውን ነገሮች ይወክላሉ። ምናልባት በትክክል ለሠራቸው ሕንፃዎች ገነ ይኖረው ይሆናል ተርጓሚ "ለመገንባት፤በጥበብና በጣም እንደደከምኩበት"
ከንቱ
ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ተን (ከንቱ) እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ ፡1፡14፡ ትርጉም የለሽ (ዘይቤአዊ ተመልከት)
ልቤን ---- ድካም ሁሉ
እዚህ ጋር ፀሐፊው ለሥሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በልቡ ይወክለል። ተርጓሚ "መድከም ጀመርኩ " ወይም "ተስፋ መቁረጥ ጀመረኩ"
Ecclesiastes 2:21
በጥበብና በእውቀት በብልኃትም ከደከመ
"የተማረውን በመጠቀም በጥበብና በብለሃት የሚሠራ"
ለሌላ ላልደከመበት
"ለሌላ ለልሠራበት "
ከንቱ
ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ (ተን) እንደሆኑ ይናገራል የመክብብ ፡1፡14፡ ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ እንደ ከንቱ (ተን) እርባና ቢስ ወይም ትርጉም የለሽ (ዘይቤአዊ ተመልከት)
ትልቅም መከራ
"ትልቅም ጥፋት"
ከፀሐይ በታች በደከመበት ድካም ሁሉና በልቡ ሃሳብ የሰው ጥቅም ምንድር ነው?
ፀሐፊው የግነት ጥያቄን ጠንክሮ የሚሠራ ሠው ምንም እንደማያገኝ አፅንኦት ለመስጠት ነው ። በመክብብ ፡1፡3፡ ላይ ያለውን ትርጉም ተመልከት ተርጓሚ "ከፀሐይ በታች ጠንክሮ የሚሠራና በልቡ ሥራውን ለመፈፀም እንደሚሞክር ሠው ምንም አያገኝም" (የግነት ጥያቄን ተመልከት)
በደከመበት ድካም ሁሉና በልቡ ሀሳብ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም ሲኖራቸው ሰወየው እንዴት በርትቶ እንደሚሰራ አፅንኦት ይሠጣሉ።
በልቡ ...... ጥረትም
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ "ተጨንቆ መሞከር"
ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ነገሮች ይገልፃል። የመክብብ ፡1፡3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "በምድር ላይ"
ሀዘን ...... ትካዜ ነው
ሁለቱ ዋይታ ተመሣሣይ ትርጉም ያላቸውና የሠውየው ሥራ ምን ያህል አድካሚ እንደሆነ አፅንኦት ለመስጠት ነው።
ልቡም በሌሊት አይተኛም
እዚህ ጋር የሰው አዕምሮ በልቡ ሲገለፅ ጥልቅ ሀሳቡን አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "አዕምሮው አያርፍም " ወይም "መጨነቁን ይቀጥላል" (ፈሊጣዊና ዘይቤአዊ ተመልከት)
Ecclesiastes 2:24
የእግዚአብሔር እጅ
እዚህ ጋር እግዚአብሔር እንዴት ለህዝቡ እንደሚያዘጋጅ አፅንኦት ለመስጠት በእጅ ይገለፃል። ተርጓሚ ከእግዚአብሔር
ያለ እርሱ ፈቃድ የበላ ደስ ብሎትም ተድላን የቀመሠ ማን ነው?
ፀሐፊው ይህን የግነት ጥያቄ ከእግዚአብሔር አቅርቦት በስተቀር ተድላ ሊኖር እንደማይችል አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ ከእግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር ማንም ሊበላ ወይም የትኛውንም አይነት ተድላ ማግኘት አይችልም።
Ecclesiastes 2:26
እግዚአብሔርን ደስ ለሚያሰኘው ሰው ይሰጥ ዘንድ
ይህ ኃጢያተኛው የሚያከማቸውን ሰጪው ማን እንደሆነ በግልፅ ሳይናገር መተርጎም ይቻላል። ተርጓሚ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ሰው ይሰጠው ዘንድ (ይኖረው ዘንድ)
ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነው
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ሀሳቡ ነገሮች እርባና ቢስና ከንቱ እንደሆኑ አፅንኦት ለመስጠት ነው።
ከንቱ
"ተን" ፀሐፊው የሚናገረው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ አድርጎ ነው። የመክብብ ፡1፡14፡ ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "እንደ ከንቱ እርባና ቢስ" ወይም "ትርጉም የለሽ" (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት ) ነፋስን እንደመከተል ፀሐፊው ሰዎች ነፋስን ለመቆጣጣር እንደሚሞክሩ እንዲሁ የሚሰሩት ነገር ሁሉ እርባና ቢስ መሆኑን ይነገራል ። የመክብብ ፡1፡14፡ ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "ነፋስን እንደመቆጣጣር ያክል እርባና ቢስ ናቸው።" (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

---

Chapter 3
Ecclesiastes 3:1
አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ከአንድ ጥግ እስከ ሌላኛው ያሉትን የተለያዩ የሕይወት ጉዳዮችን ለመግለፅ የተወሰነ የአፃፃፍ ለውጥ ይጠቀማል።
ለሁሉ ዘመን ...... ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ትርጉም ሲኖራቸው የተጣመሩትም አፅንኦት ለመስጠት ነው ። (ተመሳሳይነት ተመልከት)
ከሰማይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል። የመክብብ ፡1፡3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "በምድር ላይ" (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
የተተከለውንም ለመንቀል ጊዜ
ትርጉም ሊሆን የሚችለው 1. "የመከር ጊዜ" ወይም 2. "የመንቀል ጊዜ"
Ecclesiastes 3:4
አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ከአንድ ጥግ እስከ ሌላኛው ያሉትን የተለያዩ የሕይወት ጉዳዮችን ለመግለፅ የተወሰነ የአፃፃፍ ለውጥ መጠቀሙን ቀጥሏል።
ማቀፍ (መተቃቀፍ)
አንድን ሰው ለፍቅር ወይም ወዳጅነትን ማሳያ በክንዳችህ ውስጥ መያዝ
Ecclesiastes 3:6
አጠቃላይ መረጃ
አሁንም ፀሐፊ ከአንድ ጥግ እስከ ሌላኛው ጥግ ያሉትን የተለያዩ የሕይወት ጉዳዮች ለመግለፅ የተወሳነ የአፃፃፍ ለውጥ መጠቀሙን ቀጥሏል።
Ecclesiastes 3:8
አጠቃላይ መረጃ
ፀሐፊው ከአንድ ጥግ እስከ ሌላኛው ያሉትን የተለያዩ የሕይወት ጉዳዮች ለመግለፅና ለመደምደም የተወሰነ የአፃፃፍ ለውጥ መጠቀሙን ቀጥሏል ።
ለሠራተኛ የድካሙ ትርፍ ምንድር ነው?
ይህ ሐሳብ ቀስቃሽ ጥያቄ ሲሆን አንባቢው በቀጣዩ የውይይት ርዕስ ላይ ትኩረት እንዲሠጥ ነው። ፀሐፊው ይህን የግነት ጥያቄ የተጠቀመው የሰው ድካሙ ከንቱና ዘለቄ ትርፍ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት ነው። ጥያቄው በአረፍተ ነገር መልኩ ሲቀመጥ ተርጓሚ "ሠራተኛ ለደከመበት ትርፍ የለውም (የግነት ጥያቄ ተመልከት)
Ecclesiastes 3:11
እግዚአብሔር ...... ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሰራው
እግዚአብሔር ሁሉም ነገር በጊዜው እንዲከወን የተወሰነ ጊዜ ስጥቷል። ወይም እግዚአብሔር እያንዳንዱ ነገር እንደሆነ ትክክለኛ ጊዜ አስቀምጧል።
ዘላለምነትን በልቡ ሰጠው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እዚህ ጋር በልቡ የሚለው ቃል የሰው ልጅን ይወክላል፡፡ እዚህ ጋር "ልብ" የሰው ልጅን ሀሳብና ምኞት ይወክላል። ተርጓሚ "በሰው ልጆች ልብ ውስጥ ዘላለማዊነትን አስቀመጠ"

ከጥንት ጀምሮ እስከ ፍፃሜ ድረስ

ይህ ጅማሬንና ፍፃሜን እንዲሁም በመካከል ያሉትን ሁሉ ይወክላል።

Ecclesiastes 3:12

ሰው ደስ ከሚለውና ..... በቀር

"እንዴት ሐሴት ማድረግ እንዳለበት ማወቅ አለበት" ወይም "ሐሴት ማድረግ አለበት"

Ecclesiastes 3:14

ሊጨመርበት ወይም ከእርሱ ለጎድል አይቻልም

ይህ ገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ "ማንም ማንንም ሊጨምር ወይም ሊያጎድል አይችልም "

Ecclesiastes 3:16

በፍርድ ሥፍራ ኃጢአት በፅድቅም ሥፍራ ኃጢአት አየሁ

እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይነት ሲኖራቸው ተመሳሳይ የኃጢአት (ክፋት) ባህሪይ እንዳለ አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ፅድቅ ሥፍራ

"ፅድቅ መኖር ባለበት ቦታ"

ከፀሐይ በታች

ይህ በምድር ላይ የሚደረጉትን ለመግለፅ ነው። የመክብብ 1:3 ትርጉም ተመልከት። ተርጓሚ "በምድር ላይ" (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

እኔም በልቤ ....... አልሁ

እዚህ ጋር ፀሐፊው ለሥሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን "በልቡ" ይገልፃል። ተርጓሚ "ለራሴ አልኩ (ተናገርኩ)"

በፃድቅና በኃጢአተኛ

ይህ ስለ ፃድቅና ኃጢአተኛ ሰዎች ነው። ተርጓሚ "ፃድቅ የሆኑና ኃጢአተኛ የሆኑ" ወይም ፃድቃንና ኃጢአተኞች"

ለነገር ሁሉና ለሥራ ሁሉ

ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይነት ሲኖራቸው የሰው ልጅ ድርጊትን ሁሉ ይገልፃል።

Ecclesiastes 3:18

በልቤ ..... አልሁ

እዚህ ጋር ፀሐፊው ለሥሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በ"ልቡ" ይገልፃል። ተርጓሚ "ለራሴ ተናገርኩ"

እንደ እንስሳ መሆናቸውን

እዚህ ጋር ፀሐፊው ሰዎች እንደ እንስሳ ናቸው እያለ ነው። በቀጣዩ ቁጥር ፀሐፊው በእርግጥ ሰዎች እንዴት እንደ እንስሳ እንደሆኑ በግልፅ ያስረዳል። (ተመሳሳይ ተመልከት

Ecclesiastes 3:19

እድል ፈንታ አንድ ነው

"ለሁለቱም አንድ አይነት ነው" ወይም "አንድ አይነት ነው"

የሁሉም እስትንፋስ አንድ ነው

"ሁሉም ተመሳሳይ ይተነፍሳሉ"

ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም

የሰው ልጅ ከእንስሳ ምንም አይሻልም"

ሁሉም እንደ እስትንፋስ አይደለምን?

እዚህ ጋር ፀሐፊው ሁሉም ነገር እንደ እስትንፋስ ጊዜአዊ እንደሆነ ይናገራል። ፀሐፊው የግነት ጥያቄን ሁሉም ነገር ጊዜአዊ እንደሆነ አፅንኦት ለመስጠት ይጠቀማል። ጥያቄው በዐፍተ-ነገር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ሁሉም ነገር እስትንፋስ ነው" ወይም ሁሉም ነገር እንደ ተን ጊዜአዊ ነው" (ዘይቤአዊና ግነት ተመልከት)

ሁሉ ወደ አንድ ቦታ ይሄዳል

ይህ ማለት ሁሉም ሰውና ሁሉም እንስሳት ይሞታል ይበሰብሳልም አፈርም ይሆናል። ተርጓሚ "ሁሉም ነገር ይሞታል ወደ አንድ ቦታም ይሄዳል" አፈር

Ecclesiastes 3:21

ነፍስ ..... ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማነው?

ፀሐፊው የግነት ጥያቄን ሰዎችም እንስሳትም ከሞቱ በኋላ በእርግጥ ምን እንደሚሆን የሚያውቅ ማንም እንደሌለ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ጥያቄው በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ነፍስ ወደ ምድር..... ማንም የሚያውቅ የለም" (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

ደስ ከሚለው በቀር ሌላ

የመክብብ 3:12 ትርጉም ተመልከት

ከእርሱ በኋላስ የሚሆነውን ያይ ዘንድ የሚያወጣው ማን ነው?

ፀሐፊው ይህን የግነት ጥያቄ የሚሆነው ነገር ከሞት በኋላ የሚያይ ማንም የለም ለሚለው አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ከእኛ መካከል ከሞት በኋላ ምን እንደሚያጋጥመን ማንም የሚያውቅ የለም" (የግነት ጥያቄ ተመልከት)

---

Chapter 4

Ecclesiastes 4:1

ከፀሐይ በታች

ይህ በምድር ላይ ስለተደረጉት ነው። የመክብብ 1:3 ትርጉም ተመልከት ተርጓሚ "ከፀሐይ በታች"

እነሆም........እንባ

“ተመለከትኩ አየሁም”

የተገፉ ሰዎች እንባ

እዚህ ጋር እንባ ማልቀስን ይገልፃል። ተርጓሚ “የተገፉ ሰዎች ያለቅሱ ነበር”

በሚገፉአቸው እጅ ኃይል ነበረ

ይህ ማለት ገፊዎቻቸው ኃያል ነበሩ ማለት ነው። እዚህ ጋር “እጅ” የያዘውን ይወክላል። ተርጓሚ “ገፊዎቻቸው ኃያል ( ኃይለኛ) ነበሩ”

Ecclesiastes 4:2

እስከ ዛሬ በሕይወት ካሉት

በሕይወት የሚለው ቃል በሕይወት ያሉትን ይወክላል። እስከ ዛሬ የሚለው ሐረግ ደግሞ አሁንም በሕይወት ያሉትን ይወክላል። ተርጓሚ “እስከ ዛሬ በሕይወት ያሉትን ሰዎች”

ከሁለቱ ይልቅ ገና ያልተወለደው...........ይሻላል “ገና ያልተወለደው ከሁለቱ ይሻላል” ከእነዚህም ከሁለቱ

ይህ ሐረግ የሞቱትንና በሕይወት ያሉትን ይገልፃል። ተርጓሚ “ሁለቱም እነዚህ የሞቱትም እነዚህ በሕይወት ያሉት”

ከፀሃይ በታች

ይህ በምድር የተደረጉትን ይገልጻል (ይወክላል) የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “በምድር ላይ” (ፈሊጣዊ ተመልከት)

Ecclesiastes 4:4

በባልንጀራውም ዘንድ ቅንዓት .........አየሁ

ቅንአት የሚለው ቃል እንደ ቅፅል ተገልጾ ይሆናል። ተርጓሚ “ባልንጀራውን ቀናተኛ አደረገ” (ረቂቅ ስም ተመልከት)

በባልንጀራውም ዘንድ ቅንዓት

የጎረቤት ባልንጀራ፡ በጎረቤት ባልንጀራውን ንብረት ይሆናል የጎረቤት ባልንጀራ : በጎረቤቱ የእኛ ጥበብ ይሆናል

ከንቱ ንፋስንም እንደመከተል ነው

እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ሲሆኑ እርባና ቢስ ስለሆኑ ነገሮች አጽንኦት የሚሰጥ ሀሳብ ነው። (ተመሳሳይ ተመልት)

ከንቱ

“ተን” ፀሃፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ተን (ከንቱ) እንደሆኑ ይናገራል የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ። ተርጓሚ እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ወይም ትርጉም የለሽ (ዘይቤአው ተመልከት)

ነፋስን እንደመከተል

ፀሃፊው ሰዎች የሚያደርጉት ሁሉ ነፋስን ለመቆጣጠር እንደ መሞከር እርናባ ቢስ መሆኑን ይናገራል የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ ነው” (ዘይቤአዊ ተመልከት)

Ecclesiastes 4:5

ሰነፍ እጆቹን ኮርትሞ ይቀመጣል

“እጅን ማኮራተም” የስንፍና ምልክትና በሌላ አባባል ይህ ሰው ስራ ለመስራት ፈቃደኛ አይደለም ማለት ነው። ተርጓሚ “ሰነፍ ለመስራት ፈቃደኛ አይደለም” (ተምሳሌታዊ ድርጊትና ተመሳሳይ ተመልከት)

የገዛ ሥጋውንም ይበላል

ይህ ሰውን የራሱን ስጋ እንደሚበላ ያክል እራሱን ያጠፋል ማለት ነው። ተርጓሚ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“በውጤቱም ለራሱ ጥፋት ምክኒያት ይሆናል።” ወይም “በውጤቱም እራሱን ያጠፋል” (ዘይቤአዊ ተመልከት)
እጅ ሙሉ
“ትንሽ መጠን”
ሁለት እጅ ሙሉ
“በጣም ብዙ” የተገኘ ትርፍን ያስረዳል። ተርጓሚ “ሁለት እጅ ትርፍ” ወይም “በጣም ብዙ ትርፍ”
ነፋስን በመከተል
ፀሓፊው የሚናገረው ሰዎች የሚያደርጉት ሁሉ ነፋስን ለመቆጣጠር እንደ መሞከር እርባና ቢስ ነው። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ። ተርጓሚ “እሱም ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ ነው።” (ዘይቤአዊ ተመልከት)
Ecclesiastes 4:7
ከንቱን ነገር(ከንቱነት)
“ያለ ትርፍ እርባና ቢስ መሆን”
ደግሞ ከንቱ
“አሁንም ደግሞ የሚጠፋ ተን” ፀሓፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ“ አሁንም እንደ ከንቱ እርባና ቢስ የሆኑ ነገሮች” ወይም “አሁንም ትርጉም የለሽ ነገሮች።” (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ከፀሃይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉ ነገሮችን ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ “በምድር ላይ” (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ልጅም ሆነ ወንድም የለውም
ይህ ሰው ቤተሰብ የለውም ተርጓሚ “እሱ ቤተሰብ የለውም”
ዓይኖቹ.........አይጠግቡም
ይህ አንድ ሙሉ ሰው ለምኞቱ አፅንኦት ለመስጠት በዓይኖቹ ይወከላል። ተርጓሚ “እሱ አልረካም/ አልጠገበም”
ለማን እደክማለሁ ሰውነቴንስ መልካሙን ነገር ለምን እነፍጋታለሁ?
እኔ በጣም ተግቼ ሰውነቴን ካላስደሰትኩ ትርፍ የሚያገኘው ማን ነው?
ከንቱ
ፀሓፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “እንደ ከንቱ እርባና ቢስ” ወይም “ትርጉም የለሽ” (ዘይቤአዊ ተመልከት)
Ecclesiastes 4:9
አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ......ወዮለት
ወዮለት የሚለው ቃል መከራ እንደሚከተለው ለማሳየት ነው። ተርጓሚ “አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ሀዘንተኛ ነው( ይሆናል)”
ሁለቱ በአንድነት ቢተኙ ይሞቃቸዋል
ፀሓፊው የሚናገረው ሁለት ሰዎች በቀዝቃዛ ሌሊት አንዱ ሌላኛውን ያሞቃል ተርጓሚ “ሁለት ሰዎች በሌሊት አብረው ቢተኙ ለምቁ ይችላሉ”
አንድ ብቻውን ግን እንዴት ይሞቃል?
ይህ ስለተኛ ሠው ይገልፃል። ፀሃፊው ይህን የግነት ጥያቄ የተጠቀመው አንድ ሰው ብቻውን ቢተኛ እንደማይሞቀውና ሁለት ሲሆኑ ግን አንዱ ሌላኛውን ሊያሞቀው እንደሚችል አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በ ዓረፍተ ነገር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ሰው ብቻውን ሲሆን አይሞቀውም” ወይም “ብቻውን የሚተኛ ሰው አይሞቀውም” ( የግነት ጥያቄ ተመልከት)
Ecclesiastes 4:12
አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “አንድ ሰው ብቻውን የሆነውን ሰው ሊያሸንፍ ይችላል።”
ሁለቱ( ሁለቱ ግን)
“ግን ሁለት ሰዎች”
ይቆማሉ
“እራሳቸው ከጥቃት ይከላከላሉ”
በሦስት የተገመደ ገመድ
ይህ ልክ በሦስት ድርብ እንደተገመደ ገመድ ሦስት ሰዎች በአንድነት ሲሆኑ ጠንካራ እንደሆኑ ይናገራል። ተርጓሚ “ልክ በሦስት ድርብ እንደተገመደ ገመድ ሶስት ሠዎች ጠንካራ ናቸው ።” (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
በሦስት የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “በሦስት ድርብ የተገመደ ገመድ ሠዎች በቀላሉ አይበጥሱትም”
Ecclesiastes 4:13
ጠቢብ ብላቴና
“ጢብ ወጣት”
ከእንግዲህ ወዲህ ከማያውቅ
እዚህ ጋር ማወቅ ፈቃኝነትን ይወክላል። ተርጓሚ “ከእንግዲህ ወዲያ ፈቃደኛ ያልሆነ”
ተግሳፅን
“በተግሳጽ ስር ከሆነ በኋላ”
በመንግስቱ አገር ዳግም ችግረኛ ሆኖ ቢወለድ
ይህ ማለት ችግረኛ ወላጆች ነበሩት ማለት ነው። ተርጓሚ አንድ ቀን ከሚመራው ችግረኛ ወላጆቹ ከሚኖሩበት ምድር ተወለደ።
Ecclesiastes 4:15
X
ከጠቢቡን ብላቴና ይልቅ ጠቢብ ላይሆን ከሚችል የንጉስ ልጅ መረጡ
የሚሄዱትን ሕያዋን
ሕያዋን የሚለው ቃልና የሚሄዱትን የሚለው ቃል በመሰረቱ ተመሳሳይ ነገር ሲሆኑ ተጣምረው በሕይወት ያሉትን ሰዎች አፅንኦት ለመስጠት ነው።
ከፀሃይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ። ተርጓሚ “በምርድ ላይ” (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ሕዝብ ሁሉ አይቆጠሩም
ይህ የተጋነነ ንግግር ብዙ ቁጥር ያለውን ህዝብ እንደሆነ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ “እጅግ በጣም ብዙ ህዝብ አሉ”
ከንቱ ንፋስንም እንደመከተል
እነዚህ ሐረጎች ዘይቤአዊ ሲሆኑ እርባና ቢስና ከንቱ ስለሆኑ ነገሮች አፅንኦት የሚሰጥ ሀሳብ ነው ። (ዘይቤአዊ ተመልከት)
ከንቱ
“ተን” ፀሃፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉም ተመልከት። ተርጓሚ እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ወይም ትርጉም የለሽ ( ዘይቢአዊ ንግግር ተመልከት)
ነፋስን እንደመከተል
ፀሃፊው ሰዎች የሚያደርጉት ሁሉ ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ መሆኑን ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉም ተመልከት ተርጓሚ “ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ ነው።” (ዘይቤአዊ ተመልከት)

Chapter 5
Ecclesiastes 5:1
እግርህን ጠብቅ
እዚህ ጋር “እግርህን” የሚለው የአንድ ሠው ባህሪን ሲገልጽ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “እንዴት እራስህን እንደምትመራ ተጠንቀቅ”
Ecclesiastes 5:2
አትፍጠን.....ልብህ አይቸኩል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ሲሆኑ እግዚአብሄርን ስለሆነ ጉዳይ ከማናገርህ በፊት ማሰብ እንዳለብህ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ( ከመናገርህ በፊት ማሰብ እንዳለብህ አፅንኦት ለመስጠት)
አፍህ......ይናገር ዘንድ
እዚህ ጋር በአፍህ የሚለው ቃል ስለሚናገር ሰው አፅንኦት እና ገለፃ ለመስጠት ነው ። ተርጓሚ “ለመናገር”
ልብህ አይቸኩል
እዚህ ጋር ግለሰብ በስሜቱና ምኞቱ አፅንኦት ለመስጠት “በልቡ” ተወክሏል። ተርጓሚ “አታድርግ” ወይም “ተው”
ቃልህ ጥቂት ትሁን
“ብዙ አትናገር( አትበል)”
Ecclesiastes 5:4


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሰነፎች ደስ አይሰኙምና ለእግዚአብሔር.........ትፈፅመው ዘንድ አትዘግይ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ጋር ያደረግነውን ቃል አለመፈፀም ሞኝነት መሆኑን ነው ተርጓሚ እግዚአብሔር በሰነፎች ደስ ስለማይሰኝ የገባኸውን ቃል ከማድረግ አትስነፍ
Ecclesiastes 5:6
ሥጋህን በኃጢአት እንዲያስተው ለአፍህ እርነት አትስጥ
እዚህ ጋር "አፍህ" የሚለው ቃል ግለሰብን ሲወክል ሰውየው ደግሞ በሥጋው ተወክሏል። ተርጓሚ "የተናገርከው ኃጢአት እንዲሆን አታድርግ"
እግዚአብሔር በቃል ይቆጣ ዘንድ የእጅህንም ሥራ ያጠፋ ዘንድ ስለምን ትሻለህ?
ፀሐፊው ይህን የግነት ጥያቄ የማትፈፅመውን ቃል መስጠት ሞኝነት መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ በሐሰት ቃል እግዚአብሔርን ማስቆጣትና የእጅህን ሥራ እንዲያጠፋ ማድረግ ሞኝነት ይሆናል። (የግነት ጥያቄ ተመልከት)
የእጅህን ሥራ ያጠፋ ዘንድ
እዚህ ጋር ግለሠቡ በ"እጅ" ተወክሏል ተርጓሚ "የሠራኸውን ሁሉ ያጠፋል" ብዙ ህልም ባለበት ዘንድ እንዲሁም ደግሞ ብዙ ቃል ባለበት ስፍራ ብዙ ከንቱ ነገር አለ። ፀሐፊው ነገሮት ከንቱ እንደሆኑ እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው መሆኑን ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉም ተመልከት። ተርጓሚ "ብዙ ህልምና ብዙ ቃል እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ናቸው።"
Ecclesiastes 5:8
ድሆች ሲገፉ .......ሲነጠቁ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ሰዎች ድሆችን ሲገፉና ሲነጥቁ"
ድሆች
ይህ ችግረኛ ሠዎችን ይወክላል ተርጓሚ "ድሆች የሆኑ" ወይም "ችግረኛ"
ፍርድና ፅድቅ
ሁለቱ ቃላት በመሠረቱ ተመሣሣይ ሲሆኑ ሠዎች ስለባቸው ሁኔታ ይናገራል። ተርጓሚ "ፍትሐዊ ፍርድ"
በዚህ ነገር አትደነቅ
ሰዎች ስላሉ አትደነቅ (አትገረም)"
ሌሎች ክፉ ይላሉና
በሰዎች ላይ ሥልጣን ያላቸው ሌሎች ሰዎች አሉ። ተርጓሚ "ምድሩ የሚያመርተው መብል ... ከምድሩ ምርት (እህል)" (ረቂቅ ሥራ ተመልከት)
Ecclesiastes 5:10
ከንቱ
ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ" እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ወይም ትርጉም የለሽ" (ዘይቤአዊ ተመልከት)
ሀብት ሲበዛ
ሀብት የሚለው ቃል እንደ ቅፅል ሊገለፅ ይችላል ተርጓሚ "ሰው በጣም ሀብታም በሆነ መጠን"
የሚበሉት ይበዛሉ
አማራጭ ትርጉሞች 1) "እንዲሁ ሰው ብዙ ገንዘብ ያጠፋል (ያወጣል) 2) "እንዲሁ ሀብቱን የሚበሉት ሰዎች ይበዛሉ።"
የሚበሉት
ይህ የሚበሉት ያክል ሰዎች ሀብት ሊያጠፉ (ሊያወድሙ) ተርጓሚ "የሚጠቀሙት" (ዘይቤአዊ ተመልከት)
ሀብቱን በዓይኑ ብቻ ከማየት በቀር ለባለቤቱ ምን ይጠቅመዋል?
ፀሐፊው ይህን የግነት ጥያቄ ባለሀብቱ ከሀብታቸው ምንም እንደ ማያተርፉ አፅንኦት ለመስጠት ይጠቀማል። ጥያቄው በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ባለሀብቱ አንድ የሚያገኘው ጥቅም ሀብቱን በዓይኑ መመልከት ብቻ ነው።"
Ecclesiastes 5:12
የሠራተኛ እንቅልፉ ጣፋጭ ነው
ይህ የግለሰብ እንቅልፉ የሚበላው ጣፋጭ እንደሆነ ያክል እንቅልፉም የሞላና ሰላማዊ መሆኑን የናገራል። ተርጓሚ "የሠራተኛ እንቅልፍ ሰላማዊ ነው።" (ዘይቤአዊ ተመልከት)
እጅግ ወይም ጥቂት ቢበላ
"እጅግ ብዙ ምግብ ወይም ጥቂት ምግብ ቢበላም"
የባለጠጋ ጥጋብ ግን እንቅልፉን ይከለክለዋል።
የባለጠጋ ጥጋብ ግን እንቅልፉን ይከለክለዋል። ይህ ባለጠግነት እንቅልፍ እንደሚከለክለው ሰው ሊከለክለውና መተኛት አለመቻሉንና ስለገንዘቡም መጨነቁን ይናገራል። ተርጓሚ "ባለጠጋ ግን ሥለ ገንዘቡ ስለሚጨነቅ እንቅልፍ አይተኛም"
Ecclesiastes 5:13
ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ በምድር ላይ
በባለቤቱ ዘንድ የተቆጠበች ባለጠግነት
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ባለቤቱ ባለጠግነት ቆጠበ (አከማቸ)
በክፉ ነገር
አማራጭ ትርጉሞች 1) በመጥፎ ዕድል 2) በመጥፎ ውል
ልጅንም ቢወልድ በእጁ ምንም የለውም
እዚህ ጋር በእጁ የሚለው ቃል ባለቤትነት ይወክላል (ያሳያል) ። ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ለልጅ ምንም ይዞታ አልተወም (አላስቀመጠም) "
Ecclesiastes 5:15
ከእናቱ ሆድ ራቁቱን እንደወጣ እንዲሁ እንደ መጣሁ ይመስላል
ይህ ሰው ሲወለድ ራቁቱን እንደሆነ ያሳያል። "ራቁቱን የሚለው ቃል ያለልብስ መሆንን ብቻ ሳይሆን ሰዎች ሲወለዱ ምን ነገር (ይዞታ) እንደሌላቸው አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "ሰው ሲወለድ ራቁቱንና ምንም ነገር እንደሌለው ይህን ሕይወት እንዲሁ ይተዋል (ይሰናበታል)። "(ዘይቤአዊ ተመልከት)
ከእናቱ ሆድ ......እንደ ወጣ
"እንደ ተወለደ
ይመለሳል
"ይህ መሞትን ይገልፃል" ተርጓሚ "ይሞታል"
ከጥረቱም በእጁ ሊወስድ የሚችለውን ምንም አያገኝም
እዚህ ጋር የሰው ሀብት (ይዞታው) በጥረት ተወክሏል። ተርጓሚ "ከሀብት አንድም ነገር ከእርሱ ጋር አይሄድም"
እንደ መጣ እንዲሁ ይሄዳል
ይህ ሰው እንደሚወለድና እንደሚሞት የሚገልፅ ሲሆን ከቀድሞው ቁጥር ጋር ተመሣሣይ ሀሳብን ይገልፃል። ይህ ወንድንም ሴትንም ይወክላል። ተርጓሚ ሰዎች ወደ ዚህ ምድር ምንም ይዘው እንዳልመጡ ሁሉ እንዲሁ ሲሞቱና ይህን አለም ሲሰናበቱ ምንም ነገር ይዘው አይሄዱም።"
ድካሙም ለነፍስ ከሆነ ጥቅሙ ምንድን ነው
ፀሐፊው ለነፍስ ከመድከም ምንም ትርፍ እንደማይገኝ አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄን ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ለነፍስ ከመስራት ማንም ትርፍ የሚያገኝ የለም" (የግነት ጥያቄን ተመልከት)
ድካሙ ለነፋስ ከሆነ
ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ 1) ይህ ነፋስን ለመቆጣጠር እንደሚሞክር ሰው ዘላቂ ያልሆነ ትርፍ በቀላል ይገልፃል ተርጓሚ "ነፋስን መከተል መሞከር" ወይም "ነፋስን እንደመከተል እርባና ቢስ ድካም (ሥራ) "2) ይህ የሚያመለክተው ሰው ለትርፍ የሚተነፍሰውን አየር ብቻ ይቀበላል።"
ዘመኑን ሁሉ በጨለማ ...... ነው።
ይህ በጨለማ ስላለና በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ስለሚያዝን ሰው ይናገራል። እዚህ ጋር "ጨለማ" ኃዘንና ብስጭትን ይወክላል። "ተርጓሚ እርሱ ሕይወቱን በኃዘንና በብስጭት ያሳልፋል። " (ዘይቤአዊ ተመልከት)
ዘመኑን
እዚህ ጋር "ዘመን" የሰውን ሕይወት ይወክላል። ተርጓሚ "ሕይወቱን"
በብስጭት በደዌና በቁጣ ነው
"ብስጭት" ና "ደዌ" በቅፅል ሊገለፁ ይችላሉ። ተርጓሚ እጅግ በጣም መንከራተት ትልቅ ህመምና ብስጭት"
Ecclesiastes 5:18
እነሆ
ፀሐፊው በቀጣይ ስለሚናገረው የአንባቢውን ቀልብ ለመሳብ ይህን ቃል ይጠቀማል። ተርጓሚ "ትኩረት ስጥ" ወይም "አዳምጥ"
እኔ ያየሁት መልካምና የተዋበ
እዚህ ጋር "መልካምና" "የተዋበ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ አንድ ናቸው። ሁለተኛው የመጀመርያውን ትርጉም ያሰፋዋል። ተርጓሚ "እኔ ያየሁት ከሁሉ የተሻለ ነገር ነው።"
ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ "በምድር ላይ"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሰው እግዚአብሔር በሰጠው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ "እግዚአብሔር መኖር እስከፈቀደልን ድረስ"
ሰው ...... ይህ እድል ፈንታው ነውና
አማራጭ ትርጉሞች 1) ሰው .... ይህ ብድራቱ ነውና። 2) ሰው ሊከውናቸው (ሊያደርጋቸው) የተፈቀደለት ነውና።
Ecclesiastes 5:19
ባለጠግነትና ሀብትን
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረቱ ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው ገንዘብና ሠው ገንዘብ የሚገዛቸውን ነገሮች ሁሉ ይወክላሉ።
እድል ፈንታውን ይወስድ ዘንድ
"የተሰጠውን ሊቀበል።"
እርሱ የሕይወቱን ዘመን እጅግ አያስብም
እዚህ ጋር "እርሱ" የሚለው ቃል እግዚአብሔር ስጦታ የሰጠውን ሰው ይወክላል። "አያስብም" የሚለው ቃል ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ "እርሱ አያስታውስም" ወይም "እርሱ አያስብም"
የሕይወቱን ዘመን
ይህ በሕይወቱ ዘመን የተከሰቱትን ነገሮች ይወክላል። ይህ በግልፅ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "በሕይወቱ ዘመን የተከሰቱትን ነገሮች ሁሉ" (ፈሊጣዊ ተመልከት)
ማሰልጠኑ
"ማጨናነቁ (ሥራ ማብዛቱ)

---

Chapter 6
Ecclesiastes 6:1
በሰው ልጅ ላይ እጅግ የከበደ ነው ።
እዚህ ጋር ክፍት እንደሆነ ነገር ለመሸከም የከበደ ጭነት ያሳያል። ተርጓሚ "ለሰዎች መከራ ይሆናል።" (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
አልጎደለውም
ተርጓሚ "ሁሉ ነገር አለው"
እግዚአብሔር አላሠለጠነውም
"ችሎታ አልሠጠውም"
ከንቱ
ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም ስለሌላቸው ነገሮች ከንቱ (ተን) የሆኑ ያክል ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉም ተመልከት ። ተርጓሚ"ልክ እንደ ተን እርባና ቢስ" ወይም ትርጉም የለሽ" (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
Ecclesiastes 6:3
መቶ ልጆች ቢወልድ
"መቶ ልጅ ወለደ" ይህ መላምታዊ ሁኔታ ነው። ይህ የገነነም ሲሆን ከመቶ ልጆች በታች ላላቸውም ይሠራል። ተርጓሚ "ብዙ ልጆች ቢወልድ"
እጅግ ዘመንም በሕይወት ቢኖር ዕድሜውም እጅግ ዓመት ቢሆን
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሰረቱ በትርጉም አንድ ሲሆን አንድ ላይ የሆኑትም አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "ብዙ ዘመን/አመት/ ኖረ"
ነፍሱም መልካምን ባትጠግብ
ይህ ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት ሲሆን በ"ነፍሱ" ይገልፃል። ተርጓሚ "በመልካም አይረካም (አይደሠትም)
መቃብርንም ባያገኝ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉሞች 1) በጭራሽ ማንም አልቀበረውም" 2) "ክብርን አላገኘውም ማንም በሥርዓት አልቀበረውም።"
ከእርሱ ይልቅ ጭንጋፍ
"ምንም ላይጠቅም የተወለደ ሕፃን (ልጅ)"
በጨለማ ይሸፈናል
x
Ecclesiastes 6:5
ሺህ አመት ሁለት ጊዜ በሕይወት ቢኖር
ይህ መላምታዊ ሁኔታ ነው። "ይህ ሰው ደስ ከተሰኘ በስተቀር ምንም ያህል ዓመት በሕይወት ቢኖር ምንም እንደማይጠቅም ለማጋነን ነው።
ሺህ ዓመት ሁለት ጊዜ
"2000" ዓመት"
ሁሉ ወደ አንድ ሥፍራ የሚሄድ ......
ይህ ማለት ማንም ሰው እንደሚሞተው ይሞታል። "ይሞታልም ሁሉም ሰው ወደ ሚሄደው ይሄዳል። "ወይም" ሁሉም ሰው ወደ መቃብር እንደሚሄድ እርሱም ይሄዳል።
Ecclesiastes 6:7
ለአፍ ነው
እዚህ ጋር በሰው አፍ ውስጥ ምግብን መጨመር መመገብን ይወክላል። ተርጓሚ "ምግብን በአፍ ለማድረግ ነው። ወይም እርሱን ለመመገብ ነው።"
ነፍሱ ግን አትጠግብም
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ነፍሱን አያጠግብም "
ከሰነፍ ይልቅ ለጥበበኛ ጥቅም ምድር ነው ?
ፀሐፊው ጥበበኛ ከሰነፍ ይልቅ ዘላቂ ትርፍ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህን የግነት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ ጠቢብ ከሰነፍ የተሻለ ጥቅም እንደሌለው ይመስላል።" (የግነት ጥያቄ ተመልከት)
በሕያዋን ፊትስ መሄድ ለሚያውቅ ለድሀ ጥቅሙ ምንድር ነው ?
ፀሐፊው ድሃ ከማንም የተሻለ ዘላቂ ትርፍ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄን ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "በሕያዋን ፊት መሄድ ቢያውቅም ድሃ ጥቅም የለውም" (የግነት ጥያቄ ተመልከት)
መሄድ ለሚያውቅ
"እራሱን እንዴት እንደሚገዛ"
Ecclesiastes 6:9
በዓይን ማየት
ሰው እነዚህን ነገሮች ስላሉት በዓይኑ ማየት ይችላል። ተርጓሚ "ሰው ያለውን ነገር"
በነፍስ ከሚቅበዘበዝ
ይህ ሰው ስለሚፈልገው ነገር ግን የሚያገኘውን ይገልፃል። ተርጓሚ "የማያገኘውን መፈለግ"
ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል
እነዚህ ሁለቱ ሀረጎች ዘይቤአዊ ሲሆኑ እርባና ቢስና ከንቱ ስለሆኑ ነገሮች አፅንኦት የሚሠጥ ሀሳብ ነው።(ተመሣሣይ ተመልከት) ከንቱ "ተን" ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ :1:14፡ ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ወይም ትርጉም የለሽ" (ዘይቤአዊ ተመልከት)
ነፋስን እንደመከተል
ፀሐፊው የሚናገረው ሰዎች የሚያደርጉት ሁሉ ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ ነው። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "ነፋስን ለመቆጣጠር እንደመሞከር እርባና ቢስ ነው ።"(ዘይቤአዊ ተመልክት)
የሆነው ሰው አስቀድሞ ተጠራ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ያለውን ነገር ሁሉ ሰዎች ስም ስጥተውታል (ሰይመውታል)።"
ሰውም እንደሆና ታወቀ
ይህ በገቢር መልክ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ሰውም እንዲሆን ሰዎች አስቀድመው ያውቃሉ።"
ከሚበረታው ጋር ይፋረድ ዘንድ
"እግዚአብሔር የበረታ (የበላይ) ፈራጅ"
የሚያበዛ ብዙ ነገር
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ሰዎች ብዙ ነገር በተናገሩ ልክ"
ከንቱን የሚያበዛ ነገር
ሰው ብዙ ባወራ ልክ የማይረባ ነገር ይናገራል። ተርጓሚ "ባወራ ልክ ቃላቱ እርባና ቢስ ይሆናሉ።" ከንቱ "ያለትርፍ ጥቅም አልባ መሆን"
ለሰው ጥቅም ምንድ ነው?
ፀሐፊው ለሠው ብዙ ማውራት ትርፍ እንደሌለው አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ያ ለሠው ትርፍ የለውም"
እንደ ጥላ በሚያሳልፈው ...... ለሰው የሚሻለውን የሚያውቅ ማነው?
ፀሐፊው በእርግጥ ለሰው የሚሻለውን የሚያውቅ እንደሌለ አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል።

ተርጓሚ እንደ ጥላ በሚያልፈው ለሠው የሚሻለውን የሚያወቅ ማንም የለም። (የግነት ጥያቄ ተመልከት)
ሰው በከንቱ ወራት ቁጥርና እንደ ጥላ በሚያልፈው ዘመኑ በሕይወቱ ሳለ
ይህ ጥላ በፍጥነት እንደሚያልፍ ሁሉ ሕይወት በፍጥነት እንደምታልፍ ይናገራል። "ወራት ቁጥር" የሚለው ሀረግ የሰው ሕይወት አጭር መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ በከንቱነቱ ዘመን እንደ ጥላ አጭር ዕድሜ ውስጥ ያልፋል።
ከእርሱ በኋላ የሚሆነውን ማን ይነግረዋል?
ፀሐፊው ሰው ከሞተ በኋላ ምን እንደሚሆን እንደማይታወቅ አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ሰው ካለፈ (ከሞተ) በኋላ ማንም የሚነግረው የለም።"(የግነት ጥያቄ ተመልከት)
ከፀሐይ በታች ...... የሚሆነውን
ይህ በምድር ላይ የሆኑትን ነገሮች ይገልፃል። በመክብብ፡1፡3፡ላይ "ከፀሐይ በታች" የሚለው እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት። ተርጓሚ "በምድር ላይ የሚሆነውን"
ከእርሱ በኋላ
ይህ ለሞት የትህትና አገላለፅ ነው። ተርጓሚ "በምድር ላይ የሚሆነውን"

---

Chapter 7
Ecclesiastes 7:1
መልካም ስም
እዚህ ጋር የሰው ስም የሰውን ማንነት (ዝና) ለመግለፅ ይጠቅማል። ተርጓሚ "መልካም ማንነት (ዝና) ወይም " መልካም ስም
በልቡ ያኖረዋል
ይህ ፈሊጣዊ ነው ። ተርጓሚ"ስለዚህ ጉዳይ በጥንቃቄ መታሰብ አለበት
Ecclesiastes 7:3
ከፊት ኅዘን
ይህ ማዘንን ይገልፃል። ተርጓሚ "ሰውን ሀዘንተኛ የሚያዳርግ ልምምድ
ልብ ደስ ይሰኛል ልብ .... በደስታ
እዚህ ጋር "ልብ" የሰውን ሐሳብ ይገልፃል። "ደስታ" 1) የስሜትን ደስታና ሰላማዊ መሆንን ወይም 2) እውነትን የመረዳት ችሎታ ያስረዳል። ተርጓሚ "ትክክለኛ አስተሳሰብ"
የጠቢብን ልብ በለቅሶ ቤት ነው።
እዚህጋር ጠቢብን "በልባቸው" ተወክለዋል። ይህ የጠቢብ ሰው ለቅሶ በልቅሶ ቤት መሆንን ይናገራል። ተርጓሚ "ጠቢባን ስለሞት በጥልቀት ያስባሉ።"
የሰነፎች ልብ ግን በደስታ ቤትነው።
እዚህ ጋር ሰነፎች "በልባቸው" ተወክለዋል። ይህ ሰነፎችን በደስታ ቤት እንደመሆን የሚያስደስታቸው ነገር ብቻ ማሰባቸውን ይናገራል። ተርጓሚ "ሰነፎች ግን ስለሚያስደስታቸው ነገር ብቻ ያስባሉ።"
በለቅሶ ቤት ..... በደስታ ቤት
እነዚህ ሐረጎች በዚህ ቦታ የሆኑትን ነገር ይገለፃል።
Ecclesiastes 7:5
የጠቢባንን ተግሣፅ
ተግሣፅ የሚለው ቃል እንደ ግስ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ "ጠቢባን ሲገሥፁህ"
የሰነፎችን ዜማ ከሚሰማ
"የሰነፎችን መዝሙር ከመስማት"
ከድስት በታች እንደሚቃጠል እሾህ ድምፅ የሰነፍ ሳቅ እንዲሁ ነው።
ይህ ከድስት በታች እንደሚቃጠል እሾህ ድምፅ የሰነፍ ወሬና ሳቅ ምንም ትምህርት እንደሌለው ይናገራል። ተርጓሚ የሰነፍን ሳቅ ማዳመጥ ከድስት በታች የሚቃጠልን የእሾህ ድምጽ ከማዳመጥ ምንም የተሻለ ነገር ሰውን አያስተምርም።
ከንቱ
ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። የመክብብ ፡1፡14፡ ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "እንደ ከንቱ እርባና ቢስ" ወይም "ትርጉም የለሽ" (ዘይቤአዊ ተመልከት)
Ecclesiastes 7:7
በግፍ
ይህ አንድን ሰው ገንዘብ ወይም ሌላ ሰው እንዳያጠቃው በግድ እንዲሠጥ ማድረግ። ትክክል አይደለም
ጠቢቡን ያሳብዳዋል
አማራጭ ትርጉሞች 1) "ጠቢብን ወደ ሞኝ ይለውጣል። ወይም2)የጠቢብን ምክር የሞኝ ምክር ያደርጋል።
ልብን ያሳብደዋል
እዚህ ጋር ልብ አእምሮን ይወክላል (ይገልፃል) ተርጓሚ "ሰው በትክክል እንዳያሳብና እንዳይፈርድ ችሎታውን ያጠፋል።"
Ecclesiastes 7:8
ታጋሽም ከትዕቢተኛ ይሻለል
ተርጓሚ"ታጋሽ ሰዎች ከትዕቢተኛ ሰዎች ይሻላሉ" ወይም ያታጋሽ አመለካከት ከትዕቢተኛ አመለካከት ይሻላል።"
በነፍስህ ለቁጣ ችኩል አትሁን
እዚህ ጋር"ነፍስ" የሚለው ቃል የሰውን አመለካከት ይገልጻል። ተርጓሚ "ቶሎ አትቆጣ(አትናደድ)" "መጥፎ ንዴት (ብስጭት) አይኑርህ"
ቁጣ በሰነፍ ብብት ያርፋልና
ይህ ቁጣ በውስጡ እንደሚኖር በቁጣ ስለተሞላ ሰው ይናገራል። ይህ በሰው ልብ ውስጥ ስላለው ቁጣ ይናገራል። ምክኒያቱም ልብ የሰው ልጅ ስሜት ምንጭ ተደርጎ ስለሚታሰብ ነው። ተርጓሚ ሞኝ የሞላው ቁጣ ነው።
Ecclesiastes 7:10
ከዚህ ዘመን ይልቅ ያለፈው ዘመን በምን ተሻለ
ሰውየው ይህን ዘመን ለማማረር ይህን ግነት ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። ተርጓሚ "ከአሁን ዘመን ይልቅ ነገሮች ባለፈው ዘመን ይሻላሉ።"
የዚህን ነገር ጥበብ አትጠይቅም
እዚህ ጋር ፀሀፊው የሰውየውን ጥያቄ ለመመገሰጽ ምጸት ይጠቀማል። ( ምፀት ተመልከት)
Ecclesiastes 7:11
ፀሃይንም ለሚያዩ
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ "በሕይወት ያሉት" (ፈሊጣዊ ተመልከት)
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ "በሕይወት ያሉት" (ፈሊጣዊ ተመልከት)
አማራጭ ትርጉሞች 1) ፀሓፊው "እውቀት" ና "ጥበብ" የሚሉት ቃላትን የተጠቀመው አንድ አይነት ነገር ለማለት ነው። ወይም 2) ጥበብን የማወቅ ትርፍ ሕይወትን ስለምትሰጥ ነው።
ገንዘብ ላደረጉት ሕይወትን እንዲሰጥ ነው።
ይህ የሚናገረው ጥበብ ለዛ ሰው ሕይወት እንደምትሰጥ የሰው ሕይወትን እንደምትጠብቅ ነው። ሰው ጠቢብ ሲሆን በተሻለ ብልጽግናና ረጅም እድሜ እንዲኖር መልካም ውሳኔን ይወስናል። ተርጓሚ "ሰውን ሕይወት ይጠብቃል" ወይም "መልካም ውሳኔን እንዲወስንና ረጅም እድሜን እንዲኖር ያደርገዋል።"
Ecclesiastes 7:13
እርሱ ጠማማ ያደረገውን ማን ሊያቃና ይችላል?
ፀሓፊው እግዚአብሄር ስራውን ማንም ሊቀይር እንደማይችል አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄን ይጠቀማል። ይህ በ ዓረፍተ ነገር መልክ ሊፃፍ ይችላል።ተርጓሚ "እርሱ ጠማማ ያደረገውን ማንም ሊያቀና አይችልም።"
Ecclesiastes 7:14
በመልካም ቀን.......በክፉም ቀን
"ቀን" የሚለው ቃል ለሚከሰቱ ነገሮች ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ "መልካም ነገሮች ሲከሰቱ.....ክፉ ነገሮችም ሲከሰቱ" (ፈሊጣዊ ተመልከት)
በመልካም.....ደስ ይበልህ
"በእነዚያ መልካም ነገሮች ደስ ይበልህ"
ይህንም ያንም እንደዚያ ሰርቷል
"ይህንም ያንም" የሚለው ሐረግ ፈሊጣዊ ሲሆን "ይህኛውም" ማለት ነው ተርጓሚ " አንድ ላይ እንዲሆኑ"ወይም "መልካምም ክፉም ይኖር ዘንድ"
ከእርሱ በኋላ.....ምንም
አማራጭ ትርጉሞች 1) "ወደፊት የሚሆን ምንም ነገር" ወይም "ከሞተ በኋላ በእርሱ ላይ የሚሆን የትኛውም ነገር"
Ecclesiastes 7:15
ከንቱ በሆነ ዘመኔ
"ከንቱ በሆነ ህይወቴ"
ፃድቅ በፅድቁ
"ምንም እንኳ ጻድቅ ቢሆኑ"

ኃጥእም በክፋቱ
“ምንም እንኳ ኃጥእ ቢሆኑ”
እጅግ ፃዲቅ.....እጅግ ጠቢብም
ሁለቱ ሐረጎች በመሰረቱ ስለ አንድ ነገር ነው የሚያወሩት የተጣመሩትም ለአጽንኦት ነው።
እጅግም ፃዲቅ አትሁን
“ከሆንከው በላይ ፃድቅ ነኝ ብለህ እንዳታስብ”
እጅግ ጠቢብም አትሁን
ተርጓሚ “በራስህ አመለካከት ጠቢብ አትሁን” “በራስህ ፍርድ ጠቢብ መሆን”
እንዳትጠፋ - እራስህን ማፅደቅ ሰውን እንደሚያጠፋ ያመለክታል። ተርጓሚ “እራስህን የምታጠፋበት ምንም
ምክኒያት የለም ወይም በዚህ መንገድ ካሰብክ እራስህን ታጠፋለህ”
Ecclesiastes 7:17
ጊዜ ሳይደርስ እንዳትሞት
ፀሐፊው ሰዎች ያለ ጊዜአቸው እንዲሞቱ የሚያደርጋቸውን ነገር የሚያደርጉበት ምንም ምክኒያት የለም። ተርጓሚ “መሞት ካለብህ ቀን በፊት አስቀድመህ የምትሞትበት ምንም ምክኒያት የለም”
ይህን ብትይዝ....መልካም ነው
“ይህ የሚናገረው ሰው እንደ ዕቃ ጥበብን ለመያዝና ጠቢብ ለመሆን ስለመታገል ነው።” ተርጓሚ “ለዚህ ጥበብ እራስህን አስገዛ”
ከዚያም ደግም እጅህን ባታርቅ መልካም ነው።
ይህ የሚናገረው ፅድቅ እቃ እንደሆነ ያክል ሰው ፅድቅን ለመያዝ ስለመታገል ነው። ተርጓሚ “ፃድቅ መሆንህን ማቆም የለብህም” ወይም “ፃድቅ መሆን መምከርህን መቀጠል አለብህ”
ከሁሉ ይወጣልና
“እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር የሚጠብቀውን ሁሉ ያደርጋል”
Ecclesiastes 7:19
በከተማ ከሚኖሩ ከአስር ገዢዎች ይልቅ ጥበብ ጠቢብን ታበረታለች።
“ጥበብ ሰውን ብርቱ ታደርጋለች ፤ በከተማ ከሚኖሩ ከአስር ገዢዎች ይልቅ የበለጠ ብርቱ ታደርገዋለች”
መልካምንም የሚሰራ ኃጢአትንም የማያደርግ
“መልካምን የሚሰራና ኃጢአትን የማይሰራ”
Ecclesiastes 7:21
በሚጫወቱበት ቃል ሁሉ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “ሰዎች የሚሉትን ሁሉ”
ልብህ ያውቃልና
“አንተ ራስህ ታውቃለህ - ልብህ የሚለው ቃል ያውቃልና” ለሚለው ቃል አጽንኦት ለመስጠት ነው።
“ልብህ”
እዚህ ጋር የሰው ሐሳብ በልብህ ተገልጾአል። ተርጓሚ “በሃሳብህ”
Ecclesiastes 7:23
ይህን ሁሉ በጥበብ ፈተንሁ
አዚህ ጋር ይህን የሚለው ቃል ፀሐፊው የፃፈውን ነገሮች ሁሉ ይገልፃል። ተርጓሚ ስለፃፍኩአቸው ነገሮች ሁሉ ፈትኜ አወቅኩ።
ግን ከእኔ ራቀች
ለመረዳት ከችሎታዬ በላይ ነበረች ወይም “ነገር ግን ለማድረግ አልቻልኩም”
ራቀ እጅግም ጠለቀ
ይህ የሚናገረው በርቀት በጥልቅ ቦታ እንደተቀመጠ ነገር ጥበብን ለመረዳት ከባድ ስለመሆንን ነው። ተርጓሚ “ለመረዳት ከባድ”
የሚያገኘውስ ማን ነው?
ፀሀፊው ጥበብን መፈለግ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ አጽንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “ማንም ሊረዳ አይችልም”
በልቤ ዞርሁ
እዚህ ጋር ልብ ሃሳብን ይገልፃል። ዞርሁ የሚለው ቃል ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ “ሐሳቤን መራሁት” “ቆረጥኩ”
የነገሩን ሁሉ መደምደሚያ
“ለነገሮች ምክኒያት” መደምደሚያ የሚለው ቃል በግስ ሊገለፅ ይችላል።
ተርጓሚ“በህይወት ውስጥ የተለያዩ ነገሮች እንዴት እንደሚደመደም( መደምደም)”
Ecclesiastes 7:26
ልብዋ ወጥመድና መርባብ የሆነ እጆችዋም እግር ብረት የሆኑ ሴት
ፀሃፊው የምታማልል ሴት በእጆቹ እንስሳትን ለማጥመድ እንደያዘ ሰው ነች ይላል፡ ፀሃፊው አማላይ ሴት አጥማጅ የሆኑ ሰዎች ወጥመድ ይዘው እንደሚዞሩ አጥማጅ ስለመሆኑዋ ነው። “ልብዋ ሐሳቡዋና ስሜቱዋን ይወክላል።” ተርጓሚ “ማንኛዋም ሴት ወንዶችን በማማለል ታጠምዳለች”
ወጥመድና መርበብ
እነዚህ ሁለቱ ቃላት ሰዎች እንስሳትን በሚያጠምዱበት መንገድ እንዴት ሴት ወንዶችን እንደምታጠምድ አፅንኦት ለመስጠት ነው።
እጆቹዋ እግር ብረት የሆኑ
እዚህ ጋር “እጆቹዋ” ኃይሏንና ቁጥጥሯን ይገልፃል። ይህ የሚናገረው አማላይ ስለመሆኗና ሰዎችን የምታስርበት ሰንሰለት በእጆቿ እንዳለነው። ተርጓሚ “ማንም ከእሷማምለጥ አይችልም”
ኃጢአተኛ ግን ይጠመድባታል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ኃጢአንን ታጠምዳለች”
Ecclesiastes 7:27
አንዱን በአንዱ ላይ ጨምሬ
“ጨምሬ” የሚለው ቃል እንደ ፈሊጣዊ ይጠቅማል። ተርጓሚ “ከአንዱ በኋላ አንዱን መጨመር”
ወደ ነገር ሁሉ መደምደሚያ አደርስ ዘንድ
መደምደሚያ የሚለው ቃል በግስ ሊገለፅ ይችላል ። በመክብብ 7፡25 ፤ላይ መደምደሚያ እንዴትእንደተተረጎመ ተመልከት። ተርጓሚ በህይወት ውስጥ ነገርን ሁሉ ለመደምደም ይቻል ዘንድ።
ከሺህ ወንዶች አንድ አገኘሁ
ከአንድ ሺ ሰው አንድ ፃድቅ ከአንድ ሺህ ሰው ስብስብ አንድ ፃድቅ ብቻ ተገኘ
ከእነዚያ ሁሉ......አንዲት ሴት
ከአንድ ሺህ ሰው ስብስብ አንድ ጻድቅ ሴት አልተገኘም
Ecclesiastes 7:29
እነርሱ ግን ብዙ ብልሃት ፈለጉ
አማራጭ ትርጉሞች 1) “ብዙ ኃጢአተኛ እቅድ ሠሩ (አደረጉ)” 2) “የራሳቸውን ሕይወት ከባድ አደረጉ”
ብዙ ብልሃትን ፈለጉ
ይህ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሄዱ ጊዜ ሰብአዊነት ትክክል ወደ አለመሆን ስለመቀየር ያወራል።

Chapter 8
Ecclesiastes 8:1
እንደ ጠቢብ የሆነ ሰው ማን ነው ነገርንስ መተርጎም የሚያውቅ ማን ነው
ፀሐፊው ይህን መሪ ጥያቄ የሚጠይቀው ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር መልስ ለመስጠት ነው።
ፊቱን ታበራለች
ይህ ማለት የሰው ፊት ጠቢብ መሆኑን ያሳያል። ተርጓሚ “በፊቱ ላይ ያሳያል”
የፊቱንም ድፍረት ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ “ጨካኝ ገፅታው( ፊቱ)”
ትለውጣለች
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “ይለወጣል”
Ecclesiastes 8:2
“በእግዚአብሄር መሐላ ምክኒያት”
“ትጠብቀው ዘንድ ለእግዚአብሄር ያደረግኸው መሐላ”
ከፊቱ ትወገድ ዘንድ አትቸኩል
አማራጭ ትርጉሞች 1) ከንጉሱ ፊት ትሄድ ዘንድ አትቸኩል 2) ይህ በንጉስ ፊት ትሆን ዘንድ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። ተርጓሚ “ንጉሱን አትተወው”
የንጉስ ቃል ኃይለኛ ነውና
“ንጉስ ያለው ያ ሕግ ነው”
ማን ይለዋል ?
ይህ የሚቀጥለውን ጥያቄ ማንም አይጠይቀውም ለሚለው አፅንኦት ለመስጠት የግነት ጥያቄ ነው። ይህ ጥያቄ በዓረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ

“ማንም ሊለው አይችልም”

ይህንስ ለምን ታደርጋለህ?

ይህ የግነት ጥያቄ ተግሳፅ ነው። ይህ ጥያቄ በአረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “አደረክ ያለውን ማድረግ የለብህም”

Ecclesiastes 8:5

የጠቢብም ልብ.....ያውቃል።

እዚህ ጋር ለጠቢብ ሃሳብ( አስተሳሰብ) አጽንኦት ለመስጠት በልቡ ይገልፃል። ተርጓሚ “ጠቢብ ያውቃል”

ለነገር ሁሉ ጊዜና ፍርድ

“ነገሮችን የማድረግ ትክክለኛ ጊዜና በትክክል ማድረግ”

እንዴትስ እንደሚሆን የሚናገረው ማነው?

ይህ የግነት ጥያቄ ወደፊት ስለሚከሰት ነገር ማንም ሊያውቅ እንደማይችል አፅንኦት ይሰጣል። ጥያቄው ሲፃፍ በዓረፍተ ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። “ምን እንደሚመጣ ማንም ሊነግረው የሚችል የለም “ ( የግነት ጥያቄ ተመልከት)

Ecclesiastes 8:8

መንፈስን ለማስቀረት በመንፈስ ላይ ስልጣን ያለው የለም በሞቱም ቀን ስልጣን የለውም

ከመተንፈስ ማንም እራሱን ሊያግድ የሚችል እንደሌለ እንዲሁ የመሞት ጊዜ ሲደርስ ለመኖር የሚችል ማንም የለም

ሥልጣን ያለው.....የለም

ቁጥጥር ያለው የለም

በሞቱም ቀን

ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ “እርሱ ሲሞት” ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "የትኛውም ሰልፍ ማንንም ማሠናበት አይችልም"

ሰልፉም ቀን ስንብቻ የለም

ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ"የትኛውም ሰልፍ ማንንም አያሰናብትም" ወይም "ወታደርን የሚያሰናብት ሰልፍ የለም"

ኃጢአትም ሠሪውን አያድነውም

ይህ ኃጢአት ሠራተኛ እንዳለው አለቃ መሆኑን ይናገራል። ተርጓሚ"ክፉ ሰዎች ክፋትን በመስራት አይድኑም "

ልቤን ሰጠው

እዚህ ጋር ፀሐፊው ለስሜቱ አፅንኦት ለመስጠት እራሱን በልቡ ይገልፃል። የመክብብ 1:17 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ"እራሴን ሰጠሁ"

ወደ ተደረገው ሥራ ሁሉ

ይህ በገቢር መልኩ ሊጠቀም ይችላል። "ሠዎች የሚሰሩት የትኛውም ሥራ"

ከፀሐይ በታች

ይህ በምድር ላይ የተደረጉ ነገሮችን ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉም ተመልከት። ተርጓሚ"በምድር ላይ"

ሰው ሰውን ለመጉዳት ገዢ የሚሆንበት ጊዜ አለ።

"አንዳድ ጊዜ ጉዳት ለማድረስ አንዱ ሌላኛው ላይ ገዢ ይሆናል።"

Ecclesiastes 8:10

ኃጥኣን ተቀብረው አየሁ

ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። የሞቱ ክፉ ሰዎች የተከበረ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ተደረገላቸው ። ተርጓሚ"ሰዎች ክፍዎችን በክብር ቀበሩ"

ከቅድስት ስፍራ ወጡ ተቀበሩም በሰዎችም ተሞገሱ

ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ"ሰዎች ከቅድስት ሥፍራ ወሰዱአቸው ቀበሩአቸውም አመሰገኑአቸውም"

በክፉ ስራ ላይ ፈጥኖ ፍርድ አይፈርድምና

ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "በሥልጣን ላይ ያሉ ሠዎች ፈጥነው በክፉ ወንጀል ፍርድ አይፈርዱምና"

ልባቸው ክፉን ለመስራት ጠነከረ

እዚህ ጋር ለፍቃዳቸውና ለምኞቶቻቸው አፅንኦት ለመስጠት ሰዎችን በልባቸው ይወክላል (ይገልፃል) ተርጓሚ"የሰው ልጅ ጠነከረ" ወይም ሠው ክፉን ለመስራት ተሳበ"

Ecclesiastes 8:12

መቶ ጊዜ

"100 ጊዜ" (ቁጥር ተመልከት)

እግዚአብሔርን ለሚፈሩት....... ደኅንነት እንዲሆን

"እንዲሆን " የሚለው ቃል ፈሊጣዊ ነው። "እግዚአብሔርን ለሚፈሩት ሕይወት መልካም ይሆናል።

እግዚአብሔርን ለሚፈሩት በፊቱም ለሚፈሩት ... በፊቱም ለሚፈሩት

እነዚህሁለቱ ሐረጎች ሰዎች እግዚአብሄርን መፍራታቸውን አፅንኦት ለመስጠት አንድ ላይ የተጠመሩ ሲሆን ትርጉማቸው በመሰረቱ አንድ ነው።

ዘመኑ....አትረዝምም

ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፉ ይችላል። ተርጓሚ “እግዚአብሄር ዘመኑን አያረዝምም”

ዘመኑ እንደ ጥላ ነው

ይህ የሚናገረው የክፉ ሰው እድሜ ጥላ በፍጥነት እንደሚያልፍ ዘመኑም ፈጥኖ እንደሚያልፍ ነው ። ተርጓሚ ዘመኑ እንደ ጥላ ፈጥኖ ያልፋል

ዘመኑ

“ሕይወቱ”

Ecclesiastes 8:14

ከንቱ ነገር አለ

“ተን ነገር አለ” ፀሃፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ተን የሆኑ ያክል ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ እንደ ከንቱ እርባና ቢስ የሆነ ነገር አለ ወይም “እርባና ቢስ የሆነ ነገር አለ” (ዘይቤአዊ ትርጉም ተመልከት)

በምድር .....የሚደረግ ስራ ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “ሰዎች በምድር ላይ የሚሰሩት ነገር”

ይህም ደግሞ ከንቱ ነው

“ይህም ደግሞ ከንቱ ነው” ፀሐፊው እርባና ቢስና ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ተን የሆነ ያክል ይናገራል። የመክብብ 1:14 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ ይህም ደግሞ እንደ ከንቱ እርባና ቢስ ነው።

ከፀሐይ በታች

ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል ። የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “በምድር ላይ” ከፀሐይ በታች....እግዚአብሄር በሰጠው በሕወቱ ዘመን ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተረጓሚ “እግዚአብሄር እንዲኖር እስከፈቀደለት ድረስ”

---

Chapter 9

Ecclesiastes 9:1

ይህን ሁሉ መረምር ዘንድ በልቤ አኖርሁ

“ስለዚሁ ሁሉ በጣም በጥልቀት መረመርኩ”

በእግዚአብሄር እጅ እንዲሆኑ ይህን ሁሉ

እዚህ ጋር “እንዲሆኑ የሚለው ቃል ፃድቃንን ጠቢብን ይገልፃል ድርጊታቸውንም

በእግዚአብሄር እጅ”

እዚህ ጋር “እጅ” እግዚአብሄር ኃይልና ስልጣን ይገልፃል። ተርጓሚ "በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር"

ፍቅር ወይም ጥል .... ወደ ፊታቸው ነው።

ይህ "ፍቅር" ጥል ሰውን ለመጎብኘት ወደ ቤት እንደሚመጡ አድርጎ ይናገራል። ተርጓሚ"ፍቅር ወይም ጥልን መገናኘታቸው ነው

Ecclesiastes 9:2

የፃድቁና የበደለኛው

ይህ ሁሉንም ይገልፃል። ሁለቱ ፃድቁንም በደለኛውንም አፅንኦት ይሰጣል።

በደለኛ መልካሙና የክፉው የንፁሀኑ

እነዚህ ሁሉ ቃላት ሰዎች ሁሉ ይገልፃሉ። ተርጓሚ “በደለኞች፣መልካም ሰዎች፣ክፉ ሰዎችና ንፁሃን ሰዎች”

ንፁሃን ሰዎች

ይህ ሁሉንም ሰው ሲገልፅ ለሁለቱ ተቃራኒ፣ንፁህና ርኩስ ሰው አፅንኦት ለመስጠት ነው።(ዘይቤአዊ ተመልከት)

ንፁህ

በአካሉ ንፁህ የሆነ ያክል ለ እግዚአብሄር ዓላማ ተቀባይነት ያለው ሰው ነው

ርኩስ

በአካሉ ርኩስ (ንፁህ ያልሆነ) ያክል ለእግዚአብሄር ዓላማ ተቀባይነት የሌለው ሰው (ዘይቤአዊ ተመልከት)

መስዋዕትን የሚሰዋውና የማይሰዋው

ይህ ሰውን ይወክላል።ሁለቱ ተቃራኒ፣መስዋዕትን ለሚሰውና ለማይሰው ሰው አጽንኦት ለመስጠት።

እንደ መልካም ሰው እንዲሁ ሀጢአተኛው ሰው

ይህ ሁሉንም ሰው ይገልጻል። ለመልካሙም ለሃጢአተኛውም ለሁለቱም አጽንዖት



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይሰጣል።
ሃጢአተኛው እንደ መሃለኛው ሰው እንዲሁ መሃላን የሚፈራ ነው።
ይህ ሁሉንም ሰው ይገልጻል። መሃላን የሚምል መሃላ የሚፈራውን ሁለቱንም አጽንኦት ይሰጣል።
Ecclesiastes 9:3
በተደረገው ሁሉ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ “የሆነው ነገር ሁሉ”
ከጸሃይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልጻል የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ“በምድር ላይ”
አንድ ድርሻ
ሞት
የሰው ልጆች ልብ ክፋትን ትሞላለች በሕይወታቸውም ሳሉ እብደት በልባቸው ነው።
እዚህ ጋር ልብ የሚለው ቃል ሃሳብንና ስሜትን ይገልጻል። ተርጓሚ “የሰው ልጅ በክፋት የተሞላ ነው። ሃሳባቸውም የእብደት ነው።”
እብደት
“ስህተት” ወይንም “ከንቱነት”
ወደ ሙታን ይወርዳሉ
“”ሙታን የሚለው ቃል የሞቱ ሰዎችን ይገልጻል። እዚህ ጋር ሙታን ሰዎች ከሞቱ በኋላ የሚሄዱበትን ቦታ ይገልጻል። ተርጓሚ “ሙታን ወዳሉበት ቦታ ይሄዳሉ” ወይንም “ይሞቱና ወደ መቃብር ይሄዳሉ”
Ecclesiastes 9:4
ሕያዋን ---- ሙታን
ይህ በሕይወት ያሉትንና የሞቱትን ይገልጻል። ተርጓሚ “ በሕይወት ያሉ -- የሞቱት”
ያልሞተ ውሻ ከሞተ አንበሳ ይሻላል
ውሻ አነስተኛ እንስሳ ተደርጎ ቢገለጽም አንበሳ ደግሞ የተከበረ እንስሳ ተደርጎ ተገልጸአል። ይህ የተከበረ ሆነ ከሞተው አነስተኛ ሆኖ በሕይወት ስላለው ይናገራል። ተርጓሚእንደ አንበሳ የተከበረ ሆኖ ከመሞት እንደ ውሻ አነስተኛ ሆኖ መኖር ይሻላል።
መታሰቢያቸው ተረስቷልና
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል፡፡ ተርጓሚ “ሰዎች ይረሱአቸዋል”
Ecclesiastes 9:6
ፍቅራቸውና ጥላቸው ቅንዓታቸውም
ይህ ሙታን በሕይወት እያሉ ለሌሎች ያሳዩት ፍቅር፣ጥላቻንና ቅንዓትን ይገልፃል፡፡
በሚሰራው ነገር
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል፡፡ተርጓሚ“ሰዎች የሰሩት ማናቸውም ነገር”
ከፀሃይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል፡፡ የመክብብ 1፡3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “በምድር ላይ”
እንጀራህን በደስታ ብላ ! የወይን ጠጅህንም በተድላ ጠጣ
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው በሕይወት መሠረታዊ ድርጊቶች ( እንቅስቃሴዎች) መርካትን አፅንኦት ይሰጣል፡፡
እንጀራህን
ይህ መብልን ሁሉ ይገልጻል። ተርጓሚ “መብልህን”
የወይን ጠጅህን በተድላ ጠጣ
እዚህ ጋር “በተድላ” የሚለው ቃል ስሜትን ይገልጻል፡፡ ተርጓሚ የወይን ጠጅህን በደስታ ጠጣ
ሁልጊዜ ልብስህ ነጭ ይሁን ቅባትም ከራስህ ላይ አይታጣ
ነጭ ልብስን መልበስና ቅባትን በራስ ላይ መቀባት ሁለቱም የደስታና የበአል ምልክቶች ነበሩ፡፡
ቅባትም ከራስህ ላይ አይታጣ
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ “ራስህን ቅባት ተቀባ”
Ecclesiastes 9:9
ከምትወዳት ሚስህ ጋር ደስ ይበልህ
አንድ ሰው ሚስቱን ሊወድ ይገባል፡፡ ተርጓሚ “የምትወዳት ሚስት ስላለችህ በደስታ ከእርሷ ጋር ኑር”
ከፀሃይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልጻል የመክብብ 1:3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ “በምድር ላይ”
ዘመንህ
“የህይወት ዘመንህ”
ይህ እድል ፈንታህ ነውና
“ይህ” የሚለው ቃል ከሚስትህ ጋር በደስታ መኖርን ይገልፃል፡፡
እጅህ ለማድረግ የምታገኘውን ሁሉ
እዚህ ጋር በእጁ ተወክሎአል። ምክኒያቱም ሰው ብዙ ጊዜ ለመስራት እጁን ስለሚጠቀም ነው። ተርጓሚ “መስራት የምትችለውን ነገር ሁሉ”
ስራና አሳብ እውቀትና ጥበብ አይገኙምና
“ሥራ” “አሳብ” ና “እውቀት” የሆኑት ሰዎች በግስ ሊገለፅ ይችላሉ፡፡ ተርጓሚ “ሙታን ሥራን አይሰሩም ወይም አያስቡም ወይም አያውቁም ወይም ጥበብ የላቸውም፡፡”
Ecclesiastes 9:11
ከፀሃይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል የመክብብ 1፡3 ትርጉምን ተመልከት ተርጓሚ-በምድር ላይ
ሩጫ.....እንዳልሆነ....ሰልፍም....እንዳልሆነ
“ሩጫ ሁልጊዜ ለሯጭ እንዳልሆነ.....ሰልፍም ሁልጊዜ ለኃያላን እንዳልሆነ”
እንጀራ
እዚህ ጋር መብልን ሀሉ ይገልጻል፡፡ ተርጓሚ“ መብል”
ጊዜና እድል ሁሉ ይገናኛቸዋል
“እነዚህ ሁሉ ይገናኟቸዋል” እዚህ ጋር “ሁሉ” የሚለው ቃል ሩጫ ፣ ሰልፍ ፣እንጀራን፣ ባለጠግነትንና ሞገስን ይገልፃል፡፤
በክፉ ጊዜ ....ሲወድቅባቸው
ይህ ሰው ሲሞትን ይገልፃል፡፡ ተርጓሚ “እርሱ ሲሞት” ወይም “የሞት ጊዜ ሲመጣ”
ዓሣዎች.....እንደተያዙ ወፎችም እንዲሁ የሰው ልጆች በክፉ...ይጠመዳሉ
ይህ ሰዎች ሳይጠብቁ ስለመሞታቸው ይናገራል፡፡ ልክ እንደዚያው ሳይጠብቁ ድንገት ሰዎች እንስሳትን ይይዛሉ፡፡
የሰው ልጆች በክፉ ጊዜ ይጠመዳሉ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ይህም እንደተሰሩና በወጥመድ እንደተያዙ ሰዎች አደጋና ጥሩ ጊዜ ያልሆነ እንደሚያጋጥማቸው ይናገራል፡፡ ተርጓሚ"በሰው ልጆች ላይ ክፉ ጊዜ እየመጣ ነው"
በድንገት ሲወድቅባቸው
ይህ ፈሊጣዊ ነው ተርጓሚ"ይከሰታል ድንገት ሳይጠብቁ በአንድ ጊዜ" ወይም "ድንገት ሲመጣባቸው"
Ecclesiastes 9:13
ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል፡፡ የመክብብ 1:3 ትርጉም ተመልከት ተርጓሚበምድር ላይ (ፈሊጣዊ ተመልከት)
ታላቅ ንጉሥም መጣበት
እዚህ ጋር "ንጉሥ" የሚለው ቃል እራሱን ሠራዊቱን በሙሉ ይወክላል፡፡ ተርጓሚ "ታላቅ ንጉሥና ሠራዊቱ"
ታላቅ ግንብም ሠራባት
ይህ መውጣት እንዲችሉና ከተማዋን እንዲያጠቁ ሠራዊቱ በከተማ ዙሪያ በጭቃ የሠሩትን ግንብ ይገልፃል፡፡
ጠቢብ ድሀ ሰውም ተገኘባት
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል፡፡ ተርጓሚ"በከተማው ወስጥ ሰዎች፤ ደሀ፤ ጠቢብ ሠው አገኙ" ወይም "ደሀ ጠቢብ ሠው በከተማው ውስጥ ኖረ"
Ecclesiastes 9:16
የድሀው ጥበብ ግን ተናቀች
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል፡፡ ተርጓሚ"ሰዎች የድሀን ሰው ጥበብ ይንቃሉ"
ቃሉም አልተሰማችም
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል፡፡ "የሚለውን አይሰሙትም" ወይም "ምክሩን አይቀበሉም"
Ecclesiastes 9:17
ይልቅ የጠቢባን ቃል በፀጥታ ትሰማለች
እዚህ ጋር "ትሰማለች" የሚለው ቃል መረዳትን ይወክላል፡፡ ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል፡፡ የጠቢባን በፀጥታ የሚናገሩት ቃል መረዳት የተሻለ ቀላል ነው፡፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 10
Ecclesiastes 10:1
የሞቱ ዝንቦች እንዲሁም ትንሽ ስንፍና
ዝንቦች ሽቶን እንደሚያበላሹት ሁሉ ሰነፍም እንዲሁ የሰውን መልካም ስም ጥበብና ክብር ያጠፋል። ዝንቦች ሽቶን ያበላሻሉ
ትንሽ ስንፍና ጥበብና ክብርን ያጠፋል።
ይህ የሰው ስንፍና ጥበቡ ሰው የሆኑ ያክል ሞኝነቱ የራሱን መልካም ስም ጥበብና ክብርን እንደ ሚያበላሽና ጥበብና ክብርን ይናገራል።
የጠቢብ ልብ ...... የሰነፍ ልብ
እዚህ ጋር "ልብ" "አእምሮ" ወይም "ፈቃድን ይገልፃል። ተርጓሚ"ጠቢብ እንዴት እንደሚያስብ ..... ሰነፍ እንዴት እንደሚያስብ"
በስተቀኙ ነው ...... በስተግራው ነው
እዚህ ጋር "ቀኝና ግራ" ትክክል የሆነና ስህተት የሆነ ነገርን ይገልፃሉ። ተርጓሚ"ትክክል ነገርን ለማድረግ ..... ስህተትን ለመስራት
የሚያስበውም ሁሉ ስንፍና ነው
ይህ እንዴት እንደሚያደርግ ይገልፃል። "የማይረባ" ወይም "ደደብ ነው።"
Ecclesiastes 10:4
የገዢ ቁጣ የተነሳብህ እንደሆነ
እዚህ ጋር "ገዢ" "በስሜቱ" ይወክላል። "ገዢ በአንተ ላይ ሲቆጣ"
ትዕግሥት ታላቁን ኃጢአት ፀጥ ያደርጋል
"ፀጥ በማለት የሚቆጣን ሰው ፀጥ ማድረግ ትችላለህ"
Ecclesiastes 10:5
ከፀሐይ በታች
ይህ በምድር ላይ የተደረጉትን ይገልፃል። የመክብብ 1:3 ትርጉም ተመልከት ተርጓሚ "በምድር ላይ" ሰነፍ በታላቅ ማዕረግ ተሾመ ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ -"ገዢዎች የመሪነት ማዕረግ ለሰነፎች ይሰጣሉ"
ባለጠጎች ግን በተዋረደ ስፍራ ተቀመጡ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "ለባለጠጎች የተዋረደ ስፍራ ይሰጣሉ"
በተዋረደ ስፍራ
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ"ጥቅም የሌለው ስፍራ (ማዕረግ)"
መሳፍንትም እንደ ባሪያዎች በምድር ላይ ሲሄዱ
ይህ መሳፍንት እንደ ባሪያዎች እንደሚሄዱ ይናገራል። ምክንያቱም ባሪያዎች ተገደው ይሄዱ ነበር።ፈረስ ላይ ለመውጣትም ፈቃድ አልነበራቸውም።
Ecclesiastes 10:8
አባብ ትነድፈዋለች
ይህ በግንብ ውስጥ ይደበቅ ስለነበረው እባብ ይገልፃል።
ድንጋይን የሚፈነቅል
ይህ በድንጋይ ካብ ውስጥ መስራትንና ትልልቅ ድንጋዮች መፈንቀል ይገልፃል።
ይታመምበታል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ"እነዚያ ድንጋዮች ሊያሳምሙት ይችላሉ። ይጎዳበታል ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። "እንጨት ሊጎዳው ይችላል።
Ecclesiastes 10:12
የጠቢብ ሰው የአፍ ቃል ሞገስ ናት
እዚህ ጋር የጠቢብ ቃል በ"አፍ"ተወክሏል። ተርጓሚ"ጠቢብ የሚናገረው ነገር የተከበረ ነው።"
የሰነፍ ከንፈሮች ግን ራሱን ይውጡታል
እዚህ ጋር የሰነፍ ቃል(ንግግር) በ"አፍ" ተወክሏል። ይህ ንግግሮች የሚባሉት ያክል ሰነፉን በንግግር እንደሚያጠፉት ይናገራል።
Ecclesiastes 10:13
የአፍ ቃል መጀመሪያ ስንፍና ነው
የሰነፍ ንግግሩ በ"አፉ" ተወክሏል። ተርጓሚ "ሰነፍ መናገር ሲጀምር"
የንግግሩ ፍፃሜም ክፉ እብደት ነው
የሰነፍ ንግግሩ በ "አፍ" ተወክሏል። ተርጓሚ "ተናግሮ ሲጨርስ ክፉ እብደትን ይናገራል።
ቃሉን ያበዛል
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ"መናገሩን ይቀጥላል።" (ፈሊጣዊ ተመልከት)
በኋላ የሚሆነውን
"ወደ ፊት የሚከሰተውን ነገር"
ከእርሱ በኋላ የሚሆነውን ማን ይነግረዋል?
ፀሐፊው ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው ማንም ሰው ከሞቱ በኋላ ወደፊት የሚሆነውን የሚያውቅ እንደሌለ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህ በዐረፍተ-ነገር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ"ከእርሱ በኋላ የሚመጣውን የሚያውቅ ማንም የለም" የሚያውቅ የለም" ወይም "ከሞተ በኋል ምን እንደሚከሰት የሚያውቅ ማንም የለም"
Ecclesiastes 10:15
ያደክመዋል
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ሰነፍ በልፋቱ ደካማ ይሆናል።" ወይም "ሰነፍ በሚሰራው ስራ ይደክመዋል።"
ወደ ከተማ መሄድ አያውቅምና
አማራጭ ትርጉም 1) "ብዙ ጊዜ ወደ ከተማ የሚወስደውን መንገድ ስያገኝም" ሰነፍ በጣም ከመስራቱ የተነሳ ስለሚደክመው መንገዱን የትም ማግኘት አይችልም 2) "ወደ ከተማ የሚወስደው መንገድ ባለማወቁ" ሰነፍ በጣም ከመስራቱ የተነሳ ስለ ሚደክመው ወደ ቤት መሄድን በደንብ አያውቅም
Ecclesiastes 10:16
አንቺ አገር ሄይ ወዮልሽ
በዝህ ቁጥር ፀሐፊው ለህዝቡ እንደ ግለሰብ(እንደ አንድ ሰው) ይናገራል።
ንጉሥሽ ሕፃን የሆነ
"ይህ ማለት ንጉሡ ልምድ የሌለው ወይም ያልበሰለ"
ማልደው የሚበሉ
ይህ የሚያሳየው ገዢዎች ሀገር ከመምራት ይልቅ መዥናናት ላይ ማተኮራቸውን ነው።
ንጉሥሽ የከበረ ልጅ የሆነ
ይህ ልጅ ጥሩ ንጉሥ እንደሚሆን ታስቦ በተላላቆቹ መሠላጠኑን ያሳያል። ተርጓሚ "ንጉሥ" በከበሩ ሰዎች ሠልጥኖአል።"
ለብርታት....... ለስካር ያልሆነ
ይህ የተከበሩ ገዢዎች ለምን እንደሚበሉ ይገልፃል።
Ecclesiastes 10:18
በእጅ መታከት ቤት ያፈስባል
ሰነፍ ሰው ቤቱን በየጊዜው አያድስም/አይጠግብም። ተርጓሚ "ሰነፍ ሰው ቤቱን ስለ ማያድስ ጣሪያው ያፈሳል።"
በእጅ መታከት
እዚህ ጋር ሰው በእጅ ይወከላል። ተርጓሚ "በታካች ሰው ምክንያት" ወይም "ሰውየው ታካች በመሆኑ"
ቤት ያፈሳሳል
እዚህ ጋር ጣሪያው በሙሉ ቤቱ ተወክሏል። ተርጓሚ "ጣሪያው ያፈሳሳል"
እንጀራን ለሳቅ..... ያደርጉታል
"ሳቅ" የሚለው ቃል በ ግስ ሊገለፅ ይችላል። ተርጓሚ "ሰዎች ለመሳቅ እንጀራን ያዘጋጃሉ"
የወይን ጠጅንም ለሕይወት ደስታ ያደርጉታል
ተርጓሚ "የወይን ጠጅ ሰዎች በሕይወት እንዲደሰቱ ይረዳቸዋል።"
ሁሉም ለገንዘብ ይገዛል
አማራጭ ትርጉም 1)"ገንዘብ ፍላጎትን ሁሉ ያሟላል። 2)ገንዘብ ምግብንም ወይን ጠጅንም ያሟላል"
Ecclesiastes 10:20
በልብህ ሃሳብ እንኳን ቢሆን
የሰው ሃሳብ በሰው አእምሮ ተወክሏል። ተርጓሚ "በሃሳብህም እንኳን ቢሆን"
በመኝታ ቤትህም ባለጠጋን
"ባለጠጋን በመኝታ ክፍልህ ሳለህ" ይህ ማንም ሊሠማህ በማይችል በግል ሥፍራ እንኳን ሆነህ ባለጠጎችን መርገም የለብህም ማለት ነው።
ባለ ክንፎችም ነገሩን ይናገራሉና
እነዚህ ሁለት ሀረጎች አፅንኦት ለመስጠት ሲባል የተጣመሩ ሲሆን በመሰረቱም አንድ አይነት ነገር ይናገራሉ። ይህ የተናገርከውን የሚፈልጉና ሰዎችትንሽ ወፍ ያልከውን እንደሚሠሙ ያክል ሰምተው ለሌሎች ስለሚናገሩ ሠዎች ይናገራል። ተርጓሚ "ወፎች የተናገርከውን ሰምተው ነገሩን ለሌሎች ሠዎች ስለሚናገሩ"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 11

Ecclesiastes 11:1

እንጀራህን በውኃ ፊት ላይ ጣለው ከብዙ ቀን በኋላ ታገኘዋለህና

አማራጭ ትርጉሞች 1)ይህ ዘይቤአዊ ነው። ሰው ባለው ንብረት ላይ ለጋሽ መሆን አለበት ከዚያም ከሌሎች በቸርነት ይቀበላል። ማለት ነው 2) ሰው ሀብቱን ከባህር ማዶ ሥራ ማዋል አለበት ከዚያም ትርፉን ያገኛል። (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ለሰባት ደግሞም ለስምንት እድል ፈንታን ክፍል

አማራጭ ትርጉሞች 1) ሀብትህን ለብዙ ሠዎች ማካፈል። 2) ሀብትን ብዙ ቦታ ላይ ሥራ ላይ ማዋል።

ሰባት ደግሞም ስምንት

"7" ደግሞም "8" ሰዎች። ይህ ፈሊጣዊ ሲሆን በርከት ያሉ ሰዎች ማለት ነው። ተርጓሚ"በርከት ያሉ ሰዎች ወይም "ብዙ ሰዎች"

በምድር ላይ የሚሆነውን ክፉ ነገር ምን እንደሆነ

"ክፉ ነገሮች" የሚለው ቃል ክፉ ነገሮች ወደ ሆነ ቦታ እንደሚመጡ ነገር አድርጎ ይናገራል። እዚህ ጋር ምናልባት "በምድር ላይ" የሚለው ሐረግ እንዲያካፍል በታዘዘው ላይ የመጣ ክፉ ነገር ሊሆን ይችላል። ተርጓሚ "በአለም ላይ የሚሆነውን ክፉ ነገር።"

ደመናት ዝናብ ቢሞሉ

"ደመናት በዝናብ ጠቁረዋል"

በምድር ላይ ያፈስሱታል

"በመሬት ላይ ያፈስሱታል"

ወደ ደቡብ ወይም ወደ ሰሜን

እዚህ ጋር ደቡብና ሰሜን ሁለቱም አቅጣጫ ይወክላሉ። ተርጓሚ "በየትኛውም አቅጣጫ"

Ecclesiastes 11:4

ነፋስን የሚጠባበቅ አይዘራም

አማራጭ ትርጉሞች 1) "ለነፋስ ትኩረት የሚሰጥ የትኛውም ገበሬ ነፍስ በተሳሳተ አቅጣጫ ሲነፍስ አይዘራም" 2) "ለነፋስ በጣም ትኩረት የሚሰጥ የትኛውም ገበሬ መቼም አይዘራም"

ደመናትንም የሚመለከት አያጭድም

አማራጭ ትርጉሞች 1) ለደመናት ትኩረት የሚሰጥ የትኛውም ገበሬ ሊዘንብ ባለ ጊዜ መቼም አያጭድም" 2) ለደመናት በጣም ትኩረት የሚሰጥ የትኛውም ገበሬ መቼም አያጭድም"

የነፋስን መንገድ..... እንደማታውቅ

ይህ ነፋስ በመንገድ ላይ እንደሚራመድ አድርጎ ያናገራል። ተርጓሚ "ነፋስ ከወዴት እንደሚመጣ ወይም ወዴት እንደሚሄድ እንደማታውቅ" (ዘይቤአዊ ተመልከት)

አጥንትም በእርጉዝ ሆድ

አማራጭ ትርጉሞች 1) "አጥንት" የሚለው ቃል ሙሉ ሕፃንን ይወክላል። ተርጓሚ"ሕፃን እንዴት እንደሚያድግ ወይም 2) ቀስ በቀስ የሕፃን አጥንት እንዴት እንደሚያድግ"

Ecclesiastes 11:6

እጅህን አትተው

እዚህ ጋር እጅ ሙሉ ሰውን ይወክላል። ተርጓሚ "መስራትህን ቀጥል"

ወይም ይህ ወይም ያ ......... በማለዳ ....... በማታም

እዚህ ጋር ሁለት ሐረጎች በመሰረቱ አንድ ሲሆኑ የሰው ሥራ መቼም ቢሠራው እንደሚሣካ አፅንኦት ለመስጠት ነው። ተርጓሚ "በማለዳ የዘራኸውን ዘር ወይም በማታ የዘራኸው ዘር"

ብረሃን ጣፋጭ ነው

እዚህ ጋር ብርሃን የሚለው ቃል ፀሐይን ማየት መቻልንና በሕይወት መኖርን ይወክላል። እና ይህ የሚናገረው ስለ በሕይወት መኖር ሐሴት ማድረግን ልክ ብርሃን ጣፋጭ ነገር የሆነ ያክል። ተርጓሚ "ፀሐይን ማየት ሐሴት ነው ወይም በሕይወት መኖር ያስደስታል።"

ፀሐይም ማየት ለዓይን

"ዓይን" ሙሉ ሰውን ይወክላል። ይህ ሐሳብ ከበፊቱ ሀሳብ ጋር ተመሣሣይ ነው። ተርጓሚ "ፀሐይን እንዲያይ" ወይም "በሕይወት መኖር"

በሁለቱም ደስ ይበለው

እዚህ ጋር "በሁሉም" የሚለው ቃል ሰው በእድሜው ዘመን የሚኖረውንዘመን ይገልፃል።

የጨለማውን ዘመን ....... የሚመጣው

ቀናት እንደሚመጡ ያክል ስለ ወደፊት ይናገራል። እዚህ ጋር "ጨለማ "ሞትን" ይገልፃል። ተርጓሚ "ምን ያህል ቀናት ሟች እንደሚሆን"

ብዙ ቀን ይሆናልና

እዚህ ጋር "ብዙ" የሚለው ቃል የጨለማውን ቀናት ይገልፃል። ተርጓሚ "በሕይወት ከኖረው ዘመን የበለጠ ሟች ስለሚሆን" ወይም "ዘላለም ሟች ስለሚሆን"

የሚመጣው ነገር ሁሉ ከንቱ ነው

እዚህ ጋር "ከንቱ" የሚለው ቃል ዘይቤአዊ ነው። አማራጭ ትርጉሞች 1)"ከሞተ በኋላ ምን እንደሚከሰት ማንም የሚያውቅ የለም" 2) ሊመጣያለው ነገር ሁሉ ትርጉም የለውም"

የሚመጣው ነገር ሁሉ

አማራጭ ትርጉሞች 1) "ከሞት በኋላ የሚከሰቱ ነገሮች ሁሉ" 2) ወደ ፊት የሚከሰቱ ነገሮች ሁሉ"

Ecclesiastes 11:9

አንተ ጎበዝ በጉብዝናህ ደስ ይበልህ በጉብዝናህም ወራት ልብህን ደስ ይበለው

እነዚህ ሐረጎች አንድ አይነት ነገር ሲናገሩ አንድ ላይ የተጣመሩትም ሠው በዝናው ሊደሰት ይገባል ለሚለው ሐሳብ አፅንኦት ለመስጠት ነው።

ልብህን ደስ ይበለው

እዚህ ጋር ልብህ የሚለው ቃል ስሜትን ይወክላል። ተርጓሚ "ሐሴትን አድርግ"

በልብህም መንገድ ሂድ

እዚህ ጋር "ልብ የሚለው ቃል አእምሮን ወይም ስሜትን ሊወክል ይችላል። ተርጓሚ "የምትመኘውን መልካም ነገር ተከተል" ወይም ልትከተል የወሰድከውን መልካም ነገሮች ተከተል"

ዓይኖችህም በሚያዩት

እዚህ ጋር "አይን" ሙሉ ሠውን ይወክላል። ተርጓሚ "አይተህ የተመኘኸውን" ወይም "አይተህ በጣም የተሻለውን"

ስለዚህ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ፍርድ እንዲያወጣህ

ፍርድ የሚለው ቃል "ተጠያቂ ያደርግሃል" በሚለው ሊተካ ይችላል። ተርጓሚ "በነዚህ ነገሮች ሁሉ ምክንያት እግዚአብሔር ይፈርድብሃል" ወይም "ላደረግኸው ነገር በሙሉ ተጠያቂ ያደርግ ሃል"

ከልብህ ሃዘንን አርቅ

ለማዘን አለመፈለግ፤ ሐዘንን ማስወገድ እንደሚቻል አድርጎ ይናገራል "ልብም የሰውን ስሜት ይወክላል። ተርጓሚ "ለማዘን ፈቃደኛ አትሁን"

ሕፃንነትና ጉብዝና ከንቱዎች ናቸውና

ፀሐፊው ከንቱ እንደሚጠፉና ዘላቂ የሆነውን ያክል እርባና ቢስና ትርጉም ስለሌላቸው ነገሮች ይናገራል። ፀሐፊው ዘላቂ ጥቅም ስለሌላቸው ነገሮች ይናገራል። የመክብብ 1፡14 ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "ምክንያቱም ሕፃንነትና ጉብዝና ለዘላለም አይደሉም ወይም ምክንያቱም ለዘላለም (ሁሉ ጊዜ) ሕፃንና ጎበዝ አትሆንም።"

Chapter 12

Ecclesiastes 12:1

አስብ

ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ "አስታውስ"

የጭንቀት ቀን ሳይመጣ

ቀናት እንደሚመጡ ያክል ስለወደፊት ይናገራል። ተርጓሚ "የጭንቀት ቀን ሳይመጣብህ" ወይም "ክፉ ነገር ሳይደርስብህ በፊት" (ዘይቤአዊ ተመልከት)

ደስ አያሰኙትም የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ

ዓመታት እንደሚመጡ ያክል ስለወደፊት ይናገራል። ተርጓሚ "ሳታረጅና በመኖር ከዚህ በኃላ ደስ አልሰኝም ከማለትህ በፊት"

ሳይደርሱ ፀሐይና ብርሃን ......ከዝናብ በኋላ

ፀሐይና ጨረቃ እንደሚጠቁሩና ጥቁር ዳመናም እንዳሚመስል ያክል ስለ ማርጀትና ሞት ይናገራል። ተርጓሚ"ፀሐይና ብርሃን ሳይደርሱ ከዝናብ በኋላም ሳይመስልህ ይህንን አድርግ" (ዘጥቤዘዊ ተመልከት)

Ecclesiastes 12:3

X

ፀሐይ ምንም ተግባር መከናወን ስለቆመበት ቤት ይናገራል። ይህ ሰው ሰውነቱ

እያረጀ ሲመጣ ፈሊጣዊ ይሆናል። (ዘይቤአዊ ተመልከት)
ኃያላን ሰዎችም በሚጎብጡበት
"ኃያላን ደካማ ይሆናሉ"
ጥቂቶች ሆነዋልና ፈጭታዎች ሥራ በሚፈቱበት
"ሚፈጨው ነገር ጥቂት ከመሆኑ ፈጭታዎቸ ሥራ ያቆማሉ"
Ecclesiastes 12:4
x
ፀሐፊው ዘይቤአዊ ንግግሩን ቀጥሏል።
ደጆች በሚዘጉበት ቀን
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ"ሰዎች ወደ መንገድ የሚያሳየውን መንገድ ይዘጋሉ"
ከወፍ ድምፅ የተነሣ ሰው ሲነሣ
ይህ የወፍ ድምፅ ሰዎችን ሲቀሰቅስ ይገልፃል። ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "የወፍ ድምፅ ሰዎችን ለማስነሣት ሲቀሰቅስ"
የሚጮኹ ሴቶች ልጆች ሁሉ ዝግ ሊሉ
እዚህ ጋር ሴቶች ልጆች "ለወፎቹ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ "የወፎቹ ዜማ ዝግ ይላል"
Ecclesiastes 12:5
x
ፀሐፊው ዘይቤውን ቀጥሏል።
ለውዝም ሲያብብ
የለውዝ ተክል በበጋ ነጭ አበባን የሚያብብ ተክል ነው።
አንበጣም እንደ ሸክም ሲከብድ
አንበጣ ትልቅ ነው። ቀጥ ያለ ክንፍ ረጅም ርቀት እንዘል ወዳ ኋላ ከተጋጠሙ ረጅም እግሮች ጋር ስላረጀና ደካማ ስለሆነ እራሱን ብቻ ነው መሸከም የሚችለው።
ፈቃድም ሲጠፋ
ፈቃድ የሚለው ስውር ቃል እና ግስ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ሰዎች ከዚህ በፊት ያደረጉትን ሴይመች ሊቀሩ"
ሰው ወደ ዘላለም ቤት ሲሄድ
ይህ ሞትን ይገልፃል። ተርጓሚ "ሰው ወደ መሞቻ ስፍራው ይሄዳል። ወይም "ሰው ይሞታል ዳግም ወደ ሕይወት አይመለሥም"
አልቃሾችም በአዳባባይ ሲዞሩ
አመራጭ ትርጉሞች 1)ቀብሩን ለመመልከት አልቃሾች ወደ አዳባባይ ሲሄዱ 2) አልቃሾች ለሞት ወደ ተቃረበው ሰው ቤት ለመሄድ ወደ አዳባባይ ሲሄዱ"
Ecclesiastes 12:6
አስብ
ይህ ፈሊጣዊ ነው። ተርጓሚ"አስታውስ"
የብር ድሪ ሳይበጠስ የወርቅም ኩስኩስት ሳይሰበር ማድጋውም በምንጭ አጠገብ ሳይከሰከስ
ይህ ሞት ከእነዚህ ተሰባሪ ነገሮች አንዱ የሆነ ያክል ስለመሞት ይናገራል። ሰዎቸ እነዚህን ነገሮች ሊጠቀሙበት ድንገት እንደሚሠብሩ ሁሉ ሞትም ሰውነትን ይሰብራል።
የብር ድሪ ሳይበጠስ
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚ "የሆነ ሰው የብር ድሪ ይበጥሳል"
የወርቅ ኩስኩስት ሳይሰበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "የሆነ ሰው ማድጋ ይሰብራል"
መንኮራኩርም ሳይሰበር
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍይችላል። ተርጓሚ "የሆነሰው መንኮራኩሩን ይሰብራል"
አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ
እዚህ ጋር አፈር የሚለው ቃል የሚበሰብሰውን ሰውን አካል ይገልፃል።
Ecclesiastes 12:8
ከንቱ ፤ ከንቱ ፤ ሁሉ ከንቱ ነው
ሰባኪው ከንቱ እንዲሚጠፋና ዘለቄታ እንደ ሌላቸው ሁሉ እርባና ቢስና ትርጉም ስለሌላቸው ነገሮች ይናገራል። ፀሐፊው ዘላቂ ጥቅም ስለሌላቸው ነገሮች ይናገራል። የመክብብ፡1፡14፡ ትርጉምን ተመልከት። ተርጓሚ "ጊዜያዊና እርባና ቢስ ….. ሁሉም ነገር ትርጉም የለሽ ነው (ዘይቤአዊ ተመልከት)
ሰባኪው
የመክብብ ፡1፡1፡ትርጉምን ተመልከት
መረመረና ፈለለገ አስማማም
"በጣም አሰበም አስማማም " ወይም "በጣም አሰበበትና ፃፈ"
Ecclesiastes 12:10
በቅንም ….. ቃል ፈለገ
ሲባልም ቃለቱ ለአድማጭአስደሳች እንዲሆኑ ፈለገ ሰለሚመቹ ሳይሆን በደንብ ስለተፃፈያስደስታሉ።
የጠቢባን ቃል …..ከአንድ እረኛ የተሰጡት
ፀሐፊው ሰባኪው እረኛ በትሩን መንጋውን ለመምራት እንደ ሚጠቀም ሁሉ ሰበኪው ሰዎችን ለማስተማር የራሱን ቃለት ይጠቀማል። (ዘይቤአዊ ተመልከት)
የጠቢባን ቃል እንደ በሬ መውጊያ ነው
ይህ ተነፃፃሪ ነው። ተርጓሚ "ከብት እንዲንቀሳቀስ የበሬ መውጊያ እንደ ሚጠቅም ጠቢባንም ሰዎች እንዲንቀሳቀሱ ያበረታታሉ።
የተሰበሰቡትም ቃላት እንደተቸነከሩ ችንካሮች ናቸው
ይህ ተነፃፃሪ ነው። በደንብ በተቸነከሩ ችንካሮች እንደምትተማመን ሁሉ እንዲሁ በምሳሌ በተሰበሰቡ የጠቢባን ቃል ላይም መተማመን ትችላለህ"
የጠቢብን ቃል …..የተሰበሰቡትም
ጠቢብ ቃለት በምሳሌ የተሰበሰቡ ናቸው። ወይም "የጠቢባን አባባል"
በአንድ እረኛ የተሰጡት
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "አንድ እረኛ የሚያሰተምረው"
Ecclesiastes 12:12
ብዙ መፃሕፍትን ማድረግ ፍፃሜ የለውም
ማድረግ የሚለው ቃል ። በግስ መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ሰዎች ብዙ መፅፍትን ማድረግ መቼም አያቆሙም ።"
ሰውነትን ያደክማል
እዚህ ጋር "ሰውነት" የሚለው ቃል ሙሉ ሰውን ይወክላል። ተርጓሚ "ሰውን ያደክማል"
Ecclesiastes 12:13
የነገር ሁሉ ፍፃሜ
"በነገር ላይ የመጨረሻው መደምደሚያ"
ፍፃሜ እንስማ ይህ …..ነውና
ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል። ተርጓሚ "ከሁሉንም ነገር ከሰማህ በኋላ"
የተሰወረውንም ነገር ሁሉ
ይህ የተሰወረው ነገር እቃ እንደተደበቀ ነገር ይናገራል።ተርጓሚ "ሰዎች በድብቅ ከሚሠሩትነገር ሁሉ ጋር " (ዘይቤአዊ ተመልከት)

---

Chapter 1
Song of Solomon 1:1
አጠቃላይ መረጃ
የመጽሐፉ ክፍል አንድ ከመኃልየ መኃልይ 1:2 ይጀምራል።
የመዝሙራት መዝሙር
“ምርጥ መዝሙር” ወይም “እጅግ በጣም ምርጥ የሆነ መዝሙር”
የሰለሞን የሆነው
“ስለ ሰለሞን የሆነው” ወይም “ሰለሞን ያቀናበረው” አማራጭ የሚሆኑ ትርጉሞች ናቸው።
ፍቅርህ ከወይን ጠጅ ይልቅ
“ወይን በመጠጣት ከምደሰተው ይልቅ በአጠገቤ መሆንህ ያስደስተኛል”
ሽቱህ
“የተቀባኸው ሽቱ”
አስደሳች መዓዛ አለው
“አስደናቂ ሽታ አለው”
ስምህ እንደሚፈስ ሽቱ ነው
ሽቱ አየሩ በሚነፍስበት ጊዜ አካባቢውን የሚያዳርስ ጥሩ ሽታ አለው። ስሙ 1) ሰውየው ላለው ምስክርነት፣ ሌሎች ስለ እርሱ ስለሚያስቡት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እዚህ ጋ፣ ተናጋሪው፣ ሰዎች አድማጫቸው ጥሩ ሰው እንደሆነ ሁልጊዜ ያስባሉ ይላል፣ ወይም 2) ሰውየውን ራሱን አመልካች ይሆናል።
ከአንተ ጋር
“አንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰውየውን ስለሆነ ነጠላ ቁጥር ነው።
ውሰድ
“ሳብ” ወይም “ጎትት”፣ እዚህ ጋ ሴቲቱ ማራኪዋን ለመከተል ፈቃደኛ እንደሆነች ምርኮኛ ሆና ተገልጻለች።

እንሮጣለን
በውስጠ ታዋቂ ያለው “እኛ” የሚለው ቃል ከሰውየው ጋር ያለችውን ወጣት ሴት ያመለክታል።
ደስ ይለናል ... ሐሴት እናደርጋለን ... በዓል እናድርግ
ሴቲቱ ከአንድ ሰው በላይ አድርጋ ስለ ራሷ ትናገራለች። የተከፈተው ተለዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንደሚያደርገው ሁሉ በርካታ ትርጉሞች ተውላጠ ስሙን ወደ “እኔ” ይለውጡታል። ሌሎች ትርጉሞች እነዚህን የሴቲቱ ባልንጀሮች ስለ ሴቲቱ ወይም ስለ ሰውየው ንግግር እንደሚያደርጉ አድርገው ያቀርባሉ።
ስለ አንተ
“በአንተ ምክንያት”
በዓል እናድርግ
“እናመስግን”
ሌሎች ሴቶች አንተን ማድነቃቸው ተፈጥሮአዊ ነው
“የሚያደንቁህ ሴቶች ያደረጉት ማድረግ የሚገባቸውን ነው”
Song of Solomon 1:5
እኔ ጥቁር ነኝ፣ ነገር ግን ውብ ነኝ
“ቆዳዬ ጥቁር ነው፣ ነገር ግን ቆንጆ ነኝ” ወይም “ቆዳዬ ቢጠቁርም ቆንጆ ነኝ”
የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች
“የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች”፣ እነዚህ ወጣት ሴቶች በዚያ ስላልነበሩ ሊሰሟት አይችሉም፣ ነገር ግን ሴቲቱ እንዳሉና ሊሰሟት እንደሚችሉ ቆጥራ ትናገራለች።
እንደ ቄዳር ድንኳኖች ጥቁር
የቄዳር ዘላን ጎሳዎች ቤቶቻቸውን ለመሥራት የጥቁር ፍየሎችን ቆዳ ይጠቀሙ ነበር። ሴቲቱ የራሷን የቆዳ ቀለም ከእነዚህ ድንኳኖች ጋር ታነጻጽራለች።
እንደ ሰለሞን መጋረጃ ውብ
ሰለሞን ለራሱ ቤተ መንግሥት ወይም ለቤተ መቅደሱ የተዋቡ መጋረጃዎችን ሠርቶ ነበር። እርሷ የቆዳ ቀለሟ ቆንጆ መሆኑን ትናገራለች።
በእሳት የተለበለበ
ይህ “የተቃጠለ” ወይም “የጠቆረ” ለሚለው የሚውለው ግነት የሚያመለክተው ፀሐይ ቆዳዋን ከብሩኅነት ወደ ጥቁረት መለወጡን ነው።
የእናቴ ወንዶች ልጆች
“በእናቴ በኩል ወንድሞቼ የሆኑ”፣ እነዚህ ወንድሞች ከአንድ አባት ባይሆንም እንደ ሴቲቱ ሁሉ ከአንድ እናት የተወለዱ ይሆኑ ይሆናል።
የወይን ቦታ ጠባቂ አደረጉኝ
“የወይኑን ቦታ እንድንከባከብ አደረጉኝ”
የራሴን የወይን ቦታ ግን አልጠበቅሁም
ሴቲቱ ራሷን ከወይን ቦታ ጋር ታነጻጽራለች። ኢ.ት፡ “የራሴን የወይን ቦታ ግን መንከባከብ አልቻልኩም”
Song of Solomon 1:7
ነፍሴ የምትወድህ
ነፍስ ሰውን ገላጭ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የምወድህ”
መንጋህን የምታሰማራው
“መንጋህ ሣር እንዲግጡ የምታደርግበት”
መንጋህን የምታሳርፍበት
“መንጋህ እንዲጋደሙ የምታደርግበት”
ከጓደኞችህ መንጋ አጠገብ እንደሚቅበዘበዝ ሰው የምሆነው ለምንድነው?
ሴቲቱ ከሌሎች ሴቶች ይልቅ ከሰውየው ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዳላት አጽንዖት ለመስጠት ይህንን ጥያቄ ትጠይቃለች። ጥያቄው እንደ መግለጫ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “አንተን በምፈልግበት ጊዜ በጓደኞችህ መንጋ መካከል እንዳልቅበዘበዝ ንገረኝ”።
የምትቅበዘበዝ
“የምትዞር”፣ ሰውየውን የምትፈልግ መስላ መታየት አትፈልግም። ምናልባት ሌሎች ሰዎች የዝሙት ሥራ የምትፈልግ ሴት አዳሪ አድርገው እንዳያስቧት ሳትፈራ አትቀርም።
ጓደኞችህ
“ባልንጀሮችህ” ወይም “የሥራ ባልደረቦችህ”
Song of Solomon 1:8
በሴቶች መካከል እጅግ የተዋብሽ
“አንቺ ከሴቶቹ ሁሉ እጅግ የተዋብሽ ሆይ”
የመንጋዬን ፍለጋ ተከተዪ
“ከመንጋዎቹ ኋላ ተከተዪ”
ፍለጋ
በመሬት ላይ የሚቀር የመንጋው የኮቴ ምልክት
የፍየል መንጋዎችሽን አሰማሪ
“የፍየል ግልገሎችሽ ሣር እንዲግጡ አድርጊ” ወይም “የፍየል ግልገሎችሽ እንዲመገቡ አድርጊ”
Song of Solomon 1:9
አጠቃላይ መረጃ
ሰውየው ለሴቲቱ መናገሩን ይቀጥላል።
የኔ ፍቅር፣ በፈርዖን የሰረገላ ፈረሶች መካከል ባለች ባዝራ እመስልሻለሁ
የዚያ ዘመን አይሁድ የፈረሶችን ውበት ያደንቁ ነበር፣ እርሱ የፈርዖንን ፈረሶች እጅግ የተዋቡ ሆነው አግኝቷቸዋል። ሰውየው ወጣቷ ሴት ውብ እንደሆነች ያስባል። ኢ.ት፡ “የኔ ፍቅር፣ ከፈርዖን የሰረገላ ፈረሶች እንደ አንዱ ውብ ነሽ”
የኔ ፍቅር
“የምወድሽ”
የፈርዖን የሰረገላ ፈረሶች
“የፈርዖንን ሰረገላዎች የሚጎትቱ ፈረሶች”
ጉንጮችሽ ከጌጣጌጦቹ ጋር ውቦች ናቸው
እነዚህ ጌጣጌጦች 1) በጭንቅላት ዙሪያ በክር የሚታሰሩ ፈርጦች ወይም 2) የጆሮ ጉትቻዎች ወይም 3) ረጅም ጸጉሯን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል።
እንሠራልሻለን
ሰውየው ራሱን እንደ ብዙ ሰው አድርጎ ይናገራል። አንዳንድ ትርጉሞች ይህንን “እኔ” ወደሚል ነጠላ ቁጥር ይቀይሩታል። ሌሎች ትርጉሞች እነዚህን ቃላት የሴቲቱ ጓደኞች ንግግር እንደሆነ አድርገው ይወስዱታል።
የብር ፈርጥ
“የብር ጠቃጠቆ”
Song of Solomon 1:12
መከዳው ላይ ተጋድሞ
“ልዩ ማዕዱን ለመብላት ተቀምጧል”፣ ይህ ምናልባት በግብዣ ጠረጴዛ ዙሪያ ሰዎች ከሚጋደሙባቸው መከዳዎች አንዱን ያመለክት ይሆናል። ሰዎች ልዩ ማዕድ በሚበሉበት ጊዜ አካላቸውን የሚያሳርፉበትን የተለመደ ቃል በመጠቀም መተርጎም ትችላለህ።
ናርዶስ
ሰዎች ውድ ከሆነው ከናርዶስ ወይም የናርዶስ ተክል የሚያገኙት ዘይት (ትናንሽ ሮዝ ወይም ነጭ አበባ ያለው ተክል” ሲሆን ሰውነታቸውን ለማለስለስና አስደሳች መዓዛ እንዲኖራቸው ለማድረግ ይጠቀሙበታል።
መዓዛውን ናኘ
“መልካም ሽታውን ለቀቀው”
የእኔ ተወዳጅ በጡቶቼ ... እንደ ከርቤ መቋጠሪያ ነው
ሴቶች በአንገት ጌጣቸው ላይ አነስተኛ የከርቤ መቋጠሪያ ወይም መከዳ በጡቶቻቸው መካከል እንዲያርፍ በማድረግ በጣፋጭ መዓዛው ይደሰቱ ነበር። ይህቺ ሴት በቅርቧ ባለው ፍቅረኛዋ ተደሰታለች። እንዲህ ባለው መንገድ፣ ሌላ ማንም፣ ከፍቅረኛዋ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው እንደማትጠብቅ ለማሳየት “ለእኔ” የሚለውን ቃል ትጨምራለች። ኢ.ት፤ “በጡቶቼ ... በከርቤ መቋጠሪያ ደስ እንደሚለኝ በፍቅረኛዬ ደስ ይለኛል”።
ፍቅረኛዬ
ይህ ቃል ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ብትለው የተለመደ ሊሆን ይችላል። ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።
በጡቶቼ መካከል እንዳረፈ
ይህ ሐረግ አንባቢዎችህን የሚያሳዝን ከሆነ ሻል ባለ ቃል መጠቀም ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ለእኔ ቅርብ ሆኖ”
ፍቅረኛዬ ለእኔ እንደ ሄና የአበባ ዕቅፍ ነው
የሄና አበቦች ሰዎች ደስ የሚሰኙበት መዓዛ አላቸው። ሴቲቱ በፍቅረኛዋ ትደሰታለች። እንዲህ ባለው መንገድ ሌላ ማንም ከፍቅረኛዋ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው እንደማትጠብቅ ለማሳየት “ለእኔ” የሚለውን ቃል ትጨምራለች። ኢ.ት፡ “በሄና ዕቅፍ አበባ ሽታ ደስ እንደሚለኝ በፍቅረኛዬ እደሰታለሁ”።
የሄና አበቦች


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሰዎች ለሽቱነት የሚጠቀሙበት በአነስተኛ ሽለቆ የሚገኝ የአበባ ዓይነት
Song of Solomon 1:15
አንቺ፣ ስሚ
“አንቺ፣ ልናገረው ያለው እውነትና አስፈላጊ ስለሆነ ልብ በይ”
የእኔ ፍቅር
“የምወድህ አንተ”፣ መኃልይ 1፡9ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ዓይኖችሽ እርግቦች ናቸው
እስራኤላውያን፣ እርግቦች ገርና ለስላሳ ወፎች እንደሆኑ ያስቡ ነበር፤ ሰውየው የሴቲቱ ዓይኖች ውቦች እንደሆኑ ያስባል፤ ምክንያቱም ሴቲቱ ወደ እርሱ የምትመለከትበት አኳኋን ገር ናት ብሎ እንዲያስብ ያደርገዋል። ኢ.ት፡ “አንቺ በጣም ገር ነሽ” ወይም 2) ሰውየው የሚናገረው ስለ ሴቲቱ ነጭ የዓይኗ ክፍል ወይም የዓይኖቿ ቅርፅ የእርግቦቹን ቅርፅ ስለመምሰላቸው ነው የሚሉት አማራጭ ትርጉሞች ናቸው።
Song of Solomon 1:16
አንተ፣ ስማ
“አንተ፣ ልናገረው ያለው እውነትና አስፈላጊ ስለሆነ ልብ በል”
ውብ
በአንተ ቋንቋ፣ መልከ መልካም የሆነ ወንድ የሚገለጽበትን ቃል ተጠቀም።
የእኔ ፍቅር
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰው ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች እርሷ “የእኔ አፍቃሪ” ብላ ብትጠራው ይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመኃልየ መኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።
ለምለሞቹ ሣሮች መኝታዎቻችን ናቸው
መኝታ የሚሆኑ ይመስል ይህ የሚናገረው ስለ ለምለሞቹ ሣር ነው። ኢ.ት፡ “ለማንቀላፋት የምንተኛው በለመለሙት ሣሮች ላይ ነው”።
የለመለሙ ሣሮች
ሣሮቹ አረንጓዴ፣ እርጥብ እና በብዛት የሚያድጉ ናቸው
የቤታችን ተሸካሚዎች ዝግባዎች ናቸው፤ ወራጆቹ ጥዶች ናቸው
ሴቲቱ የሚተኙበት ቤት በሚመስል መልኩ ስለ ጫካው ታብራራለች
ተሸካሚዎች ... ወራጆች
“ተሸካሚዎች” ከግድግዳዎቹ በላይ ያለውን ሁሉ ለመሸከም የሚያገለግሉ ትላልቅ ግንዶችን ሲያመለክት “ወራጆች” የሚያመለክቱት ጣሪያውን የሚያያይዙ ረጃጅም አጠናዎችን ነው ወይም 2) “ተሸካሚዎች” የሚያመለክቱት ወራጆቹን ሆኖ “ወራጆች” እናጻዎቹ ከጣሪያ መሰሪያዎች እንዲሁም ከተሸካሚዎቹ ጋር የሚያያይዙባቸውን ፍልጦች ያመለክታሉ የሚሉት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው።
ዝግባዎች ... ጥዶች
ዝግባዎች ረጃጅምና ጠንካራ ዛፎች ናቸው። “ጥዶች” ተብሎ የተተረጎመው ቃል እንደ ዝግባ ሁሉ ለዛፎቹ የተሰጠ ጥቅል ስም ነው፣ ይሁን እንጂ እነዚህ ትንንሾች ናቸው። ዝግባና ጥድ በአንተ አካባቢ የማይታወቁ ከሆኑ ለረጅሞቹና ለጠንካራዎቹ ዛፎች ጥቅል የሆኑ ቃሎችን መጠቀም ትችላለህ።

---

Chapter 2
Song of Solomon 2:1
እኔ በአረንጓዴ መስክ እንደሚገኝ የሳሮን አበባ ነኝ
ሴቲቱ ራሷን በውብ አበቦች በሚታወቅ ቦታ ካሉ አበቦች እንደ አንዱ አድርጋ ትናገራለች
ሳሮን
ለጥ ያለ፣ዛፎች የሌሉበት፣የተለያዩ አይነት አበቦች እና ሳሮች የሚበቅሉበት ምድር ስም
በሸለቆ ያለ አበባ
ሴቲቱ ራሷን በውብ አበቦች በሚታወቅ ቦታ ካሉ አበቦች እንደ አንዱ አድርጋ ትናገራለች
የተዋበ አበባ
ብዙ ውሃ ባለበት ስፍራ የሚበቅል መልካም መዓዛ ያለው አበባ። ይህንን በመኃልይ 2፡1-2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሸለቆዎች
በተራሮች መካከል እና በውሃ አቅራቢያ የሚገኝ ለጥ ያለ ስፍራ
ወጣት ሴቶች... በእሾህ መሀከል እንዳለ ውብ አበባ
አበባ እሾህ ካለው ቁጥቋጦ የበለጠ ያማረ ነው። ሰውየው ሴቲቱ ከሌሎች ሴቶች ሁሉ ያማረች እንደሆነች ያስባል።
የኔ ፍቅር
“የምወድሽ አንቺ”። ይህንን በመኃልይ 1፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ወጣት ሴቶች
“ሌሎች ወጣት ሴቶች”
Song of Solomon 2:3
ወጣት ወንዶች ... እንደ እንኮይ ዛፍ
ሰዎች የእንኮይ ዛፍ ፍሬን ይወዳሉ፣ ነገር ግን ሌሎች የዱር ዛፎች ፍሬ አያፈሩም። ሴቲቱ ከሌሎች ወንዶች ይልቅ ከሰውየው ጋር መሆን ያስደስታታል።
የእንኮይ ዛፍ
ቢጫ እና በጣም ጣፋጭ ፍሬ የሚያፈራ ዛፍ ነው። አንባቢዎችህ ይህ ምን እንደሆነ የማያውቁ ከሆኑ በሌላ የፍራፍሬ ዛፍ ስም ወይም “የፍራፍሬ ዛፍ” በሚል ጥቅል ቃል ልትተካው ትችላለህ።
ጫካው
እዚህ ጋ፣ የዕብራይስጡ ቃል ሰዎች የማይጠቀሙበት ፥ ዛፎች የሚበቅሉበት ስፍራ ይለዋል።
ወዳጄ
ይህ ሀረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ “የኔ አፍቃሪ” ብትለው በይበልጥ የተለመደ ይሆን ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የኔ አፍቃሪ”
ከጥላው በታች በታላቅ ደስታ አቀመጣለሁ
ሴቲቱ ከሰውየው አጠገብ በመሆኗ ሀሴት እና መፅናናትን አግኝታለች።
ፍሬው ለምርጫዬ ጣፋጭ ነው
ሴቲቱ ጣፋጭ ፍሬ በመመገብና በሰውየው አጠገብ በመሆን ትደሰታች።
የወይን ቤት
ትርጉሞቹ 1) ንጉሱ ለብዙ ሰዎች ወይንና ብዙ ምግብ የሚያቀርብበትን ሰፊ ክፍል ወይም 2) ሴቲቱ እና ሰውየው ብቻቸውን ሊሆኑ የሚችሉበት በወይን ተክል ውስጥ ያለ ትንሽ ዳስ
በኔ ላይ ያለው አላማው ፍቅር ነበር
በኔ ላይ ያለው አላማው ፍቅር ነበር ትርጉሞቹ 1) ሰንደቅ አላማ ለወታደራዊ አጀብ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ወታደራዊ አጀቡ፣ ንጉሱ ብዙ ሰዎችን ወደሚመግብበት ትልቅ ክፍል ውስጥ ለመግባት የፈራችውን ሴት የሚያበረታ የሰውየውን ፍቅር የሚወክል ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ነገር ግን የፍቅር ጥበቃው መራኝ፣ ብርታትንም ሰጠኝ” ወይም 2) ሰውየው ክእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም መፈለጉን ሴቲቱ ከአስተያየቱ ተረዳች። ኢ.ት፡ “በፍቅር ዐይን አየኝ” ወይም “ባየኝ ጊዜ ከእኔ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም መፈለጉን አውቄአለሁ” ወይም 3) የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸሙ። ኢ.ት፡ “በፍቅር ሸፈነኝ”
Song of Solomon 2:5
አበረታቱኝ
“ብርታቴን መልሱልኝ” ወይም “ኃይል ስጡኝ”
በዘቢብ ጥፍጥፍ
“የዘቢብ ጥፍጥፍ እንድበላ በመስጠት” የዘቢብ ጥፍጥፍ ከደረቁ የወይን ፍሬዎች ተጠፍጥፈው የሚሰሩ ናቸው።
በእንኮይ አድሱኝ
“እንኮይ በመስጠት ደግፉኝ” ወይም “እንኮይ በመስጠት እርዱኝ”
በፍቅር ደክሜአለሁና
ፍቅር የህመም አይነት የሆነ ያህል ከፍቅሯ ብርታት የተነሳ ድካም እንደተሰማት ሴቲቱ ትናገራለች። ኢ.ት፡ “ፍቅሬ ብርቱ በመሆኑ ምክንያት ከስቻለሁ”
ግራ እጅ ... ቀኝ እጅ
“ግራ ክንድ ... ቀኝ ክንድ”
እቀፈኝ
“ይይዘኛል”
Song of Solomon 2:7
የኢየሩሳሌም ሴት ልጆች

“የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች”። እነዚህ ወጣት ሴቶች አብረዋት ስላልነበሩ ሊሰሟት አይችሉም፣ እርሷ ግን አብረዋት እንዳሉና እንደሚሰሟት አድርጋ ትናገራለች።
በሚዳቆዎቹና በሜዳ ባሉ አጋዘኖች
የኢየሩሳሌም ሴቶች ሊሰሟት ባይችሉም፣ ሴቲቱ እንደሚሰሟት አድርጋ ቃላቸውን ቢያፈርሱ ሚዳቋዎቹ እና አጋዘኖቹ እንደሚቀጧቸው ትናገራለች።
ሚዳቆዎቹ
እነዚህ አጋዘን የሚመስሉና በፍጥነት የሚንቀሳቀሱ እንስሶች ናቸው።
ሴት አጋዘን
ሴት አጋዘን
የሜዳ
“በገጠር የሚኖሩ”። ይህ ታርሶ የማያውቅ ምድር ነው።
እርሷ እስክትፈልግ ድረስ ፍቅርን አትቀስቅሱ ወይም አታነሣሡ
እዚህ ጋ “ፍቅር” መቀስቀስ እንደማይፈልግ የተኛ ሰው ተደርጎ ተነግሮለታል። ሰውየው እና ሴቲቱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽመው እስኪጨርሱ ድረስ መታወክ እንደማይፈልጉ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።
አትቀስቅሱት ወይም አታነሣሡት
ቋንቋህ ሰዎችን ከእንቅልፍ ለማስነሣት አንድ ቃል ብቻ ካለው ሁለቱን ቃላት ማዋሀድ ትችላለህ። ኢ.ት፡ “አታንቁት”
Song of Solomon 2:8
አጠቃላይ መረጃ፡
የመጽሐፉ ሁለተኛው ክፍል እዚህ ይጀምራል።
አጠቃላይ መረጃ
ሴቲቱ የምታወራው ለራሷ ወይም ለኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች መሆኑ ግልፅ አይደለም።
አድምጡ
ትርጓሜዎች ሊሆኑ የሚችሉት 1) “ልናገር ያለሁትን በጥንቃቄ አድምጡ”። በራስህ ቋንቋ አድማጮች በጥሞና እንዲያደምጡ የሚናገር ቃል ልትጠቀም ትችላለህ፣ ወይም 2) “ሲመጣ መስማት እንድትችሉ አድምጡ”
ወዳጄ
ወዳጄ ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ አገላፅ “የኔ አፍቃሪ” ብትለው በይበልጥ የተለመደ ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።
እየተወረወረ … እየዘለለ … እያየ… አተኩሮ እየተመለከተ
ሴቲቱ ሰውየው መምጣቱን ስታይ በመደነቅ የሚያደርገውን በተቻላት መጠን በጥቂት ቃላት ትገልፃለች። የአንተ ቋንቋ፣ ተናጋሪው ሊሆን ስላለ ነገር የሚደነቅበትን ስሜት የሚያሳይበት የተለየ አገላለፅ ይኖረው ይሆናል።
በተራሮች ላይ እየተወረወረ፣ በኮረብታዎች ላይ እየዘለለ
“በተራሮች ላይ እየተወረወረ፣ በኮረብቶች ላይ በፍጥነት እየሮጠ”። ሰውየው እንደ “ሚዳቋ ወይም ወንድ አጋዘን” በአስቸጋሪ መሬት ላይ በፍጥነት ወደ እርሷ እንደሚመጣ ሴቲቱ ትናገራለች (ቁ. 9)።
እንደ ሚዳቋ ወይም የአጋዘን ግልገል
ሚዳቋ እና የአጋዘን ግልገል አስቸጋሪ መሬት ላይ በፍጥነት መንቀሳቀስ ይችላሉ። ሰውየው ከእርሷ ጋር ለመሆን በተቻለው ፍጥነት እንደሚመጣ ሴቲቱ ታስባለች። በቋንቋህ ሰዎች ፈጣን ነው ብለው የሚያስቡትን እንስሳ ተጠቅመህ መተርጎም ትችላለህ።
ሚዳቋ
ይህ አጋዘን የሚመስልና በፍጥነት የሚንቀሳቀስ እንስሳ ነው። ”አጋዘኖች” የሚለውን በመኃልይ 2:7 እንዳለው በነጠላ ተርጉመው።
የአጋዘን ግልገል
“ተባእት የአጋዘን ግልገል”
ተመልከቺ
“በጥንቃቄ አድምጪ” ወይም “ልናገር ያለሁት ጠቃሚ ነገር ነው”። አድማጭ በጥሞና እንዲያዳምጥ የሚያሳስብ ቃል በራስህ ቋንቋ መጠቀም ትችላለህ።
ከግምባችን በስተጀርባ
“በግንባችን በሌላኛው ጎን”። ሴቲቱ ቤት ውስጥ ስትሆን ሰውየው ከቤት ውጪ ነው።
የኛ ግንብ
“የኛ” የሚለው ቃል ሴቲቱንና አብረዋት በቤት ያሉ ሌሎች ሰዎችን ያመለክታል።

ሴቲቱ ከራሷ ጋር የምታወራ ከሆነ አካታች ነው፣ ነገር ግን ለኢየሩሳሌም ሴት ልጆች የምትናገር ከሆነ፣ ራሷንና ጓደኞቿን ወይም ራሷን በብዙ ቁጥር የምታመለክት ከሆነ ፥ እንደ “ደስ ተሰኝተናል” … “ሐሴት እናደርጋለን” … “እንደሰት” የማያካትት ይሆናል።
በመስኮት አሻግሮ እየተመለከተ
“በመስኮቱ በኩል አተኩሮ ይመለከታል”
በርብራቡ መካከል አጮልቆ እየተመለከተ
“በርብራቡ መካከል ሰረቅ አድርጎ ያያል ”
ርብራብ
ረዘም ረዘም ያሉ እንጨቶችን አንድ ላይ በመሰካካት የተሰራ የመስኮት ወይም ሌላ በር መከለያ ነው። ርብራብ ሰዎች አጮልቀው ማየት የሚችሉበት ክፍተት አለው።
Song of Solomon 2:10
ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ “የኔ ፍቅር” ብትለው በይበልጥ የተለመደው አገላፅ ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።
የኔ ፍቅር፣ ተነሺ
“የኔ ፍቅር ከአልጋሽ ተነሺ”
የኔ ፍቅር
“አንቺ፣ የምወድሽ”። ይህንን በመኃልይ 1:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ተመልከቺ
“በጥሞና አድምጪ” ወይም “ልናገር ያለሁት ጠቃሚ ነገር ነው”። በቋንቋህ አድማጭ በጥሞና እንዲያደምጥ የሚያሳስበውን ቃል መጠቀም ትችላለህ።
ክረምቱ አልፏል፣ ዝናቡም አልፎ ሄዷል
በክረምት ከቤት ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም እጅግ ቀዝቃዛና እርጥበታማ ነው፣ ነገር ግን የቅዝቃዜውና የእርጥበቱ ጊዜ አልፏል።
ክረምቱ አልፏል
ክረምት እፅዋት የማያድጉበትና ሰዎች ቤታቸው ውስጥ ለመቆየት የሚመርጡበት የአመቱ ቀዝቃዛ ወቅት ነው። በዓመቱ ውስጥ ስላለው ስለዚያ ወቅት በቋንቋህ መጠቀም ትችላለህ።
ዝናቡ አልፎ ሄዷል
በእስራኤል ዝናብ የሚዘንበው በክረምት ብቻ ነው። እዚህ ጋ የተገለፀው የሚያረሰርስ የሙቀት ወቅት ዝናብ ሳይሆን ደስ የማይልና ቀዝቃዛ ዝናብ ነው።
Song of Solomon 2:12
አበቦቹ ብቅ ብለዋል
“ሰዎች አበቦቹን ማየት ይችላሉ”
በምድሪቱ ላይ
“በዚህ ምድር ሁሉ ላይ”
ለመከርከም
ለውበት ወይም ብዙ ፍሬ እንዲያፈራ የተክል ቅርንጫፎችን መግረዝ
የወፎች ዝማሬ
“ወፎች እንዲዘምሩ”
የእርግቦቹ ድምፅ ይሰማል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች የእርግቦቹን ድምፅ መስማት ይችላሉ” ወይም “እርግቦቹ ድምፃቸውን እያሰሙ ነው”
የበለስ ዛፉቱ አረንጓዴ በለሶቿን ታበስላለች
ዛፊቱ ፍሬዋን በራሷ እንዲበስሉ እንዳደረገቻቸው ተነግሮላታል። ይህ የጋራ ነጠላ ሲሆን በብዙ ቁጥር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “በዛፉ ላይ ያሉት በለሶች በስለዋል”
ወይኖቹ እያበቡ ናቸው
“ወይኖቹ እያበቡ ነው” ወይም “ወይኖቹ አበባ አላቸው”
ይሰጣሉ
“እነርሱ” የሚለው ቃል በወይኑ ላይ ሆነው ያበቡትን ያመለክታል።
መአዛቸው
“ጣፋጭ ሽታቸው”
የኔ ፍቅር
“አንቺ የምወድሽ”፤ ይህንን በመኃልይ 1:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Song of Solomon 2:14
አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው እየተናገረ ነው።
እርግቤ
እስራኤላውያን እርግቦችን አስደሳች ድምፅ ያላቸው ውብ ወፎች እንደሆኑ ያስቡ ነበር። ሰውየው የሴቲቱ ፊት እና ድምፅ ያማረ እንደሆነ ያስባል። አንዲትን ሴት “እርግብ” ብሎ መጥራት ቅር የሚያሰኛት ከሆነ ዘይቤአዊውን አነጋገር ልትተወው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “የእኔ ውብ ሴት”
ንቃቃቶቹ
ሰዎችን ለመሸሸግ የሚያስችል ስፋት ያለው በተራራ አለቶች ጎን ያለ ስንጥቅ
የተራራው ቋጥኞች
“በተራሮች ጎን ያሉ ቀጥ ያሉ አለቶች”
ፊትሽ
አንዳንድ ትርጉሞች ይህንን “ገፅታሽ” ወይም “ቅርፅሽ” ወይም “አንቺ የምትመስይው” ብለው ይተረጉሙታል።
Song of Solomon 2:15
ያዙ
ይህ ሴቲቱ ከአንድ በላይ ለሆኑ ወንዶች የምትናገር ይመስል ብዙ ቁጥር ነው፤ ነገር ግን አብዛኛዎቹ ትርጉሞች ለሰውየው እንደምትናገር አድርገው ይተረጉሙታል፣ ስለዚህ በነጠላ ልትተረጉመው ትችላለህ።
ቀበሮዎቹ
እነዚህ እንስሶች ትናንሽ ውሾችን የሚመስሉ ሲሆኑ በፍቅር ስነ-ግጥም ውስጥ ብዙ ጊዜ ወጣት ሴትን ሊያባልጉ የሚችሉ ጉጉ ወጣት ወንዶችን እንዲወክል ጥቅም ላይ ውለዋል።
የኛ የወይን ቦታ ... ለኛ
“እኛ” እና “ለኛ” የሚሉት ቃላት ሊሆኑ የሚችሉት 1) በመኃልይ 1፡4 እንዳለው ሌላውን ሳይሆን ሴቲቱን ራሷን የሚያመለክት ወይም 2) ሴቲቱንና ሰውየውን የሚያካትት ወይም 3) ሌሎችን ሳያካትት ሴቲቱንና የተቀሩትን ቤተሰቦቿን የሚያመለክት ይሆናል።
ቀበሮዎች
ሌላው ትርጉም ሊሆን የሚችለው “የጫካ ውሻ” ነው። የጫካ ውሻ ረጃጅም እግሮች ያሉት ቀጭን የውሻ አይነት ነው።
የሚያበላሹ ትናንሽ ቀበሮዎች
ቀበሮዎች ጉድጓድ በመቆፈርና የወይን ፍሮዎችን በመብላት የወይን ተክሎችን ያበላሻሉ። ይህ ወጣት ሴቶችን የሚያባልጉ ወጣት ወንዶችን የሚገልፅ ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል።
በማበብ ላይ
ይህ የሚያመለክተው የወይኑ ቦታ ጤናማ እንደሆነና ወይኑም ማፍራቱን ነገር ግን ለመበላት ዝግጁ አለመሆናቸውን ያመለክታል። ይህ ለማግባትና ልጆችን ለመውለድ የደረሰችን ወጣት ሴት የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል።
Song of Solomon 2:16
ወዳጄ የእኔ ነው
“ውዴ የኔ ነው”
ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ “የኔ አፍቃሪ” ብትለው በይበልጥ የተለመደ ይሆን ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።
እኔ የእርሱ ነኝ
“እኔ የእርሱ ነኝ”
ያሰማራል
“ይመግባል” ወይም “ሳር ይበላል”። ሴቲቱ ሰውየውን በአበቦች መሐከል እፅዋትን እንደሚመገብ “ሚዳቋ ወይም የአጋዘን ግልገል” አድርጋ ትናገራለች። መሰማራት ምናልባት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን የሚገልፅ ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል።
የተዋቡ አበቦች
ብዙ ውሃ ባለበት ቦታ የሚበቅሉ ባለጣፋጭ ሽታ አበቦች። በመኃልይ 2፡1 እንዳለው “ውብ አበቦች” ብለህ በብዙ ቁጥር ተርጉመው።
ንጋት
ፀሐይ የምትወጣበት የቀኑ ክፍል
ጥላዎቹ ሸሽተዋል
ሴቲቱ ጥላዎቹ ከፀሐይ ብርሐን እየሸሹ እንዳሉ አድርጋ ትገልፃቸዋለች። ኢ.ት፡ “ጥላዎቹ ጠፍተዋል”
እንደ ሚዳቋ ወይም የአጋዘን ግልገል
ይህንን በመኃልይ 2፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሚዳቋ
እነዚህ እንስሶች አጋዘን የሚመስልና በፍጥነት የሚንቀሳቀስ እንስሳ ነው። በመኃልይ 2፡7 ላይ እንዳለው “ሚዳቋዎች” በነጠላ ቁጥር ተርጉመው።
ወንድ አጋዘን
ጎልማሳ ወንድ አጋዘን
ወጣ ገባ ያለባቸው ተራሮች
“አለታማ ተራሮች” ወይም “ አስቸጋሪ ተራሮች”

---

Chapter 3
Song of Solomon 3:1
ስናፍቀው ነበር ... ላገኘው አልቻልኩም
“ከእርሱ ጋር ለመሆን ታላቅ ምኞት ነበረኝ ... የምወደው፣ ነገር ግን እርሱ በዚያ አልነበረም”
ነፍሴ የምትወደው እርሱ
ነፍስ የሰውን ሁለንተና የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እዚህ ጋ “የእኔ ፍቅር” ከሚለው ይልቅ ሴቲቱ ለሰውየው ስላላት ፍቅር ጠንከር ባለ አገላለጽ ያመለክታል።
በከተማው መሐል እሄዳለሁ
“በከተማው መሐል እዘዋወራለሁ”
በጎዳናዎቹና በአደባባዮቹ
“አደባባዮች” የሚለው ቃል ጎዳናዎች ወይም መንገዶች የሚገናኙበትን መሐል ከተማ ያመለክታል። አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ዕቃዎቻቸውን የሚሸጡበት አካባቢና ሰዎች ለመነጋገር የሚገናኙበት ስፍራ ነው።
እፈልገዋለሁ
“ላገኘው”
Song of Solomon 3:3
ጠባቂዎች
በምሽት የሕዝቡን ደኅንነት ለመጠበቅ በከተማይቱ የጥበቃ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች
ከተማይቱን ለመጠበቅ በሚዞሩበት ጊዜ
“በከተማይቱ ዙሪያ በቅጥሩ ላይ ይመላለሱ የነበሩ”
ነፍሴ የምትወደውን እርሱን
ነፍስ የሰውን ሁለንተና የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እዚህ ጋ “የእኔ ፍቅር” ከሚለው ይልቅ ሴቲቱ ለሰውየው ስላላት ፍቅር ጠንከር ባለ አገላለጽ ያመለክታል። መኃልይ 3፡1ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የአልጋ ክፍል
“የመኝታ ክፍል”
የፀነሰችኝ
ይህ ስለ እናቷ የምትናገረው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።
Song of Solomon 3:5
X
ይህንን ቁጥር በመኃልይ 2፡7 ባለው መልክ ተርጉመው
የኢየሩሳሌም ሴት ልጆች
“የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች”፣ እነዚህ ወጣት ሴቶች በዚያ ስላልነበሩ ሊሰሟት አይችሉም፣ ነገር ግን ሴቲቱ እንዳሉና ሊሰሟት እንደሚችሉ ቆጥራ ትናገራለች።
በሜዳ ባሉ ሚዳቋዎችና በሴት አጋዘኖች
ምንም እንኳን የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች በዚያ ኖረው የሚሰሟት ባይሆኑም ቃል ኪዳናቸውን ስለማፍረሳቸው ሚዳቋዎችና ሴት አጋዘኖች እንደሚቀጧቸው ሴቲቱ ትነግራቸዋለች።
ሚዳቋዎች
አጋዘን የሚመስሉና በፍጥነት የሚንቀሳቀሱ እንስሳት
ሴት አጋዘን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሴት አጋዘን
በሜዳ ያሉ
“በገጠራማ አካባቢ የሚኖሩ”፣ ይህ ያልታረሰውን መሬት ያመለክታል።
ደስ እስክታሰኝ ድረስ ፍቅርን አትቀስቅሱ ወይም አታነሣሡ
እዚህ ጋ “ፍቅር” በተኛና ሊቀሰቅሱት በማይፈልግ ሰው ተመስሎ ተነግሮለታል። ይህ የአነጋገር ዘይቤ በግብረ ሥጋ ግንኙነታቸው እስኪረኩ ድረስ መታወክ የማይፈልጉትን ወንዱንና ሴቲቱን ይወክላል። ኢ.ት፡ “በግብረ ሥጋ ግንኙነታችን እስክንረካ ድረስ አያውኩንም”።
አትቀስቅሱት ወይም አታነሣሡት
በቋንቋህ ሰዎችን ከእንቅልፋቸው ለመቀሰቀስ የምትጠቀመው አንድ ቃል ብቻ ከሆነ የእንግሊዝኛ ቃላቱን ልታጣምራቸው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “አትቀስቅሱት”።
Song of Solomon 3:6
አጠቃላይ መረጃ
የመጽሐፉ ሦስተኛው ክፍል እዚህ ጋ ይጀምራል። ክፍሉ የሰለሞንን አልጋ ከምድረ በዳው ወደ ኢየሩሳሌም ተሸክመው በሚሄዱ ስልሳ ሰዎች ገለጻ ይጀምራል።
ያ ከምድረ በዳው ወጥቶ የሚመጣው ምንድነው?
በቡድን የሆኑ ሰዎች ከምድረ በዳው ወደ ኢየሩሳሌም ይጓዛሉ። በዮርዳኖስ ሸለቆ ያለው ምድረ በዳ ዝቅ ያለ ስለሆነና ኢየሩሳሌም በተራሮች ላይ ስለምትገኝ ወደ እርሷ ለመድረስ ወደ ላይ መውጣት አለባቸው።
ያ ምንድነው?
በርካታ ትርጉሞች ይህንን “ያ ማነው” ብለው ይተረጉሙታል
እንደ ጢስ ዐምድ
ሕዝቡ በሚጓዙበት ጊዜ ብዙ አቧራ ወደ አየር ያስነሡ ስለነበር ከሩቅ ጢስ መስሎ ይታይ ነበር።
በከርቤና በዕጣን ሽቱ
“በከርቤና በዕጣን ጣፋጭ ሽታ”
ነጋዴዎች ከሚሸጧቸው ቅባቶች ሁሉ ጋር
“ለሽቱነት ተቀምመዋል” የሚሉትን ቃላት ቀደም ካለው ሐረግ ይገነዘቧቸዋል። እዚህ ጋ ሊደገሙ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “ነጋዴዎች በሚሸጧቸው ቅባቶች ሁሉ ለሽቱነት ተቀምመዋል” ወይም “ነጋዴዎች ከሚሸጧቸው ጣፋጭ ሽታ ካላቸው ቅባቶች ሁሉ ጋር”።
ቅባቶች
ጠጣር የሆነውን አንዳች ነገር በመፍጨት የሚሠራ ደቃቅ ብናኝ
ተመልከቱ
“በጥንቃቄ አድምጡ” ወይም “የምነግራችሁ ጠቃሚ የሆነ ጉዳይ ነው”። በቋንቋህ አድማጭህ በጥንቃቄ ሊሰማህ የሚያስችለውን ቃል መጠቀም ትችላለህ። አሁን ተናጋሪው በቁጥር 6 ላይ ላለው ጥያቄ መልስ ያገኛል።
አልጋ ነው
ይህ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተሸክመው ሊወስዱት የሚችሉትን አልጋ ከነአልጋ ልብሱ ያመለክታል።
ስልሳ ጦረኞች ከብበውታል፣ ስልሳ የእስራኤል ወታደሮች
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት እነዚያኑ ስልሳ ሰዎች ነው። ሁለተኛው ሐረግ “ጦረኞች” የተባሉት “የእስራኤል ወታደሮች” መሆናቸውን ያብራራል።
ጦረኞች
የሚዋጉ ሰዎች
Song of Solomon 3:8
አጠቃላይ መረጃ
በመኃልይ 3፡6 የሰለሞንን አልጋ ከምድረ በዳው ወደ ኢየሩሳሌም ስለተሸከሙት ስልሳ ሰዎች የተጀመረው ገለጻ ይቀጥላል።
አገናኝ መግለጫ
የአልጋው ገለጻ ራሱ ቁጥር 9 ላይ ይጀምራል። በቋንቋህ ዳራዊ መረጃን የሚያሳይ ቃላት ልትጠቀም ትችላለህ።
ጦርነትን ተለማምደዋል
“ጦርነቶችን በሚገባ መዋጋት ይችላሉ”
በእነርሱ ላይ ታጥቋል “እነርሱን መዋጋት ይችል ዘንድ”
የሌሊት ሽብር
የነገር ስም የሆነው “ሽብር” ሌሎችን በማጥቃት የሚያስፈራሩ ክፉ ሰዎችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በሌሊት ሌሎችን የሚያጠቁ ክፉ ሰዎች”።
ከነተቀማጩ ሊሸከሙት የሚያስችል ወንበር
ይህ ታላላቅ ሰዎች የሚቀመጡበት ወንበር ወይም የሚጋደሙበት መከዳ ነው። ሰዎች ሊሸከሙት በሚያስችላቸው ረጃጅም መሸከሚያዎች ላይ ያንጠለጥሉታል።
Song of Solomon 3:10
አገናኝ መግለጫ
ስለ አልጋው በመኃልይ 3፡9 የጀመረው ገለጻ ይቀጥላል።
የማዕዘን ቋሚ
“የ” የሚያመለክተው የንጉሥ ሰለሞንን ከነተቀማጩ ሊሸከሙት የሚያስችለውን ወንበር ነው።
መደገፊያዎች
“መደገፊያዎች” የሚለው ቃል በወንበሩ ዙሪያ ያለውን የጨርቁን ድንኳን በመደገፍ የሚቆሙትን ከብር ወይም ከእንጨት ተሠርተው በብር የሚለበጡትን ቋሚዎች ያመለክታል።
ውስጣዊ ገጽታው
“ውስጠኛው ክፍሉ”
በፍቅር
ተስማሚ ትርጉሞቹ 1) “በፍቅር” የሚለው ቃል ሴቶቹ ለሰለሞን ያላቸውን ፍቅር ለማሳየት ከነተቀማጩ የሚሸከሙበትን ወንበር በልዩ ሁኔታ ማስዋባቸውን ያመለክታል ወይም 2) “በለፋ ቆዳ” የሚሉት ናቸው።
የጽዮን ሴቶች ልጆች
“እናንተ በጽዮን የምትኖሩ ወጣት ሴቶች”
ንጉሥ ሰለሞንን አተኩራችሁ ተመልከቱ
“ንጉሥ ሰለሞንን እዩት”፣ “አተኩሮ መመልከት” የሚለው ሐረግ አንድን ሰው ወይም አንድን ነገር በብርቱ ስሜት ለረጅም ጊዜ ማየትን ያመለክታል።
አክሊሉን ደፍቶ
“አክሊሉን ለብሶ”
በልቡ የደስታ ቀን
“ልብ” የሚለው ቃል የሰውን ሁለንተና የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የእውነት ደስ በተሰኘበት ቀን” ወይም “በሕይወቱ ደስ የተሰኘበት ቀን”።

---

Chapter 4
Song of Solomon 4:1
አይኖችሽ እርግቦች ናቸው
ሊሆኑ ከሚችሉት አንዱ፣ ሰውየው የሴቲቱ ነጭ የአይን ኳሶች ወይም የአይኗ ቅርፅ እንደ እርግብ ቅርፅ መሆናቸውን እየተናገረ ይሆናል። ሌላው ሊሆን የሚችለው፣ እስራኤላውያን እርግቦች ገሮችና ለስላሳ ወፎች እንደሆኑ ያስቡ ነበር፣ ሰውየውም የሴቲቱ አይኖች ውብ እንደሆኑ ያስባል ምክንያቱም ሴቲቱ እርሱን የምታይበት አስተያየት ገር እንደሆነች እንዲያስብ አድርጎታል።
የኔ ፍቅር
“አንቺ የምወድሽ”፤ ይህንን በመኃልይ 1፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ፀጉርሽ ከገለዓድ ተራራ የሚወርድ የፍየል መንጋ ይመስላል
በእስራኤል ያሉ ፍየሎች ብዙ ጊዜ ቀለማቸው ጥቁር ነበር። የሴቲቱም ፀጉር ጥቁር ሳይሆን አይቀርም። ፍየሎቹ ጥቁር እንደነበሩ መግለፅ ያስፈልግህ ይሆናል ወይም አንባቢው ሊረዳው የሚችል ጥቁረት እና ውበትን የሚያመለክት ሌላ የንፅፅር ቃል መጠቀም ትችላለህ። ሰዎች የገለዓድ ተራራ ለምና ውብ እንደሆነ ያስቡ ነበር። ተናጋሪው ሴቲቱ ውብ እንደሆነችና የልጆቹ እናት ለመሆን ዝግጁ እንደሆነች ቆጥሯል። ከፍየሎቹ ጋር ያለውን ንፅፅር ካስወገድከው የተራራውንም ንፅፅር ማስወገድ ይኖርብሃል። ኢ.ት፡ “ጸጉርሽ ከለም መሬት በላይ እንዳለው የጥቁር ደመና ማዕበል ነው”።
Song of Solomon 4:2
ጥርሶችሽ በቅርቡ የተሸለቱ የሴት በጎች መንጋን ይመስላሉ
በጎች ከተሸለቱ በኋላ ይታጠባሉ፤ ቆዳቸውም በጣም ነጭ ሆኖ ይታያል። የሴቲቱም ጥርሶች ነጫጭ ናቸው።
በቅርቡ የተሸለቱ የሴት በጎች መንጋ
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች ሱፋቸውን የሸለቷቸውን የሴት በግ መንጋ”

ከመታጠቢያ ስፍራ የሚመጡ
ሴቶቹ በጎች ከውሃው ውስጥ ወጥተው እየመጡ ነው። ኢ.ት፡ “ሰዎች ካጠቧቸው በኋላ ከውሃው ወጥተው እየመጡ ነው”
እያንዳንዱ መንታ አለው
በጎች አብዛኛውን ጊዜ በአንዴ ሁለት ግልገሎችን ይወልዳሉ። እነዚህ መንታዎች ብዙውን ጊዜ ይመሳሰላሉ። እያንዳንዱ የሴቲቱ ጥርስ በሌላ ጎን ካለው ጋር እኩል ነው።
ከመካከላቸው አንዱም አልጎደለም
እያንዳንዱ የሴቲቱ ጥርስ በሌላ ጎን ካለው ጋር እኩል ነው። ከጥርሶቿ አንድም የወለቀ የለም።
ሐዘንተኛ
የቅርብ ሰው የሞተበት
Song of Solomon 4:3
አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ሴቲቱን ማድነቁን ይቀጥላል
እንደ ደማቅ ቀይ ክር
ደማቅ ቀይ ውብ ቀለም ነው፤ ደማቅ ቀይ ክር ደግሞ በጣም ውድ ነበር። የሴቲቱ ከንፈሮች ቀይ ነበሩ። ኢ.ት፡ “እንደ ደማቅ ቀይ ክር ብስል ቀይ ናቸው” ወይም “ቀይና በጣም ውቦች ናቸው”።
ደማቅ ቀይ
ከደም ቀለም ጋር የሚመሳሰል ደማቅ ቀይ ቀለም
አስደሳች ነው
“ያማረ ነው”
እንደ ሮማን ክፋይ ናቸው
ሮማኖች ደማቅ ቀይ፣ ክብ እና ለስላሳ ናቸው። ሰውየው የሴቲቱ ጉንጮች ውቦችና እርሷም ጤነኛ መሆኗን እንደሚያሳዩ ያስባል። ኢ.ት፡ “እንደ ሁለት የሮማን ክፋዮች ቀይና ክብ ናቸው” ወይም “ቀይ፣ ሙሉና ጤናማ ናቸው”
ከአይነርግብሽ በስተጀርባ
ይህንን በመኃልይ 4፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Song of Solomon 4:4
አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ሴቲቱን ማድነቁን ቀጥሏል።
አንገትሽ እንደ ዳዊት ግምብ ነው
ይህ እውነተኛ ግምብ ስለመሆኑ የሚያውቅ የለም። ግምብ ማለት ረጅምና ቀጭን ሕንጻ ሲሆን ዳዊት የገነባው መባሉ ውብ መሆኑን ያሳያል። ሰውየው የሴቲቱ አንገት ረጅም፤ ቀጭንና ውብ እንደሆነ ያስባል። ኢ.ት፡ “አንገትሽ እንደ ዳዊት ግምብ ረጅምና ያማረ ነው”
የዳዊት
“ዳዊት የገነባው”
በድንጋይ ድርድር የተገነቡ
ሴቶች ሙሉ አንገታቸውን የሚሸፍን የአንገት ሀብል ከጌጣጌጥ ድርድር ጋር ነበራቸው። ሰውየው እነዚህን የጌጣጌጥ ድርድሮች በግምቡ ላይ ካሉት የድንጋይ ድርድሮች ጋር ያነጻጽራቸዋል።
ከሺህ ጋሻ ጋር
ሰውየው በሴቲቱ የአንገት ሀብል ላይ ያሉትን ጌጣጌጦች በግምቡ ላይ ከተንጠለጠሉት ጋሻዎች ጋር ያነጻጽራቸዋል። የአንገት ሀብሏ አንገቷ ላይ ብዙ ዙር ዞሮ ይሆናል።
ሺህ ጋሻ
“1,000” ጋሻዎች
ሁሉም የወታደር ጋሻዎች
“የብርቱ ጦረኞች የሆኑ ጋሻዎች ሁሉ”
ሁለት ጡቶች
“ሁለት” የሚለው ቃል አላስፈላጊና ያለቦታው የገባ መስሎ ከታየህ ልታስወግደው ትችላለህ።
እንደ ሁለት የአጋዘን ግልገሎች፤ የአጋዘን መንታዎች
ሰውየው የሴቲቱ ጡቶች ተመሳሳይ፤ ለስላሳና ምናልባትም ትንንሽ እንደሆኑ ያመለክታል።
መንታዎች
ሁለት ልጆችን በአንድ ጊዜ የወለደች እናት፤ ልጆቹ መንታ ይባላሉ።
ሚዳቋ
አጋዘን የሚመስልና በፍጥነት የሚንቀሳቀስ እንስሳ ነው። ”አጋዘኖች” በመኃልይ 2፡7 እንዳለው በነጠላ ቁጥር ተርጉመው።
በተዋቡ አበቦች መካከል እየጋጠ
“በተዋቡ አበቦች መካከል እየተመገበ”፤ ሰውየው “በተዋቡ አበቦች መካከል እየጋጠ” የሚለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም፤ እነዚህ ቃላት ምንን እንደሚያመለክቱ ግልፅ አይደለም። ቃል በቃል ቢተረጎሙ የተሻለ ይሆናል።
የተዋቡ አበቦች
ብዙ ውሃ ባለበት ስፍራ የሚበቅሉ መልካም መዓዛ ያላቸው አበቦች። በመኃልይ 2፡1 ላይ እንዳለው “አበባ” የሚለውን በብዙ ቁጥር ተርጉመው።
Song of Solomon 4:6
አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ሴቲቱን ማድነቁን ይቀጥላል።
ንጋት እስኪሆንና ጥላዎቹ እስኪሸሹ ድረስ
በመኃልይ 2፡17 ያለውን ስንኝ እንደተረጎምከው በተመሳሳይ ቃላት ተርጉማቸው።
ወደ ከርቤ ተራራና ወደ ዕጣን ኮረብታ እሄዳለው
የ”ከርቤ ተራራ” እና “የዕጣን ኮረብታ” የሴቲቱን ጡቶች የሚገልፁ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። ኢ.ት፡ “የከርቤና የዕጣን ሽታ ያለባቸውን ተራሮች ወደሚመስሉት ጡቶችሽ ተጠግቼ እተኛለሁ” ወይም “ጣፋጭ ሽታ ወዳላቸው ጡቶችሽ ተጠግቼ እተኛለሁ” ወይም “ጣፋጭ ሽታ ወደሚሸቱት ተራሮች እሄዳለሁ”
የከርቤ ተራራ
“ከከርቤ የተሠራ ተራራ” ወይም “ከርቤ የሚበቅልበት ተራራ”
የእጣን ኮረብታ
“ከሚጨሰው የእጣን ጭስ የተነሳ በአየሩ ውስጥ የጭስ ደመና ያለበት ኮረብታ”
በሁሉም መልኩ ውብ ነሽ
“ሁሉም ክፍልሽ ውብ ነው” ወይም “ሁለመናሽ ውብ ነው”
የኔ ፍቅር
“አንቺ የምወድሽ”፣ ይህንን በመኃልይ 1፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ምንም እንከን የለብሽም
“ምንም የሚነቀፍ ነገር የለብሽም”
Song of Solomon 4:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ለሴቲቱ መናገሩን ይቀጥላል። እርሱ ሰው በማይኖርበት፣ አደገኛና እንግዳ በሆነ ቦታ ያሉ ይመስል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ነጻ ያለመሆናቸውን ይናገራል።
ከሊባኖስ
“ከሊባኖስ ወዲያ”
ሙሽራዬ
ይህ የዕብራይስጡ ቃል ያገባችን ሴት ወይም አንድ ሰው ወንድ ልጁን ለመዳር ያዘጋጃትን ሴት ይወክላል። በቋንቋህ ውስጥ ባል ለሚስቱ ሊጠቀም የሚችለው ጨዋነት ያለው ቃል ካለና እስካሁን በዚህ መጽሐፍ ካልተጠቀምክበት እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ትችላለህ። ካልሆነም ባል ለሚስቱ ሊጠቀምበት የሚችለውን ሌላ የጨዋነት ቃል መጠቀም ትችላለህ።
አማና
በሰሜን እስራኤል የሚገኝ የተራራ ስም
ሳኔር
በአማና እና አርሞንዔም አቅራቢያ ያለ ተራራ ስም ነው። አንዳንድ ሰዎች ይህ ራሱን አርሞንዔም ተራራን እንደሚያመለክት ያስባሉ።
ዋሻ
እንደ ጎሬ ያለ ቦታ ወይም የተቦረበረ መሬት ሆኖ አንበሶችና ነብሮች የሚኖሩበት
Song of Solomon 4:9
አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ለሴቲቱ መናገሩን ይቀጥላል።
ልቤን ሰርቀሽዋል
የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) “አሁን ልቤ ሙሉ በሙሉ ያንቺ ነው” ወይም 2) “ካንቺ ጋር የግብረ ሥጋ ለመፈጸም አጥብቄ እፈልጋለው” ናቸው።
የኔ እህት

ይህ የፍቅር አነጋገር ነው። በመሠረቱ እነርሱ ወንድምና እህት አይደሉም። ኢ.ት: “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ ፍቅር”

ሙሽራዬ

ይህ የዕብራይስጡ ቃል ያገባችን ሴት ወይም አንድ ሰው ወንድ ልጁን ለመዳር ያዘጋጃትን ሴት ይወክላል። በቋንቋህ ውስጥ ባል ለሚስቱ ሊጠቀም የሚችለው ጨዋነት ያለው ቃል ካለና እስካሁን በዚህ መጽሐፍ ካልተጠቀምክበት እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ትችላለህ። ካልሆነም ባል ለሚስቱ ሊጠቀምበት የሚችለውን ሌላ የጨዋነት ቃል መጠቀም ትችላለህ። ይህንን በመኃልይ 4:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

አማና

x

ልቤን፤ በአንድ አይታ ብቻ፤ በአንድ ጌጥ ብቻ

“ልቤ፤ ማድረግ የሚኖርብሽ አንዴ ብቻ እኔን መመልከት ወይም አንድ ጌጥ ማሳየት ነው።” የሴቲቱ ዐይንና ጌጣጌጧ ሰውየውን ወደርሷ ስቧል።

የአንገት ሀብል

ይህ የአንገት ሀብል በአንገቷ ላይ ደጋግሞ ተጠምጥሞ ይሆናል።

Song of Solomon 4:10

አጠቃላይ መረጃ፡

ሰውየው ለሴቲቱ መናገሩን ይቀጥላል።

ፍቅርሽ እንዴት ያማረ ነው

“ፍቅርሽ ግሩም ነው”

እህቴ

ይህ የፍቅር አነጋገር ነው። በመሠረቱ እነርሱ ወንድምና እህት አይደሉም። ይህንን በመኃልይ 4:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ ፍቅር”

ሙሽራዬ

ይህ የዕብራይስጡ ቃል ያገባችን ሴት ወይም አንድ ሰው ወንድ ልጁን ለመዳር ያዘጋጃትን ሴት ይወክላል። በቋንቋህ ውስጥ ባል ለሚስቱ ሊጠቀም የሚችለው ጨዋነት ያለው ቃል ካለና እስካሁን በዚህ መጽሐፍ ካልተጠቀምክበት እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ትችላለህ። ካልሆነም ባል ለሚስቱ ሊጠቀምበት የሚችለውን ሌላ የጨዋነት ቃል መጠቀም ትችላለህ። ይህንን በመኃልይ 4:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ፍቅርሽ ከወይን ጠጅ ይልቅ እጅጉን ይሻላል

“ፍቅርሽ ከወይን ጠጅ ይልቅ እጅግ የተሻለ ነው”። ተመሳሳዩን ሐረግ በመኃልይ 1፡2 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የሽቶሽ መዓዛ ከየትኛውም ቅመም

ግሱ ምናልባት ቀደም ብሎ ካለው ሐረግ ወስዶ ይሆናል። ኢ.ት: “ከየትኛውም ቅመም ይልቅ የሽቱሽ መዓዛ እጅግ የተሻለ ነው”

መዓዛ ...ሽቱ

እነዚህን ቃላት በመኃልይ 1:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት።

ቅመም

መልካም ሽታ ወይም ጣዕም ያላቸው የደረቁ እፅዋት ወይም ዘሮች

ከንፈሮችሽ ... ማር ያንጠባጥባሉ

ማር ትርጓሜዎች ሊሆኑ ለሚችሉ ለሚከተሉት 1) የሴቲቱን የአሳሳም ጣፋጭ ጣዕም ወይም 2) የሴቲቱን ቃላት ለማመልከት የዋለ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።

ከምላስሽ በታች ወተትና ማር አለ

“ወተትና ማር” በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለመደ ሐረግ ስለሆነ ቃል በቃል መተርጎም አለብህ። ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት ማር የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር 1) የሴቲቱን የአሳሳም ጣፋጭ ጣዕም 2) የሴቲቱን ቃላት ሊሆን ይችላል። ወተት የምቾት፤ ሰዎች ሕይወትን ለማጣጣም የሚኖሯቸውን በርካታ ነገሮች የሚገልፅ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ሴቲቱ ሰውየውን ስትስመው፣ እርሱ ሕይወትን ያጣጥማል።

የልብስሽ መዓዛ እንደ ሊባኖስ ሽታ ነው

“የልብስሽ ሽታ እንደ ሊባኖስ ሽታ ነው”። በሊባኖስ ብዙ የጥድ ዛፎች ይበቅሉ ነበር። የጥድ ዛፎች በጣም ጥሩ ሽታ አላቸው፤ በመሆኑም፣ሊባኖስ ንጹሕና ጣፋጭ ሽታ ሳይኖራት አልቀረችም።

Song of Solomon 4:12

አጠቃላይ መረጃ፡

ሰውየው ሴቲቱን ማድነቁን ቀጥሏል።

የኔ እህት

ይህ የፍቅር አነጋገር ነው። በመሠረቱ እነርሱ ወንድምና እህት አይደሉም። ይህንን በመኃልይ 4:9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ ፍቅር”

ሙሽራዬ

ይህ የዕብራይስጡ ቃል ያገባችን ሴት ወይም አንድ ሰው ወንድ ልጁን ለመዳር ያዘጋጃትን ሴት ይወክላል። በቋንቋህ ውስጥ ባል ለሚስቱ ሊጠቀም የሚችለው ጨዋነት ያለው ቃል ካለና እስካሁን በዚህ መጽሐፍ ካልተጠቀምክበት እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ትችላለህ። ካልሆነም ባል ለሚስቱ ሊጠቀምበት የሚችለውን ሌላ የጨዋነት ቃል መጠቀም ትችላለህ። ይህንን በመኃልይ 4:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የተቆለፈበት የአትክልት ስፍራ ነው

“ማንም ሊገባበት የማይችል የአትክልት ስፍራ”። የአትክልት ስፍራው ለሴቲቱ፤ ቁልፉ ደግሞ ለድንግልናዋ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው።

የታተመ ምንጭ

“መክደኛ ያለው ምንጭ”። ምንጩ ወይም የውሃው ጉድጓድ ሴቲቱን፤ ሽፋኑ ደግሞ ድንግልናዋን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።

ቅርንጫፎችሽ

ቅርንጫፎች ወይም የወንዝ መውረጃዎች የሴቲቱን የሰውነት ክፍል በጨዋ አነጋገር የሚገልጹ ናቸው። የእነዚህ ቃላት አጠቃቀም ቅር የሚያሰኝ ከሆነ የሰውን ሁለንተና መግለጽ በሚችል የተሻለ ምሳሌአዊ አነጋገር ተርጉመው።

ጫካ

ብዙ ዛፎች በአንድ ላይ የሚበቅሉበት ስፍራ

ከምርጥ ፍራፍሬዎች ጋር

“ምርጥ ከሆኑ የፍራፍሬ አይነቶች ጋር”

የናርዶስ ተክሎች

ሰዎች ቆዳቸውን ለማለስለስና መልካም መዓዛ እንዲኖራችው የሚጠቀሙበትን ዘይት የሚሰጥ ተክል። ይህንን በመኃልይ 1:14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሄና

ሰዎች እንደ ሽቱ የሚጠቀሚቸው ትናንሽ የበረሃ ዛፎች። ይህንን በመኃልይ 1:14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እርድ

ከአንድ ዓይነት አበባ መሐሉ ላይ ከሚገኝ ቢጫ የደረቀ ክፍል የሚገኝ ቅመም

ቀጋ

ሰዎች የቅባት ዘይት ለመስራት የሚጠቀሙበት መልካም መዓዛ ያለው ተክል

ቀረፋ

ሰዎች ለማብሰል ከሚጠቀሙበት ዛፍ ቅርፊት የሚገኝ ቅመም

ከርቤ

እንደተረጎምከው ተመልከት።

ሬት

ጣፋጭ ሽታ ያለው፣ ሰፊ ቅጠል ያለው የተክል ዓይነት

ምርጥ ቅመማ ቅመሞች ሁሉ

“ምርጥ የሆኑ ቅመሞች ሁሉ”

Song of Solomon 4:15

አጠቃላይ መረጃ

ሰውየው ሴቲቱን ማድነቁን ይቀጥላል።

አንቺ የአትክልት ቦታ ምንጭ ነሽ

“በአትክልት ቦታ ያለ ምንጭ ነሽ”። በአትክልት ቦታ የሚገኝ ምንጭ ሰዎች ለመጠጣት የሚወዱትን ጣፋጭና ንፁህ ውሃ ይሰጣል። ሰውየው በሴቲቱ አጠገብ በመሆኑ ይደሰታል።

ንፁህ ውሃ

ለመጠጥ ጥሩ የሆነ ውሃ

ከሊባኖስ የሚወርዱ ምንጮች

ሊባኖስ በዛፍ የተሸፈኑ ተራሮች ስላነበሯት ከሊባኖስ የሚወርዱት ምንጮች ንጹሕና ቀዝቃዛ ነበሩ።

የሰሜኑ ንፋስ ተነሥ፤ የደቡቡ ንፋስ ና ንፈስ

ሴቲቱ የሰሜኑ እና የደቡቡ ንፋስ ሰዎች እንደሆኑ አድርጋ ትናገራለች። ኢ.ት: “የሰሜኑ ንፋስና የደቡቡ ንፋስ መጥተው ቢነፍሱ እወዳለሁ”

የሰሜኑ ንፋስ ተነሥ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“የሰሜን ንፋስ መንፈስ ጀምር”
በአትክልት ቦታዬ ላይ ንፈስ
የአትክልት ስፍራው መልካም ሽታ ባላቸው ቅባቶች የተቀባውን የሴቲቱን ገላ የሚገልጽ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው (መኃልይ 4፡14) ፡፡
መዓዛቸውን ይስጡ
“መልካም ሽታቸውን ይልቀቁ”
ወዳጄ … ምርጥ ፍራፍሬ
ሴቲቱ ሰውየው አብሯት እንዲተኛ እየጋበዘችው ነው፡፡
ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል፡፡ በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ “የኔ አፍቃሪ” ብትለው በይበልጥ የተለመደ ይሆን ይሆናል፡፡ ይህንን በመኃልይ 1፡ 13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡ ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”፡፡
ምርጥ ፍሬ
“ግሩም ፍሬ”

## Chapter 5

### Song of Solomon 5:1

አጠቃላይ መረጃ
x
መጥቻለሁ
ተናጋሪው የሴቲቱ አፍቃሪ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡
ወደ አትክልት ቦታዬ መጥቻለሁ
“የአትክልት ቦታ” የሚለው ቃል ሴቲቱን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው፡፡ በመጨረሻም ሰውየው ከሴቲቱ ጋር ባደረጉት የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚገባ መርካት ችሎአል፡፡
እህቴ
ይህ ማፍቀርን የሚያመለክት የአነጋገር ዘይቤ ነው፡፡ በእርግጥ እነርሱ ወንድምና እህት አይደሉም፡፡ መኃልይ 4፡9ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡ ኢ.ት፡ “የእኔ ተወዳጅ” ወይም “የእኔ ተፈቃሪ”፡፡
ሙሽራዬ
ይህ የዕብራይስጡ ቃል የተዳረችን ሴት ወይም ለልጁ ሚስት ያጨለትን ሰው ያመለክታል፡፡ በቋንቋህ በዚህ መጽሐፍ ጥቅም ላይ ያልዋለ፣ ባል ለሚስቱ የሚጠቀምበት ትህትናን የተላበሰ ቃል ካለ እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ትችላለህ፡፡ ካልሆነም አንድ ሰው ከሚስቱ ጋር ሊጠቀም የሚችልበትን ሌላ የትኛውንም ትህትና የተላበሰ ቃል መጠቀም ትችላለህ፡፡ መኃልይ 4፡9ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡
ከርቤ … ቅመም … የማር እንጀራ … ማር … ወይን … ወተት
እነዚህ ሁሉ ሰውየው በሴቲቱ አካል የሚደሰትባቸው ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው (መኃልይ 1፡13፣ 2፡4፣ 4፡11 እና 4፡14)፡፡
ቅመም
ጠንካራ ሽታ ወይም ጣዕም ያላቸው ተክሎች
ብሉ … ጠጡ … በፍቅር ስከሩ
መብላትና መጠጣት የግብረ ሥጋ ግንኙነት የመፈጸም ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው፡፡ ኢ.ት፡ “በሚገባ እስክትረኩ ድረስ የግብረ ሥጋ ግንttttኙነት ፈጽሙ … የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሙ”

### Song of Solomon 5:2

አጠቃላይ ማስታወሻ
የመጽሐፉ አራተኛው ክፍል እዚህ ጋ ይጀምራል፡፡
አጠቃላይ መረጃ
ወጣቷ ሴት ሕልሟ በሁለት የተለያዩ መንገዶች እንዲተረጎሙ ጨዋነት ያለበትን ቃል በመጠቀም ትገልጻለች፤ 1) ሴቲቱ፣ ሰውየው በምሽት ሊጎበኛት ወደ ቤቷ ስለመጣበት ሕልም ትገልጻለች፤ ደግሞም 2) ሴቲቱ ከሰውየው ጋር መተኛት ስለመጀመሯ ያየችውን ሕልም ትገልጻለች፡፡
ልቤ ግን ነቅቷል
ልብ የአሳብና የስሜት ማዕከል ነው፡፡ ኢ.ት፡ “ነገር ግን በሚገባ ማሰብ እችል ነበር” ወይም “ነገር ግን ይሰማኝ የነበረውን ስሜት ዐውቅ ነበር”
የእኔ ተወዳጅ
ሐረጉ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል፡፡ በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ማለቷ በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል፡፡ መኃልይ 1፡13ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡ ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”፡፡
ክፈቺልኝ
ቃል በቃል “በሩን ክፈቺልኝ”፣ ወይም 2) በዘይቤአዊ አነጋገር “ከአንቺ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንድፈጽም ፍቀጅለኝ” ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው፡፡
እህቴ
ይህ ማፍቀርን የሚያመለክት የአነጋገር ዘይቤ ነው፡፡ በእርግጥ እነርሱ ወንድምና እህት አይደሉም፡፡ መኃልይ 4፡9ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡ ኢ.ት፡ “የእኔ ተወዳጅ” ወይም “የእኔ ተፈቃሪ”፡፡
የእኔ ፍቅር
“እኔ የምወድህ”፣ መኃልይ 1፡9ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡
እርግቤ
ይህንን በመኃልይ 2፡14 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡
እንከን የሌለብሽ
“የእኔ ፍጹም” ወይም “የእኔ ታማኝ” ወይም “የእኔ ንጹሕ”
ጤዛ
የውሃ ጠብታዎች ወይም ሌሊቱ በሚቀዘቅዝበት ጊዜ የሚፈጠር እርጥበት
ጸጉሬ በሌሊቱ እርጥበት
“ረጥቧል” የሚለውን ቃል ቀደም ብሎ ካለው ሐረግ መረዳት ይቻላል፡፡ እዚህ ጋ መደገም ይችላል፡፡ ኢ.ት፡ “ጸጉሬ በሌሊቱ እርጥበት ረጥቧል”

### Song of Solomon 5:3

“ልብሴን አውልቄአለሁ … አቆሽሻለሁ?”
ሰውየው ሲናገር በሰማች ጊዜ ሴቲቱ በልቧ ያሰበችው ይህንን ነው፡፡ ሴቲቱ እንዲህ ብላ ታስብ ነበር ተብሎ ሊተረጎም ይችላል ወይም በተከፈተው ተለዋዋጭ ትርጉም (ዩ ዲ ቢ) እንዳለው ሴቲቱ ሁኔታውንና አሳቧን ብቻ መግለጽ ትችላለች፡፡ ኢ.ት፡ “ ‘ልብሴን አውልቄአለሁ … አቆሽሻለሁ? ብዬ አሰብኩ” ወይም “ልብሴን አውልቄአለሁ፣ እንደገና ልለብሰው አልፈልግም፤ እግሬን ታጥቤአለሁ፣ እንዲቆሽሽብኝ አልፈልግም”
ልብስ
ከላይኛን ጨርቅ የሚሠራ፣ ሰዎች ከውስጥ የሚለብሱት ስስ ልብስ
እንደገና መልበስ አለብኝ?
ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ኢ.ት፡ “እንደገና መልበስ አልፈልግም”
እግሬን ታጥቤአለሁ
“እግር” ድብቅ የአካል ክፍሎችን እንዲያመለክት በጨዋነት የሚነገር ቃል ሆኖ ሳለ ይህኛው ቃል በቃል እግርን ሳያመለክት አይቀርም፡፡ ሴቲቱ በመታጠቧ ምክንያት ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ከመራቅ ይልቅ ልታደርገው የፈለገች ትመስላለች፡፡
ላቆሽሸው?
ይህ በመግለጫነት ሊተረጎም ይችላል፡፡ ኢ.ት፡ “እንዲቆሽሽብኝ አልፈልግም”፡፡
ወዳጄ እጁን በበሩ መወርወሪያ መክፈቻ በኩል እጁን ሰደደ
ቃል በቃል፣ አፍቃሪዋ በሩን ለመክፈት በበሩ ቀዳዳ በኩል እጁን ማስገባት ችሎአል ወይም 2) የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ መጀመራቸው በጨዋ አነጋገር ተገልጿል የሚሉት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው፡፡
ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል፡፡ በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ማለቷ በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል፡፡ መኃልይ 1፡13ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡ ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”፡፡
የበር መወርወሪያ
“የበር ቁልፍ”

### Song of Solomon 5:5

ለወዳጄ በሩን ልከፍትለት ተነሣሁ
ቃል በቃል፣ ሰውየውን ወደ ቤት ለማስገባት ወጣቷ ሴት ከአልጋዋ ተነሥታለች፣ ወይም 2) ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል፡፡ ኢ.ት፡ “ከወዳጄ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ራሴን አዘጋጀሁ” የሚሉት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው፡፡
እጆቼ … ጣቶቼ … የበሩን እጀታ
እነዚህ የሴቲቱንና የሰውየውን አካላት የሚያመለክቱ ጨዋ አገላለጾች ቢሆኑም ቃል በቃል መተርጎማቸው የተሻለ ነው፡፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከአርጥብ ከርቤ ጋር
“ከፈሳሽ ከርቤ ጋር”
Song of Solomon 5:6
አጠቃላይ ማስታወሻ
ሴቲቱ ሕልሟን መግለጿን ትቀጥላለች።
ወዳጄ
ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ልቤ ፈሰሰ
ልብ የሰውን ሁለንተና የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን መስመጥ፣ መጥለቅ የመድከም ወይም የማዘን ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በጣም አዝኜ ነበር”
Song of Solomon 5:7
ጠባቂዎች
በምሽት የሕዝቡን ደኅንነት ለመጠበቅ በከተማይቱ የጥበቃ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሰዎች ናቸው። ይህንን በምዕራፍ 3፡3 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በከተማይቱ ውስጥ እየተዟዟሩ በሚጠብቁበት ጊዜ
“በከተማይቱ ቅጥሮች ላይ ይመላለሱ የነበሩት”። ይህንን በመኃልይ 3፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
አገኙኝ
ሴቲቱን አገኟት
መቱኝ
“ደበደቡኝ” ወይም “ጎሰሙኝ”
አቆሰሉኝ
“እንድቆስል አደረጉኝ”
በቅጥሩ ላይ ያሉ ጠባቂዎች
“ቅጥሩን የሚጠብቁ ሰዎች”
መደረቢያ ልብስ
ሰዎች ወደ ውጭ ሲወጡ በለበሱት ልብስ ላይ ደርበው የሚለብሱት ልብስ
Song of Solomon 5:8
እንድትምሉልኝ እፈልጋለሁ
ይህንን በምዕራፍ 2፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች
“የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች”፣ እነዚህ ወጣት ሴቶች በዚያ የሉም፣ ሊሰሟትም አይችሉም፤ ነገር ግን ሴቲቱ እነርሱ እንዳሉና እንደሚሰሟት ቆጥራ ትናገራለች። ይህንን በመኃልይ 2፡7 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ማለቷ በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።
ለወዳጄ ምን እንደሆንኩ የምትነግሩት መሰላችሁ?
ሴቲቱ የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች ለወዳጇ እንዲነግሩት የምትፈልገውን በጥያቄ መልክ ታቀርብላቸዋለች። ኢ.ት፡ “ለወዳጄ እንዲህ ብላችሁ እንድትነግሩት እፈልጋለሁ”
ከፍቅሩ የተነሣ መታመሜን
ሰውየውን ሕመም እስኪሰማት ድረስ እጅግ ትወደዋለች።
Song of Solomon 5:9
ወዳጅሽ
ይህ ቃል ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሌሎች ሴቶች እርሱን በሚመለከት “አፍቃሪሽ” ማለታቸው በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። በመኃልይ 1፡13 “ወዳጄ” የሚለውን ቃል እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ከሴቶች መካከል እጅግ የተዋብሽ
“አንቺ ከሴቶች ሁሉ እጅግ የተዋብሽ ነሽ”። ይህንን በመኃልይ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ወዳጅሽ የተሻለ የሆነው ለምንድነው?
“ወዳጅሽን የተሻለ የሚያደርገው ምንድነው”
እንዲህ ያለ መሓላ እንድናደርግ የምትጠይቂን
“ይህንን መሓላ እንድናደርግ ያስደረገሽ”
እንዲህ ያለ መሓላ
መሓላ በመኃልይ 5፡8
Song of Solomon 5:10
ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ማለቷ በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።
ብሩህና ደመ ግቡ ነው
ሐረጉ የፊት ቆዳውን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ብሩህና ማራኪ የቆዳ ቀለም አለው”
ብሩህ
“ፍጹም ጤነኛ” ወይም “ንጹሕ ነው”። ሰውየው ምንም እንከን የሌለበት የፊት ቆዳ አለው።
ደመ ግቡ
ጤናማ የሆነ የቀይ ዳማ
በአሥር ሺዎች መካከል በላጭ ነው
“ከ10,000ዎች የተመረጠው”። ኢ.ት፡ “ከማንም ይልቅ የተሻለ” ወይም “እንደ እርሱ ያለ ማንም የለም”።
ራሱ ንጹሕ ወርቅ ነው
የሰውየው ራስ ለሴቲቱ ከንጹሕ ወርቅ ይልቅ የከበረ ነው።
ቁራ
በጣም የጠቆረ ላባ ያለው ወፍ
Song of Solomon 5:12
አጠቃላይ መረጃ
ወጣቷ ሴት ሰውየውን መግለጿን ትቀጥላለች።
ዓይኖቹ እንደ እርግቦች ናቸው
“ዓይኖቹ እንደ እርግቦች ናቸው” የሚለውን በመኃልይ 1፡15 እንዳለው አድርገህ ተርጉመው። 1) እስራኤላውያን እርግቦች ረጋ ያሉና ለስላሳ ወፎች እንደሆኑ ያስባሉ፣ ሴቲቱም ሰውየው ወደ እርሷ የሚያይበት አስተያየት ረጋ ያለ፣ ዓይኖቹም የተዋቡ እንደሆኑ ታስባለች። ኢ.ት፡ “ዓይኖቹ እንደ እርግብ ረጋ ያሉ ናቸው” ወይም 2) ሴቲቱ ስለ ሰውየው ነጩ የዓይን ኳስ ወይም ዓይኖቹ የእርግብ ቅርፅ እንዳላቸው እየተናገረች ነው የሚሉት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው።
በውሃ ምንጮች ዳር ያሉ እርግቦች
እስራኤላውያን ረጋ ያለን ሰው በእርጋታ በሚወርድ ምንጭ አጠገብ እንደሚቀመጡ ረጋ ያሉ ወፎች የሚቆጥሩበት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።
የውሃ ምንጮች
“በዝግታ የሚወርድ ውሃ”
በወተት የታጠቡ
ወተት የእርግቦቹን ነጭነት የሚገልጽ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “እንደ ወተት የነጡ እርግቦች” ወይም 2) ወተት የሰውየውን ነጭ የዐይን ክፍል የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የዐይን ብሌኖቹ በነጭ ወተት እንደ ታጠቡ እርግቦች ናቸው”
ፈርጥ የገባበት የከበሩ ድንጋዮች
ዐይኖቹ ውቦች ናቸው። አንጥረኛ በጥንቃቄ ያስቀመጣቸው ባለ ፈርጥ የከበሩ ድንጋዮች የተዋቡ ናቸው።
Song of Solomon 5:13
አጠቃላይ መረጃ
ወጣቷ ሴት ሰውየውን መግለጿን ትቀጥላለች።
ጉንጮቹ … የጠረኑ መዓዛ
ይህ ጉንጮቹ የቅመማ ቅመም መደቦችን እንደሚመስሉ ያብራራል፣ ምክንያቱም ሁለቱም ጣፋጭ መዓዛቸውን ይለቃሉ።
የቅመማ ቅመም መደቦች
ሰዎች ቅመማ ቅመሞችን የሚያበቅሉበት የአትክልት ስፍራ ወይም ከፊል የአትክልት ስፍራ። ቅመማ ቅመሞች ለሰዎች ደስታን ይሰጣሉ። የሰውየው አካል ለሴቲቱ ደስታን ይሰጣታል።
የሽቱ መዓዛ የሚያመጡ
“ግሩም ሽታቸውን የሚሰጡ”
ከንፈሮቹ ውብ አበቦች ናቸው
ሴቲቱ ምናልባት ከንፈሩ ውቦችና መልካም ሽታ ያላቸው በመሆናቸው ምክንያት ከተዋቡ አበቦች ጋር ታነጻጽራቸዋለች።
ውብ አበቦች
ይህንን በመኃልይ 2፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ፈሳሽን ከርቤ የሚያንጠባጥቡ
“ምርጥ ከርቤ የሚያንጠባጥብ”፣ ከንፈሮቹ የረጠቡና እንደ ግሩም ከርቤ የሚሸቱ ናቸው።
Song of Solomon 5:14
አጠቃላይ መረጃ
ሴቲቱ ስለ ሰውየው መግለጫ መሰጠቷን ቀጥላለች።
ክንዶቹ ፈርጦች በገቡበት ወርቅ የተለበጡ ናቸው
“ክንዶቹ ሁለመናቸው ፈርጥ ያለባቸው የወርቅ ዘንግ ናቸው”። ሴቲቱ ይህንን ሥዕል የምትጠቀመው ክንዶቹ ያማሩና የከበሩ ናቸው ለማለት ነው። የመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ይህንን በዘይቤአዊ አነጋገር የወንድ አካል ክፍል አድርገው ሳይረዱ አልቀሩም (መኃልይ 5፡3ን ተመልከት)፣ ነገር ግን ይህንን በትርጉም ማሳየት አስቸጋሪ ይሆናል።
ሆዱ በዕንቁ የተለበጠ የዝሆን ጥርስ ነው
“ሆዱ ዕንቁ የሞላበት ልሙጥ የዝሆን ጥርስ ነው”። ሴቲቱ ሆዱ ያማረና የከበረ ነው ለማለት ይህንን ሥዕል ትጠቀማለች።
የዝሆን ጥርስ
አጥንት የሚመስል፣ የእንስሳው ነጭ ጥርስ። ሰዎች የለሰለሱና የሚያብረቀርቁ የጥበብ ሥራዎችን ለመሥራት በዝሆን ጥርስ ይጠቀማሉ።
ዕንቁዎች
የከበሩ ድንጋዮች ሲሆኑ 1) ሰማያዊ ወይም 2) ንጹሕ ሰማያዊ ወይም ወርቃማ ናቸው።
Song of Solomon 5:15
አጠቃላይ መረጃ
ሴቲቱ ስለ ሰውየው መግለጫ መሰጠቷን ቀጥላለች።
እግሮቹ በወርቅ መሠረት ላይ የቆሙ የዕብነ በረድ ዐምድ ናቸው
ዕብነ በረድና ወርቅ ጠንካራና የተዋቡ ናቸው።
ዕብነ በረድ
የተለያየ ቀለም ያለው ጠንካራ ድንጋይ ሲሆን ሰዎች በጣም ልሙጥ እንዲሆን ይወለውሉታል
መልኩ እንደ ሊባኖስ ነው
“ሊባኖስን ይመስላል”። ሊባኖስ በርካታ ተራሮችና ጥዶች ያሉበት በጣም ውብ አካባቢ ነበር።
Song of Solomon 5:16
አጠቃላይ መረጃ
ሴቲቱ ስለ ሰውየው መግለጫ መስጠቷን ቀጥላለች።
አፉ እጅግ ጣፋጭ ነው
አፍ 1) የሰውየውን ጣፋጭ አሳሳም ወይም 2) እርሱ የሚናገራቸውን ጣፋጭ ቃላት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።
እርሱ ሁለንተናው ያማረ ነው
“የእርሱ ሁለንተናው ያማረ ነው” ወይም “ሁለመናው ያማረ ነው”
ወዳጄ ይህ ነው፣ ጓደኛዬም ይህ ነው
“ይህ” የሚለው ቃል ሴቲቱ ገለጻዋን የጨረሰችለትን ሰውዬ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የምወደው የሚመስለው ይህንን ነው፣ ጓደኛዬ የሚመስለውም ይህንን ነው”
ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ማለቷ በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።
የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች
“የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች”፣ እነዚህ ወጣት ሴቶች በዚያ ስላልነበሩ ሊሰሟት አይችሉም፣ ነገር ግን ሴቲቱ እንዳሉና ሊሰሟት እንደሚችሉ ቆጥራ ትናገራለች። ይህንን በመኃልይ 2፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Chapter 6
Song of Solomon 6:1
ወዳጅሽ የሄደው በየትኛው አቅጣጫ ነው
“ወዳጅሽ በየት በኩል ነው የሄደው ”
ወዳጅሽ ያንቺ ውድ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሌሎች ሴቶች “አፍቃሪሽ” ብለው ቢጠሩት በይበልጥ የተለመደ ይሆን ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ “ወዳጄ” የሚለውን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ ውድሽ” ወይም “አፍቃሪሽ” ወይም “የምትወጂው ሰውዬ”
በሴቶች መካከል እጅግ የተዋብሽ
“አንቺ ከሴቶች ሁሉ የተዋብሽው”። ይህንን በመኃልይ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሄዷል፣ ካንቺ ጋር እንድንፈልገው?
“ንገሪን” የሚለውን ቃል ከዐውዱ መረዳት ይቻላል። ቃሉን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። ኢ.ት፡ “ሄዷል? ከአንቺ ጋር ልንፈልገው እንድንችል ንገሪን”
Song of Solomon 6:2
ወዳጄ ወደ አትክልት ቦታው ሄዷል
“የአትክልት ቦታ” የሚለው ቃል ሴቲቱን የሚገልፅ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። በመጨረሻም ሰውየው ከሴቲቱ ጋር በፍቅር ግንኙነት ሙሉ ደስታ ማግኘት ችሏል። የዚህን ዘይቤአዊ አነጋገር ማብራሪያ በመኃልይ 5፡1 ውስጥ ተመልከት።
ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ ሰውየውን “የኔ አፍቃሪ” ብትለው በይበልጥ የተለመደ ይሆን ይሆናል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።
የቅመማ ቅመም መደብ
ሰዎች ቅመማ ቅመም የሚያበቅሉባቸው የአትክልት ስፍራዎች ወይም የአትክልት ስፍራ ክፍል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በአትክልት ስፍራ ለመሰማራትና የተዋቡ አበቦችን ለመሰብሰብ
እነዚህ ቃላት ሰውየው በሴቲቱ ገላ መደሰቱን የሚያሳዩ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው።
መሰማራት
“ይመግባል” ወይም “ሳር ይበላል”። ሴቲቱ ሰውየውን በተዋቡት አበቦች መሐከል እፅዋትን እንደሚመገብ “ሚዳቋ ወይም የአጋዘን ግልገል” ቆጥራ ትናገራለች (መኃልይ 2፡17)። መሰማራት ምናልባት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን የሚገልፅ ዘይቤአዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል (መኃልይ 2፡1-2)። “ይመግባል”ን በመኃልይ 2፡16 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የተዋቡትን አበቦች ለመሰብሰብ
“የተዋቡ አበቦችን ለመልቀም”
የተዋቡ አበቦች
ብዙ ውሃ ባለበት ቦታ የሚበቅሉ ባለጣፋጭ ሽታ አበቦች። በመኃልይ 2፡1 እንዳለው “የተዋበ አበባ” የሚለውን በብዙ ቁጥር ተርጉመው።
እኔ የወዳጄ ነኝ፣ ወዳጄም የእኔ ነው
“ወዳጄ የእኔ ነው፣ እኔም የእርሱ ነኝ” የሚለውን ተመሳሳይ ሐረግ በመኃልይ 2፡16 እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በተዋቡት አበቦች መሐከል በደስታ ይግጣል
ይህንን በመኃልይ 2፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Song of Solomon 6:4
አጠቃላይ መረጃ፡
የመጽሐፉ ክፍል አምስት እዚህ ጋ ይጀምራል
የኔ ፍቅር እንደ ቴርሳ ውብ፣ እንደ ኢየሩሳሌም ተወዳጅ
እነዚህ ከተሞች በውበታቸው የታወቁና በውስጣቸው ለመኖር የሚያስደስቱ ነበሩ። ሰውየው ሴቲቱ ውብ እንደሆነችና ከእርሷ ጋር መሆን እንደሚያስደስተው ያስባል።
የኔ ፍቅር
“አንቺ የምወድሽ”፣ ይህንን በመኃልይ 1፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ተወዳጅ
ይህንን በመኃልይ 1፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ዐርማቸውን ይዘው እንደሚያስፈሩ ወታደሮች
የሴቲቱ ውበት ኃያል ከመሆኑ የተነሣ ሰውየው ወታደሮች የመጡበት ያህል አቅመ ቢስነት እንዲሰማው አድርጎታል።
Song of Solomon 6:5
አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ሴቲቱን ማድነቁን ይቀጥላል።

አድክመውኛል

“ያስፈሩኛል”። የሴቲቱ አይኖች በጣም ከማመራቸው የተነሳ ሰውየው ኃይላቸውን መቋቋም ባለመቻሉ ፍርሐትና ድካም እንዲሰማው አድርገውታል።

ፀጉርሽ …ከገለአድ ቁልቁለት

በመኃልይ 4:1 እንዳለው “ጸጉርሽ … ከገለዓድ ተራራ” ብለህ ተርጉመው።

Song of Solomon 6:6

ጥርሶችሽ በቅርቡ የተሸለቱ የሴት በጎች መንጋ ይመስላሉ

በጎች ጸጉራቸው ከተሸለተ በኋላ ይታጠቡና ቆዳቸው በጣም ነጭ ሆኖ ይታያል። የሴቲቱ ጥርሶች ነጭ ናቸው። በመኃልይ 4:2 ላይ “ጥርሶችሽ በቅርቡ የተሸለቱ የሴት በግ መንጋ ይመስላሉ” የሚለው እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

ከመታጠቢያው ስፍራ የሚመጡ

ሴቶቹ በጎች ከውሃው ውስጥ ወጥተው እየመጡ ነው። ይህንን በመኃልይ 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “ሰዎች ካጠቡዋቸው በኋላ ከውሃው ውስጥ ወጥተው የሚመጡትን”

እያንዳንዱ መንታ አለው

በጎች አብዛኛውን ጊዜ በአንዴ ሁለት ግልገሎችን ይወልዳሉ። እነዚህ መንታዎች ብዙውን ጊዜ ይመሳሰላሉ። እያንዳንዱ የሴቲቱ ጥርስ ከአፏ በሌላኛው ጎን ካለው ጋር እኩል ነው። ይህንን በመኃልይ 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከእነርሱ አንዱም አልጎደለም

እያንዳንዱ የሴቲቱ ጥርስ ከአፏ በሌላኛው ጎን ካለው ጋር እኩል ነው። ከጥርሶቿ አንድም የወለቀ የለም።

ሐዘንተኛ

የቅርብ ሰው የሞተበት። ይህንን በመኃልይ 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

እንደ ሮማን ክፋይ ናቸው

ሮማኖች ደማቅ ቀይ፣ ክብ እና ለስላሳ ናቸው። ሰውየው የሴቲቱ ጉንጮች ያማሩና እርሷም ጤነኛ መሆኗን እንደሚያሳዩ ያስባል። ይህንን በመኃልይ 4:3ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ከአይነርግብሽ በስተጀርባ

ይህንን በመኃልይ 4:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Song of Solomon 6:8

60 ንግስቶች እና 80 ቁባቶች አሉ … ከቁጥር ያለፉ ወጣት ሴቶች

እነዚህ ቁጥሮች በጣም ብዙ፤ እጅግ ብዙ፤ ከመቆጠርም ያለፉ ናቸው። ኢ.ት: “60 ንግስቶች፣ 80 ቁባቶች … ማንም ሊቆጥራቸው የማይቻለው በርካታ ወጣት ሴቶች አሉ” ወይም “ ብዙ ንግስቶች፣ ከዚያም የሚበልጡ ቁባቶችና ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል ብዙ ወጣት ሴቶች”

እርግቤ

እስራኤላውያን እርግቦችን አስደሳች ድምፅ ያላቸው ውብ ወፎች እንደሆኑ ያስቡ ነበር። ሰውየው የሴቲቱ ፊትና ድምፅ ያማረ እንደሆነ ያስባል። አንዲትን ሴት “እርግብ” ብሎ መጥራት ቅር የሚያሰኛት ከሆነ ዘይቤአዊውን አነጋገር ልትተወው ትችላለህ። ይህንን በመኃልይ 2:14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የእኔ እንከን ዐልባ

“የኔ ፍፁም”ወይም “የኔ ታማኝ” ወይም “የኔ የዋህ”። ይህንን በመኃልይ 5:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ለእናቷ ብቸኛ ሴት ልጅ የሆነች

ይህ ግነት ነው። ኢ.ት: “ለእናቷ ልዩ የሆነች ልጅ” ወይም “ከእናቷ ከተወለዱት ከሌሎች እህቶቿ የተለየች”

የወለደቻት ሴት

“እርሷን የወለደቻት ሴት”። ይህ ሐረግ እናቷን ያመለክታል።

ወጣት ሴቶች … ንግስቶች … ቁባቶች

በቁጥር 8 የተነገረላት ሴት ናት

የተባረክሽ ብለው ጠሯት

“ነገሮች ለርሷ በጣም የተሻሉ እንደሆኑላት ተናገሩ”

Song of Solomon 6:10

አጠቃላይ መረጃ፡

የተከፈተው የቃል በቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ይህንን የሚረዳው ንግስቶቹና ቁባቶቹ ስለ ሴቲቱ እንደተናገሩት ይገነዘባል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ትርጉሞች የሚገነዘቡት እነዚህን የሰውየው ቃላት እንደሆኑ ነው።

እርሜ … እንደ ንጋት የምትታይ ይህቺ ማን ናት?

ይህንን ጥያቄ የሚጠቀሙት ወጣቷ ሴት አስደናቂ መሆኗን እንደሚያስቡ ለመናገር ነው። ኢ.ት: “ይህች አስደናቂ ሴት ናት! ዓርማ … እንደ ንጋት ትታያለች!”

እንደ ንጋት የምትታይ

ንጋት ውብ ነው። ሴቲቱ ውብ ናት። ኢ.ት: “እንደ ንጋት ወጥታ የምትታይ”

ዐርማቸውን ይዘው እንደሚያስፈሩ ወታደሮች

የሴቲቱ ውበት ኃያል ከመሆኑ የተነሣ ሌሎች ሴቶች ወታደሮች የመጡባቸው ያህል አቅመ ቢስነት እንዲሰማቸው አድርጓቸዋል። ይህንን በመኃልይ 6:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Song of Solomon 6:11

አጠቃላይ መረጃ፡

ሰውየው ለራሱ መናገሩን ያበቃል። እጽዋት በቅለው እንደሆነ ማየቱ ምናልባት የሴቲቱን ገላ በማየት ለመደሰት መፈለጉን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ይሆናል።

ጫካ

ይህንን በመኃልይ 4:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

ቡቃያ

“አዳጊ ተክሎች” ወይም “አዲስ ቦቆልቶች”

እንቡጥ አውጥቷል

እንቡጣቸው ማደግ ጀምሯል። እንቡጦች ወደፊት ተከፍተው አበቦች የሚሆኑ ትናንሽ፤ ክብ የተክል ክፍሎች ናቸው።

በመፍካት ላይ ነበሩ

“አበቦቻቸው እየተከፈቱ ነበር”

በንጉስ ሰረገላ ላይ እየጋለብኩ እንዳለሁ ያህል በጣም ደስተኛ ነበርኩ

ሰውየው ምን ያህል ደስተኛ እንደሆነ ለመግለፅ ይህን ምስል ይጠቀማል።

Song of Solomon 6:13

አጠቃላይ መረጃ

በአንዳንድ ትርጉሞች ይህ 7:1፣ የሰባተኛው ምዕራፍ የመጀመሪያ ቁጥር ነው። የተከፈተ የቃል በቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ይህንን የሚገነዘበው ሴቲቱና ጓደኞቿ እርስ በእርሳቸው እንደሚነጋገሩ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች ደግሞ ሰውየው ለሴቲቱ የሚናገረው እንደሆነ ይገነዘባሉ።

ተመለሽ … እንድናይሽ

ትርጓሜዎች ሊሆኑ የሚችሉት 1) ጓደኞቿ ሴቲቱን እያናገሯት ነው ወይም 2) ሰውየው ራሱን በብዙ ቁጥር እያመለከተ ነው።

ተመለሽ፣ ተመለሽ

“ወደ ኋላሽ ተመለሽ፣ ወደ ኋላሽ ተመለሽ”። ይህ የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው።

እንድናይሽ

አንዳንድ ትርጉሞች ብዙውን ቁጥር ሰውየው ስለ ራሱ የሚናገረውን እንደሚያመለክት ይረዳሉ። ኢ.ት: “እንዳይሽ”

አተኩሮ መመልከት

ለረጅም ጊዜ በጥሞና መመልከት

እንከን ዐልባዋን ሴት አተኩራችሁ የምትመለከቷት ለምንድነው … ሰራዊቶች

ትርጓሜዎች ሊሆኑ የሚችሉት 1) ሴቲቱ ራሷን እንደ ሌላ ሰው አድርጋ ለጓደኞቿ ትናገራለች ወይም 2) ሴቲቱ ለብዙ ወንዶች እንደምትናገር አድርጋ ለሰውየው ትናገራለች።

በሁለት ሰራዊት መሐል እንደምትጨፍር

“በሁለት ሰራዊት መሐል ስትጨፍር እንደነበረች”

---

Chapter 7

Song of Solomon 7:1

አጠቃላይ መረጃ:

በአንዳንድ ትርጉሞች ይህ 7:2 ነው፣ የሰባተኛው ምዕራፍ ሁለተኛ ቁጥር

በነጠላ ጫማዎችሽ ውስጥ ሲታዩ እግሮችሽ ምንኛ ያምራሉ

ምናልባት ሴቲቱ እየደነሰች ነው (መኃልይ 6:13) ። ኢ.ት: “በምትደንሽበት ጊዜ በነጠላ ጫማዎቹ ውስጥ እግሮችሽ እጅግ በጣም ያማሩ ናቸው”

የልዑል ሴት ልጅ

ሌላው አማራጭ ትርጉም ሊሆን የሚችለው “አንቺ ምስጉን ጠባይ ያለሽ” የሚለው

ነው።
የዳሌዎችሽ መታጠፊያዎች ዕንቁዎችን ይመስላሉ
የሴቲቱ ዳሌዎች ቅርፃቸው ለተናጋሪው ብልህ ቅርፃ ቅርፅ ሠሪ የሠራውን ውብ የከበረ ድንጋይ ያስታውሰዋል። ኢ.ት: "የዳሌዎችሽ መታጠፊያዎች ብልህ ቀራፂ እንደሚሠራቸው የተዋቡ የዕንቁ መታጠፊያዎች የተዋቡ ናቸው"።
ዳሌዎችሽ
"ዳሌዎችሽ" የሚለው ቃል የሴቲቱን ሽንጥና ከጉልበትዋ በላይ ያለውን የዳሌዋን ክፍል ያመለክታል።
የብልህ ቀራጺ እጆች የሠሩት
እጆች የሰው ምሳሌዎች ናቸው። ኢ.ት: "የብልህ ቀራጺ ሥራ" ወይም "ብልህ ቀራጺ የሠራው አንዳች ነገር"
Song of Solomon 7:2
አጠቃላይ መረጃ:
የወጣት ሴቷ አፍቃሪ የሚወዳትን እርሷን መግለጹን ይቀጥላል።
እምብርትሽ እንደ ክብ ጎድጓዳ ሳህን ነው
ጎድጓዳ ሳህን ክብ ነው። የሴቲቱ እምብርት ክብ ነው።
እምብርት
ልጅ ከእናቱ ጋር የሚያያዝበት እትብት የነበረበት፣ በሆድ ላይ የሚገኝ ምልክት
የተደባለቀ ወይን እንደማይጎድልበት
ሰዎች በግብዣ ላይ ወይንን በውሃ ወይም በቅመም ለማዋሃድ ትላልቅ ጎድጓዳ ሳህኖችን ይጠቀማሉ። ወይን መጠጣት በውበት የመደሰት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። የተጋነነው አባባል በአዎንታዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: "ሁሌም የተደባለቀ ወይን እንደ ያዘ" ወይም "ሁሌም በውበቱ ልደሰት ይሆን"።
ሆድሽ በውብ አበቦች እንደ ተከበበ የስንዴ ክምር ነው
እስራኤላውያን የስንዴ ክምርና ውብ አበቦች ሲያዩአቸው የሚያስደስቱ እንደሆኑ ያስቡ ነበር። ብዙ ስንዴ፣ ለመብላት የሚሆን ብዙ ምግብ የመኖሩ ምልክት ነበር። ስንዴን የሚወቁት ከፍ ባለና በደረቅ ስፍራ ሲሆን የተዋቡት አበቦች የሚያድጉት በዝቅተኛና እርጥበት ባለባቸው አካባቢዎች ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ምልክታዊ ድርጊት ሰዎች በአብዛኛው በአንድ ጊዜ ሊያዩት የማይችሉትን አስደሳች ዕይታ አጣምሮ ያቀርባል።
ሆድሽ እንደ ስንዴ ክምር ነው
ሰዎች ስንዴ የሚመስለውን የሰውነት የቆዳ ቀለም እጅግ የተዋበ ቀለም እንደሆነ ያስቡ ነበር፣ በክብ የተከመሩ የስንዴ ክምሮችም ያምሩ ነበር። ኢ.ት: "የሆድሽ ቀለም ያማረ ነው፣ እንደ ስንዴ ክምርም ክብ ነው"
የስንዴ ክምር
ይህ ሰዎች የማይጠቀሙበትን ገለባውን ካስወገዱለት በኋላ የስንዴ ምርት ክምር ነው።
በተዋቡ አበቦች የተከበበ
ዙሪያው በተዋቡ አበቦች"
የተዋቡ አበቦች
ብዙ ውሃ በሚገኝበት አካባቢ የሚያድጉ ጣፋጭ ሽታ ያላቸው አበቦች ናቸው። በመኃልይ 2፡1 እንዳለው በብዙ ቁጥር አድርገህ ተርጉመው።
Song of Solomon 7:3
x
የወጣት ሴቷ አፍቃሪ የሚወዳትን እርሷን መግለጹን ይቀጥላል።
ሁለት ጡቶች
"ሁለት" የሚለው ቃል የማያስፈልግና ያለ ቦታው የተቀመጠ መስሎ ከታየህ ልትሰርዘው ትችላለህ። ይህንን በመኃልይ 4፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
እንደ ሁለት የአጋዘን ግልገሎች፣ መንታ የሜዳ ፍየል
ሰውየው ምናልባት የሴቲቱ ጡቶች እኩል፣ ለስላሳና ትንሽ መሆናቸውን ያመለክታል። ይህንን በመኃልይ 4፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
መንትዮች
ከአንዲት እናት በአንድ ጊዜ የተወለዱ ልጆች። ይህንን በመኃልይ 4፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የሜዳ ፍየል
አጋዘን የሚመስልና በፍጥነት የሚንቀሳቀስ እንስሳ። በመኃልይ 2፡7 እንዳለው "የሜዳ ፍየሎች" የሚለውን በነጠላ ቁጥር ተርጉመው።
አንገትሽ እንደ ዝሆን ጥርስ ግምብ ነው
ግምብ ረጅምና ቀጥ ያለ ነው። የዝሆን ጥርስ ነጭ ነው። የሴቲቱ አንገት ረጅምና ቀጥ ያለ ነው፣ ቆዳዋም ብሩህ ቀለም አለው።
የዝሆን ጥርስ ግምብ
"ሰዎች በዝሆን ጥርስ ያስጌጡት ግምብ"
የዝሆን ጥርስ
አጥንት የሚመስል የእንስሳው ነጭ ጥርስ ነው። ሰዎች የጥበብ ሥራዎችን ለመሥራትና አንዳንድ ነገሮችን ለማሳመር በዝሆን ጥርስ ይጠቀማሉ።
ዓይኖችሽ እንደ ሐሴቦን ኩሬዎች ናቸው
የሴቲቱ ዓይኖች የጠራ የኩሬ ውሃ እንደሚመስሉ ተነግሮላቸዋል። የኩሬ ውሃ የጠራና የፀሐይ ብርሃን ሲያርፍበት ስለሚያንጸባርቅ ሲመለከቱት ያስደስታል። የሴቲቱም ዓይኖች የጠሩና አብረቅራቂዎች ናቸው፣ ስለዚህ ሲታዩ ያስደስታሉ። ይህ በምስስሎሽነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: "ዓይኖችሽ በሐሴቦን እንዳሉት ኩሬዎች የጠሩ ናቸው"
ሐሴቦን
ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ ያለች ከተማ ስም ነው
ባት ረቢ
የከተማ ስም
አፍንጫሽ በሊባኖስ እንዳለ ግምብ ነው ግምብ ረጅምና ቀጥ ያለ ነው፣ የእርሷም አፍንጫ ረጅምና ቀጥ ያለ ነው።
Song of Solomon 7:5
አጠቃላይ መረጃ:
ሰውየው ሴቲቱን መግለጹን ይቀጥላል።
የራስሽ ቅርፅ እንደ ቀርሜሎስ ነው
የቀርሜሎስ ተራራ በአካባቢው ካሉት ሁሉ ረጅም ነው። ሰውየው ከምንም ነገር በላይ የሴቲቱን ራስ ማየት ይፈልጋል። ኢ.ት: "ራስሽ በአንቺ ላይ ከምንም ነገር በላይ ከፍ ያለ ዘውድ ይመስላል"
ያልደመቀ ሐምራዊ
ሊሆን የሚችለው ሌላው ትርጉም 1) "ያልደመቀ ጥቁር" ወይም 2) "ያልደመቀ ቀይ"
ንጉሡ በረጅሙ ጸጉር ተይዞ ታስሯል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: "በጀርባሽ ላይ የወረደው ጸጉርሽ እጅግ የተዋበ ነው፣ ንጉሡ አለማድነቅ አልቻለም።
ረጅም የሴት ጸጉር
ከአንዲት ሴት ራስ ወደ ታች የሚወርድ ሽሩባ
የኔ ፍቅር፣ ታስደስቻለሽ!
"የእኔ ፍቅር። ታስደስችኛለሽ!"
Song of Solomon 7:7
አጠቃላይ መረጃ:
ሰውየው ከሴቲቱ ጋር ማድረግ የሚፈልገውን ይገልጻል።
ቁመናሽ እንደ የቴምር ዘንባባ ዛፍ ዘለግ ያለ ነው
"አቋቋምሽ እንደ ዘንባባ ዛፍ ነው"። የቴምር የዘንባባ ዛፎች ረጃጅምና ቀጥ ያሉ፣ ቅርንጫፎቻቸው አናቱ ላይ ብቻ የሚገኙና ፍሬአቸውን ከሥራቸው የሚያድርጉ ናቸው።
የቴምር ዘንባባ ዛፍ
እጅብ ብለው የሚያድጉ ጣፋጭ፣ ቡናማና ሙጫነት ያላቸውን ፍሬዎች የሚሰጥ ረጅምና ቀጥ ያለ ዛፍ
ጡቶችሽ የፍሬውን ዘለላ ይመስላሉ
ቴምር ለስላሳና ክብ ሆኖ በዘንባባ ዛፍ አናት ላይ ከቅርንጫፎቹ ሥር በሚንጠለጠሉ ረጃጅም ዘለላዎች ይገኛል። የሴቲቱ ጡቶችም ለስላሳ፣ ክብና ከክንዶቿ ዝቅ ያሉ ናቸው።
አልኩኝ
"አሰብኩኝ" ወይም "ለራሴ ተናገርኩ"። ሰውየው ይህንን የተናገረው በዝምታ ውስጥ ነው።
በቅርንጫፎቹ ... ለመውጣት እፈልጋለሁ
ሰውየው ሴቲቱን ለማቀፍ ይፈልጋል።
ጡቶችሽ እንደ ወይን ዘለላ ይሁኑ
ሰውየው ጡቶቿን ለመንካት ይፈልጋል። የወይን ዘለላዎች ክብና ለስላሳዎች ናቸው።
የአፍንጫሽ መዓዛ እንደ እንኮይ ይሁን
"አፍንጫ" የሚለው ቃል ከአፍንጫ ለሚወጣው ትንፋሽ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: "ከአፍንጫሽ የሚወጣው ትንፋሽ ሽታው እንደ እንኮይ ይጣፍጥ"

እንኮይ
የሚጣፍጥ ቢጫ ፍሬ
Song of Solomon 7:9
አጠቃላይ መረጃ፡
ሰውየው ከሴቲቱ ጋር ለማድረግ የሚፈልገውን መግለጹን ቀጥሏል።
ላንቃሽ እንደ ምርጥ ወይን ይሁን
ላንቃ የከንፈር ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ወይን ጣፋጭ ጣዕም አለው። ሰውየው የሴቲቱን ከንፈር ለመሳም ይፈልጋል።
ለወዳጄ በዝግታ ይንቆርቆርለት
"ለምወደው በዝግታ የሚንቆረቆርለት"። ሰውየው ሴቲቱን በዝግታ በመሳም ይደሰታል።
በተኙት ከንፈሮች ላይ ተንሸራቶ
"ስንተኛ በከንፈሮቻችን ላይ ይፍሰስ"
Song of Solomon 7:10
እኔ የወዳጄ ነኝ
ተመሳሳዩን ሐረግ በመኃልይ 6፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ፣ "የእኔ አፍቃሪ" ብትለው በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ "የእኔ ውድ" ወይም "የእኔ አፍቃሪ"።
እኔን ይመኛል
"ከእኔ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ይፈልጋል" ወይም "ይፈልገኛል"
ሌሊቱን በመንደሮቹ ውስጥ እናሳልፍ
እዚህ ጋ ያሉት ቃላት "መንደሮች" እና "ሌሊቱን ያሳልፋል" ተብለው ቢተረጎሙም እንኳን በመኃልይ 1፡13-14 በአንድነት እንደ "ሌሊቱን ያሳልፋል" እና "የሄና አበቦች" ተብለዋል፣ እንዲሁም በዚህና በዚያ ያለው ዐውድ የሚያመለክተው የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን ነው። የተከፈተው የቃል በቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፣ ተከታዩ ዘይቤአዊ አነጋገር ሰውየውና ሴቲቱ በመንደር ውስጥ ማደራቸውን፣ ማልደው መነሣታቸውንና ወደ ወይኑ ቦታ መሄዳቸውን ስለሚያመለክት እንዲህ ያለውን ንባብ ይመርጣል። "የሄና ተክሎች" እና "መንደሮች" የሚሉት ቃላት ድምፃቸው ተመሳሳይ ነው።

Song of Solomon 7:12
አጠቃላይ መረጃ:
ሴቲቱ ለሰውዬው መናገሯን ትቀጥላለች።
ማልዶ መነሣት
"ማልዶ መነሣት" ወይም "ማልዶ መንቃት"
እምቡጥ ይዟል
"ማበብ ጀምሯል"
ያብባል
እምቡጡ በሚከፈትበት ጊዜ ያብባል
አብቧል
"በእጽዋቱ ላይ አበቦቹ ፈክተዋል"
ፍቅሬን እሰጥሃለሁ
"ካንተ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እፈጽማለሁ"
Song of Solomon 7:13
አጠቃላይ መረጃ፡
ሴቲቱ ለሰውዬው መናገሯን ትቀጥላለች።
ለመድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ እፅዋት
ይህ ጠንካራ ነገር ግን አስደሳች ሽታ የሚለቁ እፅዋት ስም ነው። ሽታው በመጠኑ አስካሪና አነቃቂ ስለሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፍላጎትን ያነሣሣል።
መዓዛቸውን ሰጡ
"ሽታቸውን ለቀቁ" ወይም "በጣም ጥሩ ሽታ አላቸው"
በበሩ ላይ
በሮቹ የቤታቸው ነው። ኢ.ት፡ "ከቤታችን መግቢያ በላይ" ወይም "በቤታችን በሮች"
አዲስና የበሰሉ፣ ከሁሉም ዓይነት የተመረጡ ፍሬዎች
"ምርጥ የሆኑ የተለያየ ዓይነት ፍሬ፣ ከበሰለውና ከአዲሱ ፍሬ"
ለአንተ ተቀምጦልሃል
"ልሰጥህ እንድችል ተቀምጦልሃል"
ወዳጄ
ይህ ሐረግ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች ሴቲቱ፣ "የእኔ አፍቃሪ" ብትለው በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመኃልይ 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ "የእኔ ውድ" ወይም "የእኔ አፍቃሪ"።

---

Chapter 8
Song of Solomon 8:1
እንደ ወንድሜ በሆንክ
አንዲት ሴት ለወንድሟ በአደባባይ ፍቅሯን መግለፅ ትችል ነበር። ይህቺ ሴት ለሰውየው ያላትን ፍቅር በይፋ ማሳየት ትፈልግ ነበር።
አንተን በውጪ
"አንተን በይፋ"
እስምህ ነበር
አንዲት ሴት ምናልባት ለሰላምታ የወንድሟን ጉንጭ ትስም ይሆናል።
ይንቁኝ ይሆናል
"መጥፎ ሰው እንደሆንኩ ያስቡ ይሆናል"
Song of Solomon 8:2
አጠቃላይ መረጃ፡
ወጣቷ ሴት ለሰውየው መናገሯን ትቀጥላለች።
እየመራሁህ ወደ እናቴ ቤት ባመጣሁህ
ሰውየው ወንድሟ ቢሆን ኖሮ ወደ ቤተሰቧ ቤት ማምጣት ትችል ነበር። ይህ በዚያ ባህል የተለመደና አሁንም በአንዳንዶች ዘንድ ልማድ የሆነ ነው።
ያስተማረችኝ እርሷ
የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዴት እንደሚፈጸም ያስተማረቻት
እንድትጠጣው ልዩ ከሆነው ወይን፣ ከሮማኔም ጭማቂ ጥቂት በሰጠሁህ
ሴቲቱ ራሷን እንደምትሰጠውና ከእርሱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደምትፈጽም ለመናገር እነዚህን ምስሎች ትጠቀማለች።
የተቀመመ ወይን
"ወይን ከቅመማ ቅመም ጋር" ወይም "ቅመማ ቅመም ያለበት ወይን"። ይህ በግብረ ሥጋ ግንኙነት መስከርን ይወክላል።
ቀኝ እጁ ... ያቅፈኛል
ይህንን በመኃልይ 2፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ግራ እጅ ...ቀኝ እጅ
"ግራ ክንድ" ... ቀኝ ክንድ"
ያቅፈኛል
"ይይዘኛል"
Song of Solomon 8:4
እንድትምሉልኝ እፈልጋለው
ይህንን በመኃልይ 2፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የኢየሩሳሌም ሴት ልጆች
"የኢየሩሳሌም ወጣት ሴቶች"። እነዚህ ወጣት ሴቶች አብረዋት አልነበሩም፤ ሊሰሟትም አይችሉም፣ ነገር ግን ሴቲቱ አብረዋት እንዳሉና እንደሚሰሟት ቆጥራ ትናገራለች። ይህንን በመኃልይ 2፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
እስከመጨረሻው ... እንደምታደርጉት
ይህንን በመኃልይ 2፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Song of Solomon 8:5
አጠቃላይ መረጃ፡
የመጨረሻ የሆነው የመጽሐፉ ስድስተኛ ክፍል እዚህ ጋ ይጀምራል።
የምትወጣው ይህቺ ማናት
ሴቲቱ አስደናቂ እንደሆነች እንደሚያስቡ ለመናገር ይህንን ጥያቄ ተጠቅመዋል። ተመሳሳይ ሐረግ በመኃልይ 6፡10 ላይ ተተርጉሞአል። ኢ.ት፡ "በምትወጣበት ጊዜ ይህቺን አስደናቂ ሴት ተመልከቷት"
አስነሣሁህ
"ቀሰቀስኩህ" ወይም "አነሣሁህ"
የእንኮይ ዛፍ
በጣም ጣፋጭ የሆነ አነስተኛ ቢጫ ፍሬ የሚያፈራ ተክል ነው። እንባቢዎችህ ይህ

ምን እንደሆነ ካላወቁ በሌላ የፍራፍሬ ዛፍ ስም ወይም “የፍራፍሬ ዛፍ” በሚል ጥቅል ቃል ልትተካው ትችላለህ። ይህንን በመኃልይ 2:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

በዚያ

ከእንኮዩ ዛፍ በታች

አማጠችህ

“ወለደችህ”

Song of Solomon 8:6

አጠቃላይ መረጃ፡

ወጣቷ ሴት ለሰውየው መናገሯን ትቀጥላለች።

እንደ ማህተም በክንድህ፤ እንደ ማህተም በልብህ ላይ አስቀምጠኝ

ትርጓሜዎች ሊሆኑ የሚችሉት 1) ማህተሞች በጣም ጠቃሚ ከመሆናቸው የተነሳ ሰዎች ሁል ጊዜም በአንገታቸው ወይም በእጃቸው ዙርያ ያስቀምጡት ነበር። ሴቲቱ እንደ ማህተም ዘወትር ከሰውየው ጋር መሆን ትፈልጋለች ወይም 2) ማህተም ያለበት ነገር የባለቤቱን ማንነት ያሳያል፤ ሴቲቱም ራሷን በሰውየው እጅና ልብ ላይ እንደ ማህተም በማኖር ሀሳቦቹ ሁሉ፣ ስሜቶቹና ድርጊቶቹ የእርሷ እንደሆኑ ለማሳየት ትፈልጋለች።

ፍቅር እንደ ሞት የበረታ ነውና

ሞት በምድር ላይ እጅግ እጅግ ኃይለኛ የተባሉትን ሰዎች እንኳን ስለሚያሸንፍ በጣም ብርቱ ነው።

ይቅር እንደማትል እንደ ሲዖል

“እንደ ሲዖል ጨካኝ”። ሲዖል ሰዎች ከሞቱ በኋላ ድጋሚ ወደ ሕይወት እንዲመለሱ ፈፅሞ አትፈቅድም። ፍቅር መቼም ስለማይለወጥ እንደ ሲዖል ያለማቋረጥ የሚቀጥል ነው።

ነበልባሎቹ ይንቦገቦጋሉ ...ሌላ የትኛውም አይነት እሳት

ፍቅር እንደ እሳት በጣም ኃይለኛ ነው።

ይንቦገቦጋል

“በድንገት ይነዳል”

Song of Solomon 8:7

አጠቃላይ መረጃ፡

ወጣቷ ሴት ለሰውየው መናገሯን ትቀጥላለች።

የማዕበል ውኃ ፍቅርን ሊያጠፋ አይችልም

እጅግ እንደሚነድ፣ ውቅያኖስ ሙሉ ውሃ እንኳን ቢደፋበት እንደማይጠፋ እሳት፣ ፍቅር ኃይለኛ ነው።

የማእበል ውሃ

“የውቅያኖስ ውሃ” ወይም “ብዙ ውሃ”

ሊያጠፋው አይችልም

“ማጥፋት አይችልም” ወይም ”ሊያስወግደው አይችልም”

ጎርፍ ሊጠርገውም አይችልም

ኃይለኛ ጎርፍም እንኳን እስከማያንቀሳቅሰው ድረስ ፍቅር መቼም አይቀየርም፤ ሁሌም ጸንቶ ይኖራል።

ጎርፍ

በእስራኤል የዝናብ ውሃ ወደ ጠባብና ጥልቅ ሸለቆዎች ይወርዳል። ይህም ግዙፍ ቋጥኞችንና ዛፎችን ማንቀሳቀስ የሚያስችለውን ጎርፍ ይፈጥራል።

ጠርጎ ይወስደዋል

“ይዞት ይሄዳል” ወይም “ያጥበዋል”

ሰው ቢሰጥ ... ያቀረበው ፈፅሞ ይናቃል

ይህ ሊያጋጥም የሚችል ነገር ነው። ኢ.ት፡ “ሰው ቢ ... እንኳን ፈጽሞ ይናቃል”

ሰጠ

ለመስጠት አቀረበ

በቤቱ ያለውን ንብረት ሁሉ

“የእርሱ የሆነውን ነገር ሁሉ”

ስለ ፍቅር

“ፍቅርን ለማግኘት” ወይም “ፍቅርን ለመግዛት”

ያቀረበው ፈፅሞ ይናቃል

ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች ፈጽመው ይንቁታል” ወይም “ሰዎች በማፌዝ ይስቁበታል”

Song of Solomon 8:8

ትንሽ እህት

“ታናሽ እህት”

በትዳር ውስጥ ... ምን ማድረግ እንችላለን?

ተናጋሪው ለመናገር የፈለገውን ለማስተዋወቅ ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። ኢ.ት፡ “የምናደርገው ይህንን ነው ... በጋብቻ”

ለትዳር ቃል ይገባላታል

ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ይመጣና ሊያገባት ይፈልጋል”

Song of Solomon 8:9

አጠቃላይ መረጃ፡

የወጣቷ ሴት ወንድሞች እርስ በእርሳቸው መነጋገራቸውን ይቀጥላሉ።

እርሷ ግድግዳ ከሆነች ... እርሷ በር ከሆነች

ትንሿ እህት ያላደጉ ወይም በጣም ትንንሽ የሆኑ ጡቶች አሏት (መኃልይ 8:8) ።

በርሷ ላይ የብር ግምብ እንገነባለን ... በዝግባ ሳንቃ እናስጌጣታለን

x

እናስጌጣታለን

“እናስውባታለን” ወንድማማቾቹ እህታቸው ጥሩ ባል የመማረክ ዕድል እንዲኖራት በብርና በዝግባ ሊያስዉቧት ይወስናሉ፤ ይህም የሀብት ምልክት ነው።

Song of Solomon 8:10

ግንብ ነበርኩ

ግንቡ ትናንሽ ጡቶች ያሏትን ሴት የሚገልፅ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው።

አሁን ጡቶቼ እንደ ትልቅ መመሸጊያ ማማ ናቸው

የመመሸጊያ ማማዎች ረጃጅሞች ናቸው።

እኔ በአይኖቹ ፊት እንደ አንዱ ሆንኩ

አይኖቿ የዋጋ ወይም የፍርድ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በእርሱ ፍርድ እንደ አንዱ ነኝ” ወይም “እንደ አንዱ ያስበኛል”

ሰላምን ያመጣል

ሴቲቱ ሰላምን የምታመጣው ለማን እንደሆነ መግለጽ ይኖርብህ ይሆናል። ኢ.ት፡ “ሰላምን ታመጣለታለች”

ሰላም

“ደህንነት”

Song of Solomon 8:11

አጠቃላይ መረጃ፡

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡ 1) ሴቲቱ ፍቅሩን ለሚሰጣት ለሰውየው ራሷን የምትሰጥበትን መንገድ ሰለሞን የወይን ቦታውን ገንዘብ ለሚከፍሉት ሰዎች ከሚያከራይበት መንገድ ጋር ታነጻጽራለች። 2) ሰውየው ለሌላ ሰው የማይሰጣትን ሴቲቱን ሰለሞን ለሌሎች ሰዎች ከሚሰጣቸው የወይን ቦታ ጋር ያነጻጽራታል።

ብኤልሃሞን

ይህ በእስራኤል ሰሜኑ ክፍል የሚገኝ ከተማ ስም ነው።

የወይን ቦታውን ሰጠ

ኮንትራት፤ ሌሎች ሰዎች እየከፈሉት ወይኖችን በወይን ቦታው እንዲያበቅሉ ተስማምቶ በኮንትራት አከራየው

ማስተዳደር ለሚችሉ

“ሊንከባከቡ ለሚችሉ ሰዎች”

እያንዳንዱ ለፍሬው አንድ ሺህ የብር ሰቅል ማምጣት ነበረበት

ይህ ክፍያ ለወይን ቦታው ፍሬ እንደሆነ መግለጽ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ኢ.ት፡ “እያንዳንዱ ሰው ለወይኑ ቦታ ፍሬ አንዳንድ ሺህ ሰቅል ብር ለሰለሞን መስጠት ይጠበቅበታል”

አንድ ሺህ ሰቅል ብር ለማምጣት

“1000 ሰቅል የብር ለማምጣት”

የወይን ቦታዬ፣ የእኔ የራሴ

ሴቲቱ በመኃልይ 1:6 እንዳለው ራሷን የወይን ቦታ አድርጋ ታመለክታለች። እዚህ ጋ ማንም ከእርሷ ውጪ ስለ ወይን ቦታው መወሰን እንደማይችል አጽንዖት ትሰጣለች።

በፊቴ ነው

ይህ አንድ ሰው ማድረግ ስለሚፈልገው ነገር የማድረግ መብት እንዳለው የሚገልፅ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በእኔ ኃላፊነት ስር ነው” ወይም “እንደ ፈለግሁ ማድረጉ የእኔ ፈንታ ነው”

ሺህ ሰቅሎች ላንተ ናቸው፣ ሰለሞን

ሴቲቱ ሰለሞን የወይን ቦታውን በኮንትራት በማከራየት ገንዘብ ማግኘት እንደቻለ ታውቃለች፤ ነገር ግን እርሷ ገንዘብ አትፈልግም።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሰቅሎች
“ሳንቲሞች”
ሰለሞን
አንዳንድ ትርጉሞች ሴቲቱ የምትናገረው በቀጥታ ለሰለሞን እንደሆነ ይረዳሉ። ሌሎች የሚረዷት በምናቧ ለጓደኞቿ፣ ለሰውየው ወይም ለራሷ እንደምትናገር አድርገው ነው።
ሁለት መቶ ሰቅሎቹ
ተናጋሪው ካሁን በፊት ይህንን አልጠቀሰም ነበር ፤ አድማጭ ግን ሴቲቱ ሰዎቹ በወይን ቦታው ሠርተው ለሰለሞን ከከፈሉት በኋላ ለራሳቸው የሚቀራቸውን ገንዘብ እንደምታወራ ይረዳል።
Song of Solomon 8:13
አንቺ የምትኖሪ
ሰውየው የሚናገረው ለሴቲቱ ነው፤ ስለዚህ፣ “አንቺ” እና “የምትኖሪ” ነጠላ እንስት ናቸው።
ድምፅሽን እየሰማሁ
ድምፁ ሰውየው ለሚናገረው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ቋንቋህ አንድ ሰው እየሰማው ያለውን ነገር ብቻ የሚያስብ መሆኑን የሚገልፅ ቃል ካለው መጠቀም ትችላለህ። ኢ.ት፡ “መናገር ስትጀምሪ ለመስማት እየጠበቅሁ ነው” ወይም “የምትለውን ለመስማት እየጠበቅሁ ነው”
እንድሰማው ፍቀጂልኝ
“ድምፅሽን እንድሰማው ፍቀጂልኝ”
Song of Solomon 8:14
የእኔ ተወዳጅ
ሐረጉ ሴቲቱ የምትወደውን ሰውዬ ያመለክታል። በአንዳንድ ቋንቋዎች “የእኔ አፍቃሪ” ማለቷ በይበልጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። መኃልይ 1፡13ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእኔ ውድ” ወይም “የእኔ አፍቃሪ”።
ሚዳቋ
ቀጭን፣ አጋዘን መሳይ ባለ ረጅም ጠምዛዛ ቀንድ እንስሳ
ወንድ አጋዘን
ጎልማሳ ወንድ አጋዘን
የቅመማ ቅመም ተራሮች
“ቅመማ ቅመም የሞላባቸው ተራሮች”። ሴቲቱ ይህንን ዘይቤአዊ አነጋገር ሰውየው ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽም ለመጋበዝ ትጠቀምበታለች። ሰውየው በመኃልይ 4፡8 የከርቤ ተራሮችንና የዕጣን ኮረብቶችን እንዴት በዘይበአዊ አነጋገር እንደገለጻቸው ተመልከት።

---

Chapter 1
Isaiah 1:1
ኢሳይያስ ያየው ራእይ
‹‹ይህ ያህዌ ያሳየው የኢሳይያስ ራእይ ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ ያህዌ ለኢሳይያስ ያሳየው ነው››
አሞጽ
አሞጽ የኢሳይያስ አባት ነው።
ይሁዳና ኢየሩሳሌም
‹‹ይሁዳ›› ደቡባዊው የእስራኤል መንግሥት ነው። ‹‹ኢየሩሳሌም›› በጣም አስፈላጊ ከተማ ናት። የቦታዎች ስም በውስጣቸው የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ›› ወይም፣ ‹‹የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሰዎች››
በይሁዳ ነገሥታት በዖዝያን፣ በኢዮአታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን
ይህ እያንዳንዱ ንጉሥ የገዛበትን ዘመን ያመለክታል። የገዙት ተራ በተራ እንጂ፣ ሁሉም በአንድ ጊዜ አልነበረም። አማርጭ ትርጉም፣ ‹‹ዖዝያን፣ ኢዮአታም፣ አካዝና ሕዝቅያስ የይሁዳ ነገሥታት በነበሩ ጊዜ››
Isaiah 1:2
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
ሰማያት ሆይ ስሙ፤ ምድርም አድምጪ
ምንም እንኳ እነዚህ ትንቢቶች የኢየሩሳሌምና የይሁዳ ሕዝብ እንዲሰሙ የተነገሩ ቢሆኑም፣ ኢሳይያስ እንደማይሰሙ ያውቃል። ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ሰማያት›› እና ‹‹ምድር›› ያህዌ የተናገረውን መስማት እንደሚችሉ በሚያመለክት ሁኔታ መናገሩ ነበር፤ ወይም 2) ‹‹ሰማያት›› እና ‹‹ምድር›› በየአገሩ ሁሉ ያሉ ሰብዓዊ ፍጡራን ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሰማያት የምትኖሩ… በምድርም የምትኖሩ››
ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለነበሩ ሕዝብ የተገለጠ የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህን እንዴት እንደምትተረጉም በትርጉም ገጽ ስለ ያህዌ የተነገረውን ተመልከት።
መገብኋቸው እነርሱ ግን አላወቁም
ያህዌ ለሕዝቡ የተናገረውና ኢሳይያስ በያህዌ ምትክ ለእስራኤል የተናገረው ቃል
ልጆች ወለድሁ አሳደግኋቸውም
የእርሱ ቃል ምግብ፣ እስራኤላውያን ደግሞ ልጆቹ እንደ ሆኑ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳ ለሚኖሩ ሰዎች እንደ ልጆቼ ተጠነቀቅሁ››
አህያ የባለቤቱን ጋጥ
በውስጠ ታዋቂነት የተቀመጠውን መረጃ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አህያ የሚመገብበትን የጌታውን ጋጥ አወቀ›› ወይም፣ ‹‹አህያ ጌታው ለእርሱ ምግብ የሚሰጥበትን አወቀ››
እስራኤል ግን አላወቀም፤ እስራኤል አልተረዳም
ይህም ማለት፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ግን አላወቁኝም፤ ለእነርሱ የምጠነቀቅ መሆኔን አልተረዱም››
እስራኤል
ይህ የእስራኤል ሕዝብ መጠሪያ ነው። ይሁዳም የእስራኤል ሕዝብ አካል ነበረ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ››
Isaiah 1:4
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
ሕዝብ፣ ኀጢአተኛ
በሌላ መልኩ፣ 1) ኢሳይያስ ስለ እነርሱ ሁለት የተለያዩ ነገሮች እየተናገረ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ፣ እናንተ ኀጢአተኞች›› ወይም፣ 2) ስለ እነርሱ አንድ ነገር ብቻ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀጢአተኛ ሕዝብ››
ርኩሰት የተጫነው ሕዝብ
ሰው የሚሸከመው ከባድ ሸክም፣ የብዙ ኀጢአታቸው ምሳሌ ሆኗል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀጢአታቸው ጀርባቸው ላይ እንደ ተሸከሙት ከባድ ሸክም ነው፤ መራመድም ተስኖአቸዋል››
የክፉ አድራጊ ዘር
‹‹ዘር›› የሚለው ቃል ሌሎች ያደረጉትን የሚያደርጉ ሰዎች መጠሪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌሎች ያደረጉን ክፉ ነገር የሚያደርጉ ሰዎች››
በደል ፈጸሙ
ክፉ አደረጉ
ያህዌን ተዉ
‹‹ከያህዌ ራቁ››
እርሱን ናቁ
‹‹መታዘዝ አልፈለጉም›› ወይም፣ ‹‹እርሱን አላከበሩም››
እስራኤል
ይሁዳም የእስራኤል ሕዝብ አካል ነበር።
ጀርባቸውን በእርሱ ላይ አዞሩ
ምንም እንኳ በአንድ ወቅት ወዳጆቹ የነበሩ ቢሆንም፣ አሁን ግን ጨርሶ እንደማያውቁት ሆኑበት።
Isaiah 1:5
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
ለምን ዳግመኛ ትመታላችሁ? ለምንስ በዐመፅ ትጸናላችሁ?
ኢሳይያስ እንዲህ በማለት የጠየቀው፣ የይሁዳን ሕዝብ ለመገሠጽ ነው። ጥያቄዎቹን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እናንተን የቀጣበትን ነገሮች ማድረግ ቀጥላችኋል፤ በእርሱ ላይ በማመፅ ጸንታችኋል››
እናንተ
‹‹እናንተ›› የሚለው በይሁዳ የሚኖረውን ሕዝብ ሲሆን፣ ብዙ ቁጥር ነው።
ራሳችሁ በሙሉ ታውኦአል፤ ልባችሁ ሁሉ ታውኦአል
የእስራኤልን ሕዝበ ከተመታ ሰው ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተ ራሱ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደ ቆሰለ፣ ልቡ እንደ ታወከ ሰው ናችሁ›› ወይም ‹‹እናንተ መላው አእምሮውና ልቡ እንደ ታመመ ሰው ናችሁ››
ያልተጐዳ አካል የለም
ይህን ይበልጥ በተብራራ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አካላችሁ ሁሉ ተጐድቷል›› ወይም፣ ‹‹አንዳች ነገር አካላችሁን ሁሉ ጐድቶታል››
አልታጠበም፤ አልታሰረም፤ በዘይትም አልለዘበም
ምሳሌው እግዚአብሔር እስራኤልን መቅጣቱን ከአካላዊ ቁስል ገር ያነጻጽራል። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም አላጠበውም፤ አላሰረውም፤ በዘይትም አላለዘበውም››
Isaiah 1:7
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
አገራችሁ ጠፍቷል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አገራችሁን አጥፍተዋል›› ወይም፣ ‹‹ጠላቶቻችሁ አገራችሁን አጥፍተዋል››
ከተሞቻችሁ ተቃጥለዋል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከተሞቻችሁን አጥፍተዋል››
እርሻዎቻችሁን በፊታችሁ እንግዶች ያጠፏቸዋል።
‹‹የአገራችሁ ያልሆኑ ሰዎች ዐይናችሁ እያየ እህላችሁን ከእርሻዎቻችሁ ይወስዳሉ››
ጠፍ ሆኖ ይቀራል
‹‹ባድና የፈረሰ›› ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምድሩን አጥፍተዋል፤ ማንም አይኖርበትም››
በባዕድ ይነጠቃል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባዕዳን አገራችሁን ይነጥቃሉ›› ወይም፣ ‹‹የሌላ አገር ሰራዊት ጨርሶ ድል አድርጐታል››
የጽዮን ሴት ልጅ ተተወች
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጽዮንን ሴት ልጅ ትቻታለሁ››
የጽዮን ሴት ልጅ
የከተማ፣ ‹‹ልጅ›› የዚያ ከተማ ሕዝብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጽዮን ሕዝብ›› ወይም፣ በጽዮን የሚኖር ሕዝብ››
በወይን አትክልት ውስጥ እንዳለ ዳስ፣ በዱባ ተክል ውስጥ እንደሚገኝ ጐጆ ተተወች
ይህም ማለት 1) ‹‹የወይን ተክል ውስጥ እንዳለ ዳስ፣ የዱባ ተክል ውስጥ እንደሚገኝ ጐጆ አነሰች›› ወይም፣ 2) ‹‹ገበሬ ጉዳዩን ስጨርስ እንደሚተወው ወይን ተክል ውስጥ እንዳለ ዳስ የዱባ እርሻ ውስጥ እንዳለ ጐጆ ተተወች››
እንደ… ዱባ፤ እንደ ተከበበ ከተማ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። ‹‹እንደ… ዱባ እንደ ተከበበ ከተማ ሆነች››
Isaiah 1:9
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
ያህዌ… ኖሮ
ይህ የሚያመለክተው ባለፈው ጊዜ መሆን የነበረበትን፣ ግን ያልሆነ ነገርን ነው።
ትንሽ ትሩፍ
‹‹የተረፉ ጥቂቶች››
የእኛ… እኛ
እነዚህ ቃሎች የሚያመለክቱት ኢሳይያስን ሲሆን፣ የይሁዳና የኢየሩሌምንም ሕዝብ ይጨምራል።
እንደ ሰዶም በሆንን፣ ገሞራንም በመሰልን
ይሁዳ እንደ ሶዶምና እንደ ገሞራ ሊሆን ይችል የነበረበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዶምና ገሞራን እንዳጠፋ እግዚአብሔር ያጠፋን ነበር››
Isaiah 1:10
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
እናንተ የሰዶም ገዦች… እናንተ የገሞራ ሰዎች
ምን ያህል ኀጢአተኞች እንደ ሆኑ ለማሳየት ኢሳይያስ የይሁዳን ሕዝብ ከሰዶምና ከገሞራ ሕዝብ ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተ እንደ ሰዶም ሕዝብ ኀጢአተኞች የሆናችሁ ገዦች… እናንተ በገሞራ እንደሚኖሩ ዐመፀኛ የሆናችሁ ሰዎች››
የመሥዋዕታችሁ ብዛት ለእኔ ምኔ ነው?
የእስራኤልን ሕዝብ ለመገሠጽ እግዚአብሔር በጥያቄ ተጠቅሟል። ይህን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙ መሥዋዕት ማቅረባችሁ ለእኔ ምንም ማለት አይደለም››
Isaiah 1:12
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ የያህዌን ቃል ይናገራል።
ይህን ሁሉ እንድታመጡ፣ የመቅደሴን ደጅ እንድትረግጡ የጠየቃችሁ ማን ነው?
‹‹መርገጥ›› አንድ ነገር ላይ ቆሞ በእግሮች መጨፍለቅ ማለት ነው። በይሁዳ የሚኖሩ ሰዎችን ለመገሠጽ እግዚአብሔር በጥያቄ ይጠቀማል። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የመቅደሴን ደጅ እንድትረግጡ የጠየቃችሁ የለም።››
ከንቱ መባ አታምጡ
‹‹ከንቱ ስጦታዎቻችሁን አታምጡልኝ››
ዕጣናችሁን እጸየፋለሁ
‹‹እጸየፋለሁ›› የሚለውን ቃል፣ ‹‹እጠላለሁ›› በማለት መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ካህናት የሚያጨሱትን ዕጣን እጠላለሁ››
እነዚህ ክፋት የሞላባቸው ጉባኤዎቻችሁን መታገሥ አልችልም
ይህም ማለት፤ 1) ‹‹ከምታደርጓቸው ክፉ ነገሮች የተነሣ እንድትሰበሰቡ አልፈቅድላችሁም›› ወይም 2) ‹‹ከምታደርጓቸው ክፉ ነገሮች የተነሣ ስብሰባችሁን ማየት አልፈልግም››
Isaiah 1:14
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ የያህዌን ቃል ይናገራል።
አዲስ ጨረቃና የተደነገጉ በዓሎቻችሁ
‹‹አዲስ ጨረቃ›› የሚለው የአዲስ ጨረቃ በዓል የሚከበርት ነው። የተቀሩትም መደበኛ በዓሎች መጠሪያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአዲስ ጨረቃና ሌሎች መደበኛ በዓሎቻችሁን››
አዲስ ጨረቃ
አዲስ ጨረቃ ከጨለመች በኃላ ጨረቃዋ መጀመሪያ የምትታይበት ቀን ነው።
ሸክም ሆነውብኛል፤ መታገሥም አልቻልሁም
ይህ የሕዝቡን በዓል ማክበር እግዚአብሔር እንደ ከባድ ሸክም እንደሚያየው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእኔ እንደ ከባድ ሸክም ስለሆኑ መታገሥ ሰልችቶኛል››
ዐይኖቼን ከእናንተ ሰወርሁ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር፣ ‹‹ወደ እናንተ አላይም›› ወይም፣ ‹‹እናንተ የምትሉትን አልሰማም›› ማለት ነው።
እጆቻችሁ በደም ተበክለዋል
እግዚአብሔር ጸሎታቸውን የማይሰማው በዚህ ምክንያት ነው። ደም የሚያመለክተው ሌሎች ላይ የፈጸሙትን ግፍ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እጆቻችሁ እናንተ ግፍ ባደረጋችሁባቸው ሰዎች ደም ተበክለዋል›› ወይም፣ ‹‹ግፍ በማድረግ በድላችኃል››
Isaiah 1:16
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌን ቃል ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
ታጠቡ፤ ራሳችሁነ አንጹ
እዚህ ላይ ኀጢአት ማድረግ የተወ ሰው፣ አካሉን እንደ ታጠበ ሰው፣ እንደ ሆነ እግዚአብሔር ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንስሐ ግቡ፤ ከአካሉ ቆሻሻ እንደሚያጥብ ሰው ልባችሁን ከኀጢአት አንጹ››
ክፉ ሥራችሁን ከፊቴ አርቁ
እግዚአብሔር ክፉ ማድረጋቸውን እንዲተዉ እንጂ፣ ሌላ ቦታ ክፉ እንዲያደርጉ እየነገራቸው አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስታደርጉ የማየውን ኀጢአት ማድረጋችሁን ተዉ››
ፍትሕን እሹ
ሌሎችን የሚጨቁኑ ሰዎች መቃናት ያለበት ጠማማ ነገር እያደረጉ እንደ ሆነ እግዚአብሔር ይናገራል፤ ያንን እንዲያቃኑም ይጣራል። ‹‹ጭቆና›› የሚለውን ቃል በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተ የጐዳችኃቸው ምስኪን ሰዎች ካደረሳችሁባቸው ክፉ ነገር የተነሣ ከእንግዲህ እንዳይሰቃዩ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አድርጉ››
አባት ለሌለቸው ቁሙላቸው
‹‹አባት ለሌላቸው መልካም አድርጉላቸው››
ለመበለቲቱ ተማገቱ
‹‹ባሏ የሞተባትን ሴት ተከላከሉላት››
Isaiah 1:18
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ አሁንም ለይሁዳ ሕዝብ እየተናገረ ነው።
ኑና…
ቃሉን እንዲሰሙ ያህዌ በቸርነትና በፍቅር ሰዎችን ይጣራል። ‹‹እኔን ስሙ፤ ኑና›› ወይም፣ ‹‹ልብ በሉ፤ ልረዳችሁ እፈልጋለሁ፤ ኑና››
ኑና እንዋቀስ
‹‹በአንድነት ስለዚህ ጉዳይ እናስብ›› ወይም፣ ‹‹እዚህ ላይ እንወያይ›› ወይም፣ ‹‹ታዲያ፣ ምን ማድረግ አለብን?›› ስለ ወደ ፊቱ እንዲወያዩ ያህዌ ሕዝቡ ይጠራል። እዚህ ላይ፣ ‹‹እኛ›› የሚለው ያህዌንና የይሁዳን ሕዝብ ይወክላል።
ኃጢአታችሁ እንደ ዐለላ ቢቀላ እንደ በረዶ ይነጣል፤ እንደ ደም ቢቀላም እንደ ባዘቶ ነጭ ይሆናል
ሕዝቡ እንደ ባዝቶ መንጻት የነበረበትን ልብስ እንደ ለበሱና ኀጢአታቸውም ልብስ ላይ እንዳረፈ ቀይ ጠብታ እንደ ሆነ ኢሳይያስ ይናገራል። ያህዌ ኀጢአታቸውን ይቅር ካለ ልብሳቸው እንደ ገና ይነጣል።
እንደ ዐለላ
ዐለላ ደማቅ ቀይ ቀለም ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ደማቅ ቀይ››
እንደ በረዶ ይነጣል
ብዙውን ጊዜ ነጭ የቅድስናና የንጽሕና ምልክት ነው። ‹‹በረዶ›› ወደ ጠጣርነት የተለወጠ በጣም ነጭ ነገርን ያመለክታል። ይህ የሚያሳየው በጣም ነጭ የሆነ ነገርን በመሆኑ ነጭ በሆነ ሌላ ነገር መተካት ትችላላችሁ፤ ‹‹እንደ ኖራ ነጭ›› ወይም፣ ‹‹እንደ ርግብ ነጭ›› ይህም ማለት ኀጢአታቸው ይቅር ይባላል ማለት ነው።
እንደ ዐለላ ቢቀላ
ዐለላ ደብዛዛ ቀይ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ደብዛዛ ቀይ››
እንደ ባዘቶ
ባዘቶ የበግ ወይም የፍየል ጠጉር ነው። እንደ ባዝቶ መንጻትን በተመለከተ የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ባዘቶ ነጭ››
Isaiah 1:19
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር አሁንም ለይሁዳ ሕዝብ እየተናገረ ነው።
እሺ ብትሉ ብትታዘዙም
‹‹እሺ›› ማለት እና፣ ‹‹መታዘዝ›› ጥቅም ላይ የዋሉት አንድን ሐሳብ ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፈቃደኝነት ብትታዘዙ››
የምድርን በረከት ትበላላችሁ
‹‹ምድሪቱ የምትበሉት በረከት ትሰጣችኋላችሁ››
እንቢ ብላችሁ ብታምፁ ግን
‹‹አልሰማም ብላችሁ እኔ ላይ ብታምፁ››
ሰይፍ ይበላችኋል
‹‹ሰይፍ›› የሚያመለክተው የይሁዳን ጠላቶች ነው። ‹‹ይበላችኋል›› የሚለውም ቃል የይሁዳን ጠላቶች ሌላውን እንስሳ ከሚያጠቁና ከሚበሉ አራዊት ጋር ያመሳስላቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቻችሁ ይገድሏችኋል››
የያህዌ አፍ ይህን ተናግሮአል
‹‹አፍ›› የሚለው ቃል ያህዌ መናገሩንና የተናገረውም በእርግጥ የሚፈጸም መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ተናግሮአል›› ወይም፣ ‹‹ይህ እንደሚፈጸም ያህዌ ተናግሮአል››
Isaiah 1:21
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
ታማኝ የነበረችው ከተማ እንዴት…
ይህ ቃለ አጋኖ የኢየሩሳሌምን ሕዝብ በተመለከተ ኢሳይያስ ያደረበትን ቁጣና ሐዘን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእግዚአብሔር ታማኝ የነበሩት የኢየሩሳሌም ሕዝብ ላይ የሆነውን ተመልከቱ››
አመንዝራ ሆነች
ኢሳይያስ ሕዝቡን ለባልዋ ታማኝ ካልሆነች፣ ነገር ግን ገንዘብ ለማግኘት ከሌሎች ወንዶች ጋር ከምትተኛ ሴት ጋር ያመሳስላቸዋል። ሕዝቡ ሐሰተኛ አማልክት አመለኩ እንጂ፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ አልሆኑም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ አመንዝራ ሆኑ››
ቀድሞ ፍትሕ የሞላባት ከተማ
‹‹እርሷ›› የሚለው ኢየሩሳሌምና ሕዝቧን ያመለክታል። መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ከተሞችን ከሴቶች ጋር ያመሳስላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኢየሩሳሌም ሕዝብ መልካም ነበሩ፤ መልካም ነገርንም ያደርጉ ነበር››
አሁን ግን ነፍሰ ገዳዮች የሞሉባት ሆነች
‹‹እርሷ›› የሚለው ኢየሩሳሌምንና ሕዝቧን ያመለክታል። መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ከተሞችን ከሴቶች ጋር ያመሳስላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁን ግን የኢየሩሳሌም ሰዎች ነፍሰ ገዳዮች ሆኑ››
ብርሽ ዝጉአል፤ የወይን ጠጅሽ ከውሃ ጋር ተቀላቀለ
እዚህ ላይ ኢሳይያስ ብርና ወይን ጠጅን - ከሚከተሉት ጋር ያመሳስላል 1) ከኢየሩሳሌም ሕዝብ ጋር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጹሕ እንዳልሆነ ብር፣ ከውሃ ጋር እንደ ተቀላቀለ ወይን ጠጅ ሆናችኋል›› ወይም 2) ሕዝቡ ቀድሞ ያደረግ ከነበረው መልካም ነገር ጋር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቀድሞ መልካም ነገር ታደርጉ ነበር አሁን ግን መልካም ሥራችሁን ከንቱ የሚያደርግ ነገር እያደረጋችሁ ነው››
የዛገ… ብር
ብር በየጊዜው መንጻት አለበት፤ አለበለዚያ ደምቆ አይታይም።
ወይን ጠጅ… ውሃ
ውሃ የበዛበት ወይን ጠጅ በጣም አይጣፍጥም፤ እንዲያውም ከውሃ አይሻልም።
Isaiah 1:23
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌን ቃል ለሕዝቡ እየተናገረ ነው።
ገዢዎቻችሁ ዐመፀኞች ሆነዋል
‹‹መሪዎቻችሁ በእግዚአብሔር ላይ ዐምፀዋል።››
የሌቦች ግብረ አበር
‹‹ከሌሎች የሚሰርቁ ሰዎች ጓደኞች ሆነዋል››
ጉቦ… እጅ መንሻ
መሪዎቹ ፍርድ እንዲያጣምሙላቸው ሕዝቡ ለክፉ መሪዎች፣ ‹‹ጉቦ›› ይሰጣሉ። ሕጉን በመተላለፍ ጥቅም እንዲያገኙ መሪዎች፣ ‹‹እጅ መንሻ ይቀበላሉ።››
እጅ መንሻን በብርቱ ይፈልጋሉ
ጉቦ እንዲሰጠው በብርቱ የሚፈልግ ሰው እጅ መንሻ ከእርሱ ከሚሸሽና ያንን ለመያዝ ከሚሮጥ ሰው ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እውነተኛ ያልሆነ ፍርድ ለማድረግ ሰው ሁሉ አጥብቆ ገንዘብ እንዲከፈለው ይፈልጋል››
አባት ለሌላቸው አይቆሙም
‹‹አባት ለሌላቸው አይሟገቱም››
የመበለቶችንም አቤቱታ አይሰሙም
‹‹በሕግ ተላላፊዎች ላይ እንዲፈርዱላቸው መበለቶች ወደ እነርሱ ሲመጡ አይሰሟቸውም›› ወይም፣ ‹‹ከሕግ ተላላፊዎች እንዲያስጥሏቸው መበለቶች ወደ እነርሱ ሲመጡ አይረዷቸውም››
Isaiah 1:24
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌን ቃል ለይሁዳ ሕዝብ መናገር ይጀምራል።
ስለዚህ
‹‹በዚህ ምክንያት››
የሰራዊት ጌታ የእስራኤል ኀያል ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን ቃል እርግጠኝነት ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ የእስራኤል ኀያል ያህዌ እንዲህ በማለት ይናገራል።›› ወይም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ የእስራኤል ኀያል እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››
በባላንጣዎቼ ላይ ቁጣዬን አገልጣለሁ፤ ጠላቶቼንም እበቀላለሁ
ሁለቱም ሐረጎች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ነው። ‹‹ባላንጣዎቼ ላይ ቁጣዬን አገልጣለሁ›› የሚለው ይበልጥ የሚያመላክተው እርሱን ደስ እንዲለው ተቃዋሚዎቹ ላይ ያህዌ የፈቀደውን ማድረግ እንደሚችል ነው። ‹‹ጠላቶቼንም እበቀላለሁ›› የሚለው ይበልጥ የሚያመለክተው ያህዌ ጠላቶቹን በጽድቅ እንደሚቀጣ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚቃወሙኝን እቀጣለሁ›› ወይም፣ ‹‹እኔ ላይ በሚነሱት ደስ ያለኝን አደርግባቸዋለሁ፤ ጠላቶቼንም በጽድቅ እቀጣለሁ››
እጄን በአንቺ ላይ አነሣለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› ሕዝቡን ለመቅጣት የሚጠቀምበትን የእግዚአብሔር ኀይል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተ ለመቅጣት ኀይሌን ሁሉ እጠቀማለሁ››
ዝገትሽን ፈጽሜ አጠራለሁ
እግዚአብሔር የሕዝቡን ኀጢአት ለማስወገድ የሚያደርገው የእርሷን ኀጢአት ብርን ከተቀላቀለበት ቆሻሻ ነገር ከማንጻት ጋር ተመሳስሎአል። እዚህ ላይ የተጠቀመበት ቃል ብርን ከሚያነጻ ነገር ጋር ሳይሆን ሳሙና ውስጥ የሚደባለቅ ነገርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብርን ከቆሻሻ ነገር እንደሚያጠራ እሳት፣ ክፉንም ሁሉ ከመካከልሽ አስወግዳለሁ››
ዝገት
ይህ ዕቃው ንጹሕ እንዲሆን ሰዎች የሚያስወግዱት ቆሻሻና ሌላ መጥፎ ነገር ነው።
Isaiah 1:26
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
እንደ ቀድሞው... እንደ መጀመሪያው
ይህ እስራኤል በመጀመሪያ መንግሥት ስትሆን የእስራኤል ታሪክ ጅማሬ ላይ ስለ ተፈጸመው የመጀመሪያ ክፍል ለመናገር የተጠቀመባቸው ሁለት የአነጋገር መንገድ ነው።
...ተብለሽ ትጠሪያለሽ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች... በማለት ይጠሩሻል››
የጽድቅ መዲና፣ የታመነች ከተማ
‹‹መዲና›› እና ‹‹ከተማ›› የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ለእግዚአብሔር ጻድቃንና ታማኞች የሚሆነባቸው ከተሞች››
Isaiah 1:27
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌን ቃል ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
ጽዮን በፍትሕ፣ በንስሐ የሚመለሱ ነዋሪዎቿም በጽድቅ ይዋጀሉ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። የበለጠ ግልጽ ማድረግም ይቻላል። እንዲህ ማለት ሊሆን ይችላል፤ 1) ‹‹እዚያ ያሉ ሰዎች ትክክለኛ ነገር በማድረጋቸው ያህዌ ጽዮንን ይዋጃል፤ ያህዌ ትክክል የሚለውን በማድረጋቸው በንስሐ የሚመለሱትን ያህዌ ያድናል›› ወይም 2) ‹‹እርሱ ጻድቅ ስለሆነ ያህዌ ጽዮንን ይዋጃል፤ ጻድቅ ስለሆነም በንስሐ የሚመለሱትን ያድናል››
ጽዮን
ይህ በጽዮን ተራራ የሚኖሩ ሰዎች መጠሪያ ነው።
ዐመፀኞችና ኀጢአተኞች በአንድነት ይደቅቃሉ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእርሱ ላይ የሚያምፁትንና ኀጢአት የሚያደርጉትን ያህዌ ያጠፋቸዋል››
ያህዌንም የሚተዉ ይጠፋሉ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእርሱ የሚመለሱትን ያህዌ ፈጽሞ ያጠፋቸዋል›› ወይም፣ ‹‹እርሱን ችላ የሚሉትን ያህዌ ይገድላቸዋል››
Isaiah 1:29
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌን ቃል ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
የተቀደሱ ወርካ ዛፎች... አትክልት ቦታዎች
እነዚህ ሐረጐች የይሁዳ ሕዝብ ጣዖት ያመለኩባቸውን ቦታዎች ያመለክታሉ።
በ... ታፍራላችሁ
አንዳንድ ቅጂዎች፣ ‹‹ከዚህ የተነሣ ትደነግጣላችሁ›› ይላሉ። አንድ ሰው መጥፎ ነገር እንዳደረገ ሲሰማው ይደነግጣል ፊቱ ይቀላል።
ቅጠሉ እንደ ጠወለገ ወርካ፣ ውሃም እንደሌለው የአትክልት ቦታ ትሆናላችሁ
ውሃ ለዛፎችና ለአትክልት ቦታዎች ሕይወት ይሰጣል። ሕዝቡ ሕይወት ከሚሰጣቸው ከያህዌ ራሳቸውን ለይተዋል።
Isaiah 1:31
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌን ቃል ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
ብርቱ ሰው
‹‹ብርቱ ሰው›› ወይም፣ ‹‹ብርቱ የሆነ ሰው›› - ይህ የሚመለከተው ታዋቂና ሌሎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሰዎችን ሊሆን ይችላል።
ገለባ
ገለባ በቀላሉ የሚቃጠል ደረቅ ሣር ነው።
ሥራውም እንደ ብልጭታ
ይህ የሰውን ሥራ ወይም ክፉ ሥራን ገለባ ላይ ወድቆ ከሚነድ ነገር ጋር ያመሳስላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሥራው እሳት እንደሚያስነሣ ብልጭታ ይሆናል››

---

Chapter 2
Isaiah 2:1
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ የያህዌ ቃል ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
ይሁዳና ኢየሩሳሌም
‹‹ይሁዳ›› እና፣ ‹‹ኢየሩሳሌም›› እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በይሁዳና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ››
በመጨረሻዎቹ ቀኖች
‹‹ወደ ፊት››
የያህዌ ቤት ተራራ ይመሠረታል
ይህም ማለት 1) ገለጻ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያህዌ ቤት ተራራ ጸንቶ ይቆማል›› ወይም 2) በሌላ መልኩ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤተ መቅደሱ የሚሠራበትን ተራራ ያህዌ ይመሠርታል››
በተራሮችም ከፍታ ላይ
ያህዌ ግዙፍ ከፍታን በመሰለ ሁኔታ ስለ አስፈላጊነቱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም አስፈላጊ የሆኑ ተራሮች›› ወይም፣ ‹‹በዓለም ላይ በጣም አስፈላጊ የሆነ ቦታ››
ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ይላል
ኢሳይያስ ከፍታን በመጠቀም በምሳሌያዊ መንገድ ስለ ክብር ይናገራል። ይህንን በሚከተለው ሁኔታ ማስቀመጥ ይቻላል። 1) አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ከሌላው ኮረብታ የበለጠ ያከብረዋል›› ወይም፣ እዚያ የሚያመልኩ ሰዎችን ለማመልከት፣ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌሎች ሰዎችን ካከበረው የበለጠ ያህዌ እዚያ የሚያመልኩትን ሰዎች ያከብራል››
ሕዝቦች ሁሉ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሕዝቦች›› በእነዚህ አገሮች የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአገሮች ሁሉ የመጡ ሕዝቦች››
ይጐርፋሉ
ወደ ያህዌ ተራራ የሚሄዱ ሰዎች ከጐርፍ ጋር ተመሳስለዋል። ይህም ጥቂት ሳይሆኑ ብዙ ሰዎች እንደሚመጡ አጽንዖት ለመስጠት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ወንዝ ወደ እርሱ ይጐርፋሉ›› ወይም፣ ‹‹ወደ እርሱ ይሄዳሉ››
Isaiah 2:3
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
እንዲያስተምረን ያዕቆብ... እንሄዳለን
ሌላው ትርጉም፣ ‹‹ያዕቆብ ያስተምረናል... እኛም እንሄዳለን››
እርሱ መንገዱን ያስተምረናል፤ በጐዳናውም እንሄዳለን
‹‹መንገድ›› እና፣ ‹‹ጐዳና›› የሰውን አኗኗር የሚያመለክቱ ምሳሌዎች ናቸው። በቋንቋህ ሰዎች ስለሚሄዱበት መንገድ ያላችሁ ቃል አንድ ብቻ ከሆነ ሁለቱን እንደ አንድ ቃል ልትጠቀምባቸው ትችላለህ።
ሕግ ከጽዮን፣ የያህዌም ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣል
ሁለቱም ሐረጐች የሚያመለክቱት ተመሳሳይ ነገርን ነው። እውነት በኢየሩሳሌም መገኘቱን ሰዎች ሁሉ እንደሚረዱ ኢሳይያስ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጽዮን ያሉ የእግዚአብሔርን ሕግ፣ በኢየሩሳሌም የሚኖሩም የያህዌን ቃል ያስተምራሉ››
ከጽዮን ሕግ ይወጣልና
‹‹ሕግ ከጽዮን ይወጣልና›› ሕጉ ሰዎች ምንም ሳያደርጉ እንደ ወንዝ የሚወጣ ነገር መሆኑን ኢሳይያስ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሚያስተምሯቸው ሰዎች ሕጉ ከጽዮን ይወጣላቸዋል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ከጽዮን ሕጉን ይናገራል››
የያህዌ ቃል ከኢየሩሳሌም
‹‹የያህዌ ቃል ከኢየሩሳሌም ወጥቶ ይሄዳል›› የያህዌ ቃል ሰዎች ምንም ሳያደርጉ እንደ ወንዝ የሚሄድ ነገር እንደ ሆነ ኢሳይያስ ይናገራል። በውስጠ ታዋቂነት ያለውን

መረጃ የበለጠ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሚያስተምሯቸው ሰዎች ከኢየሩሳሌም የያህዌ ቃል ይወጣላቸዋል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ቃሉን ከኢየሩሳሌም ይናገራል››
Isaiah 2:4
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
ይፈርዳል
‹‹ያህዌ ይፈርዳል››
ውሳኔ ያሳልፋል
‹‹አለመግባባትን ያስወግዳል››
ሰይፋቸውን ቀጥቅጠው ማረሻ፣ ጦራቸውንም ማጭድ ያደርጋሉ
እነዚህ ቃሎች ማንኛውንም የጦር መሣሪያ ይወክላሉ።
ማረሻ… ማጭድ
እነዚህ ቃሎች ሰዎች ለሰላማዊ ጉዳይ የሚጠቀሙባቸውን መሣሪያዎች ሁሉ ይወክላሉ።
ሰይፋቸውን ቀጥቅጠው ማረሻ ያደርጋሉ
‹‹ሰይፋቸውን ዘር ለማብቀል የሚጠቅም መሣሪያ ያደርጉታል››፤ ማረሻ ዘር ለመዝራት ሲፈልጉ ሰዎች መሬቱን የሚቆፍሩበት ስለታም መሣሪያ ነው።
ጦራቸውንም ማጭድ ያደርጋሉ
‹‹ጦራቸውን ቀጥቅጠው ማጭድ ያደርጉታል›› ወይም፣ ‹‹ጦራቸውን ለተክሎች አገልግሎት የሚውል መሣሪያ ያደርጋሉ›› ማጭድ ሰዎች የማያስፈልግ ቅርንጫፍ ከአትክልቶች የሚቆርጡበት ጠማማ ቢላ ነው።
ሕዝብ በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም
‹‹አንዱ ሕዝብ ሌላው ሕዝብ ላይ ሰይፉን አያነሣም›› ሰይፍ ጦርነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንዱን ሕዝብ ሌላው ሕዝብ ላይ ጦርነት አያውጅም››
የጦርነት ልምምድም አያደርጉም
‹‹ሌላው ቀርቶ የጦርነት ዝግጅት እንኳ አያደርጉም›› ሰዎች ጦርነት ከማድረጋቸው በፊት ልምምድ እንደሚያደርጉ፣ ልምምድ ካደረጉት አንዳንዶቹም እንደማይዋጉ አንባቢዎቹ ይረዳሉ ብሎ ጸሐፊው ይጠብቃል።
Isaiah 2:5
አጠቃላይ መረጃ
2፥5 ላይ ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ፣ 2፥6 ላይ ለያህዌ ይናገራል። ሁለቱንም ጊዜ የተናገረው በግጥም መልክ ነው።
የያዕቆብ ቤት
x
Isaiah 2:7
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለያህዌ ይናገራል።
ምድራቸው በብር ተሞልቷል… ምድራቸው በፈረሶች ተሞልቷል… ምድራቸው በጣዖቶች ተሞልቷል
ምድሪቱ ሰዎች በብር፣ በፈረሶችና በጣዖቶች የሚሞሏት አንዳች ነገር እንደሆነች ኢሳይያስ ይናገራል። ‹‹ምድሪቱ›› የሚለው ሰዎች ራሳቸውን ያመለክታል፤ ‹‹ተሞልተዋል›› የሚለው ሰዎቹ የእነዚህ ነገሮች ባለቤቶች መሆናቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙ ብር… ብዙ ፈረሶች… ብዙ ጣዖቶች አሏቸው››
የእጆቻቸው ሥራ፣ የገዛ ጣቶቻቸው ያበጇቸውን
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ነው፤ በእውነት አማልክት እንዳይደሉም አጽንዖት ይሰጣሉ። በቋንቋህ ሰው ለሠራው ነገር ቃል ከሌለ ሁለቱን ሐረጎች በአንድ ማጣመር ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱ ራሳቸው የሠሯቸውን ነገሮች››
የእጆቻቸው ሥራ
‹‹እጆች›› ሰዎቹ ራሳቸውን ይወክላሉ፤ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እጃቸው የሠራውን ነገር›› ወይም፣ ‹‹የራሳቸውን ሥራ›› ወይም፣ ‹‹በእጆቻቸው የሠሩትን ነገር››
ጣቶቻቸው ያበጇቸውን
‹‹ጣቶች›› ሰዎቹ ራሳቸውን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣቶቻቸው ያበጇቸውን ነገሮች››
Isaiah 2:9
አጠቃላይ መረጃ
2፥9 ላይ ኢሳይያስ ለያህዌ መናገሩን ያበቃል። 2፥10-11 ላይ ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል። ሁለቱንም ጊዜ የሚናገረው በቅኔ መልክ ነው።
ሰዎች ዝቅ ብለዋል፤ ግለ ሰቦችም ወድቀዋል
እዚህ ላይ ሰዎች ወደ መሬት ዝቅ ማለታቸው የሚያመለክተው የታመኑበት ሁሉ ከንቱ መሆኑንና ራሳቸውንም ለመርዳት ምንም ማድረግ አለመቻላቸውን በመረዳታቸው በጣም መዋረዳቸውን ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ሰዎችን ያዋርዳል፤ የታመኑበት ሁሉ ከንቱ መሆኑንም ይረዳሉ››
ሕዝቡ
ከእንስሳት የተለዩ ሰብዓዊ ፍጡራን
ግለ ሰቦች
‹‹እያንዳንዱ ሰው››
ከእንግዲህ አታንሣቸው
‹‹አታንሣቸው›› የሚለው ያህዌ ሕዝቡን ይቅር የማለቱ ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይቅር አትበላቸው››
ወደ ዐለቶች ሂድ
ይህ የሚከተሉትን ማለት ሊሆን ይችላል። 1) ሰዎች ኮረብቶች ላይ ወዳሉ ዐለቶች መሄድ አለባቸው ወይም 2) መደበቅ የሚችሉበት ብዙ ዐለቶች ያሉበት ቦታ።
በመሬት ውስጥ ተሸሸግ
ይህ የሚከተሉትን ማለት ሊሆን ይችላል፤ 1) መሬት ውስጥ ባሉ ጉድጓዶች መደበቅ ወይም 2) መሬት ውስጥ በቆፈሩት ጉድጓድ።
ከያህዌ አስፈሪነት
እዚህ ላይ ‹‹አስፈሪ›› የሚለውን፣ ‹‹አስደንጋጭ›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአስደንጋጭ የያህዌ ፊት ለመሸሽ›› ወይም፣ ‹‹በጣም ከምትፈሩት ከያህዌ››
የግርማው ክብር
‹‹እንደ ንጉሥ እርሱ ያለው ውበትና ኀይል›› ወይም፣ ‹‹ንጉሣዊ ክብሩ›› ኢሳይያስ 2፥10 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
የዕብሪተኛ ዐይን ይሰበራል
‹‹ያህዌ የሰዎችን እብሪት ያዋርዳል›› ‹‹የሰዎች እብሪት ዐይን›› ከሰዎች ሁሉ በላይ ሆኖ መታየት ከእነርሱ የተሻለ እንደሆነ ማሰብ ማለት ነው። እዚህ ላይ ከያህዌ የተሻሉ እንደሆኑ በማሰብ ሰዎች ሁሉ በደል ፈጽመዋል፤ ያህዌን የሚያመልኩትን የሚያዩበት ሁኔታ የትዕቢታቸው መገለጫ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእርሱ የተሻሉ እንዲሆኑ በማሰባቸው ያህዌ ሰዎችን ሁሉ ያሳፍራል››
የሰዎችም ትዕቢት ይዋረዳል
‹‹የሰዎች ትዕቢት›› ትዕቢተኞችን ይወክላል፤ ‹‹ይሰበራል›› ዝቅ ይላል ወይም ያፍራል ማለት ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ትዕቢተኞችን ያዋርዳል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ትዕቢተኞች በራሳቸው እንዲያፍሩ ያደርጋል››
ያህዌ ብቻውን ከፍ ይላል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ያህዌን ብቻ ያመሰግናሉ››
በዚያን ቀን
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያ ቀን ያህዌ በሁሉም ላይ ይፈርዳል››
Isaiah 2:12
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
ረጅምና ከፍ ከፍ ያሉትን
‹‹ከፍ ያለ ሰው›› ትዕቢተኛና ከሌሎች የበለጠ እንደ ሆነ የሚያስብ ሰው ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ትዕቢተኛና ራሱን ከሌሎች በላይ ከፍ የሚያደርግ ሰው›› ወይም፣ ‹‹ትዕቢተኛና ከሌሎች የበለጠ እንደ ሆነ የሚያስብ ሰው››
ትዕቢተኛና እብሪተኛ
እብሪተኛ የሆነ ሰው ከሌሎች የበለጠ መሆኑን ይናገራል። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድነት የቀረቡት ያህዌ እንደሚቀጣቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው።
ይዋረዳል
‹‹ማንኛውም ትዕቢተኛ ይዋረዳል›› ይህን በተሻለ ሁኔታ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ያዋርደዋል››
የሊባኖስ ዝግባዎች ሁሉ… የባሳንን የወርካ ዛፍ ሁሉ
‹‹የሰራዊት ጌታ የያህዌ ቀን›› በዝግባዎችና በወርካዎች ላይ ይሆናል። ይህም

ማለት የሚከተሉትን ማለት ሊሆን ይችላል። 1) እነዚህ ዛፎች ያህዌ የሚፈርድባቸው ትዕቢተኞች ምሳሌ ናቸው። ወይም 2) እግዚአብሔር እነዚህ ግዙፍ ዛፎችን ያጠፋል።

Isaiah 2:14

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል። በሰራዊት ጌታ በያህዌ ቀን የሚሆነውን በተመለከተ ገለጻውን ቀጥሏል።

በ… ላይ

2፥14-16 እግዚአብሔር የሚያጠፋቸውን ነገሮች ይዘረዝራል። ይህም የሚከተሉትን ማለት ሊሆን ይችላል። 1) እግዚአብሔር የሚያዋርዳቸውን ክፉ ሰዎች ያመለክታል። ወይም 2) እግዚአብሔር ዝርዝሩ ውስጥ የተጠቀሱ ነገሮች ሁሉ ያጠፋል።

ተራሮች… ኮረብቶች

እነዚህ ቃሎች ትዕቢተኛ እስራኤላውያንን ያመለክታሉ። ኢሳይያስ 2፥2 ላይም ይገኛሉ።

ከፍ ያለው ሁሉ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ከፍ ያለው››

ረጅሙ ግንብ… የተመሸገው ቅጥር

ይህ የሚያመለክተው ራሳቸውን ከጠላቶቻቸው ለመከላከል ሰዎች ከተሞቻቸው ዙሪያ የሚሠሩዋቸውን ግንቦች ነው። የእስራኤላውያን ትዕቢትና ያህዌን አታስፈልገንም ማለታቸው ለኀጢአታቸው ያህዌ የሚያመጣባቸውን ቅጣት ሁሉ መቋቋም እንደሚችሉ የማሰባቸው ምሳሌ ነው።

የተመሸገው ቅጥር

‹‹ምንም የማያፈርሰው ወይም የማይሻገረው››

የተርሴስ መርኮቦች… ያማሩ ጀልባዎች

እነዚህ የሚያመለክቱት ሰዎች በባሕር ላይ ርቀው በመሄድ የተለያዩ ነገሮችን ወደ ከተሞቻቸው ለማምጣት የሚጠቀሙባቸውን መጓጓዣዎች ነው።

የተርሴስ መርከቦች

‹‹ወደ ተርሴስ የሚሄዱባቸው መርከቦች››

Isaiah 2:17

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል። በሰራዊት ጌታ በያህዌ ቀን የሚሆነውን መግለጽ ቀጥሏል። (ኢሳይያስ 2፥12)

የሰው እብሪት ይዋረዳል

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንኛውንም እብሪተኛ ሰው ይጥላል›› ወይም፣ ‹‹ማንኛውንም እብሪተኛ ዝቅ ያደርጋል››

የሰውም ኩራት ይወድቃል

‹‹ኩራት›› የሚለውን ቃል በሌላ መተካት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰዎች ኩራት እንዳልነበረ ይሆናል››

ያህዌ ብቻ ከፍ ከፍ ይላል

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። 2፥11 ላይ ይህን እንዴት እንደተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ያህዌን ብቻ ያመሰግናሉ››

ጣዖቶች ሁሉ ፈጽሞ ይወድማሉ

‹‹ጣዖቶች ሁሉ ይጠፋሉ›› ወይም፣ ‹‹ከእንግዲህ ጣዖቶች አይኖሩም››

ሰዎች ከአስፈሪነቱ… ሮጠው ይገባሉ

ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአስፈሪነቱ ሰዎች… ሮጠው ይደበቃሉ››

የዐለት ዋሻዎች

‹‹ዐለት ውስጥ ያሉ ዋሻዎች›› እነዚህ በእጅ የሚያዙ ትንንሽ ድንጋዮች ሳይሆኑ፣ በጣም ትልልቅ ዐለቶች ናቸው።

ከያህዌ አስፈሪነት ከግርማው ክብር የተነሣ

ኢሳይያስ 2፥10 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ከያህዌ አስፈሪነት

ያህዌን በጣም ከመፍራታቸው

ከግርማው ክብር የተነሣ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ክብር›› የሚለው፣ ‹‹ግርማ›› የሚለውን ቃል ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የንጉሥነት ክብሩ››

ምድርን ለማስፈራት ሲነሣ

‹‹ያህዌ ለተግባር ሲነሣና የምድር ሰዎች እንዲፈሩት ሲያደርግ››

Isaiah 2:20

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ በግጥም መልክ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል። በሰራዊት ጌታ በያህዌ ቀን የሚሆነውን በተመለከተ ገለጻ መስጠቱን ቀጥሏል። (ኢሳይያስ 2፥12)

ለፍልፈልና ለሌሊት ወፍ

ፍልፈል መሬት ቆፍሮ ውስጥ የሚኖር ትንሽ እንስሳ ነው። የሌሊት ወፍ አንዳንዴ ዋሻ ውስጥ የሚኖር ትንሽ በራሪ ፍጥረት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእንስሳት››

ወደ ድንጋይ ዋሻ… ወደ ዐለት ስንጣቂ

ቋንቋህ፣ ‹‹ዋሻ›› እና፣ ‹‹ስንጣቂ›› የሚሉ ቃሎች ከሌሉት ሁለቱን ሐረጐች እንደ አንድ ቃል ልትጠቀምባቸው ትችላለህ።

ከያህዌ አስፈሪነት

ያህዌን በጣም በመፍራታቸው። ኢሳይያስ 2፥19 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

የግርማው ክብር

‹‹የንጉሥነት ታላቅ ውበትና ኀይሉ›› ወይም፣ ‹‹የንጉሥነት ግርማው›› ኢሳይያስ 2፥10 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ምድርን ለማስፈራት ሲነሣ

‹‹ያህዌ ለተግባር ሲነሣና የምድር ሰዎች እንዲፈሩት ሲያደርግ›› ኢሳይያስ 2፥19 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እስትንፋሱ በአፍንጫው ላይ ባለች

ለመኖር መተንፈስ እንዳለበት በማሳየት የሰው ልጅ ምን ያህል ዐቅመቢስና ደካማ መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ደካማና ሟች የሆነውን›› ወይም፣ ‹‹ለመኖር በአፍንጫው መተንፈስ የሚያስፈልገውን››

አፍንጫ

ሰዎች የሚተነፍሱባቸው አፍንጫ ላይ ያሉ ቀዳዶች

ከቶ ምን የሚበጅ ነገር አለው?

ኢሳይያስ ጥያቄውን የሚያቀርበው ቀድሞውኑ የሚያውቁትን ለሰዎች ለማሳሰብ ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው ምንም ማለት አይደለም›› ወይም፣ ‹‹ሰው ምንም ዋጋ የለውም››

---

Chapter 3

Isaiah 3:1

እነሆ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እነሆ›› ለሚከተለው አጽንዖት ይሰጣል። ‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹በእርግጥ›› ተብሎ ሊተረጐምም ይችላል።

ድጋፍና ርዳታ

ሁለቱም የሚያመለክቱት ሰዎች የሚደገፉበትን ምርኩዝ ነው። እዚህ ላይ የሚያመለክተው በሕይወት ለመኖር ሰዎች በጣም የሚፈልጉትን ነገር እህልና ውሃን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድጋፍ የሚሆናችሁን ነገር ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹የምትተማመኑበትን ነገር ሁሉ››

ጀግናው… ብልኁልና አስማተኛውን

ይህ አንዳንድ ሰዎች የሚደገፉባቸው ነገሮች ዝርዝር ነው። ስለ የትኛውም ዐይነት ግለሰብ እንደ ተነገረ ስለሚያመለክቱ UDB ላይ እንዳለው በብዙ ቁጥር መተርጐም አለበት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተዋጊ ሰዎች… ብልኅ አስማተኞች››

ጥንቆላ የሚለማመድ

ይህ የእንስሳትን አካል ክፍሎች ወይም ቅጠሎችን የመሳሰሉ ነገሮች በማየት የወደ ፊቱን መናገር እችላለሁ የሚል ሰው ነው። ኢሳይያስ 2፥6 ላይ ያለውን ተመሳሳይ ቃል እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

የአምሳ አለቃው

ይህ የሚከተለውን ማለት ሊሆን ይችላል። 1) ‹‹አምሳ›› የሚለው ቃል ሰውየው የሚመራቸውን ሰዎች ቁጥር ያመለክት ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የ50 ወታደሮች አለቃ›› ወይም 2) ‹‹አምሳ›› ተብሎ የተተረጐመው ቃል የአነስተኛ ወታደራዊ ምድብ ስም እንጂ፣ ትክክለኛ ቁጥርን አይወክልም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአነስተኛ ወታደራዊ ምድብ ኀላፊ››

አምሳ

50

Isaiah 3:4

ልጆችን መሪዎች አደርጋለሁ፤ ያልበሰሉ ሕፃናትም ይገዟቸዋል

እነዚህ ሐረጐች በመሠረታዊ ደረጃ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፡፡ የሚከተለው ትርጉም ሊኖራቸውም ይችላል፤ 1) ‹‹ልጆችን መሪዎቻቸው አደርጋለሁ፤ ለጋ ወጣቶችም ይገዟቸዋል›› ወይም 2) ‹‹ለጋ ወጣቶች›› ተራና አላዋቂ ሰዎች ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያልበሰሉ መሪዎች በላያቸው እሾማለሁ፤ ለጋ ወጣቶችና መጥፎ መሪዎች ይገዟቸዋል››

አደርጋለሁ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› የሚለው ቃል ያህዌን ያመለክታል፡፡ ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ›› እንዲህ ይላል፣ ‹‹እኔ አደርጋለሁ››

ሕዝቡ እርስ በርሱ ይጨቋቈናል፤ ሰውም በባልንጀራው ላይ ይነሣል

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች እርስ በርስ ይጨካከናሉ፤ በባልንጀራቸውም ላይ ግፍ ይፈጽማሉ››

ተራው ሰው

‹‹ክብር የሌለው›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች የማያከብሩት››

የተከበረ ሰው

‹‹ክብር ያለው›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች የሚያከብሩት››

Isaiah 3:6

ይህን ፍርስራሽ በእጅህ አድርግ

‹‹እጅ›› ሥልጣንን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚህ ፍርስራሽ ላይ ኀላፊ ሁን›› ወይም፣ ‹‹በዚህ ፍርስራሽ ላይ ግዛ››

ይህን ፍርስራሽ

ይህ ማለት የሚከተሉትን ማለት ሊሆን ይችላል፤ 1) ብዙዎቹ የኢየሩሳሌም ሕንፃዎች ፈራርሰው ነበር፡፡ ወይም 2) የኢየሩሳሌም ሰዎች ሀብት ወይም መሪ አልነበራቸውም፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁን የፈረሰው ይህ ከተማ››

ፈዋሽ አልሆንም

የሰዎችን ችግር መፍታት እነርሱን መፈወስ እንደ ሆነ ተነግሮአል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፍጹም፤ እኔ ይህን ችግር መፍታት አልችልም›› ወይም፣ ‹‹የለም፤ እኔ ልረዳችሁ አልችልም››

Isaiah 3:8

አያያዥ ዐረፍተ ነገር

ነቢዩ በዚህ ሁኔታ ላይ ሐሳብ መስጠት ቀጥሏል፡፡

ኢየሩሳሌም ተሰናከለች፤ ይሁዳም ወደቀች

ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ተሰናክሎ መውደቅ እንደሆነ ተነግሯል፡፡

የክብሩ ዐይን

‹‹ዐይን›› ክቡር የሆነውን ራሱ እግዚአብሔርን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክቡር የሆነው እርሱ›› ወይም፣ ‹‹ክቡር የሆነው ያህዌ››

የፊታቸው ገጽታ ይመሰክርባቸዋል

ሰዎች ፊት ላይ የሚታየው እብሪት፣ የሰዎቹን ኩራት እንደሚመሰክርባቸው ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፊታቸው ላይ የሚታየው እብሪት ያህዌን እንደሚቃወሙ ያሳያል››

ኀጢአታቸውን እንደ ሰዶም በይፋ ይናገራሉ፤ አይደብቁትምም

በኀጢአታቸው ስለሚኩራሩ እዚህ ላይ የይሁዳ ሰዎች እንደ ሰዶም ሰዎች መሆናቸው ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ሰዶም ሰዎች ሰው ሁሉ እንዲያውቅላቸው ስለ ኀጢአታቸው ያወራሉ››

ጥፋትን በራሳቸው ላይ ያመጣሉ

አሁንም ቢሆን ጥፋት እየመጣ ነው፤ ሕዝቡ ግን እንዲመጣ ጥፋት የሚያደርገውን ሁሉ አድርገው ጨርሰዋል፡፡ የጥፋቱ መምጣት ምክንያት ራሱ ጥፋቱ እንደ ሆነ እዚህ ላይ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥፋት እንዲመጣ ምክንያት የሆነውን ሁሉ አድርገው ጨርሰዋል››

Isaiah 3:10

ጻድቃን መልካም ነገር እንደሚያገኙ ንገራቸው

‹‹ተገቢ የሆነውን ለሚያደርጉ እኔ መልካም ነገር እንደማደርግላቸው ንገራቸው››

ጻድቃን ሰዎች

ይህ በአጠቃላይ ጻድቃን ሰዎችን ይመለከታል፤ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጻድቃን የሆኑ ሰዎች››

የሥራቸውን ፍሬ ይበላሉና

ሥራ ሰዎች የሚበሉት ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎች መሆናቸው ተነግሯል፡፡ ፍሬ የመልካም ሥራ ሽልማትን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የመልካም ሥራቸውን ሽልማት ይቀበላሉና›› ወይም፣ ‹‹ስላደረጉት መልካም ሥራ ሽልማት ይቀበላሉ››

የሥራቸውን ፍሬ ይበላሉና

የዕብራይስጡ ምንባብ እዚህ ላይ በብዙ ቁጥር በሚያመለክት ተውላጠ ስም ይናገራል፤ ይሁን እንጂ ማንኛውንም ጻድቅ ሰው ይመለከታል፡፡ ተርጓሚዎች በነጠላ ቁጥር መተርጐም ይችላሉ፡- ‹‹የሥራውን ፍሬ ይበላል››

የእጁን ያገኛል

እዚህ ላይ ‹‹እጅ›› ሰው የሚያደርገውን ሥራ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ሰው ሌሎች ላይ እንደሚያደርገው ይደረግበታል፡፡››

ሕዝቤ… ሕዝቤ

ይህም ማለት 1) ኢሳይያስ እየተናገረ ነው፤ ‹‹የእኔ›› የሚለው የሚያመለክተው ኢሳይያስን ነው፤ ወይም 2) ያህዌ እየተናገረ ነው፤ ‹‹የእኔ›› የሚለው የሚያመለክተው ያህዌን ነው፡፡

ልጆች ጨቋኞቻቸው ናቸው

ይህም ማለት 1) ‹‹ወጣቶች መሪዎቻቸው ሆኑ፤ እነርሱም ሕዝቡን ይጨቁናሉ›› ወይም 2) ‹‹መሪዎቻቸው እንደ ልጆች ያልበሰሉ ናቸው፡፡ ሕዝቡንም ይጨቁናሉ››

ሴቶችም ይገዟቸዋል

ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ሴቶች ሕዝቡን ይገዛሉ›› ወይም 2) ‹‹መሪዎቻቸው እንደ ሴቶች ደካሞች ናቸው››

መሪዎችህ አሳስተውሃል፤ ከመንገድም መልሰውሃል

በጥንታዊው መካከለኛው ምሥራቅ የሕዝብ መሪዎች እረኞች እንደ ሆኑ መናገር የተለመደ ነበር፡፡ እረኞች በጐቹን ለመመገብ በመልካም መንገድ ወደ ደህና ቦታ እንደሚመሩ፤ መሪዎችም ሕዝቡን እውነቱን ማስተማርና መልካም እንዲያደርጉ ማስተማር ይኖባቸዋል፡፡ የይሁዳ መሪዎች ይህን እያደረጉ አልነበረም፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መሪዎችህ ከመልካም መንገድ የሚመልሱህ መጥፎ እረኞች ናቸው፤ ወዴት መሄድ እንዳለብህም አላሳዩህም››

Isaiah 3:13

ያህዌ ለክስ ተነሥቶአል፤ ሕዝቡን ለመክሰስ ተነሥቶአል

ያህዌ እስራኤልን ላይ ክስ ለማቅረብ ወደ ፍርድ ቤት የሄደ ይመስል፣ ኢሳይያስ ያህዌ ሕዝቡን ለመጉዳት ያሳለፈውን ውሳኔ ያመለክታል፡፡ የዚህ መስመር ሁለተኛው ክፍል ከመጀመሪያው ጋር ተመሳሳይ ነው፤ የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍርድ ቤት ውስጥ ያህዌ ቦታውን ይዞአል፤ ሕዝቡን ለመክሰስም ተዘጋጅቶአል››

ከፍርድ ጋር ይመጣል

ፍርድ ሰው ይዞት የሚመጣ አንዳች ነገር እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍርድን ያውጃል›› ወይም፣ ‹‹ፍርድን ይናገራል››

የወይኑን እርሻ አጥፍታችኋል

‹‹እናንተ›› የሚያመለክተው ሽማግሌዎቹንና መሪዎቹን ነው፡፡ ሕዝቡ የወይን እርሻ እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል፡፡ የወይን እርሻው ፍሬ እንዳይሰጥ እርሻውን እንደማይንከባከብ ሰው ሽማግሌዎቹና መሪዎቹም እስራኤላውያን እግዚአብሔርን እንዳያገለግሉ አድርገዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቤ የወይን እርሻ ነው፤ እናንተ ግን አጠፋችሁት››

ከድኾች የዘረፋችሁ በቤታችሁ አለ

‹‹ከድኾች የወሰዳችሁት ንብረት ቤታችሁ ውስጥ አለ››

ድኾች

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድኾች የሆኑ ሰዎች››

ሕዝቤን ለምን ትረግጣላችሁ፤ የድኾችንም ፊት ለምን ታደቅቃላችሁ?

ያህዌ ይህን የሚጠይቀው የሕዝቡን መሪዎች ለመክሰስ ነው፡፡ ይህን ክስ በዐረፍተ ነገር መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቤን ስለምትረግጡ፣ የድኾችንም ፊት ስለምታደቅቁ ክፉዎች ሆይ፣ በእናንተ ላይ ተቆጥቻለሁ››

ሕዝቤን የምትረግጡ

ሰዎችን ማሰቃየት ከባድ ሸክም እነርሱ ላይ መጣል እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጭካኔ ሕዝቤን የጐዳችሁ››

የድኾችን ፊት የምታደቅቁ

ሰዎችን ማሰቃየት ፊታቸውን መሬት ላይ መፈግፈግ እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድኾችን የምትጐዱና የምታሰቃዩ››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል

የሚናገረውን እርግጠኝነት ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ የሚለው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይህን ብያለሁ››


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Isaiah 3:16
የጽዮን ሴት ልጆች
እዚህ ላይ፣ ጽዮን የኢየሩሳሌም ከተማ ስትሆን፣ የራሷ ሴት ልጆች እንዳላት ሴት ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የጽዮን ሴት ልጆች››
ዐንገታቸውን እያሰገጉ
‹‹እብሪት በሚያሳይ መንገድ››
በዐይናቸውም እየጠቀሱ
ሴቶቹ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ እንደ ፈለጉ እንዲያስቡ ለማድረግ ወንዶችን ማየት።
እየተቈነኑ በመራመድ
ወንዶችን ለመማረክ በዚህ ሁኔታ ይራመዳሉ፤ ምናልባትም ቁርጭምጭሚታቸው ላይ ያለው የእግር አልቦ ከቃጭል ጋር በጌጠኛ ሰንሰለት የተያያዘ በመሆኑ በተለመደው ሁኔታ እንዳይራመዱ አድርጓቸው ይሆናሉ።
Isaiah 3:18
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ክፍል ያህዌ በእንዴት ያለ ሁኔታ የኢየሩሳሌምን ሴቶች እንደሚቀጣ መናገሩን ይቀጥላል።
ጌታ ይነጥቃቸዋል
ጌታ ሌሎች እንዲያደርጉ የሚያነሣሣው እርሱ የሚያደርገው እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጌታ ሌሎች እንዲነጥቋቸው ያደርጋል››
የእግር ዐልቦ
ከእግር ከፍ ብሎ ቁርጭምጭሚታቸው ላይ ሴቶች የሚያደርጉት ጌጥ።
የራስ መሸፈኛ
ሴቶች ራሳቸውና ጠጉራቸው ላይ የሚያደርጉት ጌጥ
የጨረቃ ቅርጽ ያለው የዐንገት ጌጥ
ሰዎችን ከክፉ ነገር ያድናል ብሎ በማሰብ ዐንገት ላይ የሚጠለቅ ባለ ጨረቃ ቅርጽ ጌጥ
የጆሮ ጉትቻ
ጆሮ ላይ የሚንጠለጠል ጌጥ
የእጅ አንባር
ሴቶች እጆቻቸው ላይ የሚያደርጉት ጌጥ
የፊት መሸፈኛ
የሴት ልጅን ፊትና ራስ የሚሸፍን በጣም ስስ ልብስ
የራስ መሸፈኛ
ሴቶች ራሳቸው ወይም ጠጉራቸው ላይ የሚያስሩት ረጅም ስስ ጨርቅ
ዐልቦ
ይህ ሴቶች ቁርጭምጭሚታቸው ላይ የሚያደርጉት ጌጥ ነው። ብዙውን ጊዜ ደስ የሚል ድምፅ እንዲኖረው ሰንሰለት ይንጠለጠልበታል።
ሻሽ
ሰዎች ወገባቸው ላይ የሚያደርጉት ጨርቅ
የሽቶ ብልቃጥ
መልካም ሽታ እንዲኖራቸው ሴቶች የሚቀቡት፣ በሰንሰለት ወይም በክር አንገታቸው ላይ የሚያንጠለጥሉት ብልቃጥ ወይም መያዣ
አሸንክታቡን
መልካም ዕድል እንዲያመጣ በማመን ሰዎች የሚያንጠለጥሉት ጌጥ

Isaiah 3:21
ቀለበቶች
ጣት ላይ የሚደረጉ ጌጣ ጌጦች
የአፍንጫ ቀለበቶች
አፍንጫ ላይ የሚደረጉ ጌጣ ጌጦች
ያማረውን ቀሚስ
ሰው ሁሉ እንዲያየው ከሌሎች ልብሶች በላይ የሚለበስ ረጅምና ሰፊ ባለ ጌጥ ቀሚስ
ካባውን
ከሌሎች ልብሶች በላይ ትከሻ ላይ የሚደረግ ልብስ
መሸፈኛውን
ኢሳይያስ 3፥19 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
የእጅ ቦርሳውን
ትንንሽ ነገሮች የሚይዙበት ቦርሳ
የእጅ መስታወት
በእጅ የሚያዝና ራስን ለማየት የሚያገለግል ትንሽ መስታወት
ጥሩ በፍታ
ሀብታዎች የሚለብሱት ስስ ልብስ
የራስ ጌጥ
ጠጉር ላይ የሚደረግ ልብስ ወይም ትንሽ ባርኔጣ
መጠምጠሚያውን
ውበት እንዲሰጣት ሴት ልጅ ላዩዋ ላይ የምትጠመጥመው ልብስ
Isaiah 3:24
ሻሽ
ሰዎች ወገባቸው ወይም ደረታቸው ላይ የሚለብሱት ልብስ። ኢሳይያስ 3፥20 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
ገመድ
ይህ የሚያመለክተው እነርሱን ሲይዟቸው ጠላቶቻቸው የይሁዳን ሰዎች የሚያስሩበትን ገመድ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ የኢየሩሳሌም ሴቶች በገመድ የሚታሰር ተራ ልብስ እንጂ፣ ሌላ ምንም የሚለብሱት እንደማይኖራቸው የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።
አምሮ በተሠራ ጠጉር ፈንታ ቡሀነት
‹‹ያመረ ጠጉር ቢኖራቸውም መላጣ ይሆናሉ››
ወንዶቻችሁ በሰይፍ፣ ይወድቃሉ ተዋጊዎቻችሁም በጦርነት ይወድቃሉ
መውደቅ መገደልን፣ ሰይፍ ጦርነትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወንዶቻችሁ በጦርነት ይገደላሉ፤ ተዋጊዎቻችሁ በውጊያ ይገደላሉ›› ወይም፣ ‹‹ጠላቶች ወታደሮቻችሁን በጦርነት ይገድሏቸዋል››
የኢየሩሳሌም ደጆች ያዝናሉ ያለቅሳሉ
እዚህ ላይ የከተማው ደጆች ከተማው ደጃፍ ላይ አደባባይ የሚቀመጡ ሰዎችን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የኢየሩሳሌም ሰዎች ከተማው በሮች ላይ ተቀምጠው ያዝናሉ ያለቅሳሉ››
ብቻዋን ትሆናለች መሬት ላይ ትቀመጣለች
ኢሳይያስ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ከጠላቶቿ የሚያድናት ሰው እንደሌላትና ወዳጆቿ ሁሉ ስለ ተውአት መሬት ላይ ተቀምጣ እንደምታለቅስ ሴት መሆናቸውን ይናገራል።

---

Chapter 4
Isaiah 4:1
በስምህ ብቻ እንጠራ
ይህ ሐረግ፣ ‹‹እናግባህ›› ማለት ነው።
የያህዌ ዛፍ ቅርንጫፍ ያማረ ይሆናል
ይህም ማለት 1) ‹‹ቅርንጫፍ›› ያህዌ በእስራኤል ምድር የሚያበቅለው እህል የሚወክል ቃል ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ የእስራኤልን እህል ያማረ ያደርጋል›› ወይም 2) ‹‹ቅርንጫፍ›› መሲሑን የሚመለከት ሊሆን ይችላል።
ያማረና የከበረ ይሆናል
‹‹ውበትና ክብር ይኖረዋል››
የምድሪቱ ፍሬ ከጥፋት ለተረፈው የእስራኤል ሕዝብ ጣፋጭና ደስ የሚያሰኝ ይሆናል
እንዳንዴ፣ ‹‹ፍሬ›› በምድሪቱ የሚገኝ ምግብን ይወክላል፤ አንዳንዴ መንፈሳዊ ባርኮትን ይወክላል። እዚህ ላይ የሚከተሉን ማለት ሊሆን ይችላል። 1) እግዚአብሔር ምድሪቱ እንደ ገና መልካም ምግብ እንድታበቅል ያደርጋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእስራኤል ያሉ ሰዎች የምድሪቱን መልካም ነገር ይበላሉ›› ወይም 2) ወደ ፊት የሚመጣው መሲሕ በምድሪቱ ላሉ ሰዎች መንፈሳዊ በረከት ይዞላቸው ይመጣል።
Isaiah 4:3
በጽዮን የቀሩት፤ በኢየሩሳሌም የተረፉት
ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች አንድ ትርጒም ነው ያላቸው። እዚህ ላይ፣ ‹‹የተረፉት›› ሲል ግለ ሰብን ሳይሆን በኢየሩሳሌም በሕይወት ያሉትን ሁሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በኢየሩሳሌም የሚቀር ሁሉ››
ቅዱሳን ተብለው ይጠራሉ
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጌታ ቅዱሳን በማለት ይጠራቸዋል›› ወይም፣ ‹‹የጌታ ይሆናሉ››
በኢየሩሳሌም በሕይወት ከተመዘገቡት ሁሉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስሙ በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች መዝገብ ያለ ሰው ሁሉ››
ጌታ የጽዮንን ሴቶች እድፍ ሲያጥብ
ይህ አባባል ኀጢአት እንደሚታጠብ እድፍ እንደ ሆነ ይናገራል፤ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታ እድፍ እንደሚያጠራ፣ የጽዮንን ሴቶች ኀጢአት ካጠበ በኃላ››
የጽዮን ሴቶች
ይህ ማለት፣ 1) የኢየሩሳሌም ሴቶች፤ ወይም 2) የኢየሩሳሌም ሕዝብ ማለት ሊሆን ይችላል።
ኢየሩሳሌምን ከተነከረችበት ደም ያነጻታል
‹‹የተነከረችበት ደም›› የሚያመለክተው ግፍንና ግድያን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጹሐንን የሚጐዱ የኢየሩሳሌምን ሰዎች ያስወግዳል››
በፍርድና መንፈስና በሚያቃጥል መንፈስ
እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ኀጢአት የሚያስወግደው በዚህ መንገድ ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹መንፈስ›› የፍርድና የማቃጠልን እንቅስቃሴ የሚወክል ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፍርድና በእሳት ነበልባል››
የፍርድ መንፈስ
ይህም ማለት 1) ያህዌ ሕዝቡን ይቀጣል፤ ወይም 2) ያህዌ ሕዝቡን በደለኛ ያደርጋል ማለት ሊሆን ይችላል።
በሚያቃጥል መንፈስ
ይህም ማለት 1) አንዳች ርኩስ ነገርን እንደሚስወግድ ያህዌ ኀጢአተኞችን ከጽዮን ያስወግዳል ማለት ሊሆን ይችላል፤ ወይም 2) ‹‹የሚያቃጥል እሳት›› የኀጢአተኞችን ሁሉ መደምሰስ ሊያመለክት ይችላል።
Isaiah 4:5
በክብሩ ሁሉ ላይ መጋረጃ
ይህም ማለት 1) የከበረችውን ከተማ የሚጋርድ መጋረጃ፤ ወይም 2) ከተማዋን የሚጋርድ መጋረጃን የያዘ የእግዚአብሔር ክብር ማለት ሊሆን ይችላል። የመጀመሪያውን ትርጉም ከያዝን ያህዌ በውስጧ ስለሚኖር ከተማዋ የከበረች ትሆናለች ማለት ነው።
መጋረጃ
ለመከለያ እንዲሆን አንዳች ነገር ላይ የተሰቀለ ጨርቅ ነው።

---

Chapter 5
Isaiah 5:1
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ገበሬውና ስለ ወይን እርሻው ምሳሌ ይናገራል። ገበሬው ያህዌን፣ የወይን እርሻው ደቡባዊውን የእስራኤል መንግሥት የይሁዳን ሕዝብ ይወክላል።
ወዳጄ
‹‹በጣም የምወደው››
በለመለመ ኮረብታ
‹‹መልካም ፍሬ በሚገኝበት ኮረብታ ላይ››
መሬቱን ቈፈረ
‹‹አፈሩን አዘጋጀ›› ይህ ለተክል ምቹ ለማድረግ መሬቱን በመቆፈሪያ መቆፈርን ያመለክታል።
በመካከሉ ማማ ሠራ
‹‹ላዩ ላይ ሆኖ ለመጠበቅ በመካከሉ ረጅም ግንብ ሠራ›› የወይን እርሻውን ለመጠበቅ አንድ ሰው ማማው ጫፍ ላይ ሆኖ ሰዎች ወይም እንስሳት ወደዚያ እንዳይገቡ ይከላከላል። ይህን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።
የወይን መጭመቂያ ጉድጓድም አበጀ
‹‹ወይኑን ለመጭመቅ ጉድጓድ ቆፈረ›› የወይን መጭመቂያ ሰዎች ወይን ፍሬውን እየረገጡ ጭማቂውን የሚያወጡበት መሬት ላይ ባለ ትልቅ ድንጋይ የተሠራ ነገር ነው።
ኮምጣጣ ፍሬ
‹‹የማይጠቅም ፍሬ›› ወይም፣ ‹‹የማይጣፍጥ ፍሬ››
Isaiah 5:3
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ወይኑ እርሻ በተናገረው ምሳሌ እግዚአብሔርን የሚወክለው ባለቤት፣ የወይን እርሻውን በተመለከተ ለኢየሩሳሌምና ለይሁዳ ሰዎች ይናገራል።
በኢየሩሳሌም የምትኖሩ የይሁዳ ሰዎች
ይህ የሚናገረው በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ነው፤ ስለዚህ በብዙ ቁጥር መናገር ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኢየሩሳሌምና በይሁዳ የምትኖሩ ሁሉ››
ኢየሩሳሌም... ይሁዳ
‹‹ይሁዳ›› የደቡባዊው እስራኤል መንግሥት ስም ነበር፤ ዋና ከተማውም ኢየሩሳሌም ነበር።
በእኔና በወይን ቦታዬ መካከል እስቲ ፍረዱ
በሁለት ነገሮች መካከል ያለ ክፍት ቦታ ብዙውን ጊዜ ከሁለት አንዱን የመምረጥን ሐሳብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማን ትክክል እንደ ነበር ፍረዱ፤ እኔ ወይስ የወይን ቦታዬ››
ከዚህ ካደረግሁለት በላይ ለወይኔ ቦታ ምን ሊደረግለት ይገባ ነበር?
ባለቤቱ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ስለ ወይን ቦታው ጠንከር አድርጐ ለመናገር ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለወይን ቦታዬ ማድረግ የምችለውን ሁሉ አድርጌአለሁ››
መልካም የወይን ፍሬ ያፈራል ብዬ ስጠብቅ ለምን ኮምጣጣ ፍሬ አፈራ?
ባለቤቱ ጥያቄውን ያቀረበው የወይን ቦታው መልካም ፍሬ ማፍራት እንደ ነበረበት ለመናገር ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የፈለግሁት ጥሩ ፍሬ እንዲያፈራ ነበር፣ ግን ኮምጣጣ ፍሬ አፈራ››
Isaiah 5:5
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ባቀረበው ምሳሌ የወይኑ ቦታ ባለቤት ስለ ወይን ቦታው መናገር ቀጥሏል።
ሐረጉን እነቅላለሁ
‹‹የቁጥቋጦውን ሐረግ እነቅላለሁ›› ሐረግ መደዳውን ያለ ቁጥቋጦ ወይም የአትክልት ቦታን ወይም ሌላ ክልልን ለመጠበቅ መደዳውን የሚተከል ዛፍ ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ሐረግ›› ምናልባት ወይን ቦታው ዙሪያ ባለው ግንብ ላይ የሚተከል እሾኻማ ቁጥቋጦ ሊሆን ይችላል።
የግጦሽ ቦታ እንዲሆን አደርጋለሁ
‹‹ከብቶች ገብተው የሚመገቡበት ቦታ አደርገዋለሁ›› ይህ ከብቶች የሚመገቡት ሣር የበዛበት ቦታ ነው።
መረጋገጫም ይሆናል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከብቶች ይረጋግጡታል››
ጠፍ መሬት አደርገዋለሁ
‹‹አጠፋዋለሁ››
ከእንግዲህ አይኮተኮትም አይታረምም
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም አይኮተኩተውም፤ አያርመውም›› ወይም፣ ‹‹ማንም የማያስፈልጉትን ቅርንጫፎች አይቆርጥም፤ ለአፈሩም ጥንቃቄ አያደርግም››
ኵርንችትና እሾኽም ይበቅልበታል
ብዙውን ጊዜ ኵርንችትና እሾኽ ጠፍ የሆኑ ከተሞችንና አገሮችን ለማመልከት ጥቅም ላይ ይውላሉ።
Isaiah 5:7
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ወይኑ ቦታ ገለጻ ይሰጣል
የሰራዊት ጌታ የያህዌ የወይን ቦታው የእስራኤል ቤት ነው።
ምሳሌው ውስጥ ያለው ወይን ቦታ የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚወክል ኢሳይያስ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ የያህዌ ወይን ቦታ የእስራኤልን ቤት ይወክላል›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ የሰራዊት ጌታ የያህዌ ወይን ቦታ ናቸው››
የእስራኤል ቤት
‹‹ቤት›› — ቤቱ ውስጥ የሚኖረውን ቤተ ሰብ ያመለክታል። እዚህ ላይ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስራኤል›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል መንግሥት›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ››
የይሁዳ ሰዎች የደስታ አትክልት ናቸው
የይሁዳ ሰዎች ያህዌ የተከለው ወይን ዛፍ መሆናቸው ተነግሯል። ይህን በምስስል ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የይሁዳ ሰዎች ለያህዌ ደስታ ያህዌ እንደ ተከለው ወይን ዛፍ ናቸው››
የይሁዳ ሰዎች
‹‹ሰዎች›› የሚወክለው የይሁዳን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የይሁዳ

ሕዝብ››
ፍትሕን ፈለገ፤ ግን ግድያ ነበረ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ፍትሕ›› የሚለውን፣ ‹‹መልካሙን ማድረግ›› ብሎ መለወጥ ይችላል። ‹‹ግድያ›› የሚለውን፣ ‹‹እርስ በርስ መገዳደል›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ሕዝቡ መልካም ነገር እንዲያደርግ ፈለገ፤ ግን እርስ በርስ ተገዳደሉ››
ጽድቅን ፈለገ
‹‹ፈለገ›› የሚለውን በዚህ ቁጥር ከተመለከትነው መረዳት ይቻላል። ትርጉሙን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ መደጋገም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጽድቅን ፈለገ›› ወይም፣ ‹‹መልካም የሆነውን እንዲያደርጉ ፈለገ››
ይልቁን የጭንቅ ጩኸት ነበረ
‹‹ነበረ›› የሚለውን ቀደም ሲል ከነበረው ቁጥር መረዳት ይቻላል። ትርጉሙን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ መደጋገም ይቻላል። ሰዎች ርዳታ ለመፈለግ የጮኹበትን ምክንያት የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይልቁን የርዳታ ጩኸት ነበረ›› ወይም፣ ‹‹ይልቁን ሌሎች ስላጠቋቸው የሚረዳቸው ሰው ፍለጋ ጩኸት ነበረ››
ጩኸት
ምናልባት ብዙ ጩኸቶችን የሚያመለክት ገለጻ ሊሆን ይችላል።
Isaiah 5:8
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ፍርድ ይናገራል
ቤትን ቤት ላይ መሬትን ከመሬት ጋር ለማያያዝ
‹‹በጣም ብዙ ቤቶችን፣ በጣም ብዙ መሬቶችን የሚወስዱ›› ለዘለቄታው ከቤተ ሰብ መሬት መውሰድን ሕጉ እንደሚከለክል ሰሚዎቹ እንደሚረዱ ኢሳይያስ ይገነዘባል። ይህን ዐረፍተ ነገር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።
የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
ወና ይቀራሉ
‹‹ማንም አይኖርባቸውም››
የዐሥር ጥማድ ወይን እርሻ
የወይን እርሻው ስፋት ያንን ለማረስ በቀን ውስጥ በሚያውላቸው ጥማድ በሬዎች ብዛት ይገመታል። እያንዳንዱ ጥማድ በሬ በቀንበር ይያያዛል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐሥር ጥማድ በሬዎች የሚያውል እርሻ››
አንድ መስፈሪያ የወይን ጭማቂ
‹‹አንድ መስፈሪያ ወይን ጭማቂ›› ወይም፣ ‹‹22 ሊትር ወይን ጭማቂ›› አንድ ጐሜር ከዐሥር ኢፍ ጋር እኩል ነው።
አንድ የጐሜር መስፈሪያ አንድ ኢፉ ብቻ ይሰጣል።
‹‹220 ሊትር ዘር 22 ሊትር እህል ብቻ ይሰጣል።›› አንድ ጐሜር ከአሥር ኢፉ ጋር እኩል ነው።
Isaiah 5:11
ማልደው ለሚነሡ… ሌሊቱን ለሚያነጉ
ይህ የሚያመለክተው አልኮል ከመጠጣት ውጪ ቀኑን ሙሉ ምንም ስለማይሠሩ ሰዎች ነው።
እስኪያነጻቸው ወይን በመጠጣት
ጠጪዎቹን የሚያሰክር ወይን ጠጅ የሚያቃጥል ወይም የሚያነድ እሳት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በወይን ጠጅ እስኪሰክሩ ድረስ››
በገና፣ መሰንቆ፣ ከበሮ፣ ዋሽንትና ወይን ጠጅ
እነዚህ የሙዚቃ መሣሪያዎችና ወይን ጠጅ ሰዎቹ በፈንጠዝያ ጊዜያቸውን እንደሚያሳልፉ ያመለክታሉ።
ከበሮ
በእጅ የሚመታ፣ እንደ ታንቡር የሚመታ ራስ ያለው የሙዚቃ መሣሪያ። ምናልባትም ተጫዋቹ ሲንጣቸው ድምፅ የሚሰጡ የብረት ቁርጥራጮች ዙሪያውን ሊኖሩት ይችላሉ። ከበሮው ተጫዋቹ በአንድ እጁ ይዞ እስኪንጠው ደረስ በጣም ትንሽ ሊሆን ይችላል።
አልሰጡም
አጥብቀው አላሰቡም
የእጆቹን ሥራ
‹‹ሥራ›› የሚለውን፣ ‹‹ያደረገውን›› ወይም፣ ‹‹የፈጠረውን›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ያደረገውን›› ወይም፣ ‹‹እርሱ የፈጠረውን››
የእጆቹን ሥራ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጆች›› አንዳች ነገር ያደረገ ሰውን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ያደረገውን››
Isaiah 5:13
አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ያመለክታሉ።
ሕዝቤ በምርኮ ተወስደዋል
በትንቢት ወደ ፊት የሚፈጸሙ ነገሮች ብዙውን ጊዜ አሁንእንደ ተፈጸሙ ተደርጐ ይነገራል። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ትንቢቱ በእርግጥ የሚፈጸም መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሌላ አገር የመጣ ጠላት ሕዝቤ እስራኤልን በባርነት ይወስዳል››
ዕውቀት በማጣት
ያላወቁት ምን እንደ ነበር ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን ወይም ሕጉን አላወቁም››
ሲኦል ሆዷን አሰፋች፤ አፏንም ያለ ልክ ከፈተች
ይህ ሐረግ የሚናገረው በመቃብር ወይም ሌሎች እንስሳትን በሚበላ አውሬ ስለ ተመሰለው ስለ ሲኦል ነው። በጣም ብዙ ሰዎች እንደሚሞቱ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሞት ብዙ ሰዎችን ለመብላት እንደ ተራበ አውሬ አፉን በሰፊው ከፍቷል››
መኳንንቱ፣ ሕዝቡ፣ መሪዎቻቸውና ረብሻኞቻቸውና ጨፋሪዎቻቸው ወደ ሲኦል ይወርዳሉ
ነቢዩ አሁን የተፈጸመ ይመሳል ስለ የወደ ፊቱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙ የእስራኤል ሰዎች፣ ታላላቅና ታናናሾቻቸው፣ መሪዎቻቸውና ጭፈራን የሚወዱ ወደ ሲኦል ይወርዳሉ››
Isaiah 5:15
ሰው ይዋረዳል፤ የሰው ልጅም ዝቅ ይላል
ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ሲሆን፣ በአንድነት የተነገሩት አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በሌላ መልኩ ማቅረብ ይቻላል። ኢሳይያስ 2፥9 ላይ ተመሳሳይ ነገርን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ ዝቅ በማድረግ ያዋርዳል››
ሰው ይዋረዳል፤ የሰው ልጅም ዝቅ ይላል
ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮች አሁን እንደ ተፈጸሙ ተደርጐ ተነግሮአል።
ሰው ይዋረዳል
ብዙውን ጊዜ እንዲህ ሲባል የሚያመለክተው እጅግ ዝቅ ማለትን ነው።
የእብሪተኛው ዐይን ይሰበራል
ብዙውን ጊዜ መሰበር የእፍረት ምልክት ነው። ኢሳይያስ 2፥11 ተመሳሳዩን ቃል እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የትዕቢተኛው ዐይን በእፍረት መሬት ያያል›› ወይም፣ ‹‹ትዕቢተኞች የነበሩ አሁን አፍረዋል››
ከፍ ከፍ ያለ
ትዕቢተኛና እብሪተኛ ሰዎች ከሌሎች ይልቅ በጣም ከፍ ከፍ ያሉ መሆናቸው ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኩሩዎች››
የሰራዊት ጌታ ያህዌ በፍትሕ ከፍ ከፍ ይላል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ትክክል በመሆኑ ሰዎች የሰራዊት ጌታ ያህዌን ያመሰግናሉ››
የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት
ከፍ ከፍ ይላል
መከበር ከፍ ከፍ ማለት እንደ ሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እጅግ ይከበራል››
በጐች በገዛ መሰማሪያቸው ይግጣሉ
ያህዌ ኢሳይያስ 5፥1 ላይ፣ ‹‹የወይን ቦታ›› ተብሎ የተጠራውን የኢየሩሳሌም ከተማ ያጠፋል። የበጐች መሰማሪያ ከመሆን ውጪ ለምንም አይጠቅምም።
ይግጣሉ
ሣር ይበላሉ
የበግ ጠቦቶችም በፍርስራሽ ላይ ሣር ይበላሉ
ይህ ጠቦቶቹ እዚያ ሣር ይበላሉ ማለት ነው። ቦታው ለሌላ ነገር አይጠቅምም።
Isaiah 5:18
ኀጢአትን በከንቱነት ገመድ ለሚስቡ፤ በደልንም በሰረገላ ማሰሪያ ለሚጐትቱ ወዮላቸው።
እነዚህ ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ነው ያላቸው። በሙሉ ኀይላቸው በገመድ ሰረገላ የሚጐትቱ ይመስል ሆን ብለው ኀጢአት በመሥራት ይጸናሉ።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እግዚአብሔር ለኀጢአታቸው ይቀጣቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰረገላን በገመድ እንደሚጐትት ሰው ኀጢአት ለማድረግ በርትቶ ለሚሠራ ሰው ወዮለት››
እንዲህ ለሚሉ
ይህ የሚያመለክተው በኀጢአት የጸኑትንና (ቁ.18) እንዲያስቆማቸው በፌዝ እግዚአብሔርን የሚገዳደሩትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እያፌዙ እንዲህ ለሚሉ››
የእስራኤል ቅዱስ ዕቅድ ትምጣ
የእግዚአብሔር ዕቅድ በራሳቸው ጊዜ ማምጣት የሚችሉት ነገር ተደርጐ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ቅዱስ ዕቅዱን ይፈጽም››
የእስራኤል ቅዱስ
ይህን ኢሳይያስ 5፥16 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጕመው።
Isaiah 5:20
ጨለማውን ብርሃን፣ ብርሃኑን ጨለማ ለሚሉ፣ መራራውን ጣፋጭ ጣፋጩን መራራ ለሚሉ
እነዚህን ነገሮች የሚያደርጉ፣ ‹‹ክፉውን መልካም፣ መልካሙን ክፉ›› እንደሚሉ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ነገሮች ተቃራኒዎች ናቸው፤ ሰዎች በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ያውቃሉ፤ አንዳንዶች ግን በሐሰት መጥፎ ነገሮች መልካም እንደሆኑ ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨለማውን ብርሃን፣ ብርሃኑን ጨለማ እንደሚሉ ሰዎች ናቸው፤ መራራውን ጣፋጭ ጣፋጩን መራራ እንደሚሉ ሰዎች ናቸው።››
በራሳቸው ዐይን አስተዋዮች የሆኑ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐይን›› የሚወክለው አስተሳሰብን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራሳቸውን እንደ አስተዋይ የሚመለከቱ››
በራሳቸውም አመለካከት ጥበበኞች ለሆኑ
‹‹ሁሉንም ነገር መረዳት የሚችሉ የሚመስላቸው››
Isaiah 5:22
ጉቦን በመቀበል በደለኛን ንጹሕ ለሚያደርጉ
ይህ ምንባብ የሚያመለክተው ፍርድ ቤት ውስጥ ስላሉ ብልሹ ዳኞች ነው።
በደለኛውን ንጹሕ ለሚያደርጉ
‹‹በደል ያለባቸውን ሰዎች ንጹሕ ናችሁ ለሚሉ››
ለበደል አልባ ፍትሕ ለሚነፍጉ
‹‹ንጹሕ ሰዎችን በአግባቡ ለማያስተናግዱ››
Isaiah 5:24
የእሳት ልሳኖች
‹‹የእሳት ነበልባል›› ወይም፣ ‹‹ነበልባል››
የእሳት ነበልባል ገለባን እንደሚበላ፣ ድርቆሽም በእሳት ጋይቶ እንደሚጠፋ
የእነዚህ ሐረጐች ትርጉም በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው። ኢሳይያስ 5፥18-23 ላይ የተጠቀሱትን ሰዎች እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእሳት ነበልባል ገለባን እንደሚያቃጥል››
ገለባ
እህል ከታጨደ በኋላ እርሻው ላይ የሚቀር ደረቅ የተክሎች አካል።
ሥራቸው ይበሰብሳል፤ አበባቸውም እንደ ትቢያ ይሆናል
እነዚህ ሰዎች እንደ ሞቱ ተክሎች እንደ ሆነ ኢሳይያስ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሥሩ እንደበሰበሰ ተክል ይሞታሉ፤ ደርቆ በነፋስ እንደሚወሰድ አበባ ይበንናሉ››
Isaiah 5:25
የያህዌ ቁጣ ነደደ
ኢሳይያስ የያህዌ ቁጣ እንደ እሳት እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ በጣም ተቆጥቷል››
እነርሱ ላይ እጁን በመዘርጋት ቀጣቸው
ነቢዩ የወደ ፊቱን አሁን እንደ ተፈጸመ ይናገራል። እንዲህ ያደረገው ትንቢቱ በትክክል እንደሚፈጸም አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብርቱ በሆነው እጁ ይቀጣቸዋል››
እጁን በእነርሱ ላይ ዘረጋ
እዚህ ላይ ‹‹እጅ›› የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኀይልና ቁጥጥር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱ ላይ ኀይሉን ገለጠ››
ሬሳዎች
የሞቱ ሰዎች
ሬሳዎቻቸው በመንገድ ላይ እንደ ተጣለ ጥራጊ ናቸው
ጥራጊ ይመስል የሞቱ ሰዎች ሬሳ መንገድ ላይ እንዲጣል ይደረጋል። ይህም ብዙዎች እንደሚሞቱና የሚቀብራቸው እንደማይኖር ያመለክታል። ‹‹ጥራጊ›› የሚለው ቃል፣ ‹‹ቆሻሻ›› ወይም፣ ‹እበት›› ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ቁጣው ገና አልተመለሰም እጁም ገና እንደ ተዘረጋ ነው።
‹‹ይህ ሁሉ ሆኖ እንኳ፣ አሁንም እንደ ተቆጣ ነው፤ እጁም››
እጁ ገና እንደ ተዘረጋ ነው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የእግዚአብሔርን ኀይልና የበላይነት ይመለከታል። ኢሳይያስ ያህዌ እንደ ሰው የሚማታ እንደ ሆነ ይናገራል። ይህ ያህዌ እስራኤልን የመቅጣቱ ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁንም ሊቀጣቸው ዝግጁ ነው››
Isaiah 5:26
ከሩቅ ያሉትን ሕዝቦች የሚጠራበትን ምልክት ያቆማል፤ ከምድር ዳርቻም በፉጨት ይጠራቸዋል።
ኢሳይያስ በሁለት የተለያዩ መንገዶች የሚናገረው ስለ አንድ ጉዳይ ነው። ከይሁዳ በጣም ርቀው ያሉት ሕዝቦች መጥተው እንዲያጠቁ ማድረጉ፣ እነርሱን ወደ ይሁዳ ለመጥራት ምልክት ማቆምና ማፏጨት ተደርጐ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከይሁዳ በጣም ርቀው ያሉትን የአሕዛብ ሰራዊት ይጠራና እንዲመጡ ይነግራቸዋል››
ማፏጨት
ሰውን ወይም እንስሳን ለመጥራት አንድ ሰው ከአፉ የሚያወጣው ከፍ ያለ ቃና ያለው ድምፅ
ይመጣሉ
‹‹የጠላት ሰራዊት ይመጣሉ››
እየተጣደፉ በፍጥነት
እነዚህ ቃሎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ ምን ያህል ቶሎ እንደሚመጡ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ፈጥነው››
Isaiah 5:27
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ይሁዳን ስለሚያጠቃው ሰራዊት መናገሩን ቀጥሏል። አሁን እንኳ እንደ መጣ አድርጐ ይናገራል። (ኢሳይያስ 5፥26 ይመ.)
ደካማ፣ ስንኩል፣ የሚያንቀላፉ፣ የሚተኛ
እነዚህ አራት ቃሎች በሥራ ከመድከም እስከ መራመድ አለመቻል፣ ንቁ ለመሆን ካለመቻል እስከ ሙሉ በሙሉ ንቁ አለ መሆን እያደጉ ይሄዳሉ፤ ስለዚህ ትርጉሙ ውስጥ አራቱም መኖር አለባቸው።
ቀበቶአቸውንም አይፈቱም
በቀላሉ ተነሥተው መዋጋት እንዲያስችላቸው ወታደሮች ሁሌም ትጥቃቸው እንደ ተጠበቀ ነው።
የጫማቸውም ማሰሪያ አይበጠስም
‹‹የጫማቸው ክር››
የፈረሶቻቸው ሸኾና እንደ ባልጩት ናቸው
‹‹ሸኾናቸው እንደ ጠንካራ ድንጋይ ነው›› ኢሳይያስ የፈረሶችን እግር ጠንካራ ክፍል ከተነካ የእሳት ብልጭታ ከሚወጣው ከጠንካራው ድንጋይ ከባልጩት ጋር ያመሳስለዋል። ይህም ማለት 1) ኢሳይያስ ሸኾናቸውን ከባልጩት ጋር ያመሳሰለው በሚሮጡበት ጊዜ የሚወጣውን ብልጭታ አስፈሪነት ለማሳየት ሊሆን ይችላል። ወይም 2) ኢሳይያስን ሸኾናቸውን ከባልጩት ጋር ያመሳሰለው ፈረሶቹ ጌቶቻቸው የሚፈልጉትን ሁሉ ለማድረግ እንዲያስችላቸው ሸኾናቸው ምን ያህል ጠንካራ እንደ ሆነ ለማሳየት ሊሆን ይችላል።
የሠረገሎቻቸው መንኰራኲሮች እንደ ዐውሎ ነፋስ ናቸው
በመንገዳቸው የሚገኙትን ሁሉ እንደሚያጠፉ ለማሳየት ኢሳይያስ የሠረገሎቹን መንኮራኩር ከዐውሎ ነፋስ ጋር አመሳስሎታል።
የሠረገሎች መንኮራኲሮች
ከእነዚህ መንኮራኲሮች ጋር የተያያዙ ስለታም ነገሮች አሉ፤ በአጠገቡ የሚያልፈውን ነገር ደቅቁታል።
Isaiah 5:29
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ይሁዳን ስለሚያጠቃው ሰራዊት መግለጹን ቀጥሏል።
ሠረገሎቹ እንደ አንበሳ ያገሳሉ፤ እንደ አንበሳ ደቦል ያገሣሉ።
እነዚህ ሐረጐች በመሠረቱ የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ነው። ድምፃቸው የይሁዳን ሕዝብ በጣም እንደሚያስፈሩ ለማመልከት ኢሳይያስ የጠላትን ሰራዊት ከአንበሳ ጋር ያመሳስላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጦርነት ጊዜ ሰራዊቱ ሲጮኹ የሚያገሣ አንበሳ ይመስላሉ››
የአንበሳ ደቦል
ወጣትነት የብርታት መገለጫ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብርቱ አንበሳ››
ያደነቱንም ይዘው ይጮኻሉ

ጠላት የይሁዳን ሕዝብ መግደሉን አንበሳ ደካማውን እንስሳ ከመግደሉ ጋር ኢሳይያስ ያመሳስላል። ይህም ማለት 1) አንበሶች ጥቃት ከማድረሳቸው በፊት ከፍ ያለ ጩኸት አያሰሙም። ወይም 2) ጸሐፊው በሁለት ቃላት የተጠቀመው አንድ ትርጉም ስላለው ነገር ለመናገር ነው።

ንጥቂያ

አራዊት አድነው የሚዙት እንስሳ

የሚያስጥልም የለም

‹‹ማንም ሊያድናቸው አይችልም››

ያገሣሉ... እንደ ባሕር ሞገድ

እነዚህ ቃሎች ቁጥር 29 ላይ፣ ‹‹ይጮኻሉ›› በሚል የተተረጐሙት ናቸው። የባሕር ሞገድን ወይም ከባድ ዝናብን ወይም ሌላ አስፈሪ ተፈጥሮአዊ ድምፅን የሚመለክት ቃል በቋንቋህ ካለ ተጠቀምበት።

ብርሃን እንኳ በደመናዎች ይጨልማል

እዚህ ላይ፣ ጨለማ መከራና ጥፋትን ይወክላል። ምሳሌያዊ ቋንቋውን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨለማው ደመና የፀሐይ ብርሃንን ፈጽሞ ይጋርዳል››

---

Chapter 6

Isaiah 6:1

ከፍ ባለና በከበረ

‹‹ከፍ ያለ››እና፣ ‹‹የከበረ›› የተሰኙት ቃሎች ዙፋኑ በጣም ከፍ ያለና በዙሪያው ካሉት ሁሉ በላይ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ። የዙፋኑ ከፍታ ጌታ ምን ያህል ታላቅና ኀያል መሆኑን ያመለክታል።

ቤተ መቅደሱን ሞላው

‹‹ቦታውን ሞላው››እዚህ ላይ ቤተ መቅደስ ለማለት ጥቅም ላይ የዋለው ቃል ብዙውን ጊዜ ቤተ መንግሥትን ነው የሚያመለክተው።

ከበላዩም ሱራፌል ነበሩ

‹‹ሱራፌል›› የሚለው ቃል፣ ሱራፍ የሚለው ብዙ ቁጥር ነው። ይህም ማለት ጌታ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ነበር፤ ሱራፌልም ለማገልገል ዝግጁ ሆነው ጌታ አጠገብ ቆመው ነበር ወይም እየበረሩ ነበር ማለት ነው።

ሱራፌል

ይህ ቃል እነዚህ ፍጡራን የእሳት ነበልባል ወይም እባብ የሚመስል ሁኔታ ሳይኖራቸው እንዳልቀረ ያመለክታል። ‹‹ሱራፌል›› ምን ማለት እንደ ሆነ በትክክል ስለማይታወቅ ‹‹ባለ ክንፍ ፍጥረቶች›› ወይም፣ ‹‹ክንፋም ሕያው ፍጥረቶች›› በማለት መተርጐም ትችላለህ። ወይም ቃሉን ወስደህ በቋንቋህ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

እያንዳንዱ ስድስት ክንፎች ነበሩት

‹‹እያንዳንዱ ሱራፍ ስድስት ክንፎች ነበሩት›› ወይም፣ ‹‹እያንዳንዱ ፍጡር ስድስት ክንፎች ነበሩት››

በሁለቱ ፊታቸውን ይሸፍኑ ነበር፤ በሁለቱ እግራቸውን ይሸፍኑ ነበር፤ በሁለቱም ይበሩ ነበር

‹‹ክንፍ›› እና፣ ‹‹ሱራፍ›› የተሰኙት ቃሎች ውስጠ ታዋቂ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እያንዳንዱ ሱራፍ በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር፤ በሁለቱ ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር፤ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር››

Isaiah 6:3

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ስለ ራእዩ መናገሩን ቀጥሏል

እርስ በርሳቸውም በመቀባበል እንዲህ ይሉ ነበር

‹‹ሱራፌል በመቀባበል እንዲህ ይሉ ነበር›› ወይም፣ ‹‹ባለ ክንፍ ፍጥረቶቹ አንዱ ለሌላው እንዲህ ይል ነበር››

ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ጌታ እግዚአብሔር

‹‹ቅዱስ›› የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ መደጋገሙ እግዚአብሔር ፍጹም ቅዱስ እንደሆኑ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታ ያህዌ ከሁሉም በላይ ቅዱስ ነው። ወይም፣ ‹‹ጌታ ያህዌ ፍጹም ቅዱስ ነው››

ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች

ይህ ምድር መያዣ እንደሆነች፣ ክብር ደግሞ መያዣውን የሚሞላ ነገር እንደ ሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር ያለ ማንኛውም ነገር የእግዚአብሔር ክብር ማስረጃ ነው››

Isaiah 6:4

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ስለ ራእዩ መናገሩን ቀጥሏል።

ከድምፃቸው ጩኸት የተነሣ የመድረኩ መሠረት ተናወጠ

‹‹ሱራፌል ሲጮኹ ድምፃቸው መድረኩንና መሠረቱን አናወጠው››

ቤቱ በጢስ ተሞላ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤተ መቅደሱን ጢስ ሞላው›› ወይም፣ ‹‹ቤተ መንግሥቱን ጢስ ሞላው››

ጠፍቻለሁ ወዮልኝ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታላቅ ችግር ውስጥ ነኝ! አስቸጋሪ ነገር ይደርስብኛል››

ከንፈሮቼ የረከሱብኝ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ከንፈሮች›› ሰው የሚናገረውን ያመለክታሉ። ሰዎች እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኝ ነገር መናገራቸው የከንፈሮቻቸው መርከስ ማለት እንደ ሆነ ተነግሯል።

ያህዌ፣ የሰራዊት ጌታ ያህዌ

‹‹የመላእክት ሰራዊት ገዢ ያህዌ››

ዐይኖቼ ዐይተዋል

‹‹ዐይኖች›› መላውን ሰው ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አይቻለሁ››

Isaiah 6:6

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ስለ ራእዩ መናገሩን ቀጥሏል።

ሱራፌል

እነዚህ ፍጥረታት እሳት፣ የእሳት ነበልባልና እባብ መሰል ሁኔታ ሳይኖራቸው አልቀረም። ‹‹ሱራፌል›› ምን ማለት እንደ ሆነ በትክክል ስለማይታወቅ፣ ‹‹ፍጡሮች›› ወይም፣ ‹‹ሕያው ነገሮች›› ወይም፣ ‹‹ኀላዌ›› በማለት መተርጐም ትችላለህ። ወይም ይህን ቃል ወስደህ ቋንቋህ ውስጥ ልትጠቀምበት ትችላለህ። ኢሳይያስ 6፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ጉጠት

ነገሮችን ለመያዝ የሚረዳ መሣሪያ

በደልህ ተወግዶልሃል፤ ኀጢአትህም ተሰርዮልሃል

እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ በደልህን አስወግዷል፤ ኀጢአትህንም ይቅር ብሎልሃል››

በደልህ ተወግዶአል

ያህዌ አንድን ሰው ከእንግዲህ እንደ በደለኛ እንደማይቆጥረው ለማሳየት፣ ‹‹በደል›› አንድ ሰው ከሌላው የሚወስደው ነገር እንደ ሆነ ተነግሯል።

Isaiah 6:8

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ስለ ራእዩ መግለጹን ቀጥሏል

የጌታም ድምፅ እንዲህ አለ

‹‹ድምፁ›› ጌታ ራሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታ እንዲህ አለ››

ማንን እልካለሁ?

ይህ የሚያመለክተው የእርሱን መልእክት ለእስራኤል ሕዝብ እንዲናገር ያህዌ አንድ ሰው እንደሚልክ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሕዝቤ መልእክተኛ እንዲሆን ማንን እልካለሁ››

ማንስ ይሄድልናል?

‹‹እኛ›› የሚለው የሚያመለክተው ያህዌንና እርሱ እየተናገራቸው ያለውን የሰማይ መማክርት ነው።

ይህ ሕዝብ

‹‹የእስራኤል ሕዝብ››

ይሰማሉ፤ ግን አያስተውሉም፤ ያያሉ ግን ልብ አይሉም

ይህም ማለት፣ 1) ‹‹አያስተውሉም›› እና፣ ‹‹ልብ አይሉም›› የሚሉት ያህዌ የሚያደርገውን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ትሰማላችሁ ግን ያህዌ እንድታስተውሉ አያደርጋችሁም፤ በጥንቃቄ ታያላችሁ ግን ያህዌ ልብ እንድትሉ አያደርጋችሁም›› ወይም 2) ‹‹መስማት›› እና፣ ‹‹ማየት›› የተሰኙት ሐረጐች ‹‹እንዲህ ቢሆን›› የሚል ሐሳብ ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብትሰሙ እንኳ አታስተውሉም፤ በጥንቃቄ ብታዩ እንኳ ልብ አትሉም››

ይሰማሉ ግን አያስተውሉም፤ ያያሉ ግን ልብ አይሉም

በውስጠ ታዋቂነት ያለውን መረጃ መግለጽ ይቻላል። ‹‹የያህዌን መልእክት



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይሰማሉ፣ ግን ምን ማለት እንደ ሆነ አያስተውሉም፤ ያህዌ እያደረገ ያለውን ያያሉ፤ ግን ምን እንደሆነ አይገነዘቡም››

Isaiah 6:10

አጠቃላይ መረጃ

ለሕዝቡ እንዲሰብክ ሲልከው ምን ማለት እንዳለበት ያህዌ ለኢሳይያስ መናገሩን ቀጥሏል።

የዚህን ሕዝብ ልብ አደንድን

‹‹ልብ›› የሚወክለው የሰውን አእምሮ ነው። በደንብ የማይሰማና መረዳት የማይችል ሰው ልቡ የደነደነ እንደሆነ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ ሕዝብ መረዳት እንዳይችል አድርግ›› ወይም፣ ‹‹የዚህን ሕዝብ አእምሮ ደነዝ አድርግ››

የዚህን ሕዝብ ልብ

‹‹ልብ›› እና፣ ‹‹የዚህ›› የሚሉትን ቃሎች በብዙ ቁጥር መተርጐም የበለጠ አግባብነት ይኖረዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእነዚህን ሰዎች ልቦች››

ልብ… አደንድን

የተሰጠው ትእዛዝ የኢሳይያስን መልእክት እንዳያስተውሉ ለማድረግ፣ ያህዌ እያደረገ ላለው የበለጠ ደንዳኖች እንዲሆኑ ያህዌ የሚጠቀምበት መሆኑ ነው።

ጆሮአቸውን ደፈን፤ ዐይኖቻቸውንም አሳውር

‹‹እንዳይሰሙ አድርገው፤ እንዳያዩ አድርገው›› ኢሳይያስ ሰዎች የያህዌን መልእክት እንዳያስተውሉ ማድረጉ ወይም እያደረገ ያለው ደንቆሮና ዕውሮች እያደረጋቸው እንደሆነ ተነግሯል።

በዐይናቸው ዐይተው፤ በጆሮአቸውም ሰምተው

x

Isaiah 6:11

ከተሞች እስኪፈራርሱ፣ ቤቶችም የሚኖርባቸው እስኪያጡ

‹‹ማንም እንዳኖርባቸው ከተሞችና ቤቶች እስኪወድሙ ድረስ››

ምድርም ፈጽሞ ባድማ እስክትሆን ድረስ

‹‹ባድማ›› መሆን እስከፊ ደረጃ ላይ መድረስ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምድሪቱ ጠፍ ምድረ በዳ እስክትሆን››

ያህዌ ሕዝቡን ወደ ሩቅ እስከሚሰድና የምድሪቱ ባዶነት ከባድ እስኪሆን

እዚህ ላይ ያህዌ ስለ ራሱ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ሕዝቡን ከምድራቸው ወደ ሩቅ አገር እስከምሰድና እዚያ ማንም እስከማይቀር ድረስ››

Isaiah 6:13

እንደገና ይጠፋል

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰራዊት እንደ ገና የእስራኤልን ምድር ያጠፋሉ››

የኮምባል ወይም የባሉጥ ዛፍ በተቆረጠ ጊዜ ጉቶ እንደሚቀር ቅዱሱም ጉቶ ሆኖ ይቀራል

ይህ ምስስል ያህዌ እስራኤልን ቢያጠፋ እንኳ፣ ከእነርሱ መካከል እርሱን የሚያገለግሉትን ለይቶ እንደሚያስቀር ያመለክታል።

ኮምበል

ወርካ የሚመስል ዛፍ

ግንድ… ጉቶ

ግንድ ጠንካራው የዛፍ አካል ነው፤ ጉቶ ዛፍ ከተቆረጠ በኃላ ምድር ውስጥ የሚቀረው ነው።

ቅዱሱም ዘር

ሰራዊቱ እስራኤልን ካጠፋ በኃላ ያህዌን የሚያገለግሉ ሰዎች እንደ ቅዱስ ዘር የተለዩ እንደሚሆኑ ተነግሯል።

Chapter 7

Isaiah 7:1

በይሁዳ ንጉሥ በአካዝ ዘመን

‹‹አካዝ የይሁዳ ንጉሥ በነበረ ዘመን›› — ይህ ታሪኩ የተፈጸመበት ነው።

ረአሶን… ፋቁሔ… ሮሜልዩ

የሰዎች ስም

ረአሶንና… ፋቁሔ… ወጡ

ነገሥታቱ የሚመሩት ሰራዊት እንደሆኑ ጸሐፊው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ረአሶንና… ፋቁሔ ከሰራዊታቸው ጋር ወጡ››

ሊወጉ ወጡ

ጸሐፊው፣ ከተማው ራሱ ውስጡ የሚኖሩ ሰዎች እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢየሩሳሌምን ሊወጉ ወጡ››

ለዳዊት ቤት ወሬ በደረሰ ጊዜ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዳዊት ቤት ወሬውን ሰሙ››

የዳዊት ቤት

‹‹ቤት›› የሚለው ቤቱ ውስጥ የሚኖሩ ቤተ ሰብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሥ አካዝና አማካሪዎቹ››

ሶርያና ኤፍሬም ተባብረዋል

‹‹ሶርያ›› እና፣ ‹‹ኤፍሬም›› ነገሥታቶቻቸውን ያመለክታል። እዚህ ላይ፣ ‹‹ኤፍሬም›› መላው ሰሜናዊ የእስራኤልን መንግሥት ነው የሚያመለክተው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ ረአሶን የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔን እየረዳ ነበር››

የዱር ዛፍ በነፋስ እንደሚናወጥ የእርሱና የሕዝቡ ልብ ተናወጠ

በዚህ ወሬ ልባቸው መናወጡ ነፋስ ሲያናውጠው ከሚናወጥ ዛፍ ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አካዝና ሕዝቡ በጣም ፈሩ››

Isaiah 7:3

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ሌሎች ላይ የደረሰው እርሱ ላይ እንደ ደረሰ ይናገራል።

ሽአር ያሹብ

ተርጓሚዎቹ፣ ‹‹ሽአር፣ ያሹብ፣ ‹ትሩፋኑ ይመለሳሉ› ማለት ነው የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይችላሉ። ትርጉሙ ለአካዝ ተስፋ ይሰጠዋል።

የላይኛው የኩሬ መስኖ ጫፍ

‹‹ውሃው በቦይ አልፎ ወደ ላይኛው ኩሬ የሚገባበት››

መስኖ

ውሃ የሚያልፍበት ሰው ሠራሽ መተላለፊያ

መንገድ

ቋንቋህ ዝቅ ያለውን ቦታ በመሙላት፣ ከፍ ያለውን በመደልደል የተመቸ እንዲሆን ሰዎች የሚሠሩትን መንገድ ወይም ጐዳና የሚያመለክት ቃል ካለው እዚህ ላይ መጠቀም ትችላለህ።

የልብስ አጣቢው መስክ

ይህ ማለት፣ 1) ሰዎች ያንን መስክ የሚጠሩበት የተለመደ ስም ሊሆን ይችላል። ወይም 2) ሰዎች ያንን መስክ፣ ‹‹የልብስ አጣቢው መስክ›› የሚል ስም ስለ ሰጡት ሊሆን ይችላል። ወይም ‹‹ሰዎች ልብስ የሚያጥቡበት ቦታ›› ወይም፣ ‹‹ሴቶች ልብስ የሚያጥቡበት ቦታ›› ማለት ሊሆን ይችላል።

የልብስ አጣቢው መስክ

ልብስ አጣቢው፣ 1) ከበጐች የተሸለተውን ጠጉር የሚያጥብ ሰው፤ ‹‹የበግ ጠጉር አጣቢው›› ወይም 2) የቆሸሸ ልብስ የምታጥብ ሴት›› ‹‹የልብስ አጣቢዋ መስክ››

ንገሩት

‹‹ለአካዝ ንገሩት››

አትፍራ፤ በእነዚህ ከእሳት ተርፈው በሚጤሱት በሁለቱ የእንጨት ጉማጆች በሶርያና በንጉሥዋ በረአሶን እንዲሁም በሮሜልዩ ልጅ ቁጣ አትሸበር

እግዚአብሔር ረአሶንና ፋቁሔን ነድዶ እሳቱ ከወጣለት፣ አሁን ግን ጭስ ብቻ ከተረፈው የእንጨት ጉማጅ ጋር ያመሳስላቸዋል። ለይሁዳ ይህን ያህል የሚያሰጉ እንዳይደሉ እግዚአብሔር አስረግጦ ይናገራል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ረአሶንና ፋቁሔን አትፍራ፤ የእነርሱ ቁጣ እሳቱ ወጥቶ ጭስ ብቻ እንደ ቀረው የእንጨት ጉማጆች ናቸው።

አትፍራ ወይም አትሸበር

‹‹አትፍራ›› እና፣ ‹‹አትሸበር›› የተሰኙት ቃሎች ትርጉም ተመሳሳይ ስለሆነ በአንድ ቃል መተርጐም ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አትፍራቸው››

Isaiah 7:5

አጠቃላይ መረጃ

ለአካዝ መናገር ያለበትን ያህዌ ለኢሳይያስ መናገሩን ቀጥሏል

ሶርያ፣ ኤፍሬምና የሮሜልዩ ልጅ

‹‹ሶርያ›› እና፣ ‹‹ኤፍሬም›› የእነዚህ አገሮችን ነገሥታት ያመለክታሉ። እንዲሁም፣ ‹‹ኤፍሬም›› ሰሜናዊውን የእስራኤል መንግሥት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ ረአሶንና የእስራኤል ንጉሥ የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ››

ሮሜልዩ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ የሰው ስም ነው። ኢሳይያስ 7፥1 ላይ እንደ ተረጐምኸው ተርጉመው።
በአንተ ላይ ክፉ መክረዋል
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› ነጠላ ቁጥር ሲሆን፣ የሚያመለክተው አካዝን ነው።
የጣብኤል ልጅ
ይህ ሰው ማን እንደሆነ አይታወቅም
Isaiah 7:7
አጠቃላይ መረጃ
ለአካዝ መናገር ያለበትን ያህዌ ለኢሳይያስ መናገሩን ቀጥሏል።
የሶርያ ራስ ረአሶን ነው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ራስ›› በጣም አስፈላጊ አካል ነው። ረአሶን ሰው እንጂ፣ ሌላ ነገር ባለመሆኑ የያህዌን ዕቅድ ማስቆም እንደማይችል ያመለክታል። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሶርያ ንጉሥ ረአሶን ነው፤ እርሱ ሰው ብቻ ነው››
ሥልሳ አምስት ዓመት
‹‹65 ዓመት››
ኤፍሬም ይበታተናል፤ ሕዝብ መሆኑም ይቀራል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ኤፍሬም›› ሰሜናዊው የእስራኤልን መንግሥት ሁሉ ያመለክታል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ሰራዊት ኤፍሬምን ይደመስሰዋል፤ በእስራኤልም ሕዝብ አይኖርም››
የሰማርያም ራስ የሮሜልዩ ልጅ ነው
ይህ ማለት ፋቁሔ የሰማርያና የመላው እስራኤል ንጉሥ ነው ማለት ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሰማርያ ንጉሥ ደካማው ፋቁሔ ነው››
በእምነታችሁ ካልጸናችሁ ፈጽሞ መቆም አትችሉም
ይህን በአዎንታዊ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በእኔ በማመን ከጸናችሁ አትናወጡም››
ካልጸናችሁ
‹‹ጽኑ ካልሆናችሁ››
Isaiah 7:10
ከጥልቁ ጥልቅ ከከፍታው ከፍታ... ጠይቅ
ያህዌ፣ ‹‹ጥልቅ›› እና፣ ‹‹ከፍታ›› በተሰኙ ቃሎች የተጠቀመው አካዝ ማንኛውንም ነገር መጠየቅ እንደሚችል ለማመልከት ነው።
ጥልቅ... ከፍታ
‹‹ጥልቅ›› እና፣ ‹‹ከፍታ›› የተሰኙትን ቃሎች በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። ‹‹በጣም ጥልቅ ከሆነብህ ቦታ... በጣም ከፍ ካለብህ ቦታ››
አልለምንም
‹‹ከያህዌ ምልክት አልጠይቅም››
Isaiah 7:13
የዳዊት ቤት
‹‹ቤት›› ማለት፣ ቤት ውስጥ የሚኖር ቤተ ሰብ ማለት ነው። ኢሳይያስ 7፥2 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹አንተ ንጉሥ አካዝና አማካሪዎችህ››
የሰውን ትዕግሥት መፈታተናችሁ አንሶ የአምላኬን ትዕግሥት ትፈታተናላችሁን?
ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ሕዝቡ ታላቅ ኀጢአት ማድረጋቸውን ነው። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የሰውን ትዕግሥት ትፈታተናላችሁ! አሁን ደግሞ የአምላኬን ትዕግሥት ትፈታተናላችሁ!››
ወጣት ሴት ትፀንሳለች
አንዳንድ የጥንት ቅጂዎችና፣ አንዳንድ የዘመኑ ቅጂዎች፣ ‹‹ድንግል ትፀንሳለች›› በማለት ተርጉመዋል፤ ሌሎች፣ ‹‹ወጣት ሴት ትፀንሳለች›› የሚል ትርጉም ይዘዋል።
ስሙንም አማኑኤል
ተርጓሚዎች፣ ‹‹አማኑኤል እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ነው›› የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይችላሉ።
ክፉውን መተውና መልካሙን መምረጥ ሲችል ቅቤና ማር ይበላል
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ሕፃኑ አድጐ ቅቤና ማር ለመብላት ሲደርስ፣ ክፉውን መተውና መልካሙን መምረጥ ይችላል›› ማለት ሊሆን ይችላል። ሕፃኑ ክፉ ከሆነው ይልቅ፣ መልካሙን የሚያውቀው ገና በሕፃንነቱ እንደሆነ ይህ አጽንዖት ይሰጣል። ወይም 2) ሕፃኑ አድጐ ክፉውን ትቶ፣ መልካሙን ሲመርጥ ቅቤና ማር ይበላል›› አይሁድ አንድ ሕፃን መልካሙን ለማድረግ ኀላፊነት የሚኖረው 12 ዓመት ሲሞላው እንደሆነ ያምናሉ። አብዛኞቹ እስራኤላውያን ስለሚገደሉ ወይም በምርኮ ስለሚወሰዱ በዐሥራ ሁለት ዓመት ውስጥ ሕዝቡ ብዙ ቅቤና ማር እንደሚበሉ ይህ አጽንዖት ይሰጣል።
ቅቤ
ሰዎች ከወተት የሚያወጡት ጠጣሩ ክፍል
ክፉውን መተው መልካሙን መምረጥ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ክፉው›› እና፣ ‹‹መልካሙ›› በአጠቃላይ ክፉና መልካም ነገሮችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ክፉ ነገሮችን በመተው መልካም ነገሮችን ለማድረግ መምረጥ››
Isaiah 7:16
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ እግዚአብሔር ለዳዊት ቤት ስለሚሰጠው ምልክት መግለጹን ቀጥሏል።
ክፉውን መተውና መልካሙ መምረጥ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ክፉው›› እና፣ ‹‹መልካሙ›› በአጠቃላይ ክፉና መልካም ነገሮችን ያመለክታል። ኢሳይያስ 7፥15 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ክፉ ነገሮችን በመተው መልካም ነገሮች ለማድረግ መምረጥ››
የሚያስደነግጡህ
‹‹የፈራሃቸው›› እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› ነጠላ ቁጥር ሲሆን፣ አካዝን ያመለክታል።
ሕዝብህ
ይህ የሚያመለክተው የይሁዳን ሕዝብ ነው።
ኤፍሬም ከይሁዳ ከተለየበት ቀን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ኤፍሬም›› እና፣ ‹‹ይሁዳ›› በዚያ አካባቢ የሚኖረውን ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ከይሁዳ ሕዝብ የተለየው የኤፍሬም ሕዝብ››
Isaiah 7:18
በዚያን ቀን
ሕፃኑ ክፉውን በመተው መልካሙን መምረጥ ከመቻሉ በፊት
ያህዌ በፉጨት
‹‹ያህዌ ይጣራል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ኑ ይላል››
ከግብፅ ወንዞች ዝንቦችን፣ ከአሦርም ምድር ንቦችን
እዚህ ላይ የግብፅና የአሦር ሰራዊት የእስራኤልን ምድር በሚወርሩ ነፍሳት ተመስለዋል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የግብፅና የአሦር ሰራዊት ከወታደሮቻቸው ጋር እንደ ዝንብና ንብ በየቦታው ይገኛሉ››
Isaiah 7:20
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ የአሦር ሰራዊት እስራኤልን የሚወርረው መቼ እንደሆነ መግለጹን ቀጥሏል።
እግዚአብሔር ከወንዝ ማዶ በተከራየው ምላጭ ማለትም በአሦር ንጉሥ ይላጫል
‹‹ምላጭ›› የአሦር ንጉሥና ሰራዊቱን ያመለክታል፤ ንጉሡ የያህዌን ሥራ የሚሠራና ለዚያም ከያህዌ ገንዘብ እንደሚቀበል ሰው እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እናንተን እንዲላጭ የአሦርን ንጉሥ ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ይጠራዋል››
በተከራየው
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በገዛው››
የራስና የእግር ጠጉራችሁን... ጢማችሁን
የአንድን ሰው አናት መላጨት መጥፎ ነው፤ ‹‹የእግርን ጠጉር›› መላጨት የባሰ መጥፎ ነው፤ ጢምን መላጨት ደግሞ ከሁሉ የባሰ መጥፎ ነው።
የራስና የእግር ጠጉራችሁን... ጢማችሁን
እግዚአብሔር የሚላጨው የማንን ራስ ጠጉርና ጢም እንደሆነ ኢሳይያስ አይናገርም፤ አካዝና አንባቢዎቹ ግን ይህ የሚያመለክተው ስለ ሰው መሆኑንና ያ ደግሞ በይሁዳ ምድር የሚኖረውን ሕዝብ ሊያመለክት እንደሚችል ይረዳሉ።
ራስ
‹‹ራስ›› እዚያ ላይ የሚበቅል ጠጉርን ይወክላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የራስ ጠጉር››
የእግር ጠጉር
ይህም ማለት 1) የሰውነት ታችኛው አካል ላይ የሚበቅል ጠጉርን በጨዋነት ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ሐረግ ሊሆን ይችላል፤ ወይም 2) እግር ላይ የሚበቀለውን ጠጉር የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።
እንዲሁም... ይላጫል
‹‹እንዲሁም ምላጩ... ይላጫል›› ቋንቋህ፣ ‹‹የሚላጭ ሰው›› እንዲኖር የሚጠይቅ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከሆነ፣ ‹‹እግዚአብሔር ይላጨዋል›› ማለት ትችላለህ።

ከሚሰጡት የተትረፈረፈ ወተት የተነሣ

‹‹የተትረፈረፈ›› የሚለውን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ብዙ ወተት ከመስጠታቸው የተነሣ››

Isaiah 7:23

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ የአሦር ሰራዊት የእስራኤልን ምድር የሚያጠቃው መቼ እንደሆነ መግለጹን ቀጥሏል።

አንድ ሺህ የወይን ተክል… ኩርንችትና እሾኽ ብቻ ይሆናል

‹‹1,000 የወይን ተክል›› ያም ማለት ኢሳይያስ በጻፈበት ጊዜ አንዳንዶቹ 1000 የወይን ተክል የያዙ የወይን እርሻ ቦታዎች ነበሩ። እነዚህ የወይን እርሻዎች ግን፣ ኩርንችትና እሾኽ እንደሚሞላባቸው ይናገራል።

ሺህ ሰቅል ብር

‹‹1,000 ሰቅል ብር›› ሰቅል የ4 ቀን ደመወዝ የሚሆን የብር ሳንቲም ነው አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹1,000 የብር ሰቅል››

ኩርንችትና እሾህ

‹‹ኩርንችት›› እና፣ ‹‹እሾኽ›› ሁለቱም የሚያመለክቱት ጥቅም የሌላቸው ተክሎችን ነው። ሁለቱንም ቃሎች መተርጐም አስፈላጊ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእሾህ ቁጥቋጦ›› ወይም፣ ‹‹የኩርንችት ቁጥቋጦ››

ምድሩ ሁሉ ኩርንችትና እሾኽ ስለሚሆን

አዳኞቹ ወደዚህ ቦታ የሚመጡበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያ ቦታ ኩርንችትና እሾኽ እንዲሁም የዱር አራዊት እንጂ፣ ሌላ ምንም ስለማይኖር››

ከዚያ በፊት በመቆፈሪያ ተቆፍረው ወደ ነበሩት ኮረብታዎች አይሄዱም

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ከዚያ በፊት እህል ለመዝራት ዝግጁ ወደ ነበሩት ቦታዎች አይሄዱም››

---

Chapter 8

Isaiah 8:1

ያህዌ እንዲህ አለኝ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› ኢሳይያስን ይመለከታል።

ታማኝ ምስክሮች እንዲሆኑ እጠራቸዋለሁ

ይህም ማለት፣ 1) ያህዌ፣ ‹‹ምስክሮች እንዲሆኑ ታማኝ ሰዎችን እየጠራሁ ነኝ›› እያለ ነው ወይም 2) ኢሳይያስ፣ ‹‹ምስክሮች እንዲሆኑ ታማኝ ሰዎችን እየጠራሁ ነኝ›› እያለ ነው። ወይም 3) ያህዌ ኢሳይያስን፣ ‹‹ምስክሮች እንዲሆኑ ታማኝ ሰዎችን ጥራ›› በማለት እያዘዘው ነው።

Isaiah 8:3

ወደ ነቢዪቱ ሄድሁ

ኢሳይያስ ነቢዪቱን ማግባቱ በግልጽ መነገር አለበት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከነቢዪቱ ሚስቴ ጋር ተኛሁ››

የደማስቆ ሀብትና የሰማርያ ምርኮ በአሦር ንጉሥ ይወሰዳል

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥ የደማስቆንና የሰማርያን ሀብት ሁሉ ይወስደዋል››

Isaiah 8:5

ይህ ሕዝብ በጸጥታ የሚፈሰሰውን የሰሊሆምን ውሆች ስለ ተወ

‹‹በጸጥታ የሚሄደው›› የተባለው የሚያመለክተው የጌታን ሕግ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ ሕዝብ እንደ ሰሊሆም ውሆች በጸጥታ የሚሄደውን የያህዌን ሕግ ስለ ተወ››

ይህ ሕዝብ

‹‹ይህ ሕዝብ ሁሉ›› እዚህ ላይ ቋንቋህ ብዙ ቁጥር የሚፈልግ ከሆነ፣ ‹‹እነዚህ ሕዝቦች ስለ ተው… ደስተኛ ናቸው›› በማለት ይህን ሐረግና የሚከተለውን ግሥ መተርጐም ይቻላል።

በረአሶንና በሮሜልዩ ልጅ ተደስቶአልና

ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። ኢሳይያስ 7፥1 ላይ የእነዚህን ሰዎች ስም እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦር ሰራዊት የሶርያን ንጉሥ ረኦሶንንና የሮሜልዮን ልጅ የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔን ድል ስላደረገ ተደስቶአል››

ስለዚህ ጌታ

ስለ ማንነቱ ለሕዝቡ ለማሳሰብ ያህዌ እርሱ ሌላ ሰው ይመስል ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ እኔ ያህዌ…››

ያመጣባቸዋል

ግሡ፣ ‹‹ያመጣባቸዋል››፤ ተውሳከ ግሡ፣ ‹‹እነርሱ ላይ››

እነርሱ ላይ

‹‹የይሁዳ ሕዝብ ላይ››

ታላቁንና ብርቱውን የኤፍራ ውሃ፤ የአሦር ንጉሥ ከነግርማ ሞገሱ

ወንዙ የሚወክለው የአሦርን ሰራዊት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ታላቅና ብርቱ ኤፍራ የሆነው ከአሦር የሚመጣው ሰራዊት››

ወንዙ

በአሦር ያለው የኤፍራጥስ ወንዝ

Isaiah 8:8

አጠቃላይ መረጃ

ጌታ የአሦር ሰራዊት እንደ ወንዝ እየጐረፈ ወደ ይሁዳ እንደሚመጣ መናገሩን ቀጥሏል።

ወንዙ እየጠራረገ ወደ ይሁዳ ይወርዳል፤ እያጥለቀለቀ ያልፋል፤ እስከ ዐንገትም ይደርሳል

የአሦር ሰራዊት እንደ ውሃ ጐርፍ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከፍ እያለ ሄዶ እስከ ዐንገታችሁ እንደሚደርስ ወንዝ እጅግ ብዙ ወታደሮች ይመጣሉ››

ወንዙ

ይህ የሚያመለክተው በአሦር ያለውን የኤፍራጥስ ወንዝ ነው። ከቤታቸው ተነሥተው በኤፍራጥስ ወንዝ በኩል የሚመጡት የአሦር ወታደሮችም ምሳሌ ነው። (ኢሳይያስ 8፥7)

የተዘረጉ ክንፎቹ ይሞላሉ

ይህም ማለት፣ 1) በምሳሌው እንዳየነው፣ ‹‹ወንዝ›› ወደ ደረቁ ምድር ‹‹ይወርዳል፣ ‹‹በክንፎቹም›› ይሸፍናል። ወይም 2) አሁን ኢሳይያስ ምሳሌውን በመለወጥ ያህዌ ምድሩን እንደሚጋርድ ወፍ እንደሆነ ይናገራል፤ ‹‹የተዘረጉ ክንፎቹ ይሸፍናሉ››

አማኑኤል

ተርጓሚዎቹ፣ ‹‹አማኑኤል›› የሚለው ስም፣ ‹እግዚአብሔር ከእኛ ጋር› ማለት ነው የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ያስፈልጋቸው ይሆናል። 7፥14 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

Isaiah 8:9

እናንተ ሰዎች እስክትደቅቁ ትሰባበራላችሁ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰራዊታችሁን እስኪደቅ እሰባብራለሁ››

በሩቅ አገር ያላችሁ አድምጡ

ኢሳይያስ በሌላ አገር ያሉ ሰዎች እንደሚሰሙት አድርጐ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሩቅ ቦታዎች ያላችሁ ሰዎች ሁሉ አድምጡ››

ለጦርነት ተዘጋጁ፤ እስክትደቅቁ ተሰባበሩ፤ ተዘጋጁ እስክትደቅቁ ተሰባበሩ

ይህ በመሠረቱ ተመሳሳይ ቢሆንም፣ የተደጋገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራሳችሁን ለጦርነት ማዘጋጀት ትችላላችሁ፤ እኔ ግን አሸንፋችኋለሁ።››

ዕቅዱ አውጡ፤ ሆኖም አይጸናም፤ ተመካከሩ ግን አይሳካም

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይሁዳን ለማጥቃት መዘጋጀት ትችላላችሁ፤ ግን አይሳካላችሁም››

አይጸናም… አይሳካም

ዕቅዱን ወይም ትእዛዝን መፈጸም ዕቅዱን ወይም ትእዛዙን ያወጣው ሰው መስማት የሚፈልገውን ማድረግ ማለት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማድረግ ያቀዳችሁትን ማድረግ አትችሉም… ወታደሮቻችሁም አዛዦቻቸው ያዘዟቸውን ማድረግ አይችሉም››

Isaiah 8:11

ብርቱ እጁን በላዬ አድርጐ ያህዌ ተናገረኝ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ብርቱ እጁን በላዬ አድርጐ›› የሚለው የያህዌን ኀይል የሚያመለክት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ በጣም ብርቱ በሆነ መንገድ ተናገረኝ››

በዚህ ሕዝብ መንገድ እንዳልሄድ አስጠነቀቀኝ

ይህ 8፥17 የሚደመደምበት ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅስ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲህ ሲል አስጠነቀቀኝ፤ ‹ይህ ሕዝብ የሚያደርገውን አታድርግ››

እነዚህ ሰዎች አድማ ነው የሚሉትን ማንኛውንምነገር አድማ አትበል

ሰዎች አድማ መኖሩን ስለሚያስቡ ስጋት አድሮባቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣

‹‹ሁሌም እርሱ መጉዳት የሚፈልግ ሰው እንዳለ እንደሚገምቱት እንደ እነዚህ ሰዎች አትጨነቅ››
ልትቀድሱ የሚገባው የሰራዊት ጌታ ያህዌን ብቻ ነው፤ ልትፈሩት የሚገባው እርሱን ነው፤ ልትንቀጠቀጡለት የሚገባውም እርሱ ነው።
ይህን በቀጥተኛ ጥቅስ የምትተረጉም ከሆነ፣ ያህዌ በመጀመሪያ ሰው ደረጃ እየተናገረ መሆኑንም መተርጐም ይኖርብሃል፤ ‹‹ነገር ግን እኔን የሰራዊት ጌታ ያህዌን ልትቀድሱኝ ይገባል፣ እኔን መፍራትና በፊቴም መደንገጥ አለባችሁ››
Isaiah 8:14
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ 8፥11-13 ላይ የጀመረውን ያህዌን ቀጥተኛ ባልሆነ ሁኔታ መጥቀሱን ኢሳይያስ ቀጥሏል። ያህዌ በመጀመሪያ ሰው ደረጃ እየተናገረ እንደሆነ በሚያመለክት ሁኔታ በቀጥታ ሊጠቀስ ይችላል።
እርሱ መቅደስ ይሆናል
‹‹መቅደስ›› የሚለው ቃል ያህዌ ሕዝቡን እንደሚጠብቅና ለእነርሱ እንደሚከላከል የሚያመለክት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እርሱ ሲሄዱ፣ እርሱ ይጠብቃቸዋል››
የሚያደናቅፍ ድንጋይ፣ የሚያሰናክልም ዐለት ይሆናል
‹‹የሚያደናቅፍ ድንጋይ›› እና፣ ‹‹የሚያሰናክል ዐለት›› የተሰኙት ያህዌ ሕዝቡን እንደሚጐዳ የሚመለክቱ ምሳሌዎች ናቸው። አንዳንዶች፣ ‹‹የሚያደናቅፍ›› እና፣ ‹‹የሚያሰናክል›› የሚለውን፣ ‹‹የሚያሰናክል››እና፣ ‹‹የሚጥል›› በማለት ይተረጉሙታል። ሌሎች ደግሞ፣ ‹‹በደል›› እና፣ ‹‹መሰናከያ›› በማለት ይተረጉማሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰዎችን እግር እንደሚመታና እንደሚያሰናክል ድንጋይ፣ ሰዎችን አደናቅፎ እንደሚጥል ዐለት ያህዌ ሕዝቡን ይጐዳል››
ለኢያሩሳሌም ሕዝብም ወጥመድና አሽክላ ይሆናል
‹‹ወጥመድ›› እና፣ ‹‹አሽክላ›› የተሰኙት ቃሎች በአመዛኙ ተመሳሳይ ናቸው፤ ያህዌ የኢያሩሳሌምን ሕዝብ ለመቅጣት ሲወስን ማምለጥ እንደማይችሉ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእርሱ ማምለጥ እንዳይችሉ የኢያሩሳሌምን ሕዝብ ያጠምዳል››
ወጥመድ
ወፍን በመረብ ወይም በቅርጫት የሚይዝ ነገር
አሽክላ
የእንስሳን እግር ወይም አፍንጫ የሚይዝ ወጥመድ
ብዙዎች ይሰናከላሉ፤ ይወድቃሉ፤ ይሰበራሉ፤ ወጥመድ ውስጥ ይገባሉ፤ ይያዛሉም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙ ሰዎች በድንጋዩ ይሰናከላሉ፤ ከወደቁም አይነሡም፤ ብዙዎች አሽክላው ላይ ይቆማሉ፤ ከዚያ መውጣትም አይችሉም››
ይጠመዳሉ ይያዛሉም
እነዚህ ቃሎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው፤ በወጥመድ እንደሚያዙ አጽንዖት ይሰጣሉ።
Isaiah 8:16
ምስክርነቴን አሽገው፤ ሕጉንም አትመው
እነዚህ ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው፤ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በላዩ ይህን መልእክት ጽፈህ፣ ጥቅልል ጽሑፉን አጥብቀህ አሽገው››
ምስክርነቴ… ደቀ መዛሙርቴ
‹‹የእኔ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማንን እንደሆነ ግልጽ አይደለም። ኢሳይያስ ወይም ያህዌ ሊሆኑ ይችላሉ። ቋንቋህ የሚፈቅድ ከሆነ ተውላጠ ስሙን አሻሚ እንደሆነ መተው ይመረጣል።
ያህዌን እጠብቃለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› የሚያመለክተው ኢሳይያስን ነው።
ፊቱን ከያዕቆብ ቤት የሰወረውን
የያህዌ፣ ‹‹ፊት›› በረከቱንና ሞገሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከያዕቆብ ቤት በረከቱን የወሰደውን›› ወይም፣ ‹‹የያዕቆብን ቤት በሞገስ ማየት የተወውን››
የያዕቆብ ቤት
የእስራኤል ሕዝብ
እኔና ያህዌ የሰጠኝ ልጆቼ ለእስራኤል ምልክትና ድንቅ ነን
‹‹እኔና ያህዌ የሰጠን ልጆቼ የእስራኤልን ሕዝብ የምናስጠነቅቅ ምልክቶች ነን›› ልጆቹ ስሞቻቸው ለእስራኤል ሕዝበ መልእክት የሆኑት ሸአብ ያሹብ እና ማኸር-ሻላል-ሃሽ-ባዝ ናቸው።
Isaiah 8:19
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ እየተናገረ ነው።
የሚያነበንቡትንና የሚያሾኮሹኩትን ሟርተኞችና መናፍስት ጠሪዎችን ጠይቁ ቢሏችሁ፤ ሕዝቡ አምላኩን መጠየቅ አይገባውምን? በሕያዋን ምትክ ሙታንን መጠየቅ ለምን አስፈለገ? ወደ ሕጉና ወደ ምስክር ቃሉ ሂዱ
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹መናፍስት ጠሪዎችንና ሟርተኞን፣ የሚያነበንቡትንና የሚያሾከሹኩትን ጠይቁ ቢላችኃል፤ ግን ሕዝቡ አምላኩን መጠየቅ የለበትምን›› ትምህርትና ምስክርነት ለማግኘት ለሕያዋን ሙታን መጠየቅ አለባቸውን?›› ወይም 2) ‹‹እነዚያን የሚያነበንቡትንና የሚያሾካሽኩትን መናፍስት ጠሪዎችን ሟርተኞች ጠይቁ ይሏችኃል፤ ሕዝቡ አምላኩን መጠየቅ የለበትምን? ሕጉንና ምስክርነቱን በተመለከተ ለሕያዋን ሙታን መጠየቅ አለባቸውን?››
እንዲህ ይሉሃል
‹‹እነርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው በያህዌ የማይታመኑን ነው። ‹‹አንተ›› የሚለው በብዙ ቁጥር ነው፤ በያህዌ የሚታመኑትን ያመለክታል።
መናፍስት ጠሪዎችንና ሟርተኞችን ጠይቁ
‹‹ምን ማድረግ እንዳለባችሁ መናፍስት ጠሪዎችንና ሟርተኞችን ጠይቁ››
መናፍስት ጠሪዎችና ሟርተኞች
ከሙታን ጋር እንነጋገራለን የሚሉ ሰዎች
የሚያነበንቡ
እንደ ወፍ ያለ ድምፅ የሚያወጡ
ሕዝቡ አምላኩን መጠየቅ አይገባውምን? በሕይወት ስላሉትስ ሙታንን መጠየቅ አለባቸውን?
ባለ ማስተዋል ከሙታን ጋር ለመነጋገር ከመሞከር ይልቅ፣ ሕዝቡ እግዚአብሔርን መጠየቅ እንዳለበት እነዚህ ጥያቄዎች ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲመራቸው ሕዝቡ ያህዌን መጠየቅ አለባቸው፤ ከሞቱ ሰዎች መልስ መፈለግ የለባቸውም››
ሕጉና ምስክሩ
ይህም ማለት 1) ‹‹የእግዚአብሔርን መመሪያና ትምህርት ልብ ብላችሁ አድምጡ›› ወይም 2) ‹‹ያኔ እኔ የሰጠሁትን ትምህርትና ምስክር ማስታወስ አለባችሁ›› (ኢሳይያስ 8፥16)
ሕጉ
ይህ ኢሳይያስ 8፥16 ላይ፣ ‹‹ሕጉ›› ተብሎ ከተተረጐመው ጋር አንድ ነው።
ምስክሩ
ኢሳይያስ 8፥16 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት
እነርሱም እንዲህ ያለውን ቃል ባይናገሩ
‹‹ሕጉንና ምስክሩን ባይናገሩ››
የንጋት ብርሃን ስለሌላቸው ነው
እግዚአብሔርን የማያውቁ ምንም ብርሃን በሌለበት ጨለማ እንደሚመላለሱ ሰዎች እንደሆኑ ኢሳይያስ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨለማ እንደዋጠው ሰው ስለሆኑ ነው››
Isaiah 8:21
ተጨንቀውና ጨፍግገው
‹‹በጣም አዝነው››
ወደ ድቅድቅ ጨለማ ይገባሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ወደ ድቅድቅ ጨለማ ያገባቸዋል።

---

Chapter 9
Isaiah 9:1
በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ብርሃን ወጣለት
መንፈሳዊ ጉስቁልና ውስጥ ያሉ ሰዎች በድቅድቅ ጨለማ እየተመላለሱ እንደሆነ ኢሳይያስ ይናገራል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጭንቀት ውስጥ ለነበረች ያህዌ ጨለማን ያስወግዳል››
ድንግዝግዝ
ይህ፣ ‹‹ከፊል ወይም ሙሉ ጨለማ›› ማለት ነው። ኢሳይያስ 8፥22 ላይ ‹‹ድንግዝግዝ›› የሚለውን በተረጐምህበት መንገድ ተርጉመው።
ተጨንቃ ለነበረች
‹‹ከባድ ስቃይና ሀዘን ውስጥ ለነበረች›› ምናልባትም ይህ የይሁዳን ሕዝብ

የሚመለከት ሊሆን ይችላል።

በቀደመው ዘመን የዛብሎንንና የንፍታሌምን ምድር አዋረደ

‹‹ምድር›› በዚያ አካባቢ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባለፈው ጊዜ ጌታ በዛብሎንና በንፍታሌም የሚኖሩትን ዝቅ አደረገ››

በኋለኛው ዘመን ግን ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ በባሕር መንገድ አጠገብ ያለውን የአሕዛብ ገሊላ ያከብራል

ይህ የሚናገረው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ስለሚወክለው ገሊላ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ ፊት ጌታ በሜዲትራንያንና በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል ባለው መንገድ ላይ ያለውን የአሕዛብ ገሊላን ያከብራል››

የአሕዛብ ገሊላ

‹‹አሕዛብ›› በገሊላ የሚኖሩ የሌላ አገር ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙ ባዕዳን የሚኖሩበት ገሊላ››

በጨለማ የሚኖር… በሞት ጥላ ምድር ለኖሩት

ኢሳይያስ በጨለማ ወይም በሞት ጥላ ምድር ውስጥ ከመኖራቸው የተነሣ የኀጢአትና የመከራ ሕይወት ስለሚኖሩ ሰዎች ይናገራል።

ታላቅ ብርሃን… ብርሃን ወጣላቸው

እዚህ ላይ ‹‹ብርሃን›› ተስፋና መዳንን ይወክላል።

የሞት ጥላ ምድር

‹‹የሞት ጥላ›› የሚለው ድቅድቅ ጨለማ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድቅድቅ ጨለማ ያለበት ምድር››

Isaiah 9:3

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የሚያድነው መቼ እንደሆነ መናገር ቀጥሏል። እነዚህ ነገሮች የሚሆኑት ወደ ፊት ቢሆንም (ኢሳይያስ 9፥1) ኢሳይያስ አሁን እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል። ይህም በትክክል እንደሚፈጸሙ አጽንዖት ይሰጣል።

ሕዝብን አበዛህ፤ ደስታቸውንም ጨመርህ

‹‹አንተ›› የሚለው የሚያመለክተው ያህዌን ነው። ‹‹እነርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው፤ እንደ እስራኤል አካል ኢሳይያስ ራሱንም ይጨምራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ አንተ ሕዝባችንና ደስታችንን እጅግ ታበዛለህ››

ሰዎች ምርት ሲሰበስቡ፣ ምርኮንም ሲካፈሉ ደስ እንደሚላቸው ሁሉ እነርሱም በፊትህ ደስ ይላቸዋል።

ያህዌ ለእስራኤል የሚሰጠው ደስታ ምርት ሲሰበስቡና ምርኮን ሲካፈሉ ደስ እንደሚላቸው ሰዎች ዐይነት ደስታ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ምርት ሲሰበስቡ፣ ጦርነት ካበቃ በኋላ ወታደሮቹ የወሰዱትን ሲከፋፈሉ ደስ እንደሚላቸው እነርሱም በፊትህ ደስ ይላቸዋል››

Isaiah 9:4

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ስለሚያድንበት ጊዜ መናገሩን ቀጥሏል። ምንም እንኳ እነዚህ ነገሮች የሚሆኑት ወደ ፊት ቢሆንም፣ (ኢሳይያስ 9፥1-2) ኢሳይያስ አሁን እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል። ይህም በእርግጥ እንደሚፈጸም አጽንዖት ይሰጣል።

ምድያም ድል በተመታ ጊዜ እንደሆነው የከበዳቸውን ቀንበር ሰብረህላቸዋል

የአሦራውያን ባርያዎች የነበሩ እስራኤላውያን ቀንበር እንደ ተሸከመ በሬ መሆናቸውን ኢሳይያስ ይናገራል። ይህ የሚሆነው ወደ ፊት ነው፤ እርሱ ግን አሁን እንደ ተፈጸመ አድርጐ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድያም ቀን እንደሆነው ሰው ቀንበርን ከበሬ ላይ እንደሚያነሣ አንተም የጨቋኞቻቸው ባርያዎች የሆኑበን የእስራኤል ሕዝብ ነጻ ታወጣለህ››

የከበደውን ቀንበር… ትከሻው… የተጨቆነበት

ኢሳይያስ የእስራኤል ሕዝብ አንድ ሰው እንዲሆኑ አድርጐ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የከበዳቸው ቀንበር… ትከሻቸው… የተጨቆኑበትን››

ትከሻው ላይ የነበረው ሞፈር

በሬ ትከሻ ላይ የሚውለው ቀንበር አካል ነው

ሞፈር

ሌላው አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በትር›› በሬዎቹ እንዲሠሩ የሚመቱበትንና ሌሎች ላይ ለመግዛት አንድ ሰው ስላለው ኀይል ምሳሌ የሆነ የእንጨት አካል ማለት ነው።

የጨቋኙ በትር

ጨቋኙ የይሁዳ ሕዝብ ላይ የነበረው ኀይል በርትተው እንዲሠሩ በሬዎቹን ለመምታት እንደሚጠቀምበት እንጨት እንደ ነበር ኢሳይያስ ይናገራል።

በምድያም ቀን እንደሆነው

‹‹ቀን›› የሚለው ቃል ከአንድ ቀን በላይ የወሰዱ ድርጊቶችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ምድያምን እንዳሸነፍህበት ጊዜ››

የጦረኞች ጫማ ሁሉ፣ በደም የተለወሰ ልብስም ሁሉ ይቃጠላል

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ በደም የተለወሰውን የወታደሮቹን ጫማና ልብሳቸውን ታቃጥላለህ።››

ለእሳቱ ማገዶ ይሆናል

ይህን በአዲስ ዐረፍተ ነገር በመተርጐም የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይቃጠላል። ልብሳቸውንና ጫማቸውን ማገዶ ታደርገዋለህ››

Isaiah 9:6

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ስለሚያድንበት ጊዜ መናገሩን ቀጥሏል (ኢሳይያስ 9፥1-2) እነዚህ ነገሮች የሚፈጸሙት ወደ ፊት ቢሆንም ኢሳይያስ አሁን እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል። ይህም በእርግጥ እንደሚፈጸሙ አጽንዖት ይሰጣል።

ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅ ተወልዶልናል

እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። ‹‹ለእኛ›› የሚለው ቃል ተናጋሪውንና ሰሚዎቹን ያጠቃልላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታ ሕፃን ልጅ ይሰጠናል››

አለቅነት በጫንቃው ላይ ይሆናል

የአለቅነት ሥልጣኑ የገዢነቱ ሥልጣኑ ምልክት የሆነው ልብስ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የገዢነት ሥልጣኑን ጫንቃው ላይ ይለብሳል›› ወይም፣ ‹‹እንደ ንጉሥ የሚገዛበት ሥልጣን ይኖረዋል››

መካር

‹‹ነገሥታትን የሚያማክር››

ለመንግሥቱ ስፋት፣ ለሰላሙም ብዛት ፍጻሜ የለውም

‹‹ጊዜ እያለፈ ሲሄድ፣ በጣም ብዛት ባላቸው ሰዎች ላይ ይገዛል፤ እጅግ በበዛ ሰላም ውስጥ ይኖራሉ››

በዳዊት ዙፋን ይገዛል

‹‹በዳዊት ዙፋን›› ላይ መቀመጥ የመግዛት መብትን ያመለክታል፤ የእስራኤል ንጉሥ የሚሆኑት የዳዊት ዘሮች ብቻ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ዳዊት ዘር የመግዛት መብት ይኖረዋል››

መንግሥቱን በፍትሕና በጽድቅ ይመሠርታል፤ ደግፎ በመያዝም ያጸናዋል።

ይህን በአዲስ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መንግሥቱ፤ መንግሥቱን ያጸናል፤ ይጠብቃል፤ መልካምና ትክክል የሆነውን ያደርጋል››።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ

ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት፡

Isaiah 9:8

ጌታ በያዕቆብ ላይ ቃል ላከ፤ በእስራኤልም ላይ ይወድቃል

‹‹ቃል መላክ›› መናገር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ተናገረ››

ያዕቆብ… እስራኤል… ኤፍሬም… ሰማርያ

እነዚህ ስሞች ሁሉ የሚያመለክቱት የሰሜናዊውን የእስራኤል መንግሥት ሰዎች ነው።

ሕዝቡ በሙሉ፣ ኤፍሬምና የሰማርያ ነዋሪዎች ይህን ያውቃሉ

የሚያውቁት ምንን እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታ እንደ ፈረደባቸው ሰዎች ሁሉ፣ ኤፍሬምና በሰማርያ የሚኖሩት እንኳ ያውቃሉ››

ጡቦቹ ወድቀዋል፤ እኛ ግን በጥርብ ድንጋይ መልሰን እንገነባለን፤ የሾላ ዛፎች ተቈርጠዋል፤ እኛ ግን በዝግባ እንተካለን

ምን ማለት እንደሆነ የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የፈረሱት ከተሞቻችንን ተራ ጡብ በጥርብ ድንጋይ መልሰን እንተካዋለን፤ ተራ የሾላ ዛፍ በነበረበትም ቦታ ዝግባ እንተክላለን››

Isaiah 9:11

ስለዚህ ያህዌ ጠላቱ የሆነውን ረአሶንን ያስነሣል

እዚህ ላይ፣ ‹‹ረአሶን›› የሚወክለው ራሱንና ሰራዊቱን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ ያህዌ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ረአሶንና ሰራዊቱን ያስነሣል››

ረአሶን

የሰው ስም። ኢሳይያስ 7፥1 ላይ ረአሶንን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት

ባላጋራዎቻቸውን ያነሣሣቸዋል

‹‹ያነሣሣል›› ለጥቃት ያነሣሣል ማለትን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የእስራኤልን ጠላቶች ያነሣሣባቸዋል››

አፋቸውን ከፍተው እስራኤልን ይቦጫጭቋቸዋል።

‹‹ይቦጫጭቋቸዋል›› የሚለው የዱር አራዊት የያዙትን እንስሳ እንዴት የሚበሉበትን ሁኔታ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዱር አውሬ ሌሎች እንስሳትን እንደሚበላ፣ የጠላት ሰራዊት የእስራኤልን ሕዝብ ያወድማል››

በዚህ ሁሉ ቁጣው ገና አልበረደም፤ ይልቁን እጁም

‹‹ይህ ሁሉ ቢሆን እንኳ አሁንም እንደ ተቆጣ ነው፤ እጁም›› ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እጁ እንደ ተዘረጋ ነው።

ኢሳይያስ ያህዌን ሌላውን ሰው ለመምታት ካሰበ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። ይህ ያህዌ እስራኤልን እንደሚቀጣ ምሳሌ ነው። ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁንም እነርሱን ለመቅጣት እንደ ተዘጋጀ ነው››

Isaiah 9:13

የሰራዊት ጌታ ያህዌ

ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

ራስንና ጅራትን

ቁጥር 15 ላይ ኢሳይያስ ይህን ምሳሌ ይገልጸዋል። ‹‹በራስ›› የተመሰሉት፣ ‹‹ሽማግሌዎችና የተከበሩ ሰዎች›› ሲሆኑ፣ ‹‹ጭራ›› ደግሞ፣ ‹‹ሐሰትን የሚያስተምሩ ነቢያት›› ምሳሌ ነው።

የዘንባባ ቅርንጫፍና ሸንበቆውን

‹‹የዘንባባ ቅርንጫፍ›› ከፍ ብሎ ዛፉ ላይ የሚያድግ ሲሆን፣ በጣም አስፈላጊና ሌሎችን የሚገዙ ሰዎች ምሳሌ ነው። ‹‹ሸንበቆ›› ጥልቅ ያልሆነ ውሃ ውስጥ የሚያድግ ሲሆን፣ በሌሎች የሚገዙ በጣም አስፈላጊ ያልሆኑ ድኾች ምሳሌ ነው።

Isaiah 9:16

ይህን ሕዝብ የሚመሩት ያስቱታል

ሕዝቡ እንዲያምፅ የሚያደርጉ መሪዎች በተሳሳተ መንገድ የሚመሩ መሪዎች እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል መሪዎች ሕዝቡ ለእግዚአብሔር እንዳይታዘዝ አደረጉ››

በእነርሱ የሚመሩ ይዋጣሉ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፤ የዚህ ትርጉም፣ 1) አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱ የሚመሩዋቸው ግራ ይጋባሉ›› ማለት ሊሆን ይችላል፤ ወይም 2) አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚመሩትን ያህዌ ያጠፋል›› ማለት ሊሆን ይችላል።

አፍ ሁሉ ከንቱ ነገር ይናገራል

‹‹አፍ›› የሚለው ሰውየውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው ሁሉ ከንቱ ነገር ይናገራል››

በዚህ ሁሉ ቁጣው ገና አልበረደም፤ ይልቁን እጁ

‹‹ይህ ሁሉ ሆኖ እንኳ፣ አሁንም እንደ ተቆጣ ነው፤ እጁም›› ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እጁ እንደ ተዘረጋ ነው

ኢሳይያስ ያህዌን ሌላውን ሰው ለመምታት እጁን ካነሣ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። ይህ ያህዌ እስራኤልን የመቅጣቱ ምሳሌ ነው። ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁንም እነርሱን ለመቅጣት እንደ ተዘጋጀ ነው››

Isaiah 9:18

ርኩሰት እንደ እሳት ይቀጣጠላል፤ ኩርንችቱንና እሾኹን ይበላል፤ ጥቅጥቅ ያለውን ደን ያነዳል

የሕዝቡ ክፉ ሥራ በአውዳሚ እሳት ተመስሎአል። እሳቱ ከእንግዲህ ሰዎች በማይኖሩባቸው ቦታዎች የሚበቅሉትን፣ ‹‹ኩርንችትና እሾኽ›› ያቃጥላል፤ ሰዎች የሚኖሩባቸውን ቦታዎች ስላጠፋ፣ ከዚያ በፊት ሰው ያልነበረበትን ‹‹ጥቅጥቅ ያለውን ደን›› ያወድማል።

ኩርንችት… እሾኽ

‹‹ኩርንችትና›› እና፣ ‹‹እሾኽ›› ጥቅም የለሽ እሾኻማ ተክሎችን ያመለክታሉ፤ ይህን በአንድ ቃል መተርጐም ይቻላል። ኢሳይያስ 7፥23 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እሾኻማ ቁጥቋጦ››

በሰራዊት ጌታ በያህዌ ቁጣ ምድር ትጋያለች

‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ›› የሚለውን ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ያለውን እንደ ተረጐምህ ተርጉመው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምድርን እንደሚያጋይ እሳት የእግዚአብሔር ጽኑ ቁጣ የእስራኤልንም ሕዝብ ያነዳል››

ማንም ወንድሙን አያድንም

‹‹አያድንም›› ከጥፋት አያወጣም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም የገዛ ወንድሙ እንዲያመልጥ መርዳት አይችልም››

Isaiah 9:20

በቀኝ እጃቸው ይነጥቃሉ፤… በግራ እጃቸው

ይህ ማለት ምግብ ካገኙ ይነጥቃሉ ማለት ነው።

እያንዳንዱ የገዛ ክንዱን እንኳ ይበላል

ይህም ማለት 1) ሰዎች የገዛ ክንዳቸውን እንኳ እስኪበሉ ድረስ በጣም ይራባሉ ማለት ሊሆን ይችላል ወይም 2) ‹‹ክንድ›› የሰውየው ወገን ማለት ሊሆን ይችላል።

በዚህ ሁሉ ቁጣው ገና አልበረደም፤ ይልቁን እጁ

‹‹ይህ ሁሉ ሆኖ እንኳ አሁንም እንደ ተቆጣ ነው፤ እጁም›› ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

አሁንም እጁ እንደ ተዘረጋ ነው

ኢሳይያስ ያህዌን ሌላውን ሰው ለመምታት እጁን ከዘረጋ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። ይህ ያህዌ እስራኤልን የመቅጣቱ ምሳሌ ነው። ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁንም እነርሱን ለመቅጣት እንደ ተዘጋጀ ነው››

Chapter 10

Isaiah 10:1

ፍትሕ የጐደለውን ሕግ ለሚያወጡ፣ ጭቆና የሞላበትን ሥርዐት ለሚደነግጉ

እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሰው ሁሉ መልካም ያልሆኑ ሕጐችንና ሥርዐቶችን ለሚያወጡ››

የድኾችን መብት ይጋፋሉ፤ የተጨቆነውን ሕዝቤን ፍትሕ ያዛባሉ

እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሕዝቤ መካከል ላሉ ድኾችና ችግረኞች ፍትሕ አያደርጉም››

ችግረኛ

‹‹ድኻ››

መበለቶችን ይበዘብዛሉ

‹‹ባሎቻቸው ከሞቱባቸው ሴቶች ማንኛውንም ነገር ይወስዳሉ››

ወላጅ የሌላቸውን ያጠቃሉ

ኢሳይያስ ወላጅ የሌላቸውን አራዊት አድነው ከሚበሏቸው እንስሳት ጋር አመሳስሎአቸዋል። ይህም ወላጅ የሌላቸው ዐቅመ ቢስ መሆናቸውንና ዳኞች በቀላሉ ሊጐዱዋቸው እንደሚችሉ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚያድነውን እንደሚያጠቃ አውሬ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ያጠቃሉ››

ታዳኝ

ኢሳይያስ 5፥29 ላይ እንዳለው፣ ‹‹ታዳኝ›› ተብሎ ተተርጉሞአል።

Isaiah 10:3

በፍርድ ቀን ምን ታደርጋላችሁ… ምን ይውጣችኋል?

ኢሳይያስ ጥያቄውን ያቀረበው ድኻውንና ደካማውን የሚጐዱ በይሁዳ ያሉ ሰዎችን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፍርድ ቀን ምንም ማድረግ አትችሉም… ምን ይሻላችኋል!››

የፍርድ ቀን

‹‹ያህዌ ለፍርድ ሲመጣ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ እናንተን በሚቀጣበት ቀን››

ርዳታ ለማግኘት ወደ ማን ትሸሻላችሁ? ሀብታችሁንስ የት ታደርጉታላችሁ?

ኢሳይያስ ጥያቄውን ያቀረበው ድኻውንና ደካማውን የሚጐዱ በይሁዳ ያሉ ሰዎችን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ርዳታ ለማግኘት የምትሄዱበት የለም፤ ሀብታችሁን የምትደብቁባትም ቦታ የላችሁም!

ምን አይተርፋችሁም፣ ትሸማቀቃላችሁ

ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ከሀብታችሁ ምንም አይተርፍም፤ ትሸማቀቃላችሁ›› ወይም 2) ‹‹ከመሸማቀቅ ሌላ የምታደርጉት ነገር የለም››

በታሳሩ ወይም በሞቱት መካከል ትሸማቀቃላችሁ

‹‹ጠላቶቻችሁ አሥረው ይወስዳችኋል ወይም ትገደላላችሁ››

በዚህ ሁሉ ቁጣው ገና አልበረደም፤

‹‹ይህ ሁሉ ሆኖ እንኳ፣ አሁንም እንደ ተቆጣ ነው›› ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
አሁንም እጁ እንደ ተዘረጋ ነው
ኢሳይያስ ያህዌን ሌላውን ሰው ለመምታት እጁን ከዘረጋ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። ይህ ያህዌ እስራኤልን የመቅጣቱ ምሳሌ ነው። ኢሳይያስ 5፥25 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁንም እነርሱን ለመቅጣት እንደ ተዘጋጀ ነው››
Isaiah 10:5
ወዮ
ይህ ቃል አሦር ላይ እግዚአብሔር የሚያመጣው ቅጣት መጀመሩን ያመለክታል።
አሦራውያን
ይህ የሚያመለክተው የአሦርን ነገሥታት ነው።
የቁጣዬ በትር የመቅሠፍቴም ዱላ በእጁ ላለው
ሁለቱም በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ያህዌ የአሦር ንጉሥን እጁ ላይ መሣሪያ ከያዘና በዚያም ሌሎችን ከሚመታ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። ይህም የአሦር ንጉሥና ሰራዊቱ ያህዌ እስራኤልን የሚቀጣበት መሣሪያዎች መሆናቸውን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቁጣዬን ለማሳየት የምጠቀምበት እጄ ላይ እንዳለ መሣሪያ ለሆነ››
እልከዋለሁ… አዝዘዋለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአሦርን ንጉሥ ነው። እግዚአብሔር ንጉሡን ብቻ ሳይሆን፣ ከእርሱ ጋር የአሦርን ሰራዊም የላከ ይመስላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦርን ሰራዊት እልካለሁ… አዝዛቸዋለሁ››
አብሪተኛ ሕዝብ ላይ፣ የሚፈስሰው ቁጣየን የሚሸከም ሕዝብ ላይ
‹‹ትዕቢት የሚላበትን እኔንም በጣም ያስቆጣኝን ሕዝብ እንዲቀጣ››
የሚፈስሰውን ቁጣዬን የሚሸከም
የእርሱ ቁጣ መያዣው ከሚችለው በላይ ሞልቶ እንደሚፈስስ ነገር እንደሆነ ያህዌ ይናገራል፣ ‹‹ሕዝቡ›› ይህን መያዣ ለመሸከም ቢሞክሩም በጣም ከባድ ነበር፤ ሞልቶ መፍሰስ ከጀመረ በኃላ እንኳ ይህዌ መጨመሩን ቀጥሏል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከቀጣኃቸው በኃላ እንኳ አሁንም የተቆጣሁት ሕዝብ››
ምርኮ እንዲያግበሰብስ
‹‹ያላቸውን ሁሉ እንዲወስድ››
የሚታደነውን እንዲወስድ
እንደ ታዳኝ ነገር ሕዝቡን እንዲወስድ። ‹‹ታዳኝ›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ኢሳይያስ 5፥29 ተመልከት።
እንደ ጭቃ እንዲረግጣቸው
ይህ ማለት፣ 1) የአሦር ሰራዊት እስራኤልን ማጥቃቱን ጭቃው ምን እንደሚሆን ደንታ ሳይኖረው ጭቃው ላይ ከሚረማመድ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ጭቃ እስኪሆኑ ድረስ ይረግጣቸዋል›› ወይም 2) እንደ ጭቃ እስኪሆኑና መነሣት እስከማይችሉ ድረስ ሕዝቡ ሌሎች ሰዎችን ይረግጣሉ። ይህ የሚያመለክተው ሙሉ በሙሉ እንደሚያሸንፏቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፈጽሞ ያሸንፏቸዋል››
Isaiah 10:7
እርሱ ግን እንዲህ አላሰበም፤ በልቡም ይህ አልነበረም
‹‹እንዲህ›› እና፣ ‹‹ይህ›› የተሰኙትን ቃሎች የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥ እኔ የነገርሁትን ለማድረግ አላሰበም፤ እንደ መሣሪያ እየተጠቀምሁበት እንደ ነበረም አላስተዋለም ነበር››
ዕቅዱ ለማጥፋት፣ ብዙ ሕዝቦችንም ለመደምሰስ ነበር
‹‹ማጥፋት›› እና፣ ‹‹መደምሰስ›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ጥቅም ላይ የዋሉት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙ ሕዝቦችን ፈጽሞ ለመደምሰስ ይፈልጋል››
የጦር አዛዦቼ በሙሉ ነገሥታት አይደሉምን?
የአሦር ንጉሥ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ሁሉም ማወቅ አለበት ብሎ ለሚያስበው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድል ባደረግሁት አገር ሁሉ ላይ ነገሥታቴን የጦር አዛዦች አድርጌአለሁ››
ካልኖ እንደ ከርከሚሽ አይደለችምን? ሐማት እንደ አርፋድ አይደለችምን? ሰማርያ እንደ ደማስቆ አይደለችምን?
የአሦር ንጉሥ እነዚህን ጥያቄዎች ያቀረበው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ካልኖ ከኩርኩማሽ የተለየች አይደለችም፤ ሐማት ከአርፋድ የተለየች አይደለችም፤ ሰማርያም ከደማስቆ የተለየች አይደለችም፤ እኔ ሁሉንም ድል አድርጌአለሁ››
ካልኖ… ከርከሚሽ… ሐማት… አርፋድ
እነዚህ ሁሉ የከተሞች ስም ናቸው።
Isaiah 10:10
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ የአሦር ንጉሥ የተናገረውን መናገር ቀጥሏል።
እጄ፣ እንዳሸነፈች ሁሉ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› ወታደራዊ ብርታትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብርቱ የሆነው ሰራዊት ድል እንዳደረገ ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹እኔ ድል እንዳደረግሁ››
የእኔ
ይህ የሚያመለክተው የአሦርን ንጉሥ ነው።
ምስሎቻቸው የበለጡትን
በዚያ ዘመን የጣዖቱ ትልቅነት ያንን የሠራውን መንግሥት ትልቅነት ያመለክታል በማለት ሰዎች ያምኑ ነበር። የአሦር ንጉሥ የኢየሩሳሌም ጣዖቶች ድል ያደረጋቸው አገሮች ጣዖቶችን ያህል ትልልቅ አልነበሩም፤ ስለዚህም እርሱን ለመቋቋም ኢየሩሳሌም ያላት ጉልበት በጣም ታናሽ እንደሆነ መናገሩ ነበር።
በሰማርያና ከንቱ በሆኑት ጣዖቶቿ እንዳደረግሁ
‹‹ሰማርያ›› የሚለው ቃል እዚያ የነበሩ ሰዎችን፣ ‹‹የእርሷ›› የሚለው የሰማርያ ከተማን ያመለክታል። ከተሞችና አገሮች ብዙውን ጊዜ በእንስታዊ ጾታ ይጠሩ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሰማርያ ሕዝብና ከንቱ በሆኑ ጣዖቶቿ እንዳደረግሁ››
በኢየሩሌምና በጣዖቶቿስ እንዲሁ አላደርግምን?
የአሦር ንጉሥ ይህን ጥያቄ ያቀረበው የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ድል እንደሚያደርግ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኢየሩሳሌምና በጣዖቶቿም በእርግጥ ይህንኑ አደርጋለሁ››
Isaiah 10:12
ጌታ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም ላይ የሚያደርገውን ከፈጸመ በኃላ እቀጣዋለሁ።
ያህዌ ስለ ራሱ እንደሌላ ሰው ይናገራል። ‹‹እኔ ጌታ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም የምሠራውን ከፈጸምሁ በኃላ እቀጣዋለሁ››
የሚያደርገው… ላይ
የመቅጣቱ ሥራ። ‹‹እቀጣለሁ… እቀጣዋለሁ››
የአሦርን ንጉሥ ልብ እብሪትና የንቀት አመለካከት እቀጣለሁ
‹‹ስለ ተናገረው እብሪትና የትዕቢት አመለካከቱ የአሦርን ንጉሥ እቀጣለሁ››
እንዲህ ብሏልና
‹‹የአሦር ንጉሥ እንዲህ ብሏልና››
አፈረስሁ… ዘረፍሁ
‹‹እኔ›› የሚለው የሚያመለክተው የአሦርን ንጉሥ ነው። እርሱ የአሦር ሰራዊት መሪ ስለ ነበር በእርሱ ትእዛዝ ሰራዊቱ ስላደረገው ሁሉ ክብሩን ይወስድ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰራዊቴ አፈረሰ… ዘረፈ››
እንደ ወይፈን
‹‹እንደ ወይፈን የበረታ›› አንዳንድ የጥንት ቅጂዎች፣ ‹‹እንደ ኀያል ሰው›› ይላሉ።
ነዋሪዎቹን አዋረድሁ
ይህም ማለት፣ 1) የአሦር ንጉሥ ድል ያደረጋቸው አገሮችን ሕዝቦች አዋርዶ ነበር፤ ወይም 2) ከእንግዲህ መግዛት እንዳይችሉ የአሕዛብ ነገሥታትን አስወግዶ ነበር ማለት ሊሆን ይችላል።
ሰበሰብሁ
‹‹እኔ›› የሚያመለክተው የአሦርን ንጉሥ ነው። የአሦር ሰራዊት መሪ ስለ ነበር በእርሱ ትእዛዝ ሰራዊቱ ላደረገው ሁሉ ክብር ይወስድ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔና ሰራዊቴ ሰበሰብን›› ወይም፣ ‹‹እኛ ሰበሰብን››
Isaiah 10:14
አጠቃላይ መረጃ
አሁንም ያህዌ የአሦር ንጉሥ የተናገረውን እየተናገረ ነው። (ኢሳይያስ 10፥13 ይመ.)
በእጄ ያዝሁ
እጅ የንጉሡን ወይም የሰራዊቱን ኀይል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኀይሌ ያዝሁ›› ወይም ‹‹ሰራዊቴ ያዘ››
ከወፍ ጐጆ እንደሚይዝ የሕዝቦችን ሀብት ያዝሁ
የአሦር ንጉሥ የሕዝቦችን ሀብት መውሰዱን ወፍ ጐጆ ውስጥ ያለውን ዕንቁላል ከሚወስድ ሰው ጋር ያመሳስለዋል። ይህም እነዚያን ሕዝቦች ድል ማድረግ ለእርሱና ለሰራዊቱ ምን ያህል ቀላል እንደ ነበር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዕንቁላል ከወፍ ጐጆ እንደሚሰበሰብ፣ ሰራዊቴ የሕዝቦችን ሀብት በቀላሉ ዘረፈ››
የተተወ ዕንቁላል እንደሚሰበሰብ እኔም ምድርን ሁሉ ሰበሰብሁ

የአሦር ንጉሥ መንግሥታትን መውሰዱን ዕንቁላል ከመውሰድ ጋር ያመሳስለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱን ለመከላከል ወፏ በሌለችበት ጊዜ ከጐጆዋ ዕንቁላሎች እንደሚሰበስብ ሰው፣ ሰራዊቴም ከአገር ሁሉ ሀብት ሰበሰበ››
ክንፉን ያራገበ አልነበረም፤ አፉን ከፍቶ የጮኸ አልነበረም
ይህ ሕዝቦችን ዕንቁላሎቿ ሲወሰዱ ዝም ብላ ከምታይ ወፍ ጋር ያመሳስላቸዋል። ይህም የአሦር ንጉሥ ሰራዊት ሀብታቸውን ሁሉ ሲወስድ ሕዝቦች ምንም አለማድረጋቸውን አጽንዖት ይሰጣል›› አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዕንቁላሎቿ ሲሰረቁ ድምፅ እንደማታሰማ ወይም ክንፏን እንደማታራግፍ ወፍ፣ እኛ ሀብታቸውን ስንዘርፍ ሕዝቦች ምንም አላደረጉም››
Isaiah 10:15
መጥረቢያ በሚቆርጥበት ሰው ላይ ይኩራራልን፤ መጋዝስ ከሚጠቀምበት ሰው ይበልጥ ራሱን ያመሰግናልን?
ተናጋሪው እነዚህን ጥያቄዎች የሚያቀርበው በአሦር ንጉሥ ለመሳለቅ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መጥረቢያ ከሚጠቀምበት ሰው የበለጠ እንደሆነ አይኩራም፤ መጋዝም ከሚቆርጥበት ሰው የበለጠ ክብር አያገኝም››
መጋዝ
እንጨት ለመቁረጥ የሚያገለግል ስለታም መሣሪያ
በትር በሚያነሣው ሰው ላይ ራሱን እንደሚነቀንቅ ወይም የእንጨት ዱላ ሰውን እንደሚያነሣ አድርጐ እንደሚኩራራ ነው
እነዚህ ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ ጥቅም ላይ የዋሉት የሁለቱን ጥያቄዎች ትርጉም ለማጠናከር ነው። ይህን በአዲስ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በትርም ሆነ ዱላ በሚያነሣው ሰው ላይ አይኩራራም››
ስለዚህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ በምርጥ ጦረኞቹ ላይ የሚያከሳ በሽታ ይልካል
እየተናገረ ያለው ያህዌ ወይም ኢሳይያስ መሆኑ ግልጽ አይደለም። ‹‹የሚያከሳ›› የሚለውን፣ ‹‹የሚያደክም›› በማለት መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ፣ ብርቱዎቹን የንጉሡን ወታደሮች ያደክማል››
ከክብሩም በታች እንደ ነበልባል የሚንቦገቦግ እሳት ይለኮሳል
ያህዌ የእርሱን ቅጣት ከእሳት ጋር ያመሳስለዋል። ይህም የሚያመለክተው የእርሱ ቅጣት የአሦርን መንግሥት ውበትና ታላቅነት ሁሉ ጨርሶ የሚያወድም መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ የታበየበትን ማንኛውንም ነገር የሚያጠፋ እሳት በመሆን ታላቅነቱን ሁሉ አወድማለሁ››
Isaiah 10:17
የእስራኤል ብርሃን እሳት ይሆናል
‹‹የእስራኤል ብርሃን›› የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ያህዌን ነው። እየተናገረ ያለው ያህዌ ወይም ኢሳይያስ መሆኑ ግልጽ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ብርሃን እኔ ያህዌ፣ የማያከብረኝን ሁሉ ማጥፋት እንደሚችል እሳት እሆናለሁ››
ቅዱሱም ነበልባል ይሆናል
‹‹የእስራኤል ቅዱስ እኔ ያህዌ እንደ ነበልባል እሆናለሁ›› ኢሳይያስ 1፥4 ላይ፣ ‹‹ቅዱስ›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
እሾኹንና ኩርንችቱን ሁሉ እሳት ይበላዋል
‹‹እሳቱ የአሦር ንጉሥ እሾኽና ኩርንችት ይበላዋል›› ተናጋሪው የአሦርን ንጉሥ ሰራዊት ከእሾኽና ከኩርንችት ጋር ያመሳስለዋል። ይህም እግዚአብሔር ምን ያህል በቀላሉ እንደሚያጠፋው አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እሾኹንና ኩርንችቱን እንደሚበላ እሳት አሦራውያንን አጠፋለሁ››
Isaiah 10:20
በዚያን ቀን
ይህ የሚያመለክተው ኢሳይያስ 10፥16-19 ላይ ያለውን ያህዌ የሚፈጽምበትን ጊዜ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያ ጊዜ››
ያመለጠ
ይህ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአሦር ሰራዊት ያመለጠ››
ድል ባደረጋቸው ላይ አይታመኑም
‹‹ጉዳት ባደረሰባቸው በአሦር ንጉሥ ከእንግዲህ አይታመኑም››
ቅዱሱ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
Isaiah 10:22
እስራኤል ሕዝብህ
እዚህ ላይ ‹‹የአንተ›› ነጠላ ቁጥር ነው። ይህም ማለት፣ 1) እግዚአብሔር ለኢሳይያስ እየተናገረ ነው፤ ‹‹አንተ›› የሚለው ኢሳይያስን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአንተ ሕዝብ እስራኤል›› ወይም 2) ለእስራኤል ሕዝብ ኢሳይያስ ወይም እግዚአብሔር እየተናገሩ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ‹‹የአንተ›› የእስራኤልን መንግሥት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስራኤል ሆይ፣ ሕዝብህ››
በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ ናቸው
ይህ አጽንዖት የሚሰጠው የእስራኤል ሕዝብ ቁጥር በጣም ብዙ እንደሚሆን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ መቆጠር አይችሉም››
ጥፋት ታውጆአል
ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእስራኤል የሚኖሩ ብዙዎችን ለማጥፋት ያህዌ ወስኖአል››
እንደ ወንዝ እየፈሰሰ ያለው ጽድቅ፣ ይህ እንዲሆን ግድ ይላል።
ይህን እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ መሆን ያለበት ፍጹም ከሆነው ጽድቅ የተነሣ ነው›› ወይም፣ ‹‹እርሱ ፍጹም ጻድቅ ስለሆነ ያህዌ ይህን ማድረግ ይኖርበታል።››
የወሰነውን ጥፋት በምድር ሁሉ ላይ ያመጣል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። ይህም ማለት፣ 1) አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ እንደ ወሰነው በምድሪቱ ያለውን ማንኛውንም ነገር ያጠፋል›› ወይም 2) አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ እንደ ወሰነው በምድሪቱ ያለውን ሕዝብ ያጠፋል››
እንደ ወሰነ
‹‹እንዳቀደው››
Isaiah 10:24
አሦራውያን
ኢሳይያስ እንደ አንድ ሰው አድርጐ ስለ አሦር ንጉሥና ስለ ሰራዊቱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥና ሰራዊቱ››
በበትር ይመታሃል፤ ሽመል ያነሣብሃል
‹‹በትር›› እና፣ ‹‹ሽመል›› የተሰኙት ቃሎች ሰዎች እንስሳትን ወይም ሌሎች ሰዎችን ለመምታት የሚጠቀሙባቸው እንጨቶች ናቸው። አሦራውያን እስራኤላውያንን ስለሚገዙበት መንገድ ነው ኢሳይያስ እየተናገረ ያለው፤ አሦራውያን እስራኤላውያንን በበትር ይመቷቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተን ይገዛል፤ ባርያዎቹም ያደርጋችኋል››
ይመታል
‹‹እርሱ›› የሚለው የአሦር ንጉሥና ሰራዊቱን የሚወክለው ‹‹አሦርን›› ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱና ሰራዊቱ ይመታሉ››
ግብፃውያን እንዳደረጉት
ይህ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግብፃውያን አባቶችህን እንደ ገዙና ባርያዎች እንዳደረጓቸው››
በቁጣዬ ይጠፋል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእርሱ ላይ ስለ ተቆጣሁ አጠፋዋለሁ››
Isaiah 10:26
የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
በጅራፍ ይገርፋቸዋል
‹‹አሦራውያንን በአለንጋ ይገርፋቸዋል›› እግዚአብሔር በእርግጥ ጅራፍ አይጠቀምም። ይህ የሚያመላክተው አሦራውያንን በጽኑ ለመቅጣት እግዚአብሔር ያለውን ኀይል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጅራፍ እንደሚገረፍ አሦራውያንን በጣም ይቀጣል››
በሔሬብ ዐለት አካባቢ ምድያምን እንደ መታ
ይህ የሚያመለክተው የምድያምን ጦር ድል እንዲያደርግ ጌዴዎን የሚባለውን ሰው እግዚአብሔር መርዳቱን ነው።
በግብፅ እንዳደረገው ሁሉ በትሩን በባሕር ላይ ያነሣል
ይህ የሚያመለክተው እነርሱ የግብፃውያን ሠራዊት የነበሩ ይመስል፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከአሦራውያን ማዳኑን ነው። ይህ የሚያመለክተው እስራኤላውያን ከግብፃውያን ሰራዊት እንዲያመልጡና የግብፃውያን ሰራዊት ግን ሰጥሞ እንዲቀር እግዚአብሔር ቀይ ባሕር እንዲከፈል ማድረጉን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አባቶቻችሁ ከግብፅ ሰራዊት እንዲያመልጡ እንደ ረዳቸው ሁሉ እናንተም ከአሦር ሰራዊት እንድታመልጡ ይረዳችኋል።››
ሸክሙ ከትከሻህ ቀንበሩም ከዐንገትህ ላይ ይነሣል

‹‹አሦር ትከሻህ ላይ ያደረገውን ሸክም ያህዌ ያነሣል፤ ዐንገትህ ላይ ያስቀመጡትንም ቀንበር ያህዌ ያስወግዳል ሁለቱ ሐረጐች የሚሉት በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው፡፡ ‹‹ሸክም›› እና፣፣ ‹‹ቀንበር›› የሚያመለክቱት ባርነትን ነው፡፡ ይህን በሌላ መልኩ መግለጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ያህዌ የጨቆኑህን አሦራውያን ያስወግዳል፤ አንተን ባርያቸው እንዳያደርጉም ያስቆማቸዋል››

ቀንበሩ ከውፍረት የተነሣ ይሰበራል

አገላለጹ ቀንበሩን የሚሸከመው እንስሳ ዐንገት በጣም እንደሚወፍርና ከዚያ በኃላ ለቀንበሩ ተስማሚ እንደማይሆን ያመለክታል፡፡ ይህ የሚያመለክተው እስራኤል በጣም ብርቱ እንደሚሆንና ከእንግዲህ አሦራውያን እርሱን መግዛት የማይችሉ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ዐንገትህ በጣም ከመወፈሩ የተነሣ ቀንበር ይሰበራል›› ወይም፣ ‹‹በጣም ብርቱ ስለምትሆን ከእንግዲህ የአሦራውያን ባርያ አትሆንም››

Isaiah 10:28

ይገባሉ... ያልፋሉ... ያከማቻሉ... ይሻገራሉ... ያድራሉ... ይደነግጣሉ... ሸሽቾ

እነዚህ ወደ ፊት የሚፈጸሙ ሁኔዎች አሁን እንኳ እንደ ተፈጸሙ አድርጐ አሳይያስ ይናገራል፡፡

ዐያት... ግሮን... ሚክማስ... ጌባ... ራማ... ጊብዓ

እነዚህ ሁሉ የአሦር ሰራዊት ያለፈባቸውና ብዙ ችግር ያደረሰባቸው ኢየሩሳሌም አጠገብ ያሉ ከተሞችና መንደሮች ናቸው፡፡

ራማ ደነገጠች የሳኦል ጊብዓ ሸሸች

‹‹ራማ›› እና፣ ‹‹የሳኦል ጊብዓ›› የሚያመለክቱት በእነዚህ ከተሞች የነበሩትን ሕዝብ ነው፡፡ አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የራማ ሕዝብ ደነገጡ የሳኦል ጊብዓ ሰዎችም ሸሹ››

Isaiah 10:30

የጋሊም ሴት ልጅ

‹‹ሴት ልጅ›› በእነዚያ ከተሞች ሚኖሩትን ሰዎች ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጋሊም›› ወይም፣ ‹‹የጋሊም ሰዎች››

ጋሊም... ላይሻ... ዓናቶት... ማድሜናህ... ጌቢም... ኖብ

እነዚህ የአሦር ሰራዊት ያለፈባቸውና ብዙ ችግር ያደረሰባቸው ኢየሩሳሌም አጠገብ የነበሩ የተጨማሪ ከተሞችና መንደሮች ስም ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ በእነዚህ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታሉ፡፡

ኖብ ላይ ይቆማል፤ እጁን ይነቀንቃል

እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› እና፣ ‹‹የእርሱ›› የአሦር ንጉሥና ወታደሮቹን ያመለክታሉ፡፡ ሰዎች በሚዝቱባቸው ላይ እጃቸውን ይነቀንቃሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥ ኖብ ላይ ይቆምና ያስፈራራል››

የጽዮን ሴት ልጅ ተራራ፤ የኢየሩሳሌም ኮረብታ

‹‹ተራራ›› እና፣ ‹‹ኮረብታ›› እነርሱ ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታሉ፡፡ ‹‹የጽዮን ሴት ልጅ ተራራ›› እና ‹‹የኢየሩሳሌም ኮረብታ›› የተሰኙት ቃሎች በአመዛኙ አንድ ዐይነት ነገር ማለት ናቸው፡፡ አሳይያስ 2፥14 ላይ እንዴት እንደ ተረጐምሃቸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የጽዮን ተራራ ሰዎችና በኢየሩሳሌም ኮረብታ የሚኖሩ ሰዎች››

Isaiah 10:33

እነሆ

ይህን፣ ‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹አድምጡ›› ወይም፣ ‹‹የምናገረውን ልብ ብላችሁ ስሙ›› በማለት መተርጐም ይቻላል፡፡

የሰራዊት ጌታ ያህዌ

አሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት፡፡

ረጃጅም ዛፎች ይገነደሳሉ... ሊባኖስም በግርማው ፊት ይወድቃል

አሳይያስ የአሦር ሰራዊት በሊባኖስ እንዳሉ ረጃጅም ዛፎች እንደሆነ ይናገራል፡፡ ሰዎች የሊባኖስን ታላላቅ ዛፎች እንደሚገነድሱ እግዚአብሔር ሰራዊቱን ይደመስሳል፡፡ ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ሰራዊቱ በጣም ብርቱ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር እርሱን ለማጥፋት ያለውን ኀይል ነው፡፡

ረጃጅም ዛፎች ይገነደሳሉ

‹‹የዛፉ ትልልቅ ቅርንጫፎች ይቆረጣሉ›› እየተናገረ ያለው የአሦር ሰራዊትን እንደሆነ ግልጽ ለማድረግ በተመሳሳይ መንገድ መተርጐም ይቻላል፤ አንድ ብርቱ ሰው ትልልቆቹን የዛፎች ቅርንጫፎች እንደሚቆርጥ የአሦርን ሰራዊት ያጠፋል፡፡

በአስፈሪ ድምፅ

‹‹ድምፅ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ድምፅ ያወጣል›› በሚል ግስ ለመተርጐም እንዲቻል ዐረፍተ ነገሩን እንደ ገና ማቀናጀት ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቅርንጫፎቹ መሬት ላይ ሲወድቁ አስፈሪ ድምፅ ይሰጣሉ›› ወይም፣ ‹‹ቅርንጫፎቹ በታላቅ ድምፅ መሬት ላይ ይወድቃሉ››

ረጃጅሞቹ ዛፎች ይቆረጣሉ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ረጃጅሞቹን ዛፎች ይቆርጣል››

ረጃጅም ዛፎች

ይህ፣ ‹‹ብርቱዎች ወታደሮች›› ማለት ነው፡፡

ከፍ ከፍ ያሉትም ይወድቃሉ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታላላቅ ሰዎችን ይጥላል፡፡

ከፍ ከፍ ያሉ

‹‹የታበዩ››

ጥቅጥቅ ያለው ደን

‹‹በተክሎች ጥቅጥቅ ያለ ጫካ›› ይህ በሚገባ ያልታወቁ ሰዎችን የሚያመላክት ምሳሌ ነው፡፡

ሊባኖስም በግርማው ፊት ይወድቃል

‹‹የሊባኖስ ጫካዎች ከእንግዲህ ታላቅ አይሆኑም›› ይህ የአሦር ሰራዊትን የሚያመለክት ምሳሌ ሊሆን ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ እጅግ ብርቱ ስለሆነ ያህዌ የአሦርን ሰራዊት ያሸንፋል››

---

Chapter 11

Isaiah 11:1

ከእሴይ ግንድ ቁጥቋጥ ይወጣል... ከሥሮቹም አንዱ ቅርንጫፍ ፍሬ ይሰጣል

አሳይያስ እሴይና ዘሮቹ ተቆርጦ እንደ ነበረ ዛፍ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ንጉሥ ስለሚሆነው የእሴይ ዘር ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዛፉ ግንድ ቅርንጫፎች እንደሚወጡ የእሴይም ዘር በእስራኤል በተረፈት ላይ ንጉሥ ይሆናል››

የእሴይ ግንድ

ግንዱ ዛፉ ከተመለመለ በኃላ የሚቀረው ክፍል ነው፡፡ ‹‹የእሴይ ግንድ›› የእሴይ ልጅ ዳዊት በአንድ ወቅት ንጉሥ ከነበረበት መንግሥት የቀረውን ያመለክታል፡፡

የያህዌ መንፈስ ያርፍበታል

እርሱ ላይ ማረፉ ከእርሱ ጋር እንደሚሆንና እንደሚረዳው ያመለክታል፡፡ ‹‹እርሱ›› የሚለው ቃል ንጉሥ የሚሆነውን ሰው ያመለክታል፡፡

የጥበብ መንፈስ.. የምክር መንፈስ... የዕውቀት መንፈስ... ያህዌን የመፍራት መንፈስ

እዚህ ላይ፣ ‹‹መንፈስ›› የሚለው ቃል የያህዌ መንፈስ የሚሰጠውን ችሎታ ወይም ባሕርይ ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥበብና ማስተዋል፤ ምክርና ኀይል፣ ዕውቀትና ያህዌን መፍራት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡››

Isaiah 11:3

አያያዥ ዐረፍተ ነገር

አሳይያስ ስለ ንጉሡ መናገሩን ቀጥሏል

ዐይኑ እንዳዩ አይፈርድም

‹‹ዐይኑ እንዳዩ›› የሚለው ሐረግ ሰውየው ላይ ለመፍረድ የሚያስችሉ አስፈላጊ ያልሆኑ ነገሮችን ማየትን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ውጫዊ ሁኔታውን በማየት ብቻ ሰውየው ላይ አይፈርድም››

ጆሮውም እንደ ሰማ አይበይንም

‹‹ጆሮው በሚሰማው አይወስንም›› - ‹‹ጆሮው እንደ ሰማ›› የሚለው ሐረግ ሰዎች ስለ ሌላው ሰው የሚናገሩን መስማት ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌሎች ስለ እርሱ የሚናገሩትን በመስማት ብቻ ማንም ላይ አይፈርድም››

ለድኾች... ለምስኪኖች... ለክፉዎች

እነዚህ ቃሎች እነዚህ ባሕርያት ያሏቸውን ሰዎች ያመለክታሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድኾች ሰዎች... ምስኪን ሰዎች... ክፉዎች ሰዎች››

በአፉ በትር ምድርን ይመታል፤ በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል

ሁለቱም ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው

በአፉ በትር ምድርን ይመታል

‹‹ምድር›› በምድር የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል፡፡ በአፉ እስትንፋስ መምታት እነርሱ ላ መፍረድንና ፍርዱም ወደ ቅጣት ማድረሱን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር ሕዝብ ላይ ይፈርዳል፤ እነርሱም ይቀጣሉ››



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል

‹‹የከንፈሩ እስትንፋስ›› እነርሱ ላይ መፍረድን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉዎች ላይ ይፈርዳል፤ እነርሱም ይገደላሉ››

የወገቡ መታጠቂያ... የጐኑ መቀነት

ይህም ማለት፣ 1) መታጠቂያ መሥራት እንዲችል የሰውን ልብስ ለመያዝ ይጠቅማል። ወይም 2) መታጠቂያ በውስጥ የሚለበስ ነው ወይም 3) መታጠቂያ ሥልጣኑን ለማሳየት ንጉሡ የሚለብሰው መጐናጸፊያ ነው።

ጽድቅ የወገቡ መታጠቂያ ይሆናል

እንደ ቀበቶ ጽድቅን ወገብ ላይ መታጠቅ ጻድቅ መሆንን ይወክላል። ይህም ማለት፣ 1) የንጉሡ ጽድቅ ለመግዛት ያስችለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጽድቅ ይገዛል››

ታማኝነትም የጐኑ መቀነት

እዚህ ሐረግ ላይ፣ ‹‹ይሆናል›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታማኝነት ጐኑ ላይ መቀነት ይሆናል››

ታማኝነት የጐኑ መቀነት

እንደ መቀነት ታማኝነትን መታጠቅ ታማኝ መሆንን ያመለክታል። ይህም ማለት፣ 1) የንጉሡ ታማኝነት ለመግዛት ያስችለዋል ማለት ነው፣ ወይም 2) የንጉሡ ታማኝነት ለመግዛት ያለውን ሥልጣን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታማኝነት እንደ መቀነት ጐኑ ላይ ይሆናል›› ወይም፣ ‹‹በታማኝነት ይገዛል››

Isaiah 11:8

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ንጉሡ በሚገዛበት ጊዜ በዓለም የሚኖረውን የተሟላ ሰላም መግለጹን ቀጥሏል

ሕፃን ልጅ በእባብ ጉድጓድ ይጫወታል

እባቡ ስለማይነድፈው ልጁ ደህና እንደሚሆን በግልጽ መነገር አለበት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕፃናት ምንም ሳይጐዳቸው በእባብ ጉድጓድ ላይ ይጫወታሉ››

እባብ... የእባብ ጉድጓድ

ይህ የሚያመለክተው በጠቅላላ መርዛማ እባቦችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እባቦች... የእባቦች ጉድጓድ››

ጡት የጣለ ሕፃን

የእናቱን ጡት ወተት መጠጣት ያቆመ

በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ ላይ

‹‹የተቀደሰ ተራራ›› በኢየሩሳሌም ያለው የጽዮን ተራራ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በያህዌ ቅዱስ ተራራ ሁሉ››

ምድር ያህዌን በማወቅ ትሞላለች

‹‹ያህዌን በማወቅ›› የሚለው ሐረግ ያህዌን የሚያውቁ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምድር ያህዌን በሚያውቁ ሰዎች ትሞላለች›› ወይም፣ ‹‹ያህዌን የሚያውቁ ምድርን ይሸፍናሉ››

ውሃ ባሕርን እንደሚሸፍን

ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው ምድር ምን ያህል ያህዌን በሚያውቁ ሰዎች እንደምትሞላ ለማሳየት ነው። ቃሎቹ ከቀደመው ሐረግ ጋር ተመሳሳይ ከሆኑ ይህ እንደሚሆን የበለጠ ግልጽ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ውሃ ባሕሮችን እንደሚሞላ››

Isaiah 11:10

የእሴይ ሥር

ይህ የሚያመለክተው ንጉሥ እንደሚሆን ኢሳይያስ 1፥1 የተነገረለትን የእሴይንና የንጉሥ ዳዊትን ልጅ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሡ የእሴይ ልጅ›› ወይም፣ ‹‹ንጉሥ የሚሆነው የእሴይ ልጅ››

ለሕዝቦች ምልክት ሆኖ ይቆማል

‹‹ምልክት›› ሰዎች ዐይተው ወደ እርሱ እንዲመጡ ንጉሡ ከፍ የሚያደርገው ባንዲራ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለሕዝቡ እንደ ምልክት ይሆናል›› ወይም፣ ‹‹ወደ እርሱ እንዲመጡ ሕዝቡን ይስባል››

ሕዝቦች

‹‹የአገሩ ሰዎች››

ጌታ እጁን ዘርግቶ የተረፈውን የሕዝቡን ቅሬታ ይሰበስባል

እጅ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኀይል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሕዝቡን ቅሬታ መልሶ ለማምጣት እንደ ገና ጌታ ኀይሉን ይጠቀማል››

ጳጥሮስ... ኤላም... ሐማት

እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው

Isaiah 11:12

ለመንግሥታት ምልክትን ያቆማል

ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ጌታ ለመንግሥታት ንጉሡን እንደ ምልክት ያቆማል›› ወይም፣ ‹‹ንጉሡ ለመንግሥታት ምልክት ያቆማል››

ለመንግሥታት ምልክት

‹‹ሰዎች የሚያዩት ባንዲራ›› ወይም፣ ‹‹መንግሥታትን ወደ ራሱ ለመጥራት ባንዲራ››

የተበተኑትን የይሁዳ ሕዝብ

‹‹በዓለም ዙሪያ የተበተኑ የአይሁድ ሕዝብ››

ከአራቱም የምድር ማእዘን

ምድር አራት ማእዘኖች እንዳሏት ተስሏል፤ እነዚህ ማእዘኖች በጣም ተራርቀው ነው ያሉት። ይህም እነዚህ ሰዎች የሚገኙባቸው መላውን ምድር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር ካሉ በጣም ሩቅ ቦታዎች እንኳ ሳይቀር›› ወይም፣ ‹‹ከምድር ሁሉ››

የኤፍሬም ምቀኝነት ያከትማል

እዚህ ላይ፣ ኤፍሬም የሰሜናዊው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። ‹‹ምቀኝነት›› የሚለውን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኤፍሬም ሕዝብ ምቀኝነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል››

ይሁዳም የኤፍሬም ጠላት አይሆንም

እዚህ ላይ ይሁዳ የሚያመለክተው የደቡባዊውን መንግሥት ሰዎች ነው። ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የይሁዳ ሕዝብ ጠላት እንዳይሆኑ ያደርጋል›› ወይም፣ ‹‹የይሁዳን ሕዝብ ጥላቻ ያስቆማል››

Isaiah 11:14

በፍልስጥኤም ተራሮች ላይ ቁልቁል ይበርራሉ

የእስራኤልና የይሁዳ ሕዝብ ሰውን ወይም እንስሳን ለማጥቃት በድንገት ቁልቁል በሚበሩ ወፎች ተመስለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እዚያ ያሉትን ሰዎች ለማጥቃት ወደ ፍልስጥኤም ተራሮች በፍጥነት ይሄዳሉ››

የግብፅ ባሕረ ሰላጤ

‹‹ባሕረ ሰላጤ›› በከፊል በመሬት የተከበበ ትልቅ የውሃ አካል ነው።

በሚጋረፍ ነፋስ እጁን በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ ያንቀሳቅሳል

እጁን በአንዳች ነገር ላይ ማንቀሳቀሱ የመለወጥ ኀይሉን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በታላቅ ኀይሉ በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ የሚጋረፍ ነፋስ ያነፍሳል››

የሚጋረፍ ነፋስ

ይህ ጥቂቱን የወንዞች ውሃ የሚያደርቅ ሞቃት ነፋስ ነው።

ከነጫማቸው መሻገር ይችላሉ

‹‹ሰዎች ጫማቸውን እንዳደረጉ እንዲሻገሩት››

Isaiah 11:16

አውራ መንገድ ይሆናል

አውራ መንገድ ብዙ ሰዎች መጓዝ የሚችሉበት ሰፊ መንገድ ነው። ‹‹ያህዌ መንገድ ያደርጋል››

ከግብፅ ምድር ሲመጡ

‹‹ከግብፅ ምድር ወጥተው ሲመጡ››

---

Chapter 12

Isaiah 12:1

አጠቃላይ መረጃ

እዚህ ላይ ኢሳይያስ እግዚአብሔር የመረጠው ንጉሥ በሚገዛበት ጊዜ የሚሆነውን መግለጽ ቀጥሏል።

Isaiah 12:3

ከድነት ምንጮች ውሃ በደስታ ትቀዳላችሁ

የዳኑት ሰዎች ከምንጭ ውሃ እንዳገኙ ሰዎች እንደሆኑ ኢሳይያስ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ከምንጭ ውሃ ሲቀዱ ደስ እንደሚላቸው እርሱ ሲያድናችሁ እናንተም ደስ ይላችኋል››

ስሙንም ጥሩ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ስሙ›› የተባለው ያህዌ ነው። ስሙን ጥሩት ማለት እርሱን ማመስገንን ወይም የእርሱን ርዳታ መለመንን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አመስግኑት›› ወይም፣ ‹‹እንዲረዳችሁ ጥሩት››

ያደረገውን በአሕዛብ መካከል አስታውቁ

‹‹ያደረገውን›› የሚለውን፣ ‹‹እርሱ አድርጐ የነበረውን›› በሚል ሐረግ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ያደረገውን ታላላቅ ነገሮች ለሕዝብ ተናገሩ››
ስሙ ከፍ ከፍ ማለቱን ዐውጁ
‹‹ስሙ›› የሚያመለክተው፣ ያህዌን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ከፍ ከፍ ያለ መሆኑን ዐውጁ›› ወይም፣ ‹‹እርሱ ታላቅ መሆኑን ዐውጁ››
Isaiah 12:5
አጠቃላይ መረጃ
ንጉሡ በሚገዛበት ጊዜ ሕዝቡ ምን እንደሚሉ ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል
በመካከላችሁ ያለው የእስራኤል ቅዱስ ታላቅ ነውና
‹‹ምክንያቱም በመካከላችሁ ያለው የእስራኤል ቅዱስ ብርቱ ነው›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል ቅዱስ ብርቱ ስለሆነ በመካከላችሁም ስለሚኖር››

---

Chapter 13
Isaiah 13:1
ስለ ባቢሎን
የከተማዋ ስም የባቢሎንን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለ ባቢሎን ሕዝብ››
አሞጽ
አሞጽ የኢሳይያስ አባት ነው። ኢሳይያስ 1፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ወደ እነርሱ ጩኹ
‹‹እነርሱ›› የሚለው የሌላ አገር ወታደሮች ያመለክታል።
በመሳፍንቱ በር
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹መሳፍንቱ የሚኖሩበት የባቢሎን በሮች›› ወይም 2) ‹‹የመሳፍንቱ ትልልቅ ቤቶች በሮች››
መሳፍንቱ
‹‹የተከበሩ ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ገዦች››
ቅዱሳኔ
‹‹እኔ ለራሴ የለየሁቸው›› ወይም፣ ‹‹ለራሴ የለየሁዋቸው ሰራዊት››
ቁጣየን እንዲፈጽሙ ተዋጊዎቼን ጠርቻለሁ
የእግዚአብሔርን ቁጣ መፈጸም እርሱ ስለ ተቆጣ ሰዎችን መቅጣትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንድቆጣ ስላደረጉን የባቢሎንን ሕዝብ እንዲቀጡ ብርቱ ተዋጊዎቼን ጠርቻለሁ››
በድል አድራጊነቴ ደስ የሚላቸውን
‹‹በተገኘው ድል ደስ የሚላቸው›› ደስ የሚላቸው ለምን እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ካደረግሁት ታላቅ ነገር የተነሣ እጅግ ደስ የሚላቸው ሕዝቤ››
Isaiah 13:4
በተራሮች ላይ እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ
‹‹አለ›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። ‹‹ብዙ›› እና፣ ‹‹ብዙ ሕዝብ›› የሚሉት ሐረጐች ተመሳሳይ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተራሮች ላይ የብዙ ሕዝብ ድምፅ አለ›› ወይም፣ ‹‹የብዙ ሕዝብ ድምፅ ተራሮች ላይ አለ››
በመንግሥታትም መካከል እንደ ተጨናነቁ ሕዝብ ድምፅ የሆነውን ውካታ
‹‹አለ›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹መንግሥታት›› እና፣ ‹‹ሕዝብ›› የሚያመለክቱት ተመሳሳይ ነገርን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአንድነት የተከማቹ የብዙ መንግሥታት ታላቅ ጩኸት አለ››
ተከማችተዋል
‹‹ተሰብስበዋል››
ከአድማሱ ባሻገር
‹‹ከአድማስ ማዶ ሩቅ ካለ ቦታ›› ወይም፣ ‹‹በጣም ሩቅ ከሆነ ቦታ››
የፍርዱ ጦር መሣሪያ
ባቢሎንን እንዲያጠቁ እግዚአብሔር የሚልካቸው ወታደሮች የጦር መሣሪያዎች እንዲሆኑ ተነግሯል። ‹‹ፍርድ›› እግዚአብሔር ባቢሎን ላይ ስለ ፈረደ ቅጣትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባቢሎንን ለመቅጣት የሚጠቀምበት ሰራዊት››
Isaiah 13:6
ጩኹ
ድምፃችሁን አሰምታችሁ ጩኹ፤ ብዙውን ጊዜ ቃሉ የሚያመለክተው ጉዳት ስለ ደረሰበት እየጮኸ ያለውን እንስሳ ድምፅ ነው።
የያህዌ ቀን ቀርቦአል
የሚሆነው ነገር በጣም እየቀረበ እንዳለ ነገር መሆኑ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያህዌ ቀን በቅርቡ ይሆናል››
ሁሉን ከሚችል አምላክ ዘንድ ጥፋት ይመጣል
‹‹ይመጣል›› የተባለው የያህዌ ቀን ነው። ‹‹ከጥፋት ጋር ይመጣል›› ማለት በዚያ ቀን ጥፋት ይሆናል ማለት ነው። ‹‹ሁሉን ከሚችል አምላክ ዘንድ ጥፋት›› ማለት ሁሉን ቻዩ ያጠፋቸዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያን ቃል ሁሉን ቻዩ አምላክ ያጠፋቸዋል››
እጆች ሁሉ ሽባ ይሆናሉ
ይህ የሚያሳየው ሰዎች ሁሉ በጣም ደካማና ምንም ማድረግ አለመቻላቸውን ነው።
የሰውም ሁሉ ልብ ይቀልጣል
ሰዎች በጣም መፍራታቸው ከልባቸው መቅለጥ ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው ሁሉ በጣም ይፈራል››
ሥቃይና ጭንቀት ይይዛቸዋል
ሰዎች ላይ ከባድ ሥቃይና ጭንቀት በድንገት መድረሱ ሥቃይና ጭንቀት ጨምድዶ እንደሚይዝ ሰው ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በድንገት ከባድ ሥቃይና ጭንቀት ይደርስባቸዋል››
ምጥ እንደ ያዛት ሴት
ምጥ ልጅ መውለድን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልጅ እንደምትወልድ ሴት ወይም፣ ‹‹ልጅ የምትወልድ ሴት እንደሚሰማት ሥቃይ››
ፊታቸው እንደ እሳት ነበልባል ይሆናል
ቀይና ፍም መሆኑ በእሳት ተመስሎአል። ፊታቸው ቀይ የሚሆንበት ምክንያት ሊሆን የሚችለው፣ 1) ሰዎቹ በጣም በመፍራታቸው ወይም 2) ሰዎቹ በጣም በማፈራቸው፤ ወይም 3) በማልቀሳቸው ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፊታቸው ቀይና ፍም ይሆናል››
Isaiah 13:9
የያህዌ ቁጣ ከጨካኝ መዓትና ከብርቱ ቁጣ ጋር ተሞልቶ ይመጣል።
ቀኑ የሚመጣው ከመዓትና ከቁጣ ጋር መሆኑ በዚያ ቀን መዓትና ቁጣ ይኖራል ማለት ነው። ‹‹መዓት›› እና፣ ‹‹ቁጣ›› የተሰኙትን ቃሎች፣ ‹‹አስፈሪ›› እና፣ ‹‹ቁጡ›› ብሎ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያ የያህዌ ቀን እርሱ አስፈሪና ቁጡ ይሆናል››
ቁጣ ተሞልቶ
እዚህ ላይ ቁጣ የሚቆጣውን ሰው መያዣ የሚሞላ ነገር መሆኑ ተነግሯል። ቁጣ ተሞልቶ በጣም ተቆጥቶ ማለት ነው።
ምድሪቱን ባድማ ለማድረግ
‹‹ባድማ›› የሚለውን ቃል፣ ‹‹የፍርስራሽ ክምር›› በሚል ቃል መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምድሪቱን የፍርስራሽ ክምር ለማድረግ››
የሰማይ ከዋክብትና ሰራዊታቸው
‹‹ሰማይ ላይ ያሉ ከዋክብት››
ብርሃናቸውን አይሰጡም
ብርሃን መስጠት፣ ‹‹ማብራት›› የሚለውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አያበሩም››
ፀሐይ ትጨልማለች
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ፀሐይን ያጨልማል›› ወይም፣ ‹‹ፀሐይ ጨለማ ትሆናለች››
Isaiah 13:11
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
በያህዌ ቀን ምን እንደሚያደርግ ያህዌ እየተናገረ ነው።
ዓለም
ይህ ሕዝብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዓለም ሕዝብ››
ክፉዎች... ትዕቢተኞች... ጨካኞች
እነዚህ ሐረጐች የሚያመለክቱት እነዚህ ባሕርያት ያሏቸውን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ሰዎች... ትዕቢተኛ ሰዎች... ጨካኝ ሰዎች››
ጨካኝ
‹‹ምሕረት የለሽ››
የጨካኞችን እብሪት ዝቅ ይላል
ብዙውን ጊዜ ዝቅ ማለት የሚያመለክተው መዋረድን ነው። የሰዎችን እብሪት ዝቅ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ማድረግ እነርሱን ማዋረድን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨካኞችን ያዋርዳል››
ከነጠረ ወርቅ ይልቅ ሰዎች ጥቂት ይሆናሉ
ጥቂት ሰዎች ብቻ የሚኖሩበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙ ሰዎች እንዲገደሉ ስለማደርግ፣ በሕይወት ያሉት ከነጠረ ወርቅ ይልቅ ያነሱ ይሆናሉ››
ሰዎች ከነጠረ ወርቅ ይልቅ ጥቂት… ከንጹሕ የኦፊር ወርቅ ይልቅ ለማግኘት የሚያስቸግር ይሆናሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፡፡
ንጹህ የኦፊር ወርቅ
ኦፊር ንጹሕ ወርቅ የነበረበት ቦታ ነው፡፡
Isaiah 13:13
አጠቃላይ መረጃ
አሁንም ያህዌ እየተናገረ ነው፡፡
እንደሚታደን ሚዳቋ፣ እረኛም እንደሌለው በግ
ምንም መከላከያ የሌላቸው የእስራኤል ሕዝብ አዳኝ ወይም የዱር አውሬ እንደሚያሳድደው ሚዳቋ ወይም በግ እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ሲያድኑት በፍጥነት እንደሚሮጥ ሚዳቋ፣ ከአራዊት እንደሚሸሽ እረኛ እንደሌለው በግ››
ሚዳቋ
አጋዛን የሚመስል እንስሳ፡፡ ሰዎች ያድኗቸዋል፤ አንዳንዴም የዱር አራዊት ያጠፏቸዋል፤ ይበሏቸዋል፡፡
እረኛ እንደ ሌለው በግ
እረኛ የሌለው በግ ከሚያጠቁትና ከሚገድሉት የዱር አራዊት የሚከላከልበት የለውም፡፡
Isaiah 13:15
የተገኘ ሁሉ ይገደላል… የተያዘም ሁሉ በሰይፍ ይሞታል
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፡፡ ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላት ያገኘውን ሰው ሁሉ በሰይፍ ይገድላል››
ሕፃናቶቻቸው ይጨፈጨፋሉ
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላት ሕፃናቶቻቸውንም ይቆራርጣል›› ወይም፣ ‹‹ጠላት ሕፃናቶቻቸው እስኪሞቱ ድረስ ይደበድባል››
በዐይናቸው ፊት
እዚህ ላይ ለሚያዩት ነገር አጽንዖት ለመስጠት ሰዎች፣ ‹‹በዐይናቸው›› ተወክለዋል፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን ለመርዳት ምንም ማድረግ እንደማይችሉ ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፊት ለፊታቸው›› ወይም፣ ‹‹ዐቅም ያጡ ወላጆቻቸው እያዩ››
ቤታቸው ይዘረፋል
ይህም ማለት ዋጋ ያለው ማንኛውም ነገር ከቤታቸው ይወሰዳል ማለት ነው፡፡ ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላት የሕዝቡን ቤት ይዘርፋል›› ወይም፣ ‹‹ጠላት ማንኛውንም ጠቃሚ ነገር ከቤታቸው ይወስዳል››
ሚስቶቻቸው ይደፈራሉ
ይህም ማለት ሚስቶቻቸው ጥቃት ይደርስባቸዋል፤ ከእነርሱ ጋር እንዲተኙ ይገደዳሉ ማለት ነው፡፡ ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ የሰዎች ሚስቶች ይደፈራሉ›› ወይም፣ ‹‹ጠላቶቻቸው ሚስቶቻቸውን ይደፍራሉ››
Isaiah 13:17
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
አሁንም ያህዌ እየተናገረ ነው፡፡
ሜዶናውያንን አስነሣባቸዋለሁ
ሰዎች አንድ ነገር ማድረግ እንዲፈልጉ ማድረግ እነርሱን ማነሣሣት እንደሆነ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሜዶናውያን እነርሱን ማጥቃት እንዲፈልጉ አደርጋለሁ››
ቀስታቸው ይናደፋል
‹‹ቀስታቸው›› ቀስቶች የሚጠቀሙ ወታደሮች ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወታደሮቻቸው ለመግደል ቀስትና ፍላጻ ይጠቀማሉ››
Isaiah 13:19
አያያዥ ዐረፍተ ነገሮች
አሁንም ያህዌ እየተናገረ ነው
በጣም የተደነቁ መንግሥታት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ ‹‹አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች በጣም የሚያደንቁት መንግሥት››
ከዚያም ባቢሎንን… እግዚአብሔር ይገለብጣታል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ ‹‹አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዚያም ሶዶምና ገሞራን እንዲያጠፋ ከመንግሥታት በጣም የተደነቀችውን፣ የከለዳውያን ትምክህት የሆነችውን ባቢሎንን እግዚአብሔር ያጠፋል፡፡››
የከለዳውያን ውበት ትምክህት
‹‹ውበት›› እና፣ ‹‹ትምክህት›› የተሰኙትን ቃሎች በሌላ መተርጐም ይቻላል፡፡ ‹‹ውበት›› የባቢሎንን ማማር ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከለዳውያን የሚመኩባት ውብ ከተማ››
የሚቀመጥባት ወይም የሚኖርባት አይኖርም
ሁለቱ ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፡፡ ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም አይኖርባትም››
ከትውልድ እስከ ትውልድ
‹‹ከትውልድ እስከ ትውልድ›› የተሰኘው ሐረግ በሚመጣው ዘመን ትውልዶች ሁሉ ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለዘላለም›› ወይም፣ ‹‹ለሁልጊዜ››
ዐረብ
የሚያመለክተው ጠቅላላ ዐረቦችን እንጂ፣ ግለሰብን አይደለም፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐረቦች›› ወይም፣ ‹‹የዐረብ ሕዝብ››
Isaiah 13:21
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ያህዌ ባቢሎን ላይ የሚደርሰውን እየተናገረ ነው፡፡
በዚያ ይተኛሉ
‹‹በባቢሎን ይተኛሉ››
ቤቶቻቸው
‹‹የሕዝቡ ቤት››
ጉጉቶች
ጉጉቶች ሌሊት የሚያድኑ የዱር ወፎች ናቸው
ሰጐኖች
ሰጐኖች በፍጥነት መሮጥ እንጂ፣ መብረር የማይችሉ የዱር ወፎች ናቸው፡፡
ጅቦች
ጅቦች ውሾች የሚመስሉ የሞቱ እንስሳዎች የሚበሉ ትልልቅ የዱር አራዊት ናቸው፡፡ ጩኸታቸው የሚስቅ ሰው ይመስላል፡፡
ባማሩ ቤቶች ያሉ ቀበሮዎች
‹‹ይጮኻሉ›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በማሩ ቤቶች ቀበሮዎች ይጮኻሉ››

---

Chapter 14
Isaiah 14:1
ያህዌ ለያዕቆብ ይራራለታል
‹‹ያዕቆብ›› የሚያመለክተው የያዕቆብን ዘር ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የያዕቆብን ዘሮች ይምራቸዋል››
ከያዕቆብ ቤት ጋር ይተባበራሉ
የያዕቆብ ቤት የሚያመለክተው የያዕቆብን ዘር እስራኤላውያንን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከያዕቆብ ዘሮች ጋር ይተባበራሉ››
ሕዝቦች ወደ ገዛ ቦታቸው ያመጧቸዋል
‹‹ሕዝቦች የያዕቆብን ዘሮች ወደ እስራኤል ምድር መልሰው ያመጧቸዋል››
የእስራኤል ቤት
ይህ የሚያመለክተው እስራኤላውያንን፣ የእስራኤል ዘሮችን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ዘሮች››
የማረኳቸውን ይማርካሉ
‹‹የእስራኤል ወታደሮች እስራኤላውያንን ማርከው የነበሩትን ይማርካሉ››
Isaiah 14:3
ከሥቃይህና ከመከራህ
‹‹የአንተ›› የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ቢሆንም፣ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው፡፡ እንዲሁም፣ ‹‹ሥቃይ›› እና፣ ‹‹መከራ›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር

ማለት ቢሆኑም፣ በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም እንድትሠቃይ ካደረጉህ ነገሮች››
ጨቋኙ እንዴት አበቃለት
‹‹ጨቋኙ አበቃለት›› ይህ ቃለ አጋኖ ነው።
የትዕቢተኛም ቁጣ አበቃለት
‹‹የትዕቢተኛ ቁጣ›› የሚለው የሚያመለክተው ሌሎች ሕዝቦችን በጭካኔ ያሠቃይ የነበረውን የባቢሎንን ንጉሥ ትዕቢት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጭካኔው አበቃለት›› ወይም፣ ‹‹ከእንግዲህ ሕዝብን አይጨቁንም››
Isaiah 14:5
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ይህ እስራኤላውያን የባቢሎን ንጉሥ ላይ የሚያዜሙት የፌዝ ዜማ ክፍል ነው።
ያህዌ የክፉዎችን ዘንግ ሰብሮአል
የክፉዎች ዘንግ ክፉዎች ሌሎች ሰዎችን የሚመቱበትን ዘንግ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ዘንጋቸውን መስበር ሌሎች ላይ የሚያደርሱትን ጭካኔ ኀይል መስበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የክፉዎችን ኀይል ደምስሶአል።››
የገዦች በትረ መንግሥት
በትረ መንግሥት የሚያመለክተው የመግዛትን ሥልጣን ነው። በትረ መንግሥቱን መስበር የገዢውን ሥልጣን መደምሰስ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የክፉ ገዦችን ሥልጣን ደምስሶአል።››
ሕዝቦችን የመታውን
‹‹ሕዝቦችን ሲመታ የነበረውን›› ክፉዎች በበትራቸው ሰዎችን ይመታሉ።
በማያቋርጥ ምት
‹‹ማቆሚያ የሌለው›› ወይም፣ ‹‹ደግሞ ደጋግሞ››
ሕዝቦችን ያስገበረውን
‹‹ሌሎች አገሮችን ድል ያደረገውን››
ያለ መከልከል የመታውን
‹‹ማቆሚያ የሌለው ጥቃት››
Isaiah 14:7
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ይህ እስራኤላውያን የባቢሎን ንጉሥ ላይ የሚያዜሙት የፌዝ ዜማ ክፍል ነው።
ምድር ሁሉ
ይህ በምድር የሚኖረውን ሁሉ ይመለከታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር የሚኖር ማንኛውም››
ጥድና የሊባኖስ ዝግባ እንኳ በአንተ ላይ ደስ አላቸው
ኢሳይያስ ዛፎች ደስ እንደሚላቸው ሰዎች እንደሆኑ ይናገራል። ይህም እግዚአብሔር የባቢሎንን ንጉሥ ማስቆሙ ታላቅ ነገር ስለሆነ፣ ቢችል ኖሮ ሌላው ቀርቶ ተፈጥሮ እንኳ ደስ እንደሚለው አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጥድ ዛፍና የሊባኖስ ዝግባ እንኳ ሳይቀር፣ በአንተ ላይ በደረሰው ደስ ይላቸዋል››
በአንተ ላይ ደስ ይላቸዋል
ደስ የሚላቸው ለምን እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ዐቅም ስላሳጣህ ደስ ይላቸዋል››
ዝቅ ዝቅ ብለሃልና
ዝቅ ዝቅ ማለት ዐቅመ ቢስና ዋጋ የሌለው መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐቅመ ቢስ ሆነሃልና››
ከበታችህ ሲኦል ልትቀበልህ ጓጉታለች
ሲኦል እንግዶችን የሚቀበል ሰው ተደርጐ ተነግሯል። ይህ የሚመለክተው ንጉሡ እንደሚሞት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሲኦል አንተን ለማስተናገድ ዝግጁ ናት››
እንዲቀበሉህ ሙታንን፣ የምድር ነገሥታትን ሁሉ ያስነሣል
‹‹ሙታንን፣ የምድር ነገሥታትን ሁሉ ያነቃል።›› ሲኦል ውስጡ ላሉት የሚነቃ ሰው ተደርጐ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሲኦል ውስጥ ያሉ የሞቱ የምድር ነገሥታት ሁሉ እንኳን መጣህ ሊሉህ ይነቃሉ››
Isaiah 14:10
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ይህ እስራኤላውን የባቢሎን ንጉሥ ላይ የሚያዜሙት የፌዝ ዜማ ክፍል ነው። እዚህ ላይ የሚያዜሙት ሲኦል ውስጥ ያሉ የሞቱ ነገሥታት ምን እንደሚሉት ነው።
ሁሉም ይናገሩሃል፤ እንዲህም ይሉሃል
‹‹እነርሱ›› የሚለው ሲኦል ውስጥ ያሉትን የሞቱ ነገሥታት ሲሆን፣ ‹‹አንተ›› የሚለው የባቢሎንን ንጉሥ ነው።
ክብርህ ወደ ሲኦል ወረደ
ክብሩ ወደ ታች ወደ ሲኦል የወረደ ይመስል፣ ከእንግዲህ ምንም ክብር እንደሌለው የሞቱ የምድር ነገሥታት ስለ ባቢሎን ንጉሥ ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ወዲህ ወደ ሲኦል ከላከህ ወዲህ ክብርህ አብቅቷል››
ከባለ አውታር የሙዚቃ መሣሪያዎችህ ጋር
ንጉሡን ለማክበር ሰዎች ባለ አውታር የሙዚቃ መሣሪያዎች ይሠራሉ። ሙዚቃው ወደ ሲኦል ስለ ወረደ ከእንግዲህ ሰዎች በሙዚቃ የባቢሎንን ንጉሥ እንደማያከብሩ የሞቱት ነገሥታት ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተን ለማክበር ሙዚቃ ከሚጫወቱ ሰዎች ድምፅ ጋር››
Isaiah 14:12
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ይህ እስራኤላውያን የባቢሎን ንጉሥ ላይ የሚያዜሙት የፌዝ ዜማ ክፍል ነው።
አንተ የንጋት ልጅ የአጥቢያ ኮከብ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ
የንጋት ኮከብ ከመንጋቱ በፊት የሚወጣ ደማቅ ኮከብ ነው። በአንድ ወቅት ታላቅ እንደ ነበር፣ አሁን ግን ምንም ማለት እንዳልሆነ ለማመልከት የእስራኤል ሕዝብ ስለ ባቢሎን ንጉሥ ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ንጋት ኮከብ ደማቅ ነበርህ፤ አሁን ግን ከሰማይ ወድቀሃል››
እንዴት ተቆርጠህ ወደ ምድር ተጣልህ
የእስራኤል ሕዝብ የባቢሎን ንጉሥ ተቆርጦ የተጣለ ዛፍ እንደሆነ ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተቆርጦ ወደ መሬት እንደ ተጣለ ዛፍ ተሸንፈሃል››
በመሰብሰቢያ ተራራ እቀመጣለሁ
ይህ የሚያመለክተው በቅርብ ምሥራቅ የነበሩ አብዛኞቹ ሰዎች የከነዓናውያን አማልክት ከሶርያ በስተ ሰሜን ባለው ቦታ ተራራ ጫፍ ላይ እንደሚሰበሰቡ እንደሚያውቀ ነው። ተራራ ላይ መቀመጥ ከአማልክት ጋር መግዛትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አማልክት በሚሰበሰቡበት ተራራ ላይ እገዛለሁ››
በሰሜን በኩል ጫፍ ላይ
‹‹በሰሜን በኩል ርቆ›› በሰሜን ያለው ተራራ ዛፎን ተብሎ ነበር የሚጠራው። አንዳንድ ዘመናዊ ቅጂዎች፣ ‹‹በዛፎን በኩል ሩቅ ቦታ›› ይላሉ።
Isaiah 14:15
አያያዥ ዐረፍተ ነገሮች
ይህ እስራኤላውን የባቢሎን ንጉሥ ላይ የሚያዜሙት የፌዝ ዜማ ክፍል ነው።
አሁን ወደ ሲኦል ወርደሃል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁን ግን እግዚአብሔር ወደ ሲኦል ጥሎሃል››
ሰውየው ይኼ ነው?
ሰዎች እንዲህ በማለት የሚጠይቁት በባቢሎን ንጉሥ ላይ ለማፌዝ ወይም በእርሱ ላይ በደረሰው የተሰማቸውን ድንጋጤ ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መቼም ሰውየው ይኼ ሊሆን አይችልም››
ምድርን ያናወጠ
ይህም ማለት 1) የንጉሡ ሰራዊት ሕዝብን ድል ለማድረግ ሲገሠግሥ ምድር ተናወጠች ማለት ሊሆን ይችላል፤ ወይም 2) የምድር ሕዝብ እርሱን በመፍራት ተንቀጠቀጡ ማለት ሊሆን ይችላል።
መንግሥታትን ያንቀጠቀጠ
ይህም ማለት 1) መንግሥታትን ድል ማድረግን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል ወይም 2) ‹‹መንግሥታትን ማሸበርን›› የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።
ዓለምን ምድረ በዳ ያደረገ
‹‹ሰዎች የሚኖሩባቸውን ቦታዎች ምድረ በዳ ያደረገ››
Isaiah 14:18
አያያዥ ዐረፍተ ነገሮች
ይህ እስራኤላውያን የባቢሎን ንጉሥ ላይ ሲያዜሙ ከነበረው የፌዝ ዜማ የመጨረሻ ክፍል ነው።
ሁሉም በክብር ተጋድመዋል
ይህ ማለት ሥጋቸው በክብር ተቀብሯል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክብር ባለው ሁኔታ የተቀበሩ ነገሥታት ሁሉ››
ነገር ግን ከመቃብር ወጥተህ ተጥለሃል
ከመቃብር ወጥቶ መጣል መጀመሪያውኑ አለመቀበርን ነው የሚያመለክተው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ግን አልተቀበርህም፤ ሥጋህ መሬት ላይ ቀርቷል››
እንደሚጣል ቅርንጫፍ
የተጣለ ቅርንጫፍ ዋጋ የሌለው ነገርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወዲያ እንደሚጣል የማይረባ ቅርንጫፍ››

ሙታን እንደ መጐናጸፊያ ይሸፍኑሃል

ይህ ማለት ብዙ ሙታን እርሱ ላይ ይሆናሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሙታን አካል ጨርሶ ይሸፍንሃል›› ወይም፣ ‹‹የሞቱ ወታደሮች ሬሳ ይከመርብሃል››

በሰይፍ የተወጉት

ይህ የሚገልጸው በዚህ ዐረፍተ ነገር መጀመሪያ ላይ ተነሥተው የነበሩትን፣ ‹‹ሙታን›› ነው። በሰይፍ መወጋት በጦርነት መገደል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጦርነት የተገደሉ››

ወደ ጥልቁ ድንጋዮች በወረዱት

ጥልቁ የሚለው የሚያመለክተው ገሃነምን ወይም ብዙ የሞቱ ሰዎች የሚጣሉበት ምድር ላይ ያለ ሰፊ ጉድጓድን ነው።

ከእነርሱ ጋር በመቃብር አትሆንም

‹‹እነርሱ›› የተባሉት ሞተው በሚገባ የተቀበሩት ሌሎች ነገሥታት ናቸው። ከእነርሱ ጋር በመቃብር መሆን እነርሱ እንደ ተቀበሩ መቀበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌሎች ነገሥታት እንደ ተቀበሩ አትቀበርም››

የክፉ አድራጊዎች ዘር ጨርሶ አይታወስም

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ስለ ክፉ አድራጊዎች ዘር የሚናገር አይኖርም››

Isaiah 14:21

ልጆቹ የሚታረዱበትን ቦታ አዘጋጅ

‹‹የሚታረዱበት›› የሚለውን፣ ‹‹የሚገደሉበት›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የባቢሎንን ንጉሥ ልጆች ለመግደል ተዘጋጁ››

ለአባቶቻቸው ርኩሰት

‹‹ርኩሰት›› የሚለውን፣ ‹‹ታላቅ ኀጢአት›› ማለት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አባቶቻቸው ለመፈጸሙት ታላቅ ኀጢአት››

ከእንግዲህ አይነሡም

‹‹መነሣት›› ኀያል መሆንን ወይም ማጥቃትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ኀያል እንዳይሆኑ›› ወይም፣ ‹‹ከእንግዲህ እንዳያጠቁ››

ምድርን እንዲወርሱ

ይህ የሚያመለክተው የምድር ሰዎችን መቆጣጠርን ሲሆን፣ እዚህ ላይ ግን እነርሱን ድል ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምድር ሰዎችን መቆጣጠር›› ወይም፣ ‹‹የምድርን ሕዝብ ድል ማድረግ››

ዓለምን በከተሞች በሙላት

ይህ ዓለም ብዙ ከተሞች እንዲኖሩዋት ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በመላው ዓለም ከተሞች መሥራት››

በእነርሱ ላይ እነሣለሁ

ይህ ማለት እግዚአብሔር እነርሱ ላይ አንዳች ነገር ያደርጋል ማለት ነው። ‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው የባቢሎንን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አጠቃቸዋለሁ›› ወይም፣ ‹‹የሚያጠቋቸው ሰዎች እልካለሁ››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል

ያህዌ ስሙን በመጥራት የተናገረው እርግጥ መሆኑን ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ የሚለው እንዲህ ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ያልሁት እንዲህ ነው››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ

ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደተረጐምኸው ተመልከት።

የባቢሎንን ስም፣ ትውልድና ትሩፋኖችዋን እቆርጣለሁ

‹‹እቆርጣለሁ›› አጠፋለሁ ማለት ነው። ‹‹ባቢሎን›› የባቢሎንን ሕዝብ ይወክላል። እንዲሁም፣ ‹‹ስም›› የባቢሎንን ዝና ወይም፣ እንደ መንግሥት ባቢሎን ራሷን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሕዝቡ ልጆችና የልጅ ልጆች ጋር ባቢሎንን አጠፋለሁ››

አደርጋታለሁ

‹‹እርሷ›› የባቢሎንን ከተማ ያመለክታል። ብዙውን ጊዜ ከተሞች በሴቶች ስም ይጠራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲህም… አደርጋታለሁ››

የጃርት መኖሪያ

ይህ የሚያመለክተው የሚኖርባቸው ስለማይኖር አራዊት በከተማው ውስጥ እንደሚኖሩ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጃርቶች የሚኖሩበት ቦታ›› ወይም፣ ‹‹የዱር አራዊት የሚኖሩበት ቦታ››

ረግረግ ቦታ

የታቆረና የተከማቸ ውሃ እንዳኖርበት ማድረግ ከተማው የእነዚህ ነገሮች መኖሪያ እንዲሆን ማድረግ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የታቆረ ውሃ መኖሪያ ቦታ››

በጥፋት መጥረጊያ እጠርጋታለሁ

ይህ የሚያመለክተው የባቢሎንን ጨርሶ መውደምና ሰዎች ጠርገው የሚጥሉት ቆሻሻ ይመስል፣ ከእንግዲህ እንደማትኖር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በመጥረጊያ እንደሚጠረግ ነገር ጨርሶ አጠፋታለሁ››

Isaiah 14:24

የሰራዊት ጌታ ያህዌ

ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እንደ ዐቀድሁት እንዲሁ ይሆናል፤ እንደ አሰብሁት ይከናወናል

እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ያቀድሁት ነገር በእርግጥ ይሆናል››

አሦራውያንን በእጄ ላይ እሰብራለሁ

መሰበር የሚወክለው ማሸነፍን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሦራውያንን በምድሬ ላይ አሸንፋቸዋለሁ›› ወይም፣ ‹‹በምድሬ ያሉትን አሦራውያን አሸንፋቸዋለሁ››

አሦራውያን

ይህ የሚወክለው የአሦራውያንን ንጉሥና ሰራዊቱን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦራውያን ንጉሥና ሰራዊቱ›› ወይም፣ ‹‹የአሦራውያን ሰራዊት››

በእግሬ እረግጠዋለሁ

ይህ የሚያመለክተው ጨርሶ ማሸነፍን ነው።

በዚያ ጊዜ ቀንበሩ ከላያቸው፣ ሸክሙም ከትከሻቸው ይነሣል

ይህ በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያ ጊዜ ቀንበሩን ከላያቸው ሸክሙንም ከትከሻው አነሣለሁ።

በዚያ ጊዜ ቀንበሩ ከላያቸው፣ ሸክሙም ከትከሻቸው ይነሣል

እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ቀንበርንና ሸክምን ማንሣት ሰዎችን ከባርነት ነጻ ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያ ጊዜ ከባዱን ሸክም ከትከሻቸው በማስወገድ እስራኤላውያንን ከአሦራውያን ባርነት ነጻ አደርጋለሁ››

ቀንበሩ… ሸክሙ

‹‹የእርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው አሦርን ነው።

ከላያቸው… ከትከሻቸው ላይ

x

Isaiah 14:26

አጠቃላይ መረጃ

እየተናገረ ያለው ኢሳይያስ ይሆናል ወይም ያህዌ ይሆናል

ለምድር ሁሉ የታቀደው ይህ ነው

‹‹የታቀደው›› የሚለውን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለምድር ሁሉ እግዚአብሔር ያለው ዕቅድ ይህ ነው››

በአሕዛብ ሁሉ ላይ የተዘረጋው እጅ ይህ ነው

እግዚአብሔር አሕዛብን ለመቅጣት መዘጋጀቱ እነርሱን ለመምታት እጁን ከመዘርጋት ጋር ተመሳስሎአል። ‹‹እጅ›› የሚለው ቃል ኀይሉን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ አሕዛብን ሁሉ የሚቀጣ የያህዌ ኀይል ነው›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ አሕዛብን የሚቀጣው እንዲህ ነው››

ማን ያስቆመዋል?

ጥያቄው ያህዌን ማንም እንደማያስቆመው አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚያስቆመው የለም››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ

ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

እጁም ተዘርግቷል

ይህ ያህዌ አሕዛብን ለመቅጣት መዘጋጀቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱን›› ለመቅጣት ተዘጋጅቶአል››

ማንስ ይመልሰዋል?

ጥያቄው የቀረበው የእግዚአብሔርን እጅ የሚመልሰው እንደሌለ ለመናገር ነው። የእርሱን እጅ መመለስ አሕዛብን እንዳይቀጣ እርሱን ማስቆም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም›› አይመልሰውም›› ወይም፣ ‹‹እነርሱን እንዳይቀጣ ማንም አይመልሰውም››

Isaiah 14:28

የመታህ በትር ተሰብሮአል

ፍልስጥኤምን የመታ በትር እነርሱን እንዲያጠቃ ሰራዊቱን የላከውን ንጉሥ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይወክላል። መሰበር መሞት ወይም መሸነፍን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰራዊቱን ወደ አንተ የላከው ንጉሥ ሞቶአል›› ወይም፣ ‹‹አንተን ያጠቃ ሰራዊት ተሸንፎአል››

ከእባቡ ሥር እፉኝት ይወጣል… ዘሩም በራሪ እሳት ይሆናል

እነዚህ ሁሉ ሐረጎች የሚያመለክቱት የእባቡ ዘር ከራሱ ከእባቡ የባሰ ጐጂ መሆኑን ነው። የንጉሡ ወራሽ ከመጀመሪያው ንጉሥ የበለጠ ኀይለኛና ጨካኝ እንደሚሆን ያመለክታሉ።

እፉኝት

የአደገኛ እባብ ዐይነት

እሳታማ በራሪ እባብ

‹‹እሳታማ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእባቡን መርዘኛነት ሲሆን፣ ‹‹በራሪ›› የሚለው ፈጣን እንቅስቃሴውን ሊያመለክት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፈጣን መርዘኛ እባብ››

የድኻ በኩር

ይህ የሚያመለክተው በጣም ድኻ የሆኑ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከድኻም ድኻ›› ወይም፣ ‹‹የሕዝቤ የባሰባቸው ድኾች››

ሥርህን በራብ እገድላለሁ፤ ትሩፍህንም አፈጃለሁ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ሥርህ›› የፍልስጥኤምን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝብህን በራብ እገድላለሁ፤ ትሩፍህንም እጨርሳለሁ››

Isaiah 14:31

ዋይ በል፣ በር፣ ጩኽ፣ ከተማ

‹‹በር›› እና፣ ‹‹ከተማ›› በከተሞች በር የሚቀመጡ ሰዎችን ይወክላል። ‹‹በከተማው በሮች ያላችሁ ሰዎች ዋይ በሉ፤ በከተሞቹም ያላችሁ ጩኹ››

ትቀልጣላችሁ

መቅለጥ ከፍርሃት የተነሣ ደካማ መሆንን ነው የሚያመለክተው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከፍርሃት የተነሣ በጣም ትደክማላችሁ››

የጢስ ደመና ከሰሜን መጥቶብሃል

ይህ የሚያመለክተው ግዙፍ ሰራዊት ከሰሜን እየመጣ መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከጢስ ደመና ጋር ከሰሜን ብዙ ሰራዊት መጥቶብሃል››

የጢስ ደመና

ይህም ማለት፣ 1) በደረቁ ዐፈር ላይ ሲጓዝ ሰራዊቱ የሚያስነሣውን የአቧራ ደመና ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአቧራ ደመና›› ወይም 2) ሰራዊቱ ከሚያጠፋውና ከሚያቃጥለው ነገር የተነሣ ብዙ ጢስ ሊኖር ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙ ጢስ››

ከሰልፉ ተነጥሎ የሚቀር የለም

‹‹ከሰልፉ ከሌሎች ኃላ በዝግታ የሚራመድ አይኖርም››

ለዚያ ሕዝብ መልእክተኞች ምን መልስ ይሰጣሉ?

ጸሐፊው ይህን ጥያቄ ያነሣው እስራኤላውያን ለመልእክተኞቹ እንዴት መናገር እንዳለባቸው የሚያቀርበውን መመሪያ ለማስተዋወቅ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለፍልስጥኤም መልእክተኞች እንዲህ በሏቸው››

ያህዌ ጽዮንን መሥርቶአታል

‹‹ያህዌ ጽዮንን ሠርቷል››

በእርሷ

‹‹በኢየሩሳሌም›› ወይም፣ ‹‹በዚያ››

ከሕዝቡ በጣም የተጐዱት

‹‹ከሕዝቡ በጣም የተጐዱ ሰዎች››

---

## Chapter 15

### Isaiah 15:1

አጠቃላይ መረጃ

ብዙውን ጊዜ ትንቢት ውስጥ ወደ ፊት የሚፈጸሙ ጉዳዮች አሁን ወይም ባለፈው ጊዜ እንደ ተፈጸሙ ተደርገው ይነገራሉ። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው በእርግጥ የሚፈጸም መሆኑን ነው።

የንግር ቃል

‹‹ያህዌ እንዲህ ይላል›› ወይም፣ ‹‹ይህ የያህዌ መልእክት ነው››

ዔር… ቂር… ዲቦን… ናባው… ሜድባ

እነዚህ ሞዓብ ውስጥ የነበሩ ከተሞችና መንደሮች ናቸው።

የሞዓብ ዔር ፈራረሰች ተደመሰሰች

‹‹ፈራረሰች›› እና፣ ‹‹ተደመሰሰች›› የተሰኙት ቃሎች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ ከተማዋ ሙሉ በሙሉ እንደምትደመሰስ አጽንዖት ይሰጣሉ። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጠላት ሰራዊት የሞዓብን ዔር ሙሉ በሙሉ ይደመስሳታል››

ሊያለቅስም ወደ ከፍታዎች ሄደ

እነዚህ ላይ፣ ‹‹ወደ ከፍታዎች›› ሲል ቤተ መቅደስ ወይም መሠዊያ የተሠራበት ኮረብታ ወይም ተራራ የመሳሰሉ ከፍታ ቦታዎችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለማልቀስ ኮረብታው ጫፍ ላይ ወዳለው ቤተ መቅደስ ሄደ››

ሞዓብ ስለ ናባው እና ስለ ሜድባ አለቀሰ

እነዚህ ቦታዎች እዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ናባው እና ሜድባ ከተማ ላይ ከደረሰው የተነሣ የሞዓብ ሕዝብ ያለቅሳል››

ራሳቸውን ሁሉ ተላጭተዋል፤ ጢማቸውን ሁሉ ተላጭተዋል

እንዲህ ያደረጉት በጣም ማዘናቸውን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራሳቸውንና ጢማቸውን ሁሉ ተላጭተው በጣም ያዝናሉ››

### Isaiah 15:3

አጠቃላይ መረጃ

እዚህም ላይ ስለ ሞዓብ ሕዝብ የተነገረው ትንቢት ቀጥሏል። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)

ማቅ ይለብሳሉ

እንዲህ የሚያደርጉት በጣም ማዘናቸውን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማቅ ለብሰው ያለቅሳሉ››

ሐሴቦን… ኤልያሌ… ያሀድ

እነዚህ የከተሞችና የመንደሮች ስም ናቸው

ሐሴቦንና ኤልያሌ ይጣራሉ

የከተሞቹ ስሞች በውስጣቸው ያለውን ሕዝብ ይወክላሉ። ‹‹የሐሴቦንና የኤልያሊ ሕዝብ ይጣራሉ››

ይርዳሉ፤ ይንቀጠቀጣሉ

መንቀጥቀጥ የፍርሃት ምልክት ሲሆን፣ ፍርሃትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከባድ ፍርሃት ይሞላባቸዋል›› ወይም፣ ‹‹በፍርሃት ይንቀጠቀጣሉ››

### Isaiah 15:5

አጠቃላይ መረጃ

ይህ ስለ ሞዓብ የተነገረው ትንቢት እየቀጠለ መሆኑን ያሳያል። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተደረጉ አድርጐ ይናገራል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)

ልቤ ለሞዓብ ያለቅሳል

እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› የሚወክለው እግዚአብሔርን ሲሆን፣ ስሜቱን ያመለክታል። ልቡ ያለቀሰ ይመስል እግዚአብሔር የተሰማውን ታላቅ ሐዘን እየተናገረ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሞዓብ ላይ በሆነው እጅግ አዝኛለሁ››

ስደተኞቿም ሸሹ

‹‹ስደተኞቹ ከሞዓብ ሸሹ›› ስደተኛ ጠላት እንዳይዘው የሚሸሽ ሰው ነው።

ዞዓር… ዔግላት ሺሊሺያ… ሉሒት… ሖሮናይም… ኒምሪም

እነዚህ የከተሞችና የመንደሮች ስም ናቸው

ስለ ውድመታቸው

‹‹ውድመት›› የሚለውን ቃል፣ ‹‹መደምሰስ›› በሚለው ቃል ለመተካት ቃላቱን መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከተማቸው ስለ ተደመሰሰች››

ያከማቹት

‹‹ማንኛውም ነገራቸው››

የዲሞን ወንዞች

ይህ የሚያመለክተው ደቡባዊ የሞዓብ ድንበር ላይ ያለውን ወንዝ ሊሆን ይችላል።

### Isaiah 15:8

አጠቃላይ መረጃ

ስለ ሞዓብ ሕዝብ የተነገረው ትንቢት ቀጥሏል። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተነገሩ አድርጐ ይናገራል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)

ጩኸታቸው ወደ ሞዓብ ዳርቻ ወጣ

ሰዎቹ ሲጮኹ ሌሎች ያንን መስማታቸው የጩኸታቸው መውጣት እንደሆነ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሞዓብ ምድር ያሉ ሰዎች ሁሉ ጮኹ››

ዋይታቸው እስከ ዔግሌምና ብኤር ኤሊም



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

‹‹ወጣ›› ውስጠ ታዋቂ ነው። ሰዎች ዋይ ሲሉ ሌሎች ያንን መስማታቸው ዋይታቸው ወደ እነዚህ ሁለት ቦታዎች ወጣ ማለት እንደሆነ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዋይታቸው እስከ ዔግላምና ብኤርኢላም ወጣ›› ወይም፣ ‹‹እስከ ዔግራምና ብኤርኤላም እንኳ ወጣ››

ዔግላም... ብኤርኤላም.. ዲሞን

እነዚህ የከተማና የመንደር ስሞች ናቸው። ዲሞን የሞዓብ አገር ዋና ከተማ ነበረች።

አንዳንድ ቅጂዎች ከዲሞን ይልቅ፣ ‹‹ዶቦን›› ይላሉ።

በዲሞን ላይ ግን ከዚያ የበለጠ ነገር አደርጋለሁ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› ያህዌን፣ ‹‹ዲሞን›› ደግሞ እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው የሚያመለክተው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዲሞን ሕዝብ ላይ የባሰ መከራ አመጣለሁ››

---

Chapter 16

Isaiah 16:1

አጠቃላይ መረጃ

ስለ ሞዓብ ሕዝብ የተነገረው ትንቢት እየቀጠለ ነው። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተደረጉ አድርጐ ይናገራል። ቁጥር አንድ የሞዓብ ገዦች እርስ በርስ የሚነጋገሩትን በተመለከተ እግዚአብሔር የተናገረው ሊሆን ይችላል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)

ለምድሪቱ ገዥ የበግ ጠቦት ላኩ

ከጠላት ሰራዊት እንዲከላከልላቸው ሞዓባውያን ለይሁዳ ንጉሥ የበግ ጠቦት ይልካሉ።

ሴላ

ይህ የከተማ ስም ነው።

የጽዮን ሴት ልጅ

የከተማው፣ ‹‹ሴት ልጅ›› ማለት የከተማው ሕዝብ ማለት ነው። ኢሳይያስ 1፥8 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። ‹‹የጽዮን ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹በጽዮን የሚኖር ሕዝብ››

እንደ ተቅበዝባዥ ወፎች፣ እንደ ተበተኑ ጐጆዎች የሞዓብ ሴቶችም በአርኖን ወንዝ መሻገሪያ እንዲሁ ይሆናሉ

ሴቶቹን ጨምሮ የሞዓብ ሕዝብ ሁሉ ከቤታቸው ይሸሻሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሞዓብ ሴቶች ጐጆ እንደሌላቸው በጐች ከአንዱ ወንዝ ወደ ሌላው ወንዝ ይቅበዘበዛሉ››

እንደ ተቅበዝባዥ ወፎች፣ እንደ ተበተኑ ጐጆዎች

እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ አንድ ነገር ማለት ናቸው።

Isaiah 16:3

አጠቃላይ መረጃ

ስለ ሞዓብ የተነገረው ትንቢት ቀጥሏል። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተደረጉ አድርጐ ይናገራል። ከቁጥር 3-4 ያለው የሞዓብ ገዦች ለይሁዳ ንጉሥ የላኩት መልእክት ሊሆን ይችላል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)።

በቀትር ጥላችሁን እንደ ሌሊት አጥሉብን

እኩለ ቀን ላይ ያለው ሙቀት ሞዓባውያን በጠላቶቻቸው የሚደርስባቸውን መከራ ያመለክታል፤ ጥላ ከጠላቶቻቸው መከለያን ያመለክታል። ጥላውን ከሌሊት ጋር ማመሳሰሉ ጠንካራ መከለያ እንደሚያስፈልጋቸው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታላቅ ጥላ ሕዝቡን ከፀሐይ ሙቀት እንደሚከላከል እናንተም ከጠላቶቻችን ከለሉን››

የሞዓብ ስደተኞች በመካከላችሁ ይኑሩ

‹‹የሞዓብ ስደተኞች ከእናንተ ጋር ይኑሩ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እናንተ›› የሚያመለክተው የይሁዳን ሕዝብ ነው።

ከአጥፊው መደበቂያ ቦታ ሁኑላቸው

መደበቂያ ቦታ ማዘጋጀት መደበቂያ ቦታ መሆን ተደርጐ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሊያጠፏቸው ከሚፈልጉ የሚደበቁበት ቦታ ስጧቸው›› ወይም፣ ‹‹ሊያጠፏቸው ከሚፈልጉ ደብቋቸው››

Isaiah 16:5

በኪዳን ታማኝነት ዙፋን ይመሠረታል

‹‹ዙፋን›› እንደ ንጉሥ የመግዛትን ሥልጣን ያመለክታል። ‹‹ታማኝነት›› የሚለውን ‹‹ታማኝ›› ማለት ይቻላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ለኪዳኑ ታማኝ ይሆናል፤ እርሱም ንጉሥ ይሾማል››

ከዳዊት ድንኳን የሆነውም በዚያ ላይ በታማኝነት ይቀመጣል

‹‹የዳዊት ድንኳን›› ዘሮቹን ጨምሮ የዳዊትን ቤተ ሰብ ይወክላል። ዙፋን ላይ መቀመጥ መግዛትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዳዊት ዘር በታማኝነት ይገዛል››

ፍትሕን ይፈልጋል

ፍትሕ መፈለግ ትክክል የሆነውን ማድረግን ያመለክታል።

Isaiah 16:6

አጠቃላይ መረጃ

ይህ ስለ ሞዓብ የተነገረው ትንቢት ቀጣይ ነው። ወደ ፊት የሚደረጉ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተደረጉ ይናገራል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)

የሞዓብን ትዕቢት፣ እብሪቱን፣ የእርሱን ፉከራና ቁጣውን ሰምተናል።

‹‹ሞዓብ›› እና፣ ‹‹የእርሱ›› የሚሉት ቃሎች፣ የሞዓብን ሕዝብ ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ የሞዓብ ሕዝብ ትዕቢተኞች፣ እብሪተኞች፣ ፎካሪችና ቁጣዎች መሆናቸውን ሰምተናል››

ሰምተናል

ይህም ማለት፣ 1) ኢሳይያስ እየተናገረ ነው፤ ‹‹እኛ›› እርሱንና የይሁዳን ሕዝብ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ወይም፣ 2) እየተናገረ ያለው እግዚአብሔር ነው፤ ‹‹እኛ›› የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል።

ትዕቢቶቹ ግን ከንቱ ቃላት ናቸው

‹‹አንዳች ነገርን አስመልክቶ የሚናገሩት ከንቱ ነው›› ወይም፣ ‹‹የሚታበዩበት ነገር እውነት አይደለም››

ስለዚህ ሞዓብ ለሞዓብ ዋይ ይላል - ሁሉም ዋይ ይላሉ

‹‹ሞዓብ›› የሚወክለው የሞዓብን ሕዝብ ነው። ‹‹የሞዓብ ሕዝብ ሁሉ ከተሞቻቸው ላይ ከሆነው የተነሣ ዋይ ይላሉ››

ስለ ቂርሐራሴት የዘቢብ ቂጣ

‹‹በቂርሐራሴት የዘቢብ ቂጣ ስለሌለ››

የዘቢብ ቂጣ

እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው የዕብራይስጥ ቃል፣ ‹‹የዘቢብ ቂጣ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች›› ማለት ሊሆን ይችላል።

ቂርሐራሴት

ቂርሐራሴት የከተማ ስም ነው።

Isaiah 16:8

አጠቃላይ መረጃ

ይህ ስለ ሞዓብ ሕዝብ የተነገረው ትንቢት ቀጣይ ነው። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተደረጉ አድርጐ ይናገራል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)

ሐሴቦን

የዚህን ከተማ ስም ኢሳይያስ 15፥4 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው

ሴባማ... ኢያዜር

እነዚህ የከተሞች ስም ናቸው

የአሕዛብ ገዦች የተመረጡ የወይን ተክሎችን ረግጠዋል

የሞዓብ ምድር በወይን ዕርሻው የታወቀ ነበር። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ስለ ሞዓብ እንደ አንድ ትልቅ የወይን እርሻ ይናገራል። ይህም ሰራዊትን የሚያመለክቱት ገዦች በሞዓብ ያለውን ማንኛውንም ነገር እንደሚያወድሙ አጽንዖት ይሰጣል

Isaiah 16:9

አጠቃላይ መረጃ

ይህ የሞዓብ ምድር እንደ አንድ ትልቅ የወይን እርሻ እንደሆነ የተነገረው ቀጣይ ነው። (ኢሳይያስ 16፥8 ይመ.)። ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል።

በእርግጥ አለቅሳለሁ

16፥9-10 ላይ፣ ‹‹እኔ›› የሚለው ያህዌን ያመለክታል።

እንባዬን አጠጣሃለሁ

ብዙ እንደሚያለቅስና የሰራዊቱም እንባ እነርሱ ላይ እንደሚወርድ ያህል እግዚአብሔር ለእነዚህ ቦታዎች ያለውን ጥልቅ ሐዘን ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለአንተ ብዙ አለቅሳለሁ››

ኢያዜር... ሴባማ

የእነዚህን ከተሞች ስም ኢሳይያስ 16፥8 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው።

ሐሴቦን... ኤልያሊ

የእነዚህን ከተሞች ስም ኢሳይያስ 15፥4 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው።
ፍሬ ባፈራሸበት ወቅት የነበረው ሆታ፣ መከርሽም ሲደርስ የነበረውን የደስታ ጩኸት አስወግጃለሁ
‹‹የደስታ ጩኸት›› በፍሬ ዛፎቻቸው መከር ደስ የተሰኙ ሰዎችን ደስታ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ከማደርገው የተነሣ ፍሬ ባፈራሸበት ወቅት የሚኖረው ደስታ አይኖርሽም››
የረጋጮችን ሆታ አጥፍቻለሁና
እዚህ ላይ ‹‹ሆታ›› ወይን ጠጅ እንዲገኝ የወይን ፍሬዎችን የሚረግጡ ሰዎችን ደስታ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ የወይን ፍሬ የሚረግጡ ሰዎች የደስታ ሆታ አይኖርም››
Isaiah 16:11
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ስለ ሞዓብ ሕዝብ የተነገረው ትንቢት ቀጣይ ነው። ወደ ፊት የሚሆን ነገሮችን እግዚአብሔር አሁን እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል። (ኢሳይያስ 15፥1-2 ይመ.)።
ስለዚህ ልቤ ለሞዓብ እንደ በገና የሐዘን እንጉርጉሮ ታሰማለች
‹‹ልቤ›› የሚለው ያህዌንና ያዘነ ስሜቱን ይወክላል። የእርሱን እንጉርጉሮ ከአሳዛኝ የበገና ዜማ ጋር ያመሳስለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ በበገና እንደሚሰማው የሐዘን ዜማ እንጐራጉራለሁ››
ሞዓብ... እርሱ ራሱ... የእርሱ
እነዚህ ቃላት ሁሉ የሞዓብን ሕዝብ ያመለክታሉ።
ውስጤ ስለ ቂርሐራሴት
‹‹ውስጤ›› የሚለው ቃል ያህዌን ያመለክታል። ‹‹እንጉርጉሮ›› የሚለው ካለፈው ሐረግ ውስጠ ታዋቂ ነው። ኢሳይያስ 16፥7 ላይ ቂርሐራሴትን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ውስጤ ስለ ቂርሐራሴት ታንጐራጉራለች›› ወይም፣ ‹‹ለቂርሐራሴት ሰዎች በጣም አዝኛለሁ››
ጸሎቱ ምንም አያደርግም
‹‹ጸሎቱ መልስ አያገኝም››
Isaiah 16:13
ቃሉ ይኸው ነው
‹‹መልእክቱ ይኸው ነው›› ይህ የሚያመለክተው 15፥1-16፥12 ላይ የተናነገረውን ሁሉ ነው።
ስለ ሞዓብ
‹‹ሞዓብ›› የሚያመለክተው የሞዓብን ሕዝብ ነው።
የሞዓብ ክብር ይጠፋል
‹‹የሞዓብ ምድር ከእንግዲህ የተከበረች አትሆንም››

---

## Chapter 17
Isaiah 17:1
ስለ ደማስቆ
ደማስቆ የከተማ ስም ነው። ኢሳይያስ 7፥8 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
የአሮኤር ከተሞች ባድማ ይሆናሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ሰዎች ሁሉ የአሮኤርን ከተማ ትተው ይሄዳሉ››
ማንም አያስፈራቸውም
‹‹እነርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው በጐቹን ነው።
የተመሸጉ ከተሞች ከኤፍሬም ይጠፋሉ
ኤፍሬም በእስራኤል ትልቁ ነገድ ነበር። እዚህ ላይ መላው የእስራኤልን ሰሜናዊ መንግሥት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእስራኤል ጠንካራ ከተሞች ይጠፋሉ››
ይጠፋሉ
ይህ ማለት ብን ብለው ይጠፋሉ ሳይሆን፣ ይደመሰሳሉ ማለት ነው።
ከደማስቆ መንግሥት
‹‹ይጠፋሉ›› ቀደም ሲል ከነበረው ቁጥር ውስጠ ታዋቂ ነው። ደማስቆ የሶርያ ንጉሥ የሚገዛበት ቦታ ነበረች። መንግሥቱ መጥፋቱ ከእንግዲህ እንደ ንጉሥ የመግዛት ሥልጣን እንደማይኖረው ነው የሚያመለክተው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከደማስቆ መንግሥት ይጠፋል›› ወይም፣ ‹‹በደማስቆ የንጉሥ ሥልጣን አይኖርም››
ሶርያ
ሶርያ የአገር ስም ነው። ኢሳይያስ 7፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
እንደ እስራኤል ሕዝብ ክብር ይሆናሉ
የእስራኤል ሕዝብ ምንም ክብር እንዳልነበራቸው ሁሉ፣ ከሶርያ የተረፉትም ምንም ክብር አይኖራቸውም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ እንደ እስራኤል ሕዝብ እነርሱም ምንም ክብር አይኖራቸውም›› ወይም፣ ‹‹በእስራኤል ሕዝብ እንዳደረግሁ እነርሱም ላይ እፍረት አመጣለሁ››
የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን ነገር እርግጠኝነት ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 14፥22 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ የሚለው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይህን ብያለሁ››
Isaiah 17:4
እንዲህም ይሆናል
ይህ ሐረግ እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው አንድ በጣም አስፈላጊ ነገር እንደሚሆን ለማመልከት ነው። ቋንቋህ ይህን የምታደርግበት መንገድ ካለው፣ እዚህ ላይ ልትጠቀምበት ትችላለህ።
የያዕቆብ ክብር ይከሳል፤ የሥጋውም ውፍረት ይመነምናል
‹‹ያዕቆብ›› የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ከእንግዲህ እስራኤል ክብር ያላት አትሆንም። ይልቁን ደካማና ድኻ ትሆናለች።
ገበሬ ሰብሉን ከሰበሰበ በኃላ እንዳለው ይሆናል፤ ...በራፋይም ሸለቆ
እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ ከቀጣ በኃላ፣ በምድሩ ምንም የሚቀር ነገር አይኖርም።
በራፋይም ሸለቆ
ይህ ሰዎች ብዙ እህል የሚያመርቱበትና የሚሰበስቡበት ሸለቆ ነው።
Isaiah 17:6
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤልን ሕዝብ መከር ከታጨደ በኃላ ካለው እርሻ ጋር ማመሳሰሉን ቀጥሏል። (ኢሳይያስ 17፥4-5 ይመ.)
ቃርሚያ ይተርፋል
እዚያ ላይ፣ ‹‹ቃርሚያ›› በእስራኤል የቀረውን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእስራኤል ጥቂት ሰዎች ይቀራሉ››
የወይራ ዛፍ በተናወጠ ጊዜ
ሰዎች የወይራ ፍሬ የሚሰበስቡት ፍሬው እንዲረግፍ ዛፉን በመነቅነቅ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ከሰበሰቡ በኃላ ዛፉ ላይ እንደሚቀር ጥቂት የወይራ ፍሬ››
አራት ወይም አምስት
ከዚህ በፊት ከነበረው ቁጥር ‹‹የወይራ ፍሬ›› የሚለው ቃል ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አራት ወይም አምስት ፍሬ››
ይላል የእስራኤል አምላክ ያህዌ
እየተናገረ ያለውን እርግጠኝነት ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ የእስራኤል አምላክ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ እኔ የእስራኤል አምላክ ያህዌ የተናገርሁት ነው››
ሰዎች ወደ ፈጣሪያቸው ይመለከታሉ... ወደ እስራኤል ቅዱስ ያያሉ
እዚህ ላይ ወደ እግዚአብሔር መመልከት እንደሚረዳቸው በእርሱ ተስፋ ማድረግን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች የፈጠራቸው የእስራኤል ቅዱስ እንደሚረዳቸው ተስፋ ያደርጋሉ››
ሰዎች ይመለከታሉ
‹‹ሰዎች›› በጠቅላላው የእስራኤል ሕዝብ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ያያሉ››
ዐይኖቻቸው ያያሉ
‹‹ዐይኖች›› የሚመለከቱ ሰዎችን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያያሉ›› ወይም፣ ‹‹ሕዝቡ ያያሉ››
የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
Isaiah 17:8
ወደ መሠዊያቸው አይመለከቱም
ወደ መሠዊያ መመልከት ጣዖቶቹ ይረዱናል በሚል ተስፋ ጣዖቶችን ማምለክን

ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መሠዊያቸው ላይ ጣዖቶችን አያመልኩም›› ወይም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ወደ መሠዊያቸው ሄደው እንዲረዷቸው አማልክቶቻችውን አይለምኑም››
በእጃቸው ወደ ሠሯቸው
መሠዊያዎቹን ወይም ጣዖቶቹን የሠሯቸው እነርሱ መሆናቸውን አጽንዖት ለመስጠት እዚህ ላይ ሰዎች ‹‹በእጃቸው›› ተወክለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእጆቻቸው የሠሯቸው›› ወይም፣ ‹‹ራሳቸው የሠሩትን››
በጣቶቻቸው ላበጇቸው… የአሼራ ዐምዶች ወይም የፀሐይ ምስሎች
ሁለተኛው ሐረግ ሰዎቹ የሠሩትን ያመለክታል። ስለ ጣቶች የተነገረው ሰዎች እንዳበጇቸውና ስለዚህ እነዚህ እውነተኛ አማልክት አለመሆናቸውን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱ ራሳቸው ላበጇቸው የአሼራ ዐምዶች ወይም የፀሐይ ምስሎች››
በእስራኤል ልጆች ምክንያት የተተውት
እነዚህን ምድሮች የተውት እነማን እንደ ነበሩ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ከመጡ በኋላ ኤጢያውያንና አሞራውያን ትተው ሄዱ››
Isaiah 17:10
አንተ ረስተሃልና
‹‹አንተ›› የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ‹‹ረስተሃል›› የሚለው ቃል እግዚአብሔርን እያስታውሱም ማለት አይደለም። እየታዘዙለት አይደለም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልታዘዝህምና››
አዳኝ አምላክህን
‹‹የሚያድንህን አምላክ››
የብርታትህን ዐለት ችላ ብለሃል
እዚህ ላይ እግዚአብሔርን ከጠላቶቻቸው ለማምለጥ ወይም ከጀርባው ለመደበቅ ሰዎች ከሚወጡበት ትልቅ ዐለት ጋር አመሳስሎታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ መከታ ዐለት የሆነልህን ችላ ብለሃል›› ወይም፣ ‹‹የከለለህን ችላ ብለሃል።
መከር ይበላሻል
‹‹የምትሰበሰቡት ብዙ ፍሬ አይኖራችሁም››
Isaiah 17:12
የብዙ ሕዝብ ጩኸት፤ እንደ ባሕር ሞገድ ያለ ጩኸት
ጩኸት በጣም ከፍ ያለ ድምፅ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ባሕር ሞገድ በጣም ከፍ ያለ የብዙ ሰዎች ድምፅ››
እንደ ውሃ ሙላት የተጣደፈ የሕዝቦች ሩጫ
የጠላት ሰራዊት ማንም የማያስቆመው ታላቅ ኀይል ይመስላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡ እንደ ውሃ ሙላት እየተጣደፉ ይመጣሉ››
የሕዝቦች ጥድፊያ
‹‹ሕዝቦች›› የሚለው ቃል የእነዚህ አገሮችን ሰራዊት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጠላት ሰራዊት ጥድፊያ››
በዐውሎ ነፋስ ፊት ተራራ ላይ እንዳለ ገለባ… በማዕበል ፊት እንደሚበተን አረም
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። የጠላት ሰራዊት በጣም ኀይለኛ ይመስላል፤ እግዚአብሔር ግን በቀላሉ ያስቆማቸዋል ያባርራቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነፋስ እንደሚያበንነው ተራራ ላይ እንዳለ ገለባ… ማዕበል ሲመጣ በንኖ እንደሚጠፋ አረም››
የ… ዕድል ፈንታ
እነርሱ ላይ የደረሰው በውርስ እንዳገኙት ዕድል ፈንታ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በ… የሚደርሰው ይኸው ነው››
የዘረፉን… የበዘበዙን
‹‹እኛን›› የሚለው ኢሳይያስንና የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታል።

---

Chapter 18
Isaiah 18:1
በኩሽ ወንዞች ማዶ ለምትገኝ ፉር ፉር የሚሉ ክንፎች ላሉበት ምድር ወዮላት
‹‹ፉር ፉር የሚሉ ክንፎች›› ማለት ሊሆን የሚችለው፣ 1) መቅዘፊያዎች ያሉባቸው ጀልባዎች ክንፎች እንዳሏቸው መነገሩ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ውሃ ላይ እንዳሉ ክንፉም ብዙ ጀልባዎች ላሏት ከኩሽ ወንዞች ማዶ ላለች ምድር ወዮላት›› ወይም 2) ፉር ፉር የሚሉ ክንፎች የሚለው የክንፋም ፍጥረቶችን ምናልባትም የአንበጣዎችን ድምፅ ሊሆን ይችላል።
ባሕሩ ላይ
የዐባይ ወንዝ በጣም ሰፊ በመሆኑ በግብፅና በኩሽ ያሉ ሕዝብ፣ ‹‹ባሕሩ›› በማለት ይጠሩት ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በታላቁ ባሕር›› ወይም፣ ‹‹በዐባይ ወንዝ ዳር››
የደንገል ዕቃ
ደንገል ዐባይ ወንዝ ዳር የሚበቅል ረጅም ተክል ነው። የደንገል ክምሮችን በአንድነት በማያያዝ ሰዎች ጀልባዎች ይሠሩ ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የደንገል ጀልባ›› ወይም፣ ‹‹ከቀጤማ የተሠሩ ጀልባዎች››
ረጅምና ለስላሳ ቆዳ… ከቅርቡም ከሩቅም ወደሚፈራ ሕዝብ… ኀያልና ረጋጭ ወንዝ በሚከፍለው ምድር የሚኖር ሕዝብ
እነዚህ ሐረጐች ሁሉ የአንድ አገር ሕዝብን ነው የሚገልጹት።
ረጅምና ቆዳው የለሰለሰ ሕዝብ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሕዝብ›› የዚያን አገር ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ረጅምና ቆዳው የለሰለሰ ሕዝብ ያሉት አገር››
በቅርብም በሩቅም ወደሚፈራ
‹‹ቅርብ›› እና፣ ‹‹ሩቅ›› የተሰኙት ቃሎች በአንድነት የቀረቡት፣ ‹‹የትም አገር›› ለማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የትም አገር የሚፈራ ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹በየትኛውም ምድር ያሉ የሚፈሩት ሕዝብ››
ኀያልና ረጋጭ ሕዝብ
መርገጥ መንግሥታትን ድል ማድረግን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀያልና ሌሎች መንግሥታን ድል የሚያደርግ ሕዝብ››
ወንዝ የሚከፍለው ምድር
የተለያዩ ክፍሎች ያሉት ምድር እንዲሆን ምናልባት ይህ በዚያ አገር የሚያልፉ ብዙ ወንዞችን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።
Isaiah 18:3
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ቁጥር 3 ኢሳይያስ 18፥2 ላይ የተጠቀሱት መልእክተኞች ለዓለም ሕዝብ መንገር ያለባቸውን ያመለክታል።
እናንት የዓለም ሕዝቦች… በምድርም የምትኖሩ ሁሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር ያላችሁ ሕዝቦች ሁሉ››
ተራሮች ላይ ምልክት ሲሰቀል ተመልከቱ፤ መለከት ሲነፋም አድምጡ
ምልክትና የመለከት ድምፅ ሰዎችን ወደ ጦርነት ለመጥራት ያገለግላሉ። እንዲመለከቱና እንዲያደምጡ የተሰጠውን ትእዛዝ ልብ እንዲሉና ለጦርነት እንዲዘጋጁ የሚያሳስብ ትእዛዝ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምልክት ተራሮች ላይ ሲሰቀልና መለከት ሲነፋ ልብ በሉ››
ምልክት ተራሮች ላይ ሲሰቀል ተመልከቱ
ምልክት ሰዎችን ለጦርነት ለመጥራት የሚያገለግል ባንዲራ ነበር። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጦርነቱን ባንዲራ ተራሮች ላይ ስትመለከቱ ልብ በሉ››
መለከት ሲነፋ አድምጡ
መለከት ሰዎችን ለጦርነት ለመጥራት ጥቅም ላይ ይውላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጦርነቱን መለከት ድምፅ ስትሰሙ ልብ በሉ››
Isaiah 18:4
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ስለ ወይን እርሻ ገበሬ በተነገረ ምሳሌ የተጠቀመው አንድን ሕዝብ እንደሚቀጣ ለማመልከት ነው። ያ ሕዝብ ኢትዮጵያ ወይም የኢትዮጵያ ጠላት ሊሆን ይችላል።
ያህዌ ያለኝ ይህን ነው
‹‹ያህዌ እንዲህ አለኝ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› ኢሳይያስን ይመለከታል።
እቤቴ ሆኜ በእርጋታ እመለከታለሁ
እግዚአብሔር የሚመለከተው ምን እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እቤቴ ሆኜ ያንን ሕዝብ በእርጋታ እመለከታለሁ›› ወይም፣ ‹‹እቤቴ ሆኜ የዚያ አገር ሕዝብ የሚያደርገውን በእርጋታ እመለከታለሁ››
በፀሐይ ሐሩር እንደሚያብረቀርቅ ትኩሳት፣ በመከርም ሙቀት እንደ ደመና ጠል
እነዚህ ሐረጐች እግዚአብሔር ሕዝቡን በእርጋታ እንደሚመለከት ያሳያሉ።

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከመከር በፊት
ይህ የወይን ፍሬ መከር ነው። ይህን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የወይን ፍሬ ከመሰብሰቡ በፊት››
የአበባው ወቅት ሲያልፍ
ይህ የሚያመለክተው የወይን ፍሬ ሲጐመራ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የወይን ዛፉ ላይ አበቦች ታይተው ሲያበቁ››
የወይን ሐረጉን ተቀጥላ በመግረዣ ይቆርጠዋል
የወይኑ ፍሬ ከመብሰሉ በፊት ያህዌ ቅርንጫፎቹን ይቆርጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍሬ ከማፍራቱ በፊት ያህዌ በመቁረጫ ቅርንጫፎቹን ይቆርጣል››
መግረዣ መንጠቆ
መግረዣ መንጠቆ ሰዎች ከወይን ዛፍና ከሌሎች ተክሎች ቅርንጫፎችን ለመቁረጥ የሚጠቀሙበት ነው።
የተንሰራፋውንም ቅርንጫፍ ቆራርጦ ያስወግደዋል
ያህዌ ቅርንጫፎቹን ለፍርድ ይጥላል
Isaiah 18:6
በአንድነት ይተዋሉ
እግዚአብሔር ምሳሌውን መናገሩን ትቶ በቀጥታ ስለ ሕዝቡ ወደ መናገር የሄደ ይመስላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተገደሉት ሁሉ በአንድነት ይተዋሉ›› ወይም፣ ‹‹ተቆርጠው እንደ ተጣሉ ቅርንጫፎች የተገደሉት ሰዎችም ሬሳዎች መሬት ላይ በአንድነት ይተዋሉ››
ወፎች በበጋ ወቅት ይበሉታል
‹‹በጋ በሚሆንበት ጊዜ ወፎች ይበሉታል›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ወፎች›› የሚለው በድን የሚበሉ ወፎችን ነው።
የምድር አራዊት ሁሉ
‹‹ማንኛውም ዐይነት የዱር አውሬ››
ክረምቱን ሁሉ ይበሉታል
‹‹ክረምት በሚሆንበት ጊዜ ይበሉታል››
ረጅምና ቆዳው የለሰለሰ ሕዝብ… ከቅርብም ከሩቅም የሚፈራ ሕዝብ… ኀያልና ረጋጭ ምድሩን ወንዞች የሚከፍሉት ሕዝብ
እነዚህ ሐረጐች የሚናገሩት ስለ አንድ አገር ሕዝብ ነው። ኢሳይያስ 18፥2 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
ረጅምና ቆዳው የለሰለሰ ሕዝብ
‹‹ረጅም የሆነና ለስላሳ ቆዳ ያለው ሕዝብ››
ከሩቅም ከቅርቡም የሚፈራ ሕዝብ
‹‹ሩቅ›› እና፣ ‹‹ቅርብ›› የተሰኙት ቃሎች በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት፣ ‹‹የትም ቦታ›› ለማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በየትም ቦታ የሚፈራ ሕዝብ›› ወይም ‹‹በምድር ያለ ሁሉ የሚፈራው ሕዝብ››
ኀይልና ረጋጭ ሕዝብ
መርገጥ ሌሎች መንግሥታትን ድል ማድረግን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብርቱ የሆነና ሌሎች መንግሥታትን ድል የሚያደርግ ሕዝብ››
የሰራዊት ጌታ ያህዌ ስም የሚጠራበት ቦታ የጽዮን ተራራ
‹‹ስም›› የሚለው የሚያመለክተው ያህዌን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ የሚኖርበት የጽዮን ተራራ››

# Chapter 19

## Isaiah 19:1

እነሆ
‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹አድምጡ›› ወይም፣ ‹‹የምናገረውን ልብ በሉ››
ያህዌ በፈጣን ደመና ይመጣል
በሰረገላ እየመጣ ያለ ይመስል ያህዌ በደመና እየሄደ እንደሆነ ተመስሎአል።
የግብፅ ጣዖቶች በፊቱ ይርዳሉ
ያህዌ ሲመጣ ጣዖቶቹ ፍርሃት እንደሚያድርባቸው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የግብፅ ጣዖቶች ያህዌ ፊት በፍርሃት ይንቀጠቀጣሉ››
የግብፃውያን ልብ በውስጣቸው ይቀልጣል
የልብ መቅለጥ የሚያመለክተው ወኔ ማጣትን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግብፃውያን ምንም ወኔ አልቀራቸውም››
ሰው በጐረቤቱ ላይ
‹‹ይነሣል›› የሚለው ካለፈው ሐረግ ውስጠ ታዋቂ ነው። ‹‹ሰው በጐረቤቱ ላይ ይነሣል››
ከተማ በከተማ ላይ
‹‹ከተማ›› የከተማውን ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአንድ ከተማ ሕዝብ፣ በሌላ ከተማ ሕዝብ ላይ ይነሣል›› ወይም፣ ‹‹በተለያዩ ከተሞች ያሉ ሰዎች እርስ በርስ ይዋጋሉ››
መንግሥት በመንግሥት ላይ
‹‹ይነሣል›› ወይም፣ ‹‹ይዋጋል›› የተሰኙ ቃላት ካለፉ ሐረጐች ውስጠ ታዋቂ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መንግሥት በመንግሥት ላይ ይነሣል›› ወይም፣ ‹‹አንድ መንግሥት ከሌላ መንግሥት ጋር ይዋጋል››
መንግሥት በመንግሥት ላይ
‹‹መንግሥት›› የሚለው ቃል ግብፅ ውስጥ ያለ ታናሽ መንግሥት ያመለክታል። ክፍለ ሀገርም ሊባል ይችላል። የዚያን መንግሥት ወይም ክፍለ ሀገር ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአንድ ክፍል ሀገር ሰዎች በሌላ ክፍለ ሀገር ሰዎች ላይ ይነሣሉ›› ወይም፣ ‹‹በተለያዩ ክፍለ ሀገሮች ያሉ ሰዎች እርስ በርስ ይዋጋሉ››

## Isaiah 19:3

የግብፅ መንፈስ በውስጡ ይደክማል፤ ምክሩን አጠፋለሁ
እዚህ ላይ የግብፅ መንግሥት አንድ ሰው እንደሆነ ተነግሯል።
የግብፅ መንፈስ በውስጡ ይደክማል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የግብፅን መንፈስ በውስጡ አደክማለሁ››
የመናፍስት ጠሪዎችን ምክር ቢፈልግ እንኳ… ምክሩን አጠፋለሁ
‹‹የመናፍስት ጠሪዎችን ምክር ፈልገው ነበር፤ ግን ምንም አይጠቅማቸውም፤ ምክሩን ከማጥፋትም አያግደኝም››
ምክሩን አጠፋለሁ
ይህም ማለት፣ 1) የሚሰጠውን ምክር ያህዌ ውጤት የለሽ ያደርገዋል፤ ወይም 2) ያህዌ ምንም ምክር እንዳይሰጥ ያደርገዋል። ይህን ዐረፍተ ነገር በሌላ ዐረፍተ ነገር መተካት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ንጉሡን የሚመክሩትን ግራ አጋባለሁ››
መናፍስት ጠሪዎች… ጠንቋዮች
እነዚህ ከሞቱ ሰዎች ጋር እንነጋገራለን የሚሉ ናቸው።
ግብፃውያንን ለጨካኝ ጌታ እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› ሥልጣንን ወይም ቁጥጥርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግብፃውያንን በጨካኝ ጌታ ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ አሳልፌ እሰጣለሁ››
ይህ የሰራዊት ጌታ የያህዌ ቃል ነው
የሚናገረው እርግጥ እንደሆነ ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 3፥15 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ የተናገርሁት ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ የተናገርሁት ነው››

## Isaiah 19:5

የባሕሩ ውሃ ይደርቃል፤ ወንዝም ባዶ እስኪሆን ይደርቃል
ግብፃውያን የዐባይ ወንዝን፣ ‹‹ባሕሩ›› በማለት ይጠሩታል። እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዐባይ ወንዝ ጨርሶ ይደርቃል››
ይከረፋሉ
‹‹መጥፎ ሽታ ይኖራቸዋል›› ወይም፣ ‹‹ይገማሉ››
እየጐደለ
‹‹እያነሰ፤ እያነሰ ይሄዳል››
ደንገሉና ቀጤማውም ይጠወልጋል
‹‹ደንገል›› እና፣ ‹‹ቀጤማ›› የተለያዩ የውሃ ውስጥ ተክል ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወንዙ ዳርቻ ያሉት ተክሎች ጠውልገው ይደርቃሉ››

## Isaiah 19:7

እንዲሁም በዐባይ ዳር የተዘራው እርሻ
‹‹ሰዎች እህል የዘሩበት ዐባይ ወንዝ አጠገብ ያለው እርሻ››
ዓሣ አጥማጆች ዋይ ይላሉ ያለቅሳሉ፤ በዐባይ ወንዝ ላይ መንጠቆአቸውን የሚጥሉ ሁሉ ያለቅሳሉ፤ በውሃው ላይ መረባቸውን የሚዘረጉ ሁሉ ያዝናሉ
እነዚህ ሦስት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። አስፈላጊ ከሆነ የሚያዝኑበትን ምክንያት መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐባይ ውስጥ ያሉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ዐሣዎች በመሞታቸው በመረብ ወይም በመንጠቆ ዓሣ የሚያጠምዱ ሰዎች ተስፋ በመቁረጥ ያለቅሳሉ››
ዐባይ ላይ መንጠቆ የሚጥሉ
ዓሣ ለመያዝ አንዳንድ ሰዎች መንጠቆው ላይ ጥቂት ምግብ ያስቀምጣሉ፤ መንጠቆውን በክር ያሰሩና ባሕር ውስጥ ይወረውሩታል። ዓሣው ምግቡን ለመብላት ሲሞክር፣ አፉ በመንጠቆው ይያዛል፤ ሰውየውም በመጐተት ዓሣውን ከውሃው ያወጣዋል።
መጣል
መወርወር
ውሃ ላይ መረብ መዘርጋት
ዓሣ ለመያዝ አንዳንድ ሰዎች ውሃው ላይ መረብ ይወረውራሉ። ዓሣው ሲጠመድ መረቡን ከዓሣው ጋር ከውሃው ስበው ያወጡታል።
Isaiah 19:9
የተበጠረውን ነጭ የተልባ እግር የሚሠሩ ሸማኔዎች ይገረጣሉ፤ የግብፅ ልብስ ሠሪዎችም ያዝናሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ አስፈላጊ ከሆነ የሚያዝኑበትን ምክንያት መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ፈትል ስለማይኖር የግብፅ ተልባ እግር ልብስ ሠሪዎች ይዋረዳሉ››
ሸመና የሚሠሩ
‹‹የሸማና መሣሪያ በመጠቀም ልብስ የሚሠሩ››
ጥጥ
ጥጥ ዐባይ ወንዝ ዳር የሚያድግ ተክል ነው። መልካምና ያማረ ልብስ ለመሥራት ሰዎች ያበጥሩት ነበር።
ይገረጣሉ
‹‹ያፍራሉ››
የግብፅ ልብስ ሠሪዎች
x
Isaiah 19:11
የጣኔዎስ አለቆች ጨርሶ ሞኞች ይሆናሉ፤ የፈርዖን ጠቢባን ምክርም ከንቱ ይሆናል
ሁለቱ ሐረጐች ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው። የፈርዖን ጠቢባን የተባሉት የጣኔዎስ አለቆች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ወይም ደግሞ እነርሱ ራሳቸውም ሞኞች የሚሆኑ ሌሎች ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።
ጣኔዎስ
ይህ በሰሜናዊ ግብፅ ያለ ከተማ ነው።
ፈርዖን እንዴት ትሉታላችሁ… ነገሥታት?
ኢሳይያስ በጥያቄ የተጠቀመው ጥበበኞች ነን በሚሉ ሰዎች ላይ ለማፌዝ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በሞኝነት ፈርዖንን… ነገሥታት››
ታዲያ፣ የአንተ ጥበበኞች ወዴት ናቸው?
ኢሳይያስ ጥያቄውን ያቀረበው በጥበበኞች ላይ ለማፌዝ ነው። ‹‹የአንተ›› የሚለው ፈርዖንን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጥበበኞች የሉህም›› ወይም፣ ‹‹ጥበበኞችህ ሞኞች ናቸው››
የሰራዊት ጌታ ያህዌ ግብፅ ላይ ያሰበውን ይንገሩህ ያሳውቁህ
ኢሳይያስ ጥበበኞቹ የእግዚአብሔርን ሐሳብ መረዳት እንዳለባቸው ቢያመለክትም፣ በእርግጥ መረዳት ይችላሉ ብሎ አያምንም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእውነት ጥበበኞች ከሆኑ፣ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ግብፅ ላይ ያሰበውን ይንገሩህ››
Isaiah 19:13
የነገዶቿ የማእዘን ራስ የሆኑት ግብፅን አስተዋታል
የጣኔዎስና የሜምፊስ አለቆች ማኅበረ ሰቡ ውስጥ አስፈላጊ ሰዎች በመሆናቸው የሕንፃዎች ማእዘን ራሶች እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መሪዎቹ ግብፅን አሳስተዋል››
የጣኔዎስ አለቆች
ጣኔዎስ ሰሜናዊ ግብፅ ላይ ያለች ከተማ ናት። ኢሳይያስ 19፥11 ላይ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
ሜምፊስ
ይህ ሰሜናዊ ግብፅ ላይ ያለ ከተማ ነው።
ግብፅን አስተዋታል
‹‹ግብፅ›› የግብፅን ሕዝብ ያመለክታል። መሳት ትክክል ያልሆነ ነገር ማድረግን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የግብፅን ሕዝብ አሳስተዋል›› ወይም፣ ‹‹የግብፅ ሕዝብ ትክክል ያልሆነ ነገር እንዲያደርግ አድርገዋል››
ያህዌ በመካከልዋ የድንዛዜ መንፈስ ቀላቅሏል
ኢሳይያስ የያህዌ ፍርድ ግብፅን የወይን ጠጅ ጽዋ እንደሚያደርጋት ይናገራል። የመሪዎቹ አስተሳሰብ ግራ መጋባት ያህዌ ከወይን ጠጅ ጋር የሚቀላቅለው ፈሳሽ እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሐሳባቸውን ግራ በማጋባት ያህዌ ፈርዶባቸዋል›› ወይም፣ ‹‹የሚያሰክር መጠጥ የሰዎችን አስተሳሰብ ግራ እንደሚያጋባ የመሪዎቿን ሐሳብ ግራ በማጋባት ያህዌ ግብፅ ላይ ፈርዷል››
ግራ መጋባት
‹‹መጣመም›› ወይም፣ ‹‹መታወክ››
በመካከልዋ
‹‹እርሷ›› ግብፅን ያመለክታል። ብዙ ጊዜ ሕዝቦች በሴቶች ይመሰላሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በግብፅ ውስጥ››
እነርሱ ግብፅን አስተዋታል
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› ቀደም ባለው ቁጥር የተጠቀሱት መሪዎች ናቸው። ‹‹ግብፅ›› የሚለው ቃል የግብፅን ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አለቆቹ የግብፅን ሕዝብ አስተዋል››
ግብፅን አስተዋል
ሕዝብን ማሳት ትክክል ያልሆነ ነገርን እንዲያደርጉ ማድረግን ይወክላል።
ሰካራም በትውከቱ እንደሚንገዳገድ
የሰከረ ሰው እንደሚንገዳገድ የግብፅ ሕዝብ ትክክል ያልሆነ ነገር እንደሚደርግ ኢሳይያስ ይናገራል።
ራስም ይሁን ጅራት
የሰውም ሆነ የእንስሳ፣ ‹‹ራስ›› መሪን ይወክላል። ‹‹ጅራት›› ተቃራኒ ሲሆን፣ ተከታዮችን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መሪም ሆነ ተከታይ››
የዘንባባ ዝንጣፊም ይሁን ደንገል
‹‹የዘንባባ ዝንጣፊ›› ዛፍ ላይ ከፍ ብሎ የሚያድግ ስለሆነ ሀብታሞችና ታላላቆችን ይወክላል። ‹‹ደንገል›› ረግረግ ውሃ ውስጥ የሚያድግ ስለሆን ድኾችና ታናናሾችን ይወክላል። ኢሳይያስ 9፥14 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ታላላቆችም ሆኑ ታናናሾች›› ወይም፣ ‹‹ሀብታሞችም ሆኑ ድኾች››
Isaiah 19:16
ግብፃውያን እንደ ሴቶች ይሆናሉ
ይህ የሚመለክተው እግዚአብሔር ሲቀጣቸው የግብፅ ሕዝብ እንደሚፈሩና ዐቅመ ቢስ እንደሚሆኑ ነው።
የሰራዊት ጌታ ያህዌ እነርሱ ላይ ካነሣው እጁ የተነሣ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሚወክለው የእግዚአብሔርን ኀይል ሲሆን፣ እነርሱ ላይ እጅ ማንሣት እነርሱን መቅጣትን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እነርሱን ለመቅጣት የሰራዊት ጌታ ያህዌ ካነሣው ኀይል እጁ የተነሣ››
የይሁዳ ምድር ለግብፅ መንገዳገድ ምክንያት ትሆናለች
‹‹የይሁዳ ምድር›› እና፣ ‹‹ግብፅ›› በእነዚያ አገሮች የሚኖረውን ሕዝብ ያመለክታሉ። ግብፃውያን ከመፍራታቸው የተነሣ ይንገዳገዳሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የይሁዳ ሕዝብ የግብፅ ሕዝብ እንዲንገዳገድ ያደርጋሉ›› ወይም፣ ‹‹የይሁዳ ሕዝብ ግብፃውያን እጅግ እንዲፈሩ ያደርጋሉ››
ስለ እርሷ ሲነገራቸው ይሸበራሉ
‹‹የእነርሱ›› እና፣ ‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ግብፃውያንን ሲሆን፣ ‹‹እርሷ›› የሚያመለክተው የይሁዳን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለግብፃውያን ስለ ይሁዳ ሕዝብ ሲነገራቸው ግብፃውያን ይሸበራሉ››
Isaiah 19:18
በግብፅ ምድር የሚናገሩ አምስት ከተሞች ይሆናሉ
ይህ የሚያመለክተው የዚያ ከተማ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በአምስት የግብፅ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች ይናገራሉ››
በከነዓን ቋንቋዎች
ይህ የሚያመለክተው በከነዓን ምድር የሚኖሩ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ቋንቋ ዕብራይስጥን ነው። እዚህ ላይ፣ ከነዓን እዚያ የሚኖር ሕዝብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የከነዓን ሕዝብ ቋንቋ››
ይምላሉ
‹‹ታማኝ ለመሆን ቃል ይገባሉ››
ከእነዚህ አንዷ ትጠራለች
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ሰዎች ከእነዚህ ከተሞች አንዷን ይጠሯታል››
የፀሐይ ከተማ ትባላለች

እዚህ ላይ፣ ‹‹ፀሐይ›› ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል፣ ‹‹ፀሐይ›› ወይም ‹‹ጥፋት›› ማለት መሆኑ ግልጽ አይደለም። ስሙ ስለ ከተማዋ የሚነግረን ምን እንደሆነም ግልፅ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የፀሐይ ከተማ የተባለች ከተማ›› ወይም፣ ‹‹የጥፋት ከተማ የተባለች ከተማ››

Isaiah 19:19

ለያህዌ ድንበር ላይ ያለ የድንጋይ ዐምድ

‹‹ድንበር›› የሚያመለክተው የግብፅን ድንበር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግብፅ ድንበር ላይ ለያህዌ የድንጋይ ዐምድ››

በግብፅ ምድር ለሰራዊት ጌታ ለያህዌ ምልክትና ምስክር ይሆናል

‹‹ምልክት›› እና፣ ‹‹ምስክር›› የተሰኙትን ቃሎች፣ ‹‹ማሳያ›› እና፣ ‹‹ማረጋገጫ›› በማለት መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐምዱ የሰራዊት ጌታ ያህዌ በግብፅ ምድር መሆኑን ያሳያል፤ ያረጋግጣል››

በግብፅ ምድር ለሰራዊት ጌታ ለያህዌ

ያህዌ በግብፅ ምድር መሆኑ የግብፅ ሕዝብ እርሱን እንደሚያመልኩ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በግብፅ ምድር ያሉ ሰዎች የሰራዊት ጌታ ያህዌን ያመልካሉ››

ሲጮኹ

‹‹ግብፃውያን ሲጮኹ››

ከሚያስጨንቋቸው የተነሣ

‹‹ሰዎች ከሚፈጽሙባቸው ግፍ የተነሣ›› ወይም፣ ‹‹ሌሎች ከሚያደርሱባቸው መከራ የተነሣ››

አዳኝና ታዳጊ ይልክላቸዋል

‹‹ያህዌ የሚያድናቸውና የሚታደጋቸው ሰው ይልክላቸዋል››

ያህዌ ያድናቸዋል

ያህዌ የሚያድናቸው ከማን እንደሆነ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ግብፃውያንን ከሚያስጨንቋቸው ያድናቸዋል››

Isaiah 19:21

ያህዌ በግብፅ የታወቀ ይሆናል

‹‹ግብፅ›› የሚያመለክተው የግብፅን ሕዝብ ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የግብፅ ሕዝብ እንዲያውቀው ያደርጋል››

ይቀበሉታል

‹‹ስለ ያህዌ እውነቱን ይቀበላሉ›› ወይም፣ ‹‹ስለ ያህዌ እውነት ጋር ይስማማሉ››

ያመልካሉ

የሚያመልኩት ማንን እንደሆነ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን ያመልካሉ››

ለያህዌ ይሳላሉ፤ ይፈጽማሉ

‹‹ለያህዌ ቃል ይገባሉ፤ ቃላቸውን ይጠብቃሉ›› ወይም፣ ‹‹ለያህዌ ቃል ይገባሉ፤ እናደርጋለን ያሉትንም ያደርጋሉ››

ያህዌ ግብፅን ይመታል

‹‹ግብፅ›› የሚያመለክተው የግብፅን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የግብፅን ሕዝብ ይመታል››

ይመታል

‹‹ይቀጣል›› ወይም፣ ‹‹ይፈርዳል››

ይመታል፤ ይፈውሳል

በዚህ ሐረግ ‹‹እነርሱ›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይመታቸዋል ደግሞም ይፈውሳቸዋል››

ይመታል፤ ይፈውሳል

ይህን ሐረግ ቀድሞ ከነበረው ሐረግ ጋር ለማያያዝ፣ ‹‹በኋላ›› ወይም፣ ‹‹ደግሞም›› በተሰኙ ቃሎች ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከመታቸው በኃላ ይፈውሳቸዋል››

Isaiah 19:23

አውራ መንገድ ይኖራል

አውራ መንገድ ብዙ ሰዎች መጓዝ የሚችሉበት ትልቅ መንገድ ነው።

አሦራዊ ይመጣል

‹‹አሦራዊ›› ከአሦር የሆነ ሰው ሲሆን፣ ግን ከአሦር ወደ ግብፅ የመጣ ማንኛውንም ሰው ይመለከታል። ‹‹አሦራውያን ይመጣሉ››

ግብፃዊ ወደ አሦር

‹‹ይመጣል›› የሚለው ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግብፃውያን ወደ አሦር ይመጣሉ››

ግብፃዊ

ይህ የሚያመለክተው ከግብፅ የሆነ ሰውን ሲሆን፣ ነገር ግን ወደ አሦር የመጣ ማንኛውንም ግብፃዊ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግብፃውያን››

ግብፃውያን ከአሦራውያን ጋር ያመልካሉ

የሚያመልኩት ማንን እንደሆነ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግብፃውያንና አሦራውያን ያህዌን ያመልካሉ››

Isaiah 19:24

እስራኤል ከግብፅና ከአሦር ጋር ሦስተኛ ይሆናል

የሦስቱ አገሮች ስም በእነዚያ አገሮች የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስራኤላውያን ከግብፃውያንና ከአሦራውያን ጋር ሦስተኛ ይሆናሉ››

ሦስተኛ ይሆናል

ይህም ማለት፣ 1) ‹‹አብረው ይሆናሉ›› ወይም 2) ‹‹ከእነርሱ ጋር ሦስተኛ በረከት›› ወይም 3) ‹‹እኩል ይሆናል›› ማለት ሊሆን ይችላል።

ሕዝቤ ግብፅ፣ የእጆቼ ሥራ አሦር፣ ርስቴ እስራኤል የተባረኩ ይሁኑ

የሦስቱ አገሮች ስም በእነዚያ አገሮች የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የግብፅ ሕዝብ ሆይ፣ ሕዝቤ ስለሆናችሁ ባርኬአችኃለሁ፤ የአሦር ሕዝብ ሆይ፣ ስለ ፈጠርኋችሁ ባርኬአችኃለሁ፤ የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ ርስቴ ስለሆናችሁ ባርኬአችኃለሁ››

የእጆቼ ሥራ

‹‹እጆች›› የእግዚአብሔርን ኀይልና ተግባር ያመለክታሉ።

---

Chapter 20

Isaiah 20:1

ታርታን

የአሦር ሰራዊት ዋና አዛዥ ስም

ሳርጐን

የአሦር ንጉሥ ስም

አሽዶድን ወግቶ ያዛት

አሽዶድ የአስዶድን ሰራዊት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአሽዶድ ሰራዊት ጋር ተዋግቶ ድል አደረገ››

ዕርቃኑንና ባዶ እግሩን ሄደ

‹‹ያለ ልብስና ያለ ጫማ ሄደ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ዕርቃኑን›› ሲል ምናልባት በውስጥ የሚለበስ ልብስ ብቻ ለብሶ ማለቱ ሊሆን ይችላል።

Isaiah 20:3

ለምልክት

‹‹ለማስጠንቀቂያ››

ለግብፅ ለኩሽ

የቦታዎቹ ስም ሕዝቡን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለግብፅ ሕዝብና ለኩሽ ሕዝብ››

የአሦር ንጉሥ ምርኮኞቹን ይወስዳቸዋል

ንጉሡ እንዲህ እንዲያደርጉ ሰራዊቱን ያዝዛል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦር ንጉሥ ሰራዊቱ ምርኮኞቹን እንዲወስዱ ያደርጋል››

የግብፅ ምርኮኞችን፣ የኩሽ ስደተኞችን

በመጀመሪያ እንደሚዋጉ ከዚያም ምርኮኞችን እንደሚወስዱ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግብፅና ኩሽን ወግቶ ሕዝባቸውን ይይዛል፤ ከዚያም ይወስዳቸዋል››

ወደ ግብፅ ውርደት

ግብፅ የግብፅን ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የግብፅ ሕዝብ ላይ ውርደት ወደሚያመጣ››

Isaiah 20:5

ይደነግጣሉ ይዋረዳሉ

‹‹ይፈራሉ፤ እፍረት ይይዛቸዋል››

ተስፋቸው ከሆነው ኩሽ፣ ክብራቸው ከሆነው ግብፅ የተነሣ

ተስፋና ክብር በእነዚህ አገሮች ወታደራዊ ኀይል መተማመናቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኩሽና በግብፅ ሰራዊት ኀይል ከመተማመናቸው የተነሣ››

በእነዚህ ባሕር ዳርቻዎች የሚኖሩ

ሜዲትራንያን ባሕር ዳርቻ የሚኖሩ ሕዝቦች

እንዲድኑን የሸሸንባቸው



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያድኑናል በማለት ሸሽተን የነበርንባቸው አገሮች››

ታዲያ፣ አሁን እንዴት እናመልጣለን?

ጸሐፊው ይህን ጥያቄ ያነሣው ሁኔታው ምን ያህል ተስፋ የሌለው መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አሁን ምንም ማምለጫ የለንም››

---

# Chapter 21

## Isaiah 21:1

ንግር

‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ የያህዌ መልእክት ነው››

ባሕሩ ዳር ስላለው ምድረ በዳ

ይህ እንደ ምድረ በዳ አድርጐ የተነገረ ቃል የሚያመለክተው የባቢሎንን ሕዝብ ነው፤ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ገና ምድረ በዳ ባያደርጋትም አሁን እንደሆነች አድርጐ ይናገራል፤ ይህም የሚያመለክተው በእርግጥ ምድረ በዳ እንደምትሆን ነው፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በቅርቡ ምድረ በዳ በምትሆን ምድር ለሚኖር ሕዝብ››

እየጠራረገ ከኔጌቭ እንደሚመጣ ዐውሎ ነፋስ

ሕዝቡን ለማጥቃት የሚመጣውን ሰራዊት እግዚአብሔር ከብርቱ ነፋስ ጋር አመሳስሎታል፡፡ ፈጣንና ኀይለኛ ሰራዊት ነው፡፡

ከምድረ በዳ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ምድረ በዳ›› የይሁዳን ምድረ በዳ ነው የሚያመለክተው፡፡

ከአሸባሪ ምድር

ሰራዊቱ የሚመጣው ታላቅ ፍርሃት ከሚያደርስ ሕዝብ ነው፡፡

የሚያስጨንቅ ራእይ አየሁ

ይህን በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ የሚያስጨንቅ ራእይ አሳየኝ››

ከሐዲ ክሕደቱን ያደርጋል

‹‹የሚያሳስቱ ያሳስታሉ››

አጥፊም ያጠፋል

‹‹የሚያጠፉ ይጠፋሉ››

ወደ ላይ ወጥታችሁ አጥቁ፣ ኤላም፣ መክበብ፣ ሜዶን

ለኢሳይያስ በተሰጠው ራእይ እግዚአብሔር እርሱን እንደሚሰሙ አድርጐ ለኤላምና ለሜዶን ሰራዊት ይናገራል፡፡

ወደ ላይ ወጥታችሁ አጥቁ፤ ኤላም፣ መክበብ፣ ሜዶን

የሚያጠቁት ባቢሎናውያንን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ላይ ወጥታችሁ ባቢሎናውያንን አጥቁ፤ እናንት የኤላም ሰራዊት ሄዳችሁ›› ባቢሎናውያንን ክበቡ፤ እናንት የሜዶን ሰራዊት››

ኤላም… ሜዶን

እዚህ ላይ፣ ‹‹ኤላም›› እና፣ ‹‹ሜዶን›› ከእነዚህ አገሮች የመጡ ሰራዊት ያመለክታል፡፡

እርሷ ያደረሰችውን ስቃይ ሁሉ አስቀራለሁ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሷ›› በባቢሎናውያን ምክንያት መከራ የደረሰባቸውን ሕዝብ ሁሉ ይወክላል፡፡ የኤላምና የሜዶንን ሰራዊት ልኮ ባቢሎናውያንን ሲደመስስ ያህዌ ስቃያቸውን ሁሉ ያስቀራል፡፡

## Isaiah 21:3

ወገቤ በስቃይ ተሞላ

ኢሳይያስ ያየው ራእይ በጣም አስጨናቂ ስለ ነበር አካላዊ ሕመም አሳድሮበት ነበር፡፡ እዚህ ላይ ስቃዩና ሕመሙ ምኑ ላይ እንደነበር ይናገራል፡፡

በምጥ ላይ እንዳለች ሴት ጭንቅ ያዘኝ

ኢሳይያስ ሕመሙን ምጥ ከያዛት ሴት ሕመም ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ይህም ሕመሙ ምን ያህል ከባድ እንደ ነበር ያመለክታል፡፡

የሰማሁትን ነገር አጐበጠኝ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የሰማሁት ነገር በሕመም አጐበጠኝ››

ባየሁት ነገር ተሸበርሁ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያየሁት ነገር በጣም አሸበረኝ››

ልቤ መታ፤ ፍርሃት አንቀጠቀጠኝ

‹‹ልቤ በፍጥነት መታ፤ እኔም ተንቀጠቀጥሁ››

## Isaiah 21:5

እነርሱ ተዘጋጁ

‹‹እነርሱ›› የተባሉ የባቢሎን መሪዎች ናቸው፡፡

ማእዱን አዘጋጁ

‹‹ማእድ›› የተባለው ግብዣው ላይ ሰዎች የሚበሉት ምግብ ነው፡፡

ሹማምንት፣ ተነሡ

እዚህ ላይ ‹‹ሹማምንቱ›› የተባሉት ሥልጣን ያላቸው ሰዎች በጠቅላላ እንጂ፣ የግድ የነገሥታት ልጆች ብቻ አይደለም፡፡

ጋሻውን በዘይት ወልውሉ

በጦርነት ጊዜ እንዳይሰነጠቁና ሁሌም ለስላሳ እንዲሆኑ ወታደሮች ጋሻዎቻቸውን በዘይት ይወለውሉ ነበር፡፡

## Isaiah 21:6

ጠባቂ አቁም

‹‹ጠባቂው በኢየሩሳሌም ቅጥር ላይ እንዲቆም ንገር››

ሰረገላ፣ ጥንድ ፈረሰኞች

‹‹በሁለት ፈረሶች የሚሳብ ሰረገላ የሚነዳ ወታደር››

## Isaiah 21:8

ጌታ ሆይ፣ በመጠበቂያው ማማ ቆሜአለሁ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ጌታ ሆይ›› የተባለው ቅጥር ጠባቂው በኢየሩሳሌም ቅጥር እንዲቆም የሚያዝዘው ባለ ሥልጣን ነው፡፡

ባቢሎን ወደቀች፤ ወደቀች

ባቢሎን ጨርሶ በጠላቶችዋ መሸነፍዋ የባቢሎን መውደቅ እንደሆነ ተነግሯል፡፡ ‹‹ባቢሎን›› የባቢሎንን ሕዝብ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የባቢሎን ሕዝብ ጨርሶ ድል ሆነ››

ወደቀች፤ ወደቀች

‹‹ወደቀች›› የሚለው ቃል የተደገመው የባቢሎን ሕዝብ በጠላቶቻቸው ጨርሶ ድል መሆናቸውን አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡

## Isaiah 21:10

የተወቃችሁና የተበራያችሁ የዐውድማዬ ልጆች

የእስራኤል ሕዝብ በባቢሎናውያን መሰቃየት ሕዝቡ ዐውድማ ላይ የሚወቃ እህልና የሚበራይ ወይን ፍሬ እንደሆነ ተነግሯል፡፡

ዐውድማዬ

‹‹የእኔ›› የሚለው ቃል ኢሳይያስን ያመለክታል፡፡

የሰራዊት ጌታ ያህዌ

ኢሳይያስ 1፥9 ላይ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት

## Isaiah 21:11

ንግር

‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ የያህዌ መልእክት ነው››

ስለ ዱማ

ይህ የኤዶም ሌላ ስም ነው፡፡ እዚህ ላይ፣ ‹‹ዱማ›› እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስለ ዱማ ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹ስለ ኤዶም ሕዝብ››

እንዲህ ሲል ጠራኝ

‹‹እኔን›› የሚለው ኢሳይያስን ነው፡፡

ሴይር

ይህ ከኤዶም በስተ ምዕራብ ያለ ተራራ ስም ነው፡፡

ጠባቂ ሆይ፣ ሊነጋ ምን ያህል ቀረው? ጠባቂ ሆይ፣ ሊነጋ ምን ያህል ቀረው?

ይህ የተደጋገመው ጥያቄውን ያቀረበው ሰው ምን ያህል እንደ ተጨነቀና ግራ እንደ ተጋባ አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡

መጠየቅ ከፈለግህ ጠይቅ፣ ደግሞም ተመልሰህ ና

‹‹ማወቅ የፈለግኸውን አሁን ጠይቀኝ፤ ደግሞም በኋላ ተመልሰህ ናና ጠይቀኝ››

## Isaiah 21:13

ንግር

‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ የያህዌ መልእክት ነው››

ስለ ዐረቢያ

ዐረቢያ የዐረቢያ ሕዝብን ይመለከታል፡፡ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ስለ ዐረቢያ ሕዝብ››

በዐረቢያ ምድረ በዳ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ዐረቢያ ደን የላትም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከዐረቢያ መንገድ በጣም ርቆ›› ወይም፣ ‹‹ከዐረቢያ ቆጥቋጦዎች ውጪ››
ሲራራ ነጋዴዎች
በአንድነት የሚጓዙ ሰዎች
የድዳን ሰዎች
እነዚህ በዐረቢያ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው።
የቴማ ምድር
ይህ አረቢያ ውስጥ ያለ ከተማ ስም ነው።
ስደተኞች
ስደተኛ ጠላት እንዳይይዘው የሸሸ ሰው ነው። ኢሳይያስ 15፥5 ላይ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
ከእንጀራ ጋር
‹‹እንጀራ›› በአጠቃላይ ምግብን ያመለክታል።
ከሰይፍ፣ ከተመዘዘ ሰይፍ፣ ከተደገነ ቀስት
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሰይፍ›› እና፣ ‹‹ቀስት›› የቴማን ነዋሪዎችን የሚያጠቁ ወታደሮችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሰይፍና በቀስት ከሚያጠቋቸው ጠላቶቻቸው››
ከጦርነት ሸክም
በጦርነቱ ጊዜ የሚደርስባቸው ሽብርና መከራ ሕዝቡ ላይ እንደ ተጫነ ከባድ ሸክም ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከጦርነት ሽብር››
Isaiah 21:16
በውል የተቀጠረ ሠራተኛ ቀን እንደሚቆጥር
‹‹በውል የተቀጠረ ሠራተኛ ዓመቱን እንደሚቆጥር›› አንድ የቅጥር ሠራተኛ በሥራ ባሳለፈው ጊዜ መሠረት እንዲከፈለው ተጠንቅቆ ጊዜ ይቆጥራል። ይህም ማለት በአንድ ዓመት ውስጥ ቄዳር ድል ትሆናለች ማለት ነው።
የቄዳር
ይህ ዐረቢያ ውስጥ ያለ አካባቢ ነው። ቄዳር የቄዳርን ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የቄዳር ሕዝብ››

---

Chapter 22
Isaiah 22:1
ንግር
‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ የያህዌ መልእክት ነው››
ስለ ራእይ ሸለቆ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሸለቆ›› በሸለቆ ውስጥ የሚኖር ሕዝብን ማለት ኢየሩሌምን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በራእይ ሸለቆ ውስጥ ስለሚኖሩ ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹በኢየሩሳሌም ስለሚኖሩ ሰዎች››
ሁላችሁም ወደ ቤቱ ሰገነት የወጣችሁበት ምክንያት ምንድነው?
ኢሳይያስ ጥያቄውን ያቀረበው በይሁዳ ሕዝብ ላይ ለማፌዝ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ ቤታችሁ ሰገነት ወጥታችሁ እዚያ መቆም የለባችም››
ጫጫታ የሞላባት ከተማ
‹‹ግብዣ ላይ ያሉ ሰዎች ሁካታ››
የተገደሉብህ ሁሉም በሰይፍ አልተገደሉም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝብህን የገደሉ የጠላት ወታደሮች አይደሉም››
በሰይፍ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሰይፍ›› ጦርነት ላይ ያሉ ወታደሮችን ይወክላል።
Isaiah 22:3
ቀስት እንኳ ሳያነሡ ተይዘዋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌላው ቀርቶ ቀስት እንኳ ያልያዙ መሪዎችህን ጠላት ማርኮአቸዋል››
ሁሉም በአንድነት ተያዙ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላት ሁሉንም በአንድነት ያዛቸው››
ስለዚህ እንዲህ አልሁ
‹‹እኔ›› የሚለው የሚያመለክተው ኢሳይያስን ነው።
ስለ ሕዝቤ ሴት ልጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሴት ልጅ›› የሚወክለው ሕዝቡን ሲሆን፣ ምናልባትም ኢሳይያስ ለእነርሱ ያለውን ፍቅር የሚያሳይ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለምወዳቸው ሕዝቤ›› ወይም፣ ‹‹ስለ ሕዝቤ››
Isaiah 22:5
ቀን አለው
‹‹ጊዜ ይኖረዋል››
የመጯጯህ፣ የመረገጥ፣ ከሰራዊት ጌታ ያህዌ ዘንድ የሆነ ግራ የመጋባት
‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ ሽብር፣ መረገጥና ግራ መጋባት ሲያደርግ››
መረገጥ
ይህም ማለት፣ 1) የሚገሠግሡ ወታደሮችን ሊያመለክት ይችላል ወይም 2) ከሽብር የተነሣ ወዴት እንደሚሄዱ እንኳ ሳያውቁ የሚሮጡ ሰዎችን ሊያመለክት ይችላል።
በራእይ ሸለቆ ውስጥ
ይህ የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው። ኢሳይያስ 22፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
ወደ ተራሮች የሚጮኹ ሰዎች
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ተራሮች ላይ ያሉ ሰዎች ጩኸታቸውን ይሰማሉ›› ወይም 2) ‹‹የሕዝቡ ጩኸት ከተራሮች ያስተጋባል››
ኤላም የፍላጻ ሰገባ ወሰደች
ሰገባ ፍላጻዎች የሚያዙበት ኮሮጆ ሲሆን፣ የቀስተኛውን መሣሪያ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኤላም ሰዎች ቀስትና ፍላጻዎቻቸውን ወሰዱ››
ቂር ጋሻዋን አነገበች
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቂር›› ወታደሮቹን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የቂር ወታደሮች ጋሻዎቻቸውን ከመያዣዎቻቸው ያወጣሉ››
ቂር
ቂር ሜዶን ውስጥ ያለች ከተማ ናት።
መልካሞቹ ሸለቆዎቻችሁ
እዚያ ላይ፣ ‹‹የእናንተ›› የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ይወክላል። ኢሳይያስ ከኢየሩሳሌም ነዋሪዎች አንዱ ስለሆነ ራሱንም ይጨምራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መልካም ሸለቆዎቻችን››
Isaiah 22:8
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ሰራዊት የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ስለሚያጠቃበት ወደ ፊት ስላለው ጊዜ መናገሩን ቀጥሏል። የኀላፊ ጊዜ የወደ ፊት ጊዜ ተደርጐ መተርጐም ይችላል።
የይሁዳን መከላከያ ወሰደ
‹‹መከላከያ›› የሚለውን የነገር ስም ግሥ አድርጐ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የይሁዳን ሕዝብ የከለለውን ማንኛውንም ነገር ወስዷል››
በዚያ ቀን የጦር መሣሪያ ተመለከትህ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ተመለከትህ›› የሚለው በአንዳች ነገር መተማመን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለራስህ ለመከላከል መሣሪያ ታገኛለህ››
የዱር ቤተ መንግሥት
ይህ የጦር መሣሪያ የሚያከማቹበት በኢየሩሳሌም የነበረው ቤተ መቅደስ አካል የነበረ ቤት ነው።
በታችኛው ኩሬ ውሃ አጠራቀምህ
ጠላቶች ከተማቸውን ሲከቡ የሚጠጡት በቂ ውሃ እንዲያገኙ ሕዝቡ ውሃ ያጠራቅማሉ።
Isaiah 22:10
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ሰራዊት የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ስለሚያጠቃበት ወደ ፊት ስላለው ጊዜ መናገሩን ቀጥሏል።
ቤቶችን ቆጠርህ
እዚህ ላይ ‹‹ቆጠርህ›› ማለት የከተማዋን ቅጥር ለመሥሪያ የሚሆን ነገር ለማግኘት ቤቶችን ማሰስን ያመለክታል።
የውሃ ማከማቻ ሠራችሁ
‹‹ማጠራቀሚያ ቦታ ሠራችሁ››
በሁለቱ ቅጥሮች መካከል
ኢሳይያስ ስለ የትኞቹ ሁለት ቅጥሮች እየተናገረ እንደሆነ ግልጽ አይደለም። ዋናው በከተማዋ ቅጥር ማከማቻ መሥራታቸው ነው።
የከተማዋ ሠሪ
ይህ የሚያመለክተው ያህዌን ነው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Isaiah 22:12

የሰራዊት ጌታ ያህዌ

ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ጠጕራችሁን እንድትላጩ

ይህ የልቅሶና የንስሐ ምልክት ነው።

እንብላ እንጠጣ፤ ነገ እንሞታለንና

እዚህ ላይ፣ ‹‹እንብላ እንጠጣ›› ድግስ ማድረግን፣ አለቅጥ መብላትንና ወይን ጠጅ መጠጣትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኛም የምንፈልገውን ያህል እየበላንና እየጠጣን አሁን ደስ ይበለን፤ ምክንያቱም በቅርቡ እንሞታለንና››

ይህን በጆሮዬ የገለጠ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ነው

‹‹ጆሮ›› የኢሳይያስን ሁለንተና ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህን የገለጠልኝ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ነው››

ይህ ኀጢአት እስክትሞቱ ድረስ አይሰረይላችሁም

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌላው ቀርቶ በምትሞቱበት ቀን እንኳ ቢሆን፣ ያደረጋችሁትን ኀጢአት ይቅር አልላችሁም››

ስትሞቱ እንኳ

ይህም ማለት፣ 1) ከሞቱ በኃላ እንኳ ያህዌ ይቅር አይላቸውም ወይም 2) እስኪሞቱ ድረስ ያህዌ ይቅር አይላቸውም።

Isaiah 22:15

ሳምናስ

ይህ በኢየሩሳሌም ያለው የንጉሡ ቤተ መንግሥት መልእክተኛ ነው።

የቤቱን ኀላፊ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ቤቱ›› በንጉሡ ቤተ መንግሥት ያሉትን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በንጉሡ ቤተ መንግሥት ለሚሠሩት ሁሉ ኀላፊ የሆነው››

እዚህ ምን ታደርጋለህ የፈቀደልህስ ማን ነው… ዐለት ውስጥ?

ያህዌ ይህን የሚጠይቀው ሳምናስ ላይ ለማፌዝ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐለቱ ውስጥ… ምንም መብት የለህም!››

መቀበሪያ እንድትወቅር… መቃብር እንድትጠርብ… ማረፊያ ቦታ እንድትጠርብ

ሦስቱም ሐረጐች የሚያመለክቱት መቃብር መሥራትን ነው።

ከፍታዎች ላይ

እስራኤል ውስጥ ታላላቅ ሰዎች ከፍታ ቦታ ላይ መቃብር ይሠሩ ነበር።

Isaiah 22:17

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ለሳምናስ የእግዚአብሔርን መልእክት መናገር ቀጥሏል።

አዙሮ አዙሮ እንደ ኳስ አጡዞ ወደ ሰፊ አገር ይወነጭፍሃል

የጠላት ወታደሮች መጥተው ሳምናስን በምርኮ ወደ ሌላ አገር መውሰዳቸው ያህዌ እንደ ኳስ ወደ ሌላ አገር እርሱን መወርወር ተደርጐ ተነግሯል።

ለጌታህ ቤት ማፈሪያ ትሆናለህ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ቤት›› ንጉሡ ቤተ መንግሥት ውስጥ የሚሠሩ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታህ ቤተ መንግሥት ውስጥ ላሉት ሁሉ እፍረት ታመጣለህ››

ከማእረግህ አወርድሃለሁ፤ ከኀላፊነትህም ትባረራለህ ወደ ታች ትጐተታለህ

ያህዌ ሳምናስን ቤተ መንግሥት ውስጥ እንዳይሠራ ማድረጉ ያህዌ እርሱን ወደ መሬት መወርወሩ እንደሆነ ተነግሯል።

ወደ ታች ትጐተታለህ

ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከክብር ቦታህ ወደ ታች አወርድሃለሁ››

Isaiah 22:20

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ለሳምናስ የእግዚአብሔርን መልእክት መናገሩን ቀጥሏል።

በዚያ ቀን ይመጣል

‹‹ይህ በዚያ ቀን ይሆናል››

ኤልያቄም… ኬልቅያስ

እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው

መጐናጸፊያህን አለብሰዋለሁ፤ መታጠቂያህንም አስታጥቀዋለሁ

ያህዌ ኤልያቂም ቤተ መንግሥት ውስጥ የሳምናስን ቦታ እንዲወስድ ማድረጉ ቤተ መንግሥት ውስጥ ሥልጣኑን የሚወክለውን የሳምናስን ልብስ ለኤልያቄም ማልበስ እንደሆነ ተናግሯል።

መጐናጸፊያህን… መታጠቂያህን

እዚህ ላይ፣ መጐናጸፊያና መታጠቂያ ቤተ መንግሥት ውስጥ ሥልጣንን ያመለክታሉ።

መታጠቂያ

ይህ ሰዎች ወገባቸው ላይ ወይም ደረታቸው ላይ የሚያደርጉት የልብስ ዐይነት ነው። ኢሳይያስ 3፥20 ላይ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።

በእጁ

‹‹እጅ›› ኀይልና ቁጥጥርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእርሱ››

እርሱ አባት ይሆናል

አልያቄም ለይሁዳ ሕዝብ ማሰቡና መጠንቀቁ እርሱ አባታቸው እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ እንደ አባት ይሆናል››

ለይሁዳ ቤት

እዚህ ላይ፣ ‹‹ቤት›› ሕዝብን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለይሁዳ ሕዝብ››

የዳዊትን ቤት መክፈቻ በትከሻው ላይ አደርጋለሁ… ማንም አይከፍትም

እዚህ ላይ ‹‹ቁልፍ›› የሚወክለው ሥልጣንን ነው። ማንም የማይከፍተው ወይም ማንም የማይዘጋው የቤተ መንግሥቱ መክፈቻ እንዳለው ሁሉ ይህም ኤልያቂም ማንም የማይቃወመው ሥልጣን እንዳለው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤተ መንግሥቱ ውስጥ በሚሠሩት ላይ ኀላፊነት እሰጠዋለሁ፤ የሚያደርገውን ውሳኔ ማንም መቃወም አይችልም።››

Isaiah 22:23

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ሳምናስን ስለሚተካው ኤልያቂም መናገሩን ቀጥሏል።

በአስተማማኝ ስፍራ እንደ ካስማ እተክለዋለሁ

ያህዌ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ የኤልያቂምን ሥልጣን ጠንካራና አስተማማኝ ማድረጉ አልያቄም ካስማ እንደሆነ፣ ያህዌ ደግሞ ቤተ መንግሥቱ ቅጥር ውስጥ ጠንካራ ቦታ ላይ እንደሚተክለው ተነግሯል።

ለአባቱም ቤት የክብር ማኅተም ይሆናል

‹‹የክብር ማኅተም›› የክብርን ቦታ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልያቂም ለቤተ ሰቡ ክብር ያመጣል››

የአባቱ ቤት

‹‹ቤት›› የሚወክለው ቤተ ሰብን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአባቱ ቤተ ሰብ›› ወይም፣ ‹‹የእርሱ ቤተ ሰብ››

የአባቱን ቤት ክብር ሁሉ እርሱ ላይ ይሰቅላሉ

ከአልያቂም የተነሣ ያህዌ መላው የአልያቂም ቤተ ሰብ እንዲከበር ማድረጉ አልያቂም ካስማ ቤተ ሰቡ ደግሞ እዚያ ካስማ ላይ የሚሰቀሉ ነገሮች እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእርሱ የተነሣ ለቤተ ሰቡ ክብር ይሰጣሉ››

ከማሰሮ ጀምሮ እስከ ጋን ድረስ ያለ የቤት ዕቃ ሁሉ

ይህ እየተናገረ ያለው ስለ ኤልያቂም ካስማ ነው። ቤተ ሰቡ ካስማ ላይ እንደሚሰቀሉ ማሰሮና ጋኖች ይሆናሉ። ይህም ከእርሱ የተነሣ ዘሮቹ ይከበራሉ ማለት ነው።

ከማሰሮ እስከ ጋን

ማሰሮ ውሃ የሚይዝ ትንሽ ዕቃ ነው፤ ጋን ውሃ የሚይዝ ትልቅ ዕቃ ነው።

Isaiah 22:25

አጠቃላይ መረጃ

ይህ ያለፈው ቁጥር ቀጣይ ምስላዊ ገለጻ ነው። (ኢሳይያስ 22፥23-24 ይመ.)

በዚያ ቀን

‹‹በዚያ ጊዜ››

ይህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ቃል ነው

የተናገረውን እርግጠኝነት ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 14፥22 ላይ እንደ ተረጐምህ ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ የሰራዊት ጌታ የያህዌ ዐዋጅ ነው››

በአስተማማኝ ስፍራ የተተከለ ካስማ… ተሰብሮ ይወድቃል

ያህዌ ሳምናስ ቤተ መንግሥት ውስጥ የነበረውን ሥልጣን እንዲያጣ ማድረጉ ሳምናስ ግድግዳ ላይ እንዳለና ተሰብሮ እንደሚወድቅ ካስማ እንደሆነ ተነግሯል። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ሳምናስ ሥልጣኑ አስተማማኝ እንደ ሆነ ማሰቡንና እግዚአብሔር ግን ያንን የሚያስወግድ መሆኑን ነው።

የተሸከመውም ሸክም ወድቆ ይከሰከሳል

እዚህ ላይ፣ ‹‹ሸክም›› የሳምናስን ኀይልና ሥልጣን ይወክላል። ሳምናስን የሚወክለው ካስማ ላይ በተሰቀለ ነገር ተመስሎአል። ያህዌ ሳምናስ ኀይልና


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሥልጣኑን እንዲያጣ ማድረጉ፣ ካስማው ላይ ተንጠልጥሎ የነበረው ዕቃ ወድቆ
መስበር ማለት እንደሆነ ተነግሯል።

Chapter 23

Isaiah 23:1

አጠቃላይ መረጃ

በ13፡1-23፡18 ኢሳይያስ እግዚአብሔር በሕዝቦች ላይ እንዴት እንደሚፈርድ መናገሩን ይቀጥላል።

ስለ ጢሮስ የተነገረ መግለጫ

"እግዚአብሔር ስለ ጢሮስ የተናገረው ይህ ነው'

የተርሴስ መርከቦች ሆይ አልቅሱ

በዚህ ስፍራ መርከቦች የሚለው በመርከቦች ላይ ያሉትን ሰዎች ይወክላል። ኢሳይያስ ሊሰሙት የሚችሉ ይመስል በተርሴስ መርከቦች ላይ ላሉ ሰዎች ይናገራል። አት፡- "እናንተ በተርሴስ መርከቦች ላይ ያላችሁ ሰዎች ተስፋ በመቁረጥ አልቅሱ' (ምትክ ስምና የ "የ' ምልክት ተመልከት)

ወደብ (ደሴት)

ቅርብ መሬትና ለመርከቦች ምቹ የሆነ የባሕር አካባቢ ነው።

ከኪቲም አገር ጀምሮ ተገልጦላቸዋል

ይህ ሀረግ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "ሰዎቹ በኪቲም ምድር እያሉ ስለ ጢሮስ ሰሙ' (የስሞች አተረጓጎም መንገድ እና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

እናንተ በባሕር ዳር የምትኖሩ ጸጥ በሉ

ኢሳይያስ ሊሰሙት የሚችሉ ይመስል በባሕር ዳር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ይናገራል። (የ "የ' ምልክት ተመልከት)

ጸጥ በሉ

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። በዚህ ስፍራ ጸጥታ ማለት ድንጋጤንና መደነቅን ማመልከት ነው። አት፡- "ደንግጡ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ባሕር ዳር

"ባሕር ዳር' በባሕር ወይም በውቅያኖስ አቅራቢያ ወይም ዙሪያ የሚገኝ መሬት ነው። በዚህ ስፍራ ከሜዲትራኒያን ባሕር ጋር በሚዋሰነው በፊንቂያ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል።

በባሕር ላይ የሚጓዝ፣ የሲዶና ነጋዴ የሞላባችሁ

በዚህ ስፍራ "ነጋዴ' ማለት ብዙ "ነጋዴዎች' ማለት ነው። አት፡- "በባሕር ላይ የሚጓዙ፣ የሲዶና ነጋዴዎች ባለጸጋ አደረጓችሁ' (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች)

የሺሖር ጥራጥሬ በብዙ ውኆች ላይ ነበር

ሺሖር በጥራጥሬ ምርቱ የሚታወቅ በግብጽ በዓባይ ወንዝ አቅራቢያ የሚገኝ ሸለቆ ስም ነው። አት፡- "በግብጽ ከሺሖር ጥራጥሬ ለማጓጓዝ በታላቅ ባሕር የሚጓዙ ሰዎች' (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

የዓባይ መከር ምርቷ ነበር

"የዓባይ መከር' በዓባይ ወንዝ አቅራቢያ የሚመረትንና በወንዝ ላይ ወደ ፊንቄ የሚጓጓዝን ጥራጥሬ ያመለክታል። (ንብረት ተመልከት)

ምርቷ

"የእርሱ ምርት።' ወንዙ የእርሷ እንደሆነ ማመልከት የተለመደ ነበር።

የአሕዛብ መናገጃ ነበረች

ንግድ ነገሮችን የመግዛትና የመሸጥ እንቅስቃሴ ነው። በዚህ ስፍራ "አሕዛብ' የሚለው ሰዎቹን ይወክላል። አት፡- "አንተ ከሌሎች ሕዝቦች የሆኑ ሰዎች ነገሮችን ለመግዛትና ለመሸጥ በሚመጡበት ስፍራ ነበርክ።' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 23:4

ወጣት ሴቶችን አላሳደግሁም... ሲል ባሕር፣ የባሕሩ ኃያል ተናግሮአል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) እግዚአብሔር የጢሮስን ከተማ፣ በከተማይቱ የሚኖሩ ሰዎችን በሚመለከት ልጆቿ እንደሆኑ አድርጎ እንደምትናገር እናት ይገልጻታል ወይም 2) እግዚአብሔር የሜዲትራንያን ባሕር እየተናገረ እንዳለ እየገለጸ ነው። የጢሮስ ሰዎች ባሕሩን አምላካቸውና አባታቸው አድርገው ይመለከቱ ነበር። በሁለቱም ትርጉሞች ተናጋሪው ልጆቹ ስለ ጠፉ ያለቅሳል። (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

Isaiah 23:6

ወደ ተርሴስ ተሻገሩ

"ጉዞአችሁን ወደ ተርሴስ አድርጉ።' ተርሴስ፣ የጢሮስ ሰዎች ለንግድ ጉዞ የሚያደርጉባት ሩቅ ቦታ ነች። ከጢሮስ ላመለጡ ብቸኛ የድኅንነት ቦታ ነች።

በቀድሞ ዘመን ተመሥርታ የነበረችው፣ ... ደስተኛይቱ ከተማ፣ ይህ ደረሰባትን

እግዚአብሔር በጢሮስ ላይ ለመሳለቅ ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በአሳብ ገላጭ አረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "ለመደላደል ... በጥንታዊቷ የጢሮስ ከተማ በሙሉ ደስታ የምትኖሩ በእርግጥ ይህ ይደርስባችኋል' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ደስተኛይቱ ከተማ

በዚህ ስፍራ "ከተማ' የሚለው ሕዝቡን ይወክላል። አት፡- "በጢሮስ ከተማ የሚኖር ደስተኛ ሕዝብ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ለመደላደል እግሮችዋ ወደ ሩቅ ወደ እንግዳ ሥፍራዎች የወሰዷት

በዚህ ስፍራ "እግር' መላውን የሰው ማንነት ይወክላል። አት፡- "ለመኖርና ገንዘብ ለማትረፍ ወደ ሩቅ ስፍራዎች የሄዱ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ወደ ሩቅ ... የወሰዷት

በዚህ ስፍራ "የወሰዷት' የሚለው የጢሮስን ሕዝብ የምትወክለውን የጢሮስን ከተማ ያመለክታል። (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 23:8

በጢሮስ ላይ ይህን ያቀደ ማነው? ... የምድር

ኢሳይያስ በጢሮስ ላይ ለመሳለቅ ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። "ይህን' የሚለው ቃል ኢሳይያስ በ23፡1-7 የገለጸውን ጢሮስን ለማጥፋት የተዘጋጀውን የእግዚአብሔር እቅድ ያመለክታል። እንዲሁም ጢሮስ የሚለው በጢሮስ የሚነሩትን ሰዎች ያመለክታል። ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በአሳብ ገላጭ አረፍተ ነገርነት ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "የጢሮስን ሰዎች ለማጥፋት ያቀደው እግዚአብሔር ነበር ... የምድር' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና ምትክ ስም ተመልከት)

ዘውዶችን ሰጪ

በዚህ ስፍራ "ዘውድ' የሚለው አንድ ሰው እንደ ገዢ በሕዝብ ላይ ያለውን ሥልጣን ያመለክታል። አት፡- "በሌሎች ላይ እንዲገዙ ለሰዎች ሥልጣንን የሚሰጥ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ነጋዴዎቿ ልዑላን ናቸው

ወደ ሌሎች አገሮች ሲሄዱ ምን ያህል ሥልጣን እንዳላቸው በአጽንዖት ለመናገር ነጋዴዎቹ ከልዑላን ጋር ተነጻጽረዋል። አት፡- "ነጋዴዎቿ እንደ ልዑላን ናቸው' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ነጋዴዎቿ ... የምድር ክቡራን ናቸው

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "የምድር ሕዝቦች እጅግ ከፍተኛ ክብር የሚሰጡአቸው ነጋዴዎቿ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ክብሯን ሁሉና ትዕቢቷን ለማዋረድ

"በገዛ ራሳቸው ክብር ስለሚመኩ እነርሱን ለማዋረድ'

ትዕቢቷ ... ክብሯ ... ክቡራኖቿ

በዚህ ስፍራ እርሷ የሚለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች የምትወክለውን የጢሮስን ከተማ ያመለክታል። አት፡- "ትዕቢታቸው ... ክብራቸው ... ክቡራኖቻቸው' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 23:10

የተርሴስ ሴት ልጅ፣ ሰው አባይን እንደሚያርስ፣ መሬትሽን እረሺ። ከእንዲህ ወዲያ በጢሮስ የገበያ ስፍራ አይኖርም

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ከእንግዲህ ወዲያ ከጢሮስ ጋር መነገድ ስለማይችሉ የተርሴስ ሰዎች እህል መዝራት እንዲጀምሩ ኢሳይያስ እየነገራቸው ነው ወይም 2) የተርሴስ ሰዎች ከጢሮስ ቁጥጥር ነፃ መሆናቸውን ኢሳይያስ እየነገራቸው ነው። አት፡- የተርሴስ ልጅ ሆይ፣ እንደ ወንዝ በአገርሽ ያልፋል። የጢሮስ ሰዎች ከእንግዲህ ወዲያ ምንም ሥልጣን አይኖራቸውም። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

የተርሴስ ሴት ልጅ

የከተማይቱ ሴት ልጅ የከተማይቱን ሰዎች ትወክላለች። አት፡- "የተርሴስ ሕዝብ' ወይም "በተርሴስ የሚኖሩ ሰዎች' (ምትክ ስም ተመልከት)

እግዚአብሔር በባሕር ላይ እጁን ዘረጋ፣ መንግሥታትን አናወጠ

ባሕርንና የኃያል መንግሥታን ሕዝቦች ለመቆጣጠር እግዚአብሔር ኃይሉን መጠቀሙ እግዚአብሔር እጅን እንደሚዘረጋና መንግሥታትን እንደሚያናውጥ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በባሕር ላይ እጁን ዘረጋ
በዚህ ስፍራ እጅ የእግዚአብሔርን ኃይልና ቁጥጥር ያመለክታል። አት፡- "በባሕር ላይ ኃይሉን አሳየ' (ምትክ ስም ተመልከት)
የተጨቆነሽ የሲዶና ድንግል ሴት ልጅ ሆይ
በዚህ ስፍራ ድንግል ሴት ልጅ የሲዶናን ሕዝብ ያመለክታል። አት፡- "የሲዶና ሕዝብ ሆይ፣ ሌላ ሕዝብ ስለሚጨቆናችሁ' (ምትክ ስም ተመልከት)
Isaiah 23:13
የከለዳውያንን አገር ተመልከቱ
ከለዳውያን በዚህ ስፍራ የባቢሎናውያን ሌላ ስም ነው። አት፡- "በባሎናውያን አገር ምን እንደሆነ ተመልከቱ' ወይም "በባቢሎን ምን እንደሆነ ተመልከቱ'
ከባቢ ግንቦች
በከተማ ግንቦች ላይ በመሆን ለማጥቃት ወታደሮች ግንቦችን ወይም የጭቃ መወጣጫዎችን ይገነባሉ።
እናንተ የተርሴስ መርከቦች አልቅሱ
በዚህ ስፍራ መርከቦች የሚለው በመርከብ ላይ ያሉትን ሰዎች ይወክላል። ይህንን በኢሳይያስ 23፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (ምትክ ስም ተመልከት)
ምሽጋችሁ ፈርሷልና
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ጠላቶች ምሽጋችሁን አፍርሰዋልና' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
Isaiah 23:15
በዚያ ቀን
"በዚያ ጊዜ' ወይም "በመቀጠል'
ጢሮስ ለሰባ ዓመት የተረሳች ትሆናለች
ከእንግዲህ ወዲያ ለመግዛትና ለመሸጥ ሕዝቡ ወደ ጢሮስ የማይሄድ እስከሆነ ድረስ፣ ከተማይቱን የመርሳት ያህል ነው። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ለሰባ ዓመታት ሕዝቡ ጢሮስን የመርሳት ያህል ይዘነጋታል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ለሰባ ዓመታት
"ለ70 ዓመታት' (ቁጥሮች ተመልከት)
እንደ አንድ ንጉሥ ዘመን
"እንደ አንድ ንጉሥ ዓመታት' ወይም "አንድ ንጉሥ የሚኖርበትን ያህል'
በጋለሞታ ዘፈን እንደሚሆን እንዲሁ ይሆናል
ይህ የጢሮስ ሰዎች ጋለሞታ እንደነበሩ አይነት መስሎ ይናገራል። ታዋቂነቷን ያጣች ጋለሞታ የቀድሞ ፍቅረኞቿን እንደገና ለማግኘት በየመንገዱ እንደምተዘፍን፣ የጢሮስ ሰዎች እንደገና ባላጸጎችና ኃያላን ይሆኑ ዘንድ ንግዱን ለማስቀጠል ከሌሎች ሕዝቦች ወደ እነርሱ የሚመለሱ ሰዎችን ለማግኘት የጢሮስ ሰዎች ጥረት ያደርጋሉ። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ትታወሺ ዘንድ
ይህ በአደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሰዎች ያስታውሱሽ ዘንድ' ወይም "ሰዎች ወደ አንቺ ይመለሱ ዘንድ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
Isaiah 23:17
በኋላም እንዲህ ይሆናል
አንድ አስፈላጊ ሁኔታ ሊሆን እንዳለ ለማመልከት ይህ ሐረግ በዚህ ስፍራ ጥቅም ላይ ውሏል። ቋንቋህ ይህን የሚያደርገበት መንገድ ካለው በዚህ ስፍራ ልትጠቀምበት ትችላለህ።
ሰባ ዓመታት
"70 ዓመታት' (ቁጥሮች ተመልከት)
እግዚአብሔር ጢሮስን ይጎበኛታል
በዚህ ስፍራ ጢሮስ የሚለው በጢሮስ የሚኖረውን ሕዝብ ይወክላል። አት፡- "እግዚአብሔር በጢሮስ የሚኖረውን ሕዝብ ይጎበኛል' (ምትክ ቃል ተመልከት)
ከምድር ... የግልሙትናን ሥራ በመሥራት እንደገና ገንዘብ ማትረፍ ትጀምራለች
ኢሳይያስ የጢሮስን ሕዝብ ከጋለሞታ ጋር ያመሳስላል። ጋለሞታ ለገንዘብ ስትል ለማንኛውም ወንድ ራሷን እንደምትሸጥ እንደዚያው የጢሮስም ሕዝብ ከ(ለ)ሁሉም መንግሥታት ይገዛሉ ይሸጣሉ። አት፡- እንደጋለሞታም ከምድር መንግሥታት ሁሉ ጋር ይገዛሉ ይሸጣሉም። (ምትክ ቃል ተመልከት)
በግምጃ ቤት አይከማችም ወይም አይጠበቅም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ነጋዴዎቹ ገንዘባቸውን ሰውረው አያከማቹም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
በእግዚአብሔር ፊት ለሚኖሩ
"እግዚአብሔርን ለሚታዘዙና ለሚያገለግሉ'
የተትረፈረፈ ምግብ ለእነርሱ ለማቅረብ
"የሚመገቡት በቂ ምግብ ይኖራቸው ዘንድ'

---

Chapter 24
Isaiah 24:1
ምድርን ባዶ ለማድረግ
"ምድርን ባድማ ለማድረግ' ወይም "በምድር ያለውን ነገር ሁሉ ለማጥፋት'
እነሆ
ይህ ቃል አስፈላጊ ሁናቴን ያመላክታል። ቋንቋህ ይህን የሚያደርግበት መንገድ ካለው፣ በዚህ ስፍራ ለመጠቀም ልታጤነው ትችላለህ።
እንደ ... እንዲሁ
እግዚአብሔር ሊያደርገው ያለው ነገር አልተገለጸም፣ ነገር ግን ይታወቃል። ይህ እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ እንደሚመለከት ያሳያል። አት፡- "እግዚአብሔር እንደሚበትን ... እንዲሁ ይበትናል' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ)
ካህኑ ... አራጣ ተቀባዩ
ኢሳይያስ በ24፡2 የተወሰኑ የሕዝቡን የመደብ ክፍሎች ይዘረዝራል። በዩዲቢ እንደሚገኘው በብዙ ቁጥር ስሞች ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ካህናቱ ... አራጣ ተቀባዮቹ' (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች)
አራጣ ተቀባዩ
"ገንዘብ ያበደረው።' አራጣ ማለት አንድ ሰው ገንዘብ ስለተበደረ ሊከፍለው የሚገባ ተጨማሪ ገንዘብ ማለት ነው።
አራጣ ከፋዩ
"ገንዘብ የተበደረው'
Isaiah 24:3
ምድር ፈጽማ ትጠፋለች፣ ትገፈፋለችም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ምድርን ፈጽሞ ያጠፋታል፣ የከበረውንም ነገር ሁሉ ያስወግዳል።' (አጓዳኝነት ተመልከት)
እግዚአብሔር ይህን ቃል ተናግሮአል
"እግዚአብሔር ይህን አደርጋለሁ አለ'
ምድር ደረቀች ጠወለገችም፣ ዓለም ደረቀች ከሰመችም
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሃረጎች ተመሣሣይ ነገር ይናገራሉ። አት፡- በምድር ያለ ነገር ሁሉ ይደርቃል ይሞታልም (አጓዳኝነት ተመልከት)
ምድር ... ዓለም
ሁለቱም በምድር ላይ ያለውን ነገር ሁሉ ይወክላሉ። (ምትክ ስም ተመልከት)
ምድር በነዋሪዎቿ ረክሳለች
ሕዝቡ ኃጢአት መሥራታቸውና ምድር በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራት ማድረጋቸው ሕዝቡ ምድርን በተጨባጭ እንድትቆሽሽ እንዳደረጓት ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሕዝቡ ምድርን አረከሷት' (ስዕላዊ ንግግር፣ አደራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ሕግጋቱን ጥሰዋል፣ ሥርዓቱን ተላልፈዋል፣ የዘላለሙንም ኪዳን አፍርሰዋል
የእግዚአብሔርን ሕግጋትና ሥርዓት አልታዘዙም፣ የእግዚአብሔርንም ዘላለማዊ ኪዳን አፍርሰዋል
Isaiah 24:6
አጠቃላይ መረጃዎች
ኢሳይያስ እግዚአብሔር በምድር ላይ በሚፈርድበት ጊዜ የሚሆነውን የወደፊቱን ጊዜ መግለጹን ቀጠለ። አንዳንድ ጊዜ ነቢያት የወደፊቱን ጊዜ ሁኔታ ባላፊ ወይም በአሁን ጊዜ እንደሆነ ነገር አድርገው ይገልጻሉ። ይህ ሁኔታው በእርግጥ እንደሚፈጸም አጽንዖት ይሰጣል። (ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)
እርግማን ምድርን ትበላለች
የእግዚአብሔር ምድርን መርገምና ማጥፋት ምድርን ፈጽሞ እንደሚበላ የዱር አውሬ ወይም ምድርን ፈጽሞ እንደሚያቃጥል እሳት ዓይነት እንደሆነ እንደ መርገም ተደርጎ ተነግሮአል። (ሥዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ነዋሪዎቿ በደለኞች ሆነው ተገኝተዋል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዘአብሔር ሕዘቡ በደለኛ መሆኑን ያስታውቃል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 24:8

አጠቃላይ መረጃዎች፡-

ኢሳይያስ እግዚአብሔር በምድር ላይ በሚፈርደበት ጊዜ የሚሆነውን የወደፊቱን ጊዜ መግለጹን ቀጠለ። አንዳንድ ጊዜ ነቢያት የወደፊቱን ጊዜ ሁኔታ ባላፊ ወይም በአሁን ጊዜ እንደሆነ ነገር አድርገው ይገልጻሉ። ይህ ሁኔታው በእርግጥ እንደሚፈጸም አጽንዖት ይሰጣል። (ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

ከበሮ ... መሰንቆ

እነዚህ የሙዚቃ መሣሪያዎች ናቸው። እነዚህን በኢሳይያስ 5፡12 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

Isaiah 24:10

አጠቃላይ መረጃዎች፡-

ኢሳይያስ እግዚአብሔር በምድር ላይ በሚፈርደበት ጊዜ የሚሆነውን የወደፊቱን ጊዜ መግለጹን ቀጠለ። አንዳንድ ጊዜ ነቢያት የወደፊቱን ጊዜ ሁኔታ ባላፊ ወይም በአሁን ጊዜ እንደሆነ ነገር አድርገው ይገልጻሉ። ይህ ሁኔታው በእርግጥ እንደሚፈጸም አጽንዖት ይሰጣል። (ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

የትርምስዋ ከተማ ፈረሰች

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "የትርምስዋን ከተማ እግዚአብሔር ያፈርሳታል።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የትርምስዋ ከተማ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ጌታ እርሷን ከማፈርሱ በፊት ከተማይቱ በትርምስ ውስጥ ነበረች፤ ሕዝቡ እግዚአብሔርን አይታዘዙም ነበር፣ መንግሥቱ ምግባረ ብልሹ ነበር፣ ከተማይቱም በመጠጣትና በጭፈራ ተሞልታ ነበር ወይም 2) እግዚአብሔር ካፈረሳት በኋላ ከተማይቱ ትርምስ ውስጥ ገብታለች። በአንድ ወቅት ጠንካራና ረጃጅም ሆነው የተገነቡት ቅጥሮችና ሕንፃዎች አሁን መሬት ላይ ፍርስራሽ ሆነዋል። በሁለቱም ትርጉሞች አንዲት ከተማ ማለት አይደለም። በአጠቃላይ ከተሞችን ያመለክታል።

ቤት ሁሉ ዝግና ባዶ ነው

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "ሕዝቡ ቤቶቻቸውን ይዘጋሉ ባዷቸውንም ይተውአቸዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ስለ ወይን ጠጁ

"ወይን ጠጅ ስለሌለ'

ደስታ ሁሉ ጨልሞአል፣ የምድሪቱም ሐሴት ጠፍቶአል

የእነዚህ ሁለት ሃረጎች ትርጉም በመሠረቱ አንድ ነው። አት፡- "ደስታ ሁሉ ከምድር ይጠፋል' (አጓዳኝነት ተመልከት)

የምድሪቱ ሐሴት

በዚህ ስፍራ "ምድር' የምድርን ሕዝብ ይወክላል። (ምትክ ቃል ተመልከት)

Isaiah 24:12

አጠቃላይ መረጃዎች፡-

ኢሳይያስ እግዚአብሔር በምድር ላይ በሚፈርደበት ጊዜ የሚሆነውን የወደፊቱን ጊዜ መግለጹን ቀጠለ። አንዳንድ ጊዜ ነቢያት የወደፊቱን ጊዜ ሁኔታ ባላፊ ወይም በአሁን ጊዜ እንደሆነ ነገር አድርገው ይገልጻሉ። ይህ ሁኔታው በእርግጥ እንደሚፈጸም አጽንዖት ይሰጣል። (ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

ከተማይቱም ባድማ ሆናለች

ባድማ የሚለው የነገር ስም ሰው የማይኖርበት ወይም ባዶ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ከተማይቱ ሰው የማይኖርባት ሆነች' ወይም "ከተማይቱ ባዶዋን ቀረች' (የነገር ስም ተመልከት)

ከተማይቱ

ይህ የተወሰነ አንድ ከተማን ሳይሆን ከተሞችን በአጠቃላይ ነው። (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች ተመልከት)

የወይራን ዛፍ እንደ መምታት፣ ከወይንም መከር በኋላ ቃርሚያውን እንደ መልቀም

ይህ እግዚአብሔር ምድሪቱን ካጠፋት በኋላ፣ ሕዝቡን ፍሬያቸው ከተለቀመ ዛፎችና የወይን ተክሎች ጋር ያስተያያል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 24:14

ድምፃቸውን ያነሣሉ፣ ስለ እግዚአብሔርም ክብር ይጮኻሉ

ድምፃቸውን ያነሣሉ የሚለው ሃረግ ድምፅን ከፍ አድርጎ መናገር የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "ለእግዚአብሔር ክብር ይዘምራሉ ይጮኻሉም' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

... ያነሣሉ ... ይጮኻሉ

በዚህ ስፍራ ... ያነሣሉ ... ይጮኻሉ የሚለው እግዚአብሔር ምድርን ካጠፋት በኋላ ገና በሕይወት ያሉትን ያመለክታል።

በደስታ ከባሕር ይጮኻሉ

በዚህ ስፍራ "ባሕር' የሚለው ከእስራኤል በምዕራብ የሚገኘውን የሜዲትራንየንን ባሕር ያመለክታል። አት፡- "በምዕራብም ወደ ባሕሩ ሲል የሚኖሩ በደስታ ይጮኻሉ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ስለዚህ በምሥራቅ እግዚአብሔርን አክብሩ

በምሥራቅ የሚለው ሃረግ ከእስራኤል በስተ—ምሥራቅ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። ኢሳይያስ እነዚህ ሕዝቦች ከእርሱ ጋር እንዳሉ አድርጎ ያዝዛቸዋል። ነገር ግን የሚናገረው እግዚአብሔር ምድሪቱን ካጠፋ በኋላ ወደፊት ለሚኖሩት ሰዎች ነው። አት፡- "ስለዚህ በስተ ምሥራቅ በሩቅ ምድር የሚኖሩ ሁሉ እግዚአብሔርን ያከብራሉ' (ምትክ ቃል፣በስፍራው ለሌለ ወይም እንደ ሰው ለተወሰደ ግዑዝ ነገር መናገርና ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

በባሕር ደሴቶች ክብር ስጡ

ኢሳይያስ በሜዲትራንየን ደሴቶች ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ከእርሱ ጋር እንዳሉ አድርጎ ያዝዛቸዋል። ነገር ግን የሚናገረው እግዚአብሔር ምድሪቱን ካጠፋ በኋላ ለሚኖሩት ሰዎች ነው። አት፡- "በደሴቶች የምትኖሩ ሁሉ ክብር ስጡ' (ምትክ ቃል፣በስፍራው ለሌለ ወይም እንደ ሰው ለተወሰደ ግዑዝ ነገር መናገርና ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

ለእግዚአብሔር ስም

በዚህ ስፍራ ስም እግዚአብሔርን ይወክላል። አት፡- "ለእግዚአብሔር' (ምትክ ቃል ተመልከት)

Isaiah 24:16

ሰምተናል

በዚህ ስፍራ ሰምተናል የሚለው ኢሳይያስንና የእስራኤል ሕዝብን ያመለክታል። ኢሳይያስ ወደ ፊት ሊሆን ያለን ነገር ገና ቀድሞ እንደ ተፈጸመ አድርጐ ይገልጻል። አት፡- "እንሰማለን' (አካታች "እኛ' ና ትንቢታዊ አላፊ ጊዜ ተመልከት)

እኔ ግን ከሳሁ፣ ከሳሁ

ኢሳይያስ ለሐዘኑ አጽንዖት ለመስጠት ይህን ሃረግ ይደጋግማል። አት፡- "በእርግጥ፣ ያታለሉ አሁንም ሌሎችን እያታለሉ ናቸው' ወይም "በእርግጥ አታላዮች እያታለሉ ናቸው' (አጓዳኝነት ተመልከት)

Isaiah 24:17

በምድር ላይ የምትኖሩ ሆይ፣ ፍርሃት፣ ገደልና ወጥመድም በእናንተ ላይ ነው

"በምድር ላይ የምትኖሩ ሰዎች ፍርሃት፣ ገደልና ወጥመድ ይገጥማችኋል'

ከገደል .. በወጥመድ ይያዛል

በዚህ ስፍራ ገደልና ወጥመድ የሚሉት ሕዝቡ ላይ ሊሆኑ ያሉትን የተለያዩ ክፉ ነገሮች ይወክላሉ። ሰዎች አንድን ክፉ ነገር ለማምለጥ ይሸሻሉ ነገር ግን ሌላ ክፉ ነገር ይገጥማቸዋል። (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

የሽብር ድምጽ

"አስፈሪ ድምጽ'

በወጥመድ ይያዛል

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ወጥመዱ ይይዘዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የሰማይ መስኮቶች ይከፈታሉ

ይህ እግዚአብሔር የሰማይ መስኮትን እንደሚከፍትና በእርሱ አማካይነት ውኃ እንዲፈስስ እንደሚያደርግ ዓይነት ብዙ መጠን ያለው ዝንብ ከሰማይ እንደሚወርድ ይናገራል። አት፡- "ሰማይ ይከፈታል የዝናብም ዶፍ ይወርዳል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የምድር መሠረቶችም ይናወጣሉ

በተለምዶ "መሠረት' የሚለው ቃል ከሥር ሆኖ ለአንድ ሕንፃ ድጋፍ የሚሰጥን የድንጋይ ክፍል (መዋቅር) ያመለክታል። በዚህም ስፍራ ምድርን በቦታዋ ደግፎ ወይም ይዞ እንዳቆመ ይታሰብ የነበረን ተመሣሣይ መዋቅር ይገልፃል። ኢሳይያስ ምድርን ደግፎ የያዛት መዋቅር እንኳን ይናወጣል ይላል። አት፡- "በጣም በሚያስፈራ ሁኔታ ምድር ትናወጣለች' ወይም "በጣም የሚያስፈራ የምድር መንቀጥቀጥ ይሆናል'

Isaiah 24:19

ምድር ፈጽሞ ተሰባበረች፣ምድር ፈራረሰች፤ ምድር በኃይል ተነዋወጠች



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እነዚህ የተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሃረጎች በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጹ ይችላሉ። አት፡- "ምድር ትሰበባረለች ትለያያለችም፤ ምድር በኃይል ትናወጣለች' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ምድር እንደ ሰካር ሰው ትንገደገዳለች፣ እንደ ዳስም ትወዘወዛለች
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ምድር እንዴት ወደ ፊት ወደ ኋላ እንደ ምትናወጥ አጽንዖት ይሰጣል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
መተላለፍዋ ይከብድባታል፣ ትወድቅማለች ደግሞም አትነሣም
ይህ ምድር ሰው እንደሆነች መተላለፍዋም ከባድ እቃ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ሰውዬው ከባድ ሸክም ለመሸከም ይጥራል ነገር ግን ክብደቱ ሰውዬው እንዲወድቅና ዳግመኛ መነሣት እንዳይችል ያደርገዋል። በዚህ ስፍራ ምድር ከኃጢአታቸው የተነሣ እግዚአብሔር ምድርን እንዲያጠፋት ያደረጉትን የምድርን ሕዝብ ትወክላለች። አት፡- "የሕዝቡ ኃጢአት ብዙ ነው ስለዚህም እግዚአብሔር ምድርን ያጠፋታል፣ ምድርም የወደቀና ዳግመኛ መነሣት ያልቻለን ሰው ትመስላለች።' (ስዕላዊ ንግግርና ምትክ ስም ተመልከት)
Isaiah 24:21
በዚያም ቀን
"በዚያን ጊዜ'
የሰማይ ሠራዊት
ሠራዊት ሲል የጦር ሠራዊት ነው። በዚህ ስፍራ "የሰማይ ሠራዊት' የሚለው በሰማይ የሚገኙትን ብዙዎች ኃያላን መናፍስት ያመለክታል። ክፉዎች እንደሆኑ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አት፡- "ኃያላን አካላት' ወይም "ክፉ መንፈሳዊያን አካላት' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
በሰማያት
"በሰማይ
ግዞተኞች በጉድጓድ እንደሚከማቹ በአንድነት ይከማቻሉ
በዚህ ስፍራ "ጉድጓድ" የሚለው በወህኒ ቤት የሚገኝን ጨለማ ክፍል ወይም ጉድጓድ ያሳያል። አት፡- እግዚአብሔር እንደ እስረኞቹ በአንድ ላይ ይሰበስባቸዋል በወህኒውም እንደኛው ክፍል ይቆልፍባቸዋል። (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ይቀጣሉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ጨረቃ ያፍራል፣ ፀሐይም ይዋረዳል
ጨረቃና ፀሐይ ታላቅ ኃይል ካለው ሰው ፊት ከመሆኑ የተነሳ እንዳፈረ ሰው ተደርገው ተገልጸዋል። እግዚአብሔር ባለበት የጨረቃና የፀሐይ ብርሃን ይደበዝዛል። (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

---

## Chapter 25

Isaiah 25:1
ስምህን አመሰግናለሁ
በዚህ ስፍራ "ስም" እግዚአብሔርን ይወክላል። አት፡- "አንተን አመሰግናለሁ' (ምትክ ስም ተመልከት)
ከጥንት የታቀዱ ነገሮች
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ከጥንት ያቀድካቸው ነገሮች' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
በፍጹም ታማኝነት
"ታማኝነት' የሚለው የነገር ስም "ታማኝ' ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "አንተ ፍጹም ታማኝ ስለሆንክ' (የነገር ስም ተመልከት)
ከተማይቱ
ይህ አንድ የተወሰነ ከተማን የሚያመለክት አይደለም። ይህ ከተሞች በአጠቃላይ ማለት ነው። (አጠቃላይ ስማዊ ሃረጎች ተመልከት)
የባዕዳን ምሽጎች
"የውጪዎች የሆኑ ምሽጎች'
የጨካኝ ሕዝቦች ከተማ
በዚህ ስፍራ "ከተማ' እና "ሕዝቦች' የሚለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላሉ። (ምትክ ስም ተመልከት)
Isaiah 25:4
መጠጊያ ... መጠጊያ ... ከውሽንፍር መሸሸጊያ፣ ከሙቀትም ጥላ ሆነሃል
እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያደርገው ጥበቃ ሕዝቡ ወደ እርሱ ለመጠበቅና ለመጽናናት እንደሚሸሹበት ስፍራ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የጨካኞችም ቁጣ እስትንፋስ ቅጥርን እንደሚመታ ዐውሎ ነፋስ በሆነ ጊዜ
ጨካኝ ሕዝቦች በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚያደርሱትን ጭቆና ግንብን እንደሚመታ ዐውሎ ነፋስ ተደርጎ ተነግሮአል:: (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
እስትንፋሱ
"ንፋሱ' ወይም "ጩኸቱ'
የጨካኞች
ይህ ስማዊ አንቀጽ ነው። አት፡- "ጨካኝ ሕዝብ' ወይም "ጨካኞች የሆኑ' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)
በደረቅ መሬት እንደ ሙቀት
ይህ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጠላቶች ምድሪቱን ከሚያደርቅ ሙቀት ጋር ያመሳስላል። ይህ ጠላቶቹ ምን ያህል የእግዚአብሔርን ሕዝብ መከራ እንዲቀበል እንዳደረጉ አጽንዖት ይሰጣል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ሙቀትም በደመና ጥላ እንዲበርድ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ልክ ደመና ከላይ ሲያልፍ ሙቀትን እንደ ሚያቀዘቅዝ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
የጨካኞች ዝማሬ ይዋረዳል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ጨካኝ ሰዎችን ከመዘመር ታስቆማለህ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
Isaiah 25:6
በዚህ ተራራ ላይ
ይህ ኢየሩሳሌምን ወይም የጽንን ተራራ ያመለክታል።
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም
ይህንን በኢሳይያስ 1:9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
የሰቡ ነገሮች ... ግብዣ
በዚህ ስፍራ "የሰቡ ነገሮች' ማለት እጅግ የተመረጠ ምግብ ማለት ነው።
የአተላ የወይን ጠጅ ግብዣ
"ያረጀ ወይን ጠጅ።' ይህ ማለት እጅግ የተመረጠ ወይን ጠጅ ማለት ነው።
በሕዝቦች ሁሉ ላይ የተጣለውን መጋረጃ፣ በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተዘረጋውን መሸፈኛ
ሞት፣ መከራና ሐዘን በምድር ያለውን ሁሉ እንደሚሸፍን ጥቁር ደመና ወይም መረብ ተደርጎ ተነገሮአል። (ስዕላዊ ንግግርና አጓዳኝነት ተመልከት)
ሞትን ለዘላለም ይውጣል
እግዚአብሔር ሰዎችን ለዘላለም እንዲኖሩ ማድረጉ ሞትን እንደሚውጥ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የሕዝቡንም ስድብ ከምድር ሁሉ ያስወግዳል
እግዚአብሔር ሕዝቡን ዳግመኛ እንዳያፈር ማድረጉ ውርደት እግዚአብሔር እንደሚያስወግደው ግዑዝ ነገር ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 25:9
ይባላል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- ሰዎች ይላሉ (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
በዚያም ቀን
"በዚያን ጊዜ'
የእግዚአብሔር እጅ በዚህ ተራራ ላይ ታርፋለች
"እጅ' የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል። የእግዚአብሔር እጅ በዚህ ተራራ ላይ ታርፋለች ማለት ሕዝቡን ይጠብቃል ማለት ነው። አት፡- "የእግዚአብሔር ኃይል በዚህ ተራራ ላይ ይሆናል' ወይም "በጽዮን ተራራ ላይ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይጠብቃል' (ምትክ ስም እና ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ጭድም በጭቃ ውስጥ እንደሚረገጥ እንዲሁ ሞዓብ በስፍራው ይረገጣል
የእግዚአብሔር የሞዓብን ሕዝብ ማጥፋት እንደሚረግጣቸውና እንደሚያድቅቃቸው ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ ሰዎች ገለባን ከጭቃ ጋር ለመደባለቅ ከሚረግጡበት መንገድ ጋር ተመሳስሎአል። (ስዕላዊ ንግግርና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ሞአብ በስፍራው ይረገጣል
በዚህ ስፍራ ሞዓብ የሞዓብን ሕዝብ ይወክላል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ሕዝቡን በሞዓብ ምድር ይረግጣል' (ምትክ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ስምና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 25:11

ሲዋኝ እጁን እንደሚዘረጋ ... እንዲሁ ... እጁን ይዘረጋል

ይህ ዘይቤአዊ ንግግር እግዚአብሔር እንዴት ክፉኛ የሞዓብን ሕዝብ እንደሚያዋርድ አጽንዖት ይሰጣል። ዋናተኛ እጆቹን በውኃ ውስጥ እንደሚዘረጋ እጆቻቸውን በጭቃ ውስጥ ይዘረጋሉ። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

በመካከሉ እጁን ይዘረጋል

"የሞዓብ ሕዝብ በጭቃ ሁሉ ወስጥ እጁን ይዘረጋል'

ዋናተኛ ሲዋኝ እጁን እንደሚዘረጋ

"እየዋኙ እንዳሉ'

ትዕቢቱን ... ያዋርዳል

የእግዚአብሔር ትዕቢተኛን ሰው ማዋረድ በሚመለከት ትዕቢት እግዚአብሔር ዝቅ እንደሚያደርገው ከፍ ብሎ እንዳለ ነገር ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ከእጆቻቸው ችሎታ ጋር

በዚህ ስፍራ "እጆች' የሚለው አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ለመሥራት የሚሆንን ኃይል ይወክላል። አት፡- "ከገነቧቸው ታላላቅ ነገሮች ጋር' ወይም "ከሠራቸው ታላላቅ ነገሮች ጋር' (ምትክ ስም ተመልከት)

የተመሸገውንም ከፍ ከፍ ያለውንም ቅጥርህን ... ወደ መሬት እስከ አፈር ደርስ ይጥለዋል

ይህ እግዚአብሔር የጦር ሠራዊቶች ቅጥሮቹን እንዲያፈርሱ ማድረጉ እርሱ ራሱ እንደሚያፈርሳቸው አድርጎ ይናገራል። አት፡- "ከፍ ከፍ ያሉትን የተመሸጉ ቅጥሮችህን ወደ መሬት ወደ አፈር ለመጣል ሠራዊት ይልካል' (ምትክ ስም ተመልከት)

ከፍ ከፍ ያሉ ምሽጎችህ

በዚህ ስፍራ ምሽጎችህ የሚለው የሚመለከትው የሞዓብ ሕዝብ ነው። ከቀደመው ጥቅስ ጋር የአሳብ ወጥነት እንዲኖረው ለማድረግ በሦሥተኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ከፍ ከፍ ያለ ምሽጋቸው' (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦሥተኛ መደብ)

---

## Chapter 26

### Isaiah 26:1

በዚያም ቀን

"በዚያን ጊዜ'

ይህ ቅኔ በይሁዳ ምድር ይዘመራል

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "በይሁዳ ምድር የሚኖሩ ሰዎች ይህን ቅኔ ይዘምራሉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የጸናች ከተማ አለችን

ይህ የኢየሩሳሌምን ከተማ ያመለክታል።

እግዚአብሔር ማዳኑን ቅጥሮቿና ምሽጎቿ ያደርጋል

ሕዝቡን ለመጠበቅና ለማዳን የሆነው የእግዚአብሔር ኃይል፣ ማዳኑ በከተማይቱ ዙሪያ እንዳለ ቅጥር ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እምነትን የሚጠብቅ ጻድቅ አገር

በዚህ ስፍራ አገር የሚለው ሕዝቡን ይወክላል። አት፡- "ጻድቅና ታማኝ ሕዝብ' (ምትክ ስም ተመልከት)

### Isaiah 26:3

በአንተ ለሚጸና አእምሮ

በዚህ ስፍራ አእምሮ የግለሰቡን አሳቦች ይወክላል። እንዲሁም በአንተ የሚለው እግዚአብሔርን ያመልክታል። በአንት የሚጸና የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- ባለማቋረጥ ስለአንተ የሚያስብ ሰው (ምትክ ስምና ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ጌታ እግዚአብሔር

ጌታ፣ የእግዚአብሔር ሌላኛው ስም ነው።

እግዚብሔር የዘላለም ዓለት ነው

እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመጠበቅ ያለው ኃይል ከጠላቶቻቸው ለማምለጥ ሕዝቡ የሚሹሸበት ትልቅ ዓለት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

### Isaiah 26:5

በትዕቢት የሚኖሩትን ዝቅ ያደርጋል

እግዚአብሔር የሚታበዩትን ማዋረዱ ትዕቢተኞች ሰዎች በከፍታ እንደሚኖሩ እርሱም ዝቅ እንደሚያደርጋቸው ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የተመሸገቸው ከተማ

ይህ የተወሰነችን አንዲትን ከተማ ሳይሆን የተመሸገቱን ከተሞች በአጠቃላይ ማለት ነው። (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች ተመልከት)

ያዋርዳል፣ ... ደረስ ያወርዳታል

እግዚአብሔር የተመሸጉትን ከተሞች የጦር ሠራዊት እንዲያጠፋቸው ማድረጉ እግዚአብሔር ራሱ እንዳደረገው ተደርጎ ተነግሮአል። (ምትክ ስም ተመልከት)

በድሀ እግርም በችግረኛም አረጋገጥ ትረገጣለች

ሁለቱም ንግግሮች ተመሳሳይ አሳብ ይናገራሉ። ይሕ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ድሆችና የተጨቆኑ ሰዎች በከተማይቱ ፍርስራሽ ላይ ይረማመዳሉ።' (አጓዳኝነትና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

### Isaiah 26:7

የጻድቃን መንገድ የቀናች ናት ... አንተ ... የጻድቃንን መንገድ ታቀናለህ

እንዚህ ሁለት ሃረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት ተመሣሣይ አሳብ ነው። እግዚአብሔርን የሚታዘዙ ሰዎች በመንገዱ እንደሚሄዱ ተደርጎ ተነግሮአል። የሚያደርጉት ትክክል መሆኑን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ማረጋገጡ መንገዳቸውን ቀናና የተስተካከለ እንደሚያደርግላቸው ተደርጎ ተነግሮአል። (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በፍርድህ መንገድ፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ተስፋ አድርገንሃል

ትክክል እንደሆነ እግዚአብሔር የበየነውን ማድረግ በመንገዱ እንደመሄድ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "አንተ ትክክል ነው ብለህ የበየንከውን በማድረግ ስለጸናን፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ተስፋ አድርገንሃል' (ስዕላዊ ንግግር ተመለከት)

በፍርድህ

"በሕግጋትህ' ወይም "በትምህርቶችህ'

ተስፋ አድርገንሃል

በዚህ ስፍራ "እኛ' የሚለው ለእግዚአብሔር እየተናገሩ ያሉትን ኢሳይያስንና ጻድቃን የሆኑ ሰዎችን ሁሉ ያመለክታል። (አግላይና አካታች "እኛ' ተመልከት)

ስምህና ክብርህ የነፍሳችን ምኞት ነው

በዚህ ስፍራ "ስም' እና "ክብር' እግዚአብሔርን ራሱን የሚወክሉትን የእግዚአብሔር ባሕርያት ይወክላሉ። አት፡- "አንተን ማክበር ብቸኛ ምኞታችን ነው' (ምትክ ስም ተመልከት)

መንፈሴ በውስጤ አጥብቆ ይፈልግሃል

እግዚአብሔርንና ሕግጋቱን ከፊቱ በተሻለ ለማወቅ መፈለግ ሰውዬው እግዚአብሔርን ለማግኘት እንደሚፈልግ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "የተሻለ እንዳውቅህ አጥብቄ እፈልጋለሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

መንፈሴ በውስጤ አጥብቆ ይፈልግሃል

በዚህ ስፍራ "መንፈስ' የተናጋሪውን ሁለንተና ይወክላል። (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

### Isaiah 26:10

ለኃጢአተኛ ሞገስ ቢደረግለት ጽድቅን አይማርም

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ለክፉ ሰዎች መልካም ቢሆንላቸውም እንኳን በጎ ማድረግን አይማሩም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ኃጢአተኛ

ይህ ክፉ ሰዎች በአጠቃላይ ማለት ነው። (አጠቃላይ ስማዊ ሃረጎች ተመልከት)

በቅኖች ምድር

"ምድር' የሚለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አት፡- "ሰዎች ትክክል የሆነውን የሚያደርጉበት ምድር' (ምትክ ቃል ተመልከት)

የእግዚአብሔርን ግርማ አያይም

"ማየት' በዚህ ስፍራ አንድን ነገር መገንዘብን ይወክላል። አት፡- "እግዚአብሔር ታላቅ እንደሆነ አይገነዘቡም' (ምትክ ስም ተመልከት)

### Isaiah 26:11

እጅህ ከፍ ከፍ አለች

እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ለመቅጣት መዘጋጀቱ ክፉ ሰዎችን ለመምታት እጆቹ እንደተነሱ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

አላስተዋሉም

"ክፉ ሰዎች ግን አላስተዋሉም'

ለሕዝብህ ያለህን ቅንዓት አይተው

"ማየት' በዚህ ስፍራ አንድን ነገር መገንዘብን ይወክላል። አት፡- "ሕዝብህን ለመባረክ አጥብቀህ እንደምትፈልግ ይገነዘባሉ' (ምትክ ቃል ተመልከት)

በሃፍረት ይከደናሉ

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ያፍራሉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የጠላቶችህ እሳት ትበላቸዋለች
የእግዚአብሔር ጠላቶቹን መቅጣትና ፈጽሞ ማጥፋት ፈጽሞ የሚያቃጥላቸውን እሳት እንደሚልክ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የጠላቶችህ እሳት
በዚህ ስፍራ "የ' የሚለው እሳቱ የጠላቶቹ ንብረት የሆነ ነው ማለት አይደለም ነገር ግን እሳቱ ጠላትን ለማጥቃት ጥቅም ላይ ለማዋል የታቀደ ነው። አት፦ "እሳትህ ፈጽሞ ያቃጥላቸዋል'
ለእኛ
በዚህ ስፍራ "እኛ" የሚለው ጻድቃን ሰዎችን ሁሉ ጨምሮ ኢሳይያስን ያመለክታል። (አግላይና አካታች "እኛ" ተመለከት)
Isaiah 26:13
ነገር ግን ስምህን ብቻ እናመሰግናለን
በዚህ ስፍራ ስም የሚለው የእግዚአብሔርን ማንነት ይወክላል። አት፦ "ነገር ግን አንተን ብቻ እናመሰግናለን' (ምትክ ቃል ተመልከት)
አይነሱም
"ወደ ሕይወት ተመልሰው አይመጡም'
መታሰቢያቸውንም ሁሉ አጥፍተሃል
እግዚአብሔር ያጠፋቸውን ሌሎች ሰዎች እንዳያስቧቸው ማድረጉ እግዚአብሔር መታሰቢያቸው እንዲጠፋ ወይም እንዲሞት እንዳደረገ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 26:15
ሕዝብን አበዛህ፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ሕዝብን አበዛህ
አጽንዖት ለመስጠት ሀረጉ ተደግሞአል። በዚህ ስፍራ ሕዝብ የሚለው ሰዎችን ይወክላል። አት፦ "በሕዝባችን ዘንድ ሰዎች በከፍተኛ ቁጥር እንዲጨምሩ አድርገሃል' (አጓዳኝነትና ምትክ ቃል ተመልከት)
Isaiah 26:16
ፈለጉህ
በዚህ ስፍራ እነርሱ የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። ይህ ኢሳይያስን ያካትታል። አት፦ "እንፈልግሃለን' (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)
ፈለጉህ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር እግዚአብሔርን እርዳታ ይጠይቁ ነበር ማለት ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
የአንተ ተግሣጽ በእነርሱ ላይ በሆነ ጊዜ
ተግሣጽ የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽነት ሊቀመጥ ይችላል። አት፦ "በገሠጽሃቸው ጊዜ' (የነገር ስሞች ተመልከት)
የፀነሰች ሴት ... በምጥ እንደምትጮኽ
ይህ ሕዝቡን ከምትወልድ ሴት ጋር ያነጻጽራል። ይህ እግዚአብሔር በሚገሥጻቸው ጊዜ ስለሚሆነው መከራቸውና ጩኸታቸው አጽንዖት ይሰጣል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 26:18
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ የይሁዳን ሕዝብ መከራ ከምትወለድ ሴት ጋር ማነጻጸሩን ይቀጥላል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ነፋስን ብቻ እንደምንወልድ ሆነናል
"አየር ብቻ እንደምንወልድ ሆነናል' ወይም "ምንም የሌለው እንደምንወልድ ሆነናል።' ይህ የሕዝቡ መከራ የሚያስከትለው ውጤር ምንም እንደሆነ አጽንዖት የሚሰጥ ዘይቤአዊ ንግግር ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
በምድርም ደኅንነት አላደረግንም፤ በዓለምም የሚኖሩ አልወደቁም
በዚህ ስፍራ "ምድር' የሚለው በምድር የሚኖሩትን ትወክላለች። ትርጉሙ ግልጽ አይደለም፣ የእስራኤል ሕዝብ በጦርነት ጠላቶቻቸውን በማሸነፍ ራሳቸውንና ሌሎች ሕዝቦችን ማዳን አልቻሉም የሚል ይመስላል። (ምትክ ስምና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
በምድርም ደኅንነት አላደረግንም
ይህ "ደኅንነት' የሚለው የነገር ስም "ማዳን' በሚል ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "የምድር ነዋሪዎችን አላዳናቸውም' (የነገር ስም ተመልከት)
በዓለም የሚኖሩ አልወደቁም
የዓለም ክፉ ሰዎች በጦርነት እንዲወድቁ አላደረግንም
Isaiah 26:19
ሙታንህ ሕያዋን ይሆናሉ
"ሙታን' የሚለው ስማዊ ቅጽል "የሞቱ' በሚል ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "የሞቱ ሕዝብህ ሕያዋን ይሆናሉ' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)
ሙታንህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) "ሙታንህ' የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል ወይም 2) "ሙታንህ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። ሁለተኛውን አማራጭ ከወሰድህ "ሙታኖቻችን' ብለህ መተርጎም ትችላለህ።
ንቁ
ይህ የሞቱ ሰዎች ሕያው መሆንን ከእንቅልፍ እንደሚነቁ አድርጎ ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በምድር የምትኖሩ ሆይ
ይህ የሞቱት የተገለጹበት ትህትና የተሞላ መንገድ ነው። አት፦ የሞቱና የተቀበሩ (የማያስደስት ቃልን በሌላ ቃል መተካት ተመልከት)
ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና
እግዚአብሔር ለሕዝቡ በበጎነት የሚሠራውና እነርሱን መልሶ ሕያዋን ማድረጉ ተክሎችን ሕያዋን እንደሚያደርግ ጠል ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ጠልህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) "ጠልህ' የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል ይኼውም እግዚአብሔር የሚሰጠውን ጠል ነው ወይም 2) "ጠልህ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል ይኼውም ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን ጠል ነው።
የብርሃን ጠል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ብርሃን ሙታንን ሕያዋን የሚያደርግበትን የእግዚአብሔርን ኃይል ያመለክታል። አት፦ "ከእግዚአብሔር የሆነ ጠል' ወይም 2) ብርሃን በተክሎች ላይ ጠል የሚሆንበትን የማለዳ ጊዜን ያመለክታል። አት፦ "የማለዳ ጠል'
ምድር ሙታኖቿን ታወጣለች
"ምድር የሞቱትን ትወልዳለች።' የእግዚአብሔር የሞቱ ሰዎችን ሕያው ማድረግ ምድር የሞቱትን እንደምትወልድ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "እግዚአብሔር የሞቱትን ከምድር እንዲነሱ ያደርጋል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 26:20
ሕዝቤ ሆይ
በዚህ ስፍራ "ሕዝቤ (የኔ ሕዝብ)' የሚለው ኢሳይያስን ያመልክታል። እንዲሁም "ሕዝቤ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።
ቁጣ እስኪያልፍ ድረስ
"ቁጣ' የሚለውን የነገር ስም "ቁጡ' በሚል ቅጽል ተርጉም። አት፦ "ከእንግዲህ ወዲያ እግዚአብሔር በእኛ ላይ ቁጡ እስከማይሆን ድረስ' (የነገር ስም ተመልከት)
ምድርም ደምዋን ትገልጣለች፣ ሙታኖችዋንም ከእንግዲህ ወዲህ አትከድንም
ነፍስ ገዳዮችን መቅጣት ይችል ዘንድ በምድር የተፈጸሙትን ግድያዎች ሁሉ እግዚአብሔር መግለጡ ምድር ራሷ ነፍስ የገደሉትን ሁሉ እንደምትገልጥ ተደርጎ ተነግሮአል። (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

Chapter 27
Isaiah 27:1
በዚያም ቀን
"በዚያን ጊዜ'
እግዚአብሔር በጠንካራ፣ በታላቅና በብርቱ ሰይፉ ይቀጣዋል
እግዚአብሔር ጠላቶቹን ለማጥፋት ያለው ኃይል ጠንካራና ትልቅ ሰይፍ እንዳለው ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በባሕር ውስጥ ያለውን አስፈሪ ፍጡር
ይህ ሌዋታንን ያመለክታል።
ለወይን ቦታው ተቀኙለት
"ስለ ወይን ቦታው ተቀኙ።' ይህ የእስራኤልን ሕዝብ ፍሬ በሚሰጥ የወይን ቦታ መስሎ ይናገራል። አት፦ "ለወይን ጠጅ የሚሆን የወይን ፍሬ እንደሚያፈራ የወይን ቦታ እንደሆኑ አድርጋችሁ ስለ እስራኤል ሕዝብ ዘምሩ።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
እኔ እግዚአብሔር ጠባቂው ነኝ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"እኔ እግዚአብሔር የወይን ቦታው ጠባቂ ነኝ'
በሌሊትና በቀን
"ሌሊት' እና "ቀን' የሚሉት ቃላት "ሁልጊዜ' ለማለት ተጣምረዋል። አት፡- "ሁልጊዜ' ወይም "ያለማቋረጥ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 27:4
አያያዥ አሳብ፡-
የእስራኤልን ሕዝብ በወይን ቦታ መስሎ መናገሩን ቀጥሏል።
አልቆጣም፣ ኦ፣ እሾህና ኩርንችት በነበሩ! በጦርነት በወጣሁባቸው ነበር
አልቆጣም። እሾህና ኩርንችት ቢኖሩ ኖሩ በጦርነት ባሰለፍኩባቸው ነበር
አልቆጣም
እግዚአብሔር ከእንግዲህ ወዲያ በሕዝቡ ላይ እንዳማይቆጣ የሚታወቅ ነው። አት፡- "ከአንግዲህ ወዲያ በሕዝቤ ላይ አልቆጣም' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ)
እሾህና ኩርንችት በነበሩ
የእስራኤል ጠላቶች በወይን ቦታ እንደሚበቅሉ እሾህና ኩርንችት ተደርገው ተገልጸዋል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
እሾህና ኩርንችት
ይህንን ሃረግ በኢሳይያስ 5፡6 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
በጦርነት በወጣሁባቸው ነበር
እግዚአብሔር ጠላቶቹን መውጋቱ ስለ እርሱ በጦሩ መካከል እንደሚገኝ ተዋጊ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በወጣሁባቸው ነበር፣ በአንድነትም ባቃጠልኋቸው ነበር
በዚህ ስፍራ ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር ጠላቶች ለመናገር የተለያዩ ምስሎችን ያጣምራል። እሾህና ኩርንችት እንደሆኑ ደግሞም በጦሩ ውስጥ እንዳሉ ወታደሮች አድርጎ ስለ እነርሱ ይናገራል። (ስላዊ ንግግር ተመልከት)
የእኔን ጥበቃ ካለገኙ
ይህ "ጥበቃ' የሚለው የነገር ስም "ጠበቀ' በሚለው ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "እንድጠብቃቸው እስካልጠየቁኝ ድረስ' (የነገር ስም ተመልከት)
ከእኔ ጋር ሰላም ያድርጉ፣ ከእኔ ጋር ሰላም ያደርጉ
"ከእኔ ጋር በሰላም ለመኖር ጠይቀዋል፣ከእ ጋር በሰላም እንዲኖሩ እፈልጋለሁ'
Isaiah 27:6
አጠቃላይ መረጃ፡-
ኢሳይያስ እየተናገረ ነው። የእስራኤልን ሕዝብ በወይን ቦታ መስሎ መገልጹን ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 27፡2 ተመልከት)
በሚመጣው ዘመን
ይህ ዘመንን እንደሚጓዝና አንድ ቦታ እንደሚደርስ አድርጎ ይናገራል። አት፡- "ወደፊት' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፣ እስራኤልም ያብባል
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ መባረኩና እንዲበለጽግ ማድረጉ ሥሩ እንደሚያድግና እንደሚያብብ ወይን ተደርጎ ተነገሮአል። አት፡- "የእስራኤል ልጆች ሥሩን እንደሚሰድድና እንደሚያብብ ወይን ይበለጽጋሉ' (ስዕላ ንግግር ተመልከት)
ያዕቆብ ... እስራኤል
በዚህ ስፍራ "ያዕቆብ' እና "እስራኤል' የያዕቆብን ልጆች የሚወክሉ ምትክ ስሞች ናቸው። (ምትክ ስም ተመልከት)
የምድርን ፊት በፍሬ ይሞላሉ
ሌላውን ሕዝብ ይረዱ ዘንድ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንዲበለጽጉ ማድረጉ ፍሬው እጅግ እንደበዛና ምድርን እንደሸፈነ ወይን ተደርገው ተገልጸዋል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 27:7
የመቱትን ሕዝቦች እንደመታ እግዚአብሔር ያዕቆብን መትቶታልን
ጥያቄው የእግዚብሔርን ቅጣት ክብደት ለማነጻጸር ጥቅም ላይ ውሏል። አት፡- "በእርግጥ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከቀጣው በላይ ጠላት ሕዝቦችን በእጅጉ ቀጥቷል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ)
ያዕቆብ ... እስራኤል
የያዕቆብን ልጆች ይወክላል። (ምትክ ስም ተመልከት)
ሌሎች ሕዝቦች በእነርሱ በተገደሉበት መገደል ያዕቆብና እስራኤል ተገድለዋልን?
ይህም ጥያቄ የእግዚአብሔርን ቅጣት ክብደት ለማነጻጸር ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እነርሱ ጠላቶቻቸውን ከሌሎች ሕዝቦች እንደገደሉ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ አልገደለም።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽና አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
በልኬቱ ተገዳደርካቸው
በዚህ ስፍራ "አንተ' የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል። የሚገባቸውን ያህል እግዚአብሔር ሕዝቡን መቅጣቱ፣ የእግዚአብሔር ቅጣት ሊለካ የሚችል ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል። አት፡- "ነገር ግን አንተ የሚገባቸውን ያህል ቀጣሃቸው።' (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞችና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ያዕቆብን ሰደደው እስራኤልን አስወገደው
ይህ የያዕቆብን ልጆች ይወክላል። አት፡- "እስራኤላውያንን ወዲያ ሰደዳቸው' (ምትክ ስም ተመልከት)
የምሥራቅ ነፋስ እንደሚነፍስበት ቀን በጠንካራ ዐውሎ አስወገዳቸው
እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ባዕድ አገር ወዲያ የሚሰድበት ኃይሉ እነርሱን ወደ ባዕድ አገር ለመውሰድ የአፉን እስትንፋስ እንደሚጠቀም ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "የእግዚአብሔር ኃይል እንደ ምሥራቅ ጠንካራ ዐውሎ ጠርጎ አስወገዳቸው' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 27:9
ስለዚህ እንዲሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) እንዲሁ የሚለው ኢሳይያስ በቀደመው ጥቅስ እንደገለጸው እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ምርኮ መሰደዱን ያመለክታል ወይም 2) እንዲሁ የሚለው ኢሳይያስ በቁጥር 9 ቀጥይ ክፍል የሚገልጻቸውን ድርጊቶች ያመለክታል።
የያዕቆብ በደል ይሰረያልና
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ከእስራኤል ኃጢአትን ያስወግዳል' ወይም "እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን ኃጢአት ይቅር ይላል።' (አድጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
የያዕቆብ በደል ... የእርሱን ኃጢአት የማስወገድ
በዚህ ስፍራ "ያዕቆብ' የያዕቆብን ልጆች ይወክላል። አት፡- "የእስራኤላውያን በደል... የእነርሱን ኃጢአት የማስወገድ' (ምትክ ስም ተመልከት)
ይህም
በዚህ ስፍራ "ይህ' በቁጥር 9 ቀጥይ ክፍል ኢሳይያስ የሚገልጻቸውን ድርጊቶች ያመለክታል።
ሙሉ ፍሬው
ፍሬ በዛፍ ላይ ወይም በወይን ተክል ላይ እንደሚያድግ ይህ የድርጊቱን ውጤቶች ይናገራል። አት፡- "ውጤቱ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የመሠዊያ ድንጋዮችን እንደ ኖራ ድንጋይ ያደርጋቸዋል ያደቅቃቸዋልም፣ የአሼራህ ዐፀዶች ወይም የማጠኛ መሠዊያዎች ጸንተው አይቆሙም
በዚህ ስፍራ እርሱ የሚለው ልጆቹን የሚወክለውን ያዕቆብን ያመለክታል። አት፡- "ለሐሰተኛ አማልክት የሚሠውባቸውን መሠዊያዎች ፈጽመው ያፈርሳሉ፣ የአሼራህን ጣዖታትና ለሐሰተኛ አማልክት እጣን የሚያቃጥሉባቸውን መሠዊያዎች ሁሉ ያስወግዳሉ።' (ምትክ ስም ተመልከት)
Isaiah 27:10
የተመሸገችው ከተማ ... ቅርንጫፍዋንም ይበላል
በዚህ ስፍራ ኢሳይያስ ወደፊት ሊሆን ያለውን ነገር ገና አስቀድሞ እንደተፈጸመ አድርጎ ይናገራል። ይህ በእርግጥ የሚፈጸም ለመሆኑ አጽንዖት ይሰጣል። (ትንቢታዊ ሃላፊ ጊዜ ተመልከት)
የተመሸገችው ከተማ ብቻዋን ሆነች፣ እንደ ምድረ በዳ ሆና የተፈታችና የተተወች መኖሪያ ናት
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል።አት፡- "ጠንካሮችና ብዙ ሰዎች ይኖሩባቸው የነበሩ ከተሞች እንደ ምድረ በዳ ባዶ ሆኑ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
የተመሸገችው ከተማ ... መኖሪያ
ይህ አንድ የተወሰነ ከተማን ወይም መኖሪያ ስፍራን ሳይሆን ከተሞችን ወይም መኖሪያ ስፍራዎችን የሚያመለክት ነው። (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች ተመልከት)
ጥጃ ይሰማራል፣ በዚያም ይተኛል፣ ቅርንጫፍዋንም ይበላል
በዚህ ስፍራ ጥጃ፣ ጥጃዎችን ወይም ከብቶችን በአጠቃላይ ያመለክታል። አት፡- "ጥጃዎች ይሰማራሉ፣ በዚያም ይተኛሉ፣ ቅርንጫፍዋንም ይበላሉ' (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች ተመልከት)
ጫፎችዋ ... የማያስተውል ሕዝብ
ሕዝቡ ሴቶች እንደሚሰብሩአቸው ደረቅ ቅርንጫፎች ተደርገው እስኪገለጹ ድረስ እግዚአብሔርን ካለመታዘዛቸው የተነሳ ጠላቶች በቀላሉ የሚያጠፏቸው ደካሞች

ሆነው ነበር። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ጫፎችዋ በደረቁ ጊዜ ይሰበራሉ፣ሴቶችም መጥተው ያቃጥሉአቸዋል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ቅርንጫፎቹ በደረቁ ጊዜ፣ ሴቶች ይመጡና ይሰብሩአቸዋል፣ለእሳት ማገዶም ያደርጓቸዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
የማያስተውልም ሕዝብ ነውና
ይህ በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፡- "ይህ እግዚአብሔርን ወይም ሕጉን የሚረዳ ሕዝብ አይደለም' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ሕዝብ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) "ሕዝብ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል ወይም 2) "ሕዝብ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ የሚጨቁኑትን የባዕድ ሕዝቦች ያመለክታል።
ስለዚህ ፈጣሪያቸው አይራራላቸውም፣ ሠሪያቸውም ምሕረት አያደርግላቸውም
ሁለቱም ሐረጎች አንድ ዓይነት ነገር ይናገራሉ። አት፡- "ስለማያስተውሉ፣እግዚአብሔር፣ የፈጠራቸው፣ ምሕረት አያደርግላቸውም' (አጓዳኝነት ተመልከት)
Isaiah 27:12
እንዲህ ይሆናል
ይህ ሃረግ አንድ አስፈላጊ ሁኔታ እንደሚፈጸም ያመለክታል።
በዚያም ቀን
"በዚያን ጊዜ'
እግዚአብሔር ይወቃል
ከባዕዳን አገር ወደ እስራኤል ምድር መልሶ ለማምጣት እግዚአብሔር ሕዝቡን መሰብሰቡ ፍሬውን ከገለባው ለመለየት ስንዴን እንደመውቃት ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ከኤፍራጥስ ወንዝ እስከ ግብጽ ወንዝ ድረስ
ኢሳይያስ የኤፍራጥስን ወንዝና የግብጽን ወንዝ የሚጠቅሰው ወደ እነዚህ ወንዞች አቅራቢያ ወደሚገኙ አገሮች ማለትም ወደ አሦርና ግብጽ የተጋዙትን የእስራኤልን ሕዝብ መልሶ ያመጣቸዋል ለማለት ነው። የኤፍራጥስ ወንዝ ከእስራኤል በስተ ሰሜን ምሥራቅ የሚገኝ ሲሆን የግብጽ ወንዝ ደግሞ ከእስራኤል በስተ ደቡብ ምዕራብ የሚገኝ ነው።
የግብጽ ወንዝ
"የግብጽ ጅረት'
አንድ በአንድ ትሰበሰባላችሁ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር አንድ በአንድ ይሰበስባችኋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ታላቅ መለከት ይነፋል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "አንድ ሰው ከፍ ባለ ድምጽ መለከት ይነፋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
በአሦር አገር የጠፉ፣ በግብጽም ምድር የተሰደዱ ይመጣሉ
መረዳት የሚቻለው መረጃ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አት፡- "በአሦር ምድርና በግብጽ ምድር በስደት ያሉና የሞቱ ወደ እስራኤል ምድር ይመለሳሉ' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)
በተቀደሰው ተራራ
"የተቀደሰው ተራራ' በኢየሩሳሌም የሚገኘው የጽዮን ተራራ ነው። ይህንን በኢሳይያስ 11፡9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

Chapter 28
Isaiah 28:1
በወይን ጠጅ በተሸነፉ በወፍራም ሸለቆአቸው ራስ ላይ ... ወዮ ለትዕቢት አክሊል
"አክሊል' የሚለው ከአበባ የሚሠራን ዘውድ ነው። በዚህ ስፍራ ከለምለም ሸለቆ በላይ የተቀመጠችውን የእስራኤልን ዋና ከተማ የሰማሪያ ከተማን ይወክላል። የአክሊል አበባዎች እንደሚያረጁና ውበታቸው እንደሚጠፋ የሰማሪያና የሕዝቧ መጥፋት ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
እነሆ
"ስሙ' ወይም "ልብ በሉ'
በወይን ጠጅ ለተሸነፉ
"በወይን ጠጅ ለሰከሩ'
ጌታ ኃያልና ብርቱ የሆነውን አንድ ሰው ይልካል
በዚህ ስፍራ አንድ ሰው የሚለው ኃያል ሠራዊቱን የሚወክለውን ኃያል ንጉሥ ያመለክታል። አት፡- "ጌታ አንድን ንጉሥ ከኃያል ሠራዊቱ ጋር ይልከዋል' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
የበረዶ ዝናብ
"የበረዶ ዝናብ' ወይም የበረዶ ወጨፎ ጠንካራ የበረዶ ክፋዮች ከሰማይ ሲወርዱ ይከሰታል። ይህ የሰማሪያን ሕዝብ ለማጥፋት እግዚአብሔር የሚልከውን የጠላት ጦር የሚያመለክት ዘይቤአዊ ንግግር ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
እያንዳንዱን አክሊል ወደ መሬት ይጥለዋል
ንጉሡና ኃያል ሠራዊቱ የሰማሪያና ሕዝብና ከተማቸውን ማጥፋቱ የሕዝቡን አክሊል ምድር ላይ እንደመጣል ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 28:3
አጠቃላይ መረጃ፡-
ኢሳይያስ የሰማሪያ ሕዝበና ከተማ አክሊል እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 28፡1-2 ተመልከት)
የኤፍሬም ሰካራሞች ትዕቢት አክሊል በእግር ይረገጣል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "የጠላት ሠራዊት አበባን በእግራቸው እንደሚያደቅቁ የሰማሪያን ትዕቢተኛ ሰካራሞች ያደቅቋቸዋል።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
የኤፍሬም ... ትዕቢት አክሊል ... በወፍራሙ ሸለቆ ራስ ላይ ያለች
"አክሊል' ከአበባ የተሠራ ዘውድ ነው። በዚህ ስፍራ ከለምለሙ ሸለቆ በላይ የተቀመጠችውን፣ የእስራኤልን ዋና ከተማ፣ የሰማሪያ ከተማን ይወክላል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የረገፈች ... ከመከር በፊት አስቀድማ እንደምትበስል በለስ ትሆናለች
ይህ ከመከር በፊት የበሰለች በለስን እንዳየና ፈጥኖ እንደሚበላ ሰው የጠላት ወታደሮች የሰማሪያን ውበት እንደሚያዩና ፈጥነው እንደሚበዘብዟት ይናገራል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 28:5
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በኢሳይያስ 1፡9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ውብ ዘውድና የውበት አክሊል ይሆናል
እንደ እውነተኛ ንጉሣቸው ለብሰውት ለሚያከብሩት ሕዝብ እግዚአብሔር ውብ ዘውድ እንደሚሆን ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ውብ ዘውድና የውበት አክሊል
የሁለቱም ትርጉም አንድ ነው። አት፡- "ውብ ዘውድ' (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)
ሕዝብ፣ በፍርድ ወንበር ላይ ለሚቀመጥም የፍትህ መንፈስ፣ ... ብርታትም
እንደ "ፍትህ' እና "ብርታት' ያሉ የነገር ስሞች በቅጽልነት እንዲገለጹ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "ሕዝብ፣ እግዚአብሔር ዳኞችን ጻድቃን እንዲሆኑ ያደርጋል እንዲሁም ብርቱዎች ያደርጋቸዋል' (የነገር ስም ተመልከት)
የፍትህ መንፈስ
የፍትህ መንፈስ ያለው ሰው የፍትሃዊነት ባሕርይ ያለውና ጻድቅ ሰው ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
በፍርድ ወንበር ላይ ለሚቀመጥ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር የዳኝነት ሥልጣን ያለው ሰው ማለት ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
በበራቸው ጠላቶቻቸውን ወደ ኋላ ለሚመልሱ ብርታትን
በዚህ ስፍራ "ወደ ኋላ ለሚመልሱ' የሚለው በጦርነት ለሚያሸነፉ የሚል ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "ጠላቶች ከተማቸውን ሲያጠቁ ጠላቶቻቸውን ያሸንፉ ዘንድ እግዚአብሔር ወታደሮቹን ብርቱዎች ያደርጋቸዋል' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 28:7
ነገር ግን እነዚህም እንኳን
"ነገር ግን መሪዎቹ እንኳን'
ካህኑና ነቢዩ
ይህ አንድ የተወሰነ ካህን ወይም ነቢይ ማለት አይደለም። ካህናትንና ነቢያትን በአጠቃላይ ያመለክታል። አት፡- "ካህናትና ነቢያት' (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች

ተመልከት)
ከወይን ጠጅ የተነሣ ይንገዳገዳሉ፣ ከሚያሰክርም መጠጥ የተነሣ ይንደፋደፋሉ
እነዚህ ሁለት ሃረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ሲሆን ሰካራሞች ከመሆናቸው የተነሣ ካህናቱና ነቢያቱ ሥራቸውን መሥራት እንዳልቻሉ አጽንዖት ይሰጣሉ። አት:- "ሰካራሞች ስለሆኑ በየአካባቢው ይንገዳገዳሉ' (አጓዳኝነት ተመልከት)
በወይን ጠጅም ይዋጣሉ
በተገቢው ሁኔታ ማሰብ እስከማይችሉ ድረስ ይጠጡ ስለነበር የወይን ጠጅ እንደዋጣቸው ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት:- "የወይን ጠጅ እንዲደነጋገርባቸው አደርጓል' (ሰስዕላዊ ንግግርና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
በራእይ ይንገዳገዳሉ በፍርድም ይደነቃቀፋሉ
በትክክል ለመራመድ አብዝተው እንደሚጠጡ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራእይ ለመረዳት ወይም መልካም ፍርድ ለማድረግ አብዝተው ይጠጣሉ።
Isaiah 28:9
እውቀትን ለማን ያስተምራል ወይስ መልእክቱን ለማን ያብራራል
ሰካራሞቹ ነቢያትና ካህናት ሊያርማቸው የሚፈልገውን ኢሳይያስን ለመተቸት ጥያቄ ይጠቀማሉ። አት:- "ሰካራሞቹ ነቢያትና ካህናት፣ 'ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር መልእክት ሊያስተምረን እየሞከረ አይደለምን!' ይላሉ' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
ወተትን ለተዉ ወይስ ጡትን ለጣሉ ነውን
እንደ ሕፃናት እንደተመለከታቸው ስለተሰማቸው ሰካራሞቹ ነቢያትና ካህናት ኢሳይያስን ለመተቸት ጥያቄ ይጠቀማሉ። አት:- "እንደ ሕፃናት ሊመለከተን አይገባም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ እና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ
ለሕፃን እንደሚናገር ኢሳይያስ ቀላል ትእዛዛትን እንደሚደጋግም ስለተሰማቸው ሰካራሞቹ ነቢያትና ካህናት ኢሳይያስን ይተቻሉ።
Isaiah 28:11
ለዚህ ሕዝብ በሚያላግጡ ከንፈሮችና በባዕድ ልሳን ይናገራል
በዚህ ስፍራ "ከንፈሮች' እና "ልሳን' የሚለው እስራኤላውያን ከሚናገሩት የተለየ ቋንቋ የሚናገሩትን ባዕዳን ይወክላል። ይህ እስራኤላውያንን የሚወጋውን የአሦራውያንን ሠራዊት እንደሚያመለክት ይጠቅማል። አት:- "እግዚአብሔር ለዚህ ሕዝብ የባዕድ ቋንቋ በሚናገሩ የጠላት ወታደሮች አማካይነት ይናገራል።' (ተለዋጭ ስም እና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
የሚያላግጡ ከንፈሮች
"የሚንተባተቡ ከንፈሮች'
ዕረፍት ይህች ናት
"ዕረፍት' የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት:- "ይህ ማረፊያ ቦታ ነው።' (የነገር ስም ተመልከት)
ለደከመው ዕረፍት ስጡ
"ዕረፍት' የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት:- "የደከመው ማንም ይምጣና ይረፍ' (የነገር ስም ተመልከት)
ይህችም ማረፊያ ናት
ማረፊያ የሚለው የነገር ስም በማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት:- "ይህ ልትታደስ የምትችልበት ቦታ ነው' (የነገር ስም ተመልከት)
Isaiah 28:13
ስለዚህ ... የእግዚአብሔር ቃል
ስለዚህ ... የእግዚአብሔር መልእክት
ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ
እነዚህ ኢሳይያስ እንዴት እያስተማራቸው እንዳለ ለመተቸት ሰካራሞቹ ነቢያትና ካህናት የሚጠቀሙባቸው ቃላት ናቸው። ይህንነ በኢሳይያስ 28:10 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ስለዚህ ሄደው ወደ ኋላ እንዲወድቁ፣ እንዲሰበሩም፣ እንዲጠመዱ፣ እንዲማረኩም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት:- "የአሦር ሠራዊት ይመጣና ያሸንፋቸው፣ ምርኮኞችም አድርጎ ይወስዳቸው ዘንድ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ሄደው ወደ ኋላ እንዲወድቁ፣ እንዲሰበሩም
ሕዝቡ በጦርነት በጠላት ሠራዊት መሸነፉ ሕዝቡ እንደሚወድቅና እንደሚሰበር ተደርጎ ተነገሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
እንዲጠመዱ
የእስራኤልን ሕዝብ የሚማርኩ የጠላት ወታደሮች እንስሳን በወጥመድ እንደሚያጠምዱ አዳኞች ተደርገው ተገልጸዋል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 28:14
ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ
"ስለዚህ የእግዚአብሔርን መልእክት ስሙ'
ከሞት ጋር ቃል ኪዳን አድርገናል፣ ከሲኦልም ጋር ተስማምተናል
በመሠረቱ ሁለቱም አረፍተ ነገሮች የሚናሩት አንድ ነገር ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) የኢየሩሳሌም መሪዎች የሙታን መኖሪያ አማልክት ከመሞት እንዲጠብቋቸው ከእነርሱ ጋር ስምምነት ለማድረግ በመጣር አስማትና ጥንቆላ ተጠቅመዋል ወይም 2) ይህ መሪዎቹ ከግብጽ መሪዎች ጋር ስምምነት ማድረጋቸውን የሚገልጽ ስዕላዊ ንግግር ነው። የኢየሩሳሌም መሪዎች ከሙታን መኖሪያ አማልክት ጋር ስምምነት እንዳደረጉ ሁሉ ግብጻውያንም ጥበቃ ማድረግ እንደሚችሉ ተማምነዋል። (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የሚያጥለቀልቅ መቅሠፍት ባለፈ ጊዜ አይደርስብንም
ይህ የእግዚአብሔር ፍርድና ቅጣት ሕዝቡን እንደሚመታ ጅራፍ ተደርጎ ተነግሮአል። ጅራፉም በኢየሩሳሌም እንደሚያልፍ ጎርፍ ተደርጎ ተነግሮአል። አት:- "ስለዚህም ሰው ሁሉ ሲሰቃይና ሲሞት፣ የሚጎዳን ምንም ነገር የለም።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ውሸትን መሸሸጊያችን አድርገናልና፣ በሐሰትም ተሰውረናልና
በመሠረቱ ሁለቱም ሐረጎች የሚናገሩት አንድ ነገር ነው። ወሸት እና ሐሰት ሰው ሄዶ እንደሚሸሸግባቸው ቦታ ተደርገው ተነግረዋል። በኢየሩሳሌም የሚገኙ መሪዎች በውሸት እንደሚታመኑ አልተናገሩም። በእርግጥ ደኅንነታቸው አስተማማኝ እንደሆነ አምነዋል። ነገር ግን በውሸት ስለታመኑ ደኅንነታቸው አስተማማኝ እንዳልሆነ ኢሳይያስ ያውቃል። አት:- "ውሸትና ሐሰት ከአደጋ ልንሸሸግባቸው እንደምንችልባቸው ቦታ ሆነዋልና' (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ውሸትን መሸሸጊያችን ... በሐሰትም ተሰውረናልና
ሊሆኑየሚችሉ ትርጉሞች:- 1) መሪዎቹ ራሳቸውን ለመጠበቅ በዋሹአቸው በገዛ ራሳቸው ውሸቶች ይታመናሉ ወይም 2) መሪዎቹ ከሙታን መኖሪያ ሐሰተኛ አማልክት ጋር ያደረጉት ኪዳን በሰላም እንደሚጠብቃቸው ይታመናሉ ወይም 3) መሪዎቹ ከግባጻውያን ጋር ያደረጉት ስምምነት በሰላም እንደሚጠብቃቸው ይታመናሉ
Isaiah 28:16
እይ
"ተመልከት' ወይም "ስማ' ወይም "ለምነግርህ ትኩረት ስጥ'
በጽዮን የመሠረት ድንጋይ አስቀምጣለሁ ... የጸናውን መሠረት
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ለመርዳት ጠንካራ ሰው መላኩ እግዚአብሔር ለአንድ ሕንፃ ጠንካራ መሠረት እንደሚገነባ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የተፈተነውን ድንጋይ
"ጠንካራ የሆነውን ድንጋይ'
አስተማማኝ መሠረት
"ጽኑ ደጋፊ'
የሚያምንም አያፍርም
"ማንም በዚህ የመሠረት ድንጋይ የሚታመን አይጸጸትም'
Isaiah 28:17
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ በኢየሩሳሌም የሚያደርገውን ሕንፃን ከሚመሠርት ገንቢ ጋር ማነጻጸሩን ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 28:16)
ለመለኪያ ገመድ ፍትህን ለቱምቢም ጽድቅን አደርጋለሁ
ሕዝቡ ፍትሐዊና ጻድቅ መሆኑን ለመወሰን እግዚአብሔር በፍርዱና በጽድቁ መሠረት መፈተኑ አንድ ነገር ተገቢ ቁመት ያለውና ፍጹም የተስተካከለ መሆኑን ለመወሰን መለኪያ መሣሪያዎች እንደሚጠቀም ግንበኛ ተደርጎ ተገልጾአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
መለኪያ ገመድ
ግንበኛ የአንድ ነገር ቁመት ትክክል እንደሆነ ለመወሰን መለኪያ ገመድ ይጠቀማል።
ቱምቢ

ግንበኛ አንድ ነገር ቀጥ ያለና የተስተካከለ መሆኑን ለመወሰን ቱምቢ ይጠቀማል።
በረዶ ጠርጎ ይወስደዋል
እግዚአብሔር ከፍተኛ መጠን ያለው በረዶ እንዲወርድ ማድረጉ የሚያጠለቀልቅ ጎርፍ እንደሚሆን ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "የበረዶ ዶፍ ያጠፋል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በረዶ ... የውኃ ሙላት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ጥፋትን የሚያስከትል የትኛውንም ነገር በአጠቃለይ የሚወክሉ ተለዋጭ ስሞች ናቸው ወይም 2) የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ለማጥፋት እግዚአብሔር የሚልከውን የጠላት ሠራዊት የሚያመለክት ስዕላዊ ንግግር ነው (ተለዋጭ ስምና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የውሸቶች መሸሸጊያ ... መሰወሪያ
ይህ ውሸቶች ሰው ሄዶ እንደሚሸሸግባቸው ቦታ አድርጎ ይናገራል። የኢየሩሳሌም መሪዎች ከእግዚአብሔር ቁጣ ይጠብቀናል ብለው የታመኑበትን ይወክላሉ። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) መሪዎቹ ራሳቸውን ለመጠበቅ በተናገሩት በገዛ ራሳቸው ውሸቶች ይታመናሉ ወይም 2) መሪዎቹ በሰላም እንዲጠብቃቸው ከሙታን መኖሪያ የሐሰት አማልክት ጋር ባደረጉት ቃል ኪዳን ይታመናሉ ወይም 3) መሪዎቹ በሰላም እንዲጠብቃቸው ከግብፃውያን ጋር ባደረጉት ስምምነት የታመናሉ። ተመሳሳይ ሐረግ በኢሳይያስ 28፡15 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (ስዕላዊ ንግግር እና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
Isaiah 28:18
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።
ከሞትም ጋር ያደረጋችሁት ቃል ኪዳን ይፈርሳል፣ ከሲኦልም ጋር የተማማላችሁት መሐላ አይቆምም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ከሞት ጋር ያላችሁን ቃል ኪዳን ከሲኦልም ጋር ያላችሁን ስምምነት እሰርዛዋለሁ።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ከሞት ጋር ... ቃልኪዳን ... ከሲኦልም ጋር ስምምነት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) የኢየሩሳሌም መሪዎች የሙታን መኖሪያ አማልክት ከመሞት እንዲጠብቋቸው ከእነርሱ ጋር ስምምነት ለማድረግ በመጣር አስማትና ጥንቆላ ተጠቅመዋል ወይም 2) ይህ መሪዎቹ ከግብጽ መሪዎች ጋር ስምምነት ማድረጋቸውን የሚገልጽ ስዕላዊ ንግግር ነው። የኢየሩሳሌም መሪዎች ከሙታን መኖሪያ አማልክት ጋር ስምምነት እንዳደረጉ ሁሉ ግብጻውያንም ጥበቃ ማድረግ እንደሚችሉ ተማምነዋል። ይህንን በኢሳይያስ 28፡15 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
አይቆምም
"አይጸናም'
የሚጠራርግ ጎርፍ ባለፈ ጊዜ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ጎርፍ ጥፋት ሊያደርስ የሚችል የትኛውንም ነገር በአጠቃለይ የሚወክል ተለዋጭ ስም ነው ወይም 2) ጎርፍ የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ለማጥፋት እግዚአብሔር የሚልከውን የጠላት ሠራዊት የሚያመለክት ስዕላዊ ንግግር ነው (ተለዋጭ ስምና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በእርሱ ትጥለቀለቃላችሁ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ያጥለቀልቃችኋል' ወይም "ያጠፋችኋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ማለዳ ማለዳ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "በየቀኑ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ቀንና ሌሊት
"ሙሉ ቀኑን' ማለት ነው። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 28:20
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።
ሰው በእርሱ ላይ ተዘርግቶ ቢተኛ አልጋው አጭር ነው፤ ሰውም ሰውነቱን መሸፈን ቢወድድ መጎናጸፊያ ጠባብ ነው
ይህ ምናልባት ሕዝቡ በዚያ ዘመን የሚያውቀው ምሳሌ ነው። በጣም አጭር እንደሆነ አልጋ ወይም በጣም ጠባብ እንደሆነ መጎናጸፊያ ከእግዚአብሔር ቅጣት በሳለም ይጠብቀናል ብለው የተማመኑበት ያሳዝናቸዋል። (ምሳሌዎች ተመልከት)
እግዚአብሔር ይነሣል
እግዚአብሔር ለሥራ መዘጋጀቱ ተቀምጦ እንደነበረና እንደሚነሣ ተደርጎ ተነግሮአል።
በፐራሲም ተራራ ... በገባዖንም ሸለቆ
እነዚህ እግዚአብሔር የጠላትን ሠራዊት በተዓምራት ያሸነፈባቸውን ቦታዎች ያመለክታሉ። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ እና የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
ራሱን ይቀሰቅሳል
"ይቆጣል
እንግዳ ሥራውን ... ያልታወቀ አድራጎቱን
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ነገር ይናገራሉ። የኢየሩሳሌም ሕዝብ ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ ከመርዳት ይልቅ የኢየሩሳለምን ሕዝብ ለማሸነፍ እግዚአብሔር የጠላትን ሠራዊት መጠቀሙ እንግዳ ሥራ ነው።
Isaiah 28:22
አሁን
ይህ "በዚቹ ቅጽበት' ማለት ሳይሆን ወደ የሚከተለው አስፈላጊ ነጥብ ትኩረትን ለመሳብ ጥቅም ላይ የዋለ ነው።
እስራታችሁ ይጠብቃል
የእግዚአብሔር ሕዝቡን መቅጣት እጅግ በከፋ ሁኔታ እስራታቸውን እንደሚያጠብቅ ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር እስራታችሁን ያጠብቃል' ወይም "እግዘአብሔር በጣም በከፋ ሁኔታ ይቀጣችኋል' (ስዕላዊ ንግግርና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በኢሳይያስ 1፡9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
በምድር ላይ የተወሰነውን ጥፋት
ጥፋት የሚለው የነገር ስም አጠፋ በሚለው ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "በመላ ምድሪቱ ሕዝቡን ያጠፋል' (የነገር ስም ተመልከት)
Isaiah 28:23
አጠቃላይ መረጃ
ይህ በ28፡29 የሚያልቀውን ምሳሌ ይጀምራል። (ምሳሌዎች ተመልከት)
አድምጡ ድምፄንም ስሙ፣ልብ አድርጉ ንግግሬንም ስሙ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት አንድ ነገር ነው። ሁለተኛው ሐረግ የመጀመሪያውን ለማጠናከር ጥቅም ላይ የዋለ ነው። (አጓዳኝነት ተመልከት)
ድምፄንም
በዚህ ስፍራ ድምፅ የሚለው ኢሳይያስ የተናገረውን ይወክላል። አት፡- "ለተናገርኩት' (ምትክ ቃል ተመልከት)
ንግግሬንም
መልእክቴንም
ለመዝራት ቀኑን ሙሉ የሚያርስ ገበሬ ሁልጊዜ ያርሳልን? ወይስ ሁልጊዜ እርሻውን ይገለግላልን? ጓሉንስ ይከሰክሳልን?
ሕዝቡ በጥልቀት እንዲያስብ ኢሳይያስ አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠቀማል። አት፡- "ገበሬ ዘርን ሳይዘራ መሬትን ደግሞ ደጋግሞ አያርስም ያለማቋረጥም አፈሩ ላይ አይሰራም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
Isaiah 28:25
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ምሳሌውን መንገሩን ይቀጥላል። (ምሳሌዎች ተመልከት)
እርሻውን ባስተካከለ ጊዜ
ገበሬው መሬቱን ባረሰ ጊዜ
ጥቁሩን አዝሙድ፣ ከሙኑንም፣ ስንዴውንም በተርታ፣ ገብሱንም በስፍራው፣ አጃንም በዳርቻው የሚዘራ አይደለምን
ኢሳይያስ የኢየሩሳሌም ሰዎች በጥልቀት እንዲያስቡ ጥያቄ ይጠቀማል። ቋንቋህ ለእያንዳንዱ የዘር ዓይነት ቃል ከሌለው ጠቅለል ተደርገው ሊገለጹ ይችላሉ። አት፡- "በእርግጥ እያንዳንዱን የዘር ዓይነት በትክክለኛው መንገድና በተገቢው ቦታ ይተክላል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
አዝሙድ ... ከሙን
እነዚህ የቅመማ ቅመም ተክሎች ስሞች ናቸው። (የማይታወቁትን ስለመተርጎም ተመልከት)
ስንዴ ... ገብስ ... አጃ
እነዚህ የእህል ተክሎች ስሞች ናቸው። ተርጓሚዎች በአጠቃለይ የእህል የዘር ዓይነቶች በሚል ሊወክሏቸው ይችላሉ። (የማይታወቁትን ስለመተርጎም ተመልከት)
ይህንም ብልሃት አምላኩ ያስታውቀዋል ያስተምረዋልም


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ነገር ይናገራሉ። አት፡- "ገበሬው እያንዳንዱን የተክል ዓይነት እንዴት መንከባከብ እንዳለበት እንዲያውቅ እግዚአብሔር ይረዳዋል' (አጓዳኝነት ተመልከት)
Isaiah 28:27
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለኢየሩሳሌም ምሳሌ መንገሩን ይቀጥላል። (ምሳሌዎች ተመልከት)
ጥቁር አዝሙድ በተሳለች ማሄጃ አያኼድም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ገበሬው የጥቁር አዝሙድን ፍሬ ከተክሉ በከባድ ማሄጃ አይለይም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ጥቁር አዝሙድ
ይህንን በኢሳይያስ 28:25 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ወይም የሰረገላ መንኮራኵር በከሙን ላይ አያዞርም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ወይም ከባድ መንኮራኩር በከሙን ዘር ላይ አያሽከረክርም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ከሙን
ይህንን በኢሳይያስ 28:25 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ነገር ግን ጥቁር አዝሙድ በሽመል ከሙኑንም በበትር ይወቃል
ፍሬውን ከተክሉ ለመለየት ለገበሬው ትክክለኛ የሆነውን መንገድ ኢሳይያስ ይገልጻል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ነገር ግን ጥቁር አዝሙዱን በሽመል ይወቃዋል፣ ከሙንም በዱላ ይወቃዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
እህል ለእንጀራ ይወቃል እንጂ ፈጽሞ አይደቅም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ገበሬ እህልን ለእንጀራ ይወቃዋል እንጂ በጣም ትንንሽ እንዲሆን አይወቃውም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
Isaiah 28:29
ይህም በጥበብ ግሩም ከሆነው መጥቶአል
ይህ በኢሳይያስ 28:23 የተጀመረውን ምሳሌ ይቋጫል። ስለ መዝራትና መውቃት የእግዚአብሔርን መመሪያ ለመስማት ገበሬዎቹ አስተዋዮቹ መሆናቸው ምሳሌው የሚያመለክተው ትምህርት ነው። ነገር ግን የኢየሩሳሌም መሪዎች በኢሳይያስ በኩል የሚናገረውን የእግዚአብሔር መመሪያ የማይሰሙ ሞኞች ናቸው። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ)
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በኢሳይያስ 1:9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

---

Chapter 29
Isaiah 29:1
ወዮ ለአርኤል
በዚህ ስፍራ አርኤል የሚለው በአርኤል ከተማ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አት፡- ለአርኤል ሰዎች እጅግ አስፈሪ ጊዜ ይሆናል (ምትክ ቃል ተመልከት)
አርኤል
የኢየሩሳሌም ሌላኛው ስም ሲሆን "መሠዊያ' ማለት ነው። "አርኤል' የሚለው ትርጉም በ29:2 ላይ አስፈላጊ ስለሆነ ከተቻለ "ኢየሩሳሌም' በማለት ፈንታ ይህንን "አርኤል' ብለህ ተርጉም።
ዳዊት ለሰፈረባት
"ዳዊት ላደረባት' ወይም "ዳዊት ለኖረባት'
ዓመት በዓመት ላይ ጨምሩ፣ በዓላትም እየዞሩ ይምጡ
"ዓመት በዓመት በዓላቶቻችሁን ማክበር ቀጥሉ።' ይህ የምፀት ንግግር ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለእርሱ በሚሠውቡት ስፍራ በዓላቶቻቸውን ማክበር እንዲቀጥሉ ይነግራቸዋል ነገር ግን እነርሱን ከማጥፋት እንደማይከለክለው ያውቃል። (ምፀት ተመልከት)
እከብባታለሁ
በዚህ ውስጥ "እኔ' የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል። ይህ እግዚአብሔር የጠላትን ሠራዊት ኢየሩሳሌምን እንዲከብብ ማደረጉን ይወክላል። (ምትክ ቃል ተመልከት)
እርሷም
በዚህ ስፍራ "እርሷ' የሚለው የአርኤልን ሕዝብ የምትወክለውን አርኤልን ያመለክታል። አት፡- "የአርኤልም ሕዝብ' (ምትክ ቃል ተመልከት)
ልቅሶና ዋይታ
በመሠረቱ ልቅሶና ዋይታ የሚሉት ቃላት ትርጉማቸው አንድ ሲሆን ለለቅሶው ክብደት አጽንዖት የሚሰጥ ነው። (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)
እንደ አርኤል
ተርጓሚዎች "አርኤል የሚለው ስም 'መሠዊያ' ማለት ነው' የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይችላሉ።
Isaiah 29:3
በዙሪያሽም እሰፍራለሁ
በዚህ ውስጥ "እኔ' የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል፡ ይህ እግዚአብሔር የጠላትን ሠራዊት ኢየሩሳሌምን እንዲከቡ ማድረጉን ይወክላል። አት፡- "የጠላቶችሽን ሠራዊት እንዲከቡሽ አዝዛለሁ' (ምትክ ቃል ተመልከት)
ቅጥር ... የከበባ ሥራ
"ቅጥር' ከረጃጅም ግንቦች ከተሞችን ለማጥቃት ሠራዊቶች የሚገነቡት ማማ ነው። "የከበባ ሥራዎች' ከተሞችን ለማጥቃት ሠራዊቶች የሚገነቧቸውን የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን ያመለክታል። (የማይታወቁትን ስለመተርጎም ተመልከት)
ትዋረጃማለሽ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ጠላትሽ ወደ ታች ያወርድሻል ወይም ጠላትሽ ዝቅ ያደርግሻል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
በመሬትም ላይ ሆነሽ ትናገሪያለሽ፣ ቃልሽም ዝቅ ብሎ ከአፈር ይወጣል፣ ድምጽሽም ከመሬት እንደሚወጣ እንደ መናፍስት ጠሪ ድምጽ ይሆናል፣ ቃልሽም ከአፈር ወጥቶ ይጮኻል
በመሠረቱ እነዚህ ሁሉ ዐረፍት ነገሮች የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ነው። አንድ ወቅት በትዕቢት ቃላት ይናገሩ የነበሩ ሰዎች ጠላታቸው ካሸነፋቸው በኋላ ደካሞችና ሐዘንተኞች እንደሚሆኑ አጽንዖት ይሰጣል። አት፡- "ሙታን ከሚያድሩበት ስፍራ መንፈስ እንደሚናገረ እንዲሁ በደካማና የሽክሹክታ ድምፅ ብቻ ትናገራላችሁ' (ዘይቤአዊ ንግግርና አጓዳኝነት ተመልከት)
Isaiah 29:5
የወራሪዎችሽ ብዛት እንደ ደቀቀ ትቢያ፣ የጨካኞችም ብዛት እንደሚያልፍ ገለባ ይሆናል
ወራሪው ሠራዊት በእግዚአብሔር ምን ያህል ደካማና እዚህ ግባ የማይባል መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል። አት፡- "እግዚአብሔር የወራሪዎችሽን ብዛትና የጨካኞቹን ብዛት በቀላሉ ያስወግዳል።' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
የወራሪዎችሽ ብዛት
ጥቃት የሚያደርሱብህ ብዙ ወታደሮች
ጨካኞቹ ... እንደ ገለባ
ተርጓሚው "ይሆናሉ' የሚለውን ማሰሪያ አንቀጽ መጠቀም ይችላል። አት፡- "ምሕረት የማያሳዩሽ ወታደሮች እንደ ገለባ ይሆናሉ' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያግዱሉ የተዘለሉ ተመልከት)
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ወደ አንቺ ይመጣል
አንቺ የሚለው ቃል የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ያመለክታል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሊረዳሽ ይመጣል' ወይም 2) "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሊቀጣሽ ይመጣል' (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች)
Isaiah 29:7
እንደ ሕልምና እንደ ሌሊት ራእይ ይሆናል
"የሌሊት ራእይ' የሚለው ሐረግ "ሕልም' ከሚለው ጋር ተመሣሣይ ነው። ሁለቱ ሐረጎች በዚያ እንዳልነበረ እንደ ወራሪው ሠራዊት ፈጥኖ እንደሚሆን አጽንዖት ይሰጣሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት እና ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)
የሕዝቦች ሁሉ ብዛት
"ከሕዝቦች ሁሉ የሆነ ታላቅ ሠራዊት'
አርኤልን የሚዋጉ
"አርኤል' የሚለው ስም የኢየሩሳሌም ሌላ ስም ሲሆን፣ በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። "አርኤልን' በኢሳይያስ 29:1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፡- "የአርኤልን ሰዎች የሚዋጉ' (ምትክ ስም ተመልከት)
ምሽጎችዋ። እርስዋን ለመጫን እርሷንና ምሽጎችዋን ይወጋሉ
"እርስዋ' የሚለው ቃል በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች የምትወክለውን አርኤልን ያመለክታል። አት፡- "ምሽጎቻቸው። የአርኤልን ከተማና መከላከያዎቿን ይወጋሉ ሕዝቡንም በታላቅ በመከራ ውስጥ እንዲገባ ያደርጋሉ።' (ምትክ ስም ተመልከት)
የተራበ ሰው በሕልሙ እንደሚበላ ይሆናል ... ጥሙ እንደማይረካ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እነዚህ ዘይቤአዊ ንግግሮች ጠላቶች ድል ቢጠብቁም እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን እንዲያሸንፉ ስላልፈቀደላቸው አልተሳካላቸውም ማለት ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

እንዲሁ የጽዮንን ተራራ የሚወጉ የአሕዛብ ሁሉ ብዛት ይሆናል

በዚህ ስፍራ የጽዮን ተራረ የሚለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አት፡- "አዎን፣ በጽዮን ተራራ የሚኖሩትን ሰዎች በሚወጉ የሕዝቦች ሠራዊት ላይ ይህ ይሆናል' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 29:9

ራሳችሁ ተደነቁ፣ ተደነቁም

"ራሳችሁ' የሚለው ቃል በኢየሩሳልም የሚኖሩትን ሰዎች ያመለከታል። ለምን እንደሚደነቁ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አት፡- "እየነገርኳችሁ ባለው ነገር ተደነቁ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ እና የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

ራሳችሁን አሳውሩ እውሮችም ሁኑ

ሕዝቡ እግዚአብሔር የሚለውን ችላ ማለታቸው ራሳቸውን እንዳሳወሩ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ለማሳያችሁ ነገር ቸልተኛና በመንፈስ እውር በመሆን ቀጥሉ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በወይን ጠጅ አይሁን እንጂ ስክሩ፤ በሚያሰክር መጠጥ አይሁን እንጂ ተንገድገዱ

ሕዝቡ ማስተዋል የጎደላቸውና እግዚአብሔር እያደረገ ያለው ነገር የማይረዱ መሆናቸው ሰካራሞች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እንደ ሰካራም ሰው ማስተዋል የጎደላችሁ ሁኑ ነገር ግን ብዙ ወይንና የሚያሰክር መጠጥ ስለጠጣችሁ አይሁን።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እግዚአብሔር የጥልቅ እንቅልፍ መንፈስ አፍስሶባችኋል

በዚህ ስፍራ "የ... መንፈስ' ማለት የእንቅልፋምነት ባሕርይ ያለው መሆን ማለት ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲተኛ ማድረጉ "መንፈሱ' በሕዝቡ ላይ የሚያፈስሰው ፈሳሽ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮል። "ጥልቅ እንቅልፍ' ማለት ሕዝቡ ማስተዋል የጎደለውና እግዚአብሔር እያደረገ ያለውን የማይረዳ ነው የሚል ትርጉም ያለው ስዕላዊ ንግግር ነው። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ዓይኖቻችሁን ከድኖታል፣ ነቢያቱን፣ ራሶቻችሁንም ሸፍኖታል፣ ባለራእዮችን

እግዚአብሔር ሕዝቡን ማስተዋል የጎደላቸውና እርሱ እየፈጸመው ያለውን የማይረዱ ማድረጉ ማየት እንዳይችሉ ዓይኖቻቸውን እንደከደነውና ራሶቻቸውን እንደሸፈነው ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እንዲሁም እግዚአብሔር የነቢያቱን ዓይኖች ከድኖአል የባለራእዮቹንም ራሶች ሸፍኖአል' ((ስዕላዊ ንግግርተመልከት))

Isaiah 29:11

ራእዩም ሁሉ እንደ ታተመ መጽሐፍ ቃላት ሆኖባችኋል

በኢየሩሳሌም የሚገኙ ሌሎቹ ነቢያት የእግዚአብሔርን መልእክት መስማትና መረዳት አልቻሉም። አት፡- "እግዚአብሔር ለእናንተ የገለጠው ሁሉ የታተመ መጽሐፍ ይመስላል።' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ታተሞአል፣ ለተማረውም ሰጡት

ይህ በአዲስ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ታትሞአል። አንድ ሰው የታተመውን መጽሐፍ ማንበብ ለሚችል ለአንድ ሰው ሰጠው።'

መጽሐፉ ማንበብ ለማይችል ለአንዱ ከተሰጠው

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "አንድ ሰው መጽሐፉን ማንበብ ለማይችል ከሰጠው' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 29:13

ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባል፣ በከንፈሮቹም ያከብረኛል

"አፍ' እና "ከንፈር' የሚሉት ቃላት ሕዝቡ የሚናገረውን ይወክላሉ። በዚህም ስፍራ አንድ ነገር መናገርን ነገር ግን በእውነታው የተባለውን የማይል ንግግርን ይወክላል። አት፡- "የኢየሩሳሌም ሰዎች በንግግር እኔን የሚያመልኩና የሚያከብሩ ያስመስላሉ' (ምትክ ስም ተመልከት)

ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው

በዚህ ስፍራ "ልብ' የሚለው የሰውን አሳብና ስሜት የሚወክል ምትክ ስም ነው። ለእግዚአብሔር በእውነት ያልተሰጠ ሕዝብ ልቡ ከእርሱ ርቆ እንደ ሄደ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ነገር ግን በአሳቡ አያከብረኝም' ወይም "ነገር ግን በእውነት ለእኔ የተሰጠ አይደለም' (ምትክ ስም እና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በሰዎች ሥርዓትና ትምህርት ብቻ ያከብሩኛል

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሰዎች እንዲያደርጉ የነገሯቸው ያ ስለሆነ ብቻ ያከብሩኛል' (አድረጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ስለዚህ፣ እይ፣ በዚህ ሕዝብ መካከል ድንቅ ነገር እንደገና አደርጋለሁ፣ በተዓምራት ላይ ተዓምራት

"ስለዚህ ተመልከትና እይ! ልታብራራቸው የማትችላቸውን አስደናቂና አስገራሚ ነገሮች በመካከልህ አደርጋለሁ'

የጥበበኞቻቸው ጥበብ ትጠፋለች፣ የአስተዋዮቻቸውም ማስተዋል ትሰወራለች

ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች አንድ ነገር ይናገራሉ። እግዚአብሔር ያደረገውን ጠቢባን ሰዎች ሊረዱና ሊያብራሩ አለመቻላቸውን እግዚአብሔር መግለጡ ጥበባቸውና ማስተዋላቸው እንደጠፋ ተደርጎ ተነግሮአል። (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 29:15

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ እየተናገረ ነው ወይም የ29፡13-14 የእግዚአብሔር ንግግር ቀጥሏል

እቅዳቸውን ጥልቅ አድርገው ከእግዚአብሔር ለሚሰውሩ

ሕዝቡ እግዚአብሔር ስለ እቅዱ ሳያውቅ ለማቀድ መሞከራቸው እግዚአብሔር ሊያይ በማይችልበት በጥልቅ ስፍራ እቅዳቸውን ለመሰውር እንደፈለጉ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እቅዳቸውን ከእግዚአብሔር ለመሰወር የሚጥሩ' ወይም "ለማድረግ ያቀዱትን እግዚአብሔር እንዳይደርስበት ለመከልከል የሚጥሩ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ሥራቸው በጨለማ የሆነ

በምስጢር ክፉ ነገሮችን እንደሚያደርጉ ተመላክቷል። አት፡- "ማንም ሊያያቸው እንዳይችል ክፉ ነገሮችን በጨለማ ውስጥ የሚያደርጉ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ማን ያየናል? ማንስ ያውቀናል የሚሉ?

የሚያደርጉትን ማንም እንደማያውቅ ማመናቸውን አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠቀማሉ። አት፡- "የምናደርገውን ማንም እግዚአብሔርም እንኳን አያየንም ወይም አያውቅም!' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

Isaiah 29:17

ሊባኖስ ወደ እርሻነት ይለወጣል፣ እርሻውም ዱር ይሆናል

ሊሁኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ ቃል በቃል የሚተረጎም፣ እግዚአብሔር በሊባኖስ የዱር ዛፍ የሚያድግባቸውን ስፍራዎች ፍሬ የሚሰጡ እርሻዎች እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው የሚናገር ነው ወይም 2) ይህ በስዕላ ንግግርነት የሚተረጎም ሲሆን የሊባኖስ ትላልቅ ደኖች ኃያላን ጨቋኝ ገዢዎችን፣ ወደ ደንነት የሚለወጠው የእርሻው ሰብል ደግሞ መከራ እያየ ያለውን ተራውን ሕዝብ የሚወክሉ ናቸው። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ሊባኖስ ወደ እርሻነት ይለወጣል

በዚህ ስፍራ "ሊባኖስ' የሚለው በሊባኖስ የሚገኘውን ትልቁን የጥድ ደን ይወክላል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ታላላቅ የሊባኖስ ደኖችን ወደ እርሻነት ይለውጣቸዋል' (ምትክ ስምና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ደንቆሮች የመጽሐፍ ቃል ይሰማሉ፣የዕውሮችም ዓይኖች ከጥልቅ ጨለማ ውስጥ ያያሉ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ ቃል በቃል እግዚአብሔር ደንቆሮች እንዲሰሙ እውሮችም እንዲያዩ ያደርጋል ማለት ነው ወይም 2) እግዚአብሔር ሕዝቡን መልእክቱን እንዲሰሙና እንዲረዱ ያስችላቸዋል የሚል ትርጉም ያለው ስዕላዊ ንግግር ነው ወይም 3) ሁለቱንም አማራጮች 1 እና 2 ማለት ሊሆን ይችላል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የዕውሮች ዓይኖች

በዚህ ስፍራ ዓይኖች የሰውን ሁለንተና ይወክላሉ። አት፡- "ዕውራን የሆኑቱ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

የተጨቆኑ እንደገና በእግዚአብሔር ደስ ይላቸዋል፣ በሰዎች መካከል ያሉ ድሆችም በእስራኤል ቅዱስ ደስ ይላቸዋል

በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉማቸው አንድ ነው። አት፡- "ድሆችና የተጨቆኑ ሰዎች እግዚአብሔር፣ የእስራኤል ቅዱሱ ካደረገው ነገር የተነሳ እንደገና ደስ ይላቸዋል።' (አጓዳኝነት ተመልከት)

Isaiah 29:20

ጨካኞች ይጠፋሉና

"ጨካኞች' የሚለው ስማዊ ቅጽል፣ በቅጽልነት ሊቀመጥ ይችላል። አት፡- "ጨካኞች ሰዎች ይጠፋሉና' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

ፌዘኞቹ ይጠፋሉና

"ፌዘኞች' የሚለው ስማዊ ቅጽል በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተርጎም ይችላል። አት፡- "የሚያፌዙ ይጠፋሉና' ወይም "የሚያሾፉ ሰዎች ይጠፋሉና' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

ክፉ ለማድረግ የሚወዱ ሁሉ ይጠፋሉ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ክፉ ማድረግ የሚወዱትን ሁሉ እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
በቃል ሰውን በደለኛ የሚያደርጉ
ይህ በችሎት አንድን ሰው በመቃወም ምስክርነትን መስጠትን ያመለክታል። አት፡- "አንድን ሰው በመቃወም የሚመሰክርና በደለኛም የሚያደርገው' ወይም "አንዳች ስሕተት ፈጽሟል በሚል ችሎት ላይ ንጽሑን ሰው በደለኛ የሚያደርግ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
በበርም ላይ ፍትሕ ለሚፈልግ ወጥመድ የሚያኖሩ ጻድቁንም በባዶ ሐሰት እንዲሸማቀቅ የሚያደርጉ
መልካሙን ሰው ለማስቆም ክፉ ሰዎች የሚያደርጉት የትኛውም ነገር አዳኝ የሚያድነውን አጥምዶ እንደሚይዝ እንደዚያው ክፉ ሰዎች ወጥመድ እንደሚያጠምዱ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ተገቢና ትክክል የሆነውን የሚያደርጉትን ለማስቆም ይጥራሉ ይዋሻሉም።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በበር ላይ ፍትሕ ለሚፈልግ
የከተማይቱ በር ብዙውን ጊዜ የከተማይቱ መሪዎች ሕጋዊ ውሳኔዎችን የሚያስተላልፉበት ቦታ ነው።
Isaiah 29:22
የያዕቆብ ቤት
በዚህ ስፍራ "ቤት' የሚለው ቤተሰብን ይወክላል። አት፡- "የያዕቆብ ትውልዶች' (ምትክ ስም ተመልከት)
አብርሃምን የተቤዠ
ይህ ምናልባት የሚያመለክተው እግዚአብሔር አብርሃምን ከትውልድ አገሩ የጠራበትንና ወደ ተስፋይቱ ምድር የላከበትን ጊዜ ነው። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ያዕቆብ ከእንግዲህ ወዲያ ... ፊቱ ... ልጆቹን ያያል
በዚህ ስፍራ "ያዕቆብ' የሚለው ትውልዶቹን ይወክላል። አት፡- "የያዕቆብ ትውልዶች ከእንግዲህ ወዲያ ... ፊታቸው ... ልጆቻቸውን ያያሉ' (ምትክ ስም ተመልከት)
ወይም ፊቱ አይለወጥም
ከእንግዲህ ወዲያ አይፈራም የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "ወይም አይፈሩም' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ነገር ግን የእጆቼን ሥራ ልጆቹን ባየ ጊዜ
በዚህ ስፍር እጅ የሚለው የእግዚአብሔርን ኃይልና ሥራ ይወክላል። አት፡- "የሰጠኋቸውን ልጆችና ያደረግሁላቸውን ሁሉ ባየ ጊዜ' (ምትክ ቃል ተመልከት)
ስሜን ይቀድሳሉ
በዚህ ስፍራ "ስም' እግዚአብሔርን ይወክላል። አት፡- "ያከብሩኛል' (ምትክ ስም ተመልከት)
የያዕቆብን ቅዱስ ስም ይቀድሳሉ
በዚህ ስፍራ "ስም' እግዚአብሔርን ይወክላል። እግዚአብሔር ራሱን "የያዕቆብ ቅዱስ' ብሎ ይጠራል። አት፡- "የያዕቆብን ቅዱስ፣ እኔን ያከብሩኛል።' (ምትክ ስምና አንደኛ፣ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)
የእስራኤልንም አምላክ
እግዚአብሔር ራሱን "የእስራኤል አምላክ' ብሎ ይጠራል። አት፡- "እኔን፣ የእስራኤልን አምላክ' (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)
በመንፈስ የሳቱ
በዚህ ስፍራ "መንፈስ' የሚለው የሰውን ውስጣዊ ማንነት ይወክላል። አት፡- "በሚያስቡት የተሳሳቱ' ወይም "በዝንባሌአቸው የተሳሳቱ' (ምትክ ስም ተመልከት)
መረዳትን ያገኛሉ
የሚረዱት ምን እንደሆነ በማብራራት ይህ በይበልጥ ገልጽ ሊሆን ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔርንና ሕግጋቱን መረዳት ይጀምራሉ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
የሚያጉረመርሙ እውቀትን ይማራሉ
የሚማሩት እውቀት ምን እንደሆነ በማብራራት ይህ በይበልጥ ግልጽ ሊሆን ይችላል። አት፡ "የሚያጉረመርሙ እግዚአብሔር የሚያስተምራቸው እውነት እንደሆነ ማወቅ ይጀምራሉ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

---

Chapter 30
Isaiah 30:1
ዓመፀኞቹ ልጆች
እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ልጆቹ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኝነት ለመግለጽ እግዚአብሔር በራሱ ስም ይናገራል። አት፡- "እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው' ወይም "እኔ፣ እግዚአብሔር ያወጀኩት ይህ ነው' (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)
እቅዶችን ያወጣሉ፣ ነገር ግን ከእኔ አይደለም
እቅዶች የሚለው የነገር ስም አቀደ በሚል ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "ነገሮችን ለማድረግ አቀዱ፣ ነገር ግን እንዲያደርጉ የምፈልገውን አልጠየቁኝም' (የነገር ስሞች ተመልከት)
ነገር ግን በመንፈሴ አይመሩም
ይህ በአደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ነገር ግን መንፈሴ አይመራቸውም' (አድራጊ ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
በኃጢአት ላይ ኃጢአት ይጨምራሉ
ኃጢአት በማድረግ መጽናት ኃጢአቶች አንዳቸው በአንዳቸው ላይ እንደሚከመሩ ቁሳ ቁሶች ተደርገው ተነግረዋል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ከፈርዖን ዘንድ ጥበቃ ፈለጉ
"ጥበቃ' የሚለው የነገር ስም "ጠበቀ' በሚለው ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "እንዲጠብቃቸው ፈርዖንን ጠየቁት' (የነገሮች ስም ተመልከት)
በግብጽ ጥላ ይሸሸጋሉ
ከጠላት ሠራዊት የሚደረገው የግብጻውያን ጥበቃ ጥላ አንድን ሰው ከሚያቃጥል የፀሐይ ሙቀት እንደሚጠብቅ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "በሰላም እንዲጠብቋቸው በግብጻውያን ይታመናሉ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 30:3
አጠቃልይ መረጃ
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።
ስለዚህ የፈርዖን ጥበቃ እፍረት በግብጽም ጥላ መሸሸግ ውርደት ይሆንባችኋል
"ጥበቃ'፣ "እፍረት' እና "ውርደት' የተሰኙት የነገር ስሞች እንደ ቅጽሎች ወይም ማሰሪያ አንቀጾች እንዲገለጹ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "ፈርዖን ይጠብቀናል ስትሉ ስለታመናችሁ ታፍራላችሁ፣ በሰላም እንዲጠብቋችሁ በግብጻውያን ስለታመናችሁ ትዋረዳላችሁ' (የነገር ስሞች ተመልከት)
በግብጽ ጥላ መሸሸግ
ከጠላት ሠራዊት የሚደረገው የግብጻውያን ጥበቃ ጥላ አንድን ሰው ከሚያቃጥል የፀሐይ ሙቀት እንደሚጠብቅ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ልዑላኖቻቸው
በዚህ ስፍራ ልዑላን ማለት ሕጋዊ ባለሥልጣን ወይም አምባሰደር ማለት ነው፣ የግድ የንጉሥ ልጆች ማለት አይደለም።
የእነርሱ ... እነርሱ ... እነሱ
እነዚህ ቃላት የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።
ዞአን ... ሓኔስ
እነዚህ በግብጽ ሰሜናዊ ክፍል የሚገኙ ከተሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
ወደ ሓኔስ ቢመጡ
በዚህ ስፍራ "መጣ' የሚለው "ሄደ' ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። (ሄደና መጣ ተመልከት)
ከሕዝቡ የተነሳ
"ከግብጽ ሕዝብ የተነሳ'
Isaiah 30:6
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ክፍል የይሁዳን ሕዝብ በሚመለከት የእግዚአብሔርን አዋጅ ማቅረቡን ይቀጥላል
አዋጅ
"እግዚአብሔር ይህን ያውጃል'
እንስትና ተባት አንበሳ፣ እፉኝትም የሚበርር ቁጡ እባብ
ይህ እንደ እነዚህ ዓይነት እንስሳትን በአጠቃላይ ያመለክታል። አት፡- "እንስትና ተባት አንበሳ በሚያድሩበት ስፍራ፣ እንዲሁም እፉኝትና እባብ ባለበት' (አጠቃላይ ስማዊ ሐረጎች ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ቁጡ በራሪ አባብ

በዚህ ስፍራ "ቁጡ' የሚለው ቃል ምናልባት የእባቡን መርዛማ መናደፍ ያመለክታል፣ "በራሪ' የሚለው ቃልም ፈጣን እንቅስቃሴውን ያመለክታል። ይህንን በኢሳይያስ 14፡ 29 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ኃብታቸውን ያግዛሉ

"የይሁዳ ሰዎች ኃብታቸውን ያግዛሉ'

እስካሁን የሚቀመጥ ረዓብ ብዬ ጠርቼዋለሁ

ስሙ ረዓብ ስለተባለ አስፈሪ የባሕር ፍጡር ታዋቂ የሆነ ታሪኮች አሉ። ረዓብ የሚለው ስም "ጥንካሬ' ወይም "አብሪት' ማለት ነው። አት፦ "ግብጽን ምንም የማያደርግ የሚጮኽ ጉረኛ ብዬ ጠርቼዋለሁ' (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

Isaiah 30:8

አጠቃላይ መረጃ

እግዚአብሔር ለኢሳይያስ መናገሩን ቀጥሏል

አሁንም

ቃሉ በዚህ ስፍራ ይሁዳን በሚመለከት የእግዚአብሔር አዋጅ ለጊዜው መቋረጡን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል።

ባሉበት

"የይሁዳ ሰዎች ባሉበት'

ለሚመጣው ዘመን

ይህ ጊዜን በሚመለከት እንደሚጓዝና አንድ ቦታ እንደሚደርስ አድርጎ ይናገራል። አት፦ "ለወደፊቱ ጊዜ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ሐሰተኞች ልጆች፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መስማት የማይወዱ ልጆች

ይህ ክፍል የእግዚአብሔር ሕዝብ ልጆቹ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "አኗኗራቸው እንደሚዋሹና እግዚአብሐር ያዘዛቸውን እንደማይሰሙ ልጆች ነው።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 30:10

አጠቃላይ መረጃ

እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል።

ከመንገድ ፈቀቅ በሉ፣ ከጎዳናውም ዘወር በሉ

ሕዝቡ እንዴት መኖር እንዳለባቸው እግዚአብሔር ያለው ፍላጎት በላዩ እንደሚከድበት መንገድ ወይም ጎዳና ተደርጎ ተነገሮአል። ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ሰውዬው ከእግዚአብሔር መንገድ ስቶ እንደሄደ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የእስራኤል ቅዱስ

ይህን ስም በኢሳይያስ 1፡4 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

Isaiah 30:12

የእስራኤል ቅዱስ

ይህን ስም በኢሳይያስ 1፡4 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ይህን ቃል አቃልላችኋል

ይህን መልእክት አቃልላችኋል

በግፍና በማታለል ታምናችኋል በእርሱም ተደግፋችኋል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፤- 1) የይሁዳ መሪዎች ሌሎችን በመጨቆንና በማታለል በሚገዙ በግብጻውያን መሪዎች ታምነዋል ወይም 2) የይሁዳ መሪዎች ገንዘባቸውን ለመውሰድና ለሚደርግላቸው ጥበቃ ለግብጻውያን መሪዎች ክፍያ ለመላክ የገዛ ሕዝባቸውን ይጮቁኑና ያታልሉ ነበር። (ስዕላዊ ንግግር ተመለከት)

በእርሱም ተደግፋችኋል

በዚህ ስፍራ "በእርሱ' የሚለው ግፍንና ማታለልን ያመለክታል። አት፦ "በእነርሱ ተደግፋችኋል' (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

በእርሱም ላይ

በአንድ ነገር ላይ መታመን ወይም መደገፍ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ ንግግር ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ስለዚህ ይህ በደል እንደ ፈረሰ ጎን ይሆንባችኋል ... በድንገት

ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ከበደላቸው የተነሣ እግዚአብሔር የይሁዳን ሕዝብ በድንገት ያጠፋቸዋል የሚል ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ለመውድቅ እንደ ቀረበ እንደ ፈረሰ ጎን

ይህ የተሰበረ የቅጥር ጎን እንደሆነ የሚታወቅ ነው። አት፦ "ለመውደቅ እንደቀረበ የፈረሰ የቅጥር ጎን' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

አወዳደቁም በድንገት እንደሚሆን

አወዳደቅ የሚለው የነገር ስም ወደቀ በሚል ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "በድንገት ይወድቃል' (የነገር ስም ተመልከት)

በድንገት፣ ፈጥኖ

እነዚህ አንድ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ቅጥሩ እንዴት ፈጥኖ እንደሚወድቅ አጽንዖት ይሰጣሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት)

Isaiah 30:14

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ እግዚአብሔር የይሁዳን ሕዝብ እንዴት እንደሚያጠፋ ይገልጻል። (ኢሳይያስ 30፡ 12-13 ተመልከት)

እርሱን ይሰብረዋል

በዚህ ስፍራ እርሱን የሚለው ሊወድቅ ያለውን የቅጥሩን ጎን ያመለክታል። የቅጥሩ ጎን የይሁዳን ሕዝብና በኢሳይያስ 30፡ 12-13 የተጠቀሰውን ኃጢአታቸውን የሚወክል ስዕላዊ ንግግር ነው። (ስዕላ ንግግር ተመልከትስ)

የሸክላ እቃ እንደሚሰበር

ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ወደ መሬት እንደ ወደቀ የሸክላ ማሰሮ የቅጥሩ ጎን ፈጥኖ እና ሙሉ ለሙሉ ይሰበራል ማለት ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

ሸክላ ሠሪ

ሸክላ ሠሪ ከሸክላ አፈር ገንቦና ማሰሮ የሚሠራ ሰው ነው።

አይገኝም

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ማንም ሊያገኘው አይችልም' ወይም "አይኖርም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የሚዛቅበት ስባሪ

"ለመዛቅ በቂ የሆነ ስባሪ'

እሳት ከምድጃ

"እሳት' የሚለው ቃል በዚህ ስፍራ አመድን ያመልክታል። አት፦ "አመድን ከእሳት ማንደጃ' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 30:15

የእስራኤል ቅዱስ

ይህን ስም በኢሳይያስ 1፡4 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

በመመለስና በማረፍ ትድናላችሁ

ንስሐ መግባት በአካል ወደ እግዚአብሔር እንደ መመለስ ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ንስሐ ከገባችሁና እንደምጠነቀቅላችሁ በማወቅ ካረፋችሁ ከጠላቶቻችሁ አድናችኋለሁ።' (ስዕላዊ ንግግር እና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በማረፍ

እግዚአብሔር እንደሚጠነቀቅላቸው ከማመን የተነሳ ሕዝቡ ማረፉን ያመለክታል። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

በጸጥታና በመታመን ኃይል ይሆንላችኋል

ጸጥታ በዚህ ስፍራ ተጨናቂና ስጉ አለመሆንን ያመለክታል። በእግዚአብሔር ከመታመናቸው የተነሣ የማይጨነቁ መሆናቸውን ያመለክታል። አት፦ ጸጥ ካላችሁና በእኔ ከታመናችሁ ትበረታላችሁ (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

በፈረስ ላይ ተቀምጠን እንሸሻለን

በግልጽ እነዚህ የይሁዳ ሰዎች ከግብጻውያን የወሰዱአቸው ፈረሶች ናቸው። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

Isaiah 30:17

ከአንድ ሰው ዛቻ የተነሳ ሺህ ሰዎች ይሸሻሉ ... ከአምስት ሰዎች ዛቻ የተነሳ ትሸሻላችሁ

"ወታደር' የሚለው ቃል ታሳቢ ሊደረግ ይቻላል። አት፦ "ከአንድ የጠላት ወታደር ዛቻ የተነሳ አንድ ሺህ ወታደሮች ይሸሻሉ ... ከአምስት የጠላት ወታደሮች ዛቻ የተነሳ ወታደሮቻችሁ ሁሉ ይሸሻሉ' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

አንድ ሺህ

"1000' (ቁጥሮች ተመልከት)

እናንተምበ በተራራ ራስ ላይ እንዳለ ሰንደቅ፣ በኮረብታም ላይ እንዳለ ሰንደቅ ዓላማ ሆናችሁ እስክትቀሩ ድረስ

ይህ ዘይቤአዊ ንግግር በተራራ አናት ላይ እንዳለ አንድ ነጠላ ሰንደቅ ዓላማ ጥቂት ሰዎች ይቀራሉ ማለት ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 30:18



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።
እናንተም ... ለእናንተ ... ይመልስላችኋል
በዚህ ስፍራ እናንተ የሚለው በጽዮን የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል።
ይመልስላችኋል
"ይረዳችኋል
Isaiah 30:20
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።
የጭንቀትን እንጀራና የመከራን ውኃ
በዚህ ስፍራ "እንጀራ" እና "ውኃ' በጣም ድሀ የሆነ ሰው ምግብ ነው። ሐረጉ እንዳለ የመከራን ጊዜና የሕዝቡን ድህነት ይወክላል። (ምትክ ስም ተመልከት)
አስተማሪህን
ይህ እግዚአብሔርን ያመለክታል።
አስተማሪህን በገዛ ዓይኖችህ ታያለህ
በዚህ ስፍራ "ዓይኖች' የሰወን ሁለንተና ይወክላሉ። አት፡- "አንተ ራስህ አስተማሪህን ታያለህ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
ጆሮችህ ይሰማሉ
በዚህ ስፍራ "ጆሮች' የሚለው የሰውን ሁለንተና ይወክላሉ። አት፡- "ትሰማለህ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
በኋላህ የሚለውን ቃል
ከኋላህ እንዲህ በማለት የሚናገረውን
መንገዱ ይህች ናት በእርስዋም ሂድ
ሕዝቡ እንዴት መኖር እንዳለባቸው እግዚአብሔር ያለው ፍላጎት በላዩ እንደሚከድበት መንገድ ወይም ጎዳና ተደርጎ ተነገሮአል። ለእግዚአብሔር መታዘዝ አንድ ሰው በእግዚአብሔር መንገድ እንደሄደ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ወደ ቀኝ ፈቀቅ ስትል ወይም ወደ ግራ ፈቀቅ ስትል
ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ከእግዚአብሔር መንግድ ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ ፈቀቅ እንደ ማለት ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 30:22
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።
እንደ አደፍ ጨርቅ ወዲያ ትወረውራቸዋለህ
ይህ ጣዖቶቻቸውን እንደ ቆሻሻ ወደዚያ ይጥሉአቸዋል የሚል ትርጉም ያለው ዘይቤአዊ ንግግር ነው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ከዚህ ሂዱ ትላቸዋልህ
ይህ ጣዖታት መስማት፣ መነሣትና አንድን ስፍራ ለቅቆ መሄድ እንደሚችሉ አድርጎ ይናገራል። ይህ ሕዝቡ ከእንግዲህ ወዲያ ጣዖታትን አይፈልጓቸውም ማለት ነው። (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)
Isaiah 30:23
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።
ይሰጣል
"እግዚአብሔር ይሰጣል'
ከምድር የተትረፈረፈ እንጀራ
በዚህ ስፍራ "እንጀራ' የሚለው ምግብን በአጠቃለይ ይወክላል። አት፡- "የምትመገበውን የተትረፈረፈ ፍሬ ምድር እንደትሰጥ ያደርጋታል' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
በዚያም ቀን
"በዚያን ጊዜ'
በመንሽና በመንሽ ሹካ የተለየውን
መንሽ እና መንሽ ሹካ ነፋሱ ሊበላ የሚችለውን ብቻ በመተው ገለባውን እንዲወስደው እህልን ወደ አየር ለመወርወር የሚያገለግሉ ናቸው። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "በመንሽና በመንሽ ሹካ ትለያለህ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
Isaiah 30:25
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል።
በረጅሙ ተራራ ሁሉ ... ሰባት ቀን የፀሐይ ብርሃን
ኢሳይያስ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከታደገ በኋላ የሚኖረውን ምናባዊ ሁኔታ ይገልጻል። የቋንቋ አጠቃቀሙ ግነታዊ ነው፤ ይህንን ኢሳያያስ እንደ ገለጸው እንደዚያው መተርጎም ይኖርብሃል።
በታላቅም እልቂት ቀን ግንቦች በወደቁ ጊዜ
"እግዚአብሔር ጠላቶቻችሁን በጨረሰና ትላልቅ ግንቦቻቸው እንዲወድቁ ባደረገ ጊዜ'
በዚያን ቀን
"በዚያን ጊዜ'
የፀሐይም ብርሃን እንደ ሰባት ቀን የፀሐይ ብርሃን ሰባት እጥፍ ይሆናል
"ሰባት ፀሐዮች እንደሚያበሩት ፀሐይ ታበራለች' ወይም "ፀሐይ በተለምዶ በሰባት ቀን የምትሰጠውን ያህል ብዙ ብርሃን በአንድ ቀን ትሰጣለች'
እግዚአብሔር የሕዝቡን ስብራት በጠገነ ዕለት፣ የቆሰለውንም በፈወሰ ዕለት
የእግዚአብሔር ሕዝቡን ማጽናናትና መከራቸው እንዲያበቃ ማድረጉ ቁስላቸውን በፋሻ እንዳሰረላቸው ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 30:27
የእግዚአብሔር ስም ... እንደምትባላ እሳት
እግዚአብሔር እጅግ መቆጣቱ ታላቅ እሳት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የእግዚአብሔር ስም ይመጣል
በዚህ ስፍራ "ስም' የሚለው እግዚአብሔርን ይወክላል። አት፡- "እግዚአብሔር ይመጣል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ከንፈሮቹ ቁጣን የሞሉ ናቸው፣ ምላሱም እንደምትባላ እሳት ናት
በዚህ ስፍራ "ከንፈር' እና "ምላስ' የእግዚአብሔርን ንግግር የሚወክሉ ምትክ ስሞች ናቸው። እንዲሁም እግዚአብሔር በታላቅ ቁጣና ኃይል መናገሩ ምላሱ እሳት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እርሱ ሲናገር ቁጣው ሁሉን እንደሚያጠፋ እሳት ነው' (ተለዋጭ ስምና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
እስትንፋሱ እንደሚያጥለቀልቅ ወንዝ ነው
ለማጥፋት ያለውን ኃይል በሚመለከት አጽንዖት ለመስጠት ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣውን አየር ከጎርፍ ጋር ያመሳስለዋል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
አሕዛብን በአጥፊ ወንፊት ሊነፋቸው
እግዚአብሔር በአሕዛብን መካከል ሰዎችን መለየቱና ክፉ ሰዎችን ማጥፋቱ እግዚአብሔር አሕዛብን በወንፊት ላይ እንዳስቀመጣቸው ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ በአዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል የሚገኙ ክፉ ሰዎችን ይለያል ያጠፋልም።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
እስትንፋሱ በሕዝብም መንጋጋ የሚስያስት ልጓም ይሆናል
እግዚብሔር የሰዎች እቅድ እንዲጨናገፍ ወይም እንዲጠፉ ለማድረግ ያለው ኃይል እስትንፋሱ ሰዎችን ከትክክለኛው መንገድ አወጥቶ እንደሚነዳ ልጓም ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በሕዝብ መንጋጋ እንዳለ ልጓም
ልጓም ሰዎች አንድን ፈረስ ለመቆጣጠርና ለመምራት በራሱ ላይ የሚያስገቡት ነገር ነው። ልጓም በፈረሱ አፍ ውስጥ የሚገባ ትንሽ ብረት ይኖረዋል። አት፡- "ልጓም በሰዎች ራስ ላይ' ወይም "ልጓም በሰዎች መንጋጋ ውስጥ' (የማይታወቅ ነገርን ስለ መተርጎም ተመልከት)
Isaiah 30:29
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል
ዝማሬ ይኖራችኋል
ዝማሬ የሚለው ስም በማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጽ ይህ ክፍል እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "ትዘምራላችሁ'
የተቀደሰው በዓል በሚከበርበት ሌሊት እንደሚሆን
ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ምን ያህል ሕዝቡ ደስተኛ እንደሚሆን አጽንዖት ይሰጣል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
የተቀደሰው በዓል በሚከበርበት
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "የተቀደሰውን በዓል በምታከብሩበት ጊዜ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
የልብ ደስታ
በዚህ ስፍራ ልብ የሰውን ውስጣዊ ማንነት ይወክላል። አት፡- "ደስ ይልሃል' (ምትክ ስም ተመልከት)
ወደ እስራኤል ዓለት ... አንድ ሰው እንደሚሄድ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ዘይቤአዊ ንግግር ሕዝቡ ምን ያህል ደስተኛ እንደሚሆን አጽንዖት ይሰጣል። (ዘይቤአዊ ንግግረ ተመልከት)
ወደ እስራኤል ዓለት
እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመጠበቅ የሚችል መሆኑ ሕዝቡ የሚወጣበትና ከጠላቶች የሚያመልጥበት ዓለት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ወደ እስራኤል የመከላከያ ዓለት' ወይም "ለእስራኤል እንደ መከላከያ ዓለት ወደሆነው' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 30:30
የክንዱን ሥራ ያሳያል
በዚህ ስፍራ "ክንድ' የሚለው የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል። እግዚአብሔር የሕዝቡን ጠላቶች በማጥፋት ኃይሉን እንደሚያሳይ ያመለክታል። አት፡- "ጠላቶቻችሁን በማጥፋት ኃያል መሆኑን ያሳይል' (ምትክ ስምና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
በሚነደድ ቁጣና በእሳት ነበልባል
የእግዚአብሔር ቁጣ እንደ ኃይለኛ ዝናብ ወይም እሳት ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- " ኃይለኛ ዝናብና የእሳት ነበልባል በሚመስል ቁጣ' ወይም "በታላቅ ቁጣ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በውሽንፍር፣ በዶፍ ዝናብ፣ እና በከባድ በረዶ ዶፍ
"ነፋስ፣ ዝናብ፣ እና በረዶ በተሞላ ኃይለኛ ዝናብ'
ከባድ የበረዶ ዶፍ
እንደ ዝናብ ከሰማይ የሚወርዱ ከበደ ከበደ ያሉ በረዶዎች
Isaiah 30:31
ከእግዚአብሔር ደምጽ የተነሳ አሦር ይሰባበራል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር በመናገር የአሦርን ወታደሮች ይሰባብራቸዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
አሦር ይሰባበራል
አሦር የእግዚአብሔር ድምጽ የሚሰባብረው እቃ እንደሆነ አድርጎ ኢሳይያስ ስለ አሦር ፍርሃት ይናገራል። አት፡- "አሦር ይደነግጣል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
አሦር
በዚህ ስፍራ የአሦርን ወታደሮች ይወክላል።
እግዚአብሔር በላዩ የሚያወርድበት የተመደበበት በትር ሁሉ
እግዚአብሔር ሠራዊቱ አሦራውያንን እንዲያሸነፉ ማድረጉ እግዚአብሔር አሦራውያንን በበትር እንደሚመታ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ይታጀባል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "የይሁዳ ሰዎች አብረውት ይሆናሉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ከበሮ
ሊመታ የሚችል ታምቡር የሚመስል ከላዩ ያለውና ሲነቃነቅ ድምጽ የሚሰጡ የብረት ቁርጥራጮች ዙሪያውን ያሉት የሙዚቃ መሣሪያ ነው። ይህንን በኢሳይያስ 5:12 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ከእነርሱ ጋር ይዋጋል
እግዚአብሔር ሠራዊቱ አሦራውያንን እንዲያሸነፉ ማድረጉ እግዚአብሔር ከጠላት ሠራዊት ጋር የሚዋጋ ተዋጊ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 30:33
ከቀድሞም ጀምሮ የማቃጠያ ቦታ ተዘገጅታለች
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ከቀድሞም ጀምሮ እግዚአብሔር የማቃጠያ ቦታ አዘጋጅቷል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ማቃጠያ ቦታ
ይህ ሐረግ "ቶፌዝ' የሚለው ቃል ትርጉም ነው። "ቶፌዝ' በአንድ ወቅት ሰዎች ልጆቻቸውን ለሐሰተኛ አማልክት መስዋዕት አድርገው ልጆቻቸውን የሚያቃጥሉበት በሂኖም ሸለቆ፣ ከኢየሩሳሌም በሰተ ደቡብ የሚገኝ ቦታ ነው። ( እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ለንጉሥም ተዘጋጅታለች
ይህ የአሦርን ንጉሥ ያመለክታል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ለአሦር ንጉሥ አዘጋጃት' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ እና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ክምር ከእሳት ጋር ተዘጋጅቷል ብዙም እንጨት
እሳት ለማንደድ ክምር ከብዙ እንጨት ጋር ተዘጋጅቷል
የእግዚአብሔር እስትንፋስ እንደ ድኝ ፈሳሽ ያቃጥለዋል
ይህ ክፍል የእግዚአብሔርን እስትንፋስ ክምሩን የሚያቃጥል የእሳት ወንዝ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

Chapter 31

Isaiah 31:1
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።
ወደ ግብጽ ለሚወርዱ
በዚህ ስፍራ ለሚወርዱ የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ከቦታ ከፍታ አንጻር ግብጽ ከኢየሩሳሌም በዝቅተኛ ስፍራ ላይ ስለምትገኝ ነው።
ለሚወርዱ
"ለሚወርዱት ለይሁዳ ሰዎች'
በፈረሶችም ለሚደገፉ
ይህ ክፍል እንደሚረዷቸው ፈረሶቻቸውን ተስፋ ስለሚያደርጉ ሰዎች በፈረሶቻቸው እንደሚደገፉ አድርጎ ይናገራል። አት፡- በፈረሶቻቸው ለሚደገፉ (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የእስራኤል ቅዱስ
ይህንን ስም በኢሳይያስ 1:4 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
እግዚአብሔርንም ለማይፈልጉ
"እንዲረዳቸው እግዚአብሔርን ለማይጠይቁ'
ክፉ ነገርንም ያመጣል
በዚህ ስፍራ "ያመጣል' የሚለው ቃል "እንዲሆን ያደርጋል' ማለት ነው። አት፡- "ክፉ ነገር እንዲሆን ያደርጋል' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ቃሉንም አይመልስም
"ቃልን መመለስ' የሚለው ይህ ሐረግ እንደሚያደርግ የተናገረውን የማይፈጽም ሰው የተናገራቸው ቃላት ወደ እርሱ መመለስ እንደሚችሉ ነገሮች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ይህን አያደርግም ይላል፣ ማለትም የተናገረውን ይፈጽማል። አት፡- "አደርገዋለሁ ብሎ የተናገረውን ያደርጋል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ይነሣል
"ይቀጣል
ክፉ ቤት
ይህ በዚያ የሚኖሩ ክፉ የሚያደርጉ ሰዎችን ያመለክታል። አት፡- ክፉ የሚያደርጉ ሁሉ (ምትክ ስም ተመልከት)
Isaiah 31:3
ግብጽ ሰው ነው
በዚህ ስፍራ ግብጽ የሚለው የግብጽን ወታደሮች ያመለክታል። አት፡- "የግብጽ ወታደሮች ሰዎች ናቸው' (ምትክ ስም ተመልከት)
ፈረሶቻቸውም ሥጋ እንጂ መንፈስ አይደሉም
ይህ ፈረሶቻቸው ፈረሶች ብቻ እንጂ መንፈሳዊ ፍጥረት አይደሉም። አት፡- "ፈረሶቻቸው ፈረሶች ብቻ ናቸው፣ ኃያላን መናፍስት አይደሉም' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
እግዚአብሔር እጁን በዘረጋ ጊዜ
እጅ የሚለው ቃል በአብዛኛው የእግዚአብሔርን ኃይልና ሥራ በሚመለከት ጥቅም ላይ ውሏል። አት፡- "እግዚአብሔር ኃይሉን እነርሱን በመቃወም በተጠቀመ ጊዜ' (ምትክ ስም ተመልከት)
ረጂው ይሰናከላል፣ተረጂውም ይወድቃል
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ነገር ይናገራሉ። መሰናከልና መውደቅ የመውደቅ ስዕላዊ ንግግሮች ናቸው። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- እነዚህ ሁለት ነገሮች ይሆናሉ፡- "የምትረዳችሁን ግብጽን አጠፋለሁ ግብጽም የምትረዳችሁን እናንተን አጠፋለሁ።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ፣ ስዕላዊ ንግግርና አጓዳኝነት ተመልከት)
ተረጂውም
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እርዳታ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚፈልገውም' (አድጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
Isaiah 31:4
አጠቃላይ መረጃ
እግዚብሔር ለኢሳይያስ ይናገራል።
እንደ አንበሳ ... የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲሁ
"አንበሳ ... በተመሣሣይ መንገድ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።' እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ የሚያድነውን ከሚጠብቅ አንበሳ ጋር ራሱን እያመሣሰለ እንዴት የእርሱ ለሆኑት ሕዝብ እንደሚከላከልና እንደማይሰጋ ይናገራል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ... በኮረብታ ላይ ይወርዳል
የመጨረሻው መስመር ከመጀመሪያው መስመር በፊት እንዲሆን ካደረግህ በይበልጥ ግልጽ ይሆናል። አት፡- "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንደ አንበሳ፣ እንደ ደቦል አንበሳ በጽዮን ተራራ፣ በዚያኮረብታ ላይ ሊዋጋ ይወርዳል።'
Isaiah 31:5
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።
እንደ ሚበርር ወፍ እንዲሁ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ይጋርዳታል
በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር እስራኤልን የሚጠብቅበት መንገድ እናት ወፍ ልጆቿን በጎጆአቸው ከምትጠብቅበት መንገድ ጋር ተስተያይቷል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ይጋርዳታል ይጠብቃታልም፤ ይጠብቃታል ያድናታልም
በከተማይ ላይ እንደሚበርር ወፍ እርሱን በመግለጥ፣ እግዚአብሔር እንዴት ኢየሩሳሌምን እንሚጠብቃትና እንደሚያድናት ይናገራል። አት፡- "ከተማይቱን ከጠላቶቿ ይጠብቃታል ይድናታልም' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
ይህን ሐረግ በኢሳይያስ 1፡9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ኢየሩሳሌም
ይህ በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አት፡- "የኢሩሳሌም ሕዝብ' (ምትክ ስም ተመልከት)
አጥብቃችሁ ወደ ዓመፃችሁበት ተመለሱ
"ወደ ዓመፃችሁበት ወደ እርሱ ተመለሱ'
የገዛ እጆቻችሁ በኃጢአት የሰራቸውን
በእጆቻቸው ለሠሩት ነገር አጽንዖት ለመስጠት ሕዝቡ "በእጆቻቸው' ተወክለዋል። አት፡- "በገዛ እጆቻችሁ በመሥራት ኃጢአት አድርጋችኋል' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
አጠቃላይ መረጃ
እግዘአብሔር አሦራውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጎ በመጥቀስ ለይሁዳ ሰዎች መናገሩን ይቀጥላል።
አሦር በሰይፍ ይወድቃል፣ በሰው ያልተሠራ ሰይፍ ይበላዋል
ሰይፍ ወታደረዊ ኃይልን ይህ በአደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "የእግዚአብሔር ሰይፍ፣ የሰውም ሰይፍ አይደለም፣ የአሦርን ሠራዊት ያጠፋል' (ምትክ ስምና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ይሸሻል
"አሦራውያን ይሸሻሉ'
ከፍርሃት የተነሣ ድፍረታቸውን ሁሉ ያጣሉ
"ድፍረት' የሚለው ቃል "ደፋር' በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "ፍርሃት' የሚለው ቃል "የፈራ' በሚል ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እጅግም ስለፈሩ ከእንግዲህ ወደያ ደፋሮች አይሆኑም' (የነገር ስም ተመልከት)
መሣፍንቱ
"መሪዎቻቸው
በእግዚአብሔር የጦርነት ሰንደቅ ዓላማ መታየት
"መታየት' የሚለው ቃል "አየ' በሚል ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "የእግዚአብሔርን ሠራዊት ሰንደቅ ዓላማ ባዩ ጊዜ' (የነገር ስም ተመልከት)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኝነት ለመግለጽ እግዚአብሔር በራሱ ስም ይናገራል። አት፡- "እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው' ወይም "እኔ፣ እግዚአብሔር ያወጅኩት ይህ ነው' (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)
እሳቱ በጽዮን እቶኑም በኢየሩሳሌም የሆነ
እነዚህ ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አጽንዖት ለመስጠት በአንድነት ጥቅም ላይ ይውላሉ። በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር መገኘትና ለመፍረድና ለማጥፋት ያለው ኃይሉ እሳት እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እስፈሪ መገኘቱ በጽዮን የሆነው' (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

---

Chapter 32
Isaiah 32:4
አጠቃለይ መረጃ
እግዚአብሔር ጻድቃን ገዢዎችን በይሁዳ ከመለሰ ወዲህ የሕዝቡን ሁኔታ ኢሳይያስ ይገልጻል።
ችኩሎች ... ተብታቦች
x
Isaiah 32:7
አታላዩ
ይህ ሌሎችን የሚያታልል ሰውን ያመለክታል። አት፡- "አታላይ ሰው' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)
በሐሰት ደሀውን ያጠፋ ዘንድ
"ደሀ' የሚለው ድሀውን ሕዝብ ያመለክታል። እንዲሁም፣ ያጠፋ ዘንድ የሚለው ሐረግ እነርሱን መግደል ማለት አይደለም ነገር ግን ስለ እነርሱ ውሸት በመናገር እነርሱን መጉዳት ማለት ነው። አት፡- ውሸት በመናገር ድሆች ሰዎችን መጉዳት' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)
ጽንቶ ይኖራል
ይህ የተሳካለት ይሆናል ማለት ነው። አት፡- "የተሳካለት ይሆናል' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 32:9
ተነሡ
"ቁሙ' ወይም "ልብ በሉ'
በምቾት
"ተማምኖ' ወይም "በደስታ'
ድምፄን
ለተናገረው አጽንዖት ለመስጠት ኢሳይያስ ራሱን በድምጹ ይወክላል። አት፡- "እኔ ስናገር' (ምትክ ስም ተመልከት)
መተማመናችሁ ይሰበራል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። ኢሳይያስ መተማመናቸው የሚሰበር ቁስ ነገር እንደሆነ አድርጎ ከእንግዲህ ወዲያ የሚተማመኑ እንደማይሆኑ ይናገራል። አት፡- "ከእንግዲህ ወዲያ የምትተማመኑ አትሆኑም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
የወይን መኸር አይኖርም
ይህ ለመልቀም የሚሆን መልካም ወይን አይኖርም ማለት ነው። አት፡- "የምትሰበስቡት ወይን አይኖራችሁም' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ማከማቸት አይመጣም
"እህል ማከማቺያ ጊዜ አይመጣም'
Isaiah 32:11
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገሩን ይቀጥላል።
ተንቀጥቀጡ
ከፍርሃት የተነሳ ተንቀጥቀጡ
በምቾት
"ተማምኖ' ወይም "በደስታ'
ልብሳችሁን አውልቁ ዕራቁታችሁንም ሁኑ
ዕራቁት ማለት ዕርቃንን መሆን ላይሆን ይችላል ነገር ግን ዝቅተኛዎቹን እንደ ውስጥ ልብስ ያሉትን መልበስ ነው። አት፡- "የክት ልብሳችሁን አውልቁና ዕረቁታችሁን ሁኑ ወይም ቁንጠኛ ልብሳችሁን አውልቁ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ወገባችሁን በማቅ ታጠቁ
ይህ የሐዘን ወይም የለቅሶ ተግባር ነው። አት፡- "ስላዘናችሁ ወገባችሁን በማቅ ታጠቁ' (ምሳሌያዊ ተግባር ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ስለተወደደችው እርሻ፣ ስለሚያፈራውም ወይን ታለቅሳላችሁ
በሚያፈራው እርሻቸውና ወይናቸው ከሚሆነው ነገር የተነሣ በማዘናቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ያለቅሳሉ ማለት ነው፡፡ አት፡- "በተወደደችው እርሻችሁና በሚያፈራው ወይናችሁ ከሚሆነው ነገር የተነሣ ታለቅሳላችሁ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
እሾህና ኩርንችት
ይህንነ ሐረግ በኢሳይያስ 5፡6 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት፡፡
ደስተኞች ቤቶች በነበሩት
ደስተኛ ሰዎች በውስጣቸው ስለነበሩ በዚህ ስፍራ ቤቶች ደስተኞች ተደርገው ተገልጸዋል፡፡ አት፡- "በነበራችሁባቸው ጊዜ ቤቶቻችሁ ደስተኞች ነበሩ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)
የፈንጠዚያ ከተማ
"ደስተኛ ከተማችሁ' ፈንጠዚያ የሚለው ቃል ግብዣና ጭፈራ ማለት ነው፡፡
Isaiah 32:14
ቤተ መንግሥቱ ይተዋልና የብዙ ሰዎችም ከተማ ትለቀቃለችና
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አት፡- "ሕዝቡ ቤተ መንግሥቱን ይተዋልና ብዙውም ሰው ከተማይቱን ይለቅቃልና' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ኮረብታው
ይህ በኮረብታው አናት ላይ የተገነባውን ምሽግ ያመለክታል፡፡ አት፡- "በኮረብታው ላይ ያለ ምሽግ' (ምትክ ስም ተመልከት)
ኮረብታውና ማማው ዋሻ ይሆናሉ
ይህ ምሽጉና ማማው ዋሻ እንደሆኑ አድርጎ መተዋቸውን ይናገራል፡፡ አት፡- "ኮረብታውና ማማው የተተውና ባዶ ይሆናሉ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
የሜዳ አህዮች ደስታ፣ የመንጎችም መሰማሪያ
ይህ እነዚህ እንስሳት በተተውት ምሽጋና ማማ መካከል የበቀለውን ሣር በደስታ ይመገባሉ ማለት ነው፡፡ አት፡- "የሜዳ አህዮችና የበግ መንጎች በዚያ የሚገኘውን ሣር ይበላሉ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ለዘላለም
ይህ ረጅም ጊዜ ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ ግነት ነው፡፡ አት፡- "እጅግ በጣም ረጅም ጊዜ' (ግነትና ማጠቃለይ ተመልከት)
መንፈሱ እስኪፈስስብን
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አት፡- "እግዚአብሔር መንፈሱን እስኪያፈስስ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
መንፈሱ እስኪፈስስብን
እግዚአብሔር መንፈሱን ለሕዝቡ መስጠቱ መንፈሱ በእነርሱ ላይ የሚያፈስሰው ፈሳሽ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል፡፡ አት፡- "መንፈሱ እስኪሰጠን' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ከላይ
በዚህ ስፍራ ሰማይ "በላይ' እንዳለ ተመላክቷል፡፡ አት፡- "ከሰማይ' (ምትክ ስም ተመልከት)
ፍሬያማው እርሻ እንደ ዱር ይቆጠራል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ፍሬያማውን እርሻ ከጥቅጥቅ ደን ጋር በማነጻጸር ከመጠን በላይ የተትረፈረፈ መሆኑን ያስተያያል፡፡ አት፡- ሰዎች ፍሬያማው እርሻ እንደ ደን ጥቅጥቅ ብሎ አደገ ይላሉ ወይም ፍሬያማው እርሻ ከመጠን በላይ የተትረፈረፈ ይሆናል (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 32:16
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ፍትህ ያድራል ... ጽድቅ ይኖራል
ኢሳይያስ "ፍትህ' እና "ጽድቅ' በእነዚህ ቦታዎች እንደሚኖር ሰው አድርጎ ይገልጻል፡፡ ይህ በእነዚህ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎች ፍትሃዊና ትክክለኛ የሆነውን ነገር ያደርጋሉ ማለት ነው፡፡ አት፡- "ሰዎች በምድረ በዳ በፍትህ ያደርጋሉ በፍሬያማ እርሻዎችም በጽድቅ ያከናውናሉ፡፡' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)
የጽድቅ ሥራ ሰላም ይሆናል፣ የጽቅም ፍሬ ለዘላለም ጸጥታና መታመን ይሆናል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተጓዳኞች ናቸው፣ ሁለቱም የጽድቅን ውጤቶች ያቀርባሉ፡፡ እነዚህ ሊጣመሩ ይችላሉ፡፡ አት፡- "በጽድቅ የሚኖሩ ሰዎች ፍሬ ለዘላለም ሰለም፣ጸጥታና መታመን ይሆናል፡፡' (አጓዳኝነት ተመልከት)
መኖሪያ
ሰዎች የሚኖሩበት ቦታ
Isaiah 32:19
በረዶ
ይህንን በኢሳይያስ 28፡2 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት፡፡
ደኑ ጠፋ፣ ከተማይቱም ፈጽማ ወደመች
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አት፡- "ደኑን ያጠፋል ከተማይቱን ፈጽሞ ያወድማል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
እንዲግጡ በሬዎቻችሁንና አህዮቻችሁን የምትልኩ፣ በውኃ ፈሳሽ አጠገብ የምትዘሩ የተባረካችሁ ናችሁ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ይህ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆነውን የእግዚአብሔርን በረከት ያመለክታል እንዲሁም ሕዝቡ ሊያደርጋቸው ስላሉ የተለመዱ ነገሮች ይናገራል፡፡ አት፡- "በውኃ ፈሳሽ ዳርቻ በሚገኝ እርሻ እህላችሁን በተከላችሁ ጊዜ በሬዎቻችሁንና አህዮቻችሁን በማሰማሪያው እንዲግጡ በሰደዳችሁ ጊዜ እግዚአብሔር ይባርካችኋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

## Chapter 33

Isaiah 33:1
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር ለአሦራውያን በግጥም ይናገራል፡፡
የማይጠፋ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አት፡- "ሌሎች የማያጠፉት' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ትጠፋለህ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አት፡- "ሌሎች ያጠፉሃል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
አሳልፈው ይሰጡሃል
"ሌሎች አሳልፈው ይሰጡሃል'
Isaiah 33:2
ክንድ ሁነን
ቢዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ክንድ ብርታቱን ያመለክታል፡፡ ይህ እገዚአብሔር እነርሱን ማበርታቱን ስለ እነርሱ ብርታቱን እንደሚጠቅም አድርጎ ይናገራል፡፡ አት፡- "ብርታት ስጠን' (ምትክ ስምና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በየማለዳው
ይህ ማለዳን ብቻ ሳይሆን ሙሉውን ቀን ያመለክታል፡፡ አት፡- "በየቀኑ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
መዳናችን
የ"መሆን' ማሰሪያ አንቀጽ ሊታክልልት ይችላል፡፡ እንዲሁም "መዳን' የሚለው ቃል "አዳኒ' በሚል ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አት፡- "መዳናችን ሁን' ወይም "አድነነ' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ እና የነገር ስም ተመልከት)
በመከራ ጊዜ
ይህ መከራ የገጠማቸውን ጊዜ ያመለክታል፡፡ አት፡- "መከራ ሲኖረን' (ባለቤትነት ተመልከት)
Isaiah 33:3
ከከፍተኛ ድምጽ የተነሣ ሰዎች ሸሹ
ከፍተኛ ድምጽ የሚለውን በሚመለከት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) የእግዚአብሔርን ድምጽ ያመለክታል፡፡ አት፡- "ከአንተ ከፍተኛ ድምጽ የተነሣ ሰዎች ሸሹ' ወይም 2) የእግዚአብሔርን ሠራዊት ከፍተኛ ድምጽ ያመለክታል፡፡ አት፡- "ከሠራዊትህ ድምጽ የተነሣ ሰዎች ሸሹ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ተነሥ
ይህ አንድ ነገር ለማድረግ መጀመር ማለት ነው፡፡ አት፡- "መሥራት ጀምር' (ፈሊጣዊ

ንግግር ተመልከት)
አሕዛብ ተበተኑ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "አሕዛብን በተንክ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
አንበጦች እንደሚሰበሰቡ ምርኮህ ይሰበሰባል፣ አንበጦች እንደሚዘልሉ ሰዎች ይዘልሉበታል
ይህ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከጠላቶቻቸው ምርኮ በማረኩ ጊዜ የሚያሳዩትን ከፍተኛ ፍጥነትና ጉጉት ምግብ በሰበሰቡ ጊዜ ከሚታየው የአንበጦች መጓጓት ጋር ያስተያያል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "አንበጦች አረንጓዴ ተክልን እንደሚበሉ በተመሣሣይ መስገብገብ ሕዝብህ ከጠላቶችህ ምርኮ ይሰበስባሉ' (ዘይቤአዊ ንግግርና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
Isaiah 33:5
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ከማንም ይልቅ ታላቅ ነው' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ጽዮንን በፍርድ በጽድቅ ይሞላታል
እግዚአብሔር በፍርዱና በጽድቁ ጽዮንን መግዛቱ ጸዮንን በፍርድና በጽድቅ እንደሞላ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ጽዮንን በፍርድና በጽድቅ ይገዛል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የዘመንህም መረጋጋት ይሆናል
እግዚአብሔር ሕዝቡን ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረጉ እርሱ ራሱ መረጋጋት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። በዘመንህም የሚለው ቃል ሕይወታቸውን ያመለክታል። አት፡- "በሕይወት ዘመንህ ሁሉ ደህንነትህን የተጠበቀ ያደርጋል' (ስዕላዊ ንግግርና ምትክ ስም ተመልከት)
የደህንነት፣ የጥበብና የዕውቀት ብዛት
ይህ እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ነገሮች ያመለክታል። "ደህንነት' የሚለው የነገር ስም "አዳነ' በሚለው ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። "ጥበብ' እና "ዕውቀት' የተሰኙት የነገር ስሞች በቅጽሎች ሊገለጹ ይችላሉ። አት፡- "የተትረፈረፈ ደህንነት፣ ጥበብና ዕውቀት ይሰጣችኋል' ወይም "ያድናችኋል እጅግም ጠቢብና አዋቂም ያደርጋችኋል' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያግዱ የተዘለሉና የነገር ስም ተመልከት)
የእግዚአብሔር ፍርሃት ሀብቱ ነው
ይህ እግዚአብሔርን መፍራት እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጠው ሀብት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እግዚአብሔርን ማክበር እግዚአብሔር የሚሰጥህ ውድ ሀብት ይመስላል' ወይም "እግዚአብሔርን መፍራት እንደ ሀብት ለአንተ ውድ ነው' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 33:7
ተመልከቱ
ይህ ቃል በዚህ ስፍራ በመቀጠል ሊነገር ወደ አለው የሕዝቡን ትኩረት ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። በተጨማሪም በዚህ ስፍራ የመጽሐፉን አዲስ ክፍል ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ውሏል። አት፡- "ስሙ'
በውክልና የተላኩ
መልእክተኞች
ለሰላም የሚሠሩ መልእክተኞች መራራ ለቅሶ ያለቅሳሉ
ይህ ሰላም በማምጣት ስላልተሳካላቸው ያለቅሳሉ ማለት ነው። አት፡- "መልእክተኞቹ ሰላም እንደሚሆን ተስፋ አድርገው ነበር ነገር ግን አልተሳካላቸውም ስለዚህም መራራ ለቅሶ አለቀሱ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
መንገዶች ባድማ ሆኑ፣ ተጓዦችም የሉም
ሁለተም ሐረጎች በመንገዶች ላይ ተጓዦች ባለመኖራቸው ላይ አጽንዖት ያደርጋሉ። እነዚህ ሊጣመሩና በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጹ ይችላል። አት፡- "ከእንግዲህ ወዲያ ሰዎች በመንገዶች ላይ አይጓዙም።' (አጓዳኝነትና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ቃል ኪዳን ፈረሰ፣ ምስክሮች ተዋረዱ፣ የሰው ልጆችም አልተከበሩም
ይህ ምንባብ በእስራኤል የነበረውን የሥነ ምግባር ውድቀት አጠቃላይ ሁኔታ ያመለክታል ወይም አገሪቱ ከአሦር ጋር አሰተማማኝ የሰላም ስምምነት ማድረግ አለመቻሏን ያመለክታል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሕዝቡ የፈጸመውን ቃል ኪዳን ሰበረ፣ ሕዝቡ የምስክሮችን ምስክርነት ችላ አለ፣ እንዲሁም ሕዝቡ እርስ በእርሱ አልተከባበረም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
Isaiah 33:9
ምድሪቱ አለቀሰች ጠወለገችም
ይህ ያለቅስ እንደ ነበረ ሰው ምድሪቱ ደረቅ እንደምትሆን ይናገራል። አት፡- "ምድሪቱ ትደርቃለች ተክሎችዋም ይጠወልጋሉ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)
ሊባኖስ አፈረ ጠወለገም
በዚህ ስፍራ "ሊባኖስ' የሊባኖስን ዛፎች ይወክላል። ይህ የዛፎችን መጠውለገንና መበስበስን የሚያፍር ሰው እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አት፡- "የሊባኖስ ዛፎች ጠወለጉ በሰበሱም' (ምትክ ስምና ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)
ሳሮን ... ባሳን ... ቀርሜሎስ
አንድ ወቅት ብዙ ዛፎችና አበባዎች በእነዚህ ቦታዎች ያድጉ ነበር።
ሳሮን እንደ ምድረ በዳ ሆነ
ይህ ሳሮን ምን ያህል ደረቅ እንደሆነ ከምድረ በዳ ጋር ያስተያያል።
ባሳንና ቀርሜሎስ ቅጠላቸውን አረገፉ
በዚህ ስፍራ ባሳንና ቀርሜሎስ በዛፎቻቸው ተወክለዋል። አት፡- "ከእንግዲህ በባሳንና በቀርሜሎስ በሚገኙ ዛፎች ላይ ቅጠል አይኖርም' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
Isaiah 33:10
እነሣለሁ
መነሣት ወይም መቆም ከእንግዲህ ወዲያ ማየትና ማሰብ እንደማይኖርና በዚያ ፈንታ የሥራ መጀመሪያ እንደሆነ የሚያሳይ ስዕላዊ ንግግር ነው። አት፡- "መሥራት እጀምራለሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
አሁን ወደ ላይ ከፍ እላለሁ፣ አሁን ከፍ ከፍ እላለሁ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሣሣይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በእግዚአብሔር መክበር ላይ አጽንዖት ያደርጋሉ። አት፡- "አሁን እኔ ራሴን አከብራለሁ፣ ሁሉ ሊያከብረኝ የሚገባኝ እንደሆነም አሳያለሁ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እና አጓዳኝነት ተመልከት)
ገለባን ትፀንሳላቸሁ፣ እብቅንም ትወልዳላችሁ
ይህ የአሦራውያን ማቀድ እናት ልጅን እንደምትወልድ እቅዶቻቸውን እንደሚፀንሱና እንደሚወልዱ አድርጎ ይናገራል። ይህ እቅዶቻቸውን ከገላባ ጋር እያስተያየ ከንቱ እንደሆኑ ይናገራል። አት፡- "እንደ ገለባና ሳር ከንቱ የሆኑ እቅዶችን ታቅዳላችሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ተቆርጦ እንደ ቀረ ደረቅ የእህል ግንድ
ፍሬ የሚሸከመው ክፍል ከተቆረጠ በኋላ በምድር ላይ የተተው ደረቅ የተክል ክፍል።
እስትንፋሳችሁ የምትበላችሁ እሳት ናት
በዚህ ስፍራ የአሦራውያን እቅዶች እንደ እስትንፋሳቸው ተጥቀስዋል። ይህ እቅዶቻቸው በተጨባጭ ሰውነታቸውን እንደሚያቃጥል አድርጎ እቅዶቻቸው ለሞት እንደሚዳርጓቸው ይናገራል። አት፡- "እቅዶቻችሁ ይገድሉአችኋል' (ምትክ ስምና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
አሕዛብም እንደ ተቃጠለ ኖራ፣ ተቆርጦም በእሳት እንደ ተቃጠለ እሾህ ይሆናሉ
ይህ የአሕዛብ አስከሬን የሚቃጠልበትን መንገድ እሾህ ከሚቃጠልበት መንገድ ጋር ያስተያያል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽም ሊገለጽም ይችላል። አት፡- "ገበሬ እሾህን እንደሚቆርጥና እንደሚያቃጥል እሳት የአሕዛብን አስከሬን ለኖራ ያቃጥላል።' (ዘይቤአዊ ንግግርና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ኖራ
የተቃጠሉ አጥንቶች አመድ
Isaiah 33:13
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።
እናንተ በሩቅ ያላችሁ የሠራሁትን ስሙ፣ እናንተም በቅርብ ያላችሁ የእኔን ኃይል አወቁ
እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ለማለት በሩቅ እና በቅርብ የሚሉትን ቃላት ይጠቀማል። ኃይል የሚለው ቃል ኃያል በሚል ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ሕዝቦች ሁሉ በሁሉ ስፍራ ያደረግሁትን ስሙ ኃያል መሆኔንም እውቁ' (ስዕላዊ ንግግርና የነገር ስም ተመልከት)
አምላክ የለሾቹን መንቀጥቀጥ ያዛቸው
ይህ የአምላክ የለሾቹ መንቀጥቀጥን በሚመለከት መንቀጥቀጣቸው የያዛቸው ጠላት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አት፡- "አምላክ የለሾቹ በመንቀጥቀጥ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተዋጡ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

ከእኛ መካከል ... ከምትነድድ?

በጽዮን የሚገኙ ኃጢአተኞች እነዚህን ጥያቄዎች እንደጠየቁ ተመላክቷል። አት "እንዲህ አሉ፣ 'ከእኛ መካከል ... ከምትነድድ?' ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ከምትባላ እሳት ጋር መኖርን የሚችል ከእኛ ማን አለ? ለዘላለም ከምትነድድ እሳት ጋር መኖርን የሚችል ከእኛ ማን አለ?

እነዚህ አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች በመሠረቱ አንድ ትገሩም ያላቸው ሲሆን ማንም ከእሳት ጋር መኖር እንደማይችል አጽንዖት ይሰጣሉ። አት፡- "ማንማ ከሚበላ እሳት ጋር መኖር አይችልም! ለዘላለም ከምትነድድ ጋር ማንም መኖር አይችልም!' ወይም "ማንም የእግዚአብሔርን ፍርድ ታግሦ መኖር አይችልም፣ እንደ ዘላለማዊ እሳት ነውና' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በጊዜያዊነት መቀመጥ

ቤቱ ባልሆነ አንድ ቦታ መኖር

Isaiah 33:15

የሚሄድ

በዚህ ስፍራ መሄድ የሚለው አኗኗርን ያመለክታል። አት፡- "የሚኖር' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

የጭቆናን ትርፍ የሚንቅ

"የጭቆና ትርፍ' የሚለው ስማዊ ሐረግ፣ በግሳዊ ሐረግ መገለጽ ይችላል። አት፡- "ሌሎች ሰዎችን በመጉዳት የሚገኝ ሀብትን የሚጠላ' (የነገር ስም ተመልከት)

ክፋትንም ከማየት ዓይኖቹን የሚከለክል

በዚህ ስፍራ ማየት አንድን ነገር ማጽደቅን ወይም ማረጋገጥን ያመለክታል። አት፡- "ክፉ ማድረግን የማያጸድቅ' (ፈሊጣዊ ንግግርን ተመልከት)

በከፍታዎች የሚያደር፣ መከለያ ስፍራው በአምባዎች መካከል የሚገኝ ምሽግ የሆነለት ሰው ይህ ነው

ይህ በኮረብታ ላይ በሚገኝ ቤቱ እንደሚኖር ደኅንነቱ ስለተጠበቀው ሰው ይናገራል። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተጓዳኝ ናቸው እንዲሁም ሁለተኛው ሐረግ ሰውዬው የሚኖርበትን ቦታ ይገልጻል። አት፡- "ለመከላከል ምቹ በሆነ ዓለታማ ቦታ፣ በኮረብታ ላይ ቤቱን እንደሠራ ሰው ደኅንነቱ የተጠበቀ ይሆናል' (ስዕላዊ ንግግርና አጓዳኝነት ተመልከት)

ከፍታዎች

ይህ ከፍ ያለ ኮረብታ ወይም በተራራ ላይ የሚገኝ ቦታ። አት፡- "ከፍ ያለ ኮረብታ' ወይም "በተራራ ላይ የሚገኝ ቦታ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በአምባዎች መካከል የሚገኝ ምሽግ

ይህ በተጨባጭ ምሽግ እንደሆኑ አድርጎ ለመከላከል ምቹ ስለሆኑ ድንጋያማ አካባቢዎች ይናገራል። አት፡- "ታላቅ የደንጋዮች ክምር' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የማይቋረጥ አቅርቦት ይኖረዋል

"ሁልጊዜ ይገኛል'

Isaiah 33:17

ዓይኖቻችሁ ያያሉ ... ያያሉ

ይህ አድማጮቹን "በዓይኖቻቸው' ይወክላቸዋል። አት፡- "ታያላችሁ ... ታያላችሁ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ንጉሡን በውበቱ

የንጉሡ ንጉሣዊ መጎናጸፊያው "እንደ ውበቱ' ተመላክቷል። አት፡- "ንጉሡ በውብ መጎናጸፊያው' (ምትክ ስም ተመልከት)

ልብህ የሚያስፈራ ነገር ያስባል

ይህ አድማጮቹን በልባቸው ይወክላቸዋል። "የሚያስፈራ' የሚለው ከአሦራውያን ጋር ያላቸውን ጦርነት ያመለክታል። ይህ በግልጽ ሊቀመጥ ይችላል። አት፡- "በጦርነት በወጓችሁ ጊዜ አሦራውያን ያሳደሩባችሁን ፍርሃት ታስታውሳላችሁ' (ተለዋጭ ስምና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ጸሐፊ ወዴት አለ? ገንዘቡንስ የመዘነ ወዴት አለ? ግንቦቹንስ የቆጠረ ወዴት አለ?

እነዚህ አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች የተጠየቁት የአሦራውያን አለቆች መሄዳቸውን በሚመለከት አጽንዖት ለመሰጠት ነው። እነዚህ ጥያቄዎች በአሳብ ገላጭ ዐረፍተ ነገርነት ሊጻፉ ይችላል። አት፡- "ለአነርሱ እንድንከፍል እንገደድ የነበረበትን የግብር ገንዘብ ይቆጥሩ የነበሩ የአሦር አለቆች ጠፍተዋል! ግንቦችን ይቆጥሩ የነበሩ ሰዎች ሄደዋል!' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ገንዘቡንስ የመዘነ

ገንዘብ ዋጋ ያለው ብረት ነበር፤ ዋጋው በክብደቱ ይወሰን ነበር።

ዓመጸኛን ሕዝብ፣ የማትረዳው የእንግዳ ቋንቋ ሕዝብ

"የማትረዳውን ቋንቋ የሚናገር ጨካኝ ሕዝብ'

Isaiah 33:20

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።

የበዓላቶቻችን ከተማ

ይህ በዚች ከተማ የራሳቸው በዓላትና ግብዣዎች ያደርጉ ነበር ማለት ነው። አት፡- "የራሳችንን ግባዣዎች እናደርግባት የነበረች ከተማ' ወይም "የራሳችንን በዓላት እናከብርባት የነበረች ከተማ' (ባለቤትነት ተመልከት)

ዓይኖቻችሁ ያያሉ

እያዩ ላሉት አጽንዖት ለመስጠት ሕዝቡ በዓይኖቻቸው ተወክለዋል። አት፤- "ታያላችሁ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

Isaiah 33:22

የእኛ ... ለእኛ

ይህ የይሁዳን ሕዝብ ጨምሮ ኢሳይያስን ያመለክታል። (አካታች "እኛ" ተመልከት)

Isaiah 33:23

ገመዶችህ ላልተዋል፤ ደቀላቸውንም አላጸኑም፤ ሸራውንም መዘርጋት አልቻሉም

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) የአሦር ሠረዊት በውኃ ላይ መሄድ እንዳልቻለ ጀልባ ነው፤ ደቀላውንና ሸራውን የሚደግፉት ገመዶች ላልተዋል ደቀላውንም የሚደግፍ ከእንግዲህ የለም ስለዚህ ሸራው ምንም አይጠቅምም (ኢሳይያስ 33፡1) ወይም 2) የይሁዳ ሰዎች ከእንግዲህ ጦርነት ላይ አይሆኑም፡ "የሰንደቅ ዓላማህን ምሰሶ የሚደግፈውን ገመድ አላልተሃል፣ ሰንደቅ ዓላመው ከእንግዲህ አይሰቀልም' (ኢሳ33፡ 17-ኢሳ 22)። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ደቀላ

ሸራውን የሚደግፍ ረጅም ምሰሶ

ሸራ

በነፋስ የሚወጠርና ጀልባውን በውኃ ላይ እንዲንቀሳቀስ የሚያደርግ ትልቅ ጨርቅ

ታላቅ ምርኮ በሚከፋፈልበት ጊዜ

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- ሀብቱን በሚከፋፈሉበት ጊዜ (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

አንካሶች

ይህ መሄድ የማይችሉ ሰዎችን ያመለክታል። አት፡- "አንካሶች የሆኑ' (ስማዊ ቅጽል)

በዚያ የሚኖሩ ሰዎች በደል ይቅር ይባልላቸዋል

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ኃጢአት ይቅር ይላል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

## Chapter 34

Isaiah 34:1

አጠቃላይ መረጃ

እግዚአብሔር በግጥም ይናገራል። (አጓዳኝነት ተመልከት)

ምድርና መላዋ፣ዓለምና ከእርስዋ የሚወጣ ሁሉ ይስሙ

በዚህ ስፍራ በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር እንዳለች አጽንዖት ለመስጠት ምድር እግዚአብሔርን መስማት እንደምትጠየቅ ተደርጎ ተነግሮአል። እነዚህ ሁለት ተጓዳኝ ሐረጎች በዓለም ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ምትክ ስሞች ናቸው። አት፡- "በሁሉ ስፍራ በዓለም በየትኛውም ቦታ፣ እያንዳንዱ ሰው እኔ የምለውን መስማት አለበት።' (ግዑዝ ነገረን እንደ ሰው ማየትና ምትክ ስም ተመልከት)

ዓለምና ከእርስዋ የሚወጣ ሁሉ

ይህ ከተጓዳኞቹ ሁለቱ ሐረጎች ሁለተኛው ነው። ባይባሉም የሚታወቁ ቃላት በዚህ ሐረግ ሊጨመሩ ይችላሉ። አት፡- "ዓለም፣ ከእርስዋ የሚወጡ ነገሮች ሁሉ መስማት አለባቸው' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

ፈጽሞ አጠፋቸው፣ ለመታረድም አሳልፎ ሰጣቸው

ብዙ ጊዜ ነቢያት ገና ወደፊት ሊሆኑ ያሉ ነገሮችን አስቀድሞውኑ እንደተፈጸሙ አድርገው ይናገራሉ። ይህም ሁኔታው በእርግጥ እንደሚፈጸም አጽንዖት ለመስጠት ነው። አት፡- "ፈጽሞ ያጠፋቸዋል፣ ለመታረድም አሳልፎ ይሰጣቸዋል' (ትንቢታዊ ኃላፊ ጊዜ ተመልከት)

Isaiah 34:3

የሟቾቻቸው ሰውነት ወደ ውጪ ይጣላል



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ማናቸውም የሞቱባቸውን አይቀብሩም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ሟቾቻቸው
ይህ የሞቱ ሰዎችን ያመለክታል። አት፡- "የሞቱት' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)
ተራሮች ደማቸውን ይጠጣሉ
"ተራሮች በደማቸው ይሸፈናሉ'
ሰማያት እንደ መጽሐፍ ጥቅልል ይጠቀለላሉ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። ይህ እግዚአብሔር በሰማይ ላይ የሚያደርገው የመጽሐፍን ጥቅልል ከሚጠቀልል ሰው ጋር ተስተያይቶአል። አት፡- "አንድ ሰው የመጽሐፍን ጥቅልል እንደሚጠቀልል እግዚአብሔር ሰማይን ይጠቀልላል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ፍሬም ከበለስ ቅጠልም ከወይን እንደሚጠውልግና እንደሚረግፍ፣ ከዋክብቶቻቸው ይከስማሉ
ይህ ሰዎች ለዘላለም በዚያ እንደሚኖሩ የሚያስቧቸው በሰማይ ያሉ ነገሮች እንኳን እንደ ቅጠል በቀላሉ እንደሚወድቁ አጽንዖት ይሰጣል። አት፡- "ቅጠል ከወይን እንደሚረግፍ ወይም የበለስ ፍሬ ከዛፍ እንደሚረግፍ እንዲሁ ከዋክብት ሁሉ ከሰማይ ይወድቃሉ' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 34:5
ሰይፌ በሰማይ ሆና ጠጥታ እስክትረካ ድረስ
እግዚአብሔር ራሱን ሰይፍ እንደታጠቀ ተዋጊ ይገልጻል። ጠጥታ እስክትረካ የሚለው ሐረግ የእግዚአብሔርን ሰይፍ እንደሚበላና እንደሚረካ ሰው አድርጎ ይናገራል። በሰማይ ብዙ ጥፋት እንደሚሆንና የእርሱን ፍጻሜ ለመግለጽ እግዚአብሔር ይህን ስዕላዊ መግለጫ ይጠቀማል። አት፡- "በሰማይ ያሉትን ነገሮች ማጥፋቴን ስፈጽም' (ስዕላዊ ንግግርና ግዑዝን እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)
ተመልከቱ
የአድማጮቹን ትኩረት ለመሳብና የተነገሩትን ነገሮች እንዲያስቡ ለማድረግ ይህ ቃል በዚህ ስፍራ ጥቅም ላይ ውሏል። አት፡- "ስሙ' ወይም "በመቀጠል'
ለጥፋት በለየኋቸው ሕዝብ ላይ፣ በኤዶምያስ ላይ ትወርዳለች
በዚህ ስፍራ ትወርዳለች የሚለው የእግዚአብሔርን ሰይፍ ያመለክታል። ይህ እግዚአብሔር ነገሮችን በሰይፍ የማጥፋቱን ስዕላዊ ንግግር ይቀጠላል። አት፡- "ላጠፋቸው ለራሴ የለየኋቸውን ሰዎች፣ የኤዶምን ሕዝብ ለመቅጣት እመጣለሁ' (ስዕላ ንግግር ተመልከት)
በኤዶም ላይ
ኤዶም የሚለው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። አት፡- "በኤዶም ሕዝብ ላይ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የእግዚአብሔር ሰይፍ በደም ተሞልታለች በበግም … ስብ ተሸፍናለች
ይህ እንስሳትን እንደሚሠዋ ካህን እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለ መግደሉ ይናገራል። የካህንን ሰይፍ በመግለጽ ይህን ያደርጋል። አት፡- "ካህን እንስሳትን እንደሚሠዋ እግዚአብሔር ይሠዋቸዋል፤ ሰይፉ በበግ ጠቦት፣ በፍየልና በአውራ በግ ደምና ስብ ተሞልታለች' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
እግዚአብሔር መሥዋዕት በባሶራ ታላቅም እርድ በኤዶምያስ ምድር አለውና
"መሥዋዕት' እና "እርድ' የሚሉት ቃላት በማሰሪያ አንቀጽነት ሊገለጹ ይችላሉ። አት፡- "እግዚአብሔር ብዙ ሰዎችን በባሶራ ይሠዋልና፣ ብዙ ሰዎችን በኤዶምያስ ያርዳልና' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ባሶራ
ይቺ በኤዶምያስ ቁልፍ ከተማ ነበረች። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)
Isaiah 34:7
ይወድቃሉ
"ይሞታሉ
ምድራቸው በደም ትሰክራለች
ይህ ምድሪቱን ከሰከረ ሰው ጋር በማስተያያት በመሬት ላይ የሚፈስሰውን የደም ብዛት ይገልጻል። አት፡- "ምድራቸው በደም ትሞላለች' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)
አፈራቸውም በስብ ትወፍራለች
በዚህ ስፍራ አፈር ማለት የመሬት ትቢያ ማለት ነው። እጅግ ብዙ እንስሳትን በመብላት ከወፈረ ሰው ጋር በማስተያየት በመሬት ትቢያ ላይ የሚፈስሰውን የስብ ብዛት ይገልጻል። (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)
Isaiah 34:8
ለእግዚአብሔር የበቀል ቀን ይሆናል
በዚህ ስፍራ "ቀን' የሚለው በቀጥታ "ቀን' ማለት ሳይሆን አንድ የተወሰነ ጊዜን የሚያመለክት ፈሊጣዊ ንግግር ነው። (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
በጽዮን ጉዳይ ብድራታቸውን መልሶ ይከፍላቸዋል
ይህ ማለት አስቀድሞ በኢየሩሳሌም ላይ ላካሄዱት ጦርነት እግዚአብሔር ይበቀላቸዋል ማለት ነው። አት፡- "በጽዮን ሰዎች ላይ ስላደረጉት እግዚአብሔር የሚገባቸውን ቅጣት ይሰጣቸዋል' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
የኤዶምያስ ፈሳሾች ዝፍት ሆነው ይለወጣሉ፣ አፈርዋም ድኝ ይሆናል
ስለ ተቃጠሉና በዝፍትና በድኝ ስለተሸፈኑ ውኃውና መሬቱ ለመጠጥና ምግብ ለማሳደግ የማይጠቅሙ መሆናቸው ፈሳሾቻቸውና ምድራቸው በተጨባጭ ዝፍትና ድኝ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "የኤዶምያስ ፈሳሾች በዝፍት የተሞሉ ይሆናሉ ምድራቸውም በሚነድድ ድኝና ዝፍት ይሸፈናል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
መሬትዋ … አፈርዋ
"የኤዶምያስ መሬት… የኤዶምያስ አፈር'
ዝፍት
ለረጅም ጊዜ የሚነድድ ወፍራም፣ ጥቁር ነገር።
በሌሊትም በቀንም ይነድዳል
ይህ ሁልጊዜ ማለት ነው። አት፡- "ሌሊቱንና ቀኑን ሙሉ ይነድዳል' ወይም "ሌሊቱንና ቀኑን ሁሉ ሳያቋርጥ ይነድዳል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ከትውልድ እስከ ትውልድ
"ከትውልድ እስከ ትውልድ' የሚለው ሐረግ ወደፊት የሚኖሩትን የሰዎች ትውልዶች ሁሉ ያመለክታል። ይህንን ሐረግ በኢሳይያስ 13፡20 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፡- "ለዘላለም' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 34:11
በዚያ ይኖራሉ
"በኤዶም ምድር ይኖራሉ'
ጉጉት
ይህንን በኢሳይያስ 13፡21 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ቁራ
ይህ ትልቅ ጥቁር አሞራ ነው። በዚህ ምንባብ የተጠቀሱትን አንዳንድ የወፍ ዓይነቶች በትክክል መለየት አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን፣ ወፎች ሁሉ ሰዎች በሌሉበት ቦታ መኖር ይመርጣሉ፣ ስለዚህ ሰው የሌለበት ቦታ ወይም ምድረ በዳን ይወክላሉ።
በውስጥዋ
"በዚያ።' ይህ ኤዶምያስን ያመለክታል።
በላያዋም የመፍረስ ገመድና የባዶነት ቱንቢ ይዘረጋባታል
ይህ የኤዶምያስን ጥፋት የሚያስከትል ጠንቃቃ ግንበኛ እንደሆነ አድርጎ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል። አት፡- "እግዚአብሔር ምድሪቱን በጥንቃቄ ይለካል፣ ከየት ማፍረስና ማጥፋት እንዳለበት ለመወሰን ይለካታል።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
መለኪያ ገመድ … ቱንቢ
እነዚህ የግንበኛ መሣሪያዎች ናቸው። ተመሣሣይ የሆኑ ቃላትን በኢሳይያስ 28፡17 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
መሳፍንቶችዋን … ልዑላንዋን
"የኤዶምያስ መሳፍንቶች … የኤዶምያስ ልዑላን'
ልዑላንዋ ሁሉ ምናምን ይሆናሉ
ይህ ልዑላኑ ንጉሣዊ የሆነ ማኅበራዊ ደረጃቸውን ማጣታቸውን ምናምን ይሆናሉ በማለት አጋኖ ያቀርበዋል። አት፡- "ልዑላኗ ሁሉ ከእንግዲህ ወዲህ አይገዙም' (ግነትን ማጠቃለያ ተመልከት)
Isaiah 34:13
እሾህ … ሳማ …አሜከላ
እነዚህ ሁሉ እሾህ ያላቸው አረሞች ናቸው። የሳማ እሾህ የሚያሳክክ መርዝ አለው።
ቀበሮዎች … ሰጎኖች … የዱር አንስሳት … ጅቦች … ጉጉቶች
የእነዚህን እንስሳት ስም በኢሳይያስ 13፡21-22 እንዳደረግኸው ተርጉም።
የሌሊት እንስሳት
በሌሊት የሚነቁና ንቁ የሆኑ እንስሳት።
ጭልፊት
ትናንሽ እንስሳትን ለምግብነት የሚገድል አሞራ።
Isaiah 34:16
በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ
የእግዚአብሔር መጽሐፍ ማለት እግዚአብሔር የተናገረውን መልእክት የያዘ ማለት ነው። አት፡- "የእግዚአብሔርን መልእክት በያዘው መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈውን

በጥንቃቄ እንብብ' (ባለቤትነት ተመልከት)
ከእነዚህ አንዱ
"ከእንስሳቱ አንዱ'
ጓደኛውን የሚያጣ የለም
ይህ በአዎንታዊ አረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እያንዳንዱ እንስሳ ጓደኛ ይኖረዋል' (ድርብ አሉታዊ ተመልከት)
አፉ አዝዞአልና
ለተናገረው አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር በአፉ ተወክሏል። አት፡- "እግዚአብሔር አዝዞልና' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
ለስፍራቸውም ዕጣ ጣለላቸው
ይህ እግዚአብሔር እንስሳት የት መኖር እንዳለባቸው መወሰኑ ለስፍራቸው በተጨባጭ ዕጣ እንደጣለላቸው ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "የት እንደሚኖሩ ወሰነ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
እጁም በገመድ ለካችላቸው
ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ሰዎች ነገሮችን የሚለኩበትን መንገድ ያመለክታል። አት፡- "ለእንስሳት መኖሪያቸውን ሰጣቸው'
ከትውልድ እስከ ትውልድ ድረስ
ከትውልድ እስከ ትውልድ የሚለው ሐረግ ወደፊት የሚኖሩትን የሰዎች ትውልዶች ሁሉ ያመለክታል። ከትውልድ እስከ ትውልድ የሚለውን ሐረግ በኢሳይያስ 13:20 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፡- "ለዘላለም' ወይም "ሁልጊዜ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

---

Chapter 35

Isaiah 35:1

ምድረ በዳውና ደረቁ ምድር ደስ ይላቸዋል፣ በረሃውም ሐሴት ያደርጋል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ትርጉም አላቸው። እነዚህ ቦታዎች ውኃን ማበብንም ስለገኙ ሰው ደስ እንደሚለው ደስ እንዳላቸው ተገልጾአል። አት፡- "እንደ ምድረ በዳው ደረቁ ምድር ደስ ይለዋል በረሃውም ሐሴት ያደርጋል' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትና አጓዳኝነት ተመልከት)
አበባ
በምድረ በዳ የሚገኙ ተክሎች ማበብ እንደ ራሱ እንደ ምድረ በዳው ማበብ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "ተክሎቹ ያብባሉ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
እንደ ጽጌ ረዳም እጅግ ያብባል
ይህ የምድረ በዳ ተክሎች የሚያብቡበትን መንገድ ብዙ አበባዎች ያሉት ጽጌ ረዳ ከሚያብበት መንገድ ጋር ያስተያያል። አት፡- "ምድረ በዳው ብዙ አዳዲስ ተክሎችንና ዛፎችን ያበቅላል' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
በደስታና በዝማሬ ሐሤትን ያደርጋል
ይህ እንደ ሰው ደስተኛ እንደሚሆንና እንደሚዘምር አድርጎ ስለ ምድረ በዳ ይናገራል። አት፡- "ቢሆንም ይሆናል ሁሉም ነገር ደስ ይለዋል ይዘምራልም' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት)
የሊባኖስ ክብር ይሰጠዋል
ይህ በአደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። ይህ እግዚአብሔር ምድረ በዳውን እንደ ሊባኖስ ታላቅ ማድረጉ ለምድረ በዳው የሊባኖስን ክብር እንደሰጠው ተደርጎ ተነግሮአል። አት፡- "እግዚአብሔር የሊባኖስን ክብር ይሰጠዋል' ወይም "እግዚአብሔር እንደ ሊባኖስ ታላቅ ያደርገዋል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የቀርሜሎስና የሳሮን ግርማ
ይህ እግዚአብሔር ምድረ በዳውን እንደ ቀርሜሎስና ሳሮን ውብ እንዲሆን ማድረጉ ለምድረ በዳው የእነርሱን ውበት እንደሰጠ ተደርጎ ተነግሮአል። ይታወቃል በሚል ያልተነገረው መረጃ ሊታከል ይችላል። አት፡- "የቀርሜሎስና የሳሮን ውበት ይሰጠዋል' ወይም "እግዚአብሔር እንደ ቀርሜሎስና ሳሮን ውብ ያደርገዋል' (ስዕላዊ ንግግርና መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)
የእግዚአብሔርንም ክብር የአምላካችንንም ግርማ
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች በመሠረቱ የሚናገሩት አንድ ነገር ሲሆን ለእግዚአብሔር መገለጥ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

Isaiah 35:3

አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለይሁዳ ሕዝብ ይናገራል።
የደከሙትን እጆች አበርቱ፣ የላሉትንም ጉልበቶች አጽኑ
"የደከሙ እጆች' እና "የላሉ ጉልበቶች' የሚሉት ቃላት የፈራን ሰው ይወክላሉ። አት፡- "ከፍርሃት የተነሳ እጆቻቸው የደከሙባቸውን አበርቱ፣ ጉልበቶቻቸውም የላሉባቸውን አጽኑ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
ፈሪ ልብ ላላቸው
በዚህ ስፍራ ሰዎች የውስጥ ስሜቶቻቸውን በሚያጎሉ በልቦቻቸው ተወክልዋል። አት፡- "የፈሩ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
ተመልከቱ
ይህ የአድማጮችን ትኩረት ቀጥሎ ወደ ሚነገረው ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። አት፡- "ስሙ'
አምላካችሁ በበቀል፣ በእግዚአብሔርም ብድራት ይመጣልና
ይህ "በቀል' እና "ብድራት' የሚሉት የነገር ስሞች "ቀጣ' በሚል ማሰሪያ አንቀጽ እንዲገለጹ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። "በቀል' እና "ብድራት' የሚሉት ቃላት ትርጉማቸው ተመሣሣይ ሲሆን እግዚአብሔር የይሁዳን ጠላቶች የሚቀጣ መሆኑን ያጎላሉ። አት፡- "ስላደረጉት ነገር አምላካችሁ ጠላቶቻችሁን ይቀጣል' (የነገር ስምና የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

Isaiah 35:5

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች የእግዚአብሔርን ሕዝብ መፃኢ ክብር መግለጽ ይጀምራሉ።
የዕውሮች ዓይኖች ያያሉ
"ዕውሮች' የሚለው ዕውሮች ሰዎችን ያመለክታል። ፈውሳቸውን ለማጉላት በዓይኖቻቸው ተወክለዋል። (ስማዊ ቅጽልና ተለዋጭ ስም ተመልከት)
የደንቆሮች ጆሮች ይሰማሉ
"ደንቆሮ' የሚለው መስማት የማይችሉትን ሰዎች ይወክላል። ፈውሳቸውን ለማጉላት በጆሮቻቸው ተወክለዋል። አት፡- "ደንቆሮች ሰዎች ይሰማሉ' (ስማዊ ቅጽልና ተለዋጭ ስም ተመልከት)
አንካሳ እንደ ሚዳቋ ይዘላል
ሚዳቋ በርቀትና በከፍታ ይዘላል። እንደ ሚዳቋ መዝለል በፍጥነትና በቀላሉ መንቀሳቀስ ለመቻል ጥቅም ላይ የሚውል ግነት ነው። አት፡- "አንካሳ ሰው ከፍ ብሎ ይዘላል' (ዘይቤአዊ ንግግር እና ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)
የድዳም ምላስ ይዘምራል
ይህ መናገር የማይችሉትን ሰዎች ያመለክታል። ፈውሳቸውን ለማጉላት በምላሳቸው ተወክለዋል። አት፡- "ድዳ ሰዎች ይዘምራሉ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
ውኃ በምድረ በዳ
ባይባልም እንደተባለ የሚታወቀውን ማሰሪያ አንቀጽ መጠቀም ይቻላል። አት፡- "ውኃ በምድረ በዳ ይፈስሳል' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)
የሚፋጅ አሸዋ ኩሬ ይሆናል
ይህ የውኃ ኩሬ በጋለ አሸዋ ውስጥ ይታያል ማለት ነው። የዚህ ዐረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም ግልጽ መሆን ይችላል። አት፡- "በሚፋጅ አሸዋ ውስጥ ኩሬ ይታያል' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
የጥማት መሬት
በዚህ ስፍራ ደረቅ መሬት እንደ ተጠማ ሰው ተደርጎ ተገልጾአል። አት፡- "ደረቅ መሬት' (ግዑዙን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)
የጥማት መሬት የውኃ ምንጭ ትሆናለች
ይህ በደረቅ መሬት ምንጭ ይታያል ማለት ነው። የዚህ አረፍተ ነገር መሉ ትርጉም ግልጽ መሆን ይችላል። አት፡- "በጥማት መሬት የውኃ ምንጭ ይታያል' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ቀበሮዎች
ይህንን በኢሳይያስ 13:22 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ቄጤማና ሸምበቆ
በደረቅ አካባቢ የሚበቅሉ ተክሎች ናቸው።

Isaiah 35:8

አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ቁጥሮች የእግዚአብሔርን ሕዝብ መፃኢ ክብር ገለጻ ይቀጥላሉ።

ቅዱስ መንገድ የሚባል አውራ ጎዳና በዚያ ይሆናል

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ቅዱስ መንገድ የሚል ስም ያለው አውራ ጎዳና በዚያ ይሆናል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

አውራ ጎዳና

ይህንን ቃል በኢሳይያስ 11፡16 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ንጹሐንም ያልሆኑ

ይህ ንጹሐን ያልሆኑ ሰዎችን ያመለክታል። እግዚአብሔር በመንፈሱ ተቀባይነት የሌለውና የረከሰ አድርጎ የሚቆጥረው ሰው በአካሉ ንጹሕ እንዳልሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "ንጹሕ ያልሆኑ ሰዎች' ወይም "በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ሰዎች' (ስማዊ ቅጽልና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በእርሷ የሚሄድባት

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። በዚህ ስፍራ መሄድ መኖርን ያመለክታል። ይህ የተቀደሰ ሕይወት የሚኖርን ሰው ያመለክታል። የዚህ አረፍተ ነገር መሉ ትርጉም ግልጽ መሆን ይችላል። አት፦ "በተቀደሰ መንገድ የሚኖር' ወይም "የተቀደሰ ሕይወት የሚኖር' (ፈሊጣዊ ንግግርና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

በዚያ አይገኙም

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊተረጎም ይችላል። አት፦ "ማንም በዚያ አያገኛቸውም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የዳኑ

ይህ እግዚአብሔር ያዳናቸውን ሰዎች ያመለክታል። አት፦ "የዳኑቱ' ወይም "እግዚአብሔር ያዳናቸው' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

Isaiah 35:10

እግዚአብሔር የተቤዣቸው

"መቤዠት' ማለት "ማዳን' ማለት ነው። ይህ እግዚአብሔር ያዳናቸውን ሰዎች ያመለክታል። አት፦ "እግዚአብሔር ያዳናቸው እነርሱ' (ስማዊ ቅጽል ተመልከት)

የዘላለም ደስታ በራሳቸው ላይ ይሆናል

ይህ የሰውን ራስ የሰው ሁለንተና ለማለት ይጠቀማል። አት፦ "ዘላለማዊ ደስታ ይኖራቸዋል' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ሐሤትና ደስታ ... ኀዘንና ትካዜ

"ኀዘን' እና "ትካዜ' እንደሆኑት ሁሉ "ሐሤት' እና "ደስታ' የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ነው። በአንድነት የእንዚህን ስሜቶች ከፍተኛ ደረጃ መድረስ ያጎላሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሣሣይነት ተመልከት)

ሐሤትና ደስታ ይቆጣጠራቸዋል

ይህ አንድን ሰው በኃይል ለመቆጣጠር የመቻልን ሰብዓዊ ችሎታ ለእነዚህ ስሜቶች በመስጠት ሕዝቡ በሐሤትና በደስታ እንደሚጥለቀለቁ ይናገራል። አት፦ "በሐሤትና በደስታ ይጥለቀለቃሉ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

ኀዘንና ትካዜ ይሸሻሉ

የሰውን የመሮጥ ችሎታ ለእነዚህ ስሜቶች በመስጠት ሕዝቡ ከእንግዲህ ወዲያ ሐዘንተኞችና የሚተክዙ እንደማይሆኑ ይናገራል። አት፦ "ከእንግዲህ ወዲያ ሐዘንተኞችና የሚተክዙ አይሆኑም' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

---

Chapter 36

Isaiah 36:1

አሥራ አራተኛ ዓመት

"14 ዓመት' (የደረጃ ቁጥር ተመልከት)

ንጉሥ ሕዝቅያስ

የዚህን ንጉሥ ስም በኢሳይያስ 1፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ሰናክሬም

ይህ የአሦር ንጉሥ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ሰናክሬም ... የተመሸጉ ከተሞችን ሁሉ ወጋቸው

በዚህ ስፍራ ሰናክሬም ራሱንና ሠራዊቱን ይወክላል። አት፦ "ሰናክሬምና ሠራዊቱ ... የተመሸጉ ከተሞችን ሁሉ ወጉ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ዋናው አዛዥ

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች ይህንን "ራፋስቂስ' ብለው ይተረጉሙታል። በአሦር የሠራዊት አመራሮች ከፍተኛ ማዕረግ ላለው ጥቅም ላይ የሚውል የአሦራውያን ቃል ነው።

ለኪሶ

ከኢየሩሳሌም ደቡብ ምዕራብ የምትገኝ ከተማ ነች። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ቱቦ

የውኃ መተላለፊያ ሰው ሰራሽ ቦይ ወይም ዋሻ። ይህንን በኢሳይያስ 7፡3 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

የአጣቢው እርሻ

አጣቢዎች፦ 1) ከበግ የተሸለተ የበግ ጸጉር የሚያጥብ ሰው፤ "የበግ ጸጉር አጣቢ' እርሻ ወይም 2) የቆሸሹ ልብሶችን የምታጥብ ሴት፤ "የልብስ አጣቢ እርሻ።' ይህንን በኢሳይያስ 7፡3 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ኬልቂያስ ... ኤልያቄም

የእነዚህን ሰዎች ስም በኢሳይያስ 22፡20 እንዴት እንደረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ሳምናስ

የዚህን ሰው ስም በኢሳይያስ 22፡15 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

አሳፍ ... ዮአስ

እነዚህ ሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

Isaiah 36:4

አላቸው

"ለኤልያቄም፣ ሳምናስ እና ዮአስ'

የመተማመኛችሁ ምክንያት ምንድር ነው?

ለመተማመኛ በቂ ምክንያት የለውም በማለት ንጉሥ ሕዝቅያስን ለመገዳደር የአሦር ንጉሥ ይህን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ በአሳብ ገላጭ አረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ለመተማመኛ አስተማማኝ ምክንያት የለህም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ለሰልፍ የሆነ ምክርና ኃይልህ

"ለሰልፍ የሆነ ምክርና ኃይል አለህ።' "ለሰልፍ የሆነ ... ኃይል' የሚለው ሐረግ በብዛቱ በቂ በኃይሉም በቂ የሆነ ሠራዊትንና የጦር መሣሪያ ያለው መሆንን ያመለክታል። አት፦ "ሰልፍ ለማድረግ በቂ ወታደራዊ ምክር፣ ኃያላን ሰዎችና የጦር መሣሪያ አለህ' (ምትክ ስም ተመልከት)

አሁን የተማመንከው በማን ነው? በእኔ ላይ እንድታምጽ ድፍረት የሰጠህ ማን ነው?

ለማመጽ ኃይል እንዳለው በማመኑ በሕዝቅያስ ላይ ለመሳለቅ የአሦር ንጉሥ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በአሳብ ገላጭ ዐረፍተ ነገርነት ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "በማንም ተማመንክ ምንም ለውጥ አያስከትልም፣ በእኔ ላይ ለማመጽ ድፍረት አይኖርህም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

Isaiah 36:6

አጠቃላይ መረጃ

ከአሦር ንጉሥ ለሕዝቅያስ የተላከው መልእክት ይቀጥላል። ዋናው አዛዡ ለሕዝቅያስ ሰዎች መልእክቱን ይናገራል። (ኢሳይያስ 36፡4-5 ተመልከት)

ተመልከት

በመቀጠል ወደ ሚናገረው የሕዝቅያስን ትኩረት ለመሳብ ሰናክሬም ይህን ቃል ይጠቀማል። አት፦ "ስማ'

በግብጽ መታመን

በዚህ ስፍራ ግብጽ የሚለው የግብጽን ሠራዊት ያመለክታል። አት፦ "በግብጻውያን ሠራዊት መታመን' (ምትክ ስም ተመልከት)

እንደ ምርኩዝ የምትጠቀምበት የተቀጠቀጠ ሸምበቆ፣ ነገር ግን ሰው ቢመረኮዘው ተሰብሮ በእጁ ይገባል ያቆስለውማል

ይህ በእነርሱ መታመኑ እንደማይረዳቸው ነገር ግን እንደሚጎዳቸው ለማጉላት የተቀጠቀጡ ሸምበቆ እንደሆኑ አድርጎ ስለ ግብጽ በተለይ ስለ ሠራዊቱና ስለ ፈርዖን ይናገራል። አት፦ "የተቀጠቀጠን ሸምበቆ ምርኩዝ አድርጎ እንደመሄድ ነው። ሰው ከተመረኮዘው ተሰብሮ በእጁ ይገባል ያቆስለውማል።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የተቀጠቀጠ ሸምበቆ

ሸምበቆ ሣር የሚመስል ረጅም፣ ቀጭን ግንድ ያለው ተክል ነው። ከተቀጠቀጠ ወይም ከተጎዳ ምንም ክብደት መሸከም አይችልም።

ምርኩዝ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከየትኛውም ዓይነት የዛፍ ቅርንጫፍ የሚሠራ አንድ ሰው በሚሄድበት ጊዜ ለመደገፊያነት የሚጠቀምበት በትር ነው።
ሕዝቅያስ የኮረብታ መስገጃዎቹንና መሠዊያዎቹን ያፈረሰበት አይደለምን … ኢየሩሳሌም
ሕዝቡን ለማሞኘትና ሕዝቅያስ ባደረገው እግዚአብሔር ስለተቆጣ አይጠብቃችሁም ለማለት የአሦር ንጉሥ እነዚህ ጥያቄዎች ይጠቀማል። ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ በአሳብ ገላጭ አረፍተ ነገርነት ሊተረጎም ይችላል። አት፡- "እርሱ፣ ሕዝቅያስ የኮረብታ መስገጃዎቹንና መሠዊያዎቹን ያፈረሰበት ነው … ኢየሩሳሌም' ወይም "እርሱ፣ ሕዝቅያስ የኮረብታ መስገጃዎቹንና መሠዊያዎቹን በማፍረስ ያቃለለው ነው … ኢየሩሳሌም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን፣ "በኢየሩሳሌም በዚህ መሠዊያ ፊት መስገድ' አላባችሁ ያለ?
ይህ በቀጥታ እንዳልተወሰደ ሊጻፍ ይችላል። "ይሁዳ' እና ኢየሩሳሌም በውስጣቸው የሚኖረውን ሕዝብ ያመለክታሉ። አት፡- "ለይሁዳና ለኢየሩሳሌም ሕዝብ በኢየሩሳሌም በዚህ መሠዊያ ብቻ መስገድ እንዳለባቸው ነገራቸው' (በቀጥታ የተወሰደና በቀጥታ ያልተወሰደ ጥቅስ እና ምትክ ስም ተመልከት)
Isaiah 36:8
አጠቃላይ መረጃ
ለሕዝቅያስ ሰዎች በመናገር የአሦር ንጉሥ ለሕዝቅያስ የላከው መልእክት ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 36፡4-5 ተመልከት)
ሁለት ሺህ ፈረሶች
"2000 ፈረሶች' (ቁጥሮች ተመልከት)
የሚጋልቡባቸውን ሰዎች ማግኘት ቢቻልህ
ዋናው አዛዥ ብዙ ወታደሮች እንደሌለው በማመልከት በሕዝቅያስና በሠራዊቱ ላይ መሳለቁን ይቀጥላል። (ምጸት ተመልከት)
Isaiah 36:9
አጠቃላይ መረጃ
ለሕዝቅያስ ሰዎች በመናገር የአሦር ንጉሥ ለሕዝቅያስ የላከው መልእክት ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 36፡4-5 ተመልከት)
ከባሪያዎቹ … አንዱን አለቃ እንኳን እንዴት መቋቋም ይቻልሃል?
ዋናው አዛዥ በሕስቅያስና ሠራዊቱ ላይ መሳለቁን ይቀጥላል። በዚህ ወስጥ "አንተ' እያለ ሲናገር የሚያመለክው ሕስቅያስን ነው፣ በእውነቱ ግን የሚያመለክተው የሕዝቅያስን ሠራዊት ነው። ይህ ጥያቄ በአረፍት ነገርነት ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "ሠራዊትህ አንዱን አለቃ እንኳን ማሸነፍ አይችልም … ከባሪያዎቹ' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና ምትክ ስም ተመልከት)
አሁንም በውኑ ያለ እግዚአብሔር ትእዛዝ ይህን አገር አጠፋ ዘንድ ወጥቻለሁን?
ዋናው አዛዥ በሕዝቅያስና በይሁዳ ሕዝብ ላይ ለመሳለቅ ሌላ ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በአረፍተ ነገርነት ሊጻፍ ይቻላል። አት፡- "በእግዚአብሔር ትእዛዝ ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት ወደዚህ መጥቼአለሁ።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ)
ያለ እግዚአብሔር
በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የሚለው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያመለክታል። አት፡- "ያለ እግዚአብሔር ትእዛዝ' (ምትክ ስም ተመልከት)
ይህን አገር አጠፋ ዘንድ … ወደዚህ አገር ወጥተህ አጥፋው
ይህ ሕዝቡን መውጋትና በሚኖሩበት ቦታ ላይ ጥፋት ማድረስ ማለት ነው። አገር የሚለው በዚህ ሰፍራ ኢየሩሳሌምን ያመለክታል። አት፡- "በዚህ ሕዝብ ላይ ውጣ ምድራቸውን አጥፋ … ይህንን ሕዝብ ውጋ ምድራቸውን አጥፋ' (ምትክ ስም ተመልከት)
Isaiah 36:11
ኤልያቄም … ኬልቂያስ … ሳምናስ
የእነዚህን ሰዎች ስም በኢሳይያስ 22፡20 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ሳምናስ
የዚህን ሰው ስም በኢሳይያስ 22፡15 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ዮአስ … ዋናው አዛዥ
የዚህን ሰው ስምና ዋና አዛዥ የሚለውን ሐረግ በኢሳይያስ 36፡2-3 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
እባክህ ለባሪያዎችህ ተናገር
ኤልያቄም፣ ሳምናስና ዮአስ ራሳቸውን የዋናው አዛዥ አገልጋዮች እንደሆኑ አድርገው ይጠራሉ። ይህ አንድ ትልቅ ሥልጣን ያለውን ሰው በትህትና ማናገሪያ መንገድ ነው።
የአረሚን ቋንቋ፣ አረማይክ
አረሚን የተወሰነ የሰዎች ቡድን ስም ነው። አረማይክ የቋንቋቸው ስም ነው።
(የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)
በቅጥርም ላይ ባሉት ሰዎች ጆሮ
በአንድ ሰው ጆሮ መናገር የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ሊሰሙህ በሚችሉበት ቦታ ላይ መናገር ማለት ነው። አት፡- "በቅጥር ላይ ያሉ ሰዎች ሊሰሙን በሚችሉበት ቦታ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
በቅጥርም ላይ ባሉት
ይህ በቅጥሩ ላይ ቆመዋል ማለት ነው። የቅጥር ላይኛው ጫፍ ሰፊና ሰዎች ሊቀመጡና ሊቆሙ የሚችሉበት ቦታ ነው። የዚህ አረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፡- "በቅጥሩ ላይ በቆሙት' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
ጌታዬ ይህን ቃል እናገር ዘንድ ወደ አንተና ወደ ወደ ጌታህ ልኮኛልን?
ዋናው አዛዥ መልእክቱ ለይሁዳ ሕዝብ ሁሉ እንደሆነ ለማጉላት ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "በእርግጥ አለቃዬ ይህን መልእክት ለአንተና መስማት ለሚችሉ ሁሉ እናገር ዘንድ ልኮኛል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
ከእናንተ ጋር … ዘንድ በቅጥር ላይ ወደ ተቀመጡት ሰዎች አይደለምን?
ዋናው አዛዥ ስላቁን ለማጉላት ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "ከእናንተ ጋር … ዘንድ ይህን ለሚሰሙ ሁሉ እናገር ዘንድ ጌታዬ ልኮኛል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
ከእናንተ ጋር ኩሳቸውን ይበሉ ዘንድ ሽንታቸውንም ይጠጡ ዘንድ
ይህ በጣም የሚያበሳጭ አሳብ ነው። ከተማይቱ በውጊያ ውስጥ ስለሆነች እና የሚበሉት ምንም ስለሌላቸው እነዚህን ነገሮች ለመብላት ይፈልጋሉ ማለቱ ነው። የዚህ አረፍተ ነገር ሙሉ አሳብ በይበልጥ ግልጽ ሊሆን ይችላል። አት፡- "ምንም የምተበሉት ስለሌላችሁ፣ እንደ እናንተ፣ በቅርቡ ኩሳቸውን ለመብላት ሽንታቸውንም ለመጠጣት ይፈልጋሉ።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ )
Isaiah 36:13
ዋናው አዛዥ
ይህን በኢሳይያስ 36፡2 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ይህችም ከተማ በአሦር ንጉሥ እጅ አትሰጥም
ይህ በአደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን በአሦር ንጉሥ እጅ አሳልፎ አይሰጣትም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
የንጉሥ እጅ
"የንጉሥ እጅ' የሚለው ንጉሡ በሌሎች ላይ ያለውን ሥልጣን ያመለክታል። አት፡- "ንጉሥ በሌሎች ላይ ያለው ሥልጣን' (ምትክ ስም ተመልከት)
Isaiah 36:16
አጠቃላይ መረጃ
ዋናው አዛዥ ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።
ከእኔ ጋር ሰላም አድርጉ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር እርስ በእርስ በሰላም ለመገናኘት ሕጋዊ ስምምነት ማድረግ ማለት ነው። አት፡- "ሰላም እንዲኖረን እንስማማ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ወደ እኔ ወጡ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግረ እጅ መስጠት ማለት ነው። አት፡- "ለእኔ እጃችሁን ስጡ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
እስክመጣና እስክወስድ
በዚህ ስፍራ የአሦር ንጉሥ ሠራዊቱን እንደራሱ አድርጎ ይናገራል። አት፡- "ሠራዊቴ እስኪመጣና እስኪወስድ' (ምትክ ስም ተመልከት)
የእህልና የወይን ጠጅ ምድር፣ የእንጀራና የወይን ምድር
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው፣ ሁለቱም ምድሪቱ ምን ያህል የበለጸገች እንደምትሆን ለማጉላት ጥቅም ላይ ውለዋል። (አጓዳኝነት ተመልከት)
የእህል ምድር … የእንጀራ ምድር
ይህ ምድራቸው እንደ እህል ባሉ የተፈጠሮ ሀብቶች የተሞላች ነች ማለት ነው። አት፡- "የተትረፈረፈ እህል ያለባት ምድር … የተትረፈረፈ እንጀራ ያለባት ምድር' (ባለቤትነት ተመልከት)
Isaiah 36:18
አጠቃላይ መረጃ
ዋናው አዛዥ የአሦርን ንጉሥ መልእክት ለይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 36፡16 ተመልከት)

ከአሦር ... ከአሕዛብ አማልክት መካከል ያዳኗቸው

ዋናው አዛዥ በይሁዳ ሕዝብ ላይ ለመሳለቅ ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ከአሦር ... ከሕዝቦች አማልክት መካካል ማንም አላዳኗቸውም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

የንጉሥ እጅ

ንጉሥ በሌሎች ላይ ያለው ሥልጣን እንደ እጁ ተገልጾአል። አት፦ "ንጉሡ በሌሎች ላይ ያለው ሥልጣን' (ምትክ ስም ተመልከት)

የሐማትና የአርፋድ አማልክት ወዴት አሉ የሴፈርዋይም አማልክት ወዴት አሉ? ሰማርያን ከኃይሌ አድነዋታልን?

ዋናው አዛዥ በይሁዳ ሕዝብ ላይ ለመሳለቅ ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። እነዚህ ጥያቄዎች ሊጣመሩና በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፉ ይችላሉ። አት፦ "የሐማት፣ የአርፋድ፣ የሴፈርዋይ እና የሰማርያ አማልክት ሕዝባቸውን ከኃይሌ አላዳኗቸውም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ሐማት ... አርፋድ

የእነዚህን ከተሞች ስም በኢሳይያስ 10፡09 ባደረኸው መሠረት ተርጉም። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)

ሴፈርዋይ

ይህ የከተማ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከእጄ ያድን ዘንድ ... ሌላ ያዳነ አምላክ አለን?

ዋናው አዛዥ በይሁዳ ሕዝብ ላይ ለመሳለቅ ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ያዳነ አምላክ የለም ... እግዚአብሔርም በኢየሩሳሌም ከእኔ ኃይል አያድናችሁም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ምድሩን

x

Isaiah 36:21

ኤልያቄም ... ኬልቅያስ ... ሳምናስ ... ዮአስ ... አሳፍ

የእነዚህን ሰዎች ስም በኢሳይያስ 36፡03 ባደረግኸው መሠረት ተርጉም። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

የቤቱ አዛዥ

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር በቤተ መንግሥት ቤተሰብ ጉዳዮች ሥልጣን ያለው ማለት ነው። አት፦ "በቤተ መንግሥቱ ላይ የተሾመ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

---

Chapter 37

Isaiah 37:1

እንዲህም ሆነ

በዚህ ስፍራ ይህ ሐረግ በታሪኩ ወስጥ አስፈላጊ የሆነን ሁኔታ ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። ቋንቋህ ይህን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ልትጠቀምበት ትችላለህ። (አዲስ ሁኔታን ማስተዋወቅ ተመልከት)

ልብሱን ቀደደ፣ ማቅም ለበሰ

ይህ የልቅሶና የጭንቀት ምልክት ነው። አት፦ "በጣም ተጨንቆ ስለነበር ልብሱን ቀደደ በማቅም ተሸፈነ' (የምልክት ተግባር ተመልከት)

ኤልያቄም ... ሳምናስ

የእነዚህን ሰዎች ስም በኢሳይያስ 36፡03 ባደረግኸው መሠረት ተርጉም። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

የቤቱ አዛዥ

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር በቤተ መንግሥት ቤተሰብ ጉዳዮች ሥልጣን ያለው ማለት ነው። አት፦ "በቤተ መንግሥቱ ላይ የተሾመ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ሁሉም ማቅ ለበሱ

ይህ የልቅሶና የጭነቀት ምልክት ነው። (የምልክት ተግባር ተመልከት)

Isaiah 37:3

እንዲህ አሉት

በሕዝቅያስ የተላኩ ሰዎች ኢሳይያስን እንዲህ አሉት

ልጅ ለመወለድ ጊዜው እንድ ደረሰ ነገር ግን እናቲቱ ለመውለድ አቅም እንዳጣች ዓይነት ነው

እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ ውስጥ እንዳሉ ለማጉላት ይህ ማስተያየት ጥቅም ላይ ውሏል። አት፦ "ልጅ ለመወለድ ጊዜው እንድ ደረሰ ነገር ግን እናቲቱ ለመውለድ አቅም እንዳጣችበት አስፈሪ የሆነ ቀን ነው' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)

... ቃል አምላክህ እግዚአብሔር ይሰማ እንደ ሆነ

ሕዝቅያስ በተዘዋዋሪ ሕዝቡ ከጸለየ ዋናው አዛዥ የተናገረውን እግዚአብሔር ሊሰማና ተግባራዊ ምላሽ ሊሰጥ ይችላል። የዚህ አሳብ ሙሉ ትርጉም በይበለጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፦ "ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ከጸለይህ መልእክቱን ይሰማ ይሆናል' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ዋናው አዛዥ

ይህንን ሐረግ በኢሳይያስ 36፡2 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ጌታው

ሐረጉ ንጉሡ የዋናው አዛዥ ጌታ ነው ማለት ነው።

አምላክህ እግዚአብሔርም ስለ ሰማው ቃል ይገሥጸው እንደሆነ

በዚህ ስፍራ አምላክህ እግዚአብሔርም ስለ ሰማው ቃል የሚለው ሐረግ የአሦር ንጉሥ የተናገረውን ያመለክታል። የዚህ አሳብ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፦ "እግዚአብሔር አምላክህ የአሦርን ንጉሥ ስለ ተናገረው ነገር ይገሥጸዋል' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ጸሎትህን ወደ ላይ አንሳ

እግዚአብሔር በሰማይ እንዳለ ለማጉላት ወደ እግዚአብሔር መጸለይ በዚህ መንገድ ተገልጾአል። ጸሎት ወደ ሰማይ ከፍ ሊደረግ እንደሚችል ቁስ ነገሮች ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "ጸልይ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

እስካሁን ቢዚህ ላሉት ለቅሬታው ጸልይ

ይህ በኢየሩሳሌም የቀሩትን ሰዎች ያመለክታል። አት፦ "እስከ አሁን በዚህ ላለን ለጥቂቶች' (ምትክ ስም ተመልከት)

Isaiah 37:5

በላዩ መንፈስን እሰድዳለሁ፣ ወሬንም ይሰማል፣ ወደ ምድሩም ይመለሳል

"በላዩ መንፈስን እሰድዳለሁ' የሚለው ሐረግ አንድ የተወሰነ ውሳኔ እንዲወስን እግዚአብሔር ተጽእኖ ያደርግበታል ማለት ነው። በዚህ ስፍራ መንፈስ የሚለው ቃል ጠንካራ ዝንባሌ ወይም ስሜት ማለት ነው። አት፦ "የተወሰነ ዘገባ ሲሰማ ወደ ምድሩ እንዲመለስ ተጽእኖ አደርግበታለሁ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ተመልከት

በዚህ ስፍራ ይህ ቃል በመቀጠል ወደ ሚነገረው የሕዝቡን ትኩረት ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። አት፦ "ስሙ'

በምድሩም በሰይፍ እንዲወድቅ አደርጋለሁ

"በሰይፍ እንዲወድቅ' የሚለው ሐረግ ጠላቱ በሰይፍ ይገድለዋል የሚል ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፦ "በገዛ ምድሩም፣ ጠላቶቹ በሰይፎቻቸው እንዲገድሉት አደርጋለሁ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 37:8

ለኪሶ

የዚህን ከተማ ስም በኢሳይያስ 36፡2 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ሰናክሬም

የዚህን ሰው ስም በኢሳያየስ 36፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ልብና

ይህ በደቡብ ይሁዳ የምትገኝ ከተማ ነች። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

የኢትዮጵያ ንጉሥ ቲርሐቅ ሊዋጋው አንቀሳቅሷል

ቲርሐቅ የሰው ስም ነው። ለመዋጋት ዝግጁ እንዲሆኑ ሠራዊቱን አንቀሳቅሷል። የዚህ አሳብ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ ሊሆን ይችላል። አት፦ "የኢትዮጵያ ንጉሥ ቲርሐቅ ሠራዊቱን አንቀሳቅሷል' (የስሞች አተረጓገም መንገድ እና እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ሊዋጋው

በዚህ ወስጥ "እርሱን' የሚለው ሰናክሬምን ይወክላል። በዚህ ስፍራ ሰናክሬም ሠራዊቱን ይወክላል። አት፦ "የሰናክሬምን ሠራዊት ሊዋጋ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ኢየሩሳሌም በአሦር ንጉሥ እጅ አትሰጥም

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። "እጅ' የሚለው ቃል የንጉሡን ወታደራዊ ኃይል ያመለክታል። አት፦ "የአሦር ንጉሥና ሠራዊቱ በኢየሩሳሌም አያሸንፉህም' (ምትክ ስምና አድራጊና ተደራጊ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 37:11

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አጠቃላይ መረጃ

ለሕዝቅያስ የተላከውን የአሦርን ንጉሥ መልእክት ይቀጥላል።

ተመልከት ሰምተሃል

በዚህ ስፍራ "ተመልከት" የሚለው ቃል በመቀጥል ለሚነገረው ተጨማሪ አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት፦ "በእርግጥ ሰምተሃል'

አንተስ ትድናለህን?

በሕዝቅያስና በሠራዊቱ ላይ ለመሳለቅ የአሦር ንጉሥ ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "ስለዚህ አንተም አትድንም' ወይም "በእርግጥ አንተንም ማንም አያድንህም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

የአሕዛብ አማልክት አዳኑአቸውን ... ተላሳር

x

Isaiah 37:14

ከመልእክተኞች እጅ

በዚህ ስፍራ ራሳቸው እንደሰጡት ለማጉላት መልእክተኞቹ በእጃቸው ተወክለዋል። አት፦ "መልእክተኞቹ ሰጡት' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ወደ እግዚአብሔር ቤት ወጣ

የእግዚአብሔር ቤት በኢየሩሳሌም በከፍታ ስፍራ ላይ ስለነበረ፣ "ወደ ላይ' እንደሆነ ተነግሮአል።

በእግዚአብሔር ፊት ዘረጋው

ደብዳቤውን በእግዚአብሔር ፊት ዘረጋው። በእግዚአብሔር ቤት መገኘት እግዚአብሔር ባለበት ከመሆን ጋር አንድ እንደሆነ ይታሰብ ነበር። ደብዳቤው ጥቅልል ስለሆነ መተርተርና መዘርጋት ነበረበት።

በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ

ኪሩቤል በቃል ኪዳኑ ታቦት የስርየት መክደኛ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ግልጽ ማድረግ ይጠበቅብሃል። ብዙ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች እግዚአብሔር በላይ በሰማይ ዙፋኑ ላይ እንደሚቀመጥ ሁሉ የቃል ኪዳኑ ታቦት እግዚአብሔር እግሩን የሚያሳርፍበት የእግሩ መረገጫ እንደሆነ አድርገው ይናገራሉ። አት፦ "በቃል ኪዳኑ ታቦት ከኪሩቤል በላይ በዙፋንህ ላይ የምትቀመጥ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

አንተ ብቻህን አምላክ ነህ

"አንተ ብቻ አምላክ ነህ'

በመንግሥታት ሁሉ ላይ

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር በመንግሥታት ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው መሆንና መግዛት ማለት ነው። አት፦ "በመንግሥታት ሁሉ ላይ ሥልጣን አለህ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ሰማይንና ምድርን ፈጥረሃል

ይህ ሁሉን ነገር ፈጥሮአል ማለት ነው። አት፦ "ሁሉን ፈጥረሃል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 37:17

አጠቃላይ መረጃ

ሕዝቅያስ ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን ይቀጥላል።

የላከውን

ሕዝቅያስ ሰናክሬም የላከውን ደብዳቤ እያመለከተ ነው። ይህ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ መሆን አለበት። አት፦ "በላከው መልእክት' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ጆሮህን መልስ

ጆሮህን አዘንብል ወይም ራስህን መልስ። ይህ አንድን ነገር በተሻለ ሁኔታ ለመስማት ራስን መመለስ ማለት ነው።

ሰናክሬም

የዚህን ሰው ስም በኢሳይያስ 36፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

አሕዛብን ሁሉና አገሮቻቸውን

ይህ አጠቃላይነት ነው። ነገሥታቱ በቅርብ ያሉትን በዙ አገራትን አጥፍተዋል፣ ነገር ግን አገራትን ሁሉ ማለት አይደለም። አት፦ "ብዙ ሕዝቦችንና አገራቸውን' (ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)

Isaiah 37:19

አጠቃላይ መረጃ

ሕዝቅያስ ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን ይቀጥላል።

የእንጨትና የድንጋይ የሰው እጅ ሥራ ነበሩ እንጂ አማልክት አልነበሩምና

ሰዎች እነዚህን ጣዖታት በገዛ እጆቻቸው ሠሯቸው ስለዚህም ከንቱ ናቸው የሚለውን ያጎላል። አት፦ "ሰዎች ከእንጨትና ከድንጋይ የሠሯቸው ሐሰተኛ አማልክት ስለሆኑ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ከኃይሉ

"ከአሦር ንጉሥ ኃይል'

መንግሥታት ሁሉ

ይህ በመንግሥታት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ያመለክታል። አት፦ "በመንግሥታት ውስጥ ያሉ ሕዝቦች ሁሉ' (ምትክ ስም ተመልከት)

አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ

"አንተ ብቻ እግዚአብሔር አምላክ ነህ'

Isaiah 37:21

መልእክት ላከ

ይህ መልእክቱን ለንጉሡ ለመስጠት መልእክተኛ ላከ ማለት ነው። አት፦ "መልእክቱን ለመስጠት አንድ ሰው ላከ' (ምትክ ስም ተመልከት)

እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ይህ ነው

"እግዚአብሔር ያለው'

በንቀት ስቃብሃለች

"ስቃብሃለች' ወይም "ተሳልቃብሃለች'

የጽዮን ድንግል ሴት ልጅ ... የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ

እነዚህ ፈሊጣዊ ንግግር ናቸው። ሁለተም ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው። የከተማይቱ ሴት ልጅ ማለት በከተማይቱ የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው። ተመሣሣይ ሐረግ በኢሳይያስ 1፡8 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፦ "የጽዮን ሰዎች ... የኢየሩሳሌም ሰዎች' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

የተገዳደርኸው የሰደብኸውስ ማን ነው ... በእስራኤል ቅዱስ ላይ ነው

በአሦር ንጉሥ ላይ ለመሳለቅ እግዚአብሔር እነዚህን አሳብ ገላጭ ጥያቄዎችች ይጠይቃል። ይህ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "አንተ እግዚአብሔርን ተገዳደርሃል ተሳድበሃልም፤ በእስራኤልም ቅዱስ ላይ ጮኸኻል፣ በትዕቢትም አድርገሃል።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ድምህን ከፍ አድርገሃል

ይህ የሰው ድምጽ ወደ ላይ ከፍ የሚድረግ ቁስ ነገር እንደሆነ አድርጎ ጮኾ መናገርን ያመለከትል። አት፦ "ጮኽሀል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ዓይኖችህን በትዕቢት ወደ ላይ አንስተሃል

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ከሆንከው በላይ ራስህን አስፈላጊ እንደሆነ በመቁጠር ወደ አንድ ነገር በትዕቢት መመልክት ማለት ነው። አት፦ "በትዕቢት መመልከት ወይም በትዕቢት ማድረግ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 37:24

አጠቃላይ መረጃ

ለአሦር ንጉሥ የሚተላለፈው የእግዚአብሔር መልእክት ይቀጥላል።

በባሪያዎችህ

ይህ መልእክት አስይዞ ወደ ሕዝቅያስ የላካቸውን አገልጋዮቹን ያመለክታል። ይህ በይበልጥ ግልጽ ሆኖ ሊቀመጥ ይችላል። አት፦ "በአገልጋዮችህ በላከው መልእክት' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ሄጃለሁ ... እቆርጣለሁ ... እገባለሁ ... ቆፈርሁ ... አደርቅሁ ... በእግሬ

በዚህ ስፍራ ሰናክሬም ብዙ ነገሮችን እንዳሸነፈ ስለራሱ ይናገራል። በእውነቱ ያሸነፋቸው በሚያዘው ሠራዊትና ሠረገሎች ነው። አት፦ "ሄደናል ... እንቆርጣለን ... እንገባለን ... ቆፈርን ... አደረቅን ... በእግራችን' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

ረጃጅሞቹን ዝግባዎቹን

"የሊባኖስን ረጃጅም ዝግባዎች'

እጅግ ፍሬያማ ወደ ሆነው ደኑ

በዚህ ስፍራ "ፍሬያማ' የሚለው ቃል ደኑ ጥቅጥቅ ያለና ጤነኛ ዛፎች የሞሉበት መሆኑን ያመለክታል። አት፦ "እጅግ ፍሬያማ ወደ ሆነው ደኑ ውስጥም' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

የግብጽንም ወንዞች ሁሉ በእግሬ ጫማ አደረቅሁ

በዚህ ስፍራ ሰናክሬም በግብጽ ወንዞች በኩል ሠራዊቱን ሲመራ እንዳደረቃቸው በመናገር ድሉንና የግብጽ ወንዞችን በማቋረጥ ያደረገውን ጉዞ አጋኖ ያቀርባል። አት፦ "ከእግሬ በታች ደረቅ እንደሆኑ አድርጌ በግብጽ ወንዞች ሁሉ በኩል ሠራዊቴን መራሁ' (ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)

Isaiah 37:26

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለአሦር ንጉሥ የላከው መልእክት ይቀጥላል።
በጥንት ጊዜ ... አልሰማህምን
ሰናክሬም አስቀድሞ የሚያውቃቸውን መረጃዎች ሊያሳስበው እግዚአብሔር ይህን አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይቻላል። አት፦ "በእርግጥ በጥንት ጊዜ ... ሰምተሃል' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
የተመሸገቱን ከተሞች የፍርስራሽ ክምር እስኪሆኑ ደረስ እንድታፈርስ
የሰናክሬም ሠራዊት ያጠፏቸውን ከተሞች እንዲያጠፉ እግዚአብሔር አቅዶ ነበር። ይህ በይበልጥ ግልጽ ሆኖ ሊቀመጥ ይችላል። አት፦ "ሠራዊትህ ከተሞችን እንዲያጠፋና የፍርስራሽ ክምር እንዲያደርጋቸው አቅጄአለሁ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
የተመሸጉትን
ጠንካራና በጽኑ የሚጠበቁ
ጥቂት ጉልበት
ደካሞች
ተሰባበሩ
ትናንሽ ቁርጥራጮች ሆኖ መሰባበር። በእጅጉ ተስፋ ለመቁረጥ ጥቅም ላይ የሚውል ስዕላዊ ንግግር ነው። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
እንዲሆን አደረግሁ
እንዲሆን ማድረግ የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር አንድ የተወሰነ ነገር እንዲፈጸም ማድረግ ማለት ነው። አት፦ "እንዲሆን አደረግሁት ወይም እነዚህ ነገሮች እንዲሆኑ አደረግሁ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
በምሥራቅ ነፋስ ፊት፣ በእርሻ ያለ ተክል፣ የለመለመ ቡቃያ፣ በእርሻ ወይም በሰገነት ላይ ያለ ሣር ናቸው
ይህ ከተሞቹን ከሣር ጋር በማስተያየት ከተሞቹ በአሦር ሠራዊት ፊት ምን ያህል ደካማና ለጉዳት የተጋለጡ እንደሆኑ ይናገራል። አት፦ "ከተሞቹ በሠራዊትህ ፊት በእርሻ እንዳለ ሣር ደካሞች ናቸው። በሰገነት ላይ እንደ በቀለና በምሥራቅ ሞቃት ነፋስ እንደተለበለበ ሣር ደካሞች ናቸው።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በምሥራቅ ነፋስ ፊት
የምሥራቅ ነፋስ ከምድረ በዳ የሚነፈስ ሞቃትና ደረቅ ነፋስ ሲሆን በነፈሰም ጊዜ ተክሎች ይሞታሉ።
Isaiah 37:28
አጠቃላይ መረጃ
ለአሦር ንጉሥ የተላከው የእግዚአብሔር መልእክት ይቀጥላል።
እኔ ግን መቀመጥህን፣ መውጣትህን፣ መግባትህን አውቃለሁ
ይህ የሕይወት እንቅስቃሴዎችን በሙሉ ያመለክታል። አት፦ "የምታደርገውን ሁሉ አውቃለሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በእኔ ላይ መቆጣትህን
"መቆጣት' የሚለው ቃል በማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እንዴት በእኔ ላይ ትቆጣለህ' (የነገር ስም ተመልከት)
ትዕቢትህ
በዚህ ስፍራ የንጉሡ ትዕቢት የንጉሡን የትዕቢት ንግግር ያመለክታል። አት፦ "የትዕቢት ንግግርህ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ትዕቢትህ ወደ ጆሮዬ ደርሶአል
ይህ የንጉሡ ንግግር ወደ ጆሮው ጉዞ እንዳደረገ አንድ ነገር እግዚአብሔር የንጉሡን ንግግር እንደሰማ ይናገራል። አት፦ "በትዕቢት ስትናገር ሰምቼአለሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ስናጋዬን በአፍንጫህ፣ ልጓሜንም በከንፈርህ አደርጋለሁ
ሰው እንስሳትን ለመምራት ስናጋና ልጓም ይጠቀማል። ይህ እግዚአብሔር ንጉሡን እንደ እንስሳ በስናጋና በልጓም እንደሚቆጣጠረው አድርጎ እግዚአብሔር ንጉሡን እንደሚቆጣጠረው ይናገራል። አት፦ "ሰው እንስሳውን ስናጋን በአፍንጫው፣ ልጓምን በአፉ በማድረግ እንደሚቆጣጠረው እቆጣጠርሃለሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በመጣህበት መንገድ እመልስሃለሁ
ይህ ንጉሡ ወደ ገዛ ትውልድ አገሩ እንዲመለስ እንደሚደረግ ያመለክታል። ይህ ምን ማለት እንደሆነ በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፦ "ወደ ገዛ አገርህ እንድትመለስ አስገድድሃለሁ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
Isaiah 37:30
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ወደ ሕዝቅያስ የላከው መልእክት ይቀጥላል። (ኢሳይያስ 37፡21 ተመልከት)
ለአንተ ምልክት
"ሕዝቅያስ፣ ለአንተ ምልክት' በዚህ ስፍራ "አንተ' ነጠላ ቁጥር ሲሆን ሕዝቅያስን ያመለክታል። (የ"አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች ተመልከት)
መትከል አለባችሁ ... ትበላላችሁ
በዚህ ስፍራ "አንተ' ብዙ ቁጥር ሲሆን የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታል። (የአንተ ልዩ ልዩ አጠቃቀሞችን ተመልከት)
በሁለተኛው ዓመት የበቀለውን
ይህ ሕዝቡ የሚበላውን ያመለክታል። ትበላላችሁ የሚለው ቃል ከቀደመው ሐረግ ጋር ተያያዞ ሊታይ ይገባል። አት፦ "በሁለተኛው ዓመት የበቀለውን ትበላላችሁ ወይም በሚቀጥለው ዓመት የበቀለውን ትበላላችሁ' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ እና የደረጃ ቁጥር ተመልከት)
ከገቦው የበቀለውን
"ከዚያ በወፍ ዘራሽ የበቀለውን' ወይም "በወፍ ዘራሽ የበቀለውን'
Isaiah 37:31
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሕዝቅያስ የላከው መልእክት ይቀጥላል።
ቅሬታ
ቅሬታ የተቀረው ከሄደ በኋላ የተረፈው የአንድ ነገር ክፍል ነው። በዚህ ስፍራ በይሁዳ የቀሩትን ሰዎች ያመለክታል።
የይሁዳ ቤት
በዚህ ስፍራ "የይሁዳ ቤት' የሚለው ትውልዱን ያመለክታል። አት፦ "የይሁዳ ትውልድ' (ምትክ ስም ተመልከት)
እንደገና ሥር ይሰድዳል ፍሬም ያፈራል
ይህ ሥር እንደሚሰድዱና ፍሬ እንደሚያፈሩ ተክሎች የይሁዳ ሰዎች ባለጸጎች እንደሚሆኑ ይናገራል። አት፦ "ሥር እንደሚሰድድና ፍሬ እንደሚያፈራ ተክል ባለጸጎች ይሆናሉ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ከኢየሩሳሌም ቅሬታ፣ ከጽዮንም ተራራ ያመለጡት ይመጣሉና
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የዳኑትን የሕዝቡን ቅሬታዎች ለማጉላት በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው። (አጓዳኝነት ተመልከት)
የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል
ይህ እግዚአብሔር ከቅንዓቱ የተነሣ አንድ ነገር ማድረጉን ቅንዓቱ ራሱ በእውነቱ ያን ድርጊት እንደፈጸመ አድርጎ ይናገራል። አት፦ "ከቅንዓቱ የተነሣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህን ያደርጋል' ወይም "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከቅንዓቱ የተነሣ ይህን ያደርጋል' (ምትክ ስም ተመልከት)
Isaiah 37:33
አይመጣም ... አይመጣም
በዚህ ስፍራ የአሦር ንጉሥ ራሱንና ሠራዊቱን ሁለቱንም ያመለክታል። አት፦ "ሠራዊቱ አይመጣም ... አይመጡም' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
በጋሻም
"በጋሻዎችም'
መክበቢያ ድልድል
ከተማን በተሻለ ለማጥቃት አንድን ሰራዊት የሚረዳ በአንድ ከተማ ቅጥር ትይዩ የሚገነባ ትልቅ የአፈር ድልድል
ይመጣል ... አይገባም
በዚህ ስፍራ የአሦር ንጉሥ ራሱንና ሠራዊቱን ሁለቱንም ያመለክታል። አት፦ "ይመጣሉ ... አይገቡም' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
ያወጀውን እርግጥኝነት ለመግለጽ እግዚአብሔር በስሙ ስለ ራሱ ይናገራል። እንደ ኢሳይያስ 30፡1 ተርጉም። አት፦ "እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው' ወይም "ይህ እኔ፣ እግዚአብሔር ያወጅኩት ነው' (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)
Isaiah 37:35
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል። ስለ እኔም ስለ ባሪያዬም ስለ ዳዊት ለእኔና ለባሪያዬ ለዳዊት ነገሮች የተሻሉ ይሆኑ ዘንድ
Isaiah 37:36
እንዲሞቱ አደረገ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር መግደል ማለት ነው። አት፦ "ግድያ' (ፈሊጣዊ ንግግር


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተመልከት)
185000 ወታደሮች
"አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ወታደሮች' (ቁጥሮች ተመልከት)
የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም እስራኤልን ለቀቀ ወደ ቤትም ሄደ በነነዌም ተቀመጠ
በዚህ ስፍራ ሰናክሬም ራሱንና ሠራዊቱን ሁለቱንም ያመለክታል። ሁሉም እስራኤልን ለቀቁ ወደ አሦር ወደ ቤት ተመለሱ። ሰናክሬም ወደ ነነዌ ከተማ ተመለሰ። አት፡- "ሰናክሬምና ሠረዊቱ እስራኤልን ለቀቁ ወደ ቤትም ሄዱ፤ ሰናክሬምም በነነዌ ቆየ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
ሰናክሬም
የዚህን ሰው ስም በኢሳያያስ 36፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
Isaiah 37:38
እየሰገደ እያለ
"ሰናክሬም እየሰገደ እያለ'
ናሳራክ
ይህ የሐሰተኛ አምላክ ስም ነው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)
አድራሜሌክ ... ሳራሳር ... አሰስራዶን
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

---

## Chapter 38

Isaiah 38:1
ቤትህን አስተካክል
ይህ አንተ ከሞትክ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያውቁ ቤተ ሰብህንና በጉዳዮችህ ላይ ኃላፊነት የተሰጣቸውን ሰዎች አዘጋጅ ማለት ነው። ይህ በይበልጥ ግልጽ ሆኖ ሊጻፍ ይችላል። አት፡- "ከሞትህ በኋላ እንዲያደርጉት የምትፈልገውን ነገር በቤተ መንግሥትህ ላሉ ሰዎች መንገር አለብህ።' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
አስብ
ፈሊጣዊ ንግግሩ ማስታወስ ማለት ነው። አት፡- "አስታውስ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
በታማኝነት በፊትህ እንደ ሄድሁ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። በዚህ ስፍራ መሄድ ማለት መኖር ማለት ነው። ሐረጉ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ መኖር ማለት ነው። አት፡- "በፊትህ በታማኝነት ኖሬአለሁ' ወይም "በታማኝነት አገልግዬሃለሁ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
በፍጽም ልቤ
በዚህ ስፍራ ልብ የአንድን ሰው ፈጽሞ መሰጠትን የሚወክለውን የውስጥ ማንነትን ያመለክታል። አት፡- "በውስጥ ማንነቴ ሁሉ' ወይም "ፍጹም በሆነ መሰጠቴ' (ምትክ ስም ተመልከት)
በዓይንህ ፊት መልካም የሆነውን
የእግዚአብሔር እይታ የእግዚአብሔርን ፍርድ ወይም ምዘና ይወክላል። አት፡- "ደስ የሚያሰኝህን' ወይም "አንተ መልካም ነው ያልከውን' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 38:4
የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የሚውል ፈሊጣዊ ንግግር ነው። አት፡- "እግዚአብሔር ይህን መልእክት ተናገረ' ወይም "እግዚአብሔር እነዚህን ቃላት ተናገረ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ተመልከት
ይህ አድማጩን በመቀጠል ለሚነገረው ነገር ትኩረት እንዲሰጥ ለመጠየቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት፡- "ስማ'
አስራ አምስት ዓመት
"15 ዓመት' (ቀጥሮች ተመልከት)
የአሦር ንጉሥ እጅ
በዚህ ስፍራ የንጉሥ "እጅ' የሚለው ኃይሉን ያመለክታል። አት፡- "የአሦር ንጉሥ ኃይል' (ምትክ ስም ተመልከት)
Isaiah 38:7
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለሕዝቅያስ መናገሩን ይቀጥላል።
ተመልከት
እግዚአብሔር በመቀጠል ወደ ሚነገረው ነገር የአድማጩን ትኩረት ለመሳብ ይህንን ቃል ይጠቀማል። "ስማ'
የአካዝ ደረጃዎች
እነዚህ ደረጃዎች በዚህ መንገድ የተጠቀሱት አካዝ ንጉሥ በነበረ ጊዜ ስለተገነቡ ነው። ይህን መረጃ በይበልጥ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)
Isaiah 38:9
በሕይወት ዘመኔ መካከል
"ከማርጀቴ አስቀድሞ።' ይህ ከማርጀት በፊት በመካከለኛ እድሜ ላይ መሞትን ያመለክታል።
በሲኦል በሮች አገባለሁ
ይህ ሲኦል መንግሥት እንደሆነና አንድ ሰው የሚገባበት በሮች እንዳሉት አድርጎ ስለመሞት ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ለቀረው ዘመኔ ወደዚያ እላካለሁ
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ዘመኔን ሁሉ ከመኖሬ በፊት ወደ መቃብር እሄዳለሁ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
በሕያዋን ምድር
ሕያዋን የሚለው አሁን በሕይውት ያሉትን ሰዎች ያመለክታል። አት፡- "ሰዎች በሕይወት በሚኖሩበት ምድር' ወይም "ሰዎች በሕይወት በሚኖሩበት በዚህ ዓለም' (ስማዊ ቅጽ ተመልከት)
Isaiah 38:12
አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቅያስ የተጻፈ ጸሎቱን ይቀጥላል።
ሕይወቴ እንደ እረኛ ድንኳን ከእኔ ተወገደች ተወሰደችም
ይህ እረኛ ድንኳኑን ከመሬት ከሚያስወግድበት መንገድ ጋር በማስተያየት እግዚአብሔር የሕዝቅያስን ሕይወት በፍጥነት እንደሚፈጽመው ይናገራል። አት፡- "እረኛ ድንኳኑን እንደሚሸክፍና ተሸክሞ እንደሚሄድ እግዚአብሔር ሕይወቴን ከእኔ ፈጥኖ ይወስዳታል።' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ሕይወቴ ተወገደች
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር ሕይወቴን ወሰዳት' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ሕይወቴን እንደ ሸማኔ ጠቀለልሁ፣ አንተ ከመጠቅለያው ትቆርጠኛለህ
ይህ ሸማኔ ልብሱን ከመጠቅለያው ከሚቆርጥበትና ከሚጠቀልልበት መንገድ ጋር በማስተያየት እግዚአብሔር የሕዝቅያስን ሕይወት በፍጥነተ እንደሚፈጽመው ይናገራል። አት፡- "ሲጨረስ ሸማኔ ልብሱን ከመጠቅለያው እንደሚቆርጥ፣ ሕይወቴን በፍጥነት ትፈጽማታለህ' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ትቆርጠኛለህ
በዚህ ውስጥ "አንተ' የሚለው ነጠላ ቁጥር ነው እግዚአብሔርንም ያመልክታል። (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች ተመልከት)
መጠቅለያ
ልብስ ለመሥራት ክሮችን ለማጠላለፍ የሚያገለግል መሣሪያ ነው።
እንደ አንበሳ አጥንቶቼን ሁሉ ሰበረ
በአንበሶች ከተበጫጨቀ ሰውነት ጋር እያስተያየ ሕዝቅያስ በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ መሆኑን ይናገራል። አት፡- "ስቃዬ በአንበሶች እንደተበጫጨቅሁ ዓይነት ነበር' (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 38:14
አጠቃላይ መረጃ
ሕዝቅያስ የተጻፈ ጸሎቱን ይቀጥላል።
እንደ ጨረባ ተንጫጫሁ፣ እንደ ርግብም አጉተመተምኩ
ሁለቱም ሐረጎች ተመሣሣይ ነገር ይናገራሉ፣ የሕዝቅያስ ጩኸቶች ምን ያህል አሳዛኝ እንደሆነም ያጎላሉ። ጨረባና ርግብ የወፍ ዓይነት ናቸው። አት፡- "ጩኸቶቼ አሳዛኝ ናቸው—የጨረባ ጫጫታና የርግብ ማጉተምተም ዓይነት ድምጽ ያሰማሉ' (አጓዳኝነትና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ዓይኖቼ
በዚህ ስፍራ ወደ አንድ ነገር መመልከቱን ለማጉላት "ዓይኖቼ' በማለት ወደ ራሱ ያመለክታል። አት፡- "እኔ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
ወደ ላይ ከማየት

ይህ እግዚአብሔር እንዲረዳው ሕዝቅያስ ወደ ሰማይ መመልከቱን ያመለክታል። የዚህ አሳብ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ መሆን ይችላል። አት፦ "ከሰማይ የሚመጣ እርዳታ እጠብቃለሁ' ወይም "እንድትረዳኝ እጠብቅሃለሁ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ)

ተጨንቄአለሁ

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "በሽታዬ አስጨንቆኛል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ምን እላለሁ?

ሕዝቅያስ ምንም የሚለው እንዳልቀረው ለማጉላት ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ በአረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። አት፦ "የምናገረው የቀረኝ ምንም ነገር የለኝም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ቀስ ብዬ ሄዳለሁ

ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። በዚህ ስፍራ እሄዳለሁ የሚለው አኗኗሩን ያመለክታል። አት፦ "በትህትና እኖራለሁ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)

ምክንያቱም በሐዘን ተሸንፌአለሁና

"ምክንያቱም ሐዘንን ጠግቤአለሁና' ወይም "ምክንያቱም በጣም አዝኛለሁና'

Isaiah 38:16

አጠቃላይ መረጃ

ሕዝቅያስ የተጻፈ ጸሎቱን ይቀጥላል።

ሕይወቴ ተመልሶ ይሰጠኝ እንደሆነ

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ሕይወቴን መልሰህ ትሰጠኝ እንደሆነ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ከጥፋት ጉድጓድ

ሕዝቅያስ አልሞተም ነገር ግን እያጣጣረ ነበር። ይህ እግዚአብሔር ከጣር እንዳዳነው ያመለክታል። የዚህ አሳብ ሙሉ ትርጉም በይበልጥ ግልጽ መሆን ይችላል። አት፦ "ከጣርና ወደ ጥፋት ጉድጓድ ከመውረድ' ወይም "ስለዚህ አልሞትኩም' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልሆነ መረጃ)

ኃጢአቴንም ሁሉ ወደ ኋላህ ጥለሃልና

ሕዝቅያስ፣ እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር ማለቱን እግዚአብሔር ወደ ኋላው እንደወረወረውና እንደረሳው ቁስ ነገር አድርጎ ይናገራል። አት፦ "ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር ብለሃልና ከእንግዲህም ወዲያ አታስበውምና' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 38:18

አጠቃላይ መረጃ

ሕዝቅያስ የተጻፈ ጸሎቱን ይቀጥላል።

ሲኦል አያመሰግንህምና፣ ሞትም አያከብርህምና

በዚህ ስፍራ "ሲኦል' እና "ሞት' የሚሉት የሞቱ ሰዎችን ያመለክታሉ። አት፦ "በሲኦል ያሉ አያመሰግኑህምና፣ የሞቱ ሰዎችም አያከበሩህም' (ምትክ ስም ተመልከት)

ወደ ጉድጓድ የሚወርዱ

"ወደ መቃብር የሚወርዱ'

በተዓማኒነትህ ተስፋ አያደርጉም

"በታማኝነትህ ተስፋ አይኖራቸውም።' በዚህ ውስጥ "አንተ' የሚለው ነጠላ ቁጥር ሲሆን እግዚአብሔርን ያመለክታል። (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች ተመልከት)

ሕያው ሰው ... ሕያው ሰው

የሞተ ሰው ሳይሆን ሕያው ሰው ብቻ፣ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ይችላል የሚለውን ለማጉላት ሕዝቅያስ ይህን ሐረግ ይደግማል። (አጓዳኝነት ተመልከት)

Isaiah 38:20

አጠቃላይ መረጃ

ሕዝቅያስ የተጻፈ ጸሎቱን ይቀጥላል።

ያድነኛል

ይህ ከሞት ጣር መዳኑን ያመለክታል። በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አት፦ "ከሞት ጣር ያድነኛል' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ)

እናከብራለን

በዚህ ውስጥ እኛ የሚለው ሕዝቅያስንና የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታል። (አካታች "እኛ' ተመልከት)

Isaiah 38:21

አሁን

ይህ ቃል በዋናው ታሪክ አቅጣጫ ውስጥ መቋረጥን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ ስለ ሕዝቅያስና ኢሳይያስ ታሪካዊ ዳራ መረጃ ይሰጣል (ታሪካዊ ዳራ መረጃ ተመልከት)

ይለብጡት

የሕዝቅያስ ባሮች ይለብጡት

የበለስ ጥፍጥፍ

ይህ ለቅባትነት ጥቅም ላይ ይውል ነበር። ይህ ምን ማለት እንደሆነ በይበልጥ ግልጽ መሆን ይችላል። አት፦ "የተፈጨ የበለስ ቅባት ተጠቀሙ' (እንደሚታወቅ ታሳበ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልሆነ መረጃ ተመልከት)

እባጭ

ያመረቀዘ ቆዳ ላይ የሚገኝ ሕመም የሚሰማበት አካባቢ

---

Chapter 39

Isaiah 39:1

ማርዱክ—በልዳን ... በልዳን

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (የስሞች አተረጓገም መንገድ ተመልከት)

ሕዝቅያስም በእነዚህ ነገሮች ደስ ተሰኘ

ይህ በይበልጥ ግልጽ መሆን ይችላል። አት፦ "የንጉሡ መልእክተኞች በደረሱ ጊዜ፣ ሕዝቅያስ ባመጡት ነገር ደስ ተሰኘ' (እንደሚታወቅ ታሳቢ የሚደረግ እውቀትና ግልጽ ያልሆነ መረጃ ተመልከት)

የከበሩ ነገሮች ግምጃ ቤቱን ለመልእክተኞቹ አሳያቸው

"ያሉትን ውድ ነገሮች ሁሉ ለመልእክተኞቹ አሳያቸው'

ግምጃ ቤት

ነገሮች የሚጠበቁበት ሕንፃ

በግምጃ ቤቱ የተገኘውን ሁሉ

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "በግምጃ ቤቱ የነበረውን ነገር ሁሉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

በቤቱና በግዛቱ ሁሉ ካለው ሕዝቅያስ ያላሳያቸው ምንም የለም

ሁሉን ነገር አላሳየም፣ ነገር ግን ሕዝቅያስ ብዙ ነገር ለማሳየቱ ትንሽ ግነት ነው። ደግሞም ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ሕዝቅያስ በቤቱና በቤተ መንግሥቱ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉንም ማለት በሚቻል ደረጃ አሳያቸው' (ድርብ አሉታዊና ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)

Isaiah 39:3

በቤቴ ያለውን ሁሉ አይተዋል። ከከበሩት ነገሮቼ ያላሳየኋቸው ምንም የለም

እነዚህ ሁለት ዐረፍት ነገሮች የሚናገሩት አንድ ነገር ሲሆን ሕዝቅያስ ለሰዎቹ ምን ያህል እንዳሳያቸው ለማጉላት ተያይዘው ጥቅም ላይ ውለዋል። (አጓዳኝነት ተመልከት)

በቤቴ ያለውን ሁሉ

ሕዝቅያስ ብዙ ነገር አሳይቶአቸዋል፣ ነገር ግን ይህ ማለት በግድ በቤተ መንግሥቱ ያለውን ሁሉ ማለት ባለመሆኑ የጅምላ ንግግር ነው። (ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)

ከከበሩት ነገሮቼ ያላሳየኋቸው ምንም የለም

ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "በቤተ መንግሥቴ የሚገኙትን ውድ ነገሮች ሁሉ አሳየኋቸው' (ድርብ አሉታዊ ተመልከት)

Isaiah 39:5

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር

ይህን ሐረግ በኢሳይያስ 1፥9 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።

ቃል

"መልእክት'

ተመልከት

በመቀጠል ወደ ሚነገረው ነገር የሕዝቅያስን ትኩረት ለመሳብ ይህ ቃል በዚህ ስፍራ ጥቅም ላይ ውሏል። "ስማ'

በቤተ መንግሥትህ የሚገኝ ነገር ሁሉ ... ወደ ባቢሎን በሚጋዝበት ጊዜ

ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "የጠላት ሠራዊት በቤተ መንግሥትህ የሚገኘውን ነገር ሁሉ ... ወደ ባቢሎን በወሰደ ጊዜ (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

Isaiah 39:7

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቅያስ መናገሩን ይቀጥላል።

ከአንተ የሚወለዱ ልጆች



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 40

Isaiah 40:1

አጽናኑ፣ አጽናኑ

አጽናኑ የሚለው ቃል አጽንዖት ለመስጠት ተደግሞአል፡፡

ይላል አምላካችሁ

በዚህ ውስጥ "አናንተ' የሚለው የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲያጽናኑ ነቢዩ የሚነግራቸውን ሰዎች ያመለክታል፡፡ (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች ተመልከት)

ለኢየሩሳሌም በፍቅር ልብ ተናገሩ

ነቢዩ ስለ ኢየሩሳሌም እግዚአብሔር ይቅር እንዳላት ሴት አድርጎ ይናገራል፡፡ ኢየሩሳሌምም በከተማይቱ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ትወክላለች፡፡ አት፡- "ለኢየሩሳሌም ሕዝብ በፍቅር ልብ ተናገሩ' (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየትና ምትክ ስም ተመልከት)

አውጁላት … ጦርነትዋ … ኃጢአትዋ … ተቀብላለች … ኃጢአትዋ

በዚህ ውስጥ የሚገኘው ተውላጠ ስም ኢየሩሳሌምን ያመለከታል፣ ነገር ግን "የኢየሩሳሌም ሕዝብ' እንደ አማራጭ ትርጉም ከተወሰደ ሊቀየር ይችላል፡፡ አት፡- "አውጁላቸው … ጦርነታቸው … ኃጢአታቸው … ተቀብለዋል … ኃጢአታቸው' (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)

ጦርነትዋ

"ጦርነት' የሚለው ቃል ሊያመለክታቸው የሚችሉ ትርጉሞች 1) ወታደራዊ ውጊያ ወይም 2) የግዳጅ የጉልበት ሥራ፡፡

ኃጢአትዋ ተሰረየ

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አት፡- "እግዚአብሔር ኃጢአትዋን ይቅር አላት' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ከእግዚአብሔር እጅ

በዚህ ስፍራ "እጅ' የሚለው እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል፡፡ አት፡- "ከእግዚአብሔር' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

Isaiah 40:3

የሚጮኽ ድምጽ

ድምጽ የሚለው "ቃል' የሚጮኸውን ሰው ይወክላል፡፡ አት፡- "የሚጮኽ ሰው' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፣ለአምላካችንም ጎዳና በበረሃ አስተካክሉ

እነዚህ ሁለት መስመሮች ተጓዳኝ ሲሆኑ በመሠረቱ የሚናገሩትም አንድ ዓይነት ነገር ነው፡፡ ለእግዚአብሔር እርዳታ የሕዝቡ ራሱን ማዘጋጀት እንዲሄድበት ለእግዚአብሔር መንገድ ማዘጋጀት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል፡፡ (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

በረሃ

ይህንን ቃል በኢሳይያስ 35፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት፡፡

ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፣ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል

እነዚህ ሐረጎች ሕዝቡ እንዴት ለእግዚአብሔር ጎዳና ማዘጋጀት እንዳለባቸው ያብራራሉ፡፡ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጹ ይችላል፡፡ አት፡- "ሸለቆውን ሁሉ ከፍ አድርጉ፣ ተራራውንና ኮረብታውን ሁሉ ዝቅ አድርጉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል

ሸለቆውን ከተቀረው መሬት ጋር የተስተካከለ ማድረግ ሸለቆውን ከፍ ማድረግ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል፡፡ አት፡- "ሸለቆው ሁሉ ይሞላል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

ጠማማውም መሬት ይቃናል፣ ስርጓጉጡም ቦታ ሜዳ ይሆናል

እነዚህ ሐረጎች ሕዝቡ እንዴት ለእግዚአብሔር ጎዳና ማዘጋጀት እንዳለባቸው ያብራራሉ፡፡ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጹ ይችላሉ፡፡ አት፡- "ጠማማውን መሬት አቃኑ፣ ስርጓጉጡንም ቦታ ሜዳ አድርጉ' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ እና መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)

የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል

ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አት፡- "እግዚአብሔር ክብሩን ይገልጻል' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)

የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና

"አፍ' የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል፡፡ አት፡- "እግዚአብሔር ተናግሮአልና' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)

Isaiah 40:6

ሥጋ ለባሽ ሁሉ ሣር ነው

"ሣር' የሚለው ቃል ሕዝቡን ያመለክታል፡፡ ሁለቱም ፈጥነው ስለሚሞቱ ተናጋሪው ሰዎች እንደ ሣር እንደሆኑ ይናገራል፡፡ አት፡- "ሰው ሁሉ እንደ ሣር ነው' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የኪዳናቸው ታማኝነት እንደ ሜዳ አበባ ነው

ተናጋሪው ሕዝቡ ለኪዳናቸው ያላቸውን ታማኝነት ከአበቦች ማበብና ፈጥኖ መሞት ጋር ያስተያያል፡፡ "ታማኝነት' የሚለው የነገር ስም "ታማኝ' በሚል ሊገልጽ ይችላል፡፡ "የኪዳን ታማኝነት' የሚለውን በኢሳይያስ 16፡5 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት፡፡ አት፡- "የሜዳ አበባ ፈጥኖ እንደሚሞት ለኪዳን ታማኝ መሆንን ፈጥነው ያቆማሉ' (ዘይቤአዊ ንግግርና የነገር ስም ተመልከት)

የኪዳን ታማኝነት

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) የኪዳን ታማኝነት ወይም 2) ውበት

የእግዚአብሔር እስትንፋስ ሲነፍስበት

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) "እግዚአብሔር እስትንፋሱን ሲያነፍስበት' ወይም 2) "እንዲነፍስበት እግዚአብሔር ነፋስ ሲልክ፡'

ሰው ሣር ነው

ሁለቱም ፈጥነው ስለሚሞቱ ተናጋሪው ሰዎች ሣር እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል፡፡ (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል

ቃሉ ለዘላለም ጸንቶ እንደሚኖር አድርጎ እግዚአብሔር የተናገረው ለዘላለም እንደሚኖር ተናጋሪው ይናገራል፡፡ (ሰስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 40:9

የምስራች የምትነግሪ ጽዮን ሆይ ከፍ ወዳለው ተራራ ውጪ

ከተራራ ጫፍ የምሥራች የምታወጅ መልእክተኛ እንደሆነች አድርጎ ጸሐፊው ስለ ጽዮን ይናገራል፡፡ (ግዑዝ ነገርን እንደ ሰው ማየት ተመልከት)

ከፍ ወደ አለ ተራራ ውጪ

የሚያውጁትን ብዙ ሰዎች መስማት እንዲችሉ መልእክተኞች እንደ ተራራ ባለ ከፍ ባለ መሬት ላይ ብዙ ጊዜ ይቆማሉ፡፡ (እንደሚታወቅ ታሳቢ የተደረገ እውቀትና ግልጽ ያልተደረገ መረጃ ተመልከት)

ጽዮን

ይህ በጽዮን የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል፡፡ አት፡- "እናንተ የጽዮን ሰዎች' (ምትክ ስም ተመልከት)

የምስራች የምታመጪ ኢየሩሳሌም ሆይ

ጸሐፊው ኢየሩሳሌም የምስራች የምታውጅ መልእክተኛ እንደሆነች አድርጎ ይናገራል፡፡ (ግዑዝ ነገር እንደ ሰው ማየትን ተመልከት)

ክንዱ ስለ እርሱ ይገዛል

በዚህ ስፍራ ክንድ የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል፡፡ አት፡- "በታላቅ ኃይል ይገዛል' (ምትክ ስም ተመልከት)

ዋጋው ከእርሱ ጋር ነው … ያዳናቸው በፊቱ ይሄዳሉ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሣሣይ ነገር ይናገራሉ፡፡ ያዳናቸው እነርሱ ዋጋው ናቸው፡፡ አት፡- "ያዳናቸውን እንደ ዋጋው ከራሱ ጋር ያመጣቸዋል' (አጓዳኝነት ተመልከት)

Isaiah 40:11

መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል

ጸሐፊው የእግዚአብሔር ሕዝብ በጎች እግዚአብሔር ደግሞ እረኛቸው እንደሆነ ይናገራል፡፡ አት፡- "እረኛ መንጋውን እንደሚመግብ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይጠነቀቃል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

Isaiah 40:12

ተራሮችን በሚዛን … የመዘነ

ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃል እንዲሁም እግዚአብሔር ብቻ እነዚህን ነገሮች ማድረግ በመቻሉ ላይ አጽንዖት ያደርጋል፡፡ አት፡- "እንዲሁም ተራሮችን በሚዛን … ማንም የለም ነገር ግን እግዚአብሔር መዘናቸው' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)

ውኆችን በእፍኙ የሰፈረ
እግዚአብሔር በውቂያኖሶች ውስጥ ምን ያህል ውኃ እንዳለ ማወቁ እግዚአብሔር ውኃን በእጁ እንደያዘ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ሰማይንም በስንዝር የለካ
"ስንዝር' እጅ እስከ መጨረሻ ሲዘረጋ በአውራ ጣትና በትንሹ ጣት መካከል ያለ የርዝመት መለኪያ ነው። እግዚአብሔር የሰማይን ርዝመት ማወቁ በእጁ እንደለካ ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የምድርን አፈር በቅርጫት ውስጥ የያዘ
እግዚአብሔር በመሬት ላይ ምን ያህል አፈር እንዳለ ማወቁ በቅርጫት ውስጥ እንደያዘው ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ተራሮችን በሚዛን፣ ኮረብቶችንም በሚዛን የመዘነ ... ?
እግዚአብሔር የተራሮች ክብደታቸው ምን ያህል እንደሆነ ማወቁ በሚዛን እንደ መዘናቸው ተደርጎ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 40:13
አጠቃላይ መረጃ
የእግዚአብሔርን ልዩ መሆን ለማጉላት ኢሳይያስ ጥያቄዎችን መጠቀሙን ይቀጥላል። (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
የእግዚአብሔርን አእምሮ ያወቀ ማን ነው? ወይም አማካሪው ሆኖ ያስተማረው ማን ነው?
ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃል፣ ማንም እነዚህን ነገሮች ማድረግ እንደማይችል አጽንዖት ይሰጣል። አት፡- "ማንም የእግዚአብሔርን አእምሮ አላወቀም፣ ወይም አማካሪው ሆኖ አላስተማረውም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
የእግዚአብሔርን አእምሮ ያወቀ
በዚህ ስፍራ "አእምሮ' የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን አሳብ ብቻ ሳይሆን ፍላጎቱንና ገፊ ምክንያቶቹን ጭምር ያመለክታል።
መመሪያን ከማን ተቀበለ?
ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃል፣ ማንም መቼም ይህን ማድረግ እንደማይችል አጽንዖት ይሰጣል። አት፡- "ነገሮችን በትክክለኛ መንገድ እንዲያደርግ ማንም አላስተማረውም። ማንም እውቀትን አላስተማረውም። የማስተዋልን መንገድ ማንም አላስተማረውም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
Isaiah 40:15
ተመልከት ... እይ
እነዚህ ቃላት በሚከተለው ላይ አጽንዖት ይጨምራሉ።
አሕዛን በገንቦ እንዳለች ጠብታ ናቸው፣ በሚዛንም ላይ እንዳለ ትቢያ ተቆጥረዋል
ነቢዩ፣ አሕዛብ ለእግዚአብሔር ምን ያህል ትንሽና እዚህ ግቡ የማይባሉ መሆናቸውን ለማጉላት ከውኃ ጠብታና ከትቢያ ጋር ያስተያያቸዋል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
በገንቦ እንዳለች ጠብታ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ገንቦ ውስጥ ጠብ ያለ የውኃ ጠብታ ወይም 2) ከገንቦው ወደ ወጪ ጠብ ያለ የውኃ ጠብታ
በሚዛን ላይ እንዳለ ትቢያ ተቆጥረዋል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እግዚአብሔር በሚዛን ላይ እንዳለ ትቢያ ይቆጥራቸዋል።' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
በእርሱ ዘንድ እንደሌለ ነገር ተቆጥረዋል
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "እርሱ እንደሌለ ነገር ይቆጥራቸዋል' (አድጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
Isaiah 40:18
እንግዲህ እግዚአብሔርን ከማን ጋር ታስተያዩታላችሁ? ከምን ጣዖትስ ጋር ታመሳስሉታላችሁ?
ከእግዚአብሔር ጋር የሚስተያይ ጣዖት እንደሌለ ለማጉላት ኢሳይያስ ሁለት ተመሣሣይ ጥያቄዎችን ይጠቀማል። አት፡- "እግዚአብሔርን የምታስተያዩበት ማንም የለም። እርሱን የምታመሳስሉበት ጣዖት የለም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና አጓዳኝነት ተመልከት)
አንተ
ይህ ብዙ ቁጥር ሲሆን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሁሉ ያመለክታል። (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች ተመልከት)
የእጅ ባለ ሙያ ቀርጾታል፡- የወርቅ አንጥረኛ በወርቅ ለብጦታል፣ የብሩንም ሰንሰለት አድርጎለታል
"ባለ ሙያ ቀርጾታል፣ ሌላኛው በወርቅ ለብጦታል የብሩንም ሰንሰለት አድርጎለታል'
Isaiah 40:21
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእግዚአብሔር ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።
አላወቃችሁምን? አልሰማችሁምን? ከመጀመሪያው አንስቶ አልተወራላችሁምን? ምድር ከተመሠረተች ጀምሮ አላስተዋላችሁምን?
እንደ ፈጣሪነቱ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ሕዝቡ ማወቅ እንደሚገባቸው አጽንዖት ለመስጠት ኢሳይያስ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማል። አት፡- "እናንተ በእርግጥ አውቃችኋል ሰምታችኋልም! ከመጀመሪያው አንስቶ ተነግሮአችኋል፤ ምድር ከተመሠረተች ጀምሮ አስተውላችኋል!' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና አጓዳኝነት ተመልከት)
ከመጀመሪያ አንስቶ አልተወራላችሁምን?
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "ከመጀመሪያው አንስቶ ሰዎች አላወሩላችሁምን?' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ምድር ከተመሠረተች ጀምሮ
ምድር እግዚአብሔር መሠረት የጣለላት ሕንፃ እንደሆነች አድርጎ እግዚአብሔር ምድርን እንደፈጠራት ነቢዩ ይናገራል። አት፡- "እግዚአብሔር ምድርን ከፈጠረበት ጊዜ አንስቶ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በምድር ክበብ ላይ የሚቀመጠው
እግዚአብሔር ምድርን መግዛቱን፣ እግዚአብሔር ከምድር ከፍ ብሎ ዙፋን ላይ እንደተቀመጠ አድርጎ ነቢዩ ይናገራል።
በእርስዋም የሚኖሩት በፊቱ እንደ አንበጣ ናቸው
ነቢዩ እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያይበትን መንገድ ሰዎች አንበጣን ከሚያዩበት መንገድ ጋር ያስተያያል። አንበጦች ለሰዎች ትንሽ እንደሆኑ እንዲሁ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ትንሽና ደካማ ናቸው። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
ሰማያትን እንደ መጋረጃ የሚዘረጋቸው እንደ ድንኳንም ለመኖሪያ የሚዘረጋቸው
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው። እግዚአብሔር ሰማያትን የፈጠረው በውሰጡ ለመኖር ድንኳን እንደሚተክል እንደሆነ አድርጎ ነቢዩ ይናገራል። አት፡- "ሰው በቀላሉ መጋረጃ እንደሚዘረጋ ወይም በውስጡ ለመኖር ድንኳን እንደሚተክል ሰማያትን ዘረጋ' (አጓዳኝነትና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 40:23
ዝቅ ያደርጋል
"እግዚብሔር ዝቅ ያደርጋል'
ገና እንደ ተተከሉ ... እነርሱም ደረቁ
አዳዲስ ተክሎች ሞቃታማ ነፋስ ሲነፍስባቸው እንደሚደርቁ አለቆች በእግዚአብሔር ፊት ተስፋ የሌላቸው እንደሆኑ ነቢዩ ይናገራል ። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
እነርሱ ገና እንደተተከሉ፣ ገና እንደተዘሩ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ የሚናገሩት አንድ ነገር ሲሆን ተክሉ ወይም ዘሩ መሬት ውስጥ የተተከለበትን ነጥብ ያመለክታሉ። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፡- "አንድ ሰው ወዲያው እንደተከላቸው ... አንድ ሰው ወዲያው እንደዘራቸው' (አጓዳኝነትና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
ነፋስ እንደ እብቅ ጠርጎ ወሰዳቸው
አለቆችን እንደ ተክል እግዚአብሔርን ደግሞ እንዲጠወልጉ በሚያደርግ ነፋስ የገለጻቸው ስዕላዊ ንግግር በዚህ ዘይቤአዊ ንግግር ቀጥሏል። ነፋስ እብቅን ጠርጎ እንደሚወስድ የእግዚአብሔር የፍርድ ነፋስ የደረቁትን ተክሎች በቀላሉ ያስወግዳቸዋል። (ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 40:25
እመሳሰለው ዘንድ ከማን ጋር አስተያያችሁኝ?
የሚመስለው ማንም እንደሌለ ለማጉላት እግዚአብሔር ሁለት ተመሣሣይ አሳብ ገላጭ ጥያቄዎችን ይጠቀማል። አት፡- "እኔን ልታስተያዩ የምትችሉበት ማንም የለም። የምመስለው ማንም የለም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና አጓዳኝነት ተመልከት)
እነዚህን ከዋክብት ሁሉ የፈጠረ ማን ነው?
ይህ እግዚአብሔር ነው የሚል ምላሽ የሚጠብቅ መሪ ጥያቄ ነው። አት፡- "እነዚህን ሁሉ ከዋክበት እግዚአብሔር ፈጠራቸው!' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
ሰልፋቸውን ይመራል
በዚህ ስፍራ "ሰልፍ' የሚለው ቃል ወታደራዊ ሰልፍን ያመለክታል። ከዋክበቱ እግዚአብሔር እንዲገለጡ የሚያዝዛቸው ወታደሮች እንደሆኑ አድርጎ ነቢዩ ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በኃይሉ ታላቅነትና በኃይሉ ብርታት
"የኃይሉ ታላቅነት' እና "የኃይሉ ብርታት' የሚሉት ሐረጎች የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያጎሉ ሁለት ተመሣሣይ ነገሮችን ይመሠርታሉ። አት፡- "በታላቅ ኃይሉና በብርቱ ኃይሉ' (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)

አንዱም አይጠፋም
አሉታዊው አሳብ አዎንታዊዉን ያጎላል። አት፦ "እያንዳንዱ ይኖራል' (ሁኔታን በማንበብ ላይ የተመሠረተ ትንቢት ተመልከት)
Isaiah 40:27
ያዕቆብ ሆይ፣ እስራኤልም ሆይ … ፍርዴ … ለምን ትላለህ? … ትናገራለህ'?
ጥያቄው እየተናገሩ ያሉትን መናገር እንደሌለባቸው ያጎላል። አት፦ "የእስራኤል ሕዝብ ሆይ … ፍርዴ … አትበል' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
ያዕቆብ ሆይ፣ እስራኤልም ሆይ … ለምን ትላለህ? ትናገራለህ?
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታሉ። አት፦ "የእስራኤል ሕዝብ ሆይ ለምን ትላለህ' (የሁለት ነገሮች ተመሣሣይነት ተመልከት)
መንገዴ ከእግዚአብሔር ተሰውራለች
የእግዚአብሔር የሚሆንባቸውን አለማወቅ እግዚአብሔር የሚጓዙበትን መንገድ እንደማያይ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "የሚሆንብንን እግዚአብሔር አያውቅም' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
አምላኬ ስለ ፍርዴ ግድ የለውም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ሌሎች በእኔ ላይ ስለሚያደርጉት ኢፍትሐዊ ነገር አምላኬ ግድ የለውም' ወይም 2) "አምላኬ ለእኔ ፍትሕን ለማድረግ ግድ የለውም'
አላወቅህምን? አልሰማህምን?
ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ማወቅ እንዳለበት ለማጉላት ኢሳይያስ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማል። እነዚህን በኢሳይያስ 40፡21 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት፡ አት፦ "በእርግጥ ታውቃላችሁ ሰምታችኋልም' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
የምድር ዳርቻ
በምድር በጣም ሩቅ የሆኑ ቦታዎች ምድር የምታልቀበት ቦታዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። እነዚህ ሐረጎች ስዕላዊ ንግግር ይፈጥራሉ በዳርቻዎችም መካከል ያሉትን ቦታዎች ሁሉ ያመለክታል። አት፦ "በጣም ሩቅ የሆኑ የምድር ቦታዎች' ወይም "መላው ምድር' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 40:29
ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፣ ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው እግዚአብሔርም ብርታት የሌላቸውን እንደሚያበረታ ያጎላሉ። (አጓዳኝነት ተመልከት)
ኃይልን ይሰጣል
"እግዚአብሔር ኃይል ይሰጣል'
እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ
የሕዝቡ ከእግዚአብሔር ኃይል መቀበል ሕዝቡ ንስር እንደሚበርር መብረር እንደቻለ ተደርጎ ተነግሮአል። ንስር ብዙ ጊዜ ለብርታትና ለኃይል ምልክት ሆኖ ጥቅም ላይ የሚውል ወፍ ነው። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ይሮጣሉ አይታክቱም፣ ይሄዳሉ አይደክሙም
እነዚህ ሁለት መስመሮች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው። ከእግዚአብሔር ኃይል የተቀበሉ ሰዎች ሳይደክማቸው መሮጥና መሄድ እንደቻሉ ተደርጎ ተነግሮአል። (አጓዳኝነትና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

---

Chapter 41
Isaiah 41:1
በፊቴ በጸጥታ አድምጡ
በዚህ ወስጥ "እኔ' የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል።
እናንተ ደሴቶች
ይህ በደሴቶችና አዋሳኝ መሬቶች ወይም ከሜዲትራኒያን ባሕር ማዶ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። (ምትክ ስምና በስፍራው ለሌለ ወይም እንደ ሰው ለተወሰደ ግዑዝ ነገር መናገር ተመልከት)
ኃይላቸውን ያድሱ
ይህንን ሐረግ በኢሳይያስ 40፡31 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
ይቅረቡ በዚያን ጊዜም ይናገሩ፣ ለክርክርም በአንድነት እንቅረብ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው። ሁለተኛው ለመጀመሪያው ምክንያትን ያቀርባል። አት፦ "ይናገሩና ከእኔ ጋር ይከራከሩ ዘንድ ይቅረቡ' (አጓዳኝነት ተመልከት)
አንዱን ከምሥራቅ ያስነሳው በጽድቅም ለአገልግሎቱ የጠራው ማን ነው?
ይህንን ገዢ ከምሥራቅ ድል አድራጊ አድርጎ ያስነሣው እርሱ እንደሆነ ለማጉላት እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። አት፦ "ይህን ኃያል ገዢ ከምሥራቅ የጠራሁት በመልካሙ አገልግሎቱም ላይ የሾምኩት እኔ ነኝ' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
አሕዛብንም አሳልፎ ሰጠው
"አሕዛብን አሳልፌ ሰጠሁት' ወይም "እነዚህን ነገሮች ያደረገ እርሱ አሕዛብን አሳልፎ ሰጠው'
ለሰይፉ እንደ ትቢያ ለቀስቱም እንደ ተጠረገ እብቅ አደረጋቸው
እነርሱን ትቢያና የተጠረገ እብቅ እንዳደረገ መነገሩ የእነዚህ ሕዝቦች ሰዎች የሠሩትን ሁሉ ፈጽሞ ለማጥፋቱ ስዕላዊ ንግግርና ግነት ነው። ከምሥራቅ የሆነው የእርሱ ሠራዊት አሕዛብን ድል ይነሣሉ በቀላሉም ይበትኑአቸዋል። (ስዕላዊ ንግግር፣ ዘይቤአዊ ንግግርና ግነትና ማጠቃለያ ተመልከት)
Isaiah 41:3
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለደሴቶችና ለአሕዛብ መናገሩን ይቀጥላል።
አሳደዳቸው በሰላምም አለፈ
"ከምሥራቅ የሆነው ገዢ አሕዛብን አሳደዳቸው'
እግሮቹ ላመል በሚረግጡበት በፈጣን መንገድ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርገሞች 1) ይህ እግሮቹ ላመል መሬቱን እንደሚነኩ ተደርጎ እርሱና ሠራዊቱ በጣም በፍጥነት መሄዳቸው የተነገረበት ስዕላዊ ንግግር ነው። አት፦ "በታላቅ ፍጥነት በሚሄድበት መንገድ' ወይም 2) "እግር' የሰውን ሁለንተና ይወክላል፣ ሐረጉም መንገዱ ከዚህ በፊት ያልሄዱበት መንገድ እንደሆነ ያመለክታል። አት፦ "አስቀድሞ ባልሄደበት መንገድ' (ስዕላዊ ንግግርና ተለዋጭ ስም ተመልከት)
እነዚህን የሠራና ያደረገ ማን ነው?
እነዚህን ነገሮች ያደረገ እርሱ እንደሆነ ለማጉላት እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ ይጠቀማል። አት፦ "እኔ እነዚህን ተግባራት ሁሉ ሠራሁ አደረግሁም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ተመልከት)
ትውልድንም ከጥንት የጠራ ማን ነው?
በዚህ ስፍራ "ትውልድ" የሚለው ቃል በታሪክ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር የፈጠራቸውንና የመራቸውን የሰው ታሪክ ሁሉ ይወክላል። ይህ አሳብ ገላጭ ጥያቄ፣ እግዚአብሔር የሚል ምላሽ ይጠብቃል። አት፦ "እኔ የሰዎችን ትውልድ ሁሉ ከመጀመሪያው ጠራሁ' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
የሠራና ያደረገ
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሠረቱ የሚናገሩት አንድ ነገር ሲሆን እነዚህን ነገሮች ሁሉ ያደረገ እግዚአብሔር መሆኑን ያጎላሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሣሣይነት ተመልከት)
ፊተኛው፣ በኋለኞችም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር ከፍጥረት በፊት ነበረ ደግሞም ከፍጥረት ፍጻሜም በኋላ ይኖራል ወይም 2) እግዚአብሔር ከመጀመሪያው የሰው ትውልድ በፊት ነበረ ደግሞም በመጨረሻው የሰው ትውልድ ጊዜም ይኖራል።
Isaiah 41:5
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።
ደሴቶች … የምድር ዳርቻች
እነዚህ ሐረጎች በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላሉ። አት፦ "በደሴቶች የሚኖሩ ሰዎች … በምድር ዳርቻች የሚኖሩ ሰዎች' (ምትክ ስም ተመልከት)
ደሴቶች
በኢሳይያስ 41፡1 በተረጎምኸው መሠረት መተርጎም ትችላለህ።
የምድር ዳርቻች
በምድር በጣም ሩቅ የሆኑ ቦታዎች ምድር የምታበቃባቸው ቦታዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "የምድር በጣም ሩቅ ቦታዎች' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ቀረቡ መጡም
እነዚህ ሁለቱ ተመሣሣዮች ሕዝቡ በአንድነት ተሰበሰቡ የሚል ትርጉም አላቸው። አት፦ "በአንድነት መጡ' (የሁለት ነገሮች ተመሣሣይነት ተመልከት)
የብረት ቅርጽ ማውጫ
ሰው በመዶሻ ብረትን ቅርጽ የሚያስዝበት የብረት ማስቀመጫ
አንጥረኛውን … አለ
በዚህ ስፍራ ማንጠር የሚለው ቃል ሠራተኞቹ ጣዖቱን መሥራት እንደጨረሱ ወርቁን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከእንጨቱ ጋር የማጠበቅን ሂደት ያመለክታል፡፡
እንዳይንቀሳቀስም በምስማር ቸነከሩት
በዚህ ውስጥ እርሱ የሚለው የሠሩትን ጣዖት ያመለክታል፡፡
Isaiah 41:8
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል
አንተ ከምድር ዳርቻዎች ያመጣሁህ፣ ከሩቅ ስፍራዎችም የጠራሁህ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት መስመሮች አንድ ዓይነት ነገር የሚናገሩ ሲሆን እግዚአብሔር እስራኤልን ሕዝብ በሩቅ ከሚገኙ አገራት ወደ ምድራቸው እንዳመጣቸው ያጎላሉ፡፡ (አጓዳኝነት ተመልከት)
የምድር ዳርቻዎች
በምድር በጣም ሩቅ የሆኑ ቦታዎች ምድር የምታበቃባቸው ቦታዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሮአል፡፡ ይህንን በኢሳይያስ 45፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት፡፡ አት፡- "የምድር በጣም ሩቅ ቦታዎች' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 41:10
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል፡፡
በጽድቄም ቀኝ እጅ ደግፌ እይዝሃለሁ
የእግዚአብሔር ሕዝቡን ማበረታታት በእጁ እንደያዛቸው ተደርጎ ተነግሮአል፡፡ (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በጽድቄ ቀኝ እጅ
በዚህ ስፍራ ቀኝ እጅ የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል፡፡ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ጻድቅ ነው በዚያም ሁልጊዜ ትክክለኛውን ነገር ያደርጋል 2) የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ድል ነሺ ነው በዚያም ሁልጊዜ የሚያደርገው ይከናወንለታል፡፡ አት፡- "ድል አድራጊ ኃይሌ' (ምትክ ስም ተመልከት)
Isaiah 41:11
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል
ያፍራሉ ይዋረዳሉም፣ ከአንተ ጋር የሚጣሉ ሁሉ
"ከአንተ ጋር የሚጣሉ ሁሉ ያፍራሉ ይዋረዳሉም'
ያፍራሉ ይዋረዳሉም
በመሠረቱ ሁለቱም ቃላት ተመሣሣይ ነገር ይናገራሉ የኀፍረታቸውንም ታላቅነት ያጎላሉ፡፡ (የሁለት ነገሮች ተመሣሣይነት ተመልከት)
እንዳልነበሩ ይሆናሉ ይጠፉማል፣ የሚቃወሙህ
"የሚቃወሙህ እንዳልነበሩ ይሆናሉ ይጠፉማል'
Isaiah 41:12
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ቀኝ እጅህን እይዛለሁና
የእግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ መርዳት ቀኝ እጃቸውን እንደያዘ ተደርጎ ተነግሮአል፡፡ (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 41:14
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል፡፡
አንተ ትል ያዕቆብ፣ የእስራኤልም ሰዎች ሆይ
በዚህ ስፍራ ያዕቆብ እና የእስራኤል ሰዎች ማለት ተመሣሣይ ነገር ነው፡፡ አት፡- "ትል የምትመስሉ የእስራኤል ሰዎች ሆይ' (የሁለት ነገሮች ተመሣሣይነት ተመልከት)
አንተ ትል ያዕቆብ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ሌሎች ሕዝቦች የእስራኤልን ሕዝብ በሚመለከት ያላቸውን አስተያየት ያመለክታል ወይም 2) ይህ ራሳቸው እስራኤላውያን ስለ ራሳቸው ያላቸውን አስተያየት ያመለክታል፡፡ ትል እንደሆኑ አድርጎ እግዚአብሔር ስለ ትንሽነታቸው ይናገራል፡፡ (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኝነት ለመግለጽ እግዚአብሔር በራሱ ስም ይናገራል፡፡ በኢሳይያስ 30፡1 እንዳለው ተርጉም፡፡ አት፡- "እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው' ወይም "እኔ፣ እግዚአብሔር ያወጅኩት ይህ ነው' (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦሥተኛ መደብ ተመልከት)
የእስራኤል ቅዱስ
ይህንን ሐረግ በኢሳይያስ 1፡4 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት፡፡
እኔ እንደተሳለች እንደ አዲስ ባለ ጥርስ ማሄጃ አድርጌሃለሁ ... ኮረብቶችን እንደ ገለባ ታደርጋቸዋለህ
ሕዝቡን ተራራሮችን ደልዳላ የሚያደርግ ስለታም ማሄጃ እንደሚያደርግ ዓይነት እስራኤል ጠላቶቹን እንዲያሸነፍ እንደሚያስችለው እግዚአብሔር ይናገራል፡፡ (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የተሳለ ስለታም ማሄጃ
ፍሬውን ከገለባው ለመለየት እንድ ሰው ስንዴ ላይ የሚጎትተው የሾሉ ብረቶች ያሉት ነገር ነው፡፡
በሁለት ወገን የተሳለ
ይህ ከስለታም ማሄጃ ጋር የሚያያዙትን የሾሉ ብረቶች ጠርዝ ያመለክታል፡፡ በሁለት ወገን የተሳሉ ናቸው ማለት በጣም ስለታም ናቸው ማለት ነው፡፡
ተራሮችን ታሄዳለህ ታደቅቃቸውማለህ
ይህ ድርብ ስዕላዊ ንግግር ነው፡፡ ተራራሮች እህልን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ስዕላዊ ንግግር ነው፤ እህልን ማሄድ ደግሞ በአቅራቢያዋ የሚገኙ ኃያላን የሆኑ ጠላት ሕዝቦችን እስራኤል እንደምታሸነፍ ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ስዕላዊ ንግግር ነው፡፡ አት፡- "እንደ ተራሮች ጠንካሮች መስለው ቢታዩም ጠላቶቻችሁን እንደ እህል ታሄዷቸዋላችሁ፣ ታደቅቋቸውማላችሁ፡' (ስዕላዊ ንግግር እና ገነትና ማጣቃለይ ተመልከት፡፡)
ኮረብቶችንም እንደ ገለባ ታደርጋቸውማለህ
ኮረብቶች በእስራኤል አቅራቢያ የሚገኙ ኃያላን የሆኑ ጠላት ሕዝቦችን የሚያመለክት ስዕላዊ ንግግር ነው፡፡ ሕዝቡ እህሉን ካሄዱት በኋላ ነፋሱ ገላባውን ጠርጎ እንዲወስደው ማድረግ የሚገባቸው መሆኑ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እንዲያጠፋ ሊፈቅዱለት የሚገባ ለመሆኑ ስዕላዊ ንግግር ነው፡፡ (ስዕላዊ ንግግርና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 41:16
አያያዥ አሳብ
እስራኤል እንዴት ጠላቶቿን እንደምታሸንፍ ለመግለጽ እግዚአብሔር እህልን ከገለባው የመለየትን ስዕላዊ ንግግር መጠቀሙን ይቀጥላል፡፡
ታበጥራቸዋለህ ... ነፋስም ይበትናቸዋል
በዚህ ውስጥ እነርሱ የሚለው በኢሳይያስ 41፡15 የተጠቀሱትን ተራሮችና ኮረብታዎች ያመለክታል፡፡ ይህ ገለባውን ለማስወገድ እህሉ የሚበጠርበትን፣ እህልን በማሄድ ሂደት ውስጥ ቀጣዩን ደረጃ ይወክላል፡፡ ገለባ በነፋስ ተጠርጎ እንደሚሄድ የእስራኤል ጠላቶች ይጠፋሉ፡፡ (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ነፋስ ይጠርጋቸዋል፤ ነፋስም ይበትናቸዋል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ዓይነት ነገር ይናገራሉ፡፡ አት፡- "ነፋስ ጠርጎ ይወስዳቸዋል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 41:17
አጠቃላይ መረጃ
እጅግ የሚያስፈልጋቸው ነገር ያላቸውን ሰዎች በሚመለከት እጅግ እንደ ተጠሙ አድርጎ፤ የእርሱንም አቅርቦት በተለምዶ ውኃ በማይታይባቸው ቦታዎች ውኃ እንደሚሰጣቸው እግዚአብሔር ይናገራል፡፡ (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 41:19
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ዝግባውንና ግራሩን ... ባርሰነቱንና የዘይቱን ዛፍ
እነዚህ የዛፍ ስሞች ናቸው፡፡ (የማይታወቁትን መተርጎም ተመልከት)
የእግዚአብሔር እጅ ይህን ሠርታለች
በዚህ ስፍራ እጅ የሚለው እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል፡፡ አት፡- "እግዚአብሔር ይህን አደረገ' (ተለዋጭ ስም ተመልከት)
Isaiah 41:21
አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሔር በሕዝቡና በጣዖቶቻቸው ላይ ይሳለቃል፡፡ ወደፊት የሚሆነውን እንዲናገሩ በመጠየቅ ጣዖታትን ይገዳደራል፣ ነገር ግን እነርሱ የማያውቁትን እርሱ ያውቃል፡፡ (ምጸት ተመልከት)
Isaiah 41:23
አያያዥ አሳቦች
እግዚአብሔር በጣዖታትና በሚያመልኳቸው ሰዎች ላይ መሳለቁን ይቀጥላል፡፡ (ኢሳ 41:21-22)
መልካሙን ወይም ክፉውን አድርጉ
"መልካም' ወይም "ክፉ' የሚሉት ቃላት ስዕላዊ ንግግር ሲሆኑ ማንኛውንም ነገር

ይወክላሉ። አት፦ "ማንኛውንም ነገር አድርጉ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የሚመርጣችሁም
በዚህ ውስጥ "እናንተ' የሚለው ጣዖታትን የሚያመለከት ነው። አት፦ "እናንተን ጣዖታትን የመረጠ ሰው' (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች ተመልከት)
Isaiah 41:25
አጠቃላይ መረጃ፡
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል
አንዱን አነሣሁ
እግዚአብሔር አንድን ሰው መሾሙን ያንን ሰው ወደ ላይ እንዳነሣ አድርጎ ይናገራል። አት፦ "አንዱን ሾምሁ' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ከፀሐይ መውጫ
ይህ ፀሐይ ወደ ምትወጣበት አቅጣጫ ወደ ምሥራቅ ያመለክታል። አት፦ "ከምሥራቅ' (ፈሊጣዊ ንግግር ተመልከት)
ስሜን የሚጠራ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እንዲሳካለት እግዚአብሔርን የሚለምን ሰው 2) እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሰው
ገዢዎችን ይረጋግጣል
የሌሎች ሕዝቦች ገዢዎችን ማሸነፍ ከእግር በታች እነርሱን መርገጥ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። አት፦ "ገዢዎችን ድል ያደርጋል' (ሰስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ጭቃ እንደሚረግጥ ሸክላ ሠሪ
እግዚአብሔር ይኼ ሰው ሌሎች ገዢዎችን የሚረግጥበትን መንገድ ከውኃ ጋር ለማደባለቅ ሸክላ ሠሪ ጭቃን ከሚረግጥበት መንግድ ጋር ያስተያያል። (ዘይቤአዊ አነጋገር ተመልከት)
እናውቅ ዘንድ ከጥንት የተናገረው ማን ነው? "እውነት ነው' እንልም ዘንግ ቀድሞ የተናገረው ማን ነው?
እግዚአብሔር ሕዝቡ በሚያመልካቸው ጠዖታት ላይ ለመሳለቅ እነዚህን አሳብ ገላጭ ጥያቄዎች ይጠቀማል። የተጠቆሙ መልሶች 1) ጣዖታት እነዚህን ነገሮች አላደረጉም 2) እነዚህን ያደረገ እግዚአብሔር ብቻ ነው። አት፦ "እናውቅ ዘንድ ከጣዖታት መካከል ማንም ይህንን ከጥንት አላስታወቀም። ‘እውነት ነው’ እንል ዘንድ ከመካከላቸው ማንም አስቀድሞ አልተናገረም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄና መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)
በእውነቱ ከመካከላቸው ማንም አልተናገረም፣ አዎ፣ ምንም ስትሉ የሰማ የለም
"በእውነቱ ከጣዖታት መካከል ማንም አልተናገረም። በእውነቱ ጣዖታት ምንም ስትሉ የሰማ የለም'
Isaiah 41:27
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል
ከመካከላቸው አንድም
"አንድም ጣዖት'
ቀልጠው የተሠሩት ምስሎቻቸው ነፋስና ባዶ ናቸው
ጣዖታት ነፋስና ባዶ ናቸው በማለት እግዚአብሔር የጣዖታትን ከንቱነት ይናገራል። አት፦ "ጣዖቶቻቸው ከንቱዎች ናቸው' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)

---

Chapter 42
Isaiah 42:1
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል
እነሆ ባሪያዬ
"ባሪያዬን ተመልከቱ' ወይም "ባሪያዬ ይኼው'
በእርሱ ደስ ይለኛል
"እጅግ ደስ የተሰኘሁበት'
Isaiah 42:3
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።
የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፣ የሚጠስንም ክር አያጠፋም
እንደ ተቀጠቀጠ ሸምበቆና እንደ ሚጤስ ክር ደካና ተስፋ የሌላቸው ሰዎች እንደሆኑ እግዚአብሔር ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
የተቀጠቀጠ ሸምበቆ
ሸምበቆ ረጅም ሣር የሚመሥል፣ ረጅም፣ ቀጭን ግንድ ያለው ተክል ነው። ከተቀጠቀጠ ወይም ከተጎዳ ምንም ክብደት መሸከም አይችልም። ይህንን በኢሳይያስ 36፡6 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት።
አይሰብርም
ባሪያዬ አይሰብርም
ደሴቶች
ይህ በደሴቶችና አዋሳኝ መሬቶች ወይም ከሜዲትራኒያን ባሕር ማዶ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። ይህንን በኢሳይያስ 41፡1 እንዴት እንደተረጎምህ ተመልከት። አት፦ "በደሴቶች የሚኖሩ ሰዎች' (ምተክ ስም ተመልከት)
Isaiah 42:5
ሰማያትን የፈጠረ፣ የዘረጋቸውም፣ ምድርን የፈጠረ
ሰማያትና ምድር እንደ ጨረቅ የዘረጋቸው እንደሆነ አድርጎ ነቢዩ ስለ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን መፍጠር ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በእርስዋ ላይ ላሉ ሰዎች እስትንፋስን፣ በእርስዋም ለሚኖሩ ሕይወትን የሚሰጥ
በመሠረቱ እነዚህ ሐረጎች የሚናገሩት አንድ ነገር ሲሆን እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው ሕይወት እንደሚሰጥ አጉልተው ይናገራሉ። እስትንፋስ የሚለው ቃል ለሕይወት ምትክ ቃል ነው። አት፦ "በምድር ለሚኖሩ ሰዎች ሕይወትን ይሰጣል' (አጓዳኝነትና ምትክ ስም ተመልከት)
ጠርቼሃለሁ
በዚህ ውስጥ "አንተ' የሚለው የእግዚአብሔርን ባሪያ ያመለክታል። (የ"አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞ ተመልከት)
ለሕዝብ ኪዳን አድርጌህ …
በዚህ ስፍራ "ኪዳን' የሚለው ቃል ኪዳኑን ለመሠረተው ወይም ተፈጻሚ ላደረገው ምትክ ስም ነው። አት፦ በሕዝቡ ዘንድ የኪዳኑን አስፈጻሚ አደርግሃለሁ … (ምትክ ስም ተመልከት)
ለአሕዛብ ብርሃን
ለአሕዛብ በጨላማ ስፍራ የሚያበራ ብርሃን እንደሚያደርገው በሚመስል መልኩ እግዚአብሔር ባሪያውን ሕዝቦችን ከእስራት የሚፈታ እንደሚያደርገው ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 42:7
አጠቃላይ መረጃ
ባሪያው የሚያደርገውን እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል
የዕውሩን ዓይን ትከፍት ዘንድ
ዕውራን ሰዎችን እንዲያዩ ማድረግ ዓይኖቻቸውን እንደ መክፈት ተደርጎ ተነግሮአል። እንዲሁም፣ ባሪያው ለዕውራን ሰዎች ማየትን የሚመለስ በሚመስል መልኩ እግዚአብሔር ያለአግባብ ያታሰሩትን አገልጋዩ ነጻ እንደሚያወጣ ይናገራል። አት፦ "ዕውሩ እንዲያይ ይደርጋል' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
እስረኛውን ከጨለማ ቤት ታወጣ ዘንድ፣ በጨለማም የተቀመጡትን ከግዞት ቤት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት አንድ ዓይነት ነገር ነው። ማሰሪያ አንቀጹ በሁለተኛው ሐረግ ላይ ሊታከል ይችላል። አት፦ "እስረኛውን ከጨለማ ቤት ታወጣ ዘንድ፣ በጨለማም የተቀመጡትን ከግዞት ቤት ታወጣ ዘንድ' (አጓዳኝነትና መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)
Isaiah 42:8
ምስጋናዬን ለተቀረጹ ምስሎች
ማሰሪያ አንቀጽ ከቀደመው ግስ ሊወሰድ ይችላል። አት፦ "ምስጋናዬን ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም' (መቅረታቸው አሳቡን ከመረዳት ስለማያጓድሉ የተዘለሉ ተመልከት)
ምስጋናዬን
ይህ እግዚአብሔር ከሕዝቡ የሚቀበለውን ምስጋናውን ያመለክታል።
እነግራችኋለሁ
በዚህ ውስጥ "እናንተ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። (የ"አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞ ተመልከት)
Isaiah 42:10
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።
ባሕርና በውስጥዋም ያላችሁ ሁሉ፣ ደሴቶችና በእነርሱም የምትኖሩ ሁሉ
"በባሕር ውስጥ የምትኖሩ ፍጥረታት ሁሉና በደሴቶች የምትኖሩ ሁሉ'
ምድረ በዳና ከተሞች ይጨኹ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ በምድረ በዳና በከተሞች የሚኖሩ ሰዎችን ያመልክታል (ምትክ ስም ተመልከት)
ቄዳር
ይህ የሰሜን አረብ ከተማ ነች። ይህ በኢሳይያስ 21:16 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።
ሴላ
በኤዶምያስ የምትገኝ ከተማ ነች። (የስሞች አተረጓጎም መንገድ ተመልከት)
Isaiah 42:12
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።
ክብርን ይስጡ
በዚህ ውስጥ "እነርሱ' የሚለው በደሴቶች ዳርቻ የሚገኙትን ሰዎች ያመለክታል።
እግዚአብሔር እንደ ተዋጊ ይወጣል፣ እንደ ተዋጊ ሰው
እግዚአብሔር የሕዝቡን ጠላቶች ሊያሸንፍ ዝግጁ ከሆነ ተዋጊ ጋር ተነጻጽሮአል። (ዘይቤአዊ ንግግር እና አጓዳኝነት ተመልከት)
ቅንዓቱን ያነሳሳል
በዚህ ስፍራ ቅንዓት ወደ ጦርነት ሊገባ ሲል ተዋጊ የሚሰማውን ስሜት ያመለክታል። እግዚአብሔር ቅንዓቱን ማነሳሳቱ፣ ነፋስ የወኃን ሞገድ እንደሚያስነሳ እርሱም እንዲሁ ቅንዓቱን እንደሚያስነሳ ተነግሮአል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 42:14
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።
ከድሮ ዘመን ጀምሮ ጸጥ ብያለሁ፣ ዝም ብያለሁ ራሴንም ገድቤአለሁ
እነዚህ ሁለት መሥመሮች አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው። የእግዚአብሔር አለመንቀሳቀስ እንደ ጸጥታና ዝምታ ተገልጾአል። (አጓዳኝነት ተመልከት)
ዝም ብያለሁ ራሴንም ገድቤአለሁ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉማቸው አንድ ሲሆን እግዚአብሔር ራሱን ከእንቅስቃሴ እንደ ገታ ያመለክታሉ። አት፦ "ምንም ከማድረግ ራሴን ገትቼአለሁ' (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)
ምጥ እንደያዛት ሴት እጮኻለሁ ... አቃስታለሁ ትንፋሼም ቁርጥ ቁርጥ ይላል
እንደሚጮህ ተዋጊ የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ከምጥ ህመም የተነሣ ከምትጮህ እርጉዝ ሴት ጋር ተነጻጽሮአል። ከተወሰነ የዝምታ ጊዜ በኋላ በድንገት የሚሆንን አይቀሬ እንቅስቃሴ ያሳላል። (ዘይአዊ ንግግር ተመልከት)
ተራሮችን አፈርሳለሁ ... ረግረጉን አደርቃለሁ
ጠላቶቹን ለማጥፋት ያለውን ታላቅ ኃይል ለመግለጽ እግዚአብሔር ይህን ስዕላዊ ቋንቋ ይጠቀማል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ረግረግ
ረግረግ ለስላሳ መሬት፣ ውኃ ያቆረበት እርጥብ መሬት ነው።
Isaiah 42:16
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል
ዕውሮችን በማያውቁት መንገድ አመጣቸዋለሁ፣ በማያውቁትም መንገድ እመራቸዋለሁ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት ተመሣሣይ ነገር ነው። አት፦ "ዕውሮችን በማያውቁት መንገድ እመራቸዋለሁ' (አጓዳኝነት ተመልከት)
ዕውሮች
ዕውሮች ስለሆኑ ማየት እንደማይችሉ አድርጎ እግዚአብሔር ሕዝቡ ተስፋ ቢስ እንደሆኑ ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
በማያውቁት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ከቶም ባልሄዱበት' 2) "ባለመዱት'
በፊታቸው ጨለማውን ብርሃን አደርጋለሁ
በጨለማ ከመሄዳቸው የተነሣ ማየት እንደማይችሉ ሕዝቡ ተስፋ ቢስ መሆናቸውን ፣ እንዲሁም የሚያደርግላቸውን እርዳት በጨለማ የሚያበራ ብርሃን እንደ ማድረግ መሆኑን እግዚአብሔር ይናገራል። (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
Isaiah 42:17
አጠቃላይ መግቢያ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል
ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ ፈጽመውም ያፍራሉ
ጣዖታትን የሚያመልኩትን መቃወም ወደ ኋላቸው እንዲመለሱና በተቃራኒ አቅጣጫ እንዲሄዱ ማስገደድ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሮአል። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "እቃወማቸዋለሁ አሳፍራቸውማለሁ' (ስዕላዊ ንግግርና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
Isaiah 42:18
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል
እናንተ ደንቆሮች ... እናንተ ዕውሮች
በዚህ ስፍራ "እናንተ' የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። እርሱን ከመስማትና ከመታዘዝ መውደቃቸውን እውሮችና ደንቆሮች እንደሆኑ አድርጎ እግዚአብሔር ይናገራል። (የ "አንተ' ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች እና ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ከባሪያዬ በቀር ዕውር ማን ነው? እንደምልከው እንደ መልእክተኛዬስ ደንቆሮ የሆነ ማን ነው?
በሕዝቡ ላይ ለመሳለቅና እንደ እነርሱም ዕውርና ደንቆሮ የሆነ ማንም እንደሌለ ለማጉላት እግዚአብሔር ይህን አሳብ ገላጭ ጥያቄ ይጠይቃል። አት፦ "እንደ ኪዳን አጋሬ ዕውር የሆነ ማንም የለም። እንደ እግዚአብሔር ባሪያም ዕውር የሆነ ማንም የለም።' (አሳብ ገላጭ ጥያቄ ተመልከት)
Isaiah 42:20
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።
ብዙ ነገርን ታያላችሁ ነገር ግን አትገነዘቡም
"ብዙ ነገር ታያላችሁ ነገር ግን ምን ማለት እንደሆነ አትረዱም'
ጆሮአችሁም ተከፍቷል፣ ነገር ግን አትሰሙም
የመስማት ችሎት የጆሮ መከት ተደርጎ ተነግሮአል። በዚህ ስፍራ መስማት የሚለው ቃል አንድ ሰው የሚሰማውን መረዳትን ያመልክታል። አት፦ "ሕዝቡ ይሰማል፣ ነገር ግን ማንም የሰሙትን አይረዳም።' (ስዕላዊ ንግግር ተመልከት)
ጽድቁን ያከብር ሕጉንም ታላቅ ያደርግ ዘንድ እግዚአብሔር ወደደ
"ሕጉን ታላቅ በማድረግ ጽድቁን ያከብር ዘንድ እግዚአብሔር ወደደ።' የሐረጉ ሁለተኛ ክፍል እግዚአብሔር ሁለተኛውን ክፍል እንዴት እንደሚፈጽም ያብራራል።
Isaiah 42:22
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል።
ይህ ግን የተበዘበዘና የተዘረፈ ሕዝብ ነው
ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ነገር ግን ጠላት ይህን ሕዝብ በዝብዞታል ዘርፎታልም' (አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
የተበዘበዘና የተዘረፈ
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት የሚናገሩት አንድ ዓይነት ነገር ሲሆን እንዴት ክፉኛ ጠላት እንደ በዘበዛቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። (የሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት ተመልከት)
ሁሉም በጉድጓድ ውስጥ ተጠምደዋል፣ በወህኒም በምርኮ ተይዘዋል
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት አንድ ዓይነት ነገር ነው። ይህ በአድራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል። አት፦ "ጠላት ሁሉንም በጉድጓድ አጠመዳቸው በወህኒም ምርኮ አድርጎ ያዛቸው' (አጓዳኝነትና አድራጊና ተደራጊ ማሰሪያ አንቀጽ ተመልከት)
Isaiah 42:23
አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ጋ ኢሳይያስ መናገር ይጀምራል።

---

Chapter 43
Isaiah 43:1
ያዕቆብ ሆይ የፈጠረህ እስራኤል ሆይ የሠራህ
ሁለቱም አነጋገሮች ተመሳሳይ ናቸው፤ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ የፈጠራችሁ››
Isaiah 43:2
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።
በውሃ ውስጥ ስታልፍ አያሰጥምህም... በእሳት ውስጥ ስትሄድ አያቃጥልህም።
ሰዎች ላይ የሚደርስ መከራና ችግር የሚያልፉበት ጥልቅ ውሃና እሳት እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። ‹‹ውሃ›› እና፣ ‹‹እሳት›› ምሳሌያዊ ሲሆኑ ማንኛውንም አስቸጋሪ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሁኔታ ያመለክታሉ።

በውሃ ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ ወንዞን ስትሻገረው አያሰጥምህም።

እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ ያህዌ ከእነርሱ ጋር ከሆነ ምንም ጉዳት እንደማይደርስባቸው አጽንዖት ይሰጣሉ።

አያቃጥልህም

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፍጹም አይፈጅህም››

ግብፅ ለአንተ ቤዛ እንድትሆን፣ ኩሽና ሳባንም በአንተ ፈንታ ሰጥቻለሁ።

እነዚህ ሁለት ሐረጐች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ እስራኤልን ሳይሆን የእስራኤል ጠላቶች እነዚህን መንግሥታት ድል እንዲያደርጉ ያህዌ እንደ ፈቀደ አጽንዖት ይሰጣል።

ሳባ

ይህ የአገር ስም ነው።

Isaiah 43:4

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

በዐይኔ ፊት ብርቅና ክቡር ስለሆንህ

‹‹ብርቅ›› እና፣ ‹‹ክቡር›› የተሰኙት ቃሎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ ያህዌ ሕዝቡን ምን ያህል እንደሚወድ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእኔ ዘንድ በጣም የተወደድህ ስለሆነ››

ስለዚህ ሰዎችን በአንተ ምትክ፣ ሕዝቦችንም በሕይወትህ ፈንታ እሰጣለሁ

ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ በአንተ ፈንታ ጠላት ሌሎች መንግሥታትን ድል እንዲያደርግ አደርጋለሁ››

ልጆችህን ከምሥራቅ አመጣለሁ፤ አንተንም ከምዕራብ እሰበስባለሁ

‹‹ምሥራቅ›› እና ‹‹ምዕራብ›› የተሰኙት አቅጣጫዎች ከሁሉም ቦታ ማለት ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተንና ልጆችህን ከሁሉም ቦታ አመጣለሁ››

Isaiah 43:6

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለሕዝቡ መናገር ቀጥሏል።

ለሰሜን… በል፤ ለደቡብ… በል

በእነዚህ ቦታዎች ያሉትን ሕዝቦች እያዘዘ ያለ ይመስል ያህዌ ለ‹‹ሰሜን›› እና፣ ለ‹‹ደቡብ›› ይናገራል።

ወንዶች ልጆቼ… ሴቶች ልጆቼ

የእርሱ የሆኑት የእርሱ ልጆች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።

በስሜ የተጠራው ሁሉ

በአንድ ሰው ስም መጠራት የዚያ ሰው መሆንን ያመለክታል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በስሜ የተጠራ ማንኛውም ሰው›› ወይም፣ ‹‹የእኔ የሆነ ሁሉ››

የሠራሁት፣ አዎን ያበጀሁት

ሁለቱም ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ የእስራኤልን ሕዝብ የሠራ እግዚአብሔር መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ።

Isaiah 43:8

ዕውር… ደንቆሮ የሆነ ሕዝብ

እርሱን የማይሰሙ ወይም የማይታዘዙ ዕውርና ደንቆሮ እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።

ከእነርሱ አስቀድሞ ይህን የነገረን፣ የቀድሞን ነገር ያወጀልን ማን ነው?

ይህ ጥያቄ ሰዎች የሚያመልኳቸውን አማልክት ይመለከታል። መልሱ ማንም ይህን ማድረግ አይችልም የሚል ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከአማልክቶቻቸው አንዱ እንኳ ይህን መናገርና የቀድሞን ነገር ማወጅ አይችልም››

የቀድሞን ነገር ያወጀልን

ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ነገሮች ከመሆናቸው በፊት ለሰዎች የመነገርን ችሎታ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የቀደሙት ነገሮች ከመሆናቸው በፊት አወጀልን››

ትክክለኛነታቸው እንዲረጋገጥ ምስክሮቻቸውን ያቅርቡ፤ ሰምተውም ያረጋግጡላቸው ‹እውነት ነው›

ምንም እንኳ ያንን ማድረግ እንደማይችሉ ቢያውቅም፣ አሕዛብ የሚያመልኳቸው አማልክት እነዚህን ነገሮች ማድረግ እንደሚችሉ የሚያረጋግጡ ምስክሮች እንዲያቀርቡ ያህዌ ይጠይቃል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ አማልክት ትክክል መሆናቸውን የሚመሰክሩ ምስክሮች አድምጠውም፣ ‹እውነት ነው› የሚሉ ምስክሮች የሏቸውም››

Isaiah 43:10

እናንተ… የእኔ አገልጋይ

‹‹እናንተ›› ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ‹‹የእኔ አገልጋይ›› ጠቅላላ መንግሥቱን ያመለክታል።

ከእኔ በፊት… ከእኔ በኋላ

በዚህ መልኩ መናገሩ ከእርሱ በፊት የነበረና ከእርሱ በኋላም እንደሚኖር ያህዌ እየተናገረ አይደለም። እርሱ ዘላለማዊ ሲሆን፣ ሕዝቡ የሚያመልኳቸው አማልክት ግን አለመሆናቸውን እያረጋገጠ ነው።

ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም

እዚህ ላይ፣ ‹‹አልተሠራም›› ሲል ያህዌ ሕዝቡ ስለሠሩዋቸው ጣዖቶች እየተናገረ ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሕዛብ ካሠሩዋቸው ጣዖቶች አንዱ እንኳ ከእኔ በፊት አልተሠሩም››

ከእኔም በኋላ አይኖርም

‹‹ከእነዚህ አማልክት አንዱም ከእኔ በኋላ አይኖርም››

እኔ፣ እኔ ያህዌ ነኝ

‹‹እኔ›› የሚለው ቃል የተደገመው አጽንዖቱ ያህዌ ላይ እንዲያተኩር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ብቻ ያህዌ ነኝ›› ወይም፣ ‹‹እኔ ራሴ ያህዌ ነኝ››

ከእኔ ሌላ አዳኝ የለም

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አዳኝ እኔ ብቻ ነኝ›› ወይም፣ ‹‹እናንተን ማዳን የምችል እኔ ብቻ ነኝ››

Isaiah 43:12

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ከእጄም ማዳን የሚችል የለም

‹‹እጅ›› የሚለው የያህዌን ኀይል ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም ከእኔ ኀይል ማዳን አይችልም።››

ማን ማጠፍ ይችላል?

ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ማንም እጁን ማጠፋ እንደማይችል ለመናገር ነው። በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። እጁን ማጠፍ አንድ ነገር እንዳያደርግ እርሱን ማገድን ይወክላል። ኢሳይያስ 14፥27 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም ሊያጥፈው አይችልም›› ወይም፣ ‹‹ማንም አያስቆመኝም››

Isaiah 43:14

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

የእስራኤል ቅዱስ

ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን ሐረግ እንዴ እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ባቢሎን ላይ እሰድዳለሁ፤ ሁሉንም እመራለሁ

ትርጉሙ ውስጥ፣ ‹‹እሰዳለሁ›› የሚለው ማንን እንደሆነ ማመልከት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባቢሎን ላይ ሰራዊት እሰድዳለሁ››

እንደ ኮብላይ ሁሉንም እመራለሁ

‹‹ባቢሎናውያንን ሁሉ ኮብላይ ይሆናሉ››

ኮብላይ

ኮብላይ ጠላት እንዳይዘው የሚሸሽ ሰው ነው።

Isaiah 43:16

መንገድ የከፈተ… እንደ ጧፍ ኩስታሪ

በእነዚህ ጥቅሶች ኢሳይያስ እስራኤላውያን በደረቅ ምድር እንዲሻገሩ፣ ግብፃውያን ግን እንዲሰጥሙ ያህዌ ባሕሩን የከፈተበትን ከግብፅ መውጣት በኋላ የነበረውን ሁኔታ እያመለከተ ነው። የዐረፍተ ነገሩን ትርጉም የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

በአንድነት ወደቁ፤ ከእንግዲህ አይነሡም

መሞት መሬት ከመውደቅ ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሉም በአንድነት ሞቱ፤ ከእንግዲህ በሕይወት አይኖሩም››

ጠፉ፤ እንደ ጧፍ ኩስታሪ ረገፉ

የሕዝቡ መሞት ከሚጠፋ ጧፍ ጋር ተመሳስሎአል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው የሚነድደውን ሻማ እንደሚያጠፋ ሕይወታቸው አብቅቷል››

Isaiah 43:18

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

የቀደመውን ነገር አታስቡ፤ ያለፈውንም አታስታውሱ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ ባለፈው ጊዜ ስለሆነው መጨነቅ እንደሌለባቸው አጽንዖት ይሰጣሉ።
እነሆ
ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው ለሚከተለው ጠቃሚ መረጃ ትኩረት ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አድምጡ›› ወይም፣ ‹‹ልብ በሉ››
አታስተውሉትምን?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው የእስራኤልን ሕዝብ ለማስተማር ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእርግጥ አስተውላችሁታል››
Isaiah 43:20
የዱር አራዊት፣ ቀበሮና ሰጐን ያከብሩኛል
እንደ ሰዎች ሁሉ እንስሳትም ያህዌን ያከብሩታል።
ቀበሮዎችና ሰጐኖች
እነዚህ ያህዌን የሚያከብሩ እንስሳት ምሳሌዎች ናቸው። ኢሳይያስ 13፥21-22 ላይ የእነዚህን እንስሳት ስም እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። ትርጒሙን ግልጽ ለማድረግ ውስጠ ታዋቂ የሆነውን መረጃ ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቀበሮዎችና ሰጐኖች ያከብሩኛል››
Isaiah 43:22
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
Isaiah 43:24
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
መልካም መዐዛ ያለው ነገር
ይህ የቅባት ዘይት ለመሥራት ጥቅም ላይ የሚውል ጣፋጭ ሽታ ያለው ተክል ነው። በእስራኤል ምድር ስለማይበቅል ከሌሎች አገሮች ይገዙት ነበር።
የኀጢአት ሸክም ጫናችሁብኝ፤ በክፉ ሥራህ አደከምኸኝ
እነዚህ ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸው፤ ያህዌ በሕዝቡ ማዘኑን አጽንዖት ይሰጣሉ።
የኀጢአት ሸክም ጫናችሁብኝ
‹‹በኀጢአታችሁ አስቸገራችሁኝ››
Isaiah 43:25
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
እኔ፣ እኔው ነኝ
‹‹እኔ›› የሚለው ቃል የተደገመው አጽንዎት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ ብቻ ነኝ››
በደልህን የምደመስስ
ኀጢአትን ይቅር ማለት፣ 1) መደምሰስና መጥረግ እንደሆነ፣ ወይም 2) የተጻፈውን ኀጢአት መሰረዝ እንደሆነ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንዳች ነገር እንደሚደመስስ ሰው ኀጢአትህን ይቅር የምል›› ወይም፣ ‹‹የተጻፈውን ኀጢአት እንደሚሰርዝ ሰው ኀጢአትህን ይቅር የምል››
ስለ ራሴ ስል
‹‹ስለ ክብሬ›› ወይም፣ ‹‹ስለ ማንነቴ››
አላስብም
‹‹አላስታውስም››
ንጹሕ መሆንህን አስረዳ
ምንም እንኳ ያንን ማድረግ እንደማይችሉ ቢያውቅም፣ እነርሱ ላይ ከቀረበው ክስ ነጻ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ያህዌ ሕዝቡን ይጠይቃል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንጹሕ መሆናችሁን ማረጋገጥ ከቻላችሁ ማስረጃ አቅርቡ››
ንጹሕ እንድትሆኑ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ንጹሕ መሆናችሁን ማስረዳት እንድትችሉ››
Isaiah 43:27
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል። የመጀመሪያው አባትህ ኀጢአት ሠርቷል ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መሥራች ሲሆን፣ አብርሃምን ወይም ይስሐቅን ነው።
ያዕቆብን ለጥፋት አሳልፌ እሰጣለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አሳልፌ›› የሚለው በሌላው ኀይል ሥር ያለ ሰውን ነው። ‹‹ጥፋት›› የሚለውን በሌላ ቃል መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠላት ያዕቆብን ጨርሶ እንዲደመስስ አደርጋለሁ››
እስራኤልን ለስድብና ለውርደት
ግሡን የዚህ ሐረግ ተጓዳኝ ከሆነው ቀደም ሲል ከነበረ ሐረግ ጋር ማያያዝ ይቻላል። ‹‹ውርደት›› የሚለውን በሌላ ቃል መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠላት እስራኤልን እንዲሰድብና እንዲያዋርድ አደርጋለሁ››

---

Chapter 44
Isaiah 44:1
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
ባርያዬ ያዕቆብ
ይህ የሚያመለክተው የያዕቆብን ዘሮች ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ባርያዎቼ የያዕቆብ ዘሮች››
በማሕፀን የሠራህና ያበጀህ
የእስራኤልን ሕዝብ መፍጠሩ በእናት ማሕፀን እንዳለ ሕፃን መሥራትና ማበጀት ማለት እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሕፃን ልጁን ማሕፀን ውስጥ እንደሚያበጅ አንተን የሠራሁ››
የመረጥሁህ ይሹሩን ሆይ
ግሡ ያለፈውን ሐረግ የሚመለከት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ የመረጥሁህ ይሹሩን ሆይ፣ አትፍራ››
ይሹሩን
ይህም የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው።
Isaiah 44:3
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
በተጠማ ምድር ላይ ውሃ፣ በደረቅ መሬት ላይ ምንጮች አፈስሳለሁ
ለእስራኤል ሕዝብ መንፈሱን መስጠቱ በተጠማ ምድር ላይ ዝናብ ማዝነብና በደረቅ መሬት ላይ ምንጮች ማፍሰስ እንደ ሆነ ያህዌ ይናገራል።
የተጠማ ምድር
ደረቅ መሬት የተጠማ ሰው ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ደረቅ መሬት››
መንፈሴን በዘርህ ላይ አፈስሳለሁ
መንፈሱን ለሕዝቡ መስጠቱ መንፈሱ እነርሱ ላይ የሚፈስስ ፈሳሽ ነገር መሆኑን ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መንፈሴን ለዘርህ እሰጣለሁ››
በረከቴንም በልጆችህ ላይ
ግሡ ባለፈው ሐረግ ተነግራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በረከቴን በልጆችህ ላይ አፈስሳለሁ›› ወይም ‹‹በረከቴን ለልጆችህ እሰጣለሁ››
በለመለመ መስክ ላይ እንደ ሣር፣ በምንጭ ዳር እንደ አኻያ ይበቅላሉ
የእስራኤል ሕዝብ መበልጸግና መብዛት ብዙ ውሃ በማግኘቱ እንዳደገ ተክል መሆናቸው ተነግሯል።
አኻያ
አኻያ ቀጫጭን ቅርንጫፎች ያሉት ውሃ አጠገብ የሚያድግ ዛፍ ነው።
Isaiah 44:5
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።
ሌላው ራሱን በያዕቆብ ስም ይጠራል
‹‹ሌላው ሰው የያዕቆብ ዘር መሆኑን ይናገራል››
ራሱን በእስራኤል ስም ይጠራል
‹‹ራሱን የእስራኤል ዘር በማለት ይጠራል››
Isaiah 44:6
የእርሱ ቤዛ
‹‹የእስራኤል ቤዛ››
የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት
እኔ የመጀመሪያው ነኝ፤ እኔ የመጨረሻው ነኝ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ሐረግ ለያህዌ ዘላለማዊ ባሕርይ አጽንዖት ይሰጣል። እንዲህ ማለት፣ 1) ‹‹ነገሮችን ሁሉ የጀመርሁ እኔ ነኝ፤ ነገሮችን ሁሉ የምጨረስ እኔ ነኝ›› ማለት ሊሆን ይችላል ወይም 2) ‹‹እኔ ሁሌም የነበርሁ፤ እኔ ሁሌም የምኖር ነኝ›› ማለት ሊሆን ይችላል።
Isaiah 44:7
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
እንደ እኔ ማን ነው? ይናገር
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው እንደ እርሱ ማንም እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ እኔ እንደሆነ የሚያስብ ካለ ይናገር››
Isaiah 44:8
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
አትፍራ አትደንግጥ
የእርሱን ማበረታቻ ለማጠናከር ያህዌ በሁለት ተመሳሳይ ገለጻዎች ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አትፍራ››
አልነገርኋችሁምን፤ ቀድሞንስ አላስታወቅኋችሁምን?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው አሁን የሆነውን አስቀድሞ መናገር የሚችል እርሱ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። ‹‹ማስታወቅ›› የሚለው ቃል፣ ‹‹መናገር›› ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከረጅም ጊዜ በፊት ነገርኋችሁ››
ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አለን?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ከእርሱ በቀር አምላክ እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእኔ በቀር አምላክ የለም››
ሌላ ዐለት የለም
ያህዌ እርሱ ሰዎች የሚጠለሉበት ትልቅ ዐለት እንደሆነ ይናገራል። ይህም ማለት ሕዝቡን ለመጠበቅ ኀይል አለው ማለት ነው።
Isaiah 44:9
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ እየተናገረ ነው።
የሚደሰቱባቸው ነገሮች ከንቱ ናቸው
‹‹ደስ የሚሰኙባቸው ጣዖቶች ከንቱ ናቸው››
ምስክሮቻቸው አያዩም ወይም አያውቁም
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ስለ ጣዖቶቹ ኀይል ምስክር እንደሆኑ የሚናገሩ እነዚህን ጣዖቶች የሚያመልኩ ሰዎችን ነው። እውነቱን መረዳት አለመቻላቸውን ያህዌ ዕውራን ናቸው ብሏል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእነዚህ ጣዖቶች ምስክር በመሆን የሚያገለግሉ ምንም እንደማያውቁ ዕውሮች ናቸው››
ያፍራሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይዋረዳሉ›› ወይም፣ ‹‹ጣዖቶቻቸው ያሳፍሩዋቸዋል››
አምላክን የሚያበጅ ወይም ጥቅም የሌለውን ጣዖት የሚቀርጽ ማን ነው?
ያህዌ ይህን ጥያቄ ያቀረበው ጣዖት የሚሠሩትን ለመገሠጽ ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አምላክ የሚሠራ ጥቅም የሌለውን ጣዖት የሚቀርጽ ሞኝ ብቻ ነው››
ጥቅም የሌለውን ጣዖት የሚቀርጽ
‹‹ጥቅም የሌለው›› የሚለው ቃል ጥቅም ካለው ጣዖት ጋር ለማነጻጸር የተነገረ አይደለም፤ ምክንያቱም ጣዖቶች ሁሉ ከንቱ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥቅም የለሽ ጣዖት የሚቀርጽ››
Isaiah 44:11
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል
ተባባሪቹ ሁሉ
ይህም ማለት፤ 1) ጣዖት ከሚሠራው ጋር የሚተባበሩ ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጣዖት ሠሪው ተባባሪዎች ሁሉ›› ወይም 2) ጣዖቱን በማምለክ ከእርሱ ጋር የሚተባበሩትን ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጣዖት የሚያመልኩ ሁሉ››
ያፍራሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይዋረዳሉ››
በአንድ ላይ ይቁሙ
‹‹ሁሉም መጥተው ፊቴ ይቅረቡ››
ይደነግጣሉ
‹‹ይሸበራሉ›› ቃሉ በፍርሃት መጉበጥ ማለት ነው።
Isaiah 44:12
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል።
ያበጀው
‹‹ጣዖቱን ያበጀው›› ወይም፣ ‹‹ጣዖቱን የፈጠረው››
Isaiah 44:13
በገመድ የለካው
በእንጨት የሚሠራውን ጣዖት ቅርጽ ለማስያዝ በገመድ ይለካ ነበር
ድርካል
ይህ የሚሠራው ሰው የት ላይ መቁረጥ እንዳለበት ለማመልከት እንጨቱ ላይ ጭረት የሚደረግበት ሹል መሣሪያ ነው።
ንድፍ ማውጫ
ይህ ሁለት ጫፎች ያሉት መሣሪያ ሲሆን፣ ጣዖቱን ቅርጽ ለማስያዝ ጥቅም ላይ ይውላል።
Isaiah 44:14
ይቆርጠዋል
‹‹አናጢው ይቆርጠዋል›› ወይም፣ ‹‹ባለ ሙያው ይቆርጠዋል››
የቆኖሮስ ዛፍ
ሁሌ ለምልሞ የሚገኝ ዛፍ
Isaiah 44:15
ከዚያም ሰው ይጠቀምበታል
‹‹ሰውየው በእንጨቱ ይጠቀማል››
ጣዖት ሠርቶ ወድቆ ይሰግድለታል
ይህ የዐረፍተ ነገሩ አካል ከመጀመሪያው ጋር በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆን፣ አጽንዖት ይሰጣል።
Isaiah 44:18
ዐይኖቻቸው ስለ ታወሩ አያዩም
ጣዖትን የማምለክን ከንቱነት መረዳት ያቃታቸው ሰዎች ዕውሮች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።
ዐይኖቻቸው አያዩም
እዚህ ላይ ‹‹ዐይኖቻቸው›› ሁለንተናቸው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታውረዋልና››
ልባቸው ማስተዋል አይችልም
እዚህ ላይ ሰዎች፣ ‹‹በልቦቻቸው›› ተወክለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መረዳት አይችልም››
Isaiah 44:19
በቀረው እንዴት ጸያፍ ነገር እሠራለሁ? ... ለግንድ መስገድ ይገባኛልን?
እነዚህ ሰዎች እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቅ እንዳለባቸው ያህዌ ይናገራል። መልሱ አሉታዊ ሲሆን፣ እነዚህን ነገሮች ማድረግ ምን ያህል ሞኝነት እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣል። ጥያቄዎቹን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለማምለክ የሚያስጸይፈውን ይህን አላደርግም... ለግንድ እንጨት ወድቄ አልሰግድም››
Isaiah 44:20
ዐመድ እንደሚበላ ነው
ጣዖት የሚያመልክ ሰው ጣዖቱን ከሠራበት እንጨት የተረፈው ተቃጥሎ ሲነድ ዐመዱን እንደሚበላ ሰው እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። ዐመድ መብላት እንደማይጠቅም ሁሉ፣ ጣዖት ማምለክም አይጠቅምም።
የተታለለ ልቡ አስሳቶታል
ልብ ውስጣዊ ሁኔታን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በመታለሉ ራሱን አስቶአል››
ራሱን ማዳን አይችልም
‹‹ጣዖት የሚያመልክ ራሱን አያድንም››
Isaiah 44:21
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል።

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ያዕቆብና እስራኤል

ይህ ከያዕቆብና ከእስራኤል የተገኘውን ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተ የእስራኤል ዘሮች››

እኔ አልረሳችሁም

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ አልረሳችሁም››

ዐመፃህን እንደ ድቅድቅ ደመና፣ ኀጢአትህንም እንደ ጭጋግ አስወግጃለሁ

ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ነፋስ ደመናን በቀላሉና በፍጥነት እንደሚያስወግደው እግዚአብሔር ኀጢአታቸውን ይቀር ብሏል።

ኀጢአትህን እንደ ጭጋግ

ግሡ ባለፈው ሐረግ ተገልጿል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ጭጋግ ኀጢአትህን አስወግጃለሁ››

Isaiah 44:23

ሰማያት ሆይ ዘምሩ… ክብር በእስራኤል

እዚህ ላይ ኢሳይያስ ያህዌን እንዲያመሰግኑ የሚያዝዛቸው ሰዎች የሆኑ ይመስል ለተለያዩ የፍጥረት ክፍሎች ይናገራል።

የምድር ጥልቆች ሆይ

‹‹ዝቅ ያላችሁ የምድር ክፍሎች›› ይህም ማለት፣ 1) ባለፈው ሐረግ ከተጠቀሱ፣ ‹‹ሰማያት›› ጋር በንጽጽር የሚቀርቡ ዋሻዎችን፣ ወይም ጉድጓዶችን ለመሳሰሉ ዝቅ ያሉ የመሬት ክፍሎችን ያመለክት ይሆናል። ወይም 2) የሞቱ ሰዎችን የሚያመለክት ሊሆን ይቸላል።

Isaiah 44:24

የተቤዦህ

ኢሳይያስ 41፥14 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት

ከማሕፀን የሠራህ

በእናቱ ማሕፀን ያለ ሕፃንን በሠራበት ሁኔታ ያህዌ የእስራኤልን ሕዝብ መፍጠሩን ይናገራል። ኢሳይያስ 44፥2 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማሕፀን ውስጥ ሕፃን እንደምሠራ የፈጠረሁህ››

ብቻውን ሰማያትን የዘረጋ

ሰማያትን መፍጠሩ እንደሚዘረጋ ነገር የሆኑ ይመስል ያህዌ ይናገራል። ኢሳይያስ 42፥5 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ምልክቶች

እነዚህ የወደ ፊቱን ለማወቅ በመሞከር ሰዎች የሚጠቀሙባቸው ምልክቶች ናቸው።

ከንቱ ተናጋሪዎች

ይህ ትርጉም የለሽ ነገሮችን የሚናገሩ ሰዎችን ያመለክታል።

Isaiah 44:26

የባርያውን ቃል ያጸና፣ የመልእክቶቹን ትንቢት የፈጸመ

ትንቢቶች እንዲፈጸሙ ማድረግ የሚችል እርሱ ብቻ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ያህዌ አንድን ነገር ደጋግሞ ይናገራል።

የባርያው ቃል… የመልእክተኞቹ ትንቢት ‹‹ቃል› እና፣ ‹‹ትንቢት›› የሚሉትን ቃሎች በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ

ትርጉም፣ ‹‹ባርያው የተናገረውን… መልእክተኞቹ ያወጁትን››

መኖሪያ ትሆናለች

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያ ሰዎች እንደ ገና ይኖራሉ››

እንደ ገና ይሠራሉ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች እንደ ገና ይሠሯቸዋል››

ፍርስራሻቸውን አነሣለሁ

‹‹ፍርስራሽ›› የሚለው ሐረግ የፈረሰ ቦታ ያመለክታል። እርሱ የሚያነሳቸው ይመስል ያህዌ እንደ ገና እንደሚሠሩ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌሎች ያወደሙትን እንደ ገና እሠራለሁ››

Isaiah 44:28

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ መናገር ቀጥሏል።

እርሱ እረኛዬ ነው

ቂሮስ እረኛቸው የሆነ ይመስል የእስራኤልን ሕዝብ እየገዛና እየጠበቀ ስላለው ቂሮስ ያህዌ ይናገራል።

እንደ ገና ትሠራለች

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡ ከተማዋን ይሥሩ››

መሠረቷ ይጣል

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች መሠረቷን ይጣሉ››

---

Chapter 45

Isaiah 45:1

ቀኝ እጁን ለያዝሁት

ያህዌ ቂሮስን መርዳቱና እንዲሳካለት ማድረጉ ቀኝ እጁን መያዝ እንደሆነ ይናገራል።

Isaiah 45:2

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለቂሮስ መናገር ቀጥሏል።

ተራሮችን እደለድላለሁ

የያህዌን ስኬት የሚያሰናክል እንቅፋትን ሁሉ ማስወገዱ በፊቱ ተራሮችን ደልዳላ ማድረግ እንደ ሆነ ያህዌ ይናገራል።

ተራሮች

በዐውዱ የተጠቀሰው የዕብራይስጥ ቃል ብዙም ጥቅም ላይ የማይውል ሲሆን፣ ትርጉሙም ግልጽ አይደለም። አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች፣ ‹‹አስቸጋሪ ቦታዎች›› ወይም፣ ‹‹ጐርበጥባጣ ስፍራዎች›› ብለዋል።

የብረት መወርወሪያዎች

ይህ የሚያመለክተው የናሱ ደጆች ላይ ያሉትን የብረት ዘንጐች ነው።

በጨለማ ያለውን ንብረት

‹‹በጨለማ›› በምስጢር ቦታ ማለት ነው። ‹‹ጨለማ ቦታ ያለ ንብረት›› ወይም፣ ‹‹በምስጢር ቦታዎች ያለ ንብረት››

Isaiah 45:4

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለቂሮስ መናገር ቀጥሏል።

ያዕቆብ… እስራኤል

ሁለቱም የሚናገረው ስለ እስራኤል ዘር ነው።

ለጦርነት አስታጥቅሃለሁ

ይህ ማለት፣ 1) ‹‹ለጦርነት አበረታሃለሁ›› ወይም 2) ‹‹ለጦርነት አዘጋጅሃለሁ›› ማለት ሊሆን ይችላል።

ከፀሐይ መውጫ እስከ ምዕራብ

ፀሐይ የምትወጣው በምሥራቅ በመሆኑ፣ ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር በየትኛውም ምድር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር ካለ ማንኛውም ቦታ››

Isaiah 45:7

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ መናገር ቀጥሏል

ብርሃንን ሠራሁ ጨለማን ፈጠርሁ፤ ሰላም አመጣለሁ፤ ጥፋትንም እፈጥራለሁ

ዐረፍተ ነገሮቹ ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆኑ፣ ያህዌ የማንኛውም ነገር ሉዐላዊ ፈጣሪ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ።

ሰማያት ከላይ አዝንቡ… ጽድቅም አብሮ ይብቀል

የእርሱ ጽድቅ ምድር ላይ እንደሚወርድ ዝናብ እንደሆነና ጽድቁና ማዳኑም ምድር ላይ የሚበቅሉ ተክሎች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።

እናንት ሰማያት

ለጊዜውም ቢሆን ያህዌ ትኩረቱን ከሕዝቡ አንሥቶ ለሰማያት መናገር ይጀምራል።

Isaiah 45:9

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ መናገር ቀጥሏል

በምድር ካሉ የሸክላ ማሰሮዎች መካከል

ያህዌ ስለ ራሱ ሲናገር እርሱ ሸክላ ሠሪ እንደሆነ፣ ከእርሱ ጋር የሚከራከረውና የተቀረው የሰው ዘር በሙሉ ሸክላዎች እንደሆኑ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከብዙ ሸክላዎች መካከል አንዱ››

የሸክላ ማሰሮ

ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ከሸክላ የተሠራ ማሰሮ›› ወይም 2) ‹‹የተሰበረ የሸክላ ማሰሮ›› ማለት ሊሆን ይችላል።



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ጭቃ ሸክላ ሠሪውን... ምን እየሠራህ ነው? ይለዋልን
ያህዌ ይህን የሚጠይቀው እርሱ የሚያደርገውን የሚከራከሩትን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጭቃ ሸክላ ሠሪውን... ምን እየሠራህ ነው? ማለት የለበትም››
Isaiah 45:10
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ የሚያደርገውን የሚከራከሩትን መገሠጽ ቀጥሏል።
አባቱን... ለምን ትወልደኛለህ? ለሚል ወዮለት
ከእርሱ ጋር የሚከራከሩ ከወላጆቻቸው ጋር የሚከራከሩ ገና ያልተወለዱ ልጆች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።
የወለድኸው ምንድነው?... ምን ወለድህ?
ያልተወለደው ልጅ ይህን የሚጠይቀው እርሱን በመወለዳቸው ወላጆቹ ላይ ለማፌዝ ነው። ይህን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አባቴ መሆን አልነበረብህም... ለምን ወለድኸኝ?›› ወይም፣ ‹‹ለእኔ ጥሩ አባት አይደለህም... እኔን በትክክል አልወለድኸኝም››
Isaiah 45:11
የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
ልጆቼ ላይ የማደርገውን ለምን ትጠይቀኛላችሁ? የእጆቼን ሥራ በተመለከተ ማድረግ ያለብኝን ትነግሩኛላችሁን?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው የሚያደርገውን የሚከራከሩትን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልጆቼ ላይ የማደርገውን አትጠይቁኝ፤ በእጆቼ ሥራ... አትጠይቁኝ››
ልጆቼ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው።
የእጆቼ ሥራ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጆች›› የሚወክሉት ያህዌን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ያደረግሁትን››
Isaiah 45:12
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል።
የእጆቼ ሥራ ነው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጆች›› ያህዌን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያን ያደረግሁ እኔ ነኝ››
ሰማያትን የዘረጋሁ
ያህዌ ሰማያትን መፍጠሩን እንደሚዘረጋ ነገር መዘርጋት እንደ ሆነ ይናገራል። ኢሳይያስ 42፥5 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
Isaiah 45:13
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል።
ቂሮስን በጽድቅ አስነሥቻለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ጽድቅ›› የሚያመለክተው ተገቢ የሆነ ሥራ ነው። ይህም ማለት፣ 1) ተገቢ የሆነውን ነገር እንዲያደርግ ያህዌ ቂሮስን አስነሣው፤ ወይም 2) ቂሮስን በማስነሣቱ ያህዌ ትክክል ነበር ማለት ሊሆን ይችላል።
ቂሮስን አስነሥቻለሁ
ቂሮስን ማስነሣቱ እርሱን ከእንቅልፍ መቀስቀሥ እንደሆነ ያህዌ ይናገራል።
መንገዱን ሁሉ አስተካክልለታለሁ
ዕንቅፋትን ማስወገዱና ቂሮስ እንዲሳካለት ማድረግ መንገዱን ማስተካከል እንደሆነ ያህዌ ይናገራል።
ከተማዬን እንደ ገና ይሠራታል
ይህ የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው።
ያለ ክፍያ ወይም ያለ ጉቦ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ክፍያ›› እና፣ ‹‹ጉቦ›› ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ቂሮስ ይህን ሁሉ የሚያደረገው ለገንዘብ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህንንም የሚያደርገው ለሚያገኘው ገንዘብ ሲል አይደለም››
የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
Isaiah 45:14
የግብፅ ሀብትና የኩሽ ንግድ፣ ቁመተ ረጃጅሞቹ የሰባ ሰዎች ወደ አንተ ይመጣሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የግብፅ ሕዝብ፣ ኩሽና ቁመተ ረጃጅሞቹ የሳባ ሰዎች ሀብታቸውንና ንግዳቸውን ወደ አንተ ያመጣሉ››
የግብፅ ሀብት
‹‹የግብፅ ጥቅም››
ሳባውያን
እነዚህ የሳባ አገር ሰዎች ናቸው።
ወደ አንተ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› የሚያመለክተው የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ነው።
Isaiah 45:16
ሁሉም ያፍራሉ፤ በአንድነት ይዋረዳሉ፤ ጣዖትን የሚሠሩ በውርደት ይመላለሳሉ
ሁለቱም መስመሮች የሚናገሩት ተመሳሳይ ነው፤ ሁለተኛው የመጀመሪያውን ርዕሰ ጉዳይ ግልጽ ያደርጋል።
ያፍራሉ፤ በአንድነት ይዋረዳሉ
‹‹ያፍራሉ›› እና፣ ‹‹ይዋረዳሉ›› የሚሉት በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆኑ፣ አጽንዖት የሚሰጡት የእፍረቱን መጠን ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጣዖቶቻቸው ሁሉንም ለእፍረት ይዳርጓቸዋል
በውርደት ይመላለሳሉ
ዘወትር ውርደት ውስጥ መኖር በውርደት መመላለስ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዘወትር ይዋረዳሉ››
እስራኤልን ያህዌ ያድነዋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የእስራኤልን ሕዝብ ያድናል››
ከእንግዲህ አታፍርም፤ አትዋረድም
‹‹አንተ›› የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። ‹‹ማፈር›› እና፣ ‹‹መዋረድ›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ማንም አያዋርድህም››
Isaiah 45:18
እንድትባክን
‹‹ባዶ እንድትሆን›› እዚህ ላይ መባከን›› ባዶ፣ ጠፍ ቦታ መሆን ማለት ነው።
መኖሪያ እንጂ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነገር ግን የሰዎች መኖሪያ እንድትሆን ወሰነ››
Isaiah 45:19
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል
Isaiah 45:20
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል
የኮበለላችሁ
ጠላት እንዳይዛቸው ወይም እንዳይገድላቸው ከቤታቸው የሸሹ ሰዎች
Isaiah 45:21
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኮብላዮቹ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 45፥20 ይመ.)
በአንድነት ይምከሩ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› የተባሉት ከአሕዛብ መካከል የኮበለሉት ጣዖቶች የሚያመልኩ ሰዎች ናቸው።
ከጥንት ጀምሮ ይህን ያሳየ ማን ነው? ያወጀውስ ማን ነው? እኔ ያህዌ አይደለሁም?
ያህዌ ጥያቄዎቹን ያቀረበው እነዚህ እንደሚሆኑ የተናገረ እርሱ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከጥንት ጀምሮ ይህን ያሳየ ማን እንደሆነ እነግራችኋለሁ። እኔ ያህዌ ነኝ››
Isaiah 45:22
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል
ትድኑ ዘንድ ወደ እኔ ተመለሱ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ እኔ ተመለሱ፤ እኔም አድናችኋለሁ››
የምድር ዳርቻዎች ሁሉ
ሩቅ ቦታ የሚኖሩ ሰዎች የምድር ዳርቻዎች ላይ እንደሚኖሩ ተነግሯል። ይህ ማለት በዳርቻዎቹ መካከል ያለ ማንኛውም ቦታ ማለትም ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር ሩቅ ቦታ ያላችሁ ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በምድር ሁሉ››

የምድር ዳርቻዎች ሁሉ
ይህ ሐረግ፣ ‹‹በምድር ዳርቻዎች ሁሉ›› የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር ሩቅ ቦታ የምትኖሩ ሁሉ›› ወይም ‹‹በምድር ሁሉ የምትኖሩ››
ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፤ አንደበትም ሁሉ በእኔ ይምላል
‹‹ጉልበት›› እና፣ ‹‹አንደበት›› የሚወክሉት ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው ሁሉ በፊቴ ይንበረከካል፤ ማንኛውም ሰው በእኔ ይምላል››
Isaiah 45:24
ይላሉ
የምድር ሕዝብ ሁሉ ይናገራሉ
በያህዌ የእስራኤል ዘር ሁሉ ይጸድቃል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ይጸድቃል›› ማለት እርሱን በማምለክ እስራኤል መልካም ማድረጓን ለአሕዛብ ማሳየት እንጂ፣ ያህዌ ኀጢአታቸውን ይቅር ይላቸዋል ማለት አይደለም። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የእስራኤልን ዘር ሁሉ ያጸድቃል›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ የእስራኤልን ዘር ጽድቅ ይገልጣል››

Chapter 46
Isaiah 46:1
ቤል ዝቅ አለ፤ ኔቦ አጐነበሰ፤ ጣዖቶቻቸው... ለደከሙ እንስሳት
ሰዎች ቤል እና ኔቦን በእንሳስት በሚሳብ ሰረገላ ላይ ማስቀመጣቸውን ኢሳይያስ የእነዚህ ጣዖቶች ዝቅ ማለትና ማጐንበስ ማለት እንደሆነ ይናገራል። ሁለቱም የሚያመለክቱት መዋረድን ነው።
ቤል... ኔቦ
እነዚህ ባቢሎናውያን የሚያመልካቸው ሁለቱ ዋና አማልክት ናቸው።
ጣዖቶቻቸው
ጣዖቶቹ ቤልና ኔቦን ይወክላሉ
ምስሎቹን አያድኑም
‹‹ቤልና ኔቦ ምስላቸውን ማዳን አይችሉም››
እነርሱ ራሳቸው በምርኮ ተወስደዋል
እነዚህ ሰዎች የሚሸከሙዋቸው ሐሰተኛ አማልክትን የሚወክሉ ጣዖቶች ወደ ምርኮ እንደ ተወሰዱ ኢሳይያስ ይናገራል።
Isaiah 46:3
እኔን ስሙ
‹‹እኔ›› ያህዌን ያመለክታል።
ከመወለዳችሁ በፊት የተሸከምኋችሁ ከማሕፀን ጀምሮ የተሸከምኋችሁ
የእስራኤል መንግሥት ሰው እንደሆነና የመንግሥቱም ጅማሬ ልጅ መወለድ እንደ ሆነ ያህዌ ይናገራል።
የተሸከምኋችሁ
የእስራኤልን ሕዝብ መርዳቱና ማዳኑ እነርሱን መሸከም እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ የተሸከምኋችሁ››
እስከ ሽምግልና እኔ ነኝ፤ እስከ ሽበትም እሸከማችኋለሁ
የእስራኤልን ሽምግልና ጠጉሩ ከሸበተ ሽማግሌ ሰው ጋር በማመሳሰል ያህዌ ይናገራል።
Isaiah 46:5
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ከማን ጋር ታወዳድሩኛላችሁ? ከማንስ ጋር እኩል ታደርጉኛላችሁ?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው እንደ እርሱ ማንም እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከማንም ጋር ልታወዳድሩኝ አትችሉም፤ ከእኔ ጋር የምታስተካክሉት እኔን የመሰለ የለም››
ከማንስ ጋር እኩል ታደርጉኛላችሁ?
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእኔ ጋር የምታመሳስሉት››
Isaiah 46:7
ያነሡታል
‹‹እነርሱ›› ጣዖቱን የሠሩ ሰዎችን ያመለክታል፤ ‹‹እርሱ›› የሠሩትን ጣዖት ያመለክታል።
Isaiah 46:8
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሕዝቡ መናገር ቀጥሏል
Isaiah 46:10
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሕዝቡ መናገር ቀጥሏል
የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ ገና የሚሆነውን አስቀድሜ ተናግሬአለሁ።
አጽንዖት ለመስጠት እየደገመ ያለው በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገርን ነው። የመጀመሪያው ሐረግ ግሥ ለሁለተኛውም ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የመጨረሻውን ከመጀመሪያው ተናግሬአለሁ፤ ገና ያልተደረገውን አስቀድሜ ተናግሬአለሁ››
ከምሥራቅ ነጣቂ ወፍ ጠርቻለሁ
ቂሮስ፣ ‹‹ነጣቂ ወፍ›› እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። ወፍ በድንገት የምታድነውን እንደምትይዝ፣ ቂሮስም በፍጥነት መንግሥታትን ድል ለማድረግ የያህዌን ዓላማ በፍጥነት ይፈጽማል።
የተናገርሁትን አደርጋለሁ፤ ያቀድሁትን እፈጽማለሁ
አጽንዖት ለመስጠት ተመሳሳዩን ነገር ደጋግሞአል።
Isaiah 46:12
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
መልካም ከማድረግ የራቃችሁ
በመደጋገም ክፉ የሚያደርጉ ሰዎች መልካም ከማድረግ የራቁ እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።
ማዳኔ አይዘገይም
ሕዝቡን ቶሎ ማዳኑ ለተግባር የማይዘገይ ሰው እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። ማዳን የሚለውን በሌላ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተን ከማዳን አልዘገይም››

Chapter 47
Isaiah 47:1
አጠቃላይ መረጃ
በዚህ ምዕራፍ የተዋረደች ንግሥት ይመስል፣ ያህዌ ስለ ባቢሎን መውደቅ ይናገራል።
ትቢያ ላይ ተቀመጪ፤ የባቢሎን ድንግል ልጅ ሆይ፣ መሬት ላይ ተቀመጪ...የከለዳውያን ልጅ ሆይ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ትቢያ ላይ መቀመጥ የውርደት ምልክት ነው።
የባቢሎን ድንግል ልጅ... የከለዳውያን ልጅ
ሁለቱም ሐረጐች የሚያመለክቱት እንደ ሴት ልጅ የተነገረላት የባቢሎንን ከተማ ነው። ከተማዋ፣ ‹‹ሴት ልጅ›› መሆንዋ ሕዝቡ ለእርሷ ያለውን ፍቅር ያመለክታል።
ያለ ዙፋን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዙፋን›› የመግዛት ሥልጣንን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያለ የመግዛት ሥልጣን››
ከእንግዲህ ውብ ወይም ለግላጋ ተብለሽ አትጠሪም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ሰዎች ውብና ለግላጋ በማለት አይጠሩሽም››
ውብና ለግላጋ
እነዚህ ሁለት ቃሎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ያማረና በምቾት መኖርን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ያማርሽ›› ወይም፣ ‹‹በጣም የተመቸሽ››
ወፍጮ
እህል ለመፍጨት የሚያገለግል ትልቅ ድንጋይ
Isaiah 47:3
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ያህዌ የተዋረደች ንግሥት የሆነችው የባቢሎንን ውድቀት መናገር ቀጥሏል።
ዕርቃንሽ ይገለጣል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዕርቃንሽን ትሆኛለሽ››
ኀፍረትሽ ይታይ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ኀፍረት›› የሚለው የሰውን ድብቅ አካል ነው። ይህን በሌላ መልኩ

መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ኀፍረትሽን ያያሉ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች ድብቅ አካልሽን ያያሉ››
የሚቤዠን
‹‹የእኛ›› የሚለው ኢሳይያስንና የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። ኢሳይያስ 41፥14 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥24 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 5፥16 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
የከለዳውያን ሴት ልጅ
ይህ ሐረግ እንደ ሴት ልጅ የተመሰለችው የባቢሎንን ከተማ ያመለክታል። ከተማዋ፣ ‹‹በሴት ልጅ›› መመሰልዋ ከለዳውያን እርሷን በጣም መወደዳቸውን ያመለክታል። ኢሳይያስ 47፥1 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
ከእንግዲህ አትጠሪም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ሰዎች አንቺን አይጠሩሽም።
የመንግሥታት ልዕልት
የባቢሎን መንግሥት ዋና ከተማ የሆነችው ባቢሎን ብዙ መንግሥታትን ትገዛ የነበረች ልዕልት እንደሆነች ያህዌ ይናገራል።
Isaiah 47:6
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ያህዌ የተዋረደች ልዕልት ስለሆነችው ስለ ባቢሎን ውድቀት መናገር ቀጥሏል።
እኔ ተቆጥቼ ነበር
‹‹እኔ›› ያህዌን ያመለክታል።
ርስቴን አርክሼው ነበር
የእስራኤል ሕዝብ የእርሱ የተለየ ርስት እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእኔ የተለየ ርስት የሆነውን ሕዝቤን አርክሼ ነበር››
አሳልፌ በእጅሽ ሰጠኋቸው
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የባቢሎንን ኀይል ወይም ቁጥጥር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሥልጣንሽ ሥር አደረግኋቸው››
በዕድሜ በገፉት ላይ ከባድ ቀንበር ጫንሽባቸው።
ባቢሎን በዕድሜ የገፉትን መጨቆንዋ እንደ እንስሳት አንገታቸው ላይ ቀንበር ማድረግ እንደሆነ ያህዌ ይናገራል።
ለዘላለም ንግሥት እሆናለሁ
እርሷ ለዘላለም የምትገዛ ይመስል ብዙ መንግሥታትን እንደ ልዕልት እንደምትገዛ ትናገራለች።
እነዚህን ነገሮች አላስተዋልሽም
እነዚህን ነገሮች ልብ ውስጥ እንደማኖር ያህዌ ስለ ነገሮች በጥንቃቄ ማሰብ እንደሚገባ ይናገራል።
Isaiah 47:8
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
እንደ ተዋረደች ንግሥት ባቢሎን እንደምትወድቅ ያህዌ መናገር ቀጥሏል።
እናንተ ደስታ የምትወዱ
‹‹እናንተ ቅምጥሎች›› ይህ የባቢሎንን ቅጥ ያጣ ፈንጠዝያ ያመለክታል።
ተማምነሽ የምትቀመጪ
ይህ ሀብቷንና ክብሯን በፍጹም እንደማታጣ በማሰብ ባቢሎን የነበራትን እኑል በራስ መተማመን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሉም ደህና እንደሆነ የምታስቢ››
መበለት አልሆንም... የወላድ መካን አልሆንም
ሌሎች መንግሥታት በፍጹም ድል እንደማያደርጓት ባቢሎን የነበራት እምነት መበለት አልሆንም፤ የወላድ መካን አልሆንም በማለት የማሰብ ያህል እንደሆነ ተነግሯል።
መበለት አልሆንም
‹‹ባል የሌላት ሴት አልሆንም››
በአንድ ቀን ውስጥ
‹‹ድንገት በአንድ ጊዜ››
Isaiah 47:10
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ያህዌ የተዋረደች ልዕልት ስለሆነችው ባቢሎን መውደቅ መናገር ቀጥሏል።
አንቺም በልብሽ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› ውስጣዊውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለራስሽ እንዲህ አልሽ››
ጥፋት ያሸንፍሻል
ጥፋት ባቢሎንን የሚያሸንፍ ሰው እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥፋት ይደርስብሻል››
ውድመት ይወድቅብሻል
የባቢሎን መውደም ከተማዋ ላይ የሚወድቅ አንዳች ነገር እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ውድመት ይመጣብሻል››
አደጋ ይመታሻል
ባቢሎን ላይ የሚደርሰው አደጋ እርሷን የሚመታ ሰው እንደሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አደጋ ይደርስብሻል››
Isaiah 47:12
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
እንደ ተዋረደች ንግሥት ባቢሎን እንደምትወድቅ ያህዌ መናገር ቀጥሏል።
መተት ማድረግሽን ቀጥዪ፤ ምናልባት አደጋን ማራቅ ትችዪ ይሆናል
መጥፎ ነገሮች እንዳይደርስባት መተት ማድረግን እንድትቀጥል በመንገር ያህዌ ባቢሎን ላይ ያፌዛል፤ ያ እንደማይረዳት ግን ያውቃል።
Isaiah 47:14
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
እንደ ተዋረደች ንግሥት ባቢሎን ላይ ስለሚደርሰው ውድቀት መናገሩን ያህዌ ቀጥሏል።
እንደ ገለባ ይሆናሉ፤ እሳትም ያቃጥላቸዋል
አስማተኞችና መተተኞች እሳት በቀላሉ እንደሚያቃጥለው ገለባ እንደ ሆኑ ያህዌ ይናገራል። ይህም ማለት እሳት ገለባ እንደሚያቃጥል፣ ያህዌ በፍጥነት ያጠፋቸዋል ማለት ነው፤ ባቢሎንን ለማዳን ዐቅም የላቸውም።
የነበልባሉ እጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› ብርታትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የነበልባሉ ኀይል››
የሚሞቁት ፍም፤ ተቀምጠው የሚሞቁት እሳት አይኖርም
ይህ ሰዎች የሚሞቁት ሳይሆን፣ የሚያጠፋ እሳት መሆኑን ያህዌ ይናገራል።

---

Chapter 48
Isaiah 48:1
ይህን ስሙ
‹‹መልእክቴን ስሙ›› ያህዌ እየተናገረ ነው።
የያዕቆብ ቤት
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቤት›› የያዕቆብን ዘር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያዕቆብ ዘሮች››
በእስራኤል ስም የተጠራችሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው ሁሉ የእስራኤል ሕዝብ እያለ የሚጠራችሁ››
ከይሁዳ ፍሬ የመጣችሁ
ይህ ሐረግ አጽንዖት የሚሰጠው እነርሱ በአካል የይሁዳ ዘር መሆናቸውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የይሁዳ ዘር ናችሁ››
በእስራኤል አምላክ የምትታመኑ
‹‹የእስራኤልን አምላክ የምትጠሩ››
ራሳቸውን ይጠራሉ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራሳችሁን ትጠራላችሁ››
የተቀደሰች ከተማ
ይህ የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው።
የሰራዊት ጌታ ያህዌ
ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
Isaiah 48:3
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ከአፌ ወጥተዋል
‹‹አፍ›› የሚናገር ሰውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህን ነገሮች


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተናግሬአለሁ››
አንገትህ እንደ ብረት ጠንክሮአል ግንባርህ እንደ ናስ ሆኖአል።
የዐንገታቸውንና የግንባራቸውን ጥንካሬ ያህዌ ከብረትና ከናስ ጥንካሬ ጋር ያመሳስለዋል። የዐንገትና የግንባር ጥንካሬ የግትርነት ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐንገትህ ብረት፣ ግንባርህም ናስ የሆነ ያህል ነው››
ስለ እነዚህ ነገሮች ገና ድሮ ነገርሁህ፤ ከመፈጸማቸው በፊት አስታወቅሁህ
ይህ አጽንዖት ለመስጠት ተመሳሳይ ነገር ሁለቴ መናገር ነው።
Isaiah 48:6
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
የተናገርሁት እውነት መሆኑን አትቀበልምን?
ያህዌ እነዚህን ጥያቄዎች ያቀረበው እውነት መሆኑን የሚያውቁትን ነገር ባለ መቀበላቸው፣ የእስኤልን ሕዝብ ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግትር ናችሁ፤ የተናገርሁት እውነት መሆኑን አትቀበሉም››
Isaiah 48:8
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
እነዚህ ነገሮች ለጆሮዋችሁ የተገለጡት አሁን እንጂ፣ ዱሮ አይደለም
ያህዌ አንዳች ነገር መናገሩ ያንን መግለጥ እንደሆነ ያመለክታል። ‹‹ጆሮ›› የሚሰሙ ሰዎችን ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ ነገሮች ለእናንተ አስቀድሜ አልገለጥሁም››
ከልደት
የሕዝቡ ጅማሬ ልደቱ እንደሆነ ያህዌ ይናገራል።
Isaiah 48:9
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ስለ ስሜ ስል ቁጣዬን አዘገያለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የያህዌን ማንነት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለ ማንነቴ ስል ቁጣዬን አዘገያለሁ››
ስለ ክብሬ ስል እናንተን ከማጥፋት እታቀባለሁ
ይህ የዐረፍተ ነገሩ ክፍል ከመጀመሪያው ክፍል ጋር በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው።
እነሆ፣ እንደ ብር ባይሆንም፣ አንጥሬሃለሁ፤ በመከራ እቶን አንጽቼሃለሁ
እነርሱ የከበሩ ማዕድኖች የሆኑ ይመስል እቶን ደግሞ እነርሱን የሚያነጻ እሳት ይመስል ያህዌ ሕዝቡን በመከራ ውስጥ እንደሚያነጻ ይናገራል።
ስሜን ለውርደት እንዴት አሳልፌ እሰጣለሁ?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ስሙን ለውርደት አሳልፎ እንደማይሰጥ አጠንክሮ ለማመልከት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም ስሜን እንዲያዋርድ አልፈቅድም››
Isaiah 48:12
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ያዕቆብና እስራኤል
ሁለቱም የሚያመለክቱት የእስራኤልን ሕዝብ ነው።
እኔ የመጀመሪያው፣ የመጨረሻውም ነኝ
ይህ ሐረግ ለያህዌ ዘላለማዊ ባሕርይ አጽንዖት ይሰጣል። ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ሁሉንም የጀመርሁ እኔ ነኝ፤ ሁሉንም የምጨርስ እኔ ነኝ›› ወይም 2) ‹‹እኔ ሁሌም የነበርሁ፣ ሁሌም የምኖር ነኝ›› ኢሳይያስ 46፥6 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
እጄ፣ ምድርን መሠረተ፤ ቀኝ እጄ ሰማያትን ዘረጋ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምድርን መሠረት አኖርሁ፤ ሰማያትንም ዘረጋሁ››
የምድር መሠረት
መሠረት ከሥር ሆኖ ሕንፃውን ደግፎ የሚይዝ የድንጋይ መዋቅር ነው። እዚህም ላይ በተመሳሳይ መልኩ ምድርን የሚይዝ መዋቅር እንደሆነ ተነግሯል። ኢሳይያስ 24፥18 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
ሰማያትን ዘረጋሁ
ያህዌ ሰማያትን መፍጠሩን አንዳች የሚዘረጋ ነገር መዘርጋት ማለት እንደሆነ አድርጐ ይናገራል። ኢሳይያስ 42፥5 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
ስጠራቸው በአንድነት ይቆማሉ
ያህዌ ሲጠራቸው መቆም ለእርሱ ለመታዘዝ ዝግጁ መሆን ማለት ነው። ምድርና ሰማያት እንደሚሰሙትና እንደሚታዘዙት ያህዌ ይናገራል።
ስጠራቸው
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ምድርና ሰማያትን ስጠራቸው›› ወይም 2) ‹‹በሰማይ ያሉ ከዋክብትን ስጠራቸው›› ማለት ሊሆን ይችላል።
Isaiah 48:14
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ከእናንተ መካከል እነዚህን ነገሮች ያስታወቀ ማን ነው?
ያህዌ ጥያቄውን ያነሣው ጣዖቶች እነዚህን ነገሮች እንዳልነገሯቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከጣዖቶቻችሁ አንዱም ይህን አልነገሯችሁም››
የያህዌ አጋር ባቢሎን ላይ ዓላማውን ይፈጽማል፤ ከለዳውያንም ላይ ፈቃዱን ያደርጋል
የያህዌ፣ ‹‹አጋር›› የተባለው ቂሮስ ነው። ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ቢሆኑም ጥቅም ላይ የዋሉት አጽንዖት ለመስጠት ነው።
ዓላማው
‹‹የያህዌ ዓላማ››
እኔ፣ እኔ
‹‹እኔ›› የሚለው የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ራሴ››
Isaiah 48:16
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
በድብቅ አልተናገርሁም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተናገርሁት በግልጽና በአደባባይ ነው››
ልከውኛል
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› የተባለው በግልጽ ያልታወቀ የያህዌ ባርያ ነው፤ ምናልባት ኢሳይያስ ወይም ቂሮስ ወይም ተስፋ የተሰጠለት መሲሕ ሊሆን ይችላል።
Isaiah 48:17
የተቤዠህ… እምላክህ
እዚህ ላይ፣ ‹‹የአንተ›› የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።
የተቤዠህ
ኢሳይያስ 41፥14 ላይ ይህን ቃል እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
መሄድ በሚገባህ መንገድ የሚመራህ
እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያህዌ ሕዝቡን ማስተማሩ እነርሱን በትክክለኛው መንገድ መምራት ማለት እንደሆነ ተነግሯል።
ትእዛዜን ሰምተህ ብቻ ቢሆን ኖሮ
ያህዌ መሆን ስለ ነበረበት ግን ስላልሆነ ነገር ይናገራል።
ሰላምህና ብልጽግናህ እንደ ወንዝ፣ መዳንህም እንደ ባሕር ሞገድ በሆነ ነበር
እነዚህ ሁለት ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ጉዳይ ነው። በሁለቱም እነዚህ በረከቶች እንደ ውሃ የሚፈስሱ ይመስል እስራኤል በረከትን እንደምትለማመድ ያህዌ ይናገራል።
መዳንህም እንደ ባሕር ሞገድ
ግሡን ካለፈው ሐረግ መውሰድ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መዳንህ እንደ ባሕር ሞገድ በፈሰሰ ነበር››
Isaiah 48:19
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ወደ ፊቱ የእስራኤል ሁኔታ መናገር ቀጥሏል።
ዘርህ እንደ አሸዋ፣ የማሕፀንህም ልጆች ስፍር እንደሌለው ትቢያ ይሆኑ ነበር
ሁለቱም ሕዝቡ መቁጠር ከሚችሉት በላይ ዘሮቻቸው ይበዙ እንደ ነበር ያመለክታሉ።
የማሕፀንህም ልጆች
የእስራኤል ሕዝብ ዘሮች እንደሚወለዱ ልጆች እንደሚሆኑ ያህዌ ይናገራል።
ስማቸው አይቆረጥም ወይም አይደመሰሰም ነበር
የእስራኤል ሕዝብ መጥፋት እንደ ልብስ ወይም እንደ ዛፍ ቅርንጫፍ መቆረጥ ወይም መደምሰስ እንደሚሆን ያህዌ ይናገራል። ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስማቸውን አልቆርጥም ወይም አልደመስስም

ነበር››
ስማቸውን
‹‹ስም›› የሚለው ቃል የእስራኤልን ስም የሚያስጠሩ ዘሮችን ያመለክታል።
አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱ››
አይቆረጥም ወይም አይደመሰስም
በዚህ ዐውድ ሁለቱም አገላለጾች የሕዝቡን መጥፋት ነው የሚያመለክቱት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አይጠፋም››
Isaiah 48:20
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
እስከ ምድር ዳርቻ
ምድር ላይ ያሉ ሩቅ ቦታዎች ስም፣ የምድር ዳርቻዎች እንደሆኑ ተነግሯል። በምሳሌያዊ አነጋገር በዳርቻዎቹ መካከል ያሉትን ቦታዎች ሁሉ ይጨምራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምድር ላይ ያሉ ሩቅ ቦታዎች ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በምድር ሁሉ››
ባርያውን ያዕቆብን
ይህ የሚያመለክተው የያዕቆብን ዘር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባርያዎቹ የእስራኤል ሕዝቦች››
Isaiah 48:21
አልተጠሙም… ውሃው ፈልቆ ወጣ
ይህ የሚያመለክተው ከግብፅ ከወጡ በኃላ በምድረ በዳ እየኖሩ ሳለ፣ ለእነርሱ ለመጠንቀቅ በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ያህዌ ያደረገውን ነው።

---

Chapter 49
Isaiah 49:1
እኔን ስሙ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› የሚያመለክተው የያህዌን ባርያ ነው።
ደሴቶች
ይህ የሚያመለክተው ደሴቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በደሴቶች የምትኖሩ››
አፌን እንደ ተሳለ ሰይፍ አደረገው
እዚህ ላይ፣ ‹‹አፍ›› እርሱ የሚናገረውን ቃል ይወክላል። የሚሠራ መሆኑን ለማሳየት ቃሉ ከሰይፍ ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቃሌን እንደሚሠራ የተሳለ ሰይፍ አድርጎታል››
በእጁ ጥላ ሰውሮኛል፤
ያህዌ ባርያውን መጠበቁና ዓላማውን በምስጢር መያዙ የያህዌ እጅ ጥላ እርሱ ላይ ማረፍ እንደሆነ ተነግሯል።
የተወለወለ ፍላጻ አደረገኝ፤ በሰገባውም ውስጥ ሸሸገኝ
ያህዌ ባርያውን መጠበቁና ዓላማውን በምስጢር መያዙ፣ በሰገባው ውስጥ መሆን ማለት እንደሆነ ተነግሯል።
ሰገባ
ፍላጻዎች የሚያዙበት ቦርሳ
Isaiah 49:3
አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል
እንዲህም አለኝ
‹‹ያህዌ እንዲህ አለኝ››
እስራኤል፣ አንተ ባርያዬ ነህ
‹‹አንተ፣ እስራኤል ብዬ የጠራሁህ ባርያየ ነህ››
Isaiah 49:5
አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል።
እስራኤልን ወደ እርሱ እንድሰበስብ
ይህ የዐረፍተ ነገሩ ክፍል ቀደም ሲል ከነበረው ጋር ተመሳሳይ ነው። በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤልን ሕዝብ መልሼ ወደ እርሱ እንዳመጣ››
በያህዌ ዐይን ከብሬአለሁ
ዐይን ማየትን፣ ማየት ደግሞ ሐሳብን ወይም ፍርድን ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ አክብሮኛል››
አምላኬ ብርታት ሆኖኛል
እግዚአብሔር ለባርያው ብርታት መስጠቱ፣ እግዚአብሔር ራሱ ብርታት ሆነለት ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አምላኬ ብርታት ሰጥቶኛል›› ወይም ‹‹አምላኬ አበርትቶኛል››
ለአሕዛብ ብርሃን አደርግሃለሁ
አገልጋዩ የያህዌን መልእክት ለአሕዛብ ማምጣቱና እንዲያስተውሉም መርዳቱ ያህዌ አገልጋዩን በአሕዛብ መካከል ብርሃን አደረገው ማለት እንደሆነ ተነግሯል። ኢሳይያስ 42፥6 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
የምድር ዳርቻዎች
በምድር ላይ በጣም ሩቅ ያሉ ቦታዎች የምድር ዳርቻዎች ላይ ያሉ ቦታዎች እንደሆኑ ተነግሯል። ምሳሌያዊ አነጋገሩ በዳርቻዎቹ መካከል ያሉትን ቦታዎችም ይጨምራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር በሩቅ ያሉ ቦታዎች ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በምድር ሁሉ››
Isaiah 49:7
ታዳጊ
ኢሳይያስ 41፥14 ላይ ይህን ቃል እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
ሕይወቱ ለተናቀ፣ በአሕዛብ ለተጠላውና የገዢዎች ባርያ ለሆነው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሕይወት›› ሰውየውን ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ለናቁት፣ አሕዛብ ለጠሉትና የገዦች ባርያ ለሆነው››
የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
Isaiah 49:8
ሞገሴን በማሳይበት ጊዜ እመልስልሃለሁ፤ በማዳን ቀን እረዳሃለሁ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው።
እመልስልሃለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› የተባለው የያህዌ አገልጋይ ነው።
በመዳን ቀን
‹‹መዳን›› የሚለውን ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተን የማድንበት ቀን ሲመጣ››
ለአሕዛብ ኪዳን አድርጌ እሰጥሃለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ኪዳን›› ኪዳኑን የሚመሠርተውን ወይም መካከለኛ የሆነውን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። ኢሳይስ 42፥6 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከሕዝቡ ጋር ለሚደረገው ኪዳን መካከለኛ አደርግሃለሁ››
ምድሪቱን እንደ ገና እንድትሠራ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ምድሪቱ›› በዚያ ምድር የነበሩና የተደመሰሱ ከተሞች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድሪቱ ያሉ የፈረሱ ቦታዎችን እንድትሠራ››
ጠፍ የሆኑ ርስቶችን እንድትመልስ
ምድሪቱ ለዘላለም ርስታቸው እንድትሆን የእስራኤል ሕዝብ የተቀበሏት ንብረት እንደሆነች ያህዌ ይናገራል። ባርያው ርስቱን የሚመልሰው ለእስራኤል ሕዝብ መሆኑ ግልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠፍ የሆነው ምድር ርስታቸው እንዲሆን ለእስራኤል ሕዝብ እንድትመልስ››
Isaiah 49:9
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለባርያው መናገር ቀጥሏል።
በመንገዱ ዳር ይመገባሉ፤ የተራቆተውም ኮረብታ ሁሉ መሰማሪያቸው ይሆናል
በነጻነትና በብልጽግና የሚኖር ሕዝቡ የሚመገቡት ብዙ ሣር እንዳላቸው በጐች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።
Isaiah 49:10
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል
አይራቡም
‹‹እነርሱ›› የሚለው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነው።
ትኩሳት ወይም የፀሐይ ቃጠሎ አይመታቸውም
እዚህ ላይ፣ ‹‹ትኩሳት›› የሚለው ቃል፣ ‹‹ፀሐይ›› የሚለውን ቃል ይገልጻል። የፀሐይ ሙቀት የጐዳቸው ሰዎች በትኩሳቱ የተመቱ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የፀሐይ ትኩሳት አይመታቸውም››


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚራራላቸው ይመራቸዋል
ያህዌ ስለ ራሱ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ይናገራል። ሕዝቡን መጠበቁና ለእርሱንም መንከባከቡ እረኛቸው እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምራራላቸው እኔ፣ እመራቸዋለሁ››
ተራሮቼን ሁሉ መንገድ አደርጋለሁ፤ ጐዳናዎቼንም አስተካክላለሁ
ሕዝቡን በሰላም መምራቱና ከመንገዳቸውም እንቅፋቶችን ማስወገዱ፣ ተራሮቹን መንገድ ጐዳናዎቹንም ማስተካከል ማለት እንደሆነ ያህዌ ይናገራል።
Isaiah 49:12
የሲኒም ምድር
ይህ ቦታ የት እንደሆነ አይታወቅም፤ ግን ከግብፅ ደቡብ ያለውን አካባቢ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።
ሰማያት ሆይ፣ እልል በሉ፤ ምድር ሆይ ደስ ይበልሽ!
ኢሳይያስ ትኩረቱን ከእስራኤል ሕዝብ ላይ አንሥቶ ሰዎች የሆኑ ይመስል ለሰማያትና ለምድር እንዲሁም ለተራሮች ይናገራል።
Isaiah 49:14
ጽዮን ግን... አለች
ጽዮን የኢየሩሳሌም ሌላ ስም ነው። ከተማዋ እግዚአብሔር ትቶኛል በማለት እንደምታማርር ሴት እንደሆነች ኢሳይያስ ይናገራል።
እናት የምታጠባውን ልጇን መርሳት ትችላለችን? ለወለደችውስ አትራራለትምን?
እርሱ በፍጹም እንደማይረሳቸውና ለእነርሱ ማሰቡንም እንደማያቆም መረዳት እንዲችሉ ለመርዳት ያህል እነዚህ ጥያቄዎች አቅርቧል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናት የምታጠባውን ልጇን መርሳት አትችልም፤ ለወለደችው መራራትዋንም አትተውም››
Isaiah 49:16
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለጽዮን መናገር ቀጥሏል።
በእጄ መዳፍ ላይ ቀርጬሻለሁ
ለጽዮን ያለውን የማይለወጥ ፍቅር ለማሳየት ያህዌ እርሷን በእጁ መዳፍ ላይ መቅረጹን ይናገራል።
ቅጥሮችሽ ሁሌም በፊቴ ናቸው
ቅጥሮቿ ሁሌም በፊቱ ያሉ ያህል እርሱ ሁሌም ለጽዮን እንደሚያስብ ያህዌ ይናገራል። ‹‹ቅጥሮች›› የከተማዋ ምሳሌ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምንጊዜም ስለ ቅጥሮችሽ አስባለሁ›› ወይም፣ ‹‹ምንጊዜም ስለ አንቺ አስባለሁ››
ልጆችሽ ፈጥነው ይመለሳሉ
በኢየሩሳሌም ለመኖር ስለሚመለሰው ሕዝብ ያህዌ ሲናገር፣ እነርሱ የከተማዋ ልጆች እንደሆኑ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፈራዎችሽ ፈጥነው ይመለሳሉ››
እኔ ሕያው እንደሆንሁ
የሚናገረው እውነት እንደሆነ ለማስረገጥ ያህዌ የሚጠቀምበት መሐላ ነው።
ይህ የያህዌ ዐዋጅ ነው
የሚናገረው እውነት መሆኑን ለማስረገጥ ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ያወጀው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ዐውጃለሁ››
እንደ ጌጥ ትለብሻቸዋለሽ፤ እንደ ሙሽራ ትጐናጸፊያቸዋለሽ
የጽዮን ነዋሪዎች ውበትና ደስታዋን ለማሳየት ከተማዋ የምትለብሳቸው ጌጥ እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።
እንደ ሙሽራ ትጐናጸፊያቸዋለሽ
ቀደም ሲል ከነበረው መስመር የሐረጉን መጨረሻ ክፍል መረዳት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሙሽራ ጌጥ እንደምትለብስ አንቺም ትለብሻቸዋለሽ››
Isaiah 49:19
አጠቃላይ መረጃ
ሴት የሆነች ይመስል ያህዌ ለጽዮን መናገር ቀጥሏል።
ባድማና ጠፍ ብትሆኚም
‹‹ባድማ›› እና፣ ‹‹ጠፍ›› የተሰኙት ቃሎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው፤ ጠላት ጽዮንን እንደደመሰሰና ባዶዋን እንደ ተዋት አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምንም እንኳ ጨርሶ ጠፍ የነበርሽ ቢሆንም››
የዋጡሽ
ጽዮንን የደመሰሰ ጠላት እርሷን ውጦ እንደ ነበር ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንቺን የዋጡ ሰዎች››
በሐዘንሽ ዘመን የወለድሻቸው ልጆች
የኢየሩሳሌም ሕዝብ በምርኮ በነበሩ ዘመን ከተማዋ ለልጆቿ ሐዘን ላይ እንደ ነበረች ሴት መሆንዋን ያህዌ ይናገራል። ሕዝቡ በምርኮ በነበረ ጊዜ የተወለዱ የከተማዋ ልጆች እንደሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡ በምርኮ በነበሩ ጊዜ የተወለዱ ልጆች የሚኖሩብሽ››
ቦታው ጠብቦናል
ይህም ማለት ሕዝቡ በጣም ብዙ ከመሆኑ የተነሣ መኖሪያ ለመሆን ከተማዋ ታንሣለች ማለት ነው።
Isaiah 49:21
አጠቃላይ መረጃ
ሴት የሆነች ይመስል ያህዌ ለጽዮን መናገር ቀጥሏል።
እነዚህን የወለደልኝ ማን ነው?
እዚያ ለመኖር ስለሚመለሱ ሰዎች ስትናገር ሕዝቡ ልጆቿ እንደሆኑ ጽዮን ትናገራላችሁ። ጥያቄው ብዙ ልጆች ስላሏት ጽዮን መደነቋን ያሳያል።
ሐዘንተኛና መካን፣ የተሰደደሁና የተፈታሁ ነበርሁ
ስለ ራሷ ስትናገር ጽዮን ብዙ ልጆች መውለድ እንደማትችል ሴት እንደ ነበረች ትናገራለች። በጣም የተደነቀችውም ለዚህ እንደ ነበር ትገልጻለች።
ሐዘንተኛና መካን ነበርሁ
‹‹በሞቱት ልጆቼና ከእንግዲህም መወለድ ባለ መቻሌ እያዘንሁ ነበር››
የተሰደደሁና የተፈታሁ
‹‹ተሰድጄ ነበር፤ ባል አልነበረኝም››
እነዚህን ልጆች ማን አሳደጋልኝ፤ ብቸኛ ነበርሁ፤ እነዚህ ከየት መጡ?
መደነቋን ለማሳየት እንደ ገና ጽዮን ጥያቄዎች ታነሣለች። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነሆ፣ ብቸኛ ነበርሁ፤ አሁን ግን እኔ ያላሳደግሁቸው እነዚህ ልጆች ሁሉ ወደ እኔ መጡ››
Isaiah 49:22
አጠቃላይ መረጃ
ሴት የነበረች ይመስል ያህዌ ለጽዮን መናገር ቀጥሏል። ብዙ ልጆች ሊኖሩዋት እንደ ቻለ ይናገራል።
እጆቼን ለአሕዛብ አነሣለሁ፤ ለሰዎችም የምልክት ባንዲራ ከፍ አደርጋለሁ
እነዚህ ሁለት አነጋገሮች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በየአገሩ ያሉ ሰዎች እንዲመጡ እጆቼንና የምልክት ባንዲራን አነሣለሁ››
ወንዶች ልጆችሽን በእቅፋቸው፣ ሴቶች ልጆችሽን በትከሻቸው ያመጧቸዋል
በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች የከተማዋ ልጆች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል። እስራኤላውያንን ታቅፈው የሌላ አገር ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚያመጡዋቸውም ይናገራል።
Isaiah 49:23
አጠቃላይ መረጃ
ሴት የሆነች ይመስል ያህዌ ለጽዮን መናገር ቀጥሏል።
ነገሥታት አሳዳጊ አባቶችሽ፣ እቴጌዎቻቸው ሞግዚቶችሽ ይሆናሉ
በጽዮን የሚኖሩ ሰዎች የከተማ ልጆች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል። ‹‹አሳዳጊ አባቶች›› እና፣ ‹‹ሞግዚቶች›› የተሰኙት ቃሎች ለልጆቹ የመንከባከብን ኃላፊነት የሚወስዱ ወንዶችና ሴቶችን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሌላ አገር ነገሥታትና እቴጌዎች ለነዋሪዎችሽ የሚያስፈልገውን ያቀርባሉ››
በግንባራቸው ተደፍተው ይሰግዱልሻል፤ የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ
እነዚህ ሐረጐች ሰዎች ለበላያቸው ፍጹም ተገዢ መሆናቸውን የሚያሳዩባቸው ሁኔታዎች ናቸው።
የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ
ይህም ማለት፣ 1) ቃል በቃል አንድ ሰው የበላዩ እግር ላይ ያለ ትቢያን እንደሚልስ ያመለክታል ወይም 2) አንድ ሰው የበላዩ ፊት በአክብሮት እጅ መንሣቱን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።
አያፍሩም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እፍረት አያደርባቸውም›› ወይም፣ ‹‹ተስፋ አይቆርጡም››
Isaiah 49:24
አጠቃላይ መረጃ
በሴት ጾታ ያህዌ ለጽዮን መናገር ቀጥሏል።
ከተዋጊ ብዝበዛ ማስጣል፤ ከጨካኝስ ምርኮኞችን ማዳን ይቻላልን?
ኢሳይያስ ጥያቄዎቹን ያቀረበው ከብርቱ ወታደር ወይም ጦረኛ አንድን ነገር መውሰድ አስቸጋሪ መሆኑን ለማመልከት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንድ ሰው ከተዋጊ ብዝበዛ ማስጣል ወይም ከብርቱ ተዋጊ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ምርኮኞችን ማዳን አይችልም››
ብዝበዛ
በጦርነት ከተሸነፉ የሚወሰዱ ጠቃሚ ነገሮች
ከተዋጊች ምርኮኞችን ይወሰዳሉ፤ ከጨካኞችም ምርኮ ይበዘበዛል
ይህዌ ያልተለመዱ ነገሮችን ሕዝቡ እንደሚያደርግ ይናገራል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከተዋጊው ምርኮኞችን እወስዳለሁ፤ ብዝበዛዎችንም እነጥቃለሁ››
ልጆችሽን አድናለሁ
በጽዮን የሚኖሩ ሰዎች የከተማዋ ልጆች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል።
Isaiah 49:26
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ እንደ ሰው ለጽዮን መናገር ቀጥሏል።
አስጨናቂዎችሽን የራሳቸውን ሥጋ አስበላቸዋለሁ
ይህም ማለት፣ 1) አስጨናቂዎቹ በጣም ስለሚርባቸው የሞቱ ወዳጆቻቸውን ሥጋ ይበላሉ ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አስጨናቂዎችሽ የራሳቸውን ሥጋ እንዲበሉ አደርጋለሁ›› ወይም 2) ጨቋኞቹ እርስ በርስ እንደሚጠፋፉ ያህዌ እየተናገረ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የገዛ ሥጋቸውን የሚበሉ ይመስል አስጨናቂዎች እርስ በርስ ይጠፋፋሉ››
እንደ ወይን ጠጅ በገዛ ራሳቸው ደም ይሰክራሉ
ይህም ማለት፣ 1) አስጨናቂዎቹ በጣም ስለሚጠሙ የሞቱ ወዳጆቻቸውን ደም ይጠጣሉ ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የወዳጆቻቸውን ደም ይጠጣሉ። በወይን ጠጅ እንደ ሰከረ ሰው ይደክማሉ›› ወይም 2) አስጨናቂዎቹ የራሳቸውን ደም የሚጠጡ ይመስል እርስ በርስ ይጠፋፋሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በወይን ጠጅ የሰከሩ ይመስል የብዙ ወጃጆቻቸውን ደም ያፈስሳሉ››

---

## Chapter 50

### Isaiah 50:1
እናታችሁን የፈታሁበት የፍቺ ወረቀት የታለ?
ከተማዋ እዚያ የነበሩ ሰዎች እናት እንደ ነበረችና ወደ ምርኮ የሰደደቻቸው ከባልዋ የተፋታች ሴት እንደሆነች ያህዌ ስለ ጽዮን ይናገራል።
እናታችሁን የፈታሁበት የፍቺ ወረቀት የታለ?
ያህዌ ይህን ጥያቄ ያቀረበው እነርሱን ወደ ምርኮ የሰደደበት ምክንያት እንዲሆን ሕዝቡ ‹‹የፍቺውን ወረቀት›› እንዲያቀርቡ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናታችሁን የፈታሁበትን የፍቺ ወረቀት አሳዩኝ››
እናንተን የሸጥኋችሁ ለየትኛው አበዳሪ ነው?
የተሸጡ ይመስል ሕዝቡን ወደ ምርኮ እንደ ሰደደ ያህዌ ይናገራል።
እናንተን የሸጥኋችሁ ለየትኛው አበዳሪ ነው?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው የማንም ዕዳ ስለሌለበት እነርሱን አለመሸጡን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ሰዎቹ ግን እንደዚያ አስበው የነበሩ ይመስላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የማንም ዕዳ ስለሌለብኝ እናንተን አልሸጥሁም››
ስለ ኀጢአታችሁ ተሸጣችኋል፤ ስለ መተላለፋችሁም እናታችሁ ተፈትታለች
ያህዌ ሕዝቡን ወደ ምርኮ የሰደደበትን ምክንያት ይናገራል፤ እነርሱ የተሸጡትና እናታቸውም የተፈታችው በዚህ ምክንያት ነበር። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለ ኀጢአታችሁ ሸጥኋችሁ፤ ስለ መተላለፋችሁም እናታችሁን ፈታሁ››

### Isaiah 50:2
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
እኔ ስመጣ ማንም ያልነበረው ለምንድነው? ስጣራ መልስ የሚሰጥ ያልነበረው ለምንድነው?
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። ሕዝቡ በምርኮ የተወሰዱት እርሱ እነርሱን ለማዳን ፈቃደኛ ባለ መሆኑ ሳይሆን፣ መልስ ስላልሰጡት መሆኑን ያህዌ አጽንዖት ሰጥቶ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ስመጣ እዚያ መኖር ሲገባችሁ አልነበራችሁም፤ ስጣራ መመለስ ነበረባችሁ ግን አልመለሳችሁም›› ወይም፣ ‹‹ልናገራችሁ ስመጣ ምላሽ አልሰጣችሁኝም››
እናንተን ለማዳን እጄ አጭር ናትን? ልታደጋችሁ ኀይል የለኝምን?
እነርሱን ለማዳን ዐቅም እንደሌለው በማሰባቸው ሕዝቡን ለመገሠጽ ያህዌ ሁለት ጥያቄዎች አቅርቧል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተን ለማዳን እጄ በእርግጥ አጭር አይደለችም፤ እናንተን ለመታደግ ኀይል አለኝ›› ወይም፣ ‹‹እናንተን ከጠላቶቻችሁ ለማዳን በእርግጥ ኀይል አለኝ››
እጄ አጭር ናትን?
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጄ›› የያህዌን ኀይል ይወክላል። ያህዌ ዐቅም ከሌለው እጁ አጥራለች ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ በቂ ኀይል የለኝምን?››
ልታደጋችሁስ ኀይል የለኝምን
‹‹እኔ ኀይል የለኝምን?››
ወንዞቹን ምድረ በዳ አደርጋለሁ
ያህዌ ወንዞቹን ማድረቁ እነርሱን ምድረ በዳ ማድረጉ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወንዞቹን እንደ ምድረ በዳ ደረቅ አደርጋለሁ››
ዓሣዎቹም ውሃ በማጣት ሞተው ይገማሉ
‹‹ውሃ ከማጣታቸው የተነሣ ዓሣዎቹ ይሞታሉ፣ ይገማሉ›› - ‹‹የእነርሱ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ባሕሮችና ወንዞችን ነው።
ሰማዩን ጨለማ አለብሰዋለሁ፤ በማቅ እሸፍነዋለሁ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ማቅ የሚያለብሰው ይመስል ሰማዩን ጨለማ እንደሚያደርገው ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥቁር ጨርቅ የለበሰ ይመስል ሰማዩን ጨለማ አደርገዋለሁ።››

### Isaiah 50:4
አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ መናገር ጀምሯል
ጌታ ያህዌ የተማሩትን አንደበት ሰጥቶኛል
‹‹አንደበት›› መናገርን ይወክላል። ይህም ማለት፣ 1) በማስተዋል መናገርን እንደ ተማረ ሰው መናገርን ያህዌ አስችሎኛል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታ ያህዌ አስተዋይ ተናጋሪ አደረገኝ›› ወይም፣ 2) ያህዌ መናገር ያለብኝን አስተማረኝ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታ ያህዌ ያስተማረኝን መናገር አስቻለኝ››
ጆሮዬ እንድትሰማ ያነቃል
‹‹ጆሮዬ›› የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን አገልጋይ ነው። ያህዌ እንዲሰማና እንዲያስተውል እርሱን ማስቻሉ ጆሮውን ከእንቅልፍ ማንቃት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ የሚናገረውን መረዳት አስቻለኝ››
በመማር ላይ እንዳለ ተማሪ
አገልጋዩን ራሱን ከአስተማሪ መናገርን ከሚማር ተማሪ ጋር ያመሳስላል። ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ከአስተማሪው እንደሚማር›› ወይም 2) ‹‹እርሱ እንዳስተማረው››

### Isaiah 50:5
አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል።
ጌታ ያህዌ ጆሮዬን ከፍቷል
ያህዌ አገልጋዩን እንዲሰማና እንዲያስተውል መርዳቱ ጆሮውን መክፈት ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጌታ ያህዌ እንድሰማና እንዳስተውል ረዳኝ››
ዐመፀኛ አልነበርሁም፤ ጀርባዬንም አላዞርሁም
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ያህዌ ለሚናገረው አለመታዘዝ እርሱ ላይ ጀርባ ማዞር እንደሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ለሚናገረው ታዘዝሁ››
ጀርባዬን ለሚገርፉኝ፣ ጢሜን ለሚነጩ ጉንጬን ሰጠሁ
ሰዎች እንዲገርፉትና ጢሙን እንዲነጩ መፍቀድ ጀርባውንና ጉንጩን ለእነርሱ መስጠት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ጀርባዬን እንዲገርፉኝ፣ ከጉንጬ ላይ ጢሜን እንዲነጩ ፈቀድሁ››
ፊቴን ከውርደትና ከትፋት አልሰወርሁም
ፊትን መሰወር ለራስ መከላከል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሲያፌዙብኝና ሲተፉብኝ ለራሴ አልተከላከልሁም››

### Isaiah 50:7
አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል።
ስለዚህ አልዋረድም
ምንም እንኳ በደል ቢፈጸምበትም ለያህዌ በመታዘዙ አይዋረድም። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህም አላፍርም››
ፊቴን እንደ ባልጩት ድንጋይ አድርጌአለሁ
‹‹ፊቴን›› የሚለው የሚያመለክተው ባርያውን ነው። ባርያው ለያህዌ ለመታዘዝ መቁረጡ ፊቱን እንደ ባልጩት ድንጋይ ማድረግ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ

ትርጉም፣ ‹‹በፍጹም ቆርጫለሁ››
እንደማላፍር አውቃለሁ
የያህዌ ባርያ የወደ ፊቱን በተስፋ ይመለከታል፤ በያህዌ ጥሪ ይተማመናል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቼ እንዳፍር ማድረግ እንደማይችሉ አውቃለሁ››
Isaiah 50:8
አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል
የሚቃወመኝ ማን ነው? እንጋጠም?... ከሳሼስ ማን ነው? እስቲ ይምጣ
የያህዌ ባርያ እነዚህን ጥያቄዎች የሚያቀርበው በኀጢአት ሊከሰሰው የሚችል እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚቃወመኝ ካለ ይገጠመኝ፤ ...የሚከስሰኝ ካለ፣ ይምጣ››
የሚፈርድብኝስ ማን አለ?
የያህዌ ባርያ ይህን የሚጠይቀው የሚፈርድበት እንደሌላ ለማስረገጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔን በደለኛ ነህ የሚለኝ የለም››
እንደ ልብስ ያረጃሉ፤ ብልም ይበላቸዋል
የያህዌን ባርያ የሚከሰስ ሰው አለመቅረቱ ከሳሾቹ እንደ ልብስ እንዳረጁና ብልም እንደ በላቸው መሆኑ ተነግሯል።
Isaiah 50:10
አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
ከእናንተ መካከል ያህዌን የሚፈራ ማን ነው? ለባርያው ድምፅ የሚታዘዝ ማነው? ብርሃን በሌለበት ድቅድቅ ጨለማ የሚመላለስ ማን ነው ከሆነ... በአምላኩ
የያህዌ ባርያ ጥያቄዎቹን ያቀረበው ከሚናገራቸው ጋር ለመተባበር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእናንተ መካከል ያህዌን የሚፈራ፣ ለባርያው ድምፅ የሚታዘዝ፣ ግን ብርሃን በሌለበት ድቅድቅ ጨለማ የሚመላለስ ሰው ካለ... በአምላኩ››
ለባርያው ድምፅ የሚታዘዝ
‹‹ድምፅ›› የሚወክለው የያህዌ ባርያ የሚናገረውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለባርያው የሚታዘዝ››
ብርሃን በሌለበት ድቅድቅ ጨለማ የሚመላለስ
መከራ ውስጥ ያሉና ዐቅመ ቢስ የሆኑ ሰዎች በጣም ጨለማ በሆነ ቦታ እንደሚመላለስ ሰው እንደሆኑ የያህዌ ባርያ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መከራ ውስጥ ያለ ዐቅመ ቢስ››
በያህዌ ስም ይታመን በአምላኩም ይደገፍ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ‹‹ስም›› የሚያመለክተው ያህዌ ራሱን ነው። በእግዚአብሔር መታመን በእርሱ መደገፍ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በአምላኩ በያህዌ ይታመን››
Isaiah 50:11
እሳት አንድዳችሁ... የሚንቦገቦግ ችቦ የያዛችሁ ሁሉ
ይህ በጨለማ እየተመላለሱ እንደሆነ ባለፈው ቁጥር የተነገረው ምሳሌ ቀጣይ ነው። በያህዌ ከመታመን ይልቅ በራሳቸው ጥበብ ለመታመን የሚሞክሩ ሰዎች በጨለማው ውስጥ ማየት እንዲያስችላቸው የራሳቸውን እሳት አንድደው ችቦ እንደያዙ ሰዎች እንደሆኑ ተነግሯል።
በሥቃይ ትጋደማላችሁ
‹‹መጋደም›› የሚያመለክተው መሞትን ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ መሞት በሥቃይ መጋደም ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በታላቅ ሥቃይ ትሞታላችሁ››

---

Chapter 51
Isaiah 51:1
እኔን ስሙ
‹‹እኔን›› የሚለው ያህዌን ያመለክታል።
ወደ ዐለቱ... የወጣችሁበትንም ጉድጓድ ተመልከቱ
አንድን ነገር መመልከት ስለዚያ ነገር ማሰብን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለ ዐለቱ.. ስለ ወጣችሁበት ጉድጓድ አስቡ››
ተቆርጣችሁ የወጣችሁበትን ዐለት፣ ተቆፍራችሁ የወጣችሁበትንም ጉድጓድ ተመልከቱ
እግዚአብሔር ስለ እስራኤል ሕዝብ ሲናገር፣ ከድንጋይ የተሠራ ሕንፃ እንደሆኑና የጥንት አባቶቻቸውም እግዚአብሔር እነርሱን የቆረጠበት ዐለት ወይም ጉድጓድ እንደሆኑ ይናገራል። ይህን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጥንት አባቶቻችሁ ተቆርጣችሁ እንደ ወጣችሁበት ዐለት፣ ተቆፍራችሁም እንደወጣችሁበት ጉድጓድ ናቸው››
ተቆርጣችሁ የወጣችሁበት ዓለት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ቆርጬ ያወጣኋችሁ ዐለት››
መሮ
‹‹በመሮ መቁረጥ›› ወይም፣ ‹‹መቆፈር››
የተቆፈራችሁበት ጉድጓድ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ እናንተን የቆፈርሁበት ጉድጓድ››
Isaiah 51:2
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
አባታችሁ፣ አብርሃም
እግዚአብሔር የጥንት ዝርያዎቻቸው አባት እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጥንት አባታችሁ አብርሃም›› ወይም፣ ‹‹የዘር ግንዳችሁ አብርሃም››
የወለደቻችሁ ሣራ
የአብርሃም ሚስት ሣራ እነርሱን የወለደች እናት እንደሆነች እግዚአብሔር ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዘር ግንዳችሁ የሆነች የአብርሃም ሚስት ሣራ››
ብቻውን በነበረ ጊዜ
ይህ ማለት ምንም ልጅ ሳይኖረው ማለት ነው። ይህን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምንም ልጅ በሌለው ጊዜ››
አበዛሁት
የአብርሃም ዘሮች መብዛት የአብርሃም መብዛት እንደሆነ እግዚአብሔር ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዘሮቹን አበዛሁ›› ወይም፣ ‹‹ብዙ ዘሮች እንዲኖሩት አደረግሁ››
Isaiah 51:3
ያህዌ ጽዮንን ያጽናናታል
ኢየሩሳሌም ተብላ የምትጠራው የጽዮን ከተማ እዚህ ላይ የጽዮንን ሕዝብ ትወክላለች። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የጽዮንን ሕዝብ ያጽናናል››
የፈራረሱ ቦታዎቿን ያጽናናል
‹‹የፈራረሱ ቦታዎች›› በእነዚያ ጠፍ ቦታዎች የሚኖረውን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፈራረሱ ቦታዎቿ የሚኖረውን ሕዝብ ያጽናናል››
የፈራረሱ ቦታዎቿ... ምድረ በዳዎቿ... በረሓ መስኮቿ
‹‹እርሷ›› የሚለው ጽዮንን ያመላክታል። ብዙውን ጊዜ ከተሞች በሴት ጾታ ያጠራሉ።
የፈራረሱ ቦታዎች
የወደሙ ቦታዎች ማለት ነው
ምድ በዳዋን፣ በረሓ መስኮቿን እንደ ዔደን፣... እንደ እግዚአብሔር ተክል ቦታ ያደርጋል
እነዚህ ሐረጐች በእስራኤል ያሉ ባዶ ቦታዎችን እግዚአብሔር ውብ እንደሚያደርግ ይናገራሉ። ትንቢቶቹ ወደ ፊት የሚሆኑት ነገሮች ባለፈው ጊዜ እንደ ተደረጉ ተነግሯል። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው በእርግጥ እንደሚፈጸም ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምድረ በዳውን በረሓ፣ መስኮቿን እንደ ዔደን... እንደ እግዚአብሔር ተክል ቦታ ያደርጋል።››
ተድላና ደስታ በውስጧ ይገኛል
ተድላና ደስታ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። እዚያ ይገኛል ማለት እዚያ ይሆናል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተድላና ደስታ እንደ ገና በጽዮን ይሆናል››
Isaiah 51:4
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።
ስሙኝ... አድምጡኝ
እነዚህ ሁለት ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። በአንድነት ሲሆኑ እንዲሰሙ የተሰጠውን ትእዛዝ ያጠናክራሉ።
ፍርዴም ለሕዝቦች ብርሃን ይሆናል
ፍርድ የእግዚአብሔርን ሕግ ይወክላል፤ ብርሃን ደግሞ እውነት የሆነውን ማወቅን ይወክላል። ይህም ማለት ሕዝቦች የእግዚአብሔርን ሕግ ያውቃሉ፤ ይታዘዛሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እውነት የሆነውን ለሕዝቦች አስተምራለሁ›› ወይም፣ ‹‹ሕዝቦች ሕጌን ያውቃሉ››

ጽድቄ ቀርቦአል
‹‹ቀርቦአል›› የሚለው ሐሳብ፣ ‹‹ደርሶአል›› ማለት ነው። የእግዚአብሔር ጽድቅ ቀርቦአል ማለት በቅርቡ ጽድቁን ይገልጣል ማለት ነው። ይህንንም የሚያደርገው ተስፋውን በመፈጸምና ሰዎችን በማዳን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በቅርቡ ጽድቄን አሳያለሁ››
ማዳኔም እየወጣ ነው
የእርሱ ማዳን ወደ እነርሱ እየወጣ ያለ ነገር እንደሆነ እግዚአብሔር ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝብን አድናለሁ››
ክንዴ በሕዝቦች ላይ ይፈርዳል
የእግዚአብሔር ክንድ ኀይሉን ይወክላል፤ ፍርዱ መግዛትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኀይሌ ሕዝቦችን እገዛለሁ››
ደሴቶች
ይህ የሚያመለክተው ከባሕር ማዶ ሩቅ አገር ደሴቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በደሴቶች የሚኖሩ ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ከባሕሩ ማዶ ባለው ምድር የሚኖሩ ሰዎች››
ክንዴንም በተስፋ ይጠብቃሉ
የእግዚአብሔር ክንድ እርሱ የሚያደርገውን ይወክላል። እዚህ ላይ ሰዎችን ማዳኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንዳች ነገር እንዳደርግ በተስፋ ይጠብቃሉ›› ወይም፣ ‹‹እንዳድናቸው በተስፋ ይጠባበቃሉ››

## Isaiah 51:6

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ዐይኖቻችሁን ወደ ሰማይ አንሡ
ዐይኖችን ማንሣት ከላይ ያለ ነገር ማየትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ ሰማይ እዩ››
እንደ ጢስ... እንደ ልብስ... እንደ አሸን
እነዚህ ሁሉ ቶሎ የሚጠፉ ጥቅም የለሽ ነገሮችን ያመለክታሉ።
ማዳኔ ግን ለዘላለም ይኖራል
እዚህ ላይ፣ የእግዚአብሔር፣ ‹‹ማዳን›› የማዳኑን ውጤት ነጻነትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አድናችኋለሁ እናንተም ለዘላለም ነጻ ትሆናላችሁ››
ጽድቄም መጨረሻ የለውም
የእግዚአብሔር ጽድቅ በጽድቅ መግዛቱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ የጽድቅ አገዛዜ መጨረሻ የለውም›› ወይም፣ ‹‹በጽድቅ ለዘላለም እገዛለሁ››

## Isaiah 51:7

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
ሕጌን በልባችሁ ያኖራችሁ
የእግዚአብሔርን ሕግ በልብ ማኖር የእግዚአብሔርን ሕግ ማወቅንና ለመታዘዝ መፈለግን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕጌን የምታውቁና የምታከብሩ››
ሰዎች ሲበድሏችሁ ተስፋ አትቁረጡ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሲበድሏችሁ ልባችሁ አይዛል››
ብል እንደ ልብስ ይበላቸዋል፤ ትል እንደ በግ ጠጉር ያነክታቸዋል
ጻድቃንን የሚበድሉ ሰዎች እንደ ልብስ ብል እንደሚበላቸው፤ እንደ በግ ጠጉር ትል እንደሚያነክታቸው እግዚአብሔር ይናገራል።
ጽድቄ ለዘላለም ይኖራል
የእግዚአብሔር ጽድቅ በጽድቅ መግዛቱን፣ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጽድቅ ግዛቴ ለዘላለም ነው›› ወይም፣ ‹‹ለዘላለም በጽድቅ እገዛለሁ››
ማዳኔም ከትውልድ እስከ ትውልድ ነው
የእግዚአብሔር ማዳን የማዳኑን ውጤት ነጻነትን ይወክላል። ‹‹ከትውልድ እስከ ትውልድ›› ለዘላለም መኖርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አድናችኋለሁ፣ እናንተም ለዘላለም ነጻ ትሆናላችሁ››

## Isaiah 51:9

የያህዌ ክንድ ሆይ ተነሥ፣ ተነሥ ኀይልህንም ልበስ
የእርሱ ክንድ ሰው የሆነ ይመስል ሰዎች የያህዌ ክንድ በፍጥነት እንዲረዳቸው ይጠይቃሉ። ለክንድ መናገር ያልተለመደ ከሆነ በቀጥታ ለያህዌ እንዲናገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ሆይ፣ ተነሥ፣ ተነሥ ኀይልህንም ልበስ››
የያህዌ ክንድ ሆይ... ተነሥ
እየረዳቸው ስላልነበረ ሰዎች የያህዌ ክንድ ከእንቅልፍ እንዲነሣ ይጠይቃሉ።
‹‹የያህዌ ክንድ›› ያህዌን በተለይም ሰዎችን መርዳቱን ይወክላል። ‹‹ተነሥ›› የሚለው ቃል የተደገመው ሰዎቹ ያህዌ ቶሎ እንዲረዳቸው አጥብቀው መፈለጋቸውን ለማሳየት ነው።
ኀይልህንም ልበስ
ኀይል በጦርነት ጊዜ ብርታት እንዲሆናቸው የሚለበስ ልብስ እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራስህን አበርታ››
ረዓብን የቆራረጥህ፣ ታላቁን ዘንዶ የወጋህ አንተ አይደለህምን?
ተናጋሪው የያህዌ ኀይል ታላቅ ነገር እንዲያደርግ አጽንዖት ለመስጠት በጥያቄዎች ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ ረዓብን የቆራረጥህ፣ ታላቁን ዘንዶ የወጋህ›› ረዓብ ባሕር ውስጥ የሚኖር እባብ ነው። ረዓብ የግብፅን መንግሥት ወይም ክፋትና ሁከት ይወክላል።
የዳኑት እንዲሻገሩ... ባሕሩን ያደረቅህ አንተ አይደለህምን?
የያህዌ ኀይል ታላቅ ነገር እንዲያደርግ አጽንዖት ለመስጠት ተናጋሪው እንደ ገና በጥያቄዎች ይጠቀማል። ይህ የሚያመለክተው እስራኤላውያን በዚያ ውስጥ ተሻግረው ከግብፃውያን ሰራዊት እንዲያመልጡ ያህዌ ቀይ ባሕርን መክፈሉን ነው።

## Isaiah 51:11

አጠቃላይ መረጃ
ይህ ከኢሳይያስ 38፥10 ጋር በጣም ይመሳሰላል።
ያህዌ የተቤዣቸው
‹‹መቤዠት›› ማለት፣ ‹‹መታደግ›› ማለት ነው። ይህ የሚያመለክተው ያህዌ የታደጋቸውን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የታደጋቸው››
ደስታ ለዘላለም ራሳቸው ላይ ይሆናል
የሰው ራስ የሰው ሁለንተና ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለዘላለም ደስ ይሰኛሉ››
ተድላና ደስታ... ሐዘንና ልቅሶ
እንደ፣ ‹‹ሐዘን›› እና ‹‹ልቅሶ›› ሁሉ፣ ‹‹ተድላ›› እና ‹‹ደስታ›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው። በአንድነት ሲሆኑ እነዚህ ስሜቶች ምን ያህል ብርቱ እንደሆኑ አጽንዖት ይሰጣሉ።
ተድላና ደስታ ያጥለቀልቃቸዋል
ይህ የሚያመለክተው እንደ ብርቱ ወንዝ ተድላና ደስታ ሕዝቡን እንደሚያጥለቀልቁ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በተድላና በደስታ ይዋጣሉ›› ወይም፣ እጅግ ደስ ይላቸዋል ሐሤትም ያደርጋሉ››
ሐዘንና ልቅሶም ከእነርሱ ይሸሻሉ
እነዚህ ስሜቶች ሸሽተው የሚያመልጡ ይመስል ሕዝቡ ከእንግዲህ ሐዘንና ልቅሶ እንደማይገጥመው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ አያዝኑም አያለቅሱም››

## Isaiah 51:12

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
እኔ፣ እኔ፣ እርሱ ነኝ
‹‹እኔ›› የሚለው የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። በቋንቋህ ይህ ያልተለመደ ከሆነ ድግግሙን መተው ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ እርሱ ነኝ››
እንደ ሣር የሆኑ ሰዎችን... ለምን ትፈራለህ?
ጥያቄው የቀረበው የጌታ ጥበቃ ያላቸው ሰዎችን መፍራት እንደሌለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ሣር የሆኑትን ሰዎች... አትፍሩ››
እንደ ሣር የሆነውን
የሰው ሕይወት አጭር መሆኑንና ቶሎ እንደሚሞት አጽንዖት ለመስጠት ሰዎችን ከሣር ጋር ይመሳስላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ሣር ኖረው በፍጥነት የሚሞቱትን›› ወይም ‹‹እንደ ሣር ጠውልገው ቶሎ የሚጠፉትን››
እንደ... የሆኑትን
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ... የሆኑ››

## Isaiah 51:13

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ያህዌን ለምን ረሳህ... ምድርን?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው እርሱን መርሳት እንደሌለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን መርሳት አልነበረብህም... ምድር››


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የፈጠረህን

ኢሳይያስ 17፥7 ላይ ይህን የያህዌን ስም እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ሰማያትን የዘረጋውን

‹‹ሰማያትን መዘርጋት›› አንድ ሰው ትልቅ ልብስ በሚዘረጋበት ሁኔታ እርሱም ሰማያትን የዘረጋ ይመስል ያህዌ ሰማያትን እንደ ፈጠረ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰማያትን እንደ ልብስ የዘረጋውን››

የምድር መሠረቶች

በተለምዶ መሠረት ከታች ሆኖ ሕንፃውን የሚደግፍ የድንጋይ ሥራ ነው። እዚህም ላይ ምድርን በቦታዋ የያዘና የቆመ መሠረት ነው ተብሎ ይታሰብ እንደ ነበር ያመለክታል። ኢሳይያስ 24፥18 ላይ ይህን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ለማጥፋት የወሰነ የጨቋኙ

‹‹ለማጥፋት የተዘጋጀ፤ የጨቋኙ ጽኑ ቁጣ››

ጽኑ ቁጣ

‹‹ጽኑ›› ማለት ‹‹ብርቱ›› ወይም ‹‹ታላቅ›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታላቅ ቁጣ››

የጨቋኙ ቁጣ የት አለ?

ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ሕዝቡ ጨቋኞችን መፍራት እንደሌለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ጨቋኞቹ ይህን ያህል አስፈሪዎች አይደሉም። ይህን በዐረፍተ ነገር መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጨቋኙ ቁጣ ያን ያህል አስፈሪ አይደለም››

Isaiah 51:14

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ዐንገታቸውን የደፉ

ይህ የሚያመለክተው የባቢሎናውያን ባርያዎች የነበሩትን እስራኤላውያን ነው። ይህ ሐረግ እንዴት ይሠሩ እንደ ነበር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባርያዎቹ››

ጥልቁ

ይህ የሚያመለክተው ሲኦልን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሲኦል ጥልቅ›› ወይም ‹‹መቃብር››

እንጀራም አይጐድልበትም

‹‹እንጀራ›› ጠቅላላ ምግብን ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምግብ አያጣም››

ባሕሩን የማማሰል

ይህ የሚያመለክተው አንድ ትልቅ ጐድጓዳ ሳህን ውስጥ ያለውን በማማሰያ እንደማማሰል ያህዌ ማዕበሉን ወደ ፊትና ወደ ኃላ፣ ወደ ላይና ወደ ታች የሚያደርገው መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባሕሩን የሚያማስለው›› ወይም፣ ‹‹ባሕሩን ወደ ላይ ወደ ታች የሚያደርገው››

ማዕበሉ እንዲያጓራ

ማጓራት ድብን ወይም አንበሳን ከመሳሰሉ በሕይወት ካሉ ነገሮች የሚወጣ ኀይለኛ፣ ጫኺ ድምፅ ነው። እዚህ ላይ ማዕበሉ ተመሳሳይ ድምፅ እንደሚያወጣ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማዕበሉ በጩኸት ይላተማል››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ

ኢሳይያስ 1፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 51:16

ቃሌን በአፍህ አኖርሁ

ይህ የሚናገረው ቃሉ አንዳች ቁሳዊ ነገር ይመስል፣ ኢሳይያስ አፍ ውስጥ በማኖር ያህዌ ለኢሳይያስ ምን ማለት እንዳለበት የነገረው መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምን እንደምትል ነግሬሃለሁ››

በእጄ ጥላ ጋረድሁህ

የያህዌ፣ ‹‹እጅ›› ኀይሉን ያመለክታል። እርሱን ለመጠበቅ እጁ የሸፈነው ይመስል ያህዌ ኢሳይያስን እንደሚጠብቀው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀይሌ ጠብቆሃል›› ወይም፣ ‹‹ጋረድሁህ፤ በሰላምም ጠበቅሁህ››

ሰማያትን የተከልሁ

‹‹መትከል›› አንድን ነገር መሬት ውስጥ ማኖር ማለት ነው። እዚህ ያህዌ ሰማያትን ማጽናቱ፣ ሰማያት እርሱ የሚዘረጋው ድንኳን እንደሆኑና በካስማ አጥብቆ የተከላቸው መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰማያትን አጸናሁ››

ምድርን መሠረትሁ

በተለምዶ፣ ‹‹መሠረት›› ማለት ሕንፃውን ደግፎ የሚይዝ ከበታቹ ያለ የድንጋይ ሥራ ነው። እዚህም ላይ ምድርን በቦታዋ የሚይዝ ተመሳሳይ ዐይነት ነገር እንደሆነ ተነግሯል። ኢሳይያስ 24፥18 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 51:17

ተነሺ ተነሺ ኢየሩሳሌም ሆይ ቁሚ

ኢየሩሳሌም እዚያ የሚኖረውን ሕዝብ ትወክላለች። ያህዌ የኢየሩሳሌም ሕዝብ እዚያ ሆነው እንደሚሰሙ አድርጐ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተነሡ፣ ተነሡ፣ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ንቁ››

ተነሺ፣ ተነሺ፣ ቁሚ

‹‹ንቂ፣ ተነሺ›› ተነሺ የሚለው ቃል መደገሙ የእስራኤል ሕዝብ እንዲነሣ የቀረበው ጥሪ አስቸኳይ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ቃል በቃል እነርሱን ከእንቅልፍ የሚቀሰቅስ ጥሪ አይደለም።

ከያህዌ እጅ የጠጣሽ... የሚያንገደግደውን ዋንጫ ጭላጭ የጨለጥሽ።

ያህዌ ሕዝቡን መቅጣቱ፤ በቁጣው ከሞላውን ዋንጫ ለመጠጣት መገደድ መሆኑ ተነግሯል። ከቁጣው ዋንጫ ከጠጡ በኃላ ብዙ ወይን ጠጅ ጠጥቶ እንደ ሰከረ ሰው ይንገዳገዳሉ።

ዝቃጭ

ዝቃጭ የሚባለው ፈሳሽ ሥር የሚቀር ጠጣሩ ነገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዝቃጩ እንኳ ሳይቀር››

ከያህዌ እጅ

ዋንጫውን ለሕዝቡ የሚሰጠው እርሱ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት እዚህ ላይ የያህዌ እጅ የሚያመለክተው ያህዌ ራሱን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ የሰጣችሁን››

ከሚያንገዳግድ ዋንጫ

‹‹በወይን ጠጅ እንደ ሰከረ ሰው እንድትንገዳገዱ ከሚያደርግ ዋንጫ››

መንገዳገድ

ቀጥ ብሎ አለመሄድ፣ ሲራመዱ መሰናከል

የመራት አልነበረም... እጇን ይዞ የወሰዳት... አልነበረም

ሁለቱ ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት በመሆናቸው መዋሐድ ይችላሉ። ይህ የሚያመለክተው ከተማዋ እንደ ሰከረች፣ እጇንም ይዞ የሚመራ እንደሌላት ሴት ኢየሩሳሌምም ዐቅመ ቢስ መሆንዋን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚረዳሽ የለም! እጇን ይዞ የሚመራት ልጅ እንደሌላት ሰካራም ሴት ነሽ››

Isaiah 51:19

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

የሚያዝንልሽ ማነው? የሚያጽናናሽ ማነው?

ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው የሚያዝንላቸው ወይም የሚያጽናናቸው አለመኖሩን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ጥያቄዎቹን ዐረፍተ ነገር ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚያዝልሽ የለም… የሚያጽናናሽ የለም››

እነዚህ ሁለት መዓቶች

ሁለቱ ‹‹መዓቶች›› የተባሉት፣ ‹‹መፈራረስና ጥፋት››፣ ‹‹ራብና ሰይፍ›› ናቸው።

መፈራረስና ጥፋት

እነዚህ ሁለት ቃሎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የጠላት ሰራዊት ምድሪቱን እንደሚያጠፋ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቻችሁ ምድራችሁን ባዶና ጠፍ አድርገዋል››

ራብና ሰይፍ

‹‹ራብ›› እና፣ ‹‹ሰይፍ›› በሕዝቡ ላይ የሚመጣውን መዓት ያመለክታሉ። ‹‹ሰይፍ›› ጦርነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ብዙዎቻችሁ›› በራብና በጦርነት ትሞታላችሁ››

በየጐዳናው ጥግ ተጋድመዋል

ይህ አጠቃላይ አነጋገር ነው። ብዙዎች በየጐዳናው ጥግ ይጋደማሉ ሲባል ሁሉም ማለት አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መንገዱ ላይ ይጋደማሉ››

በወጥመድ እንደ ተያዘ ሚዳቋ

ይህ የሚያመለክተው በወጥመድ እንደ ተያዘ ሚዳቋ ሕፃናት በጣም መድከማቸውንና ዐቅመ ቢስ መሆናቸውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በወጥመድ እንደ ተያዘ ሚዳቋ ዐቅመ ቢስ ሆነዋል›› ወይም፣ ‹‹ወጥመድ እንደ ያዘው ሚዳቋ ዐቅመ ቢስ››

ሚዳቋ

ይህ አጋዘን የሚመስል፣ ቀንድ ያለውና በፍጥነት የሚሮጥ እንስሳ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አጋዘን››

በያህዌ ቁጣ በአምላካችሁ ተግሣጽ ተሞልተዋል።

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የያህዌ፣ ‹‹ቁጣ›› እነርሱን ስለ ተቆጣ ያህዌ ሕዝቡን መቅጣቱን ያመለክታል። ይህ የሚያመለክተው በያህዌ ቁጣ የተሞሉ ያህል ሕዝቡ ክፉኛ መቀጣታቸውን ነው። ‹‹ተግሣጽ›› የሚለውን ቃል ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ስለ ተቆጣቸውና ስለ ገሠጻቸው ያህዌ ክፉኛ ቀጣቸው››

Isaiah 51:21

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

አንቺ የተጐዳሽ፣ የሰከርሽ

ያህዌ፣ ‹‹አንቺ›› የሚለው የተጐዳውን ሕዝብ ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንት የተጐዳችሁና የሰከራችሁ ሕዝብ››

ያለ ወይን ጠጅ የሰከርሽ

ከያህዌ ቁጣ ዋንጫ እንዲጠጡ በመገደድ እንደ ሰከሩ ሁሉ፣ ከመከራቸው ብዛት የተነሣ እንደ ሰካራም ስለሆኑ ሰዎች ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያህዌን ቁጣ ዋንጫ ጠጥታችሁ የሰከራችሁ›› ወይም፣ ‹‹በደረሰባችሁ ከባድ መከራ እንደ ሰካራም የሆናችሁ››

እነሆ፣ የሚያንገደግደውን ዋንጫ፣ የቁጣዬ ዋንጫ የሆነውን ጽዋ ከእጅሽ ወስጃለሁ፤ ከእንግዲህ

ቁጣው ከእነርሱ ያራቀው ዋንጫ ይመስል፣ ከእንዲህ ያህዌ በሕዝቡ እንደማይቆጣ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ በአንቺ ላይ አልቆጣም፤ ያንገዳገደሽን ጽዋ፣ ቁጣዬ የሞላበትን ዋንጫ ከአንቺ ወስጃለሁ››

እነሆ

ይህ ጥቅም ላይ የዋለው ቀጥሎ ለሚናገረው የአድማጮችን ትኩረት ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አድምጡ››

የሚያንገደግድ ዋንጫ

‹‹ዋንጫ›› የሚለው ዋንጫው ውስጥ ያለውን ለማመልከት ነው። ኢሳይያስ 51፥17 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝብን የሚያንገደግድ የወይን ጠጅ ዋንጫ››

የቁጣዬ ዋንጫ የሆነው ጽዋ

ያህዌ በቁጣው ከተሞላው ጽዋ እንዲጠጡ ያስገደደ ያህል ሕዝቡን እንደቀጣ ይናገራል። ኢሳይያስ 51፥17 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በቁጣዬ የተሞላ ጽዋ›› ወይም፣ ‹‹ቁጣዬ የሞላበት ዋንጫ››

Isaiah 51:23

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

በአስጨነቁሽ እጅ አደርገዋለሁ

በቁጣው የሞላውን ዋንጫ እንዲጠጡ ያስገደዳቸው ያህል ያህዌ ጠላቶቻቸውን እንደሚቀጣ ይናገራል።

በአስጨነቁሽ እጅ አደርገዋለሁ

ዋንጫው እጃቸው ላይ እንዲሆን በማድረግ ዋንጫው ውስጥ ካለው እንዲጠጡ ያህዌ ያስገድዳቸዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶችህን ከቁጣዬ ጽዋ ወይን ጠጅ እንዲጠጡ አስገድዳለሁ››

አስጨናቂዎችሽ

አስጨናቂዎች የሚለውን ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንቺን ያስጨነቁ›› ወይም፣ ‹‹መከራ ያደረሱብሽ››

እንድንራመድበት ጀርባሽን እንደ መሬት፣ እንደ መንገድ አድርጊልን

ጠላቶቻቸው በጀርባቸው መረማመዳቸውን መንገድ ላይ ከመራመድ ጋር ያመሳስለዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶችሽ በጀርባሽ እንዲረማመዱ መንገድ ላይ ተጋደሚ››

---

Chapter 52

Isaiah 52:1

ተነሺ ተነሺ

x

Isaiah 52:2

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

ትቢያሽን አራግፊ፣ ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ተነሺ፣ ተቀመጪ

‹‹ኢየሩሳሌም›› የምትወክለው እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኢየሩሳሌም ሰዎች፣ ትቢያችሁን አራግፉ፣ ተነሡ፣ ተቀመጡ››

ምርኮኛዪቱ፣ የዐንገትሽን እስራት አውልቀሽ ጣዪ

በባቢሎን ምርኮኞች በነበሩ ዘመን የኢየሩሳሌም ሰዎች አንገታቸው ላይ ሰንሰለት አድርገው እንደ ነበር ተመልክቶአል። ዐረፍተ ነገሩን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

የጽዮን ሴት ልጅ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። የከተማዋ፣ ‹‹ሴት ልጅ›› የከተማዋ ሕዝብ ማለት ነው። ኢሳይያስ 1፥8 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጽዮን ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹በጽዮን የምትኖሩ ሰዎች››

ያለ ዋጋ ተሸጣችሁ ነበር፤ ያለ ገንዘብ ትቤዣላችሁ

ይህ የሚያመለክተው የእስራኤል ሕዝብ ባለቤት ያህዌ መሆኑን ነው። እውነተኛ ባለቤት እንደ መሆኑ እርሱ በወደደ ጊዜ ሊሸጣቸው ወይም መልሶ ሊወስዳቸው መብት አለው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያለ ዋጋ ሸጥኋችሁ፤ ያለ ገንዘብ እቤዣችኋለሁ››

Isaiah 52:4

በመጀመሪያ

እዚህ ላይ፣ ‹‹በመጀመሪያ›› የእስራኤል ታሪክ የተጀመረበትንና ሕዝብ የሆኑበትን ጊዜ ያመለክታል።

ወደ ግብፅ... ወረደ

‹‹ወደ ግብፅ... ሄደ›› ከከነዓን ወደ ግብፅ ሲጓዙ፣ ‹‹ወረደ›› ማለት የተለመደ ነበር።

አሦር አስጨነቀው

‹‹አሦር›› የሚያመለክተው የአሦርን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሦር ሕዝብ ግፍ አደረገበት››

Isaiah 52:5

አሁን እዚህ ምን አለኝ... ሕዝቤ ያለ ምክንያት ተወስዷል?

ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ሕዝቡ የሚናገረውን ልብ እንዲሉ ነው። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አሁን የሆነውን ተመልከቱ... ሕዝቤ ያለ ምክንያት ተወስዷል››

ያህዌ እንዲህ ይላል

የሚናገረውን እርግጠኝነት ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

ሕዝቤ ያለ ዋጋ መወሰዱን ሳይ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላት ሕዝቤን ያለ ዋጋ ሲወስደው አየሁ››

ያለ ዋጋ

ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ያለ ዋጋ›› ማለት ባቢሎናውያን ሕዝቡን የወሰዱት በግፍ ወይም ያለ ምክንያት ነበር ማለት ነው፤ ወይም 2) ያህዌ የእስራኤል ሕዝብ ባለቤት መሆኑና ያለ ዋጋ ሊሸጣቸው ወይም ሊገዛቸው መብት እንዳለው የሚናገረው የኢሳይያስ 52፥3 ላይ ያለው ቀጣይ ሊሆን ይችላል።

የገዟቸው ተላልቀውባቸዋል

ይህ የሚያመለክተው ሕዝቡን ድል ያደረጉትን ባቢሎናውያንን ነው። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ቅጂዎች፣ ‹‹የገዟቸው ያለቅሳሉ›› ይላሉ። በእነዚህ ቅጂዎች መሠረት ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው በምርኮ የነበሩ እስራኤላውያንን ይመሩ የነበሩ ሰዎች ነው።

ስሜ ቀኑን ሙሉ ያለ ማቋረጥ ይሰደባል

እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የያህዌን ማንነት ይወክላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላት ሕዝቡን ሲወስድ የሚመለከቱ ስለ እኔ ያለ ማቋረጥ ክፉ ይናገራሉ››

ስለዚህ ሕዝቤ ስሜን ያውቃል

እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የያህዌን ማንነት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ ሕዝቤ በእውነት እኔ ማን መሆኔን ያውቃሉ››

Isaiah 52:7

አጠቃላይ መረጃ

ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።

መልካም ዜና ይዘው የሚመጡ መልእክተኛ እግሮች በተራሮች ላይ ምንኛ ያማሩ ናቸው

እዚህ ላይ፣ ‹‹እግሮች›› እየተራመደ ያለውን መልእክተኛ ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መልካሙን ዜና ለመናገር በተራሮች ላይ የሚመጣውን መልእክተኛ ማየት በጣም ያማረ ነው››

ለጽዮን
እዚህ ላይ ‹‹ጽዮን፣›› የጽዮንን ሕዝብ ትወክላለች። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የጽዮን ሕዝብ››
ድምፃቸውን ያነሣሉ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይጮኻሉ››
ዐይን ሁሉ
‹‹ዐይን›› መላውን ሰው ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እያንዳንዳቸው››
Isaiah 52:9
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
የኢየሩሳሌም ፍርስራሾች
ኢሳይያስ የኢየሩሳሌም ፍርስራሾች ደስ የሚሰኙ ሰዎች እንደሆኑ አድርጐ ይናገራል። ይህ ተሸንፈው የነበሩ የኢየሩሳሌምን ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኢየሩሳሌም ፍርስራሽ መካከል የምትኖሩ ሰዎች››
ኢየሩሳሌምን ተቤዥቶአልና
‹‹ኢየሩሳሌም›› ሕዝቡን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ተቤዥቶአል››
የተቀደሰ ክንዱን ይገልጣል
‹‹ክንድ›› የያህዌን ኀይል ይወክላል። ያህዌ ቅዱስና ኀያል መሆኑን ለሕዝቡ ማሳየቱ እንደ አንድ ጦረኛ ካባውን አውልቆ ክንዱን በመግለጥ ለጦርነት መዘጋጀት መሆኑ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቅድስናውንና ብርቱ ኀይሉን አሳየ››
ሕዝቦች ሁሉ፣ ምድር ሁሉ
‹‹ሕዝቦች›› እና፣ ‹‹ምድር›› በምድር ሁሉ ያሉ አገሮች ሕዝቦችን ይወክላሉ።
Isaiah 52:11
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ተለዩ፣ ተለዩ
ይህ ቃል የተደገመው ምንም እንኳ ወዲያው ባይሆንም ሕዝቡ በእርግጥ መለየት እንዳለባቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው።
ከዚያ ውጡ
የእስራኤል ሕዝብ በባቢሎን ባርያዎች እንደ ነበሩ ይታወቃል። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባርያዎች ከሆናችሁበት ምድር ውጡ።
ርኩሱንም አትንኩ
መነካት ወይም መበላት እንደሌለበት ያህዌ የተናገረለት ነገር ንጹሕ እንዳልሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የማይወደውን አትንኩ››
ከመካከልዋ ውጡ
‹‹እርሷ›› ባቢሎንን ይወክላል።
ያህዌ ፊት ፊታችሁ ይሄዳል፤ የእስራኤል አምላክ ደጀን ይሆንላችኋል
ያህዌ ሕዝቡን ከጠላቶቻቸው መጠበቁ እርሱ ፊት ፊታቸው የሚሄድ፣ እነርሱን ለመጠበቅ ከሕዝቡ ኋላ እንዳለ ጦረኛ እንደሆነ ተነግሯል።
Isaiah 52:13
ገናና ይሆናል፤ ከፍ ከፍ ይላል፤ እጅግ ይከብራል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ገናና ይሆናል›› — ‹‹ከፍ ከፍ ይላል›› — ‹‹ይከብራል›› የተሰኙት ቃሎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ቢሆኑም፣ ያህዌ ባርያውን እንደሚያከብር አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢሳይያስ 33፥10 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለባርያዬ ከፍ ያለውን ክብር እሰጠዋለሁ››
በአንተ ደንግጠዋል
‹‹አንተ›› የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን ባርያ ነው። ይሁን እንጂ፣ ተርጓሚዎች ‹‹አንተ›› የሚለውን፣ ‹‹እርሱ›› ማለት ይችላሉ።
መልኩ ከማንም ሰው የተለየ ጐስቆለ
የያህዌ ባርያ መልክ የጐሰቆለው ጠላቶቹ ክፉኛ ስለ ደበደቡት ነው። የዚህን የተሟላ ትርጉም የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶቹ ክፉኛ ስለ ደበደቡት የሰው ልጅ እንኳ አይመስልም››
Isaiah 52:15
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ባርያው መናገር ቀጥሏል
ባርያዬ ብዙ ሕዝቦችን ይረጫል
ሰዎች በያህዌ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማድረግ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ሰዎችን በመሥዋዕቱ ደም የሚረጭ ካህን እንደሆነ ተደርጐ ተነግሯል።
ይረጫል
እዚህ ላይ ‹‹ይረጫል›› ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል፣ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች እንዳደረጉት፣ ‹‹ያስደንቃል›› ወይም፣ ‹‹ያስገርማል›› ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።
ብዙ ሕዝቦች
‹‹ሕዝቦች›› የየአገሩን ሰዎች ይወክላሉ።
ነገሥታት አፋቸውን ይዘጋሉ
‹‹አፋቸውን ይዘጋሉ›› ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነገሥታት ማውራታቸውን ያቆማሉ›› ወይም፣ ‹‹ነገሥታት ዝም ይላሉ››
ያልተነገራቸው
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም ያልነገራቸው›› ወይም፣ ‹‹ማንም ያልነገራቸውን ነገር››

---

Chapter 53
Isaiah 53:1
አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ ኢሳይያስ ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን ባለፈው ጊዜ እንደ ተፈጸሙ አድርጐ ይናገራል። ይህ በእርግጥ እንደሚሆን አጽንዖት ይሰጣል።
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል።
ከእኛ የሰሙትን ያመነ ማን ነው?
ኢሳይያስ የተረዳው በጣም አስገራሚ በመሆኑ ምርኮኞቹ ያምኑ እንደሆነ ይጠይቃል። ‹‹እኛ›› የሚለው እርሱንና በምርኮ ያሉትን ይጨምራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኛ የሰማነውን ማመን በጣም ከባድ ነው››
የያህዌስ ክንድ ለማን ተገለጠ?
ክንድ የእግዚአብሔርን ኀይል ያመለክታል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ኀይሉን ለሕዝቡ ገለጠ››
እርሱ በያህዌ ፊት እንደ ቡቃያ አደገ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እርሱ›› ኢሳይያስ ከቡቃያ ጋር የሚያመሳስለው የእግዚአብሔርን ባርያ ያመለክታል። ይህም እንደ ደካማ መገለጡ ያመለክታል።
ከደረቅም መሬት
‹‹ደረቅ መሬት›› ተክል የማያድግበት ጠንካራ መሬት ሲሆን፣ የያህዌ ባርያ የሚመጣበትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፍጹም ከማይታሰብ ሁኔታ››
Isaiah 53:3
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል። (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)
በሰዎች የተናቀና የተጠላ ነበር
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች እንደ ከንቱ ነገር ቆጥረው ናቁት››
የሐዘን ሰው
‹‹ማንኛውንም ሐዘን የሚያውቅ ሰው››
ሰዎች ፊታቸውን የሚሰወሩበት
‹‹ፊት›› የሰውን ትኩረትና ኅብረት ይወክላል። ፊትን መሰወር ፊትን ማዞር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ፊታቸውን የሚያዞሩበት››
የተናቀ ነበር
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምንም ጥቅም እንደሌለው ቆጠሩት››
Isaiah 53:4
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)
ደዌያችንን ወሰዶ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ
‹‹መሸከም›› እንደ ሕመምና ሐዘን ሁሉ የነገር ስም ሲሆን፣ መውሰድን ይወክላል። ‹‹አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕመማችንና ደዌያችንን በራሱ ወሰዶ››
እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደ ተቀጣ፣ እንደ ተመታ፣ እንደ ተሠቃየም ቆጠርነው

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር እየቀጣውና እያሠቃየው እንደሆነ ቆጠርን››
Isaiah 53:5
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)
እርሱ ግን ስለ ክፉ ተግባራችን ተወጋ፣ ስለ ኀጢአታችንም ደቀቀ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ አጽንዖት የሚሰጡት የያህዌ ባርያ ያን ሁሉ መከራ የተቀበለው ስለ ሰዎች ኀጢአት መሆኑን ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእኛ ኀጢአት የተነሣ ጠላት እንዲወጋውና እንዲገድለው እግዚአብሔር ፈቀደ››
የሰላማችን ቅጣት እርሱ ላይ ነበረ
ይህ የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን ነው። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኛ በስምምነት እንድንኖር እርሱ ይህን ቅጣት ተቀበለ››
በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእርሱ ስቃይና ቁስል ፈወሰን››
Isaiah 53:6
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)
እኛ ሁላችን እንደ በግ ተቅበዘበዝን
በጎች ብዙ ጊዜ እረኛው እነርሱን ከሚመራበት መንገድ ይወጣሉ። ኢሳይያስ ይህን ሲል እግዚአብሔር ካዘዘው ይልቅ፣ እኛ የወደድነውን እናደርጋለን ማለቱ ነው።
የሁላችንም ርኩሰት
እዚህ ላይ፣ ‹‹ርኩሰት›› የኀጢአታችንን በደል ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሁላችንም ኀጢአት በደል››
Isaiah 53:7
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)
ተጨነቀ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ግፍ አደረጉበት››
አፉን አልከፈተም
‹‹አፍ›› ሰው የሚናገረውን ይወክላል። አፍን መክፈት መናገር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አልተቃወመም››
ለዕርድ እንደሚነዳ ጠቦት፣ በሸላቾቹ ፊት ዝም እንደሚል በግ
ሰዎች ሲጐዱትና ሲያዋርዱት ዝም ማለቱን አጽንዖት ለመስጠት ኢሳይያስ የያህዌን ባርያ ከጠቦትና ከበግ ጋር ያመሳስለዋል።
ለዕርድ እንደሚነዳ በግ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰው ሲያርደው ዝም እንደሚል ጠቦት››
Isaiah 53:8
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)
በማስጨነቅና በፍርድ ተወገዘ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ማስጨነቅ›› የሚለውን አንዳንድ ቅጂዎች ‹‹በእስራት›› ብለውታል። እንደ እነዚህ ቅጂዎች ከሆነ፣ የያህዌ ባርያ ይታሠራል፣ ከዚያም ይፈረድበታል፣ ይወገዛል ማለት ነው።
ከዚያ ትውልድ ስለ እርሱ የሚያስብ ማን ነው?
ጥያቄው አጽንዖት የሚሰጠው ስለ እርሱ የሚያስብ አለመኖሩን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእርሱ ትውልድ እርሱ ላይ ለሆነው የሚያስብ የለም›› ወይም፣ ‹‹በዘመኑ ከነበሩ ሰዎች መካከል እርሱ ላይ ስለ ሆነው የሚያስብ የለም።››
ከዚያ ትውልድ ስለ እርሱ የሚያስብ ማን ነው?
ይህን የዕብራይስጥ ምንባብ ብዙ ቅጂዎች በተለያየ መንገድ ተርጉመውታል። ‹‹ስለ ዘሮች የሚናገር ማን ነው?›› ወይም፣ ‹‹ስለ ዕጣ ፈንታው የሚናገር ማን ነው?››
እርሱ ግን ከሕያዋን ምድር ተቆረጠ
‹‹መቆረጥ›› መሞት ማለት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ ግን ሞተ›› ወይም፣ ‹‹ግን ሞት ወሰደው››
ስለ ሕዝቤ
‹‹ስለ እስራኤል ሕዝብ››
በአፉ ምንም ተንኰል አልተገኘም
‹‹አፍ›› ሰው የሚናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በንግግሩ ማንንም አላታለለም››
Isaiah 53:10
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ስለ ያህዌ ባርያ መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 53፥1-2 ይመ.)
ዘሩን ያያል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዘሩ›› ማለት ከባርያው መሥዋዕት የተነሣ ያህዌ ይቅር ያላቸውን ሰዎች ነው።
ዕድሜውም ይረዝማል
ይህ የሚናገረው ብዙ ዘመን እንደሚኖር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ባርያውን እንደ ገና እንዲኖር ያደርጋል››
የያህዌ ዓላማ በእርሱ ይከናውናል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ በባርያው በኩል ዓላማውን ያከናውናል››
ከሕይወቱ ስቃይ በኋላ
‹‹ሕይወቱ›› የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን ባርያ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያህዌ ባርያ መከራ ከተቀበለ በኋላ››
ብርሃን ያያል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ብርሃን›› የሚለው ሕይወትን እንደሆነ ብዙ ቅጂዎች ይገነዘባሉ። ይህም ባርያው እንደ ገና ይኖራል ማለት ነው።
ጻድቅ ባርያዬ
እዚህ ላይ፣ ‹‹የእኔ›› የሚለው ያህዌ ነው።
ርኩሰታቸውን ይሸከማል
‹‹ይሸከማል›› ማለት፣ ይወስዳል ማለት ነው። ይህም ማለት፣ 1) ‹‹ርኩሰታቸው›› የኀጢአታቸውን ቅጣት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቅጣታቸውን ይወሰድዳል›› ወይም፣ ‹‹ለኀጠአታቸው ይቀጣል›› ወይም 2) ‹‹ርኩሰታቸው›› በደልን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በደላቸውን በራሱ ይወስዳል›› ወይም፣ ‹‹ለኀጢአታቸው በደለኛ ይሆናል።››
Isaiah 53:12
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ባርያው መናገር ቀጥሏል።
ስለዚህ ድርሻውን ከታላላቆች ጋር እሰጠዋለሁ፤ ምርኮውንም ከብዙዎች ጋር ይከፋፈላል
ሁለቱም ሐረጐች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ‹‹ድርሻ›› እና ‹‹ምርኮ›› ጦርነት በድል ከተጠናቀቀ በኋላ አንድ ንጉሥ የተዘረፈውን መካፈል ወይም ለወታደሮች መሸለምን ያመለክታሉ። ይህም ማለት ከመሥዋዕቱ የተነሣ ያህዌ ባርያውን እጅግ ያከብረዋል ማለት ነው።
ብዙዎች
ብዙ ቅጂዎች ይህን፣ ‹‹አያሌ›› ወይም፣ ‹‹ብርቱዎች›› በማለት ተርጉመዋል።
ራሱን ለሞት ስላጋለጠ
‹‹መጋለጥ›› ምቹ መሆን ወይም ያለ ምንም ከለላ ማለት ነው። የያህዌ ባርያ ራሱን የሚሞትበት ሁኔታ ውስጥ አኖረ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፈቃደኝነት ለሞት መጋለጥን ተቀበለ››
ከሕግ ተላላፊዎች ጋር ተቆጠረ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች እንደ ወንጀለኛ እንዲቆጥሩት ፈቀደ››

Chapter 54
Isaiah 54:1
አንቺ መካን ሴት… ያላገባች ሴት ልጆች
እንደ ገና በኢየሩሳሌም ብዙ ሰዎች ስለሚኖሩ ደስ እንዲላቸው ያህዌ ለሕዝቡ ይናገራል። ይህንን በተመለከተ ያላገባች ሴት ብዙ ልጆች ይኖሩዋታል ማለት መሆኑን ያህዌ ይናገራል።
አንቺ ልጅ ወልደሽ የማታውቂ ዘምሪ፣ እልል በዪ፤ በደስታ ጩኺ
ይህ ከመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ጋር ተመሳሳይ ነው።
የተተወችው ሴት ልጆች በዝተዋልና


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ወደ ፊት የሚሆነው ነገር ባለፈው ጊዜ እንደ ተፈጸመ ተደርጐ ተነግሯል። ይህም ነገሩ በእርግጥ እንደሚሆን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተተወችው ሴት ልጆች እጅግ ብዙ ይሆናሉ››

የተተወችው

እዚህ ላይ፣ ‹‹የተተወችው›› ማለት ባልዋ የናቃትና የተዋት ሴት ማለት ነው።

Isaiah 54:2

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

ድንኳንሽን አስፊ… ካስማሽንም አጠንክሪ

ይህ ኢሳይያስ 54፥1 ላይ የጀመረው ምሳሌ ቀጣይ ነው። ሕዝባቸው እጅግ ስለሚበዛ እንዲዘጋጁ ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሰዎች ይናገራል፤ የሕዝባቸው መብዛት ለብዙ ልጆች የሚበቃ ክፍል እንዲኖር ድንኳንዋን እንድታሰፋ ይናገራል።

ትስፋፊያለሽ

እዚህ ላይ፣ ‹‹አንቺ›› ነጠላ ቁጥር ሲሆን፣ መካን ስለሆነች ሴት ያመለክታል። እርሷ የሚለው ራስዋን ዘሮችዋን ሁሉ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንቺና ዘሮችሽ ትስፋፋላችሁ››

ሕዝቦችን ያሸንፉሉ

‹‹ሕዝቦች›› ሰዎችን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሌላ አገር ሕዝቦችን ያሸንፋሉ››

Isaiah 54:4

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

የወጣትነት ሐፍረትና የመተውሽንም ውርደት ትረሺዋለሽ

ጠላቶቻቸው ሲያሸንፏቸው የተሰማቸው ሐፍረት ከእንግዲህ እንደማይሰማቸው ያህዌ ለሕዝቡ ይናገራል፤ ይህም ልጅ ባለመውለድዋና ባልዋ ስለ ተዋት እፍረት ከተሰማት ሴት ጋር ተመሳስሎአል።

Isaiah 54:5

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

ፈጣሪሽ ባልሽ ነው

ያህዌ ሕዝቡን መወደዱና መጠንቀቁ እርሱ ባላቸው እንደሆነ ተነግሯል።

ፈጣሪሽ

ይህን ኢሳይያስ 17፥7 እንደ ተረጐምህ ተርጉመው።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ

ይህን ኢሳይያስ 1፥24 እንደ ተረጐምህ ተርጉመው

የእስራኤል ቅዱስ

ይህን ኢሳይያስ 5፥16 እንደ ተረጐምህ ተርጉመው

የሚቤዥሽ

ይህን ኢሳይያስ 41፥14 እንደ ተረጐምህ ተርጉመው።

የምድር ሁሉ አምላክ ይባላል

ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱ የምድር ሁሉ አምላክ ነው።››

ያህዌ እንደ ሚስት… በወጣትነትዋ እንዳገባችና እንደ ተተወች ሴት ጠርቶሻል

ያህዌ ሕዝቡ ወደ ምርኮ እንዲሄድና ተመልሶ እንዲመጣ ማድረጉ፣ እርሱ ሚስቱን ትቶ እንደ ነበር፣ አሁን ግን መልሶ እንደ ተቀበላት ባል እንደሆነ ተነግሯል።

በመንፈስ ማዘን

እዚህ ላይ፣ ‹‹መንፈስ›› የሰውን ውስጣዊ ማንነት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አዘነ›› ወይም፣ ‹‹ተከዘ››

Isaiah 54:7

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

በቁጣ ጐርፍ

የያህዌ በጣም መቆጣት ሕዝብን በሚያጥለቀልቅ ጐርፍ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም በተቆጣሁ ጊዜ››

ፊቴን ከአንቺ ሰወርሁ

‹‹ፊትን መሰወር›› ያህዌ ሕዝቡን መተዉንና እንዲሠቃዩ መፍቀዱን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተውሁሽ››

ነገር ግን በዘላለም ኪዳንና ታማኝነት

‹‹ታማኝነት›› የሚለውን ‹‹ታማኝ›› በማለት መተርጐም ይቻላል። ኢሳይያስ 16፥5 ላይ፣ ‹‹ኪዳናዊ ታማኝነት›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነገር ግን እኔ ከአንቺ ጋር ላደረግሁት ኪዳን ሁሌም ታማኝ ነኝ›› ወይም፣ ‹‹ቃል የገባቡልሽን ለመፈጸም እኔ ሁሌም ታማኝ ነኝ››

ይላል፣ ያህዌ ታዳጊሽ

እዚህ ላይ ያህዌ ስለ ራሱ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ይናገራል። በመጀመሪያ ሰው መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ታዳጊሽ ያህዌ ለአንቺ የተናገርሁት ይህን ነው››

Isaiah 54:9

የኖኅ ውሆች

ይህ በኖኅ ዘመን ያህዌ ያደረገውን ጐርፍ ያመለክታል።

ተራሮች ቢወድቁና ኮረብቶችም ቢናወጡ እኔ ለአንቺ ያለኝ ፍቅር

እነዚህ መስፈርቶች ቢሟሉ ኖሮ ምን ይሆን እንደ ነበር ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተራሮች ቢወድቁ፣ ኮረብቶችም ቢናወጡ ለአንቺ ያለኝ ፍቅር››

ኮረብቶችም ቢናወጡ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ኮረብቶች ይናወጡ ይሆናል››

ለአንቺ ያለኝ ፍቅር ግን ከአንቺ አይመለስም

ያህዌ ለሕዝቡ ያለው ቀጣይ ፍቅር፣ ከሕዝቡ በማይመለስ ነገር ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንቺን መውደዴን አልተውም››

የሰላሜም ኪዳን አይናወጥም

ያህዌ ከሕዝቡ ጋር ያለውን ኪዳን አለመሻሩ፣ ኪዳኑ የማይናወጥ ነገር እንደሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰላም ኪዳኔን አልሽርም›› ወይም፣ ‹‹በኪዳኔ በሰጠሁሽ ተስፋ መሠረት ሰላሜን በእርግጥ እሰጥሻለሁ››

የሚራራልሽ ያህዌ እንዲህ ይላል

እዚህ ላይ ያህዌ ስለ ራሱ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ይናገራል። በመጀመሪያ ሰው መግለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምራራልሽ እኔ ያህዌ የምለው ይህን ነው››

Isaiah 54:11

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።

የተጨነቅሽ

እዚህ ላይ ያህዌ የምትሰማው ይመስል ለኢየሩሳሌም ይናገራል። ኢየሩሳሌም እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ትወክላለች። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተ የተጨነቃችሁ የኢየሩሳሌም ሰዎች››

በዐውሎ ነፋስ የተወሰድሽ

ሕዝቡ በዐውሎ ነፋስና በማዕበል ተወስደውና ተጐድተው እንደ ነበር ያህዌ ይናገራል። ይህም በጣም የተጐዱና መረጋጋትም እንዳልነበራቸው ያመለክታል።

ያልተጽናናሽ

‹‹አጽናኝ የሌለሽ››

በሰንፔር ድንጋይ እመሠርትሻለሁ… በከበሩ ድንጋዮች አስጌጥሻለሁ

ያህዌ ኢየሩሳሌምን እንደሚመሠርትና ውብ እንደሚያደርጋት ባማሩ ቃላት ይናገራል። ምንም እንኳ የተጋነነ ቢመስልም ያህዌ በተናገረው መሠረት መተርጐም አለበት።

የሚያብረቀርቅ ዕንቁ… ሰንፔር… ቀይ ዕንቁ

እነዚህ ሁሉ የከበሩ ድንጋዮች ናቸው። የሚያብረቀርቅ ዕንቁ ነጣ ያለ ሰማያዊና አረንጓዴ ነው፤ ሰንፔር ጥቁር ሰማያዊ ነው፤ ቀይ ዕንቁ ቀይ ሐምራዊ ነው።

Isaiah 54:13

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል

ልጆችሽ ከያህዌ የተማሩ ይሆናሉ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ልጆችሽን ሁሉ ያስተምራል››

ከያህዌ

ያህዌ በሦስተኛ ሰው ደረጃ ስለ ራሱ ይናገራል። በመጀመሪያ ሰው ደረጃ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእኔ በያህዌ››

በጽድቅ ትመሠረቻለሽ

‹‹ጽድቅ›› የሚለውን የነገር ስም፣ ‹‹ትክክል›› በሚለው መተርጐም ይቻላል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ትክክል የሆነውን ስለምታደርጊ እኔ አበረታሻለሁ››

አጠገብሽ አይደርሱም



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በከተማው ወይም በውጪ ያለ ማንም ከእንግዲህ የኢየሩሳሌምን ነዋሪዎች አያስፈራቸውም።
Isaiah 54:15
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
መከራን የሚያራግብ
‹‹የሚያራግብ›› የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ‹‹ችግር የሚፈጥር›› ወይም፣ ‹‹የሚያውክሽ›› ማለት ነው።
ይሸነፋል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ‹‹ድል ታደርጊያቸዋለሽ›› ማለት ነው።
Isaiah 54:17
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
በአንቺ ላይ የተሠራ መሣሪያ ይከሽፋል
የጠላት ሐሳብ በያህዌ ሕዝብ ላይ አለመሳካቱ፣ እነርሱ ላይ የተሠራ መሣሪያ መክሸፍ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጠላቶች አንቺ ላይ መሣሪያ ያበጁ ይሆናል፤ ግን አያሸንፉሽም››
የያህዌ ባሪያዎች ርስት ይህ ነው
ለሚያገለግሉት ሰዎች ያህዌ የሚሰጠው ሽልማት ርስታቸው እንደሆነ ተነግሯል።
ይላል ያህዌ
የተናገረው እርግጥ መሆኑን ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 30፥1 ላይ ያለውን እንደ ተረጐምህ ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የተናገረው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ የተናገርሁት ይህን ነው››

---

Chapter 55
Isaiah 55:1
በኢሳይያስ በኩል ያህዌ በምርኮ ላሉ የኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል። አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ የሚበላና የሚጠጣ ነገር በነጻ እንደሚሰጥ፣ እርሱም ሕዝቡን በነጻ እንደሚባርክ ይናገራል።
ኑ… ኑ
ይህ ቃል መደገሙ የግብዣውን አጣዳፊነት ያመለክታል።
ወይን ጠጅና ወተት ያለ ገንዘብ፣ ያለ ዋጋ ግዙ
ብዙውን ጊዜ አንዳች ነገር ለመግዛት ማንም ገንዘብ መክፈል ያለበት እንደ መሆኑ መጠን፣ ይህ ዐረፍተ ነገር ስላቅ ይመስላል። ይህ አጽንዖት የሚሰጠው እነዚህን ነገሮች በነጻ ለመስጠት የያህዌን አስደናቂ ጸጋ ነው።
Isaiah 55:2
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
እንጀራ ባልሆነ ነገር ላይ ለምን ትመዝንላችሁ… በማያጠግብስ… ለምን ጉልበታችሁን ትጨርሳላችሁ?
ያህዌ ጥያቄዎቹን ያቀረበው ሕዝቡን ለመገሠጽ ነው። ከያህዌ ውጪ ደስታ ማግኘት የሚፈልጉ ሰዎች መብል ላልሆነ ነገር ገንዘብ ከማውጣትና ለማያጠግብ ነገር ጉልበትን ከመጨረስ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንጀራ ላልሆነ ነገር ገንዘብ ማውጣት የለባችሁም… ለማያጠግብ ነገር መሥራት የለባችሁም››
ብራችሁን ለምን ትመዝናላችሁ
ይህ የሚያመለክተው ለአንዳች ነገር ለመክፈል የብር ሳንቲሞችን መቁጠርን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ገንዘብ መክፈል››
እንጀራ ላልሆነ ነገር
እዚህ ላይ፣ ‹‹እንጀራ›› በአጠቃላይ ምግብን ይወክላል። ሰዎቹ ገንዘብ ያወጡ የነበረው ምግብ ላልሆነ ነገር ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምግብ ላልሆኑ ነገሮች››
መልካም የሆነውን ብሉ፣ በጮማ ደስ ይበላችሁ
በያህዌ በረከትና ደስታ የሚተማመኑ ሰዎች ደስ የሚያሰኛቸውን መልካም ምግብ እንደሚበሉ ሰዎች መሆናቸው ተነግሯል።
በጮማ
‹‹ጮማ›› ውስጡ ብዙ ስብ ያለው ሥጋ ሲሆን፣ መልካም ምግብን የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምርጥ በሆነ ምግብ››
Isaiah 55:3
ጆሮዋችሁን መልሱ
ልብ ብሎ መስማት ጆሮን መመለስ ማለት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልብ በሉ››
አድርጌዋለሁ
ይህም ማለት፣ 1) ባለፈው ጊዜ ያህዌ ለንጉሥ ዳዊት ያደረገውን ያመለክታል። ወይም 2) ያህዌ ከዳዊት ዘሮች በአንዱ የሚያደርገውን ያመለክታል።
Isaiah 55:5
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
Isaiah 55:6
ያህዌ በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርሱን ማግኘት በሚቻልበት ጊዜ ያህዌን ፈልጉት››
ክፉ መንገዱን ይተው
‹‹ክፉ›› የሚያመለክተው ክፉ ሰውን ነው። ከዚህ በፊት ይራመዱበት በነበረው መንገድ መራመድ እንደ ተወ ሰው፣ ክፉ ሰዎችም ከእንግዲህ ኀጢአት እንደማያደርጉ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉዎች አደፍራቸውን ይለውጡ››
በደለኛም ሐሳቡን
ግሡ ካለፈው ሐረግ ጋር የተያያዘ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀጢአተኛ ሰው ሐሳቡን ይተው››
ሐሳቡን
ይህም ማለት፣ 1) ‹‹አስተሳሰቡን›› ወይም 2) ‹‹ዕቅዱን››
ያዝንለታል
‹‹ያህዌ ያዝንለታል››
ወደ አምላካችን
ግሡ በዚህ ዐረፍተ ነገር የመጀመሪያ ሐረግ ውስጥ ይገኛል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወደ አምላካችን ይመለስ››
Isaiah 55:8
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ይላል ያህዌ
የሚናገረው እርግጥ መሆኑን ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የተናገረው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››
ሰማያት ከምድር ከፍ እንደሚሉ መንገዴ ከመንገዳችሁ፣ ሐሳቤም ከሐሳባችሁ ከፍ ያለ ነው።
እርሱ የሚያስበውና የሚያደርገው ሰዎች ከሚያስቡትና ከሚያደርጉት ሰማይ ከምድር ከፍ የሚለውን ያህል ከፍ ያለ ወይም የላቀ መሆኑን ያህዌ ይናገራል።
Isaiah 55:10
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ዝናብና በረዶ… እንደማይመለስ
ይህ የሚያመለክተው ዝናብና በረዶ እንደሚተንን ነው።
እንዲሁ ቃሌ… እኔ የላክሁትን ዓላማ ይፈጽማል
ቃሉ አንድ ነገር እንዲያደርግ እንደ ተላከ መልእክተኛ እንደሆነ ያህዌ ይናገራል።
ከአፌ የወጣ ቃሌ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አፍ›› ያህዌ ራሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ የምናገረው ቃል››
ወደ እኔ ባዶውን አይመለስም
እዚህ ላይ ቃሉ ወደ ያህዌ መመለሱ እርሱ የላከውን ሥራ ማከናወኑን ያመለክታል። ‹‹ባዶውን›› አይመለስም ማለት ሥራውን ሳይፈጽም አይቀርም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሥራውን መፈጸሙ አይቀርም››
Isaiah 55:12
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
በሰላም ትመራላችሁ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሰላም እመራችኃለሁ››

ተራሮችና ኮረብቶች በፊታችሁ በእልልታ ይዘምራሉ፤ የሜዳ ዛፎች ሁሉ ያጨበጭባሉ

ተራሮችና ኮረብቶች ድምፅና እጆች እንዳሉዋቸው ሰዎች ያህዌ ሕዝቡን ሲታደግ ደስ እንደሚላቸው ያህዌ ይናገራል።

በእሾኽ ፈንታ የጥድ ዛፍ፣ በኩርንችት ፈንታ ባርሰነት ይበቅላል

‹‹እሾኽ›› እና ‹‹ኩርንችት›› የሚዋጋ እሾኽ ያላቸው ተክሎችን ያመለክታሉ። ‹‹የጥድ ዛፍ›› እና፣ ‹‹ባርሰነት›› ሁሌም ለምለም የሆኑ ዛፎችን ያመለክታሉ። እሾኻማ ተክሎች ጥፋትን ሲወክሉ፣ ለምለም ዛፎች ግን ሕይወትንና ብልጽግናን ይወክላሉ።

ለስሙ

እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የያህዌን ዝና ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለእርሱ ዝና›› ወይም፣ ‹‹ለእርሱ ክብር››

አይቆረጥም

መኖሩን የሚያቋርጥ ነገር ከዛፍ እንደ ተቆረጠ ቅርንጫፍ ወይም ከልብሱ እንደ ተቀደደ ቅዳጅ እንደሆነ ተነግሯል። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አያልቅም›› ወይም፣ ‹‹ለዘላለም ይኖራል››

---

Chapter 56

Isaiah 56:1

ማዳኔ ቅርብ ነው፤ ጽድቄም ለገለጥ ነው

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በቅርቡ አድናችኃለሁ፤ ጻድቅ መሆኔንም አሳያችኃለሁ››

አጥብቆ የያዘ

እዚህ ላይ፣ ‹‹አጥብቆ የያዘ›› ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ አንድን ነገር ማክበር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሌም ያን ለማድረግ ጠንቃቃ የሆነ››

ክፉ ከማድረግ እጁን የሚሰበስብ

እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሚወክለው መላውን ሰው ሲሆን፣ የሰውን ድርጊትና ጸባይ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ነገር የማያደርግ››

Isaiah 56:3

እኔ ደረቅ ዛፍ ነኝ

ይህም ማለት ጃንደረቦች በመኮላሸታቸው ከደረሰባቸው አካለ ጐዶሎነት የተነሣ የያህዌ ሕዝብ አካል እንዳይደሉ ሊያስቡ እንደሚችሉ ያመለክታል (ልጆች መውለድ ስለማይችሉ)። እስራኤላውያን ማኮላሸት አይፈጽሙም፤ ያን የሚያደርጉ ለቅጣት ሲባል የሌላ አገር ሰዎች ናቸው። የዕብራውያንን እምነት የተቀበሉ ጃንደረቦች መቅደስ ውስጥ እንዲያመልኩ እንደማይፈቀድላቸው ያውቃሉ። (ዘዳግም 23፥1)። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

Isaiah 56:4

በቤቴና በቅጥሮቼ

እነዚህ ሁለት ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በቤተ መቅደሴ ቅጥር ውስጥ››

ያ አይቆረጥም

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አያልቅም›› ወይም፣ ‹‹አይረሳም››

Isaiah 56:6

ራሳቸውን ከያህዌ ጋር ያቆራኙ

ይህ የሚያመለክተው ከያህዌ ሕዝብ ጋር የተባበሩ የሌላ አገር ሰዎችን ነው።

የያህዌን ስም የሚወዱ

‹‹የያህዌ ስም›› እርሱ ራሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን የሚወዱ››

የተቀደሰ ተራራ

አሳይያስ 11፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

በመሠዊያየ ተቀባይነት ያገኛል

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መሠዊያየ ላይ እቀበለዋለሁ››

ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል››

Isaiah 56:8

ይህ ከእስራኤል የተጣሉትን የሚሰበስብ የያህዌ ቃል ነው።

የተናገረው እርግጥ መሆኑን ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእስራኤል የተጣሉትን የሚሰበስብ ያህዌ እንዲህ ይላል›› ወይም፣ ‹‹ይህ ከእስራኤል የተጣሉትን የምሰበስብ እኔ ያህዌ የተናገርሁት ነው››

Isaiah 56:9

እናንተ የምድር አራዊት ሁሉ እናንተ የዱር አራዊት ሁሉ መጥታችሁ በጫጭቁ

በዱር አራዊት የሚመስላቸውን የሌላ አገር ሰራዊት መጥተው የእስራኤልን ሕዝብ እንዲያጠቁ እግዚአብሔር ይጠራል።

ጠባቂዎቻቸው ሁሉ ዕውሮች ናቸው

ይህ ማለት የእስራኤል መሪዎች ማኅበረ ሰቡ ውስጥ እየሆነ ያለውን ማየት አልቻሉም ምናልባትም አልፈለጉም ማለት ነው።

ሁሌም ዝም ያሉ ውሾች ናቸው

መሪዎቹ ሕዝቡን ማስጠንቀቅ ነበረባቸው፣ ግን ያን አላደረጉም። ማኅበረ ሰቡ ውስጥ አንድን ሰው በውሻ መመሰል ትልቅ ስድብ ነው።

ተጋድመው ያልማሉ፤ መተኛት ይወዳሉ

ይህ ማለት መሪዎቹ የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ለሕዝቡ አያመጡም፤ ግን የራሳቸውን ምቾት ብቻ ይፈልጋሉ ማለት ነው።

Isaiah 56:11

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ የሕዝቡን ክፉ መሪዎች መግለጽ ቀጥሏል።

ውሾቹ ሆዳሞች ናቸው

ያህዌ የእስራኤልን ክፉ መሪዎች ከውሾች ጋር አመሳስሎአቸዋል።

---

Chapter 57

Isaiah 57:1

የኪዳን ታማኝነት ሕዝብ

‹‹ታማኝነት›› የሚለውን፣ ‹‹ታማኝ›› ማለት ይቻላል። አሳይያስ 16፥5 ላይ፣ ‹‹ኪዳናዊ ታማኝነት›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለኪዳኑ ታማኝ የሆኑ ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹ታማኝ ሰዎች››

ተሰብስበዋል… አልጋቸው ላይ አርፈዋል

ሁለቱም የሚያመለክቱት መሞትን ነው።

ጻድቅ ከክፉ ይሰበሰባል

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጻድቃን ይሞታሉ፤ እግዚአብሔርም ክፉ ከሆነው ሁሉ ይወስዳቸዋል››

ወደ ሰላም ይገባል

‹‹ጻድቅ ወደ ሰላም ይገባል››

በቅንነት የሚመላለሱ

‹‹መልካም የሆነውን የሚያደርጉ››

Isaiah 57:3

ግን ወዲህ ኑ

እግዚአብሔር ታማኝ ያልሆኑ ሰዎች የእርሱን ፍርድ እንዲቀበሉ ወደ ፊቱ እንዲመጡ ይጣራል፤ ይህ ቀደም ሲል ከተነገረው ለጻድቃን ከተሰጠው ተስፋ በጣም የተለየ ነው።

የአስማተኛዪቱ ልጆች

ይህ አስማተኝነትን ለሚለማመዱ ትልቅ ስድብ ነው፤ ምክንያቱም አስማትንም ሆነ ጥንቆላ ባዕድ አምልኮን የሚጨምር በመሆኑ ነው።

እናንተ የአመንዝውና የጋለሞታዪቱ ልጆች

ይህ የሚያመለክተው በተግባር የተገለጠ መንፈሳዊ አመንዝራነትን ነው። እግዚአብሔርን ማምለክ ትተው በአረማውያኑ ከነዓናውያን መንገድ አማልክትንና ጣዖቶችን እያመለኩ ነበር።

የምትሳለቁት በማን ላይ ነው? ምላሳችሁን አውጥታችሁ የምታሾፉት በማን ላይ ነው?

በሐሰተኛ አምልኮ እርሱ ላይ የሚሳለቁትን ለመገሠጽ ያህዌ ጥያቄዎችን ያነሣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አፋችሁን አስፍታችሁ በመክፈትና ምላሳችሁንም በማውጣት እኔ ላይ እየተሳለቃችሁ ነው››

እናንተ የዐመፃ ልጆች፣ የሐሰት ልጆች አይደላችሁምን?

ሕዝቡን ለመገሠጽ ያህዌ ሌላ ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ የሚያመለክተው በሥጋ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የተወለዱበትን ሳይሆን መንፈሳዊ ይዞታቸውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተ የዐመፃ ልጆ፣ የሐሰትም ልጆች ናችሁ››
Isaiah 57:5
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእምነተ ቢሶቹ የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
በዐለት ሰንጣቂዎች ውስጥ… ራሳችሁን ታቃጥላላችሁ
እነዚህ ድርጊቶች ሁሉ ከጣዖት አምልኮ ጋር የተያያዙ ናቸው። ዋርካ ዛፎች ለከነዓናውያን የተቀደሱ ናቸው። እንዲህ ያለው ተግባር የሕዝቡንና የምድሩን ለም መሆን ይጨምራል በማለት ሰዎች ያስቡ ነበር።
Isaiah 57:6
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእምነተ ቢሶቹ የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ያ ለአንቺ ተመድቦአል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። የዕብራይስጡ ትክክለኛ ትርጉም ግልጽ አይደለም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያ ዕጣ ፈንታሽ ነው›› ወይም፣ ‹‹ያ የአንቺ ድርሻ ነው››
በእነዚህ ነገሮች ደስ መሰኘት አለብኝን?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ሕዝቡን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ ነገሮች እኔን ደስ አያሰኙኝም››
Isaiah 57:7
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእምነተ ቢሶቹ የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
ዐልጋሽን አነጠፍሽ
ይህ ሐሰተኛ አማልክትን ለማምለክ ሲባል ከአመንዝራዎች ጋር መተኛትን ያመለክታል።
ከፍ ባለው ተራራ
ብዙውን ጊዜ ሰዎች ሐሰተኛ አማልክትን ለማምለክ ወደ ኮረብቶችና ተራሮች ጫፍ ይሄዱ ነበር። እነዚህ ቦታዎች ለአምልኮ የተሻሉ ቦታዎች እንደሆኑ ያስቡ ነበር። ምናልባትም ይህ ኢየሩሳሌምንም የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።
ከእነርሱ ጋር ኪዳን አደረግሽ
‹‹ከእነርሱ ጋር ውል አደረግሽ››
Isaiah 57:9
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእምነተ ቢሶቹ የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ወደ ሲኦል ወረድሽ
ሰዎች በአካል የሙታን ዓለም ወደሆነው ሲኦል አልወረዱም። ከዚያ ይልቅ ሕዝቡ አዳዲስ አማልክት ለመፈለግ የትም ቦታ ለመሄድ ፈቃደኛ መሆናቸውን ያህዌ ግነታዊ በሆነ ቋንቋ መናገሩ ነው።
በእጅሽ ሕይወት አገኘሽ
ከባድ ሙከራ ካደረጉ በኋላ እንኳ ጣዖት አምላኪዎቹ አሁንም ገና ዐቅም እንዳላቸው ተረዱ። እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› — ‹‹ብርታትን›› — ‹‹ብቃትን›› ይወክላል።
Isaiah 57:11
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእምነተ ቢሶቹ የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
እኔን የዋሸሽኝ ማንን ፈርተሽ፣ ማንንስ ሠግተሽ ነው?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ሕዝቡን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔን ለመዋሸት እነዚህን ጣዖቶች በእርግጥ መፍራት አለብሽ››
እኔን አላስታወስሽም፤ ስለ እኔ አላሰብሽም
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆኑ፣ ሕዝቡ ያህዌን ማስታወስ ቢኖርባቸውም እነርሱ እንደዚያ እንዳላደረጉ አጽንዖት ይሰጣል።
ጽድቅሽንና ሥራሽንም ሁሉ አገልጣለሁ
እዚህ ላይ ክፉ ሥራቸውን ጽድቅ ብሎ በመጥራት ያህዌ በስላቅ እየተናገረ ነው።
Isaiah 57:13
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእምነተ ቢሶቹ የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
የጣዖቶችሽ ብዛት ያድኑሽ
ያህዌ በሕዝቡና በጣዖቶቻቸው እያፌዘ ነው። ምንም እንኳ እንደማያድኑዋቸው ቢያውቅም ያህዌ ጣዖቶቹ ሕዝቡን እንዲያድኑ ይናገራል።
ሁሉንም ነፋስ ይወስዳቸዋል፤ እስትንፋስ ሁሉንም ይጠራርጋቸዋል።
ጣዖቶቹ ዐቅመ ቢስና ከንቱ መሆቸውን አጽንዖት ለመስጠት በሁለት መንገዶች ተመሳሳይ ነገር ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነፋስ ወይም እስትንፋስ እንኳ ጠራርጎ ይወስዳቸዋል››
የተቀደሰ ተራራ
‹‹የተቀደሰ ተራራ›› በኢየሩሳሌም ያለው የጽዮን ተራራ ነው። ኢሳይያስ 11፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት።
Isaiah 57:14
አብጁ አብጁ! ከሕዝቤ መንገድ እንቅፋት አስወግዱ
ሕዝቡ ወደ እርሱ እንዲመለሱና እርሱን ለማምለክ እንቅፋቶች እንዳይኖሩ ያህዌ አጽንዖት በመስጠት መንገዱ በአስቸኳይ እንዲስተካከል ይናገራል። ይህ ኢሳይያስ 40፥3 ላይ ያለውን ያስተጋባል።
ከፍ ያለውና ልዕልና ያለው ይህን ይናገራል
‹‹ከፍ ያለ›› እና፣ ‹‹ልዕልና›› በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ያላቸው ቢሆኑም፣ ያህዌ ከፍ ያለ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል። ኢሳይያስ 6፥1 እና 33፥10 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። ኢሳይያስ 52፥13 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
የትሑትን መንፈስ ለማነሣሣት፣ የልበ ሰባራዎችን ልብ ለማነሣሣት
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ቢሆኑም፣ በፊቱ ትሑት የሆኑትን እንደሚያበረታና እንደሚያጽናና አጽንዖት ይሰጣል።
መንፈስ… ልብ
እነዚህ የሰውን ሐሳብና ስሜት ያመለክታሉ፤ ቃል በቃል መንፈስና ልብ ማለት አይደለም።
Isaiah 57:16
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ፊቴን ሰወርሁ
ይህ ማለት ሕዝቡን ትቶአል፤ ከእንግዲህ አይረዳቸውም አይባርካቸውም ማለት ነው።
በልቡ መንገድ ወደ ኃላ ተመለሰ
ይህ ማለት እስራኤላውያን ለሐሰተኞቹ ሲሉ እውነተኛውን አምላክ ተዉ ማለት ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ወደ ኃላ›› እና፣ ‹‹መንገድ›› የሚሉት ቦታን የሚያመለክቱ ቃላት ቢሆኑም፣ ዝንባሌንና ስሜትን ይወክላሉ።
Isaiah 57:18
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል።
መንገዱ
‹‹መንገዳቸው›› እዚህ ላይ፣ ‹‹የእርሱ›› የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።
ለእርሱ የሚያለቅሱትን አጽናኑ፣ አበርቱ
‹‹በክፉ መንገዳቸው ምክንያት ለሕዝቡ መከራ የሚያዝኑትን አጽናናቸዋለሁ››
የከንፈሮችን ፍሬ እፈጥራለሁ
‹‹የከንፈሮች ፍሬ›› ሰው የሚናገረውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዲመሰግኑኝና እንዲያከብሩኝ አደርጋለሁ››
በሩቅ ላሉት ሰላም፣ ሰላም
‹‹በሩቅ ካሉት ጋር ሰላም አደርጋለሁ›› — ‹‹ሰላም›› የሚለው ቃል የተደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው።
Isaiah 57:20
ክፉዎች ግን እንደሚናወጥ ባሕር ናቸው… ጭቃና ጉድፍ
ይህ ክፉዎችን ውሃውን ከሚያቆሽሽ ባሕሩ ዳርቻ ካለው ውሃ ጋር ያመሳስላቸዋል።

Chapter 58
Isaiah 58:1
ድምፅህን እንደ መለከት አንሣ
ይህ በኀይል ጩኽ ማለት ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹የአንተ›› የሚያመለክተው ኢሳይያስን ነው።
ለሕዝቤ ዐመፃቸውን፣ ለያዕቆብም ቤት ኀጢአታቸውን ተናገሩ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። ሁለቱ በአንድነት

ለያህዌ ሕዝብ በአስቸኳይ መናገርን ያጠናክራሉ።
Isaiah 58:3
‹‹ስለምን ብለን ጾምን›› ይላሉ፤ ‹‹አንተ ግን አላየህም? ራሳችንን ስለምን አዋረድን አንተ ልብ አላልህም?
እርሱ ችላ ያላቸው ስለ መሰላቸው የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር ላይ ለማማረር ጥያቄ አንሥተዋል።
Isaiah 58:4
አጠቃላይ መረጃ
ለጥያቄያቸው መልስ በመስጠት ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
እነሆ
‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹ልብ በሉ›› ልብ እንዲሉ በመናገር ያህዌ ለጥያቄያቸው መልስ ይሰጣል።
የግፍ ጡጫ
‹‹የግፍ ጡጫ›› — ይህ የምር መደባደባቸውን ያመለክታል። ‹‹ጡጫ›› በግልጽ የሚታይ ቁጣን ያመለክታል።
እኔ የምፈልገው ጾም ይህን ነውን… ራሱን የሚያዋርደው?
ሕዝቡን ለመገሠጽ ያህዌ ጥያቄ ያነሣል። በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን እንዳዋረዱ ያስመስላሉ፤ ግን ሰዎችን ይጐዳሉ። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለም… ራሱን እንዲያዋርድ››
ሰው ራሱን የሚያዋርደው እንደ ደንገል ራሱን ዝቅ የሚያደርገው
ይህ ሰውየው ዝቅ ብሏል፤ ግን በእውነት ትሑት አይደለም ማለት ነው። ‹‹ደንገል›› በቀላሉ የሚታጠፍ ደካማ ተክል ይወክላል።
ይህን ጾም ትለዋለህ፤ ያህዌን ደስ የሚያሰኝ ቀን ትለዋለህ?
ያህዌ ጥያቄ ያቀረበው ሕዝቡን ለመገሠጽ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መቼም እንዲህ ያለውን ጾም እኔን ያስደስታል ብለህ አታስብም!››
Isaiah 58:6
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን… ቀንበርን ሁሉ እንድትሰብሩ?
ያህዌ ጥያቄውን ያነሣው እርሱን ደስ ስለሚያሰኘው ጾም ሕዝቡን ለማስተማር ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነው… ቀንበርን ሁሉ እንድትሰብሩ››
የጭቆናን ሰንሰለት እንድትበጥሱ፣ የቀንበርን ገመድ እንድትፈቱ፣ የተጨቆኑትን ነጻ እንድታወጡ፣ ማንኛውንም ቀንበር እንድትሰብሩ
እነዚህ ሐረጐች ሁሉ ክፉዎች የበደሉዋቸውንና ያጠቁዋቸውን ሰዎች መርዳት እንዳለባቸው ያመለክታሉ።
ወደ ቤትህ እንድታስገባው… አይደለምን?
ያህዌ ሕዝቡን ለማስተማር ሌላ ጥያቄ ያነሣል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ቤትህ እንድታስገባው… ነው?››
እንጀራህን እንድትቆርስ
ይህ ሐረግ ባለቤቱ እንጀራውን በመቁረስ ምግቡን መጀመር እንዳለባት ያመለክታል።
Isaiah 58:8
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ያኔ ብርሃንህ እንደ ንጋት ጮራ ይፈነጥቃል
‹‹ይፈነጥቃል›› ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን፣ ደምቆ ያበራል ማለት ነው። ይህ ማለት ችግረኞችን ቢረዱ ከጨለማው ሌሊት በኋላ እንደሚመጣ ፀሐይ ተግባራቸው ሌሎች ሰዎች የሚያዩት ብርሃን ይሆናል ማለት ነው። ወይም ብርሃን እነርሱ ላይ የሚያበራውንና የሚባርካቸውን የጌታ ብርሃን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።
ፈውስህ ፈጥኖ ይበቅላል
ይህ ማለት ቶሎ እንደሚድን ቁስል እግዚአብሔር ቶሎ ይባርካቸዋል ይመልሳቸዋል ማለት ነው።
ጽድቅህ በፊትህ ይሄዳል፤ የያህዌ ክብር ደጀን ይሆንልሃል
ይህ ከግብፅ በወጡ ጊዜ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ያደረገውን ጥበቃ ያመለክታል። ይህ መልካም የሆነውን ቢያደርጉ እግዚአብሔር እንደ ገና ከጠላቶቻቸው ይጠብቃቸዋል ማለት ነው።
ጽድቅህ
ይህ አገላለጽ በዕብራይስጥ ጽድቅን እንዲያውም ድልን የሚሰጥ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። በዚህ ዐውድ የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። ጥቂት የዘመኑ ቅጂዎች ይህን ትርጒም ይዘዋል።
Isaiah 58:9
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ያኔ ብርሃንህ በጨለማ ይወጣል፤ ጨለማህም እንደ ቀትር ይሆናል
‹‹ብርሃንህ›› ለሰው ሁሉ ምሳሌ የሚሆን መልካም ሥራን ይወክላል፤ ‹‹ጨለማ›› ማለት ክፉ ሥራ በመልካም ሥራቸው ይሸነፋል።
Isaiah 58:11
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
በውሃ እንደ ረካ ቦታ ትሆናለህ
‹‹ውሃ›› አካባቢያቸው በቂ ባይኖረው እንኳ የሞላ ሕይወት ለመኖር የሚያስፈልገውን ሁሉ ይወክላል።
ውሃ እንደ ጠጣ አትክልት ቦታ ትሆናለህ
‹‹ውሃ የጠጣ አትክልት ቦታ›› ሙላትና መትረፍረፍን ይወክላል፤ ስለዚህ የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ይኖራቸዋል።
ውሃው እንደማይደርቅ ምንጭ
‹‹የውሃ ምንጭ›› ውሃ ውድ በሆነበት ምድር ሙላትና መትረፍረፍን ያመለክታል።
Isaiah 58:12
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ተብለህ ትጠራለህ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰዎች ይጠሩሃል››
Isaiah 58:13
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
እግርህን ከሰንበት መንገድ ብትመልስ፣ በተቀደሰውም ቀን ደስ የሚያሰኝህን ባታደርግ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እግር›› ሰዎቹን ይወክላል። እግዚአብሔር በዕረፍት ቀን ረጅም ጒዞን ወይም ሥራ አይፈቅድም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በተቀደሰው ቀኔ በሰንበት ጒዞ አታድርግ የምትፈልገውንም አታድርግ››
Isaiah 58:14
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
በምድር ከፍታዎች ላይ እንድትጋልብ አደርግሃለሁ
ይህ የሚያመለክተው በጽድቅ የመኖር ምላሽ እንዲሆን እግዚአብሔር የሕዝቡን ኀይልና ዝና ከፍ የሚያደርግ መሆኑን ነው።
የያህዌ አፍ ተናግሮአልና
‹‹አፍ›› ያህዌ የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ ተናግሮታልና››

---

Chapter 59
Isaiah 59:1
እነሆ
‹‹ተመልከቱ›› ወይም ‹‹ማወቅ አለባችሁ!›› ያህዌ ልብ እንዲሉ ለሕዝቡ ይናገራል።
የያህዌ እጅ አላጠረም
‹‹እጅ›› ኀይልና ችሎታን ይወክላል። ‹‹አጭር›› እጅ ኀይልና ችሎታ የለውም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ በቂ ችሎታ አለው››
የእናንተ… እናንተ
እነዚህ የብዙ ቁጥር ተውላጠ ስሞች እንደ አንድ ነጠላ ወገን የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታሉ።
ኀጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ እንዲሰውር አድርጓል።
‹‹ፊት›› መገኘትንና ማየትን ይወክላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ኀጢአታችሁ ከእናንተ ዘወር እንዲል አድርጐአል››
Isaiah 59:3
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
እጃችሁ በደም፣ ጣቶቻችሁም በኀጢአት ቆሽሸዋል
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› እና፣ ‹‹ጣቶች›› ድርጊታቸውን ያመለክታሉ። ይህም ማለት ግፍና ኀጢአት በመፈጸም በድለዋል ማለት ነው። ‹‹የእናንተ›› ብዙ ቁጥር ነው። አማራጭ

ትርጉም፣ ‹‹ከባድ ኀጢአቶች ፈጽማችኋል››
ከንፈሮቻችሁ ሐሰት ተናገሩ፣ ምላሶቻችሁ ሐሜት ተናገሩ
ሰዎች እንዲናገሩ የሚረዱ የአካል ክፍሎች ንግግርን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሐሰትና ሐሜት ትናገራላችሁ››
ችግር ፀነሱ፤ ኀጢአትን ወለዱ
‹‹መፅነስ›› እና ‹‹መውለድ›› ምን ያህል ተዘጋጅተው ኀጢአት እንደሚያደርጉ ያመለክታል። ‹‹እነርሱ›› የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀጢአት ለማድረግ በርትተው ይሠራሉ››
Isaiah 59:5
አጠቃላይ መረጃ
መርዛማ እባብንና የሸረሪትን ድር ምሳሌ በማድረግ ኢሳይያስ የእስራኤል ሕዝብ ስለሚሠሩት ኀጢአት መናገር ቀጥሏል።
የመርዛማ እባብ ዕንቁላሎች ቀፈቀፉ
የመርዛማ እባብ ዕንቁላሎች፣ ብዛት ያላቸው መርዛማ እባቦች ያስገኛሉ። ‹‹መርዛማ እባብ›› የሚለው የበለጠና የበለጠ ሌሎችን የሚጐዳ ሰዎቹ የሚያደርጉት ክፉ ነገር ነው።
የሸረሪት ድር አደሩ
ይህ የሚወክለው እርባና ቢስ የሰዎቹን ተግባር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥቅም የሌለው ነገርንና እንቅስቃሴን አስገኙ››
ዕንቁላላቸውን የሚበላ ይሞታል፤ ዕንቁላሉ ከተሰበረ መርዛማ እባብ ይወጣል
መርዛማ ዕንቁላል በልቶ መሞት ራስን ማጥፋትን ይወክላል። ዕንቁላሉ ሲሰበር የሚወጣው መርዛማ እባብ ጥፋትን ማስፋፋትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚሠሩት ነገር ያጠፋቸዋል፤ ጥፋቱም ወደ ሌሎች እንዲስፋፋ ያደርጋል።››
Isaiah 59:7
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
እግሮቻቸው ወደ ክፉ ይሮጣሉ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እግሮች›› ሰዎችን ይወክላሉ። ይህ የሚያመለክተው እግሮቻቸው እንደሚሮጡ ሁሉ እነርሱም ክፉ ለማድረግ ፈጣኖች መሆናቸውን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ለማድረግ ፈጣኖች ናቸው››
የመንገዶቻቸው ናቸው
‹‹መንገዶች›› አኗኗራቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሉም እንዲህ ያደርጋሉ››
በጐዳናዎቻቸው ፍትሕ የለም
‹‹ጐዳናዎቻቸው›› አኗኗራቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፍጹም ትክክል የሆነውን አያደርጉም›› ወይም፣ ‹‹የሚያደርጉት ሁሉ ክፉ ነው››
መንገዳቸውን ጠማማ አድርገውታል
‹‹ጠማማ መንገድ›› አኗኗራቸው ብልሹ መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሐሰት ይናገራሉ ያደርጋሉ፤ አታላዮች ናቸው››
Isaiah 59:9
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ፍትሕ ከእኛ ርቆአል
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኛ›› የሚወክለው ኢሳይያስንና የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ‹‹ርቆአል›› ፍትሕ መጥፋቱንና ለማግኘትም አስቸጋሪ መሆኑን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ፍትሕ ጠፍቷል፤ ለማግኘትም ያስቸግራል››
ብርሃንን ጠበቅን ግን፣ ጨለማ አየን፤ የብርሃን ጸዳል ጠበቅን ግን በጨለማ እንሄዳለን።
እያንዳንዱ ሐረግ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን መልካምነት ጠብቀው እንደ ነበርና እርሱ ግን የተዋቸው እንደሚመስል ያመለክታል።
እንደ ዕውር ቅጥሩ ላይ ተደናበርን… እንደ ሙታን
ይህ ማለት እግዚአብሔር ወደ እነርሱ ስለማይመጣ ትክክለኛውን መንገድ ለማግኘት ዐቅም እንደሌላቸው በወደ ፊቱም ተስፋ መቁረጣቸውንና በሕይወት ለመኖር ተስፋ እንደሌላቸው ያመለክታል።
Isaiah 59:11
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል።
በደላችን በዝቶአል
እዚህ ላይ ‹‹እኛ›› ኢሳይያስንና የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።
በፊትህ
እዚህ ላይ፣ ‹‹አንተ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው።
ኃጢአታችን ይመሰክርብናል
ኢሳይያስ ኀጢአትን ሰዎቹ በደለኛ መሆናቸውን ለመናገር በእግዚአብሔር ፊት እንደሚሄድ ሰው ይገልጻል።
በደላችን ከእኛ ጋር ነውና
‹‹ከእኛ ጋር›› መገንዘብን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በደላችንን እንገነዘባለንና››
Isaiah 59:14
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል
ፍትሕ ርቆአል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎቹ ፍትሕ እንዲጠፋ አድርገዋል››
ፍትሕ… ጽድቅ… እውነት… መልካም… ታማኝ
ኢሳይያስ እነዚህ ነገሮች እንደ ሰው እየሠሩ እንደሆነ ያመለክታል።
Isaiah 59:16
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል።
ሰው እንደሌለ አየ፤ ጣልቃ የሚገባ ባለ መኖሩ ተገረመ
‹‹መከራ ውስጥ ያሉትን ለመርዳት ማንም ባለ መምጣቱ ያህዌ ተገረመ›› ወይም፣ ‹‹መከራ ውስጥ ያሉትን ለመርዳት የመጣ ሰው ባለመኖሩ ያህዌ ተደነቀ››
ስለዚህ የገዛ ራሱ ክንድ ማዳን አመጣለት
የያህዌ፣ ‹‹ክንድ›› ችሎታውንና ኀይሉን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡን ለማዳን ያህዌ የራሱን ኀይል ተጠቀመ››
ጻድቁ ደግፎ ያዘው
እዚህ ላይ፣ ‹‹ጽድቅ›› የሰው ባሕርይ እንዳለው ተነግሯል። ይህን ቃል ቅጽል ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሌም እንደሚያደርገው መልካም አደረገ››
Isaiah 59:17
ጽድቅን እንደ ጥሩር አጠለቀ፤ የድነትን ቁር ራሱ ላይ ደፋ። በቀልን ለበሰ፤ ቅናትን እንደ መጐናጸፊያ ደረበ
‹‹ጥሩር››፣ ‹‹ቁር››፣ ‹‹ልብስ›› እና፣ ‹‹መጐናጸፊያ›› በጦርነትና በውጊያ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው። ሕዝቡን ለመቅጣት ያህዌ እነዚህን እንደ ለበሰ ኢሳይያስ ይናገራል።
መጐናጸፊያ
ከላይ እስከ ታች የሚዘልቅ ሰፊ ልብስ
ከፈላቸው
ኢሳይያስ ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮች ባለፈው ጊዜ እንደሆኑ አድርጐ ይናገራል። ይህም በእርግጥ ይፈጸማል ማለት ነው።
Isaiah 59:19
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል።
የያህዌን ስም ፍሩ
‹‹ስም›› የሚያመለክተው የያህዌን ዝናና ባሕርይ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን ፍሩ››
ከምዕራብ… ከፀሐይ መውጫ
ኢሳይያስ በእነዚህ ቃሎች የተጠቀመው በዓለም ሁሉም ቦታ ያሉ ሰዎችን ለማመልከት ነው።
እንደሚፍለቀለቅ ምንጭ ይመጣል
ድንገተኛና ከባድ ዝናብ እንደ ፈጣን ጐርፍ እስኪያደርጋቸው ድረስ ይሁዳ ውስጥ ያሉ ጠባብ ሸለቆዎች ደረቆች ናቸው። ያ በሚሆንበት ጊዜ ታላቅ ድምፅና ነፋስ ይኖራል።
በያህዌ እስትንፋስ ተወገዱ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያህዌ እሳት ንፋስ የሚያስወግዳቸው››
ይህ የያህዌ ቃል ነው
የሚናገረውን እርግጠኝነት ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የተናገረው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››
Isaiah 59:21


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 60
Isaiah 60:1
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
ብርሃንሽ መጥቶአልና ተነሺ አብሪ፤ የያህዌ ክብር ወጥቶልሻል
ይህ የሚያመለክተው ለኢየሩሳሌም ሰዎች ያህዌ ያደረገውን የከበሩ ነገሮች ነው። በሚያደርጉትና በሚናገሩት ያንን ክብር ማሳየትና ለወደ ፊቱም ያላቸውን ተስፋ አሁን ማሳየት አለባቸው።
Isaiah 60:2
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በእስራኤል ሕዝብ ይናገራል። ‹‹ብርሃን››ን ምሳሌ ማድረጉን ቀጥሏል። (ኢሳይያስ 60፥1 ይመ.)
ጨለማ ምድርን፣ ድቅድቅ ጨለማ ሕዝቦችን ቢሸፍንም
እነዚህ ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፤ ተያይዘው ጥቅም ላይ የዋሉት አጽንኦት ለመስጠት ነው። ‹‹መንፈሳዊ ጨለማ››ን ያመለክታሉ። ይህም ማለት የተቀሩት ሰዎች ያህዌን ወይም እርሱን ደስ እንደሚያሰኙ አያውቁም ማለት ነው። ይህ የመለኮታዊ ፍርድ ምሳሌ ነው።
በአንቺ ላይ ያህዌ ይወጣል
ይህም ማለት የእግዚአብሔር መገኘት ክብር ለእስራኤል ሕዝብ ይገለጻል፣ መሄድ ያለባቸውንም መንገድ ያሳያቸዋል ማለት ነው።
ክብሩም በአንቺ ላይ ይታያል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቦች ክብሩን በአንቺ ላይ ያያሉ።››
Isaiah 60:4
አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ ያህዌ መናገር ጀምሯል
ሁሉም ይሰበሰባሉ
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ የሚሰበሰቡትን የተቀሩትን የእስራኤል ሕዝብ ነው።
ሴቶች ልጆችሽን በዕቅፋቸው ይሸከሟቸዋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሴቶች ልጆችሽን ዐቅፈው ይሸከሟቸዋል›› ወይም፣ ‹‹ሴቶች ልጆችሽን ያዝሏቸዋል››
ከዚያም ታያለሽ ታብረቀርቂያለሽ፣ ልብሽ በደስታ ይሞላል
የሐረጐቹ ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን፣ በኢየሩሳሌም ከሚሆነው የተነሣ በጣም ደስ እንደሚላቸው አጽንዖት ይሰጣሉ።
የባሕር ብዛት
ይህ የሚያመለክተው በመርከብ ምናልባትም ከሜዲትራኒያን ባሕር ማዶ ወደ ኢየሩሳሌም የሚመጣውን ሀብትና ብልጥግና ነው።
አንቺ ላይ ይፈስሳል
ይህ የሚያመለክተው የሀብቱ ብዛት እንደ ውሃ ሙላት እንደሚሆን ነው።
Isaiah 60:6
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ግልግል ግመሎች
‹‹የግመል መንጋ››
ጌፌር... ቄዳር... ነባዮት
እነዚህ አረቢያ አካባቢ ያሉ ቦታዎች ስሞች ናቸው።
የቄዳር የበግ መንጋ ሁሉ ወደ አንቺ ይሰበሰባል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የቄዳር ሕዝብ የበግ መንጋዎቻቸውን ወደ አንቺ ይሰበስባሉ››
የነባዮት አውራ በጐች ለሚያስፈልግሽ ይውላሉ
ይህ የሚያመለክተው ለመሥዋዕት የሚያስፈልጋቸውን ነው።
መሠዊያሽ ላይ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት ይሆናሉ
‹‹እኔ ያህዌ፣ መሠዊያየ ላይ እቀበላቸዋለሁ››
Isaiah 60:8
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
እነዚህ እንደ ደመና የሚጓዙ፣ እንደ ርግቦች ወደ ጐጆአቸው የሚበርሩ እነማን ናቸው?
እዚህ ላይ ያህዌ ትኩረት ለመሳብ ጥያቄዎችና ቅኔያዊ ምስሎች ይጠቀማል። የመርከቦቹን መቅዘፍ ከደመናና ከርግቦች ጋር ያመሳስለዋል። ይህ እስራኤላውያን ወደ አገራቸው መመለሳቸውንም ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተመልከቱ፣ እንደ ደመና በፍጥነት፣ የሚጓዝ እንደ ርግቦችም ወደ ጐጆአቸው የሚመለሱ አያለሁ››
ደሴቶች
ይህ የሚያመለክተው በደሴቶች የሚኖሩ ሰዎችን ነው፤ የደሴቶች አካባቢ ማየት እንደሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ አድርጐ ያቀርባል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በደሴቶቹ ያሉ ሰዎች››
የተርሴስ መርከቦች
ብዙውን ጊዜ ይህ ለረጅም ጉዞ የሚስማሙ ብዙ የንግድ መርከቦች ነው የሚያመለክተው
የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
እርሱ አክብሮሻል
‹‹ያህዌ እናንተ የእስራኤል ሰዎችን አክብሮአል››
Isaiah 60:10
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
ቀንም ሆነ ሌሊት አይዘጉም
‹‹ቀን›› እና፣ ‹‹ሌሊት›› በአንድነት፣ ‹‹ሁልጊዜ›› ማለት ናቸው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም አይዘጋቸውም››
የመንግሥታት ብልጥግና ከንጉሦቻቸው ጋር
ይህን በሌለ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከነገሥቶቻቸው ጋር ሰዎች የመንግሥታትን ብልጥግና ወደ አንቺ እንዲያመጡ››
Isaiah 60:12
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
እነዚያ ሕዝቦች ጨርሶ ይጠፋሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእነዚያን አገሮች ሰዎች ጨርሶ አጠፋቸዋለሁ››
የሊባኖስ ክብር
ይህ የሚያመለክተው ሊባኖስ ውብ በሆነ ዛፎቿ በተለይም፣ በዝግባና በጥድ ዝነኛ መሆንዋን ነው። የዛፎቹ ሁሉ ትክክለኛ ምንነት አይታወቅም።
የእግሬ ማረፊያ
ይህ የሚያመለክተው የያህዌን ቤተ መቅደስ ነው።
Isaiah 60:14
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
የእስራኤል ቅዱስ
ኢሳይያስ 1፥4 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
Isaiah 60:15
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ማንም የማያልፍብሽ
‹‹ማንም ምድርሽን ቢንቅም፣›› ወይም፣ ‹‹ባዕዳን ምድርሽን ቢንቁም››
የሕዝቦችን ወተት ትጠጪያለሽ፣ የነገሥታትን ጡት ትጠቢያለሽ
ይህ የሚናገረው ከሌሎች መንግሥታት ስለሚገኘው ሀብትና ብልጥግና ነው። አጽንኦት ለመስጠት ሁለቱም ሐረጐች የደጋገሙት ተመሳሳይ ነገርን ነው።
ቤዛ
ኢሳይያስ 41፥14 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
የያዕቆብ ኀያል
ኢሳይያስ 49፥26 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Isaiah 60:17
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
በእንጨት ፈንታ ናስ፣ በድንጋይ ፈንታ ብረት
ያህዌ የበለጠ ዋጋ ያለው የሕንፃ መሥሪያ ነገሮች ይሰጣቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእንጨት ፈንታ ናስ አመጣለሁ፤ በድንጋይ ፈንታ ብረት አመጣለሁ››
ሰላም አለቃሽ፣ ፍትሕ ገዥሽ ይሆናል
‹‹ሰላም›› እና፣ ‹‹ፍትሕ›› ሰብዓዊ ገዦች እንደሆኑ ያህዌ ይናገራል። ይህም ማለት በእስራኤል ምድር የተሟላ ሰላምና ፍትሕ ይኖራል ማለት ነው።
ከእንግዲህ በምድርሽ ሁከት አይሰማም
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድርሽ የሁከት ወሬ አይኖርም››
ቅጥሮችሽን መዳን፣ ደጆችሽን ምስጋና ብለሽ ትጠሪያቸዋለሽ
ቁሳዊ ነገሮች መንፈሳዊ ባሕርያት ያላቸው ስሞች ተሰጥቷቸዋል። የኢየሩሳሌም ከተማ የሰላም ከተማ ትሆናለች፤ እዚያ የሚኖሩትም ያህዌን ያመሰግኑታል።
Isaiah 60:19
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ያህዌ የዘላለም ብርሃንሽ ይሆናልና
አጽንዖት ለመስጠት ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ይደግማሉ
ከእንግዲህ ፀሐይሽ አትጠልቅም፣ ጨረቃሽም አትጠፋም
በመሠረቱ ጨረቃ አትጠፋም። ይህ ግነታዊ አባባል የፀሐይና የጨረቃ ብርሃን ከያህዌ ብርሃን ያነሰ ይሆናል ማለት ነው።
Isaiah 60:21
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል
የተከልሁት ቅርንጫፍ፣ የእጆቼ ሥራ
እነዚህ ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ቢሆኑም፣ አጽንዖት ለመስጠት ተደግመዋል።
የተከልሁት ቅርንጫፍ
ያህዌ እንደ አንድ አትክልተኛ ሕዝቡን እየበቀሉ ካሉ ተክሎች ጋር ያመሳስላል። ያህዌ ሕዝቡን በእስራኤል ምድር አኑሯል። ይህ ለሕዝቡ ተስፋ ይሰጣል።
የእጆቼ ሥራ
የእስራኤልን ሕዝብ ያህዌ በብልሃት ከሠራው የእጅ ሥራ ጋር ያመሳስላል።

---

Chapter 61
Isaiah 61:1
የያህዌ መንፈስ እኔ ላይ ነው
እዚህ ላይ፣ ‹‹መንፈስ›› ሰዎችን የሚያነሣሣና የሚያንቀሳቅስ መንፈስ ቅዱስ ነው። ኢሳይያስ 11፥2 ወይም ኢሳይያስ 42፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
ለተጐዱ
ይህ ታላቅ መከራ ውስጥ ያሉ ድኾችን ወይም፣ በራሳቸው ማስወገድ የማይችሉት ችግር ውስጥ ያሉ ጭቁኖችን ያመለክታል።
ለምርኮኞች ነጻነት፣ ለእስረኞች መፈታት
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። እግዚአብሔር ለምርኮኞች ነጻነትን በእርግጥ እንደሚሰጥ ያመለክታሉ።
Isaiah 61:2
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል።
የያህዌን የሞገስ ዓመት፣ የበቀሉን ቀን
ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ወቅት ነው። ‹‹ዓመት›› እና፣ ‹‹ቀን›› አንድ የተሟላ ነገርን የሚወክሉ ምሳሌዎች ናቸው።
የያህዌን የሞገስ ዓመት
‹‹ያህዌ ለሕዝቡ መልካም ነገር የሚያደርግበት ጊዜ››
Isaiah 61:3
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል።
ለመስጠት… ለመስጠት
ኢሳይያስ ይህን የደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው
ጥምጥም
‹‹የራስ ጥምጥም›› ወይም፣ ‹‹የተዋበ የራስ መሸፈኛ›› ይህ ራስ ላይ የሚጠመጠም ረጅም የጨርቅ አካል ነው።
የደስታ ዘይት… የምስጋና መጐናጸፊያ
ሰዎች ራሳቸውን ዘይት ይቀባሉ፤ በከበረ በዓልና በደስታ ጊዜ ሰዎች ያማረ ልብስ ይለብሳሉ።
በትካዜ መንፈስ ፈንታ
‹‹በሐዘን ፈንታ›› ወይም፣ ‹‹በለቅሶ ፈንታ››
ያህዌ የተከላቸው የጽድቅ ዋርካ ዛፎች
ይህ ማለት ያህዌ ሕዝቡን፣ ጠንካራና ብርቱ አድርጓል ማለት ነው።
ለእርሱ ክብር
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሕዝቡ ኑሮ እርሱን እንዲያከብር››
Isaiah 61:4
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ በእያንዳንዱ መስመር ተጓዳኝ ሐሳብን በመጠቀም መናገር ቀጥሏል።
Isaiah 61:6
አጠቃላይ መረጃ
የያህዌ ባርያ በእያንዳንዱ መስመር ተጓዳኝ ሐሳብን በመጠቀም ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
ትጠራላችሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ይጠሯችኋል››
ዕጥፍ ይኖራችኋል
ምናልባት፣ ዕጥፍ የርስት ድርሻ ሊሆን ይችላል።
በድርሻቸው ደስ ይላቸዋል… እነርሱ… ምድራቸው የእነርሱ ይሆናል
ይህም የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ይህን በሁለተኛ ሰው ደረጃ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በድርሻችሁ ደስ ይላችኋል… እናንተ… ምድራችሁ… የእናንተ ይሆናል››
Isaiah 61:8
ዘሮቻቸው በሕዝቦች ዘንድ፣ ልጆቻቸውም በሰዎች ዘንድ የታወቁ ይሆናሉ
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ናቸው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሌላ አገር ሰዎች ዘሮቻቸውን ያውቋቸዋል››
ልጆቻቸውም በሰዎች ዘንድ
የዚህ ሐረግ ግሥ ቀደም ሲል እንደ ነበረው ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልጆቻቸው በሰዎች ዘንድ የታወቁ ይሆናሉ››
Isaiah 61:10
እኔ በያህዌ እጅግ ደስ ይለኛል
‹‹እኔ›› የሚለው ያህዌ እንደ ገና የመለሳቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ አንድ ሰው መናገራቸውን ያመለክታል።
የመዳን ልብስ አልብሶኛል፤ የጽድቅ መጐናጸፊያ ደርቦልኛል
እንደ አንድ ሰው ሆነው ለያህዌ ሲናገሩ የነበሩ ሕዝብ አሁን ሰው ሁሉ የሚያየው የመዳንና የጽድቅ ልብስ ለብሰዋል። ‹‹ልብስ›› እና፣ ‹‹መጐናጸፊያ›› ሰው ሁሉ የሚያየው ነገሮች ናቸው።
ሙሽራ ራሱን በጥምጥም እንደሚያሳምር፣ ሙሽራዪቱም ራሷን እንደምታስጌጥ
ይህ ንጽጽር ተናጋሪው እጅግ ደስ እንዳለው ያንንም ደስታ እያጣጣመ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል።
ጥምጥም
ኢሳይያስ 61፥3 ላይ ያለውን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
ምድር ቡቃያ እንደምታበቅል፣ የተክል ቦታ ችግኝ እንደሚያፈላ
ይህ በሁለት መንገድ ተመሳሳይ ነገር መናገር ነው። እግዚአብሔር የተናገረው በእርግጥ የሚፈጸም መሆኑ ከተተከለ በኋላ ከሚበቅል ተክል ጋር ተመሳስሎአል አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አትክልት ቦታ የተተከለ ዘር እንደሚበቅልና እንደሚያድግ››
ጽድቅና ምስጋናም ይበቅላል
እነዚህ ምግባሮች እንደ አትክልት ከዘር እንደሚያድጉ ተነግሯል።

---


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 62

Isaiah 62:1

ስለ ጽዮን ዝም አልልም፤ ስለ ኢየሩሳሌም ጸጥ አልልም

ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ጽዮን›› እና፣ ‹‹ኢየሩሳሌም›› በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለ ኢየሩሳሌም ሕዝብ ዝም አልልም››

ዝም አልልም

‹‹እኔ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

ጽድቋ ደምቆ እስኪወጣ፣ ድነቷ እንደ ፋና እስኪሆን ድረስ

ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት የኃላ ኀላ እግዚአብሔር መጥቶ የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚያድን ያም የብርሃን ያህል በግልጽ እንደሚታይ ነው።

Isaiah 62:3

በያህዌ እጅ የውበት አክሊል በአምላክሽ እጅ እንደ ነገሥታት ዘውድ ትሆኛለሽ

ሁለቱም ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆኑ፣ ተያይዘው የቀረቡት አጽንዖት ለመስጠት ነው። በእግዚአብሔር ኀይልና ሥልጣን ሥር ኢየሩሳሌም የንጉሥ ከተማ እንደምትሆን ይናገራሉ። የያህዌ እጅ የእርሱን ኀይልና ሥልጣን ይወክላል።

ከእንግዲህ… ‹‹የተተወች››… አትባዪም

ሁለቱም ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆኑ፣ ተያይዘው ያቀረቡት አጽንዖት ለመስጠት ነው።

ከእንግዲህ ስለ አንቺ አይባልም

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች አንቺን አይሉሽም››

ከእንግዲህ ስለ ምድርሽ አይባልም

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ሰዎች ስለ ምድርሽ አይሉም››

ምድርሽ ታገባለች

ይህ ማለት ያህዌ የእስራኤልን ሕዝብ ይወዳል፤ እንደ ባል ሁሌም ከእነርሱ ጋር ይሆናል ማለት ነው።

Isaiah 62:5

ጐልማሳ ድንግሊቱን እንደሚያገባ ልጆችሽ ያገቡሻል

‹‹ልጆችሽ›› የእስራኤልን ሕዝብ ሲሆን፣ ‹‹አንቺ›› ይሁዳንና የእስራኤልን ምድር ያመለክታል። ሰው የሚስቱ ባለቤት እንደሚሆን ሕዝቡም የምድሪቱ ባለቤት ይሆናል ማለት ነው።

ሙሽራ በሙሽራዋ ደስ እንደሚለው አምላክሽ በአንቺ ደስ ይለዋል

ይህ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ባለው ግንኙነት ደስ እንደሚሰኝ ይናገራል።

Isaiah 62:6

አድርጌአለሁ

‹‹እኔ›› የሚያመለክተው ኢሳይያስን ወይም ያህዌን ነው።

ጠባቂዎች በቅጥሮችሽ ላይ

ይህ የሚያመለክተው ነቢያትን፣ ባለ ሥልጣኖችን ወይም ምናልባትም ያለ ማቋረጥ ከተማዋን የኢየሩሳሌምን ሕዝብ የሚጠብቁ መላእክትን ይሆናል። ኢሳይያስ 52፥8 እና ኢሳይያስ 56፥10 ላይ፣ ‹‹ጠባቂዎች›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ቀንና ሌሊት ዝም አይሉም

ይህም ማለት ያለ ማቋረጥ ያህዌን ይለምናሉ ወይም እርስ በርስ ይጠራራሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቀኑን በሙሉ አጥብቀው ወደ ያህዌ ይጸልያሉ››

ዕረፍት አትስጡት

‹‹እርሱ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

Isaiah 62:8

በቀኝ እጁና በብርታቱ ክንድ

የቀኝ እጅና ክንድ ኀይልና ሥልጣንን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በኀይልና በሥልጣኑ››

ከእንግዲህ መብል እንዲሆናቸው እህልሽን ለጠላቶችሽ በእርግጥ አልሰጥም

ይህ ማለት ጠላቶቻቸው የእስራኤልን ሕዝብ አያሸንፉም፣ ከእንግዲህ እህላቸውን አይወስዱም ማለት ነው። ምናልባትም ጠላቶች በግብር መልክ ወይም ሰራዊታቸውን ለመመገብ ባለፈው ጊዜ እህላቸውን ወስደው ሊሆን ይችላል።

ከእንግዲህ መብል እንዲሆናቸው እህልሽን ለጠላቶችሽ በእርግጥ አልሰጥም… ባዕዳንም አዲሱን ወይን ጠጅሽን አይጠጡም።

እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች በአንድነት የተቀመጡት አጽንዖትና ለመስጠትና መጠናቀቅን ለማመልከት ነው።

Isaiah 62:10

ወዲህ ኑ፤ በበሩ በኩል ኑ

‹‹ኑ›› የሚለው የተደጋገመው አስቸኳይ መሆኑን ለማሳየት ነው።

ሥሩ፣ አውራ መንገዱን ሥሩ

‹‹ሥሩ›› የሚለው ቃል የተደገመው ያህዌ ባስቸኳይ መንገዱ እንዲስተካከል መፈለጉን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ‹‹አውራ መንገድ›› ሕዝቡ የሚመለስበትን መንገድ ይወክላል። ይህ ከኢሳይያስ 40፥3 እና ኢሳይያስ 57፥14 ጋር ይመሳሰላል።

ድንጋዮች ሰብስቡ

‹‹መንገዱን ለስላሳ ለማድረግ ድንጋዮቹን አውጡ›› ድንጋይ በፍጥነት ለመራመድ እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ይወክላል።

ለሕዝቦች የምልክት ባንዲራ አንሡ

የምልክት ባንዲራ የሌሎችን ትኩረት መሳብ ያመለክታል። ይህም ማለት የሌሎች አገሮች ሰዎች የእስራኤልን ምድርና አድርግላቸዋለሁ እንዳለው ያህዌ የፈጸመውን ልብ እንዲሉ ያህዌ ሕዝቡን እየጠራ ነው ማለት ነው።

Isaiah 62:11

እነሆ

‹‹ልብ በሉ››

የምድር ዳርቻዎች

ሩቅ ቦታ ያለ ስፍራ የምድር ዳርቻዎች ተብሎአል። ይህም ማለት በዳርቻዎቹ መካከል ያለውንም ቦታ ያመለክታል። ኢሳይያስ 40፥28 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሩቅ ቦታ ያሉ ስፍራዎች›› ወይም፣ ‹‹በምድር ሁሉ››

የጽዮን ሴት ልጅ

‹‹ሴት ልጅ›› የኢየሩሳሌምን (ጽዮን) ሕዝብ ይወክላል። ኢሳይያስ 1፥8 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ዋጋው ከእርሱ ጋር ብድራቱም ፊት ፊቱ ይሄዳል

እነዚህ ሐረጎች አጽንዖት ለመስጠት ተመሳሳይ ሐሳብ ይወክላሉ። ኢሳይያስ 40፥10 ላይ ተመሳሳዩን ሐረግ እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

ትጠሪያለሽ

ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ይጠሩሻል››

---

Chapter 63

Isaiah 63:1

ይህ ከኤዶም… ከባሶራ የሚመጣ ማን ነው?

ኢሳይያስ የእስራኤል ጠላት ኤዶም ላይ የሚመጣውን የያህዌን ፍርድ ለማመልከት እንደ ጠባቂ በጥያቄና መልስ መልክ ይጠቀማል። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ከኤዶም ቀይ ለብሼ ከባሶራ እመጣለሁ››

ባሶራ

ይህ የኤዶም ዋና ከተማ ነው።

እኔ ነኝ

‹‹እኔ›› ያህዌን ይወክላል።

ልብስህ ለምን ቀይ ሆነ… በወይን መጥመቂያ

ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ልብስህ ላይ ያለው ቀይ በወይን መጥመቂያ የነበርህ ሰው አስመስሎሃል››

ወይን መርገጫ

የወይን መርገጫ ዐለት ውስጥ የተፈለፈለ ጐድጓዳ ነገር ሲሆን፣ የወይን ጠጅ እንዲወጣ ሰዎች የወይን ፍሬዎቹን የሚረግጡበት ነው።

Isaiah 63:3

ወይኑን ረገጥሁ

‹‹እኔ›› የሚለው ያህዌ ነው። ይህ ምስል የሚያመለክተው ያህዌ ጠላቶቹን መደምሰሱን ነው።

የበቀል ቀን

‹‹የበቀል ጊዜ›› ወይም፣ ‹‹በቀል የሚፈጸምበት ቀን››



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በቀል
ፍትሕ ለማምጣት ያህዌ በተገቢ መንገድ ይቀጣል። የእርሱ በቀል ከሰው በቀል ይለያል።
የምቤዥበት ዓመት
‹‹ዓመት›› የሚለው እስራኤልን ለመመለስ ያህዌ የወሰነውን ጊዜ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ የምቤዥበት ጊዜ››
Isaiah 63:5
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል
የገዛ ክንዴ ግን
‹‹ክንድ›› ኀይልን ይወክላል።
በመዓቴ አሰከርኋቸው
ይህም ማለት በመዓቱና በቁጣው ብዛት ያህዌ ግራ እንዲጋቡና ዐቅል እንዲያጡ አደረጋቸው ማለት ነው።
ደማቸውን አፈሰስሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ደም›› የሚገደሉትን የያህዌን ጠላቶች ሕይወት ይወክላል።
Isaiah 63:7
የያህዌን የኪዳን ታማኝነት እናገራለሁ
‹‹ታማኝነት›› የሚለውን ቃል፣ ‹‹ታማኝ›› ወይም፣ ‹‹በታማኝነት›› በማለት መግለጽ ይቻላል። ኢሳይያስ 16፥5 ላይ ‹‹የኪዳን ታማኝነት›› የሚለውን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ለኪዳኑ እንዴት ታማኝ እንደሆነ እናገራለሁ›› ወይም፣ ‹‹እግዚአብሔር በታማኝነቱ ለሕዝቡ ያደረጋቸውን ነገሮች እናገራለሁ››
እናገራለሁ
‹‹እኔ›› የሚለው የሚያመለክተው ኢሳይያስን ነው።
ለእኛ ያደረገውን
‹‹እኛ›› ኢሳይያስንና የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።
Isaiah 63:9
በመከራቸው ሁሉ
‹‹በመከራችን ሁሉ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። የሕዝቡ አካል እንደ መሆኑ ኢሳይያስ ራሱን ጨምሯል።
እርሱ ተጨነቀ
‹‹እርሱ›› የሚያመለክው ያህዌን ነው።
የፊቱ መልአክ
ይህ የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር ፊት የተላከውን ነው።
አንሥቶ ተሸከማቸው
ይህ ከብዙ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፃውያን መጠበቁንና ማዳኑን ያመለክታል። ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።
Isaiah 63:10
እነርሱ ግን ዐመፁ
‹‹እኛ ግን ዐመፅን›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። ኢሳይያስ እንደ ሕዝቡ አካል ራሱንም ጨምሯል።
መንፈስ ቅዱሱ
‹‹የያህዌ መንፈስ ቅዱስ››
Isaiah 63:11
እንዲህ አሉ
‹‹እንዲህ አልን›› እዚህ ላይ፣ ‹‹እነርሱ›› የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። የሕዝቡ አካል እንደ መሆኑ ኢሳይያስ ራሱንም ጨምሯል።
ከባሕር ያወጣቸውን
እስራኤላውያን ተሻግረው ከግብፃውያን እንዲያመልጡ ያህዌ በተአምር ቀይ ባሕርን መክፈሉ በውስጠ ታዋቂነት ግልጽ ነው።
የመንጋው እረኞች
አንዳንዴ መሪዎች ‹‹እረኞች›› ይባላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሕዝቡ መሪዎች››
Isaiah 63:12
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥለዋል
ታላቅ ኀይሉ ከሙሴ ቀኝ እጅ ጋር እንዲሄድ ያደረገ
‹‹ቀኝ እጅ›› በሙሴ በኩል የያህዌን ኀይል ይወክላል። ይህም ማለት ሙሴ ቀይ ባሕርን እንዲከፍል ያስቻለው የእግዚአብሔር ኀይል ነበር ማለት ነው።
ሜዳ ላይ እንደሚሮጥ ፈረስ አልተሰናከሉም
ይህ ማለት ፈረስ ሜዳ ላይ እንደሚራመድ ከግብፅ ወደ እስራኤል ሲጓዙ እስራኤላውያንም ለአረማመዳቸው እርግጠኞች ነበሩ ማለት ነው።
Isaiah 63:14
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥለዋል
ወደ ሸለቆ እንደሚወርድ የከብት መንጋ… ዕረፍት
ይህ የከብት መንጋ ሣሩ ወደ ለመለመበትና ውሃ ወዳለበት ሸለቆ የመሄዱ ምስል የእስራኤልን ሕዝብ እግዚአብሔር መምራቱንና መጠበቁን አጽንዖት ይሰጣል።
ለራስህ የምስጋና ስም እንዲሆን
‹‹የምስጋና ስም›› የሰውን ዝና ክብር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለራስህ የከበረ ዝና እንዲኖርህ››
Isaiah 63:15
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሎዋል
ቅንዓትህና ታላቅ ሥራህ የት አለ?
እግዚአብሔር እየረዳቸው ስለማይመስል ጥልቅ ስሜቱን ለመግለጽ ጸሐፊው ጥያቄ ያነሣል። ጥያቄውን በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቅንዓትህንና ታላቅ ሥራህን አላየንም››
ቸርነትህና ርኅራኄህ ከእኛ ርቀዋል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቸርነትህንና ርኅራኄኅን ከእኛ አርቀሃል››
አብርሃም ባያውቀን፣ እስራኤልንም ባይገነዘበን
በጣም ተለውጠው ስለ ነበር እዚህ የእስራኤል ሕዝብ አባቶች ዘሮቻቸውን ማወቅ አልቻለም። ‹‹አብርሃም›› እና፣ ‹‹ያዕቆብ›› ከረጅም ጊዜ በፊት የነበረውን ሕዝብ ይወክላሉ።
እስራኤል
ይህ እግዚአብሔር ለ፣ ‹‹ያዕቆብ›› የሰጠውን ስም ያመለክታል።
Isaiah 63:17
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥለዋል።
ያህዌ ለአንተ ከመታዘዝ ከመንገድህ እንድንወጣ፣ ልባችንንም እንድናደነድን ለምን አደረግህኸን?
ጸሐፊው ጥያቄውን ያቀረበው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማጉረምረም ለማመልከት ነው። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ለአንተ እንዳንታዘዝ ከመንገድህ እንድንወጣና እልኸኞች እንድንሆን አደረግኸን››
ለምን ከመንገድህ እንድንወጣ አደረግኸን?
የያህዌን ትእዛዝ አለመፈጸም ከትክክለኛው መንገድ መውጣት እንደሆነ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለምን ትክክል ያልሆነ ነገር እንድናደርግ አደረግኸን››
ልባችንን አደነደንህ
ይህ ማለት ለመስማትና ለመታዘዝ ባለ መፈለግ የያህዌን ትምህርት መቃወም ማለት ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› ዝንባሌን፣ ፍላጐትንና ስሜትን ይወክላል።
Isaiah 63:18
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥለዋል።
በስምህ አልተጠሩም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ስም›› የሚለው ቃል የቤተ ሰብ ግንኙነትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤተ ሰብህ አልነበሩም››
እኛ ሆነናል… በስምህ ተጠርተናል
አንዳንድ የዘመኑ ቅጂዎች ይህን ምንባብ በተለየ መንገድ ተርጉመዋል። ‹‹በስምህ እንደ ተጠሩ ሰዎች እኛም አንተ ገዢያችን እንዳልነበርህ ሆነናል››

---

Chapter 64
Isaiah 64:1
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ መናገር ቀጥለዋል
እንዲህ አድርገህ ቢሆን

ይህ ባለፈ ታሪካቸው የሆነውን የያህዌ መገኘት መፈለጉን ኢሳይያስ ጠንከር ባለ ቃለ አጋኖ ያስተዋውቃል።
ሰማያትን በቀደድህ ኖሮ
ሰማያትን በአስደናቂ ሁኔታ በመቅደድ ያህዌ ራሱን ቢገልጥ ኖሮ። ‹‹መቅደድ›› የሚለው ልብስን ግራና ቀኝ መሰንጠቅን ያመለክታል።
ተራሮች ቢናወጡ ኖሮ
ምድር በምትንቀጠቀጥበት ጊዜ እንደሚሆነው ተራሮች ቢንቀጠቀጡ ኖሮ።
እሳት ጭራሮውን እንደሚያቃጥል ወይም እሳት ውሃ እንደሚያፈላ
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር መገኘት ተራሮችንና ሕዝቡን ማንቀጥቀጥ እንደሚችል ነው።
Isaiah 64:3
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ መናገር ቀጥለዋል።
ዐይን አላየም
‹‹ዐይን›› መላውን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም አላየም››
Isaiah 64:5
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ መናገር ቀጥለዋል
አስቡ
ይህ ‹‹አስታውሱ›› ለማለት ፈሊጣዊ ንግግር ነው።
Isaiah 64:6
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ መናገር ቀጥለዋል
የጽድቅ ሥራችን እንደ መርገም ጨርቅ ነው
‹‹የመርገም ጨርቅ›› አንዲት ሴት ከማሕፀንዋ በምትደማበት ጊዜ የምትጠቀምበት ጨርቅ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ያደረጉት ሙከራ ሁሉ አልተሳካም ማለት ነው። ይህ ዐረፍተ ነገር አስደንጋጭ መሆን አለበት።
ሁላችንም እንደ ቅጠል ጠውልገናል
ኢሳይያስ የእስራኤልን ሕዝብ ከጠወለገ ቅጠል ጋር ያመሳስላል።
በደላችን እንደ ነፋስ ጠራርጐናል
ይህም ማለት የውድቀታቸው ምክንያት እንደ ማኅበረ ሰብ የፈጸሙት ኀጢአት ነበር ማለት ነው። የሕዝቡን በደል ኢሳይያስ የያህዌን ቅጣት ካመጣባቸው ነፋስ ጋር ያመሳስለዋል።
ፊትህን ከእኛ ሰወርህ
ይህ ማለት እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመከራ ተወ ማለት ነው።
Isaiah 64:8
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ መናገር ቀጥለዋል።
እኛ ሸክላዎች ነን፤ አንተ ሸክላ ሠሪ ነህ፤ ሁላችንም የእጅህ ሥራዎች ነን።
ይህ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ፈጠረ ማለት ነው።
አስቡ
ይህ ማለት ያለፈውን አስታውሱ ማለት ነው።
ሁላችንንም ተመልከተን
ኢሳይያስ ያህዌ ያሉበትን ሁኔታ እንዲያይ ይጠይቃል።
Isaiah 64:10
አጠቃላይ መረጃ
የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ መናገር ቀጥለዋል።
የተቀደሱ ከተሞችህ ምድር በዳ ሆኑ
ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ከተሞቹ መደምሰሳቸውንና የሚኖርባቸውም እንደሌለ ነው።
አባቶቻችን አንተን ያመሰገኑበት የተቀደሰውና ያማረው ቤተ መቅደሳችን በእሳት ተደምስሶአል።
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አባቶቻችን አንተን ያመሰገኑበትን የተቀደሰውንና ያማረውን ቤተ መቅደሳችንን ጠላት በእሳት አውድሞታል››
ያህዌ ለምን ዝም ትላለህ፤ ለምን ዝም ትላለህ እኛን በማዋረድም ትጸናለህ?
እግዚአብሔር እነርሱን ለመርዳት ባለ መምጣቱ ተስፋ መቁረጣቸውን ለመግለጽ በጥያቄዎች ተጠቅመዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እባክህ ዝም አትበል፤ እባክህ ዝም አትበለን እኛንም አታዋርደን!››

---

Chapter 65
Isaiah 65:1
ዝግጁ ነበርሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እኔ›› ያህዌን ያመለክታል።
ለማይታዘዝ ሕዝብ ቀኑን ሙሉ እጆቼን ዘረጋሁ
‹‹እጆችን መዘርጋት›› ልመናን ወይም ጥያቄ ለማቅረብ አንድ ሰው የሚያደርገውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እርዳታየን እንዲቀበሉ ያለ መታከት ለማይታዘዙ ሰዎች እጆቼን ዘረጋሁ››
Isaiah 65:3
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
በአትክልት ቦታዎች… በሸክላ ወለሎች
ይህ የሚያመለክተው ከነዓናውያን ጣዖት የሚያመልኩባቸውን ቦታዎች ነው። የተቀደሱ መሠዊያዎቻቸው ያህዌ ለመሠዊያ እንዳይውል በከለከለው በሸክላ የተሠሩ ነበሩ። የያህዌ መሠዊያዎች የተሠሩት ከድንጋይ ነበር።
በመቃብር መካከል ለሚቀመጡ ሌሊቱን ሁሉ ለሚጠብቁ
ይህ ሙታንን መጠየቅን ያመለክታል፤ ያህዌ ይህን ከለክሎአል።
የዐሣማ ሥጋ የሚበሉ
ያህዌ የእስራኤል ሕዝብ ዐሣማ እንዲበሉ አልፈቀደም።
Isaiah 65:5
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤልና ስለ እስራኤል መናገር ቀጥሏል።
እነዚህ ነገሮች በአፍንጫዬ እንደ ጢስ ናቸው
እነዚህ ዘወትር የሚያውኩትን ሰዎች ያህዌ የሰውን እስትንፋስ ከሚያውክ ጢስ ጋር ያመሳስላቸዋል።
ቀኑን ሙሉ የሚቃጠል እሳት
ያህዌ የእስራኤልን ሕዝብ ቀኑን በሙሉ ዝግ ብሎ ከሚነድና ጢሱም ያለ ማቋረጥ ከሚወጣ እሳት ጋር ያመሳስላቸዋል።
Isaiah 65:6
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤልና ስለ እስራኤል ሕዝብ መናገር ቀጥሏል።
እነሆ፣ ተጽፎአል
‹‹ልብ በሉ፤ አስተውሉ››
በጭናቸው
ይህ ማለት እግዚአብሔር በሚገባ ይቀጣቸዋል ማለት ነው። ያህዌ ሕዝቡን መቅጣቱን እግሮቻቸው መካከል ከሚቀመጥ ነገር ጋር ያመሳስለዋል።
Isaiah 65:8
በወይኑ ዘለላ ውስጥ እንዳለ ጭማቂ
ያህዌ የእስራኤልን ሕዝብ ውስጡ መልካም ጭማቂ ከያዘ የወይን ዘለላ ጋር ያመሳስላቸዋል።
ዘለላ ውስጥ እንዳለ ጭማቂ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዘለላው ውስጥ ጭማቂ ስታገኙ››
ሙሉ በሙሉ አላጠፋቸውም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጻድቃን የሆኑትን አንዳንዶቹን እኖራቸዋለሁ››
Isaiah 65:9
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል
ተራራዬ
ይህ ኢየሩሳሌምና መላው ይሁዳ ውስጥ ያሉ ከፍታ ቦታዎች ያመለክታል።
ሣሮን
ይህ ለም የግጦሽ ቦታ ነው።
የአኮር ሸለቆ
ይህ ምናልባት ከኢየሩሳሌም አንሥቶ እስከ ደቡባዊ ኢያሪኮ የሚዘረጋ ሸለቆ ስም ሊሆን ይችላል። ይህም ለም የግጦሽ ቦታ ነው።
Isaiah 65:11

አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል
የተቀደሰ ተራራ
ኢሳይያስ 11፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።
ገበታ ላዘጋጁ… የድብልቅ ወይም ጠጅ ዋንጫዎችን የሞሉ
ሰዎች መብልና መጠጥ አምጥተው እንደ አምልኮ ጣዖት ፊት ያደርጋሉ
የተደባለቀ ወይን ጠጅ
ቅመማ ቅመሞች የተጨመሩበት ወይን ጠጅ
ዕድል… ዕጣ ፈንታ
እነዚህ የሐሰተኛ አማልክት ስሞች ናቸው ‹‹ጋድ›› እና፣ ‹‹ሜኒ›› በመባልም ይጠራሉ።
Isaiah 65:12
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ በእስራኤል ጣዖት ለሚያመልኩ ሰዎች መናገር ቀጥሏል።
ለሰይፍ እዳርጋችኃለሁ
‹‹ሰይፍ›› የእርሱን ጥሪ የማይሰሙትን ለመቅጣት ያህዌ የሚጠቀምበትን ማንኛውንም የጦር መሣሪያ ይወክላል።
በተጣራሁ ጊዜ አልመለሳችሁም፤ በተናገርሁ ጊዜ አልሰማችሁም
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ቢሆኑም የተደገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው።
Isaiah 65:13
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ በእስራኤል ጣዖት ለሚያመልኩ ሰዎች መናገር ቀጥሏል።
እነሆ፣ ባርያዎቼ
‹‹አስተውሉ፤ ልብ በሉ›› ያህዌ የደገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው።
ልባችሁ በማዘኑ ትጮኻላችሁ፤ መንፈሳችሁ በመሰበሩም ወዮ ትላላችሁ
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ቢሆኑም፣ የተደገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው።
መንፈሳችሁ በመሰበሩ
ይህ አገላለጽ እስከፊ ተስፋ መቁረጥና ሐዘንን፣ ከከባድ ጫና የተነሣ መሰበር ጋር ያመሳስላል።
Isaiah 65:15
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ በእስራኤል ጣዖት ለሚያመልኩ መናገር ቀጥሏል።
በእውነት አምላክ በእኔ ይባረካል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁልጊዜ እውነት የምናገር እኔ እባርከዋለሁ››
ያለፈው ዘመን መከራ ይረሳል… ይሰውራል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ እነዚህን መከራዎች ስለማላስብ ያለፈውን ዘመን መከራ ይረሱታል››
ከዐይኖቼ ይሰወራሉ
‹‹ከዐይኖች መሰወር›› ከያህዌ ትኩረትና ትውስታ መወገድን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ስለ እነርሱ አላስብም››
Isaiah 65:17
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል
እዩ
‹‹ልብ በሉ፤ አስተውሉ››
አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር
ሁለቱም በመካከል ያለውን ማንኛውንም ነገር የሚጨምሩ ጽንፎች ናቸው።
ያለፉት ነገሮች አይታሰቡም፤ አይታወሱም
ሁለቱም ሐረጐች ተመሳሳይ ነገር ማለት ሲሆኑ፣ በአንድነት የሆኑት አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባለፈው ጊዜ የሆነውን አታስቡትም››
እናንተ ደስ ይላችኃል
‹‹እናንተ›› የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ባርያዎችን ሁሉ ነው።
የልቅሶና የጩኸት ድምፅ ከእንግዲህ እርሷ ውስጥ አይሰማም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ በእርሷ ውስጥ የጭንቀት ለቅሶና ጩኸት አይሰማም››
Isaiah 65:20
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለታማኝ ሕዝቡ መናገር ቀጥሏል።
አንድ መቶ ዓመት
‹‹100 ዓመት››
እንደ ወጣት ይቆጠራል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። ‹‹ሰዎች እንደ ወጣት ይቆጥሩታል››
የተረገመ ይባላል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ይህን ሰው የተረገመ ይሉታል››
Isaiah 65:22
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለታማኝ ሕዝቡ መናገር ቀጥሏል
የሕዝቤ ዕድሜ እንደ ዛፍ ዕድሜ ይሆናል
‹‹ሕዝቤ እንደ ዛፍ ረጅም ዘመን ይኖራሉ››
ያህዌ የባረካቸው ሰዎች ልጆች ናቸው
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱ ያህዌ የባረካቸው ሰዎች ልጆች ናቸው››
Isaiah 65:24
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለታማኝ ሕዝቡ መናገር ቀጥሏል።
የተቀደሰ ተራራ
ኢሳይያስ 11፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት።

Chapter 66
Isaiah 66:1
ሰማይ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም የእግሬ ማረፊያ ናት
ያህዌ ሰማይን ከዙፋን፣ ምድርን ከእግሩ ማረፊያ ጋር የሚያመሳስለው ምን ያህል ታላቅ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ነው።
ታዲያ፣ የምትሠሩልኝ ቤት የት አለ? የማርፍበትስ ቦታ የታለ?
የሰው ልጅ ለእርሱ መኖሪያ መሥራት እንደማይችል አጽንዖት ለመስጠት ያህዌ ጥያቄዎች ያቀርባል።
Isaiah 66:2
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል
እነዚህን ነገሮች ሁሉ እጄ ሠርታለች
ያህዌ ለእርሱ ኀይልና ሥልጣን አጽንዖት በሚሰጠው በእጁ ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ሠርቻለሁ››
ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን ነገር እርግጠኝነት ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጉመው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንዲህ ብሏል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ እንዲህ ብያለሁ››
ትሑት የሆነ መንፈሱ የተሰበረ
እዚህ ‹‹የተሰበረ›› እና፣ ‹‹ትሑት›› በእውነት ትሑት የሆነና ለእምነቱ መከራ የሚቀበል ሰውን ያመለክታል።
Isaiah 66:4
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ ክፉ ሰዎች መናገር ቀጥሏል
በፊቴ ክፉ የሆነውን
እዚህ ላይ ፊት ፍርድን ወይም ውሳኔን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ነው ያልሁትን›› ወይም፣ ‹‹በእኔ ፍርድ ክፉ የሆነውን››
Isaiah 66:5
ያህዌ ይክበር
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌን አክብሩ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ራሱን ያክብር››
እነርሱ ግን ያፍራሉ
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አስፍራቸዋለሁ››
Isaiah 66:6
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ የአምላኪዎቹን ግብዝነት ቅጣት ይገልጻል
Isaiah 66:7
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር ቀጥሏል፡፡
ከማማጧ በፊት ትወልዳለች፤ በምጥ ጣር ከመያዟ በፊት ወንድ ልጅ ትገላገላለች
ያህዌ እንደምትወልድ ሴት ስለ ጽዮን ይናገራል፡፡ ምንም እንኳ ጽዮን ብትወድምም፣ ሕዝቡም እዚያ ባይኖሩም፣ በጥቂት ጥረት በፍጥነት መላው ሕዝብ ከእርሷ ይመጣል፡፡
እንደዚያ ያለ ነገር ማን ሰምቷል? እንደዚህ ያለ ማን ዐይቷል? በአንድ ቀን አገር ይወለዳልን? ሕዝብስ በቅጽበት ይገኛልን?
ይህ ሁኔታ ምን ያህል ያልተለመደ እንደሚሆን አጽንዖት ለመስጠት ያህዌ ጥያቄዎች ያነሣል፡፡ መጨረሻ ላይ ጽዮን እስከምትጠቀስ ድረስ ተከታታይ ጥያቄዎቹ ውጥረት ይፈጥራሉ፡፡
Isaiah 66:9
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ እንደ እናት ስለ ኢየሩሳሌም መናገር ቀጥሏል (ኢሳይያስ 66፥7-8 ይመ)
ሊወለድ የተቃረበውን እንዳይወለድ አደርጋለሁን... መውለድ?
ያህዌ ጥያቄውን ያቀረበው ለኢየሩሳሌም ሕዝብ የሰጠውን ተስፋ እንደሚፈጽም አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡
Isaiah 66:10
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ኢየሩሳሌም እናት እንደሆነች፣ የኢየሩሳሌም ሰዎችም የተወለዱ ልጆች እንደሆኑ ይናገራል፡፡ (ኢሳይያስ 66፥7-8 ይመ.)
ከሚያጽናኑ ጡቶቿ ትጠባላችሁ ትረካላችሁም
ይህ ማለት ኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሰላምና የመጽናናት ቦታ ትሆናለች ማለት ነው፡፡ ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በወተቷ ታረካችኋለች፤ በጡቶቿ ታጽናናችኋለች››
Isaiah 66:12
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ እንደ እናት ስለ ኢየሩሳሌም መናገር ቀጥሏል፡፡ (ኢሳይያስ 66፥7-8 ይመ.)
እንደ ወንዝ... ሞልቶ እንደ ተረፈ ወንዝ
ይህ ማለት እንደ ወንዝ ዘላቂና ብዙ የሆነ የተትረፈረፈ ብልጥግና እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያመጣል ማለት ነው፡፡
ትጠባላችሁ በዕቅፏም ትያዛላችሁ፤ በጭኖቿ ላይ ትፈነድቃላችሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በክንዶቿ ታቅፋችኋለች፤ በደስታ በጭኖቿ ትይዛችኋለች!››
እኔ አጽናናችኋለሁ፤ እናንተም በኢየሩሳሌም ትጽናናላችሁ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ በኢየሩሳሌም አጽናናችኋለሁ››
Isaiah 66:14
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝብ መናገር ቀጥሏል፡፡
ዐጥንታችሁ ይለመልማል
‹‹ዐጥንት›› መላውን አካል ያመለክታል፡፡
እንደ ሣር ቡቃያ ይለመልማል
‹‹የሣር ቡቃይ›› ቶሎ እና ጠንክሮ ማደጉ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጤናና ጥንካሬ ጋር ተመሳስሎአል፡፡
የያህዌ እጅ ለባርያዎቹ ይታወቃል፡፡
‹‹እጅ›› ኀይልን ያመለክታል፡፡ ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ኀይሉን ለባርያዎቹ ይገልጣል››
Isaiah 66:15
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝብ መናገር ቀጥሏል፡፡
ከእሳት ጋር ይመጣል
ብዙውን ጊዜ ያህዌ በብሉይ ኪዳን የሚገለጠው ቁጣውንና ፍርዱን በሚያመለክት እሳት ታጅቦ ነበር፡፡
እንደ ዐውሎ ነፋስ
ዐውሎ ነፋስ ፍርዱን እውን ለማድረግ የያህዌን ብርቱ ሥራ ይወክላል፡፡
ከሰይፉ ጋር
‹‹ሰይፍ›› ጦርነትንና ግድያን የሚወክል አንድ የጦር መሣሪያ ነው፡፡
በያህዌ የተገደሉ ብዙ ይሆናሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ብዙዎችን ይገድላል፡፡
Isaiah 66:17
አጠቃላይ መረጃ
ኢሳይያስ መናገር ቀጥሏል
ራሳቸውን ይቀድሳሉ
‹‹እነርሱ›› ያህዌን የሚያመልኩ ሆኖም ከመንገዱ በተቃራኒ የሚሄዱ ናቸው፡፡
ወደ አትክልት ቦታው ይገባሉ
ይህ ጣዖቶች ለማምለክ ሰዎች የሚሄዱበት ቦታ ነው፡፡
በመካከል ያለው
ይህ የሚያመለክተው ጣዖቶቹን ለማምለክ የሚሄዱትን ሰዎች መሪ ነው፡፡
ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን ነገር እርግጠኝነት ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል፡፡ ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጉመው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››
Isaiah 66:18
እኔ ዐውቃለሁ
‹‹እኔ›› የሚያመለክተው ያህዌን ነው፡፡
ሥራቸው... ሐሳባቸው
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ቀደም ሲል ያህዌ የተናገረላቸውን ግብዝ የሆኑ አምላኪዎችን ነው፡፡
ፉጥ... ሉድ... ቶባል... ያዋን
እነዚህ ከእስራኤል ምድር ርቀው ያሉ ቦታዎች ናቸው፡፡
Isaiah 66:20
ያመጣሉ
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው የተረፉትንና ለሕዝቡ የመሰከሩ ባዕዳን ሰዎች ነው፡፡ በምርኮ ከተወሰዱ እስራኤላውያን ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ይመለሳሉ፡፡
የተቀደሰ ተራራ
ኢሳይያስ 11፥9 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት፡፡
Isaiah 66:22
አዲሱ ሰማይና አዲሱ ምድር
ኢሳይያስ 65፥17 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት፡፡
ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረውን ነገር እርግጠኝነት ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል፡፡ ኢሳይያስ 30፥1 ላይ እንዳለው ተርጉመው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ይህን ተናግሮአል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››
Isaiah 66:24
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መናገር አቁሞአል
ይሄዳሉ
‹‹እነርሱ›› የሚያመለክተው ያህዌን ለማምለክ የመጡ ታማኝ እስራኤላውያንና ባዕዳንን ጨምሮ ሰዎችን ሁሉ ነው፡፡
ትሎቹ... እሳቱ
ለያህዌ ቅጣት አጽንዖት ለመስጠት ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ነው፡፡
የሚበሏቸው ትሎች
ትሎች የሚያመለክቱት ያህዌ ዐመፀኞች ላይ የሚያመጣውን የመበስበስና የመበላሸትን አስፈሪነት ነው፡፡
የሚበላቸው እሳት
እሳት የያህዌን ቅጣት ይወክላል፡፡
አይጠፋም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለዘላለም ይነዳል››
ሥጋ ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው ከሞት የተረፉ ሕያው ፍጥረትን ሁሉ ነው፡፡

Chapter 1

Jeremiah 1:1

ከካህናቱ አንዱ የሆነ የኬልቅያስ ልጅ ኤርምያስ

“ኤርምያስ፣ የኬልቅያስ ልጅ። ኤርምያስ ከካህናቱ አንዱ ነበር”

ኬልቅያስ

ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓናቶት

ይህ የከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የብንያም አገር

“ለብንያም ጎሳ የተሰጠች ምድር”

የእግዚአብሔር ቃል ወደ እርሱ መጣ

ይህ ፈሊጥ ጥቅም ላይ የዋለው እግዚአብሔር ለእርሱ መልእክት እንደሰጠው ለማወጅ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር መልእክት ለእርሱ ሰጠው” ወይም “እግዚአብሔር ለኤርምያስ ተናገረው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ

ይህ በብሉይ ኪዳን ራሱን ለሕዝቡ የገለጠበት የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህንን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ ለመረዳት የትርጉም ቃል ገጽ ላይ ሄደው ይመልከቱ።

በይሁዳ ንጉሥ በአሞጽ ልጅ በኢዮስያስ ዘመን

እዚህ ላይ “ዘመን” የሚለው ንጉሱ የገዛበትን ጊዜ የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የአሞጽ ልጅ ኢዮስያስ የይሁዳ ንጉሥ በነበረበት ጊዜ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አሥራ ሦስተኛው ... አሥራ አንደኛው

(ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

አሞጽ

ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በመንግስቱ

“የአሞጽ መንግስት”

እንዲህ ሲል መጣ

“የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ መጣ”

በይሁዳም ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም ዘመን

እዚህ ላይ “ዘመን” የሚለው ንጉሱ የገዛበትን ጊዜ የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የኢዮስያስ ልጅ ኢዮአቄም የይሁዳ ንጉሥ በነበረበት ጊዜ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

አምስተኛው ወር

ይህ በዕብራይስጥ የቀን መቁጠርያ አምስተኛው ወር ነው። ይህ በምዕራባውያን የቀን መቁጠርያ የሐምሌ የመጨረሻው ክፍልና የነሐሴ የመጀመርያው ክፍል ወቅት ነው። (የዕብራይስጥ ወራቶች እና ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

የሴዴቅያስ

ይህ የሴዴቅያስን አመራር የሚያመለክት ነው። ይህ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሴዴቅያስ የመንግስቱ ዘመን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የኢየሩሳሌም ሕዝብ እንደ እስረኞች በተወሰዱበት ጊዜ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። ወደ ባቢሎን እንደተወሰዱ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የባቢሎን ሰራዊት የኢየሩሳሌምን ሕዝብ እንደ እስረኞች በወሰዳቸው ጊዜ” ወይም “የባቢሎን ሰራዊት የኢየሩሳሌምን ሕዝብ እንደ እስረኞች ወደ ባቢሎን በወሰዳቸው ጊዜ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 1:4

የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ

ይህ ፈሊጥ ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር መልእክት ሰጠኝ። እንዲህ አለ” ወይም “እግዚአብሔር ይህን መልእክት ለእኔ ተናገረኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰርቼሃለሁ

“ቅርጽ ሰጥቼሃለሁ”

ከማኅፀን ከመውጣትህ በፊት

ይህ ማኅፀንን ሳንጠቅስ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከመወለድህ በፊት”

ወዮ ጌታ እግዚአብሔር

እዚህ ላይ “ወዮ” የሚለው ቃል ኤርምያስ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ለማድረግ መፍራቱን ያሳያል።

እንዴት መናገር እንዳለብኝ አላውቅም

ኤርምያስ በጉባኤ ለመናገር እንደሚፈራ ለማሳየት ምናልባት እያጋነነ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በጉባኤ እንዴት መናገር እንዳለብኝ አላውቅም” ወይም” ለሰዎች አዋጅ መናገር እንዴት እንዳለብኝ አላውቅም” (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 1:7

እነርሱን አትፍራቸው

“ሕዝቡን አትፍራ፣ እኔ ለእነርሱ እንድትናገር እልክሃለሁ”

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

“ይህ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር በቁጥር 7 እና 8 ላይ የተናገረውን የሚያመለክት ነው።

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተነገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 1:9

ከዚያም እግዚአብሔር እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ይህ እግዚአብሔርን የሚወክል ተለዋጭ ዘይቤ ሲሆን ለኤርምያስ የመናገር ልዩ ስልጣን መስጠቱን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ከዚያም እግዚአብሔር አፌን እንደ ዳሰሰኝ ሆኖ ተሰማኝ” ወይም 2) ኤርምያስ ራዕይ እያየ ነበርና እግዚአብሔር ይህን ያደረገው ለኤርምያስ የመናገር ልዩ ስልጣን እንደሰጠው ለማሳየት ምሳሌአዊ ድርጊት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ከዚያም እግዚአብሔር እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምሳሌያዊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለሁ

ይህ ሀረግ እግዚአብሔር ለኤርምያስ መልእክቱን መስጠቱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለሕዝቡ ትናገር ዘንድ እኔ መልእክቴን ለአንተ ሰጥቼሃለሁ” ወይም “ለሕዝቡ መልእክቴን እንድትናገር አስችየሃለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ፣ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ፣ ትሠራና ትተክል ዘንድ ... ሾሜሃለሁ

ኤርምያስ የእግዚአብሔር መልእክቶች እንደሚፈጸሙ ለተለያዩ መንግስታት በመናገር እነዚህን ነገሮች ይሰራል።

ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ፣ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ፣ ትሠራና ትተክል ዘንድ

አንዳንድ መንግስታትን ይነቅላል፣ ያፈርሳል፣ ያጠፋል ደግሞም ይገለብጣል፣ ሌሎች መንግስታትን ደግሞ ይሰራል እንዲሁም ይተክላል።

መንቀል

እግዚአብሔር ስለ ኤርምያስ ሲናገር መንግስታቱ ተክሎች እንደሆኑና እርሱ ከመሬት ነቅሎ እንደሚጥላቸው አድርጎ በመግለጽ በሚናገረው ቃል መንግስታትን እንደሚያፈርስ ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማጥፋት እና መገልበጥ

እነዚህ ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ኤርምያስ እነዚህን ቃላት የተጠቀመው ይህ ቃል በእርግጠኝነት እንደሚፈጸም ለማሳየት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

መስራት እና መትከል

እግዚአብሔር ስለ ኤርምያስ ሲናገር መንግስታት እንደ ሕንጻ እንደሆኑና እርሱ እንደሚገነባቸው፣ እንደ ተክሎች እንደሆኑና እርሱ እንደሚተክላቸው በዚህም ጠንካራ እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 1:11

የእግዚአብሔር ቃል ምን ታያለህ? እያለ ወደ እኔ መጣ

ይህ ፈሊጥ ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ውሏል። በ ኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ ቃላት እንዴት እንደተረጎምኻቸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር መልእክት ሰጠኝ። እንዲህ አለ፦ ‘ምን’” ወይም “እግዚአብሔር ይህንን መልእክት ለእኔ ተናገረኝ፦ ‘ምን’” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የለውዝ ቅርንጫፍ አያለሁ አልሁ

እግዚአብሔር ለኤርምያስ መንፈሳዊ ራዕይ አሳየው።

የለውዝ ቅርንጫፍ

የለውዝ ዛፍ የለውዝ ፍሬ የሚሰጥ ዛፍ ነው። (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁ

ይህ የሚወክለው እግዚአብሔር የተናገረውን እንደሚፈጽመው ዋስትና መስጠቱን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ እፈጽመው ዘንድ ቃሌን አስባለሁ” ወይም “እኔ የተናገርሁትን እንደምፈጽመው ዋስትና እሰጣለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቃሌ እተጋለሁ

“ለውዝ” እና “እተጋለሁ” የሚሉት የዕብራይስጡ ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እግዚአብሔር ቃሉን በእርግጠኝነት እንደሚፈጽም ኤርምያስ እንዲያስብ እግዚአብሔር ይፈልጋል።

Jeremiah 1:13

ሁለተኛም ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ... እያለ ወደ እኔ መጣ

ይህ “የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ መጣ” የሚለው ፈሊጥ ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣውን መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። በ ኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፣ ለውጥ የሚያስፈልግ ከሆነ ለውጥ አድርግ። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ መልእክት ሰጠኝ። እንዲህም አለኝ” ወይም “እግዚአብሔር ይህንን ሁለተኛ መልእክት ለእኔ ተናገረኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ላይ ላዩን የሚፈላ

ላይ ላዩን የሚለው የሚያመለክተው በማሰሮ ውስጥ ያለውን የውኃው የላይኛውን ክፍል ነው። ኤርምያስ ውኃው ሲፈላ ማየት ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ውኃው የሚፈላ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አፉ ከሰሜን ወደዚህ ያዘነበለ

ይህ ማሰሮው ወደ ሰሜን ማለትም ኤርምያስ ወደ ነበረበት ወደ ይሁዳ ያዘነበለ ነው ማለት ነው።

ከሰሜን ወገን ክፉ ነገር ይገለጣል

“ክፉ ነገር ከሰሜን በኩል ይወርድባቸዋል።” ይህ የሚወክለው እግዚአብሔር ከሰሜን ወደ ደቡብ ክፉ ነገር እንደሚያመጣ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ክፉ ነገር ከሰሜን ይመጣል” ወይም “እኔ ከሰሜን ክፉ ነገር እልካለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 1:15

አያያዥ ሀሳብ፦

እግዚአብሔር ከሰሜን ስለሚመጣው ክፉ ነገር ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

ሁሉ

ይህ ጅምላ ፍረጃ በሰሜናዊ ክፍል ያሉትን መንግስታት ነገስታትን ሁሉ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እያንዳንዱ ንጉስ” ወይም “የሰሜናዊው ክፍል ነገስታት በሙሉ” (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም በር መግቢያ ዙፋኑን ያስቀምጣል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) ይህ የሚወክለው በኢየሩሳሌም ላይ መግዛትን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በኢየሩሳሌም በር መግቢያ ላይ ይገዛል” ወይም 2) ይህ የሚወክለው በኢየሩሳሌም ላይ መፍረድ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በኢየሩሳሌም ላይ ይፈርዳል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዙሪያዋ በቅጥርዋ ሁሉ ላይ

“በዙሪያዋ በቅጥርዋ ሁሉ ላይ” ዙፋናቸውን ያስቀምጣሉ የሚለው በኢየሩሳሌም ዙርያ ያለውን ቅጥርዋን ለማፍረስ ለጦር ሰራዊቶቻቸው ትዕዛዝ መስጠታቸውን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በይሁዳ ዙርያ ያለውን ቅጥር ለማፍረስ ለጦር ሰራዊቶቻቸው ትዕዛዝ ይሰጣሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በይሁዳም ከተሞች ሁሉ ላይ

“በይሁዳም ከተሞች ሁሉ ላይ” ዙፋናቸውን ያስቀምጣሉ የሚለው የይሁዳ ከተሞችን ሁሉ ለማፍረስ ለጦር ሰራዊቶቻቸው ትዕዛዝ መስጠታቸውን የሚወክል ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርዴን በእነርሱ ላይ እናገራለሁ

“እነርሱን እንዴት እንደምቀጣ እናገራለሁ”

ፍርዴን በእነርሱ ላይ እናገራለሁ

“በይሁዳ ሕዝብ ላይ ፍርድን እናገራለሁ”

በእጃቸው ለሰሩአቸው ስለ ሰገዱ

ሕዝቡ ጣዖታቱን በራሳቸው እጆች ስለሰሩአቸው፣ ጣዖታቱ ሊሰገድላቸው የሚገቡ እንዳልሆኑ ሊያውቁ ይገባቸው ነበር

Jeremiah 1:17

አያያዥ ሀሳብ፦

እግዚአብሔር ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

አትፍራቸው ... በፊታቸው አስፈራሃለሁ

እዚህ ላይ “አትፍራቸው” የሚለው ከመጠን በላይ መፍራትን ይወክላል፣ “አስፈራሃለሁ” የሚለው ደግሞ ኤርምያስን በጣም እንዲፈራ ማድረግን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አትፍራ ... አስፈራሃለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ

“ትኩረት ስጥ!”

በምድሪቱ ሁሉ ላይ እንደ ተመሸገ ከተማ፣ እንደ ብረትም ዓምድ፣ እንደ ናስም ቅጥር ዛሬ አድርጌሃለሁ

እንደ እነዚህ ነገሮች ጠንካራ መሆን እግዚአብሔር እንዲናገር የነገረውን ነገር ለመናገር ልበ ሙሉ መሆንና የማይለወጥ አቋም መያዝን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በምድሪቱ ሁሉ ላይ እንደ ተመሸገ ከተማ፣ እንደ ብረትም ዓምድ እና እንደ ናስ ቅጥር ጠንካራ አድርጌሃለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብረት ... ናስ

እነዚህ በዚያን ጊዜ እጅግ በጣም ጠንካራ በመሆናቸው የሚታወቁ ነገሮች ነበሩ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ ሁሉ

ይህ የምድሪቱን ሕዝብ ሁሉ የሚወክል ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከአንተ ጋር ይዋጋሉ

ይህ የሚያመለክተው የይሁዳ ሕዝብን ነው።

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

እግዚአብሔር እርሱ የተናገረው ቃል እንደሚፈጸም እርግጠኝነቱን ለመግለጽ ስለ ራሱ በስሙ ተናግሯል። በ ኤርምያስ 1:8 ላይ ይህን እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 2

Jeremiah 2:1

የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፣ ሂድ

ይህ ፈሊጥ ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። በ ኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ ቃላት እንዴት እንደተረጎምኻቸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር መልእክት ሰጠኝ። እንዲህ አለኝ፦ ‘ሂድ’” ወይም “እግዚአብሔር ይህን መልእክት ለእኔ ተናገረኝ፦ ‘ሂድ’” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ሂድና በኢየሩሳሌም ጆሮ ተናገር

“ሂድና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ሊሰሙህ በሚችሉበት ስፍራ ተናገር”

ስለ አንቺ አስባለሁ

“ስለ አንቺ አስታውሳለሁ”

በወጣትነትሽ ጊዜ የነበረሽን የቃል ኪዳን ታማኝነት፣ ፍቅርሽንም

“ታማኝነት፣” ወጣትነት፣” እና “ፍቅር” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “ታማኝ” እና “ወጣት፣” በሚሉት ቅጽሎች እና “መውደድ” በሚለው ግስ ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ወጣት በነበርሽ ጊዜ፣ ለቃል ኪዳናችን እንዴት ታማኝ እንደነበርሽ፣ እና እንዴት እንደወደድሽኝ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእጮኝነት ጊዜአችን

እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ስለነበረው ግንኙነት ሲገልጽ ሁለቱ ለመጋባት ተጫጭተው እንደነበር አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሁለታችን እንድንጋባ በመጀርያ በተስማማንበት ጊዜ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘር ባልተዘራበት ምድር

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ማንም ሰው ዘር ባልዘራበት ምድር” ወይም “ምንም ዓይነት የምግብ ዘር ባልበቀለበት ምድር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የመከሩ በኩራት ነበረች
እግዚአብሔር ስለ እስራኤል ሲገልጽ ለእግዚአብሔር የተበረከተች ስጦታ እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ "እንደ እርሱ መከር በኩራት" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከመከሩ በኩራት የበሉት ሁሉ እንደ በደለኞች ይቈጠራሉ
እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ጥቃት ስለፈጸሙት ሲናገር ለእግዚአብሔር ብቻ የተለየውን መስዋዕት እንደበሉ አድርጎ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ "በእስራኤል ላይ ጥቃት የፈጸሙ በሙሉ ከመከሩ በኩራት እንደበሉ ሕዝብ በበደላቸው ተጠይቀዋል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉ ነገር በእነርሱ ላይ መጣባቸው
"በእነርሱ ላይ መጣባቸው" የሚለው ሀረግ በእነርሱ ላይ ሆነ ለሚለው ሃሳብ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "ክፉ ነገር በእነርሱ ላይ ሆነ" ወይም "እኔ በእነርሱ ላይ አሰቃቂ ነገር እንዲሆንባቸው አደረግሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ቃል በእርግጠኝነት እንደሚፈጸም ለመግለጽ ስለ ራሱ በስሙ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ "እግዚአብሔር ያወጀው ይህ ነው" ወይም "እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው" (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ))

## Jeremiah 2:4

የያዕቆብ ቤት የእስራኤልም ቤት ወገኖች ሁሉ
ያዕቆብና እስራኤል ለአንድ ሰው የተሰጡ ሁለት ስሞች ነበሩ፣ ስለዚህ እነዚህ ሁለት ሀረጎች የሚያመለክቱት ለአንድ የሕዝብ ወገን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "እናንተ የያዕቆብ ወገኖች ሁሉ" (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
የያዕቆብ ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የያዕቆብን ወገኖች ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "የያዕቆብ ወገኖች" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤል አገርና ሕዝብ የሆኑትን የእስራኤልን ወገኖች ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤላውያን ሕዝብ ወገኖች" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
አባቶቻችሁ እኔን ከመከተል የራቁት፣ የማይጠቅሙ ጣዖቶችን የተከተሉና ለራሳቸውም ከንቱም የሆኑ ምን ክፋት አግኝተውብኝ ነው?
እርሱ በሕዝቡ ላይ ምንም ዓይነት ክፋት ስላላደረገ ሕዝቡ እርሱን በመተው ጣዖቶችን መከተል አልነበረባቸውም ብሎ ለመናገር እግዚአብሔር እነዚህን ጥያቄዎች ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም፦ "እኔ ለአባቶቻችሁ ምንም ዓይነት ክፋት አላደረግሁም፣ ስለዚህ እኔን ከመከተል ርቀው መሄድ አልነበረባቸውም፣ የማይጠቅሙ ጣዖቶችን ተከትለው መሄድ አልነበረባቸውም። ይህንን በማድረጋቸው እነርሱ ራሳቸው የማይጠቅሙ ሆኑ!" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
እኔን ከመከተል ርቀው ሄዱ
ይህ የሚወክለው እግዚአብሔርን መተውና ለእርሱ ታማኝ ለመሆን እምቢተኛ መሆንን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "እነርሱ እኔን ትተውኛል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የማይጠቅሙ ጣዖቶችን ተከትለው ሄዱ
ይ የሚወክለው ለጣዖቶች ታማኝ መሆንንና እነርሱን ማምለክ መምረጥን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "የማይጠቅሙ ጣዖቶችን አመለኩ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የማይጠቅሙ ጣዖቶች
ሰዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ነገር ግን ምንም ዓይነት መልካም ነገር የማያመጡላቸው ጣዖቶች። ትርጉሙ ጠቃሚ የሆኑ አንዳንድ ጣዖቶች እንዳሉ ሰዎች እንዲያስቡ የሚያደርግ መሆን የለበትም።
አላሉም
ይህ በክፍሉ የተገለጸውን መናገር ይኖርባቸው እንደነበር የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "እንዲህ ማለት ነበረባቸው" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከግብጽ ምድር ያወጣን እግዚአብሔር ... ወዴት አለ?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እግዚአብሔር ለሕዝቡ አስፈላጊ መሆኑን ለማሳየት ጥቅም ላይ መዋል ነበረበት። አማራጭ ትርጉም፦ "እግዚአብሔር ያስፈልገናል። ከግብጽ ምድር ያወጣን እርሱ ነው።" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በማይኖርበት ... የመራን እግዚአብሔር ወዴት አለ?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ እግዚአብሔር ለሕዝቡ አስፈላጊ መሆኑን ለማሳየት ጥቅም ላይ መዋል ነበረበት። አማራጭ ትርጉም፦ "እግዚአብሔር ያስፈልገናል። በማይኖርበት ... የመራን እግዚአብሔር እርሱ ነው።" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ድርቅና ጥልቅ ጨለማ ያለበት ምድር
"ድርቅ ያለበት ምድር" በቂ ውኃ የሌለበት ምድር ነው። እዚህ ላይ "ጥልቅ ጨለማ" ለአደጋ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "በቂ ውኃ የሌለበት አደገኛ ምድር" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

## Jeremiah 2:7

ምድሬን አረከሳችሁ፣ ርስቴንም ጸያፍ አደረጋችሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። አማራጭ ትርጉም፦ "ኃጢአትን አደረጋችሁ የሰጠኋችሁን ምድር ደግሞ በእኔ የተጠላ እንዲሆን አደረጋችሁት!" (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሬን አረከሳችሁ
እዚህ ላይ "አረከሳችሁ" የሚወክለው ምድሪቱ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዳይኖራት ማድረግን ነው። ይህንን ያደረጉት በዚያች ምድር ሆነው ጣዖቶችን በሚያመልኩበት ጊዜ በእርሱ ላይ ኃጢአት በማድረጋቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "ምድሬን ኃጢአት በማድረጋችሁ አረከሳችኋት" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ርስቴንም ጸያፍ አደረጋችሁ
"በኃጢአታችሁ ምክንያት ርስቴን የተጠላ አደረጋችሁት" ወይም "ኃጢአት በማድረጋችሁ ርስቴን ገፊ አደረጋችሁት"
ርስቴ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦
እግዚአብሔር ስለ ምድሩ ሲናገር እርሱ እንደወረሰው አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ "የእኔ ምድር" ወይም እግዚአብሔር ለእስራኤል ስለ ሰጣት ምድር ሲናገር እርሱ ለእነርሱ እንደ ርስት እንደሰጣቸው አድርጎ ይናገራል" አማራጭ ትርጉም፦ "ለእናንተ የሰጠኋችሁ ምድር" ወይም "እንደ ርስት ለእናንተ የሰጠኋችሁ ምድር" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ
እግዚአብሔር ወዴት አለ?
ይህ ጥያቄ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ መፈለጋቸውን ማሳየት ነበረበት። አማራጭ ትርጉም፦ "እግዚአብሔርን መታዘዝ እንፈልጋለን!" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ እኔ ግድ የላቸውም
"ለእኔ የተሰጡ አልነበሩም" ወይም "እኔን ተዉኝ"
እረኞቹ በእኔ ላይ አመጹብኝ
መሪዎቹ እን እረኞች እነርሱን የሚከተሏቸው ሕዝብ ደግሞ እንደ በጎች ተደርገው ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ "መሪዎቻቸው በእኔ ላይ ኃጢአትን አደረጉ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከንቱ ነገሮችን ተከትለው ሄዱ
እዚህ ላይ "ተከትለው ሄዱ" የሚወክለው መታዘዝ ወይም ማምለክ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "ከንቱ ነገሮችን ታዘዙ" ወይም "ከንቱ ነገሮችን አመለኩ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከንቱ ነገሮች
ከንቱ ነገሮች ሰውን መርዳት የማይችሉ ነገሮች ናቸው። እዚህ ላይ ጣዖቶችን ያመለክታል።

## Jeremiah 2:9

ስለዚህ ከእናንተ ጋር እከራከራለሁ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ እየተናገረ ነው።
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ "እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው" ወይም "እኔ እግዚአብሔር የተነገርሁት ይህ ነው" (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የልጆቻችሁ ልጆች
“የወደፊቱ ትውልዳችሁ”
ወደ ኪቲም ጠረፍ ተሻገሩ
ኪቲም በምዕራብ እስራኤል ትገኝ የነበረች ደሴት ናት። አሁን ቆጵሮስ ተብላ ትጠራለች። በምዕራብ እስራኤል ሩቅ ያሉትን ምድር በሙሉ የሚወከል ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ወደ ኪቲም ውቅያኖስ በምዕራብ በኩል ሂዱና ተሻገሩ” (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ቄዳርም መልእክተኞች ላኩ
ቄዳር ከምስራቅ እስራኤል በኩል በርቀት ለሚገኝ ምድር የተሰጠ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ወደ ቄዳር ምድር በምስራቅ በኩል በርቀት ወዳሉት መልእክተኞች ላኩ” (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
በውኑ አማልክት ... አማልክቱን የለወጣቸው አንድ ሕዝብ አለን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሌሎች ሕዝቦች የራሳቸውን አማልክት ማምለክ መቀጠላቸውን ለእስራኤል ሕዝብ ለመንገር ነው። እነርሱ አማልክቶቻቸውን ለውጠው ሌሎች አማልክትን አላመለኩም። አማራጭ ትርጉም:- “አንድም ሕዝብ አማልክቱን ... አማልክቱን የለወጠ ፈጽሞ እንደሌለ ታያላችሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን ሕዝቤ ክብራቸውን ሊረዳቸው ለማይችል ነገር ለወጡ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በቀጥታ እንደማይናገር አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “ነገር ግን፣ እናንተ፣ ሕዝቤ እኔን የክብራችሁን አምላክ ሊረዳችሁ ለማይችል ነገር ለወጣችሁኝ” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ክብራቸው
ይህ መግለጫ የሚያመለክተው ክቡር የሆነውን ራሱን እግዚአብሔርን ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የከበረ አምላካቸውን” ወይም “እኔ፣ የእናንተ የከበርሁ አምላካችሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ሊረዳቸው ለማይችል ነገር
እዚህ ላይ ሐሰተኛ አማልክት ሊሰሩት በማይችሉት ነገር ተገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም:- “ሊረዱ የማይችሉ፣ ሐሰተኛ አማልክት” ወይም “ሊረዱ የማይችሉ አማልክት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

## Jeremiah 2:12

ሰማያት ሆይ፥ በዚህ ተደነቁ! እጅግም ደንግጡና ተንቀጥቀጡ
እግዚአብሔር መለስ ብሎ እዚያ ሆነው እርሱን እንደሚሰሙት አድርጎ ለሰማያት ይናገራል። እግዚአብሔር ይህን የሚናገረው እስራኤል የሰራችው ነገር እጅግ በጣም አስደንጋጭ እንደሆነ ለመግለጽ ነው። (እንቶኔ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰማያት ሆይ፥ በዚህ ተደነቁ! እጅግም ደንግጡና ተንቀጥቀጡ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) እግዚአብሔር በሰማይ ላይ ለሚገኙ ፍጡራን ይናገራል ወይም 2) እግዚአብሔር ሕዝብ እንደሆኑ አድርጎ ለራሳቸው ለሰማያት ይናገራል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
የሕያውን ውኃ ምንጭ ትተውኛል
እግዚአብሔር ስለ ራሱ የሕያው ውኃ ምንጭ እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “የእነርሱ ሕያው ውኃ ምንጭ የሆንሁትን እኔን ትተውኛል” ወይም “እንደ ሕያው ውኃ ምንጭ የሆንሁትን እኔን ትተውኛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጉድጓዶች ለራሳቸው ቆፍረዋል
እግዚአብሔር ስለ ሐሰተኛ አማልክት ሲናገር ሰዎች ውኃ ለማግኘት ሲሉ የቆፈሯቸው ጉድጓዶች እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “ለራሳቸው እንደቆፈሯቸው ጉድጓዶች ወደ ሐሰተኛ አማልክት ሄደዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጉድጓዶች
ውኃ ለማከማቸት የሚረዱ ጥልቅ ጉድጓዶች

## Jeremiah 2:14

በውኑ እስራኤል ባሪያ ነውን? የተወለደው በጌታው ቤት ነውን? ታዲያ ስለምን ለብዝበዛ ተዳረገ?
ምንም እንኳ እግዚአብሔር የሚናገረው ለሕዝቡ ቢሆንም ስለ እስራኤል ለሌላ ሰው እንደሚናገር አድርጎ ሶስተኛ ሰው ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም:- “እስራኤል፣ አንተ ባሪያ ነህ እንዴ? የተወለድከው በቤት ነው? ታዲያ ለምን ለብዝበዛ ተዳረግህ? (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እስራኤል ባሪያ ነውን? የተወለደው በጌታው ቤት ነውን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እስራኤል ለብዝበዛ መዳረግ እንዳልነበረባት ምክንያቱን ለመናገር ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እስራኤል ባርያ አይደለም። እስራኤል በቤት አልተወለደም ነበር።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
የተወለደው በጌታው ቤት ነውን?
እዚህ ላይ “በጌታው ቤት ተወለደ” የሚለው ሀረግ ለባርነት መወለድን የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የተወለደው ባርያ ሆኖ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ታዲያ ስለምን ለብዝበዛ ተዳረገ?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እስራኤል ለብዝበዛ መዳረግ እንዳልነበረባት ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ስለዚህ ለብዝበዛ መዳረግ አልነበረበትም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ታዲያ ስለምን ለብዝበዛ ተዳረገ?
እዚህ ላይ “ለብዝበዛ ተዳረገ” የሚለው ሀረግ ተጠቂ መሆንና ወደሌላ አገር ምርኮኛ ሆኖ መወሰድን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ታዲያ እስራኤል እንደ ምርኮኛ ወደሌላ የተወሰደው ለምንድን ነው” ወይም “ታዲያ የእስራኤል ጠላቶች እስራኤልን እንደ ምርኮኛ ለምን ወሰዱት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚአስለውን ይመልከቱ)
የአንበሳ ደቦሎች በእርሱ ላይ አገሡ፥ ብዙ ድምጽም አሰሙ
እግዚአብሔር እስራኤልን ስላጠቋት የእስራኤል ጠላቶች ሲናገር ጠላቶቿ የሚያገሱና እስራኤልን የሚያጠቁ አንበሶች እንደሆኑ አድርጎ ገልጿቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሩንም ባድማ አድርገውታል
ይህ ሕዝቡ ምድሩን ሲያዩ የሚያስፈራ እንደሆነ እስኪሰማቸው ድረስ ምድሩን ለማጥፋታቸው የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የእስራኤልን ምድር አፈራረሱ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የአንበሳ ደቦሎች አገሱ
ማግሳት የዱር እንስሳት ሲያጠቁ የሚያሰሙት እጅግ በጣም ከፍ ያለ ጩኸት ነው።
ከተሞቹ ተቃጠሉ፣ የሚቀመጥባቸው ማንም የለም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “የእስራኤልን ከተሞች አቃጠሉአቸው፣ አሁን በእነርሱ ውስጥ የሚኖር ማንም ሰው የለም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚቀመጥባቸው
በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች
ሜምፎስና ጣፍናስ
እነዚህ በግብጽ ምድር የሚገኙ የሁለት ከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
አናትሽን ይላጩሻል
ግብጻውያን የባርያዎቻቸውን ራስ ይላጩ ነበር፣ ይህን የሚያደርጉት የባርያ ምልክት ለመስጠት ነው።
አናትሽን ይላጩሻል
አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን ጥቅስ “አናትሽን ሰንጥቀውሻል።”
በመንገድ የሚመራሽን፣ እግዚአብሔር አምላክሽን በመተውሽ፣ ይህን በራስሽ ላይ አላመጣሽምን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ጠላቶቻቸው ያጠቋቸው በራሳቸው ጥፋት እንደሆነ እስራኤልን ለማስታወስ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “አምላካችሁ እግዚአብሔር በመንገድ ሁሉ እየመራችሁ ሳለ እናንተ ግን እርሱን በመተዋችሁ ይህን በራሳችሁ ላይ አመጣችሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

## Jeremiah 2:18

ስለዚህ አሁን፣ የሺሖርን ውኃ ትጠጪ ዘንድ በግብጽ መንገድ ለምን ሄድሽ? የኤፍራጥስን ወንዝ ውኃ ትጠጪ ዘንድ በአሦር መንገድ ለምን ሄድሽ?
እግዚአብሔር እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ግብጽንና አሦርን እነርሱን እንዲረዱአቸው መጠየቃቸው ምንም ዓይነት መልካም ነገር እንደማያመጣላቸው ለሕዝቡ ለማስታወስ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ወደ ግብጽ በመሄድ ከሺሖር ወንዝ ውኃ መጠጣት ወይም ወደ አሦር በመሄድ ከኤፍራጥስ ወንዝ ውኃ መጠጣት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ለእናንተ ምንም አይጠቅማችሁም፡፡” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ )
የሺሖርን ውኃ ትጠጪ ዘንድ በግብጽ መንገድ ለምን ሄድሽ? የኤፍራጥስን ወንዝ ውኃ ትጠጪ ዘንድ በአሦር መንገድ ለምን ሄድሽ?
እነዚህ የግብጽንና የአሦርን ሰራዊት እነርሱን እንዲረዱአቸው ለመጠየቃቸው ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ግብጻውያን እንዲረዱአችሁ ለምን ጠየቃችሁ … አሦራውያን እንዲረዱአችሁ ለምን ጠየቃችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሺሖር
ይህ ከግብጽጋር የተያያዘ የአንድ ምንጭ ስም ነው፡፡ ምናልባት የአባይ ወንዝ ገባር ሳይሆን አይቀርም፡፡ አንዳንድ ትርጉሞች አባይ ብለው ይጠሩታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የሺሖር ምንጭ” ወይም “የሺሖር ወንዝ” ወይም “የአባይ ወንዝ” (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፋትሽ ይገስጽሻል፣ ክህደትሽ ይቀጣሻል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ቅጣታቸው የክፉ ስራቸው ውጤት እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉና ከዳተኛ ስለሆንሽ እቀጣሻለሁ” (ሰውኛ ዘይቤ እና ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉና መራራ ነው
እዚህ ላይ “መራራ” የሚለው ቃል “ክፉ” የሚለውን ይገልጻል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እጅግ በጣም መራራ የሆነ ክፋት ነው” ወይም “እጅግ በጣም ክፉ ነው” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 2:20
ከጥንት ጀምሮ ቀንበርሽን ሰብሬአለሁ፤ እስራትሽንም ቈርጫለሁ አንቺም፡፡ አንቺ ግን “አላገለግልም አልሽ”
እዚህ ላይ “ቀንበርሽን ሰብሬአለሁ” እና “እስራትሽንም ቆርጫለሁ” ከባርነት እርነት እንዳወጣቸው የሚገልጹ ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው፡፡ የእስራኤል ሕዝብ በግብጽ ምድር ባሮች ነበሩ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከረጅም ጊዜ በፊት እኔ ከባርነት ነፃ አወጣኋችሁ፣ ነገር ግን አሁንም እኔን ለማምለክ እንቢ አላችሁ!” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እስራት
አንድን ሰው ወይም እንስሳ ለማሰር የሚጠቅም ሰንሰለት
ነገር ግን ከፍ ባለው ኮረብታ ሁሉ ላይ እና ከለምለምም ዛፍ ሁሉ በታች ለማመንዘር ተጋደምሽ
ለምን እንደተጋደሙ በግልጽ ሊብራራ ይችላል፡፡ እዚህ ላይ “ማመንዘር” ለእግዚአብሔር ታማኝ ያልሆነ ሰውን የሚወክል ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለባሏ ታማኝ እንዳልሆነች አመንዝራ ሚስት አንቺም ከእኔ ይልቅ ለጣዖቶች በመስገድ እነርሱን አመለክሽ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በታች
ከስር
እኔ እንደ ተመረጠች ወይን፣ ፍጹምም ንጹሕ ዘር አድርጌ ተክዬሽ ነበር
እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር ሕዝቡን እርሱ እንደተከለው እንደ ተመረጠ ወይን በከነዓን ታላቅ ሕዝብ አድርጎ እንደሰራው ይገልጻል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከሁሉ የተሻለውን የወይን ዓይነት ለመትከል እጅግ በጣም ጥሩ የሆነውን ዘር እንደሚጠቀም ገበሬ፣ እኔ እግዚአብሔር በመልካም አጀማመር እንድትጀምሩ አድርጌ ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የተመረጠ ወይን
“በጣም ጥሩ ጥራት ያለው ወይን”
ፍጹም ንጹህ ዘር
እዚህ ላይ “ንጹህ ዘር” ጥሩ ካልሆነ ዘር ጋር ያልተዳቀለ በጣም ጥሩ ዘር ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እጅግ በጣም ጥሩ ከሆነ ዘር የበቀለ”
ታዲያ አንቺ ብልሹ፣ የማይጠቅም ወይን ግንድ ሆነሽ እንዴት ተለወጥሽብኝ?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ለመለወጡና እንደ ብልሹና የማይጠቅም ወይን ግንድ ለመሆኑ ሕዝቡን ለመገሰጽ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን አንቺ ብልሹና የማይጠቅም ወይን ግንድ ሆነሽ ተለወጥሽ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በእኔ ፊት በኃጢአትሽ ረክሰሻል
በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሌለው ነገር እንደረከሰ ተደርጎ ይነገራል፡፡ እዚህ ላይ “ረክሰሻል” የሚለው ለእስራኤል ኃጢአት የማያቋርጥ ማሳሰቢያ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ኃጢአትሽን እንደ ርኩሰት አይቼዋለሁ” ወይም “ኃጢአትሽ እንደ ርኩሰት ነው፤ በደልሽ ጸንቶ ይኖራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የጌታ እግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል፡፡ ይህን ተመሳሳይ ሀረግ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 2:23
በአሊምንም አልተከተልሁም እንዴት ትያለሽ?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡ በአሊምን አላመለክሁም ብሎ ለተናገረው ለመገሰጽ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “You lie when you say, ‘በአሊምንም አልተከተልሁም’ ብለሽ መናገርሽ ዋሽተሻል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
መከተል
ይህ ለማገልገልና ለማምለክ ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንቺ እዚህና እዚያ የምትሮጥ ፈጣን ሴት ግመል ነሽ
እግዚአብሔር እስራኤል ሌሎች አማልክትን ስለማምለካቸው ሲናገር ወንድ ግመል ለመፈለግና ከእርሱ ጋር ወሲብ ለማድረግ በሌላ አቅጣጫ እንደምትሮጥ ሴት ግመል አድርጎ ገልጿቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንቺ ወንድ ግመል ለመፈለግና ከእርሱ ጋር ወሲብ ለማድረግ ወደፊትና ወደኋላ እንደምትሮጥ ፈጣን ሴት ግመል ነሽ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ፈጣን
በፍጥነት መሮጥ የምትችል
በምኞትዋ ነፋስን እንደምታሸትት፣ በምድረ በዳ እንደ ለመደች እንደ ሜዳ አህያ ነሽ
እግዚአብሔር እስራኤል ሌሎች አማልክትን ስለማምለካቸው ሲናገር ወንድ የሜዳ አህዮች ለመፈለግ እንደምትሮጥ ሴት የሜዳ አህያ አድርጎ ገልጿቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንቺ በምድረ በዳ እንደምትኖር ወጣት ሴት የሜዳ አህያ ነሽ፡፡ ወሲብ መፈጸም ስትፈልግ ከቁጥጥር ውጭ ትሆናለች፣ ወንድ የሜዳ አህያ ለመፈለግ ነፋስን ታሸትታለች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በምኞትዋ
ይህ ሀረግ ፈሊጥ ሲሆን የሚያመለክተው ሴት የሜዳ አህያ ከወንድ የሜዳ አህዮች ጋር ወሲብ ለመፈጸም የምትፈልግበትን ጊዜ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ወሲብ ለመፈጸም ስትፈልግ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ከምኞትዋ የሚመልሳት ማን ነው?
ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው ሴት የሜዳ አህያ ከወንድ የሜዳ አህያ ጋር ወሲብ ለመፈጸም ስትፈልግ ሊቆጣጠራት የሚችል ማንም እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ወሲብ መፈጸም ስትፈልግ ማንም ወደኋላ ሊመልሳት አይችልም፡፡” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
እግርሽን ባዶ ከመሆን ጕሮሮሽንም ከውኃ ጥም ከልክዪ!
እግዚአብሔር እስራኤል ሌሎች አማልክትን ለማምለክ ስለመፈለጋቸው ሲናገር እነዚህን አማልክት ለመፈለግ በምድረ በዳ ይሮጡ እንደነበር አድርጎ ገልጿቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህን ሐሰተኛ አማልክት ለመፈለግ እዚህና እዚያ መሮጥሽን እንድታቆሚ ነግሬሻለሁ፣ ምክንያቱም ይህ ሁሉ ድርጊትሽ ውጤቱ ጫማሽ እንዲያልቅና በጣም እንድትጠሚ የሚያደርግ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ተስፋ የለውም
“ራሳችንን በመከልከል ምንም ዓይነት ተስፋ የለም፡፡” ይህ ሌሎች አማልክትን ከመከተል ራሳቸውን ማስቆም እንደማይችሉ የሚያመለክት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ራሳችንን ፈጽሞ ማስቆም አንችልም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አይሆንም፣ እንግዶችን ወድጃለሁና፣ እከተላቸዋለሁም
እዚህ ላይ “እንግዶች” የሚለው ባዕዳን አማልክትን የሚወክል ነው፣ እና “እከተላቸዋለሁ” የሚለው እነርሱን ማምለክ የሚወክል ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ባዕዳን አማልክትን መከተልና እነርሱን ማምለክ አለብን!” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 2:26
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰብ ምትክ ስም ነው፡፡ በዚህ ጥቅስ የሚያመለክተው የእስራኤልን ልጆች ነው፡፡ ይህን በኤርምያስ 2:4 ላይ

እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እስራኤላውያን” ወይም “የእስራኤላውያን ሕዝብ ወገን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በተያዘ ጊዜ
ይህ ፈሊጥ አንድ ሰው የሌላውን ሰው ድርጊት ለይቶ ማወቁን የሚያሳይ ነው። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንድ ሰው ሲያገኘው” ወይም “አንዳንድ ነገሮች መስረቁን ሰዎች ባወቁ ጊዜ” (ፈሊጥ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ፥ ንጉሦቻቸው፣ አለቆቻቸው፣ ካህናቶቻቸውና ነቢያቶቻቸው
ይህ ዝርዝር የእስራኤል አካል የሆነ ማንኛውም ሰው እንደሚያፍር ያሳያል።
ግንዱን፦ ‘አንተ አባቴ ነህ’ ድንጋዩንም፦ ‘አንተ ወለድኸኝ’ የሚሉ እነዚህ ናቸው
እዚህ ላይ “ግንድ” እና “ድንጋይ” የሚሉት ከእንጨትና ከድንጋይ ተቀርታ የተሰሩ ጣዖቶችን የሚወክሉ ናቸው። እነዚህ ቀላት ጣዖቱ የተሰራው በተራ ነገሮች ስለሆነ ሊመለኩ የተገባቸው እንዳልሆኑ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ከእንጨት ተቀርጾ ለተሰራው ጣዖት ‘አንተ አባቴ ነህ’ ለተtቀረጸው ድንጋይ ደግሞ ‘አንተ ወለድኸኝ’ የሚሉ እነዚህ ሕዝቦች ናቸው። ( ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ፊታቸውንም ሳይሆን ጀርባቸውን ሰጡኝ
“ጀርባቸው ወደ እኔ ነው፤ ፊታቸው ግን ወደ እኔ ዘወር አላለም።” ይህ እግዚአብሔርን መተዋቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ፊታቸውን ከእኔ መለሱ” ወይም “ፊታቸውን ሳይሆን ጀርባቸውን ወደ እኔ መለሱ” ወይም “እነርሱ ፈጽመው ተዉኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ተነስተህ አድነን
ይህንን የተናገሩት ለእግዚአብሔር እንደሆነ ግልጽ መደረግ አለበት። “እግዚአብሔር ሆይ፣ ተነስተህ አድነን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ታዲያ ለአንተ የሠራሃቸው አማልክትህ ወዴት ናቸው?
እግዚአብሔር በዚህ ጥያቄ አማካይነት ሕዝቡ የሚያመልኩአቸው ጣዖታቱን እንዲረዷቸው ሊጠይቁአቸው እንደሚገባ ያመለክታል። እርሱ ይህንን ምፀት የተጠቀመው ሕዝቡ ሌሎች ጣዖቶችን በማምለካቸው እርሱ እንዳዘነ ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሊረዷችሁ ለራሳችሁ የሰራችኋቸውን አማልክት ልትጠይቋቸው ይገባል።” ወይም “ሊረዷችሁ ለራሳችሁ የሰራችኋቸውን አማልክት አልጠየቃችኋቸውም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
በመከራህ ጊዜ ለያድኑህ የሚችሉ ከሆነ፣ እስቲ ተነስተው ይምጡና ያድኑህ
እግዚአብሔር ሊያመለክት የፈለገው ሐሰተኛ አማልክት የሚያልኩአቸውን ሰዎች ሊረዷቸው ይገባል የሚል ነው። ሐሰተኛ አማልክት ሰዎችን ሊረዱ እንደማይችሉ ያውቃል። እርሱ ይህን ሲናገር የእርሱ ሕዝብ ሐሰተኛ አማልክትን በማምለካቸው እንዳዘነ ለማሳየት ምፀት ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጉም፦ “በመከራችሁ ጊዜ እነርሱ ሊያድኑአችሁ እንደማይችሉ ስለምታውቁ እነርሱን አልጠየቃችሁም” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 2:29
ታዲያ ለምን እኔን ክፋት እንዳደረግሁባችሁ ትከስሱኛላችሁ? በእኔ ላይ ኃጢአት ያደረጋችሁ እናንተ ሁላችሁ ናችሁ።
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው የእስራኤል ሕዝብ ክፉ እንዳደረገባቸው በማሰብ እርሱን መውቀሳቸውን ለመገሰጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እስራኤል፣ ምንም እንኳ በእኔ ላይ ኃጢአት ማድረግን ብትቀጥሉም፣ እኔን በጠራችሁ ጊዜ ሳላድናችሁ በመቅረቴ እኔ ትክክል እንዳልሆንሁ አሰባችሁ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ተግሣጽን አልተቀበሉም
እዚህ ላይ “ተግሳጽ መቀበል” ከቅጣት መማርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከተግሳጽ መማርን አልተቀበሉም” ወይም “እኔ እነርሱን በገሰጽሁ ጊዜ እኔን መታዘዝን ለመማር ፈቃደኞች አልሆኑም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰይፋችሁ እንደሚያጠፋ አንበሳ ነቢያቶቻችሁን በልቶአል
እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ ነቢያቶቻቸውን ስለመግደላቸው ሲናገር ሰይፋቸው ነቢያቶቻቸውን የበላ አንበሳ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እናንተ ነቢያቶቻችሁን እንደሚያጠፋ አንበሳ በጭካኔ በሰይፋችሁ ገደላችኋቸው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አጥፊ
መጠኑ በጣም ሰፊ የሆነ አደጋ የማምጣት ችሎታ ያለው
የዚህ ትውልድ ሰዎች ሆይ! ቃሌን አስተውሉ፣ የእግዚአብሔር ቃል
“ይህ ትውልድ” የሚለው ሀረግ ኤርምያስ ይኖር በነበረበት ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እናንተ ዛሬ የምትኖሩ ሰዎች፣ እኔ እግዚአብሔር ለእናንተ የምናገረውን ቃል አስተውሉ”
በውኑ ለእስራኤል ምድረ በዳ ወይስ ድቅድቅ ጨለማ ያለበት ምድር ሆንሁባትን?
እዚህ ላይ “ምድረ በዳ” እና “ድቅድቅ ጨለማ ያለበት ምድር” ለአደጋ ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው። እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ አደገኛ እንደሆነ በማሰባቸው እስራኤልን ለመውቀስ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ ለእናንተ እንደ ምድረ በዳ ወይም ድቅድቅ ጨለማ ያለበት ምድር እንደሆንሁባችሁ አሰባችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ )
ሕዝቤስ ስለ ምን “እኛ ተንከራትተናል ከእንግዲህ ወዲህ ወደ አንተ አንመለስም ይላል”?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡ ይህን በመናገሩ ሊገስጸው ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እናንተ ሕዝቤ ‘መሄድ ወደምንፈልገው መሄድ እንችላለን፣ ከእንግዲህ ወዲህ እግዚአብሔርን አናመልክም’ ብላችኋል።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
መንከራተት
ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ወይም ስፍራዎች ያለ ምንም ግልጽ ዓላማ ወይም አቅጣጫ መንቀሳቀስ
Jeremiah 2:32
በውኑ ቆንጆ ጌጥዋን ወይስ ሙሽራ የሰርግ ልብሷን ትረሳለችን?
“ትረሳለች” የመሚለው ቃል የሁለተኛው ሀረግ አካል ጭምር እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል። አማራጭ ትርጉም፦ “በውኑ ቆንጆ ጌጥዋን ትረሳለችን፣ ወይስ ሙሽራ የሰርግ ልብሷን ትረሳለችን?” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
በውኑ ቆንጆ ጌጥዋን ወይስ ሙሽራ የሰርግ ልብሷን ትረሳለችን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ለአንድ ሰው በጣም ጠቃሚ የሆኑትን ነገሮች የማስታወስን ሃሳብ ለማስተዋወቅ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ቆንጆ ጌጥዋን ማድረግ ፈጽሞ እንደማትረሳ፣ ሙሽራ ደግሞ የሰርግ ልብሷን መልበስ እንደማትረሳ ታውቃላችሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
የማይቆጠሩ ቀናቶች
“በጣም ረጅም ጊዜ”
ፍቅርን ለመፈለግ መንገድሽን እንዴት ታቀኛለሽ
እግዚአብሔር ፍቅርን በመፈለጋቸው ሕዝቡን እያመሰገናቸው ይታያል፣ ነገር ግን ይህ ምፀት ነው። እርሱ ለእርሱ ታማኞች ባለመሆናቸው በእነርሱ ላይ እንዳዘነ እያሳያቸው ነበር። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
ፍቅርን ለመፈለግ
እግዚአብሔር ሌሎች አማልክትን ስለሚያመልከው ሕዝቡ ሲናገር ለባሏ ታማኝ እንደልሆነችና እንዲወዳት ሌላ ወንድ እነደምትፈልግ ሴት አድርጎ ገልጷቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለክፉዎች ሴቶች እንኳ መንገድሽን አስተምረሻል
እግዚአብሔር ሕዝቡ ምን ያህል ለእርሱ ታማኝነት የጎደላቸው ስለመሆናቸው ሲናገር ለሴተኛ አዳሪዎች እንኳ እንዴት ለባሎቻቸው ታማኝ መሆን እንደሌለባቸውና ሌሎች ወንዶች የእነርሱ ወዳጆች እንዲሆኑ እንዴት መፈለግ እንዳለባቸው የሚያስተምሩ እንደሆኑ አድርጎ ገልጿቸዋል። (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
የንጹሐን ድሆች ሕይወት የሆነው ደም በልብስሽ ላይ ተገኝቶአል
በልብሳቸው የተገኘው ደም ሰዎችን እንደገደሉ ማስረጃ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በልብስሽ ላይ የተገኘው የንጹሐን ድሆች ደም እነርሱን በመግደልሽ ወንጀለኛ እንደሆንሽ ያሳያል” ወይም “የንጹሐን ድሆች ደም በመግደልሽ ወንጀለኛ ነሽ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሕይወት የሆነው ደም
“ሕይወትን የሚወክለው ደም”
እነዚህ ሰዎች በስርቆት ተግባር የተያዙ አልነበሩም

እነርሱ ሰዎችን በስርቆት ተግባር ተሰማርተው ይዘዋቸው ቢሆን ኖሮ ሰዎቹን ለመግደል ምክንያት ይሆንላቸው ነበር። ነገር ግን እነርሱ የገደሏቸው ሰዎች ንጹሐን ነበሩ። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እነዚህን ሰዎች የተለያዩ ነገሮች ሲሰርቁ አላገኛችኋቸውም” ወይም “ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳ አንድም ነገር ባይሰርቁም እነርሱን ገድላችኋቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 2:35

በእርግጥ ቁጣው ከእኔ ርቋል

እዚህ ላይ ቁጣ ከእስራኤል እንደሚርቅ ሰው ተደርጎ ተነግሯል። ርቋል የሚለው እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የነበረውን ቁጣ ማቆሙን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “በእርግጥ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር የነበረውን ቁጣ አቁሟል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ግን በአንቺ ላይ ፍርድን አመጣብሻለሁ

እዚህ ላይ “ፍርድ” ቅጣትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ እቀጣሻለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መንገድሽን እንደ ቀላል ነገር እየለዋወጥሽ ለምን ትሮጫለሽ?

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ይገስጻቸዋል ምክንያቱም እነርሱ ለእርዳታ ሲሉ ከአንድ መንግስት ወደ ሌላ መንግስት እየለዋወጡ ሲሄዱ ነበር ነገር ግን ለእርዳታ በእግዚአብሔር ላይ አልተደገፉም። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ቀላል ነገር

ያለ ጥንቃቄ ወይም ተገቢ ግንዛቤ

አንቺ ደግሞ በግብጽ ትዋረጃለሽ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ግብጽ ታዋርድሻለች”

አንቺ ደግሞ በግብጽ ትዋረጃለሽ

የእስራኤል ሕዝብ ያዝናል ምክንያቱም የግብጽ ጦር ሰራዊት እነርሱን ሊታደጋቸው አይችልም። አማራጭ ትርጉም:- “ግብጽ ሊታደግሽ ባልቻለ ጊዜ አንቺ ትዋረጃለሽ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አሦር እንዳዋረደሽ

“እንዳዋረደሽ” የሚለው ቃል ከበፊቱ ሀረግ ልንረዳው የምንችለው ነው። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “አንቺ በአሦር እንደተዋረድሽ” ወይም “አሦር አንቺን እንዳዋረደችሽ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም ትወጫለሽ

“አንቺ ከግብጽ ትወጫለሽ”

እጆችሽን በራስሽ ላይ አድርገሽ

ይህ የኃፍረት ምልክት ነው። (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺም በእነርሱ አይከናወንልሽም

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ስለዚህ እነርሱ አይረዱሽም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 3

Jeremiah 3:1

አጠቃላይ መረጃ:-

እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል። ይህ በኤርምያስ 2:1 ላይ ለኤርምያስ ሊገልጥለት የጀመረው የትንቢቱ አካል ነው።

እርሱ እንደገና ወደ እርሷ ይመለሳልን?

እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው አንድ ወንድ ሚስቱን ሌላ ወንድ ካገባት በኋላ እንደገና ወደ እርሷ ፈጽሞ እንደማይመለስ ሕዝቡን ለማሳሰብ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሐሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እንደገና ወደ እርሷ አይመለስም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ ፈጽማ አትረክስምን

እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ያገባ ወንድ ሚስቱ ሌላ ወንድ ካገባች በኋላ እንደገና ወደ ሚስቱ እንደማይመለስ ሕዝቡን ለማሳሰብ ነው ምክንያቱም ምድሪቱ በስርዓት እንደምትረክስ ስለሚያውቅ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሐሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ምድሪቱ ፈጽማ እንደረከሰች እርሱ ያውቃል።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ፈጽማ ረክሳለች

ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ ፈጸሞ ተቀባይነት ለማጣት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “በእግዚአብሔር ዘንድ ፈጽሞ ተቀባይነት ማጣት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺ ግን ከብዙ ወዳጆችሽ ጋር እንደ አመንዝራ ኖረሻል

እግዚአብሔር ብዙ ባዕድ አማልክትን የምታመልከውን እስራኤልን ከብዙ ወንዶች ጋር ወሲብ እንደፈጸመች ሴት አድርጎ ገልጿታል። አማራጭ ትርጉም:- “ሴተኛ አዳሪ ሰውነቷን ባልዋ ላልሆኑ ለብዙ ወንዶች እንደምትሰጥ እንዲሁ ፍቅርሽን እና ታማኝነትሽን ለጣዖቶች ሰጥተሻል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን ወደ እኔ መመለስ ትፈልጊያለሽ?

እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እስራኤላውያን ጣዖቶችን ስላመለኩ እግዚአብሔር እነርሱን እንደገና ወደ እርሱ እንዲመለሱ እንደማይፈቅድላቸው ለማሳየት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሐሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እንዲህም አድርጋችሁ ወደ እኔ ለመመለስ ትፈልጋላችሁ” ወይም “እንዲህም አድርጋችሁ እንደገና ወደ እኔ እንድትመለሱ እንደምፈቅድላችሁ ታስባላችሁ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እስቲ ዓይኖችሽን አንሺ

እዚህ ላይ “ዓይኖች” የሚወክለው አንድ ነገር ማየትን ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ወደላይ ተመልከቺ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አስጸያፊ ወሲብ ያልፈጸምሽበት ስፍራ ወዴት አለ?

እግዚአብሔር እስራኤል ጣዖቶችን ስለማምለኳ ሲናገር ከብዙ የተለያዩ ወንዶች ጋር ወሲብ የፈጸመች ሴት እንደሆኑ አድርጎ አቅርቦአቸዋል። ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ለእስራኤላውያን በየትኛውም ስፍራ ጣዖቶችን እንዳመለኩ እንደሚያውቅ ለእነርሱ ለመንገር ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሐሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “አስጸያፊ ወሲብ ያልፈጸምሽበት ስፍራ ምንም የለም!” ወይም “ሴተኛ አዳሪ ከብዙ ወንዶች ጋር እንደምትተኛ፣ አንቺም በሁሉም ስፍራ ጣዖታቶችሽን አምልከሻል!” (ተለዋጭ ዘይቤ እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺ በመንገድ ላይ ተቀምጠሽ ወዳጆችሽን ትጠብቂያቸው ነበር

እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር ሴተኛ አዳሪ በመንገድ ላይ ተቀምጣ በመንገድ የሚያልፈውን ወንድ ሁሉ እንደምትጠብቅ እንደዚሁ እነርሱም ጣዖትን ለማምለክ በጉጉት ይጠብቁ ነበር። አማራጭ ትርጉም:- “ሴተኛ አዳሪ በመንገድ ላይ ተቀምጣ በመንገድ የሚያልፉትን ወዳጆችዋን እንደምትጠብቅ አንቺም ያወቅሻቸውን ማንኛውንም ጣዖት ለማምለክ በጉጉት ትጠብቂ ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድረ በዳ እንደተቀመጠ ዘላን አረብ

እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር ሴተኛ አዳሪ በምድረ በዳ ተቀምጦ የሚያልፈውን ማንኛውንም ሰው መዝረፍ እንዲችል እንደሚጠብቅ እንደዚሁ እነርሱም ጣዖትን ለማምለክ በጉጉት ይጠብቁ ነበር። አማራጭ ትርጉም:- “ሊዘርፋቸው የሚችላቸውን ሰዎች ለመጠበቅ በምድረ በዳ እንደተቀመጠ ዘላን አረብ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድረ በዳ እንደተቀመጠ ዘላን አረብ

አረብ ከአረብ አገር የሆነ ሰው ነው። አንዳንድ አረቦች በምድረ በደ እንደ ዘላን ስለሚኖሩ በአጠገባቸው የሚመጡትን ሰዎች ይዘርፋሉ። አማራጭ ትርጉም:- “በምድረ በዳ የሚኖር ዘላን” ወይም “በምድረ በዳ የሚኖር ዘራፊ” (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ እና የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:3

ስለዚህ ካፊያ ተከለከለ፥ የኋለኛውም ዝናብ ጠፋ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ስለዚህ ካፊያውን ከእናንተ ከለከልሁ” ወይም “ስለዚህ ዝናብ እንዳይዘንብ ከለከልሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:6

ከዳተኛይቱ እስራኤል ያደረገችውን አየህን?

እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው የኤርምያስን ትኩረት ወደ እስራኤል



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከዳተኝነት ለመሳብ ነው። ይህ እንደ ትዕዛዝ ወይም እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከዳተኛይቱ እስራኤል ለእኔ እንዴት እንደሆነች ተመልከት።” ወይም “ከዳተኛይቱ እስራኤል ለእኔ እንዴት እንደሆነች አይተሃል።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከፍ ወዳለው ኮረብታ ወጣች

ስለ እስራኤል ሕዝብ ሲነገር እስራኤል ሴት እንደሆነች ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤል ሕዝብ ወደ ኮረብታ ወጡ” ወይም “እነርሱ ወደ ኮረብታ ወጡ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ረዘመው ተራራ ሁሉ ከለመለመ ዛፍም ሁሉ በታች

የተራራ ጫፎች እና የለመለመ ዛፍ በታች ሰዎች ጣዖቶች የሚያመልኩባቸው የተለመዱ ስፍራዎች ናቸው። “ሁሉ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ሕዝቡ በብዙ የተለያዩ ስፍራዎች ጣዖቶችን ያመልኩ እንደነበር ለማሳየት እንደ ጅምላ መግለጫ ነው። (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ሴተኛ አዳሪ አደረገች

እግዚአብሔር እስራኤል ጣዖቶችን ስለማምለኳ ሲናገር ከብዙ ወንዶች ጋር ወሲብ እንደምታደርግ ሴት አድርጎ ገልጾአታል። አማራጭ ትርጉም፡- (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከኃዲቷ እኅትዋም ይሁዳ አየች

እግዚአብሔር ስለ እስራኤልና ይሁዳ እህቶች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔን ያልታዘዙት የይሁዳ ሕዝብም አይተዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:8

አጠቃላይ መረጃ፡-

እግዚአብሔር ስለ እስራኤልና ይሁዳ ሲናገር ለእርሱ ያልታመኑ ሁለት እህትማማች ከዳተኛ ሚስቶች እንደነበሩ አድርጎ ገልጾአቸዋል።

የፍች ወረቀት

ይህ አንድ ወንድ ሚስቱን ለመፍታቱ ማረጋገጫ ለመስጠት የሚጽፈው ነገር ነው።

አመንዝራነቷ ለእርሷ ምንም አልመሰላትም

እዚህ ላይ አመንዝራነቷ “ምንም አልመሰላትም” የሚለው ሃሳብ የሚወክለው ይሁዳ ስለዚህ ጉዳይ ስሜት እንዳልሰጣት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ አመንዝራነቷ ምንም አልመሰላትም” ወይም “ስለ አመንዝራነቷ ፈጽሞ አላፈረችም”

ምድሪቱን አረከሰች

እዚህ ላይ “አረከሰች” የሚለው የሚወክለው ምድሪቱን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራት ማድረጓን ነው። ይህን ያደረጉት ጣዖቶችን ባመለኩበት ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት በማድረጋቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሷ ምድሪን አበላሸችት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርስዋም ከድንጋይና ከግንድ ጋር አመነዘረች

እዚህ ላይ “ድንጋይ” እና “እንጨት” ጣዖቶችን ለመስራት የተጠቀሙበትን የድንጋይና የእንጨት ቁሳቁሶችን ይወክላል። የሕዝቡ ጣዖት አምልኮ ዝሙት እንደፈጸሙ ተደርጎ ተነግሯል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ and ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ) ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:11

ከከሓዲዋ ይሁዳ ይልቅ ከዳተኛይቱ እስራኤል ጻድቅ ሆና ተገኘች

እስራኤልን ከይሁዳ ይልቅ “የበለጠ ጻድቅ” ሆና ተገኘች ብሎ በመጥራት ይሁዳ በጣም ኃጢአተኛ እንደሆነች እግዚአብሔር አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “እስራኤል ለእኔ ታማኝ አልነበረችም ነገር ግን ከእስራኤልም የበለጠ ይሁዳ ኃጢአተኛ ሆናለች”

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ሂድና እነዚህን ቃላት ለሰሜን ተናገር

እዚህ ላይ ሰሜን የሚለው ወደ ሰሜን ማለትም አሦር የተወሰዱትን የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሂድና እነዚህን ቃላት ለእስራኤል ሕዝብ ተናገር” ( ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:13

ኃጢአትሽን እወቂ

“ኃጢአት እንደሰራሽ እመኚ።” እግዚአብሔር ለእስራኤል ይናገር ነበር።

መንገድሽንም ከለመለመ ዛፍ ሁሉ በታች ለእንግዶች ዘረጋሽ!

“እንግዶች” የሚለው ቃል ባዕድ አማልክትን ያመለክታል። ባዕድ አማልክት ስለምታመልከው ስለ እስራኤል እግዚአብሔር ሲናገር እስራኤል ከእንግዶች ጋር ወሲብ እንደምትፈጽም ሴት አድርጎ ገልጾአታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከለመለመ ዛፍ ሁሉ በታች

ሰዎች ጣዖቶችን በዛፍ ስር ያመልኩ ነበር። “ሁሉ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የእስራኤል ሕዝብ በብዙ የተለያዩ ዛፎች ስር ብዙ አማልክትን እንዳመለኩ በጅምላ ለማሳየት ነው። (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ)

ድምጼንም አልሰማሽም

እዚህ ላይ “መስማት” የሚለው መታዘዝን ይወክላል፣ “ድምጼን” የሚለው ደግሞ እግዚአብሔር የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የተናገርሁትን አልታዘዝሽም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ባላችሁ ነኝ

እስራኤል የእርሱ እንደሆነች እግዚአብሔር ሲናገር እርሱ የእስራኤል ባል እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሚስት የባልዋ እንደሆነች ሁሉ እንዲሁ እናንተ ደግሞ የእኔ ናችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እረኞችን እሰጣችኋለሁ ... ይጠብቁአችኋል

እዚህ ላይ እግዚአብሔር ስለ መሪዎች ሲናገር እነርሱ እረኞች እንደነበሩና የሚመሩት ሕዝብ ደግሞ በጎች እንደነበሩ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ መሪዎችን እሰጣችኋለሁ ... ይመሯችኋል”` (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:16

እናንተ ትበዛላችሁ ፍሬም ታፈራላችሁ

“እናንተ” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። “ፍሬ ታፈራላችሁ” የሚለው ሀረግ ብዙ ልጆች እንደሚኖራቸው የሚያሳይ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በቁጥር እጅግ በጣም ትበዛላችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ነገር ከእንግዲህ ወዲህ ወደ ልባቸው አይመጣም

እዚህ ላይ “ወደ ልባቸው መምጣት” የሚለው ስለ ነገሩ ማሰብን ይወክለል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለወደፊት ይህን ነገር አያስቡትም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 3:17

ይህ የእግዚአብሔር ዙፋን ነው

እዚህ ላይ “የእግዚአብሔር ዙፋን” እግዚአብሔር ተቀምጦ የሚመራበትን ስፍራ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ እግዚአብሔር ከሚመራበት ስፍራ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህም ወዲህ ክፉውን እልከኛ ልባቸውን ተከትለው አይሄዱም

እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ድርጊት ሲናገር ሕዝቡ በመንገድ እንደሚጓዙ አድርጎ ገልጾታል። እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል አእምሮአቸውን ወይም ፈቃዳቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእንግዲህም ወዲህ ሊያደርጉ የሚፈልጉትን ክፉ ነገር በእልከኝነት አያደርጉትም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት ከእስራኤል ቤት ጋር አብረው ይሄዳሉ

እዚህ ላይ “አብረው ይሄዳሉ” የሚለው አንድ እንደሚሆን ያመለክታል። አማራጭ

ትርጉም፦ “የይሁዳ ቤት ከእስራኤል ቤት ጋር አንድ ይሆናሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የይሁዳንና የቢንያምን ልጆች የሚያካትተውን የይሁዳን መንግስት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ መንግስት” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የእስራኤልን መንግስት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “እስራኤል” ወይም “የእስራኤል መንግስት” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ርስት አድርጌ ለአባቶቻችሁ የሰጠኋት ምድር
እግዚአብሔር ለዘላለም ይወርሷት ዘንድ ምድሪቱን ለእነርሱ ስለመስጠቱ ሲናገር የሚወርሱት ርስት እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለዘላለም ለልጆቻቸው ይሆን ዘንድ ርስት አድርጌ ለአባቶቻችሁ የሰጠኋት ምድር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 3:19
እንደ እኔ
“እኔ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።
እንደ ወንዶች ልጆቼ ምንኛ በደስታ ልቁጠርሽ አልሁ … ሕዝቤ
ይህ የእግዚአብሔርን ፍላጎት የሚገልጽ ድምፀት-አንክሮ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እንደ ወንድ ልጄ ልንከባከባችሁ እጅግ በጣም ፈለግሁ … ሕዝቤ” (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ወንድ ልጁ ልንከባከባችሁ ፈለግሁ
እግዚአብሔር እስራኤል ወንድ ልጁ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን ለባልዋ ታማኝ እንዳልሆነች ሚስት እንዲሁ አታለላችሁኝ
እግዚአብሔር እስራኤል ለእርሱ ታማኝ ስላለመሆኗ ሲናገር ታማኝ እንዳልሆነች ሚስት አድርጎ ገልጾአታል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ያማረቻው ርስት
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሊሰጣት ስለሚፈልጋት ምድር ሲናር ርስት እንደሆነች አድርጎ ገልጾአታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የእስራኤልን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እስራኤል” ወይም “የእስራኤል መንግስት” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 3:21
ድምፅ ተሰማ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕዝብ ጩኸት ሰሙ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ሕዝብ ልቅሶና ልመና
“የእስራኤል ሕዝብ በታላቅ ጩኸት ያለቅሱና ይለምኑ ነበር”
እግዚአብሔረር አምላካቸውን ረሱ
እዚህ ላይ “ረሱ” የሚለው መተውና ችላ ማለትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አምላካቸውን እግዚአብሔርን ችላ አሉት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ከዳተኛነታችሁን እፈውሳለሁ!
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) “ከዳተኝነታችሁን እፈውሳለሁ” እግዚአብሔር ለእግዚአብሔር አለመታመኗን እንድታቆም ማድረጉን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለእኔ አለመታመንሽን እንድታቆሚ አደርጋለሁ” ወይም 2) “ከዳተኝነታችሁን እፈውሳለሁ” ስለ አለመታመኗ ይቅር እንደሚላት የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ለእኔ አለመታመንሽን ይቅር እላለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አለመታመንሽን እፈውሳለሁ
“ለእኔ አለመታመንሽን እንድታቆሚ እፈውስሻለሁ”
እነሆ! ወደ አንተ እንመጣለን
ይህ የእስራኤል ሕዝብ የሚናገረው ነገር እንደሆነ የሚታሰብ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕዝቡ እንዲህ ብለው ይመልሳሉ፣ ‘እነሆ! ወደ አንተ እንመጣለን’ ወይም “ እንዲህ ትላላችሁ፣ ‘እነሆ! ወደ አንተ እንመጣለን’” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ
x
Jeremiah 3:23
በእርግጥ መታለል ከኮረብቶች ይመጣል
እዚህ ላይ “ኮረብቶች” የሚለው ሕዝቡ በኮረብቶች ላይ የሚያደርጉትን የሐሰተኛ አማልክት አምልኮ ይወክላል። አሁን ሕዝቡ እነዚህ ሐሰተኛ አማልክት እነርሱን ሊመሩአቸውና ሊረዱአቸው እንደማይችሉ አውቀዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኛ በኮረብቶች ላይ የምናመልካቸው ሐሰተኛ አማልክት ሊመሩን አይችሉም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ከተራሮች የሚመጣ ግራ የሚያጋባ ጩኸት
ሰዎች ሐሰተኛ አማልክትን በኮረብቶችና በተራሮች ላይ ሲያመልኩ ብዙ ጩኸት ያሰማሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “እኛ ሐሰተኛ አማልክትን ስናመልክ በተራሮች ላይ ግራ የሚያጋባ ጩኸት እናሰማለን ነገር ግን እነርሱ እኛን አይረዱንም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በእውነት የእስራኤል መዳን በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ ነው
“በእውነት የእስራኤል አዳኝ አምላካችን እግዚአብሔር ነው” ወይም “በእውነት እስራኤልን ሊያድን የሚችል ብቸኛው አምላካችን እግዚአብሔር ነው”
ነውረኛ ጣዖቶች አባቶቻችን የሰሩትን ሁሉ በሉት
ይህ የእስራኤል ሕዝብ ያላቸውን ንብረት ሁሉ ለጣዖቶች መስዋዕት አድርገው ከማቅረባቸው የተነሳ ብዙ ሀብታቸውን ማጣታቸውን የሚወክል ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በጎቻቸውንና ከብቶቻቸውን፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን
ይህ የእስራኤል ሕዝብ ለጣዖቶች እያረዱ መስዋዕት አድርገው ያቀረቡት የእንስሳትና የሰዎች ዝርዝር ነው።
እንግዲህ እፍረታችንን ተከናበን እንተኛ፤ ውርደታችንም ይሸፍነን
እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ፣ ደግሞም ሕዝቡ ነውረኛ ባህርያቸውን ሙሉ በሙሉ እንደተገነዘቡ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሙሉ በሙሉ ራሳችንን እናዋርድ” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
ውርደታችንም ይሸፍነን
ውርደታቸውን ሙሉ በሙሉ መገንዘባቸው ውርደት እንደ ብርድ ልብስ ወይም ጨርቅ እነርሱን እንደሸፈናቸው ተደርጎ ተነግሯል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከልጅነታችን ጊዜ ጀምሮ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) “ከልጅነታችን ጊዜ ጀምሮ” የሚለው እያንዳንዱ ሰው ወጣት የነበረበትን ጊዜ ያመለክታል። ወይም 2) “ከልጅነታችን ጊዜ ጀምሮ” እስራኤል መጀመርያ ሕዝብ የሆነችበትን ጊዜ የሚያመለክት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “መጀመርያ ሕዝብ ከሆንንበት ጊዜ ጀምሮ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የአምላካችንንም የእግዚአብሔርን ድምፅ አልሰማንም
እዚህ ላይ “መስማት” መታዘዝን ይወክላል፣ “የእግዚአብሔር ድምፅ” ደግሞ እግዚአብሔር የተናገረውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አምላካችን እግዚአብሔር የተናገረውን አልታዘዝንም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 4
Jeremiah 4:1
እስራኤል ሆይ፣ ብትመለስ
እዚህ ላይ “መመለስ” የሚያመለኩትን ለመለወጥ ተለዋጭ ዜቤ ነው፣ እስራኤል ደግሞ የእስራኤልን ሕዝም የሚወክል ምትክ ስም ነው። ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ጣዖቶችን ያመልክ ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ የምትመለስ ከሆነ” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ የምታመልከውን የምትለውጥ

ከሆነ" ( ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- "እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው" ወይም "እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው" (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
በመመለስህ ለእኔ ትሆናለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ይህ ወደ ማን መመለስ እንዳለባቸው አጽንዖት የሚሰጥ ትዕዛዝ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "ወደ እኔ ተመለስ" ወይም "እኔን አምልክ" 2) ይህ ሁኔታዎችን የሚያብራራው የመጀመርያው ሀረግ ድጋሚ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "ወደ እኔ የምትመለስ ከሆነ" ወይም "እንደገና እኔን ማምለክ የምትጀምር ከሆነ" (ምትክ ስም እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
አስጸያፊ ነገሮችህን ከፊቴ ብታስወግድ
እዚህ ላይ "አስጸያፊ ነገሮች" የሚለው እግዚአብሔር የሚጠላቸው ጣዖቶችን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "አስጸያፊ ጣዖቶችህን ከእኔ ፊት ብታስወግድ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ከእኔ ርቀህ መቅበዝበዝ ብትተው
እዚህ ላይ "መቅበዝበዝ" የሚለው ታማኝ ላለመሆን ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "ለእኔ ታማኝ ሆነህ ብትቀጥል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሕያው እግዚአብሔር
"እግዚአብሔር በእርግጠኝነት ሕያው እንደሆነ ሁሉ።" ሕዝቡ ይህን መግለጫ የሚጠቀሙት ቀጥለው የሚናገሩት ነገር በእርግጠኝነት እውነት እንደሆነ ለማሳየት ነው። ይህ የማይናወጥ ቃል ኪዳን የማድረግ መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "እኔ በማይናወጥ መልኩ እምላለሁ" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
አሕዛብ በእርሱ ይባረካሉ
እዚህ ላይ "አሕዛብ" ለሌሎች መንግስታት ሕዝቦች ምትክ ስም ነው። "እርሱ" የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። የሚናገረው እግዚአብሔር ስለሆነ "እኔ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- "የሌሎች መንግስታት ሕዝቦች በእኔ ይባረካሉ" (ምትክ ስም እና አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
አሕዛብ በእርሱ ይባረካሉ
እዚህ ላይ "በእርሱ ይባረካሉ" የሚለው እንዲባርካቸው እግዚአብሔርን ለመጠየቃቸው ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "የሌሎች መንግስታት ሕዝቦች እንዲባርካቸው ይጠይቁታል" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ይከበራሉ
"እርሱ" የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። የሚናገረው እግዚአብሔር ስለሆነ "እርሱ" የሚለው "እኔ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- "በእኔ ይመካሉ" ወይም "እኔን ያመሰግኑኛል" (አንደኛ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ዕዳሪውን መሬታችሁን እረሱ በእሾህም ላይ አትዝሩ
እግዚአብሔር ዘር ለመዝራት መሬቱን እንደሚያዘጋጅ ገበሬ እእንደዚሁ ሕይወታቸውን እንዲያዘጋጁ ለሕዝቡ ይነግራቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 4:4
ለእግዚአብሔር ራሳችሁን ግረዙ፥ የልባችሁንም ሸለፈት አስወግዱ
እግዚአብሔር ሕዝቡ ለእርሱ ያለውን ታማኝነት በአካል በሚገለጥ የቃል ኪዳን ምልክት መግለጫ ቋንቋ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- "ራሳችሁን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አቅርቡ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ራሳችሁን ግረዙ ... የልባችሁንም ሸለፈት አስወግዱ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታወነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለተቱም አንድ ላይ ትዕዛዙን አጽንዖት ይሰጡታል። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
ቍጣዬ እንደ እሳት እንዳይወጣ የሚያጠፋውም ሳይኖር እንዳያቃጥል
እግዚአብሔር ከመጠን በላይ ስለመቆጣቱ ሲናገር ቁጣው እሳት እንደሆነ አድርጎ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- "ቍጣዬ እንደ እሳት ይነድዳል ማንም ሊያጠፋው አይችልም" ወይም "እኔ ከመጠን በላይ እቆጣለሁ እኔን ማቆም የሚችል ማንም የለም" (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቁጣ
"ታላቅ ንዴት"
በይሁዳ ዘንድ ተናገሩ በኢየሩሳሌምም ላይ አውሩ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለቱም በአንድ ላይ ትዕዛዙን አጽንዖት ይሰጡታል። (ትይዩነት/ተመሳሳይነትየሚለውን ይመልከቱ)
በኢየሩሳሌምም ላይ አውሩ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- "በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች እንዲሰሙት አድርጉ" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በአገሪቱ ላይ መለከት ንፉ
መለከት ሰዎችን ጠላቶቻቸው ሊያጠቁአቸው እየመጡ እንደሆነ ያስጠነቅቃል።
ወደ ተመሸጉት ከተሞች እንሂድ
እነርሱ ከጠላቶቻቸው ለመዳን ወደ ተመሸጉት ከተሞች ይሄዳሉ።
ክፉ ነገር ... ታላቅ ጥፋት
እነዚህ ሁለት ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ታላቅ ጥፋት" የሚለው ሀረግ "ክፉው ነገር" ምን እንደሚሆን ያብራራዋል። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ከሰሜን ክፉ ነገርንና ጽኑ ጥፋትን አመጣለሁና
ይህ እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ ክፉ ነገርንና ጽኑ ጥፋትን ለማምጣት ከሰሜን ጦር ሰራዊት እንደሚልክ የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "እኔ እናንተን እንዲያጠፋ ከሰሜን ጦር ሰራዊት እንዲመጣ አደርጋለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሰሜን
ይህ ከሰሜን የሚመጣውን የጠላት ጦር ሰራዊት የሚወክል ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 4:7
አንበሳ እየመጣ ነው
እግዚአብሔር በጣም ኃያል ስለሆነ ጦር ሰራዊት ሲናገር በጣም ኃይለኛ ተናካሽ አንበሳ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- "ኃይለኛና ምህረት አልባ ጦር ሰራዊት እየቀረበ ነው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጭፍቅ ዱር
ተጠጋግተው አብረው ያደጉ የቁጥቋጦ ክምችት
ሕዝብን የሚያጠፋ አንድ ሰው
እዚህ ላይ "አንድ ሰው" የሚለው ንጉስና ሰራዊቱን የሚወክል ነው። (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወጥቶአል
ይህ ፈሊጥ መንቀሳቀስ መጀመሩን የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "መዝመት እየጀመረ ነው" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ምድርሽን ባድማ የሚያደርግ
ይህ ሰዎች ምድሪቱን ሲመለከቱ ድንጋጤ የሚፈጥርባቸው ዓይነት ጥፋት የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "ምድርሽን ለማጥፋት" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ማቅ ልበሱ
ሰዎች በጣም ኃዘንተኞች እንደሆኑ ለመግለጽ ማቅ ይለብሳሉ። በዚህ ዓውድ ሕዝቡ ስለሰሩአቸው ክፉ ስራዎች በጣም ማዘናቸውን ለማሳየት ሊሆን ይችላ። አማራጭ ትርጉም፡- "ማዘናችሁን የሚያሳዩ ልብሶችን ልበሱ" (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ዋይ በሉ
በከፍተኛ ጩኸት ማልቀስ
የእግዚአብሔር ጽኑ ቍጣ ከእኛ ዘንድ አልተመለሰምና
"ቁጣ" ከሰዎች ሊመለስ የሚችል ሕይወት ያለው ነገር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። እዚህ ላይ "የእግዚአብሔር ቍጣ ከእኛ ዘንድ አልተመለሰም" የሚለው እግዚአብሔር አሁንም በሕዝቡ ላይ ተቆጥቷል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- "እግዚአብሔር አሁንም በሕዝቡ ላይ በጣም ተቆጥቷልና" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 4:9
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- "እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው" ወይም "እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው" (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
የንጉሡና የመኳንንቱ ልብ ይሞታል
እዚህ ላይ "ልብ" የሚለው ወኔን ይወክላል። በተጨማሪ "ልብ ይሞታል" የሚለው

ወኔ ማጣትንና መፍራትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጉሡና መኳንንቱ ወኔአቸው ይጠፋል” ወይም “ንጉሡና መኳንንቱ ይፈራሉ” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰይፍ በሕይወታቸው ላይ ተቃጥቷል
እዚህ ላይ ሕዝቡን ለመግደል ስለተዘጋጁት ጠላቶች ሲናገር ሰይፉ በሰዎች ላይ እንደሚሰነዝር ሰው ተደርጎ ተገልጾአል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶቻችን በሰይፋቸው እኛን ለማረድ ተዘጋጅተዋል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 4:11
እንዲህ ተብሎ ይነገራል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ይናገራል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚያቃጥል ነፋስ በምድረ በዳ ካሉ ከወናዎች ኮረብቶች ... ጽኑ የሆነ ነፋስ
እዚህ ላይ “የሚያቃጥል ነፋስ” የሚለው በጣም አጥፊና ምህረት አልባ ጠላትን ይወክላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይመጣል
“ይጓዛል” ወይም “ይፈጥናል”
የሕዝቤ ሴት ልጅ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደ ሴት ልጅ አድርጎ በመናገር ፍቅሩን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝቤ፣ ለእኔ እንደ ሴት ልጅ የሆኑት” ወይም “ውድ ሕዝቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አያበጥራቸውም ወይም አያጠራቸውም
“ማበጠር” እና “ማጥራት” የሚሉት ቃላት ጠቃሚ ያልሆነውን ሽፋን ከእህል ማራገፍን ያመለክታል። ለዚህ የሚያስፈልገው ቀላል ነፋስ ብቻ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “ገለባውን ከእህል ለመለየት የሚያስፈልገው ቀላል ነፋስ አይሆንም” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ and ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በእኔ ትዕዛዝ ይመጣል
“እኔ እንዲመጣ ባዘዝሁት ጊዜ ይመጣል”
በእኔ ትዕዛዝ
ይህ አገላለጽ በዕብራይስጡ በአንዳንድ የቅርብ ጊዜ ትርጉሞች “ለእኔ” ወይም “በእኔ” ተብሎ ተተርጉሟል።
ፍርዴን በእነርሱ ላይ እናገራለሁ
“ቅጣታቸውን አውጃለሁ”
Jeremiah 4:13
ተመልከቱ፣ እርሱ እንደ ደመና ያጠቃቸዋል
“እርሱ” የሚለው ቃል ጠላት የሆነውን ንጉስና ጦር ሰራዊቱን ያመለክታል። የጦር ሰራዊቱ በቁጥር ብዙ መሆን እጅግ በጣም ከባድ የደመና አውሎ ነፋስ እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ተመልከቱ፣ እንደ ታላቅ ደመና የሆኑ ብዙ ጦር ሰራዊቶች ለማጥቃት እየተሰባሰቡ ነው” ወይም “ብዙ ጦር ሰራዊቶች ለማጥቃት እየተሰባሰቡ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰረገሎቹም እንደ ዐውሎ ነፋስ ናቸው
የጠላት ሰረገሎች እንደ ዐውሎ ነፋስ እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። ዐውሎ ነፋስ ታላቅ ድምጽ ያላቸው፣ አጥፊና ፈጣን እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ሊሆኑ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚመጡት የሰረገሎቻቸው ጩኸት እንደ አጥፊ ዐውሎ ነፋስ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእኛ ወዮልን
“ይህ አሰደንጋጭ ነው”
መጥፋታችን ነውና
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ያጠፉናልና” ወይም “እነርሱ ያወድሙናልና” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ልብሽን ከክፉ ነገር አጠቢ
ይህ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሰዎች ንስሃ እንዲገቡ ማስጠንቀቂያ ነው። “ልብሽን እጠቢ” የሚለው ክፋትን ከሕይወታቸው ለማስወገድ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ ክፉ መሆን አቁሙ” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ በክፋት መኖር አቁሙ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ኃጢአት እንዴት እንደምትሰሪ ጥልቅ አሳብ የሚኖርብሽ እስከ መቼ ድረስ ነው?
ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው ሁልጊዜ እንዴት ኃጢአት መስራት እንዳለባቸው ስለማቀዳቸው ሕዝቡን ለመገሰጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእናንተ ጥልቅ ሃሳብ እንዴት ኃጢአት መስራት እንዳለባችሁ ነው” ወይም “ሁልጊዜ ኃጢአት እንዴት መስራት እንዳለባችሁ ታስባላችሁ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ )
የተናጋሪ ድምፅ ከዳን ዘንድ ዜና ያመጣል
እዚህ ላይ “ድምፅ” መልእክተኛን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልእክተኛ ይመጣና በዳን ምን እየሆነ እንዳለ ይነግራችኋል” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዳን
ይህ የሚያመለክተው ምናልባት ምዕራባዊ ኢየሩሳሌም የሆነውን የዳን አካባቢ ነው።
ከኤፍሬም ተራሮች የሚመጣው ጥፋት ይሰማል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በኤፍሬም ላይ ስለሚመጣው ጥፋት ሰዎች ይሰማሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ከዳን ... የኤፍሬም ተራሮች
ጠላቶች ወደ ዳንና ኤፍሬም እንደደረሱ በመስማት በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ጠላቶች ወደ እነርሱ እየቀረቡ እንደሆነ ይገነዘባሉ።
Jeremiah 4:16
ጠባቂዎች ይመጣሉ
“ጠባቂዎች” በከተማው የሚኖሩ ሰዎች የምግብና የውኃ አቅርቦት እንዳያገኙ ለመጠበቅ ከተማይቱን የሚከብቡ ወታደሮች ናቸው።
እነርሱ በዙሪያዋ ከብበው እንደ እርሻ ጠባቂዎች ይሆኑባታል
ሰዎች ወደ ውስጥ እንዳይገቡና ወደ ውጭ እንዳይወጡ ከተማን በጥንቃቄ መጠበቅ ሰዎች ከእርሻ እንዳይሰርቁ እርሻን በጥንቃቄ እንደሚጠብቁ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “የተመቻቸ እርሻን በጥንቃቄ እንደሚጠብቁ ጠባቂዎቿኢየሩሳሌምን በጥንቃቄ ይጠብቁአታል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሷን ዙርያዋን ሁሉ ከብበው
“እርሷ” የሚለው ቃል ኤሩሳሌምን ያመለክታል። ኢየሩሳሌም ብዙ ጊዜ እንደ ሴት እንደሆነች ተደርጋ ትነገራለች። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሷ በእኔ ላይ ዓመፀኛ ነበረች
“እርሷ” የሚለው ቃል ኢየሩሳሌምን ያመለክታል፣ የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ደግሞ ይወክላል። “እኔ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የኢየሩሳሌም ሕዝብ በእኔ ላይ አመፀኞች ነበሩ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
የገዛ ጠባይሽና ሥራሽ እነዚህን ነገሮች አድርጎብሻል
እዚህ ላይ “ጠባይ” እና “ስራ” ነገሮችን ማድረግ የሚችሉ ሰዎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። እነዚህ ረቂቅ ስሞች “የሰራችሁት ስራ” በሚለው ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት በሰራችሁት ስራ ምክንያት ነው” (ሰውኛ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ልብሽን ይሰብራል
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል ምናልባት ስሜትን ያመለክታል፣ “ልብሽን ይሰብራል” የሚለው ሀረግ ደግሞ ምናልባት በከፋ መልኩ እንዲሰቃዩ ማድረጉን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ልብሽን በጥልቀት እንደሚሰብር ይሆንብሻል” ወይም “በጣም አስደንጋጭ በሆነ ጭንቀት እንድትሰቃዩ ያደርግሻል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 4:19
ልቤ! ልቤ!
እዚህ ላይ “ልብ” እንደ ሀዘንና ፍርሃት የመሳሰሉ የሚያሰቃዩ ስሜቶች ይወክላል። ሀረጎቹ የተደጋገሙት የስቃዩ ጥልቀትን ለመግለጽ ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ በልቤ ጭንቀት አለብኝ
ተናጋሪው ከባድ አካላዊ ሕመም የሚያመጣ ከባድ ስሜታዊ ሕመም ተሰምቶታል።
በውስጤ ልቤ ታውኮብኛል

“በውስጤ ልቤ ከመጠን በላይ ይመታል።” እዚህ ላይ “ልብ” የሰውነት ክፍልን ያመለክታል። ልቤ የሚታወከው ከመደበኛው በላይ በጣም ጠንካራና ፈጣን በሆነ መልኩ ስለሚመታ ነው።

ሁከት

ግራ መጋባት፣ አመጽ፣ ወይም ምስቅልቅል የሆነ ነገር የተሞላበት፤ ያልተረጋጋ ወይም ያልሰከነ

በድንገትም ድንኳኔ ጠፉ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶች በድንገት ድንኳኔን አፈረሱት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በቅጽበት ዓይን መጋረጃዎቼ ጠፉ

“ጠፉ” የሚለው ቃል ከበፊቱ ሀረግ በሚገባ መረዳት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መጋረጃዎቼ በቅጽበት ዓይን ጠፉ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

መጋረጃዎች

መጋረጃዎች በድንኳን ውስጥ የተለያዩ ክፍሎችን ለመከፋፈል የሚሰቀሉ ጨርቆች ናቸው።

Jeremiah 4:21

እስከ መቼ የጦርነት ዓርማ እመለከታለሁ? እስከ መቼስ የመለከቱን ድምፅ እሰማለሁ?

ኤርምያስ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ለዚህ ያህል ረጅም ጊዜ የጦርነት ዓርማ ስለመመልከቱና የመለከቱን ድምፅ ስለመስማቱ ያለውን ጭንቀት ለማሳየት ነው። ጦርነቱ በፍጥነት ቢያልቅ ይመኛል። ይህ በግነት መልክ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጦርነቱ ቢያልቅና የጦርነት ዓርማው ቢወርድ እና የጦር ሰራዊቱ የመለከት ድምጽ ቢቆም እንዴት እመኝ ነበር” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የጦርነት ዓርማ

“የጦጦነት ሰንደቅ ዓላማ”

የመለከት ድምፅ

አንድ ሰው ለጦርነት ጥሪ ለማድረግ እንደ ምልክት መለከት ይነፋል።

ሕዝቤ ሰንፈዋልና … በጎ ነገርን ማድረግ አያውቁም

እግዚአብሔር እንዲህ እንደተናገረ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። ይህ ምናልባት እግዚአብሔር ጦርነቱ አሁንም ለምን እየተካሄደ እንደሆነ ለኤርምያስ የሰጠው ምላሽ ሳይሆን አይቀርም። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እንዲህ ሲል መለሰ፣ ‘በሕዝቤ ሞኝነት ምክንያት ነው … በጎ ነገርን ማድረግ አያውቁም።’” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞኝ ሕዝብ

“ደደብ ሕዝብ”

Jeremiah 4:23

አጠቃላይ መረጃ፡-

ኤርምያስ በኋላ ስለሚሆኑት ነገሮች እግዚአብሔር የሰጠውን ራዕይ ያብራራል።

እነሆ

እዚህ ላይ “እነሆ” የሚለው ቃል ተከታዩን አስደናቂ መረጃ ልብ እንድንል ያነቃናል።

ቅርጽ የለሽና ባዶ

ራእዩ ሕዝቡ በሙሉ ምርኮኛ ሆነው ከተወሰዱ በኋላ የእስራኤል ምድር ምን እንደምትመስል የሚያሳይ ትንቢት ነው።

ለሰማያት ብርሃን አልነበራቸውም

“በሰማይ ላይ ብርሃን አልነበረም”

ከተሞች በሙሉ ፈራርሰዋል

“ከተሞች በሙሉ ጠፍተዋል” ወይም “ከተሞች በሙሉ የፍርስራሽ ክምር ሆነዋል”

በእግዚአብሔር ፊት፣ በእርሱ ብርቱ ቁጣ ፊት

ይህ እነዚህ ነገሮች በሙሉ የተፈጸሙት እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝብ ላይ በመቆጣቱ ምክንያት እንደሆነ ያመለክታል።

Jeremiah 4:27

ምድር ሁሉ ባድማ ትሆናለች

“የይሁዳ ምድር ሁሉ ባድማ ትሆናለች” ወይም “የይሁዳ ምድር ሁሉ ትፈራርሳለች”

ምድሪቱ ታለቅሳለች፥ በላይም ሰማይ ይጨልማል

ምድሪቱ ራሷ ታላቅ ሃዘን እየገለጸች ነው ብሎ በመናገር ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ፍርድ አጽንዖት ይሰጣል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ኋላ አልልም

“ሃሳቤን አልለውጥም”

እነዚህን ከማድረግ አልመለስም

እዚህ ላይ “አልመለስም” የሚለው እሰራለሁ ብሎ የተናገረውን ነገር ላለመስራት መወሰኑን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እሰራለሁ ብየ የተናገርሁትን ነገር ስለመስራቱ ሀሳቤን አልለውጥም” ወይም “እኔ ለመስራት ያቀድሁትን ነገር መስራቴን አልተውም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማ ሁሉ

እዚህ ላይ “ከተማ” የሚለው በከተማ የሚኖረውን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የከተማው ሁሉ ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ፈረሰኞች

ፈረሶች የሚጋልቡ የወታደሮች በቡድን

ወደ ችፍግ ደን ይገባሉ

ለደህንነታቸው ሲሉ ወደ ችፍግ ጫካዎች ይሮጣሉ።

ከተሞች ሁሉ ባዶ ቀርተዋል፣ የሚኖርባቸው አንድም ሰው የለም

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው:: ሁለተኛው ሀረግ በመጀመርያው ሀረግ ውስጥ ያለውን ሃሳብ ያጠናክረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከተሞች ሰው አልባ ይሆናሉ። በእነርሱ ለመኖር የቀረ አንድም ሰው የለም። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 4:30

አያያዥ ሀሳብ፡-

እግዚአብሔር ለይሁዳ መናገሩን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡-

እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ ሴተኛ አዳሪ እንደነበሩ አድርጎ ይናገራቸዋል ምክንያቱም እነርሱ ሌሎች አማልክትን በማምለክ ለእርሱ ታማኞች ስላልነበሩ ነው።

አንቺ ለጥፋት የተዳረግሽ ሆይ፣ አሁን ምን ትሰሪያለሽ?

ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው ራሳቸውን ለመርዳት ሊያደርጉት የሚችሉት ምንም ነገር እንደሌለ ለእስራኤል ሕዝብ ለመንገር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አሁን ጠላቶቻችሁ ለጥፋት ዳርገዋችኋል፣ እርዳታ ለማግኘት ልታደርጉ የምትችሉት ምንም ነገር የለም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ቀይ ለበስሽ … በወርቅ አጌጥሽ … ዓይኖችሽን … በኩል ተኳልሽ

እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ ሲናገር ወንዶችን ወደራሷ ለመማረክ ራስዋን እንደምታስውብ ሴተኛ አዳሪ እንደነደበሩ አድርጎ ይናገራል። ይህ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ሴተኛ አዳሪ ቀይ ለበስሽ … በወርቅ አጌጥሽ … ዓይኖችሽን … በኩል ተኳልሽ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀይ ልብስ ለበስሽ

እዚህ ላይ “ቀይ” የሚለው ውድ የሆነ ቀይ ልብስን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ውድ የሆነ ቀይ ልብስ ለበስሽ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ራስሽን በወርቅ ጌጣጌጥ አጌጥሽ

“የወርቅ ጌጣጌጥ አደረግሽ”

የተወዳጀሻቸው ወንዶች አሁን ትተውሻል

እግዚአብሔር ይሁዳ ለባለጠግነትና ለንግድ ስለተማመነችባቸው መንግስታት ሲናገር ይሁዳን እንደተወዳጁ ወንዶች አድርጎ ገልጾአቸዋል። እነዚህ መንግስታት የእግዚአብሔርን ፍርድ ሲመለከቱ ይሁዳን ይተዉአታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ሕይወትሽን ለማጥፋት እየሞከሩ ነው

እዚህ ላይ “ሕይወትሽን ለማጥፋት እየሞከሩ ነው” የሚለው የይሁዳን ሕዝብ ለመግደል እየሞከሩ መሆናቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ አንቺን ለመግደል እየሞከሩ ነው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በወሊድ እንደምትጨነቅ

ይህ ተነጻጻሪ ዘይቤ ጥቅም ላይ የዋለው ይሁዳ ምን ያህል ክፉኛ እንደምትጨነቅ ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሴት ልጅ በምትወልድበት ጊዜ የሚሰማት ዓይነት ሕመምና ስቃይ ከባድ ጭንቀት” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የጽዮን ሴት ልጅ

እግዚአብሔር ስለ እነርሱ እንደ ሴት ልጁ አድርጎ በመናገር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ፍቅሩን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “ውድ ሴት ልጄ፣ ጽዮን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወዮልኝ

“እኔ ትልቅ አደጋ ውስጥ ነኝ”

ተዝለፈለፍሁ

“እኔ እየደከምሁ ነው”



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 5
Jeremiah 5:1
አጠቃላይ መረጃ:-
ኤርምያስ ብዙ ጊዜ ትንቢቱን የሚፈጽመወ በግጥም ቅርጽ ነው፡፡ የዕብራውያን ግጥም የተለያዩ ትይዩነቶችን ይጠቀማል፡፡ (ግጥም እና ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
በመንገዶች እስቲ ውጡ
"በመንገዶቹ በፍጥነት ሂዱ"
ተመልከቱ አስቡም
"መመልከትና ማግኘት"
የከተማዋ አደባባዮች
በከተማ ውስጥ ሰዎች የሚሰባሰቡበት ሰፊና ክፍት ቦታዎች
ፍትህን የሚያደርግ ማን ነው
"ፍትህ የሆነውን የሚያደርግ ማን ነው"
ምንም እንኳ እነርሱ ቢናገሩም
"እነርሱ" የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል፡፡
ሕያው እግዚአብሔርን
"እግዚአብሔር በእርግጠኝነት ሕያው እንደሆነ ሁሉ፡፡" ሕዝቡ ይህን መግለጫ የሚጠቀሙት ቀጥለው የሚናገሩት ነገር በእርግጠኝነት እውነት እንደሆነ ለማሳየት ነው፡፡ ይህ የማይናወጥ ቃል ኪዳን የማድረግ መንገድ ነው፡፡ ይህን ኤርምያስ 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "እኔ በማይናወጥ መልኩ እምላለሁ" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ዓይኖችህ እውነትን አይመለከቱምን?
ኤርምያስ ይህን ጥያቄ የሚጠቀመው እግዚአብሔር የሚፈልገው ታማኝነት እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ ሰዎች ታማኞች እንዲሆኑ መፈለግ ታማኝነትን መፈለግ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "አንተ ታማኝነትን ትፈልጋለህ" ወይም "አንተ ሰዎች ታማኞች እንዲሆኑ ትፈልጋለህ፡፡" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ሕዝቡን መታሃቸው እነርሱ ግን አልተሰማቸውም
እግዚአብሔር ሕዝቡን በተለያዩ መንገዶች ቀጥቷቸዋል፡፡ እዚህ ላይ እርሱ እንደመታቸው ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "አንተ ሕዝቡን ቀጣሃቸው፣ ነገር ግን ምንም ትኩረት አልሰጡም" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ግን አሁንም ለመታረም እምቢ አሉ
እዚህ ላይ "ለመታረም" የሚለው ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ከቅጣት መማርን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "ትምህርታቸውን ለመማር አሁንም እምቢ አሉ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ፊታቸውን ከድንጋይ የበለጠ አጠነከሩ
ጠንካራ ፊቶች ትዕቢተኞች እንደሆኑ የሚያሳይ በፊታቸው ያለውን ሁኔታ የሚወክል ነው፡፡ "ከድንጋይ የበለጠ ማጠንከር" የሚለው ተነጻጻሪ ዘይቤ ሰዎቹ እጅግ በጣም ትዕቢተኞች እንደሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "እነርሱ እጅግ በጣም ትዕቢተኞች ናቸው" (ምትክ ስም እና ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 5:4
ስለዚህ እንዲህ አልሁ
ኤርምያስ እየተናገረ ነው፡፡
እነዚህ ግን ቀንበሩን በአንድነት ሰብረዋል፣ እነዚህ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተሳስራቸውን ሰንሰለት ቈርጠዋል።
ቀንበርና ሰንሰለት እግዚአብሔርንና ሕዝቡን የሚያስተሳስረውን ሕጉን ይወክላል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህ አንበሳ ... ተኩላ ... የሚያደባ ተኩላ
እነዚህ ሰዎችን መግደል የሚችሉ አደገኛ እንስሳት ናቸው፡፡ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) ይህ በእርግጥ የሚናገረው ሰዎችን ስለሚገድሉ ስለ የዱር እንስሳት ነው ወይም 2) እነዚህ የዱር እንስሳት ለጠላት የጦር ሰራዊት ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህ አንበሳ ... ተኩላ ... የሚያደባ ተኩላ ... ይቦጫጭቃቸዋል
ለዚህ ተቀባይነት ያለው አንዱ ትርጉም እነዚህ እንስሳት ይሁዳን የሚያጠቃው የጠላት ጦር ሰራዊት ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "ከዱር እንደሚወጣ አንበሳ፣ ከበረሃ እንደሚመጣ ተኩላ እና እንደሚያደባ ነብር የጠላት ጦር ሰራዊት ወደ ከተማቸው ይመጣል፣ ያጠቃቸዋል፣ ደግሞም ያጠፋቸዋል፡፡ ከከተማው ወጥቶ የሚሄድ ማንኛውም ሰው ይገደላል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዱር
በአንድ ላይ ተጠጋግተው የሚበቅሉ የቁጥቋጡ ክምችት፡፡
ተኩላ
ትልቅ የዱር አደገኛ ውሻ
የሚያደባ
ለማጥቃት አጋጣሚን ለመጠቀም አድፍጦ ማየት
ነብር
ትልቅ የዱር አደገኛ ድመት
በደላቸው በዝቶአልና
"በደላቸው" የሚለው ረቂቅ ስም "ኃጢአት ሰሩ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "ብዙ ኃጢአት ሰርተዋልና" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የክህደታቸው ተግባር እጅግ ብዙ ነው
"የክህደታቸው ተግባር" የሚለው ረቂቅ ስም "እነርሱ የሰሯቸው ያለመታመን ድርጊቶች" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡" አማራጭ ትርጉም:- "እነርሱ የሰሯቸው ያለመተመን ድርጊቶች ብዙ ናቸው" ወይም "ብዙ ያለመታመን ድርጊቶች ሰርተዋል" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 5:7
እነዚህን ሰዎች ይቅር የምላቸው ለምንድን ነው?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እነዚህን ሰዎቸ ይቅር ለማለት ምንም ዓይነት ምክንያት እንደሌለው አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "ከሰሯቸው ስራዎች የተነሳ እነዚህን ሰዎች ይቅር ልላቸው አልችልም" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህ ሰዎች
የኢየሩሳሌም ሕዝብ
ወንዶች ልጆቻችሁ
እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ልጆች ያላት ሴት እንደሆነች አድርጎ እየተናገረ ነው፡፡ የኢየሩሳሌም "ወንዶች ልጆች" የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "የኢየሩሳሌም ሕዝብ" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ እስኪጠግቡ ድረስ መገብኋቸው
የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ መስጠት እነርሱን እንደመመገብ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "የሚያስፈልጋቸውን ማኛውንም ነገር ሰጠኋቸው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ አመነዘሩ፣ ወደ ሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች ብዙ ሆነው ተንጋጉ
ይህ ምናልባት ለእግዚአብሔር ታማኝ ላለመሆንና ጣዖቶችን ለማምለክ ተለዋጭ ዘይቤ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን የጣዖቶች አምልኮ አመንዝራነትን ያካትታል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "እነርሱ ለእኔ ታማኞች አልነበሩም፣ ወደ ሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች ብዙ ሆነው ተንጋጉ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች ብዙ ሆነው ተንጋጉ
"ወደ ሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች ብዙ ሆነው ሄዱ" ወይም "ብዙ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ወደ ሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች ሄዱ"
እንደ ተቀለቡ ፈረሶች ሆኑ ... ከጎረቤቶቻቸው ሚስቶች ኋላ አሽካኩ
ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ሲናገር ከሌሎች ፈረሶች ጋር ወሲብ ለመፈጸም የሚፈልጉ ፈረሶች እንደሆኑ አድርጎ ገልጾአቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "እንደ ተቀለቡ ፈረሶች ሆኑ … ከጎረቤቱ ሚስት ኋላ አሽካካ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በፍትወት የጋሉ
ወሲብ ለማድረግ የተዘጋጁ
ወሲብ ማድረግ
እንስሳት ለመራባት ወሲብ በሚያደርጉበት ጊዜ
እያንዳንዱ ሰው ከጎረቤቱ ሚስት ጋር አሽካካ
ወንድ ፈረሶች ከሴት ፈረሶች ጋር ወሲብ መፈጸም ሲፈልጉ በታላቅ ጩኸት ያሽካካሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም:- "ከአንድ ሴት ፈረስ በላይ ወሲብ እንደሚፈጽም ወንድ ፈረስ እነዚህ ሰዎች ከሌሎች ወንዶች ሚስቶች ጋር ለመተኛት ይፈልጋሉ፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህ አልቀጣቸውምን? ... እኔ ራሴ እንደዚህ ዓይነቱን ሕዝብ አልበቀልምን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የሚጠቀመው እነርሱ የሰሯቸው ነገሮች በጣም መጥፎ ከመሆናቸው የተነሳ እርሱ ምህረት አይኖረውም ነገር ግን ይቀጣቸዋል የሚለውን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሃሳብ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እነዚህን ነገሮች በማድረጋቸው ምክንያት እኔ እቀጣቸዋለሁ … እኔ ራሴ በእርግጠኝነት በእነርሱ ላይ እበቀላለሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:10

አያያዥ ሀሳብ፡-

እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል። እዚህ ላይ የሚናገረው ለእስራኤል ጠላቶች ነው።

ወደ ወይን አትክልቷ ወደ ላይ ሂዱ

ከቁጥር 10-13 እግዚአብሔር የሚናገረው ለእስራኤል ጠላቶች ነው። ይህ በትምህርተ ጥቅስ ግልጽ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እናንተ የእስራኤል ጠላቶች፣ ወደ ወይን አትክልቷ ወደ ላይ ሂዱ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ወይን አትክልቷ ወደ ላይ ሂዱና አፍርሱት

እግዚአብሔር ሲናገር እስራኤልና ይሁዳ የወይን አትክልት እንደሆኑ በዚያ የሚኖሩት ሰዎች ደግሞ ወይን እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “ለእኔ እንደ ወይን አትክልት ወደሆኑት ወደ እስራኤልና ይሁዳ ወደ ላይ ሂዱና አጥፏቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን ፈጽማችሁ አታጥፏቸው

“ሙሉ በሙሉ አታጥፏቸው”

የእነርሱን የወይን ቅርንጫፎች ገነጣጥሉ፣ እነዚህ የወይን ቅርንጫፎች ከእግዚአብሔር አይደሉምና

“የእነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የወይን አትክልቱን ነው። እግዚአብሔር የእስራኤልና የይሁዳ ሕዝቦች ወይን እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “በወይን አትክልት ያለውን ወይን እንደሚቆርጡ ገበሬዎች፣ የእስራኤልንና የይሁዳን ሰዎች ልታስወግዳቸው ይገባል ምክንያቱም የእግዚአብሔር አይደሉምና” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእስራኤልና ለይሁዳ ቤቶች

“ቤት” የሚለው ቃል ለሰውየው ልጆች ምትክ ስም ነው። በዚህ ዓውድ ይህ የሚያመለክተው ለእስራኤልና ለይሁዳ መንግስት ሕዝቦች ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ለእስራኤልና ለይሁዳ ሕዝቦች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ላይ ሐሰትን ተናገሩ ፤ እንዲህም አሉ

“እንዲህ በማለት በእግዚአብሔር ላይ ሐሰትን ተናገሩ”

ክፉ ነገርም በእኛ ላይ አይመጣብንም፣ ሰይፍንና ራብንም አናይም

እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች የሚናገሩት ተመሳሳይ ነገር ነው፣ ሁለተኛው ከአንደኛው ይልቅ ግልጽ ነው። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ ነገርም በእኛ ላይ አይመጣብንም

“በእኛ ላይ አይመጣብንም” የሚለው ፈሊጥ “በእኛ ላይ አይሆንም” ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “በእኛ ላይ መምንም ጉዳት አይደርስብንም” ወይም “ማንም አይጎዳንም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍንና ራብንም አናይም

እዚህ ላይ “ማየት” የሚለው በሁኔታ ውስጥ ለማለፍ ተለዋጭ ዘይቤ ነው፣ “ሰይፍ” ደግሞ ለጦርነት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም:- “በጦርነት ወይም በረሃብ ውስጥ አናልፍም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ነቢያቱ ነፋስ ይሆናሉ

እዚህ ላይ “ነቢያት” የሚለው ነቢያቱ ለሚናገሩት ነገር ምትክ ስም ነው፣ “ነፋስ” የሚለው ደግሞ ምንም ለማይሰራ ነገር ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የነቢያቱ ቃላት እንደሚጮህ ነፋስ ነው” ወይም “ነቢያቱ እንደ ነፋስ ይጮኻሉ፣ ነገር ግን የሚተነብዩት ነገር አይፈጸምም” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሉ በውስጣቸው የለም

እዚህ ላይ “ቃሉ” የሚለው የእግዚአብሔርን መልእክት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “የእግዚአብሔር መልእክት በእነርሱ ውስጥ የለም” ወይም “እነርሱ የሚናገሩት መልእክት ከእግዚአብሔር አይደለም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ያሉት ሁሉ በእነርሱ ላይ ይፈጸም

ነቢያቱ ስለ ምን ዓይነት ነገሮች እየተናገሩ እንደነበር በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ስለዚህ ነቢያቱ ይመጣል ብለው የተናገሩት ክፉ ነገር በእነርሱ ላይ ይምጣባቸው” ወይም “ነቢያቱ በእኛ ላይ ክፉ ነገር ይመጣል ብለው ስለተናገሩ፣ እነዚህ ክፉ ነገሮች በነቢያቱ ላይ ይምጡባቸው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:14

ምክንያቱም እናንተ

“እናንተ” የሚለው ቃል የእስራኤልንና የይሁዳ ሕዝብን ያመለክታል።

እንዲህ ብላችሁ ተናራችሁ

ሕዝቡ ምን እንደተናገሩ በኤርምያስ 5:12 ላይ ተመልከቱ።

Jeremiah 5:16

አያያዥ ሀሳብ፡-

እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

የፍላጻቸውም ሰገባ …. ሁሉም ወታደሮች ናቸው

እዚህ ላይ “የፍላጻቸውም ሰገባ” የሚለው የጠላት መንግስት ጦር ሰራዊትን ይወክላል፣ በሰገባው ውስጥ ያለው ፍላጻ ደግሞ በጦር ሰራዊቱ ውስጥ ያሉትን ወታደሮች ይወክላል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሰገባ

ፍላጻ ለመያዝ የሚጠቅም እቃ

የፍላጻቸውም ሰገባ እንደተከፈተ መቃብር ነው

የተከፈተ መቃር ብዙ አስከሬኖች በአንድ ላይ እንዲቀበሩበት የተዘጋጀ ነው። የጠላት ጦር ብዙ ሰዎችን ይገድላል። አማራጭ ትርጉም:- “የዚያ መንግስት ጦር ሰራዊት ፍላጻቸውን ተጠቅመው ብዙ ሰዎችን ይገድላሉ” ወይም “በጦር ሰራዊቱ ፍላጻዎች ምክንያት ብዙ ሰዎች ይገደላ ደግሞም ይቀበራ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ምርትህን፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህንና ምግብህን ይበላሉ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) ለወንዶችና ለሴቶች ልጆቻቸው ጥቅም ይውል የነበረው ምርታቸውና ምግባቸው ይጠፋል። አማራጭ ትርጉም:- “ስለዚህ ለወንዶችና ለሴቶች ልጆችህ ሊሆን የሚገባው ምርትህና ምግብህ ይተፋል” ወይም 2) ምርታቸው፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው እና ምግባቸው ይጠፋል። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው “መጥፋታቸው” ሃሳቡ ይገደላሉ ለሚለው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ስለዚህ ምርታችሁና ምግባችሁ ይጠፋል፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ደግሞ ይገደላሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ምርታችሁ ይጠፋል

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ስለዚህ የዚያ መንግስት ጦር ሰራዊት ልትሰበስበው ከምትጠብቀው ምርት የሚገኘውን ምግብ ይበላዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በተጨማሪ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህና ምግብህ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ ሊበሉት የሚገባውን ምግብ ጠላቶችህ ይበሉታል፤ ወይም 2) ጠላቶችህ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህን ያጠፉአቸዋል፣ ምግብህን ደግሞ ይበሉታል።

እነርሱ ይበሉታል

“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዚያን መንግስት ጦር ሰራዊት ነው።

የተመሸጉ ከተሞችህን በሰይፍ ይመታሉ

ሰይፍ የሚለው የዚያ መንግስት ሕዝብ ለሚጠቀምባቸው የተለያዩ የጦር መሳርያዎች ወካይ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ይጠብቁኛል ብለህ የምትተማመንባቸውን ጠንከራ ከተሞች ለመያዝ የጦር መሳርያዎቻቸውን ይተቀማሉ (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ የተመሸጉ ከተሞች

የተመሸጉ ከተሞች በውስጣቸው ለሚኖሩ ሰዎች ከውጭ ከሚመጡ ጠላቶቻቸው ለመከላከል በዙርያቸው የግንብ አጥር ነበራቸው።

አንተ የምትተማመንባቸው

“አንተን በደህንነት ለመጠበቅ በጥንካሬ ብቁ ናቸው ብለህ የምታስባቸውን”

Jeremiah 5:18



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብና ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል፡፡
በእነዚህ ቀናት
“በእነዚህ ቀናት” የሚለው ሀረግ ከሩቅ አገር ባዕድ መንግስት የሚመጣበትንና የእስራኤልን ሕዝብ የሚያጠቃበትን ጊዜ የሚያመለክት ነው፡፡
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል፡፡ ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ፈጽሜ አላጠፋችሁም
“አላጠፋችሁም”
እነዚህ ነገሮቸች በሙሉ በእኛ ላይ ሆኑ
“እነዚህ ነገሮች” የሚለው ሀረግ እነርሱን ለማጥቃት የጦር ሰራዊት መላን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሆኑት እኛን ለመጉዳት ነው” ወይም “እኛን ለማጥቃት የውጭ ጦር ሰራዊት ተላከ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እናተ በምድራችሁ ባዕድ እንዳገለገላችሁ እንደዚሁ እንግዶችን ሕዝቦች ማገልገል አለባችሁ
እዚህ ላይ “ባዕድ አማልክት አገለገላችሁ” የሚለው ባዕድ አማልክት ማምለካቸውን የሚወክል ነው፡፡ ባዕድ አማልክትን በማምለካቸው ምክንያት ባዕድ ሕዝብን እንዲያገለግሉ በማድረግ እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ በምድራችሁ ባዕድ አማልክትን ስላመለካችሁ ባዕድ ሕዝብን ታገለግላላችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:20

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል፡፡
ይህን አውሩ
“ይህን ተናገሩ”
የያዕቆብ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የያዕቆብን ልጆች ነው፡፡ በኤርምያስ 2፡4 ላይ እንዳደረግኸው “የያዕቆብ ቤት” ብለህ ተርጉመው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የያዕቆብ ልጆች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ በይሁዳ ይሰማ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በይሁዳ ያሉት ይህን ይስሙት” ወይም “በይሁዳ ምድር ይህን አውጁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ማስተዋል የሌላችሁ
“የማታውቁ” ወይም “ምንም ነገር የማታስተውሉ”
ማየት አትችሉም
እዚህ ላይ “ማየት አትችሉም” የሚለው አታስተውሉም ለሚለው ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ አታስተውሉም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
መስማት አትችሉም
እዚህ ላይ “መስማት አትችሉም” የሚለው አለማስተዋልን ይወክላል፡፡ “አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ አታስተውሉም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል፡፡ ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
በውኔ እኔን አትፈሩም … ፊቴስ?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመበት ሕዝቡ ከመጠን በላይ ሞኝ መሆናቸውን አጽንዖት ለመስጠት ነው፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍርሃት ስለሌላቸው ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- እኔን አለመፍራታችሁ ሞኝነት ነው … ፊቴስ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ከፊቴስ አትደነግጡምን
መደንገጡ በፍርሃት ምክንያት ነው፣ “ከፊቴ” መሆን የሚለው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ መገንዘብን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ከእኔ የተነሳ በፍርሃት ተንቀጥቀጡ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ለባህር ዳርቻ በአሸዋ አድርጌለታለሁ
“እኔ አሸዋን ለባህር ዳርቻ እንዲሆነው አስቀምጬለታለሁ”
በዘላለም ትዕዛዝ እንዳያልፍ
እግዚአብሔር ውቅያኖስን ከአሸዋ ዳርቻው አልፎ ስላለመሄዱ ሲናገር ዳርቻው እንደ ሕግ፣ ውቅያኖስ ደግሞ ሕጉን እንደሚታዘዝ ሰው አድርጎ ገልጾታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እንዳያልፍ የዘላለም ዳርቻ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቢነሳና ቢወድቅም
“ወደኋላ እና ወደፊት ቢንቀሳቀስም”
ዳርቻውን ጥሶ አያልፍም
“ውቅያኖስ ሕጌን ፈጽሞ አያፈርስም፡፡” እግዚአብሔር ስለ ውቅያኖሱ ከዳርቻው አልፎ አለመሄድ ሲናገር ዳርቻው ሕግ እንደሆነ፣ ውቅያኖሱ ደግሞ ሕጉን እንደሚያከብር ሰው አድርጎ ገለጾታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- ዳርቻውን አልፎ መሄድ አይሳካለትም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:23

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል፡፡
ይህ ሕዝብ ትዕቢተኛ ልብ አለው … ሄደውማል
የሕዝቡ ልብ ለእግዚአብሔር ያላቸውን አመለካከት ይወክላል፡፡ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚናገር ከሆነ “እናንተ” በሚለው ቃል ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን እናተ ሕዝቦች እልከኛ ልብ አላችሁ፡፡ እናንተ ሄዳችኋል” ወይም “ነገር ግን እናንተ ሕዝቦች እልከኛ ናችሁ፡፡ እናንተ ሄዳችኋል” ( ተለዋጭ ዘይቤ እና አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ በአመጽ መንገድ ወጥቶ ሄዷል
“እርሱ” የሚለው ቃል ሕዝቡን ያመለክታል፡፡ እዚህ ላይ “ሄዷል” የሚለው እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አምጸዋል ደግሞም እኔን አልታዘዙም ብለዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በልባቸው እንዲህ አላሉም
እዚህ ላይ “በልባቸው” የሚለው “ሃሳባቸውን” ይወክላል፣ “አላሉም” የሚለው ደግሞ “ማሰብን” ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ አያስቡም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለመከርም የተመደቡትን ሳምንቶች ለእኛ የሚጠብቅልንን
እዚህ ላይ “ለመከርም የተመደቡትን ሳምንቶች የሚጠብቅልን” የሚለው እነዚህ ሳምንቶች በትክክለኛው ጊዜ ለመከሰታቸው ማረጋገጥን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ የመከር ሳምንቶች ሊከሰቱ በሚገባበት ጊዜ እንዲመጡ ለእኛ የሚያረጋግጥልን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የእናተ በደል
“የእናተ” የሚለው ቃል የያዕቆብን ልጆችና የይሁዳ ሕዝብን ያመለክታል፡፡
እነዚህ ነገሮች
ይህ ዝናቡንና መከሩን ያመለክታል፡፡
ኃጢአታችሁ መልካም ነገር ወደ እናንተ እንዳይመጣ ከለከለቻችሁ
መልካም ነገር “መምጣት” የሚለው መልካም ነገር መከናወንን ይወክላል፡፡ “በኃጢአታችሁ ምክንያት መልካ ነገር በእናንተ እንዳይሆን ከለከላችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:26

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል፡፡
በሕዝቤ መካከል ክፉዎች ሰዎች ተገኝተዋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በሕዝቤ መካከል ክፉ ሰዎች አግኝቻለሁና” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ወፎችን ለመያዝ እንደሚያደፍጥ ሰው ይመለከታሉ
እግዚአብሔር አንድን ሰው ለመጉዳት ስለሚፈልጉ ክፉ ሰዎች ሲናገር ወፎችን ለመያዝ እንደሚያደፍጥ ሰው አድርጎ ገልጾታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ወፎችን ለመያዝ እንደሚያደፍጥና እንደሚጠብቅ ሰው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወጥመድን ይዘረጋሉ ሰዎችንም ያጠምዳሉ
እግዚአብሔር ሌሎች ሰዎችን ሆን ብለው ስለሚጎዱ ስለክፉ ሰዎች ሲናገር ወጥመድ እንደሚዘረጉ አድርጎ ይገልጻቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በሰዎች ጉዳት እነርሱ እንዲጠቀሙ ነገሮችን ያመቻቻሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ወፎች እንደሞሉት ጎጆ፣ ቤታቸው በማጭበርበር የተሞላ ነው
እዚህ ላይ “ማጭበርበር” የሚለው በማጭበርበር የተወሰዱ ነገሮችን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በአዳኝ እጅ እንዳለ ወፎች እንደሞሉት ጎጆ የክፉ ሰዎች ቤቶች ሰዎችን በማጭበርበር በወሰዱአቸው ነገሮች የተሞላ ነው” (ተነፃፃሪ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ከብረዋል ባለጠጎችም ሆነዋል
እዚህ ላይ “ከብረዋል” የሚለው ኃይለኛ መሆናቸውን የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ክፉ ሰዎች ኃይለኛና ባለጠጋ ሆነዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወፍረዋል ሰብተዋልም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) በሚበሉት ጤናማ ምግብ ምክንያት ቆዳቸው ያብረቀርቃል፣ ወይም 2) በአጥንታቸውና በቆዳቸው መካከል ባለው ጡንቻን ስብ ምክንያት ሰውነታቸው ለስላሳ ነው። እነዚህ ሰዎች በሚገባ እንደሚበሉ ያመለክታል።
የክፋትን ዳርቻ ሁሉ አልፈው ሄደዋል
ሁሉንም ዓይነት ክፋት መስራት በአንዳንድ ክፉ ነገሮችና በሌሎች እጅግ በጣም ክፉ በሆኑ ነገሮች መካከል የሚለይ ዳርቻ እንዳለ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ እጅግ በጣም ክፉ የሆነውንም ነገር ይሰራሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሕዝቡ ወይም የወላጅ አላባዎችን ጉዳይ መልካም እንዲሆንላቸው አልተምዋገቱላቸውም
“ለሕዝቡና ለወላጅ አልባዎች የሚያስፈልጋቸውን እንዲሰጡአቸው በገዢዎች ፊት አልተሞዋገቱላቸውም” ወይም ““ለሕዝቡና ለወላጅ አልባዎች ፍትህ እንዲሰጡአቸው በገዢዎች ፊት አልተሞዋገቱላቸውም”
ለድሆች ፍትህን አልሰጡአቸውም
“ለድሆች ፍትሃዊ የሆነውን ነገር በማድረግ እነርሱን አልረዱአቸውም”
እንደዚህ ያለውን ሕዝብ ልቀጣው አይገባኝምን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እነርሱ የሚሰሯቸው ነገሮች በጣም መጥፎ ስለሆኑ በእነርሱ ላይ ምህረት እንደማያደርግ ይልቁንም እንደሚቀጣቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። በኤርምያስ 5፡9 ላይ እንዴህ ዓይነት ተመሳሳይ ዓረፍተ ነገር እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለዚህ እኔ እቀጣቸዋለሁ፣ ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው። እኔ በእርግጠኝነት እነርሱን እበቀላቸዋለሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 5:30

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።
ግፍና አሰቃቂ ነገር ተከስቷል
ይህ በገቢር ቅርጽ የበለጠ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች በጣም አስደንጋጭና አሰቃቂ ነገሮች ይፈጽማሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በምድሪቱ
እዚህ ላይ “ምድሪቱ” የሚለው የእስራኤልን ምድር ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእስራኤል ምድር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ነቢያት በማጭበርበር ትንቢት ይናገራሉ፣ ካህናትም በራሳቸው ኃይል ያስተዳድራሉ
እነዚህ በቁጥር 30 ላይ የተነገሩት ግፎችና አሰቃቂ ነገሮች ናቸው።
ነቢያት በማጭበርበር ትንቢት ይናገራሉ
“ነቢያቱ የሐሰት ትንቢት ይናገራሉ” ወይም “ነቢያቱ ትንቢት ሲናገሩ ውሸትን ይናራሉ”
ካህናትም በራሳቸው ኃይል ያስተዳድራሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ካህናቱ ለእግዚአብሔር ስልጣን ራሳቸውን አላስገዙም። አማራጭ ትርጉም፡- “ካህናቱ በራሳቸው ስልጣን ያስተዳድራሉ” ወይም 2) ካህናቱ ነቢያቱ በሚሰጡአቸው መመርያ መሰረት ያስተዳድራሉ (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን በመጨረሻ ምን ይሆናል?
“ነገር ግን ይህ ከሆነ በኋላ በመጨረሻ ምን ታደርጋላችሁ?” እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ ለሰሩት ስራ ሲቀጣቸው ክፉ ስለመሆናቸው እንደሚጸጸቱ አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን በመጨረሻ እኔ እቀጣችኋለሁ፣ እናንተም ስለ ክፉ ድርጊታችሁ ትጸጸታላችሁ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

# Chapter 6

## Jeremiah 6:1

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር እየተናገረ ነው።
ከኢየሩሳሌም በመሸሽ ... ደህንነትን አግኙ
እዚህ ላይ “ደህንነትን አግኙ” የሚለው ለመዳን እንዲችሉ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ኢየሩሳሌምን ለቅቆ በመውጣት ... ከአደጋ ዳኑ” ወይም “ከአደጋ መዳን እንድትችሉ ... ከኢየሩሳሌም ለቅቃችሁ ውጡ” ( ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የቢኒያም ሕዝብ
እግዚአብሔር የሚናረው ለእነዚህ ነው።
በቴቁሔ መለከት ንፉ
መለከት ሰዎች ጥቃት እንደሚደርስባቸው ለማስጠንቀቅ የሚነፋ መሳርያ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጥቃት እንደሚደርስባቸው ለሕዝቡ ለማስጠንቀቅ በቴቁሔ መለከትን ንፉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ቴቁሔ
ይህ ከደቡባዊ ኢየሩሳሌም 18 ኪሎ ሜትር ያህል የሚርቅ የከተማ ስም ነው። የከተማው ስም ትርጉም “የሚነፋ መለከት” ማለት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
በቤትሐካሪም ላይ ምልክት ከፍ አድርጋችሁ አሳዩ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ምልክቱ ከእሳት የሚወጣ ጢስ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላት እየመጣ እንደሆነ ሕዝቡን ለማስጠንቀቅ ጢስ ወደ ላይ እንዲወጣ ለማድረግ በቤትሐካሪም እሳት አንድዱ” ወይም “ 2) ምልክቱ ሰንደቅ ዓላማ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላት እየመጣ እንደሆነ ሕዝቡን ለማስጠንቀቅ በቤትሐካሪም ከተማ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርጉ”
ቤትሐካሪም
ይህ ከደቡባዊ ኢየሩሳሌም 10 ኪሎ ሜትር ያህል የሚርቅ የከተማ ስም ነው። የከተማው ስም ትርጉም “የወይን አትክልት ቦታ” ማለት ነው።
ክፋት ከሰሜን ይመጣል
እዚህ ላይ “ክፋት” የሚለው ጥፋትና ጥፋቱን የሚያመጡትን ሰዎች የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶች ከሰሜን ይመጡና በእናንተ ላይ ጥፋት እንዲመጣ ያደርጋሉ” ወይም “ከሰሜን የሚመጡ ጠላቶች ያጠፉአችኋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ታላቅ ጥፋት ይመጣል
ጥፋቱ እንዴት እንደሚመጣ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶች ይመጡና ያጠፉአችኋል” ወይም “ጠላቶች ይመጡና ያፈርሷችኋል” “(ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የጽዮን ሴት ልጅ፣ ውብና ሽሙንሙን
ጽዮን ለኢየሩሳሌም ሌላኛው ስም ነው። እግዚአብሔር ስለ ኢየሩሳሌም ሲናገር ሴት እንደሆነች አድርጎ ይገልጻታል። እርሱ ለኢየሩሳሌም ያለውን ፍቅር ለማሳየት እንደ ሴት ልጅ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ ውድ ጽዮን፣ እንደ ውድና ሽሙንሙን ሴት የመሰልሽ” ወይም “የእኔ ውድ ጽዮን” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እረኞችና በጎቻቸው ወደ እነርሱ ይሄዳሉ
ብዙ ጊዜ ነገስታት የሕዝባቸው እረኞች እንደሆኑ ተደርጎ ይነገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገስታቱና ወታደሮቻቸው ወደ እነርሱ ይሄዳሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሷ ላይ በዙርያዋ በሙሉ ድንኳኖቻቸውን ይተክላሉ
“በእርሷ ላይ” የሚለው ቃል “ጽዮንን ለማጥቃት” ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሷን ለማጥቃት እነርሱ በጽዮን ዙርያ በሙሉ ድንኳኖችን ይተክላል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እያንዳንዱ መንጋውን ያሰማራል
እግዚአብሔር ነገስታቱ ምድሪቱን ለማጥፋት ጦር ሰራዊቶቻቸውን ስለመምራታቸው

ሲናገር ሳር እንዲግጡ መንጎቻቸውን እንሚያሰማሩ እረኞች አድርጎ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም:- “እያንዳንዱ ንጉስ እንደ እረኛ ጦር ሰራዊቱን ይመራል” ወይም “እያንዳንዱ ንጉስ ጦር ሰራዊቱን ይመራል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በራሱ እጅ
እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው አንድ ሰው በእጁ እንዲወስደው የተመደበለት የአንድ ነገር ድርሻ ይወክላል። እዚህ ላይ ንጉስ አሸንፎ እንዲይዘው የተመደበለት የመሬት ድርሻ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “የመሬት ድርሻውን አሸንፎ ይይዛል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 6:4
አጠቃላይ መረጃ:-
ከሚያጠቃው ጦር ሰራዊት ወገን የሆነው ንጉስ ከስልጣኑ ስር ላሉት ሰዎች ይናገራል።
ራሳችሁን አቅርቡ
ነገስታቱ ይህን እንደተናገሩ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ነገስታቱ ለጦር ሰራዊታቸው፣ ራሳችሁን አቅርቡ ብለዋቸዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ጦርነቱን ለማካሄድ ለአማልክቶቻችሁ ራሳችሁን አቅርቡ
የሚያጠቃው ጦር ሰራዊት ለአማልክቶቻቸው የአምልኮ ስርዓት በመፈጸምና መስዋዕት በማቅረብ አማልክቶቻቸው በጦርነቱ ጊዜ እንዲረዷቸው ማረጋገጫ ለመስጠት እየሞከሩ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ራሳችሁን በማንጻትና ለአማልክቶቻችሁ መስዋዕት በማቅረብ ለጦርነቱ ተዘጋጁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ተነሱ፣ እናጥቃቸው
መነሳት ወይም መቆም መመልከትንና ማሰብ በማቆም ይልቁንም እርምጃ መውሰድ መጀመርን የሚያሳይ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ማሰብ እናቁምና ለማጥቃት እንጀምር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በቀትር እናጥቃ
“ኢየሩሳሌምን በቀትር እናጥቃት”
ቀኑ እየመሸ መሆኑ በጣም መጥፎ ነው፣ የማታውም ጥላ ረዝሟል
ምንም እንኳ ቀኑ እየጨለመ ቢመጣም ጦር ሰራዊታቸው መዋጋቱን እንዲቀጥል በሚፈልጉበት ጊዜ ነገስታቱ በቀኑ መጨረሻ ይህን ንግግር ይናገራሉ”
ቀኑ እየመሸ ነው
የቀኑ የመጨረሻው ብርሃን እየጨለመ ከመምጣቱ ጋር ተነጻጽሮ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “ቀኑ እያለቀ ነው” ዌም “መጨለም ጀምሯል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ረዝሟል
“በጣም እየተለወጠ ነው” ወይም “በጣም እየረዘመ ነው”
በሌሊት
“ቢጨልምም በሌሊት ወቅት”
የእርሷ ምሽጎች
ሰዎች ብዙ ጊዜ ስለ ከተሞች ሲናገሩ ሴቶች እንደሆኑ አድርገው ይናገራሉ። እዚህ ላይ “የእርሷ” የሚለው ኢየሩሳሌምን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “የኢየሩሳሌም ጠንካራ ሕንጻዎች” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 6:6
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ጠቃሚ መልእክት ለማስተዋወቅ እነዚህን ቃላት ይጠቀማል።
የእርሷን ዛፎች ቁረጡ
እግዚአብሔር ይህንን የተናገረው ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት ለሚመጣው ጦር ሰራዊት ነው። “የእርሷ” የሚለው የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው፣ ብዙ ጊዜ ከተtሞች ሴቶች እንደሆኑ ተደርጎ ይነገራል። አማራጭ ትርጉም:- “በኢየሩሳሌም ዙርያ ያሉትን ዛፎች ቁረጡ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በኢየሩሳሌም ዙርያ የአፈር ድልድል ስሩ
የአፈር ድልድል ወደ ከተማይቱ ግንብ ጫፍ ላይ ወጥቶ በከተማይቱ ውስጥ ያለውን ሕዝብ ለማጥቃት ጠላት ከከተማይቱ ውጭ የሚገነባው ከፍተኛ የቆሻሻ ክምር ወይም በእንጨት የተሰራ መሰላል ነው።
ምክንያቱም በግፍ ተሞልታለች
እዚህ ላይ “በግፍ ተሞልታለች” የሚለው በዘያ የሚኖሩ ሰዎች ሁልጊዜ ሰዎችን መጨቆናቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ምክንቱም የእርሷ ሰዎች ሁልጊዜ እርስ በርሳቸው አንዱ ሌላውን ይጨቁናሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የውሃ ጉድጓድ ንጹህ ውሃ እንደሚያመነጭ፣ ይህች ከተማም እንዲሁ ክፋቷን ታፈልቃለች
እዚህ ላይ “ይህች ከተማም ክፋቷን ታፈልቃለች” የሚለው በከተማይቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ክፉ ነገሮችን መስራት መቀጠላቸውን ይወክላል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዓመጽና ትርምስ በእርሷ ውስጥ ይሰማል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ በእርሷ ውስጥ ዓመጽና ትርምስ እሰማለሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በሽታና ቁስልም ሁልጊዜ በፊቴ ናቸው
እነዚህ ነገሮች በእግዚአብሔር ፊት “መሆናቸው” እርሱ እነዚህን ነገሮች ማየቱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ ሁልጊዜ በሽታና ቁስል እመለከታለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ተግሳጽን ተቀበይ … ማንም ሊኖርባት እስከማይችል ደረስ ምድርሽን ባዶ አደርጋለሁ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ሲናገር ለከተማዋ ለራሷ እንሚናገር አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “ተግሳጽ ተቀበይ፣ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ሆይ … ሰው እስከማይኖርባት ድረስ ምድርሽን ባዶ አደርጋለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ተግሳጽ ተቀበይ
እዚህ ላይ “ተግሳጽ ተቀበይ” የሚለው ከተግሳጽ መማርን የሚያሳይ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ከተቀበልሽው ተግሳጽ ተማሪ” ወይም “እኔ አንቺን ስቀጣሽ ትክክለኛ የሆነውን ነገር ለማድረግ ተማሪ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ሰው የማይኖርባት ምድር
“በውስጧ የሚኖርባት ሰው የሌላት ምድር”
Jeremiah 6:9
ሰው ወይኑን እንደሚቃርም፣ እንደዚሁ እነርሱ ከእስራኤል የቀሩትን ሰዎች ፈጽሞ ይቃርሟቸዋል
እግዚብሔር በምድሪቱ የቀሩትን ሰዎች ስለሚያጠቃው ጠላት ሲናገር በወይን አትክልቱ ውስጥ ያለውን ወይን ሌሎች ከሰበሰቡት በኋላ የቀረውን ወይን ጠላት እንደሚቃርም አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- “እስራኤልን ካጠፉ በኋላ፣ በዚያ በሕይወት የሚኖሩትን ሰዎች ለማጥቃት በእርግጠኝነት እንደገና ተመልሰው ይመጣሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ በእርግጠኝነት
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል እስራኤልን ለማጥፋት እግዚአብሔር የሚልከውን ጠላት ያመለክታል።
ከወይን ቅርንጫፎቹ ወይን ለመልቀም እጅህን ወደ ቅርንጫፎቹ ደጋግመህ ዘርጋ
ሌሎች በወይን አትክልቱ ውስጥ ያለውን ወይን ከሰበሰቡ በኋላ ጠላት በዚያ የቀረውን የወይን ቃርሚያ እንደሚቃርም አድርጎ በማሳየት በእስራኤል የቀሩትን ሰዎች ጠላት እንዲያጠቃቸው እግዚአብሔር ትዕዛዝ ሰጥቷል። አማራጭ ትርጉም:- “እንደገና መጥታችሁ የቀሩትን የእስራኤል ሰዎች አጥቋቸው” ወይም “የወይን ቃርሚያ ከቅርንጫፎቹ ለመቃረም አስቀድመው ወይን ወደሰበሰቡበት የወይን ቅርንጫፍ ተመልሰው እንደሚሄዱ ሰዎች እንደዚሁ እንደገና መጥታችሁ የቀሩትን ሰዎች አጥቋቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይሰሙ ዘንድ ለማን እናገራለሁ? ለማንስ አስጠነቅቃለሁ?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ከጠላቶቻቸው ጥቃት ከተረፉ በኋላም እንኳ ቢሆን ከእስራኤል ሰዎች አንዳቸውም እርሱን እንዳልሰሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም:- ምናልባት ለሚሰሙ ሰዎች ይናገርና ያስጠነቅቅ ዘንድ አንድም ሰው ለእኔ አልቀረልኝም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ተመልከት
“እናንተ ራሳችሁ ማየት ትችላላችሁ”
የእነርሱ ጆሮዎች አልተገረዙም
ይህ እግዚአብሔርን ለመስማት እልኸኝነት የተሞላ እምቢተኝነታቸውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ጆሮዎቻቸው ዝግ ናቸው” ወይም “ለመስማት እምቢ ብለዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእነርሱ ጆሮዎች
“የእነርሱ” የሚለው ቃለ የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል።

የእግዚአብሔር ቃል ወደ እነርሱ መጥቷል
ይህ ፈሊጥ ጥቅም ላይ የዋለው እግዚአብሔር ለእነርሱ መልእክት እንደሰጣቸው ለማወጅ ነው። ይህን ያደረገው ደግሞ በነቢያት በኩል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለእነርሱ መልእክት ልኳል” ወይም “እግዚአብሔር ለእነርሱ ተናግሯል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ይህን አይፈልጉትም
“የእግዚአብሔርን ቃል መስማት እነርሱ አይፈልጉም”
Jeremiah 6:11
ነገር ግን እኔ በእግዚአብሔር ቁጣ ተሞልቻለሁ
ይህን የሚናገረው ኤርምያስ ነው። እግዚአብሔር የተሰማውን ዓይነት ተመሳሳይ ቁጣ ኤርምያስም ተሰምቶታል። በጣም መቆጣቱን ሲናገር ውስጡ በቁጣ እንደተሞላ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔም እንደ እግዚአብሔር በጣም ተቆጥቻለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ከመታገስ ደክሜአለሁ
ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ቁጣ አለመግለጹ ቁጣውን በራሱ ውስጥ አምቆ እንደያዘው አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህን ቁጣ ባለመግለጥ እጅግ ደክሜአለሁ” ወይም “ስለዚህ ቁጣ አንዳችም ነገር ባለማድረጌ በጣም ደክሜአለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በመንገድ ላይ በሚገኙ ልጆችና በተሰበሰቡ ወጣቶችም ላይ አፍስሰው
እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ስለመቅጣቱ ሲናገር የእርሱ ቁጣ ኤርምያስ በሕዝቡ ላይ ሊያፈስሰው የፈለገው ፈሳሽ ነገር እነንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በመንገድ ላይ የሚገኙትን ልጆችና የተሰበሰቡትን ወጣቶች በቁጣ ቅጣቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እያንዳንዱ ባል ከሚስቱ ጋር ይወሰዳል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ምክንያቱም ጠላቶች እያንዳንዱን ባል ከሚስቱ ጋር ይይዟቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ረጅም ዓመታት የኖረ እያንዳንዱ ሽማግሌ ይወሰዳል
“ይወሰዳል” የሚለውን ቃል ከቀደመው ሀረግ በግልጽ መረዳት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ብዙ ዓመታት የኖረ እያንዳንዱ ሽማግሌ ይወሰዳል” ወይም “ብዙ ዓመታት የኖረውን እያንዳንዱ ሽማግሌ እነርሱ ይወስዱታል” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ረጅም ዓመታት የኖረ እያንዳንዱ ሽማግሌ ይወሰዳል
“ረጅም ዓመታት የኖረ” የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ሲሆን ትርጉሙም “በጣም ያረጀ” ማለት ነው። ይህ “ሽማግሌ” የሚለውን ቃል ያጠናክረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንዳንዱ በጣም ያረጀ ሰው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ቤቶቻቸው ለሌሎች ይሆናሉ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቤቶቻቸው የሌሎች ሰዎች ንብረት ይሆናሉ” ወይም “የእነርሱ ሰዎች ቤቶቻቸውን ይወስዱታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሻዎቻቸውና ሚስቶቻቸውን በአንድ ላይ ለሌሎች ይሆናሉ
“ለሌሎች ይሆናሉ” የሚለው ሀረግ ከበፊቱ ሀረግ በሚገባ መረዳት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በተጨማሪ እርሻዎቻቸውና ሚስቶቻቸው ለሌሎች ይሆናሉ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
የምድሪቱን ነዋሪዎች በእጄ አጠቃቸዋለሁ
እዚህ ላይ “እጄ” የሚለው የእግዚአብሔርን ኃይል ይወክላል። የባዕድ ጦር ሰራዊት እስራኤልን ያጠቃበት ምክንያት እግዚአብሔር ይህን እንዲፈጽሙ ስላደረጋቸው ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በምድሪቱ የሚኖሩትን ሰዎች እኔ በራሴ ኃይል አጠቃቸዋለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 6:13
ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉም ስስታሞች ናቸው
“ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ” የሚለው ሀረግ የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ ያለምንም ደረጃ ልዩነት “ሁሉ” በሚለው ቃል ውስጥ መካተታቸው የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉም፣ አነስተኛ ስልጣን ያለው ጨምሮ፣ እያንዳዱ ሰው ስስታም ነው” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ታናሽ
ይህ አነስተኛ ስልጣን ያላቸውንና በሰዎች ፊት ብዙ ተቀባይነት የሌላቸውን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አነስተኛ ኃይል ያላቸው ሰዎች” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)
ታላቅ
ይህ ከፍተኛ ስልጣንና ደረጃ ያላቸውን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ሰዎች” ወይም “በጣም ኃይለኛ የሆኑ ሰዎች” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉም
“የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ”
ተገቢ ላልሆነ ጥቅም ሲሉ ስስታሞች ናቸው
“ጥቅም” የሚለው ረቂቅ ስም “የበለጠ ገንዘብ ማግኘት” ወይም “የበለጠ ቁሳቁሶች ማግኘት” በሚለው ሀረግ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለሰዎች ውሸትን በመናገር የበለጠ ገንዘብ ማግኘት ይፈልጋሉ” ወይም “የበለጠ ቁሳቁሶችን ማግኘት በጥብቅ ይፈልጋሉ፣ ከዚህ የተነሳ ይህን ለማግኘት ሲሉ ሰዎችን ያታልላሉ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉም ተንኮል ያደርጋሉ
“ሁሉም ሰዎችን ያታልላሉ” ወይም “ሁሉም ውሸታሞች ናቸው”
የሕዝቤን ቁስል በጥቂቱ ይፈውሳሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ቁስል ከኃጢአታቸው የተነሳ የሚገጥማቸውን ችግር የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የሕዝቤ ችግር ቀለል እንደሆነ ያስባሉ” ወይም 2) ቁስል የሕዝቡን ኃጢአት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሕዝቤ ኃጢአት እንደ ትንሽ ቁስል ቀላል እንደሆነ ያስባሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቁስልን በጥቂቱ ይፈውሳሉ
እዚህ ላይ “ጥቂት” የሚለው ቃል ቁስል ቀላል እንደሆነና ብዙ አስቸጋሪ እንዳልሆነ አድርገው በማየት ተገቢ እንክብካቤ አለመስጠትን ይወክላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰላም ሳይሆን ‘ሰላም፣ ሰላም’ ይላሉ
“‘ሁሉም ደህና ነው፣ ሁሉም ደህና ነው’ ይላሉ፣ ነገር ግን ደህና አይደለም”
አስጸያፊ ነገሮችን ሲሰሩ አፍረዋልን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡ በኃጢአታቸው ባለማፈራቸው ምክንያት ቁጣውን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም አስደንጋጭ ኃጢአት ሰርተዋል፣ ነገር ግን ምንም አያፍሩም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
እንዴት ማፈር እንዳለባቸው አያውቁም
ሰው ሲያፍር ብዙ ጊዜ ፊቱ ይቀላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፊታቸው እንኳ ፈጽሞ አልቀላም”
ከሚወድቁት ጋር ይወድቃሉ
እዚህ ላይ “ይወድቃሉ” የሚለው ይገደላሉ የሚለውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከተገደሉት ጋር አብረው አንድ ላይ ይገደላሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በምቀጣቸውም ጊዜ ይዋረዳሉ
እዚህ ላይ “ይዋረዳሉ” የሚለው መጥፋትን ይወክላል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በምቀጣቸው ጊዜ አጠፋቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 6:16
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር ይህን ለማን እንደሚናገር በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ይህን የሚናገረው ለእስራኤል ሕዝብ ነው” ወይም “እግዚአብሔር ይህን የሚናገረው ለሕዝቡ ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መንታ መንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም ... በእርሷ እንሄድባትም
መንገድ ሰዎች የሚኖሩበትን የሕይወት ዘይቤ የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ ሕይወታቸውን የሚኖሩበትን መልካሚቱን የሕይወት መንገድ ምን እንደሆነች እንዲጠይቁና በዚያ መንገድ እንዲኖሩ መጠየቅ ይፈልጋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መንታ መንገድ

ይህ ሁለት መንገዶች የሚገናኙበት ቦታ ያመለክታል።
የቀደመችውን መንገድ ጠይቁ
የቀደመችው መንገድ የአባቶቻቸውን ባህርይ፣ ከረጅም ጊዜ በፊት አባቶቻቸው እንዴት እንደኖሩ የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "አባቶቻችሁ ስለሄዱበት መንገድ ጠይቁ" ወይም "አባቶቻችሁ እንዴት እንደኖሩ ጠይቁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ መልካም መንገድ ወዴት ነው?
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፦ 1) "ይህ መልካም መንገድ" ሊኖሩበት የሚገባውን መልካም የሕይወት መንገድ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ልንርበት የሚገባ ይህ መልካም መንገድ ወዴት አለ?" ወይም 2) "ይህ መልካም መንገድ" በረከት የሚያመጣውን የሕይወት መንገድ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ "መልካ ወደሆነው ነገር የሚወስደን መንገድ ወዴት አለ" ወይም "ልንኖርበት የሚገባ በረከት የሚያመጣው መንገድ ወዴት አለ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንግዲያው በእርሷ ሂዱ
"እንግዲያው በዚያች መንገድ ሂዱ።" በዚያች መንገድ መሄድ በዚያች መንገድ መኖርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ "እንግዲያው በዚያ መንገድ ኑሩ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እኛ አንሄድም
ይህ በዚያች መንገድ አለመኖርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ "እኛ በዚያች መንገድ አንኖርም" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የመለከት ድምፅን እንድትሰሙ ጠባቂዎችን አቆምሁላችሁ
እግዚአብሔር በአደጋ ላይ ያሉትን ሕዝብ ለማስጠንቀቅ ነቢያቱ የተላኩ ጠባቂዎች እንደሆኑ አድርጎ ይናራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእናንተ አቆምሁላችሁ
"እናንተ" የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ያመክለታል።
መለከቱን እንድትሰሙ
"የመለከቱን ድምጽ እንድትሰሙ።" እግዚአብሔር ለነቢያቱ ስለሰጠው የማስጠንቀቂያ መልእክት ሲናገር መልእክቱ ስለሚመጣው አደጋ ሕዝቡን ለማስጠንቀቅ የሚነፋ መለከት እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። ነቢያቱ ይህንን ማስጠንቀቂያ ሊሰሙና ስለሁኔታው ለሕዝቡ ሊናገሩ ይገባል።
እንግዲህ ሕዝቦች ሆይ ስሙ! እናተ ምስክሮች ሕዝቡ ምን እንደሚገጥማቸው አስተውሉ፣ ምድር! ተመልከቺ
እነዚህ ሦስት አረፍተ ነገሮች በሙሉ እግዚአብሔር በአመጸኛው በይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚያደርገውን ነገር ምስክር እንዲሆኑ ለሌሎች መንግስታት ሕዝቦች የሚናገሩ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ "እናንተ ሌሎች ሕዝቦች፣ በሕዝቤ ላይ የማደርገውን ነገር ተመልከቱ" (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና እንቶኔ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንግዲህ ሕዝቦች ሆይ ስሙ!
"እንግዲህ ሕዝቦች ሆይ፣ እኔ የምናገረውን ስሙ"
እኔ በዚህ ሕዝብ ላይ ጥፋትን አመጣባቸዋለሁ
"በቅርቡ ይህን ሕዝብ በጽኑ እቀጣዋለሁ"
እናንተ ምስክሮች
"እናተ ምስክሮች የሆናችሁ"
በእነርሱ ላይ ምን እንደሚሆን
"እነርሱ" የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል።
ምድር ስሚ
"ምድር" የሚለው ቃል በምድር የሚኖሩትን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ "በምድር የምትኖሩ ሕዝቦች ስሙ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የሃሳባቸው ፍሬ
እዚህ ላይ "ፍሬ" የሚለው ቃል የሚያስከትለውን ውጤት ወይም መዘዝ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ሃሳባቸው የሚያስከትለው መዘዝ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለቃሌ ወይም ለሕጌ ትኩረት ስላልሰጡ ይልቁንም ደግሞ ስላልተቀበሉት
እዚህ ላይ "ለቃሌ ትኩረት ስላልሰጡት" የሚለው እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር አለመስማታቸውን የሚያመለክት ሲሆን "ስላልተቀበሉት" የሚለው ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕግ ለመታዘዝ አለመፈለጋቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ "እኔ የተናገርሁትን አይሰሙም። ይልቁንም ሕጌን አልታዘዙም" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 6:20
ዕጣን ከሳባ ምድር፣ ጣፋጭ ቅመም ከሩቅ አገር ቢመጣ ምን ይጠቅመmኛል?
እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመገሰጽ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፦ "ዕጣን ከሳባ ምድርና ከሩቅ አገር የሚመጣው ጣፋጭ ቅመም ለእኔ ምንም አይጠቅመኝም።" ወይም "ከሩቅ አገር የመጣው የቅመማችሁ ጣፋጭ ሽታ አልፈልገውም" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህ ጣፋጭ ሽታዎች
ሰዎች ጣፋጭ ሽታ ያላቸው ቅመሞችን ለእግዚአብሔር እንደ መስዋእት ያቃጥሉ ነበር።
በእኔ ዘንድ ተቀባይነት የላቸውም
"እኔን አያስደስተኝም" ወይም "እኔን ደስ አያሰኘኝም"
ተመልከቱ፣ እኔ
"አስተውሉ፣ ምክንያቱም እኔ የምናገረው እውነት በጣም ጠቃሚ ነው፣ እኔ"
በዚህ ሕዝብ ላይ መሰናክልን አስቀምጣለሁ
"በዚህ ሕዝብ ፊት ለፊት መሰናክል አስቀምጣለሁ።" እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ላይ እንዲመጣ ስለሚያደርገው ችግር ሲናገር ሰዎች ተደናቅፈው የሚወድቁበት እንቅፋት አድርጎ ገልጾታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ በዚያ ላይ ይደናቀፋሉ
እዚህ ላይ "ይደናቀፋሉ" የሚለው በችግሮቹ ምክንያት እንደሚጎዱ የሚያሳይ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አባቶችና ወንዶች ልጆች በአንድ ላይ
"ይደናቀፋሉ" የሚለውን ሃሳብ ከቀደመው ቃል መረዳት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ አባቶችና ወንዶች ልጆች በአንድ ላይ ይደናቀፋሉ" ወይም "አባቶችና ወንዶች ልጆች በአንድ ላይ ይጎዳሉ" (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ነዋሪዎችና ጎረቤቶቻቸው
"ጎረቤቶችና ጓደኞቻቸው"
ሕዝብ እየመጣ ነው
የእነርሱ ዓላማ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ሕዝብ እናተን ለማጥቃት እየመጣ ነው" ወይም "ጦር ሰራዊት እየመጣ ነው" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ታላቅ ሕዝብ
እዚህ ላይ "ሕዝብ" የሚለው የሕዝቡን ጦር ሰራዊት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "የታላቅ ሕዝብ ጦር ሰራዊት" (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከምድሪቱ ሩቅ ክፍል እየተነሳሳ ነው
"እየተነሳሳ" የሚለው አንድን ነገር ለማድረግ መዘጋጀትን የሚወክል ነው። ማራጭ ትርጉም፦ "ከምድሪቱ ሩቅ ክፍል ለመምጣት እየተዘጋጀ ነው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 6:23
ቀስትና ጦር ይዘዋል
"ወታደሮቹ ቀስትና ጦር ይይዛሉ"
ድምጻቸው እንደተናወጠ ባህር ነው
ወታደሮቹ የሚኖራቸው ትልቅ ድምጽ ከባህር ከሚነሳው ታላቅ ድምጽ ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ ትርጉም፦ "የጩኸታቸው ድምጽ በጣም ከፍተኛ ነው፣ እንደ ባህር ድምጽ ነው" (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በፈረሶች ላይ ሆነው ይጋልባሉ፣ ለጦር እንደተዘጋጀ ሰው ተሰለፉ
"ተሰለፉ" የሚለው ራሳቸውን አቀናጅተዋል፣ ፈረሶቻቸውን በሰልፍ ይጋልባሉ ማት ነው። "ለጦር እንደተዘጋጀ ሰው" የሚለው ለመዋጋት መዘጋጀታቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ "በተመደበላቸው ሰልፍ ፈረሶቻቸውን ይጋልባሉ፣ እናንተን ለመዋጋት ተዘጋጅተዋል" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እኛ ሰምተናል
"እኛ" የሚለው ምናልባት ኤርምያስንና የይሁዳ ሕዝብን ሳያመለክት አይቀርም።
እጆችን በጭንቀት ደክማለች
"እጆቻችን ከጭንቀት የተነሳ ደክመዋል"
ጭንቀት ይዞናል
የነበራቸው ከፍተኛ የጭንቀት ስሜት ሲገለጽ ጭንቀቱ እንደያዛቸው ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ "በጣም አስደንጋጭ ጭንቀት ይሰማናል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ልጅ እንደምትወልድ ሴት
ጠላት እነርሱን ለማጥቃት ከመምጣቱ የተነሳ የተሰማቸው ጭንቀት አንዲት ሴት ልጅ ለመውለድ ምጥ ሲይዛት ከሚሰማት ስሜት ጋር ተነጻጽሯል። አማራጭ "ልጅ

ለመውለድ እንደምታምጥ ሴት” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

## Jeremiah 6:25

አጠቃላይ መረጃ፡-

ኤርምያስ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ይናገራል፡፡ አንዳንድ ትርጉሞች እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ እየተናገረ ነው ብለው ተርጉመውታል፡፡

የጠላት ሰይፍና ድንጋጤ ከብቧችኋል

“የጠላት ሰይፍ” የሚለው ሀረግ ከሰይፎቻቸው ጋር ለማጥቃት የተዘጋጁ ጠላቶችን ይወክላል፡፡ “ድንጋጤ” የሚለው ረቂቅ ስም ሰዎች እንዲፈሩ የሚያደርጉ ነገሮችን ያመለክታል፡፡ ይህ ደግሞ ከቅጽል ጋር ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላቶች ከሰይፎቻቸው ጋር በሁሉም ስፍራ ስላሉ እያንዳንዱ ሰው በፍርሃት ይንቀጠቀጣል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ and ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የሕዝቤ ሴት ልጅ

እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደ ሴት ጠርቶ በመናገር ለእነርሱ ያለውን ፍቅር ኤርምያስ ያሳያል፡፡ ይህን ተመሳሳይ ሀረግ በኤርምያስ 4:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ “እናንተ ለእኔ እንደ ሴት ልጅ የሆናችሁ ሕዝቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማቅ ልበሺ በአመድም ላይ ተንከባለይ

ሕዝብ እነዚህን ነገሮች የሚያደርገው ከመጠን በላይ የሆነ ሃዘን እንደተሰማቸው ለማሳየት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ማቅ በመልበስና በአመድ ላይ በመንከባለል ከመጠን በላይ እንዳዘንሽ አሳዪ” (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ለአንድያ ልጅ እንደሚደረግ ልቅሶ፣ መራራ ልቅሶ አልቅሺ

ኤርምያስ የሕዝቡን ታላቅ ሃዘን እናት አንድያ ልጇ ሲሞትባት ከሚሰማት ሃዘን ጋር ያነጻጽረዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንድያ ልጅሽ እንደሞተባት እናት ሆነሽ መራራ ልቅሶ አልቅሺ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አጥፊው በድንገት በላያችን ይመጣልና

“ምክንያቱም የጠላት ጦር ሰራዊት እኛን ለማጥቃት በድንገት ይመጣልና”

## Jeremiah 6:27

አጠቃላይ መረጃ፡-

x

---

# Chapter 7

## Jeremiah 7:1

ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል እንዲህ የሚል ነው፣ ቁም

ይህ ፈሊጥ ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው፡፡ ይህን ተመሳሳይ ሀረግ በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለኤርምያስ የሰጠው መልእክት ይህ ነው፡፡ እርሱ እንዲህ አለ ‘ቁም’” ወይም “እግዚአብሔር ለኤርምያስ የተናገረው መልእክት ይህ ነው፡- ‘ቁም’” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ሕዝብ ሁላችሁ

“እናንተ የይሁዳ ሕዝብ ሁላችሁ”

## Jeremiah 7:3

አያያዥ ሀሳብ፡-

እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚነገረውን መልእክቱን ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል፡፡

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

ኤርምያስ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከእግዚአብሔር የመጣውን በጣም ጠቃሚ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው፡፡ ይህንን በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡

መንገዳችሁንና ሥራችሁን አሳምሩ እኔም እንድትኖሩ አደርጋችኋለሁ

“መንገዳችሁንና ሥራችሁን የምታስተካሉ ከሆነ እኔም እንድትኖሩ አደርጋችኋለሁ

በዚህ ስፍራ

ይህ በይሁዳ ምድር ማለት ነው፣ በቤተ መቅደስ አይደለም

እያላችሁ ራሳችሁ በሐሰት ቃል አትታመኑ

ይህ “ራሳችሁ” የሚለው ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም ለእስራኤላውያን ወደፊት የሚመጣ የግል አደጋ እንዳለ አጽንዖት የሚሰጥ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እያላችሁ፣ እናንተን እንዲጠብቃችሁ በሐሰት ቃል አትታመኑ” (ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ!የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ! የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ!

ቤተ መቅደሱ ባለቤቱ እግዚአብሔር ስለሆነና የእርሱን ሕልውና የሚወክል ስለሆነ እርሱ ይጠብቀዋል፣ የይሁዳም ሕዝብ ደህንነት ይሆንለታል፡፡ “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” የሚለው ለምን ሦስት ጊዜ እንደተደጋገመ ተቀባይነት ሊኖራቸው የሚችሉት ትርጉሞች የሚከተሉት ናቸው፡- 1) የተደጋገመው አጽንዖት ለመስጠት ነው ወይም 2) የተደጋጋመው እንደ ቤተ መቅደሱ ስነ ስርአት ተደርጎ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው ስለዚህ አንድም ሰው ሊያፈርሰው እንደማይችል ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች ነን፤ እኛ ደግም እንጠበቃለን፡፡” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

## Jeremiah 7:5

አያያዥ ሀሳብ፡-

እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚነገረውን መልእክቱን ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል፡፡

መንገዳችሁንና ስራችሁን አሳምሩ

“መንገዳችሁንና ስራችሁን አስተካክሉ፡፡” ይህንን በኤርምያስ 7:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡

ሙሉ በሙሉ ትክክለኛ ፍትህ አድርጉ

“ፍትህ” የሚለው ረቂቅ ስም “ፍረዱ” በሚለው ግስ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በትክክል ፍረዱ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

መጻተኛውን አትጨቁኑ

“መጻተኛውን በአግባቡ ያዙ”

ወላጅ አልባ

ወላጆቹ የሞቱበት ልጅ

ንጹህ ደም ባታፈስሱ

እዚህ ላይ ንጹህ ደም ማፍሰስ ሞት የማይገባቸውን ሰዎች መግደልን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ንጹህ ሰዎችን መግደል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሌሎች አማልክት መከተል

እዚህ ላይ መከተል የሚለው ለማገልገልና ለመታዘዝ ዓላማ አድርጎ ተከትሎ ለመሄድ ምትክ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሌሎች አማልክትን ማገልገል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እናተን የሚጎዷችሁ

ይህ ፈሊጥ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚያ እናንተን ይጎዷችኋልና” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ ስፍራ

እዚህ ላይ “በዚህ ስፍራ” የሚለው የይሁዳን ምድር ያመለክታል፡፡

አኖራችኋለሁ

“መኖር እንድትቀጥሉ አደርጋችኋለሁ”

ከጥንት ጀምሮ እስከ ዘላለም

“ከጥንት ጀምሮ እንዲሁም በቀጣይነት፡፡” የእነርሱ ቋሚ ንብረት ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር ምድሪቱን ለይሁዳ ሕዝብ ሰጥቷል ማለት ነው፡፡

## Jeremiah 7:8

አያያዥ ሀሳብ፡-

እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚነገረውን መልእክቱን ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል፡፡

አጠቃላይ መረጃ፡-

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “እናንተ” የሚለው ቃል የይሁዳ ሕዝብን ያመለክታል፡፡

እነሆ!

እዚህ ላይ “እነሆ” የሚለው ቃል ከዚህ በኋላ የሚከተለውን መረጃ እንደሚገባ ልብ እንድንል ያነቃናል፡፡

ትሰርቃላችሁ፥ ትገድላላችሁ፥ ታመነዝራላችሁ? በሐሰትም ትምላላችሁ፥ … የማታውቋቸውንም እንግዶች አማልክት ትከተላላችሁ?

እየፈጸሟቸው ያሉትን ኃጢአቶች እግዚአብሔር የሚያውቅ መሆኑን አስረግጦ ለማለፍ እነዚህ ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ ይጠብቃሉ፡፡ ይህ እንደ አረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ትሰርቃላችሁ፥ ትገድላላችሁ፥ ታመነዝራላችሁ፡፡ በሐሰት ትምላላችሁ፥ … የማታውቋቸውንም እንግዶች አማልክት ትከተላላችሁ፡፡” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በሐሰት ትምላላችሁ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“በመጋላችሁ እንኳ ትዋሻላችሁ”
እንግዶች አማልክት ትከተላላችሁ
እዚህ ላይ መከተል ለማገልገልና ለመታዘዝ ዓላማ በማድረግ ተከትሎ ለመሄድ ምትክ ስም ነው። ይህንን በኤርምያስ 7:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌሎች አማልክት ታገለግላላችሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ታዲያ መጥታችሁ በፊቴ ትቆሙና … እነዚህን አስጸያፊ ነገሮች ሁሉ ታደርጋላችሁ?
በቃልና በድርጊት የሚፈጽሙትን ግብዝነት እግዚአብሔር የሚያውቅ መሆኑን አስረግጦ ለማለፍ እነዚህ ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ ይጠብቃሉ። ይህ እንደ አረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደዚያ ከሆነ መጥታችሁ በፊቴ ትቆማላችሁ … እነዚህን አስጸያፊ ነገሮች ሁሉ ታደርጋላችሁ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በስሜ በሚጠራው ቤት
ይህ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ የሆነው ቤት” ወይም “እኔን የምታመልኩበት ቤተ መቅደስ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ በስሜ የሚጠራው ቤት በእናንተ ዓይን የወንበዴዎች ዋሻ ሆኖአልን?
እነርሱ ስለ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ምን እንደሚያስቡ እግዚአብሔር የሚያውቅ መሆኑን አስረግጦ ለማለፍ እነዚህ ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ ይጠብቃሉ። ይህ በዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስሜን የተሸከመው ይህ ቤት በእናንተ ዓይን የወንበዴዎች ዋሻ ነው!” ወይም “በስሜ የተጠራው ይህ ቤት ወንበዴዎች ሊሔዱና ሊሸሸጉ የሚችሉበት ስፍራ እንደሆነ የምታስቡ ትመስስላላችሁ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ስሜን የተሸከመው ይህ ቤት
የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔርን ስም እንደተሸከመ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ ከዚህ በፊት ካው ጥቅስ “በስሜ በተጠራው ይህ ቤት” ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ወንበዴዎች
የሚሰርቁና የሚዘርፉ ሃይለኛ ሰዎች
ነገር ግን እነሆ አይቻለሁ
“ነገር ግን እኔ በእርግጠኝነት እናንተ የምትሰሩት ምን እንደሆነ ተመልክቻለሁ”
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 7:12

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚያስተላልፈውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ያሉት “እናንተ” እና “የእናንተ” የሚሉት ቃላቶች የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።
በቀድሞ ዘመን ስሜ እንዲያድርበት ወደፈቀድሁበት በሴሎ ወደነበረው ስፍራ ሂዱ
እዚህ ላይ “ስሜ እንዲያድርበት ወደፈቀድሁበት” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ይህ ስፍራ እግዚአብሔር ይመለክበት የነበረ ነው የሚል ትርጉም አለው። አማራጭ ትርጉም፡- “ቀድሞ ሕዝቤ እኔን ለማምለክ እኔ ወደፈቀድሁበት በሴሎ ወዳለው ስፍራ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህን ነገሮች ሁሉ ስላደረጋችሁ
“ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች ሁሉ ስታደርጉ ስለነበራችሁ”
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደገና ደግሜ ደጋግሜ
እነዚህ ሁለት የተጣመሩ ስሞች ፈሊጥ ሲሆኑ አንድ ነገር ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ተደርጓል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በተደጋጋሚ” ወይም “ያለማቋረጥ” (ጥምር ቃል እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ በስሜ የተጠራው ቤት
ይህ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ምትክ ስም ነው። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። ይህንን በኤርምያስ 7:10 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ የሆነው ይህ ቤት” ወይም “እኔን የምታመልኩበት ይህ ቤተ መቅደስ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 7:16

አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ ለኤርምያስ ይነግረዋል። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “ይህ ሕዝብ” የሚለው የይሁዳ ሕዝብን ያመለክታል።
ለዚህ ሕዝብ አትጸልይ፣ የልቅሶ ልመና ወደ እኔ አታቅርብ ወይም እነርሱን ወክለህ ጸሎት አታድርግ፣ ወደ እኔ አቤቱታ አታቅርብ
እነዚህ አራት ነገሮች እያንዳንዱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
የልቅሶ ልመና ማቅረብ
“በሃዘን መጮህ”
እነርሱን ወክለህ
“ለእነርሱ ጥቅም” ወይም “ለእነርሱ”
አቤቱታ ወደ እኔ ማቅረብ
“ወደ እኔ መማለድ”
በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ ምን እንደሚሰሩ አትመለከትምን?
ይህ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ይጠብቃል፤ ጥያቄው የተጠየቀው እነዚህን ነገሮች በኤርምያስ ዘንድ ትኩረት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው። ይህ እንደ አረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ ምን እንደሚሰሩ ተመልከት!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
እሳቱን ማንደድ
“እሳቱን መጀመር”
ዱቄት ይለውሳሉ
በእጅ ሊጥ ማዋሃድ
ሊጥ
ለመጋገር የሚጠቅም የዱቄትና የፈሳሽ ወፍራም ውህድ
የሰማያት ንግስት
ይህ የሐሰተኛ አምላክ ስም ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “‘የሰማያት ንግስት’ የምትባል ሐሰተኛ አምላክ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔን ያናድዳሉ
“እኔን ያስቆጣሉ”

Jeremiah 7:19

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ ለኤርምያስ መናገር ቀጥለሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች “እነርሱ” እና “ራሳቸው” የሚሉት የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታል።
በእውነት እነርሱ እኔን ያስቆጡኛልን?
ይህ ጥያቄ አሉታዊ መልስ ይጠብቃል። ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ በእርግጥ ሊያስቆጡኝ አይችሉም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
ኤርምያስና የይሁዳ ሕዝብ እርሱ የሚናገረውን ነገር በጥንቃቄ ይሰሙ ዘንድ እግዚአብሔር ስለራሱ ሲናገር ሌላ ሰው እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ይህንን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ያወጀው ይህን ነው” ወይም “ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህን ነው” (ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እፍረታቸው በራሳቸው ላይ ይሆን ዘንድ እኔን ያስቆጡኝ እነርሱ ራሳቸው ኤደሉምን?
ይህ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ይጠብቃል። ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እፍረታቸው በራሳቸው ላይ ይሆን ዘንድ ራሳቸውን እያስቆጡ ነው” ወይም “እነርሱ ራሳቸውን ችግር ውስጥ እያስገቡና በራሳቸው ላይ እፍረት እያመጡ ነው!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና ከባለቤቱ ጋር የሚጣቀስ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አፍረት በእነርሱ ላይ ነው
“እፍረት” የሚለው ረቂቅ ስም “አፈሩ” በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ አፈሩ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ተመልከት
ይህ ቃል እዚህ ላይ የአንድ ሰውን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚነገረው ቁም ነገር ለመሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። አማራጭ ትርጉም፡- “አድምጥ” ወይም “እኔ ለአንተ ለምነግርህ ነገር ትኩረት ስጥ”
ቁጣየና መዓቴ በዚህ ስፍራ ላይ ይጎርፋል
እግዚአብሔር ስለ ቁጣው ሲገልጽ ሊፈስ የሚችል ነገር እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ይህን ስፍራ እቀጣለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ቁጣና መዓት
እነዚህ ቃላቶች በመሰረታዊነት ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆኑ የእግዚአብሔርን ቁጣ ጥልቀት አጽንዖት ይሰጣሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
አጎርፋለሁ
“አፈስሳለሁ”
ይነድዳል ደግሞም አይጠፋም
እግዚአብሔር ስለ ቁጣው ሲናገር ቁጣው ሊጠፋ የማይችል እሳት እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ቁጣየን አንድም ሰው ሊያስቆመው አይችልም” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ፈጽሞ አይጠፋም
“ፈጽሞ መንደድ አይቆምም”

## Jeremiah 7:21

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ ያለውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “እናንተ” እና “የእናንተ” የሚሉት የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከእግዚአብሔር የመጣውን በጣም ጠቃሚ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህንን በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
የሚቃጠለውን መስዋዕታችሁን በሌሎች መስዋዕታችሁ ላይ ጨምሩ፣ ስጋውንም ራሳችሁ ብሉ
ይህ መስዋዕታቸው በሙሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው አጽንዖት የሚሰጥ ምጸታዊ ዓረፍተ ሃሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሂዱና የሚቃጠል መስዋዕቶቻችሁን ከመስዋዕታችሁና ከስጋው ጋር አብራችሁ ብሉት” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
ድምጼን ስሙ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት ቃሉን መስማትና ለተናገረው ደግሞ መታዘዝ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የተናገርሁትን ስሙ ደግሞም ታዘዙ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ባዘዝኋችሁ መንገድ ሁሉ ሂዱ
እግዚአብሔር ቃሉን ስለመታዘዝ ሲናገር ሰው በመንገድ እንደሚሄድ እንደዚሁ አንድ ሰው በቃሉ መሄድ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ አድርጉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

## Jeremiah 7:24

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ ያለውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “እናንተ” እና “የእናንተ” የሚሉት የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ። “እነርሱ” የይሁዳ ሕዝብ አባቶችን የሚያመለክት ነው።
እነርሱ አይሰሙም ወይም ትኩረት አይሰጡም
እነዚህ ሀረጎች የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ነው፣ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
በክፉ ልባቸው አሳብና እልከኝነት
“በራሳቸው እቅድ ምክንያቱም ክፉና እልኸኞች ነበሩ”
ወደፊት ሳይሆን ወደኋላ ሄዱ
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) እርሱን በጉጉት ከመታዘዝ ይልቅ ለእግዚአብሔር ትኩረት ለመስጠት እምቢተኞች ሆኑ። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ እኔ ከመቅረብ ይልቅ ከእኔ ርቀው ሄዱ” ወይም 2) ከማሻሻል ይልቅ በክፋታቸው እየጨመሩ ሄዱ። አማራጭ ትርጉም፡- “የተሻሉ ከመሆን ይልቅ በክፋታቸው እየጨመሩ ሄዱ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አባቶቻችሁ ከግብጽ ምድር ከወጡበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ
ይህ ጅምላ ገለጻ ሲሆን ሃሳቡም በዚህ የጊዜ ርዝመት በየቀኑ ለማለት ሳይሆን በጥቅሉ በዚህ ሁሉ የጊዜ ርዝመት ለማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አባቶቻችሁ ከግብጽ ምድር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ” (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱን በቋሚነት ልኬባችኋለሁ
“እነርሱን ደጋግሜ ልኬአቸዋለሁ” ወይም “እነርሱን በተደጋጋሚ ልኬአቸዋለሁ”
እነርሱ አንገታቸውን አደነደኑ
ይህ ፈሊጥ ሲሆን ግትሮች ነበሩ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ግትሮች ሆኑ” ወይም “እኔን ተቋቋሙኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የባሰ ክፉ ነበሩ
“እያንዳንዱ ትውልድ የበለጠ ክፉ ነበረ”

## Jeremiah 7:27

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ ያለውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “ለእነርሱ” እና “እነርሱ” የሚሉት ቃላቶች የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።
ስለዚህ እነዚህን ቃላት በሙሉ ለእነርሱ ትናገራለህ ነገር ግን አንተን አይሰሙህም። እነዚህን ነገሮች ለእነርሱ ትናገራለህ ነገር ግን ለአንተ አይመልስሉህም።
እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ሃሳብ አላቸው፣ ሁለተኛው ለመጀመርያው መልእክት አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔን መልእክት ንገራቸው ነገር ግን እነርሱ አንተን አይሰሙህም ለአንተም አይመልሱልህም” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
የአምላኩ የእግዚአብሔር ድምጽ
እዚህ ላይ “የአምላኩ የእግዚአብሔር ድምጽ” የሚለው እግዚአብሔር የተናገረውን ይወክላል። ይህን በኤርምያስ 3:25 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “አምላኩ እግዚአብሔር የተናገረው ነገር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እውነት ጠፍቶአል ከአፋቸውም ተቈርጦአል
እግዚአብሔር ስለ እውነት ሲናገር ሕዝቡ ሊያጠፉት የሚችሉትና መነገሩንም ሊያስቆሙት የሚችሉት ነገር እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሕዝቡ እውነትን አጥፍተዋል፣ ከአፋቸውም ቆርጠውታል” ወይም “ሕዝቡ ውሸት ብቻ ይናገራሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እውነት ጠፍቶአል
“እውነት” የሚለው ረቂቅ ስም “እውነተኛ” በሚለው ቅጽል በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እውነተኛ የሆነው ነገር ጠፍቶአል” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

## Jeremiah 7:31

አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር የይሁዳ ሕዝብ የሰራቸውን ክፉ ነገሮች መግለጹን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “እነርሱ” እና “የእነርሱ” የሚሉት ቃላቶች የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።
የቶፌት ከፍተኛ ስፍራዎች
ይህ የእስራኤል ሕዝብ ልጆቻቸውን በእሳት በማቃጠል ለሐሰተኛ አማልክት መስዋዕት አድርገው ያቀረቡበት የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የቤን ሄኖም ሸለቆ
ይህ ሕዝቡ ለሐሰተኛ አማልክት መስዋዕት ያቀረቡበት ከኢየሩሳሌም ከተማ በደቡብ በኩል የሚገኝ የሸለቆ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
በእሳት
ይህ አመልካች መረጃ ለሐሰተኛ አማልክት እንደ መስዋዕት ይቃጠሉ እንደነበር የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ መስዋዕት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከቶ በአእምሮየ ያለሰብሁትን

እዚህ ላይ “አእምሮ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ሃሳብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከቶ ስለዚህ ነገር ፈጽሞ አላሰብሁም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህ ተመልከቱ
እዚህ ላይ “ተመልከቱ” የሚለው ቃል ለሚከተለው ነገር አጽንዖትን ይጨምራል። አማራጭ ትርጉም፡- “በእርግጥ”
የማይባልበት ቀናቶች ይመጣሉ
የወደፊት ጊዜ “ቀናቶች እየመጡ እንደሆነ” ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “ለወደፊት እንዲህ የማይባልበት” ወይም “እንዲህ የማይባልበት ጊዜ ይኖራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእንግዲህ ወዲህ … ተብሎ አይጠራም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ከእንግዲህ እንዲህ … ብለው አይጠሩትም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
አስከሬኖች ይቀብራሉ
“የሞቱ ሰዎችን ይቀብራሉ”
የሚቀር ምንም ክፍል የለም
“የሚቀር ምንም ቦታ የለም”
Jeremiah 7:33
አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚያመጣውን ፍርድ መናገሩን ቀጥሏል።
አስከሬኖች
“የሞቱ አካላት”
ይህ ሕዝብ
“የይሁዳ ሕዝብ”
የሰማይ ወፎች
“የሰማያት ወፎች” የሚለውን በኤርምያስ 4፡25 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
የምድር አውሬዎች
“የምድሪቱ የዱር እንስሳት”
የሚያባርራቸው
“የሚያስፈራራቸው”
አጠፋለሁ
“አስወግዳለሁ”
የደስታ ድምጽና የተድላ ድምጽ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። “ደስታ” እና “ተድላ” የሚሉት ረቂቅ ስሞች “መደሰት” በሚለው ግስ እና “ደስተኛ” በሚለው” ቅጽል በመmጠቀም ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚደሰቱ እና የደስተኛ ሰዎች ድምጽ” (ጥምር ቃል የሚለውን እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የሙሽራ ድምጽ እና የሙሽሪት ድምጽ
ይህ በሰርግ ስነ ስርዓት ላይ ለሚከናወኑ ነገሮች ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰርግ ስነ ስርዓት የሚያከብሩ ሰዎች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ባድማ ትሆናለች
“ባድማ” የሚለው ረቂቅ ስም “ሰው የማይኖርበት” በሚለው ቅጽል በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው የማይኖርባት ትሆናለች” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

---

# Chapter 8
## Jeremiah 8:1
አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚያመጣውን ፍርድ መናገሩን ቀጥሏል።
በዚያን ጊዜ
በኤርምያስ 7፡32 እስከ 34 ውሰጥ ያሉት ክስተቶች በሚፈጸሙበት ጊዜ።
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ያመጡአቸዋል
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የይሁዳን ሕዝብ ጠላቶች ይወክላል።
መኳንንቶቻቸው
“ነገስታቶቻቸው” ወይም “መሪዎቻቸው”
እነርሱን ይዘረጉአቸዋል
“እነርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቀደመው ጥቅስ የተዘረዘሩትን ሰዎች አጥንቶች ነው።
እነርሱ በተከተሏቸውና በአገለገሏቸው እንዲሁም አብረው በተጓዟቸውና በፈለጓቸው፣ ባመለኳቸው
እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ቃል የይሁዳ ሕዝብን የሚያመለክት ነው። እነዚህ ሦስት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው።
አብረው በተጓዟቸው
ይህ ለማገልገልና ለማምለክ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ይህንን በኤርምያስ 2፡23 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አጥንቶች አይሰበሰቡም ወይም እንደገና አይቀበሩም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አጥንቶቻቸውን ማንም ሰው አይሰበስበውም ወይም እንደገና አይቀብሯቸውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ተጣለ ጉድፍ በምድር ገጽ ላይ ይበተናል
አጥንቶች በምድር ላይ ካለ ጉድፍ ተነጻጽረዋል፣ ይህ ንጽጽር አጥንቶቹ አስጸያፊ እንደሚሆኑና እንደገና እንደማይቀበሩ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በምድረ ገጽ ላይ
“በምድር ዙርያ ሁሉ”
እነርሱን ባሳደድኳቸው ስፍራ ሁሉ
“እነርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳ ሕዝብን ነው።
ከዚህ ክፉ ሕዝብ አሁንም የቀሩት ሁሉ ከሕይወት ይልቅ ለራሳቸው ሞትን ይመርጣሉ
“ከዚህ ክፉ ሕዝብ የቀሩት ሁሉ በሕይወት ከሚኖሩ መሞት ይፈልጋሉ”
ይህ የሰራዊት ጌታ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ተመሳሳይ ቃላትን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
## Jeremiah 8:4
አያያዥ ሀሳብ፡-
እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚያመጣውን ፍርድ መናገሩን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “ለእነርሱ” እና “እነርሱ” የሚሉት ቃላቶች የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።
ለእነርሱ እንዲህ በላቸው
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ ምን መናገር እንዳለበት ለኤርምያስ እየነገረው ነው።
የወደቀ ሰው አይነሳምን? የሳተስ ሰው ለመመለስ አይሞክርምን? ታዲያ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ዘወትር ስለ ምን ባለመታመን ፊቱን አዙሮ ወደ ኋላው ይመለሳል?
እነዚህ ጥያቄዎች የይሁዳ ሕዝብ ይኖሩበት የነበረው መንገድ ትርጉም የሚሰጥ እንዳልሆነ ዋነኛ ነጥቡን በሚገባ ግልጽ አድርገዋል። እነዚህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው ሲወድቅ እንደገና ሊነሳ እንደሚችል፣ አንድ ሰው ከመንገድ ሲስት እንደገና ወደ መንገዱ ለመመለስ እንደሚሞክር ታውቃላችሁ። ይህ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ባለመታመን ፊቱን አዙሮ ወደ ኋላው መሄዱ ትርጉም የማይሰጥ ነው።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አየሩሳሌም

እዚህ ላይ “ኢየሩሳሌም” የሚለው ቃል የይሁዳን ሕዝብ በሙሉ ወካይ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ይሁዳ” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተንኮልን የሙጥኝ ብለው ይዘዋል

የይሁዳ ሕዝብ ይሰሩት የነበረው ነገር ተንኮልን አጥብቀው እንደያዙና ሊተዉት ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተንኮልን የሙጥኝ ብለው ይዘዋል

“ተንኮል” የሚለው ረቂቅ ስም ሰው ሊይዘው የሚችለው አንድ ግዑዝ ቁስ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ ይህ “አታለለ” በሚለው ግስ በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል፡፡ አንድን ነገር የሙጥኝ ብሎ መያዝ ለመውደድ ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከሚያታልላቸው ነገር ነገር ለመመለስ እምቢ አሉ” ወይም “የሚያታሉሏቸውን ሰዎች ወደዱ” (ረቂቅ ስሞች እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 8:6

አያያዥ ሀሳብ፡-

እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚናገረውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል፡፡

አጠቃላይ መረጃ፡-

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “እነርሱ” እና “ለእነርሱ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የይሁዳ ሕዝብን ነው፡፡

አደመጥሁ ሰማሁም

እነዚህ ሁለት ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ ( ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ትክክለኛውን ነገር አይናገሩም

“ትክክለኛውን ነገር አይሉም”

ስለ ክፋቱ

“ክፋት” የሚለው ረቂቅ ስም “ክፉ” የሚለውን ቅጽል በመጠቀም መተርጎም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ በመሆኑ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ምን አድርጌአለሁ?

ይህ አመልካች መረጃ የሚያሳየው ይህ ጥያቄ የይሁዳ ሕዝብ ሊጠይቀው የሚገባ እንደነበር ነው፡፡ ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ክፉ ስራ ሰርቻለሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ወደፈለጉት ይሄዳሉ

“በራሳቸው መንገድ ይሄዳሉ”

ወደ ጦርነት እንደሚሮጥ ፈረስ

ሕዝቡ የራሳቸውን መንገድ ለመከተል የነበራቸው ጉጉት ወደ ጦርነት ለመሮጥ ከተዘጋጀ ፈረስ ጉጉት ጋር ተነጻጽሯል፡፡ (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ፈረስ

ወንድ ጎልማሳ ፈረስ

ሽመላ እንኳ በሰማይ የተወሰነ ጊዜዋን ታውቃለች፤ ዋኖስ፣ ጨረባና ዋርዳም

ይህ አመልካች መረጃ የሚያሳየው እንደነዚህ የመሳሰሉ አእዋፍ የሚሰደዱበትን ማለትም በተለያዩ የዓመቱ ወቅት ምግብ ለመፈለግና ለመባዛት ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ የሚጓዙበትን ትክክለኛ ጊዜ እንደሚያውቁ ነው፡፡ (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሽመላ ... ዋኖስ፣ ጨረባና ዋርዳ

እነዚህ በሙሉ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚሰደዱ የተለያዩ ዓይነት አእዋፍ ናቸው፡፡ (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በትክክለኛው ጊዜ ወደ ስደት ይሄዳሉ፤ ነገር ግን ሕዝቤ የእግዚአብሔርን ስርዓት አያውቁም፡፡

ይህ አመልካች መረጃ የሚያሳየው ሕዝቡ በተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ስርዓት ማወቅ እንደነበረባቸው ነው፡፡ (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ስደታቸው ይሄዳሉ

“ስደት” የሚለው ረቂቅ ስም “ተሰደዱ” በሚለው ግስ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ይሰደዳሉ” ወይም “ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል ይበርራሉ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 8:8

አያያዥ ሀሳብ፡-

እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚናገረውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል፡፡

“ጥበበኞች ነን፣ የእግዚአብሔር ሕግ ከእኛ ጋር ነው” እንዴት ትላላችሁ?

እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው የይሁዳ ሕዝብ ምን እየተናገሩ እንደነበር እንዲያስቡ ለማድረግ ነው፡፡ ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ ጥበበኞች እንደሆናችሁ ታስባላችሁ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሕግ ከእናንተ ጋር በመኖሩ ነው፡፡” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ እንዴት ትላላችሁ

“እናንተ” የሚለው የይሁዳ ሕዝብን ይወክላል፡፡

በእርግጥ፣ ተመልከቱ!

እነዚህ ቃላቶች አድማጩ ለሚቀጥለው መልእክቶች የቅርብ ትኩረት እንዲሰጥ የሚናገር ነው፡፡

የጸሐፊዎቻችሁ ሐሰተኛ እስክርቢቶ

እስክርቢቶ ጸሐፊዎች የሚጽፉአቸውን ቃላት ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ጸሐፊዎቻችሁ የሚጽፉአቸው የሐሰት ነገሮች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ሐሰትን ፈጥረዋል

“ሐሰተኛ ሃሳቦች ለእናንተ ሰጥተዋል”

ጥበበኛ ሰዎች ያፍራሉ

ይህ ምጸት ነው ምክንያቱም ጥበበኞች ሰዎች ሁልጊዜ ስለ ጥበባቸው ይከበራሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ጥበበኞች እንደሆኑ የሚያስቡ ሰዎች ሃፍረት ይሰማቸዋል” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

ደንግጠዋል

ፈርተዋል ወይም ተርበድብደዋል

እነሆ!

“ትኩረት ስጡ!

ስለዚህ ጥበባቸው ምን ይጠቅማቸዋል?

ይህ ጥያቄ አሉታዊ መልስ ይጠብቃል፤ ዓላማውም አድማጮቹ የእግዚአብሔርን ቃል ተቃውመው እያሉ እነርሱ ጥበብ ብለው የሚናገሩት በእርግጥም ጠቃሚነቱ ምን ያህል ትንሽ እንደሆነ እንዲያስቡት ለመማድረግ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ጥበብ ነው ብለው የሚያስቡት ነገር ምንም መልካም ነገር አይሰራላቸውም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ምክንያቱም ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ተገቢ ላልሆነ ጥቅም ስስታሞች ናቸው ከነቢዩም ጀምሮ እስከ ካህኑ ድረስ ሁሉ በተንኰል ያደርጋሉና

ይህን በኤርምያስ 6:13 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡

ምክንያቱም ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ስስታሞች ናቸው

“ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ” የሚለው ሀረግ የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ ያለ ምንም የማንነትና የኑሮ ደረጃ ልዩነት “ሁሉ” በሚለው ቃል ውስጥ መካተታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- ምክንያቱም ስልጣን ያላቸው፣ ስልጣን የሌላቸውና ሌሎቹንም እያንዳንዳቸውን ጨምሮ ሁሉም ስስታሞች ናቸው” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ታናሹ

ይህ ከፍተኛ ስፍራ የሌላቸውና በሰው እይታ ግምት ውስጥ የማይገቡ ሰዎችን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- ዝቅተኛ ስልጣን ያላቸው” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ታላቁ

ይህ ከፍተኛ ስፍራ ያላቸውንና በሰው ዘንድ ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸውን ሰዎች ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው ሰዎች” ወይም “ከፍተኛ ኃይል ያላቸው ሰዎች” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም

“የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ”

ተገቢ ላልሆነ ጥቅም ሲሉ ስግብግብ ናቸው

“ጥቅም” የሚለው ረቂቅ ስም “የበለጠ ገንዘብ ማግኘት” ወይም “የበለጠ ቁሳቁስ ለማግኘት” በሚሉት ሀረጎች ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለሰዎች ውሸት በመናገር ብዙ ገንዘብ ያገኛሉ” ወይም “ብዙ ቁሳቁስ ለማግኘት በብርቱ ይፈልጋሉ፣ እነዚህን ለማግኘት ደግሞ ሰዎችን ያታልላሉ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም ያጭበረብራሉ

“ሁሉም ሰዎችን ያታልላሉ” ወይም “ሁሉም ውሸታሞች ናቸው”

Jeremiah 8:11

አያያዥ ሀሳብ፡-

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ የሚናገረውን መልእክት ለኤርምያስ መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ:-
በእነዚህ ጥቅሶች “እነርሱ”፣ የእነርሱ” እና ለእነርሱ” የሚሉት ቃላት የይሁዳን ሕዝብ ያመለክታሉ።
የሕዝቤን ቁስል በጥቂቱ ይፈውሳሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች:- 1) ቁስል ከኃጢአታቸው የተነሳ የሚገጥማቸውን ችግር የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የሕዝቤ ችግር ቀለል እንደሆነ ያስባሉ” ወይም 2) ቁስል የሕዝቡን ኃጢአት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “የሕዝቤ ኃጢአት እንደ ትንሽ ቁስል ቀላል እንደሆነ ያስባሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቁስልን በጥቂቱ ይፈውሳሉ
እዚህ ላይ “ጥቂት” የሚለው ቃል ቁስል ቀላል እንደሆነና ብዙ አስቸጋሪ እንዳልሆነ አድርገው በማየት ተገቢ እንክብካቤ አለመስጠትን ይወክላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰላም ሳይሆን ‘ሰላም፣ ሰላም’ ይላሉ
“‘ሁሉም ደህና ነው፣ ሁሉም ደህና ነው’ ይላሉ፣ ነገር ግን ደህና አይደለም”
አስጸያፊ ነገሮችን ሲሰሩ አፍረዋልን?
እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡ በኃጢአታቸው ባለማፈራቸው ምክንያት ቁጣውን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “በጣም አስደንጋጭ ኃጢአት ሰርተዋል፣ ነገር ግን ምንም አያፍሩም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
እንዴት ማፈር እንዳለባቸው አያውቁም
“ፊታቸው እንኳ ፈጽሞ አልቀላም።” ሰው ሲያፍር ብዙ ጊዜ ፊቱ ይቀላል።
ከሚወድቁት ጋር ይወድቃሉ
እዚህ ላይ “ይወድቃሉ” የሚለው ይገደላሉ የሚለውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ከተገደሉት ከሌሎቹ ጋር አብረው አንድ ላይ ይገደላሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በምቀጣቸውም ጊዜ ይዋረዳሉ
እዚህ ላይ “ይዋረዳሉ” የሚለው መጥፋትን ይወክላል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ በምቀጣቸው ጊዜ አጠፋቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ቅጠሉ ይረግፋል
“ቅጠሉ ይደርቃል”
እኔ የሰጠኋቸው ሁሉ ከእነርሱ ይወሰድባቸዋል
እዚህ ላይ የመጀመርያው ጽሑፍ ትርጉም ምን እንደሆነ እርግጠኛ መሆን አይቻልም።
Jeremiah 8:14
አያያዥ ሀሳብ:-
የይሁዳ ሕዝብ በሚቀጡበት ጊዜ ምን እንደሚሉ ለእኛ በመንገር እግዚአብሔር መልእክቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ:-
“እኛ”፣ “ለእኛ” እና “የእኛ” የሚሉት ቃላት የይሁዳ ሕዝብን ያመለክታሉ።
ለምን እዚህ እንቀመጣለን?
ይህ ጥያቄ የተጠየቀው የድርጊት እርምጃን ለማነሳሳት ነው። ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እዚህ መቆየት የለብንም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በአንድነት ወደዚህ ኑ፤ ወደ ተመሸጉት ከተሞች እንሂድ
`የተመሸጉ ከተሞች” ከፍተኛ የግንብ አጥር እና ጠንካራ ከለላ የነበራቸው ከተሞች ናቸው። እነዚህ ተመሳሳይ ሀረጎች በኤርምያስ 4:5 ላይ እንዴት እንደተረጎምኻቸው ተመልከት።
በዚያ እንሞታለን፣ ድምጻችንንም እናጠፋለን
እዚህ ላይ “ድምጻችንንም እናጠፋለን”የሚለው መሞት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እዚያ እንሙት” ወይም “በዚያ እንዲገድሉን ጠላቶቻችንን እንጠብቅ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር አምላካችን እንድንጠፋ አድርጎናል
እዚህ ላይ “እንድንጠፋ” የሚለው የሞት ፍርድ እንደተላለፈባቸው የሚያሳይ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር አምላካችን የሞት ፍርድ ስላስተላለፈብን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መርዝ እንድንጠጣ ያደርገናል
ይህ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ያስተላለፈውን ፍርድ የሚያሳይ ፈሊጥ ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን መልካም ነገር አይኖርም
“ነገር ግን አንድም መልካም ነገር አይሆንም”
ነገር ግን ተመልከቱ
“ነገር ግን አስተውሉ”
Jeremiah 8:16
አያያዥ ሀሳብ:-
እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ ስለሚመጣው ቅጣት መልእክቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ:-
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ “የእርሱ” እና “እነርሱ” የሚሉት ቃላት የይሁዳ ጠላቶችን ያመለክታል።
የፈረሶቹ ፉርፉርታ ከዳን ተሰማ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “የፈረሶቹን ፉርፉርታ የዳን ሕዝብ ሰምተውታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ፉርፉርታ
ፈረስ በአፍንጫው የሚያሰማው ከፍ ያለ ድምጽ
ፈረሶች
ጎልማሳ ወንዶች ፈረሶች
ምድር ሁሉ ተንቀጠቀጠች
ይህ ግነት ሲሆን የይሁዳ ሕዝብ በፍርሃት ለመንቀጥቀጣቸው ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም:- የምድሪቱ ሕዝቦች በሙሉ በፍርሃት ተንቀጠቀጡ” (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በጠንካራ ፈረሶቹ የማሽካካት ድምጽ
“የጠላትን ጠንካራ ፈረሶች ድምጽ በሰሙ ጊዜ”
ማሽካካት
ፈረስነየሚያሰማው ድምጽ
እነርሱ ይመጡና ይውጡአችኋል
እዚህ ላይ “ይውጡአችኋል” የሚለው ቃል መብላት ማት ነው። ይህ ጠላቶች እንዴት እንደሚመጡና ምድሪቱንና በእርሷ የሚኖሩትን ሰዎች እንደሚያጠፉ የሚያሳይ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እነርሱ ይመጡነና ያጠፉአችኋል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ተመልከቱ
“አሁን አስተውሉ”
እኔ በመካከላችሁ መርዘኛ እባቦች፣ በአስማት ብልሃት ልትከለክሉአቸው የማትችሉአቸውን እፉኝቶች እልክባችኋለሁ
እባቦቹና እፉኝቶቹ የጠላትን ወታደር ይወክላሉ፣ መንከሳቸው ደግሞ የጠላትን ጥቃት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ በመካከላችሁ ከቁጥጥራችሁ በላይ የሆኑ የጠላት ወታደሮችን እልካለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በአስማት ብልሃት ልትከለክሉአቸው የማትችሉአቸውን እፉኝቶች
እዚህ ላይ አስማት ማድረግ የሚለው ሀረግ እባቦችን ለመቆጣጠር መዘመር ወይም ሙዚቃ ማሰማት ነው።
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 8:18
አጠቃላይ መረጃ:-
ኤርምያስና እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ ንግግር ያደርጋሉ።
የእኔ ሃዘን አያልቅም
እዚህ ላይ “የእኔ” የሚለው ኤርምያስን ያመለክታል። የመጀመርያው የተጻፈበት ሃሳብ ግልጽ አይደለም ስለዚህ በዘመኑ ባሉት ትርጉሞች በተለያዩ መንገዶች

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተተርጉሟል።
አያልቅም
ይህ ቃል የኤርምያስን ጥልቅ ሃዘን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ግነት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጣም ታላቅ” ነው። (ግነት/ግነታዊ ቋንቋ እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ልቤ ትምሟል
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ኤርምያስን የሚወክል ሲሆን እርሱ የተሰማውን ነገርና ስሜቱን አጽንዖት የሚሰጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ በጥልቅ የውስጥ ማንነቴ ሕመም ይሰማኛል” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ!
ይህ ከዚህ ቀጥሎ ለሚነገረው ነገር አንባቢው ትኩረት እንዲሰጥ የሚያነቃ ነው። “ትኩረት ስጥ”
የሕዝቤ ሴት ልጅ
ኤርምያስ ለሴት ልጅ የሚገባውን ዓይነት ፍቅሩን ለይሁዳ ሕዝብ በሚያሳይበት መንገድ ስለ እነርሱ ይናገራል። ይህንን በኤርምያስ 4፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ ውድ ሕዝቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሩቅ አገር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ከግዞት። አማራጭ ትርጉም፡- “ከግዞት ከሩቅ አገር” ወይም 2) ከይሁዳ ምድር በሙሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “በምድራችን ዙርያ ሁሉ”
እግዚአብሔር በጽዮን የለምን? ወይስ ንጉስዋ በእርስዋ ዘንድ የለምን?
እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። የይሁዳ ሕዝብ እግዚአብ|ሔር ለምን እነርሱን እንዳላዳናቸው ግራ እንደተጋቡ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር በጽዮን ንጉስ ከሆነ ለምን እርሱ እኛን አላዳነንም?” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በተቀረጹ ምስሎቻቸውና እንዲሁም ከንቱ በሆኑ ባዕዳን ጣዖታት እኔን ለምን አስቆጡኝ?
“እኔን” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል። ይህ ጥያቄ በዓረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ እኔ እንዳድናቸው የሚፈልጉ ከሆነ በተቀረጹ ምስሎቻቸው እኔን ሊያስቆጡኝ አይገባም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ )
Jeremiah 8:20
አያያዥ ሀሳብ፡-
ኤርምያስ ስለ ይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡-
“እኛ” የሚለው ቃል የይሁዳ ሕዝብን ያመለክታል። “እኔ” እና “የእኔ” የሚሉት ቃላት ኤርምያስን ያመለክታሉ።
መከሩ አልፎአል
“የመከር ጊዜ አልፎአል”
ነገር ግን እኛ አልዳንንም
ኤርምያስ የይሁዳ ሕዝብ የሚናገሩትን ያስተላልፋል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን እግዚአብሔር እኛን አላዳነንም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በሕዝቤ ሴት ልጅ ስብራት እኔም ተሰብሬአለሁ፣ ጠቁሬማለሁ። በእርስዋ ላይ በሆኑት አስከፊ ነገሮች እኔ አዝኛለሁ፤ እኔ ተስፋ ቆርጫለሁ
እነዚህ ዓረፍተ ሃሳቦች አጽንዖት ለመስጠት ከአንድ በላይ መንገድ በመጠቀም ተመሳሳይ ሃሳብ ይገልጻሉ። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
በገለዓድ መድኃኒት የለምን? ወይስ በዚያ ሐኪም የለምን? የወገኔ ሴት ልጅ ፈውስ ስለምን አልሆነም?
እነዚህ ጥያቄዎች የጠጠየቁት የይሁዳ ሕዝብ እንዳልዳኑ ዋናውን ነጥብ ለማስተላለፍ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በገለዓድ መድኃኒት አለ፣ በዚያ ሐኪሞች አሉ፣ ስለዚህ የውድ ሕዝቤ ፈውስ ለምን እንደማይከናወን ንገሩኝ።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 9
Jeremiah 9:1
አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔርና ኤርምያስ ስለ ይሁዳ ሕዝብ መነጋገር ቀጥለዋል።
ምነው ራሴ የውሃ ምንጭ በሆነ! ምነው ዓይኖቼ የውሃ መጉረፊያ በሆኑልኝ!
ይህን የሚናገረው ኤርምያስ ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ኤርምያሰ ምን ያህል እያለቀሰ እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “የበለጠ እንባ ማፍሰስ ብችል እመኝ ነበር” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀንና ሌሊት
“ቀን” እና “ሌሊት” የሚሉትን በመጥቀስ ይህ ሀረግ ሁልጊዜ የሚል ትርጉም ይኖረዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁልጊዜ” ወይም “ያለማቋረጥ” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሕዝቤ ሴት ልጅ
እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር እንደ ሴት ልጅ በመግለጽ ለእነርሱ ያለውን ጥልቅ ፍቅር ያሳያል። እዚህ ላይ ኤርምያስ እግዚብሔር የተጠቀመበትን ተመሳሳይ ሀረግ ሕዝቡን ለመግለጽ ይጠቀማል። ይህንን በኤርምያስ 4፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፡- የእግዚአብሔር ሴት ልጅ የመሰሉትን ሕዝቤ” ወይም “ውድ ሕዝቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የተገደሉትን
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ጠላት የገደላቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሰው ቢሰጠኝ ኖሮ
“አንድ ሰው ቢሰጠኝ ኖሮ እመኝ ነበር።” አሁንም የሚናገረው ኤርምያስ ነው።
በምድረ በዳ ለሚጓዙ መቆያ የሚሆን ስፍራ
ይህ የሚወክለው በምድረ በዳ ለሚጓዙ ሰዎች ከጉዞአቸው ቆመው ሌሊቱን ተኝተው የሚያሳልፉበትን ሕንጻ ነው።
ሕዝቤን ትቼ
“ሕዝቤን ተውኋቸው”
የአታላዮች መንጋ
“ሌሎች ሰዎችን የሚያታልሉ የሰዎች ስብስብ”
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
“ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው” የሚለውን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
ሐሰትን ለመናገር ምላሳቸውን እንደ ቀስት ገተሩ
ውሸትን መናገር በክፉዎች ምላስ እንደሚሰራ ተደርጎ ተነግሯል። በተጨማሪ የተነገረ ውሸት ወደኋላ መመለስ ስለማይቻል ውሸትን መናገር ቀስትን እንደ መወርወር ተደርጎ ተነግሯል። ቀስትን የሚጠቀሙ ሰዎች የቀስቱን ገመድ ለማሰር ቀስታቸውን መያዝ አለባቸው፣ ስለዚህ እዚህ ላይ ውሸታሞች ምላሳቸውን በመጠቀም ምላሳቸውን እንደሚገትሩ ተደርገው ተጠቅሰዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ውሸታቸው በምላሳቸው እንደሚወረወር ቀስት ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን በምድር የበረቱት በታማኝነታቸው ምክንያት ፈጽሞ አይደለም
“በምድር የበረቱት ለእግዚአብሔር ታማኞች በመሆናቸው ምክንያት አይደለም፣ እነርሱ ክፉዎች ናቸውና” እና “ይህ ማለት ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ታማኞች አይደሉም ማለት ነው፣ ነገር ግን እንዲያውም እነርሱ ክፉዎች ናቸውና ኃይላቸውን ያገኙት በክፋታቸው ነው” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
ከአንድ የክፋት ተግባር ወደ ሌላ የክፋት ተግባር ይሄዳሉ
አንድን ክፉ ተግባር ከሌላው ክፉ ተግባር ቀጥሎ ስለመፈጸም ሲናገር ክፉ አድራጊዎች ከአንድ ድርጊት ወደ ሌላ ድርጊት እንደሚሄዱ ተደርጎ ተገልጦአል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ነገሮችን በማድረግ ቀጥለዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 9:4
አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ ከኤርምያስ ጋር መነጋሩን ቀጥሏል።
እናንተ እያንዳንዳችሁ
“እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳን ሕዝብ ነው።
ከጎረቤቶቻችሁ ተጠብቀቁ፣ በወንድሙም ላይ አይታመን
“አብረዋችሁ ያሉትን እስራኤላውያንን ከማመን ተጠንቀቁ፣ የራሳችሁን ወንድም ቢሆንም አትመኑ”
እያንዳንዱ ጎረቤት በሐሜት ይመላለሳል
እዚህ ላይ “ይመላለሳል” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን መኖርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እያንዳንዱ ጎረቤት አንዱ ሌላውን ያማል” ወይም “እያንዳንዱ ጎረቤት ሐሜተኛ ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እያንዳንዱ ሰው በጎረቤቱ ላይ ያፌዛል፣ እውነትን ደግሞ አይናገርም
“ሁሉም ሰዎች እርስ በርሳቸው ያፌዛሉ፣ እውነትን ደግሞ አይናገሩም”
ምላሶቻቸው ሐሰተኛ ነገሮችን ያስተምራሉ
እዚህ ላይ ለንግግራቸው አጽንዖት ለመስጠት ሲባል ሰዎች “በምላሶቻቸው” ተወክለዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ሐሰተኛ ነገሮችን ያስተምራሉ” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉንም በማድረግ ደክመዋል
“ብዙ ኃጢአት በማድረግ ደክመዋል”
መኖርያችሁ በሸንገላ መካከል ነው
እግዚአብሔር በውሸታሞች መካከል መኖር በሸንገላ መካከል መኖር እንደሆነ አድርጎ ተናግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “መኖርያችሁ በውሸታሞች መኖርያ መካል ነው” ወይም “እናንተ የምትኖሩት በውሸታሞች መካከል ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በሸንገላቸው
“እነዚህን ሁሉ ውሸቶች በመናገር”
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል፡፡ ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 9:7
አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል፡፡
ተመልከት
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ይህን ቃል የተጠቀመው የኤርምያስን ትኩረት ቀጥሎ ወደሚናገረው ንግግር ለመሳብ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አድምጥ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱን ለማንጠር
እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለመፈተንና ክፉ መንገዳቸውን ፊት ለፊት ስለመጋፈጥ ሲናገር እነርሱ ብረት እንደሆኑና እርሱ የብረቱን ቆሻሻ ለማስወገድ ብረቱን በማቅለጫ እንደሚያቀልጠው አድርጎ ገልጾታል፡፡ ( ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሕዝቤ በሰሩት ኃጢአት ምክንያት ምን ማድረግ እችላለሁ?
እግዚአብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመው ከሰሩት ስራ የተነሳ ሕዝቡን ሊጋፈጥ የሚያስፈልገው በዚህ መንገድ እንደሆነ ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ሃሳብ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከሰሩት ስራ የተነሳ ከሕዝቤ ጋር መጋፈጥ የሚገባኝ እንደዚህ ነው” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ምላሶቻቸው የተሳሉ ቀስቶች ናቸው
ይህን የሚናገረው ሰዎች በሚናገሩት ንግግር ሌሎች ሰዎችን በጣም ሲለሚጎዱ የሰዎች ምላሶቻቸው የተሳሉ ቀስቶች እንደሆኑ ተደርገው ተገልጸዋል፡፡ እዚህ ላይ ንግግራቸው “በምላሶቻቸው” ተወክሏል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ቃላቶቻቸው ሌሎች ሰዎችን እንደሚጎዱ እንደተሳሉ ቀስቶች ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በአንደበቶቻቸው ከባልንጀሮቻቸው ጋር ሰላምን ይናገራሉ
እዚህ ላይ የሰዎች ንግግር “በአንደበቶቻቸው” ተወክሏል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከባልንጀሮቻቸው ጋር ሰላም እንፈልጋለን እያሉ ይናገራሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን በልባቸው አድብተው ይጠብቁአቸዋል
እዚህ ላይ የሰዎች ፍላጎት “በልባቸው” ተወክሏል፡፡ አደን ወጥቶ ለመብላት የሚፈልገውን ለማጥቃት እንደሚያደፍጥና እንደሚጠብቅ እንስሳ እንደዚሁ እነርሱም ባልንጀሮቻቸውን ለመጉዳት የሚፈልጉ እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን እነርሱ የሚፈልጉት ነገር ባልንጀሮቻቸውን ማጥፋት ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ታዲያ ስለነዚህ ነገሮች ልቀጣቸው አይገባኝምን? … እኔ ራሴስ እንደዚህ ዓይነቱን ሕዝብ አልበቀልምን?
እግዚአብሔር እነዚህን መልስ የማይሰጥባቸውን ጥያቄዎች የተጠቀመው እነርሱ የሰሯቸው ነገሮች በጣም መጥፎ ከመሆናቸው የተነሳ በእነርሱ ላይ ምህረት እንደማይኖረውና እነርሱን ከመቅጣት ራሱን እንደማያስቆም አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ እነዚህን ተመሳሳይ ቃላት በኤርምያስ 5፡9 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ እነዚህን ነገሮች ከማድረጋቸው የተነሳ እኔ እቀጣቸዋለሁ … እኔ ራሴ በእርግጠኝነት በእነርሱ ላይ እበቀላለሁ፡፡” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል፡፡ ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 9:10
አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል፡፡ በቁጥር 12 ኤርምያስ አስተያየት ይሰጣል፡፡
እኔ የሃዘን ልቅሶ አለቅሳለሁ … ለማሰማርያዎቹ የቀብር ልቅሶ ይለቀሳል
የሞተች ሰው እንደሆነች በማሰብ እንደዚሁ እግዚአብሔር ለእስራኤል ምድር ያለቅሳል፡፡ (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የቀብር ልቅሶ ይለቀሳል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ የቀብር ልቅሶ አለቅሳለሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ማሰማሪያዎቹ
“እንስሳት ሳር የሚግጡበት የግጦሽ ስፍራ”
እነርሱ ተቃጥለዋልና
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ምክንያቱም ሰው ማሰማሪያዎቹንና የግጦሽ መሬቱን አቃጥሎአቸዋልና” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የእንድም ከብት ድምጽ ፈጽመው አይሰሙም
“በዚያ ስፍራ አንድም ሰው የከብት ድምጽ አይሰማም”
የቀበሮ መሸሸጊያ
“ቀበሮዎች የሚደበቁበት ስፍራ፡፡” ቀበሮዎች እጅግ በጣም ኃይለኛ የዱር ውሾች ናቸው፡፡
ሰው የማይኖርበት ስፍራ
“አንድም ሰው የማይገኝበት ስፍራ”
ይህን የሚያስተውል ጠቢብ ሰው ማን ነው?
እግዚአብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ የተናገራቸውን ነገሮች መረዳት የሚችል ሰው በጣም ጥበበኛ ሰው ብቻ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህን ነገሮች መረዳት የሚችሉ በጣም ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ያወራስ ዘንድ የእግዚአብሔር አፍ ለማን ተናገረ
እግዚአብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመው እነዚህን ነገሮች መናገር የሚችሉት እርሱ የተናገራቸው ሰዎች ብቻ እንደሆኑ አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህን ነገሮች ለሌሎች ማብራራት የሚችሉት ከእግዚአብሔር የተማሩ ብቻ ናቸው” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር አፍ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ንግግር በእርሱ “አፍ” ተወክሏል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰው እንዳያልፍባት ምድሪቱ ለምን ጠፋች፣ ለምንስ ወና ሆነች?
እግዚአብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመው ምድሪቱ ለምን እንደጠፋች ማብራራት የሚችለው ጥበበኛ ሰው ብቻ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰው እንዳያልፍባት ምድሪቱ ለምን እንደጠፋች እና ወና እንደሆነች ማብራራት የሚችለው ጥበበኛ ሰው ብቻ ነው፡፡” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ )
ምድሪቱ ጠፍታለች ደግሞም ወና ሆናለች
ይህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል፡፡ “ጠፋች” እና “ወና ሆነች” የሚሉት ሁለቱም ምድሪቱ ወና እንደሆነች የሚያብራሩ ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ምድሪቱ ወና ሆናለች” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 9:13

አጠቃላይ መረጃ:-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።
ምክንያቱም
“እነዚህ ነገሮች ይሆናሉ ምክንያቱም”
ሕጌን ትተዋልና
እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሕጉን አለመታዘዝ ሲናገር ከሕጉ ርቀው እንደሄዱ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም:- “ሕጌን ትተውታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ድምጼን አይሰሙም
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር “ድምጽ” እርሱ የተናገረውን ነገር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ ለእነርሱ ለነገርኳቸው ነገሮች ምንም ትኩረት አልሰጡም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ወይም በእርሱ አልሄዱም
እዚህ ላይ “መሄድ” ፈሊጥ ሲሆን “መኖርን” የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ወይም እኔ እንዲኖሩ በነገርኳቸው መንገድ አልኖሩም” ( ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ በልባቸው እልከኝነት ሄዱ
እዚህ ላይ የሕዝቡ “እልከኛ ልቦች” እልከኛ ፍላጎታቸውንና እልከኛ ፈቃዳቸውን ይወክላል። እዚህ ላይ “መሄድ” መኖርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “እነርሱ እልከኞች ነበሩና ሊኖሩ በሚፈልጉት መንገድ ኖሩ” (ምትክ ስም እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
በኣሊምን ተከተሉ
“በኣልን አመለኩ”
Jeremiah 9:15
አጠቃላይ መረጃ:-
እግዚአብሔር ስለ ይሁዳ ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ከእግዚአብሔር የመጣውን በጣም አስፈላጊ መልእክት ለማስተዋወቅ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቃላት ይጠቀማል። ይህን በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
ተመልከቱ
እግዚአብሔር ይህን ቃል የተጠቀመው ከዚህ ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “አዳምጡ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እሬት
በጣም መራራ ጣዕም ያለው ተክል
እነርሱን በማያውቋቸው ሕዝቦች መካከል እበትናቸዋለሁ
“ከዚያም እኔ ይህን ምድር እንዲለቁና በብዙ የተለያዩ አገሮች እንዲኖሩ አስገድዳቸዋለሁ”
እነርሱም ሆኑ አባቶቻቸው
ግልጽ የሆነ ግስ መጠቀም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም:- “እነርሱ ወይም የእነርሱ አባቶች አያውቁም” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእነርሱ በኋላ ሰይፍን እልካለሁ
እዚህ ላይ “ሰይፍ” የሚለው ቃል የጠላትን ጦር ሰራዊት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “እነርሱን እንዲዋጉአቸው ወታደራዊ ሰራዊት እልክባቸዋለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ እነርሱን ሙሉ በሙሉ አጥፍቻቸዋለሁ
ይህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ጠላቶቻቸው እንዲያጠፉአቸው ለማድረጉ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም:- እኔ ጠላቶቻቸው ሙሉ በሙሉ እንዲያጠፉአቸወ አድርጌአለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 9:17
አጠቃላይ መረጃ:-
እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ ለሚመጣው ለምድሪቱ ጥፋት እንዲያለቅሱ ይነግራቸዋል።
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ከእግዚአብሔር የመጣውን በጣም አስፈላጊ መልእክት ለማስተዋወቅ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቃላት ይጠቀማል። ይህን በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።
የቀብር አልቃሾችን ጥሩ፤ ይምጡ ... የሰለጠኑ ሙሾ አውራጆችን አስመጡ፤ ይምጡ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እነዚህ ሀረጎች የቀብር አልቃሾች እንዲያመጡ ሊጠሩአቸው እንደሚገባ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም:- “የሰለጠኑ አልቃሽ ሴቶች ፈልጋችሁ አግኙና እነዚህን ሴቶች ወደዚህ አምጡአቸው” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
የቀብር አልቃሾችን ጥሩ
“በቀብር ላይ ሙሾ የሚያወጡ የሰለጠኑ አልቃሽ ሴቶች ጥሩ”
ይምጡ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እንዲመጡ ለሴቶቹ ንገሯቸው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰለጠኑ ሙሾ አውራጅ ሴቶችን ለመፈለግ ሰው ላኩ
“ሰው ላኩ” የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ነው። አማራጭ “የልቅሶ ሙሾ በማውረድ የሰለጠኑ ሴቶችን ለማግኘት ሰዎችን ላኩ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የእኛ የዓይናችን ሽፋሽፍቶች ውኃን እንዲያፈልቁ ፈጥነው ለእኛ ልቅሶውን ይያዙ
x
Jeremiah 9:19
አጠቃላይ መረጃ:-
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሚናገረው እርሱ ምድሪቱን ሲያጠፋ ወደፊት የይሁዳ ሕዝብ የሚናገረውን ነው።
በጽዮን የልቅሶ ድምፅ ተሰምቶአል
ይህ የጽዮን ሕዝብ ከፍ ባለ ድምጽ ማልቀሱን የሚያመለክት ሲሆን በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “የጽዮን ሕዝብ ከፍ ባለ ድምጽ ያለቅሳሉ፣ እንዲህ እያሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እኛ እንዴት ፈራረስን
ምድሪቱ በምትጠፋበት ጊዜ የይሁዳ ሕዝብ ወደፊት የሚናገረውን እግዚአብሔር ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- “እኛ በጣም ተበሳጭተናል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ቤቶቻችንን ስላፈረሱና ምድሪቱን ስለተውን እኛ እጅግ በጣም አፍረናል
“እፍረታችን እጅግ ታላቅ ነው፣ ምክንያቱም ጠላቶች ቤቶቻችንን አፍርሰውታል የእስራኤልን ምድር ደግሞ ለቅቀን መውጣት አለብን”
የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤ ከአፉ ለሚመጣው መልእክት ተገቢ ትኩረት ስጡ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ እግዚአብሔር ቃሉን እንዲያደምጡ ለሰጠው ትእዛዝ አጽንዖት ይሰጣሉ። በሁለተኛው ሀረግ የእግዚብሔ “አፍ” ለራሱ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር የተናገረውን አድምጡ። ለቃሉ ትኩረት ስጡ” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እያንዳንዱ የጎረቤት ሴቶች የቀብር ልቅሶውን
ግልጽ የሆነ ግስ መጠቀም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም:- “ለእያንዳንዱ የጎረቤት ሴቶች የቀብር ልቅሶውን አስተምሩአቸው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 9:21
አጠቃላይ መረጃ:-
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሚናገረው እርሱ ምድሪቱን ሲያጠፋ ወደፊት የይሁዳ ሕዝብ የሚናገረውን ነው።
ወጣት ወንዶች ... በከተማይቱ አደባባይ ... ሞት በመስኮታችን በኩል መጥቶአል
የይሁዳ ሕዝብ ለወደፊት ሞትን በመስኮት ዘልሎ በመግባት በቤት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለማጥቃትና በቤተ መንግስት፣ በመንገዶችና በከተማ አደባባዮች ያሉትን ሰዎች ከሚያጠቃ ሰው ጋር ያነጻጽሩታል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቤተ መንግስታት
ነገስታት የሚኖሩበት በጣም የሚያምሩ ቤቶች። ሞት በተመሳሳይ መልኩ ወደ ባለጠጎችና ድሆች ይመጣል።
የከተማይቱ አደባባይ
የገበያ ስፍራዎች
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰውም ሬሳ እንደ ጕድፍ ... ከአጫጆች በኋላ እንደሚቀር ቃርሚያ ይወድቃል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የሰው ሬሳ እጅግ በጣም ብዙ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም:- “የሰዎች ሬሳ በየቦታው

ይወድቃል” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
የሰውም ሬሳ እንደ ጉድፍ በእርሻ ላይ ይወድቃል
ሰውነታቸውን በእርሻ ላይ ከሚወድቀው ጉድፍ ጋር በማነጻጸር የሚሞተውን በጣም ብዙ ቁጥር ያለውን ሕዝብ ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእንስሳት አዛባ በየሜዳው እንደሚወድቅ እንደዚሁ የሰዎች ሬሳ በየቦታው ይወድቃል” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአጫጆች በኋላ እንደሚቀር ቃርሚያ
ይህ ሰውነታቸውን ከአጫጆች በኋላ ከሚቀረው ቃርሚያ ጋር በማነጻጸር የሚሞተውን በጣም ብዙ ቁጥር ያለውን ሕዝብ ይገልጻል። አማራጭ ትርጉም፦ “ገበሬዎች ሰብላቸውን ካጨዱ በኋላ በየቦታው ወድቆ እንደሚቀር ቃርሚያ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱን ለመሰብሰብ አንድም ሰው አይኖርም
“የሞቱትን ሰዎች ሬሳ ለመሰብሰብ አንድም ሰው አይኖርም”
Jeremiah 9:23
አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ የእግዚአብሔር ቃላት ናቸው።
ጠቢብ በጥበቡ አይመካ
“ጠቢብ ጥበበኛ ስለሆነ በጥበቡ ሊመካ አይገባውም”
ወይም ጦረኛ በኃይሉ አይመካ
ግልጽ የሆነ ግስ መጠቀም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወይም ጦረኛ በኃይሉ ይመካ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ባለ ጠጋም በብልጥግናው አይመካ
“ሀብታም ሰው ሀብታም ስለሆነ በሃብቱ አይመካ”
በማስተዋሉና እኔን በማወቁ
“እኔ ማን እንደሆንሁ በማስተዋሉና እኔን በማወቁ።” እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ያወቁና እርሱ ማን እንደሆነ ያስተዋሉ ሰዎችን አጽንዖት ይሰጣሉ። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 9:25
አጠቃላይ መረጃ፦
እነዚህ የእግዚአብሔር ቃላት ናቸው።
ተመልከቱ
እግዚአብሔር እዚህ ላይ ይህን ቃል የተጠቀመው ከዚህ ክፍል ቀጥሎ የሚናገረውን ንግግር ሰዎች ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አድምጡ” ወይም “በእርግጥ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀናት እየመጡ ነው
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ጊዜ ይኖራል” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ስጋቸውን ብቻ የተገረዙትን
ይህ በስጋቸው በመገረዝ ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገቡትን ነገር ግን የእርሱን ሕግ በመከተል ውስጣዊ ማንነታቸውን ያልለወጡ የእስራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ውጫዊ ሰውነታቸውን በመገረዝ የለወጡ ነገር ግን ውስጣዊ ማንነታቸውን ያልለወጡ ሕዝብ በሙሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በራሳቸው ላይ ያለውን ጸጉር በአጭሩ የሚቆረጡ ሕዝቦች በሙሉ
ይህ ምናልባት የሚያመለክተው የአሕዛብ ጣዖት ለማክበር ሲሉ ጸጉራቸውን በአጭሩ የሚቆረጡ ሕዝቦችን ነው። አንዳንድ አዳዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህን የዕብራይስጥ አገላለጽ “በምድረ በዳ ጫፍ ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች በሙሉ” ብለው ተርጉመውታል።
እነዚህ ሕዝቦች የተገረዙ አይደሉምና
እዚህ ላይ “ሕዝቦች” የሚለው ቃል በእነዚህ ስፍራዎች የሚኖሩትን ሕዝቦች ነው። ያልተገረዙ እንግዳ ሰዎች በእግዚአብሔር ኪዳን ውስጥ ያልተካተቱ ለመሆናቸው ምልክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእነዚህ መንግስታት ሕዝቦች በመገረዝ ወደ እግዚአብሔር ኪዳን አልገቡም” (ምትክ ስም እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቤት በሙሉ ያልተገረዘ ልብ አላቸው
“ልብ” የሰውን ፈቃድና ፍላጎት ይወክላል። “ያልተገረዘ ልብ” እግዚአብሔርንና ሕጉን የማይከተል ሰው ባህርይ ይወክላል። ከዚህ በተጨማሪ የእስራኤል “ቤት” የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስራኤልን ሕዝብ በሙሉ የተገረዙት በውጫዊው ሰውነታቸው ብቻ ነው፣ ልባቸው ግን አልተለወጠም” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 10
Jeremiah 10:1
አጠቃላይ መረጃ፦
እግዚብሔር ለይሁዳ ሕዝብ እንደዚሁም ለግብጽ፣ ኤዶም፣ አሞን፣ ሞአብ እና ለሁሉም ሕዝቦች እንደሚቀጡ አሳስቦአቸዋል።
ቃሉን ስሙ
“መልእክቱን ስሙ”
የእስራኤል ቤት
እዚህ ላይ “የእስራኤል ቤት” የሚለው የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስራኤል ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የአሕዛብን መንገድ አትማሩ
“ሌሎች ሕዝቦች እንደሚያደርጉት እናንተ አታድርጉ”
መፍራት
መጨነቅ ወይም መሸበር
በሰማይ ምልክቶች
“በሰማይ በምታዩት እንግዳ ነገሮች”
አሕዛብ በእነዚህ ይፈራሉና
እዚህ ላይ “አሕዛብ” የሚለው በውስጣቸው የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አሕዛብ በሰማይ የተመለከቱአቸውን እንግዳ ነገሮች ይፈራሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 10:3
አጠቃላይ መረጃ፦
እግዚአብሔር የአህዛብን መንገድ እንዳይማሩና በሰማይ በሚከናወኑ ነገሮች እንዳይጨነቁ አሳስቦአቸዋል።
አናጺ
በስራው ባለሞያ የሆነ ሰው
በእጃቸው የሚሰሩት ነገር በእርሻ መሃል እንደቆመ የወፎች ማስፈራሪያ ነው
የወፎች ማስፈራርያ ወፎችን ለማስፈራራት በሰው ምስል የተሰራ ነገር ሲሆን ወፎች እህል እንዳይበሉ እነርሱን ይከላከላል። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ጣዖቶችን በእርሻ መሃል ከሚቆም የወፎች ማስፈራርያ ጋር ያነጻጽረዋል ምክንያቱም እነርሱ ምንም ነገር ለማድረግ ችሎታ ስለሌላቸው ነው። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዱባ
ረጅም፣ አረንጓዴ ቅርፊትና ውስጡ ነጭ አካል ያለው ብዙ ውኃ የሚይዝ አትክልት ነው
ተሸካሚ ያስፈልጋቸዋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሰዎች ሊሸከሙአቸው ያስፈልጋቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 10:6
አጠቃላይ መረጃ፦
ኤርምያስ ስለ ጣዖት አምልኮ እየተናገረ ነው።
ስምህም በኃይል ታላቅ ነው
እዚህ ላይ የእግዚብሔር “ስም” ራሱንና ዝናውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተ በጣም ኃያል ነህ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ አንተን የማይፈራ ማን ነው?
ኤርምያስ ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የሚጠይቀው ማንኛውም ሰው እግዚአብሔርን ሊፈራ እንደሚገባው አጽንዖት ለመስጠት ነው። እዚህ ላይ ኤርምያስ እግዚአብሔርን “የሕዛብ ንጉስ” እንደሆነ በግልጽ አስቀምጦታል። ይህ ጥያቄ በዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እያንዳንዱ ሰው ሊፈራህ ይገባል፡፡” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የሚገባህ ነው
“አንተ ለራስህ ያዘጋጀኸው ነው”
Jeremiah 10:8
ሁሉም አንድ ናቸው፣ እነርሱ ጅሎችና ሞኞች ናቸው
“ጅሎች” እና “ሞኞች” የሚሉት ቃላት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ሕዝቡ እነዚህን ጣዖቶች በማምለካቸው ምን ያህል ሞኞች እንደሆኑ አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ሁሉም ጅሎች ናቸው፣ ደቀ መዛሙርት ናቸው” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ከንቱ የሆኑና ከእንጨት የተሰሩ የጣዖቶች ደቀ መዛሙርት ናቸው
“የእንጨት ቁራጭ ከሆነው ከጣዖት ለመማር ይሞክራሉ”
ተርሴስ ... አፌዝ
ብርና ወርቅ የሚወጣባቸው ስፍራዎች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
በባለሞያና በአንጥረኛ እጅ የተሰራ ወርቅ ከአፌዝ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላ፡፡ በተጨማሪ አንጥረኛዎቹ እዚህ ላይ “በእጃቸው” ተወክለዋል ምክንያቱም ስራቸውን የሚሰሩት በእጃቸው ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የሰለጠኑ ባለሞያና አንጥረኛ የሰሩት ወርቅ ከአፌዝ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ብልኀተኞች
“የሰለጠኑ እናጺዎች”
አንጥረኞች
ማንኛውምንም ወርቅ ያልሆነውን ነገር ለመለየት ወርቅን የሚያቀልጡ ሰዎች
ልብሳቸውም ሰማያዊና ቀይ ግምጃ ነው
“ሰዎች ጣዖቶችን ሰማያዊና ቀይ ግምጃ ያለብሱአቸዋል”
ከቍጣው የተነሣ ምድር ትንቀጠቀጣለች
ይህ የሚናገረው ለእግዚአብሔር ቁጣ ስሜታዊ ምላሽ በመስጠት መሬት ስለመንቀጥቀጥዋ ነው፣ በእርግጥ ይህ የሚሆነው እግዚአብሔር ምድር እንድትንቀጠቀጥ ሲያደርጋ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ በሚቆጣበት ጊዜ ምድር ትንቀጠቀጣለች” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መንቀጥቀጥ
“መናወጥ”
Jeremiah 10:11
አጠቃላይ መረጃ፡-
እግዚአብሔር ለኤርምያስ እየተናገረው ነው፡፡
እናንተም ለእነርሱ እንዲህ ብላችሁ ትነግሩአቸዋላችሁ
“እናንተ” የሚለው ቃል እስራኤላውያንን ይወክላል፣ “እነርሱን” የሚለው ደግሞ የሌሎች መንግስታት ሕዝቦችን ይወክላል፡፡
ከምድር ይጠፋሉ
ይህ ጣዖቶቹ እንደሞቱ ተቆጥረው ስለ መጥፋታቸውና ጠቃሚነታቸውን ስለ ማጣታቸው ይናገራል፡፡ ይህ እነርሱ ኃይል እንደሌላቸው አጽንዖት ይሰጣል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከምድር ይጠፋሉ” ( ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰማያትንም የዘረጋ
ይህ እርሱ እንደዘረጋው እንደ ትልቅ አንሶላ እግዚአብሔር ሰማያትን እንደፈጠረ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰማጣትን ፈጠረ” ወይም “ሰማይን ፈጠረ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ድምጹ በሰማያት ያሉ ውሆች እንዲናወጡ ያደርጋል
እዚህ ላይ ለንግግሩ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር “በድምጹ” ተወክሏል፡፡ “ውሆች” እንዲናወጡ የሚለው ሀረግ ታላቅ ጩኸት ያለውን ማዕበል ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የእርሱ ድምጽ በሰማይ ማዕበል ይፈጥራል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ጉምን ከምድርም ዳር ወደ ላይ እንዲወጣ ያደርገዋል
ይህ እርሱ ጉም ወደ ላይ እንዲተንንና ደመና እንዲፈጠር ያደረርጋል ማለት ነው፡፡ “ከምድርም ዳር” የሚለው ሀረግ ምድርን ሁሉ የሚያመለክት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ በማንኛውም የምድሪቱ ክፍል ሁሉ ደመና እንዲፈጠር ያደርጋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ነፋስንም ከግምጃ ቤቱ ይልካል
ይህ እግዚአብሔር ነፋሳትን እንዲነፍሱ ስለማድረጉ ሲናገር ነፋሱ በግምጃ ቤት እንደተቀመጠና እርሱ ሲፈልግ እንደሚወጣ ተደጎ ተገልጦአል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ግምጃ ቤት
የተለያዩ ቁሳቁሶች የሚቀመጡበት ሕንጻ
Jeremiah 10:14
እውቀት አጥቶአል
“እውቀት የለውም” ወይም “አያውቅም”
እያንዳንዱ አንጥረኛ ከቀረጸው ጣዖት የተነሣ አፍሮአል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የእያንዳንዱ አንጥረኛ ጣዖት አሳፍሮታል” ወይም ““የእያንዳንዱ አንጥረኛ በተመለከተ ጣዖቱ አሳፍሮታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በሚቀጡበት ጊዜ እነርሱ ይጠፋሉ
ይህ ስለ ጣዖቶቹ የመጨረሻ ጥፋት ይናራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እነርሱን የሚያጠፋበት ጊዜ ይመጣል” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የያዕቆብ እድል ፈንታ
እዚህ ላይ “ያዕቆብ” የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል፡፡ እግዚአብሔር የእነርሱ “እድል ፈንታ” መሆኑ ፈሊጥ ሲሆን እርሱንያመልኩታል ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤል እድል ፈንታ” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ የሚያመልኩት” (ምትክ ስም እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የሁሉ ነገር የቀረጸ
“የሁሉ ነገር ፈጣሪ” ወይም “ሁሉን ነገር የፈጠረ”
እስራኤልም የርስቱ ነገድ ነው
ይህ እስራኤል የእግዚአብሔር እንደሆነች የሚናገር ሲሆን እግዚአብሔር በውርስ ያገኛት ነገር እንደሆነች ተደርጎ ተገልጦአል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የእስራኤልም ነገድ የእግዚአብሔር ናት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 10:17
ዕቃሽን ሰብስቢ
“ንብረትሽን ሰብስቢ”
በከበባና በጦርነት ስር የምትኖሪ
“ከተማሽ በጠላቶችሽ ጦር ሰራዊት የተከበበ” ወይም “የጠላቶችሽ ጦር ሰራዊት ከተማሽን ከብቦ ሳለ በከተማሽ ውስጥ ስትኖሪ የነበርሽ”
ተመልከቱ
እግዚአብሔር እዚህ ላይ ይህን ቃል የተጠቀመው ከዚህ ክፍል ቀጥሎ የሚናገረውን ንግግር ሰዎች ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አዳምጡ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ በምድሪቱ የሚኖሩትን ሰዎች በዚህ ጊዜ ወደ ውጪ እወረውራቸዋለሁ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ሕዝቡ ምድሪቱን ለቅቀው እንዲወጡ እንደሚያደርጋቸው ሲናገር እነርሱ ከእቃ ማስቀመጫ ውስጥ አውጥቶ የሚወረውራቸው እቃዎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጦታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ በምድሪቱ የሚኖሩትን ሰዎች ያችን ምድር እንዲለቅቁ አደርጋቸዋሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በምድሪቱ የሚኖሩትን ሰዎች
“በምድሪቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች”
ጉዳት
ታላቅ ስቃይ ወይም መከራ
Jeremiah 10:19
አጠቃላይ መረጃ፡-
ኤርምያስ እርሱ መላው የእስራኤል ነገድ እንደሆነ አድርጎ ይናራል፡፡ (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ወዮልኝ! በተሰበሩ አጥንቶቼ ምክንያት፣ ቁስሌ የማይድን ነው
ኤርምያስ ስለ ሕዝቡ ጉዳት ሲናገር በተሰበሩ አጥንቶችና በማይድን ቁስል በአካል እንደተጎዱ አድርጎ ተናግሮታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ ወዮልን! የተሰበረ አጥንትና የማይድን ቁስል እንዳለን ያህል ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን ልሸከመው ይገባኛል
እዚህ ላይ ኤርምያስ የእስራኤልን መላውን ነገድ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ልንሸከመው ይገባናል” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ድንኳኔ ፈርሷል፣ የድንኳኔ ገመዶች ሁሉ ለሁለት ተቆርጠዋል
እዚህ ላይ ኤርምያስ ጠላት ከተማቸውን ስለማፍረሱ ሲናገር ድንኳኑ እንደፈረሰ አድርጎ ተናግሮታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የእኛ ታላቅ ድንኳን የፈረሰ ያህል ነው፤

ድንኳኑን የሚያያይዙት ገመዶች ተቆርጠዋል” ወይም “ጠላት ከተማችንን ሙሉ በሙሉ አፍርሷታል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ድንኳኔ ፈርሷል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጠላቴ ድንኳኔን አፍርሶታል” ወይም “የእኛ ጠላት ድንኳናችንን አፍርሶታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ልጆቼን ከእኔ አርቀው ወስደዋቸዋል
እዚህ ላይ ኤርምያስ የእስራኤልን መላውን ነገድ ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእኛ ጠላቶች ልጆቻችንን ከእኛ አርቀው ወስደዋቸዋል” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ አይኖሩም
ልጆቹ ከእንግዲህ ወዲህ አይኖሩም የሚለው ወላጆች ከእንግዲህ ወዲህ እንደገና ሊያዩአቸው እንደማይችሉ ለመግለጥ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ከእንግዲህ ወዲህ እንደማይኖሩ ዓይነት ነው” ወይም “እነርሱ እንደገና ፈጽሞ አይመለሱም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእንግዲህ ወዲህ ድንኳኔን የሚዘረጋ ወይም የድንኳኔን መጋረጃዎች የሚያነሣ ማንም የለም
እዚህ ላይ ኤርምያስ ከተማቸውን እንደገና ለመገንባት አንድም ልጅ እንደማይኖርላቸው ስለ እነርሱ ሲናገር ከተማቸው እንደገና ልትገነባ የሚገባት ድንኳን እንደነበረች አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከተማችንን እንደገና ለመገንባት አንድም ሰው አይኖርም” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 10:21
እረኞቹ ጅሎች ናቸውና … መንጎቻቸውም ሁሉ ተበትነዋል
እዚህ ላይ የእስራኤል መሪዎች እረኞች እንደሆኑና የእስራኤል ሕዝብ ደግሞ የበግ መንጋዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሕዝባችን እረኞች ጅሎች ናቸውና … የሕዝባችን መንጎች በሙሉ ተበትነዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መንጎቻቸውም ሁሉ ተበትነዋል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የእነርሱ ጠላቶቻቸው መንጎቹን በሙሉ በትነዋቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ተመልከቱ! እየመጣ ነው፣ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ እየመጣ ነው
እዚህ ላይ እየመጣ ያለው የጠላት ጦር ሰራዊት የመሬት መንቀጥቀጥ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። “ተመልከቱ!” የሚለው ቃል ፈሊጥ ሲሆን ቀጥሎ ለሚነገረው ነገር የአድማጮችን ትኩረት ለመሳብ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አማራጭ ትርጉ፦ “ተመልከቱ! የጠላት ጦር ሰራዊት እየመጣ ነው፣ በሚመጡበት ጊዜ እንደ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ድምጽ ይኖራቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀበሮዎች
ቀበሮዎች እጅግ በጣም ኃይለኛ የዱር ውሾች
Jeremiah 10:23
አጠቃላይ መረጃ፦
ኤርምያስ ለእስራኤል ሕዝብ ይጸልያል።
የሰው መንገድ ከራ አይደለም። የሚራመድ ሰው አንዱም ቢሆን የራሱን መንገድ አያቀናም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይህን ሲል አንድ ሰው በሕይወት ጉዞው በእርሱ ላይ በሚሆኑት በተለያዩ ነገሮች ላይ በበላይነት ራሱ ሊቆጣጠረው አይችልም ለመለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ማንም ሰው በእርሱ ላይ የሚሆነውን ነገር መቆጣጠር አይችልም፣ ማንም ሰው በሕይወቱ የሚከናወነውን ነገር ራሱ አቅጣጫ ማስያዝ አይችልም” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ቁጣህን በመንግስታት ላይ አፍስሰው
እዚህ ላይ “መንግስታት” የሚለው በውስጣቸው የሚኖሩትን ሕዝብ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “በቁጣህ መንግስታትን ቅጣቸው” ወይም “በቁጣህ የሕዝቦችን መንግስታት ቅጣቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱጉም፦
ስምህን በማይጠሩ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “አንተን የማያመልኩ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ያዕቆብን አሚጥጠው ስለበሉት፣ ፈጽመው ስለዋጡት፣ ሙሉ በሙሉ እርሱን ስላጠፉት
እነዚህ ሶስት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እስራኤልን ሙሉ በሙሉ መጥፋት አጽንዖት ጠት ኤርምያስ ይህንን ሃሳብ ሶስት ጊዜ ደጋግሞታል። ይህ የሚናገረው የእስራኤልን ሕዝብ ስላጠቁት የጠላት ጦር ሰራዊት ሲሆን ጦር ሰራዊቱ የሚበላውን እንስሳ ፈልጎ እንደሚያጠቃና እንደሚበላ ሃይለኛ ተናካሽ እንስሳ ተደርጎ ተገልጦአል። አማራጭ ትርጉም፦ “እነርሱ የእስራኤልን ሕዝብ በሃይል አጥቅተውታልና ደግሞም እነርሱን ሙሉ በሙሉ ለማጥፋ በልተዋቸዋልና” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መኖርያቸውን ወና አድርገውታል
“ቤታቸውን ወና አድርገውታል”

Chapter 11
Jeremiah 11:1
ስማ የሚል፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ይህ ነው
ይህ ፈሊጥ ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። ይህን ተመሳሳይ ሀረግ በኤርምያስ 7:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ “ይህ እግዚአብሔር ለኤርምያስ የሰጠው መልእክት ነው። ስማ አለው፣” ወይም “ይህ እግዚአብሔር ለኤርምያስ የተናገረው መልእክት ነው። ስማ፣” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች
“በኢየሩሳሌም ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች”
Jeremiah 11:3
ማንኛውም ሰው የተረገመ ነው
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እኔ ማንኛውንም ሰው እረግማለሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ከግብጽ አገር ከብረት ማቅለጫው ምድጃ
ይህን የሚናገረው እስራኤላውያንን ከብረት ማቅለጫ ምድጃ ጋር በማነጻጸር እስራኤላውያን ይኖሩ የነበረውን አስከፊ ሁኔታና ጭቆና ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የግብጽ። በግብጽ ምድር በእነርሱ የሆነው እጅግ በጣም አስከፊ ነበር፤ ይህ ሁኔታቸው እነርሱ በጣም በጋለ ምድጃ ውስጥ ይኖሩ እንደነበር ያህል ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማቅለጥ
ብረትን ወደ ፈሳሽ ለመለወጥ ማቅለጥ
ድምጼን አድምጡ
“ድምጽ” የሚለው ተናጋሪው በድምጹ ለተናገረው ነገር ምትክ ስም ነው፣ “አድምጡ” የሚለው ደግሞ “ለመታዘዝ” ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የምናገረውን ታዘዙ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 11:6
የተከበረ
ትኩረት የሚሰጠውና በጣም ጠቃሚ
የዚህን ቃል ኪዳን ቃል
“የዚህ ቃል ኪዳን ውሎች”
አድርጉት
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ታዘዙአቸው” (የሚለውን ይመልከቱ)
ድምጼን ስሙ
እዚህ ላይ “ድምጽ” የሚለው ቃል ተናጋሪው በድምጹ ለተናገረው ነገር ምትክ ስም ነው፣ “ስሙ” የሚለው ደግሞ “ለመታዘዝ” ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የተናገርሁትን ታዘዙ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እያንዳንዱ ሰው በክፉ ልቡ እልከኝነት ይመላለስ ነበር
እዚህ ላይ “መመላለስ” የሚለው አንድ ሰው ለሚኖርበት የኑር ዘይቤ ፈሊጥ ነው። “ልብ” የሚለው ደግሞ ለሰው ፍላጎትና ስሜት ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እያንዳንዱ ሰው ለመለወጥ ፈቃደኛ አልሆነም፣ ይልቁንም በራሱ ክፉ ፍላጎት ይኖር ነበር” ወይም “እያንዳንዱ ሰው ለመለወጥ ፈቃደኛ አልሆነም፣ ይልቁንም ማድረግ የሚፈልጉትን ክፉ ነገሮች ማድረግ ቀጠሉ” (ፈሊጥ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህ በእነርሱ እንዲመጡ ያዘዝኳቸውን በዚህ ቃል ኪዳን ያሉትን እርግማን ሁሉ አመጣሁባቸው
“ስለዚህ እነርሱ እንዲታዘዙት በነገርኋቸው በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ ባሉት እርግማኖች ሁሉ ቀጣኋቸው”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Jeremiah 11:9

አድማ ተገኝቷል

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “አድማ አለ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አድማ

ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሕገ ወጥ የሆነ ስራ ለመስራት ያነጣጠረ ምስጢራዊ እቅድ

የኢየሩሳሌም ነሪዎች

“በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሕዝቦች”

ወደ ቀድሞ አባቶቻቸው ሓጢአት ተመለሱ

“ተመለሱ” የሚለው ቃል ፈሊጥ ሲሆን አንድን ነገር ለመስራት እንደገና መጀመር ማት ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የቀደሙት አባቶቻቸው የፈጸሙትን ተመሳሳይ ኃጢአት እነርሱም ወደ ማድረግ ተመለሱ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ተከተሉ

“ከኋላ ተከተሉ”

የእስራኤል ቤት

“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የእስራኤልን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እስራኤል” ወይም “የእስራኤል መንግስት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት

“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የይሁዳንና የቢንያምን ልጆች የሚያካትተውን የይሁዳን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ መንግስት” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 11:11

ተመልከቱ

ይህ ቃል እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቀጥሎ የሚናገረውን ንግግር ሰዎች ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “አዳምጡ” ወይም “ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ”

የይሁዳ ከተሞችና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች

እዚህ ላይ “የይሁዳ ከተሞች” የሚለው በከተሞቹ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “በይሁዳ ከተሞችና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን በእርግጠኝነት በእነርሱ በኩል አይድኑም

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ነገር ግን አማልክቶቻቸው ፈጽሞ ሊያድኗቸው አይችሉም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እኩል

“የእነርሱን ቁጥር ያህል”

መንገዶቿ

“በኢየሩሳሌም ውስጥ ያሉ መንገዶች”

Jeremiah 11:14

ስለ እነርሱ ልትማጠን አይገባህም

“ታላቅ የሃዘን ልቅሶ ልታለቅስ አይገባህም”

ወዳጄ፣ እጅግ በጣም ብዙ ክፉ ሃሳብ የነበራት በቤቴ ውስጥ ምን አላት?

እግዚአብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመበት የይሁዳ ሕዝብ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ለወደፊት ለመገኘት ምንም ዓይነት መብት እንደሌለው አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም:- ወዳጄ፣ እጅግ በጣም ብዙ የክፋት ሃሳብ የነበራት፣ በቤቴ ውስጥ ልትገኝ አይገባትም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህች ወዳጄ፣ የነበራት

የይሁዳ ሕዝብ እጅግ እንደተወደደች እንደ አንዲት ሴት ተደርጋ ተነግራለች። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ የምወዳቸው ሕዝቤ፣ የነበራቸው” ወይም “እኔ የምወዳቸው የይሁዳ ሕዝብ፣ የነበራቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ባለፉት ዘመናት እግዚአብሔር የለመለመ የወይራ ዛፍ ብሎ ጠርቶሽ ነበር

በብሉይ ኪዳን ሰዎች ብዙ ጊዜ ከዛፎችና ከተክሎች ጋር ይነጻጸሩ ነበር። ፍሬያማና ጤናማ የነበሩት የለመለሙና ጤናማ ዛፎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም:- “ባለፉት ዘመናት እግዚአብሔር እናተ እንደለመለመ የወይራ ዛፍ እንደነበራችሁ ተናግሯል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሷ ላይ እሳት ያነድድባታል

ይህ ገለጻ የዛፉን ተለዋጭ ዘይቤ ተከትሎ የተነገረ ነው። እሳቱ የሚወክለው የሕዝቡን መጥፋት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህም የታላቅ ዓውሎ ነፋስ ድምጽ ይኖረዋል

ይህ የእስከፊውን እሳት ድምጽ ከኃይለኛ ዓውሎ ነፋስ ድምጽ ጋር ያኘጻጽረዋል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅርንጫፎቹ ይሰባበራሉ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ቅርንጫፎችሽን ይሰባብራቸዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 11:17

አንቺን የተከለሽ

ይህ እግዚአብሔር የእስራኤልንና የይሁዳን ሕዝቦች ልክ እግዚአብሔር እንደተከላቸው ዛፎች እንደሆኑ አድርጎ በመግለጽ በሚኖሩበት ስፍራ እንዳስቀመጣቸው ተናግሯል። አማራጭ ትርጉም:- “ገበሬ ዛፍ እንደሚተክል እንደዚሁ አንቺን የተከለሽ” ወይም “በእስራኤልና በይሁዳ ምድር እንድትኖሪ በዚያ ያስቀመጠሽ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንቺ ላይ ክፉ ነገር አውጀውብሻል

“በአንቺ ላይ ክፉ ነገር እንዲመጣ አውጀውብሻል”

የእስራኤል ቤት

“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የእስራኤልን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እስራኤል” ወይም “የእስራኤል መንግስት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት

“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የይሁዳንና የቢንያምን ልጆች የሚያካትተውን የይሁዳን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ መንግስት” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 11:18

እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች እንዳውቃቸው አደረገኝ፣ እኔም አወቅኋቸው

“አንተ ነገሮችን ለእኔ ገለጥህልኝ፣ እኔም አወቅኋቸው።” ይህ ጠላቶቹ እርሱን ለመግደል እያቀዱ እንደነበረ እግዚአብሔር ለኤርምያስ መግለጡን የሚያመለክት ነው።

ስራቸውን እንድመለከት አደረግኸኝ

ይህ ጠላቶቹ እርሱን ለመግደል እያቀዱ እንደነበረ እግዚአብሔር ለኤርምያስ መግለጡን የሚያመለክት ነው። እዚህ ላይ የተነገረው ኤርምያስ የእነርሱን ስራዎች እንደተመለከተ አድርጎ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የእነርሱን ክፉ እቅዶች ለእኔ ገለጠልኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔም ለመታረድ እንደሚነዳ እንደ የዋህ በግ ጠቦት ሆንሁ

ይህ ኤርምያስን ለመታረድ ከሚነዳ ከየዋህ በግ ጋር በማነጻጸር ኤርምያስ እርሱን ለመግደል ጠላቶቹ ያቀዱትን እቅድ አለማወቁን ይናገራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመታረድ ወደ እርድ ቦታ እንደሚነዳ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ጠላቶቼ ወደ እርድ ቦታ እየመሩኝ ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ዛፉን ከፍሬው ጋር እንቍረጥ

እዚህ ላይ የኤርምያስ ጠላቶች እርሱን ለመግደል ስለማሰባቸው ሲናገር ኤርምያስ እነርሱ ሊያጠፉት ያቀዱት የፍሬ ዛፍ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን ከሕያዋን ምድር እናጥፋው

“እናጥፋው” የሚለው ቃል እርሱን ማጥፋት ማለት ነው። በተጨማሪ “ሕያዋን” የሚለው ሕያዋን ሕዝብን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “በእነዚህ በሕይወት በሚኖሩ ሰዎች ምድር ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይኖር እንግደለው” ወይም “በሕይወት በሚኖሩ ሰዎች ዓለም መካከል ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይኖር እናጥፋው” ( ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ስሙም ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይታሰብ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች ከእንግዲህ ወዲህ ስሙን አያስታውሱትም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ልብንና አእምሮን

“ልብ” የሚለው ሰው ለሚሰማው ስሜትና ለሚፈልገው ነገር ምትክ ስም ነው፣ “አእምሮ” ደግሞ ሰው ለሚያስበውና ለሚወስነው ነገር ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “የሰው ስሜትና ሃሳብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በቀልህን እኔ እመለከተዋለሁ

እዚህ ላይ “በቀል” የሚለው ቃል በግስ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ ስትበቀል እኔ እመለከትሃለሁ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 11:21

ዓናቶት

ይህ ካህናት የሚኖሩበት የተለየ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕይወትህን ለሚፈልጓት

ይህ ሀረግ የሚያመለክተው አንድን ሰው ለመግደል መፈለግ ወይም መሞከር ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተን ለመግደል መፈለግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ አሉ

“ለእኔ እንዲህ አሉኝ።” ሰዎቹ ለኤርምያስ እየተናገሩ ነው።

በእጃችን ትሞታለህ

እዚህ ላይ ሰዎቹ “እጃችን” የሚለውን ቃል የተጠቀሙት እነርሱ ራሳቸው እርሱን ለመግደል ማቀዳቸውን አጽንዖት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛ ራሳችን እንገድልሃለን” (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

ኤርምያስ ከእግዚአብሔር የመጣውን በጣም አስፈላጊ መልእክት ለማስተዋወቅ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቃላት ይጠቀማል። ይህን በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት።

ተመልከቱ

ይህ ቃል እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቀጥሎ የሚናገረውን ንግግር ሰዎች ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አዳምጡ”

ኃይለኛ ወጣት ወንዶች

እነዚህ በጣም ጠንካራ በሚሆኑበት የሕይወት እድሜ የሚገኙ ናቸው

በሰይፍ ይሞታሉ

እዚህ ላይ “ሰይፍ” ጦርነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በጦርነት ውስጥ ይሞታሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

አንዳቸውም አይተርፉም

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ አንዳቸውንም አልተዋቸውም” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በሚቀጡበት ዓመት

እዚህ ላይ “ዓመት” የሚለው ቃል ፈሊጥ ሲሆን እግዚአብሔር የወሰነውን የተለየ ጊዜ የሚገልጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ በሚቀጡበት ጊዜ” ወይም “እነርሱ የሚቀጡበት ጊዜ እየመጣ ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 12

Jeremiah 12:1

አጠቃላይ መረጃ፡-

ኤርምያስ ለእግዚአብሔር እየተናገረ ነው።

ክፉዎች

ይህ ክፉ ሰዎችን ይወክላ። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎች” ወይም “ክፉ የሆኑ ሰዎች” (የስም ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ተክለሃቸዋል፣ ስርም ሰድደዋል፡ ፍሬ ማፍራትንም ቀጥለዋል

እዚህ ላይ ኤርምያስ ስለ ክፉ ሰዎች ሲናገር የፍሬ ዛፎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጦአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ እንደተከልሃቸው፣ እንዲለመልሙ እንዳደረግሃቸውና ብዙ ፍሬ እንዲያፈሩ እንዳደረግሃቸው ፍሬ እንደሚሰጥ ዛፍ ናቸው (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአፋቸው አንተ ቅርብ ነህ፥ ከልባቸው ግን ሩቅ ነህ

እዚህ ላይ “አፋቸው” የሚለው ሰው የሚናገረውን ነገር ይወክላል። “ልባቸው” የሚለው ደግሞ ሰው የሚያስበውንና ስሜቱን ይወክላል። በተጨማሪ ታማኝ መሆን ለሰው ቅርብ መሆን እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል፣ ታማኝ አለመሆን ደግሞ ከሰው በጣም ሩቅ መሆን እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ ስለ አንተ ሁልጊዜ ጥሩ ነገር ይናገራሉ ነገር ግን አንተን አይወዱህም ደግሞም አያከብሩህም” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 12:3

አጠቃላይ መረጃ፡-

ኤርምያስ ለእግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል።

ልቤ

እዚህ ላይ “ልብ” የሰውን ሃሳብና እውነተኛ ስሜት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእኔ ሃሳቦች” ወይም “የእኔ የውስጥ ስሜት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ዕርድ ቦታ እንደሚወሰዱ በጎች ውሰዳቸው

እዚህ ላይ ኤርምያስ ክፉ ሰዎችን ለመቅጣት እንዲዘጋጅ እግዚብሔርን ሲጠይቅ እነርሱ ለመታረድ እንደሚወሰዱ በጎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክፉ ሰዎችን ለመታረድ እንደሚነዱ በጎች ውሰዳቸው” ወይም “ክፉ ሰዎችን ለመቅጣት ተዘጋጅ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የዕርድ ቀን

“እነርሱ የሚጠፉበት ቀን”

በእርሷ ከሚኖሩት ሰዎች ክፋት የተነሳ ምድሪቱ የምትደርቀው እስከ መቼ ነው?

በሰዎች ክፋት ምክንያት ቅጣት ስለተላለፈባቸው ምድራቸው ደርቃለች፣ ዝናብ ደግሞ አይዘንብም።

መጠውለግ

መድረቅ

እንስሳቱና ወፎቹ ተወስደዋል

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እንስሳቱና ወፎቹ ሄደዋል” ወይም “እንስሳቱና ወፎቹ በሙሉ ሞተዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በእኛ ላይ የሚሆነውን ነገር አያይም

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፡- 1) ሕዝቡ በወደፊት ሕይወታቸው በእነርሱ ላይ ምን ነገሮች እንደሚፈጸሙ እግዚአብሔር አያውቅም እያሉ ይናገራሉ ወይም 2) እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን አያውቅም። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እኛ የምንሰራቸውን ኃጢአት የተሞሉ ነገሮችን አያይም”

Jeremiah 12:5

ከፈረሰኞች ጋር እንዴት ልትወዳደር ትችላለህ

ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የሚያመለክተው እርሱ ከፈረሶች ጋር ሊሮጥ እንደማይችል ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- ከፈረሶች ጋር ፈጽሞ ልትወዳደር አትችልም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ )

ብትወድቅ

ይህ ሰው እየሮጠ ቢወድቅ የሚያመለክት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እየሮጥህ እያለህ ብትወድቅ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰላም ምድር

ይህ በፍጥነት ለመጓዝ ቀላል የሆነውን የተመቻቸ ሜዳ የሚያመለክት ሲሆን ለመንቀሳቀስ በጣም አስቸጋሪ ከሆኑት በዮርዳኖስ ወንዝ ዙርያ ካሉት የቁጥቋጦ ጥሻዎች ጋር እያነጻጸረ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በዮርዳኖስ ዙርያ ባሉት የቁጥቋጦ ጥሻዎች መካከል በእርግጠኝነት መሮጥ አትችልም”

በዮርዳኖስ ወንዝ ዙርያ ባሉት የቁጥቋጦ ጥሻዎች እንዴት ታደርጋለህ?

ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የሚያመለክተው በዮርዳኖስ ወንዝ ዙርያ ባሉት የቁጥቋጦ ጥሻዎች መካከል ሊሮጥ እንደማይችል ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በዮርዳኖስ ወንዝ ዙርያ ባሉት የቁጥቋጦ ጥሻዎች መካከል ልትሮጥ በእርግጥ አትችልም።” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የቁጥቋጦ ጥሻዎች

ብዙ ቁጥቋጦ ወይም ትንንሽ ዛፎች በአንድነት ተጠጋግተው የበቀሉበት

ተወግዘሃል

አንድን ሰው በአደባባይ በሕዝብ ፊት መወንጀል



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Jeremiah 12:7
ቤቴን ትቼአለሁ፣ ርስቴንም ጥያለሁ። የምትወድዳትን በጠላቶችዋ እጅች አሳልፌ ሰጥቻለሁ።
እነዚህ ሶስት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። አንደኛውና ሁለተኛው ዓረፍተ ነገሮች የሶስተኛውን ሃሳብ ያጠናክራሉ። (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
ቤቴን ትቼአለሁ፣ ርስቴንም ጥያለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር "ቤቱ" እና "ርስቱ" እንደሆኑ አድርጎ የገለጸበት ተለዋጭ ዘይቤ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፦ "ለእኔ እንዲሆኑ የመረጥኋቸውን የእኔ የሆኑትን የእስራኤልን ሕዝብ ትቻቸዋለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በጠላቶችዋ እጆች
እዚህ ላይ "እጆች" የሚለው በቁጥጥር ስር ማድረግን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ "በጠላቶቿ ለመሸነፍ" ወይም "በጠላቶቿ ቁጥጥር ስር እንድትሆን" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሷ ... እርሷ ተነሳችብኝ ... ከእርሷ ጋር ... እርሷን ጠላኋት
እዚህ ላይ ሕዝቡን የአንስታይ ጾታ ተውላጠ ስም በመጠቀም እግዚአብሔር ሕዘቡን እንደ ሴት ይጠራዋል። አማራጭ ትርጉም፦ "የእነርሱ ... እነርሱ ... ራሳቸውን አዘጋጁ ... ከእነርሱ ጋር ... እነርሱን ጠላኋቸው" (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሷ በራሷ ድምጽ በእኔ ላይ ተነሳችብኝ
ይህ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደ አንበሳ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። ይህ ሕዝቡ በእግዚብሔር ላይ እንደሚያገሱ አድርጎ በመግለጽ እነርሱ በእግዚብሔር ላይ እንደተነሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ "እኔን ለመቃወም በእኔ ላይ እንደምታገሳ ሆናለች"
የተወደደች ርስቴ ሌሎች አሞሮች ሊበሏት እንደ ከበቧት እንደ ዝንጕርጕር አሞራ አልሆነችምን?
እግዚአብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡ በጠላቶቻቸው እንደተከበቡ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ "የተወደደች ርስቴ በዙርያዋ ሁሉ እንደተከበበች እንደ ዝንጉርጉር አሞራና ሌሎች የሚታደኑ ወፎች ሆናለች።" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
የተወደደች ርስቴ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር የእርሱ "የተወደዱ ርስት" እነደሆኑ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ "የእኔ ሕዝብ፣ የተወደዱ ሕዝቤ ... አይደሉምን" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሌሎች አሞሮች ሊበሏት እንደ ከበቧት እንደ ዝንጕርጕር አሞራ አልሆነችምን?
እዚህ ላይ እግዚአብሔር በአደጋ ላይ ስላለውና በጠላቶቹ ስለተከበበው ስለ ሕዝቡ ሲናገር በአዳኝ ወፎች እንደተከበበ እንደ ዝንጉርጉር አሞራ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ "እርሷ እንደ ዝንጉርጉር አሞራ ሆነች፣ ጠላቶቿም ደግሞ በሁሉም አቅጣጫ እርሷን እንደሚያጠቁ እንደ አዳኝ ወፎች ሆነዋል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዝንጕርጕር አሞራ
"ያልተለመደ መልክ ያለው እንግዳ ወፍ።" ይህ ብዙ ጊዜ በሌሎች ወፎች የሚታደንና የሚበላ ወፍን ያመለክታል።
አደን የሚድኑ አሞሮች
እንስሳትን የሚያጠቁና የሚበሉ ወፎች
ሂዱ፥ የምድር አራዊትን ሁሉ ሰብስቡ፥ ይበሏትም ዘንድ አምጡአቸው
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ለማጠናከር በትዕዛዝ መልክ ይናገራል። ይህ ትዕዛዝ የተሰጠው ለተወሰነ ግለሰብ አይደለም ስለዚህ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ "በሜዳ ያሉ የምድር አራዊት ሁሉ ይምጡና ይብሏት" (እንቶኔ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 12:10
ብዙ እረኞች የወይኑን ቦታዬን አጥፍተውታል
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ምድሩና ሕዝቡ በጠላቶች ስለ መጥፋታቸው ሲናገር ሕዝቡ እረኛው እንዳጠፋው እንደ ወይን ቦታ አድርጎ ገልጦአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ "ሕዝቤና ምድሬ ብዙ እረኞች እንዳጠፉት የወይን ቦታ ናቸው" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ብዙ እረኞች አጥፍተውታል
እዚህ ላይ "እረኞች" የሚለው ቃል በጎቻቸውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፦ "ብዙ እረኞች በጎቻቸው እንዲያጠፉት ፈቅደውላቸዋል" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉንም ረጋግጠውታል
"በእግራቸው ረጋግጠውታል"
እድል ፈንታዬ የሆነው ምድር
"እኔ የተከልሁት ቦታ" ወይም "የእኔ እርሻ"
ምድሪቱ ባድማ ሆናለች
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ምድሪቱ በሙሉ ባድማ ሆናለች" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በልቡ የሚያስባት
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "የሚንከባከባት" ወይም "ትኩረት የሚሰጣት" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 12:12
አጥፊው መጥቷል
"የሚያጠፋ ጦር ሰራዊት መጥቷል"
በምድረ በዳ ባሉት ወና ኮረብቶች
"ምንም ነገር በማይበቅልባቸው በምድረ በዳ ያሉ ስፍራዎች"
የእግዚአብሔር ሰይፍ ይበላልና
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመቅጣት ስለሚጠቀምባቸው ጦር ሰራዊቶች ሲናገር እነርሱ የእርሱ "ሰይፍ" እንደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር "ሰይፍ" ሕዝቡን የሚያጠቃና የሚበላ በጣም ትልቅ እንስሳ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጦአል። አማራጭ ትርጉም፦ ""ጦር ሰራዊቶች እናንተን ለመቅጣት የምጠቀምባቸው የእኔ ሰይፍ ናቸው" ወይም "እናንተን እንዲያጠቁ የሚያጠፋ ጦር ሰራተዊት ልኬባችኋለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ እና ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከምድር ዳር ጀምሮ እስከ ምድር ዳር ደረስ
ይህ የሚያመለክተው የሕዝቡ ርስት የሆነውን መሬት በሙሉ ነው።
እነርሱ ስንዴን ዘሩ ነገር ግን እሾህን አጨዱ
"እነርሱ ስንዴን ዘሩ ነገር ግን እሾህን አጨዱ እንጂ ሌላ ነገር ምንም አልሰበሰቡም"
እነርሱ
"የእኔ ሕዝብ"
የእሾህ ጥሻ
ዙርያው በእሾህ የተሞላ ትልቅ ተክል
ደከሙ
የበለጠ ለመስራት አለመቻል፣ አቅምና ጉልበት ማጣት
ከእግዚአብሔር ጽኑ ቍጣ የተነሳ ምንም ስላላገኛችሁ ታፍራላችሁ
"ስለዚህ እግዚአብሔር እናንተን ስለተቆጣ የሰበሰባችሁት በጣም ትንሽ ስለሆነ ታፍራላችሁ።" እዚህ ላይ "የሰበሰባችሁት" የሚለው ቃል ትልቅ መጠን ያለው ማለት አይደለም፣ ነገር ግን የሚያመለክተው እጅግ በጣም ትንሽ ነገር ነው።
Jeremiah 12:14
ርስታቸውን ለመንጠቅ
"ምድሪቱን ለመውሰድ እየሞከሩ ነው"
ለሕዝቤ ለእስራኤል ያወረስሁትን ርስት
"ለሕዝቤ ለእስራኤል እንደ ርስት የሰጠሁትን"
ተመልከቱ
ይህ ቃል እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቀጥሎ የሚናገረውን ንግግር ሰዎች ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "አዳምጡ" ወይም "ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"
እነርሱን ከምድራቸው ለመንቀል
እግዚአብሔር ሕዝቡ ምድራቸውን እንዲለቅቁ ስለማስገደዱ ሲናገር እነርሱ ከምድር እንደሚነቀላቸው ተክሎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጾአቸዋል። ይህንን ሃሳብ በኤርምያስ 1:10 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፦ የራሳቸውን ምድር እንዲለቅቁ ለማድረግ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳንም ቤት ከመካከላቸው እነቅላለሁ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር የይሁዳ ሕዝብ የሎሎችን ሕዝቦች ምድር እንዲለቅቁ እንደሚያደርጋቸው ሲናገር ከምድር እንደሚነቅላቸው ተክሎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጾአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ "እኔ የይሁዳን ቤት ምድራቸውን እንዲለቅቁ አደርጋቸዋለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነቅለዋለሁ
x
Jeremiah 12:16


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አጠቃላይ መረጃ:-
ስለ ይሁዳ ጎረቤቶች የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል
እንዲህ ይሆናል
“እንዲህ ይፈጸማል”
ሕያው እግዚአብሔርን
“እግዚአብሔር በእርግጠኝነት ሕያው እንደሆነ ሁሉ።” ሕዝቡ ይህን መግለጫ የሚጠቀሙት ቀጥለው የሚናገሩት ነገር በእርግጠኝነት እውነት እንደሆነ ለማሳየት ነው። ይህ የማይናወጥ ቃል ኪዳን የማድረግ መንገድ ነው። ከበኣል ስም ይልቅ በእግዚአብሔር ስም መማል እነርሱ ከበኣል ይልቅ እግዚአብሔርን እንደሚያመልኩ ያመለክታል። ይህን ኤርምያስ 4:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ በማይናወጥ መልኩ እምላለሁ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
በሕዝቤ መካከል ይመሠረታሉ
ይህ የሚናገረው ስለ ሕዝቡ ባለጠጋ መሆን ሲሆን የተገነባ ሕንጻ እንደሆኑ ተደርገው ተገልጸዋል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ እነርሱን በሕዝቤ መካከል እመሰርታቸዋለሁ” ወይም “እኔ እነርሱን ባለጠጋ አደርጋቸዋለሁ፣ እነርሱም በሕዝቤ መካከል ይኖራሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

መካከል
መኃል
ያንን ሕዝብ ፈጽሜ እነቅለዋለሁ። በእርግጠኝነት ይነቀላል፣ ይጠፋልም
እግዚአብሔር ሕዝቡ ምድራቸውን እንዲለቅቁ ስለማስገደዱና መንግስታቸውን ስለማጥፋቱ ሲናገር ከመሬት ነቅሎ እንደሚያወጣቸው ተክሎች እንደሆኑ አድርጎ ገልጾአቸዋል። እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ስለዚህ አንድ ላይ ሊጣመሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ ይህን ሕዝብ በእርግጠኝነት በግዞት እንዲኖር አደርጋለሁ መንግስቱንም አጠፋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
በእርግጠኝነት ይነቀላል፣ ይጠፋልም
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “እኔ በእርግጠኝነት እነቅለዋለሁ፣ አጠፋውማለሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

---

## Chapter 13

### Jeremiah 13:1

የተልባ እግር
በጣም ቀጭንና ስስ የሆነ ልብስ
መታጠቂያ
ሰዎች ከልብሳቸው በታች የሚለብሱት፣ የውስጥ ልብስ
ወገብ
ብዙ ጊዜ ቀጭንና ጠባብ የሆነው በዳሌና በደረት መካከል ያለው የሰው አካል መካከለኛው ክፍል
በመጀመርያ በውኃ ውስጥ አትንከረው
“አትጠበው ወይም እርጥበት አታስነካው
ለሁለተኛም ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ
“የእግዚአብሔር ቃል መጣ” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ከእግዚብሔር ዘንድ የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ የሚጠቀም ነው። ይህንን በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከትና እንደ አስፈላጊነቱ ማንኛውንም ለውጥ አድርግ። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ መልእክት ሰጠኝ። እንዲህም አለኝ:-“ ወይም “እግዚአብሔር ይህን ሁለተኛውን መልእክት ለእኔ ተናገረኝ:-“ (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የዓለት ንቃቃት
በውስጡ አንድ ነገር ለማስቀመጥ የሚበቃ በአለት መካከል ያለ ክፍት ቦታ ወይም በአለት ላይ ያለ ስንጥቅ

### Jeremiah 13:8

የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ
“የእግዚአብሔር ቃል መጣ” የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ የሚጠቅም ነው። ይህንን በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከትና እንደ አስፈላጊነቱ ማንኛውንም ለውጥ አድርግ። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ መልእክት ሰጠኝ። እንዲህም አለኝ:-“ ወይም “እግዚአብሔር ይህን ሁለተኛውን መልእክት ለእኔ ተናገረኝ:-“ (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳና የእስራኤል
እዚህ ላይ የይሁዳና የኢየሩሳሌም የሚለው የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም:- “የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ቃሌን ለመስማት
“እኔ የተናገርሁትን ለመታዘዝ”
በልባቸውም እልከኝነት የሚሄዱ
ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “በጣም እልከኞች የሆኑና ምኞታቸውን ብቻ የሚያደርጉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደምትጣበቅ ... ከእኔ ጋር አጣብቄአለሁ
“እንደሚለጠፍ ... ከእኔ ጋር ተለጥፈዋል” ወይም “ተጠግተው እንደሚቆዩ ... ከእኔ ጋር ተጠግተው ቆይተዋል”
ቤት ሁሉ ... ቤት ሁሉ
“ሕዝብ ሁሉ ... ሕዝብ ሁሉ”
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የእስራኤልን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እስራኤል” ወይም “የእስራኤል መንግስት” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች ምትክ ስም ነው። እዚህ ላይ የይሁዳንና የቢንያምን ልጆች የሚያካትተውን የይሁዳን መንግስት ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ መንግስት” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

### Jeremiah 13:12

ማድጋ ሁሉ በወይን ጠጅ ይሞላል ... ማድጋ ሁሉ በወይን ጠጅ ይሞላል
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ማንኛውም የወይን አቁማዳ ሁሉ በወይን ጠጅ ይሞላል ... ማንኛውም የወይን አቁማዳ ሁሉ በወይን ጠጅ ይሞላል” ወይም “ማንኛውም የወይን ማሰሮ ሁሉ በወይን ጠጅ ይሞላል ... ማንኛውም የወይን ማሰሮ ሁሉ በወይን ጠጅ ይሞላል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ተመልከቱ
ይህ ቃል እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቀጥሎ የሚናገረውን ንግግር ሰዎች ትኩረት እንዲሰጡት ለማድረግ ነው። አማራጭ ትርጉም:- “አዳምጡ” ወይም “ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ”
በዚህች ምድር የሚኖሩትን ሁሉ በስካር እሞላቸዋለሁ
“የዚህችን ምድር ነዋሪዎች በሙሉ እንዲሰክሩ አደርጋቸዋለሁ”
በዳዊት ዙፋን የሚቀመጡትን ነገሥታት
እዚህ ላይ የይሁዳ ንጉስ የሚቀመጥበት ዙፋን “የዳዊት ዙፋን” በሚለው ተወክሏል። አማራጭ ትርጉም:- “በይሁዳ ዙፋን የሚቀመጡ ነገስታት” ወይም “የይሁዳ መንግስት ነገስታት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እያንዳንዱን ሰው ከሌላው ሰው ጋር፣ አባቶችንና ልጆችን በአንድ ላይ፣ እቀጠቅጣለሁ
እዚህ ላይ “እያንዳንዱ ሰው” የሚሉት ቃላቶች ወንዶችንና ሴቶችን በሙሉ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- “ከዚያም እኔ ሕዝቡ እርስ በርሳቸው እንዲጣሉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አደርጋቸዋለሁ፣ ወላጆችና ልጆች ሳይቀር እርስ በርሳቸው ይጣላሉ" (የተባዕት ቃላት ሴቶችንም ሲያካትት የሚለውን ይመልከቱ)
አባቶችና ልጆች በአንድ ላይ
ግልጽ የሆነው መረጃ ሊቀርብ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "አባቶችንና ልጆችን በአንድ ላይ አቀጠቅጣቸዋለሁ" (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም:- "እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው" ወይም "እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው" (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
አላዝንላቸውም
"ሃዘን ፈጽሞ አይሰማኝም"
ከጥፋት አላድናቸውም
"ቅጣቱን ከእነርሱ አልመልስም።" ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "እንዲጠፉ እፈቅዳለሁ"
Jeremiah 13:15
ትዕቢት
አንድ ሰው ከእውነታው ውጭ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ስለራሱ ማሰብ
እርሱ ጨለማ ያመጣል
"እርሱ ጨለማ እንዲመጣ ያደርጋል።" እዚህ ላይ ችግርና ተስፋ መቁረጥ "ጨለማ" እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አማራጭ ትርጉም:- "እርሱ ጨለማና ተስፋ መቁረጥ ያመጣል" ወይም "ትልቅ መከራ እንዲመጣ ያደርጋል"
እርሱ እግራችሁ እንዲሰናከል ከማድረጉ በፊት
እዚህ ላይ ሰው እየተራመደ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት "በእግሩ" ተገልጾአል። አማራጭ ትርጉም:- "እንድትራመድና ስትራመድ ተሰናክለህ እንድትወድቅ ከማድረጉ በፊት" (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ብርሃን ድንግዝግዝ ሲል
ማለዳ ወይም ምሽት በከፊል ጨለማ ሲሆን፣ ጸሐይ መውጣት ስትጀምር ወይም ጸሐይ መግባት ስትጀምር
ብርሃንን ተስፋ ታደርጋላችሁ፣ ነገር ግን እርሱ ስፍራውን ወደ ድቅድቅ ጨለማ ይለውጠዋል፤ ድቅድቅ ደመናም ያደርገዋል
ይህ መልካምነትንና በረከትን እንደ "ብርሃን" መከራና ተስፋ መቁረጥን ደግሞ እንደ "ጨለማ" ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም:- "እናንተ ብርሃንና በረከት ተስፋ ታደርጋላችሁ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ጨለማንና ታላቅ ተስፋ መቁረጥ ይሰጣችኋል፣ በድቅድቅ ደመናም እንደተከበባችሁ ይሰማችኋል" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔርም መንጋ ተማርኮአልና
x
Jeremiah 13:18
አጠቃላይ መረጃ:-
እግዚአብሔር ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል። እርሱ ለይሁዳ ንጉስና ለንጉሱ እናት ምን እንደሚላቸው ለኤርምያስ እየነገረው ነው።
ንግስት እናት
የንጉስ እናት
የክብራችሁ አክሊል ከራሳችሁ ወርዶአልና
ንጉሱና ንግስቲቱ እናት እንደ ንጉስና እንደ ንግስት እናት ንጉሳዊ ስልጣናቸውን እንዲወክል አክሊል በራሳቸው ላይ ያደርጋሉ። በተጨማሪ ይህ ክስተት ገና አልተፈጸመም ነገር ግን እዚህ ላይ ግን ክስተቱ እንደከናወነ ተደርጎ ተጽፏል። ይህ በወደፊት ጊዜ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "ከእንግዲህ ወዲህ ንጉስና ንግስት እናት አትሆኑም፤ አክሊሎቻችሁ፣ ኩራታችሁና ክብራችሁ በሙሉ ይወድቃል" (ምሳሌያዊ ድርጊት እና የተፈጸመ ትንቢታዊ ንግግር የሚለውን ይመልከቱ)
በኔጌቭ ያሉ ከተሞች ይዘጋሉ፣ የሚከፍታቸውም አይኖርም
ይህ ከተሞቹ ማንም ሰው ወደ ውስጥ እንዳይገባ ወይም ከከተሞቹ እንዳይወጣ ለመከልከል በጠላቶቻቸው ይከበባሉ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- "በኔጌቭ ያሉ ከተሞች ይዘጋሉ፣ አንድም ሰው ወደ ከተሞቹ መግባት ወይም ከእነርሱ መውጣት አይችልም" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በኔጌቭ ያሉ ከተሞች ይዘጋሉ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "ጠላቶቻችሁ በላይ በኔጌቭ ያሉትን ከተሞች ይዘጓቸዋል" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ይሁዳ በሙሉ ይማረካል፣ ሙሉ በሙሉ ምርኮኛ ሆኖ ይወሰዳል
እዚህ ላይ "ይሁዳ" በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "ጠላቶች የይሁዳን ሕዝብ በሙሉ ምርኮኛ አድርገው ወደ ግዞት ይወስዷቸዋል" (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 13:20
አጠቃላይ መረጃ:-
እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ እየተናገረ ነው።
ዓይናችሁን አንሥታችሁ እነዚህን ከሰሜን የሚመጡትን ተመልከቱ
እዚህ ላይ "ተመልከቱ" የሚለው ፈሊጥ ሲሆን ትኩረት ስጡና ምን እየሆነ እንዳለ አስተውሉ ማለት ነው። በተጨማሪ "ዓይናችሁን አንሥታችሁ" የሚለው ወደ አንድ ነገር መመከልት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- "ትኩረት ስጡና እነዚህ ከሰሜን የሚመጡትን አስተውሉ" (ፈሊጥ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህን ከሰሜን የሚመጡትን
ይህ ከሰሜን የሚመጣውን የጠላት ጦር ሰራዊት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም:- "ከሰሜን የሚመጣውን የጠላት ጦር ሰራዊት" ወይም "ከሰሜን የሚዘምተውን የጠላት ጦር ሰራዊት" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ለአንቺ የሰጠሽ መንጋ፥ ለአንቺ የተዋበ መንጋ የነበረው ወዴት አለ?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠየቀው የይሁዳ ሕዝብ በጠላት ጦር ሰራዊት እንደሚማረክ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ምንም እንኳ ይህ ክስተት ገና የተከናወነ ባይሆንም ይህ ጥያቄ የተጠየቀው የይሁዳ ሕዝብ እንደተማረኩ ተደርጎ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብና እንደ ወደፊት ጊዜ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "እኔ የይሁዳን ሕዝብ እንደ ተወደዱ የበጎች መንጋ እንድትጠብቂያቸው ለአንቺ ሰጥቼሽ ነበር ነገር ግን የጠላት ጦር ሰራዊት ይማርካቸዋል።" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና የተፈጸመ ትንቢታዊ ንግግር የሚለውን ይመልከቱ)
መንጋ
ይህ የይሁዳ መሪዎች እነርሱን ሊንከባከቧቸውና ሊጠብቋቸው እንደሚገባ አጽንዖት ለመስጠት የይሁዳን ሕዝብ እንደ በጎች "መንጋ" አድርጎ ይገልጻቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወዳጆችሽ እንዲሆኑ ያስተማርሻቸውን እግዚአብሔር በራስሽ ላይ አለቆች ባደረጋቸው ጊዜ ምን ትያለሽ?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው የይሁዳ መሪዎች ይመሩት የነበረው ሕዝብ ከሚያሸንፏቸው መንግስታት ጋር ሰላም እንደሆኑ ያስቡ እንደነበር አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "የእናንተ ወዳጆች እንደሆኑ ያሰባችኋቸው ሕዝብ ያሸንፏችኋል ደግሞም በእናንተ ላይ ባለስልጣን ይሆናሉ።" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህ ነገሮች እንደምትወልድ ሴት አንቺን የሚይዙ የምጥ ጣር ጅማሬዎች አይደሉምን?
እግዚብሔር ይህን መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ የተጠቀመው መማረካቸው የሚያልፉበት መከራ ጅማሬ እንደሆነ ለሕዝቡ ለመንገር ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "እነዚህ አንቺ የምትሰቃይባቸው ነገሮች ሴት ልጅ ስትወልድ የሚገጥማት የምጥ ሕመም ጅማሬ ዓይነት ነው።" (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ )
Jeremiah 13:22
አጠቃላይ መረጃ:-
እግዚአብሔር ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል። እርሱ ለይሁዳ ንጉስና ለንጉሱ እናት ምን እንደሚላቸው ለኤርምያስ እየነገረው ነው።
የልብስሽ ዘርፍ ተገልጦአል ተረከዝሽም ተገፍፎአል
ይህ የጠላት ጦር ሰራዊት አባላት የይሁዳን ሴቶች ይደፍሯቸዋል ማለት ነው። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- "የጠላት ጦር ሰራዊት አባላት የሴቶቻችሁን ቀሚስ እየገለቡ ይደፍሯቸዋል። (ለስላሴ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በውኑ የኩሽ ሕዝብ የቆዳውን ቀለም ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?
ይህ መልስ የማይሰጥበት ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው የአንድ የማይቻልን ነገር ምሳሌ ለመግለጽ ነው። ይህ ጥያቄ እንደ ዓረፍተ ሃሳብ ሊጻፍ ይችላል። በተጨማሪ

“ይችላል” የሚለው ግልጽ ግስ በሁለተኛው ሀረግ ሊቀርብ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የኩሽ ሕዝብ የቆዳውን ቀለም ሊለውጥ አይችልም፣ ነብር ደግሞ ዝንጉርጉርነትን ይለውጥ ዘንድ አይችልም፡፡” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እና አስጨማሪ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ከሆነ ምንም እንኳ ክፋትን የለመዳችሁ ብትሆኑም እናንተ ደግሞ በጎ ለማድረግ ትችላላችሁ

ይህ ዓረፍተ ሃሳብ ምጸታዊ ነው ምክንያቱም ስለ ኩሽ ሕዝብና ስለ ነብር የተሰጠው ምሳሌ የማይቻሉ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የማይቻሉ ነገሮች የተቻሉ ከሆነ እነርሱም መልካም ማድረግ እንደሚችሉ ያብራራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ነገሮች የማይቻሉ እንደሆኑ እንደዚሁ ሁልጊዜ ክፋትን ማድረግ ለለመዳችሁ ለእናንተ መልካምን ማድረግ አይቻላችሁም” (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

የምድረ በዳ ነፋስ ብትንትኑን እንደሚያወጣው ገለባ እንዲሁ እበታትናችኋለሁ

“በነፋስ እንደሚበታተን ገለባ እንዲሁ እበታትናችኋለሁ፡፡” ገለባ በነፋስ እንደሚበታተን እንደዚሁ እግዚአብሔር ሕዝቡን በዓለም ዙርያ እንደሚበታትናቸው እየተናገረ ነው፡፡ (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 13:25

እኔ ለአንቺ የሰጠሁሽ፣ ለአንቺ ያወጅኩልሽ ድርሻሽ ይህ ነው

እነዚህ ሁለቱ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በይሁዳ ሕዝብ ላይ እግዚአብሔር እንዲሆንባቸው የወሰነው እነዚህ ነገሮች እንደሆኑ አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በእናንተ ላይ እንዲሆን ያደረግሁት ነገር ይህ ነው” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው

እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እርግጠኛ እንደሆነ ለመግለጽ በስም ስለ ራሱ ይናገራል፡፡ ይህን በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው” ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርሁት ይህ ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ራሴ የልብስሽን ዘርፍ በፊትሽ እገልጣለሁ እፍረትሽም ይታያል

ይህ እግዚአብሔር እፍረት እንዲሰማቸው ያደርጋቸዋል ማለት ነው፡፡ ይህን ሲል በየትኛውም መንገድ ይደፍራቸዋል ማለት አይደለም፡፡ ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ማንኛውም ሰው እፍረትሽን እንዲያይና እፍረት እንዲሰማሽ ለማድረግ እኔ ራሴ የልብስሽን ዘርፍ በፊትሽ እንደሚገልጥ እሆናለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ማሽካካት

ይህ ወንድ ፈረስ ሴት ፈረስን ሲፈልግ የሚሰማው ድምጽ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “መመኘት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 14

Jeremiah 14:1

አጠቃላይ መረጃ፡-

እግዚአብሔር በነቢዩ በኤርምያስ በኩል ስለ ሕዝቡ አመንዝራነት ተናግሯል፡፡

ወደ ኤርምያስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው

ይህ ፈሊጥ ሲሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣውን ልዩ መልእክት ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይህን ተመሳሳይ ሀረግ በኤርምያስ 1፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ እግዚአብሔር ለኤርምያስ የሰጠው መልእክት ነው” ወይም “ይህ እግዚአብሔር ለኤርምያስ የተናገረው መልእክት ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ ታልቅስ

እዚህ ላይ “ይሁዳ” በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የይሁዳ ሕዝብ ያልቅስ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ደጆችዋም ይፈራርሱ

እዚህ ላይ “ደጆች” የሚለው ጠላቶችን ወደ ከተማ እንዳይገቡ የሚከለክልና ሰዎች የንግድና የመንግስት ስራ የሚሰሩበት ሲሆን ለይሁዳ ከተሞች ወካይ ነው፣ የይሁዳ ከተሞች ደግሞ በውስጣቸው ለሚኖሩ ሕዝቦች ምትክ ስም ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከተሞቿ ይፈራርሱ” ወይም “በከተሞቿ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ራሳቸውን ለመከላከል የሚችሉ አይሁኑ” (ወካይ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይፈራርሱ

“ፍርስራሽ ወደመሆን ይለወጡ”

ለኢየሩሳሌም የሚያደርጉት ጩኸት ከፍ ከፍ ብሎአል

“ከፍ ብሏል” የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለኢየሩሳሌም በጸሎት በታላቅ ጩኸት እየተጣሩ ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላላቆቻቸው

“ባለጠጋ ሰዎች”

አፈሩም ተዋረዱም

እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ በአንድ ላይ ባሪያዎቹ ውሃ ለማግኘት ስላልቻሉ እንዳፈሩ አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ራሳቸውን ይከናነባሉ

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ሰዎች እፍረታቸውን ለማሳየት ራሳቸውን የሚሸፍኑበት ልብስ ይለብሱ ነበር፡፡ (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 14:4

አጠቃላይ መረጃ፡-

እግዚአብሔር በነቢዩ በኤርምያስ በኩል ስለ ድርቅ ለሕዝቡ መናገሩን ቀጥሏል፡፡

አራሾች አፈሩ ራሳቸውንም ተከናነቡ

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ሰዎች እፍረታቸውን ለማሳየት ራሳቸውን የሚሸፍኑበት ልብስ ይለብሱ ነበር፡፡ (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የሜዳ አጋዘን ግልገሎቿን በሜዳ ተወች፣ ግልገሎቿን ተወቻቸው

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ የሚበላ ነገር ባለመኖሩና ልትሰጣቸው ስላልቻለች የሜዳ አጋዘን ግልገሎቿን በሜዳ እንደ ተወች አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የሜዳ አጋዘን ግልገሎቿን በሜዳ ተወች” (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ሳር የለምና

ለአጋዘን የሚሆን የሚበላ ሳር የለም ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ለእነርሱ የሚሆን የሚበላ ሳር የለምና” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ቀበሮም በነፋስ ውስጥ አለከለኩ

ይህ እንደ ቀበሮ አለከለኩ በማለት አህዮች ማለክለካቸው ይናገራል ምክንያቱ ደግሞ ጥም ስለበረታባቸው ነው፡፡ ቀበሮ ብዙ የሚያለከልኩ በጣም አደገኛ የሆኑ የዱር ውሻዎች ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እንደ ተጠማ ቀበሮ በነፋስ ውስጥ ያለከልካሉ” (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አትክልት የለምና ዓይኖቻቸው ፈዘዙ

“የሚበሉት ሳር ስለሌለ ታወሩ”

Jeremiah 14:7

አጠቃላይ መረጃ፡-

እግዚአብሔር በነቢዩ በኤርምያስ በኩል ለሕዝቡ ስለ ድርቅ ተናግሯቸዋል፡፡

ኃጢአታችን በእኛ ላይ ይመሰክርብናል

እዚህ ላይ “ኃጢአቶች” ስለ ክፉ ስራቸው በእነርሱ ላይ የሚመሰክሩ ሰዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ኃጢአታችን ለክፉ ስራችን ማስረጃ ይሰጣሉ” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ስምህ ብለህ

እዚህ ላይ የእግዚአብሔር “ስም” መልካም ማንነቱን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ መልካም ማንነትህ ብለህ” ወይም “ማንኛውም ሰው አንተ በጣም ታላቅና ቃል ኪዳንህን የምትጠብቅ እንደሆንህ ማየት ይችል ዘንድ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ተስፋ

ይህ የእግዚአብሔር ሌላ ስም ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንተ የእስራኤል ተስፋ ነህ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በምድር እንደ እንግዳ ለምን ትሆናለህ ... ግራ እንደተጋባ ሰው ለምን ትሆናለህ

እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፡፡ ሁለቱም ጥያቄዎች እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ግድ የማይሰኝ እንደሆነና እነርሱን ለመርዳት የማይችል እንደሆነ ይጠይቃሉ፡፡ (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በምድር እንደ እንግዳ ለምን ትሆናለህ፣ እንደ ባዕድ መንገደኛ ... አንድ ሌሊት ብቻ

ይህ ጥያቄ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመርዳት ቸልተኛ የሆነበት ሁኔታ እንዳለ ሲናገር እርሱ በዚያ ስፍራ ስለሚኖሩ ሰዎች ግድ የሌለው በዚያ መንገድ የሚያልፍ እንግዳ መንገደኛ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል፡፡ (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያ የሚያልፍና አንድ ሌሊት ብቻ የሚያድር ሰው



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሁለቱም ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው ስለዚህ በአንድ ላይ ሊጣመሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ "ለአንድ ሌሊት ብቻ የሚቆይ" (ትይዩነት/ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)

ግራ እንደተጋባ ሰው፣ ወይም ያድን ዘንድ እንደማይችል ተዋጊ ስለ ምን ትሆናለህ?

ይህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመርዳት ያልቻለበት ሁኔታ እንዳለ ሲናገር እርሱ ማንንም ሰው ማዳን ያልቻለ ግራ የተጋባ ተዋጊ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾአል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ግራ መጋባት

አንድን ነገር ለመረዳት ወይም በግልጽ ለማሰብ አለመቻል

ስምህ በእኛ ላይ ተጠርቷል

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። ይህ ስሙ በእነርሱ ላይ እንደተጠራ በመናገር ሕዝቡ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሆኑ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፦ "ስምህን ተሸክመናል" ወይም "እኛ የአንተ ሕዝብ ነን" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ and ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 14:10

አጠቃላይ መረጃ፦

ኤርምያስ እግዚአብሔር ሕዝቡን ብቻቸውን እንዳይተዋቸው ይጸልያል ደግሞም እግዚአብሔርን ይጠይቃል።

መቅበዝበዝን ይወድዳሉ

"ከእኔ ርቀው ሄደው መቅበዝበዝን ይወድዳሉ።" ይህ የሚናገረው ለእግዚአብሔር ታማኞች ስላልሆኑ እርሱን ስለማይታዘዙት ሕዝብ ነው፣ ሕዝቡን እርሱ ከሚኖርበት ቦታ ርቀው በመሄድ እንደተቅበዘበዙ አድርጎ ገልጦአቸዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እግራቸውንም አልከለከሉም

እዚህ ላይ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ርቀው መሄዳቸውን አጽንዖት ለመስጠት "እግሮቻቸው" በሚለው ቃል ተገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ "ራሳቸውን አልጠበቁም" (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያስባል

ይህ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "ያስታውሳል" ወይም "አይረሳም" (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ፤ በ … ስም

"መደገፍ" ወይም "መርዳት"

ማልቀስ

በሃዘን ምክንያት በታላቅ ጩኸት ማልቀስ

ለእነርሱ ፍጻሜ አበጅላቸዋለሁ

ይህ ለስላሴ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "እነርሱ እንዲሞቱ አደርጋቸዋለሁ" (ለስላሴ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ

እዚህ ላይ ጦርነት "በሰይፍ" ተወክሏል፣ ሰይፍ በውጊያ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል የተለመደ መሳሪያ ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ "በጦርነት" ወይም "በውጊያ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 14:13

አጠቃላይ መረጃ፦

እግዚአብሔር ለኤርምያስ ለይሁዳ ሕዝብ እንዳይጸልይላቸው ነገረው።

ሰይፍ አታዩም

እዚህ ላይ "ሰይፍ" ጦርነትን ይወክላል፣ "ማየት" ደግሞ በሁኔታው ውስጥ ማለፍን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ "በአንድም ጦርነት ውስጥ አታልፉም" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እውነተኛ ደህንነት እሰጣችኋለሁ

እዚህ ላይ "ደህንነት" አንድ ሰው ለሌላ ሰው ሊሰጠው የሚችለው እቃ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ "እኔ በደህንነት እድትኖሩ እፈቅድላችኋለሁ" ወይም "እኔ በሰላም እንድትኖሩ እፈቅድላችኋለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የውሸት ትንቢት ይናገራሉ

"ውሸት" የሚለው ቃል እንደ ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ "በመዋሸት ይተነብያሉ" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በስሜ

ይህ ሀረግ በእግዚአብሔር ኃይልና ስልጣን ወይም እንደ እርሱ ወኪል መናገርን ያመለክታል። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እነርሱን አልላክኋቸውም

ይህ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲያስተላልፉ መልእክት ሰጥቶ አልላካቸውም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ "እኔ ለሌሎች ሰዎች ትንቢት እንዲናገሩ አልላክኋቸውም" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከራሳቸው አእምሮ የሚወጣ

እዚህ ላይ "አእምሮ" ሃሳብን የማሰብ ችሎታ ሳይሆን የሆነ ስፍራ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አማራጭ ትርጉም፦ "እነርሱ ራሳቸው ያሰቡትን" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 14:15

አጠቃላይ መረጃ፦

ኤርምያስ ሐሰተኛ ነቢያቶች ስለሚተነብዩት ነገሮች ለእግዚአብሔር እየተናገረ ነበር።

በስሜ

ይህ ሀረግ በእግዚአብሔር ኃይልና ስልጣን ወይም እንደ እርሱ ወኪል መናገርን ያመለክታል። ይህን በኤርምያስ 14:14 ላይ እንዴት እንደተረጎምኸው ተመልከት። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም ሰይፍ አይኖርም … ሰይፍ አይኖርም

እዚህ ላይ "ሰይፍ" ጦርነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ምንም ጦርነት አይኖርም … ጦርነት አይኖርም" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያን ጊዜ ትንቢት የተነገረላቸውም ሕዝብ ከራብና ከሰይፍ የተነሣ በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ ይበተናሉ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። ይህ ማለት የቤተሰብ አባላት በሙሉ ይሞታሉ፣ ሕዝቡም አስከሬኖቻቸውን ከመቅበር ይልቅ በመንገዶቹ ላይ ይጥላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ "በዚያን ጊዜ ትንቢት የተነገረላቸው ሕዝብ በራብና በሰይፍ ይሞታሉ፣ ሕዝቡም አስከሬኖቻቸውን በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ ይጥሉአቸዋል" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሚስቶቻቸውን፣ ወንዶች ልጆቻቸውን ወይም ሴቶች ልጆቻቸውን

ይህ የሚያብራራው "እነርሱ" በሚለው ቃል የተመለከቱትን ሰዎች ነው፣ ይህም በራብና በሰይፍ የሞቱትን ሰዎች በሙሉ ማለት ነው።

እኔ ክፋታቸውን በእነርሱ ላይ አፈስስባቸዋለሁ

እዚህ ላይ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ ክፋታቸው መጠን እንደሚቀጣቸው ሲናገር የሕዝቡ ክፋት ፈሳሽ እንደሆነና እርሱ ይህን ፈሳሽ በእነርሱ ላይ እንደሚያፈስስባቸው አድርጎ ይገልጸዋል። አማራጭ ትርጉም፦ "እነርሱ ሊቀጡ እንደሚገባቸው እኔ እቀጣቸዋለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 14:17

ቀንና ሌሊት

እዚህ ላይ ሁልጊዜ ለማለት የቀኑ ሁለት ተቃራኒ ጊዜያቶች ተሰጥተዋል። አማራጭ ትርጉም፦ "ሁልጊዜ፣ ቀንና ሌሊት በሙሉ" (ወካይ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሕዝቤ ድንግል ሴት ልጅ

እዚህ ላይ እግዚብሔር የእርሱ ሕዝብ ለእርሱ ብርቅየና የተወደደ እንደሆነ ሲናገር እነርሱ የእርሱ ድንግል ሴት ልጅ እንደሆኑ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፦ "እንደ ድንግል ሴት ልጅ የምሳሳላቸው ሕዝቤ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የማይፈወስ ቁስል

ሊፈወስ የማይችል በቆዳ ላይ የሚከሰት መቆረጥ ወይም ስብራት

በሰይፍ የሞቱ

ይህ በገቢር ቅርጽ ሊብራራ ይችላል። በተጨማሪ "ሰይፍ" እዚህ ላይ ጦርነትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ "በሰይፍ የሞቱ ሰዎች" ወይም "በጦርነት የሞቱ ሰዎች" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በረሃብ ምክንያት የመጡ በሽታዎች አሉ

እዚህ ላይ "በሽታዎች" የሚለው በረሃብ ከመሰቃየታቸው የተነሳ እነዚህ በሽታዎች ያሉባቸውን ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ከረሃብ የተነሳ የታመሙ ሰዎች አሉ" (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ይቅበዘበዛሉ

ያለ ዓላማ ወዲህና ወዲያ መንቀሳቀስ

አያውቁም

እነርሱ ምን እንደማያውቁ መግለጹ ሊጠቅም ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ "ምን እንደሚሰሩ አያውቁም" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 14:19

የፈውስ ጊዜ
ግልጽ የሆነው መረጃ ሊቀርብ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “የፈውስ ጊዜን ተስፋ አደረግን” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ሆይ፥ በአንተ ላይ ኃጢአትን ሠርተናልና ክፋታችንንና የአባቶቻችንን በደል እናውቃለን
“እግዚአብሔር ሆይ፣ እኛ የሰራነውን ኃጢአትና የአባቶቻችንን በደል እናውቃለን”
Jeremiah 14:21
አጠቃላይ መረጃ:-
ኤርምያስ ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን ቀጥሏል፡፡
ስለ ስምህ ብለህ
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር “ስም” መልካም ማንነቱን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ስለ መልካም ማንነትህ ብለህ” ወይም “ማንኛውም ሰው አንተ በጣም ታላቅና ቃል ኪዳንህን የምትጠብቅ እንደሆንህ ማየት ይችል ዘንድ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የክብርህ ዙፋን
የእግዚአብሔር “ዙፋን” በጽዮን ማለትም በኢየሩሳሌም ተወክሏል፡፡ በተጨማሪ የእርሱ “ዙፋን” እርሱ እንደ ንጉስ የሚገዛበትን ስፍራ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “የአንተ የክብር ዙፋን የሚገኝባትን ጽዮንን ታዋርዳታለህን” ወይም “አንተ እንደ ንጉስ ተቀምጠህ የምትገዛባትን ጽዮንን አታዋርዳት” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ሰማያት በራሳቸው ዝናብ ማፍሰስ ይችላሉን
“ሰማያት ዝናብ መቼ ማፍሰስ እንዳለባቸው በራሳቸው መወሰን ይችላሉን?”

---

Chapter 15
Jeremiah 15:1
አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ ወደ ያህዌ ጸለየ
በእኔ ፊት ቢቆሙ እንኳን፣ ለዚህ ህዝብ አልራራም
ይህ የሚያመለክተው ያህዌ ህዝቡን እንዲያድን እንደሚለምኑ ነው፡፡ "ይህንን ህዝብ እንዳድን በፊቴ ቢቀሙ እንኳን፣ እኔ ለእነርሱ አልራራም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእኔ ይርቁ ዘንድ ከፊቴ አስወጣቸው
ያህዌ ለነገሩ ትኩረት ለመስጠት ህዝቡን ከእርሱ የማራቅን ሀሳብ ደግሞ ይናገራል
እነዚያን የተውኳቸውን
"እንዲርቁ እኔ ያንን የወሰንኩባቸውን"
ወደ ሞት መነዳት/መሄድ አለባቸው
ይህ የተነገረው ሞት ሰዎች ሊሄዱ እንደሚችሉበት ቦታ ተደርጎ ነው፡፡ "መሞት ይገባቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለሰይፍ የተመደቡት ወደ ሰይፍ መሄድ አለባቸው
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚወክለው ጦርነትን ነው፡፡ "ለ ሰይፍ" የተመደቡ ማለት እግዚአብሔር በጦርነት ውስጥ እንዲሞቱ የወሰነባቸው ማለት ነው፡፡ "እኔ በጦርነት እንዲሞቱ የወሰንኩባቸው ለሞት ወደ ጦርነት መሄድ አለባቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለረሃብ የተመደቡት ወደ ረሃብ መሄድ አለባቸው
ይህ ማለት ያህዌ እነዚህ በረሃብ እንዲሞቱ ወስኖባቸዋል፣ እናም እነዚህ ቃላት በረሃብ መሞትን "ረሃብ" ሰዎች የሚሄዱበት ስፍራ አድርጎ ይገልጻል፡፡ "በረሃብ እንዲሞቱ የወሰንኩባቸው፣ ሄደው በረሃብ መሞት አለባቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ምርኮ መነዳት/መሄድ አለባቸው
"ወደ ምርኮኝነት መሄድ አለባቸው/መማረክ አለባቸው"
Jeremiah 15:3
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ አንዳንዶቹን ወደ ሞት፣ አንዳንዶቹን በሰይፍ እንዲሞቱ፣ አንዳንዶቹ በረሃብ እንዲሞቱ፣ ደግሞም አንዳንዶቹ ምርኮኞች እንዲሆኑ ተናገራቸው፡፡
እኔ ለአራት አይነት ወገን አደርጋቸዋለሁ
ይህ ማለት ያህዌ ህዝቡን እንዲያጠፉ አራት ወገኖችን በአንድነት ይልካል፡፡ "እነርሱን ያጠፉ ዘንድ አራት ወገኖችን እልካለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰይፍ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚያመለክተው የጠላትን ወታደሮች ነው፡፡ "የጠላት ወታደሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡
እነርሱን…አደራጋቸዋለሁ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳ ሰዎችን እንጂ በቀደመው ሀረግ የተዘረዘሩትን አራቱን ወገኖች አይደለም
ምናሴ በኢየሩሳሌም… ከፈጸመው የተነሳ
ምናሴ በኢየሩሳሌም ብዙ ክፉ ነገሮችን ያደረገ በጣም ክፉ ንጉሥ ነበር፡፡ "ምናሴ በኢየሩሳሌም… ከፈጸማቸው ክፉ ነገሮች የተነሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 15:5
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የሚያጠፏቸው አራት ወገኖችን እንደሚሰድባቸው ነገራቸው- ሰይፍን፣ ውሾችን፣ ወፎችን እና አራዊቶችን፡፡
ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ለአንቺ ማን ይራራልሻል? ማንስ ለአንቺ ያለቅስልሻል?
ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ማንም ለኢየሩሳሌም እንደማያለቅስላት ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡ ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል፡፡ "ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ማንም ለአንቺ አይራራልሽም፡፡ በመጥፋትሽ ማንም አያዝንም፡፡" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ለአንቺ
እዚህ ስፍራ "ኢየሩሳሌም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው፡፡ "በኢየሩሳሌም የምትኖሩ እናንተ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አንቺ እኔን ትተሽኛል… ከእኔ ርቀሽ ሄደሻል
እዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ በእርግጥም ህዝቡ ያህዌን ቸል ማለቱን ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእኔ ርቀዋል
"እኔን ትተዋል" ወይም "ከእኔ ርቀው ሄደዋል"
በእጄ አመታችኋለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ሀይልን ነው፡፡ "እናንተን ለመምታት ሀይሌን እጠቀማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
መንሽ
ረጅም እጀታ እና የብረት ጣቶች ያለው በአየር ላይ ወደ ላይ በማንሳት እና በመጣል ጥራጥሬን ለመለየት የሚያገለግል የገበሬ መሳሪያ
ሀዘንተኛ አደርጋቸዋለሁ
"ልጆቻቸው እንዲሞቱ አደርጋለሁ" ወይም "ጠላቶቻቸው ልጆቻቸውን እንዲገድሉ አደርጋለሁ"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Jeremiah 15:8

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ማንም ሰው ለእነርሱ ግድ እንደማይለው እና ከክፉ መንገዳቸው እስካልተመለሱ ድረስ ህዝቡን እንደሚያጠፋ ተናገራቸው።

ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች

ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች

ከባህር ዳርቻ አሸዋ ይበልጥ

"በባህር ዳርቻ ከሚገኝ አሸዋ ይበልጥ።" ይህ ንጽጽር የማይቆጠር የሚለውን አጋኖ መግለጫ ነው። "ልትቆጥሩት ከምትችሉት በላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

በእኩለ ቀን አጥፊውን በወጣት ወንዶች እናቶች ላይ እልካለሁ

ይህ ማለት እናቶቻቸው ታላቅ ሀዘን ያዝኑ ዘንድ፣ ያህዌ ወጣት ወንዶችን የሚገድሉ የጠላት ወታደሮችን ይልካል ማለት ነው። "በእኩለ ቀን ወጣት ወንዶችን ለማጥፋት እና እናቶቻቸው እንዲያለቅሱ ለማድረግ እኔ የጠላት ሰራዊት እልካለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ) በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ ይወድቃል

ይህ ፈሊጥ ነው። "በእነርሱ ላይ ይደርሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ ታፍራለች ደግሞም አንገቷን ትደፋለች

"እፍራት" እና "አንገት መድፋት" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የሀፍረቱን ደረጃ/ጥልቀት ትኩረት ይሰጣሉ። "እርሷ ፍጹም ታፍራለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ይጠፋሉ

ይፍ ፈሊጥ ነው። "ጥፋታቸው መጥኖ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ገና ቀን ሳለ ፀሐይዋ ትጠልቃለች

ይህ የሚናገረው ልጆቿ ስለሞቱባት ሀዘንተኛ ስለምትሆን ሴት ነው፤ ይህም የእርሷ ህይወት ፀሐይ ቀድማ እንደጠለቀች እና ሰዓቱ ሳይደርስ እንደ ጨለመ ሆኖ ተገልጾዋል። እዚህ ስፍራ ጨለማ ሀዘንን ይወክላል። "ከሀዘንዋ የተነሳ፣ ፀሐይ እንደጠለቀች እና ቀኗ እንደጨለመ ያህል ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተረፉትን በጠላቶቻቸው ፊት ለሰይፍ አሳልፌ እሰጣለሁ

እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚወክለው የጠላትን ወታደሮች ነው። ይህ ማለት ያህዌ የጠላት ወታደሮች የቀሩትን ልጆችዋን ሁሉ እንዲገድሉ ይፈቅዳል ማለት ነው። "የጠላት ወታደሮች ከልጆችዋ በህይወት የተረፉትን እንዲገድሉ እኔ እፈቅዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 15:10

አጠቃላይ መረጃ፡

በእነዚህ ቁጥሮች ኤርምያስ ስለ መከራው ወደ ያህዌ ይጮሃል/ይናገራል ያህዌም ይመልስለታል።

አወይ ለእኔ፣ ምነው እናቴ

ኤርምያስ እንዴት እንዳዘነ ለማጉላት የሚገልጽበት መንገድ ለእናቱ የሚናገር ይመስላል። (አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

አነጋጋሪ እና የክርክር ሰው

"አነጋጋሪ" እና "አከራካሪ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በአንድነት ኤርምያስ ምን ያህል እንደሚከራከር ትኩረት ይሰጣሉ። "የሰው ሁሉ መነጋገሪያ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ለማንም አላበደርኩም፣ ወይም ማንም አላበደረኝም

ይህ የሚያመለክተው ለሰዎች ገንዘብ ማበደርን ነው። ብዙውን ጊዜ ገንዘብ ማበደር ሰዎች እርስ በእርሳቸው እንዲጋጩ ያደርጋል። "እኔ ለማንም ገንዘብ አላበደርኩም፣ አሊያም ማንም ለእኔ ገንዘብ አላበደረኝም" ወይም "ከብድር የተነሳ ማንንም አላስቆጣሁም ወይም ገንዘብ ተበድሬ ከዚያ የተነሳ ከማንም ጋር አልተጣላሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለመልካም አልታደግሁህምን?

ለዚህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በውስጠ ታዋቂነት የሚሰጠው ምላሽ "አዎን" የሚል ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "በእርግጥ ለመልካም እታደግሃለሁ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንተ ጠላቶች

ከትንቢቱ ጋር የማይስማሙት እነዚያ የኤርምያስ ጠላቶች ናቸው

በመከራ እና በጭንቀት ጊዜ

እዚህ ስፍራ "መከራ/መቅሰፍት" እና "ጭንቀት/ስቃይ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በአንድነት ሆነው የስቃዩን መጣን ያጎላሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ብረትን የሚያደቅ አለን? በተለይም ከነሐስ ጋር የተደባለቀን የሰሜን ብረት መስበር የሚችል ሰው አለን?

በእነዚህ ጥያቄዎች ያህዌ፣ የይሁዳ ጠላቶችን ጥንካሬ ከነሐስ ጋር እንደ ተደባለቀ ብረት አድርጎ ይናገራል። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ብረትን መስበር አይችልም፣ በተለይም ከነሐስ ጋር እንደ ተደባለቀው የሰሜን ብረት ያለውን ማንም አይሰብረውም።" ወይም "ነገር ግን እንደ ብረት ወይም ነሀስ ጠንካራ ሆኑት ጠላቶቹ ይሁዳን ከሰሜን ያጠቁታል፣ ደግሞም ማንም ሊያስቆማቸው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 15:13

አጠቃላይ መረጃ፡

በእነዚህ ቁጥሮች፣ ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይናገራል።

ሀብት እና ንብረት

"ሀብት" እና "ንብረት" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የሚያመለክቱትም ሰዎች ሰዎች ዋጋ አላቸው ብለው የሚቆጥሯቸውን ነገሮች ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ዝርፊያ

አንድን ከተማ ከወረሩ በኋላ በሃይል የተወሰዱ/የተሰረቁ ነገሮች

የፈጸምካቸው ኃጢአቶች በሙሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የፈጸምካቸው በደሎች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በድንበሮችሁ ውስጥ ሁሉ

"በመላው አገርህ"

የማታውቀው ምድር

"ለአንተ ባዕድ በሆነ ምድር"

እሳት ይቀጣጠላል፣ በአንተ ላይ ቁጣዬ ይነዳል

እዚህ ስፍራ ያህዌ ቁጣውን እሳት እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። "ቁጣዬ በአንተ ላይ እንደማነደው እሳት ነው" ወይም "በቁጣዬ እመጣብሃለሁ፣ ደግሞም ቁጣዬ እንደሚነድ እሳት ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማንደድ/ማቀጣጠል

እሳት መለኮስ

Jeremiah 15:15

አጠቃላይ መረጃ፡

ኤርምያስ ለያህዌ እንዲህ አለ

አንተ ታጋሽ ነህ፣ ነገር ግን እኔን እንዲወስዱኝ/እንዲገድሉኝ አትፍቀድላቸው

ኤርምያስ ያህዌን የእርሱን ጠላቶች ኃጢአት እንዳይታገስ ይጠይቃል። "ውሰደኝ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የእርሱን ወደ ሞት መሄድ ነው። "እባክህ እነርሱን መታገስህ ደግሞም እነርሱ እኔን እንዲገድሉ ፈቃድህ አይሁን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚሉትን

ይመልከቱ)

ቃሎችህ ተገኙተዋል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መልዕክትህን አድምጫለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ በልቼዋለሁ

ኤርምያስ የያህዌን መልዕክት ስለ መስማት እና መረዳት እንደ ተመገበው ምግብ አድርጎ ይናገራል። "መልዕክትህን ተረድቼዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የልቤ ደስታ

እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የአንድን ሰው ስሜቶች እና የሚሰሙትን ስሜቶች ነው። "ከሁሉም ይልቅ ይበልጥ የምወደው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ የአንተን ስም ተሸክሜያለሁ

"እኔ አንተን እንዳገለገልኩ ሰዎች ያውቃሉ"

Jeremiah 15:17

ከ… ጋር አልተቀመጥኩም፡

ይህ ፈሊጥ ነው። "እኔ ከ… ጋር ጊዜ አላጠፋሁም" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከሀይለኛው እጅህ

እዚህ ስፍራ የያህዌ "ሀይለኛ እጆች" የሚለው የሚያመለክተው የእርሱን በኤርምያስ ላይ ቁጥጥር ማድረግ እና ተጽዕኖ ማሳረፍ ነው። "አንተ በሀይል ተጫንከኝ" ወይም "በማደርገው ላይ ተጽዕኖ/ቁጥጥር ያደረግከው አንተ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስቃዬ ስለምን በዛ፣ ቁስሌስ ለምን የማይድን ሆነ?

ኤርምያስ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ስቃዩን አጉልቶ ለመግለጽ ነው። ስለ ስቃዩ የሚናገረው አካላዊ ቁስል እንደሆነ አድርጎ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መለክ ሊጻፍ ይችላል። "ስቃዬ ቀጥሏል፣ እንደማይድን ቁስል ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ለመፈወስ አልወደደም

ይህ የኤርምያስ ቁስል መፈወስ እንዳልወደደ ሰው ተደርጎ ተገልጽዋል። ይህ አድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የማይፈወስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ ለእኔ እንደሚያታልል እና እንደሚደርቅ ውሃ ትሆንብኛለህን?

ኤርምያስ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው በያህዌ ላይ መደገፍ እንደማይችል ሆኖ የተሰማውን ስሜት ለማጉላት ነው። ይህንን የተናገረው ያህዌ እንደሚደርቅ ወራጅ እንደሆነበት አጉልቶ ለመናገር ነው። "አንተ ለእኔ ሊታመኑበት እንደማይችሉት፣ ውሃ ልቀዳ ሄጄ ደርቆ እንዳገኘሁት ወራጅ እንደሆንክብኝ ያሀል ተሰምቶኛል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 15:19

እንደ አፌ ትሆናለህ

ኤርምያስ ከያህዌ አፍ ጋር የተነጻጸረው የእርሱን መልዕክት ስለሚናገር ነው። "ለእኔ ትመሰክራለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ ራስህ

እዚህ ስፍራ "አንተ ራስህ" የሚለው ተውላጠ ስም የዋለው መልዕክቱ በተለይ ለኤርምያስ እንደ ተሰጠ ትኩረት ለማድረግ ነው። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስሞች)

ለዚህ ህዝብ እንደማይደፈር የነሐስ ግድግዳ

ያህዌ ኤርምያስን ከግድግዳ ጋር የሚያነጻጽርበት ምክንያት ሰዎች እርሱን ማሸነፍ ስለማይችሉ ነው። "እንደ ነሐስ ግርግዳ ጠንካራ አደርግሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ላይ ጦርነት ያደርጋሉ

ይህ የሚገልጸው ሰዎች ከኤርምያስ ጋር እርሱ አንድ ሰራዊት የሆነ ያህል ጦርነት እንደሚያውጁበት ነው። "በአንተ ላይ ይነሳሉ" ወይም "ይቃወሙሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማዳን እና መታደግ

"ማዳን" እና "መታደግ" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን ያጎላሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተን ከ…ይታደግሃል… ደግሞም ከ…ይቤዥሃል

እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ደግሞም በአንድነት ሆነው እግዚአብሔር የሚያደርገውን ጥበቃ ለማጉላት ውለዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የክፉዎች እጅ…የጨካኝ አምባገነኖች እጅ

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የዋለው ቁጥጥርን ለመግለጽ ነው። "የክፉዎች ጭካኔ/ቁጥጥር… የጨካኝ አምባገነኖች ቁጥጥር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጨካኝ

ይህ ክፉ ሰዎችን ያመለክታል። "ክፉ ሰዎች" ወይም "ክፉ የሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ጨካኝ አምባገነኖች

ለሚገዛቸው ሰዎች አንዳች ወዳጅነት የማያሳይ ፍጹም መታዘዝን ብቻ የሚጠይቅ መሪ

---

Chapter 16

Jeremiah 16:1

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ "…አታድርግ

ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ የመጣ ልዩ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ መልዕክት ሰጠኝ። እንዲህም አለኝ፣ "…አታድርግ" ወይም "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረኝ/ያህዌ እንዲህ አለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ በበሽታ ይሞታሉ

"በሚገድል ክፉ በሽታ ይሞታሉ"

አይለቀስላቸውም ወይም አይቀበሩም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ሰው አያለቅስላቸውም ወይም ማንም አይቀብራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ላይ እንደ ፍግ ይሆናሉ

በምድሪቱ የተወለዱ ወንዶች እና ሴቶች ልጆች በምድር ላይ ከሚገኝ ፍግ ጋር የተነጻጸሩት አስጸያፊ እንደሚሆኑ እና ማንም እንደማይቀብራቸው ትኩረት ለመስጠት ነው። ተመሳሳዩ ሀረግ በኤርምያስ 8፡2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ እና በረሃብ መጨረሻቸው ይሆናል

"መጨረሻቸው ይሆናል" የሚለው ሀረግ ይሞታሉ የሚለው ቀለል ባለ መንገድ/በጨዋ አነጋገር የተገለጸበት ነው። "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚገልጸው በሰይፍ የሚዋጋን ሰራዊት ወታደሮች ነው። ሀረጉ በጦርነት ውስጥ መሞትን ይገልጻል። "በጦርነት ውስጥ ወይም በረሃብ ይሞታሉ" (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 16:5

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ "…አታድርግ

ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ የመጣ ልዩ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ መልዕክት ሰጠኝ። እንዲህም አለኝ፣ "…አታድርግ" ወይም "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረኝ/ያህዌ እንዲህ አለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልቅሶ ባለበት ስፍራ

"ልቅሶ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች በሚያለቅሱበት

ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰላሜን ከዚህ ህዝብ ወስጃለሁ... ደግሞም የጸናውን ፍቅር እና ምህረት
ያህዌ ለህዝቡ ከእንግዲህ ሰላም፣ የጸና ፍቅር እና ምህረት እንዲሌለው የገለጸው እነዚህ ከእነርሱ እንደተወሰዱ ነገሮች አድርጎ ነው። "ከእንግዲህ ለእነርሱ ሰላም አላደርግላቸውም... ወይም የጸና ፍቅር እና ምህረት አላደርግላቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ታላላቆችም ታናናሾችም ሁሉም...
ይህ የሚያመለክተው ሁሉንም አይነት ሰው ሲሆን፣ የሰዎቹ ደረጃ የተገለጸው በመጠን ነው። "ታላላቆችም ታናናሾችም" ወይም "ከደረጃቸው ባሻገር ብዙ ሰዎች፣..." (ሜሪዝም/ከዳር እስከ ዳር/ከጽንፍ እስከ ጽንፍ)
አይቀበሩም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም አይቀብራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ማንም... ሰውነቱን የሚቧጥጥላቸው ወይም ፀጉሩን የሚላጭላቸው አይኖርም
ራስን መቧጠጥ/መቁረጥ እና የራስ ፀጉርን መላጨት ከፍተኛ ሀዘንን የመግለጫ ምልክታዊ ድርጊቶች ነበሩ፤ በተለይም በጣም የሚወዱት ሰው ሲሞት ይህ ይደረግ ነበር። (ምልክታዊ/ትዕምርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 16:7

በደረሰባቸው የሞት ሀዘን ማንም አንዳች ምግብ ለሀዘኑ እነርሱን ለማጽናናት አያካፍላቸው...ማንም ለአባቱ ወይም ለእናቱ የማጽናኛ ዋንጫ/ጽዋ አይሰጥ
እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እግዚአብሔር በመሰረቱ ተመሳሳይ የሆኑትን ነገሮች ሁለቴ የተናገረው ትኩረት ለመስጠት ነው። ምግብ ወይም መይን ጠጅ ዘመድ ወደሞተባቸው ሰዎች መውሰድ የተለመደ ነበር። ያህዌ ከሰዎቹ ማጽናኛዎችን ሁሉ ያስወገደው በኃጢአታቸው ምክንያት ነበር። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማንም የማጽናኛ ዋንጫ/ጽዋ አይስጣቸው
እዚህ ስፍራ "ዋንጫ/ጽዋ" የሚለው ቃል የሚወክለው ዋንጫው/ሲኒ በውስጡ የያዘውን መጠጥ ነው። "ማንም የመጽናኛ መጠጥ አይስጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ድግስ ቤት
"ሰዎች ግብዣ የሚያደርጉበት ቤት"
የጭፍሮች አለቃ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት ከእግዚአብሔር ዘንድ መልዕክትን ሲያመጣ ለማስተዋወቅ ይጠቀምባቸዋል። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እነሆ/እዩ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ቀጥሎ ለምናገረው ትኩረት ስጡ"
የእናንተ ዐይኖች እየተመለከቱ
እዚህ ስፍራ "የእናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም የእስራኤልን ሰዎች ነው። የፈሊጣዊ አነጋገሩ ትርጉም ያህዌ ይህን የሚያደርገው እነርሱ ማየት በሚችሉበት ስፍራ ነው። "በእናንተ ፊት ለፊት" ወይም "እናንተ ማየት በምትችሉበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም መልኮች እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
በእናንተ ቀናት/ዘመን
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም በእነርሱ የህይወት ዘመን ማለት ነው። "በእናንተ የህይወት ዘመን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሀሴት እና የደስታ ድምጽ ፣ የሙሽራውና የሙሽራቱ ድምጽ
ይህ በኤርምያስ 7:34 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Jeremiah 16:10

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
አመለካችኋቸው ወድቃችሁ ሰገዳችሁላቸው
"ወድቃችሁ ሰገዳችሁ" የሚሉት ቃላት "አመለካችሁ" ከሚለው ጋር በመሰረቱ ተመሳሳይ ነው፤ ደግሞም ሰዎች በአምልኮ ጊዜ ሚኖራቸውን የሰውነት አቋም ይገልጻል። እግዚአብሔር በመሰረቱ ተመሳሳይ የሆነውን ነገር ሁለት ጊዜ የተናገረው ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 16:12

አባቶቻችሁ፣ እንዳደረጉት፣ እያንዳንዱ ሰው
"አባቶቻችሁ። እነዚህን ሰዎች ተመልከቱ እናንተም እያንዳንዱ ሰው... ትመልከታላችሁ/ይደርስባችኋል"
እንደ እልከኛ ልቡ ፈቃድ አደረገ
ያህዌ የአንድን ሰው ድርጊት ያ ሰው በጎዳና እንደሚሄድ አድረጎ ይናገራል። እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው ቃል የሚወክለው ሀሳብን ወይም ፍቃድን ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 11:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ማድረግ የሚፈልገውን ክፉ ነገር እንደ እልከኛ ልቡ ፈቃድ አደረገ" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
እኔን የሚሰማ
"አድርግ የምለውን የሚያደርግ"
ከዚህች ምድር አስወጣችኋለሁ
ያህዌ የሚናገረው ህዝቡን ከምድሪቱ እንደሚወረውራቸው ባለ መንገድ በሀይል ስለማስወጣት ነው። "ይህን ምድር ለቃችሁ እንድትወጡ እና እንድትሄዱ አስገድዳችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በቀን እና በሌሊት
የ"ቀን"እና "ሌሊት" የሁለቱም መጠቀስ የሚገልጸው ሁልጊዜ የሚለውን ነው። "ሁሌም" ወይም "ሳያቋርጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜሪዝም/ከዳር እስከ ዳር/ከጽንፍ እስከ ጽንፍ)

Jeremiah 16:14

እነሆ
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ንቁ ያነቃናል።
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ መነገር በሚያበቃበት ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ከእንግዲህ እንዲህ በማይሉበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ህያው ያህዌን/ በህያው ያህዌ ህይወት
"የያህዌ ህያውነት እርግጠኛ የሆነውን ያህል።" ሰዎችን ይህንን አገላለጽ የሚጠቀሙት ቀጥሎ የሚናገሩት ነገር በእርግጥ እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው። ይህ ጠንካራ/የከበረ ቃል ኪዳን የሚገባበት መንገድ ነው። ይህ በኤርምያስ 4:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሕያው እግዚአብሔርን/በክብር እምላለሁ/" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 16:16

ብዙ አሳ አጥማጆችን እልካለሁ... እነርሱም ህዝቡን ያጠምዳሉ
ያህዌ ህዝቡን የሚያጠቃውን እና የሚገድለውን የጠላትን ሰራዊት አሳ እንደሚይዙ አሳ አጥማጆች አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይመልከቱ)
በመሃላቸው ሆነው እንዲያድኗቸው ብዙ አዳኞችን እልካለሁ
ያህዌ ህዝቡን የሚያጠቃውን እና የሚገድለውን የጠላትን ሰራዊት እንስሳትን እንደሚየድኑ አዳኞች አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዐይኖቼ በመንገዶቻቸው ሁሉ ላይ ነው
እዚህ ስፍራ "ዐይን" የሚለው ቃል የሚወክለው የሚያደርጉትን ሁሉ የሚመለከተውን ያህዌን ነው። "የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ እመለከታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ከእኔ ፊት መሰወር አይችሉም
"እነርሱ" የሚለው ቃል ሰዎቹን ወይም ድርጊታቸውን ሊያመለክት ይችላል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እነርሱ ከእኔ ሊሰወሩ/ሊደበቁ አይችሉም" ወይም "መንገዳቸውን ከእኔ ሊደብቁ አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፋታቸው ከዐይኖቼ ፊት ሊሸሸጉ አይችሉም
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው የሚወክለው ሁሉን የሚመለከተውን ያህዌን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከእኔ ሊደበቁ አይችሉም" ወይም "መንገዳቸውን ከእኔ ሊደብቁ አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሬን አርክሰዋል
ያህዌ ህዝቡ ምድሪቱን እንዳረከሱ አድርጎ፣ በፊት ተቀባይነት ማጣቷን ይናገራል። "የእነርሱ እርክሰት" የሚሉት ቃላት በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ምድሬን ስላረከሷት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
ለእነርሱ ስሜቶች ርስቴን በአስጸያፊ ጣኦቶቻቸው ስለሞሏት
"መሙላት" የሚለው ፈሊጥ በምድሪቱ ላይ ብዙ ጣኦታትን አደረጉ ማለት ነው። "ለእነርሱ ስሜቶች" የሚሉት ቃላት በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "የእኔን ርስት በአስጸያፊ ጣኦቶቻቸው በመሙላታቸው ምክንያት" ወይም "አስጸያፊ ጣኦቶቻቸው ርስቴ ባለበት ስፍራ ሁሉ በመደረጋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
የእኔ ርስት
ያህዌ ምድሪቱ እንደ ቋሚ ሀብቱ አድርጎ የቆጠራት የእርሱ ርስት እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። "የእኔ ርስት የሆነችው ምድር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 16:19
ያህዌ፣ አንተ ጠንካራ ምሽጌ ነህ
እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለያህዌ መናገር ይጀምራል።
ምሽጌ እና መሸሸጊያዬ፣ የደህንነቴ ስፍራ
ኤርምያስ ያህዌ ለእርሱ ጠላቶቹ ሊያጠቁት የማይችሉበት ስፍራ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አንዱን ሃሰብ ሶስት ጊዜ ይደጋግማል። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)
ህዝቦች ወደ አንተ ይሄዳሉ
እዚህ ስፍራ "ህዝቦች" የሚለው ቃል የሚወክለው የተለያዩ አገራት ሰዎችን ነው። "የተለያዩ አገራት ሰዎች ወደ አንተ ይሄዳሉ" ወይም "የአገራት ሰዎች ወደ አንተ ይመጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ሄደ እና መጣ የሚሉት ቃላት አገባብ የሚሉትን ይመልከቱ)
የምድር ዳርቻ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን በምድር ላይ ሩቅ የሆነው ስፍራ ማለት ነው። ሁለቱን ጫፎች በማመሳከር፣ በመሃል የሚገኙትን ስፍራዎች ሁሉ ያመለክታል። "በምድር ሩቅ የሆነው ስፍራ" ወይም "በምድር በሁሉም ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና (ሜሪዝም/ከዳር እስከ ዳር/ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የሚሉትን ይመልከቱ))
አባቶቻችን የሚያታልሉትን ሀሰተኞች ወረሱ
እዚህ ስፍራ "ማታለል" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሀሰተኛ ጣዖቶች ነው። "አባቶቻችን አንዳች የማይጠቅሙ ሀሰተኛ ጣዖቶችን ወረሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ሄደ እና መጣ የሚሉት ቃላት አገባብ የሚሉትን ይመልከቱ)
እነርሱ ባዶናቸው፤ ከእነርሱ አንዳች ጥቅም አይገኝም
እዚህ ስፍራ "የእነርሱ" እና "ከእነርሱ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት አባቶች ያምኑባቸውን ጣዖቶች ነው። ሁለቱ ሀረጋት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፤ ሁለተኛው እንዴት "ከንቱ እንደሆኑ ያብራራል" (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰዎች ለራሳቸው አማልክትን ያበጃሉን? ነገር ግን እነርሱ አማልክት አይደሉም
ሰዎች ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቁት ሰዎች ለራሳቸው አማልክት ሊያበጁ እንደማይችሉ ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች ለራሳቸው አማልክትን ሊያበጁ አይችሉም። ያበጇቸው ነገሮች አማልክት አይደሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህ ያያሉ
"ስለዚህ፣ በእርግጥ።" እዚህ ስፍራ ያህዌ መናገር ይጀምራል። "ያያሉ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው ትኩረት ይሰጣል
እነርሱ እንዲያውቁ አደርጋለሁ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአገሩን ሰዎች ነው። ያህዌ ይህንን ሀረግ የሚደግመው ትኩረት ለመስጠት ነው።
የእኔ እጅ እና የእኔ ሀይል
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሀይልን እና ስልጣንን ነው። ሁለቱ ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ለያህዌ ታላቅ ሀይል ትኩረት ይሰጣሉ። "ታላቁ ሀይሌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)
ስሜ ያህዌ እንደሆነ ያውቃሉ
እዚህ ስፍራ " ስም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የያህዌን ማንነት ነው። "እኔ እውነተኛ አምላክ የሆንኩ ያህዌ እንደሆንኩ ያውቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 17
Jeremiah 17:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ ትንቢት የሚጽፈው በግጥም መልክ ነው። የዕብራውያን ስነግጥም የተለያዩ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤዎችን ይጠቀማል። (ስነግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
የይሁዳ ኃጢአት... በመሰዊያዎቻችሁ ቀንዶች ላይ ተጽፏል
ያህዌ ስለ ይሁዳ ኃጢአት እጅግ ታላቅ መሆን አንድ ሰው ኃጢአታቸውን በቋሚነት እንደቀረጸው እና እነርሱም ሊያቆሙት እንደማይችሉ አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ኃጢአት ተጽፏል
እዚህ ስፍራ "ይሁዳ" የሚለው ቃል የሚወክለው የይሁዳን ሰዎች ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የይሁዳ ኃጢአት ተጽፏል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ተቀርጸዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ይህ ተቀርጸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በልባቸው ጽላት ላይ ተቀርጸዋል
የህዝቡ ኃጢአተኝነት ልምዶች የተገለጸው በየራሳቸው ልቦች ላይ እንደተቀረጸ ተደርጎ ነው። "ልቦች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተና፡ ማለትም ሀሳብ፣ ስሜት እና ድርጊቶች ነው። "በማንነታቸው ላይ ተቀርጸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በመሰዊያዎቻችሁ ቀንዶች ላይ
"ቀንዶች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በመሰዊያዎች ጠርዝ የሚገኙትን ጉጦች ነው።
Jeremiah 17:3
ሀብታችሁ እና ንብረታችሁ
"ሀብት" እና "ንብረት" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤

የሚያመለክቱትም ዋጋ አላቸው ብለው የሚቆጥሯቸውን ነገሮች ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
ዝርፊያ
ይህ የሚያመለክተው ሰዎች የሰረቋቸውን ወይም በሀይል የወሰዷቸውን ነገሮች ነው።
ለእናንተ የሰጠኋችሁን ርስት ታጣላችሁ
ያህዌ ምድሪቱን በቋሚነት ለይሁዳ እንደሰጠው ርስት አድርጎ ይናገራል። "ርስት አድርጌ የሰጠኋችሁን ርስት ታጣላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በቁጣዬ ላይ ለዘለዓለም የሚነድ እሳት ለኮሳችሁ
ያህዌ የቁጣውን ታላቅነት እርሱ የተቆጣቸውን እንደሚያቃጥል እሳት አድርጎ ይናገራል። "ቁጣዬ ለዘለዓለም የሚነድ እሳት እስኪመስል ደረስ እጅግ አስቆጥታችሁኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 17:5
በሰው ልጅ ላይ የሚታመን የተረገመ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ በሰው ልጅ ላይ የሚታመንን ማንኛውንም ሰው ረግመዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ስጋን ሀይሉ ያደርጋል
እዚህ ስፍራ "ስጋ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰው ልጅን/ሰዎችን ነው። "እርሱ ለጥንካሬው በሰው ላይ ይታመናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ልቡን ከያህዌ ዞር ያደርጋል
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሀሳብን እና ስሜትን ነው። "መሰጠቱን/ጥሞናውን ከያህዌ ያርቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ትንሽ ቁጥቋጦ
ከያህዌ ይልቅ በሰው የሚታመን ሰው ለም ባልሆነ መሬት ላይ ለማደግ እንደሚታገል ተክል ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰው የማይኖርበት፣ ምድረ በዳ እና ጠፍ ምድር
"ሰው የማይኖርበት ጠፍ ምድር" የሚለው "ምድረበዳ" ከሚለው ጋር በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አለው። "ጠፍ ምድረ በዳ ማንም የማይኖርበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 17:7
በውሃ ዳር እንደ ተተከለ ዛፍ ይሆናል
በወንዝ ዳርቻ እንደ ተተከለዛፍ በያህዌ የሚታመን ሰው ሁልጊዜ ይበለጽጋል። ዝናብ በማይኖር ጊዜ አይጎዳም። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ በውሃ ዳር እንደተተከለ ዛፍ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ድርቅ ሲሆን አይፈራም… በድርቅ አመት አይሰጋም
ያህዌ ከወንዝ ውሃ ስለሚያገኝና በሙቀት እና ድርቅ ስለማይጎዳ ዛፍ፣ ከእነዚህ ነገሮች የተነሳም ዛፉ እንደማይፈራ አድርጎ ይናገራል። "ድርቅ ሲሆን አይጎዳም… በድርቅ አመትም ጉዳት አይደርስበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 17:9
ልብ ይበልጥ አስመሳይ ነው
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰዎችን አይምሮ እና ሀሳብ ነው። "የሰው ልብ ይበልጥ አስመሳይ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ማን ሊረዳው ይችላል
x
Jeremiah 17:12
የቤተ መቅደሳችን ስፍራ የክብር ዙፋን ነው
ኤርምያስ ቤተ መቅደሱ "የክብር ዙፋን" እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል፤ ምክንያቱም ያህዌ የሚኖረው እና የሚገዛው በዚያ ስለሆነ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የቤተ መቅደሳችን ስፍራ
ይህ የሚያመለክተው በእየሩሳሌም የጽዮንን ተራራ ነው
አንተን የተዉ/ቸል ያሉ ሁሉ
እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያህዌን ነው።
በምድሪቱ የሚኖሩ ከአንተ ፊታቸውን የመለሱ ሁሉ በምድር ይጻፋሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ከአንተ ፊታቸውን ያዞሩትን ሁሉ በአፈር ላይ ትጽፋቸዋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በምድር ይጻፋሉ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ አንድ ሰው ስሙን በአፈር ላይ ቢጽፍ እነዚያ ስሞች በፍጥነት እንደሚጠፉ ሁሉ ያህዌ እንዚህ ሰዎች ሞተው እንደሚረሱ የገለጸበት ዘይቤ ነው። "አንድ ሰው በአፈር ላይ እንደ ጻፋቸው ስሞች ይጠፋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) "ምድር" የሚለው ቃል ሙታን ለሚገኙበት ስፍራ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ሀረጉ ያህዌ አንድ ሰው ሙታንን በመዝገብ እንደጻፈ አድርጎ የተናገረበት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "በሙታን ስፍራ ያሉትን ይገናኛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
ያህዌ፣ የህይወት ውሃ ምንጭ
ኤርምያስ ያህዌ የህይወት መገኛ መሆኑን የሚገልጸው የህይወት ውሃ መንጭ እንደሆነ አድርጎ ነው። "ያህዌ፣ እንደ ህይወት ውሃ ምንጭ የሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የህይወት ውሃ ምንጭ
ኤርምያስ ንጹህ እና ወራጅ ውሃን የህይወት ውሃ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። "ንጹህ ወራጅ የውሃ ምንጭ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ እፈወሳለሁ… እኔ እድናለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ በእርግጥ ትፈውሰኛለህ… አንተ በእርግጥ ታድነኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራተጊ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ የውዳሴዬ ዝማሬ ነህ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እኔ የማወድስህ አንተ ነህ" ወይም 2) "በውዳሴ ለመዘመሬ ምክንያቱ አንተ ነህ"
Jeremiah 17:15
ተመልከት
"እይ" ወይም "አድምጥ" ወይም "ልነግርህ ለተዘጋጀሁት ትኩረት ስጥ"
እነርሱ እኔን እንዲህ ይሉኛል
እዚህ ስፍራ "እኔ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኤርምያስን ሲሆን "እነርሱ" የሚለው ጠላቶቹን ያመለክታል።
የያህዌ ቃል ወዴት አለ?
ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ ያነሱት/የተጠቀሙበት በኤርምያስ ላይ ለመሳለቅ ነው፤ ምክንያቱም የተናገራቸው ነገሮች ገና አልተፈጸሙም ነበር። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክም ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌ የነገረህ ነገሮች መች ተፈጸሙ" ወይም "ያህዌ ይሆናሉ ብሎ የነገረህ ነገሮች አልተፈጸሙም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ይህ ይምጣ
"ያህዌ የተናገረው ይሁን"
አንተን በመከተል እረኛ ከመሆን አልሸሸም
ኤርምያስ ህዝቡን መምራትን እና መሸከምን የሚገልጸው ራሱን በጎችን እንደሚሸከም እረኛ አድርጎ ነው። ያንን ስራ መተውን የሚገልጸው ከስራው እንደመሸሽ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ አልመኘውም
"እኔ አልፈልገውም"
ከከንፈሮቼ የወጡ ትዕዛዛት/ቃላት
እዚህ ስፍራ "ከንፈሮች" የሚለው ቃል የሚወክለው ተናገሪውን ኤርምያስን ነው። "ትዕዛዝ/ቃል" የሚለው በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "የተናገርኩት አዋጅ" ወይም "እኔ ያወጅኳቸው/የተናገርኳቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
እነርሱ ተደርገዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ አደረግኳቸው" በሚለው ውስጥ

እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 17:17
አንተ የእኔ መሸሸጊያ ነህ
ኤርምያስ ያህዌን ጠላቶቹ እርሱን ሊያጠቁት የማይችሉበት ስፍራ አድርጎ ይገልጸዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በመከራ ቀን
"በመከራ ጊዜያት"
አሳዳጆቼ ይፈሩ፣ እኔ እንዳፍር ግን አታድርግ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በአሳዳጆቼ ላይ እፍረት አምጣባቸው፣ በእኔ ላይ ግን ሀፍረት አታድርስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ይጨነቁ፣ እኔን ግን እንድጨነቅ አታድርግ
ይህ ሀረግ በመሰረቱ ከቀደመው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው፤ ደግሞም በኤርምያስ ጸሎት ላይ ትኩረት ይጨምራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እጅግ አስፈራቸው፣ እኔን ግን እንድፈራ አታድርገኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
በእጥፍ መጠን ጥፋት ሰባብራቸው
ኤርምያስ ያህዌ ጠላቶቹን እንደ ዕቃ እንዲሰባብራቸው ይናገራል። "እጥፍ መጠን" የሚለው ፈሊጥ ሁለቴ ያህል ማድረግ የሚል ትርጉም አለው። "በሙሉ ጥፋት ሰባብራቸው" ወይም "ሁለቴ ያህል አጥፋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ፈሊጥ የሚሉትን ይመልከቱ)
Jeremiah 17:19
ከዚያ በእየሩሳሌም ሌሎች በሮች ሁሉ
ግሱ ከቀደመው ሀረግ ሊገኝ ይችላል። "ከዚያ ወደ ሌሎች የእየሩሳሌም በሮች ሄደህ ቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢሊፕሲስ/የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 17:21
ለህይወታችሁ ስትሉ
"ህይወታችሁን ለመጠበቅ/ለማዳን"
እነርሱ አያደምጡም ወይም ትኩረት አይሰጡም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ሰዎቹ መስማት ያለመፍቀዳቸውን ትኩረት ይሰጣሉ። "መስማት አልፈቀዱም" ወይም "መታዘዝ አልፈቀዱም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
አንገታቸውን አደነደኑ
ኤርምያስ የሰዎቹን ግትር መሆን አንገታቸውን እንደ ገተሩ እና የማይንቀሳቀስ እንዳደረጉ አድርጎ ይገልጻል። "ግትር ሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 17:24
ይህ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
በዳዊት ዙፋን ላይ የተቀመጡ እነርሱ
እዚህ ስፍራ የይሁዳ ንጉሥ የተቀመጠበት ዙፋን የሚለው የቀረበው "የዳዊት ዙፋን" በሚል ነው። ይህ በኤርምያስ 13፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በይሁዳ ዙፋን ላይ የተቀመጡ" ወይም "የይሁዳ አገር ነገሥታት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከተማይቱ ለዘለዓለም የሰዎች መኖሪያ ትሆናለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ለዘለዓለም በዚህች ከተማ ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 17:26
በበሮችዋ ላይ እሳት አነዳለሁ
"የእየሩሳሌም በሮችን በእሳት አነዳለሁ"
ይህም ሊጠፋ አይችልም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ሊያጠፉት አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 18
Jeremiah 18:1
ከያህዌ ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል የመጣ ቃል፣ "ተነስ"
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ልዩ መልዕክት ለማምጣት ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 7፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ የሰጠው መልዕክት ይህ ነው። እንዲህ አለ፣ 'ተነስ' ወይም "ያህዌ ለኤርምያስ የተናገረው መልዕክት ይህ ነው፡ 'ተነስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሸክላ ሰሪው ቤት
"የሸክላ ሰሪው የስራ ስፍራ።" ሸክላ ሰሪ ከጭቃ ሸክላ የሚሰራ ሰው ነው።
እነሆ!
"እነሆ" የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሰው እንደሚገባ ያነቃናል። የእናንተ ቋንቋ ለዚህ የራሱ የሆነ አገላለጽ ሊኖረው ይችላል።
በሸክላ ሰሪው መንኮራኩር
የሸክላ ሰሪው መንኮራኩር የሚሽከረከር ትንሽ ጠረጴዛ ነው።
የሚሰራው ጭቃ በእጁ ላይ ተበላሸ
"ተበላሸ" የሚለው ቃል የሚሰራው ቁስ ብልሽት አለበት ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በእጁ ላይ የነበረው የሚያበጀመው የሸክላ እቃ ጥሩ አልነበረም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ያበጀው የነበረው
"ይሰራው የነበረው" ወይም "ቅርጽ ይሰጠው የነበረው"
ስለዚህም ሀሳቡን ቀየረ
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም ሌላ ነገር ለመስራት መወሰን ማለት ነው። "ስለዚህ የተለየ ምርጫ አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ዐይኖች ለማድረግ መልካም ሆኖ የታየውን
እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው የሚወክለው ማየትን ሲሆን ማየት ደግሞ የሚገልጸው አስተያየትን/ሃሳብን ነው። "ለማድረግ መልካም ሆኖ እንዳሰበው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 18:5
ከያህዌ ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል የመጣ ቃል፣ "መናገር አለብህ"
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ልዩ መልዕክት ለማምጣት ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 1፡4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ መልዕክት ሰጠኝ። እንዲህ አለ፣ 'መናገር አለብህ' ወይም "ያህዌ ይህን መልዕክት ለእኔ ተናገረ፡ 'መናገር አለብህ' በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቤት ሆይ እኔ በእናንተ ላይ እንደዚህ ሸክላ ሰሪ ማድረግ አልችልምን?
በዚህ ጥያቄ ያህዌ በእስራኤል ላይ ደስ የሚያሰኘውን ለማድረግ ስልጣን እንዳለው ትኩረት ይሰጣል። "የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ሸክላ ሰሪው በሚሰራው ሸክላ ላይ ስልጣን እንዳለው እኔ በእናንተ ላይ ማድረግ እችላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤል" ወይም "የእስራኤል መንግሥት" ወይም "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ
"የምናገረው እውነተኛ እና ጠቃሚ ስለሆነ ትኩረት ሰጥተህ ስማ"
በሸክላ ሰሪው እጅ እንደሚገኝ ጭቃ - እናንተ በእኔ እጅ እንደዚያ ናችሁ
ሸክላ ሰሪው ይሆናል በሚለው መንገድ በእጁ ያለውን ጭቃ ዳግም መስራት እንደሚችል ያህዌ እስራኤልን ዳግም መስራት እንደሚችል ያነጻጽራል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይንደዋል፣ ወይም ያፈርሰዋል
እነዚህ ሁለት አገላለጾች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በመጀመሪያው ገለጻ፣ ያህዌ አንድን መንግሥት ያ መንግሥት ተክል እንደሆነ ወይም የሚያፈርሰው ህንጻ አድርጎ ይናገራል። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ይቅር እላለሁ
"እስቀርለታለሁ" ወይም "አላመጣበትም"
Jeremiah 18:9
እገነባታለሁ ወይም እተክላታለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ያህዌ መንግሥታትን ስለ ማጠናከር የሚናገረው እርሱ እንደሚገነባቸው ህንጻዎች፣ እና እንደሚተክላቸው ተክሎች አድርጎ ነው። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
በእኔ ዐይኖች ፊት እርሷ ክፉ ብታደርግ
እዚህ ስፍራ "እርሷ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አገሪቱን ወይም መንግሥቷን ነው፣ ይህም በዚያች አገር ለሚኖሩ ሰዎች ወይም መንግሥት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ዐይኖች" የሚለው ቃል የሚወክለው ማየትን ሲሆን፣ ማየት ደግሞ ሀሳብን ወይም ፍርድን ይወክላል። "የዚያች አገር ሰዎች እኔ ክፉ ነው የምላቸውን ነገሮች ቢያደርጉ " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ድምጼን ባትሰሙ
እዚህ ስፍራ "ድምጽ" የሚለው ቃል የሚወክለው የያህዌን ንግግር ነው። እዚህ ስፍራ፣ "አለ መስማት" አለመታዘዛቸውን የሚያሳይ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ለነገርኳችሁ ባትታዘዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Jeremiah 18:11
እዩ/እነሆ
ይህ አንባቢው ቀጥሎ ለሚሆነው ትኩረት እንዲሰጥ ያደርጋል። "ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"
በእናንተ ላይ ጥፋት ለማድረስ ተነስቻለሁ። በእናንተ ላይ የጥፋት እቅድ አዘጋጅቻለሁ
ያህዌ ጥፋት ሊያመጣ መነሳቱን የገለጸው ሸክላ ሰሪው ሸክላ እንደሚያበጅ ጥፋት እርሱ የሚያበጀው አካል እንደሆነ አድርጎ ነው። ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር የመጀመሪያው የተለያዩ ቃላትን እንደተጠቀመ ሁሉ ተመሳሳይ ሃሳብን ይደግማል። "እኔ በእናንተ ላይ ጥፋት ለማምጣት ተነስቻለሁ/እቅድ አድርጌያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
እቅድ ማዘጋጀት
"እቅድ ማውጣት"
የእርሱ ክፉ መንገድ
ያህዌ የአንድን ሰው የህይወት ዘይቤ የዚያ ሰው "መንገድ" ወይም የሚሄድበት መንገድ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። "ክፉ የህይወት መንገዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህ የእናንተ መንገዶች እና ልምምዶቻችሁ መልካም ነገር ያመጡላችኋል
"መንገዶች" እና "ልምምዶች" የሚሉት ቃላት ሁለቱም የአንድን ሰው ድርጊቶች እና አጠቃላይ የህይወት ዘይቤ ያመለክታሉ። "ስለዚህ ድርጊቶቻችሁ መልካም እንዲሆንላችሁ ያደርጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን እነርሱ እንዲህ ይላሉ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳን እና የእየሩሳሌምን ነዋሪዎች ነው። ይህ ጥቅም የለውም
ለዚህ ፈሊጥ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ህዝቡ ኤርምያስ ለሚነግራቸው ጥንቃቄ አያደርጉም/ደንታ ቢስ ናቸው። "አንተ ለምትናገረው ግድ የለንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ህዝቡ ኤርምያስ የሚናገራቸውን በማድረግ መልካም እንደሚሆን አያስቡም። "የምተናገረው የሚሆን ነገር አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሱ ክፉ፣ እና ግትር ልብ የሚፈልገው
"ልብ" የሚለው ቃል የሚወክለው የሰውየውን አይምሮ እና ፈቃድ ነው። "የእርሱ ክፉ፣ እና ግትር አይምሮ/አስተሳሰብ የሚፈልገው" ወይም "በግትርነት ማድረግ የምንፈልገው ማናቸውም አይነት ክፉ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 18:13
እንደዚያ ያለ ነገር የሰማ ህዝብ ይኖር እንደሆነ ጠይቁ?
እዚህ ስፍራ "ህዝብ" የሚለው ቃል የሚወክለው በአገራት ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ነው። ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚያቀርበው የይሁዳን ህዝብ ለመገሰጽ ነው። "አንዳቸውም እንዲህ ያለ ነገር ሰምተው ያውቁ እንደሆነ እስቲ አገራትን ጠይቁ።" ወይም "በምድር ላይ በየትኛውም ስፍራ ማንም እንዲህ ያለ ነገር ሰምቶ አያውቅም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ድንግሊቱ እስራኤል አሰቃቂ ድርጊት ፈጸመች
አገራትን በሴት መግለጽ የተለመደ ነበር። ያህዌ እስራኤልን ለእርሱ ንጽህት እና ታማኝ እንደሆነች ሲገልጽ ድንግል እንደሆነች አድርጎ ሲሆን የእስራኤልን ለእርሱ ታማኝ አለመሆን የሚገልጸው "አሰቃቂ ድርጊት እንደፈጸመች" በማድረግ ነበር። "እንደ ድንግል የሆነችው እስራኤል፣ አሰቃቂ ድርጊት ፈጸመች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ዘይቤያው አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
የሊባኖስ ተራራ አለታማ ኮረብቶች በረዶ ተለይቷቸው ያውቃልን?
ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው በተራሮቹ ላይ የሚገኘው በረዶ እንደማይቀልጥ ትኩረት ለመስጠት ነው። "በሊባኖስ የሚገኘው በረዶ በጎኖቹ የሚገኙትን አለታማ ኮረብቶች ተለይቶ አያወቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በጎኖቹ የሚገኙ አለታማ ኮረብቶች
"የአለታማ ኮረብቶች ተረተር/ጎኖች"
ከተራራ የሚወርዱ፣ ከርቀት የሚመጡ እነዚያ ቀዝቃዛ ምንጮች ሊጠፉ ይችላሉን?
ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚያነሳው የተራራ ምንጮች መፍሰሳቸውን በፍጹም እንደማያቋርጡ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። ምንጮቹ የሚደርቁት ከጠፉ እንደሆነ ይናገራል። "ከርቀት የሚመጡት እነዚያ ቀዝቃዛ የተራራ ምንጮች መፍሰሳቸውን በፍጹም አያቆሙም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Jeremiah 18:15
በመንገዶቻቸው እንዲደነቃቀፉ ይሆናሉ
ያህዌ የአንድን ሰው የህይወት ዘይቤ እንደሚሄድበት መንገድ አድርጎ ሲናገር፣ ለእርሱ ታማኝ ያልሆነ ሰው በመንገዱ ላይ እየተደነቃቀፈ እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ይህ በመንገዳቸው እንዲደነቃቀፉ ያደርጋል" ወይም "ይህ በመንገዳቸው እንዲደነቃቀፉ ያደርጋል" ወይም "ይህ በመንገድ ላይ ሲራመዱ እንደሚደነቃቀፉ ያለ ይሆናል" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ዝቅ ባለ መንገድ ለመሄድ የጥንቶቹን መንገዶች ተዉ
ያህዌ የአንድን ሰው የህይወት ዘይቤ እንደሚሄድበት መንገድ አድርጎ ይናገራል። እዚህ ስፍራ "የጥንቶቹ መንገዶች" የሚለው የሚወክለው ያህዌ አባቶቻቸው እንዲኖሩበት የነገራቸውን መንገድ ሲሆን "አነስተኛ/ዝቅ ያሉ መንገዶች" የሚለው ደግሞ የሚወክለው ለያህዌ በታማኝነት አለመኖርን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አስፈሪ ሆኑ
"አስፈሪ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎችን የሚያስፈራ ነገር ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ዘለዓለማዊ የጥላቻ ድምጽ አካል
"የጥላቻ ድምጽ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠንካራ የሆነ ያለ መቀበልን መግለጫ ድምጽ ሲሆን በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች ሁሌም የጥላቻ ድምጽ የሚያሰሙበት ነገር"

በአጠገቧ ሲያልፉ
እዚህ ስፍራ "እርሷ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምድራቸውን ነው።
በጠላቶቻቸው ፊት እንደ ምስራቅ ነፋስ እበትናቸዋለሁ
ያህዌ ህዝቡን፣ አብዋራን እና ፍርስራሽን እንደሚበትን የምስራቅ ነፋስ ሆኖ በጠላቶቻቸው ፊት እንደሚያሳድዳቸው ይናገራል። "እንደ ምስራቅ ነፋስ ሆኜ በጠላቶቻቸው ፊት እበትናቸዋለሁ" ወይም "የምስራቅ ነፋስ አብዋራን እና ፍርስራሽን እንደሚበትን በጠላቶቻቸው ፊት እበትናቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱን እበትናለሁ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "የእኔ ህዝብ/ህዝቤ" የሚለውን ነው።
ጀርባዬን እንጂ ፊቴን አያዩም
"በእነርሱ ላይ ጀርባዬን አዞራለሁ፣ እንጂ ፊቴን አያዩም።" በአንድ ሰው ላይ ጀርባን ማዞር አለመቀበልን የሚያመለክት ሲሆን ወደ አንድ ሰው ፊትን መመለስ መቀበልን/ሞገስ ማግኘትን የሚያመለክት ተምሳሌታዊ ድርጊት ነው። "እኔ አልቀበላቸውም ለእነርሱ ሞገስ አልሰጥም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 18:18
በኤርምያስ ላይ እናሲር/እንማከር
"ኤርምያስን ለመጉዳት እቅድ እናውጣ"
ህጉ ከካህናቱ በፍጹም አይጠፋም፣ ወይም ምክር ከጠቢባን፣ ወይም ቃል ከነቢያት
"በፍጹም አይጠፋም" የሚሉት ቃላት በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ሀረጋት ውስጥ ሊጨመር ይችላል። ይህ በአዎንታዊ ቃላትም ሊገለጽ ይችላል። "ህጉ በፍጹም ከነቢያት ሊጠፋ፣ ደግሞም ምክር ከጠቢባን ሰዎች ሊጠታጣ፣ እና ከነቢያት ቃል ሊታጣ አይችልም" ወይም "ካህናቱ ሁሌም ህጉ ይኖራቸዋል፣ ጠቢባኑ ሰዎች ሁሌም ምክር ሊያቀርቡ፣ እና ነቢያቱ ሁሌም ቃል ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
ቃላት ከነቢያቱ
እዚህ ስፍራ "ቃላት" የሚወክለው ነቢያት የሚናገሩትን ከያህዌ ዘንድ የሆነ መልዕክት ነው። "ከነቢያቱ የያህዌ ቃላት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱን በቃላችን እናጥቃው
ሰዎቹ በኤርምያስ ላይ የሚጎዱ ቃላትን መናገርን እርሱን እንደሚያጠቁበት መሳሪያ አድርገው ይናገራሉ። "እርሱን የሚጎዱ ነገሮችን ተናገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ለእኔ ትኩረት ስጥ/ወደ እኔ አድምጥ
እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለያህዌ መናገር ይጀምራል።
ለእነርሱ መልካም በመሆኔ፣ በእውኑ ከእነርሱ የሚመጣው ጉዳት ለእኔ ሽልማት ነውን?
ኤርምያስ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው መልካም ድርጊቶች ምላሻቸው ክፉ መሆን እንደማይገባው ትኩረት ለመስጠት ነው። "ከእነርሱ የሚደርስብኝ ጉዳት ለእነርሱ መልካም የመሆኔ ምላሽ መሆን የለበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ለእኔ ጉድጓድ ቆፈሩ
ኤርምያስ ጠላቶቹ እርሱን ለመግደል ማቀዳቸውን እርሱን ለማጥመድ ጉድጓድ እንደቆፈሩ አድርጎ ይናገራል። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቁጣህን ከእነርሱ አትመልስ
እዚህ ስፍራ "ቁጣ" የሚለው ቃል የሚወክለው ያህዌ በእነርሱ ላይ ሊያደርስ ያቀደውን ቅጣት ነው። ኤርምያስ ያህዌ የእርሱን ጠላቶች አለመቅጣቱን የሚገልጸው ቁጣውን ከእነርሱ እንዳራቀ አድርጎ ነው። "ስለዚህ በቁጣህ አትቀጣቸውም/አትገስጻቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Jeremiah 18:21
ልጆቻቸውን ለረሃብ አሳልፈህ ስጣቸው
"አሳልፈህ ስጣቸው" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር አንድን ሰው በሌላው ሀይል ስር ማድረግ የሚል ትርጉም አለው። ኤርምያስ ስለ "ረሃብ/ችጋር" የሚናገረው በሌላው ሰው ላይ ስልጣን እንዳለው ሰው አድርጎ ነው። "ልጆቻቸው በረሃብ እንዲሞቱ አሳልፈህ ስጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ሰይፍ ለያዙ እጆች አሳልፈህ ስጣቸው
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው ቃል የሚወክለው ሀይልን ነው። "ሰይፍ የያዙ በእነርሱ ላይ ሀይል እንዲኖራቸው አድርግ" ወይም "በጦር ሜዳ ይሙቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሴቶቻቸው ሀዘንተኞች እና መበለቶች ይሁኑ
"የሴቶቻቸው ባሎች እና ልጆቻቸው ይሙቱ። "ሀዘንተኞች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ልጆቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች ነው።
ወንዶቻቸው ይገደሉ
ምናልባት ግሡ ከቀደመው ሀረግ ሊገኝ ይችላል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ወንዶቻቸውን ይግደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ወጣት ወንዶቻቸው በጦርነት በሰይፍ ይገደሉ
ምናልባት ግሡ ከቀደመው ሀረግ ሊገኝ ይችላል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ወጣት ወንዶቻቸውን በጦር ሜዳ በሰይፍ ይግደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
የጥፋት ጩኸት ይሰማ
"የጥፋት ጩኸት" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል።ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች የጭንቀት ጩኸትን ይስሙ" ወይም "ሰዎች የሌሎችን የጭንቀት ጩኸት ይስሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔን ለማጥመድ ጉድጓድ ቆፍረዋል፣ ለእግሬም ወጥመድ አበጅተዋል
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ኤርምያስ ጠላቶቹ እርሱን ለመግደል እያቀዱ መሆኑን የገለጸው የሚወድቅበትን ጉድጓድ እንደቆፈሩ እና እርሱን ለማጥመድ ወጥመድ እንዳዘጋጁ አድርጎ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ጉድጓድ ቆፍረዋል
ይህ በኤርምያስ 18:20 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ለእግሬ ወጥመድ አዘጋጅተዋል
እዚህ ስፍራ "እግር" የሚለው ቃል የሚወክለው ኤርምያስን ነው። "ለእኔ ወጥመድ አዘጋግተዋል/አጥምደዋል" ወይም "ውድቀቴን ለማፍጠን ወጥመድ አጥምደዋል" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ኃጢአታቸውን ከአንተ ዘንድ አትደምስስላቸው
ኤርምያስ ያህዌ የእርሱን ጠላቶች ኃጢአት ይቅር ማለቱን አንድ ሰው የእነርሱን ኃጢአት እንደመዘገበ እና ያህዌ ይንን እንደሚያጠፋው አድርጎ ይገልጸዋል። የዚህ ሀረግ ትርጉም ከቀደመው ሀረግ ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። "ኃጢአታቸውን ይቅር አትበል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአንተ ፊት የተጣሉ ይሁኑ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች በፊትህ የተጣሉ ያድርጓቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በቁጣህ ቀን
"ቁጣ" የሚለው ቃል በግስ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። "አንተ በእነርሱ ላይ ተቆጥተህ ሳለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 19
Jeremiah 19:1
የቤን ሄኖም ሸለቆ
ይህ ሰዎች ለሀሰተኛ አማልዕክት የሚሰዉበት፣ ከእየሩሳሌም ከተማ በስተ ደቡብ የሚገኝ ሸለቆ ስም ነው። ይህ በኤርምያስ 7:31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እዩ

"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"
ይህን የሚሰሙ ሁሉ ጆሮዎቻቸው ጭው ይላል
እዚህ ስፍራ "ጆሮዎች… ጭው ይላሉ" የሚለው ፈሊጥ ትርጉም እያንዳንዱ በሚሰማው ይረበሻል የሚል ነው። "ይህንን የሰማ ሁሉ ይረበሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጭው ይላል
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ይጮህባቸዋል" 2) "ይንቀጠቀጣሉ"
Jeremiah 19:4
እነርሱ እኔን ትተዋል
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳን ሰዎች ነው።
ይህንን ስፍራ በንጹሃን ደም ሞልተውታል
እዚህ ላይ "የንጹሀን ደም" የሚለው የሚወክለው የንጹሃን ሰዎችን መገደል ነው። ያህዌ የብዙ ሰዎችን መገደል አንድን ስፍራ በደም መሙላት አድርጎ ይናገራል። "በዚህ ስፍራ ብዙ ንጹሃን ሰዎችን ገድላችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ይህ ወደ አይምሮዬ አልገባም/አላሰብኩትም
እዚህ ስፍራ "አይምሮ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የያህዌን ሃሰብ/ፈቃድ ነው። በኤርምያስ 7:31 ላይ ይህ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ በፍጹም ስለዚህ አስቤ አላውቅም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 19:6
እዩ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ስፍራ ከእንግዲህ አይጠራም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ከእንግዲህ ይህን ስፍራ አይጠሩትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ቶፌት… የቤን ሄኖም ሸለቆ…የእርድ ሸለቆ
ይህ በኤርምያስ 7:31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እኔ በጠላቶቻቸው ፊት በሰይፍ እንዲወድቁ አደርጋለሁ
"በሰይፍ እንዲወድቁ" የሚለው ፈሊጥ በጦርነት ውስጥ እንዲሞቱ ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጠላቶቻቸው በሰይፍ እንዲገድሏቸው አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
እኔ እነርሱን…አደርጋለሁ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳን እና እየሩሳሌምን ህዝቦች ነው።
ህይወታቸውን በሚፈልጉ ሰዎች እጅ
ግሡ ከቀደመው ሀረግ ሊወሰድ ይችላል። "በ…እጅ መውደቅ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር በሰው መገደል የሚል ትርጉም ሲኖረው፣ "እጅ" ከሚለው ቃል ጋር የሚወክለው የሰውየውን ሁለንተና ነው። "ሊገድሏችሁ የሚፈልጉ ሁሉ እንዲገድሏቸው አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ እና ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እንደዚሁም ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
የጥላች ድምጽ አካል
"የጥላች ድምጽ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠንካራ የሆነ ያለ መቀበልን መግለጫ ድምጽ ሲሆን በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች ሁሌም የጥላቻ ድምጽ የሚያሰሙበት ነገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እንዲበሏቸው አደርጋቸዋለሁ
"በእየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎችን እንዲበሉ አደርጋለሁ"
በዚህ ከበባ
"በከበባው ምክንያት"
ከጠላቶቻቸው በደረሰባች ጭንቀት እና ህይወታቸውን በሚፈልጉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከጠላቶቻቸው እና ህይወታቸውን ከሚፈልጉ የተነሳ በላያቸው ጭንቀት ይመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 19:10
ከአንተ ጋር በሄዱ ሰዎች እየተመለከቱ
"ማየት" የሚለው ረቂቅ ስም "መመልከት" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ከአንተ ጋር የሄዱ ሰዎች እየተመለከቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙ ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክት ለማስተዋውቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ እንደገና ሊጠገን አይችልም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም ይህን እንደገና ሊጠግነው አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 19:12
ይህ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ነገሥታት
"ቤቶች" የሚለው ቃል እዚህ ስፍራ ሊገባ ይችላል። "የይሁዳ ነገሥታት ቤቶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
ንጹህ ያልሆኑ ሰዎች
ለእግዚአብሔር አላማ ተቀባይነት ያላገኙ ሰዎች የተገለጹት በአካል ንጹህ እንዳልሆኑ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 19:14
የሰራዊት ጌታ ያህዌ…እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እዩ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"
አንገታቸውን አደነደኑ ለማድመጥ እንቢ አሉ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ሁለቱም ግትር ስለሆኑ ሰዎች ይናገራሉ። በመጀመሪያው ሀረግ፣ ያህዌ ደንዳና ስለሆኑ ሰዎች አንገታቸውን እንደ ገተሩ አድርጎ ይገልጻል። "በግትርነት ለማድመጥ እምቢ አሉ" በመሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 20
Jeremiah 20:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ ትንቢት የሚጽፈው በሥነ ግጥም መልክ ነው። የዕብራውያን ስነግጥም የተለያዩ የትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ አይነቶችን ይጠቀማል። (ስነ ግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ጳስኮር… ኢሜር
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ጳስኮር ኤርምያስን መታው

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጳስኮር ራሱ ኤርምያስን መታው ማለት ሊሆን ይችላል። ወይም 2) ጳስኮር ሌሎች ሰዎች ኤርምያስን እንዲመቱት አዘዘ ማለት ሊሆን ይችላል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማሰሪያ/እግር ግንድ

ማሰሪያ ግንድ፣ ከእንጨት የተሰራ በመሃሉ ቀዳዳያለው ሰዎች የእስረኞችን እጆች፣ እግር፣ እና ጭንቅላት ለማሰሪያ/ለመጠረቅ የሚጠቀሙበት ግንድ ነው።

የላይኛው የብንያም በር

ይህ በር በከተማይቱ ቅጥር መግቢያ ከሚገኘው ተመሳሳይ ስም ካለው በር ይለያል

Jeremiah 20:3

እንዲህ ሆነ

ይህ ሀረግ እዚህ ስፍራ የዋለው ድርጊቱ የት ላይ እንደ ጀመረ ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህ የሚገልጽበት መንገድ አዚህ ስፍራ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ።

አንተ ማጎር ሚሳቢብ ነህ

የዚህ ስም ትርጉም "በሁሉም በኩል ሽብር" ወይም "በሽብር መከበብ" ማለት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እዩ፣

ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት ይጨምራል። "ቀጥሎ ለምናገረው ትኩረት ስጥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እነርሱ በጠላቶቻቸው ሰይፍ ይወድቃሉ

"በሰይፍ መውደቅ" የሚለው ፈሊጥ ትርጉም በጦርነት ይሞታሉ ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጠላቶቻቸው በሰይፍ ይገድሏቸዋል" ወይም "ጠላቶቻቸው በጦርነት ውስጥ ይገድሏቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ዐይኖችህ ይህንን ይመለከታሉ

እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው ቃል የሚወክለው ጳስኮርን ነው። "አንተ ይህን ትመለከታለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

መላዋን ይሁዳ ለባቢሎን ንጉሥ እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ሀይልን ያመለክታል። "የባቢሎን ንጉሥ መላውን ይሁዳ እንዲማርክ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 20:5

እኔ ለእርሱ እሰጠዋለሁ

እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የባቢሎንን ንጉሥ ነው።

መላው ሀብት... መላው ብልጽግናዋ፣ መላው ውድ ንብረቶቿ እና ጠቅላላ ንብረቷ

ያህዌ መሰረታዊ የሆነውን ተመሳሳይ ሀሳብ አራት ጊዜ የደገመው ትኩረት ለመስጠት ነው። ባቢሎን የእስራኤልን ጠቅላላ ሀብት፣ የንጉሡን ንብረቶች ጨምሮ ይወስዳል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህን ነገሮች በጠላቶችህ እጅ ላይ አደርጋለሁ

ነገሮችን በሰዎች እጅ ላይ ማድረግ የሚወክለው ነገሮችን ለሰዎች አሳልፎ መስጠትን ወይም ሰዎች ነገሮችን እንዲወስዱ መፍቀድን ነው። "እነዚህን ነገሮች ለጠላቶቻችሁ እሰጣለሁ" ወይም "ጠላቶቻችሁ እነዚህ ሀብቶች እንዲወስዱ እፈቅዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ እና ሀሰተኛ ትንቢት የተናገርክላቸውን የምትወዳቸውን በሙሉ በዚያ ይቀበራሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በዚያ፣ ሰዎች አንተን እና የምትወዳቸውን ሀሰተኛ ነገሮችን የተናገርክላቸውን ሁላችሁምን ይቀብሯችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 20:7

አጠቃላይ መረጃ፡

ኤርምያስ ወደ ያህዌ ይናገራል

ያህዌ፣ አንተ አታለልከኝ፣ ደግሞም እኔም ተታልዬ ነበር

አንዳንድ ዘመናዊ ቅጂዎች ይህንን የዕብራይስጥ አገላለጽ "ያህዌ፣ አንተ አሳመንከኝ፣ እኔም ደግሞ አመንኩህ" በማለት ይተረጉሙታል።

እኔ ተታልዬ ነበር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ እኔን አታለልከኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኑን በሙሉ መሳለቂያ ሆንኩ፤ ሁሉም በእኔ ላይ ያፌዛል

እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ሌሎች በእርሱ ላይ ያፌዙበትን መንገድ ትኩረት ይሰጣል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መሳለቂያ

ይህ ሌሎች የሚስቁበት እና የሚያፌዙበት ሰው ነው

ተጣራሁ ደግሞም አወጅኩ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ እናም የያህዌን መልዕክት በድፍረት ማወጁን ትኩረት ይሰጣሉ። "በግልጽ አወጅኩ" ወይም "ጮክ ብዩ አወጅኩ/ተናገርኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል በየቀኑ ዘለፋ እና መቀለጃነት አስከተለብኝ

እዚህ ስፍራ "ቃል" የሚያመለክተው የያህዌን መልዕክት ነው። "ዘለፋ" እና "ፌዝ" የሚሉት ቃላት በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ሰዎች በየቀኑ እኔን ይዘልፋሉ ደግሞም ያፌዙብኛል፤ ይህም የያህዌን መልዕክት ስላወጅኩ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእኔ መሳለቂያን ፌዝ ሆነ

"መሳለቂያ" እና "ፌዝ" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ኤርምያስን የያህዌን መልዕክት በማወጁ ሰዎች መሳለቂያ እንዳደረጉት ትኩረት ይሰጣሉ። "ሰዎች በእኔ ላያ የተሳለቁበት ምክንያት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ በእርሱ ስም አልናገርም

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በፍጹም ያህዌን አልጠቅስም ወይም ስለ እርሱ ምንም ነገር አልናገርም" ወይም 2) "ስም"የሚለው ቃል ስልጣንን ይወክላል። "ከእንግዲህ የእርሱ መልዕክተኛ ሆኜ አልናገርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በልቤ ልክ እንደ እሳት፣ በአጥንቴ ውስጥ እንደሚገኝ ሆነብኝ

እዚህ ስፍራ "ልብ" እና "አጥንት" የሚሉት ቃላት የሚወክሉት የኤርምያስን እጅግ ውስጣዊ ማንነት ነው። ኤርምያስ የያህዌን መልዕክት አለመናገር እንደማይችል የገለጸው መልዕክቱ በውስጥ እንደሚነድ እሳት መሆኑን በመግለጽ ነው። "የያህዌ ቃል በውስጤ እንደሚነድ እሳት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 20:10

ዘገባ! እኛ ይህን መዘገብ አለብን

የኤርምያስ ጠላቶች እነዚህን ቃሎች ይናገራሉ።

የእኔን መውደቅ ለማየት ይጠባበቃሉ

ኤርምያስ ጠላቶቹ እርሱን ለመክሰስ ስህተት ይሰራል ብለው እንደሚጠባበቁ የሚናገረው ከፍ ካለ ስፍራ ላይ እንደሚወድቅ ሰው አይነት እንደሆነ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምናልባት ይታለል ይሆናል... በእርሱ ላይ የበቀል እርምጃ እንወስዳለን

እነዚህን ቃሎች የሚናገሩት የኤርምያስ ጠላቶች ናቸው።

ምናልባት ይታለል ይሆናል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ምናልባት እኛ ልናታልለው እንችል ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ እንደ ሀያል ጦረኛ ከእኔ ጋር ነው

ኤርምያስ ያህዌ እርሱን መርዳቱን እና ከጠላቶቹ እርሱን ማዳኑን ያነጻጸረው ከታላቅ ጦረኛ ጋር ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚያሳድዱኝ ይሰናከላሉ

ኤርምያስ ሊጎዱት የሚፈልጉት ጠላቶቹ እርሱን እንደሚያሳድዱት እና እርሱን ለመጉዳት አለመቻላቸውን ደግሞ እንደተሰናከሉ አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እጅግ ያፍራሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ በእነርሱ ላይ ታላቅ ሀፍረት ያመጣባቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ፈጽሞ የማይረሳ ይሆናል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ይህንን ፈጽሞ አይረሱም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 20:12

ልባቸውንና ሀሳባቸውን ተመልከት

"ሃሳብ/አእምሮ" የሚለው ቃል አንድ ሰው የሚያስበውን እና ውሳኔውን የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ልብ" የሚለው ቃል ደግሞ አንድ ሰው የሚሰማውን እና መሻቱን የሚገልጽ ሜቶኖሚ ነው። "የእያንዳንዱን ሰው ሃሳብ እና ስሜት ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 20:14

አጠቃላይ መረጃ፡

ኤርምያስ ከያህዌ ጋር መነጋገርን ቀጥሏል።

የተወለድኩበት ቀን የተረገመ ይሁን

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የተወለድኩበትን ቀን ይርገሙት" ወይም "ሰዎች እኔ የተወለድኩበትን ቀን ይርገሙት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአባቴ የነገረው ሰው የተረገመ ይሁን

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ለአባቴ የነገረውን ሰው እርገሙት" ወይም "ሰዎች ለአባቴ የነገረውን ሰው ይርገሙት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 20:16

ያ ሰው

ይህ የሚያመለክተው ለኤርምያስ አባት የኤርምያስን መወለድ የነገረውን ሰው ነው

ያህዌ የጣላቸው ከተሞች

ይህ የሚያመለክተው ሰዶምን እና ገሞራን ነው።

እርሱ ርህራሄ የለውም

እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያህዌን ነው።

እርሱ የለቅሶ ድምጽ ይስማ

እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "ያንን ሰው" ነው።

እናቴን መቃብሬ አላደረግክም

ኤርምያስ ገና እናቱ እርጋዛው ሳለች ቢሞት ይሻለው እንደነበረ የተናገረው የእናቱን ማህጸን እንደ መቃብሩ በማድረግ ነበር። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለዘለዓለም ከማህጸን ባልወጣሁ

ኤርምያስ ነብሰጡር እናቱ ለዘለዓለም ሳትወልደኝ እንዳረገዘችኝ በኖረች ብሎ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መከራ እና ጭንቀት...ሀፍረት ለማየት ለምን ከማህጸን ወጣሁ?

ኤርምያስ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ለመወለድ ምንም መልካም ምክንያት እንዳልነበረ ለማማረር ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "መከራ እና ጭንቀት... እንዲሁም ሀፍረት ለማየት ካልሆነ በስተቀር እኔ የምወለድበት ምንም መልካም ምክንያት አልነበረም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መከራ እና ጭንቀት ለማየት

"መከራ" እና "ጭንቅ" የሚሉት ቃላት በመሰሩ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የአበሳውን መጠን እና ጥልቀት ያጎላሉ። "ብዙ መከራ ለመቀበል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ቀኖቼ በሀፍረት ተሞሉ

እዚህ ስፍራ "ቀኖች" የሚለው ቃል የሚወክለው የኤርምያስን የህይወት ዘመን ነው። "ህይወቴ በሀፍረት ተሞላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 21

Jeremiah 21:1

ከያህዌ ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል

ይህ ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 7፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልክተው እንደ አስፈላጊነቱ ለውጥ አድርጉ። "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠው" ወይም "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጳስኮር

ይህ በኤርምያስ 20፡1 ላይ የተጠቀሰው ጳስኮር አይደለም

ጳስኮር...መዕሤያን...መልክያ

እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ደግሞም እነርሱ እንዲህ አሉ

"ጳስኮር እና ሶፎንያስ ኤርምያስን እንዲህ አሉት"

በእኛ ምትክ ሆነህ ከያህዌ ዘንድ ምክር ፈልግልን... ጦር መጥቶብናል

ይህ በጭንቅ ሰዓት በትህትና የቀረበ ጥያቄ ነው። "እባክህ ስለ እኛ ያህዌን ለምንልን... እያጠቁን ነው"

እንዳለፈው ዘመን

"ባለፈው ዘመን እንዳደረገው"

ከእኛ እርሱን እንዲያርቀው

"እርሱ ከእኛ እንዲመለስ"

Jeremiah 21:3

እዩ

ይህ አድማጩ ቀጥሎ ለሚሆነው ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ይናገራል

ወደ ኋላ መዞር

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ዋጋ ቢስ ለማድረግ ወይም 2) ወደ ከተማ መልሶ ለመላክ

በእጅህ የሚገኙ የጦር መሳሪያዎች

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የጦር መሳሪያዎች የሚለው የሚያመለክተው እነርሱን የያዙ ወታደሮች ሲሆን "እጅ" የሚወክለው መቆጣጠርን ነው። "አንተ የምታዛቸው ወታደሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) የጦር መሳሪያዎች በቀጥታ መሳሪያዎች ማለት ሊሆን ሲችል "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው ንጉሡን እና ወታደሮቹን ሁለትንም ነው። "አንተ እና የአንተ ወታደሮች የያዛችሁት መሳሪያዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከለዳውያን

እዚህ ስፍራ ይህ ቃል ባቢሎናውያን ለሚለው ሌላው ስያሜ ነው።

እናንተን ይከባሉ

"ወደ እናንተ ይገባሉ/ይመጣሉ"

እኔ እሰበስባቸዋለሁ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ያህዌ ባቢሎናውያን ወደ ከተማይቱ እንዲገቡ ይፈቅዳል ወይም 2)ያህዌ እስራኤላውያን መሳሪያዎቻቸውን ወደ ከተማይቱ መሃል መልሰው እንዲያመጡ ያደርጋል

ከዚያም እኔ ራሴ

ይህን የሚያደርገው ያህዌ መሆኑን አጽንኦት እና ትኩረት ሰጥቶ ይገልጻል። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በተዘረጋ እጅ እና ጠንካራ ክንድ

እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ታላቅ ሀይልን የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አገላለጾች ናቸው። "በጣም በትልቅ ሀይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

በሀይል፣ በንዴት እና በታላቅ ቁጣ

እነዚህ ቀላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም የያዙ ናቸው። በአንድነት ሆነው የእርሱን ቁጣ ታላቅ ጥልቀት ያጎላሉ። "እጅግ ከፍ ባለ ታላቅ ቁጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 21:6

የዚህች ከተማ ኗሪዎች

"በእየሩሳሌም የሚኖሩ"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ/ሰይፉ

እዚህ ስፍራ ይህ የሚያመለክተው ሰይፍ የሚጠቀሙበትን ጦርሜዳ ነው። "ጦርነቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ለ..እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚያመለክተው ጠላት በእነርሱ ላይ ያለውን ሀይል ነው። "ለ… ሀይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር… የእነርሱ ጠላቶች… ህይወታቸውን የሚፈልጉ
እነዚህ ሀረጎች ሁሉ ናቡከደነጾርን እና የእርሱን ሰራዊት ያመለክታሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ህይወታቸውን የሚፈልጉ
"እነርሱን ለመግደል የሚፈልጉ"
በሰይፍ ስለት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ በጦርነት ስለ መሞት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በጦርነት/ጦር ሜዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) በራሱ በሰይፍ ይገደላሉ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አይራራላቸውም፣ አይምራቸውም፣ ወይም ርህራሄ አይኖረውም
እነዚህ ሶስት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ደግሞም ናቡከደነጾር ያለ ርህራሄ እንደሚጨክንባቸው አጽንኦት ይሰጣሉ። "አንዳች ምህረት አያሳያቸውም ወይም በፍጹም ርህራሄ አያሳያቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 21:8
ይህ ህዝብ
"የእየሩሳሌም ሰዎች"እኔ በፊታችሁ የህይወትን እና የሞትን መንገድ አስቀምጣለሁ ያህዌ ለእስራኤል ሰዎች በህይወት የሚኖሩበትን ወይም የሚሞቱበትን ምርጫ ያቀርብላቸዋል።
በሰይፍ፣ ረሃብ፣ እና መቅሰፍት
በሰይፍ መሞት የሚያመለክተው በጦርነት መሞትን ነው። "በጦርነት እና በድርቅ ደግሞም በመቅሰፍት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በጉልበቱ ፊት ለፊት መውደቅ
ይህ ተምሳሌታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚወክለው ሙሉ ለሙሉ መሸነፍን ነው። "ለ…መሸነፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
በእናንተ ላይ ተነስተዋል
"ከተለያየ አቅጣጫ ይከቧችኋል"
ህይወቱን ብቻ ይዞ ያመልጣል
ለባቢሎናውያን የተማረከ፣ ሀብቱን ቢያጣም ህይወቱን ያተርፋል።
ፊቴን በዚህች ከተማ ላይ አደርጋለሁ
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም "በጽኑ ወስኛለሁ" ማለት ነው። "ይህችን ከተማ ለመቅጣት በጽኑ ወስኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ፊቴን በእነርሱ ላይ አድርጌያለሁ
"በሁሉም ላይ በቁጣ ተነስቻለሁ"
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሷ ተሰጥታለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ አሳልፌ ሰጥቻታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ለንጉሡ እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ንጉሡ ከተማይቱን ለማጥፋት ያለውን ሀይልን ነው። "ለንጉሡ ሀይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 21:11
የይሁዳን ንጉሥ ቤት በሚመለከት፣ የያህዌን ቃል አድምጡ
ይህ ከኤርምያስ 21:12-23 ድረስ ላለው ክፍል እርእስት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። "ያህዌ ስለ ይሁዳ ንጉሥ፣ ስለ ቤተሰቡ እና ስለ አገልጋዮቹ የሚናገረውን አድምጡ"
የይሁዳ ንጉሥ ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በንጉሡ ቤት ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው ንጉሡን እና ቤተሰቡን ነው። "የይሁዳ ንጉሥ እና ቤተሰቡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የዳዊት ቤት
ይህ የሚያመለክተው "በይሁዳ ንጉሥ ቤት" እንደሚላቸውን ተመሳሳይ ሰዎች ነው። መላው የይሁዳ ነገሥታት የዳዊት ትውልድ ናቸው። "የዳዊት ትውልዶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በማለዳ ፍትህ ይሆናል
"ፍትህ" የሚለው ረቂቅ ስም ድርጊት ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። "ሁልጊዜም የምትገዟቸውን ሰዎች በትክክል አስተዳድሯቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የጨቋኙ እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ሀይልን ነው። "እነርሱን የጨቆነው ሀይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ቁጣዬ እንደ እሳት ወጥቶ ይነዳል
እዚህ ስፍራ የያህዌ ቁጣ የተነገረው ክፉ የሰሩትን እንደሚያቃጥል እሳት ተደርጎ ነው። "እናንተን በቁጣዬ በቶሎ አንዳችሁንም ሳላስቀር ቀጥቼ አጠፋችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህን ማስቀረት የሚችል የለም
ኤርምያስ በተነጻጻሪ ዘይቤ የቀረበውን የያህዌን ቅጣት በውሃ ሊጠፋ እንደማይችል ታላቅ እሳት መግለጹን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 21:13
እዩ
ይህ ሰሚው ሁሉ ቀጥሎ ሊሆን ላለው ነገር ትኩረት እንዲሰጥ ያነቃዋል። "ትኩረት ስጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
የሸለቆው ነዋሪት
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ እየሩሳሌም እንደሚለው፣ ከሸለቆብ በላይ የሚገኘውን የእየሩሳሌም ክፍል ሊያመለክት ይችላል፣ ምክንያቱም "ነዋሪት" ነጠላ ቁጥር ሴቴ ጾታ ነው ወይም 2) ይህ ሌላ ከተማን ወይም ቡድን ሊያመለክት ይችላል። ብዙ ቅጂዎች ከተማይቱን ለይቶ ከማሳወቅ ይልቅ ዋናውን መልክ ይተዉታል።
እኔ እቃወማለሁ
"እቃወማለሁ" ወይም "እኔ እቀጣለሁ"
በሜዳ የሚገኘው አለት
x

---

Chapter 22
Jeremiah 22:1
የይሁዳ ንጉሥ ቤት
"የይሁዳ ንጉሥ ቤተ መንግሥት።" "ቤት" የሚለው ቃል የተለያዩ ሰፊ ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው ንጉሡ የሚኖርበትን ንጉሣዊ ቤተመንግስት ነው።
ይህን ቃል ተናገረ/አወጀ
"ይህን መልዕክት አወጅ"
የያህዌን ቃል ስሙ
"ለያህዌ ቃል ትኩረት ስጡ"
በዳዊት ዙፋን የተቀመጥህ አንተ
ይህ የሚያመለክተው የይሁዳን ንጉሥ ነው።
በዳዊት ዙፋን ላይ የተቀመጥህ
"ዙፋን" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው ዳዊት እንደነበረው እንደ ንጉሥ ያለን ስልጣን ነው። "ከአንተ በፊት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደነበረው እንደ ንጉሥ ዳዊት አስተዳድር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በእነዚህ በሮች የሚገቡ የአንተ ሰዎች
እነዚህ በሮች የሚለው የንጉሡ ቤተ መንግስት በሮችን ነው። "ወደ ንጉሡ የሚመጡ የአንተ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ህትህን እን ጽድቅን አድርጉ
"ፍትህ" እና "ጽድቅ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ድርጊቶች ሊገለጹ ይችላሉ። "ፍትሃዊ እን ትክክለኛ ድርጊት ፈጽሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ማንም የተዘረፈውን ከጨቋኝ እጅ አድኑት
"የተጠቃውን ከጨቋኞች እጅ አድኑ"
የጨቋኝ እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚገልጸው ሀይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። "የጨቋኙ ሀይል" ወይም "እርሱን ሊጎዳው የሚችል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አትበድሉ
"በክፉ መንገድ አታድርጉ"
የሙት ልጅ
ወላጅ የሌለው ልጅ
ንጹህ ደም... አታፍስሱ
እዚህ ስፍራ "ደም...ማፍሰስ" የተያያዘው ከግድያ ጋር ነው፣ "ደም" የሚያመለክተው የተገደሉ የሰዎችን ነው። "ንጹሃን ሰዎችን... አትግደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)
በዚህ ስፍራ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እየሩሳሌም ወይም 2) መላው የይሁዳ አገር። ይህ ሰዎችን በሌላ ስፍራዎች መግደል መልካም ነው የሚል ትርጉም አይሰጥም።
Jeremiah 22:4
በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጡ ነገሥታት
"ዙፋን" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚያመለክተው ዳዊት የነበረውን አይነት ንጉሣዊ ስልጣን ነው። "በፊታቸው እንደ ዳዊት የሚመሩ ነገሥታት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የዚህ ቤት በሮች
ይህ ወደ ቤተመንግሥቱ አደባባይ የሚያስገቡ በሮችን ያመለክታል
በሰረገሎች እና ፈረሶች የሚሄዱ
ይህ ሀረግ ንጉሦቹን እንደ ሀያል እና ባለጸጋ የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ፣ የእርሱ አገልጋዮች፣ እና የእርሱ ሰዎች/ህዝብ
ይህ ዐረፍተ ነገር ሀያል እና ባለጸጋ የሚሆኑትን በሙሉ ይዘረዝራል። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "እርሱ፣ የእርሱ አገልጋዮች፣ እና የእርሱ ህዝብ በሰረገላ እና በፈረሶች ወደ ቤተ መንግሥት ይገባሉ። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ ባትሰሙ
"ትኩረት አንሰጥም ብትሉ" ወይም "እናንተ ባትታዘዙ"
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ንጉሣዊ ቤት
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ በተለይ የሚያመለክተው ንጉሣዊ ቤተመንግስትን ነው።
Jeremiah 22:6
የይሁዳ ንጉሥ ቤት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ የሚያመለክተው ንጉሡ የሚኖርበትን ንጉሣዊ ቤተ መንግሥት ወይም 2) "ቤት" በቤቱ ለሚኖሩ የይሁዳ ነገሥታት ንጉሳዊ ዝርያ ላላቸው ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የይሁዳ ንጉሣዊ ስርወ መንግሥት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ እንደ ገለዓድ፣ ወይም እንደ ሊባኖስ ከፍተኛ ስፍራ ነህ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "አንተ እንደ ገለዓድ ወይም እንደ ሊባኖስ ጫፍ ውብ ነህ" ወይም 2) "ገለዓድ ወይም የሊባኖስ ጫፍ እንደሚሰጠኝ ያህል ደስታ ትሰጠኛለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ምድረበዳነት እለውጥሃለሁ/ምድረበዳ አደርግሃለሁ
አስቀድሞ ውብ የነበረው ጠፍ እና በረሃ እንደሚሆን ተነገረ። "እንደ በረሃ ባዶ ስፍራ እንድትሆን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አጥፊዎችን በአንተ ላይ አስነሳለሁ
"አንተን እንዲያጠቁ ሰራዊት መርጫለሁ"
ምርጥ የሆኑት ጥዶችህ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የቤተመንግሥቱ አምዶች ወይም 2) የንጉሣዊ ቤተሰብ መሪ የሆኑ ወንዶች። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ እሳት ይጣላሉ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የቤተ መንግሥቱን አምዶች የሚያቃጥል እሳት ወይም 2) የንጉሣዊ ቤተሰቦች ጥፋት የተገለጸው በእሳት እንደሚቃጠሉ ተገርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 22:8
ከዚያም የብዙ አገራት ህዝቦች በዚህች ከተማ ውስጥ ያልፋሉ
እዚህ ስፍራ "ህዝቦች" የሚለው የሚያመለክተው ከእነዚያ አገራት በከተማይቱ የሚያልፉትን ሰዎች ነው። "ከዚያም ከተለያዩ አገሮች ብዙ ህዝብ በዚህች ከተማ ውስጥ ያልፋሉ" (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ወድቀው እየሰገዱ ሌሎችን አማልዕክት አመለኩ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "ወድቀው እየሰገዱ" የሚለው የሚገልጸው ሰዎቹ ሲያመልኩ ያላቸውን አቋም ነው። "ሌሎችን አማልክትን አመለኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚሉትን ይመልከቱ)
Jeremiah 22:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ የይሁዳን ንጉሥ ከመናገር ዞር ብሎ ጠቅላላ ህዝቡን መናገር ጀመረ።
የሞተው
ይህ ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም የተገደለውን ንጉሥ ኢዮስያስን ነው።
የሸሸው እርሱ
ይህ የሚያመለክተው ወደ ግብጽ የተሰደደውን ንጉሥ ኢዮአካዝን ነው።
በፍጹም ተመልሶ የትውልድ አገሩን አያይም
"በፍጹም ተመልሶ ዳግም የእስራኤልን ምድር አያይም" ወይም "በፍጹም ዳግም የትውልድ አገሩን አያይም"
Jeremiah 22:11
ኢዮአካዝ
ይህ ስም በዕብራይስጥ "ሰሎ፣" ነው፣ ነገር ግን ይበልጥ የሚታወቀው ኢዮአካዝ በሚለው ነው።
በአባቱ በኢዮስያስ ምትክ ንጉሥ ሆኖ ያገለገለው
"አባቱ ኢዮስያስ ሲሞት በምትኩ የነገሰው"
Jeremiah 22:13
ቤቱን የገነባው እርሱ...እንዲህ ይላል
እነዚህ የሚያመለክቱት ኢዮአቄምን ነው።
ቤቱን በግፍ፣ የላይኛውን ክፍሎች/ሰገነት በፍትህ አልባነት የሰራው
"ግፍ" እና "ፍትህ አልባነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የተደገሙት ትኩረት ለመስጠት ሲሆን እንደ ድርጊቶች ሊገለጽ ይችላል። "ቤቱን እና የላይኛውን ክፍሎች/ሰገነቱን ለመስራት ሰዎችን በፍትህ አልባነት አስገደደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
ቤቱ
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ ንጉሥ ኢዮአቄምን እና ቤተሰቡን ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰገነቱ ላይ ሰፊ ክፍሎች ያሉት ትልቅ ቤት… ሰፋፊ መስወኮቶች …ጥድ

እነዚህ ባህሪያት ሁሉም በጣም ውድ የሆነን ቤት ይገልጻሉ።

Jeremiah 22:15

የጥድ ሳንቃ እንዲኖርህ የፈለከው ይህ መልካም ንጉሥ የሚያደርግህ ሆኖ ነውን?

ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮአቄምን ስለ ውድ ቤተመንግሥቱ ለመገሰጽ ነው። "ከጥድ የተሰራ ቤተመንግሥት መልካም ንጉሥ አያደርግህም።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አባትህም አልበላም አልጠጣምን…. ይህን በማድረጉ ከጽድቅ ጎደለን?

ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚጠይቀው ኢዮአቄምን ስለ አባቱ ስለ ንጉሥ ኢዮስያስ አርአያነት ሊያስታውሰው ነው። "አባትህ ንጉሥ ኢዮስያስ፣ መልካም ህይወት ኖሯል፣ ሆኖም…ይህ ጽድቅ ከማድረግ አላገደውም።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍትህን እና ጽድቅን አደረገ

እነዚህ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ረቂቅ ስሞች የተደገሙ ትኩረት ለማድረግ ሲሆን እንደ ድርጊቶች ተደርገው ሊጻፉ ይችላሉ። "በፍትሃዊነት እና በትክክል አደረገ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 22:17

ሌሎችን በማጥፋትህ… ከጭንቀት በስተቀር በዐይኖችህን እና በልብህ ምንም አይኖርም

እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው ማየት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን "ልብ" የሚለው ለማሰብ ሜቶኖሚ/ ነው። "ሌሎችን ከማጥፋት … በስተቀር በፍጹም ምንም ነገር አታይም ወይም አታስብም" ወይም "የምትመለከተው እና የታስበው ሁሉ ሌሎችን ስለ ምታታልልበት መንገድ ንጹህ ደም የምታፈስበትን፣ ደግሞም ሌሎችን የምትጨቁንበትን እና የምታጠፋበትን መንገዶች ነው" በሚሉት ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ተገቢያልሆነ ትርፍ

ይህ በማታለል ወይም ተገቢያልሆኑ መንገዶችን በመጠቀም ገንዘብ ማግኘት ነው።

የንጹሃንን ደም ማፍሰስ

እዚህ ስፍራ "ደም…ማፍሰስ" የሚለው የተያያዘው ከግድያ ጋር ነው፤ "ደም" የሚያመለክተው የተገደሉትን ሰዎች ነው። "የዋህ ሰዎችን መግደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሌሎችን ማጥፋት

"ገንዘብ ለማግኘት በሌሎች ላይ የሃይል ድርጊት መፈጸም"

ለእርሱ አያለቅሱለትም

በቁጥር 18 ላይ፣ ያህዌ በቀጥታ ለኢዮአቄም መናገሩን አቁሞ ለሌሎች ሰዎች መናገር ይጀምራል። እዚህ ስፍራ "ለቅሶ" የሚለው የሚያመለክተው በኢዮአቄም ሞት ማዘንን ነው። "ኢዮአቄም በሚሞትበት ጊዜ አያለቅሱለትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

አህያ እንደሚቀበር ይቀበራል፤ ጎትተው አውጥተው ይጥሉታል

የኢዮአቄም ቀብር የተገለጸው ሰዎች አህያ በሚቀብሩበት መንገድ እንደሚደረግ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በድኑን የአህያ በድን በሚቀብሩበት መንገድ ይቀብሩሉ፤ እየጎተቱ ወስደው ይጥሉታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 22:20

አጠቃላይ መረጃ፡

እዚህ ስፍራ ያህዌ ለኢየሩሳሌም ሰዎች፣ እንደሚጠፉ እየተናገረ ይመስላል።

ድምጻችሁን አንሱ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር መጮህን ያመለክታል። በዚህ ሁኔታ፣ በሀዘን እያለቀሱ ነው። "ጩሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የዓባሪም ተራሮች

በእየሩሳሌም ደቡብ ምስራቅ የሚገኝ የተራራ ሰንሰለት (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላም በነበርክበት ጊዜ ከአንተ ጋር ተነጋግሬያለሁ

"መልካም ታደርግ በነበረበት ጊዜ ከአንተ ጋር ተነጋግሬያለሁ"

ልምድህ ይህ ነበር

"የአኗኗርህ መንገድ እንደዚህ ነበር"

ድምጼን አልሰማህም

መስማት ለመታዘዝ ሜቶኖሚ/ ነው። "አንተ እኔን አልታዘዝክም" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 22:22

ነፋስ እረኞችሽን ሁሉ ነድቶ ይወስዳቸዋል

የህ ቃላትን በመደጋገም የሚደረግ ገለጻ ነው - ያህዌ "እረኛ" የሚለውን ሃሳብ በተለያዩ ሁለት መንገዶች ተጠቅሞበታል። እዚህ ስፍራ "እረኞች" የሚለው ለእየሩሳሌም መሪዎች የቀለ ዘይቤ ነው፣ እናም ነፋስ "ነድቶ" ይወስዳቸዋል። ነፋስ ያህዌን ይወክላል። "እኔ መሪዎችሽን ነፋስ ነድቶ የወሰዳቸው ይመስል ጠርጌ እወስዳቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ምርኮ ይወሰዳሉ

"ምርኮኛ ይሆናሉ" ወይም "በስደት ይሄዳሉ"

አንተ በ'ሊባኖስ' የኖርክ ቤትህን በጥድ ቤት የሰራህ

ያህዌ ንጉሣዊውን ቤተመንግሥት እንደ 'ሊባኖስ' እና 'የጥድ ቤት' የገለጸው በብዙ ጥድ የተሰራ በመሆኑ ነው። "አንተ በሊባኖስ ጥድ በተሰራ በቤተ መንግሥት የምትኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በ …የምትኖር

ይህ "አንተ" የሚለው ተውላጠ ስም ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው ንጉሡን ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

አንተ እንዴት ታዝናለህ

የዕብራይስጡ ትርጉም ግልጽ አይደለም። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እነርሱ እጅግ ለአንተ ያዝናሉ" ወይም 2) "አንተ ታላቅ የጭንቀት ድምጽ ታሰማለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በወሊድ ላይ እንደምትገኝ ሴት የምጥ ስቃይ ሲደርስብህ

ጠላቶቹ ሲያሸንፉት ንጉሡ የሚሰማው ስቃይ ሴት ልጅ ስትወልድ እንደሚሰማት ስቃይ ጠንካራ ይሆናል። "ሴት በምጥ ሰአት እንደሚደርስባት ያለ ስቃይ በሚደርስብህ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 22:24

እኔ ህያው እንደሆንኩ

"በእርግጥ እኔ ህያው እንደሆንኩ።"ያህዌ ይህንን አገላለጽ የተጠቀመው እርሱ ቀጥሎ የሚናገረው በእርግጥ እውነት ለመሆኑን ለማሳየት ነው" ይህ ጸና መሃላ የሚደረግበት መንገድ ነው። "እኔ በህያውነቴ እምላለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም እንኳን አንተ… የቀኝ እጄ ማህተም ብትሆንም

ያህዌ ኢኮንያንን የእጁ ቀለበት ሊሆን ይችል እንደነበር ይነግረዋል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በቀኝ እጄ ያለው ማህተም

የቀለበት ማህተም አንድ ንጉሥ በመዛግብት ላይ የስልጣን ማህተሙን ለማሳረፍ ይገለገልበት ነበር። ስለዚህም የቀለበት ማህተም የአገዛዝ ስልጣንን ይወክላል። ቀኝ እጅም ደግሞ የመግዛት ስልጣንን ይወክላል። "ንግሥናዬን ስልጣን የሚያመለክተው በቀኝ እጄ ያለው የቀለበት ማህተም" በሚለው ውስጥ

እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ እጥልሃለሁ
"እኔ ከእጄ እጥልሃለሁ" ወይም "እኔ በፍጥነት ከእጄ እጥልሃለሁ"ህይወትህን ለሚፈልጓት አሳልፌ ሰጥቼሃለሁ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ህይወትህን የሚፈልጓት እንዲማርኩህ አገርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ለ...እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ የሚወክለው ሀይል እና ቁጥጥርን ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ህይወትህ ለሚፈልጉ
ይህ ሀረግ የሚወክለው አንድን ሰው ለመግደል መፈለግን ወይም መሞከርን ነው። ይህ ሀረግ በኤርምያስ 11:21 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "አንተን ለመግደል የሚሞክሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 22:27
ሊመለሱባት የሚፈልጉት ይህች ምድር
ይህ የሚያመለክተው የይሁዳን ምድር ነው።
ይህ የተናቀ እና የተሰበረ ዕቃ/ገንቦ ነውን?... አታውቅምን?
በቁጥር 28 ላይ የተናጋሪው ማን እንደሆነ ግልጽ አይደለም።
ይህ የተናቀ እና የተሰበረ ዕቃ/ገንቦ ነውን? ይህ ኢኮንያን የተባለ ሰው ማንንም ደስ የማያሰኝ ገንቦ ነውን?

ኢኮንያን የተገለጸው አንዳች ጥቅም እንደማይሰጥ ገንቦ እና በማንም እንደማይወደድ ሰው ተደርጎ ነው። ጥያቄዎቹ የሚያጎሉት ምንም ዋጋ ወይም ወዳጅ እንደሌለው ነው። "ኢኮንያን የተሰበረ ዕቃ ያህል ዋጋ የሌለው እና በእርሱ ማንም ደስ የማይሰኝበት ሰው ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
እነርሱን አውጥታችሁ ጣሏቸው
ኢኮንያን እና የእርሱ ትውልዶች የተገለጹት ከእቃ ወጥቶ እንደሚጣል ቆሻሻ ወደ ሌላ አገር እንደተጣሉ ተደርገው ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 22:29
ምድር፣ ምድር፣ ምድር
ያህዌ መልዕክቱን ለምድሪቱ ሰዎች ሁሉ የተናገረው የምኖሩባትን ምድር በመጣራት ነው። ርዕሱ የተደጋገመው ለመልዕክቱ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)
ልጅ አልባ ይሆናል
ኢኮንያን በርካታ ልጆች ነበሩት። ስለዚህ የዚህ ሀረግ ትርጉም ልጆች የሌሉት ተደርጎ ይቆጠራል ማለት ነው። ልጆቹ በእርሱ ስፍራ ተክተውት አልነገሡም። "አንዳች ልጅ እንደሌለው ይሆናል" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በዳዊት ዙፋን ላይ መቀመጥ
በዙፋን ላይ መቀመጥ በንግሥና መግዛት ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "መንገሥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 23
Jeremiah 23:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ከቁጥር 1-4 ፣ ያህዌ እስራኤልን እንደ መሰማሪያው፣ የእስራኤልን ህዝብ እንደ በጎቹ እንደዚሁም የእስራኤልን መሪዎች እንደ እረኞች አድርጎ ይገልጻል። እረኞች በጎችን የመጠበቅ ሃላፊነት አለባቸው፤ ነገር ግን መሪዎቹ ይህንን አያደርጉም ነበር። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
መንጋዬን በተናችሁ ደግሞም ነዳችኋቸው
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለተኛው በመጀመሪያው ሀረግ ላያ የለውን ሀሳብ ያጠናክራል። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 23:3
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ስለ እስራኤል ህዝብ እነርሱ የእርሱ በጎች እንደሆኑና የእስራኤል መሪዎች ደግሞ የእርሱ እረኞች እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ መሰማሪያቸው ስፍራ
ያህዌ የእስራኤልን ምድር የህዝቡ መልካም መሰማሪያ አድርጎ ይገልጻል። ይህ መልካም መሰማሪያ ፍላጎታቸውን የሚያገኙበት ለመሆኑ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ወደ መልካም መስክ" ወይም "የሚፈልጉትን ሁሉ የሚያገኙበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
ፍሬያማ ይሆናሉ ደግሞም ይበዛሉ
"መብዛት/መጨመር" የሚለው ቃል እንዴት "ፍሬያማ" እንደሚሆኑ ያብራራል። "እነርሱ በቁጥር በብዙ ይጨምራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ አስነሳለሁ
"እኔ እሾማለሁ"
ከእንግዲህ አይፈሩም ወይም አይጎዱም

"አይጎዱም"የሚለው ቃል አንድ ሰው እንዲፈሩ አድርጓቸዋል ማለት እና በመሰረቱ "ፍርሃት" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከእንግዲህ ማንም አያስፈራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከእነርሱ አንዳቸውም
"ከህዝቤ አንዱም"
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
x
Jeremiah 23:5
እዩ
ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው አስደናቂ መረጃ ትኩረት ለመስጠት የሚያነቃ ነው።
ቀናት እየመጡ ነው
መጪው ጊዜ የተነገረው ወደ ተናጋሪው ወይም ወደ አድማጩ እንደሚመጣ አካል ተደርጎ ነው። "ጊዜው ይመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ አስነሳለሁ
የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም እርሱ ተከታይ ሚሆነውን ይሾማል ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የጽድቅ ቅርንጫፍ
ይህ የዳዊት ትውልድ የሆነ መጪው ንጉሥ የተገለጸው በዛፍ ላይ እንዳደገ ቅርንጫፍ ተደርጎ ነው። "ጻድቅ ትውልድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የጽድቅ ቅርንጫፍ
አንዳንድ ዘመናዊ ቅጂዎች ይህንን "የዙፋኑ ህጋዊ ወራሽ" በሚል ይተረጉሙታል።
በምድሪቱ ፍርድን እና ጽድቅን ያደርጋል
"ፍርድ" እና "ጽድቅ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች እንደ ድርጊቶች ሊገለጹ ይችላሉ። "ሰዎች በፍትህ እና በጽድቅ እንዲያከናውኑ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በምድሪቱ
እዚህ ስፍራ "ምድር" የሚያመለክተው በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "በአገሪቱ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ይሁዳ ይድናል
እዚህ ስፍራ "ይሁዳ" የሚለው የሚያመለክተው የይሁዳ ህዝብ ነው። "የይሁዳ ሰዎች ይድናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ይሁዳ ይድናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ ይሁዳን ከጠላቶቻቸው ያድናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
እስራኤል በሰላም ይኖራል
እዚህ ስፍራ "እስራኤል" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው። "የእስራኤልን ህዝብ በሰላም ይኖራል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ይጠራል
ይህ ንጉሡን ያመለክታል
ያህዌ ጽድቃችን ነው
"ጽድቅ" የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ድርጊት/ተግባር ሊገለጽ ይችላል። " ለእኛ ትክክል የሆነው የሚያደርግ፣ ያህዌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

## Jeremiah 23:7

አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ቁጥሮች ምንም እንኳን በኤርምያስ 16፡14-15 ላይ ከሚገኘው ጋር ፍጹም አንድ ባይሆኑም በጣም ተመሳሳይ ናቸው። እነዚያ እንዴት እንደተተረጎሙ ያነጻጽሩ።
እዩ
ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው አስደናቂ መረጃ ትኩረት ለመስጠት የሚያነቃ ነው።
ቀናት እየመጡ ነው
መጪው ጊዜ የተነገረው ወደ ተናጋሪው ወይም ወደ አድማጩ እንደሚመጣ አካል ተደርጎ ነው። "ጊዜው ይመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ህያው እንደሆንኩ
"እኔ ያህዌ በእርግጥ ህያው እንደሆንኩ።" ሰዎች ይህንን አገላለጽ የሚጠቀሙት ቀጥሎ የሚናገሩት ነገር በእርግጥ እውነት መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ ጽኑ ቃል ኪዳን የማድረግ ምልክት ነው። ይህ በኤርምያስ 4፡2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።"እኔ በእርግጥ በክብሬ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሚያመጣ እና የሚመልስ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይሰጣሉ ደግሞም ሊጣመሩ ይችላሉ። "የሚመልስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤል" ወይም "የእስራኤል መንግሥት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሰሜናዊ ምድር እና እነርሱ የተሰደዱበት ምድር
ይህ የሚያመለክተው አስሩ ሰሜናዊ የእስራኤል ነገዶች ምርኮኛ የሆኑበትን እና በአካባቢያቸው በሚገኙ አገራት ውስጥ የተበተኑበትን መንገድ ነው።
ከዚያ በገዛ ምድራቸው ይኖራሉ
ይህ እስራኤላውያን ከየት እንደ ተበተኑ ያመለክታል። ይህ ይበልጥ ግልጽ ተደርጎ ሊጻፍ ይችላል። "ከዚያ ዳግም በገዛ ምድራቸው ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

## Jeremiah 23:9

አጠቃላይ መረጃ፡
ከቁጥር 9-13 ደረስ ኤርምያስ የያህዌን መልዕክት ለሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት ያደርሳል። ኤርምያስ በቁጥር 9 ላይ ይናገራል፣ ነገር ግን በቁጥር 10 ላይ የሚገኘው ቃል የኤርምያስ ይሁን የያህዌ ግልጽ አይደለም።
ነቢያትን በሚመለከት፣ ልቤ በውስጤ ተሰብሯል፣ ደግሞም አጥንቶቼ ሁሉ ተንቀጥቅጠዋል
ነቢዩ ልቡ እንደተሰበረ እና አጥንቶቹ እንደ ተንቀጠቀጡ የሚናገረው ከሀሰተኛ ነቢያት የተነሳ የሚደርስበትን ቅጣት በመፍራት ነው። "ከሀሰተኛ ነቢያት የተነሳ በሚደርሰው ታላቅ ፍርሃት አድርብኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ልቤ በውስጤ ተሰበረ
ፈሊጡ የሚናገረው ጥልቅ ሀዘንን ነው። "በጣም አዝኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አጥንቶቼ ሁሉ ተንቀጠቀጡ
እዚህ ስፍራ ምንቀጥቀጥ የተያያዘው ከፍርሃት ጋር ነው። "በጣም ፈርቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ሰከረ ሰው ሆንኩ፣ ወይን ጠጅ እንደተሞላ ሰው ሆንኩ
የሰከሩ/የጠጡ ሰዎች ራሳቸውን መቆጣጠር አይችሉም። እንደዚሁ ሁሉ፣ ኤርምያስ የያህዌን ቅጣት ከመፍራት የተነሳ ራሱን መቆጣጠር ተስኖታል። "እኔ እንደ ጠጣ ሰው ሆኛለሁ፣ ራሴን መቆጣጠር ተስኖኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሪቱ በምንዝርና ተሞልታለች
ምድሪቱ መያዣ ዕቃ ተደርጋ እና አመንዝሮች ደግሞ ዕቃውን ሙሉ ለሙሉ እንደሞሉ ቁሶች ተደርጎ ተገልጾዋል። ያም ማለት፣ በምድሪቱ የሚገኝ እያንዳንዱ ሰው ዘማዊ ሆኖ ሲገለጽ፣ ይህም በተራው በጣም ብዙ ሰዎች ዘማዊ እንደሆኑ አጋኖ ይገልጻል። (ግነት እና አጠቃላ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
አመንዝሮች
እዚህ ስፍራ ይህ ቃል ምናልበት ሁለት ስሜቶች አሉት። በቀጥታ ሲተረጎም በአገሪቱ የሚገኙ ወንዶች በገዛ ሚስቶቻቸው ላይ አመንዝረውባቸዋል ማለት ሲሆን፣ በዘይቤያዊ ትርጉሙ ጣኦት ለማምለክ ሲሉ ያህዌን ተተውታል የሚል ትርጉምም አለው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሪቱ ደረቀች
አንዳንድ ዘመናዊ ቅጂዎች ይህንን የዕብራይስጥ ሀረግ "ምድሪቱ አለቀሰች" በማለት ይተረጉሙታል።
የእነዚህ ነቢያት መንገዶች ክፉ ናቸው
የሀሰተኛ ነቢያት ክፉ ድርጊቶች የተገለጹት በክፉ መንገድ ላይ እንደተራመዱ ተደርጎ ነው። "እነዚህ ነቢያት ክፉ የሆኑ ነገሮችን እያደረጉ ነው" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

## Jeremiah 23:11

አያያዥ ሃሳብ፡
ኤርምያስ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን የያህዌ መልዕክት ማድረሱን ይቀጥላል።
ነቢያቱ እና ካህናቱ ተበክለዋል
ውሃ በቆሻሻ እንደሚበከል ነቢያቱ እና ካህናቱ በኃጢአት ረክሰዋል። "ነቢያቱ እና ካህናቱ ኃጢአተኞች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ክፋታቸውን በቤቴ እንኳን አግኝቼዋለሁ!
"ክፋት" የሚለው ረቂቅ ስም እንደ ድርጊት ሊገለጽ ይችላል። "በቤተ መቅደሴ ጭምር ክፉ ድርጊት እንደፈጸሙ አውቃለሁ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
በእኔ ቤት
ይህ የሚያመለክተው በእየሩሳሌም የሚገኘውን ቤተ መቅደስ ነው
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን

ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
"ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
መንገዳቸው በጨለማ ውስጥ በድጣማ ስፍራ እንደመሄድ ይሆናል
የድርጊታቸው አደገኛነት የተገለጸው በጨለማ በሚያድጥ የገደል ጠርዝ ተንሸራቶ እንደመውደቅ እና ራሳቸውን እንደመጉዳት ተደርጎ ነው። "ድርጊቶቻቸው በሚያድጥ ስፍራ በጨለማ እንደመራመድ ያልተረጋጉ እና አደገኞች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በእነርሱ ላይ ጥፋት አልካለሁ
ያህዌ ጥፋትን የሚገልጸው ካህናቱን እና ሀሰተኛ ነቢያቱን እንዲያጠቃ እንደሚልከው ጠላት አድርጎ ነው። "ጥፋት እንዲሰርስባቸው አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቅጣት በሚደርስባቸው አመት
"የሚቀጡበት ጊዜ ሲመጣ" ወይም "እኔ እነርሱን የምቀጣበት ጊዜ ሲደርስ"
Jeremiah 23:13
አያያዥ ሃሳብ፡
ኤርምያስ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን የያህዌ መልዕክት ማድረሱን ይቀጥላል።
ህዝቤን ከትክክለኛ መንገድ አውጥተዋል
የህዝቡ በሀሰተኛ ነቢያት መታለል የተነገረው በተሳሳተ መንገድ እንደ መምራት ተደርጎ ነው። "ህዝቤን እስራኤላውያንን አስተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዝሙት ፈጽመዋል
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ለሚስቶቻቸው ታማኞች አልነበሩም ወይም 2) ሌሎች አማልዕክትን ማምለካቸው እንደ መንፈሳዊ ዘማዊነት ተነግሯል
በማታለል ተራምደዋል
የዚህ ፈሊጥ ትርጉም የማታለል ህይወት ኖረዋል። "ከታማኝነት ውጭ መኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የክፉ አድራጊዎችን ክንዶች አበርትተዋል
እዚህ ስፍራ "እጆች" የሚለው የሚያመለክተው ጠቅላላውነ የአንድን ሰው ማንነት ነው። "ክፉ የሚያደርጉትን አበርትተዋል" ወይም "ክፉ የሚያደርጉ ሰዎችን አበረታተዋል" (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ማንም ከክፉ ድርጊቱ አልተመለሰም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "እያንዳንዱ ክፉ ስራው ቀጠለ"
ሁሉም እንደ ሰዶም ... እንደ ገሞራ ሆኑ
ሰዶም እና ገሞራ እግዚአብሔር ከሰማይ ሆኖ በእሳት ያጠፋቸው እጅግ ክፉ የሆኑ ከተሞች ነበሩ። "ሁሉም እንደ ሰዶም...እንደ ገሞራ ክፉ ሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ብዙውን ጊዜ አርምያስ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ ሀሳብን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እዩ
እዚህ ስፍራ "እዩ" የሚለው ቃል አድማጩን ቀጥሎ ለሚነገረው ጠቃሚ መረጃ ትኩረት ለመስጠት የሚያነቃ ነው።
እኔ መራራ እንጨት/ሬት እንዲበሉ እና የተመረዘ ውሃ እንዲጠጡ አደርጋቸዋለሁ
መራራ እንጨት ለመብላት ደስ የማያሰኝ በጣም መራራ የሆነ ተክል። ይህ ሀረግ የሚገልጸው ያህዌ በክፉ ነቢያት ላይ የሚያመጣውን ቅጣት ነው። በተመሳሳይ መንገድ መራራው እንጨት መራራ ሲሆን ውሃመውም የተመረዘ ነበር፣ የያህዌም ቅጣት በክፉ ነቢያት ላይ እንዲህ ያለ ይሆናል።
ላደርገው ነው
"በቶሎ አደርገዋለሁ"
ከነቢያቱ መርዝ ወጥቷል
እዚህ ስፍራ የካህናቱ ክፉ ትምህርት እና ሀሰተኛ ትንቢቶች የተገለጹት ምድሪቱን እንደሚበክሉ ቆሻሻ ነገሮች ተደርገው ነው። "ከነቢያት ክፉ መጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ብክለት
የሚገኙበትን አየርን፣ ውሃን፣ ወይም አፈርን የሚበክሉ ቆሻሻ እና ጤናማ ያልሆኑ ነገሮች
Jeremiah 23:16
አያያዥ ሃሳብ፡
ኤርምያስ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን የያህዌ መልዕክት ማድረሱን ይቀጥላል።
የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ብዙውን ጊዜ አርምያስ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ ሀሳብን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እነርሱ አምኝተዋችኋል!
"ነቢያቱ እውነት ያልሆነውን ነገር እንድታምኑ አድርገዋል!"
ከአይምሯቸው የፈለቀውን ቅዠት
እዚህ ስፍራ "አይምሮ" የሚለው የሚያመለክተው የሀሰተኛ ነቢያትን ሀሳብ ነው። "እነርሱ የሚገምቱት ቅዠት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከያህዌ አፍ ያልሆነ
እዚህ ስፍራ "አፍ" የሚያመለክተው ያህዌ የተናገረውን ነው። "ያህዌ ያልተናገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ሳያቋርጡ ይናገራሉ
"ሳያቋርጡ" የሚለው ቃል ይህ ሁሌም የሚናገሩት ነገር እንደሆነ አጋኖ በትኩረት ለመግለጽ ነው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
በእናንተ ላይ ጥፋት አይመጣም
"በእናንተ ላይ ምንም ክፉ ነገር አይደርስም"
ነገር ግን በያህዌ ምክር ላይ ማን ተገኝቷል?የእርሱን ቃል ማን አይቷል ማንስ ሰምቷል? ለእርሱ ቃል ማን ልቡን ሰጥቶ ሰምቷል?
እነዚህ ጥያቄዎች የዋሉት ካህናቱ እና ሀሰተኛ ነቢያቱ ያህዌን ባለመታዘዛቸው ለመገሰጽ ነው። "ማንም ያህዌን አላማከረውም። ማንም ያህዌ የተናገረውን አልተረዳም። ማንም የያህዌን ትዕዛዞች አልታዘዘም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ለእርሱ ቃላት ትኩረት ስጡ፣ አድምጡም
እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ነገር ይገልጻሉ። በአንድ ሀረግ ሊጠቃለሉ ይችላሉ።
"ሙሉ ለሙሉ ለቃሉን ታዘዙ"
Jeremiah 23:19
አያያዥ ሃሳብ፡
ኤርምያስ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን የያህዌ መልዕክት ማድረሱን ይቀጥላል።
ይህ ከያህዌ ዘንድ የመጣ መዕበል ነው...ቁጣው እየወጣ ነው... አውሎ ነፋስ በሃይል እየተሽከረከረ እየነፈሰ ነው
እነዚህ ሶስት ሀረጎች ሁሉም ታላቅ ማዕበልን ሲገልጹ ይህም የያህዌን ቁጣ የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ይህ በተነጻጻሪ ዘይቤ ሊገለጽ ይችላል። "የያህዌ ቁጣ እንደ ታላቅ ማዕበል፣ በቁጣ ወጥቶ እንደ አውሎ ነፋስ በሀይል እየተሽከረከረ እየመጣ ነው" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
አውሎ ነፋስ
ሀይለኛ የነፋስ ማዕበል
በክፉዎች ራስ ላይ በሃይል እየተሽከረከረ የነፍሳል
የያህዌ ቁጣ የተነገረው በክፉዎች ዙሪያ እንደሚነፍስ አውሎነፋስ ነው። "እንደ አውሎ ነፋስ በክፉዎች ላይ እየመጣ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ እስኪሆን የያህዌ ቁጣ አይመለስም
የያህዌ ቁጣ የተነገረው በራሱ ህይወት እንዳለው እና ማድረግ እንደሚችል ተደርጎ ነው። "ይህ እስኪሆን የያህዌ ቁጣውን አይመልስም/አያቆምም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በልቡ ያለውን ፈቃዱን ይፈጽማል
እዚህ ስፍራ "የልብ ፈቃድ" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ እንዲሆኑ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ነው። "ያቀደውን ቅጣት ሁሉ ፈጽሞ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የኋለኛው ዘመን
"መጪው ጊዜ"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Jeremiah 23:21

አያያዥ ሃሳብ፡

ኤርምያስ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን የያህዌ መልዕክት ማድረሱን ይቀጥላል።

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ከቁጥር 21-40 ይናገራል፡፤

እነርሱ አሁንም ትንቢት ይናገራሉ

ሀሰተኛ ትንቢት መናገራቸው ግልጽ ነው። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ሆኖም የሀሰት ትንቢት ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ምክሬ ባለበት ቢቆሙ/ቢገኙ ኖሮ

ያህዌ እነዚህ ካህናት እና ሀሰተኛ ነቢያት የያህዌ ምክር በሚገኝበት በሰማይ ቢገኙ ምን ሊሆን ይችል እንደነበረ ይናገራል። ይህ መላምታዊ ሁኔታ ሊሆን የማይችል ነው። "በእውነት ሰምተውኝ ቢሆን ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ የምገኝበት ምክር

በጥንቱ ዘመን፣ እግዚአብሔር በሰማይ ከመላዕክት ጋር ስብሰባ ያደርጋል ተብሎ ይታሰብ ነበር። ያህዌ የሚጠቅሰው ሰዎች ሊገኙበት የማይችሉትን እንደዚህ አይነቱን ስብሰባ ነው። ይህ በኤርምያስ 23:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ከዚህ ዘወር ማለት

የዚህ ፈሊጥ ትርጉም እርሱ እነዚህን ነገሮች ማድረግ ያቆማሉ ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 23:23

አያያዥ ሃሳብ፡

ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን እና በኤርምያስ 23፡ 40 ላይ የሚጨርሰውን መልዕክቱን ማድረሱን ይቀጥላል።

እኔ የቅርብ አምላክ ብቻ ነኝን… የሩቅስ አምላክ አይደለሁምን?

ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ካህናቱ እና ሀሰተኛ ነቢያቱ እርሱ በሁሉም ስፍራ እንደሚገዛ አለማሰባቸውን ለመገሰጽ ነው። "እኔ እዚህ በእየሩሳሌም ውስጥ ብቻ የምገኝ አምላክ አይደለሁም… ነገር ግን እኔ በሁሉም ስፍራ እገኛለሁ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ልመለከተው በማልችለው ስፍራ ሊደበቅ የሚችል አለን?

ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው ካህናቱ እና ሀሰተኛ ነቢያቱ እርሱ የሚያደርጉት ክፉ ነገር እርሱ እንደማይመለከት አድርገው በማሰባቸው ሊገስጻቸው ነው። "ማንም እኔ ልመለከተው በማልችለው ስውር ስፍራ መደበቅ አይችልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ሰማይንና ምድርን የሞላሁ አይደለሁምን?

ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ በሰማይ እና በምድር በሁሉም ስፍራ እንደሚገኝ ለማጉላት ነው። "እኔ በሰማይ እና በምድር በሁሉም ስፍራ እገኛለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 23:25

አያያዥ ሃሳብ፡

ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን እና በኤርምያስ 23፡ 40 ላይ የሚጨርሰውን መልዕክቱን ማድረሱን ይቀጥላል።

በሀሰት ይተነብያሉ

"ማታለል" የሚለው ቃል በገላጭ ወይም ተውሳከ ግስ ሊገለጽ ይችላል። "የሚያታልሉ/ሀሰተኛ ነገሮችን እየተነበዩ" ወይም "በሀሰት/በማታለል እየተነበዩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ስም/በስሜ

ይህ ሀረግ የሚያመለክተው በያህዌ ሀይል እና ስልጣን ወይም እንደ እርሱ ተወካይ መናገርን ነው። ይህ ሀረግ በኤርምያስ 14፡14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ህልም አለኝ!

ይህ ህልም ከእግዚአብሔር ነው ማለታቸው ነው። ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "ከያህዌ ዘንድ የሆነ/የመጣ ህልም አለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከራሳቸው አይምሮ ሀሰትን የሚተነብዩ ነቢያት፣ እና በልባቸው ውስጥ ካለው ሽንገላ የሚተነብዩ ነቢያት ትንቢት እስከ መቼ ይቀጥላል?

ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ነቢያቱ ይህንን ማድረጋቸውን መቀጠል እንደሌለባቸው ትኩረት ለመስጠት ነው።"ነቢያት ራሳቸው ያበጃቸውን ሀሰተቶች ማወጃቸው መቀጠል የለበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከራሳቸው አይምሮ የሆነ የሀሰት ትንቢት… በልቦቻቸው ካለ ሽንገላ የሆነ ትንቢት

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ሀሰተኛ ነቢያት ትንቢቶቻቸውን ራሳቸው እንደሚያበጃቸው ትኩረት ይሰጣሉ። "ከራሳቸው አይምሮ ብቻ የሚመነጩ ትንቢታዊ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ስሜን ረሱ… ስሜን ረስተዋል

እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው ቃል በአጠቃላይ የያህዌን ማንነት ያመለክታል። "ህዝቤ እኔን ከማምለክ ይልቅ በኣልን እንደሚያመልክ አድርገዋል/መርተውታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የበኣልን ስም በመምረጥ

እዚህ ስፍራ "የበኣል ስም" የሚያመለክተው በኣል የተባለውን ጣኦት ነው። "ህዝቤ እኔን ከማምለክ ይልቅ በኣልን እንዲያመልክ መርተውታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 23:28

አያያዥ ሃሳብ፡

ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን እና በኤርምያስ 23፡ 40 ላይ የሚጨርሰውን መልዕክቱን ማድረሱን ይቀጥላል።

ገለባ ከፍሬ ጋር ምን ግንኙነት አለው?

ገለባ ገበሬዎች ዋጋ ያለውን ፍሬ ከለዩ በኋላ የሚቀረው ዋጋ የሌለው እገዳ ነው። ይህ ጥያቄ ትኩረት የሚሰጠው በሀሰተኛ መልዕክት እና ከያህዌ ዘንድ በሆነው መልክት መሃል ያለውን ልዩነት ነው። "ገለባ እና ፍሬ ሙሉ ለሙሉ የተለያዩ ሁለት ነገሮች ናቸው።" ወይም "ጥቅም የሌለው ገለባ በፍጹም ዋጋ እንዳለው ፍሬ አይደለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

ቃሌ እንደ እሳት አይደለምን?… አለትን ሰብብሮ እንደሚያደቅ መዶሻስ አይደለምን?

ያህዌ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው ቃሉ ከሰዎች ተራ ቃል እጅግ እንደሚበልጥ ትኩረት ለመስጠት ነው። በዚህ መንገድ የእርሱ ቃል እንደ እሳት ወይም መዶሻ ነው። "ቃሌ እንደ እሳት ሀያል ነው… ደግሞም አለትን ሰባበብሮ እንደሚያደቅ መዶሻ ሀይለኛ ነው።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እቃወማለሁ

"እኔ ከዚህ በተቃራኒ ነኝ"

ከሌላ ሰው ቃላት ይሰርቃሉ

ይህ የሚያመለክተው ሀሰተኛ ነቢያት ሌቦች መሆናቸውን ነው። የራሳቸውን ሀሰተኛ መልዕክት ከማዘጋጀት እንኳን አልፈው እርስ በእርሳቸው መልዕክቶችን ያለፈቃድ እስኪሰራረቁ ድረስ እጅግ ክፉዎች ናቸው።

Jeremiah 23:31

አያያዥ ሃሳብ፡

ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን እና በኤርምያስ 23፡

40 ላይ የሚጨርሰውን መልዕክቱን ማድረሱን ይቀጥላል፡፡

እዩ

ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው አስደናቂ መረጃ ትኩረት ለመስጠት የሚያነቃ ነው፡፡ "ትኩረት ስጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡

በነቢያት ላይ መነሳት

"ነቢያትን በመቃወም"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ምላሶቻቸውን የሚጠቀሙ

እዚህ ስፍራ "ምላሶች" የሚለው የመናገርን ችሎታ የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሀሰት የሚያልሙ

"ከእግዚአብሔር ዘንድ ህልም አለን የሚሉ፣ ነገር ግን ከእግዚአብህር ዘንድ ያልሆኑ ናቸው"

Jeremiah 23:33

አያያዥ ሃሳብ፡

ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን እና በኤርምያስ 23፡ 40 ላይ የሚጨርሰውን መልዕክቱን ማድረሱን ይቀጥላል፡፡

አጠቃላይ መረጃ፡

ከቁጥር 33-40 ድረስ "ሸክም" የሚለውን ቃል በመደጋገም የሚደረግ አገላለጽ አለ፡፡ አንዳንዴ "መልዕክተኛ" ማለት ሲሆን በሌላ ጊዜ "ለመሸከም ከባድ የሆነ ሸክም" ማለት ይሆናል፡፡ ከተቻለ ይህ የቃላት ድግግም አገላለጽ እንዳለ ሊጠበቅ ይገባዋል፡፡

አንተን እጠይቅሃለሁ... አንተ እንዲህ ትላለህ

በእነዚህ ሁለት ሁኔታዎች "አንተ" የሚሉት ነጠላ ቁጥር ሲሆኑ ኤርምያስን ያመለክታሉ፡፡ (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

የያህዌ ሸክም ምንድን ነው?

እዚህ ስፍራ "ሸክም" ማለት ከያህዌ ዘንድ የሆነ መልዕክት ወይም ትንቢት ማለት ነው፡፡

ሸክሙ እናንተ ናችሁ... እናንተን አስወግዳለሁ

እነዚህ "እናንተ" የሚሉት ሁለት ሁኔታዎች ብዙ ቁጥር ሲሆኑ የሚያመለክቱት ሀሰተኛ ነቢያትን እና ካህናትን ነው፡፡ (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ሸክሙ እናንተ ናችሁ

እዚህ ስፍራ "ሸክም" ማለት ከባድ ሸክም ነው፡፡ ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ እነርሱ ያህዌን ያስቆጣሉ እርሱም ከእንግዲህ ከእነርሱ ጋር መሆን አይፈቅድም ማለት ነው፡፡ "እኔ እናንተን በመሸከም ያደከማችሁኝ ሸክሞች ናችሁ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ ሸክም ነው

እዚህ ስፍራ "ሸክም" ከያህዌ ዘንድ የሆነ መልዕክት ወይም ትንቢት ነው፡፡

የእርሱ ቤት/ቤቱ

እዚህ ስፍራ "ቤት" በውስጡ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው፡፡ "የእርሱ ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 23:35

አያያዥ ሃሳብ፡

ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን እና በኤርምያስ 23፡ 40 ላይ የሚጨርሰውን መልዕክቱን ማድረሱን ይቀጥላል፡፡

አጠቃላይ መረጃ፡

ከቁጥር 33-40 ድረስ "ሸክም" የሚለውን ቃል በመደጋገም የሚደረግ አገላለጽ አለ፡፡ አንዳንዴ "መልዕክተኛ" ማለት ሲሆን በሌላ ጊዜ "ለመሸከም ከባድ የሆነ ሸክም" ማለት ይሆናል፡፡ ከተቻለ ይህ የቃላት ድግግም አገላለጽ እንዳለ ሊጠበቅ ይገባዋል፡፡

እናንተ እንዲህ ማለታችሁን ትቀጥላላችሁ... 'ያህዌ የተናገረው ምንድን ነው?'

ይህን ዐረፍተ ነገር መመዝገብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ "እያንዳንዱ ሰው ወዳጁን እና ወንድሙን 'ያህዌ ምን ምላሽ ሰጠ?' ደግሞም 'ያህዌ ምን ትዕዛዝ ሰጠ/ምን አለ?'" ብሎ መጠየቁን ይቀጥላል፡፡

ነገር ግን ከእንግዲህ በኋላ 'ስለ ያህዌ ሸክም መናገር አይኖርባችሁም፣ ምክንያቱም ሸክሙ የእያንዳንዱ ሰው ቃል የራሱ ሸክም ነው፣ እናም

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሁለቱም "የሸክም" ሁኔታዎች ትርጉማቸው "መልዕክት" ማለት ነው፡፡ "ከእንግዲህ ህልማችሁን 'የያህዌ ሸክም' ብላችሁ መጥራት የለባችሁም ምክንያቱም እዚያ የእያንዳንዱ ሰው የራሱ ቃሎች ብቻ ናቸው፣ እናም" ወይም 2) የመጀመሪያው 'ሸክም' የሚለው ትርጉም "መልዕክት" ማለት ሲሆን የሁለተኛው ትርጉም "ከባድ ሸክም" ማለት ነው፡፡ "ከእንግዲህ 'ስለ ያህዌ መልዕክት' መናገር የለባችሁም ምክንያቱም እያንዳንዳችሁ የምትናገሯቸው ቃላት በዚህ መንገድ 'ከባድ ሸክም' የሆኑ ናቸው፡፡"

እናንተ የአምላካችንን ቃሎች... ገልብጣችኋል

አንድን ነበር "መገልበጥ" ያንን ነገር ማጣመም ወይም መልኩን ማበላሸት ነው፡፡ "እግዚአብሔር የተናገረውን ሳይሆን እናንተ ማለት የፈረጋችሁትን ለመናገር የሰራዊት ጌታ የህያው እግዚአብሔርን መልዕክት ቀይራችኋል"

Jeremiah 23:37

አያያዥ ሃሳብ፡

ያህዌ ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እና ካህናት በ23፡9 ላይ የጀመረውን መልዕክት ያጠናቅቃል፡፡

አጠቃላይ መረጃ፡

ከቁጥር 33-40 ድረስ "ሸክም" የሚለውን ቃል በመደጋገም የሚደረግ አገላለጽ አለ፡፡ አንዳንዴ "መልዕክተኛ" ማለት ሲሆን በሌላ ጊዜ "ለመሸከም ከባድ የሆነ ሸክም" ማለት ይሆናል፡፡ ከተቻለ ይህ የቃላት ድግግም አገላለጽ እንዳለ ሊጠበቅ ይገባዋል፡፡

አንተ የምትናገረው ይህንን ነው

እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው ኤርምያስን ነው፡፡ (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ነገር ግን እንዲህ ብትሉ... ምክንያቱም እንዲህ ብላችኋል...እኔ በምልካችሁ ጊዜ... እንዲህ አትሉም... እናንተን አነሳለሁ... እጥላችኋለሁ... መሳለቂያ አደርጋችኋለሁ

በእነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ "እናንተ" የሚለው ብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተው ካህናትን እና ሀሰተኛ ነቢያትን ነው፡፡ (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ስለዚህ፣ እነሆ

"ስለዚህ ተጠንቀቁ" ይህ አንባቢው ቀጥሎ ለሚሆነው ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ያነቃዋል፡፡

እኔ እናንተን እንስቼ ከእኔ አርቄ ልጥላችሁ ነው

ያህዌ የሚናገረው እነዚህን ካህናት እና ሀሰተኛ ነቢያት እንደሚጣል እቃ እንደሚጥላቸው እና ሩቅ ስፍራ ወደ ስደት እንደሚጥላቸው ይናገራል፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለእናንተ የሰጠኋት ከተማ

ይህ እየሩሳሌምን ያመለክታል፡፡

የማይረሳ ዘላለማዊ ሀፍረት እና ስድብ አደረግባችኋለሁ

"ለዘለዓለም በሚኖር በሀፍረት እሸፍናችኋለሁ፣ የማትረሱትን ስድብ አደርስባችኋለሁ" ወይም "ሰዎች ለዘለዓለም እንዲሳለቁባችሁ አደርጋለሁ፡፡ ሰዎች ውርደታችሁን በፍጹም አይረሱም፡፡" "ያህዌ የካህናቱን እና የሀሰተኛ ነቢያቱን ውርደት የሚናገረው ሀፍረትን እና ስድብን እንደ ልብስ በላያቸው እንደሚደርብ አድርጎ ነው፡፡

ያ አይረሳም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፡፡ "ያ ለዘለዓለም ይኖራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

## Chapter 24

### Jeremiah 24:1

እኔ

የዚህ ተውላጠ ስም ሁኔታዎች ሁሉ ኤርምያስን ያመለክታሉ

እነሆ

እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል የሚያሳየው ኤርምያስ አስደሳች የሆነ ነገር እንደተመለከተ ነው።

ይህ ራዕይ የተፈጸመው... እነርሱን ወደ ባቢሎን

ይህ የታሪኩ ክፍል የዋለው የተፈጸሙ ድርጊቶች የተፈጸሙበትን ታሪካዊ መረጃ ለመስጠት ነው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

አናጺዎች

ነገሮችን ለመገንባት/ለማነጽ ችሎታ ያላቸው ሰዎች

ብረት ቀጥቃጮች

የተለያዩ የብረት ዕቃዎችን የሚሰሩ ሰዎች

ሊበሉ አይችሉም... አይበሉም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ሊበላቸው አይችልም... ማንም አይመገባቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

### Jeremiah 24:4

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፣ "ያህዌ

ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ የተለየ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ መልዕክት ሰጠኝ። እንዲህ አለ፣ 'ያህዌ" ወይም "ያህዌ ይህንን መልዕክት እንዲህ ሲል ተናገረኝ፡ 'ያህዌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳን ስደት ለእነርሱ ጥቅም ስል እመለከታለሁ

እዚህ ስፍራ "መመልከት" የሚለው ያህዌ ለእነርሱ ይጠነቀቃል የሚል ትርጉም አለው። "እኔ ለተሰደዱት ይሁዳ በመልካም ጥንቃቄ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልክ እንደ እነዚህ መልካም በለሶች

መልካሞቹ በለሶች የሚወክሉ ወደ ከለዳዊያን ምድር በስደት የሄዱትን አይሁዶች ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ዐይኖቼን ለመልካም በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ

እዚህ ስፍራ "ዐይኖቼን አደርጋለሁ" ማለት እርሱ ያያቸዋል ማለት ነው። እነርሱን ማየት ለእነርሱ ጥንቃቄ ማድረግ ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እኔ እባርካቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ መልሼ እሰበስባቸዋለሁ፣ አላፈርሳቸውም። እኔ እተክላቸዋለሁ፣ አልነቅላቸውም

እነዚህ ሁለት ዘይቤዎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለተኛው የመጀመሪያውን ያጠናክራል። "በከለዳዊያን አገር እንዲበለጽጉ እረዳቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ መልሼ እሰበስባቸዋለሁ፣ አላፈርሳቸውም።

ያህዌ ስለ ስደተኞቹ በመልካም መሬት ላይ እንደሚተክላቸው እንጂ እንደማይነቅላቸው ተክሎች አድርጎ ይናገራል። "በምድሪቱ ላይ እንጻቸዋለሁ፣ እንጂ አላስወግዳቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔን እንዲያውቁኝ ልብ እሰጣቸዋለሁ

እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው የሚያመለክተው የእነርሱን ፍላጎቶች ነው። "እኔን ማወቅ እንዲፈልጉ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሙሉ ልባቸው ወደ እኔ ይመለሳሉ

እዚህ ስፍራ "ሙሉ ልባቸው" የሚለው "ሙሉ ለሙሉ" ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ሙሉ ለሙሉ ወደ እኔ ይመለሳሉ" ወይም "ያለመቆጠብ ወደ እኔ ይመለሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

### Jeremiah 24:8

ነገር ግን ለመበላት እጅግ መጥፎ እንደሆኑት መጥፎ በለሶች

ይህ ተነጻጻሪ ዘይቤ በእየሩሳሌም ስላሉ ክፉ ባለስልጣናት ለመበላት እጅግ እንደ ተበላሹ እንደ መጥፎ በለሶች አድርጎ ይገልጻል። መጥፎ በለሶች አንዳች ጥቅም እንደሌላቸው ሁሉ፣ እነዚህ ያህዌን የማይከተሉ ሰዎችም ጥቅም የሌላቸው ናቸው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ አስፈሪ ነገር ወደ ጥፋት አለውጣቸዋለሁ... የተዋረዱ እና መነጋገሪያ፣ መነረጓጠጫ እና ለእርግማን አደርጋቸዋለሁ

እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ ያህዌ የእየሩሳሌምን ሰዎች እንዴት በጥብቅ እንደሚፈርድባቸው ትኩረት ይሰጣሉ። ሌሎች ሰዎች የደረሰባቸውን ሲመለከቱ ይፈራሉ። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

በእነርሱ ላይ ሰይፍ፣ ችጋር፣ እና መቅሰፍት እልክባቸዋለሁ

"በጦርነት፣ በችጋር እና በበሽታ አጠፋቸዋለሁ"

ሰይፍ እሰዳለሁ

እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" ጦርነትን እና የጠላትን ሰራዊቶች ያመለክታል። "እኔ የጠላትን ሰራዊት እልካለሁ" ወይም "ጦርነት እሰዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ፣ ችጋር፣ እና መቅሰፍት

እነዚህ ነገሮች የተነገሩት የእየሩሳሌምን ሰዎች ሊያጠቁ እንደሚችሉ ህይወት እንዳላቸው ነገሮች ተደርገው ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከምድሪቱ ተደምስሰዋል

"አንዳቸውም በምድሪቱ አልቀሩም"

---

## Chapter 25

### Jeremiah 25:1

ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ይህ ነው

ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል ከያህዌ ዘንድ መሆኑ ተጠቁሟል። ይህ ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣውን ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 7:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ይህ ያህዌ ለኤርምያስ የሰጠው መልዕክት ነው" ወይም "ይህ ያህዌ ለኤርምያስ የተናገረው መልዕክት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አራተኛው... የመጀመሪያው

(ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

### Jeremiah 25:3

አሞን

ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

### Jeremiah 25:5

እያንዳንዱ ሰው ከክፉ መንገዱ እና ከብልሹ ምልልሱ ይመለስ

ኤርምያስ ሰዎች ይፈጽሙት የነበሩትን ድርጊት ስላቆሙ ሰዎች የሚናገረው እነዚያ ሰዎች ከዚያ ድርጊት ዞረው እንደተመለሱ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ክፉ መንገዱ እና የልምምዶቹ ብልሽት

"ክፉ መንገድ" እና "የልምምዶቹ ብልሽቶች" የሚሉት አገላለጾች ተመሳሳ ትርጉም ሲኖራቸው የሚያደረጓቸውን ክፉ ነገሮች ሁሉ ያመለክታሉ። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የልምምዶቹ ብልሹነቶች

"ብልሹ ድርጊቶቹ"

ሌሎች አማልዕክትን አትከተሉ

ኤርምያስ ራሱን ለጣኦት አሳላፎ የሰጠን ሰው የሚገልጸው ያሰው ያንን ጣኦት ተከትሎ እንደሄደ አድርጎ ነው። "ራሳችሁን ለሌሎች አማልዕክት አሳልፋችሁ አትስጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእጆቻችሁ ስራ እርሱን አታስቆጡት/አታነሳሱት

"እርሱን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያህዌን ነው። "የእጆቻችሁ ስራ" የሚለው ሀረግ ሊሰጠው የሚችሉት ትርጉሞች 1) ይህ የሚያመለክተው ሰዎች በእጆቻቸው የሚሰሯቸውን ጣኦታት ነው። "ያህዌን በሰራችሁት ጣኦት አታስቆጡት/አታነሳሱት" ወይም 2) "እጆች" ከሚለው ቃል ጋር እነዚያን ድርጊቶችን የሚወክል ሴኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/በመሆን የአንድን ሰው ድርጊት የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። "በምታደርጓቸው ነገሮች ያህዌን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አታስቆጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ እንዲሁም ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:7

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በእጆቻችሁ ስራ እናንተን እንድቀጣ አነሳስታችሁኛል

በኤርምያስ 25፡6 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የእጆቻችሁ ስራ" ለሚለው ሀረግ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰዎች በእጆቻቸው ለሰሯቸው ጣኦታት ማሳያ/ማመሳከሪያ ነው። "በእጆቻችሁ በሰራችኋቸው ጣኦታት ምክንያት እናንተን እንድቀጣችሁ አነሳስታችሁኛል" ወይም 2) "እጆች" ከሚለው ቃል ጋር እዚያን ድርጊቶችን የሚወክል ሴኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/በመሆን ይህ አንድ ሰው የፈጸመውን ድርጊት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው "በምታደርጓቸው ነገሮች ያህዌን አታስቆጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ እንዲሁም ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እናንተን እንድቀጣ

"በእናንተ ላይ ቅጣት እንዳደርስ"

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል

ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እዩ

"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"

እነርሱን በእዚህ ምድር ላይ አመጣለሁ

"በዚህ ምድር ላይ...ማምጣት" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም፣ እነርሱ በምድሪቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ያጠቃሉ ማለት ነው። "ይህንን ምድር እንዲያጠቁ እነርሱን አመጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለጥፋት እነርሱን አለያቸዋለሁ

"ለጥፋት ... መለየት" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም አንድን ነገር ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት ማለት ነው። "እኔ እነርሱን ሙሉ ለሙሉ አጠፋቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ማስፈራሪያ አደርጋቸዋለሁ

"ማስፈራሪያ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ምልክ ሊተረጎም ይችላል። "እኔ እነርሱን ሰዎችን የሚያስፈራሩ ነገሮች አደርጋቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለጥላቻ አደርጋቸዋለሁ

"ጥላቻ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠንካራ ተቀባይነትን የማጣት ድምጽ የሚያመለክት ሲሆን በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች የሚጠሉት አካል"

Jeremiah 25:10

የወፍጮ ድንጋዮች

እነዚህ ሁለት ትላልቅ ክብ ድንጋዮች ሲሆን እህል ለመፍጨት ያገለግላሉ

የደስታ እና የሀዘን ድምጽ፣ የሙሽራው እና የሙሽራይቱ ድምጽ

ይህ በኤርምያስ 7፡34 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ይህ ምድር በሙሉ ሰው የማይኖርበት እና የሚያስፈራ ይሆናል

"ሰው የማይኖርበት" እና "የሚያስፈራ" የሚሉት ቃላት በግሳዊ ሀረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እኔ ይህ ምድር ሰው የማይኖርበት እና ሰዎችን የሚያስፈራ እንዲሆን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:12

ሰባው አመት ሲፈጸም

"ከሰባዎቹ አመታት በኋላ" ወይም "ሰባ አመታት ካለፉ በኋላ"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ ወዲያኛው ሰው የማይኖርበት

"ሰው የማይኖርበት/ጠፍ" የሚለው ስም በቅጽል መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ለዘለዓለም ሰው የማይኖርበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈው ነገር ሁሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ኤርምያስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጻፋቸው ነገሮች ሁሉ" ወይም "አንድ ሰው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጻፋቸው ነገሮች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እንደ ስራቸው መጠን እንደ እጆቻቸው ስራዎች እመልስላቸዋለሁ

ያህዌ የአገሪቱን ህዝቦች ስላደረጉት ነገር የሚያደርስባቸውን ቅጣት የሚገልጸው ለእነርሱ መልሶ ክፍያ እንደሚያደርግ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ድርጊቶች እና የእጆቻቸው ስራዎች

እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "የእጆቻቸው ስራ" የሚለው ፈሊጥ "እጆች" ከሚለው ቃል ጋር ሰውየውን የሚወክል ሴኔቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ በመሆን የሚያመለክተው የአንድን ሰው ድርጊቶች ነው። "እነርሱ ያደረጓቸው ነገሮች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ፈሊጣዊ አነጋገር እንዲሁም ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:15

ይህንን የቁጣ ወይን ጠጅ ጽዋ ውሰዱ

ያህዌ እጅግ ከፍ ያለውን ቁጣውን የገለጸው በወይን እንደተሞላ ጽዋ አድርጎ ነው። "ቁጣዬን የሚወክውን ይህን የወይን ጽዋ ውሰዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አገራቱ ሁሉ ... እንዲጠጡት አድርጉ

"አገራት" የሚለው ቃል የሚወክለው የአገራቱን ሰዎች ነው። ያህዌ ህዝቡ ቁጣው እንደሚደርስበት የገለጸው በዋንጫው ውስጥ ያለውን ወይን እንደሚጠጡ አድርጎ ነው። "የአገራቱ ሰዎች ሁሉ ... ወይኑን እንዲጠጡ አድርጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ይጠጣሉ ከዚያም ይንገዳገዳሉ በብስጭት ይጮሃሉ

ያህዌ ህዝቡ ስለ ቁጣው መፍራቱን የገለጸው ህዝቡ የጽዋውን ወይን ጠጥቶ እንደ ሰከረ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በመካከላቸው ከምልከው ሰይፍ አስቀድሞ

እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚወክለው ጦርነትን ነው። "በመሃላቸው እንዲደርስ ከምፈቅደው ጦርነቶቹ የተነሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 25:17

አያያዙ ሀሳብ፡

ይህ ምንባብ የያህዌን እጅግ ከፍ ያለ ቁጣ፣ የአገራቱ ህዝቦች ከጽዋው እንደ ጠጡ አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ መላው አገራት ... ከዚያ እንዲጠጡ አድርጌያለሁ

"አገራት" የሚለው ቃል የሚወክለው የአገራቱን ህዝቦች ነው። "እኔ የሁሉም አገር ሰዎች ... ከጽዋው ወይኑን እንዲጠጡ አድርጌያለሁ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አስፈሪ የሆነ ነገር

"አስፈሪ" የሚለው ቅጽል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎችን የሚያስፈራ ነገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ለጥናቻ እና እርግማ የሚዳርግ ነገር

"ጥላቻ" የሚለው ቃል የሚገልጸው ጠንካራ ነቀፌታን/ተቀባይነት ማጣትን የሚያመለክት ድምጽን ነው። "ጥላቻ" እና "እርግማን" የሚሉት ሁለቱም በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ሰዎች የሚጠሉት እና የሚረግሙት ነገር" በሚለው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ውስጥ እንደሚገኘው።
እነርሱ በዚህ በዛሬው ቀን እየሆኑ ናቸው
ለዚህ ሀረግ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የኤርምያስ መጽሐፍ የተጻፈበትን ጊዜ እና ኤርምያስ ይህንን ትንቢት ከተናገረ በኋላ ያለውን ጥቂት ጊዜ ይመልከቱ። ወይም 2) ይህ ማለት ኤርምያስ እዚህ ስፍራ የተነበያቸው ነገሮች መሆን ጀምረዋል።
Jeremiah 25:19
አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ምንባብ የያህዌን እጀግ ከፍ ያለ ቁጣ፣ የአገራቱ ህዝቦች ከጽዋው እንዲጠጡ እንዳደረጋቸው በዘይቤ መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንደዚሁም ደግሞ ሌሎችም አገራት ሊጠጡት ይገባል
"አገራት" የሚለው ቃል የሚወክለው የአገራቱን ህዝቦች ነው። "ከሌላ አገር የሆኑ ሰዎችም ደግሞ ከጽዋው ወይን መጠጣት ይኖርባቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የተደባለቀ ቅርስ ያላቸው ህዝቦች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አባቶቻቸው ከተለያየ የህዝብ ወገን የሆኑ ሰዎች። ወይም 2) በግብጽ የሚኖሩ የባእድ አገር ሰዎች።
ዖጽ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 25:22
አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ምንባብ የያህዌን እጀግ ከፍ ያለ ቁጣ፣ የአገራቱ ህዝቦች ከጽዋው እንዲጠጡ እንዳደረጋቸው በዘይቤ መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ባህሩ
ይህ የሜዲትራንያንን ባህር ያመለክታል
ድዳን፣ቴማን፣ እና ቡዝ
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የጭንቅላቶቻቸውን ፀጉር ከጎን እና ጎን የሚቆረጡ ሁሉ
ይህ ምናልባት ሰዎች ፀጉራቸውን በአጭር የሚቆረጡ፣ የአህዛብን አምላክ ለማክበር ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል። አንዳንድ ዘመናዊ ቅጂዎች ይህንን የዕብራይስጥ አገላለጽ "በበረሃማው ዳርቻ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ" በሚል ይተረጉሙታል። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 9:26 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እነርሱም ደግሞ ይህን መጠጣት አለባቸው
"እነርሱም ደግሞ ከጽዋው መጠጣት አለባቸው"
Jeremiah 25:24
አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ምንባብ የያህዌን እጀግ ከፍ ያለ ቁጣ፣ የአገራቱ ህዝቦች ከጽዋው እንዲጠጡ እንዳደረጋቸው በዘይቤ መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ዘምሪ
ይህ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
እያንዳንዱ ከወንድሙ ጋር
ይህ ከአንዱ በመቀጠል ሌላው እያንዳንዱ ሰው የሚል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ከአንዱ በመቀጠል ሌላው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉም ጽዋውን ከያህዌ እጅ መጠጣት አለባቸው
እዚህ "ጽዋው" በውስጡ ለያዘው ወይን ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ/ ነው። "እነዚህ ሁሉ ሰዎች በያህዌ እጅ ካለው ጽዋ መጠጣት አለባቸው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 25:27
አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ምንባብ የያህዌን እጀግ ከፍ ያለ ቁጣ፣ የአገራቱ ህዝቦች ከጽዋው እንዲጠጡ እንዳደረጋቸው በዘይቤ መግለጹን ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
በመካከላችሁ ከምልከው ሰይፍ አስቀድሞ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚወክለው ጦርነትን ነው። "በመካከላችሁ እንዲደርስ ከምፈቅደው ጦርነቶቹ አስቀድሞ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በእኔ ስም የተጠራችው ከተማ
ይህ እየሩሳሌምን ሲያመለክት በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽም ይችላል። "በስሜ የተጠራችው ከተማ" ወይም "በስሜ የጠራኋት እየሩሳሌም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እናም እናንተ ራሳችሁ ከቅጣት ነጻ መሆን ይገባችኋልን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ህዝቡን ለመገሰጽ እና እንደሚቀጣቸው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "ስለዚህም እናንተ ራሳችሁ ከቅጣት ነጻ እንሆናለን ብላችሁ ታስባላችሁ?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በምድሪቱ ነዋሪዎች ላይ ሁሉ ሰይፍ እጠራለሁ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚወክለው ጦርነትን ነው። ያህዌ በህዝቡ ላይ ጦርነት ማወጅን የተናገረው በእነርሱ ላይ ሰይፍ እንደሚጠራ አድርጎ ነው። "እኔ በምድሪቱ ነዋሪዎች ላይ ሁሉ ጦርነት አውጃለሁ" ወይም "እኔ በምድሪቱ ነዋሪዎች ላይ ሁሉ ጦርነት አመጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Jeremiah 25:30
ያህዌ እንደ አንበሳ ይጮሃል
ኤርምያስ የያህዌን በጣም መጮህ የተናገረው እንደ አንበሳ እንደሚያገሳ አድርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከፍ ካሉ ስፍራዎች
ይህ ሀረግ ለሰማይ ሜቶኖሚ ነው። "ከሰማይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ መንጋ/ህዝብ ላይ እጅግ ይጮሃል
ኤርምያስ ስለ ያህዌ እርሱ አንበሳ እንደሆነ እና የእርሱ ህዝብም የበግ መንጋ እንደሆነ አድርጎ ነው። በጎች አንበሳ ሲያጠቃቸው ተስፋ ቢስ እንደሚሆኑ፣ ህዝቡ ያህዌ ሊቀጣቸው ሲመጣ ተስፋ ቢስ ይሆናሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የወይን ፍሬ የሚረግጡ
ይህ በወይን መጭመቂያ በእግራቸው ወይን ስለሚጨምቁ ሰዎች ይናገራል።
እስከ ምድር ዳርቻ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን በምድር ዳርቻ የሚገኝ ስፍራ የሚል ትርጉም አለው። ሁለቱንም ጫፎች በማመላከት፣ በመሃል የሚገኙ ስፍራዎችን ሁሉ ያሳያል። "በምድር ላይ የሚገኝ ሩቅ ስፍራ" ወይም "በምድር ላይ ወደ ሁሉም ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር እና ከአጽናፍ አጽናፍ የሚሉትን ይመልከቱ)
በስጋ ለባሽ ላይ ሁሉ
እዚህ ስፍራ "ስጋ" የሚለው የሚወክለው ሰብአዊነትን ነው። "በሁሉም የሰው ልጅ" ወይም "በሁሉም ሰው ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ለሰይፍ የሚዳርጋቸው ክፉዎች
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል ወታደሮች እንደ ጦር መሳሪያ የሚጠቀሙበትን መሳሪያ ሲያመለክት ይህም ጦርነትን ይወክላል። "ለሰይፍ መዳረግ" የሚወክለው ሰዎች በጦር ሜዳ መሞታቸውን ነው። "ክፉ ሰዎች በጦር ሜዳ እንዲሞቱ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 25:32

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እዩ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"ጥፋት ከአገር ወደ አገር ይዛመታል ያህዌ በእያንዳንዱ አገር ታላቅ ጥፋት እንደሚሆን "ጥፋትን" ከአንድ አገር ወደሌላ አገር እንደሚሄድ ሰው አድርጎ ይናገራል። "በየአገሩ ታላቅ ጥፋት ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ታላቅ ነፋስ ከምድር ዳርቻ ይነሳል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ያህዌ ስለ በቢሎናውያን ሰራዊት እና ስለሚያደርሱት ጥፋት እንደ ታላቅ ማዕበል አድርጎ ይናገራል። ወይም 2) ያህዌ ታላቅ ቁጣውን ብዙ ጥፋት እንደሚያደርስ ታላቅ ማዕበል አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በያህዌ የተገደሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም አያለቅስላቸውም፣ አይሰበስባቸውም፣ ወይም አይቀብራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በምድር ላይ እንደ ፍግ ይሆናሉ
በድኖቹ በምድር ላይ ከወደቀ ፍግ ጋር የተነጻጸሩት፣ አስጸያፊ እንደሚሆኑ እና ማንም የማይቀብራቸው ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። በኤርምያስ 16፡4 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይልከቱ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 25:34
እረኞች
ያህዌ ስለ እስራኤል መሪዎች ለህዝቡ ሃላፊነት እንዳለባቸው እና እንደሚጠብቁት እረኞች አድርጎ እና በውስጠ ታዋቂነት እነርሱ በጎች እንደሆኑ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በአፈር ላይ ተንከባለሉ
ይህ የሀዘን፣ ለቅሶ ወይም ጭንቀት ምልክት ነው። (ምልክታዊ/ትምዕርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ የመንጋው ጠባቂዎች
ይህም ሀረግ እንደዚሁ፣ ህዝቡን ለመጠበቅ ሃላፊነት ያለባቸውን እና እንደ በግ መንጋ የተገለጸውን ህዝብ የሚጠብቁትን የእስራኤልን መሪዎች ያመለክታል። "እናንተ የእስራኤል መሪዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የመታረጃችሁ ቀን ቀርቧል
ብዙውን ጊዜ የሚታረዱት በጎች ናቸው፣ ነገር ግን እዚህ ስፍራ ያህዌ እረኞቹን አርዳለሁ ይላል። "መታረድ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "እናንተን የማርድበት ጊዜ ደርሷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምጸት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
እንደ ውብ ሸክላ ስትወድቁ ትበታተናላችሁ
ያህዌ ስለ እስራኤል መሪዎች መጥፋት መሬት ላይ ወድቆ እንደ ደቀቀ የሸክላ ስብርባሪ አድርጎ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እንደ ውብ ሸክላ ትወድቃላችሁ የደቀቀ ስብርባሪያችሁ ምድር ላይ ይበታተናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ያህዌ መሰማሪያቸውን ይደመስሳል
መሪዎቿ በሰላም እየኖርን ነው ብለው
ያህዌ መሰማሪያቸውን ያጠፋል
ያህዌ መሪዎቿ መንጋውን የሚንከባከቡበት "መሰማሪያ" መልካም እንደሆነ እና በሰላም እየኖሩ እንደሆነ ስለሚያስቡ መሪዎች ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 25:37
ስለዚህ ሰላማዊዎቹ መሰማሪያዎች ይደመሰሳሉ
ያህዌ ለእስራኤል መሪዎች እረኞች እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ይቀጥላል። እዚህ ስፍራ አገሪቱ እነርሱ በሰላም እየኖሩባት እንደሆነ የሚያስቧት "መሰማሪያ" እንደሆነች ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሰላማዊዎቹ መሰማሪያዎች ከያህዌ ታላቅ ቁጣ የተነሳ ይደመሰሳሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከእርሱ ታላቅ ቁጣ የተነሳ ያህዌ ሰላማዊዎቹን መሰማሪያዎች ይደመስሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ እንደ ደቦል አንበሳ፣ ከዋሻው ወጥቷል
ያህዌ ህዝቡን በከፍተኛ ቁጣ መቅጣቱ የተገለጸው፣ ያህዌ አደን ለማደን ከዋሻው እንደወጣ አንበሳ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ምድራቸው ማስደንገጫ/ማስፈራሪያ ይሆናል
"አስፈሪ/አስቃቂ" የሚለው ቃል በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "ምድራቸው ሰዎችን የሚያስፈራ ስፍራ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የጨቋኖች ቁጣ
ይህ የእስራኤልን ጠላቶች ቁጣ ያመለክታል።

---

Chapter 26
Jeremiah 26:1
ይህ ቃል እንዲህ ሲል ከያህዌ ዘንድ መጣ
ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። በኤርምያስ 18፡1 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልክተው እንደ አስፈላጊነቱ ለውጥ ያድርጉ። "ይህ መልዕክት የመጣው ከያህዌ ዘንድ ነው። እርሱ እንዲህ አለ" ወይም "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ቃል እንዲህ ሲል ከያህዌ ዘንድ መጣ
ያህዌ መልዕክቱን ለማን እንደ ሰጠ፣ ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ይህ ቃል ወደ ኤርምያስ ከያህዌ ዘንድ እንዲህ ሲል መጣ" ወይም "ያህዌ ይህን መልዕክት ለኤርምያስ ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ከተሞች
"ከተሞች" የሚለው ቃል በከተማዋ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ከይሁዳ ከተማ የመጡ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከነገርኩህ ቃል አንዳች አታጉድል!
"ከነገርኩህ አንዳች ነገር አታስቀር!"
እያንንዱ ሰው ከክፉ መንገዱ ይመለሳል
ያህዌ የአንድ ሰው የአኗኗር ስልት "መንገድ" እንደሆነ ወይም ሰውየው የሚጓዝበት ጎዳና እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። "እያንዳንዱ ሰው ክፉ የአኗኗር መንገዱን ያቆማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህም ከማደርሰው ጥፋት እመለሳለሁ/ይቅር እላለሁ
ይህ ሁኔታን መሰረት ያደረገ ጥፋት/ቅጣት ነው። ይሁዳ ንስሃ ከገባ፣ እግዚአብሔር ጥፋት አያደርስም ይልቁንም ያድናቸዋል።
የልምምዶቻቸው ክፋት
"እነርሱ የሚኖሩበት ክፉ ምነገድ" ወይም "እነርሱ የሚያደረጓቸው ክፉ ነገሮች"
Jeremiah 26:4
በፊታችሁ ባስቀመጥኩት በህጌ ለመሄድ እናንተ እኔን የማትሰሙኝ ካልሆነ
ያህዌ የሰውን የህይወት ስልት ያሰው እንደሚሄድበት ጎዳና አድርጎ ይናገራል። "እኔን ያማትታዘዙኝ እና የሰጠኋችሁን ህግ የማትጠብቁ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህንን ቤት እንደ ሴሎ አደርጋለሁ
ያህዌ በሴሎ የሚገኘውን የማምለኪያ ስፍራ አጥፍቷል፣ ደግሞም ይህንን የአምልኮ ስፍራ ማስፈራሪያ አድርጎታል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህችን ከተማ ለእርግማን አደርጋታለሁ
ያህዌ ከተማይቱን ወደ ምን እንደሚለውጥ የተነገረው ከተማይቱን ለምን እንደሚያውላት የተነገረ ሜቶኖሚ/ ነው። "ይህችን ከተማ ሌሎች መቀጣጫ/ይህችን ከተማ ባጠፋሁበት መንገድ ሌሎችን ከተሞች እንዳጠፋ ሰዎች እንዲጠይቁኝ አደርጌ/ እንድትሆን አድርጌ አጠፋታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በምድር ላይ በሚገኙ አገራት ሁሉ ፊት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"በምድር ላይ የሚገኙ አገራት ሁሉ እኔ ይህንን ሳደርግ ይመለከታሉ"

Jeremiah 26:7

የያህዌ ቤት

ቤተ መቅደሱ

ሰዎች ሁሉ እርሱን ይዘውት እንዲህ ይላሉ፣ "በእርግጥ አንተ ትገደላለህ!"

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ህዝቡ የሀሰት ሰላምን እውሸት ማመን መረጠ እንጂ ከእውነቱ ጋር መጋጠምን አልወደደም፣ ወይም 2) ህዝቡ ሌሎች ነቢያት የሚናገሩትን ሀሰተኛ ሰላም አመነ፣ ኤርምያስን ግን መወገር እንደሚገባው ህዝቡን ከትክክለኛ መንገድ እንዳወጣ ሀሰተኛ ነቢይ ተመለከተው።

ከበውት...ለምን ትንቢት ትናገራለህ? አሉት

ይህ ግሳጼ በዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከበውት….ይህን ትንቢት መናገር አልነበረብህም" አሉት። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 26:10

አዲሱ በር

ሰዎች ወደ ቤተ መቅደሱ የሚገቡበት የአዲሱ በር ስም።

በገዛ ጆሯችሁ እንነተው ሰምታችኋል

"እናንተ ሰምታችኋል"

ይህ ቤት እና ይህ ከተማ

"በያህዌ ቤተመቅደስ የሚያመለኩ ሰዎች እና በእየሩሳሌም ከተማ የሚኖሩ"

Jeremiah 26:13

መንገዶቻችሁ...ልምምዶቻችሁ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። "እናንተ የምታደረጎቸው ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌን ድምጽ ስሙ

ድምጽ ለሰውየው ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው፤ ደግሞም ይኸው ቃል "አድምጡ" ወይም "ታዘዙ" በሚል ሊተረጎም ይችላል። "ያህዌን ታዘዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በዐይኖቻችሁ መልካም እና ትክክል ሆኖ የሚገኘውን ለእኔ አድርጉ

"መልካም" እና "ትክክል" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ዐይን የሚለው ለሰው አስተሳሰብ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ማድረግ ይገባል የምትሉትን ትክክለኛ ለገር ለእኔ አድርጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የንጹሃንን ደም በራሳችሁ፣ በከተማይቱ እና በነዋሪዎቿ ላይ እያመጣችሁ ነው

ደም በግፍ ለሚደርስ ሞት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን፣ በአንድ ሰው ላይ ደም ማምጣት በጥቃት ለደረሰ ሞት ተጠያቂ ማድረግ ነው። "ራሳችሁን እና ይህችን ከተማ እንዲሁም ነዋሪዎቿን በግፍ ለሚደረግ የንጹሃን ሰዎች ሞት ተጠያቂ እያደረጋችሁ ነው።" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህች ከተማ እና ነዋሪዎቿ

እነዚህ አንድ ህዝብ የተገለጸበት ተመሳሳይ መንገድ ናቸው። ይህም ምናልባት በመጀመሪያ እንደ ቡድን ከዚያም እንደ ግለሰቦች የተነገረ ነው። ከተማይቱ የሚለው በከተማዋ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ ነው። "በከተማይቱ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ እና በዚህ የሚኖሩ እያንዳንዳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ለጆሯችሁ

ጆሮ የሚለው ጆሮ ለሚሰማው ሜቶኖሚ/ ነው። "እናንተ እንድትሰሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 26:16

በያህዌ በአምላካችን ስም

የሰው ስም ለስልጣኑ ሜቶኖሚ/ ነው። "በእግዚአብሔር በአምላካችን በያህዌ ስልጣን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 26:18

አጠቃላይ መረጃ፡

ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ

ሞሬታዊ

ከሞሬት ከተማ ወይም አካባቢ የሆነ/የመጣ ሰው

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል

ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ጽዮን እንደ እርሻ ትታረሳለች...የቤተ መቅደሱ ተራራ ዳዋ የወረሰው ኮረብታ ይሆናል

"ጽዮን " እና "የቤተ መቅደሱ ኮረብታ" የሚሉት የሚያመለክቱት አንድን ስፍራ ነው። ገበሬ መሬቱን ሲያርስ አፈሩን ይገለብጣል፣ በእርሻው ውስጥ የሚገኙ ቅጠላ ቅጠሎች ሁሉ ይነቃቀላል። ቁጥቋጦ ማንም ለምንም የማይፈልጋቸውን አረሞች የያዘ ነው። እነዚህ ሁለት ዘይቤዎች በተመሳሳይ ጊዜ ቃል በቃል እውነተ ተደርገው አይወሰዱም፣ ነገር ግን ይህ አገላለጽ ያህዌ ወራሪዎች የቤተ መቅደሱን አካባቢ ሙሉ ለሙሉ መደምሰስ እንዲችሉ እንደሚፈቅድላቸው በትኩረት ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕዝቅያስ... ለሞት ተሰጠን?

ተናጋሪዎቹ አድማጮቻቸው እነርሱ የሚናገሩትን እንዲሰሟቸው እየሞከሩ ነው። "ሕዝቅያስ ራሱን ለሞት አሳልፎ እንዳልሰጠ... እናተ ራሳችሁ በሚገባ ታውቃላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

መላው ይሁዳ

ምድሪቱ የሚለው ለመላው በዚያ ለሚኖረው ህዝብ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "መላው የይሁዳ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ...እርሱስ ያህዌን አልፈራምን፣ ደግሞስ የያህዌን ፊት በትህትና አልፈለገምን?

ተናጋሪዎቹ አድማጮቻቸው እነርሱ የሚናገሩትን እንዲሰሟቸው እየሞከሩ ነው። "እነርሱ…ሕዝቅያስ ራሱን ለሞት አሳልፎ እንዳልሰጠው እናተ ራሳችሁ በሚገባ ታውቃላችሁ ስለዚህም ያህዌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌን ፊት በትህትና ፈለገ

ፊት የሚለው መላ ሰውነትን የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የያህዌ ቁጣ እንዲበርድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ በገዛ ህይወታችን ላይ የባሰ ጥፋት እንፈጽማለን?

ተናጋሪዎቹ አድማጮቻቸው እነርሱ ከሚናገሩት ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ እየሞከሩ ነው። "ህይወታችን" የሚለው ቃል ለሰዎቹ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ኤርምያስን ብንገድለው፣ በራሳችን ህይወት ላይ የከፋ ክፉ ነገር እንፈጽማለን" ወይም "በራሳችን ላይ የከፋ ነገር ማድረግ አንፈልግም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 26:20

አያያዥ ሀሳብ፡

ኤርምያስ ስለ ራሱ ህይወት መናገሩን አቁሞ በሌሎች ነቢያት ላይ የሆነውን መናገር ይጀምራል

በመሃል እንዲህ ነበር

"እኔ የምናገራችሁ እየተፈጸመ ሳለ፣ እንዲህ ነበር

በያህዌ ስም

የአንድ ሰው ስም ለስልጣኑ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በኤርምያስ 26፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በያህዌ ስልጣን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህች ከተማ እና በዚህች ምድር ላይ የተነገረ ትንቢት

"ከተማ" እና "ምድር" የሚሉት ቃላት በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "በዚህች ከተማይቱ እና በዚህች ምድር ላይ መጥፎ ነገሮች እንደሚደርሱ ትንቢት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱን ቃል ሰማ

"እርሱ የተናገረውን ነገር ሰማ"



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Jeremiah 26:22

አያያዥ ሀሳብ፡

ይህ የኦርዮ ታሪክ መጨረሻ ነው

ኤልናታን…ዓክቦር…አኪቃም… ሳፋን

የወንድ ስሞች ናቸው (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

አስክሬን/ሬሳ

የሞተ ሰውነት

የአኪቃም እጆች… ከኤርምያስ ጋር ነበር

እጅ የሚለው እጅ ለሚሰራው ሜቶኖሚ/ ነው። አኪቃም ወታደር አልነበረም፣ ስለዚህም ምናልባት እርሱ ከህዝቡ ጋር እየተነጋገረ ሀሳባቸውን እንዲቀይሩ ማድረግ ሳይችል አልቀረም። "አኪቃም … ኤርምያስን መርዳት ችሎ ነበር" ወይም "አኪቃም… ሰዎች በኤርምያስ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱበት ሊጠብቀው ችሎ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለመገደል/ለሞት ለሰዎች እጅ አልተሰጠም ነበረ

እጅ የሚለው እጅ ለሚሰራው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አኪቃም ሰዎች ኤርምያስን ለመግደል ሀይል እንዲኖራቸው አልፈቀደላቸውም" ወይም "ህዝቡ ኤርምያስን መግደል አልቻለም ምክንያቱም አኪቃም ይህን እንዲያደርጉ ሀይል አልሰጣቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 27

Jeremiah 27:1

ማነቆ

አንድ ሰው በነጻነት እንዳይንቀሳቀስ የሚከለክል ነገር

ከዚያም በኋላ አስወጣቸዋለሁ

ይህ ኤርምያስ በርካታ ማነቆ እና ቀንበር በዝርዝር ወደ ተጠቀሱት መንግስታት ይልካል ለማለት የተነገረ ይመስላል። ነገር ግን በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ይህን "ከዚያም መልዕክት ላክ" በማለት ተተርጉሟል።

በእነዚያ ንጉሦች አምባሳደሮች እጅ … ወደ ይሁዳ ላካቸው

እጅ የሚለው ለሰውየው ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። " ወደ ይሁዳ፣ … በእነዚያ ነገስታት አምባሳደሮች በኩል ውሰዳቸው" (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ ለአለቆቻቸው ትዕዛዞችን ስጥ

ኤርምያስ ብዙ ሰንሰለቶችን እና ቀንበር ለእያንዳንዱ አምባሳደር/መልዕክተኛ እንደዚሁም ሰንሰለቶቹን እና ቀንበሩን በተመለከተ ለእያንዳንዱ ንጉሥ መልዕክት ይልካል።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ… እንዲህ ይላል

ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Jeremiah 27:5

በታላቁ ሀይሌ እና በተዘረጉ ክንዶቼ

"የተዘረጉ/የተመሱ እጆች" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ታላቅ ሀይልን ሲሆን የመጀመሪያውን ሀረግ ያጠናክራል። "በጣም ታላቅ በሆነው ሀይሌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

በዐይኖቼ ፊት ትክክለኛ ለሆነው ይህን እሰጠዋለሁ

ሌላው ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም "እኔ ለማንኛውም ለወደድኩት ሰው ይህን እሰጣለሁ"

እኔ… እነዚህን ምድሮች ሁሉ ለናቡከደነጾር … ለአገልጋዬ ሰጥቼዋለሁ

እጅ የሚለው በእጅ ለሚሰራው ሀይል የተሰጠ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ሲሆን፣ "ምድር" በእነዚያ ምድሮች ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ ነው። "እኔ… በዚህ ምድር የሚኖሩ ሰዎችን በባሪያዬ… በናቡከደነጾር ስልጣን ስር አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ምድር ጊዜው ደርሷል

የጊዜውን ባህርይ ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። "የእርሱን ምድር የምደመስስበት ጊዜ ደርሷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ይገዛሉ

እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የባቢሎንን መንግስት የሚወክለውን ናቡከደነጾርን ነው። "ባቢሎንን ይረታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 27:8

ያ አንገቱን በንጉሡ ቀንበር ስር አያደርግም

የንጉሡ ባሪያ መሆን የተገለጸው እንስሳ እንደመሆን እና ከባድ ስራ ይሰራ ዘንድ ንጉሡ በአንገቱ ላይ ቀንበር እንደጫነበት ሰው ተደርጎ ነው። "ደግሞስ የማን ህዝብ በፈቃዱ ለንጉሡ ባሪያ ሳይሆን ይቀራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ እጅ እኔ ይህን ደምስሻለሁ

እዚህ ስፍራ እጁ የሚለው ለናቡከደነጾር ሀይል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው፣ ወይም ለናቡከደነጾር ሰራዊት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ሊሆን ይችላል። "ይህንን ለማጥፋት የናቡከደነጾርን ሀይል ተጠቅሜያለሁ" ወይም "የናቡከደነጾር ሰራዊት ይህንን ማጥፋት እንዲችል አቅም ሰጥቼዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 27:9

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ በኤርምያስ በኩል ለይሁዳ ህዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

ሟርተኛ ትንቢት ተናጋሪ

ወደፊት የሚሆነውን የሚናገሩ ሟርተኛ ሰዎች

አንገቱን በንጉሡ ቀንበር ስር የሚደርግ አገር

የንጉሡ ባሪያ መሆን የተገለጸው በትከሻው ላይ ንጉሡ ለከባድ ስራ ቀንበር እንደጫነበት እንስሳ ተደርጎ ነው። ተመሳሳይ የሆኑት ቃላት በኤርምያስ 27፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። "በፈቃደኝነት የንጉሡ ባሪያ የሆኑ አገራት ህዝቦች" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንገቱ ላይ የሚያደርግ አገር

እዚህ ስፍራ አገር የሚለው ለዚያ አገር ህዝብ ሜቶኖሚ/ ነው። "አንገቱን ዝቅ የሚያደርግ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ማልማት/ማረስ

ይህ ማለት መሬትን የምግብ እህል ለማብቀል ማዘጋጀት ማለት ነው

በውስጧ ቤታቸውን ይሰራሉ

"በራሳቸው ምድር ቤቶቻቸውን ይሰራሉ"

Jeremiah 27:12

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ በኤርምያስ በኩል ለይሁዳ ንጉሥ መናገሩን ቀጥሏል።

አንገታችሁን ከባቢሎን ንጉሥ ቀንበር በታች አድርጉ

እዚህ ስፍራ የንጉሡ ባሪያ መሆን የተገለጸው ከባድ ስራ ይሰራ ዘንድ ንጉሡ በትከሻው ላይ ቀንበር እንደጫነበት እንስሳ ተደርጎ ነው። ተመሳሳይ የሆኑት ቃላት በኤርምያስ 27፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

የእናንተን አንገታችሁን ዝቅ አድርጉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"የእናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሴዴቅያስን እና የይሁዳን ሰዎች ስለሆነ ብዙ ቁጥር ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)
የባቢሎን ንጉሥ… ለምን ትሞታለህ?
ኤርምያስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው የንጉሡ ድርጊት ወደ ሞት ስለሚመራው ሊያስጠነቅቀው ነው። "ንጉሥ ሆይ…ይህንን ሳታደርግ ብትቀር፣ በእርግጥ ትሞታለህ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 27:14
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በኤርምያስ በኩል ለይሁዳ ንጉሥ እና ህዝብ መናገሩን ቀጥሏል።
ቃሎቻቸውን አትስሙ
ያህዌ ህዝቡን ስለ ሀሰተኛ ነቢያት እርሱ እንዳልላካቸው እና እየዋሸዋቸው እንደሆነ ያስጠነቅቃል።
እኔ ወደ እናንተ አልላኳቸውም
"እኔ እነርሱን ስላልላኳቸው"
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
በስሜ ሀሰትን ይተነብያሉ
"በስሜ" የሚለው ሀረግ የሚወክለው በያህዌ ሀይል እና ስልጣን ወይም የእርሱ ወኪል ሆኖ መናገርን ነው። እዚህ ስፍራ እነዚህ ነቢያት መልዕክታቸውን ከያህዌ እንደተቀበሉ ይናገራሉ፣ ነገር ግን ከእርሱ አልተቀበሉም። "ሀሰት/ማታለል" የሚለው ረቂቅ ስም "ያታልላሉ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "በሀሰት ተንቢት ሲናገሩ ከእኔ ተቀብለው እንደሚናገሩ ወራሉ፣ ሆኖም ግን እያታለሏችሁ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
እኔ አባርራችኋለሁ
"እኔ አገራችሁን ለቃችሁ እንድትወጡ አስገድዳችኋለሁ"
Jeremiah 27:16
አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ የያህዌን ቃል መናገሩን ቀጥሏል።
የያህዌ ቤት እቃዎች አሁን ከባቢሎን መመለስ ይጀምራሉ!
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ሰዎች ከያህዌ ቤተ መቅደስ የወሰዷቸውን የወርቅ እቃዎች መመለስ ይጀምራሉ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለምን ይህች ከተማ ትፈራርሳለች?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ህዝቡን ለማስጠንቀቅ ነው። "ያህዌ እንድታደርጉ የሚፈልገውን ማድረግ ብትጀምሩ ይህችን ከተማ ከመፍረስ ልታድኑ ትችላላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)እነርሱ ነቢያት ከሆኑ እና፣ በእውነት የያህዌ ቃል ወደ እነርሱ መጥቶ ከሆነ እነርሱ ይለምኑ ይህ ያህዌ እውነት እንዳልሆነ የሚያውቀው መላምታዊ ሁኔታ ነው። "ነቢያት ቢሆኑ እና የያህዌ ቃል በእርግጥ ወደ እነርሱ መጥቶ ቢሆን፣ ይለምኑ ነበር" ወይም "ነቢያት ስላልሆኑ እና በእውነት የያህዌ ቃል ወደ እነርሱ ስላልመጣ አይለምኑም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የያህዌ ቃል በእርግጥ ወደ እነርሱ መጥቶ ቢሆን ኖሮ
"የያህዌ ቃል" የሚለው ሀረግ የሚለው የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሀነን መልዕክት ነው። "በእውነት ያህዌ መልዕክት ሰጥቷቸው ቢሆን ኖሮ" ወይም "በእውነት ያህዌ ለእነርሱ መልዕክት ተናግሮ ቢሆን ኖሮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
የያህዌ ቃል… የሰራዊት ጌታ ያህዌን አለመኑም
ያህዌ ራሱን በሶስተኛ መደብ ይገልጻል። "የእኔ ቃል… የእኔ ነው፣ የሰራዊት ጌታ ያህዌን አልለመኑም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ንጉሥ ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል የተለያዩ ሰፊ ትርጉሞችን ይይዛል። በዚህ ሁኔታ ንጉሡ የሚኖርበትን ንጉሳዊ ቤተመንግስትን ያመለክታል። "የይሁዳ ንጉሥ ቤተ መንግስት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
Jeremiah 27:19
አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ የያህዌን መልዕክት ማምጣቱን ቀጥሏል።
የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
አምዶቹ፣ "ባህር/ገንዳ" ተብለው የሚታወቁት ትላልቆቹ ሳህኖች እና የእርሱን መሰረት
እነዚህ በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚገኙ እቃዎች ነበሩ። "ባህሩ" ትልቅ የነሐስ ጎድጓዳ ሣህን ነው።
ኢዮአኪን
የዕብራይስጡ ጽሁፍ "ኢኮንያን" ይላል፣ ይህ "ኢዮአኪን" ለሚለው የተሰጠ አማራጭ ስም ነው። ብዙ ዘመናዊ ቅጂዎች ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ያው ንጉሥ የተጠቀሰበትን "ኢዮአኪን" የሚለውን ስም ይጠቀማሉ።
Jeremiah 27:21
አጠቃላይ መረጃ:
ኤርምያስ የያህዌን ቃሎች መናገሩን ቀጥሏል።
የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
የይሁዳ ንጉሥ ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል የተለያዩ ሰፊ ትርጉሞችን ይይዛል። በዚህ ሁኔታ ንጉሡ የሚኖርበትን ንጉሳዊ ቤተመንግስትን ያመለክታል። "የይሁዳ ንጉሥ ቤተ መንግስት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ወደ ባቢሎን ይመጣሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች እነርሱን ወደ ባቢሎን ያመጧቸዋል" ወይም "እኔ ወደ ባቢሎን አመጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ እነርሱን እመልሳቸዋለሁ
እንባቢ ያህዌ የሚረዳው ህዝብ እንዳለ ይረዳል።

---

Chapter 28
Jeremiah 28:1
አጠቃላይ መረጃ:
ሐናንያ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ይናገራል
በአራተኛው አመት በአምስተኛው ወር
ይህ በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር አምስተኛው ወር ነው። ይህም በበጋ ወራት ነው። ምዕራባውያን ቀን መቁጠሪያ በሐምሌ መጨረሻ እና በነሐሴ መጀመሪያ ላይ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)
ዓዙር
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰራዊት ጌታ ያህዌ… እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እኔ በባቢሎን ንጉሥ የተጫነውን ቀንበር ሰብሬያለሁ
ሐናንያ ህዝቡ በባርነት ውስጥ መሆኑን የተናገረው እነርሱን ከባድ ስራ ይሰሩ ዘንድ ባቢሎናውያን ቀንበር እንደጫኑባቸው በሬዎች አድርጎ ነው። "ከእንግዲህ ወዲያ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ለባቢሎን ንጉሥ ባሮች እንዳትሆኑ አድርጌያለሁ" ወይም "ከባቢሎን ንጉሥ ባርነት ነጻ አውጥቻችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 28:3

አጠቃላይ መረጃ፡

ሐናንያ መናገሩን ቀጥሏል

ኢዮአኪን

የዕብራይስጡ ጽሁፍ "ኢኮንያን" ይላል፣ ይህ "ኢዮአኪን" ለሚለው የተሰጠ አማራጭ ስም ነው። ብዙ ዘመናዊ ቅጂዎች ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ያው ንጉሥ የተጠቀሰበትን "ኢዮአኪን" የሚለውን ስም ይጠቀማሉ።

የተላኩት

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ የላኳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 28:5

ያህዌ የተናገርከውን ትንቢት ያጽና

"ያህዌ በእውነት የተናገርከውን ትንቢት ያረጋግጥ"

Jeremiah 28:8

ከረጅም ዘመን በፊት ከእኔ እና ከአንተ አስቀድሞ የኖሩ ነቢያት

"ከእኔ እና ከአንት ከዘመናት በፊት የኖሩ ነቢያት"

ይህ ሲሆን እርሱ በእርግጥ ያህዌ የላከው ነቢይ መሆኑ ይታወቃል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ይህ ሲሆን እርሱ በእርግጥ ያህዌ የላከው እውነተኛ ነቢይ መሆኑ ታውቃለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 28:10

ልክ እንደዚህ

"ልክ ሐናንያ በኤርምያስ አንገት ላይ ያለውን ቀንበር እንዳነሳ"

ከእያንዳንዱ ህዝብ አንገት በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነጾር የተጫነውን ቀንበር እኔ እሰብራለሁ

ሐናንያ በባርነት ውስጥ የሚገኘው ህዝብ እንደ በሬዎች እንደሆነ እና ባቢሎናውያን ህዝቡ ላይ ለከባድ ስራ ቀንበር እንደጫኑበት አድርጎ ይናገራል። "እኔ መላው ህዝብ ከእንግዲህ የንጉሥ ናቡከደነጾር ባሪያ እንዳይሆን አደርጋለሁ" ወይም "እኔ እያንዳንዱን አገር ከባቢሎን ንጉሥ ከናቡከደነጾር ባርነት ነጻ አወጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ አገር

"አገር" የሚለው ቃል ለዚያ አገር ህዝብ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "የሁሉም አገር ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነጾር የተጫነ ቀንበር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር የጫነው ቀንበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የተጫነ

በህዝብ ላይ የተደረገ

Jeremiah 28:12

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ ኤርምያስ መጣ፣ "ሂድ

"ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠው። እንዲህም አለው፣ 'ሂድ" ወይም "ያህዌ ይህንን መልዕክት ለኤርምያስ ነገረው፡ 'ሂድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የእንጨቱን ቀንበር ሰብረሃል፣ ነገር ግን እኔ በምትኩ የብረት ቀንበር አደርጋለሁ

"አንተ ደካማውን ቀንበር ሰበርክ ነገር ግን እኔ ይህንን አንተ ልትሰብረው በማትችለው ቀንበር እተካለሁ"

የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል

ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ናቡከደነጾርን እንዲያገለግሉት በእነዚህ ሁሉ አገራት አንገት ላይ የብረት ቀንበር አድርጌያለሁ

ያህዌ አገራትን የናቡከደነጾር ባሪያዎች እንደሚያደርግ የሚናገረው ከባድ ስራ እንዲሰሩ በበሬዎች ላይ ቀንበር እንደሚጭንባቸው አይነት አድርጎ ነው። "እኔ እነዚህን ሁሉ አገራት ባሮች አድርጌያለሁ፣ እናም እነርሱ ናቡከደነጾርን ማገልገል ይኖርባቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 28:15

እናንተ በያህዌ ላይ አምጸኛችኋል

"ያህዌ ለምን ስለ ራሱ በስም እንደተናገረ ግልጽ አይደለም። "አንተ ሰዎች በእኔ ላይ እንዲያምጹ ገፋፍተሃቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሦስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰባተኛው ወር

ይህ በዕብራውያን የወራት አቆጣጠር ሰባተኛው ወር ነው። ይህ በምዕራባውያን ወራት አቆጣጠር የመስከረም ወር መጨረሻ እና የጥቅምት ወር መጀመሪያ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 29

Jeremiah 29:1

ከእየሩሳሌም የወጣ

"ከእየሩሳሌም የታወጀ"

የቀሩት ሽማግሌዎች

"አሁንም ገና በህይወት የሚገኙ ሽማግሌዎች"

ኢዮአኪን

የዕብራይስጡ ጽሁፍ "ኢኮንያን" ይላል፣ ይህ "ኢዮአኪን" ለሚለው የተሰጠ አማራጭ ስም ነው። ብዙ ዘመናዊ ቅጂዎች ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ያው ንጉሥ የተጠቀሰበትን "ኢዮአኪን" የሚለውን ስም ይጠቀማሉ።

እቴጌይቱ እናቱ

የንጉሡ እናት

ከፍተኛ መኳንንት/ባለስላጣናት

"ዋና ዋና ባለስልጣናት"

በኤልዓሣ እጅ

ኤርምያስ የመጽሐፍ ጥቅልሉን ወደ ባቢሎን እንዲወስድ ለኤልዓሣ ሰጠው። እንባቢው ምናልባት ኤልዓሣ በመንገድ ሲጓዝ የጥቅልሉን መጽሐፍ ደህንነት ለመጠበቅ ሲል በመያዣ እንደጠበቀው ሊረዳ ይችላል። (ስእክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ኤልዓሣ...ሳፋን...ገማርያ...ኬልቅያስ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 29:4

የሰራዊት ጌታ ያህዌ፣ የእስራኤል አምላክ ...ለምርኮኞች ሁሉ እንዲህ ይላል

ሰዎች በዚያ ማህበረሰብ ደብዳቤ ሲጽፉ፣ መጀመሪያ ስማቸውን ይጽፋሉ፣ ከዚያም የሚጽፉለትን ሰው ስም፣ ቀጥሎም የደብዳቤውን ዋና ክፍል ይጽፋሉ። ያህዌ ራሱ ደብዳቤውን እንደጻፈ አድርጎ በስም ይናገራል።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል

ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ቤቶችን በስራታችሁ ኑሩባቸው። ተክል ተክላችሁ ፍሬዎቻቸውን ብሉ

ያህዌ በዚያ ስፍራ ለረጅም ጊዜ እንደሚኖሩ እየነገራቸው ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 29:6

ለወንዶች ልጆቻችሁ ሚስቶችን ውሰዱ፣ ደግሞም ልጆቻችሁን ለባል ስጡ

ወላጆች የልጆቻቸውን ጋብቻ መምረጣቸው የተለመደ ነበር

የከተማይቱን ሰላም ፈልጉ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የከተማይቱ ሰላም ለሰዎች በሰላም መኖር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "የከተማይቱ ሰዎች በሰላም እንዲኖሩ የምትችሉትን ነገር ሁሉ አድርጉ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከተማይቱ...ለእስረኟ...እርኟ ሰላም እንድትሆን
እነዚህ ቃላት የባቢሎንን ከተማ ያመለክታሉ
Jeremiah 29:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለተማረኩ እስራኤላውያን መናገሩን ይቀጥላል።
የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እናንተ ለራሳችሁ ያልሟችሁ
ሌላው ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም 1) እነዚህ ቃላት የሚያመለክቱት ህልሞችን ሳይሆን ሀሰተኛ ነቢያቱን እና ጠንቋዮችን ወይም 2) "በሀሰት ይተነብያሉ" የሚለው የሚያመለክተው ህልሞችን ሲሆን "እኔ አልልክኋቸውም" የሚለው ነቢያቱን እና ጠንቋዮቹን ያመለክታል።
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 29:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ምርኮኛ በሆኑ እስራኤላውያን ላይ ምን እንደሚደርስ መናገሩን ቀጥሏል
እናንተ
ምርኮኛ የሆኑ እስራኤላውያን
ሰባ አመታት
"70 አመታት" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 29:12
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ምርኮኛ በሆኑ እስራኤላውያን ላይ ምን እንደሚደርስ መናገሩን ቀጥሏል
ወደ እኔ ትጣራላችሁ
ጸሎት የተገለጸው በከፍተኛ ድምጽ እንደመጣራት ተደርጎ ነው
እኔም እሰማችኋለሁ
ይህ የሚያመለክተው ያህዌ እነርሱ የሚፈልጉትን እንደሚሰጣቸው ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ ትፈልጉኛላችሁ
ያህዌ የሚጠይቀውን ለማወቅ መፈለግ የተገለጸው ያህዌ የት እንዳለ ለማግኘት እንደ መሞከር ተደርጎ ነው። "እኔ እንድታደርጉ የምጠይቀውን፣ እናንተ ለማድረግ ትፈልጋላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ በሙሉ ልባችሁ እኔን ትፈልጋላችሁ
"እናንተ እኔን የምትፈልጉት ሙሉ ለሙሉ በቅንነት ይሆናል"
ለእናንተ እገኛለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔን እንድትፈልጉኝ እፈቅድላችኋለሁ" ወይም "እኔን ማግኘት ትችላላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እድል ፈንታችሁን ዳግም እመልሳለሁ
"ነገሮች ዳግም ለእናንተ መልካም እንዲሆኑ አደርጋለሁ" ወይም "ዳግም መልካም ህይወት እንድትኖሩ አደርጋለሁ"
እንድትሰደዱ አደርጋለሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ወደ ስደት እልካችኋለሁ" ወይም "ስደተኞች እንደትሆኑ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመለከቱ)
Jeremiah 29:15
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤርምያስ ምርኮኛ ለሆኑ እስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል
በዳዊት ዙፋን ላይ ሚቀመጠው ንጉሥ
በዙፋን ላይ መቀመጥ ንጉሥ ሆኖ መግዛት ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "እስራኤላውያንን ዳዊት ይገዛ እንደነበረው የሚገዛ ንጉሥ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
እዩ
ይህ አንባቢውን ቀጥሎ ለሚሆነው ነገር ያነቃዋል። "ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ትኩረት ስጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
እኔ ሰይፍ፣ ረሃብ፣ እና ጥፋት በእነርሱ ላይ ልልክባቸው ነው
"ሰይፍ" የሚለው ቃል ለጦርነት ሜቶኖሚ/ነው። ሰይፍ፣ ረሃብ እና ጥፋት የተነገሩት እስራኤልን ለመጉዳት ያህዌን እንደሚታዘዙ ሰዎች ተደርገው ነው። "እኔ በጦርነት፣ በረሃብ፣ እና በበሽታ እንዲሞቱ ልቀጣቸው ተነስቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ሰውኛ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ለመበላት እንደማይችል እጅግ እንደ ተበላሸ በለስ አደርጋቸዋለሁ
የተበላሸ በለስ ጥቅም የለውም ምክንያቱም ሊበላ አይችልም፣ እንደዚያው ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ ምንም የማይጠቅም አድርጎ አይቶታል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 29:18
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ በእስራኤላውያን ላይ የሚሆነውን መናገሩን ቀጥሏል።
ለድንጋጤ፣ ለእርግማን እና ንቀት እንዲሁም ለሀፍረት
እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲይዙ፣ የሌላ አገር ሰዎች ያህዌ በይሁዳ ህዝብ ላይ ያደረሰውን ሲሰሙ ምን ምላሽ እንደሚሰጡ ይገልጻል
ንቀት
ሰዎች አንድን ነገር ሳይቀበሉ ሲቀሩ የሚያሰሙት ድምጽ ነው
እናንተ አትሰሙም
"እናንተ አትታዘዙም"
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 29:22
ስለ እነዚህ ሰዎች መረገም በባቢሎን በተማረኩ አይሁዶች ዘንድ ሁሉ ይወራል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በባቢሎን የሚገኙ የይሁዳ ምርኮኞች ስለ እነዚህ ሰዎች መረገም ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የተጠበሰ
ይህ ቃል ብዙውን ጊዜ ምግብን ሙሉ በሙሉ ማቃጠልን ሳይሆን፣ በሚነድ እሳት

ላይ ወይም በመጥበሻ ከሚገባው በላይ ማብሰልን ያመለክታል። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ዩፊምዝም/የማያስደስትን ቃል ሻልባለ ቃል መተካት/ ነው። "እስከ ሞት መቃጠል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) የንጉሡ ወታደሮች እሳቱ ቀስ በቀስ ጠብሶ እስከሚገድላቸው ድረስ በምሰሶ ላይ አስረው ወደ እሳቱ አቅረበው ይለበልቧቸዋል፣ ነገር ግን አካላቸውን ሙሉ ለሙሉ እንዳያቃጥለው ከእሳቱ ራቅ ያደረጓቸዋል። (ዩፊምዝም/የማያስደስትን ቃል ሻልባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ አውቃለሁ፣ እኔ ምስክር ነኝ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ያህዌ የሚደጋግማቸው ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 29:24

ሸማያ…መዕሴያ…ዮዳሄ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ኔሔላማዊ

ይህ የሰዎች ቡድን የወል ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰራዊት ጌታ ያህዌ… እንዲህ ይላል

ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በገዛ ራስህ ስም

"ስም" የሚለው ቃል ለየሰዎች ስልጣን እና ክብር ያመለክታል። "በራስህ ስልጣን እና ክብር ላይ ተመስርተህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማሰሪያ/የእንጨት ቀንበር

በቅጣት ላይ የሚገኝን ሰው እግርን እና እጆችን ወይም ጭንቅላትን ውስጡ አስገብቶ ማሰሪያ ከእንጨት የተሰራ ቀንበር

Jeremiah 29:27

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ እየሩሳሌም ወደሚገኙ ሰዎች ሸማያ የላከውን ደብዳቤ ያጠናቅቃል

የሚቃወምህን…የዓናቶቱን ኤርምያስ ለምን አልገሰጽከውም?

ሸማያ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው የእየሩሳሌም ሰዎች ኤርምያስን ባለመቃወማቸው ሊገስጻቸው ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል፡ "የሚቃወምህን…ዓናቶቱን ኤርምያስን እንድትገስጽ እፈልጋለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እኛ ልኳል

ኤርምያስ ምን እንደላከ ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። "እርሱ ወደ እኛ መልዕክት ልኳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቶችን በስራታችሁ ኑሩባቸው። ተክል ተክላችሁ ፍሬዎቻቸውን ብሉ

ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በኤርምያስ 29፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ነቢዩን ኤርምያስን በመስማት

"ስለዚህም ነቢዩ ኤርምያስ፣ እርሱ ይህን ሲያነብ ሊሰማ ይችላል ።" ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በኤርምያስ 2፡2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

Jeremiah 29:30

የያህዌ ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ "ላክ

ይህ ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በኤርምያስ 1፡4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠው። እርሱ እንዲህ አለ፣ 'ላክ" ወይም "ያህዌ ለኤርምያስ ይህንን መልዕክት ነገረው፡ 'ላክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኔሔላማዊ ሸማያ

ይህ የወንድ ስም በኤርምያስ 29፡24 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

መልካም የሆነው

ይህ እንደ ስማዊ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። "መልካም የሆኑት ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ በያህዌ ላይ አመጽ ተናግሯል

ያህዌ ስለ ራሱ ለምን በስም እንደተናገረ ግልጽ አይደለም። "እርሱ ሰዎች በእኔ ላይ እንዲያምጹ አነሳስቷል" (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 30

Jeremiah 30:1

ከያህዌ ዘንድ ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል፣ የመጣ ቃል

ፈሊጡ የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ተመሳሳይ የሆነ ሀረግ በኤርምያስ 1፡4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፤ እንደ አስፈላጊነቱም ግልጽ አድርጉት። "ያህዌ ለኤርምያስ የሰጠው መልዕክት ይህ ነው። እንዲህ አለ" ወይም "ያህዌ ለኤርምያስ ይህንን መልዕክት ሰጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ ተመልከት

"በጥንቃቄ አድምጥ ።" ይህ ሀረግ ያህዌ ቀጥሎ የሚናገረውን በጥንቃቄ ለመስማት ትኩረት ይፈጥራል

እኔ ሀብታችሁን የምመልስበት…ቀናቱ እየቀረቡ ነው

የሀብት/ዕድል ጊዜ የተገለጸው "ቀናት እየመጡ" እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ ዘይቤ በኤርምያስ 7፡32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደፊት … እድላችሁን አድሳለሁ" ወይም "እድላችሁን የማድስበት ጊዜ ይመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የህዝቤን የእስራኤልን እና ይሁዳን እድል ፈንታ አድሳለሁ

"ለህዝቤ ለእስራኤል እና ለይሁዳ ነገሮች ዳግም፣ መልካም እንዲሆኑ አደርጋለሁ" ወይም "ህዝቤ እስራኤል እና ይሁዳ ዳግም መልካም ህይወት እንዲኖሩ አደርጋለሁ።" በኤርምያስ 29፡14 ላይ ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

Jeremiah 30:4

አጠቃላይ መረጃ፡

ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ መልዕክቱን የሚጽፈው በግጥም ነው። የዕብራውያን ስነግጥም የተለያዩ የትይዩ ንጽጽራዊ ግጥም መልኮችን ይጠቀማል። (ስነግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ሰምተናል

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እነዚህ የያህዌ ራሱን "እኛ" ሲል የሚገልጽባቸው ቃሎች ናቸው። "እኔ ሰምቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) "እናንተ በከንቱ ትጮሃላችሁ ምክንያቱም አንዳች ሰላም የለም።"

Jeremiah 30:6

ወንድ አምጦ ይወልድ እንደሆነ ጠይቃችሁ እወቁ

"ወንድ አምጦ እንደማይወልድ ታውቃላችሁ"

እያንዳንዱ ወንድ ስለምን እጁን በወገቡ ላይ አድርጎ ልጅ ለመውለድ እንደምታምጥ ሴት ሆኖ እመለከታለሁ? ለምንስ የሁሉም ፊት ገረጣ?

ልትወልድ የምታምጥ ሴት አንዳች ነገር ማድረግ የምትችል ስትሆን፣ ታላቅ ስቃይም ይሰማታል። ወጣት ወንዶች በታላቅ ፍርሃት ውስጥ ሆነው መዋጋት ተስኗቸዋል።

"ወጣት ወንዶች በምጥ ላይ እንደምትገኝ ሴት ወገባቸውን ይዘዋል፣ ደግሞም እጅግ ስለፈሩ የታመሙ ይመስላሉ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)
የያቆብ ትውልድ ግን ከመከራ ይተርፋል
ያዕቆብ የሚለው ስም ለያዕቆብ ትውልዶች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "የያዕቆብን ትውልድ ግን እኔ ከዚህ አድናለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
Jeremiah 30:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል።
የአንገታችሁን ቀንበር እሰብራለሁ፣ ደግሞም ሰንሰለታችሁን እበጥሳለሁ
ባሪያ መሆን የተገለጸው እንደ እንስሳ ቀንበር እንደ መጫን እና እንደ እስረኛ ሰንሰለት እንደመልበስ/በሰንሰለት እንደ መታሰር ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አምላካቸውን ያህዌን ያመልኩታል... ንጉሣቸው... በእነርሱ ላይ
ያህዌ ስለ ያዕቆብ ትውልድ መናገሩን ቀጥሏል። "አምላካችሁን ያህዌን ታመልኩታላችሁ... ንጉሣችሁ... በእናነት ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ንጉሣቸው ዳዊት
ይህ ከዳዊት ትውልዶች ለአንዱ ሜቶኖሚ/ ነው። "ከንጉሣቸው ከዳዊት ትውልድ የሆነ " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 30:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል።
ባሪያዬ ያዕቆብ... እስራኤል
"ያዕቆብ" እና "እስራኤል" የእስራኤላውያን አባቶች ስሞች ናቸው፣ ደግሞም እነዚህ ስሞች ለእስራኤላውያን ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "እናንተ የእስራኤል ሰዎች ...የያዕቆብ ትውልዶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
አትጨነቁ
"ተስፋ አትቁረጡ"
እነሆ እኔ እንደሆንኩ እዩ
"እኔ ለምን እኔ ነኝ እንደምል በጥንቃቄ አድምጡ"
ከምርኮ ምድር
"ምርኮ" የሚለው ረቂቅ ስም፣ "ምርኮኛ" የሚለውን ስም በመጠቀም መተረጎም ይችላል። "ምርኮኛ ከነበሩበት ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ያዕቆብ ይመለሳል... እርሱ በሰላም ይቀመጣል
የያዕቆብ ስም ለትውልዶቹ ሜቶኖሚ/ ነው። ያህዌ ለያዕቆብ የሚናገረው ለሌላ ሰው እንደሚናገር አድርጎ ነው። ያዕቆብ ወዴት እንደሚመለስ ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። "ያዕቆብ ወደ ራሱ ምድር ይመለሳል... በሰላም ይጠበቃል" ወይም "የያዕቆብ ትውልዶች ይመለሳሉ... ደህንነታቸው ይጠበቃል" ወይም "እናንተ የያዕቆብ ትውልዶች ትመለሳላችሁ... ደህንነታችሁ ይጠበቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
አስተማማኝ
"በደህና መጠበቅ"
እኔ እናንተን ከበተንኩሉበት
"እኔ ከላክኋችሁ ስፍራ"
ነገር ግን በእርግጥ እኔ አላጠፋችሁም
"ነገር ግን እኔ ሙሉ ለሙሉ አላጠፋችሁም" (ዩፊምዝም/የማያስደስትን ቃል ሻልባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
በእርግጥ ሳልቀጣችሁ አልቀርም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "በእርግጥ እቀጣችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አሉታዊ ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 30:12
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል።
ጉዳታችሁ የማይድን ነው ቁስላችሁ መርቅዟል...ለቁስላችሁ ፈውስ የለውም
ይህ ማለት ያህዌ እነርሱን ማንም ሊረዳቸው የሚችል እስማይገኝ ድረስ እጅግ በጣም ቀጥቷቸዋል ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ እናንተ የሚማጸን አይኖርም
"ምህረት እንዳደርግላችሁ ስለ እናንተ ወደ እኔ ልመና የሚያቀርብ ማንም የለም"
Jeremiah 30:14
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል።
ወዳጆቻችሁ ሁሉ
ያህዌ የእስራኤልን ሰዎች ከባሏ ውጭ ሌሎች ፍቅረኞችን እንደምትይዝ ታማኝ ያልሆነች ሚስት ይገልጻቸዋል። እዚህ ስፍራ "ፍቅረኞች" የሚለው የሚያመለክተው ሌሎች ሀገራትን ነው። እስራኤላውያን በያህዌ ከመታመን ይልቅ ከእነርሱ ጋር ተባብረው ጣኦቶቻቸውን ያመልካሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ እናንተን አይፈልጉም
"እነርሱ ከእንግዲህ የእናንተ ወዳጆች መሆን አይፈልጉም"
ጠላት እንደሚያቆስል አቆሰልኳችሁ
ያህዌ በጠላቶቹ ላይ እንደሚያደርግ በህዝቡ ላይ አደረገባቸው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የጨካን ጌታ ቅጣት/እርምት
ያህዌ ህዝቡን ጨካኝ ጌታ አመጸኛ ባሪያን እንደሚቀጣ ቀጣቸው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ ደረሰባችሁ ጉዳት ለምን ለእርዳታ ትጣራላችሁ?
እዚህ ስፍራ ያህዌ ጥያቄ የሚጠይቀው ህዝቡ ለምን አሁን እርዳታ እንደሚጠይቁት እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። "ጉዳት የደረሰባችሁ እና አሁን እርዳታ ለማግኘት የምትጣሩት እኔን ባለመታዘዛችሁ ምክንያት ነው" ወይም "በደረሰባችሁ ጉዳት እርዳታ ለማግኘት ጥሪ አታሰሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለምልልሰዳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ከቁጥር ያለፈው ኃጢአታችሁ
"የእናንተ ኃጢአት ለመቁጠር እጅግ ብዙ ነው"
Jeremiah 30:16
ስለዚህም እናንተን የሚፈጅ/የሚበላ ሁሉ ይፈጃል/ይበላል
ህዝቡን ማጥፋት የተገለጸው እርሱን እንደ መፍጀት ወይም መብላት ተደርጎ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ስለዚህም እናንተን ያጠፉትን፣ ጠላቶቻቸው ደግሞ እነርሱን ያጠፏቸዋል" ወይም "እናንተን ያጠፉትን ሁሉ እኔ አጠፋቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመለከቱ)
የዘረፏችሁ...ይዘረፋሉ/ይቀማሉ
መዝረፍ ማለት ከሰላማዊ ህዝብ ሀይል ተጠቅሞ መቀማት/መስረቅ ሲሆን ዝርፊያ ሰዎች የቀሙት ነገር ነው።
ማበላሸት...ብልሹ
እዚህ ስፍራ ማበላሸት ማለት አንድ ወገን ካሸነፈው ጠላት መውሰድ ሲሆነ፣ የተወሰዱት ነገሮች የተበላሹ ናቸው።
መፈወስ...ቁስሎች
እነዚህ ቃላት በኤርምያስ 30፡12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን

ይመልከቱ)
እነርሱ እናንተን፡ የተናቁ ይሏችኋል
የተናቀ ማለት ሌሎች ሰዎች የማይቀበሉት ወይም ከእነርሱ ጋር ህብረት እንዲያደርግ የማይፈቅዱለት ሰው ማለት ነው። "የተናቁ ብለው ይጠሯችኋል" ወይም "እነርሱ፣ ‘ማንም እናንተን አይፈልግም' ይላሉ"
ማንም ለዚህች ለጽዮን ግድ አይለውም
"ጽዮን" የሚባለው ስፍራ ስም በጽዮን ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ ነው። "ማንም ለጽዮን ሰዎች ግድ የለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
Jeremiah 30:18
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል።
እዩ/እነሆ
"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም " ቀጥሎ ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ"
የያዕቆብን ድንኳን ዕድል ፈንታ እመልሳለሁ፣ ለቤቱም እራራለሁ
ሰዎች የሚኖሩበት ስፍራ በነዚያ ፍራዎች ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "የያዕቆብን ትውልድ እድል ፈንታ ልመልስ ተዘጋጅቻለሁ፣ ደግሞም ለእነርሱ እራራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያም በፍርስራሾች ክምር ላይ ከተማ ይመሰረታል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። የሚገነቧት ከተማ እየሩሌም እንደሆነች ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። "ከዚያም እየሩሳሌምን በፍርስራሾቿ ላይ ይመሰርታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያም የምስጋና ዝማሬ እንደዚሁም የደስታ ድምጽ ከእነርሱ ዘንድ ይሰማል
"ከዚያም እነርሱ የምስጋና እና ሀሴት መዝሙሮችን ይዘምራሉ"
እኔ አበዛቸዋለሁ እንጂ አላሳንሳቸውም
"በቁጥር እንዲበዙ አደርጋለሁ እንጂ እንዲመናመኑ አላደርግም"
ስለዚህም ዝቅዝቅ አይሉም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ዝቅ አድርጎ አይመለከታቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 30:20
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤላውያን መናገሩን ቀጥሏል።
ማህበራቸው በፊቴ ይጸናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ በፊቴ እንደ ህዝብ አጸናቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ እኔ በድፍረት መቅረብ የሚችል ማን ነው?
ያህዌ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ ካላቀረበው በስተቀር ማንም ደፍሮ ወደ እርሱ መቅረብ እንደማይችል ትኩረት ለመስጠት ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 30:23
እነሆ፣ የያህዌ ፈተና፣ የእርሱ ቁጣ፣ ወጥቷል
ይህ የእግዚአብሔርን ቁጣ እና ቅጣት ማዕበል እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። ይህ የእርሱን ክፉ ሰዎችን የማጥፋት ሀይል እና ችሎታ ያጎላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የልቡ ሃሳብ
"ሀሳብ/ፈቃድ" የሚለው ረቂቅ ስም "አሰበ" የሚለውን ግስ ተጠቅሞ መተርጎም ይቻላል። ልብ የሚለው ቃል ለጠቅላላው የሰው ማንነት ሴኔቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "እርሱ ሊያደርግ ያሰበው/ የፈቀደው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 31
Jeremiah 31:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ ትንቢቱን የሚጽፈው በግጥም መልክ ነው። የዕብራውያን ስነግጥም የተለያዩ ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤዎችን ይጠቀማል። (ስነግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
በዚያን ጊዜ
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ክፉዎችን የሚቀጣበትን ጊዜ ነው።
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሰይፍ የተረፉት በበረሃ ሞገስ ያገኛሉ
"ሞገስ ማግኘት" የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ከሰይፍ ላመለጡ ሰዎች እኔ በበረሃ ስፍራ ጸጋን በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከሰይፍ ያመለጡ
"ሰይፍ" የሚለው ቃል ጦርነት ለሚለው ሜቶኖሚ/ ነው። "ከጦርነት ያመለጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በበረሃ ለእስራኤል እረፍት ለመስጠት እወጣለሁ
ሊሰጥ የሚችለው አማራጭ ትርጉም "እስራኤል ረፍት ለማግኘት ወደ በረሃ ይወጣል"
ያህዌ ለእኔ ተገለጠልኝ
ኤርምያስ ስለ እራሱ፣ እርሱ የእስራኤል ህዝብ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በቃል ኪዳን ታማኝነት እኔ አንቺን ወደ ራሴ ሳብኩሽ
"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ታማኝ" ወይም "በታማኝነት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ለቃል ኪዳኔ ታማኝ ሆኜ ወደ ራሴ አቀረብኩሽ" ወይም "እኔ በታማኝነት ወድጄ ወደ ራሴ አቀረብኩሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 31:4
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤል ህዝብ መናገሩን ይቀጥላል።
እኔ ዳግመኛ እሰራሻለሁ እንቺም ትጸኛለሽ
ያህዌ በአላማ እስራኤልን እንደሚያጸና ትኩረት ለምጠት ሃሳቡን ይደግማል። ቋንቋችሁ የድርጊት ግስን ብቻ የሚጠቀም ከሆነ እና ለሃሳቡ ትኩረት ለምጠት ሌላ አማራጭ መንገድ ካላችሁ እዚህ ሰስፍራ ይህን መጠቀም ትችላላችሁ። "እኔ እናንተን ዳግም አጸናለሁ። ይህን እስታውሱ፡ እኔ አጸናችኋለሁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ድንግሊቱ እስራኤል
አገራትን በሴት መግለጽ የተለመደ ነገር ነበር። ሆኖም፣ "ድንግል" የሚለው ቃል አንድን ሰው አግብታ ስለማታውቅ ወጣት ሴት እና ለባል ታማኝ ለመሆን እድል አግኝታ ስለማታውቅ ሴት እንዲያስብ ያደርገዋል። ስለዚህ እስራኤልን ድንግል ብሎ መጥራት ምጸታዊ የሆነ አነጋገር ነው። ይህ በኤርምያስ 18፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በሀሰት ለእኔ ራሷን ሙሉለሙሉ ታማኝ አድርጋ እንዳቀረበች የምታስመስለው እስራኤል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ምጸት የሚሉትን ይመልከቱ)
ከበሮ መሰል የሙዚቃ መሳሪያ/ታምቦሪኒ
እናቱ ከበሮ የሚመስል ቁርጥራጭ ብረቶች ከጎኑ ያሉት እና ሲመቱት ብረቶቹ እየተንቃጨሉ ድምጽ የሚሰጥ የሙዚቃ መሳሪያ። (የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 31:7


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የደስታ ጩኸት ጩኹ… እልል በሉ…ምስጋና ይሰማ…በሉ

ያህዌ ለመላው የዓለም ህዝብ በአጋኖ ይናገራል፣ ለዚህ እነዚህ ግሶች ብዙ ቁጥር ናቸው፡፡ (አጋኖ እና ተውላጠ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

የአገራቱ አለቆች

"የአገራቱ ታላላቅ ሰዎች የሚባሉ የህዝብ ክፍሎች" ወይም "ከሌላው ይልቅ ከፍ ያለ ስፍራ የተሰጣቸው የህዝብ ክፍሎች"

ምስጋና ይሰማ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል፡፡ "እያንዳንዱ ድምጻችሁን እንዲሰማ አድርጉ"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:8

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እንዴት የእስራኤልን ህዝብ ከተማረኩበት ከባቢሎን እንደሚመልስ መናገሩን ቀጥሏል፡፡

እነሆ

"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ቀጥሎ የምነግራችሁን ለመስማት ትኩረት ስጡ"

እነርሱን ለማምጣት

"እስራኤላውያንን ለማምጣት"

ደስታቸውን ሲገልጹ እኔ እመራቸዋለሁ

ያህዌ ይመራቸዋል እነርሱም ወደ ያህዌ ይጸልያሉ፡፡ አንዳንድ ጥንታዊ ቅጂዎች፣ "ያህዌ ይመራቸዋል ደግሞም ያጽናናቸዋል" ይላሉ፡፡

እኔ ለእስራኤል አባት እሆናለሁ፣ ኤፍሬም በኩሬ ይሆናል

እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" ለ "እስራኤል" ሌላው ስሙ ነው፡፡ "ለእስራኤል ህዝብ እንደ አባት እሆናለሁ፣ እነርሱም ለእኔ እንደ በኩር ልጅ ይሆኑኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

የመጀመርያ ልጇ/ የኩር ልጁ

የበኩር ልጅ ልዩ ክብር እና ሀላፊነት አለበት

Jeremiah 31:10

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እንዴት የእስራኤልን ህዝብ ከተማረኩበት ከባቢሎን እንደሚመልስ መናገሩን ቀጥሏል፡፡

አድምጡ … ተናገሩ

ያህዌ ለአገራት ይናገራል፣ ስለዚህ እነዚህ ግሶች ብዙ ቁጥር ናቸው፡፡ (ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤልን የበተናት እርሱ መልሶ ይሰበስባታል ደግሞም ይተብቃታል

ያህዌ ስለ ራሱ እንደ ሌላ አድርጎ ይናገራል፤ ስለ እስራኤል ህዝብ ደግሞ እርዳታ ያጣች ሴት አድርጎ ይናገራል፡፡ "እኔ ህዝቤ እስራኤል በአገራት መሃል እንዲበተን አድርጌያለሁ፣ ነገር ግን አሁን ወደ ቤታቸው እመልሳቸዋለሁ ደግሞም እጠብቃቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ተውላጠ ስሞች እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እረኛ በጎቹን እንደሚጠብቅ

እረኛ በጎቹን ይጠብቃል ይንከባከባልም፣ እናም ያህዌ እስራኤላውያንን እንደሚንከባከብ እና እንደሚጠብቅ ቃል እየገባ ነው፡፡" (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ያዕቆብን እንደ ተቤዠ ለእርሱ እጅግ ከባድ ከሆነበት እጅ እንዳዳነው

እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ የእስራኤልን ህዝብ የታደገው ያህዌ እንደሆነ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ "ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ እጅግ ከባድ ከሆኑባቸው "ጠላቶቻቸው ታድጓል በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:12

በጽዮን ኮረብቶች/ከፍታዎች

"በጽዮን፣ በከፍታ ስፍራ" ወይም "በጽዮን ተራራ፡፡" ከኮረብታ ጫፍ መሆን ለድተኛነት ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው፡፡ የእናንተ ቋንቋ የተራራን ጫፍ ከሀዘን ጋር የሚያያይዝ ከሆነ፣ እዚህ ስፍራ ይህንን ዘይቤ አለመጠቀም ይመረጣል፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በውሃ እንደ ረሰረሰ የአትክልት ስፍራ

ይህ ማለት ጠንካራ እና ጤናማ ይሆናሉ፣ እንዲሁም ይበለጽጋሉ ማለት ነው፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ዳግም በፍጹም ሀዘንተኛ አይሆኑም

"በፍጹም" የሚለው ቃል አጠቃላይ አስተያየት ነው፡፡ እስራኤላውያን ከእንግዲህ ከሞላ ጎደል ሁሌም ደስተኞች ይሆናሉ፡፡ (ኩሸት እና አጠቃላ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:13

ሀዘናቸውን እኔ ወደ ደስታ/በዓል እለውጣለሁ

"ሀዘን" እና "ደስታ/በዓል" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በግስ መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ፡፡ "ከእንግዲህ እንዲያዝኑ አላደርግም በዚህ ፈንታ ደስተኛ አደርጋቸዋለሁ" ወይም "ከእንግዲህ አያዝኑም ነገር ግን ደስተኛ አደርጋቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡

እኔ አደርጋለሁ/እለውጣለሁ

"ያህዌ ይለውጣል"

የካህናቱን ህይወት አትረፍርፌ እሞላለሁ

"መትረፍረፍ" የሚለው ረቂቅ ስም "ብዙ መላካም ነገሮች" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ የካህናቱ ህይወት የተነገረው ዝናብ አግኝቶ ሙሉ ለሙሉ ለምለም እንደሆነ መስክ ነው፡፡ ህይወት የሚለው ለሰውየው ሜቶኖሚ/ ነው፡፡ "እኔ ለካህናቱ የሚፈልጉትን መልካም ነገር ሁሉ እሰጣቸዋለሁ" ወይም "ካህናቱን በመልካም ነገሮች አረካለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች እና ዘይቤያዊ አነጋገር እንደዚሁም ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ህዝቤ በመልካምነቴ ራሳቸውን ይሞላሉ

"መልካምነቴ ህዝቤን ያረካል"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:15

በራማ ድምጽ ተሰማ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል፡፡ "እኔ በራማ ድምጽ ሰማሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሄል ለልጇችዋ አለቀሰች

ራሄል የያዕቆብ/እስራኤል ሚስት ነበረች፤ ደግሞም የዮሴፍ እና ብንያም ነገዶች እናት ነበረች፡፡ የእርሷ ስም በባቢሎናውያን ልጆቻቸውን ለገደሉባቸው ወይም ማርከው ለወሰዱባቸው የእስራኤል እናቶች ሜቲኖሚ/ ነው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በህይወት የሉምና ስለ እነርሱ መጽናናት አልቻለችም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ልጆቿ ሞተዋልና፣ ማንም እንዲያጽናናት አልፈቀደችም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:16

ድምጽሽን ከልቅሶ ከልክይ፣ ዐይኖችሽንም ከእንባ

ድምጽ እና ዐይኖች የተገለጹት ራሄል ከመንቀሳቀስ እንዲገቱ እንደምትፈልጋቸው ሰዎች ተደርገው ነው፡፡ "ጮክ ብለሽ ማልቀስሽን አቁሚ፣ በጩኸት ማንባትሽንም አቁሚ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጽሽን ያዢው…ዐይኖችሽ… ስራሽ…ልጆችሽ… እድልሽ… ትውልድሽ

ያህዌ ለእስራኤላውያን የሚናገረው ለራሄል እንደሚናገራት አድርጎ ነው (ኤርምያስ 31፡15)፣ ስለዚህ ሁሉም "የአንቺ" የሚሉት ሁኔታዎች እና ትዕዛዞች ነጠላ ቁጥር ናቸው፡፡ (አንተ/አንቺ የሚለው ተውላጠ ስም መልኮች እና አጋኖ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን

ይመልከቱ)
Jeremiah 31:18
በእርግጥ የኤፍሬምን ሀዘን ሰምቻለሁ
ኤፍሬም በእስራኤል የነበረው ትልቅ ነገድ አባት ነበር። የእርሱ ስም ለእስራኤል ህዝብ ሜቶኖሚ/ ነው። "እኔ በእርግጥ የኤፍሬምን ትውልዶች ሀዘን ሰምቻለሁ" ወይም "እኔ በእርግጥ የእስራኤልን ህዝብ ሀዘን ሰምቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ቀጣኸኝ፣ እኔም ተቀጣሁ
ተናጋሪው ሀረጉን የሚደግመው፣ አንድም ያህዌ እርሱን እጅግ እንደቀጣው ለማሳየት ወይም ያህዌ እርሱን በቅጣት ሊያስተምረው የፈለገውን ማወቁን/መረዳቱን ለመናገር ነው። "እኔ ተቀጣሁ" የሚለው ቃል በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተ እኔን ቀጣኸኝ። አዎን፣ አንተ እኔን ክፉኛ ቀጣኸኝ" ወይም "አንተ ቀጣኸኝ፣ እኔም ከአንተ የተማርኩት ስትቀጣኝ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
እንዳልተገራ ወይፈን ተቀጣሁ
ሰዎች ወይፈን ሲገሩ፣ ይገርፏቸዋል፣ ካልሆነ እንዲጨነቁ ያደርጋሉ። ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ እንዲጨነቅ አድርጓል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መቅጣት
ሌላው አማራጭ ትርጉም "ስርአት ማስያዝ" ነው
ጭኔን ጻፍሁ/ጭኔን በእጄ መታቱ
በሀዘን። በእናንተ ቋንቋ ሰዎች ማዘናቸውን ለመግለጽ የተለየ ሀረግ ወይም ድርጊት የሚጠቀሙ ከሆነ እዚህ ስፍራ ያንን ተክታችሁ መጠቀም ትችላላችሁ። "ግንባሬን ፈተግሁ" በሚለውውጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ትምዕርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ አፈርኩ ተዋረድኩም
"ሀፍረት" እና "ውርደት" የሚሉት ቃላት በመረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ ሀፍረት የሚለውን ሀሳብ ያጎላሉ። "እኔ ሙሉ ለሙሉ አፍሬ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
ኤፍሬም የእኔ ውድ ልጄ አይደለምን? እርሱ ለእኔ ውድ አይደለምን፣ አስደሳች ልጄ አይደለምን?
ያህዌ ህዝቡን ለማጽናናት እየሞከረ በማባባት ይናገራል። እነዚህ ጥያቄዎች በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። "ኤፍሬም ወድ ልጄ ነው። እርሱ የእኔ ውድ ነው፣ ደስ የምሰኝበት ልጄ ነው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 31:21
አጠቃላይ መረጃ፡
እግዚአብሔር ከቁጥር 7 ቀጥሎ መናገሩን ይቀጥላል።
ለራስሽ የመንገድ ምልክት አድርጊ...መንገድን የሚመሩ ዓምዶችን ትከይ...አዕመሮሽን አረጋጊ..
መውሰድ ይኖርብሻል... እንደገና ተመለሽ
"አንቺ ራስሽ" እና "የአንቺ" እና "አንቺ" የሚሉት እነዚህ ትዕዛዞች እና ሁኔታዎች የሚያመለክቱት "ድንግሊቱን እስራኤልን" ሲሆን ሁሉም ነጠላቁጥር ናቸው። (ተውላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ድንግሊቱ እስራኤል ሆይ፣ ተመለሽ!
እግዚአብሔር የተለወጠችውን እስራኤል እያመለከተ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንቺ እምነት የለሽ ልጄ እስከ መቼ ታወላውያለሽ?
ያህዌ ለህዝቡ እነር በለመታዘዛቸው ምክንያት መታገሱ እያበቃ እንደሆነ ይናገራል። "እኔን መታዘዝ ለመጀመር አታቅማሙ" በሚለው ውስጥ እደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ማወላወል
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ምን ማድረግ እንደሚገባ መወሰን አለመቻል 2) ብዙውን ጊዜ በትክክለኛው መንገድ ውጭ መሄድ፣ ሲሆን ይህ ያህዌን ያለመታዘዝ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በምድር ላይ እንግዳ/አዲስ ነገር - አንዲት ሴት ብርቱ ወንድን ስትጠብቅ/ስትከብ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰዎች ሴቶችን ለመጠበቅ ማንም ባያስፈልጋቸው ደህንነት ይሰማቸዋል ወይም 2) ይህ ማንም የማይጠብቀውን ነገር ለመግለጽ ፈሊጥ ነው። "በምድር ላይ አዲስ ነገር - ሴት አንድን ወንድ እንደ መጠበቅ የመሰለ እንግዳ ነገር" በሚለው ውስጥ እደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 31:23
የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል
ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ህዝቡ
እዚህ ስፍራ ይህ የይሁዳን ሰዎች ያመለክታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ የሚኖርባችሁ እናንተ የተቀደሳችሁ ስፍራዎች፣ እናንተ የተቀደሳችሁ ተራሮች፣ ያህዌ ይባርካችሁ
እየሩሳሌም በተራራ ላይ ስትሆን፣ መቅደሱ የታነጸው በእየሩሳሌም ከፍተኛ ስፍራ ነበር። "ያህዌ መቅደሱ በሚገኝበት ከእርሱ ጋር በእየሩሳሌም የሚኖሩትን ይባርክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አጋኖ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
አንቺ የተቀደስሽ ተራራ
መቅደሱ የቆመበባት የጽዮን ተራራ
ይሁዳ እና መላው ዜጎችዋ በአንድነት በዚያ ይኖራሉ
ይሁዳ የተባለው ሰው ስም፤ የእርሱ ትውልዶች፣ የይሁዳ ነገድ የሆኑ ሰዎች የሚኖሩባት፣ እና የይሁዳ ከተማ፣ ይሁዳ የተባለው ሰው ቤተሰብ እንደሆኑ ተደርጎ፣ በይሁዳ ምድር "በዚያ" የሚኖሩ በሙሉ የተገለጹበት ሜቶኖሚ/ ነው። "ይህ ምድሪቱን ይሁዳ ከቤተሰቡ ጋር እንደኖርባት ቤት ያደርጋታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ገበሬዎች እና ከከብቶቻቸው ጋር የወጡ ደገኛሉ
"ደግሞም ገበሬዎች እና ከከብቶቻቸው ጋር የወጡ እነርሱም ደግሞ በዚያ ይኖራሉ"
ከከብቶቻቸው ጋር የወጡ
በጎችን እና ፍየሎችን የሚጠብቁ ሰዎች
ያድሱ ነበር
"እኔን አደሱኝ"
Jeremiah 31:27
ተመልከቱ
"ትኩረት ስጡ" ወይም "አድምጡ"
እኔ የማይበት...ቀናት እየደረሱ ነው
መጪው ጊዜ የተገለጸው "ቀናት እየመጡ" እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ ዘይቤ በኤርምያስ 7:32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በመጪው ጊዜ ... እኔ እያለሁ" ወይም "እኔ የማይበት... ጊዜ ይኖራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ከሰው እና አራዊት ዘር ጋር የእስራኤልን እና የይሁዳን ቤቶች እመለከታለሁ
"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖር ቤተሰብ ሜቶኖሚ/ ነው፤ በዚህ ሁኔታ እነዚህ የእስራኤል እና የይሁዳ ሰዎች ሰዎች ናቸው። ቤት በተራው ያህዌ ዘር የሚዘራበት ሜዳ ሆኖ ሲገለጽ፣ ለምግብ፣ ለወተት፣ እንደዚሁም ለቆዳ የሚያሳድጓቸው እንስሳት እንዲሁም በቁጥር የሚበዛው ህዝብ ያን ዘር እንደሆኑ ተደርጎ ተገልጽዋል። "የይሁዳ እና የእስራኤል ሰዎች እንዲበዙ እና እያሌ ከብቶች እንዲኖራቸው አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
እነርሱን እነቅላቸው ዘንድ በእይታ ስር እጠብቃቸዋለሁ
"እነርሱን የምነቅልበትን መንገድ እመለከታለሁ"

generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መንቀል... ማስወገድ...መጣል...ማጥፋት

እነዚህ ሀሳቦች በኤርምያስ 1፡9 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

እነርሱን እንጽ እና እተክል ዘንድ

ያህዌ እስራኤላውያንን ቤት ወይም የምግብ ሰብል እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። "እነርሱን አበረታ እና አበዛ ዘንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:29

አባቶች የኮመጠጠ የወይን ፍሬ በሉ፣ ነገር ግን የልዶች ጥርስ ደነዘዘ/ጠረሰ

እነዚህ ቃላት፣ ያህዌ በአባቶች ጥፋት ልጆችን መቅጣቱን በማማረር ሰዎች ሲናገሩ ኤርምያስ የሰማው ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። (ምሳሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የቆመጠጠ የወይን ፍሬ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በውስጡ ብዙ አሲድ የያዘ የወይን ፍሬ። ወይም 2) ያልበሰለ/ያልደረሰ የወይን ፍሬ። በባህላችሁ ወይን ተክል ከሌለ፣ ፍራፍሬ የሚለውን አጠቃላይ ቃል መጠቀም ሊያስፈልግ ይችላል።

ጥርስ ጠረሰ/ደነዘዘ

ለዚህ ሰዎች ጎምዛዛ ፍራፍሬ ወይም ያልበሰለ ፍራፍሬ ሲመገቡ አፋቸውን የሚሰማቸውን ስሜት የሚገልጽ በቋንቋችሁ የሚገኝ የተለመደ ቃል ተጠቀሙ

እያንዳንዱ ሰው በጥፋቱ/ኃጢአቱ ይሞታል

"እያንዳንዱ ሰው በራሱ ኃጢአት ምክንያት ይሞታል"

የጎመዘዘ የወይን ፍሬ የሚበላ ሰው ሁሉ፣ ጥርሱ ይጠርሳል/ይደነዝዛል

ኤርምያስ ሰዎች ከገዛ ባህሪያቸው የተነሳ እንደሚጨነቁ ለመግለጽ ምሳሌያዊ አነጋገሩን ይጠቀምበታል። (ምሳሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:31

ተመልከቱ

"አድምጡ" ወይም "ቀጥሎ ለምነግራችሁ ትኩረት ስጡ"

የምሰራባቸው ቀናት... እየመጡ ነው

የወደፊቱ ጊዜ የተገለጸው "ቀናት እየመጡ" እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር በኤርምያስ 7፡32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደፊት... እኔ እንጻለሁ" ወይም "እኔ የማንጽበት ጊዜ...ይመጣል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት

"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤል" ወይም "የእስራኤል መንግሥት" ወይም "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት

"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው፣ የይሁዳን እና የብንያምን ትውልድ የሚያጠቃልለውን የይሁዳን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ይሁዳ" ወይም "የይሁዳ መንግሥት" ወይም "የይሁዳ ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እጃቸውን እይዛለሁ

አፍቃሪ ባል አብረው ሲራመዱ የሚስቱን እጅ እንደሚይዝ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:33

የእስራኤል ቤት

"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤል" ወይም "የእስራኤል መንግሥት" ወይም "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ህጌን በእነርሱ መሃል አደርጋለሁ፣ ደግሞም በልባቸው ላይ እጽፈዋለሁ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፣ የያህዌ ህግ የእነርሱ አንድ ክፍል እንጂ በድንጋይ ላይ ተጽፎ የተቀመጠ ብቻ አለመሆኑን ትኩረት ይሰጣሉ። እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው "ስሜትን" ወይም "ሀሳብን/አእምሮን" ነው። "ህጌ የሃሳባቸው እና ስሜታቸው ክፍል ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ከእነርሱ ከታናናሾቹ ጀምሮ እስከ ታላላቆቹ ድረስ

ይህ ሀረግ ከታናሹ እስከ ታላላቆች ድረስ እያንዳንዱን ሰው ያመለክታል። "አንድም ሳይቀር እያንዳንዳቸውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ከአጽናፍ አጽናፍ/ከዳር እስከ ዳር የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:35

እነዚህ ዘላቂ ነገሮች ከጠፉ ብቻ...የእስራኤል ትውልዶች አገር ከመሆን ለዘለዓለም ያቆማሉ

ይህ ያህዌ ፈጽሞ ይሆናል የማይለው መላምታዊ ሁኔታ ነው። "እነዚህ ዘላቂ ነገሮች በፍጹም አይጠፉም...እንደዚሁ ሁሉ የእስራኤል ትውልዶች አገር ከመሆን በፍጹም አያቆሙም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:37

ከፍ ያሉት ሰማያት መለካት ከተቻሉ ብቻ፣ እና ታች ያሉ የምድር መሰረቶች መታወቅ ከቻሉ ብቻ ያኔ እኔ የእስራኤልን ትውልድ እጥላለሁ

ይህ ያህዌ ፈጽሞ ይሆናል የማይለው መላምታዊ ሁኔታ ነው። "በከፍታ ያሉ ሰማያት በፍጹም ሊለኩ አይችሉም፣ ከታች የሚገኙ የምድር መሰረቶችም በፍጹም ሊታወቁ አይችሉም፣ እንደዚሁ ሁሉ የእስራኤልን ትውልዶች እኔ ፈጽሞ አልተውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በከፍታ ያሉ ሰማያት...የምድር መሰረቶች

እነዚህ ሀረጎች መላውን ፍጥረት ያመለክታሉ። (ከአጽናፍ አጽናፍ/ከዳር እስከ ዳር የሚለውን ይመልከቱ)

ከታች የሚገኙ የምድር መሰረቶች ሊታወቁ ይችላሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "አንድ ሰው እስከ ምድር መሰረት ድረስ ሊቆፍር ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከታች የሚገኝ መሰረት

"ጥልቁ ስፍራ።" "መሰረት" የቤቱ ሌሎች ክፍሎች ሁሉ የሚያርፉበትነው።

መጣል

መወርወር ወይም አለመቀበል

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 31:38

ተመልከቱ፣ ቀኖች እየመጡ ነው

"በቶሎ እንደሚሆን እኔ ለምናገረው ነገር ትኩረት ስጡ!"

ከተማይቱ የምትገነባበት… ቀናት እየመጡ ነው

መጪው ጊዜ የተገለጸው "ቀናት እየመጡ" እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር በኤርምያስ 7:32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በመጪው ጊዜ … ከተማይቱ ዳግም ትገነባለች" ወይም "እኔ ያህዌ የተናገርኩት/ያወጅኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማይቱ ዳግም ለእኔ ትሰራለች/ትታነጻለች

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እነርሱ ከተማይቱን ዳግም ለእኔ ይገነባሉ" ወይም "እኔ ከተማዋን ዳግም እንዲገነቡ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሐናንኤል ግንብ…የማዕዘን በር…የጋሬብ ኮረብታ…ጎዓ…ቄድሮን ሸለቆ…ፈረስ በር

እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

መላው ሸለቆ… ለያህዌ የተለየ ይሆናል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "መላውን ሸለቆ ለእኔ…ይለያሉ/ይቀድሳሉ" ወይም "መላውን ሸለቆ … ለእኔ ይቀድሳሉ/ይለያሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይለያሉ

"ይቀድሳሉ"

ከተማይቱ ዳግም አትጠፋም ወይም አትፈርስም

ከተማይቱ የተገለጸችው ተክል እንደሆነች እና አንድ ሰው ከመሬት ሊነቅላት እንደሚችል፣ ወይም ግንብ ሆና ሊያፈርሳት እንደሚችል ተደርጋ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ዳግም ማንም ከተማይቱን እንዲያፈርሳት ወይም እንዲነቅላት እኔ አልፈቅድም" ወይም "ማንን ከተማይቱን ዳግም አያጠፋትም ወይም አይደመስሳትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 32

Jeremiah 32:1

ይህ ከያህዌ ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል ነው

ይህ ፈሊጥ የዋለው እግዚአብሔር ለኤርምያስ መልዕክት እንደ ሰጠው ለማወጅ ነው። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 1:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠው" ወይም "ያህዌ ኤርምያስን ተናገረው/እንዲህ አለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ በነገሰ በአስረኛው አመት፣ በናቡከደነጾር አስራ ስምንተኛ አመት

"ሴዴቅያስ ለዘጠኝ አመታት የይሁዳ ንጉሥ ከሆነ በኋላ እና ናቡከደነጾር ከአስራ ሰባት አመታት በላይ ከነገሰ በኋላ"

ነቢዩ ኤርምያስ ታስሮ ነበር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ኤርምያስን እስረኛ አድርገውት ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ነቢዩ ኤርምያስ ታስሮ ነበር

እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንደሚጠቅስ ግልጽ አይደለም። በዩዲቢ ውስጥ እንደሚገኘው የመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ትችላላችሁ። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

በይሁዳ ንጉሥ ቤት የንጉሡ ዘብ ጠባቂዎች አደባባይ

ይህ በግንብ የተከበበ እና እስረኞችን የሚጠብቁበት/የሚያስሩበት ከንጉሡ ቤተመንግስት ጋር የተያያዘ ክፍት ስፍራ ነው።

Jeremiah 32:3

የይሁዳ ንጉሥ ሴዴቅያስ እርሱን አስሮት ነበር

ሴዴቅያስ ይህንን እንዲያደርግ ሌሎች ሰዎች ረድተውት እንደነበረ አንባቢው ይረዳ ዘንድ መተረጎሙ ይመረጣል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱን አስሮት ነበር

እዚህ ስፍራ "እርሱን" የሚለው የሚያመለክተው ኤርምያስን ነው። እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንደሚጠቅስ ግልጽ አይደለም። በዩዲቢ ውስጥ እንደሚገኘው የመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ትችላላችሁ። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለምን እንዲህ ብለህ፣ ትንቢት ተናገራለህ

ሴዴቅያስ ጥያቄውን የሚጠቀምበት ኤርምያስን ለመገሰጽ ነው። "ትንቢት መናገርህን መቀጠልህ ስህተት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህችን ከተማ ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነጾር እጅ አሳልፌ ልሰጣት ነው

ያህዌ ስለ ከተማይቱ፣ አንድ ሰው ለሌላው ሊያቀብለው እንደሚችለው ትንሽ እቃ አድርጎ ይናገራል። "እጅ" የሚለው ቃል እጅ ለሚሰራው ስራ ሀይል ወይም ቁጥጥር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት / ነው። "ይህችን ከተማ በባቢሎን ንጉሥ ቁጥጥር ስር ላደርጋት ነው" ወይም " የባቢሎን ንጉሥ በዚህች ከተማ ላይ ያሻውን እንዲፈጽም ልፈቅድለት ተነስቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር ወይም ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሱ ይማርካታል

አንባቢው የባቢሎን ንጉሥ ከተማይቱን እንዲቆጣጠር ሌሎች ሰዎች እንደረዱት ይገነዘብ ዘንድ መተርጎሙ ይመረጣል።

ለእርግጥ ለባቢሎን ንጉሥ እጅ ተላልፎ ይሰጣል

"እጅ" የሚለው ቃል ለሀይል ወይም እጅ የሚሰራውን ለመቆጣጠር ሜቶኖሚ/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ በእርግጥ በባቢሎን ንጉሥ ቁጥጥር ስር አደርገዋለሁ" ወይም "እኔ በእርግጥ የባቢሎን ንጉሥ በእርሱ ላይ ያሻውን እንዲፈጽም እፈቅዳለሁ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከንጉሡ ጋር አፍ ለአፍ ይናገራል፣ ደግሞም ዐይኖቹ የንጉሡን ዐይን ይመለከታሉ

እዚህ ስፍራ "አፍ" እና "ዐይን" የሚወክሉት መላውን ሰውነት ነው። "ሴዴቅያስ ራሱ ንጉሥ ናቡከደነጾርን ይመለከተዋል በቀጥታም ከእርሱ ጋር ይነጋገራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ትዋጋላችሁ

እዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው ብዙ ቁጥር ነው። (አንተ የሚለው ተውላጠ ስም መልኮች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:6

ኤርምያስ እንዲህ አለ፣ "የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፣ 'እነሆ፣ የአጎትህ የሰሎም ልጅ አናምኤል ወደ አንተ መጥቶ፣ "በዓናቶት ያለውን የእኔን መሬት ለራስህ ግዛ፣ ይህን የመግዛቱ መብት የአንተ ነውና" ይልሃል።'""

ይህንን ቀጥተኛ ወዳልሆነ ንግግር መተርጎም ሊያስፈልግ ይችላል። "ኤርምያስ እንዲህ አለ፣ የያህዌ ቃል ወደ እርሱ መጥቶ በዓናቶት ያለውን የአጎቱን የሰሎምን ልጅ የአናምኤልን መሬት ለራሱ ይግዛ ይህን መሬት መግዛት መብቱ የኤርምያስ ነውና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቀጥተኛ የሆነ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

ኤርምያስ እንዲህ አለ

እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንደሚጠቅስ ግልጽ አይደለም። በዩዲቢ እንደ ተተረጎመው አንደኛ መደብን በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል እነሆ፣ እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ

ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ እንዲህ ሲል፣

መልዕክት ሰጠኝ። 'ተመልከት/እነሆ" ወይም "ያህዌ ይህን መልዕክት ለእኔ ነገረኝ፡ 'እነሆ/ተመልከቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አናምኤል... ሰሎም

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓናቶት

ይህ የቦታ ስም ነው። ይህ በኤርምያስ 1:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:8

አጠቃላይ መረጃ፡

ኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል፣ ነገር ግን ስለ ራሱ የሚናገረው በአንደኛ መደብ ነው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

የዘብ ጠባቂዎች አደባባይ

ይህ በግንብ የተከበበ እና እስረኞችን የሚጠብቁበት ከንጉሡ ቤተመንግስት ጋር የተያያዘ ክፍት ስፍራ ነው። ይህ በኤርምያስ 32፡2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

አስራ ሰባት ሰቅሎች

አንድ ሰቅል 11 ግራም ነው። "17 ሰቅል" ወይም "187 ግራም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መጽሐፍ በተጻፈበት ጊዜ የገንዘብ መጠን መለኪያ እና ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:10

አጠቃላይ መረጃ፡

ኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

ጥቅልሉ ታትሞበት፣ ደግሞም ምስክሮች ምስክርነት ሰትተውበት

ይህ የሚያመለክተው አንድ ሰው መሬት ለመግዛት በሰነዱ ላይ የሚያደርገውን ፊርማ ነው። ኤርምያስ ይህንን መሬት መግዛን ለማረጋገጥ ሌሎች ሰዎች ምስክሮች ይሆናሉ።

ምስክሮች ምስክር ይሆናሉ

"መሬቱን ስገዛ ሰዎች ተመልክተዋል፣ ስለዚህ እኔ መሬቱን ለመግዛቴ ለሌሎች መናገር ይችላሉ"

የታተመ ነበር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ እንዳተምኩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ያልታተመበት ሰነድ

"ክፍት ቅጂ" ወይም "በላዩ ማህተም የሌለበት ሰነድ"

ባሮክ...ኔርያ...መሕሤያ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የዘብ ጠባቂዎች አደባባይ

ይህ በግንብ የተከበበ እና እስረኞችን የሚጠብቁበት ከንጉሡ ቤተመንግስት ጋር የተያያዘ ክፍት ስፍራ ነው። ይህ በኤርምያስ 32፡2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Jeremiah 32:13

አጠቃላይ መረጃ፡

ኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

በእነርሱ ፊት

እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው አናምኤልን፣ ምስክሮችን፣ እና በዚያ የነበሩ አይሁዳውያንን ነው።

የሰራዊት ጌታ ያህዌ... እንዲህ ይላል

ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ቤቶች፣ እርሻዎች፣ እና የወይን ቦታዎች ዳግም በዚህ ስፍራ ይገዛሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "የእስራኤል ሰዎች ዳግም በዚህ ምድር ቤቶችን፣ የወይን ቦታዎችን እና እርሻዎችን ይገዛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:16

አጠቃላይ መረጃ፡

ኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል። ረጅም ጸሎት ጀመረ፣ ከረጅም እንጉርጉሮ ጋር ምስጋና ጭምር አቀረበ።

የግዢ ደረሰኝ

ይህ ማለት የታተመው ጥቅልል እና ያልታተመ ጥቅልል ነው

አወይ፣ ጌታ ያህዌ! እነሆ!

እዚህ ስፍራ "አወይ/ወየው" የሚለው ቃል በዚህ ጸሎት ኤርምያስ ማዘኑን፣ ማጉረምረሙን እና እንጉርጉሮ ማሰማቱን ያመለክታል። "እነሆ/እዩ" የሚለው ቃል ቀጣዮቹ ቃላት ለጸሎቱ በጣም አስፈላጊ የሆነ መግቢያ ወይም ዳራ መሆኑን ያመለክታል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

በታላቅ ጥንካሬህ እና በተነሳው ክንድህ

"የተነሳ ክንድ" የሚለው ሀረግ ለክንድ ጥንካሬ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው፤ ስለዚህም "ታላቁ ጥንካሬህ" የሚሉት ቃላት እና "የተነሱት ክንዶችህ" የሚለው ጥንድ ትርጉምን ይሰጣል። "በታላቁ ሀይልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ የቃል ኪዳን ታማኝነትን ለሺህዎች አሳይተሃል

"ታማኝነት" የሚለው ረቂቅ ስም "ታማኝ" ወይም "በታማኝነት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "አንተ ለሺህዎች ለቃል ኪዳንህ ታማኝ ነህ" ወይም "አንተ ቃል ኪዳንህን ትጠብቃለህ፣ ደግሞም ሺህዎችን በታማኝነት ትወዳለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰዎችን ጥፋት ከእነርሱ በኋላ በሚመጡት ልጆቻቸው ጭን ላይ አፍስስ

"ጥፋት" የሚለው ቃል ያህዌ ህዝቡን ለመቅጣቱ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው፤ ምክንያቱም እነርሱ ክፉ ነገሮችን በማድረግ ጥፋተኞች ናቸው። የያህዌ ህዝቡን መቅጣት የተገለጸው ፈሳሽ በትልቅ ማጠራቀሚያ የሞላ ፈሳሽን እንዳፈሰሰባቸው ወይም በተቀመጡበት በጭናቸው ላይ ትንንሽ እቃዎችን እንደጣለባቸው ተደርጎ ተገልጽዋል። "አንተ ልጆችን በወላጆቻቸው ኃጢአት ምክንያት ትቀጣለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:19

አጠቃላይ መረጃ፡

ኤርምያስ ለእንጉርጉሮው መግቢያ የሚሆነውን ጸሎት ወደ ያህዌ ማቅረቡን ቀጥሏል

ዐይኖችህ ለሰዎች መንገዶች ሁሉ የተከፈቱ ናቸው

የተከፈቱ ዐይኖች ሰው ለሚመለከተው ነገር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት / ነው። ሰው እንዴት እንደሚኖር የተገለጸው በጎዳና ላይ እንደሚራመድ ተደርጎ ነው። "አንተ ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ ትመለከታለህ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእያንዳንዱ ሰው ለባህሪው እና ለተግባሩ የሚገባውን መስጠት

ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው "ባህሪይ" እና "ተግባር/ድርጊት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በግስ መልካቸው ሊተረጎሙ ይችላሉ። "እናም ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ስራው መልካምነት ወይም ክፋት ይከፍለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ በግብጽ ምድር ድንቅ እና ምልክቶችን አድርገሃል

ይህ እግዚአብሔር በቀድሞው ዘመን ሀይሉን ተጠቅሞ የእስራኤልን ህዝብ ከግብጽ ባርነት ነጻ ያወጣበትን ድርጊት ያመለክታል።

እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ

"እስከዚህ ቀን"

በሰው ልጆች ሁሉ መሃል

"በሰዎች ሁሉ መሃል"

ስምህን ታዋቂ አደረግህ

እዚህ ስፍራ "ስም" የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ክብር ነው። "እራስህን ገናና አደረግህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በብርቱ እጅ፣ በተዘረጋ ክንድ

"በብርቱ እጅ" የሚለው ለጥንካሬ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን፤ "የተዘረጋ ክንድ" የሚለው ለክንድ ጥንካሬ ሜቶኖሚ/ ነው። ስለዚህም "በብርቱ እጅ" የሚለው ሀረግ እና "የተዘረጋ ክንድ" የሚሉት ሀረጎች ጥንድ ትርጉም ይሰጣሉ። "በታላቁ ጥንካሬህ/ሀይልህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Jeremiah 32:22

አጠቃላይ መረጃ:

ኤርምያስ ወደ ያህዌ መጸለዩን ቀጥሏል። የእንጉርጉሮ ለቅሶውን ማቅረቡን ጨረሰ። ("ወየው፣" ኤርምያስ 32:17) "ከዚህ ርስት ወሰዱ" ከሚሉት ቃላት ጋር "ነገር ግን እነርሱ አልታዘዙም" በሚለው ሰቆቃውን ይጀምራል።

ለእነርሱ ሰጠሃቸው

"ለእስራኤል ሰዎች ሰጠህ"

ማር እና ወተት የምታፈስ ምድር

"ማር እና ወተት የሚፈስባት ምድር።" እግዚአብሔር ምድሪቱ ለተክሎች እና ለእንስሳት መልካም እንደሆነች የተናገረው ከእነዚያ እንስሳት እና ተክሎች የሚገኘው ወተት እና ማር በምድሪቱ ላይ እንደሚፈስ አድርጎ ነው። ኤርምያስ 11:5 ላይ ይህ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ከብት ለማርባት እና ተክል ለማብቀል እጅግ ምቹ የሆነ ምድር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን እነርሱ ድምጽህን አልታዘዙም

ድምጹ ተናጋሪው ለሰጠው መልዕክት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ነገር ግን እነርሱ አንተ የተናገርከውን አልታዘዙም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:24

አጠቃላይ መረጃ:

ኤርምያስ ወደ ያህዌ መጸለዩን ቀጥሏል።

የአፈር ቁልሉ እርሷን ለመያዝ እስከ ከተማይቱ ደርሷል

የአፈሩ ቁልል እና ጠላት በላያቸው ቆሞ ሊያጠቃት በከተማይቱ ዙሪያ ገነባው፣ የተገለጸው አጥቂዎቹ ራሳቸው ከተማይቱን ለመውረር እንደ ደረሱ ተደርጎ ነው። "ጠላት ያበጀው አፈር ቁልል፣ ጠላት ሊይዛት እስከሚያስችለው ለከተማይቱ እጅግ ቅርብ ነው" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከሰይፍ የተነሳ

"ሰይፍ" የሚለው ቃል ወታደሮች ሰይፍ በሚጠቀሙበት፣ ለጦርነት ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ምክንያቱም ወታደሮች ጥቃት ያደርሳሉ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ረሃብ፣ እና መቅሰፍት

እነዚህ ረቂቅ ስሞች በግሳዊ ሀረግ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ህዝቡ የሚመገበው ምግብ የለውም፣ ደግሞም እያንዳንዱ ሰው ከህመም የተነሳ ደካማ ሆኗል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከተማይቱ ለከለዳውያን እጅ ተላልፋ ተሰጥታ ነበር

እዚህ ስፍራ "እጅ" ማለት ሀይል ወይም መቆጣጠር ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "አንተ እየሩሳሌምን ለከለዳውያን ወታደሮች አሳልፈህ ሰጥተሃታል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ይህ ይሆናል፣ አንተ ታያለህ

"አንተ በግልጽ እንደምታየው፣ ይህ ይሆናል"

ምስክሮች ይህን መስክረዋል

"አንተ መሬን ስትገዛ ሰዎች ተመልክተዋል፣ ስለዚህም እነርሱ ለሌሎች ሰዎች አንተ መሬቱን እንደገዛህ መናገር/መመስከር ይችላሉ"

ከተማይቱ ተሰጥታለች

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ ይህችን ከተማ ልሰጣት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:26

የያህዌ ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ "ያህዌ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። በኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ፣ እንዲህ ሲል መልዕክት ሰጠው። 'ያህዌ" ወይም "ያህዌ ይህንን መልዕክት ለኤርምያስ ሰጠው፡ 'ያህዌ"

ወደ ኤርምያስ መጣ

እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንደጠቀሰ ግልጽ አይደለም። በዩዲቢ እንደ ተተረጎመው አንደኛ መደብን በመጠቀም መተረጎም ይቻላል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእኔ እጅግ ከባድ የሆነ ነገር አለን?

ያህዌ ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ ማንኛውንም ነገር ማድረግ እንደሚችል ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ለእኔ እጅግ ከባድ የሆነ ነገር የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ፣ እኔ አሳልፌ እሰጣታለሁ

"በጥንቃቄ አድምጡ! አሳልፌ የምሰጣት እኔ ነኝ"

ይህችን ከተማ ለከለዳውያን እጅ እሰጣለሁ

ያህዌ ስለ ከተማይቱ፣ ትንሽ እቃ እንደሆነች እና ለሰው እጅ እንደሚሰጣት አድርጎ ይናገራል። "እጅ" የሚለው ቃል እጅ ወደ ድርጊት ለሚለውጠው ሀይል ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ይህችን ከተማ በከለዳውያን ሀይል ስር አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:29

አጠቃላ መረጃ:

ያህዌ ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

እኔን ለማነሳሳት

"እኔ በጣም እቆጣ ዘንድ"

በዐይኖቼ ፊት ክፉ ያደርጋሉ

እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው ሜቶኖሚ የሚወክለው እግዚአብሔር የተመለከተውን ነገር ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እኔ ክፉ የምለውን ነገር ማድረግ" ወይም 2) "እኔ እየተመለከትኩ መሆኑን እያወቁ ክፉ ማድረግ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከወጣትነታቸው አንስቶ

የአንድ ሰው ወጣት መሆን ለእስራኤል ህዝብ በመጀመሪያ አገር መሆን ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "ወጣት ከነበሩበት ጊዜ አንስቶ" ወይም "አገር ሆነው ከተመሰረቱበት ጊዜ አንስቶ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእጆቻቸው ልምምዶች

"እጆች" የሚለው ቃል አንድ ሰው በእጆቹ ለሚሰራቸው ነገሮች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ያደረጓቸው ክፉ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:31

አጠቃላ መረጃ:

ያህዌ ለኤርምያስ መናገሩን ቀጥሏል።

ይህች ከተማ ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ የእኔን ቁጣ እና ንዴት ታነሳሳ ነበር

እዚህ ስፍራ "ከተማ" የሚለው በውስጧ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ ነው። "ቁጣ" እና "ንዴት" በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲይዙ ምን ያህል በጣም እንደተቆጣ ያጎላሉ። "የእየሩሳሌም ሰዎች ከተማቸውን ከገነቡበት ጊዜ አንስቶ እኔን በጣም አስቆጥተውኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ጥንድ ትርጉም የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔን የሚያነሳሳ ነበር

"ማነሳሳት" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። "የሚያነሳሳ ነገር ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ እስከ ዛሬው ቀን ደረሰ ቀጥሏል

"አሁን ደረስ እኔን ማስቆጣታቸውን ቀጥለዋል"

ከገጽታዬ ፊት/ከፊቴ

ፊት ለአንድ ሰው መገኘት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ከእኔ መገኘት" ወይም "ሙሉ ለሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 32:33
አጠቃላ መረጃ:
ያህዌ ለኤርምያስ የእስራኤል ህዝብ ስላደረገው ነገር መናገሩን ቀጥሏል፡፡
ከፊታቸው ይልቅ ጀርባቸውን አዙረውብኛል
አንድ ሰው ፊቱን ወደ ሌላ ሰው ማድረጉ እየማ መሆኑን ያሳያል፣ ጀርባውን መስጠቱ ደግሞ ለመስማት አለመፍቀዱን ያሳያል፡፡ "እኔን በጥንቃቄ ከመስማት ይልቅ፣ ሙሉ ለሙሉ ሊሰሙኝ አልፈቀዱም" ወይም "እኔን ለመስማት አልፈቀዱም/ለመስማት ተቃወሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ትዕምርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
እርማትን/ተግሳጽን ለመቀበል
"በትክክል ምላሽ መስጠትን ለመማር"
አስጸያፊ ጣኦቶቻቸው
"እኔ የምጠላቸው ጣኦቶቻቸው"
በስሜ የተጠራው ቤቱ
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚወክለው ያህዌን ነው፡፡ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል፡፡ "የእኔ የሆነው ቤት" ወይም "እነርሱ እኔን የሚያመልኩበት ህንጻ/ቤት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
የሄኖም ሸለቆ
ይህ በኤርምያስ 7፡31 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡
ይህን በፍጹም በልቤ አላሰብኩም/ወደ አዕምሮዬ አልገባም
እዚህ ስፍራ "ልብ/አዕምሮ" የሚያመለክተው የያህዌን ፈቃድ/ሀሳብ ነው፡፡ "እኔ በፍጹም አላሰብኩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Jeremiah 32:36
እናንተ የተናገራችሁት
እዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው ብዙ ቁጥር ነው፡፡ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኤርምያስን እና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ይገልጻል፣ ወይም 2) ሁሉንም ሰዎች ያመለክታል፡፡ (አንተ/አንቺ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)
እርሷ ለባቢሎን ንጉሥ እጆች ተሰጠች
እዚህ ስፍራ "እጅ" ማለት ሀይል ወይም ቁጥጥር ማለት ነው፡፡ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ያህዌ ለባቢሎን ንጉሥ እርሷን/ከተማይቱን እንዲገዛ ሀይል ሰጠው" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
እነርሱን ለመሰብሰብ
"የእኔን ህዝብ ለመሰብሰብ"
ንዴት፣ መዓት፣ እና ታላቅ ቁጣ
ሶስቱም ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲይዙ እርሱ ምን ያህል እንደተቆጣ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ "ከመጠን ያለፈ ቁጣ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
በደህንነት
"እነርሱ በሰላም ባሉበት"
Jeremiah 32:38
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ መናገሩን ቀጥሏል፡፡
እኔን ለማክበር አንድ ልብ እና አንድ መንገድ
የእስራኤል ሰዎች ያህዌን ለማክበር በአንድነት መስራት ይፈልጋሉ፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን
"ዘለዓለማዊ ስምምነት"
መልካም ከማድረግ ወደ ኋላ አልመለስም
"መልካም ማድረግን አላቆምም"
በእነርሱ ልብ ለእኔ ክብርን አኖራለሁ
ክብር የተገለጸው ጠጣር አካል እንደሆነ እና ማንም ከዚያ ሊያሰወግደው እንዳይችል ተደርጎ በመያዣ ውስጥ እንደተቀመጠ ተደርጎ ነው፡፡ "እነርሱ ሁልጊዜም እንዲያከብሩኝ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዜቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚህ የተነሳ እነርሱ በፍጹም ከእኔ ፊታቸውን አይመልሱም
"ከዚህ የተነሳ እኔኝ መታዘዝ እና ማምለክ በፍጹም አያቆሙም"
Jeremiah 32:41
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ መናገሩን ቀጥሏል፡፡
ለእነርሱ መልካም ማድረግ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው እስራኤላውያንን ነው፡፡
እኔ እነርሱን በዚህች ምድር በታማኝነት እተክላቸዋለሁ
ያህዌ የእርሱ ህዝብ ህይወት በአትክልት ስፍራ እንደተከለው ትክል ለዘለአለም እንደሚኖር አድርጎ ይናገራል፡፡ "እኔ እስራኤላውያንን በቋሚነት በዚህ ምድር አስቀምጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በሙሉ ልቤ እና በህይወቴ ሁሉ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በአንድነት የአንድን ሰው ሁለንተና የሚያመለክት ፈሊጣዊ አገላለጽን ይሰጣሉ፡፡ "በፍጹም ማንነቴ" ወይም "በሙሉ ልቤ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ጥንድ ትርጉም እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
እኔ እነዚህን ሁሉ ታላላቅ ጥፋቶች በዚህ ህዝብ ላይ አምጥቻለሁ፣ እንደዚሁ ደግሞ መልካም ነገሮችን ሁሉ ለዚህ ህዝብ አደርጋለሁ
"እነዚህ ሁሉ መጥፎ ነገሮች በዚህ ህዝብ ላይ እንዲደርስ አድርጌያለሁ፣ አሁን ደግሞ መልካም ነገሮች እንዲሆንላቸው አደርጋለሁ"
Jeremiah 32:43
ከዚያ የእርሻ መሬቶች በዚህ ምድር ይገዛሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ከዚያ ሰዎች በዚህ ምድር የእርሻ መሬት ይገዛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ እንደዚህ ትላላችሁ
እዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤል ሰዎችን ነው፡፡ (አንተ/አንቺ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)
ለከለዳውያን እጆች ተሰጥታ ነበር
እዚህ ስፍራ "እጅ" ለሀይል ወይም ቁጥጥር ሜቶኖሚ/ ነው፡፡ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ያህዌ ለከለዳውያን ይህን ሰጣቸው" ወይም "ያህዌ ለከለዳውያን በእርሷ ላይ ሀይል ሰጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ))
በታተሙ ጥቅልሎች ላይ ጻፉ፡ ምስክሮችን ይጠራሉ
"የታተሙ ጥቅልሎች" አንድ ሰው መሬት ለመግዛት የሚፈርምበት ውል ነው፡፡ ሌሎች ሰዎች ግዢውን ለማረጋገጥ ምስክር ይሆናሉ፡፡
እድል ፈንታቸውን/ሀብታቸውን እመልስላቸዋለሁ
"ነገሮች ተመልሰው መልካም እንዲሆንላቸው አደርጋለሁ" ወይም "ዳግም ወደ መልካም ህይወት እመልሳቻለሁ" ተመሳሳይ የሆኑ ቃሎች በኤርምያስ 29፡14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ፡፡
ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 33
Jeremiah 33:1
አጠቃላይ መረጃ:
ስነግጥም እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ
የያህዌ ቃል ለሁለተኛ ጊዜ፣ በዘብ ... በነበረበት ጊዜ ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ "ያህዌ
"የያህዌ ቃል ወደ… መጣ" የሚለው ፈሊጥ የዋለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው፡፡ በኤርምያስ 1፡13 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ኤርምያስ በዘብ… በነበረበት ጊዜ ያህዌ ለኤርምያስ እንዲህ ሲል ለሁለተኛ ጊዜ መልዕክት ሰጠው፡ 'ያህዌ" ወይም "ኤርምያስ በዘብ… በነበረበት ጊዜ ያህዌ ይህን ሁለተኛ መልዕክት ለኤርምያስ ሰጠው፡ 'ያህዌ"… በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን

ይመልከቱ)

ወደ ኤርምያስ መጣ

እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንሚጠቅስ ግልጽ አይደለም። አንደኛ መደብን በመጠቀም መተረጎም አስፈላጊ አይደለም። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ሊያጸናቸው ያበጃቸው ማን ነው

ነገሮች ለዘለዓለም ይኖሩ ዘንድ የፈጠራቸው ማን ነው

እስከዚህ ድረስ ተዘግቶበት ነበር

"እስከ አሁን ድረስ እስረኛ ነበር"

የዘብ ጠባቂዎች አደባባይ

ይህ በግንብ የተከበበ እና እስረኞችን የሚጠብቁበት/የሚያስሩበት ከንጉሡ ቤተመንግስት ጋር የተያያዘ ክፍት ስፍራ ነው። ይህ በኤርምያስ 32:2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Jeremiah 33:4

ከወውጊያ እና ከሰይፍ የተነሳ ከፈራረሱት

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰዎቹ ከለዳውያንን ለመከላከያ ቅጥር ለመገንባት ቤቶችን አፈረሱ። "ከውጊያ እና ሰይፍ ራሳቸውን ለመከላከል ሰዎች የከተማዋን ቤቶችን አፈራረሱ" ወይም 2) "ጦርነት ለማድረግ ሲሉ በጦርነት ከበባ አመጽ ለማነሳሳት ከለዳውያን ያፈራረሷቸው ቤቶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ

ይህ ወታደሮች በሰይፍ ሲገድሉ ለሰዎች በጥቃት መገደል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በቁጣዬ እና በመአቴ

"ቁጣ" እና "መአት" የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የቁጣውን ታላቅነት ያጎላሉ። "ከመጠን በላይ በሆነው ቁጣዬ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ፊቴን እሰውራለሁ/እደብለሁ

ያህዌ በ"ፊቱ" ተወክሏል። ይህ ሀረግ የሚያሳየው የያህዌን በከተማይቱ ደስ አለመሰኘት ነው። "እኔ ከእናንተ ዞር ብያለሁ" ወይም "ከእንግዲህ ለእናንተ ጥበቀ አላደርግም/እተዋችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 33:6

የይሁዳን እና እየሩሳሌምን ሀብት/ምርኮ እመልሳለሁ

"ለይሁዳ እና እስራኤል ነገሮች መልካም እንዲሆኑ አደርጋለሁ" ወይም "ይሁዳ እና እስራኤል ዳግም በመልካም እንዲኖሩ አደርጋለሁ።" ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በኤርምያስ 29:14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ይህች ከተማ... ለእርሷ ያደረግኩትን... ለራሷ የሰጠሁትን

ከተማይቱ የሚለው በከተማዋ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ ነው። "በዚህች ከተማ የሚኖሩ ሰዎች ...በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች የማደርገው... በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች የምሰጠው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለመላው የምድር አገራት የውዳሴ እና ክብር ዝማሬ

"ዝማሬ" የሚለው ቃል ሰዎች ስለ ሚዘምሩት ዝማሬ አካል ሜቶኖሚ/ ነው። "የምድር ወገኖች ሁሉ የውዳሴ እና ክብር ዝማሬ ለእኔ ለያህዌ ስለሚያቀርቡት ነገር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይፈራሉ ይንቀጠቀጡማል

"ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ" የሚለው ሄንዲያዲስ/ሁለት በ'እና' የሚገኛኙ ቃላት አንድን ጥልቅ ሀሳብ የሚገልጹበት ዘይቤያዊ አነጋገር/ በአንድ ግስ ሊተረጎም ይችላል። "በፍርሃት ይንቀጠቀጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሄንዲያዲስ/ ሁለት በ'እና' የሚገኛኙ ቃላት አንድን ጥልቅ ሀሳብ የሚገልጹበት ዘይቤያዊ አነጋገር/ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርሃት

ሌላው ሊሰጥ የሚችለው ትርጉም "አክብሮታዊ ፍርሃት" የሚል ነው።

ለእርሷ ከምሰጠው ሰላም እና መልካም ነገሮች ሁሉ የተነሳ

"ሰላም" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ለእርሷ ከምሰጠው ሰላም እና መልካም ነገሮች ሁሉ የተነሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 33:10

ሰውም እንስሳም የማይኖርባት ምድረ በዳ ናት፣" ምድረ በዳ በሆኑት በይሁዳ ከተሞች፣ እና በእየሩሳሌም መንገዶች ሰውም ሆነ እንስሳት አይኖሩም

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ይሁዳ ምድረበዳ መሆኗን ያጎላሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቤት

በእየሩሳሌም የሚገኘው ቤተ መቅደስ

የምድሪቱን እደል ፈንታ እድሳለሁ

"ምድር" የሚለው ቃል በምድሪቱ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ዳግም በምድሪቱ ለሚኖሩ ሰዎች ነገሮችን መልካም አደርጋለሁ" ወይም "በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎችን ዳግም በመልካም እንዲኖሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በኤርምያስ 29:14 ላይ እንዴት እንደተተረጎሙ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አስቀድሞ ወደ ነበሩበት

ይህ ወደ ባቢሎን ከመሰደድ አስቀድሞ የነበረውን ጊዜ ያመለክታል። ይህ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "እነርሱ አስቀድመው ወደ ነበሩበት፣ እስራኤላውያንን ለምርኮ ወደ ባቢሎን እስዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 33:12

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል

ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ከያህዌ ዘንድ ጠቃሚ መልዕክትን ለማስተዋወቅ ነው። ይህ በኤርምያስ 6:6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ከብቶች ዳግም በሚቆጥሯቸው እጅ ስር ያልፋሉ

ይህ የእረኞች በጎቻቸው ከእጃቸው ስር ሲሄዱ የሚያደርጉትን በጎቻቸውን የመቁጠር እና የመጠበቅ ልምምድ ያመለክታል። "እረኞች በጎች በሚያልፉበት ጊዜ እንደ ቀድሞው በጎቻቸውን ይቆጥራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 33:14

እነሆ/እዩ

"በጥንቃቄ አድምጡ"

እኔ የምሰራባቸው...ቀናት እየመጡ ነው

መጪው ጊዜ የተነገረው "ቀናት እየመጡ" እንደሆነ ተደርጎ ነው። ይህ ዘይቤ በኤርምያስ 7:32 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ በመጪው ጊዜ... እሰራለሁ" ወይም "እኔ የምሰራበት...ጊዜ ይኖራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት

"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤል" ወይም "የእስራኤል መንግሥት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት

"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው፣ የይሁዳን እና የብንያምን ትውልድ የሚያጠቃልለውን የይሁዳን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ይሁዳ" ወይም "የይሁዳ መንግሥት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእነዚያ ቀናት ወይም በዚያን ጊዜ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"በዚያን ጊዜ" የሚለው ሀረግ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖረው "በእነዚያ ቀናት" የሚለውን ሀረግ ያጠናክራል። "በእነዚያው በራሳቸው ቀናት" ወይም "በዚያኑ በራሱ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

ለዳዊት የጽድቅ ቅርንጫፍ እንዲበቅል አደርጋለሁ

ያህዌ የዳዊትን ትውልድ የሚገልጸው የዛፍ ግንድ ቅርንጫፍ እንደሆነ አድርጎ ነው። "እኔ ጻድቅን ሰው ከዳዊት እንዲመጣ እና ለዳዊት ዘር ክብር እንዲያመጣ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱ

የእስራኤል ህዝብ። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ… እየሩሳሌም

እነዚህ ሁለት የከተሞች ስሞች በእነዚያ ከተሞች ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። "የይሁዳ ሰዎች… የእየሩሳሌም ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ ይድናል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ ይሁዳን አድነዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እየሩሳሌም በደህንነት/በሰላም ትኖራለች

"የእየሩሳሌም ሰዎች ከጠላቶቻቸው የተጠበቁ ይሆናሉ"

እርሷ የምትጠራበት ይህ ይሆናል

ያህዌ ስለ እየሩሳሌም ከተማይቱ ሴት እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "እርሷን የሚሯት እንዲህ ብለው ነው" ወይም "እኔ ከተማይቱን የምጠራት እንዲህ ብዬ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Jeremiah 33:17

ከዳዊት ትውልድ የሆነ ሰው አይታጣም

"ሁልጊዜም ከዳዊት ትውልድ የሆነ ሰው ይገኛል"

ከዳዊት ትውልድ የሆነ ሰው

ወንድ የሆነ የንጉሥ ዳዊት ትውልድ

በእስራኤል ቤት ዙፋን ላይ ለመቀመጥ

ዙፋን ለንጉሡ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በእስራኤል ቤት ላይ ንጉሥ ለመሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት

"ቤት" የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በዚህ ሁኔታ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መንግሥት ነው። ይህ በኤርምያስ 3:18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤል" ወይም "የእስራኤል መንግሥት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የሚቃጠል መስዋዕት በፊቴ ለማንሳት/ለማቅረብ ከሌዊ ካህናት መሃል ሰው አይታጣም

"ሁሉም ከሌዊ ካህናት የሚቃጠል መስዋዕት የሚያነሳ ሰው አይታጣም"

የሚቃጠል መስዋዕት የሚያነሳ/የሚያቀርብ

"የሚቃጠሉ መስዋዕቶች የሚያቀርብ"

Jeremiah 33:19

የያህዌ ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ "ያህዌ

x

Jeremiah 33:23

የያህዌ ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ "እንዲህ አለኝ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። በኤርምያስ 1:4 ላይ ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ፣ እንዲህ ሲል መልዕክት ሰጠው። 'እንዲህ አለኝ" ወይም "ያህዌ ይህንን መልዕክት ለኤርምያስ ሰጠው፡ 'እንዲህ አለው"

ወደ ኤርምያስ

እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንደጠቀሰ ግልጽ አይደለም። አንደኛ መደብን በመጠቀም መተረጎም አያስፈልግም። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ህዝብ እንዲህ ሲል አላስተዋልክም፣ 'የ… እነርሱ።'"

ያህዌ ህዝቡ ምን እንዳለ ኤርምያስ እንዲያስተውል ፈልጓል። ይህ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ይህ ህዝብ 'የ…እነርሱ' ሲል ምን እየተናገረ እንደጀሆነ ልታስተውል ይገባሃል" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚህ መንገድ፣ አይታዩም… እያሉ ህዝቤን አዋርደዋል

"በእርግጥ እነርሱ እየተናገሩ የሚገኙት ህዝቤ እርባና ቢስ እና ዳግም አገር ሆኖ የማይቆም እንደሆነ አድርገው ነው"

ህዝቤ… በእነርሱ እይታ ከእንግዲህ አገር አይሆንም

እይታ ማሰብ ለሚለው ሜቶኖሚ/ ነው። "ከእንግዲህ ህዝቤን እንደ አገር አያስቡም/ አያዩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 33:25

እኔ አልመሰረትኳቸውም… እናም እኔ ካላጸናኋቸው…እኔ እጥላቸዋለሁ…እናም አልመልሳቸውም

ይህ ያህዌ በፍጹም ይሆናል የማይለው መላምታዊ ሁኔታ ነው። "እኔ መስርቻለሁ… እና እና አጽንቻለሁ… ስለዚህ እኔ በፍጹም አልጥልም … እናም እኔ እመልሳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እድል ፈንታቸውን /ሀብታቸውን እመልሳለሁ

"ዳግም ነገሮች ለእነርሱ መልካም እንዲሆኑ አደርጋለሁ" ወይም "እኔ እነርሱ ዳግም በመልካም እንዲኖሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በኤርምያስ 29:14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።

ለ…ምህረት አሳያለሁ

"በ…ላይ ርህራሄ አለኝ" የሚለው በ(ኤርምየስ 30:18) ላይ እንደተተረጎመው ይተርጉሙት።

---

Chapter 34

Jeremiah 34:1

ናቡከደነጾር የእርሷ ከተሞች… በነበረ ጊዜ፣ ከያህዌ ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣው ቃል እንዲህ ሲሉ፡"ያህዌ

"ከያህዌ ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል" የሚለው ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። ተመሳሳይ የሆነው በኤርምያስ 7:1 ላይ የሚገኘው ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎም ይመልከቱ እና እንደ አስፈላጊነቱ ለውጥ አድርጉበት። "ይህ ናቡከደነጾር የእርሷን ከተሞች በ…. ጊዜ ያህዌ ለኤርምያስ የሰጠው መልዕክት ነው" እንዲህም አለ፣ 'ያህዌ" ወይም "ናቡከደነጾር የእርሷን ከተሞች በ…ጊዜ፣ ያህዌ ለኤርምያስ ይህን መልዕክት ሰጠው፡ 'ያህዌ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ኤርምያስ

እዚህ ስፍራ ኤርምያስ ለምን ራሱን በስም እንደጠቀሰ ግልጽ አይደለም። አንደኛ መደብን በመጠቀም መተረጎም አያስፈልግም። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ጦርነት ማወጅ

"መዋጋት"

የእርሷ ከተሞች ሁሉ

ይህ የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም ዙሪያ የሚገኙ ከተሞችን ሁሉ ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህችን ከተማ አሳልፎ ለመስጠት

ይህ በኤርምያስ 32:28 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ

ለባቢሎን ንጉሥ እጅ

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል እጅ ለሚሰራው የመቆጣጠር ስራ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ከእርሱ ቁጥጥር አታመልጥም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በእርግጥ ትያዛለህ ደግሞም ተላልፈህ ትሰጣለህ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ባቢሎናውያን በእርግጥ ይይዙሃል፣ አንተም አልፈህ ተሰጣለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Jeremiah 34:4

በሰይፍ አትሞትም።

"ሰይፍ" የሚለው ቃል በጦርነት ለመሞት ሜቶኖሚ/ ነው። "በጦርሜዳ አትሞትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ለአባቶችህ ቀብር የሚነድ እሳት

ሰዎቹ በቅርቡ ለሞቱ ሰዎች ክብር ቅመም ያቃጥላሉ። የሞቱትን ሰዎች አካል/ አስክሬን አያቃጥሉም።

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 34:6

ለኪሶ እና ዓዜቃ

እነዚህ የከተሞች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ የይሁዳ ከተሞች የተመሸጉ ከተሞች ሆነው ይኖራሉ

"ባቢሎናውያን ገና ያልያዝዋቸው ብቸኞቹ የተመሸጉ የይሁዳ ከተሞች"

Jeremiah 34:8

ከያህዌ ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል

ይህ ፈሊጥ የዋለው ከያህዌ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማሰተዋወቅ ነው። በእርግጥ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት እስከ ኤርምያስ 34፡12 ድረስ አልጀመረም። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በኤርምያስ 7፡1 እንዴት እንደ ተተረጎም ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠው" ወይም "ያህዌ ለኤርምያስ መልዕክት ነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቃል

መልዕክት

ንጉሥ ሴዴቅያስ ቃል ኪዳን ካደረገ በኋላ...የእርሱ ወንድም

እነዚህ ቃላት ሁሉም በኋላ ለሚገለጹ ድርጊቶች የመረጃ ዳራ/መነሻ ይሰጣሉ። (የመረጃ ዳራ/ የመረጃ መነሻ የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 34:10

አያያዥ ሀሳብ፡

ኤርምያስ በኤርምያ 354፡8 ላይ የሚጀምረውን የመረጃ ዳራ መስጠቱን ይቀጥላል።

Jeremiah 34:12

አያያዥ ሀሳብ፡

በኤርምያስ 34፡8-11 ውስጥ ከሚገኘው የመረጃ ዳራ በኋላ ኤርምያስ ታሪኩን ከኤርምያስ 34፡8 እንደገና ይጀምራል።

የያህዌ ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፣ "ያህዌ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር የዋለው ከእግዚአብሔ ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ነው። በኤርምያስ 1፡4 ላይ ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ለኤርምያስ፣ እንዲህ ሲል መልዕክት ሰጠው። 'ያህዌ" ወይም "ያህዌ ይህንን መልዕክት ለኤርምያስ ሰጠው፡ 'ያህዌ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የባርነት ቤት

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ባሮች የነበራችሁበት ስፍራ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ሰው ወንድሙን፣ ራሱን ለእናንተ የሸጠውን ዕብራዊ ወገን እና የሚያገለግለውን ነጻ ማድረግ አለበት

"እያንዳንዳችሁ ወገናችሁ የሆኑትን ራሳቸውን ለእናንተ የሸጡትን እና ለእናንተ ባሪያ የነበሩትን ነጻ ማውጣት አለባችሁ"

ነጻነቱን ሰጥቶ ይልቀቀው

"እናንተ ከማገልገል ነጻ እንዲወጡ ልትለቋቸው ይገባል"

ጆሯቸውን ወደ እኔ...አላዘነበሉም

በተሻለ ሁኔታ ለማድመጥ ወደ ተናጋሪው ጭንቅላትን ማዘንበል፣ ጆሮን ማስጠጋት፣ ተናጋሪው ለሚናገረው ትኩረት ለመስጠት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "እኔ ለተናገርኩት ...ትኩረት አልሰጡም" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 34:15

አሁን እናንተ ራሳችሁ ንስሃ ገባችሁ

እዚህ ስፍራ "አሁን" የሚለው ቃል የዋለው ቀጥሎ ለሚሆነው ጠቃሚ ነገር ነው።

በትክክል በእኔ ዐይኖች

እዚህ ስፍራ "ዐይኖች" የሚለው ለአንድ ሰው አስተያየት ወይም ሀሳብ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሆኖ የቀረበ ነው። "እኔ ትክክል ነው የምለው" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በስሜ የተጠራው ቤት

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "የእኔ የሆነው ቤት" ወይም "እነርሱ እኔን የሚያመልኩበት ቤት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው (አድራጊ ወይም ተደርጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መልሳችሁ ስሜን አረከሳችሁ

የአንድ ሰው ስም ሰዎች ስለዚያ ሰው ለሚያስቡት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ትክክል የሆነውን ማድረግ አቁማችሁ፣ በምትኩ ሰዎች እኔ ክፉ እንደሆንኩ እንዲያስቡ የሚያደርጉ ነገሮችን አደረጋችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Jeremiah 34:17

ስለዚህም እነሆ!

"አድምጡ!" ወይም "ቀጥሎ ልነግራችሁ ላለው ጠቃሚ ነገር ትኩረት ስጡ!"

እኔ ለእናንተ ነጻነትን ላውጅ ነው...ለሰይፍ፣ ለመቅሰፍት፣ እና ረሃብ ነጻ መሆንን

ኤርምያስ "ነጻነት" የሚለውን የተጠቀመው በምጸት ነው፤ ሰዎች በመከራ ሃሴት እንደሚያደርጉ በምጸት ይናገራል። "ለእናንተ አበሳን አውጃለሁ... በሰይፍ፣ በመቅሰፍት፣ እና ችጋር የሚደርስ አበሳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ለእናንተ ነጻነት ማወጅ

"እናንተ ነጻ እንደሆናችሁ ማወጅ"

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ

ይህ ሰይፍ ለያዙ ወታደሮች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "የጠላት ወታደሮች እናንተን ለመግደል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በምድር ግዛት ሁሉ ፊት በእናንተ ላይ አሰቃቂ ነገር አደርጎለሁ

እዚህ ስፍራ "እይታ" የሚወክለው ፍርድን ወይም ሚዛንን ነው። "ግዛት" የሚለው ቃል በግዛቶቹ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "በእያንዳዱ ምድር ግዛት የሚኖር ህዝብ እናንተ በአሰቃቂ ሁኔታ እንደምትኖሩ እንዲያስቡ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ወይፈን ሲያርዱ ... ሲያልፉ... በወይፈኑ መሃል ሲያልፉ

ይህ ምንባብ የሚገልጸው ሰዎች ቃል ኪዳኑን እንዴት እንደሚፈጽሙ ነው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ፊት ይፈጽማሉ

"ከእኔ ጋር ይስማማሉ" ወይም "እኔ እየተመለከትኩ ይፈጽማሉ"

Jeremiah 34:20

ለጠላቶቻቸው እጅ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል ጠላቶች በእጆቻቸው ተጠቅመው በሀይል ለሚፈጽሙት ወይም ለሚያደርጉት ቁጥጥር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "ጠላቶቻቸው በእነርሱ ላይ ሙሉ ሀይል እንዲኖራቸው እፈቅዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ( ይመልከቱ።

ህይወታቸውን ይፈልጋሉ

ሊገድሏቸው ይፈልጋሉ የሚለውን ሻል ባለ አነጋገር መግለጫ ነው። (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻልባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ያህዌ ስለ ራሱ በስሙ የሚናገረው/የሚምለው የተናገረው ነገር እርግጠኛ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ በኤርምያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ያዘዘው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያዘዝኩት ይህንን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ለጠላቶቻቸው እጅ

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል የሚወክለው በቁጥጥር ስር ማድረግን ነው።

"በጠላቶቻቸው እንዲያዙ" ወይም "በጠላቶቻቸው ስር እንዲሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይነሳሉ

"ለመዋጋት ይመጣሉ"

አመጣቸዋለሁ

የባቢሎንን ሰራዊት አመጣለሁ

---

## Chapter 35

### Jeremiah 35:1

በይሁዳ ንጉሥ .... ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲህ የሚል ቃል ወደ ኤርምያስ መጣ፡ ወደ ሬካባውያን ሄደህ...

‹‹ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲህ የሚል ቃል ወደ ኤርምያስ መጣ›› የሚለው ዐረፍተነገር የተጠቀመው ከእግዚአብሄር ለየት ያለ መልዕክት እንዳለ ለማሳየት ነው። በኤርምያስ 1፡4 ላይ ተመሳሳይ መልዕክት የያዘ ዐረፍተነገር አለ። ‹‹ እግዚአብሄር በይሁዳ ንጉስ ዘመን ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠ..... እርሱም ‹ሂድ› ወይም ‹‹ በይሁዳ ንጉስ ዘመን እግዚአብሄር ለኤርሚያስ እንዲህ ሲል ተናገረ....‹ሂድ› ›› (ዐረፍተነገሩን ተመልከት)

ለኤርምያስ

ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል

ሬካባውያን

ይህ አንድን ህዝብ የሚያመለክት ነው (ስም አተረጓጎም የሚለውን ተመልከት)

የእኔ ቤት

መቅደሱን

### Jeremiah 35:3

ያአዛንያን.....ካባስ.....ሃናን........ጌዴልያም....መዕሤያ.......ሰሎም

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው

### Jeremiah 35:5

ሬካባውያን

ኤርምያስ 35፡2 የተተረጎመበትን ይመልከቱ

ኢዮናዳብ........ሬካብ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው

በምትኖሩባት ምድር ላይ ብዙ ዘመን እንድትኖሩ

‹‹በምትኖሩባት ምድር ላይ ብዙ ዘመን እንድትኖሩ›› ‹‹ዘመን›› የሚለው ጊዜን አመላካች ነው

### Jeremiah 35:8

የኢዮናዳብን ቃል

‹‹ቃል›› የሚለው የኢዮናዳብን ትእዛዝ ለማመልከት ነው።

ዕድሜያችንን ሁሉ

‹‹ዕድሜያችንን ሁሉ›› የሚለው ጊዜን አመላካች ነው

### Jeremiah 35:12

የእግዚአብሄር ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ ‹‹.....እግዚአብሄር...››

ይህ ዐረፍተነገር የተጠቀመው ከእግዚአብሄር ለየት ያለ መልዕክት እንዳለ ለማሳየት ነው። ኤርምያስ 1፡4 ላይ ተመሳሳይ ጥቅሶች የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር ለኤርምያስ መልዕክት ሰጠው። እርሱም ‹እግዚአብሄር...› አለ ወይም ‹እግዚአብሄር ይህንን መልዕክት ለኤርምያስ ተናገረ፡ ‹እግዚአብሄር....›››

ለኤርምያስ

ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል

ኤርምያስ እነዚህን ቃላቶች በአብዛኛው የሚጠቀመው ከእግዚአብሄር ቁልፍ መልዕክቶችን ማስተላለፍ ሲኖርበት ነው። ኤርምያስ 6፡6 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ

ቃሌን ትሰሙ ዘንድ ተግሳጽን አትቀበሉምን?

እግዚአብሄር እስራኤልን ተግሳጹን እንዲሰሙት እየተናገራቸው ነው። ‹‹ ተግሳጼን መቀበል እዲሁም ቃሌን መስማት አለባችሁ››

ይላል እግዚአብሄር

እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1፡8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››

የሬካብ ልጅ ኢዮናዳብ ልጆቹ የወይን ጠጅ እንዳይጠጡ ያዘዛቸው ቃል ተፈጸመ

ይህ ሲተረጎም ‹‹የሬካብ ልጅ የሆነው የኢዮናዳብ ልጆች አባታቸው የወይን ጠጅ እንዳይጠጡ ያዘዛቸውን ፈጽመዋል››

ኢዮናዳብ........ሬካብ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው

### Jeremiah 35:15

ታመልኳቸው ዘንድ ሌሎች አማልክትን አትከተሉ

ሌሎች አማልክትን መከተል ማለት የአማልክቱን ህግጋት መከተል/መተግበር ማለት ነው

### Jeremiah 35:17

ተመልከት

ቃሉ አንባቢው ትኩረት ሰጥቶ እንዲመለከተው አመላካች ነው

### Jeremiah 35:18

ኤርምያስም አለ

ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል

ሬካባውያን

ይህ አንድን ህዝብ የሚያመለክት ነው ኤርምያስ 35፡2 የተተረጎመበትን ይመልከቱ

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል

ኤርምያስ እነዚህን ቃላቶች በአብዛኛው የሚጠቀመው ከእግዚአብሄር ቁልፍ መልዕክቶችን ማስተላለፍ ሲኖርበት ነው። ኤርምያስ 6፡6 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ

ኢዮናዳብ........ሬካብ

እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው

---

## Chapter 36

### Jeremiah 36:1

አጠቃላይ መረጃ

ግጥምና ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ

እንዲህም ሆነ

ይህን ቃል የተጠቀመው አዲስ የታሪክ ጅማሬ ለማሳየት ነው።

በይሁዳ ንጉስ....በኢዮአቄም በአራተኛው ዓመት...

ኢዮአቂም ከሶስት ዓመት በላይ የይሁዳ ንጉስ ሆኖ ቀይቶ ነበር። ኤርምያስ 25፡1 የተተረጎመበትን ይመልከቱ

ይህ ቃል

‹‹ይህ ቃል›› የሚለው ቀጣዩን መልዕክት የሚያመለክት ነው

ለኤርምያስ

ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል

እርሱም አለ

‹‹ እግዚአብሄርም አለ››

‹‹በአሕዛብም ሁሉ ላይ››

‹‹አሕዛብ ሁሉ››

ከተናገርኩበት ቀን

‹‹ለአንተ ከተናገርኩበት ቀን››

ከኢዮስያስ ዘመን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

‹‹ ኢዮስያስ ንጉስ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ቀን ደረስ ››
ምናልባት የይሁዳ ቤት
ምናልባት የይሁዳ ህዝቦችን
አደርግባችኋለሁ
x
Jeremiah 36:4
ኤርምያስም..... ለኤርምያስ አፍ......... አዘዘው.....
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል
ባሮክም እግዚአብሄር ለእርሱ የተናገረውን ቃል ሁሉ ከኤርምያስ አፍ በመጽሐፍ ክርታስ ጻፈ
እግዚአብሄር ለኤርምያስ የተናገረውን ኤርምያስ ሲናገር ባሮክ በመጽሐፍ ክርታስ ጻፈ
በክርታሱ አንብብ
‹‹ከክርታሱ ላይ ጮክ ብለህ አንብብ›› ወይም ‹‹ከክርታሱ ላይ አውጅ›› ለማለት ነው
አንብበው
‹‹ጮክ ብለህ አንብብ›› ወይም ‹‹ አውጅ››
በእግዚአብሄር ቤት በሕዝቡ ጆሮ
‹‹በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ ያሉ ሕዝቦች ይሰሙ ዘንድ›› ኤርምያስ 2:2 የተተረጎመበትን መንገድ ተመልከት
በከተሞቻቸው በሚወጡ በይሁዳ ሰዎች ሁሉ ጆሮ
‹‹ከከተሞቻቸው የመጡ የይሁዳ ሰዎች ሁሉ ይሰሙ ዘንድ›› ኤርምያስ 2:2 የተተረጎመበትን መንገድ ተመልከት
Jeremiah 36:7
አጠቃላይ መረጃ
ኤርምያስ ለባሮክ ትዕዛዙን ይቀጥላል
ምናልባት ጸሎታቸው በእግዚአብሄር ፊት ትወድቅ ይሆናል
እግዚአብሄር ጸሎታቸውን ሰምቶ ይፈጽምላቸዋል
ጸሎታቸው
‹‹ጸሎታቸው›› ሲል የእግዚአብሄር ቤት ሕዝቦችን እንዲሁም ከከተሞቻቸው የመጡትን የይሁዳን ሕዝቦችን ለማመልከት ነው
ሁሉም ከክፉ መንገዱ
‹‹መንገዱ›› ሲል የአንድን ሰው የህይወት መርህን ወይም አንድ ሰው የሚመራበትን መንገድ ለመግለጽ ነው። ኤርምያስ 18:11 የተተረጎመበትን መንገድ ተመልከት
ቁጣው እና መአቱ
ከፍተኛ ቁጣ
Jeremiah 36:9
እንዲህም ሆነ
ኤርምያስ 36:1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
በኢዮአቄም በአምስተኛው ዓመት በዘጠነኛው ወር...በይሁዳ ንጉስ
ይህ ዘጠነኛው ወር በእብረውያን የቀን መቁጠሪያ ሲሆን ይህም በምእራባውያን የቀን አቆጣጠር ላይ የኖቬምበር መጨረሻዎቹ ላይ እና ዲሴምበር መጀመሪያዎቹ ላይ ይገኛል። “ኢዮአቄም በይሁዳ ንጉስ ከሆነ ከአራት አመት በላይ ሲሆን በዘጠነኛው ወር አካባቢ ነው”
በይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ልጅ በኢዮአቄም
ኤርምያስ 25:1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
አዋጅ ነገሩ።
ለሁሉም ሰው በፍጥነት እየሄዱ እነደሆነ ተናገሩ
የኤርምያስ ቃል
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም።
በሳፋን ልጅ በገማርያ
ይህ የሰው ስም ነው
ፀሃፊው
ፀሃፊ የነበረው
በእግዚአብሔር ቤት በአዲሱ በር መግቢያ
አዲሱ የእግዚአብሄር ቤት መግቢያ በር
አነበበ
ድምፁን ከፍ አድርጎ የኤርምያስን ቃል አነበበ
በህዝቡ ሁሉ ጆሮ
ሁሉም ህዝብ እንዲሰሙት። ተመሳሳይ ቃላትን በኤርምያስ 2:2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
Jeremiah 36:11
ጊዜ
ይህን ቃል የተጠቀመው ቀጥሎ የተነሳውን ሃሳብ ትኩረት እንዲሰጠው ለማድረግ ነው
የሳፋንም ልጅ የገማርያ ልጅ ሚክያስ
ሚክያስ የገማርያ ልጅ ነው ገማርያ የሳፋን ልጅ ነው።
ሚክያስ
ይህ የሰው ስም ነው
እነሆም
ተመልከት ወይም ልብ በል
ኤሊሳማ...ድላያ
ይህ የሰዎች ስም ነው
ሸማያ
በኤርምያስ 26:20 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት
የአክቦር ልጅ ኤልናታን
በኤርምያስ 26:22 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
የሳፋን ልጅ ገማርያ
በኤርምያስ 36:10 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ሴዴቅያስ
በኤርምያስ 1:3 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ሐናንያ
በኤርምያስ 28:1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
አለቆቹም ሁሉ
ሁሉም አለቆች
Jeremiah 36:13
ሚክያስ
የዚህን ሰው ስም በኤርምያስ 36:11 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
የሰማውን ቃል ነገራቸው
ይህ ለአለቆቹ እንደተናገረ በኤርምያስ 36:12 ያመለክታል
በህዝቡ ጆሮ
ህዝቡ እንዲሰሙ። ተመሳሳይ ቃላት በኤርምያስ 2:2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ይሁዲ...ናታንያ...ሰሌምያ...ኩሲ
እንዚህ የሰው ስሞች ናቸው
በህዝቡ ጆሮ
ህዝቡ እንዲሰሙ። ተመሳሳይ ቃላት በኤርምያስ 2:2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ክርታሱን...አነበበው
ድምፁን ከፍ አድርጎ ክርታሱን አነበበው
Jeremiah 36:16
...ጊዜ
ይህን ቃል ሲጠቀም በታሪኩ ውስጥ ትኩረት የሚሰጠውን ታሪክ ለማሳየት ነው
በሰሙ ጊዜ
ይህ ቃል የሚያመለክተው አለቆቹን ነው
ይህንን ቃል ሁሉ
የባሮክ ቃል ከክርታሱ ተነበበ
እንዴት እንደፃፍከው ንገረን
እንዴት ፃፍከው
ይህን ቃል ከአፉ ይነግረኝ ነበር፥ እኔም በመጽሐፉ ላይ በቀለም እጽፍ ነበር
በኤርምያስ 36:4 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ከአፉ ይነግረኝ
ኤርምያስ ሲነግረው ባሮክ የሚናገረው ይፅፍ ነበር
በቀለም እፅፍ ነበር
ቀለምን ተጠቅሜ እፅፍ ነበር
ቀለም
ጠቆር ያለ ፈሳሽ ለመፃፊያ የሚያገለግል
አንተና ኤርምያስ
አንተ ብቻ ሳይሆን ኤርምያስም ጭምር መሸሸግ አለበት።
ወዴት እንደሆናችሁ

ይህ ባሮክንና ኤርምያስን ያመለክታል።
Jeremiah 36:20
..ገቡ
ይህ ቃል የሚያመለክተው አለቆቹን ነው
ክርታሱንም በጸሐፊው በኤሊሳማ ጓዳ አኑረውት
በፀሃፊው በኤሊሳም ክፍል ክርታሱን አስገቡት
ፀሀፊው ኤሊሳም
ፀሀፊው ኤሊሳም የሚለውን በኤርምያስ 36፡12 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ይሁዲ
የዚህን ሰው ስም በኤርምያስ 36፡14 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
በንጉሡና በንጉሡ አጠገብ በቆሙት አለቆች ሁሉ ጆሮ አነበበው
ንጉሱ ሊሰማው በሚችልበት ቦታ ላይ። ተመሳሳይ ቃላት በኤርምያስ2፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
በዘጠነኛው ወር
በእብራውያን የቀን አቆጣጠር ዘጠነኛው ወር ሲሆን የሚዘሩበት ጊዜ አልቆ ቀዝቃዛው ጊዜ መጀመሪያ አካባቢ ነው። እንደ ምእራባውያን የቀን አቆጣጠር የኖቬምበር መጨረሻዎቹ እና የዲሴምበር መጀመሪያዎቹ ላይ ነው።
በፊቱም በምድጃ ውስጥ እሳት ይነድድ ነበር።
የሚነደው እሳት በምድጃ ውስጥ ሆኑ ከፊት ለፊቱ ነበር
ምድጃ
የእሳት ማንደጃ ሲሆን ሰዎች ከቦታ ቦታ ያንቀሳቅሱታል
Jeremiah 36:23
ባነበበ ቁጥር..
ይህን ቃል ሲጠቀም በታሪኩ ላይ ትኩረት ለመስጠት ነው (ታሪካዊ ዳራውን ተመልከት)
ይሁዲም
በኤርምያስ 36፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
አምድ
እነዚህ በክርታሱ የሚገኙ የቃላት አምድ ነው
ቀደደው
ክርታሱን ቀደደው
በካራ
ፀሀፊዎች የሚጠቀሙትን ካራ ተጠቅሞ ቀደደው
በምድጃ
በኤርምያስ 36፡22 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ክርታሱም በምድጃ ውስጥ ባለው እሳት ፈፅሞ እኪቃጠል ድረስ
ክርታሱ ሙሉ በሙሉ እስኪጠፋ ድረስ
ይህን ቃል ሁሉ
ኤርምያስ ሲናገር ባሮክ ክርታስ ላይ የፃፈው ቃል ነው።
ልብሳቸውንም አልቀደዱም
ሰዎች ልብሶቻቸውን የሚቀዱት እጅግ በጣም ሲያዝኑ ነው። “ልብሳቸውን በመቅደድ አላዘኑም”
Jeremiah 36:25
ኤልናታንና ድላያ ገማርያም
እነዚህን ስሞች በኤርምያስ 36፡12 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ንጉሱን ለመኑት
ንጉሱን ለመኑት
ይረሕምኤልንና የዓዝርኤልን ...ሠራያን የዓብድኤልንም...ሰሌምያን
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው
ልጅ ነብዩን ኤርምያስ...ሰወራቸው
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል
Jeremiah 36:27
ባሮክ ከኤርምያስ አፍ የጻፈውን ቃል ካቃጠለ በኋላ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ
“የእግዚአብሄር ቃል ወደ” የሚለው ቃል ልዩ የሆነ መልእክት ለመናገር ሲፈልግ የሚጠቀመው ነው። ተመሳሳይ አረፍተነገር በኤርምያስ 1፡4 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እግዚአብሄር ለኤርምያስ እንዲህ ሲል ተናገረ”
ከኤርምያስ አፍ የጻፈውን...ወደ ኤርምያስ መጣ
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል
ከኤርምያስ አፍ የጻፈውን
በኤርምያስ 36፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ዳግመኛ ሌላ ክርተስ ውሰድ
ለራስህ ሌላ ክርታስ ውሰድ
ክርታስ ላይ የነበረውን የቀድሞውን ቃል
የመጀመሪያው ክርታስ
ከሰውና ከእንስሳም ባዶ ያደርጋታል ብለህ ለምን ጻፍህበት?
ኢዮአቄም ይህንን ጥያቄ ኤርምያስ የባቢሎን ንጉስ መጥቶ እንደሚያጠቃቸው መፃፍ እንዳልነበረበት ለማሳየት ነው። “መፃፍ አልነበረብህም”
ያፈርሳታል
እርሱ ያጠፋታል
Jeremiah 36:30
ዳዊት ዙፋን ላይ ተቀማጭ አይኖርለትም
ተቀማጭ የሚለው ንጉስ ሆኖ የሚመራ ማለት ነው። “ዳዊት ዙፋን ላይ ተቀማጭ አይኖርለትም” የሚለውን በኤርምያስ 29፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “ዳዊት እስራኤላውያንን እንደመራቸው አይኖርም”
ሬሳውም...ይጣላል
“ሰዎች ሬሳን ወደውጭ ይጥሉታል”
ሬሳውም
የሞተው ሰውን
በቀን ለትኩሳት
ቀን ባለው ደረቅ ሙቀት ይጋለጣል
ውርጭ
በቀዝቃዛ ሌሊቶች ላይ በሳር ላይ በረዶ የሚሰራ
ሁሉ በእነርሱ ላይ
ሁሉ በእነርሱ ላይ
Jeremiah 36:32
ወስጄ...እርሱም በቃል የነገርኩትን ሁሉ ፃፈበት
ኤርምያስ ለምን ራሱን በስሙ እንደገለጸ ግልፅ አይደለም። በመጀመሪያ መደብ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል
ለባሮክ ሰጠሁት እርሱም በቃል የነገርሁትን ሁሉ ፃፈበት
በኤርምያስ 25፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎመወ ተመልከት። “ኤርምያስ ሲናገር ባሮክ ፃፈው”
የይሁዳ ንጉስ ኢዮአቄም ባቃጠለው
የይሁዳ ንጉስ ኢያአቄም በእሳት ውስጥ ያቃጠለው
ተፅፎ የነበረውንና እኔም እንደገና በተጨማሪ የነገርሁትን ተመሳሳይ ቃል ሁሉ ፃፈበት
“ኤርምያስ እና ባሮክ ክርታሱላይ ብዙ ቃላቶችን ከመጀመሪያው ክርታስ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ጨምረናል”

---

Chapter 37
Jeremiah 37:1
ኢኮንያን
በዕብራይስጡ ጽሁፍ ‹‹ኮንያ›› የሚለው ቃል ይገኛል። ይህም የኢኮንያን ሌላ ስም ሲሆን ብዙ አዲስ ትርጉሞች ተመሳሳይ ንጉስን ለማመልከት ‹‹ኢኮንያን›› የሚለውን ስም ይጠቀማሉ
የአገሩም
የይሁዳ ምድር
በነብዩ በኤርምያስ እጅ የተናገረውን
እጅ የሚለው ሰውን ያመለክታል። “ኤርምያስ እንዲናገር አደረገው”
የተናገረውን
እግዚአብሄር የተናገረውን
ነብዩ ኤርምያስ
ኤርምያስ ራሱን በስሙ የሚጠራው ምክንያቱ ግልፅአደለም
Jeremiah 37:3


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ዬካልን
የሰው ስም ነው
ሰሌምያ
ይህን የሰው ስም በኤርምያስ 36፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ካህኑን የመዕሤያን ልጅ ሶፎንያስን
የነዚህ ሰዎች ስም በኤርምያስ 21፡1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ስለ እኛ
“ለኛ” ወይም “ለኛ ጥቅም” “እኛ” የሚለው ቃል ንጉስ ሴዴቅያስ እና የተቀሩት የይሁዳ ህዝብን ነው
ኤርምያስ በሕዝቡ መካከል ይወጣና ይገባ ነበር።
“ይወጣና ይገቡ” የሚለው በነፃነት መንቀሳቀሱን ያሳያል። “ኤርምያስ መሄድ የፈለገበት ቦታ እንደ ልቡ ይንቀሳቀሳል”
በግዞት ቤት ገና አላገቡትም ነበርና
“ምክንያቱም ማንም እስርቤት አላስገባውም እና”
ይወጣና ይገባ ነበር
በሕዝቡ መካከል ይመላለስ ነበር
ከብበዋት
ኤርምያስ 32፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ ኤርምያስ መጣ።
“የእግዚአብሄር ቃል ወደ” የሚለው ቃል ልዩ የሆነ መልእክት ለመናገር ሲፈልግ የሚጠቀመው ነው። ተመሳሳይ አረፍተነገር በኤርምያስ 1፡4 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እግዚአብሄር ለኤርምያስ እንዲህ ሲል ተናገረ”
እንዲህ በሉት
ይህ ንጉስ ሴዴቅያስ ወደ ኤርምያስ የላካቸውን ሁለት ሰዎችን ያመለክታል። የሰሌምያን ልጅ ዮካልንና ካህኑን የመዕሴያን ልጅ ሶፎንያስን
ከእኔ ትጠይቁ ዘንድ
“እኔ” የሚለው ቃል እግዚአብሄርን ያመለክታል
እነሆ
ተመልከት ወይም ልብ በል
ይህችን ከተማ ይዋጉአታል ይይዙአትማል በእሳትም ያቃጥሉአታል
ጦርነት መዋጋት መያዝ እና ማቃጠልን ከኤርምያስ 34፡22 ጋር አነፃፅር
Jeremiah 37:9
ራሳችሁን አታታሉ
“ራሳችሁን” የሚለው ቃል ንጉስ ሴዴቅያስ እና የተቀሩትን የይሁዳ ህዝብን ያመለክታል።
ከለዳውያን በእርግጥ ከእኛ ዘንድ ይሄዳሉ
የይሁዳ ህዝብ ከለዳውያን ስለሄዱ ሰላም እናገኛለን ብለው ያስባሉ። “ሰላም እንሆናለን ምክንያቱም ከለዳውያን ከእኛ ዘንድ ሄደዋልእና”
ተነስቶ
የተወጉት ይነሱ ነበር
Jeremiah 37:11
በተመለሰ ጊዜ
ይህን ቃል ሲጠቀም የአዲስ ታሪክ መጀመሪያ እንደሆነ ለማመልከት ነው
የርስት እድል ፈንታ
ትንሽ መሬት ወይም ጥቂት መሬት
በህዝቡ መካከል
በዘመዶቹ መካከል። ኤርምያስ በቢኒያም የምትገኝ አናቶ ከምትባል ከተማ ነው። ኤርምያስ 1፡1 ተመልከት
ብንያምም በር
የመግቢያ በር ስም ነው
የሪያ
ይህ ሰው ስም ነው
ሰሌምያ
የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደተተረጎመ በኤርምያስ 36፡14 ተመልከት
ሐናንያ
የዚህን ሰው ስም በኤርምያስ 28፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
መኮብለልህ
ችግርን መሸሽ እና እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎችን ትቶ መሄድ
Jeremiah 37:14
መኮብለሌ
ችግርን መሸሽ እና እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎችን ትቶ መሄድ
የሪያ
ይህ ሰው ስም ነው
አለቆች
ኤርምያስ 1፡18 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
የፀሀፊውን የዮናታንን
ፀሀፊ የነበረውን ዮናታንን። ይህ የሰው ስም ነው
Jeremiah 37:16
ኤርምያስም ወደ ጉድጓድ ቤት ወደ ጓዳዎቹ ገባ
“አለቆችም ኤርምያስን ወደ ጉድጓድ ቤት ወደ ጓዳዎቹ አስገቡት”
አስመጣው
ኤርምያስን አስመጣው
በቤቱ
የንጉሱ ሴዴቅያስ ቤተመንግስት
በባቢሎን ንጉሥ እጅ አልፈህ ትሰጣለህ አለ
“እጅ” የሚለው ጉልበትን ወይም በእጅ ያለን ቁጥጥርን ያመለክታል። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ቃላት በኤርምያስ 32፡4 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “በባቢሎን ንጉስ ቁጥጥር ስር አሳልፌ እሰጥሃለሁ” ወይም “የባቢሎን ንጉስ የወደደውን እንዲያደርግ እፈቅዳለሁ”
Jeremiah 37:18
በግዞት ቤት … ምን በድያችሁ ነው?
ኤርምያስ ይህን ጥያቄ ምንም ጥፋት እንዳላጠፋ ለመናገር ይጠቀማል። “ምንም በደል አላደረኩባችሁም…በግዞት ቤት”
ህዝብህን
የይሁዳ ህዝብ
የጣላችሁኝ
ያስቀመጣችሁኝ
ትንቢት ይናገሩላችሁ የነበሩ ነቢያቶቻችሁ ወዴት አሉ?
ኤርምያስ ይህን ጥያቄ ትንቢት የተናገሩት ውሸታቸውን እንደሆነ እና እርሱ እውነቱን ስለተናገረ ሌላ ምንም ስህተት እንዳላደረገ ለማሳየት የጠየቀው ነው። “የናንተ ነቢያት ትንቢት የሚናገሩላችሁ…በዚህ ከተማ ላይ ስህተት ነው ነገር ግን እኔ እውነቱን ነው የተናገርኩት”
ነቢያቶቻችሁ
ይህ ቃል የሚያመለክተው ንጉስ ሴዴቅያስ እና የይሁዳ ህዝብን ነው
እናንተና በዚህች አገር አይመጣባችሁም
እናንተን እና አገራችሁን አያጠቃችሁም
ልመናዬ ወደ አንተ ይድረስ
ለምህረትህ ልመናዬን ስማኝ ወደ አንተም ይድረስ። ለምህረትህ ልመናቸው ወደ እግዚአብሄር ይድረስ የሚለውን በኤርምያስ 36፡7 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት።
የፀሀፊው ወደ ዮናታን ቤት
ፀሀፊ ወደ ሆነው ዮናታን ቤት። ኤርምያስ 37፡15 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት።
ከግዞት ቤት አደባባይ
ይህ ከንጉሱ ቤተመንግስት ጋር አብሮ ያለ ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ይህም ደግሞ ለእስረኞች የተዘጋጀ ቦታ ነው። ኤርምያስ 32፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
እንጀራም…ይሰጡት ነበር
“ሰራተኞቹ ለኤርምያስ እንጀራ ይሰጡት ነበር”
ከጋጋሪዎች መንገድ ይሰጡት ነበር
ጋጋሪዎች ከሚሰሩበት መንገድ

---

Chapter 38
Jeremiah 38:1
ሰፋጥያስ…ማታን…ጎዶልያስ…ጳስኮርም…ዮካል…ሰሌምያም…ጳስኮር…መልክያም
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው
በዚህች ከተማ የሚቀመጥ በሰይፍና በራብ በቸነፈርም ይሞታል

“በዚህች ከተማ የሚቀመጥ በሰይፍ በረሃብ እና በቸነፈር ይሞታል” ወይም “በዚህች ከተማ የሚቀመጥ በሰይፍ በረሃብ እና በቸነፈር እገድላለሁ”
ነፍሱም እንደ ምርኮ ትሆንለታለች
ለባቢሎናውያን እጅ የሚሰጥ በህይወት ይሆናል ምንም ያለውን ነገር በሙሉ ቢያጣም፡፡ በኤርምያስ 21፡9 ላይ እንዴት እንደ ተረጎመው ተመልከት
ይህች ከተማ በባቢሎን ንጉሥ ሠራዊት እጅ በእርግጥ ትሰጣለች
“እጅ” የሚለው ጉልበትን ወይም በእጅ ያለን ቁጥጥርን ያመለክታል፡፡ “የባቢሎን ሰራዊት ኢየሩሳሌምን እንዲያሸንፉ እፈቅዳለሁ”
እርሱም ይይዛታል
እንባቢው ሊረዳው የሚገባው ነገር ሌሎችም የባቢሎን ንጉስ ከተማዋን ሲይዝ እንዳገዙት ነው፡፡ “ሰራዊቱ ይይዙአቸዋል”
Jeremiah 38:4
ይህ ሰው እንዲገደል
ይህን ሰው ለማስገደል ማዘዝ
በዚህች ከተማ የቀሩትን የሰልፈኞቹን እጅ የሕዝቡንም ሁሉ እጅ ያደክማልና
እጅ ያደክማል የሚለው የሚፈራን ሰው ያመለክታል፡፡ “በዚህች ከተማ የቀሩትን ሰልፈኞዎችን ድፍረታቸውን እያጡ ነው”
ይህ ሰው ክፋትን እንጂ ለዚህ ሕዝብ ሰላምን አይመኝለትምና አሉት
“ኤርምያስ ህዝቡ ሰላም እንዲሆኑ አይመኝም ነገር ግን በህዝቡ ላይ ክፉ ነገር እንዲሆን ነው የሚመኘው”
በእጃችሁ ነው
እጅ የሚለው እጅ ያለውን ሃይል የሚያሳይ ነው፡፡ “በእሱ ላይ ማድረግ የፈለጋችሁትን አድርጉ”
Jeremiah 38:6
በግዞት ቤቱም አደባባይ ወደ ነበረው ወደ ንጉሡ ልጅ ወደ መልክያ ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት
ኤርምያስን በገመድ ወደታች ላኩት፡፡ ነገር ግን ጣሉት የሚለው ጥሩ እንክብካቤ በጎደለበት በመጥፎ ቦታ እንዳስገቡት አግንኖ እየተናገረ ነው፡፡ “ኤርምያስን ወደ ጉድጓድ ገፈተሩት”
ጉድጓድ
ጥልቅ የተቆፈረ ሰዎች የዝናብ ውሃ የሚያጠራቅሙበት እና የሚቀዱበት ቦታ
ከግዞት ቤት አደባባይ
ይህ ከንጉሱ ቤተመንግስት ጋር አብሮ ያለ ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ይህም ደግሞ ለእስረኞች የተዘጋጀ ቦታ ነው፡፡ ኤርምያስ 32፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ኤርምያስን በገመድ አወረዱት
ወደ ጉድጓዱ እንዴት እንደጣሉት ይናገራል
Jeremiah 38:7
አቤሜሌክ
በንጉሱም ቤት የነበረው…አቤሜሌክ የሚለውን ቃል ሲጠቀም የአዲስ ታሪክ ጅማሬን ሊያመለክት ፈልጎ ነው
ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ
የኢትዮጲያዊ ሰው ስም ነው፡፡
ንጉሱም…
ይህን ቃል ሲጠቀም በታሪኩ ውስጥ ትኩረት የሚሰጠውን ታሪክ ለማሳየት ነው (ታሪካዊ ዳራውን ተመልከት)
በቢንያም በር ተቀምጦ
ንጉስ ሴዴቅያስ ፍርድ እየሰጠ እና ክስ እየሰማ ይሆናል፡፡
ብንያም በር
ይህ የኢየሩሳሌም መግቢያ ሲሆን በያዕቆብ ልጅ በብንያም ስም ተሰይሟል
Jeremiah 38:10
ሰላሳ ሰዎች
ሰላሳ ሰዎች
በገመድ አወረደው
ገመድን በመጠቀም ወደታች አወረደው
Jeremiah 38:12
በብብትህ ከገመዱ በታች አድርግ
በእጅህ እና በገመዱ መሃከል አድርግ
ኤርምያስን በገመዱ ጎተቱት
ኤርምያስን የጎተቱት ከአቤሜሌክ ጋር አብረው የነበሩት ሰላሳ ሰዎች ናቸው
ከግዞት ቤት አደባባይ
ይህ ከንጉሱ ቤተመንግስት ጋር አብሮ ያለ ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ይህም ደግሞ ለእስረኞች የተዘጋጀ ቦታ ነው፡፡ ኤርምያስ 32፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
Jeremiah 38:14
ብነግርህ በውኑ አትገድለኝምን?
ኤርምያስ ይህን ጥያቄ የጠየቀው እውነቱን መልስ ቢነግረው ንጉሱ እንደሚገድለው ስላሰበ ነው፡፡ “እውነቱን ብነግርህ አንተ እኔን ትገድለኛለህ”
ሕያው እግዚአብሔርን!
“እግዚአብሄር አምላክ ህያው እንደሆነ”፡፡ ህዝቡ ይህን የሚናገሩት ቀጥለው የሚናገሩት እውነት እንደሆነ ለመግለፅ ነው፡፡ “ህያው እግዚአብሄር” ኤርምያስ 4፡2 ፡፡
ለእነዚህ ሰዎች እጅ አሳልፌ አልሰጥህም
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ስላላቸው ሰዎች ይናገራል፡፡ “ሰዎች እንዲይዙአችሁ አለፈቅድም”
ነፍስህን ለሚሹ
ይህ ሀረግ አንድስ ሰው ለመግደል መፈለግን ያመለክታል፡፡ በኤርምያስ 11፡21 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት፡፡
Jeremiah 38:17
የእስራኤል አምላክ
“የእስራኤል ህዝብ አምላክ”
ይህችም ከተማ በእሳት አትቃጠልም
“የባቢሎናውያን ሰራዊት ከተማዋን አያቃጥሉአትም”
ይህች ከተማ በከለዳውይያን እጅ ትሰጣለች
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ወይም እጅ የሚለማመደው ስልጣንን ነው፡፡ ኤርምያስ 38፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት፡፡ “ከለዳውያን ይህንን ከተማ እንዲያሸንፉ እፈቅዳለሁ” ወይም “በዚህ ከተማ ላይ የፈለጉትን እንዲያደርጉ ለከለዳውያን እፈቅዳለሁ”
ከእጃቸው አታመልጥም
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ወይም እጅ የሚለማመደው ስልጣንን ነው፡፡ “ከእነርሱ ጉልበት ልታመልጥ አትችልም”
Jeremiah 38:19
በኮበለሉት
ችግርን ማምለጥ እና እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎችን ትቶ መሄድ፡፡ ኤርምያስ 37፡13 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
እጅ አሳልፈው ይሰጡኛል
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ወይም እጅ የሚለማመደው ስልጣንን ነው፡፡ “ከለዳውያን በኮበለሉት በይሁዳ ቁጥጥር ስር አሳልፎ ይሰጡኛል” ወይም “ከለዳውያን ለኮበለሉት ለይሁዳ ህዝብ የፈለጉትን እንዲያደርጉ አሳልፎ ይሰጡኛል”
እነርሱም ያፌዝቡኛል
“እነርሱም” የሚለው ቃል የኮበለሉትን የይሁዳ ህዝብን ነው፡፡
Jeremiah 38:20
አሳልፈው አይሰጡህም
“ከለዳውያን ለይሁዳ አሳልፈው አይሰጡህም” “አይሰጡህም” ሲል ሴዴቅያስን ነው፡፡
እግዚአበሄር ያሳየኝ ቃል ነው
ይህ አረፍተነገር የሚያሳየው ኤርምያስ ቀጥሎ ሊናገር ያለውን ነገር ነው፡፡
Jeremiah 38:22
አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርምያስ ከንጉስ ሴዴቅያስ መነጋገሩን ቀጠለ
የቀሩትን ሴቶች ሁሉ…ወደ ባቢሎን ንጉሥ አለቆች ያወጣሉ
እንባቢው ሊረዳው የሚገባው ነገር አለቆች እነዚህን ሴቶች እንደ ባሪያ አድርገው ነው የወሰዱአቸው፡፡ “የቀሩትን ሴቶች ሰራዊቱ ያመጣቸዋል…ከባቢሎን ንጉስ አለቆች”
ባለምዋሎችህ አታልለውሃል
“ጓደኞችህ አታልለውሃል”
እግሮችህ ግን አሁን በጭቃ ውስጥ ከገቡ
ንጉሱ ከአሁን በኋላ የሚያደርገው ምንም ነገር የለም
ሚስቶችችህንና ልጆችህንም ሁሉ ወደ ከለዳውያን ያወጣሉ
እንባቢው ሊረዳው የሚገባው ነገር አለቆች እነዚህን ሰዎች እንደ ባሪያ አድርገው ነው የወሰዱአቸው፡፡ “ሰራዊቱ ሚስቶችችህንና ልጆችህን ወደ ከለዳውያን ያመጡአቸዋል”
ከእጃቸው አታመልጥም

“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ወይም እጅ የሚለማመደው ስልጣንን ነው። “ከሃይላቸው ልታመልጥ አትችልም”
በባቢሎን ንጉሥ እጅ ትያዛለህ እንጂ ከእጃቸው አታመልጥም ይህችም ከተማ በእሳት ትቃጠላለች።
“እጅ” የሚለው ቃል ሃይል ወይም እጅ የሚለማመደው ስልጣንን ነው። አንባቢው ሊረዳው የሚገባው ንጉሱ ይህን ለማድረግ ሌሎች እንደረዱት ነው። “አንተን የባቢሎን ንጉሱ ሰራዊቶች ይይዙሃል ደግሞም ከተማዋን በእሳት ያነዱታል።”
Jeremiah 38:24
ዮናታን
የዚህን ሰው ስም በኤርምያስ 37፡15 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት
Jeremiah 38:27
ከእርሱ ጋር መነጋገርን ተው
“ንጉሱና ኤርምያስ እርስ በእርስ የተነጋገሩትን ነገር”
ከግዞት ቤት አደባባይ
ይህ ከንጉሱ ቤተመንግስት ጋር አብሮ ያለ ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ይህም ደግሞ ለእስረኞች የተዘጋጀ ቦታ ነው። ኤርምያስ 32፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ኢያሩሳሌም እስከተያዘችበት ቀን ድረስ
“የባቢሎን ሰራዊት ኢያሩሳሌምን እስከሚይዝበት ቀን ድረስ”

---

Chapter 39
Jeremiah 39:1
ወደ ኢያሩሳሌም መጥተው
ኢያሩሳሌምን ሊወጉ መጡ
በይሁዳ ንጉስ በሴዴቅያስ በዘጠነኛው አመት በአስረኛው ወር
ይህ ሴዴቅያስ ከነገሰ በእብራውያን ቀን መቁጠሪያ ከስምንት አመት እና ከአስረኛው ወር በኋላ ነው።
ዘጠነኛው…አስረኛው…አስረአንደኛው…አራተኛው
ቁጥሮች ናቸው
በሴዴቅያስም በአሥራ አንደኛው ዓመት በአራተኛው ወር ከወሩም በዘጠነኛው ቀን
ይህ በዕብራውያን የቀን መቁጠሪያ የይሁዳ ንጉስ ሴዴቅያስ ከነገሰ ከአስር አመት እና አራተኛው ወር በኋላ ነው። አስረአንደኛው ቀን ማለት እንደ አውሮፕያን ቀን አቆጣጠር የጁላይ ወር መጀመሪያ አካባቢ ነው። “ሴዴቅያስ ከነገሰ ከአስራአንደኛው አመት አራተኛው ወር እና ዘጠኛው ቀን”
ሳርሳር ሳምጋርናቦ እና ሠርሰኪም
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው
በመካከለኛው በር
የከተማዋ የመካከለኛው በር። በመሪዎች የከተማው መግቢያ በር ጋር በመቀመጥ አስፈላጊ ነገሮች ላይ መወያት የተለመደ ነው
Jeremiah 39:4
በሌሊትም በንጉሡ አትክልት መንገድ በሁለቱ ቅጥር መካከል ከነበረው ደጅ ከከተማይቱ ወጡ
በዓረባም መንገድ ወጡ
በንጉሱ የአትክልት መንገድ በለሊት ወጡ
በኢያሪኮ ሜዳ
ቀጥ ያለ ሰፊ ሜዳ ሲሆን ከሸለቆ መጨረሻ በስተደቡብ ላይ ይገኛል
በሃማት ምድር ወዳለችው ሪብላ
ሪብላ የሃማት ክልል ውስጥ የምትገኝ ከተማ ስትሆን ሶሪያ የሚባለው ነው።
ተከታተላቸው…አገኙት ይዘውም
ተከትሎ ያዛቸው
ፍርድን በእርሱ ላይ ተናገረ
እንዴት እንደሚቀጣው ወሰነ
Jeremiah 39:6
የሴዴቅያስን ልጆች በዓይኑ ፊት በሪብላ ገደላቸው
በአይኑ የሚወክለው ሙሉ ሰውን ሲሆን አንባቢበው ሊረዳ ሚገባው ሌሎችም የሃቢሎን ንጉስ የሴዴቅያስን ልጅ ሲገድል እንደረዱት ነው። “ሴዴቅያን በማስገደድ የንጉሱ ሰራዊት ልጁን ሲገድሉ ተመለከተ”
የሴዴቅያስንም አይን አወጣ
የንጉሱ ሰዎች የሴዴቅያስን አይነ ስውር ሆነ። የባቢሎን ንጉስ የሴዴቅያስን አይን ከጭንቅላቱ ማውጣቱን ግልፅ አደለም። አንባቢው ሊረዳው የሚገባው ነገር ሌሎች የባቢሎንን ንጉስ የሴዴቅያስን አይን ሲያጠፋ እንደአገዙት ነው።
Jeremiah 39:8
የንጉሱን…ቤቶች
የሴዴቅያስን ቤት
የህዝቡን ቤቶች
የኢያሩሳሌም ህዝብ ቤቶች
ናቡዘረዳን
ይህ የሰው ስም ነው
የዘበኛ አለቃ
የናቡዘረዳን ዘበኛ
በከተማይቱ የቀሩትን ህዝብ
“በከተማዋ እየኖሩ ያሉ ህዝቦችን”
ድሆች
“ምንም ነገር የሌላቸው”
Jeremiah 39:11
ናቡሻዝባንም…ንዶልያስ…አኪቃም…ሳፋን
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው
…ዋና ዋና አለቆች ሁሉ ላኩ
ሰዎቹን የላኩት ኤርምያስን ይዘው እንዲያወጡት ነው።
ከግዞት ቤት አደባባይ
ይህ ከንጉሱ ቤተመንግስት ጋር አብሮ ያለ ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ይህም ደግሞ ለእስረኞች የተዘጋጀ ቦታ ነው። ኤርምያስ 32፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
በህዝብ መካከል
“በይሁዳ በቀሩት በህዝብ መካከል”
Jeremiah 39:15
አጠቃላይ ሃሳብ
ይህ የተፈፀመው በምእራፉ የመጀመሪያ ክፍል ነው።
..ታስሮ ሳለ
ይህንን ቃል ሲጠቀም ወደ ዋና ታሪኩ ለመመለስ ነው። ጸሐፊው ናቡከነደፆር ኤርምያስን እንዲይዙት ከሰጠው ትእዛዝ በኋላ እግዚአብሄር ለኤርምያስ የተናገረውን ለመግለጽ ነው። (ታሪካዊ ዳራ እና የጊዜ ቅደም ተከተል የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ ኤርምያስ መጣ።
“የእግዚአብሄር ቃል ወደ” የሚለው ቃል ልዩ የሆነ መልእክት ለመናገር ሲፈልግ የሚጠቀመው ነው። ተመሳሳይ አረፍተነገር በኤርምያስ 1:4 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እግዚአብሄር ለኤርምያስ እንዲህ ሲል ተናገረ “ውሰድ””
በግዞትም ቤት አደባባይ
ይህ ከንጉሱ ቤተመንግስት ጋር አብሮ ያለ ሰፊ ክፍት ቦታ ሲሆን ይህም ደግሞ ለእስረኞች የተዘጋጀ ቦታ ነው። ኤርምያስ 32፡2 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ለኢትዮጵያዊውም ለአቤሜሌክ
የዚህን ሰው ስም በኤርምያስ 38፡7 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት።
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6፡6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ለበጎነት ሳይሆን ለክፋት ቃሌን በዚህች ከተማ ላይ አመጣለሁ
ክፉን ነገር በዚህች ከተማ ላይ አመጣለሁ እንደተነገርኩት ለክፋት ይሆናል።
በዚያን ቀን በፊትህ ይፈፀማል
በዛች ቀን ላይ የሚፈጠረውን ታያለህ
Jeremiah 39:17
አጠቃላይ ሀሰብ
እግዚአብሄር ለኤርምያስ መናገር ቀጠለ
በዚያ ቀን
ይህ የሚያመለክተው ባቢሎናውያን የኢያሩሳሌምን ግንብ አፍርሰው ከተማዋን የሚያጠፉባት ቀን ነች
ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1:8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››
በምትፈራቸው ሰዎች እጅ አልሰጥህም

“እጅ” የሚለው ሃይል እና ጉልበትን ያመለክታል። “የምትፈሩአቸው ሰዎች አይነኩአችሁም” ወይም “እናንተ በምትፈሩት በማንም ስልጣን ስር እንድትሆኑ አልፈቅድም”
በሰይፍ አትወድቅም
ሰይፍ የሚለው በጦርነት መሞትን ያመለክታል። “ማንም በሰይፍ አይገድሏችሁም” ወይም “በጦርነት አትሞቱም”
እድንሃለሁ ነፍስህም
በሂወት ትሆናለህ

---

Chapter 40
Jeremiah 40:1
ከእግዚአብሄር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል ይህ ነው።
ይህ አረፍተነገር እግዚአብሄር ለኤርምያስ የሰጠው መልእክት እንደሆነ ይናገራል። ኤርምያስ 32:1 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እግዚአብሄር ለኤርምያስ መልእክት ሰጠው” ወይም “እግዚአብሄር ለኤርምያስ ተናገረ”
ናቡዘረዳን
ይህ የሰው ስም ነው። ኤርምያስ 39:9 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ወደ ባቢሎን በተማረኩት
“የጦር ሰራዊቱ በምርኮ ወደ ባቢሎን ሊወስዱአቸው ”
Jeremiah 40:3
ይህ ነገር
ክፉ ነገር
አሁንም እነሆ
ናቡዘረዳን ለኤርምያስ ስለ አሉበት ጊዜ ልብ እንዲል የተናገረው ነው።
መልካም መስሎ ወደሚታይህ
“ወደሚታይህ” ሲል አንድ ሰው ምን እንደሚያስብ ለመግለፅ ነው። “ትክክል ነው ብለህ የምታስበውን”
Jeremiah 40:5
ጎዶልያስ…አኪቃም…ሳፋን
እነዚህ የሰዎች ስም ናቸው። ኤርምያስ 39:14 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
በህዝቡ መካከል
ከይሁዳውያን መካከል
መልካም መስሎ ወደሚታይህ
“ወደሚታይህ” ሲል አንድ ሰው ምን እንደሚያስብ ለመግለፅ ነው። “ትክክል ነው ብለህ የምታስበውን”
በአገሩ ውስጥ በቀሩት
በይሁዳ የቀሩት
Jeremiah 40:7
…በሰሙ ጊዜ
ይህን ቃል የአዲስ ታሪክ ጅማሬን ያመለክታል
ወደ ባቢሎን ያልተማረኩትን
“የጠላት ሰራዊት ወደ ባቢሎን ያልተላኩ”
እስማኤል…ናታንያ…ዮሀናን..ዮናታን..ቃሬያም…ሰሪያ…ተንሑሜትም…የዩፌ…ያእዛንያ
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።
የነጦፋዊውም…የማዕካታዊው
የነጦፋ እና የማዕካታ አካባቢ ህዝቦች
Jeremiah 40:9
እንዲህ ብሎ ማለ
“ለይሁዳዊ አለቃ ማለ”
እነሆ
ተመልከት ወይም ልብ በል
የበጋ ፍሬ
በበጋ ጊዜ የሚያፈራ ፍሬ
በያዛችኋቸውም
በናንተ ቁጥጥር ስር አርጋችኋል። “በያዛችኋቸውም” የሚለው የወታደሮች ቃል ሲሆን ገዳሊያሰራዊትን እየወሰደ ነበር (ኤርምያስ 40:7) ያሸነፋችሁ ከሆነ ነው ካልሆነ ሙሉ ከተማው ትወሰዳለች
Jeremiah 40:11
የይሁዳን ቅሬታ
የይሁዳ ህዝብ ቅሬታ
እንደ ሾመው… በላያቸው
“እንዳስቀመጠው…እንዲቆጣጠር እንዲመራ”
ሳፋንንም ልጅ የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን
ኤርምያስ 39:14 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
በላያቸው
በይሁዳ ህዝብ ላይ
ሁሉ ከተሰደዱበት ስፍራ ሁሉ
“ባቢሎናውያን ካሳደዱአቸው ቦታ”
ወይንና የበጋንም ፍሬ እጅግ ብዙ አከማቹ
እጅግ ብዛት ያለቸውን ወይንና የበጋ ፍሬዎችን
የበጋ ፍሬ
በበጋ ጊዜ የሚያፈራ ፍሬ
Jeremiah 40:13
ዮሀናን…ቃሬያም
እነዚህ ስሞች በኤርምያስ 40:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ጎዶልያስ
የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደተረጎመው በኤርምያስ 39:14 ላይ ተመልከት
የአሞን ልጆች ንጉሥ በኣሊስ ይገድልህ ዘንድ የናታንያን ልጅ እስማኤልን እንደ ሰደደ ታውቃለህን?
ዮሃናን እና የሰራዊት አዛዦች ጎዶልያስን እንዲጠነቀቅ የጠየቁት ጥያቄ ነው።
“የአሞን ህዝብ ንጉስ በኦሊስ አንተን ለመግደል የናታንያን ልጅ እስማኤልን እንደላከ ልትረዳ ይገባል።”
በኦሊስ
ይህ የሰው ስም ነው
እስማኤል… ናታንያን
በኤርምያስ 40:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
አኪቃም
ይህ ስም በኤርምያስ 26:24 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት
Jeremiah 40:15
ዮሃናን… ቃሬያም
እነዚህን የሰው ስሞች በኤርምያስ 40:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ጎዶልያስ
ይህን ስም በኤርምያስ 39:14 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
እስማኤል… ናታንያን
በኤርምያስ 40:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ማንም ሳያውቅ
ማንም እኔ እንዳረኩት አያቅም
ነፍስህን ስለ ምን ይገድላል
ዮሃናን የጎላድያስን አስተሳሰብ ለመቀየር የሞከረበት ጥያቄ ነው። እርሱ እንዲገድልህ ልትፈቅድለት አይገባም
እሱ ከገደለህ እኮ በዙሪያህ ለተሰበሰቡት የአይሁድ መበታተን ምክንያት ይሆናል በይሁዳ ምድር ከምርኮ በቀሩትም ህዝብ ላይ ታላቅ መቅሰፍትን በማምጣት ያጠፋቸዋል
ዮሃናን ጎላድያስ ሊያደር ያቀዳቸውን ነገሮች ካደረገ ምን ሊሆን እንደሚችል ጎላድያስ እንዲያስብ ይናገራል። “ይህን ካደረክ ባንተ የተሰበሰበው ይሁዳ ይበታተናል ቀሪው ይሁዳ ደግሞ ይጠፋል”
አይሁድ
ብዙ የአይሁድ ህዝብን ያመለክታል
በዙሪያ ለተሰበሰቡት
“ወዳንተ ለመጡት” ወይም “እግዚአብሄር ወዳንተ ያመጣቸው”
መበታተን
“ከለዳውይን እንዲበትኑአቸው” ወይም “ወደ ተለያዩ ብዙ ምድር እንዲሄዱ”
በይሁዳ ምድር ከምርኮ በቀሩትም ህዝብ ላይ ታላቅ መቅሰፍትን በማምጣት ያጠፋቸዋል
“ከለዳውያን የቀሩትን ይሁዳን ያጠፋሉ” ወይም “የይሁዳን የቀሩትን ያጠፋል”
በይሁዳ…የቀሩትን
በይሁዳ የቀሩትን ህዝብ። በኤርምያስ 40:11 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
አኪቃም


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህን ስም እንዴት እንደተረጎመው በኤርምያስ 26፡24 ላይ ተመልከት

Chapter 41

Jeremiah 41:1

በሰባተኛውም ወር

በእብራውያን ቀን አቆጣጠር ሰባተኛው ወር ነው። ይህም እንደ ምዕራባውያን አቆጣጠር የሴፕቴምበር መጨረሻዎቹ ላይ እና ኦክቶበር መጀመሪያዎቹ ላይ ነው።

የኤሊሳማ ልጅ የናታንያ

እነዚህን ስሞች በኤርምያስ 40፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

እስማኤል

ይህ የሰው ስም ነው

የሳፋንን ልጅ የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን

የእነዚህን ሰዎች ስም በኤርምያስ 39፡14 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

በአገሩ ላይ የሾመውን

“በአገሩ” የሚለው ህዝቡን ያመለክታል። “በይሁዳ ህዝብ ላይ ሾመው”

እስማኤልም....ገደላቸው

“እስማኤል” የሚለው ቃል ራሱን እና ከእርሱ ጋር የነበሩትን አስር ሰዎችን ያመለክታል። “እስማኤል እና አስር ሰዎች...ገደሉአቸው”

በዚያም የተገኙትን የከለዳውያንን ሰልፈኞች

“በዛም ያሉትን የከለዳውያን ሰራዊቶችን”

Jeremiah 41:4

በሁለተኛው ቀን

“ሁለተኛው” የሚለው ሁለት ቁጥርን ሲያመለክት ሊሆን የሚችለው ትርጉሙ ደግሞ 1) ከቀን በኋላ ወይም 2) ከሁለት ቀናት በኋላ ነው

ሰማንያ ሰዎች

ሰማንያ ሰዎች

ጢማቸውን ላጭተው ልብሳቸውንም ቀድደው ገላቸውንም ነጭተው

ይህ የሚያመለክተው ሰዎቹ ሃዘን ላይ እንደሆኑ ነው።

በእጃቸው

በእጃቸው መያዝ በቁጥጥር ስር ማዋል ወይም መሸከምን ያመለክታል። “በቁጥጥራቸው ስር”

ወደ እግዚአብሄር ቤት ያቀርቡ ዘንድ

እግዚአብሄርን በመቅደሱ ውስጥ ማምለክ

Jeremiah 41:6

ሊገናኛቸው

ሰማንያ ሰዎቹን ሊገናኝ

የናታንያ ልጅ እስማኤል ከእርሱም ጋር የነበሩ ሰዎች ገደሉአቸው፥ በጉድጓድም መካከል ጣሉአቸው

በኤርምያስ 41፡8 ላይ እስማኤል እና አብረውት ያሉ ሰዎች ሰማንያ ሰዎችን አልገደሉአቸውም ነበር። እነዚህ ሰማንያ ሰዎችን አብዛኛውን መግደላቸውን መናገር ይቻላል። “የናታንያ ልጅ እስማኤል እና አብረውት የነበሩ ሰዎች አብዛኛዎችቹን ሰማንያ ሰዎችን ገደሉአቸው እናም ጉድጓድ ውስጥም ጣሉአቸው”

Jeremiah 41:8

አስር ሰዎች ተገኙ

ከሰማንያ ሰዎቹ መሃል እንደተገኙ ይናገራል።

በሜዳ የተሸሸገ ስንዴና ገብስ ዘይትና ማርም አለንና

ይህ የሚያመለክተው ስንዴና ገብስ ዘይትና ማርም ለእስማኤል እና ከእርሱ ጋር አብረው ለነበሩት ሰዎች እንደሚሰጡ ያሳያል። “በሜዳ የተሸሸገ ስንዴና ገብስ ዘይትና ማርም አለንና እሱን እንሰጣችኋለን”

በሜዳ የተሸሸገ ስንዴና ገብስ ዘይትና ማርም አለንና

ለወደፊት የቀመጠ አስፈላጊ ነገሮች

እስማኤልም ከጎዶልያስ ጋር የገደላቸውን የሰዎች ሬሳ የጣለበትን ጉድጓድ ...የእስራኤልን ንጉሥ ባኦስን

ይህ የኋላ ታሪክ ሲናገር እስማኤል የተጠቀመውን የውሃ ጉድጓድ ያመለክታል። ንጉስ አሳ ንጉስ ባኦስ ሲያጠቁአቸው የራሱ ሰዎች ውሃ እንዲያገኙ ሰዎቹን ያስቆፈራቸው ጉድጓድ ነው።

ንጉስ አሳ...የሰራው ጉድጓድ

“ንጉስ አሳ” የሚለው የሱን ሰዎችን ያመለክተል። “ንጉስ አሳ ሰዎቹን እንዲቆፍሩ አዘዘ”

የእስራኤል ንጉስ ባኦስን

“ንጉስ በኦስ” ራሱን እና ሰራዊቱን ይወክላል። “የእስረኤል ንጉስን ባኦስንነ ሰራዊቱን”

የናታንያም ልጅ እስማኤል...ሞላበት

“እስማኤል” ራሱን እና አብረውት ያሉትን ሰዎችን ያመለክታል። “እስማኤልና አብረውት ያሉት ሰዎች...ሞሉት”

በሞቱት

“የሞቱት” ወይም “እነርሱ በገደሉአቸው”

Jeremiah 41:10

እስማኤል ማርኮ

“እስማኤል” ራሱን እና አብረውት ያሉትን ሰዎችን ያመለክታል። “እስማኤልና አብረውት ያሉት ሰዎች ማርከው”

ናቡዘረዳን

የዚህ ሰው ስም በኤርምያስ 39፡9 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት

ወደ አሞን ልጆች ይሄድ ዘንድ ተነሣ

ወደ አሞናውያን ምድር ተጓዘ

Jeremiah 41:11

ዮሀነን...ቃሬያም

የእነዚህን ሰዎች ስም በኤርምያስ 40፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት።

የናታንያ ልጅ እስማኤል...በሰሙ ጊዜ

“እስማኤል” ራሱን እና አብረውት ያሉትን ሰዎችን ያመለክታል። “እስማኤል እና አብረውት የነበሩት ሰዎች...በሰሙ ጊዜ”

Jeremiah 41:13

ከእስማኤል ጋር የነበሩት ህዝብ ሁሉ

“ህዝብ” የሚለው እስማኤል እና አብረውት ያሉት ሰዎች የማነረኩአቸውን ያመለክታል።

እስማኤል...የማረካቸው

“እስማኤል” የሚለው ቃል ራሱን እና አብረውት የነበሩትን ሰዎችን ሁሉ ነው። “እስማኤል እና አብረውት ያሉት ሰዎች የማረኩአቸውን”

Jeremiah 41:15

ወደ አሞን ልጆች ሄደ

“ሄደ” የሚያመለክተው እስማኤልን ሲሆን ይህም ደግሞ ራሱን እና አብረውት ያሉትን ስምንት ሰዎችን ያመለክታል። “ወደ አሞን ልጆች ሄዱ”

ያስመለሱአቸውን

“ያስመለሱአቸውን”

የአኪቃምን ልጅ ጎዶልያስን በምጽጳ ከገደለው በኋላ

ፀሃፊው ታሪኩን ቆም ያደረገው የበፊቶቹን ድርጊቶችን ለማመልከት ሲሆን የድርጊቶቹ አቀማመጥ ለመረዳት እንዲሆን አድርጎ ነው።

ሰልፈኞች

የጦር ሰራዊቱን ያመለክታል

ከገባኦን ያስመለጡአቸውን

“ከገባኦን ያስመለጡአቸውን”

Jeremiah 41:17

ይሄዱ ዘንድ

ዮሀናን አብረውት ያሉት እና ያመለጡት ህዝቦች ሁሉ ሄዱ

በጌሮት ከመዓም

ይህ የቦታ ስም ነው

ከለዳውያንን ፈርተዋልና

ይህ የሚያመለክተው ከለዳውያን እንዳያጠቁአቸው መፍራታቸውን ነው። “ከለዳውያን ያጠቁናል ብለው አስበውዋልና”

በአገሩ ላይ የሾመውን

“አገሩ” የሚለው ቃል ሕዝብን ያመለክታል። “በይሁዳ ህዝብ ላይ የሾመውን”

Chapter 42

Jeremiah 42:1
የሀናን ቃሬያም
እነዚህን ሰዎች በኤርምያስ 40፡13 እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት
ያእዛንያ…ሆሻያም
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው
ሕዝብም ሁሉ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ
ይህ በህዝቡ ያሉ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ሰዎችን ያመለክታል። “ታናሹም” እና “ታላቁ” የሚለው በጣም አስፈላጊ ሰዎችን እና ተራው ሰውን ያመለክታሉ። “በሁሉም ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎችን በአጠቃላይ” ወይም “በጣም አስፈላጊው ሰው እና ተራው ሰው ሁሉ”
ህዝብ ሁሉ
ይህ ሁሉንም ግለሰብ ላያካትት ይችላል። “ሁሉ” ሲል ብዙ ህዝቦች ለማለት ፈልጎ ነው። “ብዙ ህዝብ”
ልመናችን፥ እባክህ፥ በፊትህ ትድረስ
“እባክህን ልመናችንን ስማን”
Jeremiah 42:4
እነሆ
ተመልከት ወይም ልብ በል
ከእናንተም ምንም አልሸሽግም
“ከእናንተም ምንም አልሸሽግም” የሚለው ሀረግ ሁሉንም ነገር በግልፅ መንገር ማለት ነው። “እግዚአብሄር የነገረኝን ሁሉንም ነገር እነግራችኋለሁ”
አምላክህ እግዚአብሄር
ይህ ቃል ለመግባት መጀመሪያ ነው።
እውነተኛ እና ታማኝ
እነዚህ ሁለት ቃላት አንድ ሃሳብ ይጋራሉ። እንዚህ ቃላት እግዚአብሄር እንደ እውነተኛ ማንም እንደ ማይቃወመው ምስክር አርጎ ይናገራል። “ታማኝነት”
መልካም ወይም ክፉ ቢሆን
ህዝቡ የእግዚአብሄር መልስ ምንም ቢሆን ምን እንደሚታዘዙ አስረግጠው እንደሚናገሩ ያሳያል። “ምንም አይነት መልስ ቢሰጠን”
የአምላካችንን የእግዚአብሄር ቃል እንሰማለን።
“ቃል” የሚለው እግዚአብሄር የሚናገረውን ያመለክታል። “አምላካችን እግዚአብሄር የሚናገረውን” ወይም “አምላካችንን እግዚአብሄር እንታዘዛለን”
Jeremiah 42:7
የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ መጣ።
ይህ አረፍተነገር እግዚአብሄር ለኤርምያስ የሰጠው መልእክት እንደሆነ ለማሳየት ነው። እንደዚህ ተመሳሳይ አረፍተነገር በኤርምያስ 1፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት። “እግዚአብሄር ለኤርምያስ መልእክትን ሰጠው”
ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ
ይህ በህዝቡ ያሉ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ሰዎችን ያመለክታል። “ታናሹም” እና “ታላቁ” የሚለው በጣም አስፈላጊ ሰዎችን እና ተራው ሰውን ያመለክታሉ። “በሁሉም ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎችን በአጠቃላይ” ወይም “በጣም አስፈላጊው ሰው እና ተራው ሰው ሁሉ”
ህዝቡንም ሁሉ ጠራ
ይህ ሁሉንም ግለሰብ ላያካትት ይችላል። “ሁሉ” ሲል ብዙ ህዝቦች ለማለት ፈልጎ ነው። “ብዙ ህዝብ”
ጸሎታችሁን በፊቱ አቀርብ ዘንድ
“ጸሎታችሁን ሁሉ ወደሱ አቀርባለሁ” ህዝቡን ለእግዚአብሄር እንዲጠይቁ እንደ ኤርምያስ የህዝቡን ፀሎት ይዞ ወደ እግዚአብሄር እንደሚቀርብ አርጎ መስሎ ይናገራል። “ፀሎታችሁን እነግርላችኋለሁ”
እሰራችኋለሁ እንጂ አላፈርሳችሁም
እግዚአብሄር የእስራኤልን ህዝብ እንደ ሚገነባ እና እንደ ሚፈርስ አድርጎ መስሎ ይናገራል። “አበለፅጋችኋለሁ እንጂ አላጠፋችሁም”
እተክላችኋለሁ እንጂ አልነቅላችሁም
እግዚአብሄር የእስራኤል ህዝብን እንዴት እንደ ሚበለፅጉ እና እነደማይጠፉ በሌላ አነጋገር ይናገራል። እንደ ተክል መስሎ ይናገራል ልክ እንደ ግንብ እንደመሰላቸው።
ስላደረግሁባችሁ ክፉ ነገር ተጸጽቻለሁና
ክፉ ነገር የሚለው አንድ ሰው ሌላ አንድ ሰው ላይ የሚየመጣው ነገር ነው። “የመጣባችሁን ክፉ ነገር እከለክላለሁ”
Jeremiah 42:11
ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ የገለጸበት ምክንያት ቃሉን አስረግጦ ለመናገር ስለፈለገ ነው።፤ ኤርምያስ 1፡8 የተተረጎመበትን መንገድ ይመልከቱ። ‹‹እግዚአብሄር የተናገረው ይህንን ነው›› ወይም ‹‹እኔ እግዚአብሄር የተናገርኩት ይህንን ነው››
አድናችሁ ዘንድ … አስጥላችሁ
“አድናችሁ” እና “አስጥላችሁ” የሚሉት ቃላት አንድ አይነት ሃሳብ ሲኖራቸው እግዚአብሄር የእውነት እንደሚያድን የሚናገር ነው። “ሙሉ በሙሉ እንዲያድናችሁ”
ከእጁም አስጥላችሁ ዘንድ
“እጅ” የሚለው ቃል ሀይል ወይም ስልጣንን ያመለክታል። “ከህይሉ እስጥላችሁ ዘንድ” ወይም “ከእርሱ አስጥላችሁ ዘንድ”
Jeremiah 42:13
የአምላካችሁንም የእግዚአብሔርን ቃል ባትሰሙ
“ቃል” የሚለው ትእዛዙን ያመለክታል። አለመታዘዝ ህዝቡ የእግዚአበሄርን ትእዛዛቱን አለመስማት እንደሆነ ይናገራል። “የእኔ አምላካችሁን እግዚአብሄር ትእዛዝ እነኳን ባታከብሩም”
ሰልፍ ወደማናይባት የመለከትም ድምፅ ወደማንሰማባት
ሁለቱም ቃላት የሚናገሩት ጦርነት ላይ ስለሚታየው እና ስለሚሰማው ነው። “ጦርነትን የማናይበት ወደማያጋጥመን”
ወደማንራብባትም
መራብ የሚለው ድርቅን ለማመልከት ይጠቀማል።
Jeremiah 42:15
አሁን
“አሁን” የሚለው ቃል የአሁኑን ጊዜ ሳይሆን የሚያመለክተው ወደ ትኩረት ወደ ሚሻ ነጥብ እንሚያመራ ለማተኮር ነው።
የእግዚአብሄርን ቃል
የእግዚአብሄርን መልእክት
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6፡6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
የምትፈሩት ሰይፍ በዚያ በግብጽ ምድር ያገኛችኋል
“ሰይፍ” የሚለው ጦርነትን ያመለክታል። እስራኤላውያን ግብፅ ቢሄዱም ጦርነት እዛም ተከትሎአቸው እንደሚሄድ እና እንደሚደርስባቸው መስሎ ይናገራል። “የጦርነት መጥፎ ገፅታውን ታዩታላችሁ”
የምትደነግጡበት ራብ በዚያ በግብጽ ይደርስባቸኋል፥
እስራኤላውያን ረሃብ ይመጣባቸዋል ግብፅ ቢሆኑም እንኳን። “በእስራኤል የምትደነግጡበት ረሃብ ግብፅ ብትሄዱ እንኳን በዛ በረሃብ ትሰቃያላችሁ”
በሚያቀኑ ሰዎች ሁሉ
ሰዎች የሚለው ሁሉንም ህዝብ ያመለክታል ምክንያቱም የቤተሰቦቻቸው መሪዎች ናቸውና። “የሚያቀና ማንም ሰው”
ይገቡ ዘንድ በዚያም ይቀመጡ ዘንድ ፊታቸውን
ትቶ መውጣት
ከማመጣባቸው ክፉ ነገር
ክፉ ነገርን ማምጣት እነደ አንድ እቃ ወደ ሰው እንደ ማምጣት መስሎ ይናገራል። “በነሱ ላይ የማመጣውን ክፉ ነገር”
Jeremiah 42:18
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው። ኤርምያስ 6፡6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ቍጣዬና መዓቴ በኢየሩሳሌም በሚኖሩ ላይ እንደ ፈሰሰ
እግዚአብሄር በቁጣ ህዝቡን ሲቀጣ እነደ መአት እና ቁጣው ፈሳሽ ነገር እንደሆኑና በህዝቡ ላይ እንደሚያፈሰው ይናገራል። “እጅግ በጣም ስለተቆጣሁ የኢያሩሳሌምን ህዝብ እቀጣለሁ”
መዓቴና ቁጣዬ
ሁለቱም ቃላት አንድ አይነት ነገር ሲያመለክቱ ምን ያህል እንደተቆጣ አግንኖ ያሳያል። “ከባዱ መዓቴ”
እንዲሁ…መዓቴ ይፈስስባችኋል
እግዚአብሄር በቁጣ ህዝቡን ሲቀጣ እነደ መአት እና ቁጣው ፈሳሽ ነገር እንደሆኑና በህዝቡ ላይ እንደሚያፈሰው ይናገራል። “እጅግ በጣም ስለተቆጣሁ የኢያሩሳሌምን ህዝብ እቀጣለሁ”

እናንተም ለጥላቻና ለመደነቂያ ለመረገሚያና ለመሰደቢያ ትሆናላችሁ
እነዚህ ሁሉ የሚናገሩት አንድ አይነት ሃሳብ ሲሆን ሌሎች ከተማዎች የይሁዳን ህዝብ እግዚአብሄር ከቀጣቸው በኋላ እንዴት እንደ ሚንቁአት ይናገራል፡፡ "በናተ ላይ የደረሰውን ክፉ ነገር ሲያዩ ህዝብ ሁሉ ይደነቃል እነሱም ይረግሟቹአል ደግሞም መሰደቢያ ትሆናላችሁ"
እንዳስጠነቀቅኋችሁ በእርግጥ እወቁ
ይህ አረፍተ ነገር የሚያመለክተው እያስጠነቀቃቸው መሆኑን ነው፡፡ "አስጠንቅቄአችኋለሁ"
Jeremiah 42:20
እኛም እናደርገዋለን
"እኛ እናደርገዋለን"
አልሰማችሁም
ልብ ብላችሁ አልሰማችሁም
የአምላካችሁን የእግዚአብሄርን ቃል
"ቃል" የሚለው ትእዛዙን ያመለክታል፡፡ "አምላካችሁ እግዚአብሄርን ያዘዘውን ትእዛዝ"
አሁን
"አሁን" የሚለው ቃል የአሁኑን ጊዜ ሳይሆን የሚያመለክተው ወደ ትኩረት ወደ ሚሻ ነጥብ እንሚያመራ ለማተኮር ነው፡፡
በሰይፍና በራብ እንድትሞቱ
"ሰይፍ" የሚለው ጦርነትን ያመለክታል፡፡ "በጦርነት ትሞታላችሁ"
ሄዳችሁ እንድትቀመጡ በወደዳችሁበት ስፍራ
የወደዱት ስፍራ ግብፅ ነው፡፡ "በግብፅ ሰላም ነው ብላችሁ የምታስቡት ምድር እንኳን"

---

Chapter 43
Jeremiah 43:1
በፈጸመ ጊዜ
ይህ ሃረግ የአንድን ታሪክ ጅማሬን ያመለክታል፡፡
አዛርያስ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) ይህ የኤርምያስ ሌላኛው ስሙ ነው ኤርምያስ 42፡1 ወይም 2) የህ የዮሃናን ሌላ ልጁ ነው፡፡
ሆሻያ
በኤርምያስ 42፡1 ላይ የዚህ ሰው ስም እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት
የቃሬያም... ዮሀናን
በኤርምያስ 40፡13 ላይ የነዚህ የሰዎች ስም እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት፡፡
አነሳስቶአል
ሰው ላይ መጥፎ ነገርን ለማድረግ ማነሳሳት
ከለዳውያን...በእጃቸው አሳልፍ ትሰጠን ዘንድ
"እጅ" የሚለው ቃል ሃይልን ወይም ጉልበትን ያመለክታል፡፡ "ለከለዳውያን አሳልፎ ትሰጠን ዘንድ"
እንዲገድሉን ወደ ባቢሎንም እንዲማርኩን
"እንዲገድሉን" መግደልን ያመለክታል፡፡ "ከለዳውያን እንዲገድሉን ወይም ደግሞ በባቢሎን እንድንማረክ"
Jeremiah 43:4
ሁሉ ህዝቡም
ይህ ሁሉንም ግለሰብ ላያካትት ይችላል፡፡ "ሁሉ" ሲል ብዙ ህዝቦች ለማለት ፈልጎ ነው፡፡ "ብዙ ህዝብ"
የእግዚአብሔርን ቃል አልሰሙም
"ቃል" የሚለው የእግዚአብሄርን ትዕዛዛትን ነው፡፡ "አልሰሙም" የሚለው ቃል አለማክበርን ያመለክታል፡፡ "የእግዚአብሄርን ትእዛዛት አላከበሩም"
በአህዛብ መካከል ተበታትነው ከቆዩ
"እግዚአብሄር በታተናቸው"
ናቡዘረዳን
የዚህን ሰው ስም እንዴት እንደተረጎመው በኤርምያስ 39፡9 ተመልከት
ጎዶሊያስ...አኪቃም...ሳፋን
የነዚህን ሰዎች ስም እንዴት እንደተረጎመው በኤርምያስ 39፡14 ተመልከት
ጣፍናስ
የዚህን የከተማ ስም በኤርምያስ 2፡16 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
Jeremiah 43:8
በጣፍናስም የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ...ውሰድ
"የእግዚአብሄር ቃል ወደ" የሚለው ቃል ልዩ የሆነ መልእክት ለመናገር ሲፈልግ የሚጠቀመው ነው፡፡ ተመሳሳይ አረፍተነገር በኤርምያስ 1:4 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት፡፡ "እግዚአብሄር ለኤርምያስ እንዲህ ሲል ተናገረ "ውሰድ""
የይሁዳም ሰዎች እያዩ
"የይሁዳም ሰዎች እየተመለከቱ"
ጭቃ
ድንጋይን ለማጣበቅ የሚጠቀሙበት ነው
በፈርዖን ቤት ደጅ
የፈርዖን የንጉሱ ቤት
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር
ኤርምያስ ማስተዋል ያለብንን መልእክት ሲያስተላልፍ የሚጠቀመው ሀረግ ነው፡፡ ኤርምያስ 6፡6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
ባሪያዬን የባቢሎንን ንጉሥ ናቡከደነፆር አመጣለሁ፥ ዙፋኑንም እኔ በሸሸግኋቸው በእነዚህ ድንጋዮች ላይ አኖራለሁ እርሱም ማለፊያውን ድንኳኑን በላያቸው ይዘረጋል
"ዙፋኑን" የሚለው የንግስናው ስልጣንን ያመለክታል፡፡ "በግብፅ ህዝብ ላይ ንጉስ እንዲሆን አደርጋለሁ፡፡ ዙፋኑን እና ድንኳኑን እናንተ በቀበራችሁት ድንጋይ ላይ ይሆናል፡፡"
ዳስ
ትልቅ ድንኳን
Jeremiah 43:11
አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር መልእክቱን መናገሩን ቀጠለ
መጥቶም
ይህ የሚያመለክተው የናቡከደነፆር ሙሉ ሰራዊትን ነው፡፡ "የናቡከደነፆር ሰራዊት ይመጣል"
ለሞትም የሚሆነውን ለሞት
"ይሞታል ብዬ የወሰንኩት ሁሉ ይሞታል"
ለምርኮ የሚሆነውን ለምርኮ
"ይማረካል ብዬ የወሰንኩት ሁሉ ባቢሎናውያን ይማረካል"
ለሰይፍም የሚሆነውን ለሰይፍ አሳልፎ ይሰጣል
"ሰይፍ" ጦርነትን ያመለክታል፡፡ "በጦርነት ይሞታል ብዬ የወሰንኩ በጦርነት ይሞታል"
እሳትን ያነዳል
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሄር እየተናገረ እንደሆነ ነው፡፡ እግዚአብሄር የባቢሎን ሰራዊት ልኮ እሳት እንደሚያነደዱ ይናገራል፡፡ "የባቢሎን ሰራዊት እሳት እንዲያነዱ አደርጋለሁ"
ያቃጥላቸውማል ይማርካቸውማል
የግብፅ ጣኦቶችን ያቃጥላሉ ወይም ይወስዱአቸዋል፡፡
በሳር እና ሳር በል በሆኑ እንሳዎች የተሞላ መሬት
ወጥተው እንዲባረሩ አደርጋለሁ
የባቢሎናውያን ህዝብን ያመለክታል።
በእረሱዋ ላይ እሾመዋለሁ
“እኔ የምሾመው”
እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ሊቋቋመኝ የሚችልስ ማን ነው?
እግዚአብሄር እነዚህን ጥያቄዎች እንደሱ ያለ ማንም እንደሌለ አግንኖ የሚያሳይ ነው።
ሊቋቋመኝ የሚችልስ ማን ነው?
ማን ነው እኔን ሊቀይረኝ የሚችለው።
የሚቃወመኝ እረኛ ማን ነው
እግዚአብሄር ይህን ጥያቄ ማንም እነደማያሸንፈው ለማሳየት ሲሆን “እረኛ” የሚለው ደግሞ ንጉስ የሚለውን እንደሆነ ያሳያል።
Jeremiah 50:45
አጠቃላይ ሀሳብ
እነዚህ ቁጥሮች ከኤርምያስ 49፡20 እና ኤርምያስ 49፡21 ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ ስላላቸው እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
እግዚአብሔር በባቢሎን ላይ የመከረባትን ምክር፥ በከለዳውያንም ምድር ላይ ያሰባትን አሳብ
እነዚህ ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም ቢኖራቸውም በአንድ ላይ ሲሆኑ ግነትን

ያሳየናል። “እግዚአብሄር ለባቢሎን ህዝብ እና ለከለዳውያን ህዝብ ሃሳብ አስቦአል።
”
በእውነት የመንጋ ትናንሾች ይጎተታሉ
እግዚአብሄር የባቢሎንን ህዝብ እንደሚቀጣ መናገሩን ቀጥሎአል። “ትንሹዋ መንጋ ራሱ ይጎትታታል”
የመንጋ ትናንሾች
ትናንሽ እና ደካማ የባቢሎን ህዝብ እንደ ትንሽ የበግ መንጋ አርጎ ይናገራል። “ትናንሾችና ደካሞችም”
ማደሪያቸውን ባድማ ያደርግባቸዋል
የባቢሎን ምድር እንደ የመንጋ ማደሪያ አርጎ ይናገራል። “መልካሙን ማደሪያ ባድማ ያደርገዋል።”
ከባቢሎን መያዝ ድምፅ የተነሳ ምድር ተናወጠች
ይህ ባቢሎን ሀያል ከተማ እንደሆነች እና የሷ ድምፅ መሬትን አንቀጠቀጠ።
”የባቢሎን ውድቀት እነደ መሬት መናወጥ ነው”
ድንጋጤ
ህመም ወይም ደስተኛ አለመሆን
የድንጋጤ ጩኸት
የህመም ወይም የስቃይ ጩኸት

---

Chapter 51

Jeremiah 51:1

አጠቃላይ ሐሳብ
ኤርሚያስ በብዛት የሚፅፋቸው ትንቢቶች በግጥም መልክ ነው።
እነሆ
ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር በማስተዋል እንዲሰሙ ያመለክታል
አጥፊውን ነፋስ
የሚያጠፋ ነፋስ ወይም ደግሞ የሚያጠፋ መንፈስ። ይህ ማለት እግዚአብሄር የጠላት ሰራዊት ሄደው ባቢሎንን እነዲያጠቁ ያስነሳል።
ከለዳውያን
በባቢሎን ክልል የሚገኙ ህዝቦች ናቸው።
በባቢሎንም ላይ የሚዘሩትን ሰዎች ... በዙሪያዋ ይከብቡአታል
“በዙሪያዋ” ብሎ የሚያመለክተው ባቢሎንን ሲሆን በባቢሎን ለሚኖሩ ሰዎች መጠሪያቸው ነው።
በመከራም ቀን
ይህ ሀረግ “መከራ ቀን” የሚለው በእብራውያን “መቼ” ሚለውን ያመለክታል።

Jeremiah 51:3

ቀስተኛው ቀስቱን ይገትር ለጐበዛዝትዋ አትዘኑ
እግዚአብሄር በድንገተኛ እንዲያጠቁ ስለፈለገ ለቀስተኛው ለጦርነት የዝግጅት ጊዜ የላቸውም።
“በከለዳውያን ምድር ተገድለው”
ጠላቶቻቸው የገደሉአቸውን ያመለክታል

Jeremiah 51:5

“...እስራኤልም ሆነ ይሁዳ በአምላኩ በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ዘንድ አልተጣለም”
“እስራኤል” እና “ይሁዳ” ብሎ ሲናገር በእስራኤል እና በይሁዳ የሚገኙ ሰዎችን ለማመልከት ነው።
ምድራቸው በእስራኤል ቅዱስ ላይ በተሠራው በደል ምንም እንኳ የተሞላች ብትሆን፥
በዚህ ክፍል የተናገረው ምድር ላይ የሚኖሩት ሰዎች ከሰሩት በደል የተነሳ ልክ እቃ ማጠራቀሚያን እንደሚሞላ እነሱም ምድርን ሞሉአት።
በበደልዋ አትጥፉ
ይህ ሐረግ ባቢሎን ልክ እነደ ሴት አርጎ ሲናገር እግዚአብሄር ባቢሎንን ሊያጠፋ እንደሆነ ያመለክታል።
እርሱም ብድራትዋን ይከፍላታልና
በዚህ ሀረግ ባቢሎን ልክ እንደ ሴት አረጎ ሲናገር ህዝቡ ከሰራው በደል ምክንያት እግዚአብሄር የሚገባቸውን ቅጣት እንደሚቀጣቸው ያመለክታል

Jeremiah 51:7

ባቢሎን በእግዚአብሄር እጅ ውስጥ ምድርን ሁሉ ያሰከረች የወርቅ ፅዋ ነበረች
“ምድርን ሁሉ” ሲል በባቢሎን ዙሪያ የሚኖሩ ሰዎችን ሲሆን የሚያመለክተውም 1) “ያሰከረች” ብሎ ሲናገር እግዚአብሄር ለባቢሎን አሳልፎ ስለሰጣቸው ከተሞች ነው 2) ሌላው ደግሞ ከባቢሎን ጋር አብሮ በመሆን ጣኦት አምልኮ ሲጀምሩ እና ጦርነት ሲሆን ነው
ባቢሎን በእግዚአብሄር እጅ ውስጥ ... የወርቅ ፅዋ ነበረች
ባቢሎን እግዚአብሄር ለራሱ አላማ የሚጠቀምባት ከተማ ነበረች። በእርሱም እጅ እንዳለ የወርቅ ፅዋ እንደሆነች ይናገራል።”እጅ” የሚለው ቃል የእግዚአብሄርን ሃይል ወይም ሃያልነት ያመለክታል።
አሕዛብም ከጠጅዋ ጠጥተዋል ስለዚህ አሕዛብ አብደዋል
የዚህ ትርጉም ሊሆን የሚችለው 1) ባቢሎን ሌሎች ከተማዎችን አሸንፈው እና አጥፍተዋል 2) ሌሎች ከተሞች በእሷ ሀብት እና ሀያልነት ክፉ ሆነዋል።
አብደዋል
በትክክል ማሰብ አለመቻል
ባቢሎን በድንገት ወድቃ ጠፍታለች
እግዚአብሄር ባቢሎንን አጠፋ
“...አልቅሱላት”
በከፍተኛ ድምፅ እና ረጅም የሆነ ለቅሶ ሲሆን ምን ያህል እንዳዘነ ያሳያል
“...ትፈወስም እንደሆነ”
ምናልባት እግዚአብሄር ከፈወሳት

Jeremiah 51:9

አጠቃላይ ሐሳብ
እግዚአብሄር ባቢሎንን ተጠቅሞ ይሁዳን ሲቀጣ ወይ የይሁዳ ህዝቦችን ወይም በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ቃሉን የሚናገሩትን ሰዎችን ነው።
“ባቢሎን... እርስዋ ግን አልተፈወሰችም ፍርድዋ እስከ ሰማይ ደርሶአልና፥ እስከ ደመናም ድረስ ከፍ ከፍ ብሎአልና ትታችኋት..”
ባቢሎን የሚለው የሚያመለክተው በውስጧ የሚኖሩት ህዝቦችን ሲሆን ልክ እንደ ሴት መስሏታል።
“..እርስዋ ግን አልተፈወሰችም”
እኛ ግን ልናድናት አልቻልንም።
“...ፍርድዋ እስከ ሰማይ ደርሶአልና፥ እስከ ደመናም ድረስ ከፍ ከፍ ብሎአልና”
ፍርድዋ ልክ እነደ እቃ ተከምሯል። “...ሰማይ ደርሶአልና እስከ ደመናም ድረስ..” ሲል ግነት ሲሆን ይህም ምን ያህል በጣም ከፍታን ያመለክታል
እግዚአብሔር ጽድቃችንን አውጥቶአል
እግዚአብሄር እስራኤላውያንን በሰሩት ሀጥያት ቅጣት ቀጥቶአቸው ነበር አሁን ግን ወደሱ መልሶአቸዋል።

Jeremiah 51:11

አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርሚያስ ለባቢሎን ሰዎች እና ለጠላቶቻቸው እንደሚናገር ያህል ለኢየሩሳሌም ሰዎች እግዚአብሄር ባቢሎንን እንደሚያጠፋ እና ባቢሎናዊያንን ከጦርነት ከመዘጋጀታቸው በፊት እንደሚሸነፉ ሲናገር ነበር።
“በባቢሎን ቅጥር ዓላማውን አንሡበት”
የባቢሎን ቅጥርን ለመምታት ምልክት ሰጠ
ጥበቃን አፅኑ
ጥበቃዎቹ ጠንካራ እና ጥሩ መሳሪያ ያላቸው መሆኑን አረጋግጡ
“ተመልካቾችን አቁሙ”
በቂ ከተማዋን የሚመለከቱ ሰዎች መኖራቸውን አረጋግጡ
ድብቅ ጦር አዘጋጁ
ይህ ድንገት ከከተማዋ ሸሽቶ የሚያመልጥ ካለ ለመያዝ አዘጋጁ

Jeremiah 51:13

አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርሚያስ በኢየሩሳሌም ያሉ ህዝቦችን ልክ ሲናገር እንደማይሰሙት የባቢሎን ህዝቦች መናገሩን ቀጥሎአል።
ፍጻሜሽ ደርሶአል
“ፍፃሜሽ ደርሶአል” የሚለው ሐረግ እግዚአብሄር ህዝቡ የሚጠፋበት ጊዜ እንደቀረበ ይናገራል።
እንደ አንበጣ..
ከተማዋን የሚወሩ እጅግ በጣም ብዙ ሰራዊትን ያመለክታል
እነሱም ጩኸት ያነሱብሻል
የሠራዊቱ ጩኸትን ያመለክታል።

Jeremiah 51:15


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ድምፁን ባሰማ ጊዜ ውሆች በሰማይ ይታወካሉ
የእግዚአብሄር ድምፅን ከመብረቅ ነጎድጓድ ድምፅ እና ከዝናብ ጋር ያነፃፅረዋል።
ከቤተ መዛግብቱ
ይህ ስፍራ ወደፊት እንጠቀምበታለን ብለው የሚያስቡትን ሚቀመጥበት ቦታ ነው።
Jeremiah 51:17
አጠቃላይ ሐሳብ
በኤርሚያስ 10፡14-16 ላይ እንዳለው ተተርጉሟል
“ሰው ሁሉ እውቀት አጥቶ ሰንፎአል”
የእውቀት ማጣት ወይም አለማወቅ
አንጥረኛም ሁሉ ከቀረፀው ምስል…
አንጥረኛ የተባለ ሁሉ የሰሩት እና የቀረፁት የጣኦት ምስል አሳፍሮአቸዋል
በተጐበኙ ጊዜ ይጠፋሉ
የተቀረፁት ምስሎች እግዚአብሄር እንደሚያጠፋቸው ወይም እንደሚያፈራርሳቸው ያመለክታል።
የያእቆብ እድል ፈንታ
“ያዕቆብ” የሚለው ስም የሚያመለክተው የእስራኤል ህዝብን ሲሆን እግዚአብሄር እድል ፈንታቸው ሲሆን እርሱን ያመልኩታል
የሁሉ ፈጣሪ
እርሱ ሁሉንም የፈጠረ ነው
እስራኤልም የርስቱ ነገድ ነው።
እስራኤልን እግዚአብሄር ወርሶታል ይህም እስራኤል የ እግዚአብሄር ነገድ ነው።
Jeremiah 51:20
አንቺ
የባቢሎን ሰራዊትን ያመለክታል
እሰባብራለሁ
እግዚአብሄር ህዝቡን እንደሚቀጣ ይናገራል
በአንቺ
እጠቀምብሻለሁ እያለ ነው
Jeremiah 51:22
በአንቺም…እሰባብራለሁ
እግዚአብሄር ህዝቡን እንደሚቀጣ ይናገራል (ኤርሚያስ 51፡20 ተመልከት)
በአንቺ
እጠቀምብሻለሁ እያለ ነው (ኤርሚያስ 51፡20 ተመልከት)
Jeremiah 51:24
በአይናችሁ ፊት… እከፍላለሁ
የስራቸውን ስከፍላቸው በአይናችሁ ታያላችሁ
ይላል እግዚአብሄር
ይህ ሀረግ እግዚአብሄር እራሱ በስሙ ጠርቶ ያዛል።
Jeremiah 51:25
አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ለሚሰሙት የኢየሩሳሌም ህዝቦች ልክ እንደ ማይሰሙት የባቢሎን ህዝቦች ይናገራል። የባቢሎን ህዝቦችን ልክ እንደ እራሳቸው ሲናገር ከተማዋን ደግሞ ልክ እንደ ተራራ ይናገራል።
አንተ…አጥፊ ተራራ
ይህ የሚያመለክተው 1) እግዚአብሄር ባቢሎን ልክ ህዝቦችን እና ንብረቶችን እንደ ሚያጠፋ ተራራ ይናገራል። 2) ባቢሎን ወንበዴዎች የሚኖሩበት እና የሚደበቁበት ተራራ
እጄንም አዘረጋብሃለሁ
“እጄንም” ሲል የእግዚአብሄርን ሀይል ለማመልከት ነው።
ከድንጋዮችም ላይ አንከባልልሃለሁ
እግዚአብሄር ባቢሎንን እንደ ተራራ መናገር ትቶ እንደ ሚያፈራርሰው እና እንደሚጥለው ቤት ይናገራል
ከድንጋዮቹም
ይህ የሚያመለክተው የተራራ ጫፍ ነው
የተቃጠለም ተራራ አደርግሀለሁ
እግዚአብሄር ባቢሎንን እንደ ሚያጠፋ ትልቅ ተራራ ሳይሆን እርሱ እንዳጠፋው ተራራ አርጎ ይናገራል።
ለዘላለም ባድማ ትሆናለህ
ማንም መልሶ እንዳይገነባህ ለዘላለም አጠፋሀለሁ
ይላል እግዚአብሄር
ይህ ሀረግ እግዚአብሄር እራሱ በስሙ ጠርቶ ያዛል።
Jeremiah 51:27
በምድር ላይ ዓላማን አንሡ በአሕዛብም መካከል መለከት ንፉ
ሁለቱም “መለከት ንፉ” እና “አላማን አንሱ” ሰራዊቱን ለውጊያ ተነሱ ማለት ነው።
አላማን አንሱ
ትልቅ “የጦር ሜዳ ባንዲራ” ሲሆን ወታደሮቹ ጦርሜዳላይ የሚከተሉት ነው።
አህዛብንም አዘጋጁባት
የባቢሎን ከተማ እንደ ሴት መስሎአት ሲናገር የባቢሎንን ህዝብ ውጉአቸው እያለ ነው
አራራት…ሚኒን…አስከናዝ
እነዚህ የሀገራት ስሞች ናቸው
እነደ ጠጉራም ኩብኩባ ፈረሶችን በላይዋ አውጡ
እግዚአብሄር ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ ፈረሶች ከሰራዊቶች ጋር አምጡ ይላል
ነገሥታት አለቆችንም ሹማምቶችንም
ኤርሚያስ 51፡23 ተመልከት
Jeremiah 51:29
ምድር ተናወጣለች ታመመችም
“ምድር” የሚለው በባቢሎን የሚኖሩትን ህዝቦችን ሲያመለክት በባቢሎን የሚኖሩ ህዝቦች በፍርሀት እና ጭንቀትን እንደሚናወጡ ያመለክታል።
ታመመችም
ስቃይ እና የሚያስነባ ለቅሶ
በባቢሎን ላይ
ይህ በባቢሎን ያሉ ህዝቦችን ላይ መሆኑን ያመለክታል
ባድማ ያደርጋት
ምንም ህይወት አይኖርም ትጠፋለች
Jeremiah 51:30
አጠቃላይ ሀሳብ
እግዚአብሄር ገና ወደፊት የሚፈፀመውን እንደተፈፀመ አርጎ ይናገራል።
ማደሪያዎችዋም ነድደዋል መወርወሪያዎችዋም ተሰብረዋል
ከተማዋን በሴት መስሏታል
ከተማው እንደ ተያዘች…
ሙሉ ከተማዋን ጠላቶቿ አሸንፈው ያዙአት
መልካምዎችዋም እንደ ተያዙ
መልካምዎችዋም እንደ ተያዙ
መልካምዎችዋም
ከወንዝ በላይ ያለ ድልድይ
ቅጥርዋም
እርጥበት ያለበት ቦታ ላይ ሳር እና ጥልቅ የሆነ ጭቃ ሲኖር
ደነገጡ
ግራ መጋባት
Jeremiah 51:33
የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላልና
ኤርሚያስ በብዛት ይህን ሀረግ ከእግዚአብሄር የተላከ ቁልፍ መልእክት ለማሳወቅ ይጠቀማል።
የባቢሎን ልጅ ናት
ይህ የባቢሎን ህዝቦች ስም ነው።
አውድማ
እነደ አውድማ እግዚአብሄር የባቢሎን ህዝብ እንደሚቀጣ ያሳያል
አውድማ እንደ ተረገጠ ጊዜ
እግዚአብሄር የባቢሎን ልጅን እንደ ቀጣ ይናገራል
የመከር ጊዜ ይደርስባታል
“መከር” የሚለው የሰሩትን የሚያገኙበት ጊዜን ያመለክታል። ባቢሎን የሃጥያቷን ዋጋ ትቀበላለች፡
Jeremiah 51:34
አጠቃላይ ሐሳብ
እዚህ ላይ እንደ ሴት መስሎ የሚናገረው የኢየሩሳሌምን ከተማ ሲሆን የኢየሩሳሌም ከተማ ደግሞ የኢየሩሳሌምን ህዝብ ይመስላል።
ከፋፈለኝም


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የዚህ ትርጉም ይሆናል ተብሎ ሚታሰበው 1) በትክክል ማሰብ እንዳልችል አደረገኝ 2) ጎዳኝ
እንደ ባዶ ዕቃም አደረገኝ
ባቢሎን ከእስራኤል ያላትን ሁሉ ወሰደችባት
እንደ ዘንዶም
ባቢሎንን በዘንዶ ይመስላታል
ዋጠኝ
የኢየሩሳሌምን ውድቀት በመዋጥ ይመስለዋል
ከሚጣፍጠውም ምግቤ ሆዱን ሞላ
ባቢሎን በዘንዶ መስሎ ኢየሩሳሌም ያላትን በሙሉ እንደወሰዳት ከዚህ ቀደም ባለው ሃሳብ አይተናል። “ጣፋጭ ምግብ” ኢየሩሳሌም የነበራትን ጥሩ ጥሩ ነገሮች ያመለክታል
እኔንም ጣለኝ
ናቡከደነፆር የሚፈልገውን ወስዶ የማይፈልገውን ደግሞ ጣለው።
በፅዮን የምትቀመጥ
በፅዮን የምትቀመጥ
በእኔ በስጋዬ...ደሜ
እነዚህ ሀረጎች ሴትን ያመለክታል
በከለዳውያን ምድር በሚኖሩት
ከለዳውያን ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች
Jeremiah 51:36
አጠቃላይ ሐሳብ
እግዚአብሄር ለእስራኤላውያን በቁጥር 34 እና 35 ባቀረቡት ጥያቄ ምላሽን ይሰጣል
እነሆ፥ እምዋገትልሻለሁ በቀልሽንም እበቀልልሻለሁ
ፍርድቤት እንዳለ ጠበቃ እግዚአብሄር ለእስራኤላውያን ይሟገታል።
የድንጋይ ቍልልና
የድንጋይ ክምር የሆኑ ቤቶች
የቀበሮ ማደሪያ
የቀበሮ መኖሪያ
መደነቂያም
የሚያስፈራ ነገር
ማፍዋጫም
ሰዎች እጅግ በጣም የማይወዱትን ነገር በድምፅ ሚያሳውቁበት
የሚቀመጥባትም ሰው አይገኝም
ምንም አይነት ህይወት ያለው አይኖርም
Jeremiah 51:38
ያገሳሉ
ከፍተኛ የሆነ አንበሶች የሚያሰሙት ጩኸት
ያጕረመርማሉ
እንስሶች በፍራቻ ሰዓት የሚያሰሙት ድምፅ ነው
ደስ እንዲላቸው
ወታደር ጠላቶቹን ሲያሸንፍ ደስ እንደሚለው ሌላው ሊሆን የሚችለው ትርጉም ደግሞ ሰክረው ነበር
ለዘላለምም አንቀላፍተው እንዳይነቁ
ይሞታሉ
ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
እንደ ጠቦቶችና... አውራ ፍየሎችም
ጠቦት እና ፍየሎች ለመታረድ እየሄዱ ነገር ግን አያቁም ልክ እንደዚሁ ባቢሎናውያንን እግዚአብሄር እንደሚያጠፋቸው አያውቁም
Jeremiah 51:41
ሼሻክ(ባቢሎን) እንዴት ተያዘች...ባቢሎንም በአህዛብ መካከል መደነቂያ እንዴት ሆነች
“እንዴት” የሚለው ቃል በሰው አይን ከባድ የሆነ ነገር መፈፀሙን የሚያመለክት ነው። “ሼሻክ(ባቢሎን) እንዴት ተያዘች...ባቢሎንም በአህዛብ መካከል መደነቂያ እንዴት ሆነች” ይህን ሐረግ “ባቢሎን የተበላሸ እና የፈራረሰች ከተማ ትሆናለች ብለን አናስብም ነበረ” እንደማለት ነው።
የምድርን ሁሉ ምስጋና እንዴት ወሰደች
“ምስጋና” የሚለው ሰዎች የሚያመሰግኑት ሲሆን “ምድርም” ሲል በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። ይህም “በምድር ላይ ሁሉ የምትመሰገነው ባቢሎን በጠላቶቿ ተያዘች” እንደማለት ነው።
ባህር በባቢሎን ላይ ወጣ በሞገዱም ብዛት...
የባቢሎን ጠላት አሸነፉአት “በሞገዱም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ብዛት ያለው ህዝብ ሲያሸንፍ ሲሆን “ባህር” እና “ውሃ” ደግሞ በብዛት የሚያመለክተው ከተማን ወይም ሀገርን ያመለክታል።
በሞገዱም ብዛት ተከደነች
ይህ “ሞገዱ ባቢሎንን ሸፈነ ወይም ከደነ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።
Jeremiah 51:43
ከተሞችዋ
የባቢሎን ከተሞች
ቤልን እቀጣለሁ
ቤል በባቢሎን ከተማ ሙሉ የሚመለክ ጣኦት ነው።
የዋጠውንም ከአፉ አስተፋዋለሁ
የሚሰዋውን መስዋዕት በሙሉ ቤል እንደበላ እግዚአብሄር ያመለክታል።
አህዛብም ከዚያ ወዲያ ወደእርሱ አይሰበሰቡም
በተለያዩ ከተማዎች የሚገኙ አህዛቦች ወደባቢሎን መጥተው መስዋእትን መሰዋትን ያቆማሉ።
Jeremiah 51:45
በምድርም ከሚሰማ ወሬ
በምድር ላይ ወሬ ስትሰሙ በማለት መተርጎም ይቻላል።
አለቃም በአለቃ ላይ ይነሳል
አለቃ ከተማን ያመለክታል
Jeremiah 51:47
እነሆ
ተመልከቱ ወይም በማስተዋል አድምጥ
የምቀጣበት ዘመን ይመጣል
የምቀጣበት ጊዜው ይደርሳል...እቀጣለሁ ኤርሚያስ 7፡32 እንዴት እነደተረጎመው ተመልከት
የተቀረፁትን የባቢሎን ምስሎችን የምቀጣበት ዘመን ይመጣል
የተቀረፁ ምስሎችን እንደሚያጠፋ እግዚአብሄር ይናገራል።
ባቢሎን... ምድርዋም ሁሉ...ተወግተው የሞቱት ሁሉ በመካከልዋ...እንዲሁ በባቢሎን
በባቢሎን ያሉ ህዝቦችን እንደ ባቢሎን ከተማ ይመስላል የባቢሎንን ከተማ ደግሞ እንደ ሴት ይመስላል።ይህም”የባቢሎን ህዝቦች...ምድራቸውም ሁሉ...ተወግተው የሞቱት ሁሉ በባቢሎን መካከል”
ሰማይና ምድር
“ሰማይና ምድር” እነደ ሰው ይመስላቸዋል።
ይላል እግዚአብሄር
እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት
አጥፊዎች...ይመጡባታል
የባቢሎናዊያን ጠላቶች ምድሪቱን ሊያፉአት ይመጣሉ
Jeremiah 51:50
አጠቃላይ ሀሳብ
ኤርሚያስ በቁጥር 50 ላይ ለእስራኤላውያን ይናገራል
ከሰይፍ ያመለጣችሁ ሆይ
“ሰይፍ” የሚለው ወታደሮች የሚዩዝትን ሰይፍ ሲሆን ጦርነትን ያመለክታል።
እግዚአብሄርን ከሩቅ አስቡ ኢየሩሳሌምንም በልባችሁ አስቡ
“ከሩቅ አስቡ” እና “በልባችሁ አስቡ” የሚሉት ሀረጎች አስታውሱ የሚለውን ያመለክታል
ስድብን
ሰውን ሊያሳዝን እና የሚያስከፋ ቃላት
ነውር ፊታችንን ከድኖታል
ተናጋሪው የአለመቀበል ምላሹን እየተናገረ ያለው ፊቱን የሸፈነው ሸፋን እንዳለ አርጎ ነው።
Jeremiah 51:52
እነሆ
ተመልከቱ ወይም በማስተዋል አድምጥ

የምቀጣበት ዘመን ይመጣል

የምቀጣበት ጊዜው ይደርሳል…እቀጣለሁ ኤርሚያስ 7:32 እንዴት እነደተረጎመው ተመልከት

ይላል እግዚአብሄር

እግዚአብሄር ራሱን በስሙ በመጥራት ያዛል። ኤርሚያስ 1:8 ላይ እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የተቀረፁትን ምስሎችን የምቀጣበት ዘመን ይመጣል

የተቀረፁ ምስሎችን እንደሚያጠፋ እግዚአብሄር ይናገራል።

የተቀረፁ ምስሎችዋን… በምድርዋም ላይ…ባቢሎን…ከፍታ ብታፀና… ይመጡባታል

የባቢሎን ህዝቦችን እንደ ከተማ መስሎ ሲናገር ከተማዋን ደግሞ እንደ ሴት ይመስላል። "የተቀረፁ ምስሎቻቸውን…በምድራቸው ላይ…ባቢሎናውያን….ከፍታ ቢያፀኑም…ወደነሱ ይመጡባቸዋል"

ያንቋርራሉ

ከህመም እና ማዘን ብዛት የሚመጣ ለቅሶ

ባቢሎን ምንም ወደ ሰማይ ብትወጣ…ከፍታ ብታፀና… አጥፊዎች ይመጡባታል

ይህ የማይሆነውን ቢሆን እንኳን እያለ ያወራል። "ባቢሎን ወደ ሰማይ አትወጣም… ከፍታ አታፀናም… ቢሆንም ግን አጥፊዎች ከኔ ይመጡባታል"

Jeremiah 51:54

ከባቢሎን ጩኸት፥ ከከለዳውያንም ምድር የታላቅ ጥፋት ድምፅ ተሰምቶአል።

አንድ ሃሳብ በሁለት መንገድ አግንኑ ያሳያል

ባቢሎንን አጥፍቶአታልና… ከእርሷም ታላቁን ድምፅ

የባቢሎን ህዝቦችን እንደ ከተማ መስሎ ሲናገር ከተማዋን ደግሞ እንደ ሴት ይመስላል። "የባቢሎን ህዝቦችን አጥፍቶአቸዋልና… ከእነርሱም ታላቁን ድምፅ…"

ሞገዳቸውም…የድምፃቸው ጩኸት ተሰምቶአል።

"ሞገዳቸውም" የሚለው የባቢሎን ህዝብ ጠላትን ሲያመለክት "የድምፃቸው ጩኸት ተሰምቶአል" የሚለው የጠላቶቻቸውን ድምፅ ያመለክታል።

ሞገዳቸውም እንደ ብዙ ውኆች ይተምማል

ይህ ጠላቶቻቸው ልክ እነደ ውቅያኖስ እና እንደ ወንዝ ሞገድ ከፍተኛ ድምፅ እያሰሙ እንደሚመጡ ያመለክታል

በባቢሎን ላይ መጥቶባታልና…በባቢሎን ላይ… ሓያላኖችዋ

የባቢሎን ህዝቦችን እንደ ከተማ መስሎ ሲናገር ከተማዋን ደግሞ እንደ ሴት ይመስላል።

ሃያላኖችዋ ተያዙ

ጠላቶቿ ያላትን ሃያላኖችዋን ተያዙ

Jeremiah 51:57

መሳፍንቶችዋንና ጥበበኞችዋንም አለቆችዋንና ሹማምቶችዋን ሃያላኖችዋንም…ረጃጅሞችም በሮችዋ

የባቢሎን ህዝቦችን እንደ ከተማ መስሎ ሲናገር ከተማዋን ደግሞ እንደ ሴት ይመስላል። "መሳፍንቶቻቸውንና ጥበበኞቻቸውንም አለቆቻቸውንና ሹማምንቶቻቸውን ሃያላኖቻቸውንም…ረጃጅም በሮቻቸው" ብሎ ማንበብ ይቻላል።

ለዘለአለም እንቀላፍተው አይነቁም

ይሞታሉ። ኤርሚያስ 51:39 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄ እንዲህ ይላል፡-

ኤርምያስ በብዛት እግዚአብሄር የሚናገረውን ቁልፍ መልእክት ለማሳየት የሚጠቀመው ነው። ኤርሚያስ 6:6 እንዴት እንደተረጎመው ተመልከት

ሰፊው የባቢሎን ቅጥር ፈፅሞ ይፈርሳል

የባቢሎን ሰፊው ቅጥር ወራሪዎች ፈፅሞ ያፈራርሱታል

ረጃጅሞችም በሮችዋ በእሳት ይቃጠላሉ

ረጃጅም በሮችዋን በእሳት ያቃጥሉባቸዋል

ሁሉም በእሳት የደጋያል

ከተማዋ ለማድረግ የምትሞክረው በሙሉ በእሳት ይነዳል።

Jeremiah 51:59

ሠራያ…ኔርያ…መህሴያ

የወንድ ስሞች ናቸው።

በነገሰ በአራተኛው አመት

ሶስት አመት ነግሶአል ይህ አራተኛው አመቱ ነው

ስለ ባቢሎን የተፃፈው

እርሱ ስለ ባቢሎን የፃፈው

Jeremiah 51:61

እንስሳ

የቤት እንስሳን ያመለክታል ምክንያቱም ኤርምያስ 51:37 ባቢሎናውያን የቀበሮ ማደሪያ እነደሆነች ይናገራል

Jeremiah 51:63

ባቢሎን ትሰጥማለች

በዙሪያዋ፟ቿ ያሉ ድንጋዮች ከውሃ በታች ይሆናሉ ባቢሎንም ከተማ መምሰሏን ቀርቶ በውሃ ትሰጥማለች

አትነሳምም

ከተማ አትሆንም

---

Chapter 52

Jeremiah 52:1

አጠቃላይ ሐሳብ

በ ኤርሚያስ51:64 ላይ "የኤርምያስ ቃል እስከዚህ ድረስ ነው።" ብሎ ስለሚያልቅ እና በስር ያሉ ቃላቶች በሌሎች የመፅሀፍ ክፍሎች ስለሚገኙ ብዙ ምሁራን ይህ ምዕራፍ በኤርምያስ ብቻ እንዳልተፃፈ ይናገራሉ። ከዚህም ጋር በተያያዘ ኤርሚያስ እና ባሮክ እንደፃፉት ይታሰባል።

አሚጣል

ይህ የሴት ስም ነው።

ሊብና

ይህ የቦታ ስም ነው።

ኤርሚያስ

ኤርሚያስ የሚለው ስም ይህን መፅሀፍ የፃፈው ነብዩ ኤርሚያስን ሳይሆን ሌላ ኤርሚያስ የሚባል ሰውን ነው ሚያመለክተው

በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ።

"የእግዚአብሄር ፊት" የሚያመለክተው የእግዚአብሄርን ፍርድ ወይም እይታ ነው።

Jeremiah 52:4

ሴዴቅያስም በነገሠ በዘጠነኛው ዓመት በአሥረኛው ወር ከወሩም በአሥረኛው ቀን

ሴዴቅያስም ከነገስ ከስምንት አመት በአስረኛው ወር እና ወሩ ከገባ በአስረኛው ቀን

በዘጠነኛው አመት

"ዘጠነኛው አመት"

በአሥረኛው ወር ከወሩም በአሥረኛው ቀን

በእብራውያን የቀን መቁጠሪያ አስረኛው ቀን ነው። አስረኛው ቀን በፈረንጆች ቀን አቆጣጠር ጃንዋሪ የሚባለው ወር ጋር ይጠጋል።

በኢየሩሳሌም ላይ መጥተው ከበቡአት

የናቡከደነፆር ሠራዊት ኢየሩሳሌምን ከበቡአት

እስከ ንጉሡ እስከ ሴዴቅያስ እስከ አሥራ አንደኛው ዓመት

ሴዴቅያስ ከነገሰ ጀምሮ ከ አስር አመት በላይ

አስራ አንደኛው አመት

አስራ አንደኛው አመት

ከተማይቱም … ተከብባ ነበር።

ከተማይቱ በሰራዊቱ ተከብባ ነበር

Jeremiah 52:6

በአራተኛውም ወር በዘጠነኛው ቀን

በእብራውያን የቀን አቆጣጠር አራተኛው ወር ሲሆን ይህም በበጋ ወቅት ነው። ዘጠነኛው ቀንም እንደ አውሮፕያን አቆጣጠር ጁላይ ወር አካባቢ ይገኛል። ሴዴቅያስም ለ አስር አመት ሶስት ወር ስምንት ቀናት ነግሶ ነበር።

በከተማይቱ

ይህ ኢያሩሳሌም ከተማን ያመለክታል።

ከተማይቱ ተሰበረች

ባቢሎናዊያን የከተማዋን ግንብ አፈራርሰው ገቡ።

በሁለቱም ቅጥር

የንጉሱ የአትክልት ስፍራ ቅጥር እና የከተማዋ ቅጥር።

ሜዳ

ቀጥ ያለ መሬት

ሠራዊቱም ሁሉ ከእርሱ ዘንድ ተበትነው ነበር

የከለዳዊያን ሰራዊት በሙሉ ተበተኑ፣ ሙሉ ሰራዊቱ በተለያየ አቅጣጫ ተበተኑ።



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Jeremiah 52:9
በሐማት ምድር ወዳለችው ወደ ሪብላ
ሪብላ በሃማት ክልል የምትገኝ ከተማ ነች
ፍርድን በእርሱ ላይ ተናገረ
እንዴት እንደሚቀጣ ወሰነ
የሴዴቅያስን ልጆች በፊቱ ገደላቸው
“በፊቱ ገደላቸው” ሲል አይኑ እያየ ለማለት ነው። አንባቢው ጨምሮ ሊረዳው ያለበት ነገር ሌሎችም የባቢሎን ንጉስ የሴዴቅያስን ልጆች ሲገድል እጃቸው ነበረ።
የሴዴቅያስንም ዓይኖች አወጣ
የንጉሱ ሰዎች ሴዴቅያስን አይነ-ስውር አረጉት። የባቢሎን ንጉስ የሴዴቅያስን አይን ከጭንቅላቱ ማውጣቱን የሚያስረዳ ግልፅ ነገር የለም። ሌላው አንባቢው ጨምሮ ሊረዳው ያለበት ነገር ሌሎችም የባቢሎን ንጉስ የሴዴቅያስን አይን ሲያጠፋ እጃቸው ነበረ።
እስኪሞትም ድረስ
ሴዴቅያስ እከሞተበት ቀን ድረስ
Jeremiah 52:12
በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር በአሥራ ዘጠነኛው ዓመት በአምስተኛው ወር ከወሩም በአሥረኛው ቀን
ንጉስ ናቡከደነፆር ለአስራ ስምንት አመታት አራት ወር እና ለዘጠኝ ቀን ነግሶ ነበር። በእብራውያን ቀን አቆጣጠር አምስተኛው ወር ሲሆን ወቅቱም በጋ ነው። አስረኛው ቀን ደግሞ እንደ አውሮፕያውያን ቀን አቆጣጠር በነሱ ኦውገስት ተብሎ የሚጠራው ወር መጀመሪያ አካባቢ ይገኛል።
አስራ ዘጠነኛው አመት
በአስራ ዘጠነኛው አመት
ናቡከደነፆር
ይህ የሰው ስም ነው።
ዘበኞች
እነዚህ ስራቸው አንድን ነገር መጠበቅ ነው።
Jeremiah 52:15
የእጅ ጥበብ አዋቂዎች
እግዚአብሄርን ለማምለክ የሚጠቅሙ ውብ የሆኑ እቃዎችን የሚሰሩ ሰዎች ናቸው።
ናቡዘረዳን
ይህ የሰው ስም ነው
የምድርን ድሆች
“በምድር ላይ የሚኖሩ ድሆች”
Jeremiah 52:17
አንዱ ኩሬ
እግዚአብሄር የሚመለክበት የገንዳ ውሃ ነው።
Jeremiah 52:20
አሥራ ስምንት ክንድ - አሥራ ሁለት ክንድ
1 ክንድ 46 ሳንቲሜትር ርዝመት አለው። “18 ክንድ…12 ክንድ” ወይም “ወደ 8.3 ሜትር…5.5 ሜትር”
“ባዶ”
አምዶቹ ውስጣቸው ባዶ ነበሩ

Jeremiah 52:22
ጉልላት
የናሱ የላይኛው ክፍል
5 ክንድ
1 ክንድ 46 ሳንቲሜትር ርዝመት አለው።”5 ክንድ” ወይም “2.3 ሜትር”
Jeremiah 52:24
ሠራያን
የወንድ ስም ናቸው (ኤርምያስ 36፡26 ተመልከት)
በረኞች
የከተማዋን ዋና መግቢያ በር የሚጠብቁ
… ሰዎች ወሰደ
ሰዎችን ለውጊያ ወሰደ
Jeremiah 52:26
ናቡዘረዳን
የወንድ ስም ነው(ኤርምያስ 39፡9 ተመልከት)
ሪብላ
ይህ የከተማ ስም ነው።
Jeremiah 52:28
በሰባተኛው - አስራስምንተኛ- ሃያ ሶስተኛ
ተራ ቁጥሮች ናቸው
ናቡዘረዳን
የወንድ ስም ነው(ኤርምያስ 39፡9 ተመልከት)
3,023 … 832 … 745 … 4,600
“ሶስት ሺህ ሃያሶስት- ስምንት መቶ ሰላሳ ሁለት - ሰባት መቶ አርባ አምስት - አራት ሺህ ስድስት መቶ”
Jeremiah 52:31
ዮአኪን በተማረከ በሠላሳ ስድስት ዓመት
ዮአኪን ከተማረከ 36 አመታት ተቆጥረዋል
በአሥራ ሁለተኛው ወር ከወሩም በሀያ አምስተኛው ቀን
በእብራውያን ካላንደር አስራ ሁለተኛው ወር የመጨረሻው ወር ነው። ሃያምስተኛው ቀን በ ውጮቹ ማርች መሀከል ላይ ይገኛል።
እንዲህም ሆነ
ይህ ሃረግ የአንድ ታሪክ መጀመሪያን ያመለክታል
ዮርማሮዴክ
በባቢሎን ከንጉስ ናቡዘረዳን ቀጥሎ ነገሰ።
Jeremiah 52:32
በመልካምም ተናገረው
“ዮርማሮዴክ ዮአኪንን በመልካም ተናገረው”
ዙፋኑንም ከእርሱ ጋር በባቢሎን ከነበሩት ነገስታት ዙፋን በላይ አደረገለት
“ዙፋኑን ከንጉሱ ከዮርማሮዴክ ጋር አስጠጋው”
በወህኒም ውስጥ ለብሶት የነበረውን ልብስ ለወጠለት
አንባቢው ሊረዳው የሚገባው ነገር “በወህኒም ውስጥ ለብሶት የነበረውን ልብስ ለወጠለት”

---

Chapter 1
Lamentations 1:1
ብቻዋን . . . ተቀመጠች
ይሄ የሚያመላክተው የእየሩሳሌም ከተማ ባዶዋን መቅረቷን ነው፤ በቻዋን ከተቀመጠች ሴት ጋር ንጽጽርን ያደርጋል። “የተተወች ሆና ቀረች”
ተቀመጠች
“ቀረች” የሰቆቃወ ጸሓፊ የእየሩሳሌምን ከተማ በሴት ይመስላታል።
እንደ መበለት
ይህ እየሩሳሌም ያለ ከለላ እንደቀረች አድርጎ ይናገራል፤ ስጋት ውስጥ ያለች እና የተጋለጠች መበለት።
በአውራጆች መካከል ልዕልት የነበረች
እየሩሳሌም እንደ ልዕልት የተከበረች እንደነበረች ይናገራል። “በሕዝቦች መሃከል እንደ ልእልት ነበረች።”
ተገዢ ሆናለች
“ባሪያ ሆናለች” በሌላ መልኩም ሊገለፅ ይችላል። “ባሪያ ለመሆን ተገዳለች።”
እጅግ ታለቅሳለች፥ እንባዋም በጉንጭዋ ላይ አለ
ጸሃፊው እየሩሳሌምን ስሜት እንዳለው ሰው አደርጎ ይገልፃታል። ከተማዋ ሲባል ግን በውስጧ የሚኖሩ ሰዎችንም ይወክላል። “በእርሷ የሚኖሩ እጅግ ያለቅሳሉ፥ እምባቸውም በጉንጫቸው ላይ አለ።”
የሰቆቃ ድምፅ ታሰማለች ታለቅሳለች
የሰቆቃ ድምፅ ማሰማት ማለት አንድ ሰው ጮክ ብሎ ሲያለቅስ የሚያሰማው ደምፅ ነው። “ጮክ ብላ ታለቅሳለች።”
ከውሽሞችዋ ሁሉ የሚያጽናናት የለም፤ ወዳጆችዋ ሁሉ ወነጀሉአት ጠላቶችም ሆኑአት
ይህ የሚናገረው ለእየሩሳሌም ታማኝ የነበሩ አሁን ግን የከዷት የሰዎች ስብስብ እንዳለ ነው፤ እነኚህ ሰዎችም በአፍቃሪዎች እና ጓደኞች ተመስለዋል።
Lamentations 1:3
መጨነቅና ስለ ባርነት ብዛት
“በመከራና በመረገጥ ብዛት”
ይሁዳ ተሰዷል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እዚህ ጋር ይሁዳ የሚለው የሚናገረው ስለ ነዋሪዎችዋ ነው። “የይሁዳ ሰዎች ወደ ስደት ሄደዋል።” ወይንም “ የይሁዳ ሰዎች ወደ ባዕድ ሃገር ተወስደዋል።”
ትኖራለች. . .ተቀመጠች
እዚህ ጋር ይሁዳ በሴት ትመሰላለች። “እርሷ” የሚለው የይሁዳ ነዋሪዎችንም ያመላክታል። “ህዝቦቿ ይኖራሉ. . . ይቀመጣሉ።“
የምታርፍበት ቦታ አጣች
”አላረፈችም“ ወይንም ”ሁልግዜ በፍርሃት ውስጥ ነች።“
በጭንቀቷ መካከል ሳለች አሳዳጆቿ ሁሉ አገኟት።
ይህ የሚናገረው የይሁዳ ሰዎች አንዲት ሴት በሚያሳደዷት እና በሚፈልጓት ሰዎች እንደምትያዝ ተያዙ የሚለውን ነው።
አሳዳጆቿ ሁሉ አገኟት።
“ያሳድዷት የነበሩ ሁሉ ሊይዟት ቻሉ።” ወይንም “ያድናት የነበሩ ሁሉ አገኟት።”
በጭንቀቷ መካከል
“ጭንቅ” የሚለው ቃል በሌላ መልኩ ሲገለጥ፤ “የሚያስጨንቁአት ሁሉ ተጨንቃ አገኙአት”
Lamentations 1:4
የጽዮን መንገዶች ያለቅሳሉ
ወደ ጽዮን የሚወስዱ መንገዶች ሰው እንደሚያለቅስ ያለቅሳሉ ይላል።
በዓላቷን ለማክበር
“እግዚአብሔር እንዲያከብሩ የነገራቸው በዓላት።”
በበሮቿ የሚገባና የሚወጣ የለም
“እርሷ” የሚለው ጽዮንን ያመላክታል። “የጽዮን ደጆች ባዶ ናቸው።”
ደላግሏ ክፉኛ አዝነዋል፤ እርሷም በምሬት ትሰቃያለች።
የጽዮን ሕዝቦች ስቃይ እንደ ሴት ልጅ ስቃይ ተገልጿል። “ደናግሎችዋም ተጨነቁ እርስዋም በምሬት አለች”
ባላጋሮቿ ገዦቿ ሆኑ፤ ጠላቶቿ ተመችቶአቸዋል።
“አስጨናቂዎችዋ ራስ ሆኑ ጠላቶችዋም ተከናወነላቸው፤”
ከኀጢአቷ ብዛት የተነሣ፤ እግዚአብሔር ከባድ ሐዘን አምጥቶባታል።
ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር ስለ ጽዮን ሕዝቦች በደል ሲል ሴት ልጅን እደሚቀጣ ጽዮንን እደቀጣ ነው። “ስለ ኃጢአትዋ ብዛት እግዚአብሔር አስጨንቆአታል”
ልጆችዋ በጠላት ፊት ተማርከው፤ ወደ ግዛት ሄደዋል።
“ተማርከው” የሚለው ቃል በግስ መልኩም ሊገለጽ ይችላል። “ሕፃናቶችዋ በአስጨናቂዎች ፊት ተማርከዋል”
Lamentations 1:6
የጽዮን ሴት ልጅ፡ ግርማ ሞገሷ ሁሉ ተለይቶአታል።
ይህ የአንድ ሰውን ውበት በሚመስል መልኩ በጽዮን የነበረው ውብ ነገር ሁሉ እንደ ጠፋ ይናገራል። “ከጽዮን ሴት ልጅ ውበትዋ ሁሉ ወጥቶአል”
የጽዮን ሴት ልጅ
ይህ በዘይቤአዊ አገላለፅ የእየሩሳሌምን ስም እንደ ሴት ሲመሰል ነው።
መሳፍንቶቿ መሰማርያ እንዳጣ ዋልያ ናቸው።
ይህ የጽዮንን መሳፍንቶች የሚበላውን ሳር እንዳጣ ዋልያ የገልፃቸዋል። “አለቆችዋ ማሰማርያ እንደማያገኙ ዋላዎች ሆኑ”
ዋልያ
ዋልያ መካከለኛ መጠን ያለው፤ ሳር በል፤ በሰዎች ለምግብነት የሚታደን እንስሳ ሲሆን፤ ለማየትም የሚማርክ እንስሳ ነው።
በድካም ሸሹ
“ተዳክመው ሄዱ” ወይንም “ለመሮጥ እንኳን የበረቱ አይደሉም።
አሳዳጆቻቸው
“ከሚያባርሩአቸው ፊት”
Lamentations 1:7
በተጨነቀችባቸውና በተንከራተተችባቸው ቀናት
“በጭንቀትዋና በመከራዋ ወራት”
ኢየሩሳሌም . . . ታስባለች፤
እዚህ ግር “እስራኤል” የሚለው በውስጧ የሚኖሩትን ሕዝቦች ነው። “ታስባለች” የሚለው ገላጭ ነው። “ኢየሩሳሌም . . . አሰበች”
የከበረን ነገር ሁሉ
ዋጋ ያላቸውን “ሀብት” ያመላክታል። በጭንቀትዋና በመከራዋ ወራት የነበረላትን
ከጥንት ጀምሮ
“በጥንት ዘመን” ይህ የሚያመላክተው እስራኤላውያን ከመማረካቸው በፊት ያለውን ነው። “ይህ መከራ ከመድረሱ በፊት”
ሕዝብዋ በአስጨናቂዎች እጅ በወደቀ ጊዜ የሚረዳትም በሌላት ጊዜ
”እጅ“ የሚለው ቃል የጠላቶችዋን መያዝ ያሳያል። “ሕዝቦቿ በጠላት እጅ በወደቁ ጊዜ፣ የረዳት ማንም አልነበረም”
አስጨናቂዎች አዩአት በመፍረስዋም ሳቁ
ይህ የሚያመላክተው በእየሩሳሌም መፍረስ መሳለቃቸው እና መደሰታቸውን ነው።
በመፍረስዋም
”መፍረስ“ የሚለውን ቃል እንደ ግስ ልንጠቀመው እንችላለን። “በመፈራረሷ“ ወይንም “በሚያፈራርሷት ወቅት”
Lamentations 1:8
ኢየሩሳሌም እጅግ ኃጢአት ሠርታለች፤ ስለዚህ ረክሳለች።
ይህ ስለእየሩሳሌም እድፈት ሲናገር ከሴት ልጅ የወር አበባዋን የምታይበትን ወቅት አንፃር ይናገረዋል። በሙሴ ሕግ መሰረት፤ የኢየሩሳሌም እድፈት ከሴት ልጅ የወር አበባ እድፈት ትይዩ ይታያል። “ኢየሩሳሌም ከባድ ኀጢአት ሠርታለች፤ ስለዚህም የረከሰች ሆናለች”
ኢየሩሳሌም እጅግ ኃጢአት ሠርታለች፤
ይህ ክፍል እየሩሳሌምን በሴት ይመስላል፤ ክፍሉም እስራኤላውያንን ይወክላል። “የኢየሩሳሌም ሠዎች ከባድ ኀጢአት ሠርተዋል”
ረክሳለች
“እየረከሰች ነው” ተብሎም ሊገለፅ ይችላል።
ኀፍረተ ሥጋዋ
“ዕራቍቷ” በዚህ ክፍል እየሩሳሌምን ኀፍረተ ሥጋዋ በተጋለጠባት እና በተዋረደች ሴት ይመስላታል።
አደፍዋ በልብስዋ ዘርፍ ነበረ
በሙሴ ሕግ መሰረት፤ ሴት ልጅ የወር አበባዋን የምታይበትን ወቅት እንደ እድፈት ይታያል። ይህንንም የኢየሩሳሌም እድፈት ከሴት ልጅ የወር አበባ አንፃር ይናገረዋል።
“ርኵሰቷ በቀሚሷ ላይ ታየ“
አደፍዋ
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ መልኩ ተቀባይነት የሌለው ወይንም የተበላሸ ሰውን፤ በአካሉ እንደ ቆሸሸ የገልፀዋል።
አወዳደቋ አስደንጋጭ ሆነ
”አወዳደቋ“ የሚለው ቃል ዘይቤአዊ ቃል ነው
አቤቱ . . . መከራዬን ተመልከት
ሊሆን የሚችሉት ትርጓሜዎች፤ 1 እዚህ ጋር የሰቆቃወ ጸሓፊ በቀጥታ እግዚአብሔርን ያናግራል። ወይንም 2 ኢየሩሳሌም ሰው እግዚአብሔርን እንደሚያናግር ስታወራ ተገልፃለች።
ተመልከት
“ልብ በል”
ጠላት ከፍ ከፍ ብሎአል
ይህ የሚያመላክተው የጠላት ሠራዊት በጣም እንደበዛ እና እንዳየለ፤ ኢየሩሳሌምንም እንዳሸነፈ ነው። “ጠላት ድል አድርጎአልና”
Lamentations 1:10
እጁን ዘረጋ
ይህ ዘይቤአዊ አባባል ሲሆን፤ “ወሰደ” ወይንም “ሠረቀ”
በከበረ ነገርዋ
ይህ የሚያመላክተው የከበረ ሃብቷን ነው።
አይታለች
“እርሷ” የሚለው እየሩሳሌምን ነው።
አሕዛብ
ይህ የተለያዩ ሌላ ህዝቦችን ያመላክታል፤ እንጂ በዛ የሚኖሩትን ሕዝቦች በሙሉ ማለቱ አይደለም።
ያዘዝሃቸው
አንተ የሚለው ቅላፄ ለእግዚአብሔር የተጠቀሰ ነው።
Lamentations 1:11
እንጀራ
ይህ በአጠቃላዩ ስለ ምግብ ይናገራል። “ምግብ”
የከበረ ሀብታቸውን ስለ መብል ሰጥተዋል
ይህ የሚያሳየው ሀብታቸውንና ንብረታቸውን ለምግብ ለውጠዋል። “የከበረ ሀብታቸውን በምግብ ይለውጣሉ”

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የከበረ ሀብት

ዋጋ ያለውን ንብረት ያመላክታል።

ሰውነታቸውን ለማበርታት

”በሕይወት ለመኖር“ ወይንም “ጉልበታቸውን ለመመለስ”

አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፤ አስበኝ፤ ተመልከተኝም

እዚህ ጋር እስራኤል በቀጥታ እግዚአብሔርን ታናግራለች።

እናንት መንገድ ዐላፊዎች ሁሉ፤ ይህ ለእናንተ ምንም አይደለምን?

ይህ በእየሩሳሌም ጎን ለሚያልፉ እና ለማይገዳቸው ሰዎች እንደ ክስ የሚቀርብ አባባል እንጂ መልስ የሚጠበቅለት ጥያቄ አይደለም “እናንተ መንገድ አላፊዎች ሁሉ፥ በእናንተ ዘንድ ምንም የለምን?”

ለእናንተ ምንም አይደለምን

አሁንም ኢየሩሳሌም ትናገራልች፤ የማትናገረው ግን ለእግዚአብሔር ሳይሆን በጎን ለሚያልፉ ሰዎች ነው።

ተመልከቱ፥ እዩ

እነኚህ ቃላት በትርጉም ተመሳሳይ ሲሆኑ፤ በአንድ ላይ አንባቢውን አይቶ ማንም ብዙ እንዳልተጎዳ እንዲረዳ ይጋብዛል።

በእኔ ላይ እንደ ተደረገው እንደ እኔ መከራ

አሁን እየሆነ እያለ ተደርጎም ሊገለፅ ይችላል፤ “እግዚአብሔር በእኔ ላይ እያመጣ ያለው መከራ።”

በጽኑ ቍጣው ቀን

እዚህ ጋር “ቀን” የሚለው ዘይቤአዊ ገላጭ ነው።

Lamentations 1:13

ከከፍታ

ይሄ ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “ሠማይ”

እሳትን ወደ አጥንቴ ሰደደ በረታችበትም

ይህ እግዚአብሔር እስራኤልን ሰውን በእሳት እንደሚቀጣ እየቀጣ እንደሆነ ያመላክታል። “ህመም ያለበትን ቅጣት ወደ ውስጥ ሰውነቴ ልኳል፤ እርሱም አጥፍቶኛል“ ወይንም “እርሱ የጥፍት ቅጣትን ወደ መሃል እስራኤል ልኳል፤ ከተማዋንም አፈራርሷታል”

እሳትን ወደ አጥንቴ ሰደደ

እዚህ ጋር “እሳት” ህመምን ይወክላል “አጥንትም” የውስጥ ሰውነትን። “ወደ አጥንቴ ህመምን ልኳል” ወይንም “ወደ ውስጥ ሰውነቴ ህመምን ልኳል”

ለእግሬ ወጥመድ ዘረጋ

ይሄ የሚያመላክተው የእግዚአበሔር እስራኤልን እንደሰው ውጠመድን በማዘጋጀት መቅጣት ነው። ብዚውን ግዜ እንስሳት ለማጥመድ የሚጠቀሙበትን ዓይነት ወጥመድ።

ወደ ኋላም መለሰኝ

ይሄ ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “አልፎ ከመራመድ ከለከለኝ”

የኃጢአቶቼ ቀንበር በእጁ ተይዛለች፤ ታስረው በአንገቴ ላይ ወጥተዋል

x

Lamentations 1:15

ኃያላኖቼ

“እጅግ ጠንካራዎቹ ወታደሮች”

ጉባኤን

እስራኤልን ሊወጋ የመጣው ሰራዊት የተገለጸው አንድን ሰው ሊከሱ እና ሊኮንኑ በአንድ ላይ እንደተሰበሰቡ ሰዎች ነው። “ታላቅ ሰራዊት”

ጕልማሶቼን ያደቅቅ ዘንድ

ይህ የሚናገረው የጠላት ሰራዊት የእስራኤልን ሰራዊት የማድቀቅ ያህል እንደረታ ነው። “ጕልማሶቼን ይረታ ዘንድ”

ጕልማሶቼን

በጉብዝና ወቅታቸው ላይ ያሉ ወንዶች።

ጌታ . . . በመጥመቂያ እንደሚረገጥ አድርጎ ረገጣት

የእግዚአብሔር ቅጣት የተመሰለው፤ በመጠመቅያ ውስጥ የወይንን ጭምቂ ለማውጣት ውይንን በሚረግጥ ሰው ነው። “እግዚአብሔር በወይን መጭመቂያ ውስጥ ረገጣት”

ድንግሊቱን የይሁዳን ልጅ

ይህ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም አገላለፅ ሲሆን፣እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል።

Lamentations 1:16

ሊያጽናናኝ የቀረበ፣ መንፈሴንም ሊያረጋጋ የሞከረ ማንም የለም

እየሩሳሌም ተሚያጽናናት እንደሌለ እና ቢኖርም ይረዳት ዘንድ በአካባቢው እንደሌለ “ነፍሴንም የሚያበረታት፤ መንፈሴን የሚያረጋጋ”

መንፈሴንም ሊያረጋጋ

“ነፍሴንም የሚያበረታት”

ጽዮን እጆቿን ዘረጋች

ጸሓፊው እየሩሳሌምን በሦስተኛ ወገን በሴት የመስላታል። “እየሩሳሌም እጆችዋን እርዳታ ፍለጋ ዘርግታለች።

በያዕቆብ ዙሪያ ያሉትን

“በያዕቆብ ዙሪያ ያሉት ሰዎች” ወይንም “በያዕቆብ ዙሪያ ያሉ አሕዛብ”

በያዕቆብ ዙሪያ ያሉትን እንዲያስጨንቁት አዘዘ

እዚህ ጋር ያዕቆብ የሚለው የሚያመላክተው ከእርሱን ትውልድ ነው። “በያዕቆብ ዘር ዙሪያ ያሉት ጠላቶቻቸው ሳይሆኑ አይቀርም”

ርኩስ

በመንፈሳዊ መልኩ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ወይንም ሰወነቱ እንደ ቆሸሸበት ሰው የቆሸሸ።

Lamentations 1:18

እግዚአብሔር ጻድቅ ነው

ይህ የሚያመላክተው እግዚአበሔር የደረገውን ነገር ሲሆን፤ ያደረገውንም የደረገው ፃድቅ ስለሆነ ነው። “እግዚአበሔር የደረገውን ከፅድቁ ተተነሳ አደረገ” ወይንም ”እግዚአበሔር ያደረገው ትክክል ነው።“

መከራዬንም ተመልከቱ

“መከራዬ” የሚለው ቃል “ሃዘን” መሚለው ሊገለፅ ይችላል። “ምን ያህል እንዳዘንኩኝ ተመልከት”

ደናግሎቼና ጐበዛዝቴ ተማርከው ሄዱ

እዚህ ጋር ከእየሩሳሌም በምርኮ የተወሰዱት ሁሉ የተወከሉት “ደናግሎቼ” እና “ጐበዛዝቴ” በሚለው ነው። “አብዛኞቹ ሕዝቦቼ፤ ደናግሎቼ እና ጐበዛዝቴን ጨምሮ በምርኮ ተወሰዱ።”

ጐበዛዝቴ

ይህ የሚያመላክተው በዘመናቸው ጉብዝና ዘመናት ያሉትን ወንዶችን ነው።

ወዳጆቼን ጠራኋቸው

“ወዳጆቼን እንዲረዱኝ ተጣራሁ” ወይንም “ውሽሞቼን ለዕርዳታ ተጣራሁ”

እነርሱም አታለሉኝ

ይህ የሚያመላክተው መክዳታቸውን ነው። “እነርሱ ግን ከዱኝ”

ሰውነታቸውን ያበረቱ ዘንድ

“ሕይወታቸውን ለማትረፍ” ወይንም “ጉልበታቸውን ለመመለስ”

Lamentations 1:20

አቤቱ፥ ተጨንቄአለሁና፥ ተመልከት

እየሩሳሌም ስለራሷ እንደሴት ሆና መናገሯን ቀጥላለች። እዚህ ጋር ድግሞ እግዚአብሔርን በቀጥታ ታዋራዋለች።

አንጀቴም ታውኮብኛልና

“መታወክ” የሚለው ቃል የሚያመላክተው የሚረብሽ እንቅስቃሴን ሲሆን። ይህም በቀጥታ የአንጀትን መንቀሳቀስ ለማመላከት ሳይሆን በሴት የተመሰለችው እየሩሳሌም እየተሰማት ያለውን ስሜት ለማሳየት ነው። “ውስጤን ይቆርጠኛል” ውይንም “ሆዴን ያመኛል”

ልቤ በውስጤ ተገላበጠብኝ

በእየሩሳሌም የተመሰለችው ሰው፤ ስሜቷን ለመግለፅ ወደ “ልቧ” ታመላክታላች። “ልቤ ተሰብሯል” ወይንም “እጅጉን አዝኛለሁ”

በውጭ ሰይፍ ይፈጀል

“ሰይፍ” የሚለው የሚያመላክተው ጠላትን ነው። ”ሰይፍ ልጆቼን አጠፋ”

በቤትም ሞት አለ

ሊሆን የሚችሉት ትርጉሞች 1 “በቤት ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ እየሞቱ ነው” ውይንም 2 “የሞቱት ሰዎች በቤት ውስጥ ተደርገዋል”

Lamentations 1:21

እኔ እየጮኽሁ እንደማለቅስ ሰምተዋል

“ሰዎች የሥቃይ ልቅሶዬን ሰሙ” እየሩሳሌም በሴት ተመስላ መናገርዋን ቀጥላለች።

አንተ አድርገኸዋል

“አንተ” የሚለው የሚያመላክተው እግዚአብሔርን ነው።

የተናገርኸውን ቀን ታመጣለህ

“ቀን” የሚለው ዘይቤአዊ ገላጭ ሲሆን፤ የሆነ ክስተትን ያመላክታል። “ቃል እንደ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ገባኸው አድርገሃል።”
እነርሱም እንደ እኔ ይሆናሉ
እስራኤል መከራን እንደተቀበለች የእስራኤል ጠላቶችም መከርን እንዲቀበሉ የቀረበ ጥያቄ ነው። “እነርሱም እንደ እኔ ይሁኑ”
ክፋታቸው ሁሉ ወደ ፊትህ ይድረስ
ይህ እግዚአብሔር የእስራኤል ጠላቶች ላይ ስለ ክፋታቸው እንዲፈርድ የቀረበ ጥያቄ ነው። “ወደ ፊትህ ይድረስ” የሚለው ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “ያደረጉትን ክፋት ሁሉ ልብ በል” ወይንም “ስለክፋታቸው ሁሉ ፍረድባቸው።”
ስለ ኃጢአቴ ሁሉ እንዳደረግህብኝ አድርግባቸው
ይህ እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝቦችን እንደቀጣ ጠላቶቻቸውን እንዲቀጣ የቀረበ ጥያቄ ነው። ”በእኔ ላይ እንዳደረግኽብኝ፣በእነርሱም ላይ አድርግባቸው“
ልቤም ደክሞአል
እዚህ ጋር “ልብ” የሚለው ሙሉ ሰውን ያመላክታል። “ደክምያለሁ”

Chapter 2

Lamentations 2:1

ጌታ በቍጣው የጽዮንን ሴት ልጅ እንደ ምን አደመናት
እግዚአብሔር ለእየሩሳሌም ያለውን ቁጣ በጥቁር ደመና ይመስለዋል። ሊኖሩት የሚችሉት ትርጉሞች፤ 1 እግዚአብሔር በእየሩሳሌም ባሉ ሰዎች ላይ ጥፋትን እንደሚያመጣ እየዛተ ነው ወይንም 2 እግዚአብሔር ሐዝቦቹ ላይ ጥፋትን አምጥቷል
የጽዮንን ሴት ልጅ ... የይሁዳን ሴት ልጅ
እነኚህ ለእየሩሳሌም የተሰጡ ቅኔአዊ ስሞች ሲሆኑ፤ በሴትም መስሏቸዋል።
የእስራኤልን ውበት ከሰማይ ወደ ምድር ጣለ
“የእስራኤል ውበት” የሚለው እየሩሳሌምን ነው። በእስራኤል ያሉ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን እንዳጡ፤ እናም እርሱ ከመገኘቱ አውጥቶ እንደጣላቸው ይናገራል። “ከሰማይ ወደ ምድር” የሚለው የሚያሳየው በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ያህል ሞገስን እንዳጡ ነው። “የእስራኤል ውበት የሆነችው እየሩሳሌም በእግዚአብሔር ፊት ሁሉንም ሞገስን አጥታለች” ወይንም “እየሩሳሌም ሁሉንም ሞገስዋን በእግዚአብሔር ፊት አጥታለች“
የእግሩን መረገጫ አላሰበም
ከዚህ በፊት እግዚአብሔር እየሩሳሌምን “የእግሩ መረገጫ” ብሏት እንደሚያውቅ ሲያመላክት፣ የሚወክለውም በእነርሱ ላይ የነበረውን ሥልጣን እና እነርሱም መገዛታቸውን ነው። እግዚአብሔር የእየሩሳሌምን የእግር መረገጫነት መርሳቱን እና መሻሩን ያመላክታል። “እየሩሳሌም የእግሩ መቀመጫ ከመሆን ሽሯታል።
አላሰበም
እግዚአብሔር እየሩሳሌምን የረሳት ያህል ችላ እንዳላት ያመላክታል። “ችላ ብሏታል” ወይንም “ትኩረት አልሰጣትም።
በቍጣውም ቀን
እዚህ ጋር ቀን የሚለው የተወሰነን የግዜ ክፍልን የሚያመላክትበት ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “ቍጣውን በሚገልጽበት ግዜ . . . በቍጣውም ግዜ” ወይንም “ቁጣውን በሚያሳይበት ግዜ. . . በቁጣው ግዜ”
ዋጠ
እግዚአብሔርን በሚባላ እንስሳ መስሎ ከተማይቷን ፈጽሞ እንዳጠፋት የሚያሳይበት መንገድ ነው። “ፈጽሞ አጥፍቷት”
የያዕቆብን ማደሪያዎች ሁሉ
እዚህ ጋር “የያዕቆብ ማደሪያዎች” የሚለው በከተማው ይኖሩ የነበሩ የእርሱን ትውልዶች ያሳያል።
በመዓቱ የይሁዳን ሴት ልጅ አምቦች አፈረሰ
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 በይሁዳ የፈራረሱ ከተሞች 2 የፈራረሱ የእየሩሳሌም ቅጥሮ ች።

Lamentations 2:3

በጽኑ ቍጣው የእስራኤልን ቀንድ ሁሉ ቀጠቀጠ
ይሄ የሚናገረው እግዚአብሔር የእስራኤልን ቀንድ ሰበረ የሚለው ኋይሏን ወሰደ እንደማለት ነው። “ቀንድ” የሚለው የእንስሳን ቀንድ ነው። “የእስራኤልን ጉልበት ወሰደ”
ቀኝ እጁን ከጠላት ፊት ወደ ኋላ መለሰ
እዚህ ጋር የእግዚአብሔር “ጠበቃ በቀኝ እጁ” የወከላል፤ “እግዚአብሄር እኛን መጠበቅ አቁሟል”
በዙሪያውም እንደሚባላ እንደ እሳት ነበልባል ያዕቆብን አቃጠለ
በእሳት የተቃጠለ ያህል እግዚአብሔር በቁጣው ያዕቆብን አጥፍቷል። “በእሳት እንደሚቃጠል እግዚአብሔር በቁጣው ያዕቆብን አጥፍቷል።”
ያዕቆብ
“ያዕቆብ” የሚለው የእርሱ ትውልዶች የሚኖሩበት ነው። “እስራኤል”
ቀስቱን እንደ ጠላት ገተረ፥ እንደ አስጨናቂ ቀኝ እጁን አጸና
አንድ ወታደር ቀስቱን ለመወንጨፍ መገተር ይኖርበታል፤ እናም እዚህ ጋር እግዚአብሔር እስራኤልን ለመውጋት እየተዘጋጀ እንደሆነ ይገልፃል። “እንደ ጠላት ቀስቱን ገተረ፤ ቀኝ እጁ ተዘጋጅታለች”
በጽዮን ሴት ልጅ ድንኳን
“የጽዮን ሴት ልጅ” የእየሩሳሌም ዘይቤያዊ ሰም ሲሆን፣ በሴትም ይመስላታል። “በጽዮን ሴት ልጅ ድንኳን” የሚለው እየሩሳሌምን እንደድንኳን ሲገልፃት ሰዎቻቸው እንደዛ እንዲሚኖሩ ያሳያል። “በእየሩሌም የሚኖሩት”

Lamentations 2:5

ዋጠ
እግዚአብሔርን በሚባላ እንስሳ መስሎ ከተማይቷን ፈጽሞ እንዳጠፋት የሚያሳይበት መንገድ ነው።
አዳራሾችዋን ... አምቦችዋን
እስራኤልን በሴት ይመስላታል
በይሁዳም ሴት ልጅ ኀዘንና ልቅሶ አበዛ
“ኀዘን”ና “ልቅሶ” የሚሉትን ቃላት በድርጊት መልኩ ሊገለፁ ይችላሉ። “የይሁዳ ሴት ልጆች ብዙ እንዲያዝኑ እና እንዲያለቅሱ ብዙ ብዙ አድርጓል።”
በይሁዳም ሴት ልጅ
ይሄ ቅኔአዊ በሴት የተመሰለ የእየሩሳሌም ስም ነው። “ይሁዳ”
ማደሪያውን እንደ አትክልት ስፍራ ባዶ አደረገ
ማደርያው እንደ አትክልት ሥፍራ በቀላሉ መነቀሉን ያሳያል። እግዚአብሔር የእስራኤል ጠላቶች እንዲያጠፉት ፈቀደ። እርሱ እራሱ አይደለም ያጠፋው። “ጠላቶቻቸው ማደሪያውን በቀላሉ እንደ አትክልት ሥፍራ እንዲጠፋ ያደረገው እርሱ ነው“
አትክልት ስፍራ
ትንሽ የአትክልት እና እርሻ ሥራ መስሪያ ዕቃዎች ማስቀመጫ ወይንም የሰራተኛው መጠለያ።
የበዓሉን ስፍራ አጠፋ
እግዚአብሔር የእስራኤል ጠላቶች እንዲያጠፉት ፈቀደ። እርሱ እራሱ አይደለም ያጠፋው። “የበዓሉን ስፍራ እንዲጠፋ ያደረገው እርሱ ነው” ወይንም “የእስራኤል ጠላቶች የበዓሉን ስፍራ እንዲያጠፉት ፈቀደ”
በጽዮን ዓመት በዓሉንና ሰንበቱን አስረሳ
በቀጠታ መልኩ መገለፅ ይችላል። “የጽዮን ሕዝብ በዓሉንና ሰንበቱን እንዲረሱ አደረጋቸው”
በጽኑ ቍጣው
“በእነርሱ ላይ እጅጉን ስለተቆጣ”

Lamentations 2:7

የቤተ መንግሥቶቿን ቅጥሮች፣ ለጠላት አሳልፎ ሰጠ
ለጠላት የሚለው ወደ ጠላትእጅ ታልፎ መሰጠትን የመላክታል። “እግዚአብሔር ጠላቶቻቸው የቤተመንግስቶቿን ቅጥር እንዲይዙ ፈቅዷል”
የቤተመንግሥቶቿን ቅጥሮች
“እሷ” የሚለው የሚናገረው ሰል ማደሪያው ወይንም ስለ እየሩሳሌም ነው። 1 “የማደሪያው ቅጥሮች” ወይንም 2 “የእየሩሳሌም ቤተመንግስቶች ቅጥር” “ቅጥር” የሚለው ቃል ለሙሉ ሕንፃው ምትክ ሲሆን ሕንፃው ደግሞ ለሙሉ እየሩሳሌም።
በዓመት በዓል ቀን እንደሚደረገው በእግዚአብሔር ቤት በጎይል ጮኹ
ይሄ ምፀታዊ የእስራኤል ደስታ፣ በዓል ማክበር እና የባቢሎናውያን የድል ጩኸት ንፅፅር ነው። “በእግዚአብሔር ቤት ድምጻቸውን ከፍ አደረጉ፤ እስራኤላውያኑ በበዓላቸው ያደርጉት እንደነበረ”
በጎይል ጮኹ
ይህ ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “ባማየል ጮኽ”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

## Lamentations 2:8

በጽዮን ሴት ልጅ ዙሪያ ያለውን ቅጥር፣ እግዚአብሔር ለማፍረስ ወሰነ

እግዚአብሔር የእየሩሳሌም ጠላቶች ቅጥሮቿን እንዲያፈርሱ መረጠ። እርሱ እራሱ ግን አላጠፋትም።

በጽዮን ሴት ልጅ

ይህ በቅኔአዊ አገላለፅ የእየሩሳሌምን ስም እንደ ሴት ሲመሰል ነው።

የመለኪያ ገመድ ዘረጋ

ከማጥፋቱ በፊት ቅጥሯን ምን ያህል እንደ ሚያፈርሰው ለማወቅ እንደሚለካ ሰው ይናገራል። “ቅጥሯን እንደለካ ሰው”

ከማጥፋትም እጆቹን አልሰበሰበም

ያለ ሁለት አሉታዊ አገላለፅ ለዘገብም ይችላል። ብሎም እግዚአብሔር የተመሰለው በእጆቹ ነው። “በእጆቹ ቅጥሮቿን አፍርሷል” ወይንም “ቅጥሮቿን አፍርሷል”

ምሽጎችና ቅጥሮች እንዲያለቅሱ አደረገ ፤ በአንድነትም ጠፉ

ምሽጎቿና ቅጥሮቿ በሰው ተመስለው፣ እንዳለቀሱ እና እንደሞቱ አድርጎ ይናገራል። “ምሽጎችና ቅጥሮቿን ስላጠፋ፤ አልቅሰው እንደደከሙ ሰዎች ሆነዋል“

ምሽጎች

ጥንታዊ ከተሞች ከአጥቂዎች የሚለይ ዋና “ቅጥር” ነበራቸው በውጪም በኩል ከ ቅጥሩ የሚከለክል ምሽግ።

## Lamentations 2:10

የጽዮን ሴት ልጅ

ይሄ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን ፣ እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል።

ዝም ብለው በመሬት ላይ ተቀምጠዋል

ብዙ ግዜ ሰዎች በመንገድ ዳር የሚቀመጡት ሃዘን ላይ ሲሆኑ ነው። “አዝነው በጸጥታ መንገድ ላይ ተቀምጠዋል”

ትቢያን በራሳቸው ላይ ነሰነሱ

ይሄ የማልቀስ እና የማዘን ምልክት ነው። “ሃዘናቸውን ለማሳየት በራሳቸው ላይ ዐመድ ነስንሰው እና ማቅ ለብሰው”

ራሳቸውን ወደ ምድር አዘነበሉ

ይሄ የማዘን ምልክት ነው። “በአዘኔታ አንገታቸውን ወደ መሬት አቀርቅረው”

## Lamentations 2:11

ዐይኔ በለቅሶ ደከመ

ይሄ ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። “ማልቀስ እስከማልችል ድረስ አለቀስኩ”

አንጀቴም ታወከ

“መታወክ” ማለት በኋይል መንቀሳቀስ ማለት ነው፤ ብዙውን ግዜ በክብ መሸከርከር ነው። አንጀቱ የእውነትም ተሸከርክሯል ማለት አይደለም ነገርግን ጸሓፊ የተሰማው ስሜት ነው። “ ”ጎኔን አመመኝ” ወይንም “ሆዴን አመመኝ”

ጉበቴ በምድር ላይ ተዘረገፈ

ጸሓፊው በውስጥ ሰውነቱ የተሰማውን ሃዘን፤ የውስጥ ክፍሎቹ መሬት ላይ የተዘረገፉበት ያህል እንደሆነ ይናገራል። “መላ ሰውኔቴ ሃዘን ላይ ነው”

ስለ ወገኔ ሴት ልጅ

ይሄ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን ፣ እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል።

እህልና የወይን ጠጅ ወዴት አለ?

ይሄ መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ ዓይነት ሲሆን፤ የሚበላን መፈለግ ላይ ያተኩራል። ልጆቹ ለእናታቸው ምግብ እንደሚፈልጉ እየተናገሩ ነው። እህልና የወይን ጠጅ የ ሚለው የ ሚያሳየው ምግብ እና መጠጥን ነው። ጥያቄው በሌላ መልኩ ሊጻፍ ይችላል። “የምንበላውን እና የ ምንጠጣውን ስጡን”

እንደ ተወጋ ሰው በዛሉ ጊዜ

ከረሃብ የተነሳ ሕፃናቱ እንደቆሰለ ሰው ዝለዋል።

ነፍሳቸውም በእናቶቻቸው ብብት በወጣች ጊዜ

የሕፃናቶቹን መሞት እንደሚፈስ ፈሳሽ ይመስለዋል። “በእናታቸው እጅ ቀስ ብለው ይሞታሉ”

## Lamentations 2:13

የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ ሆይ፥ ምን እመሰክርልሻለሁ?

እየሩሳሌምን ለመርዳት ምን ማድረግ እንዳለበት እንዳላወቀ ለማስታወቅ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው እንጂ መልስ የሚጠይቅበት ጥያቄ አይደለም። ጥያቄ ባልሆነ መልኩ ሊጻፍም ይችላል፤ “ልለው የምችለው ነገር የለም. . . እየሩሳሌም”

የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ ... ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ ሆይ

ይሄ ቅኔ አዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን ፣ እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል። “ጽዮን” ሌላው የእስራኤል ስም ነው

በምንስ እመስልሻለሁ? ድንግሊቱ የጽዮን ልጅ ሆይ

እየሩሳሌምን ለማጽናናት ምን ማድረግ እንዳለበት እንዳላወቀ ለማስታወቅ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው እንጂ መልስ የሚጠይቅበት ጥያቄ አይደለም። ጥያቄ ባልሆነ መልኩ ሊጻፍም ይችላል፤ “ላወዳድርሽ የምችለው ነገር የለም. . . ጽዮን ሆይ”

ስብራትሽ እንደ ባሕር ታላቅ ነው

ባህር ታላቅ እንደ ሆነ የእየሩሳሌምም ስብራት እና ሰቆቃ እንዲሁ ነው። “ጉዳትሽ እንደ ባህር ታላቅ ነው”

የሚፈውስሽ ማን ነው?

“ማን ይፈውስሻል” ቀድሞ እንደነበረው ሊመልሳት የሚችል ማንም እንደ ሌለ ለመግለጽ የተጠቀመበት መንገድ ነው እንጂ መልስ የሚጠብቅ ጥያቄ አይደለም። በሌላ መልኩም ሊጻፍ ይችላል፤ “ማንም ሊፈውስሽ አይችልም” ወይንም “ማንም ሊመልስሽ አይችልም”

ምርኮሽንም ይመልሱ ዘንድ በደልሽን አልገለጡም

“ምርኮኛነትሽን ለማስቀረት፣ ኀጢአትሽን አይገልጡም”። “ምርኮሽን” ይሚለው የሰውን ሃብት እና ብልፅግና ያሳያል።

ከንቱና የማይረባ ነገርንም አይተውልሻል

አይተውልሻል የሚለው ”ተናግረዋል“ በሚለው ሊገለጽ ይችላል። “ከንቱና የማይረባ ነገርንም ተናግረውልሻል”

## Lamentations 2:15

እጃቸውን ... ያፍዋጫሉ ፥ ራሳቸውንም ያነቃንቃሉ

ሌሎችን ለመስደብ እና እነርሱ ላይ ለማሾፍ የሚደረጉ ድርጊቶች ናቸው። “እጃቸውን እያጨበጨቡ. . . እያፏጩ እና ራሳቸውንም ያነቃንቃሉ”

በኢየሩሳሌም ሴት ልጅ

ይሄ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን ፣ እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል።

በውኑ የውበት ፍጻሜና የምድር ሁሉ ደስታ የሚሉአት ከተማ ይህች ናትን?

ይሄ ምላሽ የማይጠብቀው ጥያቄ የፌዝ ንግግር ነው። ጥያቄ ባልሆነ መልኩ ሊጻፍ ይችላል። ““የውበት ፍጻሜ” እና “የምድር ሁሉ ደስታ” የተባለችው ከተማ ውበትም ድስታም የለባትም።

የውበት ፍጻሜ

በፍፁም ውብ

ጥርሳቸውን እያፋጩ

ይሄ የሰውን ቁጣ እና በሌላው ላይ ማፌዝን ነው የሚያሳየው።

ውጠናታል

እንስሳ ምግቡን እንደሚውጥ እየሩሳሌምን አጥፍተናታል። “እየሩሳሌምን ሙሉ ለሙሉ አጥፍተናታል”

አግኝተናታል አይተናትማል

ይህ ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው። “ሲፈፀም ለማየት እጅግ ጓጉተን ነበር”

## Lamentations 2:17

አፈረሰሽ

“አፈረሰ”

ደስ አሰኘብሽ

ጠላት ስላሸነፈሽ ተደሰተብሽ ለማለት ነው። “አንቺን በማሸነፍ መደሰት”

የሚያስጨንቁሽንም ቀንድ ከፍ ከፍ አደረገ

“ቀንድ”   የእንስሳ  የሚያሳየው ጥንካሬን ነው። “የጠላቶቻችንን ጉልበት ጨመርህ”

## Lamentations 2:18

ልባቸው ወደ ጌታ ጮኸ

የሰውን የውስጥ ማንነትን ለመወከል ነው “ልብ” ያለው። ሊንረው ይሚችለው ትርጉም 1  የእየሩሳሌም ሠዎች፤ “የእየሩሳሌም ሠዎች ከውስጥ ማንነታቸው ወደ ጌታ ጮኍ” ወይንም 2  ቅጥሩን በሰው ይወክለዋል፤ “ቅጥሮቻችሁ፣ ከውስጥ ማንነታቸው ወደ እግዚአብሔር ይጮሃሉ”

የጽዮን ሴት ልጅ ቅጥር ሆይ፥ እንባሽን ... አፍስሺ ... በጐዳና ሁሉ

ጸሓፊው ስለ እየሩሳሌም ቅጥር መናገር ፈልጓል። ቅጥርሽ ብሎ የሚናገረውን የእየሩሳሌም ሠዎ ች እንዲናገሩ የ ሚፈልገውን ነው። “እናንተ የጽዮን ሴት ልጅ ቅጥር” የሚለው በቀጥታ ለ“ቅጥሯ” ሲሆን ሌላው ግን ለሠዎቹ የተነገረ ነው።

የጽዮን ሴት ልጅ

ይሄ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን ፣ እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል።

እንባሽን እንደ ፈሳሽ አፍስሺ

ሠዎቹ እጅግ ስላለቀሱ እምባቸው እንደ ወራጅ ውሃ ነው። “እጅግ ብዙ ብዙ አለቀሱ”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ቀንና ሌሊት
ሁለቱ ተቃራኒ የግዜ መለክያዎች የተገለጹት ሁል ግዜ ለማለት ነው። “ሁል ግዜ”
ለሰውነትሽ ዕረፍት አትስጪ ፤ የዓይንሽ ብሌን አታቋርጥ
“ለራስሽ ዕረፍትን አትስጪ፣ ዐይኖችሽ ከማንባት አያቋርጡ ”
በሌሊት በመጀመሪያ ክፍል
“በሌሊቱ ብዙውን ግዜ” ይሄ የሚያመላክተው ጠባቂ በሚመጣበት የትያውም ግዜ።
በጌታም ፊት ልብሽን እንደ ውኃ አፍስሺ
“ልብሽን እንደ ውኃ አፍስሺ” የሚለው ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው። የእግዚአብሔርን መገኘት ለመግለፅ በፊት ይገለፃል። “በውስጥ ሰውነታችሁ የሚሰማችሁን ለእግዚአብሔር ንገሩት”
እጆችሽን ወደ እርሱ አንሺ
x
Lamentations 2:20
ፍሬያቸውን
ስለ ልጆ ች እየተናገረ ሲሆን ከእናታቸው ማህፀን እንደወጣ ፍሬ ይመስላቸዋል። “የወለዷቸውን ሕፃናት” ወይንም “የራሳቸውን ልጅ”
በውኑ ካህኑና ነቢዩ በጌታ መቅደስ ውስጥ ይገደላሉን?
ይሄ ጥያቄ ምላሽን የሚጠብቅ ጥያቄ ሳይሆን፤ ካህናት እና ነብያት ሊገደሉ እንደማይገባ ለማስረገጥ ነው። በሌላ መልኩ ሲፃፍ “ካህናቱ እና ነብያቱ በእግዚአብሔር ማደሪያ ሊገደሉ አይገባም”
በውኑ ካህኑና ነቢዩ ... ይገደላሉን?
በቀጥታ መልኩ ሲፃፍ “ጠላቶቻችን ካህናቱን እና ነብያቱ ሊገድሉ ይገባልን ”
Lamentations 2:21
ብላቴናውና ሽማግሌው በመንገዶች ላይ ተጋደሙ
እዚህ ጋር የሚናገረው ስለ ሞቱ ሰዎች እንደሆነ ያመላክትል። “የብላቴኖች እና ሽማግሌዎች ሬሳ በመንገዶች ላይ ተጋድሟል”
ብላቴናውና ሽማግሌው
ይሄ ክፍል የሚናገረው ስለ ሰዎች ነው። ሁለቱ ተቃራኒ የእድሜ ክልል የተጠቀሱት ሁሉንም ሰዎ ች ለመወከል ነው። “ወጣቱም ሽማግሌውም” ወይንም “በሁሉም የ ዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎች”
ደናግሎቼና ጐበዛዝቴ በሰይፍ ወድቀዋል
ሰይፍ የሚለው የሚወክለው ጠላቶቹን ነው። የተገደሉትም በጠላቶቻቸው ነው። “ደናግሎቼና ጐበዛዝቴ በጠላቶቻቸው ተገድለዋል”ወይንም “ጠላቶቼ ደናግሎቼን እና ጐበዛዝቴን ገድለዋቸዋል”
ገደልሃቸው
እግዚአብሔር እራሱ የገደላቸው ያህል ሰዎቹ እንዲገደሉ መፍቀዱን ይናገራል። “እንዲገደሉ ፈቀድክ” ወይንም “ይሄ እንዲፈጠር ፈቀድክ”
እንደ በዓል ቀን ... ከዙሪያዬ ጠራህ
“ሊቡሉ እንደሚመጡ” ይቡሉ ዘንድ እንደሚመጠ እግዚአብሔር እንዴት ጠላቶቹን እንደጠራ።
የሚያስፈሩኝን
ጸሓፊው የሚፈራቸው ሰዎች “የሚያስፈራሩኝ” በሚል ተገልጿል። “የፈራኋቸው አጥቂዎቼ”
ከዙሪያዬ
ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው። “በሁሉም አቅጣጫ”
በእግዚአብሔር ቍጣ ቀን
“ቀን” የሚለው በዘይቤአዊ አገላለጽ የተጻፈ ሲሆን የተወሰነ ግዜን የወክላል። “በእግዚአብሔር በቍጣው በተገለጠ ግዜ”

---

Chapter 3
Lamentations 3:1
መከራ ያየ
“ያየ” ልምድ ያለውን ያሳል። “መከራን የተለማመደ” ወይንም “የተጎዳ”
በቍጣው በትር
“በትር ስር” የሚለው በበትር መመታትን ያሳያል። የእግዚአብሔርን ቅጣት በእርሱ በትር እንደመመታት ይተካዋል። “እግዚአብሔር እጅግ ስለተቆጣ በበትር መጥቶኛል” ወይንም “እግዚአብሔር እጅግ ስለተቆጣ በኋይል ቀጣኝ”
ከፊቱ አሰወጣኝ
“ከእርሱ እንደሄድ አደረገኝ”
በብርሃን ሳይሆን በጨለማ እንድሄድ አደረገኝ
“ጨለማ” የሚለው የሚወክለው መከራን ነው። “በብርሃን ሳይሆ ን በጨለማ እንደሚሄድ ሰው ያለ ምንም ተስፋ እጅጉን እንድጎዳ አደረገ”
እጁን በላዬ ላይ መለሰ
“እጁን በላዬ ላይ መለሰ” የሚለው እርሱን ማጥቃትን ይወክላል። ጸሓፊው እግዚአብሔር መጠፎ ነገርን እንዲደርስበት መፍቀዱን እንዳጠቃው አድርጎ ይናገራል። “አጥቅቶኛል” ወይንም “ሰውን እንደሚያጠቃ ብዙ መጥፎ ነገሮች እንዲደርስብኝ አድርጎኛል”
ሥጋዬንና ቁርበቴን አስረጀ፥ አጥንቴን ሰበረ
ሊሆን የሚችሉት ትርጉሞች፤ 1 ከመደብደብ የተነሳ የሚሆን ነገር ነው ወይንም 2 እግዚአብሔር እርሱን የቀጣበት ሌላ መንገድ ነው።
Lamentations 3:5
ቅጥር ሠራብኝ
የቅጥር ሥራ የሚለው ቅጥር ያላቸው ከተማዎች ላይ ተንጠላጠሎ ለመውረር እንዲያስችላቸው የሚሰሩት ነው።
ቅጥር ሠራብኝ
ሊሆን የሚችሉት ትርጉሞች፤ 1 ጸሓፊው እግዚአብሔር በከተማ ላይ መጣፎ ነገር ላማድረስ እንደሚቀጥር ክፋት እንዲደርስበት እንዳደረገ ይናገራል። “ጠላት በከተማ ላይ ጥቃትን ለማደረስ እንደ ሚቀጥርእግዚአብሔር አጠቃኝ” ወይንም 2 ጸሓፊው እግዚኧብሔር ጠላት እየሩሳሌምን እንደሚወር እንደፈቀደ እግዚአብሔር አጠቃኝ ለማለት ነው። “ጠላት በዙሪያዬ ቅጥርን እንዲሰራ እግዚአብሔር አደረገ”
በምሬትና በድካም ዙሪያዬንም ከበበኝ
እግዚአብሔር ምሬትና ድካምን እዲለማመዱ ፈቅዷል። “ምሬትና ድካምን እደለማመድ አድርጓል” ወይንም “መከራን እና ብዙ ችግር እንዲደርስብኝ አድርጓል”
ምሬት
“ምሬት” የሚለው መከራን ያሳያል።
ከሞቱ ብዙ ጊዜ እንደሆናቸው፣ በጨለማ አንድኖር አደረገኝ።
“ጨለማ” የሚለው የሚናገረው ስለ መከራ ነው። ጸሓፊው የደረሰበትን መከራ መጠን ለመግለፅ ቀድሞ የሞቱ ሰዎች ከተለማመዱት ድቅድቅ ጨለማ ጋር ያወዳድረዋል። “እንዲደርስብኝ ያደረገው መከራ በመቃብር ውስጥ እንዳለ ጨለማ ነው” ወይንም “ ቀድማውንም የሞቱ ሰዎች ያሉበት ጨለማ ውስጥ ያለው ያህል እጅጉን መከራ ያደርስብኛል”
በቅጥር ውስጥ ዘጋብኝ፤ ስለዚህ ማምለጥ አልቻልሁም፤ የእስር ሰንሰለቴንም አከበደብኝ።
ይሄ ከእስር ቤት ማምለጥ እንዳቃተው ሰው ቀጣይነት ያለውን መከራ መቀበልን ያሳያል። ጸሓፊው መከራውን ማስቆም አልቻለም። “መከራዬ ቀጥሏል፤ በዙሪያዬ ቅጥርን የሰራ፣ ከባድ ሰንሰለትን ያደረገንኝ ያህል ነው፤ ማምለጥ ተስኖኛል”
ብጣራና ብጮኽ እንኳ . . . መስማት አልፈለገም
ጸሓፊው እግዚአብሔር ጸሎቱን ጆሮውን ደፍኖ አልሰማም እንዳለው ያህል እንደማይሰማው ይናገራል። “ጸሎቴን አልሰማም ይላል”
Lamentations 3:9
መንገዴን . . . ዘጋ
ጸሓፊው ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው ከመከራው እንዳያመልጥ መንገዱን እንደዘጋ ነው። “መንገዴን እደዘጋ ነው”
በተጠረቡ ድንጋዮች ዘጋ
“የተጠረቡ ድንጋዮች” አንድ ላይ አድርገው ሕንፃን ለመገንባት ሰዎች ድንጋይን ይጠርባሉ።
ጐዳናዬንም አጣመመ
የተጣመሙ መንገዶች ሠዎችን ወደ ሚፈልጉበት ቦታ አያደርሱም። እዚህ ጋር መከራን ለማምለጥ የሚሆን መንገድን ይወክላሉ። “መንገዴን እንዳጣመመ ነው” ወይንም “መከራዬ እንዲያቆም ለማድረግ ሞክሪያከሁ፤ ነገር ግን ለማምለጥ የሚሞክርን ሰው መንገድ እንደሚያጣምም እግዚአብሔር ከለከለኝ”
አሸምቆ እንደ ተኛ ድብ፥ እንደ አደባም አንበሳ
ጸሃፊው እግዚአብሔር ክፋት እንዲሆንበት ሊያደርግ፤ አውሬ ለአደን እንደሚያደፍጥ ተዘጋጅቶ እየጠበቀ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል።
መንገድ ጐትቶ አሰወጣኝ፤ ቈራረጠኝም፤


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 "ከመንገድ አወጣኝ" ወይንም 2 "መንገዴ በተሳሳተ መታጠፍያ እንዲታጠፍ አደረክ"
ያለ ረዳትም ተወኝ
"ተስፋ ቢስ አደረገኝ" ወይንም "ምንም እርዳታን እንናገኝ አልፈቀደም"
Lamentations 3:12
ቀስቱን ገተረ፤
አንድ ወታደር ቀስቱን ለመወንጨፍ መገተር ይኖርበታል፤ እናም እዚህ ጋር እግዚአብሔር እስራኤልን ለመውጋት እየተዘጋጀ እንደሆነ ይገልፃል። "እግዚአብሔር ቀስቱን ገተረ፤ ለማጥቃት እጁ ተዘጋጅታለች"
የሰገባውን ፍላጻዎች በኩላሊቴ ውስጥ ተከለ
ጸሓፊው የተሰማውን የውስጥ ኋዘን ለመግለፅ እግዚአብሄር ኩላሊቱን በቀስት እንደወጋ ያህል ይገልጸዋል። "ሓዘኔ ታላቅ ነው፤ ኩላሊቴ በቀስት እንደተወጋ ያህል ነው"
ኩላሊቴ
ኩላሊት የሚያሳየው የሰውን ስሜት ነው። ትርጓሜውም "በጥልቅ ሰውኔቴ ውስጥ" ወይንም "ልቤ"
ሰገባ
ከኋላ የሚታጠቁት ፍላፃ ማስቀመጫ ቦርሳ
ለወገኔ ሁሉ ማላገጫ
"ሁሉ" የሚለው አብዛኛውን ያመላክታል። "ለአብዛኛው ሰው ማላገጫ" ወይንም "ሁሉም ሰው የሚያሾፍበት"
ማላገጫ
ብዙ ሰዎች የሚያሾፉበት ሰው
ምሬት ሞላብኝ
እዚህ ጋር "ምሬት" የሚለው መከራ መቀበልን ይወክላል። ጸሓፊውን የሚያጠግብ ነገር የሆነ ያህል ድረስ። "እጅግ በጣም መከራን እንዲደርስብኝ አድርጓል "
በእሬትም አጠገበኝ
ከአበባ እና የተወሰነ አትክልት የሚሰራ መራራ መጠጥ ነው። የሄንን መጠጥ መጠጣት መከራ መቀበልን ያመላክታል። "በጣም መራራ ነገርን እንድጠጣ እንዳስገደደኝ ያህል ነው"
Lamentations 3:16
ጥርሴን በድንጋይ ሰበረ
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 ድንጋይ እዲያኝክ ያደረገው እስኪመስለው ያህል እግዚአብሔር እንዳዋረደው። "አዋርዶኛል፤ ሌላን ሰው ድንጋይ እንዲበላ እንዳደረገ ሰው" ወይንም 2) ጸሓፊው እግዚአብሔር ፊቱን ከመሬት ጋር አጣብቆ እንዳዋረደው አድርጎ ነው የገለጸው። ""አዋርዶኛል፤ የሌላን ሰው ፊትን ከመሬት ጋር እንዳጣበቀ ሰው""
በትቢያ ውስጥ ረጋገጠኝ
ጸሓፊው እግዚአብሔር ወደ ትቢያ ውስጥ እንደገፋው እና እንዳዋረደው አድርጎ ይናገራል።
በትቢያ
ሊዋጋው የማይችለው ነገር ከመሆኑ የተነሳ እራሱን ሊያሳንስበት የሚችለው ትንሹ ደረጃ ለማለት ነው።
ነፍሴ ሰላምን አጣች
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 የጸሓፊው ልምምድ ሰላማዊ አይደሉም "በሕይወቴ ሰላም የለኝም" ወይንም ጸሓፊው ሰላም አይሰማውም "በነፍሴ ሰላም አይሰማኝም"
ኋይሌ፤ ከእግዚአብሔርም ተስፋ ያደረግሁት ሁሉ ሄዶአል
ጸኋፊው መከራን መቋቋም ስለሚያስችለው ኋይሉ ይናገራል፤ ብሎም በእግዚአብሔር ላይ ስላለው ተስፋ ሊናገር ሕይወት እንዳላቸው እና አሁን እንደሞቱ ነገሮች አድርጎ ይናገራል። "ከዚህ በላይ መከራን መቀበል እና በእግዚአብሔር እንደሚረዳው ተስፋ ማድረግን እንዳቃተው"
ኃይሌ
አንዳንድ ቅጂዎች "ክብሬ" ወይንም "ተድላዬ"
Lamentations 3:19
እሬትንና ሐሞት
እሬት የሚለው ከተወሰነ ተክል የሚነኝ ውስጡ መራራ ሰሳች የሚነኙ። "እሬትን" እና "ሐሞት" የሚሉት በአንድ ላይ መከራን ይወክላሉ።
ነፍሴም በውስጤ ተዋርዳለች
ጸሓፊው ስለ ጥልቅ ኋዘኑ እና ምስቅልቅሉ፤ አንገቱን እንዳቀረረ ሆኖ ይናገራል።
"ደብሮኛል" ወይንም "ተስፋ ቆርጫለሁ"
ሆኖም ይህን አስባለሁ
ሆን ብሎ ስለአንድ ነገር ማሰብን ያሳያል። "ይህን" የሚለው ጸሓፊው በመቀጠል ሊናገር ስለሚያስብበት ነገር ነው። "ስለዚህ ነገር ላስብ ወሰንኩኝ" ወይንም "ይህንን አስታውሳለሁ"
ተስፋ አለኝ
"ተስፋ አደርጋለሁ"
Lamentations 3:22
ከእግዚአብሔር ታላቅ ፍቅር የተነሣ
"ታላቅ ፍቅር" የሚለው "ባታማኝነት መውደድ" በሚለው ሊገላጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ህዝቡን በታማኝነት መውደዱን አያቆምም"
ርኅራኄው አያልቅም
"ርኅራኄው" የሚለው ቃል "ግድ ማለት" በሚለው ሊተረጎም ይችላል። "መከራን ለሚቀበሉ ግድ መሰኘትን አያቆምም"
ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው
"ነው" ይሚለው የእግዚአብሔርን "ታላቅ ፍቅር" እና "ርኅራኄ" ነው። አዲስ ነው ማለቱ እግዚአብሔር እነርሱን ማድረግ አ ለማቆሙን ያሳያል።
ታማኝነትህም
"የአንተ" የሚለው እግዚአብሔርን ነው።
እግዚአብሔር ዕድል ፈንታዬ ነው
እግዚአብሔር ለሁሉም የ እስራኤል ነገድ መሬትን ሲሰጥ "ዕድል ፈንታ" ነው ነበር ያለው። የሚያስፈልገው ዕድል ፈንታ እግዚአብሔር እንደሆነ ነው ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው። "እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ስለሆነ፤ የሚያስፈልገኝ ሁሉ አለኝ "
Lamentations 3:25
እርሱን ተስፋ ለሚያደርጉት
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 "በእሩሱ ላይ የሚደገፉ ሁሉ" ወይንም 2 "እርሱ የሆነ ነገርን እስከሚያደርግ ድረስ የሚጠብቅ"
ለሚፈልገውም ሰው
"መፈለግ" የሚለው ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1እግዚአብሔርን ዕርዳታ መጠየቅ 2 እግዚአብሔርን ለማወቅ መፈለግ
በወጣትነቱ ቀንበር ቢሸከም
ቀንበር የሚለው የሚያመላክተው መከራን ነው። "በወጣትነት" የሚለው ልጅነትን ያመላክታል። "በልጅነት ግዜው የደረሰበት መከራ
ብቻውን ዝም ብሎ ይቀመጥ
"ዝም ብሎ" የሚለው አለመናገርን ያመላክታል። እዚህ ጋር አለማጉረምረምን ለማለት ነው። "ያለመናገር በቻውን ይቀመጥ" ወይንም "ሳያጉረመርም ብቻውን ይቀመጥ"
አሸክሞታልና
"ቀንበሩ ሲጫንበት" ቀንበር የሚለው የሚያመላክተው መከራን ነው። "መከራን ሲቀበል"
ፊቱን በዐቧራ ውስጥ ይቅበር
ፊትን በዐቧራ መቅበር አንገትን ወደ ምድር ማቀርቀርን ያመላክታል። "እዛው ፊቱን ወደ መሬት አዘቅዝቆ ይቆይ"
Lamentations 3:30
ጉንጩን ለሚመታው ሰው ይስጥ
በውስጥ ታዋቂነት "እርሱ" የሚለው መከራን የሚቀበል ወይንም እግዚአብሔርን የሚጠባበቅ ማንንም ነው። "ጉንጩን ይስጥ" የሚለው የሚወክለው ሰው ጉንጩን እንዲመታ መስጠትን ነው። "ፊቱን እንዲመቱት ለሰዎች ይፍቀድ"
ውርደትንም ይጥገብ
ጸሓፊው የሚናገረው በውስጡ እንደ ውሃ ውርደትን ሊሞላ እንደሚችል ዕቃ ነው። በውርደት መሞላት ማለት በጣም መዋረድ ማለት ነው። ማስተላለፍ የፈለገው በዚህ ግዜ መታገስ እንዳለበት ነው። "ብዙ ይዘለፍ" ወይንም "ሰዎች ሲያዋርዱት ይታገስ"
መከራን ቢያመጣ እንኳ
"እግዚአብሔር ሰዎች መከራ እንዲደርስባቸው በያረግም" ወይንም "ሰዎችን ቢቀጣም"
ይራራል
"በእነርሱ ላይ ርህራሄ ይኖረዋል"
ሆን ብሎ ችግርን፣ ወይም መከራን አያመጣምና

“ሆን ብሎ” የሚለው ፍላጎትን እና እርካታን ያመላክታል፤ “በሰዎች ላይ መከራን በማምጣት ደስ አይለውም” ወይንም “ሰዎችን በመቅጣት እርካታን አያገኝም”
በሰው ልጆች ላይ
ይሄ በአጠቃላይ ስለ ሰዎች ይናገራል። “ሰዎች” “የሰው ልጆች”
Lamentations 3:34
ሰው መብቱ ሲነፈገው ... ሰው ፍትሕ ሲጓደልበት፣
“ሰዎች ሲደቁ…የሰውን ፍትህ ሲለነፍግ… ፍትህ ሲለነፍጉ”
በእግር ሲረገጡ
እዚህ ጋር “በእግር ሲረገጡ” የሚለው ሰዎችን ማንገላታትን እና ማጉላላትን ያሳያል። “ማንገላታት” ወይንም “ማጉላላት”
ሰው መብቱ ሲነፈገው፣
ይሄ ሰው የሚገባውን ነገር መንፈግን ያመላክታል። “የሰውን መብት ምከልከል” ወይንም “ሰው የሞ ገባውን ነገር እንዳያገኝ መከልከል”
በልዑል ፊት
“በልዑል ፊት” አንድን ነገር ማድረግ የሚወክለው እግዚአብሔር እያየ ማለት ነው። ““በልዑል እያየ እንደሆነ እያወቅሁ”
ሰው ፍትሕ ሲጓደልበት፣
“ፍትሕ ሲጓደል” ማለት ፍትኋዊ ነገርን አለማድረግ ማለት ነው። “አንድን ሰው በህግ ፊት በስህተት መዳኘት ማለት ነው” ወይንም “በዳኛ ፊት የሚቀርብን ሰው ፍርድ እንዳያገኝ ማድረግ ማለት ነው”
Lamentations 3:37
ጌታ ያላዘዘውን የሚልና የሚፈጽም ማን ነው?
ጸሓፊው ምላሽ የማይሰጠውን ጥያቄ የሚጠቀመው እግዚብሔር እንዲሆን የተናገረው ነገር ብቻ እንደሚሆን ነው። “ማንም ተናግሮ አልሆነም፤ እግኤአብሔር ካላለው በስተቀር” ወይንም “እግዚአብሔር ካላዘዘው በስተቀር ሰው ስላለው የሆነ ነገር የለም”
Lamentations 3:40
ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ
“ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ” የሚለው የሚወክለው ለእርሱ መገዛትን ነው። “እንደገና ለእግዚአብሔር እንገዛ”
ልባችንን ከእጆችን ጋር . . . በሰማይ እናንሣ
“እጅን ወደ ሰማይ ከፍ ማድረግ” የሚያሳየው ከልብ መጸለይን ነው። ለእስራኤላውያን እጅን ወደላይ ከፍ አድርጎ መጸለይ ልማድ ነበረ። “እጃችንን ወደ ላይ ከፍ አድርገን ከልባችን እንጸልይ” ወይንም “ወደላይ ከፍ ባለ እጅ ከልባችን እንጸልይ”
ዐምፀናል፤ ኀጢአትም ሠርተናል
ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ሲሆኑ፤ “ማመጽ” እና “ኋጥያት” መስራት ሁለቱም እግዚአብሔር ላይ ማመጽ እንደሆኑ ያሳያል።
ራስህን በቍጣ ከደንህ
እዚህ ጋር ቁጣን እግዚአብሔር የሚደርበው ልብስ አድርጎ ይናገረዋል። ብዙውን ግዜ በዕብራይስጥ ስሜት እንደ ልብስ ይገለፃል። “እጅግ በጣም ተናደሃል”
ገደልኸን
“ብዙዎቻችንን ገደልኸን”
ያለ ርኅራኄም
“ርኅራኄ” የሚለው የሚያሳየው ማዘንን ነው። “አላዘንክልንም”
Lamentations 3:44
ጸሎት እንዳያልፍ፣ ራስህን በደመና ሸፈንህ
ይሄ የሚያመላክተው እግዚአብሄር ላለመስማት እንደወሰነ ነው። “ጸሎታችንን አልሰማም አልክ፤ ጸሎታችንም አንተ ጋር እንዳይደርስ በዙሪያህ ደመናን ሸፈንክ”
በአሕዛብ መካከል አተላና ጥራጊ አደረግኸን
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 እግዚአብሔር እስራእኤላውያን በአሕዝብ ዘንድ ዋጋ ቢስ እንዲባሉ አደረክ። “አሕዛብ እንደ አተላ እና ቆሻሻ እንዲታሰቡ አደረክ” ወይንም 2) እግዚአብሔር ሕዝቡን በአሕዛብ መሃከል እንዲኖሩ ማድረጉ እንደ ቆሻሻ መጣል ነው። “እንደቆሻሻ በአሕዛብ መሃከል ጣልከን”
በችግርና በሽብር ተሠቃየን
“ችግር” እና “”ሽብር” ፥ “ጥፋት” እና “በመፈራረስ” የሚሉት በድርጊት መልኩ ሊገለፅ ይችላል። “እየተሸበርን ነው፤ ተጠምደናል እና እየፈረስን እና እየጠፋን ነው” ወይንም “ተሸብረናል ተጠምደናል። በአጠቃላይም ልንጠፋ ነው”
በችግር
ይሄ የሚያመላክተው ወደ ጉድጓድ መውደቅን ያመላክታል። በሁሉም መልኩ መጠመድን ያመላክታል።
በእኛ ላይ
“በእኛ ላይ የሆነው”
በጥፋትና በመፈራረስ፣
ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ሲሆኑ፤ የእየሩሳሌምን መፍረስ ያመላክታሉ። “የሙሉ ለሙሉ ጥፋት”
Lamentations 3:48
የእንባ ጐርፍ ከዐይኔ ፈሰሰ
ጸሓፊው የተሰማውን ሃዘን እና ያለቀሰውን በማጋነን፤ እንደጎርፍ የሚያክል ለቅሶ እንዳለቀሰ ይገልጻል። “ውሃ በወንዝ እንደሚፈስ እምባዬ ከዓይኖቼ ይፈሳል”
ሕዝቤ አልቋልና
በቀጠታ መልኩ መገለፅ ይችላል። “ጠላቶቼ ሕዝቤን አጠፋ”
ያለ ዕረፍት፣ ያለ ማቋረጥ
ሁለቱም ቃላት ትርጉማቸው አንድ ዓይነት ነው። ጸሓፊው ማልቀሱን እንደቀጠለ እና ዓይኑን በማልቀስ ዕረፍት ባጣ ሰው ይወክለዋል። “ያለ ማቆም”
እግዚአብሔር ከላይ፣ ከሰማይ እስኪያይ ድረስ
ጸሓፊው እግዚአብሔር ቢያይ በሎ ምን ተስፋ እንደሚያደርግ በግልፅ ጽፏል። “እግዚአብሔር ከላይ፣ ከሰማይ ሕዝቡ ላይ የደረሰውን እስኪያይ ድረስ”
Lamentations 3:51
ማየቴ፣ ነፍሴን አስጨነቃት
ማየቴ የሚለው የሚወክለው የሚያየውን ነገር ነው። “የማየው ነገር ነፍሴን አስጨነቃት”
በከተማዬ ባሉት ሴቶች ሁሉ ላይ የደረሰውን
የከተማው ሴት ልጆች መከራን እየተቀበሉ መሆኑ ግልጽ ነው። “የከተማዬ ሴት ልጆች መከራን እየተቀበሉ ስለሆነ” ወይንም “የከተማዬ ሴት ልጆች መከራን ሲቀበሉ ስለማይ”
በከተማዬ ባሉት ሴቶች ሁሉ
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 የእየሩሳሌም ሴቶች ወይንም 2 በእየሩሳሌም የሚኖሩ ሁሉ
ያለ ምክንያት ጠላቶቼ የሆኑ፣ እንደ ወፍ አደኑኝ
ጸሓፊው ሰዎች የሚያድኑትን እንስሳ ለገድሉ እንደሚፈልጉ እርሱንም እንደ ሚፈልጉት ይናገራል። በቀጥታ መልኩ “የሚያደኑትን ወፍ እንደ ሚፈልጉ ጠላቶቼ ሊገድሉኝ ፈለጉኝ”
ሕይወቴን በጕድጓድ ውስጥ ሊያጠፉ
“ወደ ጉድጓድ ወረወሩኝ” ወይንም “ወደ ጉድጓድ ጣሉኝ”
ድንጋይም በላዬ አደረጉ
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 “ወደ እኔ ድንጋይን ወረወሩ” ወይንም 2 “ጉድጓዱን በድንጋይ ሸፈኑ”
ውሃ ሞልቶ በዐናቴ ላይ ፈሰሰ
“በጉድጓዱ ያለው ውሃ ከአናቴ በላይ ወጣ”
ጠፍቻለሁ ብዬ
“ጠፍቻለሁ” የሚለው መገደልን ይወክላል። በጣም ቶሎ መሞትን ያሳያል “ልሞት ነው”
Lamentations 3:55
የአንተን ስም ጠራሁ
የእግዚአብሐር ስም ማለት ባህሪውን ይወክላል። “ስም መጥራት” የሚለው የእግዚአብሔርን ባህሪ ማመንን እና መጣራትን የመላክታል።
በጥልቁ ጕድጓድ ውስጥ
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 ጸሓፊው የተወረወረበትን ጉድጓድ ያመላክታል “ከተወረወርኩበት ጉድጓድ ስር” ወይንም 2 ጸሓፊው በቅርብ እንዳይሞት ስለፈራ፤ ከሞቱ ሰዎች ጋር እንደሆነ አድርጎ ይናገራል “ከሙታን መሃከል”
ልመናዬን ሰምተሃል
“ልመና” የሚለው የተናገረውን ነገር ያሳያል። “ያልኩትን ሰማህ”
ጆሮህን አትከልክል
“ጆሮህን መከልከል” የሚለው ለመስማት አለመፈለግን ያመላክታል። “አልሰማም አትበል”
ቀረብኸኝ
ብዙውን ግዜ ሰዎች ሊረዱት የሚፈልጉትን ሰው ይቀርባሉ። “ቀረበኝ” የሚለው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መርዳትን ያመለክታል “ረዳኸኝ”
Lamentations 3:58
ጌታ ሆይ፤ ለእኔ ተሟገትኽልኝ፤ ሕይወቴንም ተቤዠህ
እግዚአብሔር በፍርድ ፊት እንዳይሞት እንደተሟገተለት፤ ጸሓፊው እግዚአብሔር ጠላቶቹ እንዳይገሉት እንዳደረገ ይናገራል። “ሕይወቴን ከጠላቶቼ አዳንካት። በፍርድ ፊት እንደተሟገትክልኝ ነው”
ለእኔ ተሟገትኽልኝ፤
“ተሟገትክልኝ” የሚለው እርሱን ወክሎ እንደተከራከረለት ይናገራል። “ለእኔ ስትል ጉዳዬን ተከራክልክ”
ፍርዴን ፍረድልኝ
እዚህ ጋር እግዚአብሔር ጠበቃ መሆኑ ይቀርና ዳኛ ይሆናል። እግዚአብሔር ለእርሱ እንዲፈረድለት እየጠየቀ እንደሆነ ያስታውቃል። “ስለ እኔ ውሳኔን ወስን፤ እናም ትክክል እንደሆንኩኝ ለጠላቶቼ አስታውቅልኝ”
በቀላቸውን ሁሉ፣ በእኔም ላይ ያሰቡትን ዐድማ አየህ
“ስድባቸው” የሚለው ቃል እና ወይንም “ዕቅዳቸውን” የሚለው በድርጊታዊ ቃል ሊገለፅ ይችላል። “እንዴት እንደሰደቡኝ አይተሃል ምን ያህንም በእኔ ላይ እንደዶለቱ”
ስድባቸውን ሁሉ፣ በእኔ ላይ ያሰቡትን ዐድማ ሁሉ ሰማህ
“ስድባቸው” የሚለው ቃል “ፌዛቸው” ወይንም “ትንኮሳቸው” በሚለው ቃል ሊገለጽ ይችላል። ለጎዱት ዕቅድ እንደነበራቸው በግልጽ ሊባል ይችላል። “እንዴ እንደተነኮሱኝ አይተሃል. . . ለእኔም የነበራቸውን ዕቅድ እንዲሁ” ወይንም “ሲያፌዙብኝ አይተሃል. . . ሊጎዱኝ ዕናቀዱብኝም እንዲሁ”
Lamentations 3:62
ይህም ቀኑን ሙሉ በእኔ ላይ፣ ጠላቶቼ የሚያውጠነጥኑትና የሚያንሾካሹኩት ነው
ጸሓፊው የጠላቶቹን ክስ ቀኑን ሙሉ ለዋጋ እንደሚመጡ ጦሮች ያስመስለዋል። “ጠላቶቼ በእኔ ላይ ሲናገሩ እና ሲከሱኝ ይውላሉ”
ጠላቶቼ የሚያውጠነጥኑት
የሚያውጠነጥኑት የሚለው የሚሉትን ያሳያል። “የጠላቶቼ ቃላት”
ቆመውም ሆነ ተቀምጠው
ሁለቱ ድርጊቶች ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ይገልፃሉ። “የሚያደርጉት ሁሉ”
Lamentations 3:64
የሚገባውን መልሰህ ክፈላቸው
“መልሰህ ክፈላቸው” የሚለው መቀጣታቸውን ያሳያል። ያደረጉት ነገር በግልጽ ሊዘረዘር ይችላል። “ እግዚአብሄር ሆይ ባደረጉት መጠን ቅጣቸው” ወይንም “እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔን አሳዝነውኛል እና እባክህ አሳዝናቸው”
በልባቸው ላይ መጋረጃን ዘርጋ
“ልብ” የሚለው የሰዎቹን ስሜት እና አመለካከት ብሎም “ኀፍረት ማጣት” ለማለት ሲሆን ትርጉም በኃጥያታቸው ማፈር ያለባቸውን ያህል አለማፈርን ያሳያል። አለማፈራቸውም እግዚአብሔር ይበልጥ እንዲቀጣቸው ያደርጋል። “ስለ ኃጥያታቸውም እንዳያፍሩ ታደርጋቸዋልህ”
ርግማንህም በላያቸው ይሁን
ርግማን የሚለው “መርገም” ወይንም “መኮነን” ሊባል ይችላል። “እርገማቸው” ወይንም “ኮንናቸው”
ከ . . . ሰማያት በታች
“ከሠማይ በታች” የሚለው “በምድር ላይ ያሉት ነገሮች በሙላ” ማለት ነው።

---

Chapter 4
Lamentations 4:1
ወርቁ እንዴት ደበሰ! ንጹሑስ ወርቅ እንዴት ተለወጠ!
የእስራኤል ሕዝብን ማንፀባረቁን ባቆመ ወርቅ ይመስለዋል፣በዚህም ምክንያት ዋጋውን አጥቷል። “የእስራኤል ሕዝብ ማንፀባረቁን እንዳቆመ ወርቅ ነው፤ ውበቱን እንዳጣ ንጹህ ወርቅ ናቸው።”
ንጹሑስ ወርቅ እንዴት ተለወጠ!
ይህ ጸሓፊው ነተፈጠረው ነገር እንዴት እንዳዘነ በአንክሮ ሲገልፅ ነው።
የከበሩ ድንጋዮች፣ በየመንገዱ ዳር ተበታትነዋል
ቤተመቅደሱ በመፍረሱ የከበሩ ድንጋዮች በከተማው ተበትነዋል። የሰዎችንም መበተን የሚያሳይ ዘይቤአዊ አገላለጽ ሊሆ ን ይችላል።
በየመንገዱ ዳር
“መንገዶች በሚገጥምብቸው ቦታዎች በሙሉ” ወይንም “በ ሁሉም መንገዶች”
የከበሩ የጽዮን ወንዶች ልጆች
በከተማው ያሉ ሰዎች በከተማው ወንድ ልጆች ተመስለዋል። ሊኖሩትም የሚችሉት ትርጉም 1 የእየሩስሌምን ወጣት ወንዶች ብቻ ማለቱ ነው ወይንም 2 ሁሉንም በእየሩሳሌም ያሉ ሰዎች ለማለት ነው
የሸክላ ሠሪ እጅ እንደ ሠራው፣ እንዴት አሁን እንደ ሸክላ ዕቃ ሆኑ
ጸሓፊው የጽዮንን ልጆች ዋጋ ባጡ የሸክላ ዕቃዎች ይመስላቸዋል። “ሰዎች ዋጋ እንደሌላቸው የሸክላ ዕቃዎች ቆጠሯቸው”
Lamentations 4:3
ቀበሮዎች እንኳን ግልገሎቻቸውን ለማጥባት
ይሄ የቀበሮዎች ግልገሎቻቸውን ማጥባት ያሳያል
ቀበሮዎች
ኃይለኛ የዱር ውሾች
የወገኔ ልጅ ግን እንደ ምድረ በዳ ሰጐን
በእየሩሳሌም ያሉ ሰዎች ለልጆቻቸው ክፉ ስለሆኑ በሰጎን ተመስለዋል።
የወገኔ ልጅ
ይሄ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን ፣ እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል። “ሕዝቤ”
ሰጐን
እንቁላሎቻቸውን ትተው የሚሄዱ ትልቅ የወፍ ዝርያ።
Lamentations 4:4
ጡት የሚጠባው የሕፃን ምላስ ከጥም የተነሣ ወደ ትናጋው ተጣበቀ
“ከውሃ ጥም የተነሣ፣ የሕፃናት ምላስ ከላንቃቸው ጋር ተጣበቀ”
ይበሉ
“ይመገቡ”
በመንገድ ጠፉ
“እነኚህ ሰዎ ች ቤት የላቸውም ስለዚህም በየመንገዱ ላይ ተንከራተቱ”
ሐምራዊ ግምጃ ለብሰው ያደጉ
በቀጥታ መልኩ “በቀይ ግምጃ ለብሰው ያድጉ” ወይንም ”ሲያድጉ ሐምራዊ ግምጃ ይለብሱ የነበሩ“
ሐምራዊ ግምጃ
ይሄ ልብስ የሚወክለው ውድ፣ የከበረ እና ምቹ ልብስ ማለት ነው። ስለዛ ቢያንስ ከመሃከል ላይ ሓምራዊ ልብስ ነበረ። “የተቀማጠለ ውድ ልብስ”
“በዐመድ ክምር ላይ ተኙ”
የሚኖሩበት ቤት ስለሌላቸው ነው። “የፍግ ክምር አቀፉ”
Lamentations 4:6
ከሰዶም ኃጢአት ይልቅ የወገኔ ሴት ልጅ ኃጢአት በዛች
ኃጥያት የሚለው ቅጣት በሚለው ሊተካ ይችላል። “የወገኔ ሴት ልጅ ከሰዶም ይልቅ ተቀጣ”
የወገኔ ሴት ልጅ
ይሄ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም ሲሆን በሴት መስለዋታል።
ድንገት ከተገለበጠች
ተገለበጠች የሚለው ሰዶምን ነው። በቀጥታ መልኩም ለገለፅ ይችላል፤ “እግዚአብሔር በቅጽበት እንዳጠፋት”
የማንም እጅ ሳይወድቅባት
በቀጥታ መልኩም ሊገለፅ ይችላል፤ “ማንም እጁን ሳያሳርፍባት”
የማንም እጅ ሳይወድቅባት
ሰዎች አንዳንድ ግዜ ሲጨንቃቸው እና ነገሮችን ማስተካከል ሲያቅጣቸው፥ እጃቸውን ያሻሉ ያስተካክላሉ። በውስጥ ታዋቂነት እሷ የሚለው፣ እየሩሳሌምን ነው። “ስለሷ ማንም አልገደደውም ”
Lamentations 4:7
አለቆችዋ ከበረዶ ይልቅ ጥሩ፥ ከወተት ይልቅ ነጭ ነበሩ
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 የእየሩሳሌም መሪዎች ጤነኛ ስለነበሩ ለመመልከት እራሱ የሚያምሩ ነበሩ ወይንም 2 መሪዎችዋ በህሊናቸው እንደ በረዶ ንፁህ እና እንደ ወተት የነጡ ናቸው።
አለቆችዋ
“የእየሩሳሌም መሪዎች”
ገላቸው ከቀይ ዕንቍ ይልቅ ቀይ ነበረ
“ሰውነታቸው ከቀይ ዕንቍ የቀላ” ይሄ ጤንነታቸውን ያመለክታል። “ሰውነታቸው ጤነኛ እና ቀይ ነበረ”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከቀይ ዕንቍ
ጠንካራ ቀይ ከባህር የሚገኝ ለማስጌጥ የሚጠቅም ድንጋይ
ሰንፔር
ውድ ሰማያዊ ቀለም ያለው የከበረ ድንጋይ ለማጌጫነት የሚውል።
ፊታቸው ከጥቀርሻ ይልቅ ጠቍሮአል
ይሄ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት ፡ 1 የመሪዎቻቸውን ቆዳ ፀሓይ አጥቁሮታል ወይንም 2 እየሩሳሌም ስትቃጠል የነካቸው ጭስ ፊታቸውን አጥቁሯቸዋል።
በመንገድም አልታወቁም
በቀጥታ መልኩ ፡ "ማንም አይቶ ሊለያቸው አልቻለም" ሊባል ይችላል።
ቁርበታቸው ወደ አጥንታቸው ተጣብቆአል
ከቆዳቸው ሥር ጮማም ሆነ ጡንቻ እንዳልነበረ ያሳያል።
ደርቆአል፤ እንደ እንጨት ሆኖአል
የደረቀው ቆዳቸው ከእንጨት ጋር ተመስሏል
Lamentations 4:9
በሰይፍ የሞቱ
"ሰይፍ" የሚለው የጠላታቸውን እነርሱን መውጋት ያመላክታል። በቀጥታ መልኩ "የጠላት ሰራዊት የገደላቸው" ሊባል ይችላል።
በራብ ከሞቱት
"ራብ" የሚያሳየው መራብን ነው። በቀጥታ መልኩ "በምግብ ማጣት የሞቱት" ሊባል ይችላል።
ደርቀው ያልቃሉ
"እጅግ በጣም የደረቁት እና የደከሙት"
እነዚህ የምድርን ፍሬ አጥተው ተወግተውም ቀጥነዋል
"የምድርን ፍሬ" የሚለው ስለ ምግብ መብላት የሚናገር ነው። የምግብ ማጣት ሰዎችን እንደሚወጋ ሰይፍ ተደርጎ ነው የተገለፀው። "ይበሉ ዘንድ በቂ ምግብ ስላልነበረ ነው የሞቱት"
የርኅሩኆች ሴቶች እጆች
እዚህ ጋር ሴቶቹ "በእጆች" ነው የተመሰሉት። እጅግ ተርበው ስለነበረ ድሮ በመልካምነት ይታወቁ የነበሩት እና ለልጆቻቸው ርህራሄን ያደርጉ የነበሩት፤ አሁን ልጆቻቸውን ለምግብነት ቀቀሏቸው። "ርህሩህ ሴቶች" ወይንም "ከዚህ በፊት ርህሩህ ሆነው የሚያውቁ ሴቶች"
መብል ሆኑአቸው
"ልጆቻቸው ለሴቶቹ ምግብ ሆኑ"
የወገኔ ሴት ልጅ
ይህ ቅኔአዊ የእየሩሳሌም ስም አገላለፅ ሲሆን፣እዚህ ጋር በሴት ይመስላታል። "ሕዝቤ"
Lamentations 4:11
እግዚአብሔር መዓቱን ፈጽሞአል፥ ጽኑ ቍጣውን አፍስሶአል
እግዚአብሔር በጣም ተቆጦቷል፤ መቆጣቱንም ለማሳያት ሁሉንም አድርጓል።
ጽኑ ቍጣውን አፍስሶአል
የእግዚአብሔር ሕዝቡን መቃጣት የእርሱ ቁጣ እየተቃጠለ በሚፈስ ፈሳሽ ተገልጿል። "እጅግ ከመናደዱ የተነሳ፤ ሕዝቡን ቀጣ" ወይንም "በታላቅ ቁጣ ለሕዝቡ ምላሽን ሰጠ"
እሳትን በጽዮን ውስጥ አቃጠለ
እግዚአብሔርን ሲወክል፤ እርሱም የእስራኤል ጠላቶች እሳትን እንዲጀምሩ አድርጓል። "በጽዮን እሳት እንዲጀምር አድርጓል "
መሠረትዋንም በላች።
"መሠረትዋ" የሚለው የሚወክለው ሙሉ ከተማዋን ይወክላል፤ በስተመጨረሻ ሊፈርስ የሚችለውንም ክፍል ጨምሮ። "ከተማዋን ያቃጠለው፣እስከ መሰረትዋ"
Lamentations 4:12
የምድር ነገሥታት በዓለምም የሚኖሩ ሁሉ . . . አላመኑም
"የምድር ነገሥታት፣ ወይም ከዓለም ሕዝብ አንዳቸውም አላመኑም"
አስጨናቂና ጠላት
ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ሲሆኑ ጸሓፊው ማስረገጥ የሚፈልገው እየሩሳሌምን ለጎዱ የሚፈልጉ ጠላቶች እንዳሉ ነው። "ጠላቶችም ሆኑ ወራሪዎች" ወይንም "የትኛውም ዓይነት የእየሩሳሌም ጠላት"
ስለ ነቢያቶችዋ ኃጢአትና ስለ ካህናቶች በደል
ሁለቱ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ናቸው። "ከነቢያት ኀጢአት፣ ከካህናቷም መተላለፍ የተነሣ"
የጻድቃንን ደም በውስጥዋ ስላፈሰሱ
ካህናቱም ነብያቱም ሰው በመግደል ወንጀለኞች ሆኑ። "ደም ማፍሰስ የሚለው" መግደልን ይወክላል። "የጻድቃንን ደም አፍስሰዋልና"
Lamentations 4:14
ታውረው በመንገድ ላይ ተቅበዘበዙ
ካህናቶቹ እና ነብያቱ የሚሄዱበትን ባለማወቅ በመንገድ ላይ ስለሚባዝኑ በዓይነ ስውር ተመስለዋል። "እንደ ዓይነ ስውር በመንገድ ላይ ይባዝናሉ"
በደም እጅግ ረክሰዋል
"ረክሰዋል" የ ሚለው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ለማለት ነው። ካህናቶቹ እና ነብያቱ ሰዎችን የገደሉ በመሆናቸው በስርዓት ቆሽሸዋል፤ እግዚአብሔርንም ለማምለክ ወይንም ከሰዎች ጋር ለመሆን አይችሉም።
በደም እጅግ ረክሰዋል
"ባፈሰሱት ደም ረክሰዋል" ሊኖረው የሚችለው ትርጉም 1 ደማቸው በልብሳቸው ላይ አለ ወይንም 2 "ደም" የሚለው መግደልን ለማመልከት ነው
እናንተ ርኵሳን፥ ራቁ
"ሂዱ! እናንት ርኵሳን"
ራቁችሁም ሂዱ፥ አትንኩ
"ወግዱ! ወግዱ! አትንኩ"
Lamentations 4:16
በተናቸው
"ነብያት እና ካህናቱን በትኖአቸዋል"
ከእንግዲህ ወዲህ አይመለከታቸውም
"ከእንግዲህ ወዲያ አይጠብቃቸውም"
Lamentations 4:17
ዓይናችን ወደ ከንቱ ረዳታችን ገና ሲመለከት ጠፍቶአል
"በከንቱ ርዳታን ስንጠባበቅ፣ዐይኖቻችን ደከሙ"
ረዳታችን
"ርዳታን" ወይንም "ሠዎች እንዲረዱን"
በከንቱ
"ወደ ከንቱ"
ማዳን የማይቻለውን ሕዝብ ጠብቀናል
ሌላ ሕዝብ መጥቶ እንዲታደጋቸው ተስፋን አድርገው እንደነበረ ያሳያል። "ሊያድን ከማይችል ሕዝብ ርዳታ ጠበቅን"
ፍለጋችንን ተከተሉ
ጠላቶቻችን "እግር እግራችንን ተከታተሉን"
ፍጻሜያችን ቀርቦአል
"መጨረሻችን ቀርቦአል" ወይንም "ጠላቶቻችን በቅርቡ ያጠፉናል"
ፍጻሜያችን
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1 "መጨረሻችን" ከተማቸውን ሲያመላክት፣ ጠላቶቻቸው ከተማዋን ስለሚያጠፏት እና ስለሚማርኳቸው ሊኖሩባት አይችሉም፤ "መጨረሻችን" ወይንም "ጥፋታችን" 2 "ፍጻሜያችን" የሚለው የሕይወታቸውን ፍፃሜ ያሳያል፤ "ሞታችን" ወይንም "የመሞቻችን ግዜ"
ቀኖቻችንም ተቈጥረዋል
መቆጠር ማለት ትንሽ መሆንን ያሳያል። "ዕድሜያችን አልቆአል"
ፍጻሜያችን ደርሶአል
"ደርሷል" የሚለው ሊመጣ ይችል እንደነበረ እንደሚጠብቁት ያሳያል። "ፍጻሜያችን መጥቶአልና" ወይንም "ጠላቶቻችን ይዋጉን ነበር"
Lamentations 4:19
ከሰማይ ንስሮች ይልቅ፥ ጠላቶቻችን ፈጣኖች ናቸው
አሳዳጆቻችን ከሰማይ ንስር ይልቅ ፈጣኖች ሆኑ። ንስር ሌላ እንስሳን ለማደን በጣም ፈጣን ናቸው። "የሚያሳድዱን ከንስር ይልቅ ፈጣን ናቸው"
በምድረ በዳ ሸመቁብን
"ሊያጠቁን አደቡብን"
የሕይወታችን እስትንፋስ
ይሄ ክፍል የሚናገረው ስለ ንጉሱ ነው። እስትንፋስ እንደ ሆነ ተመስሎ ይናገራል፤ እስትንፋስ ሰውነትን በሕይወት ያኖራል፥ እናም ንጉሱ እየገዛቸው እና ከጠላት እየጠበቃቸው ሕዝቡን በ ሕይወት ያኖራቸዋል። "እንደ እስትንፋሳችን የሆነው እርሱ" ወይንም "ሕይወታችንን የሚጠብቀው እርሱ"
በእግዚአብሔር የተቀባው

"መቀባት" የሚለው የሚወክለው ንግስናን ነው። እግዚአብሔር ንጉስ እንዲሆን የሚፈልገውን እንዲቀቡለት ተናግሯል። "እግዚአብሔር ንጉስ ይሆን ዘንድ እንዲቀባ የመረጠው " ወይንም "እግዚአብሔ ር የመረጠው ንጉስ"
በወጥመዳቸው ተያዘ
"ወጥመዳቸው" የሚለው ጠላቶቹ ሊይዙ ያቀዱበትን ያሳያል። በቀጣታ መልኩም እንዲህ ሊገለጽ ይችላል፤ "በእቅዳቸው መሰረት ጠላቶቻችን የያዙት እርሱን ነው" ወይንም "ንጉሳችንን ለመያዝ ጠላቲቻችን እቅድን አወጡ፤ ደግሞም ያዙት "
ብለን አስበን ነበር
ይሄ አባባል ስለንጉሱ ይበልጥ እንድናውቅ ያደርገናል። ንጉሱ ከመጠመዱ በፊት ያደርግልናል ብለው ተስፋ አድርገው የነበረውን ያሳያል። በቀጥታ መልኩም ሊገለፅ ይችላል፤ "ስለ እርሱ እንዲህ ብለን ቢሆንም ኖሮ "
በጥላው ሥር በአሕዛብ መካከል እንኖራለን
"ጥላው" የሚለው የእርሱን ጥበቃ ያመለክታል። "በእርሱ ጥበቃ በአሕዛብ መሃከል እንኖራለን" ወይንም "በአሕዛብ መሃከል መኖር ቢኖርብንም፤ እርሱ ይጠብቀናል"
ደስ ይበልሽ፤ ሐሴትም አድርጊ
"ደስ" እና "ሓሴት" ማድረግ ማለት ተመሳሳይ ነገር ሲሆን የተደገመውም ጉዳዩ ላይ ትኩረት ለመስጠት ነው። ጸሓፊው እነኝህን ቃላት የሚጠቀመው ሰዎቹላይ እንደማፊዝ ነው። ኤዶማውያን በእስራኤል መፍረስ ደስ እንዲሚሰኙ ያውቃል።

"እጅግ ደስ ይበላችሁ"
Lamentations 4:21
የኤዶምያስ ሴት ልጅ
በኤዶም ይኖሩ የነበሩ ሰዎች በሴት ተመስለዋል። የእስራኤላውያን ጠላቶች ነበሩ።
ነገር ግን ለአንቺም ደግሞ ጽዋው ይደርስሻል
ጽዋ የሚለው የሚያሳየው ቅጣትን ነው። "ነገር ግን እግዚአብሔር እራሱ ይቀጣችኋል"
የጽዮን ልጅ ሆይ
የእየሩሳሌም ሰዎች በሴት ተመስለዋል።
ቅጣትሽ ያበቃል
"ቅጣትሽ ያበቃል" ቅጣት የሚለው ቃል በቀጥታ፥ በ"መቅጣት" ሊተካ ይችላል። "እግዚአብሔር ይቀጣችኋል"
የስደትሽን ዘመን አያራ ዝምም
"እግዚአብሔር የስደትሽን ዘመን አያራ ዝምም" ወይንም እግዚአብሔር ከዚህ በላይ በስደት እንድትቆዪ አያደርግም"
ክፋትሽንም ይፋ ያወጣል
በሌሎች የማይታወቁ ኃጥያቶች በሆነ ነገር እንደተሸፈኑ ናቸው። መሸፈኛውን ማንሳት ማለት ሌሎች ሰዎች እንዲያውቁት ማድረግ ማለት ነው። "ኃጥያትሽን ይገልጠዋል" ወይንም "ኃጥይት እንደሰራሽ ሌሎች ሰዎች እንዲያውቁ ያደርጋል"

---

Chapter 5
Lamentations 5:1
አቤቱ፥ የሆነብንን አስብ
"አስብ" የሚለው ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። "አቤቱ፥ የሆነብንን አስታውስ"
ተመልከት ስድባችንንም እይ
"ውርደታችንን እይ፤ ተመልከትም"
ርስታችን ለመጻተኞች፣ ቤቶቻችን ለባዕዳን ዐልፈው ተሰጡ
በቀጠተኛ አገላለፅም ሊቀመጥ የሚችል ዓረፍተ ነገር ነው። "ርስታችን ለእንግዶች፥ ቤቶቻችን ለሌሎች አሳልፈህ ሰጠህ" ወይንም "ርስታችን ለእንግዶች፥ ቤቶቻችን ለሌሎች ታልፈው እንዲሰጡ ፈቀድክ።
ወላጅ አልባና አባት የሌላቸው ሆንን ፤ እናቶቻችን እንደ መበለቶች ሆኑ
የእየሩሳሌም ሰዎች ለጠብቃቸው የሚችል ማንም የለም፤ ምክንያቱም ወንዶች ልጆቻቸው ወይ በጦርነት ላይ ሞተዋል አልያም ደግሞ በምርኮ ተወስደዋል። ይህ ደግሞ የሚያመላክተው በእስራኤል የቀሩት ወላጅ አልባዎች እና መበለቶች መሆናቸውን ነው።
ወላጅ አልባና አባት የሌላቸው
እነኚህ ቃላት አንድ አይነት ትርጉም ሲኖራቸው፤ አባት የሌላቸው ሰዎችን ያመላክታል
ውኃችንን በብር ጠጣን እንጨታችንን በዋጋ ገዛን
ይህ የሚያሳየው በአንድ ግዜ በነፃ ይጠቀሙ የነበሩትን ውሃ እና እንጨት ጠላቶቻቸው እያስከፈሏቸው እንደሆነ ነው። "የራሳችን የሆነውን ውሃ ለመጠጣት እና የራሳችንን እንጨት ለመጠቀም መክፈል አለብን"
እንጨታችንን በዋጋ ገዛን
ይሄ በቀጥታ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። "ጠላቶታችን የገዛ እንጨታችንን ይሸጡልናል"
Lamentations 5:5
አሳዳጆቻችን
"የሚያሳድዱን ጠላቶቻችን" ይሄ የሚያመላክተው ባቢሎናውያንን ነው።
ዕረፍትም የለንም
ይህ አባባል "ዕርፍትን" ተፈልጎ እንደሚገኝ ቁስ አድርጎ ይገልፀዋል። "ማረፍ አልቻልንም"
እንጀራ እንጠግብ ዘንድ፣ ለአሦርና ለግብፅ እጃችንን ሰጠን
"ሰጠን" የሚለው ዘይቤአዊ አገላለፅ ነው። "የምንበላውን እናገኝ ዘንድ ከአሦርና ከግብፅ ጋር ስምምነትን አደረግን" ወይንም "በሕይወት እንኖር ዘንድ እንድንበላ ዘንድ ለአሦርና ለግብፅ ተማርከናል"
የሉም
ይህ የሚያመላክተው መሞታቸውን ነው። "አለፉ" ወይንም "ሞተዋል"
እኛም በደላቸውን ተሸከምን
"በደል" የሚለው ከአባቶቻቸው ኃጥያት ምክንያት የመጣ ቅጣትን ያመላክታል። "የኃጥያታቸውን ቅጣት ተሸክመናል"

Lamentations 5:8
ባሪያዎች ሠልጥነውብናል
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1 "በእኛ ላይ እየሰለጠኑ ያሉት እራሳቸው በባቢሎን ሐገር ጌቶች ያላቸው ሰዎች ናቸው።" 2 በባቢሎን ሃገር ባርያ የነበሩ ሰዎች ናቸው አሁን በእኛ ላይ የሰለጠኑት"
ከእጃቸው የሚታደገን
"እጅ" የሚለው ቃል የሚያመላክተው ቁጥጥርን ነው። "ከቁጥጥራቸው የሚታደገን"
እንጀራ
"እንጀራ" የሚለው በአጠቃላይ ምግብን ነው የሚያመላክተው። "ምግብ"
ከምድረ በዳ ሰይፍ የተነሣ
በሰይፍ የሚገድሉ ወንበዴዎች ናቸው ሰይፍ ተበለው የተገለፀው "በምድረበዳ በሰይፍ የሚገድሉ ወንበዴዎች ስላሉ"
ከሚያቃጥል ከራብ ትኩሳት የተነሣ ቁርበታችን እንደ ምድጃ ጠቈረ
ይሄ የሚያመላክተው ከሰዎቹ የቆዳ ትኩሳት የተነሳ ሰውነታቸው ተቃጥሏል። ከረሃባቸው የተነሳ ትኩሳት ይዟቸዋል። "ቆዳችን የምጣድ ያህል ያተኩሳል፤ መቃጠላችንም ከረሃባችን የተነሳ ነው"
Lamentations 5:11
ሴቶች በጽዮን፣ ደናግል በይሁዳ ከተሞች ተደፈሩ
ሁለቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው፤ ማለት የሚፈልጉትም የሴቶቻቸው ክብር መነካቱን ነው። ተደፈሩ የሚለውም ለጽዮን ሴት ልጆችም ለደናግሎቹም ነው።
ሴቶች ... ደናግል ... ተደፈሩ
በቀጥታም አገላለፅ ለቀመጥ ይችላል፤ "ጠላቶቻችን ሴቶቻችንን ደፈሩ. . . ድንግሎቻችንንም" ወይንም "ጠላቶቻችን የሴቶቻችንን ክብር ነክተዋል . . . የደናግሎቻችንንም"
አለቆች በእጃቸው ተሰቀሉ
ሊሆን የሚችለው ትርጉም 1 "እነርሱ" የሚለው በውስጥ ታዋቂ ያለው ቃል የሚናገረው ስለጠላቶ ቻቸው ነው ፤ "በእነርሱ እጅ አለቆች ተሰቀሉ" 2 የአለቆቹን እጆች አስረው፤ እግራቸውን ከመሬት ከፍ አርገው አንጠልጥለው አሰሯቸው።
ሽማግሌዎችም አልተከበሩም
በቀጠታ መልኩም ሊገለፅ ይችላል፤ "ለሽማግ ሌዎቹም ምንም ክብር አላሳዩአቸውም"
Lamentations 5:13
ጐልማሶች ... ተገደዱ
ይህ በቀጠታ መልኩም ሊገለፅ ይችላል፤ "ጎልማሶቹንም አስገደዷቸው"
ወንዶች ልጆች በዕንጨት ሸክም ተንገዳገዱ
ወንዶች ልጆች የዕንጨት ሸክም እንዲሸከሙ ተገደዱ። "ከባድ የእንጨት ሸክም በመሸከማቸው ወንዶች ልጆች ተንጎደጎዱ" ወይንም "ወንዶች ልጆች የዕንጨት

ሽክም እንዲሸከሙ በመገደዳቸው ተንገደገዱ”
ከከተማዪቱ በር
ሽማግሌዎች ሕጋዊ ምክር የሚሰጡበት ቦታ ሲሆን፤ ሰዎችም ለማህበራዊ ግንኙነቶች ይገናኙበታል።
ጐልማሶች ዝማሬያቸውን አቁመዋል
በከተማይቱ በር ላይ በሚደረጉ ማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ ሙዚቃ መጫወት አንዱ ልማድ ሲሆን፤ አሁን ግን ጎልማሶቹ ትተዉታል። “ ጐልማሶች ሙዚቃ መጫወት አቁመዋል”
Lamentations 5:15
የልባችን ደስታ
”ልብ” የሚለው ሙሉ ሰውነትን ሲያመላክት ስሜትን ግን በይበልጥ ያመላክታል። “ደስታችን”
አክሊል ከራሳችን ወድቆአል
ሊኖረው የሚችለው ትርጉም፤ 1 ለበዓል በራሳችን ላይ አበባን አናደርግም ወይንም 2 “አክሊል” የሚለው የሚያመላክተው ንጉሶቻቸውን ሲሆን “ራስ” የሚለው ደግሞ የሥልጣን ቦታን ያሳያል። “ንጉስ አልባ ሆነናል።”
Lamentations 5:17
ከዚህ የተነሣ ልባችን ደከመ
“ልብ” የሚለው ስሜትን ሲያመላክት፤ በስሜት የመታመም ያህል ተስፋ መቁረጥን ያሳያል። “በዚህም ምክንያት ተስፋ ቆርጠን ነበር”
ከእነዚህ የተነሣም ዐይናችን ፈዘዘ
ከማልቀሳቸው የተነሳ ማያት አቃታቸው። “እንባ ከመሙላታቸው የተነሳ ማያት አልቻልንም”
ስለ ጽዮን ተራራ፥ ባድማ ሆናለችና
ባዶዋን የቀረችው የጽዮን ተራራ
ቀበሮች
እነዚህ ኋይለኛ የዱር ውሾች ናቸው።
Lamentations 5:19
አንተ ለዘላለም ትገዛለህ
ይሄ የሚያመላክተው ንግስናን እና መግዛትን ነው። “እንደ ንጉስ ግዛ ”
ከትውልድ እስከ ትውልድ
ዘይቤአዊ አገላለጽ ሲሆን። “ሁልግዜ” ለማለት ነው
ለምን ፈጽመህ ትረሳናለህ? ስለምንስ ለረዥም ጊዜ ትተወናለህ?
እግዚአብሔር እረስቶናል የሚለውን ሃሳብ ለማስተላለፍ ጸሓፊው ምልሽ የማይሰጠው ጥያቄን ይጠይቃል። በዓረፍተ ነገር መልኩም ሊጻፍ ይቻላል። “ለዘላለም ልትረሳን የመሰላል፤ ተመለሰህም ለረጅም ግዜ ላትመጣ።”
ወደ አንተ መልሰን
”ወደራስህ መልሰን“
ዘመናችንን እንደ ቀድሞው አድስ
ዘመናችን የሚለው ሕይወታችውን ነው። “ሕይወታችንን ቀድሞ እንደነበረው መልካም አድርገው” ወይንም “ቀድሞ ታላቅ እንደነበርነው ታላቅ አርገን”
ፈጽመህ ካልጣልኸን፣ ከመጠን በላይ ካልተቈጣኸን
ሊኖር የሚችለው ትርጉም፤ 1 ጸሓፊው እግዚአብሔር አይመልሳቸው ዘንድ ተቆጥቶ እንዳይሆን ፈርቷል ወይንም 2 ጸሓፊው ማለት የፈለገው እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለተቆጣ አይመልሳቸውም
ከመጠን በላይ ካልተቈጣኸን
ይህ የሚያመላክተው የእግዚአብሔርን ሊለካ የማይችን የህል የተለቀ ቁጣ ነው። የማጋነን ዓይነት አገላለፅ ነው። “እጅግ ተቆጣኸን”

---

Chapter 1
Ezekiel 1:1
በሠላሳኛው ዓመት
ይህ የሕዝቅኤል ሠላሳኛው ዕድሜ ነው። (ደረጃን የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ተመልከት)
አራተኛው ወር፣ የወሩም አምስተኛው ቀን
“የአራተኛው ወር አምስተኛው ቀን”። ይህ በዕብራውያን የቀን አቆጣጠር አራተኛው ወር ነው። በምዕራባውያኑ አቆጣጠር አምስተኛው ቀን የሰኔ ወር መጨረሻ አካባቢ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ደረጃን የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ተመልከት)
እንዲህ ሆነ
እዚህ ጋ ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አስፈላጊ የሆነውን ሁነት ለማመላከት ነው። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ጋ መጠቀም እንደምትችል አስብ።
በምርኮኞቹ መካከል እኖር ነበር
“እኔ” የሚለው ቃል ሕዝቅኤልን ያመለክታል። “እኔ ከምርኮኞቹ አንዱ ነበርኩኝ”
የእግዚአብሔርን ራዕዮች አየሁ
“እግዚአብሔር ያልተለመዱ ነገሮችን አሳየኝ”
ንጉሡ ዮአኪን የተማረከበት አምስተኛ ዓመት ነበር
በመጽሐፉ ሁሉ፣ ሕዝቅኤል ትንቢቶቹን መናገር የሚጀምረው ዮአኪን ኢየሩሳሌምን ለቆ እንዲሄድ ባቢሎናውያን ካስገደዱት ጊዜ ጀምሮ ነው።
ወደ ሕዝቅኤል ... በዚያ በእርሱ ላይ
ሕዝቅኤል ሌላ ሰው ይመስል ስለ ራሱ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ወደ እኔ ወደ ሕዝቅኤል ... በዚያ በእኔ ላይ” (ተውላጠ ስም የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሕዝቅኤል መጣ
“የእግዚአብሔር ቃል ወደ -- መጣ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልዕክት ለማሳወቅ ነው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል መልዕክት ሰጠው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ቡዝ
የአንድ ሰው ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የኮቦር ቦይ
ይህ ከለዳውያን የአትክልት ቦታቸውን ለማጠጣት የቆፈሩት ወንዝ ነው። “የኮቦር ወንዝ”
የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ ነበረች
አብዛኛውን ጊዜ “እጅ” ጥቅም ላይ የዋለው የአንድን ሰው ኃይል ወይም ተግባር ለማመልከት ነው። አንድ ሰው እጁን በሌላው ላይ ሲያደርግ፣ በዚያ ሰው ላይ ኃይል ይኖረዋል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር እየተቆጣጠረው ነበር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን ራሱን ለሕዝቡ የገለጠበት የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህንን እንዴት መተርጎም እንደሚኖርብህ ለማወቅ ስለ እግዚአብሔር የቃል ገጽን ትርጉም ተመልከት።
Ezekiel 1:4
ዐውሎ ንፋስ
ይህ ከፍተኛ የንፋስ ግፊት ያለበት ዐውሎ ነው።
ከሰሜን ይመጣ ነበር
ሰሜን ማለት ፀሐይ ስትወጣ በምታያት ጊዜ በስተግራህ ያለ አቅጣጫ ማለት ነው።
በውስጡ እሳት የሚነድበት ታላቅ ደመና
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። “ዐውሎው በውስጡ እሳት የሚነድበት በጣም ታላቅ ደመና ነበረው”
እሳት የሚነድበት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የመብረቅ ብልጭታ” ወይም 2) “የማያቋርጥ መብረቅ” የሚሉት ናቸው።
ብሩህነት ዙሪያውን ከቦት እና ውስጡን ሞልቶት
“በጣም ብሩህ የሆነ ብርሃን በደመናው ዙሪያና በውስጡም ነበር”
የሙጫ መልክ
“እንደ ሙጫ ያለ ብሩህ ቢጫ” ወይም “ብሩህ ቢጫ” ወይም “ደማቅ ቢጫ”
ሙጫ
ጌጣ ጌጥን ለማስዋብ ጥቅም ላይ የሚውል ደማቅ ቢጫ ሙጫ
በመካከል
“በዐውሎው መካከል”
የአራት ሕያው ፍጡር አምሳያ
እዚህ ጋ የነገር ስም የሆነው “አምሳያ” ትርጉሙ ሕዝቅኤል ያያቸውን እንደ እነዚህ ያሉ ነገሮችን የሚመስሉትን ነው። ቃሉ ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “አራት ሕያዋን ፍጡራንን የሚመስሉ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
መልካቸው ይህንን ይመስል ነበር
የነገር ስም የሆነው “መልክ” እንደ ግሣዊ ሐረግ ሆኖ መተርጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ይህንን ይመስሉ ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሰው መልክ ነበራቸው
የነገር ስም የሆነው “መልክ” እንደ ግሣዊ ሐረግ ሆኖ መተርጎም ይችላል። አ.ት፡ “አራቱ ፍጡራን ሰዎችን ይመስሉ ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ሆኖም እያንዳንዳቸው አራት ፊት ነበራቸው፣ ለእያንዳንዱ ፍጡርም አራት ክንፍ ነበራቸው
“ሆኖም እያንዳንዳቸው አራት የተለያየ ፊትና አራት ክንፍ ነበራቸው”። እያንዳንዱ ፍጡር በፊት ለፊቱ፣ በስተኋላውና ከራሱ ሁለት ወገን ላይ ፊት ነበረው።
Ezekiel 1:7
ሆኖም የእግሮቻቸው መዳፍ የጥጃ ኮቴዎችን ይመስል ነበር
“ሆኖም እግሮቻቸው የጥጃ ኮቴዎችን ይመስሉ ነበር” ወይም “ሆኖም እግሮቻቸው የጥጆችን እግር ይመስል ነበር”
የጥጃ ኮቴዎች
የጥጃ እግር ጠንካራው ክፍል
እንደ ተወለወለ ነሐስ ያብለጨልጭ ነበር
“እንደ ተወለወሉ ነሐሶች ያብለጨልጩ ነበር”። ይህ የፍጡራኑን እግሮች ይገልጻል። አ.ት፡ “እንደ ተወለወለ ነሐስ ያብለጨልጩ ነበር”
በአራቱም በኩል
“በአካላቸው በአራቱም በኩል”
የአራቱም ፊታቸውና ክንፎቻቸው ይህንን ይመስል ነበር
“የአራቱ ፍጡራን ክንፎችና እግሮች ይህንን ይመስል ነበር”
በሚሄዱበት ጊዜ ዘወር አይሉም ነበር
“ፍጡራኑ በሚጓዙበት ጊዜ ዘወር አይሉም ነበር”
Ezekiel 1:10
የፊታቸው መልክ የሰውን ፊት ይመስል ነበር
ሕዝቅኤል የፍጡራኑን የፊት ለፊት ገጽታቸውን ይገልጻል። የነገር ስም የሆነው “መልክ” ማለት ለሕዝቅኤል የሰው ፊት መስሎ የታየው ነው። ቃሉ ወደ ግሣዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የእያንዳንዱ ፍጡር ፊት የሰውን ፊት ይመስል ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
በስተቀኛቸው አራቱም የአንበሳ ፊት ነበራቸው
“በእያንዳንዳቸው ራስ በስተቀኝ ያለው ፊታቸው የአንበሳ ፊት ይመስል ነበር”
በስተግራቸው አራቱም የበሬ ፊት ነበራቸው
“በእያንዳንዳቸው ራስ በስተግራ ያለው ፊታቸው የበሬ ፊት ይመስል ነበር”
አራቱም የንስር ፊት ደግሞ ነበራቸው
“በእያንዳንዳቸው ራስ በስተኋላ ያለው ፊታቸው የንስርን ፊት ይመስል ነበር”
እያንዳንዱ ፍጡር የሌላውን ፍጡር ክንፍ የሚነኩ ጥንድ ክንፎች ነበሩት፣ ክንፎቻቸው ወደ ላይ ተዘርግቶ ነበር
“እያንዳንዱ ፍጡር ሁለት ክንፎች ነበሩት፣ አንደኛው ክንፉ በአንድ በኩል ያለውን ፍጡር ክንፍ ይነካ ነበር፣ ሌላኛው ክንፉ በሌላ በኩል ያለውን ፍጡር ክንፍ ይነካ ነበር”
ደግሞም በጥንድ ክንፎቻቸው አካላቸውን ይሸፍኑ ነበር
ይህ እንደ አዲስ ዐረፍተ ነገር መተርጎም ይችላል። “የእያንዳንዱ ፍጡር ሁለት ክንፎቻቸው አካሉን ይሸፍኑት ነበር”
እያንዳንዱ ወደ ፊት ቀጥ ብሎ ይሄድ ነበር
“እያንዳንዱ ፍጡር ወደ ፊት እያየ ይጓዝ ነበር”
Ezekiel 1:13
የሕያዋን ፍጡራኑን መልክ አስመልክቶ፣ ገጽታቸው የእሳት ፍም ይመስል ነበር
የነገር ስም የሆነው “መልክ” ማለት እነዚህ ነገሮች ምን እንደሚመስሉ ሕዝቅኤል ያያቸው ናቸው። “መልክ” እና “ገጽታ” ሁለቱም የነገር ስም ሲሆኑ ወደ ግሥነት ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “የሕያዋን ፍጡራኑ መልክ ከእሳት ፍም ጋር የሚመሳሰል ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
የመብረቅ ብልጭታዎች ነበሩ
“ከእሳቱ መብረቅ ወጣ”
ሕያዋኑ ፍጡራን በዝግታ ወደ ፊትና ወደ ኋላ ይሄዱ ነበር፣ መብረቅ ይመስሉም ነበር
መብረቁ ይበራና ወዲያው ይጠፋ ነበር፣ ፍጡራኑም ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው በፍጥነት ይንቀሳቀሱ ነበር። የነገር ስም የሆነው “ገጽታ” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሕያዋኑ ፍጡራን በዝግታ ወደ ፊትና ወደ ኋላ ይሄዱ ነበር፣ መብረቅ ይመስሉም ነበር” (Simile እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 1:15
የመንኰራኵሮቹ ገጽታና መዋቅር ይህንን ይመስል ነበር
“የመንኰራኵሮቹ መልክና አሠራር ይህንን ይመስል ነበር”
እንደ ቢረሌ
ቢረሌ በአብዛኛው ቢጫ ወይም ወርቃማ ቀለም ያለው ንጹሕ የከበረ የድንጋይ ዓይነት ነው። “እንደ ቢረሌ ድንጋይ ንጹሕና ቢጫ” ወይም “እንደ ከበረ ድንጋይ ንጹሕና ቢጫ”
አራቱም ተመሳሳይ መልክ ነበራቸው
እዚህ ጋ፣ የነገር ስም የሆነው “መልክ” አራቱ መንኰራኵሮች ምን ይመስሉ እንደነበር ያመለክታል። ቃሉ ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “አራቱም መንኰራኵሮች ይመሳሰሉ ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ገጽታቸውና አሠራራቸው አንዱ መንኰራኵር ከሌላው መንኰራኵር ጋር ተላልፎ የተያዘ ይመስል ነበር
“ገጽታ” እና “አሠራር” የሚሉት የነገር ስሞች እንደ ግሥ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አ.ት፡ “አንደኛው መንኰራኵር በሌላኛው መንኰራኵር ውስጥ አልፎ የተሠራ ይመስል ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 1:17
በየትኛውም በአራቱ አቅጣጫዎች ይሄዱ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የእነርሱ” የሚያመለክተው ፍጡራኑን ነው። አ.ት፡ “ፍጡራኑ ወደሚመለከቷቸው ከአራቱ አቅጣጫዎች በየትኛውም ቀጥ ብለው ይሄዱ ነበር” ወይም 2) “የእነርሱ” የሚያመለክተው መንኰራኵሮቹን ነው የሚሉት ናቸው።
የክበብ ጠርዛቸው
“የመንኰራኵሮቹ ክበብ ጠርዛቸው ይህንን ይመስል ነበር”
ረጅምና አስፈሪ ነበሩ
“የክበቦቹ ጠርዞች በጣም ረጅምና አስገራሚ ነበሩ” ወይም “የክበቦቹ ጠርዞች ረጅምና አስፈሪ ነበሩ”
የክበቦቹ ጠርዞች ዙሪያቸውን በዐይን የተሞሉ ነበሩ
“ምክንያቱም በአራቱም መንኰራኵሮች ዙሪያ በክበቦቹ ጠርዞች ላይ በጣም ብዙ ዐይኖች ነበሩባቸው”
Ezekiel 1:19
ሕያዋኑ ፍጡራን ከመሬት በሚነሡበት ጊዜ
ፍጡራኑ ምድርን ከለቀቁ በኋላ በአየር ላይ ይበሩ ነበር። አ.ት፡ “ፍጡራኑ ምድርን ለቀው ወደ አየር በሚወጡበት ጊዜ” (See: Assumed Knowledge and Implicit Information)
መንኰራኵሮቹም ደግሞ ወደ ላይ ተነሡ
“መንኰራኵሩም ደግሞ ምድርን ለቆ ወደ አየር ወጣ”
መንፈስ ወደሚሄድበት ሁሉ እነርሱም ሄዱ
“እነርሱ” የሚለው ቃል ፍጡራኑን ያመለክታል።
በአጠገባቸው መንኰራኵሮቹ ተነሡ
“መንኰራኵሮቹ ከሕያዋን ፍጡራኑ ጋር ወደ አየር ላይ ወጡ”
የሕያው ፍጡሩ መንፈስ በመንኰራኵሮቹ ውስጥ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሕዝቅኤል አንድ ፍጡር የሆኑ በሚመስል መልኩ የሚናገረው በቁጥር 19 ስላሉት “ፍጡሮች” ነው። አ.ት፡ “የሕያዋን ፍጡራኑ መንፈስ በመንኰራኵሮቹ ውስጥ ነበር” ወይም 2) ሕዝቅኤል የአነጋገር ዘይቤን ይጠቀማል። አ.ት፡ “የሕይወት መንፈስ በመንኰራኵሮቹ ውስጥ ነበር” ወይም “ሕያው መንፈስ በመንኰራኵሮቹ ውስጥ ነበር” ወይም 3) በፍጡራኑና በመንኰራኵሮቹ ውስጥ የነበረው መንፈስ አንድ ነበር። አ.ት፡ “ለፍጡራኑ ሕይወት የሰጣቸው ያው መንፈስ ለመንኰራኵሮቹም ደግሞ ሕይወትን ሰጣቸው” የሚሉት ናቸው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 1:22
የተስፋፋ የጠፈር መልክ
እዚህ ጋ፣ የነገር ስም የሆነው “መልክ” ማለት “የተስፋፋ የጠፈር መልክ” መስሎ ለሕዝቅኤል የታየው ነው። ቃሉ በግሣዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “የተስፋፋ ጠፈር ይመስል የነበረው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
የተስፋፋ ጠፈር
ጠፈሩ በግማሽ የተቆረጠ ክፍት ኳስ ይመስል ነበር። “የተስፋፋ” ማለት በጣም ሰፊ ማለት ነው። “ከላይ ወደ ታች የተደፋ ትልቅ ጓድጓዳ ሳህን”
ግርምት ቀስቃሽ መስታወት መሰል ድንጋይ
“ግርምት ቀስቃሽ በረዶ” ወይም “ሰዎች በሚያዩት ጊዜ እንዲደነቁ የሚያስደርጋቸው መስታወት መሰል ድንጋይ”
ከራሳቸው በላይ ተዘርግቷል
“ተስፋፊው ጠፈር ከፍጡራኑ ራስ በላይ ተዘርግቶ ነበር” ወይም “ተስፋፊው ጠፈር ከፍጡራኑ ራስ በላይ ሰፊ ቦታ ይዞ ነበር”

ከጠፈሩ ስር
“ከጠፈሩ በታች”
እያንዳንዱ ሕያዋን ፍጡራን ደግሞ ራሳቸውን የሚሸፍኑበት ጥንድ ክንፍ ነበራቸው፤ እያንዳንዱ የራሱን አካል የሚሸፍንበት ጥንድ ክንፍ ነበረው
“እያንዳንዱ ሕያው ፍጡር አካላቸውን የሚሸፍኑባቸው ሌላ ሁለት ክንፍ ነበራቸው”
Ezekiel 1:24
ከዚያም የክንፎቻቸውን ድምፅ ሰማሁ። እንደ ብዙ ውኆች ድምፅ ያለ፣ በሚሄዱበት ሁሉ እንደ ሁሉን ቻዩ ድምፅ ያለ።
“በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቷቸው ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ትርጉሞች 1) በዚህ ቁጥር ፊት ያሉት ቃላት ሁሉ “በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ የክንፎቻቸውን ድምፅ ሰማሁ። እንደሚጎርፍ ውሃ ድምፅ ያለ፤ እንደ ሁሉን ቻዩ ድምፅ ያለ፤” ወይም 2) “ክንፎች፣ እንደሚጎርፍ ውሃ ድምፅ ያለ፤ እንደ ሁሉን ቻዩ ድምፅ ያለ፤ በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ እንደ --- ያለ ድምፅ” የሚሉት ቃላት ይከተሏቸዋል የሚሉት ናቸው።
እንደ ... ውኆች። እንደ ... የሚሄዱበት። እንደ ... የዝናብ ማዕበል። እንደ ... ሰራዊት።
ሕዝቅኤል ባየው ነገር መደነቁን በማሳየት ላይ ስለ ነበር እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች የተሟሉ አይደሉም። እንደ ሙሉ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎሙ ይችላሉ፡ “ክንፎቹ እንደ ... ውሃ ድምፅ ነበር። በሚሄዱበት እንደ ... ድምፅ ነበር። እንደ ... የዝናብ ማዕበል ድምፅ ነበር። እንደ ... ሰራዊት ድምፅ ነበር” (See: Simile)
ብዙ ውኆች
ይህ ማለት በቀላሉ “ብዙ ውሃ” ማለት ነው። ይህ ከፍተኛ ድምፅ ያለውን ወንዝ ወይም ታላቅ ፏፏቴን ወይም በውቅያኖስ ላይ የሚጋጩ ሞገዶችን ሊያመለክት ይችላል። እነዚህ ሁሉ ከፍተኛ ድምፅ ያላቸው ናቸው።
እንደ ሁሉን ቻዩ ድምፅ ያለ
መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ጊዜ ነጎድጓድን እንደ “የሁሉን ቻዩ ድምፅ” አድርጎ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ድምፁ የሁሉን ቻዩን አምላክ ድምፅ ይመስል ነበር” ወይም “እርሱ የሁሉን ቻዩን ነጎድጓድ ድምፅ ይመስል ነበር” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እንደ ዝናብ ማዕበል ድምፅ ያለ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እንደ ታላቅ ማዕበል ድምፅ ያለ” ወይም 2) “እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ያለ” የሚሉት ናቸው። ኢ.ት፡ “እንደ ታላቅ ማዕበል ድምፅ ያለ ታላቅ ድምፅ ነበር” ወይም “እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ያለ ታላቅ ድምፅ ነበር” (See: Simile)
በሚቆሙበት ጊዜ ሁሉ
“ፍጡራኑ እንቅስቃሴያቸውን በሚያቆሙበት ጊዜ ሁሉ”
ክንፎቻቸውን ዝቅ ያደርጉ ነበር
“ፍጡራኑ ክንፎቻቸው በጎናቸው እንዲወርዱ ያደርጉ ነበር”። ይህንን ያደረጉት ክንፎቻቸውን ለመብረር በማይጠቀሙበት ጊዜ ነበር።
ከጠፈሩ በላይ አንድ ድምፅ መጣ
“ከጠፈሩ በላይ የነበረ አንድ ሰው ተናገረ”። ይህ የማን ድምፅ እንደሆነ መናገር ከፈለግህ ምናልባት የእግዚአብሔር ድምፅ እንደሆነ መግለጽ ይኖርብሃል (ሕዝቅኤል 1፡3)።
Ezekiel 1:26
ከራሳቸው በላይ
“ከፍጡራት ራስ በላይ”
የዙፋን መልክ ነበረው
እዚህ ጋ፣ የነገር ስም የሆነው “መልክ” ማለት ሕዝቅኤል ዙፋን መስሎ የታየው ነበር። ቃሉ በግሣዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ዙፋን ይመስል ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ሰንፔር
የጠራ ሰማያዊና በጣም አንጸባራቂ የሆነ በጣም ውድ ድንጋይ
የዙፋን መልክ በነበረው ላይ
የነገር ስም የሆነው “መልክ” በግሣዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ዙፋን በሚመስለው ላይ --- ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
መልኩ የሰው ገጽታ ያለው የሚመስል
የነገር ስሞች የሆኑት “መልክ” እና “ገጽታ” በግሣዊ ሐረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። ይህ ማን እንደሆነ መናገር ከፈለግህ ምናልባት እግዚአብሔር እንደሆነ መናገር ይኖርብሃል (ሕዝቅኤል 1፡3)። ኢ.ት፡ “ሰውን መስሎ ከሚታየው ጋር የሚመሳሰል አንዳች ነገር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 1:27
ከወገቡ በላይ ያለው ገጽታ
ከወገቡ በላይ ያለው የሰውየው አካል እሳት ያለበት የጋለ ብረት ይመስል ነበር። የነገር ስም የሆነው “ገጽታ” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ከወገቡ በላይ ይታይ የነበረው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ከወገቡ በታች ያለው ገጽታ ዙሪያው በሙሉ የእሳትና የብርሃን ገጽታ ነበረው
“ገጽታ” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ወገቡ መስሎ ከሚታይ ገጽታው በታች ዙሪያው እሳትና ብሩህ ብርሃን የሚመስል አየሁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
በዝናባማ ቀን በደመና ውስጥ የሚታይ የቀስተ ደመና ገጽታን የሚመስል ብሩህ ብርሃን ከቦት ነበር
“ገጽታ” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የከበበው ብሩህነት ልክ በዝናባማ ቀን በደመና ውስጥ የሚታየውን ቀስተ ደመና ይመስል ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ቀስተ ደመና
ፀሐይ ከተመለካቹ በስተኋላ በምትወጣበት ጊዜ በዝናብ ውስጥ የሚታይ ልዩ ልዩ የብርሃን ቀለማት
እርሱም የእግዚአብሔር መልክ አምሳያ ነበር
“አምሳያ” የሚለው የነገር ስም ትርጉሙ ሕዝቅኤል ሲያየው የእግዚአብሔርን ክብር ይመስል የነበረው ነው። “አምሳያ” እና “መልክ” ሁለቱም ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎሙ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ክብር መስሎ ይታይ ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
በግንባሬ ተደፋሁ
“በምድር ላይ ሰገድሁ” ወይም “በምድር ላይ ተጋደምሁ”። ሕዝቅኤል የወደቀው በአደጋ ምክንያት አይደለም። ወደ ምድር ዝቅ ያለው እግዚአብሔርን መፍራቱንና ማክበሩን ለማሳየት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
አንድ የሚናገርን ድምፅ ሰማሁ
“ድምፅ” የሚለው ቃል ሰውን የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ሲናገር ሰማሁ” ወይም “አንድ ሰው ተናገረ፣ እኔም ድምፁን ሰማሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 2
Ezekiel 2:1
ተናገረኝ
የአንተ ቋንቋ ተናጋሪውን መለየት ካለበት “አንድ ሰውን የሚመስል” በማለት ቢለየው ይመረጣል (ሕዝቅኤል 1፡26)። ያ “መንፈስ ቅዱስ” አልነበረም።
የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ኢ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”
መንፈስ ቅዱስ
ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ትርጉሞች 1) “መንፈስ” ወይም 2) “ነፋስ” የሚሉት ናቸው።
ወደ እስራኤል ሕዝብ፣ በእኔ ላይ ወዳመፀው ወደ አመፀኛው ሕዝብ
“ወደ እስራኤላውያን፣ በእኔ ላይ ወዳመፁት አመፀኛ ሕዝቦች”። “የእስራኤል ሕዝብ” እና “አመፀኛ ሕዝብ” ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት አንዱን ሕዝብ ነው። ኢ.ት፡ “ወደ እስራኤል ሕዝብ፣ በእኔ ላይ ወዳመፀው ሕዝብ” (See: Doublet)
እስከዚህ ቀን ድረስ
“አሁን እንኳን” ወይም “ዛሬም እንኳን”። ይህ ማለት የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ቀጥለዋል።
Ezekiel 2:4
ልጆቻቸው
በእግዚአብሔር ላይ አምፀው የነበሩትን የቀደመውን የእስራኤል ትውልድ ልጆች ሲሆን ሕዝቅኤል በሚጽፍበት ወቅት በእስራኤል የሚኖረውን ሕዝብ ያመለክታል።
የእልኸኝነት ፊት አላቸው
“እልኸኛ መሆናቸውን የሚያሳይ የፊት ገጽታ አላቸው”
እልኸኛ ፊትና ደንዳና ልብ
“እልኸኛ ፊት” የሚሉት ቃላት ውጫዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበትን መንገድ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚያመለክት ሲሆን “ደንዳና ልብ” የሚሉት ቃላት ደግሞ የሚያስቡበትንና የሚሰማቸውን መንገድ የሚያመለክቱ ናቸው። (See: Doublet)
እልኸኛ
ይህ የሚያስበውን ወይም የሚያደርገውን ለመቀየር እምቢተኛ የሚሆንን ሰው ይገልጻል።
ደንዳና ልብ
ዐለቶች መቼም ቢሆን እንደማይለወጡና እንደማይለሰልሱ ሁሉ እነዚህ ሰዎችም አይለወጡም፣ ክፉ ነገር በሚያደርጉበት ጊዜም አይጸጸቱም። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በመካከላቸው ነቢይ ነበረ
“ሊሰሙት ያልፈቀዱት ያ ሰው ነቢይ ነበር”
Ezekiel 2:6
የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡ 1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”
ኩርንችትና እሾህ … ጊንጥ
እነዚህ ቃላት ሕዝቅኤል እግዚአብሔር የሚለውን በሚነግራቸው ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ በቅንነት እንዳልተቀበሉት ይገልጻል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ኩርንችትና እሾህ
ኩርንችት ቅርንጫፉ የሚዋጋ ጫፍ ያለው ቁጥቋጦ ነው። በቅንርጫፉ ላይ ያሉት ሹሎች እሾህ ተብለው ይጠራሉ።
ጊንጥ
ጊንጥ ሁለት የፊት ለፊት ጥፍሮች፣ ስድስት እግሮችና አለብላቢ መናደፊያ ረጅም ጅራት ያለው ትንሽ እንስሳ ነው። ሲናደፍ በጣም ያሳምማል።
ቃላቸውን አትፍራ
“እነርሱ የሚናገሩትን አትፍራ”
ከፊታቸው የተነሣ አትደንግጥ
“ፊታቸው” የሚለው ቃል ሕዝቡ በፊት ገጽታቸው የሚያስተላልፉትን መልዕክት የሚያሳይ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “አንተን ከሚያዩበት መንገድ የተነሣ እኔን ለማገልገል ያለህ ፍላጎት አይጥፋብህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 2:7
እጅግ አመፀኞች ናቸው
“በጣም አመፀኞች ናቸው” ወይም “በእኔ ላይ ፈጽመው አምፀውብኛል”
ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2:5 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 2:9
አንድ እጅ ወደ እኔ ተዘርግቶ ነበር
ይህ፣ 1) በሰማያት ውስጥ ያለ አንድ ሰው እጁን ወደ ሕዝቅኤል ዘርግቶለታል፤ ሕዝቅኤል ማየት የቻለው ከእጁ እስከ ክርኑ ወይም እስከ ትከሻው ያለውን ብቻ ነው፣ ወይም 2) “የሰው ልጅ የሚመስለው” እጁን ዘርግቷል (ሕዝቅኤል 1፡26)።
የተጻፈበት ጥቅልል
“ጽሑፍ ያለበት ጥቅልል”
ዘረጋው
በውስጠ ታዋቂ ያለው “እርሱ” የሚያመለክተው “የሰው ልጅ የሚመስለውን” ነው (ሕዝቅኤል 1፡26)።
በፊት ለፊቱና በጀርባው ላይ በሁለቱም በኩል ተጽፎበት ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው በፊት ለፊቱና በስተጀርባው በሁለቱም በኩል ጽፎበት ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በላዩ ላይ ሙሾ፣ ለቅሶና ዋይታ ተጽፎበት ነበር
ይህ የነገር ስም የሆኑትን “ሙሾ”፣ “ለቅሶ”፣ እና “ዋይታ”ን ለማስቀረት እንደገና መነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እነዚህ ሰዎች እንደሚያዝኑ፣ አንድ የሚወዱት ቢሞትባቸው እንደሚሆኑት ሁሉ እንደሚያዝኑና የከፋ ነገር እንደሚደርስባቸው አንድ ሰው ጽፎበት ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

Chapter 3
Ezekiel 3:1
ተናገረኝ
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “አንድ ሰው የሚመስል” የተባለለትን ነው (ሕዝቅኤል 1:26)
የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡ 1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”
ያገኘኸውን
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር እየሰጠው ያለውን የመጽሐፍ ጥቅልል ነው (ሕዝቅኤል 2፡9ን ተመልከት)
የእስራኤል ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤላውያንን የሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ያ ጥቅልል
ብዙ ትርጉሞች “ጥቅልሉ” ወይም “ይህ ጥቅልል” የሚል አላቸው።
በዚህ ጥቅልል ሆድህን መግበው፣ ጨጓራህንም ሙላው
“ሆድ” የሚለው ቃል ሰዎች ከውጭ ሊያዩት የሚችሉትን የሰውነት ክፍል ያመለክታል። “ጨጓራ” የሚለው ቃል ደግሞ በሆድ ውስጥ ያለውን ውስጣዊ ብልት ያመለክታል።
እርሱም እንደ ማር ይጣፍጥ ነበር
ማር ይጣፍጣል፣ ጥቅልሉም ይጣፍጥ ነበር።
Ezekiel 3:4
ተናገረኝ
የአንተ ቋንቋ ተናጋሪውን መለየት ካለበት “አንድ ሰውን የሚመስል” በማለት ቢለየው ይመረጣል (ሕዝቅኤል 1፡26)። እርሱ “መንፈስ ቅዱስ” አልነበረም።
የእስራኤል ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤላውያንን የሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እንግዳ ንግግር ወይም አስቸጋሪ ቋንቋ
“እንግዳ ወይም አስቸጋሪ ቋንቋ የሚናገር”
እንግዳ ንግግር ወደሚናገሩ ወደ ብዙ ሰዎች አይደለም
“ሕዝባቸው እንግዳ ቋንቋ ወደሚናገር ብርቱ ሕዝብ አልካሁህም”
ወደ እነርሱ ብልክህ ኖሮ ይሰሙህ ነበር
ይህ ሊሆን የሚችል፣ ነገር ግን ያልሆነ መላ ምታዊ ሁኔታ ነው። እግዚአብሔር የሕዝቅኤልን ቋንቋ መረዳት ወደማይችሉ ሕዝቦች አልላከውም።
ወደ እነርሱ ብልክህ ኖሮ
“እነርሱ” የሚለው ቃል ከእስራኤል ሌላ ብርቱ የሆነን ሕዝብ ያመለክታል።
ግንባረ ጠንካራ እና ልበ ደንዳና
በመሠረቱ የሁለቱም ትርጉም ተመሳሳይ ነው። ኢ.ት፡ “በጣም አመፀኞች” ወይም “በጣም እልኸኞች”
ግንባረ ጠንካራ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “ለለውጥ ፈቃደኛ አለመሆን” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ልብ ደንዳና
ይህ ሐረግ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንደተቋቋሙትና ሊታዘዙት ፈቃደኞች አለመሆናቸውን ይጠቁማል። ሕዝቡ ለማድረግ የሚፈልጉትን የሚወስኑበትን በአካል ውስጥ የሚገኘውን ስፍራ ለመግለጽ ልብ ጥቅም ላይ ውሏል። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 3:8
ተመልከት!
እዚህ ጋ፣ "ተመልከት" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንዲሰጥ ሕዝቅኤልን ያነቃዋል።
ፊትህን እንደ ፊታቸው እልኸኛ አድርጌዋለሁ
"ፊት" እና "ፊታቸው" የሚሉት ቃላት ጥቅም ላይ የዋሉት ዐረፍተ ነገሩ ስለሚናገርላቸው ሕዝብ ነው። ኢ.ት፡ "አንተንም እንደ እነርሱ እልኸኛ አድርጌሃለሁ" (See: Synecdoche)
ግንባርህን እንደ ግንባራቸው ጠንካራ አድርጌአለሁ
"ግንባር" ፊት ለፊት ወይም ከቅንድብ በላይ ያለው ክፍል ሲሆን ሰውየው ስለሚያስበው ነገር ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ "ጠንካራ አድርጌሃለሁ . . . ስለዚህ የምትሠራውን ሥራ አታቆምም" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ግንባርህን ከባልጩት ይልቅ እንደሚጠነክር እንደ አልማዝ አድርጌዋለሁ
"ግንባርህን ከባልጩት ይልቅ ጠንካራ እንደሆነ ድንጋይ አድርጌአለሁ"
ባልጩት
ከጥንካሬው የተነሣ ከብረት ወይም ከሌላ ድንጋይ ጋር ሲያጋጩት እሳት የሚፈጥር ጠንካራ ድንጋይ
ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡5 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ "የሕዝብ ወገን" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 3:10
በልብህ ተቀበላቸው፣ በጆሮዎችህም አድምጣቸው
እዚህ ጋ፣ "ልብ" የሰውን አዕምሮ ይወክላል። ኢ.ት፡ "በጥንቃቄ አድምጣቸው፣ አስታውሳቸውም" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከዚያም ወደ ምርኮኞቹ ሂድ
"ምርኮኞች" የሚለው ቃል በባቢሎን የሚኖሩትን የእስራኤል ሕዝብ ያመለክታል።
ሕዝብህ
"የሕዝብህ ወገን"፣ ባቢሎናውያን ወደ ባቢሎን ሳይወስዱት በፊት ሕዝቅኤል በይሁዳ ይኖር ነበር።
ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Ezekiel 3:12
"የእግዚአብሔር ክብር ከስፍራው ይባረክ!" የሚል ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ድምፅ ከበስተኋላዬ ሰማሁ
አንዳንድ ትርጉሞች "ስፍራ … ይባረክ!" የሚሉትን ቃላት "ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ" የተናገረው አድርገው ይወስዳሉ፤ "'የእግዚአብሔር ክብር ከስፍራው ይባረክ!' የሚለውን ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ድምፅ ከበስተኋላዬ ሰማሁ"። ሌሎች የምድር መንቀጥቀጡን ድምፅ የእግዚአብሔር ክብር ከስፍራው ሲለቅ የነበረው ድምፅ አድርገው ይረዳሉ፣ "የእግዚአብሔር ክብር ስፍራውን ሲለቅ ከበስተኋላዬ ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ድምፅ ሰማሁ"።
ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ድምፅ
ድምፁ ከመሬት መንቀጥቀጥ፣ እንደ መሬት መንቀጥቀጥ ከፍ ካለ ድምፅ፣ ወይም ከክንፎችና ከመንኩራኲሮች መጥቶ እንደሆን ግልጽ አይደለም። ኢ.ት፡ "ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ድምፅን የሚመስል ድምፅ" ወይም "የሚናገርን ድምፅ፤ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ድምፅን የሚመስል ድምፅ" ወይም "ከፍ ያለ የጉርምርምታ ድምፅ"
የእግዚአብሔር ክብር
ይህንን በሕዝቅኤል 1፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ድምፅ
"እንደ መሬት መንቀጥቀጥ ድምፅ ያለ ከፍተኛ፣ ጥልቅና ኃይለኛ የጉርምርምታ ድምፅ"
Ezekiel 3:14
በሩቅ፣ እኔም በመንፈሴ ቁጣ በምሬት ሄድኩኝ
"ምሬት" እና "ቁጣ" የሚሉት ቃላት የቁጣ ዓይነቶች ናቸው። ይህ እንደ ሁለት ዐረፍተ ነገር ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ "በሩቅ። መራራ ነበርኩኝ፣ መንፈሴም ቁጣን ተሞልቶ ነበር" ወይም "በሩቅ። በጣም መራራና ቁጡ ነበርኩኝ"
ምሬት
ሕዝቅኤል አፉ ላይ መጥፎ ጣዕም የተሰማው እግዚአብሔር መጥፎ ጣዕም ያለውን ነገር እንዲበላ ስላስገደደው ይመስል በእግዚአብሔር ላይ ስለመቆጣቱ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔር እጅ በኃይል ተጭኖኝ ነበር
ለማድረግ የማይፈልጋቸውን ነገሮች እንዲያደርግ እግዚአብሔር ያዘዘውና ወደ ምድር የገፋው ይመስል ሕዝቅኤል ማዘኑንና መድከሙን ይናገራል።(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔር እጅ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እጅ" የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው የአንድን ሰው ኃይል ወይም ተግባር ለማመልከት ነው። ኢ.ት፡ "የእግዚአብሔር ኃይል" ወይም 2) ለተማረኩት እስራኤላውያን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔርን ስላልታዘዘ እግዚአብሔር እንደ ተቆጣው ሕዝቅኤል አውቋል የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቴል አቪቭ
በባቢሎን ያለች መንደር ስትሆን ከዋና ከተማዋ በስተደቡብ - ምስራቅ 80 ኪ.ሜ ላይ የምትገኝ፣ ባቢሎን በመባልም ትጠራ ነበር (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የኮቦር ቦይ
ይህ ከለዳውያን የአትክልት ቦታቸውን ለማጠጣት ቆፍረውት የነበረ ወንዝ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 1፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በመገረም ፈዘዝኩኝ
"እጅግ ስለተገረምኩኝ ምንም ለማድረግ አልቻልኩም"
Ezekiel 3:16
የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ "እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ጠባቂ
የአንድ ከተማ ሕዝብ እንዲዘጋጅና እንዲድን ጠባቂው ጠላት በመምጣት ላይ መሆኑን እንደሚያስጠነቅቅ ሁሉ ሕዝቅኤል የእስራኤልን ሕዝብ እንዲያስጠነቅቅ እግዚአብሔር ነግሮታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእስራኤል ቤት
"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ "እስራኤላውያንን" ወይም "የእስራኤል ሕዝብ ወገን" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ኃጢአተኛው በሕይወት ይኖር ዘንድ ስለ ክፉ ሥራው ማስጠንቀቂያ
ኃጢአተኛው ክፉ ሥራ መሥራቱን ማቆም እንዳለበት ግልጽ ማድረግ ይኖርብሃል። ኢ.ት፡ "ኃጢአተኛው በሕይወት ይኖር ዘንድ ክፉ ሥራውን ከመሥራት እንዲያቆም ማስጠንቀቂያ"
ኃጢአተኛው
"ክፉ ሕዝብ"
ደሙን ከእጅህ እፈልጋለሁ
ይህ አንድን ሰው በግድያ ወንጀል በኃላፊነት ወይም በበደለኝነት ስለመያዝ የተነገረ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ "አንተ ራስህ እንደገደልከው ቆጥሬ እፈርድብሃለሁ" (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ከኃጢአቱ ወይም ከክፉ ሥራው አይመለስም
"ከክፉ ሥራው" የሚለው ሐረግ ትርጉሙ "ከኃጢአቱ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ኢ.ት፡ "ክፉ ነገሮችን ማድረጉን አያቆምም"
Ezekiel 3:20
በፊቱ ማሰናከያ ማስቀመጥ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) "ክፉ ነገር እንዲደርስበት አድርግ" ወይም 2)

“በግልጽ ኃጢአትን እንዲሠራ አድርገው” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በኃጢአቱ ይሞታል
“እንደ ኃጢአተኛ ይሞታል” ወይም “እኔን ስላልታዘዘኝ እንደ በደለኛ ሰው ይሞታል”
ደሙን ከእጅህ እፈልጋለሁ
ይህ አንድን ሰው በግድያ ወንጀል በኃላፊነት ወይም በበደለኝነት ስለመያዝ የተነገረ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:18 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “አንተ ራስህ እንደገደልከው ቆጥሬ እፈርድብሃለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታልና
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “አስጠንቅቀኸዋልና” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 3:22
የእግዚአብሔር እጅ
“እጅ” የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ የአንድን ሰው ኃይል ወይም ተግባር ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት: “የእግዚአብሔር ኃይል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔር ክብር
ይህንን በሕዝቅኤል 1:28 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።
የኮቦር ቦይ
ይህ ከለዳውያን የእትክልት ቦታቸውን ለማጠጣት ቆፍረውት የነበረ ወንዝ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 1:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።
በግንባሬ ተደፋሁ
“በምድር ላይ ሰገድሁ” ወይም “በምድር ላይ ተጋደምኩ”። ሕዝቅኤል የወደቀው በአደጋ ምክንያት አይደለም። እርሱ በምድር ላይ የወደቀው ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮትና ፍርሐት ለማሳየት ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 1:28 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 3:24
ተናገረኝ
የአንተ ቋንቋ ተናጋሪውን መለየት ካለበት “አንድ ሰውን የሚመስል” በማለት ቢለየው ይመረጣል (ሕዝቅኤል 1:26)። እርሱ “መንፈስ ቅዱስ” አልነበረም።
በላይህ ላይ ገመድ ዘርግተው ያስሩሃል፣ ስለዚህ በመካከላቸው መውጣት አትችልም
ይህ በቀጥታ መተርጎሙ እጅግ የተሻለ ነው።
Ezekiel 3:26
የአፍህን ላንቃ
“ከውስጥ የአፍህን የላይኛውን ክፍል”
ዲዳ ትሆናለህ
“መናገር አትችልም”
ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2:5 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “የሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አፍህን እከፍተዋለሁ
“መናገር እንድትችል አደርግሃለሁ”
የማይሰማ አይሰማም
“ለመስማት እምቢተኛ የሆነ አይሰማም”
ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

---

Chapter 4
Ezekiel 4:1
የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”
የኢየሩሳሌምን ከተማ ቅረጽ
ሕዝቅኤል ሥዕል ሊሥል እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። ኢ.ት: “የኢየሩሳሌምን ከተማ ሥዕል ሣል”
በእርሷ ላይ ከበባን አድርግባት
“ከተማይቱን ለመማረክ ክበባት”
በእርሷ ላይ ምሽግን ሥራባት
“በእርሷ ላይ ጠንካራ ግንብ ሥራባት”። ሕዝቡ ከተማይቱን ትቶ እንዳይወጣ ግንቡ ያግደዋል።
በእርሷ ላይ የማጥቂያ መሰላል አቁምባት
“ጠላት እንዲገባባት በስተውጪዋ መሰላል ሥራባት”። ኢየሩሳሌም በውስጧ የሚኖረውን ሕዝብ ለመከላከል በዙሪያዋ ቅጥር ነበራት። ጠላት ወደ ውስጥ መግባት የሚችለው በቅጥሩ ላይ መዝለል የሚያስችለው መሰላል ከኖረው ብቻ ነበር።
በዙሪያዋ የግንብ ማፍረሻ መሣሪያ አኑርባት
“ሰዎች በሮቹን ሰብረው ወደ ውስጥ መግባት እንዲችሉ ትላልቅ ግንዶችን በዙሪያዋ አስቀምጥ”። “ግንብ ማፍረሻ መሣሪያዎች” ሰብረው ወደ ውስጥ መግባት እንዲቻላቸው በውትድርና ውስጥ ያሉ በርካታ ወንዶች አንሥተው ግንቡን ወይም በሩን የሚመቱባቸው ረጃጅም ዛፎች ወይም ምሶሶዎች ናቸው።
ፊትህን በእርሱ አቅጣጫ አዙር
ይህ በከተማይቱ ምሳሌ ላይ አፍጥጦ እንዲመለከት የተሰጠ ትዕዛዝ ከተማይቱ የመቀጣቷ ምልክት ነው። ኢ.ት: “በከተማይቱ ላይ አፍጥጥባት” ወይም “ጉዳት ይደርስባታልና በከተማይቱ ላይ አፍጥጥባት”
ፊትህን አቅና
እዚህ ጋ “ፊት” ፍላጎትን ወይም አትኩሮትን የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “ፊትህን አቅና” የሚያመለክተው በአንድ ነገር ላይ በቀጥታ ማተኮርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 4:4
የእስራኤልን ቤት ኃጢአት በእርሱ ላይ አኑርበት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ስለ እስራኤላውያኑ ኃጢአት ቅጣቱን በምልክትነት ተሸከም” ወይም 2) “በኃጢአታቸው ምክንያት በጎንህ በመተኛት መከራን ተቀበል” የሚሉት ናቸው።
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ኃጢአታቸውን ትሸከማለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በኃጢአታቸው ምክንያት አንተ በደለኛ ትሆናለህ” ወይም 2) “በኃጢአታቸው ምክንያት ትቀጣለህ”። ከእነዚህ ትርጉሞች ሁለቱም ክፍት በሆነው ተለዋዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ላይ እንደተመለከተው በ”ምልክታዊነት” ይገለጻል።
የእስራኤልን ቤት በመቃወም ተጋደም
“የእስራኤልን መንግሥት በቁጣ እያየህ ተጋደም”
የሚቀጡባቸውን ዓመታት እንዲወክል አንድን ቀን የምመድብልህ እኔው ራሴ ነኝ
“በምቀጣቸው ዓመታት ቁጥር ልክ ተመሳሳይ ቀናትን በጎንህ እንድትተኛ የማዝህ እኔው ራሴ ነኝ”
በእያንዳንዱ በሚቀጡበት ዓመት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በየዓመቱ ስለ ኃጢአታቸው ይቀጣሉ ወይም 2) በየዓመቱ ኃጢአትን ሠርተዋል የሚሉት ናቸው።
390 ቀናት
“ሦስት መቶ ዘጠና ቀናት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Ezekiel 4:6
በእነዚህ ቀናት
የእስራኤል መንግሥት እንደምትከበብ ለማመልከት ሕዝቅኤል በግራ ጎኑ የሚተኛባቸው ቀናት
ኃጢአትን ትሸከማለህ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ስለ ኃጢአት በደለኛ ትሆናለህ” ወይም 2) “ስለ ኃጢአት ተቀጣለህ”። ከእነዚህ ትርጉሞች ሁሉቱም ክፍት በሆነው ተለዋዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ላይ እንደተመለከተው በ”ምልክታዊነት” ይገለጻል። እነዚህን ቃላት በሕዝቅኤል 4፡4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።
የይሁዳ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የይሁዳን ዘሮች ያመለክታል። እነዚህን ቃላት በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የይሁዳ ሕዝብ ወገን” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለእያንዳንዱ ዓመት አንድ ቀን መድቤልሃለሁ
“ይህንን አንድ ቀን እኔ ለምቀጣቸው ለእያንዳንዱ ዓመት እንድታደርገው አደርግሃለሁ”
ፊትህን በተከበበችው በኢየሩሳሌም አቅጣጫ አድርግ
ይህ በኢየሩሳልም ምሳሌ ላይ አፍጥጦ እንዲመለከት የተሰጠ ትዕዛዝ ኢየሩሳሌም የመቀጣቷ ምልክት ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 4፡3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “በተከበበችው በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ አፍጥጥባት” ወይም “ጉዳት ይደርስባታልና በተከበበችው በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ አፍጥጥባት”
ፊትህን አቅና
እዚህ ጋ “ፊት” ፍላጎትን ወይም አትኩሮትን የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “ፊትህን አቅና” የሚያመለክተው በአንድ ነገር ላይ በቀጥታ ማተኮርን ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእርሱ ላይ ትንቢት ተናገር
“በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጡ ስላሉት መጥፎ ነገሮች ትንቢት ተናገር”
እይ
“ተመልከት” ወይም “አድምጥ” ወይም “የምነግርህን ልብ በል”
ማሰሪያ አጥልብሃለሁ
ማሰሪያ አንድን ሰው ከመንቀሳቀስ የሚገድቡ ገመዶች ወይም ሰንሰለቶች ናቸው። “ማሰሪያ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ያሰረበትን አንዳች ነገር አመልካች ዘይቤአዊ አነጋገር ወይስ በቀጥታ የሚታይ ገመድ ተጠቅሞ እንደሆነ ግልጽ አይደለም። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 4:9
ስንዴ፣ ገብስ … ማሽላ፣ ---
እነዚህ የተለያዩ የጥራጥሬ ዓይነቶች ናቸው።
ባቄላ
ሐረግ፣ ዘሩ ሊበላ የሚችል፣ በተናጠል የሚያድግ ያለበለዚያ ፍሬ አልባ የሚሆን
ምስር
ይህም እንደ ባቄላ ነው፣ ነገር ግን ዘሩ በጣም ትንሽ፣ ክብና በመጠኑ ጠፍጠፍ ያለ ነው። (የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)
390 ቀናት
“ሦስት መቶ ዘጠና ቀናት” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
በቀን ሃያ ሰቅል
“በቀን 20 ሰቅል”። አንድ ሰቅል የ11 ግራም ያህል ክብደት አለው። ኢ.ት፡ “በየቀኑ 200 ግራም እንጀራ” (ቁጥሮች እና ክብደት በመጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ተመልከት)
የኢን ስድስተኛ
“1/6ኛ ኢን” ወይም “የኢን ስድስተኛ ክፍል” ወይም “ግማሽ ሊትር ገደማ”
አንድ ኢን
አንድ ኢን 3.7 ሊትር ነው።
Ezekiel 4:12
ትበላዋለህ
“እርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እንጀራን ነው (ሕዝቅኤል 4:9)።
የገብስ እንጀራ
ከገብስ የሚዘጋጅ ዝርግ እንጀራ (ሕዝቅኤል 4:9) (የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)
ከሰው በሚወጣ ሰገራ ትጋግረዋለህ
“በደረቅ የሰው ሰገራ እሳት በማንደድ ታበስልበታለህ”። የአንተ ቋንቋ ይህንን በትህትና የሚገልጽበት መንገድ ይኖረው ይሆናል።
ይወገዳሉ
በኃይል ይባረራሉ
Ezekiel 4:14
ኦ! ጌታ እግዚአብሔር
“ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህንን ማድረግ አይገባኝም”። ጌታ እንዲያደርግ ባዘዘው ነገር ሕዝቅኤል በጣም ተረብሿል።
ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2፡4 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። እዚህ ጋ ሕዝቅኤል እየተናገረ ያለው ለጌታ ነው።
የተበከለ ሥጋ ወደ አፌ ከቶ ገብቶ አያውቅም
“የተበከለ ሥጋ ከቶ በልቼ አላውቅም”
የተበከለ ሥጋ
“አስቀያሚ፣ እርኩስ ሥጋ”። ይህ በበሽታ ወይም በእርጅና ምክንያት ከሞተ ወይም በሌላ እንስሳ ከተገደለ እንስሳ የመጣ እርኩስ ሥጋን ያመለክታል።
ተመልከት
“ስማ” ወይም “አሁን ለምነግርህ ጠቃሚ ነገር ትኩረት ስጥ”
ሰጥቼሃለሁ
“እንድትጠቀምበት እፈቅድልሃለሁ”
የከብት ፍግ
ከከብቶች የሚገኝ ኩበት። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚገልጽበት የትህትና አገላለጽ ይኖረው ይሆናል።
የሰው ሰገራ
ከሰው የሚወጣ ጠጣር ሰገራ። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚገልጽበት የትህትና አገላለጽ ይኖረው ይሆናል። ይህንን በሕዝቅኤል 4፡12 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።
Ezekiel 4:16
እነሆ
“ተመልከት” ወይም “ስማ” ወይም “የምነግርህን ልብ በል”
በኢየሩሳሌም የእንጀራን በትር እሰብራለሁ
“የኢየሩሳሌምን የምግብ አቅርቦት አቆማለሁ”
የእንጀራ በትር
አቅርቦቱ በትር ተብሎ ተጠርቷል፤ ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች መንገድ ለመሄድና ሥራቸውን ለመሥራት ምርኩዝ እንደሚፈልጉ ሁሉ ሰዎች በሕይወት ለመኖር ምግብ ይፈልጋሉ። እንጀራ ሁሉንም ዓይነት ምግብ ይወክላል። ኢ.ት፡ “የምግብ አቅርቦት” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Synecdoche የሚለውን ተመልከት)
እንጀራን በስጋት መጥነው ይበላሉ
እንጀራውን ለምን እንደሚመጥኑት ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። “ላይበቃቸው እንደሚችል በማሰብ እንጀራቸውን በጥንቃቄ ይከፋፍላሉ”
መመጠን
ለብዙ ሰዎች የማይበቃ ሲሆን የአንድን ነገር አነስተኛ መጠን መስጠት ነው።
እርሱን በመንቀጥቀጥ መመጠን
“መደንገጥ” የሚለው ቃል የመፍራት ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን “መንቀጥቀጥ” ፍርሃትን ይወክላል። ኢ.ት፡ “እየደነገጡ መመጠን” ወይም “እየፈሩ መመጠን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እያንዳንዱ ሰው በወንድሙ ተስፋ ይቆርጣል፣ መንምኖም ይጠፋል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “እያንዳንዱ ወንድሙ ምን ያህል ምግብ በመብላት መንምኖ እንደሚጠፋ በማየት ይጨነቃል”
መንምኖ መጥፋት
“መንምኖ መጥፋት” የሚለው ሐረግ በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውለው ለሥጋ ወይም ለሚበሰብስ እንጨት ነው። እዚህ ጋ በዘይቤአዊ አነጋገር ክፉ ሰዎች ምግብ ስለሌላቸው እንደሚከሱና እንደሚሞቱ ያሳያል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 5
Ezekiel 5:1
የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”
የጸጉር ቆራጭ ምላጭ
“ጸጉር ለመቁረጥ የሚያገለግል ምላጭ”
በራስህና በጺምህ ላይ ምላጭ አሳልፍ
“ጸጉርህንና ጺምህን ተላጨው” ወይም “ከራስህ ላይ ጸጉርህን፣ ከፊትህም ላይ ጺምህን አስወግድ”
አንድ ሦስተኛውን አቃጥለው
“ከጸጉርህ አንድ ሦስተኛውን አቃጥለው” )
መካከል
መካከል
የከበባዎቹ ቀናት በሚያበቁበት ጊዜ
“የኢየሩሳሌም የከበባዎቹ ቀናት ባበቃ ጊዜ” ወይም “ኢየሩሳሌም እንዴት በከበባ ስር እንደምትወድቅ የምታሳይበት ቀናት በሚያበቁበት ጊዜ”
አንድ ሦስተኛውን ጸጉር ውሰድ
“ከሦስቱ የጸጉር ክምሮች አንደኛውን ውሰድ”
እርሱን በከተማይቱ ዙሪያ ሁሉ በሰይፍ ምታው
“እርሱን በከተማው ሁሉ ላይ በሰይፍህ ምታው”
Ezekiel 5:3
ነገር ግን ውሰድ ... ከዚያም ውሰድ
ሕዝቅኤል ጸጉሩንና ጺሙን በተላጨ ጊዜ ጸጉሩን ከማቃጠሉ በፊት ይህንን ማድረግ ነበረበት (ሕዝቅኤል 5፡1-2)። እነዚህን ቁጥሮች ከእነዚያ ቁጥሮች በፊት ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። “ይሁን እንጂ ጸጉርህንና ጺምህን በምትላጭበት ጊዜ ከማቃጠልህ በፊት . . . ውሰድ። ከዚያም ጸጉሩን በንፋስ ላይ ከበተንከው በኋላ ውሰድ” (የሁነቶች ቅደም ተከተል እና የቁጥር መሸጋገሪያ የሚለውን ተመልከት)
ከእነርሱ ላይ ጥቂት ቁጥር ያለውን ጸጉር
“ከክምሩ ላይ ጥቂት ጸጉሮችን”
በአንድ ላይ እሰራቸው
“እነርሱን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጸጉሮቹን ነው። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጸጉሮቹ ሕዝቅኤል ሊያስራቸው እስኪችል ድረስ ረጅም ነበሩ ወይም 2) ሕዝቅኤል ጸጉሮቹን በአንድ ላይ መስፋት ወይም ማጣበቅ ነበረበት 3) ሕዝቅኤል ጸጉሮቹን በልብስ እጥፋት ውስጥ ማስቀመጥ ነበረበት የሚሉት ናቸው።
በልብስህ እጥፋት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በክንድህ ላይ ያለ ልብስ” (“የልብስህ እጅጌዎች”) ወይም 2) “የልብስህ ዘርፍ” (“የልብስህ ጠርዝ”) ወይም 3) መታጠቂያ ላይ የሚሸጎጥበት የልብስ እጥፋት የሚሉት ናቸው።
እሳት ከዚያ ወደ እስራኤል ቤት ሁሉ ይወጣል
“እሳት ከዚያ ይስፋፋል፣ የእስራኤልን ሕዝብ በሙሉ ያቃጥላል”። እስራኤል በዚያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች የሆኑ ያህል (ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ ከቤቱ ውጭ ነበሩ) እግዚአብሔር በቤቱና በእስራኤል ሕዝብ ላይ እሳት በመለኮስ እስራኤልን እንዴት እንደሚቀጣት ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 5:5
ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።
ይህቺ ኢየሩሳሌም ናት
“ይህ ቅርጽ ኢየሩሳሌምን ይወክላል” (ሕዝቅኤል 4:1)
በሀገሮች መካከል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በኢየሩሳሌም ዙሪያ ሁሉ ሌሎች ሀገሮች ነበሩ ወይም 2) “ከሌሎች ሀገራት ሁሉ ይልቅ በጣም ጠቃሚ” የሚሉት ናቸው።
አስቀምጫታለሁ
ኢየሩሳሌም “እርሷ” እና “የእርሷ” ተብላ ተመልክታለች (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
ሌሎች ምድሮች
“አጎራባች ሀገሮች” ወይም “በዙሪያዋ ያሉ ሀገሮች”
ሕዝቡ ፍርዴን አልተቀበሉም
“ኢየሩሳሌምና የእስራኤል ሕዝብ ፍርዴን ለመታዘዝ እምቢ ብለዋል”
Ezekiel 5:7
ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት
ምክንያቱም እንቺ ከማንም ይልቅ አስቸጋሪ ነሽ
“ምክንያቱም ኃጢአተኝነትሽ ከማንም ይልቅ የከፋ ነው” ወይም “ምክንያቱም ከማንም ይልቅ ሲበዛ የማትታዘዢ ነሽ”
የከበቡሽ ሁሉ
“በዙሪያሽ ያሉ ሁሉ”
በሕጌ አልሄዱም
መሄድ የአንድን ሰው የሕይወት አኗኗር የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በሕጌ መሠረት አልኖሩም” ወይም “ሕጌን አልታዘዙም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ወይም በድንጋጌዬ መሠረት አድርገዋል
“ወይም ድንጋጌዎቼን ታዘዋል”
እነሆ!
“ተመልከቱ!” ወይም “ስሙ!” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ!”
ፍርዴን በመካከላችሁ እፈጽማለሁ
“በተለያየ መንገድ እፈርድባችኋለሁ” ወይም “እቀጣችኋለሁ”።
Ezekiel 5:9
ያላደረግሁትንና ዳግመኛም የማላደርገውን
“ቀድሞ ያላደረግሁትንና ዳግመኛ በተመሳሳይ መንገድ የማላደርገውን” ወይም “ቀድሞ ከቶ ያላደረግሁትንና ዳግመኛም ከቶ የማላደርገውን”።
በአስጸያፊ ተግባሮችሽ ሁሉ ምክንያት
“በምታደርጊያቸው አስጸያፊ ነገሮች ሁሉ ምክንያት”። ሕዝቡ ጣዖታትንና ሐሰተኞች አማልክትን ያመልኩ ስለ ነበር እግዚአብሔር ተቆጥቷል።
በመካከልሽ አባቶች ልጆቻቸውን ይበላሉ፣ ወንዶቹ ልጆችም አባቶቻቸውን ይበላሉ
ሕዝቅኤል የሚነግራቸው ምናልባት ሕዝቡ የሚበሉትን ምግብ በሚያጡበት ጊዜ በእርግጠኝነት ምን ሊሆን እንዳለ ነው።
ፍርድን እፈጽምብሻለሁ
“እፈርድብሻለሁ” ወይም “የከፋ ቅጣት እቀጣሻለሁ”
የቀራችሁትን ሁሉ በተለያየ አቅጣጫ እበትናችኋለሁ
“የቀራችሁትን ሁሉ ወደ ተለያዩ ቦታዎች እንድትሄዱ አስገድዳችኋለሁ”
Ezekiel 5:11
ሕያው እንደ መሆኔ
“ሕያው መሆኔ እርግጥ የመሆኑን ያህል”። እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚናገረው የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ለማሳየት ይህንን አገላለጽ ይጠቀማል። ይህ ጽኑ ተስፋ የመስጫ መንገድ ነው። ኢ.ት፡ “ጽኑ መሐላ አደርጋለሁ” (የአነጋገርዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ኢ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት
ማርከስ ... መቅደስ
እግዚአብሔር ለራሱ አገልግሎት ብቻ የለየውን ስፍራ አበላሽተውታል
በሚያስጠሉ ነገሮቻችሁ ሁሉ
“ከምጠላቸው ነገሮቻችሁ ሁሉ ጋር”። ይህ ጣዖታትን እንደሚያመለክት ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። “ከምጠላቸው ጣዖቶቻችሁ ሁሉ ጋር” ወይም “አስጸያፊ

ከሆኑት ጣዖቶቻችሁ ሁሉ ጋር”
አስጸያፊ ከሆኑት ተግባሮቻችሁ ሁሉ ጋር
“እናንተ ከምታደርጓቸው አስጸያፊ ነገሮቻችሁ ሁሉ ጋር”
ዓይኔ አይራራልሽም
ዓይን ባለቤቱ ስለሆነው ስለ ሰው የተነገረ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “አልራራልሽም”
አልምርሽም
“ያለ ጥርጥር እቀጣሻለሁ”
በመካከልሽ በረሃብ ይጠፋሉ
“በረሃብ ምክንያት ከእነርሱ ብዙዎቹ ይሞታሉ”
Ezekiel 5:13
ቁጣዬ ይፈጸማል
“ተቆጥቼ ለማድረግ የፈለግሁትን ሁሉ ስላደረግሁ ከዚህ በኋላ አልቆጣም”
ንዴቴ በእነርሱ ላይ እንዲበርድ አደርጋለሁ
“ንዴት” የሚለው ቃል ብርቱ ቁጣ ማለት ሲሆን እዚህ ጋ ቅጣትን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “በሚገባ ስለቀጣኋቸው እነርሱን መቅጣቴን አቆማለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ረክቻለሁ
እግዚአብሔር ለምን እንደሚረካ ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። ኢ.ት: “በበቂ ሁኔታ ስለቀጣኋቸው እረካለሁ”
በእነርሱ ላይ ንዴቴን በምፈጽምበት ጊዜ
“እነርሱን መቅጣቴን በምጨርስበት ጊዜ”
Ezekiel 5:15
በቁጣና በንዴት
“ቁጣ” እና “ንዴት” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነገር ሲሆን እግዚአብሔር በጣም ስለመቆጣቱ አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት: “በጣም ስለተቆጣሁሽ”
የረሃብን አሰቃቂ ፍላጻዎች በእንቺ ላይ እወረውራለሁ
“ፍላጻዎች” የሚለው ቃል ሕዝቡ ለረጅም ጊዜ ምግብ በሚያጡበት ጊዜ የሚሰማቸውን ብርቱ ህመም የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “የጽኑ ረሃብ ህመም እንዲሰማችሁ አደርጋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ረሃብን አበዛባችኋለሁ
“ረሃባችሁን አስከፊ አደርገዋለሁ” ወይም “ረሃባችሁ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ አደርጋለሁ” ወይም “የምትበሉት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያነሰባችሁ እንደሚሄድ እርግጠኛ ሁኑ”
የእንጀራችሁን በትር መስበር
“በትር” ሰዎች ለድጋፍ የሚመረኮዙት ነገር ነው። ይህ ሐረግ ሕዝቡ የተማመነበትን የምግብ አቅርቦት የማስወገድ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። “የእንጀራ በትር” በሕዝቅኤል 4፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልከት። ኢ.ት: “የምግብ አቅርቦታችሁን አቋርጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በመካከላችሁ ቸነፈርና ደም ያልፋል
በሽታና አስከፊ ሞት በከተማው ውስጥ በመዘዋወር ያገኙትን ሁሉ በሚገድሉ ወታደሮች ተመስለዋል። ኢ.ት: “ብዙ ሰዎች በበሽታ ይሞታሉ፣ ሌሎች ብዙዎች ደግሞ በጦርነት ይሞታሉ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
በእናንተ ላይ ሰይፍን አመጣለሁ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉትን ወታደሮች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “እኔ ራሴ ወታደሮች መጥተው እንዲገድሏችሁ አደርጋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 6
Ezekiel 6:1
የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንዳች ነገር መናገሩን ለማስታወቅ ጥቅም ላይ የዋለ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እግዚአብሔር እነዚህን ቃላት ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”
ፊትህን በእስራኤል ተራሮች ላይ አንሣ
ይህ በዚያ ያሉትን ሰዎች ስለ መቅጣቱ ምሳሌ ይሆን ዘንድ በተራሮቹ ላይ እንዲያፈጥ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 4፡3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “በእስራኤል ተራሮች ላይ አፍጥጥ” ወይም “በዚያ የሚኖሩት ሰዎች ጉዳት ያገኛቸው ዘንድ በእስራኤል ተራሮች ላይ አፍጥጥ”
ፊትህን በእስራኤል ተራሮች ላይ አቅና
ፊትህን በእስራኤል ተራሮች ላይ አቅና የእስራኤል ተራሮች የሚገኙት ርቀት ላይ ነበር፤ በመሆኑም ሕዝቅኤል ሊያያቸው አይችልም፤ ነገር ግን በዚያ አቅጣጫ ማፍጠጡ የመጎዳታቸው ምልክት ነበር። ኢ.ት: “ወደ እስራኤል ተራሮች ዙርና አፍጥጥባቸው” ወይም “በዚያ ያሉ ሰዎች ጉዳት እንዲደርስባቸው በእስራኤል ተራሮች አቅጣጫ አፍጥጥ”
ፊትህን አቅና
እዚህ ጋ “ፊት” የትኩረት ወይም የመመልከት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእስራኤል ተራሮች
“በእስራኤል ምድር ያሉ ተራሮች”
እነሆ!
“ተመልከቱ!” ወይም “ስሙ!” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ!”
ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።
ሰይፍን አመጣባችኋለሁ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉትን ወታደሮች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “ወታደሮች መጥተው እንዲገድሏችሁ እጠራቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 6:4
ከዚያም መሰዊያዎቻችሁ ወና ይሆናሉ፣ ዐምዶቻችሁም ይሰባበራሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ወደ ፊት ሰዎች በመሰዊያዎቻችሁ ላይ አይሰውም፣ ጠላቶቻችሁም ዐምዶቻችሁን ይሰባብራሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እጥላለሁ … አጋድማለሁ … እበትናለሁ
እግዚአብሔር ወደ እነዚህ ነገሮች ወታደሮችን እንደሚልክ ይናገራል (ሕዝቅኤል 6፡ 3)። ኢ.ት: “… እንዲጥሉ ወታደሮችን እልካለሁ፤ እነርሱ … ያጋድማሉ … ይበትናሉም”
ሙታኖቻችሁን
“የሞቱትን ሰዎቻችሁን”
Ezekiel 6:6
ከተሞች ባድማ ይሆናሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “የጠላት ወታደሮች ከተሞቻችሁን ባድማ ያደርጋሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ይሰበራሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “የጠላት ወታደሮች መሰዊያዎቻችሁን ይሰባብራሉ” ወይም “የጠላት ወታደሮች ይሰባብሯቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ዐምዶቻችሁ ይቆራረጣሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። “ዐምዶች”ን በሕዝቅኤል 6፡4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “ዐምዶቻችሁን ይቆራርጧቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሥራዎቻችሁ ተጠርገው ይወሰዳሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ሥራዎቻችሁን ማንም አያስብም” ወይም “የሠራችኋቸውን ሁሉ ያጠፏታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሙታን በመካካላችሁ ይጋደማሉ
“ጠላት ብዙ ሰዎችን ሲገድል ታያላችሁ”
እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃላችሁ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ኢ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትረዳላችሁ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትገነዘባላችሁ”

## Ezekiel 6:8

ከሰይፍ ያመለጡ ጥቂቶች

“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉ ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ወታደሮቹ የማይገድሏቸው ጥቂቶች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በየሀገሩ በምትበተኑበት ጊዜ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “በተለያዩ ሀገሮች በምበትናችሁ ጊዜ” ወይም “በሌሎች ሀገሮች እንድትኖሩ በማስገድዳችሁ ጊዜ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከእኔ በራቀው ሴሰኛ ልባቸው አዝኛለሁ

እግዚአብሔር ከብዙ ሰዎች ጋር እንደምትተኛ እንደ አንዲት ሴት አድርጎ የተናገረው ስለ እስራኤል ነው። ኢ.ት፡ “ልክ ሚስቴ እኔን ትታ ከሌሎች ወንዶች የተኛች ያህል አዝኛለሁ” )

ከጣዖቶቻቸው ኋላ በሚያመነዝሩ ዓይኖቻቸው

እግዚአብሔር አንዲት ያገባች ሴት ሌሎች ወንዶችን እንደምታይና ከእነርሱ ጋር ለመተኛት እንደምትመኝ አድርጎ የሚናገረው ስለ እስራኤላውያን ነው። ኢ.ት፡ “በነገራችን ላይ ጣዖታትን ለማምለክ በብርቱ ተመኝተዋል”

ስለ ሠሩት ክፋት የጥላቻ ፊት ያሳያሉ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ባደረጓቸው ክፉ ነገሮች ምክንያት ራሳቸውን መጥላታቸውን የፊት ገጽታቸው ያሳያል” ወይም 2) “ያደረጓቸውን ክፉ ነገሮች መጥላታቸውን ፊታቸው ያሳያል” የሚሉት ናቸው።

## Ezekiel 6:11

ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

እርሱ የሚናገረው አስፈላጊ መሆኑን ለሕዝቅኤልና ለሕዝቡ ለማስታወስ እግዚአብሔር ስለ ራሱ በስሙ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እኔ ጌታ እግዚአብሔር ይህንን እናገራለሁ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ጌታ እግዚአብሔር

ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

እጆችህን አጨብጭብ፣ በእግሮችህም እርገጥ

ሕዝቅኤል የሕዝቡን ትኩረት ለማግኘት ይህንን ምልክታዊ ተግባር ይፈጽም ነበር። ይህ የድጋፍ ጭብጨባ አልነበረም።

ወይኔ

ይህ ቃል የተነገረው በእነዚያ ክፉ ነገሮችን የሚሠሩ ሰዎችን ባዩት እና በክፉ አድራጊዎች ላይ ክፉ ነገሮች ውጤት ሆነው እንደሚደርሱባቸው በተገነዘቡ ሰዎች ነው። የአንተ ቋንቋ ተመሳሳይ ቃል ካለው እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ያስፈልግህ ይሆናል።

የእስራኤል ቤት

“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሰይፍ፣ በረሃብ እና በቸነፈር ይወድቃሉ

“መውደቅ” “መሞት”ን በጨዋነት የመግለጫ ቃል ነው። “ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉ ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።

በእነርሱ ላይ ንዴቴን እፈጽማለሁ

“በእነርሱ ላይ ቁጣዬን አረካለሁ” ወይም “ዳግመኛ እስከማልቆጣ ድረስ እቀጣቸዋለሁ”

## Ezekiel 6:13

ከፍ ባለው ኮረብታ ሁሉ ላይ በመሰዊያዎቻቸው ዙሪያ

“ከፍ ባለ ኮረብታ ሁሉ ላይ ባሉት በመሰዊያዎቻቸው ዙሪያ” የሚለው ሌላው ሊሆን የሚችል ትርጉም ነው።

ኮረብታ -- በተራሮቹ ጫፍ ሁሉ ላይና ከለመለሙት ዛፎችና ቅጠሉ ጥቅጥቅ ያለ ዋርካ ስር

“ኮረብታ፣ በተራሮች ጫፍ ሁሉ ላይ፣ ከእያንዳንዱ የለመለመ ዛፍ ስር እና ከእያንዳንዱ ቅጠሉ ጥቅጥቅ ያለ ዋርካ ስር”

የለመለመ

ጤናማና የሚያድግ

ዋርካ

ለአምላኪዎች ጥላ የሚሰጣቸው ጠንካራ እንጨት ያለው ረጅም ዛፍ

ራብላ

የአንዲት ከተማ ስም (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

---

# Chapter 7

## Ezekiel 7:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ

x

## Ezekiel 7:3

ፍጻሜው በአንቺ ላይ ነው

ስለ “ፍጻሜ” የተነገረው ዘራፊ ሰዎችን እንደሚያጠቃቸው ተደርጎ ነው። ኢ.ት፡ “ሕይወትሽ አልቋል” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ቁጣዬን እልክብሻለሁ

“ቁጣ” እግዚአብሔር በሰዎቹ ላይ እንደሚወረውረው ፍላጻ ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ተቆጥቻለሁ፣ ስለዚህ እቀጣሻለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንደ መንገዶችሽ

“እንደምትሠሪያቸው ነገሮች” ወይም “በምትሠሪው ክፉ ነገሮች ምክንያት”

አስጸያፊነትሽን በሙሉ በአንቺ ላይ አመጣለሁ

“እነዚያን እጅግ የምጠላቸውን ነገሮች በማድረግሽ እቀጣሻለሁ”

ዓይኖቼ አይራሩልሽም

ዓይን ባለቤቱ የሆነውን ሰውን ይወክላል። ኢ.ት፡ “አልራራልሽም”

መንገድሽን በአንቺ ላይ አመጣለሁ

አንድ ሰው የሕይወት ዘይቤው እንደሚሄድበት ጎዳና ሆኖ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “ስላደረግሻቸው ነገሮች እቀጣሻለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አስጸያፊነትሽ በመካከልሽ ይሆናል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በአስጸያፊነታችሁ ምክንያት ሁላችሁንም እቀጣችኋለሁ” ወይም 2) “ጣዖታትን ማምለካችሁን እስከ ቀጠላችሁ ድረስ ይህ ይደርስባችኋል” የሚሉት ናቸው።

እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ዕወቁ

እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ኢ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ተረዱ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ተገንዘቡ”

## Ezekiel 7:5

ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

እርሱ የሚናገረው አስፈላጊ መሆኑን ለሕዝቅኤልና ለሕዝቡ ለማስታወስ እግዚአብሔር ስለ ራሱ በስሙ ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እኔ ጌታ እግዚአብሔር ይህንን እናገራለሁ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

ጌታ እግዚአብሔር

ይህንን በሕዝቅኤልል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

ጥፋት! ለየት ያለ ጥፋት! እነሆ መጥቶአል

እነዚህ ቃለ-አጋኖዎች ምንባቡን በጣም ከባድ ያደርጉታል ማለት ነው። ኢ.ት፡ “እነሆ፣ ቀድሞ ማንም ያልተለማመደው ዓይነት አስከፊ ጥፋት እየመጣ ነው”

እነሆ፣ እርሱ

“እርሱ እንደሚሆን በፍጹም አትጠራጠሪ”

ፍጻሜ በአንቺ ላይ ተነሣሥቶአል

እየመጣ ያለው ፍርድ ከእንቅልፉ በሚነቃ ጠላት ተመስሎ ተነግሯል። (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)

ከእንግዲህ ተራሮች ደስተኞች አይሆኑም

“ተራሮች” የሚለው ቃል በተራሮች ላይ የሚኖሩትን ሰዎች የሚያመለክት ፈሊጣዊ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በተራሮች ላይ የሚኖሩት ሰዎች ከእንግዲህ ምንም ደስታ አይኖራቸውም” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 7:8

ብዙም ሳይቆይ

“በጣም በቅርቡ”

በአንቺ ላይ ንዴቴን አፈሳለሁ፣ በላይሽ ላይ ቁጣዬን እሞላለሁ

እግዚአብሔር በእንስራ ውስጥ እንደሚያፈሰው ውሃ “አፈሳለሁ” እና “እሞላለሁ” የሚሉትን ቃላት የሚጠቀመው ስለ ቁጣው ለመናገር ነው። እነዚህ ሐረጎች እግዚአብሔር ሕዝቡን በአስከፊ ሁኔታ እንደሚቀጣቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት፡ “በጣም ስለተቆጣሁ በብርቱ እቀጣችኋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና Parallelism የሚለውን ተመልከት)

ንዴት

“ቁጣ” ወይም “ታላቅ ቁጣ”

ዐይኔ በርኅራኄ አይመለከትም

ዓይን ባለቤቱ የሆነውን ሰውን ይወክላል። ኢ.ት፡ “በርኅራኄ አልመለከታቸውም” ወይም “አልራራላቸውም”

አልምርሽም

“ያለ ቅጣት አልተውሽም” ወይም “እቀጣሻለሁ”

እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቂ ዘንድ አስጸያፊ ተግባርሽ በመካከልሽ ይሆናል

ይህንን በሕዝቅኤል 7:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት

Ezekiel 7:10

እነሆ ቀኑ! እነሆ ደርሷል!

“እነሆ! ቀኑ እየደረሰ ነው!” የትኛው ቀን እየደረሰ እንዳለ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። ኢ.ት፡ “እነሆ! አንቺን የምቀጣበት ቀን እየደረሰ ነው!”

እነሆ

“ተመልከት” ወይም “ስማ” ወይም “የምነግርህን ልብ በል”

የጥፋት ፍርድ ወጥቶ ሄዷል

“ጥፋት ወደ እስራኤል መምጣት ጀምሯል” ወይም “በጣም አስፈሪ ነገሮች መምጣት ጀምረዋል”

በትሩ አብቧል፣ እብሪት እምቡጥ ይዟል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የእስራኤል ሕዝብ ትዕቢታቸውን አብዝተዋል” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ በጣም ቁጡና ትዕቢተኛ ሆነዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጭካኔ ወደ አመፅ በትርነት አድጓል

“የሕዝቡ አመፅ በይበልጥ ክፉ ነገሮችን ወደ ማድረግ መርቷቸዋል”

Ezekiel 7:12

ጊዜው ደርሷል፤ ቀኑ ቀርቧል

“ጊዜው” እና “ቀኑ” ሁለቱም እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የሚቀጣበትን ጊዜ ያመለክታሉ። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ቅጣት በቅርቡ ይደርሳል”

ቁጣዬ በመላው ሕዝብ ላይ ነው

“በመላው ሕዝብ ላይ ተቆጥቻለሁ”

በርካታ ሕዝብ

በጣም ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ። እዚህ ጋ፣ ቃሉ የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው።

ሁለቱም በሕይወት እስካሉ ድረስ

“ገዢው” እና “ሻጩ” (7:12) ሁለቱም በሕይወት እስካሉ ድረስ

መላውን ሕዝብ የሚመለከተው ራዕይ አይለወጥም

“እግዚአብሔር ያሳየኝን በመላው ሕዝብ ላይ በእርግጥ ያደርጋል”

አንዳቸውም አይበረቱም

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ማናቸውንም አያበረታም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 7:14

መለከቱን ነፍተዋል

“ከጠላት ጋር እንዲዋጉ ሕዝቡን ለመጥራት መለከቱን ነፍተዋል”

ቁጣዬ በመላው ሕዝብ ላይ ነው

“በመላው ሕዝብ ላይ ተቆጥቻለሁ” ይህንን በሕዝቅኤል 7:12 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

ሰይፉ በስተውጭ ነው

“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉ ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡

ሕንጻው

ከተማው

ረሃብና ቸነፈር በከተማው ውስጥ ያሉትን በማጥፋት ላይ እያለ

“ማጥፋት” የሚለው ቃል “ፈጽሞ መደምሰስ” ለሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በከተማይቱ ውስጥ ያለው አብዛኛው ሕዝብ በረሃብና በበሽታ ይሞታል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሸለቆ እንዳሉ እርግቦች ሁሉም ያለቅሳሉ

እርግቦች አንድ ሰው በማያቋርጥ ሕመም ወይም ጥልቅ ሐዘን ውስጥ ሲሆን የሚያሰማውን ዓይነት የማቃሰት ድምፅ በዝግታ ያወጣሉ። ኢ.ት፡ “ሁሉም እጅግ አዝነው ያለቅሳሉ፣ ድምፃቸውም የእርግብ መንጋ ድምፅ ይመስላል”

Ezekiel 7:17

እጅ ሁሉ ይዝላል፣ ጉልበትም ሁሉ እንደ ውሃ ይሆናል

እጆችና ጉልበቶች ስለ ሕዝቡ ስለ ራሱ የሚወክሉ ናቸው። ኢ.ት፡ “መሥራት እስከማይችሉ ድረስ ሁሉም እጅግ ይፈራሉ፣ ጉልበታቸውም መቆም እስከማይችል ድረስ ደካማ ይሆናል”

መዛል

መደረግ ያለበትን ለማድረግ አለመቻል

ጉልበት ሁሉ እንደ ውሃ ይሆናል

ሊሆን የሚችለው ሌላው ትርጉም፣ ሰዎቹ ሁሉ እጅግ ስለ ፈሩ ፊኛዎቻቸውን መቆጣጠር እንዳቃታቸው የሚያሳየው “ጉልበት ሁሉ ከውሃ ጋር ይንሳፈፋል” የሚለው ነው።

ጉልበት ... እንደ ውሃ የደከመ

ውሃ ሊቆም አይችልም፣ ጉልበታቸው እጅግ ስለሚደክም ሕዝቡ በእግሮቻቸው ለመቆም አይችሉም። (See: Simile)

ሽብር ይሸፍናቸዋል

ሽብር እንደ ልብስ ተደርጎ ተነግሮለታል። ኢ.ት፡ “ምን ያህል እንደ ፈሩ ሁሉም ያያል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በራሳቸው ሁሉ ላይ በራነት

ጸጉርን መላጨት የሐዘን ምልክት ነበር። ኢ.ት፡ “ሁሉም ጸጉራቸውን ይላጫሉ”

በእግዚአብሔር የመዓት ቀን

“እግዚአብሔር በቁጣው በሚሠራበት ቀን” ወይም “እግዚአብሔር በሚቀጣቸው ጊዜ”

ቀኑ

ይህ 24 ሰዓት ካለው ቀን የበለጠ ወይም ያነሰ ጊዜ ሊሆን ይችላል።

ረሃባቸው አይረካም

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ረሃባቸውን ለማርካት አይችሉም” ወይም “ያላቸውን ሁሉ ከበሉ በኋላ እንኳን ገና የተራቡ ይሆናሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ኃጢአታቸው ማሰናከያ ሆኖባቸዋል

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ምክንያቱም የነበራቸው ብዙ ወርቅና ብር ወደ ኃጢአት መርቷቸዋል” ወይም 2) “ክፉዎች ስለሆኑ፣ ምን ያህል ክፉዎች እንደሆኑ ለማሳየት ኃጢአትን ይሠራሉ” የሚሉት ናቸው።

Ezekiel 7:20

ከእነርሱ ጋር

ከተዋቡ ዕንቁዎቻቸው ጋር

እነዚያን ነገሮች በእንግዶች እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ

“እጅ” የሚለው ቃል ቁጥጥርን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። “እነዚያን ጣዖታት የማያውቋቸው ሰዎች በቁጥጥራቸው ስር እንዲያደርጉት እሰጣቸዋለሁ” ወይም “እነዚያን ጣዖታት ለማያውቁ ሰዎች እሰጣቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ብዝበዛ

በጉልበት የተወሰዱ ወይም የተሰረቁ ነገሮች ናቸው

ያረክሷቸዋል

የእስራኤል ሕዝብ የሠሯቸውን ጣዖታት እንግዶቹና ክፉዎቹ ሰዎች ያረክሷቸዋል።

ፊቴን እሰውራለሁ

“ትኩረት አልሰጥም” ወይም “በሌላ አቅጣጫ እመለከታለሁ” ወይም “ልብ አልልም”

የከበረ ስፍራዬ

"የምወደው ስፍራ"። ይህ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ያመለክታል።
ሽፍቶች
የሚሰርቁና የሚያጠፉ ጨካኞች
Ezekiel 7:23
ሠንሠለት አዘጋጅ
ሰንሰለት ባሮችን ወይም እስረኞችን ለማሰር ጥቅም ላይ ይውላል። እግዚአብሔር ይህንን የሚለው ሕዝቡ ባሮች ወይም እስረኞች እንደሚሆኑ ለማሳየት ነው።
ምድሪቱ በደም ፍርድ ተሞልታለች
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ሌሎችን በጭካኔ ገድለዋለና እግዚአብሔር በሀገሪቱ ሁሉ ላይ ይፈርዳል" ወይም 2) "በሀገሪቱ ውስጥ በየቦታው ያሉ ፍርድ ቤቶች ሰዎችን በመግደል ላይ ናቸው"። እዚህ ጋ፣ "ደም" የሚለው ቃል ግድያና ሞትን ይወክላል የሚሉት ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከተማይቱ ጭካኔን ተሞልታለች
ከተማይቱ የዕቃ መያዣ በምትመስልበት መልኩ ተነግሮላታል፣ ጭካኔም በዕቃ መያዣ ውስጥ እንደሚደረግ ቁስ ተነግሮለታል። የነገር ስም የሆነው "ጭካኔ" እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ "በከተማይቱ ውስጥ ጭካኔ በየስፍራው አለ" ወይም "በከተማይቱ የሚኖሩ ብዙ ሰዎች በሌሎች ላይ የጭካኔ ተግባር እየፈጸሙባቸው ነው" (ዘይቤአዊ አነጋገር እና የነገር ስም የሚለውን ተመልከት))
እነርሱ ቤቶቻቸውን ይወርሳሉ
ክፉዎች የእስራኤላውያኑን ቤት ይወስዳሉ
ለኃያላኑ ትዕቢት መጨረሻን አደርጋለሁ
"በእስራኤል ውስጥ ያሉ ብርቱ ሰዎች በራሳቸው መመካታቸውን እንዲያቆሙ አደርጋለሁ"
ቅዱስ ስፍራዎቻቸው ሁሉ ይረክሳል!
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ "የአምልኮ ስፍራዎቻቸውን ጠላት ያረክሳቸዋል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የተቀደሱ ስፍራዎቻቸው
ጣዖታትን የሚያመልኩባቸውን ስፍራዎች
ፍርሐት ይመጣል
"ሕዝቡ ይፈራል"
ሰላምን ይፈልጋሉ
"ከጠላቶቻቸው ጋር ሰላምን ለመፍጠር ይሞክራሉ"
ነገር ግን አንዱም አይሆንም
"ነገር ግን ከጠላቶቻቸው ጋር ሰላምን ለመፍጠር አይችሉም"
Ezekiel 7:26
ጥፋት በጥፋት ላይ ይመጣል
ጥፋት በራሱ ሊንቀሳቀስ እንደሚችል ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ "ከአንዱ ኋላ ሌላኛው ጥፋት ይመጣል" (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
ከነቢይ ራዕይን ይፈልጋሉ
"ነቢያት ምን ዓይነት ራዕይ እንዳዩ ይጠይቋቸዋል"
ሕጉ ከካሕናት፣ ምክርም ከሽማግሌዎች ይጠፋል
"ካሕናቱ ሕጉን አያስተምሩም፣ ሽማግሌዎቹም ጥሩ ምክር ለመስጠት አይችሉም"። ይህ የሚሆነው እግዚአብሔር ጥበብን ስለማይሰጣቸው ነው።
መስፍኑ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "የንጉሡ ወንድ ልጅ" ወይም 2) ከንጉሡ ውጪ የንጉሣዊ ቤተሰብ አባላት የሆኑ ወንዶች ሁሉ የሚሉት ናቸው።
ተስፋ መቁረጥን ይለብሳሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ልብስ አንድ ሰው "ተስፋ አይኖራቸውም" ለሚል ስሜቱ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው ወይም 2) "በማልቀስ ላይ መሆኑን የሚያሳይ ልብስ ይለብሳል" የሚሉት ናቸው። (የአነጋገር ዘይቤ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የምድሪቱ ሰዎች እጆቻቸው በፍርሐት ይንቀጠቀጣል
"እጆች" የሚለው ቃል ሕዝቡን ይወክላል። ኢ.ት፡ "የምድሪቱ ሕዝብ እጆቻቸው እስኪንቀጠቀጡ ድረስ እጅግ ይፈራሉ"

---

Chapter 8
Ezekiel 8:1
እንዲህ ሆነ
እዚህ ጋ፣ ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማመልከት ነው። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለ እዚህ ጋ ልትጠቀምበት እንደምትችል አስብ።
በስድስተኛው ዓመት
ይህ ስድስተኛ ዓመት የትኛውን ጊዜ እንደሚያመለክት ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። ኢ.ት፡ "ንጉሡ ኢዮአቂም በተማረከ በስድስተኛ ዓመት"
በስድስተኛው ወር፣ በወሩም በአምስተኛው ቀን
ይህ በዕብራውያኑ የቀን አቆጣጠር ስድስተኛ ወር ነው። በምዕራባውያኑ አቆጣጠር አምስተኛው ቀን የመስከረም ወር መጀመሪያ አቅራቢያ ነው። ኢ.ት፡ "የስድስተኛው ወር አምስተኛ ቀን" (የዕብራውያን ወራት እና ደረጃን አመልካች ቁጥር የሚለውን ተመልከት)
የጌታ እግዚአብሔር እጅ እንደገና በእኔ ላይ ወደቀች
ኋላ ላይ ሕዝቅኤል እጅ የሚመስል ነገር ስለሚያይ ይህ በቀጥታ መተርጎም ይኖርበታል። ሌሎች እጁን የእግዚአብሔርን ኃልዎት ወይም ኃይል የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር አድርገው ይመርጡት ይሆናል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጌታ እግዚአብሔር
ይህንን በሕዝቅኤል 2:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።
በእኔ ላይ ወደቀች
"ያዘችኝ"
አንድ የሰው መልክ አምሳያ
እዚህ ጋ፣ የነገር ስም የሆነው "መልክ" ማለት ለሕዝቅኤል ሰው መስሎ የታየው ነገር ነው። "መልክ" እና "አምሳያ" ሁለቱም ከግሳዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎሙ ይችላሉ። ኢ.ት፡ "አንድ ሰው የሚመስል ታይቶ ነበር" (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
የጋለ ብረት
ብረት በጣም ሲሞቅ ይግልና ቢጫ ወይም ብርቱካናማ ቀለም ይኖረዋል።
የወገቡ አምሳያ ... የሚያንጸባርቅ ነገር አምሳያ
የነገር ስም የሆነው "አምሳያ" እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ "ወገቡን መስሎ የታየው ... አንጸባራቂ ነገር መስሎ የታየው" (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 8:3
ያዘ
"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምናልባት "ሰው የሚመስለውን ምስል" ይሆናል (ሕዝቅኤል 8:2)።
በሰማይና በምድር መካከል
"በመሬትና በጠፈር መካከል"
ከእግዚአብሔር በሆነው ራዕይ ወደ ኢየሩሳሌም አመጣኝ
"በራዕይ" የሚለው ቃል ትርጉም፣ ይህ ልምምድ የመጣው በሕዝቅኤል አሳብ ውስጥ ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች በሚያሳየው ጊዜ አካሉ በዚያው በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ይሆናል ማለት ነው።
ሰሜናዊ ውስጠኛው በር
"የቤተ መቅደሱ ሰሜናዊ ውስጠኛው በር"። ቤተ መቅደሱ ውስጠኛና ውጪኛ በሆኑ ሁለት ግምቦች የተከበበ ነበር። ይህ በር በስተሰሜን በውስጠኛው ግምብ ላይ ነበረ።
ታላቅ ቅንዓት የሚያነሣሣው ጣዖት
"እግዚአብሔር በጣም እንዲቀና የሚያደርገው ጣዖት"
ሜዳው ላይ ዐይቼው እንደነበረው ራዕይ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ሜዳው ላይ በነበርኩበት ጊዜ በራዕይ ዐይቼው የነበረውን ያንኑ የሚመስል" ወይም 2) "ሜዳው ላይ በነበርኩበት ጊዜ ያየሁትን ያንኑ የሚመስለውን" የሚሉት ናቸው።
ሜዳው
ጥቂት ዛፎች ያሉበት ዝርግ የሆነ ሰፊ መሬት
Ezekiel 8:5
የሰው ልጅ
"የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "ከሰው የተወለደ ልጅ"። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ "ሟች ሰው" ወይም "ሰው"
ዓይኖችህን አንሣ ... ዓይኖቼን አነሣሁ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ የሚያሳየው ወደ አንድ ነገር መመልከት እንደነበረበት ነው። ኢ.ት: “ወደ ላይ እይ … ወደ ላይ እየ” ወይም “ፊትህን አዙርና ተመልከት … ፊቴን አዙሬ ተመለከትኩ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ወደ መሰዊያው ወደሚያመራው በር
“ሰዎች ወደ መሰዊያው ለመድረስ አልፈው የሚሄዱበት በር”
የሚያደርጉትን ታያለህ?
የሕዝቅኤልን ትኩረት ሰዎቹ ወደሚያደርጉት ነገር ለማምጣት እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። ኢ.ት: “ሰዎቹ እዚህ ጋ የሚያደርጉትን ነገር የምጠላበትን ምክንያት እንድትረዳ እፈልጋለሁ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 8:7
አደባባዩ
የትኛው አደባባይ መሆኑን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። “የቤተ መቅደሱ አደባባይ”
Ezekiel 8:10
እነሆ
ይህ ቃል የሚያሳየው ሕዝቅኤል ባየው ነገር መደነቁን ነው። የአንተ ቋንቋ ይህንን ለማሳየት ሌላ ቃል ይኖረው ይሆናል።
የተለያዩ በደረታቸው የሚሳቡ ነገሮች እና እርኩሳን አራዊት
“በግድግዳው ላይ የተቀረጹ፣ የተለያዩ በደረታቸው የሚሳቡ እንስሶች እና እርኩሳን አራዊት”። “በደረታቸው የሚሳቡ ነገሮች” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ነፍሳትን እና ሌሎች ትናንሽ እንስሶችን ነው።
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዙሪያውን በግንቡ ላይ
የትኛው ግንብ እንደሆነ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። ኢ.ት: “በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ባለው ግንብ ላይ”
ያዕዛንያ … ሳፋን
የወንዶች ስም ነው (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የዕጣን ማጨሻ
ሰዎች እግዚአብሔርን ወይም ሐሰተኞች አማልክትን በሚያመልኩበት ጊዜ ዕጣን የሚያጨሱበት ጎድጎድ ያለ ዕቃ
Ezekiel 8:12
የእስራኤል ቤት ሽማግሌዎች በጨለማው ውስጥ የሚያደርጉትን ታያለህ?
ሽማግሌዎቹ የሚያደርጉትን እንዲያይ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እያዘዘው ነው። ኢ.ት: “የእስራኤል ቤት ሽማግሌዎች በጨለማው ውስጥ የሚያደርጉትን እይ”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በጣዖቱ ድብቅ ጓዳ
“ጣዖቱን ሲያመልክ ማንም ሊያየው የማይችልበት ክፍል”
Ezekiel 8:14
በሰሜን ወዳለው የእግዚአብሔር ቤት መግቢያ በር
ይህ በሕዝቅኤል 8:3. ያለው ዓይነት ሳይሆን የሰሜኑ ውጫዊ በር ነበር
እነሆ!
ይህ ቃል የሚያሳየው ሕዝቅኤል ባየው ነገር መደነቁን ነው።
ለተሙዝ ማልቀስ
ሐሰተኛው አምላክ ተሙዝ ሞቶ ስለነበረ አዘኑ (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
አንተ ሰው … ይህንን ታያለህ?
ሕዝቅኤል እያየ ስላለው ነገር እንዲያስብ እግዚአብሔር ያዘዋል። ኢ.ት: “አንተ ሰው … ስለዚህ ነገር አስብ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 8:16
እነሆ!
ይህ ቃል የሚያሳየው ሕዝቅኤል ባየው ነገር መደነቁን ነው።
መተላለፊያ
በረድፍ ወይም በቋሚ እንጨት ድጋፍ የመግቢያውን ፊት የሚሸፍን
ፊታቸው ወደ ምስራቅ ዞሮ
“ወደ ምስራቅ ይመለከቱ ነበር”
Ezekiel 8:17
አንተ ሰው … ይህንን ታያለህ?
ሕዝቅኤል እያየ ስላለው ነገር እንዲያስብ እግዚአብሔር ያዘዋል። ኢ.ት: “ አንተ ሰው … ስለዚህ ነገር አስብ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
በዚህ ቦታ እነዚህን አስጸያፊ ነገሮች ማድረጋቸው ለይሁዳ ቤት ይህ ቀላል ነገር ነው?
እግዚአብሔር በይሁዳ ቤት ላይ መቆጣቱ ትክክል መሆኑን ለማሳየት ይህንን ጥያቄ ያቀርባል። ኢ.ት: “በዚህ ቦታ በሚያደርጓቸው በእነዚህ አስጸያፊ ተግባሮች ምክንያት በይሁዳ ቤት ላይ ብቆጣ ልክ ነኝ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የይሁዳ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የይሁዳን ዘሮች ያመለክታል። እነዚን ቃላት በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምካቸው ተመልከት። ኢ.ት: “የይሁዳ ሕዝብ ወገን” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ምድሪቱን በአመፅ ሞልተዋታል
“በሀገሩ ሁሉ የአመፅን ተግባር ይፈጽማሉ” ወይም “በሀገሪቱ ሁሉ እርስ በእርሳቸው ይገዳደላሉ”
ቁጣዬን ለማነሣሣት
“እንድቆጣ ለማድረግ”
ቅርንጫፉን ወደ አፍንጫዎቻቸው አቅርበዋል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰዎቹ ለሐሰተኛ አምልኮ ቅርንጫፎችን ይጠቀሙ ነበር ወይም 2) ሰዎቹ በእግዚአብሔር ላይ ማመፃቸውን ለማሳየት ቅርንጫፎቹን ይጠቀሙባቸው ነበር የሚሉት ናቸው። “ቅርንጫፍ… ወደ አፍንጫዎቻቸው” የሚሉት ቃላት ምናልባት በቀጥታ የዛፍ ቅርንጫፍና አፍንጫን ያመለክት ይሆናል ወይም የእጅ እንቅስቃሴን የሚገልጽ ስያሜ ይሆናል። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ዓይኔ ርኅራኄ አይኖረውም
ዓይን ባለቤቱ የሆነውን ሰውን ይወክላል። ኢ.ት: “በርኅራኄ አልመለከታቸውም” ወይም “አልራራላቸውም”
አልምራቸውም
“ገና እቀጣቸዋለሁ”
በታላቅ ድምፅ በጆሮዬ ላይ ቢጮኹም እንኳን
“በታላቅ ድምፅ በጸሎታቸው ወደ እኔ ቢጮኹም”
አልሰማቸውም
“አላዳምጣቸውም”

---

Chapter 9
Ezekiel 9:1
እኔ እየሰማሁ ጮኸ
“ሲጣራ ሰማሁት”
ጮኸ
(በሕዝቅኤል 8:2) “ሰው የሚመስለው” ጮኸ
የጥፋት መሣሪያ

ሰዎችን ወይም ነገሮችን ለማጥፋት የሚያገለግል የጦር መሣሪያ
ማረጃ የጦር መሣሪያ
ብዙ ሰዎችን መግደያ የጦር መሣሪያ
እነሆ
“እይ” ወይም “ስማ” ወይም “የምነግርህን ልብ በል”
ወደ ሰሜን ወደሚመለከተው የላይኛው በር
“የላይኛው የሰሜኑ በር” ወይም “የውስጠኛው አደባባይ የሰሜኑ በር”
በፍታ
ከእጽዋት የሚሠራ ጠንካራና ለስላሳ ጨርቅ። በሞቃታማ አካባቢ በሚኖሩ በርካታ ሰዎች የሚለበስ። ኢ.ት፡ “ለስላሳ ጨርቅ” (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
የጸሐፊ ዕቃ
ጸሐፊ የሚጽፍባቸው የጽሕፈት መሣሪያዎች
ነሐስ
ደማቅ ያልሆነ ወርቃማ ቀለም ያለው ብረት። ለጥንካሬ ቆርቆሮ ተጨምሮበት በአብዛኛው ከመዳብ የሚሠራ (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 9:3
ከነበረበት ከኪሩቤል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “አራት ክንፍ ካላቸው ፍጡራን ከበላያቸው” (ሕዝቅኤል 1:5) ወይም 2) በቤተ መቅደሱ ውስጥ በቅድስተ ቅዱሳኑ ስፍራ ከሁለት ኪሩቤሎች መካከል የሚሉት ናቸው። ይህንን በቀጥታ ለመተርጎም ሞክር።
የቤቱ መግቢያ በር
“ቤት” የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ያመለክታል።
በፍታ
ይህንን በሕዝቅኤል 9:2 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ትመልከት።
የጸሐፊ ዕቃ
ጸሐፊ የሚጽፍባቸው የጽሕፈት መሣሪያዎች። ይህንን በሕዝቅኤል 9:2 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።
አቃስትና በረጅሙ ተንፍስ
እነዚህ ድምፆች ሰዎች በጣም ሐዘን በሚሰማቸው ወይም ስለ አንድ ነገር በሚተክዙበት ጊዜ የሚያሰሟቸው ናቸው።
በከተማይቱ መካከል ስለተፈጸመው አስጸያፊ ተግባር
“በከተማይቱ ስለተፈጸመው አስፈሪ ነገሮች” ወይም “በከተማይቱ ውስጥ ሰዎች ስለሚያደርጓቸው አስከፊ ነገሮች”
Ezekiel 9:5
እኔ እየሰማሁ ለሌሎቹ ተናገራቸው
“ሌሎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሕዝቅሌ 9:1 ያሉትን ጠባቂዎች ነው።
ዓይኖችህ አይራሩ
ዓይን ባለቤቱ የሆነውን ሰውን ይወክላል። ኢ.ት፡ “አትራራላቸው” (See: and Synecdoche)
አትማራቸው
“ከመግደል አትመለስ”
በራሱ ላይ ምልክት አድርግ
እነዚህ በኢየሩሳሌም ስለተፈጸሙ አስጸያፊ ተግባሮች ሲያለቅሱ የነበሩ ሰዎች ናቸው። “ምልክት” የሚለውን በሕዝቅኤል 9:4 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።
በመቅደሴ ጀምሩ
ሰዎቹ በመቅደስ ምን ማድረግ እንደሚጀምሩ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። ኢ.ት፡ “በመቅደሴ ምልክቱ የሌለበትን ሰው መግደል ጀምሩ”
ሽማግሌዎቹ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ሰባዎቹ የእስራኤል ቤት ሽማግሌዎች” (ሕዝቅኤል 8:11) ወይም 2) የትኛውም “ሽማግሌ” (የቁጥሩን መጀመሪያ ተመልከት)።
Ezekiel 9:7
ቤቱ
ቤተ መቅደሱ
ከተማይቱን አጠቁ
“ከተማ” የሚለው ቃል በከተማይቱ ለሚኖሩ ሰዎች ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በከተማይቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች አጠቁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በግንባሬ ተደፋሁ
“በምድር ላይ ሰገድሁ” ወይም “በምድር ላይ ተጋደምኩ”። ሕዝቅኤል የወደቀው በአደጋ ምክንያት አይደለም። እርሱ ምድር ላይ የወደቀው እግዚአብሔርን መፍራቱንና ማክበሩን ለማሳየት ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 1:28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ኦ፣ ጌታ እግዚአብሔር
ሕዝቅኤል ይህንን የሚለው ሰዎቹ በኢየሩሳሌም ላይ እንዲያደርጉት ጌታ በነገራቸው ነገር ምክንያት በጣም ስለ ደነገጠ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 4:14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በኢየሩሳሌም ላይ መዓትህን በማፍሰስ የእስራኤልን ትሩፋን በሙሉ ታጠፋለህ?
እግዚአብሔር ትሩፋኑን እንዳያጠፋቸው ሕዝቅኤል እየለመነ ነው። ኢ.ት፡ “እባክህን፣ በኢየሩሳሌም ላይ መዓትህን በማፍሰስ የእስራኤልን ትሩፋን በሙሉ አታጥፋቸው!” (የአነጋገር ዘይቤ እና ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
በኢየሩሳሌም ላይ መዓትህን በማፍሰስ
መዓት እግዚአብሔር ከዕቃ ውስጥ አውጥቶ እንደሚያፈስሰው ፈሳሽ ተደርጎ ተነግሯል። “ኢየሩሳሌም” የሚለው ቃል በከተማይቱ የሚኖሩትን ሰዎች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። የነገር ስም የሆነው “ማፍሰስ” እንደ ግሥ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “መዓትህን በኢየሩሳሌም ላይ በምታፈስበት ጊዜ” ወይም “በጣም ስለ ተቆጣኻቸው የኢየሩሳሌምን ሰዎች በምትቀጣቸው ጊዜ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 9:9
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እጅግ ታላቅ
“በጣም ታላቅ”
ምድሪቱ በደም፣ ከተማይቱም በጥመት የተሞላች ናት
እዚህ ጋ፣ “ምድር” በደም እንደ ተሞላች ዕቃ ተደርጋ ተነግሮላታል። “ደም” እዚህ ጋ የመግደል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “ከተማ” በውስጡ “ጥመት”ን እንደ ያዘ ዕቃ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “በምድሪቱ ሁሉ ላይ ሰዎች ንጹሐንን እየገደሉ ነው፣ በከተማው ሁሉ ላይ ሰዎች አስከፊ ነገሮችን እያደረጉ ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዐይኔ አይራራም
ዐይን ባለቤቱ የሆነውን ሰውን ይወክላል። ኢ.ት፡ “በርኅራኄ አላያቸውም” ወይም “አልራራላቸውም”
ሁሉንም በራሳቸው ላይ አመጣለሁ
የአንድን ሰው ተግባር በራሱ ላይ ማምጣት የሚወክለው እርሱን ስለ ክፉ ተግባሩ መቅጣትን ነው። ኢ.ት፡ “የሚገባቸውን ቅጣት መስጠት”

Chapter 10
Ezekiel 10:1
በጉልላቱ አቅጣጫ
“በክቡ ጣራ አቅጣጫ”
ኪሩቤል
ይህንን በሕዝቅኤል 9:3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሰንፔር የሚመስል
ጠቃሚ የሆነ ሰማያዊ ወይም አረንጓዴ የከበረ ድንጋይ
የዙፋን አምሳያ
“የሆነ ነገር የሚመስል፣ ዙፋን የሚመስል”። ሕዝቅኤል ዙፋን ስለመሰለው ነገር በእርግጠኝነት ለመናገር አይፈልግም።
በፍታ
ከእጽዋት የሚሠራ ጠንካራና ለስላሳ ጨርቅ። በሞቃታማ አካባቢ በሚኖሩ በርካታ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሰዎች የሚለበስ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 9፡2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ለስላሳ ጨርቅ” (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
በመንኩራኩሮቹ መካከል ሂድ
“መንኩራኩሮች” የሚለውን ቃል በሕዝቅኤል 1፡15 እንዳለው አድርገህ ተርጉመው።
የሚነድ ከሰል
ከሰል እሳት ከነደደ በኋላ የሚቀር የተቃጠለ የእንጨት ቁርጥራጭ ነው። ጥቁር ቢሆንም በእሳት በሚያያዝበት ጊዜ ቀይና ብርቱካናማ ቀለም ይኖረዋል፤ ከሰል በመባልም ይታወቃል።
በከተማይቱ ላይ በትነው
“በከተማይቱ ላይ እርጨው” ወይም “በከተማይቱ ላይ አሰራጨው”
Ezekiel 10:3
በውስጠኛው አደባባይ ... ኪሩቤል ቆመ
ይህ ቀጥሎ ለሚመጡት ሁነቶች ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ኪሩቤል
ይህንን በሕዝቅኤል 9፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
በስተቀኙ
አንድ ሰው ወደ ምስራቅ በሚመለከትበት ጊዜ የደቡቡ አቅጣጫ “በስተቀኙ” ይሆናል። ኢ.ት፡ “በደቡብ በኩል”
ቤቱ
ቤተ መቅደሱ
የእግዚአብሔር ክብር
ይህንን በሕዝቅኤል 1፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሞላው
የእግዚአብሔር ክብር ሞላው
Ezekiel 10:6
እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው እንቅስቃሴው የሚጀምርበትን ጊዜ ለማመልከት ነው። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለ እዚህ ጋ ልትጠቀምበት እንደምትችል አስብበት።
እግዚአብሔር በፍታ የለበሰውን ሰውዬ -- ብሎ ባዘዘው ጊዜ
ይህ በሕዝቅኤል 10፡2 ተሰጥቶ የነበረው መረጃ የተደገመበት ነው። ሕዝቅኤል በ10፡3-5 ስለ ኪሩቤል እና ስለ እግዚአብሔር ክብር ከተናገረ በኋላ ላይነን ለብሶ ስለነበረው ሰው ወደ መናገሩ ይመለሳል።
በፍታ የለበሰው ሰው
“በፍታ”ን በሕዝቅኤል 9፡1 እንዳለው አድርገህ ተርጉመው።
በመንኩራኩሮቹ አጠገብ
“መንኩራኩር”ን በሕዝቅኤል 1፡15 እንዳለው አድረገህ ተርጉመው።
በኪሩቤል ላይ አንድ የሰው እጅ የሚመስል ከክንፎቻቸው ሥር አየሁ
“ኪሩቤል ከክንፎቻቸው ሥር የሰው እጅ የሚመስል ነገር ኖሮአቸው አየሁ”
Ezekiel 10:9
እነሆ
ሕዝቅኤል ባየው ተደንቋል
መንኩራኩሮች
ይህንን በሕዝቅኤል 1፡15 ላይ እንዴት እንደተርጎምከው ተመልከት።
ኪሩቤል
ይህንን በሕዝቅኤል 9፡3 ላይ እንዴት እንደተርጎምከው ተመልከት።
ኪሩብ
ይህ የ”ኪሩቤል” ነጠላ ቁጥር ነው።
የመንኩራኩሮቹ አምሳያ ልክ እንደ ቢረሌ ድንጋይ አንጸባራቂ ነበር
“አምሳያ” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሡ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “መንኩራኩሮቹ የቢረሌ ድንጋይ መስለው ይታዩ ነበር” ወይም “መንኩራኩሮች ሆነው የታዩት የቢረሌ ድንጋይ ይመስሉ ነበር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
የቢረሌ ድንጋይ
እዚህ ጋ የተጠቀሰው “ቢረሌ” በጣም ከባድና ዋጋ ያለው ድንጋይ ነው። ይህ ቢረሌ ምናልባት አረንጓዴ ወይም ሰማያዊ ነበር። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
የአራቱም አምሳያ አንድ ዓይነት መልክ ነበር
“አምሳያ” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። “መልክ” የሚለው የነገር ስም እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “አራቱም ተመሳሳይ መልክ ነበራቸው” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
አንደኛው መንኩራኩር በሌላኛው መንኩራኩር ተሰባጥሮ
“መሰባጠር” የሚለው ቃል “ማቋረጥ” ወይም “በሌላው ሥር ማለፍ” ማለት ነው።
በየትኛውም በአራቱ አቅጣጫ ይሄዱ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “የእነርሱ” የሚያመለክተው ፍጡራኑን ነው። ኢ.ት፡ “ፍጡራኑ በሚመለከቱባቸው ከአራቱ በየትኛውም አቅጣጫ ቀጥ ብለው ይሄዱ ነበር” ወይም 2) “የእነርሱ” የሚያመለክተው መንኩራኩሮቹን ነው የሚሉት ናቸው።
ራሳቸው የዞረበትን የትኛውንም አቅጣጫ ይከተሉ ነበር
“ራስ” ለሚለው ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ክንፍ ያላቸውን ፍጡራን ይመለከታል። ኢ.ት፡ “ክንፍ ያላቸው ፍጡራን በሚመለከቱበት በየትኛውም አቅጣጫ ይሄዱ ነበር” ወይም 2) ይህ የሚያመለክተው ከፊት ያለውን መንኩራኩር ነው የሚሉት ናቸው። ኢ.ት፡ “የፊተኛው መንኩራኩር በሚሄድበት በየትኛውም አቅጣጫ ይከተሉት ነበር”።
Ezekiel 10:12
አካላቸው በሙሉ
“የኪሩቤል ሙሉ አካላቸው”
መንኩራኩሮች
“መንኩራኩሮች” የሚለውን ቃል በሕዝቅኤል 1፡15 እንዳለው አድርገህ ተርጉመው።
መንኩራኩሮቹ “ተሽከርካሪ” ተብለው ተጠሩ
“ተሽከርካሪ” ማለት “መሾር” ማለት ነው። እዚህ ጋ ይህ የመንኩራኩሮቹ ስም ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው መንኩራኩሮቹን ‘ተሽከርካሪ’ ብሎ ጠርቷቸዋል” ወይም “የመንኩራኩሮቹ ስም ‘ተሽከርካሪ’ ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እያንዳንዳቸው አራት ፊት ነበራቸው
“እያንዳንዱ ኪሩብ አራት ፊት ነበረው” ወይም “ለእያንዳንዱ ኪሩቤል አራት ፊት ነበራቸው”። እያንዳንዱ ፍጥረት በፊት ለፊቱ፣ በስተኋላው፣ በራሱ ግራና ቀኝም ፊት ነበረው። ይህንን በሕቅኤል 1፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Ezekiel 10:15
ኪሩቤል
ይህንን በሕዝቅኤል 9፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሕያዋን ፍጡራን
ይህንን በሕዝቅኤል 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የኮቦር ቦይ
ይህ ከለዳውያን የአትክልት ቦታቸውን ለማጠጣት የቆፈሩት ወንዝ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 1፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት
ተነሣ
“ወደ ሰማይ ወጣ”
በአጠገባቸው ገና ቆመው ነበር
“መንኩራኩሮቹ ከኪሩቤል ጋር ነበሩ”። ኢ.ት፡ “መንኩራኩሮቹ ከኪሩቤል ጋር ተንቀሳቀሱ”
ጸንተው ቆሙ
“ጸንተው ቆዩ” ወይም “አልተንቀሳቀሱም”
የሕያው ፍጡሩ መንፈስ በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ነበር
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሕዝቅኤል በቁጥር 15 ላይ ስለ “ፍጡራን” የሚናገረው አንድ ፍጡር እንደሆነ አድርጎ ነው። ኢ.ት፡ “የሕያዋን ፍጡራኑ መንፈስ በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ነበር” ወይም 2) ሕዝቅኤል የሚጠቀመው የአነጋገር ዘይቤን ነው። ኢ.ት፡ “የሕይወት መንፈስ በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ነበር” ወይም “ሕያው መንፈስ በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ነበር” ወይም 3) በፍጡራኑ እና በመንኩራኩሮቹ ውስጥ ያለው መንፈስ አንድ ነው የሚሉት ናቸው። ይህንን በሕዝቅኤል 1፡22 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ለፍጡራኑ ሕይወት የሰጣቸው ያው መንፈስ ለመንኩራኩሮቹ ደግሞ ሕይወትን ሰጣቸው” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 10:18
የእግዚአሐብር ክብር
ይህንን በሕዝቅኤል 1፡28 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ቤቱ
ቤተ መቅደሱ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በላዩ ቆመ
“በላዩ ቆየ” ወይም “በላዩ ላይ ጠበቀ”
ከላይ መጣባቸው
“ከኪሩቤል በላይ ወጣ”
Ezekiel 10:20
ሕያዋን ፍጡራን
ይህንን በሕዝቅኤል 1፡13 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የኮቦር ቦይ
ይህ ከለዳውያን የአትክልት ቦታቸውን ለማጠጣት የቆፈሩት ወንዝ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 1፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
የሰው እጅ የሚመስል
እዚህ ጋ የነገር ስም የሆነው “መምሰል” ሕዝቅኤል ሲያየው የሰው መስሎ የታየው ነገር ማለት ነው። ቃሉ ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የሰው እጅ የሚመስል ነገር” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
የፊታቸው መልክ ቀድሞ ያየሁትን የሚመስል ነበር
የነገር ስም የሆነው “መምሰል” ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ፊታቸው ቀድሞ ያየሁትን ፊት ይመስላል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
ቀጥ ብለው ወደፊት ሄዱ
“ወደፊት እያዩ” ወይም “በቀጥታ ወደፊት እያዩ”
በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ስዕላዊ ንግግሮች በዘይቤአዊ አነጋገር ተነግረዋል
በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ዘይቤአዊ አነጋገር በመጠቀም “ይህቺ ከተማ ማሰሮ ናት፣ በማሰሮው ውስጥ ያለው ሥጋም እኛ ነን” ይሉ ነበር፣ ትርጉሙም በኢየሩሳሌም ምንም ጉዳት አይደርስባቸውም ማለት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 11
Ezekiel 11:1
ወደ ምስራቅ ወደሚመለከተው ወደ ምስራቁ የእግዚአብሔር ቤት መግቢያ
ይህ በር የቤተ መቅደሱን አካባቢ የሚከበው ግንብ አካል ነው። ኢ.ት፡ “በምስራቁ በኩል የእግዚአብሔርን ቤት በሚከበው ግንብ ላይ ያለው በር” ወይም “በቤተ መቅደሱ አደባባይ በምስራቁ ግንብ ላይ ያለው በር”
የእግዚአብሔር ቤት
ይህንን በሕዝቅኤል 8፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል የሚቀጥለው አስገራሚ መረጃ ላይ እንድናተኩር ያነቃናል።
ሃያ አምስት ሰዎች
“25 ሰዎች” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
የዓዙር ልጅ ያእዛንያ እና የበናያስ ልጅ ፈላጥያ
እነዚህ የወንዶቹ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
በመካከላቸው
“በሃያ አምስቱ ሰዎች መካከል”
Ezekiel 11:2
የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”
ቤቶች የሚሠሩበት ጊዜ አሁን አይደለም
ይህ ሕዝቡ ደህንነት ስለተሰማቸው አሁን ላይ ቤት ለመሥራት እንዳላሳሰባቸው ያሳያል። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች “ቤቶቻችንን የምንሠራበት ጊዜ አሁን ነው” የሚል ይነበብባቸዋል። ይህም ማለት፣ ሕዝቡ ደህንነት ስለተሰማቸው ቤቶችን ለመሥራት ፈልገዋል።
ይህቺ ከተማ ማሰሮ ናት፣ እኛም ሥጋ ነን
ሕዝቡ ስለ ራሳቸው የተከተፈ ሥጋ እንደሆኑና ከተማይቱም እንደ ሥጋ ማስቀመጫ ወይም ማብሰያ ማሰሮ እንደሆነች አድርገው ይናገራሉ። ዘይቤአዊው አነጋገር በከተማይቱ ውስጥ እነርሱ አስፈላጊዎችና ጉዳት የማይደርስባቸው መሆናቸውን ይጠቁማል። ኢ.ት፡ “ማሰሮ ሥጋን እንደሚከልል ይህቺም ከተማ እንደ ማሰሮ ትከልለናለች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ማሰሮው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሥጋ ለማስቀመጥ የሚያገለግል ማሰሮ ወይም 2) ሥጋ ለማብሰል የሚያገለግል ማሰሮ የሚሉት ናቸው።
Ezekiel 11:5
የእግዚአብሔር መንፈስ ወደቀብኝ
ሕዝቅኤል ትንቢት እንዲናገር የእግዚአብሔር መንፈስ እርሱን ማነሣሣቱና ማስታጠቁን የእግዚአብሔር መንፈስ እንደወደቀበት አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔር መንፈስ ሥልጣንን ሰጠኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የምትናገሩት ይህንን ነው
“እነዚህን ነገሮች ተናግራችኋል”። ይህ ሕዝቡ በሕዝቅኤል 11፡3 ይናገሩት የነበረውን ያመለክታል።
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ በዓመታት ውስጥ የነበሩትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እስራኤላውያን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሥጋው የገደላችኋቸው ሰዎች ናቸው፣ ማሰሮው ደግሞ ከተማይቱ ናት
እግዚአብሔር የተገደሉትን ሰዎች እንደ ተከተፈ ሥጋ፣ ከተማይቱንም ሥጋው እንደሚቀመጥበት ወይም እንደሚበስልበት ማሰሮ አድርጎ ይናገራል። ይህንን ዘይቤአዊ አነጋገር በሕዝቅኤል 11፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የገደላችኋቸው ሰዎች በማሰሮ ውስጥ ያለ ሥጋ የሚመስሉ ናቸው፣ ከተማይቱም ማሰሮ ትመስላለች። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እናንተ ግን ከውስጧ ልትወጡ ነው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ይሁን እንጂ ከውስጧ ላወጣችሁ ነው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 11:8
ሰይፍን ፈርታችኋል፣ ሆኖም ሰይፍን አመጣባችኋለሁ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል በሰይፎቻቸው ሰዎችን የሚገድሉትን ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ጦርነትን ፈርታችኋል፣ ሆኖም የሚወጋችሁን የጠላት ሰራዊት አመጣባችኋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይህ የጌታ እግዚአብሔር መግለጫ ነው
እግዚአብሔር የሚናገረው የሚፈጸም መሆኑን ለመግለጽ ስለ ራሱ በስሙ ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “ይህንን የተናገርኩት እኔ ጌታ እግዚአብሔር ነኝ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
በባዕዳን እጅ አሳልፌ እሰጣችኋለሁ
እዚህ ጋ “እጅ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ይወክላል። ኢ.ት፡ “በባዕዳን ኃይል ሥር አደርጋችኋለሁ” ወይም “ባዕዳን እንዲይዙአችሁ አደርጋቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በሰይፍ ትወድቃላችሁ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል በሰይፎቻቸው ሰዎችን የሚገድሉትን ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በሰይፎቻቸው ይገድሏችኋል” ወይም “በጦርነት ትሞታላችሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ዕወቁ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ተረዱ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ተገንዘቡ”
Ezekiel 11:11
ይህቺ ከተማ የማብሰያ ማሰሮ አትሆንላችሁም፣ እናንተም ሥጋ አትሆኑም
ሕዝቡ ስለ ራሳቸው የተከተፈ ሥጋ እንደሆኑና ከተማይቱም እንደ ሥጋ ማስቀመጫ

ወይም ማብሰያ ማሰሮ እንደሆነች አድርገው ተናግረው ነበር። እግዚአብሔር ይህ እውነት አይደለም ይላል። ይህንን ዘይቤአዊው አነጋገር በሕዝቅኤል 11፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “ማሰሮ ሥጋን እንደሚከልል ይህቺም ከተማ እንደ ማሰሮ አትከልላችሁም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእስራኤል ድንበር ውስጥ
“በእስራኤል ምድር”
በትዕዛዛቱ አልሄዳችሁም
ሰው በመንገድ ላይ እንደሚሄድ ትዕዛዛቱን የሚጠብቁ በእነርሱ ላይ እንደሚሄዱ አድርጎ እግዚአብሔር ይናገራል። ኢ.ት: “ትዕዛዛቱን ያልጠበቃችሁለት እርሱ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 11:13
እንዲህ ሆነ
እዚህ ጋ፣ ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው እንቅስቃሴው የሚጀምርበትን ጊዜ ለማመልከት ነው። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለ እዚህ ጋ ልትጠቀምበት እንደምትችል አስብበት።
የበናያስ ልጅ ፈለጥያ
ይህ የአንድ ሰው ስም ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 11፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
በግንባሬ ተደፋሁ
“በምድር ላይ ሰገድሁ” ወይም “በምድር ላይ ተጋደምኩ”። ሕዝቅኤል የወደቀው በአደጋ ምክንያት አይደለም። እርሱ በምድር ላይ የወደቀው ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮትና ፍርሐት ለማሳየት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ኦ፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ
“ኦ” የሚለው ቃል ፍርሐትንና ሐዘንን የሚገልጽ ድምፅ ነው። ኢ.ት: “ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ አይሁን” ወይም “አይ፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ” (ቃልአጋኖ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 11:14
የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ወንድሞችህ! ወንድሞችህ!
ይህ አጽንዖት ለመስጠት ሁለት ጊዜ ተነግሯል
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: “የእስራኤል ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እነዚያ ሁሉ በኢየሩሳሌም በሚኖሩት የተነገረላቸው ናቸው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ስለ እነርሱ ስለ ሁሉም ይናገራሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እነዚያ ሁሉ የተነገረላቸው ናቸው
አንዳንድ ትርጉሞች “ሁሉም የእነርሱ ናቸው” የሚል አላቸው
ይህቺ ምድር ርስታችን ሆና ተሰጥታናለች
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ይህቺን ምድር ርስት አድርጎ ሰጥቶናል” ወይም “ይህቺ ምድር ርስታችን ሆናለች” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 11:16
መቅደሳቸው ሆኜ ነበር
እግዚአብሔር በምርኮ ባለው ሕዝብ መካከል ማደሩን ሲገልጽ መቅደስ እንደሆነላቸው አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “ከእነርሱ ጋር ነበርኩ” ወይም “እንደ አምልኮ ስፍራቸው ነበርኩ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከሕዝቦች መካከል እሰበስባችኋለሁ፣ ከየሀገራቱም መልሼ አከማቻችኋለሁ
በመሠረቱ የእነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉም አንድ ነው። ድግግሞሹ አጽንዖት የሚሰጠው እግዚአብሔር ምርኮኞቹን ወደ እስራኤል ምድር ለመመለስ የሰጠው ተስፋ እርግጥ መሆኑን ነው። ኢ.ት: “ከየሀገራቱ ሁሉ መልሼ አመጣችኋለሁ”
ከተበተናችሁበት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እናንተን ከበተንኩበት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የሚያስከፋውን ነገር ሁሉ እና የሚያስጸይፈውን ተግባር ሁሉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ እግዚአብሔር ጣዖታትን ሁሉ ከእስራኤል እንደሚያስወግድ አጽንዖት ይሰጣሉ።
የሚያስከፋውን ነገር ሁሉ
ይህ ማለት የሚያስጠሉ ወይም የሚያስቀይሙ ነገሮችን ማለት ነው። እዚህ ጋ፣ ይህ የሚያመለክተው ጣዖታትን ነው።
Ezekiel 11:19
አንድ ልብ እሰጣቸዋለሁ ... የሥጋ ልብ እሰጣቸዋለሁ
እግዚአብሔር አንድ ልብና አንድ መንፈስ እንዳለው እንደ አንድ ሰው አድርጎ የሚናገረው በምርኮ ስላሉት እስራኤላውያን ሁሉ ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አንድ ልብ እሰጣቸዋለሁ
እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ፈሊጣዊው አነጋገር የሚወክለው ፈቃድን እና ስሜትን ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሁሉ አንድ ልብ የሰጣቸው ያህል ተመሳሳይ የሆነ አዲስ ስሜት እንደሚጋሩ ይናገራል (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አዲስን መንፈስ በውስጣቸው አደርጋለሁ
እዚህ ጋ “መንፈስ” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር አሳብንና ጸባይን ይወክላል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ አዲስ መንፈስ የሰጣቸው ያህል አዳዲስ አሳቦችን እንዲያስቡ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከሥጋቸው ውስጥ የድንጋይን ልብ አወጣለሁ፣ የሥጋንም ልብ እሰጣቸዋለሁ
ሕዝቡ የድንጋይ ልብ ስለነበራቸው እልኸኛ እንደሆኑና የሥጋ ልብ ሲኖራቸው በፈቃደኝነት የሚታዘዙ እንደሚሆኑ እግዚአብሔር ይናገራል። ሁለቱን ልቦች በማቀያየር በፈቃደኝነት የሚታዘዙ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል። ኢ.ት: “እልኸኛ መሆናቸውን እንዲያቆሙ አደርጋቸዋለሁ፣ በምትኩም በፈቃደንነት እንዲታዘዙኝ አደርጋቸዋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በትዕዛዛቴ ይሄዳሉ፣ ሕግጋቴንም ይፈጽማሉ፣ ያደርጓቸዋልም
እነዚህ ሐረጎች ሁሉ ሕዝቡ እግዚአብሔር እንዲያደርጉት ያዘዛቸውን እንደሚታዘዙ የሚገልጽ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። የተደጋገሙት አጽንዖት ለመስጠት ነው። (See: Parallelism)
በትዕዛዛቴ ይሄዳሉ
እግዚአብሔር የእርሱን ትዕዛዛት መጠበቅ አንድ ሰው በመንገድ ላይ እንደሚሄድ ሁሉ በትዕዛዛቱ ላይ እንደ ሄደ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “ትዕዛዛቴን ይጠብቃሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ወደ አስከፊ ነገሮቻቸው በውዴታ የሚሄዱትን እነዚያን
እግዚአብሔር ስለ አንድ ሰው ሥራ ሲናገር ያ ሰው ተራምዶ እንደሚሄድ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “ሕይወታቸውን አስከፊ የሆኑ ነገሮቻቸውን ለመሥራት በትጋት የሚሰጡትን እነዚያን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የሚያስከፉ ነገሮች
ይህ የሚያስጠሉና የሚያስቀይሙ ነገሮችን ማለት ነው። እዚህ ጋ፣ ይህ የሚያመለክተው ጣዖታትን ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 11፡18 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ሥራቸውን በራሳቸው ላይ አመጣባቸዋለሁ
እዚህ ጋ “ሥራ” የሚለው ፈሊጣዊው አነጋገር የሚወክለው የድርጊቶቻቸውን ውጤት ነው። “በራሳቸው ላይ አመጣባቸዋለሁ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ትርጉሙ ውጤቱን ይቀበላሉ የሚል ነው። ኢ.ት: “በድርጊቶቻቸው ምክንያት በውጤቱ መከራን እንዲቀበሉ አደርጋቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 11:22
ኪሩቤል
ይህንን በሕዝቅኤል 9፡3 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Ezekiel 11:24
ያየሁት ራዕይ ከእኔ ላይ ተነሥቶ ወደ ላይ ሄደ
ሕዝቅኤል ስለ ራዕዩ ማብቃት ሲናገር በእርሱ ላይ እንደነበረና ከዚያም ተለይቶት እንደ ሄደ እንደ አንዳች ቁስ አድርጎ ይገልጸዋል። ኢ.ት: “ያየሁት ራዕይ አበቃ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Chapter 12
Ezekiel 12:1
የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ኢ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”
አመፀኛ ቤት
አመፀኛ ቤት “ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ በዓመታት ውስጥ የነበሩትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “አመፀኛ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሊያዩበት ዐይን አላቸው ነገር ግን አያዩም ... መስሚያ ጆሮ አላቸው ነገር ግን አይሰሙም
የሕዝቡ የእግዚአብሔርን መልዕክትና እርሱ እየሠራ ያለውን ለመረዳት አለመቻል በአካላቸው ለማየትና ለመስማት እንዳልቻሉ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 12:3
ስለዚህ አንተ
“በመሆኑም፣ የምነግርህ ይህንን ነው”
በዐይናቸው ፊት
“እነርሱ እያዩህ”
ምናልባት ማየት ይጀምሩ ይሆናል
ሕዝቡ የእግዚአብሔርን መልዕክትና እርሱ እየሠራ ያለውን ለመረዳት መቻላቸው በአካላቸው ማየት እንደቻሉ ተደርጎ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አመፀኛ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “አመፀኛ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 12:4
በዐይናቸው ፊት
“እነርሱ እያዩህ”
እንደ ምልክት አድርጌሃለሁ
እዚህ ጋ “ምልክት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለሚመለከቱት የተለየ ማስጠንቀቂያን የሚያስተላልፍን ነገር ነው። ሕዝቅኤል የሚናገረውንና የሚያደርጋቸውን ነገሮች እነዚህን እግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ መሆናቸውን ይናገራል። ኢ.ት፡ “ማስጠንቀቂያ እንድትሆን አድርጌሃለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእስራኤል ቤት
x
Ezekiel 12:7
ልክ እንደታዘዝኩት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ልክ እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ግድግዳውን በእጅ በመቆፈር ነደለው
“ግድግዳውን በእጆቼ በመቆፈር ነደልኩት”
በጨለማ ውስጥ
“በምሽት”
Ezekiel 12:8
የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የሰው ልጅ ሆይ፣ ያ አመፀኛው ቤት፣ የእስራኤል ቤት ‘የምታደርገው ምንድነው’ ብለው አይጠይቁህም?
ሕዝቡ ይህንን ጥያቄ ሕዝቅኤልን ጠይቀውት ስለነበረ -- ቀድሞውኑ የሚያውቀውን አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቀዋል። ኢ.ት፡ “የሰው ልጅ ሆይ፣ ያ አመፀኛው የእስራኤል ቤት ‘የምታደርገው ምንድነው?’ ብሎ እየጠየቀ ነው” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የእስራኤል ቤት፣ ያ አመፀኛ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። “አመፀኛ ቤት” የሚለውን በሕዝቅኤል 2፡5 ላይ እንዳለው አድርገህ ተርጉመው። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ፣ ያ አመፀኛ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የምታደርገው ምንድነው
ሕዝቡ ሕዝቅኤል ሲያደርግ የነበረውን ስላዩ፣ ጥያቄአቸው ያንን ለምን እንዳደረገ የማወቅ ፍላጎታቸውን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የምታደርጋቸው ነገሮች ትርጉማቸው ምንድነው?”
በመካከሏ ያሉት
“በመካከሏ” የሚለው ቃል ኢየሩሳሌምን ሲያመለክት፣ “እነርሱ” የሚያመለክተው “የእስራኤል ቤት”ን ነው። ኢ.ት፡ “በኢየሩሳሌም ያሉትን”
Ezekiel 12:11
እኔ ምልክታችሁ ነኝ
እዚህ ጋ “ምልክት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለሚያዩት አንድ የተለየ ማስጠንቀቂያ የሚያስተላልፍን ነገር ነው። ሕዝቅኤል ስለ ራሱና ስለሚያደርጋቸው ነገሮች ያ ማስጠንቀቂያ እርሱ መሆኑን ይናገራል። ኢ.ት፡ “እኔ ለእናንተ ማስጠንቀቂያ ነኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እንዲሁ ይደረግባቸዋል
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ሕዝብ ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሌሎች እንዲሁ ያደርጉባቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በጨለማ
“በምሽት”
ግድግዳውን ይነድላሉ
“እነርሱ” የሚለው ቃል በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ሕዝብ ያመለክታል።
ፊቱን ይሸፍናል
“መስፍኑ ፊቱን ይሸፍናል”
መረቤን በእርሱ ላይ እዘረጋለሁ፣ በወጥመዴም ይያዛል
እግዚአብሔር ከለዳውያን መስፍኑን እንዲይዙት ማስቻሉን፣ እርሱ ራሱ ባጠመደው ወጥመድ መስፍኑን እንደሚይዘው አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ወደ ባቢሎን አመጣዋለሁ
እግዚአብሔር ከለዳውያን መስፍኑን ወደ ባቢሎን እንዲያመጡት ማስቻሉን እርሱ ራሱ መስፍኑን ወደዚያ እንደሚያመጣው አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ከለዳውያን ወደ ባቢሎን እንዲያመጡት አደርጋቸዋለሁ”
Ezekiel 12:14
ከበስተኋላቸው ሰይፍን እስዳለሁ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል በሰይፎቻቸው የሚገድሉትን የጠላት ሰራዊት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በሰይፍ የሚያሳድዷቸውን ሰራዊት እልክባቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያውቃሉ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይረዳሉ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይገነዘባሉ”
በሀገራት መካከል በምበትናቸውና በምድር ሁሉ ላይ በምዘራቸው ጊዜ
የእነዚህ ሁለት ሐረጎች መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። ኢ.ት፡ “እርስ በእርሳቸው

እንዲለያዩና በተለያየ ሀገር እንዲኖሩ በማደርጋቸው ጊዜ”
ከሰይፍ፣ ከረሃብና ከቸነፈር አድናቸዋለሁ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፎቻቸውን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉ ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። በረሃብ ወይም በቸነፈር ስላለመሞታቸው ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። ኢ.ት፡ “በጦርነት፣ በረሃብ እና በበሽታ ምክንያት ከመሞት እጠብቃቸዋለሁ”
Ezekiel 12:17
የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 12:19
ምድሪቱ ፈጽማ ትበዘበዛለች
“ፈጽማ” የሚለው ቃል በምድሪቱ ያለውን ሁሉ ያመለክታል። “ትበዘበዛለች” ማለት ሕዝቡ በምድሪቱ ላይ ያለውን ሁሉ ያወድማሉ ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በምድሪቱ ያለውን ሁሉ ሌሎች ያወድሙታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሰዎች ይኖሩባቸው የነበሩ ከተሞች ወና ይሆናሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች የኖሩባቸው ከተሞች ባድማ ይሆናሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 12:21
የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በእስራኤል ምድር፣ “ቀኖቹ ረዝመዋል፣ ራዕይም ሁሉ ከንቱ ሆኗል” የሚለው ይህ ምሳሌአችሁ ምንድነው?
ሕዝቅኤል አስቀድሞ የሚያውቀውን አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቀዋል። ጥያቄው ምሳሌውን ለሚጠቀሙ ሰዎች ለስለስ ያለ ተግሳጽ ነው። ኢ.ት፡ “በእስራኤል ምድር የሚኖሩ ሰዎች እንዲህ የሚል ምሳሌ አላቸው፣ ‘ቀኖቹ ረዝመዋል፣ ራዕይም ሁሉ ከንቱ ሆኗል’” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ቀኖቹ ረዝመዋል፣
የዚህ አነጋገር ዘይቤ ትርጉም ብዙ ቀናት አልፈዋል የሚል ነው። ኢ.ት፡ “ብዙ ቀናት አልፈዋል” ወይም “ሰዓቱ አልፏል” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ራዕይም ሁሉ ከንቱ ሆኗል
ይህ ማለት ነቢያቱ ተቀብለው ለሕዝቡ ያስተላለፏቸው ራዕዮች ሳይፈጸሙ ቀርተዋል ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ትንቢታዊ ራዕዮች ሁሉ ሳይፈጸሙ ቀርተዋል”
ቀኖቹ ቀርበዋል
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው እስራኤል የሚፈረድባት ጊዜ መድረሱን ነው። ኢ.ት፡ “የፍርድ ቀን በቶሎ ይመጣል”
ራዕይ ሁሉ ይፈጸማል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ራዕይን ሁሉ እፈጽማለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 12:24
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እስራኤላውያንን” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የምናገረውን ቃል እፈጽማለሁ
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም እግዚአብሔር የሚናገረውን ይፈጽማል የሚል ነው። ኢ.ት፡ “የምናገራቸውን ነገሮች አደርጋቸዋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ከዚህ በኋላ ጉዳዮቼ አይዘገዩም
“ጉዳይ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር ይሆናሉ ያላቸውን ነገሮች ነው። ኢ.ት፡ “ከዚህ በኋላ የተናገርኩት አይዘገይም” ወይም “የተናገርኩት በቶሎ ይፈጸማል”
ይህንን ቃል እናገራለሁ
“ይህንን መልዕክት እናገራለሁ” ወይም “ይህንን ትንቢት እናገራለሁ”
በዘመናችሁ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ የሚያመለክተው አንድ ሰው የሚኖርበትን የሕይወት ዘመን ነው። ኢ.ት፡ “በሕይወት እያላችሁ” ወይም “በሕይወት በምትኖሩበት ዘመን” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
አመፀኛ ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “አመፀኛ ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 12:26
የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እርሱ የሚያየው ራዕይ ከአሁን በኋላ ለረጅም ዘመን የሚሆን ነው፣ የሚተነብየውም ለሩቅ ዘመን ነው
ሁለቱም ሐረጎች የሕዝቅኤል ማስጠንቀቂያ በሩቅ ዘመን እንጂ በእነርሱ የሕይወት ዘመን እንደማይደርስ የእስራኤል ሕዝብ የተናገሩባቸው መንገዶች ናቸው።
ከእንግዲህ ቃሎቼ አይዘገዩም፣ ነገር ግን እኔ የተናገርኩት ቃል ይፈጸማል
እነዚህ ሐረጎች በሁለቱም መንገድ እግዚአብሔር የሰጣቸው ማስጠንቀቂያዎች በቶሎ እንደሚፈጸሙ ለእስራኤል ሕዝብ የተናገረበት ነው።
ከእንግዲህ ቃሎቼ አይዘገዩም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ከእንግዲህ የተናገርኩትን ቃል አላዘገይም” ወይም “ከእንግዲህ አደርገዋለሁ ብዬ የተናገርኩትን ከማድረግ አልዘገይም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እኔ የተናገርኩት ቃል ይፈጸማል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የተናገርኩትን ቃል እፈጽማለሁ” ወይም “የተናገርኩትን አደርገዋለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Chapter 13
Ezekiel 13:1
የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ

መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ይህንን በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”
ከገዛ ስሜታቸው ተነሥተው የሚተነብዩ
“የሚሰማቸውን ነገር ብቻ የሚተነብዩ”
የገዛ ራሳቸውን መንፈስ የሚከተሉ
እዚህ ጋ፣ “መንፈስ” የሚለው ቃል የሚወክለው የሰውየውን አሳብና አስተሳሰብ ነው። “መከተል” ማለት አሳባቸው እንዲያደርጉት የሚያመለክታቸውን እንደሚያደርጉ የሚያሳይ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “እንደ ገዛ አሳባቸው የሚያደርጉ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በወና ምድር እንዳሉ ቀበሮዎች
ምግብ እንደሚለቃቅሙና ወና ሆነው በተተዉ ከተሞች መካከል መጠለያ እንደሚፈልጉ ቀበሮዎች ነቢያቱ ለራሳቸው ትርፍ ሲሉ በኢየሩሳሌም መፍረስ እየተጠቀሙባት ነው። (See: Simile)
ቀበሮዎች
ከውሾች ጋር የሚዛመዱና ወና በሆኑ አካባቢዎች ምግባቸውን የሚለቃቅሙ የዱር እንስሳዎች ናቸው።
Ezekiel 13:5
በእስራኤል ቤት ዙሪያ ያለውን ግንብ
ይህ የኢየሩሳሌምን ከተማ የሚከብበውን ግንብ ያመለክታል።
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በጦርነት መቋቋም
እዚህ ጋ ግልጽ ያልተደረገውን መረጃ መጨመር ትችላለህ። ኢ.ት፡ “የጠላትን ሰራዊት መቋቋም” ወይም “ከተማይቱን መከላከል”
የእግዚአብሔር ቀን
ይህ እግዚአብሔር በጠላት ሰራዊት አማካይነት በሕዝቡ ላይ የሚፈርድበትን ጊዜ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን” ወይም “እንዲወጓችሁ እግዚአብሔር የጠላትን ሰራዊት በመላክ በእናንተ ላይ የሚፈርድበት ቀን”
እኔ ራሴ ባልተናገርኩበት ጊዜ ሐሰተኛ ራዕዮች አልነበሯችሁም?
ሐሰተኞቹን ነቢያት ለመገሰጽ እግዚአብሔር በጥያቄ መልክ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እኔ ራሴ ያልተናገርኩት . . . ሐሰተኛ ራዕዮች ነበሯችሁ” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ሐሰተኛ ራዕዮች ነበሯችሁ፣ የውሸት ትንቢትም ተናገራችሁ
x
Ezekiel 13:8
ይህ የጌታ እግዚአብሔር ንግግር ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።ኢ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
እጄ በነቢያት ላይ ትሆናለች
እዚህ ጋ፣ “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው። እጁ በእነርሱ ላይ መሆኗ ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም እርሱ በኃይሉ ይቀጣቸዋል ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ነቢያትን እቀጣቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በሕዝቤ ጉባዔ ውስጥ አይሆኑም
ይህ ማለት እግዚአብሔር እነዚህን ሐሰተኞች ነቢያት የእስራኤል ሕዝብ አካል አድርጎ አይቆጥራቸውም።
ወይም በእስራኤል ቤት መዝገብ አይጻፉም
ይህ ምናልባት የእስራኤል ዜጎች የሚመዘገቡበትን መንግሥታዊ መዝገብ ያመለክት ይሆናል። ይህ በአድርጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በእስራኤል ቤት መዝገብ ላይ ማንም ስማቸውን አይጽፍም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እኔ ጌታ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃላችሁ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን እንደሚያውቁ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትረዳላችሁ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ ጌታ እግዚአብሔር መሆኔን ትገነዘባላችሁ”
Ezekiel 13:10
በዚህ ምክንያት
“በዚህ” የሚለው ቃል ሐሰተኛ ራዕዮችን ለሕዝቡ የሚያስታውቁትንና ውሸትን የሚነግሯቸውን ነቢያት ያመለክታል።
ሕዝቤን አስተዋል
ነቢያቱ ሕዝቡ ይሄዱበት ከነበረው መንገድ ላይ ያሳቷቸው ይመስል ሕዝቡን ስለማሳሳታቸውና ውሸትን እንዲያምኑ ስለማድረጋቸው እግዚአብሔር ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በኖራ የሚለስኑትን ግንብ ይገነባሉ
እዚህ ጋ፣ “ግንብ” የቆመው እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊሰጣቸው ቃል ለገባውና ሐሰተኞቹ ነቢያት ለሕዝቡ ለነገሯቸው ለሰላምና ደህንነት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ኖራ … በኖራ መለሰን
“ኖራ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተበላሸውን ለመሸፈንና ገጽታውን ነጭ ለማድረግ ጥቅም ላይ የሚውለውን የነጭ ፈሳሽ ውሁድ ወይም ቀለምን ነው።
እርሱን እንዲጥለው የበረዶ ድንጋይን፣ ሰባብሮ እንዲጥለውም ዐውሎ ነፋስን እልካለሁ
እግዚአብሔር ግንቡን እንደሚያፈራርስ ብርቱ ዐውሎ በሚመስል መልኩ በሕዝቡ ላይ የሚልከውን ፍርዱን ያመለክታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የበረዶ ድንጋይ
በዶፍ ዝናብ ወቅት አንዳንዴ ከሰማይ የሚወድቁ ሁሉም ዓይነት በረዶዎች
ሌሎች፣ “የለሰናችሁበት ኖራ የት አለ?” አላሏችሁም?
ሌሎች ኖራዎቻቸው ምን እንደሆነባቸው ነቢያቱን እንደሚጠይቋቸው አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት፡ “ያለ ጥርጥር ሌሎች እንዲህ ይሏችኋል፣ ‘የለሰናችሁበት ኖራ የት አለ’ “(ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የለሰናችሁበት ኖራ የት አለ?
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ሕዝቡ የሚገምተውና የሚመልሰው ቅንነት ያለበት ጥያቄ ነው ወይም 2) ይህ ሕዝቡ በፌዝ የሚጠይቀው ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ነው የሚሉት ናቸው። ኢ.ት፡ “የለሰናችሁበት ኖራ ምንም አልጠቀመም”። (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 13:13
ዐውሎ ንፋስ አመጣለሁ … ፈጽሞ ያጠፋዋል።
እግዚአብሔር ግንቡን የሚያፈራርስ ብርቱ ዐውሎ በሚመስል መልኩ በሕዝቡ ላይ የሚልከውን ፍርድ ያመለክታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በመዓቴ … በቁጣዬ … በመዓቴ
“በመዓቴ ምክንያት … በቁጣዬ ምክንያት … በመዓቴ ምክንያት”
ተገልጦ ይቀራል
“አይሸፈንም”
በመካከሏም ድምጥማጣችሁ ይጠፋል
“በመካከሏ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር የሚያፈርሰውን የግንቡን ድንጋዮች ያመለክታል። ግንቡ በሚፈርስበት ጊዜ ይገድላቸው ይመስል እግዚአብሔር ሕዝቡን በፍርዱ እንደሚያጠፋቸው ይናገራል።(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ድምጥማጣቸው ይጠፋል
“ይጠፋሉ”
እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንኩ ያውቃሉ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች

ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይረዳሉ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይገነዘባሉ”

Ezekiel 13:15

በቁጣዬ ድምጥማጣቸውን አጠፋለሁ

“በጣም ስለ ተቆጣሁ ድምጥማጣቸውን አጠፋለሁ”

በኖራ ለስነውታል

“ኖራ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተበላሸውን ለመሸፈንና ገጽታውን ነጭ ለማድረግ ጥቅም ላይ የሚውለውን የነጭ ፈሳሽ ውሁድ ወይም ቀለምን ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 13፡10 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

ስለ ኢየሩሳሌም ትንቢት የተናገሩና የሰላምን ራዕይ ያዩላት የእስራኤል ነቢያት

ይህ ሐረግ “በኖራ የተለሰኑት ሰዎች” እነማን እንደ ሆኑ ያብራራል።

ለእርሷ የሰላምን ራዕይ

“እርሷ” የሚለው ቃል ኢየሩሳሌምን ያመለክታል።

Ezekiel 13:17

ፊትህን በሴቶቹ ልጆች ላይ አቅና

ይህ ሴቶቹን የመቅጣት ምልክት ይሆን ዘንድ እነርሱን አፍጥጦ እንዲመለከት የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። “በእነርሱ ላይ ፊትህን አቅና” የሚለውን በሕዝቅኤል 4፡3 ላይ እንዳደረግኸው ተርጉም። ኢ.ት፡ “በሴቶቹ ልጆች ላይ አፍጥጥባቸው”

በእነርሱ ላይ ፊትህን አቅና

እዚህ ጋ “ፊት” በትኩረት ወይም በጥሞና የመመልከት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፣ “ፊትህን አቅና” የሚወክለው አፍጥጦ መመልከትን ነው። ኢ.ት፡ “አፍጥጠህ እይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሕዝብህ ሴቶች ልጆች

የአነጋገር ዘይቤው እንደ ሕዝቅኤል ሁሉ የዚያው ሕዝብ ወገን የሆኑትን ሴቶች ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሴቶች” ወይም “የሀገርህ ሴቶች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ከራሳቸው አዕምሮ አውጥተው ይተነብያሉ

“በገዛ ራሳቸው አዕምሮ ያሰቧቸውን ነገሮች ብቻ እየተነበዩ” ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 13፡2 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

በ -- ላይ ትንቢት ተናገር

“ስለሚደርሱባቸው አስከፊ ነገሮች ትንቢት ተናገር”። ይህንን በሕዝቅኤል 4፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

በእጆቻቸው ሁሉ ላይ የአስማት ክታብ ሰፍተዋል

ይህ ማለት የአስማቱን ክታቦች በአንድ ላይ በመስፋት በእጆቻቸው ላይ አስረውታል ማለት ነው እንጂ በቀጥታ በእጆቻቸው ላይ ሰፍተውታል ማለት አይደለም።

ክታብ

አስማታዊ ኃይል አለው ተብሎ የሚታመንበት ቁስ

ሰዎችን ለማጥመድ ተጠቅመውበታል

እግዚአብሔር ስለ እነዚህ ሴቶች በክታቦቻቸው አማካይነት እንስሶችን አድነው ያጠምዱ ይመስል ሰዎችን ለማሳሳት ውበታቸውን፣ ምስጢራቸውንና ውሸታቸውን እንደሚጠቀሙ እግዚአብሔር ይናገራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎችን ለማጥመድ የሚጠቀሙባቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ለራሳቸው የተለያየ መጠን ያለው መሸፈኛ ያበጃሉ

ይህ ማለት የተለያየ ቁመት ባላቸው ሰዎች ራስ ላይ ለማድረግ መሸፈኛዎችን ያበጃሉ። ኢ.ት፡ “የተለያየ ቁመት ላላቸው ሴቶች ራስ መሸፈኛዎችን ያበጃሉ”

ሕዝቤን አጥምዳችሁ የገዛ ራሳችሁን ሕይወት ታድናላችሁ?

እነዚህን ነገሮች የሚያደርጉትን ሴቶች ለመገሰጽ እግዚአብሔር ይህንን እንደ ዋነኛ ጥያቄ አድርጎ ይጠይቃል። ይፋ ያልሆነው መልስ “አይደለም” የሚል ነው። ኢ.ት፡ “ሕዝቤን ካጠመዳችሁ በኋላ የገዛ ራሳችሁን ሕይወት ማዳን እንደምትችሉ አታስቡ!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 13:19

እፍኝ ገብስና ቁራሽ እንጀራ

ገብስ እንጀራ ለመጋገር የሚያገለግል ጥራጥሬ ሲሆን “ቁራሽ” የሚለው ቃል አነስተኛ መጠን ያለው እንጀራ ነው። ሁለቱም ሐረጎች አነስተኛ የምግብ መጠን ሲሆኑ ሴት ነቢያቱ ምን ያህል አነስተኛ ክፍያ እንደሚከፈላቸው አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውለዋል።

Ezekiel 13:20

ወፎችን ይመስል የሕዝቡን ሕይወት ለማጥመድ የምትጠቀሙበት የአስማት ክታብ

ሰዎቹ ሴቶች በክታቦቻቸው የሚያጠምዷቸውን ወፎች ይመስል እግዚአብሔር የአስማት ክታባቸውን በመጠቀም ሰዎችን ስለሚያሳስቱ ስለ እነዚህ ሴቶች ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክታብ

አስማታዊ ኃይል አላቸው ተብለው የሚታመኑ ቁሳቁሶች

ለማጥመድ

“ለመያዝ” “በወጥመድ ለመያዝ”

ከክንዳችሁ ላይ እቀድዳቸዋለሁ

“ክታቦቹን ከክንዶቻችሁ ላይ እቀድዳለሁ”

ሕዝቤን ከእጃችሁ አድናቸዋለሁ

እዚህ ጋ “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። ኢ.ት፡ “ሕዝቤን ከኃይላችሁ አድናቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእንግዲህ በእጆቻችሁ አይጠመዱም

እዚህ ጋ “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። ሴቶቹ ሰዎችን በእጆቻቸው ያጠመዷቸው ይመስል ሰዎቹ በእነዚህ ሴቶች ቁጥጥር ስር ስለ መሆናቸው እግዚአብሔር ይናገራል። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በእጆቻችሁ እንዳለ የሚታደን እንስሳ ከእንግዲህ አታጠምዷቸውም” ወይም “ከእንግዲህ በኃይላችሁ አትቆጣጠሯቸውም” (ፈሊጣዊ አነጋገር፣ ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 13:22

የጻድቁን ሰው ልብ ተስፋ ስላስቆረጣችሁ

እዚህ ጋ “ልብ” የሚወክለው ሰውየውንና ስሜቶቹን ነው። ኢ.ት፡ “ጻድቁን ሰው ተስፋ ማስቆረጥ”

ከመንገዱ ተመልሶ

የሚያደርገውን ነገር ማቆሙ ወደ ሌላ አቅጣጫ እንደ መመለስ ተመልክቷል። ኢ.ት፡ “የሚያደርገውን ማቆም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የሐሰት ራዕዮች ወይም መተንበይን መቀጠል

እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት ወደ ፊት እንደሚሆን መናገርን ነው። ኢ.ት፡ “የሐሰት ትንቢቶችን መናገር ቀጥሉ”

ሕዝቤን ከእጃችሁ አድናቸዋለሁ

እዚህ ጋ “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 13፡21 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ሕዝቤን ከኃይላችሁ አድናቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 14

Ezekiel 14:1

ከእስራኤል ሽማግሌዎች ጥቂቶቹ ወደ እኔ መጥተው በፊት ተቀመጡ

ሽማግሌዎቹ በሕዝቅኤል ፊት የተቀመጡት በእርሱ አማካይነት ጌታን ለመጠየቅ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የሰው ልጅ

“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ኢ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”

ጣዖቶቻቸውን በልባቸው አኑረዋል

ሽማግሌዎቹ “ጣዖቶቻቸውን በልባቸው” ያኖሩ ይመስል እግዚአብሔር ሽማግሌዎቹ ራሳቸው ጣዖታትን ስለ ማምለካቸው ይናገራል። ኢ.ት፡ “ራሳቸውን ለጣዖታት ሰጥተዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በገዛ ፊታቸው ላይ የኃጢአታቸውን ማሰናከያ አስቀምጠዋል

እግዚአብሔር ሽማግሌዎቹ የሚያመልኳቸውን ጣዖታት የሚሰናከሉባቸው



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መሰናከያዎች እንደ ሆኑ፣ እነዚያን ጣዖታት ለማምለክ መጨከናቸውንም ማሰናከያዎቹን በፊታቸው እንዳስቀመጡ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ወደ ኃጢአት የሚመራቸውን ነገሮች ለማምለክ ያለ ማወላወል ጨክነዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የኃጢአታቸውን ማሰናከያ

ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች 1) ጣዖታቱ ሽማግልዎቹን ወደ ኃጢአት የሚመሩ ማሰናከያዎች ናቸው ወይም 2) ጣዖታትን ማምለክ ሽማግሌዎቹ እንዲሰናከሉ የሚያደርጋቸው ኃጢአት ነው የሚሉት ናቸው።

ከቶ በእነርሱ ልጠየቅ ይገባል?

ሽማግሌዎቹ ሊጠይቁት እንደማይገባቸው አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። ይህ ጥያቄ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ደግሞም ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እንዲጠይቁኝ ከቶውኑ ልፈቅድላቸው ይገባኛል?” ወይም “ከቶ ሊጠይቁኝ አይገባቸውም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:4

ስለዚህ ይህንን አስታውቃቸው

“እነርሱ” የሚለው ቃል “ከእስራኤል ሽማግሌዎች የሆኑትን ሰዎች” ያመለክታል።

የእስራኤል ቤት

“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጣዖታቱን በልቡ የሚያኖር እርሱ

እግዚአብሔር፣ ሕዝቡ ጣዖታትን ለማምለክ ራሳቸውን መስጠታቸውን፣ ጣዖቶቻቸውን በልባቸው እንዳኖሩት አድርጎ ይናገራል። ይህንን ዘይቤአዊ አነጋገር በሕዝቅኤል 14፡3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ራሱን ለጣዖታት የሚሰጥ እርሱ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የኃጢአቱን ማሰናከያ በፊቱ የሚያስቀምጥ

እግዚአብሔር ሕዝቡ የሚያመልኳቸውን ጣዖታት የሚሰናከሉባቸው መሰናከያዎች እንደ ሆኑ፣ እነዚያን ጣዖታት ለማምለክ መጨከናቸውንም ማሰናከያዎቹን በፊታቸው እንዳስቀመጡ አድርጎ ይናገራል። ይህንን ዘይቤአዊ አነጋገር በሕዝቅኤል 14፡3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ወደ ኃጢአት የሚመራቸውን ነገሮች ለማምለክ ያለ ማወላወል የጨከኑ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከዚያም ወደ ነቢይ መጥቶ

ጌታን ለመጠየቅ ወደ ነቢይ የሚሄድ ሰው

እኔ እግዚአብሔር፣ እንደ ጣዖታቱ ብዛት እመልስለታለሁ

ይህ ሐረግ ሕዝቡ የሚያመልኳቸውን ብዙ ጣዖታት ያመለክታል። የእግዚአብሔር ምላሽ አስከፊነት የሚያመልኳቸውን የጣዖታት ብዛት ያህል ታላቅ እንደሚሆን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ብዙ ጣዖታትን ያመልካልና እኔ እግዚአብሔር ተገቢውን መልስ እሰጠዋለሁ”

የእስራኤልን ቤት ልብ እመልስ ዘንድ

እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል የሚወክለው የሕዝቡን አዕምሮና ፍቅር ነው። እግዚአብሔር ልባቸውን ይማርከዋቸው ይመስል ልባቸው እንደገና ለእርሱ የተሰጠ እንዲሆን እንደሚያደርገው ይናገራል። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ እንደገና ለእኔ የተሰጡ እንዲሆኑ አደርጋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በጣዖቶቻቸው ከእኔ ርቆ የነበረውን ልባቸውን

እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል የሚወክለው የሕዝቡን አዕምሮና ፍቅር ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ጣዖቶቻቸውን ለማምለክ እኔን የተዉኝን ሁሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:6

ንስሐ ግቡ፣ ከጣዖቶቻችሁም ተመለሱ! አስጸያፊ ከሆኑ ተግባሮቻችሁ ሁሉ ፊታችሁን መልሱ

እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች ለእስራኤል ሕዝብ ጣዖታትን ማምለካቸውን እንዲያቆሙ የተነገሯቸው መንገዶች ናቸው።

ንስሐ ግቡ፣ ተመለሱም

“ንስሐ ግቡ” እና “ተመለሱ” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። በአንድነት የሚያጠናክሩት ጣዖታትን ማምለካችሁን አቁሙ የሚለውን ትዕዛዝ ነው።

ፊታችሁን መልሱ

እዚህ ጋ “ፊት” የሚለው ቃል የሚወክለው ሕዝቡን ነው። ኢ.ት፡ “ተመለሱ”

Ezekiel 14:7

የእስራኤል ቤት

“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጣዖታቱን በልቡ የሚያኖረውን

እግዚአብሔር፣ ሕዝቡ ጣዖቶቻቸውን በልባቸው እንዳኖሩ አድርጎ ጣዖታትን ለማምለክ ራሳቸውን ስለ ሰጡ ሰዎች ይናገራል። ይህንን ዘይቤአዊ አነጋገር በሕዝቅኤል 14፡3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ራሱን ለጣዖታት የሚሰጥ እርሱ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የኃጢአቱን ማሰናከያ በፊቱ የሚያስቀምጥ

እግዚአብሔር ሕዝቡ የሚያመልኳቸውን ጣዖታት የሚሰናከሉባቸው መሰናከያዎች እንደ ሆኑ፣ እነዚያን ጣዖታት ለማምለክ መጨከናቸውንም ማሰናከያዎቹን በፊታቸው እንዳስቀመጡ አድርጎ ይናገራል። ይህንን ዘይቤአዊ አነጋገር በሕዝቅኤል 14፡3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ወደ ኃጢአት የሚመራውን ነገሮች ለማምለክ ያለ ማወላወል የሚጨክን” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ፊቴን በዚያ ሰው ላይ አደርጋለሁ

እግዚአብሔር ፊቱን በዚያ ሰው ላይ በሚያደርግበት መልኩ ያንን ሰው እንደሚቃወመው ይናገራል። ኢ.ት፡ “በዚያ ሰው ላይ እሆናለሁ” ወይም “ያንን ሰው እቃወማለሁ”

ፊቴን አደርጋለሁ

እዚህ ጋ “ፊት” ትኩረትን ወይም በአትኩሮት መመልከትን እና “ፊቴን አደርጋለሁ” የሚያመለክተው አፍጥጦ ማየትን ነው። ኢ.ት፡ “ማፍጠጥ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምልክትና ምሳሌ አደርገዋለሁ

እዚህ ጋ “ምልክት” የሚለው ቃል ለሚያዩት የተለየ ማስጠንቀቂያ የሚያስተላልፍ አንድን ነገር ያመለክታል። ምሳሌ የሚለው ቃል፣ ሰዎች ያንን ምልክት በሚያዩበት ጊዜ ስለ እርሱ የሚናገሩትን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ያ ሰው ማስጠንቀቂያና ምሳሌ እንዲሆን አደርገዋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከሕዝቤ መካከል አስወግደዋለሁ

እግዚአብሔር ከእንግዲህ የራሱ ሕዝብ ወገን እንዳይሆን የሚያደርገውን ያንን ሰው አንድ ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ ላይ እንደሚቆርጥ ከሕዝቡ እንደሚቆርጠው ይናገራል። ኢ.ት፡ “ከእንግዲህ የሕዝቤ አካል እንዳይሆን አደርገዋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃላችሁ

እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትረዳላችሁ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ትገነዘባላችሁ”

Ezekiel 14:9

እጄን በእርሱ ላይ አነሣለሁ

የእግዚአብሔር “እጅ” እርሱ የሚሠራውን ያመለክታል። ኢ.ት፡ “በእርሱ ላይ ክፉ አደርጋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የራሳቸውን ኃጢአት ይሸከማሉ

እዚህ ጋ “ኃጢአት” የሚለው ቃል የሚወክለው ሰዎች ኃጢአትን በማድረጋቸው በራሳቸው ላይ የሚያመጡትን በደል ነው። ሕዝቡ ኃጢአትን ይሸከሙት ይመስል እግዚአብሔር የሚናገረው በኃጢአታቸው ምክንያት ስለሚደርስባቸው መከራ ነው። ኢ.ት፡ “በገዛ ራሳቸው የኃጢአት ውጤት ምክንያት መከራን ይቀበላሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት

“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ ወገን” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔን ከመከተል አይባዝኑም
እርሱን ከማምለክ በስተቀር ከእንግዲህ እርሱን ባለ መከተል እንደማይባዝኑ እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ከእንግዲህ እኔን ማምለካቸውን አያቆሙም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር ስለሚናገረው ቃል እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረውን ይህንን ነው” ወይም “እኔ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:12

ምድር በእኔ ላይ ኃጢአትን ስትሠራ
“ምድር” የሚለው ቃል የሚወክለው በምድሪቱ ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። ኢ.ት፡ “በምድሪቱ ላይ የሚኖሩት ሰዎች በእኔ ላይ ኃጢአትን በሚሠሩበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእንጀራውን በትር እሰብራለሁ
በትር ይመስል እግዚአብሔር የሚናገረው ስለ እንጀራ አቅርቦት ነው። “እንጀራ” የሚለው ቃል ሁሉንም ዓይነት ምግብ ይወክላል። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 4:16 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የምግብ አቅርቦቱን አቋርጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰውንና እንስሳን ከምድሪቱ ላይ እቆርጣለሁ
ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ እንደሚቆርጥ ይቆርጣቸው ይመስል እግዚአብሔር ሰዎችንና እንስሳትን እንደሚገድላቸው ይናገራል። ኢ.ት፡ “በምድሪቱ የሚኖረውን ሰውንና እንስሳን ሁሉንም ግደል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:15

እነዚህ ሦስት ሰዎች
ኖኅ፣ ዳንኤል እና ኢዮብ
ሕያው እንደ መሆኔ
“ሕያው መሆኔ እርግጥ የመሆኑን ያህል”። እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚናገረው የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ለማሳየት ይህንን አገላለጽ ይጠቀማል። ይህ ጽኑ ተስፋ የመስጫ መንገድ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ጽኑ መሐላ አደርጋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የገዛ ራሳቸውን ሕይወት ብቻ ያድናሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የገዛ ራሳቸውን ሕይወት ብቻ ማዳን ይችላሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:17

በምድሪቱ ላይ ሰይፍን ባመጣ
“ሰይፍ” የሚለው ቃል ሰይፍን በመጠቀም ሰዎችን የሚገድሉ ወታደሮችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “
ሰይፍ ሆይ በምድሪቱ መካከል እለፍ
እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚለው ቃል የሚወክለው በሰይፍ የሚገድሉ የጠላት ሰራዊት ወታደሮችን ነው። ኢ.ት፡ “ሰራዊት ሆይ፣ በምድሪቱ መካከል እለፍ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከእርሱ ላይ ሰውና እንስሳውን ቁረጥ
ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ እንደሚቆርጥ ይቆርጣቸው ይመስል እግዚአብሔር ስለ ሰዎችና እንስሳት መገደል ይናገራል። ኢ.ት፡ “በምድሪቱ የሚኖረውን ሰውንና እንስሳን ሁሉንም ግደል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እነዚህ ሦስት ሰዎች
ኖኅ፣ ዳንኤል እና ኢዮብ
የእነርሱ ሕይወት ብቻ ይድናል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የራሳቸውን ሕይወት ብቻ ማዳን ይችላሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:19

መዓቴን ባፈስ
ከመያዣ ዕቃው የሚያፈስሰው ፈሳሽ ይመስል እግዚአብሔር መዓቱን ስለሚገልጽበት ሁኔታ ይናገራል። ኢ.ት፡ “መዓቴን እገልጣለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰውንና እንስሳን ቁረጥ
ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ እንደሚቆርጥ ይቆርጣቸው ይመስል እግዚአብሔር ሰዎችንና እንስሳትን ስለ መግደል ይናገራል። ኢ.ት፡ “ሰውንና እንስሳን ሁሉንም ግደል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእነርሱ ሕይወት ብቻ ይድናል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የራሳቸውን ሕይወት ብቻ ማዳን ይችላሉ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:21

ሰውንና እንስሳን ከእርሷ ለመቁረጥ
ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ እንደሚቆርጥ ይቆርጣቸው ይመስል እግዚአብሔር ሰዎችንና እንስሳትን ስለ መግደል ይናገራል። “እርሷ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው። ኢ.ት፡ “በኢየሩሳሌም የሚኖረውን ሰውና እንስሳ በሙሉ ለመግደል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 14:22

እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።
በውስጧ የቀረ ... በእርሻ ላይ የተደረገ
“እርሷ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው።
መንገዳቸውንና ተግባራቸውን
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት የእስራኤል ሕዝብ ያደረጉትን ነው። ኢ.ት፡ “የአኗኗር መንገዳቸው” ወይም “የሚያደርጓቸው ነገሮች”
ስለ ቅጣቱ ተጽናኑ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ስለ ቅጣቱ ያጽናናችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 15

Ezekiel 15:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ኢ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”
በደን ውስጥ በዛፎች መካከል ከሚገኙ ቅርንጫፎች ካሏቸው ዛፎች ሁሉ የወይን ሐረግን የተሻለ የሚያደርገው ምንድነው?
ሕዝቅኤል አስቀድሞ ስለሚያውቀው ስለ አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቀዋል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የወይን ሐረግ በደን ውስጥ ከሚገኝ ቅርንጫፍ ካለው ከየትኛውም ዛፍ የተሻለ አይደለም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ሰዎች የሆነ ነገር ለመሥራት ከወይን ሐረግ እንጨትን ይወስዳሉ?
ሕዝቅኤል አስቀድሞ ስለሚያውቀው ስለ አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቀዋል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች የሆነ ነገር ለመሥራት ከወይን ሐረግ እንጨትን አይወስዱም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የትኛውንም ነገር ያንጠለጥሉበት ዘንድ ከእርሱ መስቀያ ያበጁበታል?
ሕዝቅኤል አስቀድሞ ስለሚያውቀው ስለ አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቀዋል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ነገሮችን በእርሱ ላይ ለመስቀል ከእርሱ መስቀያን አያበጁም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት
እንዲነድ እሳት ላይ ቢጥሉት ... ለአንዳች ነገር ይጠቅማል?
ሕዝቅኤል አስቀድሞ ስለሚያውቀው ስለ አንድ ነገር ለማስታወስ እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቀዋል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እንዲነድ እሳት ላይ ቢጥሉት ... ለምንም አይጠቅምም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት

እንዲነድ እሳት ላይ ቢጥሉት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው እንዲነድ እሳት ላይ ቢጥለው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 15:7
ፊቴን በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ
እግዚአብሔር ፊቱን በእነርሱ ላይ በማድረጉ እንደሚቃወማቸው ይናገራል። ኢ.ት፡ “በእነርሱ ላይ እሆናለሁ” ወይም “እቃወማቸዋለሁ”
ፊቴን --- አደርጋለሁ
እዚህ ጋ “ፊት” የትኩረት ወይም የአስተውሎት ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “ፊቴን -- አደርጋለሁ” የሚያመለክተው ማፍጠጥን ነው። ኢ.ት፡ “ማፍጠጥ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያውቃሉ
እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይረዳሉ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይገነዘባሉ”
ከእሳቱ ቢወጡም እሳቱ ገና ያቃጥላቸዋል
በእሳት የሚቃጠሉ በሚመስልበት ሁኔታ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ስለሚያመጣው ቅጣት ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እሳቱ ያቃጥላቸዋል
እነርሱም በእሳት የሚቃጠሉ ይመስል እግዚአብሔር ነገሮችን ስለሚያቃጥል እሳት ይናገራል። ኢ.ት፡ “እሳቱ ያጠፋቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ኃጢአትን አድርገዋል
“በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ኃጢአትን አድርገዋል” ወይም “በዚያ የሚኖሩት ሰዎች ኃጢአትን ሠርተዋል”
ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 16
Ezekiel 16:1
የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የሰው ልጅ
“የሰብዓዊ ፍጡር ልጅ” ወይም “ከሰው የተወለደ ልጅ”። ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ በማለት ይጠራዋል። እግዚአብሔር ዘላለማዊና ኃያል ነው፣ ሰዎች ግን አይደሉም። ኢ.ት፡ “ሟች ሰው” ወይም “ሰው”
ጅማሪሽና ልደትሽ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። ሰዎች ከተማይቱን በመሠረቱ ጊዜ የከተማይቱ ልደት እንደ ሆነ አድርጎ እግዚአብሔር ይናገራል። ( ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አባትሽ አሞራዊ ነበረ፣ እናትሽም ኬጢያዊት ነበረች
የእስራኤል ሕዝብ ምድሪቱን ድል ከማድረጋቸው በፊት ጣዖት አምላኪ የሕዝብ ወገን የሆኑት አሞራውያንና ኬጢያውያን በምድሪቱ ይኖሩ ነበር። ኢየሩሳሌም በዝሙት መወለዷን ለመግለጽ አባትና እናቷ የዚህ ሕዝብ ወገን እንደ ነበሩ እግዚአብሔር ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 16:4
እናትሽ እንብርትሽን አልቆረጠችውም
እዚህ ጋ “እንብርት” የሚያመለክተው ከእንብርት ጋር የተያያዘውን እትብት ያመለክታል። ኢ.ት፡ “እናትሽ እትብትሽን አልቆረጠችውም”
የማንም ዐይን አልራራልሽም
እዚህ ጋ “ዐይን” የሚለው ቃል የሚወክለው የሚያየውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “ካየሽ ሁሉ የራራልሽ የለም”
ሕይወትሽ የተጠላ
“ወላጆችሽ ጠልተውሽ ስለ ነበር”
ሜዳ ላይ ተጥለሽ ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ወላጆችሽ ሜዳ ላይ ጥለውሽ ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 16:6
በአጠገብሽ ሳልፍ
እግዚአብሔር አዲስ በተወለደችው ሕፃን አጠገብ ያልፍ ነበር
በደምሽ እንዳለሽ ተናገርኩሽ
ግልጽ ያልሆነው መረጃ ከቀደም ካለው ሐረግ ሊሟላ ይችላል። ኢ.ት፡ “በደምሽ ላይ ተጋድመሽ እያለሽ ተናገርኩሽ”
በእርሻ ላይ እንዳለ ተክል እንድታድጊ አደረግሁሽ
እዚህ ጋ፣ እግዚአብሔር በፍጥነት ማደጓን በቶሎ ከሚያድጉ ተክሎች ጋር ያነጻጽራል።
በዛሽ፣ ታላቅም ሆንሽ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። ሁለቱም የሚያመለክቱት ማደጓንና መርዘሟን ነው። ኢ.ት፡ “ጎለመስሽ፣ ረዘምሽም”
የዕንቁዎች ዕንቁ ሆንሽ
እዚህ ጋ፣ ኢየሩሳሌምን የምትወክለው ሴት ከሴቶች ሁሉ እጅግ የተዋበች ይመስል ከዕንቁዎች ሁሉ ብልጫ ያላት ተደርጎ ተነግሮላታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የዕንቁዎች ዕንቁ ሆንሽ
አንዳንድ የቅርብ ጊዜ ትርጉሞች “በዕንቁ ለማጌጥ በቃሽ” ይላሉ።
ዕርቃንሽን እና ራቁትሽን
የሁለቱም ቃላት ትርጉም አንድ ነው። ኢ.ት፡ “ባዶ ዕርቃን”
Ezekiel 16:8
ተመልከት!
እዚህ ጋ “ተመልከት” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።
የፍቅር ጊዜ መጣልሽ
ይህ አባባል ወጣቷ ሴት ለጋብቻ ዕድሜ መድረሷን እግዚአብሔር ዓይቷል ለማለት ነው።
ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው
እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 16:9
ባለ ጥልፍ ልብስ
“የተዋቡ ልብሶች”። መጥለፍ ማለት በቁርጥራጭ ጨርቆች የተሠራውን ንድፍ በአንድ ላይ መስፋት ነው።
በጌጣጌጥ አስዋብኩሽ
“ጌጣ ጌጥ አደርግሁልሽ”
Ezekiel 16:13
በወርቅና በብር አጌጥሽ፣ የተመረጠ በፍታም ለበስሽ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በወርቅና በብር አስጌጥኩሽ፣ የተመረጠ በፍታም አለበስኩሽ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በሀገራት መካከል ዝናሽ ወጣ
“በብዙ ሀገር የሚኖሩ ብዙ ሕዝቦች ማን እንደ ነበርሽ አወቁ”
እርሱም ፍጹም ነበር
“ውበትሽ ፍጹም ነበር”
Ezekiel 16:15
በገዛ ራስሽ ውበት ታመንሽ

“የገዛ ውበትሽን መተማመኛሽ አደረግሽው”

እንደ አመንዝራ ሴት አደረግሽ

ከተማይቱ ገንዘብ ለመቀበል በምትኩ ከሌሎች ወንዶች ጋር በመተኛት ታማኝነቷን እንዳጎደለች ሚስት አድርጎ እግዚአብሔር ስለ ኢየሩሳሌም ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የአመንዝራነት ሥራሽን አፈሰስሽ

እግዚአብሔር ግብረ ገብነት የጎደለውን የኢየሩሳሌምን ተግባር በፈሳሽ ይመስለውና እነዚያን ተግባራት በተደጋጋሚ መፈጸሟን ፈሳሾቹን ከመያዣው ማፍሰስ እንደ ሆነ አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ውበትሽ የእርሱ እንዲሆን

ይህ የዕብራይስጡ ሐረግ በዘመናዊ ትርጉሞች ውስጥ በብዙ የተለያዩ መንገዶች ተተርጉሟል። ለምሳሌ፣ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች “ራስሽን ትሰጪው ዘንድ” ወይም “የእርሱ ሆንሽ”

Ezekiel 16:17

የወንድ ምስሎች

“የወንዶች ሐውልት” ወይም “ወንዶችን የሚመስሉ ጣዖታት”

አመንዝራ ሴት እንደምታደርገው ከእነርሱ ጋር አደረግሽ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ይህ ወጣቷ ሴት ከወንድ ምስሎች ጋር ስለ መተኛቷ የትህትና አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ከእነርሱ ጋር ተኝተሻል” ወይም 2) ይህ ምስሎቹን ማምለኳ ከእነርሱ ጋር እንደ ተኛች አድርጎ እግዚአብሔር የተናገረበት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “አመለክሻቸው” (Euphemism እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከምርጥ ዱቄት ጋር ዘይትና ማር አደረግሽላቸው

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በምርጥ ዱቄት የጋገርኩትን እንጀራ፣ ዘይትና ማር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በፊታቸው አቀረብሽላቸው

“በፊት ለፊታቸው መስዋዕት አድርገሽ አቀረብሽላቸው”

Ezekiel 16:20

ለእኔ የወለድሻቸውን

“ልጆቼ የነበሩትን”

እንደ ምግብ እንዲበሏቸው ለምስሎቹ ሰዋሻቸው ... በእሳት እንዲያልፉ አደረግሻቸው

እዚህ ጋ፣ እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ ስላደረጉት አንድ ነገር ይናገራል። ልጆቻቸውን ለአሕዛብ ጣዖታት ሰውተዋል።

እንደ ምግብ እንዲበሏቸው ለምስሎቹ ሰዋሻቸው

በእነዚህ ጥንታዊ የጣዖት አምላኪዎች መስዋዕት አማልክቱ የሚቀርብላቸውን ምግብ እንደሚበሉ ሰዎች ያምኑ ነበር። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ምስሎቹ እንደ ምግብ እንዲበሏቸው ለእነዚያ ምስሎች መስዋዕት አደረግሻቸው”

የአመንዝራነትሽ ሥራ አነስተኛ ጉዳይ ነው? አረድሻቸው

ሴቲቱ አመንዝራነቷ ሳያንሳት ልጆቿን ደግሞ ለመሰዋት መወሰኗ ላይ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ያረድሻቸው የአመንዝራነትሽ ሥራ አነስተኛ ጉዳይ እንደ ሆነ ስላሰብሽ መሆን አለበት” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በእሳት እንዲያልፉ አደረግሻቸው

ለምስሎቿ የሚቃጠል መስዋዕት እንዲሆኑ እሳት ውስጥ እንደጨመረቻቸው ግልጽ አይደለም። ኢ.ት፡ “የሚቃጠል መስዋዕት አድርጋ ሰዋቻቸው”

ዕርቃንሽን እና ራቁትሽን

የእነዚህ የሁለቱም ቃላት ትርጉም አንድ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 16፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ባዶ ዕርቃን”

Ezekiel 16:23

ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው

እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

በየአደባባዩ ለራስሽ የማምለኪያ አዳራሽ ሠራሽ

ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) ጣዖታቷን የምታመልክበት ወይም 2) የዝሙት ተግባሯን የምትፈጽምበት ሥፍራ ሠርታለች የሚሉት ናቸው።

Ezekiel 16:25

በየመንገዱ ራስ ላይ

እግዚአብሔር የመንገድ መጀመሪያን ራስ እንደ ሆነ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “በየመንገዱ መጀመሪያ ላይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 16:27

ተመልከት!

እዚህ ጋ “ተመልከት” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

በእጄ አመታሻለሁ

እዚህ ጋ “እጅ” የሚወክለው ኃይልን ነው። ኢ.ት፡ “እንቺን ለመምታት ኃይሌን እጠቀማለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምግብሽን አቆርጣለሁ

እግዚአብሔር የምግብ አቅርቦት ማቋረጥን ምግብን እንደ መቁረጥ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “የምግብ አቅርቦትሽን አቆማለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሕይወትሽን አሳልፌ እሰጣለሁ

እዚህ ጋ “ሕይወት” ሰውን ይወክላል። ኢ.ት፡ “አሳልፌ እሰጥሻለሁ”

ለፍልስጥኤማውያን ሴቶች ልጆች

እዚህ ጋ የፍልስጥኤምን ከተሞች እግዚአብሔር እንደ ፍልስጥኤም ሴቶች ልጆች አድርጎ ይናገራል። ከተሞቹ በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላሉ። ኢ.ት፡ “የፍልስጥኤም ሰዎች” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 16:30

እነዚህን ሁሉ ነገሮች፣ እፍረት ዐልባ የአመንዝራነት ሥራ የምትሠሪው . . . ልብሽ ምን ያህል ታማሚ ቢሆን ነው?

እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ለመገሰጽ ምላሽ የማይሻውን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ ንግግር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እነዚህን ሁሉ ነገሮች፣ እፍረት ዐልባ የአመንዝራነት ተግባር የምትፈጽሚው ልብሽ በጣም ስለ ታመመ መሆን አለበት!” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ልብሽ ምን ያህል ታማሚ ቢሆን ነው

እዚህ ጋ “ልብ” የሚለው ቃል ፈቃድን እና ስሜትን ይወክላል። ልቧ የታመመ ይመስል ፍላጎቷን ለመቆጣጠር እንዳልቻለች እግዚአብሔር ይናገራል። ኢ.ት፡ “ፈቃድሽ ምን ያህል ደካማ የሆነ ሰው ነሽ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በየጎዳናው ራስ ላይ

እግዚአብሔር የጎዳናን መጀመሪያ ራስ እንደ ሆነ አድርጎ ይናገራል። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 16፡25 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “በየጎዳናው መጀመሪያ ላይ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የማምለኪያ አዳራሾችሽን ሠራሽ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ጣዖታቷን የምታመልክበት ወይም 2) የዝሙት ተግባሯን የምትፈጽምበት ሥፍራ ሠርታለች የሚሉት ናቸው። ይህንን በሕዝቅኤል 16፡24 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።

Ezekiel 16:32

ከባልሽ ይልቅ እንግዶችን ትቀበያለሽ

ይህ አንድን ሰው ከእርሷ ጋር እንዲተኛ እንደምትቀበለው ያመለክታል። ኢ.ት፡ “በአልጋሽ ላይ ከባልሽ ይልቅ እንግዶችን ትቀበያለሽ”

Ezekiel 16:35

ዝሙትሽን አፈሰስሽ

ፈሳሽ የሆነ ይመስል እግዚአብሔር ስለ ኢየሩሳሌም ዝሙት ይናገራል፤ ይህንን ብርቱ የዝሙት ፍላጎትዋን ለማርካት ደጋግማ መፈጸሟን ደግሞ ከዕቃ መያዣው እንደሚፈስ ፈሳሽ አድርጎ ይገልጸዋል። ኢ.ት፡ “የዝሙት ፍላጎትሽን ለማርካት በተደጋጋሚ ፈጸምሽው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዝሙትሽን አፈሰስሽ

አንዳንድ የቅርብ ዓመታት ትርጉሞች “ብልጽግናሽን አፈሰስሽ” ብለው ይተረጉሙታል።

የልጆችሽን ደም ሰጠሻቸው

ይህ የሚያመለክተው ለጣዖታት መስዋዕት እንዲሆኑ የተገደሉትን ልጆች ነው።

እነሆ

እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።

ስለዚህ ሙሉ ራቁትነትሽን ያያሉ
በሌሎች ፊት የአንድን ሰው ልብስ መግፈፍ ያንን ሰው ለማዋረድ በማሰብ የሚደረግ ተግባር ነው። “ራቁትነት” የሚለው ቃል እንደ ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ስለዚህ ሙሉ በሙሉ ራቁትሽን መሆንሽን ማየት ይችላሉ”
Ezekiel 16:38
የደም መፍሰስ
ይህ ሐረግ በየትኛውም መልኩ የተፈጸመ ግድያን ይወክላል። ኢ.ት፡ “ግድያ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ስለ ደም መፋሰስ ቁጣዬን እና ርኅራኄዬን በአንቺ ላይ አመጣለሁ
እዚህ ጋ “ደም መፋሰስ” በየትኛውም መልኩ የተፈጸመ ግድያን ይወክላል። ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር የደም መፋሰስን በእርሷ ላይ ያመጣ ይመስል ስለ ግድያዋ እንደሚቀጣት ይናገራል። ኢ.ት፡ “ነፍስ ስለ ማጥፋትሽ በቁጣዬና በርኅራኄዬ እቀጣሻለሁ” ወይም 2) እግዚአብሔር የደም መፋሰስን በእርሷ ላይ ያመጣ ይመስል እርሷን ስለ መግደል ይናገራል። ኢ.ት፡ “በቁጣዬና በርኅራኄዬ ደምሽን አፈስሳለሁ” የሚሉት ትርጉሞች ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእጃቸው እሰጥሻለሁ
እዚህ ጋ “እጆች” የሚወክሉት ኃይልን ወይም ቁጥጥርን ነው። ኢ.ት፡ “በቁጥጥራቸው ስር እንድትሆኚ አደርግሻለሁ” ወይም “በአንቺ ላይ ኃይል እንዲኖራቸው እፈቅድላቸዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የማምለኪያ አዳራሽሽን አፈርሰዋለሁ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ጣዖታቷን ያመለከችበትን ወይም 2) የዝሙት ተግባሯን የፈጸመችበትን ሥፍራ ያጠፉታል የሚሉት ናቸው። በሕዝቅኤል 16፡24 ላይ “የማምለኪያ አዳራሽ” የሚለውን እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት።
ዕርቃንሽን እና ራቁትሽን
የሁለቱም ቃላት ትርጉም አንድ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 16፡7 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ባዶ ዕርቃን”
Ezekiel 16:40
በአንቺ ላይ ብዙ የቅጣት ዓይነት እፈጽምብሻለሁ
“ቅጣት” የሚለው ቃል ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “በተለያየ መንገድ እቀጣሻለሁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
በብዙ ሴቶች ፊት
“ብዙ ሴቶች ሊያዩአት በሚችሉበት ስፍራ” ወይም “ብዙ ሴቶች እያዩአት”
በአንቺ ላይ ንዴቴን አበርዳለሁ፤ ቁጣዬም ይተውሻል
“ንዴት” እና “ቁጣ” የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር ስለ ተቆጣ የሚፈጽማቸው ቅጣቶች መሆናቸውን ያመለክታል። በመሠረቱ የሁለቱም ሐረጎች ትርጉም አንድ ነው። ኢ.ት፡ “ከእንግዲህ ስለማልቆጣሽ አንቺን መቅጣቴን አቆማለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 16:43
ልብ በይ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉሙ ማስታወስ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “አስታውሽ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በቁጣ እንድንቀጠቀጥ አድርገሽኛል
እዚህ ጋ “መንቀጥቀጥ” የሚያመለክተው አንድ ሰው እጅግ በሚቆጣበት ጊዜ የሚታይበትን አካላዊ ምላሽ ያመለክታል። ኢየሩሳሌም እነዚህን ነገሮች ስታደርግ ልጅ በነበረችበት ጊዜ እግዚአብሔር ያደረገውን አላሰበችም።
እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።
ስላደረግሽው ነገር እኔ ራሴ ቅጣቱን በራስሽ ላይ አመጣለሁ
“በራስሽ ላይ አመጣለሁ” የሚለው የአነጋገር ዘይቤ ይህንን ቅጣት ትቀበላለች ማለት ነው። ይህንን የአነጋገር ዘይቤ በሕዝቅኤል 11፡21 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ስለ ጸባይሽ በምትቀበይው ቅጣት እንድትሰቃዪ አደርግሻለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 16:44
እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።
ባሏን የጠላችውን
“ባሏን የጠላችውን”
እናትሽ ኬጢያዊት ነበረች፣ አባትሽም አሞራዊ ነበር
የእስራኤል ሕዝብ ምድሪቱን ድል ከማድረጋቸው በፊት ጣዖት አምላኪ የሕዝብ ወገን የሆኑት አሞራውያንና ኬጢያውያን በምድሪቱ ይኖሩ ነበር። ኢየሩሳሌም በዝሙት መወለዷን ለመግለጽ አባትና እናቷ የዚህ ሕዝብ ወገን እንደ ነበሩ እግዚአብሔር ይናገራል። እነዚህን ሐረጎች በሕዝቅኤል 16፡3 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምካቸው ተመልከት። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 16:46
ታላቅ እህትሽ ሰማርያ ነበረች ... ታናሽ እህትሽ በስተደቡብ የምትኖረዋ ናት፣ እርሷም ሰዶም ናት
ሰማርያና ሰዶም ሁለቱም በጣዖት አምልኮአቸውና በኃጢአታቸው ምክንያት እግዚአብሔር የፈረደባቸው ከተማዎች ነበሩ። እግዚአብሔር እነዚህ ከተሞች ኢየሩሳሌም የጣዖት አምላኪዎችና የኃጢአተኞች ቤተሰብ መሆኗን ለመግለጽ እህቶቿ መሆናቸውን ይናገራል።
Ezekiel 16:47
በመንገዳቸው ብቻ አልሄድሽም
የአንድ ሰው የአኗኗር መንገድ ያ ሰው በጎዳና ላይ እንደሚሄድ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እንደ እነርሱ ብቻ አላደረግሽም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእነርሱን ጠባይና ልምምድ ቀዳሽ
እዚህ ጋ “ጸባይ” እና “ልምምድ” የሚሉት ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። ኢ.ት፡ “ሲያደርጓቸው የነበሩትን ነገሮች ቀዳሽ”
ሕያው እንደ መሆኔ
“ሕያው መሆኔ እርግጥ የመሆኑን ያህል”። እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚናገረው የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ለማሳየት ይህንን አገላለጽ ይጠቀማል። ይህ ጽኑ ተስፋ የመስጫ መንገድ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ጽኑ መሐላ አደርጋለሁ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 16:49
በእርጋታዋ አብረተኛ፣ ስለ የትኛውም ነገር ቸልተኛና ግድ የለሽ
እግዚአብሔር ሰዶምን ከበቂ በላይ ምግብ እንዳላትና ያለ ሥጋት እንደምትኖር ባለጸጋ ሴት አድርጎ ይገልጻታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የድኾችንና የችግረኞችን እጅ አላበረታችም
እዚህ ጋ “እጅ” የሚለው ቃል የሚወክለው በእጆቻቸው የሚሠሩትን ሰዎች ነው። “ድኻ” እና “ችግረኛ” የሚሉት ቃላት እንዲህ ያሉት ሰዎች ራሳቸውን መርዳት የማይችሉ መሆናቸው ላይ አጽንዖት የሰጣሉ። ኢ.ት፡ “ራሳቸውን መረዳት ያልቻሉትን ሰዎች አልረዳቻቸውም” (See: Synecdoche and Doublet)
Ezekiel 16:51
እህቶችሽ ከአንቺ ይሻሉ እንደነበር አሳይተሻል
ኃጢአተኞቹ ሰማርያና ሰዶም ከኢየሩሳሌም ይልቅ ጻድቅ እንደ ነበሩ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ሐረግ ሦስት ጊዜ ይጠቀማል።
በተለይ አንቺ፣ የገዛ ራስሽን ኃፍረት አሳየሽ
የኢየሩሳሌም ሰዎች ምን ያህል ያለ እፍረት እንዳደረጉ አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን ሐረግ ሁለት ጊዜ ይጠቀማል።
የገዛ ራስሽን ኃፍረት አሳየሽ
“እፈሪ” ወይም “ውርደትሽን ተሸከሚ”
Ezekiel 16:53
ምርኮአቸውን
“ሀብታቸውን”
ኃፍረትሽን ታሳያለሽ
“ታፍሪአለሽ” ወይም “ውርደትሽን ትሸከሚያለሽ”
ትዋረጃለሽ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አዋርድሻለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
መጽናናት ትሆኛቸዋለሽ
“መጽናናት” የሚለው ስም ከግሣዊ ሐረግ ጋር ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዶምና ሰማርያን ታጽናኚአለሽ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
እህትሽ ሰዶምና ሴት ልጆቿ ወደ ቀድሞው ሁኔታቸው ይመለሳሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እህትሽን ሰዶምን እና ሴት ልጆቿን ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው እመልሳለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሰማርያና ሴቶች ልጆቿ ወደ ቀድሞው ይዞታቸው ይመለሳሉ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እህትሽን ሰዶምን እና ሴት ልጆቿን ወደ ቀድሞ ይዞታቸው እመልሳለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ይዞታ
x
Ezekiel 16:56
እህትሽ ሰዶም እንኳን በአፍሽ አልተጠራችም
እዚህ ጋ “አፍ” የሚለው ቃል የሚወክለው ተናጋሪውን ሰው ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “የእህትሽን የሰዶምን ስም እንኳን አልጠራሽም” (Synecdoche እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ኃጢአተኝነትሽ ከመገለጡ በፊት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ኃጢአተኝነትሽን ከመግለጥሽ በፊት” ወይም “ኃጢአተኝነትሽን ከመግለጤ በፊት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
አንቺ መሣለቂያ ነሽ
ይህ ሰዎች ስለ አንዳች ነገር በመጥፎ የሚናገሩላትን ኢየሩሳሌምን ያመለክታል።
ለኤዶም ሴቶች ልጆችና ለፍልስጥኤም ሴቶች ልጆች በሙሉ
ይህ ቃል ተበዳሪው ለተበደረው ገንዘብ የሚከፍለውን ገንዘብ ያመለክታል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ አዳዲስ ትርጉሞች በዚህ ምንባብ ያለውን “የትኛውም ወለድ” የሚለውን “እጅግ የበዛ ወለድ” ብለው ይተረጉሙታል።
ባልንጀሮችሽን በመጨቆን ጎድተሻቸዋል
ይህ ማለት እጅግ የበዛ ወለድ በማስከፈል ባልንጀሮቻቸውን ጨቁነዋል። ኢ.ት: “ባልንጀሮቻችሁን በመጨቆን ድኻ እ”ድርጋችኋቸዋል” ወይም “እጅግ ብዙ ወለድ በማስከፈል ባልንጀሮቻችሁ እንዲደኸዩ አድርጋችኋል”
እረስተሽኛል
እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እምቢ ማለት የእርሱን መኖር እንደ መርሳት ማለት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይህ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ነው

እግዚአብሔር የንግግሩን እርግጠኝነት ለመግለጽ የራሱን ስም በመጥራት ይናገራል። ይህንን በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “እኔ፣ ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 22:13

እጄን አማታሁ

“በአንቺ ላይ ቡጢዬን ወዝውዣለሁ” ወይም “በአንቺ ላይ እጆቼን አጨብጭቤአለሁ”። ይህ ቁጣንና ተቃውሞን የሚያሳይ ምልክታዊ ድርጊት ነው። ኢ.ት፡ “በአንቺ ላይ ቁጣዬንና ተቃውሞዬን አሳይቻለሁ” (ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)

በመካከልሽ የተደረገውን ደም ማፍሰስ

“በውስጥሽ ያሉ ሰዎች የፈጸሙት ግድያ”

እኔ ራሴ ከአንቺ ጋር በምነጋገርበት ጊዜ በልበ ሙሉነት ትቆሚያለሽ? በእነዚያ ቀናት እጆችሽስ ይጠነክራሉ?

እግዚአብሔር በሚቀጣቸው ጊዜ ምን ያህል እንደሚጎዱ አጽንዖት ለመስጠት ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ ይጠቀማል። ይህ ጥያቄ ምናልባት እንደ ንግግር ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት፡ “እኔ ራሴ ከአንቺ ጋር በምነጋገርበት ቀን በልበ ሙሉነት አትቆሚም፣ እጆችሽም አይጠነክሩልሽም” (ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

በልበ ሙሉነት ትቆሚያለሽ?

እዚህ ጋ ስሜቱና ፈቃዱ ላይ አጽንዖት ለመስጠት ሙሉው ሰው “ልብ” በሚል ቃል ተመላክቷል። እዚህ ጋ የ “መቆም” አሳብ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን በድፍረት ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ትቆሚያለሽ?” ወይም “ደፋር ትሆኛለሽ?” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

እጆችሽስ ይጠነክራሉ?

እዚህ ጋ ሙሉው ሰው በ “እጆቹ” ተመላክቷል። ኢ.ት፡ “ብርቱ ትሆኛለሽ?” (See: Synecdoche)

ስለዚህ በሀገራት መካከል እበትንሻለሁ፣ በምድር ሁሉ ላይ እበታትንሻለሁ

የእነዚህ ሁለት ሐረጎች መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። ተመሳሳዩን ሐረግ በሕዝቅኤል 12፡15 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “ስለዚህ እርስ በእርሳቸው እንዲለያዩና በተለያየ ሀገር እንዲኖሩ አደርጋቸዋለሁ”

ማጽዳት

አንድ የማይፈለግን ነገር ማስወገድ

እርኩስ

እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ሁኔታው ተቀባይነት የለውም ወይም እረክሷል የሚለው አንድ ሰው፣ እርሱ በአካሉም የረከሰ ያህል ተቆጥሮ ተነግሮለታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስለዚህ፣ በሀገሮች ዐይን ፊት እርኩስ ትሆኛለሽ

እዚህ ጋ “ሀገሮች” የሚያመለክተው በእነዚያ አካባቢዎች የሚኖሩትን ሰዎች ነው። “ዐይን” ማየትን፣ ማየትም አሳብን ወይም ውሳኔን ይወክላል። ኢ.ት፡ “ስለዚህ፣ ሀገሮች እርኩስ እንደሆንሽ ይቆጥራሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሀገሮቹ

እዚህ ጋ “ሀገሮች” የሚያመለክተው በእነዚያ አካባቢዎች የሚኖሩትን ሰዎች ነው። ኢ.ት፡ “በሌሎች ሀገሮች የሚኖሩ ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ያውቃሉ

እግዚአብሔር ሰዎች እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ ብሎ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን ሰዎች ያውቃሉ ማለቱ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እውነተኛው አምላክ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይረዳሉ” ወይም “ፍጹም ኃይልና ሥልጣን ያለኝ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ይገነዘባሉ”

Ezekiel 22:17

የእግዚአብሔር ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ቤት አለው

“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፤ በመሆኑም፣ ይህ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ያሉትን የያዕቆብን ዘሮች፣ እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እስራኤላውያን አላቸው” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ ወገን አላቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ጉድፍ ሆኑብኝ

ጉድፍ፣ ብር ወይም ወርቅ በምድጃ ላይ ከነጠረ በኋላ የሚቀር ብካይ ነው። እዚህ ጋ ሕዝቡ እንደ ጉድፍ እንደማይጠቅሙት እግዚአብሔር ይናገራል። ኢ.ት፡ “ለእኔ እንደ ጉድፍ የማይጠቅሙኝ ሆነዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሁሉም ከነሐስና ከቆርቆሮ እንደሚተርፍ … በምድጃችሁ እንዳለ የብር ጉድፍ ናቸው

ሕዝቡ ጉድፍ የሆኑ ይመስል ምንም የማይጠቅሙት እንደሆኑበት እግዚአብሔር መናገሩን ይቀጥላል። ኢ.ት፡ “ሁሉም ምድጃ ውስጥ ብርን ካቀለጥከው በኋላ ከነሐስና ከቆርቆሮ፣ ከብረትና ከእርሳስ እንደሚቀር ትራፊ የማይጠቅሙ ናቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነሆ

“ተመልከቱ” ወይም “ስሙ” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ”

Ezekiel 22:20

በቁጣዬና በመዓቴ እሰበስባችኋለሁ

በ “ቁጣዬ” እና “መዓቴ” የሚሉት ሐረጎች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት እርሱ እጅግ መቆጣቱን አጽንዖት ለመስጠት ነው። ኢ.ት፡ “በታላቁ ቁጣዬና መዓቴ ምክንያት እሰበስባችኋለሁ” ወይም “በብርቱ ተቆጥቼ እሰበስባችኋለሁ” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እሰበስባችኋለሁ፣ የቁጣዬንም እሳት አነድባችኋለሁ

ይህ ብረታ ብረቱን ወደ ምድጃው የሚሰበስበውንና እንዲግል እሳት የሚያነድበት ሰው ምስል ነው። እንዲግል የሚያነደው እሳት የሆነ ይመስል እግዚአብሔር የሚናገረው ስለ ቁጣው ታላቅነት ነው። ኢ.ት፡ “እሰበስባችኋለሁ፣ ቁጣዬንም በእናንተ ላይ እንደ እሳት አነደዋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በእርሱ ትቀልጣላችሁ

“በእርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው።

ቁጣዬን አፍስሼባችኋለሁ

እግዚአብሔር ቁጣው በእነርሱ ላይ የሚያፈሰው ፈሳሽ የሆነ ይመስል ሕዝቡን ስለ መቅጣት ይናገራል። ኢ.ት፡ “በቁጣዬ ቀጥቻችኋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Ezekiel 22:23

የእግዚአብሔር ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለሕዝቡ አንድን ነገር ለማስታወቅ የሚጠቀምበት የአነጋገር ዘይቤ ነው። ይህንን በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ይህንን መልዕክት ተናገረ” ወይም “እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር ተናገረ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አንቺ ያላነጹሽ ምድር ነሽ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። እዚህ ጋ፣ “ምድር” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እስራኤልንና በዚያ የሚኖሩትን ሕዝብ ነው። ኢ.ት፡ “ንጹሕ ያልሆነው ምድርና ሕዝብ አንቺ ነሽ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ያላነጹሽ

እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ሁኔታው ተቀባይነት እንደሌለው ወይም እንደ ረከሰ የሚቆጥረው ሰው ያ ሰው በአካሉም እንደ ረከሰ ተቆጥሮ ተነግሮለታል።(ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በቁጣ ቀን ምንም ዝናብ የለም

ዝናብ የእግዚአብሔር በረከት ምሳሌ ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት፡ “በቁጣ ቀን ምንም በረከት የለም” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

በመካከሏ የነቢያቶቿ ሤራ አለ

“እርሷ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እስራኤልን ነው። ኢ.ት፡ “በእስራኤል ያሉ ነቢያት ሤራዎችን አሲረዋል”

ሤራ

ሕገ ወጥ ወይም የሚጎዳ ነገር ለማድረግ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች በምስጢር የሚደረግ ዕቅድ

ልክ እያገሳ ንጥቂያውን እንደሚቦጫጭቅ አንበሳ ሕይወትን ያጠፋሉ፣ የከበረውን ሀብትም ይወስዳሉ

ይህ የእስራኤልን ነቢያት ንጥቂያዎቻቸውን ከሚያጠቁና ከሚገድሉ አናብስት ጋር ተነጻጽረዋል። ኢ.ት፡ “ያደኑትን እንደሚያጠቁና እንደሚገድሉ የሚያገሱ አንበሶች

ሰዎችን ይገድላሉ። የሰዎችን የከበሩ ሀብቶች ይወስዳሉ”
በውስጣ ብዙ መበለቶች እንዲኖሩ ያደርጋሉ
“እርሷ” የሚለው ቃል እስራኤልን ያመለክታል። ያገቡትን ወንዶች በመግደል “ብዙ መበለቶች እንዲኖሩ ያደርጋሉ”። ኢ.ት: “ባሎቻቸውን በመግደል ብዙ ሴቶችን መበለቶች ያደርጓቸዋል”
Ezekiel 22:26
እርሷ
ይህ ተውላጠ ስም ኢየሩሳሌምን ያመለክታል።
በሕጌ ላይ ያምፃሉ
“ሕጌን አይታዘዙም”
እርኩሱ እና ንጹሑ
ይህ እርኩስና ንጹሕ የሆኑ ነገሮችን ያመለክታል። እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ሁኔታው ተቀባይነት የለውም ወይም እረክሷል የሚለው አንድ ነገር፣ እርሱ በአካሉም የረከሰ ያህል ተቆጥሮ ተነግሮለታል። ኢ.ት: “እርኩስ የሆኑና ንጹሕ የሆኑ ነገሮች” (ስማዊ ቅጽል እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዐይኖቻቸውን ከሰንበቶቼ ይደብቃሉ
ሕዝቡ ዐይኖቻቸውን ከሰንበት ይደብቁ ይመስል ይህ የሚናገረው ሰንበትን ቸል ስለማለታቸውና ስላለመጠበቃቸው ነው። ኢ.ት: “ሰንበቶቼን ቸል ይላሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ስለዚህ በመካከላቸው ተንቁአለሁ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “በመካከላቸው ይንቁኛል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
መሳፍንቶቿ በውስጧ ልክ ንጥቂያቸውን እንደሚቦጫጭቁ ተኩላዎች ናቸው
ይህ የእስራኤልን መሳፍንት ንጥቂያዎቻቸውን ከሚያጠቁና ከሚገድሉ ተኩላዎች ጋር ያነጻጽራቸዋል።
ደም ያፈሳሉ፣ ሕይወትንም ያጠፋሉ
በመሠረቱ የእነዚህ ሁለት ሐረጎች ትርጉም አንድ ሲሆን መሳፍንቱ በሚፈጽሟቸው ግፎች ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት: “ሰዎችን ይገድላሉ”
ነቢያቶቿ በኖራ ቀብተዋቸዋል
ይህ የሚናገረው ነቢያቱ በኖራ እንደሚቀቡት አንዳች ነገር እነዚህን ኃጢአቶች ለመደበቅ መሞከራቸውን ነው። ኢ.ት: “ነገሩ ነቢያቶቿ ኃጢአታቸውን በኖራ የቀቡት ያህል ነው” ወይም “ነቢያቶቻቸው እነዚህን ክፉ ነገሮች ለመደበቅ ይሞክራሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ኖራ
ይህ ከነጭ ቀለም ጋር ተመሳሳይ ሲሆን አንዳንድ ነገሮችን ነጭ ለማድረግ የሚቀባ ውሁድ ነው።
ሐሰትን ተንብየውላቸዋል
x

Ezekiel 22:29
ተጨቁነዋል … ተበዝብዘዋልም
የታወቁት ቃላት መረጃ ሊጨመርባቸው ይችላል። ኢ.ት: “ሰዎችን ጨቁነዋል … ሌሎችንም በዝብዘዋል”
መቀማት
ይህ የሚያመለክተው አንድ ሰው ሌላውን ገንዘብ እንዲሰጠው የሚያስፈራራበትን ወይም የሚጎዳበትን ሁኔታ ነው።
ድኻውንና ችግረኛውን
ይህ ድኾችንና ችግረኞች ሰዎችን ያመለክታል። ኢ.ት: “እነዚያ ድኻና ችግረኛ የሆኑ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
Ezekiel 22:30
ቅጥርን የሚሠራ ከእነርሱ አንድ ሰው
ይህ የሚናገረው ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ለመከላከል ቅጥር የሚሠራ ሰውን ይመስል ስለ ሕዝቡ ለመጸለይና ወደ ንስሐ ሊመራቸው ኃላፊነት ስለሚወስድ አንድ ሰው። ኢ.ት: “ከመካከላቸው ልክ ቅጥርን እንደሚሠራ የሚያደርግን ሰው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በፈረሰው በኩል በፊቴ የሚቆም
“በፈረሰው” የሚያመለክተው በቅጥሩ መካከል ያለውን ክፍተት ነው። ይህ የሚናገረው ከተማይቱን ለመከላከል በፈረሰው በኩል እንደሚቆም ተዋጊ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ስለሚከላከል ሰው ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እንዳላጠፋት ስለምድሪቱ
እዚህ ጋ፣ “ምድር” በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። ኢ.ት: “እንዳላጠፋቸው ስለ ሕዝቡ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
መዓቴን አፈስባቸዋለሁ
መዓቱ በእነርሱ ላይ የሚያፈሰው ፈሳሽ የሆነ ይመስል ይህ የሚናገረው እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለሚቀጣበት ሁኔታ ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
መዓት
ፍትሕ በማጣት የሚሰቃይ ሰው ቁጣ
በመዓቴ እሳት እጨርሳቸዋለሁ
ይህ የእግዚአብሔር ፍርድ ምን ያህል ከባድ እንደ ሆነ ከእሳት ጋር በማነጻጸር ይናገራል። እዚህ ጋ፣ ሕዝቡን ማጥፋት እነርሱን እንደ “መጨረስ” ተደርጎ ተመልክቷል። ኢ.ት: “እንደሚንበለበል እሳት ብርቱ በሆነው ቁጣዬ አጠፋቸዋለሁ” ወይም “በቁጣዬ አጠፋቸዋለሁ”
መንገዳቸውን በራሳቸው ላይ አመልሳለሁ
አንድን ነገር በሰው ራስ ላይ ማስቀመጥ ሸክም እንዲሸከሙ ወይም ስለ ጉዳዩ ኃላፊነት እንዲወስዱ ማድረግን ያመለክታል። ኢ.ት: “ስላደረጉት ነገር ኃላፊነት እንዲወስዱ አደርጋቸዋለሁ”

Chapter 23
Ezekiel 23:1
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በዘይቤ ኢየሩሳሌምን እና ሰማርያ ከተሞችን ለእርሱ እንዴት ታማኝ እንዳልሆኑ እንደ ሁለት ዘማዊያት እህትማማቾች አድርጎ ይናገራል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን አንዳች ነገር ለማስተዋወቅ ያገለገለ ፈሊጥ ነው ። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላቶች ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ይህን ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው እንጂ ሌላ አለመሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘላዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰብአዊ ፍጡር ግን እንዲያ አይደለም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ጡቶቻቸው ተዳበሰዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወንዶች ጡቶቻቸውን ዳበሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ እና ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የድንግልና ጡቶቻቸው አጎጠጎጤአቸው ተዳብሷል
ይህ ሀረግ ከመጀመሪያው ሀረግ ጋር በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አለው፤ ትኩረት የሚሰጠውም የሁለቱን ወጣት ሴቶች ስነምግባር የጎደለው ባህርይ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወንዶቻቸው የድንግልና ጡቶቻቸውን አጎጠጎጤ ዳበሱ" (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
መዳበስ
በፍቅር ወይም በልስላሴ መነካት
እነርሱ የእኔ ሆኑ
ይህ ማለት እርሱ አገባቸው ደግሞም ሚስቶቹ ሆኑ። "እነርሱ የእኔ ሚስቶች ሆኑ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የስሞቻቸው ትርጉም ይህ ነው፡ ኦሖላ ማለት ሰማርያ ማለት ሲሆን፤ ኦሖሊባ ማለት ኢየሩሳሌም ናት።
"ኦሖላ ሰማርያን ትወክላለች፤ ኦሖሊባ ደግሞ ኢየሩሳሌምን ትወክላለች።" በዚህ ዘይቤ ሰማርያ የተገለጸችው ኦሖላ እንደሆነች እና ኢየሩሳሌም ደግሞ ኦሖሊባ እንደሆነች ተደርጎ ነው። ይህ የመሚገልጸው እነዚህ ከተሞች ታማኝ እንዳልሆኑ ሚስቶች እንዴት ለያህዌ ታማኞች እንዳልነበሩ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኦሖላ
ይህ የሴት ስም ሲሆን ትርጉሙ "የእርሷ ድንኳን" ማለት ነው ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ኦሖሊባ
ይህ የሴት ስም ሲሆን ትርጉሙ "የእኔ ድንኳን በእርሷ ነው" (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 23:5
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሷ የእኔ በነበረች ጊዜ
ይህ የሚያመለክተው እርሷ መቼ የእርሱ ሚስት እንደነበረች ነው። "እርሷ የእኔ ሚስት እስከ ነበረች ጊዜ ድረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በላያቸው የነበሩ
"ይገዟቸው የነበሩ"
የአሶር ምርጥ ወንዶች የነበሩ ሁሉ
ይህ የሚገልጸው "እነርሱ" የሚለው ቃል ማንን እንደሚያመለክት ነው።
አብራቸው ካመነዘረቻቸው እና ከጣኦቶቻቸው ጋር ሁሉ ረክሳለች
ይህ የሚያመለክተው ከእነዚህ ሁሉ ወንዶች ጋር መተኛቷን እና ጣኦቶቻቸውን ማምለኳን ነው። "ከሁሉም ጋር በመተኛት እና ጣኦቶቻቸውን በማምለክ ራሷን አርክሳለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መርከስ/ንጹህ አለመሆን
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር ንጹህ አድርጎ የማይቆጥረው ወይም የረከሰ ሰው በአካል እንደቆሸሸ ተደርጎ ይገለጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 23:8
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በላይዋ የሴሰኝነት ባህሪያቸውን መፈጸም
ይህ የሚናገረው ወንዶቹ በእርሷ ላይ የፈጸሙት የሴሰኝነትን ባህርይ በላይዋ እንዳፈሰሱት ታላቅ የጎርፍ ውሃ ተደርጎ ነው። "በእርሷ ላይ ሴሰኝነት መፈጸም" ወይም "በእርሷ ላይ ማመንዘር" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሷ ላይ ፍርድ ፈጸሙ
ይህ ፈሊጥ ነው። "ስለ መዋረዷ አወሩ" ወይም "በእነርሱ መሃል መጥፎ ስም ነበራት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 23:11
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ኦሖሊባ
ይህ የሴት ስም ሲሆን ትርጉሙ "የእኔ ድንኳን በእርሷ ነው" ማለት ነው። ይህ ስም በሕዝቅኤል 23:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
መርከስ/ንጹህ አለመሆን
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር ንጹህ አድርጎ የማይቆጥረው ወይም የረከሰ ሰው በአካል እንደቆሸሸ ተደርጎ ይገለጻል። ይህ ስም በሕዝቅኤል 23:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ለሁለቱም እህትማማቾች ተመሳሳይ/አንድ ነበር
ይህ የሚያመለክተው ሁለቱም እንዴት ራሳቸውን እንዳረከሱ ነው። "ሁለቱም እህትማማቾች በምንዝርና ተግባራቸው ረክሰዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 23:14
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጥምጥም
ከረጅም ጨርቅ የተሰራ እንደ ባርኔጣ በወንድ በራስ ላይ የሚጠቀለል
የሰረገላ አዛዦች መልክ እና አምሳያ ያላቸው ወጣቶች ቡድን
"መልክ" እና "አምሳያ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በግሳዊ ሀረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። "የሰረገላ አዛዦች ቡድኖች ያላቸውን መልክ የያዙ እና የወጣትነት መልክ ያላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የሰረገለኞች ቡድን
ሰረገላ የሚነዱ እና ከሰረገለው ፊት እና ጎን የሚሮጡ ወታደሮች
የባቢሎን ወንዶች ልጆች
"ባቢሎናውያን"
Ezekiel 23:16
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የምንዝርናዋ መኝታ
ይህ የሚያመለክተው ከወንዶች ጋር ያመነዘረችበትን ስፍራ እና የዝሙት ተግባሯን ነው። "ያመነዘረችበት መኝታ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መርከስ/ንጹህ አለመሆን
እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር ንጹህ አድርጎ የማይቆጥረው ወይም የረከሰ ሰው በአካል እንደቆሸሸ ተደርጎ ይገለጻል። ይህ ስም በሕዝቅኤል 23:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህም ራሷን ከእነርሱ ዘወር አደረገች
ይህ ፈሊጥ ነው። "ስለዚህም እነርሱን ተወች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 23:18
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 23:20
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አባለዘራቸው እንደ አህያ የሆነ
የወንዶችን አባለዘር መጠን ከአህያ ጋር የሚያነጻጽረው የኦሖሊባ ፍላጎት ምን ያህል ክፉ እንደነበር ለማሳየት ነው። ይህ ግነት ነው፤ የእነርሱ እንደ አህያ ማከል አይችልም። "አባለዘራቸው እንደ አህያ በጣም ትልቅ የሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ኩሸት እንደዚሁም አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
የዘር ፍሰታቸው እንደ ፈረስ የሆነ
x
Ezekiel 23:22
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ!
"አድምጡ!" እዚህ ስፍራ "እነሆ!" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው አስደናቂ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል።
በአንቺ ላይ ከየስፍራው እነርሱን አስነሳብሻለሁ
"ከሁሉም አቅጣጫ እንዲነሱብሽ አደርጋለሁ"
ከእነርሱ ጋር ባቢሎናውያንን እና ከለዳውያንን፣ የፋቁድ፣ ሱሔ፣ እና ቆዓ እንደዚሁም አሶራውያንን ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው በእነዚህ ስፍራዎች የሚኖሩትን ህዝቦች ሁሉ ሳይሆን፤ ነገር

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ግን የእነዚህ ስፍራዎችን ወታደሮች ነው። " ከእነርሱ ጋር የባቢሎን እና የከለዳውያን፣ የፋቁድ፣ ሱሔ፣ እና ቆዓ እንደዚሁም የአሶር ወታደሮችን ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

ፋቁድ፣ ሱሔ፣ እና ቆዓ

እነዚህ ባቢሎን ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች ስሞች ናቸው። እነዚህ ስፍራዎች ከዚያ አስፍራ የመጡ ወታደሮችን ይገልጻሉ። " ከፋቁድ፣ ሱሔ፣ እና ቆዓ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ሁሉም ፈረስ ጋላቢ የሆኑ... ጠንካራ፣ ውብ ወንዶች፣ ገዢዎች እና አዛዦች

ይህ ከአሶር የመጡ ኦሖላ አብራቸው የተኛቻቸው አሁን ግን በእርሷ ላይ የተነሱባትን ወንዶች መግለጫ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 23:6 ላይ ከተሰጠው መግለጫ ጋር ተመሳሳይ ነው።

Ezekiel 23:24

አጠቃላይ መረጃ:

ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንቺ ላይ ይመጡብሻል

ይህ ፈሊጥ ነው። "ጥቃት ያደርሱብሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መሳሪያ ይዘው

እዚህ ስፍራ "መሳሪያ" ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃል የተለመደ አይደለም። በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች በዚህ መንገድ ይተረጉሙታል፣ ሆኖም ግን አንዳንድ ቅጂዎች ይህንን ሀረግ ያስወጡታል።

ትላልቅ ጋሻዎችን፣ ትንንሽ ጋሻዎችን፣ እና የወታደር ቆቦችን በዙሪያሽ ሁሉ ያመጣሉ

እነዚህ የመከላከያ ዕቃዎች የተለያዩ የወታደር ክፍሎችን ለማመልከት ያገለግላሉ። "ትላልቅ ጋሻዎችን፣ ትንንሽ ጋሻዎችን የያዙ እና ቆብ የደፉ ወታደሮች ጥቃት ያደርሱብሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በአንቺ ላይ የቅናቴን ቁጣ አመጣለሁ፤ በሀይል ይነሱብሻል

እዚህ ስፍራ ያህዌ ወታደሮች እንዲያጠቋቸው የሚፈቅደው በእነርሱ ላይ ስለተቆጣ ሲሆን ቁጣውም ተገለጸው በላያቸው እንዳስቀመጠው ነገር ተደርጎ ነው። "በእናንተ በጣም ስለቀናሁ፣ በሀይል እንዲያጠቋችሁ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አፍንጮቻችሁን እና ጆሮቻችሁን ይቆርጣሉ

ይህ በባቢሎን ውስጥ ያገባች ሴት ስታመነዝር የሚደርስባትን ቅጣት የሚገልጽ ነው። "አፍንጫሽን እና ጆሮዎችሽን በመቁረጥ እንደ ዘማዊ ሴት ይቀጡሻል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የቀሩት ሰዎችሽ በሰይፍ ይወድቃሉ

"መውደቅ" የሚለው ቃል "መሞት" ለሚለው ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት ሲሆን፤ "ሰይፍ" የሚለው ቃል በሰይፍ ለሚገድሉ ወታደሮች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

የቀሩት ሰዎችሽ/ትሩፋኑ በእሳት ይበላሉ

ይህ ትሩፋኑ በእሳት እንደሚቃጠሉ ይገልጻል፤ እዚህ ስፍራ እሳት እንደሚያጠቃቸው እና እንደሚበላቸው እንስሳ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በህይወት የተረፉት በእሳት ይቃጠላሉ" ወይም "እሳት በህይወት የተረፉትን ያቃጥላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:26

አጠቃላይ መረጃ:

ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከግብጽ ምድር

ይህ የሚያመለክተው ዘማዊነቷ ከግብጽ እንደ ጀመረ ነው። "በግብጽ ምድር የጀመርሽው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እነርሱ ዐይኖችሽን በምኞት አታነሽም

ይህ አንድ ነገር ለመመልከት ጭንቅላታቸውን የሚያዞሩ ሰዎችን ለማመልከት የሚውል መንገድ ነው። እዚህ ስፍራ መመልከት የሚወክለው ፍላጎትን ነው። "በምኞት ወደ እነርሱ አትመለከቺም" ወይም "እነዚህን መገሮች አትፈልጊም/ አትመኚም" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ ወዲያ ስለ ግብጽ አታስቢም

እዚህ ስፍራ "ግብጽ" የምትወክለው በግብጽ ውስጥ ያደረገቻቸውን አሳፋሪ ነገሮች ነው። "ከእንግዲህ ወዲያ በግብጽ ውስጥ ያደረግሻቸውን ነገሮች አታስቢም" ወይም "ከዚህ በኋላ በግብጽ ያደረግሽውን አታስቢም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:28

አጠቃላይ መረጃ:

ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!

"ትኩረት ስጡ፣ ምክንያቱም ቀጥሎ የምናገረው እውነተኛ እና ጠቃሚ ነገር ነው"

ለምትጠዪቸው እጅ አሳልፌ እሰጣችኋለሁ...አምልጣችኋቸው ለነበሩት እጅ መልሼ እሰጣችኋለሁ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይህ ማለት ያመነዝሩባቸው በነበሩ ሰዎች ይያዛሉ። "የምትጠዪቸው እና ከእጃቸው አምልጣችሁ የነበሩት መልሰው እንዲይዟችሁ እፈቅዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እጃቸው

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው ቃል መቆጣጠርን/መልሶ መያዝን ያመለክታል። "በቁጥጥራቸው ስር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርቃን እና መራቆት

እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ሙሉ ለሙሉ እርቃን መቅረቷን ትኩረት ይሰጣል። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

እርቃንሽ አይሸፈንም

x

Ezekiel 23:30

አጠቃላይ መረጃ:

ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23:34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ነገሮች በድርጊቶችሽ በአንቺ ላይ ይፈጸሙብሻል

"እነዚህ ነገሮች በአንቺ ላይ ከድርጊትሽ የተነሳ ይፈጸምብሻል" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እነዚህ ነገሮች በአንቺ ላይ ይሆናሉ ምክንያቱም አንቺ የፈጸምሽው አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ አመንዝራ ማድረግ፣ ህዝቦችን ተከትሎ ማመንዘር

ሕዝቅኤል ይሁዳን ስለምትወክለው (ሕዝቅኤል 23:4) ኦሖሊባ፣ ለገንዘብ ስትል ከተለያዩ አገራት ህዝቦች ወንዶች ጋር እንደምትተኛ ሴት አድርጎ ይናገራል። ሕዝቅኤል፣ የይሁዳ ሰዎች የሌሎችን አገራት ሀብት እና ሀይል ለማግኘት ሲሉ የእነርሱን አማልክት በማምለካቸው ምክንያት ያህዌ እንደሚቀጣቸው እንዲያውቁ ይፈልጋል። "ከሌሎች አገራት ወንዶች ጋር በመዘሞት እንደ አመንዝራ ሴት ይፈጽማሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በጣኦቶቻቸው ረከሰች

ጣኦትን በማምለክ ረከሰች። "ጣኦቶቻቸውን በማምለክ ረከሰች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መርከስ/ንጹህ አለመሆን

እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር ንጹህ አድርጎ የማይቆጥረው ወይም የረከሰ ሰው በአካል እንደቆሸሸ ተደርጎ ይገለጻል። ይህ ስም በሕዝቅኤል 23:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስዚህ የእርሷን የቅጣቷን ጽዋ በእጅሽ አስጨብጥሻለሁ

ይህ የሚያመለክተው ኦሖሊባ የምትቀበለው ቅጣት የወይን ጽዋ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "ስለዚህ እህትሽ በተቀጣችበት ተመሳሳይ መንገድ እንድትቀጪ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:32

አጠቃላይ መረጃ:

ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። ይህ ዘይቤ እስከ ሕዝቅኤል 23፡34 ድረስ ይቀጥላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺም የእህትሽን ጽዋ ትጎነጫለሽ/ትጠጪለሽ

እዚህ ስፍራ ያህዌ ቅጣትን ሴቲቱ የምትጠጣው የወይን ጽዋ አድርጎ ይናገራል። "እንደ እህትሽ አንቺም ተመሳሳይ የቅጣት ጽዋ ትጠጪለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእህትሽ ጽዋ ይኸውም

እዚህ ስፍራ "ጽዋው" የሚወክለው በጽዋው ውስጥ የሚገኘውን ነው። "ከእህትሽ ጽዋ ይኸውም" ወይም "በእህትሽ ጽዋ ውስጥ ሚገኘውን ሁሉ፣ ደግሞም የእርሷ ጽዋ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መሳቂያ... መሳለቂያ

እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ከሞኝነት ባህሪው የተነሳ የሚሳቅበት እና የሚተች ሰው ባህሪን ያመለክታሉ። መናቅ በአንድ ነገር ወይም በአንድ ሰው ላይ ማፌዝ ወይም ማወረድ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ጽዋ ብዙ መጠን ይይዛል

ይህ ዐረፍተ ነገር በጽዋው ውስጥ የሚገኘው አይልም ምክንያቱም ሕዝቅኤል 23 31 ላይ ያለውን በማንበብ ይታወቃል። "ይህ ጽዋ ብዙ መጠን ያለው ቅጣት ይዟል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:33

አጠቃላይ መረጃ:

ያህዌ የኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ከተሞችን እንደ ሁለት አመንዝሮች አድርጎ በዘይቤ መግለጹን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በስካር እና በሀዘን ትሞያለሽ

ይህ ጠጪነት እና ሀዘን ሰውነቷን እንደተቆጣጠረው አድርጎ በጣም ጠጪ እና ሀዘንተኛ ስለመሆን ይናገራል። "በጣም ሰካራም እና ሀዘንተኛ ትሆኛለሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የፍራቻ እና የጥፋት ጽዋ

"ፍራቻ እና ጥፋት የሚያስከትል ጽዋ።" እዚህ ስፍራ "ፍራቻ" እና "ጥፋት" የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ቅጣቷ ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን ትኩረት ይሰጣሉ። "በዚያ ጽዋ ውስጥ የሚገኘው ፍራቻን እና ጥፋትን ያስከትላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

የእህትሽ የሰማርያ ጽዋ

የኦሖሊባ እህት የሆነችው ኦሖላ የምትወክለው ሰማርያን ነው። ሰማርያ የተጠራችው በስሟ ነው፤ ነገር ግን እንደ እህት ተጠቅሳለች። ጽዋው እርሷ ለምትቀበለው ቅጣት ምልክት ነው። "ይህ ሰማርያን የምትወክለው እህትሽ የምትጠጣው ራሱ ያው የቅጣት ጽዋ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጡቶችሽን ብጪ

"ጥቶችሽን ቁረጪ"

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ/አዋጅ ነው

ያህዌ ስለሚያዘው/አዋጁ እርግጠኝነት ለመናገር በራሱ ይምላል/በስሙ ያውጃል። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የጌታ የያህዌ አዋጅ ይህ ነው" ወይም "እኔ፣ ጌታ ያህዌ ያወጅኩት/ቃሌ ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:35

ከኋላሽ ጥለሽኛል

ያህዌ እርሱ በእርሷ እንተተወ እና ኦሖሊባ እንደ ረሳችው አድርጎ ይናገራል። "እኔን ትተሻል/ጥለሽኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:36

የሰው ልጅ፣ በኦሖላ እና ኦሖሊባ አትፈርድምን?

ያህዌ ይህንን ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የተጠቀመው ለሕዝቅኤል እንደ ተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ይህ ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊጻፍ ይችላል። የኢየሩሳሌም እና የሰማርያ ከተሞች በኦሖላ እና ኦሖሊባ ተወክለዋል። "የሰው ልጅ ሆይ፣ በኦሖላ እና ኦሖሊባ አትፈርድም!" ወይም "የሰው ልጅ ሆይ፣ በኦሖላ እና ኦሖሊባ በተወከሉት በእነዚያ ሁለት ከተሞች ህዝቦች ላይ ፍረድ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ

"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በእጆቻቸው ላይ ደም አለ

ይህ ፈሊጥ ነው። "እነርሱ ሰዎችን ገድለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:38

አጠቃላይ መረጃ:

ያህዌ የኢየሩሳሌም እና የሰማርያ ሰዎች እንዴት ለእርሱ ታማኞች እንዳልሆኑ ይናገራል።

መርከስ/ንጹህ አለመሆን

እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር ንጹህ አድርጎ የማይቆጥረው ወይም የረከሰ ሰው በአካል እንደቆሸሸ ተደርጎ ይገለጻል። ይህ ስም በሕዝቅኤል 23፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሰንበቴን ባረከሱበት በዚያው ቀን

"በዚያው ቀን" የሚለው ሀረግ "ቤተ መቅደሴን አረከሱ" የሚለውን የቀደመውን ሀረግ ያመለክታል። "ቤተ መቅደሴን ባረከሱበት በዚያው ቀን ሰንበቴንም አረከሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!

"ትኩረት ስጡ፣ ምክንያቱም ቀጥሎ የምናገረው እውነተኛ እና ጠቃሚ ነገር ነው"

በቤቴ መሃል

ይህ በአጠቃላይ ቤቱን ያመለክታል። "መሃል" የሚለው ትኩረት የሚሰጠው የተደረገው የሆነው በግልጽ በቤተ መቅደስ ሲሆን መላውን ስፍራ አርክሷል። "በቤቴ/በራሴ ቤት" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 23:40

አጠቃላይ መረጃ:

ያህዌ ዳግም የኢየሩሳሌም እና የሰማርያ ከተሞችን ሁለት ዘማዊያን እንደሆኑ አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መልዕክተኛ ወደሚላክላቸው፣ ከሩቅ አገር ለሚመጡ ወንዶች መልዕክተኛ ላክሽ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይህ ማለት ወደ እነርሱ እንዲመጡ ሩቅ አገር ወዳሉ ወንዶች መልዕክተኛ ላኩ። "ከሩቅ ስፍራ ወደሚመጡ ወንዶች መልዕክተኞች ላክሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!

"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ቀጥሎ ለምነገረራችሁ ትኩረት ስጡ"

ገላሽን ታጠብሽ፣ ዐይንሽን ተኳልሽ፣ ደግሞም ራስሽን በጌጣጌጥ አስዋብሽ

እነዚህ ነገሮች አንዲት ሴት ራሷን ለአንድ ወንድ ይበልጥ ውብ ሆና ለማሳየት የምታደርጋቸው ነገሮች ናቸው።

አንቺ ገላሽን ታጠብሽ...ተቀመጥሽ

እዚህ ስፍራ "አንቺ" የሚለው ቃል ወደ ነጠላ ቁጥር ይለውጣል፣ እናም አንደኛይቱን እህት ያመለክታል፣ ነገር ግን ሁኔታው ምናልባት ለሁለቱም ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል። በእናንተ ቋንቋ ሀሳቡን ለመግለጽ አንዲቱ እህት መለየት የሚኖርባት ከሆነ ኦሖሊባ መሆኗን ጥቀሱ። (አንተ/አንቺ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይምልከቱ)

ቅመሜ እና ዘይቴ

እነዚህ ነገሮች ያህዌን ለማምለክ የሚያገለግሉ ነገሮች ናቸው።

Ezekiel 23:42

አጠቃላይ መረጃ:

ያህዌ ዳግም የኢየሩሳሌም እና የሰማርያ ከተሞችን ሁለት ዘማዊያን እንደሆኑ አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ስለዚህም የብዙ ህዝብ ጩኸት በዙሪያዋ ነበር
የብዙ ህዝብ ጩኸት የሰዎቹን ብዛት ያመለክታል። "ስለዚህም ብዙ የሚጮሁ ሰዎች ድምጽ በዙሪያዋ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በዙሪያዋ ነበር… በእጆቻቸው ላይ
"በዙሪያዋ ነበር… በእርሷ እና በእህቷ እጆች ላይ።" ይህ ሀረግ የሚጀምረው አንደኛይቱን እህት በማመልከት ነው፤ ነገር ግን ሁኔታው ለሁለቱም እህትማማቾች ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል።ይችላል። በእናንተ ቋንቋ ሀሳቡን ለመግለጽ አንዲቱ እህት መለየት የሚኖርባት ከሆነ እዚህ ስፍራ ኦሖሊብን ጥቀሱ። በሀረጉ ሁለተኛ ክፍል "የእነርሱ" በሚለው ቃል ሁለቱንም እህትማማቾች ወደማመልከት ይመጣል
ሳባውያን ይመጡ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሳባውያን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለሳባ መምጣታቸውን ነው። "ሳባውያን ይመጡ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚሉትን ይመልከቱ)
አምባር ያደርጉ ነበር
"እነርሱ" የሚለው ቃል ወንዶችን ያመለክታል።
Ezekiel 23:43
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ዳግም የኢየሩሳሌም እና የሰማርያ ከተሞችን ሁለት ዘማዊያን እንደሆኑ አድርጎ ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የተተወችው እርሷ…ከእርሷ ጋር፣ ደግሞም እርሷ ከእነርሱ
ይህ የሚያመለክተው ከሁለቱ እህትማማቾች አንዷን ሲሆን ነገር ግን ሁኔታው ማናልባት ለሁለቱም ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል። በቋንቋችሁ አንደኛው እህት ተለይታ መገለጽ ካለባት ኦሖሊብን ጥቀሱ።
እነርሱ ወደ እርሷ ሄደው ወንዶች ወደ ዘማዊት ሴት እንደሚሄዱ ከእርሷ ጋር ተኙ
ይህ የሚያነጻጽረው ወንዶች ከዘማዊት ሴት ጋር እንደሚተኙ በዚያው መንገድ ከእርሷ ጋር ማድረጋቸውን ነው። "ወንዶች ከዘማዊት ሴት ጋር እንደሚተኙበት መንገድ ከእርሷ ጋር ተኙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ እርሷ ሄዱ/ገቡ
"እርሷ ወደ ነበረችበት ስፍራ ሄዱ" ወይም "ወደ እርሷ ሄዱ"
በዚህ መንገድ ከኦሖላ እና ከኦሖሊባ ጋር ተኙ
"ከኦሖላ እና ከኦሖሊብ ጋር የተኙት እንደዚህ ነው"
ፍርድ ስጥ/አሳልፍ
ይህ ፈሊጥ ነው። "ኮንን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ደም ያፈሰሱ…ደም በእጃቸው አለ
ይህ ፈሊጥ ነው። "ሰዎችን የገደሉ…ነብሰ ገዳዮች" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 23:46
ሰዎችን አስነሳባቸው
"አስነሳባቸው" የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ብዙ ህዝብ ሰብስብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእነርሱ ላይ ደግሞም አሳልፈህ ስጣቸው
"በኢየሩሳሌም እና ሰማርያ ላይ ደግሞም አሳልፈህ ስጣቸው"
እነርሱን አሳልፈህ ስጣቸው
ያህዌ ለእነርሱ ጥበቃ ማድረጉን ትቷል ደግሞም ለመከራ አሳልፎ ሰጥቷቸዋል
እንዲሸበሩ እና ለዝርፊያ/እንዲዘረፉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች እንዲያሸብሯቸው እና እንዲዘርፏቸው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱን ቆርጦ መጣል
ይህ ፈሊጥ ነው። "እንዲገድሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 23:48
ስለዚህ እነርሱ የእናንተን…ያደርጋሉ
"ስለዚህም ሰዎቹ የእናንተን …ያደርጋሉ" እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሕዝቅኤል 23፡47 የተጠቀሱትን "ሰዎች" ነው።
ነውረኛ ባህሪሽን በአንቺ ላይ ያደርጉብሻል
ይህ ፈሊጥ ነው። "አሳፋሪ ባህሪሽ የሚያስከትልብሽ ጥፋት እንዲደርስብሽ ያደርጋሉ" ወይም "በአሳፋሪ ባህሪሽ ይቀጡሻል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የኃጢአታችሁን ዋጋ ከጣኦቶቻችሁ ጋር ተቀበሉ
"ከጣኦቶቻችሁ ጋር ኃጢአታችሁ የሚያስከትልባችሁን ሀላፊነት ተቀሉ።" ይህ የሚያመለክተው በኃጢአጣታቸው እንደሚቀጡ ነው። "ጣኦቶቻችሁን በማምለክ ለፈጸማችሁት ኃጢአት ቅጣታችሁን ተቀበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 24
Ezekiel 24:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ሕዝቅኤልን እንዲህ አለው/ተናገረው
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነብዩ ወይም ለህዝቡ አዲስ ነገርን ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በዘጠነኛው አመት
"በ9 ነኛው አመት።" ይህ የሚያመለክተው በንጉሥ ኢዮአቄም አገዛዝ ስር ለምን ያህል ጊዜ በስደት እንደቆዩ ነው። "በንጉሥ ኢዮአቄም ስደት በዘጠነኛው አመት" (ተከታታ ቁጥሮች እና (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ))
አስረኛው ወር፣ በወሩ በአስረኛው ቀን
"በአስረኛው ወር በወሩ በአስረኛው ቀን" ወይም "በ10ኛው ወር በ10ኛው ቀን።" ይህ በዕብራውያን ዘመን አቆጣጥር አስረኛው ወር ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)
የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር"
የባቢሎን ንጉሥ ከቧታል
የባቢሎን ሰራዊት የተገለጸው በመሪው ነው። "የባቢሎን ንጉሥ ሰራዊት ከቧታል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 24:3
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከ ሕዝቅኤል 24፡14 ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ አመጸኛ ቤት
ይህ በቤቱ ውስጥ ስለሚኖር ቤተሰብ፣ በዚህ ሁኔታ ለዘመናት የያዕቆብ ትውልድ ስለሆነው ስለ እስራኤል የተነገረ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 2፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ይህ አመጸኛ ህዝብ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ቅንጥብጣቢውን ምግብ ሰብስቡ
እዚህ ስፍራ "ምግብ" በተለይ የሚያመለክተው ስጋን ነው። "ቅንጥብጣቢውን ስጋ አስቀምጡ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ከመንጋው ምርጡን
እዚህ ስፍራ "መንጋ" የሚያመለክተው በጎችን ነው፣ የወፍ መንጋን አይደለም።
ከስሩ የአጥንት ክምር
በአንዳንድ ባህል ከእንጨት ይልቅ አጥንት ረጅም ጊዜ መንደድ ስለሚችል እሳት ውስጥ አጥንት ይጨምራሉ። ይህ የሚገልጸው ምርጥ የሆኑት አጥንቶች በማሰሮ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ውስጥ ከተጨመሩ በኋላ የሚቀሩትን አጥንቶች ነው። "የተቀሩትን አጥንቶች እሳቱን ለማቀጣጠል ከማሰሮው ስር ጨምር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:6

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከ ሕዝቅኤል 24፡14 ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የደም ከተማ

እዚህ ስፍራ "ደም" የሚያመለክተው "ግድያን" ነው። "የነብሰ ገዳዮች ከተማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ማብሰያ ማሰሮ

ያህዌ ኢየሩሳሌምን ከማብሰያ ማሰሮ ጋር ማነጻጸሩን ይቀጥላል። "እንደ ማብሰያ ማሰሮ ናት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዝገት

በብረት ላይ የሚገኝ ቀላ ያለ ነገር። ዝገት ብረትን በመብላት ቀስ በቀስ ያጠፋዋል።

ጥቂት በጥቂቱ ውሰድ

ያህዌ ይህንን ትዕዛዝ ለአንድ የተወሰነ ሰው አልሰጠም። ይህ በዚህ ዘይቤያዊ አነጋገር ለአንድ የተወሰነ ሰው ያልተሰጠ አጠቃላይ ትዕዛዝ ነው።

ዕጣ አትጣል፣ ሁሉንም አውጣ

ዕጣ መጣል/ማውጣት የትኛው ቁራጭ ስጋ እንደሚወጣ የመምረጫ መንገድ ነበር፣ ነገር ግን ያህዌ ሁሉም ቁርጥራጭ ስጋ እንዲወጣ ስለፈለገ ዕጣ መጣል አላስፈለገም።

Ezekiel 24:7

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከ ሕዝቅኤል 24፡14 ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሷ ደም በመሀሏ ነው

ይህ ማለት በኢየሩሳሌም የተገደሉት ሰዎች ደም እስከ አሁን በዚያ አለ። "ከእርሷ መሃል የተገደሉት ሰዎች ደም እስከ አሁን በዚያ አለ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሷ

"የእርሷ" የሚለው ቃል፣ በማብሰያ ማሰሮ የተገለጸችውን ኢየሩሳሌምን ያመለክታል

በአፈር እንዲሸፈን በመሬት ላይ አላፈሰሰችውም፣ ነገር ግን በጠፍጣፋው አለት ላይ አደረገችው

ይህ ኢየሩሳሌምን ሰዎችን እንደገደለች እና ደማቸውንም የት ማፍሰስ እንደመረጠች አድርጎ በሰውኛ ይገልጻታል። "የተገደሉት በጠፍጣፋ አለት ላይ እንጂ፣ ደማቸውን ሊደብቅ በሚችል በአፈር ላይ አልነበረም" ወይም "ደማቸው በጠፍጣፋ አለት ላይ እንጂ አፈር ሊሸፍነው በሚችለው ስፍራ ላይ አልፈሰሰም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰወኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠፍጣፋ አለት ላይ አፈሰሰችው

"ደማቸውን በገላጣ አለት ላይ አፈሰሰች"

ስለዚህም ቁጣዬን ለበቀል አነሳሳች

እዚህ ስፍራ ያህዌ ራሱ በኢየሩሳሌም ሰዎችን በገደሉ ላይ በቀልን ስለመውሰዱ ይናገራል። "እኔ ራሴ ተመልክቼ በቁጣዬ እበቀል ዘንድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም መሸፈን አይችል ዘንድ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ስለዚህም ምንም ይሸፍነው ዘንድ እንዳይችል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:9

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከ ሕዝቅኤል 24፡14 ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የደም ከተማ

እዚህ ስፍራ "ደም" የሚያመለክተው "ግድያን" ነው። "የነብሰ ገዳዮች ከተማ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የእንጨት ክምሩንም አበዛለሁ

የእንጨት ክምር ኢየሩሳሌምን በሚወክለው የማብሰያ ገንቦ ስር እንደሚገኝ ተጠቁሟል። "ከስርሽ በሚገኘው እሳት ከቀድሞ የበለጠ የእንጨት ክምር አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እሳቱን አንድድ

"እሳቱን ቆስቁስ"

አጥንቶቹ ይረሩ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አጥንቶቹን አቃጥል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:11

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከ ሕዝቅኤል 24፡14 ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

መለብለብ

የአንድን ነገር ገጽ/ላዩን ማቃጠል

በመሆኑም በላዩ የሚገኘው ንጹህ ያልሆነ ነገር ይቀልጣል፣ ዝገቱም በእሳቱ ይበላል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የሚገኝበትን ንጹህ ያልሆነ ነገር ማቅለጥ እና ዝገቱን በእሳት መብላት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መርከስ/ንጹህ አለመሆን

እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር ንጹህ አድርጎ የማይቆጥረው ወይም የረከሰ ሰው በአካል እንደቆሸሸ ተደርጎ ይገለጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የብረት ዝገት

ዝገት

ተበላ

ተቃጥሎ አለቀ

እርሷ ደከመች

እዚህ ስፍራ "እርሷ የሚለው ቃል የማብሰያ ገንቦን ያመለክታል። ይህች የማብሰያ ገንቦ በዘይቤ ኢየሩሳሌምን የምትወክል ናት። "ኢየሩሳሌም ደከመች" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልፋት

ከባድ ስራ

ነገር ግን ዝገቷ በእሳትም አለቀቃትም

"አለቀቃትም/ለቋት አልሄደም" የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ነገር ግን እሳቱ ዝገቷን ከእርሷ አቃጥሎ አላስወገደም" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:13

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከ ሕዝቅኤል 24፡14 ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣዬን በአንቺ ላይ እስካበርድ ድረስ

ይህ ያህዌ በቁጣው ህዝቡን እንደሚቀጣ እና ህዝቡን የሚቀጣው "ቁጣው" እንደሆነ አድርጎ ይገልጻል። "እናንተን ቀጥቼ እስካበቃ እና በእናንተ ላይ መቆጣቴን እስክጨርስ ድረስ" ወይም "እናንተን እስክቀጣ ድረስ እና በእናንተ ላይ መቆጣቴን እስካበቃ ድረስ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:14

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል በምሳሌ ኢየሩሳሌምን ስለሚወክል የማብሰያ ማሰሮ ይናገረዋል። ይህ ምሳሌ እስከዚህ ቁጥር መጨረሻ ድረስ ይቀጥላል። (ምሳሌዎች/በምሳሌ መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

አሊያም ይህን ከማድረግ አላርፍም/አላቆምም


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"አሊያም እናንተን ከመቅጣት አላርፍም።" እዚህ ስፍራ "ይህን" የሚለው የሚያመለክተው ያህዌ ህዝቡን መቅጣቱን ነው።

እንደ መንገድሽ እና እንደ ስራሽ ይከፍሉሻል/ይፈርዱብሻል

ይህ የሚገልጸው ያህዌ ህዝቡን የሚቀጣው/የሚፈርድባቸው በመንገዳቸው ምክንያት ሲሆን፤ "መንገዳቸው" ራሱ እንደሚፈርድባቸው አድርጎ ነው። "በተግባራችሁ እና በመንገዳችሁ እፈርድባችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ ያህዌ አዋጅ/ትዕዛዝ ነው

ያህዌ የተናገረውን እርግጠኝነት ለማጽናት በራሱ ይምላል/ በስሙ ይምላል። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህ ነው" ወይም "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:15

የያህዌ ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የዐይኖችህ መሻት ከ…

ይህ የሚያመለክተው የሕዝቅኤልን ሚስት ነው። ያህዌ ሕዝቅኤልን ሚስቱን በሚመለከትበት የሰውነቱ ክፍል ያመለክታል። "ከ…በጣም የምትወዳት፣ ሚስትህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክዲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በመቅሰፍት

"በበሽታ"

ማዘን ወይም ማልቀስ የለብህም፣ እምባህ መፍሰስ የለበትም

እነዚህ ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ይሰጣሉ፤ ትኩረት የሚሰጡት ሕዝቅኤል ሚስቱ በሞተች ጊዜ ማልቀስ እንደሌለበት ነው። "ማዘን ወይም ማልቀስ የለብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሞተው/ራሳው

ይህ የሚያመለክተው የሞተችውን ሚስቱን ነው። "የሞተችው ሚስትህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ጥምጥም

በጭንቅላት ላይ የሚጠቀለል ከረጅም ጨርቅ የተሰራ የራስ መሸፈኛ

ነጠላ ጫማ/ሰንደል

በቁርጭምጭሚት ዙሪያ ማሰሪያ ያለው የሚጫሙት ቀላል ጫማ።

የፊትህን ጽጉር/ጺምህን አትሸፍን

በእስራኤል ወንዶች ሀዘናቸውን ለመግለጽ ጺማቸውን ይላጫሉ፣ ከዚያም ጺማቸው መልሶ እስኪበቅል ድረስ ፊታቸውን ይሸፍናሉ። ያህዌ ሕዝቅኤልን ጺሙን እንዳይሸፍን አዘዘው፤ ይህም ሀዘኑን ለመግለጽ ጺሙን አለመላጨቱን ለማሳየት ነው። "ጺምህን በመሸፈን አታልቅስ" ወይም "ጺምህን በመላጨት እና በመሸፈን አትዘን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:18

በማለዳ/በጥዋት

"በማግስቱ ጠዋት"

Ezekiel 24:19

አጠቃላይ መረጃ፡

የእስራኤል ሰዎች ሕዝቅኤልን ይጠይቁታል፣ሕዝቅኤል ደግሞ ያህዌ ለእነርሱ የተናገረውን ይነግራቸዋል።

የያህዌ ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት

"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ሲሆን በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የያቆብ ትውልድ የሆኑትን እስራኤላውያንን ያመለክታል። ይህ በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ወገን ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ

እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚመጣው መረጃ ንቁ ሆነን እንድንጠብቅ ያደርጋል።

የነፍሳችሁ ኩራት… ቤተመቅደስን አረክሳለሁ - ደግሞም ልጆቻችሁ

"የነፍሳችሁ… ኩራት የሆነውን ቤተ መቅደሴን አረክሳለሁ። ልጆቻችሁ…"

የሃይላችሁ ኩራት

ይህ የሚገልጸው የቤተመቅደሱ ህንጻ ህዝቡ የሚኮራበት ነገር መሆኑን ነው። ይህ የተገለጸው ለኩራታቸው መነሻ ከመሆን አልፎ "ኩራታቸው" እንደሆነ ነው። "የምትመኩበት/የምትኮሩበት ህንጻ" ወይም "የብርቱ ኩራታችሁ ምክንያት/መገኛ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የዐይኖቻችሁ ምኞት

እዚህ ስፍራ ያህዌ ህዝቡን የገለጸው "በዐይኖቻቸው" ነው። "ዐይኖቻችሁን ልታሳርፉባቸው የምትወዷቸው ህንጻዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክዲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የነፍሳችሁ ናፍቆት

እዚህ ስፍራ ያህዌ ለውስጣዊ ስሜታቸው ትኩረት በመስጠት ህዝቡን የሚገልጸው "በነፍሳቸው" ነው። "በእርግጥ የምትወዱት ህንጻ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክዲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻችሁ… በሰይፍ ይወድቃሉ

ይህ ጠላቶቻቸውን በሰይፎቻቸው ይገልጻል። "ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻችሁ… በጦርነት ይገደላሉ" ወይም "ጠላቶቻችሁ ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻችሁን… በሰይፍ ይገድላሉ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:22

ትቀልጣላችሁ

እዚህ ስፍራ "መቅለጥ" የሚለው እየሟሸሹ መምጣትንና መሞትን የሚገልጽ ዘይቤ ነው። "በጣም ትከሳላችሁ ደግሞም ቀስ በቀስ ትሞታላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በኃጢአታችሁ/በበደላችሁ

ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር የእነዚህን ሰዎች ኃጢአት ይቅር እንደማይል ነው። "ኃጢአታችሁን ይቅር አልልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ማቃሰት

ይህ እርዳታ የሚፈልግ እና በብዙ ስቃይ ውስጥ የሚገኝ መናገር ያቃተው ሰው የሚያሰማው ድምጽ ነው።

ስለዚህም ሕዝቅኤል ለእናንተ ምልክት ይሆናል

እዚህ ስፍራ "ምልክት" የሚለው ቃል ለሚመለከቱት ሰዎች ልዩ ማስጠንቀቂያ የሚያስተላልፍን ነገር ያመለክታል። ያህዌ ስለ ሕዝቅኤል እና የሚወስዳቸውን እርምጃዎች እንደዚህ ማስጠንቀቂያ አድርጎ ይናገራል። ይህ ዘይቤ በሕዝቅኤል 12፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ስለዚህም ሕዝቅኤል ለእናንተ ማስጠንቀቂያ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 24:25

የምይዘው መቅደሳቸው

እዚህ ስፍራ ያህዌ ቤተመቅደሳቸውን መደምሰሱን እንደሚይዘው አንድ ሰው አድርጎ ይናገራል። "ቤተመቅደሳቸውን እኔ እደመስሰዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ደስታቸው እና ኩራታቸው የሆነውን

"ደስታ/ሀሴት" እና "ኩራት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች በስማዊ ሀረጎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ደስታ የሚያደርጉበት እና የሚኮሩበት/የሚመኩበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስደተኛ

በጦርነት ወይም በሌላ ጥፋት መከራ ምክንያት አገራቸውን ለቀው ለመሄድ የተገደዱ

አፎቻችሁ ይከፈታሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ሕዝቅኤል የተሰጠው መረዳት እና የመናገር ችሎታ በአፉ መከፈት ተገልጾዋል። "እኔ አፍህን እከፍተዋለሁ" ወይም "መናገር የሚገባህን ታውቃለህ" ወይም "ምን መናገር እንዳለብህ እንድታውቅ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

አንተ ትናገራለህ - ከእንግዲህ ወዲያ ዝም አትልም

እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ሕዝቅኤል ይናገራል የሚለውን ይገልጻሉ። መናገሩ እንደማይቀር ትኩረት ለመስጠት በሁለተኛው ሀረግ በአሉታ ተገልጾዋል። (ምጸት/ላይዶክስ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ ምልክት ትሆናለህ

እዚህ ስፍራ "ምልክት" የሚለው ቃል ለሚመለከቱት ልዩ ማስጠንቀቂያ እንደሚያስተላልፍ ያመለክታል። ያህዌ ሕዝቅኤልን እና ድርጊቱን እንደዚህ ማስጠንቀቂያ አድርጎ ይናገራል። ይህ ዘይቤ በሕዝቅኤል12፡6 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "አንተ ለእነርሱ ማስጠንቀቂያ ትሆናለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ

ያህዌ ይህንን ሲናገር ሰዎች እርሱ ያህዌ እንደሆነ ያውቃሉ፤ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

## Chapter 25

### Ezekiel 25:1

የያህዌ ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ

"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ወደ አሞን ሰዎች ፊትህን አዙር

አሞን ሩቅ ስፍራ ነበር፣ ስለዚህ ሕዝቅኤል በዚያ የሚገኙ ሰዎችን ማየት አይችልም፣ ነገር ግን ወደዚያ አቅጣጫ መመልከት ያንን ህዝብ የመጉዳት ምልክት ይሆናል። በሕዝቅኤል 6፡2 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ አሞን ህዝብ ዞረህ ተመልከት" ወይም "በዚያ ያለው ህዝብ ጥፋት እንዲደርስበት ወደ አሞን አቅጣጫ ተመልከት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/መልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

የአሞን ህዝብ

"የአሞን ትውልድ" ወይም "በአሞን ምድር የሚኖሩ"

በእነርሱ ላይ ትንቢት ተናገር

"በእነርሱ ላይ ስለሚደርስባቸው ክፉ ነገሮች ትንቢት መናገር።" ይህ ማለት በአሞን ሰዎች ላይ ስለሚደርስ አስከፊ/አስጨናቂ ነገሮች ትንቢት መናገር ማለት ነው። በሕዝቅኤል 4፡7 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

### Ezekiel 25:3

አጠቃላይ መረጃ፡

ለአሞን ሰዎች ምን መናገር እንዳለበት ያህዌ ለሕዝቅኤል ይነግረዋል።

የጌታ የያህዌን ቃል ስሙ

"ይህን ከጌታ ያህዌ ዘንድ የመጣ መልክዕክት ስሙ"

እናንተ፣ "አሃ!" ብላችኋል

"አዳንቃችኋል።" እዚህ ስፍራ "አሃ" የሚለው ቃል ሰዎች በአንዳች ነገር ደስ ሲሰኙ የሚያሰሙት ነው። በዚህ ሁኔታ ሰዎች ደስ የተሰኙት በእስራኤል እና ይሁዳ ላይ ክፉ ነገር ስለደረሰ ነው።

መቅደሴ በረከሰ ጊዜ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የጠላት ሰራዊት ባረከሰው ጊዜ በመቅደሴ ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድሪቱን በመቃወም ...ቤቱን በመቃወም

"በምድሪቱ ላይ.. በቤቱ ላይ"

የይሁዳ ቤት

"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የይሁዳ ትውልድ የሆኑትን ያመለክታል። ይህ በሕዝቅኤል 3፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የይሁዳ ወገን ህዝብ" ወይም "የይሁዳ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ

"ተመልከቱ" ወይም "ቀጥሎ ለምናገረው ትኩረት ስጡ"

በምስራቅ ለሚኖሩ ሰዎች ርስታቸው አድርጌ እሰጣችኋለሁ

ይህ የሚናገረው የአሞንን ምድር የሚወረው እና የምድሪቱን ሀብት እንደዚሁም በላይዋ የሚገኘውን ነገር ሁሉ የሚወስደው የጠላት ሰራዊት የአሞንን ህዝብ ርስቱ አድርጎ እንደወሰደ እንደሚቆጠር አድርጎ ነው። እዚህ ስፍራ የጠላት ሰራዊት የአሞንን ህዝብ ባሪያ እንደሚያደርግ አያመለክትም። "ከእናንተ በስተ ምስራቅ የሚመጣ ሰራዊት እንዲወራችሁ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእናንተ ላይ ይሰፍራሉ፤ ደግሞም በመሃላችሁ ድንኳናቸውን ይጥላል

"ድንኳን ጥለው በአገራችሁ ይኖራሉ"

የምድራችሁን ፍራፍሬ ይበላሉ፤ ወተታችሁንም ይጠጣሉ

የፍራፍሬውን እና ወተቱን መገኛ ለይቶ መናገር ሊጠቅም ይችላል። "ከዛፎቻችሁ ፍሬዎችን ይበላሉ የከብቶቻችሁን ወተት ይጠጣሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የአሞን ሰዎች የመንጋ መሰማሪያ

እዚህ ስፍራ "የአሞን ሰዎች" የሚለው የሚያመለክተው የአሞን ሰዎችን ምድር ነው። እንደዚሁም በዚህ ሀረግ መነሻ ላይ በውስጠ ታዋቂነት የሚገኘው መረጃ ሊጨመር ይችላል። "የቀረውን የአሞን ሰዎች ምድር የመንጋ መሰማሪያ አደርገዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና የተዘለለ/የተተወ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ

ያህዌ ይህንን ሲናገር ሰዎች እርሱ ያህዌ እንደሆነ ያውቃሉ፤ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

### Ezekiel 25:6

እጃችሁን አጨብጭባችኋል፣ በእግራችሁም መሬቱን መትታችኋል/ደቅታችኋል

እነዚህ ድርጊቶች ብርቱ ስሜትን መግለጫ ናቸው። በዚህ ሁኔታ ሰዎቹ ተደስተዋል በእስራኤል ላይ ያላቸውን ንቀትም አሳይተዋል። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጣችሁ በእስራኤል ላይ ያለ ንቀት በሙሉ

እዚህ ስፍራ "የእስራኤል ምድር" የሚለው ሀረግ የሚገልጸው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "በእስራኤል በሚኖሩ ሰዎች ላይ ያላችሁ ጥላቻ ሁሉ" በሚለው ውስጥ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና የተዘለለ/የተተወ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነሆ

"ተመልከቱ" ወይም "ቀጥሎ ለምናገረው ትኩረት ስጡ"

በእጄ እኔ እመታችኋለሁ

"በሀይለኛው እጄ እኔ እመታችኋለሁ" እዚህ ስፍራ ያህዌ ህዝቡን በቀጥታ በእጁ እንደሚመታቸው አድርጎ ይናገራል። "እኔ እቀጣችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተን ለህዝብ/አገራት ዝርፊያ አድርጌ እሰጣችኋለሁ

"እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአሞን ሰዎችን ሲሆን ነገር ግን ለምድራቸው እና ሀብታቸውም ደግሞ ሜቶኖሚ/ ነው። "ጠላት እንደያሸንፋችሁ ደግሞም ምድራችሁን እና ሀብታችሁን እንዲዘርፍ አደርጋለሁ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተን ከህዝቡ እለያለሁ... ከአገራት መሃል እንድጥጠፉ አደርጋለሁ

በመሰረቱ እነዚህ ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው ፤ ከእንግዲህ አገር ሆነው እንደማይቀጥሉ እና ያህዌ የአሞንን ሰዎች ሙሉ ለሙሉ እንደሚያጠፋ ትኩረት ይሰጣሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 25:8

ሞአብ እና ሴይር

እነዚህ ስፍራዎች በውስጣቸው የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታሉ። "የሞአብ እና ሴይር ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ ተመልከቱ! የይሁዳ ቤት እንደ...ነው

"የይሁዳን ቤት ተመልከቱ። እንደ...ነው"

የይሁዳ ቤት...ነው

"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የይሁዳ ትውልድ የሆኑትን ያመለክታል። ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የይሁዳ ወገን ህዝብ" ወይም "የይሁዳ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ! እኔ እከፍታለሁ

"ተመልከት! እኔ እከፍታለሁ" ወይም "ስማ! እኔ እከፍታለሁ" ወይም "ቀጥሎ ለምናገረው ትኩረት ስጥ! እኔ እከፍታለሁ"

ከከተማው ዳርቻ ጀምሬ፣ የሞአብን ቁልቁለቶች እከፍታለሁ

ይህ ማለት እርሱ ሞአብን ራሷን ለማጥቃት በመጀመሪያ ለታደሮች መንገዱን ለመጥረግ በሞአብ ዳርቻ የሚገኙ ከተሞችን ያጠፋል። "በድንበሮቿ የሚገኙ ከተሞችን በማጥፋት/በመደምሰስ ወደ ሞአብ የሚወስደውን ጥርጊያ እከፍታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእርሱ ከተሞች በመጀመር

እዚህ ስፍራ የሞአብ ከተማ የተነገረው ወንዴ በሆነ ተውላጠ ስም "የእርሱ" በሚለው ነው። "በእርሱ ከተሞች በመጀመር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የቤት የሺሞት፣ በአልሜዎን፣ እና ቂርያትይም

"ከታላቂቆቹ ከተሞች ከቤት የሺሞት፣ አልሜዎን፣ እና ቂርያትይም እጀምራለሁ።" እነዚህ ሶስት ስፍራዎች ከተሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በአሞን ህዝቦች ላይ የተነሱትን የምስራቅ ሰዎች

"አሞንን ያጠቁትን ከምስራቅ ሰዎች የሆኑትን እነዚያኑ ሰራዊት እልካለሁ"

እነርሱን እንደ ንብረት/ሃብት አድርጌ እሰጣለሁ

እዚህ ስፍራ ያህዌ አሞንን ከምስራቅ ለመጣው ሰራዊት እንደ ንብረት አድርጎ አሳልፎ እንደ ሰጠ ይናገራል። "ሰራዊት እነርሱን እንዲይዝ እፈቅዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም አሞን ሰዎች በአገራት መሃል መታሰቢያ አይኖራቸውም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ስለዚህም አገራት የአሞንን ሰዎች አያስታውሱም/ይረሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 25:12

ኤዶም ተቀብሏል

እዚህ ስፍራ "ኤዶም" የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "የኤዶም ሰዎች ተቀብለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት

"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመናት የይሁዳ ትውልድ የሆኑትን ያመለክታል። ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የይሁዳ ወገን ህዝብ" ወይም "የይሁዳ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ኤዶምን በእጄ እመታለሁ

እዚህ ስፍራ ያህዌ ህዝቡን በቀጥታ በእጁ እንደሚመታ አድርጎ ይናገራል። ተመሳሳይ ሆነው ሀረግ በሕዝቅኤል 25:7 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ ኤዶምን እቀጣለሁ። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከቴምና ጀምሮ እስከ ድዳን...አጠፋቸዋለሁ

"ኤዶምን ከቴምና እስከ ድዳን...አጠፋለሁ።" እነዚህ በኤዶም ሁለት ጫፎች በተቃራኒ አቅጣጫ የሚገኙ ከተሞች ናቸው። ይህ ማለት ያህዌ መላዋን ኤዶምን ያጠፋታል ማለት ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ ይወድቃሉ

"መውደቅ" የሚለው ቃል የሚወክለው መገደልን ሲሆን "ሰይፍ" የሚለው በጦርነት የሚያጠፏቸውን ጠላቶቻቸውን ያመለክታል። "ጠላቶቻቸው በሰይፍ ይገድሏቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 25:14

በቀሌን በኤዶም ላይ በህዝቤ በእስራኤል አማካይነት አወርድባቸዋለሁ

እዚህ ስፍራ የእስራኤል "እጅ" የሚለው የእስራኤልን ሰራዊት የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ያህዌ በኤዶም ህዝብ ላይ በቀል ስለመፈጸም የሚናገረው እንደ ብርድልብስ ሆኖ ቁጣው እንደሚሸፍናቸው አድርጎ ነው። "በቀል" የሚለው ረቂቅ ስም "ቀጣ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ህዝቤ እስራኤል የኤዶምን ህዝብ እንዲቀጣ እጠቀምበታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በኤዶም ላይ እንደ ቁጣዬ እና ሀይሌ ያደርጉባቸዋል

"ለኤዶማውያን ቁጣዬን እና ሀይሌን ያሳያሉ" ወይም "ኤዶማውያንን እንደ ቁጣዬ እና ሀይሌ ይቀጧቸዋል"

ቁጣዬ እና ሀይሌ

"ሀይል/ንዴት" የሚለው ቃል በመሰረቱ "ቁጣ" የሚለውን ተመሳሳይ ነገር አጠናክሮ ይገልጻል። "ሀይሌ እና ቁጣዬ" ወይም "እጅግ ከፍ ያለው ቁጣዬ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በቀሌን ያውቃሉ

"በቀል" የሚለው ረቂቅ ስም "ቀጣ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "የኤዶም ሰዎች እኔ እንደቀጣኋቸው ያውቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 25:15

ፍልስጤማውያን በክፋት ተነስተው በቀል ፈጸሙ፤ ደግሞም ከራሳቸው ውስጥ ይሁዳን ደጋግመው ለማጥፋት ሞከሩ

"ከራሳቸው ውስጥ" የሚለው አገልለጽ ፈሊጣዊ ነው። "ፍልስጤማውያን ይሁዳን ስለሚጠሉ በራሳቸው ሀይል ደጋግመው ሊያጠፏቸው ሞከሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳን ለማጥፋት

እዚህ ስፍራ "ይሁዳ" የሚለው የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "ዛሬ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የይሁዳ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ

ይህ አንባቢው ቀጥሎ ለሚመጣው ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ይነግረዋል። "ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ልነግራችሁ ላለው ነገር ትኩረት ስጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በፍልስጤማውያን ላይ እጄን እዘረጋለሁ

እዚህ ስፍራ የያህዌ ሀይል የተወከለው በእርሱ "እጅ" ነው። "ሀይለኛው እጄን በፍልስጤማውያን ላይ አዞራለሁ" ወይም "ታላቁን ሀይሌን በፍልስጤማውያን ላይ አዞራለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እቆርጣለሁ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "እኔ እደመስሳለሁ" ወይም "እኔ አስወግዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከሊታውያን

ፍልስጤም ውስጥ በከሊታ ከተማ የሚኖሩ ሰዎች (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

---

## Chapter 26

### Ezekiel 26:1

በአስራ አንደኛው አመት

"በ11ኛው አመት።" ይህ ማለት ንጉሥ ኢዮአቄም በምርኮ ወደ ባቢሎን ከተወሰደ ከአስራ አንድ አመት በኋላ ማለት ነው። "ከንጉሥ ኢዮአቄም ስደት፣ በአስራ አንደኛ አመት" (ተከታታይ ቁጥር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በወሩ የመጀመሪያ ቀን

"በወሩ 1ኛ ቀን።" ሕዝቅኤል በዕብራዊያን የወር አቆጣጠር የትኛው ወር ማለቱ እንደሆነ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ

"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ጢሮስ ኢየሩሳሌምን በመቃወም ተናግሯል

እዚህ ስፍራ "ጢሮስ" እና "ኢየሩሳሌም" የሚሉት የከተማ ስሞች በእነዚያ ከተሞች ነዋሪዎች የሆኑ ሰዎችን ይወክላል። "የጢሮስ ሰዎች ጠኢየሩሳሌምን ሰዎች በመቃወም ተናገሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አሃ!

"አሃ" የሚለው ቃል ሰዎች አንዳች ነገር ሲያገኙ የሚያሰሙት ድምጽ ነው። "አዎን" ወይም "ይህስ ታላቅ ነገር ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

የህዝብ መግቢያ በሮች ተሰበሩ

የጢሮስ ሰዎች እነዚህን ቃላት የተጠቀሙት ኢየሩሳሌም በዙሪያዋ የሚገኙ አገራት ነጋዴች የሚያልፉባት ከተማ በር እንደሆነች ለመግለጽ ነው። ይህ በአድራጊ አረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰራዊቶች የህዝብ መግቢ በሮችን ደረመሱ/ደመሰሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እርሷ ፊቷን ወደ እኔ መለሰች

እዚህ ስፍራ "እርሷ" የሚለው ቃል በማጠፊያዎቻቸው ወደ ጢሮስ ለመክፈት "የዞሩትን" የከተማይቱን "በሮች" የሚለውን ቃል ያመለክታል። የዚህ ሀረግ ትርጉም አሁን ጢሮስ ኢየሩሳሌምን ተክታ የብዙ አገራት ነጋዴዎች በውስጧ የሚተላለፉባት ከተማ ሆነች ማለት ነው። "በሮቹ ለእኔ ተከፈቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ እጠግባለሁ/እሞላለሁ

እዚህ ስፍራ "መጥገብ/መሞላት" የሚለው የሚገልጸው መበልጸግን ነው። "እኔ እበለጽጋለሁ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሷ ፈረሰች

"ኢየሩሳሌም ፈረሰች"

### Ezekiel 26:3

እነሆ

"አድምጡ" ወይም "ልነግራችሁ ላለው ነገር ትኩረት ስጡ!"

በባህር ላይ እንደሚነሳ ማዕበል ብዙ አገራትን በእናንተ ላይ አስነሳለሁ

እዚህ ስፍራ "አገራት" የሚለው ቃል ጠላቶቻቸውን ያመለክታል። "በማዕበል እንደሚናወጥ ባህር ከተለያዩ አገራት በእናንተ ላይ ሰራዊት አስነስቼ እንዲመጧችሁ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከላይዋ አቧራዋን ጠርጌ እንደተጋለጠ አለት አደርጋታለሁ

ያህዌ እንዴት ጢሮስን ሙሉ ለሙሉ እንደ ሚደመስስ ይናገራል። "ሰራዊት ሙሉ ለሙሉ ከተማይቱን እንዲደመስስ እና በዚያ አንዳች እንዳያስቀሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

### Ezekiel 26:5

አያያዥ ሀሳብ

"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"

እርሷ ትመጣለች

የጢሮስ ከተማ እዚህ ቦታ የተነገረችው ሴት እንደሆነች ተደርጎ ነው። "ጢሮስ ትመጣለች" ወይም "እርሷ ትመጣለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በባህሩ መሃል መረብ የማድረቂያ ስፍራ

የጢሮስ ከፊሉ ስፍራ ደሴት ነበር። ይህ አገላለጽ በጢሮስ ላይ ጥፋት ያስከተለውን የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የአሳ ማጥመጃ መረቦችን ለማድረቂያ የሚያገለግል ባዶ ደሴት" ወይም "ሰው የማይኖርበት ሰዎች አሳ ማጥመጃ መረባቸውን የሚያደርቁበት ደሴት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ለአገራት ዝርፊያ/ብዝበዛ ትሆናለች

"ዝርፊያ" ማለት ሰዎች ሰርቀው ወይም በሃይል የሚወስዷቸው ነገሮች ማለት ነው። እዚህ ስፍራ ጢሮስ ተዘረፈች የሚለው የሚወክለው ሀብቷ በሌሎች አገራት መወሰዱን የሚገልጽ ነው። "የአገራት ሰራዊቶች ከጢሮስ ውድ የሆኑ ሀብቶቿን ሁሉ ይወስዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በሜዳ ያሉ ልጃችዋ ሁሉ በሰይፍ ይታረዳሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የጠላት ሰራዊቶች በሜዳዎች ያሉ ልጃችዋን በሰይፍ ያርዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሜዳ ያሉ ሴት ልጃችዋ

x

### Ezekiel 26:7

አያያዥ ሀሳብ

"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"

እነሆ

"ተመልከቱ" ወይም "አድምጡ" ወይም "ልነግራችሁ ላለው ነገር ትኩረት ስጡ!"

የነገሥታት ንጉሥ፣ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር

"የነገሥታት ንጉሥ" የሚለው ሀረግ እርሱ ሌሎች ነገስታት ሁሉ የሚታዘዙት ከነገሥታቱ በላይ ታላቅ እንደሆነ የሚያሳይ ማዕረግ ነበር። "ታላቁ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት

እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በብዙ ህዝብ ላይ ታላቅ
ይህ የሚያጎላው የናቡከደነጾርን ሰራዊት ብዛት ነው
እርሱ ይፈጃል
እዚህ ስፍራ "እሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ናቡከደነጾርን ሲሆን ለእርሱ ሰራዊት ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የእርሱ ሰራዊት ይገድላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የእናንተ ሴቶች ልጆች በመስክ ውስጥ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "የእናንተ ሴቶች ልጆች" የሚያመለክተው በመስክ የሚሰሩትን የጢሮስን ወጣት ሴቶች ወይም 2) "የእናንተ ሴቶች ልጆች" የሚለው የጢሮስን ዋና ከተማ ለሚደግፉ በአቅራቢያ ለሚገኙ ከተሞች እና መንደሮች የዋለ ሜቶናሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። በሕዝቅኤል 26፡6 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በደሴቱ ዳርቻ ባለው መሬት የሚገኙ ሴቶች ልጆቻችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 26:9

አያያዥ ሀሳብ
"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"
አጠቃላይ መረጃ፡
በዚህ ሀረግ "እርሱ" እና "የእርሱ" የሚሉት ቃላት ይህ ድርጊት የሚፈጽሙትን የባቢሎንን ንጉሥ ናቡከደነጾርን እና በናቡከደነጾር ሰራዊት ውስጥ የሚገኙ ወታደሮችን ያመለክታሉ። "የእናንተ" የሚለው ቃል ጢሮስ ከተማን ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በግድግዳ ማፍረሻ ቅጥራችሁን ያፈርሳል፣ መዶሻውም/መሳሪያ ማማችሁን ያደቃል
ምንም እንኳን ግድግዳ ማፍረሻ እና መዶሻው/መሳሪያ የጢሮስን ቅጥር እና ማማ እንደሚያፈርስ ተደርጎ ቢነገርም፣ የናቡከደነጾር ወታደሮች ቅጥሮችንና ማማዎችን ለማፍረስ ይጠቀሙባቸው ነበር። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ግድግዳ ማፍረሻ መሳሪያ
"ግድግዳ ማፍረሻ" በሰራዊት ውስጥ የሚገኙ ብዙ ወንዶች ቅጥሮችን ወይም በሮችን ሰብረው ወደ ውስጥ ለመግባት የሚይዟቸው ትላልቅ እንጨቶች ወይም ግንዶች ናቸው።
መሳሪያዎች/መዶሻ
ከብረት የተሰራ ማማዎችን ለማፍረስ የሚያገለግል መሳሪያ/መዶሻ
ወደ በራችሁ ሲገባ፣ ቅጥራቸው ወደ ፈረሰባቸው ሰዎች ከተማ እንደሚገቡ ወንዶች ሆኖ ይገባል
እዚህ ስፍራ ያህዌ የናቡደነጾር ሰራዊት ወደ ጢሮስ ከተማ የሚገባበትን ሁኔታ የገለጸው በተነጻጻሪ ዘይቤ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቅጥሮቻቸው የፈረሱባቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ቅጥሮቿን ካፈረሱ በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 26:12

አያያዥ ሀሳብ
"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል" በዚህ ሀረግ "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በናቡከደነጾር ሰራዊት ውስጥ የሚገኙ ወታደሮችን ነው። "የእናንተ" እና "እናንተ" የሚለው የሚያመለክተው የጢሮስ ከተማን ነው።
ሃብታችሁን እና ሸቀጣሸቀጣችሁን ይቀማሉ ይዘርፋሉ
"ሃብታችሁን ይዘርፋሉ" እና "እና ሸቀጣሸቀጣችሁን ይቀማሉ" የሚሉት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የተደጋገሙት ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቅንጦት
ውድ እና ምቾት የሚሰጥ
ድንጋዮቻችሁ/የድንጋይ ፍርስራሻችሁ፣ ሳንቃዎቻችሁ፣ እና ሸክላዎቻችሁ
ይህ የሚያመለክተው ቅጥሮች እና ቤቶች ከፈራረሱ በኋላ የሚቀረውን ነው
በውሃ ውስጥ
"በባህር"
የበገናችሁ ድምጽ ከእንግዲህ አይሰማም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከእንግዲህ በገናችሁ አይሰማም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በገላጣ ሜዳ ላይ እንደሚገኝ አለት አደርጋችኋለሁ
ይህ ዘይቤ የሚገልጸው ያህዌ ጢሮስን ከደመሰሰ በኋላ የሚሆነውን ነው። በሕዝቅኤል 26፡4 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የአሳ መረብ ለመድረቅ የሚሰጣበትን ቦታ ትሆናላችሁ
ይህኛውም ዘይቤ ያህዌ ጢሮስን ካጠፋ በኋላ ውጤቱን ይገልጻል። በሕዝቅኤል 26፡5 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መረቦች.... ስፍራ ትሆናላችሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መረቦች... ስፍራ አደርጋችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 26:15

አያያዥ ሀሳብ
"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"
ደሴቲቱ... በመሃላችሁ አንቀጠቀጥምን?
ይህ ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ይጠብቃል፤ ደግሞም የጢሮስን ውድመት አጉልቶ ያሳያል። ይህ በዐረፍተ ነገር መልል ሊተረጎም ይችላል።"ደሴቲቱ በመሃላችሁ... ትንቀጠቀጣለች።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ደሴቶቹ አይንቀጠቀጡምን
እዚህ ስፍራ "ደሴቶቹ" የሚለው የሚወክለው በደሴቶቹ የሚኖሩ ሰዎችን ነው።"በደሴቶቹ የሚኖሩ ሰዎች በፍርሃት አይንቀጠቀጡምን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የባህሩ ልዑላን
"የባህሩ ዳርቻዎች ልዑላን"
እየተንቀጠቀጡ ይለብሳሉ
ይህ ዘይቤ ልዑላኑ ፍርሃትን ልብሳቸው ያደረጉት ይመስል በፍርሃት መንቀጥቀጣቸውን ይገልጻል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእናንተ ምክንያት ይደነግጣሉ
"በእናንተ ላይ ከደረሰው ክፉ ነገር የተነሳ መናገር ይሳናቸዋል"

Ezekiel 26:17

አያያዥ ሀሳብ፡
"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"
አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ሀረጎች፣ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው "የባህሩን ዳርቻ ልዑላን" ሲሆን በቀደመው ሀረግ ደግሞም "እናንተ" የሚለው ጢሮስን ያመለክታል።
"ድምጽን ማሰማት"
"መዘመር"
በመርከበኞች የተያዛችሁት እናንተ እንዴት እንደተደመሰሳችሁ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በመርከበኞች የተያዛችሁትን - እናንተን ¬እንዴት ጠላቶቻችሁ እንዳጠፏችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በአካባቢያቸው በሚኖሩ ላይ ሁሉ ስለ ራሳቸው ሽብር ያሰራጫሉ
"ሽብር" የሚለው ረቂቅ ስም "መሸበር" በሚለው ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "በዚሪያቸው ያሉ ሰዎች ሁሉ እንዲሸበሩ አደረጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
በውድቀታችሁ ቀናት የባህር ዳርቻዎቹ ይናወጣሉ። የባህሩ ደሴቶች በስፍራችሁ ከመጥፋታችሁ የተነሳ በፍርሃት ይዋጣሉ
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች በትረጉም ተመሳሳይ ናቸው፤ ደግሞም በጢሮስ ጥፋት በዙሪያ ያሉ ሰዎች የሚያሳዩትን ምላሽ ያጎላሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የባህር ዳርቻዎቹ ይናወጣሉ
እዚህ ስፍራ "የባህር ዳርቻ" የሚለው የሚወክለው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "የባህሩ ዳርቻ ነዋሪዎች ተናወጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከእንግዲህ በስፍራችሁ አትገኙም
የጢሮስ ጥፋት እንደ ሰው ሞት ሆኖ ተገልጽዋል። " እናንተ ጠፍታችኋል" ወይም

"ከእንግዲህ በህይወት አትቀጥሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 26:19

አያያዥ ሀሳብ፡

"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"

እኔ አንቺን ሳበጅህ

እዚህ ስፍራ "አንቺ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጢሮስ ከተማን ነው። በተጻፈበት ቋንቋ "አንቺ" የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ሴቴ ጾታን ያመለክታል።

እንደ ሌሎች ሰው የማይኖርባቸው ከተሞች ሳደርግሽ

እዚህ ስፍራ ጢሮስ ከሌሎች ሰው ከማይኖርባቸው ከተሞች ጋር ተነጻጽራለች። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጥልቆቹ

እዚህ ስፍራ "ጥልቆቹ" ማለት የባህር ጥልቅ ውሃ ማለት ነው። "ጥልቅ ውሃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽሎች የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ጥንቱ ጊዜ ፍርስራሽ በምድር ዝቅተኛ ስፍራ እንድትኖሪ፣ ወደ ጉድጓድ እንደሰመጡት እንደ ጥንት ዘመን ህዝብ ዝቅ አደርግሻለሁ

ያህዌ በጢሮስ ላይ የሚያደርሰው ወደ መቃብር ከወረዱ ሰዎች ጋር እና ከፈራረሱ ከተሞች ጋር ተነጻጽሯል። (ሰውኛ ዘይቤ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጉድጓድ

ይህ ከመቃብር ጋር ይነጻጸራል። ምክንያቱም መቃብር ወደ ሙታን ዓለም መግቢ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ እንደዚሁም ደግሞ ጉድጓድ ያንን ዓለም ይወክላል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በህያዋን ምድር መቆም

ይህ የሚወክለው የከተማይቱን የቀደመ መልክ መታደስ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንቺ ላይ ጥፋት አመጣለሁ

"ጥፋት" የሚለው ረቂቅ ስም "አሳዛኝ" በሚለው ቅጽል ወይም "ደመሰሰ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ፍጻሜሽን አሳዛኝ አደርገዋለሁ" ወይም "እኔ አንቺን እደመስሳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ በኋላ ዳግም ህልውና የምታገኚ አትሆኝም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ይፈልጉሻል ነገር ግን ፈጽሞውኑ ዳግም ሊያዩሽ/ሊያገኙሽ አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልቱ)

---

## Chapter 27

Ezekiel 27:1

የያህዌ ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የነገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ

"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የእንጉርጉሮ እርዳታ

"እንጉርጉሮ" የሚለው ይህ ረቂቅ ስም "ለቅሶ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። "አልቃሽ መሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ለጢሮስ እንዲህ በል

እዚህ ስፍራ "ጢሮስ" የሚለው ቃል በጢሮስ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። "ለጢሮስ ሰዎች እንዲህ በላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በባህሩ መግቢያ በሮች ለሚኖሩ

"በባህሩ በሮች ለሚኖሩ" ወይም "በባህሩ መግቢያ ለሚኖሩ"

ጢሮስ ሆይ፣ እንዲህ ብለሻል

እዚህ ስፍራ "ጢሮስ" የሚለው ቃል በጢሮስ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል። "የጢሮስ ሰዎች፣ እንዲህ ብላችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ በውበት ፍጹም ነኝ

"ውበት" የሚለው ረቂቅ ስም "ውብ" በሚለው ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። "እኔ ፍጹም ውብ ነኝ" ወይም "ሙሉ ለሙሉ/እንከን የለሽ ውብ ነኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 27:4

አያያዥ ሀሳብ፡

"ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል"

አጠቃላይ መረጃ፡

በእነዚህ ሀረጋት "የአንቺ" እና "አንቺ" የሚሉት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

አጠቃላይ መረጃ፡

የጢሮስ ከተማ እዚህ ስፍራ እና በተከታዮቹ ጥቅሶች የተገለጸችው ውብ መርከብ ተደርጋ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደቦችሽ

"ድንበሮችሽ"

የባህር ልብ

"የባህር መሃል"

ሳንቃ/ጣውላ

ረጅም፣ ጠፍጣፋ እንጨት፣ ወፍራን ሳንቃ

መስቀያ

የመርከብ ሸራ የሚይዙ በመርከብላ ላይ የሚገኙ ብዙ ሰዎች

Ezekiel 27:6

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል። የጢሮስ ከተማ ውብ መርከብ እንደሆነች ተደርጎ መብራራቱ ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡

በእነዚህ ሀረጋት "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው ጢሮስን የሚገነቡትን ነው። "የአንቺ" የሚለው ጢሮስን ያመለክታል።

የጀልባ መቅዘፊያዎች

ሰዎች ጀልባ ለመቅዘፍ የሚገለገሉበት ረጅም የሆነ በአንድ ጫፉ ጠፍጣፋነት ያለው እንጨት።

የጀልባ ወለል

ሰዎች ሊራመዱበት የሚችሉት የጀልባዋ ክፍል

እነርሱን ይሸፍናሉ

"ይሸፍኗቸዋል"

ከዝሆን ጥርስ

ነጭ፣ ውብ፣ እና ጠንካራ ከእንስሳ ጥርስ የተሰራ ነገር

የመርከብ ሸራ

ረጅም የሆነ ነፋስ መርከቧን እንዲያንቀሳቅስ የሚያደርግ ሸራ

የመርከቦችሽ ሸራ ቀለማቸው ውብ የሆኑ ከግብጽ በመጣ የሀር ጨርቅ ነው

የመርከቦች ሸራ ከጢሮስ አርማ ወይም ባንዲራ ጋር ተነጻጽሯል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመለከቱ)

Ezekiel 27:8

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል። የጢሮስ ከተማ ውብ መርከብ እንደሆነች ተደርጎ መብራራቱ ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡

"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

አራድ

ይህ ስም የሲዶና አስተኛ የባርህ ዳርቻ ስያሜ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የጢሮስ ጠቢባን

"የጢሮስ አዋቂዎች"

መርከበኛ/መርከብ መሪ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የመርከብ መሪ መርከቢቱ ወደምትሄድበት ስፍራ እየተቆጣጠረ የሚነዳ ሰው ነው
ባይብሎስ
ይህ የሶሪያ ባህር ዳርቻ የሆነች ከተማ ስያሜ ነው። ሌሎች ቅጂዎች ጌባል ብለው ይጠሯታል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ እና የቅጂ ልዩነቶች የሚሉትን ይመልከቱ)
መገጣጠሚያሽን ደፈኑ
"ስንጥቅሽን ጠገኑ" ወይም "ሽንቁርሽን ጠገኑ"
መርከበኞች
መርከበኛ በመርከብ ላይ ከሚሰሩ ሰዎች አንደኛው ነው
Ezekiel 27:10
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡
"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።
ፋርስ፣ ሉድ… ሊቢያ…አራድ…ሔሌክ…ገማድ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንቺ የጦር ሰዎች
"በአንቺ ጦር የሚዋጉ ወንዶች" ወይም "ጦረኞችሽ/ሰራዊትሽ ሆነው የሚያገለግሉ"
ድምቀትሽ/ሞገስሽ የሆኑ
"ድምቀት" የሚለው ረቂቅ ስም "መድመቅ" በሚለው ቅጽል ተተክቶ ሊተረጎም ይችላል። "እንደምን ድምቀት/ሞገስ ነበረሽ" ወይም "ምንኛ ግርማ ነበረሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ውበትሽን ደመደሙ/ፈጸሙ
"ውበት" የሚለው ረቂቅ ስም "ውብ" በሚለው ቅጽል ተተክቶ ሊተረጎም ይችላል። "ውበትሽን ደመደሙ" ወይም "ፍጹም ውብ አደረጉሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 27:12
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ሀረጋት ውስጥ "የአንቺ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጢሮስን ነው።
ብር፣ ብረት፣ ቆርቆሮ፣ እና እርሳስ
በዚያን ወቅት ያገለግሉ የነበሩ ብረታ ብረቶች ናቸው
ዕቃዎችሽ
"ለገበያ/ሽያጭ የምታቀርቢያቸው ነገሮች"
ያዋን
ይህ የባህር ዳርቻ የሆነ ስፍራ ነው ዴዳን ተብሎም ይታወቃል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የሸቀጥ ንግድሽን ይለዋወጡ ነበር
"በሸቀጣሸቀጥሽ ይነግዱ/ይለዋወጡ ነበር"
Ezekiel 27:14
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ሀረጋት ውስጥ "የአንቺ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጢሮስን ነው።
ቤት ቴርጋማ…ሮሆደስ
እነዚህ የቦታ ስሞች ነበሩ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ያልተኮላሸ ፈረስ
ወንድ ፈረስ
ንግዱ በእጆችሽ ላይ ነበር
እዚህ ስፍራ ነገሮች በእጅ ላይ መሆን የሚለው ምናልባትም እነዚያን ነገሮችን መያዝን በዘይቤ የሚገልጽ ወይም የእነዚያ ነገሮች ባለቤት መሆንን ሊያመለክት ይችላል። "ለእነርሱ ልትሸጭላቸው የምትችያቸው ነገሮች ባለቤት ነበርሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ቀንድ
የአንዳንድ እንስሳትን ረጅም ጥርስ ያመለክታል
ጥቁር እንጨት
ጥቁር ቡናማ በጣም ከባድ እና ጠንካራ የሆነ እንጨት
Ezekiel 27:16
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡
"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።
አራም ነጋዴ ነበረች
እዚህ ስፍራ "አራም" የሚለው የሚያመለክተው የአራም ሰዎችን ነው። "የአራም ሰዎች ነጋዴዎች ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ነጋዴ
"በንግድ የተሰማራ"
ብሩህ አረንጓዴ የከበረ ድንጋይ/ዛጎል
እጅግ ውድ የሆነ የከበረ አረንጓዴ ድንጋይ ነው
ሀምራዊ
እዚህ ስፍራ ሀምራዊ ጨርቅ ወይም ሱፍ ክር የሚያመለክተው የዕቃውን ቀለም ነው። "ሀምራዊ ጨርቅ" ወይም "ሀምራዊ ክር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)
ሉል
ነጭ እና ጠንካራ የሆነ በባህር ውስጥ ከሚገኙ ፍጥረቶች የሚገኝ ውብ ዶቃ
ቀይ እንቁ
ቀይ እንቁ፣ ውድ ዋጋ ያለው እጅግ ውድ ድንጋይ
ይሁዳ እና የእስራኤል ምድር ከአንቺ ጋር ይገበያዩ ነበር
እዚህ ስፍራ "ይሁዳ እና የእስራኤል ምድር" የሚሉት የሚያመለክቱት የእነዚያን ስፍራዎች ሰዎች ነው። "የይሁዳ እና የእስራኤል ሰዎች ከአንቺ ጋር ይገበያዩ/ይነግዱ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሚኒት…ኬልቦን…ዛሐር
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ነበሩ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ጣፋጭ/ኬክ
እዚህ ስፍራ "ጣፋጭ/ኬክ" ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጡ ቃል ትርጉም በእርግጠኝነት አይታወቅም። ሌሎች ትርጉሞች ሌላ አይነት ምግብ አድርገው ሊተረጉሙት ይችላሉ።
አጣን
ጣፋጭ ማዕዛ ያለው ከዛፍ የሚገኝ ሙጫ
የተትረፈረፈ ሀብት
"ብዙ ሀብት" ወይም "ታላቅ ንብረት"
Ezekiel 27:19
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡
"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።
ዳን..ያዋን…ኡሴል..ድዳን..ዐረብ.. ቄዳር
እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ዳን እና ያዋን
ይህ ለዳን እና ያዋን ነዋሪዎች ሜቶናሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። "የዳን እና ያዋን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የሚቀጠቀጥ/የሚጠፈጠፍ ብረት
በመዶሻ ቅርጽ ሊይዝ የሚችል የብረት አይነት
ቀረፋ
ከዛፍ ቅርፊት የሚገኝ የቅመም አይነት። "ብርጉድ" የዚህ አይነቱ ቅመም ሌላ ስም ነው። (በእርግጠኝነት የማይታወቁትን ነገሮች መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
ጠጅ ሳር
እንደ ሽቶ የሚያገለግል እና ሰዎች ለመድሀኒትነት የሚጠቀሙበት የሳር አይነት
ደዳን …ነበረች
ይህ ለድን ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። "የድዳን ሰዎች … ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የኮርቻ ጨርቅ/ምንጣፍ
የኮርቻ ምንጣፍ በፈረስ ወይም ከኮርቻ ስር የሚደረግ ለመቀመጫነት የሚውል

ቁራጭ ጨርቅ ነው።

አረብ

ለአረብ ሰዎች የሚውል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ ነው። "የአረብ አገር ሰዎች" ወይም "አረቦች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 27:22

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

ሳባ…ራዕማ…ካራን…ካኔ…ዔደን… ሳባ…አሦር…ኪሌማድ

እነዚህ የቦታዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የከበሩ ድንጋዮች

"ውድ ዋጋ ያላቸው ድንጋዮች"

ካራን፣ ካኔ እና ዔደን፤ ከአንቺ ጋር የሚነግዱት ከሳባ፣ አሦር እና ኪልማድ ጋር በመሆን ነበር

ይህ ከእነዚህ ስፍራዎች የሆኑ ሰዎችን ያመለክታል። የካራን፣ ካኔ እና የዔደን ሰዎች፤ ከሳባ፣ አሦር እና ኪልማድ ሰዎች ጋር በመሆን አብረውሽ ይነግዱ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 27:24

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

ከአንቺ ጋር የሚነግዱት እነዚህ ነበሩ

"እነርሱ ከአንቺ ጋር ይነግዳሉ"

ባለ ብዙ ጌጥ ሀምራዊና በሚያምሩ ቀለማት ተጠለፉ ልብሶች

"ብዙ ቀለም ያላቸው እና ጌጠኛ ሀምራዊ ልብሶች"

በብዙ ቀለማት ያጌጡ፣ ጥልፎች፣ እና አምረው የተሰሩ ካባዎች

"ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ባለ ብዙ ህብር ካባዎች"

የጢሮስ መርከቦች ነጋዎችሽን ያመላልሱ ነበር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የጢሮስ መርከቦች ነጋዴዎችሽን ያጓጉዙ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እጅግ በሀብት በተሞሉ ጭነቶች በልጽገሽ/ተሞልተሽ ነበር

የጢሮስ ብልጽግና የተገለጸው በጭነት እንደተሞላች መርከብ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የባህሮች ልብ

"በባህር መሃል።" ይህ በሕዝቅኤል 27፡4 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 27:26

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው።

አጠቃላይ መረጃ፡

የጢሮስ ከተማ እዚህ ስፍራ እና በተከታዮቹ ቁጥሮች ውስጥ የተገለጸችው እንደ ፈራረሰች መርከብ ተደርጋ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አስጨናቂዎችሽ

"አንቺን የሚያስጨንቁሽ ሰዎች"

ሰፊ ባህር

"ታላቅ ውሃ"

የምስራቅ ነፋስ

"ከምስራቅ የሚነፍስ ጠንካራ ነፋስ"

በእነርሱ መሃል

"የባህር ልብ" ወይም "በባህሩ መሃል።" ይህ በሕዝቅኤል 27፡4 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

ባህረኞች

ጀልባ የሚቀዝፉ ሰዎች/ መርከብ የሚነዱ ወንዶች

ቡድን

በቡድን የሚሰሩ ሰራተኞች

የባህር ጥልቀት

"የባህር ልብ" ወይም "በባህሩ መሃል።" ይህ በሕዝቅኤል 27፡4 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።

በጥፋትሽ/በምትደመሰሽበት እለት

x

Ezekiel 27:28

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል። የጢሮስ ከተማ የተሰበረች መርከብ ሆና መገለጽዋ ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

"አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በባህሩ የሚገኙ ከተሞች ይንቀጠቀጣሉ

እዚህ ስፍራ "በባህሩ የሚገኙ ከተሞች" የሚለው የሚወክለው በእነዚያ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "በባህሩ በሚገኙ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች ይንቀጠቀጣሉ/ በጭንቀት ይርዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መቅዘፊያውን የሚይዙ ሰዎች በሙሉ

"አስጨናቂዎች ሁሉ"

በምሬት ያለቅሳሉ

"በከፍተኛ ሀዘን ያለቅሳሉ"

በራሳቸው ላይ ትቢያ ይነሰንሳሉ። በአመድ ላይ ይንከባለላሉ

እነዚህ የሀዘን እና በምሬት የማልቀስ መገለጫዎች ናቸው። (ትምዕርታዊ/ ምልክታዊ ድርጊቶች የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 27:31

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል። የጢሮስ ከተማ የተሰበረች መርከብ ሆና መገለጽዋ ቀጥሏል።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡

በዚህ ቁጥር "እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቁጥር 28 እና 29 ላይ የተጠቀሱትን ሰዎች ነው። "አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ አንቺ ራሳቸውን ይላጫሉ፣ ደግሞም ማቅ ይለብሱልሻል

እነዚህ የሀዘን እን ልቅሶ መገለጫዎች ናቸው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

መላጨት

በራስ ላይ ምንም ፀጉር ያለማስቀረት

የሰቆቃቸውን ጩኸት ያሰማሉ

"ሰቆቃ" የሚለው ረቂቅ ስም "አለቀሱ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ጮኸው ያለቅሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ሙሾ አወጡ

"በቀብር ላይ የሚከናወን የለቅሶ ግጥም"

አሁን በባህሩ መሃል ዝምታ ውስጥ የገባ እንደ ጢሮስ ያለ ማን ነው?

ይህ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ ሲጠብቅ፣ ለጢሮስ ከሌሎች ከተሞች ሁሉ የተለየ ትኩረት ይሰጣል። ጥያቄው በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "የትኛውም ሌላ አሁን ከተማ በባህሩ መሃል ዝምታ ውስጥ እንደገባችው እንደ ጢሮስ አይደለም።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን ዝምታ ውስጥ የገባች

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል።"አሁን ጠላቶቿ ጸጥ ያሰኟት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 27:34

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል። የጢሮስ ከተማ የተሰበረች መርከብ ሆና መገለጽዋ ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ፡

በእነዚህ ቁጥሮች "አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ጢሮስን

ነው።

በጥልቁ ውሃ፣ በወንዙ በተንኮታኮትሽ/በጠፋሽበት ጊዜ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ባህሩ፣ ጥልቁ ውሃ በከደነሽ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መንኮታኮት

"መንኮታኮት" ወደ ቁርጥራጭነት መሰባበር ነው።

ቡድን

በቡድን የሚሰሩ ሰራተኞች

በአንቺ ላይ በደረሰው ደነገጡ

"በአንቺ ላይ በደረሰው ደንግጠውና በፍርሃት ተውጠው ነበር"

ንጉሦቻቸው በፍርሃት ተንቀጠቀጡ

"ፍርሃት" የሚለው ረቂቅ ስም "በፍርሃት" በሚለው ተውሳከ ግስ ሊተረጎም ይችላል። "ንጉሦቻቸው በፍርሃት ተንቀጠቀጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ፊታቸው ተንቀጠቀጠ

እዚህ ስፍራ "ፊት/ገጽ" የሚለው የሚወክለው የአንደን ሰው ሁለንትና ነው። "ይንቀጠቀጡ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በአንቺ ላይ በአድናቆት አፏጩ

ማፏጨት በጥርስ መሃል የፉጨት ድምጽ ማሰማት ነው። በስጋት፣ በሃዘን ወይም በአድናቆት ጊዜ ሊሰማ ይችላል። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ማስፈራሪያ/ለድንጋጤ ሆንሽ

"ፍርሃት" የሚለው ረቂቅ ስም "አሰቃቂ" በሚለው ቅጽል ሊተረጎም ይችላል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አሰቃቂ/አስፈሪ ሆንሽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

---

## Chapter 28

### Ezekiel 28:1

የያህዌ ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የነገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ

"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ልብህ ታበየ

እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የጢሮስን ገዢ ፈቃድ ወይም ሀሳብ ነው። "አንተ ትዕቢተኛ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ትዕቢተኛ

በስህተት ስላ ራስ ጠቃሚነት አለአግባብ ከፍ አድርጎ ማሰብ።

በአማልክት ስፍራ ወንበሬን አስቀምጣለሁ

"በአማልዕክት ዙፋን እቀመጣለሁ።" እዚህ ስፍራ በአማልዕክት ወንበር መቀመጥ የሚለው የሚወክለው፤ ራሱን ከአማልዕክት አንዱ አድርጎ በመቁጠር በተመሳሳይ ከፍ ባለ ስፍራ እቀመጣለሁ ማለቱን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የባህሮች ልብ

"በባህሮች መሃል።" ይህ በሕዝቅኤል 27:4 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ልብህን እንደ አምላክ ልብ አድርገሃል

እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው አዕምሮን ወይም ሃሳብን ነው። አምላክ ራሱን ከሰዎች የተሸለ አድርጎ ያስባል። "የአምላክ አዕምሮ አለኝ ብለህ ታስባለህ" ወይም "ራስህን ከሌሎች ሰዎች የተሻለ አድርገህ ለማሰብ ፈቅደሃል" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከዳንኤል ይልቅ ብልህ እንደሆንክ ታስባለህ

እዚህ ስፍራ የጢሮስ ገዢ ምን ያህል ብልህ እንደሆነ እንደሚያስብ ራሱን ከነቢዩ ዳንኤል ጋር አነጻጽሯል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

### Ezekiel 28:4

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ በሕዝቅኤል፣ ለጢሮስ ገዢ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

በእነዚህ ቁጥሮች "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የጢሮስን ገዢ ነው።

ራስህን በጥበብ እና ችሎታ ባለጸጋ አድርገሃል

"ጥበብ" እና "ችሎታ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ጠቢብ" እና "አዋቂ/ክህሎት ያለው" የሚሉ ቅጽሎችን በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። "በራስህ ጥበብና ችሎታ ባለጸጋ ሆነሃ" ወይም "ጠቢብ እና አዋቂ በመሆን ባለጸጋ ሆነሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ገላጭ ተውላጠ ስሞች እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ወርቅ እና ብር አከማችተሃል

"ወርቅና ብር ሰብስበሃል"

ግምጃ ቤት

ውድ የሆኑ ነገሮች የሚቀመጡበት አስተማማኝ ስፍራ

በታላቅ ጥበብህ እና በንግድህ ሀብትህን አብዝተሃል፣ ስለዚህም ከሃብት ብዛት የተነሳ ልብህ ኮርቷል

"ጥበብ" እና "ሀብት" የሚሉትን ረቂቅ ስሞች "ጠቢብ" እና "ሃብታም" የሚሉ ቅጽሎችን በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። "በጣም ጠቢብ በመሆን እና በንግድህ ሀብትህ እየጨመረ ሄዷል፤ በሀብትህ ብዘትም ምክንያት ልብህ ይበልጥ ታብይዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ልብህ ትዕቢተኛ ነው

እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የጢሮስን ገዢ ፈቃድ ወይም ሃሳብ ነው። "አንተ ትዕቢተኛ ነህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

### Ezekiel 28:6

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ በሕዝቅኤል፣ ለጢሮስ ገዢ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

በእነዚህ ቁጥሮች "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የጢሮስን ገዢ ነው።

ልብህን እንደ አምላክ ልብ አድርገሃል

እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው አዕምሮን ወይም ሃሳብን ነው። ስለ ራሱ ከሰዎች እንደሚሻል እና አምላክ ነኝ ስለሚል ሰው። በሕዝቅኤል 28:2 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ቁጥር እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የጥበብህ ውበት

"ውበት" እና "ጥበብ" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ውብ" በሚል ቅጽል እና "በጥበብ" የሚል ተውሳከ ግስ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። "አንተ በጥበብህ የፈጸምካቸው ውብ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ክብርህን ያዋርዳሉ

"ድምቀት/ክብር" የሚለው ረቂቅ ስም "ደማቅ" የሚለውን ቅጽል በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። "ክብርህ ምንኛ ተዋረደ" ወይም "ግርማህ ምንኛ ረከሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

### Ezekiel 28:8

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ በሕዝቅኤል፣ ለጢሮስ ገዢ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

"እነርሱ" የሚለው ቃል የባዕዳንን ሰራዊት ያመለክታል። በእነዚህ ቁጥሮች "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የጢሮስን ገዢ ነው።

ጥልቅ ወደ ጉድጓድ

እዚህ ስፍራ "ጉድጓድ" የሚያመለክተው ወቃብርን ወይም ወደ ሲኦል መውረድን ነው። "ወደ መቃብር መውረድ"በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በባህሮች ልብ

"በባህሮች መሃል"



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በእውነት አንተ፣ በገዳይህ ፊት ቆመህ "እኔ አምላክ ነኝ ትላለህን?"
ይህ ጥያቄ፣ አምላክ ነኝ የሚል በሰው የሚጠፋ መሆኑን የሚያጎላው ይህ ምጸት አሉታዊ ምላሽ ይጠብቃል። ጥያቄው በዐረፍተ ነገር መለክ ሊጻፍ ይችላል። "በገዳይህ ፊት ቆመህ 'አምላክ ነኝ' አትልም!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ምጸት የሚሉትን ይመልከቱ)
በ…ፊት
እዚህ ስፍራ ፊት የሚወክለው ሌላ ሰው በሚገኝበት መገኘትን ነው። "በ…መገኘት" ወይም "ፊት ለፊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
በ…እጅ
እዚህ ስፍራ በአንድ ሰው እጅ መሆን የሚወክለው/የሚገልጸው በእነርሱ ቁጥጥር ስር መውደቅን ነው። "በ…ቁጥጥር ስር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በባዕዳን እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የባዕዳን ሰራዊትን ድርጊት የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። "በባዕዳን ሰራዊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 28:11
ዳግም የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፣ የሰው ልጅ
"የያህዌ ቃል ዳግም ወደ…መጣ" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ ውሏል። ይህ ተመሳሳይ ቃል በሕዝቅኤል 18፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ዳግም መልዕክት ሰጠኝ፡ እንዲህም አለኝ፣ የሰው ልጅ ሆይ" ወይም "ያህዌ ይህን ሁለተኛ መልዕክት ተናገረኝ፡' የሰው ልጅ ሆይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ተነስ
"ዘምር"
አንተ የፍጹምነት ተምሳሌት ነበርክ
"ተምሳሌት" እን "ፍጹምነት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ሙሉ ለሙሉ" እና "ፍጹም" የሚሉ ቃላትን በመጠቀም ሊተረጎሙ ይችላሉ። "አንተ ሙሉ ለሙሉ ፍጹም ነበርክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ውድ የሆኑ የከበሩ ድንጋዮች ሸፍነውህ ነበር
"ውድ የሆኑ ድንጋዮችን ሁሉ ለብሰህ ነበር"
ቀይ እንቁ፣ ቶጳዝዮን፣ አልማዝ፣ በርሌ፣ መረግድ፣ ኢያስጲድ፣ ሰንፔር፣ በሉር እና የሚያብረቀርቅ ዕንቁ
እነዚህ የተለያየ ቀለም ያላቸው የከበሩ ድንጋዮች ናቸው። (የማይታወቀውን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
የሚገኙባቸው እና በብዛት ያሉባቸው
ውድ የሆኑትን የከበሩ ድንጋዮች የያዙ ቁርጥራጭ ብረቶች
የተዘጋጁት በተፈጠርክበት ቀን ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተን በፈጠርኩበት ቀን እነዚህን እኔ አዘጋጀኋቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ዝግጁ
"ዝግጁ ማድረግ"
Ezekiel 28:14
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ በሕዝቅኤል፣ ለጢሮስ ንጉሥ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ቁጥሮች "አንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጢሮስን ንጉሥ ነው።
ኪሩቤል
ይህ በሕዝቅኤል 10፡9 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
የእሳት ፍም የመሰሉ ድንጋዮች
"የእሳት ድንጋዮች።" ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በሕዝቅኤል 28፡13 ላይ ለሚገኙት ውብ ቀለም እና ብሩህነት ላላቸው ድንጋዮች የተሰጠ ዘይቤያዊ አነጋገር ወይም 2) "በቅዱሱ የእግዚአብሔር ተራራ" ላይ የሚገኙ ሌሎች እሳታማ ድንጋዮች (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ከተፈጠርክበት ቀን አንስቶ በውስጥህ ጥፋት እስከ ተገኘብህ ደረስ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንተን ከፈጠርኩበት ቀን አንስቶ በውስጥህ ጥፋት እስካገኘሁበት ደረስ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 28:16
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ በሕዝቅኤል፣ ለጢሮስ ንጉሥ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ቁጥሮች "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የጢሮስን ንጉሥ ነው።
ታላቅ ንግድ
"ብዙ የንግድ ዕቃ"
በጥቃት ተሞልተህ ነበር
ያህዌ ስለ ጢሮስ ንጉሥ በጥቃት እንደ ተሞላ እቃ መያዣ አድርጎ ይናገራል። ንጉሡ ለራሱ እና ለህዝቡ ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ነው።"ጥቃት" የሚለው ረቂቅ ስም "አጥቂ" የሚለውን ቅጽል በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። "አንተ እና የአንተ ህዝብ ሙሉ ለሙሉ አጥቂዎች ነበራችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ዘይቤያዊ አነጋገር እና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እንደዚሁም ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
ጠባቂ ኪሩብ
"ኪሩብን የሚጠብቅ"
የእሳት ድንጋዮች
"የእሳት ድንጋይ።" ይህ በሕዝቅኤል 28፡14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) 1) በሕዝቅኤል 28፡13 ላይ ለሚገኙት ውብ ቀለም እና ብሩህነት ላላቸው ድንጋዮች የተሰጠ ዘይቤያዊ አነጋገር ወይም 2) "በቅዱሱ የእግዚአብሔር ተራራ" ላይ የሚገኙ ሌሎች እሳታማ ድንጋዮች (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ልብህ ትዕቢተኛ ነበር
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው በሃሳቡ ላይ ትኩረት በማድረግ የሰውን ሁለንተና ነው። "አንተ ትዕቢተኛ ነበርክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ትዕቢተኛ
በስህተት ራስን ከአግባብ ውጭ ጠቃሚ አድርጎ መቁጠር።
በውበትህ ልብህ ታብዮ ነበር፤ ከድምቀትህ የተነሳ ጥበብህን አበላሸህ
"ውበት"፣ "ጥበብ" እና "ድምቀት" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "ውብ"፣ "ብልህ" እና "ደማቅ" በሚሉ ቅጽሎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። "ውብ ስለነበርክ ልብህ ታበየ፤ ድምቀት ስለነበረህ በመኩራራትህ ጥበብ የሌለህ ሆንክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
በንጉሦች ፊት
"በንጉሦች ፊት ለፊት"
ስለዚህም ይመለከቱህ ይሆናል
"ለዚህም እነርሱ አንተን ይመለከቱ ይሆናል"
Ezekiel 28:18
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ በሕዝቅኤል፣ ለጢሮስ ንጉሥ መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።
አጠቃላይ መረጃ፡
በእነዚህ ቁጥሮች "አንተ" እና "የአንተ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት የጢሮስን ንጉሥ ነው።
አንተን ይፈጅሃል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"አንተን ይበላሃል።" እዚህ ስፍራ እሳቱ የተገለጸው እርሱን ጨርሶ እንደሚበላው ተደርጎ ነው። "አቃጥሎ ይጨርስሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ አመድነት ይለውጥሃል

የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም አመድ ብቻ እስኪቀር ድረስ መቃጠል ማለት ነው። "አመድ ያደርግሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መራድ

መናወጥ ወይም በፍርሃት መንቀጥቀጥ

ከእንግዲህ ለዘለዓለም አትገኝም

ይህ በሕዝቅኤል 27:36 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 28:20

የያህዌ ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የነገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ

"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ፊትህን በሲዶን ላይ አድርግ

ሲዶን ሩቅ ነበረች፣ ስለዚህም ሕዝቅኤል ሊመለከታት አይችልም ነበር፣ ነገር ግን ወደዚያ አቅጣጫ ማየት በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን የመጉዳት ምልክት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በሕዝቅኤል 6:2 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሃሳብ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ ሲዶን ፊትን አዙረህ ተመልከት" ወይም "በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ጥፋት ይደርስባቸው ዘንድ ወደ ሲዶን ተመልከት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕምርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

ዳግም ትንቢት ተናገር

"ሊደርሱ ስላሉት መጥፎ ነገሮች ትንቢት ተናገር" ይህ በሕዝቅኤል 4:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

እነሆ!

"ተመልከት!" ወይም "አድምጥ!" ወይም "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ!"

በመሃላችሁ ክብር አገኛለሁ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በመሃላችሁ ክብሬን እገልጻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ

ያህዌ ይህንን ሲናገር ሰዎች እርሱ ያህዌ እንደሆነ ያውቃሉ፤ ሰዎች እርሱ ብቻ ሉዓላዊ/የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሃይል ያለው መሆኑን እንደሚያውቁ እያመለከተ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 6:7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ፣ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ፣ ያህዌ ሉዓላዊ ሀይል እና ስልጣን እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በመሃላችሁ ፍትህ ሳደርግ

"ፍትህ" የሚለው ረቂቅ ስም "ፈረደ" የሚለውን ግስ በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። "እኔ በምፍርድባችሁ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

በእናንተ ዘንድ ቅዱስ መሆኔን አሳቀውቃለሁ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ቅዱስ መሆኔን ለማሳየት በአንተ እጠቀምብሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 28:23

አያያዥ ሀሳብ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ሲዶን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

በእነዚህ ቁጥሮች "አንቺ" እና "የአንቺ" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ሲዶንን ነው።

በጎዳናዎችሽ ደም

እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው የሚያመለክተው የሲዶንን ሰዎች ደም እና ጠላቶቻቸው የሚገድሏቸውን ሰዎች ደም ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የታረዱት ይወድቃሉ

እዚህ ስፍራ "የታረዱ" የሚለው ጠላቶቻቸው የሚገድሏቸው የሲዶን ሰዎች ማለት ነው። "የታረዱት ሰዎች ይወድቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)

ሰይፍ በላያችሁ ሲመጣ

እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የጠላትን ሰራዊት ስለ ማጥቃት የሚውል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የጠላት ሰራዊት ሲያጠቃችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቧን ከሚንቁ በዙሪያዋ ከሚገኙ የእስራኤልን ቤት በእሾህ እና አሜኬላ ከሚወጉ

እዚህ ስፍራ እሾህ እና አሜኬላ የሚወክለው ስቃይና መከራ የሚያስከትሉ ነገሮችን ነው። "በእስራኤል ቤት ዙሪያ በሁሉም ስፍራ የሚገኙ ሰዎች እንደ እሾክ ይሆኑባቸዋል፣ እንደ እሾህ ይወጓቸዋል ደግሞም ያዋርዷቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእስራኤል ቤት

"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። በዚህ ሁኔታ የእስራኤል ትውልጆች ያመለክታል።ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ህዝብ ወገን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 28:25

የእስራኤል ቤት

"ቤት" የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ነው። በዚህ ሁኔታ የእስራኤል ትውልጆች ያመለክታል።ይህ በሕዝቅኤል 3:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እስራኤላውያን" ወይም "የእስራኤል ህዝብ ወገን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከተበተኑበት

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ እነርሱን ከበተንኩበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም አገራት ሊመለከቱ ይችላሉ

"በዚህ አይነት መንገድ አገራት እንደሚመለከቱት"

ባሪያዬ ያዕቆብ

እዚህ ስፍራ "ያዕቆብ" የሚወክለው የያዕቆብን ትውልድ ነው። "የባሪያዬ የያዕቆብ ትውልጆች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጧ

"በምድሪቱ"

ፍርዴን በሁሉም ላይ ስፈጽም

"ፍርድ" የሚለው ረቂቅ ስም "ፈረደ" የሚለውን ግስ በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። "በሁሉም ላይ በምፈርድበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 29

Ezekiel 29:1

በአስረኛው አመት

ይህ ዮአኪን በስደት ላይ የነበረበት አስረኛው አመት መሆኑ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ንጉሥ ዮአኪን በስዳት ላይ በነበረበት በአስረኛው አመት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተከታታይ ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በአስረኛው ወር፣ በወሩ አስራ ሁለተኛ ቀን

"በአስረኛው ወር በአስራ ሁለተኛው ቀን።" ይህ በዕብራውያን የወራት አቆጣጠር



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አስረኛው ወር ነው። አስራ ሁለተኛው ቀን በምዕራባዊያኑ አቆጣጠር ወደ ጥር መጀመሪያ አካባቢ ነው። (የዕብራዊያን ወራት እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የነገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ተናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ

"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ፊትህን በፈርኦን ላይ አድርግ

ይህ ፈርኦንን እና ህዝቡን ለመቅጣት ወደ ፈርኦን እንዲመለከት በምልክትነት የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ፈርኦን የሚገኘው በርቀት ነበር፣ ሕዝቅኤል ሊመለከተው አይችልም ነበር። ነገር ግን እርሱ ወዳለበት መመልከቱ ፈርኦንን እና ህዝቡን ለመቅጣት እንደ ምልክት ተደርጎ ይወሰድ ነበር። በሕዝቅኤል 6፡2 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ ሃሳብ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ወደ ፈርኦን አቅጣጫ ዞረህ ተመልከቱ" ወይም "እርሱ እና ህዝቡ ይቀጡ ዘንድ ፈርኦን ወደሚገኝበት አቅጣጫ ተመልከት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ እና በመላው ግብጽ ላይ ትንቢት ተናገር

"በእርሱ እና በግብጽ በሚገኙ ላይ ሁሉ ስለሚደርሱ አስጨናቂ ነገሮች ተናገር"

ታላቁ የባህር አውሬ

"በውሃ ውስጥ የሚኖር ትልቅ ፍጡር።" ያህዌ ፈርኦንን በውሃ ውስጥ የሚኖር ትልቅ አውሬ ብሎ ይጠራዋል። አውሬው ምናልባት አዞ ሊሆን ይችላል። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ አገላለጽ/ቋንቋ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 29:4

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ፈርኦን መልዕክት መስጠቱን፤ ፈርኦን በውሃ ውስጥ እንደሚኖር አውሬ መሆኑን እና የግብጽ ሰዎች አሳ መሆናቸውን መናገሩን ቀጥሏል። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ አገላለጽ/ቋንቋ የሚለውን ይመልከቱ)

መንጠቆዎች

ስል እና ቆልመም ያለ ቁራጭ ብረት፣ ወይም ሰዎች አሳ እና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች እንስሳትን የሚያጠምዱበት እንጨት

ቅርፊት

በአሳ፣ አዞ፣ እና ሌሎች እንስሳት ላይ የሚገኝ ጠንካራ ቁርጥራጭ ቆዳ

የሚያነሳችሁ አይኖርም፣ ወይም ማንም አያነሳችሁም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ይህ በሜዳ/በዱር የሚሞቱ መሆኑን ያሳያል። "ማንም በድናችሁን አንስቶ ወይም ሰብስቦ አይቀብርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 29:6

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ፈርኦን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ

ያህዌ ይህንን ሲናገር ሰዎች እርሱ ያህዌ እንደሆነ ያውቃሉ፤ ሰዎች እርሱ ብቻ ሉዓላዊ/የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሃይል ያለው መሆኑን እንደሚያውቁ እያመለከተ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ፣ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ፣ ያህዌ ሉዓላዊ ሀይል እና ስልጣን እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ የሸምበቆ አገዳ ነበሩ

"እነርሱ" የሚለው ቃል የግብጽን ነዋሪዎች ያመለክታል። የሸምበቆ አገዳ አስተማማኝ አይደለም ምክንያቱም በቀላሉ ተሰባሪ ነው። ያህዌ እነርሱን እንደ ሸምበቆ አገዳ የሚገልጻቸው፣ ግብጻውያን በጦርነት ወቅት እነርሱን እንዲረዱ ስለጠየቋቸው እና ግብጻውያን ስላልረዷቸው ነው። "እነርሱ እንደ ሸምበቆ አገዳ ሊታመኑባቸው የማይቻል ነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሸምበቆ

በውሃ አጠገብ የሚበቅል እና ረጅም ሳር የመሰለ ተክል ነው

አገዳ

ረጅም በትር የሚመስል የቁጥቋጦው ክፍል ነው። ሰዎች እንደ በትር ሊጠቀሙባቸው ሲችሉ ነገር ግን እንደ እንጨት በትር ቁጥቋጦ ጠንካራ ባለመሆኑ በቶሎ ተሰባሪ ነው።

እነርሱ በእጃቸው እናንተን ሲይዟችሁ

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በግብጻውያን ላይ መታመናቸው ተሰባሪ የሸምበቆ ምርኩዝ እንደመደገፍ አድርጎ ይናገራል። "እነርሱ በአንተ ሲታመኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አንተን ሲደገፉ

"እነርሱ" የሚለው ቃል እስራኤላውያንን ሲይመለክት "አንተ" የሚለው ፈርኦንን ወይም ፈርኦንን እና ግብጽን ያመለክታል።

እግራቸው እንዳይጸና አደረግህ

ግብጽ እስራኤላውያንን ስላልረዳች፣ እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ባቢሎናውያንን መቋቋም አልቻሉም። እግዚአብሔር ራሳቸውን መከላከል አለመቻላቸውን የገለጸው እግራቸው መጽናት እንዳልቻለ አድርጎ ነው። "እግራቸው መጽናት እንዳልቻለ ሰው አደረግሃቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 29:8

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ፈርኦን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል

እነሆ!

"ተመልከት!" ወይም "አድምጥ!" ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት ይሰጣል። ይህ ጌታ ለፈርኦን ያለው መልዕክት ነው። "ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በአንተ ላይ ሰይፍ አመጣለሁ

እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" ለጦርነት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት ሲሆን/፣ "በአንተ ላይ ሰይፍ አመጣለሁ" የሚለው የጠላት ሰራዊት ግብጽን ለመውጋት ለመምጣቱ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "ጠላቶችህ አንተን ለመውጋት እንዲመጡ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ላይ ሰይፍ

"አንተ" የሚለው ቃል ግብጽን ያመለክታል። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ከአንተ ሰውንና አራዊትን በአንድነት እቆርጣለሁ

እዚህ ስፍራ "ሰውንና አራዊትን እቆርጣለሁ" የሚለው ሰዎችንና እንስሳትን ለማጥፋት የዋለ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። እግዚአብሔር የጠላት ሰራዊት ይህንን እንዲያደርግ በማድረግ ይፈጽመዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ በአንተ እና በወንዝህ ላይ ተነስቻለሁ

"አንተ" የሚለው ቃል ፈርኦንን ያመለክታል። እግዚአብሔር ፈርኦንን በወንዝ ውስጥ እንደሚኖር አውሬ ይገልጸዋል።

የግብጽን ምድር ሰው የማይኖርበት እና የጠፋ አደርገዋለሁ

"ግብጽን ለጥፋት እና ውድመት ሀይል እሰጣለሁ" ሰው የማይኖርበት እና የጠፋ የሚሉት የተገለጹት በግብጽ ላይ ሀይል እንዳላቸው ሰዎች ተደርገው ነው። "ግብጽ ሰው የማይኖርባት እና የጠፋች እንድትሆን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ የጠፋ ምድር ትሆኛለህ

እዚህ ስፍራ "አንተ" ፈርኦንን ሲያመለክት የሚገዛትን ግብጽንም ይወክላል። "አገርህ የጠፋ ምድር ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ከሚግዶል እስከ ሲና ደግሞም እስከ ኩሽ ድንበሮች ድረስ

ይህ መላውን ግብጽ ያመለክታል። እነዚህ ስፍራዎች የት እንደሆኑ ይበልጥ በግልጽ ሊጻፉ ይችላል። "በሰሜን ከሚግዶል በደቡብ እስከ ሲና ደግሞም ሩቅ በስተ ደቡብ እስከ ኩሽ ድንበር ድረስ በመላው ግብጽ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጽንፍ/ ከዳር እስከ ዳር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሚግዶል
ይህ በግብጽ በስተሰሜን ዳርቻ የሚገኝ የቦታ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሴና
ይህ በደቡባዊ ግብጽ የሚገኝ ከተማ ስም ነው። አሁን አስዋን ተብላ ትጠራለች። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የኩሽ ድንበሮች
እነዚህ የኩሽ ድንበሮች በሴና በስተ ደቡብ ነበሩ። አንዳንድ ቅጂዎች በዘመናችን ከግብጽ በስተደቡብ የሚገኙትን አገራት በመጠቀም ሱዳን ወይም ኢትዮጵያ ይላሉ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 29:11
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ፈርኦን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል
የማንም ሰው እግር/ኮቴ በላይዋ አያልፍም
እዚህ ስፍራ "የሰው እግር" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "ማንም ሰው በግብጽ ምድር በኩል አያልፍም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ የግብጽን ምድር ሰው የማይኖርበት/ ምድረ በዳ አደርጋለሁ
"ባድማ/ሰው የማይኖርበት/" የሚለው "ጠፍ/ባድማ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "የግብጽን ምድር ባድማ አደርጋታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ግብጽን ከአገራት መሃል አጠፋታለሁ/እበትናታለሁ
እዚህ ስፍራ "ግብጽ" የምትወክለው የግብጽን ህዝብመ ሲሆን፣ "መበተን" የሚገልጸው የእነርሱን ወደ ሌላ ስፍራ መሄድ ነው። "ግብጻውያንን በአገራት መሃል እበትናቸዋለሁ" ወይም "የግብጽ ሰዎች ወደ ሌሎች አገራት ሄደው እንዲኖሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Ezekiel 29:13
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ፈርኦን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል
ግብጽን እሰበስባለሁ/እጠራለሁ
እዚህ ስፍራ "ግብጽ" ለግብጽ ህዝብ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን፣ "መሰብሰብ" የሚለው ደግሞ ወደ ግብጽ ለመመለሳቸው ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። "የግብጽን ህዝብ ወደ ግብጽ እንዲመለስ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
እነርሱ ከተበተኑበት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ እነርሱን ከበተንኩበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የግብጽን እድል ፈንታ እመልሳለሁ
"የግብጽ እድል ፈንታ" የሚለው ሀረግ ወደ ሌሎች አገራት ለተወሰደው የግብጽ ህዝብ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "የግብጽን ህዝብ ወደ ነበረበት እመልሳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የጳትሮስ ግዛት
ጳትሮስ በኩሽ ምድር እና በደለሉ መሃል የሚገኘው የግብጽ ደቡባዊ ክፍል ነው። ይህ የላይኛው ግብጽ ተብሎም ይጠራል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ዝቅተኛው ግዛት
እዚህ ስፍራ "ዝቅተኛ" የሚለው የሚወክለው የማይጠቅም የሚለውን ነው። "ታናሽ መንግስት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 29:15
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል፣ ስለ ፈርኦን መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል
ከመንግሥቱ አናሳ
እዚህ ስፍራ "አናሳ" የሚለው የሚወክለው ከሁሉም ዝቅ ያለ ዋጋ ስፍራ የያዘ መሆኑን ነው። "ከመንግሥታት ዝቅተኛው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከመንግሥታት መሃል ከእንግዲህ ወዲያ አይነሳም
እዚህ ስፍራ "መነሳት" የሚለው የሚወክለው ጠቃሚ መሆንን ነው። "ከእንግዲህ ወዲያ ዳግም በመንግስታት መሃል ጠቃሚ አይሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ አጠፋቸዋለሁ
"እኔ ትንሽ አደርጋቸዋለሁ።" እዚህ ስፍራ "እነርሱን አጠፋለሁ" የሚለው የሚወክለው ግብጽን ደካማ እና ጥቅም የሌላት ማድረግን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከእንግዲህ ግብጻውያን ለእስራኤል ቤት የኩራት ምክንያት አይሆኑም
"ኩራት" የሚለው ረቂቅ ስም "መታመኛ" ወይም "መደገፊያ" በሚል ግስ ሊተረጎም ይችላል። "የእስራኤል ቤት ከእንግዲህ በግብጻውያን አይታመንም/አይደገፍም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው የእስራኤልን ሰዎች ነው። "የእስራኤልን ሰዎች" ወይም "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ እስራኤል ለፈጸመው በደል ማስታወሻ ይሆናሉ
ግብጽ እንዴት ማስታወሻ እንደምትሆን በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ማስታወሻ" እና "ኃጢአት/በደል" የሚሉት ረቂቅ ስሞች "አስታውስ" እና "ኃጢአት" በሚሉ ግሶች ሊገለጹ ይችላሉ። "እኔ በግብጽ ላይ ያደረግኩትን ሲመለከት እስራኤል እንዴት አስራኤልን እንደበደለ ያስታውሳል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
እነርሱ ለእርዳታ ወደ ግብጽ ሲመለሱ
እዚህ ስፍራ "ለእርዳታ …መመለስ" የሚለው "እርዳታ …መጠየቅ" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ግብጻውያን እንዲረዷቸው በጠየቁ ጊዜ ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 29:17
እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ የተፈጸመን ጠቃሚ ትዕይንት ለማጉላት/ለማመልከት ነው። በእናንተ ቋንቋ ይህን ለማድረግ የሚጠቀምበት መንገድ ካለ እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።
በሃያ ሰባተኛው አመት
ይህ ንጉሥ ዮአኪን እና የይሁዳ ህዝብ በስደት ወደ ባቢሎን ከተወሰደ በኋላ ነበር። "ንጉሥ ዮአኪን በተሰደደ በሃያ ሰባተኛው አመት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተከታታይ ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
በመጀመሪያው ወር መጀመሪያ
"በመጀመሪያው ወር በመጀመሪያው ቀን።" ይህ በዕብራውያን ወር አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። የመጀመሪያው ቀን በሚያዚያ መጀመሪያ አካባቢ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
በጢሮስ ላይ ከባድ ስራ መስራት
የሚሰሩት ከባድ ስራ አይነቱ በግልጽ ሊቀርብ ይችላል። "ጢሮስን ለማጥቃት በከባድ መስራት። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እያንዳንዱ ራስ… እያንዳንዱ ትከሻ

ይህ የባቢሎንን ወታደሮች ራሶች/ጭንቅላቶች እና ትከሻዎች ያመለክታል።
እያንዳንዱ ራስ እስኪመለጥ ድረስ ይፈቀፈቅ ነበር
የወታደር ኮፍያቸው ወይም በጭንቅላታቸው ላይ የሚሸከሟቸው ከባድ ነገሮች ፀጉራቸውን ከራሳቸው ላይ ይመልጠው ነበር
እያንዳንዱ ትከሻ ይቆስል ነበር
የጦር ዕቃቸው ወይም በትከሻቸው የሚሸከሟቸው ከባድ ነገሮች የትከሻቸውን ቆዳ ይመልጠው ነበር። "እያንዳንዱ ትከሻ እስኪቆስል ድረስ ይላጥ ነበር" ወይም "እያንዳንዱ ትከሻ ተፈግፍጎ ይቆስል ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
እርሱ እና የእርሱ ሰራዊት ከጢሮስ ምንም ክፍያ አልተቀበሉም
እዚህ ስፍራ "ክፍያ" የሚወክለው የናቡከደነጾር ሰራዊት ጢሮስን በማሸነፉ የሚበዘብዘውን ነው። እግዚአብሔር ስለእነዚህ ነገሮች እነርሱ ለእርሱ በመስራታቸው እንደሚከፍላቸው አድርጎ ይናገራል። "እርሱ እና ሰራዊቱ ከጢሮስ እንደ ሽልማት አንዳች ዋጋ ያለው ነገር አላገኙም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 29:19
እነሆ!
"ተመልከት!" ወይም "አድምጥ!" ይህ ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው ትኩረት ይሰጣል።"ቀጥሎ ለምነግርህ ትኩረት ስጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
የግብጽን ምድር ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነጾር እሰጣለሁ
ያህዌ የባቢሎን ሰራዊት ግብጽን እንዲያሸንፍ ማድረጉን፣ እግዚአብሔር ግብጽን ለናቡከደነጾር እንደሚሰጥ አድርጎ ይናገራል። "የናቡከደነጾር ሰራዊት፣ የባቢሎን ንጉሥ ግብጽን እንዲያሸንፍ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የሰራዊቱ ደሞዝ ይሆናል
እግዚአብሔር ስለእነዚህ ነገሮች፤ የናቡከደነጾር ሰራዊት ለእርሱ በመስራታቸው የሚከፍላቸው ነገር እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። "የእርሱ ሰራዊት እነዚህን ነገሮች ክፍያው እንደሆነ አድርጎ ይቀበላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 29:21
እኔ ለእስራኤል ቤት ቀንድ አበቅላለሁ
የእንስሳ ቀንድ እንስሳውን ጥንካሬ ይወክላል፣ ስለዚህም ቀንድ ለጥንካሬ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን ማጠንከሩን እስራኤል በእንስሳ በመመሰል እና እርሱ ቀንድ እንድታበቅል ማድረጉን ይናገራል። "እኔ የእስራኤልን ህዝብ አበረታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው በቤቱ ለሚኖሩ ሜቶኖሚ/ ነው። እዚህ ስፍራ ይህ የሚወክለው እግዚአብሔር እስራኤል ብሎ የሚጠራቸውን የያቆብ ትውልድ ነው። "የእስራኤልን ሰዎች" ወይም "የእስራኤል ህዝብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በመሃላቸው መናገር
"ለእነርሱ መናገር"

Chapter 30
Ezekiel 30:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ሕዝቅኤል ያህዌ ስለ ሰጠው መልዕክት ይናገራል።
የያህዌ ቃል መጣ
x
Ezekiel 30:4
አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ያህዌ ስለ ግብጽ የተናገራቸው ቃላት ናቸው።
ከዚያም በግብጽ ላይ ሰይፍ ይሆናል/ይመጣል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚወክለው ጥፋት ሚያደርስን ሰራዊት ወይም ጦርነት ነው። "በግብጽ ላይ ጦርነት ይሆናል" ወይም "የጠላት ሰራዊት ግብጽን ያጠቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በኩሽ ጭንቀት ይሆናል
"ጭንቀት" የሚለው ረቂቅ ስም ሰዎች እንዴት እንደሚሰማቸው በመግለጽ መተርጎም ይቻላል። "የኩሽ ሰዎች በጣም ያዝናሉ" ወይም "የኩሽ ሰዎች ይጨነቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የተገደሉ ሰዎች በግብጽ ሲወድቁ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "መውደቅ" መሞት ለሚለው ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል ተክቶ መጠቀም/ ነው። "የግብጽ ሰዎች በጦርነት ሲሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) "መውደቅ" በድናቸው ወድቆ በምድር ላይ ሲጋደም። "በግብጽ የሚኖሩ ሰዎች በጦርነት ሲሞቱ እና ሲወድቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል ተክቶ መጠቀም የሚለውን ይመልከቱ)
ሀብቷን ሲዘርፉ
"ጥቃት አድራሾች የግብጽን ሀብት ሲዘርፉ"
መሰረቶቿ ሲፈርሱ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "አጥቂዎች በግብጽ የሚገኙ ቅጥሮችን/ህንጻዎችን መሰረቶች ሲደመስሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ኩሽ እና ፉጥ፣ ልድያና መላው አረብ፣ እንዲሁም ሊብያ
እነዚህ ስሞች የእነዚህን አገራት ሰዎች ያመለክታሉ። "የኩሽ እና ፉጥ፣ ልድያና መላው አረብ፣ እንዲሁም ሊብያ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሊብያ
ሊብያ ከግብጽ በስተ ምዕራብ የምትገኝ አገር ናት። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ልድያ
ይህ ምናልባት አሁን ቱርክ ውስጥ የምትገኘውን የልድያን ግዛት ሊያመለክት ይችላል።
የቃል ኪዳን ህዝብ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ቃለ ኪዳኑ" የሚያመለክተው ያህዌ ከእስራኤላውያን ጋር ያደረገውን ስምምነት ነው። "በግብጽ የሚኖሩ አይሁዶች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) "ቃለ ኪዳኑ" የሚያመለክተው ግብጽ ከሌሎች አገራት ጋር ያደረገችውን ስምምነት ነው። "ከግብጽ ጋር ቃል ኪዳብን ያላቸው የአገራት ህዝቦች" ወይም "የግብጽ ተባባሪዎች/አጋሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉም በሰይፍ ይወድቃሉ
እዚህ ስፍራ ሰይፍ የሚወክለው ጦርነትን ነው። "ሁሉም በጦርነት ይወድቃሉ" ወይም "ሁሉም በጦርነት ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉም በሰይፍ ይወድቃሉ
እዚህ ስፍራ "ሁሉም" የሚለው ቃል አጠቃላይ ነው። ይህ ማለት ብዙ ሰዎች ይሞታሉ ማለት ነው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት ሚሉትን ይመልከቱ)
Ezekiel 30:6
ያህዌ ይህን አለ
"ያህዌ የተናገረው ይህ ነው/ ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ይህ ዐረፍተ ነገር ያህዌ ሊናገር ያለውን ያስተዋውቃል።
ስለዚህ እነዚያ
"ሰዎች በዚህ መንገድ" ወይም "አገራት በዚህ ሁኔታ"
ግብጽን የሚደግፍ
"ግብጽን የሚረዳ"
ይወድቃሉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"ይሞታሉ" ወይም "ወደ ጥፋት/መበስበስ ይመጣሉ"
የጥንካሬዋ ኩራት ይዋረዳል
ይህ የሚወክለው ግብጽ ከእንግዲህ በሀይላቸው እንደማይመኩ ነው። የማይኩራሩበት ምክንያት ከእንግዲህ አቅም ስለማይኖራቸው ነው። "ግብጽ ከእንግዲህ በሃይላቸው አይኩራሩም" ወይም "ከእንግዲህ ግብጽ የሚኮሩበት አቅም አይኖራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከሚግዶል እስከ ሴና
ሕዝቅኤል በግብጽ ድንበሮች የሚገኙ ከተሞችን የሚጠቅሰው መላውን ግብጽ ለማመልከት ነው። "በመላው ግብጽ" ወይም "ከግብጽ ሰሜናዊ ድንበር አንስቶ እስከ ግብጽ ደቡባዊ ድንበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜሪዝም/ከዳር እስከ ዳር/ከጽንፍ እስከ ጽንፍ)
ወታደሮቻቸው በሰይፍ ይወድቃሉ
እዚህ ስፍራ "መውደቅ" የሚለው የሚወክለው መሞትን ሲሆን፣ "ሰይፍ" ጦርነትን ይወክላል። "የግብጽ ወታደሮች በጦርነት ያልቃሉ" ወይም አጥቂ ሰራዊት የግብጻውያንን ወታደሮች በጦርነት ይፈጃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
በተተወው ምድር/ባድማ መሃል ሆነው ይደነግጣሉ
"የግብጽ ተባባሪ አገሮች ወታደሮች በምድረበዳው/ባድማ ላይ ሲቀሩ ይደነግጣሉ"
በ...መሃል
"መካከል" ወይም "በመከበብ"
ከተሞቻቸው ከፈራረሱ ከተሞች መሃል ይሆናሉ
በፈራረሱ ከተሞች "መሃል" መሆን የሚለው የሚወክለው እንደ ሌሎች አገሮች የፈራረሱ ከተሞች መፈራረስን ነው። "ከተሞቻቸው እንደ ሌሎች አገሮች ከተሞች ይፈራርሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 30:8
አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ያህዌ ስለ ግብጽ የተናገራቸው ቃላት ናቸው።
ከዚያም እነርሱ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ከዚያም ሰዎች" ወይም 2) "ከዚያም ግብጻውያን"
እነርሱ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ ያውቃሉ
ያህዌ እርሱ ብቻ የበላይ እና ስልጣን ያለው መሆኑን እንደሚያውቁ እያመለከተ ነው። ይህ ተመሳሳይ ሀረግ በሕዝቅኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። "እውነተኛው ብቸኛ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ ያውቃሉ" ወይም "እኔ፣ ያህዌ ሉዓላዊ ሀይል እና ስልጣን እንዳለኝ ይረዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በግብጽ ላይ እሳት ሳስቀምጥ
እዚህ ስፍራ "በግብጽ ላይ እሳት ማስቀመጥ" የሚለው የሚወክለው ወደ ግብጽ ለጥቃት ወታደሮችን መላክ እና እሳት መለኮስን ነው። "ወደ ግብጽ ግብጽን እንዲያቃጥሏት ወታደሮችን ስልክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ረዳቶቿ ሁሉ ተደምስሰዋል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የግብጽን አጋሮች ሁሉ እደመስሳለሁ" ወይም "ወታደሮች ግብጽን የሚረዱትን ሁሉ ሲደመስሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
መልዕክተኞች አርፈው የተቀመጡትን ኩሽ ለማሸበር ከእኔ ፊት በመርከብ ይወጣሉ
መልዕክተኞች በወሬው የሚደናገጡትን፣ የግብጽን ጥፋት ወደ ኩሽ ይዘው ያመጣሉ
አርፈው የተቀመጡ ኩሽን ለማሸበር
"ተረጋግተው የተቀመጡትን ኩሽ ለማስፈራራት"
በግብጽ የጥፋት ቀን በመሃላቸው ጭንቀት ይሆናል
"ጭንቀት" የሚለው ረቂቅ ስም እና "ጥፋት" የሚሉት "መከራ" እና "ቅጣት" በሚሉ ቃላት ሊተረጎሙ ይችላሉ። "የኩሽ ሰዎች ግብጽን በምቀጣበት ቀን መከራ ይቀበላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ የሚሆነውን ያጎላል። "በእርግጥ!" ተብሎም ሊተረጎም ይችላል።
ይህ እየመጣ ነው
"ይህ" የሚለው የሚያመለክተው ግብጽ በምትቀጣበት ጊዜ ኩሽ አብሮ ሲቀጣ የሚደርስበትን "ታላቁን ስቃይ" ወይም "ታላቅ ሀዘን" ነው።
Ezekiel 30:10
ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
"እንዲህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቀጥሎ ምን እንደሚሆን ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ተመልከቱ።
በብዙ ግብጻውያን ላይ ፍጻሜ አደርጋለሁ
"ከእንግዲህ ግብጽ ብዙ ህዝብ እንዳይኖራት ይህን አደርጋለሁ"
በናቡከደነጾር እጅ
እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው የናቡከደነጾርን ወታደራዊ ሀይል ነው።ይህንን ቅጣት የሚያደርሰው ናቡከደነጾር ይሆናል።
እርሱ እና ከእርሱ ጋር ያለው ሰራዊቱ...ምድሪቱን ያጠፏታል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ናቡከደነጾርንና ሰራዊቱን... ምድሪቱን እንዲያጠፉ አመጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ እና የእርሱ ሰራዊት...ምድሪቱን ለመደምሰስ ይመጣሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እርሱ እና የእርሱ ሰራዊት ... የግብጽን ምድር እንዲያጠፉ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ እና ከእርሱ ጋር ያለ ሰራዊቱ፣ ለምድሪቱ ድንጋጤ ይሆናሉ
ያህዌ ናቡከደነጾርን "ለምድሪቱ ድንጋጤ" የሚለው መላው አገር የእርሱን ሰራዊት እጅግ ስለሚፈራ ነው። "እርሱ እና ከእርሱ ጋር ያለ ሰራዊቱ፣ ብዙ አገራትን ያስሸበሩ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰይፋቸውን በግብጽ ላይ ይመዛሉ
እዚህ ስፍራ " ሰይፋቸውን ይመዛሉ" የሚለው የሚወክለው በሰይፋቸው መዋጋታቸውን ነው። "ሰይፋቸውን ይዘው ግብጽን ይወጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሪቱን በተገደሉ ሰዎች ሙሏት
ይህ ባቢሎናውያን በጣም ብዙ ግብጻውያንን እንደሚገድሉ በግነት የተነገር ነው። የግብጽን ምድር የሚሞላ እስኪመስል ድረስ እጅግ ብዙ ግብጻውያን ይገደላሉ። "በድን በየስፍራው እስኪገኝ ድረስ እጅግ ብዙ ሰዎችን ግደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
Ezekiel 30:12
አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ያህዌ ስለ ግብጽ የተናገራቸው ቃላት ናቸው።
እኔ ወንዞች ደረቅ ምድር አደርጋለሁ
"የግብጽን ወንዞች አደርቃለሁ"
ምድርቱን ለክፉ ሰዎች እጅ አሳልፌ እሸጣለሁ
አንድ ሰው የሸጠውን እቃ ለገዢው አሳልፎ እንደሚሰጥ ያህዌ ግብጽን ባቢሎናውያን እንዲቆጣጠሯት አሳልፎ ይሰጣታል። "ምድሪቱን ክፉ ሰዎች እንዲቆጣጠሯት አሳልፌ እሰጣታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሷ ሙላት
"በምድሪቱ የሚገኝ ነገር ሁሉ"
Ezekiel 30:13
ጌታ ይህዌ እንዲህ ይላል
"እንዲህ" የሚለው ቃል ቀጥሎ የሚሆነውን ያመለክታል። ይህ በሕዝቅኤል 5፡5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ዋጋ ቢስ ለሆኑ ጣኦቶች ፍጻሜ አመጣለሁ
"ዋጋ ቢስ የሆኑ ጣኦቶችን አጠፋለሁ"
ሜምፊስ

ሜምፊስ በግብጽ ውስጥ የሚገኝ ትልቅ ከተማ ነበር። በአሁኗ ካይሮ አቅራቢያ ትገኝ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በግብጽ ምድር የሚገኝ ልዑል /የግብጽ ልዑል

"በግብጽ ምድር ከፍተኛ መሪ"

በግብጽ ምድር ሽብር አሰዳለሁ

እዚህ ስፍራ "በምድሪቱ ሽብት መስደድ" የሚለው የሚወክለው የምድሪቱ ሰዎች በጣም እንዲፈሩ ማድረግን ነው። "የግብጽ ሰዎች በጣም እንዲፈሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጳትሮስ

ይህች በደቡብ ግብጽ የምትገኝ አካባቢ ነበረች

በጣኔዎስ እሳት አነዳለሁ

"ጣኔዎስን በእሳት አቃጥላለሁ"

ጣኔዎስ

ጣኔዎስ በግብጽ ትገኝ የነበረች ሌላዋ ትልቅ ከተማ ነበረች

በቴቤስ የፍርድን ተግባር አፈጽማለሁ

"የፍርድን ተግባር" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ቅጣትን ነው። "ቴቤስን እቀጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ቴቤስ

ይህች የደቡባዊ ግብጽ ዋና ከተማ ነበረች

Ezekiel 30:15

አጠቃላይ መረጃ፡

እነዚህ ያህዌ ስለ ግብጽ የተናገራቸው ቃላት ናቸው።

በፔሉሲየም ላይ ቁጣዬን አፈሳለሁ

እዚህ ስፍራ "ቁጣዬን አፈሳለሁ" የሚለው የሚገልጸው ከታላቅ ቁጣው የተነሳ ህዝቡን መቅጣቱን ነው። "ፔሉሲየምን በታላቅ ቁጣ እቀጣለሁ" ወይም "እጅግ ከመቆጣቴ የተነሳ፣ ፔሉሲየምን እጅግ አድርጌ እቀጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ፔሉሲየም

በሰሜናዊ ግብጽ የምትገኝ የምሽግ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

የቴቤስን አእላፋት/አያሌ እቆርጣለሁ

እዚህ ስፍራ "መቁረጥ" የሚለው የሚገልጸው ሰዎችን መግደልን ነው። "በቴቤስ በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች እገድላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቴቤስ

ይህች የደቡባዊ ግብጽ ዋና ከተማ ነበረች።ይህ በሕዝቅኤል 3፡14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

ፔሉሲየም በታላቅ ስቃይ ውስጥ ትገባለች

እዚህ ስፍራ "ፔሉሲየም" በፔሉሲየም ከተማ ዙሪያ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን፤ "በታላቅ ስቃይ ውስጥ መሆን" የሚለው "ተሰቃዩ" በሚለው ግስ ሊተረጎም ይችላል። " የፔሉሲየም ሰዎች እጅይ ይሰቃያሉ" ወይም " የፔሉሲየም ሰዎች ከፍተኛ ስቃይ ያገኛቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ቴቤስ ትንኮታኮታለች/ትሰባበራለች

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጠላት የቴቤስን ቅጥሮች እና ግንቦች ይሰባብራል" ወይም "ጠላት ቴቤስን ያጠፋታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሜምፊስ ጠላት በየቀኑ ይገጥማታል

እዚህ ስፍራ "የጠላት መግጠም" የሚወክለው ጠላት ማየትን ወይም የጠላትን መኖር ነው። የከተማይቱ ስም በከተማይቱ ለሚኖሩ ሰዎች ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "የሜምፊስ ሰዎች በየዕለቱ ጠላት ይገጥማቸዋል" ወይም "ጠላት በየእለቱ የሜምፊስን ሰዎች ይዋጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሜምፊስ

ሜምፊስ በግብጽ በጣም ትልቅ ከተማ ነበረች። ይህ በሕዝቅኤል 30፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Ezekiel 30:17

አጠቃላይ መረጃ፡

እነዚህ ያህዌ ስለ ግብጽ የተናገራቸው ቃላት ናቸው።

ሄልዮቱ እና ቡባስቱ

እነዚህ በሰሜን ግብጽ የነበሩ ከተሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ ይወድቃሉ

እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ውጊያን ወይም ጦርነትን ነው። "በውጊያ ይሞታሉ" ወይም "በጦርነት ይሞታሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ጣፍናስ

ይህ በሰሜን ግብጽ የሚገኝ ትልቅ ከተማ ነበር።

ቀኑ ብርሃኑን አይሰጥም

ቀኑ የተገለጸው ራሱ ብርሃኑን ይዞ እንደሚያስቀር ተደርጎ ነው። "ቀኑ ይጨልማል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የብርታቷ ኩራት ያበቃል

ይህ የሚወክለው ግብጽ ከእንግዲህ በጥንካሬዋ ልትመካ እንደማትችል ነው። ከእንግዲህ ሊኮሩ የማይችሉበት ምክንያት አቅም ስለሚያጡ ነው። "ከእንግዲህ ግብጽ በብርታቷ አትመካም" ወይም "ከእንግዲህ ግብጻውያን የሚኮሩበት ብርታት አይኖራቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ደመና ይሸፍናታል

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጥቁር ጨለማ የሚወክለው የግብጽ ሰዎች ምን ያህል ሀዘን እንደሚወድቅባቸው ነው። "በግብጽ ላይ ደመና ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ከሚደመሰሰው ነገር ላይ ሁሉ ከሚነሳው አቧራ በግብጽ ላይ ደመና ይሆናል። "በግብጽ ላይ የደመና አብዋራ ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሴት ልጆቿ

x

Ezekiel 30:20

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ የፈርኦንን ሰራዊት ደካማ እንደሚያደርግ የሚናገረው፣ የፈርኦንን ክንድ እንደ መስበር እና የተሰበረው የፈርኦን ክንድ ፈውስ እንደሌለው እንደዚህም ሰራዊቱ ዳግም ጠንካራ ሊሆን እንደማይችል አድርጎ ነው። (ምሳሌዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም እንዲህ ሆነ

ይህ ሀረግ እዚህ ስፍራ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማመልከት ነው። ቋንቋችሁ ይህን ለማድረግ መንገድ ካለው፣ እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

አስራ አንደኛው አመት

ይህ ንጉሥ ዮአኪን በስደት ወደ ባቢሎን በሄደ አስራ አንደኛው አመት ነው። ይህ በሕዝቅኤል 26፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

በመጀመሪያው ወር፣ በወሩ ሰባተኛ ቀን

"በመጀመሪያው ወር በሰባተኛው ቀን።" ይህ በዕብራውያን የወር አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር ነው። ሰባተኛው ቀን በምዕራባዊያን አቆጣጠር ሚያዚያ መጀመሪያ አካባቢ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ

"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘላዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እኔ የፈርኦንን ክንድ ሰብሬያለሁ

 

እዚህ ስፍራ "ክንድ" የሚወክለው የንጉሥን ጠንካራ ሰራዊት ነው። (ምሳሌዎች እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
እነሆ
"ቀጥሎ የምናገረው እውነተኛ እና ትልቅ ነገር ስለሆነ ትኩረት ስጡት"
ክንዱ አልተጠቀለለም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ክንዱን ማንም አላሰረውም" ወይም "ማንም ክንዱን አልጠቀለለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ወይም እንዲፈወስ በጨርቅ/ፋሻ አልታሰረም
እዚህ ስፍራ "እንዲፈወስ በጨርቅ/ፋሻ መጠቅለል" የሚለው የሚያመለክተው አጥንቱ መልሶ እንዲጠገንእና እንዲፈወስ ክንዱን ጠበቅ አድርጎ በፋሻ መጠቅለልን ነው።
Ezekiel 30:22
አጠቃላይ መረጃ፡
እግዚአብሔር ስለ ፈርኦን ሰራዊት እንደ ተሰበረ ክንድ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። እንደዚሁም ደግሞ የባቢሎንን ሰራዊት ማጠንከርን የባቢሎን ንጉሥን ክንድ እንደ ማጠንከር አድርጎ ይናገራል።
ጌታ ያህዌ ይህን አለ/ያህዌ እንዲህ አለ
ይህ በሕዝቅኤል 3፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ጠንካራው እና የተሰበረው ሁለቱም
"ጤነኛ የሆነው ክንድ እና አስቀድሞ የተሰበረው ክንድ ሁለቱም"
ሰይፉ ከእጁ እንዲወድቅ አደርጋለሁ
"ከፈርኦን እጅ ሰይፉን መትቼ አስጥለዋለሁ"
ግብጽን በህዝቦች መሃል እበትናለሁ፣ እናም እነርሱን በምድር ዙሪያ እበትናቸዋለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። በሕዝቅኤል 12፡15 ላይ ተመሳሳይ ሆነው ሀረግ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በምድር ዙሪያ
"ሰዎች በሚኖሩበት ስፍራ ሁሉ"
የባቢሎንን ንጉሥ ክንዶች አበረታለሁ
"የባቢሎንን ንጉሥ ክንዶች ጠንካራ አደርጋለሁ"
በባቢሎን ንጉሥ ፊት ያቃስታል
"የባቢሎን ንጉሥ ግብጽን ሊያጠቃ ሲመጣ፣ ፈርኦን ያቃስታል።"
ማቃሰት
ማቃሰት ሰዎች ብዙ ስቃይ ሲደርስባቸው ወይም ሲያጣጥሩ የሚያሰሙት ድምጽ ነው።
የሚያጣጥር ሰው ማቃሰት
"ሰው እያጣጣረ ሲያቃስት" ወይም "እያጣጣረ እንደሚገኝ ሰው"
Ezekiel 30:25
አጠቃላይ መረጃ፡
እግዚአብሔር ስለ ግብጽ እና ባቢሎን ሰራዊቶች የንጉሦቻቸው ክንድ እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። እንደዚሁም የባቢሎንን ሰራዊት ሌሎችን ለማጥቃት እንዲችሉ እርሱ ሰይፍ እነዳለውና ሰይፉንም በባቢሎናውያን ንጉሥ እጅ ላይ እንዳስቀመጠው አድርጎ ይናገራል። (ምሳሌዎች የሚለውን መልከቱ)
እኔ የባቢሎን ንጉሥን ክንዶች አጠነክራለሁ
እዚህ ስፍራ "ክንዶች" የሚለው ለሰራዊቱ ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "የባቢሎንን ንጉሥ ሰራዊት አበረታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የፈርኦን ክንዶች በሚወድቁበት ጊዜ
እዚህ ስፍራ "የፈርኦን ክንዶች" የሚለው ለእርሱ ሰራዊት ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ነው። "በሚወድቁበት ጊዜ" የሚለው የሚወክለው መድከምን ነው። "ነገር ግን የፈርኦን ሰራዊት ጠላት ማሸነፍ የማይችሉ ይሆናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያም እነርሱ
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተከታዩን ሊሆን ይችላል 1) "ግብጻውያንን" ወይም 2) "ያህዌ ያደረገውን የሰሙትን ሰዎች ሁሉ"
ከዚህ ጋር እርሱ የግብጽን ምድር ያጠቃል
"እናም የባቢሎን ንጉሥ በእኔ ሰይፍ የግብጽን ምድር ያጠቃል"
ግብጽን በህዝብ መሃል እበትናለሁ ደግሞም በምድር ሁሉ እበትናቸዋለሁ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይህ በህዝቅኤል 12፡ 15 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 31
Ezekiel 31:1
እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ የተፈጸመን ጠቃሚ ትዕይንት ለማጉላት/ለማመልከት ነው። በእናንተ ቋንቋ ይህን ለማድረግ የሚጠቀምበት መንገድ ካለ እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።
በአስራ አንደኛው አመት
"በ11ኛ አመት።" ይህ ማለት ንጉሥ ዮአኪን ባቢሎን በስደት ከተወሰደ ከአስራ አንድ አመት በኋላ ማለት ነው። ይህ በህዝቅኤል 26፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ንጉሥ ዮአኪን በተሰደደ በአስራ አንደኛው አመት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተከታታይ ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
በሶስተኛው ወር፣ በወሩ ሶስተኛ ቀን
"በሶስተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን።" ይህ በዕብራውያን አቆጣጠር ሶስተኛው ወር ነው። ይህ የመጀመሪያ ቀን በምዕራባውያን አቆጣጠር በሰኔ መጀመሪያ አቅራቢያ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
በታላቅነትህ፣ ማንን ትመስላለህ?
"እንዳንተ ታላቅ ማን ነው?" ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው አዲስ ርዕስ ለማስተዋወቅ ነው። ፈርኦን የእርሱ አገር ከሁሉም ታላቅ እንደሆነ ያስባል፣ እግዚአብሔር ግን ስለ ሌላ ታላቅ አገር ሊናገር ነው። "አንተ ሀይሉ እንደ አንተ አገር ታላቅ የሆነ ሌላ አገር እንደሌለ ታስባለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 31:3
አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ስለ አሦር እግዚአብሔር ለፈርኦን የተናገራቸው ቃሎች ናቸው። እግዚአብሔር በትልቅ በጥድ ዛፍ መልክ በምሳሌ መልዕክቱን ተናግሯል። (ምሳሌዎች የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ!
"ተመልከት!" ወይም "አድምጥ!" ወይም "ልነግርህ ስላለው ነገር ትኩረት ስጥ!"
አሦር የጥድ ዛፍ ነበር
በዚህ ምሳሌ፣ እግዚአብሔር ስለ አሦር ታላቅ ዛፍ እንደነበረ በመናገር ስለ አሦራውያን ምን ያህል ታላቅ እና ሀይለኛ እንደነበሩ አጉልቶ ይናገራል። ምሳሌው እስከ ሕዝቅኤል 31፡9 ድረስ ይቀጥላል። "አሦር እንደ ጥድ ዛፍ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምሳሌዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ቅርንጫፎቹ የዛፉን አናት አበጁ
"አናቱ ከሌሎች ዛፎች በላይ ነበር።" አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ይህንን "የዛፉ ጫፍ ደመና ደርሷል" በማለት ተርጉመውታል።
በብዙ ውሃ አደጓል
"ጥድ ብዙ ውሃ ስላላው፣ በጣም ትልቅ ሆኖ ያድጋል"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ጥልቁ ውሃ ግዙፍ አድርጎታል
"ከምድር ጥልቅ ስፍራ የሚገኘው ውሃ ጥድ በጣም ትልቅ ሆኖ እንዲያድግ አድርጓል"
ጅረቶች በሜዳ ወደሚገኙ ዛፎች ሁሉ ፈሰሱ
"የወንዞች ምንጮች በሜዳ ወደሚገኙ ዛፎች ሁሉ ይፈሳሉ"
Ezekiel 31:5
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።
ታላቅ ቁመቱ በሜዳ ከሚገኙ ሌሎች ዛፎች ሁሉ ይበልጣል
"ጥዱ ከማናቸውም በሜዳ ከሚገኙ ዛፎች ይልቅ ትልቅ ነበር"
ቅርንጫፎቹ በጣም ብዙ ይሆናሉ
"በጣም ብዙ ቅርንጫፎችን ያበቅላል"
በሚያድጉበት ጊዜ ከሚያገኙት ብዙ ውሃ የተነሳ
"ብዙ ውሃ ስላለው"
እያንደንዱ የሰማይ ወፍ በቅርንጫፎቹ ላይ ጎጆ ይሰራል
"በሰማይ የሚበሩ ሁሉም አይነት ወፎች በቅርንጫፎቹ ላይ ጎጆ ይሰራል"
የሜዳ ፍጥረታት ሁሉ በጥላው ስር ልጆቻቸውን ሲወልዱ
"እናም በሜዳ የሚኖሩ ሁሉም ፍጥረታት ከጥድ ዛፍ ቅርንጫፍ በታች ሲወልዱ"
ከጥላው ስር የሚኖሩ ህዝቦች ሁሉ
"በዚያ ዛፍ ስር የሚኖሩ ታላላቅ ህዝቦች ሁሉ።" እዚህ ስፍራ "ህዝቦች" የሚለው የሚወክለው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። "ከነዚያ አገራት ሁሉ የሆኑ ሰዎች በዚያ ዛፍ ጥላ ስር ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በታላቅነቱ እና በቅርንጫፎቹ ርዝመት ውብ ነበር
"በጣም ትልቅ እና ቅርንጫፎቹም በጣም ረጃጅም ስለነበሩ ውብ ነበር።"
Ezekiel 31:8
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።
በእግዚአብሔር ገነት ያሉ ዝግባዎች/ ጥዶች ሊስተካከሉት አይችሉም
እነዚህ እግዚአብሔር ለፈርኦን የተናገራቸው ቃላት እንደመሆናቸው፣ በመጀመሪያ መደብ ሊተረጎሙ ይችላሉ። "በገነቴ የሚገኙ የጥድ ዛፎች እንደነዚያ ዛፎች ያህል ትልልቅ አልነበሩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ገነት
ይህ "ኤደን ገነት" ለሚለው ሌላው የአገላለጽ መንገድ ነው።"
ከጥድ ዛፎች መሃል የትኛውም ቅርንጫፉ
ያህዌ ዛፎቹ ምን ያህል ቅርንጫፍ እንዳላቸው እያነጻጸረ ነበር። "ከእስታ ዛፎቹ የትኛውም እንደ ጥድ ዛፍ ብዙ ቅርንጫፎች የሉትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ዝግባ ዛፎች
የዝግባ ዛፍ በጣም ብዙ ቅርንጫፎች አሉት። በጣም ሊያድጉ ይችላሉ። "ዝግባ" በህዝቅኤል 27:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ
ተራው/ማናቸውም ዛፍ የእርሱን ያህል ቅርንጫፍ አይኖረውም
ያህዌ የጥድን ዛፍ ረጅም ቅርንጫፎች ከተራ ዛፎች ቅርንጫፎች ጋር እያነጻጸረ መሆኑ ተጠቅሶ ነበር። "ማናቸውም ዛፍ እንደ ጥድ ዛፍ ያህል ቅርንጫፍ የለውም" ወይም "የትኛውም ዛፍ የጥድ ዛፍን ያህል ረጅም ቅርንጫፎች የለውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ተራ ዛፍ
ተራ ዛፍ ረጅም፣ቅጠላማ ጠንካራ ቅርንጫፍ ያለው ዛፍ ነው። ከበርሰነት ዛፍ ጋር ተመሳሳይ ነው። (የማይታወቀውን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)
በውበቱ እርሱን የሚመስል ነበር
"የጥድ ዛፍን ያህል ውበት አለው"
ከብዙ ቅርንጫፎቹ ጋር ውብ አድርጌ ሰራሁት
"ብዙ ረጃጅም ቅርንጫፎችን በማድረግ ጥድን አስዋብኩት"
ቀኑበት
"በጥድ ዛፍ ቀኑበት"
Ezekiel 31:10
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።
ስለዚህም ጌታ ያህዌ እንዲህ አለ
ያህዌ እስከ ተናገረ ድረስ ይህ በአንደኛ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "ስለዚህ፣ ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
የዛፉን ጭንቅላት በቅርንጫፎቹ መሃል አደረገ
"ጫፉ ከሌሎች ዛፎች ቅርንጫፎች በላይ ነበር።" አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች "የዛፉ ጭንቅላት እስከ ደመና ደርሶ ነበር" ሲሉ ተርጉመውታል።
ለታላላቅ አገራት እጅ አሳላፌ ሰጥቼዋለሁ
"እጅ" የሚለው ቃል በቁጥጥር ስር ማድረግን ይወክላል። "በጠንካራ አገራት ሀይል ስር አድርጌዋለሁ" ወይም "የታላላቅ አገሮችን ሀይል በላዩ አምጥቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አውጥቼ ጥየዋለሁ
"ክፉ ከመሆኑ የተነሳ፣ ጥዱን ከሚበቅልበት ምድር አውጥቼ ጥየዋለሁ"
Ezekiel 31:12
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።
ለሁሉም ህዝብ ሽብር የሆነው ማን ነበር
"ሽብር" የሚለው ረቂቅ ስም "ፍርሃት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። እዚህ ስፍራ "አገሮች" የሚለው የሚወክለው የአገሮችን ህዝቦች ነው። "የአገራትን ህዝቦች ያስፈራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
አቆርጠዋለሁ
"ጥዱን ቆርጬ እጥለዋለሁ"
ትልቁ ቅርንጫፍ ተገንጥሎ ይወድቃል
"ባዕዳን የጥዱን ትልቅ ቅርንጫፍ ይሰብሩታል"
ትልቅ ቅርንጫፍ
ትልቅ ቅርንጫፍ በጣም ትልልቅ የሆኑ የዛፍ ቅርንጫፎች ናቸው። ብዙውን ጊዜ፣ በርካታ ትንንሽ ቅርንጫፎች በላዩ ይበቅሉበታል።
ከጥላው ስር ይወጣሉ
"የጥዱን ጥላ ይተዋሉ"
Ezekiel 31:13
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።
የሰማይ ወፎች ሁሉ
"በሰማይ ላይ የሚበሩ ወፎች ሁሉ"
ግንድ
ግንድ ከምድር በላይ የሚገኘው በጣም ወፍራም የሆነ ሌላውን የዛፉን ክፍል የሚሸከም ነው።
እያንዳንዱ የሜዳ እንስሳ ከቅርንጫፉ ስር ይሰበሰባል
"የዱር እንስሳት በጥድ ቅርንጫፍ መሃል ይኖራሉ"
የትኞቹም ሌሎች ዛፎች በውሃ እንደ እርሱ አላደጉም
"ሌሎች የትኞቹም አይነት ዛፎች እንደ እርሱ ብዙ ውሃ አላገኙም"
ቅርንጫፋቸውን ከሁሉም ከፍ አስካሉት ዛፎች ድረስ ከፍ ያደርጋሉ
"ከሌሎች ዛፎች ቅርንጫፎች በላይ ያድጋሉ።" አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን "ጫፋቸውን በደመና መሃል ያደርጋሉ" ብለው ይገልጻሉ።
በውሃ ዳርቻ ያደጉ ሌሎች የትኞቹም ዛፎች እስከዚያ ድረስ ከፍ ብለው አያድጉም
"የትኞቹም ብዙ ውሃ ያገኙ ሌሎች ዛፎች ዳግም እስከዚያ ከፍታ ድረስ አያድጉም"
ሁሉም ከምድር በታች እንዲሆኑ ሞት ተፈርዶባቸው ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ደግሞም "ሞት" የሚለው ረቂቅ ስም "ሞተ" ሊባል ይችላል። "ስለዚህም እኔ ሁሉም እንዲሞቱ እና ከምድር በታች እንዲወርዱ አደረግሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)
ወደ ምድር ጥልቅ ከወረዱ፣ ከሰው ልጆች መሃል
"ከሞቱ እና ወደ መቃብር ከወረዱ ሰዎች ጋር መሆን"
ወደ ጉድጓድ
ይህ መቃብርን ያመለክታል፤ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሞት ዓለም መግቢያ ተደርጎ

ይታሰብ ነበር፣ ጉድጓድም ደግሞ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 26:20 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 31:15
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል። እዚህ ስፍራ፣ ያህዌ ውሃዎች፣ ሊባኖስ፣ እና የዱር ዛፎች ሁሉም ለጥዱ እንዳዘኑ አድርጎ፤ በተቆረጠው ጥድ ምክንያት ስለተፈጠረው ታላቅ ሀዘን ይናገራል።
ጥዱ ወደ ሲኦል በወረደ ቀን
"ወደ ሲኦል መውረድ" የሚለው ሀረግ "መሞት" ማለት ነው። "ጥዱ በሚሞትበት ቀን" ወይም "ጥዱ በሚቆረጥበት ቀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ወደ ምድር ሀዘንን አመጣለሁ
"ሀዘን" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ምድር እንድታዝን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሱ ላይ ጥልቅ ውሃ አከድናለሁ
"መክደን" የሚለው ቃል ምናልባት ሊያመለክት የሚችለው ለሀዘን ልብስ መልበስን ይሆናል። "የምንጮች ውሃ ለጥዱ እንዲያዝን አደርጋለሁ" ወይም "የሚያጠጣው የምንጭ ውሃ ለእርሱ እንዲያዝን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የውቅያኖስ ውሆችን ወደ ኋላ እመልሳለሁ
"በውቅያኖስ ያለ ውሃ ምድርን እንዳያጠጣ አደርጋለሁ"
ታላላቅ ውሆችን እይዛለሁ
"ከእንግዲህ በቂ ውሃ እንዳይገኝ አደርጋለሁ"
ለእርሱ ወደ ሊባኖስ ሀዘን አመጣለሁ
"ሀዘን" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ሊባኖስ ለጥዱ እንዲያዝን አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 31:16
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።
ወደ ጉድጓድ ከወረዱት ጋር ወደ ሲኦል ስጥለው
እዚህ ስፍራ "ወደ ሲኦል መጣል" የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ መግደል ማለት ነው። "ጉድጓዱ" የሚያመለክተው መቃብርን ነው፤ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሙታን ዓለም መግቢያ ተደርጎ ሲታሰብ፣ ጉድጓድም ደግሞ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 31:14 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "እኔ ጥዱን ስገድል እና እርሱም ከሞቱት ጋር ሁሉ ወደ ሲኦል ሲወርድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
በምድር ታችኛው ክፍል
"እነዚያ ቀድሞውኑ በምድር ጥልቅ ስፍራ ያሉ ናቸው።" ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ቀድሞውኑ ሞተው የነበሩ እና አሁን በሲኦል የሚገኙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የተመረጡ እና የሊባኖስ ምርጥ ዛፎች፤ ውሃ በሚገባ የጠጡ ዛፎች
"ውሃ በሚገባ ያገኙ፣ ሁሉም የሚፈልጋቸው የሊባኖስ ምርጥ ዛፎች" ይህ በምድር ታችኛው ስፍራ የሚገኙ የኤደንን ዛፎች መግለጽ ነው።
የተመረጠ
ይህ በጣም ጥሩ ስለሆነ ሁሉም የሚፈልገው ነገር ነው
Ezekiel 31:17
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ ጥድ የሚናገረው ምሳሌ ቀጥሏል።
እነርሱም ደግሞ ከእርሱ ጋር ወደ ሲኦል ይወርዳሉ
እዚህ ስፍራ "ወደ ሲኦል... ይወርዳሉ" የሚለው መሞት ለሚለው ፈሊጣዊ አገላለጽ ነው። "እነዚያ የሊባኖስ ዛፎች ይሞታሉ፣ ደግሞም ከጥዱ ጋር ወደ ሲኦል ይወርዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በሰይፍ የተገደሉ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው የሚወክለው በጦርነት የተዋጓቸውን ጠላቶቻቸውን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጠላት በሰይፍ የገደላቸው" ወይም "በጦርነት የሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ደራጊ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 32
Ezekiel 32:1
እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህንን ለማድረግ የሚችልበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።
በአስራ ሁለተኛው ወር... በወሩ መጀመሪያ
ይህ በዕብራውያን አቆጣጠር አስራ ሁለተኛው እና የመጨረሻው ወር ነው። የመጀመሪያው ቀን በየካቲት መጨረሻ አቅራቢያ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)
በአስራ ሁለተኛው ወር
ይህ የሚያመለክተው የንጉሥ ዮአኪንን ግዛት አስራ ሁለተኛ አመት ነው። "በንጉሥ ዮአኪን ስደት አስራ ሁለተኛ አመት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተከታታይ ቁጥሮች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
ከፍ ማድረግ
"መዘመር"
አንተ ልክ እንደ ደቦል አንበሳ ነህ... በባህር ውስጥ እንደሚኖር አውሬ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እርሱ እንደ አንበሳ ነኝ ብሎ ያስብ ነበር፣ ነገር ግን እርሱ በእርግጥ እንደ አውሬ ብቻ ነበር፣ ወይም 2) እርሱ እንደ አንበሳ እና አውሬ ነበር።
በአገራት መሃል እንደ ደቦል አንበሳ
አንበሶች ከሌሎች እንስሳት ይልቅ ጠንካራ እንደሆኑ፣ ግብጽ ከሌሎች አገራት ይልቅ ጠንካራ ነበረች። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በባህሮች ውስጥ እንዳለ አውሬ
ፈርኦን ሀያል ነበር፣ ነገር ግን እርሱ በውሃ ውስጥ እንዳለ እንደዚህ አውሬ ለሌሎች ችግር ምክንያት ነበር። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አውሬ
አውሬ ትልቅ እና አደገኛ እንስሳ ነው። ይህኛው አዞ ሊሆን ይችላል። ይህ በሕዝቅኤል 29:3 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።
Ezekiel 32:3
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ፣ አውሬ እንደሆነ፣ ምናልባት በውሃ ውስጥ የሚኖር አዞ እንደሆነ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል
ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
ይህ በሕዝቅኤል 5:5 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
በብዙ ጉባኤ ፊት በአንተ ላይ ወጥመዴን እዘረጋለሁ
እግዚአብሔር ፈርኦንን የሚቀጣበት መንገድ የተገለጸው ንጉሡ አውሬ ሆኖ በወጥመድ እንደሚያዝ ተደርጎ ነው። "ስለዚህም እኔ ብዙ ህዝብ ሰብስቤ በፊታቸው ወጥመዴን በአንተ ላይ እዘረጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በሜዳ ላይ እተውሃለሁ
"በሜዳ ላይ ያለ ተስፋ እጥልሃለሁ።" በውሃ ውስጥ በነበረበት ጊዜ አስፈሪ እና ሀይለኛ የነበረው አውሬ፤ በደረቅ ምድር ላይ ሲጣል አንዳች ማድረግ አይችልም።
የሰማይ ወፎች ሁሉ
"በሰማይ ላይ የሚበሩ ወፎች በሙሉ"
በምድር ላይ የሚኖሩ እንስሳች ሁሉ ረሃብ አንተን በመብላት ይረካል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የምድር እንስሶች ሁሉ እስኪጠግቡ ድረስ በድንህን እንዲመገቡ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 32:5
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ስለ ፈርኦን መናገሩን እና ፈርኦንን በውሃ ውስጥ ከሚኖረው አውሬ ጋር ማነጻጸሩን ቀጥሏል።
በትል የተሞላው ሬሳህ
ትሎች እርሳህ እንዲበሰብስ ያደርጋሉ። "የበሰበሰው በድንህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የምንጭ ዳርቻዎች በደምህ ይሞላሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ምንጮችን በደምህ እሞላቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 32:7
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ በግብጽ ላይ የሚያደርገውን ለፈርኦን መናገሩን ቀጥሏል።
እኔ አንተን በማጠፋበት ጊዜ
የሰውን ህይወት እንደሚጠፋ ሻማ አድርጎ መናገር የተለመደ ነበር። "እኔ አንተን በምደመስስበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ሰማያትን እከድናለሁ
ያህዌ ሰማያትን ሸፍኖ ከዋክብትን እንደሚያጨልም አድርጎ ይናገራል። "በሰማይ ያለው ነገር ሁሉ እንዲጨልም አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በምድርህ ላይ ጨለማ አመጣለሁ
ጨለማ የተገለጸው አንድ ሰው በሁሉም ነገር ላይ እንደሚዘረጋው ነገር ተደርተጎ ነው። "ምድርህን ጨለማ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 32:9
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለፈርኦን መናገሩን ቀጥሏል።
በብዙ ሰዎች ላይ ፍርሃት አመጣለሁ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚወክለው የሰዎችን ስሜት ነው። "የብዙ ሰዎች ልብ እንዲፈራ/እንዲሸበር አደርጋለሁ" ወይም "ብዙ ሰዎች እንዲፈሩ/እንዲሸበሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ በማታውቀው ምድር
ያህዌ ግብጽን የሚያጠፋበት መንገድ፣ ፈርኦን በማያውቃቸው የተለያዩ አገሮች የሚኖሩ ሰዎች ጭምር እንዲፈሩ ያደርጋል።
በአገራት መሃል አንተን የምጥልበት ጊዜ ሲመጣ
በንጉሡ የተመሰለው የግብጽ ህዝብ የተገለጸው እንደሚናድ ህንጻ ተደርጎ ነው። "አገራት እኔ አንተን የጣልኩበትን መንገድ ሲሰሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ሰይፌን ሳወዛውዝ
እዚህ ስፍራ ሰይፍ ማወዛወዝ የሚወክለው ሰይፍን መጠቀምን ነው። "ሰይፌን ስጠቀምበት/በሰይፌ ስበቀል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በእያንዳንዱ ቅጽበት ሁሉም በአንተ ምክንያት ይንቀጠቀጣሉ
እዚህ ስፍራ "መንቀጥቀጥ" ሰዎች በጣም በፈሩ ጊዜ የሚሆኑትን ያሳያል። "እያንዳንዳቸው ከፍረሃታቸው የተነሳ መንቀጥቀጣቸው ይቀጥላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
አንተ በምትወድቅበት ቀን
መውደቅ የሚለው ሀሳብ ("መውደቅ") የሚወክለው መሞትን ነው። "እኔ አንተን በማጠፋበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 32:11
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለፈርኦን መናገሩን ቀጥሏል።
የባቢሎን ንጉሥ ሰይፍ በአንተ ላይ ይመጣል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚወክለው ሰራዊትን ነው። "የባቢሎን ሰራዊት ንጉሥ አንተን ያጠቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እያንዳንዱ ተዋጊ ለህዝብ ሽብር ይሆናል
"ሽብር" የሚለው ረቂቅ ስም "አሸባሪ" ወይም "አስፈሪ" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "እያንዳንዱ ተዋጊ ህዝብን ያሸብራል" ወይም "ከእነርሱ እያንዳንዱ ህዝቡ እንዲፈራ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የግብጽን ኩራት ከንቱ ያደርጋል
"መኩራት" የሚለው ረቂቅ ስም "ኩራት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ከእንግዲህ ግብጻውያን እንደይኮሩ ያደርጋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
አእላፋቶቿን ያጠፋል
እዚህ ስፍራ "ሁሉ" የሚለው ምናልባት የንጉሡን ብዙ ቁጥር ያለውን ወታደር፣ እና ምናልባትም ሌሎች ሰዎችንም ጨምሮ ሊሆን ይችላል። "በግብጽ የሚኖሩ አያሌ ሰዎችን ይገድላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
Ezekiel 32:13
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ መናገሩን ቀጥሏል።
ከብዙ ውኆች አጠገብ
"ብዙ ውሃ በሚገኝበት ስፍራ"
የሰው እግር ውኆችን አያናውጥም
እዚህ ስፍራ እግር ለሰው ሁለንተና ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "ከእንግዲህ ሰዎች በእግራቸው ውኆችን አይበጠብጡም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ውኆችን መበጥበጥ
ንጹሁን ውሃ ማደፍረስ
የከብቶች ኮቴ ይበጠብጣቸዋል
ኮቴ ለከብቶች ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ/ ነው። "ከብቶች በኮቴያቸው ይበጠብጧቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያም ውሃቸውን አጠራለሁ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ውሃውን የጠራ አደርገዋለሁ" ወይም 2) "ውሃውን ንጹህ አደርጋለሁ።" ማንም ውሃውን በማይበጠብጠው ጊዜ፣ ዝቃጩ ከታች ይቀመጣል፣ ውሃውም ንጹህ ይሆናል"
ወንዛቸው እንደ ዘይት እንዲፈስ አደርጋለሁ
ዘይት በቀስታ እና በእርጋታ ይፈሳል። "ወንዞቹ እንደ ዘይት በቀስታ እንዲፈሱ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 32:15
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ መናገሩን ቀጥሏል።
የግብጽን ምድር የተረሳች/የተተወች በማደርግበት ጊዜ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የግብጽን ምድር ማንም የማይኖርበት በማደርግበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ

የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሪቱ ፍሬያማነቷን ባጣች ጊዜ
"አገሪቱ ሀብቷን እንድታጣ ባደረግሁ ጊዜ"
በውስጧ የሚኖሩትን በጠቃሁ ጊዜ
እዚህ ስፍራ ማጥቃት የሚለው ሀሳብ የሚወክለው ማጥፋትን/መደምሰስን ነው። "በውስጧ የሚኖሩትን ሁሉ ባጠፋሁ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሷ ውስጥ… በእርሷ ላይ
በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ቋንቋ አገራትን እና ምድርን በሴት ጾታ መግለጽ የተለመደ ነበር። "በእርሷ ውስጥ.. በእርሷ ላይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ እርሱ ያህዌ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ ሲል፣ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የህዝቦች ሴት ልጅ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "የሌሎች አገራት ሴቶች" ወይም 2) "የሌሎች አገራት ሰዎች"
በግብጽ ላይ፣ በእርሷ አእላፋት/ብዙዎች ላይ
"ስለ ግብጽ፣ ስለ እርሷ አእላፋት/ብዙዎች" ወይም "በግብጽ ላይ ስለሚደርስ ጥፋት፣ በአእላፍቶቿ/በበርካታ ሰዎቿ ላይ ስለሚደርስ ጥፋት"
Ezekiel 32:17
እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህንን ለማድረግ የሚችልበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።
በአስራ ሁለተኛው አመት
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ባቢሎናውያን እስራኤላውያንን ወደ ባቢሎን በወሰዱ በአስራ ሁለተኛው አመት ሆነ ወይም 2) ይህ ባቢሎናውያን ዮአኪንን ወደ ባቢሎን በወሰዱ በአስራ ሁለተኛው አመት ሆነ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
እነርሱን አዋርዳቸው - እርሷ እና የግርማዊ ህዝቦቿን ሴት ልጇቿ
እግዚአብሔር ለህዝቅኤል ይህ ይሆን ዘንድ ትንቢታዊ ትዕዛዝ እየሰጠው ሊሆን ይችላል
የእርሷ
ዳግም፣ የግብጽ ምድር በሴት ተገልጻለች
የግርማዊ ህዝቧቿ ሴት ልጆች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "የሃያላን ሀገሮች ህዝቦች" ወይም 2) "ሌሎች ሀያልን ሀገሮች"
የታችኛው ምድር
"ከምድር በታች የሚገኝ ስፍራ።" ሰዎች ሲሞቱ፣ ምድር ውስጥ ይቀበራሉ። ስለዚህ "ወደታች ከምድር በታች… አውርዳቸው" ማለት "ግደላቸው" ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ጉድጓድ ከወረዱት ጋር
"ከሌሎች ከሞቱት ከእያንዳንዳቸው እና ወደ አፈር ከገቡት ጋር"
ጉድጓዱ
"ጉድጓዱ" የሚለው የሚያመለክተው መቃብርን ነው፣ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሞት ዓለም መግቢያ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ እንደዚሁም ደግሞ ጉድጓድ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 31፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 32:19
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል። ስለ ግብጽ ህዝብ በሴት ጾታ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ በእርግጥ ከሌሎቹ በውበት ትበልጣላችሁን? ታች ወርዳችሁ ካልተገረዙት ጋር ተጋደሙ።
ይህ ጥያቄ ነው ደግሞም ነቢዩ ግብጻውያንን እንዲጠይቅ ያዛል፡ "ወደ ታች ውረዱ፣ ደግሞም ካልተገረዙት ጋር ተጋደሙ። ሁሉንም እንዲህ ብለህ ጠይቅ፡ ‘እናንተ ከሁሉም ይልቅ የተዋባችሁ ናችሁን?'" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ታች ውረዱ
ወደ ታች ወደ ሲኦል መውረድ እንዳለባቸው ያመለክታል። "ወደ ታች ወደ ሲኦል ውረዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ተጋደሙ
በሞት እንደሚሆነው። የእናንተ ቋንቋ ሞተው ለተጋደሙ ሰዎች በህይወት እያሉ ከተጋደሙ ሰዎች የተለየ ቃል ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።
እናንተ በእርግጥ ከሌላው ይልቅ የተዋባችሁ ናችሁን?
ይህ ጥያቄ በእርግጥ ዐረፍተ ነገር ይሰራል። "እናንተ ከማንም ይልቅ ውብ አይደላችሁም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ይወድቃሉ
"ግብጽ እና ህዝቧ ይወድቃሉ"
በሰይፍ የተገደሉ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው የሚወክለው በጦርነት የተዋጓቸውን ጠላቶቻቸውን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ጠላት በሰይፍ የገደላቸው" ወይም "በጦርነት የሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
ሰይፍ ተመዞ ነበር!
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" በሰይፎች ስለሚዋጉ ሰዎች ለጦርነት ሜቶኖሚ/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ጦርነት ተጀመረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ለሰይፍ ተሰጥታ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ግብጽን ለሰይፍ አሳልፌ ሰጥቻታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሷን እና አእላፋቷን ይይዛሉ
"ጠላቶቿ ግብጽን እና ህዝቧን ይይዛሉ"
ስለ ግብጽ እና ረዳቶቿ
"ስለ ግብጻውያን እና ከእነርሱ ጋር ስለሚተባበሩ"
Ezekiel 32:22
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል በሲኦል ስለሚገኙ ህዝቦች መናገሩን ቀጥሏል። ምክንያቱም ያህዌ ለሕዝቅኤል ለወደፊቱ ጊዜ፣ ወይም ስለአሁን ጊዜ ወይም ስለ መጪው ጊዜ የሚያሳየው ለእነዚህ ቁጥሮች እና ለተከታዮቹ ቁጥሮች ተስማሚ ሊሆን ይችላል።
አሦር ከመላው ጉባኤዋ ጋር በዚያ ናት
የአሦር ምድር በሴት ተገልጻለች። "የአሦር ህዝብ እና መላው ሰራዊቷ በዚያ በሲኦል አሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሷ ጉባኤ
"የእርሷ ሰዎች ሁሉ በአንድነት"
ሁሉም በሰይፍ ተገደሉ
"ሰይፍ" የሚለው ቃል ሰዎችን ለመግደል ሰይፍ ለሚጠቀሙ ወታደሮች ሜቶኖሚ/

ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ወታደሮች እነርሱን በሙሉ ለመግደል ሰይፍ ተጠቅመዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
በጉድጓዱ ስርጓድ ተጨመሩ
"ጉድጓዱ" የሚለው የሚያመለክተው መቃብርን ነው፣ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሞት ዓለም መግቢያ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ እንደዚሁም ደግሞ ጉድጓድ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 31፡18 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በሰይፍ የወደቁት፣ የተገደሉት ሁሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በጦርነት የተገደሉ ተላቶች ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
በሰይፍ የወደቁ
እዚህ ስፍራ "መውደቅ" የሚለው ቃል "ሞት" ለሚለው ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት/ ነው። (ዩፊምዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)
በህያዋን ምድር ይሸብር የሚያመጡ
"ሽብር" የሚለው ረቂቅ ስም "ፍርሃት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "በህይወት ባለሁበት ጊዜ ሰዎች እጅግ እንዲፈሩ ምክንያት የነበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የህያዋን ምድር
ይህ የሚወክለው በህይወት የነበሩተን ሰዎች ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 32:24
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል በሲኦል ስለሚገኙ ህዝቦች መናገሩን ቀጥሏል።
ኤላም በዚህ ናት
እዚህ ስፍራ "ኤላም" የዚያን አገር ሰዎች ያመለክታል። "የኤላም ሰዎችም በዚያ በሲኦል አሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የእርሷ አእላፋት
ሊሰጡ የሚችሉት ትርጉሞች 1) የእርሷ አያሌ ሰዎች ወይም 2) የእርሷ ሰራዊት
መቃብሯ ዙሪያዋን ከቧታል
ይህ በሕዝቅኤል 32፡22 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ሁሉም ተገደሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የእርሷ ጠላቶች ሁሉንም ገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚያ በሰይፍ የወደቁ
በሕዝቅኤል 32፡23 ላይ እንደሚገኘው "በሰይፍ የወደቁ" በሚል ይተርጎም።
በሰይፍ
እዚህ ስፍራ "በሰይፍ" የሚለው ሰዎችን ለመግደል ሰይፍ ለሚጠቀሙ ወታደሮች ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "በጦርነት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሳይገረዙ ወደ ታች የወረዱ
"ወደ ታች ሲወርሱ ያልተገረዙ የነበሩ"
ወደ ምድር ታችኛው ክፍል
"በምድር ጥልቅ ታችኛው ስፍራ ማኖር/ማድረግ" ወይም "በምድር ጥልቅ ታች" በሕዝቅኤል 26፡20 ላይ የሚገኘው "በምድር ታችኛው ስፍራ" የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ሽብር ያመጡ
"ሽብር" የሚለው ረቂቅ ስም "ፍርሃት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ሽብር ያመጡ" የሚለው በሕዝቅኤል 32፡23 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመለከቱ። "በህይወት በነበሩበት ጊዜ ሰዎች እጅግ እንዲፈሩ ምክንያት የሆኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የህያዋን ምድር
ይህ በህይወት የነበሩ ሰዎችን ያመለክታል። "የህያዋን ምድር" የሚለው በሕዝቅኤል 32፡23 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመለከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የራሳቸውን ሀፍረት የተሸከሙ
ሀፍረት የተገለጸው አንድ ሰው በሄደበት ተሸክሞት እንደሚንቀሳቀስ ነገር ተደርጎ ነው። "ሀፍረት የተሰማቸው" ወይም "አሁን የተዋረዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ጉድጓዱ
"ጉድጓዱ" የሚለው የሚያመለክተው መቃብርን ነው፣ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሞት ዓለም መግቢያ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ እንደዚሁም ደግሞ ጉድጓድ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 32፡23 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ለኤላም እና ለአእላፋቷ የሚተኙበት አልጋ አዘጋሁላቸው
ለሙታን በሲኦል የተዘጋጀላቸው ስፍራ የተገለጸው ሙታኑ የሚተኙበት አልጋ እንደተሰጣቸው ተደርጎ ነው። ለኤላም እና ለመላው ሰዎቿ አልጋ አዘጋጅተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በግድያው መሃል
"በተገደሉት ሰዎች ሁሉ መሃል"
ሁሉም ያልተገረዙ ነበሩ
እስራኤላውያን ያልተገረዙ ሰዎችን አያከብሩም። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በሰይፍ ተወጉ፣ ምክንያቱም
እዚህ ስፍራ "ተወጉ" የሚለው ቃል "ተገደሉ" ለሚለው ሜቶኖሚ/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። "ጠላቶቻቸው በሰይፍ ገደሏቸው ምክንያቱም..." በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ኤላም በተገደሉት ሁሉ መሃል ናት
ይህ ከመጀመሪያው የቁጥሩ ክፍል ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው። "የሞቱ ሰዎች በመሃላቸው እንድትጋደም ለኤላም ስፍራ ሰጧት"
Ezekiel 32:26
አያያዥ ሀሳብ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል በሲኦል ስለሚገኙ ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል
ሞሳህ...ቶቤል
እነዚህ ስሞች በሕዝቅኤል 27፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎሙ ይመልከቱ።
በሰይፍ የተገደሉ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚወክለው ጦርሜዳን ነው። "በጦር ሜዳ የተገደሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሽብራቸውን ወደ ህያዋን ምድር አመጡ
ሰዎች እንዲፈሩ ማድረግ የተገለጸው አንደን አካል ወደ እነርሱ እንደ ማምጣት ድርጊት ተደርጎ ነው። "ሽብር" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። "በህያዋን ምድር የሚገኙትን ሁሉ አሸበሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉም... የህያዋን ምድር
በሕዝቅኤል 32፡25 ላይ የሚገኘው "ሁሉም... የህያዋን ምድር" የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
በደላቸው በአጥንቶቻቸው ላይ
ምንም እንኳን አንድ ሰው ጋሻዎቻቸው በሞታቸው እንደሚጋርዳቸው ቢያስብም፣ የጦረኞች በደል አካላቸውን ሸፍኗል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ በህያዋን ምድር የጦረኞች ሽብር ነበሩ
"በህይወት ሳሉ፣ ጦረኞችን በጣም ያስፈራሉ"
በህያዋን ምድር
እነዚህ ጦረኞች ይኖሩበት የነበረበት ጊዜ የተገለጸው ስፍራ ተደርጎ ነው። "በህይወት በነበሩበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 32:28
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ መናገሩን ቀጥሏል።
እናንተ... ትሰበራላችሁ
እዚህ ስፍራ "ትሰበራላችሁ" የሚለው የሚወክለው "መደምሰስን" ነው። ይህ

በዐድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ እደመስሳችኋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
በ…መሃል
"በ…መካከል
ተወግተው የነበሩ
እዚህ ስፍራ "ተወግተው" የሚለው ቃል "ተገድለው" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ይህ በሕዝቅኤል 32፡25 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ጠላቶቻቸው የገደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በሰይፍ
ይህ የሚወክለው በጦርነት ውስጥ መሆንን ነው። "በጦር ሜዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ኤዶም ከነገሥታቷ እና መሪዎቿ ጋር በዚያ አለች
እዚህ ስፍራ "ኤዶም" የምትወክለው የኤዶምን ሰዎች ነው። "የኤዶም ሰዎች ከነገሥታቶቻቸው እና ከመሪዎቻቸው ጋር በሲኦል ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ጉድጓዱ
"ጉድጓዱ" የሚለው የሚያመለክተው መቃብርን ነው፣ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሞት ዓለም መግቢያ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ እንደዚሁም ደግሞ ጉድጓድ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 32፡25 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 32:30
የሰሜኑ ልዑላን
"በሰሜን ያለውን ህዝብ የሚገዙ ልዑላን"
በዚያ አሉ
"በሲኦል ናቸው"
ወደ ታች ወረዱ
"ወደ ሲኦል ወረዱ"
ተወግተው ነበር
እዚህ ስፍራ "ተወግተው" የሚለው ቃል "ተገድለው" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት / ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ተመሳሳዩ ቃላቶች በህዝቅኤል 32፡25 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ጠላቶች በሰይፍ ከገደሏቸው ጋር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በሰይፍ
ይህ የሚወክለው በጦርነት ውስጥ መሆንን ነው። "በጦር ሜዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የራሳቸውን ሀፍረት የተሸከሙ
ሀፍረት የተገለጸው አንድ ሰው በሄደበት ተሸክሞት እንደሚንቀሳቀስ ነገር ተደርጎ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 32፡25 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሀፍረት የተሰማቸው" ወይም "አሁን የተዋረዱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጉድጓዱ
"ጉድጓዱ" የሚለው የሚያመለክተው መቃብርን ነው፣ ምክንያቱም መቃብር ወደ ሞት ዓለም መግቢያ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፣ እንደዚሁም ደግሞ ጉድጓድ ያንን ዓለም ይወክላል። ይህ በሕዝቅኤል 32፡29 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
Ezekiel 32:31
ፈርኦን ይመለከታል/ያያል
ይህ ፈርኦንንነ ማንን እንደሚመለከት በመግለጽ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል።"ፈርኦን ከሌሎች አገራት የሆኑትን የሞቱ ሰዎች ሁሉ ይመለከታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ አእላፋቶቹ ይጽናናል
ፈርኦን የሚጽናናው የሌሎች ታላላቅ ነገሥታት ሰራዊትም ጭምር በመገበላቸው መሆኑ ተጠቁሟል። "መላው ሰራዊቱ የተገደለበት እርሱ ብቻ ባለመሆኑ ራሱን ያጽናናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በሰይፍ የተወጉ
በሕዝቅኤል 31፡17 ላይ "በሰይፍ የተገደሉ" የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
በህያዋን ምድር ማሸበሪያ አደረግሁት
"ፈርኦን ገና በህይወት ሳለ፣ ሰዎችን መሸበሪያ አደረግሁት"
ባላተገረዙት መሃል ይጋደማል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሌሎች ባልተገረዙት መሃል ያጋድሙታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ ሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 33
Ezekiel 33:1
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
በማናቸውም ምድር ሰይፍ ይሆናል
"ሰይፍ" የሚለው ቃል ጥቃት የሚያደርስን የጠላት ሰራዊት ያመለክታል። እንደዚሁም ደግሞ "ምድር" በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። "የማናቸውንም ምድር ሰዎች የሚያጠቃ ሰራዊት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱን ጠባቂ/ጉበኛ ማድረግ
"እርሱን እንደ ዘብ መሾም" ወይም "እርሱን ጠባቂ/ጉበኛ ማድረግ"
ሰይፍ ይመለከታል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የጠላትን ሰራዊት ይወክላል። "የጠላትን ሰራዊት ያያል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ትኩረት አትስጡ
"ማጠንቀቂያውን ቸል በሉ"
የእያንዳንዱ ደም በገዛ ራሱ ላይ ነው
እዚህ ስፍራ "ደም" ሞትን ይወክላል። "በገዛ ራሱ ላይ" የሚለው ሀረግ ያ ሰው ተጠያቂ ይሆናል ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ቢሞቱ ተጠያቂነቱ የራሳቸው ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Ezekiel 33:5
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤላውያን በሕዝቅኤል በኩል መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል
ደሙ በእርሱ ላይ ነው
እዚህ ስፍራ "ደም" የአንድን ሰው ሞት ይወክላል። "በእርሱ ላይ" የሚለው ሀረግ ሰውየው ሃላፊነቱን ይወስዳል ለሚለው ፈሊጥ ነው። "በሞት የራሱ ጥፋት ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
የገዛ ህይወቱን ያተርፋል
"ራሱን ከሞት ይጠብቃል"
ሰይፍ በሚመጣበት ጊዜ
"ሰይፍ" የሚለው ቃል የጠላትን ሰራዊት ያመለክታል። "የጠላት ሰራዊት እየመጣ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሳለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሰዎች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ባለመደረጉ ምክንያት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ደግሞም እርሱ ሰዎችን አላስጠነቀቀም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰይፍ መጣ ደግሞም ሳይመርጥ ህይወት ቀጠፈ
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የጠላትን ሰራዊት ይወክላል። "የጠላት ሰራዊት መጥቶ ሁሉንም ገደለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ያ ሰው በራሱ ኃጢአት ይሞታል
"ያ ሰው በራሱ ኃጢአት ምክንያት ይሞታል"
የእርሱን ደም ከጠባቂው/ጉበኛው እፈልጋለሁ
እዚህ ስፍራ "ደም" የአንድን ሰው ሞት ይወክላል። "ደሙን ከእርሱ እፈልጋለሁ" የሚለው ሀረግ የአንድን ሰው ሀላፊነት የሚመለከት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "የዚያን ሰው ሞት የጉበኛው ጥፋት አድርጌ እውደዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Ezekiel 33:7
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።
የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የእስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ከአፌ ቃሎቼን ትሰማለህ፣ ደግሞም በእኔ ምትክ ሆነህ ታስጠነቅቃቸዋለህ
እዚህ ስፍረ "አፍ" የሚለው የሚወክለው ያህዌ የተናገረውን ነገር ነው። "እኔ የምናገረውን መልዕክት አንተ ትሰማለህ፣ ከዚያም በእኔ ምትክ ሆነህ እነርን ታስጠነቅቃቸዋለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በእኔ ምትክ ሆነህ አስጠንቅቃቸው
"የእኔ ተወካይ ሆነህ አስጠንቅቃቸው" ወይም "የእኔን ማስጠንቀቂያ ስጣቸው"
ይህንን አታውጅ
"ይህንን አትናገር"
ስለ እርሱ መንገድ
"እርሱ የሚያደርግበት መንገድ" ወይም "እርሱ የሚያደርጋቸው ነገሮች" በሕዝቅኤል 7:3 ላይ "የአንተ መንገዶች" የሚለው እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።
ደሙን ከእጅህ እፈልጋለሁ
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚወክለው የአንድን ሰው ሞት ነው። "ከእጅህ...እፈልጋለሁ" የሚለው ሀረግ አንድ ሰው ሀላፊነት አድርጎ መውሰድን/መጠየቅን የሚገልጽ ፈሊጥ ነው። "አንተን ለእርሱ ሞት ተጠያቂ አድርጌ እወስዳለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
እርሱ ምናልባት ከዚያ ይላል፣ ከመንገዱ ሳይመለስ ቢቀር
በተለመደ መንገድ ያደርገው የነበረውን ማድረግ ያቆመ አንድ ሰው የተገለጸው በአካል ዞሮ ወደ ኋላ መሄድ እንደጀመረ ተደርጎ ነው። "ክፉ ነገሮችን ማድረግን ሊያቆም ይችላል፣ እናም ክፉ ነገሮችን ማድረግ ባያቆም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የራስህን ህይወት ታድናለህ
"ራስህን በህይወት ትጠብቃለህ"
Ezekiel 33:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤላውያን በሕዝቅኤል በኩል መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል
የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የእስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ይህን ትናገራለህ
"አንተ የተናገርከው ይህ ነው"
መተላለፋችን እና ኃጢአታችን በላያችን ነው
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በእኛ ላይ" የሚለው ስለ መተላለፋቸው እና ኃጢአታቸው በደለኛነት ተሰምቷቸዋል የሚል ትርጉም የያዘ ዘይቤ ነው ወይም 2) "በእኛ ላይ" የሚለው ስለ መተላለፋቸው እና ኃጢአታቸው ያህዌ እንደሚቀጣቸው ተረድተዋል የሚል ትርጉም የያዘ ዘይቤ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእነርሱ ዘንድ ሸታችን እየተበላሸ ነው
"በእነርሱ ምክንያት የእኛ ሸታ እየተበላሸ እየሄደ ነው።" በኃጢአት ምክንያት መጥፋት የተገለጸው የሰው ስጋ እየበሰበሰ እንደሆነ ተደርጎ ነው። "እነርሱ እያጠፉን ነው" ወይም "እየገደሉን ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእነርሱ ዘንድ
"በእነርሱ ምክንያት"
እንዴት በህይወት መኖር እንችላለን?
ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቁት የመኖር ተስፋ እንደሌላቸው ትኩረት ሰጥተው ለመናገር ነው። "እንዴች የመኖር ተስፋ የለንም።" ወይም "በእርግጥ እንሞታለን።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በህያውነቴ እምላለሁ
"እኔ በእርግጥ ህያው እንደሆንኩ።" ያህዌ ይህንን አገላለጽ የሚጠቀመው ቀጥሎ የሚናገረው በእርግጥም እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው። ይህ የጸና ቃል ኪዳን የመግባት ምልክት ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።" በህያውነት እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ ከበደለኛው ሰው ሞት ምክንያት ደስ አልሰኝም
"ሞት" የሚለው ረቂቅ ስም "ሞተ" ተብሎ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "በደለኛው" የሚለው ስማዊ ቅጽል "በደለኛ ሰዎች" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "በደለኛ ሰዎች በመሞታቸው እኔ ደስ አልሰኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ስማዊ ቅጽሎች የሚሉትን ይመልከቱ)
ክፉ ሰው በንስሃ ከመንገዱ ቢመለስ
እዚህ ስፍራ "መንገድ" የሚለው የሚወክለው አንድ ሰው የሚያደርገውን ነገር የሚያደርገው እንዴት እንደሆነ ነው። "በደለኛው ክፉ ነገሮችን ማድረጉን ቢተው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ስለምን ትሞታላችሁ?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠቀመው የእስራኤል ሰዎች እንዲሞት እንደማይፈልግ ትኩረት ሰጥቶ ለመግለጽ ነው። "የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ሞትን አትምረጡ!" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 33:12
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤላውያን በሕዝቅኤል በኩል መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል
ጻድቁ ሰው ኃጢአት ቢሰራ የቀደመው ጽድቁ አያድነውም!
"ጽድቅ" የሚለው ረቂቅ ስም "ትክክለኛ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። ከእግዚአብሔር ቅጣት እንደማይተረፉ ተጠቁሟል። "ጻድቃን ሰዎች ኃጢአት ማድረግ ቢጀምሩ፣ አስቀድሞ የሰሩት ትክክለኛ ነገር እነርን ከመቅጣት አያቆመኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
የክፉ ሰው የቀደመ ክፋት እንዲጠፋ አያደርገውም
"ክፋት" የሚለው ረቂቅ ስም "ክፉ" በሚለው ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "ክፉ ያሆነ ነገር ያደረገ ሰው በቀደመው ክፋቱ አይጠፋም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ጽድቁ ቢመለስ/ቢዞር
ሰውየው ያንን የሚያስበው አስቀድሞ ትክክለኛ ስለነበረ ነው፤ ቢበድል እንኳን ያህዌ እርሱን አያጠፋውም። "ጽድቅ" የሚለው ረቂቅ ስም "ትክክለኛ" በሚል ቅጽል ሊገለጽ ይችላል። "አስቀድሞ በሰራቸው ትክክለኛ ነገሮች ላይ ቢጸና" በሚለው

ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
አፍትሃዊ ነገሮችን ቢያደርግ
"ክፉ የሆነውን ቢያደርግ" ወይም "ክፉ ነገሮችን ቢያደርግ"
እኔ አላስበውም
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ስለዚያ ነገር አላስብም" ወይም "አላስታውስበትም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 33:14
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤላውያን በሕዝቅኤል በኩል መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል
ለክፉዎች
"ክፉዎች" የሚለው ስማዊ ቅጽል "ክፉ ሰው" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡ "ለክፉ ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ይመልከቱ)
ለብድር መያዣ የያዘውን ቢመልስ
"የብድር መያዣውን መልሶ ቢሰጥ"
የብድር መያዣ
አንድ ሰው ለሌላው ሰው የተበደረውን እንደሚመልለት ለማረጋገጥ አበዳሪው ዘንድ የሚተወው አንዳንድ ነገር
ለሰረቀው የሚያቀርበው ካሳ
"የሰረቀውን መመለስ" ወይም "ለሰረቀው ዋጋውን መልሶ መክፈል"
ህይወት በሚሰጥ ደረጃ መራመድ
በአንድ ሁኔታ ማድረግ ወይም ማከናወን መራመድ እንደሆነ ተደርጎ ተገልጽዋል። "ህይወት በሚሰጡ ህጎች መሰረት መኖር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 33:17
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለእስራኤላውያን በሕዝቅኤል በኩል መልዕክቱን መስጠቱን ቀጥሏል
የአንተ ህዝብ
እነዚህ የእስራኤል ሰዎች ናቸው። "የአንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕዝቅኤልን ነው፡፡
የጌታ መንገድ… ተገቢ ያልሆኑ የእናንተ መንገዶች
ባህሪያት ወይም ድርጊቶች የተገለጹት አንድ ሰው የሚሄድበት መንገድ ወይም ጎዳና እንደሆኑ ተደርጎ ነው። "ይህ ጌታ ያደረገው… እናንተ ያደረጋችሁት ተገቢ ያልሆኑ ነገሮች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን እነዚህ የእናንተ መንገዶች ናቸው
"የእናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰዎች ነው። ይህ በሶስተኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል፡፡ "ነገር ግን ይህ የእነርሱ መንገድ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ከጽድቁ ቢመለስ
ከዚያ በኋላ አንድ ነገር አለማድረግ የተገለጸው በአካል ከአንድ ነገር ዞሮ እንደ መመለስ ተደርጎ ነው። "ትክክለኛ የሆነውን ነገር ማድረግ ማቆም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በዚያው ውስጥ ሆኖ መሞት
"በኃጢአቱ ምክንያት መሞት"
ከክፉ ስራው ቢመለስ
ከዚያ በኋላ አንድ ነገር አለማድረግ የተገለጸው በአካል ከአንድ ነገር ዞሮ እንደ መመለስ ተደርጎ ነው። "ትክክለኛ የሆነውን ነገር ማድረግ ማቆም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእነዚያ ነገሮች ምክንያት
"ፍትሃዊ እና ትክክለኛ ነገር በማድረጉ ምክንያት"
የአንተ ህዝብ/ህዝብህ
እነዚህ የእስራኤል ሰዎች ናቸው
የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው የሚወክለው ሰዎችን ነው። "የእስስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 33:21
እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን ለማድረግ የሚችልበት መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።
አስራ ሁለተኛው አመት… አምስተኛው ቀን… አስረኛው ወር
12ኛ አመት… 5ተኛ ቀን… 10ኛ ወር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በአስረኛው ወር በአምስተኛው ቀን
ይህ በዕብራውያን አቆጣጠር አስረኛው ወር ነው። አምስተኛው ቀን በምዕራባውያን ዘመን አቆጣጠር ጥር መጀመሪያ አካባቢ ነው። (የዕብራውያን ወራት እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)
የእኛ ምርኮኛ
እዚህ ስፍራ "እኛ ራሳችን" የሚለው የሚያመለክተው በባቢሎናውያን ንጉሥ ዮአኪን ኢየሩሳሌምን ለቆ እንዲወጣ ካደረጉት ጊዜ አንስቶ በባቢሎን የነበሩትን ሕዝቅኤልን እና እስራኤላውያንን ነው። "እኛ ምርኮኛ ከሆንን በኋላ" ወይም "ባቢሎናውያን እኛን ወደ ምርኮ ከወሰዱን በኋላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አካታች ያልሆነ እና የሆነ "እኛ" እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከኢየሩሳሌም ያመለጠ ሰው ወደ እኔ መጣ
"ከኢየሩሳሌም ያመለጠ አንድ ሰው ወደ እኔ መጣ" ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን ደምስሰው ህዝቧን ሲገድሉ ጥቂት ሰዎች ብቻ አመለጡ።
ከተማይቱ ተያዘች
"ከተማይቱ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው "ኢየሩሳሌምን" ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፡፡ "ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን ደመሰሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የያህዌ እጅ በእኔ ላይ ነበረች
x
Ezekiel 33:23
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚያ ፍርስራሾች
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እነዚያ የግንብ ፍርስራሾች" 2) "እነዚያ የፈራረሱ ከተሞች"
እርሱ ምድሪቱን ወረሰ
ያህዌ ምድሪቱን ለአብርሃም መስጠቱ የተገለጸው አብርሃም ምድሪቱን እንደ ወረሰ ተደርጎ ነው። "ያህዌ ምድሪቱን ለእርሱ ሰጠ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ምድሪቱ
"የእስራኤል ምድር"
ምድሪቱ ለእኛ ተሰጥታ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፡፡ "ያህዌ ምድሪቱን ለእኛ ሰጠን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ርስት አድርጎ
"ርስት" የሚለው ረቂቅ ስም "መውረስ" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡ "ስለዚህም እኛ እርሷን መውረስ እንችል ዘንድ" (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 33:25
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ በእስራኤል ፍርስራሽ ላይ ስለሚኖሩ ሰዎች ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።
እናንተ ደም በላችሁ
በውስጡ ደም ያለበትን/ ደሙ ገና ከውስጡ ያልወጣን ስጋ መብላታቸው ተጠቅሷል። ያህዌ በስጋ ውስጥ ያለ ደም ተንጠፍጥፎ እንዲወጣ አዟቸው ነበር። "በውስጡ ደም ያለበትን ስጋ በላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ዐይኖቻችሁን ወደ ጣኦቶቻችሁ አነሳችሁ
"ወደ ጣኦቶቻችሁ ተመለከታችሁ" ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ጣኦቶቻችሁን አመለካችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰዎችን ደም አፈሰሳችሁ
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚወክለው የሰውን ህይወት ነው። ደም ማፍሰስ መግደል ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ሰዎችን ገደላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
በእርግጥ ምድሪቱን መውረስ ይገባችኋልን?
ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ህዝቡን ለመገሰጽ ነው። "ይህንን ምድር መውረስ አይገባችሁም!" ወይም "ይህ ምድር አይገባችሁም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በሰይፎቻችሁ ተማምናችኋል
እዚህ ስፍራ "ሰይፎች" የሚያመለክተው የጥቃት ተግባር መፈጸምን ነው። "የምትፈልጉትን ለማግኘት በሰይፎቻችሁ የጥቃት ተግባር ፈጽማችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አስጸያፊ ተግባር ፈጽማችኋል
"እኔ በጣም የምጠላውን ተግባር አድርጋችኋል"
እያንዳንዱ ወንድ የጎረቤቱን ሚስት አርክሷል
የጎረቤቶቻቸውን ሚስቶች አብረው በመተኛት ማርከሳቸው ተጠቁሟል። "እያንዳንዱ ወንድ ከጎረቤቱ ሚስት ጋር ተኝቷል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 33:27
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በእስራኤል ፍርስራሽ ላይ ስለሚኖሩ ሰዎች ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።
በህያውነቴ
"እኔ ህያው እንደሆንኩ።" ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ቀጥሎ የሚናገረው በእርግጥ እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው። ይህ የከበረ ቃል መግቢያ መንገድ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በክብሬ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በፍርስራሹ የቀሩት በቀስት ይወድቃሉ
"በቀስት ይወድቃሉ" የሚለው ሀረግ ፈሊጣዊ ነው። "ጠላት በፍርስራሽ ውስጥ የቀሩትን ይገድላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በምሽጎች እና በዋሻዎች ውስጥ የተደበቁት በመቅሰፍት ይሞታሉ
"መቅሰፍት በምሽጎች እና በዋሻዎች ውስጥ የሚኖሩትን ይገድላቸዋል"
ምሽጎች
ምሽግ ሰዎች ራሳቸውን ከሚያጠቋቸው ጠላቶች ለመጠበቅ የሚገነቡት ግንብ ነው
ዋሻዎች
ዋሻዎች በተራራ አተገብ/ጎን ወይም ከምድር በታች ሚገኙ የተፈጥሮ አዳራሾች/ ቤቶች ናቸው። ብዙውን ጊዜ ከአለት የተሰሩ ናቸው።
እርሷ ኩራቷ ያበቃል
"እርሷ" የሚለው ቃል ምድሪቱን ያመለክታል፣ ይህም የምድሪቱን ነዋሪዎች የሚያመለክት ነው። "የምድሪቱ ሰዎች ከእንግዲህ ጠንካራ ነን ብለው የሚኮሩበት ነገር አይኖርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ተራሮች ይደመሰሳሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከእንግዲህ በእስራኤል ተራሮች ማንም አይኖርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በእነርሱ በኩል የሚያልፍ አይኖርም
"በምድሪቱ ወይም በተራሮቿ ላይ አቋርጦ የሚጓዝ አይኖርም"
እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ እርሱ ያህዌ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ ሲል፣ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የፈጸሙት ከፍተኛ ጥላቻ ሁሉ
"ጥላቻ" የሚለው ረቂቅ ስም "የምጠላቸው ነገሮች" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "እነርሱ ያደረጓቸው እኔ የምጠላቸው ነገሮች በሙሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ አድርገዋቸዋል
"ሰዎቹ አድርገዋቸዋል/ፈጽመዋቸዋል"
Ezekiel 33:30
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል መናገሩን ቀጥሏል።
ከያህዌ ዘንድ የወጣ
"ይናገር ዘንድ ያህዌ ለእርሱ የሰጠው" ወይም "ያህዌ ለእርሱ የሰጠው"
ትክክለኛ ቃላት በአፋቸው አለ፣ ነገር ግን ልባቸው ፍትሃዊ ያልሆነ ጥቅምን ይከተላል
እዚህ ስፍራ "አፎች" የሚለው የሚወክለው ንግግርን ነው። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እነርሱ እኔን ስለ መውደዳቸው ይናገራሉ፣ ልባቸው ግን ፍትሃዊ ያልሆነ ጥቅምን ይከተላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ልባቸው ፍትሃዊ/ተገቢ ያልሆነ ጥቅምን ይከተላል
እዚህ ስፍራ "ልቦች" የሚለው የሚወክለው ፍላጎትን ነው። "በልቦቻቸው ትክክለኛ ያልሆነ ጥቅምን ለማግኘት ይፈልጋሉ" ወይም "ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ነገሮችን ለማግኘት ይፈልጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Ezekiel 33:32
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ እስራኤል ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል።
አንተ ለእነርሱ ደስ እንደሚያሰኝ መዝሙር ሆነህላቸዋል
እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው የሚያመለክተው ሕዝቅኤልን ሲሆን፣ እርሱ ደግሞ የተናገረውን መልዕክት ይወክላል። ይህ የሕዝቅኤልን መልዕክት ደስ ከሚያሰኝ ዝማሬ ጋር ያነጻጽራል፤ ይህም ማለት ሰዎች እርሱን መስማት ያስደስታቸዋል፣ ነገር ግን መልዕክቱን ለመታዘዝ ስፍራ አይሰጡም። "ቃሎችህ ደስ የሚያሰኝ ዝማሬ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ደስ የሚያሰኝ ዝማሬ
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ውብ ዝማሬ" ወይም 2) "የፍቅር ዝማሬ" ወይም "ስለ ፍቅር የተዘመረ"
በክር የሙዚቃ ማሳሪያ በሚገባ የተጫወቱት
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው በክር የሙዚቃ መሳሪያ በሚገባ የተጫወተው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የክር ሙዚቃ መሳሪያ
ሰዎች ሙዚቃ ለመጫወት የሚጠቀሙበት የክር ሙዚቃ መሳሪያ
ይህ ሁሉ በሚሆንበት ጊዜ
"ይህ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር የተናገራቸው ነገሮች ሁሉ እንደሚፈጸሙ እና ሕዝቅኤል ስለ ነገሩ ለህዝቡ እንደተናገረ ነው።
እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ!" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው ነገር ትኩረት ይሰጣል። "በእርግጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
በመሃላቸው ነቢይ እንዳለ
"እኔ አንተን ወደ እነርሱ በእርግጥ ነቢይ አድርጌ እንደ ላክሁህ"

Chapter 34
Ezekiel 34:1
አጠቃላይ መረጃ:
በምዕራፍ 34፣ ያህዌ፣ የእስራኤል ህዝብ እንደ በግ መንጋ እንደሆኑ እና የእስራኤል መሪዎች ደግሞ መንጋውን እንደሚጠብቁ እረኞች ተደርገው ነገር ግን ድርሻቸውን ሳይወጡ እንደቀሩ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የያህዌ ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ይህ በሕዝቅኤል 3:16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ

"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ።" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም። ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

የእስራኤል ጠባቂ

የእስራኤል መሪዎች እረኞች እንደሆኑ ተደርጎ ተገልጸዋል። እረኛ መንጋውን እንደሚንከባከብ የህዝባቸው ጠባቂ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸው ነበር። "እንደ እረኞች የሆኑ የእስራኤል መሪዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እራሳቸውን ይንከባከቡ ነበር

መሪዎቹ ህዝቡን ከመጠበቅ ይልቅ የራሳቸውን ምቾት መጠበቃቸው የተገለጸው ራሳቸውን እንደሚጠብቁ ተደርጎ ነው። "ራሳቸውን ይመግባሉ፣ ራሳቸውንም ብቻ ይንከባከባሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እረኞች መንጋውን ሊጠብቁ አይገባምን?

ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት መሪዎች ህዝቡን ባለመንከባከባቸው ሊገስጻቸው ነው። "እረኞች መንጋውን ሊመግቡ፣ ሊንከባከቡትም ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ስቡን ተመገባችሁ... ሐር ለበሳችሁ

የእስራኤል መሪዎች እንደ መጠፎ እረኛ ከመንጋው ምርጡን እያረዱ የሚበሉና የበጉን ጸጉር እየለበሱ ለመንጋው ግን ገድ እንደማየላቸው ተደርጎ መገለጹ ቀጥሏል። "እናንተ ለመንጋው ግድ እንደሌለው የሰባውን እንደሚመገብ... ሱፉን እንደሚለብስ እረኛ ብቻ ናችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ ስቡን ተመገባችሁ

የሰባው ክፍል የሚገኘው ከበጎች እና ፍየሎች ነው። "የቡን እና ፍየሉን ስብ ክፍል ትመገባላችሁ" ወይም "እናንተ የበጎቹን እና ፍየሎቹን ምርጥ ክፍል ትመገባላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሱፉን ትለብሳላችሁ

"ከበጎች የሚገኘውን ሱፍ ትለብሳላችሁ"

የሰባውን

"የሰባውን የበግ እና ፍየል ጠቦት"

ፈጽሞውኑ አትጠብቋቸውም

"መንጋውን አትመግቡም፣ እንክብካቤም አታደርጉለትም"

Ezekiel 34:4

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ በሕዝቅኤል በኩል ለእስራኤል መሪዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ፣ የእስራኤል መሪዎችን ደግሞ ለመንጋው ግድ እንደማይላቸው እረኞች አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሽታ ይዟቸዋል

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ታመዋል" ወይም 2) "ደካማ ናቸው"

የተሰበሩትን አልጠገናችሁም

"ለቆሰሉት በተሰበሩ አጥንቶቻቸው ዙሪያ ጨርቅ አልጠቀለላችሁም"

እነዚያ የተሰበሩት

"አጥንታቸው የተሰበረ በጎች" ወይም "የተጎዱ በጎች"

አልጠገናችኋቸውም

"አልመለሳችኋቸውም"

የተረሱት

"የተተዉ በጎች" ወይም "ሌሎች ያባረሯቸው"

የጠፉ

"በተጎቹ ወይም ፍየሎቹ" የሚሉት ቃላት ከዚህ ሀረግ ወጥተዋል/ተትተዋል፣ ነገር ግን በውስጠ ታዋቂነት እንደሚታወቁ ይታሰባል። "የጠፉት በጎች ወይም ፍየሎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

በጥንካሬ እና በሃይል

"በሀይል እና በጭካኔ"

ከዚያም ያለ እረኛ ተበተኑ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከዚያም ተበተኑ፣ ምክንያቱ እረኛ ስላልነበራቸው ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሜዳ ላሉ አምሬዎች ሁሉ ምግብ ሆኑ

"የዱር እንስሳት ሁሉ ሊያጠቋቸው እና ሊበሏቸው ይችላሉ"

በምድር ላይ ሁሉ ተበተኑ

"መንጋዬ በምድር ላይ ሁሉ ተበተነ"

Ezekiel 34:7

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ በሕዝቅኤል በኩል ለእስራኤል መሪዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ፣ የእስራኤል መሪዎችን ደግሞ ለመንጋው ግድ እንደማይላቸው እረኞች አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌን ቃል ስሙ

ይህ ከያህዌ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። "የያህዌን መልዕክት አድምጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሕያውነቴ

"እኔ ሕያው እንደሆንኩ።" ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ቀጥሎ የሚናገረው በእርግጥ እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው። ይህ የከበረ ቃል መግቢያ መንገድ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "በክብሬ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው

ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በሕዝቅኤል 5:11 ላይ እንዴት እንተተረጎመ ይመልከቱ። "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

መንጋዬ ስለተዘረፈ እና በሜዳ ለሚገኝ አውሬ ምግብ ስለሆነ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በሜዳ ያሉ አውሬዎች ሁሉ መንባዬን ስለሰረቁ እና ስለበሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝርፊያ

የተሰረቁ ነገሮች

በሜዳ ያሉ አውሬዎች ሁሉ

እዚህ ስፍራ "ሁሉ" የሚለው በግ የሚበሉ የዱር እንስሳትን ሁሉ የሚያመለክት አጠቃላይ መገለጫ ነው። "በሜዳ የሚገኙ የዱር እንስሳት ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

እረኛ ባለመኖሩ ምክንያት

"እረኛ ስለ ሌላቸው"

ከእረኞቼ አንዱም መንጋዬን አልተመለከተም

"ከእረኞቼ አንዱም መንጋዬን ለማግኘት አልሞከረም"

ራሳቸውን ጠበቁ

"ራሳቸው ተንከባከቡ" ወይም "ራሳቸውን መገቡ፣ ለራሳቸው እንክብካቤ አደረጉ"

የእኔን መንጋ አልጠበቁም

"የእኔን መንጋ አልመገቡም፣ መንጋዬን አልተንከባከቡም"

Ezekiel 34:9

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ በሕዝቅኤል በኩል ለእስራኤል መሪዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ፣ የእስራኤል መሪዎችን ደግሞ ለመንጋው ግድ እንደማይላቸው እረኞች አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌን ቃል ስሙ

"የያህዌን መልዕክት አድምጡ።" ይህ ከያህዌ ልዩ መልዕክት ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጥ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል

ይህ በአንደኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ እንዲህ እላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!

እዚህ ስፍራ "እነሆ!" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው ነገር ትኩረት ይሰጣል። "በእርግጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እኔ በእረኞች ላይ ተነስቻለሁ

"እኔ እረኞችን እቃወማለሁ"

በጎቼን ከእጃቸው እጠይቃለሁ

"ከእጃቸው...መጠየቅ" የሚለው ሀረግ አንድን ሰው ለአንድ ነገር ተጠያቂ ወይም በሀላፊነት ተጠያቂ ማድረግ ማለት ነው። "በመንጋዬ ላይ ለደረሰው ክፉ ነገር ሁሉ ተጠያቂ አደርጌ እይዛቸዋለሁ" ወይም "በመንጋዬ ላይ እንዲደርስ ላደረጉት ክፉ ነገር ሁሉ እቀጣቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መንጋውን ከመጠበቅ ሃላፊነት ላይ አደመስሳቸዋለሁ

"ከእንግዲህ መንጋውን እንዲጠብቁ አልፈቅድላቸውም" ወይም "ከዚህ በኋላ የመንጋው ጠባቂ እንዲሆኑ አልተዋቸውም/አላደርግም"

ራሳቸውን ተንከባከቡ/ጠበቁ

"ራሳቸውን መገቡ ወይም ለራሳቸው እንክብካቤ አደረጉ"

ከእነርሱ አፍ

እዚህ ስፍራ "አፍ" የሚወክለው መብላትን ነው። "ከእንግዲህ አይበሏቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

መንጋዎቼ ከእንግዲህ ለእነርሱ ምግብ አይሆኑም

"እረኞቹ ከእንግዲህ የመንጋዬን በጎች እና ፍየሎች አይበሉም"

Ezekiel 34:11

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ በሕዝቅኤል በኩል ለእስራኤል መሪዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። እዚህ ስፍራ ስለ ራሱ የእነርሱ እረኛ እንደሆነ እና እንደሚንከባከባቸው ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል

ይህ በአንደኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ!

እዚህ ስፍራ "እነሆ!" የሚለው ቃል እረኞች ቀጥሎ ለሚሆነው አስደናቂ መረጃ ትኩረት እንዲሰጡ ያነቃል።

የሚሆነውን ይመረምራሉ

"ወደፊት ይመለከታሉ"

በተበተኑ መንጋዎቹ መሃል

"በተበታተኑ መንጋዎቹ ጋር"

ተበታትነው ነበር

በመንጋው ውስጥ የሚገኙ እንስሳት መበታተናቸው ተጠቁሟል፣ ምክንያቱ የሚጠብቃቸው ወይም የሚንከባከባቸው እረኛ አለመኖሩ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የሚንከባከባቸው እረኛ በማጣታቸው ተበታተኑ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እንዲሁም አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ደመና እና ጨለማ በሆነ ቀን

"በደማናማ እና ጨለማ ቀን።" ጥፋቶች የተገለጹት የጨለማ ቀን እንደሆኑ እንደሆኑ ተደርጎ ነው። "ችግር እና ጥፋት በደረሰባቸው ቀን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አምጧቸው

"በጎቼን እና ፍየሎቼን አምጧቸው" ወይም "መንጋዬን አምጡ"

ከህዝብ መሃል

"ከሌሎች ህዝቦች ጋር ከሚኖሩበት ስፍራ"

በለመለመ መስክ አሰማራቸዋለሁ... በምድሪቱ ማረፊያ ሁሉ

ያህዌ ህዝቡን ከስደት ወደ ምድራቸው ይመልሳቸዋል። ይህም በመሆኑ እርሱ ሊንከባከባቸው እና በደህንነት ሊጠብቃቸው እንደሚችል የተገለጸው፣ ብዙ ስፍራ፣ ምግብ እና ውሃ በሚያገኙበት የሚያስቀምጣቸው እረኛቸው እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መሰማሪያ

በጎች እና ፍየሎች ሊበሉት የሚችሉት ሳር እና ቅጠል/ትንንሽ ተክል የሚገኝበት መሬት

መስፈሪያ

ይህ ሰዎች የሚኖሩበት ቦታ ነው። ብዙውን ጊዜ ሰዎች ሲሰፍሩ ቤት ሰርተው ይቀመጣሉ

Ezekiel 34:14

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ በሕዝቅኤል በኩል ለእስራኤል መሪዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል። እዚህ ስፍራ ስለ ራሱ የእነርሱ እረኛ እንደሆነ እና እንደሚንከባከባቸው ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የግጦሽ ስፍራቸው

"ለሚመገቡ/ሊግጡ የሚችሉበት ስፍራ"

ሰፊ መሰማሪያ

"ብዙ ሳር እና ተክል የሚገኝበት እንስሳት ግጦሽ መሬት"

መጋጥ

እንስሳት ሳር እና ሌሎች ተክሎች ማግኘታቸው

እኔ ራሴ

"እኔ ራሴ" የሚለው ትኩረት ይጨምራል። እግዚአብሔር ይህን የሚያደርገው እረኞች ያንን ባለማድረጋቸው ነው። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እረኞች... ይሆን

"ይመግቧቸው እና ይንከባከቧቸው...ይሆን

እንዲጋደሙ ያደርጉ ይሆን

"እንዲያርፉ ይተዋቸው ይሆን"

የጠፉት

"በጎቹ ወይም ፍየሎች" የሚሉት ቃላት በእዚህ ሀረግ ተዘለዋል/ተትተዋል፤ ሆኖም ግንዛቤ እንደሚያገኑ ይታሰባል። "የጠፉት በጎች ወይም ፍየሎች" (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

የተጣሉትን ጠግኑ

"ሌሎች ያባረሯቸውን/ያስወጧቸውን መልሷቸው"

የተሰበሩትን በጎች ጠግኑ

"የተሰበረውን በግ አጥንቱን በጨርቅ ጠቅልሉ" ወይም "የማናቸውንም በግ ቁስል ዙሪያውን በጨርቅ ጠቅልሉ"

የሰባውን እና ጠንካራውን/ጤናማውን

"በግ" የሚለው ቃል በውስጠ ታዋቂነት አለ። "የሰባው እና ጠንካራው/ጤናማውን በግ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተዘለለ/የተተወ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 34:17

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ በሕዝቅኤል በኩል ለእስራኤል መሪዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ መልዕክቱን ለሕዝቅኤል መስጠቱን ቀጥሏል። አሁን መልዕክቱ ለእስራኤል ህዝብ ነው።

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ፤ ስለ ራሱ የእነርሱ እረኛ እንደሆነ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል

ይህ በአንደኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህ ነው"

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

እነሆ፣ እኔ

"ትኩረት ስጡ፣ ምክንያቱም እኔ የምናገረው እውነተኛም ጠቃሚም ነውና"

እኔ በበጎች እና በበጎች መሃል ዳኛ እሆናለሁ

"እኔ በአንደኛው በግ እና በሌላኛው መሃል ዳኝነት እሰጣለሁ"

አውራ በጎች እና ወንድ ፍየሎች

ወንድ በጎች እና ፍየሎች ብዙውን ጊዜ በመንጋው ውስጥ ጠንካሮቹ ናቸው፤ ደግሞም የሚፈልጉትን በመንጋው ውስጥ ከሚገኙት እንስሳት ያገኛሉ።

ይህ … በቂ አይደለምን

እግዚአብሔር እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመው፣ በመንጋው ውስጥ የሚገኙትን፤ ለደካሞቹ በማያዝኑ ጠንካራ እንስሳት የተገለጹትን የእስራኤል መሪዎችን ለመገሰጽ ነው። ይህንን በዩዲቢ እንደሚገኘው በዐረፍተ ነገር መልክ መተረጎም ይቻላል። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 34:20

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ፤ ስለ ራሱ የእነርሱ እረኛ እንደሆነ መግለጹን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል

ይህ በአንደኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእነርሱ

"ለመንጋዬ"

እነሆ!

እዚህ ስፍራ "እነሆ" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው ትኩረት ይጨምራል። "በእርግጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እኔ ራሴ

"እኔ ራሴ" የሚለው ፍርድ የሚሰጠው ያህዌ ለመሆኑ ትኩረት ይሰጣል። (ደጋጋሚ ተውላጠ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በሰቡት በጎች እና በከሱት መሃል ይፈርዳል

"የሰቡት በጎች እና ፍየሎች የከሱትን በጎች እና ፍየሎች መንከባከባቸውን እና እርስ በእርሳቸው በሚገባ መተያየታቸውን ያረጋግጣል"

የሰቡት በጎች እና የከሱት በጎች

በእስራኤል መሪዎች እና ጠንካራ ሰዎች፣ በመንጋው ውስጥ እንደሚገኙ ወፍራም እና ጠንካራ እንስሳ ተደርገው ይገለጻሉ። ደሃ እና ደካማ ሰዎች በመንጋው ውስጥ እንደሚገኙ የከሱ እና ደካማ እንስሳ ይገለጻሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለእናንተ

"እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሌሎችን በጎች እና ፍየሎች በሚገባ ያልተንከባከቡ በጎችን እና እንስሳትን ነው።

በአጠገባችሁ

"በአካላችሁ ጎን"

ወጉ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ቀጡ" ወይም "ገፉ" 2) "በሱ" ወይም "ጠረቆሱ"

በተኗቸው

"በተለያዩ አቅጣጫዎች እንዲበታተኑ አደረጓቸው"

ከምድሪቱ እንዲሄዱ

"ከእስራኤል ምድር እንዲሰደዱ"

Ezekiel 34:22

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ፤ ስለ ራሱ የእነርሱ እረኛ እንደሆነ መግለጹን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ አይበዘበዙም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም እንዲበዘብዛቸው አልፈቅድም" ወይም "ማንም እንዲሰርቃቸው አልፈቅድም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ በኋላ ዘረፋ አይሆንም

"ከዚህ በኋላ የሚሰረቅ ነገር አይኖርም።" እረኞቹ እና የዱር እንስሳቱ ከያህዌ መንጋ በጎቹን እና ፍየሎቹን ይሰርቁ ነበር።

በላያቸው አንድ እረኛ አስቀምጣለሁሁ

"በላያቸው አስቀምጣለሁ" የሚለው ሀረግ ፈሊጥ ሲሆን ትርጉሙ አንድ ሰው ሌላውን እንዲያስተዳድር ማድረግ ማለት ነው። "አንድ እረኛ በበጎቼ እና ፍየሎቼ ላይ እሾማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አገልጋዬ ዳዊት

እዚህ ስፍራ "ዳዊት" የተጠቀሰው ለዳዊት ትውልድ ነው። "የአገልጋዬ የዳዊት ትውልድ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እረኛ ይሆናቸዋል

በእስራኤል ህዝብ ላይ ንጉሥ የሚሆነው የዳዊት ትውልድ የተገለጸው የእነርሱ እረኛ እንደሚሆን ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእነርሱ መሃል ልዑል/ገዢ ይሆናል

"ገዢያቸው ይሆናል"

Ezekiel 34:25

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ እስራኤል ሰዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል።

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች እንደ በጎች መንጋ አድርጎ መግለጹን ቀጥሏል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሰላም ቃል ኪዳን

"ሰላም የሚያመጣ ቃል ኪዳን"

ክፉ የዱር እንስሳት

እነዚህ በጎችን እና ፍየሎችን መግደል የሚችሉ የዱር እንስሳት ናቸው።

እኔ በእነርሱ እና በኮረብቶቼ ዙሪያ በሚገኙ ስፍራዎች በረከትንም ጭምር አመጣለሁ

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን "እነርሱን እና በኮረብቶቼ ዙሪያ የሚገኙ ስፍራዎችን ወደ በረከት እለውጣቸዋለሁ" ብለው ይተረጉማሉ።

የእኔ ኮረብታ

ይህ የሚያመለክተው የጽዮንን ተራራ ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝናብን እልካለሁ

"እንዲዘንብ አደርጋለሁ"

በጊዜው

"በትክክለኛው ጊዜ"

እነዚህም የበረከት ዝናብ ይሆናሉ

"ይህ ዝናብ በረከት ይሆናል"

ምድር ፍሬዋን ትሰጣለች

"ምድር የሚበላ ታበቅላለች" ወይም "ምግብ በምድር ይበቅላል"

አስተማማኝ ይሆናል

"ደህና ይሆናል"

እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ

ያህዌ እርሱ ያህዌ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ ሲል፣ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው። ይህ በሕዝቅኤል6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የቀንበራቸውን እስራት ስሰብር

ባርነት የተገለጸው እንደ አንዳንድ እንስሳት ሰዎች ላይ ቀንበር እንደሚጫንባቸው ተደርጎ ነው። "ከባርነት ነጻ ሳወጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በባርነት ከያዝዋቸው እጅ

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚወክለው ሀይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። "ባሪያ አድርገው ከተቆጣጠሯቸው እጅ" ወይም "እነርሱን ባሪያዎች ካደረጓቸው እጅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 34:28


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ስለ እስራኤል ሰዎች መልዕክት መስጠቱን ቀጥሏል፡፡
ከእንግዲህ ወዲያ ለአገራት ብዝበዛ አይሆኑም
እዚህ ስፍራ "አገራት" የሚለው የሚወክለው የአገራትን ህዝቦች ነው፡፡ "የተለያዩ አገራት ሰዎች ከዚህ በኋላ እነርሱን አይበዘብዙም/አይሰርቁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ዝርፊያ
እነዚህ የተሰረቁ ወይም በሀይል የተወሰዱ ነገሮች ናቸው፡፡ "ዝርፊያ" የሚለቀው በሕዝቅኤል 7፡21 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡
የችጋር ምርኮኛ መሆን
"መራብ" ወይም "ከምግብ እጥረት የተነሳ ረሀብተኛ መሆን"
የአገራትን ንቀት አይሸከሙም
እዚህ ስፍራ "አገራት" የሚለው የሚገልጸው የአገራት ህዝቦችን ነው፡፡ "ንቀት" የሚለው ረቂቅ ስም በግስ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡፡ "ከእንግዲህ የተለያዩ አገራት ሰዎች አይሰድቧቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 34:30
እኔ፣ ያህዌ አምላካቸው እኔ ከእነርሱ ጋር ነኝ
እዚህ ስፍራ "እኔ...ከእነርሱ ጋር ነኝ" የሚለው ያህዌ ይረዳቸዋል ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡ "እኔ፣ ያህዌ አምላካቸው፣ እኔ እረዳቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከእነርሱ ጋር፡፡ እነርሱ የእኔ ህዝብ ናቸው
ይህ በአንድ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ "እነርሱ የእኔ ህዝብ ናቸው፣ እኔ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚወክለው ሰዎችን ነው፡፡ "የእስራኤል ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ለእናንተ ለበጎቼ፣ ለመሰማሪያ መንጋዎቼ
ይህ የእስራኤል ህዝብ ለእርሱ የበጎች መንጋ እንደሆኑ እና ያህዌ እረኛቸው እንደሆነ ይገልጻል፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

# Chapter 35

## Ezekiel 35:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ለሕዝቅኤል ትንቢት እንዲናገር ይነግረዋል፡፡ ሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ መናገር ይኖርበታል፣ ነገር ግን መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ህዝብ ነው፡፡
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር ለነቢዩ ወይም ለህዝቡ የተናገረውን ነገር ለማስተዋወቅ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡ ይህ በሕዝቅኤል 3፡16 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ያህዌ ይህንን መልዕክት ነናገረ" ወይም "ያህዌ እነዚህን ቃላት ተናገረ/ ያህዌ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ልጅ
"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ፡፡" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም፡፡ ይህ በሕዝቅኤል 2፡1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡
ፊትህን ወደ ሴይር ተራራ መልስ
የሴይር ተራራ ሩቅ ነው፣ ስለዚህ ሕዝቅኤል ሊመለከተው አይችልም፤ ነገር ግን ያህዌ በዚያ ላሉ ሰዎች ቅጣት እንዲደርስባቸው እንደ ምልክት ወደዚያ አቅጣጫ እንዲያይ ያዘዋል፡፡ ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በሕዝቅኤል 6፡2 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ወደ ሴይር ተራራ ዞረህ ትኩር ብለህ ተመልከት" ወይም "በዚያ የሚኖሩ ጥፋት ይደርስባቸው ዘንድ ወደ ሴይር ትኩር ብለህ ተመልከት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
የሴይር ተራራ እና በእርሱ ላይ የተነገረ ትንቢት
"የሴይር ተራራ፡፡" ያህዌ ለሕዝቅኤል የሚሰማ ይመስል ለሴይር ተራራ እንዲናገር ይናገረዋል፡፡ መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ህዝብ ነው፡፡ "የሴይር ተራራ እና የኤዶም ሰዎች ከፈጸሙት ነገር የተነሳ በእርሱ ላይ የተነገረ ትንቢት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእርሱ
"ለተራራው" ወይም "ለኤዶም ሰዎች"
የሴይር ተራራ ሆይ እነሆ! እኔ በአንተ ላይ ነኝ፣ በእጄ እመታሃለሁ ደግሞም ጠፍ እና ምድረበዳ አደርግሃለሁ
ያህዌ ለሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ ልክ እንደሚሰማው አድርጎ እንዲናገር ያዘዋል፡፡ መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ህዝብ ነው፡፡ "የሴይር ተራራ ሆይ ስማ፣ በእጄ እመታሃለሁ ደግሞም የአንተ ህዝብ ካደረገው የተነሳ ጠፍ እና ምድረበዳ አደርግሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ!
እዚህ ስፍራ "እነሆ!" የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚሆነው ትኩረት ይጨምራል፡፡ "አድምጡ!" ወይም "በእርግጥ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡
እኔ በአናንተ ላይ ነኝ
"እኔ ጠላታችሁ ነኝ" ወይም "እኔ እቃወማችኋለሁ"
በእጄ እመታችኋለሁ
እዚህ ስፍራ "እጅ" ሀይልን ይወክላል፡፡ "እናንተን ለመምታት ሀይሌን እጠቀማለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ሰው የማይኖርበት ምድር/ጠፍ አደርግሃለሁ
"ጠፍ/ምድረበዳ" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል ሊተረጎም ይችላል፡፡ "ምድረ በዳ አደርግሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

## Ezekiel 35:4
አጠቃላይ መረጃ፡
ሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ የሚናገረውን መልዕክት ይቀጥላል፡፡ መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ሰዎች ነው፡፡
እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ
ያህዌ እርሱ ያህዌ እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ ሲል፣ የመጨረሻው ከፍተኛ ስልጣን እና ሀይል ያለው እውነተኛው አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ እንደሚገባቸው እየተናገረ ነው፡፡ ይህ በሕዝቅኤል6፡7 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እኔ ያህዌ እንደሆንኩ እወቁ" ወይም "እኔ ያህዌ የመጨረሻው ስልጣን እና ሀይል እንዳለኝ እወቁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለሰይፍ እጅ አሳልፈህ ሰጠሃቸው
የዚህ ዘይቤ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) "በሰይፍ ለሚገድሏቸው ጠላቶቻቸው አሳልፈህ ሰጠሃቸው" ወይም 2) "በሰይፍ ገደልካቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በጉዳታቸው ጊዜ
"በጥፋት ጊዜ"
በህያውነቴ
"እኔ ህያው እንደሆንኩ፡፡" ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ቀጥሎ የሚናገረው በእርግጥ እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ ይህ የከበረ ቃል መግቢያ መንገድ ነው፡፡ ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "በክብሬ እምላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የጌታ የያህዌ ትዕዛዝ ነው
ያህዌ ራሱን በስሙ የሚገልጸው/የሚምለው፤ የተናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳወቅ ነው፡፡ ይህ በሕዝቅኤል 5፡11 ላይ እንዴት እንንተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ጌታ ያህዌ የተናገረው ይህንን ነው" ወይም "እኔ ጌታ ያህዌ የተናገርኩት ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ለደም ማፍሰስ አዘጋጃችኋለሁ
እዚህ ስፍራ "ደም ማፍሰስ" መግደል ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ለጠላቶቻችሁ ብዙዎቻችሁን መግደልን ቀላል አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ደም ማፍሰስ ይከተላችኋል

እዚህ ስፍራ "ደም መፍሰስ" መግደል ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። ያህዌ ስለ ደም ማፍሰስ የሚናገረው ሊያባርራቸው እንደሚችል ሰው አድርጎ ነው። "ጠላቶቻችሁ ቁልቁል አሳደው ይገደሏችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ደም ማፍሰስን አልጠላችሁምና

እዚህ ስፍራ "ደም መፍሰስ" መግደል ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ጠላት የእስራኤልን ህዝብ በጭካኔ ሲገድል ይህን ድርጊት አልጠላችሁምና" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 35:7

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ ሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ የሚናገረውን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ሰዎች ነው።

ከእርሱ በዚያ የሚያልፈውንም ቆርጬ ስጥል እና እንደ ገና ስመለስ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ቆርጦ መጣል" የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ማጥፋት/መደምሰስ ማለት ነው። "ወደ እርሱ የሚገቡትንም ሆነ የሚወጡትን ሁሉ አጠፋለሁ ወይም 2) "ቆርጦ መጣል" አንድ ሰው አንድ ነገር እንዳያደርግ ማስቆም ለሚለው ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። "ሰዎች ወደ እርሱ እንዳይገቡና እንዳይወጡ/ እንዳይመላለሱ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ የተገደሉ

እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው የሚወክለው በጦርነት የተዋጓቸውን ጠላቶቻቸውን ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ይህ በሕዝቅኤል 31:17 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "ጠላት በሰይፍ የገደላቸው" ወይም "በጦርነት የሞቱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ለአንዴው ጠፍ የሆነ

"እስከ ወዲያኛው ምድረ በዳ የሆነ።" ይህ ጥፋቱን ትኩረት ሰጥቶ ለማጋነን የተነገረ ሊሆን ይችላል። "ከእንግዲህ ሰዎች በእናንተ ከተሞች ውስጥ አይኖሩም" (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት ሚሉትን ይመልከቱ)

ነገር ግን እናነተ ታውቃላችሁ

"እናንተ" የሚለው ብዙ ቁጥር ነው። እግዚአብሔር በአንድ ተራራ ለሚኖሩ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በሴይር ተራሮች ለሚኖሩ ሰዎች እየተናገረ ነው። (አንተ/አንቺ የሚለው ነጠላ ቁጥር ተውላጠ ስም መልኮች)

Ezekiel 35:10

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ ሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ የሚናገረውን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ሰዎች ነው።

አንተ እንዲህ ብለሃል

"አንተ" የሚለው ቃል የሴይር ተራሮችን ያመለክታል። ሕዝቅኤል ለተራራው የሚናገረው ተራራው እንደሚሰማው አድርጎ ነው። መልዕክቱ ለኤዶም ሰዎች ነው። "ህዝቦችህ እንዲህ ብለዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ሁለት ምድሮች

"የእስራኤል እና ይሁዳ ምድሮች"

የእኔ ይሆናሉ

"የእኔ" የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ሊገለጽ ይችላል። "የእኛ ይሆናሉ"

እኛ

"እኛ" የሚለው ቃል የኤዶምን ሰዎች ያመለክታል።

ያህዌ ከእነርሱ ጋር በነበረበት ጊዜ እንኳን

ያህዌ እስራኤልን እና ይሁዳን ይጠብቅ እንደነበር ተጠቁሟል። "ነገር ግን ያህዌ እስራኤልን እና ይሁዳን እየጠበቀ በዚያ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ቁጣችሁ እና ቅናታችሁ አደርግባችኋለሁ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በቁጣችሁ እና ቅናታችሁ ምክንያት እቀጣችኋለሁ" ወይም 2) "በቁጣና ቅናት በእስራኤል ህዝብ ላይ እንዳደረጋችሁት ልክ እንደዚያው እኔም በእናንተ ላይ በቁጣ እና ቅናት አደርግባችኋለሁ"

Ezekiel 35:12

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ ሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ የሚናገረውን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ሰዎች ነው።

በእስራኤል ተራሮች ላይ

እዚህ ስፍራ "ተራሮች" የሚለው የሚወክለው መላውን የእስራኤል ምድር ነው። (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ተደምስሰዋል

ይህ ሀረግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በፍርስራሾች ስር ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ እንድንበላቸው ለእኛ ተላልፈው ተሰጥተዋል

የሴይር ተራሮች ህዝብ የእስራኤልን ምድር ወስደው ለራሳቸው መጠቀሚያ ማድረጋቸው የተገለጸው የዱር እንስሳት እንደሆኑ እና የእስራኤል ተራሮችን እንደሚበሉ ተደርጎ ነው። "እነርሱ በዚህ ያሉት እኛ እንደንበላቸው ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

Ezekiel 35:14

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ ሕዝቅኤል ለሴይር ተራራ የሚናገረውን መልዕክት ይቀጥላል። መልዕክቱ ለመላው የኤዶም ሰዎች ነው።

ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል

ይህ በአንደኛ መደብ ሊገለጽ ይችላል። "እኔ፣ ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተን ምድረ በዳ/ጠፍ ምድር አደርግሃለሁ

እዚህ ስፍራ "አንተ" የሚለው የሴይር ተራሮችን ነው፣ ነገር ግን መልዕክቱ ለኤዶም ሰዎች ነው። "ጠፍ/ሰው የማይኖርበት ምድር" የሚለው ረቂቅ ስም በቅጽል መልክ ሊጻፍ ይችላል። "የአንተ ህዝብ ባደረገው ነገር ምክንያት አንተን ሰው የማይኖርበት ምድረ በዳ አደርግሃለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

መላዋ መሬት ሀሴት ታደርጋለች

እዚህ ስፍራ "መሬት" የሚለው ቃል የሚወክለው የምድር ሰዎችን ነው። "መላው" የሚለው ቃል በሴይር ተራሮች አቅራቢያ ብቻ የሚኖሩ ሰዎችን የሚያመለክት ማጠቃለያ ነው። "እኔ የአንተን ደስታ መደምሰሴን የሚያውቁ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እስራኤል ሰው የማይኖርባት በመሆኗ ምክንያት በህዝቧ ርስት አንተ ሀሴት በምታደርግበት ጊዜ

ይህ የሚገልጸው ያህዌ ለእስራኤላውያን ርስት አድርጎ የሰጣቸውን ምድር ነው። "የእስራኤልን ምድር ሰው የማይኖርበት ባደረግሁ ጊዜ አንተ ሀሴት እንዳደረግህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በአንተ ላይም እንደዚያው አደርጋለሁ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እኔ ምድርህን ሰው የማይኖርበት አደርጋለሁ" ወይም 2) "የአንተ ምድር ሰው የማይኖርበት በሚሆንበት ጊዜ እኔ ሀሴት አደርጋለሁ" ወይም 3) "አንተ ጠፍ/ሰው የማይኖርበት ስፍራ በመሆንህ ምክንያት ሌሎች ደስ እንዲላቸው አደርጋለሁ"

የሴይር ተራራ እና መላው ኤዶም፣ ሰው የማይኖርበት ትሆናላችሁ

ያህዌ ለህዝቅኤል ለሴይር ተራራ መስማት እንደሚችል አድርጎ መናገሩን እንዲቀጥል ይነግረዋል። መልዕክቱ ለኤዶም ህዝብ ሁሉ ነው። "የሴይር ተራራ እና መላውን ኤዶም ሰው የማይኖርባቸው አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ... እነርሱ ያውቃሉ

"እነርሱ" የሚለው ቃል ሊያመለክት የሚችለው 1) "የመሬት ሰዎች" ወይም 2) "የእስራኤል እና የይሁዳ ሰዎች"

Chapter 36

Ezekiel 36:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ሕዝቅኤልን ትንቢት እንዲናገር ይነግረዋል፡፡ ሕዝቅኤል የሚናገረው ለእስራኤል ተራሮች ነው፣ ነገር ግን ለመላው የእስራኤል ሰዎች ነው፡፡

የሰው ልጅ

"የሰብአዊ ፍጡር ልጅ" ወይም "የፍጥረታዊ ሰው ልጅ፡፡" እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን እንዲህ ብሎ የሚጠራው ሕዝቅኤል ሰው ብቻ መሆኑን ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እና ሀያል ነው፣ ሰዎች ግን እንዲህ አይደሉም፡፡ ይህ በሕዝቅኤል 2:1 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ፡፡ "ሟች የሆነ ሰው" ወይም "ሰብአዊ ፍጡር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡

ለእስረኤል ተራሮች ትንቢት ተናገር

እግዚአብሔር ሕዝቅኤል ለተራሮች ሰዎች እንደሆኑ አድረጎ እንዲናገር ይፈልጋል፡፡ መልዕክቱ ለእስራኤል ሰዎች ነው፡፡ (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሃ

ይህ የደስታ ስሜት መግለጫ ነው፡፡ "በጣም ደስ ተሰኝቻለሁ" ወይም "ይህ ድንቅ ነገር ነው" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡

ጥንታዊ ከፍተኛ ስፍራዎች

"በጣም ጥንታዊ ተራሮች፡፡" ይህ የእስራኤልን ከፍተኛ ተራሮች ያመለክታል፡፡

የእኛ ርስት ሆንክ

"አሁን የእኛ ሆንክ"

አንተ ጠፍ በመሆንህ ምክንያት

"ጠፍ" የሚለው ረቂቅ ስም "ሰው የማይኖርበት" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡ "አንተ የእስራኤል ተራራ ሰው የማይኖርበት በመሆንህ ምክንያት "በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከሁሉም አቅጣጫ ከመጣብህ ጥቃት የተነሳ

"ከሁሉም አቅጣጫ ጥቃት ስለደረሰብህ" ወይም "ጠላቶችህ በሁሉም አቅጣጫ ስላጠቁህ"

የሀሜተኛ ከንፈሮች እና ምላሶች መነጋገሪያ፣ የሰዎች መተረቻ ሆንክ

እዚህ ስፍራ፣ "ከንፈሮች" እና "ምላሶች" የሚወክሉት የሰዎችን ንግግር ነው፡፡ "ሰዎች ስለ አንተ መጥፎ ነገሮችን ይናገራሉ፣ አገሮችም ደግሞ ስለ አንተ ክፉ ወሬ ያወራሉ" (ስኔክቲክ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

Ezekiel 36:4

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ ያህዌ ለሕዝቅኤል ለእስራኤል ተራሮች ትንቢት እንዲናገር መንገሩን ይቀጥላል፡፡ መልዕክቱ ለመላው የእስራኤል ሰዎች ነው፡፡

አጠቃላይ መረጃ፡

እነዚህ አንድ ሰው በእጁ ይዞ ሊጠጣባቸው የሚችሉ መጠጫዎችና ሌሎች ዕቃዎች ናቸው፡፡
አባቱ ናቡከደነፆር የወሰዳቸውን
እዚህ ላይ “ናቡከደነፆር” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የናቡከደነፆርንሠራዊት ነው፡፡“የአባቱ የናቡከደነፆርሠራዊት”ወይም “አባቱ የወሰደው የናቡከደነፆር ሠራዊት”
Daniel 5:3
ከእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የመጡት የወርቅ ዕቃዎች
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የናቡከደነፆር ወታደሮች ከቤተመቅደስ የወሰዷቸው የወርቅ ዕቃዎች”
ከቤተ መቅደስ ማውጣት፤ከእግዚአብሔር ቤት
“ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውጪ” “የእግዚአብሔር ቤት” የሚሉት ሐረጎች ስለ ቤተመቅደሱ የበለጠ ነገር ይነግረናል፡፡
Daniel 5:5
በዚያም ሰዓት
“ያንን ባደረጉበት ቅፅበት” ወይም “በድንገት”
ልስን
በሚደርቅበት ወቅት የለሰለሰ ጠንካራ ገፅታ የሚኖረው ሆኖበግድግዳ ወይም በጣሪያ ላይ የሚለሰን ሲሚንቶ ወይም ጭቃ ነው፡፡
የንጉሡ ፊት ተለወጠ
“ፊቱ ገረጣ” ይሄ የሆነው ከመፍራቱ ተነሳ ነው፡፡
ጉልበቱ
“እግሮቹ”
ጉልበቶቹም ተብረከረኩ
ይሄ የነበረበት የከፍተኛ ፍርሃት ውጤት ነው፡፡
Daniel 5:7
በባቢሎን ውስጥ በጥበባቸው የታወቁትን
ይሄ የሚያመለክተው ከሙታን ጋር እንነጋገራለን የሚሉትን፤ጥበበኞችንና ኮከብ ቆጣሪዎችን ነው፡፡
ይህንን ፅሕፈት ያነበበ ፍቺውንም ያሳየኝ ሐምራዊ ግምጃ ይለብሳል፤የወርቅ ማርዳም በአንገቱ ዙርያ ይደረግለታል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ይህንን ፅሑፍና ትርጉሙን ለሚያብራራልኝ ለማንኛውም ሰው ሀምራዊ የሆነ አልባሳትና የወርቅ ሠንሠለት በአንገቱ ላይ አደርግለታለሁ፡፡”
ሐምራዊ ግምጃ መልበስ
ሐምራዊ ግምጃ እምብዛም ያልተለመደና ንጉሣዊ ባለሥልጣናት ብቻ የሚያደርጉት ነገር ነው፡፡ “ንጉሣዊ አልባሳትን መልበስ”
ሦስተኛ ገዢ
“በደረጃ ሶስተኛ የሆነ ገዢ”
Daniel 5:8
ብልጣሶር
ይሄ የናቡከነፆር ልጅ ሲሆን አባቱ ሲሞት ንግሥናውን የተረከበው ሰው ነው፡፡ይህንን ሥም በትንቢተ ዳንኤል5፡1 ላይ እንዴት እንደየፋችሁት ተመልከቱ፡፡
ፊቱ ተለወጠበት
“ፊቱ ደም ገረጣ” የንጉሡ ፊት በትንቢተ ዳንኤል 5፡6 ከነበረው ይልቅ የገረጣ ነበረ፡፡
ሃሣቡ አስቸገረው
ሊገባው አልቻለም፤ግራ ተጋባ፡፡
Daniel 5:10
ንግሥቲቱ

አንዳንድ ዘመናዊ የሆኑ የመፅሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ይህንን የሚያያይዙት ከንግሥቲቱ ማለትም ከንጉሱ እናት ጋር ነው፡፡በጥንቷ ባቢሎን የንጉሱ እናት ከፍተኛ የሆነ ክብር ይሰጣቸው ነበር፡፡

ንጉሥ ሆይ ሺህ ዓመት ንገስ!

ይሄ ንጉሱን ሠላምታ የማቅረብ የተለመደ ሥርዓት ነው፡፡

ፊትህም አይለወጥ

“ፊትህ እንዲህ የሚገረጣበት ምክኒያት የለም”

Daniel 5:11

የቅዱሳን አማልዕክት መንፈስ

ንግስቲቷ የዳንኤል ኃይል የሚመነጨው ናቡከደነፆር ያመልካቸው ከነበሩት ጣዖታት ነው ብለው ያምኑ ነበር፡፡ይህንን ሐረግ በትንቢተ ዳንኤል 4፡8 ላይ እንዴት አድርጋችሁ እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡

በአባትህም ዘመን

“አባትህ ይገዛ በነበረበት ወቅት”

እንደ አማልዕክት ያለ ጥበብ፤ማስተዋልና ዕውቀትም ተገኘበት

ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ልክ እንደ አማልዕክቶች ያለ ጥበብ፤ማስተዋልና ዕውቀት አለው፡፡”

ንጉሥ ናቡከደነፆር፤ንጉሡ አባትህ

“አባትህ ንጉሡ ናቡከደነፆር”

እነዚህ መልካም ነገሮች ሁሉንጉሱ ብልጣሶር ብሎ በሰየመው በዳንኤል ዘንድ ተገኘ፡፡

ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ንጉሡ ብልጣሶሰር ብሎ የሰየመው ይሄው ራሱ ዳንኤል እነዚህ ሁሉ መልካም ነገሮች የሞሉበት ሰው ነበረ፡፡”

የተፃፈውን

“በግድግዳው ላይ የተፃፈውን” በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በግድግዳው ላይ በእጅ የተፃፈው ነገር”

Daniel 5:13

የዚያን ጊዜም ዳንኤል ወደ ንጉሱ ፊት ገባ

“በዚያን ጊዜ ወታደሮቹ ዳንኤልን ወደ ንጉሡ ፊት እንዲቀርብ አደረጉት”

ንጉሡ አባቴ ከይሁዳ የማረካቸው

በዚህ ሐረግ ውስጥ“አባት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ወታደሮችን ሁሉ ነው፡፡“የአባቴ ወታደሮች ከይሁዳ የማረካቸው፡፡”

የአማልዕክት መንፈስ

የዳንኤል ኃይል የሚመነጨው ራሱ ብልጣሶር ያመልካቸው ከነበሩ ጣዖታት ነው ብሎ ያምን ነበር፡፡ይሄንን በትንቢተ ዳንኤል 14፡8 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡

ዕውቀት ማስተዋልና ጥበብ በአንተ ውስጥ ተገኝቷል፡፡

ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ብሩህ የሆነ አዕምሮና ድንቅ የሆነ ጥበብ ባለቤት ነህ፡፡”

Daniel 5:15

ጠቢባንና አስማተኞች ወደ እኔ ገብተው ነበር

ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡ “የታወቁ ሰዎች …በፊቴ ቀርበው ነበር”

ያስታውቁኝ ዘንድ

“እንዲነግሩኝ”

ሐምራዊ ግምጃ ትለብሳለህ፤የወርቅ ማርዳም በአንገትህ ዙሪያ ይደረግልሃል

ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ሐምራዊ የሆነ ልብስና የአንገት ወርቅ እሰጥሃለሁ”

ሐምራዊ ልብስ መልበስ

ሐምራዊ ልብስ እምብዛም ያልተለመደ ሲሆን ይለብሱ የነበሩትም ንጉሣውያን ባለሥልጣናት ብቻ ነበሩ፡፡“በንጉሣዊ አልባስ መዋብ”

ሶስተኛ ገዢ

“በማዕረግ ሶስተኛ የሆነ ገዢ”

Daniel 5:17

ሥጦታህ ለአንተ ይሁን

“ሥጦታህን አልፈልገውም”

ወገኖች፤አህዛብና በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩሁሉ

ይሄ ሐረግ“ሁሉ”የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ሠፊ ቁጥር ያለውን ሕዝብ አጠቃልሎ ለመግለፅ ነው፡፡“ከተለያዩ ወገኖች የሆኑና የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ሰዎች”

ወገኖች፤አህዛብና በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሁሉ

እዚህ ላይ “ወገኖች” እና “ቋንቋዎች”የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ከተለያዩ ወገኖች የሆኑና የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሕዝቦችን ነው፡፡ትንቢተ ዳንኤል 3፡4ን3 እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡ “ከተለያዩ ወገኖች የሆኑ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሕዝቦች”

ይንቀጠቀጡና ይፈሩ ነበር

በመሠረቱ እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ፍርሃቱ ከፍተኛ ስለመሆኑ አፅንዖት ይሰጣሉ፡፡“በጣም ፈርተውት ነበር”

የፈቀደውን ይገድል

ይሄ ሐረግ ራሱ ናቡከደነፆር ሰዎቹን ገደላቸው ማለቱ ሣይሆን ያዘዛቸው ሰዎች ናቸው ተግባራዊ ያደረጉት ለማለት ነው፡፡“ናቡከደነፆር ሊገድላቸው የፈለጋቸውን ሰዎች ወታደሮቹን በማዘዝ እንዲገደሉ አደረጋቸው፡፡”

የፈቀደውን በሕይወት ያኖር

“ከፍ ለማድረግ የፈለገውን ሰው ከፍ ያደርግ ነበር”

የፈቀደውን..የፈለገውን

እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው፡፡

የፈቀደውንም ያዋርድ ነበር

“ለማዋረድ የፈለገውን ያዋርድ ነበር”

Daniel 5:20

ልቡ ታበየ

እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱ ንጉሱን ነው፡፡“ንጉሱ ግትር ሰው ነበር”

መንፈሱ በጠነከረ

እዚህ ላይ“መንፈስ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱ ንጉሱን ነው፡፡ግትር መሆኑ የሚገለፀው ልክ ጠንካራ እንደሆነ በሚመስል መልኩ ነው፡፡

በሚያውክ ሁኔታ

ሥርዓት አልባና ከልክ ባለፈ መልኩ በራስ መተማመን

ከመንግሥቱ ዙፋን ተዋረደ

እዚህ ላይ“ዙፋን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለመግዛት የሚያበቃውን ኃይል ነው፡፡ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ሰዎች መንግሥቱን ወሰዱበት”

ከሰው ልጆች ተለየ

ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ሰዎች ከአጠገባቸው እንዲሄድ አስገደዱት”

ልቡም እንደ አውሬ ልብ ሆነ

“ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አስተሳሰቡን ነው፡፡ “ልክ እንደ እንስሳ ማሰብ”

ጠል

ማለዳ በሚሆንበት ወቅት በመሬት ላይ የሚታይ አርጥበታማ ነገር፡፡

የሚወድደውን ሁሉ

“የሚመርጠውን ሁሉ”

Daniel 5:22

ብልጣሶር

ይሄ ከአባቱ በመቀጠል ንጉስ የሆነው የናቡከደነፆር ልጅ ነው፡፡በትንቢተ ዳንኤል 5፡1 ላይ ይህንን ሥም እንዴት እንደፃፋችሁት ተመልከቱ፡፡

ልብህን አላዋረድክም

እዚህ ላይ“ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ወደራሱ ወደ ብልጣሶር ነው፡፡“ራስህን አላዋረድክም”

በሰማይ ጌታ ላይ ኮራህ

በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ልበ እርሱ ላይ እንደመኩራት ተቆጥሮ ተገልፆአል፡፡“በእግዚአብሔር ላይ አምፀሃል”

ከቤቱ

እዚህ ላይ “ቤቱ”ምንና የት እንደሆነ ግልፅ በሆነ መልኩ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በኢየሩሣሌም ውስጥ ከሚገኘው ቤተመቅደሱ”

ትንፍሽህን በእጁ የያዘው እግዚአብሔር

እዚህ ላይ “ትንፋሽ”የሚለው ቃል ሕይወትን የሚያመለክት ሲሆን “እጅ”የሚለው ቃል ደግሞ ሥልጣንን ወይም መግዛትን የሚያመለክት ነው፡፡“ትንፋሽ የሚሰጥህ እግዚአብሔር” ወይም“በሕይወትህ ላይ ሁሉ ገዢ የሆነው እግዚአብሔር”

መንገድህን ሁሉ

“የምታደርገውን ሁሉ”

ይህ ፅሕፈት ተፃፈ

ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ይህንን መልዕክት ፃፈ”

Daniel 5:25


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህም ፅሕፈት ተፅፏል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እጁ የፃፈው መልዕክት ይሄ ነው፡፡”
ማኔ፤ቴቄል፤ፋሬስ
እነዚህ በአረማይክ ቋንቋ ግድግዳው ላይ የተፃፉ ቃላት ናቸው፡፡
“ማኔ”…እግዚአብሔር መንግሥትህን ቆጠረው
“ማኔ”ማለት እግዚአብሔር ቆጠረው ማለት ነው፡፡
“ቴቄል” ተመዘንህ
“ቴቄል”ማለት በሚዛን ተመዘንህ ማለት ነው፡፡
“ፋሬስ” መንግሥትህ
“ፋሬስ”ማለት መንግሥትህ ማለት ነው፡፡
በሚዛን ተመዘንክ ቀለህም ተገኘህ
ንጉሱ ግዛቱን የመግዛቱን ጉዳይ በተመለከተ ጠቃሚ መሆን አለመሆኑን ለመናገር በሚዛን እንደሚመዘን ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው፡፡ ይሄ ማለት ንጉሱ የመግዛት ብቃት የለውም ማለት ነው፡፡ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር የመግዛት ብቃትህን መዝኖ የመግዛት ብቃት እነደሌለህ ደርሶበታል፡፡”

መንግሥትህ ተከፈለ ለሜዶንና ለፋርስ ሰዎች ተሰጠ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር መንግሥትህ ከፍሎ ለሜዶንና ለፋርስ ሰዎች ሰጥቷቸዋል፡፡”
Daniel 5:29
ብልጣሶር
ይሄ ከአባቱ በመቀጠል ንጉስ የሆነው የናቡከደነፆር ልጅ ነው፡፡በትንቢተ ዳንኤል 5:1 ላይ ይህንን ሥም እንዴት እንደፃፋችሁት ተመልከቱ፡፡
የወርቅ ማርዳ በአንገቱ ላይ ተደረገለት
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የወርቅ ሀንሠለት በአንገቱ ዙሪያ አደረጉለት”
በመንግሥቱም ላይ ሶስተኛ ገዢ
“ቁጥር ሶስት ገዢ”
መንግሥትን ተረከበ
“የመንግሥቱ ገዢ ሆነ”
ዕድሜው ስድሳ ሁለት በነበረ ጊዜ
“ዕድሜው ስድሳ ሁለት አካባቢ በነበረ ወቅት”

---

Chapter 6
Daniel 6:1
ሃሣብን ማያያዣ
በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙት ክስተቶች የተከናወኑት ፋርሶች ባቢሎናውያንና ከለዳውያንን ድል ካደረጉ በኋላ ነበር፡፡ሜዶን በባቢሎን ውስጥ መግዛት ጀመረ፡፡
ዳርዮስን ደስ አሰኘው
“ንጉስ ዳርዮስ ውሳኔ አሣለፈ”
120 መሣፍንት
“አንድ መቶ ሃያ የግዛት ባለሥልጣናት”
በእነርሱ ላይ
“በእነርሱ ላይ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው 120ውን የግዛት ባለሥልጣናትን ነው፡፡
ንጉሡም እንዳይጎዳ
“ከንጉሡ ምንም ዓይነት ነገር እንዳይሰረቅ” ወይም “ማንም ሰው ከንጉሱ እንዳይሰርቅ”
በላያቸው አደረገ
“የበላይ እንዲሆን ተደረገ” ወይም “ከ…ይልቅ የበለጠ ብቃት ነበረው”
መልካም የሆነ መንፈስ ነበረው
እዚህ ላይ“መንፈስ” የሚለው ቃል የሚመለክተው ዳንኤልን ነው፡፡እጅግ በተለየ መልኩ ብቃት የነበረው ሰው ነበር ማለት ነው፡፡ “ልዩ የሆነ ሰው ነው”
መልካም መንፈስ
ከሌሎች ይልቅ የተሻለ ነገሮችን እንዲያከናውን የሚረዳው መንፈስ፡፡
ይሾመው ዘንድ
“ሥልጣንን ይሰጠው ዘንድ” ወይም “በኃላፊነት ቦታ ላይ ማስቀመጥ”
Daniel 6:4
የዚያን ጊዜ አለቆችና መሳፍንቱ ስለ መንግሥቱ
ሌሎቹ ባለሥልጣናት በዳንኤል ላይ ቀኑበት፡፡ይሄ የበለጠ ሊብራራይችላል፡፡“የዚያን ጊዜ ሌሎች አለቆችና መሳፍንቱ ቀኑበት፡፡ስለሆነም ዳንኤል በሚሰራው የመንግሥት ሥራ ውስጥስህተት መፈለግ ጀመሩ፡፡”
በእርሱ ላይ ሰበብና በደል ሊያገኙበት አልቻሉም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በሚሰራው ሥራ ላይ ምንም ዓይነት ሰበብና በደል ሊያገኙበት አልቻሉም፡፡”
ችላ ማለት
ኃላፊነትን በአግባቡ አለመገንዘብ
ዳንኤልን በመቃወም ማጉረምረም
“ዳንኤልን በሚመለከት ሰበብ መፈለግ”
Daniel 6:6
አንድ ዕቅድ በንጉሡ ፊት አመጡ
“አንድ ዕቅድ በንጉሱ ፊት አቀረቡ”
ሺህ ዓመት ንገሥ
ለአንድ ንጉሥ የሚሰጥ የተለመደ የሠላምታ አቀራረብ ነው፡፡
ለሰላሣ ቀናት
“ለሠላሳ ቀናት”

ማንም ሰው ልመና ቢለምን
“ማንም ጥያቄ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር”
ያ ሰው በአንበሣ ጉድጓድ ውስጥ ይጣል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ወታደሮችህ ያንን ሰው በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ መጣል ይኖርባቸዋል፡፡”
የአንበሣ ጉድጓድ
ይሄ አንበሶች የሚጠበቁበትን ቤት ወይም ጉድጓድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፡፡
Daniel 6:8
ሃሣብን ማያያዣ
በቁጥር 8 ላይ አስተዳዳሪዎቹ ለንጉሡ መናገራቸውን ይቀጥላሉ፡፡
በሕጉ በተደነገገው መሠረት
“በሕጎቹ መሠረት”
ሊለወጥ አይችልም
“ሊሰረዝ አይችልም”
አዋጁን በሕግ ማፅናት
“ሥርዓቱን ወደ ሕግ መለወጥ”
Daniel 6:10
ዳንኤልም ሰነዱ ተፈርሞ በሕግነት እንደፀና በወቀ ጊዜ
ዳንኤል ወደ እግዚአብሔር ከመፀለዩ በፊት ስለ አዲሱ ሕግ መውጣት ዕውቀቱ እንደነበረው ግልፅ ማድረጉ ለታሪኩ ጠቃሚ ነው፡፡
የእልፍኙ መስኮቶችም በኢየሩሣሌም አንፃር ተከፍተው ነበር
ይሄ የዳንኤል ጠላቶች ወደ እግዚአብሔር ይፀልይ እንደነበረ ስለማወቃቸው የቆየ መረጃ እንዳላቸው የሚገልፅ ነው፡፡
በአምላኩ ፊት አመሰገነ
“እግዚአብሔርን አመሰገነ”
ሤራ
ለክፋት የታቀደ ዕቅድ
Daniel 6:12
ትዕዛዝ አልፃፍክምን?.....አንበሶች?
ይህንን ጥያቄ የጠየቁበት ምክኒያት ንጉሱ ትዕዛዝ ማውጣቱን እነዲያረጋግጥላቸው ነበር፡፡
ልመና እንዳያቀርብ
“ጥያቄ የሚጠይቅ”
የአንበሶች ጉድጓድ
ይሄ ምናልባትም አንበሶች ተጠብቀው የሚኖሩበትን ክፍል ውስጥ ወይም ጉድጓድ ለማመልከት ሊሆን ይችላል፡፡
በሕጉ እንደተደነገገው
“በሕጉ መሠረት”
Daniel 6:13
ያ ዳንኤል የሚባለው ሰው
ይህ ዳንኤልን በማክበር የሚደረግ ምልከታ አይደለም፡፡ይህንን ሐረግ የተጠቀሙት ዳንኤልን እነደ ከፍተኛ ባለሥልጣንነቱ የሚገባውን ክብር ሆነ ብለው ለመንፈግ

ነበር።
የይሁዳ ምርኮኞች ከሆኑት መካከል አንዱ ነው
“ከይሁዳ ተሰድዶ የመጣው”
ትዕዛዝህን ለመቀበል ፈቃደኛ አይደለም
የዚህ ዘይቤያዊ አነጋገር ትርጉም ችላ ይልሃል ማለት ነው።“እርሱ አይታዘዝህም”
በአዕምሮው ያሰበውን አደረገ
እዚህ ላይ “አዕምሮ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አስተሳሰቡን ነው።“እንዴት ማድረግ እንደሚኖርበት በእጅጉ አሰበበት”
ደከመ
ይሄ የሚያመለክተው አካላዊ ድካምን ሣይሆን የአዕምሮ ድካምን ነው።
Daniel 6:15
ሕጉ ....አይለወጥም
ሰዎቹ የንጉሱ ሕግ ወይም የንጉሱ ትዕዛዝ ሊለወጥ የማይቻል መሆኑን እያሣሰቡ ነው ያሉት።ዳንኤል ወደ አንበሶቹ ግድጓድ መጣል ይኖርበታል።አስፈላጊ ከሁነ ይሄ ሊብራራ ይችላል።“ሕጉ…አይለወጥም።ዳንኤልን ወደ አንበሶች ጉድጓድ መጣል ይኖርባቸዋል።”
Daniel 6:16
ዳንኤልን አመጡት
“ወታደሮቹ ዳንኤልን ሄደው አመጡት”
የአንበሣ ጉድጓድ
ይሄ አንበሶች ተጠብቀው የሚኖሩበትን ክፍል ወይም ጉድጓድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
የምታመልከው አምላክ እርሱ ያድንህ
ንጉሱ ዳንኤልን ለማዳን ያለውን ምኞት እየገለፀ ነው።
ያድንህ
“ከአንበሶች ያድንህ”
Daniel 6:17
X
ይሄ አንበሶች ተጠብቀው የሚኖሩበትን ክፍል ወይም ጉድጓድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡
ንጉሱም በዳንኤል ላይ የተደረገው እንዳይለወጥ በቀለበቱና በመኳንንቱ ቀለበት አተመው
በቀለበት የመታተሙ ጠቀሜታ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።ንጉሱና መኳንንቱ በሰም በተሰራ ማህተም በቀለበታቸው አተሙት።ንጉሱ ፊርማውን በሰም ውስጥ አድርጎ ካተመ በኋላ መኳንንቶቹም በተመሳሳይ ሁኔታ አደረጉ።ማንም ሰው ቢሆን ዳንኤልን ለመርዳት በሚል ሰበብ ማሕተሙ ያዘለውን ትዕዛዝ ለመሻር አልተፈቀደለትም ነበር።
በዳንኤል ላይ የተወሰነው ነገር እንዳይለወጥ
“ማንም ሰው ቢሆን ዳንኤልን ለማገዝ አይችልም ነበር”
ሳይበላም አደረ
ይህ ድርጊት የሚያሣየው ንጉሱ የዳንኤል ጉዳይ ምን ያህሰል ያስጨነቀው መሆኑን ነው።
የሚያዝናኑ ነገሮች በፊቱአልቀረቡለትም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሚያዝናናው ማንም ሰው አልነበረም”
እንቅልፍም ከእርሱ ራቀ
እንቅልፍ ልክ ከንጉሱ እየሮጠ እንደሚሄድ ዓይነት ነገር ነው የተገለፀው።“በዚያን ሌሊት ሁሉ እንቅልፍ ሳይዘው አሳለፈ”
Daniel 6:19
አልበደልሁም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ምንም ዓይነት ስህተት እንዳልፈፀምኩ ያውቃል።”
ጉዳት አልደረሰበትም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በዳንኤል ላይ ምንም ቁስል አላገኙበትም”
Daniel 6:24
የአንበሶች ጉድጓድ
ይሄ አንበሶች ተጠብቀው የሚኖሩበትን ክፍል ወይም ጉድጓድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
ወደ ጉድጓዱ መጨረሻ ሳይደርሱ
“በአንበሶቹ ጉድጓድ ወለል ላይ ከመድረሳቸው በፊት”
አጥንታቸውንም ሰባበሩ
“አጥንታቸውን አደቀቁት”
ወገኖች፤አህዛብና ቋንቋዎች
እዚህ ላይ “አህዛብ” እና “ቋንቋዎች”የሚለው ቃል የሚወክለው ከተለያዩ ነገዶች የመጡና የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሰዎችን ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 6፡7 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። “ከተለያዩ ነገዶች የመጡና የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሰዎች”
በምድር ሁሉ
ንጉሥ ዳርዮስ መልክዕቱን የፃፈው ሠፊ ለነበረው ግዛቱ ሁሉ ነበር።ምንም እንኳን በምድር ላይ የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ የሚያጠቃልል ባይሆንም እዚህ ላይ “በምድር ሁሉ”የሚለው ቃል መንግሥቱ ምን ያህል ሠፊ እንደነበረ አፅንዖት ለመሥጠት ነው።“በመንግሥቱ ውስጥ”
ሰላም ይብዛላችሁ
ይሄ በሁሉም የሕይወት ዘርፎች ለአንድ ሰው መለካም ይሆንለት ዘንድ ለመመኘት የሚቀርብ የሠላምታ ዓይነት ነው።
Daniel 6:26
ሐሣብን ማያያዣ
በዚህ ውስጥ ዳርዮስ በግዛቱ ውስጥ ለሚገኙ ሁሉ መልዕክት ማስተላለፉን ይቀጥላል።
መንቀጥቀጥና መፍራት
እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ በመሆናቸው ሊጣመሩ ይችላሉ።“በፍርሃት መራድ”
የዳንኤል አምላክ
“ዳንኤል የሚያመልከው አምላክ”
ሕያው የሆነ አምላክ፤ለዘላለም የሚኖር
“ሕያው የሆነ” እና “ለዘላለም የሚኖር”የሚሉት ሁለት ቃላትእግዚአብሔር ለዘላለም ስለመኖሩ ተመሳሳይ የሆነ ሃሣብን የሚገልፁ ናቸው።
መንግሥቱ…ግዛቱ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“መንግስቱን ማንም አያጠፋውም”ወይም “መንግሥቱ ለዘላለም ይኖራል”
ግዛቱም እስከ መጨረሻ ድረስ ይኖራል
“ለዘላለም ይነግሳል”
ዳንኤልንም ከአንበሶች አፍ አድኖታል
“ኃይለኛ የሆኑ አንበሶች ዳንኤልን እንዲጎዱት አልፈቀደላቸውም”
Daniel 6:28
በዳርዮስ መንግሥትና በፋርሳዊው በቂሮስ መንግሥት
የፋርሱ ቂሮስ ከዳርዮስ በመቀጠል የነገሰ ንጉሥ ነበር።

---

Chapter 7
Daniel 7:1
አጠቃላይ መረጃ
ምዕራፍ 7 እና 8 በቅደም ተከተላቸው መሠረት የተቀመጡ አይደሉም።በምዕራፍ 6 ላይ የቀረበው ዳርዮስና ቂሮስ ከመግዛታቸው አስቀድሞ ብልጣሶር ንጉሥ በነበረበት ወቅት የተከናወነ ነው።
አጠቃላይ መረጃ
በዳንኤል ራዕይ ውስጥ ሌሎች ነገሮችን የሚያመላክቱ እንስሳትን ተመለከተ። ከራዕዩ በኋላ የእነዚህን ተምሣሌቶች ትርጉም ያብራራል።
ብልጣሶር
ይሄ ከእርሱ በኋላ ንጉሥ የሆነው የናቡከደነፆር ወንድ ልጅ ሥም ነው።ይህንን እንዴት እንደፃፋችሁት በትንቢተ ዳንአል 5፡1 ላይ ተመልከቱ።
ሕልምና ራዕይ
ሁለቱም “ሕልም”እና “ራዕይ” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በዚህ ምዕራፍ ላይ የተገለፀ ውን ተመሳሳይ ሕልም ነው።“ሕልም ባለመበት ወቅት ያያው ራዕይ”
አራቱ የሰማይ ነፋሳት
“በሥፍራው ያሉ ነፋሳት ሁሉ”ወይም “በአራቱም አቅጣጫዎች ያሉ ኃይለኛ ነፋሳት”
ይጋጩ
“ተላተመ” “ተናወጠ” “ለከፍተኛ ማዕበል መነሳት መንስኤ ሆነ”
Daniel 7:4
መጀመሪያይቱ አንበሣ ትመስል ነበር የንስርም ክንፍ ነበራት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይሄ ተምሣሌታዊ ፍጥረት እንጂ በምድር ላይ የሚኖር የእንስሳ ዘር አይደለም።
ክንፎችዋም ከእርስዋ እስኪነቀሉ ድረስ አይ ነበር፤ከምድርም ከፍ ከፍ ተደረገች፤እንደ ሰውም በሁለት እግር እንድትቆም ተደረገች
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል። “የሆነ ሰው ክንፎችዋን ነቅሎ ከምድር ላይ ካነሳት በኋላ ልክ እንደ ሰዎች በሁለት እግሮቿ እንድትቆም አደረጋት።”
የሰውም ልብ ተሰጠው
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አስተሳሰብን ነው።ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሆነ ሰው እንደ ሰው የማሰብ ችሎታ እንዲኖራት አደረገ”
ሁለተኛው እንሥሳ…እንደ ድብ
ይሄ በገሃዱ ዓለም የሚገኝ እንስሳ አይደለም።ከድብ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ተምሳሌታዊ እንስሳ ነው።
የጎድን አጥንት
ከጀርባ የአጥንት አከርካሪ ጋር የሚገናኙ ሠፊና ጠምዛዛ የሆኑ የደረት አጥንቶች ናቸው።
ተባለላት
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሆነ ሰው ተናገረው”
Daniel 7:6
ነብር የምትመስል ሌላ እንስሳ
ይሄ በገሃዱ ዓለም የሚገኝ ነብር አይደለም።ከነብር ጋር ተመሳሳይ የሆነ ተምሳሌታዊ እንስሳ ነው።
አራት ክንፎች…አራት ራሶች
አራቱ ክንፎችና አራቱ ራሶች ተምሣሌታዊ ቢሆኑም ትርጉም ግን ግልፅ አይደለም።
አራት ራሶች ነበሩት
“እንስሳው አራት ራሶች ነበሩት”
ግዛትም ተሰጣት
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሆነ ሰው መግዛት እንደትችል ሥልጣንን ሰጣት”
አራተኛው እንስሳ…አስር ቀንዶች ነበሯት
ይሄኛውም በገሃዱ ዓለም የሚገኝ እንሥሳ አይደለም።ተምሣሌታዊ ፍጥረት ነው።
በእግር ተረገጠ
“በላዩ ላይ ተራምዶ ፈጨው”
Daniel 7:8
አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል በትንቢተ ዳንኤል 7፡7 ስለ አራተኛው እንስሳ በራዕይ የተመለከተውን መግለፁን ይቀጥላል።
ቀንዶቹ
“ቀንዶች የሥልጣን ተምሣሌት ሲሆኑ ኃይለኛ የሆኑ መሪዎችን የሚያመለክት ነው።”
በፊቱም ከቀደሙት ቀንዶች ሶስቱ ከሥራቸው ተነቃቀሉ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ትንሹ ቀንድ ቀደሙትን ሶስት ቀንዶች ነቃቀላቸው”
ስለ ትላልቅ ነገሮች የሚያወሳ የትዕቢት አፍ
እዚህ ላይ ቀንዱ አፉን በመጠቀም የትዕቢት ንግግር ይናገር ነበር።“ቀንዱ አፍ የነበረው ሲሆን ትላልቅ ነገሮችን እንደሚፈፅም ይናገር ነበር።”
Daniel 7:9
አጠቃላይ መረጃ
አብዛኛዎቹ ከቁጥር 9 እስከ 14 ድረስ ያሉት ክፍሎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ተምሣሌታዊ አነጋገሮች ናቸው።ከዚህ የተነሣ ሌሎች ቅጂዎች በቅኔያዊ ዘይቤ ያቀርቧቸዋል።
ዙፋኖች ተዘረጉ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሆነ ሰው ዙፋኖቹን በየሥፍራቸው አስቀመጣቸው።”
በዘመናት መካከል
ይሄ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሥም ሲሆን ለዘላለም የሚኖር ነው የሚል ፍቺ ያለው ነው።“ለዘላለም የኖረው”ወይም “ዘወትር ሕያው የሆነው”
ተቀመጠ…ልብሱ…የራሱም ጸጉር
ይሄ ዓረፍተ ነገር እግዚአብሔርን ልክ እንደ ሰው ልብስ ለብሶ እንደሚቀመጥ ዓይነት አድርጎ ይገልፀዋል።እግዚአብሔር እንደዚህ ነው ማለት ሣይሆን ዳንኤል እግዚአብሔርን በራዕይ ያየው በዚህ መልኩ ነበር።
Daniel 7:10
አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል በሰማይ የሚካሄደውን ፍርድ በሚመለከት የተመለከተውን ራዕይና በትንቢተ ዳንኤል 17፡7 ላይ ስለተመለከተው አራተኛው እንስሳ የሚሰጠውን መልስ በሚመለከት ገለፃ ማድረጉን ይቀጥላል።
አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 9 እስከ 14 ውስጥ የሚገኘው ክፍል ተመሳሳይ ትርጉምና ተምሣሌታዊ ቋንቋ ያለው ናቸው።ከዚህ የተነሣ አንዳንድ ቅጂዎች በቅኔያዊ ዘይቤ እንዲቀርብ አድርገውታል።
የውኃ ፈሳሽም ከፊቱ ይወጣ ነበር
ከእግዚአብሔር ፊት እሣቱ በፍጥነት የመውጣቱን ነገር ልክ እሣት ያለበት ወንዝ እንደሚፈስስ ዓይነት ተደርጎ ቀርቧል።“ልክ በወንዝ ውስጥ እንዳለ ውኃ እሣት ከፊቱ ወጣ”
በፊቱ
“በፊቱ” ቃል የሚያመለክተው ራሱን እግዚአብሔርን ነው።በትንቢተ ዳንኤል 7፡9 ላይ ከዘመናት በፊት የሚለውን ይመልከቱ።
ሚሊዮኖች
ይሄ ምናልባት የሚያመለክተው የተወሰነ ቁጥርን ሣይሆን ትልቅ ቁጥር ያለውን ሕዝብ ሊሆን ይችላል። “እልፍ አዕላፋት” ወይም “10 ሺዎች ጊዜ አሥር ሺዎች” ወይም “ለመቁጠር የሚያዳግቱ ሕዝቦች”
ፍርድም ሆነ
ይሄ ማለት ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር ማሰረጃውን ለማጤንና ፍርድ ለመሥጠት ተዘጋጅቷል ማለት ነው።“ፈራጁ ፍርድን ለመሥጠት ተዘጋጅቶ ነበር”ወይም “ዳኛው ተቀምጦ ነበር”
መፃሕፍትም ተገለጡ
እነዚህ መፃሕፍት በፍርድ ዙፋኑ ፊት ጠቃሚ ሆኑ ማስረጃዎችን የያዙ ናቸው።“ማስረጃ የያዙት መፃሕፍት ተከፈቱ”
Daniel 7:11
አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል በሰማይ የሚካሄደውን ፍርድ በሚመለከት የተመለከተውን ራዕይና በትንቢተ ዳንኤል 17፡7 ላይ ስለተመለከተው አራተኛው እንስሳ የሚሰጠውን መልስ በሚመለከት ገለፃ ማድረጉን ይቀጥላል።
አውሬው ተገደለ…እስኪቃጠል ድረስ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አራተኛውን አውሬ ገደሉት፤አካሉን አጠፉ፤እንዲያቃጥለውም ለሆነ ሰው ሰጡት”
አውሬው ተገደለ
አውሬው የእንዲገደል የተደረገበት ምክኒያት ዳኛው ጥፋተኛ መሆኑን በመወሰኑ ነው። “አውሬውን አረዱት”ወይም “ዳኛው ውሳኔውን ካስተላለፈ በኋላ አውሬውን ገደሉት”
አውሬው
ይሄ የሚያመለክተው አስር ቀንዶች ስለነበሩትና በትዕቢት ይናገር ስለነበረው አውሬ ነው።“እጅግ አስፈሪ የሆነ አውሬ”ወይም “በትዕቢት የተወጠረ ቀንዶች ያሉት”
የቀሩት አራቱ አውሬዎች
“የቀሩት ሶስቱ አውሬዎች” ቢባል የበለጠ ግልፅ ይሆናል።
ግዛታቸውም ተወሰደ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ዳኛው የመግዛት ሥልጣናቸውን ነጠቃቸው” ወይም “የገዢነታቸው ዘመን ተጠናቀቀ”
የሕይወታቸው ዕድሜ እስከ ዘመንና ዘመን ድረስ ተራዘመ
x
Daniel 7:13
አጠቃላይ መረጃ
አብዛኛዎቹ ከቁጥር 9 እስከ 14 ድረስ ያሉት ክፍሎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ተምሣሌታዊ አነጋገሮች ናቸው።ከዚህ የተነሣ ሌሎች ቅጂዎች በቅኔያዊ ዘይቤ ያቀርቧቸዋል።
አንዱ ሲመጣ ተመለከትኩ…የሰው ልጅ የሚመስል
ዳንኤል የተመለከተው ሰው የተለመደው ዓይነት ሰው አይደለም፤ነገር ግን የሰው ዓይነት ቅርፅ ነበረው።“በዚያን ሌሊት የሰው ልጅ የሚመስል ሲመጣ ተመለከትኩ። ማለትም የሰው ምስል ነበረው”
ከሰማይ ደመናት ጋር
“በሰማይ ላይ ካሉ ደመናት ጋር”

እስከ ዘመንና ጊዜ ደረስ
ይሄ የሚያመለክተው ዘላለማዊ የሆነውን እግዚአብሔርን ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 7:9 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
ወደ ፊቱም አቀረቡት
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ለዘላለም በሸመገለው ፊት አቀረቡት” ወይም “በፊቱ ቀረበ”
ግዛትና ክብር መንግሥትም “lk” ተሰጠው
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሰው ልጅ የሚመስለው ለመግዛት፤ክብርና መንግሥታዊ ሥልጣን ተሰጠው።”
የመንግሥት ሥልጣን
እዚህ ላይ ይሄ የሚያመለክተው “ሥልጣንን” ነው።
ወገኖች፤አህዛብና ቋንቋዎች
እዚህ ላይ “አህዛብ”እና “ቋንቋ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ የተለያዩ ወገኖችን ነው።ይህንን በትንቢተ ዳንኤል 3:4 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመለከቱ።
የዘላለም ነው …በፍፁም የማይጠፋ ነው
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው፡
Daniel 7:15
በሥጋዬ ውስጥ መንፈሴ ደነገጠች… የራሴም ራዕይ አስቸገረኝ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያሣዩት ዳንኤል ምን ያህል ጭንቀት ውስጥ የገባ መሆኑን ነው።ሁለተኛው አባባል መንፈሱ ምን ያህል እንዳዘነ በማብራራት ስለ አንደኛው አባባል የበለጠ መረጃ ይሰጠናል።
በሥጋዬ ውስጥ መንፈሴ ደነገጠች
እዚህ ላይ “መንፈስ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዳንኤል ራሱን ዳንኤልን ነው።“በውስጤ ሐዘን ገባ”
እዚያ ከቆሙት አንዱ
ይሄ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ከሚቆሙት ሰማያዊ ፍጥረታት አንዱ ነው።የዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/እነዚህ መላዕክት፤እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ መናፍስት2/እነዚህ ሞተው የነበሩና አሁን በሰማይ ውስጥ የሚገኙ ናቸው።
እውነቱን ጠየቅኩት
“እንዲነግረኝ”ወይም “እንዲያብራራልኝ”
እነዚህ ነገሮች
“የተመለከትኳቸው ነገሮች”
Daniel 7:17
ቁጥራቸው አራት የሆኑ እነዚህትላልቅ አውሬዎች
“እነዚህ አራት ታላላቅ እንስሳት”
አራት ነገሥታት ናቸው
“አራት ነገሥታትን ይወክላሉ።”
ከምድር የሚነሱ አራት ነገሥታት
እዚህ ላይ“ከምድር”ማለት በእርግጥም ሰዎች ናቸው ማለት ነው።“በምድር ላይ ሥልጣን የሚይዙ አራት ነገሥታት” ወይም“ከሕዝቦች መካካል የሚነሱና ነገሥታት የሚሆኑ አራት ሰዎች።”
ይወርሳሉ
“ይገዙታል”
ከዘላለም እስከ ዘላለም
ይሄሃሣብ የተደጋገመበት ምክኒያት ይሄ መንግሥት መጨረሻ እንደሌለው አፅንዖት ለመሥጠት ነው።
Daniel 7:19
እጅግ የሚያስደነግጥ
“እጅግ የሚያስፈራ”
በእግር መርገጥ
“በላዩ ላይ ተራምዶ አደቀቀው”
በራሱ ላይ አሥር ቀንዶች
“በአራተኛው አውሬ ላይ ያለው አሥር ቀንድ”
አደገ፡፡ሶስቱ ቀንዶች ከመውደቃቸው በፊት
“አደገና ሶስቱም ቀንዶች በፊቱ ወደቁ።”ወይም “አደገና ሶስት ያህል የሚሆኑት ቀንዶች በፊቱ የወደቁት በእርሱ ምክኒያት ነው።”
በፊቱም ሶስት ቀንዶች ስለ ወደቁ
እዚህ ላይ “ወደቀ” የሚለው ቃል እምብዛም ደስ የማያሰኝን ቃል በተሻለ ቃል የመጠቀም ዘዴ ሲሆን ትርጉሙም ፈፅሞ ጠፉ ማለት ነው።“ሶስቱን ቀንዶች ያጠፋው”
በትዕቢት የሚናገር አፍ
“በጉራ የተቃኘው አፉ”ወይም “በጉራ የተሞላው የአዲሱ ቀንድ አንደበት”
አብሮቸው ከነበሩት ይልቅ ታላቅ ይመሰል ነበር
ዓይንና አፍ የነበረው ቀንድ ከሌሎች ቀንዶች ይልቅ ታላቅ ይመሰል ነበር።
Daniel 7:21
ይሄ ቀንድ
“አራተኛው ቀንድ” ይሄ የሚያመለክተው በትንቢተ ዳንኤል 17:20 ላይ የተጠቀሰውን ቀንድ ነው።
በዘመናት የሸመገለው እስኪመጣ …ፍርድም እስኪሰጥ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የሸመገለው እስከሚመጣና ፍትህ እስኪገለጥ ደረስ”
በዘመናት የሸመገለው
ይሄ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ስያሜ ሲሆን ዘላለማዊ ስለመሆኑ አፅንዖት ለመስጠት ታስቦ የተደረገ ነው።ይሄንን በትንቢተ ዳንኤል 7:9 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
ቅዱሳኑም መንግሥቱን ወሰዱ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር መንግሥቱን ለተቀደሱ ሕዝቦቹ ሰጠ።”
Daniel 7:23
አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 23 እስከ 27 ድረስ ያለው አብዛኛው ክፍል ተምሣሌታዊ ቋንቋ ነው።
ያ ሰው የተናገረው ይሄንን ነው
ይሄ ሰው በትንቢተ ዳንኤል 7:16 ላይ ዳንኤል የተገናኘው ነው።
ያ ሰው እንዲህ አለ
“ያ ሰው መለሰ”
ስለ አራተኛው አውሬና…ስለ አሥሩ ቀንዶች
“አራተኛውን አውሬ በተመለከተ…አሥሩን ቀንዶች በተመለከተ”ወይም “አሁን፤ስለ አራተተኛው አውሬ…አሁን፤ስለ አሥሩ ቀንዶች”
ይበላል…ያደቅቃትማል
እዚህ ላይ አራተኛው መንግሥት ዓለምን ያጠፋል ማለት ሣይሆን በጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ያጠቃል፤ድል ያደርጋል እንዲሁም በምድር ላይ የሚገኙትን መንግሥታት ሁሉ ያጠፋል ማለት ነው።
ከዚህ መንግሥት አሥር ነገሥታት ይነሣሉ
አንዱ ሌላው እየተካ ይገዛሉ።ይሄ ግልፅ በሆነ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።”ከዚህ ከአራተኛው መንግሥት በላይ አስር ነገስታት በመከታተል ይነግሳሉ።”
ከእነርሱም በኋላ ሌላ ይነሳል
ይሄ ንጉሥ ከአስሩ መካከል አይደለም።ምናልባትም እርሱን “አስራ አንደኛው ንጉሥ”ማለቱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።“ከዚያ በመቀጠል አስራ አንደናው ንጉሥ ኃያል እየሆነ ይመጣል”
ከፊተኞቹ የተለየ ይሆናል
“ከሌሎቹ አስር ነገሥታት የተለየ ይሆናል።”
Daniel 7:25
አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል በራዕይ የሚመለከተው ሰው መናገሩን ይቀጥላል።
አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 23 እስከ 27 ድረስ ያለው አብዛኛው ክፍል ተምሣሌታዊ ቋንቋ ነው።
በልዑልም ላይ ቃልን ይናገራል
ይሄ ማለት አዲሱ ንጉስ ሙሉ በሙሉ የሚቃወምና በልዑሉ ላይ መጥፎ ነገሮችን የሚናገር ነው ማለት ነው።
ቅዱሳን
“የእግዚአብሔር የተቀደሱ ሕዝቦች”
ክብረ በዓላትንና ሕግን ይለውጥ ዘንድ
ሁለቱም ቃላት የሚያመለክቱት የሙሴን ሕግ ነው።በብሉይ ኪዳን ዘመን ክብረ በዓላት የኃይማኖት አስፈላጊ የሆኑ ክፍሎች ነበሩ።
እነዚህ ነገሮች በእጁ ተላልፈው ይሰጣሉ
እዚህ ላይ “በእጁ” የሚለው ቃል በቁጥጥር ሥር ማድረግን የሚያመለክት ነው። ይሄ በገቢር መልክ መገለፅ ይችላል።“አዲሱ ንጉሥ ኃይማኖታዊ ክብረ በዓላትንና

ሕጎችን በበላይነት ይቆጣጠራል።”
አንድ ዓመት፤ሁለት ዓመት እና ግማሽ ዓመት
ይሄ “ሶስት ዓመት ተኩል” ማለት ነው።ይሄ እሥራኤላውያን የሚቆጥሩት የተለመደ ዓይነት አቆጣጠር አይደለም።“አንድ ዓመት ሲደመር ሁለት ዓመት ሲደመር ግማሽ ዓመት”
ፍርድም ይሆናል
ይሄ ዳኛው መረጃዎቹን ለመመርመርና ፍርድ ለመስጠት ይዘጋጃል ማለት ነው።“ዳኛው ፍርድን ይፈርዳል” ወይም “ዳኛው ለመፍረድ ይቀመጣል”
መንግሥታዊ ሥልጣኑን ይወስዱበታል
“የፍርድ ቤቱ አባላት ከአዲሱ ንጉስ መንግሥታዊ ሥልጣኑን ይነጥቁታል”
ንጉሣዊ ሥልጣን
አዚህ ላይ ይሄ የሚያመለክተው “ሥልጣንን”ነው።ይሄንን በትንቢተ ዳንኤል 7:14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
እስከ ፍፃሜም ድረስ ያፈርሱትና ያጠፉት ዘንድ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በመጨረሻ ያቃጥሉትና ያጠፉት ዘንድ”ወይም “በመጨረሻም ንጉሣዊ ሥልጣኑን ፈፅሞ ያጠፉታል።”
Daniel 7:27
አጠቃላይ መረጃ
በዳንኤል ራዕይ ውስጥ የተከሰተው ሰው ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 23 እስከ 27 ድረስ ያለው አብዛኛው ክፍል ተምሣሌታዊ ቋንቋ ነው።
መንግሥትም ግዛትም ለሕዝብ ይጥ ዘንድ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር መንግሥትንና ግዛትን ለሕዝቡ ይሰጣል።”
መንግሥትና ግዛት
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ይህም መንግሥታዊ ሥልጣንን ሁሉ የሚመለከት ነው።
የመንግሥቱ ታላቅነት
“ታላቅነት” የሚለው አሕፅሮተ ሥም “ታላቅ” በሚለው ቅፅል ሊተረጎም ይችላል።“ስለ መንግሥታቱ ታላቅ የሆነው ነገር ሁሉ”
ከሰማይም በታች ያሉ መንግሥታት
“ከሰማይ በታች ያሉ ሁሉ” የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር የሚያመለክተው በምድር ላይ የሚገኙትን መንግሥታት ነው።“.....በምድር ላይ ካሉ መንግሥታት መካከል”
መንግሥቱ
“የልዑሉ መንግሥት”
የዘላለም መንግሥት
“ለዘላለም ፀንቶ የሚኖር መንግሥት” ወይም “መጨረሻ የሌለው መንግሥት”
የነገሩም ፍፃሜ እስከዚህ ድረስ ነው
ይሄ ማለት ዳንኤል ራዕዩን ማካፈል አቁሟል ማለት ነው።“በራዕይ ያየሁት ይህንን ነው” ወይም “በራዕይ የተመለከትኩት የመጨረሻው ገለፃዬ እዚህ ላይ ያበቃል”
ፊቴም ተለወጠብኝ
“ፊቴ ገረጣብኝ”

---

Chapter 8
Daniel 8:1
አጠቃላይ መረጃ
ምዕራፍ 7 እና 8 የተቀመጡት በቅደም ተከተል አይደለም።ይሄ የተከናወነው በምዕራፍ 6 ላይ በተጠቀሰው መሠረት ዳርዮስና ጢሮስ ከመግዛታቸው አስቀድሞና ብልጣሶር ንጉስ ሆኖ ይገዛ በነበረበት ወቅት ነበር።
አጠቃላይ መረጃ
በዳንኤል ራዕይ ውስጥ የሌሎች ነገሮች ተምሣሌቶች የሆኑ አውሬዎችን ተመልክቷል።በኋላ ላይ በራዕዩ ውስጥ የእነዚያን ተምሣሌቶች ትርጉም የሆነ ሰው ያስረዳዋል።
በሶስተኛውም ዓመት
“ሶስት ዓመት ሲሆነው”
ብልጣሶር
ይህ ሰው ከአባቱ በኋላ ንግስናውን የተረከበው የናቡከደነፆር ልጅ ነው።
ከመጀመሪያው በተጨማሪ ሌላ ራዕይ ተገለጥኝ
ይሄ አንባቢው ዳንኤል የተመለከተው ሁለተኛ ራዕዩ እንደሆነ እንዲያውቀት ለማድረግ የተሰጠ መረጃ ነው።“ሁለተኛ ራዕይ ተገለጠልኝ”
ቅጥር
የሚጠበቅና ቁጥጥር የሚደረግለት ቅጥር ያለው ከተማ
ሱሳ...ኤላም...ኡባል ቦይ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።
ቦይ
ቦይ ጠባብና ሰው ሰራሽ የሆነ የውኃ ማስኬጂያ ነው።
Daniel 8:3
ሁለት ቀንዶች ነበሩት አውራ በግ
አውራ በጎች ሁለተ ቀንዶች እንደሚኖራቸው የታወቀ ነው። እነዚህ ቀንዶች ግን ተምሣሌታዊ ትርጉም አላቸው።
አንዱ ግን ከሁለተኛው ከፍ ያለ ነበር
“ከአጭሩ ይልቅ ረዘም ያለው አስተዳደጉ ዝግታ ነበረው።አጭር የሆነው ግን ከእርሱ የበለጠ እያደገ ሄደ።”
አውራ በጉ ሲፈተለክ አየሁት
“አውራ በጉ ሲሮጥ አየሁት”ወይም “አውራ በጉነን በጣም ሲሮጥ አየሁት”
ከእጁም የሚያድን አልነበረም
አውራ በጎች እጆች የላቸውም።እዚህ ላይ “እጅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአውራውን በግ ኃይል ነው።“ማንንም ቢሆን ከእርሱ እጅ ለማዳን” ወይም “ማንንም ቢሆን ከሥልጣኑ ለማዳን”
Daniel 8:5
በምድር ሁሉ ፊት
“በምድር ሁሉ ፊት” የሚለው ሐረግ ከሩቅ ሥፍራ ነው የመጣው ለሚለው ሃሣብ በተጋነነ መልኩ የቀረበ ነው።“ከምድር ገፅ ፊት ካለ ከሩቅ ሥፍራ”
ፍየሉ በዓይኖቹ መካከል ታላቅ ቀንድ ነበረው
ፍየሎች በራሳቸው ጎንና ጎን ሁለት ቀንዶች አሏቸው።ይሄ ምስል ማብራሪያ የሚያስፈልገው ነው።“ፍየሉ ግንባሩ መሐል ላይ ታላቅ የሆነ ቀንድ ነበረው።”
አውራ በጉን በወንዙ ፊት ቆሞ አየሁት
ይሄ ሐረግ ፍየሉ የት ሥፍራ ላይ እንደነበረ መረጃ ለመስጠት የቀረበ ነው።
በኃይሉም ቁጣ
“በጣም ተበሳጭቶ ነበር”
Daniel 8:7
ረገጠው
አንድን ነገር ረግጦ ማድቀቅ
አውራ በጉ በኃይሉ
“አውራ በጉ ከፍየሉ ይልቅ በበለጠው ኃያልነቱ”
ፍየሉ እጅግ ታላቅ ሆነ
“ፍየሉ ታላቅና ብርቱ ሆነ”
ትልቁ ቀንድ ተሰበረ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ትልቁን ቀንድ የሆነ ነገር ሰበረው”
ወደ አራቱም የሰማይ ነፋሳት
እዚህ ላይ“አራቱ የሰማይ ነፋሳት” ዘይቤያዊ አገላለፅ ሲሆን ነፋሣት የሚነፍሱባቸውን አራቱን ዋና ዋና አቅጣጫዎች የሚያመለክት ነው። (ሰሜን፤ምሥራቅ፤ደቡብ፤ምዕራብ)“ከአራት የተለያዩ አቅጣጫዎች”
Daniel 8:9
እጅግ ታላቅ ሆነ
“ነገር ግን እጅግ ታላቅ ሆነ”
ወደ ደቡብም ወደ ምሥራቅም ወደ መልካሚቱም ምድር
ይሄ ምናልባትም ወደ እነዚያ አቅጣጫዎች ማመልከት ማለት ሊሆን ይችላል።“ደወ ደቡብ አቅጣጫ አመለከተ።ከዚያም ወደ ደቡብ ካመለከተ በኋላ ወደ መልካሚቱ የእሥራኤል ምድር አቅጣጫ ተጓዘ።”
መልካሚቱ ምድር
ይሄ የእሥራኤልን ምድር የሚያመለክት ነው።
እስከ ሠራዊትም አለቃ ድረስ ራሱን ከፍ አደረገ
እዚህ ላይ ቀንዱ የሰው ችሎታ ተሰጥቶት በጦርነት ውስት እንዲሳተፍ ሆኗል።
ከሠራዊቱ የተወሰኑ ከፍሎች ...ወደ ምድር ተጣሉ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ቀንዱ አንዳንድ የሠራዊቱን ክፍሎችና


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከዋክብትን ወደ ምድር ጣለ።"
ረገጣቸውም
እዚህ ላይ ቀንዱ የሰው ችሎታ ተሰጥቶት ከዋክብትንና ሠራዊቱን በእግሩ ይረግጣል።
Daniel 8:11
ሃሣብን ማያያዣ
ዳንኤል ቀንዱን በተመለከተ በራዕይ ያየውን ነገር መግለፁን ይቀጥላል።
አጠቃላይ መረጃ
ቀንዱ የሰው ብቃቶች ተሰጥተውታል።
የሠራዊቱ አለቃ
ይሄ የሚያመለክተው የመላዕክት ሠራዊት አለቃ የሆነውን ራሱን እግዚአብሔርን ነው።
ከእርሱን የተነሳ የዘወትሩ መሥዋዕት ተሻረ
"ተሻረ"ማለት ቀንዱ መሥዋዕት ማቅረቡን አቋረጠ ማለት ነው።እዚህ ላይ "እርሱ"የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሠራዊት አለቃ የሆነውን እግዚአብሔርን ነው።"ሰዎች በየጊዜው የሚያቀርቡለትን መሥዋዕት እንዲቆም አደረገው።"
የመቅደሱ ሥፍራ ፈረሰ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።"ቤተመቅደሱን አረከሱት"
የሰማይ ሠራዊት ሲረገጡ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል። "ቀንዱ የሰማይ ሠራዊትን ረገጠ"
ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ማታና ጥዋት
ይሄ ምናልባትም ወደ እነዚያ አቅጣጫዎች አመለከተ ማለት ሊሆን ይችላል።እዚህ ላይ"ማታና ጥዋት" አጠቃላይ አነጋገር ሲሆን በመሐል ያሉ ነገሮችን ሁሉ የሚያካትት ማለትም ሙሉ ቀን ወይም ሃያ አራት ሰዓት ማለት ነው።"2,300 የፀሐይ መግቢያዎችና የፀሐይ መውጫዎች"
ከዚያም በኋላ መቅደሱ ይነፃል
"መቅደሱ ነፅቶ ዳግም ወደ ተገቢው ሥርዓቱ ይመለሳል"
Daniel 8:15
በኡባል ወንዝ መካከል የሚጮኽውን የሰው ድምፅ
እዚህ ላይድምፁን በመስናት ብቻ የሰው ማንነት እንዲሰጠው ሆኗል።"ከኡባል ወንዝ የሚጮህ ሰው"
የኡባል ቦይ
ቦይ ሰው ሰራሽ የሆነ ጠባብ የውኃ ማስኪያጃ ነው።
በግምባሬ ተደፋሁ
ይሄ አንድ ሰው በመሬት ላይ ሙሉ በሙሉ በሰውነቱ የሚወድቅበት የአምልኮ ዓይነት ነው።
በመጨረሻ ዘመን
"የመጨረሻ ቀናት"ወይም "የዓለም መጨረሻ"። "ይሄ የዓለም መጨረሻ የሚያመለክት ሣይሆን የመጨረሻው ዘመን ከመድረሱ በፊት ሊሆኑ ስላሉ ክስተቶች የሚያወሳ ነው።"
Daniel 8:18
ጥልቅ እንቅልፍ
እንደዚህ ዓይነት እንቅልፍ አንድ ሰው በከባድ እንቅልፍ ከመያዙ የተነሳ ለመንቃት እንኳን የሚያዳግተው የእንቅልፍ ዓይነት ነው።
በመቅሠፍቱ ዘመን
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ፍርድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ነው።ይሄ የበለጠ ግልፅ ሊደረግ ይችላል።"እግዚአብሔር በቁጣው ፍርድ በሚፈርድበት ወቅት"
በመጨረሻ ዘመን የሚሆነውን
"የዓለም መጨረሻ በሚሆንበት ወቅት"
Daniel 8:20
አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በራዕይ ስላያቸው ተምሣሌታዊ ነገሮች መልአኩ ለዳንኤል ገለፃ ያደርግለታል።በመሠረቱ ቀንዶቹና እንስሳቱ የሚወክሉት የሰው ልጆች የሆኑ ገዢዎችንና መንግሥታትን ነው።
የነበሩ ሁለት ቀንዶች
"ሁለት ቀንዶች…የሚወክሉት"
የሜዶንና የፋርስ ነገሥታት
ለእነዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት፦1/የሜዶንንና የፋርስን ነገሥታት የሚያመለክት ነው። ወይም 2/ይሄ ንጉሱ የሜዶንና የፋርስን መንግስታት የሚያመለክትበት አጠራር ነው።"የሜዶንና የፋርስ መንግሥታት"
በዓይኖቹ መካከል ያለው ታላቅ ቀንድ
"በዓይኖቹ መካከል ያለው ታላቅ ቀንድ የሚወክለው"
Daniel 8:22
አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በራዕይ ስላያቸው ተምሣሌታዊ ነገሮች መልአኩ ለዳንኤል ገለፃ ያደርግለታል።በመሠረቱ ቀንዶቹና እንስሳቱ የሚወክሉት የሰው ልጆች የሆኑ ገዢዎችንና መንግሥታትን ነው።
እርሱም በተሰበረ ጊዜ በእርሱ ፋንታ አራቱ ተነሱ
"ታላቁ ቀንድ በተሰበረ ጊዜ ሌሎች አራት ተነሱ"
ከወገኑ አራት መንግሥታት ይነሳሉ
አራቱ ቀንዶች የሚወክሉት አራቱን አዳዲስ መንግስታትን ነው።ይሄ የለጠ ግልፅ ሊደረግ ይችላል።"አራቱን መንግሥታት የሚወክሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው መንግሥት የተከፋፈለ ይሆናል።"
ነገር ግን በኃይል አይተካከሉትም
"ሆኖም በታላቁ ቀንድ ከተመሰለው ንጉስ ጋር የሚመጣጠን ጉልበት አይኖራቸውም።"
በእነዚያ መንግሥታትየመጨረሻ ዘመናቸው
"እነዚያ መንግሥታት መጨረሻቸው ሲደርስ"
በተሞላች ጊዜ
"ሙሉ በሆነ ጊዜ" ወይም"ሥራቸውን ባጠናቀቁ ጊዜ"
ፊተ ጨካኝ
ይሄ የእምቢተኛ ፊት ያለው ወይም ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆነ
Daniel 8:24
አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በራዕይ ስላያቸው ተምሣሌታዊ ነገሮች መልአኩ ለዳንኤል ገለፃ ያደርግለታል።በመሠረቱ ቀንዶቹና እንስሳቱ የሚወክሉት የሰው ልጆች የሆኑ ገዢዎችንና መንግሥታትን ነው።
በራሱ ኃይል አይደለም
"ኃይሉን የሚያገኘው በሌላ አማካይነት ነው"
ማታለል እየበለፀገ እንዲሄድ ያደርጋል
እዚህ ላይ "ማታለል" የሚለው ቃል የሚገለፀው ባለፀጋ እየሆነ እንደሚሄድ ሰው ነው።"የማታለል መጠኑ እየጨመረ ይሄዳል።"
በእጁ ያከናውናል
እዚህ ላይ"እጅ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አገዛዙን ነው።"በአገዛዙ ሥር"
የነገሥታት ንጉሥ
ይሄ የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።
እርሱ ይሰበራል
እዚህ ላይ"እርሱ"የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሥልጣኑን ነው።ይሄ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።"በማንም የሰው ጉልበት ሣይሆን"ወይም"በመለኮታዊ ኃይል"
Daniel 8:26
አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ራዕዩን በሚመለከት በሰም ማህተም እንደሚዘጋ የተጠቀለለ ፅሑፍ በሚመስል መልኩ ነው የሚናገረው።ማህተሙ እስኪከፈት ድረስ ይሄንን ፅሑፍ ማንም ሰው እንዳይመለከተው ያግደዋል።"በራዕዩ ተመልክተህ የፃፍከውን ዝጋውና በማሕተም አትመው" ወይም"ራዕዩን በሚመለከት ለማንም ሰው አትናገር"
Daniel 8:27
ተረታሁ፤አያሌ ቀንም ታመምኩ
"ደክሞኝና ሕመም ይዞኝ ለብዙ ቀናት አልጋዬ ላይ ተኛሁ"
የንጉሡን ሥራ ላከናወን ሄድኩ
"ንጉሡ የሰጠኝን ሥራ ላከናውን ሄድኩ"
ስለ ራዕዩም እደነቅ ነበር
"ስለ ራዕዩ እገረም ነበር"ወይም "የሕልሙን ጉዳይ በተመለከተ ግራ ተጋብቼ ነበር"

---

Chapter 9


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Daniel 9:1
አጠቃላይ መረጃ
ምዕራፍ 7 ና 8 በቅደም ተከተላቸው መሠረት የተቀመጡ አይደሉም፡፡ብልጣሶር ንጉሥ ከመሆኑ በፊት የተከናወኑ ናቸው፡፡አሁን ደግሞ ምዕራፍ 9 በምዕራፍ 6 ላይ ንጉሥ ወደሆነው ወደ በዳርዮስ ዘመን ወደተከናወኑት ክስተቶች ይመለሳል፡፡
በባቢሎን መንግሥት ላይ ንጉሥ ሆኖ የተሾመው አሕሻዊሮስ ነበረ
ይሄ አሕሻዊሮስ ማን እንደነበረ የጀርባ ታሪኩ መረጃ ለመስጠት ታስቦ የተደረገ ነው፡፡
በባቢሎን መንግሥት ላይ ንጉሥ ሆኖ የተሾመው
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በባቢሎን ግዛት ሁሉ የነገሰው”ወይም “ባቢሎናውያንን ድል የነሳቸው”
በመንግሥቱ
“በአገሩ ላይ”ወይም “በግዛቱ ላይ”
ያህዌ
ይሄ በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገለፀላቸው ስሙ ነው፡፡
ኢየሩሣሌም በምትተውበት በሰባው ዓመት
“ከዚህ በኋላ ኢየሩሣሌም ትጠፋለች፤ለሰባ ዓመትም እንደፈረሰች ትቀራለች”
መተው(ተ ይጠብቃል)
ይሄ ማንም ሰው አያግዛትም ወይም በዚያን ወቅት ማንም ቢሆን ኢየሩሣሌምን አያድሳትም ማለት ነው፡፡
Daniel 9:3
ፊቴን ወደ ወደ ጌታ አምላክ አቀናሁ
እዚህ ላይ“ፊት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዳንኤልን መሻት ነው፡፡“ትኩረቴን በጌታ በእግዚአብሔር ላይ አደረግኩ” ወይም “የሃሣቤን አቅጣጫ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ አደረግኩ”
እርሱን ለመፈለግ
እግዚአብሔርን ለማወቅና ርሱን ለማስደሰት የሚፈልጉ ሰዎች እየዞሩ እንደሚፈልጉት ዓይነት ነው የቀረበው፡፡
መፆም፤ማቅ መልበስና በአመድ ላይ መቀመጥ
እነዚህ ንሥሐ የመግባትና የማዘን ተምሣሌታዊ ድርጊቶች ናቸው፡፡
ስከ ኃጢአታችን ንሥሐ ገባሁ
“ኃጢአታችንን ተናዘዝኩ”
ቃል ኪዳንንና ምሕረትን የምትጠብቅ
“በቃል ኪዳንህ ውስጥ አደርገዋለሁ ያልከውን ሁሉ የምታደርግና እነዚያን በታማኝነት የምትወዳቸው”
Daniel 9:5
አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ስለ እሥራኤል ሕዝብ መፀለዩን ይቀጥላል፡፡
በድለናል፤ክፋትንም አድርናል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ቃላት አንድ ሃሣብን የሚያንፀባርቁ ቢሆኑም አፅንዖት ለመሥጠት ሲባል በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይገልፁታል፡፡
ትዕዛዛትህና ፍርድህ
“ትዕዛዝ”እና “ፍርድ”የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የሚያመለክቱትም በአጠቃላይ ሕጉን ነው፡፡
ባሪዎችህን አልሰማንም
እዚህ ላይ“አልሰማንም”ማለት መልዕክታቸውን ሰምተን አልታዘዝንም ማለት ነው፡፡“የነቢያቶችህን መልዕክት አልሰማንም”
በስምህ የተናገሩትን
እዚህ ላይ “ሥም”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሥልጣን ነው፡፡“በሥልጣን የተነገረ” ወይም“አንተን በመወከል የተናገረ”
ለአገሩም ሕዝብ
እዚህ ላይ“አገሩ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እሥራኤልን ነው፡፡“የእሥራኤል ሕዝብ”
Daniel 9:7
አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ስለ እሥራኤል ሕዝብ መፀለዩን ይቀጥላል፡፡
ጌታ ሆይ ፅድቅ ለአንተ ነው
እዚህ ላይ ፃድቅ የሚለው ቃል ልክ “ፅድቅ”እግዚአብሔር ባለቤቱ እንደሆነ ዕቃ ተደርጎ ነው፡፡“ፅድቅ” የሚለው አሕፅሮተ ሥም “ፃድቅ”ተብሎ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ጌታ ሆይ አንተ ፃድቅ ነህ”
ለእኛ ዛሬ የፊት ሐፍረት ሆኖብናል...ለሕዝባችን
ሐፍረት የሚለው ቃል እዚህ ሥፍራ ላይ የተገለፀው ልክ“ሐፍረት”ሕዝቡ ባለቤት እንደሆነበት ዕቃ ተደርጎ ነው፡፡“ሐፍረት” የሚለው ተውላጠ ሥም “አፈረ”ተብሎ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እኛን በሚመለከት ግን በሰራነው ሥራ አፍረናል...ሕዝቡ”
ዛሬ ያለነው እኛ
“እኛ”የሚለው ቃል ዳንኤልንና እሥራኤልን የሚያካትት ቢሆንም እግዚአብሔርን ግን አያጠቃልልም፡፡
የፊት ሐፍረት ሆኖብናል
ይሄ ዘይቤያዊ አነጋገር ሐፍረታቸው ለሰው ሁሉ የሚታይ ነው ማለት ነው፡፡
በአንተ ላይ በበደልነው በደል ምክኒያት
“ምክኒያቱም በእጅጉ በድለንሃል” ወይም“ ምክኒያቱም ለአንተ ፈፅሞ ታማኞች አልነበርንም፡፡”
Daniel 9:9
አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ስለ እሥራኤል ሕዝብ ወደ ጌታ መፀለዩን ይቀጥላል፡፡
ምህረትና ይቅርታ ለጌታ ለአምላካችን ናቸው
እነዚህ ባህርያት ስላሉት የጌታ ንብረቶች እንደሆኑ ተደርጎ ነው የሚነገረው፡፡“አምላካችን እግዚአብሔር በምሕረት የተሞላና ይቅር ባይ ነው”
Daniel 9:12
አጠቃላይ መረጃ
ዳንኤል ስለ እሥራኤል ሕዝብ ወደ ጌታ መፀለዩን ይቀጥላል፡፡
ከሰማይ ሁሉ በታች
ይሄ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው፡፡“በዓለም ሁሉ”
ምንም አልደረገም
“ምንም ነገር አልተደረገም፡፡“ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡” “ምንም ነገር አልተከሰተም”
በኢየሩሣሌም እንደተደረገው
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“በኢየሩሣሌም ያደረግከው”
በሙሴ ሕግ እንደተፃፈ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ሙሴ በሕጉ እንደፃፈው”
ከበደላችን ዘወር እንድንል
እዚህ ላይ ከክፉ ነገር ራስን የማቀብ ድርጊትን ዘወር ከማለት ጋር በማመሳሰል ይነገራል፡፡ “ከክፉ ድርጊቶቻችን መታቀብ”
እግዚአብሔር ክፉ ነገርን አዘጋጅቷል
“እግዚአብሔር ይህንን ጥፋት አዘጋጅቷል”
ድምፁን አልታዘዝንም
እዚህ ላይ “ድምፅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ያዘዛቸው ነገሮችን ነው፡፡“እርሱ ያዘዘንን ነገር አላደረግንም”
Daniel 9:15
ኃያል በሆነ እጅ
እዚህ ላይ “ኃያል እጅ”የሚለው ቃል ብርታት ለሚለው ሜቶኒሚ ነው፡፡
ዛሬም ለራስህ ዝነኛ የሆነ ሥምን አድርገሃል
እነዚህ ሁለት አንቀፆች በመሠረቱ ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን አንድ ላይ እንዲሆኑ የተደረጉት ኃጢአት ምን ያህል ክፉ ነገር እንደሆነ አፅንዖት ይሰጡ ዘንድ ነው፡፡
እኛ ኃጢአትን ሠርተናል፤ክፋትንም አድርገናል
እነዚህ ሁለት አንቀፆች በመሠረቱ ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ቢሆንም “እኛ”የሚለው ቃል እግዚአብሔርን አያካትትም፡፡
ቁጣህና መአትህ
“ቁጣ”እና “መአት”የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ወደ ድርጊት በሚገባበት ወቅት የእግዚአብሔር ቁጣ ምን ያህል አደገኛ ሊሆን እንደሚችል አፅንዖት ይሰጣል፡፡
የተቀደሰው ተራራህ
ይሄ ተራራ ቅዱስ የሆነበት ምክኒያት እግዚአብሔር መቅደስ እዚያ በመሆኑ ምክኒያት ሊሆን ይችላል፡፡
የእኛ ኃጢአት...አባቶቻችን
እዚህ ላይ“ኃጢአት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ሣይሆን ዳንኤልንና እሥራኤልን ነው፡፡

መሰደቢያ
“ለአክብሮት ማጣት ዒላማ”
Daniel 9:17
አሁን
እዚህ ላይ “በአሁኗ ደቂቃ”ማለት ሣይሆን የሚቀጥለው የዳንኤል የፀሎት ምዕራፍ ሊጀመር ስለመሆኑ የማሳያ መንገድ ነው።
ባሪያህ...ስለ ምሕረት የሚለምነውን የእርሱን ልመና
“ባሪያህ” እና “የእርሱ”የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ዳንኤልን ነው። እግዚአብሔርን ስለማክበሩ እንደ ምልክት ይሆን ዘንድ ስራሱ በሶስተኛ መደብነት(ሰዋሰው)ይናገራል።
ልመናና ምሕረት
“ስለ ምሕረት መለመን”
ፊትህን አብራ
ፀሐፊው አገዛ በማድረጉ የእግዚአብሔር ፊት እንደ ብርሀን እንዳበራ በሚመስል መልኩ ይናገራል። “በቅንነት አገዛ ማድረግ” ወይም “ማድላት”
መቅደስህ
ይሄ የሚያመለክተው በኢየሩሣሌም ያለውን ቤተመቅደስ ነው።
ጆሮህን አዘንብለህ ስማ
“ጆሮን ማዘንበል”የሚለው ቃል ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ማዳመጥ ማለት ነው። እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ዳንኤል ለሚፀልየው ፀሎት እግዚአብሔር ትኩረት እንዲሰጠው ላለው ፍላጎት አፅንዖት ይሰጡታል።“እባክህን ስማ“
ዓይንህን ገልጠህ ተመልከት
“ዓይን መግለጥ” የሚለው ቃል ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ማየት ማለት ነው።“ዓይንን መግለጥ”ዘይቤያዊ አነጋገር ሲሆን ማዳመጥ ማለት ነው።እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ዳንኤል ለሚፀልየው ፀሎት እግዚአብሔር ትኩረት እንዲሰጠው ላለው ፍላጎት አፅንዖት ይሰጡታል።“አስበን”ወይም “ተመልከት”
ሥምህ ተጠርቶባታል
እዚህ ላይ“ሥም”የሚወክለው ባለቤት መሆንን ነው።“የአንተ ከተማ ናት” ወይም “አንተ ንብረት ናት”
አትዘግይ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“በፍጥነት ወደ ተግባር ግባ”
Daniel 9:20
ሕዝቤ እሥራኤል
“ወገኔ የሆነው የእሥራኤል ሕዝብ”
የእግዚአብሔር የተቀደሰ ተራራ
ተራራዎቹ የተቀደሱ የሚሆኑት በቤተ መቅደሱ ምክኒያት ሊሆን ይችላል።“የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ያለበት ተራራ”
ሰው የሆነው ገብርኤል
የሰው መልክ ይዞ በትንቢተ ዳንኤል18፡16 ላይ የተገለጠውም ራሱ መልአኩ ገብርኤል ነው።“ሰው መስሎ የተገለጠው ገብርኤል”
አስቀድሜ በራዕይ ያየሁት
ይሄ ዳንኤል ነቅቶ እያለ የተመለከተው የመጀመሪያው ራዕይን የሚመለከት ሊሆን ይችላል።“ከዚህ በፊት በነበረው ራዕይ”ወይም “የቀደመው ራዕይ”
እየበረረ ወደ እኔ መጣ
“በፍጥነት ወደ እኔ እየበረረ መጣ”
በማታ መሥዋዕት ጊዜ
አይሁድ ሕዝቦች ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት በየምሽቱ ለእግዚብሔር መሥዋዕትን ያቀርቡ ነበር።
Daniel 9:22
ጥበብና ማስተዋል
“ጥበብ”እና“ማስተዋል”የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን መልዕክቱን ሙሉ በሙሉ ለመራድተ እንዲችል ገብርኤል አገዛ እንደሚያደርግለት አፅንዖት ለመሥጠት ነው።
ትዕዛዝ ተሰጠ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ትዕዛዝን ሰጠ”
ቃሉን መርምር
“ስለ መልዕክቱ አስብ”
ራዕዩ
ይሄ ኤርምያስን በተመለከተ በትንቢተ ዳንኤል 9፡2 ላይ ያለውን ትንቢት የሚያስታውስ ነው።
Daniel 9:24
ሰባ ሱባዔዎች...ሰባት ሱባዔዎች...እና ስድሳ ሁለት ሱባዔዎች
ይሄ የእሥራኤላውያን የሚቆጥሩበት የተለመደ ዓይነት አቆጣጠር አይደለም።“ሰባ ጊዜ ሰባት ዓመታት....ሰባት ጊዜ ሰባት ዓመታት....እና ስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባት ዓመታት”
በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ ላይ ሰባ ሱባዔ ተቆጥሯል
እግዚአብሔር የደነገገው በዚህ ጥቅስ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ለሕዝቡና ለእሥራኤል የሚያደርግ መሆኑን ነው።
የአንተ ሕዝብና የአንተ ቅድስት ከተማ
እዚህ ላይ “የአንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዳንኤልን ነው።ሕዝቡ የእሥራኤል ሕዝብ ሲሆን የተቀደሰችው ከተማ ደግሞ ኢየሩሣሌም ናት።
ዓመፃን ይጨርስ በደልንም ያስተሰርይ ዘንድ
ሃሣቡ የተደጋገመበት ምክኒያት ይሄ ነገር በእርግጥ የሚከናወን መሆኑን አፅንዖት ለመሥጠት ነው።
ራዕይን ተሸክሞ መሄድ
እዚህ ላይ “ተሸክሞ መሄድ”የሚለው ቃል ዘይቤያዊ አገላለፅ ሲሆን ትርጉሙ መፈፀም ማለት ነው።“ራዕዩን ተግባራዊ ማድረግ”
ራዕዩና ትንቢቱ
ከዚህ አውድ አንፃር እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።ለዳንኤ የሚያረጋግጡት ነገር ቢኖር የኤርምያስ ራዕይ በእርግጥም ትንቢት የነበረ መሆኑን ነው።
ማወቅና ማስተዋል
እነዚህ ቃላት በአንድነት ጥቅም ላይ የዋሉት ጣሚነቱን የበለጠ ግልፅ ለማድረስ ነው።“በግልፅ ልትረዳው ያስፈልጋል”
የተቀባ
መቀባት አንድ ሰው መመረጡ የሚታወቅበት ምልክት ነው።“እግዚአብሔር የሚቀባው ሰው”
ሰባ ሱባዔዎች...እና ስድሣ ሁለት ሱባዔዎች
እነዚህ ሲደመሩ 69 የሚሆኑ ሲሆን በቁጥር 24 ላይ ከተጠቀሱት 70ዎቹ ውስጥ ናቸው።
ኢየሩሣሌም ትሰራለች
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች ኢየሩሣሌምን እንደገና ይሠሯታል።”
የምሽግ ጉድጓድ
በከተማ ወይም በሕንፃ ዙሪያ ያለና ብዙ ጊዜ ውኃ ያለበት ጥልቅ ጉድጓድ
የጭንቀት ዘመን
“ታላቅ ችግር ያለበት ዘመን”
Daniel 9:26
ስድሳ ሁለት ሱባዔዎች
ይሄ እሥራኤላውያን የሚቆጥሩበት የተለመደ የአቆጣጠር ዓይነት አይደለም።“ስድሣ ሁለት ጊዜ ሰባት”
መሢሁም ይገደላል፤በእርሱም ዘንድ ምንም አይኖርም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሰዎች መሢሁን ያጠፉታል፤ምንም ነገር አይቀርለትም”
የተቀባው
መቀባት የሚለው ቃል አንድ ሰው መመረጡን የሚያሣይ ተምሣሌታዊ ድርጊት ነው።“እግዚአብሔር የሚቀባው ሰው” ወይም “እግዚአብሔር የሚመርጠው ሰው ”
የሚመጣው አለቃ
ይሄ ባዕድ የሆነ ገዢ እንጂ “የተቀባው ገዢ”አይደለም።“የሚመጣው ባዕድ ገዢ”ወይም “የሚመጣው ኃይለኛ ገዢ”
ፍፃሜውም በጎርፍ ይሆናል
ሠራዊቱ ከተማዋንና ቅዱስ ሥፍራውን ጎርፍ ነገሮችን እንደሚያጠፋ እንዲሁ ያጠፏታል።
ጥፋትም ተቆጥሯል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር በከተማዋና በመቅደሱ ላይ ጥፋትን አዝዟል”ወይም “እግዚአብሔር ሠራዊቱ ሁሉንም ነገር እንዲያጠፋ አዝዞታል”

Daniel 9:27
ያደርጋል..ያደርጋል
ይሄ መሢሁን የሚያጠፋውን አዲሱን ገዢ የሚያመለክት ነው።

## Chapter 10

### Daniel 10:1

በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ በሦስተኛው ዓመት
“የፋርስ ንጉሥ በነገሰ በሦስተኛው ዓመት”
ለዳንኤል ነገር ተገለጠለት
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ለዳንኤል መልዕክትን ገለጠለት”
ማስተዋል
አንድ ሰው ሊረዳ ከሚችለው በላይ መገንዘብ

### Daniel 10:2

ቅንጡ የሆኑ ነገሮች
እነዚህ ውድ የሆኑና በቀላሉ የማይገኙ የምግብ ዓይነቶች ናቸው።
ሶስት ሣምንት ሙሉ እስኪደርስ ድረስ
“ሶስት ሣምንት እስኪጠናቀቅ ድረስ”

### Daniel 10:4

ከመጀመሪያውም ወር በሃያ አራተኛው ቀን
ይሄ የዕብራውያን የመጀመሪያ ወር ነው።በምዕራባውያን የቀን አቆጣጠር መሠረት ሃያ አራተኛው ቀን የሚውለው በመጋቢት ወር አጋማሽ አካባቢ ነው።
ወገቡን የታጠቀ
“ቀበቶ አድርጎ ነበር”
አፌዝ
አፌዝ የቦታ ሥፍራ ነው።ያለበት ትክክለኛ ሥፍራ አልተገለፀም።
ሰውነቱ እንደ ቶፓዝ ነበረ
ሰውነቱ ከቶፓዝ የተሰራ ይመስልበሰማያዊና በቢጫ ብርሃን ያብረቀርቅ ነበር።“ሰውነቱ እንደ ቶፓዝ አብረቀረቀ”
ቶፓዝ
ሰማያዊ ወይም ቢጫ የከበረ ድንጋይ ሲሆኑ ቤሪል፤ፔሪዶትና ክራሶላይት በመባልም ይታወቃሉ።
ፊቱም እንደ መብረቅ አምስያ ነበረ
ፊቱ ልክ መብረቅ አበራ።“ልክ እንደመብረቅ ብርሃን ፊቱ በብርሃን ደመቀ”
ዓይኖቹም እንደሚንበለበል ፋና
የሚንበለበሉ ችቦዎች ይመስልዓይኖቹ እጅግ ብሩህ ነበሩ።“ዓይኖቹ ብሩህ ከመሆናቸው የተነሣ ችቦዎች ዓይኖቹ ውስጥ የሚንበለበሉ ይመስል ነበር።”
ክንዶቹና እግሮቹም እንደ ጋለ ናስ
ከተወለወለ ነሐስ የተሰሩ ይመስል ክንዶቹና እግሮቹ ያብረቀርቁ ነበር።“ክንዶቹና እግሮቹ የተወለወለ ነሐስ ይመስል ከውስጣቸው የሚፈልቀው ብርሃን አካባቢውን ሁሉ ያዳርሳል።”
የቃሉም ድምፅ እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ነበረ
ድምፁ ከመጉላቱ የተነሣ ብዙ ሰዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሚነጋገሩ ይመስላል። ድምፁ ከመጉላቱ የተነሣ ብዙ ሰዎች በጋራ ጮኸው የሚጣሩ ነው የሚመስለው።

### Daniel 10:7

እኔም ብቻዬን ቀርቼ ራዕዩን ተመለከትኩ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ማንም አጠገቤ አልነበረም።እናም አየሁ”
ደም ግባቴም ወደ ማሽብሸብ ተለወጠብኝ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“መልካም የነበረው ገፅታዬ ወደ አስከፊ ገፅታ ተለወጠ”
ደም ግባቴ
ይሄ የሚያመለክተው ጤነኛ የሆነን ሰው ገፅታ ነው።“ጤነኛ ገፅታ ያለው ፊቴ”
የፈራረሰ ገፅታ
ጤነኛ ያልሆነና የገረጣ ፊት ከሚፈርስ ሕንፃ ጋር ተመሳስሎ ቀርቧል።“የገረጣ”
የቃሉንም ድምፅ ሰማሁ
ይሄ አንድ ሰው በራዕዩ ውስጥ ያነጋገረው እንደነበረ የሚያሣይ ነው።ይሄ የበለጠ ሊብራራ ይችላል።“የሆነ ሰው የሚናገረውን ንግግር ሰማሁ”
ደንግጬ በምድር ላይ በግምባሬ ተደፋሁ
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/ዳንኤል ካየው ነገር የተነሳ እጅግ በመፍራቱ በምድር ላይ ተደፍቶ ራሱን ሳተ 2/ዳንኤል ራሱን ከሳተ በኋላ በምድር ላይ ተደፋ።

### Daniel 10:10

እንዲት እጅ ዳሰሰችኝ
እዚህ ላይ የሰው እጅ የሚወክለው ያንኑ ሰው ነው።ምናልባትም ዳንኤል በትንቢተ ዳንኤል 10:5-6 የየው ሰው ሊሆን ይችላል።“አንድ ሰው በእጁ ነካኝ”
እጅግ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ
ይሄኛው በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር እንደ ትልቅ ሰው የሚመለከትህ ዳንኤል ሆይ”
እንደ ትልቅ ሰው የሚመለከትህ
የከበርክና የምትወደድ

### Daniel 10:12

የምነግርህን ቃል አስተውል
“ራዕዩን ለመረዳት ዝግጁ ሁን”
ፀሎትህ ተሰምቶልሃል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“እግዚአብሔር ፀሎትህን ሰምቶታል”
አለቃ
ይሄ የሚያመለክተው በሰው ልጆች ላይ ሥልጣን ያለውን መንፈስ ነው።
የፋርስ ንጉሥታት
ይሄ ምናልባት ለፋርስ ንጉሥ ተገዢ የሆኑ በፋርስ መንግሥት ውስጥ ይገዙ የነበሩትን ነገሥታት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።
ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል
“የመላዕክት አለቆች ከሆኑት መካከል አንዱ የሆነው ሚካኤል”

### Daniel 10:14

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
ፊቴን ወደ ምድር አቀረቀርኩ
“ወደ ምድር አቀርቅሬ ቀረሁ” ዳንኤል ይህንን ያደረገበት ምክኒያት ከትህትና የተነሳ አክብሮትን ለመሥጠት ወይም ከመፍራቱ የተነሳ ሊሆንም ይችላል።

### Daniel 10:16

የሰው ልጅ የሚመስል
ይሄ ምናልባት ከዳንኤል ጋር የተነጋገረውን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።ሆኖም አንዳንድ ቅጂዎች ከሌላ ሰው ጋር እንደተነጋገረ አድርገው ነው የተረጎሙት።“ይሄኛው፤የሰው ልጅ የሚመስለው”
የሰው ልጅ የሚመስለው
ይሄ አገላለፅ የሚያመለክተው በአጠቃላይ የሰው ልጆችን ነው።“እንደ ሰው ልጅ”
ጭንቀት
ብርቱ የሆኑ ስሜታዊ ሕመሞች
ይህ የጌታዬ ባሪያ ከጌታዬ ጋር ይናገር ዘንድ እንዴት ይችላል?
ዳንኤል ይህንን ጥያቄ በሚጠይቅበት ጊዜ እኔ ከመልአክ ጋር በእኩል ደረጃ መነጋገር የምችል ሰው ስላልሆንኩ ከመልአክ ጋር መነጋገር አልችልም ማለቱ ነው። እነዚህ ዓረፍተ ነገሮች ሊጣመሩ ይችላሉ።“የአንተ ባሪያ ስለሆንኩ መልስ ልሰጥህ አልችልም”
እስትንፋስም አልቀረልኝም
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው መተንፈስን ነው።“መተንፈስ አልቻልኩም” ወይም “ለመተንፈስ ከባድ ነው።”

### Daniel 10:18

ሰው የሚመስለው
“የሰው ምስል ያለው”
በርታ፤ፅና
“በርታ”የሚሉት ቃላት የተደጋገሙት አፅንዖት ለመስጠት ነው።
የተወደድህ ሰው ሆይ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“አንተ እግዚአብሔር የሚወድህ”
በረታሁ
ይሄኛው በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ጠንካራ ሆንኩ”

### Daniel 10:20


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የፋርስ አለቃ
“አለቃ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች የሚኖሩበትን ምድር የሚገዛውንና የሚጠብቀውን መንፈስ ነው።“የፋርስ አለቃ መንፈስ”
ነገር ግን እነግርሃለሁ
ይሄ የሚያሳየው ከመሄዱ በፊት መልአኩ ይህንን ጉዳይ ለዳንኤል የሚነግረው መሆኑን ነው።“ነገር ግን በመጀመሪያ እነግርሃለሁ”
በእውነት ፅሑፍ ውስጥ የተፃፈውን
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“የእውነት መፅሐፍ የሚናገረው ነገር” ወይም “በእውነት መፅሐፍ ላይ የሆነ ሰው የፃፈው”
ብርቱ መሆኑን ያሣያል
“ብርቱ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ይሰጣል”
ከአለቃችሁ ከሚካኤል በቀር ማንም የሚያፀናኝ የለም
“ከእነርሱ ጋር በምዋጋበት ወቅት ከእኔ ጋር በማበር ብርቱ መሆኑን የሚያሣየኝ የእናንተ አለቃ የሆነው ሚካኤል ብቻ ነው”ወይም “ከእነርሱ ጋር ስዋጋ እገዛ የሚያደርግልኝ የእናንተ አለቃ የሆነው ሚካኤል ብቻ ነው”
አለቃችሁ ሚካኤል
“አለቃችሁ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ነው።የሚያመለክተውም ዳንኤልንና የተቀረውን የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።“የሕዝባችሁ አለቃ የሆነው ሚካኤል”
አለቃችሁ ሚካኤል
“ጠባቂያችሁ የሆነው መልአኩ ሚካኤል”

---

Chapter 11

Daniel 11:1

አጠቃላይ መረጃ
በትንቢተ ዳኤል ከምዕራፍ11:1 እስከ ምዕራፍ 12:4 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ በምዕራፍ 10 ላይ ለዳንእል የሚናገረው በእውነት መፅሐፍ ላይ የተፃፈውን ነው።ይሄ በትንቢተ ዳንኤል 10:21 ላይ እፈፅመዋለሁ ብሎ እንደተናገረው ነው።
በዳርዮስ በመጀመሪያ ዓመት
ዳርዮስ የሜዶን ንጉሥ ነበረ።“የመጀመሪያው ዓመት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ንጉሥ የሆነበትን የመጀመሪያውን ዓመት ነው።“በመጀመሪያው በዳርዮስ የአገዛዝ ዘመን”
ሦስት ነገሥታት በፋርስ ይነሣሉ
“ሦስት ነገሥታት በፋርስ ላይ ይነግሳሉ”
አራተኛውም ከሁሉ ይልቅ እጅግ ባለጠጋ ይሆናል
“ከእነርሱ በኋላ ከሦስቱ ይልቅ ብዙ ገንዘብ ያለው አራተኛ ንጉሥ ሥልጣኑን ይይዛል”
ኃይል
ለዚህ ቃል ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/ሥልጣን2/የወታደር ኃይል
ሁሉን ያስነሳል
“ሁሉንም ሰዎች ለመዋጋት ፈቃደኞች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል”

Daniel 11:3

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
ኃያልም ንጉሥ ይነሣል
አብዛኛውን ጊዜ የመነሣት ወይም የመቆም ሃሣብ የሚነገረው ኃያል እየሆነ ለሚመጣ ሰው ነው።“ኃያል ንጉሥ መግዛት ይጀምራል”
እጅግ ታላቅ የሆነ መንግሥትን የሚገዛ
ይህንን ቃል በአግባቡ ሊገልፁ የሚችሉት “የመንግሥቱ ሥፋት እጅግ ታላቅ ይሆናል” ወይም “ንጉሡ ግዛቱን የሚያስተዳድረው እጅግ ታላቅ በሆነ ኃይል ነው።”
መንግሥቱ ይሰበራል፤ይከፋፈላልም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“መንግሥቱ ይሰባበራል”ወይም “መንግሥቱየተቆረረጠ ይሆናል”
አራቱ የሰማይ ነፋሣት
ይህንን በትንቢተ ዳንኤል7:2 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
ለራሱ ዘር ግን አይደለም
ያለመከፋፈልና ያለመሰጠት ሃሣብ በዚህ ሥፍራ ላይ ይጠቀሳል።“ዘሩ ግን አይከፋፈልም”ወይም “በራሱ ዘር መካከል አይከፋፈልም”
ከራሱ ዘር በስተቀር መንግሥቱ ይነቀላል
እዚህ ሥፍራ ላይ መንግሥቱ ልክ አንድ ሰው ከሥሩ ነቅሎ እንደሚያጠፋው ዕፅዋት ተመስሎ ነው የቀረበው።ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡“ሌላ ኃይል መጥቶ ካጠፋውና ከነቀለው በኋላ የእርሱ ዘሮች ልሆኑ ሌሎች ሰዎች መጥተው በበላይነት ይገዛሉ።”

Daniel 11:5

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
ከአለቆቹም አንዱ ይበረታል ይሠለጥንማል
የደቡቡ ንጉሥ የሠራዊት አለቃ የሰሜኑ ንጉሥ ይሆናል።
ሕብረት ይፈጥራሉ
የደቡቡ ንጉሥ ከሰሜኑ ንጉሥጋር ሕብረት ይሄ ሕብረት ሁለቱም አገሮች ሊጠብቁት የሚገባ በሕግ የተደገፈ ሕብረት ነው።“ደቡቡ ንጉሥና የሰሜኑ ንጉሥ በጋራ ለመሥራት ቃል ይገባሉ።”
የደቡብም ንጉሥ ሴት ልጅ ቃል ኪዳን ለማድረግ ወደ ሰሜን ንጉሥ ትመጣለች
የደቡቡ ንጉሥ ሴት ልጁን ለሰሜኑ ንጉሥ ይድራል።ጋብቻው በሁለቱ ነገሥታት መካከል የተደረገውን ሥምምነት ያፀናዋል።
የክንድዋ ኃይል…ክንዱም
እዚህ ላይ“ክንድ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሥልጣንን ነው።
ባዶዋን ትቀራለች
ይሄ እርሷንና ሕብረቱን የመሰረቱትን ሰዎች የመግደልን ሤራ የሚያመለክት ይመስላል።ይሄ ሐረግ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ባዶዋን ያስቀሯታል”

Daniel 11:7

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
ከሥርዋ ቅርንጫፍ
ቤተሰቡ በዛፍ ተመስሎ ተገልጿል።ሥሩ ቅድመ አያቶቻቸውን የሚያመለክት ሲሆን ቅርንጫፉ ደግሞ ትውልዱን የሚያመለክት ነው።“የቅድመ አያቶቿ ዘር” ወይም “ከትወልዷ አንዱ”
የእርሷ ሥር
“የእርሷ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በትንቢተ ዳንኤል 11:6 ላይ የተጠቀሰችውን የደቡቡን ንጉሥ ሴት ልጅ ነው።
እርሱ ሠራዊቱን ያጠቃል
“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእርሷን ዘርና እዚህ ላይ ደግሞ ሠራዊቱን ነው። “እርሱና ሠራዊቱ የሰሜኑን ንጉሥ ያጠቃሉ።”
እነርሱን ይዋጋቸዋል
“እነርሱ” የሚለው ቃል የሚወክለው ወታደሮችንና የጠላት ሠራዊትን ነው።“የጠላት ወታደሮችን ይዋጋቸዋል።”
ነገር ግን እርሱያፈገፍጋል
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰሜኑን ንጉሥ ነው።

Daniel 11:10

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
ልጆቹም
“የሰሜኑ ንጉሥ ወንድ ልጆች”
ብዙ ሠራዊትን ይሰበስባል
“በውጊ ላይ ሊሣተፉ የሚችሉ ብዙ ሰዎችን ይሰበስባል”
ይጎርፍማል
ብዛትያለው ሠራዊት ምድሪቱን የመሸፈኑ ነገር ከሚጎርፍ ውኃ ጋር ተመሳስሎ ቀርቧል።“ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ከመሆኑ የተነሣ ምድሪቱን ይሸፍኗታል።”

Daniel 11:11

አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
ብዙ ሕዝብንም ለሠልፍ ያቆማል
“ታላቅ ሠራዊትን ይሰበስባል”
ሠራዊቱም አልፎ በእጁ ይሰጣል
እዚህ ላይ“እጅ”የሚለው ቃል የሚወክለው የሰሜኑ ንጉሥ ተቆጣጣሪ መሆኑን

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነው።“ንጉሡ ሠራዊቱን ለደቡቡ ንጉሥ አሣልፎ ይሰጣል።”
ሠራዊቱ ይጋዛል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችል ይሆናል።“የደቡቡ ንጉሥ የሰሜኑን ሠራዊት ይማርካል”
ይታበያል
ይታበያል የሚለው ቃል የሚያመልከተው እጅግ ኩራተኛ መሆኑን ነው።“እጅግ ይኮራል”
አዕላፋትንም እንዲወድቁ ደርጋል
እዚህ ላይ መውደቅ የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጦርነት ውስጥ መሞትን ነው።“ሠራዊቱ ከጠላቶቹ መካከል ብዙ ሺዎችን እንዲገድሉ ያደርጋል።” ወይም “በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ጠላቶቹን የሚገድል ይሆናል።”
አዕላፍ
“ብዙ ሺዎች”
Daniel 11:13
አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
ከቀደመውም የበለጠ ብዙ ሕዝብ ለሠልፍ ያቆማል
እዚህ ላይ ማቆም የሚለው ሃሣብ ማመፅን የሚያመለክት ነው።“ብዙ ሕዝብ በንጉሡ ላይ ያምፃል።”
የአመፅ ልጆች
ይሄ አገላለፅ የሚያመለክተው አመፀኛ የሆኑ ሰዎችን ነው።
ያደናቅፋቸዋል
እዚህ ላይ “መደናቀፍ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው መውደቅን ነው።“ስኬታማ አይሆኑም”
Daniel 11:15
አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
የሰሜኑም ንጉሥ ይመጣል
“የሰሜኑ ንጉሥ”የሚለው ቃል የእርሱንም ሠራዊት ያካትታል።“የሰሜኑ ንጉሥ ሠራዊት ይመጣል።”
ጉብታዎችን ይወስድ ዘንድ አፈርን ይደለድላል
ይሄ የሚያመለክተው ሠራዊቱ በእነርሱ ላይ ጥቃት ለማድረስ ይችል ዘንድ የከተማዋ ከፍታ ቦታ ላይ ለመድረስ አፈር የመደልደላቸውን ሁኔታ ነው።ወታደሮችን ባሪያዎች በቅርጫት ውስጥ አፈር በማስቀመጥ ወደ ከፍታ ቦታ ላይ ከወሰዱት በኋላ ጉብታ እንዲፈጥርላቸው ይከምሩታል።
ምሽግ መሥራት
አንድን ከተማ ከጠላት ለመከላከል የሚገነባ ቅጥር ወይም በወታደሮች አማካይነት የጠላት ወታደሮችን ለመከላከል የሚገነባ ምሽግ።
በፊቱም የሚቆም የለም
እዚህ ላይ የሚቆም የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመዋጋት ብቃቱን ነው።“ከእነርሱ ጋር እየተዋጉ መቀጠል ያዳግታቸዋል።”
በእርሱም ላይ የሚመጣው ግን እንደ ፈቃዱ ያደርጋል
“ወራሪው ንጉሥ በዚያኛው ንጉሥ ላይ የፈለገውን ነገር ሊያደርግ ይችላል።”
ይቆማል
እዚህ ላይ መቆም የሚያመለክተው መግዛትን ነው።“ንጉሱ መግዛት ይጀምራል”
መልካሚቱ ምድር
ይሄ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ምድር ነው።ይሄንን በትንቢተ ዳንኤል 8:9 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።
በእጁም ውስጥ ጥፋት ይሆናል
እዚህ ላይ “ጥፋት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የማውደምን ኃይል ነው። የማጥፋት ኃይል የሚለው አባባል አንድ ሰው በእጁ ሊይዘው እንደሚችል ዓይነት ቁስ ተደርጎ ነው የተገለፀው።“ማንኛውንም ነገር የማጥፋት ኃይል አለው።”
Daniel 11:17
አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
ፊቱን ያቀናል
ይሄ አንድ ሰው አንድ ነገር ለመፈፀም ከወሰነ በኋላ ውሳኔውን ለመቀልበስ ፈቃደኛ አለመሆኑን የሚገልጥ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።
ከመንግሥቱም ኃይል ሁሉ ጋር ይመጣ ዘንድ
ይሄ ወታደራዊ ኃይልን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።“ሠራዊቱ ካለው ኃይል ሁሉ ጋር ይመጣል”
የሴት ልጅ
ይሄ ሴት ለሚለው ቃል ውብ የሆነ አገላለፅ ነው።
ዕብረቱን ያስቆማል
“የሰሜኑ ንጉሥ ዕብረቱን እንዲያቆም ያደርገዋል።”
ዕብረቱንም በራሱ ላይ ይመልስበታል
“የሰሜኑ ንጉሥ በሌሎች ላይ ዕብረተኛ ስለነበረ ለሥቃይ ይዳርገዋል።”
ፊቱን ይመልሳል
“የሰሜኑ ንጉሥ ሃሣቡን ይለውጣል”
አይገኝምም
ይሄ ይሞታል ለሚለው ቃል በሌላ መልክ የቀረበ አገላለፅ ነው።ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ይሰወራል”ወይም“ሕይወቱ ያልፋል”
Daniel 11:20
አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
በእርሱም ሥፍራ ሌላ ሰው ይነሣል
በንጉሱ ቦታ ላይ ሌላ ሰው ይነሣል ማለት ቀድሞ በነበረው ንጉሥ ቦታ ላይ ሌላ ሰው ይቀመጣል ማለት ነው።“በዚያ ንጉሥ ምትክ ሌላ ሰው የሰሜን ንጉሥ ይሆናል።”
እርሱ ይሰበራል
እዚህ ላይ “እርሱ”የሚለወው ቃል የሚያመለክተው አዲሱን ንጉሥ ነው።መሰበር የሚለው ቃል የሚመለክተው መሞትን ነው።“የአዲሱ ንጉሥ ሕይወት ያልፋል።”
በቁጣ ሣይሆን
ለዚህ ሃሣብ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/ማንም ሰው በንጉሡ ላይ አልተበሳጨም 2/የንጉሱ የሞቱ ሁኔታና ምክኒያት በምሥጢር መያዛቸው።
ሕዝቡ የመንግሥትነትን ሥፍራ ሊሰጠው የማይፈልገው የተጠላ ሰው
የንጉሥ ዘር ባለመሆኑ ምክኒያት ሕዝቡ እርሱን እንደ ንጉሥ ለመቀበል ፈቃደኛ አይሆንም።“የማይቀበሉትና ንጉሥ እንዳይሆን የሚፈልጉት ሰው”
የሚጎርፍም ሠራዊት ከፊቱ ይወሰዳል
ይወሰዳል የሚለው ቃል የሚወክለው ይጠፋል የሚለውን ቃል ነው።“ጎርፍ በሚጓዝበት ነመንገድ ሁሉ ያለውን ነገር እያጠፋ እንደሚሄድ ሁሉ እንደዚሁ እርሱም ታላቅ ሠራዊትን ያጠፋል።”
እርሱና የቃል ኪዳኑ አለቃ ይሰበራሉ
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሠራዊቱንና የቃል ኪዳኑን አለቃ ያጠፋል”
የቃል ኪዳኑ አለቃ
የካህናቱ መሪ።“ይሄ ሐረግ እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የሆነውን ኃይማኖታዊ ሥልጣን የያዘውን ሰው ማለትም ሊቀ ካህንንየሚያመለክት ነው።”
Daniel 11:23
አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
ከእርሱም ጋር ከተወዳጀ በኋላ
ይሄም በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሌሎች ገዢዎች የሠላም ውልበሚያደርጉበት ወቅት”
በተከታዮቹ መካከል ይበትናል
“ለተከታዮቹ ያከፋፍላል”
ብዝበዛውን፤ምርኮውንና ሃብቱን
“እርሱና ሠራዊቱና ድል ካደረጓቸው ሕዝብ ላይ የሚወስዷቸው ውድ የሆኑ ዕቃዎች”
Daniel 11:25
አጠቃላይ መረጃ
መልአኩ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል።
ኃይሉንና ልቡን ያነሳል
እዚህ ላይ ኃይልና ልብ(ማለትም ጉብዝና)የሚገለፁት ወደ ድርጊት ለመግባት ይችሉ ዘንድ ሰው እንደሚያነቃቸው ዓይነት ተደርገው ነው።“ራሱን ኃያል ያደርጋል፤ጎበዝም ይሆናል።”
ልብ
እዚህ ላይ ልብ የሚለው ቃል የሚወክለው ጉብዝናን ነው።
ከታላቅ ሠራዊት ጋር
“በሚሰበስበው ታላቅ ሠራዊት”

ጦርነትን ያውጃል

“ከእርሱ ጋር ይዋጋል”

አይቋቋምም

አይቋቋምም የሚለው ቃል የሚያሣየው መሸነፍን ነው።“የሰሜኑ ንጉሥ ይሸነፋል ወይም ሠራዊቱ ይሸነፋል።”

መልካም የሆነውን ምግቡን የሚመገቡ ሰዎች

ይሄ የሚያመለከተው የንጉሡ አማካሪዎችን ነው።እጅግ ታማኝ የሆኑ የንጉሡ አማካሪዎች ከንጉሱ ጋር መብላታቸው የተለመደ ነገር ነበር።“የንጉሱ ምርጥ የሆኑ አማካሪዎች”

ሠራዊቱም ይጎርፋል

እዚህ ላይ የአንድ ሠራዊት ድል መደረግ ልክ ጠራርጎ ከሚወስድ ጎርፍ ጋር ተመሳስሎ ቀርቧል።“ጠላት ሠራዊቱን ፈፅሞ ያጠፋዋል ወይም ጎርፍ በመንገዱ ከላይ የሚያገኘውን ሁሉ ጠራርጎ እንደሚወስድ እንዲሁ ጠላቱ ፈፅሞ ያጠፋዋል።”

ብዙዎች ተገድለው ይወድቃሉ

እዚህ ላይ “ይወድቃሉ”የሚለው ዘይቤያዊ አነጋገር የሚያመለክተው በጦርነት አውድማ መሞትን ነው።ስለሆነም “መውደቅ”እና “መሞት”የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።“ከእርሱ ሠራዊት መካከል ብዙዎቹ በጦርነት ውስጥ ይሞታሉ።”

አንዱ በሌላው ላይ ክፋትን ያደርግ ዘንድ በልቡ ይሻል

እዚህ ላይ “ልብ”የሚለው ቃል የሚወክለው የሰውን መሻቶች ነው።እዚህ ላይ መሻቶች የሚለው ቃል ልክ አንድ ሰው የሆነ ቦታ ላይ ሊያስቀምጠው እንደሚችል ዕቃ ዓይነት ተመስለው ቀርበዋል።“አንዱ በሌላው ላይ ክፋትን ለማድረግ ቁርጥ የሆነ ሃሣብ አላቸው።”

በአንድ ገበታ ይቀመጣሉ

በአንድ ገበታ መቀመጥ የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጋራ ሆኖ መወያየትን ነው።

አይከናወንላቸውም

“ውይይታቸው አይጠቅማቸውም”

ፍፃሜው እስከተወሰነ ጊዜ ነው

ይሄ ስብሰባቸው ለምን ሊሳካ እንደማይችል ይገልፃል።“የድርጊታቸው ውጤት የሚመጣው እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ ነው።”

## Daniel 11:28

ብዙ ሐብት፤ልቡም በተቀደሰ ቃል ኪዳን ላይ ይሆናል

እዚህ ላይ“ልብ”የሚለው ቃል የሚወክለው አዕምሮን ወይም የአንድን ሰው አስተሳሰቦች ነው።“ልቡም በ…ላይ ይሆናል” የሚለው ቃል አንድን ነገር ለመቃወም መቁረጥ ማለት ነው።ይሄ በአዲስ ዓረፍተ ነገር ሊገለፅ ይችላል።“ብዙ ሐብት። የተቀደሰውን ቃል ኪዳን ለመቃወም ቁርጥ ሃሣብ ያደርጋል።”

ልቡም ቃል ኪዳኑን በመቃወም ላይ ይሆናል

ንጉሱ ቃል ኪዳኑን የመቃወም ድርጊቱ የሚያመለክተው እሥራኤላውያን ለቃል ኪዳኑ እንዳይታዘዙ ለማድረግ ያለውን ፍላጎት ነው።“እሥራኤላውያን የተቀደሰው ቃል ኪዳኑን ከመታዘዝ እንዲታቀቡ ለማድረግ ቁርጥ ሃሣብ ማድረግ።”

የተቀደሰው ቃል ኪዳን

“ቅዱስ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ከእሥራኤላውያን ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን ነው።ቃል ኪዳኑ ከራሱ ከእግዚአብሔር የመነጨ በመሆኑ መከበርና ለእርሱ መታዘዝ እንደሚገባ የሚያሣይ ነው።“እሥራኤላውያን ሁሉ ሊታዘዙት የሚገባ ቃል ኪዳን”

ያደርጋል

ይሄ የሚያሣየው ንጉሱ በእሥራኤል ላይ የተወሰነ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን ነው።“የሚሻውን ነገር በእሥራኤል ላይ ያደርጋል።”

## Daniel 11:29

የኪቲም መርከቦች ይመጡበታል

መርከቦቹ የሚያመለክቱት በእነዚያ መርከቦች ውስጥ ሠራዊት የሚመጣ መሆኑን ነው።“ሠራዊቱን ለመዋጋት በኪቲም መርከብ ተጉዞ ሠራዊት ይመጣል።”

ኪቲም

ይሄ በሜዲቴራንያን ባህር ውስጥ በሚገኘው በቆጵሮስ ደሴት ላይ መሥፈርን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

በቅዱሱም ቃል ኪዳን ላይ ይቆጣል

“ቅዱሱን ቃል ኪዳን ይጠላል”

ለእነዚያ አድልዎ ያደርጋል

“ለእነዚያ ያደላል”ወይም “እነዚያን ይረዳቸዋል”

## Daniel 11:31

የእርሱ ሠራዊቶቹ ይቆማሉ

“የእርሱ ሠራዊት ይገለጣል”ወይም “የእርሱ ሠራዊት ይመጣል”

መቅደሱንም ግንቡንም

“ሰዎች እንደ ምሽግ የሚጠቀሙበት ቤተ መቅደስ”

የዘወትሩንም መሥዋዕት ያስቀራሉ

“መሥዋዕት ያስቀራሉ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች መሥዋዕት እንዳያቀርቡ መከልከልን ነው።“ካህናቱ የዘወትር የሚቃጠል መሥዋዕት እንዳያደርጉ ያግዷቸዋል”

ከባድ ሐዘንን የሚያስከትለው በደል

ይሄ የሚያመለክተው ጣኦት ቤተ መቅደስን ለሐዘን እንደሚያደርጋት ማለትም እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን ትቶ እንዲሄድ ማድረጉን ነው።“እግዚአብሔርን በቤተመቀደስ ውስጥ ከመኖር የሚያግደው አስፀያፊ ጣኦት”ወይም “ቤተ መቅደስን የሚያቆሽሸው አስፀያፊ ነገር”

ቃል ኪዳኑን ክፉኛ ተቃወመው

“ቃል ኪዳኑን ክፉኛ ተቃወመው”

እንዲረክሱ ይገፋፋቸዋል

“ወደ ክፋት እንዲያመሩ ይገፋፋቸዋል”

አምላካቸውን የሚያውቁትን

እዚህ ላይ“ማወቅ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው“ታማኝ መሆንን”ነው።“ለአምላካቸው ታማኝ የሆኑ”

ይበረታሉ፤ያደርጋሉም

“ይፀናሉ፤ይቋቋሙዋቸዋልም”

## Daniel 11:33

በሰይፍና በእሣት ነበልባል ይወድቃሉ

እዚህ ላይ “መውደቅ”የሚለው ቃል ሞትን ጨምሮ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ጥፋት ሊደርስ የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው።እዚህ ላይ “ሰይፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጦርነትንና በውጊያ ውስጥ መሳተፍን ሲሆን “ነበልባል” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ደግሞ እሣትን ነው።“በውጊያ ውስጥ ሕይወታቸው ያልፋል እንዲሁም ተቃጥለው ይሞታሉ”

እነርሱ

ይሄ የሚያመለክተው ከእሥራኤላውያን መካከል ጥበበኛ የሆኑትን ሰዎች ነው።

በምርኮኝነት ይወድቃሉ፤ለዘመናት ለመበዝበዝ

እዚህ ላይ “መውደቅ”የሚለው ቃል ሞትን ጨምሮ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ጥፋት ሊደርስ የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው።“መበዝበዝ”የሚለው ሐረግ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ባሪያዎች ይሆናሉ፤ጠላቶቻቸው ለዘመናት ንብረቶቻቸውን ይዘርፋሉ”

በጥቂት ዕርዳታ ይረዳሉ

ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል።“ሌሎች ሰዎች በትንሹ እገዛ ያደርጉላቸዋል”

ብዙ ሰዎች በግብዝነት ወደ እነርሱ ይሰበሰባሉ

ይሄ የሚያመለክተው ጥበበኛ ሰዎችን የሚያግዙ የሚመስሉትን ሰዎች ነው።ሆኖም በእውነትም ሊያግዟቸው ስለፈለጉ አይደለም።

ይሰበሰባሉ

እዚህ ላይ“ይሰበሰባሉ”የሚለው ቃል የሚወክለው “ለመርዳት ይመጣሉ”የሚለውን ሃሣብ ነው።“ሊያግዟቸው ይመጣሉ”

አንዳንድ ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች ይወድቃሉ…እስከ ዘመን ፍፃሜ

እግዚአብሔር ይበቃል እስኪል ድረስ ሥቃዩ የሚቀጥል ይሆናል።

አንዳንድ ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች ይወድቃሉ

እዚህ ላይ “መውደቅ”የሚለው ቃል ሞትን ጨምሮ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ጥፋት ሊደርስ የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው።

በእነርሱ ላይ የማጥራት ሥራ ይከናወን ዘንድ

እዚህ ላይ“ዘንድ” ማለት “ከውጤቱ ጋር በተያያዘ”ማለት ነው።“በውጤቱም የማጥራት ሥራ ይከናወንባቸዋል”

ይነጥሩና፡ይጠሩ ዘንድ ይነጡም

ሶስቱ የሥራ ክንወኖች እዚህ ላይ የተገለፁት በዕቃዎች ተመስለው ነው።ሆኖም በፍዝ ወይም በተገብሮ መልክ እንደ ድርጊት ሊገለፁ ይችላሉ።“ይነጥራሉ፡ይጠራሉ፤ ይነፃሉ” ወይም “የሚደርስባቸው ሥቃይ ያነጥራቸዋል፤ያጠራቸዋል፤ያነፃቸዋል”

ማንጠር

ይሄ ብረትን በእሣት ውስጥ በማቅለጥ የማጥራትን ሂደት የሚያመለክት ነው።

እግዚአብሔር የረሱ የሆነው ሕዝብ ታማኝ እንዲሆንለት የማድረጉን ጉዳይ አንድ ሠራተኛ ብረቱ እንዲጠራ ለማድረግ በእሣት ውስጥ ከማስቀመጥ ሁኔታ ጋር አመሳስሎ ነው የተናገረው፡፡
ማንፃት
ይሄ የሚያመለክተው ሰዎችን ከኃጢአትና ከሌሎች ክፉ ዓይነት ድርጊቶች እንዲለዩ በማድረግ ሰዎች፤ሥፍራዎች ወይም ቁሣቁሶች ለእግዚአብሔር የሚመቹ እንዲሆኑ ማድረግን ነው፡፡
ማጥራት
ይሄ ሃሣብ ማንጠር ከሚለው ቃል ጋር ተመሣሣይ ነው፡፡የሚነጥር ብረትን ይጠራል ማለትም ይቻላል፡፡
የፍፃሜ ዘመን
“በማጠናቀቂያ ቀናት” ወይም“የዓለም መጨረሻ”
የተወሰነው ቀን ይመጣል
እዚህ ላይ “የተወሰነው ቀን” ሲል እግዚአብሔር የቀጠሮ ሰዓት መወሰኑን የሚያመለክት ነው፡፡ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“እግዚአብሔር ለወደፊት ቀጠሮ ቀጥሯል”
Daniel 11:36
X
“ንጉሡ የወደደውን ሁሉ ያደርጋል”
ንጉሡ
ይሄ የሚያመለክተው የሰሜኑን ንጉሥ ነው፡፡
ራሱንም ከፍ ከፍ ያደርጋል፤ራሱን ታላቅ ያደርጋል
“ራሱንም ከፍ ከፍ ያደርጋል”የሚለውና ”ራሱን ታላቅ ያደርጋል” የሚለው ቃልተመሳሳይ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን ንጉሱ እጅግ የሚኮራ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡
ራሱን ከፍ ከፍ ያደርጋል
እዚህ ላይ ይሄ የሚያመለክተው እጅግ እየኮራ መሆኑን ነው፡፡
ራሱን ታላቅ አደረገ
እዚህ ላይ ይሄ የሚያመለክተው እጅግ አስፈላጊ ሰውና ኃያል ሰው ለመሆን የማስመሰሉን ነገር፡፡
የአማልዕክት አምላክ
ይሄ የሚያመለክተው እውነተኛ ሆነውን አንዱን አምላክ ነው፡፡“ታላቅ የሆነውን እግዚአሔር” ወይም“እርሱ ብቻ እውነት የሆነ አምላክ”
አስገራሚ ነገሮች
“አሰቃቂ ነገሮች”ወይም“አስደንጋጭ ነገሮች”
ቁጣውም አስኪፈፀም ደረስ
ይህ ሐረግ መጋዘኑ ፈፅሞ እስኪሞላ ደረስ ቁጣውን እንደሚያከማችና በኋላም ወደ ተግባር እንደሚገባ ዓይነት አድርጎ ነው የሚገልፀው፡፡“የእግዚአብሔር ቁጣ የመጨረሻ ደረጃ ላይ እስኪደርስ ደረስ”ወይም“እርምጃ ለመውሰድ ይችል ዘንድ የእግዚአብሔር ቁጣ ጫፍ እስኪደርስ ደረስ”
በሴቶች ዘንድ የሚወደድ አማልዕክት
ይሄ የአህዛብ ጣኦት የሆነውንና ታሚዝ በሚል ሥያሜ የሚታወቀውን ጣኦት የሚያመለክት ይመስላል፡፡
የአምባዎች አምላክ
ምናልባትም ይሄ ንጉሥ ይሄ የሐሰት አምላክ የሌሎች ሰዎችን ምሽጎች እያጠቃ የእርሱን ይዞታ ግን በሰላም እንዲጠበቅ የሚያደርግለት መሆኑን አምኖ ሊሆን ይችላል፡፡“ምሽጎችን የሚጠብቅ የጣዖት አምላክ”
በእነዚህ ፋንታ
“እነዚህ”የሚለው ቃል በትንቢተ ዳንኤል 11:37 ላይ የተጠቀሱትን ጣዖታት የሚያመለክት ነው፡፡
ምድርንም በዋጋ ይከፍላል
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/“ምድሪቱን በሥጦታ መልክ ለተከታዮቹ ይሰጣል”ወይም 2/“ለተከታዮቹ መሬቱን ይሸጣል፡፡”
Daniel 11:40
በፍፃሜ ዘመንም
“የመጨረሻ ቀናት”ወይም “የዓለም መጨረሻ”
የደቡቡ ንጉሥ …የሰሜኑ ንጉሥ
እነዚህ ሐረጎች ነገሥታቱንና ሠራዊታቸውን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ “የደቡቡ ንጉሥና ሠራዊቱ ”….“የሰሜኑ ንጉሥና ሠራዊቱ”
እንደ አውሎ ነፋስ ይመጣበታል
ከባድ በሆነ ውጊያ ጠላትን ለማጥቃት ልክ አውሎ ነፋስ እንደተነሳ ተደርጎ ነው የሚነገረው፡፡“እንደ ኃይለኛ አውሎ ነፋስ ጥቃት ይሰነዝርበታል”ወይም “በብርቱ ይዋጋል”
ይጎርፍማል
አንድ ሠራዊት አገሩን ሲወርር ጎርፍ እንደተከሰተ ዓይነት ተደርጎ ነው የሚነገረው፡፡
ያልፍማል
ሠራዊቱን የሚያቆም ኃይል አይኖርም፡፡“ማንም ሊያስቆመው በማይችል መልኩ በምድሪቱ ውስጥ ያልፋል፡፡”
መልካሚቱ ምድር
ይሄ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ምድር ነው፡፡
ይወድቃል
እዚህ ላይ መውደቅ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመሞትን ድርጊት ነው፡፡“ይሞታል”
ነገር ግን እነዚህ ከእጁ ይድናሉ
እዚህ ላይ“እጅ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኃይልን ነው፡፡“ነገር ግን እነዚህ ከእርሱ ኃያል ጥቃት ያመልጣሉ”ወይም “ነገር ግን እነዚህን አገሮች ለማጥፋት ይሳነዋል”
Daniel 11:42
አጠቃላይ መረጃ
ይሄ ስለ ሰሜኑ ንጉሥ ብቻ የሚያወሳ ነው፡፡
እጁን በአገሮች ላይ ይዘረጋል
እዚህ ላይ“እጅ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሥልጣንንና በበላይነት መቆጣጠርን ነው፡፡“የቁጥጥር ሥርዓቱን በተለያዩ አገሮች ውስጥ ያስፋፋል”
በአገሮች
እዚህ ላይ ሃሳቡ ብዙ አገሮች ወይም የተለያዩ ምድሮች ለማለት ነው፡፡
የግብፅ ምድርም አትድንም
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“የግብፅ ምድር አታመልጥም”
የልብያና የኢትዮጵያ ሰዎችም ይከተሉታል
“የልብያና የኢትዮጵያ ሕዝብ”ልብያ ከግብፅ በስተ ምዕራብ ያለች አገር ስትሆን “ኢትዮጵያ ደግሞ ከግብፅ በስተ ደቡብ የምትገኝ አገር ናት”
Daniel 11:44
አጠቃላይ መረጃ
ይሄ አሁንም የሚያወሳው ስለ ሰሜኑ ንጉሥ ነው፡፡
በታላቅ ቁጣ ይወጣል
“ቁጣ” የሚለው አሕፅሮተ ሥም ተናደደ በሚለው ቃል ሊገለፅ ይችላል፡፡ከሠራዊቱ ጋር አብሮ እንደሚሄድ በግልፅ ሊነገር ይችላል፡፡“በጣም ይናደዳል፡ ይወጣልም”ወይም “በጣም ከመናደዱ የተነሣ ከሠራዊቱ ጋር ይወጣል”
መውጣት
“መውጣት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠላትን የማጥቃት ድርጊትን ነው፡፡
ብዙዎችንም ያጠፋ ዘንድ
“ብዙ ሰዎችን ያጠፋ ዘንድ”
ንጉሣዊ የድንኳን መኖሪያው
ይሄ ንጉሱ በጦርነት ወቅት ከሠራዊቱ ጋር በሚሆንበት ወቅት የሚኖርባቸው ቅንጡ የሆኑ ድንኳኖችን የሚያመለክት ነው፡፡
በባህርና በከበረው በቅዱስ ተራራ ላይ
ይሄ ምናልባትም በሜዲቴራንያን ባህርና በኢየሩሣሌም ተራራ መካከል የሚገኘውን ግዛት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፡፡
የከበረው በቅዱስ ተራራ
ይሄ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የነበረበትን የእሥራኤል ተራራ ነው፡፡

Chapter 12
Daniel 12:1
አጠቃላይ መረጃ
በትንቢተ ዳንኤል 10:5 ላይ ለዳንኤል የተገለጠው መልአክ መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ሚካኤል ታላቁ አለቃ

ሚካኤል የመላዕክት አለቃ ነው፡፡“ልዑል የሚል ስምም ተሰጥቶታል”
ሚካኤል...ይነሣል
እዚህ ላይ“ይነሣል”የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም መገለጥ ማለት ነው፡፡“ሚካኤል...ይገለጣል፡፡”
ሕዝብህ ይድናል
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያድን ስለመሆኑ የበለጠ ልታብራሩ ትችላላችሁ፡፡“እግዚአብሔር ሕዝብህን ያድናቸዋል”
Daniel 12:3
ጥበበኞችም እንደ ከዋክብት ይደምቃሉ
ይህ የእግዚአብሔር ሰዎች ጥበባቸውን ለሌሎች ሰዎች ማካፈላቸውን የሚያመለክት ነው፡፡
ብዙ ሰዎችንም ወደ ፅድቅ የሚመልሱ
የሚሄዱበትን አቅጣጫ የሳቱ እንደሆኑ ዓይነት በሚመስል አቀራረብ ሌሎች ሰዎች ከእግዚአብሔር መለያየታቸውን እንዲገነዘቡ እገዛ የሚያደርጉ ሰዎችን የሚያመለክት ነው፡፡ “ሌሎች ሰዎች በፅድቅእንዲኖሩ የሚያስተምሩ ሰዎች”
የሚመልሱ...ለዘላለም እንደ ከዋክብት ይደምቃሉ
እነዚህ ሰዎች ከሚያበሩ ከዋክብት ጋር ተነፃፅረዋል፡፡“የሚመልሱ...ከዘላለም እስከ ዘላለም እንደ ከዋክብት ያበራሉ”
እነዚህን ቃላት ዝጋ፤መፅሐፉንም አትም
እዚህ ላይ “ቃላት”የሚለው ቃል የሚያመለክተው መፅሐፉን ነው፡፡“ይህንን መፅሐፍ ዘግተህ በማህተም አትመው፡፡”
እስከ ዘመን ፍፃሜ ድረስ
“የማጠናቀቂያ ቀናት”ወይም “የዓለም መጨረሻ”
በብዙ እዚህና እዚያ ይሮጣሉ፤ዕውቀትም ይበዛል
ይህ መፅሐፉ በማህተም በሚዘጋበት“የመጨረሻ ዘመን”ከመድረሱ በፊት የሚከናወን ድርጊት ነው፡፡ይሄ የበለጠ ሊብራራ ይችላል፡፡“ይሄ ከመሆኑ በፊት ብዙ ሰዎች ተጨማሪ ነገሮችን ለመማርና የበለጠ ነገር ለማወቅ ወደተለያዩ ሥፍራዎች ይጓዛሉ፡፡”
Daniel 12:5
አጠቃላይ መረጃ
በትንቢተ ዳንኤል 10፡1 ላይ ማየት የጀመረውን ራዕይ ቀጣዩን ክፍል መናገር ይቀጥላል፡፡
ሁለት ሌሎች ቆመው ነበር
“ሌሎች ሁለት መላዕክት ቆመው ነበር”
በፍታም የለበሰውን ሰው
ይሄ የሚያመለክትው በወንዙ አጠገብ ቆሞ የነበረውን መልአክ ሣይሆን በትንቢት ዳንኤል1፡5 ላይ ለዳንኤል የተገለጠለትን መልአክ ነው፡፡ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ከተልባ እግር የተሰራ ልብስ ለብሶ የነበረው ሰው”ወይም “መልአኩ በፍታ ለብሶ ነበር”
ከወንዙ ውኃ በላይ
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/ከተልባ እግር የተሰራ ልብስ የለበሰው መልአክ ከወንዙ በላይኛው ክፍል ላይ ነበር፡፡ወይም 2/መልአኩ ከወንዙ ትይዩ ባለው የላይኛው የውኃ ክፍል ላይ ነበር፡፡
የዚህ ድንቅ ፍፃሜ እስከ መቼ ድረስ ነው?
“እነዚህ አስገራሚ የሆኑ ነገሮች እስከ መቼ ድረስ ይቆያሉ?”ይሄ የሚያመለክተው ክንውኖቹ ከጀመሩበት ወቅት አንስቶ እስከ ፍፃሜ ድረስ ያለውን ጊዜ ነው፡፡
እነዚህ አስገራሚ የሆኑ ክንውኖች
መልአኩ ለዳንኤል በተናገረበት ወቅት በዚህ ራዕይ ውስጥ የታዩት ነገሮች አልተከናወኑም ነበር፡፡ይሄ በእርግጥም በትንቢተ ዳንኤል 12፡1-4 ያሉትን ክንውኖች የሚያመለክት ሲሆን ምናልባትም በምዕራፍ 11 ካለው ራዕይ የተከናወኑ ነገሮችን አካትቶ ሊሆን ይችላል፡፡
Daniel 12:7
በፍታም ልብስ የለበሰው
ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡ነው፡፡ይሄ በገቢር መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡“ከተልባ እግር የተሰራ ልብስ ለብሶ የነበረው ሰው”ወይም “መልአኩ በፍታ ለብሶ የነበረው መልአክ”
ከወንዙ ውኃ በላይ
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/ከተልባ እግር የተሰራ ልብስ የለበሰው መልአክ ከወንዙ በላይኛው ክፍል ላይ ነበር፡፡ወይም 2/መልአኩ ከወንዙ ትይዩ ባለው የላይኛው የውኃ ክፍል ላይ ነበር፡፡
ለዘላለም የሚኖረው
“ለዘላለም ነዋሪ የሆነው እግዚአብሔር”
ለዘመንና ለዘመናት ለዘመንም እኩሌታ
ይሄ የሚጀመርበትን ወቅት አሻሚ እንደሆነ ብንተወው የተሻለ ነው፡፡የሚጀምርበትን ጊዜ ማወቅ ካለባችሁ ምናልባትም ሶስት ተኩሉ ዓመታት የሚጀምሩት በትንቢተ ዳንኤል 12፡1 ላይ ተከናውነው በነበሩ ድርጊቶች ነው፡፡
Daniel 12:8
ጌታዬ
ዳንኤል ለእርሱ ያለውን አክብሮት ለማሣየት ከተልባ እግር የተሰራ ልብስ የለበሰውን መልአክ “ጌታዬ”በማለት ነው የሚገልፀው፡፡
ቃሉ እስከ ፍፃሜ ድረስ የተዘጋና በማሕተም የታተመ ነው
ዳንኤል የተሰጠው ራዕይ ለሌሎች ሰዎች መገለጥ የሌለበት ምሥጢር ነበር፡፡ መፅሐፉ በማሕተም የተዘጋ በመሆኑ ማንም ሰው ሊገልጠው አይችልም ነበር፡፡“የፃፍካቸውን ቃላት በማህተም መዝጋት ይኖርብሃል፡፡”
Daniel 12:10
አጠቃላይ መረጃ
የበፍታ ልብስ የለበሰው መልአክ ለዳንኤል መናገሩን ይቀጥላል፡፡
ሰዎች ይጠራሉ፤ይነፃሉ፤ይነጥሩማል
ማጥራቱን የሚያከናውነው እግዚአብሔር ነው፡፡በመሠረቱ እነዚህ ሶስት ቃላት ተመሣሣይ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ናቸው፡፡“እግዚአብሔር ያጠራል፤ያነፃል፤ብዙ ሰዎችንም ያነጥራል”
ማንጠር
የዚያ አካል ያልሆነን ማናቸውንም ነገር በማስወገድ እንዲጠራ ማድረግ፡፡
ክፉዎች ግን ክፋትን ያደርጋሉ
ክፉ ሰዎች አመፅን ወይም ኃጢአት የሆኑ ነገሮችን ያደርጋሉ፡፡
ክፉዎችም ሁሉ አያስተውሉም
“እነዚያ ለእግዚአብሔር የሚታዘዙ ጠቢባንና የሚያስተውሉ ናቸው፡፡”
የዘወትሩም መሥዋዕት...ከቆመ
የቤተ መቅደሱን መሥዋዕቶች የሚያስቆመው የሰሜኑ ንጉሥ ነው፡፡“የሰሜኑ ንጉሥ የዘወትሩን መሥዋዕት በማስወገድ በምትኩ ሐዘንን የሚያስከትለውን ርኩሰት ይተክላል፡፡”
ፍፁም ባዶነትን የሚያስከትለው ርኩሰት
ይሄ የሚያመለክተው ጣዖቱ ለቤተ መቅደሱ ባዶ መሆን ምክኒያት እንደሚሆን ማለትም እግዚአብሔር ቤተመቅደሱን የሚተው መሆኑን ነው፡፡“እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን ትቶ እነዲሄድ መንስዔ የሚሆነው አስፀያፊ ጣዖት ”ወይም “ቤተ መቅደሱ እንዲቆሸሽ የሚያደርገው አስፀያፊ ነገር”
1,290 ቀናት
“አንድ ሺህ ሁለት እና መቶ ዘጠና ቀናት”ወይም “አንድ ሺህ ሁለት መቶ ቀናት” እዚህ ላይ “ቀናት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተወሰኑ ዘመናትን ነው፡፡አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ቀናት የሚለውን ቃል የሚጠቀሙ ቢሆንም ይሄ ዓመታት የሚለውንም ሊያመለክት ይችላል፡፡
Daniel 12:12
አጠቃላይ መረጃ
ከተልባ እግር የተሰራ ልብስ የለበሰው መልአክ ዳንኤልን ማነጋገሩን ይቀጥላል፡፡
የሚታገስም ምስጉን ነው
“በታማኝነት የሚቆይ”
1,335 ቀናት
“አንድ ሺህ ሶስት መቶ ሠላሣ ሶስት ቀናት”ወይም “አንድ ሺህ ሶስት መቶ እና ሠላሣ አምስት ቀናት” እዚህ ላይ “ቀናት”የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ በተለምዶ ቀናት ተብሎ የሚጠራው የተወሰኑ ዘመናትን የሚያመለክት ነው፡፡ይህም ሆኖ ቀናትንም የሚመለከት ነው፡፡
መሄድ ይኖርብሃል
“ዳንኤል መሄድ ይኖርብሃል” ይሄ ዳንኤል ሕይወቱ እስከሚያልፍበት ወቅት ድረስ ነገሥታቱን ማገልገል እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡
ታርፋለህ
ይሄ “ትሞታለህ”ለማለት ጨዋ የሆነ አነጋገር ነው፡፡
ትቆማለህ
ይሄ ፃድቅ የሆኑ ሰዎች ከሞት የሚነሱበትን የመጀመሪያውን ትንሣኤ የሚያመለክት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 1
Hosea 1:1
የመጣው የያህዌ ቃል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። "ያህዌ አምላክ የተናገረው ቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ብኤሪ
ይህ የወንድ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ዖዝያ ... ኢዮአታም ... አካዝ ... ሕዝቅያስ ... ኢዮርብዓም ... ዮአስ
በዚህ መጽሐፍ የተከናወኑ ድርጊቶች በእነዚህ ነገሥታት ዘመን የተፈጸሙ ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ
ይህ እግዚአብሔር ለህዝቡ በብሉይ ኪዳን የገለጸው ስሙ ነው። ይህ እንዴት እንደሚተረጎም ስለ ያህዌ የትርጉም ቃል ገጽን ይመልከቱ።
ታላቅ ምንዝርና
እዚህ ስፍራ "ምንዝርና " ሚለው የሚገልጸው ህዝቡ ለእግዚአብሔር ታማኝ አለመሆኑን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 1:3
ጎሜር ... ዴቤላይም
እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
የኢዩ ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" ማለት "ቤተሰብ" ማለት ሲሆን የኢዩን ትውልድ ያጠቃልላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቤት
ይህ አገላለጽ የእስራኤልን መንግሥት ያመለክታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእስራኤል ቀስት
እዚህ ስፍራ "ቀስት" የሚለው የሚያመለክተው የሰራዊቱን ሃይል ነው። "የእስራኤል የጦር ሃይል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)
Hosea 1:6
ሎ-ሩሃማ
የዚህ ስም ትርጉም "አልምርም" ማለት ነው። ተርጓሚው ይህንን ትረጉም እንደ ስም አድርጎ ማቅረብን ሊመርጥ ይችላል። "አልምርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 1:8
ሎ-ሩሃማ
የዚህ ስም ትርጉም "አልምርም" ማለት ነው። ተርጓሚው ይህንን ትረጉም እንደ ስም አድርጎ ማቅረብን ሊመርጥ ይችላል። ይህንን ስም በሆሴዕ 1:6 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "አልምርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሎ-ዓሚ
የዚህ ስም ትርጉም " ህዝቤ አይደላችሁም" ማለት ነው። ተርጓሚው ይህንን ትረጉም እንደ ስም አድርጎ ማቅረብን ሊመርጥ ይችላል። ""ህዝቤ አይደላችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 1:10
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው
እንደ ባህር ዳርቻ አሸዋ
ይህ የእስራኤላዊያንን ቁጥር ብዛት ያጎላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ/ሲሚሊ የሚለውን ይመልከቱ)
ሊሰፈር ወይም ሊቆጠር የማይችል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ማንም ሊሰፍረው ወይም ሊቆጥረው የማይችል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ተብሎ በተነገረላቸው ስፍራ ይሆናል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር በተናገራቸው ስፍራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእነርሱ በተነገረበት ስፍራ
ይህ አገላለጽ ምናልባት በእስራኤል ነገሥታት ወንጀል በሚፈጸምባት ከተማ እና በእነርሱ ላይ የእግዚአብሔር ቅጣት ምልክት የነበረችን ኢዝራኤልን የሚመለከት ይሆናል።
ለእነርሱ ይህ ይነገራል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ለእነርሱ ይላቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በአንድነት ይሰባሰባሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር በአንድነት ይሰበስባቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በምድሪቱ ይገናሉ
ይህ አገላለጽ የእስራኤል ህዝብ በምርኮ የነበሩባትን ምድር ያመለክታል
የኢዝራኤል ቀን
ይህ እግዚአብሔር ህዝቡን ወደ እስራኤል ምድር የሚመልስበትን ጊዜ ያመለክታል። የዚህ ሃሳብ የተሟላ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 2
Hosea 2:1
አያያዥ ሃሳብ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው
ህዝቤ!
ይህ አጋኖ እንደ ሙሉ ሃሳብ ሊገለጽ ይችላል። "እናንተ የእኔ ህዝብ ናችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)
ርህራሄ ተደርጎልሻል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ያህዌ ርህራሄ አድርጎልሻል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ርህራሄ
"ደግነት" ወይም "ምህረተ"
Hosea 2:2
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው
ሙግት
ይህ በህግ አደባባይ አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ የሚያቀርበው ክርክር ነው
እናታችሁ
እዚህ ስፍራ "እናት" የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን አገር ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሷ ሚስቴ አይደለችም
ያህዌ እስራኤልን እንደ ሴት እየተናገረ ለእርሱ ከእንግዲህ እንደ ሚስት እንዳልሆነች ይነግራታል። ይልቁንም እስራኤል ያህዌን ከመከተል እና ከማምለክ ፊቷን አዙራለች። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)
እኔም ባሏ አይደለሁም
ያህዌ ከእንግዲህ ከእስራኤል ጋር ባል ለሚስቱ እንደሚሆነው ግንኙነት ሊኖረው አይችልም። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)
የምንዝርና ተግባሯ
አመንዝራ የሆነች ሴት ከሌላ ሰው ጋር ለመተኛት ባሏን ትተዋለች። እስራኤል በያህዌ ላይ ያደረገችው እንደዚሁ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)
ከጡቶቿ መካከል
ይህ ምስላዊ ዘይቤ እስራኤል በያህዌ ላይ ሳይሆን በጣኦት መታመኗን ያሳያል። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)

ዕርቃኗን ገፍፌ እንደተወለደችበት ቀን እራቁትነቷን አገልጣለሁ
ያህዌ ከእንግዲህ እስራኤልን አይጠብቃትም አይንከባከባትም፤ ምክንያቱም ከእርሱ እርቃለችና። በእስራኤል ባሎች ሚስቶቻቸውን ለማልበስ በህግ ይገደዱ ነበር። አንድ ወንድ ይህንን አለማድረጉ ሚስቱን ያለመቀበሉ ምልክት ነበር። የዚህ ሙሉ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ በረሃ አደርጋታለሁ
ያህዌ እስራኤልን ባዶ እና የማታበቅል በረሃማ ስፍራ እስክትመስል ይለውጣታል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ/ሲሚሊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከጥማት የተነሳ እገድላታለሁ
እዚህ ስፍራ "ጥማት" የሚለው የሚያመለክተው በጣኦታተት ላይ ሳይሆን፤ በያህዌ ላይ መታመንና እርሱን ማምለክ ያለውን አስፈላጊነት፣ ካልሆነ እስራኤል እንደ አገር መቀጠል የማትችል መሆኑን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 2:4
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው
የምንዝርና ልጆች ናቸውና
እስራኤላዊያን የሚያደርጉት የያህዌ ያልሆኑ ይመስል ነው። አባቶቻቸው እግዚአብሔርን እንዳላመለኩት ሁሉ፣ እነርሱም አላመለኩትም። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እናቶቻቸው አመንዝሮች እንደነበሩ
ሌሎች አማልዕክትን የተከተሉት የቀደሙት ትውልዶች ለያህዌ ታማኝ ባለመሆናቸው አመንዝሮች ተደርገው ነበር የተቆጠሩት። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ፍቅረኞቼን ተከትዬ እሄዳለሁ፣ እነርሱ ዳቦዬን እና ውሃዬን፣ የሃር ልብሴን እና ሱፌን፣ ዘይቴን እና መጠጤን ሰጥተውኛልና።
እዚህ ስፈራ "ፍቅረኞቼ" የሚለው የሚያመለክተው እስራኤል ከያህዌ ይልቅ ልታመለክ የመረጠቻቸውን በዓልን እና ሌሎች ሃሰተኛ አማልዕክትን ነው። የተዘረዘሩት ነገሮች ሰዎች ለመኖር የሚያስፈልጓቸው ነገሮች ናቸው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 2:6
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው
ስለዚህ መንገዷን በእሾች ለመዝጋት አጥርባታለሁ። መውጫ መንገድ እንዳታገኝ በዙሪያዋ ግንብ እገነባለሁ።
ይህ ክፍል ህዝቡ ስኬት እና ብልጽግና እንዳያገኝ ያህዌ እንደሚከለክለው ያመለክታል፣ ምክንያቱ እነርሱ ጣኦት ማምለካቸውን መቀጠላቸው ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ተመሳሳይ ንጽጽራዊ ዘይቤ/ፓራራሊዝም የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያም እንዲህ ትላለች፣ "ከአሁኑ ይልቅ ለእኔ የመጀመሪያው ባሌ የተሻለ ስለነበረ ወደ እርሱ እመለሳለሁ።"
እስራኤላውያን ወደ ያህዌ የሚመለሱት ለእርሱ ባላቸው ፍቅር ምክንያት ሳይሆን፣ ነገር ግን በበኣል አምልኳቸው ተስፋ ስለቆረጡ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 2:8
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው
እርቃኗን ትሸፍንበት የነበረውን ሀር እና ሱፌን መልሼ እወስዳለሁ
ይህ ማለት ማናልባት የእስራኤል መኸር እና ከብቶች ከንቱ ይሆናል ማለት ሊሆን ይችላል። ያህዌ በረከቱን ከእስራኤል ያርቃል፣ ህዝቡም በአደጋ ስጋት ውስጥ ብቻውን ይሆናል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)
እራቁትነትዋን ልትሸፍንበት ትጠቀምበት የነበረው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ሰዎች ራሳቸውን ለመሸፈን ይጠቀሙበት የነበረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 2:10
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለሆሴዕ እየተናገረ ነው
ከዚያም በፍቅረኞቿ ፊት እርቃኗን እገልጣለሁ
ይህ ማለት እግዚአብሔር የእስራኤልን ህዝብ በአካባቢው ባሉ ሌሎች ህዝቦች ፊት ያዋርዳቸዋል። ይህንን በሆሴዕ 2፡3 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ማንም እርሷን ከእጄ አያድናትም
ማንም እስራኤልን ሊረዳት አይሞክርም። እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን የመቅጣት ሃይል ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)
Hosea 2:12
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ በእራኤል ላይ ስለሚያደርገው ለሆሴዕ እየተናገረ ነው
ፍቅረኞቼ ለእኔ የሰጡኝ ዋጋዎቼ/ክፍያዎቼ እነዚህ ናቸው
ይህ የሚያመለክተው እስራኤል ከሃሰተኛ አማልዕክት ወይም ከበኣል የተቀበለቻቸውን ክፍያዎች ነው። ይህ ቀጥተኛ ጥቅስ ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅስ ሆኖ ሊጻፍ ይችላል። "እንግዲህ እነዚህ ፍቅረኞቿ ለእርሷ የሰጧት ወጋዎች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)
ጫካ አደርገዋለሁ
ያህዌ ሌሎች ዛፎች እና አረም እንዲበቅል በመፍቀድ የወይን ተክሉን እና የፍሬ ዛፉን ያጠፋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ የያህዌ አዋጅ ነው/ ያህዌ የተናገረው ይህ ነው
ያህዌ የአዋጁን እርግጠኝነት ለመግለጽ ስለ እራሱ በስሙ ተናገረ። "ያህዌ ያወጀው/የተናገረው ይህ ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያወጅኩት/የተናገርኩት ይህ ነው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 2:14
አያያዥ ሃሳብ፡
ያህዌ ስለ እራኤል እየተናገረ ነው።
ስለዚህ መልሼ የራሴ ላደርጋት ነው
"እኔ ያህዌ እርሷን ወደ ራሴ እመልሳለሁ"
የአኮር ሸለቆ እንደ ተስፋ በር
ያህዌ እስራኤልን ከግብጽ መርቶ እንዳወጣ፣ እስራኤል ዳግም በያህዌ ተስፋ እንድታደርግ ወደ አኮር ሸለቆ ይመራታል
ከግብጽ እንደ ወጣችበት ወራት፣ በወጣትነት ወራቷ ታደርግ እንደነበረው ከዚያ ሆና ትመልስልኛለች፣
ያህዌ እስራኤል ህዝብ በንስሃ እንደሚመለሱ እና ዳግም እርሱን አምላካቸው አድርገው ማምለክን እንደሚመርጡ ተስፋ ያደርጋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ትመልሳለለች
አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች የዕብራይስጡ ቃል "ትዘምራለች" እንደሚል ይወስዱታል።
Hosea 2:16
በዚያን ቀን ይሆናል
ይህ የሚያመለክተው እስራኤል ያህዌን ብቻ ማምለክ የምትመርጥበትን ቀን ነው
ይህ የያህዌ አዋጅ ነው/ ያህዌ የተናገረው ይህ ነው
ያህዌ የአዋጁን እርግጠኝነት ለመግለጽ ስለ እራሱ በስሙ ተናገረ። ይህንን በሆሴዕ 2፡13 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "ያህዌ ያወጀው/የተናገረው ይህ ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያወጅኩት/የተናገርኩት ይህ ነው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ባሌ
ይህ ማለት ሚስት ለባሏ እንደምትሆን የእስራኤል ህዝብ ያህዌን የሚወድ እና ለእርሱ ታማኝ ይሆናል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በኣሌ
"በኣል" ማለት "ጌታ" ማለት ሲሆን ከነዓናውያን የሚያመልኳቸውን ሀሰተኛ አማልክትንም ያመለክታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከአንደበቷ የበኣልን ስሞች አስወግዳለሁ
እስራኤላዊያን ዳግም የበኣልን ስሞች እና ጣዖታትን አይጠሩም። ህዝቡ የተወከለው በአንደበቶቻቸው ነው። "የበኣልን ስሞች እንዳትጠሩ አደርጋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲኪ/ ዘይቤያዊ አነጋጋር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 2:18
አያያዥ ሃሳብ

ያህዌ ለእስራኤል ምን እንደሚያደርግ ለሆሴ እየተናገረ ነው
በዚያን ቀን
ይህ ሀረግ በእስራኤል እና በያህዌ መሃል ስላለው የወደፊት መታደስ ለመናገር ውሏል።
ለእነርሱ ቃል ኪዳን አደርጋለሁ
የያህዌ አዲሱ ቃል ኪዳን ለእንስሳት ሳይቀር ሰላምን ይጨምራል
ቀስትን፣ ሰይፍን፣ እና ከምድሪቱ ጦርነትን አስወግዳለሁ፣ እናንተም በደህንነት እንድታርፉ አደርጋለሁ
ያህዌ የእስራኤልን ጠላቶች ከዙሪያቸው ያርቃል፣ ከዚህ በኋላ ጦርነት አይኖርም፣ ህዝቡ በሰላም ይጠበቃል። እዚህ ስፍራ "ቅስት፣ ሰይፍ፣ እና ጦርነት" የሚሉት ቃላት ሁሉም ጦርነት የሚለውን ቃል ይገልጻሉ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በደህንነት እንዲያርፉ
ይህ አገላለጽ በደህንነት መኖርን ያመለክታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 2:19
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ምን እንደሚያደርግ ለሆሴ እየተናገረ ነው
ለዘለዓለም ባልሽ ልሆን ቃል ኪዳን አገባልሻለሁ
ያህዌ ልክ እንደ ባል ይሆናል፣ እስራኤል እንደ ያህዌ ሚስት ትሆናለች። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)
በጽድቅ፣ በፍትህ፣ ለቃልኪዳን ታማኝ በመሆን፣ እና በምህረት
ይህ ረቂቅ ስሞችን ለማስቀረት እንደገና ሊጻፍ ይችላል። "ትክክል፣ፍትህ ያለበት፣ ታማኝ እና ምህረት የሞላበትን ነገር አድርጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
አንቺም ያህዌን ታውቂያለሽ
እዚህ ስፍራ "ማወቅ" የሚለው እንደ አምላካቸው ለያህዌ እውቅና መስጠትንና ለእርሱ ታማኝ መሆንን ነው።
Hosea 2:21
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ምን እንደሚያደርግ ለሆሴ እየተናገረ ነው።
ይህ የያህዌ አዋጅ ነው/ ያህዌ የተናገረው ይህ ነው
ያህዌ የአዋጁን እርግጠኝነት ለመግለጽ ስለ እራሱ በስሙ ተናገረ። ይህንን በሆሴዕ 2፡13 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "ያህዌ ያወጀው/የተናገረው ይህ ነው" ወይም "እኔ ያህዌ ያወጅኩት/የተናገርኩት ይህ ነው። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ምድር ለእህል፣ አዲስ ወይን፣ እና ለወይራ ዘይት ምላሽ ይሰጣል፤ እነርሱም ለኢይዝራኤል ምላሽ ይሰጣሉ።
ምድር ለእህል፣ አዲስ ወይን፣ እና ለወይራ ዘይት የሚያስፈልገውን ትሰጣለች። እነዚህ ነገሮች ደግሞ የኢዝራኤልን ፍላጎቶች ያሟላሉ። ምድሪቱ እና እነዚህ ምርቶች የሌሎችን ፍላጎት ማሟላት እንደሚችሉ ሰዎች ሆነው ተገልጸዋል። (ሰውኛ የሚለውን ዘይቤ ይመልከቱ)
ኢዝራኤል
እዚህ ስፍራ የዚህ ሸለቆ ስም መላውን የእስራኤል ህዝብ ይወክላል። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 2:23
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለእስራኤል ምን እንደሚያደርግ ለሆሴ እየተናገረ ነው። ለእኔ ለራሴ በምድሪቱ እተክላታለሁ እግዚአብሔር ዳግም ህዝቡን በምድራቸው ደህንነት እና ብልጽግና ሲሰጣቸው፣ እነርሱ የተገለጹት በእርሻ ሰብል ነው። "ገበሬ ሰብሉን ዘርቶ እንደሚንከባከብ እስራኤልን እንከባከባለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)
ሎ-ሩሃማ
የዚህ ስም ትርጉም "አልምርም" ማለት ነው። ተርጓሚው ይህንን ትርጉም እንደ ስም አድርጎ ማቅረብን ሊመርጥ ይችላል። ይህንን ስም በሆሴዕ 1፡6 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። "አልምርም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ሎ-ዓሚ
የዚህ ስም ትርጉም " ህዝቤ አይደላችሁም" ማለት ነው። ተርጓሚው ይህንን ትርጉም እንደ ስም አድርጎ ማቅረብን ሊመርጥ ይችላል። ይህንን ስም በሆሴዕ 1፡9 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።"ህዝቤ አይደላችሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ዓሚ አታህ
የዚህ ስም ትርጉም "እናንተ የእኔ ህዝብ ናችሁ" ማለት ነው። ተርጓሚው ይህንን ትርጉም እንደ ስም አድርጎ ማቅረብን ሊመርጥ ይችላል። "እናንተ የእኔ ህዝብ ናችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 3
Hosea 3:1
ደግም ሂድ፣ በባሏ የተወደደችን ነገር ግን አመንዝራ የሆነችን ሴት ውደድ
ይህ ተመልሶ በሆሴዕ 1፡2 ያለውን ነገር ያመለክታል። ያህዌ ዳግም ሆሴዕን አመንዝራ ሴትን እንዲወድ ይነግረዋል።
እኔ ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ እንደምወደው ልክ እንደዚያው አመንዝረይቱን ሴት ውደዳት
አመንዝራዋን ሴት በመውደድ፣ ሆሴዕ ያህዌ ለእስራኤል ላለው ፍቅር ምሳሌ ይሆናል። (ትዕምርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ወደሌሎች አማልዕክት ዞር ቢሉ እና የዘቢብ ጥፍጥፍ ቢወዱም
ህዝቡ ሀሰተኛ አማልዕክት በሚያመልኩበት በኣላት ወቅት የዘቢብ ወይም በለስ ጥፍጥፍ ይመገባሉ
አስራ አምስት ሰቅል ጥሬ ብር/ አስራ አምስት የብር ቁርጥራጮች/ እና አንድ ቆሮስ/ጋሎን ተኩል መስፈሪያ ገብስ
ይህ አንድ ባሪያ የመግዣ ዋጋ ነበር።
አስራ አምስት ቁርጥራጭ
"15 ቁርጥራጭ" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
እና አንድ ቆሮስ/ጋሎን ተኩል መስፈሪያ ገብስ
ይህ ወደ ዘመናዊ መለኪያ ሊለወጥ ይችላል። ወደ "330 ሊትር ገብስ" (መጽሀፍ ቅዱሳዊ የመጠን መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 3:4
የእስራኤል ህዝብ ያለ ንጉሥ፣ ያለ ልዑል፣ ያለ መስዋዕት፣ ያለ ድንጋይ አምድ፣ ያለ ኤፉድ ወይም ያለ ነፍስ ወከፍ ጣኦታት ለአያሌ ዘመናት ይኖራል
በማመንዘሯ ምክንያት ሆሴዕ ያለ ሚስቱ እንደሚኖር ሁሉ፣ አመንዝራለችና እስራኤል ያለ ንጉሥ እና እግዚአብሔርን ሳታመልክ ትኖራለች።
አምላካቸውን ያህዌን ፈለጉ
እዚህ ስፍረ "ፈለጉ" ማለት እግዚአብሔር እነርሱን እና አምልኳቸውን እንዲቀበል ጠየቁት ማለት ነው
ንጉሣቸው ዳዊት
እዚህ ስፍራ "ዳዊት" የሚወከለው የዳዊትን ትውልዶች ነው። "የዳዊት ዘር ንጉሣቸው እንዲሆን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)
በመጨረሻው ቀናት
"በመጪው ዘመን"
እየፈሩ እና እየተንቀጠቀጡ በያህዌ እና በእርሱ መልካምነት ፊት ይቀርባሉ
እዚህ ስፍራ "መንቀጥቀጥ" የሚለው የሚገልጸው የአክብሮትን እና ትህትናን ስሜት ነው። "ወደ ያህዌ ይመለሳሉ፣ ራሳቸውን በፊቱ ያዋርዳሉ፣ እርሱን ያከብራሉ፣ የእርሱን በረከቶችም ይለምናሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)

---

Chapter 4
Hosea 4:1
አጠቃላይ መረጃ
ይህ ምዕራፍ ታማኝ ባልሆኑት እስራኤላዊያን ላይ የያህዌን ክርክር በማቅረብ ይጀምራል
ያህዌ ከምድሪቱ ነዋሪዎች ጋር ሙግት አለው
ያህዌ የእስራኤል ህዝብ እንደበደለው እና ቃል ኪዳኑን እንዳፈረሰ ይናገራል፤ ያህዌ

ይህን የሚናገረው በፍርድ ቤት እንደሚከሳቸው አድርጎ ነው።
መግት
ይህ በህግ አደባባይ አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ የሚያቀርበው ክርክር ነው። ይህንን በሆሴዕ 2፤2 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።
ህዝቡ ሁሉንም ወሰኖች ጥሰዋል
እዚህ ስፍራ "ወሰኖች" የሚለው የሚገልጸው ህጉ የሚፈቅደውን መጠን ነው። "ህዝቡ በሁሉም መንገድ ህጉን አልታዘዘም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋር የሚለውን ይመልከቱ)
በደም ማፍሰስ ላይ ደም ማፍሰስ ይጨምራል
እዚህ ስፍራ "ደም ማፍሰስ" የሚለው የሚገልጸው "ግድያን" ነው፤ ይህም ብዙውን ጊዜ የተጠቂውን ደም መፍሰስ ይጨምራል። "በግድያ ላይ ግድያ ጨመራችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት)
Hosea 4:3
ስለዚህም ምድሪቱ ድርቅ እየመታት ነው
ይህ አገላለጽ ለረጅም ጊዜ ዝናብ የታጣበትን የድርቅ ጊዜ ያመለክታል።
እየኮሰመኑ መሄድ
ከህመም እና ምግብ ከማጣት የተነሳ ደካማ እየሆኑ እና እየሞቱ መሄድ
ይወሰዱ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እየሞቱ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 4:4
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው
መግት
ይህ በህግ አደባባይ አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ የሚያቀርበው ክርክር ነው።
ማንም ሌላውን አይክሰስ
ማንም ሰው ሌላውን ሰው በማናቸውም ነገር መክሰስ የለበትም፤ ምክንያቱም እያንነዱ ሰው በአንድ ነገር ጥፋተኛ ነውና።
ካህናቶቻችሁ ይደነቃቀፋሉ
እዚህ ስፍራ "መደናቀፍ" የሚለው እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ወይም እርሱን መታመን ማቆምን ጭምር ያመለክታል።
Hosea 4:6
አጠቃላይ መረጃ
በምዕራፍ 4፡6 ያህዌ ስለ እስራኤል ህዝብ ለካህናቱ ይናገራል። በምዕራፍ 4፡7 ስለ ካህናቱ እርሱ ይናገራል እንጂ ለእነርሱ አይናገርም። ተርጓሚው የዩዲቢን ምሳሌነትን ሊከተል ይችላል፤ ይህም ያህዌን፣ ለካህናቱ ሲናገር በምዕራፍ 4፡7 እንደሚገልጸው አይነት ነው።
ህዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቷል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ህዝቤ ጠፍቷል ምክንያቱም እናንተ፣ ካህናቱ፣ ይታዘዙኝ ዘንድ ስለ እኔ በሚገባ አላስተማራችኋቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ዕውቀት
እዚህ ስፍራ "ዕውቀት" የሚለው የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን እውቀት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ክብራቸውን በውርደት ለወጡ
አማራጭ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት1) "ክብር" ያህዌን የሚወክል ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። "ሀፍረት" ጣኦታትን የሚወክል ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። " ታላቁን አምላካቸውን እኔን ማምለክ ትተዋለ፣ አሁን አሳፋሪ ጣኦታቶቻቸውን ያመልካሉ" 2) አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን የሚተረጉሙት "ክብራቸውን በውርደት እለውጣለሁ" በሚል ነው። ይህ ማለት ያህዌ ካህናቱ የሚያከሯቸውን ነገሮች ይወስድባቸዋል ደግሞም ካህናቱ እንዲያፍሩ ያደርጋል። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 4:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ ስለ ካህናቱ መናገሩን ቀጠለ
በህዝቤ ሀጢአት እነርሱ ይባላሉ
ህዝቡ ሲበድል፣ እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸው መስዋዕት ያቀርባሉ። ካህናቱ እነዚህን መስዋዕቶች መብላት ይፈቀድላቸው ነበር። የካህናቱ ለኃጢአት የቀረበውን መስዋዕት መብላታቸው የህዝቡን ኃጢአት እንደተመገቡ ተደርጎ ይነገራል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀትና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እንዲሁም ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ክፋታቸውን እጅግ ይጨምራሉ
ካህናቱ ህዝቡ በጢአቱ እየከፋ እንዲሄድ ይፈልጋሉ፤ ይህም እነርሱ የሚበሉትን ህዝቡ የሚያቀርበው መስዋዕት እንዲጨምር ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀትና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ)
በካህናቱ ላይ እንደሚሆነው እንደዚያው በህዝቡ ላይ ይሆናል
"ህዝቡና ካህናቱ በተመሳሳይ መንገድ ይቀጣሉ"
ልምምዶቻቸው
"ልምዶቻቸው" ወይም "የእነርሱ ባህርይ"
Hosea 4:10
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው
ነገር ግን አይበዙም
"ልጆች አይወልዱም"
ርቀው ሄደዋል
ህዝቡ እግዚአብሔርን ማምለክ እና መከተል አቁመዋል።
ከያህዌ
ያህዌ ስለ እራሱ በሶስተኛ መደብ እየተናገረ ነው። ይህ በአንደኛ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "ከእኔ" በሚል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 4:11
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው ሴሰኝነት፣ አሮጌ ወይን ጠጅ፣ እና አዲስ ወይን ጠጅ ማስተዋላቸውን ወስደውባቸዋል የእስራኤል ሰዎች ከጋብቻ ውጭ ይሴስናሉ፤ ደግሞም ብዙ የወይን ጠጅ ይጠጣሉ። እነዚህን ነገሮች በማድረግ የያህዌን ትዕዛዛት ረሱ። እዚህ ስፍራ እነዚህ ድርጊቶች የተነገሩት ሌሎች ሰዎች ያህዌን የመታዘዛቸውን ጠቀሜታ እንዳይረዱ እንደሚከላከሉ ሰዎች ተደርገው ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ዘንጎቻቸው ትንቢት ለመናገር ምሪት ሆናቸው
ጣኦት አምላኪዎች የወደፊቱን ለመተንበይ ዘንጎችን ይጠቀማሉ። እዚህ ስፍራ ዘንጎች የተነገሩት ትንቢትን እንደሚናገሩ ሰዎች ተደርገው ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሴሰኛ አስተሳሰብ አሳታቸው
ጣኦታትን ማምለክ እና ከቤተ ጣኦት አመንዝሮች ጋር መዘሞታቸው የእስራኤል ሰዎች በእነዚህ መንገዶች ሁሌም በያህዌ ላይ በደል እንዲፈጽሙ ፍላጎት አሳደረባቸው። እዚህ ስፍራ "አስተሳሰብ/አዕምሮ" የተነገረው ህዝቡ ያህዌን እንዳይታዘዝ ማሳመን እንደሚችል አንድ ሰው ተደርገው ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አሳቷቸው
ህዝቡ እንዲበድል አሳመኑ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 4:13
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው
በተራሮች አናት... በኮረብቶች
ህዝቡ ጣኦታታትን በእነዚህ ስፍራዎች ማኖሩ የተለመደ ነበር፣ በብሉይ ኪዳን እነዚህ ስፍራዎች ብዙውን ጊዜ "ከፍተኛ ስፍራዎች" ተብለው ይጠሩ ነበር።
የተቀደሱ ዝሙት አዳሪዎች
እነዚህ ሴቶች ጣኦታቱን ለማምለክ የሚመጡ ወንዶች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት የሚፈጽሙ ነበሩ። ይህ ድርጊት ለሀሰተኛ አማልክቶቻቸው ክብር የሚፈጸም የተቀደሰ ድርጊት ተደርጎ ይታይ ነበር።
ስለዚህ ይህ የማያስተውል ህዝብ ወደ ጥፋት ይሄዳል
ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ ያጠፋል ምክንያቱም እነርሱ አያስተውሉም ወይም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት አይጠብቁም። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 4:15

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ስለ ይሁዳ እና ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

ይሁዳ አይበድል

እግዚአብሔር እስራኤል ምን ያህል በደለኛ እንደሆነች ስላየ ይሁዳ ተመሳሳይ ነገር እንዲፈጽም አልፈለገም

ወደ ጌልገላ አትሂዱ፣ እናንተ ሰዎች ሆይ፣ ወደ ቤትአዌንም አትውጡ

የይሁዳ ህዝብ በእነዚያ ስፍራዎች ጣኦት ለማምለክ ወደ ጌልገላ ወይም ወደ ቤትአዌን ከተሞች እንዳይሄድ ማስጠንቀቂያ ተሰጠው። ጌልገላ በአንድ ወቅት ያህዌ የሚመለክበት ስፍራ ነበር፣ ነገር ግን የጣኦት ማምለኪያ ስፍራ ሆነ።

ቤትአዌን

ይህ ከተማ በእስራኤል ሰሜናዊ ግዛት እና በደቡባዊ ግዛት በቢንያም ነገድ ድንበር መሃል የሚገኝ ነበር። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እልኸኛ ጊደር

እስራኤል ጌታዋን ከማትታዘዝ ትንሽ ላምጋር ተነጻጽራለች። (ተነጻጻሪ ዘይቤ/ሲሚሊ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ እነርሱን እንዴት በለመለመ መስክ እንደሚገኙ ጠቦቶች ያሰማራቸዋል?

ያህዌ ጥያቄውን የተጠቀመበት ህዝቡን መንከባከብ መቀጠል እደማይችል በትኩረት ለመናገር ነው፤ ምክንያቱም ህዝቡ እልከኛ ነው። ያህዌ ከእንግዲህ ህዝቡን አይንከባከበውም የሚለው የተገለጸው ከእልከኝነታቸው የተነሳ እርሱ በጎቹን ከእንግዲህ ይሰማሩ ዘንድ ወደ መስክ እንደማይወስድ እረኛ ተደርጎ ነው። "ያህዌ የሚያምጽን ህዝብ አያሰማራም" ወይም "ስለዚህም ያህዌ እነርሱን መንከባከቡን አይቀጥልም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያው አነጋገር ወይም ቃለ ምልልሳዊ/ሬቶሪካል ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)

ያህዌ እንዴት

እዚህ ስፍራ ያህዌ በሶስተኛ መደብ ስለ እራሱ እየተናገረ ነው። ይህ በአንደኛ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "እኔ እንዴት" በሚል። (አንደኛ፣ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመለከቱ)

Hosea 4:17

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

ኤፍሬም ከጣኦት ጋር ተጣምሯል፤ እርሱን ተዉት

እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" መላውን ሰሜናዊ የእስራኤል ግዛት ይወክላል። ይህ አገላለጽ በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን የሚገልጽ ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። ያህዌን ከማምለክ ይልቅ ጣኦታትን ማምለክ መረጡ። ያህዌ ሆሴዕን ህዝቡን ከመንገዱ ይመለስ ዘንድ ለመገሰጽ እንዳይሞክር አዘዘው። የእስራኤል ህዝብ አይሰማም። (ስኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ እና ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ዘይቤዎች ይመልከቱ)

መሪዎቿ ሀፍረታቸውን እጅግ ወደዱ

መሪዎቿ ጣኦታትን ሲያመልኩ እና በያህዌ ላይ ፊታቸውን ሲያዞሩ በሚያደርጉት አያፍሩም ነበር

ነፋስ በክንፎቹ ጠቅልሎ ይወስዳታል

እዚህ ስፍራ "ነፋስ" የሚለው የሚወክለው በእስራኤል መንግሥት ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ እና ቁጣ ነው። ያህዌ የጠላት ሰራዊት የእስራኤልን ህዝብ እንዲያሸንፍ እና ምርኮ አድርጎ እንዲውዳቸው ይፈቅዳል። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሚቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ዘይቤያዊ አነጋገሮች ይመልከቱ)

---

Chapter 5

Hosea 5:1

አያያዥ ሃሳብ

ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

በምጽጳ መጥመድ፣ በታቦርም ላይ የተዘረጋ መረብ ሆናችኋል

ወጥመድ እና መረብ ሁለትም ነገሮች ታዳኝን ማጥጃ ናቸው። በዚህ ሁኔታ፣ ካህናቱ እና የንጉሥ ቤት ህዝቡን ወደ ጣኦት አምልኮ ሲያማልሉ ከያህዌ ሊያርቋቸው መንገዶችን አበጅተዋል። ምጽጳ እና ታቦር በእስራኤል ምድር ጣኦታት ማምለኪያ ስፍራዎች ነበሩ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

አመፀኞች ለግድያ በርትተዋል

እዚህ ስፍራ "አመፀኞች" የሚለው የሚያመለክተው ከያህዌ ርቆ የሸሸውን ህዝብ ነው፤ "ለግድያ በርትተዋል" የሚለው ንጹሃን ሰዎችን መግደልን ወይም ለአህዛብ ጣኦታት የሚቀርቡ እንስሳትን ማረድን ሊያመለክት ይችላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አመፀኞች

ተርጓሚው ይህንን "እናንተ አመፀኞች፣" ብሎ ሊተካው ይችላል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በትክክል ለአመፀኞች የእስራኤል ሰዎች እየተናገረ ነው።

በማረድ

አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች የዕብራይስጡን አገላለጽ ክፋትን እንደሚገልጽ አድርገው ይተረጉሙታል

እኔ ሁሉንም እቀጣለሁ

ተርጓሚው ይህንን "እኔ ሁላችሁንም እቀጣለሁ" ብሎ ሊተካው ይችላል።

Hosea 5:3

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

ኤፍሬምን አውቃለሁ፣ እስራኤልም ከእኔ የተሰወረ አይደለም

እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" እና "እስራኤል" ሁለቱም መላውን ሰሜን የእስራኤል መንግሥት እና በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታሉ። እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር እነርሱ ምን አይነት እንደሆኑ እና ምን እያደረጉ እንደሆነ ሁሉን አውቃለሁ ይላል። (ስኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ ሚቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠትእና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ኤፍሬም፣ አሁን አንተ እንደ አመንዝራ ሆነሃል

ኤፍሬም እንደ አመንዝራ ቀርቧል፣ ምክንያቱም አምንዝራ ሴት ለማንም ወንድ ታማኝ እንደማትሆን ህዝቡ ለእግዚአብሔር የማይታመን ሆኗል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘማዊ አስተሳሰብ በውስጣቸው ስላል

ይህ ማለት ለእግዚአብሔር ታማኝ ያለመሆን ፍላጎት አላቸው። ጣኦታትን ማምለክ ይፈልጋሉ።

ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ... ያህዌን አያውቁም

ተርጓሚው ይህንን "ወደ እኔ ለመመለስ... እኔን አያውቁም፣" ወይም "ወደ እኔ ለመመለስ... እኔን፣ ያህዌን አያውቁም " በሚል መተካት ይችላል።

ያህዌን አያውቁም

ከእንግዲህ እስራኤል በማናቸውም መንገድ ያህዌን አይታዘዝም። አምላካቸው አድርገው ለያህዌ እውቅና አይሰጡም።

Hosea 5:5

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

የእስራኤል ኩራት በራሱ ላይ ይመሰክርበታል

ይህ "ኩራትን" በእስራኤል ህዝብ ላይ በፍርድ ቤት በተቃውሞ እንደሚመሰክር አንድ ሰው አድርጎ ይገልጸዋል። በኩራት የተሞላው ዝንባሌያቸው እና ባህሪያቸው ያህዌን መታዘዝን አሻፈረኝ በማለተቸው ጥፋተኞች መሆናቸውን ያሳያል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ) ስለዚህ እስራኤል እና ኤፍሬም በጥፋታቸው ይሰናከላሉ፤ ይሁዳም ደግሞ አብሯቸው ይሰናከላል ከኩራታቸው እና ከበደላቸው የተነሳ ሁለቱ መንግሥታት ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሔርን የማይታዘዙ ይሆናሉ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ለያህዌ ታማኞች አልነበሩም፣ ህጋዊ ያልሆኑ ልጆችን ወልደዋልና

አማራጭ ትረጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት 1) ይህ ማለት እስራኤላዊያን ከሌሎች ህዝቦች ጋር ተጋብተው ነበር፤ ከእነርሱም ልጆች ወልደው ነበር ወይም 2) ይህ ማለት እስራኤላዊ ወላጆች ለያህዌ ታማኞች አልነበሩም ደግሞም ልጆቻቸው ጣኦታትን እንዲያመልኩ ያስተምሯቸው ነበር

የአዲስ ጨረቃ በዓላቸው፣ ከእርሻቸው ጋር እነርሱንም አብሮ ያጠፋቸዋል

የእስራኤል ህዝብ በአዲስ ጨረቃ በዓል ማክበር ይጠበቅባቸው ነበር። በዚህ ስፍራ ይህ አገላለጽ የአዲስ ጨረቃ በዓል፣ ህዝቡን እና እርሻቸውን እንደሚበላ አውሬ የሚገልጸው ይመላል። የሆነ ሆኖ፣ ይህንን አገላለጽ መተረጎም ከባድ ነው፣ ብዙ ትርጎሞች የሚተረጎሙት እንዲህ አይነቱን ስሜት ሳይረዱት ነው። ሆኖም፣



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አጠቃላይ ትረጉሙ፤ ለእርሱ ታማኝ ባለመሆኑ እግዚአብሔር ህዝቡን ይቀጣዋል የሚል መሆኑ እርግጥ ነው። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 5:8

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው በጊብዓ የቀንደ መለከትን ድምጽ፣ በራማ እንቢልታን ንፉ እዚህ ስፍራ "ቀንደ መለከት" እና "እንቢልታ" ማለት ተመሳሳይ ማለት ነገር ነው። ይህ ትዕዛዝ ለጊብዓ እና ራማ ሰዎች የተሰጠው ጠላት እየመጣ እንደሆነ ለማሳወቅ ነው። (ጥንድ ትረጉም/ደብሌት የሚለውን ይመልከቱ)

በቤትአዌን የለቅሶ ድምጽ አሰሙ፡ "ብንያም ሆይ፣ እኛ እንከተልሃለን!" በሉ

እዚህ ስፍራ "ብንያም" የሚለው የሚወክለው ከብንያም ወገን የሆኑ ወታደሮችን ነው።ይህ ምናልባት ህዝቡን ወደ ጦርነት ለመምራት ለእርሱ የቀረበ ጥያቄ ይሆናል። ነገር ግን ዘመናዊ ትረጉሞች ይህንን አገላለጽ ለመተረጎም የተለያዩ ሙከራዎችን አድረገዋል። (ስኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤትአዌን

ይህ ከተማ በእስራኤል ሰሜናዊ ግዛት እና በደቡባዊ ግዛት በቢንያም ነገድ ድንበር መሃል የሚገኝ ነበር። ይህንን በሆሴዕ 4፤15 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በእስራኤል ነገዶች መሃል በእርግጥ የሚሆነውን አውጃለሁ/ተናግሬያለሁ

"እኔ ያወጅኩትን/የተናገርኩትን ለእስራኤል ነገዶች አደርገዋለሁ"

Hosea 5:10

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ስለ ይሁዳ እና እስራኤል እየተናገረ ነው።

የይሁዳ መሪዎች የድንበር ምልክት የሆነ ድንጋይን እንደሚያነሱ ናቸው

"የድንበር ድንጋይ ማንሳት" የሚለው የሚያመለክተው የአንድ ሰው ድንበር የሆነን በመሬት ላይ የሚገኝ ምልክትን ማንቀሳቀስን ነው፤ ይህ በእስራኤል ህግ ወንጀል ነበር። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣዬን በእነርሱ ላይ እንደ ውሃ አዘንባለሁ

በይሁዳ ላይ የያህዌ ቁጣ እንደሚያጠፋቸው ትልቅ ወራጅ ውሃ ይሆናል። በቅዱሳት መጽሐፍት፣ ስሜቶች እና የስነምግባር ደረጃዎች ብዙውን ጊዜ እንደ ፈሳሽ ሆነው ይገለጻሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኤፍሬም የደቀቀ ነው፣ እርሱ በፍርድ የደቀቀ ነው

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ይህ ሃሳብ ትኩረት እንዲያገኝ ሁለት ጊዜ ተደጋግሞ ተጽፏል። እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" የሚለው የእስራኤልን ሰሜናዊ ግዛት ህዝብ ያመለክታል። "እኔ የእስራኤልን ህዝብ ክፉኛ እቀጣለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ፣ (ሲኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ))

ጣኦታትን ተከትለዋል

እዚህ ስፍራ "ተከትለዋል" የሚለው የሚያመለክተው አምልኮን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጣኦታት

እዚህ ስፍራ "ጣኦታት" ተብሎ በተተረጎመው የዕብራይስጡ ቃል ትረጉሙ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፤ በዘመናዊ ትረጉሞች ውስጥ በተለያዩ ብዙ መንገዶች ተተርጉሟል።

Hosea 5:12

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ስለ ይሁዳ እና እስራኤል እየተናገረ ነው።

ለኤፍሬም እንደ ብል፣ ለይሁዳ ቤት እንደ ነቀዝ እሆናለሁ

ብል በቁራጭ ሱፍ ላይ ነቀዝ በቁራጭ እንጨት ላይ ሁለቱም አጥፊዎች ናቸው። ያህዌ ሁለቱንም መንግሥታት ያጠፋል (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብል...ነቀዝ

እነዚህ ሁለት ቃላት በተለያየ መንገድ ይተረጎማሉ ምክንያቱም የዕብራይስጡ ቃል ትርጉም አንድም በጣም ሰፊ ነው ወይም በእርግጠኝነት ለመተረጎም ያዳግታል።

ኤፍሬም ህመሙን፣ ይሁዳም ቁስሉን አየ

ኤፍሬም (የሰሜን እስራኤል መንግሥት) እና ይሁዳ (የደቡብ እስራኤል መንግሥት) ሁለቱም በአደጋ ውስጥ እንደሆኑ አውቀዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለሰውን ይመልከቱ)

ከዚያም ኤፍሬም ወደ አሦር ሄደ፣ ይሁዳም ወደ ታላቁ ንጉሥ መልዕክተኛ ላከ

ኤፍሬም እና ይሁዳ ያህዌን እርዳታ ከመለመን ይልቅ አሦርን እርዳታ ለመኑ። "ታላቅ ንጉሥ" ለአሦር ነገሥታት ማዕረግ ነበር።

እርሱ ግን አልቻለም

እዚህ ስፍራ "እርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የአሦርን ንጉሥ ነው

Hosea 5:14

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ስለ ይሁዳ እና እስራኤል እየተናገረ ነው።

ስለዚህ ለኤፍሬም ልክ እንደ አንበሳ እሆናለሁ

ያህዌ ኤፍሬምን ሊከታተል እና እንደ አንበሳ ሊያጠቃው ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በይሁዳ ቤት ላይ እንደ ደቦል አንበሳ

ያህዌ ይሁዳንም በተመሳሳይ መንገድ ሊያየው ነው። ያህዌ በሰሜኑም በደቡቡም መንግስታት አለመደሰት እያሳየ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ፣ እኔ ራሴ

ያህዌ በህዝቡ ላይ ሁሉ ፍርድ የሚያመጣው እርሱ መሆኑን እያጎላ ነው

እበታተናለሁ

አንበሳ የሚበላውን እንስሳ እንደሚበታተትን፣ ያህዌ ህዝቡን ከቤታቸውና ከአገራቸው ይበታትናቸዋል

እሄዳለሁ ደግሞም ወደ ስፍራዬ እመለሳለሁ

ያህዌ አመጸኛ ህዝቡን ይተወዋል

ፊቴን ይሻሉ

በአምልኮ እና መስዋዕት በማቅረብ ወደ እግዚአብሔር መገኘት ለመምጣት ሞክሩ። "ለእነርሱ ትኩረት እንድሰጥ ይጠይቁኛል" (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከተ)

---

Chapter 6

Hosea 6:1

አያያዥ ሃሳብ

የእስራኤል ህዝብ ለመመለስ ፍላጎታቸውን ተናገሩ

እርሱ ሰባብሮናል ... እርሱ አቁስሎናል

እግዚአብሔር የእስራኤልን ህዝብ የቀጣው እርሱን ስላልታዘዙ እና ጣኦታትን ስለመለኩ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይፈውሰናል... እርሱ ቁስላችንን ይጠግናል

እስራኤል እነርሱ ሲመለሱ እግዚአብሔር ምህረት እንደሚያበዛላቸው እና ከችግራቸው ነጻ እንደሚያወጣቸው ታምናለች። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከሁለት ቀናት በኋላ ያነቃናል፡ በሶስተኛው ቀን ያስነሳናል

ይህ የሚወክለው አጭር ጊዜን ነው። እስራኤል ከጠላቶቻቸው ሊያድናቸው እግዚአብሔር በቶሎ እንደሚመጣ ያምናሉ። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለት ቀናት ... በሶስተኛው ቀን

"2 ቀናት ... 3ተኛ ቀን" (ቁጥሮች እና ተከታታይ ቁጥሮች የሚሉትም ይመልከቱ)

ያህዌን እንወቅ

እዚህ ስፍራ "ማወቅ" ማለት የእግዚአብሔርን ባህሪ እና ህጎች ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ለስርሱ ታማኝ መሆንንም ይጨምራል።

የእርሱ መምጣት እንደ ንጋት የተረጋገጠ ነው

ፀሐይ በየማለዳው መውጣቷ እርግጥ የሆነውን ያህል ያህዌ ህዝቡን ለመርዳት ይመጣል።

Hosea 6:4

አያያዥ ሃሳብ

ያህዌ እየተናገረ ነው

እናንተን ምን ላድርግ?

እግዚአብሔር ትዕግቱ እያለቀ መሆኑን እና የቀረው ፍርድ ብቻ እንደሆነ እየተናገረ ነው። " በእናንተ ላይ ምን እንደሚደረግ ማወቅ አስቸጋሪ ነው!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም በነቢያቱ ቆራረጥኳቸው

ያህዌ በነቢያቱ አማካይነት፣ አመጸኛ በሆነው ህዝብ ላይ ጥፋትን አወጀ። እዚህ ስፍራ "ወደ ቁርጥራጭ መቆራረጥ" በሚል የተጠቀሰው ጥፋት እንደ ፍርዱ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የተረጋገጠ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ድንጋጌዎችህ እንደ ብርሃናት ናቸው
እዚህ ስፍራ ነቢዩ ሆሴዕ ለእግዚአብሔር እየተናገረ ነው። እግዚአብሔር በአንድ ሰው ላይ የሞትን ትዕዛዝ ቅጣት አድርጎ ሲሰጥ እንደ አስደንጋጭ የሚመታ መብረቅ ይመስላል ማለቱ ሊሆን ይችላል። ወይንም ልክ ብርሃን ነገሮች እንዲታዩ እንደሚያደርግ፣ የእግዚአብሔር ትዕዛዛት ሰዎች እውነቱን እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል ማለቱ ሊሆን ይችላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ድንጋጌዎችህ
"የያህዌ ትዕዛዛት"
Hosea 6:6
አያያዥ ሃሳብ
ያህዌ እየተናገረ ነው
እኔ ታማኝነትን እፈልጋለሁ እንጂ መስዋዕትን አይደለም
ይህ ሰዋሰዋዊ አወቃቀር በዕብራይስጡ በዚህ ስፍራ "ይበልጥ" የሚለውን ያመለክታል፤ ተከታዩ መስመር እንደሚያሳየው ("እናም የእግዚአብሔር እውቀት ከሚቃጠል መሰዋዕቶች ይልቅ")። "እኔ ከመስዋዕት ይልቅ ታማኝነትን እሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
እንደ አዳም
አማራጭ ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት 1) ይህ የመጀመሪያውን ሰው አዳምን ያመለክታል ወይም 2) እስራኤል ውስጥ አዳም በምትባል ከተማ የሚኖሩ ሰዎችን የሚወክል ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመናት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። "በአዳም ከተማ ውስጥ እንደሚኖሩ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 3) ይህ በአጠቃላይ ሰዎችን ያመለክታል። "አዳም" የሚለው ቃል ትርጉሙ "ሰው" ወይም "የሰው ዘር" ማለት ነው። "እንደ ሁሉም የሰው ዘር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 6:8
አያያዥ ሃሳብ
ያህዌ እየተናገረ ነው
ገለዓድ አንድ ከተማ ናት… በደም የተበከለች
"በደም የተበከለች" ይህ ምናልባት ክፉ አድራጊዎችን እና የእነርሱን የግድያ ተግባር የሚወክል ይሆል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ካህናቱ በሴኬም መንገድ ለግድያ በአንድነት ተሰበሰቡ
ይህ ምንን እንደሚያመለክት አናውቅም። ካህናቱ በእርግጥ የሃይማኖት እና ፖለቲካ ዋንኛ መአከል ወደ ሴኬም በሚሄዱበት ወቅት መንገድ ላይ ሰዎችን በማጥቃት ጥፋተኞች ነበሩ? ወይስ ነቢዩ ካህናቱ የያህዌን እውነተኛ እውቀት እና አምልኮ "ገደሉ" እያለ ነውን? ይህንን አገላለጽ የተቻለውን ያህል ግልጽ አድርጎ መተረጎም ይመረጣል
Hosea 6:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እየተናገረ ነው
የኤፍሬም ዘማዊነት
እዚህ ስፍራ "ዘማዊነት" የሚለው የሚያመለክተው የኤፍሬምን ሃሰተኛ አማልዕክት ማምለክ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እስራኤል ረከሰች
እስራኤል በእግዚአብሔር ፊት የረከሰችው በድርጊቶቿ ምክንያት ነው
ይሁዳ ሆይ፣ ለአንተም የመከር ጊዜ ተመድቦብሃል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " ይሁዳ ሆይ፣ ለአንተ የመከር ጊዜ መድቤያለሁ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
መከር
እዚህ ስፈፍራ "መከር" የሚለው የሚወክለው በእስራኤል እና በይሁዳ ላይ እግዚአብሔርን የመጨረሻ ፍርድ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እድሎች
ብልጽግና እና ደህንነት

---

## Chapter 7

Hosea 7:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እየተናገረ ነው
እስራኤልን መፈወስ እፈልጋለሁ
ዳግም እስራኤል ለእግዚአብሔር ታማኝ እንድትሆን ማድረግ እና የእርሱ በረከት ተቀባይነት የተገለጸው እንደ ፈውስ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ማታለንን ይለማመዳሉ
ሰዎች ምርቶችን የሚሸጡት እና የሚገዙት በሃሰት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የዘራፊ ቡድን
ይህ ያለምክንያት ሌሎች ሰዎችን የሚያጠቃ ቡድን ነው
ድርጊታቸው ከቧቸዋል
እዚህ ስፍራ የሰዎቹ ክፉ ስራዎች የተነገሩት ምናልባት በወንጀላቸው ሊከሷቸው የተዘጋጁ ሌሎች ሰዎች እንደሆኑ ተደርገው ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ በፊቴ ናቸው
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የተገለጸው፣ መገኘቱን እና ህልውናውን በሚያጎላው በእርሱ "ፊት" ነው። "ደግሞም እኔ ሁሉንም አያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/ ዘይቤያዊ አነጋገር- የአንደን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 7:3
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እየተናገረ ነው
ንጉሡን በክፋታቸው
የዕብራይስጡ ጽሁፍ በተለያዩ ስፍራዎች ግልጽ አይደለም። ሆኖም፣ ብዙዎች ይህንን የተረጎሙት የንጉሡ መኳንንት ለእግዚአብሔር ታማኝ እንዳልሆኑ በመግለጽ እና እንደዚሁም ንጉሡን ለመግደል እንዳቀዱ፣ ከዚያም በመቀጠል እቅዳቸውን እንደፈጸሙ ነው። ይህ ከአንድ ጊዜ በላይ የሆነ ይመስላል። እነዚህ ወንጀሎች የተገለጹት አገሪቱ እንደ ሰጠመችበት ክፋት መገለጫ ተደርገው ነው።
እነርሱ ሁሉም ዘማዊያን ናቸው
ጣኦታትን በማምለክ እና ለያህዌ ታማኝ ባለመሆን መንፈሳዊ ዘማዊነት የፈጸሙ ሰዎች። እነዚህ ሰዎች ምናልባትም ከሌሎች ሰዎች ጋር በመተኛት ለባሎቻቸው ወይም ለሚስቶቻቸው ታማኝ ያልነበሩ ናቸው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በዳቦ ጋጋሪው እንደጋለ ምድጃ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። ይህ ማለት ህዝቡ ክፉ ለማድረግ ጽኑ ፍላጎት አለው። "ዳቦ ጋጋሪ እንደሚቆሰቁሰው ምድጃ" (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የሊጡ መቡካት
ይህ ዳቦ የመድፋት ሂደት አንድ ክፍል ነው
በንጉሣችን የበዓል ቀን
ይህ ምናልባት በንጉሡ ተይዞ የሚከበር በዓል ይሆናል
እርሱ በገዛ እጆቹ አደረገ
ይህ ምናልባት ከአንድ ሰው ጋር መተባበር ወይን ማበር ማለት ሊሆን ይችላል። ንጉሡ ከመኳንንቱ ጋር ማፌዝ በሌለበት ነገሮች ወይም ሰዎች ምናልባትም በእግዚአብሔር እንኳ ሳይቀር አፌዘ ማለት ሊሆን ይችላል። (ፈሊጣው አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 7:6
አጠቃላይ መረጃ
የቤተ መንግሥት መኳንንት ሴራ ተገልጽዋል። ንጉሣቸውን ለመግደል የገፋፋቸው ቁጣቸው ነው።
ልባቸው እንደ ጋለ ምድጃ ነው
ይህ ማለት በምድጃ ላይ እንደሚነድ እሳት፣ እነዚህ ሰዎች ጠንካራ ክፉ መሻቶች አሏቸው። የሰዎቹ መሻቶች በእነርሱ "ልቦች" ተገጽዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
ቁጣቸው ጤሰ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"ጤሰ" የሚለው ቃል ትርጉሙ አንድ ነገር ካለ ነበልባል ቀስ በቀስ ነደደ ማለት ነው፡፡ "ቁጣቸው በቀስታ እና በጸጥታ እያደገ ሄደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ሚንበለበል እሳት ከፍ ብሎ ነደደ
የቁጣቸው ጥንካሬ የተገለጸው እግጅ የሚነድ እሳት እንደሆነ ተደርጎ ነው፡፡ "በጣም እየከፋ ሄደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘ፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ሁሉም እንደ ምድጃ የጋሉ ናቸው
ይህ የእነርሱን ቁጣ ከምድጃ እንደሚወጣ ሙቀት ያነጻጽረዋል፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ገዢዎቻቸውን ፈጁ
ይህ የቤተ መንግሥት መኳንንት ነገስታቶቻቸውን ገደሉ ለማለት ይመስላል፡፡
Hosea 7:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እየተናገረ ነው
ኤፍሬም ከአህዛብ ጋር ተደባለቀ
ይህ ምናልባት የሰሜን መንግሥት ነገሥታት፣ ከጥቃት ለመዳን ራሳቸውን ከሌሎች መንግስታት ጋር ለማቆራኘት ያደረጉትን ጥረት የሚያሳይ ይሆናል
ኤፍሬም ያልተገላበጠ ቂጣ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" የሚያመለክተው የእስራኤልን ሰሜናዊ መንግሥት ነው፡፡ በምድጃ ውስጥ ለበለጠ ጥንካሬ ተነባብሮ እንዳልተጋገረ ነጠላ ቂጣ፣ መንግሥቱ ደካማ ነው፡፡ "የኤፍሬም ሰዎች ማንም እንዳላገላበጠው ቂጣ ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ስኔክቲክ/ ዘይቤያዊ አነጋገር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላው ነገር መሰየም፣ እና ዘይቤያዊ አነጋገር፣ እንዲሁም አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ሽበት ወጣበት
እዚህ ስፍራ "ሽበት" የሚወከወለው የእርጅና ዘመንን ነው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን እርሱ አላወቀም
ሆኖም፣ ይህ "የእርጅና ዘመን" የሚለው የሰሜኑ መንግሥት እየደከመ መምጣቱ በግልጽ መናገሪያ መንገድ ነው፣ ምክንያቱም መንግሥቱ "ማርጀቱን" አላወቀም፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 7:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እየተናገረ ነው
የእስስራኤል ኩራት በራሱ ላይ ይመሰክርበታል
ይህ "ኩራትን" በፍርድ ቤት በእስስራኤል ህዝብ ላይ እንደሚመሰክር አንድ ሰው አድርጎ ይገልጸዋል፡፡ ይህ ማለት ኩራት የተሞላው ዝንባሌያቸው እና ባህሪያቸው ያህዌን መታዘዝ በማቆም በደለኛ እንዳደረጋቸው ያሳያል፡፡ (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወይም ደግሞ አላዩትም
የእስራኤል በያህዌ ላይ ፍላጎት ማጣት የተገለጸው ልክ እርሱ እንደጠፋ እና እነርሱም ሊፈልጉት ይሞክሩ እንዳልነበረ ነው፡፡ "ለእነርሱ ትኩረት እንዲሰጣቸው እነርሱም ሊያገኙት አይሞክሩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ሁሉ ሆኖ
እዚህ ስፍራ "ይህ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔር ባዕዳን እንዲያሸንፏቸው መፍቀዱን እና እነርሱን ደካማ እንዳደረጋቸው ነው፡፡
ኤፍሬም እንደ ርግብ ነው፣ ንቁ ያልሆነና የሚታለል
ርግብ ሞኝ ወፍ ናት ተብሎ ይታሰብ ነበር፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ግብፅ ... አሦር
እነዚህ እስራኤል እርዳታ ልትጠይቃቸው የምትችላቸው ሃያላን መንግሥታት ነበሩ
Hosea 7:12
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እየተናገረ ነው
መረቤን በላያቸው እዘረጋለሁ
ይህ ወፎች የሚጠመዱበት መንገድ ነው፡፡ ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ ከርግብ ጋር ማነጻጸሩን ቀጥሏል፡፡ እነርሱ ወደ ግብፅ ወይም አሦር ለእርዳታ ሲሄዱ፣ ያህዌ እነርሱን ይቀጣቸዋል፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ሰማይ ወፎች እነርሱን ከላይ አወርዳቸዋለሁ
ያህዌ በእስራኤል ላይ የሚፈርድበትን መንገድ በመረብ የሚያጠምዳቸው ወፎች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል፡፡ "አዳኝ ወፎችን እንደሚያጠምድ እኔ እነርሱን አጠምዳቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
አብረው ሲበሩ
ይህ አገላለጽ ወፎችን በማጥመድ የተገለጸውን ዘይቤያዊ አነጋገር አስፋፍቶ ያቀርባል፡፡
Hosea 7:14
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እየተናገረ ነው
በአልጋዎቻቸው ላይ ሆነው ያለቅሳሉ
በጣኦት አምላኪዎች ዘንድ የአምልኮ ምግብን በመከዳቸው ወይም በአልጋቸው ላይ ጋደም ብለው መመገብ የተለመደ ነገር ነበር፡፡
ከእኔ ዘወር ብለዋል
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔርን ማምለክ መተዋቸው ከእርሱ ዘወር ማለት በሚል ተነግሯል፡፡ "እነርሱ እኔን ማምለክ ትተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ምንም እንኳን እኔ ባሰለጥናቸው እና እጆቻቸውን ባጠነክርም
እግዚአብሔር እስራኤላዊያን እርሱን እንዲዋጉ እና እንዲታዘዙት ያሰለጠነበት መንገድ የተነገረው ወንዶቻቸውን ለጦርነት ያሰለጥን እንደነበር ተደርጎ ነው፤ይህ በወታደራዊ ዘይቤ የቀረበ ሊሆን ይችላል፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 7:16
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እየተናገረ ነው
እነርሱ እንደ ረገበ ቀስት ናቸው
ይህም፣ የቀስት መወርወሪያ የሌለው ቀስት ፣ ወይም በሚገባ ያልተወጠረ፡፡ (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በምላሳቸው ብልግና ምክንያት
እዚህ ስፍራ "ምላስ" የሚለው የሚያመለክተው አለቆቻቸው የሚናበሩትን ነው፡፡ "እኔን ስለተሳደቡ" ወይም "እኔን ስለተራገሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ በግብፅ ምድር ለእነርሱ መሳለቂያነት የሚውል ይሆናል
"መሳለቂያ" የሚለው ረቂቅ ስም እንደ አድራጊ ሊጻፍ ይችላል፡፡ "በግብጽ የሚኖሩ ህዝቦች በእስራኤል ላይ የሚዘብቱት እና የሚሳለቁት ለዚህ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ረቂቅ ስያሜዎች የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 8
Hosea 8:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ የሰሜኑን መንግሥት ለመውጋት ስለሚመጣው የአሦር ሰራዊት እየተናገረ ነው
ንስር በያህዌ ቤት ላይ እየመጣ ነው
ንስር፣ አዳኝ ወፍ፣ አንዳንድ ጊዜ የእስራኤልን ጠላቶች ለመወከል ያገለግላል፡፡ "ንስር ሌላን እንስሳ እንደሚያድን፣ የእስራኤል ጠላቶች ህዝቤን ለመያዝ መጥተዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋል
እዚህ ስፍራ "አፍርሰዋል" የሚለው የሚገልጸው "አልታዘዙም፣" "ጥሰዋል" የሚለውን ነው (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
አንተን ያውቃሉ
"ለአንተ ታማኝ ናቸው"
Hosea 8:4
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እየተናገረ ነው ነገር ግን የሆነው ይህ ነው፤ ተቆርጠው ሊወድቁ ይችላሉ ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡፡ "ነገር ግን ውጤቱ የሚሆነው እኔ ህዝቡን ማጥፋቴ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን

ይመልከቱ)

ጥጃችሁ ተቀባይነት አላገኘም

ሊሰጡ የሚችሉ አማራጭ ትርጓሜዎች 1) ይህ የነቢዩ ንግግር ነው። "ያህዌ የእናንትን ጥጃ አልተቀበለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። ወይም 2) ያህዌ እየተናገረ ነው። "እኔ ራሴ የእናንተን ጥጃ አልተቀበልኩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የእናንተ ጥጃ

ህዝቡ ጥጃ የሚመስል ጣኦት ያመልካል፣ ስለዚህ ያህዌ ስለአምልኳቸው ራሱን ጥጃውን እንደሆነ አድርጎ እየተናገረ ነው። "ጥጃ ጣኦታችሁን ለምታመልኩ፣ የእናንተ አምልኮ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ቁጣዬ በእነዚህ ህዝቦች ላይ እየነደደ ነው

ቁጣ ብዙውን ጊዜ እንደ እሳት ተደርጎ ይነገራል። "እኔ በዚህ ህዝብ በጣም ተቆጥቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እስከ መቼ በደለኛ ሆነው ይቀጥላሉ?

ያህዌ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው ህዝቡ ንጹህ ባለመሆኑ ቁጣውን ለመግለጽ ነው። "በዚህ ህዝብ ላይ ተቆጥቻለሁ ምክንያቱም ንጹህ ለመሆን ምንም ፍላጎት የላቸውም።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 8:6

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እየተናገረ ነው

ህዝቡ ነፋስን ይዘራል ዐውሎ ነፋስን ያጭዳል

ነፋስን መዝራት ወይም ነፋስን መትከል እርባና በሌለው ወይም አጥፊ በሆነ መንገድ መስራት ነው። ዐውሎ ነፋስን ማጨድ ከራስ ድርጊት የተነሳ በጥፋት መከራን መቀበል ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የቆመው ተክል ራስ/ዛላ የለውም

እዚህ ስፍራ "ራስ/ዛላ" የሚለው የሚያመለክተው ፍሬ የሚገኝበትን የተክሉን ክፍል ነው። ራስ/ዛላ የሌለው አገዳ ለገበሬም የሚሰው ምንም ነገር የለም። በተመሳሳይ መንገድ፣ የእስራኤ ድርጊቶች አንዳች መልካም ውጤት አያስገኝም። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ መድረስ ቢመጣም እንኳን፣ ባዕዳን ይበሉታል

ማናቸውም የእራኤል ድርጊት ጥሩ ውጤት ማምጣት ቢችል እንኳን፣ የእስራኤል ጠላቶች መጥተው ከእነርሱ ይወስዱታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 8:8

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እየተናገረ ነው

እስራኤል ተዋጠች

"ተዋጠች" ማለት መሸነፍ እና በምርኮ መወሰድ ማለት ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የእስራኤል ጠላቶች እስራኤላዊያንን ወደ ሌላ ምድር ወሰዷቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደ ዱር አህያ ብቻቸውን

ሰዎች ብዙውን ጊዜ አህያን እንደ ደደብ/ግትር ይቆጥራሉ። ይህ ማለት የእስራኤል ህዝብ ያህዌን መስማትን ይቃወማል ነገር ግን በምትኩ ለእርዳታ ወደ አሦር ህዝብ ይሄዳል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኤፍሬም ለራሱ ፍቅረኞችን ቀጠረ

ኤፍሬም ከሌሎች ህዝቦች ጋር ያለው አንድነት የተገለጸው ኤፍሬም ለዘማዊነቱ እንደከፈለቸው ተደርጎ ነው። "የእስራኤል ህዝብ ለሌሎች አገራት ይጠብቋቸው ዘንድ ለመክፈል ሞከሩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በሃያል ንጉሥ ተጽዕኖ ምክንያት

ይህም፣ የአሦር ንጉሥ፣ "ታላቁ ንጉሥ" ተብሎም ይጠራል፤ ህዝቡን ያስጨንቃልና ነው።

Hosea 8:11

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እየተናገረ ነው

ህጌን ለእነርሱ አስር ሺህ ጊዜ ልጽፍላቸው እችላለሁ፣ እነርሱ ግን

ያህዌ የይሆናል ሁኔታን እየገለጸ ነው። እዚህ ስፍራ "አስር ሺህ ጊዜ" የሚለው የቱንም ያህል ጊዜ ለህዝቡ ህጉን ቢሰጣቸውም እነርሱ ግን እርሱን ለመታዘዝ አለመፍቀዳቸውን በተጋነነ መልክ የሚገልጽ ነው። "ምንም እንኳን ህጌን በጣም ብዙ ጊዜ ብሰጣቸውም፣ እነርሱ ግን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታእና ኩሸት/ሃይፐርቦል-እጅግ የተነጋነነ አገላለጽ እና ማጠቃለያ/ጠቅላላ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

አስር ሺህ

"10,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 8:13

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እየተናገረ ነው

ወደ ግብጽ ይመለሳሉ

በኃጢአታቸው ምክንያት፣ እግዚአብሔር ህዝቡን ለግብፃዊያን እንደ ባሪያ አድርጎ ይሰዳቸዋል።

---

# Chapter 9

Hosea 9:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

ነገር ግን የእህል አውድማ እና የወይን መጭመቂያው እነርሱ አይመግባቸውም

ይህ የሚገልጸው የእህል አውድማ እና የወይን መጭመቂያው ራሳቸው ሌላውን የሚመግቡ ሰዎች እንደሆኑ ተደርጎ ነው። ይህ ማለት መከሩ የህዝቡን ፍላጎት ለማሟላት የሚበቃ የፍሬ አይሰጥም፣ የወይን መከሩም በቂ የወይን ጠጅ አይሰጥም ማለት ነው። (ሰውኛ ዘይቤ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

የእህል አውድማ

ይህ እህል ለመውቃት የሚውል ሰፊ ስፈራ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ለማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ በዓላት ማክበሪያ የሚያገለግል ስፍራም ነው። የቤተ ጣኦት ዘማዊያት ለጣኦት የሚደረገውን የመከር በዓል ለማክበር ወንዶቹን ለመርዳት ይመጣሉ።

አዲሱ ወይን አይበቃቸውም

ወይን ጠጅ ለማዘጋጀት በቂ የወይን ጭማቂ አይኖርም

Hosea 9:3

አጠቃላይ መረጃ፡

ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

የያህዌ ምድር

ይህ አገላለጽ የሚያመለክተው ያህዌ የእስራኤልን ምድር እንደ እስራኤላውያን ንብረት ሳይሆን እንደ ራሱ ንብረት ማየት መቀጠሉን ነው።

ንጹህ ያልሆነ ምግብ

ይህ እስራኤላውያን በያህዌ ዘንድ ተቀባይነት ያሳጣናል በማለት ሊመገቡት የማይፈቅዱት ምግብ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

መስዋዕታቸው እንደ ለቀስተኞች ምግብ ይሆንባቸዋል

እዚህ ስፍራ "የቀስተኞች ምግብ" የሚለው የሚያመለክተው ሰዎች በለቅሶ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ የሚመገቡትን ነው፣ ምክንያቱም በልቅሶ ላይ ሲሆኑ ስለሚረክሱ እና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ስለሚያጡ ነው። ይህ ማለት ያህዌ የህዝቡን መስዋዕት እንደ ረከሰ ይቆጥረዋል ደግሞም እነርሱንም አይቀበላቸውም። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱ ምግብ ለእነርሱ ብቻ ይሆናቸዋል፤ ወደ ያህዌ ቤት አይመጣም

የእስራኤል ህዝብ የሚመገቡት ምግብ ይኖራቸዋል፣ ነገር ግን ያህዌ ያንን በመስዋዕትነት አይቀበለውም

ወደ ያህዌ ቤት አይመጣም

ንጹህ ያልሆነው ምግብ ወደ ስፍራዎች በራሱ መሄድ እንደሚችል ተደርጎ ተነግሯል። እውነታው ግን በእርግጥ፣ ሰዎች ይዘውት ሊሄዱ ያስፈልጋል። (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 9:5

አጠቃላይ መረጃ፡

ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

በያህዌ በዓል ዕለት፣ በተወሰነው ክብረ በዓል ምን ታደርጋላችሁ?
ሆሴዕ ይህንን ጥያቄ ያነሳው ህዝቡ ክብረ በዓሉን ስለረሳ፣ ጠላቶቻቸው ስላሸንፏቸው እና በምርኮ ስለወሰዷቸው፤ በዓሉን ማክበር አለመቻላቸውን ማጉላት ስለፈለገ ነው። "ያህዌ ለእናንተ የወሰነውን ክብረ በዓል ማክበር አትችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
የተወሰነው የክብረ በዓሉ ቀን... ለያህዌ ክብረ በዓል ቀን
ሁለቱም አገላለጾች አንድ ትርጉም አላቸው (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ቢያመልጡ እንኳን
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው አሁንም የሚገልጸው የእስራኤልን ህዝብ ነው። ይህንን በሁለተኛ መደብ በመግለጽ መቀጠል ይችላሉ። "አንተ ብታመልጥ" በሚል። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ግብፅ ይሰበስባቸዋል፣ ደግሞም ሜምፎስ ይቀብራቸዋል
ግብፅ እና ሜምፎስ በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። "የግብፅ ሰራዊት ይማርካችኋል። እናንተ በዚያ ትሞታላችሁ፣ በሜምፎስ ከተማ የሚኖሩ ሰዎች ይቀብሯችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የብር ሃብታቸውን እሾህማ ቁጥቋጦ ይወርሰዋል
ቁጥቋጦ እስራኤላውያን ብራቸውን ባከማቹበት ስፍራ ይበቅላል የተባለው ቁጥቋጦ እንደ ሰብአዊ ጠላት ሆኖ ውድ ሃብታቸውን ለራሳቸው እንደወሰዱ የተገለጸበት ነው። "እሾህማ ቁጥቋጦ የብር ሃብቶቻቸውን ባከማቹበት ስፍራ ይበቅላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እሾሃማ ቁጥቋጦ ይወርሳቸዋል፣ እሾህ ድንኳኖቻቸውን ይሞላዋል
እዚህ ስፍራ "እሾሃማ ቁጥቋጦ" እና "እሾህ" የሚለው ተመሳሳይ ነገርን ይገልጻል። እሾሃማ ቁጥቋጦ እና እሾህ ማደጉ የሚወክለው ሰው የማይኖርበትን ምድር እና በረሃማነትን ነው። (ጥንድ ትረጉም እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
የእነርሱ ድንኳኖች
እዚህ ስፍራ "ድንኳኖች" የሚለው የሚወክለው የእስራኤላውያንን ቤቶች ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
Hosea 9:7
አጠቃላይ መረጃ፡
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው
የቅጣት ቀናት እየመጡ ነው፣ የፍርድ ቀናትም እየመጡ ነው
ሆሴዕ እነዚህን ሁለት ተመሳሳይ ነገሮች የሚናገረው ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ ለክፉ ተግባሮቻቸው በቶሎ እንደሚቀጣ ትኩረት ለመስጠት ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን መልከቱ)
ነቢዩ ሞኝ ነው፣ መንፈሳዊ ነኝ ሚለውም ሰው እንደ እብድ ነው
እነዚህ ሀረጋት በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሰዎች ነቢዩን እንደ እብድ ሰው ይቆጥሩታል ወይም 2) ነቢያት ህዝቡ ከሚሰራው ኃጢአት የተነሳ እንደ እብድ ሆነነዋል። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ነቢዩ ሞኝ ነው፣ መንፈሳዊ ነኝ ሚለውም ሰው እንደ እብድ ነው
እዚህ ስፍራ "ነቢይ" እና "መንፈሳዊ ሰው" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት ከእግዚአብሔር መልዕክት ተቀብያለሁ የሚል አንድ ሰው ነው። እነዚህ ሰዎች ሃሰተኛ ነቢያት መሆናቸው ተመላክቷል፤ እነርሱ ራሳቸው ብቻ ከእግዚአብሔር መልዕክት ተቀብያለሁ ሲሉ ያስባሉ። (ጥንድ ትረጉም እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
በታላቅ ኃጢአታችሁ እና በታላቅ ጠላትነታችሁ ምክንያት
"ታላቅ ኃጢአት" እና "ታላቅ ጠላትነት" የሚሉት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉምን ይጋራሉ። የህዝቡ ኃጢአተኛነት ራሱን የሚገልጸው በያህዌ እና በነቢያቱ ላይ ባላቸው ጠላትነት ነው። (ጥንድ ትርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 9:8
አጠቃላይ መረጃ፡
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው
ነቢዩ በኤፍሬም ላይ ለአምላኬ ዘበኛ ነው
"ዘበኛ" ከከተማ ውጭ ሆኖ አደጋ መምጣት አለመምጣቱን ይጠብቃል። ነቢዩ ህዝቡ ኃጢአት ሲሰራ እና አምላኩ ህዝቡን ሊቀጣ ባለበት ጊዜ ለከተማይቱ እንደ ዘበኛ ሆኖ ያስጠነቅቃል። "ነቢዩ በኤፍሬም ላይ ለእግዚአብሔር እንደ ዘበኛ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ነቢዩ በኤፍሬም ላይ ለአምላኬ ዘበኛ ነው
አንዳንድ ትረጉሞች ይህንን ክፍል "ነቢዩ ከአምላኬ ጋር በኤፍሬም ላይ ዘበኛ ነው" ብለው ይተረጉሙታል።
ነቢዩ ነው
ይህ የሚያመለክተው በአጠቃላይ እግዚአብሔር ለሾማቸው ነቢያት ሁሉ ነው። "ነቢያት ናቸው" ወይም "እውነተኛ ነቢያት ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የጋር/የወል ስማዊ ሀረግ የሚለውን ይመልከቱ)
ኤፍሬም
እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" የሚለው የሚወክለው መላውን የእስራኤል ህዝብ ነው። (ስኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
የወፍ ወጥመድ በመንገዱ ሁሉ ነው
የ "ወፍ ወጥመድ" ወፍን ለመያዝ የሚያገለግል ማጥመጃ ነው። ይህ ማለት የእስራኤል ህዝብ የእግዚአብሔርን ነቢይ ለማስቆም የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። "ህዝቡ በሚሄድበት ሁሉ ለእርሱ ወጥመድን ያስቀምጣሉ" ወይም "ህዝቡ እረሱን ለመጉዳት የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በጊብዓ ዘመን እንደነበረው ራሳቸውን እጅግ በኃጢአት በክለዋል
"የእስራኤል ህዝብ ኃጢአት በማድረግ ከዘመናት አስቀድሞ በጊብዓ ዘመን ያደርጉት እንደነበረው እጅግ ረክሰዋል" ይህ ምናልባት በመሳፍንት ምዕራፍ 19 እስከ ምዕራፍ 21 በሚገኘው ታሪክ ውስጥ በብንያም ነገድ ከተፈጸመው አሰቃቂ ድርጊት ጋር የሚነጻር ነው።
Hosea 9:10
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እየተናገረ ነው
እኔ እስራኤልን ሳገኛት
ይህ የሚያመለክተው ያህዌ ከእስራኤል ህዝብ ጋር እነርሱን የራሱ ልዩ ህዝብ አድርጎ ለይቶ በመጀመሪያ ግንኙነት መጀመሩን ነው።
ይህ በበረሃ ወይን፤ በበለስ ዛፍ ላይ እንደ የወቅቱን የበኩራት ፍሬ እንደማግኘት ነበር።
እነዚህ ሁለቱም ሃሳቦች የሚያጎሉት አንድን ሰው ደስ የሚያሰኙትን ሁኔታዎች ነው። ይህ ማለት ከእስራኤል ህዝብ ጋር ግንኙነት ሲጀመር ያህዌ እጅግ ደስተኛ ነበር። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
በዓል ፌጎር
ይህ በሞዓብ ምድር የሚገኝ የበዓል ሃሰተኛ አማልዕክት ይመለኩበት የነበረበት ተራራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 9:11
አጠቃላይ መረጃ፡
ያህዌ እየተናገረ ነው
ክብራቸው እንደ ወፍ በሮ ይጠፋል
የኤፍሬም ወገን፣ ወይም የእስራኤል ሰሜናዊ መንግሥት በሌላው መንግት ዘንድ ክብር ያሰጣቸው የነበረውን ማናቸውንም ነገር ያጣሉ። ወፍ በሮ እንደሚጠፋ ክብራቸው በፍጥነት ይጠፋ። "ክብራቸው ወፍ በሮ እንደሚጠፋ ከእነርሱ ይጠፋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእነርሱ ዘወር ስል
እግዚአብሔር የሰሜኑን መንግሥት መርዳት ሲያቆም፣ የሚሆነው በአካል ከእነርሱ እንደ ተለያቸው ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 9:13
አጠቃላይ መረጃ፡
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው
ልክ እንደ ጢሮስ፣ ኤፍሬምን በለምለም መስክ ተተክሎ አየሁት
ይህ ህዝቡ በለምለም መስክ እንደ ተተከለ ዛፍ በመልካም ስፍራ እንደሆነ ይናገራል። "የእስራኤል ህዝብ በአንድ ወቅት እንደ ጢሮስ ከተማ፣ ደግሞም በለመለመ ምስክ እንደ ተተከለ ዛፍ ውብ እና አስደሳች ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ኤፍሬም ... ጢሮስ
እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" የሚለው የሚወክለው መላውን የእስራኤል ህዝብ ነው።

እነዚህ ስፍራዎች በውስጣቸው የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታሉ። (ስኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
ነገር ግን ኤፍሬም ልጆቹን አሳልፎ ይሰጣል
"ልጆች" የሚለው ቃል የአገሪቱን ሰዎች ያመለክታል። "ነገር ግን የእስራኤል ሰዎች ልጆቻቸውን አሳልፈው ይሰጣሉ። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚውን ይመልከቱ)
ያህዌ ሆይ አድርግባቸው፣ - ምን ታደርግባቸዋለህ? እባክህ አድርግባቸው
ሆሴዕ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ያህዌ ለእስራኤል ህዝብ የሚገባቸውን እንዲያደርግባቸው በጉልህ ማሳየት ስለፈለገ ነው። " ያህዌ ሆይ፣ እኔ የምጠይቀው ይህንን ነው፤ እንድታደርግባቸው፣ እባክህን ስጣቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ)
ጽንስ የማይሸከም ማህጸን
"የማይሸከም" ማህጸን ማለት ጽንሱ እንዲጨነግፍ እና የተረገዘው እንዲሞት ማለት ነው። ሆሴዕ የአገሪቱ ሴቶች ሁሉ እንደዚያ እንዲሆኑ እየጠየቀ ነው።
Hosea 9:15
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው
ከቤቴ አስወጣቸዋለሁ
ያህዌ እስራኤልን ከምድሩ፣ ማለትም ከከነዓን ምድር እንደሚያስወጣቸው እየተናገረ ነው። እዚህ ስፍራ "ቤቴ" የሚለው የሚወክለው ከነዓንን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚውን ይመልከቱ)
መኳንንቶቻቸው
ንጉሡን የሚያገለግሉ ወንዶች
Hosea 9:16
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ በቁጥር 16 ላይ እየተናገረ ነው። ሆሴዕ በቁጥር 17 መናገር ይጀምራል።
ኤፍሬም ታመመ፣ ዛፎችም ስራቸው ደረቀ፤እንዳች ፍሬ አልሰጡም
ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ ፍሬ እንደማያፈራ እና ለመቆረጥ እንደተዘጋጀ የታመመ ዛፍ አድርጎ ይናገራል። ይህ ህዝቡ ደካማ እንደሆነ፣ ጠላቶቻቸው በቶሎ እንደሚመጡና እንደሚያሸንፏቸውም የሚናገር ሃሳብ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 10

Hosea 10:1
አጠቃላይ መረጃ:
ሆሴዕ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው።
እስራኤል ብዙ የሚያፈራ የተንዠረገገ የወይን ተክል ነው
እስራኤል የተገለጸችው በጣም ፍሬያማ እንደሆነ የወይን ተክል ነው። ህዝቡ ለጊዜው በለጸገና ጠንክሮ ነበር። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የተንዠረገገ የወይን ተክል
ይህ ወይን ከተለመደው ይበልጥ ያፈራል ፍሬው በመመረለት መጠን… ምድሩ ብዙ ሲያፈራ እነዚህ ሁለቱም አገላለጾች፤ ህዝቡ ሲበለጽግ፣ እየጠነከረ እና ሃብት እያገኘ ሲመጣ የሚል ተመሳሳይ ትርጉም ይሰጣሉ።
ልባቸው በማታለል የተሞላ ነው
"ልባቸው" የሚለው የሚገለጸው መላው ማንነታቸውን፣ በስሜታቸው እና ፍላጎታቸው ላይ ትኩረት በማድረግ ነው። "እነርሱ አታላዮች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲኪ/ የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
አሁን ኃጢአታቸውን መሸከም አለባቸው
እዚህ ስፍራ "ኃጢአት" የሚለው ከዚህ ጋር ለተያያዘ የሚደርስ ቅታትን የሚያመለክት ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት/ ነው። ይህ ቅጣት የተገለጸው ለመሸከም ከባድ እንደሆነ ክብደት ነው። "አሁን ያህዌ በኃጢአታቸው ምክንያት የሚቀጣቸው ጊዜ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
Hosea 10:3
አጠቃላይ መረጃ:
ሆሴዕ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው።
እናም ንጉሡ - ለእኛ ምን ማድረግ ይችላል?
ህዝቡ ንጉሦቻቸው ሊረዷቸው እንዳልቻሉ ይናገራሉ። "ምንም እንኳን አሁን ንጉሥ ቢኖረንም፣ እኛን ሊረዳን አልቻለም " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ባዶ/የማይጠቅሙ ቃላትን ይናገራሉ
እዚህ ስፍራ "ባዶ /የማይጠቅሙ ቃላት" የሚለው የሚያመለክተው ሃሰትን ነው። "ሃሰት ይናገራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህ በእርሻ ዳርቻ እንደሚበቅል መርዛማ አረም ፍርድ ፈጥኖ ይበቅላል
እነዚያ ሰዎች በህጎቻቸው እና በህጋዊ ውሳኔዎቻቸው ፍርድ ብለው የሚጠሩት የተገለጸው ፈጥኖ እንደሚያደነቁል/እንደሚበቅል ተክል ነው። "ስለዚህ ውሳኔዎቻቸው ፍትሃዊ አይደሉም፣ ይልቁንም ጎጂዎች ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በእርሻ ዳርቻ እንደሚበቅል መርዛማ አረም
የእነርሱ ሃሰት እና ፍትህ አልባነት በህዝባቸው መሃል ተስፋፍቶ እንደ መርዛማ ተክሎች ሁሉንም ሰው ጎዳው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 10:5
አጠቃላይ መረጃ:
ሆሴዕ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው።
ቤትአዌን
ይህ ከተማ በእስራኤል ሰሜናዊ ግዛት እና በደቡባዊ ግዛት በቢንያም ነገድ ድንበር መሃል የሚገኝ ነበር። ይህንን በሆሴዕ 4:15 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ አሦር በምርኮ ይወሰዳሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አሦራውያን እነርሱን በምርኮ ይወስዷቸዋል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ኤፍሬም ይዋረዳል፣ እስራኤልም በጣኦቷ ታፍራለች
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ደግሞም የእስራኤል ህዝብ በጣም ያፍራል፤ ምክንያቱም ጣኦታትን አምልኳልና " በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ጣኦቷ
ብዙ ቅጂዎች በዚህ ክፍል የሚገኘውን የዕብራይስጡን ቃል "ምክር፣" "እቅድ፣" ወይም "አስተሳሰብ" ብለው ተርጉመዋል
Hosea 10:7
የሰማርያ ንጉሥ ይደመሰሳል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አሦራውያን የሰማርያን ንጉሥ ይደመስሳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በውሃ ላይ እንደሚንሳፈፍ ቁራጭ እንጨት
ይህ ማለት የሰማርያ ንጉሥ የውሃ ማዕበል እንደሚያንገላታው ትንሽ ቁራጭ እንጨት አቅመቢስ ይሆናል ማለት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የክፋት ከፍ ያሉ ስፍራዎች ይደመሰሳሉ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አሦራውያን የእስራኤል ህዝብ ኃጢአት ያደርግባቸው የነበሩ ከፍተኛ ስፍራዎችን ይደመስሳሉ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰዎቹ ተራሮችን "ጋርዱን!" ኮረብቶችን "በላያችን ውደቁ!" ይላሉ
በእርግጥ ሰዎች ማሰብ ከማይችሉ ወይም ከማይሰሟቸው ነገሮች ጋር አይነጋገሩም። ተርጓሚዎች ቋንቋቸው እንዲህ አይነቱን ንግግር የማይፈቅድላቸው ከሆነ ለዚህ ምንባብ የተለየ አቀራረብ ሊመርጡ ይችላሉ። "ሰዎቹ እንዲህ ይላሉ፣ 'ተራሮች እንዲሸፍኑን እንፈልጋለን!' ደግሞም 'ኮረብቶች በእኛ ላይ እንዲወድቁብን እንፈልጋለን!'" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አፖስትሮፊ የሚለውን ይመልከቱ)
Hosea 10:9
አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ እየተናገረ ነው
በጊብዓ ዘመን
ይህ ምናልባት በመሳፍንት ምዕራፍ 19 እስከ ምዕራፍ 21 በሚገኘው ታሪክ ውስጥ በብንያም ነገድ ከተፈጸመው አሰቃቂ ድርጊት ጋር የሚነጻር ነው። ይህንን በሆሴዕ 9:


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

9 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

በዚያ እናንተ ታስታውሳላችሁ

ይህ ክፍል ምናልባት በጊዜው የነበሩ ሰዎች አባቶቻቸው በጊብዓ ያደርጉት የበረውን በተመሳሳይ መንገድ ማድረግ ቀጥለው ሊሆን ይችላል። "እናንተም ልክ እነርሱ ያደርጉት እንደነበረው ታስባላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ጦርነት በጊብዓ የኃጢአተኞችን ልጆች አልጨረሰምን?

ያህዌ ጥያቄውን የተጠቀመበት በጊብዓ ኃጢአተኞች በራሳቸው በእርግጥ ጦርነቱን መወጣት እንዳለባቸው በአጽንኦት ለመናገር ነው። ደግሞም ይህ ሲገለጽ ሰዎቹ ጦርነትን መወጣት ያለባቸው ጠላቶቻቸው ሲመጡባቸው ጦርነት ሰው ሆኖ እንሚይዛቸው ተደርጎ በማቅረብ ነው። "ጦርነት በእርግጥ በጊብዓ ኃጢአት ባደረጉ ላይ ይመጣባቸዋል" ወይም "ጠላቶች በእርግጥ በጊብዓ ኃጢአት የሰሩትን ያጠፋቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የኃጢአተኞች ልጆች

እዚህ ስፍራ "የአባቶቻቸው ልጆች" የሚለው ፈሊጥ ነው፤ ትርጉሙ "የአባቶቻቸው ባህሪ ያላቸው" ማለት ነው። "ኃጢአት ያደረጉ" ወይም "ክፉ አድራጊዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 10:10

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እየተናገረ ነው

እጥፍ ኃጢአት/በደል

ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን የኃጢአት ብዛት ነው። ኤፍሬም እንደ ተገራች መውቃት እንደምትወድ ጊደር ነው ጊደር ማበራየት ትወዳለች ምክንያቱም ቀንበር ሳይጫንባቸው በነጻነት በዙሪያ መዞር ይችላሉ። ያህዌ የእስራኤል ህዝብ ነጻ ሆኖ ያሻውን ደስተኛ ህይወት መኖር ይችላል እያለ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በምቹ ጫንቃዋ ላይ ቀንበር እጭናለሁ፣ በኤፍሬም ላይ ቀንበር አስቀምጣለሁ

እዚህ ስፍራ "ቀንበር" የሚያመለክተው መከራን እና ባርነትን ነው። ያህዌ ለእስራኤል ህዝብ ደግ ነበር፣ ህዝቡ ግን ለእርሱ ታማኝ አልበረም። ስለዚህም እርሱ ይቀጣቸዋል ደግሞም ለባርነት አሳልፎ ይሰጣቸዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ ያርሳል፣ ያዕቆብ መሬቱን ያለሰልሳል

እዚህ ስፍራ "ይሁዳ" የሚያመለክተው የደቡቡን መንግሥት ህዝብ ነው፤ "ያዕቆብ" ደግሞ የሰሜኑን መንግሥት ህዝብ ያመለክታል። ይህ ማለት እግዚአብሔር በሁለቱም መንግሥታት ላይ አስጫቂ ጊዜን ያመጣል ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

መከስከሻ

መሬትን ለማለስለስ እና ከታረሰ በኋላ ዘርን አፈር ለማልበስ የሚያገለግል መሳሪያ

Hosea 10:12

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እየተናገረ ነው

ጽድቅን ለራስህ ዝራ፣ የቃል ኪዳንን ፍሬ በታማኝነት አጨድ

ጽድቅ እና የቃል ኪዳን ታማኝነት የተነገሩት እንደሚዘራ እና እንደሚታጨድ እህል ነው። ረቂቅ ስም የሆኑት "ጽድቅ" እና "ታማኝነት"፤ "ትክክል" እና "ታማኝ" ተብለው ሊጻፉ ይችላሉ። "አሁን እረስ፣ ደግሞም ትክክል የሆነውን አድርግ፤ ይህ ሲሆን የታማኝነትን ፍቅር ፍሬ ማጨድ ትችላለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

ያልታረሰ መሬታችሁን እረሱ

መሬት "ሳይታረስ ሲቀር" በላዩ ለመዝራት ዝግጁ አልተረገም ማለት ነው። ያህዌ ህዝቡ ንስሃ እንዲገባ እፈልጋለሁ ማለቱ ነው፤ ስለዚህ ትክክል የሆነውን ማድረግ መጀመር ይችላሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ኀጢአትን አርሳችርኋል፤ እፍትሃዊነትን አጭዳችኋል

ኀጢአት እና እፍትሃዊነት የተገለጹት ሊዘራ እና ሊታጨድ የሚችል ሰብል እንደሆኑ ተደርጎ ነው (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የማታለልን ፍሬ ተመግባችኋል

የማታለል ውጤቱ የተገለጸው ሊበላ እንደሚችል ምግብ ነው። "አሁን አንዳችሁ ሌላችሁን ማታለላችሁ የሚያስከትለውን የመከራ ውጤት እየተቀበላችሁ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 10:14

አጠቃላይ መረጃ ሰልማን፣ ቤትአርብኤልን በጦርነት ቀን እንዳፈራረሰው ይሆናል

የሚመጣው ጦርነት የተነጻጸረው ከረጅም ጊዜ አስቀድሞ ከተደረገ ጦርነት ጋር ነው።

ሰልማን

ይህ በ740 ዓመተ ዓለም ግድም የቤትአርብኤልን ከተማ የደመሰሰ ንጉሥ ስም ነው። ሰራዊቱ ሴቶችን እና ልጆችን በጥቃቱ ወቅት ፈጅቷል። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤትአርብኤል

ይህ የንፍታሌም ነገድ ከተማ አይነት ስያሜ ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህም ቤቴል ሆይ፣ ከታላቅ ኀጢአትሽ የተነሳ በአንቺም ላይ እንደዚሁ ይሆናል

እዚህ ስፍራ "ቤቴል" የሚለው የሚወክለው በዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። ነቢዩ የቤቴልን ሰዎች በዚያ ሆነው እንደሚያደምጡት አድርጎ ይናገራል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና አፖስትሮፊ የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 11

Hosea 11:1

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ፣ ወላጅ ልጁን እንደሚንከባከብ፤ እስራኤልን ስለመንከባከብ ይናገርል

እስራኤል ወጣት ሰው በነበረበት ወቅት

ያህዌ ስለ እስራኤል ሰዎች ወጣት ሰው እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። ያህዌ ከአገሪቱ ጋር በመጀመሪያ ግንኙነት ሲጀምር የነበረውን ሁኔታ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልጄን ከግብጽ ጠራሁት

"ወንድ ልጅ" የሚለው የሚያመለክተው የእግዚአብሔር አብን ህዝብ ነው። "ልጄን ከግብጽ አወጣሁት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አብዝተው በተጠሩ መጠን፣ አብዝተው ከእርሱ ራቁ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "የእኔ ህዝብ እንዲሆኑ አብዝቼ በጠራኋቸው መጠን፣ አብዝተው ተቃወሙኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 11:3

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ለእስራኤል እንዴት እንደሚጠነቀቅ እየተናገረ ነው

እንዴት መራመድ እንደሚችል ለኤፍሬም ያስተማርኩት እኔ ነበርኩ

ያህዌ እስራኤልን መራመድ እንደሚማር ትንሽ ልጅ ይገልጻታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቻቸውን ይዤ አነሳኋቸው

ይህ አገላለጽ ቀደም ሲል በቀረበው ዘይቤያዊ አነጋገር ላይ የሚቀጥል ነው። "ለእነርሱ ጥንቃቄ አደረግሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በፍቅር እጅ፣ በሰብአዊነት ገመድ ይዤ መራኋቸው

ያህዌ ህዝቡን ሰው ሊረዳው እና ሊገነዘበው በሚችለው መንገድ ወደዳቸው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ)

ቀንበሩን ከጫንቃቸው እንደሚያቀል ሰው ሆኜላቸው ነበር

ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ የሚገልጸው እርሱ ከስራው እንዳሳረፈው ከባድ የስራ ጫና እንዳለበት እንስሳ ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እነርሱ ጎንበስ ብዬ መገብኳቸው

ይህ አገላለጽ እስራኤል እንደ ትንሽ ልጅ የቀረበበትን ዘይቤ የሚቀጠል ነው። ያህዌ ለአካላዊ ፍላጎቶቻቸው የሚያስፈልገውን ሁሉ ይሰታቸዋ ማለት ሊሆን ይችላል።

Hosea 11:5

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ስለእስራኤል እየተናገረ ነው

ወደ ግብጽ ምድር አይመለሱምን?

ይህ ጥያቄ እስራኤል ዳግም አንድ ጊዜ በግብጽ በነበሩበት ጊዜ እንደነበሩት



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ባሪያዎች ይሆናሉ ማለትን ያመለክታል። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ እኔ መመለስን እምቢ በማለታቸው አሦር አይገዛቸውምን?
የእስራኤል ህዝብ ለያህዌ ታማኝ መሆንን ስላልወደዱ የአሦር ምርኮኛ ይሆናሉ። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
በከተሞቻቸው ላይ ሰይፍ ይመጣል
እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው የሚወክለው የእስራኤልን ከተሞች የሚደምሱ ጠላቶቻቸውን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለው ይመልከቱ)
የበሮቻቸውን መወርወሪያ ደምስሱ
በሮች የከተማዋ ነዋሪዎች ከጠላቶቻቸው በደህንነት እንዲጠበቁ ያደርጋል፣ መወርወሪያዎቹ ደግሞ በሮቹ እንዲቆለፉ ያስችላሉ። መወርወሪያዎቹን መደምስ ማለት የህዝቡን ደህንነት ማጣት ማለት ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለው ይመልከቱ)
እጅግ ከፍ ወዳለው ቢጠሩም
እዚህ ስፍራ እግዚአብሔር በሶስተኛ መደብ ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። ይህ በአንደኛ መደብ ሊጻፍ ይችላል። "እጅግ ከፍ ወዳልኩት ወደ እኔ ቢጠሩም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ)
ማንም ሊረዳቸው አይችልም
ያህዌ እስራኤልን እንዲረዳት አይፈቅድም፤ ምክንያቱም እነርሱ ከእርሱ ፊታቸውን አዙረዋል።

Hosea 11:8

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለእስራኤል እየተናገረ ነው
ኤፍሬም ሆይ፣ እንዴት ልተውህ እችላለሁ? እስራኤል ሆይ፣ እንዴት አሳልፌ ልሰጥሽ እችላለሁ?
ያህዌ ህዝቡን እጅግ ስለሚወድ ሙሉ ለሙሉ አያጠፋውም። ይህ ከጥያቄ መልክ ወጥቶ በዐረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል። "ኤፍሬም ሆይ፣ እኔ አልተውህም። እስራኤል ሆይ፣ እኔ አልጥልሽም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
እንዴት እንደ አዳማ አደርግሃለሁ? እንዴትስ እንደ ሲባዩ አድግሃለሁ?
ያህዌ ህዝቡን እጅግ ስለሚወድ ሙሉ ለሙሉ አያጠፋውም። ይህ ከጥያቄ መልክ ወጥቶ በዐረፍተ ሃሳብ ሊተረጎም ይችላል፡ "በአዳማ ላይ እንዳደረግኩት በአንተ ላይ ማድረግ አልገልግም ወይም በሶዶም ላይና በሲባዩ ከተሞች ላይ እንዳደረግኩት አላደርግብህም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን መልከቱ)
እኔ እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይደለሁም
እግዚአብሔር በፍጥነት ለመበቀል እንደሚወስኑት እንደ ሰዎች አይደለም
ልቤ በውስጤ ተለወጠ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ እና ውሳኔ ነው (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለው ይመልከቱ)
በቁጣ አልመጣም
"ቁጣ" የሚለው ረቂቅ ስም "ቁጡ" በሚለው ገላጭ ሊጻፍ ይችላል። "ወደ እናንተ መጥቼ በእናንተ ቁጡ አልሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 11:10

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ህዝቡን መቼ እንደሚያድስ እየተናገረ ነው
እነርሱ ያህዌን ይከተላሉ
ያህዌን ማምለክ እና ማክበር እርሱን መከተል ሆኖ ቀርቧል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ እንደ አንበሳ ያገሳል
ያህዌ ህዝቡን ወደ ምድሩ መመለስን የሚቻል ነገር አድረጎታል፤ ይህም እርሱ ህዝቡን እየጠራ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ እርግብ ... እንደ ወፍ እየተንቀጠቀጡ ይመጣሉ
ወፍ ወደ ጎጆዋ እንደምትመለስ ወደ አገራቸው በፍጥነት ይመለሳሉ። "መንቀጥቀጥ" ምናልባት የወፍ ክንፎች መርገብገብን ያመለክታል። እንደዚሁም ምናልባት የሰዎችን የትህትና ስሜት እና ለእግዚአብሔር ያላቸውን አምልኮ ያመለክታል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የያህዌ አዋጅ/ ያህዌ የተናገረው
"ያህዌ ያወጀው/የተናገረው" ወይም "ያህዌ በታላቅነቱ የተናገረው" ይህንን በሆሴዕ 2:13 እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

Hosea 11:12

አጠቃላይ መረጃ:
ያህዌ ስለ እስራኤል እና ስለ ይሁዳ እየተናገረ ነው
ኤፍሬም በሃሰቱ፣ የእስራኤል ቤትም በማታለሉ ከብቦኛል
የሃሰት እና የማታለል ድርጊቶች የተነገሩት የሰሜን መንግሥት ሰዎች ያህዌን እንደ ከበቡበት ቁሳዊ ነገሮች እንደሆኑ ተደርጎ ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
ነገር ግን እስከ አሁን ይሁዳ ከእኔ ጋር ነው
እዚህ ፍራ "ይሁዳ" የሚለው የሚያመለክተው በዚያ የሚኖሩ ህዝቦችን ነው። ይህ ከእርሱ ጋር "አብሮ መሄድ" በሚል ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆንን ይገልጻል። ሆኖም፣ ብዙ ቅጂዎች ለዚህ አስቸጋሪ ምንባብ የተለያየ ትርጉም አላቸው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትንው ይመልከቱ)

---

## Chapter 12

### Hosea 12:1

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው
ኤፍሬም ነፋስ ይመገባል
እዚህ ስፍራ "ኤፍሬም" የሚለው የሚወከወለው መላውን የእስራኤል ህዝብ ነው። እንደዚሁም "ነፋስ" የሚለው የሚወከወለው ጥቅም የሌለውን ነገር ወይም ጊዜያዊ የሆነን ነገር ነው። የእስራኤል ህዝብ የሚያደርገው የማይጠቅመው ነገር የተገለጸው ነፋስ እንደሚበሉ ተደርጎ ነው። (ስኔክቲኪ/ ዘይቤያዊ አነጋጋር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ፤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
የምስራቅን ነፋስ ይከተላል
የምስራቅ ነፋሳት በጣም ሞቃት እና ምድርን የሚያጠፉ ነበሩ። ራሳቸውን የሚያጠፋ ነገሮችን የሚሰሩት ሰዎች የተገለጹት የምስራቅን ነፋስ እየተከተሉ እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)
የወይራ ዘይት ወደ ግብጽ ይልካሉ
የእስራኤል ሰዎች ለግብጽ ንጉሥ፣ ይረዳቸው ዘንድ ለማግባባት የእጅ መንሻ አድርገው የወይራ ዘይት ይልካሉ
ያህዌ ከይሁዳ ጋር ሙግት አለው
ያህዌ የይሁዳ ሰዎች እርሱን መበደላቸውን እና ቃል ኪዳኑን ማፍረሳቸውን በፍርድ ቤት እየከሰሳቸው እንደሆነ አድርጎ ይናገራቸዋል። ተመሳሳዩን ሀረግ በሆሴዕ 4:1 እንዴት እንደ ተረጎሙት ይመልከቱ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በይሁዳ ላይ... ያዕቆብን በድርጊቱ ይቀጣዋ ... ለስራውም ይከፍለዋል
እዚህ ስፍራ "ይሁዳ" እና "ያዕቆብ" ሁለቱም የይሁዳን ህዝብ ይወክላሉ። "በይሁዳ ሰዎች ላይ... ለድርጊታቸው እቀጣቸዋለሁ.. ለስራቸውም እከፍላቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)
ሙግት
ይህ በህግ አደባባይ አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ የሚያቀርበው ክርክር ነው። ይህንን በሆሴዕ 2:2 ላይ እንዴት እንደተረጎሙት ይመልከቱ።

### Hosea 12:3

አጠቃላይ መረጃ:
ነቢዩ ሆሴዕ የእስራኤላዊያን አባት ስለሆነው ስለ ያዕቆብ እየተናገረ ነው
በማህጸን ሳለ ያዕቆብ የወንድሙን ተረከዝ ያዘ
ያዕቆብ የወንድሙን የብኩርና ስፍራ ለመውሰድ ፈለገ፣ ስለዚህም ወንድሙ በኩር እንዳይሆን ለማድረግ ሞከረ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከመልአክ ጋር ታግሎ አሸነፈ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ያዕቆብ ይባርከው ዘንድ ከመልአክ ጋር ታገለ። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 12:5

አጠቃላይ መረጃ:

ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

እርሱ የሚጠራበት ስሙ ነው

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። እዚህ ስፈራ "ስም" የሚለው የሚወክለው የእግዚአብሔርን ባህሪይ ነው። "ስሙ ወደ እርሱ የምንጸልይበት ነው" ወይም "ስሙ እርሱን የምናመልክበት ነው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚሉትን ይመልከቱ)

ቃል ኪዳናዊ ታማኝነትንና ፍትህን መጠበቅ

ይህ የእግዚአብሔርን ህግ መጠበቅን እና ትክክል የሆነውን ማድረግን ያመለክታል

Hosea 12:7

አጠቃላይ መረጃ:

ነቢዩ ሆሴዕ ስለ እስራኤል እየተናገረ ነው

ሃሰተኛ መለኪያዎች/ሚዛን

ነጋዴዎች የሚገዙተን ወይም የሚሸጡትን ምርት በትክክል የማይለካ ሚዛንን ይጠቀማሉ።

ማጭበርበር ይወዳሉ

ነጋዴዎቹ ደንበኞቻቸውን በመዋሸትና መውሰድ ከሚገባቸው ባላይ ገንዘብ በመውሰድ ያታልላሉ

በእርግጥ ባለጸጋ ሆኛለሁ፣ የሚበቃ ሃብት አግኝቻለሁ

እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የኤፍሬም ሰዎች ራሳቸውን ባለጸጋ አድርገው ይቆጥራሉ የሚል ትርጉም አለው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃብት አግኝቻለሁ

በንግድ ሃብታም መሆን የሚለው ሃብት ማግኘት ተብሎ ተገልጽዋል። "ብዙ ገንዘብ አፍርቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በእኔ ዘንድ አንዳች በደል ፣ አንዳች ኀጢአት የሚሆን ነገር አያገኙም

እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የኤፍሬም ሰዎች ራሳቸውን ንጹህ አድርገው ይቆጥራሉ የሚል ትርጉም አለው። አንድ ሰው ሃጢአት አደረገ የሚለውን ማወቅ የተገለጸው በዚያ ሰው ውስጥ ሃጢአት ማግኘት በሚል ነው። " አንዳች ኀጢአት አድርገሃል ብለው ሊናገሩኝ አይችሉም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ ትርጉም እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

Hosea 12:9

አጠቃላይ መረጃ:

ያህዌ ለእስራኤል ህዝብ እየተናገረ ነው

ከግብጽ ምድር .... እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ

አማራጭ ትርጉሞች የሚሆኑት 1) "አባቶቻችሁን ከግበጽ ምድር ያወጣሁት፣ እኔ ያህዌ አምላካችሁ ነኝ" ወይም 2) "በግብጽ ምድር ከነበራችሁበት ጊዜ አንስቶ አምላካችሁ እኔ እግዚአብሔር ነበርኩ" ወይም 3) "በግብጽ ምድር በነበራችሁበት ወቅት እኔ አምላካችሁ ሆንኩ"

እኔ ዳግም በድንኳኖች እንድትኖሩ አደርጋለሁ

አማራጭ ትርጉሞች የሚሆኑት 1) ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ ከቤታቸው በሃይል ለማስወጣትና በድንኳኖች እንዲኖሩ ለማድረግ አስፈራራቸው። ስለዚህ፣ እዚህ ላይ "በድንኳኖች ውስጥ መኖር" የሚለው የሚወክለው በስደት መውጣትን ነው፣ ወይም 2) ይህ ከስደታቸው በኋላ ዳግም በድንኳኖች እንደሚኖሩ ቃል ኪዳን ነው፣ እናም ያህዌ እስራኤላውያን ከግብጽ በወጡ ጊዜ እንዳደረገው እነርሱን ይንከባከባል። ስለዚህ፣ እዚህ ላይ "በድንኳኖች ውስጥ መኖር" የሚለው የሚወክለው ያህዌ ሲንከባከባቸው ወደ መልካም ሁኔታ መመለሳቸውን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

በነቢያት እጅ

እዚህ ስፍራ "እጅ" የሚለው የሚገልጸው ድርጊት የሚፈጽምን ነው። "በነቢያት አማካይነት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሲኔክዶኪ/ ዘይቤያዊ አነጋገር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ።)

Hosea 12:11

አጠቃላይ መረጃ:

ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

መሰዊያዎቻቸው እንደ እርሻዎች ዳርቻ የድንጋይ ክምር ይሆናሉ

ሰዎች የሚያመልኩበት መሰዊያ ይፈራርስና የድንጋይ ክምር ይሆናል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያዕቆብ ወደ አራም ምድር ኮበለለ፤እስራኤል ሚስት ለማግኘት ተገዛ

እዚህ ስፍራ "ያዕቆብ" እና "እስራኤል" የሚሉት ሁለቱም ቃላት አንድን ሰው ያመለክታሉ። የያዕቆብ ስም ቆይቶ እስራኤል ተባለ።

Hosea 12:13

አጠቃላይ መረጃ:

ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

በአንድ ነቢይ

ያ ሰው፣ ሙሴ ነው

በማስመረር

ሰዎቹ ያህዌ እጅግ እንዲቆጣ አደረጉ

ስለዚህ ጌታው ደሙን በእርሱ ላይ ተወው

እዚህ ስፍራ "ደም" የሚለው የሚያመለክተው ህዝቡ ሌሎችን በመግደል በራሱ ላይ ያመጣውን በደል ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ሃፍረቱን ወደ ራሱ ይመልስበታል

አንድ ሰው ከራሱ ድርጊት የተነሳ ስቃይ እንዲደርስበት የማድረግ ሃሳብ የተገለጸው፤ እነዚያ ድርጊቶች ቁሳዊ ነገሮች ሆነው፣ በተወረወሩ ጊዜ ተመልው በወርዋሪው ላይ እንደሚወድቁ ተደርጎ ነው። "ከራሱ አሳፋሪ ድርጊቶች የተነሳ እንዲሰቃይ አደርገዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 13

Hosea 13:1

አጠቃላይ መረጃ:

ያህዌ እየተናገረ ነው

ፍሬም ሲናገር

ሆሴዕ "ኤፍሬም" የሚለውን ቃል የተጠቀመው፣ ምንም እንኳን ከአስሩ ነገዶች የአንዱ ስም የነበረ ቢሆንም፣ መላውን የሰሜን መንግሥት ለማመልከት ነው። ሆሴዕ እንደ አሁኑ ጊዜ ሳይሆን የሰሜኑ መንግሥት ጠንካራ እና የተከበረ ስለነበረበት ስለ ቆየ የጥንት ዘመን የሚናገር ይመስላል። (ሲኔቲክ/ዘይቤያዊ አነጋገር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውም ይመልከቱ)

መንቀጥቀጥ ነበር

ህዝቡ ይንቀጠቀጥ እንደነበር ይታወቃል ምክንያቱም ኤፍሬምን ይፈሩት ነበር። ይህ በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "በህዝቡ መሃል መንቀጥቀጥ ነበር" ወይም "ሰዎች በፍርሃት ይንቀጠቀጡ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱን በእስራኤል አላቀ

እዚህ ስፍራ "አላቀ" ማለት ራስን ጠቃሚ አድርጎ ማሳየት ማለት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን በዓልን በማምለክ ኀጢአተኛ ሆኖ ተገኘ፣ ሞተም

የኤፍሬም ሰዎች በዓልን ምማለክ ሲጀምሩ፣ ደካሞች እየሆኑ ይመጣሉ፤ ጠላቶቻቸውም ያሸንፏቸዋል። እዚህ ስፍራ "ሞተ" የሚለው የሚያመለክተው አገሪቱ እየደከመች መምጣቷን ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን በደላቸው እየጨመረ ሄደ

እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የኤፍሬምን ምሳሌነት የተከተሉትን የኤፍሬምን ነገድ እና መላውን የእስረኤል አገር ነው

እነዚህ ለጣኦት መስዋዕት የሚያቀርቡ ሰዎች ጥጃዎቹን ይስማሉ

የጣኦት አምልኮ አንዱ ክፍል የተቀረጸውን የጥጃ ጣኦት ምስል መሳም ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:3

ስለዚህ እንደ ማለዳ ደመና ይሆናሉ... እንደ ጤዛ...እንደ ገለባ.. ከምድጃ እንደሚወጣ ጢስ

እነዚህ አገላለጾች እስራኤል ያህዌን ከማለክ ይልቅ ጣኦት ማምለኩን የሚቀጥል ከሆነ ጊዜያዊ እና በቶሎ የሚጠፋ መሆኑን ያሳያሉ። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ በነፋስ የሚነዳ ነው

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ነፋስ ነድቶ የሚወስደው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:4

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ ህዝቡን በበረሃ የሚንከራተት የበግ መንጋ እንደሆኑ አድርጎ እየተናገረ ነው። እነርሱን በዚያ ስፍራ የኔ ናቸው እንዳለ እየተናገረ ነው።

በበረሃ ሳለህ አውቅሁህ

ያህዌ ዕብራውያንን የራሱ ምርት ህዝብ እንደሆኑ እና እንደ ሚንከባከባቸው ይናገራል።

መሰማሪያ ባገኛችሁ ጊዜ ትረካላችሁ

በበጎች ተምሳሌት የሚነገረው አገላለጽ ቀጥሏል

ልባችሁ ከፍ አለ

ማን አለብኝነት ልብን ከፍ በማድረግ ተገልጽዋል። "ኮራህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:7

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እየተናገረ ነው

እንደ አንበሳ... እንደ ነብር... እንደ ድብ... አንበሳ ይመስል...እንደ ዱር አውሬ

እነዚህ ሌሎችን እንስት የሚያጠቁና የሚገድሉ የዱር እንስሳት ናቸው። ያህዌ ህዝቡን በኀጢአታቸው ምክንያት እንደሚያጠፋቸው መናገሩን ቀጥሏል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ልጆቿን/ግልገሎቿን እንደ ተቀማች ድብ

"ታጠቃለች" የሚለው ቃል የተተወው በውስጠ ታዋቂነት የታወቀ ስለሆነ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል፡ "ድብ ልጆቿን የወሰደባትን እንስሳ እንደምታጠቃ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢሊፒሲስ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንበሳ ይመስል

"ይበላቸዋል" የሚለው የተተወው በውስጠ ታዋቂነት የታወቀ ስለሆነ ነው።ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንበሳ እንደሚበላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኢሊፒሲስ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:9

አጠቃላይ መረጃ፡

አጠቃላይ መረጃ፡

ማን ሊረዳህ ይችላል?

ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው የእስራኤልን ህዝብ ማንም ሊረዳው እንደማይችል ለማጉላት ነው። "ማንም ሊረዳህ የሚችል የለም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለው ይመልከቱ)

በከተሞቻችሁ ሁሉ ውስጥ ሊያድናችሁ የሚችል ንጉሣችሁ አሁን የት አለ? 'ንጉስ እና ልዑል ስጠኝ' ብላችሁ እኔን የጠየቃችኋቸው መሪዎቻችሁ የት አሉ?

ያህዌ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠይቃቸው እስራኤላውያን በእርሱ ላይ ሲያምጹ ማንም ንጉሥ ወይም መሪ ሊያድናቸው እንደማይችል ሊነገራቸው ነው። ከጥፋት ሊያድናቸው የሚችለው ያህዌ ብቻ ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:12

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እየተናገረ ነው

የኤፍሬም በደል ተከማችቷል፣ ኀጢአቱም ሞልቷል

እነዚህ ሁለት ሀረጋት ተመሳሳይ ናቸው፤ትረጉማቸውም በመሰረታዊነት አንድ አይነት ነገር ነው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ)

ሞልቷል/ተከማችቷል

የሰሜኑ መንግሥት ሀጢአት እና በደል ለጉዳይ ሊጠበቅ እንደሚችል ቁሳዊ አካል እንደሆኑ ተደርጎ ቀርቧል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ልጅ የመውለድ ምጥ አይነት ስቃይ በእርሱ ላይ ይመጣል

እዚህ ስፍራ ያህዌ የእስራኤል ህዝብ ሊደርስበት ያለውን መከራ ልጅ ሲወለድ ሴት ያለባትን የምጥ ስቃይ ያህል እንደሆነ ይናገራል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን እርሱ ብልህ ያልሆነ ልጅ ነው፣ የመወለድ ሰአት በደረሰ ጊዜ፣ ከማህጸን አይወጣም

አሁን ያህዌ የእስራኤልን ህዝብ የሚገልጸው እናት እንደምትወልደው ህጻን ነው። ህጻኑ ብልህ አይደለም ምክንያቱም ለመወለድ አልፈለገም። ህዝቡ ንስሃ ሊገባ እና ያህዌን ሊታዘዝ አልፈለገም። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:14

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እየተናገረ ነው

ከሲኦል እጅ አድናቸዋለሁን? ከሞት እታደጋቸዋለሁን?

ያህዌ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው ለእስራኤል ህዝብ ከመሞት እንደማያድናቸው ሊነግራቸው ነው። በእርግጥ ይቀጣቸዋል። "በእርግጥ ከሞትና ወደ ሲኦል ከመውረድ አላድናቸውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሞት ሆይ መቅሰፍትህ የት አለ? ሲኦል ሆይ ጥፋትህ ወዴት አለ?

ሰዎች የሆኑ ያህል፣ ያህዌ ለ"ሞት" እና "ሲኦል" እየተናገረ ነው። ያህዌ ጥያቄዎቹን የተጠቀመባቸው ሰዎቹን በቶሎ እንደሚያጠፋቸው ለመናገር ነው። "የእስራኤል ሰዎች እንዲሞቱ አሁን መቅሰፍትን አደርጋለሁ። አጠፋቸዋለሁ ደግሞም ወደ ሲኦል እልካቸዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሰውኛ፣ ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከዐይኖቼ ርህራሄ ተሰውሯል

ርህራሄ እንዳለ እንዳያስቡ ርህራሄ እንደሚደበቅ ነገር ተደረጓ ተገልጽዋል፣ ስለዚህም ሊታይ አይችልም። ረቂቅ ስም የሆነው "ርህራሄ" ከገላጭ ጋር ሊተረጎም ይችላል። "እኔ ለእነርሱ ርህራሄ የለኝም" ወይም "እኔ ለእነርሱ ርህሩህ አልሆንም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ረቂቅ ስሞች የሚሉትን ይመልከቱ)

Hosea 13:15

አጠቃላይ መረጃ፡

ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

ወንድሞቹ

ይህ አገላለጽ በሰሜን መንግሥት ዙሪያ ለሚገኙ አገራት፣ በተለይ የደቡብ መንግሥት ለሆነው ለይሁዳ የቆመ ይመስላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የምስራቅ ነፋስ፣ የያህዌ ነፋስ ይመጣል

ከምስራቅ የሚመጣ ነፋስ በጣም ሞቃት እና አጥፊ ነበር። እዚህ ስፍራ ያህዌ የእስራኤልን ሰዎች እንዲያጠፉ ከምስራቅ የሚልካቸውን ወታደሮች ያመለክታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የኤፍሬም ምንጮች ይደርቃሉ፣ ጉድጓዶቹም ውሃ አይኖራቸውም

ሆሴዕ እግዚአብሔር እንዴት የእስራኤልን ሰዎች እንደሚቀጣ መግለጹን ይቀጥላል። እዚህ ስፍራ ውሃ ህይወትን፣ ጥንካሬን እና ብርታትን ይወክላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእርሱ ግምጃ ቤት

ይህ ሁሉንም የህዝቦች ሃብት ያመለክታል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 13:16

አጠቃላይ መረጃ፡

ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

በአምላኳ ላይ አምጻለችና ሰማሪያ ኀጢአተኛ ትሆናለች

እዚህ ስፍራ "ሰማርያ" የሚለው በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ ሀጢአተኛ የሆኑትን በከተማይቱ የሚኖሩትን ሰዎች ያመለክታል። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ይወድቃሉ

እዚህ ስፍራ "ይወድቃሉ" የሚለው መሞትን ይወከወላል። (ዩፊምዝም/የማያስድትን ቃለ ሻል ባለ ቃል መተካት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰይፍ

እዚህ ስፍራ "ሰይፍ" የሚለው የሚወክለው በጦርነት ጊዜ ሰይፍ የሚይዙ የጠላት ወታደሮችን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ትንንሽ ልጆቻቸው ተደፍጥጠው ቁርጥራጭ ይደረጋሉ፣ ነብሰጡር ሴቶቻቸው በገሃድ ይደፈራሉ

እነዚህ ሀረጋት በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፉ ይችላሉ። "ጠላት ትንንሽ ልጆቻቸውን ደፍጥጠው ይቆራርጣሉ፣ ነብሰ ጡር ሴቶችን በገሃድ ይደፍራሉ" በሚለው ውስጥ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 14

Hosea 14:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

በኀጢአታችሁ ምክንያት ወድቃችኋል

ሃጢአት መስራት እዚህ ስፍራ የተገለጸው መውደቅ እንደሆነ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቃላቶቻችሁን ይዛችሁ

ይህ ምናልባት በንስሃ የመመለስ እና የውዳ ቃላት ማለት ሊሆን ይችላል። "ኀጢአታችሁን ተናዘዙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የከንፈሮቻችን ፍሬ

አንድ ሰው የሚናገረው የከንፈሩ ፍሬ ይባላል። ዘመናዊ ቅጆዎች ለዚህ አስቸጋሪ ምንባብን የተለያዩ ትርጉሞች አሏቸው። "ቃሎቻችን እና የውዳሴ ዝማሬዎቻችን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪ በመነሳት ለአንድ ነገር ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 14:3

አጠቃላይ መረጃ፡

ሆሴዕ እየተናገረ ነው

ለእጆቻችን ስራ

እዚህ ስፍራ ሰዎች ነገሮችን የሚሰሩ ሰዎችን ለማመላከት በ"እጆቻቸው" ተወክለዋል። "ለሰራናቸው ጣኦታት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲኪ/ዘይቤያዊ አነጋጋር- የአንድን ነገር ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ።)

አባት የሌለው ሰው

ይህ አገላለጽ ምናልባት ለመላውን አገር የሚወክል ይሆናል። ይህ የእግዚአብሔርን ታላቅ ርህራሄ ያመለክታል

ርህራሄ ማግኘት

እዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር የርህራሄ ስራ አንድ ሰው በአከል አግኝቶት እንደ ሚለማመደው ነገር ተገልጸዋል። "ርህራሄ" የሚለው ረቂቅ ስም ከገላጭ ጋር ሊተረጎም ይችላል። "ርህራሄ ያለውን ማግኘት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 14:4

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እየተናገረ ነው እኔ መሸሻቸውን እፈውሳለሁ/አስቀራሉ ህዝቡ ከእግዚአብሔር መሸሹን ማስቆም የተገለጸው እርሱ እንደሚፈውሳቸው ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የእነርሱ ፊታቸውን ማዞር

የህዝቡ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ የተገለጸው በአካል ከእርሱ ፊታቸውን እንዳዞሩ ተደርጎ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ለእስራኤል እንደ ጤዛ እሆናሉ፤ እርሱም ውብ አበባ ይሆናል።

እግዚአብሔር እዚህ ስፍራ የተገለጸው ለተክሎች ተፈላጊውን እርጠበት እንደሚሰጥ ጤዛ ሲሆን፣ እስራኤል አንድ ሰው እንደሆነና እንደሚፈካ አበባ ሆኖ ቀርቧል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ዘይቤያዊ አነጋገር የሚሉትን ይመልከቱ)

እንደ ሊባኖስ ዝግባ ስር ይሰዳል

እዚህም ስፍራ እንደ ተክል የቀረበው የእስራኤል ስዕል ቀጥሏል፣ በዚህ ጊዜ ግን እስራኤል ሊባኖስ እንደምትታወቅበት እንደ ረጅም የዝግባ ዛፍ ቀርቧል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በሊባኖስ እንደሚገኝ ዝግባ ... ስሮቹ ይዘረጋሉ

ምንባቡ በተመሳሳይ ምስል ይቀጥላል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 14:7

አጠቃላይ መረጃ፡

ያህዌ እየተናገረ ነው

በጥላው ስር የሚኖረው ህዝብ ይመለሳል

የእስራኤል ህዝብ ዳግም አንደገና በእግዚአብሔር ተጠብቆ ይኖራል። እስራኤል በጥላው ስር እንደምትኖር ተገልጸዋል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ዳግም እንደ እህል ይለመልማሉ እንደ ወይን ተክል ያብባሉ

የእስራኤል አዲሱ ብልጽግናዋ በእርሻ/ግብርና ቃላት ተገልጸዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝናው እንደ ሊባኖስ ወይን ይሆናል

የሊባኖስ ወይን ታዋቂ እንደነበረ ሁሉ፣ እስራኤልም ታዋቂ ይሆናል። "በየስፍራው ያሉ ህዝቦች ስለ እስራኤል ያውቃሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በጣኦታቱ ላይ ሌላ ምን ተጨማሪ ነገር ማድረግ ይኖርብኛል?

ይህ የንባብ ክፍል የሚያጎላው ከዚህ ወዲያ የእስራኤል ህዝብ ጣኦት አምላኪነቱን እንደማይቀጥል ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሌም ቅጠሉ አረንጓዴ የሆነ ዝግባ

ዝግባ አመቱን በሙሉ ቅጠሉ አረንጓዴ የሆነ ዛፍ ነው። ይህ የሚወክለው የያህዌ ለእስራኤል ያለውን በረከት ነው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የአንቺ ፍሬ ከእኔ የሚመጣ ነው

እዚህ ስፍራ "ፍሬ" የሚወክለው ከያህዌ የሚመጣውን ማናቸውንም መልካም ነገር ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Hosea 14:9

አጠቃላይ መረጃ፡

ነቢዩ ሆሴዕ እየተናገረ ነው

እነዚህን ነገሮች የሚረዳ ብልህ እርሱ ማን ነው? ያውቃቸው ዘንድ እነዚህን ነገሮች ማን ይረዳል?

ነቢዩ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው ብልህ ህዝብ ይረዳል ደግሞም የተነገረውን ይሰማል ለማለት ነው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

የያህዌ መንገዶች ትክክል ናቸው፣ ጻድቁም በእነርሱ ይሄዳል

የያህዌ ትዕዛዛት የተገለጹት እንደሚሄዱባቸው መንገዶች ተደርገው ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Chapter 1

Joel 1:1

አጠቃላይ መረጃ

እግ/ር በሥነ-ግጥም በኢዮኤል በኩል ለእስራኤል ይናገራል

ወደ ኢዮኤል የመጣዉ የእግዚአብሔር ቃል

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር እግዚአብሔርለኢዮኤል የሰጠዉን መልዕክት ለማወጅ ነዉ። ተርጓሚ " እግዚአብሔር (ያህዌ) ለኢዮኤል የሰጠዉ መልዕክት " ወይም "እግዚአብሔር ለኢዮኤል የተናገረዉ መልዕክት " (ፈሊጣዊ ተመልከት)

ያህዌ

ይህ ስም በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር እራሱን ለህዝቡ የገለጠበት ነዉ። (በትርጉም ገፅ ላይ ያህዌ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት)

ባቱኤል

የኢዮኤል አባት (የስም ትርጉም ተመልከት)

ይህ በዘመናችሁ ወይስ በአባቶቻችሁ ዘመን ሆኖ ነበርን?

ኢዮኤል ማለት ያለበትን እንዲያደምጥ ሽማግሌዎችን እያዘጋጀ ነዉ። ይህ በዚህ መልኩ ሊተረጎም ይችላል ተርጓሚ "እንደዚህ አይነት ነበር ፈፅሞ በእናንተም በአባቶቻችሁ ላይ ሆኖ አያዉቅም (የግነት ጥያቄን ተመልከት)

ልጆቻችሁም ለኋለኛዉም ትዉልድ

የጎደሉትን ቃላት መሙላት ይኖርብህ ይሆናል። ተርጓሚ "ልጆቻችዉ ከእነርሱ በኋላ ላሉት ትዉልድ ይንገሩ "

Joel 1:4

የአንበጣ መንጋ

ብዛት ያለዉ የነፍሳት ቁጥር (ቡድን) በአንድ ላይ የሚበር በሰፊ ማሳ ላይ ያለን እህል የሚበላና እንደ ፌንጣ የሆነ ብዛት ያለዉ የነፍሳት ቡድን።

የአንበጣ መንጋ :ትልቁ አንበጣ : ፌንጣ : አባጨጌሬ

በቅድመ ተከተል እዚህ መብረር የሚችል ትልቅ አንበጣ፣በጣም ትልቅና መብረር የሚችል አንበጣ፣ ክንፍ ያለዉ አንበጣ ነገር ግን በጣም ትንሽ እና ገና የተወለደና


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚሆነው ይህ ነው። ሁሉም
የእግዚአብሄርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል
ስም የሚለው ቃል የአንድ አካል ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ይህ በገቢር መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ እግዚአብሄር ስሙን የሚጠራ ሁሉ ይድናል ። ( ፈሊጣዊ ንግግር ተመልክት)
በጽዮን ተራራ በእየሩሳሌም
ይህ ጠአንድ ቦታ ስም ነው ። ተርጓሚ - “በጽዮን ተራራ ነእየሩሳሌም”
ከቅሪቶቹ እግዚአብሄር የጠራቸው
“ይገኛሉ” የሚለው ቃል ከበፊቱ ዐረፍተ ነገር መረዳት ይቻላል። እዚህ ጋር ሊደገም ይችላል። ተርጓሚ - “ከቅሪቶቹ መካከል እግዚአብሄር የጠራቸው ይኖራሉ።”
ቅሪቶች
በመከራ ለምሳሌ ጦርነትና ጥፋት መካከል የኖሩ (የተረፉ)

Chapter 3

Joel 3:1

እነሆም
“እድምጥ ” ወይም “ትኩረት ስጥ”
በዚህ ወራት እና በዚህ ዘመን
በዚህ ወራት የሚለው ሀረግ በነዚያ ቀናት ከሚለው ሀረግ ጋር አንድ ሲሆን ይህንኑ ሀረግ ለማጠንከር ነው። ተርጓሚ “በነዚያ ወሳኝ ቀናት” ወይም “በዚያን ጊዜ”
የይሁዳን እና የኢየሩሳልምን መርኮ በምመልስበት ጊዜ
“ምርኮኞችን ወደ ይሁዳ እና ኢየሩሳሌም በምልክበት ጊዜ”
የኢዮሣፍጥ ሸለቆ
ኢዮሳፈጥ ትርጉሙ እግዚአብሔር ይፈርዳል ማለት ሲሆን የይሁዳ ንጉስ እና ከኢዮኤል በፊት የኖረ ሰው ነው። በዚህ ስም የሚታወቅ ቦታ የለም። የሸለቆው ስምም ከዚህ ኢዮሣፍጥ ከሚባለው ስም የተነሳ ሲሆን በዚህ መልኩ ቢተረጎም መልካም ነው።
ስለ ህዝቤ እና ስለ ርስቴ እስራኤል
እነዚህ ሀረጎች እንዴት እግዚአብሔር እስራኤልን እንደሚያይ እና የራሱ የሆነ ውድ ሕዝብ መሆኑን አጽንኦት ይሰጣል። ተርጓሚ - የእስራኤል ህዝብ ርስቴ (የእኔ ርስት)
ወንድ ልጅን ለጋለሞታ ዋጋ ሰጡ ሴት ልጅን ለወይን ጠጅ ሸጡ ጠጡም
የህ ከፈጸሙአቸው ድርጊቶች መካከል በእነዚህ ሁለት ልጆች ላይ ግን ምን እንዳፈፀሙባቸው አያመለክትም። ተርጓሚ ወንድ ልጅን ለጋለሞተኛ ሴት ልጅን በወይን ይጠጡ ዘንድ ለወጡአቸው።

Joel 3:4

የፍልስጥኤምም . . . ከእናነተ ጋር ለእኔ ምን አላኝ;
እግዚአብሔር የሚሠሙትን ህዝብ ሲያበረታ በሌላ ደግሞ አልሰማ ያሉትን የፍልስጥኤምን ህዝብ ደግሞ የገልጻል። የከተሞቹ ስሞች በከተማው ለሚኖሩ ህዝቦች (አህዞብ) ዘይቤአዊ ንግግር ናቸው። እነዚህ ቃላት እንደ አርፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ተርጓሚ “ፍልስጥኤም በእኔ የመናደድ መብት የለህም።”
ብድራትን ትመልሱልኛላችሁ;
“ትበቀሉኛላቹ;” እግዚአብሔር ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ህዝቡ ምን እደረገ እነዳለ እንዲያስብ ነው። ተርጓሚ “እኔ መበቀል የምትችሉ መስላችኋል ነገር ግን አትችሉም”
ፈጥኜ በችኮላ ብድራታጭሁን በራሳችሁ ላይ እመልሳለሁ
"በራሳችሁ" የሚለዉ ቃል ግለሰብን ያመለክታል እግዚአብሄር እንድተመም የፈለጉትን ህመም እርሱ እንድታመም እግዚአብሄር ያደርጋል። ተርጌሚ "ለእኔ ያሰባችሁትን ብድራት ነእናንተ ላይ አደርጋለሁ"
ብድራት
"በቀል " ወይም "መልስ መክፈል"

Joel 3:7

ተመልከት
"ትኩረት ስጥ" ወይም "አድምጥ"
እነርሱን ከሸጣችሁነት ስፍራ
የእስራኤል ህዝብ በባርነት ከነበሩበት ስፍራ ለቀዉ ወደ እስራኤል ምድር ይመለሳሉ።
ብስራታችሁንም .............. እመልሳለሁ
"የሚገባችሁን መልስ መስጠት
ወንዶችና ሴቶች ልጃችሁን በይሁዳ ልጆች እጅ እሸጣለዉ
እጅ የሚለዉ ቃል እጅ ለተለማመሰዉ ሀይል (ጉልበት) ወይም ደግሞ ለሰዉ ዘይቤአዊ አገላለፅ ሊሆን ይችላል ። ተርጌሚ "ወንዶችና ሴቶች ልጃችሁን ሸጬ ይሁዳን የራሴ አደርጋለሁ።"(ፈሊጣዊና ዘይቤአዊ ንግግር ተመልከት
የሳባ ሰዎች
የሳባ ምድር ህዝብ (የስም ትርጉም ተመልከት )

Joel 3:9

ኃያላንን አሥለሱ
"ኃያላንን ለዉጊያ ማዘጋጀት
ማረሻችሁን ሰይፍ ማጭዳችሁንም ጦር ለማድረግ ቀጥቅጡ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ ትርጉም አላቸዉ ሁለቱም የእርሻ መሣሪያዎችቻቸዉን ወደ ጦር መሣሪያ እንዲለዉጡ ያስተምራቸዋል።
ማረሻዎች (ማረሻ)
ዘርን ለመዝራት መሬት የሚታረስበት መሣሪያ
ማጥድ
ቅርንጫፎችን (እህል)ለማጨድ የሚያገለግል

Joel 3:11

ቸኩላችሁ ኑ ተሰብሰቡ
እነዚህ ቃላት በኢዮኤል 3፡9 ወስጥ ስለሚጀምረዉ ጦርነት የምፀት ጥሪ ነዉ። (ምፀት ተመልከት)
ተሰብሰቡ
ይህ መሰብሰብ ለዉጊያዉ (ጦርነት) ነዉ። ይህ በግልፅ ሲቀወጥ ተርጌሚ"እራሳችሁን ለጦርነት (ዉጊያ) አሰባስቡ"
አቤቱ ኃያላኖችህን ወደዛያ አዉርድ
ኢዮኤል ለይዉዳ ህዝብ በአህዛብ መካከል እንዳያዉጁ እየነገራቸዉ ነዉ። (ኢዮኤል 3፡9) ።ወይም ኢዮኤል የእግዛብሔርን ቃልት አቋርጦ አጠረ ያለ ፀሎት ስፀልይ ነዉ። በሁለቱም መልኩ ሊተረጎም ይችላል።

Joel 3:12

አህዛብ ይነሱ ........ በዙሪያ ባሉ አሕዛብ ሁሉ
"አህዛብ" የሚለዉ ቃልና "በዙሪያ ባሉ አህዛብ " የሚለዉ ሐረግ ስለ አንድ ህዝብ ነዉ የሚናገረዉ። እነዚህም በይሁዳ ዙሪያ ያሉ ናቸው።በኢየሩሳሌም ላይ በፈፀሙት ግፍ ምክኒያት በኢዩሳፍጥ ሸለቆ ይፈረድባቸውል።
የኤዮሳፍጥ ሸለቆ
የኢዮሳፍጥ የስሙ ትርጓሜ እግዚአብሄር ይፈረዳል ማለት ሲሆን ይህ ሰው የየረሁዳ ንጉሥ የነበረና ከኢዮኤል በፊት የኖረ ነው። በዚህ ስም የሚታወቅ ቦታ የለም ሸለቆው ከእህ ኢዩሳፍጥ ከሚባለው ሰው ስም የተነሳ መሠየሙን መተርጎም የተሻለ ነው። ( በኢዮኤል 3፡2 ላይ ትርጉም ተመልከት) ማጭድ ስደዱ
ግብፅ ምድረ-በዳ ..... ይሆናል
"ማንም በዚያ እስከማይኖር ድረስ ሁሉም ግብፅን ለቆ ይወጣል። " ሁሉም
ኤዶሚያስ በረሃ ይሆናል
ማንም ከዚህ በፊት እንዳልኖረበት ሁሉም ኤዶምን ለቆ ይወጣ።
በይሁዳ ልጆች ላይ ስላደረጉት ግፍ
ግብፅና ኤዶም የአመፅን ነገር በይሁዳ ህዝብ ላይ ስላደረጉ
በአገራቸዉ ንፁሐን ደም አፍስሰዋልና
ይህ አረፍተ ነገር የሚገለፀዉ "ኤዶም" ና "ግብፅን" ነዉ። ንፁሐን ደም የሚለዉ ሐረግ እነሱ ስለገደሏዉ ሰዎችን የገለፁበት ዘይቤአዊ ንግግር ነዉ። ተርጌሚ - "የግብፅ ህዝብና የኤዶም ህዝብ የይሁዳ ንፁሐን ሰዎችን ስለገደሉ።"

Joel 3:20

x
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጌሚ-" ሰዎች ለዘላለም በይሁዳ ይኖራሉ።"
እየሩሳሌም ለልጅ ልጅ መኖሪያ ይሆናል
ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ሰዎች በእየሩሳሌም ለዘላለም ይኖራሉ።
እኔም ንፁህ ያዳደጉትን ደማቸውን ንፁህ አዲርገዋለዉ
ደም የሞት ዘይቤአዊ ንግግር ነዉ። ተርጌሚ "እስካዛሬ ያልተቀጡ የእስራኤል ህዝብን የገዳሉ ጠለየችን እቀጣቸቀለሁ።"

Chapter 1
Amos 1:1
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር በአሞፅ አማካይነት ቀኔያዊ በሆነ ቋንቋ ይናገራል።(ቅኔያዊና ፓራሌሊዝም የሚለውን ይመልከቱ)
ከላም ጠባቂዎች መካከል የነበረው አሞፅ ስለ እሥራኤል ያየው ቃል ይህ ነው
ተቁሔ በተሰኘ ሥፍራ ውስጥ በእረኝነት ሥራ ላይ ከተሰማሩ ሰዎች መካከል አንዱ የሆነው አሞፅ የእሥራኤልን ጉዳዮች በተመለከተ የተቀበለው ራእይ ነበረ።( አክቲቭ ወይም ፓሲቭ የሚለውን ይመልከቱ)
ጉዳዮቹ እነዚህ ናቸው
“መልዕክቱ ይሄ ነው” በተቁሔ “ተቁሔ”የአንድ ከተማ ወይም መንደር ስም ነው፡
እነዚህን ነገሮች ተቀበላቸው
ይሄ በአድራጊ ግሥ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ሰጠው”(አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)
በይዳ ንጉሥ በዖዝያን ዘመን፤በእሥራኤልም ንጉስ በዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም ዘመን
“በ… ዘመን”የተሰኙት ቃላት ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን እያንዳንዱ ለንግሥናው በራሱ ፈቃድ ሥልጣኑን የሚቀቀበትን ሁኔታ የሚያመለክትነው።የአሞፅ ትርጉም “ዖዝያን የይሁዳ ንጉሥ በነበረበት ወቅትና ኢዮርብዓም የእስራኤል ንጉሥ በነበረበት ወቅት ነው”( ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የመሬት መናወጡ ከሆነበት ሁለት ዓመት በፊት
የታሰበው ቀድሞ የሰው ሰዎች ግዙፍ የሆነ የመሬት መንቀጥቀጥ በሚከሰትበት ወቅት ሊያወቁ ይችላሉ ተብሎ ነው።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ውስጣዊ ወይም ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር በፅዮን ሆኖ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጮሃል
እነዚህ ሁለት አረፍተ ነገሮች ተመሣሣይ የሆኑ ትርጉሞች ነው ያላቸው።እግዚአብሔር በአንድ አገር ላይ ፍርድን ለመፍረድ በሚዘጋጅበት ወቅት ከፍተኛ ጩኸት የሚያሠማ ስለመሆኑ ሁለቱም በጋራ አፅንኦትን ይሰጣሉ።
እግዚአብሔር ይጮሃል
ፀሐፊው የእግዚአብሔርን ድምፅ ከአንበሣ ማጓራት ጋር ወይም ከመብረቅ ድምፅ ጋር ያመሳስለዋል።(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር
ይሄ ሥም እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ለሕዝቡ የተገለፀው ሥም ነው፡ ይንንነበዘአግባቡ ለመተርጎም እንዲቻላችሁ የትርጉም ቃላትን ገፅ ይመልከቱ።
Amos 1:3
ስለሶስት ወይም ስለ አራት ኃጢአቶች
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው።ይሄ የተወሰኑ ኃጢአቶች ብቻ ናቸው የተፈፀሙት ለማለት ሣይሆን ወደ እግዚአብሔር ፍርድ እንዲያመራ ያደረገው የብዙ ኃጢአቶች ድምር መሆኑን ለማመልከት ነው።
ደማስቆ
እዚህ ላይ “ደማስቆ”የሚወክለው በደማስቆ ከተማ ውስጥ ነዋሪ የሆኑትን ሰዎች ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
እዚህ ላይ እግዚአብሔርደማስቆ በገለዓድ ላይ የፈፀመችው ነገር እህልን በብረት መንኮራኩር ወይም በመሣሪያ ከማበራየት ጋር ያመሳስለዋል።(ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ) ይመልከቱ)
ገለዓድ
እዚህ ላይ ገለዓድ የሚለው ቃል የገለዓድን ሕዝብ የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም“ የገለዓድ ሕዝብ” (ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የሚገናኙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ))
በአዛሄል ቤት ላይ እሣትን እልካለሁ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ከሚባላ እሣት ጋር በሚመሳሰልበት መልኩ በአዛሄል ቤት ላይ ፍርድን የሚያመጣ ስለመሆኑ ይናገራል።(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)
የአዛሄል ቤት
“ቤት”የሚለው ቃልበቤት ውስጥ ስለሚኖሩ ቤተሰቦች የተነገረ አባባል ነው። (ከዋናው ሃሣብ ጋር የሚገናኙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ) በዚህ አውድ መሠረት ይሄ የሚያመለክተው ደማስቆ በነበረበት ሥፍራ ላይ በአገሪቱ ላይ ገዢ የነበሩትን ትውልዶች ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የሚገናኙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የወልደ አዴርን አዳራሾች ትበላለች
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ቅጥርን ከሚበላ እሣት ጋር ተመሳስሎ ነው የተነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገሩን ይመልከቱ)
አዛሄል…ወልደ አዴር
እነዚህ የሰው ስሞች ናቸው።
Amos 1:5
ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በደማስቆ ላይ የፍርድ መልዕክቱን መናገር ይቀጥላል።
ሰውዬውን አስወግድ
እዚህ ላይ “አስወግድ”ማለት ማጥፋት ወይም ማሳደድ ማለት ነው።የልብስ ቁራጭ እንደሚቆረጥ ወይም አንድ ቅርንጫፍ ከዛፍ ላይ እንደሚቆረጥ ዓይነት ማለት ነው። የአሞፅ ትርጉም “ሰውዬውን ማጥፋት”ወይም “ሰውዬውን ማሳደድ”(-ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የአዌን ሸለቆ
ይሄ የአንድ ቦታ ሥም ሲሆን ትርጉሙም “የክፋት ሸለቆ”ማለት ነው።ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት ነገሮች ደግሞ 1/ይሄ በዚያ ግዛት ሥር የሚገኝ የአንድ ሥፍራ ስም ነው።ወይም 2/ይሄ የደማስቆ ወይም የአካባቢው ግዛት ነው።የአሞፅ ትርጉም “የክፋት ሸለቆ”
በትር የያዘውንም
ይህ የዚያ ከተማ ወይም ግዛት ገዢ የሚለው ቃል ከዋናው ሃሣብ ጋር የሚገናኙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል ነውው።የአሞፅ ትርጉም “የ….. ገዢ”
የኤደን ቤት
ይሄ የአንድ ሥፍራ ስም ሲሆን ትርጉሙም “የደስታ ቤት” ማለት ነው።ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት ነገሮች ደግሞ 1/ይሄ በዚያ ግዛት ሥር የሚገኝ የአንድ ሥፍራ ስም ነው።ወይም 2/ይሄ የደማስቆ ወይም የአካባቢው ግዛት በሌላ ቃል ሲገለፅ ነው። የአሞፅ ትርጉም “የደስታ ቤት”(ስሞችና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውሉ ቃላት እንዴት ነው መተርጎም የሚኖርባቸው? የሚለውን ይመለከቱ።)
ቂር
ይሄ የሃራም ሕዝብ ከመጀመሪያ አንስቶ የነበሩበት የአንድ ግዛት ሥም ነው።
Amos 1:6
ስለሶስትና ስለአራት ኃጢአቶች
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገርነው፡የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለት ሣይሆን ብዙ ኃጢአቶች የእግዚአብሔር ፍርድ እንዲመጣ ምክኒያት መሆናቸውን ለማመለከት ነው።እነዚህን ቃላት በአሞፅ 1:3 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ይመልከቱ።
ጋዛ
እዚህ ላይ “ጋዛ”የሚለው ቃል የሚወክለው የጋዛ ግዛትን ሕዝብ ነው። የአሞፅ ትርጉም “የጋዛ ሕዝብ”( (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ))
መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን ይጠቀማል።
“አሣልፍህ ስጣቸው”
“አሳልፈህ ስጣቸው” ወይም “ለሽያጭ አቅርባቸው”
“ኤዶምያስ”
እዚህ ላይ“ኤዶምያስ” የሚለው ቃል የኤዶምያስን አገር ሕዝብ የሚወክል ነው። የአሞፅ ትርጉም “የኤዶም ሕዝብ”(ሲኖኒምን ይመልከቱ)
አዳራሾችዋን ትበላለች
እዚህ ላይ የእግዙአብሔር ፍርድ ቅጥርን ከሚበላ እሣት ጋር ተመሳስሎ የተነገረ ነው።(ምሳሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)
Amos 1:8
ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በጋዛ ላይ ሊያመጣ ያለውን የፍርድ መልዕክት መናገሩን ይቀጥላል።
ሰውዬውን ቁረጠው
እዚህ ላይ “ቁረጠው”የሚለው ቃል ትርጉም አንድ ሰው የልብስ ቁራጭን እንደሚቆርጥ ወይም ደግሞ ቅርንጫፍን ከዛፍ ላይ እንደሚቆርጥ ማጥፋት ወይም ደግሞ ከሥፍራው ማሳደድ ማለት ነው።የአሞፅ ትርጉም “ሰውየውን አጥፋው”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ወይም“ሰውዬውን ከሥፍራው አሳድደው”(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)
በትሩን የሚይዘው ሰው
ይሄ የዚያ ከተማ ወይም ግዛት በሌላ ቃል ሲገለፅ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ገዢው”((ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ))
በአቃሮን ላይ እጄን እዘረጋለሁ
እዚህ ላይ“አቃሮን” የሚያመለክተው የአቃሮንን ከተማ ሰዎች ነው።የአሞፅ ትርጉም “የኤክሮን ሕዝብ” ((ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ))
Amos 1:9
ስለ ሶስት ወይም ስለ አራት ኃጢአቶች
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው።የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለት ሣይሆን ብዙ ኃጢአቶች የእግዚአብሔር ፍርድ እንዲመጣ ምክኒያት መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።ይሄ በአሞፅ 1:3 ላይ እንዴት እንደሚተረጎም ይመልከቱ።
ጢሮስ
እዚህ ላይ“ጢሮስ”የሚለው ቃል የሚመለክተው የጢሮስን ከተማ ሕዝብ ነው። የአሞፅ ትርጉም “የጢሮስ ሕዝብ”(ሜቶኖሚን ይመልከቱ)
መቅሰፍቴን ከማድረግ ልመለስም
እግዚአብሔር ቅጣትን ተግባራዊ እንደሚያደርግ አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን ይጠቀማል። ይሄ በአሞፅ 1:3 ላይ እንዴት እንደሚተረጎም ይመልከቱ። (በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)
የወንድማማችነታቸው ቃል ኪዳን
“እንደ ወንድማቸው ለመቁጠር የገቡት ስምምነት”
አዳራሾችዋን በእሣት ይበላል
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚነገረው ቅጥርን ከሚበላ እሣት ጋር ተመሳስሎ ነው።(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)
Amos 1:11
ስለ ሶስትና ስለ አራት ኃጢአቶች
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው። የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለት ሣይሆን ብዙ ኃጢአቶች የእግዚአብሔር ፍርድ እንዲመጣ ምክኒያት መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።ይሄ በአሞፅ 1:3 ላይ እንዴት እንደሚተረጎም ይመልከቱ።
ኤዶምያስ
እዚህ ላይ“ኤዶምስ”የሚለው ቃል የኤዶምያስን አገር ሕዝብ የሚያመለክት ነው። የአሞፅ ትርጉም “የኤዶምያስ ሕዝብ ”( ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
እግዚአብሔር ቅጣትን ተግባራዊ የሚያደርግ እንደሆነ አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን ይጠቀማል።ይሄ በአሞፅ 1:3 ላይ እንዴት እንደሚተረጎም ይመልከቱ።(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)
ወንድሙን አሳደደ
የኤዶምያስ ትውልድ ሲወርድ ሲዋርድ የመጣው የእሥራኤል ሕዝብ ዘር ከተመዘዘበት ከያዕቆብ ወንድም ከነበረው ከዔሳው እነው የሚል ግምት አለ።እዚህ ላይ “ወንድሙ”የሚለው ቃል የሚወክለው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።የአሞፅ ትርጉም “የእስራኤልን ሕዝብ አሳደደ” (ግምታዊ ዕውቀት፤ውስጣዊ ወይም ያልተገለፀ መረጃንና ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ ይመልከቱ)
ርህራሄንም ሁሉ ጥሏልና
“ርህራሄን አላሳያቸውም”
ቁጣውም ሁልጊዜ ነድዷልና፤መዓቱንም ለዘላለም ጠብቋልና
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን የቁጣውን መቀጠል አፅንዖት ለመስጠት ይደጋገማሉ።“ንዴት” እና “ቁጣ” የተሰኙት አሕፅሮተ ሥም “የንዴት” እና “የቁጣን” ቅፅል በመጠቀም ሊተረጎሙ ይችላሉ፡የአሞፅ ትርጉም“ ማቋረጫ በሌለው መልኩ ይበሳጭና ዘወትር ይቆጣ ነበር”(ተመሳሳይነትንና አሕፅሮተ ሥምን ይመልከቱ)
ቁጣውም ሁልጊዜ ነድዷልና
ይሄ የማይቋረጥ ቁጣውን ለመግለፅ በማጋነን መልክ የቀረበ ነው።(ሆን ብሎ አጋኖ መናገርንና አጠቃላይነትን ይመልከቱ)
ቴማንና ባሶራ
እነዚህ የቦታ ስሞች ናቸው።ስሞች እንዴት ሊተረጎሙ እንደሚገባ ተመልከቱ።
የባሶራን አዳራሾች በእሣት ይበላል
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ አዳራሾችን በእሣት ከሚበላ እሣት ጋር በማመሰሰል ይናገራል።(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)
Amos 1:13
ስለሶስት ወይም ስለአራት ኃጢአት
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው።የተወሰኑ ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለቱ ሣይሆን ወደ እግዚአብሔር ፍርድ እንዲያመራ ያደረገው የብዙ ኃጢአቶች ድምር መሆኑን ለማመልከት ነው።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።
መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
እግዘዚአብሔርቅጣቱ የሚጠብቃቸው ስለመሆኑ አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን እዚህ ላይ ይጠቀማል።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)
ዳርቻቸውን ያሰፉ ዘንድ
“ድንበራቸውን ማስፋት”ወይም “ግዛታቸውን ማስፋት”
Amos 1:14
ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር የፍርድ መልዕክትን በአሞን ሕዝብ ላይ መናገሩን መቀጠል።
አዳራሾችዋን በእሣት ይበላል
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ፍርድ አዳራሾችን በእሣት ከሚበላ እሣት ጋር ተመሳስሎ ይነገራል።(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)
በዓውሎ ነፋስም ቀን በጨኸት
ከአሞን ሕዝብ ጋር የሚደረገውን ግጭት ከአስፈሪ አውሎ ንፋስ ጋር ያመሳስለዋል። “ግጭቱን ከታላቅ አውሎ ንፋስ ጋር ያመሳስለዋል”(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)
ማዕበል ...አውሎ ነፋስ
እነዚህ ሁለት ዓይነት ከባድ አውሎ ነፋሣት ናቸው።
አውሎ ነፋስ
በፍጥነት በሚሽከረከርበትና በሚንቀሳቀስበት ወቅት ጥፋት ሊያደርስ የሚችል አውሎ ነፋስ
ንጉሣቸው ይማረካል
“መማረክ”የሚለው “አሕፅሮተ ሥም ተማረከ”በሚለው ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ይሄ እየተከናወነ ያለ ነገርን እንደሚያመለክት ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶቻቸው ንጉሱን በማጋዝ እስረኛ አድርገው ይወስዱታል። ”(አሕፅሮተ ሥምን፤ አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

---

# Chapter 2

## Amos 2:1

ስለ ሶስት ወይም ስለ አራት የይሁዳ ኃጢአት ስለ ሶስት ወይም ስለ አራት
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው።የተወሰኑ ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለቱ ሣይሆን ወደ እግዚአብሔር ፍርድ እንዲያመራ ያደረገው የብዙ ኃጢአቶች ድምር መሆኑን ለማመልከት ነው።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።
ሞአብ
ይሄ የሞዓብን ሕዝብ የሚወክል ነው።የአሞፅ ትርጉም “የሞዓብ ሕዝብ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ ይመልከቱ)
መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
ያእግዚአብሔር ቅጣቱ ተግባራዊ የሚሆንባቸው እንደሆነ አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን እዚህ ላይ ይጠቀማል።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)
አጥንቶችን አቃጠለ
“እነርሱ” የሚለው ቃል ሞአብን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም“የሞአብ ሕዝብ አጥንቶችን አቃጠለ”
እስከ መጨረሻ
“ወደ አፈርነት”

Amos 2:2
ሃሣብንማያያዝ
እግዚአብሔር በሞአብ ሕዝብ ላይ የፍርድ መልዕክቱን መናገሩን ይቀጥላል።
ቂርዮት
ይህ የአንድ ከተማ ሥም ነው።(ስሞችን እንዴት እንደምትተረጉሙ አስተውሉ)
ሞአብ ይሞታል
እዚህ ላይ ሞአብ የሚለው ቃል የሞአብን ሕዝብ ይወክላል።የአሞፅ ትርጉም "የሞአብ ሕዝብ ይሞታል"(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
በከፍተኛ ውካታ
ውካታና ከፍተኛ ጩኸት ነው።
በውስጧ ያለው ፈራጅ
"የሞአብ ገዢ"
አለቆቿንሁሉሉ
"ባለሥልጣናቱ በሙሉ"ወይም "መሪዎቿ በሙሉ"
Amos 2:4
ስለ ሶስት ወይም ስለ አራት
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው።የተወሰኑ ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለቱ ሣይሆን ወደ እግዚአብሔር ፍርድ እንዲያመራ ያደረገው የብዙ ኃጢአቶች ድምር መሆኑን ለማመልከት ነው።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።
ይሁዳ
ይሄ የሚወክለው የይሁዳን ሕዝብ ነው።የአሞፅ ትርጉም "የይሁዳ ሕዝብ"ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ )
መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ቅጣቱ እንደማይቀርላቸው አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን ይጠቀማል።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)
ሐሰታቸው
ይሄ አገላለፅ ምናልባትም የሐሰት አምላኮችንና ጣዖታትን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።የአሞፅ ትርጉም "ጣዖት ማምለካቸው"(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)
መንገዳቸውን ስተው ሄዱ
ጣዖታትን ማምለካቸው ሰዎች ከጀርባቸው ሆነው እንደሚከተሏቸው ዓይነት ተደርጎ ነው የተገለፀው።
የኢየሩሣሌምን አዳራሾች በእሣት ይበላል
እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ አዳራሾችን በእሣት እንደሚበላ እሣት ተመስሎ ነው የተነገረው።(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)
Amos 2:6
ስለ ሶስት ወይም ስለ አራት ኃጢአቶች
ይሄ ቅኔያዊ አነጋገር ነው።እዚህ ላይ የተወሰኑ ኃጢአቶች ተፈፅመዋል ማለቱ ሣይሆን ወደ እግዚአብሔር ፍርድ እንዲያመራ ያደረገው የብዙ ኃጢአቶች ድምር መሆኑን ለማመልከት ነው።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።
እሥራኤል
ይሄ የእሥራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ቃል ነው።
መቅሰፍቴን ከማድረግ አልመለስም
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ቅጣቱ እንደማይቀርላቸው አፅንዖት ለመስጠት ሁለት አሉታዊ ነገሮችን ይጠቀማል።እነዚህን በአሞፅ 1:3 የሚገኙትን ቃላት እንዴት እንደተረጎማችኋቸው ተመልከቱ።(በተዘዋዋሪ መንገድ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)
ቅንነት ያለው
ይሄ በአጠቃላይ ቅን ሰዎችን የሚያመለክት ነው።
ችግረኞች
ይሄ በአጠቃላይ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ይመለከታል።
Amos 2:7
ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የፍርድ መልዕክቱን ማስተላለፉን ይቀጥላል።
አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ "እነርሱ"የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።
የድሆችን ራስ በምድር ትብያ ላይ ይረግጣሉ
እሥራኤላውያን ድሆችን የሚይዙበትን አያያዝ ሰዎች መሬትን በእግራቸው በኃይል ከመርገጣቸው ጋር እያነፃፀረ ይናገራል።(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)
መርገጥ
በተደጋጋሚ በኃይልና በጭካኔ መርገጥ
ድሃው
ይሄ ድሃውን ሕዝብ በአጠቃላይ የሚመለከት ነገር ነው።የአሞፅ ትርጉም "ድሃ ሕዝብ "( አሕፅሮተ ቅፅል ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
የተጨቆኑ ሰዎችን ይገፋሉ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር የተጨቆኑ ሰዎች ተገቢ ባልሆነ መልኩ እየተያዝን ነው ብለው አቤት በሚሉበት ወቅት ሊሰሟቸው ፈቃደኛ አለመሆናቸውን የሚያሣይ ነው።(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የተጨቆኑ
ይሄ በአጠቃላይ የተጨቆኑ ሰዎችን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም "የተጨቆኑ ሰዎች" (አሕፅሮተ ቅፅል ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
ቅጣት የተጣለባቸው ሰዎች
ይሄ በአድራጊ ግሥ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም "ቅጣት የጣሉባቸው ሰዎች"(አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)
Amos 2:9
ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የፍርድ መልዕክቱን ማስተላለፍ ይቀጥላል።
ቁመቱ እንደ ዝግባ ቁመት፤ብርታቱም እንደ ኮምቦል ዛፍ
ይሄ ግነት ነው።አሞራውያን ምን ያህል ረዣዥሞችና ጠንካሮች እንደነበሩ ለመግለፅ በግዛቱ ውስጥ ከሚገኙ ረዥምና ጠንካራ ዛፎች ጋር ያነፃፅራቸዋል።የአሞፅ ትርጉም " እንደ ግዙፍ ዛፎች ጠንካራ የነበሩ" (ሆን ብሎ አጋኖ መናገርን፤አጠቃላይነትንና ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)
ዝግባ
የጥድ ዛፎች
ኮምቦል
የሾላ ዛፎች
ፍሬውንም ከላዩ ሥሩንም ከታች አጠፋሁ
አንድ ዛፍ ከላይ ወደ ታች ሊጠፋ እንደሚችል ሁሉ እንዲሁ እግዚአብሔር አሞራውያንን እንዴት ፈፅሞ እንዳጠፋቸው የሚገልፅ ነው።የአሞፅ ትርጉም "ፈፅሜ አጠፋኋቸው"(ፈሊጣዊ አነጋገርንና ምሕፃረ ቃል የሚለውን ተመልከቱ)
Amos 2:11
ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የፍርድ መልዕክቱን ማስተላለፍ ይቀጥላል።
አጠቃላይ መረጃ
"የእናንተ"እና "እናንተ"የሚሉት ጥቅሶች የእሥራኤልን ሕዝብ የሚያመለክቱ ናቸው።
ከፍ አለ
"ሹመት ሰጠው"
የእሥራኤል ሕዝብ ሆይ እንደዚህ አይደለምን?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው በተናገረው ነገር ላይ አፅንዖት ለመስጠት ነው።ይሄ አድራጊ ግሥ መልክ ሊገለፅ የሚችል ነው።የአሞፅ ትርጉም "እናንተ የእሥራኤል ሕዝብ ሆይ ያልኩት ነገር እውነት እንደሆነ ታውቃላችሁ!"(አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ንግግር
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ራሱን የሚገልፀው በስሙ ነው።የአሞፅ ትርጉም "እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው "ወይም "ይህንን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ"(አንደኛ፤ሁለተኛ፤ሶስተኛ ሰው)
Amos 2:13
ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የፍርድ መልዕክቱን ማስተላለፉን ይቀጥላል።
አጠቃላይ መረጃ
በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ "እናንተ"የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው።
አስተውል

ይሄ አንባቢው የሚቀጥለው ነገር ምን እንደሆነ ትኩረቱን እንዲያደርግ የሚያሳስብ ነው።የአሞፅ ትርጉም “አዳምጡ”ወይም “ልነግራችሁ ላሰብኩት ነገር ትኩረትን ሥጡ”

እነሆ ነዶ የተሞላች ሠረገላ እንደምትደቅቅ እንዲሁ አደቅቃችኋለሁ

በእሥራኤል ሕዝብ ላይ እግዚአብሔር የሚፈርደውን ፍርድ የሚያነፃፅረው ከባድ በሆነ ነገር ከመፍጨት ጋር ነው።

ደካማ… ብርቱ ፤ኃያል

እነዚህ ቅፅል ስሞች በአጠቃላይ ሕዝብን የሚያመለክቱ ናቸው።የአሞፅ ትርጉም “ደካማ… ብርቱ ፤ኃያል”ወይም ደግሞ “ደካማ ሰው… ብርቱሰው፤ኃያል ሰው” (አሕፅሮተ ቅፅል ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 2:15

ሃሣብን ማያያዝ

እግዚአብሔር በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የፍርድ መልዕክቱን ማስተላለፍ ይቀጥላል።

ቀስተኛውም አይቋቋምም

እዚህ ላይ“መቋቋም” ሲባል አንድን ሥፍራ በጦርነት መያዝ ማለት ነው።

በሩጫ ፈጣን የሆነ ሰው አያመልጥም

ሊነገር ያታሰበው መረጃ በሩጫ ፈጣን የሆነ ሰው እንኳን ከጠላት አያመልጥም ለማለት ነው።የአሞፅ ትርጉም “ፈጣን ሯጭ የሆነውም ይማረካል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ የሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ራቁት ሆኖ መሸሽ

ከዚህ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ ትርጉሞች 1/ “መሣሪያውን እንደያዘ ሮጠ”የሚል ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ ወይም 2/ዝም ብለን በግርድፉ የምናነበው ከሆነ ደግሞ “ልብሱን ሳይለብስ ሮጠ”ማለትም ነው።( ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ ይመልከቱ)

በዚያን ቀን

“በዚያን ጊዜ”

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ በራሱ ሥም ነው የሚናገረው።በአሞፅ 2:111 ላይ ይሄንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። የአሞፅ ትርጉም “እግዚአብሔር የተናገረው ይሄንን ነው” ወይም “ይህንን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ”(የመጀመሪያውን ሁለተኛውን ወይም ሶስተኛውን አካል ተመልከቱ)

---

Chapter 3

Amos 3:1

እንዲህ ይላል

“ይህንን መልዕክት አዳምጡ”ወይም “ይሄንን መልዕክት ስሙ”

እግዚአብሔርእናንተን በመቃወም ተናግሯል… በአጠቃላይ ወገኑን በመቃወም

“እግዚአብሔር ስለ እናንተ የተናገረው ይሄ ቃል … በአጠቃላይ ስለ ወገኑ”ወይም “እግዚአብሔር ለእናንተ ያለው መልዕክት….ስለ ወገናችሁ በአጠቃላይ”

እናንተ የእሥራኤል ልጆች ሆይ …. ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ ወገን ሁሉ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ስለሆኑ ሁለት ሕዝቦችን የሚያመለክቱናቸው። የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚላቸው ከግብፅ ምድር የወጡትን ትውልዶች ነው።

ወገን ሁሉ

እዚህ ላይ “ወገን ሁሉ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው መላ አገሪቱን ነው። የእሥራኤል ሕዝቦች ሁሉ የያዕቆብ ትውልዶች ናቸው።የአሞፅ ትርጉም “አገሪቱ በአጠቃላይ”ወይም “ነገዱ በአጠቃላይ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከምድር ወገን ሁሉ እናንተን ብቻችሁን አውቄችኋለሁ

ይሄ ሊታዘዙለት ይገባቸው እንደነበረ የሚያመለክት ነው።ይሄ ግልፅ በሆነ መልኩ ሊነገር ይችላል።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትንና ግልፅ የሆነ መረጃ የሚለውን የሚለውን ይመልከቱ)

የምድር ነገዶች ሁሉ

እዚህ ላይ “ነገዶች”የሚለው ቃል አገራትንና ሕዝብን ይወክላል።የአሞፅ ትርጉም “በምድር ላይ ያሉ አገራት ሁሉ”ወይም “በምድር ላይ የሚገኙ ነገዶች ሁሉ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ስላደረጋችሁት ኃጢአት ሁሉ እበቀላችኋለሁ።

የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንዳልተቀበሉ በግልፅ ማወቅ ይቻላል።የአሞፅ ትርጉም “ነገር ግን አልታዘዛችሁኝም።ስለሆነም ስላደረጋችሁት ኃጢአት ሁሉ እቀጣችኋለሁ።”( በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ የሆነ መረጃ የሚለውን)

በእውነት እግዚአብሔር ሳይናገር ምንም ነገር አይፈፅምም።…ነቢያት

ይሄ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “በእውነትም እግዚአብሔር አምላክ ነገርን ወደ ግልፅ ያመጣዋል…ምንም ነገር ከማድረጉ በፊት ለነቢያት ይናገራል”ወይም “እግዚአብሔር ሰዎችን የሚቀጣው ለአገልጋዮቹ ለነቢያት ዕቅዱን ካሳወቀ በኋላ ነው።”( ሁለት አሉታዊ ነገሮች የሚለውን ይመልከቱ)

አንበሣ ሲያገሳ የማይፈራ ማን ነው?

አሞፅ አንበሣ በሚያጓራበት ወቅት ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ሰዎችን በጥያቄ መልክ ያሳስባል።ይሄ እንደ መግለጫ ሊወሰድ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “አንበሣው አግስቷል፤ስለሆነም ሁሉም ሰው እንደሚፈራ እናውቃለን።”ወይም “አንበሳ ስላገሳ በእርግጥም ሰው ሁሉ በፍርሃት ይዋጣል።”(የተሳካ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 3:7

ጌታ እግዚአብሔር ተናገረ፤ትንቢትን የማይናገር ማነው?

አሞፅ ይህንን ጥያቄ እዚህ ላይ የሚጠይቀው እግዚአብሔር በሚናገርበት ወቅት ነቢያት የሚያደርጉትን ነገር በተመለከተ ሕዝቡ አስቀድመው ስላወቁት ነገር አፅንዖት ለመስጠት አስቦ ነው።ይሄ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊወሰድ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “እግዚአብሔር አምላክ ስለተናገረ ነቢያት እንደሚተነብዩ እናውቃለን።”ወይም“እግዚአብሔር አምላክ ተናግሯል፤ከዚህ የተነሣ በእርግጥም ነቢያት ይተነብያሉ።”

Amos 3:9

ተሰብሰቡ

ይሄ ትዕዛዝ በአዛጦንና በግብፅ ስላሉት ጠላቶች የተሰጠ ትዕዛዝ ነው።

ይሄ የእግዚአብሔርአዋጅ ነው

“እግዚአብሔር ያወጀው ይህንን ነው”ወይም “ያህዌ በለሆሳስ ያለው ይህንን ነው”ይሄ ሐረግ በሌላው መልዕክት ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ እውነተኛ መሆኑን የሚገልፅ ነው።

በመካከልዋም ያለውን ግፍ ተመልከቱ

“በመካከልዋም”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰማርያን ከተማ ነው።ከተማዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠሩ የነበሩት በሴት ፆታ ነበር።(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)

በመካከልዋም ያለውን ግራ መጋባት ተመልከቱ

እዚህ ላይ “በመካከልዋም ያለውን ግራ መጋባት ተመልከቱ” የሚለው ቃል በዚያ በሚካሄደው ጦርነትና አመፅ መካከል ሰዎች ያለባቸውን ፍርሃት ለማመልከት ነው።“ግራ መጋባት ”የሚለው ቃል ግልፅ የሆነ ትርጉም እንዲይዝ ለማድረግ በግሣዊ ሐረግ መተርጎም ይቻላል።የአሞፅ ትርጉም “በሰማርያ የሚገኙ ሰዎች እንዴት እንዳመፁ”ወይም “የሰማርያ ሰዎች እርስ በእርሳቸው እንዴት እንደተዋጉ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀት፤ግልፅ የሆነ መረጃ የሚለውንና አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ምን ዓይነት ነው?

“በውስጧ ያለው ጭቆና”የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው በሰማርያ ውስጥ ሰዎችን ስለሚጨቁኑ መሪዎች ነው።የሆነው “ጭቆና”የሚለው አሕፅሮተ ሥም “መጨቆን”ወይም “ለሥቃይ መዳረግ”ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። (አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

ትክክለኛ የሆነ ነገርን ማድረግ አያውቁበትም

እዚህ ላይ “አመፅና ጥፋት”የሚለው ቃል ነገሮችን በአመፅና በማውደም መንጠቅን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “ከሌሎች ላይ በአመፅ የነጠቁትን ገሮች ያከማቻሉ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 3:11

ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

ይሄንን ለማን ለመናገር እንደፈለገ በግልፅ ማስቀመጥ ይቻላል፤የአሞፅ ትርጉም “ስለሆነም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በሠማርያ ለሚኖሩ እሥራኤላውያን የሚናገረው ይህንን ነው።”

ምድሪቱን ጠላት ይከብባታል።



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ምድሪቱ በጠላት ትከበባለች
አዳራሾችዋን ይበዘብዛሉ
“በአዳራሾቻችሁ ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ ይሰርቃሉ።”
እረኛ ከአንበሣ አፍ እንደሚድን…እንዲሁየእሥራኤልን ሕዝብ ይታደጋል
ጌታ እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ መታደግ አንድን እንስሳ ከአንበሣ አፍ ለማዳን ሊሳካ ካልቻለ ጥረት ጋር ያነፃፅረዋል።በከፊል ይድናሉ።(ተነፃፃሪነት የሚለውን ይመልከቱ)
እረኛ ከአንበሣ አፍ ውስጥ ሁለት እግሮችን ወይም የጆሮ ጫፍን ብቻ እንደሚያድን
እዚህ ላይ እረኛው የእንስሳውን ሙሉ አካል ለማስጣል ሙከራ ስለማድረጉ ነው የሚገልፀው።የአሞፅ ትርጉም “እረኛው እንስሳውን ከአንበሣ አፍ ለማስጣል የሞከረ ቢሆንም ለማዳን የቻለው ግን ሁለት እግርና የጆሮን ጫፍ ብቻ ነው።”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ውስጣዊ ወይም ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ እረኛው … አንበሳው
እዚህ ላይ“እረኛው” እና “አንበሳው”የተሰኙት ሐረጎች ማንኛውንም እረኛና አንበሳ የሚያመለክቱ ናቸው።(የመጀመሪያ ሥም(ሰዋሰው) ሐረጎች የሚለውን ተመልከቱ)
የአልጋ ማዕዘን ብቻ ይቀርላቸዋል
ይሄ ሐረግ ሙሉ በሙሉ ሊድኑ የማይችሉ መሆኑን ነው የሚያሣየው።ንብረታቸው ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ የሚሰረቅ ይሆናል።ይህንን ክፍል በዕብራይስጥ ቋንቋ ለመረዳት አስቸጋሪ ሲሆን አንዳንድ የዘመኑ የትርጉም ቅጂዎች ግን ለየት ባለ መንገድ ይተረጉሙታል።
መከዳ
ይሄ ሰው ሊጋደምበት የሚልና ልስላሴ ያለው ትልቅ ወንበር ነው።
Amos 3:13
የያዕቆብ ቤት
“ቤት”የሚለው ቃል በቤት ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች በሌላ ቃል ለመጥራት የሚውል ነው።በዚህ ሁኔታ ይሄ የሚያመለክተው የያዕቆብን ትውልድ ነው ። የእሥራኤል ሕዝብ ነበሩ።የአሞፅ ትርጉም “የያዕቆብ ትውልዶች”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ሥሙን እየጠራ ስለ ራሱ ይናገራል።“ይሄ የሠራዊት የእግዚአብሔር ንግግር ነው የሚለውን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ” በአሞፅ 2፡11 ላይ ያለውን።የአሞፅ ትርጉም “የሠራዊት የሆነው ጌታ እግዚአብሔር ያወጀው ይህንን ነው ” ወይም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው።” (መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛውን ክፍል የሚለውን ይመልከቱ።)
የእሥራኤልን ኃጢአት በምበቀልበት ቀን
“የእሥራኤልን ኃጢአት ስቀጣ”
የቤቴልን መሠዊያዎች እበቀላለሁ
ሰዎች የሐሰት ጣዖታትን በየመሰዊያዎቻቸው በማምለካቸው በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትን ሠርተዋል።እዚህ ላይ “መሠዊያዎችን አፈርሳለሁ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕዝቡን እንደሚቀጣና ጣዖቶቻቸውን የሚያጠፋ መሆኑን ነው። የአሞፅ ትርጉም “በቤቴል ውስጥ የሚገኙትን ጣዖታት አጠፋለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ተመልከቱ)
የመሠዊያው ቀንዶች ይሰበራሉ ወደ ምድርም ይወድቃሉ
ይሄ አድራጊ ግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶች የመሠውያውን ቀንዶች ይሰብራሉ፤ቀንዶችም በምድር ላይ ይወድቃሉ” (አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)
የመሠዊያውን ቀንዶች
ሰዎች ጣዖታትን በየመሠዊያዎቻቸው ያመልኩ ነበር።በየመሠዊያዎቹ የማዕዘን ጫፍ ላይ የወይፈን ቀንዶች ምስል ነበረባቸው።እነዚህ ቀንዶች የጣዖቶቻቸው ጥንካሬ መገለጫዎች ነበሩ።
Amos 3:15
የክረምት ቤትና የበጋ ቤት
አንዳንድ ባለፀጋ የሆኑ ሰዎች በአንደኛው ቤታቸው ውስጥ በክረምት ወራት የሚኖሩበት ሲሆን በሁለተኛው ቤታቸው ውስጥ ደግሞ የበጋ ወራት በሚሆንበት ወቅት ይኖሩበታል።ይሄ ማንኛውንም የክረምትና የበጋ ቤቶችን ያመለክታል።የአሞፅ ትርጉም“የመጀመሪያ ሥም(ሰዋሰው) ሐረጎች የሚለውን ተመልከቱ ”
በዝሆን ጥርስ የተሰሩት ቤቶች ይጠፋሉ
እግዚአብሔር ቤቶቹ ሕይወት እንዳላቸውና ሟቾች እንደሆኑ በመቁጠር ይናገራቸዋል።የአሞፅ ትርጉም “በዝሆን ጥርስ የተሰሩት ቤቶች ይጠፋሉ”(ግዑዝ ነገሮች ሕይወት እንዳላቸው ተደርገው ሲገለፁ የሚለውን ይመልከቱ)
በዝሆን ጥርስ የተዋቡ ቤቶች
“በዝሆን ጥርስ የተዋቡ ቤቶች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በየግድግዳዎቻቸውና በቤት ቁሣቁሶቻቸው ላይ በዝሆን ጥርስ የተዋቡትን ነገሮች ነው።የዝሆን ጥርስ እጅግ ውድ ከመሆኑ የተነሳ በዝሆን ጥርስ የተዋቡ ቁሣቁሶች ያሏቸው ሰዎች ባለፀጋ የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው።
የዝሆን ጥርስ
የግዙፍ እንስሳት ጥርሶችና ቀንዶች
ታላላቅ ቤቶችም ይፈርሳሉ
“ትላልቅ ቤቶች አይኖሩም”እዚህ ላይ “ይፈርሳሉ”የሚለው ቃል የሚወክለው ፈፅመው ይደመሰሳሉ የሚለውን ነው።
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የተናገረው ነገር እውነት ስለመሆኑ ማረጋገጫ ለመስጠት ራሱን በተመለከተ በራሱ ሥም ይናገራል።“እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው” ወይም “ሥላሴዎችየተናገሩት ይህንን ነው።” (የመጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

---

# Chapter 4

## Amos 4:1

እናንተ የባሳን ላሞች ሆይ ፤እናንተ በሰማርያ ተራሮች ላይ የምትኖሩ
አሞፅ በሰማርያ ለምትኖር እሥራኤላዊ ሴት ውስጥ ከጠገቡ ላሞች ጋር በማመሳሰል ይነግራታል።የአሞፅ ትርጉም “በሰማርያ ተራራ ላይ የምትኖሩ እናንተ ባለፀጋ የሆናችሁ ሴቶች፤ ከጠገቡ የባሳን ላሞች ጋር የምትመሳሰሉ”(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)
ድሆችን የምትጨቁኑ
“ድሆች”የሚለው ቃል ድሃ የሆኑ ሰዎችን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “እናንተ ድሃ ሰዎችን የምትጨቁኑ”(አሕፅሮተ ቅፅል ሥምን ይመልከቱ)
ችግረኞችን የምታስጨንቁ
“ማስጨነቅ”የሚለው ቃል ሰዎችን መልካም ባልሆነ አያያዝ መያዝን የሚያመለክት ነው።“ችግረኞች”የሚለው ሐረግ ዕርዳታ የሚሹ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። የአሞፅ ትርጉም “እናንተ ችግረኞችን የምታስጨንቁ”ወይም “የተቸገሩ ሰዎችን የምትጎዱ”(ምሣሌያዊ አነጋገርና አሕፅሮተ ቅፅል ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
ጌታ እግዚአብሔር በቅዱስነቱ ምሏል
ይሄ ማለት እግዚአብሔር አንድ ነገር ለማድረግ ቃል መግባቱንና የገባውን ቃል የሚፈፅመው ቅዱስ በመሆኑ ነው ማለት ነው።
እነሆ ቀን በእናንተ ላይ ይመጣል
“እናንተ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሰማርያ ውስጥ የሚገኙ የእሥራኤል ሴቶችን ሲሆን ወንዶቹንም ያካትታል።
እነርሱ እናንተን በመቃጥን የሚወስዱበት ቀን ይመጣል
ቀናቶቹ ራሣቸው ጥቃት የሚፈፀሙባቸው ይመስል በሕዝቡ ላይ ክፉ ነገሮች እንደሚመጡ ይናገራል።“እነርሱ”የሚለው ቃል ጠላቶቻቸውን የሚያመለክት ነው። የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶቻችሁ እናንተን በመጠንቆ የሚወስዱበት ጊዜ ይመጣል” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በወጥመድ ጠምደው ይወስዷችኋል፤ቅሬታችሁንም በዓሣ መያዣ መንጠቆ ይይዛችኋል
በመሠረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሣሣይ የሆነ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ሰዎች ልክ እንደ ዓሣ በሰዎች ሊያዙ እንደሚችሉ አፅንዖት የሚሰጥ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ልክ እንስሳ እንደሚያዝ ይዘው ይወስዷችኋል”ወይም ደግሞ “ክፉኛ ያሸንፏችሁና በጭካኔ እየጎተቱ ይወስዷችኋል”(ንፅፅርንን እና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

## Amos 4:3

ሃሣብን ማያያዝ
እግዚአብሔር ለእሥራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል
በሬማንም ትጣላላችሁ
ይሄ እንደ አድራጊ ግሥ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ወደ ሬማንም ይጥሏችኋል”ወይም “እንድትሄዱ ያስገድዷችኋል” (አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሬማን

ይሄ የማናውቀው የአንድ ቦታን ሥም ወይም የሬማን ተራራ የሚያመለክት ነው፡፡ አንዳንድ ዘመናዊ የሆኑ ቅጂዎች በዚያ መልኩ ይተረጉሙታል፡፡(ሥሞችን እንዴት እንደምትተረጉሙ ተመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለመግለፅ እግዚአብሔር ስለራሱ የራሱን ስም በመጥቀስ ይናገራል፡፡እነዚህን ቃላት በአሞፅ 2፤11 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡የአሞፅ ትርጉም "እግዚአብሔር የተናገረው ይህንን ነው"ወይም "እኔ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው"(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል የሚለውን)

Amos 4:4

ሃሣብን ማያያዝ

እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን መናገሩን ይቀጥላል

አጠቃላይ መረጃ

እግዚአብሔር በቁጥር 4 ላይ አጠቃላይ የሆኑ ትዕዛዛትን የሚሰጥ ቢሆንም ይህንን የሚያደርገው ግን መቆጣቱን ለመግለፅ ነው፡፡

ወደ ቤቴል ሄዳችሁ ኃጢአትን ሥሩ፤ወደ ጌልጌላ ሄዳችሁ ኃጢአትን አብዙ

ሰዎች መሥዋዕትን ለማቅረብ ወደ ቤቴልና ወደ ጌልጌላ የሚሄዱ ቢሆንም ይሄንን የሚያከናውኑት ግን ኃጢአትን በመፈፀም ጭምር ነበር፡፡እግዚአብሔር ይሄንን ትዕዛዝ የሚያስተላልፈውእነዚህን ተግባራት በመፈፀማቸው በእነርሱ ላይ ቁጣውን ለመግለፅ ነው፡፡እነዚህ ትዕዛዛት በመግለጫ መልኩ ሊገለፁ ይችላሉ፡፡የአሞፅ ትርጉም "እናንተ ወደ ቤቴል የምትሄዱት ለአምልኮ ቢሆንም ኃጢአትን ታደርጋላችሁ፡፡አምልን ለማድረግ ወደ ጌልጌላ ትሄዳላች የምትሄዱት ግን የበለጠ ኃጢአትን ለማድረግ ነው፡፡"(ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

በየማለዳውም መሥዋዕታችሁን፤በየሦስተኛውም ቀን አሥራታችሁን አቅርቡ…በፈቃዳችሁም የምታቀርቡትን አውጁና አውሩ

እግዚአብሔር ይህንን ትዕዛዝ የሚያስተላልፈው ምንም እንኳን እነዚህን መልካም የሚመስሉ ነገሮችን ቢያደርጉም በሌላ በኩል ኃጢአት መሥራታቸውን ባለማቋረጣቸው ነው፡፡እነዚህ ትዕዛዛት እንደ መገለጫ ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡የአሞፅ ትርጉም"መሥዋታችሁን አምጡ …በየሶስተኛውም ቀናት የምሥጋና መሥዋዕትን ሰው፤የምታቀርቡትንም አውጁና አውሩ"(ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)

በየሶስተኛውም ቀናት

ከዚህ ጋር ሊስማሙ የሚችሉ ትርጉሞች 1/በሶስተኛው ቀን ወይም 2/በየሶስት ቀናት፡፡ እሥራኤላውያን አሥራታቸውን በየሶስት ዓመቱ ያወጡ ስለነበረ አንዳንድ ቅጂዎች "በየሶስት ዓመት"ይሉታል፡፡

አውጁት

"ከእነርሱ የተነሣ ኩሩ"

እናንተ የእሥራኤል ሕዝብ ሆይ ይሄ ያረካችኋል

እግዚአብሔር በሚሰጡት ሥጦታና በሚሰውት መሥዋዕት ስለሚኩራሩ ይገስፃቸዋል፡፡እግዚአብሔር ደስ ይለዋል ብለው ቢያስቡም እርሱ ግን ደስ አልተሰኘባቸውም፡፡የአሞፅ ትርጉም "የእሥራኤል ሕዝብ ሆይ ይሄ ያስደስታችኋል እኔን ግን አያስደስተኝም"(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለመግለፅ እግዚአብሔር በራሱ ሥም ይናገራል፡፡ በአሞፅ 2፤11 ላይ ይሄንን ተመሳሳይ ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡ የአሞፅ ትርጉም "ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው"ወይም "ይህንን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ"(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል)

Amos 4:6

ሐሣብን ማያያዝ

እግዚአብሔር ለእሥራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል፡፡

የጥርስ ማጥራትንአደረግኩላችሁ

እዚህ ላይ የጥርስ ማጥራት የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጥርስን ሊያቆሽሽ የሚችል ምግብ በአፍ ውስጥ አለመግባቱን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም "እንድትራቡ አደረግኋችሁ" ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እንጀራን ማጣት

"እንጀራን ማጣት" ሰጠኋችሁ የሚለው ቃል እንጀራ እንዲያጡ ምክኒያት እንደሚሆንባቸው መግለፁ ሲሆን "እንጀራ"የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው በአጠቃላይ የምግብ ዘርን ነው፡፡

ወደ እኔ አልተመለሳችሁም

ወደ እግዚአብሔር መመለስ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራስን እንደገና ለእርሱ ማስገዛትን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም "እንደገና ለእኔ አልተገዛችሁም" (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለመግለፅ እግዚአብሔር በራሱ ሥም ይናገራል፡፡ ይናገራል፡፡እነዚህን ቃላት በአሞፅ 2፤11 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡"ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይሄንን ነው"ወይም "ይሄንን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ"(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል)

ዝናብም ከለከልኳችሁ

"በሰብላችሁ ላይ ዝናብ እንዳይዘንብ ከለከልኩ"

መከርን ለመሰብሰብ ገና ሶስት ወራት ሲቀሩ

ሕዝቡ ዝናብ እንደሚያስፈልጋቸው በግልፅ ሊነገር ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም "መከር ለመሰብሰብ ገና ሶስት ወራት በቀረበት ወቅት ሰብሎቻችን ዝናብ ያስፈልጋቸው ነበር" (በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንዱ ወገን ዝናብ ዘንቧል

ይሄ በአድራጊ ግሥ ሊገለፅ ይችላል፡፡"አንዱ ወገን"የሚለው ቃል የሚወክለው ማንኛውንም የተወሰነየመሬት ክፍል ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም "በቁራጭ መሬት ላይ ዘነበ"ወይም "በተወሰኑ የመሬት ክፍሎች ላይ ዘነበ" (አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝናብ ያልዘነበበት ምድር

ይሄ የሚያመለክተው ዝናብ ያልዘነበበትን ማንኛውንም ሥፍራ ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም "ዝናብ ያልዘነበበት የተወሰ የመሬት ክፍል" (የመጀመሪያ ሥም(ሰዋሰው) ሐረጎች የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 4:8

ሁለት ወይም ሶስት የተጎዱ ከተማዎች

እዚህ ላይ "ከተማዎች" የሚለው ቃል የሚመለክተው የዚያ ከተማ ነዋሪዎችን ነው፡፡ የአሞፅ ትርጉም "የሁለት ወይም የሶስት ከተማ ሕዝቦች ተንገዳገዱ፡፡"(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በዋግውና በአረማሞ መታኋችሁ

እዚህ ላይ "መታኋችሁ"የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰብላቸውን መውደም ነው፡፡"የአሞፅ ትርጉም "እህላችሁን በዋግና በአረማሞ መታሁባችሁ"ወይም"እህላችሁን በዋግና በአረማሞ ደመሰስኩት"(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ዋግ

ይሄ ዕፅዋትን የሚደርቅና የሚገድል ነገር ነው፡፡

ወደ እኔ አልተመለሳችሁም

"ወደ እግዚአብሔር መመለስ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራስን ለእግዚአብሔር ፈፅሞ እንደገና ማስገዛትን ነው፡፡ይሄንን በአሞፅ 4፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም"ራሳችሁን እንደገና ፈፅሞ አላስገዛችሁልኝም፡፡" (ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለመግለፅ እግዚአብሔር በራሱ ሥም ይናገራል፡፡ እነዚህን ቃላት በአሞፅ 2፤11 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡"ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው"ወይም "ይህንን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ"(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል)

Amos 4:10

በግብፅ እነደነበረው ቸነፈርን ሰደድኩባችሁ

"በግብፅ ላይ እንዳደረግኩት እንዲሁ በእናንተም ላይ ቸነፈርን ላክሁ"ወይም "በግብፅ ላይ ቸነፈርን እንደላክሁ እንዲሁ በእናንተም ላይ ቸነፈርን እልካለሁ"

ቸነፈርን ላክሁባችሁ

"በእናንተ ላይ አሰቃቂ ነገር እንዲሆንባችሁ አደረግኩ"

ጎበዛዝታችሁን በሠይፍ ገደልኩ

እዚህ ላይ"በሠይፍ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጦርነትን ነው፡፡እግዚአብሔር ጠላቶች እንዲነሱባቸውና እንዲዋጉዋቸው በማድረግ በሕይወት እንዳይኖሩ አደረጓቸው፡፡አሞፅ ትርጉም"ጠላቶቻችሁ በጦርነት ወቅት ሰዎቻችሁን እንዲገድሉ አደረግኳቸው፡፡" (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል

የሚለውን ይመልከቱ)

ፈረሶቻችሁን ሁሉ በመማረክ ይዘው ሄዱ

እግዚአብሔር ጠላቶቻቸው ፈረሶቻቸውን እንዲወስዱ ማድረጉን ልክ ራሱ እንደፈፀመው ዓይነት አስመስሎ ይናገራል፡፡የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶቻችሁ ፈርቾችሁን እንዲወስዱባችሁ አደረግኩ፡፡”

የሠፈራችሁንም ግማት ወደ አፍንጫችሁ እንዲወጣ አደረግኩ

ግማት መጥፎ የሆነ ሽታ ነው፡፡ግማቱ እስከ አፍንጫቸው ደረሰ መምጣቱ የሚያመለክተው ፈፅሞ ደስ የማይል ነገር እያሸተተቱ መሆናቸውን ነው፡፡ሽታው የሚመጣው ከሞቱ ሰዎች አካል እነደሆነ በግልፅ ያመለክታል፡፡የአሞፅ ትርጉም “በሠፈራችሁ ውስጥ ደስ የማይል የሞቱ ሰዎችን አካላት እንድታሸቱ አደረግኳችሁ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእሣት ውስጥ እንደ ተነጠቀ ትንታግ

እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሚናገረው በዚያ በጦርነትና በችነፈር ወቅት ልክ አንድ ሰው በትርን ከእሣት ጎትቶ እንደሚያወጣ በሕይወት ተርፈው ያሉትን ሰዎች የሚመለከት ነው፡፡(አንድ ሰው ከእሣት ውስጥ ጎትቶ እንደሚያወጣው በትር አንዳንዶቻችሁ በሕይወት ቆያችሁ፡፡) (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እኔ አልተመለሳችሁም

ወደ እግዚአብሔር መመለስ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራስን ለእርሱ እንደገና ፈፅሞ ለእግዚአብሔር ማስገዛትን ነው፡፡ይሄንን በአሞፅ 4፡6 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡የአሞፅ ትርጉም“ራሳችሁን እንደገና ፈፅሞ አልተገዛችሁልኝም፡፡” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

የተናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለመግለፅ እግዚአብሔር በራሱ ሥም ይናገራል፡፡ እነዚህን ቃላት በአሞፅ 2፤11 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡“ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው”ወይም “ይህንን የተናገርኩት እኔ እግዚአብሔር ነኝ”(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል)

Amos 4:12

ሃሣብን ማያያዝ

እግዚአብሔር ለእሥራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል፡፡

አምላካችሁን ለመገናኘት ተዘጋጁ

እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርገው በእሥራኤል ሕዝብ ላይ ፍርድ እንደሚፈርድባቸው ለማስጠንቀቅ ነው፡፡(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካልና )

እነሆ ተራራሮችን የሠራ …የልቡንም ሃሣብ የሚገልፅ..ስሙ…ነው

እዚህ ላይ አሞፅ ስለ እግዚአብሔር እንደሚናገር ወይም እግዚአብሔር ስለራሱ እንደሚናገር ግልፅ አይደለም፡፡እግዚአብሔር ስለ ራሱ የሚናገር ከሆነ “እኔ” ወደሚሉ ቃላት ሊተረጎም ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም “እኔ ተራራሮችን የምሰራ.....ሃሣቤን የምገልፅ…ስሜ …. ነው፡፡”(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካልና በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትየሚለውን ይመልከቱ )

ንጋትን ጨለማ የሚያደርግ

ከዚህ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ ትርጉሞች 1/እግዚአብሔር የቀን ብርሃን እያለ ከባድ ደመና በማምጣት ቀኑን ድቅድቅ ጨለማ ሊያደርገው ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም “ማለዳን ጨለማ ሊያደርግ ይችላል፡፡”ወይም 2/እግዚአብሔር ቀናት በአስቸኳይ እንዲያልፉ በማድረግ እያንዳንዱ ቀን ጨለማ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡የአሞፅ ትርጉም “ማለዳና ምሽት ያደርጋል”

በምድር ከፍታዎች ላይ የሚረግጥ

እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ ገዢ እንደመሆኑ በምድር ከፍታዎች ላይ የሚራመድ እንደሆነ ይናገራል፡፡የአሞፅ ትርጉም “በምድር ሁሉ ላይ ይገዛል”ወይም “በምድር ላይ የሚገኙትንና ከፍታ ያላቸውን ቦታዎች እንኳን ይገዛል፡፡”(ምሣሌያዊን አነጋገርን ይመልከቱ)

ስሙ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው

ሙሉ ስሙን በማወጅ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች እንደሚፈፅም ይናገራል፡፡ ቋንቋችሁ ሰዎች ይህንን እንዲያደርጉ የሚያደርግበት መንገድ ሊኖረው ይችላል፡፡

---

Chapter 5

Amos 5:1

የእሥራኤል ቤት

“ቤት”የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች የተሰጠ ሌላ ቃል ነው፡፡በዚህ ሁኔታ የእሥራኤልን ትውልድ ያመለከታል፡፡የአሞፅ ትርጉም “እናንተ የእሥራኤል ሕዝብ”ወይም “እናንተ የእሥራኤል ነገዶች”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የእሥራኤል ድንግል ወደቀች …ከእንግዲህ ወዲህ አትነሣም

“ድንግሊቷ እሥራኤል”የሚለው ቃል የእሥራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ነው፡፡አንድ ወጣት ልጅ በውድቀት ውስጥ ሆና የሚታደጋት ሰው እንዳጣች ዓይነት የእሥራኤል ሕዝብ የሚጠፋ እንደሆነና ዳግም ጠንካሮች ሆነው እንዳይወጡ የሚያግዛቸው አገር እንደማይኖር ነው የሚናገረው፡፡ኤቲ “የእሥራኤል ሕዝብ እንደወደቀች ወጣት ልጅ…ከውድቀቷ የሚያነሳት አንድ ሰው እንኳን የለም”(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

በራሷ አገር ተገፍታለች

ይሄ በአድራጊ ግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም “ሰዎች ትተዋታል” ወይም “እግልለዋታል”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ )

Amos 5:3

ሺህ ከሚወጣባት ከተማ መቶ ይቀርላታል፤መቶም ከሚወጣባት ከተማ ለእሥራኤል አሥር ይቀርላታል

እነዚህ ሐረጎች ብዙ ወታደሮችን የሚልኩ ከተማዎችን የሚያመለክት ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “በሺዎች የሚቆጠሩ ተዋጊዎችን ይዛ የወጣች ከተማ …በመቶዎች የሚቆጠሩ ተዋጊዎችን ይዛ የወጣች”(የመጀመሪያ ሥም(ሰዋሰው) ሐረጎች የሚለውን ይመልከቱ)

በሺዎች የሚቆጠሩ ተዋጊዎችን ይዛ የወጣች ከተማ… በመቶዎች የሚቆጠሩ ተዋጊዎች ብቻ ይቀሩላታል

“በሺዎች”እና “በመቶዎች” የሚሉት ሐረጎች እስከ ሺህና እስከ መቶ የሚደርሱ ወታደሮች መኖራቸውን የሚያመለክት ነው፡፡(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ መቶ ተዋጊዎች ይቀርላታል

“ግድያ ያልተፈፀመባቸው መቶ ተዋጊዎች ይኖራችኋል”ወይም “በሕይወት የሚኖሩ መቶ ተዋጊዎች ብቻ ይኖራችኋል፡፡”እዚህ ላይ “ይቀርላታል” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በጠላት እጅ ያልተገደሉትን ነው፡፡

Amos 5:4

እኔን ፈልጉኝ

እዚህ ላይ“ፈልጉኝ”የሚለው ቃል ወደ ቤቴል በመሄድ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው መጠየቅን የሚያመለክት ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ዕርዳታ ለመሻት ወደ ቤቴል አትሂዱ”(ምሣሌያዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

ወደ ጌልጌላም አትግቡ

“እና ወደ ጌልጌላ አትግቡ”

በእርግጥ ጌልጌላ በምርኮነት ትወሰዳለች

እዚህ ላይ “ጌልጌላ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጌልጌላን ሕዝብ ሲሆን “በምርኮነት መወሰድ” የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው በምርኮኛነት ተይዞ መወሰድን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም“በእርግጥ ጌልጌላ በምርኮነት ትወሰዳለች”ወይም “በእርግጥም ጠላቶቻችሁ የጌልጌላን ሕዝብ በኃይል በመያዝ ይዘዋቸው ይሄዳሉ፡፡”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀት የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቴልም ከንቱ ትሆናለች

እዚህ ላይ “ከንቱ ትሆናለች”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጥፋቷን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ቤቴል ፈፅሞ ትጠፋለች”ወይም “ጠላቶች ቤቴልን መሉ ለሙሉ ያወድሟታል”(ምሣሌዊ አነጋገርን ይመልከቱ)

Amos 5:6

እግዚአብሔርን ፈልጉት

እዚህ ላይ “እግዚአብሔርን ፈልጉት” የሚለው ቃል ከእርሱ ዕርዳታን መፈለግን የሚያመለክት ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጥሩት”ወይም “እኔ እግዚአብሔርን ለዕርዳታ ጠይቁኝ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እሣት ይነሳል

“እንደ እሣት ይነሳል”የሚለው ቃል የሚወክለው እሣት ነገሮችን እንደሚያጠፋ እንዲሁ የነገሮችን መውደም ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም ተነፃፃሪ”

የዮሴፍ ቤት

ይሄ ሐረግ ለዮሴፍ የዘር ሐረግ እንደ ሌላ ስም የተሰጠ ነው፡፡እዚህ ላይ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሚያመለክተው አብዛኛው የዘር ሐረጋቸው ከዮሴፍ ትውልድ የሆኑትንና በሰሜኑ የእሥራኤል ግዛት የሚገኙትን ነገዶች ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “የዮሴፍ ትውልዶች”ወይም “እሥራኤል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ይበላል
“እርሱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እሣቱን ሲሆን “ይበላል” የሚለው ቃል የሚመለክተው ደግሞ ሁሉንም ነገር ፈፅሞ የሚያጠፋ መሆኑን ነው፡፡እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የሚያጠፋ መሆኑን ለማመልከት እሣት ሁሉንም ነገር ከማጥፋቱ ጋር ተነፃፅሯል፡፡የአሞፅ ትርጉም “ሁሉን ነገር ያጠፋል”ወይም “ሙሉ በሙሉ ያጠፋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሚያቆመው ሰው አይኖርም
“የሚያቆመው አይኖርም”ወይም “ሁሉንም ነገር ለማጥፋት የሚያቆመው ነገር አይኖርም”
ፍርድን ወደ እሬት ነገር ለወጡ
እዚህ ላይ “እሬት”የሚለው ቃል የሚወክለው ሰዎችን የሚጎዳ ድርጊትን ሲሆን “ፍርድን ወደ እሬት ነገር ለወጡ”የሚለው ቃል ደግሞ መልካም ነገርን ከማድረግ ይልቅ ሰዎችን የመጉዳትን ሃሣብ የሚያመለክት ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ፍትሃዊ የሚመስል ነገርን እያደረጉ እነርሱ ግን ሰዎችን ይጎዳሉ”ወይም “ትክክለኛ የሆነውን ነገር እየተቃወሙ ከዚያ በተቃራኒው ሰዎችን የሚጎዳ ነገርን ይሰራሉ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ፅድቅንም በምድር ላይ ይጥላሉ
ይሄ የሚያመለክተው ፅድቅን እንደማይረባ ነገር መቁጠራቸውን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ፅድቅን አስፈላጊ እንዳልሆነ ቆሻሻ ነገር መቁጠር”ወይም “ፅድቅ የሆነውን ነገር ትፀየፉላችሁ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Amos 5:8
ሰባቱን ከዋክብትና ኦርዮን የተባለውን ኮከብ
ሰዎች በሰማይ ከዋክብት ላይ ያለሉን ሥርዓቶች በመመልከት ስም አውጥተውላቸዋል፡፡ሁለቱ ሥርዓቶች እነዚህ ናቸው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ከዋክብቶቹ” እና“የከዋክብት ክምችቶቹ” (ያልታወቁ ነገሮችን ይመልከቱ)
የሞትን ጥላ ወደ ንጋት የሚለውጠው …ቀኑንም በሌሊት የሚያጨልመው
“የሌሊቱን ጨለማ ማለዳ ያደርገዋል እንዲሁም ቀኑን ጨለማ ያደርገዋል” ይሄ ለወቅቶች የጊዜ መለዋወጥ ምክኒያት የሚሆነውን የሚያመለክት ነው፡፡
የባህሩንም ውሆች ጠርቶ በምድር ላይ የሚያፈስሳቸውን
ይሄ የሚያመለከተው እግዚአብሔር የባህርን ውሃ በዝናብ መልክ በምድር ላይ እንዲዘንብ ማድረጉን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “የባህር ውሆችን ይወስድና በምድር ገፅ ላይ እንዲዘንቡ ያደርጋቸዋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስሙ እግዚአብሔር ነው
እግዚአብሔር ስሙን በሚያውጅበት ወቅት እነዚህን ነገሮች ተግባራዊ ለማድረግ ኃይሉንና ሥልጣኑን ነው የሚያውጀው፡፡
በብርቱዎች ላይ ድንገተኛ ጥፋትን ያመጣል
“ጥፋት” የሚለው አሕፅሮተ ሥም “ጥፋት ይመጣል”ከሚለው ግሥ አንፃር ሊተረጎም ይችላል፡፡“ብርቱዎች”የሚለው ቃል ጠንካራ የሆኑ ሰዎችን በተለይም ወታደሮችን የሚያመለክት ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “በብርቱዎች ላይ ድንገተኛ ጥፋትን ያመጣል”ወይም “ወታደሮቹን በድንገት ያጠፋቸዋል”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
ጥፋት በተቀጠረ ቅጥር ላይ ይመጣ ዘንድ
“ጥፋት” የሚለው -አሕፅሮተ ሥም“ጥፋትን አደረገ”ከሚለው ግሥ አንፃር ሊተረጎም ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም “ቅጥሮቹ ይደመሰሱ ዘንድ”ወይም “ቅጥሮቹን ያፈርሳል”(አሕፅሮተ ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
Amos 5:10
ማንኛውንም ሰው ይፀየፋሉ
“የእሥራኤል ሕዝብ ማንኛውንም ሰው ይፀየፋሉ፡፡”
እናንተ ድሃውን ረግጣችኋልና የስንዴውንም ቀረጥ ከእነርሱ ወስዳችኋልና
“እናንተ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሕዝብ ነው፡፡እዚህ ላይ “እየረገጣችሁ”የሚለው ቃል ደሃ የሆኑ ሰዎች መጥፎ በሆነ ሁኔታ መያዛቸውን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም“ ድሃ ሰዎችን በከፍተኛ ደረጃ እየጨቆናችሁ የተወሰነ ስንዴ ትወስዱባቸዋላችሁ፡፡”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የተወሰነውን የስንዴ ክፍል ከእርሱ ውሰድ
“የተወሰነውን የስንዴ ክፍል እንዲሰጥህ አድርገው”
ድንጋይን ሰሩ
“ድንጋዮችን መጥረብ”ወይም “ሰዎች የጠረቧቸው ”
የእነርሱን የወይን ጠጆች አትጠጡም
“የእነርሱ ” ቃል የሚያመለክተው የወይን እርሻዎችን ነው፡፡ይሄ በመሠረቱ ማንም ሰው ወይንን እንደማይጠምቅና ወይንን ለመጥመቅ ቢፈልጉ እንኳን መልካም የሆነ የወይን ፍሬ ሊገኝ እንደማይችል ለማመልከትም ሊሆን ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም“በወይን እርሻዎቻችሁ ውስጥ ከሚገኙ ወይኖች ለራሳችሁ ወይንን አትጠምቁም”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Amos 5:12
እውነተኛየሆኑ ሰዎችን አስጨንቁ፤ጉቦን ተቀበሉ እንዲሁም የተቸገረውን ወደ በሩ አደባባይ ውሰዱ
እነዚህ ጥቂት የሆኑ የሰራቸው የኃጢአቶቻቸው ዝርዝሮች ናቸው፡፡
ትክክለኛ
“ትክክለኛ” የሚለው ቃል እውነተኛ የሆኑ ሰዎችን የሚያመለክት የአሕፅሮተ ቅፅል ሥም(ሰዋሰው) ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ትክክለኛ ሰዎች”ወይም “ፃድቅ ሰዎች”( አሕፅሮተ ቅፅል ሥም የሚለውን ይመልከቱ)
ጉቦን ተቀበሉ
“ሰዎች ክፉ ነገሮችን እንድትሰሩ ለማድረግ ጉቦን ይክፈሏችሁ”ወይም “ሰዎች ስለሌላ ሰዎች በውሸት እንድትናገሩ ገንዘብ ይክፈሏችሁ”
የተቸገረውን ወደ ከተማው አደባባይ ውሰዱ
እዚህ ላይ “የተቸገረውን ወደ ከተማው አደባባይ ውሰዱ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ድሃ ሰዎች ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲሄዱ ማስገደድን ነው፡፡ድሃ ሰዎች በከተማው አደባባይ የሆኑበትን ምክኒያት ግልፅ ለማድረግ ይቻላል፡፡የአሞፅ ትርጉም “ድሃ ሰዎች በከተማ ደጅ ውስጥ ለሚገኙ ዳኞች ጉዳያቸውን እንዳያቀርቡ አድርጉ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)
የተቸገሩ ሰዎች
“የተቸገሩ ሰዎች” የሚለው ቃል የተቸገሩ ሰዎችን የሚያመለክት አሕፅሮተ ቅፅል ሥም ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም“የተቸገሩ ሰዎች”(አሕፅሮተ ቅፅል ሥምን ይመልከቱ)
አስተዋይ የሆነ ሰው ሁሉ ዝምይላል
ክፉ ሰዎች እንዳይጎዷቸው የሚፈልጉ ሰዎች ክፉ ሥራዎቻቸውን ተቃውመው ከመናገር ተቆጥበዋል፡፡የአሞፅ ትርጉም “አስተዋይ ሰዎች ክፉ ሰዎች የሚያደርጉትን ክፉ ነገሮች ከመናገር ተቆጥበዋል፡፡”
ክፉ ዘመን ነውና
እዚህ ላይ“ክፉ ዘመን”የሚለው ቃል ሰዎች ክፉ መሆናቸውንና ክፉ ተግባር መፈፀማቸውን የሚያመለክት ነው፡፡(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል)
Amos 5:14
መልካሙን እሹ፤ ክፉውን ነገር ተፀየፉ
“ክፉ ሥራዎችን ተፀየፉ፤መልካም የሆኑ ሥራዎችን ውደዱ” “መልካም” እና “ክፉ”መልካም የሆኑ ድርጊቶችንና ክፉ የሆኑ ድርጊቶችን ይወክላሉ፡፡
በከተማው አደባባይ ፍትህን አድርጉ
እዚህ ላይ “ፍትህን አድርጉ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ፍትህ ስለመረጋገጡ እርግጠኛ መሆንን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም“በከተማው አደባባይ ላይ ፍትህ መከናወኑን እርግጠኛ ሁኑ” ወይም “በእነዚህ የከተማ አደባባዮች ላይ ዳኞቹ ፍትህን ስለ ማድረጋቸው እርግጠኞች ሁኑ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በከተማው አደባባይ ላይ
የከተማው የአደባባይ ደጆች ወፍራምና ጠንካራ በመሆናቸው ሰዎች ከሞቃቱ የፀሐይ ትኩሣት ራሣቸውን የሚያስጠልሉበት ከመሆኑም ባሻገር የንግድ ልውውጥ የሚደረግባቸውና ዳኝነት የሚሰጥባቸው ሥፍራዎች ነበሩ፡፡ የአሞፅ ትርጉም “በፍርድ አደባዮቻችሁ”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ )
የዮሴፍ ቅሬታ
እዚህ ላይ “ቅሬታ”የሚለው ቃል ሌሎቹ ከተገደሉና በምርኮ ከተወሰዱ በኋላ በእሥራኤል አገር ውስጥ የሚቀሩትን ሰዎች የሚያመለክት ነው፡፡እዚህ ላይ “ዮሴፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው አብዛኛዎቹ የዮሴፍ የዘር ሐረግ የሆኑትን በሰሜን ክፍል ያለውን የእሥራኤል ግዛት ነው፡፡ በአሞፅ 5፤6 ላይ “የዮሴፍ ቤት”የሚለውን ቃል እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡የአሞፅ ትርጉም “እስከ አሁን ድረስ በሕይወት ያሉ የዮሴፍ የዘር ሐረጎች”ወይም “በሕይወት የተረፉ እሥራኤላውያን” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል

የሚለውን ይመልከቱ)
Amos 5:16
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
“የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይሄንን ነው”
በየመንገዱ ሁሉ ላይ ወዮ ወዮ ይባላል
“ሰዎች በየሜዳው ያለቅሳሉ”
ዋይታ
ረዥም ጊዜ የሚወስድ፤ከፍተኛ ድምፅ ያለበት የሚያሳዝን ለቅሶ
በበሩ አደባባይ
በከተማ ውስጥ የሚገኙና ሰዎች የሚሰባበሰቡባቸው ሠፋፊ ሥፍራዎች
አልቃሾችም ወደ ዋይታ ይጠራሉ
“ይጠራሉ”የሚለው ቃል ከዓረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ጀምሮ ሃሣቡ ግልፅ ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “አልቃሾችን እንዲያለቅሱ ይጠሯቸዋል”(ምልክቶች እንጂ ቃላት ጥቅም ላይ የማይውሉበት የሚለውን ይመልከቱ)
በመካከላችሁ አልፋለሁ
እግዚአብሔር በተወሰኑ ሰዎች መካከል ወቅት ወደ እነርሱ እንደሚመጣና በመካከላቸው እያለፈ የሚቀጣቸው በሚመስል መልኩ ይናገራል፡፡የአሞፅ ትርጉም “መጥቼ እቀጣችኋሁ”ወይም “እቀጣችኋለሁ”
Amos 5:18
የእግዚአብሔር ቀን እንዲመጣ ለምን ትናፍቃላችሁ?
እግዚአአብሔር ይሄንን ጥያቄ የእግዚአብሔር ቀን በፍጥነት እንዲመጣ በመናፈቃቸው ሊገስፃቸው የተናገረው ነው፡፡ይሄ እንደ መግለጫ ሊገለፅ ይችላል፡፡ የአሞፅ ትርጉም “የእግዚአብሔርን ቀን ናፈቃችሁ” ወይም “የእግዚአብሔርን ቀን መናፈቅ የለባችሁም”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ተመልከቱ)
ጨለማ ነው እንጂ ብርሃን አይሆንም
እዚህ ላይ“ጨለማ”የሚያመለክተው ጥፋት የሚከሰትበትን ወቅት ሲሆን “ብርሃን”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ደግሞ መልካም ጊዜ የሚከሰትበትን ወቅት ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “የጨለማና የጥፋት ጊዜ እንጂ የብርሃንና የበረከት ጊዜ አይሆንም”ወይም “በዚያን ዕለት ጥፋት እንጂ በረከት አይኖርም”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
በውኑ የእግዚአብሔር ብርሃን ሣይሆን ጨለማ አይደለምን?
ይሄ ጥያቄ አፅንዖት የሚሰጠው መጥፎ ነገሮች የሚከናወኑ መሆኑን ነው፡፡እንደ መግለጫ ሊገለፅ ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም “የእግዚአብሔር ቀን በእርግጥም ጨለማ እንጂ ብርሃን አይሆንም”ወይም “በእግዚአብሔር ቀን በእርግጥ መልካም ያልሆኑ ነገሮች ይከሰታሉ”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ተመልከቱ)
ድቅድቅ ጨለማ እንጂ ብርሃን አይሆንም
“በውኑ የእግዚአብሔር ቀን”የሚሉትን ቃላት ከቀደመው ዓረፍተ ነገር መረዳት ይቻላል፡፡ከዚህ በፊት እንደነበረው ጥያቄ በእግዚአብሔር ቀን አሰቃቂ ነገሮች፤መልካም ያልሆኑ ነገሮች እንደሚከሰቱ አፅንዖት ሰጥቶ ይናገራል፡፡ይሄ አንደ መግለጫ ሊነገር ይችላል፡፡“መልካም ነገር ሣይሆን ክፉ ነገሮች የሚከሰቱበት ጊዜ ይሆናል፡፡”(በሙያ የታገዘ ጥያቄንና ተመሣሣይነት የሚለውን ተመልከቱ)
Amos 5:21
ዓመት በዓላችሁን ጠልቼዋለሁ፤ተፀይፌዋለሁም
“ዓመት በዓላችሁን”የሚለው ቃል “ጥላቻ”ለሚለው ቃል ትልቅ መግለጫ ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ቃላት በጋራ ሲነገሩ እግዚአብሔር ዓመት በዓላቸውን ምን ያህል እንደጠላው ትልቅ ማሣያ ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ዓመት በዓላችሁን በጣም እጠላዋለሁ”
የተቀደሰውም ጉባዔያችሁ ደስ አያሰኙኝም
“የተቀደሱት ጉባዔዎቻችሁ ደስ አያሰኙኝም”
Amos 5:23
የዝማሬህንም ጩኸት ከእኔ ዘንድ አርቅ
ይሄ የዝማሬው ጩኸት ልክ እነደ ዕቃ ወደ ሌላ ሥፍራ ሊወሰድ የሚችል በሚመስል መልኩ ነው የተገለፀው፡፡ይሄ የሚያመለክተው ዝማሬው መቆም ያለበት መሆኑን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “የጩኸት ዝማሬያችሁን መዘመሩን አቁሙ”
ጩኸት
ደስ የማሰኝ ድምፅ
ነገር ግን ፍርድ እንደ ውኃ፤ፅድቅም እንደማይደርቅ ፈሳሽ ይፍሰስ
ይሄ ቃል የሚያመለክተው ብዙ ፍትህና ፅድቅ እንዲኖር ምክኒያት ስለመሆን ነው፡፡ የአሞፅ ትርጉም “እንደሚፈስስ ውኃ ይሆን ዘንድ ብዙ ፍትህ ይኑር፤ሳያቋርጥ እንደሚፈስስ ምንጭ ይሆን ዘንድ ፅድቅ ይኑር” ወይም “ፍትህ እንደ እንደ ፈሳሽ ይክበብ፤ፅድቅም እንደማይቋረጥ ምንጭ ይክበብ፡፡”(ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Amos 5:25
እሥራኤል ሆይ መሥዋዕትን አቅርባችሁኛልን?
የዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ 1/እግዚአብሔር ይሄንን ጥያቄ ያነሣው መሥዋዕትን ባለማቅረባቸው ሊገስፃቸው ፈልጎ ነው ወይም ደግሞ 2/እግዚአብሔር ይሄንን ጥያቄ ያነሣው ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ መሥዋዕት እጅግ አስፈላጊው ነገር እንዳልሆነ ሊያሳስባቸው ፈልጎ ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም“እሥራኤል ሆይ መሥዋዕት ልታመጡልኝ አያስፈልጋችሁም ነበር” (በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ተመልከቱ)
አቅርባችሁኛልን?
እግዚአብሔር እየተናገራቸው ያሉትን እሥራኤላውያን የሚናገራቸው ልክ በበረሃ ሲጓዙ ከነበሩት ወገኖች ጋር እንደነበሩ አስመሰሎ ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “የቀደሙት አባቶቻችሁ አምጥተውልኛል?” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ )
የእሥራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ወስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ሌላው ሥም ነው፡፡በዚህ አውድ ውስጥ ይሄ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ትውልዶች ነው፡፡በአሞፅ 5:1 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ፡፡የአሞፅ ትርጉም“እናንተ የእሥራኤል ቤት ሆይ” ወይም “እናንተ የእሥራኤል ነገድ የሆናችሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የሞሎክን ድንኳንና የሬፋን ኮከብ አነሳችሁ
እዚህ ላይ“ኮከብ አነሳችሁ”የሚለው ቃል እነርሱን ማምለካቸውን የሚያመለክት ነው፡፡“የሞሎክን ኮከብ አነሳችሁ …የሬፋንንንም”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ሞሎክ …ሬፋን
እነዚህ የሁለት ጣዖታት ሥሞች ናቸው፡፡ሰዎች እነርሱን እንዲወክሏቸው ጣዖታትን ቀርፀዋል፡፡(ሥሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ ተመልከቱ)
ሬፋን
አንዳንድ ቅጂዎች ይሄንን“ኪዩም”ብለው ይተረጉሙታል፡፡
Amos 5:27
መዋቅር ያለውና በሕግ የተገደበ
ከቁጥር 9 እና 10 በስተቀር ይሄ ምዕራፍ በቅኔያዊ ዘይቤ መፃፉን ይቀጥላል፡፡ እነዚህ ሁለት ጥቅሶች ብዙ ሳቢ የሆኑ ገፅታዎችን ያዘሉ ናቸው፡፡
በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሌሎች አስቸጋሪ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች
ሁኔታው ግልፅ ባለመሆኑና ዝርዝር ነገሮቹን በቀላሉ ማግጣጠም አስቸጋሪ በመሆኑ ቁጥር 9-10ን ለመተርጎም አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡እነዚህን ጥቅሶች በአግባቡ ለመተርጎም ከቀሩት አንዳንድ አጠራጣሪ ነገሮች ጋር አይያዞ መተርጎሙ ይበጃል፡፡ እነዚህን ጥቅሶች ከመተርጎም በፊት በቅድሚያ የተለያዩ ቅጂዎችን ማንበቡ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

Chapter 6
Amos 6:1
ተዘልለው ለተቀመጡ
“ተዘልለው የተቀመጡ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች ምቹ ሁኔታ ውስጥ ከመኖራቸው የተነሣ ስለ እግዚአብሔር ፍርድ ብዙም ትኩረት የማይሰጡ መሆኑን ነው፡፡
ምርጥ የሆነው አገር ውስጥ የሚኖሩ የተከበሩ ሰዎች
“በዚህ ታላቅ አገር ውስጥ የሚኖሩ የተከበሩ ሰዎች”የሚለው ቃል ምናልባትም እግዚአብሔር እነዚህ ሰዎች ስለራሣቸው ያላቸውን አስተሳሰብ በተመለከተ በምፀት የሚናገረው ነገር ሊሆን ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም “ምርጥ በሆነ አገር ውስጥ ምርጥ የሆንን ሰዎች ነን ብለው የሚያስቡ ሰዎች”
የእሥራኤልም ቤት ይመጣል
“ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች እንደ አጠቃላይ መጠሪያ ነው፡፡በዚህ አውድ አንፃር የእሥራኤልን የዘር ሐረግ የሚመለከት ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም“የእሥራኤል ነገድ እየመጣ ነው፡፡” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን

ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ሊረዳ መጣ
እዚህ ላይ“መጣ” የሚለው ቃል “ይሄዳል”ተብሎ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ለመርዳት ይሄዳል” (መሄድና መምጣት የሚለውን ተመልከቱ)
ካልኔ
ይሄ የከተማ ሥም ነው።(ሥሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ ተመልከቱ)
ከሁለቱ መንግሥታቶች ይልቅ የተሻሉ ናቸውን?
ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ይህንን ጥያቄ ከሌሎች መንግሥታት ይልቅ የእሥራኤልና የይሁዳ መንግሥታት የተሻሉ ናቸው የሚለውን ሃሣብ አፅንዖት ለመስጠት ይጠቀሙበታል። የአሞፅ ትርጉም “የእናንተ ሁለት መንግሥታት ከእነርሱ ይልቅ የተሻሉ ናቸው”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ድንበራችሁ ከድንበራቸው ይልቅ ይሰፋልን?
ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ይህንን ጥያቄ ከሌሎች መንግሥታት ይልቅ የእነርሱ መንግሥታት የተሻሉ ናቸው የሚለውን ሃሣብ አፅንዖት ለመስጠት ይጠቀሙበታል።የአሞፅ ትርጉም“ከእናንተ ይልቅ ድንበሮቻቸው ያነሱ ናቸው”ወይም “እነዚያ አገራት ከይሁዳና ከሰማርያ ይልቅ አነስተኞች ናቸው።”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Amos 6:3
ክፉውን ቀን ከእናንተ ለምታርቁ
እግዚአብሔር ጥፋትን ሊያመጣ አይችልም የሚል አስተሳሰብን ልክ ሰዎች “የጥፋት ቀንን” እንደ ዕቃ ከአጠገባቸው ዘወር እንደሚያደርጉት ዓይነት ነገር ተገልጿል።የአሞፅ ትርጉም “ይሄንን ለማመን የማይፈልጉትን ሰዎች ጥፋትን እንዲለማመዱ አደርጋቸዋለሁ።” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የግፍንም ወንበር ለምታቀርቡ
እዚህ ላይ “ወንበር” የሚለው ቃል ግዛትንንና መግዛትን የሚያመለክት አጠቃላይ ሥም ነው።እዚህ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ጥፋትን እንዲያመጣ ክፉ ሥራዎችን የሚሰሩ ሰዎች “አመፅን” በመሥራት አመፁ ራሱ በላያቸው ላይ እንዲሰለጥን እንደፈቀዱ ተደርጎ ነው የተገለፀው።የአሞፅ ትርጉም “ለመሆኑ ክፉ የሆኑ ሰዎች እንዲያጠፏችሁ እንደልክ ምክኒያት የሆኑት ሰዎች እነማን ይሆኑ?” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውለውን ቃል ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ለምትተኙ...በምንጣፋችሁ ላይ
በዚያን ወቅት እስራኤላውያን ምግባቸውን የሚመገቡት መሬት ላይ በተነጠፈ ጨርቅ ላይ ወይም ተራ የሆነ መቀመጫን በመጠቀም ነበር።
በዝሆን ጥርስ የተሰሩ አልጋዎች
“በዝሆን ጥርስ የተዋቡ አልጋዎች” ወይም “ውድ የሆኑ አልጋዎች”
የዝሆን ጥርስ
ግዙፍ ከሆኑ እንስሳት የሚገኙ ነጭ ጥርሶችና ቀንዶች (የማይታወቁ የሚለውን ትርጉሙት)
ምንጣፍ
እንደ ሰነፍ ሰዎች መተኛት
መከዳ
ለመተኛት የሚበቃ ለስላሣ የሆነ መቀመጫ
Amos 6:5
የዜማን ዕቃ የምታዘጋጁ
ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1/አዳዲስ ዝማሬዎችንና እነዚህን ዝማሬዎች በሙዚቃ መሣሪያዎች ለመጫወት አዳዲስ ፈጠራዎችን ይፈጥራሉ።2/አዳዲስ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ይሰራሉ።
በፉጋ ወይን ጠጅ ይጠጣሉ
ይሄ የሚያመለክተው ከተለመደው የወይን መጠጫ ይልቅ ትልቅ የወይን መጠጫን ስለሚጠቀሙ ብዙ ወይንን ይጠጣሉ የሚለውን ነው።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውለውን ቃልና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ ዮሴፍ መከራ አያዝኑም
እዚህ ላይ“ዮሴፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የዘር ሐረጉን ነው።የአሞፅ ትርጉም “በቅርብ ጊዜያት ውስጥ በጠላቶቻቸው ስለሚጠፉት የዮሴፍ ትውልዶች አያዝኑም”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
Amos 6:7
ስለዚህ በምርኮ መጀመሪ ይማረካሉ
“ወደ ምርኮ ከሚጋዙት ሰዎች የመጀመሪያዎቹ ይሆናሉ”ወይም “በመጀመሪያ በምርኮነት እልካቸዋለሁ”
ተደላድለው ከተቀመጡበት ዘንድ ዘፈን ይርቃል
“ተዘልለው ድግስ የሚደግሱበት ምቹ የሆነ ጊዜ አይሆንላቸውም”
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ እግዚአብሔር ስለራሱ በራሱ ሥም ይናገራል።በአሞፅ 3፤143 ላይ ይሄንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። የአሞፅ ትርጉም“ይሄ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ነው”ወይም “ይሄ እኔ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተናገርኩት ቃል ነው።”(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካል የሚለውን ይመልከቱ)
የያዕቆብን ትዕቢት ተፀይፌያለሁ
እዚህ ላይ “ያዕቆብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የያዕቆብን ትውልድ ነው። የአሞፅ ትርጉም “ማስተዋል የሌላቸው ከመሆናቸው የተነሣ የያዕቆብን ቤት ተፀየፍኩ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
አዳራሾቹንም ጠልቻለሁ
እግዚአብሔር አራሾቻቸውን የጠላው አዳራሾቻቸው ለሠላማችን መሠረቶች ናቸው ብለው ስለሚምኑ ነው።የአሞፅ ትርጉም “የእሥራኤልን ሕዝብ የጠላሁበት ምክኒያት በእኔ ሣይሆን በአዳራሾቻቸው ስለሚታመኑ ነው።”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ግልፅ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)
Amos 6:9
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር የእሥራኤልን ሕዝብ ለጠላቶቻቸው አሣልፎ በሚሰጥበት ወቅት ሊፈጠሩ ይችላሉ ብሎ የገመታቸውን ሁኔታዎች በአሞፅ 6፡9-10 ላይ ይገልፀዋል። (ግምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)
አሥር ሰዎች በአንድ ቤት ውስጥ ቢቀሩ እነርሱ ይሞታሉ
ይሄ የሚያመለክተው አሰቃቂ ነገር እንደሚከናወንና እነዚህ አሥር ሰዎች ለመደበቅ ወደ ቤት ውስጥ የሚገቡ መሆኑን ነው።የአሞፅ ትርጉም“አሥር ሰዎች ቤት ውስጥ የሚደበቁ ቢሆኑም እንኳን እነርሱም ይሞታሉ።”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አጥንቱንም ከቤቱ ያወጡ ዘንድ የሰው ዘመድና አቃጣዩ ባነሱት ጊዜ በቤቱም ውስጥ ያለውን እስከ አሁን ድረስ ገና ሰው በአንተ ዘንድ አለን? ባለው ጊዜ...
የእነዚህ ቃላት ትርጉም ግልፅ አይደለም።ለእነዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/ “የሰዎቹ ቤተሰብ” የሚባለው ሰው “አካላቸውን ወስዶ” “ሬሣቸውን የሚያቃጥለውን” ሰው ሲሆን ይህ ሰው አሥሩ የቤተሰቡ አባላት ሕይወት ካለፈ በኋላ በቤት ውስጥ ተደብቆ ከነበረ ሰው ጋር እየተነጋገረ ነው ወይም 2/ “ሬሣቸውን ለመውሰድ የሚመጣው ሰው”“የሰዎቹ የቅርብ ዘመድ”“ሬሣውን ከሚገንዘው ሰው የተለየ ሰው ነው”እርስ በእርሳቸውም በቤት ውስጥ ይነጋገራሉ።የአሞፅ ትርጉም“የሰዎቹ የቅርብ ዘመዶች ሬሣዎቹን ወስደው ከቤቱ ውስጥ ከወጡ በኋላ ሬሣዎቹን የሚያቃጥለው ሰው ደግሞ ከእነርሱ ጋር አብሮ ይሄዳል...በቤት ውስጥ በነበሩበት ወቅት ቅርብ ዘመዳቸው የሆነው ሰው ሬሣዎቹን ለሚያቃጥለው ሰው “በአንተ ዘንድ አለን?”ብሎታል።
ሬሣን ማቃጠል የሞተን የሰው አካል ማቃጠል ሬሣዎችን ማምጣት
“የሞተ አካልን መሰብሰብ”
የእግዚአብሔርን ሥም እንጠራ ዘንድ አይገባንምና ዝም በል ይለዋል
የዚህ ትርጉም ግልፅ አይደለም።ይሄ ጥያቄውን የጠየቀው ሰው ፍርሃት እንደያዘውና የሚመልሰውም ሰው የእግዚአብሔርን ሥም በግድየለሽነት እንደሚጠራ ነው የሚያመለክተው።ይህንን የሚያደርግ ከሆነ የእግዚአብሔርትኩረት ወደ እርሱ በመሳብ በሕይወት እንዳይኖሩ ሊያደርጋቸውም ይችላል።(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ )
Amos 6:11
ተመልከቱ
“ስሙ”ወይም “ትኩረታችሁን ወደዚህ አድርጉ”
ታላቁንም ቤት በማፍረስ፤ታናሹንም ቤት በመሰባበር ይመታል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ የሆኑ ትርጉሞች ያላቸው ናቸው።“ትልቁ ቤት”እና “ትንሹ ቤት”በሚለው መካከል ያለው ንፅፅር ትርጉም ሁሉንም ቤቶች የሚመለከት ጉዳይ መሆኑን ነው።(ተመሳሳይነት የሚለውን ይመልከቱ)
ታላቁንም ቤት ያፈርሳል

ይሄ በአድራጊ ግሥ ሊገለፅ ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም“ጠላት ትልቁን ቤት ወደ ፍርስራሽነት ይለውጠዋል፡፡”(አድራጊ ግሥንና ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ፍርስራሽነት…ወደ አመድነት

ለእነዚህ ሐረጎች ሁለቱንም ቃላት መጠቀም ትችላላችሁ፡፡

ታናሹንም ቤት በመሰባበር

ይሄ ሰዎች በገባቸው መረጃ አኳያ ሊገለፅ የሚችል ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶች ትንሹን ቤት ወደ አመድነት ይለውጡታል፡፡” (ቃላትን ሳይጠቀሙ ሃሣብን በምልቶች(ሥነፅሑፋዊ) መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 6:12

አጠቃላይ መረጃ

ግሣፄን ያደርግ ዘንድ ሃሣባቸውን ወደ እርሱ እንዲሰበስቡ ለማድረግ አሞፅ ሁለት የበሰሉ ጥያቄዎችን ያቀርባል፡፡

ፈረሶች በጭንጫ ላይ ይጋልባሉን?

አንድ ፈረስ ጉዳት ሳይደርስበት በዓለታማ ኮረብታዎች ላይ ሊጋልብ አይችልም፡፡ አሞፅ እነዚህን ሁለት የበሰሉ ጥያቄዎችን የጠየቀው አድራጎታቸውን ለመገሰፅ ነው፡፡ የአሞፅ ትርጉም “ፈረሶች በዓለታማ ኮረብቶች ላይ ሊሮጡ አይችሉም፡፡”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ )

በሬዎች በዚያ ላይ ያርሳሉን?

ሰው በዓለታማ ሥፍራ ላይ ሊያርስ አይችልም፡፡አሞፅ እነዚህን ሁለት ሬቶሪክ ጥያቄዎችን የጠየቀው አድራጎታቸውን ለመገሰፅ ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ሰው በዓለታማ ሥፍራ ላይ በበሬ አያርስም፡፡”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ፍርድን ወደ ሀሞት ለውጣችኋል

ትክክለኛ የሆነ ነገርን የማዛባት ጉዳይ መሪዎች“ፍትህን ወደ ሐሞትነት”እንደለወጡ ተደርጎተነፃፅሯል፡፡የአሞፅ ትርጉም“ትክክለኛ የሆነ ነገርንታጣምማላችሁ” ወይም “ቅን ሰዎችን የሚጎዱ ሕጎችን ታወታላችሁ፡፡”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የፅድቅንም ፍሬ ወደ ሐሞት

ይሄ ከመጀመሪያው የዓረፍተ ነገር ክፍል ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ትክክለኛ ነገሮችን ማዛባት ሰዎች የፅድቅን ፍሬ በመውሰድ ወደ መራራ ጣዕም እንደለወጡትተደርጎ ተነፃፅር፡፡የአሞፅ ትርጉም “ትክክለኛ የሆነ ነገርን ታጣምማላችሁ ”ወይም “ትክክለኛ ነገር ያደረጉትን ሰዎች ትቀጣላችሁ”(ንፅፅርና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ሐማትና…ዓረባ

እነዚህ የከተማ ስሞች ናቸው፡፡(እነዚህን ስሞች እንዴት እንደምትተረጉሟቸው እዩ)

ዓረባን በኃይላችን ቀንድ ወሰድን አይደለንምን?

ሰዎቹ በራሣቸው ኃይል ከተማዋን እንደወሰዱዷትአፅንዖት ለመስጠት በጥያቄ መልክ ያቀርባሉ፡፡የአሞፅ ትርጉም “ዓረባን የያዝናት በራሣችን ጉልበት ነው” (በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 6:14

እዩ

“ስሙ”ወይም “ትኩረት ሥጡ”

የእሥራኤል ቤት

“ቤት ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎችን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም“የእሥራኤል ሕዝብ”( ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር እንዲህ ይላል

እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ስለ ራሱ በራሱ ሥም ይናገራል፡፡ይሄንን በአሞፅ 3፤13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡የአሞፅ ትርጉም“የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር እንዲህ ይላል”ወይም “ይህንን የተናገርኩት የሠራዊት ጌታ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡፡”(የመጀመሪያ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካልን ይመልከቱ)

ከሐማት ጀምሮ እስከ ዓረባ ወንዝ ደረስ

እዚህ ላይ“ሐማት”የሚለው ቃል የእሥራኤል ሰሜናዊ ክፍልን የሚያመለክት ሲሆን “የዓረባ ወንዝ”ደግሞ ደቡባዊውን ክፍል የሚያመለክት ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ከሰሜናዊው የአገራቸው ድንበር ጀምሮ እስከ ደቡባዊ ድንበር ድረስ ”( ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)“

የምንጭ ጅረት

በክረምት ወራት ብቻ የሚፈስስ አነስተኛ የሆነ ወንዝ

---

Chapter 7

Amos 7:1

እዩ ….ተመልከቱ

ፀሐፊው አንድ አስገራሚ ነገር ለመናገር የተዘጋጀ እንደሆነ ለአንባቢው ይናገራል፡፡ ቋንቋችሁ ይሄንን የሚገልፅበት የተለየ መንገድ ሊኖረው ይችላል፡፡

አንበጣ

በአሞፅ 4፤9 ላይ ይሄንን እንዴት አድርጋችሁ እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡

የንጉሡ ሰብል ከታጨደ በኋላ

“ንጉሡ ከታጨደው ውስጥ የእርሱን ድርሻ ከወሰደ በኋላ”

“እባክህ ይቅር በል”

“የአንተ ሕዝብ”እና “እኛ” የሚለው ነገር ግልፅ ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “እባክህ ሕዝብህን ይቅር በል”ወይም “እባክህን ይቅር በለን”( ቃላትን ሳይጠቀሙ በምልክቶች (ሥነፅሑፍ) ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)

ያዕቆብ እጅግ ታናሽ ነውና እንዴት ይቆማል?

እዚህ ላይ“ያዕቆብ” የሚለው ቃል የእሥራኤልን ትውልድ ለማመልከት የዋለ ቃል ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “እኛ እሥራኤላውያን እንዴት እድርገን ነው በሕይወት የምንቆመው?እኛ እጅግ ታናናሾችና ደካሞች ነን” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 7:4

ተመልከቱ

ፀሐፊውአንድ አስገራሚ ነገር ለመናገር የተዘጋጀ እንደሆነ ለአንባቢው ይናገራል፡፡ ቋንቋችሁ ይሄንን የሚገልፅበትየራሱ ሆነ መንገድ ሊኖረው ይችላል፡፡

ጌታ እግዚአብሔር በእሣት ለመፍረድ ጠራ

“ጌታእግዚአብሔር ሰዎችን ለመቅጣት የሚቃጠል እሣትን ተጠቀመ”

ያዕቆብ እጅግ ታናሽ ነውና እንዴት ይቆማል?

እዚህ ላይ “ያዕቆብ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ትውልዶች ነው፡፡ በአሞፅ 7፤2 ላይ ይሄንን እንዴት አድርጋችሁ እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡የአሞፅ ትርጉም “እሥራኤላውያን እንዴት አድርገው ነው በሕይወት የሚኖሩት?እኛ እጅግ ታናናሾችና ደካሞች ነን፡፡” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 7:7

ቱምቢ

በአንደኛው ጫፍ ላይ ከበድ የሚል ነገር ያለው ሆኖ ግንባታዎች በሚካሄዱበት ወቅት ግድግዳዎቹ ከላይ እስከ ታች ደረስ ቀጥ ብለው እንዲቆሙ ለማድረግ የሚረዳ ገመድ ነው፡፡

የምታየው ምንድነው?

እግዚአብሔር ለአሞፅ ትምህርት ለመሥጠት ጥያቄ በመጠየቅ ይቀርባል፡፡የአሞፅ ትርጉም “የምታዩትን ንገሩኝ”(በሙያ የታገዘ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በሕዝቤ በእሥራኤል መካከል ቱምቢ አደርጋለሁ

ሕዝቡ አመፀኞች መሆናቸውን በማየትና ፍርድ ለመሥጠት ያለውን ሃሣብ ለመግለፅ እሥራኤላውያን እንደ ግድግዳ እንደሚመሰሉና እግዚአብሔር ድግሞ ቱምቢን በመጠቀም ግድግዳው ቀጥተኛ እንዳልሆነ ያረጋገጠ በሚመስል መልኩ ነው የሚናገረው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ሕዝቤ እሥራኤል አመፀኞች ናቸው፡፡ከላይ እስከ ታች ደረስ እንዳልተስተካከለ ግድግዳዎች ናቸው”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 7:9

የይሥሐቅም የኮረብታው መስገጃዎች ይፈርሳሉ፤የእሥራኤልም መቅደሶች ባድማ ይሆናሉ፤በኢዮርብዓምም ቤት ላይ በሠይፍ እነሣለሁ

እዚህ ላይ “ሠይፍ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠላትን ነው፡፡ይሄ የራሱ በሆነ አገላለፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም “የኢዮርብዓምን ቤት የሚያጠቃ ሠራዊት እልካለሁ፤እነርሱም የይሥሐቅን የኮረብታ መስገጃዎችና የእሥራኤልን ቤተ መቅደሶች ባድማ ያደርጋሉ”( ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃልን እና አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ )

ይሥሐቅ …እሥራኤል

እነዚህ ሁለቱም ቃላት የእሥራኤልን ቤት የሚያመለክቱ ናቸው፡፡የአሞፅ ትርጉም

“የይሥሐቅ ትውልድ”…“የእሥራኤል ሕዝብ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የኢዮርብዓም ቤት

እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቤተሰብን ነው፡፡በአሞፅ 1፤1 ላይ እንዳደረጋችሁት ሁሉ ኢዮርብዓም የሚለውን ቃልንም ተርጉሙት፡፡የአሞፅ ትርጉም “ኢዮርብዓምና ቤተሰቡ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 7:10

የቤቴል ካህን አሜስያስ

ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት 1/አሜስያስ በቤቴል ውስጥ የቀረ ብቸኛ ካህን ነበር 2/ አሜስያስ በቤቴል ውስጥ ለነበሩ ካህናት አለቃ ነበር

አሜስያስ

ይሄ የአንድ ሰው ሥም ነው፡፡(ሥሞች እንዴት ነው መተርጎም የሚኖርባቸው? የሚለውን ይመልከቱ)

አሞፅ በእሥራኤል ቤት መካከል አምፆብሃል

እዚህ ላይ“ቤት” የሚለው ቃል የሚወክለው “ሕዝቦችን” ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “አሞፅ እዚሁ በእሥራኤላውያን መካከል ሆኖ መጥፎ ነገርን እያሴረባችሁ ነው”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ )

ምድሪቱ ቃሉን ሁሉ ልትሸከም አትችልም

እዚህ ላይ“ምድር” የሚለው ቃል የሚያመለክተው “ሕዝቦችን” ነው፡፡እዚህ ላይ “ሠላምን ማናጋት” የሚለው ሃሣብ የተገለፀው አሞፅ ካባድ እንደሆነ ግዑዝ ዕቃ እንደሆነና ምድሪቱ ለመሸከም እንዳቃታት ተደርጎ ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “እርሱ የሚናገረው ቃል የሕዝቡን ሠላም ያናጋል”ወይም “የሚናገረው መልዕክት በሕዝቡ መካከል ችግር እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውንና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ ይመልከቱ)

ኢዮርብዓም በሠይፍ ይሞታል

እዚህ ላይ“ሠይፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠላቶችን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶች ኢዮርብዓምን ይገድሉታል”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 7:12

በዘያም እንጀራን ብላ በዚያም ትንቢትን ተናገር

እዚህ ላይ “እንጀራን ብላ”የሚለው ቃል የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙም ገንዘብ ማግኘት ወይም አንድ ነገርን በመሥራት ለኑሮ የሚበቃ ነገር ማግኘትን ነው የሚያመለክተው፡፡የአሞፅ ትርጉም “እዚያ ሥፍራ ላይ ትንቢት ስለምትናገር ገንዘብ የሚከፍሉህን ሰዎች ፈልግ”ወይም “እዚያ ሥፍራ ላይ ትንቢት ተናገርና ምግብ ያቅርቡልህ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሥ መቅደስና የመንግሥት ቤት ናትና

እዚህ ላይ“የንጉሥ መቅደስ” እና “የመንግሥት ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተመሳሳይ ሥፍራዎችን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ንጉሡ የሚያመልክበት አገር አቀፉ የመቅደስ ሥፍራ እዚህ ነው፡፡”

Amos 7:14

የከብቶች መንጋ ጠባቂ

በአሞፅ 1፤1 ላይ “እረኛ”ትብሎ ስለሚጠራ ምናልባት “በጎችን”የሚጠብቅ ለማለት ይሆናል፡፡

ዋርካ

ዋርካዎች እስከ 15 ሜትር የሚደርስ ቁመት አላቸው፡፡የአሞፅ ትርጉም“የሾላ ዛፎች”(የማይታወቁ ነገሮችን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 7:16

አሁን

እዚህ ላይ“አሁን” የሚለው ቃል ተከትለው በሚመጡት ሃሣቦች ላይ ትኩረትን እንዲያደርጉ ለማስቻል ጥቅም ላይ የዋለ ነው፡፡

በይሥሐቅም ቤት ላይ አትስበክ

እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሥሐቅን የትውልድ ሐረግ ነው፡፡ የአሞፅ ትርጉም“ ለይሥሐቅ ትውልድ አትስበክ፡፡” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ወንዶችና ሴቶች ልጆችህም በሠይፍ ይወድቃሉ

እዚህ ላይ“ሠይፍ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠላቶችን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶች ወንዶችና ሴት ልጆቻችሁን ይገድላሉ፡፡”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን)

ምድርህም በገመድ ተለክታ ትከፈላለች

ይሄ በአድራጊ ግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም “ሌሎች ሰዎች ምድራችሁን ይወስዱና ይከፋፈሉታል”(አድራጊ ግሥ ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

የረከሰች ምድር

በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ሕዝብ የሞላበት ምድርን በተመለከተእዚህ ላይ የሚገለፀው ልክ ምድሪቱ እንደረከሰች ተደርጎ ነው፡፡እዚህ ላይ ይሄ የሚያመለክተው የእሥራኤልን ሰሜናዊ ክፍል ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ባዕድ አገር”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

## Chapter 8

Amos 8:1

የቃርምያ ፍሬ የሞላበትን ዕንቅብ ተመልከት!

እዚህ ላይ“ተመልከት”የሚለው ቃልአሞፅ አንድ ደስ የሚያሰኝ ነገር መመልከቱን ያሣያል፡፡፡የአሞፅ ትርጉም“የቃርምያ ፍሬ የሞላበትን ዕንቅብ ተመለከትኩ”

የበጋ ፍሬ

“የደረሰ ፍሬ”

አሞፅ ሆይ የምታየው ምንድነው?

እግዚአብሔር አሞፅን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀማል፡፡የአሞፅ ትርጉም “አሞፅ የምታየው ነገር ምን እንደሆነ ንገረኝ ”(በሙያ የታገዘ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያን ቀን

“በዚያን ወቅት”

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ስለ ራሱ በራሱ ሥም ይናገራል፡፡ይህንን በአሞፅ 4፡5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡የአሞፅ ትርጉም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይሄንን ነው”ወይም “እኔ እግዚአብሔር የተናገርኩት ይህንን ነው”(መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሦስተኛ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

ፀጥታ

ለዚህ ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉት ነገሮች 1/እግዚአብሔር ሊያመጣ ያለውን ከባድ ቅጣት ፀጥ ብለው እንዲያዳምጡ እየነገራቸው ነው፡፡ ወይም 2/እግዚአብሔር ቅጣቱን ካመጣባቸው በኋላ ከመፀፀታቸው የተነሣ ሰዎች ፀጥ ይላሉ፡፡

Amos 8:4

ይህን ስሙ

አሞፅ እየተናገረ ያለው ድሆችን ስለሚጎዱ ሐብታም ነጋዴዎች ነው፡፡

ችጋረኛውን የምትውጡ የአሩንም ድሃ የምታጠፉ እናንተ ሆይ

ይሄ አሕፅሮተ ቅፅል ሥምን (ሰዋሰው)በማስወገድ “ችግረኛ” እና “ድሃ”የሚለው አፅንዖት ለመሥጠት ይሆናል ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም “እናንተ ለተቸገሩ ሰዎች እንቅፋት የምትሆኑና በምድሩ ላይ የሚኖሩትን ድሆች በኃይል የምታስወግዱ”(አሕፅሮተ ቅፅል ሥም የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ የምትረግጡ

ሰዎችን መጉዳት ሰዎችን በእግር እንደመርገጥ ተደርጎ ተደርጎ ተነግሯል፡፡የአሞፅ ትርጉም “እናንተ ሰዎችን የምትጎዱ”ወይም “እናንተ ሰዎችን የምታስጨንቁ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

“እህልን እንሸጥ ዘንድ መባቻው መቼ ያልፋል?ስንዴውን እንደንሸምት ሰንበት መቼ ያልፋል?” ይላሉ፡፡

እነዚህን ጥያቄዎች ነጋዴው የሚጠይቀው ነጋዴዎቹ ዕቃዎቻቸውን የሚሸጡበትን ትክክለኛ ጊዜ እንዲያውቁት አፅንዖት ለመስጠት ነው፡፡ይሄ እንደ ቀጥተኛ ያልሆነ አባባል ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም“እህልን እንሸጥ ዘንድ መባቻው መቼ ያልፋል? ስንዴውን እንደንሸምት ሰንበት መቼ ያልፋል?የሚል ጥያቄን ዘወትር ይጠይቃሉ፡፡”(በሙያ የታገዘ ጥያቄና ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ አባባሎች የሚለውን ይመልከቱ)

የኢፍ መሥፈሪያውንም እያሳነስን ፤በሐሰተኛም ሚዛን እያታለልን

ነጋዴዎቹ የውሸት ሚዛንን በመጠቀም በፊት ከነበረው ይልቅ ብዙ ነገር እንደሰጡ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በማስመሰል ክፍያውንም ከወትሮው እንዲቀንስ ያደርጋሉ ማለት ነው።
ችጋረኛውንም በአንድ ጥንድ ጫማ እንገዛ ዘንድ
“እንገዛ ዘንድ”የሚለው ቃል ግልፅ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ችግረኞችን በአንድ ጥንድ ጫማ መግዛት”(ቃላትን ሳይጠቀሙ በምልከቶች ብቻ (ሥነፅሑፍ) ሃሣበን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ )

Amos 8:7

እግዚአብሔር በያዕቆብ ክብር እንዲህ ብሎ ምሏል
እዚህ ላይ “የያዕቆብ ክብር”የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። እንዲሁም “ያዕቆብ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእርሱ የዘር ሐረግ የሆኑትን እሥራኤላውያንን ነው።የአሞፅ ትርጉም“እግዚአብሔር በራሱ ሥም እንዲህ ብሎ ምሏል”ወይም “እሥራኤላውያን የሚመኩበት እግዚአብሔር ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ )
በውኑ ምድሪቱ ስለዚህ ነገር አትናወጥምን?በእርሷም የሚኖር ሁሉአያለቅስምን?
እዚህ ላይ አሞፅ የናይል ወንዝ ማዕበል ከፍና ዝቅ እንደሚል ሁሉ እግዚአብሔር ሕዝቡ ላይ በሚፈርድበት ወቅት ምድሪቱን ከማናወጡ ጋር ያነፃፀረዋል።(ተነፃፃሪ የሚለወን ይመልከቱ)
የግብፅ ወንዝ
ይሄ የናይል ሌላኛው ስሙ ነው።

Amos 8:9

በዚያን ቀን ይመጣል
“በዚያን ዘመን ይፈፀማል”
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ስለ ራሱ በራሱ ሥም ይናገራል።ይሄንን በአሞፅ 4፤5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው” ወይም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ያለው ይሄንን ነው” (መጀመሪያ፤ሁለተኛና ሦስተኛ የሚለውን ይመልከቱ)
ራስ መንጨትንም በሁሉ ላይ አመጣለሁ
አንድ ሰው ራሱን የሚላጨው ሐዘን ላይ መሆኑን ለመግለፅ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ራሣችሁን እንደትላጩ ያደርጋችኋል” (ተምሣሌታዊ ድርጊትን ይመልከቱ)
ለአንድያ ልጅ እንደሚለቀስ ለቅሶ
አንድ ልጅ ብቻ እንዳላቸውና ያ አንዲያ ልጃቸው እንደሞተባቸውየሚገልፅ ነው። የአሞፅ ትርጉም “አንድ ልጅ ብቻ ኖሯቸው ለእርሱ እንደሚያለቀሱ”(ቃላትን ሳይጠቀሙ ሃሣብን መግለፅ የሚለውን ይመልከቱ)
ፍፃሜውንም መራራ አደርገዋለሁ
አሰቃቂና መጥፎ ነገሮች በቀን ብርሃን መከናወናቸው ልክ ቀኑ ራሱ መራራ ጣዕም እንዳለው ዓይነት ተደርጎ ተነግሯል።የአሞፅ ትርጉም“ በዚያን ወቅት የሚከናወኑ ነገሮች ሁሉ ለታላቅ ሐዘን ይዳርጓችኋል።”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 8:11

ዘመን ይመጣል
ይሄ ልክ ቀኑ ራሱ “እየተራመደ እንደሚመጣ” ዓይነት ተገልጿል።የአሞፅ ትርጉም “ቀን ይመጣል” ወይም “ለወደፊቱ” (ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል
እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ስለ ራሱ በራሱ ሥም ይናገራል።ይሄንን በአሞፅ 4፤5 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው” ወይም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ያለው ይሄንን ነው” (የመጀመሪያው፤ሁለተኛውንና ሦስተኛውን ይመልከቱ)
እነሆ በምድር ላይ ራብን በምሰድድበት ዘመን ...የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት እንጂ
ሰዎች ከእግዚአብሔር መልዕክት ለመስማት ፈልገው እግዚአብሔር ለመናገር ፈቃደኛ ስለማይሆንየቃሉ ረሃብ እንደሚመጣባቸው ተደርጎ ነው የተገለፀው።የአሞፅ ትርጉም “በምድሪቱ ውስጥ ከረሃብ ጋር የሚመሳሰል ነገር በማመጣበት ወቅት... ሆኖም የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር ቃል
ይሄ በመጀመሪያው ማንነት ለገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም “ከእኔ የሆነ ቃል፤እግዚአብሔር”ወይም “የእኔ መልዕክቶች” (የመጀመሪያ፤ሁለተኛና ሦስተኛ የሚለውን ይመልከቱ)
ከባህርም እስከ ባህር ድረስ ከሰሜንም እስከ ምሥራቅ ድረስ ይቅበዘበዛሉ
እዚህ ላይ“ከባህር እስከ ባህር”እና “ከሰሜን እስከ ምሥራቅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእሥራኤልን ምድር ሁሉ ነው።የአሞፅ ትርጉም “የእግዚአብሔርን ቃል ለማግኘት እዚህና እዚያ እያሉ ይቅበዘበዛሉ።”(ምሕፃረ ቃል የሚለውን ይመልከቱ))
ከባህር እስከ ባህር ድረስ
ይሄ የሚያመለክተው በደቡብ በኩል ሙት ባህርንና በምዕራብ በኩል ደግሞ የሜዲቴሪያን ባህርን ነው።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀት የሚልውን ይመልከቱ)

Amos 8:13

በዚያን ዘመን
“በዚያን ወቅት”
ይዝላሉ
ጉልበት ሁሉ ሲሟጠጥ
በሰማርያ ኃጢአት
እዚህ ላይ “ኃጢአት” የሚለው ቃል ሰዎች በሰማርያ ውስጥ የሚያመልኳቸውን ጣዖታት የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “የሰማርያ ጣኦት”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ዳን ሆይ ሕያው አምላክህን
ይሄ ከአምልኮ ጋር በተያያዘ መሐላ የማድረጊያ መንገድ ነው።ሰዎቹ ሕያው ነው የሚሉትን የዳንን አምላክ ማመናቸውን ስላወጁ ቃል የገቡትን ነገር በተግባር እንደሚፈፅሙት አፅንዖት ሰጥተው መናገራቸው ነው።
የቤርሳቤህን መንገድ ብለው የሚሉ
ይሄ ምናልባትም ሰዎች ጣዖታትን ለማምለክ ወደ ቤርሳቤህ ጉዞ በሚያደርጉበት ወቅት የሚያልፉባቸውን መንገዶች የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።እዚህ ላይ እንደገና የሚያሣየው ከአምልኮ ጋር የተያያዘ መሐላ የማድረግ ብቸኛ መንገዳቸው መሆኑን ነው።የተሳሉትን ነገር ለማድረግ ይችሉ ዘንድ ወደ ቤርሳቤህ የሚወስደው መንገድ በእርግጥ አለ ብለው ይናገራሉ።
ይወድቃሉ
ይሄ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።የአሞፅ ትርጉም “ይሞታሉ”(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 9

Amos 9:1

አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለአሞፅ ሌላ ራዕይን ያሣየዋል።
በራሣቸውም ሁሉ ላይ ሰባብራቸው
እግዚአብሔር እነዚህን ትዕዛዛት ለማን እንደሚናገር ግልፅ አይደለም።
መድረኮቹ ይናወጡ ዘንድ ፤ጉልላቶቹን ምታ
ይሄ እግዚአብሔር ስለ ጉልላቶቹና ስለ መቅደሱ መሠረቶች በተገናኘ መልኩ የተናገረው ነገር ነው።(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀት የሚለውንና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መድረኮቹ ይናወጡ ዘንድ
እዚህ ላይ “መድረኮቹ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቤተ መቅደሱን በአጠቃላይ ነው።የአሞፅ ትርጉም “ቤተ መቅደሱ በሙሉ ይናወጥ ዘንድ”(አጠቃላይ ሃሣቡን በአጭር ንግግር የመግለፅ ዘዴ የሚለውን ይመልከቱ)
በራሳቸውም ላይ ሰባብራቸው
እዚህ ላይ“ራስ”የሚለው ቃል በአጠቃላይ ማንነቱን የሚያመለክት ነው።የአሞፅ ትርጉም “መቅደሱ በሰዎች ላይ ወድቆ ይገድላቸው ዘንድ ጉልላቶቹን ምታ”(አጠቃላይ ሃሣቡን በአጭር ንግግር የመግለፅ ዘዴ የሚለውን ይመልከቱ)
የቀሩትን በሰይፍ እገድላለሁ
እዚህ ላይ“ሰይፍ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተዋጊዎች በሠይፋቸው የሚያጠቁበትን ሁኔታ ነው።የአሞፅ ትርጉም “የተቀሩትን የሚገድል የጠላት ሠራዊትን እልካለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ሲዖል ቢወርዱ እጄ ከዚያ ታወጣቸዋለች፤ወደ ወደ ሰማይም ቢወጡ ከዚያ አወርዳቸዋለሁ
እግዚአብሔር ወደ ሲዖል የሚሰደዱበትን ሁኔታ ወይም ሞትን ለማምለጥ ሲሉ ወደ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሰማይ የመሄዳቸውን ጉዳይ የተጋነነ በሚመስል መልኩ አቅርቦታል፡፡እዚህ ላይ “ሲዖል” እና “ሰማይ”እንደ ምሕፃረ ቃል ሆኖ ሥፍራዎችን በሙሉ የሚወክል ነው፡፡ የአሞፅ ትርጉም “ወደ ሲዖልና ወደ ሰማይ ቢሄዱ እንኳን ከእኔ ሊያመልጡ አይችሉም፡፡” (ሆን ብሎ አጋኖ መናገርን፤አጠቃላይነትንና ምሕፃረ ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እጄ ከዚያ ታወጣቸዋለች

እዚህ ላይ“እጅ”የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ኃይል ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ከዚያ አወጣቸዋለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 9:3

በቀርሜሎስ ራስ ውስጥ ቢሸሸጉ ....በጥልቅ ባህርም ውስጥ ከዓይኔ ቢደበቁ

እግዚአብሔር ወደ ቄርሜሎስ ተራራ ራስ ሊሸሸጉ የሚሮጡትን ወይም ለመደበቅ ወደ ጥልቅ ባህር የሚሄዱትን በሚመለከት የተጋነነ ገፅታን ያቀርባል፡፡እዚህ ላይ “በቀርሜሎስ ራስ”እና “ጥልቅ ባህር”ሥፍራዎችን ሁሉ የሚያመለክቱ ምሕፃረ ቃሎች ናቸው፡፡የአሞፅ ትርጉም “በቄርሜሎስ ራስ ላይ ቢሸሸጉ እንኳን...የማላይ መስሏቸው ወደ ባህር ጥልቅ ለመሄድ ቢሞክሩ እንኳን”(ሆን ብሎ አጋኖ መናገርን፤አጠቃላይነትንና ምሕፃረ ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እባብ

ያልታወቀ አደገኛ እንስሳ፤በኤደን ገነት የታየው ወይም በተለምዶ የምናውቀው ዓይነት እባብ ያልሆነ፡፡

በጠላቶቻቸውም ተማርከው ቢሄዱ

ይሄ አድራጊ ግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል፡፡የአሞፅ ትርጉም “ጠላቶች ቢማርኳቸውና ወደ ባዕድ አገር ይዘዋቸው ቢሄዱ እንኳን ”(አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ ሰይፍን አዝዛለሁ እርሱም ይገድላቸዋል

እዚህ ላይ“ሠይፍ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጠላቶችን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “እዚያ ጠላቶቻቸው እንዲገድሏቸው አደርጋለሁ”(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 9:5

ሙላዋም እንደ ወንዝ ትነሣለች እንደ ግብፅ ወንዝም ትወርዳለች

እዚህ ላይ“ወንዙ”እና “የግብፅ ወንዝ” የሚሉት ሁለቱም ቃላት የሚያመለክቱት የናይልን ወንዝ ነው፡፡እግዚአብሔር ምድሪቱ እንድትናወጥ የሚያደርግበትን መንገድ ከናይል ወንዝ መነሳትና መስጠም ጋር ያነፃፅረዋል፡፡(ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ (ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ))

ደረጃዎቹን በሰማይ ላይ የሰራ

ይሄ ምናልባት የጥንት ሰዎች ወደ እግዚአብሔርቤተመንግሥት የሚያመራው መንገድ በደረጃዎች ነው ብለው ስለሚያስቡ ይሆናል፡፡ሆኖም አንዳንድ ቅጂዎች “ቤተመንግሥት” እና “ክፍሎች”የሚል ትርጉም ባለውበተለየ የዕብራይስጥ ቃል እንዲነበብ ይፈልጋሉ፡፡እዚህ ላይ “ደረጃዎቹ”የሚለው ቃል የእግዚአብሔር መንግሥት ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ሃሣብ ያለው ሊሆን ይችላል፡፡(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ጠፈሩንም በምድር ላይ የመሠረተ

እዚህ ላይ“ጠፈር” የሚለው ቃል የመፅሐፍ ቅዱስ ፀሐፊዎች የሚገልፁት በምድር ላይ እንዳለ ጉልላት ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ሠማይን በምድር ላይ ይዘረጋል፡፡”(በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የባህሩንም ውኃ ጠርቶ..... በምድር ፊት ላይ

ይሄ የሚያመለክተው የባህር ውኃ በምድር ላይ እነደ ዝናብ እንዲዘንብ ማድረጉን ነው፡፡በአሞፅ 5:8 ላይ ይሄንን እንዴት እንደምትተረጉሙት ተመልከቱ፡፡ኤቲ “ውኃውን ወስዶ በምድር ላይ እንዲዘንቡ ያደርጋቸዋል”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር ስሙ ነው

እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ለማከናወን ኃይሉንና ሥልጣኑን ያውጃል፡፡ይሄንን በአሞፅ 2፤111 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡የአሞፅ ትርጉም “አዎ የእሥራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ምድር አወጣሁ፤ፍልሥጤማውያንንም ከከፍቶር ሶርያውያንንም ከቂር አወጣሁ፡፡”የአሞፅ ትርጉም(በሙያ ላይ የተደገፈ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ቂር

በአሞፅ 1፤5 ላይ የዚህን ሥፍራ ሥም እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ፡፡

የእግዚአብሔር ዓይኖች በኃጢአተኞች መንግሥት ላይ ናቸው

እዚህ ላይ “ዓይኖች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ስለራሱ በሶስተኛ አካልነቱ ሲናገር ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “እኔ እግዚአብሔር የዚህ መንግሥት ሰዎች እጅግ ኃጢአተኞች እንደሆኑ አይቻለሁ” (ሚቶኖሚ አንደኛ፤ሁለተኛና ሶስተኛ አካልን ይመልከቱ)

ከምድርም ፊት አጠፋታለሁ

“ከምድርም ፊት”የሚለው አነጋገር “ሙሉ በሙሉ” ማለት ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም“ይህንን መንግሥት ሙሉ ለሙሉ አጠፋዋለሁ” (ፈሊጣዊ አነጋገርን ተመልከቱ)

Amos 9:7

የያዕቆብ ቤት

እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል የሚወክለው ቤተሰብን ሲሆን “ያዕቆብ”የሚለው ደግሞ የእርሱን ትውልዶች የሚገልፅ ነው፡፡(ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Amos 9:9

የእሥራኤል ቤት

እዚህ ላይ “ቤት” የሚለው ቃል የሚያመለክትው ቤተሰብን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “የእሥራኤል ሕዝብ”( ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

እህልም በወንፊት እንደሚነፋ የእሥራኤልን ቤት በአህዛብ መካካል አነፋለሁ፡፡ነገር ግን አንዲት ቅንጣት በምድር ላይ አትወድቅም

እዚህ ላይ የሚያሣየው እህል በወንፊት ውስጥ ሲያልፍና ደንጋዮቹ ተንገዋለው ሲቀሩ ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም፡- ኃጢአተኛ የሆነውን የእሥራኤልን ሕዝብ እግዚአብሔር ያስወግደዋል የሚል ሃሣብ ነው ያለው፡፡(ተነፃፃሪ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንፊት

ብዙ ቀዳዳዎች ያሉት ወለል ሲሆን ትልልቅ ነገሮችን በውስጡ የማያሣልፍ ነው፡፡

የሕዝቤ ኃጢአተኞች ሁሉ በሠይፍ ይወድቃሉ

እዚህ ላይ“ሠይፍ” የሚለው ቃል የሚመለክተው ጠላቶችን ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም“ጠላቶች የሕዝቤን ኃጢአተኞች ሁሉ ይገድላሉ”( ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል የሚለውን ይመልከቱ )

ክፉው ነገር አይደርስብንም፤አያገኘንም

ጥፋትን መተግበር ልክ ጥፋት አንድን ሰው እንደሚውጠውና እንደሚያገኘው ተደርጎ ነው የተገለፀው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ጥፋት እኛን ሊያገኘን አይችልም”ወይም “መጥፎ ነገር አይደርስብንም” (ሲ ሜታፎር)

Amos 9:11

በዚያ ቀን

“በዚያን ዘመን”

የወደቀችውን የዳዊትን ድንኳን አነሣለሁ

የእሥራኤልን ሕዝብ እንደገና ታላቅ ማድረግን በተመለከተ ልክ የዳዊት ምንግሥት ድንኳን እንደሆነና እግዚአብሔር ደግሞ አንስቶ እንደገና እንደሚተክለው ተደርጎ ቀርቧል፡፡የአሞፅ ትርጉም “የዳዊት ድንኳን ልክ እንደወደቀ ድንኳን ቢሆንም እንኳን እርሱ ግን መልሶ ያቆመዋል፡፡”(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የተናደውንም ቅጥሯን አጠግናለሁ

“ቅጥሯን አድሳለሁ”

የፈረሰውንም አድሳለሁ፤እንደ ቀደመውም ዘመን እሠራታለሁ

“የፈሰውን እንደገና አድሼ ከብዙ ዘመን በፊት እንደነበረችው ጠንካራ አድርጌ አቆማታለሁ፡፡”

አዳራሾች

ወድቀው የቀሩ የየአዳራሾቹየተወሰኑ ክፍሎች

የኤዶምያስ ቅሬታ

“የቀረው የኤዶምያስ ግዛት”

ስሜ የተጠራባቸውን አህዛብን ሁሉ

እዚህ ላይ “ስም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው፡፡“በስሜ የተጠሩት”የሚለው አነጋገር ትርጉሙ በአንድ ወቅት የእግዚአብሔር ንብረት እንደነበሩየሚያሣይ ነው፡፡ ይሄ ማለት ባለፉት ጊዜያት ሕዝቡ ድልን አግኝተው እነዚህን ግዛቶች ተቆጣጥረዋቸው ነበር ማለት ነው፡፡የአሞፅ ትርጉም “ለእኔ የነበሩ አህዛብ ሁሉ”ወይም “ባለፉት ጊዜያት እሥራኤላውያን ድል እንዲነሷቸው ያደረግኳቸውን አህዛብ” (ከዋናው ሃሣብ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመግለፅ የሚውል ቃል፤ፈሊጣዊ አነጋገር፤በግምት ላይ የተመሠረተ ዕውቀትና ግልፅ ያልሆነ መረጃ የሚለውን



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ስለ ራሱ በራሱ ሥም ይናገራል።ይሄንን በአሞፅ 3፤13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው" ወይም "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ያለው ይሄንን ነው"(የመጀመሪያ፤ሁለተኛና ሦስተኛ የሚለውን ይመልከቱ)

## Amos 9:13

እዩ

ፀሐፊው አንድ አስደናቂ የሆነ ነገርን ሊናገር እንደተዘጋጀ ለአንባቢያን ይናገራል። ምናልባት ቋንቋችሁ ይህንን የሚገልፅበት መንገድ ሊኖረው ይችል ይሆናል።

ወራት ይመጣል... አራሹ

ወደፊት የሚመጡ ቀናቶች "ወራት እንደሚመጡ" በሚመስል መልኩ ተገልጿል። የአሞፅ ትርጉም "ወራት ይመጣል...አራሹ ሰው"ወይም "ወደፊት...አራሹ ሰው"(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

አራሹ... ዘርን የሚዘራው

እነዚህ እግዚአብሔር በእሥራኤል ውስጥ ባለፀግነትን ዳግም ለማምጣት መፈለጉን የሚያሣዩ ሁለት ገፅታዎች ናቸው።ይሄ የሚያሣየው እህል እጅግ በፍጥነት ከማደጉ የተነሳ ሰዎች እህሉን ለመሰብሰብ የሚያዳግታቸው እንደሆንና ብዙ የወይን ፍሬ ከመኖሩ የተነሳ ሰዎች ወይኑን ገና እየጠመቁ እያሉ ገበሬዎች ሌላ ተጨማሪ የወይን እርሻን የሚያርሱ መሆናቸውን ነው።

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ስለ ራሱ በራሱ ሥም ይናገራል።ይሄንን በአሞፅ 3፤13 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ።የአሞፅ ትርጉም "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚናገረው ይህንን ነው" ወይም "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ያለው ይሄንን ነው"(የመጀመሪያ፤ሁለተኛና ሦስተኛ የሚለውን ይመልከቱ)

ተራሮችም በተሃውን የወይን ጠጅ ያንጠባጥባሉ፤ኮረብቶችም ሁሉ ይቀልጣሉ

እነዚህ ሁለት መሥመሮች ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ነው ያላቸው።እጅግ ብዛት ያላቸው የወይን ዘለላዎችና ወይኖች ልክ በተራሮችና በኮረብታዎች ላይ እንደሚፈስሱ ተደርጎ ነው የቀረበው።(ንፅፅርንን እና ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

## Amos 9:14

በምድራቸውም እተክላቸዋለሁ፤ከእንግዲህ ወዲህ ከሰጠኋቸው ከምድራቸው አይነቀሉም

ሕዝቡን እንደገና ወደ አገራቸው መመለስንና ከጠላቶቻቸው ተጠብቀው መቆየታቸውን ልክ እሥራኤል አትክልት እንደሆነና እግዚአብሔር ደግሞ በመሬት ውስጥ እንደሚተክለውና ማንም ሊነቅለው እንደማይችል ዓይነት ተመስሎ ተገልጿል።የአሞፅ ትርጉም "ሊነቀል እንደማይችል አትክልት በምድራቸው ለዘላለም እንዲኖሩ አደርጋቸዋለሁ"(ምሣሌያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ከምድራቸው አይነቀሉም

ይሄ አድራጊ ግሥ መልክ ሊገለፅ ይችላል።የአሞፅ ትርጉም "ማንም ሰው ቢሆን ከምድራቸው ሊነቅላቸው አይችልም።" (አድራጊ ግሥን ወይም ተካፋይ ያልሆነ የሚለውን ይመልከቱ)

መንቀል

ከመሬት ውስጥ አትክልትና ሥር ሲነቀል።

---

# Chapter 1

## Obadiah 1:1

የአብድዮ ራዕይ

"ይህ የመፅሐፍ ርዕስ ነዉ " "ራዕይ " የሚለዉ ቃል አጠቃላይ ከያህዌ የሆነ መልዕክት ነዉ እንጂ አብድዮ መልዕክት ወይም የአብድዮ ትንቢት "

ጌታ ያህዌ ስለ ኤዶም ይህን ብሏል

ይህ ለአንባቢዉ የአብዲዮ መፅሐፍ መልዕክት ስለ ኤዶም መሆኑን ነዉ።

ያህዌ

ይህ ስም እግዚብሔር በብሉይ ኪዳን ለህዝቡ እራሱን የገለጠበት ነዉ።(በትርጉም ገፅ ላይ ያለዉን የያህዌን ትርጉም ተመልከት )

- መልክተኛ ተልኳል

ይህ በገቢር መልኩ ልቀመጥ ይችላል ተርጌሚዉ "ያህዌ መልዕክተኛ ልኳል "

ተነስ

"መቆም " ይህ ቃል ህዝብን ዝግጁ ለማድረግ ይጠቅም ነበር።

እሷን ለመቋቋም ተነስ

እሷ የሚለዉ ቃል ኤዶምን ህዝብ ለመግለፅ የተጠቀሰ ሲሆን የኤዶም ህዝብ የቅፅል ስም ነዉ። ስለዚህ " እነሱን" እየተባለ ልተረጎምም ይችላል።

እነሆ እሠራሃለዉ /አበጃጃሃለዉ /

ቁጥር 2 ስጀምር አብድዮ ያህዌ በቀጥታ ለኤዶም እንደተናገረ ፅፏል።

ተነሽ/ተነስ

ይህ ለአንባቢዉ ምን ልከተል እንደሚችል የተለየ ትኩረት እንዲሰጥ ያነቃዋል። ተርጌሚዉ " ልነግርህ ስላለዉ ነገር ተመልከት ወይም ትኩረት ስጥ"

በአህዛብ መካከል ታናሽ አደርግሃለዉ በአህዛብም ትናቃለህ

እነዚህ ሁለት ሓረጎች በትርጉም አንድ ሲሆን ኤዶም የነበራትን ታላቅነት እንደምታጣ ትኩረት ለመስጠት ነዉ።

በአህዛብ መካከል ታናሽ አደርግሃለዉ

በቀላሉ ልታለዩ የሚችል የሆነስ በመጠን (በይዘት) የማይረባ ስለመሆን ተናግሯል ተርጌሚዉ-- በአህዛብ መካከል የማትረባ አደርግሀለዉ

በብዙ ትናቃለህ( ትናቂያለሽ)

ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። ተርጓሚው "የሌላ ሀገር ህዝቦች ይጠሉሻል/ሃል"

## Obadiah 1:3

አጠቃላይ መረጃ

የአብድዩ ራእይ፡አዳምን በተመለከተ ቀጥሏል

የልብህ ትዕቢት አታልሎሃል

"ልብህ ከስሜት ጋር ተመሳስሏል፡ የኤዶማዊያን ትዕቢት ስለ ጥበቃቸው እንዲታለሉ አድርጓቸዋል። ተርጓሚው "ትዕቢትህን አታልሎሀል" ወይንም "ትዕቢትህን የማትረታ አድርገህ እንድታስብ አድርጎሃል "

በተሰነጠቀ ዓለት ውስጥ

"በተሰነጠቀ ዓለት ውስጥ" እዚህ ጋር ሃሳቡ በአለት ስለተከበበ የተጠበቀ ቦታ ነው ።

ከፍ ባለው መኖሪያህ (ማደሪያህ)

"በከፍታ ቦታ ላይ በተሰራው መኖሪያህ ውስጥ"

በልብህ

እዚህ ጋር "በልብህ" ምሳሌያዊ ንግግር ሲሆን "ለራስህ" ተርጓሚው"ለራስህ ትላለህ" ወይም "ታስባለህ"

ወደ ምድር የሚያወርገኝ ማነው?

ይህ ጠያቄ የሚያመለክተው አዳማዊያን ትዕቢተኛና ማነም እንደማይነካቸው ማሰባቸውን ነው። ተርጓሚው - "ማንም ወደ ምድር ሊያወርዳቸው አይችልም" ወይም "ከየትኛው ሰልፍ እድናለው"

እንደ ንስር መጥቀህ ብትወጣ ቤትህም በከዋክብት መካከል ቢሆን

እነዚህ ሁለት ግነቶች ኤዶም በጣም በከፍታ ቦታ ላይ ቤቱን መስራቱን በማንም በማይደረስ ከፍታ ላይ ብሎ ይናገራል። ተርጓሚው " እረግርሀለሁ ክንፍ ኖሮህና ከንስር በላይ ብትበር ቤትህም በኳክብት መካከል ቢሆን"

ከዚያ አወርድሃለው

ትዕቢት ከከፍታ ጋር ሲመሳሰል ትህትና ደግሞ ዝቅ ከማለት ጋር ተመሳስሏል።"ለማውረድ" ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙ አንድን ሰው ትሁት ማድረግ ነው። ተርጓሚው - ትሁት አደርግሃለው ( ፈሊጣዊ ትርጉም ተመልከት)

## Obadiah 1:5

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ በአብድ በኩል ለኤዶም መልዕክቱን መስጠት ቀጥሏል

ሌቦች ቢመጡብህ ወይም ወንበዴዎች በሌሊት ቢመጡ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ሲሆኑ የሚያመለክቱትም ለሌቦች ወይም ለሚሰርቁ ሰዎች ትኩረት ለመስጠት ነው። አንድ ላይ መሆንይችላሉ። ተርጓሚው - "ዘራፊዎች ወደ አንድ ሰው ቤት በሌሊት ሰብረው ሲገቡ" (see Hendiadys)

ወንበዴዎች በሌሊት ቢመጡ

ወይም "ወንበዴዎች በሌሊት ቢመጡ"

ወንበዴዎች

ከሌሎች እቃን ወይም ንብረትን የሚሰርቁ ሰዎች

አንተ ግን ምንኛ ጠፋህ!

ያህዌ ይህን ሐረግ በሌላ አረፍተ ነገር መካከል የተጠቀመው ምን ያህል የኤዶም


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ቅጣት አስደንጋጭ እንደሆነ ለመግለፅ ነው፡፡ ተርጓሚው “ፈፅሞ ጠፍተሃል”

ወይንንም የሚጠብቁ ደ አንተ ቢመጡ ቃርሚያ አያስቀሩምን?

ይህ ጥያቄ የሚያመለክተው ምን ያህል የያህዌ ቅጣት በኤዶም ላይ ከወይን ቆራጮችም የከፋ መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ ይህ በግልፅ ሲቀመጥ ተርጓሚው - ወይን ቆራጮች ወደ አንተ ቢመጡ የተወሰነ ወይን ይተዋሉ; እኔ ግን ሁሉን ከአንተ እወስዳለው፡፡

ኤሳው ምንኛ ተመረመረ፤ የተሸሸገበት ነገር ምንኛ ተፈለገ

ይህ በገቢር ሊፃፍ ይችላል፡፡ ተርጓሚው - ወዮ፤ጠላቶች ከኤሳው ሁሉንም ነገር ዘረፉ ፤ የተሸሸገበት ነገሩንም አገኙበት ( see Active or Passive)

ኤሳው

የኤዶም ህዝብ ከ ኤሳው የዘር ሐረግ ነበሩ፡፡ ስለዚህ ፤ በዚህ መጽሀፍ ውስጥ “ኤዶም” እና “ኤሳው” ሚናገሩት ስለ አንድ ወገን ህዝቦች ነው፡፡

ተመረመረ ( ምስቅልቅሉ ወጣ)

ይህ ጠላቶች የኤሳው ነገር ፈልገው ያለው ውድ ንብረቶች እንደወሰዱበትና ምስቅልቅል እንዳወጡ ወይም እንዳጠፉ ማለት ነው፡፡

Obadiah 1:7

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ መልዕክቱን በአብድዩ በኩል ለአሳቢ መስጠቱን ቀጥሏል

የተማማላሃቸው ሰዎች ሁሉ-----ከአንተ ጋር ሰላም የነበሩ -----እንጀራህንም የተመገቡ

ሦስቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት ስለ ኤዶም ወዳጆች ነው

ወዳጆችህ ( የተማማልሃቸው)

ወዳጆችህ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ስለ ኤዶም ህዝብ ነው

ወደ ዳርቻ ሰደዱህ

“ከምድራቸው አሳደዱህ” የኤዶም ህዝቦች ወደ ወዳጆቻቸው ምድር ለመሰደድ ይሞክራሉ ነገር ግን ማምን በምድራቸው እንዲቆዩ አልተዋቸውም፡፡

ማስተዋል በእርሱ ዘንድ የለም

በሚከተሉት መልኩ ሊተረጎም ይችላል፡-

ወዳጆቹ ስለ ኤዶም ያሉት ተርጓሚ፡ “ኤዶም ምንም መረዳት የለውም” ስለከዳተኞቹ የተባለው ዓ.ነገር ተርጓሚው “ይህን ለምን እንዳደረጉ ማንም ሊረዳ አይችልም፡፡”

በዚያ ቀን ……ከኤሳው ተራራ …..አላጠፋምን? ይላል እግ/ር

እግ/ር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው የኤዶምን መጥፋት ለማስረገጥ ነው፡፡ ተርጓሚው “በዚየያ ቀን በእርግጥ ከኤሳው ተራራ…. አጠፋለው”

የኤሳው ተራራ

ይህ የሚያስረዳው የኤሳው ምድር በአብዛኛው ተራራማ መሆኑንና ይህም የኤዶምን ምድር ለመግለፅ ነው፡፡

የታመንካቸው ሰዎች አታለሉህ

“ብርቱ ተዋጊዎችህ ይደነግጣሉ ”

ቴማን

ይህ በኤዶም ምድር የሚገኝ ግዛት ነው( ተመልከት የስም ትርጓሜ)

ሰዎች ሁሉ ከኤሳው ተራራ በመገደል ይጠፉ ዘንድ

ይህ በገቢር መልኩ ሊፃፍ ይችላል፡፡ ተርጓሚው “ጠላቶች ስለገደሏቸው ሰዎች በኤሳው ተራራ አይኖሩም” ወይም በኤሳው ተራራ የተገኘ ሰው ሁሉ ስለሚገደል ( see Active or passive)

ይለያሉ/ ወደ ፍጻሜ ይመጣሉ

“ይጠፋሉ

Obadiah 1:10

አጠቃላይ መረጃ

እግዚአብሄር መልእክቱን ለኤዶም በአብድዩ በኩል መስጠቱን ቀጥሏል፡፡

ወንድምህ ያዕቆብ

እዚህ ጋር ያዕቆብ የሚወክለው የዘር ሃረጉን ነው፡፡ ምክኒያቱም ያዕቆብ የኤሳው ወንድም ስለሆነ የኤዶም ሰዎች የያዕቆብ ዘር ሐረግ ልጆች ወንድም እንዲሆኑ ተደርጎ ስለተነገረ ተርጓሚው “ የያዕቆብ ዘር ሃረግ (ነገድ) የሆኑትን ዘመዶችህ”

እፍረት ይከድንሃል

በኣንድ ነገር መከደን የህይወት ልምምድን ማሳያ ፈሊጣዊ ንግግር ነው፡፡ ተርጓሚው - ፈጽሞ ታፍራለህ ( ፈሊጣዊ ተመልከት)

ለዘላለም ትጠፋለህ

ይህ በገቢር መልኩ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚው - በፍፁም ዳግመኛ ተመልሶ አይኖርም

በፊቱ አንፃር በቆምህ ቀን

አይቶ ለመረዳት ምንም አለማድረግ

እንግዶች

ለኬላ ወገን የሆኑ ሰዎች

ጭፍራቸውን

ይህ ስለያዕቆብ ሲሆን የእስራኤልን ህዝብ ለመግለፅ ነው፡፡

በኢየሩሳሌምም ዕጣ ተጣጣሉ

ይህ ሐረግ የሚያሳው ከኢየሩሳሌም የዘረፉትን ውድ ንብረቶች ማን እንደሚወስድ ለመወሰን ነው፡፡

ከእነርሱ እንዳንዱ ነበርክ

“አንተ ደግሞ እንደ እንግዶችና እንደ ባዕዳኑ ነበርክ” ይህ የሚያሳየው እስራኤልን አለመረዳታቸው ነው፡፡ ቋንቋ ሲቀመጥ፡ ተርጓሚው “አንተም ልክ እንደጠላቶች ነበርክ እስራኤልንም አልረዳህም፡፡”

Obadiah 1:12

አጠቃላይ መረጃ

እግዚአብሄር ለኤዶም መልዕክቱን በአብድዩ በኩል መላኩን ቀጥሏል

አጠቃላይ መረጃ

ቁጥር 12፡-14- እግዚአብሄር ለኤዶም ሕዝብ እስራኤልን ባለመንከባከባቸው ተደጋጋሚ ትእዛዝ መስጠቱን የያዘ ክፍል ነው፡፡

ደስ አይበልህ ( ደስ ይልህ ዘንድ )

እርካታ አይሰማህ

በመከራ ቀን ወንድምህን

ወንድምህ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእስራኤልን ህዝብ ነው፡፡ ምክኒያቱም ያዕቆብና ኤሳው ወንድማማች ስለነበሩ፡፡

በመከራው ቀን

“ክፉ ነገር ባጋጠመው ጊዜ”

ቀን(ቀኑ)

ይህ ባቢሎን እስራኤልን በተደጋጋሚ ያጠቃበትና ያጠፋበት ቀንን ለማመልከት ነው

በጥፋታቸው ቀን

“ጠላቶቻቸው ባጠፏቸው ጊዜ”

በመከራቸው ቀን

በተጨነቁ ጊዜ

ጥፋት…….ውድመት……መፈራረስ

ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ሲሆኑ አንድ ቃል ብቻ ያለው ቋንቋ በዚያው ቃል ሦስቱንም ትርጉም መጠቀም ይቻላል፡፡

በመከራቸው ላይ

መጥፎ ነገር ስለደረሰባቸው( በእነርሱ ላይ ስለደረሰ)

በሀብታቸው ላይ እጅህን አትዘርጋ

“ሀብታቸውን አትውሰድ” ወይም “ሀብታቸውን አትዝረፍ”

መንታ መንገድ

ሁለት መንገዶች የሚገናኙበት ቦታ

የሸሹትንም ለመግደል

“ለማምለጥ የሚያገለግሉትንም የእስራኤልን ህዝብ ለመግደል” ወይም ለማምለጥ የሚሞክሩትን ለመያዝ

ከእርሱ የቀሩትን አሳልፈህ አትስጥ

“በህይወት ያሉትን ይዘህ ለጠላቶቻቸው አትስጥ”

Obadiah 1:15

አጠቃላይ መረጃ

በቁጥር 15 ላይ እግዚአብሄር መልዕክቱን ያጠቃልላል ከ16-21 በላይ ክፍል ላይ እግዚአብሄር በአብድዩ በኩል ለ ይሁዳ ህዝብ የኤዶም ምድር እንደሚወርሱ ይናገራቸዋል፡፡

የእግዚአብሄር ቀን…….ቀርቧልና…..በራስህ ላይ ይመለሳል

የመጽሀፍ ቅዱስ አዋቂዎች ቁጥር 15 ከቁጥር 14 ጋር ተያያዥነት እንዳለውና የመጀመሪያው ክፍል መደምደሚያ ወይም ለቁጥር 16 የመጀመሪያ ክፍል መሆኑን እርግጠኛ አይደሉም

የእግዚአየእግዚአብሄር ቀን በአህዛብ ሁሉ ላይ ቀርቧልናብሄር ቀን በአህዛብ ሁሉ ላይ ቀርቧልና

“እግዚአብሄር አምላክ ጌታ መሆኑን ለአህዛብ ሁሉ የሚያሳይበት ቀን ጊዜው አሁን ነው ”

አንተ እንዳደረግኸው እንዲሁ ይደረግብሃል

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ በገብር መልክ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ተርጓሚው “በሌሎች ያደረግኸውን እንዲሁ በአንተ ላይ አደርጋለሁ፡፡”
ፍዳህንም በራስህ ላይ ይመለሳል
በራስህ ላይ ይመለሳል የሚለው ለነዚያ ነገሮች ይቀጣሉ ማለት ነው፡፡ ተርጓሚው “ለሰራኸው ሥራ መከራን ታያለህ”
አንተ
አንተ ሚለው ቃል ብዙ ወይ የወል ሲሆን የእስራኤልን ህዝብ ያመለክታል ተብሎ ይታሰባል
እንደ ጠጣችሁ
ይሁዳ ከጠላቶቹ የተቀበለው ቅጣት ልክ እንደ መራራ( ኮምጣጣ) መጠጥ መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ ተርጓሚው “መከራን እንደጠጣችሁ” ወይም “እንደቀጣኋችሁ”
በቅዱስ ተራራዬ
ይህ እየሩሳሌምን ለማለት ነው፡፡
እንዲሁ አህዛብ ሁሉ ዘወትር ይጠጣሉ
እግዚአብሄር በአህዛብ ሲቀጣቸው ተገለፀበትን ንግግር ዘወትር መራራ መጠጥን እንደጠጡ ተደርጎ ተመስለሏል፡፡ ተርጓሚ “አህዛብ ሁሉ መከራን ዘወትር ይጠጣሉ” ወይም “አህዛብን ሁሉ ሁሉ ያለማቋረጥ እቀጣለሁ”
ይጠጣሉ፤አዎን ይጠጣሉ ይጨልጡማል እንዳልሆኑም ይሆናሉ
እግዚአብሄር ቅጣትን የመጣበት ዘይቤያዊ አነጋገር ቀጥሏል፡፡ይጨልጣሉ የሚለው ቃል የሚገልፀው ቅጣትን በሙላት ይለማመዳሉ ማለት ሲሆን ውጤቱም ፈጽሞ እንደሚጠፉ ነው፡፡ ተርጓሚው “የቅጣቱን ፅዋ ፈጽመው እስኪጠፋ ይጠጣሉ” ወይም ፈፅሜ እስካጠፋቸው ድረስ በተደጋጋሚ እቀጣቸዋለው”

Obadiah 1:17

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 16-21 እግዚአብሔር የይሁዳ ሕዝብ የኤዶምን ምድር እንደሚወርሱ በአብዲዩ በኩል ይናገራል፡፡
የሚያመልጡ ይሆናሉ
እነዚህ እግዚአብሔር ከተማዋን ቀጥቶ ካበቃ በኋላ በሕይወት ያሉ የእሩሳሌም ህዝብ ናቸው ይህም በግልጽ ተርጓሚው “ከእግዚአብሔር ቅጣት ያመለጡ የተወሰኑ የእስራኤል ህዝቦች” ማለት ነው፡፡
እርሱም ቅዱስ ይሆናል
“እርሱ”የሚለው ቃል የፅዮን ተራራን ያመለክታል፡፡
የያዕቆብን ቤት እሳት የዮሴፍን ቤት ነበልባልም
እግዚአብሔር ስለ ያዕቆብና ዮሴፍ ቤት ሲናገር እሳት እንዲሆኑ አድርጎ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክኒያት ኤሳውን ልክ እንደ እሳት ፈጥነው ጨርሰው ስለሚያጠፉ ነው፡፤
የያዕቆብ ቤት
ቤት የሚለው ቃል ዘይቤያዊ ሲሆን በቤት ውስጥ ስለሚኖረው ነፍስ( ህይወት) ለማለት ነው፡፡ በዙህ መልኩ የይዕቆብን የዘር ሐረግ( ነገድ) ለማመልከት ነው፡፡ ተርጓሚው - ዬዕቆብ የዘር ሐረግ ( ነገድ)
ገለባ
እህል ከተወቃበት ( ከተሰበሰበ) በኋላ መሬት ላይ የሚቀር
እነርሱንም
ይህ ቃል የሚያመለክተው የያዕቆብና የዮሴፍ ቤትን ነው፡፡
ያቃጥሏቸዋል
ያቃጥሏቸዋል የሚለው የኤዶም ሕዝብ የሆኑትን ኤሳውን የዘር ሐረግ ይወክላል፡፡
ከኤሳው ቤት ቅሬታ የለውም
“አንድም ሰው ከለኤሳው ቤት አይተርፍም”
የኤሳው ቤት
ቤት የሚለው ቃል ዘይቤያዊ ሲሆን በቤት ውስጥ ስላሉት የቤተሰብ አባላት ነው፡፡ ይህም የኤሳው የዘር ሐረግ ይወክላል፡፡ ተርጓሚው “የኤሳው የዘር ሃረግ” ( ዘይቤን ተመልከት)
እግዚአብሄርም ተናግሯልና
ይህ የቃለ መሃላ ቀመር ሲሆን እግዚአብሄር ስለተናገረ ብቻ የሚፈፅም መሆኑን ነው፡፤

Obadiah 1:19

አጠቃላየ መረጃ
ከቁጥር 16-21 እግዚአብሄር የይሁዳ ህዝብ የኦዳምን ምድር እንደሚወርስ በአብድዩ በኩል ይናገራል፡፡
የደቡብም ሰዎች የኤሳውን ተራራ ይወርሳሉ
“በደቡብም የሚኖሩ እስራኤላውያን የዶማውያንን ምድር ይወስዳሉ”
የቆላውም ሰዎች
በምዕራብ ኮረብታማ የሚኖሩ እስራኤላውያን በምርኮ የፍልስጤማውያንን ምድር በምርኮ ይወርሳሉ ፡፡
ይወርሳሉ
ይህ በአጠቃላይ የእስራኤልን ሕዝብ ለመግለፅ ነው፡፡
ብንያምም ይወርሳል
“የብንያም ጎሳ ይወርሳል” ወይም የብንያም ዘር ሐረግ ( ነገድ) ይወርሳል፡፡

Obadiah 1:20

አጠቃላይ መረጃ
ከቁጥር 16-21 እግዚአብሄር የይሁዳ ሕዝብ የኤዶምን ምድር እንደሚወርስ በአብድዩ በኩል ይናገራል፡፡
ይህም የ እስራኤል ልጆች የጭፍራቸው ምርኮ
ምርኮኞች ከሰምን የእሰራኤል መንግስት ወደ ሶርያ መወሰዳቸውን ከእየሩሳሌም ውጭ የሚኖሩ ይሁዳ ህዝቦች ወደ በባቢለን ተወስዷል፡፤ ሁለቱም ትርጉም ሊሆን ይችላል፡፤
ጭፍራ
ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ
እስከ ሰራጵያ ድረስ
ሰራጵያ ከእስረኤል በስተሰቤን በሜርትራንያን ባህር ዳርቻ በጠየርና በሲዶን መካከል የምትገኝ የፎኒሺያን ከተማ ነበረች፡፤
የኢየሩሳሌም ምርኮኞች
ይህ ቡድን ወገን) ከእየሩሳሌም ውጪ የኖሩ ነበሩ ሲሆን ከሰሜን መንግስት ከሆኑት እስራኤላውያን ወይም አይሁድ ህዝብ ይለያሉ፡፤
ስፋራድ
አቅጣጫው የማይታወቅ የቦታ ስም ነው፡፤ አንዳንድ ዋቂዎች እንደሚሉት በሊዲያ ግዛት የምትገኝ የሳርድስ ከተማ ነች ( የስም ትርጉም ተመልከት)
በኤሳውያን ተራራ ላይ ይፈርዱ ዘንድ አዳኞች ወደ ፅ ዮን ተራራ ላይ ይወጣሉ፡፡
-አዳኞች እስከ እየሩሳሌም ይሄዳሉ ከዚያም ሆነው ኤዶምን የገዛሉ
አዳኞች
”እግዚአብሄር ኤዶምን ሊቀጣ የሚጠቀምበቸው የተለያዩ የእስራኤል የጦር መሪዎች” .”የተወጁት” እና የተመለሱት የአይሁድ ምርኮኞች ይገልፃል፡፡ በሁለቱም መልኩ ሊተረጎም ይችላል፡፡
መንግስቱም ለእግዚአብሄር የሆናል
እግዚአብሄር እራሱ በመንግስት ላይ ገዢ እንደሆነ የሚያሳይ ሀረግ ነው፡፡ ተርጓሚው” እግዚአብሄር ንጉሳቸው ይሆናል”

---

Chapter 1

Jonah 1:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ይህ እግዚአብሔር መናገሩን የሚያመለክት አባባል ነው፡፡ ‹‹እግዚአሔር መልእክቱን ተናገረ››
የእግዚአብሔር ቃል
‹‹የእግዚአብሔር መልእክት››
ያሕዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ የገለጠላቸው የእግዚአብሔር ስም ነው፡፡ ይህንን ለመተርጎም ስለ ያሕዌ በትርጉም ቃል ገጽ ውስጥ የተሰጠውን ማብራሪያ ተመልከት፡፡
አማቴ
ይህ የዮናስ አባት ስም ነው፡፡ (ስሞችን ስለመተርጎም የሚለውን ተመልከት)
ተነሣና ወደ ታላቂቱ ከተማ፣ ወደ ነነዌ ሂድ
‹‹ወደ አስፈላጊዋ ከተማ ወደ ነነዌ ሂድ››
ተነሣና ሂድ
ይህ ወደ ሩቅ ሥፍራ ስለመሄድ የተለመደ አገላለጽ ነው፡፡
በእርስዋ ላይ ስበክ
እግዚአብሔር የሚያመለክተው የከተማዋን ሕዝቦች ነው፡፡ በእርስዋ ላይ ‹‹ ሕዝቡን

አስጠንቅቃቸው››
ክፋታቸው ወደ ፊቴ ወጥቶአል
‹‹ ያለማቋረጥ ኃጢአትን ያደርጉ እንደነበር አውቃለሁ።
ከእግዚአብሔር ፊት ለመሸሽ ተነሣ
‹‹ ከእግዚአብሔር ፊት መሸሽ›› ‹‹ተነሣ›› የሚለው የሚየመለክተው ዮናስ ከነበረበት ሥፍራ መሄዱን ነው።
ከእግዚአብሔር ፊት
እዚህ እግዚአብሔር በሕልውናው ተገልፆአል።
ወደ ተርሴስ ሂደ
‹‹ ወደ ተርሴስም ሂደ።›› ተርሴስ የምትገኘው ከነነዌ በተቃራኒ በኩል ነው። ይህ የበለጠ ግልጽ የሚሆነው ዮናስ ግን ከእግዚአብሔር ፊት ወደ ተርሴስ ይኮበልል ዘንድ ተነሣ በሚለው ላይ ነው።
ወደ ኢዮጴም ወረደ
‹‹ዮናስ ወደ ኢዮጴ ሄደ››
መርከብ
‹‹መርከብ›› በባሕር ላይ ብዙ ተጓዦችን ወይም ከባድ ጭነት ተሸክሞ የሚጓዝ ትልቅ ጀልባ ነው።
ዋጋ ከፈለ
‹‹ዮናስ ለጉዞው ከፈለ››
ወደ መርከቧ ገባ
‹‹ በመርከቧላይ ወጣ››
ከእነርሱ ጋር
‹‹ከእነርሱ ጋር›› የሚለው ቃል በመርከቧ ውስጥ አብረው የሚጓዙትን ያመለክታል።
ከእግዚአብሔር ፊት ኮበለለ
እዚህ ላይ እግዚአብሔር ሕልውናው ፊት በሚለው ቃል ተወክላል።
‹‹ከእግዚአብሔር ፊት ኮበለለ››
Jonah 1:4
ወዲያውም እንዲህ ሆነ
መርከቢቱም ልትሰበር ቀረበች በማለት ‹‹ሰዎቹ አሰቡ››
ልትሰበር ቀረበች
ይህ በድርጊታዊ አገላለጽ ሊቀርብ ይችላል። ‹‹ልትሰባበር’
መርከበኞቹ
በመርከቧ ላይ የሚሠሩ
የራሱን አምላክ
እዚህ ላይ ‹‹አምላክ›› የተባለው ሰዎች የሚያመልኳቸውን የስህተት አማልክትና ጣዖታት ለማመልከት ነው።
በመርከቧ ውስጥ የነበረውን ዕቃ ወደ ባሕር ጣሉ
‹‹ሰዎቹ በመርከቧ ውስጥ የነበረውን ከባድ ነገር ወደ ብሕር ውስጥ ጣሉ።›› ይህ የተደረገው መርከቧን ከመስጠም ለመጠበቅ ነው።
ቀላል ለማድረግ
መርከቢቱ ቀላል ስትሆን በተሻለ ሁኔታ ትንሳፈፋለች። ‹‹ መርከቧ በተሻለ ሁኔታ እንድትሳፈፍ››
ነገር ግን ዮናስ ወደ መርከቧ ውስጠኛው ክፍል ውርዶ ነበር።
ዮናስ ይህን ያደረገው ማዕበሉ ከመነሣቱ አስቀድሞ ነበር።
ወደ መርከቧ ውስጠኛው ክፍል
‹‹ወደ መርከቧ ውስጥ››
በዚያ በከባድ እንቅልፍ ተኝቶ ነበር
‹‹በዚያ ከባድ እንቅልፍ ተኝቶ ነበር›› ወይም ‹‹ በዚያ ተኝቶ ነበር ከባድ እንቅልፍም ወስዶት ነበር።›› ከዚህ የተነሳ ማዕበሉ ሊቀሰቅሰው አልቻለም።
Jonah 1:6
የመርከቡም አለቃ ወደ እርሱ መጥቶ እንዲህ አለው
‹‹ የመርከቡ ኃላፊ ወደ ዮናስ ሄዶ እንዲህ አለው››
ተኝተህ ምን ትሠራለህ? ‹‹ስለምን ተኝተሃል?›› ይህን ሓሳባዊ ጥያቄ ያቀረበው ዮናስን ለመውቀስ ነው። ‹‹ማንቀላፋትህን አቁም!››
ተነሣ !
ይህ አንድ ነገርን ለማድረግ መቀስቀስን ያመለክታል። ለዮናስ፣ የመርከቡ አለቃ በሰላም ለመጓዝ ተነሥቶ አምላኩን ይለምን ዘንድ ነገረው።
አምላክህን ጥራ!
‹‹ወደ አምላክህ ጸልይ!›› ‹‹ጥራ›› የሚለው ቃል የአንድን ሰው ቀልብ የሚስብ ነው።
ምናልባት አምላክህ ስለ እኛ አስቦ ከጥፋት እንድን ይሆናል
የዮናስ አምላክ እንደሚያድናቸው በስውር የተገለጸው መረጃ በገሃድ እንዲታወቅ ይሆናል። ‹‹ ምናልናት የአንተ አምላክ ይሰማንና ከጥፋት ያድነናል እንዲህ ከሆነ አንሞትም።››
ሁሉም ለእርስ በርሳቸው ተነጋገሩ
‹‹መንገዶኞችም ሁሉ እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ››
ኑ፣ እጣ እንጣጣል፣ ይህ በእኛ ላይ የደረሰብን ክፉ ነገር በማን ምክንያት እንደሆነ እናውቃለን
‹‹ይህን መከራ ማን እንዳመጣብን ለማወቅ እጣ መጣል አለብን›› ሰዎቹ ሊያውቁ የሚፈልጉትን ለማሳወቅ አማልክቱ እጣው በማን ላይ እንደሚወድቅ እነደሚቀጣጠሩ የምናሉ። ይህ መለኮታዊ አሠራር ነው።
ይህ ክፉ
ይህ አስቸጋሪውን ማዕበል ያመለክታል።
እጣው በዮናስ ላይ ወደቀ
‹‹እጣው ዮናስ በደለኛ መሆኑን ያሳያል››
Jonah 1:8
ከዚያም ዮናስን እንዲህ አሉት
‹‹ከዚያም በመርከቧላይ የሚሠሩት ሰዎች ዮናስን እንዲህ አሉት››
ይህ ክፉ ነገር በእኛ ላይ እንዲሆን ምክንያት የሆነው ማን እንደሆነ እባክህ ንገረን።
‹‹ ይህ ክፉ ነገር በእኛ ለላይ እንዲሆን ያደረገው ማን ነው?››
እግዚአብሔርን ፍራ
‹‹መፍራት›› የሚለው ቃል ዮናስ ለእግዚአብሔር ጥልቅ አክብሮት እንዳለው ያመለክታል።
ይህ ያደረግኸው ነገር ምንድን ነው?
በመርከቢቷ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ይህንን መልስ የማይፈልጉበትን ጥያቄ ማቅረባቸው በዮናስ ላይ ምን ያህል እንደተበሳጩበት ያሳያል። ‹‹ እስከፊ ነገር አድርገሃል።››
እርሱ ከእግዚአብሔር ፊት ኮብልሎ ነበር
እዚህ ላይ እግዚአብሔር በሕልውናው ተገልጾአል። ዮናስ ከእግዚአብሔር ፊት የኮበለለው እግዚአብሔር ያለው በእስራኤል ምድር ብቻ እንደሆን በማሰብ ነው። ‹‹ ዮናስ ከእግዚአብሔር ፊት እየሸሸ ነበር››
እርሱ ነግሮአቸው ነበርና።
የነገራቸው በግልጽ ሊብራራ ይችላል። ‹‹ለእነርሱ ነግሮአቸዋልና፣ ‹ከእግዚአብሔር ለመሸሽ መከርኩኝ።› ››
Jonah 1:11
ዮናስን እንዲህ አሉት
‹‹በመርከቧ ላይ የነበሩት ሰዎች ዮናስን እንዲህ አሉት›› ወይም ‹‹መርከበኞቹ ዮናስን እንዲህ አሉት››
ባሕሩ ጸጥ እንዲል ምን እናድርግብህ? ‹‹ባሽሩን ጸጥ ለማድረግ በአንተ ላይ ምን እናድርግ››
ባሕሩ የበለጠ መናወጡን ቀጠለ
ምን ማድረግ እንዳለባቸው የጠየቁበት ምክንያት ይህ ነበር። ምክንያት በቁጥር 11 ላይ መጠቀስ ይችላል።
ይህ ታላቅ ሞገድ ያጋጠማችሁ በእኔ ምክንያት እንደሆነ አውቃለሁ
‹‹ይህ ታላቅ ሞገድ የእኔ ስህተት መሆኑን አውቃለሁ››
የሆኖሆኖ ፣ ሰዎቹ ወደ ምድሩ ሊመለሱ አጥብቀው ቀዘፉ
ሰዎቹ ዮናስን ወደ ባሕር ሊጥሉት አልፈለጉም፣ ስለሁነም ልክ ባሕሩን እንደሚቆፍሩ ወደ ምድሩ ለመድረስ አጥብቀው ቀዘፉ።
ባሕሩ እጅግ የበለጠ ይናወጥ ነበር
‹‹ ማዕበሉ የበለጠ የከፋ ሆነ፣ ሞገዱም ከፍተኛ ሆነ››
Jonah 1:14
ስለዚህ
‹‹በዚህ ምክንያት›› ወይም ‹‹ባሕሩ እጅግ በመናወጡ ምክንያት››
ወደ እግዚአብሔር ጮሁ
‹‹ሰዎቹ ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ››
በዚህ ሰው ነፍስ ምክንያት አታጥፋን
‹‹ይህ ሰው እንዲሞት በማድረጋችን እባክህ አትግደለን›› ወይም ‹‹እኛ ይህ ሰው እንዲሞት ልናደርግ ነው። ነገር ግ እባክህ አትግደለን››
የዚህን ሰው ሞት በደል በእኛ ላይ አታድርግ

‹‹ በእርሱ ሞት እኛን አትውቀሰን›› ወይም ‹‹ይህ ሰው ሲሞት እኛን እንደ በደለኛ አትቁጠረን፡፡›› ጸሐፊው ስለ ‹‹በደል›› በሰው ላይ እንደሚጫን ነገር አድርጎ ይናገራል። ይህም ያንን ሰው ተጠያቂ የሚያደርግ መሆኑን ያመለክታል።

ባሕሩም ከመናወጡ ጸጥ አለ።

‹‹ባሕሩ በአደገኛ ሁኔታ መንቀሳቀሱን አቆመ›› ወይም ‹‹ባሕሩ ተረጋጋ››

እግዚአብሔርን እጅግ ፈሩ

‹‹በእግዚአብሔር ኃይል እጅግ ተደነቁ››

Jonah 1:17

አጠቃላይ መረጃ

አንዳንድ ትርጉሞች ይህንን ቁጥር የምእራፍ 2 የመጀመሪያ ቁጥር ያደርጉታል። የእናንተ ቋንቋ ትርጉም እንደሰጠው ቁጥር ለዚህ ጥቅስ ቁጥር መስጠት ትችላላችሁ።

አሁን

ይህ ቃል በእንግሊዝኛው የታሪኩን አዲስ ጅማሬ ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል።

ሦስት ቀናት እና ሦስት ሌሊቶች

‹‹ሦስት ቀናት እና ሌሊቶች››

---

Chapter 2

Jonah 2:1

እግዚአብሔር አምላኩ

ይህ ማለት ‹‹እግዚአብሔር፣ እርሱ የሚያመልከው አምላክ፡፡›› ‹‹የእርሱ›› የሚለው ቃል ዮናስ እግዚአብሔርን የግሉ ብቻ አድርጎታል ማለት አይደለም።

እንዲህ አለ

‹‹ዮናስ አለ››

ስለ መከራዬ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ

‹‹ስለ ታላቁ መከራዬ ወደ እግዚአብሔር ጸለይሁ፡፡›› ምንም እንኳን ዮናስ ወደ እግዚአብሔር ቢጸልይም፣ እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ስም ተጠቀመ እንጂ ‹‹አንተ›› አላለም። ‹‹ እግዚአብሔር ሆይ፣ ስለ መከራዬ ወደ አንተ እጣራለሁ››

እርሱ መለሰልኝ

‹‹ እግዚአብሔር መለሰልኝ›› ወይን ‹‹ መልስ ሰጠኝ››

ከሲዖል ሆድ ውስጥ

‹‹ከሲዖል መካከል›› ወይም ‹‹ከሲዖል ጥልቀኛው ክፍል፡፡›› እንደሚከተሉት ሊተረጎሙ ይችላል 1. ዮናስ በአሳ አንባሪው ሆድ ውስጥ መሆኑን በሲዖል ውስጥ እንደ ሆነ ይናገራል ወይም 2. ዮናስ ቶሎ እንደሚሞትና ወደ ሲኦል እንደሚወርድ አምኖአል ወይም 3. እንደ ሞተና ወደ ሲዖል እንደወረደ ይናገራል።

Jonah 2:3

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ በዮናስ 2:2 የተጀመረው የዮናስ ጸሎት ተከታይ ክፍል ነው። በቁጥር 4 ዮናስ ከዚህ ጸሎት በፊት ስለ ጸለየው ጸሎት ይናገራል።

ወደ ጥልቁ፣ ወደ ባሕሩ ልብ

ይህ ዮናስ የነበረበትን የባሕሩን ስፋት ያመለክታል።

ወደ ባሕሩ ልብ ውስጥ

‹‹ ወደ ባሕሩ ታችኛው ክፍል››

ፈሳሾችም በዙሪያዬ ነበሩ

‹‹የባሕሩ ውኃ በዙሪያዬ ከበበኝ››

ማዕበል እና ሞገዶች

እነዚህ በባሕሩ ታችኛ ክፍል ያሉ የሚረብሹ ነገሮች ናቸው።

እኔም ተጣልሁ

ይህ እንደ ተግባር ሊገለጽ ይችላል። ‹‹አንተም አስወገድከኝ›› ወይም ‹‹ወደዚያ ላክኸኝ››

ከዓይኖችህ ፊት

እዚህ ላይ እግዚአብሔር የተገለጸው በ ‹‹ዓይኖቹ›› ነው። ‹‹ ከአንተ››

ነገር ግን ወደ መቅደስህ ደግሞ እመለከታለሁ

ዮናስ ከዚህ ሁሉ ከደረሰበት ባሻገር ፣ ቤተ መቅደሱን እንደሚያይ ተስፋ ያደርጋል።

Jonah 2:5

አጠቃላይ መግለጫ

ይህ በዮናስ 2:2 የተጀመረው የዮናስ ጸሎት ተከታይ ክፍል ነው።

ውኃዎቹ

‹‹ውኃዎቹ›› ባሕሩን ያመለክታሉ

አንገቴ

አንዳድ ትርጉሞችበዚህ ክፍል የተገለጸውን የዕብራውያኑን ቃል የሚረዱት ‹‹ ሕይወቴ›› በሚል ቃል ነው። በዚህ ትርጉም ውኃዎቹ የዮናስን ሕይወት ሊወስዱ ተቃርበው ነበር።

ጥልቁ ሁሉ በዙሪያዬ ነበር

‹‹የጥልቁ ውኃ በዙሪያዬ ነበር››

የባሕር ሣር

በባሕር ውስጥ የሚበቅል ሣር

በምድርና በመወርወሪያዎችዋ ለዘላለም ተዘጋሁ

ዮናስ መሬትን እንደ እስር ቤት በምሳሌነት ተጠቀመ። ‹‹ መሬት እኔን ለዘላለም ለመዝጋት እንደ እስር ቤት ነበረች››

ነገር ግን አንተ ሕይወቴን ከጉድጓዱ ውስጥ አወጣሃት

ዮናስ የሞትን ሥፍራ ጉድጓድ እንደሆነ ይናገራል። ‹‹ ነገር ግን አንተ ሕይወቴን ከሞት ሥፍራ አዳንሃት›› ወይም ‹‹ ነገር ግን አንተ ሕይወቴን ሙታን ከሚኖሩበት ሥፍራ አዳንሃት››

እግዚአብሔር አምላኬ!

በአንዳንድ ቋንቋዎች፣ ይህንን በአረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ወይም ‹‹አንተ›› ከሚለው ቀጥሎ ማስቀመጡ የተለመደ ነው።

Jonah 2:7

የትርጉም ማስታወሻዎች አጠቃላይ መረጃ

ይህ በዮናስ 2:2 የተጀመረው የዮናስ ጸሎት ተከታይ ክፍል ነው።

እግዚአብሔርን ጠራሁ አሰብሁትም

ዮናስ ወደ እግዚአብሔር ስለጸለየ፣ በአንዳንድ ቋንቋዎች ‹‹ እግዚአብሔር ሆይ ስለ አንተ አሰብኩኝ›› ወይም ‹‹ እግዚአብሔር ሆይ ስለ አንተ አሰብሁኝ›› መባሉ ግልጽ ነው።

ስለዚህ ጸሎቴ ወደ አንተ፣ ወደ ቅዱስ መቅደስህ ገባች

ዮናስ ጸሎቱ ወደ እግዚአብሔር ወደ መቅደሱ እንደሚጓዝ ይናገራል። ‹‹ ስለዚህ አንተ በቅዱስ መቅደስህ ጸሎቴን ሰማህ››

በማይረቡ አማልክት ላይ ትኩረታቸውን አድርገዋል ‹‹ሕዝቡ በማይረቡ አማልክት ላይ ትኩረታቸውን አድርገዋል››

የፍቅር ታማኝነትን ጥለዋል

‹‹ ለእነርሱ ታማኝ የሆንክላቸውን፣ አንተን ትተዋል››

Jonah 2:9

አጠቃላይ መረጃ

ይህ በዮናስ 2:2 የተጀመረው የዮናስ ጸሎት ተከታይ ክፍል ነው።

እኔ ግን፣ እኔ

ይህ አገላለጽ ዮናስ በሚናገርባቸው ሰዎች እና በእርሱ መካከል ያለውን ንጽጽር የሚያሳይ ነው። እነርሱ በማይረቡ አማልክት ላይ ትኩረታቸውን አድርገዋል፣ እርሱ ግን እግዚአብሔርን ያመልካል። ‹‹እኔ ግን››

እኔ ግን በምሥጋና ቃል እሠዋልሃለሁ

ይህም ማለት ዮናስ ለእግዚአብሔር መስዋዕትን እያቀረበ ያመሰግናል ማለት ነው። ዮናስ እግዚአብሔርን በመዝሙር ወይም በእልልታ ለማመስገን የተዘጋጀ ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም።

ደኅንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ይመጣል።

ይህ በተለየ ቃል ሊገለጽ ይችላል ስለዚህ ‹‹ ደኅንነት›› የሚለው ቃል ‹‹መዳን›› ተብሎ መገለጽ ይቻላል። ሰዎችን የሚያድነው ‹‹እግዚአብሔር›› ነው።

በደረቁ ምድር ላይ

‹‹ በመሬቱ ላይ›› ወይም ‹‹ወደ ባሕሩ ዳር››

---

Chapter 3

Jonah 3:1

የእግዚአብሔር ቃል መጣ

ይህ እግዚአብሔር ተናገረ የሚለውን የሚገልጽ አባባል ነው። ዮናስ 1:1 ላይ ‹‹እግዚአብሔር መልእክቱን ተናገረ›› የሚለው እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የእግዚአብሔር ቃል

እዚህ ላይ ‹‹ቃል›› የሚለው የእግዚአብሔርን መልእክት ይተካል፡፡ ‹‹የእግዚአብሔር መልእክት››

ተነሥ፣ ወደ ታላቂቱ ከተማ፣ ወደ ነነዌ ሂድ

‹‹አስፈላጊ ወደሆነችው የነነዌ ከተማ ሂድ››

ተነሥ

ይህ የሚያመለክተው ከሥፍራው በቶሎ እንዲሄድ ነው፡፡

እንድትሰጣት ያዘዝኩህን መልእክት አውጅላት

‹‹እንድትነግራቸው የነገርኩህን ለሽዝቡ ንገራቸው››

ዮናስም ተነሥቶ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ወደ ነነዌ ሄደ

‹‹በዚህ ጊዜ ዮናስ እግዚአብሔርን ታዘዘ ወደ ነነዌም ሄደ››

ስለዚህ ዮናስ ተነሣ

‹‹ስለዚህ ዮናስ ከባሕሩ ዳርቻ ሄደ፡፡›› ‹‹ተነሣ››´የሚለው ቃል ዮናስ የነበረበትን ሥፍራ ትቶ መሄዱን ያመለክታል፡፡

አሁን

ይህ ቃል ታሪኩን ቆም አድርጎ ስለ ነነዌ መረጃ ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋለ ነው፡፡

የሦስት ቀናት የእግር ጉዞ

‹‹የሦስት ቀናት ጉዞ የምትጠይቅ ከተማ፡፡›› አንድ ሰው ከተማይቱን ሙሉ ለሙሉ ለማቋረጥ ሦስት ቀናት መጓዝ አለበት፡፡

Jonah 3:4

ከአንድ ቀን ጉዞ በኋላ በጩኸት ተናገረ

ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች፡- 1. ‹‹ዮናስ የአንድ ቀን ጉዞ ከተጓዘ በኋላ በጩኸት ተጣራ›› ወይም 2. ዮናስ በመጀመሪያው ቀን እየተጓዘ እያለ፣ በጩኸት ተናገረ፡፡››

ከአንድ ቀን ጉዞ በኋላ

‹‹ አንድ ቀን ያህል ከሄደ በኋላ›› የአንድ ቀን ጉዞ ሰዎች በቀን ውስጥ ተሚሄዱት የተለመደ ጉዞ ነው፡፡

ጮኸ እንዲህም አለ

‹‹አወጀ›› ወይም ‹‹ጮኸ››

አርባ ቀናት

‹‹40 ቀናት››

ሁሉም ማቅ ለበሱ

ሰዎቹ ሁሉ ለምን ማቅ እንደለበሱ የበለጠ ግልፅ ሊደረግ ይችላል፡፡ ‹‹ ሁሉም ማቅ የለበሱት ኃጢአት በማድረጋቸው ናዘናቸውን ለማሳየት ነው››

ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ ደረሰ

‹‹ በጣም ታላቅ ከሆኑት እስከ ዝቅተኞች ሰዎች ድረስ›› ወይም ‹‹ተላላቆችንና ታናናሾችን ሰዎች ሁሉ ጨምሮ››

Jonah 3:6

ዜናዎች

‹‹የዮናስ መልእክት››

ከዙፋኑ ተነሣ

‹‹ከዙፋኑ ብድግ አለ›› ወይም ‹‹ ከዙፋኑ ብድግ ብሎ ቆመ፡፡›› ነጉሡ ትህትናውን ለማሳየት ዙፋኑን ለቅቆ ወረደ፡፡

ዙፋን

ዙፋን ንጉሥ የሚቀመጥበት ወንበር ነው፡፡ ዙፋኑ የተቀመጠበት ንጉሥ መሆኑን ያመለክታል፡፡

እንዲህ የሚለውን አዋጅ አስተላለፈ

‹‹ ይፋ የሆነውን ማስጠንቀቂያ እንዲህ በማለት አስተላለፈ›› ወይም ‹‹ለነነዌ ሰዎች ለመናገር መልእክተኞቹን ላከ››

ሹማምንት

ከተማዋን ለመግዛት እንዲችል ንጉሡን የሚረዱ አስፈላጊ ሰዎች

የቀንድ ከብቶች መንጎች

ይህ ሁለት ዓይነት እንስሶችን ያመለክታል፡፡ ‹‹መንጎች ወይም በጎች››

ምንም ይብሉ ውኃም አይጠጡ

‹‹ምንም መብላትና መጠጣት የለባቸውም፡፡›› የማይበሉበትና የማይጠጡበት ምክንያት ‹‹በኃጢአታቸው ማዘናቸውን ለማሳየት ነው›› ተብሎ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

Jonah 3:8

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ ንጉሱ ለነነዌ ሰዎች የነገራቸው ቀጣይ ክፍል ነው፡፡

ነገር ግን ሁለም

‹‹ሁለም››

ሰዎች እና እንስሶች ሁሉም ማቅ ይልበሱ

ይህ በድርጊት ቅርጽ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ‹‹ሕዝቡና እንስሳቱ ማቅ ይልበሱ›› ወይም ‹‹ ሕዝቡ ራሳቸውንና እንስሶቻቸውን ማቅ ያልብሱ››

እንስሶች

እንስሶች የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎች በባለቤነት የያዙአቸው መሆኑን ነው፡፡

ወደ እግዚአብሔር ጮሁ

‹‹ከልባቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ፡፡›› ይጸልዩበት የነበረው ምክንያት ግልጽ ነው፡፡ ‹‹ወደ እግዚአብሔር ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ምህረትን ጠየቁ››

በእጁ ከነበረው ክፉ ነገር

ይህ ማለት ‹‹ካደረገባቸው ክፉ ነገር››

ማን ያውቃል?

ንጉሡ ይህን ንግግርን የሚያሳምር ጥያቄ የተጠቀመው ሕዝቡ አይቻልም ከሚለው አስተሳሰብ ወጥተው፣ ኃጢአትን ማድረግ ቢተዉ እምደማይገድላቸው እንዲያስቡ ነው፡፡ ‹‹አናውቅም፡፡›› ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ወይም ‹‹ምናልባት›› በሚለው ቃል በመግለጽ ከሚቀጥለው ዐረፍት ነገር ጋር ማያያዝ ይቻላለ፡፡

እግዚአብሔር ይጸጸትና ሐሳቡን ይቀይር ይሆናል

‹‹እግዚአብሔር የተለየ ነገር ሊያደርግ ይወስን ይሆናል›› ወይም ‹‹ እግዚአብሔር ሊያደርገው የተናገረውን አያደርግ ይሆናል››

አንጠፋም

‹‹ አንሞትም፡፡›› እዚህ ላይ አንጠፋም የሚለው በባሕር ውስጥ አንሰጥምም ከሚለው ጋር ይስማማል፡፡

Jonah 3:10

እግዚአብሔር ያደረጉትን ተመለከተ

‹‹እግዚአብሔር ክፉ ነገር ማድረጋቸውን እንዳቆሙ ተረዳ››

ከክፉ መንገዳቸው ተመለሱ

ጸሐፊው ሰዎቹ ኃጢአት ማድረጋቸውን ሲናገር ልክ ጀርባቸውን ለአንድ ነገር እንደሰጡ አድርጎ ነው፡፡

እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እንደሚያመጣ የተናገረውን ቅጣት ከማድረግ ተመለሰ

እዚህ ላይ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እንደሚያመጣ የተናገረውን ቅጣት፣ ልክ አሳቡን እንደቀየረ፣ ላለማድረግ መወሰኑን ያመለክታል፡፡ ‹‹እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እንደሚያመጣ የተናገረውን ከማድረግ ሓሳቡን ቀይሮ ተመለሰ›› ወይም ‹‹እግዚአብሔር እንደተናገረው ሳይሆን ላይቀጣቸው ወሰነ››

አላደረገውም

እግዚአብሔር ሊያደርግ ያቀደው ግልጽ ተደርጎአል፡፡ ‹‹አልቀጣቸውም›› ወይም ‹‹አላጠፋቸውም››

---

Chapter 4

Jonah 4:1

አኽ፣ ያሕዌ

‹‹አኽ›› የሚለው ቃል የዮናስን የድንጋጤ ስሜት ያሳያል፡፡

ወደ አገሬ ስመለስ ያልኩት ይሄ አይደለምን?

ዮናስ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው እርሱም ምን ያህል እንደተናደደ ለእግዚአብሔር ለማሳየት ነው፡፡ ዮናስ ወደ አገሩ ሲመለስ የተናገረው በግልፅ ሊብራራ ይችላል፡፡ ‹‹በአገሬ ሳለሁ እኔ የነነዌን ሕዝብ ባስጠነቅቅ፣ እነርሱ ንስሃ እንደሚገቡ፣ አንተም እንደማታጠፋቸው አውቄ ነበር››

ወደ ተርሴስ ለመኮብለል ፈጥኜ ነበር

የሚከተሉትን ትርጉሞች መጠቀም ይቻላል 1. ‹‹ይህን ለመከላከል ወደ ተርሴስ ለመኮብለል ሞክርኩ›› ወይም 2. ‹‹እኔ በፍጥነት ወደ ተርሴስ ለመኮብለል ሞከርኩ›› ወይም 3. ወደ ተርሴስ ለመኮብለል የቻልኩትን አደረግሁ፡፡››

ከቃል ኪዳኑ ታማኝነት ጋር በጽናት መቆም

‹‹ በጣም ታማኝ›› ወይም ‹‹አንተ ሕዝብን በጣም ትወዳለህ››

ጥፋትን ከመላክ ተመለስክ

ይህ ማለት ‹‹በኃጢአተኞች ላይ ጥፋትን እንደምትልክ ተናግረህ ነበር፣ ነገር ግን ይህን ላማድረግ ወሰንክ፡፡›› ‹‹ኃጢአት ያደረጉትን ሰዎች ላለመቅጣት ወሰንክ››

ነፍሴን ከእኔ ውሰድ

ዮናስ ለመሞት የፈለገበት ምክንያት በግልጽ ሊብራራ ይችላል። ‹‹ነነዌን አጠፋለሁ ብለህ ካላጠፋሃት፣ እኔ እንድሞት ፍቀድልኝ››
ለእኔ ከመኖር መሞት ይሻለኛል
‹‹ከመኖር መሞትን እመርጣለሁ›› ወይም ‹‹ ለመሞት ስለምፈልግ ለመኖር አልፈልግም››
Jonah 4:4
ይህን ያህል ልትናደድ መልካም ነውን?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ ያቀረበው ዮናስ ሊቆጣበት በማይገባው ጉዳይ ይህን ያህል በመቆጣቱ ሊወቅሰው ነው። ‹‹መቆጣትህ መልካም አይደለም››
ከከተማዋ ወጥቶ ሄደ
‹‹የነነዌን ከተማ ለቅቆ ሄደ››
በከተማዋ የሚሆነውን
‹‹በከተማዋ ላይ ምን እንደሚሆን።›› ዮናስ እግዚአብሔር ከተማዋን ያጠፋት ወይም አያጠፋት እንደሆነ ለማየት ፈልጎአል።
Jonah 4:6
በዮናስ ላይ እንደ ጥላ ነበረች
‹‹በዮናስ እራስ ላይ ለጥላ››
ጭንቀቱን ለማስታገስ
‹‹ዮናስን ከፀሐይ ትኩሳት ለመከላከል››
ነገር ግን እግዚዘአብሔር ትልን አዘጋጀ
‹‹ እግዚአብሔር ትልን ላከ››
ተክሏን አጠቃቻት
‹‹ትሏ ተክሏን በላቻት››
ተክሏ ጠወለገች
ተክሏ ደረቀች ሞተችም። ‹‹ተክሏ ሞተች››
Jonah 4:8
እግዚአብሔር የምሥራቅን ሞቃት ነፋስ አዘጋጀ
እግዚአብሔር የምሥራቅን ሞቃት ነፋስ በዮናስ ላይ እንዲነፍስበት አደረገው። ነፋስ ሞቃት ወይም ቀዝቃዛ ቢሆን ይህን መሞከር ትችላለህ። ‹‹እግዚአብሔር እጅግ ሞቃት የምሥራቅን ነፋስ በዮናስ ላይ እንዲነፍስ ላከው››
ፀሐይ መታችው
‹‹ፀሐይዋ እጅግ ታቃጥል ነበር››
በዮናስ እራስ ላይ
ዮናስ ጭንቅላቱ በፀሐይዋ ሙቀት ተቃጥሎ ነበር።
ተዝለፍልፎ ነበር
‹‹እጅግ ደክሞ ነበር›› ወይም ‹‹ኃይሉን አጥቶአል››
ለእኔ ከመኖር መሞት ይሻለኛል
‹‹ከመኖር መሞትን እመርጣለሁ›› ወይም ‹‹ለመሞት ስለምፈልግ ለመኖር አልፈልግም›› ዮናስ 4:3 ን እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።
ይህን ያህል ስለ ተክሏ ልትናደድ መልካም ነውን?
እግዚአብሔር ዮናስን ስለ ተክሏ መሞት እያዘነ ነገር ግን የነነዌን ሰዎች እንዲያጠፋቸው መፈለጉ የማይገባ እንደሆን ወቀሰው። ‹‹ስለ ተክሏ ሞት መቆጣትህ መልካም አይደለም››
ይህን ያህል ስለ ተክሏ ልትናደድ መልካም ነውን?
የተደበቀው መረጃ መገለጽ ይችላል። ‹‹ከተክሏ ሞት ይልቅ ለነነዌ ሰዎች ሞት የበለጠ ግድ ሊልህ ይገባሃል።››
እኔ እስከ ሞት ድረስ ልቆጣ መልካም ነው።
‹‹መቆጣቴ መልካም ነው። እኔ አሁን ከልክ በላይ ስለተናደድኩ መሞት እፈልጋለሁ!››
Jonah 4:10
እግዚአብሔር አለ
እግዚአብሔር ዮናስን ማናገሩ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ‹‹እግዚአብሔር ዮናስን አለው››
ለታላቂቱ ከተማ ለነነዌ---ለከብቶቿም አላዝንምን?
እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው እርሱ ለነነዌ ያለውን ኀዘኔታ ለማስገንዘብ ነው። ‹‹ለዚያች ታላቅ ከተማ---ለከብቶቿም ርኅራሔ ሊኖረኝ ይገባል።››
ሌሎችም ብዙዎች አሉ
ይህ ለአዲስ ዐረፍተ ነገር ጅማሬ ሊሆን ይችላል። ‹‹ብዙዎች አሉ።›› ወይም ‹‹ብዙ አለው››
አንድ መቶ ሃያ ሺህ ሰዎች
120,000 ሰዎች
ግራ እና ቀኛቸውን ለማያውቁ
ይህ አባባል ‹‹በትክክል እና ትክክል ባልሆነው መካከል ያለውን ልዩነት ለማያውቁ›› ለማለት የተነገረ ነው።
ብዙ ከብቶችም
ጸሐፊው የነነዌ ንስሃ የመግባት ጥልቀቱ ምን ያህል እንደሆነ ላማሳየት እና እግዚአብሔርም ምን ያህል እንደተገነዘባቸው ያመለከተበት አገላለጽ ነው።

---

Chapter 1
Micah 1:1
ትንቢተ ሚክያስ 1:1 የትርጉም ማስታወሻ
አጠቃላይ መረጃ፡ እግዚአብሔር በሚክያስ አማካይነት በግጥም መልክ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።
የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ የአነጋገር ዘይቤ እግዚአብሔር ለአንድ ሰው መልዕክት እንደሰጠው ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል።
ያህዌ ይህ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያስታወቀው ስሙ ነው። ይህ እንዴት እንደሚተረጎም ለመረዳት የትርጉም ቃል ገጽ የሚለውን ተመልከት።
የሞሬሽታዊው ይህ ማለት በይሁዳ ካለው ከሞሬሽት የመጣ መሆኑን ያመለክታል።
በይሁዳ ነገሥታት በኢዮአታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን “ኢዮአታም፣ አካዝና ሕዝቅያስ የይሁዳ ነገሥታት በነበሩበት ጊዜ”
ያየው “በራዕይ የሰማው”
Micah 1:2
x
አጠቃላይ መረጃ፡ ሚክያስ 1:2-7 የሚናገረው በሰማርያ ላይ ሊሆን ስላለው የእግዚአብሔር ፍርድ ነው
ሕዝቦች ሁሉ ስሙ፤ ምድርና በእንቺም ውስጥ ያሉ ሁሉ ስሙ የሚክያስ ትንቢት በዚህ ይጀምራል። ምድር ራሷ እንኳን ትሰማው ይመስል ሚክያስ የሚናገረው በምድር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉና ለሰማርያ ሕዝብ ነው።
እርሱ ይወርዳል፣ በምድር ከፍታዎችም ላይ ይራመዳል ሚክያስ እግዚአብሔርን ከሰማይ ወርደው በተራሮች አናት ላይ እንደሚሰለፉ ብርቱ ወታደሮች አድርጎ ይናገራል።
… ይራመዳል “… ይሰለፋል”
የምድር ከፍታዎች “ከፍ ያሉ ተራራዎች”
ተራሮች ከበታቹ ይቀልጣሉ፤ ሸለቆዎቹ ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ፣ ውኆችም በጠባብ ስፍራ እንደሚወርዱበት ድንጋይ ይሰነጠቃሉ ሚክያስ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር፣ ምድር በምትንቀሳቀስበት ጊዜ በግለቱ እንደሚያቀልጣት አንዳች ጠጣር ነገር ይገልጠዋል። ኢ.ት፡ “በላያቸው
Micah 1:5
x
በእስራኤል ቤት ኃጢአት ምክንያት “ቤት” የሚለው ቃል በቤት ውስጥ የሚኖሩትን ቤተ ሰቦች፣ በዚህ ስፍራ ደግሞ የእስራኤልን ሕዝብ የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ በእኔ ላይ ኃጢአትን ስላደረጉ”። ይህ ሁሉ “ጌታ ይመጣና ይፈርዳል”
የያዕቆብ በደል ምንድነው? “ያዕቆብ” የሚለው ስም በሰሜናዊ እስራኤል የሚኖሩ ዘሮቹን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው።
ሰማርያ አይደለችምን? እዚህ ጋ “ሰማርያ” በዚያ የሚከናወነውን ክፉ ተግባር ገላጭ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ሚክያስ ሕዝቡ እውነት ምን እንደሆነ እንዲያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ያቀርባል። ኢ.ት፡ “ሰማርያ መሆኗን ታውቃላችሁ”።
የይሁዳ ከፍ ያለ ቦታ ምንድነው? እዚህ ጋ “ከፍ ያለ ቦታ” ለመላው የጣዖት አምልኮ ልማድ ምሳሌ ነው። “ይሁዳ” በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች ምሳሌአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የይሁዳ ሕዝብ ጣዖትን ለማምለክ የሚሄዱት የት ነው?”
ኢየሩሳሌም አይደለችምን? በዚያ የሚከናወነውን ክፉ ተግባር ገላጭ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ሚክያስ ሕዝቡ እውነት ምን እንደሆነ እንዲያውቁ አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ያቀርባል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ኢየሩሳሌም እንደሆነች ታውቃላችሁ”።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Micah 1:6
x
አደርጋለሁ እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው
ሰማርያ … ድንጋዮቿ … መሠረቶቿ … የተቀረጹ ምስሎቿ … የተቀበለቻቸው ስጦታዎች … ጣዖታቷ … ስጦታዎቿን ሰበሰበች … ይሆናሉ እግዚአብሔር ከተማይቱን በሴት በመመሰል ስለ ሰማርያ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ሰማርያ… ድንጋዮቿ … በከተማው ያሉ ቤቶች መሠረታቸው … በከተማው የተቀረጹት ምስሎች … ሰዎች በከተማው ውስጥ ላለው መቅደስ የሰጡት ስጦታ … በከተማው ያሉ ጣዖታት … የከተማው ሕዝብ በልጽጓል … ስጦታዎቹ … ይሆናሉ”።
ድንጋዮቿን እንዳለሁ እዚህ ጋ “እርሷ” የሚያመለክተው የሰማርያን ከተማ ነው።
የተቀረጹት ምስሎቿ ሁሉ ይደቅቃሉ ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የተቀረጹ ምስሎቿን ሁሉ አደቃለሁ”።
ስጦታዎቿ ሁሉ … በእሳት ይቃጠላሉ ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የተቀበለችውን ስጦታ በሙሉ በእሳት አቃጥለዋለሁ”
የተቀበለችው “ሰዎች የሰጧትን”
ስጦታዎቿን የዝሙት አዳሪነቷ ዋጋ አድርጋ ስለሰበሰበች አሁንም የዝሙት አዳሪነቷ ዋጋ ይሆናሉ ሰዎች የዝሙት አዳሪን እንደሚከራዩ እግዚአብሔር ለጣዖታት ስጦታዎችን ስለሚሰጡ ሰዎች ይናገራል። አሦራውያን ሰማርያን በሚያጠፉበት ጊዜ የሰማርያ ሰዎች ለጣዖቶቻቸው የሰጧቸውን ስጦታዎች ወስደው ለገዛ ራሳቸው ጣዖታት በስጦታነት ያበረክቷቸዋል።
Micah 1:8
x
ሚክያስ 1፡8-16 የሚናገረው በይሁዳ ላይ ስለሚሆነው የእግዚአብሔር ፍርድ ነው።
የሀዘን እንጉርጉሮን እንጎራጉራለሁ እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሚክያስን ነው።
የሀዘን እንጉርጉሮን እንጎራጉራለሁ፣ አለቅሳለሁም “የሀዘን እንጉርጉሮ” የሚያመለክተው ውስጣዊውን ሀዘን ሲሆን “ለቅሶ” ደግሞ የሀዘንን ድምፅ በጩኸት የመግለጥን ተግባር ያመለክታል።
ባዶ እግሬንና ራቁቴን እሄዳለሁ ይህ የከፍተኛ ለቅሶና ጉዳት ምልክት ነው። ሌላው አማራጭ ትርጉም “እንደ ሰው ልብሴን የገፈፈኝን ዓይነት ሰው እመስላለሁ፤ ራቁቴን እሆናለሁ”
ራቁት ምናልባት ከወገብ በታች ማገልደም ብቻ ይሆናል
እንደ ቀበሮዎች. . . እንደ ጉጉቶች ቀበሮዎችና ጉጉቶች የሚኖሩት ወና በሆነ ምድር ሲሆን ከፍ ያለው ድምፃቸው ዋይ የሚሉ ወይም የሚያለቅሱ ሰዎችን ድምፅ ይመስላል።
ቁስሏ ሊድን የማይችል ነው እዚህ ጋ “እርሷ” የሚያመለክተው የሰማርያን ከተማ ነው። ይህም የጠላት ሰራዊት በዚያ የሚኖረውን ሕዝብ ከማጥፋት ምንም ነገር ሊገታው አይችልም ማለት ነው።
ወደ ይሁዳ መጥቷል ሚክያስ እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ ለመፍረድ የላከውን ሰራዊት ለመግለጽ በዘይቤአዊ አነጋገር ተላላፊ በሽታ የሚለውን ይጠቀማል። እዚህ ጋ “እርሱ” የሚያመለክተው “ቁስል”ን ሲሆን እርሱም እግዚአብሔር ሰማርያን ለመቅጣት የሚጠቀምበት ሰራዊት ነው።
ቤትሌፍራ “ ‘የትቢያ ቤት’ የሚል የከተማ ስም ነው” የሚል የግርጌ ማስታወሻ ልትሰጠው ያስፈልግህ ይሆናል።
በትቢያ ላይ እንከባለላለሁ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች የሆኑ ሰዎች ሀዘናቸውን መሪር በሆነ መንገድ ይገልጻሉ። ኢ.ት፡ “መሬት ላይ እንከባለላለሁ” ወይም “በጭቃ ላይ እንከባለላለሁ”።
እዚህ ጋ የመንደሮቹ የስማቸው ትርጉም ለሚክያስ አስፈላጊዎች ናቸው። በግርጌ ማስታወሻ ላይ የቦታዎቹን የስማቸውን ትርጉም ማካተት ያስፈልግህ ይሆናል።
Micah 1:11
x
ሻፊር ከ”ራቁትነት እና ኃፍረት” ጋር ሲነጻጸር የከተማይቱ ስም “ውብ” ከሚለው ድምፅ ጋር ይመሳሰላል።
በራቁትነትና ኃፍረት ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሕዝቡ ሙሉ በሙሉ ራቁቱን እንደሚሆን ግልጽ ያደርጋል። ኢ.ት፡ “ሙሉ በሙሉ ራቁታቸውንና የሚያፍሩ ይሆናሉ”
ጸዓናን የዚህች ከተማ ስም ትርጉሙ “ውጪ” የሚል ነው። ለመውጣትና ለማገዝ እጅግ ፈርተዋል።
ቤትኤጼል የዚህች ከተማ ስም ትርጉም “የምትወሰድ ቤት” ማለት ነው።
መከላከያቸው ተወስዷልና ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ሊከላከልላቸው የሚችለውን ነገር ሁሉ እኔ አስወግጃለሁና”።
ማሮት የዚህች ከተማ ስም ትርጉም “መራራነት” የሚል ነው።
አደጋ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዷል “አደጋ” የሚለው የነገር ስም እዚህ ጋ ከኮረብታ ላይ ተንከባሎ እንደሚወርድ ጠጣር ነገር ተገልጿል። እንደ ግስ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ክፉ ነገሮች እንዲመጡ አድርጓል”።
Micah 1:13
x
ለኪሶ “ለኪሶ” የሚለው ስም በዕብራይስጥ “ለሰረገሎቹ” ከሚለው ድምፅ ጋር ይመሳሰላል። ሕዝቡ ለውጊያ ሳይሆን ለመሸሽ ሰረገላዎቻቸውን ያስጋልባሉ። ለኪሶ በይሁዳ ከምትኖረው ከኢየሩሳሌም ቀጥሎ እጅግ አስፈላጊ ከተማ ነበረች።
የጽዮን ሴት ልጅ “ሴት ልጅ” የሚለው ቃል ለከተማይቱ ሰዎች የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የጽዮን ሕዝብ” ወይም “በጽዮን የሚኖረው ሕዝብ”።
የእስራኤል መተላለፍ በእናንተ ዘንድ ተገኝቷልና ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የእስራኤል ሕዝብ እንዳደረጉት አልታዘዝ ብላችኋል”።
ሞሬሼትጌት “ ‘ሞሬሼት’ የሚለው ስም ትርጉም ‘መለየት’ ማለት ነው የሚለውን በግርጌ ማስታወሻ ላይ መጨመር ያስፈልግህ ይሆናል። በተጨማሪም ‘ዕጮኛ’ ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው”። በዚህ ዘይቤአዊ አነጋገር ሞሬሼት አሦር የሚወስዳት ሙሽሪት ስትሆን የ “መሰናበቻ ስጦታ”ው ወደ ትዳሯ ይዛው እንድትሄድ ቤተ ሰቦቿ የሚሰጧት ስጦታ ነው።
አክዚብ “የዚህች ከተማ ስም በዕብራይስጥ “አታላይ ነገር” ከሚለው አገላለጽ ጋር ፍጹም ተመሳሳይነት አለው” በማለት በግርጌ ማስታወሻ ላይ ልትጨምረው ያስፈልግህ ይሆናል።
Micah 1:15
x
እንደገና አመጣብሻለሁ እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።
መሪሳ “የዚህ መንደር ስም ‘ድል አድራጊ’ ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው” በማለት የግርጌ ማስታወሻ ልታደርግለት ያስፈልግህ ይሆናል።
ዓዶላም ይህ በፍልስጥኤም የልዑላኑ ከተማ ስም ነው።
ራስሽን ተላጪ፣ ጸጉርሽንም ተቆረጪ የሚያለቅሱት እስራኤላውያን ራሳቸውን በክብ መላጨት ነበረባቸው። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “ራሳችሁን በተለመደው ሳይሆን ሰፋ ክቦችን በማድረግ ተላጩት” ወይም 2) በቅደም ተከተል ሊሆኑ ያሉትን ነገሮች በመግለጽ “ጸጉራችሁን በሙሉ ተቆረጡት፣ ራሳችሁንም ተላጩት”።

---

Chapter 2
Micah 2:3
x
አንገቶቻችሁን ልታስወጡ ከማትችሉበት እግዚአብሔር ቀንበርን በአንገታቸው ዙሪያ ያደረገ ይመስል ሕዝቡን ስለሚቀጣበት ሁኔታ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ልታመልጡ ከማትችሉበት”።
ስለ እንቺ ይዘፍናሉ “በእንቺ ላይ ለመቀለድ ይዘፍኑብሻል” የሀዘን እንጉርጉሮ እንጎራጉሪ “ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይጮኻሉ”። የሚወድዷቸው የሞቱባቸው ይመስል ለማልቀስ ያስመስላሉ።
እኛ እስራኤላውያን . . . ለከዳተኞች ይህ ጠላቶቻቸው በእስራኤላውያን ላይ ለመሳቅና በስቃያቸው ለመሳለቅ የሚዘፍኑት ዘፈን ነው።
ከእኔ እንዴት መንጠቅ ይችላል? የእስራኤል መሪዎች ከድኾች የወሰዱባቸውን መሬት እግዚአብሔር ከእነርሱ ወስዶ ለሌላ ሰው በመስጠቱ በሚሰማቸው መደነቅ ላይ ጠላት ይሳለቃል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ተደርጎ መተርጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ከእኔ ለመውሰድ ማሰቡ ስሕተት ነው!”
ስለዚህ፣ እናንተ ባለጸጎች በእግዚአብሔር ጉባዔ ውስጥ መሬት የሚካፈል ትውልድ አይኖራችሁም። አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) ሚክያስ ወደ ፊት ከምርኮ በኋላ የሚመለሱት ተመላሾች ምድሪቱን ስለሚከፋፈሉበት ጊዜ ይመለከታል ወይም 2) እርሱ የሚናገረው በዘመኑ ልማድ መሠረት እንደ ነገድ ወይም ጎሳ ምድራቸውን በማከፋፈል ለግለ ሰቦች ስለሚሰጡበት ጊዜ ነው።
Micah 2:9
በረከቴን ከታናናሽ ልጆቻቸው ለዘላለም ትወስዳለህ
ይህ በጥቅሉ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጣቸውን በረከት ያመለክታል። 1)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በእስራኤል ባለ ርስት የሆኑትን 2) የወደፊቱን ተስፋ ሰጪ ሁኔታ ወይም 3) የልጆቹን አባቶች፣ አገር ለመገንባት ጠንክረው የሚሠሩትን ገበሬዎች ያመለክት ይሆናል።
በረከቱን
ሚክያስ እርሱ ራሱ እግዚአብሔርን እንደሆነ አድርጎ ይናገራል።
በፍጹም መጥፋት ጠፍቷል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ፈጽሜ አጠፋዋለሁ”
ወደ እናንተ ቢመጣ … ቢተነብይላችሁ
ሚክያስ የሚናገረው ስለ ይሁዳ ሕዝብ ነው፤ ስለዚህ በሁለቱም ጊዜ “እናንተ” ብቁ ቁጥር ነው።
ተቀባይነት ይኖረዋል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ሕዝቡ ይቀበለዋል” ወይም “ትቀበሉታላችሁ”።
Micah 2:12
አጠቃላይ መረጃ:
እግዚአብሔር መናገሩን ቀጥሏል። በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ እግዚአብሔር ራሱን የሕዝቡ ጠባቂ እረኛ አድርጎ ያሳያል። እርሱ የሚናገረው ምናልባትም በተለይ ከአሦር ተመልሰው በኢየሩሳሌም ለሚኖሩት ነው።
ያዕቆብ፣ እናንተን ሁላችሁንም
ሚክያስ የሚናገረው ለአንዳንድ የያዕቆብ ዝርያዎች ሲሆን “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው።
ሰባሪው መንገዳቸውን ይከፍታል … እግዚአብሔር በራሳቸው ላይ ይሆናል።
ይህ ከተከበበ ከተማ ሕዝቡን እየመራ የሚሄደው ንጉሥ ሥዕል ነው።
የሚክያስ 03 ዋና ነጥቦች ፍትሕ የዚህ ምዕራፍ ዋና ጭብጥ ነው
ፍትሐዊ ያልሆነ ማኅበረ ሰብ እንደ ኃጢአተኛ ይቆጠራል። የሙሴን ሕግ እንደሚቃረን ይቆጠርም ነበር። እነዚህ መንግሥታት ፍትሕ ካልነበራቸው ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ ነበሩ ማለት ነው።
አስፈላጊ ምሳሌአዊ አነጋገር በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በዘይቤአዊ አነጋገር ቀርቧል
የሕዝቡ መሪዎች እስራኤላውያኑን እንዴት እንደያዟቸው የሚያሳዩ ጉልህ ሥዕሎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህ ሁኔታዎች እንደ ዘይቤአዊ አነጋገር ካልተወሰዱ ዘበት ሆነው ይቀራሉ።

---

Chapter 3
Micah 3:1
ተናግሬአለሁ
እዚህ ጋ በውስጠ ታዋቂነት ያለው “እኔ” የሚያመለክተው ሚክያስን ነው።
ፍትሕን ልታውቁ አይገባችሁም?
ሚክያስ በመሪዎቹ ላይ ይቆጣል። ይህ የማሳመኛ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “አድራጎታችሁ ፍትሕን ማወቅ እንደማያስፈልጋችሁ የምታስቡ ያስመስላችኋል”።
መልካምን ትጠላላችሁ፣ ክፋትንም ትወድዳላችሁ
እነዚህ ስማዊ ቅጽሎች እንደ ቅጽል ሊተረጎሙ ይችላሉ። ኢ.ት: “መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ ትጠላላችሁ፣ ክፉ የሆነውን ነገር ሁሉ ትወድዳላችሁ”
እናንተ ቆዳቸውን የምትገፉ፣ ሥጋቸውን ከአጥንታቸው የምትለዩ … በመጥበሻ እንዳለ ሥጋ
መሪዎቹ በድኾቹ ላይ ያላቸው ጭከና ሥጋ ሻጭ ለሥጋ የሚሆኑትን እንስሳት እንደሚቆራርጥ በዘይቤአዊ አነጋገር ተገልጿል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Micah 3:4
ወደ እግዚአብሔር ጩኹ
“ለዕርዳታ ወደ እግዚአብሔር ተጣሩ”
እርሱ አይመልስላችሁም
“እንዲያደርግ የምትጠይቁትን አያደርግም”
ፊቱን ከእናንተ ይሰውራል
ፊትን መሰወር ለመስማት ያለመፍቀድ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “ፊቱን ከእናንተ ይሰውርና ይደብቃል” ወይም “ሊረዳችሁ ፍላጎት እንደሌለው ታያላችሁ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Micah 3:5
ሕዝቤን የሚያስቱ
በመልካም መንገድ መሄድ እግዚአብሔርን የመታዘዝ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። መሳት ደግሞ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን በዚህ ጉዳይ ምናልባት ባለማወቅ ይሆናል። ኢ.ት: “ሕዝቤ እንዲይታዘዘኝ የሚመሩት”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አንዱ የሚበሉትን አንዳች ነገር ከሰጣቸው ‘ሰላም’ን ያውጁለታል።
ሚክያስ በእርግጥ ሊሆን ያለውን ሁኔታ ለመግለጽ ዘይቤአዊ አነጋገርን ይጠቀማል። “የሚበሉት አንዳች ነገር” የሚለው ሐረግ አነስተኛ ክፍያን ለመግለጽ የዋለ ምጸታዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ምጸት የሚለውን ተመልከት)
በአፋቸው አንዳች በማያኖር ጦርነት ሊያውጁበት ራሳቸውን ይሰጣሉ
ሚክያስ በእርግጥ ሊሆን ያለውን ሁኔታ ለመግለጽ ዘይቤአዊ አነጋገርን ይጠቀማል። “በአፋቸው አንዳች በማያኖር” የሚለው ሐረግ የፈለጉትን ያለመስጠት መጸታዊ ግነት ነው። ኢ.ት: “ጥቂት የሚከፍሏቸውን ሰዎች ለማጥፋት የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ምጸት የሚለውን ተመልከት)
ለእናንተ ጨለማ ይሆናል … በእነርሱ ላይ ቀኑ ይጨልምባቸዋል
ጨለማ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ያለመናገሩ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ራዕይ አይኖራችሁም
“ከእንግዲህ ራዕይ አታዩም”
ባለ ራዕዮች ያፍራሉ፣ ንግርተኞችም ይደናገራሉ
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ባለ ራዕዮች እንዲያፍሩ አደርጋለሁ፣ ንግርተኞችንም አደናግራቸዋለሁ”።
ሁሉም ከንፈሮቻቸውን ይሸፍናሉ
እዚህ ጋ “ከንፈሮች” መናገርን ይወክላል። ኢ.ት: “ከእንግዲህ አይናገሩም”
ከእኔ ዘንድ ምንም መልስ አይኖርም
“ዝም እላለሁ”
Micah 3:8
እኔ ግን
እዚህ ጋ “እኔ” እውነተኛውን፣ ራሱን ከሐሰተኞች ነቢያት የለየውን ሚክያስን ያመለክታል።
በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይልን፣ ፍትሕና ብርታትንም ተሞልቻለሁ
ሚክያስ ራሱን እግዚአብሔር ፈሳሽ እንደሚያፈስበት መያዣ ዕቃ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት: “የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይልን፣ ፍትሕንና ብርታትን ሰጥቶኛል” ወይም “እንድጠነክር፣ ፍትሕ ምን እንደሆነ እንድሰብክና ብርቱ እንድሆን የእግዚአብሔር መንፈስ አስችሎኛል”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለያዕቆብ መተላለፉን፣ ለእስራኤልም ኃጢአቱን ለማስታወቅ
እዚህ ጋ “ያዕቆብ” እና “እስራኤል” የያዕቆብን ዘሮች የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። ሚክያስ ሁለቱን ስሞች የሚጠቀመው ዘሮቹ ሁሉ በኃጢአት በደለኞች ስለመሆናቸው አጽንዖት ለመስጠት ነው። የነገር ስም የሆኑትን “መተላለፍ” እና “ኃጢአት” ግሥ በመጨመር መተርጎም ይቻላል። ኢ.ት: “የያዕቆብ ዘሮች የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጣሳቸውን ለማስታወቅ፣ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ኃጢአትን መሥራታቸውን እነግራቸዋለሁ”።
Micah 3:9
የያዕቆብ ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተ ሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። በዚህ ጉዳይ ቃሉ የያዕቆብን ዘሮች ያመለክታል። ኢ.ት: “የያዕቆብ ዘሮች”።
የእስራኤል ቤት
“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የለሚኖሩትን ቤተ ሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። በዚህ ጉዳይ ቃሉ የእስራኤል ሕዝብ የሆነውን የእስራኤልን ዘር ያመለክታል። ኢ.ት: “የእስራኤል ዘሮች” ወይም “እናንተ እስራኤላውያን”።
መጥላት
ከፍተኛ ጥላቻ
ጽዮንን በደም፣ ኢየሩሳሌምንም በኃጢአት ትገነባላችሁ
እዚህ ጋ “ደም” በፈሊጣዊ አነጋገር መግደል ማለት ሲሆን “ጽዮን” እና “ኢየሩሳሌም” በሕንጻ ተመስለዋል። ሚክያስ ባለጸጎች ሰዎችን መግደላቸውና ኃጢአት መሥራታቸውን ይናገራል፤ በሌላ አነጋገር ድርጊቶቻቸው ሰዎች ቤቶችን ለመሥራት የሚጠቀሙባቸውን ጡቦችና እንጨቶች ይመስላሉ። ኢ.ት: “ጽዮንን እና ኢየሩሳሌምን ታላቅ ለማድረግ በምትሠሩበት ጊዜ ትገድላላችሁ፣ ሌሎች የከፉ ኃጢአቶችንም ትሠራላችሁ” ወይም “በጽዮን ስታመልኩ ሳላችሁ ትገድላላችሁ፣


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በኢየሩሳሌም ስትበለጽጉ ሳላችሁም ሌሎች ኃጢአቶችን ትሠራላችሁ”። (ዘይቤአዊ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ከእኛ ጋር አይደለምን?
መሪዎቹ እግዚአብሔር አብሯቸው እንዳለ አጥብቀው ያምናሉ። ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንዳለ እናውቃለን!” ወይም “ለማድረግ የምንፈልገውን እንድናደርግ እግዚአብሔር እንደሚረዳን እናውቃለን”።
ክፉ
በሚክያስ 1:12 “አደጋ”ን እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Micah 3:12
በእናንተ ምክንያት
እዚህ ጋ “እናንተ” የሚያመለክተው ካህናቱን፣ ነቢያቱንና መሪዎቹን ነው (ሚክያስ 3፡ 11)።
ጽዮን የታረሰ እርሻ ትሆናለች ... የመቅደሱም ኮረብታ የቁጥቋጦ ዋሻ ይሆናል
“ጽዮን” እና “የመቅደሱ ኮረብታ” የሚያመለክቱት አንዱን ስፍራ ነው። ገበሬ እርሻ በሚያርስበት ጊዜ ዐፈሩን ይገለብጠዋል፣ በዚያ የበቀሉትን እጽዋት ሥር ሁሉ ይነቅላል። የቁጥቋጦ ዋሻ ለምንም በማይጠቅም በችፍግ የተሞላ ነው። እነዚህ ሁለት ዘይቤአዊ አነጋገሮች በተመሳሳይ ጊዜ ቃል በቃል እውነት ሊሆኑ አይችሉም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የመቅደሱን አካባቢ ፈጽመው እንዲያጠፉ ለወራሪዎቹ እንደሚፈቅድላቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የታረሰው መሬት
“ገበሬ ያረሰው መሬት”
የቁጥቋጦ ዋሻ
ትናንሽ እንጨትነት ያላቸው እጽዋት የሚበቅሉበት አካባቢ ነው።

---

Chapter 4
Micah 4:1
ተራሮቹ ... በሌሎች ተራሮች
እግዚአብሔር የቤት መቅደሱን ተራራ ከሌሎች ተራሮችና ኮረብቶች ሁሉ ማላቁ ቤተ መቅደሱን በምድር ላይ እጅግ አስፈላጊ ቦታ ስለ ማድረጉ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔር ቤት ተራራ ይመሠረታል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱ የሚገነባበትን ተራራ ይመሰርታል” ወይም “እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱ ታላቅ ሆኖ የሚገነባበትን ተራራ ይሠራል”።
በሌሎች ተራሮች ላይ
የጽዮን ተራራ ከተራሮች ሁሉ እጅግ አስፈላጊው ይሆናል። በተጨማሪም ይህ ተራራ በሚዋሰንበት አካባቢ ብቻ ሳይሆን በዓለም ከፍተኛው ተራራ ይሆናል ማለት ሊሆን ይችላል።
ከኮረብቶች በላይ ከፍ ይላል
ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ከኮረብቶች በላይ ከፍ ያደርገዋል” ወይም “እግዚአብሔር ከኮረብቶች ይልቅ ያልቀዋል”።
ሕዝቦች ወደ እርሱ ይጎርፋሉ
ምንጭ ከተለያየ አቅጣጫ ወደ አንድ ስፍራ ባለማቋረጥ ይጎርፋል። ብዙ ሕዝቦች ከተለያየ አቅጣጫ ወደ ቤተ መቅደሱ ተራራ ይመጣሉ። ኢ.ት: “የአገራቱ ሕዝቦች እንደ ምንጭ ወደ እርሱ ይጎርፋሉ” ወይም “የአገራቱ ሕዝቦች ወደ እርሱ ይሄዳሉ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Micah 4:2
ብዙ አገሮች
“አገሮች” የሚለው ቃል በፈሊጣዊ አነጋገር የአገራቱን ሕዝቦች ያመለክታል። ኢ.ት: “ሕዝቦች ከብዙ አገራት”።
ይመጣሉ
x
Micah 4:4
ሰዉን ሁሉ ከወይኑ በታች፣ ከበለሱንም በታች ያስቀምጡታል
“ወይን” እና “በለስ” ሁለቱም የብልጽግና ምልክቶች ናቸው። ይህ ሐረግ ሰዎች በብልጽግና እና በሰላም የሚኖሩበትን አኳኋን ይገልጻል። የወይን ፍሬ ወይም የበለስ ዛፍ የማይታወቅ ከሆነ ጠቅለል ባለ መንገድ ልትተርጉመው ትችላለህ። ኢ.ት: “በገዛ ራሳቸው የአትክልት ቦታና በመስኮቻቸው በሰላም ይቀመጣሉ”።
የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር አፍ ተናግሯልና
አፍ የሰውነት መግለጫ ምሳሌ ነው። ኢ.ት: “የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ተናግሯልና”።
ሕዝቦች በአምላካቸው ስም ይሄዳሉ ... እኛ በእግዚአብሔር ስም እንሄዳለን
በመንገድ መሄድ የአንድን ሰው የሕይወት አኗኗር የሚያሳይ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። በአንዱ ስም መሄድ የማምለክና የመታዘዝ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “ሕዝቦች አምላካቸውን ያመልካሉ፣ ይታዘዛሉም ... እኛ እግዚአብሔርን እናመልካለን፣ እንታዘዛለንም”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Micah 4:6
በዚያን ቀን
“በዚያን ጊዜ” ወይም “እነዚያን ነገሮች በማደርግበት ጊዜ”፤ እነዚህ ቃላት “የመጨረሻዎቹን ቀናት” ያመለክታሉ (ሚክያስ 4:1)። “ቀን” የሚለው ቃል የተወሰኑ ቀናትን ወይም ዓመታትን እንኳን ሊያመለክት ይችላል።
አንካሳው
ይህ በትክክል መራመድ የማይችሉትን ያመለክታል። አንካሳ መሆን የትኛውንም ዓይነት የአካል ጉዳተኝነት የሚያሳይ ምሳሌ ነው።
የተጣሉትን እሰበስባለሁ
“ከኢየሩሳሌም ያስወጣኋቸውን እሰበስባቸዋለሁ”
ተሰደው የወጡትን ወደ ብርቱ ሕዝብ
“እመልሳለሁ” የሚለውን ቃል ቀድም ብሎ ካለው ሐረግ መረዳት ይቻላል። ሊደጋገሙ ይችላሉ። “ተሰደው የወጡትን” የሚለው ሐረግ በገቢራዊ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “አሳድጄ ያስወጣኋቸውን ወደ ብርቱ ሕዝብነት እመልሳቸዋለሁ” ወይም “በግድ ያባረርኳቸውን ብርቱ ሕዝብ እንዲሆኑ አደርጋቸዋለሁ”።
አንተን የመንጋውን መጠበቂያ ማማ፣ የጽዮን ሴት ልጅ ኮረብታ፣ ለአንተ የቀድሞ ግዛትህ ይመለስልሃል
ሚክያስ ይሰማው ይመስል ለቤተ መቅደሱ ተራራ በሚናገርበት ጊዜ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ መናገሩ ነው። ሚክያስ መልዕክቱን ለሕዝቡ ማድረሱን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። ኢ.ት: “የቤተ መቅደሱን ተራራ በሚመለከት፣ እግዚአብሔር እናንተን የሚመለከትበት ስፍራ፣ በጎቹ፣ የኢየሩሳሌም ሕዝብ ስለ ቀድሞ ግዛቱ የሚመኩበት ስፍራ ይመለሳል”።
ለመንጋው የመጠበቂያ ማማ
በመጠበቂያ ማማው ላይ ሆኖ መንጋውን እንደሚጠብቅ እረኛ የኢየሩሳሌም ሕዝብ በዙሪያቸው የሚኖሩትን ሌሎች ሕዝቦች እንደሚጠብቁ ተነግሯል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የጽዮን ሴት ልጅ ... የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ
በስፍራው የሚኖሩ ሰዎች ስፍራው እንደ እናት፣ እነርሱ እንደ ሴት ልጆች እንደሆኑ ተቆጥሮ ተነግሯል። ኢ.ት: “በጽዮን የሚኖሩ ሰዎች ... በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ኮረብታ
አንዳንድ የዘመናችን ትርጉሞች ይህንን የዕብራይስጥ ቃል “ትልቅ ምሽግ” ወይም “ጠንካራ ምሽግ” ማለት እንደሆነ ይረዳሉ።
ለአንተ፣ የቀድሞ ግዛትህ ይመለስልሃል
የነገር ስም የሆነው “ግዛት” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ቀድሞ ታደርግ እንደነበረው አገሮችን ትገዛለህ” ወይም “ቀድሞ እንዳደረግኸው አገራቱን እንድትገዛ አደርግሃለሁ”።
Micah 4:9
አሁን ድምፅህን ከፍ አድርገህ የምትጮኸው ለምንድነው?
ሚክያስ ሕዝቡ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ለምን እንዲህ ባለ መንገድ እንደሚናገር እንዲያስቡ ለማድረግ በመሞከር በሕዝቡ ላይ ያላግጥባቸዋል። ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “ምን ያህል እንደምትጮኹ ተመልከቱ” ወይም “በኃይል የምትጮኹት ስለምን እንደሆነ በጥንቃቄ አስቡ”።
በመካከላችሁ ንጉሥ የለም? አማካሪዎቻችሁ ሞተዋል? እንደምታምጥ ሴት ሕመም የያዛችሁ ለዚህ ነው?
ሚክያስ በሕዝቡ ላይ ማላገጡን ቀጥሏል። እነዚህ ጥያቄዎች እንደ መግለጫዎች ሊተረጎሙ ይችላሉ። ኢ.ት: “ንጉሥ አላችሁ፣ ነገር ግን ምንም አይጠቅማችሁም። ጥበበኞቻችሁ ገና በሕይወት አሉ፣ ነገር ግን ምንም የሚነግሯችሁ ጥበብ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የላቸውም። ለዚህ ነው ልጅ እንደምትወልድ ሴት ድምፃችሁን አውጥታችሁ የምታለቅሱት”።

እንደምታምጥ ሴት የታመማችሁት

ሚክያስ ጠላት ከከተማቸው እንዲወጡ ሲያስገድዳቸው ሕዝቡ የሚገጥማቸውን ሥቃይ አንዲት ሴት ልጅ በምትወልድበት ጊዜ ከሚሰማት ሕመም ጋር ያነጻጽረዋል።

በዚያ ትድናላችሁ። በዚያ እግዚአብሔር ያድናችኋል

እግዚአብሔር እንደሚያደርግ የተናገረውን እንደሚያደርግ አጽንዖት ለመስጠት በገቢራዊና በኢገቢራዊ ድምፀ በሁለቱም ተመሳሳዩን ነገር ይናገራል። ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “በዚያ እግዚአብሔር ያድናችኋል። በዚያ እርሱ ያድናችኋል”።

ከጠላቶቻችሁ እጅ

“እጅ” ለሚለው ቃል የሚከተሉት ተስማሚ ትርጉሞች ናቸው፣ 1) እጅ ለሚሠራበት ኃይል ፈሊጣዊ አነጋገር ይሆን ይሆናል፣ ኢ.ት፡ “የጠላቶቻችሁ ኃይል” ወይም 2) ስለ ሰው ምሳሌ ይሆን ይሆናል። ኢ.ት፡ “ጠላቶቻችሁ”።

Micah 4:11

የረከሰች ትሁን

ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እናርክሳት”።

ዓይኖቻችን በመፈንደቅ ጽዮንን ይዩ

ዐይን የሰውን ሁለንተና የሚወክል ምሳሌ ነው። ኢ.ት፡ “ጽዮንን በመፈንደቅ እንያት” ወይም “ወራሪዎች ጽዮንን ሲያጠፏት በማየት ደስ ይበለን”።

በዐውድማ ላይ ለመወቃት እንደተዘጋጀ የእህል ክምር አንድ ላይ ሰብስቧቸዋል

ጸሐፊው እግዚአብሔር የእህሉን ክምር ዐውድማው ላይ እንዳደረገና ሊወቃው እንደተዘጋጀ ገበሬ አገሮችን ለማጥፋት መዘጋጀቱን ይናገራል።

Micah 4:13

የጽዮን ሴት ልጅ ሆይ፣ ተነሺ ውቂ ...ቀንድሽ ...ኮቴዎችሽ ... ታደቂያቸዋለሽ

“ያንቺ” እና “አንቺ” የተባሉት ሁሉ እንዲሁም ትዕዛዛት “የጽዮንን ሴት ልጅ” የሚያመለክቱ ሲሆኑ ነጠላ ቁጥርና አስታይ ናቸው።

የጽዮን ሴት ልጅ ሆይ፣ ተነሺ ውቂ፣ ቀንድሽን ብረት አደርገዋለሁ፣ ኮቴሽንም ነሐስ እንዲሆኑ አደርጋቸዋለሁ

እግዚአብሔር የጽዮንን ሕዝብ ስንዴ እንደሚወቃ ብርቱ በሬ፣ ጠላቱንም እንደ ስንዴ አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና የሚለውን ተመልከት)

ቀንድሽን ብረት አደርገዋለሁ፣ ኮቴሽንም ነሐስ እንዲሆኑ አደርጋቸዋለሁ

አንባቢህ በሬን ወይም ብረትን ወይም ነሐስን የማያውቅ ከሆነ ዘይቤአዊውን አነጋገር ልትተወው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ጠላቶችህን ሁሉ ማሸነፍና ማጥፋት እንድትችል አደርግሃለሁ። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የግፍ ሀብታቸውን

“ግፍን በማድረግ ያገኙትን ሀብት” ወይም “ከሌሎች ሰዎች የሰረቋቸውን ነገሮች”

ሀብታቸውን

የነገር ስም የሆነው “ሀብት” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የራሳቸው ያደረጓቸው ነገሮች”

---

Chapter 5

Micah 5:1

የወታደሮቹ ሴቶች ልጆች

የአንዲት ከተማ ሕዝብ እንደ ሴት ተቆጥረው ተነግሮላቸዋል። ወታደሮቹ ከተማይቱን አጥቅተዋታል። ኢ.ት፡ “ወታደሮቹ የሚያጠቋችሁ የከተማይቱ ሕዝብ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤልን ገዢ ጉንጩን በበትር ይመቱታል

በትር ባለ ማዕረግ የሆነ ሰው የበታቹን የሚቀጣበት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። የአንድን ሰው ጉንጭ መምታት ከመጉዳት ያለፈ ስድብ ነበር። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር የእስራኤልን ፈራጆች ወራሪዎች እንዲሰድቧቸው በማድረግ ይቀጣቸዋል!”። (ዘይቤአዊ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእስራኤል ፈራጅ

ይህ ምጸት ንጉሡ አብላጫውን ኃይልና ሥልጣኑን በማጣቱ ፈራጅ ብቻ መሆኑን ያሳያል።

Micah 5:2

አንቺ ቤተ ልሔም ኤፍራታ

እግዚአብሔር ለቤተ ልሔም ከተማ ለራሷ በሚናገርበት መልኩ ለይሁዳ ሕዝብ፣ በተለይም ለቤተ ልሔም ሕዝብ ይናገራል።

ኤፍራታ

ይህ ቤተ ልሔም የምትገኝበት አካባቢ ስም ወይም የቤተ ልሔም ሌላኛው ስሟ ወይም ይህችኛዋን ቤተ ልሔም ከሌላው መለያ ይሆን ይሆናል። ቤተ ልሔም ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ ስድስት ማይል ርቀት ላይ ትገኛለች። የንጉሥ ዳዊት የትውልድ መንደር ነበረች። ተርጓሚዎች የሚከተለውን የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይኖርባቸው ይሆናል፤ “ ‘ኤፍራታ’ የሚለው ስም ትርጉም ‘ፍሬአማ መሆን’ ማለት ነው”።

በይሁዳ ጎሳዎች መካከል ታናሽ ብትሆኚም አንድ ከአንቺ የሚወጣ አለ

“በይሁዳ ጎሳዎች ውስጥ ብዙ ሕዝብ ያለው ሌላ ቢኖርም ከሕዝብሽ የሚመጣው አንድ ነው”

ወደ እኔ ይመጣል

እዚህ ጋ “እኔ” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።

ጅማሬው ከጥንት ዘመን፣ ከዘላለም የሆነ

ይህ ከንጉሥ ዳዊት ጥንታዊ ቤተ ሰብ የሚመጣውን ገዢ ያመለክታል። “ከጥንት ዘመን” እና “ከዘላለም” የሚሉት ሐረጎች ትርጉማቸው በመሠረቱ አንድ ሆኖ የቤተ ሰቡ የትውልድ ሐረግ ምን ያህል ረጅም መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ።

ስለዚህ

“የተናገርኩት እውነት ስለሆነ” ወይም “ምክንያቱም በኋላ ይህ ገዢ ይመጣል”

ይተዋቸዋል

የእስራኤልን ሕዝብ ይተዋቸዋል

የምታምጠው እርሷ ልጅ እስከምትወልድበት ጊዜ ድረስ

ይህ ገዢው የሚወለድበትን የተወሰነ ጊዜ ያመለክታል።

የቀሩት ወንድሞቹ

በምርኮ ያሉ “የቀሩት የገዢው እስራኤላውያን ጓደኞች”

Micah 5:4

እርሱ በእግዚአብሔር ኃይል ይቆማል፣ መንጋውንም ይጠብቃል

በጎቹን የሚመግብና የሚጠብቅ እረኛ ለእስራኤል ሕዝብ የሚያስፈልጋቸውን የሚያቀርበውንና የሚጠብቃቸውን ገዢ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ሕዝቡን እንዲመራለት እግዚአብሔር ኃይልን ይሰጠዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በአምላኩ በእግዚአብሔር ስም ግርማ

የሰውየው ስም ስላለው ሥልጣን ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “አምላኩ እግዚአብሔር እንዲገዛ ሥልጣንን ስለሰጠው ሰዎች ያከብሩታል”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነርሱ ይኖራሉ

የእስራኤል ሕዝብ ይኖራሉ

ይኖራሉ

“በሰላም ይኖራሉ”

እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ታላቅ ይሆናል

በየአገሩ ያለ ሕዝብ ሁሉ ለእስራኤል ገዢ ክብርን ይሰጠዋል

ሰባት እረኞችንና ስምንት መሪዎችን እናስነሣባቸዋለን

እዚህ ጋ “እረኞች” የሚለው ቃል በሌላ አነጋገር “ሰዎችን የሚመሩ” ሲሆኑ በፈሊጣዊ አነጋገር “ገዢዎች” ማለት ነው። “ሰባት ... እና ስምንት” የሚለው ሐረግ “ከበቂ በላይ” ለሚለው የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት፡ “በቂ፣ ከበቂም እንኳን በላይ የሆኑ መሪዎች” ወይም “በሰዎች ላይ ከበቂ በላይ የሆኑ እረኞችና መሪዎች”

Micah 5:6

የአሦራውያንን ምድር በሰይፍ፣ የናምሩድንም ምድር በበሩ ላይ በእረኝነት ይጠብቃሉ

ሰይፍ በጦርነት ውስጥ ለመግደያነት በፈሊጣዊነት ተነግሯል። እዚህ ጋ እስራኤላውያን በጎችን ከመጠበቅ ይልቅ ያረዷቸው በሚመስል መልኩ በአሦራውያን ላይ ገዢ መሆናቸው በምጸት ተነግሯል። የአሦር ምድር በዚያ ለሚኖሩ ሰዎች ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። የከተሞቹ በሮች ሕጋዊ ንግድ የሚካሄድባቸው ስፍራዎች ነበሩ። ኢ.ት፡ “የአሦርን ሕዝብ ይወጋሉ፣ የናምሩድን ምድር ክተሞችም ይገዛሉ”።

ጦርነት

የናምሩድ ምድርም

“በእረኝነት ይጠብቃሉ” የሚሉትን ቃላት ከዐረፍተ ነገሩ መነሻ መረዳት ይቻላል። ሊደጋገሙ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “የናምሩድን ምድር በእረኝነት ይጠብቃሉ”።

የናምሩድ ምድር

ይህ የአሦር ምድር ሌላው ስሙ ነው። ናምሩድ አደን ያደን የነበረ የቀድሞ ገዢ ነበር። ተርጓሚዎች ይህንን የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይኖርባቸው ይሆናል፤ “ ‘ናምሩድ’ የሚለው ስም ትርጉም ‘ዓመፅ’ ማለት ነው”።

ያድናል

ገዢው ያድናል

ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ጠል፣ በሣሩ ላይ እንደሚወርድ ካፊያ

ጠልና ዝናብ ምድሪቱን በማረስረስ አንዳንድ ነገሮች እንዲበቅሉ ያደርጋሉ። እስራኤላውያን በመካከላቸው የሚኖሩባቸው ሕዝቦች በሰላም እንዲኖሩ ያደርጓቸዋል።

ሰውን የማይጠብቅ ሣር፣ የሰው ልጆችንም አይጠብቁም

“ሣር ሰውን ወይም የሰው ልጆችን አይጠብቅም”፤ ጠልንና ዝናብን የሚያርከፈክፍ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

Micah 5:8

አጠቃላይ መረጃ፡

እግዚአብሔር ሕዝቡን በጦርነት ከቀጣቸው በኋላ በሕይወት ያሉት እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ፈጽመው ድል እንደሚያደርጉና እንደሚገዟቸው እግዚአብሔር ተስፋ ይሰጣል።

የያዕቆብ ትሩፍ

ከጦርነቱ የሚተርፉ የያዕቆብ ተወላጆች

በአገራት መካከል፣ በብዙ ሕዝቦች መካከል

እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ሲሆን “የያዕቆብ ትሩፍ” በብዙ የተለያዩ አገሮች እንደሚኖሩ አጽንዖት ይሰጣሉ።

በጫካ እንስሶች መካከል እንዳለ አንበሳ፣ በበግ መንጋም መካከል እንዳለ የአንበሳ ደቦል

አናብስት በጫካ የሚኖረውን የትኛውንም እንስሳ መግደልና መብላት ይችላሉ፣ በጎችንም በቀላሉ ይገድላሉ። ኢ.ት፡ “እንደ ተናካሽ የዱር እንስሳት፣ ምስኪን ከብቶችን እንደሚገድሉ የዱር እንስሶች”

በመካከላቸው በሚሄድበት ጊዜ

የአንበሳ ደቦል በበግ መንጋ መካከል በሚሄድበት ጊዜ

አላያቸው ላይ ይከመርባቸውና ይዘነጣጥላቸዋል

“ይዘልባቸውና ይጥላቸዋል፣ ከዚያም ይዘነጣጥላቸዋል”

እጅህ … ጠላቶችህ

ጸሐፊው የሚናገረው እግዚአብሔርን ነው፤ በመሆኑም “አንተ” የተሰኙት ሁለቱም ተባዕት ነጠላ ቁጥር ናቸው።

እጅህ በጠላቶችህ ላይ ይነሣል

እጅ በፈሊጣዊ አነጋገር ለመሥራት ያለውን ኃይል ገላጭ ነው ወይም የሰውን ሁለንተና የሚወክል ምልክት ነው። እጅን ማንሣት ኃይልን መግለጥ ነው። ኢ.ት፡ “ጠላቶችህን ሙሉ በሙሉ ድል ታደርጋቸዋለህ”።

ያጠፋቸዋል

እጅ የሰውን ሁለንተና የሚወክል ምልክት ነው። ኢ.ት፡ “ታጠፋቸዋለህ”

Micah 5:10

በዚያን ቀን

“በዚያን ጊዜ” ወይም “እነዚያን ነገሮች በማደርግበት ጊዜ”። እነዚህ ቃላት “የመጨረሻዎቹን ቀናት” ያመለክታሉ (ሚክያስ 4፡1)። “ቀን” የሚለው ቃል የተወሰኑትን ቀናት ወይም ዓመታትን እንኳን ሊያመለክት ይችላል።

ከመካከልህ ፈረሶችህን አጠፋለሁ፣ ሰረገላዎችህንም አወድማለሁ

እስራኤላውያን ፈረሶችን እና ሰረገላዎችን ለጦርነት ብቻ ይጠቀሙ ነበር፤ ምናልባት በዙሪያቸው ካሉ አምላክየለሽ አገራት ጋር ተገበያይተው ይሆናል። ሰዎች በእርሱ ከመታመን ይልቅ እንዲጠብቋቸው በጦር መሣሪያዎቻቸው መታመናቸውን እግዚአብሔር አይፈልግም።

ከመካከልህ ፈረሶችህን … ሰረገላዎችህን … ምድርህን … ምሽጎችህን

እግዚአብሔር እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።

Micah 5:12

በእጅህ ያለውን ጥንቆላ

በ”እጅ” መሆን የሚወክለው ሰውየው የሚያደርገውን ተግባር ነው። ኢ.ት፡ “አንተ የምታደርገው ጥንቆላ”

እጅህ … ትፈቅዳለህ … የተቀረጸው ምስልህ … ድንጋይህ …በመካከልህ። ትፈቅዳለህ … እጆችህ … አሼራህ … በመካከልህ … ከተሞችህ

እግዚአብሔር እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጥሏል።

የእጆችህን ሙያ

የንገር ስም የሆነው “ሙያ” “ሥራ” በሚል ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እጆችህ የሠሩትን”።

የአሼራ ምስልህን ምሶሶ እነቅላለሁ

እግዚአብሔር ከመሬት ውስጥ እንደሚነቅላቸው ዛፎች ስለ አሼራ ምስል ምሶሶ ይናገራል። ኢ.ት፡ “የአሼራ ምስልህን ምሶሶ ከምድር ውስጥ እነቅላለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 6

Micah 6:1

መዋቅሩና አቀራረቡ

ይህ ምዕራፍ የተጻፈው እንደ ፍርድ ቤት ጉዳይ ወይም እግዚአብሔር በራሱ ሕዝብ ላይ ሙግት እንዳለው ሆኖ ነው።

በሙግቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች በዚህ ምዕራፍ ለመተርጎም አስቸጋሪ ከሚሆኑት ውስጥ ናቸው

ሙሴ፣ አሮንና ማርያም በእስራኤል ላይ ለእግዚአብሔር ምስክር ሆነው ተጠቅሰዋል። አክዓብና ዖምሪ እግዚአብሔርን እንዳልተከተሉ ክፉ ነገሥታት ሆነው ተጠቅሰዋል። ለሙሴ ሕግ መታዘዝ ለሕጉ ካለመታዘዝ ጋር ተነጻጽሯል።

እንግዲህ ስሙ … የእግዚአብሔርን ሙግት ስሙ

ሚክያስ ሊሰሙት ይችሉ ይመስል ለተራሮች ሲናገር የሚናገረው ለእስራኤል ሕዝብ ነው፤ ስለዚህ በሁለቱም አገላለጽ “ስሙ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው።

ተነሥ … አቅርብ … ድምፅህ …

ሚክያስ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል፤ ስለዚህ ትዕዛዞቹና “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው።

ተነሥና በተራሮቹ ፊት ነገርህን አቅርብ፤ ኮረብቶቹም ድምፅህን ይስሙ

እግዚአብሔር በፍርድ ቤት እንዳለና ተራሮችና ኮረብቶች ፈራጆቹ እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። የእስራኤል ሕዝብ ያደረጉትን ለምን እንዳደረጉ ለዳኞቹ እንዲናገሩ ያዛቸዋል።

ተራሮቹ … ኮረብቶቹ … የጸኑት የምድር መሠረቶች

ሚክያስ ሰዎች እንደሆኑ ቆጥሮ ለእነዚህ ነገሮች ይናገራል። ሚክያስ ተራሮችን፣ ኮረብቶችንና የምድርን መሠረቶች በሕዝቡ ጣዖት አምላኪነት ላይ ዘላለማዊ ምስክር አድርጎ ያቀርባቸዋል።

Micah 6:3

ሕዝቤ ሆይ፣ ምን አድርጌአችኋለሁ? ያደከምኋችሁ በምንድነው? መስክሩብኝ!

እግዚአብሔር መልካም አምላክ ስለመሆኑና ሕዝቡ እርሱን ማምለካቸውን እንዲያቆሙ የሚያስደርግ ምንም ነገር እንዳላደረገ አጽንዖት ለመስጠት ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት፡ “ሕዝቤ ሆይ፣ እኔ ለእናንተ መልካም ነበርኩኝ። በእኔ ምክንያት የምትደክሙበትን ምንም ነገር አላደረግሁም። እንዳደረግሁ ካሰባችሁ አሁን መስክሩብኝ”።

ለእናንተ … አደከምኳችሁ? መስክሩ … አመጣኋችሁ … አዳንኳችሁ … ማርያምን ለእናንተ … አስቡ … ሄዳችሁ … ታውቁ ዘንድ

ሚክያስ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ለሕዝቡ ይናገራል፤ ስለዚህ ትዕዛዞቹ ሁሉና “አንተ” የሚሉት ሁሉ ተባዕታዊ ነጠላ ቁጥር ናቸው።

የባርነት ቤት

ቤት አንድ ሰው ለረጅም ጊዜ የሚኖርበት ስፍራ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። የንገር ስም የሆነው “ባርነት” “ባሪያዎች ልትሆኑ” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ለረጅም ጊዜ ባሪያዎች ሆናችሁ የኖራችሁበት ስፍራ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ባላቅ የመከረውን

“ባላቅ እናንተን ለመጉዳት ያቀደውን”

በለዓም እንዴት … እንደ መለሰለት

በለዓም ባላቅ በጠራው ጊዜ በመምጣቱ ለባላቅ ታዞአል። ኢ.ት፡ “በለዓም ባላቅ እንዲያደርግ የጠየቀውን … እንዴት እንዳደረገ” ወይም 2) ባላቅ እንዳዘዘው እስራኤላውያንን በመርገም ፈንታ ለምን እንደባረካቸው በለዓም ለባላቅ አብራራለት። ኢ.ት፡ “በለዓም ለባላቅ የነገረውን” ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው።

ቢዖር

ይህ የበለዓም አባት ስም ነው።

ሰጢም

ይህ በሞዓብ የሚገኝ የቦታ ስም ነው።

ስለዚህ የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሥራዎች ታውቁ ዘንድ

እግዚአብሔር በገዛ ስሙ ወደ ራሱ ያመለክታል። ኢ.ት: “እኔ እግዚአብሔር ያደረግሁላችሁን የጽድቅ ነገሮች ታስታውሱ ዘንድ”።

Micah 6:6

ወደ እግዚአብሔር ምን ላምጣ ... እግዚአብሔር? አሮጌ ... ልምጣ? ዘይት ... እግዚአብሔር ደስ ይለዋል? ኃጢአት ... ልስጠው?

ሚክያስ፣ እግዚአብሔር ምን እንዲያደርግ እንደሚፈልግበት በእውነት ለማወቅ እንደሚፈልግ ሰው ሆኖ ይናገራል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) ጥያቄ ይጠይቅና በቁጥር 8 ለጠየቀው ጥያቄ መልስ ይሰጣል ወይም 2) ሕዝቡን ለማስተማር በጥያቄ ይጠቀማል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ሆይ፣... ለእግዚአብሔር ምንም ማምጣት እንደማያስፈልገን አውቃለሁ ወይም ልምጣ ... አሮጌ፣ እና ዘይት ወይም ... ኃጢአት ...ብሰጥ”

ሺዎችን አውራ በጎች ... አሥር ሺዎች የዘይት ወንዞችን

“1,000 የአውራ በጎች መንጋ ... 10,000 የዘይት ወንዞችን”

እርሱ ነግሯችኋል

“እግዚአብሔር ነግሯችኋል”

ደጎና፣ እግዚአብሔር ከእናንተ የሚፈልገው፤አድርጉ ... እግዚአብሔር

በርካታ ትርጉሞች የሚሉት፣ “ደኅና/ እግዚአብሔር ከእናንተ የሚፈልገው ምንድነው? እግዚአብሔር ... እንድታደርጉ ይፈልጋል” ወይም “ደኅና፤ እግዚአብሔር ... እንድታደርጉ እንጂ ከእናንተ የሚፈልገው ምንድነው?”

ደግነትን ውደዱ

የነገር ስም የሆነው “ደግነት” ቅጽሉን “ደግ” በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። ኢ.ት: “ለሰዎች ደግ መሆንን ውደዱ”።

Micah 6:9

የእግዚአብሔር ድምፅ ከተማይቱን ይጣራል

ድምፅ ሰውየውን ሲወክል ከተማ ደግሞ በውስጡ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ጥሪ ያስተላልፋል”።

አሁን እንኳን ጥበብ ለስምህ ዕውቅና ትሰጣለች

ጥበብ እንደ ሰው ተነግሮላታል፣ በፈሊጣዊ አነጋገር ጥበበኛን ሰው ያመለክታል። እዚህ ጋ “ስም” የሚለው ቃል ስለ ሰውየው ስለ ራሱና ሰዎች ስለ ሰውየውና ስለ ሥልጣኑ የሚያስቡትን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “ጥበበኛው ሰው ይፈራሃል” ወይም “ጥበበኛ ሰው አንተ መልካም መሆንህን ያውቃል፣ ይታዘዝሃልም”።

በትሩንና በስፍራው ያስቀመጠውን እርሱን ልብ በሉ

እዚህ ጋ “በትር” እግዚአብሔር “በስፍራው ያስቀመጠው” እና የራሱን ሕዝብ የሚቀጣበትን የጠላትን ሰራዊት ያመለክታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አታላዮች በሆኑ በክፉዎች ቤት ውስጥ ባለጸግነት አለ

በማታለል የተገኘ ባለጸግነት ሰዎች በማታለል ተግባር ያገኙትን ባለጸግነት የሚያሳይ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “ክፉው” የሚለው ቃል ክፉዎች ሰዎችን ያመለክታል። ቤቶች አንድ ሰው የራሱ ንብረት የሚያደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ የሚያመልክት ምሳሌ ነው። ኢ.ት: “ክፉዎች ሰዎች ባለጸግነትን ለማግኘት የማታለልን ተግባር ፈጽመዋል”።

ሐሰተኛ መለኪያ

ሰዎች ብልጽግናቸውን ለማብዛት የሚገበያዩአቸውን ሌሎች ሰዎች በሚዛን በማጭበርበር የሚጠቀሙበት ትክክለኛ ያልሆነ መስፈሪያ ነው።

Micah 6:11

በ ... የሚመዝነውን ሰው ንጹሕ እንደሆነ ልቁጠረው?

ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: “በ ... የሚመዝነውን ሰው በእርግጠኝነት ንጹሕ አድርጌ አልቆጥረውም”።

የሚያጭበረብሩ ሚዛኖች

ሻጮች ገዢዎችን የሚያጭበረብሩባቸው ሚዛኖች

ባለጸጋ ሰዎች ሁከትን የተሞሉ ናቸው

ባለ ጸጎች ሰዎች የሆነን ነገር እንደሚይዝ ዕቃ ተቆጥረዋል፤ ሰዎች እርስ በእርሳቸው በቁጣ የሚያደርጉት ነገር በዕቃ ውስጥ እንደሚያኖሩት ፈሳሽ ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት: “ባለ ጸጎች ሰዎች በሁሉም ላይ በቁጣ ያደርጋሉ” ወይም “ባለጸጎች ሰዎች ሁል ጊዜ በቁጣ ያደርጋሉ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በአፋቸው ውስጥ ያለው ምላሳቸው አታላይ ነው

ምላስ የሰው ምሳሌው ነው። ኢ.ት: “የሚናገሩት ሁሉ ውሸት ነው”

Micah 6:13

አንተን በኃይለኛ ምት እመታሃለሁ

እግዚአብሔር ሕዝቡን በኃይለኛ ምት ይመታቸዋል ማለት እንደሚቀጣቸው የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “ክፉኛ ቀጥቻችኋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ባዶነታችሁ በውስጣችሁ ይኖራል

አንድ ሰው ወይም እንስሳ ሲራብ አንዳች ነገር በዕቃ ውስጥ በሚደረግበት መልኩ ሕዝቡ በመያዣ ዕቃ ተመስለው ተነግሮባቸዋል። ኢ.ት: “ትራባላችሁ፣ ራሳችሁን ለማርካት ጠግባችሁ አትበሉም”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የዖምሪ ሥርዓትና የአክዓብ ቤት ሥራዎች ሁሉ ተጠብቀዋል

ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል፣ አንተም ዋናውን ቃል የገደፉት በገደፉበት ቦታ ቃላቱን ማሟላት ይኖርብህ ይሆናል። ኢ.ት: “ዖምሪ ያዘዘውን ፈጽመሃል፣ የአክዓብ ቤት ያደረጋቸውን እነዚያኑ ነገሮች አድርገሃል”።

ዖምሪ ... አክዓብ

ሁለቱም ሰዎች የሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥት ነገሥታት ነበሩ። እግዚአብሔር ሁለቱም እጅግ ክፉዎች እንደነበሩ ተመልክቶአል።

የአክዓብ ቤት

“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተ ሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “የአክዓብ ዘሮች”።

በምክራቸው ሄደሃል

በመንገድ ላይ መሄድ አንድ ሰው የሚኖረውን ሕይወቱን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “ዖምሪና አክዓብ ሕዝቡ እንዲያደርጉ የነገሯቸውን አንተ ታደርጋለህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የፈራረሰ ከተማ አደርግሃለሁ፣ እናንተን ነዋሪዎቿንም የመሳለቂያ ምልክት

ሚክያስ ሊሰማው ለማይቻለው ለከተማው ለራሱ የሚናገር ይመስል ሊሰሙት ለሚችሉት ለከተማይቱ ሰዎች ይናገራል። ዋና ቃል ገዳፊዎች የተውአቸውን ቅላት ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። ኢ.ት: “ከተማህን ፍርስራሽ አደርጋታለሁ፣ እናንተን ነዋሪዎቿንም የመሳለቂያ ምልክት አደርጋችኋለሁ” ወይም “የፈራረሰች ከተማ አደርግሃለሁ፣ የከተማይቱ ነዋሪዎች፣ የሚያዩህም ሁሉ እንዲሳለቁብህ አደርጋለሁ” ወይም “ከተማይቱን ፍርስራሽ አደርጋታለሁ፣ በነዋሪዎቿም ላይ ሰዎች እንዲሳለቁ አደርጋለሁ”።

የሕዝቤን ወቀሳ ትሸከማለህ

“ሕዝቤ ስለሚወቅስህ መከራን ታያለህ”

Micah 6:16

የዖምሪ ሥርዓትና የአክዓብ ቤት ሥራዎች ሁሉ ተጠብቀዋል

ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል፣ አንተም ዋናውን ቃል የገደፉት በገደፉበት ቦታ ቃላቱን ማሟላት ይኖርብህ ይሆናል። ኢ.ት: “ዖምሪ ያዘዘውን ፈጽመሃል፣ የአክዓብ ቤት ያደረጋቸውን እነዚያኑ ነገሮች አድርገሃል”።

ዖምሪ ... አክዓብ

ሁለቱም ሰዎች የሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥት ነገሥታት ነበሩ። እግዚአብሔር ሁለቱም እጅግ ክፉዎች እንደነበሩ ተመልክቶአል።

የአክዓብ ቤት

“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ቤተ ሰቦች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “የአክዓብ ዘሮች”።

በምክራቸው ሄደሃል

በመንገድ ላይ መሄድ አንድ ሰው የሚኖረውን ሕይወቱን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “ዖምሪና አክዓብ ሕዝቡ እንዲያደርጉ የነገሯቸውን አንተ ታደርጋለህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የፈራረሰ ከተማ አደርግሃለሁ፣ እናንተን ነዋሪዎቿንም የመሳለቂያ ምልክት

ሚክያስ ሊሰማው ለማይቻለው ለከተማው ለራሱ የሚናገር ይመስል ሊሰሙት ለሚችሉት ለከተማይቱ ሰዎች ይናገራል። ዋና ቃል ገዳፊዎች የተውአቸውን ቅላት ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። ኢ.ት: “ከተማህን ፍርስራሽ አደርጋታለሁ፣ እናንተን ነዋሪዎቿንም የመሳለቂያ ምልክት አደርጋችኋለሁ” ወይም “የፈራረሰች ከተማ አደርግሃለሁ፣ የከተማይቱ ነዋሪዎች፣ የሚያዩህም ሁሉ እንዲሳለቁብህ አደርጋለሁ” ወይም “ከተማይቱን ፍርስራሽ አደርጋታለሁ፣ በነዋሪዎቿም ላይ ሰዎች እንዲሳለቁ አደርጋለሁ”።

የሕዝቤን ወቀሳ ትሸከማለህ

“ሕዝቤ ስለሚወቅስህ መከራን ታያለህ”



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

# Chapter 7

## Micah 7:1

በበጋ የተሰበሰበውን ፍሬ፣ የተለቀመውንም ወይን መስያለሁ

ሚክያስ አጫጆች አጭደው ከጨረሱት በኋላ ምግብ የሚሆነውን እንደሚፈልግ ሰው ታማኝ ሰዎችን እንደፈለገ ነገር ግን አንድም ሰው እንዳጣ ይናገራል። ፍሬ ለመሰብሰብ የሚፈልገው ሰው አሳቡ በግልጽ መቀመጥ መቻል አለበት። ኢ.ት፡ “የበጋው ፍሬ ከተሰበሰበ በኋላ ፍሬ የሚፈልገውን፣ ወይኑ ከተለቀመም በኋላ ቃርሚያውን እንደሚለቅም ሰው መስያለሁ”።

የወይን ዘለላል የለም … የበሰለው የመጀመሪያ በለስ የለም

ሚክያስ ለመበላት ጥሩ እንደሆነ ፍሬ ታማኝና ትክክለኛ ስለሆኑ ሰዎች ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ታማኞች ሰዎች ከምድሪቱ ጠፍተዋል፤ አንድም ትክክለኛ የሆነ ሰው የለም … ሁሉም ደም ለማፍሰስ ያደባሉ፤ እያንዳንዱ ያጠምዳል

እነዚህ ግነቶች ናቸው። ኢ.ት፡ “ታማኞች ሰዎች ከምድሪቱ እንደ ጠፉ ይሰማኛል፣ ትክክለኛ ሰው የለም፣ ሁሉም ደም … የሚያደቡ ይመስለኛል፣ እያንዳንዱም ያጠምዳል።

ደም ለማፍሰስ

ደም የንጹሐንን ሞት የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ንጹሐን ሰዎችን ለመግደል”

## Micah 7:3

እጆቻቸው በጣም ጥሩዎች ናቸው

እጅ የሰው ምሳሌ ነው። ኢ.ት፡ “ሕዝቡ በጣም ጥሩዎች ናቸው”።

ከእነርሱ እጅግ የተሻለው እንደ አሜከላ ነው፣ እጅግ ትክክለኛው ከእሾኽ ኩርንችት የከፋ ነው

አሜከላና እሾህ ለምንም የማይጠቅሙና የሚነካቸውን የሚጎዱ ናቸው። እስራኤላውያን ገዢዎች እና ፈራጆች አንዳች መልካም አላደረጉም፣ ሕዝቡንም ጎዱት።

እጅግ ትክክለኛው

“ከእነርሱ መልካም የሆነውን ለማድረግ የሚጥሩት”

በጠባቂዎቻችሁ አስቀድሞ የተነገራችሁ፣ የምትቀጡበት ቀን ይህ ነው

ሚክያስ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል፣ ስለዚህ በሁለቱም ሁኔታ “የእናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። “ጠባቂ” የሚለው ቃል ነቢያትን የሚመለከት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ነቢያቶቻቸው እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው ነግረዋቸዋል”።

ግራ የሚጋቡበት ሰዓት አሁን ነው

የነገር ስም የሆነው “ግራ የሚጋቡበት” እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የሚሆነውን ነገር የማይረዱበት ጊዜ አሁን ነው”።

## Micah 7:5

የትኛውንም ባልንጀራችሁን አትታመኑ … የገዛ ቤቱን ሰዎች

ሚክያስ ከእንግዲ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል አንድም ደግ፣ ታማኝና ለእግዚአብሔር የሚገዛ እንደሌለ ማሳየቱን ቀጥሏል። እዚህ ጋ ጓደኞቻቸውን ወይም ቤተ ሰቦቻቸውን መታመን እንደማይችሉ አጽንዖት ይሰጣል።

ምራት በአማቷ ላይ

“ትነሣለች” የሚለው ቃል ቀደም ብሎ ካለው ሐረግ ምን ማለት እንደሆነ መረዳት ይቻላል። እዚህም ሊደገሙ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “ምራት በአማቷ ላይ ትነሣለች”።

የገዛ ቤቱ

“ቤት” የሚለው ቃል በቤቱ ውስጥ የሚኖሩ ቤተ ሰቦችን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የገዛ ቤተ ሰቡ”

## Micah 7:7

አጠቃላይ መረጃ፡

ሚክያስ በቁጥር 8 ላይ አንዲት ሴት ጠላቷ ለሆነች ለሌላይቱ ሴት በምትናገርበት መልኩ መናገር ይጀምራል። ይህቺ ምናልባት የእስራኤል ሕዝብ የምትወክለው፣ “ለወታደሮቹ ሴት ልጅ” የምትናገር (ሚክያስ 5፡1)፣ እስራኤልን ወግተው የነበሩትን አገሮች የምትወክል የጽዮን ሴት ልጅ ትሆን ይሆናል (ሚክያስ 1፡13)። በእንግሊዝኛው “ዩ” ያሉበት ትዕዛዛቱና ምሳሌዎቹ ሁሉ አነስታይ ጾታ ነጠላ ቁጥር ነው።

ለእኔ ግን

እዚህ ጋ “እኔ” የሚያመለክተው ሚክያስን ነው።

የድነቴን አምላክ እጠብቃለሁ

“ድነት” የሚለው የነገር ስም እንደ ግሥ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “የሚያድነኝን እግዚአብሔርን እጠብቃለሁ” ወይም “አዳኙን እግዚአብሔርን እጠብቃለሁ”።

ይሰማኛል

“መስማት” የሚለው ቃል መስማትንና ማድረግን ይወክላል። ኢ.ት፡ “ሊረዳን ይነሣል”

መውደቅ …መነሣት

እነዚህ ቃላት በአደጋ ምክንያት መከራንና ከዚያ ማገገምን የሚያመለክቱ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በጨለማ መቀመጥ

እነዚህ ቃላት በአደጋ ምክንያት መከራ መሠቃየትን የሚያመለክቱ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

## Micah 7:9

ቁጣውን እታገሳለሁ

ቁጣ ሚክያስ በእግዚአብሔር ተገዶ እንደ ተሸከመው ጠጣር ነገር ተደርጎ ተነግሯል። ኢ.ት፡ “እርሱ ስለተቆጣኝ እሰቃያለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ስለ ጉዳዬ እስኪሟገትልኝና እስኪፈርድልኝ ድረስ

የእስራኤልን ሕዝብ የጎዱትን ሌሎች ሕዝቦች እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል።

ይሟገትልኛል

እግዚአብሔር በፍርድ ቤት ለሚክያስ እንደሚከላከልለት ሆኖ ተነግሮለታል። ኢ.ት፡ “ከሚጎዱኝ ያድነኛል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይፈርድልኛል

“ፍትሕን ያመጣልኛል”

ወደ ብርሃን ያመጣኛል

ሚክያስን ከጨለማ (ሚክያስ 7፡8) ወደ ብርሃን ማምጣት በመከራው ምክንያት መሰቃየቱ ማብቃቱንና በሰላም ሊኖር መቻሉን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በፍትሑ ይታደገኛል

“ፍትሕን ያመጣልኛል፣ ይታደገኛልም”

## Micah 7:10

አጠቃላይ መረጃ፡

ሚክያስ አንዲት ሴት ጠላቷ ለሆነች ለሌላይቱ ሴት በምትናገርበት መልኩ መናገሩን የቀጠለበትንና በምዕራፍ 7፡8 የጀመረውን ግጥም ይጨርሳል። ይህቺ ምናልባት የእስራኤል ሕዝብ የምትወክለው፣ “ለወታደሮቹ ሴት ልጅ” የምትናገር (ሚክያስ 5፡ 1)፣ እስራኤልን ወግተው የነበሩትን አገሮች የምትወክል የጽዮን ሴት ልጅ ትሆን ይሆናል (ሚክያስ 1፡13)። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አምላክህ … ያለች ጠላቴ … ዓይኖቼ

“ጠላቴ”፣ “ያለች”፣ “ያንተ”፣ እና “የእኔ” የሚሉት ቃላት እዚህ ጋ የሚያመለክቱት በግጥሙ ውስጥ ያለችውን ሴት ሲሆን አነስታይ ነጠላ ቁጥር ነው።

አምላክህ እግዚአብሔር ወዴት ነው?

ጠላት በእስራኤል ሕዝብ ላይ ለመሳለቅ በጥያቄ ይጠቀማል። እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ሊረዳህ አይችልም”።

ዓይኖቼ

በዚህ ስፍራ ቃሉ የሚያመለክተው የሰውን ሁለንተና ነው። ኢ.ት፡ “እኔ” ወይም “እኛ”።

ትረገጣለች

ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ጠላቶቿ ይረግጧታል”

በመንገድ እንዳለ ጭቃ

አንዳች ክፉ እንደሚያደርጉ ሳያስቡ በጭቃ ላይ እንደሚሄዱ ሰዎች የእስራኤልን ጠላቶች አንዳች ክፉ እንደሚያደርጉ ሳያስቡ ከሚያጠፉ ጋር ተነጻጽረዋል።

## Micah 7:11

ቅጥሮቻችሁን የምትሠሩበት ጊዜ ይመጣል

እዚህ ጋ “ቅጥሮች” የሚያመለክተው ከጠላቶቻቸው ጥበቃና ደህንነት ያገኙባቸውን በከተሞቻቸው ዙሪያ ያሉትን ቅጥሮች ነው።

ዳርቻዎችሽ እስከ ሩቅ ድረስ ይስፋፋል

ይህ በገቢራዊነት ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ምድርሽን እጅግ ያሰፋዋል” ወይም “እግዚአብሔር የመንግሥትሽን ስፋት እጅግ ያበዛዋል”

ወንዙ

የወንዙን ስም ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል። ኢ.ት፡ “የኤፍራጥስ ወንዝ”

ከባህር እስከ ባህር

የባህሮቹን ስም ግልጽ ማድረግ ይኖርብህ ይሆናል. “በምዕራብ ካለው

ከሜዲትራንያን ባህር በስተምስራቅ እስካለው ሙት ባህር ድረስ”
ከተራራ እስከ ተራራ
“ከአንዱ ተራራ እስከ ሌላኛው”። ሚክያስ ስለ አንድ ስለ ታወቀ ተራራ አይናገርም።
ምድሪቱ ባድማ ትሆናለች
“ምድሪቱ ባዶ ትሆናለች” ወይም “በምድሪቱ ላይ ማንም አይኖርም”
በሥራቸው ፍሬ ምክንያት
ፍሬ የቀደመውን ሥራ ውጤት የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ሥራቸው ባስከተለው ውጤት ምክንያት” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Micah 7:14
ሕዝብህን በበትርህ ጠብቅ፣ የርስትህንም መንጋ
ሚክያስ ወገኖቹን የእስራኤልን ሕዝብ እንደገና እንዲጠብቃቸው በመጠየቅ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል። እረኛ በጎቹን ለመጠበቅና ለመምራት አርጩሜ እንደሚጠቀም ሁሉ እዚህ ጋ “በትር” የእግዚአብሔርን መሪነትና ምሪት ሰጪነት ያመለክታል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በጥሻ ውስጥ ለብቻቸው ይኖራሉ፣ በለመለመው መስክ መካከል
ሚክያስ የሚመገቡት ብዙ ሣር ባለበት መስክ እንደሚገጡ ከብቶች ሳይሆን በጫካ ውስጥ እንደሚደበቁ የዱር እንስሳት መስሎ ሕዝቡን ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ጥሻ
አንስተኛ እንጨት ያላቸው ዕጽዋት የሚያድጉበት ስፍራ
ባሳንና ገለዓድ
እነዚህ አካባቢዎች የምግብ እህል ለማብቀል ለም መሬት በመሆናቸው ይታወቃሉ
እንደ ቀደመው ዘመን
ዳዊት ንጉሥ በነበረበት ጊዜ፣ ከብዙ ዓመታት በፊት ባሳንና ገለዓድ የእስራኤል ክፍል ነበሩ
እንደ ቀድሞው ... ተአምራትን
እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይናገራል።
Micah 7:16
አገሮች
“አገሮች” የሚለው ቃል በብዙ አገሮች የሚኖሩትን ሰዎች የሚመለከት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በአቅራቢያ ያሉ አገሮች ሕዝቦች” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እጆቻቸውን በአፋቸው ላይ ይጭናሉ
ስላደረጉት ነገር ማፈራቸውን ለማሳየት ይህንን ያደርጋሉ።
ጆሮዎቻቸው ይደነቁራሉ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ነው። ማንኛውም ሰው የሚናገረው የትኛውም ነገር በእነርሱ ላይ ለውጥ አያመጣም።
እንደ እባብ አፈር ይልሳሉ
እባቦች አፈር በላያቸው ላይ እንዲሆን መሬቱን ቀድደው ይገባሉ፣ እዚህጋም ምናልባት አፈር መላሳቸው የተጋነነ ቢሆንም ሰዎች ከእባቦች ጋር ተነጻጽረዋል። እነዚህ ሰዎች 1) ቃል በቃል በአፍረት መሬት ላይ ይቀመጣሉ ወይም 2) በመሬት ላይ የተጋደሙ ያህል በአፍረት ይዋረዳሉ የሚሉት ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ናቸው።
ዋሻዎቻቸው
ሰዎቹ በእንስሳ ተመስለዋል፣ ምክንያቱም በ”ዋሻ” የሚኖሩ እንስሶች ናቸው። ኢ.ት፡ “ቤቶቻቸው” ወይም “መደበቂያ ስፍራዎቻቸው”
Micah 7:18
ርስታቸውን ... የሚወስድ እንዳንተ ያለ አምላክ ማነው?
ሚክያስ እንደ እግዚአብሔር ያለ ሌላ አምላክ እንደሌለ አጽንዖት ይሰጣል። ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ርስትን ... የሚወስድ እንዳንተ ያለ አምላክ እንደሌለ አውቃለሁ”።
የርስቱን ትሩፋን
“እነዚያ ከቅጣቱ የተረፉ የእርሱ ምርጥ ሕዝቦች”
አንተ ... የርስቱ ትሩፍ? እርሱ በቃል ኪዳን ታማኝነቱ ደስ ስለሚሰኝ ለዘላለም አይቆጣም
እዚህ ጋ “የእርሱ” እና “እርሱ” የሚሉት ቃላት በሁለተኛ መደብ ሊነገሩ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “አንተ ... የርስትህ ትሩፍ፣ ለዘላለም የማትቆጣው በቃል ኪዳን ታማኝነትህ ደስ ስለምትሰኝ ነው?” ወይም “አንተ ... የርስትህ ትሩፍ ነህ? በቃል ኪዳን ታማኝነትህ ደስ ስለሚልህ ለዘላለም አትቆጣም”
በቃል ኪዳን ታማኝነቱ ደስ ይለዋል
“ታማኝነት” የሚለው የነገር ስም “ታማኝ” ተብሎ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ለቃል ኪዳኑ ታማኝ በመሆን ደስ ይለዋል” ወይም “ለሕዝቡ ታማኝ በመሆኑ ደስ ይለዋል”
ያልፈዋል
ይተወዋል
ቁጣውን አይጠብቅም
“ተቆጥቶ አይቆይም”
Micah 7:19
ትፈቅዳለህ
እዚህ ጋ “አንተ” የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው።
በእኛ ላይ
እዚህ ጋ “በእኛ” የሚያመለክተው ሚክያስንና ሕዝቡን እንጂ እግዚአብሔርን አይደለም።
ያለመታመናችንን በእግርህ ሥር ትረግጠዋለህ። ኃጢአታችንን ወደ ባህሩ ጥልቅ ትጥለዋለህ
አለመታመን እና ኃጢአት እንደ ጠጣር ነገር ተቆጥረው ተነግረዋል። ኢ.ት፡ “አለመታመናችንን እና ኃጢአታችንን ምንም እንዳልሆኑ ቆጥረህ ትቀበለናለህ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 1
Nahum 1:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ናሆም የነነዌን መጥፋት የሚገልጸው በግጥም ነው (ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)
ስለ ነነዌ የተሰጠ መግለጫ። የኤልቆሻዊው የናሆም የራዕይ መጽሐፍ
እነዚህ ቃላት የመጽሐፉ ሁሉ መግቢያ ናቸው። “ይህ ስለ ነነዌ መግለጫ የሚሰጠው የኤልቆሻዊው የናሆም የራዕይ መጽሐፍ ነው” ተብሎ እንደ ሙሉ ዐረፍተ ነገር ሊቀርብ ይችላል። (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ኤልቆሻዊው
ከኤልቆሼ መንደር የሆነ አንድ ሰው (ስሞች እንዴት እንደሚተርጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Nahum 1:2
አጠቃላይ መረጃ፡
ናሆም እግዚአብሔር አምላክ በጠላቶቹ ላይ ሊፈርድና የራሱን ሕዝብ ለማዳን እንደሚመጣ በመግለጽ ይጀምራል። ራዕዩ በዘይቤአዊ ቋንቋ የተሞላና የተለያዩ ተመሳሳይነትን የሚጠቀም ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)
ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገለጠላቸው የእርሱ ስም ነው። ይህንን እንዴት መተርጎም እንዳለብህ ለማወቅ ስለ ያህዌ የሚተረጎሙ ቃላትን ገጽ ተመልከት።
ቁጣን የተሞላ
“በጣም ተቆጣ”
ለ--- ቁጣውን ይጠብቃል
“በ--- ላይ መቆጣቱን ይቀጥላል”
ለቁጣ የዘገየ
“በቶሎ የማይቆጣ”
አመጸኛውን ሳይቀጣ አይተውውም
ይህ የተጋነነ አሉታዊ አባባል በአዎንታዊነት ሊተረጎም ይችላል። “እርሱ አመጸኛውን ለመቅጣት ሁሌም እርግጠኛ ነው” ማለት ይቻላል። (ንቀት የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር አምላክ በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው፣ ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው
የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔር አምላክን ሀልዎት ከብርቱ ማዕበል ጋር ያመሳስሉታል። እዚህጋ እግዚአብሔር አምላክ በሰዎች ላይ ለመፍረድ በሚመጣበት ጊዜ በኃይለኛ የነፋስ ማዕበል ተቀምጦ እግሮቹ ትቢያውን በመርገጣቸው ደመናትን ይፈጥራል። (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
የእግሮቹ ትቢያ
“እግሮቹ በመርገጣቸው የሚነሣ ትቢያ”
Nahum 1:4
አጠቃላይ መረጃ፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ናሆም እግዚአብሔር አምላክ በጠላቶቹ ላይ ለመፍረድና የራሱን ሕዝብ ለማዳን ስለ መምጣቱ መግለጹን ቀጥሏል።

ባሳን ደክሟል፣ ቀርሜሎስም እንዲሁ፤ የሊባኖስ አበቦችም ጠውልገዋል

“ደክሟል” ተብሎ የተተረጎመው ቃል “ጠውልጓል” ወይም “ደርቋል” ማለት ሊሆን ይችላል። ባሳን ሰዎች በጎቻቸውንና ከብቶቻቸውን የሚያሰማሩበት የታወቀ የግጦሽ መሬት ነበር። “ቀርሜሎስ” የቀርሜሎስን ተራራ የሚያመለክት ሲሆን በተክል ዛፎች ይታወቃል፣ ከሊባኖስ ተራሮች የሚወርድበት በረዶ አካባቢው ለምነቱን ጠብቆ እንዲቆይ አድርጎታል። እግዚአብሔር አምላክ ወንዞቹን ሁሉ ስለሚያደርቃቸውና ድርቅን ስለሚያመጣባቸው እነዚህ ለም መሬቶች በለምነታቸው አይቀጥሉም። ኢ.ት፡ “የባሳን እርሻዎች ይጠወልጋሉ፣ የቀርሜሎስ ተራራ ዛፎች ይደርቃሉ፣ የሊባኖስ አበቦችም ይጠወልጋሉ”። (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ኮረብቶች ቀለጡ

አማራጭ የሚሆኑ ትርጉሞች 1) ኮረብቶች እንደ ቀለጡ የተነገረው በመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት ኮረብቶቹ ተገልብጠው ብትንትናቸው በመውጣቱ ወይም 2) ኮረብቶች እንደ ቀለጡ የተነገረው የውሃው ማዕበል በኮረብቶቹ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ስለ ሸረሸራቸው ይሆናል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ምድር ትፈርሳለች

ተራሮችና ኮረብቶች ይፈርሳሉ ወይም 2) መላው ምድር በኃይል ይናጣል የሚሉ አማራጭ ትርጉሞች ናቸው።

ዓለምና የሚኖሩባት ሰዎች ሁሉ

እዚህ ጋ “ዓለም” የሚለው ቃል በምድር ላይ ሰዎች የሚኖሩበትን ስፍራ ያመለክታል። (መግደፍ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 1:6

አጠቃላይ መረጃ፡

ናሆም እግዚአብሔር አምላክ በጠላቶቹ ላይ ለመፍረድና የራሱን ሕዝብ ለማዳን ስለ መምጣቱ መግለጹን ቀጥሏል።

በቁጣው ፊት ማን ይቆማል? የቁጣውንስ ትኩሳት ማን ሊቋቋም ይችላል?

በመሠረቱ እነዚህ ሁለት የማሳመኛ ጥያቄዎች ትርጉማቸው ተመሳሳይ ነው። በሚከተለው መሠረት ሊተረጎሙ ይችላሉ፤ ኢ.ት፡ “በቁጣው ፊት ማንም ሊቆም አይችልም! የቁጣውን ትኩሳት ማንም ሊቋቋም አይችልም!” (ተመሳሳይነት እና የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

የቁጣው ትኩሳት

“የቁጣው ብርታት” ወይም “የቁጣው መጠን”

ቁጣው እንደ እሳት ፈሰሰ

ናሆም የእግዚአብሔርን ቁጣ እንደሚፈስ ፈሳሽና እንደሚያቃጥል እሳት አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት “ቁጣውን እንደ እሳት ያፈስዋል” ወይም “የቁጣውን ትኩሳት ይገልጣል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዐለቶችን ይሰባብራቸዋል

ይህ በገቢራዊነት ሊገለጽ ይችላል። ኢ.ት፡ “ዐለቶችን ይሰባብራቸዋል” ወይም “ዐለቶቹን እንዲሰባበሩ ያደርጋቸዋል” (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 1:7

መሸሸጊያ. . . በእርሱ የሚታመኑትን

ናሆም እግዚአብሔርን ሰዎች ሊጎዱአቸው ከሚፈልጉት እንደሚደበቁበት ስፍራና በእርሱ የሚታመኑትን በዚያ አስተማማኝ ስፍራ ከለላ እንደሚሰጣቸው መስሎ ይናገራል (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመከራ ቀን

“በመከራ ጊዜ” ወይም “መከራ በሚመጣበት ጊዜ”። እዚህ ጋ “ቀን” የሚለው ቃል አጠቃላዩን ጊዜ ያመለክታል።

ጠላቶቹን ፈጽሞ ያጠፋቸዋል

“ፈጽሞ ያጠፋቸዋል” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ጠላቶቹ እንዲሞቱ እንደሚያደርጋቸው ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ጠላቶቹን ሙሉ በሙሉ ያጠፋቸዋል” ወይም “ጠላቶቹን ሁሉ ይገድላቸዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በሚያጥለቀልቅ ጎርፍ

እግዚአብሔር ጠላቶቹን በታላቅ የጥፋት ጎርፍ እንደሚያሰጥማቸውና ከሞት ማምለጥ እንዳይችሉ እንደሚያደርጋቸው ናሆም ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ወደ ጨለማ ያሳድዳቸዋል

እዚህ ጋ “ጨለማ” የሚለው ቃል የሙታን መኖሪያ የሆነውን ጨለማ ስፍራ ይወክላል። እግዚአብሔር ጠላቶቹን ወደዚህ ጨለማ ስፍራ እያሳደደ እንደሚገድላቸው ናሆም ይናገራል። ኢ.ት፡ “ጠላቶቹ ሁሉ እንዲሞቱ ያደርጋቸዋል” (ፈሊጣዊ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Nahum 1:9

አጠቃላይ መረጃ፡

እግዚአብሔር ምን ሊያደርግባቸው እንዳለ ናሆም ለነነዌ ሕዝብ ይነግራቸዋል

እናንተ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ የምታሤሩት ምንድነው?

ይህ የማሳመኛ ጥያቄ በእግዚአብሔር ላይ የሚታቀደው ክፉ ዕቅድ ከንቱ መሆኑ ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ኢ.ት፡ “እናንተ ሰዎች፣ በእግዚአብሔር ላይ ማሤራችሁ ከንቱ ነው” (የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ፈጽሞ ያጠፋል

“ፈጽሞ ያጠፋል” የሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር አንድ ነገር ዳግመኛ እንዳይኖር እንደሚያደርግ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የምታደርጉትን ሙሉ በሙሉ ያስቆማችኋል” ወይም “ሤራችሁ እንዲከሽፍ ያደርጋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መከራ ዳግመኛ አይነሣም

“መከራ” እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የሚፈጽመውን ቅጣት የሚያሳይ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ዳግመኛ አይቀጣችሁም” ወይም 2) “መከራ” ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ በማሤር የሚፈጥሩትን ችግር ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ዳግመኛ ችግር አትፈጥሩም” አማራጭ ትርጉሞች ናቸው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ትመልከት)

እንደ እሾህ ቁጥቋጦ ይጠላለፋሉ

አንድ በእሾህ ቁጥቋጦ የተጠላለፈ ሰው ራሱን በቀላሉ ማላቀቅ እንደማይቻለው ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ የሚያሤሩ ሰዎችም እርሱ ከሚያመጣባቸው መከራ ራሳቸውን ማስመለጥ አይቻላቸውም ወይም 2) ልክ የእሾህ ቁጥቋጦዎችን በአንድ ላይ ሲያከማቿቸው ፈጥነው እንደሚነዱ እንደዚሁ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የሚያሤሩትን ፈጥኖ ያጠፋቸዋል የሚሉት ለዚህ ዘይቤአዊ አነጋገር አማራጭ ትርጉሞች ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በገዛ መጠጣቸው ይበከላሉ

በሚያሰክር መጠጥ እጅግ እንደ ሰከሩ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ የሚያሤሩ በዕቅዳቸው ምክንያት ሥቃይ እንደሚደርስባቸው ናሆም ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እንደ ደረቅ ገለባ በእሳት ይነድዳሉ

እሳት የደረቀውን ገለባ እንደሚያነደው እግዚአብሔርም በእርሱ ላይ ያሤሩትን እሳት በሚያነድዳቸው መልኩ ፈጽሞ እንደሚያጠፋቸው ናሆም ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

በእሳት ይነድዳሉ

ናሆም ልክ እሳት አንድን ነገር እንደሚያነድደው ፈጽሞ ስለሚያቃጥለው እሳት ይናገራል (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፋትን አበረታተዋል

ሰዎች ክፉ ነገሮችን እንዲያደርጉ አበረታተዋቸዋል

Nahum 1:12

አጠቃላይ መረጃ፡

እግዚአብሔር ስለ ነነዌ ለእስራኤላውያን ይነግራቸዋል

ብርቱዎችና ብዙዎች ቢሆኑም እንኳን

ይህ አሦራውያንን ወይም የነነዌን ሰዎች ያመለክታል

የሆነው ሆኖ ይሸለታሉ

እግዚአብሔር እንደሚሸልታቸው በጎች የነነዌን ሰዎች እንደሚያጠፋቸው ይናገራል። ይህ በገቢራዊነት ሊገለጽ ይችላል። ኢ.ት፡ “የሆነው ሆኖ እሸልታቸዋለሁ” ወይም “የሆነው ሆኖ አጠፋቸዋለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

አሁን የዚያን ሕዝብ ቀንበር ከአንተ ላይ እሰብራለሁ፤ ሰንሰለቶችህንም እበጥሳለሁ

አሦራውያን የጫኑባቸውን ቀንበርና ሰንሰለት በሚሰብርበት መልኩ እግዚአብሔር ይሁዳን ከአሦር ጭቆና ነጻ እንደሚያወጣቸው ይናገራል (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Nahum 1:14

የተቀረጹትን ምስሎችና ቀልጠው የተሠሩትን ምስሎች ከአማልክቶችህ ቤት አጠፋለሁ

አንድ ሰው ቅርንጫፍን ከዛፉ ላይ እንደሚሰብር እግዚአብሔር የአሦራውያንን

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አማልክት በመሰባበር እንደሚያጠፋ ይናገራል። “ቤት” የሚለው ቃል ሕዝቡ እነዚህን ጣዖታት የሚያመልኩባቸውን መቅደሶች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በአማልክቶቻችሁ መቅደስ ያሉትን የተቀረጹትንና ቀልጠው የተሠሩትን ምስሎች አጠፋለሁ” (ዘይቤአዊ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

መቃብራችሁን እቆፍራለሁ

ደግሞም እግዚአብሔር በሚቆፍርላቸው መቃብር ውስጥ የሚቀብራቸው ይመስላል። ኢ.ት፡ “መቃብር እቆፍርላችሁና በዚያ ውስጥ እቀብራችኋለሁ” (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 1:15

የምሥራችን የሚያመጣ ሰው እግሮች በተራሮች ላይ ናቸው

እዚህ ጋ “እግሮች” አንድን መልዕክት ለማስታወቅ የሚሮጥን ሰው ይወክላል። ኢ.ት፡ “የምሥራችን የሚያመጣ አንድ ሰው በተራሮች ላይ ነው”። (ምሳሌአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ክፉው . . . እርሱ

ናሆም የነነዌን ሕዝብ እንደ አንድ ሰው አድርጎ ይገልጻቸዋል።

እርሱ ፈጽሞ ተቆርጧል

አንድ ሰው ቅርንጫፍን ከዛፍ ላይ እንደሚቆርጥ የነነዌ ሕዝብ በመቆረጥ ፈጽመው እንደሚጠፉ ናሆም ይናገራል። ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ፈጽሞ ጠፍቷል” ወይም “እግዚአብሔር ፈጽሞ አጥፍቶታል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

Chapter 2

Nahum 2:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ናሆም አብዛኛውን ጊዜ ትንቢቱን በግጥም መልክ ይጽፋቸው ነበር። የዕብራይስጡ ግጥም የተለያዩ ተመሳሳይነቶችን ይጠቀማል። እዚህ ጋ የነነዌን መጥፋት መተረክ ይጀምራል። (ግጥም እና ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)

አንቺን ረጋግጦ የሚያደቅሽ እርሱ

“አንቺ” የሚለው ቃል ነነዌን ያመለክታል። ናሆም የሸክላ ማሰሮን እንደሚሰባብር ነነዌን በመሰባበር ስለሚያጠፋ ሰራዊት ወይም ወታደራዊ መሪ ይናገራል። ኢ.ት፡ “አጥፊሽ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አንቺን የሚረጋግጥሽ እርሱ

“እርሱ” የተባለው ሰው ግልጽ አይደለም፣ ስለዚህ የወል ቃል በመጠቀም ተርጉም። ኢ.ት፡ “አንድ አንቺን የሚሰባብርሽ”

በአንቺ ላይ እየመጣ ነው

“በአንቺ ላይ ይመጣል” የሚለው አነጋገር ሊያጠቃሽ ማለት ነው። ኢ.ት፡ “ሊያጠቃሽ ተዘጋጅቷል” (አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በከተማው ቅጥር ላይ ሰዎችን አቁሚ፣ መንገዶችሽን ጠብቂ፣ ራስሽን አበርቺ፣ ሰራዊትሽን ሰብስቢ

ናሆም ለነነዌ ሕዝብ ይናገራል። ጠላት ከተማይቱን እንደሚያጠፋት ቢያውቅም ለጦርነት እንዲዘጋጁ ይነግራቸዋል። (ምጸት የሚለውን ተመልከት)

በከተማው ቅጥር ላይ ሰዎችን አቁሚ

ነነዌ የሚከባት ሰፊና ጠንካራ ቅጥር ነበራት። ይህ አጥቂዎችን ለመዋጋት ወታደሮችን በግምቡ ጫፍ ላይ ማስፈር መቻላቸውን ያመለክታል። አስፈላጊ ከሆነ ይህንን ጠቅለል ባለ ሐረግ መተርጎም ይቻላል። ኢ.ት፡ “በምሽጎችሽ ላይ ሰው አኑሪ” ወይም “መከላከያሽን አዘጋጂ” (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

መንገዶችሽን ጠብቂ

ይህ ጠላት እንዳይቀርባቸው ለመከላከል ወደ ከተማይቱ የሚወስደውን መንገድ በወታደሮች ማስጠበቅን ያመለክታል።

ራስሽን አበርቺ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን ትርጉሙም ራስን ለተግባር ማዘጋጀት ማለት ነው። እዚህ ጋ ቃሉ ለወታደራዊ ተግባር ጥቅም ላይ ውሏል። ኢ.ት፡ “ራስሽን ለጦርነት አዘጋጂ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር እንደ እስራኤል ግርማ ሁሉ የያዕቆብን ግርማ ያድሳል

“ያዕቆብ” እና “እስራኤል” የሚሉት ቃላት ከያዕቆብ ለተወለዱት ሕዝቦች ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “ያዕቆብ” የሚለው ቃል የደቡቡን መንግሥት እና “እስራኤል” የሚለው የሰሜኑን መንግሥት ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የእስራኤልን ግርማ ለማደስ ቃል እንደገባ ሁሉ የይሁዳንም ግርማ ያድሳል” ወይም 2) “ያዕቆብ” እና “እስራኤል” ሁለቱም የሚያመለክቱት የሰሜኑና የደቡቡ መንግሥት ተደምረውና ሁለቱ የግጥም መስመሮች ተመሳሳይ ሆነው መላውን ሕዝብ ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)

ዘራፊዎቹ

በተለይ በጦርነት ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን በኃይል አስገድደው የሚሰርቁ ሰዎች

የወይን ቅርንጫፎቻቸውን አጥፍተዋል

አማራጭ የሚሆኑት ትርጉሞች 1) እስራኤል ቅርንጫፎቹን አሦራውያን ገነጣጥለው ባዶውን እንዳስቀሩት ወይን አሦራውያን ንብረታቸውን አስገድደው መውሰዳቸውን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ያለ ቅርንጫፍ እንደ ቀረ ወይን ንብረታቸውን ዘርፈዋቸዋል” ወይም 2) “የወይን ቅርንጫፎች” የሚሉት ቃላት በየአገራቱ ለእርሻ በሚውሉ መስኮች ላይ ናቸው። ኢ.ት፡ “የሰብል ማሳዎቻቸውን አጠፉ” (ዘይቤአዊ እና ምሳሌአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Nahum 2:3

የኃያላኑ ጋሻ ቀይ ነው

አማራጭ ትርጉሞቹ 1) ጋሻዎቹ በብረት ገጽታቸው ላይ የፀሐይ ብርሃን በሚያንጸባርቅበት ጊዜ ቀልተው ይታያሉ ወይም 2) ጋሻዎቹ በቀይ ቀለም በተነከሩ ቆዳዎች የተሸፈኑ ናቸው።

ኃያላኑ

ነነዌን “የሚረጋግጡ” እና “ብትንትኗን የሚያወጡ” ወታደሮች ናቸው (ናሆም 2፡1)

ሰረገሎቹ በብረቶቻቸው ያብረቀርቃሉ

ይህ የሚያመለክተው ከብረት በተሠሩት ሰረገላዎች ላይ የፀሐይ ብርሃን ማንጸባረቁን ሳይሆን አይቀርም።

እንዲዘጋጁ በተደረጉበት በዚያን ቀን

ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ወታደሮቹ ባዘጋጇቸው ጊዜ” ወይም “ወታደሮቹ እንዲዋጉ ባዘጋጇቸው ጊዜ”። (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

እጀታቸው ከጥድ መሳይ ዛፍ የተሠሩ ጦሮች በአየር ላይ ይወዛወዛሉ

ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ወታደሮቹ ጦራቸውን በአየር ላይ ያወዛውዛሉ” (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

ጥድ መሳይ ዛፍ

እንጨቱ ለጦር መሳሪያነት የሚመረጥ የዛፍ ዓይነት ነው። (ያልታወቁትን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)

ሰረገሎቹ በየጎዳናው ይፈጥናሉ

“ወታደሮቹ ሰረገላዎቹን በጎዳናዎቹ ላይ በስድነት ይነዷቸዋል”

ፋና ይመስላሉ

ናሆም በሰረገላዎቹ ላይ የሚንጸባረቀውን የፀሐይ ብርሃን የእሳት ብርሃን ከሚሰጠው ፋና ጋር ያነጻጽረዋል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)

እንደ መብረቅ ይሮጣሉ

ናሆም በሰረገላዎቹ ላይ የሚንጸባረቀውን የፀሐይ ብርሃንና ሰረገላዎቹ የሚያደርጉትን ፈጣን እንቅስቃሴ በሰማይ ላይ በፍጥነት ከሚንጸባረቀው መብረቅ ጋር ያነጻጽራል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 2:5

አንቺን ረጋግጦ የሚያደቅሽ እርሱ

“አንቺ” የሚለው ቃል ነነዌን ያመለክታል። ናሆም የሸክላ ማሰሮን እንደሚሰባብር ነነዌን በመሰባበር ስለሚያጠፋ ሰራዊት ወይም ወታደራዊ መሪ ይናገራል። ይህንን በናሆም 2፡1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት፡ “የሚያጠፋሽ እርሱ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በዘመቻቸው

(የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

እነዚህን ተዋጊዎች ለመከላከል ታላቁ ጋሻ ተዘጋጅቷል

ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ተዋጊዎቹ ራሳቸውን ለመከላከል ታላቁን ጋሻ ያዘጋጃሉ” (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

ታላቁ ጋሻ

ይህ በከተማው ውስጥ ያሉት ሰዎች እነርሱን ለማጥቃት ከሚወነጭፏቸው ቀስቶችና ሌሎች ተስፈንጣሪዎች ራሳቸውንና መሰበሪያ መሣሪያዎቻቸውን ለመከላከል ከተማውን የከበቡት ሰዎች በፊት ለፊታቸው የሚያደርጉትን ታላቅ መከላከያ ያመለክታል።

Nahum 2:6

የወንዞቹ በሮች ወለል ብለው ተከፈቱ

ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ጠላት የወንዞቹ በሮች እንዲከፈቱ ያስገድዳል” (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

የወንዞቹ በሮች

ይህ የሚያመለክተው የወንዙን ፍሰትና አቅጣጫ የሚቆጣጠሩትን በሮች ነው።

ሁዛብ ልብሷን ተገፈፈችና ተወሰደች

ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ጠላት የሁዛብን ልብስ ይገፍና ይወስዳታል” (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

ሁዛብ ልብሷን ተገፈፈችና ተወሰደች

“ሁዛብ” የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም በእርግጠኝነት አይታወቅም። ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉ ሁለቱ፣ 1) በነነዌ የነበረች ንግሥት ስም ይሆንና ዐረፍተ ነገሩ የሚለው አጥቂዎቹ ወታደሮች እርሷን ለማዋረድ ልብሶቿን እንድታወልቅ በማድረግ ወደ ምርኮ ወስደዋታል ወይም 2) የጣዖት ስም ይሆንና ዐረፍተ ነገሩ አጥቂዎቹ ወርቅና ብሩን ከጣዖቱ ላይ በመግፈፍ ወስደውታል ማለት ሊሆን ይችላል። (ያልታወቁትን ተርጉም እና የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ሴቶች አገልጋዮቿ እንደ ዕርግብ ያለቃቅሳሉ

የሴት አገልጋዮቹ የሚያሰሙት የልቅሶ ድምፅ ዕርግቦቹ የሚያሰሙትን ድምፅ ይመስላል።

ሴት አገልጋዮቿ

“ሁዛብ” የሚለው ቃል ንግሥቲቱን የሚያመለክት ከሆነ እንግዲያው ይህ ሐረግ የሚጠብቋትን ወጣት ሴቶች ያመለክታል። “ሁዛብ” የሚለው ቃል ጣዖትን የሚያመለክት ከሆነ ይህ ሐረግ የመቅደስ ዝሙት አዳሪ ወጣት ሴቶችን ያመለክታል።

ደረታቸውን እየደቁ

የአንድ ሰው ደረት መደቃት ታላቅ ለቅሶን የሚያመለክት እንቅስቃሴ ነው። (ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)

Nahum 2:8

ነነዌ እንደሚያፈስ የኩሬ ውሃ ናት፣ ሕዝቧም እንደ ውሃ ፈሳሽ ይሸሻል

ናሆም ሕዝቡ ከነነዌ ከተማ የሚሸሽበትን ሁኔታ ግድብ በሚፈርስበት ጊዜ ውሃው ከማከማቻው ጎርፎ ከመውረዱ ጋር ያነጻጽረዋል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)

ብሯን በዝብዙ. . . የነነዌን የተዋቡ ነገሮች

እዚህ ጋ ተናጋሪው ማን እንደሆነ ግልጽ አይደለም። ይህ ምናልባት ናሆም ለተዋጊዎቹ አቅጣጫ የሚሰጥበት ይሆን ይሆናል ወይም ምናልባት ተዋጊዎቹ ለእርስ በእርሳቸው አቅጣጫ የሚሰጡበትና የሚነጋገሩበት ሊሆን ይችላል። (ምናባዊውን ሰው መናገር የሚለውን ተመልከት)

ብሩን በዝብዙ፣ ወርቁን በዝብዙ

“በዝብዙ” የሚለው ቃል በማስገደድ የሚሰረቁ ነገሮች፣ አብዛኛውን ጊዜ በጦርነት ወቅት ማለት ነው። አ.ት፡ “ብሩን በብዝበዛ ውሰዱ፣ ወርቁን በብዝበዛ ውሰዱ” ወይም ”ብሩን ውሰዱ፣ ወርቁን ውሰዱ”

ለእርሱም ማብቂያ የለውም

“ማብቂያ የለውም” የሚሉት ቃላት አንድ ነገር በብዛት መኖሩን ለመግለጽ የተነገረ ግነት ነው። አ.ት፡ “እጅግ ብዙ አለ” (ግነት እና ማጠቃለያ የሚሉትን ተመልከት)

የነነዌ የተዋቡ ነገሮች ክብር ሁሉ

ይህ ሐረግ በነነዌ የነበረውን ብር፣ ወርቅ፣ እና ሌሎች ሀብቶች ያመለክታል። ግሱ ምናልባት ቀደም ካለው ሐረግ ሊወሰድ ይችላል። አ.ት፡ “ለነነዌ የተዋበ ሀብት ሁሉ ለክብሩ ማብቂያ የለውም” ( መግደፍ የሚለውን ተመልከት)

የእያንዳንዱ ልብ ይቀልጣል

ናሆም ልክ ልባቸው እንደ ሰም የቀለጠ ይመስል ሕዝቡ አቅም እንዳጣ ይናገራል። አ.ት፡ “እያንዳንዱ አቅም አጥቷል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእያንዳንዱ ጉልበት ይብረከረካል

ይህ በታላቅ ፍርሃት ምክንያት የሚፈጠረውን አካላዊ ምላሽ ያሳያል። የሕዝቡ እግር ያለ መጠን በመንቀጥቀጡ ጉልበቶቻቸው ስለሚጋጩ መራመድም ሆነ መርጥ አይችሉም።

Nahum 2:11

አጠቃላይ መረጃ፡

በእነዚህ ቁጥሮች ናሆም የነነዌን ሕዝብ በአንበሳ መንጋና የነነዌን ከተማም በአንበሶች ዋሻ መስሎ ይናገራል። ዘይቤአዊው አነጋገር አንበሶች አደን አድነው የገደሏቸውን እንስሶች ወደ ዋሻቸው እንደሚያመጡ አሦራውያን ሕዝቡን ድል እንደሚያደርጉና ሀብታቸውን የራሳቸው አድርገው እንደሚወስዱ ያሳያል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

አንዳች የማይፈሩት. . . የአንበሶቹ ዋሻ ወዴት ነው?

ናሆም በምትጠፋዋ በነነዌ ላይ ለመሳለቅ የማሳመኛ ጥያቄን ይጠቀማል። አ.ት፡ “አንዳች የማይፈሩት. . . የአንበሶቹ ዋሻ የትም አይገኝም” ወይም “አንዳች በማይፈሩት. . . የአንበሶች ዋሻ ላይ የሆነውን ተመልከቱ!”። (የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ንጥቂያውን አነቀው

“ንጥቂያውን አፈነው” ይህ አንበሶች አብዛኛውን ጊዜ የሚያድኑትን እንስሳ ጉሮሮውን በመንከስ የሚገድሉበትን ሁኔታ ያመለክታል። አ.ት፡ “የነጠቀውን ገደለው” (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ዋሻውን በንጥቂያው ሞልቶታል፣ መኖሪያውንም በእንስሳቱ ቁርጥራጭ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳዩን ነገር በተለያየ መንገድ የሚናገሩ ናቸው። ለሁለተኛው ሐረግ ምናልባት ግስ መጨመር ይኖርበታል። አ.ት፡ “ዋሻውን በንጥቂያው ሞልቶታል፣ መኖሪያውንም በእንስሳቱ ቁርጥራጭ ሞልቶታል”። (ተመሳሳይነት እና መግደፍ የሚለውን ተመልከት)

Nahum 2:13

እነሆ፣ እኔ በእናንተ ላይ ነኝ

እዚህ ጋ እግዚአብሔር መናገር ይጀምራል

እነሆ

“ተመልከቱ” ወይም “አድምጡ” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ”።

ደቦል አንበሶቻችሁን ሰይፍ ይበላቸዋል

እዚህ ጋ “ሰይፍ” የሚለው ቃል በሰይፍ የሚዋጉትን ወታደሮች የሚያመለክት ሲሆን ንጥቂያውን ሰው እንደሚበላው ዓይነት ተደርጎ ተነግሯል። ናሆም ደግሞ የነነዌን ሕዝብ እንደ አንበሶች በመቁጠር መናገሩን ቀጥሏል። አ.ት፡ “ተዋጊዎች ሰዎቻችሁን በሰይፍ ይገድላሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር፣ ሰውኛ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የምትገድሉትን እንስሳ ከምድራችሁ አጠፋለሁ

እግዚአብሔር ሕዝቦችን በሚያድኑ አንበሶች ስለተመሰሉት የነነዌ ሰዎች ይናገራል። አማራጭ የሚሆኑት ትርጉሞች፣ 1) “የሚገደል እንስሳ” የሚሉት ቃላት ካጠቋቸው ላይ የወሰዷቸውን ነገሮች የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን የሚገድሉትን እንስሳ እንደሚያጠፋባቸው ሁሉ እግዚአብሔር እነዚያን ነገሮች ከእነርሱ እንደሚወስድባቸው ይናገራል ወይም 2) ታዳኞቻቸው የሆኑ ይመስል የነነዌ ሕዝብ ስለበዘበዟቸው ሕዝቦች እግዚአብሔር ይናገራል፣ እርሱ የሚገድሉትን እንስሳ በሚያጠፋባቸው መልኩ በተጨማሪ ሌሎች ሕዝቦችን እንዳይበዘብዙ ይከለክላቸዋል። አ.ት፡ “ሌላ የትኛውንም ሕዝብ እንዳትገድሉ እከለክላችኋለሁ”። (ዘይቤአዊ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከእንግዲህ የመልዕክተኞቻችሁ ድምፅ አይሰማም

ይህ አሦራውያን በሌሎች ሕዝቦች እጅ እንዲሰጧቸው ወይም እንዲገብሩላቸው ለመጠየቅ የሚልኳቸውን መልዕክተኞች ሳያመለክት አይቀርም። ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ዳግመኛ የመልዕክተኞቻችሁን ድምፅ የሚሰማ አይኖርም”። (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)

Chapter 3

Nahum 3:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ናሆም አብዛኛውን ጊዜ ትንቢቱን የጻፈው በግጥም መልክ ነው። የዕብራይስጥ ግጥም የተለያዩ ተመሳሳይነትን ይጠቀማል። እዚህ ጋ የነነዌን ጥፋት መግለጹን ይቀጥላል። (ግጥም እና ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት))

በደም የተሞላች ከተማ

እዚህ ጋ “ደም” የሚለው ቃል የሚወክለው ደም ማፍሰስን ሲሆን ነፍስ ያጠፉትን ሰዎች ያመለክታል። አ.ት፡ “በነፍሰ ገዳዮች የተሞላች ከተማ”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ሐሰትን ሁሉ የተሞላ ነው

እዚህ ጋ “ሐሰት” የሚለው ቃል ውሸትን ለሚናገሩ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “በውሸተኞች የተሞላ ነው”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የጅራፍ ድምፅና የሚንገጫገጭ መንኰራኲር ጩኸት፣ የፈረሶችና የሰረገላዎች ዝላይ
እነዚህ ሐረጎች ፈረሶቹን በመግረፍ የሚነዷቸው ሰዎች በጎዳናዎቹ በሚገሰግሱበት ጊዜ የሰረገላዎቹን ድምፅ የሚገልጹ ናቸው።
Nahum 3:3
ብዙ ሬሳ፣ እጅግ ብዙ አስክሬን
በመሰረቱ እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ሲሆን አጥቂዎቹ የረፈረፏቸው በጣም ብዙ አስክሬኖች እንደነበሩ የሚያመለክት ነው። (ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)
ሬሳ
የሞቱ ሰዎች አካል
ለአስክሬኖቹ ስፍር ቁጥር የላቸውም
“ስፍር ቁጥር የላቸውም” የሚሉት ቃላት አጥቂዎቹ የገደሏቸውን እጅግ ብዙ ቁጥር ያለው አስክሬን ለመግለጽ የቀረበ ግነት ነው። ኢ.ት: “ለመቁጠር እጅግ ብዙ የሆኑ አስክሬኖች ነበሩ” ወይም “እጅግ የበዙ አስክሬኖች ናቸው”። (ግነት እና ማጠቃለያ የሚለውን ተመልከት)
የውቧ ዘማዊት የዝሙት ተግባር
ናሆም በውበቷ ወንዶችን እንደምታስት አመንዝራ የነነዌ ከተማ ሌሎች ሕዝቦች እንዲገዙላት ስለምታደርግበት ሁኔታ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በጥንቆላ የተካነች
ናሆም የነነዌ ከተማ በሌሎች ላይ ድግምት እንደሚያደርግ ጠንቋይ ሌሎች ሕዝቦች እንዲገዙላት ስለምታደርግበት ሁኔታ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እርሷ አሕዛብን በዝሙትዋ ሕዝቦችንም በጥንቆላዋ የምትሸጥና
እዚህ ጋ “የምትሸጥ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የነነዌ ሰዎች ሌሎች አሕዛቦችንና ሕዝቦችን ለባርነት እንደዳረጓቸው ነው። ነነዌ ውበቷን፣ ኃይሏንና ተጽዕኖ ፈጣሪነቷን ሌሎችን ባሪያዎቿ ለማድረግ ትጠቀምበታለች። ኢ.ት: “በዝሙትዋና በጥንቆላዋ ሌሎች አሕዛቦች ባሪያዎቿ እንዲሆኑ የምታደርግ”።(የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
Nahum 3:5
እዩ
“ተመልከቱ” ወይም “አድምጡ” ወይም “የምነግራችሁን ልብ በሉ”
ቀሚስሽን ፊትሽ ላይ አገልበዋለሁ፣ ኃፍረትሽንም ለአሕዛብ አሳያለሁ
ይህ አመንዝራዎችን በማኅበረሰቡ ፊት ለፊት ልብሳቸውን በመግፈፍ በይፋ የማዋረድን ልማድ ያመለክታል። ይህ የነነዌ ከተማ አመንዝራ መሆኗን እግዚአብሔር በዘይቤአዊ አነጋገር መናገሩን የቀጠለበት ነው። ኢ.ት: “አንድ ሰው የአመንዝራይቱን ልብስ ፊቷ ድረስ በመግለብና በሰዎች ሁሉ ፊት ኃፍረቷን በማሳየት እንደሚያዋርዳት በይፋ አዋርድሻለሁ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እፍረትሽን ለመንግሥታት
ይህ ሐረግ የነነዌን ልብስ የመግለብን ዓላማ ያብራራል። ከበስተኋላው ካለው ሐረግ ግሱን መውሰድ ያስፈልግ ይሆናል። ኢ.ት: “እፍረትሽን ለመንግሥታት አሳያለሁ” (መግደፍ የሚለውን ተመልከት)
አስቀያሚ ቆሻሻ እደፋብሻለሁ
“አስቀያሚ ቆሻሻ” የሚሉት ቃላት ልዩ ልዩ ዓይነት ቆሻሻን ያመለክታል። በአንድ ሰው ላይ ቆሻሻ መወርወር የከፍተኛ ንቀት ምልክት ነበር። ኢ.ት: “አንድ ሰው በሌላው ላይ አስቀያሚ ቆሻሻ እንደሚወረውርበት ለአንቺ ያለኝን ንቀት አሳያለሁ”። (ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)
የሚያለቅስላት ማነው?
ሰዎች አሉታዊው መልስ ላይ አጽንዖት ለመስጠት ይህንን የማሳመኛ ጥያቄ ይጠይቃሉ። ኢ.ት: “ማንም አያለቅስላትም”። (የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ሊያጽናናሽ የሚችልን ሰው ከወዴት አገኛለሁ?
ነነዌን ለማጽናናት የሚችል አንድም እንደማይኖር አጽንዖት ለመስጠት እግዚአብሔር ይህንን የማሳመኛ ጥያቄ ይጠቀማል። ኢ.ት: “የሚያጽናናሽ አንድም አይኖርም”። (የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
Nahum 3:8
አጠቃላይ መረጃ:
ናሆም ከተማው ራሱ እነርሱን እንደሆነ አድርጎ ለነነዌ ሕዝብ ይናገራል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አንቺ ከራሷ ከቲቤስ ትሻያለሽ?
ናሆም አስቀድሞ ለተገመተው አሉታዊ ምላሽ አጽንዖት ለመስጠት ይህንን የማሳመኛ ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት: “አንቺ ከቲቤስ ከራስዋ አትሻይም”። (የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ቲቤስ
ይህ አሦራውያን ድል አድርገዋት የነበረችው የግብፅ የቀድሞዋ ዋና ከተማ ነበረች። (‘ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ’ የሚለውን ተመልከት)
በዐባይ ወንዝ ዳር የተሠራች ነበረች
“በዐባይ ወንዝ ዳር የተቋቋመች ነበረች”
ውቅያኖሱ መከላከያዋ የነበረ፣ ባህሩ ራሱም ግድግዳዋ የነበረ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። “ውቅያኖስ” እና “ባህር” የሚሉት ቃላት ሁለቱም በከተማይቱ አጠገብ የሚፈሰውን የዐባይን ወንዝ ያመለክታሉ። ኢ.ት: “አንዳንድ ከተሞች ለራሳቸው ቅጥር እንዳላቸው ሁሉ የዐባይ ወንዝ መከላከያዋ ነበር”። (ዘይቤአዊ አነጋገር እና ተመሳሳይነት የሚለውን ተመልከት)
“ኩሽና ግብፅ ጉልበቶቿ ነበሩ
“ኢትዮጵያና ግብፅ አበረቷት” ወይም “ኩሽና ግብፅ ተባባሪዎቿ ነበሩ”
ለእርሱ ፍጻሜ አልነበረውም
“እርሱ” የሚለው ቃል ኩሽና ግብፅ ለቲቤስ የሰጧትን “ጉልበት” ያመለክታል። ለእርሱ ፍጻሜ አልነበረውም ሲል እጅግ ታላቅ የሆነውን ጉልበት የሚገልጽ ግነት ነው። ኢ.ት: “ኃይላቸው እጅግ ታላቅ ነበር”። (ግነት እና ማጠቃለያ የሚለውን ተመልከት)
ፉጥና ሊቢያ
እነዚህ ለቲቤስ ቅርብ የሆኑ በሰሜን አፍሪካ የሚገኙ የቦታ ስሞች ናቸው። (‘ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ’ የሚለውን ተመልከት)
Nahum 3:10
አጠቃላይ መረጃ:
ናሆም እነርሱ ከተማይቱን ራሷን እንደሆኑ አድርጎ ስለ ነነዌ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይሁን እንጂ ቲቤስ ተወሰደች
“ቲቤስ” የሚለው ቃል በቲቤስ ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ይወክላል። ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ቲቤትን የወጓት ሕዝቧን ወሰዱ”። (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)
ወደ ምርኮ ሄደች
“እርሷ” የሚለው ቃል ቲቤስን ሲያመለክት በእርስዋ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። ኢ.ት: “ወደ ምርኮ ሄዱ”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሕፃናት ልጆቿ ተፈጠፈጡ
ይህ ወታደሮቹ ሕፃናትን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ መግደላቸውን የሚገልጽ ነው። ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “የጠላት ወታደሮች ሕፃናቱን ፈጠፈጧቸው” ወይም “የጠላት ወታደሮች ሕፃናቱን ደብድበው ገደሏቸው”። (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)
በየጎዳናው ራስ ሁሉ ላይ
የጎዳናው ጅማሬ እንደ ራስ ተቆጥሮ ተነግሮለታል። በተጨማሪም፣ “ሁሉ” ማጠቃለያ ሲሆን በከተማው ሁሉ ያሉ በርካታ ስፍራዎች ማለት ነው። ኢ.ት: “በየጎዳናው ማዕዘን ላይ” ወይም “በከተማው ሁሉ ባሉት ጎዳናዎች”። (ዘይቤአዊ አነጋገር፣ ግነት እና ማጠቃለያ የሚለውን ተመልከት)
ታላላቅ ሰዎቿ ሁሉ በሰንሰለት ታሰሩ
ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ታላላቅ ሰዎቿን ሁሉ በሰንሰለት አሰሯቸው”። (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)
አንቺ ደግሞ ትሰክሪያለሽ
እዚህ ጋ “አንቺ” የሚለው ቃል ነነዌን ያመለክታል። ብዙ ወይን ጠጥተው እንደ ሰከሩ ሰዎች የነነዌ ሰዎች በጦርነት እንደሚሰቃዩና እንደሚሞቱ ናሆም ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Nahum 3:12
አጠቃላይ መረጃ:
ናሆም እነርሱ ከተማይቱን ራሷን እንደሆኑ አድርጎ ስለ ነነዌ ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ምሽጎችሽ ሁሉ
“ምሽጎች” ለሚለው ቃል አማራጭ የሚሆኑት ትርጉሞች 1) እርሱ የነነዌን ከተማ

የሚከበውን ቅጥር፣ ምሽግ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ምሽጎችሽ ሁሉ” ወይም “መከላከያዎችሽ ሁሉ” ወይም 2) እርሱ የአሦርን ድንበር በሚዋሰነው አካባቢ ነነዌን የሚያጠቁትን የጠላት ሰራዊት የሚከላከሉትን የተመሸጉ ከተሞች ያመለክታል። (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ምሽጎችሽ ሁሉ ሊበሉ እንደ ደረሱ የመጀመሪያ የበለስ ዛፍ ናቸው፤ ከተነቀነቁ በበላተኛው አፍ ውስጥ ይወድቃሉ
አንድ ሰው የበሰለውን የበለስ ፍሬ እንዲወርድ ማድረግ እንደሚቀለው ሁሉ ተዋጊዎቹ ነነዌን ድል ማድረጋቸው ቀላል መሆኑን በንጽጽር ይናገራል። ኢ.ት፡ "አንድ ሰው የበለስን ዛፍ በመነቅነቅ የሚወድቀውን የበሰለ ፍሬ መብላት እንደሚችለው ሁሉ ጠላቶችሽ ምሽጎችሽን በቀላሉ ያፈርሱታል”። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)
በመጀመሪያ የበሰለውን በለስ
ይህ የሚያመለክተው በዛፉ ላይ በመጀመሪያ የሚበስለውን በለስ ነው። እነዚህ በለሶች በቀላሉ ስለሚወድቁ አንድ ሰው ፍሬዎቹ እንዲወድቁ ለማድረግ ዛፉን መነቅነቅ ብቻ ይኖርበታል። ዘግየት ብለው የሚበስሉትን በለሶች አንድ ሰው ዛፉ ላይ ወጥቶ በእጁ እንዲለቅማቸው ግድ ይሆንበታል። (የተገመተ ዕውቀትና የተሰወረ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ከተነቀነቁ
“ዛፎቹ ከተነቀነቁ” ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ዛፎቹን ቢነቀንቃቸው”።(ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)
በበላተኛው አፍ ውስጥ ይወድቃሉ
“በለሶቹ በበላተኛው አፍ ውስጥ ይወድቃሉ”፣ ይህ ግነት ነው። በለሶቹ ከዛፉ ላይ ወደሚመገበው ሰው አፍ ውስጥ ይወድቃሉ በማለት ናሆም አጽንዖት የሚሰጠው በለሶቹ ወዲያውኑ ለመበላት የተዘጋጁ መሆናቸውን ነው። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው በለሶቹን ወዲያውኑ ሊበላቸው ይችላል”። (ግነት እና ማጠቃለያ የሚሉትን ተመልከት)
በመካከልሽ ያሉት ሰዎች ሴቶች ናቸው
በዚህ ጥንታዊ ባህል በጥቅሉ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ በአካላዊ ብቃታቸው ደካሞች መሆናቸውን ጨምሮ በተለያየ ምክንያት ተዋጊዎች አልነበሩም። እዚህ ጋ፣ በከተማው የነበሩት ሰዎች ሁሉ ሴቶች የሆኑ ይመስል ናሆም የነነዌ ተዋጊዎች ለመዋጋት እንደዛሉና ድፍረት እንዳጡ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ሰዎቻችሁ ሁሉ ደካሞችና ራሳቸውን መከላከል የማይችሉ ሴቶችን ይመስላሉ”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የምድርሽ በሮች ለጠላቶችሽ ወለል ብለው ተከፍተው ነበር
ይህ በገቢራዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የምድርሽ በሮች ለጠላቶችሽ ወለል ብለው ተከፍተዋል” ወይም “የሆነ ሰው የምድርሽን በሮች ለጠላቶችሽ ወለል አድርጎ ከፍቶላቸዋል”። (ገቢራዊ ወይም ተገብሮአዊ የሚለውን ተመልከት)
የምድርሽ በሮች ለጠላቶችሽ ወለል ብለው ተከፍተው ነበር
አማራጭ የሚሆኑት ትርጉሞች 1) በቁ. 12 ላይ “ምሽጎች” የሚለው ቃል የነነዌን መከላከያ የሚያመለክት ከሆነ እንግዲያው “የምድርሽ በሮች” የሚለው በነነዌ ዙሪያ ቅጥር ላይ የነበሩትን በሮች ያመለክታል” ወይም 2) በቁ. 12 ላይ “ምሽጎች” የሚለው ቃል አሦርን በሚያዋስነው ድንበር አካባቢ የሚገኙትን የተመሸጉ ከተሞች የሚያመለክት ከሆነ ደግሞ “የምድርሽ በሮች” የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር የጠላት ሰራዊት ወደ ምድሪቱ እንዳይገባ የሚከላከሉት በሮች እነዚያ ከተሞች መሆናቸውን ያመለክታል የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
መቆለፊያዎቻቸውን እሳት በልቶታል
አማራጭ የሚሆኑት ትርጉሞች 1) በቁ. 12 ላይ “ምሽጎች” የሚለው ቃል የነነዌን መከላከያ የሚያመለክት ከሆነ እንግዲያው “መዝጊያዎቻቸው” የሚለው በነነዌ ዙሪያ ባለው ቅጥር ላይ በሮቹ የተዘጉባቸውን መቆለፊያዎች ያመለክታሉ” ወይም 2) በቁ. 12 ላይ “ምሽጎች” የሚለው ቃል አሦርን በሚያዋስነው ድንበር አካባቢ የሚገኙትን የተመሸጉ ከተሞች የሚያመለክት ከሆነ ደግሞ “መቆለፊያዎቻቸው” የሚለው ቃል እነዚያ ከተሞች የጠላት ሰራዊት ወደ ምድሪቱ እንዳይገባ የሚከላከሉ የተዘጉ በሮች መሆናቸውን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እሳት በልቷቸዋል
እሳት ይባላ ይመስል ናሆም ስለማቃጠሉና ስለማጥፋቱ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እሳት አጥፍቶታል” ወይም “እሳት እንድዶታል”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Nahum 3:14
አጠቃላይ መረጃ፡
ናሆም ስለ ነነዌ ሕዝብ እነርሱ ከተማይቱን ራሷን እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ይቀጥላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለከበባው ውሃ ለመቅዳት ሂጂ. . . ለጡቦቹ ጭቃ ርገጪ
ናሆም የሚናገረው ለነነዌ ሕዝብ ነው። ጠላት ከተማይቱን እንደሚያጠፋት ቢያውቅም ለጦርነት እንዲዘጋጁና ቅጥሮቹን እንዲጠግኑ ይነግራቸዋል። (ውስጠ ወይራ የሚለውን ተመልከት)
ታላላቅ ምሽጎቻችሁን አጠናክሩ
“ምሽጎቻችሁን ጠግኑ”
የሸክላ ዐፈር ፈልጊና ጭቃውን አቡኪ፤ ለጡቦቹ የሚሆን ቅርፅ አውጪ
እነዚህ ሐረጎች የከተማይቱን ቅጥር ለመጠገን የሚጠቀሙባቸውን የጭቃ ጡብ ስለመሥራታቸው ያመለክታል።
በዚያ እሳት ይበላሻል
እሳት ይባላ ይመስል ናሆም ስለሚያቃጥልና ስለሚያጠፋ እሳት ይናገራል። ኢ.ት፡ “በዚያ እሳት ያጠፋችኋል” ወይም “በዚያ ጠላቶቻችሁ በእሳት ያነዷችኋል”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰይፍ ያጠፋሻል
ይህ “ሰይፍ” የሚለው ቃል ጠላቶቻቸው የሚያጠቁባቸውን ሰይፎች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ጠላቶቻችሁ በሰይፎቻቸው ይገድሏችኋል”። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የአንበጣ ኩብኩባ ሁሉን እንደሚበላ ይበላሻል
“እርሱ” የሚለው ቃል የሚገድላቸውን እንደሚበላ በሰውኛ የተነገረለትን “ሰይፍ” ያመለክታል። ወታደሮች ሰይፎቻቸውን በመጠቀም በነነዌ ያሉትን ሁሉ የሚገድሉበት ሁኔታ በመንገዱ ያገኘውን ሰብል ሁሉ ከሚበላው የአንበጣ መንጋ ጋር ተነጻጽሯል። ኢ.ት፡ “የአንበጣ መንጋ በመንገዱ ያገኘውን ሁሉ በቀላሉ እንደሚበላ የጠላቶቻችሁ ሰይፍ ሁላችሁንም ይገድላችኋል”። (ሰውኛ እና ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት))
ራስሽን እንደ ኩብኩባ አርቢ፣ እንደ አንበጣም አብዢ
እነዚህ ቃላት ናሆም በነነዌ የሚኖረውን ሕዝብ ቁጥር በመንጋ ውስጥ ካሉት እጅግ ብዙ ቁጥር ካላቸው አንበጣዎች ጋር የሚያነጻጽርበትን አዲስ አንቀጽ ይጀምራሉ።
Nahum 3:16
አጠቃላይ መረጃ፡
ናሆም ስለ ነነዌ ሕዝብ እነርሱ ከተማይቱን ራሷን እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ይቀጥላል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የነጋዴዎችሽን ቁጥር በሰማይ ካሉት ከዋክብት ይልቅ አብዝተሻቸዋል
ይህ ግነት አጽንዖት የሚሰጠው በነነዌ ይኖሩና ይሠሩ በነበሩ እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው ነጋዴዎች ላይ ነው። ኢ.ት፡ “በሰማይ ካሉት ከዋክብት ብዛት የሚበልጥ ነጋዴዎች ያሉሽ ይመስል” ወይም “ከብዛታቸው የተነሣ ማንም ሊቆጥራቸው የማይቻለው ነጋዴዎች አሉሽ”። (ግነት እና ማጠቃለያ የሚለውን ተመልከት)
እንደ አንበጣ ኩብኩባ ናቸው፤ ምድሪቱን ይበዘብዙና በረው ይሄዳሉ
ናሆም እነዚህ ነጋዴዎች ሸቀጦቻቸውን በነነዌ ሸጠው ካተረፉ በኋላ ጦርነቱ ሲጀመር ከከተማይቱ መሸሻቸውን በመንገዳቸው ያገኙትን ሰብል ሁሉ ከበሉ በኋላ በረው ከሚሄዱ አንበጣዎች ጋር ያነጻጽራል። (ምስያ የሚለውን ተመልከት)
የጦር አዛዦችሽ በብርድ ቀን በቅጥሩ ስር እንደሚሰፍር የአንበጣ መንጋ ናቸው፤ ነገር ግን ፀሐይ ሲወጣ በረው ይሄዳሉ
ናሆም በነነዌ የሚኖሩ የጦር አለቆች ጦርነቱ ሲጀመር መሸሻቸውን ቅዝቃዜ በሚሆንበት ጊዜ ቆይተው ፀሐይ ሲወጣና አየሩ ሲሞቅ በረው ከሚሄዱ አንበጣዎች ጋር ያነጻጽራቸዋል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)
ማንም ወዴት እንደሚሄዱ አያውቅም
“እናም ወዴት እንደሄዱ ማንም አያውቅም”
Nahum 3:18
እረኞችሽ አንቀላፍተዋል፤ ገዢዎችሽ አርፈው ተኝተዋል
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራሉ። ናሆም በጎቻቸውን እንደሚንከባከቡ እረኞች በመቁጠር ለአሦር መሪዎች ይናገራል። እርሱ ያንቀላፉ ይመስል ስለ እረኞቹና ስለ ገዢዎቹ ይናገራል። ኢ.ት፡ “እረኞች የሚመስሉ መሪዎቻችሁ ሞተዋል፤ ገዢዎቻችሁ በሙሉ ሞተዋል” (ተመሳሳይነት እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሕዝብሽ በተራሮች ላይ ተበትኗል
ናሆም እረኞቻቸው ከሞቱ በኋላ እንደተበተኑ በጎች ስለ ነነዌ ሕዝብ ይናገራል። ኢ.ት፡ “ሕዝብሽ እንደ በጎች በተራሮች ላይ ተበትነዋል”። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቁስልሽ ሊፈወስ የማይችል ነው። ቁስልሽ የከፋ ነው

ንጉሡ በማይድን ቁስል የተሰቃየ ይመስል ናሆም የነነዌ መጥፋትና የንጉሥዋ ድል መደረግ የማይቀር መሆኑን ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቁስልሽ ሊፈወስ የማይችል ነው

“ፈውስ” የሚለው ቃል በግሳዊ ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ቁስልሽን ማንም ሊፈውስ አይችልም”። (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ከጽኑው ክፋትህ ያመለጠ ማነው?

ይህ የማሳመኛ ጥያቄ አጽንዖት የሚሰጠው አስቀድሞ በሚገምተው አሉታዊ ምላሽ ላይ ነው። በአሦር አቅራቢያ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ሁሉ ጽኑ በሆነው በአሦር ክፋት ምክንያት ተሰቃይተው ነበር። ኢ.ት፡ “ከጽኑው ክፋትህ ማንም ያመለጠ የለም”። (የማሳመኛ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 1

## Habakkuk 1:1

ነቢዩ ዕንባቆም የተቀበለው መልእክት

እነዚህ ቃሎች የመጽሐፉን ሁለት ምዕራፎች ያስተዋውቃሉ። ዕንባቆም ይህን መልእክት ከያህዌ መቀበሉ ይታወቃል። ይህን የተሟላ ዐረፍተ ነገር አድርጐ ማቅረብ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነቢዩ ዕንባቆም ከያህዌ የተቀበለው መልእክት ይህ ነው።››

ያህዌ

ይህ በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ የተገለጠ የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህን እንዴት እንደምትተረጉመው ከቃላት ትርጉም ስለ ያህዌ የተነገረውን ተመልከት።

ለርዳታ እየተጣራሁ አንተ የማትሰማው እስከ መቼ ነው?

ያህዌ እንዲረዳው ዕንባቆም ረጅም ጊዜ ወደ እርሱ ሲጮኽ እንደ ነበር አንባቢ መረዳት አለበት። ተስፋ በመቁረጡና ያህዌ እስኪመልስለት ድረስ ምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለበት ማወቅ ስለ ፈለገ ይህን ጠይቆአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንተ መልስ እስክትሰጠኝ ከእንግዲህ ለርዳታ መጮኽ ያለብኝ ምን ያህል ጊዜ ነው?››

## Habakkuk 1:3

አጠቃላይ መረጃ

ዕንባቆም ወደ እግዚአብሔር መጮኹን ቀጥሏል።

ጥፋትና ግፍ በፊቴ አለ

‹‹ጥፋት›› እና ‹‹ግፍ›› የተሰኙትን ቃሎች ግሣዊ ሐረግ አድርጐ መተርጐም ይቻላል። ‹‹በፊቴ›› የሚለው ፈሊጥ እነዚህ ነገሮች የተፈጸሙት ዕንባቆም በዐይኑ እየተመለከተ እንደ ነበር ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ነገሮችን ሲያጠፉና ግፍ ሲፈጽሙ በዐይኔ ዐይቻለሁ›› ጠብና ጭቅጭቅ በዝቶአል ‹‹ጠብ›› የሚለው ቃል በሰዎች መካከል አለ መግባባት መኖሩን የሚያመለክት ሲሆን፣ እንደ ግሣዊ ሐረግ መተርጐም ይቻላል። ልክ አንድ ሰው ወደ ላይ ከፍ ያለ ይመስል ዕንባቆም በሰዎችም መካከል ጠብ ከፍ እያለ መምጣቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሰዎች መካከል ጠብ እየበዛ መጥቷል››

ክፉዎች ጻድቃንን ይከባሉ

ክፉዎች ጻድቃንን የመክበበቸውን ያህል ዐመፀኞች ጻድቃን ላይ ብዙ ግፍና መከራ እየፈፀሙ እንደ ሆነ ዕንባቆም ይናገራል።

ሕግ ደክሟል

ሰዎች ለሕጉ አለ መታዘዛቸውን ወይም ተግባር ላይ አለማዋላቸውን ዕንባቆም የሕግ መድከምንና ምንም ማድረግ አለመቻልን ደካማ ከመሆን ጋር አመሳስሎታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንም ሕግ አያከብርም››

ሐሰተኛ ፍርድ በዝቶአል

ዳኞች ትክክል የሆነ ፍርድ እንዳደረጉ ቢናገሩም፣ ለሕዝቡ ግን ‹‹ሐሰተኛ ፍርድ›› ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዳኞች በሐሰት ይፈርዳሉ››

## Habakkuk 1:5

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለዕንባቆም እየመለሰ ነው

ተደነቁ፤ ተገረሙ

‹‹መደነቅ›› እና ‹‹መገረም›› ተመሳሳይ ትርጉም ነው ያላቸው። ሁለቱ በአንድ ሆነው ለጉዳዩ አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ተደነቁ››

በዘመናችሁ

ይህ አነጋገር የሚያመለከተው የዕንባቆምን ሕይወት ዘመን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሕይወት ዘመናችሁ››

ቢነገራችሁም እንኳ

ይህን፣ ‹‹አንድ ሰው ቢነግራችሁ እንኳ›› ወይም፣ ‹‹ስለዚያ ስትሰሙ›› በማለት መግለጽ ይቻላል።

ተመልከቱ!

እዚህ ላይ፣ ‹‹ተመልከቱ!›› የሚለው ቃል የማሰሙትን አስደናቂ ነገር ልብ ማለት እንዳለባቸው ያመለክታል።

ከለዳውያንን አስነሣለሁ

ያህዌ ኀይለኞቹ ከለዳውያንን እንደሚያነሣቸው ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከለዳውያንን በጣም ኀይለኛ ሕዝብ አደርጋለሁ››

ጨካኝ

አማራጭ ትርጉሞቹ፣ 1) ‹‹ግፈኛ›› ወይም 2) ‹‹ፈጣን››

በምድሪቱ ስፋት

ይህ ማለት፣ 1) ይሁዳ ውስጥ ማንኛውም ቦታ ወይም 2) በዓለም ውስጥ ባለ ማንኛውም ቦታ ማለት ሊሆን ይችላል። የከለዳውያን ሰራዊት ኀያል እንደ ሆነ አጽንዖት ለመስጠት የታሰበ ግነት ሊሆን ይችላል።

የሚያስፈሩና የሚያስደነግጡ ናቸው

‹‹የሚያስፈሩ›› እኛ፣ ‹‹የሚያስደነግጡ›› የተሰኙት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ሁለቱ በአንድነት ሆነው ከለዳውያን ሌሎች ሰዎች ላይ ለሚያሳድሩት ፍርሃት አጽንዖት ይሰጣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌሎች ሰዎችን እጅግ ያሸብራሉ››

ፍርዳቸውና ክብራቸው ከራሳቸው ይወጣል

‹‹ክብራቸው›› የሚለው ለራሳቸው ካላቸው አመለካከት የሚነሣ ትዕቢትን ይወክላል። ከእነርሱ የሚወጣው ፍርድና ክብር ለራሳቸው ካላቸው አመለካከት የሚነሣ ውጤት እንደ ሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ትዕቢተኞች በመሆናቸው ምን መፍረድ እንዳለባቸው በራሳቸው ይወስናሉ››

## Habakkuk 1:8

ፈረሶቻቸው… ፈረሶቻቸው

የከለዳውያን ሰራዊት ፈረሶች

ነብር

ግዙፍ፣ ፈጠን ድመት

የማታ ተኩላ

ምግባቸውን ማታ ማታ የሚያድኑ ተኩላዎች ያመለክታል።

ፈረሰኞቻቸው

ፈረሶች የሚጋልቡ የከለዳውያን ሰራዊት

ነጥቆ ለመብላት እንደሚቸኩል አሞራ ይበራሉ

አሞራ ምግቡን ለመያዝ ፈጣን እንደ ሆነ ሁሉ፣ ከለዳውያንም ጠላቶቻቸውን ድል ለማድረግ ምን ያህል ፈጣን መሆናቸውን ያህዌ ይናገራል።

ሰራዊታቸው እንደ ምድረ በዳ ነፋስ ወደ ፊት ይገሠግሣል

ምድረ በዳ ላይ እንደሚነፍስ ነፋስ ከለዳውያን ምን ያህል በፍጥነት እንደሚንቀሳቀሱ ያህዌ ይናገራል።

ምርኮኞችን እንደ አሸዋ ይሰበስባል

ይህን፣ 1) አንድ ሰው በእጁ አሸዋ እንደሚያፍስ ከለዳውያንም በቀላሉ ሰዎችን ምርኮኛ እንደሚያደርጉ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አንድ ሰው አሸዋ እንደሚሰበስብ እነርሱም ምርኮኛ ይሰበስባሉ›› ወይም 2) እነዚያ ሰዎች ምድረ በዳ ውስጥ እንዳለ አሸዋ የሆኑ ይመስል፣ ከለዳውያንም እጅግ ብዙ ምርኮኛ ይሰበስባሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምድረ በዳ አሸዋ የሚያህል ምርኮኛ ይሰበስባሉ››

## Habakkuk 1:10

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ስለ ከለዳውያን ሰራዊት ገለጻውን ቀጥሏል።

ነገሥታትን ይንቃሉ፤ በገዞችም ላይ ያፌዛሉ

በመሠረቱ የእነዚህ ሐረጐች ትርጉም ተመሳሳይ ነው። ‹‹ማፌዝ›› የሚለውን ቃል፣ ግሣዊ በሆነ ሐረግ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ነገሥታትን ይንቃሉ፤ መሪዎችም ማላገጫዎቻቸው ናቸው።›› ወይም፣ ‹‹እነርሱ የሚያደርጉት፣ ነገሥታትንና ገዞች ላይ ማፌዝ ብቻ ነው››

እንደ ነፋስ አልፈው ይሄዳሉ

በፍጥነት የሚንቀሳቀስ ነፋስ የሆኑ ይመስል፣ የከለዳውያን ሰራዊት እያንዳንዱን ድል በማድረግ ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው እንደሚሸጋገሩ ያህዌ ይናገራል።

ጉልበታቸውን አምላካቸው ያደረጉ በደለኞች ናቸው

ይህ የሚያመለክተው የከለዳውያንን ሠራዊት ነው።

### Habakkuk 1:12

አጠቃላይ መረጃ

ዕንባቆም ስለ ከለዳውያን ለያህዌ ይናገራል።

ከዘላለም ጀምሮ ያለህ አይደለህምን? የእኔ አምላክ፣ የእኔ ቅዱስ

ዕንባቆም ይህን መልስ የማያስፈልገው ጥያቄ የሚያቀርበው አዎንታዊ ምላሽ በመጠበቅ ነው። እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእርግጥ አንተ ከዘላለም ጀምሮ ነህ፤ አምላኬ ያህዌ የእኔ ቅዱስ››

ከዘላለም ጀምሮ

‹‹ዘላለማዊ››

እንዲፈርዱ ሾመሃቸዋል፤ ዐለት ሆይ፣ ይቀጡ ዘንድ ሥልጣን ሰጠሃቸው።

የሚናገረው ስለ ከለዳውያን ነው። ‹‹ፍርድ›› እና፣ ‹‹ቅጣት›› የተሰኙትን ቃሎች ግሥ አድርጐ መተርጐም ይቻላል። ከለዳውያን የያህዌ ሕዝብ ላይ እንደሚፈርዱና እንደሚቀጡ አንባቢው መረዳት አለበት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡን እንዲቀጡ ሾምሃቸው፤ ዐለት ሆይ፣ ሕዝብህን እንዲቀጡ ሥልጣን ሰጠሃቸው››

ዐለት

ምንም ጉዳት እንዳይደርስበት ያህዌ ጠባቂው መሆኑንና ጠላቶቹ እንዳይደርሱበት የሚቆምት ዐለት መሆኑን ዕንባቆም ይናገራሉ

### Habakkuk 1:13

አጠቃላይ መረጃ

ዕንባቆም ስለ ከለዳውያን ለያህዌ መናገሩን ቀጥሏል

ዐይኖችህ... እጅግ ንጹሐን ናቸው

እዚህ ላይ፣ ‹‹ዐይኖች›› ሁሉን የሚያይ ያህዌን ይወክላሉ። ‹‹አንተ እጅግ ንጹሕ ነህ››

ከሐዲዎችን

ይህ የሚያመለክተው ከለዳውያንን ነው። መካድ እምነተ ቢስና የተናገሩትን የሚያጥፉ፣ ሰዎችን ይመለከታል።

ክፉው ከራሱ ይልቅ ጻድቅ የሆነውን ሲውጠውስ ለምን ዝም ትላለህ?

ልክ የሚውጧቸው ይመስል፣ ክፉዎች ሌሎች ሰዎችን እንደሚያጠፉ ዕንባቆም ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ሰው ከእርሱ የበለጠ ጻድቅ የሆነውን ሲያጠፋው ለምን ዝም ትላለህ?››

ከእርሱ ይልቅ ጻድቅ የሆነውን

ይህ የሚያመለክተው ዕንባቆም እየተናገረላቸው ያሉትን እስራኤላውያን ነው። እነዚህ ሰዎች ራሳቸው ክፉ መሆናቸውን፣ ሆኖም ከከለዳውያን፣ ‹‹ይልቅ ጻድቅ›› ወይም የከለዳውያንን ያህል ዐመፀኞች አለመሆናቸውን አንባቢው መረዳት አለበት።

በባሕር ውስጥ እንዳለ ዓሣ አደረግሃቸው

ከለዳውያን ምንም ፀፀት ሳይሰማቸው ሌሎችን የሚገድሉበትን መንገድ፣ ዓሣ ሲያጠምዱ ምንም ፀፀት ከማይሰማቸው ሰዎች ጋር አመሳስሎአቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ከዓሣ የበለጠ ዋጋ እንዳይኖራቸው አደረግህ››

ገዥ እንደሌላቸውም የሚርመሰመሱ ፍጥረታት አደረግህ

‹‹የሚርመሰመሱ›› የሚለው ጥቃቅን ትሎችንና ፍጥረታት ያመለክታል። የሚርመሰመሱ ፍጥረታት የሚያደራጃቸውና የሚከላከልላቸው እንደሌላቸው ሁሉ፣ ሕዝቡ በከለዳውያን ሰራዊት ፊት መከላከያ የላቸውም። ግሡ ካለፈው ቁጥር ጋር የተያያዘ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል። ሰዎች ገዥ እንደሌላቸው የሚርመሰመሱ ፍጥረታት መከላከያ የሌላቸው እንዲሆኑ አደረግህ።

### Habakkuk 1:15

X

1፥15-17 ላይ ያለው፣ ‹‹እርሱ›› እና፣ ‹‹የእርሱ›› የሚለው ነጠላ ቁጥር ሁሉንም የባቢሎን ወታደሮች የሚወክል አንድ የባቢሎን ወታደር ያመለክታል። ይህን ተውላጠ ስም ወደ ብዙ ቁጥር መለወጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያመጣናል... ሁላችንንም ይይዘናል››

በመረቡ ይይዛቸዋል፤ በአሽክላው ውስጥ ይሰበስባቸዋል

ይህ የሚናገረው ስለ አጠቃላይ ሰዎች ነው። ይህ ዕንባቆምንም እንዲጨምር አድርጐ ሊተረጐም ይችላል። ‹‹ሁላችንንም በመረቡ ይይዘናል፤ በአሽክላው ውስጥ ይሰበስበናል››

መንጠቆ... መረብ... አሽክላ

እነዚህ ዓሣ ለማጥመድ የሚጠቅሙ ናቸው።

ለመረቡ ይሠዋል፤ ለአሽክላውም ያጥናል

ሕዝብንና መንግሥታትን ድል ለማድረግ ከለዳውያን የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ዓሣ ለማጥመድ የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ያህል መሆናቸውን ዕንባቆም ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎችን ድል ለማድረግ የሚጠቀሙባቸውን መሣሪያዎች መሥዋዕት ያቀርቡላቸዋል፤ ዕጣን ያጥኑላቸዋል››

ታዲያ መረቡን ባለ ማቋረጥ መጣል ሕዝቦችንስ ያለ ርኅራኄ መግደል አለበትን?

ዕንባቆም ይህን የሚጠይቀው ተስፋ ስለ ቆረጠና ይህ የሚቀጥለው ለምን ያህል ጊዜ መሆኑን ማወቅ ስለ ፈለገ ነው። ያህዌ ከለዳውያን ሕዝቦችንና መንግሥታትን ማጥፋታቸውን እንዲቀጥሉ ይፈቅድላቸዋል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹መረባቸውን ባለ ማቋረጥ እንዲጥሉና ያለ አንዳች ርኅራኄ ሕዝቦችን እንዲያጠፉ ትፈቅድላቸዋለህን?››

መረቡን ባለ ማቋረጥ መጣል

ያለ ማቋረጥ መረቡን እንደሚጥል ዓሣ አጥማጅ፣ ከለዳውያንም ተጨማሪ መንግሥታት ድል ለማድረግ እየተዘጋጁ መሆናቸውን ዕንባቆም ይናገራል።

---

## Chapter 2

### Habakkuk 2:1

በመጠበቂያ ላይ እቆማለሁ፤ በምሽጉ ቅጥር ላይ ወጥቼ እቆያለሁ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች የሚያመለክቱት በመሠረቱ አንድ ዐይነት ስለሆኑ ነገሮች ነው።

ይህም፣ ዕንባቆም ምሽጉ ቅጥር ላይ ወዳለ መጠበቂያ ወጥቶ ነበር ማለት ነው፤ ወይም 2) መጠበቂያው ላይ ወጥቶ የመልእክተኛውን መምጣት እንደሚጠብቅ ሰው የያህዌን ምላሽ በናፍቆት እንደሚጠብቅ ዕንባቆም በምሳሌ እየተናገረ ነው።

ምን እንደሚለኝ አያለሁ

‹‹ያህዌ ምን እንደሚናገረኝ አያለሁ››

ለክርክሬም የምሰጠውን መልስ ለማወቅ እጠባበቃለሁ

‹‹መልስ›› የሚለው መልስ መስጠትን ያመለክታል። ተናግሮ ስለ ነበረው ነገር፣ ዕንባቆም ምን መልስ እንደሚሰጥ እያሰበ ነው።

### Habakkuk 2:2

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለዕንባቆም ይመልስለታል

ራእዩን ጻፈው፤ በሰሌዳም ላይ ቅረጸው

ሁለቱም ሐረጐች ስለ አንድ ዐይነት ጉዳይ በተለያዩ መንገዶች ይናገራሉ።

አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህን ራእይ በግልጽ ሰሌዳ ላይ ጻፈው››

ሰሌዳ

ይህ ለመጻፊያ የሚያገለግል ጠፍጣፋ ድንጋይ ወይም ሸክላ ነው።

የሚያነበው ሰው እንዲፈጥን ይህም፣ 1) መልእክቱን ለማድረስ መልእክተኛው ከቦታ ወደ ቦታ እየሮጠ እያለ በቀላሉ ማንበብ እንዲችል መልእክቱ በጣም ቀላል ነው ማለት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰሌዳውያን የሚያነበው ሰው እየሮጠ እያለ ማንበብ እንዲችል›› ወይም 2) የሚያነበው እየሮጠ ያለ ይመስል አንባቢው በፍጥነት ማንበብ እንዳለበት ያህዌ የሚናገረው ምሳሌ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰሌዳውን የሚያነብ በፍጥነት ማንበብ እንዲችል››

ራእዩ... ስለ መጨረሻው ይናገራል

ራእዩ መናገር የሚችል ሰው እንደ ሆነ አድርጐ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ራእዩ... መጨረሻ ላይ ይፈጸማል›› ወይም፣ ‹‹ራእዩ... በመጨረሻ እውነት ይሆናል›› ቢዘገይም እንኳ ጠብቀው በእርግጥ ይመጣል፤ ከቶም አይዘገይም፤ ራእዩ ቶሎ የታሰበው ቦታ ከመድረስ የሚዘገይ ሰው ይመስል፣ ለመፈጸም ረጅም ጊዜ እንደሚወስድ ያህዌ ይናገራል።

አይዘገይም

ይህም፣ ‹‹ጊዜ አያልፍም›› ወይም 2) ‹‹ቶሎ ይመጣል›› ማለት ሊሆን ይችላል።

### Habakkuk 2:4

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱን ቀጥሏል። እዚህ ላይ ከለዳውያን ትዕቢተኞች፣ ጠጥቶ የማይጠግብ ሰካራም መሆናቸውን ይናገራል።

ተመልከቱ

‹‹ተመልከቱ›› የሚለው ለሚከተለው ነገር አጽንዖት ይሰጣል።

ታብዮአል

ትዕቢተኛው ሰው፣ ‹‹መታበዩን›› ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ትዕቢተኛ ሆኖአል››

የወይን ጠጅ አታሎታል

ብዙ ወይን ጠጅ መጠጣት የሰውን ሚዛን እንዴት እንደሚያዛባ ያህዌ ይናገራል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከወይን ጠጅ እርሱ የፈለገውን አያገኝም››
ከቶ አያርፍም
እዚህ ላይ፣ ‹‹ማረፍ›› የሚለው ቃል ቤት ውስጥ መኖርን የሚያመለክት ሲሆን፣ ማረፊያ ቦታ ማጣትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምንም ዕረፍት እንዳይኖረው››
ምኞቱን እንደ መቃብር ያሰፋል፤ እንደ ሞት ከቶ አይጠግብም
መቃብርና ሞት ፍጹም የማይጠግቡ ከመሆናቸው የተነሣ ሰዎች ሁሌም እንደሚሞቱ ሁሉ፣ እነዚህም በልተው አይጠግቡም። በተመሳሳይ መንገድ ሁልጊዜ የበለጠ ይፈልጋል፤ ግን በቃን አይልም።
ሕዝቦችን ለራሱ ይሰበስባል፤ ሰዎችንም ሁሉ ማርኮ ይወስዳል።
የእነዚህ ሁለት ሐረጐች ትርጉም ተመሳሳይ ነው። ሰዎችን ድል ማድረግና መቆጣጠር፣ ሰዎችን ለራስ መሰብሰብ እንደ ሆነ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የየአገሩ ሰዎችን ድል እያደረገ ለራሱ ይሰበስባል››
Habakkuk 2:6
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱንና ከለዳውያን እንደ አንድ ሰው እንደ ሆኑ መናገሩን ቀጥሏል።
እንዲህ እያሉ ሁሉም አይሣለቁበትምን?
‹‹ሁሉም›› የሚለው ቃል ዕንባቆም 2፥5 ላይ የተጠቀሱትን መንግሥታትና ሕዝቦች ያመለክታል። በጥያቄ መልክ የቀረበው ዐረፍተ ነገር አዎንታዎ ምላሽ የሚጠብቅ በመሆኑ፣ እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ መንግሥታትና ሕዝቦች ሁሉ ይሳለቁበታል››
የራሱ ያልሆነውን ለሚሰበስብ ወዮለት
የራሱ ያልሆኑ ነገሮችን በመሰብሰብ ንብረት ማከማቸቱ ተነግሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእርሱ ያልሆነውን በመሰብሰብ ሀብታም ለሚሆን ወዮለት››
ሰዎች ላይ ያለህን ዕዳ ሸክም የምታበዛው እስከ መቼ ነው?
‹‹ዕዳ›› የሚለው ቃል ዕዳቸውን እስኪከፍሉ ድረስ፣ ሰዎች ለተበደሩት ነገር የሚሰጡትን፣ ‹‹መያዣ›› ያመለክታል። አንድ ሰው እንዲህ ያሉ መያዣዎች እያበዛ ሲሄድ ሸክሙም ይጨምራል።
ሰዎች ላይ ያለህን ዕዳ ሸክም የምታበዛው እስከ መቼ ነው?
የሰዎችን ሀብት የሚዘርፉ ከለዳውያን የራሳቸው ባልሆነው ነገር ሰዎች መያዣ እንዲሰጧቸው ያስገድዳሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌሎችን በመዝረፍ ራስህን ሀብታም የምታደርገው እስከ መቼ ነው?››
ድንገት አይነሡብህም? ነቅተውስ አያስደነግጡህምን?
በጥያቄ መልክ የቀረበው ዐረፍተ ነገር አዎንታዎ መልስ ይጠብቃል። እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድንገት ይነሡብሃል፤ ነቅተውም ያስደነግጡሃል››
‹‹ባለ ዕዳ ያደረግሃቸው››
ዕብራይስጡ፣ ‹‹ወለድ የምታስከፍላቸው›› ወይም፣ ‹‹ባለ ዕዳዎችህ›› ማለት ሊሆን ይችላል። በዚህ ዐውድ ውስጥ ሁለቱንም ትርጉሞች ይዞአል። ባለ ዕዳ የሆኑትና የተጨቆኑት መልሰው እርሱን እንደሚጨቁኑ የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው።
አያስደነግጡህምን?
ይህም የሚያመለክተው ስለ ባለ ዕዳዎቹ ነው። አስገድዶ እንዲከፍሉ ካደረገው መያዣ የተነሣ በቀል እንደሆን ከለዳውንን በማጥቃት ያስደነግጣቸዋል።
ነቅተው አይነሡብህምን?
ከለዳውያን ላይ የሚነሡ ሕዝቦች ድንገት፣ ‹‹ከእንቅልፍ›› — ‹‹ነቅተው›› እንደሚነሡ ተነግሮአል።
ዘረፋ
በኀይል መንጠቅ ወይም መውሰድ
የሰው ደም አፍሰሃልና
‹‹ደም ማፍሰስ›› — ‹‹መግደል›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎችን ገድለሃልና››
Habakkuk 2:9
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱንና ለከለዳውያን እንደ አንድ ሰው መናገሩን ቀጥሏል።
ክፉ ትርፍ የሚፈልግ
በዐመፅ ጥቅም የሚያገኝ ሰው፣ በዚያ ጥቅም መኖሪያውን እንደሚሠራ ተነግሯል››
በተጭበረበረ ትርፍ መኖሪያውን የሚገነባ
በተጭበረበረ ትርፍ መኖሪያውን… ሲል፣ 1) ‹‹መኖሪያ›› የሚለው በዐመፅ የተገነባውን የባቢሎን መንግሥት ለማመልከት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዐመፅ ባገኘው ሀብት መኖሪያ ቤቱን የሠራ ወይም፣ 2) ‹‹መኖሪያ›› ሲል ‹‹ቤተ ሰብን›› ማለት በዐመፅ ቤተ ሰቡን ሀብታም ያደረገ ሰው ማለቱ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በግፍ በተገኘ ሀብት ቤተ ሰቡን ሀብታም ያደረገ››
ከጠላት እጅ ለማምለጥ፣ ቤቱን በከፍታ ላይ ለሚሠራ
ይህ ቤቱን የሠራ ሰው እንደ ወፍ ጐጆ በከፍታ ላይ ሠርቶአል። አጥቂ እንስሳ የወፍ ጐጆው ላይ መድረስ እንደማይችል ሰውየውም ቤቱ የተጠበቀና ምንም አደጋ የማይደርስበት እንደ ሆነ ያስባል።
ከጠላት እጅ ለማምለጥ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የተባለው ኀይል ማለት ነው፤ ‹‹ጠላት›› የሚለውም ክፉ ነገር የሚያደርግ ሰው ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከጠላት ኀይል ለማምለጥ›› ወይም፣ ‹‹ጉዳት ከሚያደርሱ ሰዎች ለማምለጥ››
በገዛ ቤትህ ላይ ውርደትን… አምጥተሃል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ውርደትን አምጥተሃል›› የሚለው ሐረግ ሰውየው ያቀደው ነገር እርሱ ላይ ውርደት እንዳመጣበት ያመለክታል። ‹‹ቤት›› ለሚለው ቃል አንድ አማራጭ ትርጉም፣ የባቢሎን መንግሥት ሰው በዐመፅ በተገኘ ገንዘብ የሠራው ቤት መሆኑን ማመልከት ሊሆን ይችላል። ‹‹ባቀድኸው ዕቅድ የሠራኸው ቤት ላይ ውርደትን አመጣህ›› — ‹‹ቤት›› የሚለው ሌላ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቤተ ሰብ›› ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ባቀድኸው ዕቅድ ቤተ ሰብህ ላይ ውርደትን አምጥተሃል››
ብዙ ሰዎችን ነጥለሃል
ብዙ ሰዎችን መግደል ቅርንጫፍ ከዛፍ ላይ እንደሚነጠል እነዚያን ሰዎች መቁረጥ ወይም መነጠል እንደ ሆነ ተነግሯል።
በገዛ ራስህ ላይ ኀጢአት ሠርተሃል
‹‹በገዛ ራስ ላይ ኀጢአት ማድረግ›› ሞትና ጥፋት የሚያስከትል ነገር ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የራስህን መጥፊያ ሠርተሃል›› ወይም፣ ‹‹የገዛ ሞትህን አምጥተሃል››
ድንጋይ ከቅጥሩ ውስጥ ይጮኻል፤ ከእንጨት የተሠሩ ተሸካሚዎችም ይመልሱለታል።
እዚህ ላይ ሰውየው ቤቱን የሠራባቸው ነገሮች ያደረገውን ወንጀል እንደሚመሰክሩ ሰዎች ተመስለዋል። አንተ ባለህበት አገር ሰዎች ቤት ለመሥራት የሚጠቀሙት ከዚህ በተለየ ነገር ከሆነ እዚህ ላይ እነዚያን ነገሮች መጠቀም ትችላለህ።
ይጮኻል
‹‹አንተን በመቃወም ይጮኻል›› ወይም፣ ‹‹አንተን በመክሰስ ይጮኻል››
ይመልሱለታል
‹‹ከድንጋዩ ጋር ይስማማሉ››
Habakkuk 2:12
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱንና ከለዳውያንን እንደ አንድ ሰው አድርጐ መናገሩን ቀጥሏል።
ከተማን ደም በማፍሰስ ለሚሠራ፣ በወንጀልም ለሚመሠርታት ወዮለት
ሁለቱም ሐረጐች በተለያየ መንገድ ስለ አንድ ዐይነት ነገር ይናገራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከገደሉዋቸው ሰዎች በዘረፉት ከተሞቻቸውን ለሠሩ
ከለዳውያን የተሰጠ ማስጠንቀቂያ››
x
ከተማን ደም በማፍሰስ ለሚሠራ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ደም›› ግድያን ያመለክታል። ሰውየው ከተማን የሠራው እርሱ ከገደላቸው ሰዎች በተዘረፉ ነገሮች መሆኑ ተመልክቷል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎችን በመግደልና ያላቸውን ነገር በመዝረፍ ከተማን የሚሠራ››
በወንጀልም ለሚመሠርታት
ሰውየው ከተማ የሠራው ከገደላቸው ሰዎች በዘረፈው ነገር መሆኑን ያመለክታል። እዚህ ላይ፣ ‹‹መመሥረት›› የሚለው ቃል ‹‹መጀመር›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በክፉ ምግባር ባገኘው ትፍፉ ከተማ መሥራት የሚጀምር››
ሰዎች ለእሳት ማገዶ እንዲሆን እንዲለፉ፣ ሕዝቦችም በከንቱ እንዲደክሙ ያህዌ ጸባኦት ወስኖ የለምን?
ጥያቄው የቀረበ አዎንታዊ ምላሽ በመጠበቅ ነው። ሁለቱ ቁልፍ ቃሎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ፣ ሰዎች የሚሠሩት ሥራ ዘላቂነት እንደሌለው ያመለክታሉ። ጥያቄውን እንደ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች በርትተው የሚሠሩዋቸው ነገሮች በእሳት ተቃጥለው እንዲጠፉ የወሰነ ያህዌ ነው››
ሰዎች ለእሳት ማገዶ እንዲሆን እንዲለፉ።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ማለት ሰዎች የሚለፉባቸው ነገሮች ለእሳት ማገዶ እንዲሆኑ ተወስኖአል ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች የሚለፉባቸው ነገሮች ለእሳት ማገዶ ይሆናሉ››
ውሃ ባሕርን እንደሚሸፍን ሁሉ፣ ምድርም የያዌን ክብር በማወቅ ትሞላለች
ውሃ ባሕርን እንደሚሸፍን ሁሉ በየአገሩ ያሉ ሰዎችም፣ የያህዌን ክብር እንደሚያውቁ ንጽጽሩ ያመለክታል፡፡
ውሃ ባሕርን እንደሚሸፍን ሁሉ፣ ምድር የያህዌን ክብር በማወቅ ትሞላለች
‹‹በማወቅ›› የሚለውን፣ ‹‹ያውቃሉ›› በማለት መተርጐም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድሩ ሁሉ ያሉ ሰዎች የያህዌን ክብር ያውቃሉ››
Habakkuk 2:15
X
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱንና እንደ አንድ ሰው አድርጐ ለከለዳውያን መናገሩን ቀጥሏል፡፡
ባልንጀሮቹን አስገድዶ ለሚያጠጣ… እስኪሰክሩም ድረስ…
ከለዳውያን ሌሎች ሕዝቦች ላይ ያደረጉት ጭካኔ ባልንጀሮቹን ለማዋረድ ሲል በግድ እንዲሰክሩ በሚያደርግ ሰው ተመሳስሎአል፡፡ባልንጀሮቹን አስገድዶ ለሚያጠጣ
ኀፍረተ ሥጋቸውን ለማየት
ይህ በሌሎች ፊት እንዲዋረዱ ለማድረግ ሰዎችን በአደባባይ ዕርቃናቸውን እንዲሆኑ ከማድረግ ጋር ይመሳሰላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዕርቃናቸውን በማድረግ ሕዝብ ፊት እንዲዋረዱ››
በክብር ፈንታ ዕፍረት ትሞላለህ
የከለዳውያን አጥብቆ ክብራቸውን መፈለግ በመስገብገብና በብዛት ከሚበሉትና ከሚጠጡት ምግብ ጋር ተመሳስሎአል፡፡ ክብር ከማግኘት ይልቅ፣ ዕፍረትን ይለብሳሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስትፈልግ የነበረውን ክብር ሳይሆን፣ ራስህ ላይ ውርደት ታመጣለህ››
ጠጣ
ሌሎች ሰዎች ከለዳውያን ላይ የሚያደርጉት ነገር እነርሱ አስገድደው ሌሎችን እንዳጠጡ ሁሉ፣ እነርሱም ተገድደው ወይን ጠጅ እንዲጠጡ ከማድረግ ጋር ተመሳስሎአል›› አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከጽዋው ጠጣ›› ወይም፣ ‹‹ወይን ጠጁን ጠጣ››
ያልተገረዘ ኀፍረተ ሥጋህ ይገለጥ
ይህ ሐረግ ኀፍረተ ሥጋቸውን ለማየት ከለዳውያን በማስገደድ ሌሎች እንዲጠጡ ሲያስገድዱ ከነበረበት ሁኔታ ጋር ይመሳሰላል፡፡ እዚህ ላይ፣ ‹‹ያልተገረዘ ኀፍረተ ሥጋህ›› የሚለው ዕርቃናቸውን በመሆን መዋረዳቸውን ብቻ ሳይሆን፣ አለ መገረዛቸው የያህዌ ሕዝብ አለመሆናቸውን ጭምር በግልጽ ያሳያል፡፡
በያህዌ ቀኝ እጅ ያለው ጽዋ ይመለስብሃል
ያህዌ ከለዳውያንን መቅጣቱ በእጁ ከያዘው ጽዋ ወይን ጠጅ ከመጠጣት ጋር ተመሳስሎአል፡፡ የያህዌ ቀን እጅ ኀይሉን ይወክላል፡፡
በያህዌ ቀኝ እጅ ያለው ጽዋ
‹‹ያህዌ በቀኝ እጁ የያዘው ጽዋ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ከያዘው ጽዋ››
ክብርህን ውርደት ይሸፍነዋል
ከለዳውያን ላይ የሚደርሰው ውርደት አለን ብለው ያስቡ የነበረውን ክብር እንደሚሸፍን አንዳች ነገር ተገልጾአል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክብርህን ውርደት ይተካዋል›› ወይም፣ ‹‹ከማክበር ይልቅ ሰዎች ያዋርዱሃል››
Habakkuk 2:17
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱንና እንደ አንድ ሰው ለከለዳውያን መናገሩን ቀጥሏል፡፡
በሊባኖስ ላይ የሠራኸው ግፍ ያጥለቀልቅሃል፡፡
ሊባኖስ ላይ ለሠሩት ግፍ የሚደርስባቸው ቅጣት እነርሱን እንደሚያጥለቀልቅ አንዳች ነገር ተነግሮአል፡፡
በሊባኖስ ላይ የሠራኸው ግፍ
‹‹ሊባኖስ›› የሚለው ቃል ተመሳሳይ ትርጉም፣ 1) የሊባኖስን ዱር ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሊባኖስ ዛፎች ላይ የሠራኸው ግፍ›› ወይም 2) የሊባኖስን ሕዝብ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሊባኖስ ሕዝብ ላይ የሠራኸው ግፍ››
እንስሳቱን ማጥፋትህም ያስደነግጥሃል
ከለዳውያን የሊባኖስ እንስሶችን በማጥፋታቸው የሚደርስባቸው ቅጣት እነርሱን ከሚያስደነግጥ ሰው ጋር ተመሳስሎአል፡፡
የሰውን ደም አፍስሰሃልና… በውስጣቸው የሚኖሩትንም ሁሉ
ዕንባቆም 2፥8 እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት
የሰውን ደም አፍስሰሃልና
‹‹የሰው ደም ማፍሰስ›› — ‹‹መግደል›› ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎችን ገድለሃልና››
Habakkuk 2:18
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ ለዕንባቆም መመለሱንና እንደ አንድ ሰው ለከለዳውያን መናገሩን ቀጥሏል፡፡
የተቀረጹ ምስሎች ምን ጠቀሙህ?
ጥያቄው የቀረበው አሉታዊ መልስ በመጠበቅ ነው፡፡ ጥያቄው እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የተቀረጹ ምስሎች ምንም አልጠቀሙህም›› ‹‹አንተ›› የሚለው የሚያመለክተው ከለዳውያንን ነው፡፡
የቀለጠ ብረት
ይህ የሚያመለክተው በፈሳሽ መልክ ያለ ብረት ነው፡፡
የሐሰት መምህር
ይህ የሚያመክተው ምስሎቹን የተቀረጸው ወይም ያበጀውን ሰው ነው፡፡ የሐሰት አምላክ መቅረጹ ሐሰት ማስተማሩ ነው፡፡
ሕይወት የሌለውንም ድንጋይ
ግሡ ካለፈው ሐረግ ጋር ይያያዛል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕይወት የሌለውንም ድንጋይ… ለሚል ወዮለት››
በውኑ ማስተማር ይችላሉን?
ጥያቄው የቀረበው አሉታዊ መልስ በመጠበቅ ነው፡፡ ጥያቄው እንደ ዐረፍተ ነገር ሊተረጐም ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነዚህ ነገሮች ማስተማር አይችሉም›› ወይም፣‹‹እንጨትና ድንጋይ ማስተማር አይችሉም››
እነሆ… ተለብጦአል
‹‹ተመልከቱ፤ የተለበጠ መሆኑን ማየት ትችላላችሁ››
በወርቅና በብር ተለብጦአል
ይህን ድርጊትን በሚያመለክት ሁኔታ መተርጐም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንጨቱን ወይም ድንጋዩን ሰው በወርቅና በብር ለብጦታል››
እስትንፋስም የለውም
‹‹እስትንፋስ የለውም›› በሕይወት አይደለም፤ ሞቷል ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕይወት የለውም›› ወይም፣ ‹‹በድን ነው››
ምድር ሁሉ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ምድር›› በምድሪቱ የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድሪቱ የሚኖር ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹በምድር የሚኖር ሁሉ››

---

Chapter 3
Habakkuk 3:1
የነቢዩ የዕንባቆም ጸሎት
እነዚህ ቃሎች የዚህን መጽሐፍ ሦስተኛ ምዕራፍ ያስተዋውቃሉ፡፡ ይህን በተሟላ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ ነቢዩ ዕንባቆም ወደ እግዚአብሔር ያቀረበው ጸሎት ነው››
ዝናህን ሰምቻለሁ
የዚህ አማራጭ ትርጉም፣ 1) ቀድሞ ስላደረግኸው ሰዎች ሲናገሩ ሰምቻለሁ›› ወይም 2) ‹‹የተናገርኸውን ሰምቻለሁ››
ሥራህን አድስ
ቀድሞ ያደረገውን አሁንም እንዲያደርግ ዕንባቆም ያህዌን ይጠይቃል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ቀድሞ ያደረግኸውን ዛሬም አድርግ›› ወይም ‹‹ድሮ ያደረግኸውን አሁንም አድርግ››
በእነዚህ ዘመኖች መካከል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሕዝቡን ለመታደግ ያህዌ ባለፈው ጊዜ ካደረገው ጋር በሚቀራረን መልኩ ዕንባቆም ይህን ጸሎት ያቀረበበትን ዘመን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዘመናችን››
እንዲታወቁ አድርግ
‹‹ሥራህ እንዲታወቅ አድርግ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች ሥራህን እንዲያውቁ አድርግ››
Habakkuk 3:3
አጠቃላይ መረጃ
ያህዌ መጥቶ ጠላቶቹ ላይ እንደሚፈርድና ሕዝቡን እንደሚያድን የተቀበለውን ራእይ ዕንባቆም መግለጽ ጀምሮአል፡፡ ራእዩ እስከ ዕንባቆም 3፥15 ይቀጥላል፡፡ ንግግሩ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ምሳሌያዊ አነጋገር የሞላው ሲሆን፣ የተለያዩ ተዛማጅ ሐሳቦችንም ያቀርባል።

እግዚአብሔር ከተማን፣ ቅዱሱም ከፋራን ተራራ መጣ።

ቴማንና የፋራን ተራራ የሚኙት ከይሁዳ በስተ ደቡብ ነው። ከሲና ተራራ በኩል እግዚአብሔር ወደ ይሁዳ እንደሚመጣ ዕንባቆም ይናገራል።

ክብሩ ሰማያትን ሸፈነ

‹‹ግርማው ሰማይን ሸፈነ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ክብር›› የሚለው ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ብዙውን ጊዜ ከእግዚአብሔር ሐልዎት ጋር የሚያያይዙትን ደማቅ ብርሃን ያመለክታል።

ውዳሴውም ምድርን ሞላ

‹‹ውዳሴ›› ሰዎች እርሱን እንዲያመሰግኑ የሚያደርገውን የእግዚአብሔር ባሕርያት ያመለክታል አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ምድርም ክብሩን ተሞልታ ነበር››

Habakkuk 3:4

አጠቃላይ መረጃ

ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጽን ቀጥሏል።

ጸዳሉ እንደ ፀሐይ ብርሃን ነው።

እዚህ ላይ፣ ‹‹ጸዳል›› ብዙውን ጊዜ ከያህዌ ክብር ጋር የሚያያዘውን ድምቀት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ይህም ማለት 1) የያህዌ ክብር ድምቀት እንደ መብረቅ ብርሃን ነው ወይም 2) የያህዌ ክብር ድምቀት እንደ ፀሐይ መውጣት ነው ማለት ሊሆን ይችላል።

ሁለት ጨረሮች ከእጁ ወጡ

የመብረቁ ድምቀት ያህዌ በእጁ የሚይዛቸው ሁለት የጨረር መሣሪያዎች እንደ ሆኑ ዕንባቆም ይናገራል

ኀይሉም በዚያ ተሰውሮአል

‹‹በዚያ›› የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን እጅ ነው። ይህም ማለት፣ 1) ዕንባቆም ማየት የቻለው የመብረቅ ብልጭታዎች በያህዌ እጅ ውስጥ የተሰወረው ኀይል ሙላት አነስተኛ መገለጫ ነው፤ ወይም 2) ሊጠቀምበት ዝግጁ እስኪሆን ደረስ ያህዌ ኀይሉን እጁ ውስጥ ይሰውራል ማለት ሊሆን ይችላል።

Habakkuk 3:6

አጠቃላይ መረጃ

ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጽ ቀጥሏል።

ቆመ

ይህ ማለት ያህዌ መራመዱን አቁሞ ቀጥ ብሎ ቆመ ማለት እንጂ፣ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ቆመ ማለት አይደለም

ምድርን ለካ/መዘነ

ይህም ማለት 1) ‹‹ለካ/መዘነ›› የሚለው፣ ‹‹አናወጠ›› ተብሎ ሊተረጐም ይችላል ወይም 2) አንድ ድል አድራጊ ሰው ለባለ ሥልጣኖቹ ከማከፋፈሉ በፊት ምድሪቱን ተዘዋውሮ እንደሚያይ አሰሰ ማለት ሊሆን ይችላል።

የዘላለም ተራሮች... የጥንት ኮረብቶች

‹‹ዘመን ከመቆጠሩ በፊት የነበሩ ተራሮች… እስከ ዘመን ፍጻሜ ድረስ የሚዘልቁ ኮረብቶች›› የምትጠቀምበት ቋንቋ፣ ‹‹ኮረብቶች›› እና፣ ‹‹ተራሮች›› ወይም ‹‹ዘላለም›› እና ‹‹የጥንት›› ለተሰኙት የተለየ ቃሎች ከሌሉት UDB ላይ እንደ ተደረገው በአንድነት ልታያይዛቸው ትችላለህ።

የዘላለም ተራሮች ተፈረካከሱ

አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የዘላለም ተራሮች እንኳ ፈራረሱ›› ወይም፣ ‹‹የዘላለም ተራሮችን እንኳ ፈረካከሰ››

የጥንት ኮረብቶች ዝቅ አሉ

በያህዌ ፊት ዝቅ ብለው የሚሰግዱ ይመስል፣ የጥንት ኮረብቶችም እንደ ሌላው መሬት ደልዳላ ሆኑ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹የጥንት ኮረብቶች ተናዱ››

መንገዱ ዘላለማዊ ነው

‹‹መንገድ›› ለሚለው አማራጭ ትርጕም፣ 1) ስለ ያህዌና ስለ ሥራው የሚናገር ምሳሌያዊ አገላለጽ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹እርሱ ዘላለማዊ ነው›› ወይም 2) ዕንባቆም በራእዩ ያህዌ ሲመላለስ ማየቱን አመልካች ሊሆን ይችላል፤ በጥንት ጊዜ ያህዌ በዚሁ መንገድ ሲመላለስ መኖሩንም ያሳያል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በጥንቱ መንገድ ተመላለሰ››

Habakkuk 3:7

አጠቃላይ መረጃ

ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጹን ቀጥሏል።

የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ፣ የምድያምም መኖሪያዎች ሲታወኩ አየሁ

አማራጭ ትርጕሞቹ፣ 1) ‹‹ድንኳን›› እና፣ ‹‹መኖሪያ›› የተሰኙ ቃሎች በእነዚህ ድንኳኖች የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በኢትዮጵያ ድንኳኖች የሚኖሩ ሰዎች ሲጨነቁ፣ በምድያም ምድር በድንኳኖች የሚኖሩ ሰዎች ሲታወኩ አየሁ›› ወይም 2) ድንኳኖቹ በመከራ የሚናወጡ ሰዎች የሆኑ ይመስል፣ ምናልባት እዚህም ላይ ዕንባቆም በኢትዮጵያና በምድያም ያሉ ድንኳኖች በማዕበል መናወጣቸውን ማመልከቱ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹መከራ ውስጥ እንዳሉ ሰዎች የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ፣ የምድያም ምድር ድንኳኖችም እንደ ሰዎች ሲታወኩ አየሁ።››

ኩሻዊ

ይህ ቃል፣ 1) በእርግጠኝነት የማይታወቅ ሕዝብ መጠሪያ ወይም 2) ኩሽ እንደ ማለት ይሆናል።

በፈረሶችህና በድል አድራጊ ሠረገሎችህ በጋለብህ ጊዜ

‹‹ፈረሶችህ›› እና፣ ‹‹ድል አድራጊ ሠረገሎችህ›› የሚሉት ሐረጐች ስለ ተመሳሳይ ነገር ያመለክታሉ። ይህም ያህዌ በፈረሶችህ በሚጐተት ሠረገላ ወደ ጦር ሜዳ እንደሚገባ ጦረኛ መሆኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹በፈረሶች በሚጐተት ሠረገላህ ወደ ድል ጋለብህ››

Habakkuk 3:9

አጠቃላይ መመሪያ

ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጹን ቀጥሏል።

ቀስትህን ከማኅደሪያው አወጣው

ይህ ማለት ያህዌ ቀስቱን ከማኅደሩ አወጥቶ ለማስፈንጠር መዘጋጀቱን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ቀስትህን ለማስፈንጠር ተዘጋጅህ

ምድርን በወንዞች ከፈልህ

ይህም ማለት፣ 1) ‹‹በሚያልፉበት ቦታ ምድርን የሚከፍሉ ወንዞች ፈጠርህ›› ወይም 2) ‹‹ምድርን ከፈልህ፤ ወንዞችም ፈሰሱ›› ማለት ሊሆን ይችላል።

ተራሮች አዩህ፤ ተጨነቁም

የያህዌ መገለጥ ተራሮቹ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ በስቃይ እንደ ተጨነቁ ሰዎች እንዳደረጋቸው ተነግሮአል። ይህ ተራሮቹ በምድር መንቀጥቀጥ መናወጣቸውን ወይም ከማዕበሉ የሚነሣው ውሃ ተራሮቹን መሸርሸሩን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

የውሃ ሞገድ ዐልፎ ሄደ

ይህም ማለት፣ 1) የዝናብ ወጀብ ተራቶች ላይ ወረደ ወይም 2) ዝናቡ ተራሮች ላይ የሚፈሱ ታላላቅ ጅረቶች ፈጠረ›› ማለት ሊሆን ይችላል

ቀላዩ ደነፋ

ነፋሱና ማዕበሉ በላዩ ሲያልፉ ባሕሩ ያሰማው ታላቅ ድምፅ፣ በከፍተኛ ድምፅ እንደሚደነፋ ሰው ዐይነት ነበር። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ጥልቁ ባሕር ጮኸ››

ማዕበሉንም ወደ ላይ አነሣ

ባሕሩ ውስጥ ያለው ውሃ ወደ ላይ መነሣትና ነፋሱ ባሕሩ ላይ ያስነሣው ማዕበል፣ ነፋሱ እንደ ሰው ማዕበሉን ወደ ላይ ማንሣቱን ያመለክታል።

Habakkuk 3:11

አጠቃላይ መረጃ

ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጹን ቀጥሏል

ፀሐይና ጨረቃም በቦታቸው ቆሙ

ፀሐይና ጨረቃ ጒዞአቸውን እንዳቆሙ ሰዎች እነርሱም በሰማይ ላይ መጓዛቸውን እንዳቆሙ ይናገራል። አማራጭ ትርጕም፣ ‹‹ፀሐይና ጨረቃ መንቀሳቀሳቸውን አቆሙ››

በቦታቸው

‹‹በሰማይ››

ከሚወረወሩ ፍላጾችህ፣ ከሚያብረቀርቅ የጦርህ ነጸብራቅ

እነዚህ ሁለት ሐረጐች አንድ ዐይነት ትርጕም አላቸው፤ ፀሐይና ጨረቃ የቆሙት ለምን እንደ ነበረም ይናገራሉ። ሰማይ ላይ የሚታየው የመብረቅ ብልጭታ ያህዌ ከቀስቱ የሚያስፈነጥራቸው ፍላጻዎች ወይም ሰማይ ላይ እንደሚወረወር አብረቅራቂ ጦር እንደ ነበር ይናገራል።

ከሚወረወሩ ፍላጾችህ

‹‹የሚወረወሩ ፍላጾችህ ነጸብራቅ››

መዓት

ግፍ የደረሰበት ሰው ቁጣ

ሕዝቦችን ረገጥሃቸው

ያህዌ ሕዝቦችን መቅጣቱ እነርሱን መርገጥ ማለት እንደ ሆነ ተነግሮአል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ረገጥሃቸው የሚለው ገለባውን ከእህል ለመለየት በሬዎች ወይም ሌሎች እንስሶች እህል ላይ የሚረማመዱበትን ሁኔታ ያመለክታል።
Habakkuk 3:13
አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጹን ቀጥሏል። በዚህ ቁጥር ያለውን የመጨረሻ ዐረፍተ ነገር ለመተርጐም ያስቸግራል። ይህን ለመተርጐም ከታች ባሉ ዐረፍተ ነገሮች ያሉትን እያንዳንዱን የትርጉም ማስታወሻዎች ተመልከት።
ሕዝብህን ለመታደግ… ወጣህ
‹‹ለመታደግ›› የሚለውን ግሥ ማድረግ ቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝብህን ለማዳን ወጣህ››
የቀባኸውንም ለማዳን
‹‹አንተ የቀባኸውን›› ይህ ሐረግ ያህዌ የመረጠውን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉሙ፣ 1) ‹‹አንተ የመረጥኸውን ሕዝብ›› ወይም፣ ‹‹አንተ የመረጥኸውን መንግሥት›› ወይም 2) ‹‹አንተ የመረጥኸውን ንጉሥ››
የክፋትን ቤት ራስ ቀጠቀጥህ፤ ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩም ዕርቃኑን አስቀረኸው
ይህም ማለት 1) መሪን መግደልና ሕዝቡን ማጥፋት ቤትን እንደ ማፍረስ መሆኑን ያሳያል። እዚህ ላይ መሪው ራስ ማለትም የቤቱ ጣራ ሲሆን፣ ‹‹እግር ጥፍር›› እና፣ ‹‹አንገት›› የቀረው የቤቱ አካል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዐመፅን ቤት ጣራ አፈረስህ፤ የቀረውንም የቤቱን አካል አወደምህ›› ወይም፣ ‹‹የዐመፅ መንግሥትን መሪ ገደልህ፤ መንግሥቱንም ፈጽሞ ደመሰስህ›› ወይም 2) መሪውን መግደልና ከሕዝቡም ክብርንና ኀይልን ማስወገድ የሰውን ራስ እንደ ማፍረስና ልብሱን መግፈፍ ማለት እንደ ሆነ ተነግሯል። እዚህ ላይ መሪው፣ ‹‹ራስ ሲሆን፣ ‹‹ቤት›› ደግሞ አካል የሆኑ ሰዎች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ክፉ ሕዝብና መሪያቸው ራሱን እንዳፈረስኸው፣ ከእግሩ እስከ አንገቱ ዕርቃኑን እንዳስቀረኸው ሰው ናቸው›› ወይም፣ ‹‹የዐመፀኛ ሕዝብን መሪ ገደልህ፤ የሕዝቡንም ኀይል ፈጽመህ አስወገድህ››
Habakkuk 3:14
አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም የያህዌን ራእይ መግለጹን ቀጥሏል።
የሰራዊት አለቃ ራስ፣ በገዛ ጦሩ ወጋህ
ይህ የሚናገረው ስለ ከለዳውያን መሪ ነው። ይህም ማለት፣ 1) ጦረኞቹ አካል ሲሆኑ፣ መሪው ደግሞ ራስ መሆኑን የሚያሳይ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጦረኞቹን የሚመራውን በገዛ ራሱ ጦር ወጋህ›› ወይም 2) ‹‹ራስ›› የሚለው ቃል የእያንዳንዱን ጦረኛ ራስ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በመሪው ጦር የእያንዳንዱን ጦረኛ ራስ ወጋህ››
እንደ ዐውሎ ነፋስ… የመጣውን
የእስራኤልን ሕዝብ ሲያጠቁ የከለዳውያን ኀይልና ፍጥነት በድንገት ከሚመጣ ዐውሎ ነፋስ ጋር ተነጻጽሮአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ ማዕበል ፈጥነው ይመጣሉ››
ምስኪኑን በስውር በመዋጥ የሚደሰተውን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ደስታ›› የሚለው በክፉ ሥራ ደስ መሰኘት ሲሆን፣ ግሥ አድርጐ መተርጐም ይቻላል። ጦረኞቹ ሕዝቡ ላይ ጭካኔ መፈጸማቸውና መግደላቸው፣ በስውር በማድባት ንጥቂያቸውን እንደሚውጡ አራዊት ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በስውር ሕዝብን እንደሚወጡ አራዊት ደስ ይላቸዋል›› ወይም፣ ‹‹ድኾችን ሲጨቆኑ ደስ ይላቸዋል፤ ንጥቂያውን ዋሻው ውስጥ እንደሚበላ አውሬም ይበሏቸዋል››
ታላላቅ ውሆችን ከመርህ
ያህዌ ውሆችን ማናወጡ ውሆችን ከመከመር ጋር ተመሳስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ታላላቅ ውሆችን ከመርህ››
Habakkuk 3:16
አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም በያህዌ ራእይ የተሰማውን መግለጹን ቀጥሏል።
እኔ ሰማሁ
ምናልባትም ዕንባቆም የሰማውን መግለጽ ትችላለህ። ይህም ማለት፣ 1) ‹‹በዚያ ራእይ ማንኛውንም ነገር ሰማሁ›› ወይም 2) ‹‹ያህዌ እንደ ታላቅ ዐውሎ ነፋስ ሲመጣ ሰማሁ›› ማለት ሊሆን ይችላል።
ልቤም ደነገጠብኝ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልቤ›› የሚለው፣ ‹‹ሆዴ›› ማለትም ይሆናል። የምትናገረው ቋንቋ ታላቅ ፍርሃትን ለመግለጽ የሚጠቀምበት ውስጠኛ የአካል ክፍል ካለው በዚያ መጠቀም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የልቤ ምት ፈጠነ›› ወይም፣ ‹‹ሆድ ዕቃዬ ተገላበጠ››
ከንፈሬ ከድምፁ የተነሣ ተንቀጠቀጠ
የከንፈር መንቀጥቀጥ ከታላቅ ፍርሃት ጋር የሚመጣ ሌላው ድንገተኛ ምላሽ ነው።
ፍርሃት እስከ ዐጥንቴ ዘልቆ ገባ
ዕንባቆም የተሰማውን ደካማነት ፍርሃት ወደ ዐጥንቱ ዘልቆ ከመግባት ጋር አስመስሎታል። እዚህ ላይ በቋንቋህ ያለውን ፈሊጣዊ አነጋገር መጠቀም ትችላለህ
እግሬም ተብረከረከ
‹‹እግሬ›› የሚለው ከበታቹ ያለውን ነገር ያመለክታል። ይህም ማለት፣ 1) ‹‹እግሬ ተንቀጠቀጠ›› ወይም 2) ‹‹በቆምሁበት ተንቀጠቀጥሁ›› ማለት ሊሆን ይችላል።
Habakkuk 3:17
አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም በያህዌ ራእይ የተሰማውን መግለጽ ቀጥሏል
የወይራ ዛፍ ፍሬ ባይሰጥ
‹‹የወይራ ዛፍ ባያፈራ›› ወይም፣ ‹‹የወይራ ዛፍ ፍሬ ቢነፍግም››
የበጐች ጉረኖ እንኳ ባዶውን ቢቀር
‹‹ጉረኖ›› የበጐችና የፍየሎች መኖሪያን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጐች ሁሉ ቢሞቱ፤ ጉረኖውም ባዶውን ቢቀር››
Habakkuk 3:18
አጠቃላይ መረጃ
ዕንባቆም በያህዌ ራእይ የተሰማውን መግለጽ ቀጥሏል፤ እርሱን ለማመስገንም ወስኖአል።
የድነቴ አምላክ
‹‹ድነት›› የሚለውን ግሥ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሚያድነኝ አምላክ››
እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል፤ በከፍታዎችም ላይ ያስሄደኛል
ያህዌ እንደሚጠብቀውና በአስቸጋሪ ዘመን ውስጥ ማለፍ እንደሚስችለው ለማሳየት ዕንባቆም ድንጋያማና አደገኛውን ተራራ በቀላሉ መውጣት እንደሚችል የዋላ እግር እንደሚያደርገው ይናገራል።

---

Chapter 1
Zephaniah 1:1
አጠቃላይ መረጃ:- የመጣው የያህዌ ቃል
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ከእግዚአብሔር የመጣ ጠቃሚ መልእክት ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልእክት ሰጠ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይህን መልእክት ተናገረ››
ያህዌ
ይህ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለሕዝቡ የገለጠው የእግዚብሔር ስም ነው። ይህን እንዴት እንደምትተረጉም፤ ስለ ያህዌ ከቃላት ትርጉም ገጽ ተመልከት።
የጐዶልያስ ልጅ፤ የአማርያ ልጅ፤ የሕዝቅያስ ልጅ
ይህ የሶፎንያስ ዘሮች ዝርዝር ነው። ይህ ‹‹የ… ልጅ›› የሚለው ሐረግ ሰፋ ባለ መልኩ፣ ‹‹…ትውልድ›› ማለት ነው። እዚህ ላይ፣ ‹‹ሕዝቅያስ›› የሚለው ንጉሥ ሕዝቅያስን ያመለክታል። ይህን በጣም ግልጽ ማድረግ ይቻላል፤ ‹‹ከሕዝቅያስ የተወለደው የአማርያ የልጅ ልጅ ልጅ የጐዶልያስ ልጅ።››
ማንኛውንም ነገር ከምድር ላይ አጠፋለሁ… ሰውን ከምድር ገጽ በማስወግድበት ጊዜ
‹‹ማንኛውም ነገር›› እና ‹‹ሰውን ከምድር በማስወገድበት ጊዜ›› የተሰኙ ቃሎች ምን ያህል በሰዎች ኀጢአት መቆጣቱን ለማሳየት ሆን ብሎ ያህዌ የተጠቀመባቸው ናቸው። ያህዌ ንስሐ የማያደርጉ ኀጢአተኞችንና ሕይወት ያላቸው ነገሮችን ሁሉ ያጠፋል።
ከምድረ ገጽ ማንኛውንም ነገር ማጥፋት
‹‹በመላው ምድር ላይ ያለውን ማንኛውንም ነገር ማጥፋት››
ይህ የያህዌ ቃል ነው
የተናገረው በእርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በማንሣት ስለ ራሱ ይናገራል። ‹‹ያህዌ እንዲህ አለ›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ።››
ሰውንና እንስሳን
‹‹ሕዝብንና እንስሳን››
ማጥፋት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተቃራራቢ ትርጉሙ 1) ከፍርዱ በኃላ የሚቀረውን የፍርስራሽ ክምር ወይም 2) ያህዌ የሚያጠፋቸው ጣዖቶችን ሊያመለክት ችላል።
መቁረጥ
ስለ ማጥፋት ሲናገር አንድ ነገር ከአካሉ ቆርጦ ስለ መጣል ይናገራል።
‹‹ማስወገድ››
Zephaniah 1:4
አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥2-18 የያህዌን ፍርድ ያመለክታል። ቁጥር 1፥4-16 ያህዌ የይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚያመጣውን ፍርድ ያመለክታል።
እጄን በይሁዳ ላይ… አነሣለሁ
ይህ እግዚአብሔር እንደሚቀጣ የሚያመለክት ፈሊጥ ነው። ‹‹ይሁዳን እቀጣለሁ››
የበአልን ትሩፍ፣ የጣዖታቱንና የአመንዝራ ካህናቱን ስም… በሰገነት ላይ ወጥተው የሚሰግዱትን…
የሚሰግዱትንና የሚምሉትን… አጠፋለሁ
‹‹አጠፋለሁ›› የሚለው ግሥ የሚያመለከተው እነዚህን ሐረጐች ሁሉ ቢሆንም፣ ድግግሞሽን ለማስወገድ ሲባል ጥቅም ላይ የዋለው አንዴ ብቻ ነው። ‹‹የበአልን ትሩፍ፣ የጣዖታቱንና የአመንዝራ ካህናቱን ስም… በሰገንት ላይ ወጥተው የሚሰግዱትን… የሚሰግዱትንና የሚምሉትን… አጠፋለሁ››
መቁረጥ
ማጥፋት አንድን ነገር ከአካሉ ቆርጦ መጣል ማለት እንደ ሆነ ተነግሮአል። ሶፎንያስ 1፥3 ላይ ይህን እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። ‹‹ማስወገድ››
የአመንዝራ ካህናቱን ስም ሁሉ ከዚህ ስፍራ አጠፋለሁ።
እዚህ ላይ ስማቸውን አጠፋለሁ ሲባል ሰዎች እንዲረሷቸው አደርጋለሁ ማለት ነው። ‹‹ጣዖት የሚያመልኩትን ካህናት ሰዎች ሁሉ እንዲረሷቸው አደርጋለሁ››
በንጉሣቸው
‹‹በሚልኮምም›› ለሚለው አማራጭ ትርጉም ለማግኘት የግርጌ ማስታወሻውን ተመልከት።
ያህዌን አልፈለጉም፤ እንዲመራቸውም አልጠየቁም
ያህዌን መፈለግ 1) ከእግዚአብሔር ርዳታ መለመን ወይም 2) ስለ እግዚአብሔር ማሰብና ለእርሱ መታዘዝን ያመለክታል። ስለ ያህዌ አላሰቡም ወይም እንዲመራቸው አልለመኑም።
Zephaniah 1:7
አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥2-18 የያህዌን ፍርድ ያመለክታል። ቁጥር 1፥4-16 በይሁዳ ሕዝብ ላይ የያህዌን ፍርድ ያሳያል።
አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥8-13 ላይ ያህዌ ሲናገር እንመለከታለን። ስለ ራሱ ሲናገር በመጀመሪያና በሦስተኛ ሰው ይጠቀማል።
ዝም በሉ
ይህ ፈሊጣዊ ንግግር ነው። እዚህ ላይ ዝምታ የድንጋጤና የመደነቅ ምልክት ነው። ‹‹ደንግጡ››
ያህዌ መሥዋዕት አዘጋጅቶአል፤ እንግዶቹንም ቀድሶአል
የይሁዳ ሰዎች እንደ ያህዌ መሥዋዕት ጠላት የሆኑት ሕዝብ መሥዋዕቱን እንደሚበሉ የእርሱ እንግዶች ተገልጠዋል። በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ ይህ፣ ‹‹ያህዌ የይሁዳን ሕዝብ እንደ መሥዋዕት አዘጋጅቶአል፤ ጠላት የሆኑትን ሕዝብ በእንግድነት ጠርቷል›› ሊባል ይችላል።
እንግዶቹንም ቀድሶአል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ቀድሶአል›› ወደ ግብዣ ጠርቷል ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጣዊ ንግግር ነው።
አዘጋጅቶአል
ይህ ቃል ይሁዳ ላይ የያህዌ ፍርድ የሚጀመርበትን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል።
እንግዳ ልብስ የሚለብሱትን ሁሉ
ለባሕላቸው ያላቸውን ፍቅርና ባዕዳን ጣዖቶቻቸውን ማምለካቸውን ለማሳየት እስራኤላውያን ከባዕዳን ጋር የሚመሳሰል ልብስ መልበሳቸውን የሚያመለክት ሐረግ ነው። ‹‹ባዕዳን ጣዖታትን የሚያመልኩ ሁሉ››
በዚያን ቀን
‹‹በያህዌ ቀን››
በመድረኩ ላይ የሚዘሉትን ሁሉ
አማራጭ ትርጉሞቹ፣ 1) ይህ ዳጎን የሚባለውን ለማምለክ መድረኩ ላይ የዘለሉትን ሰዎች የሚያመለክት ነው፤ ወይም 2) የአረማውያንን አማልክት ለማምለክ መድረኩ ላይ የዘለሉትን ሰዎች ያመለክታል፤ ወይም 3) ወደ ዙፋን የወጡ ንጉሣውያን ባለ ሥልጣኖች ያመለክታል።
የአማልክቶቻቸውን ቤት በዐመፅና በማጭበርበር የሚሞሉትን እቀጣለሁ
‹‹ዐመፅ›› እና ‹‹ማጭበርበር›› የተሰኙት ድርጊትን ያመለክታሉ። ‹‹ዐመፅ የሚያደርጉና በአማልክቶቻቸው ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚዋሹትን እቀጣለሁ።››
Zephaniah 1:10
አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥2-18 የያህዌን ፍርድ ያመላክታሉ። ቁጥር 1፥4-16 በይሁዳ ላይ የያህዌን ፍርድ ያመለክታሉ።
አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥8-13 ላይ ያህዌ ይናገራል። የሚናገረው የመጀመሪያ መጠሪያን በመጠቀምና ስለ ራሱ በሦስተኛ መጠሪያ በመናገር ነው።
በዚያን ቀን
‹‹የያህዌ ቀን›› ሶፎንያስ 1፥9 የተረጐምህበትን ሁኔታ ተመልከት።
የያህዌ አነጋገር
እየተናገረ ያለው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ‹‹ያህዌ የተናገረው›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ በመሐላ የተናገረው››
የዓሣ በር
የዓሣ በር በኢየሩሳሌም ከተማ ግንብ ከነበሩ በሮች አንዱ ነው።
በሁለተኛው አደባባይ ዋይታ
‹‹በሁለተኛው አደባባይ… ዋይ በሉ።›› ‹‹ሁለተኛው በር›› አዲሱ የኢየሩሳሌም ክፍል ነው።
ታላቅ ሽብር ይሰማል
ይህ የሚያመለክተው ግንቡ ሲወድቅ የሚሰማውን ጩኸት ነው። ይህን፣ ‹‹ግንቡ ሲወድቅ የሚኖረው ታላቅ ድምፅ›› በማለት መተርጐም ይቻላል።
ከኮረብቶችም
ይህ የሚናገረው ኢየሩሳሌም ዙሪያ ስላሉት ኮረብቶች ነው።
ነጋዴዎቻችሁ ሁሉ ይደመሰሳሉ፤ በብር የሚነግዱትም ሁሉ ይሞታሉ።
እነዚህ ሁለት ሐረጐች የሚናገሩት ስለ አንድ ሕዝብ ሲሆን፣ ንግዳቸው እንደሚጠፋ አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ ውለዋል። ‹‹ዕቃዎችን የሚገዙና የሚሸጡ ይገደላሉ።››
በብር የሚነግዱ
ይህ የሚመለከተው ነጋዴዎችን ነው። ሳንቲሞች ከመሠራታቸው በፊት ለገዙት ዕቃ ለመክፈል ሰዎች ብርና ወርቅ ይመዝኑ ነበር።
ይደመሰሳሉ
አንድን ነገር ከአካሉ ቆርጦ መጣልን በሚያመለክት ሁኔታ ይደመሰሳሉ በሚለው ቃል ተጠቅሞአል። ይህን ሶፎንያስ 1፥3 ላይ ከተረጐምህበት ሁኔታ ተመልከት። ‹‹አጠፋለሁ››
Zephaniah 1:12
አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥2-18 ስለ ያህዌ ፍርድ ይናገራል። ቁጥር 1፥4-16 የይሁዳ ሕዝብ ላይ ስለሚመጣው የያህዌ ፍርድ ይናገራል።
አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 1፥8-13 ላይ ያህዌ ይናገራል። የሚናገረው የመጀመሪያ መጠሪያ በመጠቀምና ስለ ራሱ በሦስተኛ መጠሪያ በመጠቀም ነው።
በዚያ ዘመን ይሆናል
ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው ኢየሩሳሌም በጠላቶቿ የተደመሰሰችበትን ጊዜ ለማመልከት ነው።
ኢየሩሳሌምን በመብራት እፈትሻለሁ
መብራት አብርቶ የሚያያቸው ይመስል ያህዌ ስለ ኢየሩሳሌም ሰዎች ሁሉ እንደሚያውቅ ያህዌ ይናገራል።
በዝቃጭ ላይ እንደ ቀረ የወይን ጠጅ የሆኑትን
ከመከራ ሁሉ ያረፉ ይመስላቸዋል።
‹ክፉም ሆነ መልካም ያህዌ ምንም አያደርግም› ይላሉ
ይህን ቀጥተኛ ጥቅስ፣ ‹‹በልባቸውም ክፉም ሆነ መልካም ያህዌ ምንም አያደርግም›› በማለት ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል።
በልባቸው… ይላሉ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር እንዲህ በማለት ያስባሉ ማለት ነው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ክፉም ሆነ መልካም ያህዌ ምንም አያደርግም
እዚህ ላይ፣ ‹‹ክፉም ሆነ መልካም›› ሲል በመካከል ያሉትን ሁሉ ይጨምራል። ‹‹እግዚአብሔር ምንም አያደርግም››
ሙሉ በሙሉ ይደመሰሳል
‹‹ምንም የሚቀር የለም››
Zephaniah 1:14
አጠቃላይ መረጃ
ሶፎንያስ 1፥2-18 የያህዌን ፍርድ ያመለክታል። ቁጥር 1፥4-16 በይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚመጣውን የያህዌ ፍርድ ያመለክታል።
ቅርብ ነው፤ ቅርብ ነው፤ ፈጥኖም ይመጣል
‹‹ቅርብ›› የሚለው ቃል መደጋገምና፣ ‹‹ፈጥኖም ይመጣል›› የሚለው ሐረግ ያህዌ ሕዝቡ ላይ የሚፈርደው በቅርቡ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል። ‹‹ሳይውል ሳያድር ቶሎ ይሆናል››
የያህዌ ቀን
ሶፎንያስ 1፥7 የተረጐምህበትን ሁኔታ ተመልከት።
ጦረኛው ምርር ብሎ ይጮኻል
አማራጭ ትርጉሙ 1) ተስፋ በመቁረጥ የሚጮኽ ወታደር፤ ወይም 2) የወታደር የጦርነት ጩኸት ሊሆን ይችላል።
ያ ቀን… ቀን
እነዚህ ቃሎች ቁጥር 14 ላይ ያለውን፣ ‹‹የያህዌ ቀን›› ያመለክታሉ።
ያ ቀን የመዓት ቀን የዉጊያ ቀን
ቁጥር 15-16 በአንድነት ሆነው ስለዚህ የመጨረሻ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚያስከትለው ከባድ ጥፋት አጽንዖት የሚሰጡ የተለያዩ የአነጋገር መንገዶች አሉት።
የመከራና የጭንቀት ቀን
‹‹መከራ›› እና ‹‹ጭንቀት›› የተሰኙት ቃሎች የሚያመለክቱት ስለ ተመሳሳይ ነገር ቢሆንም፣ ስለ ሕዝቡ ጭንቀት ከባድ መሆን አጽንዖት ይሰጣሉ። ‹‹ሰዎች ከባድ ጭንቀት ውስጥ የሚሆኑበት ቀን››
የሁከትና የጥፋት ቀን
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሁከት›› የሚያመለክተው መለኮታዊ ፍርድን ነው። ‹‹ጥፋት›› የሚለው ቃል የዚያን ፍርድ ውጤት ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አውዳሚ የሁከት ቀን›› ወይም፣ ‹‹አውዳሚ ፍርድ››
የጨለማና የጭጋግ ቀን
‹‹ጨለማ›› እና ‹‹ጭጋግ›› ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ የጨለማውን ከባድነት ያመለክታል። ሁለቱም የሚያመለክቱት የጥፋት ወይም የመለኮታዊ ፍርድን ጊዜ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጨለማ የዋጠው ቀን›› ወይም ‹‹አስፈሪ የፍርድ ቀን››
የደመናና የድቅድቅ ጨለማ ቀን
ይህኛውም የሚናገረው ስለ ተመሳሳይ ሁኔታ ሲሆን፣ ቀደም ሲል የነበረውን ሐረግ ሐሳብ ያጠናክራል። ‹‹ደመና›› እና፣ ‹‹ድቅድቅ ጨለማ›› የተሰኙትን የመሳሰሉ ሐረጎች መለኮታዊ ፍርድን ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጥቁር ደመና የሞላበት ቀን››
የመለከት ድምፅና የጦርነት ጩኸት የሚሰማበት ቀን
‹‹መለከት›› እና፣ ‹‹የጦርነት ጩኸት›› የተሰኙት ቃሎች እዚህ ላይ የሚያሳዩት ተመሳሳይ ነገርን ነው። ሁለቱም ወታደሮች ለጦርነት እንዲዘጋጁ መጥሪያ መንገዶች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች የጦርነት ጥሪ የሚያሰሙበት ቀን››
በተመሸጉ ከተሞችና በረጃጅም ግንቦች ላይ
ሁለቱም ሐረጐች የሚያመለክቱት ወታደራዊ ምሽጐችን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሚገባ የተመሸጉ ከተሞች››
Zephaniah 1:17
አጠቃላይ መረጃ
1፥2-18 የያህዌን ፍርድ ያመለክታል። 1፥17-18 በእያንዳንዱ ኀጢአተኛ ላይ ወደ ፊት የሚመጣውን የመጨረሻ የያህዌ ፍርድ ያመለክታል።
እንደ ዕውር እንዲራመዱ
ከያህዌ ፍርድ የተነሣ ሰዎች ግራ ይጋባሉ፤ እነርሱ ሲራመዱ የሚመለከቱ ሰዎች ዕውር እንደ ሆኑ ያስባሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ዐይናቸው እንደ ታወረ ሰዎች ግራ በመጋባት ይመላለሳሉ››
ደማቸው እንደ ትቢያ ይፈስሳል
የሚፈሰሰው ደማቸው እንደ ትቢያ ዋጋ ቢስ ነው። ይህን፣ ‹‹የሚፈስሰው ደማቸውን ጠላቶቻቸው እንደ ትቢያ ይቆጥሩታል›› በማለት መተርጐም ይቻላል።
ሥጋቸውም እንደ ጉድፍ ይጣላል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ይፈስሳል›› የሚለው ግልጽ ሆኗል። ይህን፣ ‹‹ጠላቶቻቸው ሥጋቸውን ይቆርጣሉ፤ እንደ ጉድፍ እንዲበሰብስም ያደርጋሉ›› በማለት መተርጐም ይቻላል።
የቅንዓቱ እሳት
‹‹እሳት›› የያህዌን ቁጣ ከባድነት ያመለክታል። ይህን፣ ‹‹ቅንዓቱ እንደ ታላቅ እሳት ነው›› በማለት መተርጐም ይቻላል።
በምድር በሚኖሩ ሁሉ ላይ
ይህ የሚያመለክተው ዐመፀኞችን መሆኑ ግልጽ ነው። ይህንን፣ ‹‹በምድር የሚኖሩ ዐመፀኞች ሁሉ›› በማለት የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።

Chapter 2
Zephaniah 2:1
አጠቃላይ መረጃ
2፥1-3 ላይ ያህዌ ለይሁዳ መናገሩን ቀጥሏል፤ ንስሐ እንዲገቡ ይነግራቸዋል።
በአንድነት ተሰብሰቡ
እነዚህ ሁለት ቃሎች ተመሳሳይ ናቸው። በኀጢአታቸው ንስሐ ለመግባት ሰዎች በአንድነት እንዲሰበሰቡ የተሰጠውን ትእዛዝ ያጠናክራሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁላችሁም በአንድነት ተሰብሰቡ››
እፍረት የሌላችሁ ሕዝብ
ሕዝቡ በኀጢአታቸው አላዘኑም
የተወሰነው ጊዜ ሳይደርስ
ይህ ያህዌ በወሰነው ጊዜ የሚመጣውን ቅጣት ነው የሚያመለክተው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እናንተን ከመቅጣቱ በፊት››
ያ ቀን… የያህዌ ጽኑ ቁጣ… የያህዌ የመዐት ቀን
እነዚህ ሐረጐች ሁሉም የሚያመለክቱት፣ ‹‹የያህዌ ቀን››ን ነው። እነዚህን ሐረጐች ሶፎንያስ 1፥7-9 ላይ ተመሳሳይ ሐረጐችን በተረጐምህበት ሁኔታ ተርጉማቸው።
ቀኑ እንደ ገለባ ሳይጠራረጋችሁ
ገለባ ነፋስ ጠርጐ የሚወስደው የማያስፈልግ የፍሬው አካል ነው። በተመሳሳይ መንገድ የፍርድ ቀን ቶሎ ይመጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ገለባ በነፋስ እንደሚጠረግ ያ ቀን በፍጥነት ይመጣል።
የያህዌ ጽኑ ቁጣ በእናንተ ላይ ሳይመጣ፤ የያህዌ የመዓት ቀን ሳይደርስባችሁ››
የያህዌ ፍርድ ምን ያህል ከባድ መሆኑን ለማመልከትና ሰዎች በአስቸኳይ ንስሐ እንዲገቡ አጽንዖት ለመስጠት ነቢዩ በጣም የሚመሳሰሉ ሐረጐች ተጠቅሟል።
የያህዌ ቁጣ
ይህ የእግዚአብሔርን ቅጣት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የያህዌ ቅጣት››
ያህዌን እሹ
ያህዌን መሻት፣ 1) የእግዚአብሔርን ርዳታ መለመንን ወይም 2) ስለ እግዚአብሔር ማሰብንና ለእርሱ መታዘዝን ይወክላል።
ጽድቅንና ትሕትናን ፈልጉ
‹‹ጽድቅ›› እና፣ ‹‹ትሕትና›› የተሰኙት ድርጊትን የሚያመለክቱ ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ትክክል የሆነውን ለማድረግና ትሑት ለመሆን ፈልጉ››
በያህዌ የቁጣ ቀን ትሰወሩ ይሆናል
ይህን፣ ‹‹በቁጣው ቀን ያህዌ ይሰውራችኋል›› በማለት መተርጐም ይቻላል።
Zephaniah 2:4
አጠቃላይ መረጃ
2፥4-15 ላይ ያህዌ በይሁዳ ዙሪያ ባሉ አገሮች ላይ ስለሚመጣው የእርሱ ፍርድ ይናገራል።
ጋዛ… አስቀሎና… አሽዶድ… አቃሮን
እነዚህ በዚያ ዘመን የነበሩ አራቱ የፍልስጥኤም ከተሞች ናቸው።
ባድማ ይሆናሉ… ይፈራርሳሉ
የእነዚህ ሁለት ሐረጐች ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን፣ እነዚህ ከተሞች ሙሉ በሙሉ እንደሚጠፉ አጽንዖት ይሰጣል።
አሽዶድ በቀትር ትባረራለች
እዚህ ላይ ‹‹እነርሱ›› የሚለው የፍልስጥኤማውያንን ጠላቶች ነው። ‹‹ቀትር›› ለሚለው አማራጭ ትርጉም፣ 1) ጠላቶች አሽዶድን ከቀትር በፊት ድል ያደርጓታል፤ ወይም 2) ሕዝቡ ዕረፍት ላይ እያሉና ምንም ሳያስቡ ጠላቶች አሽዶድን በቀትር ያጠቋታል የሚል ሊሆን ይችላል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አቃሮንም ትነቀላለች
የአቃሮን መሸነፍ ከመሬት ተነቅሎ በሚጣል ዛፍ ተመስሎአል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአቃሮንን ሰዎች ዛፍ ከሥሩ እንደሚነቀል ይነቅሏቸዋል›› ማለት ለሆን ይችላል፡፡
በባሕር ዳርቻ የምትኖሩ የከሊታውያን ሰዎች
የመጀመሪያው ሐረግ ከሊታውያን የሚኖሩበትን ይመለክታል፡፡
የፍልስጥኤማውያን ምድር ከነዓን
ፍልስጥኤማውያን ከከነዓን ከሚኖሩ ሕዝቦች አንዱ ነበሩ
ከነዋሪዎችሽም የሚተርፍ የለም
‹‹ምንም እስከማይተርፍ ደረስ›› - ይህ፣ ‹‹ነዋሪዎቿ ሁሉ ይሞታሉ›› ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፡፡
Zephaniah 2:6
አጠቃላይ መረጃ
2፥4-15 ላይ ያህዌ በይሁዳ ዙሪያ ባሉ አገሮች ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ይናገራል፡፡
በባሕሩ ዳር ያለው ምድር፣ የእረኞች መኖሪያና የበጐች በረት ይሆናል
ይህ የፍልስጥኤም ከተሞች ጠፍተዋል፣ አሁን ያለው ሜዳ ብቻ ነው ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የዕብራይስጡ ትርጉም ግልጽ ስላይደለ አንዳንድ የዘመኑ ትርጉሞች በተለያየ ሁኔታ ተርጉመውታል፡፡
የበጐች በረት
የበጐች በረት በጐቹን በአንድነት ለማኖር የተከለለ ትንሽ ቦታ ነው፡፡
ሕዝባቸው
‹‹የይሁዳ ሕዝብ››
ያርፋሉ
‹‹ለመተኛት ያርፋሉ››
Zephaniah 2:8
አጠቃላይ መረጃ
2፥4-15 ላይ ያህዌ በይሁዳ ዙሪያ ባሉ አገሮች ላይ ስለሚመጣው የእርሱ ፍርድ ይናገራል
ፌዝ... ስድብ
‹‹ፌዝ... ስድብ›› የተሰኙት ሁለት ሐረጐች የሚናገሩት ስለ አንድ ዐይነት ነገር ሲሆን፣ ሞዓብና አሞን ያህዌን መሳደባቸውን አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡
ድንበራቸውን አልፈዋል
ይህ የሚያመለክተው እነርሱን ለማጥቃት የይሁዳን ክልል መሻገራቸውን ሊሆን ይችላል
በሕያውነቴ
‹‹እኔ ሕያው እንደ መሆኔ›› ያህዌ በዚህ አገላለጽ የሚጠቀመው ቀጥሎ የሚናገረው ፍጹም እውነት መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡
ይህ የመሐላ ቃል ነው፡፡ ‹‹እጥብቄ እምላለሁ›› ይህ የሰራዊት ጌታ የእስራኤል አምላክ የያህዌ ቃል ነው
የሚናገረው እርግጠኛ መሆኑን ለማሳየት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ የእስራኤል አምላክ ያህዌ እንዲህ ይላል›› ወይም፣ ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ የእስራኤል አምላክ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››
እንደ ሰዶም... እንደ ገሞራ
እነዚህን ሁለት ከተሞች በጣም ዐመፀኞች ስለ ነበሩ ከሰማይ በወረደ እሳት አጥፍቶአቸዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ሙሉ በሙሉ መደምሰሳቸውን ነው፡፡ ይህን ግልጽ በሆነ ሁኔታ፣ ‹‹እንደ ሰዶም... እንደ ገሞራ ሙሉ በሙሉ አጥፍቶአቸዋል›› ብሎ መተርጐም ይቻላል፡፡
ዐረም እንደ ዋጠው እንደ ጨው ጉድጓድ
‹‹እሾህ የሞላበት የጨው ጉድጓድ›› ይህ የሚያመለክተው ጠፍና ጥቅም የሌለውን ምድር ነው፡፡
ከሕዝቤ የቀሩ... ከወገኔ የተረፉ
ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ሲሆን፣ እስራኤላውያን ከያህዌ ቅጣት እንደሚተርፉ ያመለክታሉ፡፡
Zephaniah 2:10
አጠቃላይ መረጃ
2፥4-15 ላይ ያህዌ በይሁዳ ዙሪያ ባሉ አገሮች ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ይናገራል፡፡
የያህዌን ሕዝብ ሰድበው ዝተውበታልና... እርሱም በምድሩ ያሉትን አማልክት ይዘልፋል፡፡
ያህዌ በፈሊጣዊ መንገድ ይናገራል፡፡ እነዚህን አማልክት ሲያገለግሉ የነበሩ ሰዎች የያህዌን ሕዝብ እንደ ሰደቡና እንደ ዛቱ ያህዌም እነዚህን ከንቱ አማልክት ይዘልፋል፡፡
Zephaniah 2:12
አጠቃላይ መረጃ
2፥14-15 ላይ ያህዌ በይሁዳ ዙሪያ ባሉ አገሮች ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ይናገራል፡፡
ኢትዮጵያውያን ሆይ፣ እናንተም በሰይፌ ትወጋላችሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹በሰይፌ ትወጋላችሁ›› ማለት በጦርነት ትገደላላችሁ ማለት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተ የኢትዮጵያ ሰዎች በጦርነት እንድትገደሉ አደርጋለሁ››
የእግዚአብሔር እጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› ኀይልን፣ ‹‹የእግዚአብሔር ኀይል››ን ያመለክታል፡፡
ፍጹም ባድማ
‹‹ባድማ›› ድርቀትን ያመለክታል፤ ‹‹የፈራረሰና የሚኖርበት የሌለ››
እንደ ምድረ በዳ ደረቅ
ይህ ማለት ምንም የማይበቅልበት ደረቅ ይሆናል ማለት ነው፡፡
የበግና የፍየል መንጋዎች
‹‹ማንኛውም ዐይነት እንስሳ››
ጉጉትና ጃርት
ምን ማለት እንደ ሆነ ግልጽ አይደለም፡፡
ከዝግባ የተሠሩ ተሸካሚዎች
ግንቡ ተንዶ ሲወድቅ ለጌጥና ድጋፍ እንዲሆኑ የተሠሩ ተሸካሚዎች ብዙውን ጊዜ ቆመው ይቀራሉ፡፡
ጩኸታቸው በየመስኮቱ ያስተጋባል
‹‹ከየመስኮቱ ጩኸት ይሰማል››
ግንዶች
ግንዶች ረጃጅምና ወፍራም እንጨቶች ሲሆኑ፣ ሕንፃውን ደግፈው ያቆማሉ፡፡
Zephaniah 2:15
አጠቃላይ መረጃ
2፥4-15 ላይ ያህል በይሁዳ ዙሪያ ባሉ አገሮች ላይ የሚመጣውን ፍርድ ይናገራል፡፡
ደስተኛዪቱ ከተማ
‹‹በራስዋ የምትኮራ ከተማ›› ይህ የሚያመለክተው ሶፎንያስ 2፥13 ላይ ያህዌ ስለ እርሷ መናገር የጀመረውን የነነዌን ከተማ ነው፡፡
በልቧ... ያለች
አባባሉ፣ ‹‹ለራስዋ አለች›› ወይም፣ ‹‹አሰበች›› ማለት ነው፡፡ ስለ ከተማዋ የሚናገረው መናገር እንደሚችል ሰው አድርጐ ነው፡፡ በዚያ ከተማ የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላል፡፡
እኔ ብቻ ነኝ ከእኔ በቀር ማንም የለም
እኔ ብቻ ነኝ ያለችበትን ምክንያት መግለጹ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ታላቋ ከተማ ነኝ፤ ከእኔ የሚወዳደር የለም››
አስፈሪ
‹‹ለማየት የሚያስፈራ ቦታ››
ያፌዙባታል እጃቸውንም በንቀት ያወዛውዙባታል
ፌዝ ጮኽ ያለ ድምፅ ነው፡፡ ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ሰዎች ነነዌ ላይ በጣም መቆጣታቸውን ነው፡፡

---

Chapter 3
Zephaniah 3:1
አጠቃላይ መረጃ
3፥1-5 ላይ ሶፎንያስ ለኀጢአተኞቹ የኢየሩሳሌም ሰዎች የያህዌን የፍርድ መልእክት ይናገራል፡፡ ከተማዋ ውስጧ የሚኖሩ ሰዎችን ትወክላለች፡፡ ይህን ግልጽ ለማድረግ፣ ‹‹እርሷ›› እና፣ ‹‹የእርሷ›› የሚለውን ነጠላ ቁጥር፣ ‹‹እነርሱ›› እና፣ ‹‹የእነርሱ›› በሚለው ብዙ ቁጥር መተካት ሊጠቅም ይችላል፡፡
ዐመፀኛዪቱ ከተማ
የዐመፃቸውን ምንነት መዘርዘር ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በእግዚአብሔር ላይ ያመፁ የከተማዪቱ ሰዎች››
ጨቋኛ ከተማ ረከሰች
‹‹የከተማዋ ሰዎች ጨቋኞች ሆኑ፤ ስለዚህም በፊቴ ረከሱ››
የእግዚአብሔርን ድምፅ አልሰማችም
ድምፅ ተናጋሪው የሚናገረውን ይወክላል፤ መስማት መታዘዝን ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ለነገራት ቃል አልታዘዘችም››


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Zephaniah 3:3
አጠቃላይ መረጃ
3፥1-5 ላይ ሶፎንያስ ለኀጢአተኞቹ የኢየሩሳሌም ሰዎች የያህዌን የፍርድ መልእክት ይናገራል። ከተማዋ ውስጧ የሚኖሩ ሰዎችን ትወክላለች። ይህን ግልጽ ለማድረግ፣ ‹‹እርሷ›› እና፣ ‹‹የእርሷ›› የተሰኙትን ነጠላ ቁጥሮች፣ ‹‹እነርሱ›› እና፣ ‹‹የእነርሱ›› በማለት መተካት ይቻላል።
ሹሞቿ የሚያገሡ አንበሶች
አንበሶች የሚያገሡት ከያዙት ንጥቂያ ሌሎች እንስሳትን ለማባረር ነው። የኢየሩሳሌም ሹሞች በእጃቸው ንጥቂያ እንደ ያዙ አንበሶች ተመስለዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የኢየሩሳሌም ሹመኞች እንደሚያገሡ አንበሶች ስግብግብ ናቸው››
ገዦቿ ለነገ የማይሉ የምሽት ተኵላዎች ናቸው
ሌሊት ከማደናቸው በፊት ተኵላዎች ይራባሉ። ገዦቹ በተራቡ ተኵላዎች ተመስለዋል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ገዦቿ ለሌሎች ምንም እንደማያስተርፉ የተራቡ ተኵላዎች ናቸው››
ነቢያቱ ትዕቢተኞች አታላዮችም ናቸው
‹‹ነቢያቷ ማንንም አይሰሙም፤ የሚታመኑም አይደሉም››
ቅዱስ የሆነውን ያረክሳሉ
‹‹ለተቀደሰው ነገር አክብሮት የላቸውም››
በሕግም ላይ ያምፃሉ››
‹‹ሕጉን ተላልፈዋል››
Zephaniah 3:5
አጠቃላይ መረጃ
3፥1-5 ላይ ሶፎንያስ ለኀጢአተኞቹ የኢየሩሳሌም ሰዎች የያህዌን የፍርድ መልእክት ይናገራል።
ያህዌ ጻድቅ ነው፤ ፈጽሞ አይሳሳትም
ሁለቱም ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ሲሆን፣ በዐመፀኞቹ የኢየሩሳሌም ሰዎች መካከል እንኳ ያህዌ ጻድቅ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል።
በመካከልዋ
‹‹በእነርሱ መካከል››
‹‹በየማለዳው››
ይህ ፈሊጣዊ ቃል፣ ‹‹ሁልቀን›› ወይም፣ ‹‹በየቀኑ›› ማለት ነው።
ቅን ፍርድ ይሰጣል
ያህዌ ለሰው ሁሉ ያለው ቅን ፍርድ እንደ አንድ ስጦታ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ለሰዎች ቅን ፍርድ ያደርጋል››
ብርሃን ውስጥ አይሸሸግም
የያህዌ ፍርድ ሁሌም ግልጽ የመሆኑን እውነት አጽንዖት ለመስጠት አሉታዊ አነጋገርን ተጠቅሟል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የእርሱ ቅን ፍርድ ለሰው ሁሉ በግልጽ ይታያል››
ዕፍረት አያውቁም
‹‹አያፍሩም››
Zephaniah 3:6
አጠቃላይ መረጃ
3፥6-7 ሌሎች ኀጢአተኞች ከተሞች ላይ እንዴት እንደ ፈረደ ባለ መማራቸው ያህዌ የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ይገሥጻል። ይህን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ቁጥር 6 መጀመሪያ ላይ ያህዌ እንዲህ ይላል የሚል መጨመር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።
ማንም እንዳያልፍባቸው መንገዳቸውን ባድማ አደረግሁ፤ ከተሞቻቸው ተደምስሰዋል አንድም ሰው የለም።
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች የሚናገሩት ስለ አንድ ጉዳይ ሲሆን፣ የከተማዎቹ መደምሰስ እርግጥ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣሉ።
ማንም እንዳያልፍባቸው
‹‹ማንም አያልፍባቸውም››
ነዋሪም ከቶ አይገኝባቸውም
‹‹እዚያ ማንም አይኖርም›› — ይህን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ፣ ‹‹ሁሉም ይሞታሉ›› ማለት ይቻላል።
እኔም፣ ‹‹ትፈሪኛለሽ… ቅጣቴም በእርሷ ላይ አይደርስም ብዬ ነበር።››
እኔን ይፈሩኛል፤ አስቀድሞ እንዳልሁት ከቤቶቻችው እንዳይነቀሉ እርምት ይቀበላሉ ብዬ ነበር።››
ከቤታቸውም አይቆረጡም
እዚህ ላይ፣ ‹‹አይቆረጡም›› የሚለው መወገድን ያመለክታል። ይህንንም፣ ‹‹ከቤታቸው እንዳላስወግዳቸው›› ማለት ይቻላል።
ክፋትን በመፈጸም እየተጉ ሄዱ
‹‹ክፉ ነገሮችን በማድረግ››
Zephaniah 3:8
አጠቃላይ መረጃ
3፥8 ላይ ያህዌ በሕዝቦች ሁሉ ላይ እንደሚፈርድ ያስጠነቅቃል።
እስከምፈርድበት ቀን ድረስ ጠብቁኝ
ይህ ሐረግ ፍርዱን እየጠበቁ እንደ ነበር ያመለክታል።
ያህዌ እንዲህ ይላል
እየተናገረ ያለው እርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌ የተናገረው ይህን ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህ እኔ ያህዌ የተናገርሁት ነው››
ሰለባ ለመያዝ እነሣለሁ
ያህዌ ሕዝቦች ላይ የሚያመጣው ፍርድ የተራበ እንስሳ ታናሹን እንስሳ በሚያጠቃበት ሁኔታ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰላባውን እንደሚይዝ እንስሳ እኔም ተነሥቼ አጠፋቸዋለሁ››
አሕዛብን ልሰበስብ፤ መንግሥታትን ላከማች
እነዚህ ሁለት ሐረጐች የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ሲሆን፣ ያህዌ ሕዝቦች ሁሉ ላይ እንደሚፈርድ አጽንዖት ይሰጣል።
ቁጣዬ — የቁጣዬ እሳት
‹‹ቁጣ›› እና፣ ‹‹የቁጣ እሳት›› በመሠረቱ አንድ ናቸው፤ የሚያመለክቱት የያህዌ ቁጣ ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹እንደ እሳት የሚነድ ቁጣዬ››
በቅናቴ ቁጣ እሳት አቃጥላቸዋለሁ!
እዚህ ላይ የያህዌ ቁጣ በሚያቃጥል እሳት ተመስሎአል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ቅናቴ መላውን ምድር እንደ እሳት ያቃጥላል››
Zephaniah 3:9
አጠቃላይ መረጃ
3፥9-10 ላይ ያህዌ ከፍርድ በኃላ ሕዝቦችን እንደሚያድስ ይናገራል።
አጠቃላይ መረጃ
3፥11-13 ላይ ያህዌ ከፍርድ የተረፉ ትሩፋንን ያጽናናል።
አንደበታቸውን አጠራለሁ
‹‹አንደበት›› የመናገር ችሎታን ያመለክታል። ‹‹ሕዝቡ እውነትን›› እንዲናገሩ አደርጋለሁ››
የያህዌን ስም እንዲጠሩ
ይህ ያህዌን ያመልካሉ ለማለት ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያህዌን እንዲያመልኩ››
ተስማምተው እንዲያገለግሉ
‹‹ተስማምተው›› በአንድነት ሆነው ማለት ነው።
ከኩሽ ወንዞች ማዶ
ይህ የሚያመለክተው በዚህ ዘመን ሱዳን ያለችበትን ሊሆን ይችላል።
በዚያ ቀን… በዚያ ጊዜ
‹‹በዚያ ጊዜ… ያ ሲሆን›› ይህ የሚያመለክተው የያህዌን ቀን ወዲያውኑ ተከትሎ የሚኖረውን የሰላምና የመታደስ ጊዜ ነው።
በዚያ ቀን ባደረጋችሁት አታፍሩም።
ይህ ድርጊትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ባደረጋችሁ ነገር ከእንግዲህ በፍጹም አታፍሩም››
በትዕቢታቸው የሚደሰቱትን
‹‹በጣም የሚታበዩ ሰዎች ሁሉ››
Zephaniah 3:12
አጠቃላይ መረጃ
3፥11-13 ላይ ያህዌ ከፍርድ የተረፉ የእስራኤል ትሩፋንን ያጽናናል።
የዋሃንንና ትሑታንን በመካከላችሁ አስቀራለሁ… የእስራኤልን ትሩፋን
በመጀመሪያው ሐረግ፣ ‹‹ትሩፋኑን›› በሁለተኛው ሐረግ አስቀምጦአል።
የያህዌን ስም መጠጊያ ያደርጋሉ
ያህዌ ለእነዚህ ትሩፋን የሚያደርገው ጥበቃ እርሱ መጠጊያ ወይም መጠለያ ከመሆኑ ጋር ተመሳስሎአል። እዚህ ላይ፣ ‹‹የያህዌ ስም›› ማንነቱን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ያህዌ ይመጣሉ፤ እርሱም ይረዳቸዋል››
ኀጢአት አይሠሩም
‹‹ክፉ ነገር አያደርጉም››


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ምላሳቸውም ሐሰት አይናገርም፤ በአንደበታቸውም ተንኰል አይገኝም
‹‹ምላስ... በአንደበታቸው›› የሚለው ምላስ አንደበት እንዲናገር የሚያደርገውን ነገር ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ማንኛቸውም ክፉ ነገር አይናገሩም›› ወይም፣ ‹‹ክፉ ነገር አያወሩም››
ይበላሉ ይተኛሉ
ያህዌ ለእስራኤል ሕዝቡ ስለሚያደርገው ቸርነት ሲናገር እነርሱ በሰላም ተመግበው የሚያርፉ በጐቼ መሆናቸውን ያመለክታል።
Zephaniah 3:14
አጠቃላይ መረጃ
3፥14-20 ላይ ሶፎንያስ ደስ እንዲላቸው ከፍርድ ለተረፉ ትሩፋን ይናገራል።
የጽዮን ልጅ... የኢየሩሳሌም ልጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልጅ›› በከተማው የሚኖሩትን ሁሉ ይመለከታል።
ደስ ይበልሽ፤ ሐሤትም አድርጊ
ሁለቱም ሐረጐች አንድ ዐይነት ትርጉም ቢኖራቸውም፣ ምን ያህል ደስ ሊላቸው እንደሚገባ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በጣም ደስ ይበላችሁ››
በፍጹም ልብሽ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› የሰውን ውስጣዊ ሁለንተና ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በፍጹም ሁለንተናሽ››
ያህዌ ቅጣትሽን አስወግዶአል
ቅጣትን ማስወገድ ቅጣትን መተው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ አንቺን መቅጣቱን ትቶአል››
ከእንግዲህ ወዲያ አንዳች ክፉ ነገር አትፈሪም
‹‹ክፉ›› የሚለው ድርጊትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ ሰዎች ይጐዱኛል ብለሽ አትፈሪም››
በዚያ ቀን
‹‹በዚያ ቀን›› ወይም፣ ‹‹ያ በሚሆንበት ጊዜ›› ይህ የሚያመለክተው የያህዌን ቀን ወዲያውኑ ተከትሎ የሚመጣውን የሰላምና የመታደስ ጊዜ ነው።
ለኢየሩሳሌም... ለጽዮን እንዲህ ይሏታል
ስሞቹ የሚያመለክቱት እዚያ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። ‹‹ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ለጽዮን ሕዝብ እንዲህ ይላል››
እጆችሽ አይዛሉ
ደካማና ዐቅም ቢስ መሆን በእጆች መዛል ተመስሎአል። እዚህ ላይ ‹‹እጆች›› የሰውን ሁለንተና ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አትድከሚ››
Zephaniah 3:17
አጠቃላይ መረጃ
3፥14-20 ላይ ሶፎንያስ ከፍርድ የተረፉ ትሩፋን ደስ እንዲሰኙ ይናገራል።
የሚታደግ ኀያል ነው
‹‹እርሱ ኀያል ነው፤ ያድንሻል›› ያህዌ በብርቱ ጦረኛ ተመስሎአል። ‹‹እርሱ ብርቱ ጦረኛ ነው፤ ድል ይሰጣችኋል››
በአንቺ እጅግ ደስ ይለዋል... በዝማሬም በአንቺ ሐሤት ያደርጋል።
የእነዚህ ሁለት ሐረጐች ትርጉም ተመሳሳይ ሲሆን፣ የተደጋገመት ትሩፋኑ ወደ እርሱ በመመለሳቸው ያህዌ ምን ያህል ደስ መሰኘቱን አጽንዖት ለመስጠት ነው።
በፍቅሩ ያሳርፍሻል
አማራጭ ትርጉሞቹ፣ 1) ‹‹በፍቅሩ ጸጥ ያሰኝሻል›› ወይም 2) ‹‹እርሱ ስለሚወድሽ ያድንሻል›› ሊሆኑ ይችላሉ።
ከእንግዲህ ዕፍረት አትሸከሚም
ዕፍረት ሰዎች ላይ እንደ ሸክም መሆኑን ይናገራል። ‹‹ከእንግዲህ በዚያ ነገር አታፍሪም››
Zephaniah 3:19
አጠቃላይ መረጃ
3፥19-20 ላይ ሶፎንያስ በቀጥታ ከፍርድ የተረፉ የእስራኤል ትሩፋን ደስ እንዲሰኙ ይናገራል።
እነሆ
ይህ የሚያመለክተው አንባቢው ለሚከተለው ትኩረት እንዲሰጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹ልብ በሉ››
ያስጨነቁሽን ሁሉ እቀጣለሁ
ይህም፣ ‹‹አንቺን ያስጨነቁትን በእርግጥ እቀጣቸዋለሁ›› ማለት ነው።
አንካሶችን እታደጋለሁ፤ የተበተኑትንም እሰበስባለሁ
በምርኮ የነበሩት እስራኤላውያን አንካሶችና የተበተኑ እንደ ነበሩ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንደ አንካሶችና እንደ ተበተኑ ሰዎች የሆኑትን የእስራኤል ትሩፋን እታደጋለሁ››
አንካሳ
መራመድ የማይችል ሰው ወይም እንስሳ
ለውዳሴና ለክብር አደርጋቸዋለሁ
እዚህ ላይ የተሟላ ሐሳቡ፣ ‹‹የምስጋና ምክንያት አድርጋቸዋለሁ›› ማለትም፣ ‹‹ሌሎች ያመሰግናቸዋል››
ውርደታቸውን ወደ ዝና እለውጣለሁ
ውርደትና ዝና እንደ ድርጊት ሊነገሩ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከእንግዲህ ሰዎች እንዲያከብሯቸው እንጂ፣ እንዲያፍሩ አላደርግም››
በዚያ ጊዜ እመራችኋለሁ፤ በዚያ ጊዜ በአንድነት እሰበስባችኋለሁ።
እነዚህ ሁለት ሐረጐች የሚናገሩት ስለ ተመሳሳይ ነገር ሲሆን፣ በምርኮ ያሉ ሰዎችን ያህዌ ወደ ትውልድ አገራቸው እንደሚያመጣ ያመለክታሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዚያ ጊዜ በአንድነት ሰብስቤ ወደ ትውልድ አገራችሁ አመጣችኋለሁ››

---

Chapter 1
Haggai 1:1
ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት
‹‹በንጉሥ ዳርዮስ ሁለተኛ ዓመት›› ወይም፣ ‹‹ዳርዮስ ንጉሥ በሆነ በሁለተኛው ዓመት››
ዳርዮስ... ሐጌ... ዘሩባቤል... ሰላትያል.. ኢያሱ... ኢዮሴዴቅ
የሰዎቹ ስም በሙሉ እነዚህ ናቸው
በስድስተኛው ወር የመጀመሪያ ቀን
‹‹በስድስተኛው ወር የመጀመሪያው ቀን።›› ስድስተኛ ወር የሆነው በአይሁድ ቀን አቆጣጠር ነው። የመጀመሪያ ቀን በምዕራባውያን ቀን መቁጠሪያ ነሐሴ አጋማሽ ላይ ነው።
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ ቃል ከእግዚአብሔር ስለ መጣ ልዩ ቃል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልእክት ሰጠ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይህን መልእክት ተናገረ››
ያህዌ
ይህ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ለሕዝቡ የተገለጠ የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህ እንዴት እንደሚተረጐም ከቃላት ትርጉም ገጽ ስለ ያህዌ የተጻፈውን ተመልከት።
በነቢዩ በሐጌ እጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱ ሐጌን ነው። መልእክቱን ለማስተላለፍ ያህዌ በሐጌ በኩል ተጠቀመ። ሐጌ 1፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሐጌ በኩል››
የያህዌ ቤት
ቤተ መቅደሱ
Haggai 1:3
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ከእግዚአብሔር የመጣ ልዩ ቃል ያመለክታል። ሐጌ 1፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልእክት ሰጠ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይህን መልእክት ተናገረ››
በሐጌ እጅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹እጅ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራሱ ሐጌን ነው። ትእዛዙን ለሕዝቡ ለማድረስ ያህዌ በሐጌ በኩል ተጠቀመ። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ከሐጌ 1፥1 ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣
ይህ ጊዜው ነውን?
ያህዌ ሕዝቡን እየገሠጸ ነው። ይህ መልስ የማያስፈልገው ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይችላል። ‹‹ይህ ጊዜው አይደለም››
ይህ ቤት
የያህዌ ቤተ መቅደስ
መስከር አልቻላችሁም
መስከር ቀርቶ ጥምን ለማስታገሥ እንኳ በቂ ወይን ጠጅ የለም። ይህ ዐረፍተ ነገር መስከር ጥሩ ነገር ነው ማለት አለመሆኑን አንባቢው መረዳት አለበት።
X

ደመወዝ ተቀበላችሁ ግን በቀዳዳ ኰረጀ የማስቀመጥ ያህል ነው የሆነባችሁ። አስፈላጊ ነገሮች ለመግዛት በቂ ገንዘብ አለማግኘት በቀዳዳ ኰረጀ ገንዘብ በማስቀመጥ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሠራተኛው የተቀበለው ደመወዝ የሚያስፈልገውን ነገር ከመግዛቱ በፊት አለቀ››

Haggai 1:7

እንጨት አምጡ

ቤተ መቅደስ ለመሥራት ይህ አንድ አስፈላጊ ነገር ብቻ ነው።

አነሆ

‹‹ተመልከቱ›› ወይም፣ ‹‹አድምጡ›› ወይም፣ ‹‹የምነግራችሁን ልብ በሉ››

እፍ አልሁበት

ያህዌ እፍ ስላለበት እንደ ዐመድ በነነ፤ ስለዚህ ሰዎቹ የሚፈልጉትን አላገኙም። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የምታገኙት ነገር እንዳይኖር አደረግሁ››

ያህዌ ጸባኦት እንዲህ ይላል

እርሱ የሚናገረው እርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

Haggai 1:10

ሰማያት ጠል ከለከሉ

ሌሊት የሚታየው ጠል ከሰማይ ደመና ሆኖ በሚወርድ ዝናብ ተመስሎአል። ሰማይ ስጦታ መስጠት እንዳልፈለገ ሰው ወይም ልጁን መመገብ እንደማይፈልግ ወላጅ ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰማዩ ጠል እንዲዘንብ›› ወይም፣ ‹‹ጠል ዝናብ እንዲሆን አልፈለገም››

ምድር ላይ ድርቅ ጠራሁ

ለረጅም ጊዜ ዝናብ አለመዝነቡ ምድሪቱን ደረቅ እንዲያደርግ ያህዌ በነገረው ሰው ተመስሎአል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምድር ላይ እንዳይዘንብ ከለከልሁ››

በአዲሱ ወይን ጠጅ በዘይቱ

ወይን ጠጅና ዘይት፣ የወይን ፍሬና የወይራ ፍሬ፣ ተተኪ ስም ነው።

በእጆቻችሁም ሥራ ላይ

ይህ ሐረግ፣ ‹‹ብዙ በደከማችሁበት›› ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። እጅ የሚሠራው ሥራ የሰው ልፋት ውጤት ተተኪ መጠሪያ ነው። እጅ ሰውን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በርትታችሁ የሠራችሁት››

Haggai 1:12

ዘሩባቤል… ሰላትያል… ኢያሱ… ኢዮሴዴቅ… ሐጌ

እነዚህን ስሞች እንዴት እንደተረጐምህ ከሐጌ 1፥1 ተመልከት።

ለያህዌ ድምፅ… ለሐጌ መልእክት ታዘዙ

ድምፅና መልእክት ሰዎችን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለያህዌና ለሐጌ ታዘዙ››

ሕዝቡ የያህዌን ፊት ፈሩ

የዚህ አማራጭ ትርጉም፣ 1) ፊት ያህዌን ይወክላል። ‹‹ሕዝቡ ያህዌን ፈሩ›› ወይም 2) ፊት የያህዌን ሓልዎት ይወክላል። ‹‹ሕዝቡ በያህዌ ሓልዎት ውስጥ መሆን ፈሩ››

ይህ የያህዌ ቃል ነው

‹‹ይህ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም፣ ‹‹ይህን የተናገርሁ እኔ ያህዌ ነኝ››

Haggai 1:14

ያህዌ የይሁዳን ገዥ የሰላትያልን ልጅ የዘሩባቤልን መንፈስ፣ የሊቀ ካህናቱን የኢዮሴዴቅን ልጅ የኢያሱን መንፈስና ከምርኮ የተረፈውን ሕዝብ ሁሉ መንፈስ አነሣሣ

መንፈስን ማነሣሣት ለሥራ ማነሣሣት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ የይሁዳን ገዥ የሰላትያልን ልጅ የዘሩባቤልን እንዲሁም የሊቀ ካህናቱን የኢዮሴዴቅን ልጅ የኢያሱን መንፈስና ከምርኮ የተረፈውን ሕዝብ ለሥራ አነሣሣ››

ትሩፋን

ባቢሎን ውስጥ በምርኮ የነበሩና በሕይወት ኖረው ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱ ሰዎች በስድስተኛው ወር ሃያ አራተኛው ቀን ይህ ማለት ራእዩ በመጣ በ23ኛው ቀን ማለት ነው። ይህ በአይሁድ አቆጣጠር ስድስተኛ ወር ነው። በምዕራውያን ቀን አቆጣጠር ሃያ አራተኛው ቀን የሚውለው መስከረም አጋማሽ ላይ ነው። በምዕራውያን ቀን አቆጣጠር ሃያ አራተኛው ቀን የሚውለው መስከረም አጋማሽ ላይ ነው።

ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት

‹‹ንጉሥ ዳርዮስ በነገሠ ሁለተኛው ዓመት›› ወይም፣ ‹‹ዳርዮስ ንጉሥ በሆነ በሁለተኛው ዓመት››

---

Chapter 2

Haggai 2:1

በሰባተኛው ወር በሃያ አንደኛው ቀን

ይህ የዕብራውያን ቀን አቆጣጠር ሰባተኛ ወር ነው። በምዕራባውያን ቀን መቁጠሪያ ሃያ አንደኛው ቀን የሚውለው ጥቅምት አጋማሽ ላይ ነው።

የያህዌ ቃል መጣ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልእክት ለማመልከት ነው። ሐጌ 1፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልእክት ሰጠ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይህን መልእክት ተናገረ››

በሐጌ እጅ

‹‹እጅ›› የሚለው ቃል ሐጌ ራሱን ያመለክታል። ይህን መልእክት ለመስጠት ያህዌ በሐጌ ተጠቅሞአል። 1፥1 ላይ ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በሐጌ በኩል››

ሐጌ… ዘሩባቤል… ሰላትያል… ኢያሱ… ኢዮሴዴቅ

የእነዚህ ሰዎች ስም እንዴት እንደ ተረጐምህ ሐጌ 1፥1 ተመልከት።

Haggai 2:3

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ እየተሠራ ስለ ነበረው ቤተ መቅደስ ለሕዝቡ ይናገራል። ናቡከደነፆር ሙሉ በሙሉ ያወደመውን የድሮውን ቤተ መቅደስ አባቶቻቸው ሠርተው በነበረበት ቦታ ነበር እየሠሩት የነበረው ይህ ቤተ መቅደስ ከድሮው ቤተ መቅደስ በጣም ያነሰ ነበር።

ይህን ቤት በቀድሞ ክብሩ ሳለ ያየ በመካከላችሁ ማን አለ?

አዲሱ ቤተ መቅደስ ያው እንደ ቀድሞ እንደ ነበር አድርጐ ያህዌ ለሕዝቡ ይናገራል። ልብ እንዲሉ የቀድሞውን ቤተ መቅደስ አይተው ለነበሩ ሰዎች ይናገራል። ይህን መልስ የማያስፈልገው ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህን ቤተ መቅደስ በቀድሞ ክብሩ ያያችሁ ሰዎች ልብ እንድትሉ እፈልጋለሁ››

አሁንስ ምን መስሎ ይታያችኋል?

ስለ አዲሱ ቤተ መቅደስ የሚያስቡትን እንደሚያውቅ ያህዌ እየነገራቸው ነው። አዲሱ ቤተ መቅደስ እንደ ቀድሞው ቤተ መቅደስ እንደ ነበር ይናገራል። ይህን መልስ የማያስፈልገው ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህ አዲስ ቤተ መቅደስ የምታስቡትን አውቃለሁ››

በፊታችሁ ምንም እንዳይደለ የሚቆጠር አይደለምን?

አዲሱ ቤተ መቅደስ በጣም ትንሽ ስለ ነበር ማዘናቸውን እንደሚያውቅ ያህዌ ለሕዝቡ ይነግራቸዋል። ይህን መልስ የማያስፈልገው ጥያቄ እንደ ዐረፍተ ነገር መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህን ያህል ጠቃሚ እንዳይደለ የምታስቡትን አውቃለሁ››

አሁን በርታ

‹‹ከአሁን ጀምሮ ብርቱ ሁን››

ያህዌ እንዲህ ይላል

እርሱ የሚናገረው እርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ይህን ተናግሮአል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል

እርሱ የሚናገረው እርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ይናገራል። ከሐጌ 1፥9 ይህን እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊ ጌታ ያህዌ ይህን ተናግሮአል›› ወይም፣ ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

Haggai 2:6

ሰማያትን… ምድርን… ባሕርን… የብስን… ሕዝቦችን ሁሉ አናውጣለሁ

‹‹ምድርን አናውጣለሁ›› የሚለው፣ ‹‹የምድር መንቀጥቀጥ አመጣለሁ›› የምድር መንቀጥቀጡም፣ ‹‹ባሕርን›› እና፣ ‹‹የብሱን›› ያናውጣል ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፤ ይህ መላውን ምድር የሚመለከት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ሰማያትና ሕዝቦች እንደ ግዑዝ ነገሮች እንደሚናወጡ ያህዌ ይናገራል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አናውጣለሁ
ፍሬ ወይም ሌላ ነገር እንዲወድቅ ዛፍን ወደ ፊት ወደ ኃላ ለማነቃነቅ በምትጠቀምበት ግሥ መጠቀም ትችላለህ።
ይህንም ቤት በክብር አሞላዋለሁ
ክብር እንደ አንድ ጠጣር ወይም ፈሳሽ አንድን መያዣ ማለት ቤተ መቅደሱን እንደሚሞላ አድርጎ ያህዌ ይናገራል። አማራጭ ትርጉሞቹ፣ 1) ቤተ መቅደሱ በጣም ያማረ ይሆናል፤ ‹‹ይህን ቤተ መቅደስ በጣም ያማረ አደርገዋለሁ›› ወይም 2) ብርና ወርቁን እንዲሁም ሌላውን ሀብት ጨምሮ፣ ‹‹ሕዝቦች ሁሉ የሚያመጡትን ብርና ወርቅ›› ይመለከታል፤ ‹‹ሕዝቦች ወደዚህ ቤት ብዙ ያማሩ ነገሮች ያመጣሉ››
Haggai 2:8
ብሩ የእኔ ነው፤ ወርቁም የእኔ ነው
‹‹ብርና ወርቅ›› ሕዝቦች ወደ ቤተ መቅደሱ የሚያመጡትን ሀብት ሁሉ ይወክላል። (ሐጌ 2፥7)
የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረው እርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን እንዴት እንደ ተረጎምኸው ከሐጌ 1፥9 ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይህን ይላል›› ወይም፣ ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››
Haggai 2:10
በዘጠነኛው ወር በሃያ አራተኛው ቀን
ይህ በዕብራውያን ቀን አቆጣጠር ዘጠነኛው ወር ነው። በምዕራባውያን አቆጣጠር ሃያ አራተኛውን ቀን የሚውለው ታህሳስ አጋማሽ ላይ ነው።
ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት
‹‹ዳርዮስ ንጉሥ በሆነ በሁለተኛው ዓመት›› ወይም፣ ‹‹ዳርዮስ ከነገሠ ሁለት ዓመት ሲሆነው››
ዳርዮስ... ሐጌ
የእነዚህን ሰዎች ስም እንዴት እንደ ተረጐምህ ሐጌ 1፥1 ተመልከት።
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣውን ልዩ መልእክት ለማመልከት ነው። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ሐጌ 1፥1 ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልእክት ሰጠ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይህን መልእክት ተናገረ››
ለያህዌ የተለየ ምግብ... ቅዱስ
‹‹ለያህዌ የተለየ›› እና ‹‹ቅዱስ›› የተሰኙት ቃሎች የአንድ የዕብራይስጥ ቃል ትርጉም ናቸው። ‹‹የተቀደሰ ምግብ... ቅዱስ››
Haggai 2:13
በሞት ምክንያት
‹‹የሞተ ሰው ሥጋ ቢነካ››
ሐጌም እንዲህ አለ፣ ‹‹እንደዚሁ... የረከሰ ነው››
ሐጌ ለካህናቱ የሰጠው መልስ ለካህናቱ እንዲናገር ያህዌ የነገረውን ነበር። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ስለዚህም ሐጌ መለሰላቸው፣ እንዲሁ... የረከሰ ነው በማለት የያህዌን ቃል ነገራቸው።››
ይህ ሕዝብና ይህ ወገንም በፊቴ እንደዚሁ ነው
‹‹ይህን ሕዝብና ይህን ወገን የምመለከተው እንደዚሁ ነው።›› አንድ ቅዱስ ነገር የረከሰውን ቢነካ ርኩሱ ነገር እንደሚቀደስ ያህዌ ለካህናቱ ያሳስባል። ከዚያም ጣዖትን ያመልኩ ስለ ነበር የረከሱ እንዲሆኑ እንደሚያስብና በዚህም ምክንያት እነርሱ የሚነኩት ሁሉ እንደሚረክስ ያሳስባቸዋል።
ይህ የያህዌ ቃል ነው
የሚናገረው በእርግጥ መሆኑን ለማመልከት ያህዌ ስሙን በመጥራት ስለ ራሱ ይናገራል። ሐጌ 1፥9 እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ እንዲህ ይላል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››
Haggai 2:15
በቤተ መቅደስ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ከመነባበሩ በፊት
ይህን ተግባርን በሚመለከት ሁኔታ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የቤተ መቅደሱን የመጀመሪያውን ድንጋይ ከማስቀመጣችሁ በፊት››
ሃያ መስፈሪያ
‹‹20 መስፈሪያ›› አንድ፣ ‹‹መስፈሪያ›› ልኩ ስንት እንደ ሆነ አይታወቅም
አምሳ ማድጋ
‹‹50 ማድጋ›› አንድ ‹‹ማድጋ›› ልኩ ስንት እንደ ሆነ አይታወቅም
የእጃችሁን ሥራ ሁሉ
‹‹የሠራችሁትን ሁሉ›› ወይም፣ ‹‹ሰብላችሁን››
ያህዌ እንዲህ ይላል
የሚናገረው በእርግጥ መሆኑን ለማመልከት ስሙን በመጥራት ያህዌ ስለ ራሱ ይናገራል። ሐጌ 1፥9 እንዴት እንደ ተረጐምህ ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ይህን ተናግሮአል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››
Haggai 2:18
በዘጠነኛው ወር ሃያ አራተኛ ቀን
ይህ በዕብራውያን አቆጣጠር ዘጠነኛ ወር ነው። በምዕራባውያን አቆጣጠር ሃያ አራተኛው ቀን የሚውለው ታህሳስ መሐል ነው። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ሐጌ 2፥10 ላይ ተመልከት።
‹‹የያህዌ ቤተ መቅደስ መሠረት እስከ ተጣለበት ቀን ድረስ››
ይህን፣ ‹‹የያህዌን ቤተ መቅደስ መሠረት በጣላችሁበት›› በማለት መተርጐም ይቻላል።
በጐተራው የቀረ ዘር ይገኛልን?
ያህዌ ለሚሰጣቸው ተስፋ ቃል ሕዝቡን እያዘጋጀ ነው። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጐተራ ውስጥ ምንም ዘር እንደ ሌላ ማየት ትችላላችሁ››
የወይኑ፣ የበለሱ ዛፍ፣ የሮማኑና የወይራው ዛፍ
‹‹የወይን፣ የበለስ፣ የሮማንና የወይራ ዛፎቻችሁ
ሮማኑ
ይህ አንድ ዐይነት ጣፍጭ ፍራፍሬ ነው። ስለዚህ ዛፍ እየተነገረ መሆኑን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሮማን ዛፍ››
Haggai 2:20
የያህዌ ቃል መጣ
ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር የተለየ መልእክት መምጣቱን ለማመልከት ነው። ሐጌ 1፥1 ላይ ይህን እንዴ እንደ ተረጐምኸው ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ መልእክት ሰጠ›› ወይም፣ ‹‹ያህዌ ይህን መልእክት ተናገረ››
ሐጌ... ዘሩባቤል
እነዚህ የሰዎች ስም ናቸው። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ሐጌ 1፥1 ላይ ተመልከት።
በወሩ ሃያ አራተኛ ቀን
ይህ የሚናገረው ስለ የትኛው ወር እንደ ሆነ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በዘጠነኛው ወር ሃያ አራተኛ ቀን››
ሰማያትንና ምድርን እንደማናወጥ
‹‹ምድርን አናውጣለሁ›› የሚለውን፣ ‹‹የምድር መናወጥ አመጣለሁ›› በማለት መተርጐም ይቻላል። ሰማያትም እንደሚናወጡ ነገሮች አድርጐ ያህዌ ይናገራል። ይህ ሐሳብ እንዴት እንደ ተተረጐመ ሐጌ 2፥6 ተመልከት።
አናወጠ
ይህን ግሥ ዛፍ ላይ ያለ ፍሬ ወይም ሌላ ነገር እንዲወድቅ ዛፉን ወዲያ ወዲህ ከመነቅነቅ ጋር ማመሳሰል ይቻላል። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው 2፥6 ተመልከት።
ሰማያትንና ምድርን
ይህ፣ ‹‹መላውን ፍጥረት›› ወይም፣ ‹‹ማንኛውንም ነገር›› እንደ ማለት ነው።
የመንግሥታትን ዙፋን እገለብጣለሁ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ዙፋን›› የሚወክለው ላዩ ላይ የሚቀመጠውን ንጉሥ ነው። ‹‹በንጉሥ የሚገዛ አገር››
የመንግሥታትን ኀይል አጠፋለሁ
ምናልባትም እነዚህ፣ ‹‹መንግሥታት›› የእስራኤል ጠላቶች መሆናቸውን ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእስራኤል ጠላት የሆኑ መንግሥታት ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይበረቱ ይህን አደርጋለሁ››
እያንዳንዳቸው በገዛ ወንድሞቻቸው ሰይፍ ወድቃሉ።
እዚህ ላይ ሰይፍ አሰቃቂ አሟሟትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እያንዳንዱ ሰው በገዛ ራሱ ወንድም ይገደላል››
Haggai 2:23
በዚያን ቀን
‹‹እኔ በምሠራበት ቀን››
የሰራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ ይላል

የሚናገረው በእርግጥ መሆኑን ለማመለክከት ስሙን በመጥራት ያህዌ ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምኸው ሐኄ 1፥9 ተመልከት። ‹‹ይህ የሰራዊት ጌታ ያህዌ የተናገረው ነው›› ወይም ‹‹እኔ የሰራዊት ጌታ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

ዘሩባቤል... ሰላትያል

የእነዚህን ሰዎች ስም እንዴት እንደ ተረጐምህ ሐኄ 1፥1 ተመልከት

ያህዌ እንዲህ ይላል

የሚናገረው በእርግጥ መሆኑን ለማመልከት ስሙን በመጥራት ያህዌ ስለ ራሱ ይናገራል። ይህን እንዴት እንደ ተረጐምህ ሐኄ 1፥9 ተመልከት። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ያህዌ ይህን ተናግሮአል›› ወይም፣ ‹‹እኔ ያህዌ ይህን ተናግሬአለሁ››

እንደ ማተሚያ ቀለበቴ አደርግሃለሁ

ሥልጣን እንዳላቸው ለማሳየት ሰነዶች ላይ ለማተም ነገሥታት የቀለበት ማተሚያ ይጠቀማሉ። እርሱ የያህዌን ቃል ስለሚናገር ዘሩባቤል ይህን ሥልጣን ከያህዌ ተቀብሏል።

---

Chapter 1

## Zechariah 1:1

በስምንተኛው ወር

ይህ የዕብራይስጡ ስምንተኛው ወር ነው። በምዕራባውያኑ (ጎርጎሳውያኑ) የዘመን አቆጣጠር በጥቅምት ወር መጨረሻና በኅዳር ወር መጀመሪያ ግድም የሚውለው የዓመቱ ክፍል ነው። (‘የዕብራውያኑ ወራትና መደበኛ ቁጥሮች’ የሚለውን ይመልከቱ)

የዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ሁለተኛው ዓመት

“የንጉሥ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ሁለተኛው ዓመት” ወይም “ንጉሥ ዳርዮስ ንጉሥ ከሆነ በኋላ በሁለተኛው ዓመት” (‘መደበኛ ቁጥሮች’ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የሚውለው ከእግዚአብሔር የመጣን የተለየ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። ትኩ. “እግዚአብሔር መልእክት ሰጠ (አስተላለፈ)” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ተናገረ” (‘ፈሊጣዊ አነጋገር’ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ

ይህ በብሉይ ኪዳን ለነበሩት ሕዝቡ የገለጠው የእግዚአብሔር ስም ነው። ይህን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ በሚመለከት በትርጉም ቃል ገጽ ስለ ያሀዌ የተጠቀሰውን ይመልከቱ።

በራክዮ ... አዶ

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (‘ስሞችን እንዴት መተረጎም እንደሚገባ’ የሚለውን ይመልከቱ)

እግዚአብሔር በአባቶቻችሁ ላይ እጅግ ተቆጥቶ ነበር

“በቀደሙት አባቶቻችሁ ላይ በጣም ተቆጥቶ ነበር”

ወደ እኔ ተመለሱ ... እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ

ለሚመለስ ወይም እንደገና ለሚመለስ አንድ ሌላ ሰው የአመለካከት ለውጥ እያደረገ እንደሆነ አድርጎ ያህዌ ይናገራል። ሕዝቡ ወደ ያህዌ ተመለሱ ማለት እንደገና ለእርሱ የተሰጡ ይሆናሉ እርሱንም ያመልኩታል ማለት ሲሆን ያህዌ ወደ ሕዝቡ ተመለሰ ማለት ደግሞ እንደገና ይባርካቸዋል፣ ይረዳቸዋልም ማለት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

## Zechariah 1:4

ከክፉ መንገዳችሁና ከክፉ ሥራችሁ ተመለሱ

አንዳንድ ድርጊቶችን ከማድረግ መቆጠብ እነዚያን ድርጊቶች ከማድረግ እንደመመለስ ሆኖ ይነገራል። ‘ክፉ መንገዳችሁ’ እና ‘ክፉ ሥራችሁ’ የሚሉት ሐረጎች በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ነው። አት. “ክፉ ሥራዎቻችሁን ሁሉ መሥራት አቁሙ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ጥምር አገላለጽ የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱ ግን አልሰሙም እኔንም አላደመጡም

የእነዚህ የሁለቱም ሐረጎች ትርጉም የእስራኤል ሕዝብ ለያህዌ ሕግጋት አይታዘዙም ነበር ማለት ነው። ትኩ. “ነገር ግን ሕግጋቴን አያደምጡም” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ... እንዲህ ይላል

እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1፡3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

አባቶቻችሁ አሁን የት አሉ? ነቢያቱስ ወዴት አሉ? ለዘላለም በሕይወት ይኖራሉን?

ምላሽ የማይጠብቁት እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ለቀደሙት አባቶቻቸው የእግዚአብሔርን መልእክት ያወጁላቸው ቀደምት አባቶችም ሆኑ ነቢያት የሞቱ ስለመሆናቸው አጽንዖት ይሰጣሉ። ጥያቄዎቹ በገለጻ መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አት. “አባቶቻችሁም ሆኑ ነቢያቶቻችሁ እዚህ የሉም፣ ምክንያቱም ሁሉም ሞተዋል” (መልስ የማይጠብቁ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ለባሪያዎቼ ለነቢያት ያዘዝኋቸው ቃልና ሥርዓት በአባቶቻችሁ ላይ አልደረሰምን

ይህ መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ አጽንዖት የሚሰጠው አዎንታዊ መልስ የሚጠብቅ መሆኑን ነው። ያህዌ የሚናገረው የሕዝቡ ቀደምት አባቶች እግዚአብሔርን ያለመታዘዛቸውን ውጤት እንደተቀበሉ ሲሆን ቃሉና ሥርዓቱ እነርሱን እንዳሳደዳቸውና እንደያዛቸው ሰው ሆኖ ቀርቧል። ጥያቄዎቹ በገለጻ መልክ ሊተረጎሙ ይችላሉ። አት. “ነገር ግን ለባሪያዎቼ ለነቢያት ያዘዝኳቸው ቃሎቼና ሥርዓቶቼ አባቶቻችሁን ይዘዋቸዋል።” ወይም “ነገር ግን አባቶቻችሁ ባሪያዎቼ ነቢያት እንዲነግሯቸው ያዘዝኳቸውን ቃሎቼንና ሥርዓቶቼን ባለመታዘዛቸው ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸዋል።” (መልስ የማይጠብቁ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

ቃሎቼና ሥርዓቶቼ

እነዚህ ቃላት ሁለቱም ነቢያት ለሕዝቡ ቀደምት አባቶች የያህዌን መልእክት ያወጁበትን መንገድ ለመግለጽ የዋሉ ናቸው። (ጥምር አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዶቻችንና ሥራዎቻችን

‘መንገዶች’ እና ‘ሥራዎች’ የሚሉት ቃላት ሁለቱም በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ነው። ትኩ. ‘ባሕሪዎቻችን’ (ጥምር አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

## Zechariah 1:7

በሁለተኛው ዓመት፣ ሳባጥ በሚባለው በዐሥራ አንደኛው ወር በሃያ አራተኛው ቀን

‘ሳባጥ’ የሚባለው በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር አሥራ አንደኛው ወር ነው። ሃያ አራተኛው ቀን በአውሮፓውያን (ግሪጎርያን) አቆጣጠር በየካቲት ወር አጋማሽ ላይ የሚውል ነው። (የዕብራውያን ወሮች፣ መደበኛ ቁጥሮች እና ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚሉትን ይመልከቱ)

ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት

“የንጉሥ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ሁለተኛው ዓመት” ወይም “ንጉሥ ዳርዮስ ንጉሥ ከሆነ በኋላ በሁለተኛው ዓመት” በዘካርያስ 1፡1 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። (‘መደበኛ ቁጥሮች’ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል እንዲህ ሲል መጣ

ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የሚውለው ከእግዚአብሔር የመጣን የተለየ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። በዘካርያስ 1፡1 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “እግዚአብሔር መልእክት ሰጠ (አስተላለፈ)” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ተናገረ” (‘ፈሊጣዊ አነጋገር’ የሚለውን ይመልከቱ)

በራክዮ ... አዶ

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (‘ስሞችን እንዴት መተረጎም እንደሚገባ’ የሚለውን ይመልከቱ)

ተመለከትሁ

እዚህ ላይ ‘መመልከት’ የሚለው ቃል ዘካርያስ ባየው ነገር እንደተደነቀ ያመለክታል።

ባርሰነት ዛፎች

ደማቅ አበቦች ያሉት አነስተኛ የዛፍ ዓይነት ነው። (የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

እኔም፣ “ጌታ ሆይ፣ እነዚህ ምንድን ናቸው?” አልሁ። ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክም ...

እዚህ ላይ ዘካርያስ ማንነቱ ያልተገለጸውን መልአክ እያነጋገረ ነው። ይህ ‘በመጋላ (ቀይ) ፈረስ ላይ ከተቀመጠው ሰው’ ጋር ተመሳሳይ አይደለም።

ጌታ ሆይ፣ እነዚህ ምንድን ናቸው?

“ጌታው፣ እነዚህ ነገሮች ምንድን ናቸው?” እዚህ ላይ ‘ጌታ’ የሚለው የትሕትና አነጋገርን የሚያመለክት ነው።

## Zechariah 1:10

በባርሰነት ዛፎች መካከል ቆሞ የነበረው ሰው ... በባርሰነት ዛፎች መካከል ቆሞ የነበረው የያህዌ መልአክ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት በዘካርያስ 1:8 ላይ ‘በአምባላይ (ቀይ) ፈረስ ላይ ተቀምጦ’ የነበረውን ሰው ነው። ትኩ. “በባርሰነት ዛፎች መካከል ቆሞ የነበረው ሰው … በባርሰነት ዛፎች መካከል ቆሞ የነበረው የያህዌ መልአክ” (‘ፈሊጣዊ አነጋገር’ የሚለውን ይመልከቱ)

### እነዚህ እነዚያ ናቸው … መለሱም … እንደዚህም አሉ

‘እነዚህ’ እና ‘እነርሱ’ የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በባርሰነት ዛፎች መካከል ከነበረው ሰው ጀርባ የነበሩትን መጋላ (ቀይ)፣ ሐመር (የቀይ ዳማ) እና አምባላይ (ነጭ) ፈረሶችን ነው። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡- 1) በውስጠ-ታዋቂነት በፈረሶቹ ላይ የሚቀመጡ ሌሎች ሰዎች አሉ፣ እነዚህ ቃላትም የሚያመለክቱት እነዚያን በፈረሶቹ ላይ የሚቀመጡትን ነው። 2) ፈረሶቹ መነጋገር እንደሚችሉ ተደርገው የሰውኛ ገጽታ ተሰጥቷቸዋል። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና ሰውኛ የሚሉትን ይመልከቱ)

### በምድር ሁሉ መመላለስ

እየተመላለሱ ምድርን እንዲቃኙ ያህዌ እነዚህን መላኩ ውስጠ-ታዋቂ ነው። ይህ የባዘኑ ወይም የጠፉ መሆናቸውን አያመለክትም። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

## Zechariah 1:12

### ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ይሁዳ ከተሞች

እዚህ ላይ ‘ኢየሩሳሌም’ እና ‘ከተሞች’ የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በእነዚያ ከተሞች የሚኖሩትን ሕዝቦች ነው። አት. “ለኢየሩሳሌም ሕዝቦችና ለይሁዳ ከተሞች ሕዝቦች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

### ደስ በሚያሰኝና በሚያጽናና

“በመልካም የሚያጽናና ቃል”

## Zechariah 1:14

### ለኢየሩሳሌም ቀንቻለሁ

እዚህ ላይ ‘ቀንቻለሁ’ የሚለው እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመጠበቅ የነበረውን ጠንካራ ፍላጎት ያመለክታል።

### ሰላም አለ በሚሉ ሕዝቦች ላይ ግን በጣም ተቆጥቻለሁ

‘ሰላም አለ’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሕዝቡ በሰላምና በዕርጋታ እንደሚኖሩ እያሰቡ መሆኑን ነው። አት. “ሰላማቸውንና ደህንነታቸውን እያጣጣሙ ባሉት ሕዝቦች በጣም ተቆጥቻለሁ” (‘ፈሊጣዊ አነጋገር’ የሚለውን ይመልከቱ)

### በመጠኑ ብቻ ተቆጥቼባቸው ነበር

“በኢየሩሳሌም ሕዝብ ላይ የተቆጣሁት በመጠኑ ብቻ ነበር”

### ጥፋቱ እንዲብስ አደረጉ

“ሰላም አለ የሚሉት” ሕዝቦች ጥፋቱ እንዲብስ አደረጉ። ይህ ማለት ምንም እንኳን ያህዌ ኢየሩሳሌምን ለመቅጣት እነዚህን ሕዝቦች ቢጠቀምባቸውም እነርሱ ግን ያህዌ እነርሱ እንዲያደርጉ ካቀደው በላይ በኢየሩሳሌም ላይ ጉዳት አደረሱ ማለት ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

## Zechariah 1:16

### በምሕረት ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሻለሁ

ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡- 1)ምንም እንኳን ሕዝቡ ወደ ምርኮ በሄዱበት ጊዜ ያህዌ ኢየሩሳሌምን የተዋት ቢሆንም፣ አሁን ግን ሕዝቡ ከምርኮ በተመለሱ ጊዜ እርሱም ወደ ኢየሩሳሌም ይመለሳል ወይም 2) ያህዌ ወደ ከተማይቱ እንደገና እየተመለሰ በሚመስል ሁኔታ ለኢየሩሳሌም በነበረው አመለካከት ላይ ለውጥ እንዳደረገና እንደገና እንደሚባርካቸው እንደሚረዳቸውም እየተናገረ ነው። አት. “ለኢየሩሳሌም እንደገና ምሕረቴን አሳያለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

### ቤቴ በውስጥዋ ይሠራል

‘በውስጥዋ’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ሲሆን ‘ቤቴ’ የሚለው ደግሞ ለቤተ መቅደሱ ስመ-ምስል ስያሜ ነው። ይህ በተናጋሪ አነጋገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ሕዝቡ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደሴን ይገነባሉ” (ስመ-ምስል ስያሜ እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

### ይህ የሠራዊት ጌታ የያህዌ አዋጅ ነው

እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ ያወጀው ይህንን ነው” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ ያወጅሁት ይህንን ነው” (መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው የሚሉትን ይመልከቱ)

### መለኪያ ገመድም በኢየሩሳሌም ላይ ይዘረጋል

ይህ የሚያመለክተው ገንቢዎች ከተማይቱን እንደገና ለመገንባት መሣሪያዎቻቸውን እንደሚጠቀሙ ነው። ይህ በአናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ገንቢዎች የመለኪያ ገመዳቸውን በኢየሩሳሌም ላይ ይዘረጋሉ” ወይም “ሕዝቡ ኢየሩሳሌምን እንደገና ይገነባሉ” (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

### በድጋሚ ተጣራና እንደዚህ በል

እነዚህን ቃላት የተናገረው ዘካርያስን ሲያነጋግር የነበረው መልአክ ነው።

### ከተሞቼ እንደገና በበጎነት ይትረፈረፋሉ

‘ከተሞቼ’ የሚለው የሚያመለክተው የይሁዳን ከተሞች ሲሆን በእነዚያ ከተሞች የሚኖሩትንም ሕዝቦች ይወክላል። በውሃ መያዣ በርሜል የተመሰሉትን እነዚያን ከተሞች፣ በጎነት የሚያጥለቀልቅ ውሃ እንደሆነ ሁሉ የእነዚያን ከተሞች ነዋሪዎች በበጎነት እንደሚያጥለቀልቃቸውና እንደገና ባለጠጎች እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ያህዌ ይናገራል። አት. “ከተሞቼ እንደገና ባለጠጎች ይሆናሉ” ወይም “በይሁዳ ከተሞች ያሉት ሕዝቦች እንደገና ባለጠጎች ይሆናሉ” (ስመ-ምስል ስያሜ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

### ያህዌ ጽዮንን እንደገና ያጽናናል

እዚህ ላይ ‘ጽዮን’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው በከተማ የሚኖሩትን ሰዎች ነው። አት. “ያህዌ በጽዮን የሚኖረውን ሕዝብ እንደገና ያጽናናል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

## Zechariah 1:18

### ዓይኖቼን አነሳሁ

‘ዓይኖቼ’ የሚለው ቃል የሚመለከተውን ሰው ይወክላል። አት. “ወደ ላይ ተመለከትሁ” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

### እነዚህ ይሁዳን፣ እስራኤልንና ኢየሩሳሌምን የበታተኑ ቀንዶች ናቸው

ቀንዶች ብዙውን ጊዜ ወታደራዊ ኃይልን የሚወክሉ ተምሳሊቶች በመሆን ጥቅም ላይ ይውላሉ። እዚህ ላይ በተምሳሌትነተ የሚወክሉት የእስራኤልን መንግሥት ድል ያደረጉትን ኃያላን መንግሥታትን ነው። ‘ይሁዳ፣ እስራኤልና ኢየሩሳሌም’ የሚሉት ቃላት የሚወክሉት በእነዚያ ስፍራዎች የሚኖሩትን ሰዎች ነው። አት. “እነዚህ ቀንዶች የሚወክሉት ይሁዳን እስራኤልንና ኢየሩሳሌምን የበታተኑትን መንግሥታት ነው” (ተምሳሌታዊ ቋንቋ እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)

## Zechariah 1:20

### አራት ሙያተኞች

‘የብረት አንጥረኞች’ ወይም ‘የብረት-ሥራ ሠራተኞች’

### እነዚህ ሰዎች

ይህ የሚያመለክተው አራቱን ሙያተኞች ነው።

### እነዚህ ይሁዳን የበታተኑ ቀንዶች ናቸው

እነዚህ ቀንዶች የእስራኤልን መንግሥት ድል ያደረጉትን ኃይለኛ መንግሥታት በተምሳሌትነት ያመለክታሉ። ‘ይሁዳ’ የሚለው ቃል በይሁዳ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። በዘካርያስ 1:19 ላይ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “እነዚህ ቀንዶች የይሁዳን ሕዝብ የበታተኑትን መንግሥታት ይወክላሉ።” (ተምሳሌታዊ ቋንቋ እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)

### ማንም ራሱን ቀና ማድረግ እንዳይችል

የይሁዳን ሕዝብ በአሰከፊ ሁኔታ ሲጨቁኑ የነበሩት መንግሥታት ማንም ሰው ራሱን ቀና ማድረግ እንዳይችል እንዳደረጉ ተነግሮላቸዋል። አት. “በጣም እንዲሰቃዩ አደረጓቸው።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

### በይሁዳ ምድር ላይ ቀንዳቸውን መንግሥታት ቀንዶች ሰብሮ ለመጣል ነው

ወታደራዊ ኃይላቸውን በመጠቀም ይሁዳን ድል ለማድረግ የተነሱትን መንግሥታት ያህዌ መንግሥታቱ ቀንዳቸውን እንዳነሱ አድርጎ እየተናገረ ነው። የእነዚህን መንግሥታት ወታደራዊ ኃይል ሲደመስሱ የነበሩት አራቱ ሙያተኞች የመንግሥታቱን ቀንድ ሰብረው ወደ መሬት እንደጣሉ አድርጎ እየተናገረ ነው። አት. “በይሁዳ ምድር ላይ ወታደራዊ ኃይላቸውን የተጠቀሙትን የመንግሥታቱን ኃይል ለመደምሰስ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

### ቀንድ ያነሱትን የመንግሥታቱን ቀንዶች ለመስበር

“መንግሥታቱ ያነሷቸውን ቀንዶች ለመስበር”

---

Chapter 2

## Zechariah 2:1

ዓይኖቼን አነሳሁ

‘ዓይኖቼ’ የሚለው ቃል የሚመለከተውን ሰው ይወክላል። አት. “ወደ ላይ ተመለከትሁ” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

የመለኪያ ገመድ

አንድ ሰው ሕንፃዎችን ወይም ተለቅ ያለ የመሬት ይዞታን ለመለካት የሚጠቀምበት የተወሰነ ቁመት ያለው ገመድ

እርሱም እንደዚህ አለኝ

ስለሆነም የመለኪያውን ገመድ የያዘው ሰው እንደዚህ አለኝ

## Zechariah 2:3

ሌላ መልአክ ሊገናኘው መጣ

ይህ መልአክ ከዚህ በፊት ያልተከሰተ አዲስ ተሳታፊ ነው። (ቀደም ያሉና አዲስ ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለተኛውም መልአክ እንደዚህ አለው

ሁለተኛውም መልአክ እኔን ሲያነጋግረኝ የነበረውን መልአክ እንደዚህ አለው።

ኢየሩሳሌም በገላጣ ስፍራ ትቀመጣለች ... አውራዎችም በውስጥዋ

‘በገላጣ ስፍራ ትቀመጣለች’ የሚለው ሐረግ ቅጠር የሌላትን ከተማ ለሚገልጸው ቃል ትርጉም ሆኖ ያገለግላል። በከተማይቱ እጅግ ብዙ ሰዎች ስለሚኖሩ በዙሪያዋ ቅጥር መሥራት እስከማይቻል ደረስ በጣም ሰፊ ትሆናለች። አት. “ኢየሩሳሌም በዙሪያዋ ቅጥር አይኖራትም ... አውሬዎችም በውስጥዋ ...” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ ለእርሷ በዙሪያዋ የእሳት ቅጥር እሆንላታለሁ

ሰዎች ለጥበቃ ዓላማ በከተሞቻቸው ዙሪያ ቅጥር ይገነባሉ። እዚህ ላይ ያህዌ እርሱ ራሱ በዙሪያዋ የእሳት ቅጥር እንደሆነላት ሁሉ ኢየሩሳሌምን እንደሚጠብቃት ነው የሚናገረው። አት. “የእሳት ቅጥር በዙሪያዋ እንደሚሆንላት እኔ ኢየሩሳሌምን እጠብቃታለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ... እንዲህ ይላል

እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1፡4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

ዘካርያስ 2፡6-7 የትርጉም ማስታወሻዎች ኑ፣ ኑ

እነዚህ ሁለት ቃላት ጥድፊያን ያመለክታሉ፣ ለሚከተለውም ትዕዛዝ አጽንዖት ይሰጣሉ። ቃላቱ በቋንቋችሁ ጥድፊያን በሚያመለክት ሐረግ ሊተረጎም ይችላል። አት. “ሩጡ፣ ሩጡ” ወይም “ቶሎ በሉ፣ ቶሎ በሉ” (ጣምራ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰሜን ምድር

ይህ የሚያመለክተው ባቢሎንን ነው።

እንደ አራቱ የሰማይ ነፋሳት በትኛችኋለሁ

‘አራቱ የሰማይ ነፋሳት’ የሚለው ሐረግ ‘በሁሉም አቅጣጫ’ ማለት ነው። ያህዌ ሕዝቡ በብዙ የተለያዩ አገሮች እንዲኖሩ ማድረጉን ነፍስ ከማንኛውም አቅጣጫ መንፈስ ከሚችልበት መንገደ ጋር ያነጻጽረዋል። አት. “በየአቅጣጫው በትኛችኋለሁ። (ንፅፅሮሽ የሚለውን ይመልከቱ)

ከባቢሎን ሴት ልጅ ጋር የምትኖሪ

‘ባቢሎን ሴት ልጅ’ የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው የባቢሎንን ከተማ ነው። ያህዌ ስለ ከተማዋ ሴት ልጅ እንደሆነች አድርጎ እየተናገረ ነው። አት. “እናንተ በባቢሎች የምትኖሩ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

## Zechariah 2:8

አጠቃላይ መረጃ

ዘካርያስ አሁን መናገር ይጀምራል፣ ደግሞም ኢየሩሳሌምን በዘረፏት መንግሥታት ላይ ይፈርድ ዘንድ ያህዌ እንዴት እንደላከው ይናገራል።

በዘረፉአችሁ

በዘረፉአችሁ በሚለው በውስጠ-ታዋቂ ‘እናንተ’ የሚለው የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው።

የሚነካችሁ

‘መንካት’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለመጉዳት የታሰበን መንካት ነው። አት. “የሚጎዳችሁ ማንም ቢሆን” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር ዓይን ብሌን

የዓይን ብሌን በጣም ስስ (ለጉዳት የተጋለጠ) ከሆኑት የዓይን ክፍሎች አንዱ ነው። ‘የዓይን ብሌን’ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል እጅግ ዋጋ ያለውን ነገር ያመለክታል። እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ታላቅ እሴት ሰጥቷታል ማለት ነው። አት. “ለእግዚአብሔር እጅግ ታላቅ ዋጋ ያለው” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

እጄን በእነርሱ ላይ አነሳለሁ

እጅን በአንድ ሌላ ሰው ላይ ማንሳት የጠላትነት አዝማሚያ ነው። እዚህ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን የሚጎዷትን ያጠቃል የሚል ተምሳሌታዊ ትርጉም አለው። አት. “እኔ ራሴ እዋጋቸዋለሁ” ወይም “እኔ ራሴ አጠቃቸዋለሁ” (ተምሳሌታዊ ተግባር የሚለውን ይመልከቱ)

ለባሪያዎቻቸው ዝርፊያዎች ይሆናሉ

‘ዝርፊያ’ የሚለው ቃል በግሥ መልኩ ሊተረጎም ይችላል። ትኩ. “ባሪያዎቻቸው ይዘርፏቸዋል”

## Zechariah 2:10

የጽዮን ልጅ ሆይ፣ እልል በዪ

‘ጽዮን’ የሚለው ‘ከኢየሩሳሌም’ ጋር አንድ ነው። ነቢዩ ስለ ከተማይቱ ሴት ልጅ እንደሆነች አድርጎ ይናገራል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1) ዘካርያስ ከተማይቱን መዘመር በሚችል ሰው በሰውኛ ይገልጻታል። ትኩ. “ጽዮን፣ እልል በዪ” ወይም 2) ‘የጽዮን ልጅ’ በከተማይቱ ለሚኖሩ ሕዝቦች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። ትኩ. “የጽዮን ሕዝቦች፣ እልል በሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ፣ ሰውኛ እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)

እኔ ራሴ ልመጣና በመካከላችሁ ልሰፍር ነው

“እኔ ራሴ ልመጣና በመካከላችሁ ልኖር ነው” ‘መስፈር’ ማለት ድንኳን መትከልና በድንኳኑ ተጠቅሞ መኖር ማለት ነው።

ያህዌ ... እንዲህ ይላል

እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1፡4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

ታላላቅ ሕዝቦች ወደ ያህዌ ይጠጋሉ

ዘካርያስ የታላላቅ መንግሥታት ሕዝቦች የያህዌ ሕዝቦች እንደሚሆኑና ራሳቸውን ወደ ያህዌ እንዳስጠጉ ሁሉ እርሱን እንደሚያመልኩት አድርጎ ይናገራል። አት. “የታላላቅ መንግሥታት ሕዝቦች የያህዌ ሕዝቦች ይሆናሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)

በዚያ ቀን

‘በዚያን ጊዜ’

በመካከልሽም እሰፍራለሁ

‘በመካከልሽም እኖራለሁ’

## Zechariah 2:12

ያህዌ ሕጋዊ ንብረቱ እንደሆነች አድርጎ ይሁዳን ይወርሳል

ዘካርያስ የሚወርሳት ቋሚ ንብረቱ እንደሆነች ሁሉ ያህዌ ይሁዳን እንደራሱ ምድር አድርጎ እንደሚናገር ይገልጻል። አት. “ያህዌ ይሁዳ ቋሚ ንብረቱ እንደሆነች አድርጎ ይናገራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሥጋ ለባሽ ሁሉ

እዚህ ላይ ‘ሥጋ ለባሽ’ የሚለው ቃል የሰው ልጆችን ይወክላል። ትኩ. “ሕዝቦች ሁሉ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ተነሥቶአል

ቸል ካለበት ሁኔታ አንድ ሰው ለሥራ እንዳንቀሳቀሰው ሁሉ ያህዌ ተግባሩን መፈጸም አድርጎ ዘካርያስ ይናገራል። ይህ እንቅስቃሴው ወደ ኢየሩሳሌም የመመለስ ተግባሩን እንደሚያመለክት ተደርጎ ተወስዷል። አት. “እየመጣ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከተቀደሰ ስፍራው

እዚህ ላይ ‘የተቀደሰ ስፍራ’ የሚለው የሚያመለክተው ሰማይን ነው እንጂ በኢየሩሳሌም ያለውን ቤተ መቅደስ አይደለም። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 3

Zechariah 3:1

አጠቃላይ መረጃ

ያህዌ ለዘካርያስ ስለ ካህኑ ስለ ኢያሱ ራዕይ ያሳየዋል፡፡

ስለ ኃጢአት ሊከሰው በቀኙ በኩል ቆሞ ነበር

"ኢያሱን ስለ ኃጢአት ሊከሰው ዝግጁ ሆኖ ሰይጣን ከኢያሱ በስተቀኝ ቆሞ ነበር፡፡"

ይህ ከእሳት የተነጠቀ ትግታግ አይደለምን?

የያህዌ መልአክ ይህንን ምላሽ የማይሻ ጥያቄ የጠየቀው ለሚጠበቀው አዎንታዊ ምላሽ አጽንዖት ለመስጠት ነው፡፡ ይህ አባባል በገለጻ መልክ ሊቀርብ ይችላል፡፡ አት. "ኢያሱ ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ ነው፡፡" (ምላሽ የማይጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእሳት የተነጠቀ ትግታግ

ትንታግ እየተቃጠለ ያለ ጉርማጅ እንጨት ነው፡፡ የያህዌ መልአክ ኢያሱ ከባቢሎን ምርኮ ተርፎ መምጣቱን እንጨቱ ሙሉ በሙሉ ከመቃጠሉ በፊት አንድ ሰው ከእሳት ውስጥ መዞ እንዳወጣው እየተናገረ ነው፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢያሱም ያደፈ ልብስ ለብሶ ነበር

በዚህ ራዕይ 'ያደፉ ልብሶች' የኃጢአተኛነት ተምሳሌት ናቸው፡፡ (ተምሳሌታዊ ቋንቋ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 3:4

ከፊቱ ቆመው የነበሩትን

በፊቱ በሚለው በውስጠ-ታዋቂ 'ከእርሱ' (ፊት) የሚለው ቃል የሚያመለክተው መልአኩን ነው፡፡ ቃሉ የሚያመለክተው በዚያ የነበሩትን ሌሎች መላእክትን ነው፡፡

እነሆ (አስተውል)

"ልነግርህ ያለሁት እውነተኛና አስፈላጊም ስለሆነ ልብ አድርገው"

ኃጢአትህን ከአንተ አስወግጃለሁ

የኢያሱ ልብሶች የኃጢአተኛነት ተምሳሌት ስለነበሩ፣ ልብሱን በማስወገድ መልአኩ የኢያሱን ኃጢአተኛነት እያስወገደ ነበር፡፡ ኃጢአትን ማስወገድ የሚለው አገላለጽ ፈሊጣዊ አባባል ሲሆን ትርጉሙም የኢያሱን በደል ከእርሱ አርቆለታል ማለት ነው፡፡ አት. "ኃጢአትህን ከአንተ አርቄያለሁ" (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ

እዚህ ላይ 'ጥሩ ልብስ' በተምሳሌትነት የሚወክለው ጽድቅን ነው፡፡ (ተምሳሌታዊ ቋንቋ የሚለውን ይመልከቱ)

አድርጉለት

እዚህ ላይ በውስጠ-ታዋቂ 'እነርሱ' (ያድርጉለት) የሚለው የሚያመለክተው በዚያ የነበሩትን ሌሎች መላእክት ነው፡፡

ጥምጥም

በራስ ላይ የሚጠመጠም ረጅም የጨርቅ ቁራጭ

Zechariah 3:6

አበክሮ ኢያሱን አዘዘው

ጠበቅ ባለ ሁኔታ ኢያሱን አዘዘው፡፡

በመንገዱ ብትሄድ ትዕዛዜንም ብትጠብቅ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ናቸው፡፡ ያህዌ ስለ መታዘዝ የሚናገረው ሰውዬው በያህዌ መንገድ ላይ እንደሚራመድ አድርጎ ነው፡፡ አት. "የምትታዘዘኝ ከሆነና ትዕዛዜን የምትጠብቅ ከሆነ" (ትይዩነት እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

ቤቴን ታስተዳድራለህ በአደባባዮቼም ላይ ኃላፊ ትሆናለህ

እዚህ ላይ 'ቤቴ' የሚለው ቃል ለቤተ መቅደሱ ምስለ-ምስል ስያሜ ሲሆን 'አደባባዮቼ' የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው በቤተ መቅደሱ ዙሪያ የነበረውን ግቢ ነው፡፡ ቃላቱ በአንድነት ኢያሱ በአጠቃላይ በቤተ መቅደሱ ይዞታ ላይ ሥልጣነ ይኖረዋል የሚል ትርጉም አላቸው፡፡ አት. "በመቅደሴና በቅጥር ገቢው ላይ ሥልጣን ይኖርሃል" (ምስለ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በፊቴ በሚቆሙት መካከል ትገባና ትወጣ ዘንድ

'…መካከል ትገባና ትወጣ ዘንድ' የሚለው ሐረግ ኢያሱ ወደ ያህዌ ዘንድ የመግባት መብት ያለው ቡድን አካል እንደሚሆንና ከእነርሱም እኩል መብት እንደሚኖረው የሚገልጽ ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ አባባል ነው፡፡ አት. "እነዚህ በፊቴ ያሉት እንደሚመጡ ሁሉ በፊቴ ትመጣ ዘንድ" (ፈሊጣዊ አባባል፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 3:8

አጠቃላይ መረጃ

የያህዌ መልአክ ለኢያሱ መናገሩን ይቀጥላል፡፡

ከአንተ ጋር የሚኖሩት ወዳጆችህ

ይህ ሐረግ የሚያመለክተው በኢያሱ መሪነት ሥር በቤተ መቅደስ የሚያገለግሉትን ሌሎች ካህናትን ነው፡፡ ትኩ. "ከአንተ ጋር የሚኖሩት ሌሎች ካህናት" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ምልክት የሚሆኑ ሰዎች ናቸው

እዚህ ላይ 'ምልክት' ለሚመለከቱት አንድ የተለየ ትርጉም የሚያስተላልፍ ነገርን የሚያመለክት ነው፡፡ ያህዌ በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉት ካህናት ያህዌ ባሪያውን እንደሚያመጣ የሚያመለክቱ ምልክቶች እንደሆኑ አድርጎ እየተናገረ ነው፡፡

ባሪያዬ ቁጥቋጡ

'ቁጥቋጡ' የሚለው ቃል እዚህ ላይ የሚያመለክተው በያህዌ ሕዝብ ላይ እንደ ንጉሥ የሚያገለግለውን መሲሐዊ ማንነት ነው፡፡ ያህዌ ስለዚህ ሰው ከዛፍ ላይ እንደበቀለ ቅርንጫፍ (ቁጥቋጥ) እንደሆነ አድርጎ ነው የሚናገረው፡፡ 'ቁጥቋጥ' የማዕረግ ስም ስለሆነ በአናንተም ቋንቋ ከዚህ ጋር በሚመጥን ቃል መተርጎም አለበት፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በኢያሱ ፊት ያስቀመጥሁት ድንጋይ

እዚህ ላይ 'ድንጋይ' የሚለው ቃል ምናልባት የከበረ ድንጋይን ወይም ዕንቁን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም፡፡

በአንዱ ድንጋይ ላይ ሰባት ዓይኖች አሉ

ብርሃን የሚያንፀባርቁት የድንጋይ ገጽታዎች ዓይኖች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል፡፡ አት. "በዚህ አንድ ድንጋይ ሰባት ገጽታዎች አሉት" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ቅርጽ እቀርጻለሁ

ጽሑፉን በድንጋዩ ላይ እንደሚቀርጽ በውስጠ-ታዋቂ ግልጽ ነው፡፡ አት. "በ ድንጋዩ ላይ ጽሑፍ እቀርጻለሁ፡፡" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

መቅረጽ

በሹል ብረት መጫር ወይም መቦርቦር

ያህዌ … እንዲህ ይላል

እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል፡፡ በዘካርያስ 1፡4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ፡፡ አት. "የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል" ወይም "እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው" ('መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው' የሚለውን ይመልከቱ)

የዚህችንም ምድር በደል በአንድ ቀን አስወግዳለሁ

እዚህ ላይ 'ምድር' የሚለው ቃል በምድሪቱ የሚኖሩትን ሕዝቦች ይወክላል፡፡ አት. "በዚህ ምድር የሚኖሩትን ሕዝቦች ኃጢአት በአንድ ቀን አስወግዳለሁ፡፡" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 3:10

በዚያን ቀን

'በዚያን ወቅት'

እያንዳንዱን በገዛ ወይኑን በለሱ ሥር ሆኖ ባልንጀራውን ይጋብዛል

'ወይን' እና 'የበለስ ዛፍ' ሁለቱም የብልጽግና ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ ይህ ሐረግ ሕዝቡ በብልጽግናና በሰላም የሚኖሩበትን ተግባሮች ይገልጻል፡፡ አት. "በሰላም ስለሚኖሩ እያንዳንዱ ጎረቤቱን እንዲመጣና በወይኑና በበለሱ በታች እንዲያርፍ ይጋብዛል" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

---

Chapter 4

Zechariah 4:1

አንድ ሰው ከእንቅልፉ እንደሚነቃ አነቃኝ

ዘካርያስ መልአኩ በነበረበት ጥልቅ ሃሳብ ጣልቃ የገባበትን መንገድ አንድ ሰው ሌላውን ሰው ከእንቅልፉ ከማንቃት ጋር አነፃፅሮታል፡፡ አት. "ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ይበልጥ ንቁ እንድሆን አደረገኝ፡፡" (ንፅፅሮሽ የሚለውን ይመልከቱ)

የመቅረዝ መኮስተሪያ

እሳት የሚለኮስበት የመቅረዙ ጫፍ

በስተግራ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በዚህ ሐረግ ላይ የተደረገው ግድፈት ቀደም ካለው ሐረግ ሊታከልበት ይችላል። (ግድፈት የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 4:4

እነዚህ ምን ማለት እንደሆኑ አታውቅምን?

መልአኩ ይህንን መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የጠየቀው ዘካርያስ እነዚህ ምን ማለት እንደሆኑ ሊያውቅ እንደሚገባው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ መልክ ሊተረጎምም ይችላል። አት. "በእርግጥ እነዚህ ምን ማለት እንደሆኑ ታውቃለህ።" (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 4:6

አያያዥ መግለጫ

ከዘካርያስ ጋር የሚነጋገረው መልአክ ራዕዩን መግለጹን ይቀጥላል።

በኃይልና በብርታት አይደለም

በዚህ ሐረግ ውስጥ ግሥ ስለሌለበት በቋንቋችሁ ግሥ መጨመር አስፈላጊ ይሆናል። አት. "በኃይልና በብርታት አይሳካላችሁም።" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በኃይልም ሆነ በብርታት አይሆንም

ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1) 'ኃይል' እና 'ብርታት' የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ትርጉማቸው አንድ ሲሆን አጽንዖት የሚሰጡትም የዘሩባቤልን ኃይል ታላቅነት ነው ወይም 2) 'ኃይል' የሚለው ቃል የሚያመለክተው ወታደራዊ ጥንካሬን ሲሆን 'ብርታት' የሚለው ቃል ደግሞ የዘሩባቤልን ሥጋዊ አቅም ወይም ጉልበት ነው። አት. "በእርግጥ በአንተ ጥንካሬ አይደለም" ወይም "በወታደራዊ ጥንካሬም ሆነ በራስህ ጉልበት አይደለም" (ጣምራ አገላለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

ትልቅ ተራራ ምንድን ነህ? በዘሩባቤል ፊት ሜዳ ትሆናለህ

ይህ ያህዌ ዘሩባቤል የሚያጋጥሙት መሰናክሎች እንደ ትልቅ ተራራ እንደሆኑ አድርጎ የተናገረበት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ይህንን መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የጠየቀው እነዚህ መሰናክሎች ለዘሩባቤል ስኬት ምንም ተግዳሮት እንደማይሆኑ አጽንዖት ለመስጠት ነው። ጥያቄው በገለጻ መልክ ሊተረጎምም ይችላል። አት. "ታላቅ ተራራ፣ አንተ ምንም አይደለህም፤ ዘሩባቤል ሜዳ ያደርግሃል" ወይም "መሰናክሎች እንደ ተራራ ታላላቅ መስለው ቢታዩም፣ አንድ ሰው በተስተካከለ ሜዳ ላይ እንደሚራምድ ያህል ዘሩባቤል ድል ይነሣቸዋል።" (ተለዋጭ ዘይቤ እና መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የሚሉትን ይመልከቱ)

መደምደሚያውን ድንጋይ ያወጣል

መደምደሚያ ድንጋይ አንድ ነገር በሚገነባበት ጊዜ በመጨረሻ የሚቀመጠው ድንጋይ ነው። ይህ የሚያመለክተው በቤተ መቅደሱ ድምድማት ላይ የሚቀመጠውን ድንጋይ ነው። አት. "በቤተ መቅደሱ አናት ላይ የሚቀመጠውን ድንጋይ ያወጣል" ወይም "የቤተ መቅደሱን ግንባታ ያጠናቅቃል" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሞገስ ይሁንለት! ሞገስ ይሁንለት! እያሉ እየጮኹ

ለዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት፡ - 1) 'ሞገስ' የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሞገስ ሲሆን ሕዝቡም እግዚአብሔር የተጠናቀቀውን ቤተ መቅደስ እንዲባርክ እየጠየቁ ነው። አት. "'እግዚአብሔር ይባርከው! እግዚአብሔር ይባርከው!' እያሉ ሕዝቡ እየጮኹ ሳሉ" ወይም 2) 'ሞገስ' የሚለው ቃል የሚያመለክተው ውበትን ሕዝቡም የተጠናቀቀው ቤተ መቅደስ ምን ያህል ውብ እንደሆነ እየተናገሩ ነው። አት. "ሕዝቡ 'ውብ! ውብ እኮ ነው!' ብለው እየጮኹ ሳለ" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 4:8

አያያዥ መግለጫ

ከዘካርያስ ጋር የሚነጋገረው መልአክ ራዕዩን መግለጹን ይቀጥላል።

የያህዌ ቃል ወደ እኔ መጣ እንዲህ ሲል፡ - "የዘሩባቤል እጆች ..."

ፈሊጣዊው አባባል ጥቅም ላየ የዋለው ከእግዚአብሔር የመጣን የተለየ መልእክት ለማስተዋወቅ ነው። አት. "እግዚአብሔር መልእክትን ሰጠኝ፣ እንዲህም አለኝ፡ - 'የዘሩባቤል እጆች ...'" ወይም "ያህዌ ይህንን መልእክት ነገረኝ፡ - 'የዘሩባቤል እጆች ...'" (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

የዘሩባቤል እጆች ... መሠረት ጣሉ ... የሚፈጽሙትም የእርሱ እጆች ናቸው

እዚህ ላይ 'እጆች' የሚለው ቃል የሚወክለው ዘሩባቤልን ነው። አት. "ዘሩባቤል መሠረቱን ጥሏል ... የሚፈጽመውም እርሱ ነው።" (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

የዚህን ቤት መሠረት

እዚህ ላይ 'ቤት' የሚለው ቃል የሚወክለው ቤተ መቅደሱን ነው። አት. "የዚህ ቤተ መቅደስ መሠረት" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የጥቂቱን ነገር ቀን የናቀ ማን ነው? ይህ ሕዝብ ይደሰታል

ዘካርያስ ይህንን መልስ የማይጠብቀውን ጥያቄ የተጠቀመበት በተለይ 'የጥቂቱን ነገር ቀን' ስለናቁት ለመናገር ነው። አባባሉ በገለጻ መልክ ሊተረጎም ይችላል። አት. "የጥቂቱን ነገር ቀን የናቁ ይደሰታሉ" (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የጥቂት ነገሮች ቀን

'የጥቂት ነገሮች ጊዜ' ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን ሲገነቡ የነበሩበትንና ጥቂት እርምጃ እያሳዩ የመሰሉበትን ጊዜ ነው። አት. "የሥራው እርምጃ ዘገምተኛ የነበረበት ጊዜ" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ቱንቢው

ይህ የሚያመለክተው የሕንፃው ግድግዳዎች ትክክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሕንፃውን የሚገነቡ የሚጠቀሙበት ከገመድ ጫፍ ከባድ ነገር የታሠረበት መሣሪያ ነው።

እነዚህ ሰባት መቅረዞች ... ሁለት የወይራ ዛፎች

እነዚህ የሚያመለክቱት ዘካርያስ በዘካ.4፡2-3 ላይ የተመለከታቸውን ሰባት መቅረዞችና ሁለት የወይራ ዛፎችን ነው።

እነዚህ ሰባቱ መቅረዞች በምድር ሁሉ የሚዘዋወሩ የያህዌ ዓይኖች ናቸው

እነዚህ ሰባት መቅረዞች በተምሳሌትነት የያህዌን ዓይኖች ይወክላሉ፣ ነገር ግን ቃል በቃል የያህዌ ዓይኖች አይደሉም። መልአኩ የይህዌ ዓይኖች በመላው ምድር እንደሚዘዋወሩ አድርጎ የያህዌ ዓይኖች በምድር የሚደረገውን ሁሉ እንደሚመለከቱ ይና ገራል። አት. "እነዚህ ሰባት መቅረዞች በመላው ምድር የሚደረገውን ማንኛውንም ነገር የሚመለከቱትን የያህዌን ዓይኖች ይወክላሉ።" (ተምሳሌታዊ ቋንቋ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 4:12

እነዚህ ሁለት የወይራ ቅርንጫፎች ምንድን ናቸው?

እዚህ ላይ ዘካርያስ ጥያቄውን በመቀየር ከሁለቱ የወይራ ዛፎች ጋር ስለተያያዙት ቅርንጫፎች ይጠይቃል።

ሁለቱ የወርቅ ቧንቧዎች

እነዚህ ቧንቧዎች ቀደም ባለው የዘካርያስ ራዕይ መግለጫ ላይ አልተጠቀሱም ነበር። ከመቅረዙ ዘንግ መቀመጫ ላይ ካለው ማሰሮ ጋር የተያያዙ እንደሚሆኑና ለሚነደው የመቅረዝ ዘንግ ዘይት የሚያቀብሉ ሳይሆኑ አይቀሩም።

ወርቃማው ዘይት

እዚህ ላይ 'ወርቃማ' የሚለው የሚያመለክተው የዘይቱን ቀለም እንጂ ዘይቱ ከወርቅ የተሠራ ነው ማለት አይደለም።

እነዚህ ምን እንደሆኑ አታውቅምን?

መልአኩ ይህንን መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የጠየቀው ዘካርያስ እነዚህ ምን ማለት እንደሆኑ ሊያውቅ እንደሚገባው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ መልክ ሊተረጎምም ይችላል። አት. "በእርግጥ እነዚህ ምን ማለት እንደሆኑ ታውቃለህ።" (መልስ የማይጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 4:14

እነዚህ አዲስ የወይራ ዘይት ልጆች ናቸው

እነዚህ እነዚህን ሕዝቦች በተምሳሌትነት ይወክላሉ እንጂ ቃል በቃል ሕዝቡ አይደሉም። አት. "እነዚህ ሁለት ቅርንጫፎች የአዲስ የወይራ ዘይት ልጆችን ይወክላሉ" (ተምሳሌታዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

የአዲስ የወይራ ዘይት ልጆች

ይህ ፈሊጣዊ አባባል እነዚህ ሰዎች በአዲስ የወይራ ዘይት ተቀብተዋል ማለት ነው። የተቀባ ሰው በያህዌ የተመረጠ ወይም ለተለየ ተግባር የተሾመ ነው። አት. "የተቀቡ ሰዎች" ወይም "ያህዌ የሾማቸው ሰዎች" (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

በጌታ ፊት የሚቆሙ

'...ፊት መቆም' እርሱን ለማገልገል በአንድ ሰው ሕላዌ ፊት መቆም ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 5



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Zechariah 5:1
ከዚያ በኋላ ዘወር አልሁ
‘አልሁ’ በሚለው በውስጠ-ታዋቂ ‘እኔ’ የሚለው የሚያመለክተው ዘካርያስን ነው፡፡
እነሆ
‘እነሆ’ የሚለው ቃል ዘካርያስ በተመለከተው ነገር እንደተገረመ ያሳያል፡፡
ርዝመቱ ሃያ ክንድ ወርዱ አሥር ክንድ
አንድ ‘ክንድ’ 46 ሴንቲ ሜትር ነው፡፡ አት. “ርዝመቱ 9.2 ሜትር፣ ወርዱ 4.6 ሜትር” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርቀት የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 5:3
አጠቃላይ መረጃ
ከዘካርያስ ጋር የሚነጋገረው መልአክ ራዕዩን መግለጹን ይቀጥላል፡፡
ይህ … እርግማን ነው
‘ይህ’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመጽሐፉን ጥቅልል ነው፡፡ የመጽሐፉ ጥቅልል በጥቅልሉ ውስጥ ለተጻፈው ስመ-ምስል ስያሜ ነው፡፡ አት. “በዚህ መጽሐፍ ጥቅልል ውስጥ ያለው እርግማን ነው፡፡” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ በምድር ሁሉ የሚወጣ
‘በምድር ሁሉ’ የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው በምድሩ ያለውን ማንኛውንም ስፍራ ነው፡፡ ርግማኑ በምድሪቱ ውስጥ በሚኖር በማንኛውም ሰው ላይ እንደሚደርስ ይጠቁማል፡፡ አት. “በመላ ምድሪቱ ባለ ማንኛውም ሰው ላይ ማለት ነው” (ፈሊጣዊ አባባል፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
የሚሰርቅ ሁሉ ይጠፋል … በሐሰት የሚምል ሁሉ ይጠፋል
እነዚህን ሕዝቦች ከምድሪቱ የሚያስወግደው ያህዌ አንድ ሰው ከዛፍ ላይ ቅርንጫፍ እንደሚቆርጥ ሲቆርጣቸው እንደነበረ ተደርጎ ተነግሯል፡፡ ይህ በተናጋሪ መልክ ሊቀርብ ይችላል፡፡ አት. “ያህዌ ማንኛውንም ሌባ ያስወግዳል … ያህዌ በሐሰት መሐላ የሚምለውን ሁሉ ያስወግዳል” ወይም “ያህዌ ማንኛውንም ሌባ ከምድሪቱ ያስወግዳል … ያህዌ ከምድሪቱ በሐሰት የሚምለውን ማንኛውንም ሰው ያስወግዳል፡፡” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)
በአንድ በኩል የሚለውን … በሌላ በኩል የሚለውን
“የመጽሐፉ ጥቅልል በአንድ በኩል የሚለው … የመጽሐፉ ጥቅልል በሌላ በኩል የሚለው”
አመጣዋለሁ
“እልከዋለሁ”
ያህዌ … እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል፡፡ በዘካርያስ 1፡4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ፡፡ አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)
እንጨቱንና ድንጋዩን ያጠፋል
የሌባውንና በሐሰት የሚምለውን ቤቶች የሚያጠፋው ርግማን ሰዎቹ የሚኖሩባቸው ቤቶች የተሠሩባቸውን የሕንፃ ቁሳቁሶች እንደሚያቃጥል ተደርጎ ተነግሯል፡፡ አት. “እንጨቱንና ድንጋዩን ያጠፋል” ወይም “ሙሉ በሙሉ ያጠፋዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 5:5
ዓይኖችህን አንሣ
‘ዓይኖች’ የሚለው ቃል የሚወክለው የሚመለከተውን ሰው ነው፡፡ አት. “ወደ ላይ ተመልከት” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ሊመጣ ያለውን እፍ የያዘ ቅርጫት ነው
‘ኢፍ’ ደረቅ ነገሮች የሚለኩበት የልኬት መስፈሪያ ሲሆን መጠኑም 2.2 ሊትር ነው፡፡ እዚህ ላይ ቃሉ አንድ ኢፍ ደረቅ ነገሮች ለሚይዘው መስፈሪያ ስመ-ምስል ስያሜ ነው፡፡ አት. “ይህ ሊመጣ ያለው የመለኪያው ቅርጫት ነው” ወይም “ይህ ሊመጣ ያለው ትልቅ መስፈሪያ ነው” (መጽሐፍ ቅዱሳዊ የፍሳሽ መጠን እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)
በምድሪቱ ሁሉ ላይ ያለው የሕዝቡ በደል
ቅርጫቱ የሕዝቡን በደል በተምሳሌትነት ይወክላል ነገር ግን ቃል በቃል በደላቸው አይደለም፡፡ አት. “ይህ ቅርጫት በመላው ምድሪቱ ያሉትን ሰዎች በደል ይወክላል፡፡” (ተምሳሌታዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)
ከእርሳስ የተሠራው ክዳን ተነሣ
ይህ በተናጋሪ መልኩ ሊቀርበ ይችላል፡፡ አት. “አንድ ሰው ከቅርጫቱ ላይ የእርሳሱን ክዳን አነሣ” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከበታቹም በውስጡ የተቀመጠች ሴት ነበረች
“ከእርሳሱ ክዳን በታች በቅርጫቱ ውስጥ የተቀመጠች ሴት ነበረች”
Zechariah 5:8
ይህች ርኩሰት ናት
ሴትዮዋ ርኩሰትን ትወክላለች፡፡ አት. “ይህች ሴት ርኩሰትን ትወክላለች” (ተምሳሌታዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)
መልሶ አስገባት … የእርሳሱንም ክዳን …ገፍቶ
“መልሶ አስገባት … የእርሳሱንም ክዳን ገፍቶ” ‘መልሶ አስገባት’ ወይም ‘ወረወራት’ የሚለው ቃል መልአኩ እነዚህን ነገሮች በእንዴት ያለ ኃይል እንዳከናወነ ያመለክታል፡፡ ሴቲቱንም ሆነ ክዳኑን ቃል በቃል አልወረወራቸውም፡፡
ዓይኖችህን አንሣ
‘ዓይኖች’ የሚለው ቃል የሚወከለው የሚመለከተውን ሰው ነው፡፡ አት. “ወደ ላይ ተመልከት” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)
በክንፎቻቸውም ንፋስ ነበረ
ይህ ፈሊጣዊ አባባል ይበሩ ነበር የሚል ትርጉም አለው፡፡ አት. “ይበሩ ነበር” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)
ክንፎቻቸውም እንደ ሽመላ ክንፎች ነበሩ
ሽመላ ከሁለት እስከ አራት ሜትር ርዝመት የሚሆን ክንፍ ያለው ትልቅ የወፍ ዘር ነው፡፡ ዘካርያስ የሴትዮዋን ክንፍ ስፋት መጠን ከሽመላ ክንፍ ጋር ያነጻጽረዋል፡፡
ቅርጫቱንም በምድርና በሰማይ መካከል አነሡት
‘ምድር’ እና ‘ሰማይ’ የሚሉት ቃላት ሰማይን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋሉ የ… ዓይነት ናቸው፡፡ ሁለቱ ሴቶች ከቅርጫቱ ጋር መብረራቸው ውስጠ-ታዋቂ ነው፡፡ አት. “ቅርጫቱን ወደ ሰማይ አነሱትና በረሩ” (…ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
Zechariah 5:10
ቤተ መቅደስ ይሠሩለት ዘንድ ወደ ሲናር ምድር ይወስዱታል
የተደረገው ግድፈት ቀደም ካለው ቁጥር ሊወሰድ ይችላል፡፡ አት. “ቅርጫቱን የሚወስዱት በሲናር ምድር ቤተ መቅደስ ሊሠሩለት ነው፡፡” (ግድፈት የሚለውን ይመልከቱ)
ቅርጫቱ እዚያ ይቀመጣል
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊቀርብ ይችላል፡፡ አት. “ቅርጫቱን እዚያ ያስቀምጡታል” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)
በተዘጋጀለት ስፍራ
‘በተዘጋጀለት ስፍራ’ የሚሉት ቃላት አንድን መድረክ ወይም ቅርጫቱን የሚያስቀምጡበት አንድ ዓይነት የተዋቀረ ዝግጅትን ያመለክታል፡፡

Chapter 6
Zechariah 6:1
ዓይኖችህን አንሣ
‘ዓይኖች’ የሚለው ቃል የሚወከለው የሚመለከተውን ሰው ነው፡፡ ትኩ. “ወደ ላይ ተመልከት” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)
ከሁለቱ ተራሮች መካከል … ተራሮቹም የናስ ተራሮች ነበሩ
ሁለተኛው ሐረግ በአንደኛው ሐረግ ያሉትን ተራራዎች ስለገለጻቸው ሁለቱ በአንድነት ሊጣመሩ ይችላሉ፡፡ ትኩ. “በሁለቱ የናስ ተራሮች መካከል”
የመጀመሪያው ሠረገላ … መጋላ (ቀይ) ፈረሶች ነበሩት
ፈረሶቹ ሠረገሎቹን እንደሚስቡ ውስጠ-ታዋቂ ነው፡፡ አት. “የመጀመሪያውን ሠረገላ የሚስቡት ቀይ ፈረሶች ነበሩት” ወይም “የመጀመሪያውን ሠረገላ የሚስቡት ቀይ ፈረሶች ነበሩ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
Zechariah 6:5
እነዚህ አራት የሰማይ ንፋሶች ናቸው
ሐረጉ የሚያመለክተው ንፋስ የሚነፍስባቸውን አራት አቅጣጫዎች ማለትም ሰሜንን፣ ምሥራቅን፣ ደቡብንና ምዕራብን ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች ይህንን ዕብራይስጣዊ አገላለጽ ‘አራቱ መናፍስት’ ማለት እንደሆነ አድርገው ይተረጉሙታል፡፡
ከምድር ሁሉ ጌታ ፊት ቆመው ከነበሩት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

‘…ፊት መቆም’ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል እርሱን ለማገልገል በአንድ ሰው ሕላዌ ፊት መቆም ማለት ነው። ይህንን በዘካርያስ 4፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የምድርን ሁሉ ጌታ ማገልገል” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

የባለ አምባላይ (ነጭ) ፈረሶች ወደ ምዕራብ አገር

አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች ይህንን የዕብራይስጥ ሐረግ “ነጫጮቹ ፈረሶች ከእነርሱ በኋላ ይሄዳሉ” የሚል ትርጉም ጥቁሮቹን ፈረሶች ተከትለው ወደ ሰሜን አገር እንደሚሉ አድርገው ያቀርባሉ።

የባለ አምባላይ (ነጭ) ፈረሶች … የባለ ዝንጉርጉር ፈረሶች

እዚህ ላይ ፈረሶቹ የሚስቧቸውን ሠረገሎች ይወክላሉ። አት. “ነጫጭ ፈረሶች ያሉት ሠረገላ … ነው፤ ዝንጉርጉር ፈረሶች ያሉት ሠረገላ … ነው” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 6:7

ጮኾ እንዲህ አለኝ

“መልአኩ ጮክ ብሎ እንዲህ አለኝ”

እነሆ

“ወደ ጥቋቁሮቹ ተመልከተ”

መንፈሴን በሰሜን ምድር አሳርፈውታል

‘መንፈሴ’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያህዌን ነው፣ ስለሆነም ብዙ ትርጉሞች ‘የያህዌ መንፈስ’ በማለት ትርጉሙን ቀይረውታል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ 1) ‘መንፈሴ’ የሚለው ቃል የያህዌን ስሜት ይወክላል፣ እርሱንም ማሳረፍ ማለት ሠረገሎቹ ያህዌ በሰሜኑ ምድር ከእንግዲህ እንዳይቆጣ ያደርጉታል ማለት ነው። ትኩ. “የሰሜኑን ምድር በሚመለከት ያለኝን ቁጣ ያረጋጉታል” ወይም 2) ‘መንፈሴ’ የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ሕላዌ ይወክላል፣ ስለዚህ ሠረገሎቹ በሰሜን የሚኖሩት አይሁድ የእግዚአብሔርን በረከት እንዲያጣጥሙ ያደርጓቸዋል። ትኩ. “መንፈሴ በሰሜኑ ምድር እንዲያርፍ ያደርጉታል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 6:9

የያህዌ ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ … ውሰድ

ይህ ፈሊጣዊ አባባል አንድ የተለየ መልእክትን ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት. “ያህዌ እንዲህ የሚል መልእክት ሰጠኝ፡ ‘…ውሰድ’” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ነገረኝ፡ ‘…ውሰድ’” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ኤልዳይ፣ ጦብያ፣ ዮዳኤ፣ … ኢዮሴዴቅ

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያው ቀን

‘ዛሬ’

Zechariah 6:12

እንዲህ ብለው ንገረው

“ለኢያሱ እንደዚህ ብለህ ንገረው”

ስሙ ቅርንጫፍ የተባለው

‘ቅርንጫፍ’ የሚለው ቃል በያህዌ ሕዝብ ላይ በንጉሥነት የሚያገለግለውን መሲሐዊ ግለሰብ ያመለክታል። ያህዌ ይህ ሰው በዛፍ ላይ እንደበቀለ ቅርንጫፍ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ‘ቅርንጫፍ’ የሚለው ቃል ሹመትን የሚያመለክት በመሆኑ በእናንተም ቋንቋ ከዚሁ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ቃል መተርጎም አለበት። በዘካርያስ 3፡8 ላይ ይህንን ቃል እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱም በቦታው ይንሰራፋል

‘ይንሰራፋል’ የሚለው ቃል የአንድን ተክል ዕድገት ያመለክታል፣ ስለሆነም ሰውዬው ‘ቅርንጫፍ’ ነው የሚለውን ተለዋጭ ዘይቤ ይቀጥላል። ይህ ሰውዬው የቤተ መቅደሱን እንደገና መታነጽ ለመቆጣጠር እንደሚገለጥ ወይም ወደ ሥልጣን እንደሚመጣ የሚያመለክት ይመስላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በዙፋኑ የሚቀመጥ ካህን ይሆናል

ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ 1) ‘ቅርንጫፉ’ ንጉሥም ካህንም እንደሚሆን፣ ወይም 2) ‘ቅርንጫፉ’ ንጉሥ ንጉሣዊ ሥልጣኑን የሚጋራ ሌላ ሰው ደግሞ ካህን እንደሚሆን ነው። አት. “በዙፋኑ ላይ ካህን ይኖራል”

በሁለቱም መካከል የሰላም ምክር እንዲኖር ያደርጋል

‘ሁለቱ’ የሚለው ቃል የንጉሥነትና የካህንነት ሚናዎችን ያመለክታል። የዚህ ሐረግ ትርጉም ቀደም ባለው ሐረግ ትርጉም ላይ የተመሠረተ ነው። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ 1) ‘ቅርንጫፉ’ በታማኝነት የንጉሥነትና የካህንነት ተግባሩን ይወጣል እንጂ አንደኛውን ተግባር ለመፈጸም ብሎ ሌላኛውን አይተውም፣ ወይም 2) እንደ ንጉሥ የሚያገለግለውና እንደ ካህን የሚያገለግለው ሁለቱም በየግላቸው በታማኝነት ተግባራቸውን ያከናውናሉ፣ በአንድነትም በሰላም ሥራቸውን የሚያከናውኑ ይሆናሉ።

Zechariah 6:14

አክሊሉም … ይሰጣል

ይህ በተናጋሪ መልኩ ሊቀርብ ይችላል። አት. “አክሊሉን ትሰጣለህ” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

ኤልዳይ፣ ጦብያ፣ ዮዳኤ፣ … ሔን

እነዚህ የሰዎች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

ለሶፎንያስ ልጅ ለሔን እንደ መታሰቢያ

አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች ይህንን ሐረግ፣ “ለሶፎንያስ ልጅ ለጋስነት እንደ መታሰቢያ” ወይም “ለጋስ ለሆነው ለሶፎንያስ ልጅ እንደ መታሰቢያ” ብለው ይተረጉሙታል። በተጨማሪም አንዳንድ ዘመናዊ ትርጉሞች ‘ሔን’ የሚለውን ስም ‘ኢዮስያስ’ እንደሚል አድርገው ይተረጉሙታል።

በሩቅ ያሉት

ይህ በባቢሎን የቀሩትን ነው የሚያመለክተው። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እናንተም ታውቃላችሁ

በብዙ ቁጥር ‘እናንተም’ የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። (አንተ እና እናንተ የሚሉት አቀራረብ የሚለውን ይመልከቱ)

በእውነት የአምላካችሁን የያህዌን ድምፅ ስሙ

እዚህ ላይ ‘መስማት’ ማለት መታዘዝ ማለት ነው፣ ‘ድምፅ’ የሚለውም የሚወክለው ያህዌ የሚናገረውን ቃል ነው። አት. “በእውነት አምላካችሁ ያህዌ የሚናገረውን ታዘዙ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 7

Zechariah 7:1

በአራተኛው ቀን

‘አራተኛው ቀን ሲሆን’ (መደበኛ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ካሴሉ

‘ካሴሉ’ በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር ዘጠነኛው ወር ነው። የካሴሉ ወር በአውሮፓውያን (በጊሪጎሪያን) ዘመን አቆጣጠር ወደ ኅዳር ወር መጨረሻ አካባቢ ነው። (የዕብራውያን ወሮች እና ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚሉትን ይመልከቱ)

የያህዌ ቃል ወደ ዘካርያስ መጣ

ይህ ፈሊጣዊ አባባል አንድ የተለየ መልእክትን ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት. “ያህዌ ለዘካርያስ መልእክት ሰጠው” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ለዘካርያስ ነገረው” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ሳራሳርና ሬጌሜሌክ

እዚህ ላይ ‘መለመን’ ማለት መማፀን ወይም አጣዳፊ ጥያቄ ማቅረብ ማለት ነው።

በያህዌ ፊት

እዚህ ላይ ‘ፊት’ የሚለው ለያህዌ ሕላዌ ስመ-ምስል ስያሜ ነው። አት. “ያህዌ በተገኘበት” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በአምስተኛው ወር ማዘን … ይገባኛል

“5ተኛው ወር በሚሆንበት ጊዜ ማዘን ይገባኛል?” በግምታዊው እውቀት መሠረት በኢየሩሳሌም የነበረው ቤተ መቅደሱ በባቢሎናውያን የፈረሰው በዚህ ወር ስለነበረ የአይሁድ ሕዝቦች በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር በአምስተኛው ወር በከፊል ይጾሙ ነበር። አምስተኛው ወር በአውሮፓውያን (ጊሪጎሪያን) አቆጣጠር በሐምሌ ወር መጨረሻና በነሐሴ ወር መጀመሪያ ላይ ይውላል። (መደበኛ ቁጥሮች፣ ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና የዕብራውያን ወሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

በጾም አማካይነት

‘በመጾም’

Zechariah 7:4

የሠራዊት ጌታ የያህዌ ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ … ተናገር



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ፈሊጣዊ አባባል አንድ የተለየ መልእክትን ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንዲህ የሚል መልእክት ሰጠኝ፡ ‘…ተናገር’” ወይም “የሠራዊት ጌታ ያህዌ ይህንን መልእክት ነገረኝ፡ ‘…ተናገር’” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

በአምስተኛው ወርና በሰባተኛው ወር

‘5ተኛውና 7ተኛው ወሮች ሲሆኑ’ (መደበኛ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

በአምስተኛው

‘ወር’ የሚለው ቃል በመተርጎም ወቅት ሊጨመር ይችላል። አት. “በአምስተኛው ወር” (ግድፈት የሚለውን ይመልከቱ)

በሰባተኛው ወር

በግምታዊው እውቀት መሠረት የባቢሎን ንጉሥ በይሁዳ ላይ ገዢ አድርጎ ከሾመው ከጎዶልያስ መገደል በኋላ በኢየሩሳሌም ቀርተው የነበሩት አይሁድ ወደ ግብፅ የሸሹት በዚህ ወር ስለነበረ አይሁድ ያለቅሱ ነበር። ሰባተኛው ወር በአውሮፓውያን (ጊሪጎሪያን) አቆጣጠር በመስከረም ወር መጨረሻና በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ይውላል። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና የዕብራውያን ወሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

ለእነዚህ ሰባ ዓመታት

በግምታዊው እውቀት መሠረት የእስራኤል ሕዝቦች በባቢሎን ለሰባ ዓመታት ባሪያዎች ሆነው ነበር። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና ቁጥሮች የሚሉትን ይመልከቱ)

የጾማችሁት በእርግጥ ለእኔ ነበርን?

ጥያቄው የተጠየቀው ሕዝቡ የመጾማቸው እውነተኛ ምክንያት ምን እንደነበረ እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። በገለጻ መልክ ሊተረጎም ይችላል፡ -አት. “በእርግጥ ትጾሙ የነበረው ለእኔ አልነበረም” (መልስ የማያጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ትበሉና ትጠጡ የነበረው

ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ 1) ሃይማኖታዊ በዓላትን ሲያከብሩ ፈንጠዝያ ያደርጉና ይጠጡ የነበሩት፣ ወይም 2) በማይጾሙበት ጊዜ ሁሉ ሲበሉና ሲጠጡ የነበሩት

ትበሉና ትጠጡ የነበረው ለራሳችሁ አልነበረምን?

ጥያቄው የተጠየቀው ሕዝቡ በሚበሉበትና በሚጠጡበት ጊዜ ያህዌ ያከብሩ እንደነበረ ወይም እንዳልነበረ እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። አት. “ትበሉና ትጠጡ የነበራችሁት ለራሳችሁ ነበር” (መልስ የማያጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

የተናገረው ቃል ይህ አልነበረምን … ለምዕራብ

ያህዌ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ሕዝቡን ለመዝለፍ ነው። ይህ ጥያቄ በገለጻ መልክ ሊተረጎም ይችላል። አት. “እነዚህ ተመሳሳይ ቃላት ናቸው … ለምዕራብ” (መልስ የማያጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀደሙት ነቢያት አንደበት

እዚህ ላይ ‘አንደበት’ የሚለው በአንደበት ለተነገረው ቃል ስም-ምስል ስያሜ ነው። አት. “በቀደሙት ነቢያት ቃል” ወይም “በቀደሙት ነቢያት በኩል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁንም በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ናችሁ

“አሁንም በኢየሩሳሌም እየኖራችሁ ነው”

ኮረብቶች ግርጌ

ከተራራው ወይም ከሰንሰለታማ ተራሮች በስተግርጌ ያሉ ኮረብቶች

Zechariah 7:8

የያህዌ ቃል ወደ ዘካርያስ መጣ … እንዲህም አለው ‘ያህዌ …’

ይህ ፈሊጣዊ አባባል አንድ የተለየ መልእክትን ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። አት. “ያህዌ ለዘካርያስ መልእክት ሰጠው፣ እንዲህም አለው ‘ያህዌ’” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ለዘካርያስ ነገረው፡ - ‘ያህዌ’” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

በእውነተኛ ፍትሕ ዳኙ፣ ታማኝነትንና ምሕረትን አድርጉ

የነገር ስም የሆኑት ‘ፍትሕ’፣ ‘ታማኝነት’ እና ‘ምሕረት’ በቅጽል መልክ ሊገለጹ ይችላሉ። አት. “በምትዳኙበት ጊዜ፣ ፍትሐዊ ሁኑ፣ ለኪዳኑ ታማኝ፣ መሐሪም ሁኑ” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እያንዳንዱ ሰው ይህንን ያድርግ

‘ይህንን’ የሚለው ቃል እያንዳንዱ ሰው እንዴት መዳኘት እንዳለበት የሚያመለክት ነው።

መበለት

ባሏ የሞተባት ሴት

ድኀ-አደግ (ወላጁን-ያጣ)

ወላጆቹ የሞቱበት ልጅ

መጻተኛ

ከራሱ አገር ወደ ሌላ አገር የሄደ ሰው

ከእናንተ ማንኛችሁም በሌላው ላይ በልባችሁ ክፉ ነገር አታስቡ

እዚህ ላይ ‘ልብ’ የሚለው የአንድን ሰው ሃሳብ ይወክላል። አት. “ክፋትን ለማድረግ ዕቅድ ማቀድ የለባችሁም” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 7:11

በእልኸኝነት ጀርባቸውን አዞሩ

ይህ ባለቤቱ በጫንቃው (ትከሻው) ላይ ቀንበር እንዳይጭንበት የሚከለክል በሬ ምስል ነው። አት. “እልኸኛ መሆን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዳይሰሙ ጆሮአቸውን ደፈኑ

ይህ ከያህዌ የሆነውን መልእክት እንዳይሰሙ የሆነ ነገር ጆሮአቸው ውስጥ የሚያደርጉ ሰዎች ምስል ነው። ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ለመስማትና ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎችን ይወክላል። አት. “ለመስማት እምቢ አሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ የያህዌን ሕግ ወይም ቃሉን እንዳይሰሙ ልባቸውን እንደ ድንጋ አጠነከሩ

ያህዌን ለመስማትና ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆኑት ሕዝቦች ከማይበገር ድንጋይ ጋር ተነፃፅረዋል። እዚህ ላይ ልብ የሰውን ፈቃድ ወክሏል። አት. “የሠራዊት ጌታ የያህዌን ሕግ ወይም ቃሉን እንዳይሰሙ በእልኸኛነት እምቢ አሉ” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀደም ባሉት ጊዜያት

“ባለፉት ዘመናት”

በነቢያቱ አንደበት

እዚህ ላይ ‘የነቢያቱ አንደበት’ የሚለው ነቢያቱ በአንደበታቸው ለተነገሩት ቃል ስም-ምስል ስያሜ ነው። ትኩ. “በነቢያቱ ቃል አማካይነት” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 7:13

በዐውሎ ነፋስ እበትናቸዋለሁ

ያህዌ በመንገድ ላይ ያገኘውን ሁሉ እንደሚበትታትን ዓውሎ ንፋስ ሕዝቡን እንዴት እንደሚበታትናቸው እየተናገረ ነው። አት. “ዓውሎ ንፋስ ነገሮችን (ዕቃዎችን) እንደሚበትታትነ እበትትናቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓውሎ ንፋስ

በሚጓዝበት ጊዜ እጅግ ፈጣን ሽክርክሪት የሚሠራና ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ጠንካራ ንፋስ

መልካሚቱን ምድር

‘ደስ የምትል ምድር’ ወይም ‘ፍሬያማ ምድር’

Chapter 8

Zechariah 8:1

የያህዌ ቃል ወደ እኔ መጣ … እንዲህም አለኝ ‘ያህዌ …’

ይህ ፈሊጣዊ አባባል አንድ የተለየ መልእክትን ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። በዘካርያስ 7:4 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “ያህዌ መልእክት ሰጠኝ፣ እንዲህም አለኝ ‘ያህዌ’ ” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ነገረኝ፣ እንዲህም አለኝ ፡ -‘ያህዌ’” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ ጽዮን እጅግ ቀንቻለሁ

“ጽዮንን ለመከላከል ጠንካራ ፍላጎት አለኝ”

ለጽዮን

እዚህ ላይ ‘ጽዮን’ የጽዮንን ሕዝብ ይወክላል። አት. “ለጽዮን ሕዝብ” ወይም “ለኢየሩሳሌም ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በታላቅ ቁጣ

በግንዛቤ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ይህ ቁጣ በጽዮን ጠላቶች ላይ ነው። አት. “በጠላቶቿ ላይ በታላቅ ቁጣ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ የያህዌ ተራራ

በግንዛቤ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ይህ የኢየሩሳሌም ከተማ

የተገነባችበት ስፍራ ያለበትን የጽዮን ተራራን ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 8:4

በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ

"በኢየሩሳሌም ይኖራሉ"

በጣም ስለሚያረጁ … በእጆቻቸው ይይዛሉ

ሰዎች በጣም እስከሚያርጁ ድረስ በሕይወት መኖራቸው፣ ከተማይቱ ለረጅም ጊዜ በሰላምና በብልጽግና እንደምትቆይ ያመለክታል። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የከተማይቱ መንገዶች … ይሞላሉ

የከተማይቱ አደባባይ ስፍራዎች መደበኛ ሥራቸውን በሚያከናውኑ ሰዎች ይሞላሉ።

Zechariah 8:6

… ዓይኖች ፊት የማይቻል መስሎ የሚታይ ነገር ቢኖር

ዓይኖች መመልከትን ያመለክታሉ፣ መመልከት ደግሞ ሃሳብንና ብያኔን ይወክላል። አት. "አንድ ነገር ለ… የማይቻል መስሎ የሚታይ ቢሆን እንኳ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የዚህ ሕዝብ ትሩፋን

"በሕይወት ያሉት የይሁዳ ሕዝቦች"

በዓይኖቼ ፊት የማይቻል መስሎ ሊታይ ይገባል

ሕዝቡ በተስፋ ቃሎቹ እንዲያምኑ ለማግባባት ጥያቄው አሉታዊ መልስ ይጠብቃል። በገለጻ መልክ ሊተረጎም ይችላል። ትኩ. "በእርግጥ ለእኔ ይቻለኛል!" (መልስ የማያጠብቅ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በዓይኖቼ

ዓይኖች መመልከትን ያመለክታሉ፣ መመልከት ደግሞ ሃሳብንና ብያኔን ይወክላል። አት. "ለእኔ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ … እንዲህ ይላል

እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1፡4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. "የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል" ወይም "እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው" ('መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው' የሚለውን ይመልከቱ)

ሕዝቤን ላድናቸው (ላወጣቸው) ነው

በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ሕዝቡ ስደት ላይ ናቸው። አት. "ወደ ምርኮ የሄዱትን ሕዝቤን የይሁዳን ሰዎች ላድናቸው (ላወጣቸው) ነው" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ፀሐይ ከምትወጣበት ምድርና ፀሐይ ከምትጠልቅበት ምድር

ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1) ሕዝቡ ተሰደው የሄዱባቸውን የተለዩ አገሮች ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ቅኔያዊ የአገላለጽ መንገድ ነው። አት. "ከምሥራቅ በኩል ካለው ምድርና በምዕራብ በኩል ካለው ምድር" ወይም 2) ይህ ከሁሉም አቅጣጫ የሚል ትርጉም ያለው … አባባል ነው። ትኩ. "በማንኛውም አቅጣጫዎች ካሉት ከሁሉም አገሮች" (… የሚለውን ይመልከቱ)

በእውነትና በጽድቅ አምላካቸው እሆናለሁ

የነገር ስሞች የሆኑትን 'እውነት' እና 'ጽድቅ' የሚሉትን በማስወገድ ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አት. "አምላካቸው እሆናለሁ። ለእነርሱ ታማኝ እሆንላቸዋለሁ፣ ትክክለኛ በሆነ መንገድም አደርግላቸዋለሁ" (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 8:9

የቤቴ መሠረት ሲጣል

ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. "የቤቴን መሠረት ባነጻችሁበት ጊዜ" (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

እጆቻችሁን አበርቱ

ይህ ለሥራው ድፍረት አገኙ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. "ጠንክሩ ደግሞም በርቱ" (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነዚህ ቀናት በፊት

እዚህ ላይ 'እነዚያ ቀናት' የሚለው የሚያመለክተው የይሁዳ ሕዝብ ቤተ መቅደሱን መገንባት የጀመሩበትን ጊዜ ነው።

ሰብልም አልተሰበሰበም ነበር

"የሚመረት ምንም ሰብል አልነበረም"

ሰውም ሆነ እንሰሳ የሚያተርፈው ነገር አልነበረም

ሰዎቹም ሆኑ እንሰሶቹ መሬታቸውን ማረሳቸው ጥቅም አልነበረውም፣ ምክንያቱም ምንም ምግብ አያገኙበትም ነበር።

ይመጣም ሆነ ይሄድ ለነበረው ለማንኛውም ሰው

ይህ … ሰዎች ይሄዱባቸው የነበሩትን በማንኛውም ስፍራ የነበሩትን ሁሉንም የሕይወት ክንዋኔዎች የሚመለከት ነው። (… የሚለውን ይመልከቱ)

ማንኛውም ሰው በባልንጀራው ላይ እንዲነሳ አድርጌያለሁ

"ማንኛውም ሰው በሌላው ሰው ላይ እንዲነሳበት አድርጌያለሁ"

Zechariah 8:11

አሁን ግን እንደ ቀድሞው ዘመን አይሆንም፣ ከሕዝቤ ትሩፋን ጋር እሆናለሁ

"አሁን በእነዚህ የሕዝቡ ትሩፋን ላይ ቀድሞ እንዳደረግሁባቸው አላደርግባቸውም"

ቀደም ባሉት ዓመታት

'ባለፈው ጊዜ' ከግንዛቤ የተገኘው ይህ መረጃ የሚያመለክተው ሕዝቡ ቤተ መቅደሱን እንደገና መገንባት የጀመሩበትን ጊዜ ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የዚህ ሕዝብ ትሩፋን

ከግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ይህ ከምርኮ የተመለሱት የሕዝቡ ትሩፋን ናቸው። አት. "ከምርኮ የተመለሰው ሕዝብ" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የሰላም ዘር ይዘራል

ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. "ሕዝቡ በሰላም ዘር ይዘራሉ" (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ … እንዲህ ይላል

እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1፡3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. "የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል" ወይም "እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው" ('መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው' የሚለውን ይመልከቱ)

ምድር ምርቷን ትሰጣለች፣ ሰማይም ጠሉን ይሰጣል

ምድርና ሰማያት የሚፈለገውን እንደሚሰጡ ሰዎች ተደርገው ተነግረዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህን ነገሮች አወርሳለሁ

"እነዚህ ነገሮች ሁሉ እንዲኖሯቸው"

Zechariah 8:13

አናንተ ለሌሎች አገሮች የእርግማን ምሳሌ ሆናችሁ ነበር

በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ያህዌ ቤተ መቅደሱ እንዲፈርስና ሕዝቡ እንዲማረክ የፈቀደበት መንገድ ሌሎች አገሮች በያህዌ መረገም ማለት ምን እንደሆነ እንደ ምሳሌ እንዲጠቀሙበት አድርጓል። አት. "በቀጣኋችሁ ጊዜ ሌሎች አገሮች እኔ አንድን ሕዝብ በረገምኩ ጊዜ ምን እንደሚሆን ትምህርት ተማሩ" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤትና የእስራኤል ቤት

'ቤት' የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ሰዎች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። በዚህ ዓውድ በይሁዳና በእስራኤል መንግሥታት የሚኖሩትን ሕዝቦች ያመለክታል። አት. "የይሁዳና የእስራኤል ሕዝብ" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በረከት ትሆናላችሁ

ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ -1) በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት የይሁዳና የእስራኤል ሕዝቦች በአካባቢያቸው ላሉት ሕዝቦች በረከት እንደሚሆኑ ነው። አት. "በአካባቢያችሁ ላሉት አገሮች በረከት ትሆናላችሁ" ወይም 2) በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት በአካባቢያቸው ያሉት ሕዝቦች በያህዌ መባረክ ምን ማለት እንደሆነ እንደሚመለከቱ ነው። ትኩ. በምባርካችሁ ጊዜ ሌሎች አገሮች አንድን ሕዝብ ስባርክ ምን እንደሚሆን ይማራሉ። 3) ያህዌ የይሁዳንና የእስራኤልን ሕዝብ ይባርካል። አት. "ብዙ መልካም ነገሮችን እሰጣችኋለሁ" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እጆቻችሁን አበርቱ

ይህ ለሥራው ብርቱ መሆንን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. "ጠንክሩ ደግሞም በርቱ" (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ጉዳት ላደርስባችሁ

'ልቀጣችሁ'

ቁጣዬን ባነሳሱት ጊዜ

'ባስቆጡኝ ጊዜ'

ሐዘኔታ አላሳየሁም

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

‘ቅጣቴን ለማሳነስ አልወሰንኩም’
አያሩሳሌም
ይህ ለኢያሩሳሌም ሕዝብ ስመ-ምስል ስያሜ ነው። አት. “የኢያሩሳሌም ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ቤትና የእስራኤል ቤት
‘ቤት’ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ሰዎች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። በዚህ ዓውድ በይሁዳና በእስራኤል መንግሥታት የሚኖሩትን ሕዝቦች ያመለክታል። አት. “የይሁዳና የእስራኤል ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 8:16
ልታደርጓቸው የሚገባችሁ
‘ልታደርጓቸው’ በሚለው በውስጠ-ታዋቂ ‘እናንተ’ የሚለው የሚያመለክተው የይሁዳን ሕዝብ ነው።
እያንዳንዱ ሰው ከጎረቤቱ ጋር እውነትን ይነጋገር
የነገር ስም የሆነው ‘እውነትን’ የሚለው እውነት የሚለውን ቅጽል በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አት. “እያንዳንዱ ሰው ለጎረቤቱ እውነት የሆነውን መናገር አለበት።” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ለጎረቤቱ
እዚህ ላይ ጎረቤት የተባለው በአቅራቢያ የሚኖር ሰው ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ሰው ነው።
በአደባባያችሁም በእውነት፣ በፍትሐዊነትና ሰላምን በማስፈን ፍረዱ
የነገር ስም የሆኑትን ‘እውነት’፣ ‘ፍትሐዊነት’ እና ‘ሰላም’ በማስወገድ በድጋሚ ሊገለጽ ይችላል፡ - አት. “በአደባባዮቻችሁ ውሳኔ በምታደርጉበት ጊዜ እውነትና ትክክል በሆነ መንገድ እንዲሁም ሰዎች እርስ በርሳቸው በሰላም ሊኖሩ በሚችሉበት መንገድ ፍረዱ” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
በአደባባዮቻችሁ
በግምታዊው እውቀት መሠረት ይህ የሚያመለክተው ፍርድ የሚሰጥባቸውን ስፍራዎች ነው። አት. “ፍርድ በምትሰጡባቸው ቦታዎች”
በሐሰት መማልን አትውደዱ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ይህ የሚያመለክተው በፍርድ ሸንጎ የሚከናወነውን መሐላ ነው። አትአ. “በፍርድ ሸንጎ ጉዳዮች ላይ ሰዎች ሲዋሹ አትቀበሏቸው” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 8:18
የያህዌ ቃል ወደ እኔ መጣ ... እንዲህም አለኝ ‘ያህዌ ...’
ይህ ፈሊጣዊ አባባል አንድ የተለየ መልእክትን ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። በዘካርያስ 7:4 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “ያህዌ መልእክት ሰጠኝ፣ እንዲህም አለኝ ‘ያህዌ’” ወይም “ያህዌ ይህንን መልእክት ነገረኝ፣ እንዲህም አለኝ : -‘ያህዌ’” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ እኔ መጣ
እዚህ ላይ ‘እኔ’ የሚለው የሚያመለክተው ዘካርያስን ነው።
የአራተኛው፣ የአምስተኛው፣ የሰባተኛውና የአሥረኛው ወር ጾሞች
የ4ኛው፣የ5ኛው፣የ7ኛውና የ10ኛው ወር ጾሞች (መደበኛ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
የአራተኛው ወር ጾሞች
በግምታዊ እውቀት መሠረት ባቢሎናውያን የኢያሩሳሌምን ጥሰው የገቡት በከፊል በአራተኛው ወር በዚህ ወቅት ስለነበረ አይሁዳውያን በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር በከፊል በአራተኛው ወር ያለቅሱ ነበር። አራተኛው ወር በአውሮፓውይን (ጊሪጎርያን) ዘመን አቆጣጠር በሰኔ ወር መጨረሻና በሐምሌ ወር መጀመሪያ ላይ ይውላል። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና የዕብራውያን ወሮች የሚሉትን ይመልከቱ)
አምስተኛው ወር
በግምታዊ እውቀት መሠረት ባቢሎናውያን ቤተ መቅደሱን ያፈረሱት በዚህ ወቅት ስለነበረ አይሁዳውያን በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር በከፊል በአምስተኛው ወር ይጾሙ ነበር። አምስተኛው ወር በአውሮፓውይን (ጊሪጎርያን) ዘመን አቆጣጠር በሐምሌ ወር መጨረሻና በነሐሴ ወር መጀመሪያ ላይ ይውላል። በዘካርያስ 7:3 ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና የዕብራውያን ወሮች የሚሉትን ይመልከቱ)
ሰባተኛው ወር
በግምታዊው እውቀት መሠረት የባቢሎን ንጉሥ በይሁዳ ላይ ገዢ አድርጎ ከሾመው ከጎዶልያስ መገደል በኋላ በኢያሩሳሌም ቀርተው የነበሩት አይሁድ ወደ ግብፅ የሸሹት በዚህ ወር ስለነበረ አይሁድ ያለቅሱ ነበር። ሰባተኛው ወር በአውሮፓውያን (ጊሪጎሪያን) አቆጣጠር በመስከረም ወር መጨረሻና በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ይውላል። በዘካርያስ 7:5 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና የዕብራውያን ወሮች የሚሉትን ይመልከቱ
አሥረኛው ወር
በግምታዊው እውቀት መሠረት ባቢሎናውያን ኢያሩሳሌምን መክበብ የጀመሩት በዚህ ወር ስለነበረ አይሁድ ያለቅሱ ነበር። አሥረኛው ወር በአውሮፓውያን (ጊሪጎሪያን) አቆጣጠር በታህሣሥ ወር መጨረሻና በጥር ወር መጀመሪያ ላይ ይውላል። (ግምታዊ እውቀት፣ ውስጠ-ታዋቂ መረጃ እና የዕብራውያን ወሮች የሚሉትን ይመልከቱ)
የሐሴት፣ የተድላና የደስታ በዓላት
የነገር ስሞች የሆኑት ‘ሐሴት’ እና ‘ተድላ’ ቅጽልን በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አት. “በሐሴትና በተድላ የተሞሉ የደስታ በዓላት” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
የይሁዳ ቤት
‘ቤት’ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩት ሰዎች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። በዚህ ዓውድ የይሁዳንና የቢንያምን ዝርያዎችን በሚያካትተው በይሁዳ መንግሥት የሚኖሩትን ሕዝቦች ያመለክታል። አት. “የይሁዳ ሕዝቦች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
ፍቅር፣ እውነትና ሰላም
የነገር ስሞች የሆኑት ‘እውነት’ እና ‘ሰላም’ ቅጽልን በመጠቀም ሊተረጎም ይችላል። አት. “እውነትና ሰላም የሞላበትን ውደዱ” (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 8:20
ሕዝቦች እንደገና ይመጣሉ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ሕዝቡ የሚመጡት ወደ ኢያሩሳሌም ነው። አት. “ሕዝቦች እንደገና ወደ ኢያሩሳሌም ይመጣሉ።” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ወደ ሌላ ከተማ ይሄዳሉ
ይህ በሌላይቱ ከተማ ለሚኖሩት ሕዝቦች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። አት. “በሌላይቱ ከተማ ወዳሉት ሕዝቦች ይሄዳሉ።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
መለመን
እዚህ ላይ ’መለመን’ የሚለው መማፀን ወይም በአጣዳፊ ሁኔታ መጠየቅ ማለት ነው።
በያህዌ ፊት
እዚህ ላይ ‘ፊት’ የሚለው ለያህዌ ሕላዌ ስመ-ምስል ስያሜ ነው። በዘካርያስ 7:2 ላይ ይህንን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “ያህዌ በተገኘበት” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
የሠራዊት ጌታ ያህዌን ፈልጉ
ያህዌን ለማወቅና እርሱን ለማስደሰት የሚፈልጉ ቃል በቃል እርሱን ለማግኘት እንደሚፈልጉት ተደርገው ተጠቅሰዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ኃያላን መንግሥታት
ይህ በኃያላን መንግሥታት ውስጥ ለሚኖሩ ሕዝቦች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። አት. “የኃያላን መንግሥታት ሕዝቦች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 8:23
የልብሳችሁን ዘርፍ አጥብቀው በመያዝ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት መጻተኞቹ ወይም እንግዶቹ ሰዎች የእነርሱን ትኩረት ለማግኘት የልብሳቸውን ዘርፍ እንደሚይዙ ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከእናንተ ጋር አብረን እንሂድ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ኢያሩሳሌም እንደሚሄዱ ነው። አት. “ከእናንተ ጋር ወደ ኢያሩሳሌም እንሂድ” (ግምታዊ እውቀት

Chapter 9

Zechariah 9:1

… በሚመለከት ይህ የያህዌ ቃል አዋጅ ነው

“ይህ ስለ … የያህዌ መልእክት ነው”

የሴድራክና የደማስቆ ምድር

እዚህ ላይ ‘ሴድራክ’ እና ‘ደማስቆ’ በእነዚያ ስፍራዎች የሚኖሩትን ሕዝብ ያመለክታሉ። አት. “የሴድራክ ምድርና የደማስቆ ከተማ ሕዝቦች” (ስመ-ምስል ስያሜ እና ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሴድራክ

የሴድራክ አድራሻ አሁን የት እንደሆነ አይታወቅም።

ማረፊያ ቦታው

“የሴድራክ ሕዝብ ማረፊያ ቦታ”

የሰዎች ሁሉና የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ዓይኖች ወደ እግዚአብሔር አቅንቷል

እዚህ ላይ ‘ዓይኖች’ የሚመለከቱትን ነገር ያመለክታል። አት. “የሰው ልጆች ሁሉና የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ወደ ያህዌ ይመለከታሉ።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ሐማት

ይህ በዚያ ምድር የሚኖሩትን ሕዝቦች ያመለክታል። አት. “የሐማት ምድር ሰዎች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ጢሮስና ሲዶና

ይህ በዚያ ምድር የሚኖሩትን ሕዝቦች ያመለክታል። አት. “የጢሮስና የሲዶና ምድር ሰዎች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በጣም ጥበበኞች ስለሆኑ

ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1) ለዕርዳታ ወደ ያህዌ በመመልከታቸው ሕዝቡ ጠቢባን ናቸው ወይም 2) ዘካርያስ የሐማት ሰዎች በእርግጥ ጠቢባን ነበሩ ማለቱ ሳይሆን ሽሙጥ አነጋገር እየተጠቀመ ነበር። ትኩ. “ምንም እንኳን በጣም ጠቢባን ነን እያሉ የሚያስቡ ቢሆኑም” (ሽሙጥ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 9:3

ለራሷ ምሽግ ሠርታለች

እዚህ ላይ የጢሮስ ከተማ በሴት ተመስላለች። አት. “ጠንካራ ምሽግ ሠርታለች” ወይም “ከፍ ያለ ቅጥር ሠርታለች” (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

ብርን እንደ አፈር የነጠረንም ወርቅ እንደ መንገድ ላይ ጭቃ ቆልላለች

ጢሮስ ምን ያህል ባለጠጋ እንደነበረች አጽንዖት ለመስጠት ያህዌ የግነት አነጋገር ይጠቀማል። አት. “በመንገድ ላይ እንዳለ ጭቃ ብርንና ወርቅን አከማችታለች” (ግነት እና ጥቅል አባባል የሚባሉትን ይመልከቱ)

እነሆ፣ ጌታ ይወስድባታል

እዚህ ላይ ‘እነሆ’ የሚለው ቃል ተአንባቢው ለሚቀጥለው አስፈላጊ ገለጻ ትኩረት እንዲሰጥ ያሳስበዋል። አት. “አስተውል! ጌታ የጢሮስን ሀብት ይወስድባታል።”

በባሕር ላይ ያላትን ኃይል ይደመስሳል

‘በባሕር ላይ ያላት ኃይል’ የሚያመለክተው ለንግድና ለወረራ የሚውሉትን መርከቦች ነው። አት. “ሰዎች በባሕር ላይ ውጊያ የሚያካሂዱባቸውን የጢሮስን መርከቦች ይደመስሳል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በእሳት ፈጽማ ትጠፋለች

ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ጠላቶች ከተማይቱን እስክትወድም በእሳት ያቃጥሏታል” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 9:5

አስቀሎና፣ ጋዛ፣ አቃሮንም … ተስፋዋ

እነዚህ ከተሞች እያንዳንዳቸው በውስጣቸው የሚኖሩ ሕዝቦችን ያመለክታሉ። አት. “የአስቀሎና ሕዝቦች … የጋዛ ሕዝቦች … የአቃሮን ሕዝቦች ተስፋዎች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

አይታ

ጢሮስ ስትወድም ታያለች

እንግዶች ቤታቸውን በአሽዶድ ያደርጋሉ

“እንግዶች አሽዶድን ወስደው በዚያ ይኖራሉ”

የፍልስጥኤማውያንንም ትምክህት አቆርጣለሁ

እዚህ ላይ ‘እቆርጣለሁ’ የሚለው ትምክህታቸውን አስቆማለሁ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “ፍልስጥኤማውያን ከእንግዲህ በራሳቸው እንዳይመኩ አደርጋቸዋለሁ።” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ደሙን ከአፋቸው ነውራቸውንም ከጥርሳቸው መካከል አወጣለሁ

እዚህ ላይ ‘ደም’ ደም በውስጡ ላለበት ሥጋ፣ ‘ነውር’ ደግሞ ለጣዖት ለቀረበ ሥጋ ስመ-ምስል ስያሜዎች ናቸው። አት. “በውስጡ ደም ያለበትን ሥጋ ከእንግዲህ እንዲበሉ አልፈቅድላቸውም፣ ለጣዖት የሚያቀርቡትንም ምግብ እንዳይበሉ እከለክላቸዋለሁ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 9:8

በምድሬ ዙሪያ እሰፍራለሁ

እግዚአብሔር ምድሩን ለመጠበቅ በዙሪያው እንደሰፈረ ሠራዊት አድርጎ ስለ ራሱ ይናገራል። አት. “ምድሬን እጠብቃለሁ።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን

‘በዚያን ጊዜ’

በራሴ ዓይኖች እመለከታለሁ

‘በራሴ ዓይኖች’ የሚለው የያህዌን የግል ትኩረት ይወክላል። አት. “እኔ በግሌ ምድሬን እመለከታለሁ።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 9:9

አጠቃላይ መረጃ

ከቁ.9-13 ባሉት ተናጋሪው ያህዌ ይመስላል።

የጽዮን ልጅ ሆይ፣ በታላቅ ሐሴት ድምፅሽን አሰሚ፣ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ በደስታ እልል በዪ

የእነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ነው፣ ሁለቱም ደስ እንዲላቸው የተሰጠውን ትዕዛዝ ያጠናክራሉ። ያህዌ የኢየሩሳሌም ሕዝቦች እዚያ እንደነበሩ አድርጎ እየተናገረ ነው፣ እነርሱ ግን እዚያ አልነበሩም። (ትይዩነት እና የሌለን እንዳለ አድርጎ መናገር የሚሉትን ይመልከቱ)

የጽዮን ሴት ልጅ፣ የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ

‘ጽዮን’ እና ‘ኢየሩሳሌም’ አንድ ናቸው። ነቢዩ ስለ ከተማይቱ ሴት ልጅ እንደሆነች አድርጎ እየተናገረ ነው። በዘካርያስ 2:10 ላይ የጽዮን ሴት ልጅ የሚለውን እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ።

እነሆ

ይህ አንባቢው ለሚቀጥለው አስደናቂ ገለጻ የተለየ ትኩረት እንዲሰጥ ያሳስበዋል። አት. “ልብ በል” ወይም “እዚህ ላይ አስደናቂ እውነታ አለ”

ንጉሥሽ ወደ አንቺ በጽድቅ ይመጣል፣ያድንሽማል

“ንጉሥሽ ጻድቅ ነው፣ የሚመጣውም ሊያድንሽ ነው።”

በአህያ ላይ በአህያይቱም ውርንጫ ላይ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ናቸው፣ የሚናገሩትም ስለ አንድ እንስሳ ነው። ሁለተኛው ሐረግ ግልገል አህያ እንደሆነ መግለጫ ይሰጣል። አት. “በግልገል አህያ ላይ” (ጥምር አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ሠረገላውንም ከኤፍሬም እቆርጣለሁ

እዚህ ላይ ‘እቆርጣለሁ’ የሚለው እደመስሳለሁ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “በእስራኤል ያሉትን ለጦርነት የሚያገለግሉትን ሠረገሎች እደመስሳለሁ”

ፈረሶችንም ከኢየሩሳሌም

ስለ ‘ሠረገላ’ እና ስለ ‘ቀስት’ መጠቀሱ ፈረሶቹ ለጦርነት የሚያገለግሉ እንደነበሩ ያመለክታል። ይህንን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አት. “በኢየሩሳሌም ያሉት የውጊያ ፈረሶች” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ቀስቱ ከውጊያ ይቆረጣል

እዚህ ላይ ቀስት በጦርነት ጥቅም ላይ የሚውሉትን መሣሪያዎች ይወክላል። አት. “የጦር መሣሪያዎች ሁሉ ይደመሰሳሉ” (በከፊል የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

ሰላምን ለሕዝቦች ይናገራል

እዚህ ላይ ሰላምን የማወጅ ተግባር ሰላም የማድረግን ተግባር ይወክላል። አት. “ንጉሣችሁ ለሕዝቦች ሰላምን ያመጣላቸዋል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ግዛቱም ከባሕር እስከ ባሕር፣ ከወንዙ እስከ ምድር ዳርቻ ይሆናል

‘ከባሕር እስከ ባሕር’ እና ‘ከወንዙም እስከ ምድር ዳርቻ’ የሚሉት ሐረጎች

ትርጉማቸው አንድ እንደመሆኑ በአንድ ላይ ሊጣመሩ ይችላሉ። አት. “መንግሥቱ በመላው ምድር ላይ ይሆናል” (ጥምር አባባል የሚለውን ይመልከቱ)
ወንዙ
ይህ ምናልባት የኤፍራጥስን ወንዝ ሳያመለክት አይቀርም።
Zechariah 9:11
አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.9-13 ተናጋሪው ያህዌ ይመስላል።
አንቺ ጽዮን
እዚህ ላይ ‘አንቺ’ የሚለው ነጠላ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም ‘ጽዮን’ እየተባለችም የምትጠራውን የኢየሩሳሌምን ከተማ ነው።
ውሃ ከሌለበት ጉድጓድ
ይህ ደረቅ ጉድጓድ የባቢሎን ስደትን ይወክላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ምሽጎቻችሁ ተመለሱ
ኢየሩሳሌም ደህንነት ያለባት ስፍራ እንደሆነች እየተነገረ ነው። አት. “ደህንነታችሁ ወደሚጠበቅበት ወደ አገራችሁ ተመለሱ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የተስፋ እስረኞች
አገላለጹ በምርኮ ላይ ሳሉ እግዚአብሔር ገና ያድነናል ብለው ሲያምኑ የነበሩትን እስራኤላውያንን ያመለክታል። ትኩ. “በያህዌ ላይ ገና ያምኑ የነበሩ እስረኞች”
ሁለት እጥፍ አድርጌ እመልስላችኋለሁ
“ከእናንተ የተወሰደው እጥፍ ሆኖ ይመለስላችኋል”
ይሁዳን እንደ ቀስቴ እገትረዋለሁ
የይሁዳ ሕዝብ እግዚአብሔር ወደ ጦርነት እንደወሰደው ቀስት እንደሆኑ ተደርገው ተጠቅሰዋል። እዚህ ላይ ‘ይሁዳ’ የዚያ አገር ሕዝቦችን ያመለክታል። አት. “የይሁዳ ሕዝቦች እንደ ቀስቴ እንዲሆኑ አደርጋቸዋለሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)
በኤፍሬምም ኮረጆዎቼን እሞላለሁ
ያህዌ የሰሜኑን መንግሥት የእስራኤልን ሕዝብ በጠላቶቹ ላይ የሚወረውራቸው ቀስቶች እንደሆኑ አድርጎ ይናገራል። ኮሮጆ አንድ ወታደር ቀስቶቹን የሚይዝበት ከረጢት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ጽዮን ሆይ፣ ልጆችሽን አስነሣለሁ፣ ግሪክ ሆይ፣ በአንቺ ላይ
እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ ለሁለት የተለያዩ አገር ሕዝቦች እየተናገረ ነው። (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 9:14
አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.14-16 ዘካርያስ እግዚአብሔር እስራኤልን ከጠላቶቿ እንዴት እንደሚያድናት ይገልጻል።
ለእነርሱ ይገለጣል
‘ለእነርሱ’ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነው። አት. “በሰማይ ላይ በሕዝቡ ይታያል” ወይም “ወደ ሕዝቡ ይመጣል”
ፍላጻውም እንደ መብረቅ ይወጣል!
እስራኤላውያን አንዳንድ ጊዜ የመብረቅ ብልጭታ እግዚአብሔር የሚወረውረው ቀስት እንደሆነ አድርገው ያስባሉ። (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)
መለከትን ንፋ
መለከቶች የአውራ በግ ቀንዶች ናቸው። ሰዎች በጦርነት ጊዜ ምልክቶችን ለመስጠት በሌሎችም አጋጣሚዎች ይነፏቸዋል። እዚህ ላይ መለከቱ የተነፋው ለጦርነት ምልክት እንዲሆን ነው።
ከቴማንም ከዓውሎ ነፋስ ጋር ይጓዛል
ቴማን ከይሁዳ በስተደቡብ በኩል ያለ ስፍራ ነበር። እስራኤላውያን አንዳንድ ጊዜ ከደቡብ በሚነፍሰው ኃይለኛ ዓውሎ ነፋስ እንደሚጓዝ አድርገው ያስቡ ነበር። አት. “ከቴማን ከሚነፍሰው ዓውሎ ነፋስ ጋር ይጓዛል”
ይደመስሷቸዋል
“የይሁዳ ሕዝብ ጠላቶቻቸውን ይደመስሳሉ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በድንጋይ ወንጭፍም ያሸንፋሉ
ለድንጋይ መወርወሪያ የሚጠቅሙ ወንጭፎች በዘካርያስ ዘመን የተለመዱ ነበሩ። እዚህ ላይ ‘የወንጭፍ ድንጋይ’ እስራኤልን ለማጥቃት የሚጠቀሙባቸውን ወታደሮችን ያመለክታል። አት. “በወንጭፍና በድንጋይ የሚያጠቋቸውን ጠላቶች ድል ያደርጋል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያ በኋላም ይጠጣሉ፣ ወይን ጠጅ ጠጥቶ እንደሰከረ ሰውም ይጮኻሉ
የይሁዳ ሕዝብ እንደ ጯኺ ሰካራሞች በጠላቶቻቸው ላይ ስላገኙት ድል ይጮኻሉ፣ ድላቸውንም ያከብራሉ። አት. “ከዚያ በኋላ ይጮኻሉ፣ እንደ ሰከሩ ሰዎችም ድላቸውን በጩኸት ያከብራሉ” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ወጭት በወይን ጠጅ ይሞላሉ
ይህ ምናልባት ካህናት የእንሰሶችን ደም ወደ መሠዊያ ለመውሰድ የሚጠቀሙበትን ወጭት ሳያመለክት አይቀርም። አት. “ካህናት ደሙን ወደ መሠዊያ እንደሚወስዱባቸው ወጭቶች በወይን ጠጅ የተሞሉ ይሆናሉ።” (ምስስሎሽ፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
የመሠዊያውን ማዕዘኖች
መሠዊያዎች ወደ ውጭ ወጣ ወጣ ያሉ በእንስሳ ደም የረሰረሱ ማዕዘኖች አሏቸው። አት. “የመሠዊያው ማዕዘኖች በደም የተነከሩ እንደሆኑ ሁሉ እነርሱም እንደዚሁ የረሰረሱ ይሆናሉ” (ምስስሎሽ፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
Zechariah 9:16
አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.14-16 ዘካርያስ እግዚአብሔር እስራኤልን ከጠላቶቿ እንዴት እንደሚያድናት ይገልጻል።
እንደ ሕዝቡ መንጋ እግዚአብሔር ያድናቸዋል
የእስራኤል ሕዝብ የሚንከባከባቸውና የሚጠብቃቸው የእግዚአብሔር በጎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)
የአክሊል ዕንቁዎች ናቸው
የእስራኤል ሕዝብ ምን ያህል የከበረ እንደሆነ በሚያመለክተው የንጉሡ አክሊል ላይ የተደረጉ ውድ ዕንቁዎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “በአክሊል ላይ እንደተደረጉ ውብ የከበሩ ድንጋዮች ናቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ምን ያህል መልካምና ምን ያህል ውብ ይሆናሉ!
ይህ ቃለ-አጋኖ እንጂ ጥያቄ አይደለም። አት. “እጅግ መልካምና ውብ ይሆናሉ።” (ቃለ-አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)
እህል ጎልማሶችን፣ ጣፋጭ ወይንም ደናግሉን ያሳምራል
ማንኛውም ሰው የተትረፈረፈ ምግብና መጠጥ እንደሚኖረው ለማመልከት ይህ ዓረፍተ ነገር የትይዩነት አወቃቀር ይጠቀማል። አንባቢዎቻችሁ ወንዶቹ ብቻ እንደሚበሉ፣ ሴቶቹ ብቻ እንደሚጠጡ የሚያስቡ ከሆነ አባባሉን መለወጥ ሊያስፈልጋችሁ ይችላል። አት. “ሁሉም ሰዎች፣ ወንዶችም ሴቶችም የተትረፈረፈ የሚበላና የሚጠጣ ይኖራቸዋል” (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)
ጎልማሶቹ ... ደናግሉ
ሁለቱ ቃላት ትይዩዎች ናቸው፣ በአንድነትም መላውን የእስራኤል ሕዝብ ይወክላሉ። (በከፊል የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)
እህል ... ጣፋጭ ወይን ጠጅ
ሁለቱ ቃላት ትይዩዎች ናቸው፣ በአንድነትም ሁሉንም የተለያዩ ምግቦችና መጠጦች ይወክላሉ። (ትይዩነት እና በከፊል የተወከለ አካል የሚሉትን ይመልከቱ)

Chapter 10
Zechariah 10:1
አጠቃላይ መረጃ
ዘካርያስ ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።
ነገድጓዶችን ይፈጥራል
“ዝናብ እየጎረፈ የሚወጣባቸውን ደመናዎች ይፈጥራል”
በእርሻ ላይ ሰብል
“በእርሻ ላይ ሰብል እንዲበቅል ያደርጋል”
በቤት ውስጥ የተቀረጹ ጣዖቶች ሐሰት ይናገራሉ
“በቤት ውስጥ የተቀረጹ ጣዖቶች ሐሰተኛ መልእክት ይሰጣሉ” ዘካርያስ ጣዖቶች በእርግጥ ይናገራሉ የሚል ሃሳብ እየሰጠ አይደለም። ሰዎች ከጣዖቶች ሰማን እያሉ ስለሚናገሯቸው መልእክቶች እያመለከተ ነው። UDB ይህንን ግልጽ ያደርገዋል።
ሟርተኞች የውሸት ራዕይ ያያሉ
“ሟርተኞች ሐሰት የሆነ ራዕይ ይመለከታሉ”
አታላይ ሕልሞችን ይናገራሉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት እነርሱ እነዚህ ሕልሞች ሐሰት እንደሆኑ ያውቃሉ። ይህንን በግልጽነት ማቅረብ ይቻላል። አት. “ሰዎችን ለማታለል ሲሉ ሟርተኞች ስለ ሕልማቸው ይዋሻሉ።” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከንቱ መጽናናት
ለጊዜው የሚያባብሉ እንጂ ዘላቂ ዕርዳታ የማይሰጡ ቃላትን የሚያመለክት ነው።
እንደ በጎች ይቅበዘበዛሉ
እውነቱን የሚናገሩ ነቢያት የሌላቸው ሕዝቦች ወዴት እንደሚሄዱ የሚነግራቸው እረኛ የሌላቸው በጎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “ሐሰተኛ ነቢያትን የሚያዳምጡ ሕዝቦች በየት በኩል እንደሚሄዱ እንደማያውቁ በጎች ናቸው።” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)
እረኛ ስለሌላቸው ይሰቃያሉ
እውነቱን የሚናገሩ ነቢያት የሌላቸው ሕዝቦች ወዴት እንደሚሄዱ የሚነግራቸው እረኛ ስለሌላቸው የሚሰቃዩ በጎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “ሐሰተኛ ነቢያትን የሚያዳምጡ ሕዝቦች የሚመራቸው እረኛ ስለሌላቸው እንደሚሰቃዩ በጎች ናቸው።” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 10:3
አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.3-5 የሚናገረው ያህዌ ይሁን ወይም ዘካርያስ በያህዌ ምትክ ሆኖ እየተናገረ እንደሆነ ግልጽ አይደለም።
ቁጣዬ በእረኞች ላይ ነዶአል
እዚህ ላይ “እረኞች” የእግዚአብሔርን ሕዝብ መሪዎች ይወክላል። የያህዌ የቁጣ ብርታት የሚነድ እሳት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አት. “በሕዝቤ እረኞች ላይ ያለኝ ቁጣ እንደ እሳት ብርቱ ነው።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የምቀጣው ተባዕት ፍየሎችን፣ መሪዎችን ነው
ተባዕት ፍየሎች ከእንስቶቹ ይልቅ በኃይለኝነታቸው በተለይ የታወቁ ናቸው። እዚህ ላይ ‘ተባዕት ፍየሎች’ ጨቋኝ የነበሩትን የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች ይወክላሉ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሠራዊት ጌታ ያህዌ ለመንጋው ለይሁዳ ቤትም ይጠነቀቃል
እዚህ ላይ ያህዌ ለሕዝቡ የሚያደርገው እንክብካቤ እረኛ ለበጎቹ እንደሚያደርገው እንክብካቤ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አት. “እረኛ ለበጎቹ እንክብካቤ እንደሚያደርግላቸው የሠራዊት ጌታ ያህዌ ለይሁዳ ቤት እንክብካቤ ያደርጋል”
የይሁዳ ቤት
‘ቤት’ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። እዚህ ላይ የሚያመለክተው የይሁዳንና የቢንያምን ዝርያዎች የሚያካትተውን የይሁዳን ሕዝብ ነው። ትኩ. “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ጦርነት ፈረሶቹ ያደርጋቸዋል
ያህዌ የሕዝቡን ተለዋጭ ዘይቤ ተካላካይ ከሌላቸው በጎች ወደ ጦርነት ፈረሶች ይለውጣል። አት. “በውጊያ ላይ ብርቱ እንደሆኑ የጦርነት ፈረሶች ያደርጋቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምስስሎሽ የሚሉትን ይመልከቱ)
Zechariah 10:4
አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.3-5 የሚናገረው ያህዌ ይሁን ወይም ዘካርያስ በያህዌ ምትክ ሆኖ እየተናገረ እንደሆነ ግልጽ አይደለም።
ከይሁዳ የማዕዘን ራስ ድንጋይ ይመጣል
“የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ ከይሁዳ ይመጣል” በጣም አስፈላጊ የሆነው ገዢ የሕንፃው ዋና መሠረት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አት. “ከይሁዳ ዝርያዎች አንዱ በጣም አስፈላጊ የሆነው ገዢ ይሆናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የማዕዘን ራስ ድንጋይ ... የድንኳን ካስማ ... የውጊያ ቀስት
ለእነዚህ ሶስት ነገሮች ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት፡ - 1) ከይሁዳ ነገድ የሚመጣውን መሲሑን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋሉ ተምሳሌታዊ አባባሎች ሊሆኑ ይችላሉ፣ ወይም 2) ከይሁዳ የሚመጡ የተለያዩ መሪዎችን ሊያመለክት ይችላል። (ተምሳሌታዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)
ከእርሱም የድንኳን ካስማ
“ከእርሱ ዘንድ የድንኳን ካስማ ይመጣል” የድንኳን ካስማ ሰዎች የሚኖሩባቸውን ድንኳኖች የሚደግፉትን ገመዶች የሚይዘው ነው። እዚህ ላይ በጣም አስፈላጊ የሆነው ገዢ ድንኳኑን በስፍራው እንደሚይዘው የድንኳኑ ዋና ካስማ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አት. “አገሪቱን በአንድነት አስተባብሮ የሚይዘው መሪ ከይሁዳ ይመጣል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእርሱ ዘንድ የጦርነቱ ቀስት ይመጣል
“የጦርነቱ ቀስት ከእርሱ ዘንድ ይመጣል” እዚህ ላይ በጣም አስፈላጊ የሆነው ገዢ በጦርነት ጊዜ ጥቅም ላይ እንደሚውለው የጦርነት ቀስት እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አት. “ወታደራዊው መሪ ከይሁዳ ይመጣል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእርሱ ዘንድ ማናቸውም መሪዎች በአንድነት ይመጣሉ
“ማንኛውም መሪ ከይሁዳ ይመጣል”
እንደ ተዋጊዎች ይሆናሉ ... በውጊያ ወቅት ያሉ መንገዶች
ከይሁዳ የሚመጡት ገዢዎች ድል አድራጊ ተዋጊዎች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “በጦርነት ኃይለኞች ይሆናሉ፣ ጠላቶቻቸውንም እንደ መንገድ ጭቃ ይረግጣሉ” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)
በጦርነት ጊዜ ጠላቶቻቸውን እንደ መንገድ ጭቃ ይረግጣሉ
እንደ ጭቃ መርገጥ ሙሉ በሙሉ ድል ነሷቸው ለማለት የዋለ ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “ጠላቶቻቸውን ሙሉ በሙሉ ድል የሚያደርጉ” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ ከእነርሱ ጋር ነው
እዚህ ላይ ‘ከእነርሱ ጋር’ የሚለው ሊረዳቸው በዚያ እንደሚገኝ የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “ያህዌ ይረዳቸዋል” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)
የጦር ፈረሶችን የሚጋልቡትን ያሳፍራሉ
እዚህ ላይ ኃፍረት መሸነፍን የሚያጅብና የሚወክል ነው። አት. “የጦር ፈረሶችን የሚጋልቡትን ድል ያደርጋሉ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 10:6
አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.6-12 ላይ ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።
የይሁዳ ቤት
‘ቤት’ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። እዚህ ላይ የሚያመለክተው የይሁዳንና የቢንያምን ዝርያዎች የሚያካትተውን የእስራኤልን መንግሥት ነው። አት. “ይሁዳ” ወይም “የይሁዳ መንግሥት” ወይም “የይሁዳ ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
የዮሴፍ ቤት
‘ቤት’ የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ስመ-ምስል ስያሜ ነው። እዚህ ላይ የሚያመለክተው የይሁዳንና የቢንያምን ዝርያዎች የሚያካትተውን የይሁዳን መንግሥት ነው። አት. “እስራኤል” ወይም “የእስራኤል መንግሥት” ወይም “የእስራኤል ሕዝብ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
አልጣልኳቸውም
ይህ ስለ ሕዝቡ ያህዌ እንደሚያወልቀውና እንደሚጥለው እንደተቀዳደ ወይም እንደ ቆሸሸ ልብስ ይናገራል። ይህ መተውን ወይም መጣልን በተምሳሌትነት ይገልጻል። አት. “አልጣልኳቸውም” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተምሳሌታዊ ተግባር የሚሉትን ይመልከቱ)
ኤፍሬም እንደ ተዋጊ ይሆናል
‘ኤፍሬም’ እዚህ ላይ ሰሜናዊውን የእስራኤል መንግሥት ያመለክታል። ተዋጊዎች ብርቱዎች ናቸው። አት. “ኤፍሬም እጅግ ብርቱ ይሆናል” (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)
የወይን ጠጅ የጠጡ ደስ እንደሚላቸው ልባቸው ሐሴት ያደርጋል
እዚህ ላይ ‘ልብ’ መላውን ሰው ያመለክታል። ወይን ጠጅ በመጠጣት ደስ እንደሚለው ሁሉ እነርሱም እንደዚሁ ደስ ይላቸዋል። አት. “በጣም ደስ ይላቸዋል” (በከፊል የተወከለ አካል እና ምስስሎሽ የሚሉትን ይመልከቱ)
ልጆቻቸው ይመለከታሉ ሐሴትም ያደርጋሉ ... በእኔም ደስ ይላቸዋል
“ለእነርሱ ያህዌ ስላደረገላቸው ነገር ልጆቻቸው የተደረገውን ተመልክተው ደስ ይላቸዋል!”
Zechariah 10:8
አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.6-12 ላይ ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።
እፏጫለሁ
ማፏጨት በተጋጠሙ ከንፈሮች መካከል በሚወጣ ትንፋሽ ከፍተኛ የሚያቃጭል ድምፅ ነው። እዚህ ላይ እንደተደረገው ብዙውን ጊዜ ለሌሎች ሰዎች ምልክት ለመሰጠት የሚደረግ ነው።
በሕዝቦች መካከል ዘራኋቸው

የሕዝቡ መማረክ ያህዌ በሩቅ አገር እንደተከላቸው ዘሮች እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በቂ ስፍራ እስከማይገኝላቸው ድረስ
ሕዝቡ ወደ ይሁዳ መመለሳቸውን ስለሚቀጥሉ እዚያ ለመኖር ምንም ተጨማሪ ሕዝብ ለመቀበል ቦታ እስከማይኖር ድረስ የተጨናነቀ ይሆናል። ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ሙሉ በሙሉ ምድሪቱን ይሞሏታል”
Zechariah 10:11
አጠቃላይ መረጃ
ከቁ.6-12 ላይ ያህዌ ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።
በእነርሱ የመከራ ባሕር ውስጥ አልፋለሁ
የእግዚአብሔር ቃል ብዙውን ጊዜ ባሕር የብዙ ችግሮችና ጭንቀቶች ምስል እንደሆነ ያመለክታል። እዚህ ላይ ያህዌ በእነዚህ ጭንቀቶች ውስጥ ሲያልፉ ሕዝቡን እንደሚያጅባቸው እየተናገረ ነው። አት. “እኔ ከእነርሱ ጋር አሄዳለሁ፣ በብዙ ጭንቀቶቻቸው ውስጥ በሚያልፉበትም ጊዜ እረዳቸዋለሁ።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የዚያንም ባሕር ማዕበል እመታለሁ
እዚህ ላይ የባሕሩን ማዕበል ‘እመታለሁ’ የሚለው ማዕበሉ እንዳይከሰት አስቆመዋለሁ ለማለት የሚውል ፈሊጣዊ አባባል ነው። የሕዝቡን ጭንቀት ማስቆም የዚያን ባሕር ማዕበል እንደማረጋጋት ሆኖ እየተነገረ ነው። አት. “ያንን የመከራ ባሕር ማዕበል እንዲቆም አደርገዋለሁ” (ፈሊጣዊ አባባል እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
የዓባይም ጥልቅ ሁሉ ይደርቃል
“የዓባይ ወንዝ ውሃውን ሁሉ እንዲያጣ አደርገዋለሁ”
የአሦርም ግርማ ይዋረዳል
እዚህ ላይ ‘የአሦር ግርማ’ የአሦርን ጦር ሠራዊት የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም። (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
የግብፅም በትረ መንግሥት ከግብፃውያን ይወገዳል
እዚህ ላይ ‘የግብፅ በትረ መንግሥት’ የግብፅን ፖለቲካዊ ኃይል የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም። አት. “ግብፅ ሌሎች አገሮችን የመግዛት ኃይሏ ያበቃል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
በእኔ በራሴ አበረታቸዋለሁ
“ብርቱ እንዲሆኑና በእኔ እንዲያምኑ አደርጋቸዋለሁ”
በስሜም ይመላለሳሉ
እዚህ ላይ ‘በስሜ’ የሚለው ያህዌ የሚለውን ያደርጋሉ የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “እኔ እንዲያደርጉ እንደምፈልግባቸው ይታዘዙኛል ያከብሩኛልም።” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1፡4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 11
Zechariah 11:1
ሊባኖስ ሆይ፣ እሳት እንዲያወድማቸው በሮችሽን ክፈቺ
ሊሆን ያለውን መቋቋም አለመቻሉ ሊባኖስ በሮችዋን እንደምትከፍት ሆኖ እየተነገረ ነው። እዚህ ላይ ‘ሊባኖስ’ የሊባኖስን ሕዝብ የሚወክል ስመ-መስል ስያሜ ነው። አት. “የሊባኖስ ሕዝብ ሆይ፣ እሳት ሊያወድም ስለሆነ ተዘጋጁ” ወይም “የሊባኖስ ሕዝብ ሊያወድም ያለውን እሳት ለማስቆም አትሞክሩ” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ስመ-ምስል ስያሜ የሚሉትን ይመልከቱ)
እሳት ዝግባዎችሽን እንዲያወድም
እሳት ዝግባዎችን ፈጽሞ ማቃጠሉ እሳት ዝግባዎቹን እንደሚያወድም ተደርጎ ተነግሯል። አት. “እሳት ሙሉ በሙሉ ዝግባዎችሽን እንዲያወድም” ወይም “እሳት ሙሉ በሙሉ ዝግባዎችሽን እንዲያቃጥል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የጥድ ዛፎች ሆይ፣ የዝግባ ዛፎች ወድቀዋልና አልቅሱ
የጥድ ዛፎች እንደ ሰው እንደሚያዝኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “ዛፎች ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ በኃዘን ያለቅሱ ነበር። ዝግባዎቹ ስለተቃጠሉና ስለወደቁ የጥድ ዛፎቹ ለብቻቸው ቆመዋል።” (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)
የከበሩትም ጠፍተዋል
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ግርማ ያላቸው የዝግባ ዛፎች ከእንግዲህ የሉም” ወይም “የዝግባ ዛፎቹ በአንድ ወቅት ግርማ ያላቸው ነበሩ፣ አሁን ግን ጠፍተዋል።” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)
የባሳን ወርካዎች ሆይ፣ አልቅሱ፣ ጠንካራ የነበረው ደን ጠፍቶአልና
የባሳን ወርካዎች እንደ ሰው እንደሚያዝኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. “ጥቅጥቅ ያሉት ደኖቻቸው ስለተመነጠሩ፣ የባሳን ወርካዎች ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ ያለቅሱ ነበር።” (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)
እረኞች ዋይ ይላሉ
“እረኞች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ያለቅሳሉ”
ክብራቸው ተገፎአልና
እዚህ ላይ ‘ክብራቸው’ የሚለው ምናልባት እረኞች በጎቻቸውን የሚያሰማሩባቸውን ለምለም ግጦሽ የሚወክል ሳይሆን አይቀርም። አት. “ለምለም ግጦሾቻቸው ጠፍተዋልና” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
የዮርዳኖስ ወንዝ ትዕቢት ወድሟል
እዚህ ላይ ‘ትዕቢት’ ምናልባት የሚለው በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ የበቀሉትን ደኖች የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም። አት. “ይኖሩባቸው በነበሩት በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ የነበሩት ዛፎችና ቁጥቋጦዎች ስለወደሙ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 11:4
አጠቃላይ መረጃ
በ11፡4-17 የሁለት እረኞች ታሪክ ቀርቧል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ -1)ያህዌ ሕዝቡን እንዴት እንደሚይዝ ለመግለጽ በተምሳሌታዊ ተግባር ዘካርያስ የአንድ መንጋ እረኛ ይሆናል። 2)ያህዌ ሕዝቡን እንዴት እንደሚይዝ ለማስተማር ዘካርያስ ምሳሌ ይናገራል። ከእነዚህ ሁለት ትርጉሞች የትኛው ትክክል እንደሆነ እርግጠኛ ስላልሆነ፣ በትርጉም ወቅት ማንኛውንም ትርጉም አለመወሰን መልካም ይሆናል። (ተምሳሌታዊ ተግባር እና ምሳሌዎች የሚሉትን ይመልከቱ)
ለዕርድ የተለዩትን መንጋዎች ጠብቅ
“ባላቤቶቻቸው ለዕርድ ያቀዷቸውን በጎች ተንከባከብ”
አልተቀጡም
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ማንም አይቀጣቸውም” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)
የምድሪቱ ነዋሪዎች
“የምድሩ ሕዝብ”
ያህዌ ... እንዲህ ይላል
እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1፡4 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. “የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል” ወይም “እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው” (‘መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው’ የሚለውን ይመልከቱ)
ተመልከቱ
“አድምጡ” ወይም “ልብ አድርጉ”
እኔ ራሴ
‘ራሴ’ የሚለው ቃል እነዚህን ነገሮች የሚያደርገው ይህዌ እንደሆነ አጽንዖት ለመስጠት ነው። (አጽንዖት የሚሰጡ ተወላጠ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ሰውን ሁሉ ለባልንጀራው እጅና ለንጉሡ እጅ አሳልፎ መስጠት
እዚህ ላይ ‘እጅ’ ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ይወክላል። አት. “ሕዝቡ እርስ በርሳቸው እንዲጎዳዱ አደርጋለሁ፣ ንጉሡም ይጨቁናቸዋል።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
ማናቸውንም ከእጃቸው አላድናቸውም
እዚህ ላይ ‘እጅ’ ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ይወክላል። አት. “ከሚጎዷቸው አላድናቸውም” ወይም “አላድናቸውም” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 11:7
የበግ ንግድ የሚሠሩ
“በጎችን የሚገዙና የሚሸጡ”
ሞገስ
ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን ‘ፀጋ’፣ ‘ውበት’ እና ‘ደስ የሚል’ ብለው

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይተረጉሙታል
በእነርሱ ምክንያት ትዕግሥት አጣሁ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1) ‘እነርሱ’ የሚለው ሶስቱን እረኞች ያመለክታል። ወይም 2) ‘እነርሱ’ የሚለው የበጎቹን ባለቤት ያመለክታል።
የሚጠፉት ይጥፉ
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡ - አት. “እያለቁ ያሉት በጎች ይለቁ” ወይም “የሚቅበዘበዙትና የሚጠፉት በጎች ይጥፉ” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 11:10
ኪዳኑ ፈርሶአል
ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡ - አት. “ኪዳኑ አበቃ” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)
ያህዌ እንደተናገረ አወቅሁ
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት የሚመለከቱት በበትሩ መሰበር አማካይነት ያህዌ መልእክት እንደሰጣቸው አውቀው ነበር የሚል ነው። አት. “ያህዌ መልእክት እንደሰጣቸው አውቀዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ሰላሳ የብር መክሊት
በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ይህ ለእረኛ በጣም ዝቅተኛ ክፍያ ነው። አት. “ሰላሳ መክሊት ብር ብቻ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ሰላሳ መክሊት
’30 መክሊቶች’ (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 11:13
አጠቃላይ መረጃ
ስለ እረኞችን ስለ በጎች የሚነገረው ምሳሌ ቀጥሏል።
ግምጃ ቤት
ይህ በያህዌ ቤተ መቅደስ ካህናቱ ገንዘብ የሚያስቀምጡበት ቦታ ነው። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን ‘አንጥረኛ’ ብለው ይተረጉሙታል። ይሄ ሰው (አንጥረኛው) ዕቃዎችን (ድስቶችን፣ ማንቆርቆሪያዎችን) ለመሥራት ብረታ ብረትን የሚያቀልጥ ሰው ነው። እዚህ ላይ ያህዌ ክፍያው እጅግ ዝቅ ያለ በመሆኑ እረኛው ምን ያህል እንደተዋረደ ለመግለጽ ብሩን ያቀልጠዋል ማለት ፈልጎ ነው።
በጣም ጥሩ ዋጋ
የያህዌን ሥራ ለሚሠራ ይህ በጣም ዝቅተኛ ክፍያ ለመሆኑ እዚህ ላይ ያህዌ የሽሙጥ አነጋገር እየተጠቀመ ነው። አት. “ከሞኝነት የሚቆጠር እጅግ ዝቅ ያለ ገንዘብ” (ሽሙጥ የሚለውን ይመልከቱ)
በይሁዳና በእስራኤል መካከል
እዚህ ላይ ‘ይሁዳ’ በደቡባዊው መንግሥት የነበረው ሕዝብ፣ ‘እስራኤል’ ደግሞ በሰሜናዊው መንግሥት የነበረውን ሕዝብ ይወክላሉ። አት. “በይሁዳ ሕዝብና በእስራኤል ሕዝብ መካከል” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 11:15
አጠቃላይ መረጃ
ይህ በዘካርያስ 11:4 ስለ ሁለቱ እረኞች የተጀመረውን ታሪክ ይቀጥላል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፡ - 1) ያህዌ ሕዝቡን እንዴት እንደሚይዝ ለመግለጽ በተምሳሌታዊ ተግባር ዘካርያስ የአንድ መንጋ እረኛ ይሆናል። 2)ያህዌ ሕዝቡን እንዴት እንደሚይዝ ለማስተማር ዘካርያስ ምሳሌ ይናገራል። ከእነዚህ ሁለት ትርጉሞች የትኛው ትክክል እንደሆነ እርግጠኛ ስላልሆነ፣ በትርጉም ወቅት ማንኛውንም ትርጉም አለመወሰን መልካም ይሆናል። (ተምሳሌታዊ ተግባር እና ምሳሌዎች የሚሉትን ይመልከቱ)
አንድን እረኛ በቦታው ላስቀምጥ ነው
እዚህ ላይ ‘በቦታው ማስቀመጥ’ ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “በምድሪቱ እረኛን ልሾም ነው” ወይም “ኃላፊነት ያለውን እረኛ በምድሪቱ ላስቀምጥ ነው።” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)
የሰባውን በግ
‘እጅግ የሰባውን በግ’ ወይም ‘ምርጥ የሆነውን በግ’
ሰኮናቸውን ይቀለጣጥማል
ይህ ምናልባት በክፋት የሚፈጸም ድርጊት ሳይሆን አይቀርም።
Zechariah 11:17
ሰይፍ
እዚህ ላይ ‘ሰይፍ’ ሕዝቡን የሚያጠቁትን ጠላቶች ይወክላል። አት. “ጠላቶች” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
በክንዱና በቀኝ ዓይኑ ላይ ይምጡበት
እዚህ ላይ ‘ይምጡበት’ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. “ቀኝ ክንዱን ያቁስሉት ደግሞም ቀኝ ዓይኑን ይውጉት” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)
ክንዱ
የእርሱ ‘ክንድ’ የመዋጋት ኃይሉን ይወክላል። (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀኝ ዓይኑ
አንድ ወታደር ቀኝ ዓይኑን በግራ እጁ በያዘው ጋሻ ዙሪያ ያለውን ለማየት ይጠቀምበታል። ቀኝ ዓይኑ ከቆሰለ በጦርነት ጊዜ ለመዋጋት መመልከት አይችልም። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ክንዱ ትስለል
“ክንዱ ትበስብስ” ወይም “ክንዱ ፈጽማ ከጥቅም ውጪ ትሁን”

---

Chapter 12
Zechariah 12:1
አጠቃላይ መረጃ
እነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ ያለውን ጥቃትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናቸው የሚናገረውን ክፍል ይጀምራል።
ይህ እስራኤልን በሚመለከት የያህዌ ቃል አዋጅ ነው
“ይህ እስራኤልን በሚመለከት ያህዌ ያወጀው መልእክት ነው”
ሰማያትን የዘረጋ
ይህ ሰማይ እንደ ብራና የተጠቀለለና መዘርጋት እንደሚያስፈልገው የሚናገር ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አት. “ሰማይን የፈጠረ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የምድርን መሠረት ያስቀመጠ
ይህ ምድርን መሠረት እንዳለው ሕንፃ አድርጎ የሚናገር ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አት. “ምድርን በሞላ በስፍራው የሚያስቀምጥ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በሰው ውስጥ የሰውን ልጅ መንፈስ የቀረጸ
ይህ መንፈስን ሸክላ ሠሪ እንደሚቀርጸው ሸክላ አድርጎ የሚናገር ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አት. “የሰውን ልጅ መንፈስ የሚፈጥር”
ኢየሩሳሌምን የሚያንገዳግድ ጽዋ አደርጋታለሁ
ያህዌ ኢየሩሳሌምን ለመቅጣት እንደሚጠብቃት ማድረጉን ኢየሩሳሌምን የአልኮል መጠጥ እንደሚያደርጋትና በአካባቢው ያሉት ሕዝቦች ጠጥተዋት እንደሚንገዳገዱ አድርጎ እየተናገረ ነው። አት. “በቅርቡ ኢየሩሳሌምን የምታንገዳግድ ጽዋ እንደማደርጋት ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ጽዋነት
እዚህ ላይ ‘ጽዋ’ ጽዋውንና በጽዋ ውስጥ ያለውን ይወክላል። አት. “በወይን ጠጅ ወደተሞላ ጽዋነት” ወይም “በአልኮል መጠጥ እንደተሞላ ጽዋ” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሷን የከበቧት
እዚህ ላይ ‘እርሷን’ የሚለው የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው። በዕብራውያን ዘንድ አንድ አገር ወይም አንድን ከተማ ሴት እንደሆነች አድርጎ መናገር የተለመደ ነው። (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)
ኢየሩሳሌምን ለሕዝቦች ሁሉ ከባድ ዐለት አደርጋታለሁ
ያህዌ ኢየሩሳሌምን የአካባቢውን ሕዝቦች ለመቅጫ መጠቀሙ ኢየሩሳሌምን ከባድ ዐለት እንደሚያደርጋት ተደርጎ ተነግሯል። አት. “ኢየሩሳሌምን ለሕዝቦች ከባድ ዐለት እንደማደርጋት ያለ ይሆናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Zechariah 12:4
የትርጉም ማስታወሻዎች
እነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ ያለውን ጥቃትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናቸው መናገር ይቀጥላሉ።
በዚያን ቀን
“ሠራዊቱ ኢየሩሳሌምን በሚያጠቁበት ጊዜ”
ያህዌ … እንዲህ ይላል

እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. "የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል" ወይም "እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው" ('መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው' የሚለውን ይመልከቱ)

በይሁዳ ቤት ላይ ዓይኖቼን እከፍታለሁ

እዚህ ላይ በአንድ ሰው ላይ ዓይንን መክፈት ለዚያ ሰው በጎ ለማድረግ መፈለግን የሚገልገጽ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። አት. "ለይሁዳ በጎ ነገርን አደርጋለሁ" ወይም "የይሁዳን ቤት እጠብቃለሁ" ([[rc://*/ta/vol.1/translate/fig/metaphor]] ይመልከቱ)

የይሁዳ ቤት

እዚህ ላይ 'ቤት' የሚወክለው ሕዝብን ነው። አት. "የይሁዳ ሕዝብ" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

በልባቸው እንደዚህ የሚሉ

እዚህ ላይ 'በልባቸው' የሚለው የአንድን ሰው ሃሳብ ይወክላል። አት. "ለራሳቸው የሚያስቡ" ወይም "ለራሳቸው የሚሉ" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ብርታታችን ናቸው

የነገር ስም የሆነው 'ብርታት' 'ጠንካራ' ወይም 'ማደፋፈር' ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አት. "ጠንካራ አድርገን" ወይም "አደፋፍረን" (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የሠራዊት ጌታ ያህዌ፣ አምላካቸው

"የሠራዊት ጌታ ያህዌ፣ የሚያመልኩት አምላካቸው"

Zechariah 12:6

አጠቃላይ መረጃ

እነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ ያለውን ጥቃትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናቸው መናገር ይቃጥላሉ።

በእንጨት መካከል እንዳለ የእሳት ምድጃ ... በነዶም መካከል

ይህ ምስስሎሽ ያህዌ የይሁዳን መሪዎች ጠንካሮች እንዲሆኑና ሕዝባቸውም ጠላቶቻቸውን ድል ወደ ማድረግ እንዲመሩ ያስችላቸዋል ማለት ነው። አት. "በተከመረ እንጨት መካከል እንደ እሳት ምድጃ ... በእርሻ ውስጥ የቆመ ያልታጨደ ነዶ" (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

የእሳት ምድጃ

የጥንት ሰዎች የሚነድ ከሰልን ይዘው የሚሄዱባቸው የሸክላ ማሰሮዎች

የፋና ነበልባል

በአንድ ጫፍ በኩል የሚነድና አንድ ሰው በሚጓዝበት ጊዜ ብርሃን የሚሰጥ ወይም እሳትን አንድ ሌላ ስፍራ የሚያደርስ

በዙሪያው ያሉትን ሰዎች ይበላል

ሰዎቹን ፈጽሞ መደምሰስ የይሁዳ ሰዎች ሰዎቹን እንደሚበሏቸው ተደርጎ ተነግሯል። አት. "የአካባቢውን ሕዝቦች ያጠፋሉ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀኛቸውና በግራቸው

እዚህ ላይ 'ቀኝ' እና 'ግራ' የሚለው በሁሉም አቅጣጫ የሚለውን ይወክላል። አት. "በሁሉም አቅጣጫ" (... የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌም በድጋሚ በስፍራዋ ትቀመጣለች

እዚህ ላይ 'ኢየሩሳሌም' በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። አት. "የኢየሩሳሌም ሕዝቦች እንደገና በራሳቸው ከተማ ይኖራሉ" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 12:7

አጠቃላይ መረጃ

እነዚህ ጥቅሶች በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ ያለውን ጥቃትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናቸው መናገር ይቃጥላሉ።

የይሁዳ ድንኳኖች

እዚህ ላይ 'ድንኳኖች' ቤቶችን ይወክላሉ፣ ቤቶች ደግሞ በውስጣቸው የሚኖሩ ሰዎችን ይወክላሉ። አት. "የይሁዳ ሕዝብ" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የዳዊት ቤት

ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፦ - 1)የዳዊት ዝርያዎች ወይም 2)የሕዝቡ የገዢ መደብ (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእነርሱ መካከል ደካማው እንደ ዳዊት ይሆናል

ይህ ምስስሎሽ ደካሞች የሆኑት ጠንካሮች ይሆናሉ የሚል ትርጉም አለው። አት. "ደካሞች የሆኑት እንደ ዳዊት ብርቱዎች ይሆናሉ" (ምስስሎሽ የሚለውን ይመልከቱ)

የያህዌ መልአክ

ይህ ሕዝቡን እንዲጠብቅ በያህዌ የተላከ መልአክ ነው።

Zechariah 12:10

በዳዊት ቤትና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ላይ የርህራሄና የልመናን መንፈስ አፈሳለሁ

ሕዝቡ ርህሩህ እንዲሆኑና እንዲለምኑ መደረጋቸው መንፈሱ በእነርሱ ላይ የሚያፈሰው ፈሳሽ እንደሆነ ተደርጎ እየተነገረ ነው። አት. "የዳዊት ቤትና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ለሌሎች ምሕረት የሚያደርጉ እንዲሆኑና ምሕረት እንዳደርግ ወደ እኔ የሚጸልዩ እንዲሆኑ አደርጋቸዋለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

የርህራሄና የልመና መንፈስ

እዚህ ላይ ይህ የርህራሄና የልመና ባሕርይ ይኖራቸዋል ማለት ነው።

የዳዊት ቤት

እዚህ ላይ 'ቤት' ዝርያዎችን ይወክላል። አት. "የዳዊት ዝርያዎች" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የወጉትን

"በስለት ወግተው የገደሉትን"

ለአንድያ ልጅ

'ልጁ' ሞቷል የሚል ግንዛቤ አለ። አት. "ለሞተው አንድያ ልጅ" (ግድፈት የሚለውን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም የሚደረገው ልቅሶ ለሐዳድ ሪሞን እንደተደረገው ልቅሶ ይሆናል

ሐዳድ ሪሞን መልካሙ ንጉሥ ኢዮስያስ ከመጊዶ ጦርነት በኋላ በደረሰበት የጦርነት ቁስል የሞተበት ስፍራ ሊሆን ይችላል። በዚያ ስፍራ ስለ እርሱ ሞት በየተወሰኑ ወቅቶች የማልቀስ ልማድ የነበረ ይመስላል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ሰዎች ሐዳድ ሪሞን በየዓመቱ እንደሚሞት የሚታመን የሐሰት አምላክ ስም ነው ብለው የሚያስቡ ሲሆን፤ ይህም ኩነት አምላኪዎቹን እንዲያለቅሱ ያደርጋቸዋል። (ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

መጊዶ

ይህ በእስራኤል የሚገኝ ሜዳ ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 12:12

ምድሪቱ ታለቅሳለች

ይህ በይሁዳ ምድር የሚኖሩትን ሕዝቦች ሁሉ ይወክላል። አት. "በይሁዳ ምድር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ያለቅሳሉ" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

የዳዊት ቤት ነገድ ... የናታን ቤት ነገድ ... የሌዊ ቤት ነገድ

እዚህ ላይ 'ቤት' ዝርያዎችን ይወክላል። አት. "የዳዊት ዝርያዎች" ... "የናታን ዝርያዎች" ... "የሌዊ ዝርያዎች" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 13

Zechariah 13:1

ከኃጢአትና ከርኩሰተ የሚያነጻ ምንጭ ይከፈታል

የሕዝቡ ኃጢአት ይቅር መባሉ በተከፈተ የውሃ ምንጭ ኃጢአታቸው እንደሚታጠብላቸው ሆኖ ተነግሯል። ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. "ኃጢአታቸውንና ርኩስታቸውን የሚያነጻ ምንጭ እንደሚከፈት ያለ ነው" (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

ምንጭ

ከመሬት ውስጥ ውሃ በተፈጥሮ የሚፈልቅበት ቦታ

የይሁዳ ቤት

እዚህ ላይ 'ቤት' የሚወክለው ዝርያዎችን ነው። አት. "የይሁዳ ዝርያዎች" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ... እንዲህ ይላል

እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1:3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. "የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል" ወይም "እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው" ('መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው' የሚለውን ይመልከቱ)

የጣዖታቱን ስም ከምድሪቱ እቆርጣለሁ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሕዝቡ ከእንግዲህ የጣዖታቱን ስም እንዳይጠሩ መደረጋቸው ያህዌ "የጣዖታቱን ስም ከምድሪቱ" እንደሚቆርጥ ተደርጎ ተነግሯል። አት. "ሕዝቡ ከእንግዲህ የጣዖታቱን ስም እንዳይጠሩ አደርጋቸዋለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእንግዲህ አይታወሱም

ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡ - አት. "ከእንግዲህ ስለ ጣዖታት እንዳያስቡ" (ፈሊጣዊ አባባል እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

ነቢያትንና የርኩሰት መንፈስን ከምድሪቱ አስወግዳለሁ

ነቢያት የሚለው 'የሐሰት ነቢያት'ን ሊያመለክት ይችላል። የርኩሰት መንፈስ በአካላዊ ሁኔታ የቆሸሸ እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አት. "ከምድሪቱ የሐሰት ነቢያትንና ርኩስ መንፈሳቸውን አስወግዳለሁ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 13:3

መተንበይ

በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ይህ የሐሰት ትንቢቶች ናቸው። አት. "በሐሰት ትንቢት መናገር" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የወለዱት አባቱና እናቱ

የአንድ ሰው የራሱ ወላጆች ልጃቸውን እንደዚህ በማድረጋቸው የተሰማን አድናቆት ለመግለጽ 'የወለዱት' የሚለው ቃል 'አባቱና እናቱ' የሚለውን ይገልጻል። አት. "የራሱ አባትና እናት" (መለየት ከማስታወቅ ወይም ከማስታወስ ጋር ሲነጻጸር የሚለውን ይመልከቱ)

አትኖሩም

ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል፡ -አት. "መሞት ይገባችኋል"

በያህዌ ስም ሐሰት ተናግረሃል

በአንድ ሰው ስም መናገር በእርሱ ኃይልና ሥልጣን መናገር ወይም የእርሱ ወኪል ሆኖ መናገር ማለት ነው። አት. "በያህዌ ስም እንናገራለን ትላላችሁ፣ ነገር ግን ሐሰት ትናገራላችሁ" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ይወጉታል

"ወግተው ይገድሉታል"

Zechariah 13:4

እያንዳንዱ ነቢይ

ይህ ሐሰተኛ ነቢያትን ያስገነዝባል። አት. "ማንኛውም ሐሰተኛ ነቢይ" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ጠጉራም ልብስ አይለብስም

ነቢያት ብዙውን ጊዜ ከእንሰሳት ጠጉር የተሠራ ከበድ ያለ ልብስ በላያቸው ይደርቡ ነበር። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከአፈር ጋር የተያያዘ ሥራ የምሠራ ነኝ "ገበሬ ነኝ" ገና ልጅ ሳለሁ ሥራዬ ከምድሩ ጋር የተያያዘ ነበር

ገበሬ የሆንኩት ገና ልጅ ሳለሁ ነበር። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህንን፡ -"ልጅ ሳለሁ አንድ ሰው ባሪያ እንድሆን ሸጠኝ" እንደሚል አድርገው ይተረጉሙታል።

በክንድህ መካከል ያሉት ቁስሎች ምንድን ናቸው?

"በደረትህ ላይ ያሉት እነዚያ ቁስሎች እንዴት ሊደርሱብህ ቻሉ?" ይህ ሐሰተኛ ነቢያት በሥርዓቶቻቸው ወቅት ራሳቸውን ሲያቆስሉ የነበሩበትን ግልጽ ልማድ ያመለክታል። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

እንዲህ ብሎ ይመልሳል

በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት የሚሰጠው ምላሽ ውሸት ነው። አት. "እንዲህ በማለት ውሸት ይነግረዋል" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Zechariah 13:7

አጠቃላይ መረጃ

ዘካርያስ ብዙውን ጊዜ ትንቢትን በሥነ-ግጥም መልክ ጽፏል። የዕብራውያን ሥነ-ግጥም የተለያዩ ትይዩነቶችን ይጠቀማል። (ሥነ-ግጥም እን ትይዩነት የሚሉትን ይመልከቱ)

አጠቃላይ መረጃ

እዚህ ላይ ያህዌ መናገር ይጀምራል።

ሰይፍ ሆይ፣ በእረኛዬ ላይ ተነሥ

"አንተ ሰይፍ፣ ሂድና በእረኛዬ ላይ ጥቃት ፈጽም" እዚህ ላይ ያህዌ እንደ ሰው አድርጎ ለሰይፉ ይናገራል። እዚህ ላይ ጠላቶችን ይወክላል። አት. "እናንተ ጠላቶች፣ ሂዱና በእረኛዬ ላይ ጥቃት ፈጽሙ።" (ሰውኛ የሚለውን ይመልከቱ)

እረኛዬ

ይህ የእግዚአብሔር አገልጋይ እረኛ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አት. "እንደ እረኛ የሆነው አገልጋዬ" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአጠገቤ የቆመው ሰው

ይህ ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. "የቅርብ ወዳጄ የሆነው ሰው" ወይም "ባልንጀራዬ የሆነው ሰው" (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ያህዌ ... እንዲህ ይላል

እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1፡3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. "የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል" ወይም "እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው" ('መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው' የሚለውን ይመልከቱ)

መንጋው ይበተናል

የእግዚአብሔር ሕዝብ መንጋ እንደሆኑ ተደርገው ተነግረዋል። አት. "ሕዝቤ እንደ በጎች ይሸሻሉ።" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በታናናሾች ላይ እጄን አዞራለሁ

"እጅን ማዞር" የሚለው ፈሊጣዊ አባባል በአንድ ሰው ላይ በጠላትነት መነሳት የሚል ትርጉም አለው። አት. "ታናናሾችን አጠቃለሁ።" (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ታናናሾች

ይህ ምናልባት ደካማና የሚከላከልላቸው የሌላቸውን እስራኤላውይንን ሁሉ የሚመለከት ሳይሆን አይቀርም።

Zechariah 13:8

ያህዌ ... እንዲህ ይላል

እያወጀ ያለውን ነገር እርግጠኛነት ለመግለጽ ያህዌ ስለ ራሱ ስሙን በመጥቀስ ይናገራል። በዘካርያስ 1፡3 ላይ ተመሳሳይ የሆነውን ሐረግ እንዴት እንደተረጎማችሁት ዞር ብላችሁ ተመልከቱ። አት. "የሠራዊት ጌታ ያህዌ እንደዚህ ብሎ ተናግሯል" ወይም "እኔ የሠራዊት ጌታ ያህዌ የምናገረው ይህንን ነው" ('መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሰው' የሚለውን ይመልከቱ)

ከሕዝቡ አንድ ሶስተኛው ተመትቶ ይጠፋል፣ አንድ ሶስተኛው ብቻ ይቀራል

እየተገደሉት ያሉት ሰዎች ከልብስ ላይ ጨርቅ እንደሚቀደድ ወይም ከዛፍ ላይ ቅርንጫፍ እንደሚሰበር ተደርገው ተነግረዋል። አት. "ከሶስት ሰዎች ሁለቱ ይሞታሉ። ከሶስት ሰዎች አንዱ ብቻ በምድሪቱ ይቀራል።" (ተለዋጭ ዘይቤ እና ክፍልፋዮች የሚሉትን ይመልከቱ)

ያንን ሲሶ (አንድ ሶስተኛ) በእሳት ውስጥ አሳልፈዋለሁ

ብረታ ብረት እንዲጠራ ወይም እንዲጠነክር በእሳት ውስጥ ያልፋል። ይህ አገላለጽ እዚህ ላይ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ይበልጥ ታማኞች ይሆኑ ዘንድ በመከራ ውስጥ ማለፋቸውን የሚገልጽ ተለዋጭ ዘይቤ በመሆን ያገለግላል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብር እንደሚጠራ አጠራቸዋለሁ፣ ወርቅ እንደሚፈተን እፈትናቸዋለሁ

ማጥራት እንደ ብር ያሉ የከበሩ ብረታ ብረቶችን ይበልጥ የጠሩ ማድረግን ያመለክታል። እንደ ብርና እንደ ወርቅ ያሉት ምን ያህል የጠሩና ጠንካራ መሆናቸውን ለማወቅ ይፈተናሉ። እዚህ ላይ ማጥራትና መፈተን ሁለቱም ሕዝቡ ይበልጥ ለእግዚአብሔር ታማኞች እንዲሆኑ ተለዋጭ ዘይቤ አገላለጾች ናቸው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ስሜን ይጠራሉ

እዚህ ላይ 'ስም' የሚለው ያህዌን ይወክላል። ትኩ. "ወደ እኔ ይጣራሉ" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 14

Zechariah 14:1

አጠቃላይ መረጃ

ይሀ ምዕራፍ ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት ይገልጻል።

ብዝበዛችሁ በመካከላችሁ የሚከፋፈልበት የያህዌ ቀን ይመጣል

ወደፊት የሚመጣ ጊዜ 'ቀን እንደሚመጣ' ተደርጎ ተነግሯል። 'የሚከፋፈልበት'

የሚለው ቃል በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ያህዌ ፈጥኖ ይፈርድባችኋል፣ ጠላቶቻችሁም ንብረቶቻችሁን ሁሉ እንዲወስዱና ዓይኖቻችሁ እያዩ ለራሳቸው እንዲከፋፈሉት ይፈቅድላቸዋል።” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሁሉንም መንግሥታት በኢየሩሳሌም ላይ ለጦርነት እሰበስባቸዋለሁ

እዚህ ላይ ‘ሁሉንም መንግሥታት’ የሚለው ብዙ መንግሥታት ለማለት የማጠቃለል አባባል ነው። አት. “ብዙ መንግሥታት ኢየሩሳሌምን እንዲያጠቋት አደርጋለሁ።” (ግነት እና የማጠቃለል አባባል የሚሉትን ይመልከቱ)

ከተማይቱ ትያዛለች

ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ጠላቶቻችሁ ከተማይቱን ይይዟታል።” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤቶች ይበዘበዛሉ፣ ሴቶችም ይደፈራሉ

ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ጠላቶች ቤቶችን ይበዘብዛሉ፣ ሴቶችንም ይደፍራሉ።” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚቀረው ሕዝብ ከከተማይቱ አይወገድም

ሕዝቡን ከከተማይቱ አለመውሰድ ሕዝቡ ‘እንደማይወገድ’ ተደርጎ ተነግሯል። ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ጠላቶቻችሁ ቀሪው ሕዝብ በከተማይቱ እንዲቆይ ይፈቅዱለታል።” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

## Zechariah 14:3

አጠቃላይ መረጃ

እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ። ያህዌ እንደሚመጣና እንደሚዋጋ ተዋጊ ተደርጎ ተገልጾአል።

በጦርነት ጊዜ እንደሚዋጋ

“በቀደሙት ጊዜያት በጦርነት ሲዋጋ እንደነበረ”

በዚያን ቀን

“በዚያን ወቅት”

እግሮቹ በኢየሩሳሌም ተራራ ላይ ይቆማሉ

እዚህ ላይ ‘እግሮቹ’ የሚለው ያህዌን ይወክላል። አት. “በኢየሩሳሌም ተራራ ላይ ይቆማል።” (በክፋይ የተወከለ አካል የሚለውን ይመልከቱ)

የኢየሩሳሌም ተራራም ተከፍሎ … ታላቅ ሸለቆ ይሆናል

ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “የያህዌ ሕላዌ የኢየሩሳሌምን ተራራ ሁለት ቦታ ከፍሎ ታላቅ ሸለቆ በዚያ እንዲፈጠር ያደርጋል።” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

## Zechariah 14:5

አጠቃላይ መረጃ

እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

እናንተ ትሸሻላችሁ

እዚህ ላይ ‘እናንተ’ የሚለው የብዙ ቁጥር ሲሆን የሚያመለክተውም የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ነው። (አንተ እና እናንተ የሚገለጽባቸው መልኮች የሚለውን ይመልከቱ)

በእግዚአብሔር ተራሮች መካከል

ይህ የኢየሩሳሌም ተራራ ለሁለት ከተከፈለ በኋላ የሚፈጠሩትን ተራራዎች ይመለከታል።

አጼል

ይህ ከኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ የሚገኝ ከተማ ወይም መንደር ስም ነው። (ስምን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ ቀደም እንደሸሻችሁ ትሸሻላችሁ

እዚህ ላይ ‘ትሸሻላችሁ’ በሚለው በውስጠ ታዋቂ ‘እናንተ’ የሚለው የሚያመለክተው የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ነው። ነገር ግን ‘እንደሸሻችሁ’ የሚለው የሚያመለክተው ከብዙ ዓመታት በፊት የተፈጸመ ድርጊትን በመሆኑ የሸሹት ቀደምት አባታቶቻቸው ናቸው። አት. “ቀደምት አባቶቻችሁ እንደሸሹ ትሸሻላችሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያን ዘመን

እዚህ ላይ ‘በ … ዘመን’ የሚለው ፈሊጣዊ አባባል ሲሆን ዖዝያን ንጉሥ በነበረበት ጊዜ ማለት ነው። አት. “ዖዝያን ንጉሥ በነበረበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ቅዱሳኑም

ይህ ምናልባት የእግዚአብሔርን መላእክት የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም።

## Zechariah 14:6

አጠቃላይ መረጃ

እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

በዚያን ቀን

“በዚያን ወቅት”

ብርሃን አይኖርም

በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ከፀሐይ የሚገኝ ብርሃን አይኖርም። አት. “የፀሐይ ብርሃን አይኖርም” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ያህዌ ዘንድ ብቻ የታወቀ ቀን

ይህ በተናጋሪ መልክ ሊገለጽ ይችላል። አት. “ያ ቀን መቼ እንደሚጀምር የሚያውቀው ያህዌ ብቻ ነው።” ወይም “ያህዌ ብቻ ያ ቀን መቼ እንደሚጀምር ያውቃል።” (ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚለውን ይመልከቱ)

የሕይወት ውሃ

ይህ በመደበኛነት በአንድ ቦታ የረጋ ወይም ጭርቃ ውሃ ሳይሆን ወረጅ ወይም ፈሳሽ ውሃ ማለት ነው። (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

የምሥራቅ ባሕር

ይህ ከኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ ያለውን ሙት-ባሕርን ያመለክታል።

የምዕራብ ባሕር

ይህ ሜዲትራኒያን ባሕርን (ታላቁን ባሕር) ያመለክታል።

## Zechariah 14:9

አጠቃላይ መረጃ

እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

ያህዌ አንዱ አምላክና ስሙም ብቻ ይኖራል

እዚህ ላይ ‘ስሙ’ የያህዌን ዝናና ባሕርዩን ይወክላል። ትኩ. “ሕዝቡ ያህዌ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ያውቃሉ” ወይም “ሰዎች ብቻኛውንና እውነተኛ የሆነውን የሆነውን ያህዌን ብቻ ያመልካሉ።” (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ምድር ሁሉ

በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ይህ የይሁዳ ምድር ነው። አት. “መላው የይሁዳ ምድር” (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

አረባ

ይህ በዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ ያለ ሜዳ ስም ነው። (ስምን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

ጌባ

ይህ በሰሜን ይሁዳ ዳርቻ ያለ ከተማ ስም ነው። (ስምን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

ሪሞን

ይህ በኢየሩሳሌም በስተደቡብ ያለ ከተማ ስም ነው። (ስምን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌም ከፍ ከፍ በማለት ትቀጥላለች

ይህ ከፍ በማለት የምትቀጥለውን ኢየሩሳሌምን ከባሕር ጠለል በላይ ከፍታቸው ዝቅ ካለው ከአካባቢው ቦታዎች ጋር ያለውን ቅራኔ ያሳያል። ቅራኔውን ‘ነገር ግን’ የሚለውን ቃል በመጨመር ማመልከት ይቻላል። ይህ በተናጋሪ መልክም ሊገለጽ ይችላል። አት. “ኢየሩሳሌም ከፍ እንዳለች ትቆያለች።” (አያያዥ ቃላት እና ተናጋሪ ወይም አናጋሪ የሚሉትን መልከቱ)

የብንያም በር … የመጀመሪያው በር … የማዕዘን በር

እነዚህ በኢየሩሳሌም ከተማ ቅጥር በስተ ሰሜንምሥራቅ በኩል ያሉ የበሮች ስሞች ናቸው። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች ፡ - 1)’የመጀመሪያው በር’ እና ‘የማዕዘን በር’ አንድ ዓይነት በሮች ናቸው ወይም 2) ’የመጀመሪያው በር’ እና ‘የማዕዘን በር’ የተለያዩ በሮች ናቸው። (ስምን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ፣ ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የሐናንኤል ግንብ

ይህ በስተሰሜን ቅጥር ባለው የከተማይቱ መካላከያ ጠንካራውን ስፍራ ያመለክታል። ይህ ምናልባት ሐናንኤል በተባለ ሰው የተገነባ ሳይሆን አይቀርም። (ስምን እንዴት መተርጎም እንደሚገባ የሚለውን ይመልከቱ)

የንጉሡ የወይን ጠጅ መጥመቂያ

ይህ ምናልባት ለንጉሣዊው ቤተ ሰብ የወይን ጠጅ የሚዘጋጅበት ሳይሆን አይቀርም።

ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብምዕራብ በኩል የሚገኝ ስፍራ ነበር። (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ኢየሩሳሌም በሰላም ትኖራለች

እዚህ ላይ 'ኢየሩሳሌም' ሕዝቡን ትወክላለች። አት. "ሕዝቡ በሰላም በኢየሩሳሌም ይኖራሉ።" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 14:12

አጠቃላይ መረጃ

እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

ገና በእግሮቻቸው ቆመው ሳሉ

"ቆመው ሳሉ" ይህ ሥጋቸው ምን ያህል ፈጥኖ እንደሚበሰብስ አጽንዖት ይሰጣል። ለመተኛት እንኳን ጊዜ አይኖራቸውም።

በመካከላቸውም ከያህዌ ዘንድ ያ ታላቅ ፍርሃት ይመጣባቸዋል

'ፍርሃት' የሚለው የነገር ስም 'ድንጋጤ' ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። አት. "ያህዌ ሕዝቡ በጣም እንዲደነግጡ ያደርጋቸዋል" (የነገር ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

የአንዱ እጅ የሌላውን እጅ ይይዛል፣ የአንደኛውም እጅ በሌላው እጅ ላይ ይነሳል

እነዚህ ፈሊጣዊ አባባሎች በሌላው ሰው ላይ በጠላትነት መነሳትን የሚያመለክቱ ናቸው። አት. "እያንዳንዱ ሰው ሌላውን ሰው ይይዘዋል፣ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ።" (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 14:14

አጠቃላይ መረጃ

እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

ይሁዳም ኢየሩሳሌምን ይወጋል

'ይሁዳ' እና 'ኢየሩሳሌም' በዚያ የሚኖሩትን ሕዝቦች ይወክላሉ። አት. "በይሁዳ ያሉት ሌሎች ሕዝቦች እንኳን ከኢየሩሳሌም ጋር ይዋጋሉ።" (ስመ-ምስል ስያሜ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳም ከኢየሩሳሌም ጋር ይዋጋል

በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች፡ - "ይሁዳም በኢየሩሳሌም ይዋጋል" ተብሎ ይነበባል።

ሀብቱን ይሰበስባሉ

ውድ የሆኑትን ንብረቶች ሁሉ ይይዛሉ።

በተትረፈረፈ መጠን

'በከፍተኛ መጠን'

Zechariah 14:16

አጠቃላይ መረጃ

እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

በኢየሩሳሌም ላይ ከመጡት

"በ … ላይ መጡ" የሚለው ፈሊጣዊ አባባል ነው። አት. "ኢየሩሳሌምን ያጠቁት" (ፈሊጣዊ አባባል የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያ ይልቅ ከዓመት ወደ ዓመት ይወጣሉ

ከዚያ ይልቅ ወደ ኢየሩሳሌም በየዓመቱ ይወጣሉ።

የመጠለያዎች በዓል

'የማረፊያ ቦታዎች በዓል' ወይም 'የዳሶች በዓል' ወይም 'የድንኳኖች በዓል'

ከያህዌ ዘንድ የሆነ ቸነፈር መንግሥታትን ያጠቃል

አንድን ሕዝብ በቸነፈር እንዲሰቃይ ማድረግ ቸነፈሩ እንደ ሠራዊት ሕዝቡን እንደሚያጠቃው ተደርጎ ተነግሯል። አት. "በመንግሥታት ሕዝቦች መካከል ያህዌ ቸነፈር እንዲመጣ ያደርጋል።" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Zechariah 14:19

አቃላይ መረጃ

እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

Zechariah 14:20

አጠቃላይ መረጃ

እነዚህ ጥቅሶች ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የሚደረገውን የመጨረሻ ጦርነትና እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያድናት መግለጽ ይቀጥላሉ።

በፈረሶቹ ላይ ያሉት ሻኩራዎች እንደዚህ ይላሉ

በፈረሶቹ ባሉት ሻኩራዎች ላይ ያሉት ጽሑፎች እንደዚህ ይላሉ።

በያህዌ ቤት ያሉት ምንቸቶች

ለእነዚህ ምንቸቶች በቤተ መቅደሱ አደባባይ ሥጋን ለመቀቀያ ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር። አት. "ቤተ መቅደሱ አደባባይ የነበሩት የማብሰያ ምንቸቶች" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከመሠዊያው ፊት ለፊት እንዳሉት ሳህኖች

በግንዛቤ በተገኘው መረጃ መሠረት ምንቸቶቹ የመሥዋዕቱን ደም ለመቀበል እንደሚያገለግሉት ሳህኖች የተቀደሱ ይሆናሉ የሚል ነው። አት. "በመሠዊያው እንዳሉት ሳህኖች የተቀደሱ ይሆናሉ።" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ያለ ማንኛውም ምንቸት ለሠራዊት ጌታ ለያህዌ የተለየ ይሆናል

ልዩ ልዩ ዓይነት ምንቸቶችና ቁሳቁሶች በተለይ ለያህዌ አምልኮና ለመሥዋዕቶቹ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተሠርተው ነበር። እነዚህ ለምንም ሌላ ጥቅም እንዳይውሉ የተለዩ ተደርገው ይቆጠሩ ነበር።

ከእንግዲህ ወዲህ ነጋዴዎች በያህዌ ቤት አይኖሩም

ሕዝቡ በቤተ መቅደስ ለያህዌ ተገቢ መሥዋዕቶችን እንዲያቀርቡ የሚያስፈልጓቸውን ለሕዝቡ መሸጥ በነጋዴዎች ዘንድ የተለመደ ነበር። አት. "ከእንግዲህ ሰዎች በያህዌ ቤተ መቅደስ የሚሸጡም የሚገዙም አይሆኑም።" (ግምታዊ እውቀት እና ውስጠ-ታዋቂ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ነጋዴዎች

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች 'ነጋዴዎች' የሚለውን 'ከነዓናውያን' ብለው ይተረጉሙታል።

---

Chapter 1

Malachi 1:4

ኤዶምያስ እንዲህ ቢል፤

"ኤዶምያስ" በዚህ ስፍራ የኤዶምን ህዝብ ይወክላል 'የኤዶማዉያን እንዲህ ቢሉ ወይንም የኤዶም ህዝብ እንዲህ ቢል'

እኔ ወደታች እወረውራለሁ

በዚህ ስፍራ 'ወደታች እወረውራለሁ' የሚለው 'አፈርሳለሁ' ለማለት እንደሆነ ይለመታል።

የበደል አገር

'በደለኛ' የሚለው ቃል 'የበደለኛ ህዝብ አገር' ለማለት ነው።

በአይኖቻችሁ ይህንን ታያላችሁ

በዚህ ስፍራ "በአይኖቻችሁ" የሚለው ህዝቡን ይወክላል። ስለዚህ "እናንተ ራሳችሁ ይህንን ታያላችሁ" ይባል።

Malachi 1:6

ስሜን የምታቃልሉ

በዚህ ስፍራ "የኔ ስም" የሚለው እግዚአብሔርን የሚለውን ያመለክታል እን"ደጠላችሁኝ ያሳያል"

ስምህን እንዴት አቃለልን ?

በዚህ ስፍራ ካህናት የሚጠይቁት ጥያቄ እግዚአብሔርን በእርግጥ አላቃለልንም እያሉ ነበር።ስለሆነም እንዲህ ይባል፤ "እኛ ስምህን ያቃለልን ይመስለሀል?" ወይም "ስምህን እንዴት አድርገን እንዳቃለልን እስቲ ንገረን?"

እርኩስ እንጀራ (ምግብ)

"እርኩስ" የሚለው ቃል የሚገልጸው ለእግዚአብሔር መቅረብ የማይገባውን መሰዋዕት ማቅረብን ነው

እንዴት አረከስንህ?

በዚህ ስፍራ ካህናት የሚጠይቁት ጥያቄ እኛ ስምህን አላረከስንም የሚል ነበር። ይህም እንደዚህ ቢባል፤ " እኛ አላረክስንህም" ወይም "እንዴት ነው ያረከስንህ?"

አረከስንህ

ይህ አገላለጽ ለእግዚአብሔር የማይገባውን መሰዋእት ማቅረብ እግዚአብሔር እንደመሳደብ ይቆጠራል የሚለውን ይገልጻል።

ገበታ

ይህ መሰዉያውን ያሳያል።

የእግዚአብሔር ገበታ የተነቀፈ ነው በማለታችሁ ነው።

እግዚአብሔር ለካህናቱ የሰጠው ምላሽ እንዲህ የሚል ነበር፤(ግልጽ ሲደረግ)፤"የእግዚአብሔር ገበታ የተናቀ ነው በማለት እኔን አርክሳችሁዋል"

የተነቀፈ / የተናቀ
ዋጋ እንደሌለው የተቆጠረ
Malachi 1:8
ዕውር መሥዋዕትንም ስታቀርቡ ይህ ክፉ አይደለምን?
በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ጥያቄውን በመጠቀም ህዝቡን ይገስጻል።ስለዚህ እንዲህ ይባል “ለእግዚአብሔር ዕውር እንስሳን መሰዋእት ማቅረብ ክፉ እንደሆነ በደንብ ታውቃላችሁ”
አንካሳውንና የታመመውን ስታቀርቡ ይህ ክፉ አይደለምን?
በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ጥያቄውን በመጠቀም ህዝቡን ይገስጻል። ስለሆነም እንዲህ ይባል “ አንካሳና የታመመዉን እንስሳ ማቅረብ ክፉ እንደሆነ እያወቃችሁ መሰዋዕት ታቀርባላችሁ።
ያንን ለአለቃህ አቅርብ፥ በውኑ በአንተ ደስ ይለዋልን? ወይስ ፊትህን ይቀበላልን?
የመጀመሪያው አረፍተነገር በትእዛዝ መልክ ለመከራከሪያነት የቀረበ ስለሆነ እንደዚህ ይባል “ያንን ለአለቃህ ብታቀርብ ይቀበለሃል ወይ ወይንም ፊትህን ይቀበላል ወይ?”
ይቀበለሃል ወይንም ፊትህን ይቀበላል ወይ?”
በዚህ ስፍራ ማለት የተፈለገው እግዚአብሔር ህዝቡን ለማስታወስ ጥያቄ በመጠየቅ አለቃችሁ በፍጹም እንዲህ አይነቱን አካላ ስንኩል እንስሳ አይቀበልም ነው።
ፊትህን ወደ ላይ ከፍ ያደርጋል
ፊትን ወደ ላይ ከፍ ማድረግ የሚለው ፈሊጥ በሞገስ ግለሰቡን መቀበልን ያመለክታል። ስለሆነም “ በጥሩ ሁኔታ ይቀበለሃል” ወይም “ እንተን ለመርዳት ፈቃደኛ ነው” ማለት ይቻላል።
መስጠት (ስጦታን)
አክብሮትን ለማሳየት ስጦታን እንደመስጠት
አሁንም ጸጋን ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔርን ለምኑ፥
ሚልክያስ ለእግዚአብሔር በቀጥታ አይናገርም። ነገርግን እስራኤልን በቀጥታ እንዲህ በማለት ይናገራል፤ እነሱን በወቀሳ መልክ እግዚአብሔር ምህረት ያድርጋል እያላችሁ ታስባላችሁ ይላቸዋል።
ይእግዚአብሔርን ፊት እየጠየቁ መቀጠል
እዚህ ላይ “ፊት” የሚለው ቃል እግዚአብሔርንና የሱን መገኘት ነው። ስለሆነም “ እግዚአብሔር በሚገኝበት እሱን ፈልግ” ይባል።
ይህን ስጦታ ከእጃችሁ የተሰጠ ሲሆን ከቶ ፊታችሁን ይቀበላልን
በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የሚጠይቀው በጥያቄ ዉስጥ ህዝቡን ለመገሰጽ ፈልጎ ነው። ስለሆነም “ለእግዚአብሔር የማይመጥን መሰዋዕት ብታቀርብ በእርሱ አንድ ተቀባይነት የለውም” ይባል።
በእጃችሁ ባለው በዚህ ስጦታ
ይህ አስቸጋሪ የሆነ የዕብራይስጥ ሐረግ በተለያየ መንገድ ሊተረጎም ይችላል።
በእጅህ ውስጥ

x
Malachi 1:10
ከሆነ ብቻ
የከፍተኛ ፍላጎት መግለጫ
በመሠዊያዬ ላይ እሳትን በከንቱ እንዳታቃጥሉ
በዚህ ስፍራ “በመሰውያየ ላይ እሳት ማቃጠል” የሚለው የሚያመለክተው ለእግዚአብሔር መሰዋእት በመሰውያው ላይ ማቅረብን ነው።ስለሆነም “ተቀባይነት የሌለውን ስጦታ ማቃጠል ተገቢ አይደለም” ይባል።
ከእጃችሁ
እዚህ ላይ “እጃችሁ” የሚለው “እናንተ” የሚለውን ይወክላል። ስለሆንም “ከእናንተ” ይባል።
ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ
ይህ አገላለጽ “በሁሉም ስፍራ” ለማለት ነው።
ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና
እዚህ ላይ “የኔ ስም” የሚለው አባባል የእግዚአብሔርን ዝናና ክብር ለማመልከት ነው። ስለሆነም “በሌሎች ህዝቦች ላይ እከብራለሁ” ይባል።
በሁሉም ስፍራ ዕጣንና ንጹህ ስጦታ በስሜ ይቀርባል
ይህ አገላለጽ እንደሚከተለው ሊቀርብ ይችላል፡ “ከእነዚህ አገሮች ሰዎች እኔን ለማምለክ እጣንና ንጹህ ስጦታን ያቀርባሉ”።
በኔ ስም
በዚህ ስፍራ “ስም” እግዚአብሔርን ይወክላል። ስለሆነም “ለኔ” ይባል።
ፍሬው፥ መብሉም
አማራጭ ትርጉሞች 1) “በመሰውያ ላይ የተሰዋ የእንስሳት ስጋ ሆኖ ከብልቱ ካህናት የሚበሉት” ወይም 2) በመሰውያ ላይ የተሰዋ ስጋ”
Malachi 1:13
ጢቅ አላችሁበት
እክብሮት በመንፈግ ድምጽ ማሰማት
በውኑ ከእጃችሁ ይህን ልቀበለውን?
በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ሊገስጻቸው ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። ስለሆነም “እኔ ይህንን በእርግጥ ከእናንተ አልቀበልም” ይባል።
ከእጃችሁ
በዚህ ስፍራ “እጃችሁ” የሚለው የሚወክለው “እናንተ” ነው።
ስሜም በአሕዛብ ዘንድ የተከበረ ነው ።
ይህ በቀጥታ ንግግር ሊገለጽ ይችላል። “ሌሎች ህዝቦች ስሜን ያከብራሉ” ይባል።
ስሜ ይከብራል
እዚህ ላይ “የኔ ስም” የሚለው እግዚአብሔርን ይወክላል። ስለሆነም “እኔ እከብራለሁ” ይባል።

---

## Chapter 2

Malachi 2:1
በልባችሁ አኑሩት
ይህ የሚያመለክተው አንድ ነገር በጣም አስፈላጊ/ ጠቃሚ መሆኑን ነው። ስለሆነም “በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ቁጠሩት ይባል።
ለስሜ ክብር ስጡት
‘ክብር” የሚለው ቃል እብደ ግስ (ድርጊት ገላጭ) ሊወሰድ ይችላል። ስለሆነም “የኔን ስም አክብሩ” ይባል።
የኔ ስም
ይህ በዚህ ስፍራ እግዚአብሔርን ያመለክታል።
እኔ በእናንተ ላይ እርግማን እልካለሁ
“እርግማን” ረቂቅ ስም ሲህን እንደ ግስ ያገለግላል። ስልሆነም “እኔ እረግማችሁዋለሁ” ይባል።
እናንተ አትእዛኤን በልባችሁ አላኖራችሁም
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ትእዛዝ በጣም ጥቃሚ/አስፈላጊ መሆኑን ነው።
Malachi 2:3
ፋንድያ በፊታችሁ ላይ እበትናለሁ
እዚህ ላይ “ፋንድያ በፊታችሁ ላይ” የሚለው ሐረግ ማዋረድ/ ማሳፈር የሚለውን ለማመልከት ነው።

የመሥዋዕታችሁንም ፋንድያ
እዚህ ላይ “መሰዋዕት” የሚለው ቃል በእስራኤል በእላት ላይ ካህናት ለመሰዋእትን እንስሳት ይመለከታል። “ፋንዲያ/እበት” የሚለው ቃል እንስሳቱ ለመሰዋዕት ከመታረዳቸው የሚጥሉትን ቆሻሻ ወይንም ከታረዱ በሁዋላ ስጋቸው ሲበለት ከሰውነታቸው የሚወጣውን ለማመልከት ሊሆን ይችላል። የቤተመቅደስ ሰራተኞች እበቱን ከቤተመቅደሱ ዉጪ ወይንም ከእየሩሳሌም ዉጪ ይጥሉታል።
ከእርሱም ጋር በአንድ ላይ ይወስዳችሁዋል
ይህ ለትርጉም የሚያስቸግር አገላለጽ ቢሆንም እንደዚህ ማለት ይቻላል “እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር( ከእበቱ ጋር) ይወስዳችሁዋል። ስለሆነም “በእበት መጣያ ላይ ይወረውሩአችሁዋል፤እግዚአብሔር በእርግጥ ከእበት መጣያ ጋር እንድትወሰዱ ያደርጋል”።
ከእርሱም ጋር በአንድ ላይ ይወሰዳችሁዋል
ለዚህ አባባል ሁለት አማራጮች አሉ፤ 1) እግዚአብሔር ታማኝ ያልሆኑትን ካህናት በሞት በመቅጣት ሬሳቸው ከእንሰሳት እበት መጣያ ላይ እንዲጣሉ ያደርጋል ወይንም 2) እግዚአብሔር ታማኝ ያልሆኑትን ካህናት በአስከፊና በአሰቃቂ ሁኔታ በሞት በመቅጣት ሬሳቸዉን ከእንስሳት ፋንዲያ ጋር እንዲጣሉ ያደርጋል።
ሌዋዊ
በዚህ ስፍራ ሌዋዊ የሚለው ቃል የሌዊን ተወላጆችና ዘሮቹን ለማለት ነው። ስለዚህ “ ቃልኪዳኔ ከእናንተ ከሌዊ ዘሮች ጋር ነው” ይባል።

Malachi 2:5
ቃል ኪዳኔ ከእርሱ ጋር የሕይወትና የሰላም ቃል ኪዳን ነበረ
በዚህ ስፍራ ለማለት የተፈለገው ውጤት ቃልኪዳን በራሱ ቃልኪዳን መሆኑን ነው። ስለሆነም “ከሌዊ ጋር ያለው የቃልኪዳን ዐላማ ካህናቱ በብልጽግናና በሰላም መኖር ነበር” ይባል።
ይፈራ፥ እርሱም እኔን ፈራኝ፥
ይህ አባባል “ከእርሱ ጋር ያለኝ ቃልኪዳን እርሱ እንዲፈራኝና እሱ እንደፈራኝም ነበር” ይባል።
ከስሜም የተነሣ ደነገጠ
በዚህ ስፍራ “የኔ ስም” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔርን ይወክላል።
ምንም ዉሸት አልተገኘበትም
ለማለት የተፈለገው “ ምንም ዉሸት የለበትም” ነው።
በእሱ ከንፈሮች
በዚህ ስፍራ “ከንፈሮች” የሚለው የሰውየውን የመናገር ችሎታን ይወክላል።
እሱ ከኔጋር ይሄዳል
በዚህ ስፍራ መሄድ የሚለው መኖርን እንዲሁም በተወሰነ የህይወት ምንገድ መኖርን ያሳያል።
በሰላምና በቅንነት
በዚህ ስፍራ ሐረጉ የሚያመለክተው የሌዋውያን የኖሩበትን የህይውት ስርዐት ነበር። ስለሆነም “ሰላማዊና ቅንነት” ይባል።
ብዙዎችን ከኃጢአት መለሰ
በዚህ ስፍራ ሰዎች ኃጢአት መስራት እንዲያቆሙና ከህጢያት ፊታቸዉን እንዲመልሱ ለማለት ስለሆነ “ እሱ ብዙ ሰዎች ከህጢአት እንዲመልሱ አደረገ” ይባል።
የካህናቱ ከንፈሮቹ እውቀትን መጠበቅ ይገባቸዋል
በዚህ ስፍራ እዉቀት የተባለውን ነገር ካህናቱ መጠበቅ ይገባቸዋል። ስለሆነም “እውቀትን መጠበቅ” የሚለው ሃሳብ እዉነተኛ የሆነው ስለ እልዚአብሔር ያለ እዉቀት ለማለት ነው።
ከንፈሮች
በዚህ ስፍራ “ከንፈሮች” የሚለው የሰውየውን የመናገር ችሎታን ይወክላል።
መመሪያ መፈለግ
በዚህ ስፍራ መመሪያ የቀረበው ሊታይ የሚችል እንደ አንድ ነገር ነበር። ይህንን ዐረፍተነገር እንደሚከተለው ማስተካከል ይቻላል። “መመሪያ ለመቀበል መፈለግ” ወይም “ካህናቱ እውነቱን እንዲሩዋቸው መፈለግ”።
ከእርሱ አፍ
በዚህ ስፍራ “አፍ” ሰውየው የሚናገረውን ይወክላል።
Malachi 2:8
እናንተ ግን ከእውነት መንገድ ፈቀቅ ብላችኋል
ቀጥተኛና ትክክለኛ የሆነውን መንገድ መከተል ለማለት ነው።
ብዙዎች እንዲሰናከሉ አድርጋችሁዋል
ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ እንደማሰናከል ይቆጠራል።
በሕግም ብዙዎች እንዲሰናከሉ አድርጋችሁዋል
“በሕግም” የሚለው አገላለጽ “መሰናከል” የሚለውን አውድ ይሰጣል። ስለዚህ “እናንተ ብዙዎች ለሕጉ እንዳይታዘዙ አድርጋችሁዋል” ይባል።
በሕዝብ ሁሉ ፊት
ይህ ሃሳብ ሕዝቡ የካህናቱን ክፉ ባህሪይ ማወቃቸውን ያመለክታል።
መንገዴን እንዳልጠበቃችሁ
በዚህስፍራ “መንገድ” የሚለው “ፍላጎት” ወይም “ባህሪይ” የሚለዉን ያመለክታል።
በሕግም ለሰው ፊት አዳልታችሁዋል
“ለምትወዱአቸው ሰዎች ቀላል ምስፈርት ስታስቀምጡ፤ ለምትጠሉዋቸው ሰዎች ግን አስቸጋሪ መስፈርት ታስቀምጣላችሁ”።
አድልዖ ማሳየት
በዚህ ስፍራ አንድን ሰው ከሌላው አብልጦ መውደድን ያመለክታል፤ስለዚህ “አንዱን ከሌላው አስበልጣችሁ እንድምትወዱ እወቁ” ይባል።
Malachi 2:10
ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን?
ሚልክያስ የሱ ወገን የሆኑትን እስራኤላውያንን ቀደም ሲል የሚያውቁትን ነገር ለማሳሰብ ጥያቄ ይጠይቃቸዋል፤ ስለሆነም መባል ያለበት “ሁላችንም አንድ አባት ያለን፤የእኛ አምላክም ከእኛ አንድ ህዝብ እንደፈጠረ ታውቃላችሁ” ወይም “ሁላችሁም እንደምታዉቁት እግዚአብሔር የእስራኤላውያን ሁሉ አባት ነው፥ ምክንያቱም እግዚአብሔር መንግስታችንን/ሕዝባችንን የመሰረተው እሱ ስለሆነ ነው”።
አንድ አምላክስ አልፈጠረምን?
ይህጥያቄ የሚገልጸው ቀጥሎ ያለዉን አረፍተነገር ነው፤ “በእርግጥ አንድ አምላክ ሁላችንንም ፈጥሮናል”።
ፈጥሮናል
ይህ አረፍተነገር የሚያሳየው እግዚአብሔር አይሁዳውያንን አንድ ህዝብ እንዲሆኑ ማድረጉ ነው።
የአባቶቻችንን ቃል ኪዳን ለማስነቀፍ እኛ እያንዳዳችን ወንድማችንን ስለ ምን አታለልን?
ሚልክያስ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቀው የራሱ ወገን የሆኑትን እስራኤላውያንን ለመገሰጽ ፈልጎ ነው። ስለዚህ ይህ ጥያቄ ቀጥሎ ባለው መንገድ ወደ አረፍትነገር ሊቀየር ይችላል። “አሁን እንደምታደርጉት እኛ በእርግጥ ወንድሞቻችንን በክፉ በማየትና ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ባለመታዘዝ የእግዚአብሔርን ቃልኪዳን ማቃለል የለብንም”።
ይሁዳ አታልሎአል
በዚህስፍራ “ይሁዳ” የሚለው ቃል አይሁዳውያን የሚኖሩበት ስፍራ ያሉትን የአይሁድ ህዝብ ሲወክል ለእግዚአብሔር አለመታመናቸውን ለመግለጽ “ይሁዳ” ብሎዋል። ስለዚህ “የአይሁድ ህዝብ ለእግዚአብሔር አልታመነም” ይባል።
በእስራኤልና በኢየሩሳሌም ውስጥ ርኩሰት ተሠርቶአል
ይህንን አገላለጽ ቀጥሎ ባለው መንገድ ማቅረብ ይቻላል፤ “በእስራኤልና በእየሩሳሌም ያሉ ሰዎች አስጸያፊ ነገሮችን ሰርተዋል”።
እግዚአብሔር ቅዱስ ስፍራ ይሁዳ ስላረከሰ
በዚህ ስፍራ “ይሁዳ” የእስራኤልን ህዝብ ይወክላል።ስልዚህ “የይሁዳ ህዝብ/አይሁዳውያን የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን ስፍራ ስላረከሱ” ሊባል ይችላል።
የእንግዳውንም አምላክ ልጅ ሚስት አድርጎ አግብቶአልና
በዚህ ስፍራ የይሁዳ ህዝብ እንደ አንድ ሰው ስም ”ይሁዳ” ተብለዋል። ስለሆነም ፤ “ይሁዳ ጣዖት አምላኪ የሆነች የሌላ አገር ህዝብ ሴት አግብቶአል” ይባል።
እንዲህ የሚያደርገውን ሰው እግዚአብሔር ከያዕቆብ ድንኳን ቆርጦ ያጥፋው
በዚህ ስፍራ አንድን ነገር ማጥፋት ማለት ከአንድ ነገር ላይ ቆርጦ መጣል ማለት ነው።ስለሆነም “እንደዚህ የሚያደርገውን ሰው እግዚአብሔር ያጥፋው” ወይም “ከእስራኤል ህዝብ መካከል እንደዚህ የሚያደርገውን ሰው እግዚአብሔር ይግደለው” ይባል።
የያዕቆብ ድንኩዋን
በዚህ ስፍራ “የያዕቆብ ድንኩዋን” የሚያመለክተው የእስራኤል ህዝብ ነው።
ያዕቆብ
በዚህ ስፍራ “ያዕቆብ” የሚያመለክተው እስራኤላውያንን ነው፥ ምክንያቱም እስራኤላውያን ሁሉ የከያዕቆብ ተወላጆች ስለሆኑ ነው።
እግዚአብሔር የሚጠራውንና የሚመልሰውን
ይህ አገላለጽ “አንድም ሳይቀር ሁሉንም” ለማለት ነው።
Malachi 2:13
መሠዊያውን በእንባ ትከድናላችሁ።
ይህ አባባል በፌዝ መልክ በማጋነን የሰዎቹን እንባና ለቅሶ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ሰዎቹ ምንም ሀዘን አይሰማቸውም ለማለት ነው።
በለቅሶና በሀዘን
“ለቅሶ” እና “ሀዘን” የሚሉ ቃላት በተመሳሰለ አገላለጽ ለቅሶ የሚለዉን ሃሳብ ለማጠንከር ነው። ስልዚህ “በከፍተኛ ለቅሶ” ይባል።
እግዚአብሔር ቍርባኑን ዳግመኛ እንዳይመለከት፥
እዚህ ላይ ቁርባኑን አይመለከትም የሚለው ስጦታውን በመቀበል ለሰጪው አድልዖ ማድረግን ያሳያል።
እግዚአብሔር ቍርባኑን ዳግመኛ እንዳይመለከት
ይህም የሚያመለክተው እነዚህ በእግዚአብሔር መሰውያ ላይ የሚያለቅሱ ሰዎች መሰዋዕት ለእሱ እንዳቀረቡ ነው።
ከእጃችሁ
በዚህ ስፍራ “እጅ” የሚለው የሚያመለክተው ሰጭው ስጦታ መስጠቱን ነው።
Malachi 2:14
ስለ ምንድር ነው?
የዚህ ጽሁፍ ሙሉ ሃሳብ “እግዚአብሔር ለምን ወደ ስጦታችን አይመለከትም?”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ወይም “ከእጃችን ስጦታችንን ደስ ብሎት አይቀበልም” ነው።
የወጣትነት ሚስትህ
“ወጣት በነበርክ ጊዜ ያገባሃት ሚስትህ”
እግዚአብሔር በአንተና በልጅነት ሚስትህ መካከል ምስክር ስለ ሆነ ነው
በዚህ ዐረፍተነገር መሰረት ይህቺ ሴት በዚህ ጊዜ በህይወት አለች።
ባንተና በልጅነት ሚስትህ መካከል ምስክር
የዚህ አረፍተነገር ትርጉም፥ የጋብቻ ቃልኪዳኑን የሚያፈርሰውን ማንኛውን እስራኤላዊ እግዚአብሔር ይቀጠዋል ነው።
እግዚአብሔር የሕይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን?
ይህ ዐረፍተነገር እንደሚከተለው ሊገለጽ ይችላል፥ “እግዚአብሔር በመንፈሱ
አንድ አድርጋቸው
ይህ አገላለጽ ባልና ሚስት አንድ ስጋ ይሆንሉ የሚለውን ስለሚያመለክት “ ባልና ሚስት አንድ አካል/ስጋ አደረገ” ይባል።
ከእግዚአብሔር የሆነ ስጦታ
እግዝዚአብሔርን የሚያከብሩና ለሚታዘዙ ልጆች
ሚስትህ ባልንጀራህና የቃል ኪዳንህ ሚስት ናት
ይህ ዐረፍተነገር የሚያሳየው ብዙ እስራኤላውያን ሚስቶቻቸውን እንደ ፈቱ ነው።
በቃልኪዳን
“በጋብቻ ቃልኪዳን ተስማምታችሁዋል”፥
Malachi 2:17
እግዚአብሔርን በቃላችሁ አታክታችኋል
እግዚአብሔር እንደሚሰለች ተደርጎ ቢቀርብም እርሱ ግን በአካል የማይደክም ወይም ስሜታዊ የሆነ አምላክ አይደለም። ምናልባት እግዚአብሔር ተናዶአል ማልት ይቻላል። ስለሆነም “እግዚአብሔርን አናዳችኋል” ይባል።
ያታከትነው በምንድር ነው?
ይህ ጥያቄ የሚያሳየው ህዝቡ ምንም ስህተት እንዳልሰሩ ነው ። ስለዚህ በሚከተለው አገላለጽ ዐረፍተነገሩን መግለጽ ይቻላል።”በእርግጥ እኛ እሱን አላሰለቸንም”
በማለት
በዚህ ስፍራ አጠቃላይ መልዕክቱ “እንደዚህ በማለት አታክታችሁታል” ። የነብዩ ጥያቄ መልስ እንደዚህ መሆን አለበት።
በዓይናችሁ
አይኖች ማየት ሲወክሉ ፥ ማየት ደግሞ ሃሳባቸውን ይወክላል። ስለዚህ “በእናንተ ሃሳብ” ወይም “በውሳኔአችሁ” ይባል።
የፍርድ አምላክ ወዴት አለ?
ካህናቱ ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ህዝቡ ሀጢያት ቢሰራም ባይሰራም እግዚአብሔር ስለ ህዝቡ ደንታ የለውም ወይም ክፉ አድራጊዎችን በፍጹም አይቀጣም፥ ስለዚህ “እግዚአብሔር በፍጹም ክፉሰዎችን አረሳም” ይባል።
የፍርድ አምላክ
ክፉሰዎችን በትክክል የሚቀጣ እግዚአብሔር

---

Chapter 3
Malachi 3:1
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ህዝብ በቁጥር አንድ መናገር ሲጀምር፥ ሚልክያስ ደግሞ በቁጥር ሁለት መናገር ይጀምራል።
እይ
“ተመልከት” ወይም “አዳምጥ” ወይም “ስለምነግርህ ነገር አጽንዖት ስጥ”
መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል
በዚህ ስፍራ ህዝቡ እግዚአብሔርን ለመቀበል መዘጋጀት ማለት እግዚአብሔር የሚሄድበትን መንገድ መጥረግ እንደማለት ነው።
እናንተም የምትፈልጉት ጌታ. . . የምትወዱትም የቃል ኪዳን መልእክተኛ፥
አንዳንድ የመጸሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይሄንን ቁጥር የሚገልጹት ስለ አንድ ሰው እንደተነገረ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ግልጽ እንዳልሆነ በመቀበል ግልጽ ለማድረግ ባለመፈለጋቸው እንድዚሁ ትተውታል።እኛም ግልጽ አይደለም እንላለን።
የቃልኪዳን መልእክተኛ
አብዛኛዎቹ ትርጉሞች ይህንን ክፍል ግልጽ ስላልሆነ እንዳለ አስቀምጠውታል። ሆኖም ግን ተርጉዋሚዎች “መልእክተኛ” በሚለውና “ቃልኪዳኑ” በሚለው መካከል ያለውን ግንኙነት “መልእክተኛው”እንደተሰጠው ተሰፋና ቃልኪዳኑ ደግሞ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባውን ለማመልከት እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል። ሌላው አማራጭ ደግሞ መልዕክተኛ የተባለዉ ሰው ቃልኪዳኑን እንደሚያጸና ወይም አዲስ ቃልኪዳን እንደሚያውጅ መግለጽ ነው።
ነገር ግን እርሱ የሚመጣበትን ቀን መታገሥ የሚችል ማን ነው? እርሱስ በተገለጠ ጊዜ የሚቆም ማን ነው?
እነዚህ መልስ የማያስፈልጋቸው ጥያቄዎች የሚገልጹት ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊት መቆም እንደማይችል ነው።ሁለቱን ጥያቄዎች በማዋሃድ በአንድ አረፍተነገር እንደሚከተለው መግለጽ ይቻላል። “ማንም ቢሆን እግዚአብሔር ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ በፊቱ ሊቆም አይችልም”
እሱ በሚመጣበት ቀን
በዚህ ስፍራ “ቀን” የሚለው “ጊዜ” የሚለዉን ይወክላል፥ ስልሆነም “ በሚመጣበት ጊዜ” ይባል።
መታገስ የሚችል
በዚህ ስፍራ “መቆም” የሚለው የአንድን ሰው ጥቃት ወይም ተቃውሞን መቋቋምን ያሳያል።
እርሱ እንደ አንጥረኛ እሳትና እንደ አጣቢ ሳሙና ይሆናል
ይህ ዐረፍተነገር እግዚአብሔር በሚመጣበት ጊዜ ማንም ሰው ሊቆም አይችልም ለሚለው ምክንያት ለመስጠት ነው። ፍርድ ለመስጠት የእግዚአብሔር ሃይል ሰዎች ሓጢያት መስራታቸውን እንዲያቆሙ የተባለው ልብስ ለማንጻት ጠንካራ ሃይል እንዳለው ሳሙና ወይንም ብረታብረት ለማቅለጥ ሓይል እንዳለው እሳት ነው።
የእነዚህ የአባባል መንገዶች የእግዚአብሔር ሃይል ማንኛውንም ነገር ለመስራት የሚከለክለው የለም ለማለት ነው።
የሌዊንም ልጆች ያጠራል፥
ለሌዊ ልጆች ይቅር ማለትና የሐጢአት መንገድ እንዳይከተሉ ማድረግ ብረታብረትን እንደማጥራት ይታያል። ስለዚህ “እሱ የሌዊን ልጆች ያስተካክላል፥ ሐጢያታቸውን ይቅር ይላል” ይባል።
የሌዊ ልጆች
በዚህ ስፍራ “ልጆች”የሚለው ዘሮቻቸውን ይወክላል።ወንድ የሌዊ ዘሮች ካህናት ወይም የቤተመቅደስ ሰራተኞች ናቸው።
እሱ ይቀመጣል
በዚህ ስፍራ መቀመጥ የብር አንጥረኛን ተግባር ያመለክታል።ይሄውም የብር አንጥረኛው ብር ወይም ወርቅ በሚያነጥርበት ጊዜ ቁጭ ብሎ እንደሚያነጥር ለማለት ነው። እንደዚሁም ደግሞ ንጉስ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ንጉስ ፍርድ እንደሚሰጥ ያለውን ተግባር ያመለክታል።
እሱ እንደ ወርቅና ብር ያነጥራቸዋል
በዚህ ስፍራ ሰዎች ከእንግዲህ ሰዎች የሀጢያት መንገድ አይከተሉም፥ ነገርግን የወርቅና የብር አንጥረኛ የበለጠ እንደሚያጠራ የሚለዉን ያሳያል።
እነርሱም ለእግዚአብሔር በጽድቅ ቍርባንን የሚያቀርቡ ይሆናሉ
በዚህ ስፍራ “የጽድቅ” ማለት እግዚአብሄርን በጽድቅ ለማምለክ መሻት ማለት ስልሆነ፥ “እግዚአብሔርን ለማምለክ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለውን ቁርባን/ስጦታ ያመጣሉ” ለማለት ነው ።
Malachi 3:4
x
ሚልክያስ ንግግሩን በቁጥር 4 ሲቀጥል እግዚአብሔር ደግሞ እንደገና ንግግሩን በቁጥር 5 ይቀጥላል።
የይሁዳና የኢየሩሳሌም ቍርባን
“ይሁዳ” እና “ኢየሩሳሌም” የሚሉት ቃላት በእነዚያ ስፍራ የሚኖሩትን ህዝብ ይወክላሉ። ስለሆነም “በይሁዳና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ህዝቦች የሚያመጡት ስጦታ/ቁርባን” ይባል።
እንደ ዱሮው ዘመንና እንደ ቀደሙት ዓመታት
እነዚህ ሁለቱ ሐረጎች አንድ ሲሆኑ ትኩረት የሚያደርጉት ግን ስጦታው/ቁርባኑ እግዚአብሔርን ያስደስት እንደነበር ነው። ስለዚህ “ባለፉት ዘመናት እንደነበረው” መባል አለበት።
ለፍርድ ወደ እናንተ እቀርባለሁ
በዚህ ስፍራ “ፍርድ” የመፍረድ ተግባርን ያመለክታል። ስለዚህ “ወደ እናንተ ቀርቤ እፈርድባችሁዋለሁ” መባል አለበት።
የምንደኛውን ደመወዝ በሚከለክሉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ተቀጥረው የሚሰሩትን ሰራተኞች ደመወዛቸውን በመከልከል ማሰቃየት”
የመጻተኛው ላይ ፊት ማዞር
የመጻተኛው የሚገባውን በመከልከል የሚጨቁኑ፥የአንድን ሰው መብት መከልከል ማለት ፊትን ከአንድ ሰው ላይ ማዞር እንደ ማለት ነው።ስለዚህ “በእስራኤል ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች መብት ትከለክላላችሁ” ማለት ይገባል።
Malachi 3:6
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ መናገሩን ቀጠለ።
ወደፍጻሜ አልመጣችሁም
“ የጠፋችሁ አይደላችሁም”
ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከሥርዓቴ ፈቀቅ ብላችኋል፥ እርሰዋንም አልጠበቃችሁም ችሁ
እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ማለት ፊትን ከእርሱ ላይ ማዞር ማለት ነው። ስለዚህ “ ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ስርአቴን አልጠበቃችሁም” ይባል።
ወደ እኔ ተመለሱ፥ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ
በዚህ ስፍራ እርስ በርስ መዋደድ ማለት ፊትን ወደእያንዳንዱ ማዞር ማለት ነው። ስለዚህ “ውደዱኝ አክብሩኝ እኔ ደግሞ እረዳችሁአለሁ” መባል አለበት።
የምንመለሰው እንዴት ነው?
ሰዎች ይህንን ጥያቄ የሚጠይቁት መቸነው ለእግዚአብሔር ያልታዘዝነው ለማለት ነው። ይሄንን ደግሞ በሚቀጥለው መንገድ መግለጥ ይቻላል፤ ከአንተ ወደየትም ስላልሄድን ወደአንተ እንዴት እንመለሳለን”።
Malachi 3:8
ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን?
ይህ ጥያቄ የሚያመለክተው ስርቆት/ ዘረፋ በጣም ክፉ መሆኑን ነው።እግዚአብሔር በዚህ ዐረፍተነገር ውስጥ እንደ ሶስተኛ ተናጋሪ ሆኖ ቀርቦአል። ስለሆነም እንደሚከተለው ይገለጽ “ሰው በእርግጥ እግዚአብሔርን መስረቅ የለበትም” ውይም “ማንም እኔን ምስረቅ የለበትም”
የሰረቅንህ በምንድር ነው?
ይህ ጥያቄ የሚያመለክተው ህዝቡ እግዚአብሄር እንደሚሰርቁ እድርገው ስለማይቆጥሩ ነው። ስለሆነም “እኛ አንተን አልሰረቅንህም” ይባል።
በአሥራትና በበኵራት
ይህ መልስ የተሰጠው ከእግዚአብሔር ስለ ሆን ሙሉ መልስ ነው። ስለዚህ “አስራትና በኩራቴን በመከልከል እኔን ሰርቃችሁኛላችሁ” ይባል።
በእርግማን ርጉሞች ናችሁ
በግልጽ “በእርግጥ ረግሜአችሁአልሁ” ማለት ይቻላል።
ሰርቃችሁኝል፥ ሕዝቡን ሁሉ
በዚህ ስፍራ “ሕዝብ” የሚለው የሚወክለው እግዚአብሄር እየተናገራቸው ያለውን ህዝብ ነው። ስለዚህ “በአገሩ ያላችሁ ህዝቦች ሁሉ” ማለት ይቻላል።
Malachi 3:10
አጠቃላይ መረጃ
እግዚአብሄር ለእስራኤል ህዝብ መናግሩን ቀጥሎ
ሙሉ አስራት
“አሥራቱን ሁሉ”
የኔ ቤት
በዚህ ስፍራ “ቤት” የሚለው ቤተመቅደሱን ይወክላል።ስለሆነም “የኔ ቤተመቅደስ” ይባል።
እናም አሁን በዚህ ፈትኑኝ . . . የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ፥
በዚህ ስፍራ “ፈትኑኝ” የሚያመለክተው ሰዎች የሚያደርጉትናማድረግ ያለባቸውን ነው። በዚህ ስፍራ “ብትፈትኑኝ” የሚለው በሁለት ዐረፍተነገሮች ሊከፈል ይችላል።ስለ ሆነም “እናም ብትፈትኑኝ. . . የሰማይ መስኮቶችን እከፍታለሁ” ወይም “ካደረጋችሁ . . . እናም ልትፈትኑኝ ትችላላችሁ፥የሰማይን መስኮት እከፍታለሁ” መባል አለበት።
አሕዛብ ሁሉ የተባረኩ ብለው ይጠሩአችኋል
በዚህ ስፍራ የተባረኩ የሚለው መባረክን ያመለክታል። ስለዚህ “አህዛብ ሁሉ እናንተ እንደተባረካችሁ ያውቃሉ” ይሁን።
አህዛብ ሁሉ
ይህ አገላለጽ በአገር ሁሉ ያሉትን ሕዝቦች ይመለከታል። ስለሆነም “በሁሉም አገር ያሉ ሕዝቦች” ይባል።
የተድላ ምድር
በዚህ ስፍራ “ተድላ” የሚወክለው የምድሪቱን ኑዋሪዎች የኑሮ ሲሆን በደስታ/ በተድላ መሆኑን ነው።
Malachi 3:13
አጠቃላይ መረጃ
ቁጥሮቹ አዲስ ሃሳብ ይጀምራሉ፥ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ይናገራል።
ቃላችሁ በእኔ ላይ ጠንካራ ሆኖአል/በእኔ ላይ ጠንካራ ቃል ትናገራላችሁ።
በዚህ ስፍራ “ጠንካራ” ድፍረት የሚለውን ይወክላል፥ እንዲሁም ደግሞ “ቃላችሁ” የሚለው አባባል “እናንተ ያላችሁት” ማለት ስለሆነ “ ስለ እኔ እናንተ ያላችሁት ድፍረት ነው” መባል አለበት።
እኛ በአንተ ላይ ምን ክፉ ነገር ተናገርን?
ሰዎች እኛ ስለ እግዚአብሔር ምንም ክፉ ነገር አልተናገርንም ስለሚሉ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃሉ። ይህ ደግሞ በሚከተለው ዐረፍተነገር ሊገለጽ ይችላል “እኛ እርስበርሳችን ስላንተ ምንም ክፉነገር አልተናገርንም”።
እናንተ ‘እግዚአብሔርን ማገልገል ከንቱ ነው፤ ትእዛዞቹን መጠበቅና እንደ ሐዘንተኞች በሠራዊት አምላክ ፊት መመላለስ ምን ይጠቅመናል?’
ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ እርስ በርስ የሚጠያየቁት ቀጥሎ የተጠቀሰውን ለማለት ፈልገው ነው። “የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጠበቅና በፊቱ በሐዘን ማግልገል አይጠቅምም”።
በሰራዊት ጌታ ፊት በሐዘን መሄድ
በዚህ ስፍራ “በሐዘን መሄድ” የሚለው ሐረግ “በሐዘን ስሜት” የሚለውን ይወክላል፤ምናልባትም ስለ ሀጢያታቸው ማዘንን ይጠቁማል።
በሠራዊት ጌታ ፊት
ይህ አገላለጽ ሰዎች የሚሰሩትን እግዚአብሔር ያውራል የሚለውን ይጠቁማል።
የተባረኩ ክፉዎች እንላለን
በዚህ ስፍራ “የተባረኩ የተባሉት” የሚለው ሐረግ መባረክን ያመለክታል። ስለዚህ “ክፉዎች ተባርከዋል” እንላለን።
የተባረኩ ክፉዎች እንላለን
ይህ አገላለጽ እንደሚከተለው ሊቀርብ ይችላል፥” ክፉዎች በብልጽግና ይኖራሉ እንላለን”።
ያመልጣሉ
“ከእግዚአብሔር ቁጣ ያመልታሉ” ለማለት ነው።
Malachi 3:16
እግዚአብሔርን የሚፈሩና ስሙንም የሚያከብሩ ሰዎች ለተግባራቸው መታሰቢያ በመጽሐፍ ተጻፈ።
ይህም ማለት 1)እስራኤላውያን መጸሐፍ የጻፉት ለእግዚአብሔር ቃል የገቡትና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎችን ስም ዝርዝር ለማስታወስ ነበር፥ ወይም 2)እግዚአብሔር በመንግስተ ሰማይ አንድ ሰው እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎችን ስም እንዲጽፉ ያደርጋል ማለት ነው።
መታሰቢያ መጽሐፍ
ይህ አገላልጽ የሚያመለክተው ሕዝቡ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን፤ ክስተቶችንና ባለፉት ዘመናት የኖሩትን ሰዎች ለማስታውስ የሚረዱ መጸሀፍትን ለማመልከት ነው።
ስሙን ማክበር
በዚህ ስፍራ “የሱን ስም” የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል።
Malachi 3:17
እነሱ የኔ ይሆናሉ
“እነሱ የኔ ሕዝብ ይሆናሉ”
የእኔ የግሌ ገንዘብ ይሆናሉ
በዚህ ስፍራ “ንብረት” የሚለው የአንድን ሰው የግል ንብረት ያመለክታል። ይህን ሀሳብ በሚቀጥለው መንገድ መግለጥ እንችላለን፥”እነሱ ለኔ ሙሉ በሙሉ የተገቡ ይሆናሉ”።
እኔ በምሠራበት ቀን
የዚህ አገላለጽ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በፍርድ ጊዜ አመጸኞቹን እስራኤላውያን በሚቀጣበትና ለታማኞቹ እስራኤላውያን ድል የሚሰጥበትን ነው።
በመካከል ልዩነት ይሆናል
“በመካከል ልዩነት ታያላችሁ” ወይም “በልዩነት ትታያላችሁ”

Chapter 4


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Malachi 4:1

እይ

“ተመልከት” ወይም “አድምጥ” ወይም “ለምነግርህ ነገር ትኩረት ስጥ”

ጊዜው እየመጣ ነው፥ እንደ ገለባ በእሳት የሚቃጠሉበት

ሊመጣ ያለው የጥፋት ቀን ራሱ እንደሚያቃጥል ይነገራል። የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ብዙውን ጊዜ እሳት እንደ ሆነ ይነገራል።

ትዕቢተኞች . . . ክፉ አድራጊዎች

x

ሁሉም ትዕቢተኞችና ክፉአድራጊዎች ገለባ ይሆናሉ

እነዚህ ህዝቦች ገለባ ስለሆኑ ዕድላቸው መቃጠል ነው። በመጸሐፍ ቅዱስ ሰዎች በዕጽዋትና በዛፍ መመሰላቸው የተለመደ ነው። ስለዚህ “ሁሉም ትዕቢተኞች እንደ ደረቀ ገለባ ይቃጠላሉ” ይባል።

ቀኑ ሲመጣ ያቃጥላቸዋል

በዚህ ስፍራ “ቀኑ” የሚለው በዚያን ቀን የሚሆነውን ያመለክታል። ስለሆነም “በዚያን ቀን እኔ አቃጥላቸዋለሁ" ይባል።

ከእነርሱ ሥር፥ ወይም ቅርንጫፍ አይቀርም

ይህ አገላለጽ ሰዎችን በዕጽዋትና በዛፎች እየመሰለ ይቀጥላል። ስለዚህ ስርና ቅርንጫፍ አይኖራችሁም ሲል በእርግጥ ትሞታላችሁ ለማለት ነው። ስለሆነም “ምንም አይቀርም” ይባል።

እናንተ ስሜን የምትፈሩ

በዚህ ስፍራ “የኔ ስም” የሚለው እግዚአብሔርን ይተካል።

የጽድቅ ፀሐይ ይወጣላችኋል፤ ፈውስንም በክንፎችዋ ውስጥ ትሆናለች

ይህም ማለት 1) እግዚአብሔር በጽድቅ በሚሰራበት በዚያን ቀን ሕዝቡን ይፈውሳል ወይም 2) በዚያን ቀን እግዚአብሔር ሕዝቡን በጽድቅ ይገልጣል ይፈዉሳቸዋልም

ፈውስ በክንፎቹ ውስጥ

አማራጭ ትርጉሞች 1) የአንድ ሰው ፈውስ ጸሀይ በክንፎችዋ ተሸክማ እንደምታደርስ ነገር ይነገራል 2) ፈውስ የሚሰራው በክንፎች ስር እንደሆነ፥ ማለትም እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያደርገው ጥበቃ ናቸው።

ክንፎች

በጥንታዊ የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ፀሐይ ክንፍ እንዳላትና ሰማይን እንደምታቋዋርጥ ይታሰብ ነበር። በዚህም መሰረት ሁለት አማራጭ ትርጉሞች እንደሚከተለው ነው። 1) የፀሀይ ህይወት ሰጪ ጨረሮች በክንፍዋ እንዳለ ይነገራል። ወይም 2) ክንፎቹዋ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሰላምና ደህንነት በመስጠት እንደ እንደሚሸፍናቸው ነው።

ከጕረኖ እንደ ተለቀቀ ጥጃ ትቦርቃላችሁ

እንደተለቀቃችሁ የእግዚአብሔር ሕዝብ ፤ ተብሎ የተነገረው እንደ ተለቀቀ ጥጃ ወደመሰማሪያ መሄድን ያመለክታል።

ክፉዎች በእግራችሁ ጫማ ሥር እንደ ዐመድ ሆነው ይረገጣሉ

በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ሕዝብ በተቃጠው በጠላት ሬሳ ላይ ይራመዳሉ ለማለት ነው።

ዐመድ ይሆናሉ

የእስራኤል ጠላቶች ተቃጥለው አመድ ይሆናሉ ለማለት ነው።

Malachi 4:4

በሲና ተራራ ላይ ለአገልጋዬ ለሙሴ የሰጠሁትን ትምህርት ሕግና ትእዛዝ አስታውሱ

“ትምህርት” የተባለው የተማሩትን ለማለት ነው። ስለዚህ “ አገልጋዬን ሙሴን ያስተማርኩትን” ይባል።

አስታውሱ

በዚህ ስፍራ “አስታውሱ” የተባለው “ ስለዚህ ነገር አስቡ” እንዲሁም “ታዘዙ” ለማለት ነው።

ሆሬብ

ይህ የሲና ሌላው ስም ነው።

እስራኤል ሁሉ

በዚህ ስፍራ “እስራኤል ሁሉ” የሚለው በእስራኤል አገር የሚኖሩትን ሕዝብ ለማለት ነው።

ሕጉን/ደንብ

ይህ ሕግ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ሁሉ የሰጠው ነው።

ትዕዛዞች

እነዚህ ሕጋዊ ዉሳኔዎች በየእለቱ በህይወታቸው በአጠቃላይ ሕጉ እንዴት ስራላይ ሊዉል እንደሚችል ግልጽ የሚያደርጉ ናቸው።

ታላቁና አስፈሪው የእግዚአብሔር ቀን መምጣት

የዚህ ቀን መምጣት የተገለጸው እየመጣ ነው በማለት ነው።ስለዚህ “ታላቁና አስፈሪው የእግዚአብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት” ይባል።

ታላቁና አስፈሪው የእግዚአብሔር ቀን

ይህ አገላለጽ የሚያመለክተው እግዚአብሔር የመከራ ቀን የሚያመጣበትን ጊዜ ነው።

እርሱ የወላጆችን ልብ ወደ ልጆች፥ የልጆችንም ልብ ወደ ወላጆች ይመልሳል

በዚህ ስፍራ ይመልሳል/ ይለዉጣል የተባለው ልባቸውን ይመልሳል ለማለት ነው።

---

Chapter 1

Matthew 1:1

ማቴዎስ 1:1-3

አጠቃላይ መረጃ ጸሐፊው ኢየሱስ ከዳዊት እና ከአብርሃም ዘር እንደመጣ ለማሳየት ጽሑፉን የጀመረው ከኢየሱስ የዘር ሀረግ ነው። ይህ የዘር ሀረግ ዝርዝር እስከ ዲረስ ይቀጥላል MAT 1:17 የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ ይህ የኢየሱስ ትውልድ ዝርዝር ነው። የዳዊት ልጅ፥ የአብርሃም ልጅ በኢየሱስ፥ በዳዊት እና በአብረሃም መካከል ብዙ ትውልዶች አሉ። በዚህ ሥፍራ "ልጅ" ማለት "ዘር' ማለት ነው። "የዳዊት ልጅ የሆነው እርሱ የአብርሃምም ልጅ ነው።" የዳዊት ልጅ አንዳንድ ጊዜ "የዳዊት ልጅ" የሚልው ሀረግ እንደ ስያሜ ሆኖ ያገልግላል ነገር ግን በዚህ ሥፍራ ላይ የኢየሱስን ቅድመ አያቶች ለማሳየት የገባ ቃል ነው። አብርሃም የይሳቅ አባት ነው። ይህንን በተለያዩ መንገዶች መተርጎም ይቻላል። በዬትኛውም መንገድ ተርጉሙት በዘር ሀርግ ዝርዝር ውስጥ ተመሳሳ በሆነ መልኩ መተርጎሙ ጥሩ ነው። ትርጉም: "አብርሃም የይሳቅ አባት ሆነ" ወይም "አብርሃም ይሳቅ የሚባል ልጅ ነበረው።" ፋሬስንና ዛራን . . . ኤስሮምን . . . አራም እነዚህ የሰዎች ስም ። ፋሬስን . . . አባት ነው ኤስሮም . . . ነው።

Matthew 1:4

ማቴዎስ 1፥4-6

ሰልሞንም የቦኤዝ አባት ነው "ሰልሞን የቦኤዝ አባት ነው፤ የቦኤዝ እናት ደግሞ ረአብ ናት" ወይም "ሰልሞን እና ረአብ የቦኤዝ ወላጆች ናቸው።" ቦኤዝ የኢዮቤድ አባት ነው፤ የኢዮቤድም እናት ሩት ናቴ" ወይም "ቦኤዝ እና ሩት የኢዮቤድ ወላጆች ናቸው። ዳዊትን የኦርዮ ሚስት ከነበረችው ምስቱ ሰሎሞንን ወልዶ አባቱ ሆን ወይም "ዳዊት እና የኦርዮ ሚስት የነበረችው ምስቱ የሰለሞን ወላጆች ናቸው። የኦርዮ ሚስት የነበረችው ሰለሞን የተወለደው ኦርዩ ከሞተ በኃላ ነው።

Matthew 1:7

ማቴዎስ 1፥ 7-8

አሳ አንዳንድ ጊዜ "አሳፍ" ተብሎ ይተረጎማል። የዖዝያን ትክክለኛ ስሙ ሮብዓም፥ ስለዚህም "አባት" የሚለው ቃል "የዘር ሀረግ" ተብሎ መተርጎም ይችላል። ሰሎሞንም ሮብዓምን ወለደ፤ ሮብዓምም አቢያን ወለደ፤ (UDB).

Matthew 1:9

ማቴዎስ 1፥ 9-11

አሞን አሞን አንዳንድ ጊዜ "አሞፅ" ተብሎ ይተረጎማል። ኢዮስያስ የኢኮንያንን አባት ነው እውነታው ኢዮስያስ የኢኮንያንን አያት ነው። በባቢሎንም ምርኮ ጊዜ "ወደ ባቢሎን በምርኮ ተገደው እንዲሄዱ ሲድረግ" ወይም "ባቢሎናዊያን ቁጥጥር በሆኑ ጊዜና ወደ ባቢሎን እንዲሄዱ ስያስገድዷቸው።" በቋንቋችሁ ማን ወደ ባቢሎን እንደሄደ መግለጽ አስፈላጊ ከሆነ እንዲህ ማለት ትችላላችሁ "እስራኤላዊያን" ወይም "በይሁዳ ይኖሩ የነበሩ እስራኤላዊያን" ባቢሎን በዚህ ሥፍራ ላይ ባቢሎን የሚለው ቃል የሚያመለክተው ባቢሎን የተሰኘችውን ሀገር እንጂ የባቢሎን ከተማን ብቻ አይደለም።

Matthew 1:12

ማቴዎስ 1፥ 12-14

ከባቢሎንም ምርኮ በኋላ MAT 1:11. ላይ ከተጠቀምከው ቃል ጋር ተመሳሳይ ቃልን ተጠቀም። ሰላትያል የዘሩባቤል አባት ነው እውነታው ሰላትያል የዘሩባቤል አያት ነው።

Matthew 1:15

ማቴዎስ 1፥ 15-17

አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጸሐፊው በ MAT 1:1. ላይ የጀመረውን የኢየሱስን የትውልድ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሀርግ ያጠናቅቃል። ኢየሱስን የወለደችው ማሪያም ኤቲ: "ኢየሱስን የወለደችው ማሪያም" ( ይመልከቱ) ክርስቶስ የተባለው ይህ እንዲህ ልተረጎም ይችላል፡ ኤቲ: "ሰዎች ክርስቶስ ብለው የሚጠሩት።" ( ተመልከቱ) ዐሥራት አራት "14" ( ተመልከቱ) የባቢሎን ምርኮ [MAT 1:11](). ላይ ከተጠቀምከው ቃል ጋር ተመሳሳይ ቃልን ተጠቀም።

Matthew 1:18

ማቴዎስ 1፥ 18-19

አጠቃላይ መረጃ ይህ ክፍል ጸሐፊው ለኢየሱስ መወለድ ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን የገለጸበት የታሪኩ አዲሱ ጅማሬ ነው። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ነበር "እናቱ ማርያም ዮሴፍን ልታገባ ነበር።" ብዘመኑ ወላጆች ለልጆቻቸው ትዳር አጋር ያዘጋጁ ነበር። ኤቲ: "የኢየሱስ እናት የሆነችው ሪያም ወላጆቿ ለዮሴፍ እርሷን ለመዳር ተስማምተዋል።" ( ተመልከት) እናቱ ማርያም ታጭታ ነበር ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ በነበረበት ወቅት ኢየሱስ አለመወለዱን በሚያሳይ መንገድ ተርጉሙት። ኤቲ: "ኋላ ላይ ኢየሱስን የወለደችው ማሪያም ታጭታ ነበር" ሳይገናኙ "ከመጋባታቸው በፊት።" ይህ ዮሴፍ እና ማሪያም አብረው ከመተኛታቸው በፊት" የሚለውን የሚያመልክት ይሆናል። ኤቲ: "አብረው ከመተኛታቸው በፊት"። ( ተመልከት) አርግዛ ተገኘች ይህ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ልጅ ልትወልድ እንደሆነ አወቁ” ወይም “አረገዘች።” ( ተመልከት) በመንፈስ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ማሪያም ከሰው ጋር ሳትተኛ ማርገዝ እንድትችል አደረጋት። ባሏ ዮሴፍ ዮሴፍ ማሪያምን ገና አላገባትም ነበር ይሁን እንጂ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ትዳር ለመጋባት ቃል ከተገባቡ ምንም እንኳ አብረው መኖር ባይጀምሩም አይሁዶች ባል እና ምስት አድርገው ይቆጥሯቸው ነበር። ከእርሷ ጋር የተነበረውን እጮኝነት ለማቆም “ለመጋባት የነበራቸውን እቅድ ለመሰረዝ”

Matthew 1:20

ማቴዎስ 1፡ 2-22

እንዳሰበው “ዳዊት እንዳሰበው” በሕልም ተገለጠለት “ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦለት” የዳዊት ልጅ በዚህ ሥፍራ “ልጅ” ማለት “የልጅ ልጅ” ማለት ነው። በማሕጸኗ ውስጥ የተሸከመችው ልጅ የተጸነሰው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “መንፈስ ቅዱስ ማሪያም እንዲትጸንስ አደረገ።” ( ተመልከት) ወንድ ልጅ ትወልዳለች እግዚአብሔር መልአክን ስላዘዘ መልአኩ የተወለደው ወንድ ልጅ እንደሆነ ያውቅ ነበር። እንዲህ ብለሽ ትጠሪዋለሽ ይህ ትዕዛዝ ነው። ኤቲ: “እንዲህ ብለሽ ጥሪው” ወይም “እንዲህ የሚል ስም ልትሰጪው ይገባል። ያድናልና በዚህ ሥፍራ ላይ ተርጓሚዎች እንዲህ የሚል የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ይችላሉ፡ “ኢየሱስ የሚለው ስም ጌታ ያድናል ማለት ነው። ሕዝቡን ይህ የሚያመለክተው አይሁዳዊያንን ነው

Matthew 1:22

ማቴዎስ 1:22-23

አጠቃላይ መረጃ ጸሐፊው የኢየሱስ አወላለድ በቅዱሳት መጽሐፍት አስቀድሞ በተነገረው መሠረት መሆኑን ለማሳየት ከነብይ ኢሳያስ መጽሐፍ ጠቅሶዋል። ( ተመልከት) ይህ ሁሉ ሆነ መልአኩ መናገር አቁሟል። አሁን ማቴዎስ መልአኩ የተናገረው ነገር ምን ያኽል አስፈላጊ እንደሆነ እያብራራ ነው። ጌታ በመላዕክቱ አማካኝነት የተናገረው ነገር ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፡ ኤቲ: “ጌታ ለነብይ ኢሳያስ ከብዙ ዘመናት በፊት የተናገረው እንዲጸፍ የነገረው ነገር።” ( ተመልከት) እነሆ . . . አማኑኤል በዚህ ሥፍራ ላይ ማቴዎስ ከነብዩ ኢሳያስ መጽሐፍ ጠቅሷል። እነሆ ይህ ቃል ሰዎች ከዚህ በኋላ ለሚነገረው ነገር አጽኖት እንዲሰጡ የሚጨመር ቃል ነው፡ ኤቲ: “ተመልከቱ” ወይም “አድምጡ” ወይም “አሁን ለምነግራችሁ ነገር ትኩረት ስጡ”:: አማኑኤል ይህ የወንድ ስም ነው። ( ተመልከት) “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው” ማለት ነው ይህ በኢሳያስ መጽሐፍ ውስጥ የለም። ማቴዎስ የስሙን ትርጉም እያብራራ ነው። ይህን ለብቻው በአንድ ዐረፍተ ነገር መተርጎም ትችላላችሁ። ኤቲ: “የዚህ ስም ትርጉም “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው” ማለት ነው።

Matthew 1:24

ማቴዎስ 1:24-25

አያያዥ ዐረፍተ ነገር ጸሐፊው የኢየሱስ አወላለድን ምን ይመስል እንደነበር የሰጠውን ገለጻ አጠናቀቀ። የጌታ መልአክ ባዘዘው መሠረት መልአኩ ዮሴፍን ማሪያምን ምስቱ አድርጎ እንዲወስዳት እና የልጁንም ስም ኢየሱስ እንዲለው አዘዘው። እርሱም እርሷን ምስቱ አድርጎ ወሰዳት “አባባት” ለልጁ ዮሴፍ እውነተኛ አባቱ አለመሆኑን ግልጽ መሆኑን እርግጠኞች ሁኑ። ኤቲ: “ወንድ ልጅ” ወይም “ለልጇ” እና ኢየሱስ ብሎ ስም ጠራው “ዮሴፍ ሕጻኑን ኢየሱስ የሚል ስም አወጣለት”

---

Chapter 2

Matthew 2:1

ማቴዎስ 2:1-3

አጠቃላይ መረጃ የታሪኩ አዲስ ክፍል የሚጀምረው በዚህ ሥፍራ ላይ ነው። ከዚያም እስከ ምዕራፉ መጨረሻ ድረስ ይሄዳል። ጸሐፊው ሄሮዶስ አዲሱን የአይሁድ ንጉሥ ለመግደል ስላደረገው ሙከራ ይነግረናል። ቤተልሔም ይሁዳ “በይሁዳ ግዛት ውስጥ የሚትገኝ የቤተልሔም ከተማ” ሄሮዶስ ንጉሥ በነበረበት ዘመን “በዚያ ሄሮዶስ ንጉሥ ሆኖ ሳለ” ሄሮዶስ ሄሮዶስ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ታላቁን ሄሮዶስን ነው። የተማሩ ሰዎች “ክዋክብትን ያጠኑ ሰዎች” (UDB) ከምስራቅ የመጡ “ከይሁዳ በስተምስራቅ በኩል ከሚገኝ ሀገር የመጡ” የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ዬት አለ? ሰዎቹ ከክዋክብት ጥናታቸው የአይሁድ ንጉሥ ለመሆን የተወለደ ልጅ እንዳለ አውቀዋል። በዬት ሥፍራ እንዳለ ለማወቅ ፈልገዋል። ኤቲ: “የአይሁድ ንጉሥ ለመሆን አንድ ልጅ ተወልዷል። ዬት ነው ያለው?” የእርሱ ኮከብ ኮከቧ ትክክለኛ ባለቤት ልጁ ነው እያሉ አይደለም። ኤቲ: “ስለ እርሱ የሚትናገረው ኮከብ” ወይም “ከእርሱ መወለድ ጋር የተያያዘችው ኮከብ” በምስራቅ “በምስራቅ በወጣች ጊዜ” ወይም “በሀገራችን ሳለን” ማምለክ አማራጭ ትርጉሞች 1) ልጁ መለኮት እንደሆነ ተገንዝበው ለማምለክ ፈልገዋል ወይምመ 2) እንደ አንድ ንጉሥ ልያከብሩት ፈልገዋል። ቋንቋዎችሁ ሁለቱንም ትርጉሞች መያዝ የሚችል ቃል ካለው በዚህ ሥፍራ ላይ ይህንን ቃል መጠቀምንን ከግንዛቤ ውስጥ አስገቡ። ተጨነቀ “ፈራ”። ይህ ልጅ ንግሥናዬን ይቀማኛል ብሎ በመፍራት ተጨነቀ። ኢየሩሳሌም በሙሉ በዚህ ሥፍራ ላይ “ኢየሩሳሌም” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሰዎችን ነው። እንዲሁም “ሁሉም” ማለት “ብዙ” ማለት ነው። ማቴዎስ በዚህ ሥፍራ ላይ ብዙ ሰዎች በዚህ ጉዳይ መጨነቃቸውን ለማመልከት ግነት ተጠቅሟል። ኤቲ: “በኢየሩሳሌም ያሉ ብዙ ሰዎች።” (UDB) ( and ተመልከት)

Matthew 2:4

ማቴዎስ 2:4-6

አጠቃላይ መረጃ በቁጥር 6 ላይ ካህናት አለቆች እና ጸሐፊት ክርስቶስ በቤተልሔም ከተማ እንደሚወል ከሚልክያስ መጽሐፍ በመጥቀስ አሳይተዋል። በቤተልሔም ይሁዳ “በይሁዳ ግዛት የሚትገኘው ቤተልሔም ውስጥ” ይህ በነብያት የተነገረው ነገር ነው ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፡ ኤቲ: “ይህ ነቢያት ከብዙ ዘመናት በፊት የጻፉት ነገር ነው።” (: ተመልከት) እና አንች፣ ቤተልሔም . . . ኢስራኤል ከሚልክያስ መጽሐፍ ላይ እየጠቀሱ ነው። አንች፣ ቤተልሔም . . . ከይሁዳ መሪዎች መካከል መጨረሻ አይደለሽም ሚልክያስ በቤተልሔም ይኖሩ ለነበሩ ሰዎች ከእርሱ ጋር እንደሆኑ አድርጎ ይነግራቸው ነበር ነገር ግን እነርሱ ጋር ከእርሱ ጋር አልነበሩም። በተጨማሪም “የመጨረሻ አልነበሩም” ይህ አዎንታዊ በሆነ ሀረግ ሊተረጎም ይችላል። ኤቲ: “እናንተ የቤተልሔም ሰዎች . . . ከተማችሁ በይሁዳ ግዛት ውስጥ ከሚገኙ ከተሞች መካል ትልቁ ነው።” ( እና ተመልከቱ) ሕዝቤን ኢስራኤል የሚጠብቅ ማን ነው ሚልክያስ እነዚህን ገዥዎችን እንደ እረኛ አድርጎ ይናገራቸዋል። ይህ ማለት ሕዝቡን የሚመሩ እና የሚንከባከቡ። ኤቲ: “እረኛ በጎቹን እንደሚመራ ሁሉ ሕዝቤን የሚመራ ማን ነው” ( ተመልከት)

Matthew 2:7

ማቴዎስ 2፡ 7-8

ሄሮዶስ በሚስጥር የተማሩ ሰዎችን ጠራቸው ይህ ማለት ሄሮዶስ የተማሩ ሰዎችን ሌሎች ሰዎች ሳያውቁ በድብቅ አስጠርቶ አናገራቸው ማለት ነው። ኮከቡ የታየው በትክክል መቼ እንደሆነ ጠያቃቸው ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊተረጎም ይችላል። ኤቲ: “ከዚያም እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፣ “ኮከቡ በትክክል የታየው መቼ ነበር?” ( ተመልከት) ኮከቡ የታየው መቼ ነበር ይህ የተማሩት ሰዎች ከኮቡን መቼ እንደተመለከቱት በተዘዋዋር መንገድ እንደነገሩት ያሳያል። የተማሩትም ሰዎች ለሄሮዶስ ኮከቡን መቼ እንደተመለከቱ ነገሩት። ( ተመልከት) ጨቅላው ሕጻን ይህ ኢየሱስ የሚያመለክት ነው። ቃል አምጡልኝ ኤቲ: “አሳውቁኝ” ወይም “ንገሩኝ”( ተመልከት) እንዳመልከው ይህንን በ [MAT 2:2]() ላይ በተረጎምከው መሠረት ተርጉመው።

Matthew 2:9

ማቴዎስ 2፡ 9-10

ከእነርሱ በኋላ “ከተማሩተ ሰዎች በኋላ” በምስራቅ ተመለከቱ “በምስራቅ በኩል

ስወጣ አዩት" ወይም "በሀገራቸው አዩት" ከፊት ፊታቸው ይሄድ ነበር "ይመራቸው ነበር" ወይም "መንገድ ያሳያቸው ነበር" ቀጥ ብሎ ቆመ "ቆመ" ጨቅላው ሕጻን ያለበት "ጨቅላው ሕጻን ያለበት ሥፍራ ስደረሰ"

Matthew 2:11

ማቴዎስ 2:11-12

አያያዥ ዐረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ የታሪኩ ፍሰት ወደ ማሪያም፣ ዮሴፍ እና ትንሹ ኢየሱስ ወደ ሚኖሩበት ቦታ ተለውጧል። ሄዱ "የተማሩት ሰዎች ሄዱ" አምልኮ ይህንን በ MAT 1:2 ላይ በተረጎምከው መሠረት ተርጉመው። ንብረታቸው በዚህ ሥፍራ ላይ "ንብረታቸው" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ንብረታቸውን ብዙ ጊዜ የሚይዙበት ሳጥን ወይም ሻንጣን ነው። ኤቲ: "ንብረታቸውን የሚይዙበት ሻንጣ።" ." ( ተመልከት) እግዚአብሔር አስጠነቀቃቸው "ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር አስጠነቀቃቸው። ሄሮዶስ ልጁን ሊገድለው እንደሚፈልግ እግዚአብሔር ያውቃል። ወደ ሄሮዶስ እንዳይመለሱ ይህ በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ ተደርጎ መተርጎም ይችላል። ኤቲ: "እንዲህ በማለት "ወደ ንጉሥ ሄሮዶስ ተመልሳችሁ እንዳትሄዱ።" ( ተመልከቱ)

Matthew 2:13

ማቴዎስ 2:13-15

አጠቃላይ መረጃ በቁጥር 15 ላይ ጸሐፊው ክርስቶስ በግብጽ ምድር እንደሚቆይ ከነብዩ ሆሴን ይጠቅሳል። ሄዱ "የተማሩት ሰዎች ሄዱ" ለዮሴፍ በሕልም ተገለጠለት "ዮሴፍ ሕልም እያለመ ሳለ ወደ እርሱ መጣ" ተነስ፣ ያዝ . . . ሽሽ . . . ቆይ . . . አንተ እግዚአብሔር ለዮሴፍ ተናገረው። ስለዚህ ሁሉም በነጠላ ቁጥር ሊሆኑ ይገባቸዋል። . ( ተመልከት) እስክነግርህ ድረስ የዚህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል። ኤቲ: "መመለስህ ሰላም እንደሆነ እኔ እስክነገር ድረስ" ( ተመልከት) ቆየ ይህ ዮሴፍ፣ ማሪያም እና ኢየሱስ በግብጽ ምድር ውስጥ መቆየታቸውን ያሳያል።::: ኤቲ: "በዚያ ቆዩ" ( ተመልከት) ሄሮዶስ እስኪሞት ድረስ ሄሮዶስ [MAT 2:19](). ድረስ አልመተም። ይህ ዓረፍተ ነገር በግብጽ ምድር ውስጥ ለምን ያኽል ጊዜ እንደቆዩ ያሳያል እንዲሁም በእነዚህ ጊዜያት ሄሮዶስ እንደሞተ አይናገረም። ልጄን ከግብጽ ምድር ጠራሁት "ልሄን ከግብጽ ጠራት" ልጄ በሆሴ ውስጥ ይህ እስራኤላዊያንን የሚያመለክት ቃል ነው። ማቴዎስ ይህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለመናገር ይህንን ክፍል ጠቅሶታል። ይህንን ብቸኛ ልጅ ወይም የመጀመሪያ ልጅን በሚያሳይ ቃል ተርጉሙት።

Matthew 2:16

ማቴዎስ 2:16-16

አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ የታርኩ ፍሰት ወደ ሄሮዶስ ይመለሳልና የተማሩት ሰዎች እንዳታለሉት ሄሮዶስ ባወቀ ጊዜ ያደረገውን ይነግረናል። አጠቃላይ መረጃ ይህ ሁኔታ የተከሰተው ጸሐፊው [MAT 2:15](). ላይ የጠቀሰው እና ሄሮዶስ ከመሞቱ በፊት ነው። ( ተመልከት) የተማሩት ሰዎች ቀለዱበት ይህ እንዲህ ባለ መልኩ ሊገለጽ ይችላል: ኤቲ: "የተማሩት ሰዎች ሸውደውት ሄደው አዋረዱት"። ( ተመልከት) ሰዎችን ልኮ ሁሉንም ልጆች አስገደላቸው ሄሮዶስ ልጆቹን እርሱ ራሱ አልገደላቸውም። ኤቲ: "ሁሉንም ወንድ ልጆችን ይገድሉ ዘንድ ግን ትዕዛዝ ሰጣቸው" ወይም "ሁሉንም ወንድ ሕጻናትን ይገድሉ ዘንድ ወታደሮቹን ላካቸው።" ( ተመልከት) ሁለት እና ከሁለት ዓመት በታች የሆኑትን "2 ዓመት እና ከዚያ በታች ያሉትን" (UDB) ( ተመልከት) እንደገዜው "በጊዜው መሠረት"

Matthew 2:17

ማቴዎስ 2:17-18

አጠቃላይ መረጃ በይሁዳ ግዛት ውስጥ የነበሩት ወንድ ልጆች ሁሉ መገደላቸው በቅዱሳት መጽሐፍት በተነገረው መሠረት መሆኑን ጸሐፊው ነብዩ ኤርሚያስን በመጥቀስ ጽፏል። ይህም ተፈጸመ ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: "ይህ ተፈጸመ" ወይም "የሄሮዶስ ተግባር ተፈጸመ።" ( ተመልከት) የተፈጸመው ነገር በነብይ ኤርሚያስ አስቀድሞ ተነግሮ ነበር ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊተረጎም ይችላል። ኤቲ: "ገታ በነብይ ኤርሚያስ አማካኝነት ከብዙ ዘመናት በፊት እንደተናገረው።" ( ተመልከት) ድምፅ ተሰማ . . . ከእንግዲህ የሉም ማቴዎስ ነብዩን ኤርሚያስን እየጠቀሰ ነው ድምፅ ተሰማ ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል: ኤቲ: "ሰዎች ድምፅ ሰሙ" ወይም "ከፍተኛ ድምፅ ነበር። ( ተመልከት) ራሔል ስለልጆቿ አለቀሰች ራሔል ይህ ነገር ከመሆኑ ብዙ ዓመታት በፊት ነው የኖረችው። ይህ ትንቢት የሚያሳያው ከብዙ ዓመታት በፊት የሞተችው ራሔል ስለ ልጆቿ ማልቀሷን ነው። መጽናናትንም እንቢ አለች ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: "ማንም ሊያጽናናት አልቻለም።" ( ተመልከት) የሉምና "ልጆቿ ጠፍተዋል እንዲሁም እንደገና ፈጽመው አይመለሱም። በዚህ ሥፍራ "የሉም" የሚለው ቃል ለዘብ ባለ ቃል መሞታቸውን የሚያሳይ ነው። ኤቲ: "ስለሞቱ"። ( ተመልከት)

Matthew 2:19

ማቴዎስ 2:19-21

አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ የታርኩ ፍሰት ዮሴፍ፣ ማሪያም እና ጨቅላው ኢየሱስ ወደሚኖሩበት ወደ ግብጽ ተቀይሯል። እነሆ ይህ በትልቁ ታርክ ውስጥ አንድ ሌላ ሁኔታ የመጀመሩ ምልክት ነው። ከዚህ ቀደም ካሉት ሁኔታዎች ውስጥ ከነበሩት ሰዎች ተጨማሪ ሰዎችን ሊጨምር ይችላል። በቋንቋችሁ ይህንን የሚትገልጹበት መንገድ ሊኖራችሁ ይችላል። የሕጻኑን ሕይወት የሚፈልጉት ሰዎች ኤቲ: "ሕጻኑን ለመግደል የሚፈልጉት ሰዎች"። ( ተመልከት) የሚፈልጉት ሰዎች ይህ ንጉሥ ሄሮዶስን እና አማካሪዎቹን የሚያመለክት ነው።

Matthew 2:22

ማቴዎስ 2:22-23

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ በ [MAT 2:1]() የተጀመረው ታርክ ሄሮዶስ የአይሁድ አዲሱን ንጉሥ ለመግደል ያደረገው ሙከራ የመጨረሻው ክፍል ነው። ይህንን በሰማ ጊዜ "ዮሴፍ ይህንን ስሰማ ግን" አርኬላዎስ ይህ የሄሮዶስ ልጅ ስም ነው። ( ተመልከት) ፈራ "ዮሴፍ ፈራ" በነቢያቱ የተነገረው ነገር ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: "ከብዙ ዘመናት በፊት ጊዜ በነቢያቱ አማካኝት እንደተናገረው።" ( ተመልከት) ናዝራዊ ተብሎ ይጠራል በዚህ ሥፍራ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው። ከእርሱ በፊት ይኖሩ የነሩ ነቢያት ስለ እርሱ ስባገሩ መስሑ ወይም ክርስቶስ ብለው ይጠሩታል። ኤቲ: "ሰዎች ክርስቶስ ናዝራዊ ነው ይላሉ።" ( ተመልከት)

Chapter 3

Matthew 3:1

ማቴዎስ 3: 1-3

አጠቃላይ መረጃ: ይህ ጸሐፊው የመጥመቁ የሐንስን ታሪክ የተነናገረበት አዲስ የታሪኩ አካል መጀመሪያ ነው። በቁ. 3 ላይ ጸሐፊው የኢየሱስ አገልግሎት መንገድን ያዘጋጅ ዘንድ መጥመቁ የሐንስ በእግዚብሔር የተመረጠ መሆኑን ከነብዩ ኢሳያስ መጽሐፍ ጠቅሶ ጽፏል። በእነዚህ ቀናት ይህ ዮሴፍ እና የእርሱ ቤተሰብ ከግብጽ ምድር ወደ ናዝሬት ከተመሰሉ ብዙ ዓመታት በኋላ የሆነ ነው። ይህ ምናልባትም ኢየሱስ አገልግሎቱን ለመጀመር በተቃረበበት ጊዜ የተፈጸመ ነገር ይሆናል። ኤቲ: "ከዚያ በኋላ" ወይም "ከጥቂት ዓመታት በኋላ" ንሰሓ ግቡ ይህ በቅርጹ ብዙ ቁጥር ነው። የሐንስ ይህንን ለሕዝቡ እየተናገረ ነው። ( ተመልከት) የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለች "የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለች" የሚለው ሀረግ እግዚአብሔር ንጉሥ ሆነ መግዛቱን ያሳያል። ይህ ሀረግ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ይገኛል። ከተቻለ በትርጉምህ ውስጥ "ሰማይ" የሚል ቃልን ተጠቀም። ኤቲ: "በሰማይ የሚኖር አባታችን ራሱን እንደ ንጉሥ አድርጎ በቅርቡ ያሳያል።" ( ተመልከት) በነብዩ ኢሳያስ አስቀድሞ ስለ እርሱ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ይህ ስለሆነ ነው ይህ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ። "ነብዩ ኢሳያስ ስለ መጥመቁ የሐንስ እንዲህ ሲል ተናግሯል።" ( ተመልከት) የአንድ ሰው ድምፅ በዚህ ሥፍራ ላይ "ድምፅ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሉ ሰውን ነው። ኤቲ: "አንድ ሰው አለ።" ( ተመልከት) የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ መንገዱንም አቅኑ "የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ መንገዱንም አቅኑ"። ይህ በዮሐንስ ሰዎችን ለኢየሱስ መምጣት ሰዎችን በንሰሓ የሚያዘጋጅ ምሳሌያዊ መልዕክት ነው። ( ተመልከት)

Matthew 3:4

ማቴዎስ 3:4-6

አሁን . . . የበረሃ ማር "አሁን" የሚለው ቃል በታሪኩ ፍሰት ውስጥ በዚህ ሥፍራ ለአንባቢው ምልክት እንዲሰጥ ተብሎ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። በዚህ ሥፍራ ማቴዎስ ስለ መጥመቁ የሐንስ የኋላ ታሪክ መረጃን ይሰጣል። ( ተመልከት) የግመል ጠጉር ይለብስ ነበር እንዲሁም ጠፍርንም ይታጠቅ ነበር ይህ የዮሐንስ አለባበስ ከእርሱ በፊት ይኖሩ እንደነበሩ ነብያት በተለይም እንደ ለነብዩ ኤልሳ ትንብታዊ መልዕክት ነበረው። ( እና ተመልከት) ኢያሩሳሌም፣ ይሁዳ ሁሉ እና በአከባቢው ያሉ ሁሉ ይህ በዚህ አከባቢ ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን የሚያመለክት ነው። በዚህ ሥፍራ "ሁሉም" የሚለው ቃ "ብዙ" ማለት ነው። ማቴወዎስ ወደ መጥመቁ የሐንስ የመጡት ብዙ ሰዎች መሆናቸውን አጽኖት ይሰጠቃል። ( እና ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በእርሱ ተጠመቁ ይህ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “የሐንስ አጠመቃቸው።” ( ተመልከቱ) እነርሱ ይህ ማለት ከኢየሩሳሌም፣ ከይዳ እና ከዮርዳኖስ ዙሪያ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች መምጣታቸውን ያመለክታል።

### Matthew 3:7

ማቴዎስ 3፡7-9

አጠቃላይ መረጃ መጥመቁ የሐንስ ፈርሳዊያንን እና ሳዱቃዊያንን ይገስጻቸው ጀመረ። እናንተ የመርዛማ እባብ ልጆች ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። መርዛማ እባቦች አደገኛ ናቸው እንደሁም ክፋትን ይወክላሉ። ኤቲ፡ “እናንተ መርዛማ እባቦች!” ወይም “ልክ እንደ መርዝማ እባቦች ክፉዎች ናችሁ።” ( ተመልከት ከሚመጣው ቁጣ እንድታመልጡ ማን አስጠነቀቃችሁ የሐንስ ፈርሳዊያንን እና ሳዱቃዊያንን ለማስጠንቀቅ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዳይቀጣቸው የሐንስ ያጠምቃቸው ዘንድ ይጠይቁት ነበር። ይሁን እንጂ ኃጢአት ማድረጋቸውን ማቆም አይፈልጉም ነበር። ኤቲ፡ “በዚህ ዓይነት መንገድ ከእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ አይቻልም።” ወይም “እኔ ስላጠመኳችሁ ከእግዚአብሔር ፍርድ የሚታመልጡ አይመስላችሁ።” ( ተመልከት) ከሚመጣው ቁጣ እንድታመልጡ “ቁጣ” የሚለው ቃል በዚህ ሥፍራ ጥቅም ላይ የዋለው የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማመለከት ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ ይህ ከእግዚአብሔር ቅጣት ቀድሞ የሚመጣ ስለሆነ ነው። ኤቲ፡ “ከሚመጣው ቅጣት ለማምለጥ” ወይም “ከእግዚአብሔር ቅጣት ለማምለጥ።” ( ተመልከት) የንሰሓን ፍሬ አፍሩ “አፍሩ” የሚለው ቃል ምሳሌያዊ አነጋገር ሲሆን የሰውዬውን ተግበባራት ያሳያል። ኤቲ፡ “ተግባራችሁ በእውነት ንሰሓ እንደገባችሁ ያሳይ።” ( ተመልከት) አባታችን አብረሃም አለልን “አብረሃም አባታችን ነው” ወይም “እኛ የአብረሃም ዘሮች ነን።” የአይሁድ መሪዎች የአብረሃም ዘሮች በመሆናቸው ምክንያት እግዚአብሔር እንደማይቀጣቸው ያስቡ ነበር።” ( ተመልከት) እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ ይህ የሐንስ ቀጥሎ ስለሚናር ነገር አጽኖት እንድሰጠ ያሳያል። ከእነዚህ ድንጋዮች እግዚአብሔር ልጆችን ማስነሳት ይችላል “ከእነዚህ ድንጋዮች ሳይቅር እግዚአብሔር ለአብረሃም ለልጆችን አበጅቶ ለአብረሃም መስጠጥ ይችላል።”

### Matthew 3:10

ማቴዎስ 3፡ 10-12

አያያዥ ዓረፍተ ነገር መጥመቁ የሐንስ ፈርሳዊያንን እና ሳዱቃዊያንን መገሰጹን ቀጥሏል። በዛፉ ሥር ላይ መሳሩ ተቀምጦዋል። መልካምን ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ተቆርጦ ወደ እሳት ይጣላል። ይህ ምሳሌ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ለመቅጣት ተዘጋጅቷል። ይህ በዚህ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “እግዚብሔር ምሳሩን አንስቷል። መጥፎ ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎችን ለመቁረጥ እና ለማቃጠል ተዘጋጅቷል” ወይም “አንድ ሰው መጥፎ ፍሬ የሚያፈራን ዛፍ ለመቁረጥ እና ለማቃጠል ምሳሩን እንደሚያዘጋጅ ሁሉ እግዚአብሔርም ስለኃጢአታችሁ ሊቀጣችሁ ተዘጋጅቷል። ( እና ተመልከት) ለንሰሓ “ንሰሓ እንደገባችሁ የሚያሳይ ነገር” ነገር ግን ከእኔ በኋላ የሚመጣው ኢየሱስ ከዮሐንስ በኋላ የሚመጣው ነው። ከእኔ ይልቅ ኃይለኛ ነው “ከእኔ ይልቅ በጣም ጠቃሚ ነው።” በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት ያጠምቃችኋል ይህ ምሳሌ የዮሐንስን ጥምቀት ለወደፊት ከሚሆነው በእሳት መጠመቅ ጋር ያነጻጽራል። ይህ ማለት የዮሐንስ ጥምቀት ሰዎች ከኃጢአታቸው መንጻታቸው ውጫዊ ምሳሌ ሆኖ የሚያገለግል ብቻ ነው። በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት መጠመቅ ግን ሰዎችን በእውነት ከኃጢአታቸው ያነጻል። ከዮሐንስ ጥምቀት ጋር ለማነጻጸር ይረዳ ዘንድ በትርጉማችሁ ውስጥ ከተቻለ “መጠመቅ” የሚለውን ቃል ጥቅም ላይ አውሉት። ( ተመልከት) ስንዴውን ከገለባው መለየት እንዲችል መንሹ በእጁ ላይ ነው ይህ ምሳሌ ስንዴ ከገለባ እንደሚለይ ሁሉ ክርስቶስ ጻድቅ የሆኑ ሰዎችን ኃጢአተኞች ከሆኑን ይለያል። ኤቲ፡ “ክርስቶስ በእጁ መንሽን እንደያዘ ሰው ነው።” ( ተመልከት) መንሽ በእጁ ላይ ነው በዚህ ሥፍራ “በእጁ ላይ ነው” የሚለው ሀረግ ሰውየው ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ያሳያል። ኤቲ፡ “ክርስቶስም መንሹን በእጁ ይዟል ምክንያቱም ዝግጁ ነው።” መንሽ ይህ የስንዴ ነዶን ወደ ሰማይ በመወርወር በንፋስ አማካኝነት ገለባውን ከፍሬው ለመለየት የሚረዳ መሣሪያ ነው። ክብደት ያለው ፍሬው መደመሬት ስወድቅ የማይፈለገው ገለባው ግን በንፋስ ይወሰዳል። ከሹካ ጋር ተመሳሳይ ቅርጽ ያለው ሲሆን መንሽ ግን የሚሠራው ከእንጨት ነው። ( ተመልከት) አውድማ “እህል የሚወቃበት ሜዳ” ወይም “ፍሬው እና ገለባው የሚለይበት ሥፍራ” ምርቱንም ወደ ጎተራው ይከተዋል . . . ገለባውን ግን ወደ ማይጠፋ እሳት ውስጥ ይጨምረዋል።

ይህ እግዚአብሔር እንዴት ጻድቃንን ከኃጢአትን እንደሚለይ የሚያሳይ ምሳሌ ነው። ገበሬ ስንዴውን ወደ ጎተራው እንደሚያስገባ ሁሉ ጻድቃንም ወደ ሰማይ ይሄዳሉ እንዲሁም እንደ ገለባው ያሉትን ሰዎች እግገዚአብሔር ወደ ማይጠፋ እሳት ውስጥ ይጨምራቸዋል። ( ተመልከት) ወደማይጠፋ ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላለል። ኤቲ፡ “ነዶ ወደማያልቅ።” ( ማይጠፋ እሳት ውስጥ ይጨምራቸዋል። ( ተመልከት))

### Matthew 3:13

ማቴዎስ 3፡13-15

አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ጸሐፊው ታርኩ በኋላ ላይ የዮሐንስን ኢየሱስን ወደ አጠመቀበት ይቀይረዋል። በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ

ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “የዮሐንስ ያጠምቀው ዘንድ።” ( ተመልከት) አንተ ወደ እኔ ትመጣለህ? እኔ በአንተ እጅ መጠመቅ ያስፈልገኛል።

ኢየሱስ ለጠየቀው ጥያቄ የዮሐንስ በአግራሞት በጥያቄ መልክ ስመልስ እናያለን። ኤቲ፡ “አንተ ከእኔ ይልቅ አስፈላጊ ነህ። እኔ አንተን ማጥመቅ የለብኝም። አንተ እኔ ማጥመቅ አለብህ።” ( ተመልከት) ለእኛ በዚህ ሥፍራ “እኛ” የሚለው ቃል ኢየሱስን እና ዮሐንስን የሚታመለክት ናት። ( ተመልከት)

### Matthew 3:16

ማቴዎስ 3፡16-17

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ ስለ መጥመቁ ዮሐንስ የተነገረው ታርክ መጨረሻ እና ኢየሱስን ካጠመቀ በኋላ ምን እንደሆነ የተገለጸበት ክፍል ነው። ከተጠመቀ በኋላ ይህ በቀጥታ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ዮሐንስ ኢየሱስን ካጠመቀ በኋላ።” ( ተመልከት) እነሆ “እነሆ” የሚለው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ማስረጃ አስገራሚ ስለሆነ አጽኖት ለመስጠት ነው። ሰማያት ለእርሱ ተከፈቱ ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ኢየሱስ ሰማያት ተከፍቶ ተመለከተ” ወይም “እግዚአብሔር ሰማያትን ለኢየሱስ ከፈተ”። ( ተመልከት) በእርግም አምሳሌ ወረደ አማራጭ ትርጉሞች እነዚህ ናቸው 1) መንፈስ በእርግም አምሳሌ መውረዱን የሚያመለክት ቀጥተኛ ትርጉም ወይም 2) እርግም በቀስታ እንደሚትወርድ ሁሉ ልክ እንደዚሁ መንፈስ ቅዱስ በቀስታ በኢየሱስ ላይ መውረዱን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። ( ተመልከት) እንዲህ የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ “ኢየሱስ ድምፅ ከሰማይ ሰማ።” (UDB) ( ተመልከት) ልጅ ይህ የኢየሱስ በጣም አስፈላጉ የማዕረግ ስም ነው፣ የእግዚአብሔር ልጅ። ( ተመልከት)

---

## Chapter 4

### Matthew 4:1

ማቴዎስ 4፡1-4

አጠቃላይ መረጃ በዚህ ሥፍራ ላይ ጸሐፊው ኢየሱስ በምድረ በዳ 40 ቀናትን ያሳለፈበትን፣ በሴጣን የተፈተነበትን የታሪኩን አዲስ ክፍል ይጀምራል። በቁጥር 4 ላይ ኢየሱስ ከዘዳግም መጽሐፍ በተወሰዱ ጥቅሶች አማካኝነት ሴጣንን ስገስጸው እንመለከታለን። ኢየሱስ በመንፈስ ተመርቶ

ይህ በቀጥታ በዚህ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “መንፈስ ኢየሱስን መራው።” ( ተመልከት) በዳብሎስ ይፈተን ዘንድ ይህ በቀጥታ በዚህ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ዳብሎስ እርሱን መፈተን ይችል ዘንድ።” ( ተመልከት) ዳቢሎስ . . . ፈታኙ እነዚህ ሁለት ቃላት የሚያመለክቱት አንድ ነው። እነዚህ ሁለቱን ለመተርጎም አንድ ቃል መጠቀም ትችላላችሁ። ጾመ . . . ተራበ ይህ ስለኢየሱስ የተባለ ነው። አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እዘዝ የዚህ ሀረግ አማራጭ ትርጓሜዎች 1) ይህ ፈተና ኢየሱስ ለራሱ ጥቅም ተዓምራትን ይሠራ ዘንድ የቀረበ ፈተና ነው። ኤቲ፡ “አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ስለዚህ ማዘዝ ትችላለህ።” 2) ይህ የሚያመለክተው በኢየሱስ ላይ የቀረበውን ክስ ነው። ኤቲ፡ “የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህ ትዕዛዝ በመስጠት አረጋግጥ።” ሴጣን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንደሚያውቅ ማሰቡ ይበልጥ ተመራጭ ነው።

የእግዚአብሔር ልጅ ይህ በኢየሱስ እና በእግዚአብሔር መካከሎ ያለውን ግንኙነት የሚገልጽ ስም ነው። ( ተመልከት) ድንጋዩ ዳቦ እዲሆን እዘዝ ይህንን በቀጥጣ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ለእነዚህ ድንጋዮች እንዲህ ብለህ ተናገር፣ ዳቦ ሁኑ!” ( ተመልከት)

ዳቦ ኤቲ፡ “ምግብ” ( ተመልከት)

እንዲህ ተብሎ ተጽፏል ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ሙሴ ከብዙ ዘመናት በፊት እንዲህ በማለት ጽፏል።” ( ተመልከት)

የሰው ልጅ በዳቦ ብቻ አይኖርም ይህ በቀላሉ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ከምግብ በላይ ሌላ በጣም አስፈላጊ ነገር አለ ማለት ነው።

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ማንኛውም ቃ እንጂ በዚህ ሥፍራ “ቃል” እና “አፍ” የሚሉ ቃላት እግዚአብሔር የተናገራቸውን ነገሮችን ያመለክታሉ። ኤቲ: “እግዚአብሔር የተናገራቸውን ነገሮች በማድመጥ እንጂ።” ( ተመልከት)
Matthew 4:5
ማቴዎስ 4:5-6
አጠቃላይ መረጃ፡ በቁጥር 6 ላይ ሴጣን ከመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ውስጥ ኢየሱስን ለመፈተን ሲል የሆነ ሀሳብ ስወስድ እናያለን።
አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ራስህን ወደታች ወርውር የዚህ ሀረግ አማራጭ ትርጉሞች 1) 1) ይህ ፈተና ኢየሱስ ለራሱ ጥቅም ተዓምራትን ይሠራ ዘንድ የቀረበ ፈተና ነው። ኤቲ: “አንተ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆንህ ራስህን ወደታች መወርወር ትችላለህ።” ወይም 2) ይህ የሚያመለክተው በኢየሱስ ላይ የቀረበውን ክስ ነው። ኤቲ: “አንተ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆንህ ራስህን ወደታች በመወርወር አረጋግጥ።” (UDB) ሴጣን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንደሚያውቅ ማሰቡ ይበልጥ ተመራጭ ነው።
የእግዚአብሔር ልጅ ይህ በኢየሱስ እና በእግዚአብሔር መካከሎ ያለውን ግንኙነት የሚገልጽ ስም ነው። ( ተመልከት)
ራስህን ወደታች ወርውር “ወደታች ራስህን ወርውረህ ውደቅ” ወይም “ወደታች ዝለል”
እንዲህ ተብሎ ተጽፏልና ይህ በዚህ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “መዝሙረኛው በመመጽሐፉ ውስጥ እንዲህ ብሎ ጽፏልና” ወይም “በቅዱሳት መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ተብሏልና።” ( ተመልከት)
ይጠብቁህ ዘንድ መልአክቱን ስለአንተ ያዛልና “አንተን እንዲጠብቁህ እግዚአብሔር መልአክቱን ስለአንተ ያዛል።” ይህ እንዲህ ተብሎ በትምህረተ ጥቅስ ውስጥ ሊተረጎም ይችላል። ኤቲ: “እግዚአብሔር ለመልአክቱ እንዲህ ይላቸዋል፣ “ጠብቁት።” ( ተመልከት)
ያነሱሃል “መልአክቱ ይይዙሃል”
Matthew 4:7
ማቴዎስ 4:7-9
አጠቃላይ መረጃ፡ በቁጥር 7 ላይ ኢየሱስ ሴጣንን የገሰጸው ከዘዳግም መጽሐፍ ውስጥ በተወሰደ ጥቅ አማካኝነት ነው።
እንደገና እንዲህ ተብሎ ተጽፏል ኢየሱስ እንዲህ ማለቱ እንደገና ከመጽሐፍ ቅዱስ መጥቀሱን የሚያመለክት ነው። ኤቲ: “እንደገና ሙሴ በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ የጻፈውን ነገር እነግርሃለሁ።” ( እና ተመልከት)
አትፈታተኑት በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማንኛውንም ሰው ነው። ኤቲ: “ማንም እርሱን መፈታተን የለበትም” ወይም “ማንኛውም ሰው እርሱን መፈታተን የለበትም።”
እንደገና ዲቢሎስ “በመቀጠልም ዲቢሎስ”
እንዲህ አለው “ዲቢሎስ ኢየሱስን እንዲህ አለው።”
እነዚህን ነገሮች ሁሉ እሰጥሃለሁ። “እነዚህ ነገሮች ሁሉ እሰጥሃለሁ።” ፈታኙ አንዳንዶቹን ሳይሆን “ሁሉንም ነገሮች” እንደሚሰጠው አጽኖት ሰጥቶዋል።”
Matthew 4:10
ማቴዎስ 4:10-11
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ይህ ሴጣን ኢየሱስን እንዴት እንደፈተነው የሚያወሳው ታሪክ የመጨረሻው ክፍል ነው።
አጠቃላይ መረጃ፡ በቁጥር 10 ላይ ኢየሱስ ከዘዳግም መጽሐፍ ውስጥ በመውሰድ ሴጣንን ገስጾታል።
እንዲህ ተብሎ ተጽፏልና ይህ በዚህ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “መዝሙረኛው በመመጽሐፉ ውስጥ እንዲህ ብሎ ጽፏልና” ወይም “በቅዱሳት መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ተብሏልና።” ( ተመልከት)
አንተ አለብህ በዚህ ሥፍራ “አንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማንኛውንም ሰው ነው። ( ተመልከት)
እነሆ “እነሆ” የሚለው ቃል ከዚህ በመቀጠል የሚሰጠው መረጃ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን የሚያመለክት ነው።
Matthew 4:12
ማቴዎስ 4:12-13
አጠቃላይ መረጃዎች፡ ይህ ኢየሱስ በገሊላ አገልግሎቱን የጀመረበትን መንገድ ጸሐፊው የገለጸበት አዲሱ የታሪኩክፍል ጅማሬ ነው። እነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ እንዴት ወደ ገሊላ እንደመጣ ያብራራሉ። ( ተመልከት)
አሁን ይህ ቃል በታሪኩ ፍሰት ውስጥ ያለውን ክፍተት ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው። ማቴዎስ በዚህ ሥፍራ ላይ የታሪኩን አንዲስ ጅማሬ ክፍል ይናገራል።
የሐንስ ተሠረ ይህ በቀጥታ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ንጉሡ የሐንስን አሠረው።” ( ተመልከት)
በዛብሎን እና ንፍታሌን አገር እነዚህ ከብዙ ዓመታት በፊት ከሌላ ሀገር የመጡ ሰዎች ቦታወን ከመቆጣጠራቸው በፊት በእነዚህ ሥፍራዎች ይኖሩ የነበሩ ጎሣዎች ስም ነው። ( ተመልከት)
Matthew 4:14
ማቴዎስ 4:14-16
አጠቃላይ መረጃ፡ በቁጥር 15 እና 16 ላይ ኢየሱስ በገሊላ የነበረው አገልግሎት ከዚህ በፊት ተነግሮ የነበረ ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን ለማሳየት ጸሐፊው ከነብዩ ኢሳያስ መጽሐፍ ይጠቅሳል።
እንዲህም ሆነ ይህ ኢየሱስ ቅፍርናሆም ወደ ተሰኘው መንደር ለመኖር መምጣቱን ያመለክታል።
ከዚህ በፊት እንደተነገረው ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል፡ ኤቲ: “እግዚአብሔር እንደተናገረው።” ( ተመልከት)
የዛብሎን እና የንፍታሌን አገር . . . የአሕዛብ ገሊላ እነዚህ ሁሉ ስሞች አንድን አከባቢ የሚያመለክቱ ናቸው። ይህ በአንድ ዓረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ኤቲ: “በዛብሎን እና ንፍታሌን አገር . . . ብዙ አሕዛብ የሚኖሩበት የገሊላ መንድ።”
በባሕር መንገድ ይህ የገሊላን ባሕርን ያመለክታል።
በጨለማ የተቀመጠ ሕዝብ ታላቅ ብርሃንን አየ በዚህ ሥፍራ “ብርሃን” የሚለው ቃል ግብረገባዊ ጨለማን ወይም ሰዎችን ከእግዚአብሔር የለየውን ኃጢአትን የሚያመለክት ነው። ይህ አሁን ከእግዚአብሔር ዘንድ ተስፋን ያገኙ ነገር ግን አስቀድሞ ምንም ተስፋ ያልነበራቸውን ሕዝቦች ያሳያል። ( ተመልከት)
በዚያ አከባቢ የሚኖሩ እና በሞት ጥላ ሥር ላሉ ሕዝቦች ብርሃን ወጣላቸው ይህ ከመጀመሪያው የዓረፍተ ነገሩ ክፍል ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። በዚህ ሥፍራ ላይ “አከባቢ እና በሞት ጥላ ሥር” የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው መንፈሳዊ ሞት ወይም ከእግዚአብሔር መለየት ነው። ( እና ተመልከት)
Matthew 4:17
ማቴዎስ 4: 17-17
መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንሰሓ ግቡ ይህን በ MAT 3:2 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Matthew 4:18
ማቴዎስ 4:18-20
አጠቃላይ መረጃ ይህ በታሪኩ ውስጥ ኢየሱስ በገሊላ ስለነበረው አገልግሎት አስመልክቶ አዲስ ታሪክ የተጀመረበት ነው። በዚህ ሥፍራ ሰዎች የእርሱ ደቀ መዛሙርት ይሆኑ ዘንድ መሰብሰብ ጀመረ።
መረባቸውን ወደ ባሕሩ ይጥሉ ነበር ኤቲ: “ዓሳ ለማጥመድ መረባቸውን ወደ ውሃው ውስጥ ይጨምሩ” ( ተመልከት)
ተከተሉኝ ኢየሱስ ጴጥሮስ እና እንድርያስን ይከተሉት፣ ከእርሱ ጋር ይኖሩ እና የእርሱ ደቀ መዛሙርት ይሆኑ ዘንድ ጠራቸው። ኤቲ: “ደቀ መዛሙርቴ ሁኑ።” ሰዎችን የሚታጠምዱ አደርጋችኋለሁ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ጴጥሮስ እና እንድርያስ እውነተኛውን መልዕክት ለእግዚአብሔርን ሕዝብ በማስተማሪ ሌሎችም ደግሞ ኢየሱስን እንዲከተሉ ያደርጋሉ። ኤቲ: “ዓሳ ታጠምዱ በነበረበት መንገድ እናንተም ሰዎችን እንዴት መሰብሰብ እንደሚትችል አስተምራችኋለሁ።” ( ተመልከት)
Matthew 4:21
ማቴዎስ 4:21-22
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ይሆኑ ዘንድ ተጨማሪ ሰዎችን ጠራ። ጠራቸው “ኢየሱስ የሐንስ እና ያዕቆብን ጠራቸው።” ይህ ሀረግም ኢየሱስ ይከተሉት፣ ከእርሱ ጋር ይኖሩ እና የእርሱ ደቀ መዛሙርት ይሆኑ ዘነድ ጠራቸው ማለት ነው።
ወዲያውኑ “በዚያኑ ጊዜ”
ታንኳቸውን ትተው . . እና ተከተሉት ይህ የሕይወት ዘይቤ ለውጥ መሆኑን መግለጽ በጣም አስፈላጊ ነው። እነዚህ ሰዎች ወደ ዓሳ አጥማጅነታቸው እና የቤተሰባቸውን ሥራ ከዚያን ጊዜ ጀምረው በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ኢየሱስን ለመከተል ትተዋለል።
Matthew 4:23
ማቴዎስ 4:23-25
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ይህ ኢየሱስ በገሊላ የጀመረው አገልግሎት ታሪክ የመጨረሻው ክፍል ነው። እነዚህ ቁጥሮች ምን እንዳደረገ እና ሰዎች የሰጡት ምላሽ ምን እንደሆነ ጠቅለል አድርጎ ያሳየናል። ([[End of Story]] ተመልከት)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በምኩራቦቻቸው እያስተማረ “በገሊላ ውስጥ በሚገኙ ምኩራቦች ውስጥ እያስተማረ” ወይም “በእነዚህ ሰዎች ምኩራብ ውስጥ እያስተማረ።”
የመንግስቱን ወንጌል እየሰበከ በዚህ ሥፍራ ላይ “መንግስት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚብሔር ንጉሥ ሆኖ መንገሡን ነው። ኤቲ፡ “ወንጌልን ማለትም እግዚአብሔር እንዴት ራሱን ንጉሥ አድርጎ እንደገለጠ እየሰበከ” (UDB) ( ተመልከት)
ሁሉንም ዓይነት በሽታዎች እና ደዌዎች “ማንኛውንም በሽታ እና ደዌ።” “በሽታ” እና “ደዌ” የሚሉት ቃላት በጣም የተቀራረቡ ናቸው ነገር ግን ከተቻለ በሁለት የተያዩ ቃላት አማካኝነት ቢተረጎሙ መልካም ነው። “በሽታ” አንድ ሰው እንዲታመም የሚያደርገው ነገር ነው። “ደዌ” አካላዊ ድክመት ወይም በሽተኛ በመሆን በአካል ላይ የሚሆን ህመም ነው።
በዳቢሎስ የተያዙ ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “በዳቢሎስ የተያዘ” ወይም “ዳቢሎስ የተቆጣጠራቸው።” ( ተመልከት) የሚጥል በሽታ “የሚጥል በሽታ ያለባቸው” ወይም “ካለባቸው በሽታ የተነሳ የሚወድቁትን” ሽባዎችን “መራመድ የማይችሉትን” ከዐሥሩም ከተሞች ይህ “ዐሥር ከተማዎች” ስም ነው። ." (UDB) ይህ ከገሊላ ባሕር በደቡብ ምስራቅ በኩሉ የሚገኘውን አከባቢ መጠሪያ ስም ነው። ( ተመልከት)

Chapter 5

Matthew 5:1

ማቴዎስ 5:1-4

አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ይህ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስመተማር የጀመረበት አዲስ ታሪክ ጅማሬ ክፍል ነው። ይህ ክፍል እስከ ምዕራፍ 7 ደረስ ይቀጥላል እንዲሁም ብዙ ጊዜም የተራራው ስብከት ተብሎ ይጠራል።
አጠቃላይ መረጃ፡ በቁጥር 3 ላይ ኢየሱስ የተባረኩ ሰዎች ባሕርያት ምን ምን እንደሆኑ መግለጽ ይጀምራል።
አፉን ከፍቶ ኤቲ፡ “ኢየሱስ መናገር ጀመረ” ( ተመልከት)
አስተማራቸው “እነርሱን” የሚለው ቃል ደቀ መዛሙርቱን የሚያመለክት ነው።
በመንፈሰስ ድሆች ይህ ማለት ትሁት የሆነ ማለት ነው። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር እንደሚያስፈልጋቸው ያወቁ።” ( ተመልከት)
መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና በዚህ ሥፍራ ላይ “መንግስተ ሰማየት” የሚያመለክተው እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ መግዛቱን። ይህ ሀረግ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው የሚገኘው። ከተቻለ በትርጉማችሁ ውስጥ “ሰማይ” የሚለው ቃል እንዲኖር አድርጉ። ኤቲ፡ “በሰማይ ያለው እግዚአብሔር ንጉሣቸው ይሆናልና።” ( ተመልከት)
የሚያለቅሱ ያዘኑበት ምክንያት ሊሆን የሚችለው 1) በዚህ ዓለም ኃጢአት ወይም 2) በራሳቸው ኃጢአት ወይም 3) በሌላ ሰው ሞት ምክንያት። ቋንቋችሁ ካላስገደዳችሁ በስቀተር ምክንያቱን አትግለጹ።
ይጽናናሉና ይህ እንዲህ በቀጥታ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር ያጽናናቸዋል።” ( ተመልከት)

Matthew 5:5

ማቴዎስ 5:5-8

የዋሆች “ትሁታን” ወይም “በራሳቸው ኃይል የማይታመኑት”
ምድርን ይወርሳሉ “እግዚአብሔር ምድርን ሁሉ ይሰጣቸዋል”
ጽድቅን የሚራቡ እና የሚጠሙ ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ከልቡ የሚሻ ሰው ማለት ነው። ኤቲ፡ “ውሃ እና ምግብን ሰው እንደሚሻ ሁሉ በጽድቅ ለመኖር የሚሹ” ( ተመልከት)
ይሞላሉ ይህ እንዲህ ተብሎ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር ይሞላቸዋ” ወይም “እግዚብሔር ያረካቸዋል።” : ( ተመልከት)
ልበ ንጹሖች
“ልባቸው ንጹሕ የሆኑ ሰዎች።” በዚህ ሥፍራ “ልብ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአንድ ሰውን ፍላጎት ነው። ኤቲ፡ “እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚፈልጉ ሰዎች።” ( ተመልከት)
እግዚአብሔርን ያዩታል በዚህ ሥፍራ ላይ “ማየት” የሚለው ቃል በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ መኖር መቻልን የሚያመለክት ነው። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መኖር እንዲችሉ ይፈቅድላቸዋል።”

Matthew 5:9

ማቴዎስ 5:9-10

አስታራቂዎች እነዚህ ሌሎች ሰዎች እርስ በእርሳቸው ሰላም እንዲሆኑየሚያግዙ ሰዎችን ናቸው። የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና ይህ በእንዲህ ዓይነት መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር ልጆቼ ብሎ ይጠራቸዋልና” ወይም “የእግዚአብሔር ልጆች ይሆናሉና።” (: ተመልከት)
የእግዚአብሔር ልጅ “ልጆች” የሚለውን ቃል በእናንተ ቋንቋ ለሰው ልጅ ወይም ሕጻናት በተለምዶ የሚትጠቀምበትን ተመሳሳይ ቃላት መጠቀሙ ጥሩ ነው።
የሚሰደዱ ይህ በቀጥታ በዚህ ዓይነት መልኩ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ሌሎእ ሰዎች በተገቢው መንገድ ያልያዟቸው ሰዎች።” ( ተመልከት)
ስለጽድቅ “እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ነገር በማድረጋቸው ምክንያት” መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና ይህንን በ [MAT 5:3] ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

Matthew 5:11

ማቴዎስ 5:11-12

አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ኢየሱስ የተባረኩ ሰዎች ባሕርያትን ማብራሩትን ጨርሷል።
የተባረካቹ ናችሁ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። ( ተመልከት)
ስለ አንተ በውሸት ክፉ ነገሮችን ሁሉ ይናገራሉ። “ስለ አንተ ሁሉንም ዓይነት ክፉ ውሸትን ይናገራሉ” ወይም “እውነት ያልሆነ መጥፎ መጥፎ ነገሮችን ይናገራሉ”
ስለ እኔ ሲባል “እኔን በመከተልህ ምክንያት” ወይም “በእኔ በማመንህ ምክንያት”
ደስ ይበላችሁ እንዲሁም ሐሴትም አድርጉ “ደስ ይበላችሁ” እና “ሐሴት አድርጉ” የሚሉት ሁለቱ ቃላት ተመሳሳይ መልዕክቶችን የሚያስተልፉ ናቸው። ኢየሱስ አድማጮቹ ደስ ይበላችሁ ብቻ አላላቸው ነገር ግን ከተቻለ ከመደሰት በላይ እንዲያደርጉ ነግሮዋቸዋል። ( ተመልከት)

Matthew 5:13

ማቴዎስ 5:13-14

አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንደ ጨው እና ብርሃን ይሆኑ ዘንድ ማስተማር ጀመረ።
እናንተ የምድር ጨው ናቸው አማራጭ ትርጓሜዎች 1) ጨው ለምግብት ጣእም እንደሚሰጥ ሁሉ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በዓለም ውስጥ ያሉ ሰዎች መልካም ይሆኑ ዘንድ ተጽእኖ ፈጣሪዎች መሆን ይኖርባቸዋል ወይም 2) ልክ ጨው ምግብ ለረጅም ጊዜ ሳይበላሽ እንዲቆይ እንደሚያደረግ ሁሉ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሰዎች ሙሉ ለሙሉ እንዳይበላሹ የሚያደርጉ ሊሆኑ ይባል። ኤቲ፡ “ለዓለም ሕዝቦች እናንተ ልክ እንደ ጨው ናችሁ” ወይም “ጨው ለምግብ እንደሆነ ሁሉ እናንተም ለዓለም እንደዚሁ ናችሁ።” ( ተመልከት)
ጨው ጣእሙን ካጣ አማራጭ ትርጉሞች 1) “ጨው ጨው የሚሠራውን ነገር መሠርት የሚያስችለውን ኃይሉን ካጣ” ((UDB) ወይም 2) “ጨው ጣዕሙን ካጣ።” ( ተመልከት)
እንዴት ጨው የሚሰጠውን ጥቅም ሊሰጥ ይችላል? “እንደገና እንዴት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል?” ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀማል። ኤቲ፡ “እንደገና ጠቃሚ መሆን የሚችልበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም።” ( እና ተመልከት)
ወደ ውጪ ከመጣል እና በሰዎች ከመረገጥ በስቀር ይህ እንዲህ ባለ መንገድ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል፡ ኤቲ፡ “በመንገድ ዳር ይጥሉታል፤ ሰዎችም ይረገጡታል።” (See: ተመልከት)
እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ይህም ማለት የኢየሱስ ተከታዮች የእግዚአበብሔር እውነት ያለበትን መልዕክት እግዚብሔርን ወደ ማያውቁት ሰዎች ሁሉ ድረስ የሚያደርሱ ናቸው። ኤቲ፡ “እናንተ በዓለም ውስጥ ላሉ ሰዎች ልክ እንደ ብርሃን ናችሁ።” (See: ተመልከት)
በተራራ ላይ ያለች ከተማ ፈጽሞ ልትደበቅ አትችልም ይህ ሰዎች የከተማዋን ብርሃን በምሽት መመልከት ይችላሉ ማለት ነው። ይህ በቀጥታ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “በምሽት በተራራ ላይ ያለች ከተማን ብርሃን ማንም ሰው ሊከልል አይችልም። ( እና ተመልከት)

Matthew 5:15

ማቴዎስ 5:15-16

መብራት የሚያበራ ሰውም እንዲሁ “ሰዎች መብራትን እንዲሁ አብርቶ ከእንቅብ በታች አያኖረውም “መብራቱን ከቅርጫት በታች አያኖረውምለለ”። ይህ ማለት መብራን አብርቶ ሰዎች እንዳያዩት መደበቅ ሞኝነት ነው የሚል ነግግር ነው።
ብርሃናችሁ በሰዎች ሁሉ ፊት ያብራ ይህ ማለት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሌሎች

ሰዎች የእግዚአብሔር እውነት ከእነርሱ መማር በሚችሉበት መንገድ መኖር አለባቸው ማለት ነው። ኤቲ፡ “ሕይወታችሁ ልክ እንደ መብራት በሰዎች ፊት ይብራ።” ( ተመልከት)
በሰማይ የሚኖረው አባታችሁ “አባት” የሚለውን ቃል በጥሩ ሁኔታ ለመተርጎም በቋንቋችሁ ውስጥ አንድን አባት ለመጥራት የሚትጠቀሙትን ቃል ተጠቀሙ።

## Matthew 5:17

ማቴዎስ 5፡17-18

አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን መጽሕፍት ውስጥ የተጻፉትን ሕግጋት ለመፈጸም እንደመጣ ማስተማሪ ጀመረ። ነቢያት ይህ ነቢያት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የጻፏቸውን መጽሐፍትን ያመለክታል። ( ተመልከት) እውነት እላችኋለሁ “እውነት እላችኋለሁ።” ይህ ሀረግ ኢየሱስ ቀጥሎሊናገረው ያለው ሀሳብ አጽኖት ልሰጥበት የሚገባ መሆኑን ያመለክታል። ሰማይና ምድር ያልፋሉ ኤቲ፡ “እግዚአብሔር የፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ ያልፋሉ።” ( ተመልከት) አንድት ነጥብ “ከፊደል ትንሽዋ እንኳ ሳትቀር። ይህ ከቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ በሰዎች ይህንን ያኽለ አስፈላጊ አይደሉም ተብሎ የሚቆጠሩት እንኳ ሳይቀሩ የሚለውን ለማሳየት የቀረበበ ምሳሌያዊ ንግግር ነው። ኤቲ፡ “አስፈላጊ የማይመስሉ ሕግጋት እንኳ ሳይቀሩ”። ( ተመልከት) ሁሉ ነገር ይፈጸማል ይህ በግልጽ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር በሕግ ውስጥ የተጻፉትን ነገሮች ሁሉ ፈጽሟል። ( ተመልከት)

## Matthew 5:19

ማቴዎስ 5፡19-20

የተላለፈ ማንኛውም ሰው “የማይታዘዝ ማንኛውም ሰው” ወይም “ሳይታዘዝ የቀረ ማንኛውም ሰው” ከእነዚህ ትዕዛዛት መካከል ትንሹን “ከእነዝህ ትዕዛዛት መካከል፣ ጥቅሟ በጣም ትንሽ የሆነችውን ትዕዛዛ እንኳ ሳይቀር” ተብሎ ይጠራል ይህ እንዲህ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ያንን ሰው አግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ይጠራዋል።” ( ተመልከት) በመንግስተ ሰማይ ውስጥ ትንሽ “መንግስተ ሰማይ” ሚለው ሀረግ የእግዚአብሔር አገዛዝ ያመለክታል። ይህ ሀረግ የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው። የሚቻል ከሆነ “በትርጉማችሁ ውሰጥ “ሰማይ” የሚለው ቃል ተጠቀሙ። ኤቲ፡ “በመንግስተ ሰማይ ውስጥ አስፈላጊነቱ ትንሽ ይሆናል” ወይም “በሰማይ የእግዚአብሔ አገዛዝ ውስጥ ያለው ጠቀሜታ በጣም ትንሽ ይሆናል።” ( ተመልከት) ጠብቋቸው እንዲሁም አስተምሯቸው “እነዚህ ትዕዛዛት ሁሉ ታዘዙ እንዲሁም ሌሎችም ይህንኑ ያደርጉ ዘንድ አስተምሯቸው።” ታላቅ “በጣም አስፈላጊ” እንዲህ ብዬአችኋለሁ ይህ ኢየሱስ ከዚህ በመቀጠል ስለሚናገረው ነገር አጽኖት ይሰጣል። አንተ . . . እናንተ . . . አንተ ይህ ብዙ ቁጥርን ያመለክታል። ( ጽድቃችሁ ካልበለጥ . . . ልትገቡ አትችሉም ይህ በአዎንታዊ መንገድ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ጽድቃችሁ መብለጥ አለበት . . . ለመግባት። ( ተመልከት)

## Matthew 5:21

ማቴዎስ 5፡21-22

አያያዥ ዓረፍ ነገር ኢሰየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን ለመፈጸም መምጣቱን ማስተማሩን ቀጥሏል። በዚህ ሥፍራ ስለ ነፍስ ማጥፋት እና ንዴት ተናግሯል። አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ ለተሰበሰቡት ሰዎች እንደ ግለሰብ እያንዳንዳቸው ምን ሊያጋጥማቸው እንደሚችል እየተናገረ ነው። “ሰምታችኋል” የሚለው ሀረግ ውስጥ ያለው “እናንተ” የሚለው ቃል እና “እላችኋለሁ” ሀረግ ብዙ ቁጥር ነው። “አትግደል” የሚለው ሀረግነጠላ ቁጥር ነው ይሁን እንጂ በብዙ ቁጥር ሊተረጎም ይችላል። በጥት ዘመን እንዲህ ተብሎ ተነግሯቸዋል ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ተናግሮ ነበር። ( ተመልከት) ነፈስ ያጠፋ ማንኛውም ሰው ፍርድ አለበት በዚህ ሥፍራ “ፍርድ” የሚለው ቃል ይህ ሰው እንዲገደል የሚያዘውን ሕግ የሚያሳይ ነው። ኤቲ፡ “ሌላ ሰው የገደለ ማንኛው ሰው ላይ ዳኛው ይፈርዳል።” ( ተመልከት) ግዲያ. . . ግድያዎች ይህ የሚያመለክተው ቃል ሆኖ ነፍስ ማጥፋት እንጂ ሁሉንም ዓይነት የግዲያ አይነቶችን አይደለም። ነገር ግን እኔ እንዲህ እላችኋለሁ “እኔ” የሚትለው ቃ አጽኖታዊ ናት። ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ የተናገረው ነገር እግዚአብሐየር በመጀመሪያ ከሰጠው ትዕዛዝ ጋር የሚስተካከል ነው። ስትተረጉም ይህንን አጽኖት በሚያሳይ ሀረግ ለመተርጎም ሞከር። ወንድም ይህ አማኝን እንጂ በሥጋ ወንድምን ወይም ጎረበትን የሚያመለክት አይደለም። ፍርድ ይገባዋል በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ሰው ፍርድ ሳይሆን በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሰውን እግዚአብሔር የሚያመጣውን ፍርድ ነው። ( ተመልከት) እርባና የሌለው . . . ሞኝ ይህ በትክክል ማሰብ የማይችሉ ሰዎች የሚሰደቡትን ስድብ የሚያመለክት ነው። “እርባና ያሌለው” የሚለው ቃል “አእምሮ የሌለው” ከሚለው ቃል ጋር ተቀራራቢ ሲሆን “ሞኝ የሚለው ደግሞ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ጋር ተያያዥነት ያለው ሀሳብ ነው። ሸንጎ ይህ በኢየሩሳሌም የሚገኘው የሸንጎ ሳይሆን በአከባቢው ያለው ሸንጎ ነው።

## Matthew 5:23

ማቴዎስ 5፡23-24

እንተ ኢየሱስ በቡድን ላሉ ሰዎች እያንዳንዳቸው ምን እንደሚያጋጥማቸው እየተናገረ ነው። “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። እናንተ ግን በቋንቋች በብዙ ቁጥር ሊትተረጉሙት ትችላላችሁ። ( ተመልከት) መባህን “ስጦታ ስትሰጥ” ወይም “ስጦታህ ስታቀርብ” በመሠዊያው ላይ ይህ በኢየሩሳሌሚ ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚገኘውን የእግዚአብሄርን መሠዊያ የሚያመለክት ነው። ኤቲ፡ “በቤተ መቅዲስ ውስጥ በሚገኘው የእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ።” ( ተመልከት) በዚያ ሳለህ ቢታስታውስ “በመሠዊያው ፊት ቆመህ ሳለ ቢታስታውስ” ወንድምህ አንዳች ነገር ከአንተ ጋር እንዳለው “አንተ ባደረከው አንድ ነገር የተነሳ ወንድም በአንተ የተቆጣ መሆኑን ካስታወስክ” በመጀመሪያ ሂድና ከወንድምህ ጋር ታረቅ ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “ከሰውዬው ጋር ሰላምን ፍጠር።” ( ተመልከት)

## Matthew 5:25

ማቴዎስ 5፡ 25-26

ከአንተ . . . ጋር ተስማማ ኢየሱስ በቡድን ላሉ ሰዎች እያንዳንዳቸው ምን እንደሚያጋጥማቸው እየተናገረ ነው። “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። እናንተ ግን በቋንቋች በብዙ ቁጥር ሊትተረጉሙት ትችላላችሁ። ( ተመልከት) ከከሳሽ ጋር ይህ ሰው ሌላኛውን ሰው በደል እየነቀሰ የሚወቅስ ሰው ነው። በዳኛ ፊት ሆኖ ሌላኛው ሰው የበደለውን በደል በመናገር ይከሳል። ለዳኛ አሳልፎ ይሰጥሃል በዚህ ሥፍራ ላይ “አሳልፎ ይሰጥሃል” የሚለው ሀረግ ትርጉሙ አንድን ሰው በሌላ ሰው ቁጥጥር ሥር እንዲሆን መስጠትን ያመለክታል። ኤቲ፡ “ዳኛው በሕጉ መሠረት እንዲፈርድብህ ያደርጋል።” ( ተመልከት) ዳኛውም ለወህኒ ጠባቂዎች አሳልፎ ይሰጥሃል በዚህ ሥፍራ ላይ “አሳልፎ ይሰጥሃል” የሚለው ሀረግ ትርጉሙ አንድን ሰው በሌላ ሰው ቁጥጥር ሥር እንዲሆን መስጠትን ያመለክታል። ኤቲ፡ “ዳኛውም ለወህኒ ጠበቂ አሳልፎ ይሰጥሃል።” ( ተመልከት) የወህኒ ጠባቂ ይህ ሰው ሰው በዳኛው የተሰጠውን ውሳኔ የሚያስፈጽም ግለሰብ ነው። ወደ ወህኒ ትጣላለህ ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “የወህኒ ጠባቂው በወህኒ ቤት ውስጥ እንዲትታሠር ያደርጋል።” ( ተመልከት) እውነት እውነት እላችኋለሁ “እውነት እውነት እላችኋለሁ”። ይህ ሀረግ ኢየሱስ ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር አጽኖት እንዲንሰጥ ያደርገናል። ከዚያ ሥፍራም “ከወህኒ ቤት”

## Matthew 5:27

ማቴዎስ 5፡27-28

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን ለመፈጸም መምጣቱን ማስተማሩን ቀጥሏል። በዚህ ሥፍራ ስለዝሙት እና ምኞች ማስተማር ጀምሯል። አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “ሰምታችኋል” በሚለው ሀረግ ውስጥ የሚገኘው “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው። “አታመንዝር” የሚለው ትዕዛዝ “አንተ” የሚለውን ቃ በውስጡ ይዞዋል ይሁን እንጂ “አንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር መተርጎም ትችላለህ። ( ተመልከት) እንዲህ እንደተባለ ሰምታችኋል ይህ በቀጥታ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ፡ “እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል።” ( ተመልከት) መፈጸም ይህ ቃል አንድን ነገር ማድረግን ያመለክታል። እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ ይህንን በ MAT 5:22 እንደ ተረጎማችሁት ተመልከቱ። ሴትን ተመልክቶ በልቡ የተመኛት ማንኛውም ሰው አመንዝሯል ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ሴትን ተመልክቶ በልቡ የተመኛት ማንኛውም ሰው ካመነዘረ ሰው እኩሉ ጥፋተኛ መሆኑን ያሳያል። ( ተመልከት) የተመኛት “እንዲሁም የተመኛት” ወይም “ከእርሷ ጋር ለመተኛት የተመኘ ሰው” በልቡ በዚህ ሥፍራ “ልብ” የሚያመለክተው የአንድን ሰው ሀሳብ ነው። ኤቲ፡ “በአእምሮው” ወይም “በሀሳቡ”። ( ተመልከት)

## Matthew 5:29

ማቴዎስ 5፡29-30

የአንተ . . . ከ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “አንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው ይሁን እንጂ በብዙ ቁጥር መተርጎም የግድ ሊሆንብህ ይችላል። ( ተመልከት) የቀኝ ዐይንህ ካሰናከለችህ በዚህ ሥፍራ “ዐይን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድ ሰው የሚያየውን ነው። እንዲሁም “መሰናከል” ምሳሌያዊ ንግግር ሲሆን “ኃጢአት” ማለት ነው። ኤቲ፡ “የሚትመለከተው ነገር እንድትሰናከል የሚያደርግ ከሆነ” ወይም “ከሚታየው ነገር የተነሳ ኃጢአት ማድረግ የሚትሻ ከሆነ።” ( እና ተመልከት) ቀኝ ዐይን . . . ቀኝ እጅ ከግራ ዐይን ወይም እጅ በተቃራኒው በጣም ጠቃሚው ዐይን

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ወይም እጅ። “ቀኝ” የሚለው ቃል “አስፈላጊ የሆነ” ወይም “ብቸኛ” በሚሉ ቃላት ለትተረጉማቸው ትችላለህ። ( ተመልከት) አውጥተህ “በኃይል ማስወገድ” ወይም “ማጥፋት”። ቀኝ ዐይን የሚለው በቀጥታ ካልተጠቀሰ “ዐይንህ አጥፋ” ብለህ ልትተረጉም ትችላል። ዐይን የተጠቀሰ ከሆነ “አጥፋቸው” ብለህ ልትተረጉም ትችላለህ። አውጣው . . . ቁረጠው ኢየሱስ የኃጢአትን አደገኝነት ላይ አጽኖት በመስጠት ለዚህ ሰዎች መስጠት ስላለባቸው ምላሽ ግነት የተሞላት መልኩ ተናግግሯል። ( ተመልከት) አውጥተህ ጣለው “አስወግደው” ከሰውነት ክፍለህ አንዱ ይጥፋ “ከሰውነት ክፍልህ አንዱን ማጣት ይሻላል።” መላ አካልህ ወደ ሲኦል ከሚጣል ይልቅ ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላለል: ኤቲ: “እግዚአብሔር መላ አካልህን ወደ ሲኦል ከሚጨምረው ይልቅ።” ( ተመልከት) ቀኝ እጂህ ካሰናከለችህ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የአንድ ሰው ሁለተናዊ ተግባርን ከእጁ ጋር ታያይዛለች። ( ተመልከት)

Matthew 5:31

ማቴዎስ 5:31-32

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን እንዴት ለመፈጸም እንደመጣ ማስተማሩ ቀጥሏል። በዚህ ሥፍራ ላይ ስለፍች ማስተማር ጀምሯል። እንዲህም ተብሏል “የተናገረው” እግዚአብሔር ነው። ኢየሱስ የእርሱ ተቃርኖ ከእግዚብሔር ወይም ከእግዚብሔር ቃል ጋር አለመሆኑን ለመግለጽ ነው ይህን ዓይነት ንግግር የተናገረው። ይልቁንም ፍች የተፈቀደው ለትክክለኛ ምክንያት ብቻ ነው። ወንዱ ምንም እንኳ በትዕዛዛቱ መሠረት የፍች ወረቀቷን ለሚስቱ ቢሰጣትም እንኳ ፍትሓዊ አይደለም። ( ተመልከት) ሚስቱን የሚሰዳት ይህ ፍችን የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። ( ተመልከት) ይስጣት “ልሰጣት ይገባል” እኔ ግን እንዲህ እላለሁ ይህንን በ [MAT 5:22](MAT 5:22) በምን ዓይነት መንገድ እንደተረጎማችሁ ተመልከቱ። አመንዝራ ያደርጋታል ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ሚስቱን የፈታት ሰው “እንድታመነዝር ያደርጋል”። በብዙ ባሕሎች ውስጥ እንደገና ማግባት ትችላለች ነገር ግን የተፋታችው ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ከሆነ ግን እንዲህ አይነቱ ትዳር ዝሙት ነው። ከተፋታች በኋላ ይህ በቀጥታ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ባሏ ከፈታት በኋላ” ወይም “ፍች የፈጸመችው ሴት”። ( ተመልከት)

Matthew 5:33

ማቴዎስ 5:33-35

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን እንዴት ለመፈጸም እንደመጣ ማስተማሩ ቀጥሏል። በዚህ ሥፍራ ላይ ስለመሃላ ማስተማር ጀምሯል። አጠቃላይ መረጃ: ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “ሰምታችኋል በሚለው ሀረግ ውስጥ ያለው “እናንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር የተገለጸ ነው። ይሁን እንጂ “አትማል” እና “ፈጽማቸው” በሚለው ውስጥ ያለው “አንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር የተገለጸ ነው። እንደገና አንተ “አንተም ደግሞ” ወይም “ሌላ ምሳሌ ይኼው። አንተ” እንዲህ ሲባል ሰምታችኋል . . . በውሸት አትማሉ በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር እና ከቃሉ ጋር በግልጽ የሚስማማ ነገር ስናገር ትመለከታላችሁ። ይሁን እንጂ ሰዎችን ለማሳመን የእነርሱ ያልሆነ ነገር እንዳይናገሩ ያሳስባቸዋል። ኤቲ: “የሃይማኖት መሪዎቻችሁ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ብለው ነግረዋችኋል . . . አትማሉ።” ( ተመልከት) በውሸት አትማሉ መኃላችሁን ፈጽሙ እንጂ አማራጭ ትርጉሞች 1) የማትፈጽሙትን ነገር አደርጋለሁ ብላችሁ በእግዚአብሔር ፊት አትማሉ ወይም 2) አንድ ነገር ውሸት መሆኑን እያወቃችሁ በእግዚአብሔር ፊት እውነት ነው ብላችሁ አትማሉ። እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ በ [MAT 5:22](MAT 5:22) የሚገኘውን በምን መንገድ እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። ፈጽሞ አትማሉ . . . የታላቁ ንጉሥ ከተማ በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ የተናገረው ማንም ሰው ፈጽሞ መማል እንዳሌለበት ነው። አንዳንዶች አንድ ሰው የማለው ከእግዚአብሔር ውጪ በሆነ ነገር ማለትም በሰማይ፣ በምድር ዌም በኢየሩሳም የማለ ከሆነ መሃላውን ሳይፈጽም ቢቀር ይህን ያኽል ጉዳት የለውም ብለው ሳያስተምሩ አልቀሩም። ኢየሱስ ይህም ቢሆን እንደ ማንኛውም መሃላ መጥፎ ነው ምክንያቱም ሁሉ ነገር የእግዚአብሔር ስለሆነ ነው። ፈጽሞ አትማሉ ለዚህ ትዕዛዝ የሚሆን ቃል በቋንቋችሁ በብዙ ቁጥር የሚገኝ ከሆነ በዚህ ሥፍራ ይህንን ቃል ተጠቀሙ። “በውሸት አትማሉ” የሚለው ሀረግ አድማጮች መማል እንደሚቻል ነገር ግን በውሸት መማል የማይቻል እንደሆነ ያሳያል። “ፈጽሞ አትማሉ” የሚለው ሀረግ ግን ሁሉንም ዓይነት መሃላዎችን ይከለክላል። የእግዚአብሔር ዙፋን ነው በዚህ ሥፍራ ላይ “ዙፋን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ መግዛቱን ነው። ኤቲ: “የእግዚአብሔር አገዛዝ”። ( ተመልከት) የእግሩ መረገጫ ናት ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር ምድርም ቢትሆን የእግዚአብሔር መሆኗን ያሳያል። ኤቲ: “ንጉሥ እግሩን የሚያሳርፍበት የእግሩ መርገጫ ሥፍራ ዓይነት ናት። ( ተመልከት) የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና “ይህች ከተማ የታላቁ ንጉሥ የእግዚአብሔር ከተማ ናትና።”

Matthew 5:36

ማቴዎስ 5:37-38

አጠቃላይ መረጃ: ከዚህ በፊት በነበረው ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር ዙፋን፣ የእግሩ መረገጫ እና ምድራዊ ቤተ ጭምር ሊምሉበት የሚገባ የእርሱ ንብረት አለመሆኑን ገልጾዋል። በዚህ ሥፍራ ላይ ደግሞ በራሳቸው ላይ ባለው ጸጉር እንኳ መማል እንደማይገባቸው ይናገራል። እናንተ . . . አንተ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “አትማል” እና “አትችልም” በሚሉ ሀረጋት ውስጥ ያለው “አንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር የተገለጸ ነው። ይሁን እንጂ በምትተረጉሙበት ጊዜ በብዙ ቁጥር ልትተረጉሙ ትችላላችሁ። ( ተመልከት) መሃላ በ [MAT 5:34](MAT 5:34)እንዴት እንደተረጎምክ ተመልከት። ንግግርህ “አዎ፣ አዎ ወይም አይ ፣ አይ” ይሁን” “አዎ ማለት ከፈለግህ “አዎ” በል እንዲሁም “አይ” ማለት ከፈለግህ “አይ” በል።

Matthew 5:38

ማቴዎስ 5:38-39

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን እንዴት ለመፈጸም እንደመጣ ማስተማሩ ቀጥሏል። በዚህ ሥፍራ ላይ ጠላትን ስለመበቀል ማስተማር ጀምሯል። አጠቃላይ መረጃ: ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “ሰምታችኋል” እና “እኔ እንዲህ እላችኋለሁ” በሚለው ሀረግ ውስጥ የሚገኘው “እናንተ” የሚለው ቃል የተገለጸው በብዙ ቁጥር ነው። “ማንም ቢመታህ” የሚለው ሀረግ ውስጥ የሚገኘው “አንተ” የሚለው ቃል ግን በብዙ ቁጥር መተርጎም ትችላላችሁ። ( ተመልከት) እንዲህ መባሉን ሰምታችኋል ይህንን በ [MAT 5:33](MAT 5:33) እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከት። ዐይን ለዐይን ጥርስ ለጥርስ የሙሴ ሕግ የጎዳንን ሰው በተመሳሳይ መንገድ እንዲጎዳ ያዛል ይሁን እንጂ ከዚያ በላይ እንዲጎዳ አያደርግም። እኔ ግን እንዲህ እላለሁ ይህንን በ [MAT 5:22](MAT 5:22).እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከት። ክፉውን “ክፉ የሆነ ሰው” ወይም “የጎዳችሁ ሰው” (UDB) ቀኝ ጉንጫችሁን የመታችሁ ኢየሱስ በኖረበት ባሕል ውስጥ የአንድን ሰው ቀኝ ጉንጭ በጥፊ መምታት ስድብ ነው። ልክ እንደ ዐይን እና እጅ ሁሉ ቀኝ ጉንጭም በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። ጉንጭን በጥፊ መምታት ትልቅ ስድብ ነው። መምታት “በጥፊ መምታት”። ይህ ማለት በቃሪያ ጥፉ አንድን ሰው መምታት ማለት ነው። ሌላኛውንም ፊት አዙሩለት “ሌላኛውን ፊታችሁን የሚታችሁ ዘንድ አዙሩለት”

Matthew 5:40

ማቴዎስ 5:40-42

አጠቃላይ መረጃ: ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “ፍቀድ”፣ “ሂድ”፣ “ስጥ” እና “አትመለስ” በሚሉ ቃላት ውስጥ ያለው “አንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር የተገለጸ ነው። ( ተመልከት) ኮትህ . . . መጎናጸፊያ “ኮት” በሰዉነት ላይ እንደ ቲሸርት የሚጠለቅ ነው። “መጎናጸፊያ” ከእነዚህ ይልቅ ውድ የሆነ “ከኮት” ላይ ለሙቀት የሚደረብ እንዲሁም በሽት ለሙቀት የሚለበስ ነገር ነው። ይወስድ ዘንድ ፍቀድለት “ለዚያ ሰው ስጠው” ማንምን ሰው “እንዲሁም ይህ ሰው”። በዚህ ሥፍራ ላይ በተዘዋዋሪ መንገድ የተጠቀሰው የሮማዊያን ወታደር ነው። ( ተመልከት) አንድ ምዕራፍ አንድ የሮም ወታደር በዚያ ዘመን አንድን ሰው አንድ ዕቃ ተሸክሞ እንዲሄድ በሕግ ማስገደድ የሚችለው አንድ ሺህ እርምጃዎች ያኽል ነው። “ማይል” የሚለው ቃል የሚያምታታ ከሆነ “አንድ ኪሎ ሜትር” ወይም “ረጅም ርቀት” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ከእርሱ ጋር አብረኸው እንዲትሄድ ያስገደደ ሰውን ያመለክታል። ከእርሱ ጋር እጥፍ መንገድ ሂደት “አስገድዶህ እንዲትሄድ ያደረግህን ምዕራፍ ያኽል ሂደት ከዚያም ሌላ አንድ ማዕራፍ ጨምርለት።” “ማይል” የሚለው ቃል የሚያምታታ ከሆነ “ሁለት ኪሎ ሜትር” ወይም “እጥፍ ርቀት” ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አትከልክል “እንዲሁም ሊበደርህ የሚፈልግ ሰውን አትከልክል።” ይህ በአውንታዊ መንገድ ሊገለጽ ይገባል። ኤቲ: “አበድር”።

Matthew 5:43

ማቴዎስ 5:43-45

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን እንዴት ለመፈጸም እንደመጣ ማስተማሩ ቀጥሏል። በዚህ ሥፍራ ላይ ጠላትን ስለመውደድ ማስተማር ጀምሯል። አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “የሚወድሁን ውደድ . . . የሚጠሉህ ጥላ” የሚለው ብቻ በነጠላ ቁጥ የተጻፈ ሲሆን እነዚህም ቢሆን በብዙ ቁጥር

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መተርጎም ትችላህ። ለሌሎች “እናንተ” የሚል ቃል ባለባቸው ሥፍራዎች ሁሉ እና “ፍቅር”እና “ጸሎት” ቦታዎች በብዙ ቁጥር የተገለጹ ናቸው። ( ተመልከት) እንዲህ እንደተባለ ሰምታችኋል ይህንን በ MAT 5:33. እንደተረጎማችሁት ተመልከት። ባለንጀራህን “ባለንጀራ” የሚለው ቃል አንድ ሰው በመልካም መንገድ ማስተናገድ የሚሻውን የተመሳሳይ ማህበረሰብ ወይም ቡድን አባላትን የሚያመለክት እንጂ በአከባቢያችን የሚኖሩ ሰዎችን ሁሉ አያመለክትም። ይህንን የብዙ ቁጥርን በሚያመለክት ቃል ልትተረጉሙት ትችላላችሁ። እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ ይህንን በ MAT 5:22. እንደተረጎማችሁት ተመልከት። የአባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ “ልጆች” የሚለው ቃል በጥሩ ሁኔታ ለመተርጎም በቋንቋችሁ ለሰው ልጆችን ወይም ሕጻናት የሚትጠቀሙትን ቃል ተጠቀሙ። አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። ( ተመልከት)

Matthew 5:46

ማቴዎስ 5:46-48

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን እንዴት ለመፈጸም እንደመጣ ያስተማረውን ትምህርት በዚህ ክፍል ውስጥ ያጠናቅቃል። ይህ ክፍል የሚጀምረው በ MAT 5:17 ላይ ነው። አጠቃላይ መረጃ: ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። ለምሳሌ ያኽል “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር አመልካች ነው። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሚገኘው ጥያቄ መጠይቃዊ ነው። ( እና ተመልከት) ታላቅ ይህ አድማጮቹ መልካምነት ያለውን መሻት የሚያሳይ አጠቃላይ ቃል ነው።አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። ( ተመልከት)

---

Chapter 6

Matthew 6:1

ማቴዎስ 6:1-2

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ በ MAT 5:3ላይ የተጀመረውን የተራራው ስብከቱን ማስተማር ቀጥሏል። በዚህ ክፍል ውስጥ “የጽድቅን ተግባራት” የሆኑትን አስራት ማውጣት፣ ጸሎት እና ጾምን አስመልክቶ አስምሯል። አጠቃላይ መረጃ: ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “እናንተ” የሚለው ቃል ሁሉም በብዙ ቁጥር የተገለጸ ነው። በሰዎች ለመታየት ለሰዎች ብለው የሚያደርጉ ሰዎች እርሱን እያከበሩት እንዳልሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ያመለክታል። ይህ እንዲህ ባለ መልኩ በቀጥታ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ስላደጋችሁት ነገር ሰዎች ያመሰግናችሁ ዘንድ በሰዎች ፊት የሚታደርጉት ከሆነ፡” ( እና ተመልከት) አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። ( ተመልከት) ለራስህ መለከት አታስነፋ ይህ ምሳሌ የሚያሳየው የሰዎችን ትኩረት ሆን ብለህ ለመሳብ የተለያዩ ነገሮችን ማድረግ ነው። ኤቲ: “በብዙ ሰዎች መካከል መለከት በታላቅ ድምፅ እንደሚነፋ ሰው ወደ ራስህ የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ጥረት አታድረግ።” ( ተመልከት) እውነት እልሃለሁ “እውነቱን እነግርሃለሁ”። ይህ ሀረግ ኢየሱስ በመቀጠል ስለሚናገረው ነገር አጽኖት የሚሰጥ ሀረግ ነው።

Matthew 6:3

ማቴዎስ 6:3-4

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ኢየሱስ ስመ ስጦታ መስተማሩን ቀጥሏል። አጠቃላያ መረጃ: ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር አመልካች ነው። ግራ እጅህ ቀኝ እጅህ የሚሰጠውን አይወቅ ይህ የሚታደርገው ነገር ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ምስጥር መሆን እንዳለበት የሚያሳይ ምሳሌ ነው። ምንም እንኳ ሁለቱም እጆች ብዙ ጊዜ ነገሮችን በጋራ የሚያከናውኑ ቢሆንም እንኳ፣ አንዱ የሚያደርገውን ሌላኛው “የሚያውቅ” ቢሆንም እንኳ ለድሆች በሚትሰጥበት ጊዜ እነዚህ በጣም የሚቀራረቡ እጆች እንኳ አንደኛው የሌላኛውን ማወቅ የለበትም። ( ተመልከት) ስጦታችሁ በድብቅ ይሁን ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ሌሎች ሰዎች መስጠትህ ሳያውቁ ለድሆች ልትሰጥ ትችላለህ።” ( ተመልከት) ይሸልምሃል “ሽልማት ይሰጥሃል።” (UDB)

Matthew 6:5

ማቴዎስ 6:5-7

አያያዥ ዓረፍተ ነገሮች ኢየሱስ ስለ ጸሎት እንዲህ በማለት ማስተማር ጀመረ። ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በቁጥር 5 እና 7 ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር አመልካች ቃል ሲሆን በቁጥር 6 ላይ ግን በነጠላ ቁጥር ተገልጾዋል። ይሁን እንጂ ይህንን በብዙ ቁጥር ልትተረጉመው ትችላለህ። ( ተመልከት) ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉትን ያዩላቸው ዘንድ በዚህ ሀረግ ውስጥ ተመልካቾቹ ድርጊቱን ተመልክተው ክብር እንደሚሰጧቸው በተዘዋዋር መንገድ ያሳያል። ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ሰዎች ያዮዋቸው እና ክብር ይሰጧቸው ዘንድ።” ( እና ተመልከት) እውነት እውነት እላችኋለሁ “እውነቱን እነግራቿለሁ”። ይህ ሀረግ ኢየሱስ በመቀጠል ለመናገረው ነገረ ትኩርት እንዲነሰጥ ያደርገናል። ወደ እልፍኝህ ግባ። በርህንም ዝጋ “ለብቻ ወደምትሆንበት ሥፍራ ግባ” ወይም “ለብቻ መሆን ወደምትችልበት ሥፍራ ሂድ” በውስር ያለው አባት ለዚህ አማራጭ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔርን ማንም ሰው ማየት አይችልም ወይም 2) እግዚአብሔር በዚያ ለብቻው ከሚጸልየው ሰው ጋር አለ። አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። ( ተመልከት) በስውር የሚታደርገውን የሚያይ አባት “አባትህ በስውር የሚታደርገውን ያያል” በከንቱ አትድገም “ትርጉም የሌሽ ቃላትን አትደጋግም” ይሰማል ይህ እንዲህ በቀላሉ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “የሐሰት አማልክቶች ይሰሟቸዋል።” ( ተመልከት) ብዙ በመናገራቸው “በረጃጅም ጸሎቶቻቸው” ወይም “ በብዙ ቃሎቶቻቸው።”

Matthew 6:8

ማቴዎስ 6:8-10

አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። “እንዲህ ጸልዩ” እስከሚለው ድረስ ለቡድን ተናግሯል። “እናንተ” ከሚለው ቀጥሎ ያለው “ሰማያዊ አባታችሁ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር ነው የተቀመጠው። (See: ተመልከት) አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። ( ተመልከት) ስምህን ይቀደስ በዚህ ሥፍራ ላይ “ስም” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን የሚያመለክት ነው። ኤቲ: “ቅዱስ እንደሆንክ ሁሉም ሰው ይወቅት።” ( ተመልከት) መንግስትህ ትምጣ በዚህ ሥፍራ “መንግስት” የሚለው ቃል እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ ሆኖ የሚገዛበትን የሚያመለክት ቃል ነው። ኤቲ: “በሁሉም ላይ ገዥ ሁን እና ሙሉ ለሙሉ ሁሉን ግዛ።” ( ተመልከት) ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እዲሁም በምድር ላይ ትሁን ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “በሰማይ ያሉት ሁሉም እንደሚታዘዙህ ሁሉ በምድር ላይ ያሉት ሁሉ ይታዘዙህ።” ( ተመልከት)

Matthew 6:11

ማቴዎስ 6:11-13

አጠቃላይ መረጃ “እኛ” እና “የእኛ” የሚሉት ቃላት ኢየሱስ እየተናገራቸው ያለውን የተሰበሰበውን ሕዝብ ያመለክታል። ( ተመልከት) የእለት እንጀራችንን በዚህ ሥፍራ ይ “እንጀራ” የሚለው ቃል በአጠቃላይ ምግብን ያመለክታል። ( ተመልከት) ብድር ብድር አንድ ሰው ያለበት ዕዳ ነው። ይህ ኃጢአትን በምሳሌ ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። ( ተመልከት) ባለዕዳ ባለዕዳለ ከሌላ ሰው የተበደረ ሰው ነው። ይህ ኃጢአትን በምሳሌ ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። ( ተመልከት) ወደ ፈተና አታግባን “ፈተና” የሚለው ቃል በግሥ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ምንም ነገር እንድፈትነን አትፍቀድለት” ወይም “ኃጢአትን እንድንመኝ የሚያደረግ ማንኛውንም ነገር ሕይወታችን ውስጥ አትፍቀድ።” ( ተመልከት)

Matthew 6:14

ማቴዎስ 6:14-15

አጠቃላይ መረጃ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚገኝበት ሥፍራ ሁሉ በብዙ ቁጥር ነው። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ሌሎች ሰዎችን ይቅር ካላሉ በግል ምን እንደሚደርስባቸው እየነገራቸው ነው። ተመልከት) መተላለፍ “ስህተት” ወይም “ኃጢአት” አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። ( ተመልከት)

Matthew 6:16

ማቴዎስ 6:16-18

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ስለ ጾም ማስተማር ጀመረ። አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በቁጥር 17 እና 18 ላይ “አንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር የተገለጸ ሲሆን በቁጥር 16 ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ እንዲሆን በብዙ ቁጥር ልትተረጉመው ትፈልግ ይሆናል። ( ተመልከት) በተጨማሪ “እንዲሁም” ፊታቸውን ያጎሳቁላሉ ግብዞች ፍታቸውን አይታጠቡም ወይም ጸጉራቸውን አያበጥሩም። ይህንን የሚያደርጉት ሆን ብለው እየጾሙ መሆናቸውን ለማሳየት የሰዎችን ትኩረት

ለመሳብ እና ከእርሱ ክብር ለማግኘት ሲሉ ይህንን ያደርጋሉ፡፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ “እውነት እውነት እላችኋለሁ፡፡” ይህ ሀረግ ኢየሱስ በመቀጠል ለሚናገረው ነገር ትኩረት መስጠቱን ያመለክታል፡፡ ራስህን ዘይት ተቀባ “ዘይት ተቀባ” ወይም “ጸጉርህን አበጥር”፡፡ ራስህን “ተቀባ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለጸጉር የተለመደውን እንክብካቤ ማድረግ ነው፡፡ “ከክርስቶስ” “የተቀባው” መሆኑ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ኢየሱስ ማለት የፈለገው ሰዎች ጾም እየጾሙም ሆነ ሳይጾሙ ተመሳሳይ መሆን አለባቸው ነው፡፡ በስውር ያለው አባት . . . በስውር የሚያይ ይህንን እንዴት በ MAT 6:6. እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡ አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው፡፡ ( ተመልከት)

Matthew 6:19

ማቴዎስ 6:19-21

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ ስለ ገንዘብ እና ንብረት ማስማር ጀመረ፡፡ አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ “አንተ” የሚል ቃል ጥቅም ላይ በዋለባቸው ሥፍራዎች ከቁር 21 በስተቀር ብዙ ቁጥርን ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ በቁትር 21 ላይ ነጠላ ቁጥር ነው፡፡ ( ተመልከት) ንብረት “ሀብት” ብል እና ዝገት የሚበሉት “ብል እና ዝገት የሚያበላሹት ሀብት” ብል ብል ልብስን የሚያበላሹ በራሪ ነፍሳት ናቸው፡፡ ዝገት ብረት ውሃ ሲነካው የሚፈጠር ቡናማ ቀለም ያለው ነገር ነው፡፡ store up for yourselves treasures in heaven This is a metaphor that means do good things on earth so God will bless you in heaven. በሰማይ ሀብትን አከማቹ ይህ ምሳሌ የሚያሳየው እግዚአብሔር በሰማይ ይበባርካችሁ ዘንድ በምድር ላይ ሳላቹ መልካምን ነገር አድርጉ፡፡ ( ተመልከት) ልብህም ደግሞ በዚያ ይሆናል በዚህ ሥፍራ ላይ “ልብ1 ማለት አሳብ እና ፍላጎት ማለት ነው፡፡ ( ተመልከት)

Matthew 6:22

ማቴዎስ 6:22-24

አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው፡፡ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ “አንተ” የሚል ቃል ጥቅም ላይ በዋለባቸው ሥፍራዎች ውስጥ በነጠላ ቁጥር የተጠቀሰ ሲሆን አንተ ግን በብዙ ቁጥር ለመተርጎም ታስብ ይሆናል፡፡ ( ተመልከት) ዐይን የሰውነት ብርሃን ነች . . . ጨለማው ምን ያኽል ታላቅ ይሆን ይህ ማየት የሚችል ጤናማ ዐይንን አንድን ሰው ዐይነ ሥውር ከሚያደረግ በሽታ ጋር ያነጻጽራል፡፡ ይህ ምሳሌ የሚያመለክተው መንፈሳዊ ጤንነትን ነው፡፡ ብዙ ጊዜ አይሁዳዊያን “መጥፎ ዐይንን” ከስስት ጋር ያይዙታል፡፡ ትርጉሙም አንድ ሰው ሁለተናውን ለእግዚአብሔር ከሰጠ እንዲሁም ሁሉንም ነገር ከእግዚአብሔር አንጻር መመልከት ከቻለ ትክክለኛውን ነገር ያደርጋል፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ሰው ስስታም ከሆነ ክፋትን ያደርጋል፡፡ ( ተመልከት) ዐይን የሰውነት ብርሃን ነው የዚህ ምሳሌያዊ ንግግር ትርጉም ልክ መብራት በጨለማ ውስጥ ሰው አጥርቶ እንዲያይ እንደሚያደርግ ሁሉ ዐይንም አንድ ሰው በደንብ ማየት እንዲችል ያደርገዋ፡፡ ኤቲ: “እንደ መብራት ዐይን ነገሮችን በግልጽ ማየት እንድትችል ያደርጋል፡፡” ( ተመልከት) ዐይን ይህንን በብዙ ቁጥር ልትተረጉመው ትችላለህ፤ “ዐይኖች”፡፡ ዐይንህ መጥፎ ቢሆን ይህ ምትሃትን አያመለክትም፡፡ አይሁዶች ብዙ ጊዜ ስስታምነትን በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ይገልጹታል፡፡ ( ተመልከት) አንዱን ይወዳል ሌላኛውን ይጠላል ወይም ለአንዱ ይገዛል ሌላኛውን ደግሞ ይንቃል ሁለቱም በመሠረታዊ ሀሳባቸው አንድ ናቸው፡፡ አጽኖት የሚሰጡት አንድ ሰው እግዚአብሔር መውደድ እና መገዛት እንዲሁም ገንዘብንም መውደድና ለእርሱ መገዛት በአንድ ጊዜ አይችልመም፡፡ ( ተመልከት) ለሀብት እና ለእግዚአብሔር መገዛት አትችሉም፡፡ “በአንድ ጊዜ እግዚአብሔርን እና ገንዘብን መውደድ አትችሉም፡፡”

Matthew 6:25

ማቴዎስ 6:25-26

እላችኋለሁ ይህ ኢየሱስ ከዚህ በመቀጠል የሚናገረው ነገር አጽኖት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ያሳያል፡፡ ለእናንተ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው፡፡ “እናንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር የተገለጸ ነው፡፡ ( ተመልከት) ሕይወት ከመብል እንዲሁም ሰውነት ከልብስ አይበልጥምን? በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ ሰዎችን ለማስተማር ጥያቄን ተጠቅሟል፡፡ ኤቲ: “በእርግጥ ሕይወት ከምግብ እንዲሁም አካል ከምንለብሰው ልብስ ይበልጣል፡፡” ( ተመልከት) ጎተራ እህል ማጠራቀሚያ ሥፍራ፡፡ አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው፡፡ ( ተመልከት) Are not you of much more value than they? Jesus uses a question to teach the people. AT: "Obviously you are more valuable than birds." አንተ ከእነርሱ ይልቅ በጣም ኩቡር አይደለህምን? ኢየሱስ ሰዎችን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀማል፡፡ ኤቲ: “ከሰማይ ወፎች ይልቅ አንተ ክቡር ነህ፡፡” ( ተመልከት)

Matthew 6:27

ማቴዎስ 6:27-29

አጠቃላይ መረጃ: ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው፡፡ “እናንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር የተገለጸ ነው፡፡ ( ተመልከት) ከእናንተ መካከል በመጨነቅ በእድሜው ላይ ስንዝር ታኽል የጨመረ ማን ነው? ኢየሱስ ሰዎችን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀማል፡፡ ይህ ማለት ማንም በጭንቀት ረጅም እድሜ መኖር የሚችል የለም፡፡ ( ተመልከት) አንድ ክንድ “አንድ ክንድ” ከከግማሽ ሜትር ትንሽ የሚያንስ ነው፡፡በዚህ ሥፍራ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው አንድ ሰው በእድሜው ላይ ምንም መጨመር እንደማይችል በምሳሌ ለመግለጽ ነው፡፡ ( እና ተመልከት) ስለምትለብሱት ነገር ስለምንት ትጨነቃላችሁ? ኢየሱስ ሰዎችን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀም ነበረው፡፡ ኤቲ: “ምን እለብሳለሁ ብላችሁ አትጨነቁ፡፡” ( ተመልከት) ስለአንድ ነገር ማሰብ “መጨነቅ” አበቦች የሜዳ አበቦች ( ተመልከቱ) እላችኋለሁ ይህ ኢየሱስ ከዚህ በመቀጠል የሚናገረው ነገር አጽኖት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ያሳያል፡፡ ማንም እንደነዚህ አግጦ አያውቅም ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ኤቲ: “እንደነዚህ የሜዳ አበቦች ያጌጠ ልብስ ማንም ለብሶ አያውቅም፡፡”

Matthew 6:30

ማቴዎስ 6:30-31

አጠቃላይ መረጃ: ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው፡፡ “እናንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር የተገለጸ ነው፡፡ እነዚህ ሣሮች እንደዚህ ካለበሳቸው ይህ ምሳሌ እግዚአብሔር አበቦችን እንዲህ ውብ ካደረጋቸው ማለት ነው፡፡ ( ተመልከት) ሣር በቋንቋችሁ ሣር የሚለው ቃል የሚያካትት እና ከከዚህ በፊት የሜዳ አበባዎች ተብሎ የተተረጎመውን የሚያካትት ከተገኘ ያንን ቃል ተጠቀም፡፡ ወደ ማቃጠያ እቶን የሚጣለውን አይሁዳዊያን ምግባቸውን ለማብሰል ሣርን ይጠቀማሉ፡፡ ይህ በቀጥታ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ኤቲ: “ወደ ማቃጠያ ይጥለዋል” ወይም “አንድ ሰው እንዲቀጣል ያደርገዋል፡፡” ( ተመልከት) እናንተ ምን አያለብሳችሁም . . . እምነት? ኢየሱስ ሰዎችን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀም ነበር፡፡ ኤቲ: “በእርግጠኝነት ያለብሳችኋል . . . እምነት፡፡” ( ተመልከት) እናንተ እምነት የጎደላችሁ “እናንተ ትንሽ እምነት ያላችሁ፡፡” በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነት በጣም ትንሽ ከመሆኑ የተነሳ ኢየሱስ ሰዎችን ይገስጻቸዋል፡፡ ስለዚህ “እነዚህ ሁሉ ምክንቶች”

Matthew 6:32

ማቴዎስ 6:32-34

አሕዛብም እነዚህ ነገሮች ሁሉ ይፈልጋሉ “አሕዛብም ነገ ምን እንደሚበሉ፣ እንደሚጠጡ እና እንደሚለብሱ ይጨነቃሉ፡፡” በሰማይ ያለው አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ያውቃል ኢየሱስ በዚህ ንግግሩ ውስጥ በተዘዋዋር መልኩ የሚያስረግጠው ነገር መሠረታዊ ፍላጎቶቻችሁ በእግዚአብሔር በእርግጠኝነት ይሟላሉ፡፡ አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው፡፡ ( ተመልከት) በመጀመሪያ መግስቱን እና ጽድቁን ፈልጉ በዚህ ሥፍራ ላይ “መንግስቱ” የሚለው ቃል እግዚብሔር እንደ ንጉሥ መግዛቱን የሚያመለክት ነው፡፡ ኤቲ: “ንጉሥ የሆነውን እግዚአብሔርን አገልግል እንዲሁም መልካም የሆነውን ነገር አድርግ፡፡” ( ተመልከት) እነዚህ ሁሉ ነገሮች ይጨመሩልሃል ይህ በቀጥታ እንዲህ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ኤቲ: “እግዚአብሔር እነዚህ ነገሮች ያዘጋጅልሃል፡፡” ( ተመልከት) ስለዚህ “በእነዚህ ሁሉ ምክንቶች” tomorrow will be anxious for itself Jesus is describing "tomorrow" as if it is a person that can worry. Jesus means that a person will have enough to worry about when the next day comes. ነገ ስለራሱ ይጨነቅ በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ “ነገን” ልክ እንደ ሰው የሚጨነቅ አድርጎ ያቀርበዋል፡፡ ኢየሱስ አንድ ሰው ነገ ስመጣ በዚያ ቀን በቂ የሚጨነቅበት ነገር አለው ማለቱ ነው፡፡ ( ተመልከት) ለዛሬ የራሱ ክፋት ይበቃዋል “እያንዳንዱ ቀን በውስጡ በቂ የሆነ ክፋትን ይዟል” ወይም “ሁሉም ቀናት በቂ ችግሮች አሏቸው”

Chapter 7

Matthew 7:1
ማቴዎስ 7:1-2
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ በ in MAT 5:3 በተጀመረው የተራራው ስብከት ውስጥ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስተማሩን ቀጥሏል። አጠቃላይ መረጃ: ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “እናንተ” የሚለው ቃል እና የተሰጡት ትዕዛዛት በብዙ ቁጥር ተገልጸዋል። ( ተመልትከት) አትፍረድ በዚህ ሥፍራ ላይ “አትፍረድ” የሚለው ቃል ጠንከር ያለ “ጠንከር ያለ ማውገዝን” ወይም “ጥፋተኛ አድርጎ መወሰንን” የሚያመለክት ቃል ነው። ኤቲ: “በሰዎችን ላይ አትፍረድ”። ( ተመልከት) አይፈረድብህም ይህ በግልጽ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “መጥፎ ፍርድ አይፈረድብህም።” ( ተመልከት) Be sure the reader understands the statement in 7:2 is based on what Jesus said in 7:1. ምክንያቱም ኢየሱስ በ7:2 ላይ የተናገረው ንግግር መሠረቱ በ7:1ላይ የተናገረው መሆኑን እርግጠኞች ሁኑ። በፈረዳችሁት ፍርድ እናንተም ላይ እንዲሁ ይፈረዳል ይህ በዚህ መልኩ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “በሌሎች ሰዎች ላይ በፈረዳችሁበት መጥን ልክ እናንተም ላይ እግዚአብሔር ይፈርዳል።” ( ተመልከት) በዚያው ልክ ይፈረዳል ይህ እንዲህ በቀጥታ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “እግዚአብሔር በዚያው ልክ ይፈርዳል።” ( ተመልከት)
Matthew 7:3
ማቴዎስ 7:3-5
አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “አንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር ተገልጾዋል ይን እንጂ በብዙ ቁጥር ልትተረጎማቸው ትችላለህ። ስለምን ታያለህ . . . እንዴትስ ትለዋለህ ኢየሱስ እነዚህን ሁሉት ጥያቄዎች የተጠቀመው ሰዎችን ለማስተማር እና አመለካከታቸውን እንደገና ይመለከቱት ዘንድ ነው። የሌሎች ሰዎች ኃጢአት ላይ ጣታቸውን ከመቀሰራቸው በፊት ለራሳቸውን ኃጢአት ትኩረት መስጠት ስለፈለገ ነው። ( ተመልከት) በጣም ትንሽ ብናኛ “ቆሻሻ”(UDB) ወይም “ብናኝ” ወይም “አፈር”። ወደ ሰዎች ዐይን ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚገባን ነገር ለመግለጽ የሚትጠቀሙትን ቃል ተጠቀም። ይህ በሰዎች ውስጥ የሚያጋጥምም በጣም ትንሹን ስህተትን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋ ምሳሌ ነው። ( ተመልከት) ወንድም ይህ የሥጋ ወንድምን ወይም ጎረቤትን ሳይሆን አማኝን የሚያመለክት ነው። ምሰሶ አንድ ሰው በቆረጠው ዛፍ ውስጥ የሚገኘው ትልቁ ክፍል ምሰሶ ነው። ይህ ወደ ሰዎች ዐይን ለመግባት በጣም ትልቅ የሆነ ግንድ ነው። ይህ በሰው ሕይወት ውስጥ ያለ በጣም ትልቅ ስህተትን ያሳያል። እና ተመልከት)።
Matthew 7:6
ማቴዎስ 7:6-6
አጠቃላይ መረጃ: ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “እናንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ተገልጸዋል። ውሾች . . . እሪያዎች አይሁዶች እነዚህ እንስሳት ቆሻሾች አድርገው ይቆጥሯቸዋል እንዲሁም እግዚአብሔርም እነዚህን እንስሳት እንዳይበሉ አዞዋቸዋል። ይህ ቅዱስ ለሆነው ነገር ዋጋ የማይሰጡ ኃጢአተኛ ሰዎችን ለማመልከት የቀረበ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። ይህንን ቃል በቁሙ መተርጎሙ ባጣም ጥሩ ነው። ( ተመልከት)። እንቁዎች እነዚህ በጣም ትንንሽ፣ ውድ የሆኑ ድንጋዮች ናቸው። ይህ ስለእግዚአብሔር ወይም ስለውድ ነገሮች በአጠቃላይ ማወቅ ጋር ተያያዥነት ያለው ምሳሌያዊ ንግግር ነው። ( ተመልከት) በእግሮቻቸው ልረጋግጡት ይችላሉ “እሪያዎቹ ይረጋግጡታል” እናም ወደ ትፋታቸው ይመለሳሉ “እናም ውሾች ወደ ትፋታቸው ይመለሳሉ”
Matthew 7:7
ማቴዎስ 7:7-10
አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “እንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ተገልጸዋል። ( ተመልከት)። ጠይቁ . . . ፈልጉ . . . እንኳኩ ይህ ወደ እግዚአብሔር መጸለይን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ ምሳሌያዊ ንግግር ነው። በዚህ ሥፍራ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ግሥ እግዚአብሔር ምላሽ እስኪሰጠን ድረስ እንዲንጸለይ የሚያደርግ ነው። በቋንቋችሁ አንድን ነገር መልሳችሁ መልሳችሁ ማድረግ እንዳለባችሁ የሚገልጽ ቃል ካለ ይህንን ቃል ተጠቀሙ። ( ተመልከት) ጠይቁ ይህ ከእግዚአብሔር የሆነ ነገርን ጠይቁ ማለት ነው። (UDB) ይሰጣችኋል ይህ እንዲህ ባለ መልኩ በቀጥታ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “የሚያስፈልጋችሁን ነገር እግዚአብሔር ይሰጣችኋል። ( ተመልከት) ፈልጉ “ስለምትፈልጉትን ነገር የእግዚአብሔርን ፊት ፈልጉ” እንኳኩ በር ማንኳኳት በቤት ውስጥ ያለ ሰው በሩን እንዲከፍትላችሁ በትህትና መጠየቅ ነው። በእናንት ባሕል ውስጥ በር ማንኳኳት ትህትና ካልሆነ ሰዎች በእናንተ ባሕል ውስጥ በር እነንዲከፈትላቸው በትህትና የሚጠይቁ በምን ዓይነት መንገድ ነው፣ ይህንንም ቃል ተጠቀሙ። ኤቲ: “እግዚአብሔር በሩን እንዲከፍትላችሁ እንደሚትልጉ ንገሩት።” ወይም ከእናንተ መካከል ማን ነው . . . ድንጋይ? ኢየሱስ ሰዎችን ለማስተማር ጥያቄን ይጠቀማል። ኤቲ: “ከእናንተ መካከል ማንም የለም . . . ድንጋይ።” ( ተመልከት) ቁራጭ ዳቦ ይህ በአጠቃላይ ምግብን ያመለክታል። ኤቲ: “የሆነ ምግብ።” ( ተመልከት) ድንጋይ. . . ዓሳ . . . እባብ እነዚህ ስሞች በቁማቸው መተርጎም አለባቸው። ወይም ኣሳ ጠይቋችሁ እባብ የምትሰጡት? ኢየሱስ ለማስተማር ሌላ ጥያቄ ጠየቃቸው። በዚህ ሥፍራም ኢየሱስ ስለ ሰውዬው እና ልጁ እየተናገረ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው። ኤቲ: “ከእናንተ መካከል ልጁ ዓሳ ጠይቆት እባብ የሚሰጠው ማንንም የለም።” ( እና ተመልከት)
Matthew 7:11
ማቴዎስ 7:11-12
አጠቃላይ መረጃ ኢየሱስ በቡድን ለሚያደምጡ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያጋጥማቸው በመናገር ላይ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ “እንተ” የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ተገልጸዋል። ( ተመልከት)። በሰማይ ያለው አባታችሁ አስበልጦ ምን ያኽል አይሰጣችሁ . . . እርሱ? በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ ሕዝቡን ለማስተማር ጥየቄን ተጠቀሟል። ኤቲ: “በሰማይ ያለው አባታችሁ በእርግጠኝነት ይሰጠዋል . . . እርሱ።” ( ተመልከት) አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። ( ተመልከት) ሰዎችን እንዲያደርጉላችሁ የሚትፈልጉትን ነገር ሁሉ “ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የሚትልጉትን ነገር ሁሉ” (UDB) ሕግ እና ነቢያት እነዚህ ናቸው በዚህ ሥፍራ ላይ “ሕግ” እና “ነቢያት” የሚለው ቃል ሙሴ እና ነቢያት የጻፏቸወ መጽሐፍትን ያመለክታል። ኤቲ: “ይህ ሙሴ እና ነቢያት የጻፉጽ ስለዚህ ጉዳይ ነው። ( ተመልከት)
Matthew 7:13
ማቴዎስ 7:13-14
አጠቃላይ መረጃ: ስለ ሁለቱ በሮች እና መንገዶች አጽኖት መስጠት ያስችለ ዘንድ ስትተረጉም “ሰፍ” የሚለው ቃል “ጠባብ” ከሚለው በተቻለ መጠን የሚለይ መሆኑን አሳይ። በጠባቢ በር ግቡ . . የሚገኙት ጥቂቶች ናቸው ይህ በመንገድ ላይ የሚሄድ እና ወደ መንግስቱ በበር የሚገባ ሰው ምስል ነው። ወደ አንደኛው መንግስት መግባት ቀላል ሲሆን ወደሌላኛው መንግስት መግባት ግን ከባድ ነው። ይህ ሰዎች የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ሰዎች ከባድ የሆነውን በሕይወታቸው እግዚአብሔርን መታዘዝ መቀበል እንደሚኖርባቸው ለማሳየት የቀረበ ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር የተመታዘዝ ቀላሉን መንገድ ከመረጡ ወደ ስኦል ይገባሉ። ( ተመልከት) በጠባቢ በር ግቡ ይህንን ወደ ቁጥር 14 መጨረሻ ልትወስዱት ትችላላችሁ፡ “ስለዚህ በጠባቡ በር ግቡ”። በር . . . መንገድ አማራጭ ትርጉሞች 1) ይህ ወደ መንግስቱ መግቢያ በር እና ወደ በሩ የሚወስድ መንገድን ያመለክታል። ይህ ከሆነ በUDB ላይ ያለውን ቅደም ተከተል ልታለዋውጠው ትችላለህ። ወይም 2) “በር” እና “መንገድ” ሁለቱም የመንግስቱ መግቢያነ ናቸው። ይህ ከሆነ ቅደም ተከተሉን ማለዋወጥ አይኖርብህም። ( ተመልከት) ወደ ጥፋት . . . ወደ ሕይወት እነዚህ በግስ ልተረጎሙ ይችላሉ። ኤቲ: “ወደምትሞቱበት ሥፍራ . . . በሕይወት ወደሚትኖርቡት ሥፍራ” ( ተመልከት)
Matthew 7:15
ማቴዎስ 7፡ 15-17
ተጠንቀቁ “ራሳችሁን ጠብቁ” የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡ ነገር ግን ተኩላዎች ከሆኑ ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር መልካም እና መርዳት የሚፈልጉ መስለው የሚመጡ ነገር ግን ክፉ የሆኑ እና ከሚጎዷችሁ ሐሰተኛ ነቢያት ራሳችሁን ጠብቁ። ( ተመልከት) በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ ይህ ምሳሌዊ ንግግር የሰውን ተግባር የሚያመለክት ነው። ኤቲ: “ዛፍ በፍሬው እንደሚታወቅ ሁሉ ሐሰተኛ ነቢያት በሥራቸው ይታወቃሉ።” ( ተመልከት) ሰዎች ከኩርንችት. . . ይለቅማሉን ኢየሱስ ጥየቄን ሰዎችን ለማስተማር ተጠቅሟል። ሰዎች ለዚህ ጥያቄ ምላሱ አይ መሆኑን ማወቅ አለባቸው። ኤቲ: “ሰዎች ከኩርንችት . . . አይለቅሙም።” ( ተመልከት) መልካም ዛፉ ሁሉ መልካ ፍሬን ያፈራል ኢየሱስ የፍሬን ምሳሌ በመጠቀም ጥሩ ሥራ ወይም ቃል ስለሚያመጡ ስለጥሩ ነቢያት መናገሩን ቀጥሏል። ( ተመልከት) የተበላሸ ዛፍ መጥፎ ፍሬ ያፈራል ኢየሱስ የፍሬን ምሳሌ በመጠቀም መጥፎ ሥራ ስለሚሠሩ መጥፎ ነቢያት መናገሩን ቀጥሏል። ( ተመልከት)

Matthew 7:18
ማቴዎስ 7:18-20
መልካምን ፍሬ የማያፈራውን ዛፍ ይቆረጣል እንዲሁም ወደ እሳት ይጣላል ኢየሱስ የፍሬውን ምሳሌ ሐሰተኛ ነቢያትን ለማመልከት ተጠቅሞዋል። በዚህ ሥፍራ ላይ በመጥፎ ዛፍ ላይ ምን እንደሚሆን ብቻ ተናግሯል። ይህ በተዘዋዋር መንገድ የሚያሳየው በሐሰተኛ ነቢያት ላይ ተመሳሳይ ነገር ነው። ( እና ተመልከት) ይቆረጣል፣ ወደ እሳትም ይጣላል ይህ በዚህ መንገድ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ይቆርጡትና ያቃጥሉታል። “ ( ተመልከት) በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ “እርሱን” የሚለው ቃል ነብያቱን ወይም ዛፎቹን ሊያመለክት ይችላል። የዛፉ ፍሬ እና የነቢያቱ ድርጊት የሁለቱም መልካ ወይም መጥፎ ሊሆን ይችላል። ከተቻለ ከሁለቱ አንዱን በሚያመለክት መልኩ ተርጉሙት። ( ተመልከት)
Matthew 7:21
ማቴዎስ 7: 21-23
ወደ መንግስተ ሰማያት ይገባል በዚህ ሥፍራ ላይ “መንግስት” የሚለው ቃ እግዚአብሑር እንደ ንጉሥ መግዛቱን ያመለክታል። “መንግስተ ሰማያት” በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። ከተቻለ “ሰማይ” የሚለውን ቃል በትርጉማችሁ ውስጥ ለማኖር ጥረት አድርጉ። ኤቲ: “እግዚአብሔር ራሱን እንደ ንጉሥ በሚገልጥበት ጊዜ በሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር ይኖራል።” ( ተመልከት) የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ማንኛውም ሰው “የአባቴን ፍላጎት የሚፈጽም ማንም ሰው” አባት ይህ የእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ የማዕረግ ስም ነው። ( ተመልከት) በዚያ ቀን ኢየሱስ “በዚያ ቀን” በማለት የተናገረው አድማጮቹ በዚያ ቀን የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የፍርድ ቀንን እንደሆነ እንደሚገባቸው ታሳቢ በማድረግ ነው። አንባቢዎቻችሁ በግልጽ በዚያ ቀን የሚለው ሀረግ ትንቢት አልተናገርንምን . . . ሴጣንን አላወጣንምን . . . ብዙ ተዓምራትን አላደረግንምን? ሰዎች እነዚህ ነገሮች ማድረጋቸው ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ኤቲ: “ትንቡትን ተናግረናል . . . ሴጣንን አስወጥተናል . . . ታላላቅ ተዓምራን አድርገናል።” ( ተመልከት) እኛ ይህ “እኛ” የሚለው ቃ ኢየሱስን አያካትትም። ( ተመልከት) በስምህ በዚህ ሥፍራ ላይ “በስምህ” የሚለው ቃል በኢየሱስ ስልጣን እና ስም” ማት ነው። ( ተመልከት) ታላላቅ ነገሮችን “ተዓምራትን” አላውቃችሁም ይህ ማለት ይህ ሰው የኢየሱስ አይደለም ማለት ነው። ኤቲ: “አንተ የእኔ ተከታይ አይደለህም” ወይም “ከአንተ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለኝም።” ( ተመልከት)
Matthew 7:24
ማቴዎስ 7:24-25
ስለዚህ “በዚህ ምክንያት” ቃሎቼ በዚህ ሥፍራ ላይ “ቃሎቼ” የሚለው ቃል ኢየሱስ የተናገራውን ቃላት ያመለክታል። ( ተመልከት) በዓለት ላይ ቤትን የሠራን ጠቢብ ሰው ይመስላሉ ኢየሱስ የእርሱን ቃል የሚጠብቁ ሰዎችን ምንም ነገር ልጎዳው በማይችል መሠረት ላይ ቤታውን ከሠሩ ሰዎች ጋር ያነጻጽራል። ( ተመልከት) ዓለት ይህ በመሬት የላይኛው ክፍል ላይ ከመገኘው አፈር እ አሸዋ ቀጥሎ የሚገኝ ነው። በዚህ ላይ ቤቱን የገነባ ይህ በቀጥታ እንዲህ ልገለጽ ይገባል። ኤቲ: “የገነባው” ( ተመልከት)
Matthew 7:26
ማቴዎስ 7:26-27
አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ በ MAT 5:3. የተጀመረው የኢየሱስ የተራራው ስብከት መጨረሻ ነው። ሞኝ ሰው ቤቱን በአሸዋ ላይ ይሠራል ኢየሱስ ከዚህ በፊት ያቀረበውን ንጽጽር ቀጥሏል። ትዕዛዛቱን ያልታዘዙ ሰዎችን ቤታቸውን በአሸዋ ላይ ከሠሩ ሞኝ ሰዎች ጋር አነጻጽሯል። ቤቱን ዝናብ፣ ጎርፍ እና አውሎ ንፋስ ልያጠፋው በሚችል አሸዋማ መሬት ላይ የሚሠራ ሞኝ ሰው ብቻ ነው። ( ተመልከት) ወደቀ በቋንቋችሁ አንድ ቤት መውደቁን ለመግለጽ የሚትጠቀሙትን የተለመደ ቃል በዚህ ሥፍራ ላይ ተጠቀሙ። ጥፋቱ እጅግ በጣም የከፋ ይሆናል ዝናቡ፣ ጎር እና አውሎ ንፋሱ ቤቱን ፈጽሞ ያጠፋዋል።
Matthew 7:28
ማቴዎስ 7: 28-29
አጠቃላይ መረጃ እነዚህ ቁጥሮች ኢየሱስ በተራራው ስብከት ውስጥ ስላስተማራቸው ትመህርቶች የሰጠውን ምላሽ ምን ይህንን ከፈጸመ በኋላ ይህ ሀረግ የተራራው ስብከት መጨረሻ ለመሆኑ ምልክት ነው። ኤቲ: በመጨረሻውም” በትምህርቱ እጅግ በጣም ተገረሙ በ7:29 ላይ ኢየሱስ ባስተማረው ትምህርት ብቻ ሳይሆን ባስተማረበት መንገድም እንደተገረሙ በግልጽ ማየት ይቻላል። ኤቲ: “በማስተማር ዘዴውም እጅግ በጣም ተገረሙ።”

---

Chapter 8
Matthew 8:1
ማቴዎስ 8:1-3
አጠቃላይ መረጃ: ይህ በታሪክ ውስጥ ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን የፈወሰበት የአዲሱ ክፍል ጅማሬ ነው። ይህ ጭብጥ በእነዚህ ውስጥ ይቀጥላል MAT 9:35. ( ተመልከት) ኢየሱስ ከተራራ በወረደ ጊዜ ብዙ ሕዝብ ተከተለው “ኢየሱስ ከተራራ ከወረደ በኋላ ብዙ ሕዝብ ከተለው።” ይህ ሕዝብ በተራራው ከእርሱ ጋር የነበሩትን እንዲሁም ያልነበሩትንም ሊያካትት ይችላል። እነሆ “እነሆ” የሚለው ቃል በታሪክ ውስጥ አዲስ ሰውን ያስተዋውቀናል። በቋንቋችሁ ይህንን የሚታደርጉበት ቃል ሊኖራችሁ ይችላል። ለምጻም “ለምጽ ያለበት ሰው” ወይም “የቆዳ በሽታ ያለበት ሰው።” (UDB) በፊቱ ሰገደ ይህ በኢየሱስ ፊት ያሳየው ትህትና የሞላበት አቀራረብ ምልክት ነው። ( ተመልከት) ፈቃደኛ ከሆንክ “ከፈለግህ” ወይም “ፍላጎት ካለህ”። ለምጻሙ ሰው ኢየሱስ እርሱን የመፈወስ ኃይል እንዳለው አውቋል ይሁን እንጂ ኢየሱስ እርሱን ለመንካት ፈቃደኛ ይሁን አይሁን ግን አላወቀም። ልታነጻኝ ትችላለህ በዚህ ሥፍራ ላይ “ልታነጻኝ” የሚለው ቃል መፈወስን እና በማህህበረሰቡ ውስጥ እንደገና ተቀላቅሎ መኖርን የሚያመለክት ቃል ነው። ኤቲ: “ልትፈውሰኝ ትችላለህ” ወይም 1እባክህ ፈውሰኝ”። (UDB) ( ተመልከት) ወዲያው “በዚያን ጊዜ” ከለምጹ ነጻ “ንጻ” የሚለው የኢየሱስ ንግግር ውጤቱ የሰውዬው መፈወስ ነው። ይህ እንዲህ ባለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ጤነኛ ሆነ” ወይም “ለምጹ ለቀቀው” ወይም “ከለምጹ ነጻ”። ( ተመልከት)
Matthew 8:4
ማቴዎስ 8:4-4
ለእርሱ ይህ ኢየሱስ የፈወሰውን ሰው ያመለክታል። ለማንም አትናገር “ለማንም ምንም አትናገር” ወይም “እኔ እንደፈወስኩህ ለማንም አትናገር” ለካህናት ራስህን አሳይ የአይሁዳዊያን ሕግ የተፈወሰ ሰው ቆዳውን ለካህናት ማሳየት እንዳለበት ይጠይቃል። እነርሱም ቆዳውን ከተመለከቱ በኋላ ከሕዝቡ ጋር እንዲቀላቀል ይፈቅዱለታል። ( ተመልከት) ለእርሱ ምስክር ይሆንህ ዘንድ በሙሴ ትዕዛዝ መሠረት መስዋዕትን አቅርብ በሙሴ ሕግ መሠረት ከለምጽ የተፈወሰ ሰው የምስጋና መስዋዕትን ለከካህናት ማቅረብ ይኖርበታል። ካህናቱ ስጦታውን ከተቀበሉ ሕዝቡ ይህ ሰው መፈወሱን ያውቃሉ። ( ተመልከት) ለእነርሱ ይህ የሚያመለክተው 1) ካህናትን ወይም 2) ሌሎች ሰዎችን ወይም 3) ኢየሱስን የሚተቹ ሰዎችን ሊሆን ይችላል። ከተቻለ ከእነዚህ ቡድኖች መካከል ዬትኛውንም የሚያመለክትን ስም ተጠቀሙ። ( ተመልከት)
Matthew 8:5
ማቴዎስ 8:5-7
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ የታሪኩ ክፍል ውስጥ ጸሐፊው ወደሌላ ጊዜ እና ቦታ በመሄድ ኢየሱስ ሌላ ሰው የፈወሰበትን ሁኔታ ያሳያል። ወደ እርሱ መጥቶ ጠየቀው “በዚህ ሥፍራ “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው። ሽባ “ከበሽታው የተነሳ ከቦታ ቦታ መዘዋወር የማይችል” ኢየሱስም እንዲህ አለው። “ኢየሱስ ለመቶ አለቃው እንዲህ አለው” መጥቼ እፈውሰዋለሁ “ወደ ቤትህ መጥቼ ባርያህን አድነዋለሁ።”
Matthew 8:8
ማቴዎስ 8:8-10
ወደ ቤቴ ጣሪያ ሥር ግባ “”የቤቴ ጣሪያ ሥር” የሚለው ሀረግ “ቤቴ” ማለት ነው። ( ተመልከት) ቃል ተናገር በዚህ ሥፍራ “ቃል” የሚለው ቃል ትዕዛዝ ስጥ ማለት ነው። ኤቲ: “ትዕዛዝ ስጥ”። ( ተመልከት) ይፈወሳል ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ይድናል።” ( ተመልከት) በስልጣን ሥር ያለ ይህ በዚህ መልኩ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “በሌላ ሰው ሥልጣን ሥር ያለ ማንኛውም ሰው።” ( ተመልከት) በሥልጣን ሥር . . . በእኔ ሥር በአንድ ሰው “ሥር” መሆን ማለት የሌላ ሰው ትዕዛዝ እንደሚበልጥ በማወቅ ትዕዛዙን መቀበል። ( ተመልከት) ወታደሮች “የሰለጠኑ ተደባዳቢዎች” እውነት እልሃለሁ “እውነት እልሃለሁ።” ይህ ሀረግ ኢየሱስ በቀጣይነት የሚናገረው ነገር ላይ ትኩረት እንዲደረግ ይጋብዛል። እንዲህ ዓይነት እምነት በእስራኤል እንኳ አላገኘሁም የኢየሱስ አድማጮች የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆኑ የሚያስቡት በእስራኤል ያሉ አይሁዳዊያን ከማንም ይልቅ ታላቅ የሆነ እምነት እንደሚኖራቸው ያስቡ ነበር። ኢየሱስ ግን ተሳስተዋል በማለት ተናግሯል።

የመቶ አለቃው እምነት ከሁሉ ታላቅ ነበር። ( ተመልከት)
Matthew 8:11
ማቴዎስ 8:11-13
አንተ በዚህ ሥፍራ ላይ “አንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ሲሆን “እርሱን የሚከተሉትን ሰዎችን” ነው። [MAT 8:10](). (: ተመልከት) ከምስራቅ እና ከምዕራብ ተቃራኒ የሆኑትን “ምቅራቅ” እና “ምዕራብ”ን በመጠቀም “በሁሉም አከባቢ” የሚል መልዕክት አስተላልፏል። ኤቲ: “በሁሉም አከባቢ” ወይም “በሁሉም አቅጣጫ ከሩቅ ሥፍራ” ( ተመልከት) በማዕድ ይቀመጣሉ በዚያ ባሕል ውስጥ ያሉ ሰዎች ምግብ በሚመገቡበት ወቅት በጠረጴዛ ዙሪያ ይቀመጣሉ። ይህ ሀረግ የሚያመለክተው በጠረጴዛው ዙሪያ የሚቀመጡት ቤተሰብ እና የቅርብ ጓደኞች ናቸው። ኤቲ: “እንደ ቤተሰብ ከዳኞች ጋር መኖር”። ( ተመልከት) በመንግስተ ሰማያት በዚህ ሥፍራ “መንግስት” የሚለው ቃል እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ የሚገዛበትን የሚያመለክት ነው። “መንግስ ሰማያት” የሚለው ሀረግ ጥቅም ላይ የዋለው በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው። ከተቻለ “ሰማይ” የሚለውን ቃል በትርጉማችሁ ውስጥ ላማስቀመጥ ሞክሩ። ኤቲ: “በሰማይ ያለው አምላካችን ንጉሥ መሆኑን በሚሳይበት ጊዜ።” ( ተመልከት) የመንግስቱ ለልጆች ይጣላሉ ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “እግዚአብሔር የመንግስቱን ልጆች አውጥቶ ይጥላቸዋል።” ( ተመልከት) የመንግስ ልጆች “የ. . . ልጆች” የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው የእርሱ የሆኑት ፤ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔር መንግስት የሆኑት ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ሥፍረ ምጸታዊ ንግግር አለ ምክንያቱም እንግዶች ወደ መንግስቱ እንዲገቡ ሲደረግ “ልጆች” ወደ ውጪ ይጣላሉ። ኤቲ: “እግዚአብሔር ይገዛቸው ዘንድ የፈቀዱለት”። ( እና ተመልከት) ወደ ውጭ ጨለማ ይህ እግዚአብሔርን ያልተቀበሉት ዘላለማዊ መዳረሻቸው ምን እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ኤቲ: “ከእግዚአብሔር የራቀ ጨለማ ሥፍራ” ወይም “ስኦል”። ( ተመልከት) ለእናንተ ይሆን ዘንድ ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ለእናንተ አደርገዋለሁ።” ( ተመልከት) ባሪያው ተፈወሰ ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ኢየሱስ ባሪያወን ፈወሰ።” ( ተመልከት) በዚያው ሰዓት “ኢየሱስ ባሪያውን እፈውሰዋለሁ ብሎ በተናገረበት ቅጽበት”
Matthew 8:14
ማቴዎስ 8:14-15
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ጸሐፊው ታሪኩን ወደ ሌላ ጊዜ እና ቦታ በመቀየር ኢየሱስ ሌላ ሰው የፈወሰበትን ሁኔታ ያሳየናል። ኢየሱስ መጥቶ ደቀ መዛሙርቱ ምናባት ከእርሱ ጋር ልሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን የታሪኩ ዋና ትኩረት ኢየሱስ ስላደረገው እና ሰስለተናገረው ነገር ነው። በዚህ ሥፍራ ደቀ መዛሙርቱን የጠቀሰበት ምክንት የተሳሳተ ትርጉም እንዳይኖር በማለት ነው። የጴጥሮስ አማች “የጴጥሮስ ምስት እናት” ንዳዱ ትቷት ሄደ በቋንቋችሄ እንዲህ ያለ ሰውኛ የአጻጻፍ ስልት ማለትም ንዳድ በራሱ አስቦ አንድን ነገር እንደሚፈጽ የሚሳይ ሰውኛ የአነጋገር ስልት ካለ “ተሸለት” ወይም “ኢየሱስ ፈወሳት” ተብሎ ልተረጎም ይችላል። ( ተመልከት) ተነስታ “ከተኛችበት አልጋ ተነስታ”
Matthew 8:16
ማቴዎስ 8:16-17
አያያዥ ዓረፍተ ነገር› በዚህ ሥፍራ የታሪኩ ፍሰት በዚያው ቀን ምሽት ላይ ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን ወደ ፈወሰበት እና ሴጣንን ከብዙ ሰዎች ወደአወጣበት ታርክ ይዞራል። አጠቃላይ መረጃ: በቁጥር 17 ላይ ጸሐፊው የኢየሱስ የፈውስ አገልግሎቱን በነብያት የተነገው ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን ከነብዩ ኢሳያስ መጽሐፍ ውስጥ በመጥቀስ ጽፏል። በመሸም ጊዜ ይህ ከሰንበት በኋላ መሆኑን ያሳያል ምክንያቱም አይሁዳዊየን በሰንበት ቀን ሥራ አይሠሩም ወይም መንገድ አይሄዱም። እስኪመሽ ድረስ ጠብቀው ሰዎችን ወደ ኢየሱስ አመጡ። የተሳሳተ ትርጉምን ከማስወገድ አንጻር ካልሆነ በስተቀር ሰንበት የሚለው ቃል መጥቀሱ አስፈላጊ አይደለም። ( ተመልከት) በዳብሎ የተያዙ ብዙ ሰዎችን ወደ እርሱ አመጡ ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ብዙ በዳብሎስ የተያዙ” (UDB) ወይም “በዳብሎስ ቁጥር ሥር የሆኑ ብዙ ሰዎች” ( ተመልከት) በቃሉ መናፍስቱን አስወጣ በዚህ ሥፍራ “ቃል” የሚለው ቃል ትርጉሙ ትዕዛዝ ነው። ኤቲ: “መንፈሱ እንዲወጣ አዘዘ።” ( ተመልከት) በነብይ ኢሳያስ የተነገረው ትንቢትን ይፈጽም ነበር ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ነብዩ ኢሳያስ ለእስራኤል ሕዝብ የተናገረው የትንቢት ቃልን ኢየሱስ ፈጸመው። () ተመልከት) ድካማችን ተቀበለ ደዊያችንንም ተሸከመ ማቴዎስ ከነብዩ ኢሳያስ መጽሐፍ በዚህ ሥፍራ ላይ ጠቅሷል። እነዚህ ሁለቱ ሀረጋት በመሠረታዊ መልዕክታቸው ተመሳሳይ ናቸው። ሁለቱም አጽኖት የሚሰጡት እርሱ ሁሉንም በሽታችንን ፈውሷል። ኤቲ: “የታመሙትን ፈውሷል እንዲሁም ደና አድርጓቸዋል። ( ተመልከት)
Matthew 8:18
ማቴዎስ 8:18-20
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ ታሪኩ ኢየሱስ ልከተሉት ለሚፈልጉ ሰዎች የሰጠው ምላሽ ምን እንደሆነ ወደማሳየት ይሄዳል። አሁን በዚህ ሥፍራ ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በዋናው ታርክ ውስጥ አዲስ ታሪክ መጀመሩን ለማሳየት ነው። ማቴዎስ በዚህ ሥፍራ ላይ የታሪኩን አዲስ ክፍል ይነግረናል። መመሪያዎች ሰጠ “ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው” ከዚያ ማለትም ኢየሰስ “መመሪያዎችን ከሰጠ በኋላ ነገር ግን ወደ ታንኳይቱ ከመግባቱ በፊት በዬትም ሥፍራ “በዬትኛውም ቦታ” ቀበሮዎች ጉድጓድ አላቸው እንዲሁም የሰማይ ወፎች ጎቾ አላቸው ቀበሮዎች ቀበሮዎች እንደ ውሻ ያሉ እንስሳት ናቸው። በጎጆዋቸው ውስጥ ያሉትን አእዋፋት እና ሌሎች ትንንሽ እንስሳትን ይበላሉ። ቀበሮዎች በእናንተ ዙሪያ የማይታወቁ ከሆነ እንደ ውሻ ያለ በማለት አጠቃላይ ቃልን ተጠቀሙ። ( ተመልከቱ) ጉድጋዶች ቀበሮዎች ለመኖሪያቸው የሚሆን ጉድጓድን ይቆፍራሉ። ቀበሮወችን ለማመልከት የተጠቀማችኋቸው እንስሳት የሚኖሩበትን ሥፍራ ግለጹ። የሰው ልጅ ኢየሱስ ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። ( ተመልከት) ራሱን የሚያሳርፍበት ሥፍራ ይህ የመተኛ ሥፍራን ያመለክታል። ኤቲ: “የሚተኛበት የራሱ ሥፍራ የለውም።” ( ተመልከት)
Matthew 8:21
ማቴዎስ 8:21-22
በመጀመሪያ አባቴን እንድቀብረው ፍቀድልኝ የሰውዬው አባት መሞቱን እና ወዲያው መቅበር እንዳለበት በእርግጠኝነት ማወቅ አይቻልም ወይም አባቱ እስኪሞት እና እስኪቀበር ድረስ ለረጅም ጊዜ መቀየት ይኖርበት አይኖርበት የሚታወቅ ነገር የለም። ዋናውን ነጥብ ይህ ሰው ኢየሱስን ከመከተሉ በፊት ሌላ አዲስ ነገር ማድረግ ይፈለጋል ማለት ነው። ሙታን ሙታናቸውን ይቀብሩ ዘንድ ተዋቸው በዚህ ሥፍራ ላይ ኢየሱስ በቀጥታ የሞቲ ሰዎች ሌሎች የሞቱትን ይቅበሩ ማለቱ አይደለም። “ሙታን” የሚለው ቃል አማራጭ ትርጉሞች 1) በቅርብ ጊዜ ስለሚሞቱ ሰዎች የሚነገር ምሳሌያዊ አነጋገር ወይም 2) ኢየሱስን የማይከተሉ እና መንፈሳዊ ሞት የሞቱ ሰዎችን ለማመልከት የሚውል ሚሳሌያዊ አነጋገር። ዋናው ነጥብ ማንኛውም ኢየሱስን መከተል ለሚወድ ሰው ምንም ነገር ሊያዘገየው አይገባም። ( ተመልከት)
Matthew 8:23
ማቴዎስ 8:23-25
አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ የታሪኩ ፍሰት ኢየሱስ እና ደቀ መዛሙር የገሊላን ባሕር ሽሻገሩ የተነሳውን ማዕበል ኢየሱስ እንዴት ጸጥ እንዳደረገው ወደሚያሳይ ታሪክ ይለወጣል። ወደ ታንኳይቱ ገቡ “ወደ ተንኳ ገቡ” ደቀ መዛሙርቱ ተከተሉት ለ”ደቀ መዛሙር” እና “ተከተል” ለሚለው ቃል በ([MAT 8:21-22]()). ላይ የተጠቀምከውን ተመሳሳይ ቃላትን ተጠቀም። እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይራል። ኤቲ: “በድንገት”(UDB) ወይም “ያለምንም ማስጠንቀቂያ” ባሕሩም በታላቅ ማዕበል ተናወጠ ኤቲ: “ታላቅ ማዕበል ባሕሩን አናወጠው” በዚህም ምክንያት ታንኳይቱን ውሃ ሞላት ይህ እንዲህ ልገለጽ ይችላል። ኤቲ: “ስለዚህም ምክንያት ታንኳይቱን ውሃ ሞላት”። ( ተመልከት) ተነስ አድነን አሉት የዚህ ሀረግ አማራጭ ትርጓሜዎች 1) በመጀመሪያ ኢየሱስን ከተኛት ቀስቅሰው “አድነን” አሉት ወይም 2)ኢየሱስን እየቀሰቀሱት “አድነን” አሉት። እኛ . . . እኛ ይህ ቃል ሁሉን የሚያጠቃልል ወይም የማያጠቃልል አድርገን የሚንተረጉመው ከሆነ ሁሉን የሚያጠቃልል ቃልን ብንጠቀም መልካም ይሆናል። ደቀ መዛሙርቱ ምናልባት ኢየሱስ እነርሱን እና ራሱን ከትንኳይቱ መስጠም እንዲታደግ ያቀረቡት ጥያቄ ሊሆን ይችላል። ( ተመልከት) መሞታችን ነው “ልንሞት ነው”
Matthew 8:26
ማቴዎስ 8: 26-27
ለእነርሱ “ለደቀ መዛሙርቱ” ለምን ፈራችሁ . . . እምነት? ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጥያቄ በመጠየቅ ይገስጻቸዋል። ኤቲ: “ልትፈሩ አይገባም . . እምነት” ወይም “የምትፈሩበት አንዳች ምክንያት የለም . . . እምነት።” ( ተመልከት) እናንተ ትንሽ እምነት ያላችሁ ይህንን በ MAT 6:30 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። ንፋስን እና ባሕር የሚታዘዙለት ይህ ምን ዓይነት ሰው ነው? “ንፋስና ባሕር ይታዘዙታል! ምን ዓይነስ ሰው ነው? ይህ የደቀ መዛሙርቱን አግራሞት የሚያሳይ ጥያቄ ነው። ኤቲ: “ይህ ከሌሎች ሰዎች ሁሉ የተለየ ነው! ንፋስ እና ማዕበል ሳይቀር ይታዘዙታል!” ( ተመልከት) ንፋስ እና ባሕር ሳይቀር ይታዘዙታል ሰዎች ወይም እንስሳት ቢታዘዙት ወይም ባይታዘዙት ብዙም አያስደንቅም ነገር ግን ንፋስ እና ውሃ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እርሱን መታዘዛቸው በጣም አስደናቂ ነገር ነው። ይህ በሰውኛ የቀረበው ሀሳብ ተፈጥሮአዊ ነገሮች ልክ እንደ ሰው ሰምተው ምላሽ መስጠጥ ይችላሉ።
( ተመልከት)

Matthew 8:28

ማቴዎስ 8:28-29

አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ ጸሐፊው ከዚህ በፊት ወደ ጀመረው ኢየሱስ በሽተኞችን ወደሚፈውስበት አገልግሎት ታሪኩ ተመልሶ እናገኘዋለን። በዚህ ታሪክ ውስጥ መጀመሪያ ላይ ኢየሱስ ሁለት በዲብሎስ እስራት ተይዘው የነበሩትን ሰዎች ነጻ ሲያወጣ እንመለከታለን። በዚያኛው በኩል "ከገሊላ ባሕር ማዶ" የጌርጋሴኖን ሀገር ጌርጋሴኖን የጌርጋ ከተማ ስም ነው። ( ተመልከት) እነርሱም ሰው በዚያ መንገድ ማለፍ እስኪሳነው ድረስ በጣም አስቸጋሪዎች ነበሩ እነዚህን ሁለት ሰዎችን የያዙት ዲብሎሶች በጣም አደገኞች ከመሆናቸው የተነሳ ማንም ሰው በዚያ በኩል ማለፍ አይችልም ነበር። እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይራል። የእግዚአብሔር ልጅ ከአንተ ጋር ምን አለን? ይህንን ጥያቄ የጠየቁት በቁጣ ነበር። ( ተመልከት) የእግዚአብሔር ልጅ ይህ ኢየሱስ ከእግዚብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ መጠሪያ ስሙ ነው። ( ተመልከት) ጊዜው ሳይደርስ ልትሣቅየን ወደዚህ መጣህን? ሁለተኛው ጥያቄም ሰላማዊ የሆነ ጥያቄ አልነበረም። ትረጉሙም "እግዚአብሔር እኛን ለመቅጣት የወሰነው ጊዜ ሳይደርስ መጥተህ እኛን በመቅጣት እግዚአብሔርን መታዘዝ መተው የለብህም።" ( ተመልከት)

Matthew 8:30

ማቴዎስ 8:28-29

አያያዥ ዓረፍተ ነገር በዚህ ሥፍራ ላይ ጸሐፊው ከዚህ በፊት ወደ ጀመረው ኢየሱስ በሽተኞችን ወደሚፈውስበት አገልግሎት ታሪኩ ተመልሶ እናገኘዋለን። በዚህ ታሪክ ውስጥ መጀመሪያ ላይ ኢየሱስ ሁለት በዲብሎስ እስራት ተይዘው የነበሩትን ሰዎች ነጻ ሲያወጣ እንመለከታለን። በዚያኛው በኩል "ከገሊላ ባሕር ማዶ" የጌርጋሴኖን ሀገር ጌርጋሴኖን የጌርጋ ከተማ ስም ነው። ( ተመልከት) እነርሱም ሰው በዚያ መንገድ ማለፍ እስኪሳነው ድረስ በጣም አስቸጋሪዎች ነበሩ እነዚህን ሁለት ሰዎችን የያዙት ዲብሎሶች በጣም አደገኞች ከመሆናቸው የተነሳ ማንም ሰው በዚያ በኩል ማለፍ አይችልም ነበር። እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይራል። የእግዚአብሔር ልጅ ከአንተ ጋር ምን አለን? ይህንን ጥያቄ የጠየቁት በቁጣ ነበር። ( ተመልከት) የእግዚአብሔር ልጅ ይህ ኢየሱስ ከእግዚብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ መጠሪያ ስሙ ነው። ( ተመልከት) ጊዜው ሳይደርስ ልትሣቅየን ወደዚህ መጣህን? ሁለተኛው ጥያቄም ሰላማዊ የሆነ ጥያቄ አልነበረም። ትረጉሙም "እግዚአብሔር እኛን ለመቅጣት የወሰነው ጊዜ ሳይደርስ መጥተህ እኛን በመቅጣት እግዚአብሔርን መታዘዝ መተው የለብህም።" ( ተመልከት)
አሁን ይህ ቃል ጸሐፊው የታሪኩን ቀጣይ ክፍል ከመተረኩ በፊት አንባቢዎቹ ማወቅ ያለባቸውን አንድ መረጃ እንደሚሰጣቸው ያሳያል። ኢየሱስ ወደዚያ ሥፍራ ከመምጣቱ በፊት አሳማዎች በዚያ ሥፍራ ነበሩ። ( ተመልከት) ካስወጣኸን ኤቲ፡ "ልታስወጣን ስለሆነ" እኛ ይህ ሁሉን አቀፍ ነው፤ ትርጉሙም ለአሳማዎች ብቻ ነው። ( ተመልከት) እነርሱ በሰውዬው ውስጥ ያለው እርኩስ መንፈስ እርኩስ መንፈሱም ከሰውዬው ውስጥ ወጥቶ ወደ አሳማዎቹ ገባ ኤቲ፡ "እርኩስ መንፈሱም ከሰውዬው ውስጥ ወጥቶ ወደ አሳማዎቹ ገባ" እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይራል። ከተራራው አፋፍ ወደታች ሮጡ ኤቲ፡ "በፍጥነት ከተራራው አናት ወደታች ሮጡ" በውሃ ውስጥ ሞቱ ኤቲ፡ "በውሃ ውስጥ ወድቀው ሰመጡ"

Matthew 8:33

ማቴዎስ 8:33-34

አያያዥ ዓረፍተ ነገር ይህ ኢየሱስ በእርኩስ መንፈስ የተያዙ ሁለት ሰዎችን ኢየሱስ የፈወሰበት ታሪክ ማጠቃለያ ነው። አሳማዎች የሚያሰማሩ "አሳማዎችን የሚጠብቁ" በእርኩስ መንፈስ የተያዙት ሰዎች ምን እንደሆኑ ኤቲ፡ "በእርኩስ መንፈስ የተያዙትን እነነዚህ ሰዎች ለማገዝ ኢየሱስ ያደረገው ነገር" እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይራል። በሁሉም ከተሞች ይህ ማለት ብዙ ወይም አብዛኞቹ ሰዎች ማለት እንጂ ሁሉም ሰዎች ማለት የግድ አይደለም። ( ተመልከት) አከባቢ ኤቲ፡ "ከተማዋ እና በአካቢው ያሉት"

Chapter 9

Matthew 9:1

ማቴዎስ 9:1-2

ማቴዎስ 9:1-2 አያያዥ ዓረፍተ ነገር ጸሐፊው በ MAT 8:1 የጀመረው ኢየሱስ ሰዎችን ከበሽታ የፈወሰበትን ታሪክ እንደገና ወደ መተረክ ተመልሷል። በዚህ ታሪክ ውስጥ ኢየሱስ ሽባውን ሰው እንዴት እንደፈወሰው ይተርካል። ኢየሱስ ወደ ታንኳይቱ ገባ ደቀ መዛሙርቱም ከእርሱ ጋር ሄደው ሊሆን ይችላል። ታንኳ ይህ ምናልባት በ MAT 8:23 ላይ የተገለጸው ታንኳ ሊሆን ይችላል። ግራ መጋባትን ለማስወገድ ከፈለግህ ብቻ ይህንን መግለጽ ትችላለህ። ወደ ገዛ ከተማው መጣ ኤቲ፡ "ወደመከኖርበት ከተማ" (UDB) እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይኖራል። እነርሱ . . . እነርሱ ይህ ሽባውን ሰው ወደኢየሱስ ያመጡትን ሰዎች ያመለክታል። ሽባውንም ሰው ሊያመለክት ይችላል። ልጅ ይህ ሰው በእርግጥ የኢየሱስ ልጅ አይደለም። ኢየሱስ በዚህ ሥፍራ ላይ በትህትና እያናገረው ነው። ይህ ሰዎችን ግራ የሚያጋባ ከሆነ እንዲህ በማለት ሊትተረጉመው ተትችላለህ "ወዳጄ ሆይ" ወይም "አንተ ጎበዝ" ወይም ከተውኑ ልትተው ትችላለህ። ኃጢአትህ ተሰሪያልሃለች ኤቲ፡ "እግዚአብሔር ኃጢአትህን ሠሪዮልሃል" ወይም "ኃጢአትን ሠሪዬልሃለሁ" ( ተመልከት)

Matthew 9:3

ማቴዎስ 9:3-6

እነሆ ይህ በትልቁ ታሪክ ውስጥ የአንድ አዲስ ነገር ጅማሬ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው። በቋንቋችሁ ውስጥ ይህንን ማሳየት የሚቻልበት መንገድ ይኖራል። ከእነርሱ መካከል ይህ "ለእነርሱ ለራሳቸው" "በመካከላቸው" ወይም "እርስ በእርሳቸው"፣ "በራሳቸው አፍ" እግዚአብሔርን ይሳደባል እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችላቸው ነገሮች ኢየሱስ ማድረግ እችላለው እያለ ነው። የልባቸውን ሀሳብ አውቆ ኢየሱስ ሀሳባቸውን ያወቀው በልዕለ ተፈጥሮ ኃይል አማካኝነት ነው ወይም እርሱ በእርሳቸው ስነጋገሩ ተመልክቶ ነው። በልባችሁ ስለምን ክፋትን ታስባላችሁ? ኢየሱስ ይህንን የተናገረው ጸሐፊትን ለመገሰጽ ነው። ( ተመልከት)
ለራሳቸው እንዲህ ብለው አሰቡ እያንዳንዱ ጸሐፍት ለራሳቸው እንዲህ ብለው አሰቡ፤ ይሁን እንጂ እርስ በእርሳቸው አልተነጋገሩም። በልባችሁ ስለምን እንዲህ ታስባለህ? ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ የጠየቀበት ምክንያት ጸሐፍት የእርሱን ሥልጣን በመጠራጠራው ነው። አማራጭ ትርጓሜ: "ሥልጣኔን መጠራጠር የለባችሁም!" ልባቸውም ይህ "ልብ" የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ የሰዎችን አመለካከት፣ ስሜት፣ ፍላጎት ወይም ፈቃድ ለማመልከት ነው። ዬትኛው ይቀላል . . . . ሂድ? ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ጸሐፍት ሰውዬው ሽባ የሆነው በኃጢአቱ ምክንያት ነው የሚል እምነት ነበራቸው። ሰውዬው ኃጢአቱ ይቅር ከተባለለት መራመድ ይችላሉ። ኢየሱስ ሽባውን ሰው ከፈወሰው ጸሐፍት ኢየሱስ ኃጢአትን የማስተሰረይ እንደሚችል ልቀበሉ ይገባቸዋል ማለት ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “ሽባውነን ሰው ኃጠአትህ ተሰረየችልህ ማለት ቀላል ነው!”
Mark 2:10
ማርቆስ 2:10-12
ይህንን ታውቁ ዘንድ "ይህንን አረጋግጥላችኋለሁ" የሰው ልጅ በዚህ ሥፍራ ላይ ራሱን “የሰው ልጅ” በማለት ይጠራል። እናንተ ጸሐፍት እና ሕዝቡ ለሽባው ሰው እንዲህ አለው "መራመድ ለማይችለው ሰው እንዲህ አለው" በሁሉም ሰዎች ፊት "በዚያ ሥፍራ በተሰበሱት ሰዎች ዐይን ፊት”
Mark 2:13
ማርቆስ 2: 13-14
ሕዝቡም ወደ እርሱ መጥተው "ሕዝቡም እርሱ ወደአለበት ሥፍራ መጥተው"
Mark 2:15
ማርቆስ 2:15-16
የሌዊ ቤት "የሌዊ ቤት" በጣም ብዙ ሰዎች የከተሉት ስለነበር ከብዙ ቀራጮች እና ኃጢአተኞች ጋር ኢየሱስ እና የእርሱ ደቀ መዛሙርት ጋር ምግብ ይበሉ ነበር። "ኢየሱስን ይከተሉት የነበሩት ብዙ ቀራጮች እና ኃጢአተኛ ከእየሱስ እና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ምግብ ይበሉ ነበር።" ከቀራጮች እና ከኃጢአተኞች ጋር ስለምን ይበላል? ጸሐፍት እና ፈሪሳዊያን ይህንን ጥያቄ የጠየቁት የኢየሱስን ከሁሉም ጋር መሆንን ትክክል አለመሆን ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጓሜ: ቀረጥ ከሚሰበስቡ ኃጢአተኛ ሰዎች ጋር መብላት እና መጠጣት የለበትን!"
Mark 2:17
ማርቆስ 2:17-17
እንዲህ አላቸው "ለፈሪሳዊያን እንዲህ አላቸው" ጤነኛ የሆኑ ሰዎች ሐኪም አያስፈልጋቸውም፤ ሐኪም የሚያስፈልጋቸው በሽተኞች ብቻ ናቸው ኢየሱስ በዚህ ሥፍራ ላይ ኃጢአተኛ መሆናቸውን የሚያውቁ ሰዎችን መታመማቸውን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጓሜ: "ጻድቃን እንደሆኑ የሚያስቡ ሰዎች እገዛ አይፈልጉም፤ መታመማቸውን የሚያውቁ ሰዎች ብቻ ናቸው ከሌሎች እገዛ የሚፈልጉት! እኔ ጻድቅ የሆኑትን ሰዎች ለመጥራት አልመጣሁም። ይልቁንም ኃጢአተኛ የሆኑ ሰዎችን ለመጥራት ነው የመጣሁት። ኢየሱስ የመጣው እነዛን ለሚሹ ሰዎች መሆኑን አድማጮቹ እንዲገነዘቡ ይፈልጋል። ለትርጓሚዎች ምክር: "የመጣሁት ኃጢአተኞች መሆናቸውን ለተገዘነቡ ሰዎች እንጂ ራሳቸውን ጻድቅ አድርገው ለሚቆጥሩ ሰዎች አይደለም።"
Mark 2:18
ማርቆስ 2: 18-19
ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ አይጾሙም መጾም ማለት ምግብ አለመብላት ማለት ነው። ጾም በማይጾምበት አከበቢ ባለ ቋንቋ ውስጥ አውንታዊ ዓረፍተ ነገሮችን መጠቀም የተሻለ ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “ይሁን እንጂ ደቀ መዛሙርትህ ያለማቋረጥ ይበለላሉ።” ሠርገኞች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ይጾናሉን? ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ እርሱን እና ደቀ መዛሙርቱን ከሙሽራ እና የእርሱ ጓደኛ ጋር ለማነጻጸር ተጠቅሞበታል። አማራጭ ትርጓሜ: “እኔ ከእነርሱ ጋር እስካለሁ ድረስ ደቀ መዛሙርቴ በእዚህ ደስ ይላቸዋል።
Mark 2:20
ማርቆስ 2:20-21
ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ዘመን ይመጣል ኢየሱስ ስለሞቱ፣ ትንሳዔው እና እርገቱ ስናገር ራሱን ከሙሽራ ጋር ያነጻጽራል። ቋንቋችሁ ዋነ ገጸባህርው ማን እንደሆነ መግለጽ የሚፈልገው ከሆነ በተቻለ መጠን ጠቅላል ባለ ቋንቋ ግለጸው። ለተርጓሚዎች ምክር: "ሙሽራውን ይወስዱታል" ወይም “ሙሽራው ከእነርሱ ይሄዳል።" እነርሱ . . . እነርሱ በሠርጉ ላይ የታደሙት ሰዎች ማንም አዲስ እራፍ ጨርቅን በአሮጌ ልብስ ላይ የሚጥፍ የለም አዲስ እራፍ ጨርቅን በአሮጌ ልብስ ላይ መጣፍ በአሮጌው ጨርቅ ላይ ያለውን ቀዳዳ ይበልጥ ያሰፋዋል ምክንያቱም አዲሱ ጨርቅ በቀላሉ አይተጣጠፍምና ነው። አዲሱ ጨርቅ እና አሮጌው ልብስ፣ ሁለቱም ይበላሻሉ።
Mark 2:22
ማርቆስ 2: 22 -22
ማንም አዲስን የወይን ጠጅ በአሮጌ አቆማዳ ውስጥ የሚያስቀምጥ የለም ኢየሱስ በዚህ ሥፍራ ላይ የእርሱ ትምህርት እነና የደቀ መዛሙርቱን ከአዲስ የወይን ጠጅ እና አቆማዳ ጋር አነጻጽረዋል።ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር “የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት እና የፈርሳዊያን ደቀ መዛሙረት ለምን እንደሚጾሙ ነገር ግን የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን ለምን አይጾሙም” ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል። አማራጭ ትርጓሜ:


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ማንም አዲስ ትምህርት ሌላ ልምምድ ውስጥ ውስጥ ላሉ ሰዎች አደራ ብሎ አይሰጥም።" አዲስ የወይን ጠጅ "የወይን ፍሬ ጁስ"። ይህ ገና ያልፈለ፣ አልኮል ያሌለው ወይንን ያሳያል። በአከባያችቹ የወይን ፍሬ የማይታወቅ ከሆነ ለፍራፍሬ መጠሪያ የሚሆን አጠቃላይ ቃልን ተጠቀሙ። አሮጌ አቁማዳ ይህ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለን አቁማዳ ያመለክታል። አቁማዳ ይህ ከእንስሳት ቆዳ የሚሠራ ከረጢት ነው። “አቁማዳ” ወይም “የቆዳ ከረጢት” ተብሎ ይጠራል "skin (UDB)። ወይኑ የቆዳውን ከረጢት ይቀደዋል አዲሱ ወይን ስፈለ እና ስገላበጥ ከዚያ በላይ መለጠጥ ስለማይችል ይቀደዋ። ይጠፋል "ይበላሻል" (UDB) አዲስ የወይን አቁማዳ "አዲስ የወይን አቁማዳ" ወይም “አዲስ የወይን መያዥያ”። ይህ ከዚህ በፊት ወይን ተይዞበት የማያውቅን የወይን አቁማዳን ያመለክታል።

Mark 2:23

ማርቆስ 2:23-24

እነሆ፣ በሰንበት ያልተፈቀደውን ስለ ምን ያደርጋሉ? አሉት። ፈርሳዊያኑ ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ኢየሱን ለመውቀስ ነው። አማራጭ ትርጓሜ: “ተመልከት! የአይሁድ ሕግ ስለ ስንበት የሚናገረውን ሕግ ይሽራሉ።" እሸት እየቀጠፉ ይበላሉ . . . በሰሰንት ያልተፈቀደውን ነገር ያደርጋሉ። በሌሎች ሰዎች ማሳ ውስጥ ያለን እሸት ቀጥፎ መብላት ስርቆት አይባልም ። ጥያቄው ይህንን በሰንበት ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይም አይደለም የሚል ነው። ይህንን ነገር እሼት እሸት ይህ የስንዴ ዘላላ ገና ሳይደርቅ ያለውን ያመለክታል። በዚህ የስንዴ ተክል እናት ላይ ፍሬዎቹ ይገኛሉ። ተመልከት "አሁን ለምነገር ነገር ትኩረት ስጥ"

Mark 2:25

ማርቆስ 2: 25-26

ዳዊት ባስፈለገውና በተራበ ጊዜ፣ እርሱ አብረውት ከነበሩት ጋር ያደረገውን፣ . . . አላነበባችሁምን? አላቸው። ኢየሱስ ጸሐፍት እና ፈርሳዊያን ታሪኩን ከዚህ በፊት ማንበባቸውን ያውቃል። ይሁን እንጂ ሆን ብለው ታሪኩ ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በትክክል አልተረዳችሁትም በማለት ኢየሱስ ይከሳቸዋል። አማራጭ ትርጉሞች: “ዳዊት እና ከእርሱ ጋር የተነበሩት ሰዎች ያደረገጉትን አስታውሱ . . . ይህንን እንዳደረገ ታውቃላችሁ" አብያተር በአይሁድ ታሪክ ውስጥ ዳዊት በኖረበት ዘመን ከነበሩት ሊቀ ካህናት መካከል አንዱ ነው። እርሱ እንዴት ወደ እግዚብሔር ቤት እንደገባ "ዳዊት ወደ እግዚአብሔር ቤር ገብቶ" (UDB)

Mark 2:27

ማርቆስ 2: 27-28

ሰንበት ስለ ሰው ተፈጥሮአል አማራጭ ትርጓሜ: "እግዚአብሔር ሰንበትን የፈጠረው ለሰው ልጆች መልካምነት ነው" እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም፤ አማራጭ ትርጓሜ: "እግዚአብሔር ሰውን ለሰንበት መልካምነት አልፈጠረውም"

Chapter 3

Mark 3:1

ማርቆስ 3።1-2

ኢየሱስ ወደ ምኩራብ ገባ "ኢየሱስ ወደ ምኩራብ ገባ " እጁ የሰለለች ሰው "እጁ ሽባ የሆነችበት ሰው ነበር" ይህንን ሰው ይፈውሰው እንደሆነ ለማየት ይከታተሉት ነበር "ፈርሳዊያን ኢየሱስ ይህንን ሰው ይፈውሰው እንደሆነ ለማየት ይከታተሉት ነበር"

Mark 3:3

ማርቆስ 3:3-4

ተነሣና በሁሉም መካከል ቁም "ተነሣና በዚህ ሕዝብ መካከል ቁም።" ለመግደል . . . ተፈቅዷልን? ጸሐፊው “ሁሉም ዝም ማለታቸውን” ስለገለጸልን ኢየሱስ እነርሱን መጠየቁን እና መልስ እንዲሰጡት እየተጠበቀ እንደሆነ እንመለከታለን። ለተርጓሚዎች: "በሰንበት መልካም ነገርን ማድረግ ወይም መጉዳት ነው የተፈቀደው፤ ነፍስ ማዳን ወይስ መግደል።” በሕግ የተፈቀደው በሙሴ ሕግ መሠረት

Mark 3:5

ማርቆስ 3:5-6

እጅህን ዘርጋ "እጅህን ዘርጋ" ኢየሱስ የሰውዬውን እጅ ፈወሰ "ኢየሱስ እጁን አዳነ" ወይም "ኢየሱስ የሰውዬውን እጅ ከዚህ በፊት እንደነበረው ደህና አደረገለት" ከሄሮድስ ወገን ጋር ተማከሩበት። አማራጭ ትርጓሜ: "ከሄሮዶስ ወገን ከሆኑት ጋር ተሰበሰቡ" ወይም "ከሄሮዶስ ወገን ከሆኑት ጋር ተሰብስበው እቅድ አወጡ"

Mark 3:7

ማርቆስ 3፡ 7-8

ማደረገውን ነገር ሁሉ ሰማ "ኢየሱስ ስላደረገው ታላላቅ ተአምራት ሁሉ ሰማ" ወደ እርሱም መጥተው "ሕዝቡም ወደ ኢየሱስ ወደአለበት መጥተው"

Mark 3:9

ማርቆስ 3፡ 9-10

ለደቀ መዛሙርቱ ጀልባ ያዘጋጁለት ዘንድ ጠየቃቸው "ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፡ ጀልባ አዘጋጁልኝ።" የሕዝቡ ተጽእኖ እጅግ በጣም ከባድ ነበር። "ሕዝቡ እርሱን ለመንካት ወደፊት ይጋፉ ነበር" (UDB) ችግር ያለባቸው ሁሉ እርሱን ለመንካት ይጋፉ ነበር "የታመሙ ሁሉ እርሱን ለመንካት ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ስለነበር እርስ በእርሳቸው ይገፋፋሉ"

Mark 3:11

ማርቆስ 3፡ 11-12

እነርሱ . . . እነርሱ . . . እነርሱ በእርኩሳን መናስፍት ቁጥጥር የሆኑት ሰዎች አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ኢየሱስ በእርኩሳን መናስፍት ላይ ያለው ስልጣን ተያያዥነቱ “የእግዚአብሔር ልጅ1,” ከሚለው የእርሱ የማዕረግ ስም ጋር ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ይህ ወሳኝ የሆነ የኢየሱስ የማዕረግ ስም ነው።

Mark 3:13

ማርቆስ 3፡ 13-16

ከእርሱ ጋር ይሆኑ ዘንድ እንዲሁም ወንጌልን እንዲሰብኩ ይልካቸው ዘንድ ነው “ከእርሱ ጋር ይሆኑ ዘንድ እንዲሁም ወንጌልን እንዲሰብኩ ይልካቸው ዘንድ ነው” ወይም ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ እና ወንጌልን እንዲሰብኩ እንዲልካቸው" (UDB)

Mark 3:17

ማርቆስ 3፡ 17-19

ታዴዎስ "ታዴዎስ" የኢየሱስ 12 ሐዋርያት ይሆኑ ዘንድ ከተመረጡት ሰዎች መካከል አንዱ ነው።

Mark 3:20

ማርቆስ 3:20-22

እንደገናም ብዙ በጣም ብዙ ሰዎች ከመሰብሰባቸው የተነሳ ምግብ እንኳ ለመብላት አልቻሉም ነበር። "በጣም ብዙ ሕዝብ እንደገና ከመሰብሰቡ የተነሳ ምግብ ለመብላት እንኳ ጊዜ አላገኙም ነበር ወይም" ወይም "እርሱ በሚቆይበት ሥፍራ ላይ እንደገና ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ። በእርሱ ዙሪያም በጣም ብዙ ሰዎች ነበሩ። እርሱ እና የእርሱ ደቀ መዛሙርት ምግብ ለመብላት በቂ ጊዜ እንኳ ማግኘት አልቻሉም።" (UDB) እርሱን ለመያዝ መጡ የእርሱ ቤተሰብ አባላት ወደ ቤት መጥተው ለመያዝ እና እነርሱ ጋር ወደ ቤት በጉልበት እንዲሄድ መጡ።

Mark 3:23

ማርቆስ 3፡ 23-25

ሴጣን እንዴት ሴጣንን ልያስወጣ ይችላል? "ሴጣን ራሱን ማስወጣት አይችልም" ወይም "ሴጣን የራሱ በሆኑት እርኩሳን መናስፍት ተቃራኒ አይሆንም"

Mark 3:26

ማርቆስ 3፡ 26-27

Mark 3:28

ማርቆስ 3፡ 28-30

Mark 3:31

ማርቆስ 3፡ 31-32

መልዕክተኛ ወደእርሱ ዘንድ ሰደዱና አስጠሩት። "የኢየሱስ እናት እና ታናሽ ወንድሙ አንድ ሰው ወደ ቤቱ ውስጥ ልከው እነርሱ በውጪ እንደሚገኙ ለኢየሱስ ይናገርውና ውጪ ወጥቶ እንዲያናግራቸው ይነግረው ዘንድ መልዕክተኛ ላኩበት።"

Mark 3:33

ማርቆስ 3:33-35

በውስጧ ተቀመጠ "ወደ ተንኳይቱ ገብቶ ተቀመጠ"

Chapter 4

Mark 4:1

ማርቆስ 4:1-2

እናም ወደ ባሕሩ ውስጥ ገፏት “እናም ተንኳይቱን ወደ ባሕሩ ውስጥ ገፏት

Mark 4:3



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ማርቆስ 4:3-5
አደጉ "በፍጥነት ማደግ ጀመሩ"
Mark 4:6
ማርቆስ 4:6-7
ጠቀለጉ "ተቃጠሉ"
Mark 4:8
ማርቆስ 4፡ 8-9
የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ "በጥሞና የሚሰማ ሰው የዚህን ነገር ትርጉም በሚገባ ይረዳል"።
Mark 4:10
ማርቆስ 4፡ 10-12
ለእናንተ ተሰጥቶዋችኋል "እግዚአብሔር ሰጥቶዋችኋል" ወይም "እኔ ሰጥቼአችኋዋለሁ" ያያሉ ግን አያስተውሉም "ይመለከታሉ ነገር ግን ለማስተዋል አይፈልጉም" ወይም "ይመለከታሉ ግን አይረዱም"
Mark 4:13
ማርቆስ 4፡ 13-15
ይህንን ምሳሌ ተረድታችሁታልን? እንዲህ ከሆነ እንዴት ሌሎችን ምሳሌው መረዳት ትችላላችሁ? "የዚህን ምሳሌ ትርጉም መረዳት የማትችሉ ከሆነ የተቀሩትን ምሳሌዎችንም መረዳት አትችሉም።"
Mark 4:16
ማርቆስ 4፡ 16-17
Mark 4:18
ማርቆስ 4፡ 18-20
የዚህ ዓለም ሀሰብ አማራጭ ትርጉም: "አሁን ስላለው ሕይወት ግድ የሚላቸው" የባለጠግነት ምኞት አማራጭ ትርጉም: "እርካታ የማይሰጡት በሀብት የሚገኘው ደስታ" የሌሎች ነገሮች ምኞች "ከሀብት ውጪ ያሉት ሌሎች መሻቶች"
Mark 4:21
ማርቆስ 4፡ 21-23
መብራትን ከእንቅብ ወይም ከአልጋ በታች ለማኖር ወደ ቤት ውስጥ ያመጡታልን? "መብራትክ ከእንቅብ ወይምከአልጋ በታች ለማኖር በእርግጠኝነት ወደ ቤት ውስጥ አታመጡም።" የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ ይህንን በ MRK 4:9 ላይ በተረጎማችሁት መሠረት ትርጉሙት።
Mark 4:24
ማርቆስ 4፡ 24-25
በሠፈራችሁት መሥፈሪያ ልክ ትቀበላላችሁ፤ እንዲያው ከዚያ በላይ ታገኛላችሁ "የበለጠ ባደመጣችሁ ቁጥር እግዚብሔር የለልጥ መረዳትን ይሰጣችኋል።" ማንም . . . "ቃሌን የተረዳ ማንም ሰው ቢሆኖር።"
Mark 4:26
ማርቆስ 4፡ 26-29
ዘርን እንደሚዘራ ሰው "ዘሩን እንደሚዘራ ገበሬ" ማጭድ የእርሻ ምርት ለማጨድ የሚገለግል መሣሪያ
Mark 4:30
ማርቆስ 4፡ 30-32
"የእግዚብሔርን መንግስት ከምን ጋር እናነጻጽራታለን እንዲሁም በምን ምሳሌ እንገልጻታለን? "በዚህ ምሳሌ አማካኝነት የእግዚአብሔር መንግሰት ምን እንደሚትመስል ማስረዳት ይቻላል።
Mark 4:33
ማርቆስ 4፡ 33-34
ማድመጥ እስከቻሉ ድረስ "መረዳት እስከቻሉ ድረስ"
Mark 4:35
ማርቆስ 4፡ 35-37
Mark 4:38
ማርቆስ 4፡ 38-39
ስንጠፋ ግድ አይልህምን? "ለሁኔታው ትኩረት እንድትሰጠው እንፈልጋለን፤ ልንሞት ነው!" - ልንሞት ነው በዚህ ሥፍራ ላይ "እኛ" የሚለው ቃል ደቀ መዛሙርቱን እና ኢየሱስን የሚያካትት ነው። ገሰጸው "በቁጣ አስተካከለው" ወይም "መገሰጽ" ሠላም፣ ጸጥ በል። "ሠላም" እና "ጸጥ በል" ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ናቸው።
Mark 4:40
ማርቆስ 4፡ 40-41
እንዲህ የምትፈሩ ስለ ምን ነው? "በጣም በመፍራታችሁ በጣም አፍሬባችኋለሁ።" ይህ ማን ሊሆን ይችላል "ይህ ሰው ማን እንደሆነ በጥንቃቄ ልናሰብ ይገባናል!"

---

Chapter 5
Mark 5:1
ማርቆስ 5፡ 1-2
Mark 5:3
ማርቆስ 5፡ 3-4
እግሮቹ በሰንሰለት የታሠሩ "በሰንሰለት እግሮቹ የታሠሩ" እርሱን መያዝ "እርሱን መቆጣጠር"
Mark 5:5
ማርቆስ 5፡ 5-6
Mark 5:7
ማርቆስ 5፡ 7-8
ይጮኽ ነበር "እርኩስ መንፈሱ ይጮኽ ነበር" ከአንተ ጋር ምን አለኝ? አማራጭ ትርጉም: "ከአንተ ጋር ምንም ጉዳይ የለኝ" አታሰቃየኝ "አታዘቃየኝ" (UDB) የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ? በእግዚአብሔር በራሱ አምልሃለሁ እባክህ አታሰቃየኝ። “የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ” እርኩሳን መናፍስትን የማሰቃየት ኃይል አለው። የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ይህ የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ የማዕረግ ስሙ ነው።
Mark 5:9
ማርቆስ 5፡ 9-10
እርሱም እንዲህ አለው፣ "ስሜ ሠሰራዊት ነው፣ ምክንያቱም ብዙዎች ነን።" በሰውዬው ውስጥ ያሉት እርኩሳን መናፍስስት ለኢየሱስ እንዲህ አሉት፤ በዚህ ሰው ውስጥ ያለው አንድ እርኩስ መንፈስ ብቻ ሳይሆን ብዙ እርኩሳን መናፍስት ናቸው።
Mark 5:11
ማርቆስ 5፡ 11-13
እርሱም ፈቀደላቸው "ኢየሱስ ለእርኩሳን መናፍስቱ ፈቀደላቸው" ወደ ሁለት ሺህ አከባቢ የሚጠጉ አሳማዎች "ወደ 2000 አከባቢ የሚጠጉ አሳማዎች"
Mark 5:14
ማርቆስ 5፡ 14-15
ወደ አእምሮውም ተመለሰ "ወደ አእምሮው ተመለሰ"
Mark 5:16
ማርቆስ 5፡ 16-17
በእርኩስ መናፈስት ተይዞ የነበረውም ሰው "በእርኩሳን መናፍስት ቁጥጥር ሥር የነበረው ሰው"
Mark 5:18
ማርቆስ 5፡ 18-20
ዐሥር ከተሞች ከገሊላ በባሕር በደቡብ ምሥራቅ አከባቢ
Mark 5:21
ማርቆስ 5፡ 21-24
Mark 5:25
ማርቆስ 5:25-27
ለዐሥራ ሁለት ዓመታት "ለ 12 ዓመታት"
Mark 5:28
ማርቆስ 5፡ 28-29
Mark 5:30
ማርቆስ 5፡ 30-32
“አሁን የነካኝ ማን ነው?” ትላለህን አማራጭ ትርጉም: “በዚህ ግርግር ውስጥ ሆነህ ማን እንደነካህ መጠየቅህ በጣም አስገርሞናል”
Mark 5:33
ማርቆስ 5፡ 33-34
ሴት ልጅ ኢየሱስ ይህንን ቃል የተጠቀመው በምሳሌያዊ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ማሳየት የፈለገውም ይህች ሴት በእርሱ ማመኗን ነው።
Mark 5:35
ማርቆስ 5፡ 35-35
መምህሩን ከዚህ በላይ ለምን ታስቸግረዋለህ? አማራጭ ትርጉም: "መምህሩን

ከዚህ በላይ አታስቸግረው።"
Mark 5:36
ማርቆስ 5፡ 36-38
ሲንጫጩና ሲያለቅሱ በዚህ ሥፍራ ላይ “ሲንጫጩ” እና “ሲያለቅሱ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጓሜዎች አሏቸው። አማራጨ ትርጉም፡ "ሲያለቅሱ በታላቅ ድምፅ ይጮኹ ነበር"
Mark 5:39
ማርቆስ 5፡ 39-40
ስለምን ተቆጣችሁ፣ ስለምንስ ታለቅሳላችሁ? አማራጭ ትርጉም፡ "መንጫጫትም ሆነ ማልቀስ የለባችሁም።"
Mark 5:41
ማርቆስ 5፡ 41-43
የዐሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜ ነበራት "ዐሥራ ሁለት ዓመቷ ነበር" በጣም አስጠነቀቃቸው "አጥብቆ ነገራቸው"

Chapter 6
Mark 6:1
ማርቆስ 6፡ 1-3
ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ የያቆብም የዮሳም የይሁዳም የስምዖንም ወንድም አይደለምን? እኅቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን? አሉ፤ "እርሱ ተራ ጸራቢ ነው! እርሱ እና የእርሱን ቤተሰቦች እናውቃቸዋለን! እናቱ ማሪያምንም እናውቃታለን! ታናናሽ ወንድሞቹን እና ያዕቆን፣ የዩሳም፣ ይሁዳ እና ስምኦን እናውቃቸዋለን! እንዲሁም ታናሽ እህቱ ከእኛ ጋር በዚህ ትኖራለች!"
Mark 6:4
ማርቆስ 6፡ 4-6
ነቢይ ከ . . . ይከበራል "ሰዎች በእርግጠኝነት ሰዎች እኔን እንዲሁም ሌሎች ነቢያትን በሌሎች ሥፍራዎች ያከብራሉ ይሁን እንጂ በገዛ ሀገራችን ግን አይደለም! ዘመዶቻችን እና በገዛ ቤታችን ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች እንኳ ሳይቀሩ እኛን አያከብሩንም!"
Mark 6:7
ማርቆስ 6፡ 7-9
ሁለት ሁለት "2 በ 2" ወይም "በጥንድ" ሁለት እጀ ጠባቢ አትልበሱ "ተጨማሪ ከነቴራ አትያዙ።"
Mark 6:10
ማርቆስ 6፡ 10-11
ለቃችሁ እስኪትሄዱ ድረስ በዚያ ቆዩ "ከተማውን ለቃችሁ እስኪትሄዱ ድረስ በዚያው ቤት ውስጥ ቆዩ።"
Mark 6:12
ማርቆስ 6፡ 12-13
Mark 6:14
ማርቆስ 6፡ 14-15
መጥመቁ የሐንስ ከሞት ተንስቷል "እግዚአብሔር መጥመቁ የሐንስን ከሞት አስነስቶታል"
Mark 6:16
ማርቆስ 6፡ 16-17
የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት "የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት"
Mark 6:18
ማርቆስ 6፡ 18-20
ትጠላው ነበር "ትቃወመው"
Mark 6:21
ማርቆስ 6፡ 21-22
Mark 6:23
ማርቆስ 6፡ 23-25
በሣህን "በትሪ"
Mark 6:26
ማርቆስ 6፡ 26-29
ስለማለላት እና ለእንግዶቹ ሲል "ቃል ሲገባላት እንግዶቹ ስለሰሙት፣" በሣህን "በትሪ ላይ"
Mark 6:30
ማርቆስ 6፡ 30-32
Mark 6:33
ማርቆስ 6፡ 33-34
Mark 6:35
ማርቆስ 6፡ 35-36
Mark 6:37
ማርቆስ 6፡ 37-38
ሁለት መቶ ዲናር "200 ዲናር።" ዲናር የሮማዊያን ከመዳብ የተሠራ የመገበያያ ገንዘብ ነበር። አምስት እንጀራ እና ሁለት ዓሣዎች "5 እንጀራ እና 2 ዓሣዎች።" .
Mark 6:39
ማርቆስ 6፡ 39-41
በመቶ መቶዎች እና በሃምሳ ሃምሳዎች "100 የሚቆጠሩ እና 50 የሚቆጠሩ።" አምስት እንጀራ እና ሁለት ዓሣዎች "5 እንጀራ እና 2 ዓሣዎች።" .
Mark 6:42
ማርቆስ 6፡ 42-44
ዐሥራ ሁለት ቅርጫቶች "12 ቅርጫቶች" አምት ሺህ ወንዶች አማራጭ ትርጉም፡ "5,000 ወንዶች እና የእነርሱ ቤተሰቦች"
Mark 6:45
ማርቆስ 6፡ 45-47
ቤተሳይዳ ይህ ከገሊላ ባሕር በስተሰሜን በኩል የሚትገኝ ከተማ ናት።
Mark 6:48
ማርቆስ 6፡ 48-50
ከሌሊቱ አራተኛው ክፍል ይህ ከንጋቱ 9 ሰዓት እስከ ፀሐይ መውጫ ያለውን ጊዜ ያመለክታል። በርቱ!...አትፍሩ እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጥቅም ላይ የዋሉትም “እኔን አትፍሩ!” የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ነው”
Mark 6:51
ማርቆስ 6፡ 51-52
ይህንን አልተረዱም ነበር "መረዳት የነበራቸው ያኸል እርሱ ምን ያኸል ኃይለኛ እንደነበር አልተገነዘቡም ነበር።"
Mark 6:53
ማርቆስ 6፡ 53-55
ቃሬዛ "ሰዎችን ለመሸከም የሚሆን አልጋ"
Mark 6:56
ማርቆስ 6፡ 53-55
ቃሬዛ "ሰዎችን ለመሸከም የሚሆን አልጋ"

Chapter 7
Mark 7:1
ማርቆስ 7:1-1
Mark 7:2
ማርቆስ 7፡ 2-4
የናስ ዕቃዎች፣ እና የመመገቢያ ፍረሽን እንኳ ሳይቀር በዚያ ዘመን ይኖሩ የነበሩ አይሁዳዊያን ምግብ የሚመገቡት በፍራሽ ላይ ተቀምጠው ነበር። አማራጭ ትርጉሞች፡ “መያዥያዎች እንዲሁም የመመገቢያ መቀመጫዎች”
Mark 7:5
ማርቆስ 7፡ 5-5
ደቀ መዛሙርትህ ለምን እንደ ሽማግሌዎች ወግ አይኖሩም፣ ስለምንስ እጃቸውን ሳይታጠቡ ይበላሉ? "የአንተ ደቀ መዛሙርት የሽማግሌዎችን ወግ ይተላለፋሉ! የእኛን ሥርዓት በመጠቀም እጆቻቸውን መታጠብ አለባቸው!" ዳቦ ምግብ
Mark 7:6
ማርቆስ 7፡ 6-7
ስለእናንተ ግብዝነት ኢሳያስ በደንብ ትንቢትን ተናግሯል፡ እንዲህ ብሎም ጽፏል፡ ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ቃላት ኢሳያስ ከተናገራቸው የተወሰዱ ናቸው ISA 29:13-14።

Mark 7:8
ማርቆስ 7፡ 8-10
ማጥበቅ ጠንከር አድርጎ ክፋትን የሚናገሩ "የሚረግሙ"
Mark 7:11
ማርቆስ 7፡ 11-13
ከእኔ ታገኝ የነበረው እርዳታ ሁሉ ቁርባን ነው ለቤተ መቅደስ ቃል የተገባ ማንኛውም ገንዝብ ወይም ሌሎች ማንኛውም ነገሮች ለሌላ ዓላማ መዋል እንደሌለባቸው የጸሐፍት ትውፍት ይናገራል። ቁርባን ጸሐፍው በዚህ ቃል አማካኝነት ማስተላለፍ የፈለገው ነገር የዚህ ቃል ንባብ ከሚሰጠው ድምጽ ጋር ተያያዥነት ስላለው በተቻለ መጠን በቋንቋችሁ ከዚህ ቃል ጋር ተቀራረቢ ድምጽ ያለውን ቃል ተጠቀሙ።
Mark 7:14
ማርቆስ 7፡ 14-16
ሁላችሁም አድምጡኝ እንዲሁም የሚናገረውን ነገር ተረዱ በዚህ ክፍል ውስጥ “ማድመጥ” እና “መረዳት” የሚሉት ሁለት ቃላት እርስ በእርሳቸው የተገናኙ ናቸው። ኢየሱስ እነዚህ ቃላት በአንድነት በንግግሩ ውስጥ የተጠቀመበት ምክንያት አድመወጮቹ እርሱ እየተናገረ ላለው ነገር ትኩረት ይሰጤ ዘንድ ነው። ከሰው የሚወጣው ያ ነው "የሰው ውስጡ ነው” ወይም “ሰው የሚያስበው ወይም የሚያደርገው ያ ነው"
Mark 7:17
ማርቆስ 7፡ 17-19
እናንተ ደግሞ እንደዚህ የማታስተውሉ ናችሁን? አማራጭ ትርጉም: "ይህንን ሁሉ ከተናገርኩ እና ካደረኩ በኋላ በትክክል ትገነዘባላቸሁ ብዬ አስቤ ነበር።"
Mark 7:20
ማርቆስ 7፡ 20-23
Mark 7:24
ማርቆስ 7፡ 24-26
በፊቱ ወደቀ "ተንበረከከ" ትውልድዋም ሲሮፊኒቃዊት በሦሪያ ሀገር ውስጥ በሚትገኝ ፊኒቃ በተባለች ከተማ ውስጥ ነው የተወለደችው።
Mark 7:27
ማርቆስ 7፡ 27-28
ልጆቹ በፊት ይጠግቡ "ልጆች መጀመሪያ መብላት ይኖርባቸዋል" ወይም "በመጀመሪያ ልጆች መመገብ ይገባቸዋል።" ልጆች አይሁዳዊያን። አማራጭ ትርጉሞች፡ "በመጀመሪያ አይሁዶችን ማገልገል ይገባኛል።" ዳቦ ምግብ ውሾች አሕዛብ። በጠረጴዛ ሥር ያሉት ውሾች እንኳ ከልጆች እጅ የወዳደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ፡ "እኔን ከአሕዛብ ወገን የሆንኩትንም በተመሳሳይ መንገድ ልታገለግለኝ ትችላለህ።" ፍርፋሪዎች የዳቦ ፍርፋሪዎች
Mark 7:29
ማርቆስ 7፡ 29-30
Mark 7:31
ማርቆስ 7፡ 31-32
አልፎ መጣ "በውስጡ አልፎ ሄደ" ዐሥር ከተሞች "ዐሥሩ ከተሞች፣" ከገሊላ ሀይቅ በደቡብ ምስራቅ በኩል የሚገኝ አከባቢ። ደንቆሮ "መስማት የማይችል ሰው" መናገር የማይችል፣ አንደበተ ኰልታፋ "ግልጽ በሆነ መንገድ መናገር የማይችል"
Mark 7:33
ማርቆስ 7፡ 33-35
ኤፍታህ ጸሐፊው አይህ ቃል ሲነበብ የሚያስማውን ድምጽ አንባቢያኑ እንዲሰሙት ስለሚፈለግ በተቻለ መጠን በቋንቋቹ ፍደላት አማካኝነት ይህንን ቃል ለመጻፍ ጥረት አድርጉ። ቃተተ ደስተኛ አለመሆኑን ለማሳየት ወደ ውስጥ ሳብ አድርጎ ወደ ውጪ ተነፈሰ ምላሱን ያሠረው ነገር ተፈታ "ምላሱን ያሠረው ነገርን ኢየሱስ አስለቀቀው" ወይም "ግልጽ በሆነ መንገድ እንዳይናገር ካደረገው ነገር ኢየሱስ ፈወሰው"
Mark 7:36
ማርቆስ 7፡ 36-37

---

Chapter 8
Mark 8:1
ማርቆስ 8፡ 1-4
ሦስት ቀናት "3 ቀናት" ራሳቸውን ሊስቱ ይችላሉ አማራጭ ትርጉሞች፡ 1) "ለአጭር ጊዜ ራሳቸውን ሊስቱ ይችላሉ" ወይም 2) "ደካማ ሊሆኑ ይችላሉ" እነዚህን ሁሉ ሰዎች መመገብ የሚችል በቂ ምግብ ከዬት ማግኘት ይቻላል? ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ይህንን ሁሉ ሰው መመገብ የሚያችል ምግብ እንዲፈልጉ መጠየቁ በጣም አስገርሟቸዋል። አማራጭ ትርጉም: "ያሉበት ቦት በቂ ለዚህ ሁሉ ሕዝብ የሚሆን ምግብ የማይቻልበት ሥፍራ አይደለም!"
Mark 8:5
ማርቆስ 8፡ 5-6
ተቀመጡ ሰዎች ምግብ ለመመገብ ጠረጴዛ በማይኖርበት ሥፍራ ላይ ሰዎች ምግብ የሚመገቡበትን መንገድ የሚትገልጽበትን መንገድ የሚገልጽ ቃልን ተጠቀም።
Mark 8:7
ማርቆስ 8፡ 7-10
ዳልማኑታ ከገሊላ ባሕር በሰሜን ምዕራብ በኩሉ የሚገኝ አከባቢ ነው።
Mark 8:11
ማርቆስ 8፡ 11-13
ፈለጉት "ለማግኘት ጥረት አደረጉ" በጥብቅ ይህንን በ MRK 7:34 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ይህ ትውልድ ለምን ምልክትን ይሻል በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ ኢየገሰጻቸው ነው። አማራጭ ትርጉም: “ይህ ትውልድ ምልክትን መሻት አልነበረበተም።” ይህ ትውልድ ይህንን ያደርጋል "ሁላችሁም ይህንን ታደርጋላችሁ"
Mark 8:14
ማርቆስ 8፡ 14-15
ተጠንቀቁ እንዲሁ ራሳችሁን ጠብቁ በዚህ ሥፍራ ጥቅም ላይ የዋሉት እነዚህ ሁለት ቃላት የጋራ ፍች ሲኖራው ሁለቱም ጥቅም ላይ የዋሉበት ምክንያት አጽኖት ለመስጠት ነው። ከፈርሳዊያን እና ከሄሮዶስ ወገን እርሾ አማራጭ ትርጉም: "ከፈርሳዊያን የሐሰት ትምህርት እና ከሄሮዶስ ወገን የሐሰት ትምህርት"
Mark 8:16
ማርቆስ 8፡ 16-17
እንጀራ ስለሌለ ስለምን በመካከላችሁ ትከራከራላችሁ? ኢየሱስ እርሱ እየነገራቸው እና እያደረገ ያለውን ነገር መረዳት ባለመቻላቸው ተስፋ ቆረጠ። አማራጭ ትርጉም: "እኔ እየተናገርኩ ያለሁት ስለ ግዑዝ እንጀራ ነው ብላችሁ ማሰብ የለባችሁም።"
Mark 8:18
ማርቆስ 8፡ 18-19
ዓይን ሳላችሁ አታዩምን? ጆሮስ ሳላችሁ አትሰሙምን? ትዝስ አይላችሁምን? ኢየሱስ ምንም ልገነዘቡ ባለመቻላቸው ተስፋ ቆርጦዋል። አማራጭ ትርጉም: “የሚያይ ዐይን አላችሁ ይሁን እንጂ የሚትመለከቱትን ነገር አትረዱም! የሚሰማ ጆሮ አላችሁ ይሁን እንጂ የሚትሰሙትን ነገር አትረዱም! እነዚህ ሁሉ ልታስታውሱ ይገባ ነበር!"
Mark 8:20
ማርቆስ 8፡ 20-21
ትስዝ አይላችሁምን? አማራጭ ትርጉም: "ስለቁሳዊ እንጀራ እያወራሁ እንዳልሆነ በዚህ ጊዜ መገንዘብ ነበረባችሁ።"
Mark 8:22
ማርቆስ 8፡ 22-23
ቤተ ሳይዳ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ የሚትገኝ ከተማ
Mark 8:24
ማርቆስ 8፡ 24-26
Mark 8:27
ማርቆስ 8፡ 27-28
Mark 8:29
ማርቆስ 8፡ 29-30
Mark 8:31
ማርቆስ 8፡ 31-32
የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል፥ ከሽማግሌዎችም ከካህናት አለቆችም ከጻፎችም ሊጣል፥ ሊገደልም ወደ ሕይወት ሊነሣ እንዲገባው አማራጭ ትርጉም: "ሽማግሌች እና የካህናት አለቆች እንዲሁም ጻፎችም የሰው ልጅነን አይቀበሉመም እንዲሁም ይገድሉታል። ይሁን እነንጂ እግዚአብሔር ወደ ሕይወት መልሶ ያመጣዋል።" ሦስት ቀናት "3 ቀናት"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Mark 8:33
ማርቆስ 8፡ 33-34
Mark 8:35
ማርቆስ 8፡ 35-37
ስለዚህ ኢየሱስ የመሞታቸው ምክንያት ወንጀለኞች ስለሆኑ እንዳልሆነ እና በምንም ምክንያት እንደሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ይህንን እንዲያስታውሱ ይነግራቸዋ።(MRK 8:34).
Mark 8:38
ማርቆስ 8፡ 38-38
የሰው ልጅ ... በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመጣ ጊዜ የሰው ልጅ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ አባቱ ባለው ክብር እርሱም ተመልሶ ይመጣል። የሰው ልጅ ይህ የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ የማዕረግ ስም ነው።

Chapter 9
Mark 9:1
ማርቆስ 9፡ 1-3
ተለወጠ "ወደ ሌላ ቅርጽ ተለወጠ" ወይም "የበለጠ የተለመ ሆኖ ታያቸው" (UDB) እንደ ብርሃን አንጸባራቂ "በጣም ነጭ" አጣቢም በምድር ላይ እንደዚያ ሊያነጣው "ማንጽያ" የሚባለው ከልብስ ላይ ቆሻሻን ለማንጻት እና ነጭ ለማድረግ የሚያገለግል ኬሚካል ነው። “የሚያነጻ” ቆሻሻን የሚያነጻ ሰው።
Mark 9:4
ማርቆስ 9፡ 4-6
ፈሩ "በጣም ፈሩ"
Mark 9:7
ማርቆስ 9፡ 7-8
ማርቆስ 9፡ 7-8
ይህ የሚወደው ልጄ ነው። እርሱን ስሙት። እግዚአብሔር “ስለሚወደው ልጁ”፣ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነው ስለ ልጁ ያለውን ፍቅር የገለጸበት መንገድ ነው። የሚወደው ልጄ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ የማዕረግ ስም ነው።
Mark 9:9
ማርቆስ 9፡ 9-10
ስለዚህም ይህንን ነገር በልባቸው ይጠበቅት ነበር "ይህ ነገር ሲሆን ላልተመለከተ ለማንም ሰው ሳይናገሩ፣ ስለዚህ ነገር ከማንም ጋር አይነጋገሩም ነበር።" ከሞት መነሳት "ከሞተ በኋላ ተመልሶ እንደገና በሕይወት መኖር"
Mark 9:11
ማርቆስ 9፡ 11-13
ኤልያስማ ይህንን በእርግጥ አድርጓል . . . ሰዎችም ጠልተውታል? ኤልያስ ከሰማይ እንደሚመጣ፣ ከዚያም መስሑ የሆነው የሰው ልጅ መጥቶ ይነግሣል እንዲሁም ይገዛል ተብሎ አስቀድሞ ትንቢት ተነግሯል። ሌሎች ትንቢታዊ መልዕክቶችም የሰው ልጅ መከራን እንዲቀበል እና በሰዎች እንዲጠላ የትንቢት መልዕክት ተናግረዋል። ደቀ መዛሙርቱ እነዚህ ሁለት ትንቢታዊ መልዕክቶች እንዴት አንድ ሊሆኑ እንደሚችሉ አልገባቸው ስለዚህም ግራ ገብቷቸዋል። ኤልያስ ይመጣል በትንቢት መልዕክቶች ብዙ ጊዜ ሁለትዮሽ ፍጻሜ አላቸው።
Mark 9:14
ማርቆስ 9፡ 14-16
ስከራከሩ "ስወያዩ" ወይም "ስጨቃጨቁ" ወይም "ስጠያየቁ"
Mark 9:17
ማርቆስ 9፡ 17-19
ከእርሱ ውስጥ ለማውጣት "ከልጄ ውስጥ ለማስወጣት" ወይም "እርኩስ መንፈሱን ለመማባረር" እታገሳችኋለሁ "እችላችኋለሁ" ወይም "አልፋችኋለሁ"
Mark 9:20
ማርቆስ 9፡ 20-22
አዘነላቸው "አሳዘኑት" ወይም "ራራላቸው"
Mark 9:23
ማርቆስ 9፡ 23-25
ኢየሱስም እንዲህ አለው፣ “ቢቻልህስ”? ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል”። ኢየሱስ የሰውዬውን ጥርጣሬ ገሰጸው። አማራጭ ትርጉም፡ “ኢየሱስ ሰውዬውን እንዲህ አለው፣ “ስለምን ከቻልክ ትላለህ”? ለምያምንስ ሁሉ ይቻለዋል።” ወይም "ኢየሱስ ሰውዬውን እንዲህ አለው፣ “ከቻልክስ” ማለት የለብህም!” ለምያምንስ ሁሉ ይቻለዋል።”
Mark 9:26
ማርቆስ 9፡ 26-27
ልጁ የሞተ ይመስል ነበር "ልጁ የሞተ ይመስል ነበር" ወይም "ልጁ የሞተ ሰው ይመስል ነበር"
Mark 9:28
ማርቆስ 9፡ 28-29
እንዲህ ዓይነቱን በጸሎት ካልሆነ ማስወጣት አይቻልም ቃ“አይቻልም” እና “ካልሆነ በስተቀር” የሚሉት ቃላት ሁለቱም አሉታዊ ቃላት ናቸው። በአንዳንድ ቋንቋዎች ውስጥ አዎንታዊ ቃላትን መጠቀሙ አግባብ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ “እንዲህ ዓይነቱን ማስወጣት የሚቻው በጸሎት ብቻ ነው።”
Mark 9:30
ማርቆስ 9፡ 30-32
በዚያ አልፎ ሄደ "በዚያ አለፈ" ወይም "በዚያ አለፈ" ሦስት ቀናት "3 ቀናት"
Mark 9:33
ማርቆስ 9፡ 33-35
Mark 9:36
ማርቆስ 9፡ 36-37
Mark 9:38
ማርቆስ 9፡ 38-39
እርኩስ መናፈስትን ማስወጣት "ዳቢሎስን ማስወጣት"
Mark 9:40
ማርቆስ 9፡ 40-41
እንዳይጠፋ "እንዳይጠፋ" የሚለው ቃል አሉታዊ ነው። በአንዳንድ ቋንቋዎች ውስጥ አዎናታዊ ዓረፍተ ነገሮችን መጠቀም የተለመደ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ "ይቀበላል" (ተመልከት:
Mark 9:42
ማርቆስ 9፡ 42-44
የወፍጮ ድንጋይ እህል ለመፍጨት የሚያገለግል ትልቅ ድንጋይ የማይጠፋ እሳት "የማጥፋ እሳት"
Mark 9:45
ማርቆስ 9፡ 45-46
እንዲሁም ወደ ሲኦል ይወረወራል "እንዲሁም እግዚአብሔር ወደ ሲኦል ይወረውረዋል"
Mark 9:47
ማርቆስ 9፡ 47-48
ትላቸው "የሞተውን አካላቸውን የሚበላ ትል"
Mark 9:49
ማርቆስ 9፡ 49-50

Chapter 10
Mark 10:1
ማርቆስ 10፡ 1-4
Mark 10:5
ማርቆስ 10፡ 5-6
እናንተ ልበ ደንዳኖች "እናንተ እልከኞች"
Mark 10:7
ማርቆስ 10፡ 7-9
ከእንግዲህ ሁለት አይደሉም ግን አንድ ሥጋ ይሆናሉ ይህ እንደ ባል እና ምስት ያላቸውን አካላዊ ትሥሥር የሚያሳይ ምሳሌያዊ ንግግር ነው።
Mark 10:10
ማርቆስ 10፡ 10-12
Mark 10:13

ማርቆስ 10፡ 13-14
ሕጻናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ፍቀዱላቸውለ ፈጽሞ አትከልክሏቸው። እነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው በድጋሜ የተጻፈውም አጽኖት ለመስጠት ሲባል ነው። አማራጭ ትርጉም: “ሕጻናት ወደ እኔ እንዲመጡ አድርጓቸው።” አትከልክሏው ይህ በላሁት አሉታዊ ንግግር ነው። በአንዳንድ ቋንቋዎች ውስጥ አዎንታዊ ቃላትን መጠቀም የተለመደ ነው። አማራጭ ትርጉም: “ፍቀዱላቸው።”
Mark 10:15
ማርቆስ 10፡ 15-16
Mark 10:17
ማርቆስ 10፡ 17-19
መልካም ብለህ ለምን ትረጠራኛለህ? አማራጭ ትርጉም: "በዚህ ንግግር ውስጥ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚታስተፈለልፈው መልዕክት በጥንቃቄ ማወቅ ይኖርብሃል )
Mark 10:20
ማርቆስ 10፡ 20-22
Mark 10:23
ማርቆስ 10፡ 23-25
ሀብታም ወደ እግዚአብሔር መንግስት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ውስጥ በትሾልክ ይቀላል። ለግመል በመርፌ ቀዳዳ ውስጥ ማለፍ ፈጸሞ የማይቻላት ነገር ነው። እንደዚሁም ሀብታም ሰዎች እግዚአብሔርን የሕይወታቸውን ንጉሥ አድርጎ መቀበል በጣም አስቸጋር ነው። የመርፌ ዐይን/ ቀዳዳ “የመርፌ ዐይን” በመርፌ አናት ላይ የሚገኝ ቀዳዳ ነው።
Mark 10:26
ማርቆስ 10:26-28
ታዲያ ማን ሊድን ይችላል? "ስለዚህ ማንም ሊድን አይችልም።"
Mark 10:29
ማርቆስ 10፡ 29-31
ከተውቱ መካል . . . የማይቀበል አይኖርም "ከተውት መካከል . . . የማይቀበል አይኖርም።" ለእኔ ሲል "ለእኔ ጥቅም" ወይም "ለእኔ ጥቅም ሲል" ይህንን ዓለም "ይህን ሕይወት" ወይም "በአሁኑ ዘመን" በሚመጣው ዘመን "በሚመጣው ሕይወት" ወይም "በሚመጣው ጊዜ"
Mark 10:32
ማርቆስ 10፡ 32-34
የሰው ልጅን አሳልፈው ይሰጡታል "ሰዎች የሰው ልጅ አሳልፈው ይሰጡታል" ወይም "ሰዎች የሰው ልጅን አሳለፈው ይሰጡታል"
Mark 10:35
ማርቆስ 10፡ 35-37
Mark 10:38
ማርቆስ 10፡ 38-40
የሚጠጣው ጽዋ ኢየሱስ ይህንን ሀረግ የተጠቀመው ስለሚቀበለው መከራ ለመግለጽ ነው። የሚጠመቀውን ጥምቀት ኢየሱስ ይህንን ሀረግ የተጠቀመው ስለሚቀበለው መከራ ለመግለጽ ነው።
Mark 10:41
ማርቆስ 10፡ 41-42
ገዡዎች ተብለው በሚጠሩት "ገዡዎች ተብለው በሌሎች በሚቆጠሩት" ተቆጣጣሪዎች "የሚቆጣጠሩ" ወይም "ኃይል ያላቸው" መለማመድ "የሚጠቀሙ"
Mark 10:43
ማርቆስ 10፡ 43-45
ትልቅ የሚሆን "የሚከበር" ወይም "የሚሞገስ" ማንም "ዬትኛውም ሰው" የሰው ልጅ ሊገለገል ሳይሆን "የሰው ልጅ ሰዎች እንዲገለግሉት አልመጣም"
Mark 10:46
ማርቆስ 10፡ 46-48
በርጤሜዎስ የአንድ ሰው ስም ጤሜዎስ ይህ በመንገድ ላይ ስለለምን የነበረው ለማኝ አባት ነው።
Mark 10:49
ማርቆስ 10፡ 29-50
እንዲጠሩት አዘዘ "ሰውዬውን ይጠሩት ዘንድ አዘዛቸው" ጠንከር በል "አትፍራ"
Mark 10:51
ማርቆስ 10፡ 51-52
መመልከት "የማየት ክህሎት" ወዲያው "በዚያን ጊዜ" ወይም "ያለምንም መዘግየት"

---

Chapter 11
Mark 11:1
ማርቆስ 11፡1-3
ቤተ ፋጌ የመንደሯ ስም
Mark 11:4
ማርቆስ 11፡4-6
Mark 11:7
ማርቆስ 11፡7-10
ሆሣዕና የዚህ ቃል ትርጉም ምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም ይሁን እንጂ እንኳ ደህና መጡ እና ምስጋና ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ ቢተረጎም መልካም ነው፤ ማለትም “እግዚአብሔር ይመስገን” (UDB)።
Mark 11:11
ማርቆስ 11፡11-12
Mark 11:13
ማርቆስ 11፡ 13-14
Mark 11:15
ማርቆስ 11፡ 15-16
Mark 11:17
ማርቆስ 11፡ 17-19
“ቤተ ለአሕዛቡ ሁሉ የጸሎት ቤት ይባልል” ተብሎ አልተጻፈምን? "በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ እግዚአብሔር “ቤቴ ከሁሉም ሕዝቦች የመጡ ሰዎች የሚጸልዩበት ቤት ይሆናል” በማለት የተናገረው ተጽፏል፤ ነገር ግን እናንት ወሮበላዎች ለእናንተ መደበቂያ ዋሻ አደረጋችሁት!"
Mark 11:20
ማርቆስ 11፡ 17-19
“ቤተ ለአሕዛቡ ሁሉ የጸሎት ቤት ይባልል” ተብሎ አልተጻፈምን? "በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ እግዚአብሔር “ቤቴ ከሁሉም ሕዝቦች የመጡ ሰዎች የሚጸልዩበት ቤት ይሆናል” በማለት የተናገረው ተጽፏል፤ ነገር ግን እናንት ወሮበላዎች ለእናንተ መደበቂያ ዋሻ አደረጋችሁት!"
Mark 11:22
ማርቆስ 11፡ 22-23
በልቡ ሳይጠራጠር ቢያምን "ሳይጠራጠር" የሚለው ቃል ባለሁት አሉታዊ ቃል ነው። ትርጉሙም “በእውነት ቢያምን” ማለት ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው አጽኖት ለመስጠት ሲባል ብቻ ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው። አንዳንድ ቋንቋዎች አጽኖት የሚቀጠሙት ሌላ መንገድ ነው። አማርጭ ትርጉም: “በእውነት ቢያምን”
Mark 11:24
ማርቆስ 11፡ 24-26
ቆማችሁ ስትጸልዩ በዕብራዊን ባሕል መሠረት ወደ እግዚብሔር የሚደረግ ጸሎት የሚደረገው ተቁሞ ነው።
Mark 11:27
ማርቆስ 11፡ 27-28
እነዚህ ነገሮች የሚታደርገው በምን ሥልጣን ነው “እነዚህ ነገሮች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበሩት የሸያጮችን ጠረጴዛዎች መገለባበጡን እና የሚያድርጉትን እና የሚያስተምሩትን ነገር በመቃወም መነናገሩን የሚያመለክት ቃል ነው። እነዚህ ነገሮች የሚታደርገው በምን ሥልጣን ነው እንዲሁም እነዚህ ነገሮች እንዲታደረግ ሥልጣን ማን ሰጠህ አማራጭ ትርጉም: "እነዚህን ነገሮች ለማድረግ ሥልጣን የለህም ምክንያቱም እኛ ይህንን ሥልጣን አልሰጠንህም"
Mark 11:29
ማርቆስ 11፡ 29-30
የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ወይም ከሰዎች ናት? ምንም እንኳ ኢየሱስ ለዚህ ጥያቄ ምላሹ ምን እንደሆነ ቢያውቅም ይህን ጥያቄ የጠየቃቸው የሃይማኖት መሪዎቹ

ለእርሱ ሥልጣን የጠየቁት ጥያቄ መሠረቱ ምን አመክኒዬ እንደሆነ ለመፈተን ነው።
Mark 11:31

ማርቆስ 11፡ 31-33

Chapter 12

Mark 12:1

ማርቆስ 12፡ 1-3

የወይን እርሻውን አከራይቶ ሄደ የእርሻው ባለቤት ወይኑን ይንከባከቡለት ለሌሎች ሰዎች ሰጠ።

Mark 12:4

ማርቆስ 12፡ 4-5

Mark 12:6

ማርቆስ 12፡ 6-7

ገበሬዎቹ ከባለቤቱ የወይን እርሻውን ለመንከባከብ የተረከቡት ገበሬዎች

Mark 12:8

ማርቆስ 12፡ 8-9

ማርቆስ 12፡ 8-9 ስለዚህ የወይን እርሻው ባለቤት ምን ያደረጋል? አማራጭ ትርጉም: "የወይን እርሻው ባለቤት ምን እንደሚያደርግ እነግራችኋለሁ።

Mark 12:10

ማርቆስ 12፡ 10-12

ማርቆስ 12፡ 10-12 ይህን የቅዱስ መጽሐፍ ክፍል አላነበባችሁምን? አማራጭ ትርጉም: "በእነዚህ የቅዱስ መጽሐፍ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን እነዚህን ቃላት በጥንቃቄ አስቡ።"

Mark 12:13

ማርቆስ 12፡ 13-15

ስለምን ትፈትኑኛላችሁ? "እኔን መከሰስ ያስችላችሁ ዘንድ ትክክል ያልሆነ ነገር እስኪናገር ድረስ እየፈለጋችሁ መሆኑን አውቃለሁ።" ዲናር ይህ ገንዘብ የአንድ ቀን የሥራ ደሞዝን ያክላል።

Mark 12:16

ማርቆስ 12፡ 16-17

አንድ አመጡለት "ፈርሳዊያን እና ሄሮዶሳዊያን የሮም መንግስት ፍራንክ አመጡለት" የቄሣርን ለቄሣር ስጡ አማራጭ ትርጉም: "የሮም መንግስት የሆነውን ነገር ለሮም መንግስት ስጡ፣" .

Mark 12:18

ማርቆስ 12፡ 18-19

ሙሴ እንዲህ ብሎ ጽፎልናል፣ 'የአንድ ሰው ወንድም . . . ለወንድሙ ልጅ ይውለድለት።' አማራጭ ትርጉም: "ሙሴ እንዲህ ሲል ጽፏል የአንድ ሰው ወንድም ከሞተ . . ለወንድሙ ልጅ ይውለድለት።

Mark 12:20

ማርቆስ 12፡ 20-23

በትንሳዔ ጊዜ፣ ከሞት ሲነሳ የማን ምስት ትሆናለች? አማራጭ ትርጉም: "በትንሳዔ ጊዜ፣ ከሞት ሲነሳ የእነዚህ ሰባት ወንድመማማቾች ምስት መሆን አትችልም!"

Mark 12:24

ማርቆስ 12፡ 24-25

ስህተታሁ ይህ አይደለምን . . . የእግዚአብሔር ኃይል? "የተሳሳታችሁት በዚህ ምክንያት ነው . . . የእግዚአብሔር ኃይል።"

Mark 12:26

ማርቆስ 12፡ 26-27

ከሞት ይነሳሉ "እግዚአብሔር ያስነሳቸዋል፣"

Mark 12:28

ማርቆስ 12፡ 28-31

Mark 12:32

ማርቆስ 12፡ 32-34

Mark 12:35

ማርቆስ 12፡ 35-37

ታዲያ ጸሐፍት እንዴት ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው ይላሉ? አማራጭ ትርጉም: "የአይሁድ ሕግ ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው ብለው የሚያስተምሩት እነዚህ ሰዎች ተሳተዋል!" የዳዊት ልጅ "ልጅ" የሚለው ቃል በዚህ ሥፍራ ጥቅም ላይ የዋለው ዘር የሚለውን ለማመለከት ነው። ታዲያ እንዴት የዳዊት ልጅ ሊሆን ይችላል? አማራጭ ትርጉም: "የዳዊት ልጅ መሆን አይችም!"

Mark 12:38

ማርቆስ 12፡ 38-40

Mark 12:41

ማርቆስ 12፡ 38-40

Mark 12:43

ማርቆስ 12፡ 43-44

እውነት እውነት እላችኋለሁ ይህንን በ MRK 11:23 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁት ተመልከቱ። የመባ ሳጥን ይህ ሳጥን በቤተ መቅደሱ ውስጥ መባ ለመሰብሰብ የሚው ሳጥን ነው። የተትረፈረፈ "በጣም ብዙ" ድህነት "እጥረት" ወይም "ድህነት"

Chapter 13

Mark 13:1

ማርቆስ 13፡ 1-2

ይህንን ትልቅ ሕንጻ ትመለከታለህን? አማራጭ ትርጉም: "እነዚህ ሕንጻዎች እንዴት እንደሚያምሩ ተመልከት።

Mark 13:3

ማርቆስ 13፡ 3-4

እነዚህ ነገሮች "አሁን የነገርከኝ ነገሮች"

Mark 13:5

ማርቆስ 13፡ 5-6

በእኔ ስም ብዙ ሰዎች ይመጣሉ "ስም" የሚለው ቃል የኢየሱስን ስልጣን የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም፡ ብዙዎች የእኔ ስልጣን እና ከእኔ ፈቃድ እንደጋኙ በመናገር ይመጣሉ፣"

Mark 13:7

ማርቆስ 13፡ 7-8

ወሬ "የስህተት ትምህርት" ወይም "ወሬ"

Mark 13:9

ማርቆስ 13፡ 9-10

ለእነርሱ ምስክር ይሆናቸው ዘንድ "ለእነርሱ ምስክር ይሆናቸው ዘንድ" የሚለው ሀረግ "እውነት እንደሆነ ለማሳየት" ወይም "እውነቱ ዬቱ እንደሆነ ለማረጋገጥ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

Mark 13:11

ማርቆስ 13፡ 11-13

አባት ልጁን "አባት ልጁን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል።" እስከመጨረሻ የሚጸና ሰው እርሱ ይድናል አማራጭ ትርጉም: "እስከመጨረሻ የሚጸናውን እግዚአብሔር ያድነዋል።"

Mark 13:14

ማርቆስ 13፡ 14-16

የጥፋት እርኩሰት "ክፉ የሆነ የጣኦት አምልኮ" ወይም "እርባና ያሌለው ክፋት"

Mark 13:17

ማርቆስ 13፡ 17-20

the elect, those he chose "እርሱ የመረጣቸው" የሚለው ሀረግ "የተመረጡት" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። እነዚህ ሁለቱ በአንድነት እግዚአብሔር እነዚህ ሕዝቡን መምረጡን አጽኖት በመስጠት ይናገራሉ።

Mark 13:21

ማርቆስ 13፡21-23

የተመረጠ ሰዎች እንዲቀደሱ እግዚአብሔር ይመርጣል፣ ጥሩ መንፈሳዊ ፍሬን እንዲያፈሩ እርሱ ራሱ ሰዎችን ይለያል። ለዚህም ነው "የተመረጡት" ተብለው የሚጠሩት።

Mark 13:24

ማርቆስ 13፡ 24-27

ፀሐይ ይጨልማል "እግዚአብሔር ፀሐይ እንዲትጨልም ያደርጋል።" በሰማይ ያሉት ኃይላት ሁሉ ይናወጣሉ "እግዚአብሔር በሰማይ ያሉት ኃይላት ሁሉ ያናውጣልይናወጣሉ"
Mark 13:28
ማርቆስ 13፡ 28-29
Mark 13:30
ማርቆስ 13፡ 30-32
እውነት እውነት እላችኋለሁ ኢየሱስ ያስተማራቸው ነገር ሁሉ እርሱ በተናገረው መንገድ እየተፈጸመ መሆኑን አጽኖት በመስጠት በመናገር ላይ ነው። ያልፋሉ "ያበቃሉ" Father “አባት” የሚለው ቃል በቋንቋችሁ በተለምዶ ለሰው አባት መጠሪያነት የሚትጠቀሙበትን ቃል ተጠቀሙ።
Mark 13:33
ማርቆስ 13፡ 33-34
አስተውሉ “አስተውሉ” ወይም “እያስተዋላችሁ” የሚለው ቃል ኃጢአትን እና ክፋትን ሁል ጊዜ መጠንቀቅ እና በንቃት መጠበቅን ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪ “ሁል ጊዜ ዝግጁ መሆንን” ማለትም ሊሆን ይችላል።
Mark 13:35
ማርቆስ 13፡ 35-37
የአውራ ዶሮ ጩኸት አውራ ዶሮ ጥዋት በማለዳ የሚያሰማው ጩኸት ነው። የአውራ ዶሮ በጥዋት የሚያሰማው ጩኸት የአውራ ዶሮ በጥዋት የሚያሰማው ጩኸት

---

Chapter 14
Mark 14:1
ማርቆስ 14:1-2
Mark 14:3
ማርቆስ 14፡ 3-5
ለምጻሙ ስምዖን ይህ ሰው ከከዚህ በፊት ለምጽ ያለበት ቢሆንም አሁን ግን ታሞ አይደለም። አልባስጥሮስ ይህ ለስላሳ “ነጭ ድንጋይ” ነው። የዚህ ሁሉ ብክነት ምክንያቱ ምንድ ነው? አማራጭ ትርጉም: "እንዲህ ዓይነቱን ውድ ሽቶ ለማባከን የሚሆን ምንም በቂ ምክንያት የለም።” ይህ ሽቶ ልሸጥ ይችላል "ይህንን ሽቶ ሸጠን” ወይም “ይህንን ሽቶ ሸጣ” ሦስት መቶ ዲናር "300 ዲናር።" ዲናር የሮማዊያን የብር ሳንቲም ነው።
Mark 14:6
ማርቆስ 14፡ 6-9
ስለምን ታደክሙኣታላችሁ? አማራጭ ትርጉም: “ልታስቸግሯት አይገባም።"
Mark 14:10
ማርቆስ 14:10-11
ማርቆስ 14:10-11 የአስቆሮቱ ይሁዳ ይህንን በ [MRK 3:17]
Mark 14:12
ማርቆስ 14፡ 12-14
የእንግዳ ማረፍያ ክፍል an extra room for visitors ለእንግዶች ማረፊያነት የሚዘጋጅ ትርፍ ክፍል
Mark 14:15
ማርቆስ 14፡ 15-16
Mark 14:17
ማርቆስ 14፡ 17-19
በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ ሳለ በምግብ የጠረጴዛ ዙሪያ እንግዶች ተቀምጠው ሳለ። አንድ በአንድ ይህ ማለት “ተራ በተራ” እያንዳንዱ ደቀ መዝሙር እንዲህ ሲል ጠየቀው። እኔ አይደለሁም "በእርግጠኝነት ጠላቶችህ እንዲይዙህ የማግዛቸው እኔ አይደለሁም!"
Mark 14:20
ማርቆስ 14፡ 20-21
Mark 14:22
ማርቆስ 14፡ 22-25
ማርቆስ 14፡ 22-25
Mark 14:26
ማርቆስ 14፡ 26-27
መዝሙር። የመዝሙር ዓይነት ነው። በዚህ ወቅት የብሉይ ኪዳን መዝሙር መዘመር ባሕል ነበር።
Mark 14:28
ማርቆስ 14፡ 26-27
መዝሙር። የመዝሙር ዓይነት ነው። በዚህ ወቅት የብሉይ ኪዳን መዝሙር መዘመር ባሕል ነበር።
Mark 14:30
ማርቆስ 14፡ 30-31
እውነት እውነት እልሃለሁ ይህንን በ MRK 11:22 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ትክደኛለህ "አላውቀውም ትላለህ”
Mark 14:32
ማርቆስ 14፡ 32-34
ነፍስ “ነፍስ” የሚለው ቃል አንዳንድ ጊዜ ሙሉ ሰውን ለማመልከት በምሳሌያዊ መልኩ ጥቅም ላይ ይውላል።
Mark 14:35
ማርቆስ 14፡ 35-36
ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ "እያለፈበት ያለውን መከራ መቋቋም የሚያስችለው ጥንካሬ ያስፈልገዋ።” አባ "አባ" የግሪክ ቃል ሲሆን ልጆች አባታቸውን ለመጥራት የሚጠቀሙበት ቃል ነው። ይህ ቅርብ የሆነ ግነኙነት መኖሩን ያሳያል። ይህ ቃል ኢየሱስ አባቱን የጠራበትን መንገድ የሚሳይ በመሆኑ ይህንን የግሪክ ቃል በትርጉማችሁ ውስጥ እንዳለ መስቀመጡ አስፈላጊ ነው። ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ ጽዋ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስ ለሸከመው ያለውን የእግዚአብሔር ቁጣን ነው። ኢየሱስ . . .. እንዲህ አለ፣ "አባ አባት . . . ይህን ጽዋ ከእነተ አሳልፍ። ይሁን እንጂ የኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን።" ኢየሱስ አባቱን ለሰው ልጆች ኃጢአት ሲል የሚቀበለውን መከራ ይተውለት ዘነድ አባቱን ይጠይቃል። ነገር ግን አባቱ የእርሱን ብቸኛ፣ ፍጹም ልጅ መስዋእትነት ለእርሱ የማይቆጠር ቅድስና ይፈልጋል። ስለዚህ ኢየሱስ የመስቀልን መከራ ተቀበለ። አባት ይህ የእግዚአብሔር አባት ወሳኝ የማዕረግ ስሙ ነው።
Mark 14:37
ማርቆስ 14፡ 37-39
ተኝተው አገኛቸው "ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ ተንኝተው አገኛቸው" ስምኦን ተኝተሃል "አትተኙ ንቁ ቢዬአችሁ ሳለ አንተ ስምኦን ተኝታችኋልን ነቅታቹ ለአንድ ሰዓት እንኳ መጠበቅ አቃታችሁን? "ነቅታችሁ መቆየት ፈጽሞ አቃታችሁን" መንፈስስ ተዘጋጅታለች፥ ሥጋ ግን ደካማ ነው "አእምሮዋችሁ ማድረግ የሚፈልገውን ነገር አካላችሁ ማድረግ አይችልም።" ሥጋ "አካል"
Mark 14:40
ማርቆስ 14፡ 40-42
ተኝተው አገኛቸው "ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ እና ያዕቆብ ተኝተው ነበር" አሁንም ተኝታችኋልን? አማራጭ ትርጉም: "አሁንም ተኘንታችኋልን1 እረፍት እያደረጋችሁ ነውን!"
Mark 14:43
ማርቆስ 14፡ 43-46
እጃቸውን ጫኑበት "ያዙት"
Mark 14:47
ማርቆስ 14፡ 47-50
ወንበዴ እንደምትይዙ ሰይፍና ጐመድ ይዛችሁ ልትይዙኝ መጣችሁን? "ወንበዴ ለመያዝ እንደሚመጣ ሰው ሰይፍ እና ጎመድ ይዛችሁ እኔን ለመያዝ መጣችሁ።”
Mark 14:51
ማርቆስ 14፡ 51-52
ነጠላ ከጥጥ ፈትል የሚሠራ ልብስ
Mark 14:53
ማርቆስ 14፡ 53-54
Mark 14:55
ማርቆስ 14፡ 55-56
Mark 14:57
ማርቆስ 14፡ 57- 59
ሰምተነዋል “እኛ” የሚለው ቃል በኢየሱስ ላይ በሐሰት የመሰከሩበትን ሰዎችን ያመለክታል።
Mark 14:60


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ማርቆስ 14፡ 60--62
ከእርሱ መካከል ቆሞ ነበር "ከካህናት አለቆች፣ ጸሐፍት እና ሽማግሌዎች መካከል ቆሞ" እኔ ነኝ ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን የጠራበት ቃል ነው።
Mark 14:63
ማርቆስ 14፡ 63-65
ልብሱን ቀደደ ኢየሱስ በተናገረው ቃል መቆጣጡት የሚያሳይ ምልክት ነው ሁሉም ፈረዱበት "ሸንጎው ሙሉ ለሙሉ በኢየሱስ ላይ ፈረደ"
Mark 14:66
ማርቆስ 14፡ 66-68
Mark 14:69
ማርቆስ 14፡ 69-70
ከእነርሱ መካከል አንዱ "ከደቀ መዛሙርቱ መካከል አንዱ"
Mark 14:71
ማርቆስ 14፡ 71-72
ተሰበረ “ተሰበረ” የሚለው ቃል በጣም መደንገጡን ወይም በጣም ማዘኑን የሚያሳይ ነው።

---

Chapter 15
Mark 15:1
ማርቆስ 15፡ 1-3
አንተ አልክ "አንተ ራስህ መሰከርክ።"
Mark 15:4
ማርቆስ 15፡ 4-5
Mark 15:6
ማርቆስ 15፡ 6-8
Mark 15:9
ማርቆስ 15፡ 9-11
ማርቆስ 15፡ 9-11 ለቀቁት "እንዲሄድ ፈቀዱለት" ወይም "ፈቱት"
Mark 15:12
ማርቆስ 15፡ 12-13
ማርቆስ 15፡ 12-13
Mark 15:14
ማርቆስ 15፡ 14-15
ኢየሱስን ገረፉት በልዩ መግረፊያ ኢየሱስን እንዲያመው አድርገው ገረፉት አሳልፈው ሰጡት ይህንን በ MRK 15:1 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
Mark 15:16
ማርቆስ 15፡ 16-18
የወታደሮች ካንፕ ይህ ወታደሮች የሞቆዩበት ሥፍራ ነው። ጭፍራ "በጣም ብዙ" ወይም “ ብዙ” ቀይ ልብስም አለበሱት፥ ይህ የመሳለቅ ምልክት ነው። እንዲህ ዓይነት ቀለም ያለው ልብስ የነገስታት ልብስ ሲሆን ይህንን ዓይነት ልብስ እርሱን በማልበስ “የአይሁድ ንጉሥ” በሚለው የኢየሱስ የማዕረግ ስሙ ላይ እየጠሳለቁ ነበር።" እንዲህ እያሉ ይሰግዱለትም ጀመር፣ “የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ እጅ ይነሱት ጀመር፤” እንደገና ወታደሮቹ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ መሆኑን ስላላመኑበት በኢየሱስ ላይ ይሳለለቁ ነበር።
Mark 15:19
ማርቆስ 15፡ 19-21
Mark 15:22
ማርቆስ 15፡ 22-24
Mark 15:25
ማርቆስ 15፡ 25-28
ወንበዴዎች "የታጠቁ ዘራፊዎች"
Mark 15:29
ማርቆስ 15፡ 29-30
Mark 15:31
ማርቆስ 15፡ 31-32
Mark 15:33
ማርቆስ 15፡ 33-35
Mark 15:36
ማርቆስ 15፡ 36-38
የሚቆመጥት ወይን "ኮምጣጤ" የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ለሁለት ተቀደደ የቤተ መቅደሱን መጋረጃ እግዚብሔር ሁለት ቦታ ቀደደው።
Mark 15:39
ማርቆስ 15፡ 39-41
የእግዚአብሔር ልጅ ይህ የኢየሱስ ወሳኝ የሆነ የማዕረግ ስም ነው። ሰሎሜ
Mark 15:42
ማርቆስ 15፡ 42-44
Mark 15:45
ማርቆስ 15፡ 45-47
መከፈኛ ጨርቅ ከጥጥ ተክል የተሠራ ልብስ (ይህንን በ14፡ 51-52 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።) ኢየሱስ የተቀበረበት ሥፍራ "ዮሴፍ እና ሌሎች የኢየሱስን በድን የቀበሩበት ሥፍራ"

---

Chapter 16
Mark 16:1
ማርቆስ 16፡ 1-2
ቆንጆ ሽታ የሚሸት "ጥሩ መዓዛ ያለው"
Mark 16:3
ማርቆስ 16፡ 3-4
Mark 16:5
ማርቆስ 16፡ 5-7
ተነስቷል! "እርሱ ተነስቷል" ወይም "እግዚአብሔር ከሞት አስነስቶታል!" ወይም "ከሞት በራሱ ተነስቷል!"
Mark 16:8
ማርቆስ 16፡ 8-8
Mark 16:9
ማርቆስ 16፡9-11
በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን "በሰንበት"
Mark 16:12
ማርቆስ 16፡ 12-13
Mark 16:14
ማርቆስ 16፡ 14-16
የልብ ድንዳኔ አማራጭ ትርጉም፡ "ለማመን አለመፈለግ"
Mark 16:17
ማርቆስ 16፡ 17-18
ማርቆስ 16፡ 17-18
Mark 16:19
ማርቆስ 16፡ 19-20
No text

---

Chapter 1
Luke 1:1
አጠቃላይ መረጃ፦
ሉቃስ ለምን ወደ ቴዎፍሎስ እንደሚጽፍ ያብራራል።
በእኛ ዘንድ ስለተፈጸሙት ነገሮች
“በእኛ መካከል ስለተፈጸሙት ነገሮች” ወይም “በእኛ መካከል ተከስተው ሰለነበሩት ነገሮች”
በእኛ ዘንድ
ቴዎፍሎስ ማን እንደነበር በእርግጠኝነት የሚያውቅ ሰው የለም። ቴዎፍሎስ ክርስቲያን የነበረ ከሆነ ግን “እኛ” የሚለው ገላጭ እርሱንም ያካትት የነበረ ይሆናል፣ ካልሆነ ግን እርሱን የሚያካትት አይሆንም። (አካታች “እኛ” እና አግላይ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እና አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)
የቃሉ አገልጋዮችና የዓይን እማኞች የነበሩ
“የዓይን እማኝ” ማለት አንድ ነገር ሲከሰት በዓይኑ የተመለከተ ማለት ነው፣ አገልጋይ ማለት ደግሞ የእግዚአብሔርን መልዕክት ለሰዎች በመናገር እግዚአብሔርን የሚያገለግል ሰው ነው። እንዴት የቃሉ አገልጋዮች እንደተባሉ ግልጽ አድርጎ መናገር ያስፈልጋል። አማራጭ ትርጉም፦ “የተከሰተውን የተመለከቱና መልዕክቱን በመናገር እግዚአብሔርን ያገለገሉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የቃሉ አገልጋዮች
“ቃሉ” የሚለው ቃል የሚወክለው ከብዙ ቃላት የተገነባ አንድን መልዕክት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የመልዕክቱ አገልጋዮች” ወይም “የእግዚአብሔር መልዕክት አገልጋዮች” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
በትክክል አጥንቼ
“ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ የተመረመረ።” ሉቃስ በትክክል ምን እንደተከሰተ ለማወቅ በጥንቃቄ ምርምር አድርጓል። እርሱ ስለተከሰቱት ነገሮች የጻፋቸው ነገሮች ትክክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ ድርጊቱን በዓይናቸው ከተመለከቱ ከተለያዩ ሰዎች ጋር በመነጋገር የድርጊቶቹን እርግጠኝነት እንዳረጋገጠ ይገመታል።
የከበርክ ቴዎፍሎስ
ሉቃስ ይህንን ያለው ለቴዎፍሎስ የነበረውን ክብርና አክብሮት ለማሳየት ፈልጎ ነው። ይህ ክፍል በባህላችሁ የተከበሩ ሰዎች የሚሰጣቸውን ስያሜ በመቀየር መጻፍ ይቻላል። አንዳንድ ሰዎች ሰላምታን በመጠቀም “ለቴዎፍሎስ” ወይም “የተወደድክ ቴዎፍሎስ” ብለው መጻፍን ይመርጣሉ።
የከበርክ
“የተከበርክ” ወይም “ክቡር”
ቴዎፍሎስ
የዚህ ሥም ትርጉም “የእግዚአብሔር ወዳጅ” ማለት ነው። ይህ ስም የዚህን ሰው ባሕርይ የሚገልጽ ስያሜ ሊሆን ይችላል፣ ወይም ትክክለኛው የዚህ ሰው መጠሪያም ሊሆን ይችላል። በርካታ ትርጉሞች እንደ መጠርያ ስም አድርገው ተርጉመውታል። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 1:5
አያያዥ ሀሳብ፦
መልዓኩ የዮሐንስን ውልደት ተነበየ
አጠቃላይ መረጃ፦
ዘካርያስ እና ኤልሳቤጥን ለመጀመርያ ጊዜ እናያቸዋለን። ቀጥሎ ያሉት ጥቅሶች ስለ እነርሱ የጀርባ ታሪክ የበለጠ መረጃ ይነግሩናል። (የጀርባ ታሪክ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 1:8
እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ ከተሰጠው የጀርባ ታሪክ መረጃ ወደ ሌላ ታሪክ ትኩረት እንደተቀየረ የሚያሳይ ሐረግ ነው።
ዘካርያስ በእግዚአብሔር ፊት የክህነት ስራውን እየሰራ ነበር
ይህ ዘካርያስ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ መሆኑን፣ የክህነት ስራዎቹም እግዚአብሔርን የማምለክ ስርዓት አካላት መሆናቸውን ያሳያል። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በክፍሉ ተራ
“የእርሱ ቡድን ተራ ሲሆን” ወይም “የእርሱ ቡድን የማገልገል ጊዜያቸው በደረሰ ጊዜ”
እንደ ካህናት ሥርዓት ... ዕጣን ለማጠን እጣ ደረሰበት
ይህ ዓረፍተ ነገር ስለ ካህናት ስራዎች መረጃን ይሰጣል። (የጀርባ ታሪክ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ስርዓት
“ባሕላዊው መንገድ” ወይም “ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት”
እጣ ደረሰበት
ምልክት ያለበትን ድንጋይ ወደ መሬት በመጣል እንደ እጣ በማውጣት አንድን ነገር ለመወሰን እንዲረዳቸው ይጠቀሙ ነበር። ካህናቱ በሚያወጡት እጣ ውስጥ የትኛው ካህንን ለተለያዩ ስራዎች መምረጥ እንዳለባቸው እግዚአብሔር ምሪትን እንደሚሰጣቸው ያምኑ ነበር።
እጣን ለማጠን
ካህናቱ በየጠዋቱና በየማታው ጣፋጭ ሽታ ያለውን እጣን በመቅደሱ ውስጥ በሚገኝ መሰዊያ ላይ በማቃጠል ለእግዚአብሔር እንደ መስዋዕት ያቀርቡ ነበር።
ሕዝቡ ሁሉ
“ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ” ወይም “ብዙ ሰዎች”
በውጪ
ቅጥር ግቢው ቤተ መቅደሱ ዙሪያ የሚገኝ የተከለለ ቦታ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ከቤተ መቅደሱ ሕንጻ ውጪ” ወይም “ከቤተ መቅደሱ ውጪ ባለው ቅጥር ግቢ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 1:11
አያያዥ ሀሳብ፦
ዘካርያስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ስራውን እያከናወነ እያለ የእግዚአብሔር መልዓክ መልዕክትን ሊሰጠው ይመጣል።
አሁን
ይህ ቃል በታሪክ ውስጥ ለሚከሰት ክስተት መጀመርያን ያሳያል።
ታየው
“በድንገት ወደ እርሱ መጣ” ወይም “በድንገት ከዘካርያስ ጋር ነበር” ይህ መልዓኩ በእርግጥም ከዘጋርያስ ጋር እንደነበርና ራዕይ እንዳልነበር ያሳያል።
ዘካርያስም ... ደነገጠ ... ፍርሃትም ወደቀበት
እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ፣ ዘካርያስ ምን ያህል እንደፈራ ያሳያሉ።
ዘካርያስ ባየው ጊዜ
“ዘካርያስ መልዓኩን ባየው ጊዜ” ዘካርያስ የፈራው የመልዓኩ መልክ አስፈሪ ስለነበር ነው። ዘካርያስ ክፉ የሆነ ነገር አልሰራም፣ ስለዚህ መልዓኩ ቅጣት ይጥልብኛል ብሎ አልፈራም።
ፍርሃት ወደቀበት
x
Luke 1:14
ታላቅ ይሆናል
“የዚህም ምክንያት ታላቅ ስለሚሆን ነው” ዘካርያስና “ብዙዎች” ደስ የሚላቸው የሐንስ “በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ” ስለሚሆን ነው። ተከትሎ ያለው የቁጥር 15 ክፍል እግዚአብሔር የሐንስ እንዴት እንዲኖር እንደሚፈልግ ይናገራል።
ደስታና ተድላ ይሆንልሃል
“ደስታ” እና “ተድላ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ይህም ምን ያህል ደስታ እንደሚሆን ትኩረት ለመስጠት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ታላቅ ደስታ ይሆንልሃል” ወይም “እጅግ ደስተኛ ትሆናለህ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
በመወለዱም
“በመወለዱ ምክንያትም”
በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ይሆናል
“ለጌታ እጅግ ጠቃሚ ሰው ይሆናል” ወይም “እግዚአብሔር እርሱን እጅግ ጠቃሚ ሰው አድርጎ ያየዋል”
በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “መንፈስ ቅዱስ ኃይልን ይሰጠዋል” ወይም “መንፈስ ቅዱስ ምሪትን ይሰጠዋል።” ይህ አርፍተ ነገር ክፉ መንፈስ ሰውን እንደሚያረገው አይነት እንዳይመስል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በእናቱ ማሕጸን
“ገና በእናቱ ማሕጸን ውስጥ ሳለ” ወይም “ገና ሳይወለድ”
Luke 1:16
ብዙዎቹ የእስራኤል ሕዝቦች ወደ አምላካቸው እግዚአብሔር ይመለሳሉ
እዚህ ላይ “ይመለሳሉ” የሚለው ቃል አንድ ሰው ንስሃ ገብቶ እግዚአብሔርን ማምለክ መጀመርን የሚያመለክት ዘይቤ ነው። ይህም በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱም ብዙዎች የእስራኤል ሕዝቦችን ንስሐ እንዲገቡና አምላካቸው እግዚአብሔርን እንዲያመለኩ ያደርጋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በአምላክ ፊት ይሄዳል
ጌታ ከመምጣቱ በፊት፣ ጌታ እንደሚመጣ ለሰዎች ይሰብካል።
በጌታ ፊት
እዚህ ላይ “ፊት” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ሕልውና የሚያሳይ ፈሊጥ ነው። በአንዳንድ ትርጉሞች ላይ ተጽፎ ላይገኝ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦
“ጌታ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በኤልያስ መንፈስና ኃይል
“ኤልያስ በነበረው መንፈስና ኃይል፡፡” “መንፈስ“ የሚለው የእግዚአብሔርን መንፈስ ወይም ኤልያስ የነበረውን አስተሳሰብ ሊያሳይ ይችላል፡፡ “መንፈስ” የሚለው ቃል የሞትን ወይም የክፉን መንፈስ በሚለው እንዳይተረጎም ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች ይመልስ ዘንድ
“አባቶች ስለ ልጆቻቸው እንዲያስቡ ደግሞ ጠየቃቸው” ወይም “አባቶች ከልጆቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያድሱ ዘንድ”
ልባቸውን ይመልሳል
እዚህ ላይ ልብ አቅጣጫውን እንደሚቀይር ነገር ተደርጎ ተቀምጧል። ይህ የአንድ ሰው አስተሳሰብን ስለመቀየር ያመለክታል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ
“የማይታዘዙትን ወደ ጻድቃን ጥበብ ለመመለስ” ወይም “የማይታዘዙት ጠቢብ እንዲሆኑና የጻድቅ ሰዎችን ተግባር እንዲፈጽሙ ለማሳመን”
የማይታዘዙት
ይህ የሚያሳየው ጌታን የማይታዘዙትን ሰዎች ነው፡፡
ለጌታ የተዘጋጁትን ሕዝብ እንዲያሰናዳ
ሕዝቡ ምን ለማድረግ እንደሚዘጋጁ በግልጽ ማሳየት ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “መልዕክቱን ለማመን የተዘጋጁ ሕዝቦችን ለጌታ ማሰናዳት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 1:18
ይህን በምን አውቃለሁ?
“የተናገርኸው ነገር እንደሚፈጸም በእርግጠኝነት ማወቅ የምችለው እንዴት ነው?” እዚህ ላይ “ማወቅ” የሚለው ቃል በልምድ መማር ማለት ነው፣ ይህን ሃሳብ ያነሳው ዘካርያስ እንደ ማረጋገጫ ምልክት ጠይቆ ስለነበር ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ነገር እንደሚፈጸም ለእኔ ለማረጋገጥ ምን ልታደርግ ትችላለህ”
እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ
ይህ ለዘካርያስ እንደ ተግሳጽ ተደርጎ ተጽፏል፡፡ ከእግዚአብሔር ቀጥታ የመጣው የገብርኤል መገኘት ብቻ ለዘካርያስ በቂ ማረጋገጫ መሆን ነበረበት፡፡
የምቆመው
x
Luke 1:21
አሁን
ይህ በታሪኩ ውስጥ ቤተ መቅደስ ውስጥ ከተከሰተው ነገር ከቤተ መቅደስ ውጪ ወደተከሰተው ነገር ትኩረቱ መቀየሩን ያሳያል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ እየተከሰተ በነበረ ጊዜ” ወይም “መልዓኩና ዘካርያስ እየተነጋገሩ በነበረ ጊዜ”
በቤተ መቅደስ ውስጥ ራዕይ እንዳየ ተገነዘቡ፡፡ እርሱም ምልክቶችን ያሳያቸው ነበር፣ ዲዳም ሆኖ ቆየ
እነዚህ ነገሮች በተመሳሳይ ሰዓት የተከሰቱ እንደሆን ይገመታል፣ የዘካርያስ ምልክቶችም ሕዝቡ እርሱ ራዕይን እንዳይ እንዲገነዘቡ አድርገዋቸዋል፡፡ የነዚህን ቅደም ተከተል መቀየር አድማጩ የበለጠ መረዳት እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ዘካርያስ ምልክቶችን ያሳያቸው ነበር ዲዳም ሆኖ ኖረ፡፡ ስለዚህ በቤተ መቅደስ ውስጥ ሳለ ራዕይን እንደተመለከተ ሕዝቡ ተገነዘበ”
ራዕይ
ቀድሞ የተሰጠው መግለጫ ገብርኤል በእርግጥም ወደ ዘካርያስ ወደ ቤተ መቅደሱ እንደመጣ ያሳያል፡፡ ሕዝቡ ይህንን ባለማወቅ ዘካርያስ ራዕይ እንደተመለከተ አሰቡ፡፡
Luke 1:24
ከነዚህም ቀናት በኋላ
“እነዚህ ቀናት” የሚለው ሐረግ ዘካርያስ በቤተመቅደስ ውስጥ ያገለገለባቸውን ቀናት ያመለክታል፡፡ ይህ ምንን እንደሚያመለክት የበለጠ ግልጽ አድርጎ ማስረዳት ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ዘካርያስ በቤተመቅደስ ካገለገለበት ጊዜ በኋላ” (የአዲስ ሁነት መግቢያ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሚስቱ
“የዘካርያስ ሚስት”
ራሷን ደበቀች
“ከቤት አልወጣችም” ወይም “ ብቻዋን ቆየች”
ጌታ እንዲህ አድርጎልኛል
ይህ ጌታ ልጅ ማርገዝ እንድትችል እንዳስቻላት ያሳያል፡፡
እንዲህ አድርጎልኛል
ይህ አዎንታዊ የሆነ ግነት ነው። ጌታ ባደረገላት ነገር በጣም ደስተኛ ናት፡፡
በቸርነቱ ተመልክቶኛል
እዚህ ላይ “መመልከት” የሚለው ፈሊጥ ፈሊጥ ሲሆን ትርጉሙም “መንከባከብ” ወይም “በሚገባ መያዝ“ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በርህራሄ ተመለከተኝ” ወይም “አዘነልኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ነቀፌታዬን
ይህ እርሷ ልጆች ባለመውለዷ ይሰማት የነበረውን ነቀፋ ያሳያል፡፡
Luke 1:30
ማርያም ሆይ አትፍሪ
መልዓኩ ማርያም እርሱን አይታ እንድትፈራ አይፈልግም ምክንያቱም እግዚአብሔር መልካም መልዕክትን እንዲያደርስ ስለላከው ነው፡፡
በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አግኝተሻል
“ሞገስን ማግኘት” የሚለው ፈሊጥ በአንድ ሰው ዘንድ መልካም ተቀባይነትን ማግኘት ነው። የአርፍተ ነገሩን ቅደም ተከተል በመቀየር እግዚአብሔርን የድርጊቱ ባለቤት አድርጎ ማሳየት ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ጸጋውን ሊሰጥሽ ወስኗል” ወይም “እግዚአብሔር ቸርነቱን ላንቺ እያሳየ ነው” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ... ኢየሱስ ... የልዑል ልጅ
ማርያም “ወንድ ልጅን” ትወልዳለች ስሙም “የልዑል ልጅ” ይባላል፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ከሰው እናት የተወለደ የሰው ልጅ ነው፣ እርሱ የእግዚአብሔርም ልጅ ነው፡፡ እነዚህ ቃላት በጥንቃቄ መተርጎም አለባቸው፡፡
ይባላል
የዚህ ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉት 1) “ሰዎች ... ብለው ይጠሩታል” 2) “እግዚአብሔር ... ይጠራዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የልዑል ልጅ
ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለሆነው ለኢየሱስ እጅግ ወሳኝ የሆነ ስያሜ ነው፡፡ (ልጅ እና አባትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል
ዙፋን የሚየያሳየው የንጉስን የመግዛት ስልጣን ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አባቱ ዳዊት ይገዛ እንደነበር እርሱም እንዲገዛ ስልጣንን ይሰጠዋል” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ለመንግሥቱም መጨረሻ አይኖርም
“መጨረሻ አይኖርም” የሚለው አሉታዊ መግለጫ ለዘላለም የሚቀጥል መሆኑን አጽንኦት ይሰጣል። አርፍተ ነገሩ በአዎንታዊ ሐረግ መገለጽ ይችላል፡፡ “መንግስቱ እስከመጨረሻ አያበቃም” አማራጭ ትርጉም፡- (ምፀት የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 1:34
ይህ እንዴት ይሆናል
ምንም እንኳ ማርያም ነገሩ እንዴት እንደሚከሰት ባይገባትም፣ መከሰቱን ግን አልተጠራጠረችም፡፡
ከማንም ጋር ተኝቼ አላውቅም
ማርያም ይህንን ትህትና የተሞላበት አገላለጽ የተጠቀመችው እርሷ ከማንም ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ፈጽማ እንደማታውቅ ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ድንግል ነኝ” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይሆናል
የማርያም እርግዝና የሚጀምረው መንፈስ ቅዱስ ወደ እርሷ በመምጣት ነው፡፡
በአንቺ ላይ ይሆናል
“ይቆጣጠርሻል”
የልዑልም ኃይል
ማርያም ድንግል እያለች ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ሁኔታ እንድታረግዝ የሚያደርጋት የእግዚአብሔር “ኃይል” ነበር፡፡ይህ አካላዊ ወይም ወሲባዊ ትርጉም ያለው እንዳይመስል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፣ ይህ ተዓምር ነበር፡፡
በአንቺ ላይ ይሆናል
“እንደ ጥላ ይከልልሻል”
የሚወለደውም ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የሚወለደውንም ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ብለው ይጠሩታል” ወይም “የሚወለደውም ሕጻን ቅዱስ ይሆናል፣ ሰዎችም የእግዚአብሔር ልጅ ብለው ይጠሩታል፡፡ (ገቢር/አድራጊ ወይም

ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ቅዱሱ
“ቅዱሱ ልጅ” ወይም “ቅዱሱ ሕጻን”
የእግዚአብሔር ልጅ
ይህ ለኢየሱስ የተሰጠ ልዩ መጠርያ ማዕረግ ነው። (ልጅ እና አባትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 1:36
ዘመድሽን ተመልከች
“ትኩረት ስጪ፣ ምክንያቱም አሁን የምነገርሽ ነገር እውነትና እጅግ ጠቃሚ ነው፣ ዘመድሽ”
Luke 1:39
አያያዥ ሀሳብ፦
ማርያም የሕንስን ልትወልድ የነበረችውን ዘመዷን ኤልሳቤጥን ለመጎብኘት ወደ እርሷ ሄደች። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)
ተነሳች
ይህ ፈሊጥ ከተቀመጠችበት ተነሳች የሚለውን ትርጉም ብቻ ሳይሆን፣ “ተዘጋጀች” የሚለውንም ትርጉም ይይዛል። አማራጭ ትርጉም፦ “ጀመረች” ወይም “ተዘጋጀች” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ተራራማው ሀገር
“በተራራ የተሞላው አካባቢ” ወይም “የእስራኤል ተራራማው ክፍል”
ሄደች
x
Luke 1:42
ድምጿን ከፍ አድርጋ ... በጩኸት ተናገረች
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም ሲይዙ ኤልሳቤጥ ምን ያህል ደስተኛ እንደነበረች አጽንኦት ይሰጣሉ።ሁለቱን አደባልቆ አንድ ሐረግ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በአድናቆት ጮኸች” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ድምጿን ከፍ አደረገች
ይህ ፈሊጥ “ድምፁዋን አጩሃ ተናገረች” የሚለውን ትርጉም የያዘ ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ
“ከሴቶች መካከል” የሚለው ፈሊጥ “ከሌላ ሴት በሙሉ የተሻለች” የሚለውን ትርጉም ይይዛል። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
የማሕጸንሽ ፍሬ
የማርያም ልጅ እዚህ ላይ አንድ ተክል እንደሚያፈራው ፍሬ ተደርጎ ተጽፏል። አማራጭ ትርጉም፦ “በማሕጸንሽ ውስጥ ያለው ሕጻን” ወይም “የምታረግዥው ሕጻን” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ሆነልኝ?
ኤልሳቤጥ መልስ ፈልጋ ጥያቄን እየጠየቀች አይደለም። የጌታ እናት ወደ እርሷ በመምጣቷ ምን ያህል እንደተደነቀችና ደስተኛ እንደነበረች እያሳየች ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የጌታዬ እናት ወደ እኔ መምጣቷ እንዴት የሚደንቅ ነው!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
የጌታዬ እናት
ኤልሳቤጥ ማርያምን “የጌታዬ እናት” ብላ እንደጠራቻት “አንቺ” የሚለውን መግለጫ በመጨመር የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “አንቺ የጌታዬ እናት” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
እነሆ
ይህ ኤልሳቤጥ ቀጥላ ለምትናገረው አስገራሚ ነገር ማርያም ትኩረት እንድትሰጥ የሚናገር ቃል ነው።
የሰላምታሽ ድምጽ ወደ ጆሮዬ በደረሰ ጊዜ
የአንድን ነገር ድምጽ መስማትን “ድምጹ ወደ ጆሮ ደረሰ” በማለት ሊገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “የሰላምታሽን ድምጽ በሰማሁ ጊዜ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
በደስታ ዘለለ
“በድንገት በደስታ ተንቀሳቀሰ” ወይም “በጣም ከመደሰቱ የተነሳ በኃይል ዞረ”
ከጌታ የተነገራትን የምታምን የተባረከች ናት
ኤልሳቤጥ ለማርያም ስለ ራሷ ስለ ማርያም ነበር የምትነግራት። አማራጭ ትርጉም፦“ከጌታ የተነገረሽን የምታምኚ አንቺ የተባረክሽ ነሽ” (አንደኛ፣ ሁለተኛና ወይም ሶስተኛ መደብ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የምታምን ... የተባረከች ናት
በተደራጊ ቅርጽ የተቀመጠው ግስ በአድራጊ ቅርጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስላመነች እግዚአብሔር ይባርካታል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የእነዚህ ነገሮች ፍጻሜ ይሆናልና
“እነዚህ ነገሮቸ በእርግጠኝነት ይፈጸማሉ” ወይም “እነዚህ ነገሮች እውን ይሆናሉ”
ከጌታ ለእርሷ የተነገራት ነገሮች
መልእክቱን ሲናገር የሰማችው መልአኩ ገብርኤልን ነው (ሉቃስ 1:26 ይመልከቱ)፣ ነገር ግን መልእክቱ (“እነዚህ ነገሮች”) በዋነኛነት የመጣው ከጌታ ነበር። ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከጌታ የሰማችው መልእክት” ወይም “መልአኩ የነገራት የጌታ መልእክት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 1:46
አጠቃላይ መረጃ፦
ማርያም ለአምላኳና ለአዳኟ የምስጋናን መዝሙር መዘመር ትጀምራለች።
ነፍሴ ታመሰግነዋለች ... መንፈሴም ሐሴት ታደርጋለች
ሁለቱም “ነፍስ” እና “መንፈስ” የአንድ ሰው መንፈሳዊ ማንነት አካላት ናቸው። ማርያም አምልኮዋ ከውስጥ የመነጨ እንደሆነ ለማሳየት እንደዚህ ብላለች። አማራጭ ትርጉም፦ “የውስጥ ማንነቴ ያምሰግናል ... ልቤም እጅግ ሐሴትን አድርጓል” ወይም “አመሰግናለሁ ... ሐሴትም አደርጋለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
በ ... ሐሴትን አድርጋለች
“በ ... እጅግ ደስታ ተሰምቷታል” ወይም “በ ... እጅግ ተደስታለች”
አዳኜ እግዚአብሔር
“እኔን ያዳነኝ እግዚአብሔር” ወይም “የሚያደነኝ እግዚአብሔር”
Luke 1:48
እርሱም
“ምክንያቱም እርሱ”
ተመልክቷል
“በእንክብካቤ ተመለከተ” ወይም “በጥንቃቄ”
በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ
“ድህነት።” የማርያም ቤተሰብ ሃብታም አልነበረም።
እነሆም
ይህ ሐረግ ተከትሎ ለሚመጣው ንግግር ትኩረት እንዲሰጥ ያደርጋል።
ከአሁን በኋላ
“አሁንና ለወደፊቱ”
ትውልድ ሁሉ
“በእያንዳንዱ ትውልድ ያሉ ሕዝቦች በሙሉ”
ብርቱ የሆነው
“ኃይለኛው እግዚአብሔር”
ስሙም
እዚህ ላይ “ሰሙ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሙሉ የእግዚአብሔር ማንነትን ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “እርሱም” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 1:50
ምህረቱ
“የእግዚአብሔር ምህረት”
ከትውልድ እስከ ትውልድ
“ከአንድ ትውልድ እስከ ቀጣይ ትውልድ” ወይም “በእያንዳንዱ ትውልድ ውስጥ” ወይም “በማንኛውም ጊዜ ላይ ለሚኖሩ ሕዝቦች”
በክንዱ ኃይልን አሳይቷል
x
Luke 1:52
ገዢዎችን ከዙፋናቸው አውርዷል
ዙፋን ማለት ገዢ የሚቀመጥበት ወንበር ነው፣ ወንበሩ የስልጣኑም ምልክት ነው። ገዢ ከዙፋኑ ከወረደ በኋላ ሊገዛበት የሚችል ስልጣን የለውም ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የገዢዎችን ስልጣን ወስዷል” ወይም “ገዢዎች መግዛትን እንዲያቆሙ አድርጓቸዋል” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
ዝቅ ያሉትንም ከፍ አደረጋቸው


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በዚህ የቃላት መግለጫ መሰረት፣ ከፍተኛ ስፍራ ያላቸው ሰዎች ዝቅተኛ ስፍራ ካላቸው ይልቅ እጅግ ከፍ ያሉ እንደሆኑ ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “ትሁት ሰዎችን ታላቅ አደረጋቸው” ወይም “ሌሎች ሰዎች ያላከበሯቸውን ሰዎች እርሱ አከበራቸው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝቅ ያሉትን

“በድህነት ውስጥ ያሉትን።” ይህ በሉቃስ 1:48 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከት።

የተራቡትን መግቧል ... ባለጠጎችንም ባዶ እጃቸውን ልኳቸዋል

በእነዚህ ተቃራኒ ድርጊቶች መካከል ያለው ልዩነት ከተቻለ በትርጉሙ ላይ ግልጽ ይደረግ።

የተራቡትን በመልካም ነገር አጠገበ

የዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) “ለተራቡት ጥሩ የሚበላ ምግብ ሰጣቸው” ወይም 2) “ለተቸገሩት መልካምን ነገር ሰጣቸው”

Luke 1:54

አጠቃላይ መረጃ፡-

ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም ስለ እስራኤል የተቀመጠው መረጃ ሳይቀየር እንዲተላለፍ የእነዚህን ቁጥሮች ቅደም ተከተል በመቀያየር አንድ የመሸጋገርያ ቁጥር አድርጓቸዋል። (የጥቅስ ድልድዮች የሚለውን ይመልከቱ)

ረድቷል

x

Luke 1:56

አያያዥ ሀሳብ፡-

ኤልሳቤጥ ልጇን ትወልደዋለች ከዛም ዘካርያስ ለሕጻኑ ስም ያወጣለታል።

ወደ ቤቷ ተመለሰች

“ማርያም ወደ ቤቷ (ወደ ማርያም) ቤት ተመለሰች” ወይም “ማርያም ወደ ራሷ ቤት ተመለሰች”

አሁን

ይህ ቃል በታሪኩ ውስጥ ቀጣይ ክስተት መጀመሩን ይናገራል።

ልጇን ተገላገለች

“ልጇን ወለደች”

ጎረቤቶቿና እና ዘመዶቿ

“የኤልሳቤጥ ጎረቤቶችና ዘመዶች”

ታላቅ ምህረቱን እንዳሳያት

x

Luke 1:59

እንዲህም ሆነ

ይህ ሐረግ እዚህ ላይ ዋናው የታሪክ መስመር ተቆርጦ ሌላ ታሪክ ሊነገር መጀመሩን ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል። እዚህ ላይ ሉቃስ አዲስ ታሪክ መናገር ይጀምራል። (የአዲስ ሁኔት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

በስምንተኛው ቀን

እዚህ ላይ “ስምንተኛው ቀን” የሚለው ቃል ከሕጻኑ ውልደት በኋላ ያለውን ቀን ያሳያል ይህም ከመጀመርያው ቀን ጀምሮ ወይም ሕጻኑ ከተወለደበት ጀምሮ ተቆጥሮ ያለውን ቀን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በሕጻኑ ሕይወት በስምንተኛው ቀን” (ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)

ሕጻኑን ሊገርዙት መጡ

ይህ ብዙ ጊዜ አንድ ሰው ልጁን በሚገርዝበት ጊዜ ወዳጆቹ በዚያ ተገኝተው ከቤተሰቡ ጋር ሆነው የሚያከብሩበት ስነ ስርዓት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለሕጻኑ የግርዘት ሥርዓት መጡ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

... ብለው ሊጠሩት ነበር

“... ብለው ስም ሊያወጡለት ነበር” ወይም “... የሚል ስም ሊሰጡት ፈልገው ነበር”

በአባቱ ስም

“የአባቱን ስም”

በዚህ ስም

“በዚያ ስም” ወይም “በተመሳሳይ ስም”

Luke 1:64

አፉ ተከፈተ ... ምላሱም ተፈታ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች ዘካርያስ በድንገት መናገር መቻሉን አጽንኦት ይሰጣሉ። (ፈሊጥ እና ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

አፉ ተከፈተ እና ምላሱም ተፈታ

እነዚህ ሐረጎች በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር አፉን ከፈተለት ምላሱንም ፈታለት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አካባቢ ይኖሩ በነበሩ ላይ ሁሉ ፍርሃት ሆነ

“ከዘካርያስ እና ኤልሳቤጥ አካባቢ ይኖሩ በነበሩ ላይ ሁሉ” ለምን ፈርተው እንደነበር ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእነርሱ አካባቢ ይኖሩ የነበሩት ሁሉ እግዚአብሔር ለዘካርያስ እንዲህ በማድረጉ በእግዚአብሔር እጅግ ተደነቁ“ (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ አካባቢ ይኖሩ በነበሩ ላይ

“ሁሉ” የሚለው ቃል ጅምላ ፍረጃ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እነርሱ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ” ወይም “በዚያ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ብዙ ሰዎች” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ ነገሮች መከሰታቸው በይሁዳ ተራራማው ከተማ ሁሉ ተዳረሰ

“እነዚህ ነገሮች መከሰታቸው ... ተዳረሰ” የሚለው ሐረግ ሰዎች ስለ እነርሱ ማውራታቸውን የሚያሳይ ዘይቤ ነው። ጥቅም ላይ የዋለው ተደራጊ ቅርጽ በአድራጊ ቅርጽ መቀየር ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እነዚህ ነገሮች በሙሉ በይሁዳ ተራራማው ከተማ ይኖሩ በነበሩ ሰዎች ይወሩ ነበር” ወይም “በይሁዳ ተራራማው ከተማ የሚገኙ ሕዝቦች ስለ እነዚህ ነገሮች ያወሩ ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰሟቸው ሁሉ

“ስለተከሰቱት ነገሮች የሰሙ በሙሉ”

በልባቸው አኖሯቸው

ስለ ተከሰቱ ነገሮች ነገር ደጋግሞ ማሰላሰልና ማሰብ ነገሮቹን በልብ ውስጥ በጥንቃቄ እንደማኖር ተደርጎ ይታሰባል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ እነዚህ ነገሮች በጥንቃቄ ያስቡና ያሰላስሉ ነበር” ወይም “ስለ እነዚህ ክስተቶች ደጋግመው ያስቡ ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እያሉ በልባቸው አኖሯቸው

“እየጠየቁ በልባቸው አኖሯቸው”

ይሄ ሕጻን ምን ይሆን ይሆን?

“ይህ ሕጻን አድጎ ምን ዓይነት ልዩ ሰው ይሆን ይሆን?” ይህ ጥያቄ ሰዎቹ ስለ ሕጻኑ በሰሙት ነገሮች ያደረባቸውን መገረም ለመግለጽ የተጠቀሙበት መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ይሄ ልጅ አድጎ ምን ዓይነት ልዩ ሰው ይሆን ይሆን?” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የጌታ እጅ ከእርሱ ጋር ነበር

“የአምላክ እጅ” የሚለው ሐረግ የአምላክን ኃይል ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “የአምላክ ኃይል ከእርሱ ጋር ነበር” ወይም “አምላክ በእርሱ ውስጥ በኃይል ይሰራ ነበር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:67

አያያዥ ሀሳብ፡-

ዘካርያስ በልጁ በዮሐንስ ላይ ምን እንደሚሆን ተናገረ።

አባቱ ዘካርያስ መንፈስ ቅዱስን ተሞላቶ ትንቢት ተናረ

ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “መንፈስ ቅዱስ አባቱን ዘካርያስን ሞላው፣ ዘካርያስም ትንቢት ተናገረ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አባቱ

የዮሐንስ አባት

.... እያለ ትንቢትን ተናገረ

በራሳችሁ ቋንቋ ውስጥ ቀጥተኛ ጥቅሶችን የማስተዋወቂያ የተለመዱ መንገዶችን አስብ። አማራጭ ትርጉም፡- “ትንቢትን ተናገረ እንዲህም አለ” ወይም “ትንቢትን ተናገረ፣ የተናገረውም እንዲህ ነው ... “ (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)

.... እያለ ትንቢትን ተናገረ

በራሳችሁ ቋንቋ ውስጥ ቀጥተኛ ጥቅሶችን የማስተዋወቂያ የተለመዱ መንገዶችን አስብ። አማራጭ ትርጉም፡- “ትንቢትን ተናገረ እንዲህም አለ” ወይም “ትንቢትን ተናገረ፣ የተናገረውም እንዲህ ነው ... “ (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር

እዚህ ላይ “እስራኤል” የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ ነው። በእግዚአብሔር እና በእስራኤል መካከል ያለው ግንኙነት የበለጠ ቀጥተኝነት ባለው መልኩ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “በእስራኤልን ላይ የሚገዛው አምላክ እግዚአብሔር” ወይም “እስራኤል የምታመልከው አምላክ እግዚአብሔር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕዝቡ

“የእግዚአብሔር ሕዝብ”

Luke 1:69

የመዳንን ቀንድ አስነስቶልናል

የአንድ እንስሳ ቀንድ ራስን የመከላከል አቅሙን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። ማስነሳት ማለት ደግሞ ያልነበረን ማኖር ወይም አንድን ድርጊት መጀመርን ያሳይል። እዚህ ላይ መሲሑ እስራኤልን የማዳን ኃይል እንዳለው እንደ ቀንድ ምሳሌ ተደርጎ ተመስሏል። አማራጭ ትርጉም:- “(እግዚአብሔር) እኛን የማዳን ኃይል ያለውን ሰው ሰጥቶናል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በአገልጋዩ በዳዊት ቤት

“የዳዊት ቤት” የሚወክለው ቤተሰቡን ነው በተለይም ደግሞ ዘሮቹን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “በአገልጋዩ በዳዊት ቤተሰብ” ወይም “የአገልጋዩ ዳዊት ዘር የሆነ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

እንደተናገረ

“እግዚአብሔር እንዳለው”

ድሮ በነበሩት በነብያቱ አፍ እንደተናገረው

እግዚአብሔር በነብያቱ አፍ ተናገረ የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔር ነብያቱን እርሱ እንዲላቸው የፈለገውን እንዲናገሩ ማድረጉን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም:- “ድሮ የኖሩትን ቅዱሳን ነብያቱን እንዲናገሩ ያደረጋቸውን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

ድሮ የኖሩትን … ማዳኑ ከጠላቶቻችን ነው

“ማዳን” የሚለው ረቂቅ ቃል “መታደግ” እና “ማትረፍ” በሚሉት ግሶች ተለውጦ መገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ድሮ የኖሩትን …. እርሱም ከጠላቶቻችን ይታደገናል።” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

ከሚጠሉን … ከጠላቶቻችን

እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ይይዛሉ፣ የተደጋገሙትም ጠላቶቻቸው ምን ያህል ይቃወሟቸው እንደነበረ አጽንኦት ለመስጠት ነው። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

እጅ

እጅ የሚለው ቃል አንድ ሰው ኃይሉን የሚለማመድበትን እጅ የሚወክል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ኃይል” ወይም “ቁጥጥር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:72

ለ …. ምህረትን ማሳየት …

“ለ … መሃሪ መሆን” ወይም “ለ … እንደ ምህረቱ ማድረግ”

አስታወሰ

እዚህ ላይ “አስታወሰ” የሚለው ቃል ቃለኪዳንን መጠበቅ ወይም አንድን ነገር መፈጸምን ያሳያል።

ቅዱስ ኪዳኑን፣ የተናገረውንም መሃላ

እነዚህ ሁለት ሐረጎት ተመሳሳይ ትርጉምን ይይዛሉ። መደጋገማቸው እግዚብሔር ለአብርሃም የገባው ቃልኪዳን ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ያሳያል። (ትይዩነት የሚለውን ይመልከቱ)

ሰጠን

“እኛ … ማድረግ እንድንችል አደረገ”

ከጠላቶቻችን እጅም ነጻ ወጥተን እርሱን ያለ ፍርሃት እንድናገለግለው

ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ከጠላቶቻችን እጅ ካስመለጠን በኋላ ያለ ፍርሃት እርሱን እንድናገለግለው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጠላቶቻችን እጅ ወጥተን

x

Luke 1:76

አዎ፣ አንተ ደግሞ

ዘካርያስ ይህንን ሐረግ ቀጥታ ለልጁ መናገር መጀመሩን ለማሳየት ይጠቀማል። በራሳችሁ ቋንቋ ይህንን ንግግር ለመጀመር የሚሆን መንገድ መጠቀም ይቻላል።

አንተ ሕጻን ሆይ ነብይ ትባላለህ

ሰዎች እርሱ ነብይ እንደሆነ ይረዳሉ። ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ሰዎች አንተ ነብይ መሆንህን ያውቃሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የበላይ የሆነው

እነዚህ ቃላት እግዚአብሔርን ለመግለጽ የምንጠምባቸው ለስላሴ ዘይቤያዊ ቃላት ናቸው። አማራጭ ትርጉም:- “የበላይ የሆነውን የሚያገለግል” ወይም “የበላይ ለሆነው ለእግዚአብሔር የሚናገር” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ከጌታ ፊት ትሄዳለህ

ጌታ ከመምጣቱ በፊት እርሱ ሄዶ ጌታ ወደ እነርሱ እነደሚመጣ ይነግራቸዋል። ይህንን በሉቃስ 1:17.

በጌታ ፊት

የአንድ ሰው “ፊት” የዛን ሰው መገኘት ይወክላል። ብዙ ጊዜ በትርጉሞች ላይ ተጽፎ አይገኝም። አማራጭ ትርጉም:- “ጌታ” ይህን በሉቃስ 1:17 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።. (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

መንገዱን ለማዘጋጀት

ይህ የሐንስ ሰዎች የጌታን መልዕክት እንዲሰሙና እንዲያምኑ ያዘጋጃቸዋል የሚለውን መልዕክት የያዘ ዘይቤ ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በኃጢአታቸው ምህረት ማግኘት … የድነትን እውቀት ትሰጣለህ

“እውቀት ትሰጣለህ” የሚለው ሐረግ ማስተማር የሚለውን ትርጉም የያዘ ዘይቤ ነው። “ድነት” እና “ምህረት” የሚሉት ረቂቅ ቃላት “ማዳን” እና “ይቅር ማለት“ በሚሉት ቃላት ሊገለጹ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም:- “ለሰዎች በኃጢአታቸው ይቅር መባል መዳናቸውን ያስተምራል” ወይም “ለሰዎች እንዴት እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር በማለት እንዳዳናቸው ያስተምራል” (ምትክ ስም እና ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:78

በአምላካችን ርህራሄና ምህረት

የእግዚአብሔር ምህረት ሰዎችን እንደሚረዳ መግለጽ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም:- “ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእኛ ሩህሩህና መሃሪ ስለሆነ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከላይ የመጣ የጸሐይ ብርሃን …. እንዲያበራ

ብርሃን ብዙ ጊዜ የእውነት ምሳሌ ነው። እዚህ ላይ አዳኙ ለእኛ የሚሰጠው መንፈሳዊ እውነት ዓለምን ሁሉ በብርሃን የሚሞላ የጸሐይ ብርሃን ተደርጎ ተመስሏል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ማብራት

“እውቀት መስጠት” ወይም “መንፈሳዊ ብርሃንን መስጠት”

በጨለማ ለተቀመጡ

ጨለማ እዚህ ላይ የመንፈሳዊ እውነት እጦትን ወይም አለመገኘትን ይወክላል። እዚህ ላይ መንፈሳዊ እውነት የሌላቸው ሰዎች በጨለማ ውስጥ እንደተቀመጡ ተደርገው ተመስለዋል። አማራጭ ትርጉም:- “እውነትን የማያውቁ ሕዝቦች” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጨለማ … የሞት ጥላ

እነዚህ ሁለት ሐረጎች አንድ ላይ በመሆን እግዚአብሔር ምህረቱን ለእነርሱ ከማድረጉ በፊት ሰዎች ላይ የነበረውን ጥልቅ ጨለማ አስከፊነት ይገልጻሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

በሞት ጥላ

ጥላ ብዙ ጊዜ ሊመጣ ያለውን ነገር ይገልጻል። እዚህ ላይ እየመጣ ያለን ሞትን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም:- “ለሞቱ ያሉ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

እግሮቻችንንም በሰላም መንገድ ይመራል

እዚህ ላይ “መምራት” የሚለው ቃል ማስተማር ለሚለው ቃል ዘይቤ ነው፣ “የሰላም መንገድ” የሚለው ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር በሰላም መኖርን የሚወክል ዘይቤ ነው። “እግሮቻችንን” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ሙሉ ማንነት የሚወክል ነው። አማራጭ ትርጉም:- “ከእግዚአብሔር ጋር በሰላም መኖርን ያስተምረናል”(ተለዋጭ ዘይቤ እና ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 1:80

አጠቃላይ መረጃ:-

ይህ የሐንስ እያደገ ስለመጣባቸው አመታት ይናገራል።

አሁን

ይህ ቃል ዋናው የታሪክ መስመር መቋረጡን ያመለክታል፡፡ ሉቃስ ስለ የሐንስ ውልደት ከመናገር በፍጥነት ወጥቶ የሐንስ አድጎ ያደርግ ስለነበረው አገልግሎት ይናገራል፡፡

በመንፈስ ጠነከረ

“በመንፈስ እየበሰለ መጣ” ወይም “ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት አጠነከረ”

በምድረ በዳ ነበር

“በምድረ በዳ ኖረ” ሉቃስ የሐንስ በምን እድሜ ላይ በምድረ በዳ መኖር እንደጀመረ አይናገርም፡፡

እስከ ታየበት ቀን ድረስ

ይህ ከጊዜ ጋር በተያያዘ ያቆመበትን ነጥብ የግድ አያመለክትም፡፡ የሐንስ በአደባባይ መስበክ ከጀመረ በኋላም እንኳ ቢሆን በምድረ በዳ ይኖር ነበር፡፡

በአደባባይ መታይ እስኪጀምር

“በአደባባይ መስበክ እስከሚጀምር ደረስ”

እስከጀመረበት ቀን

ይህ በጠቅላላው “ጊዜውን” እና “ሁኔታውን” ለመናገር ጥቅም ላይ ነው የዋለው፡፡

---

## Chapter 2

### Luke 2:1

አጠቃላይ መረጃ፡-

ይህ ማርያምና ዮሴፍ በኢየሱስ ውልደት ወቅት ለምን በጉዞ ላይ እንደነበሩ ጠቅላላ የጀርባ መረጃን ይሰጣል፡፡

አሁን

ይህ ቃል የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ይናገራል፡፡ (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ ሆነ

ይህ ሐረግ ቦታው የአዲስ ታሪክ ጅማሬ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ቋንቋችሁ ለታሪክ መጀመርያ የተለየ መግለጫ ካለው እሱን መጠቀም ይቻላል፡፡ አንዳንድ ትርጉሞች ይህንነ ሐረግ አያካትቱትም፡፡

አውግስጦስ ቄሣር

“ንጉሥ አውግስጦስ” ወይም “አጼ አውግስጦስ” አውግስጦስ የሮም ግዛት የመጀመርያው ንጉሥ ነበር፡፡ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ትዕዛዝ ያለበት ጽሑፍ ላከ

ይህ ትዕዛዝ በተለያዩ መልዕክተኞች አማካኝነት በግዛቱ ውስጥ እንደተሰራጨ ይገመታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ትዕዛዝ ያለበትን ጽሑፍ በመልዕክተኞች ላከ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

በዓለም ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ ቆጠራ እንዲደረግ

ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በዓለም ላይ የሚኖሩትን ሕዝቦች በሙሉ እንዲመዘግቡ” ወይም “በዓለም ላይ የሚገኙ ሕዝቦችን በሙሉ እንዲቆጥሩና ስማቸውን እንዲመዘግቡ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ዓለም

እዚህ ላይ “ዓለም” የሚለው ቃል አውግስጦስ ቄሣር ይገዛ የነበረውን የዓለም ክፍል ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “በግዛቱ ውስጥ” ወይም “የሮም ዓለም” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

ቄሬኔዎስ

ቄሬኔዎስ የሦርያ ክፍለ ሐገርን እንዲገዛ የተሾመ ሰው ነው፡፡ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ሁሉም ... ሄደ

“ሁሉም ጉዞ ጀመሩ” ወይም “ሁሉም እየሄዱ ነበር”

ወደ ከተማው

ይህ የሰዎች አባቶችና አያቶች ይኖሩበት የነበረውን ከተማ ይወክላል፡፡ ሰዎች በተለያየ ከተሞች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አባትና አያቶቻቸው ይኖሩበት ወደነበረው ከተማ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለቆጠራው ለመመዝገብ

“በመዝገብ ውስጥ ስማቸውን ለማስመዝገብ” ወይም “መንግስት እያደረገ ባለው ቆጠራ ውስጥ ለመካተት”

### Luke 2:4

አጠቃላይ መረጃ፡-

ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም አርፍተ ነገሮቹን ለማሳጠር እነዚህን ሁለት ቁጥሮች አንድ ላይ በማድረግ አንድ የመሸጋገርያ ቁጥር አድርገዋቸዋል፡፡ (የጥቅስ ድልድዮች የሚለውን ይመልከቱ)

ዮሴፍም

ይህ ዮሴፍን በታሪኩ ውስጥ እንደ አንድ ተሳታፊ አድርጎ ያስተዋውቀዋል፡፡ (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ቤተልሔም ወደተባለችው የዳዊት ከተማ

“የዳዊት ከተማ” የሚለው ሐረግ ቤተልሔም ምን አይነት ወሳኝ ከተማ እንደሆነች የሚያሳይ የቤተልሔም ከተማ ስም ነው፡፡ ምንም እንኳ ትንሽ ከተማ ብትሆንም ንጉሥ ዳዊት የተወለደው በዚች ከተማ ነው፣ መሲሑም በዚው ከተማ እንደሚወለድ የሚናገር ትንቢት ነበር፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የንጉሥ ዳዊት ከተማ ወደነበረችው ወደ ቤተልሔም” ወይም “ንጉሥ ዳዊት ወደተወለደበት ከተማ ወደ ቤተልሔም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የዳዊት ወገንና ቤት ስለነበር

“ምክንያቱም ዮሴፍ የዳዊት ዘር ስለነበር”

ለመጻፍ

ይህ ማለት በሕዝብ ቆጠራው ውስጥ እንዲያካትቱት ለመንግስቱ ሹማምንት ለማሳወቅ ማለት ነው፡፡ የሚቻል ከሆነ የመንግስት የሕዝብ ቆጠራን የሚገልጽ ቃል ተጠቀም፡፡

ከማርያም ጋር

ማርያም ከዮሴፍ ጋር ከናዝሬት ተነስታ ተጉዛ ነበር፡፡ ሴቶችም እንደወንዶች ቀረጥ ይጣልባቸው ስለነበረ እርሷም አብራ ተጉዛ መመዝገብ ነበረባት፡፡ (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ታጭታ የነበረችው

“እጮኛው” ወይም “ለእርሱ ቃል ገብታለት የነበረች” እጮኛ የነበሩ ጥንዶች በሕግ እንደተጋቡ ተደርገው ይታሰባሉ ነገር ግን በመካከላቸው ምንም አይነት አካላዊ ግንኙነት አይኖርም ነበር፡፡

### Luke 2:6

አያያዡ ሀሳብ፡-

ይህ የኢየሱስን ውልደትን እና ለበግ ጠባቂዎች የመላዕክቱን ብስራት ይናገራል፡፡

አጠቃላይ መረጃ፡-

ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም (እነ ዮሴፍ) የቆዩበትን ቦታ ዝርዝር መረጃ ለመጠበቅ ሲባል እነዚህን ቁጥሮች ቅደም ተከተላቸውን በመቀያየር አንድ መሸጋገርያ ቁጥር አድርጓቸዋል፡፡ (የጥቅስ ድልድዮች የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ

ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ ቀጣዩ ክስተት መጀመሩን ያሳያል፡፡ (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

በዚያም ሳሉ

“ማርያምና ዮሴፍ በቤተልሔም እያሉ”

ልጇን የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ

“ልጇን የምትገላገልበት ጊዜ ደረሰ”

በረዥም የጨርቅ ብጣሽ ጠቀለለችው

በአንዳንድ ባህሎች እናቶች ልጆቻቸውን በጨርቅ ወይም በብርድ ልብስ በመጠቅለል እንዲመቻቸው ያደርጋሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሙሉ ሰውነቱን በጨርቅ ጠቀለለችው” ወይም “በብርድ ልብስ አጥብቃ ጠቀለለችው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በግርግም አስቀመጠችው

ይህ በተለየ ሁኔታ የሚሰራ እንስሶች እንዲበሉ መኖ ወይም ሌላ የከብት ምግብ የሚቀመጥበት የምግብ ማስቀመጫ ሳጥን ነገር ነው፡፡ ንጹህ እንደነበረና ለስላሳና ጠንከር ያለ ለሕጻኑ የሚመች መተኛ የሚሆን የሳር ድርቆሽ ክምር እንደነበረው ይገመታል፡፡ ከብቶች ከዋናው ቤት ሳይርቅ ቅርብ የሆነ ቦታ ላይ መኖርያ ይሰራላቸዋል፣ ይህም እነርሱን ለመመገብና ለመጠበቅ እንዲመች ነው፡፡ ማርያምና ዮሴፍ በእንስሳት መኖርያ ውስጥ ነበር ይቆዩ የነበረው፡፡

በእንግዶች ማረፍያ ውስጥ ለእነርሱ ቦታ አልነበረም

“በእንግዶ ማረፍያ ክፍል ውስጥ እነርሱ ሊያርፉ የሚችሉበት ቦታ አልነበረም” ቦታ ያለመኖሩ ምክንያት ብዙ ሰዎች ለመመዝገብ ወደ ቤተልሔም መጓዛቸው እንደሆነ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይገመታል። ሉቃስ ይህንን እንደ ተጨማሪ የጀርባ መረጃ ይናገራል። (የጀርባ ታሪክ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 2:8
የጌታ መልዓክ
“ከጌታ የተላከ መልዓክ” ወይም “ጌታን ያገለግል የነበረ መልዓክ”
ታያቸው
“ወደ እረኞቹ መጣ”
የጌታ ክብር
የብርሃኑ ምንጭ ከመልዓኩ መታየት ጋር በተመሳሳይ ሰዓት መጥቶ የነበረው የጌታ ክብር ነው።.
Luke 2:10
አትፍሩ
“መፍራት አቁሙ”
Luke 2:13
ብዙ የሰማይ ሰራዊት
“የሰማይ ሰራዊት” የሚለው ሐረግ ቃል በቃል የመላዕክትን ሰራዊትን፣ ወይም የተቀናጀ የመላዕክትን ስብስብ ሊወክል ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ከሰማይ ብዙ መላዕክት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን እያመሰገኑ
“ለእግዚአብሔር ምስጋናን በመስጠት”
ክብር በከፍታ ለሚኖረው ለእግዚአብሔር ይሁን
የዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት 1) ”በከፍታ ለሚኖረው ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን ወይም” 2) “ከፍ ያለ ክብር ለእግዚአብሔርን ይሁን”
እርሱ የሚደሰትባቸው ሰዎች ባሉበት በምድርም ሰላም ይሁን
“በምድር ያሉ እግዚአብሔር የሚደሰትባቸው ሰዎች ሰላምን ያግኙ”
Luke 2:15
እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ መልዓክቶቹ ከሄዱ በኋላ እረኞቹ ወዳደረጉት ነገር የታሪኩን ትኩረት ይቀይራል።
ከእነርሱ
“ከእረኞቹ”
እርስ በርሳቸው
“አንዱ ለሌላው”
“እናድርግ (እንይ፣ እንሂድ) … ለእኛ (የተገለጠልን)”
እረኞቹ እርስ በርሳቸው እየተነጋገሩ ስለነበር፣ “እኛ” የሚል መደብ ያላቸው ቃላት በአካታች ቅርጻቸው ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። (አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)
እናድርግ (እንይ፣ እንሂድ)
“ማድረግ አለብን”
የተከሰተውን ይሄን ነገር
ይህ የሚወክለው የሕጻኑን ውልደት እንጂ የመላዕክቱን መታየት አይደለም።
በግርግም ተቀምጦ
ይህ ሰዎች እንስሶች የሚበሉትን እንደ ሳር ድርቆሽ አይነት ምግብ እንዲበሉ የሚያስቀምጡበት የተለየ ሳጥን ነገር ነው። ይህ በሉቃስ 2:7 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ።
Luke 2:17
የተነገራቸውን
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “መላዕክቱ ለእረኞቹ የነገሯቸውን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
(ስለዚህ) ሕጻን
“ሕጻኑ”
በእረኞቹ የተነገራቸውን
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እረኞቹ የነገሯቸውን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በልቧ ውስጥ ትጠብቀው ነበር
አንድ ሰው አንድ ነገር ዋጋ እንዳለው ወይም የከበረ እንደሆነ ካሰበ ልቡ ውስጥ “ይጠብቀዋል።” ማርያም ስለ ልጁ የተነገሩትን ነገሮች በሙሉ እጅግ የከበሩና ትልቅ ዋጋ እንዳላቸው ታስብ ነበር። አማራጭ ትርጉም፦ “በጥንቃቄ ታሰላስል ነበር” ወይም “በደስታ ታስበው ነበር” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 2:21
አጠቃላይ መረጃ፦
እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን የሰጠው ሕግ ወንድ ሕጻናትን መቼ መገረዝ እንዳለባቸውና ወላጆቹ ደግሞ ምን ዓይነት መስዋዕት ማምጣት እንዳለባቸው ይነግሯቸዋል።
በስምንተኛው ቀን ማለቂያ
ይህ ሐረግ አዲስ ክስተት ከመከሰቱ በፊት ያለፈውን ጊዜ ይናገራል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)
በስምንተኛው ቀን ማለቂያ
“በሕጻኑ ሕይወት በስምንተኛው ቀን ማለቂያ።” ልጁ የተወለደበት ቀን እንደ አንደኛ ቀን ይቆጠራል።
Luke 2:22
የታዘዘው ቀን ብዛት ባለፈ ጊዜ
ይህ ከዚህ አዲስ ክስተት በፊት ያለፈውን ጊዜ ያሳያል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)
የታዘዘው ቀን ብዛት
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር ያዘዘው የቀን ብዛት” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ለመንጻታቸው
“እነርሱ በስርዓቱ መሰረት ንጹሕ እንዲሆኑ።” እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ድርሻም ማብራራት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር እንደገና ንጹሃን እንደሆኑ እስኪቆጥራቸው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለጌታ ሊያቀርቡት
x
Luke 2:25
አያያዥ ሀሳብ፦
ማርያምና ዮሴፍ በቤተ መቅደስ ውስጥ እያሉ ሁለት ሰዎች ያገኛሉ፣ እነዚህም ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመሰግነውና ስለሕጻኑ ትንቢትን የተናገረው ስምኦንና ነብይቷ ሃና ናቸው።
እነሆ
“እነሆ” የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ አዲስ ውስጥ አዲስ ሰውን ያስተዋውቃል። ቋንቋችሁ ይህንን ማሳያ የራሱ መንገድ ሊኖረው ይችላል። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)
ጻድቅና ትጉ ነበር
እነዚህ ረቂቅ ቃላት እንደ ድርጊት ተደርገው መገለጽ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፦ “ጽድቅን ይፈጽም ነበር፣ እግዚአብሔርንም ይፈራ ነበር” ወይም “የእግዚአብሔርን ሕግ ይታዘዝ ነበር እግዚአብሔርንም ይፈራ ነበር።
የእስራኤል መጽናናት
“እስራኤል” የሚለው ቃል የእስራኤልን ሕዝብ የሚወክል ምትክ ስም ነው። “ማጽናናት” ማለት አንድን ሰው “ማበረታታት” ነው። “የእስራኤል መጽናናት” ማለት ክርስቶስ ወይም መሲሑ ለእስራኤል ሕዝብ የሚያመጣውን መጽናናት የሚወክል ሐረግ ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “የእስራኤል ሕዝብን የሚያጽናናው” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ ነበር
“መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ጋር ነበር” እግዚአብሔር በተለየ መንገድ ከእርሱ ጋር ነበር፣ በሕይወትም ጥበብና ምሪትን ይሰጠው ነበር።
በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት ነበር
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “መንፈስ ቅዱስ አሳይቶት ነበር” ወይም “መንፈስ ቅዱስ ነግሮት ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በጌታ የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንደማያይ
“ሳይሞት በፊት በጌታ የተቀባውን መሲህ ያየዋል”
Luke 2:27
በመንፈስ ተመርቶ
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “መንፈስ ቅዱስ እንደመራው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
መጣ
አንዳንድ ቋንቋዎች “ሄደ” ሊሉ ይችላሉ።
ወደ ቤተ መቅደስ ውስጥ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ወደ ቤተ መቅደስ ቅጥር ግቢ ውስጥ” ወደ ቤተ መቅደስ ሕንጻ ውስጥ መግባት የሚችሉት ካህናት ብቻ ናቸው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ወላጆቹ
“የኢየሱስ ወላጆች”
እንደ ሕጉ ልማድ
“እንደ እግዚአብሔር ሕግ ልማድ”
ወደ እጆቹ ውስጥ አስገባው
“ስምኦን ሕጻኑን ኢየሱስን ወደ እጆቹ አስገባው” ወይም “ስምኦን ኢየሱስን በእጆቹ ያዘው”
አሁን ባርያህን በሰላም አሰናብተው
“እኔ አገልጋይህ ነኝ፣ በሰላም አሰናብተኝ” ስምኦን ስለራሱ ነበር የሚያወራው።
መሰናበት
ይህ “መሞት” ለሚለው ቃል ለስላሴ ዘይቤ ነው። (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ ቃልህ
“ቃል” የሚለው “ቃልኪዳን” ለሚለው ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እንደገባኸው ቃልኪዳን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 2:30
ዓይኖቼ አይተዋል
ይህ አገላለጽ “በግሌ አይቻለሁ” ወይም “እኔ እራሴ አይቻለሁ” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
ማዳንህን
ይህ አገላለጽ ድነትን የሚያመጣውን ሰው ስምኦን በእጁ ይዞት የነበረውን ሕጻኑን ኢየሱን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የላክከውን አዳኝ” ወይም “እንዲያድን የላክከውን” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ የላክኸው
የቀደመው ሐረግ እንደተተረጎመት አተረጓጎም፣ ይህ “አንተ የላክኸውን” ወደሚለው ሊለወጥ ይችላል።
ያዘጋጀኸውን
“ያሰብከውን” ወይም “እንዲከሰት ያደረግከውን”
ለአህዛብ የሚገልጥ ብርሃን
ይህ ዘይቤ ሕጻኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅና መረዳት እንዲችሉ ይረዳቸዋል የሚለውን ይገልጻል። እዚህ ላይ የአሕዛብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መረዳት ሰዎች አንድን ቁስ ለማየት ብርሃንን እንደሚጠቀሙት ተደርጎ ተመስሎ ቀርቧል። አሕዛብ የሚመለከቱት ምን እንደሆነ በግልጽ ማሳየት አለብህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ሕጻን ብርሃን ሰዎች አጥርተው መመልከት እንዲችሉ እንደሚያደርግ፣ ልክ እንደዛ እርሱም አሕዛብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲሁ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚገልጥ
የሚገለጠው ነገር ምን እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔርን እውነት የሚገልጥ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለሕዝብህ ለእስራኤል ክብር
“እርሱ ለሕዝብህ ለእስራኤል ክብር መምጣት ምክንያት ይሆናል”
Luke 2:33
ስለ እርሱ በተባሉት ነገሮች
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስምኦን ስለ እርሱ በተናገራቸው ነገሮች” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእናቱ ለማርያም እንዲህ አላት
“ለሕጻኑ እናት ለማርያም እንዲህ አላት።“ ማርያም የስምኦን እናት የሆነች መስሎ እንዳይታይ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠይቃል።
እነሆ
ስምኦን ይሄን አገላለጽ የሚጠቀመው ለማርያም ቀጥሎ የሚነግራት ነገር እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ለማሳየት ነው።
ይህ ሕጻን በእስራኤል ለብዙዎች መውደቅና መነሳት ተሸሟል
“መውደቅ” እና “መነሳት” የሚሉት ቃላት ከእግዚአብሔር መራቅ እና ወደ እግዚአብሔር መጠጋት የሚሉትን ትርጉም ይዘዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ሕጻን በእስራኤል ለብዙዎች ከእግዚአብሔር የመራቅና ለብዙዎችም ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ምክንያት ይሆናል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ለሚቃወሙትም ምልክት
“ብዙ ሰዎች ስለሚቃወሙት ስለ እግዚአብሔር መልዕክት ምልክት”
በነፍስሽ ውስጥ ሰይፍ ያልፋል
ይህ ዘይቤ ማርያም ወደፊት የሚሰማትን ጥልቅ የሆነ ሀዘን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሐዘንሽ ልብሽ በሰይፍ እንደተወጋ ያህል እጅግ ጥልቅ ይሆናል“ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የብዙ ልቦች አሳብ ይገለጥ ዘንድ
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሰዎችን ውስጣዊ ማንነት ይወክላል። ይህ በአድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የብዙ ሰዎችን ሃሳብ ይገልጥ ዘንድ” ወይም “ብዙ ሰዎች በድብቅ የሚያስቡን ይገልጥ ዘንድ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 2:39
አያያዥ ሀሳብ፦
ማርያም ዮሴፍና ኢየሱስ ቤተልሔም ከተማን ለቅቀው ኢየሱስ ልጅነቱን ወደሚያሳልፍባት ወደ ናዝሬት ከተማ ይመለሳሉ።
በጌታ ሕግ መሰረት እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸውን
ይህ በአድራጊ ቅርጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “የእግዚአብሔር ሕግ እንዲያደርጉ የሚያዝዘውን” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 2:41
አያያዥ ሀሳብ፦
ኢየሱስ 12 ዓመት ሲሞላው ከቤተሰቡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። በዚያም እያለ የቤተ መቅደስ መምህሮችን ጥያቄዎች ይጠይቃቸው ነበር፣ እርሱም የእነርሱን ጥያቄዎች ይመልስላቸው ነበር።
ለፋሲካ በዓል ... ወላጆቹ ሄዱ
ይህ ተጨማሪ የጀርባ መረጃ ነው። (የጀርባ ታሪክ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ወላጆቹ
“የኢየሱስ ወላጆች”
ደግመው ወጡ
ኢየሩሳሌም በእስራኤል ከሚገኙ ከሌሎች ቦታዎች በመሬት ከፍታ ከፍ ብላ የምትገኝ ከተማ ነበረች፣ ስለዚህ ወደ ኢየሩሳሌም ስለመሄድ ሲወራ “መውጣት” ተብሎ ሊገለጽ ይችላል።
በሥርዓቱ ሰዓት
“በተለመደው ሰዓት” ወይም “በየዓመቱ ያደርጉ እንደነበረው”
የክብረ በዓሉንም ሙሉ ቀናት ቆይተው ከጨረሱ በኋላ
“ክብረ በዓሉ የሚከበርባቸው ቀናት ካለፉ በኋላ” ወይም “ክብረ በዓሉ መከበር ላለበት ቀናት አክብረው ከጨረሱ በኋላ”
ግብዣ
x
Luke 2:45
እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ የተከሰተን ወሳኝ ክስተት ያሳያል። ቋንቋችሁ እንደዚህ ዓይነትን ነገር ማሳያ መንገድ ካለው እሱን መጠቀም ይቻላል።
በቤተ መቅደስ
ይህ የመቅደሱ ቅጥር ግቢን ያሳያል። ወደ ቤተ መቅደስ ውስጥ መግባት የሚችሉት ካህናት ብቻ ነበሩ። አማራጭ ትርጉም፡- “በመቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ” ወይም “በቤተ መቅደስ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በመካከል
ይህ ቃል በቃል መሃል ላይ ማለት አይደለም። ይልቁንም “አብሮ ሆኖ” ፣ “በእነርሱ መካከል” ወይም “በእነርሱ ተከብቦ” የሚለውን ትርጉም ይይዛል።
አስተማሪዎቹ
“የኃይማኖት መምህሮች” ወይም “ስለ እግዚአብሔር ለሰዎች ያስተምሩ የነበሩ”
የሰሙት ሁሉ ይገረሙ ነበር
12 ዓመቱ የሆነና፣ የኃይማኖት ትምህርት ያልተማረ አንድ ልጅ በጥሩ ሁኔታ ጥያቄዎችን መመለስ መቻሉ እንዴት እንደሆነ አልገባቸውም።
በማስተዋሉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ምን ያህል ማስተዋል በመቻሉ” ወይም “ስለ እግዚአብሔር ብዙ ማስተዋል በመቻሉ”
መልሶቹ
“እንዴት በጥሩ ሁኔታ እንደመለሰላቸው” ወይም “ጥያቄዎቻቸውን በጥሩ ሁኔታ በመመለሱ”
Luke 2:48
ሲያዩት
“ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስን ሲያገኙት”
ለምን እንዲህ ታደርገናለህ?
ይህ ቀጥተኛ ያልሆነ ተግሳጽ ነው ይህም እርሱ ወደ ቤት ሲሄዱ አብሯቸው ስላልነበረ ነው። ይህ ስለ እርሱ እንዲጨነቁ አድርጓቸው ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “እኛን እንዲህ እንድንሆን ማድረግ አልነበረብህም!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ስሙ
ይህ ቃል ብዙ ጊዜ አንድ አዲስ ወይም ወሳኝ የሆነ ሁነት ሊጀምር መሆኑን ለማሳየት ጥቅም ላይ የሚውል ነው። ከዚህ በተጨማሪ ይህ አዲስ ድርጊት የት እንደሚጀምር ላማሳየት ሊጠቅም ይችላል። በቋንቋችሁ ውስጥ በእንዲህ ዓይነት መንገድ ጥቅም ላይ የሚውል ሀረግ ካለው እዚህ ላይ ለመጠቀም አግባብነት ያለው መሆኑን አስብ።
ለምን ፈለጋችሁኝ?
ኢየሱስ ወላጆቹን በለስላሴው ለመገሰጽ ሁለት ጥያቄዎችን ይጠቀማል፣ እርሱ ያልተረዱት በሰማይ ያለው አባቱ የሰጠው ዓላማ እንዳለም ይነግራቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ እኔ መጨነቅ የለባችሁም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
(... ማድረግ) እንዳለብኝ .... አታውቁም?
ኢየሱስ ወላጆቹ አባቱ ሊያደርገው የሰጠው ዓላማ እንዳለ ማወቅ እንዳለባቸው ለመንገር ሁለተኛውን ጥያቄ ይጠቀማል። “(ማድረግ) እንዳለብኝ ማወቅ ነበረባችሁ” አማራጭ (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ አባቴ ስራ
የዚህ ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉ 1) ኢየሱስ እነዚህን ቃላት በጥንቃቄ መርጦ የተናገረው አባቱ የሰጠውን ስራ እየሰራ እንደሆነ ለማሳየት ነው፣ ወይም 2) እነዚህ ቃላት ኢየሱስ የነበረበትን ቦታ፣ “የአባቴ ቤት” የሚያስረዳ ፈሊጥ ነው። ቀጣዩ ቁጥር የኢየሱስ ወላጆች ኢየሱስ የሚነግራቸውን ነገሮች አልተረዱትም ስለሚል ይህን ከዚህ በላይ ለማብራራት ባይሞከር ጥሩ ነው።
የአባቴን ስራ
የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ፣ በ12 አመቱ የእውነት አባቱ የማርያም ባል የነበረው ዮሴፍ ሳይሆን እግዚአብሔር እንደነበር አስተውሎ ነበር። (ልጅ እና አባትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 2:51
ከእነርሱ ጋር ወደ ቤት ተመለሰ
“ኢየሱስ ከማርያምና ከዮሴፍ ጋር ወደ ቤት ተመለሰ”
ይታዘዛቸው ነበር
“ለእነርሱ ይታዘዝ ነበር” ወይም “ሁልጊዜ ለእነርሱ ይታዘዝ ነበር”
እነዚህን ነገሮች በልቧ ትጠብቃቸው ነበር
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት ወይም አእምሮ የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጥንቃቄ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ታስብ ነበር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ )
በጥበብና በቁመት አደገ
“ጠቢብና ጠንካራ ሆነ” እነዚህ አእምሮአዊና አካላዊ እድገትን ያመለክታሉ።
በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት አደገ
ይህ መንፈሳዊና ማሕበራዊ እድገትን ያሳያል። እነዚህ ተነጣጥለው መጻፍ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር አብዝቶ ባረከው፣ በሰዎችም ዘንድ የበለጠ የተወደደ ሆነ”

---

Chapter 3
Luke 3:1
አያያዥ ሀሳብ፡-
ነቢዩ ኢሳይያስ እንደ ተነበየው፣ ዮሐንስ መልካም ዜናን ለህዝቡ መስበክ ጀመረ።
አጠቃላይ መረጃ፡-
እነዚህ ጥቅሶች የኢየሱስ የአክስት ልጅ ዮሐንስ አገልግሎቱን ሲጀምር ምን እየተደረገ እንደሆነ ለመናገር የጀርባ ታሪክ መረጃን ይሰጣሉ።
ጢባርዮስ ቄሳር በነገሰ በአስራ አምስተኛው አመት
“ጢባርዮስ ቄሳር ለአስራ አምስት አመታት በመራ በዚያ ጊዜ” (ደረጃ የሚያሳይ ቁጥር የሚለውን ይመልከቱ)
ፊሊጶስ... ሊሳንዮስ
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ኢጡሪያስ እና ጥራኮኒዶስ... ሳቢላኒስ
እነዚህ የግዛት ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ሐና እና ቀያፋ ሊቃነ ካህናት በነበሩ ጊዜ
“ሐና እና ቀያፋ እንደ ሊቀ ካህናት ባንድነት በሚያገለግሉበት ጊዜ።” ሐና ሊቀ ካህን ነበር፣ ሮማውያን አማቹን ቀያፋን እንደ ሊቀ ካህን እንዲተካው ከሾሙት በኋላ እንኳን ሳይቀር አይሁዶችም ለእርሱ እውቅና መስጠታቸውን ቀጥለዋል።”
የእግዚአብሔር ቃል መጣ
ጸሐፊው የእግዚአብሔር መልእክት እርሱን ወደሚያዳምጡት ሰዎች የሚንቀሳቀስ ሰው እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር መልእክቱን ተናገረ”
Luke 3:3
የንስሀን ጥምቀት መስበክ
“ጥምቀት” እና “ንስሀ” የሚሉት ስሞች እንደ ድርጊት ሊገለፁ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱም ሰዎች ንስሀ እየገቡ እንደሆነ ለማሳየት መጠመቅ እንዳለባቸው ሰበከ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
ለኃጢአት ስርየት
እነርሱ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር እንዲል ንስሀ ይገባሉ። “ይቅርታ” የሚለው ስም እንደ ድርጊት ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኃጢአታቸው ይቅር እንዲባል” ወይም “እግዚአብሔር ኀጢአታቸውን ይቅር እንዲል” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 3:4
አጠቃላይ መረጃ፡-
ጸሐፊው ሉቃስ መጥምቁ ዮሐንስን የሚመለከት ምንባብ ከነቢዩ ኢሳይያስ ጠቀሰ።
በነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ እንደ ተፃፈ
እነዚህ ቃላቶች ከነቢዩ ኢሳይያስ የተወሰደ ጥቅስ ያቀርባሉ። እነርሱ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፁ ይችላሉ፣ የትዘለሉት ቃላቶችም መቅረብ ይችላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ ነቢዩ ኢሳይያስ የእርሱን ቃላት በያዘውን መጽሐፍ እንደፃፈው እንደዚያው ሆነ” ወይም “ዮሐንስ ነቢዩ ኢሳይያስ በመፅሀፍ የፃፈውን መልእክት ፈፀመ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
በበረሃ ውስጥ የሚጮኽ የአንድ ሰው ድምፅ
ይህ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በበረሃ ውስጥ የሚጮኽ የአንድ ሰው ድምፅ ተሰማ” ወይም “እነርሱ በበረሃ ውስጥ የሚጮኽ የአንድ ሰው ድምፅ ሰሙ”
የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ ጎዳናውንም አቅኑ
ሁለተኛው ትእዛዝ ለመጀመሪያው በይበልጥ ዝርዝር ይጨምርለታል ወይም ያብራራዋል።
የጌታን መንገድ አዘጋጁ
“ለጌታ መንገዱን አዘጋጁ።” ይህን ማድረግ የጌታ መልእክት ሲመጣ ለመስማት መዘጋጀትን ይወክላል። ሰዎች ከኀጢአታቸው ንስሀ በመግባት ይህን ያደርጉታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ሲመጣ የጌታን መልእክት ለመስማት ተዘጋጅ” ወይም “ንስሀ ግባ፣ ለሚመጣው ጌታ የተዘጋጀህ ሁን” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
መንገድ
“መተላለፊያ” ወይም “ጎዳና”
Luke 3:5
ሸለቆው ሁሉ ይሞላል... ተራራው እና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይላል
ሰዎች በጣም ወደ እነርሱ እየመጣ ላለ ከፍተኛ ስልጣን ያለው ሰው መንገድ ሲያዘጋጁ፣ ከፍተኛ ቦታዎችን ይቆርጡና መንገዱ ደልዳላ እንዲሆን ዝቅተኛ ቦታዎችን ይሞላሉ። ይህ በፊተኛው ጥቅስ ውስጥ የተጀመረው ተለዋጭ ዘይቤ

አካል ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ሸለቆው ሁሉ ይሞላል
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በመንገዱ ውስጥ ዝቅተኛ ቦታውን ሁሉ ይሞላሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ተራራው እና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይላል
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ተራራውን እና ኮረብታውን ሁሉ ደልዳላ ያደርጋሉ” ወይም “በመንገዱ ውስጥ ከፍተኛ ቦታውን ሁሉ ያስወግዳሉ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔርን ማዳን ማየት
ይህ እንደ ድርጊት ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እንዴት ሰዎችን ከኃጢአት እንደሚያድን ማወቅ” (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 3:7
በእርሱ ለመጠመቅ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ዮሐንስ እነርሱን እንዲያጠምቃቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እናንተ የእፉኝት ልጆች
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። እዚህ ላይ “ልጆች” “የወላጆቹ ባህርይ ያለው” ማለት ነው። እፉኝቶች ክፋትን የሚወክሉ እና አደገኛ የሆኑ መርዛማ እባቦች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ ክፉ መርዛማ እባቦች” ወይም “እናንተ እንደ መርዛማ እባብ ክፉ ናችሁ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማን አስጠነቀቃችሁ... ከሚመጣው?
እርሱ በእርግጥ መልስ እንዲሰጡ እየጠበቀ አልነበረም። ዮሐንስ ህዝቡን እየገሰፀ ነበር ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዳይቀጣቸው እነርሱን እንዲያጠምቅ እየጠየቁት ነበር ነገር ግን ኃጢአት መስራታቸውን ማቆም አልፈለጉም። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእግዚአብሔር ቁጣ በእንዲህ ዓይነት መንገድ መሸሽ አትችሉም!” ወይም “ከእግዚአብሔር ቁጣ በመጠመቅ ብቻ ማምለጥ አትችሉም!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ከሚመጣው ቁጣ
“ቁጣ” የሚለው ቃል እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ቅጣት ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል ምክንያቱም የእርሱ ቁጣ ይቀድመዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር እየላከ ካለው ቅጣት” ወይም “እርሱ ሊተገብረው ካለው ከእግዚአብሔር ቁጣ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 3:8
ለንስሀ የሚገባ ፍሬ አፍሩ
በዚህ ተለዋጭ ዘይቤ ውስጥ፣ የሰው ባህርይ ከፍሬ ጋር ተነፃፅሯል። ልክ ተክል ለተክሉ አይነት ተገቢ የሆነ ፍሬ እንዲያፈራ እንደሚጠበቅ ሁሉ እርሱ ንስሀ እንደገባ የሚናገር ሰው በፅድቅ እንዲኖር ይጠበቃል፡፡. አማራጭ ትርጉም፡- “ንስሀ እንደገባህ የሚያሳይ የፍሬ አይነት አፍራ“ ወይም “ከኃጢአትህ መመለሰስህን የሚያሳዩ መልካም ነገሮችን አድርግ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በልባችሁ መናገር
“ለራሳችሁ መናገር” ወይም “ማሰብ”
አብርሀም አባታችን አለን
“አብርሀም የእኛ የዘር ግንድ ነው” ወይም “እኛ የአብርሀም ተወላጅ ነን።” ይህንን ለምን እንደሚሉ ግልፅ ካልሆነ፣ የተጠቀሰውን መረጃ ደግሞ መጨመር ትችላለህ፡- “እግዚአብሔር እኛን እንዳይቀጣን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለአብርሃም ልጆች ማስነሳት
“ለአብርሃም ልጆች መፍጠር”
ከእነዚህ ድንጋዮች
ዮሐንስ ምናልባትም በዮርዳኖስ ባህር ያሉትን ትክክለኛ ድንጋዮች እያመለከተ ነበር።
Luke 3:9
ምሳር በዛፎች ስር ተቀምጧል
የዛፎችን ስር መቁረጥ እንዲችል ቦታው ላይ ያለ ምሳር ሊጀምር ስላለው ቅጣት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ምሳሩን በዛፎች ስር እንዳስቀመጠ ሰው እንደዛው ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ማንኛውም ዛፍ... ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል
እዚህ ላይ “እሳት” ለቅጣት ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ማንኛውንም ዛፍ ይቆርጣል... እናም ወደ እሳት ውስጥ ይጥለዋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 3:10
አያያዥ ሀሳብ፡-
የሐንስ ሰዎች ከህዝቡ ውስጥ ለሚጠይቁት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ጀመረ።
እርሱን ጠየቁት፣ እንዲህ አያሉ
x
Luke 3:12
ለመጠመቅ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ዮሐንስ እነርሱን እንዲያጠምቃቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ተጨማሪ ገንዘብ አትሰብስቡ
“ተጨማሪ ገንዘብ አትጠይቁ” ወይም “ተጨማሪ ገንዘብ አትውሰዱ።” ቀረጥ ሰብሳቢዎች መሰብሰብ ከነበረባቸው ገንዘብ ተጨማሪ እየሰበሰቡ ነበር። ዮሐንስ ያንን ማድረግ እንዲያቆሙ ነገራቸው።
እንድትሰበስቡ ከታዘዛችሁት
ይህ የቀረጥ ሰብሳቢዎቹ ስልጣን ከሮም እንደመጣ ለማሳየት ተገብሮ/ተሳቢ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሮማውያን እንድትወስዱ ስልጣን ከሰጧችሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 3:14
እኛስ? እኛ ምን ማድረግ አለብን?
“እኛ ወታደሮችስ፣ ምን ማድረግ አለብን?” “እኛ” እና “ለኛ” የሚሉት ቃላት ውስጥ የሐንስ አልተካተተም። ወታደሮቹ የሐንስ ለሰተበሰበው ህዝብ እና ለቀረጥ ሰብሳቢዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንደተናገረ አመልክተዋል እነርሱም እንደ ወታደሮች ምን እንደሚያደርጉ ማወቅ ይፈልጋሉ። (አግላይ እና አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)
ማንንም በሐሰት አትክሰሱ
ወታደሮቹ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ በሰዎች ላይ ሐሰተኛ ክስ እያዘጋጁ የነበረ ይመስላል። ይህ በትክክል ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በተመሳሳይ መንገድ፣ ከእነርሱ ገንዘብ ለማግኘት ማንንም ሰው በሀሰት አትክሰሱ” ወይም “ንፁሁን ሰው ህገወጥ ነገር ሰርቷል ብላችሁ አትናገሩ”
ደመወዛችሁ ይብቃችሁ
“በክፍያችሁ የረካችሁ ሁኑ”
Luke 3:15
ሕዝቡም
“ምክንያቱም ሕዝቡ።” ይህ ወደ ዮሐንስ መጥተው የነበሩትን ሰዎች ያመለክታል።
ሁሉም ሰዎች በልባቸው ስለ ዮሐንስ፣ ይህ ክርስቶስ ይሆንን ብለው ሲያስቡ ነበር
“ሁሉም ሰው ስለ ዮሐንስ ምን ማሰብ እንዳለበት እርግጠኛ አልነበረም፤ ራሳቸውንም “እርሱ ክርስቶስ ይሆንን?” ብለው ጠየቁ” ወይም “ማንም ሰው ስለ ዮሐንስ ምን ማሰብ እንዳለበት እርግጠኛ አልበነረም ምክንያቱም እርሱ ምናልባት ክርስቶስ ይሆናል ብለው እያሰቡ ነበር።”
ዮሐንስ ለሁሉም እንዲህ ሲል መለሰላቸው
ታላቅ ሰው ስለ መምጣቱ ዮሐንስ የሰጠው መልስ ዮሐንስ ክርስቶስ እንዳልሆነ በግልፅ ያመለክታል። ይህንን ለአንባቢው በትክክል መግለፅ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ዮሐንስ ለሁሉም እንዲህ በማለት እርሱ ክርስቶስ እንዳልሆነ ያብራራል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እኔ በውሀ አጠምቃችኋለሁ
“እኔ ውሀን በመጠቀም አጠምቃለሁ” ወይም “እኔ በውሀ አማካኝነት አጠምቃለሁ”
የእርሱን ጫማ ጠፍር እንኳ ለመፍታት የማይገባኝ
“የእርሱን ጫማ ጠፍር እንኳን ለማላላት በቂ ያልሆንሁ።” የጫማን ጠፍር መፍታት የባሪያ ተግባር ነበር። የሚመጣው እርሱ በጣም ታላቅ ስለሆነ ዮሐንስ የእርሱ ባሪያ ለመሆን እንኳን የሚገባ እንዳልሆነ እየተናገረ ነበር።
እርሱ በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት ያጠምቃችኋል
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ሰውን ከውሀ ጋር የሚያገናኘውን የውሀ ጥምቀት እነርሱን ከመንፈስ ቅዱስ እና ከእሳት ጋር ከሚያገናኘው መንፈሳዊ ጥምቀት ጋር ያወዳድራል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እሳት

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እዚህ ላይ “እሳት” የሚለው ቃል ሊያመለክት የሚችለው 1) ፍርድ ወይም 2) ማንጻት፡፡ “እሳት” የሚልወን እንዳለ መተው ይመረጣል፡፡ (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:17

መንሹም በእጁ ነው

“መንሽ ይዟል ምክንያቱም እርሱ ዝግጁ ነው፡፡” የሐንስ ክርስቶስ በህዝብ ላይ ለመፍረድ ስለመምጣቱ ሲናገር እርሱ የስንዴውን ፍሬ ከገለባው ለመለየት የተዘጋጀ ገበሬ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “እርሱ ዝግጁ እንደሆነ ገበሬ በህዝብ ላይ ለመፍረድ ዝግጁ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መንሽ

ይህ የስንዴውን ፍሬ ከገለባው ለመለየት ስንዴውን ወደ አየር የሚበትን መሳሪያ ነው፡፡ ከባድ ፍሬዎች ወደ ታች ይወድቃሉ የማይፈለገው ገለባ ደግሞ በንፋስ ይወሰዳል፡፡ ከሹካ መሰል ማበጠርያ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

አውድማውንም ፈፅሞ ያጠራል

አውድማ የመውቃት ዝግጅት ላይ ስንዴው የሚከመርበት ቦታ ነበር፡፡ አውድማውን “ማጥራት” ፍሬዎቹን ወቅቶ መጨረስ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የእርሱን ፍሬዎች ወቅቶ መጨረስ”

ስንዴውን ይሰበስባል

ስንዴው የሚጠበቅ እና የሚከማች ተቀባይነት ያለው አዝመራ ነው፡፡

ገለባውን ያቃጥለዋል

ገለባው ለምንም ጠቃሚ አይደለም፣ ስለዚህ ሰዎች ያቃጥሉታል፡፡

Luke 3:18

አጠቃላይ መረጃ፦

x

Luke 3:21

አያያዥ ሀሳብ፦

ኢየሱስ አገልግሎቱን የጀመረው በጥምቀቱ ነው፡፡

አጠቃላይ መረጃ፦

የቀደመው ጥቅስ ሄሮድስ የሐንስን ወህኒ ቤት አስገባው ይላል፡፡ በቁጥር 21 ላይ የጀመረው መግለጫ የሐንስ ከመታሰሩ በፊት የተከሰተ እንደሆነ ግልፅ ማድረግ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም ቁጥር 21ን “ነገር ግን የሐንስ ወህኒ ቤት ከመግባቱ በፊት” ብሎ በመጀመር ግልጽ ያደርገዋል፡፡ (የሁነቶች ቅደም ተከተል የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ሆነ

ይህ ሀረግ በታሪኩ ውስጥ የአዲስ ክስተት ጅማሬን ያመላክታል፡፡ የአንተ ቋንቋ ይህንን ለማድረግ መንገድ ካለው፣ እርሱን እዚህ ላይ ለመጠቀም ማሰብ ትችላለህ፡፡ (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ህዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ

“የሐንስ ህዝቡን ሁሉ ባጠመቀበት ጊዜ፡፡” “ህዝቡ ሁሉ” የሚለው ሀረግ ከየሐንስ ጋር የነበሩትን ህዝብ ያመለክታል፡፡ (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ

ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “የሐንስ ደግሞ ኢየሱስን አጠመቀው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰማይ ተከፈተ

“ሰማይ ክፍት ሆነ፡፡” ይህ ከተራ የደመና መጥራት የበለጠ ነው፣ ነገር ግን ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ አይደለም፡፡ ምናልባትም በሰማይ ውስጥ ቀዳዳ ታየ ማለት ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ

“መንፈስ ቅዱስ በሰውነት ቅርፅ በኢየሱስ ላይ እንደ ርግብ ወረደ”

ድምፅ ከሰማይ መጣ

እዚህ ላይ “ድምፅ ከሰማይ መጣ” የሚለው ሰዎች በምድር ላይ ሆነው እግዚአብሔር ከሰማይ ሲናገር መስማታቸውን ይወክላል፡፡ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ተናገሮ እንደነበረ ግልፅ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ድምፅ ከሰማይ ተናገረ” ወይም “እግዚአብሔር ከሰማይ ኢየሱስን እንዲህ በማለት ተናገረ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ልጄ

ይህ ለኢየሱስ አስፈላጊ ስም ነው፣ የእግዚአብሔር ልጅ፡፡ (ልጅ እና አባትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:23

አጠቃላይ መረጃ፦

ሉቃስ የኢየሱስን የዘር ግንድ አባቱ ነው ተብሎ በሚታሰበው በዮሴፍ መስመር በኩል ይዘረዝራል፡፡

በጀመረበት ጊዜ

እዚህ ላይ ይህ ሀረግ ጥቅም ላይ የዋለው መረጃው ከታሪክ ወደ ኢየሱስ እድሜ እና የዘር ግንድ የጀርባ ታሪክ መለወጡን ለማመልከት ነው፡፡ (የጀርባ ታሪክ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰላሳ አመታት እድሜ

“30 አመት” (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ የዮሴፍ ልጅ ነበር (እንደመሰላቸው)

“እርሱ የዮሴፍ ልጅ እንደሆነ ይታሰብ ነበር” ወይም “ሰዎች እርሱ የዮሴፍ ልጅ ነው ብለው ያምኑ ነበር”

የኤሊ ልጅ፣ የማቲ ልጅ፣ የሌዊ ልጅ

በአንተ ቋንቋ ሰዎች በብዛት የዘር ግንድ እንዴት እንደሚዘረዝሩ አስብ፡፡ በሙሉ ዝርዝሩ ውስጥ አንድ አይነት አፃፃፍ መጠቀም አለብህ፡፡ ሊሆኑ የሚችሉ አቀራረቦች 1) “የኤሊ ልጅ ማን ነበር፣ የማቲ ልጅ ማን ነበር፣ የሌዊ ልጅ ማን ነበር” ወይም 2) “ዮሴፍ የኤሊ ልጅ ነበር፣ ኤሊ የማቲ ልጅ ነበር፣ ማቲ የሌዊ ልጅ ነበር” ወይም 3) “የኤሊ አባት ማቲ ነበር፣ የማቲ አባት ሌዊ ነበር” (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:25

የማታትዩ ልጅ፣ የአሞፅ ልጅ… ዮዳ

ይህ የኢየሱስ የዘር ግንድ ዝርዝር ቀጣይ ነው፡፡ የፊተኛው ቁጥር ላይ የተጠቀምክበትን አንድ አይነት አቀራራብ ተጠቀም፡፡ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:27

የዮናን ልጅ፣ የሬስ ልጅ… ሌዊ

ይህ የኢየሱስ የዘር ግንድ ዝርዝር ቀጣይ ነው፡፡ የፊተኛው ቁጥር ላይ የተጠቀምክበትን አንድ አይነት አቀራራብ ተጠቀም፡፡ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

የሰላትያል ልጅ

ሰላትያል የሚለው ስም ሺያልትያል ለሚለው ስም ሌላ የቃላት አፃፃፍ ሊሆን ይችላል (አንዳንድ የእንግሊዘኛ ትርጉሞች እንደሚጠቀሙት)፣ ነገር ግን በሚገባ መለየት አስቸጋሪ ነው፡፡

Luke 3:30

የስምኦን ልጅ፣ የይሁዳ ልጅ… ነአሶን

ይህ የኢየሱስ የዘር ግንድ ዝርዝር ቀጣይ ነው፡፡ የፊተኛው ቁጥር ላይ የተጠቀምክበትን አንድ አይነት አቀራራብ ተጠቀም፡፡ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:33

የአሚናዳብ ልጅ፣ የአድሚን ልጅ… ሳላ

ይህ የኢየሱስ የዘር ግንድ ዝርዝር ቀጣይ ነው፡፡ የፊተኛው ቁጥር ላይ የተጠቀምክበትን አንድ አይነት አቀራራብ ተጠቀም፡፡ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 3:36

የቃይንም ልጅ፣ የአርፋክስድ ልጅ… አዳም

ይህ የኢየሱስ የዘር ግንድ ዝርዝር ቀጣይ ነው፡፡ የፊተኛው ቁጥር ላይ የተጠቀምክበትን አንድ አይነት አቀራራብ ተጠቀም፡፡ (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አዳም፣ የእግዚአብሔር ልጅ

“አዳም፣ በእግዚአብሔር የተፈጠረ” ወይም “አዳም፣ ከእግዚአብሔር የነበረ” ወይም “አዳም፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ማለት የምንችለው”

Chapter 4

Luke 4:1
አያያዥ ሀሳብ፡-
ኢየሱስ ለ40 ቀን ፆመ፣ ዲያቢሎስም ኃጢአት እንዲያደርግ እርሱን ማሳመን ለመሞከር ተገናኘው፡፡
ከዚያም ኢየሱስ
የሐንስ ኢየሱስን ካጠመቀው በኋላ፡፡ (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)
በመንፈስ ተመርቶ
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "መንፈስ እርሱን መራው" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ለ40 ቀን ተፈተነ
ብዙ እትሞች የተፈተነው 40 ቀኑን በሙሉ ነው ይላሉ፡፡ ይህንን ግልፅ ለማድረግ ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም "እርሱ እዚያ በነበረበት ጊዜ፣ ዲያቢሎስ እርሱን መፈተን ቀጥሏል" ብሎ ገልፆታል፡፡
አርባ ቀን
"40 ቀን" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 4:3
የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ
ዲያቢሎስ ኢየሱስ "የእግዚአብሔር ልጅ" እንደሆነ ለማረጋገጥ ይህንን ተአምራት እንዲያደርግ ተገዳደረው፡፡ (ልጅ እና አባትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
ይህ ድንጋይ
ዲያቢሎስ በእጁ ድንጋይ ይዟል ወይም በአቅራቢያው ወዳለ ድንጋይ ጠቁሟል፡፡
ኢያሱስ መለሰለት፣ ". . . ብቻ . . . ተብሎ ተፅፏል፡፡"
ኢየሱስ የዲያቢሎስን ተግዳሮት አለመቀበሉ በመልሱ ላይ በግልፅ ይታያል፡፡ ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም እንዳደረገው፣ ለአንባቢዎችህ ይህንን በትክክል መግለፅ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ኢየሱስ 'አይሆንም፣ ይህንን አላደርግም ምክንያቱም . . . ብቻ . . . ተብሎ ተፅፏል' ብሎ መለሰ፡፡" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ተፅፏል
የተጠቀሰው በብሉይ ኪዳን ከሙሴ ፅሁፎች ውስጥ ነው፡፡ ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ሙሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፅፏል" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም
"እንጀራ" የሚለው ቃል በአጠቃላይ ምግብን ያመለክታል፡፡ ምግብ ከእግዚአብሔር ጋር ሲወዳደር፣ ብቻውን፣ ሰውን በህይወት ለማቆየት በቂ አይደለም፡፡ ኢየሱስ ለምን ድንጋዩን ወደ እንጀራ እንደማይቀይር ለመናገር መጽሐፍ ቅዱስን ጠቀሰ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ሰዎች በእንጀራ ብቻ መኖር አይችሉም" ወይም "ሰውን እንዲኖር የሚያደርገው እንጀራ ብቻ አይደለም" ወይም "እግዚአብሔር ከእንጀራ ይበልጥ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች አሉ ብሏል" (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 4:5
ኢየሱስን መራው
እርሱ በተራራ ላይ ኢየሱስን መራው፡፡ (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
በቅፅበታዊ ጊዜ
"በቅፅበት" ወይም "ባንዳፍታ"
እነርሱ ለእኔ ተሰጥተዋል
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡ ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው 1) የግዛቶቹ ስልጣን እና ውበት ወይም 2) ግዛቶቹ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- " እግዚአብሔር እነርሱን ለእኔ ሰጥቶኛል " (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የምትሰግድ ከሆነ... የምታመልከኝ
እነዚህ ሁለት ሀረጎች በጣም ተመሳሳይ ናቸው፡፡ መጣመር ይችላሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "እኔን ለማምለክ የምትሰግድ ከሆነ" (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ይሆናል
"እነዚህን ሁሉ ግዛቶች ከነ ውበታቸው ለአንተ እሰጥሀለሁ"
Luke 4:9
በጣም ከፍተኛ ቦታ
ይህ የቤተ መቅደስ ጣሪያ ጠርዝ ነበር፡፡ አንድ ሰው ከዚህ ከወደቀ፣ በጠና ይጎዳል ወይም ይሞታል፡፡
የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ
ዲያቢሎስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንዲያረጋግጥ እየተገዳደረው ነው፡፡
የእግዚአብሔር ልጅ
ይህ ለኢየሱስ ጠቃሚ ስም ነው፡፡ (ልጅ እና አባትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
ራስህን ወርውር
"ወደ መሬት ዝለል"
ተብሎ ተፅፏልና
ከመዝሙረ ዳዊት የጠቀሰው ጥቅስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነ እርሱ አይጎዳም ማለት እንደሆነ ዲያቢሎስ ያመለክታል፡፡ ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም እንዳደረገው፣ ይህ በትክክል ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "አንተ አትጎዳም፣ ምክንያቱም ተብሎ ተፅፏል" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ተፅፏል
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ጸሐፊው ፅፏል" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ትእዛዝ ይሰጣል
"እርሱ" እግዚአብሔርን ያመለክታል፡፡ ዲያቢሎስ ኢየሱስ ከህንፃው እንዲዘል ለማሳመን በመጣር ከመዝሙረ ዳዊት ጥቅስ በከፊል ጠቅሷል፡፡
Luke 4:12
ተብሎአል
ኢየሱስ ለምን ዲያቢሎስ እርሱ እንዲያደርግ የነገረውን እንደማያደርግ ለዲያቢሎስ ተናገረ፡፡ የእርሱ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆን በትክክል ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "አይሆንም፣ ይህን አላደርግም፣ ምክንያቱም ተብሎአል" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ተብሎአል
ኢየሱስ ከኦሪት ዘዳግም ውስጥ የሙሴን ፅሁፍ ጠቀሰ፡፡ ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ሙሴ ብሏል" ወይም "ሙሴ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብሏል" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ጌታን አምላክህን አትፈታተነው
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢየሱስ ከቤተ መቅደሱ በመዝለል እግዚአብሔርን መፈታተን የለበትም፣ ወይም 2) ዲያቢሎስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለማየት ኢየሱስን መፈታተን የለበትም፡፡ ይህንን ጥቅስ ትርጉሙን ለማብራራት ከመሞከር ይልቅ እንደ ተገለፀው መተርጎም የተሻለ ነው፡፡
ሌላ ጊዜ እስከሚመጣ
"ሌላ አመቺ ጊዜ እስከሚገኝ"
ኢየሱስን መፈተን ጨረሰ
ይህ ዲያቢሎስ በፈተናው ስኬታማ ነበር የሚል መልእክት አያስተላልፍም፡፡ ኢየሱስ እያንዳንዱ ሙከራውን ተቋቁሟል፡፡ ይህ በትክክል ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- "ኢየሱስ ኃጢአት እንዲያደርግ ለማሳመን መሞከሩን ጨረሰ" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 4:14
አያያዥ ሀሳብ፡-
ኢየሱስ ወደ ገሊላ ተመለሰ፣ በምኩራብ አስተማረ፣ እዚያ ላሉ ሰዎችም እርሱ የነቢዩ ኢሳይያስን ትንቢት እየፈፀመ እንደሆነ ነገራቸው፡፡
ከዛም ኢየሱስ ተመለሰ
ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሁነትን ይጀምራል፡፡ (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)
በመንፈስ ኃይል
"መንፈስም ኃይል እየሰጠው ነበር፡፡" የሰው ልጆች በተለምዶ ማድረግ የማይችሉትን ነገር እንዲያደርግ እያስቻለው፣ እግዚአብሔር በልዩ መንገድ ከኢየሱስ ጋር ነበር፡፡
የእርሱ ዝና ተሰፋፋ
"ስለ ኢየሱስ ሰዎች ዝናውን አስፋፉ" ወይም "ሰዎች ለሌሎች ሰዎች ስለ ኢየሱስ ተናገሩ" ወይም "ስለ እርሱ ያለ እውቀት ከሰው ወደ ሰው ተላለፈ፡፡" ኢየሱስን የሰሙ ሰዎች ለሌላ ሰዎች ስለ እርሱ ተናገሩ፣ ከዚያም እነዚህ ሌላ ሰዎች ለበለጡ ሌላ ሰዎች ስለ እርሱ ተናገሩ፡፡
በዙሪያው ላለው ሀገር በሙሉ
ይህ በገሊላ ዙሪያ ያሉ ቦታዎችን እና አካባቢዎችን ያመለክታል፡፡
እርሱ በሁሉም ተመሰገነ
"እያንዳንዱ ሰው ስለ እርሱ ታላቅ ነገርን ተናገረ" ወይም "ሁሉም ሰው ስለ እርሱ

በመልካም መንገድ ተናገረ”
Luke 4:16
እርሱ ያደገበት
“ቤተሰቦቹ እርሱን ያሳደጉበት” ወይም “ልጅ እያለ የኖረበት”
ልማዱ እንደነበረው
“በእያንዳንዱ ሰንበት እንደሚያደርገው፡፡” በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ መሄድ የእርሱ የአብዛኛውን ጊዜ ልምምድ ነበር፡፡
የነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ ተሰጠው
ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው የነቢዩ ኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጠው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ
ይህ በብራና ላይ የተፃፈውን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያመለክታል፡፡ ኢሳይያስ መልእክቱን ከብዙ አመት በፊት ፅፎታል፣ እናም ሌላ ሰው ፅሁፎቹን ወደ ብራና ገልብጧል፡፡
የተፃፈበት ስፍራ
“እነኚህ ቃላቶች ያሉበት የብራናው ስፍራ፡፡” ይህ አረፍተ ነገር ወደ ቀጣዩ ቁጥር ይቀጥላል፡፡
Luke 4:18
የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው
“መንፈስ ቅዱስ በልዩ መንገድ ከእኔ ጋር ነው፡፡” አንድ ሰው ይህንን ሲል፣ የእግዚአብሔርን ቃል ነው የምናገረው እያለ ነው፡፡
እርሱ ቀብቶኛል
በብሉይ ኪዳን፣ ሰው ልዩ ተግባር ለማድረግ ስልጣን እና ሀይል ሲሰጠው የስርአት መፈጸሚያ ዘይት በሰውየው ላይ ይፈስ ነበር፡፡ ኢየሱስ ይህንን ተለዋጭ ዘይቤ መንፈስ ቅዱስ እርሱን ለዚህ ስራ ለማዘጋጀት በእርሱ ላይ እንደነበር ለማመላከት ተጠቀመበት፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “መንፈስ ቅዱስ በኃይል ሊሞላኝ በእኔ ላይ ነው” ወይም “መንፈስ ቅዱስ ስልጣን እና ሀይልን ሰጠኝ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ድሆች
“ድሀ ሰዎች”
ለታሰሩት ነፃነትን ማወጅ
“ምርኮኛ ሆነው ለተያዙ ህዝቦች በነፃ መሄድ እንደሚችሉ መንገር” ወይም “የጦርነት ታሳሪዎችን ነፃ ማውጣት”
ለታወሩት መልሶ ማየት
“ለታወሩት ማየትን መስጠት” ወይም “የታወሩት እንደገና ማየት እንዲችሉ ማድረግ”
የተጨቆኑትን ነፃ ማውጣት
“በግፍ የሚሰቃዩትን ነፃ ማውጣት”
የተወደደውን የጌታን አመት ለማወጅ
“እግዚአብሔር ህዝቡን ለመባረክ ዝግጁ እንደሆነ ለእያንዳንዱ ሰው መናገር” ወይም “ይህ እግዚአብሔር ቸርነቱን የሚያሳይበት አመት እንደሆነ ማስታወቅ”
Luke 4:20
ብራናውን ጠቀለለው
ብራና ውስጡ ያለውን ፅሁፍ ለመጠበቅ እንደ ቱቦ በመጠቅለል ነበር የሚዘጋው፡፡
ጠባቂ
ይህ መጽሐፍ ቅዱስ የያዙትን ብራናዎች በተገቢው ጥንቃቄ እና ክብር የሚያወጣ እና የሚያስቀምጥ የምኩራብ ሰራተኛን ያመለክታል፡፡
Luke 4:23
አጠቃላይ መረጃ፡-
ናዝሬት ኢየሱስ ያደገበት ከተማ ነው፡፡
Luke 4:25
አጠቃላይ መረጃ፡-
ኢየሱስ በምኩራብ ውስጥ ለሚያዳምጡት ህዝብ እነርሱ ስለሚያውቋቸው ነቢያት፣ ስለ ኤልያስ እና ኤልሳዕ አስታወሳቸው፡፡ (የጀርባ ታሪክ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ
“በእውነት እነግራችኋለሁ፡፡” ኢየሱስ ይህንን ሀረግ የተከታዩን አረፍተ ሀሳብ ጥቅም፣ እውነት እና ትክክለኛነት አፅንኦት ለመስጠት ይጠቀመዋል፡፡
መበለቶች
መበለቶች ባሎቻቸው የሞተባቸው ሴቶች ናቸው፡፡
በኤልያስ ዘመን
ኢየሱስ እየተናገራቸው ያሉት ህዝብ ኤልያስ ከእግዚአብሔር ነቢያት አንዱ እንደሆነ ያውቁ ነበር፡፡ አንባቢዎችህ ያንን ካላወቁ፣ ይህንን ያልተገለፀ መረጃ እንደ ዩዲቢ የሚባለው ትርጉም ግልፅ ማድረግ ትችላለህ፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ኤልያስ በእስራኤል ውስጥ እየተነበየ በነበረበት ጊዜ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰማይ ተዘግቶ ሳለ
ይህ ተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ ሰማይ ከእርሱ ምንም ዝናብ እንዳይወርድ የተዘጋ ጣሪያ እንደሆነ ተደርጎ ተስሏል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከሰማይ ምንም ዝናብ ባልወረደ ጊዜ” ወይም “ከቶ ምንም ዝናብ በሌለ ጊዜ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ታላቅ ራብ
“አሳሳቢ የምግብ እጥረት፡፡” ራብ ሰብሎች ለህዝቡ በቂ ምግብ የማያፈሩበት ረጅም ጊዜ ነው፡፡
ወደ ሰራፕታ… እዚያ ወደ ምትኖር መበለት
በሰራፕታ ከተማ የሚኖሩ ህዝቦች አህዛብ ነበሩ፣ አይሁድ አልነበሩም፡፡ ኢየሱስን እያዳመጡ ያሉት ሰዎች የሰራፕታ ህዝብ አህዛብ እንደሆኑ ይገባቸዋል፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ሰራፕታ ውስጥ ለምትኖር ከአህዛብ ወገን የሆነች መበለት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ሶርያዊው ንዕማን
ሶርያዊ ከሶርያ አገር የሆነ ሰው ነው፡፡ የሶርያ ህዝቦች አህዛብ ነበሩ፣ አይሁድ አልነበሩም፡፡ አማራጭ ትርጉም፡- “ከሶሪያ የሆነው አህዛቡ ንዕማን” (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 4:28
በምኩራቡ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ሁሉ እነዚህን ነገሮች ሲሰሙ ቁጣ ሞላባቸው
የናዝሬት ህዝብ እግዚአብሔር በአይሁድ ፋንታ አህዛብ የረዳበትን መጽሐፍ ኢየሱስ ስለጠቀሰ በእጅጉ ተናደው ነበር፡፡
በግድ ከከተማው ወደ ውጪ አስወጡት
“ከተማውን እንዲለቅ አስገደዱት” ወይም “ከከተማው ወደ ውጪ በሀይል ገፉት”
ወደ ገደል አፋፍ
“የገደል ጠርዝ”
በመካከላቸው አልፎ ሄደ
“በተሰበሰው ህዝብ መካከል” ወይም “ እርሱን ለመግደል በሚሞክሩት ህዝብ መካከል”
ወደ ሌላ ቦታ ሄደ
“እርሱ ሄደ” ወይም “በራሱ መንገድ ሄደ” ኢየሱስ ህዝቡ እርሱ እንዲሄድ ለማስገደድ ከሚሞክሩበት ቦታ ይልቅ እርሱ ለመሄድ ያቀደበት ቦታ ሄደ፡፡
Luke 4:31
አያያዥ ሀሳብ፡-
ከዚያም ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም ሄደ፣ እዚያ ምኩራብ ውስጥ ላሉ ሰዎች አስተማረ፣ ርኩስ ጋኔንም ግለሰቡን ለቆ እንዲወጣ አዘዘ፡፡
ከዚያም እርሱ
“ከዚያም ኢየሱስ፡፡” ይህ አዲስ ሁነትን ያመለክታል፡፡ (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ቅፍርናሆም ወረደ
“ወረደ” የሚለው ሀረግ እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቅፍርናሆም ከናዝሬት በከፍታው ዝቅ ያለ ስለሆነ ነው፡፡
ቅፍርናሆም፣ የገሊላ ከተማ
“ቅፍርናሆም፣ በገሊላ ውስጥ ሌላ ከተማ”
መገረም
በእጅጉ መደነቅ
እርሱ በሥልጣን ተናገረ
“ሥልጣን እንዳለው ሰው ተናገረ” ወይም “የእርሱ ቃላት ትልቅ ኃይል ነበራቸው”
Luke 4:33
አሁን… ሰው ነበር
ይህ ሀረግ በታሪኩ ውስጥ የአዲስ ገፀ ባህርይ መግባትን ለማመላከት ይጠቅማል፤ በዚህ ጊዜ፣ ርኩስ መንፈስ የተቆጣጠረውን ሰው፡፡ (የአዲስና የቀድሞ

ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

ግልፅ ያልሆነ የርኩስ መንፈስ ያለበት

“ግልፅ ያልሆነ ርኩስ መንፈስ የተቆጣጠረው” ወይም “በክፉ መንፈስ ቁጥጥር ስር ያለ”

በጉልህ ድምፅ ጮኸ

“በሀይል ጮኸ”

እኛ ከአንተ ጋር ምን አለን

ይህ ጠብ አጫሪ መልስ “እኛ ምን የጋራ ነገር አለን?” ወይም “እኛን ለማስቸገር አንተ ምን መብት አለህ?” የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጥ ነው፡፡ (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

የናዝሬቱ ኢየሱስ፣ እኛ ከአንተ ጋር ምን አለን

ይህ ጥያቄ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊጻፍ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “የናዝሬቱ ኢየሱስ፣ አንተ ከእኛ ጋር ምን አለህ!” ወይም “እኛ ከአንተ ጋር ምንም የለንም፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ!” ወይም “አንተ እኛን ለማስቸገር ምንም መብት የለህም፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 4:35

ኢየሱስ ርኩስ መንፈሱን ገሰፀው፣ እንዲህ በማለት

“ኢየሱስ ርኩስ መንፈሱን ተቆጣው፣ እንዲህ በማለት” ወይም “ኢየሱስ በሀይል ርኩስ መንፈሱን ተናገረው”

ከእርሱ ወጣ

ርኩስ መንፈሱ ግለሰቡን መቆጣጠር እንዲያቆም አዘዘው፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ብቻውን ተወው” ወይም “በዚህ ሰው ውስጥ ከዚህ በኋላ አትኑር”

እነዚህ ምን አይነት ቃላት ናቸው

ኢየሱስ ርኩስ መንፈስ ሰውን ትቶ እንዲወጣ ለማዘዝ ስልጣን ስላለው ህዝቡ እንዴት ተደንቀው እንደነበር እየገለፁ ነበር፡፡ ይህ እንደ አረፍተ ሀሳብ ሊጻፍ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “እነዚህ ቃላት ድንቅ ናቸው!” ወይም “የእርሱ ቃላት ድንቅ ናቸው!” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ግልፅ ያልሆነውን መንፈስ በስልጣን እና በሀይል አዘዘ

“እርሱ ግልፅ ያልሆነውን መንፈስ ለማዘዝ ስልጣን እና ሀይል አለው”

እንደዚሁ ስለ እርሱ ዝና መስፋፋት ጀመረ… በዙሪያ ባለ ክልል

ይህ በታሪኩ ውስጥ በተከሰቱ ክስተቶች አማካኝነት ስለተፈጠረው ነገር የሚናገር መግለጫ ነው፡፡ (የታሪክ መጨረሻ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ እርሱ ዝና መስፋፋት ጀመረ

“ስለ ኢየሱስ ወሬዎች መስፋፋት ጀመሩ” ወይም “ህዝቡ ስለ ኢየሱስ ዝና ማስፋፋት ጀመሩ”

Luke 4:38

አያያዥ ሀሳብ:-

ኢየሱስ አሁንም ቅፍርናሆም ውስጥ ነው፣ ነገር ግን አሁን የስምዖንን አማት እና ብዙ ሰዎችን በፈወሰበት በስምኦን ቤት ውስጥ ነው፡፡

ከዚያም ኢየሱስ ሄደ

ይህ አዲስ ሁነትን ይገልፃል፡፡ (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

የስምዖን አማት

“የስምዖን ሚስት እናት”

እየተሰቃየች ነበር

ይህ “በጣም ታማ ነበር” የሚል ትርጉም ያለው ፈሊጥ ነው፡፡ (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)

ኃይለኛ ትኩሳት… ትኩሳቱን ገሰፀው

x

Luke 4:40

እጆቹን ጫነ

“እጆቹን አስቀመጠ” ወይም “ነካ”

አጋንንትም ደግሞ ወጡ

ኢየሱስ አጋንንት ከተቆጣጠራቸው ሰዎች አጋንንቶች እንዲለቁ እንዳደረገ ያመለክታል፡፡ ይህ በትክክል ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ኢየሱስ ደግሞ አጋንንቶች እንዲወጡ አስገደዳቸው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መጮህ እና መናገር

እነዚህ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ምናልባትም የፍርሀት ወይም የንዴትን ጩኸትን ያመለክታሉ፡፡ አንዳንድ ትርጉሞች አንድ ስያሜን ብቻ ይጠቀማሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “መጮህ” ወይም “መንጫጫት” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 4:42

አያያዥ ሀሳብ:-

ሕዝቡ ኢየሱስ በቅፍርናሆም እንዲቆይ ቢፈልጉም፣ በሌላ የአይሁድ ምኩራቦች ለመስበክ ሄደ፡፡

በነጋ ጊዜ

“ፀሐይ ስትወጣ”

ጭር ያለ ቦታ

“ሰው ለቅቆ የሄደበት ቦታ” ወይም “ምንም ሰው የሌለበት ቦታ”

ለሌላ ብዙ ከተሞች

“በሌላ ብዙ ከተማ ላሉ ሰዎች”

ይህ እዚህ የተላኩበት ምክንያት ነው

ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “ይህ እግዚአብሔር እኔን እዚህ የላከበት ምክንያት ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ይሁዳ

ኢየሱስ ገሊላ ውስጥ ስለነበር፣ “ይሁዳ” የሚለው ስም እዚህ ላይ ምናልባትም በዚያን ጊዜ አይሁዶች የኖሩበትን ክልል በሙሉ ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም:- “አይሁዶች የኖሩበት”

---

# Chapter 5

## Luke 5:1

አያያዥ ሀሳብ:-

ኢየሱስ በስምዖን ጴጥሮስ ጀልባ በጌንሳሬጥ ሀይቅ ላይ አስተማረ፡፡

አሁን ይህ ሆነ

ይህ ሀረግ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ለማመላከት እዚህ ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የአንተ ቋንቋ ይህንን የማድረግ መንገድ ካለው፣ እዚህ ላይ እርሱን ለመጠቀም ማሰብ ትችላለህ፡፡ (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔርን ቃል ማዳመጥ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እግዚአብሔር እነርሱ እንዲሰሙ የሚፈልገውን መልእክት ማዳመጥ” ወይም 2) “ስለ እግዚአብሔር የሆነውን የኢየሱስ መልእክት ማዳመጥ”

የጌንሳሬጥ ሀይቅ

እነዚህ ቃላት የገሊላን ባህር ይወክላሉ፡፡ ገሊላ በሀይቁ ምዕራብ ጎን ነው፣ የጌንሳሬጥ መሬት በምስራቅ ጎን ነበር፣ ስለዚህ በሁለቱም ስሞች ይጠራ ነበር፡፡ አንዳንድ የእንግሊዘኛ እትሞች ይህንን እንደ ትክክለኛ የውሀው አካል ስም “የጌንሳሬጥ ሀይቅ” ብለው ይተረጉሙታል፡፡

መረባቸውን እያጠቡ

አሳ ማጥመጃ መረባቸውን እንደገና ለአሳ መያዣነት ለመጠቀም እያፀዱ ነበር፡፡

ከጀልባዎቹ አንዱ፣ የስምዖን የነበረው

“የስምዖን ንብረት የነበረው ጀልባ”

ከመሬት ጥቂት አርቆ በውሀው ውስጥ እንዲያስቀምጥ እርሱን ጠየቀ

“ስምዖንን ጀልባውን ከባህር ዳርቻው ራቅ እንዲያደርገው ጠየቀ”

ተቀመጠ እና ሕዝቡን አስተማረ

መቀመጥ ለአስተማሪ የተለመደ ሁኔታ ነበር፡፡

ከጀልባው ውስጥ ህዝቡን አስተማረ

“ጀልባው ውስጥ እንደተቀመጠ ሆኖ ህዝቡን አስተማረ፡፡” ኢየሱስ ከባህር ዳርቻው አጭር ርቀት ላይ በሚገኘው ጀልባው ውስጥ ነበር እናም በባህር ዳርቻው ላይ ለነበሩ ሰዎች እየተናገረ ነበር፡፡

## Luke 5:4

መናገሩን ሲጨርስ

“ኢየሱስ ሕዝቡን ማስተማር ሲጨርስ”

በቃልህ

“ምክንያቱም አንተ ይህንን እንዳደርግ ስለነገርከኝ”

ማንቀሳቀስ

ከባህር ዳርቻው ለመጣራት በጣም ሩቅ ነበሩ፣ ስለዚህ ምናልባትም እጃቸውን በማውለብለብ፣ የሰውነት እንቅስቃሴን አደረጉ፡፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መስጠም ጀመሩ
“ጀልባዎቹ መስጠም ጀመሩ።” ምክንያቱ በትክክል ሊገለፅ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “አሳው በጣም ከባድ ስለነበር ጀልባዎቹ መስጠም ጀመሩ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 5:8
በኢየሱስ ጉልበት ላይ ወደቀ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “በኢየሱስ ፊት ተንበረከከ” ወይም 2) “በኢየሱስ እግር ስር ሰገደ” ወይም 3) “የኢየሱስ እግር ስር ባለው መሬት ላይ ተኛ።” ጴጥሮስ በአጋጣሚ አልወደቀም። ይህንን የክብር እና የትህትና ምልክት እንዲሆን ለኢየሱስ አድርጎታል። (ምሳሌያዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
ኀጢአተኛ ሰው
እዚህ ላይ “ሰው” የሚለው ቃል “ጎልማሳ ወንድ” ለማለት እንጂ በይበልጥ አጠቃላይ ለሆነው “የሰው ልጅ” አይደለም።
የተያዘ ብዙ አሳ
“ብዙ ቁጥር ያለው አሳ”
የስምዖን ባልንጀሮች
“አሳ በማጥመድ ንግዱ ውስጥ የስምዖን ባልንጀሮች”
ሰውን ትይዛለህ
አሳን የማጥመድ ምስል ክርስቶስን እንዲከተል ሕዝብን ለመሰብሰብ እንደ ተለዋጭ ዘይቤ ጥቅም ላይ እየዋለ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎችን ታጠምዳለህ” ወይም “ለእኔ ሰውን ትሰበስባለህ” ወይም “ሰዎች የእኔ ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ታመጣለህ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 5:12
አያያዥ ሀሳብ፦
ኢየሱስ ሌላ ስሙ ባልተጠቀሰ ከተማ ለምፃም ፈወሰ።
እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ክስተት መከሰቱን ያሳያል።
በለምጽ የተሸፈነ ሰው
“ቆዳው በለምጽ የተሸፈነ ሰው።” ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ገጸ ባሕርይን ያስተዋውቃል። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)
በፊቱ ተደፋ
እዚህ ላይ “በፊቱ ተደፋ” የሚለው ሰገደ የሚለውን ትርጉም የያዘ ፈሊጥ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ተንበርክኮ በፊቱ መሬቱን ነካ” ወይም “በመሬት ላይ ሰገደ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ፈቃድህ ከሆነ
“የምትፈልግ ከሆነ”
ልታነጻኝ ትችላለህ
እዚህ ላይ ሰውየው ኢየሱስ እንዲፈውሰው እየጠየቀው እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ይህ በግልጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ማንጻት ስለምትችል እባክህ አንጻኝ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አንጻኝ … ንጻ
ይህ ሥርዓታዊ ንጽህናን ያመለክታል፣ ሰውየው በለምጹ ምክንያት ንጹህ እንዳልነበረ መረዳት ይቻላል። ካለበት በሽታም ኢየሱስ እንዲፈውሰው እየጠየቀው ነበር። ይህ ግልጽ በሆነ መንገድ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ካለብኝ ለምጽ ፈውሰኝ … የተፈወስክ ሁን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለምጹ ለቀቀው
“ከዚያ ጊዜ ኋላ ለምጽ አልነበረበትም”
Luke 5:14
¬ለማንም እንዳይነግር
ይህ በቀጥታ በጥቅስ መልክ መተርጎም ይቻላል። “ለማንም እንዳትናገር።” በግልጽ መቀመጥ የሚችል ሌላም ያልተገለጸ መረጃ አለ። አማራጭ ትርጉም፡- “መፈወስህን ለማንም እንዳትናገር” (ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች እና አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለ መንጻትህ መስዋዕትን
x
Luke 5:15
ስለ እርሱ ወሬ
“ስለ ኢየሱስ ይወራ የነበረ ወሬ።” ይህ “ኢየሱስ ለምጽ ያለበትን ሰው የመፈወሱ ወሬ” ወይም “ኢየሱስ በሽተኞችን ስለመፈወሱ ወሬ” ሊሆን ይችላል።
ስለ እርሱ የነበረው ወሬ ግን በርቀት አብዝቶ ተሰፋፋ
“ስለ እርሱ የነበረው ወሬ እስከ ሩቅ ቦታዎች ድረስ ተዳረሰ” ይህ በገቢር ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰዎች በሌሎች ቦታዎች ለሚገኙ ሰዎች ስለ እርሱ ያወሩ ነበር” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ምድረ በዳ
“ባዶ ቦታዎች” ወይም “ሌሎች ሰዎች የማይገኙባቸው ቦታዎች” “
Luke 5:17
አያያዥ ሀሳብ፦
ኢየሱስ አንድ ህንጻ ላይ ያስተምር በነበረበት በአንድ ቀን ሰዎች አንድ ሽባ የነበረ ሰውን ኢየሱስ እንዲፈውሰው አመጡለት።
እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ክፍል መጀመሩን ያሳያል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 5:18
አንዳንድ ሰዎች መጡ
እነዚህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሰዎች ናቸው። ቋንቋችሁ አዲስ ሰዎች መሆናቸውን የሚናገር አገላለጽ ሊኖረው ይችላል። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)
ምንጣፍ
መተኛ ምንጣፍ ወይም አልጋ ወይም ቃሬዛ
ሽባ የነበረ
“ራሱን ማንቀሳቀስ የማይችል የነበረ”
የሰው ጭንቅንቅ ብዙ ስለነበር እርሱን ይዘው ሊያስገቡት አልቻሉም ስለዚህ ...
በአንዳንድ ቋንቋዎች የዚህን ቅደም ተከተል መቀየር የተለመደ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰውየውን ወደ ውስጥ ማስገባት አልቻሉም ምክንያቱም የሰው ጭንቅንቁ ከባድ ስለነበር ነው፣ ስለዚህ”
በሰዉ መጨናነቅ ምክንያት
ሰዎቹ መግባት ያልቻሉበት ምክንያት ክፍሉ በሰዎች ተጨናንቆ ስለነበርና ለእነርሱ የሚሆን ቦታ ስላልነበር እንደሆነ ግልጽ ነው። (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ወደ ሰገነቱ ወጡ
ቤቶች ጠፍጣፋ የሆነ ጣርያ ነበራቸው፣ አንዳንድ ቤቶች ደግሞ ወደ እነዚህ ጣርያዎች መውጫነት የሚያገለግሉ መሰላሎች ወይም ደረጃዎች ነበሯቸው። ይህን በግልጽ ማሳየት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ወደ ጠፍጣፋው የቤት ጣርያ ወጡ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከኢየሱስ ፊት
“ከኢየሱስ ፊት ለፊት” ወይም “ኢየሱስ ከነበረበት ቀጥታ ፊትለፊት”
Luke 5:20
ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ … አለ
ኢየሱስ ሽባውን ሰው መፈወስ እንደሚችል ሰዎቹ እንደሚያምኑ ግልጽ ነው። ይህን በግልጽ ማሳየት ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኢየሱስም ሰዎቹ እርሱ ሰውየውን ሊፈውሰው እንደሚችል እንዳመኑ ሲረዳ እንዲህ አለው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተ ሰው
ይህ ስሙን ከማያውቁት ሰው ጋር ሲነጋገሩ ሰዎች የሚጠቀሙት የተለመደ ቃል ነው። አግባብ የሌለው አነጋገር አልነበረም፣ ግን የተለየ አክብሮትም አያሳይም። አንዳንድ ቋንቋዎች ይህን ለማሳየት “ወዳጄ” እና “ጌታዬ” የመሰሉ ቃላትን ሊጠቀሙ ይችላሉ።
ኃጢአትህ ተሰረየችልህ
ይህ በገቢር ቅርጽ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይቅር ተብለሃል” ወይም “ኃጢአትህን ይቅር ብዬሃለሁ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ስለዚህ ጥያቄ ማቅረብ ጀመሩ
“ስለዚህ ነገር ተወያዩ” ወይም “ስለዚህ ነገር ምክንያቶችን ሰጡ።” የጠየቁትን ጥያቄ በግልጽ ሊብራራ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኢየሱስ ኃጢአትን ይቅር ለማለት ስልጣን ያለው መሆኑንና አለመሆኑን መወያየት ጀመሩ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 5:22
ያስቡ የነበሩትን ተረድቶ

ይህ ሐረግ የሚያሳየው እነርሱ ድምጽ ሳያወጡ እያሰላሰሉ እንደነበር ኢየሱስ ግን ይናገሩ የነበረውን ሳይሆን ያስቡ የነበረውን እንደተረዳ ያሳያል።
በልባችሁ ይህን ለምን ትጠይቃላችሁ?
ይህ በአረፍተ ሃሳብ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በልባችሁ ውስጥ ስለዚህ ነገር ምንም አይነት ሙግት ውስጥ መግባት የለባችሁም” ወይም “ኃጢአትን ይቅር የማለት ስልጣን እንዳለኝ መጠራጠር የለባችሁም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
በልባችሁ ውስጥ
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው ቃል የሰውን አእምሮ ወይም የውስጥ ማንነት የሚወክል ምትክ ስም ነው። (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
የትኛው ይቀላል ... ተነሳና ተመላለስ
ጻፎቹ እርሱ ኃጢአትን ይቅር የማለት ስልጣን እንዳለው ወይም እንደሌለው የሚያረጋግጥላቸው ነገር ምን እንደሆነ እንዲያስቡ ይህን ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ 'ኃጢአትህ ተሰረየችልህ' አልኩ፣ እናንተ 'ተነስና ተመላለስ' ማለት ይከብዳል ብላችሁ ታስቡ ይሆናል ምክንያቱም ሰውየውን መፈወስ መቻሌና አለመቻሌ በሰውየው ተነስቶ መሄድና አለመሄድ ይታወቅ ነበር።” ወይም “እናንተ 'ተነስና ሂድ' ከማለት 'ኃጢአትህ ተሰረየችልህ' ማለት ይቀላል ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ማለት ይቀላል
እዚህ ላይ በንግግር ያልተገለጸው እንድምታ አንድ ነገር “መናገር ይቀላል ምክንያቱም ምን እንደተከናወነ ማንም ማወቅ አይችልም” ነገር ግን ሌላውን ነገር “መናገር ይከብዳል ምክንያቱም ሁሉም ሰው ምን እንደተከናወነ ያውቃል።” ሰዎች የሰውየው ኃጢአት ተሰርዮለት እንደሆነ ሰዎች ማየት አይችሉም፣ ነገር ግን ሰውየው ከተነሳና ከተራመደ እንደተፈወሰ ሁሉም ያውቃሉ። (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
እንድታውቁ
ኢየሱስ ለጻፎቹና ለፈሪሳውያኑ ነበር ሲያወራ የነበረው። “እናንተ” የሚለው የባለቤት መግለጫ ብዙ ቁጥርን ያመለክታል። (የሁለተኛ መደብ ቅርጾች የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ልጅ
ኢየሱስ ስለራሱ ነበር የሚያወራው።
እልሃለሁ
ኢየሱስ ይህን የተናገረው ለሽባው ሰው ነው። “አንተ” የሚለው የድርጊት ተቀባይ ገላጭ ነጠላ ቁጥር ነው።
Luke 5:25
ወዲያውኑም ተነሳ
“በፍጥነት ተነሳ” ወይም “ቶሎ ተነሳ”
ተነሳ
እዚህ ላይ ሰውየው መፈወሱን መናገር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሰውየውም ተፈወሰ! ተነሳም”
በፍርሃት ተሞሉ
x
Luke 5:27
አያያዥ ሀሳብ፡-
ኢየሱስ ቤቱን ለቅቆ በወጣ ጊዜ ሌዊ የሚባል አንድ አይሁዳዊ ቀረጥ ቀራጭን እንዲከተለው ጥሪ ያቀርብለታል። ሌዊ ባዘጋጀው ትልቅ ድግስ ላይ የኢየሱስ መታደም ጻፎችና ፈሪሳውያንን እጅግ ያናድዳቸዋል።
እነዚህ ነገሮች ከተከሰቱ በኋላም
“እነዚህ ነገሮች” የሚለው ሐረግ ቀደም ባሉ ቁጥሮች ላይ የተከሰቱትን ነገሮች ይወክላል። ይህ አዲስ ክስተት መጀመሩን ያሳያል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)
የቀረጥ ቀራጭ ተመለከተ
“አንድ ቀራጭን በትኩረት ተመለከተ” ወይም “አንድ ቀራጭን አጥብቆ ተመለከተ”
ተከተለኝ
አንድን ሰው “መከተል” ማለት የዚያ ሰው ደቀ መዝሙር መሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ደቀ መዝሙሬ ሁን” ወይም “እንደ አስተማሪ ተከተለኝ” (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ሁሉንም ነገር ትቶ
“የቀራጭነት ስራውን ትቶ”
Luke 5:29
አያያዥ ሀሳብ፡-
በድግሱ ላይ ኢየሱስ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጋር ያወራ ጀመር።
በቤቱ
“በሌዊ ቤት”
በማዕድ አብረው ተቀምጠው
በግብዣ ላይ የግሪክ የአመጋገብ ዘይቤ መደገፊያ ባለው መቀመጫ ላይ ተጋድመውና በመቀመጫቸው በግራ በኩል ባለው ድጋፍ ላይ ትራስ አስቀምጠው እዚያ ላይ በመደገፍ ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “በአንድ ላይ ምመብላት” ወይም “በማዕድ መብላት” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ለደቀ መዛሙርቱ
“ለኢየሱስ ደቀ መዛሙርት”
ከኃጢአተኞች ጋር ለምን ትበላላችሁ
ጻፎችና ፈሪሳውያን የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ከኃጢአተኞች ጋር አብረው መብላታቸውን ለመቃወም ይህንን ጥያቄ ይጠይቃሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ከኃጢአተኞች ጋር አብራችሁ መብላት የለባችሁም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
... ከኃጢአተኞች ጋር አብራችሁ ትበላላችሁ ትጠጣላችሁም
ፈሪሳውያንና ጻፎች ኃይማኖተኛ ሰዎች ኃጢአተኛ ብለው ከሚያስቧቸው ሰዎች ጋር አብረው መሆን እንደሌለባቸው ያምኑ ነበር። “እናንተ” የሚለው ገላጭ ብዙ ቁጥር አመልካች ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ባለጤናዎች ... ሕመምተኞች
x
Luke 5:33
አሉት
“የኃይማኖት መሪዎቹ ለኢየሱስ ... አሉት”
ከእነርሱ ጋር .... ሊያደርግ ይችላል?
ኢየሱስ ሰዎቹ ከዚህ ቀደም የሚያውቁትን ነገር ደግመው እንዲያስቡ በማለት ይሄንን ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። ይህ በአረፍተ ሃሳብ መልክ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ዕድምተኞቹ ጹሙ የሚላቸው ማንም የለም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
የሰርጉ ታዳሚዎች
“እንግዶቹ” ወይም “ወዳጆች” እነዚህ ከሚያገባ ወንድ ጋር ሆነው አብረው ደስታውን የሚጋሩ ሰዎች ናቸው።
የሙሽራው ዕድምተኞች እንዲጾሙ ማድረግ
መጾም ሐዘንን ማሳያ ነው። የኃይማኖት መሪዎቹ ሙሽራው አብሯቸው እያለ ዕድምተኞቹ ሊጾሙ እንደማይችሉ ገብቷቸዋል። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ቀን ይመጣል
“በቅርብ” ወይም “አንድ ቀን”
ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት
ኢየሱስ ራሱን ከአንድ ሙሽራ ጋር ደቀ መዛሙርቱን ደግሞ ከሚዜዎች ጋር በንጽጽር ያቀርባል። ዘይቤውን አያብራራውም ስለዚህ ትርጉም ላይ እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ዘይቤው ይብራራ። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 5:36
አጠቃላይ መረጃ፡-
ኢየሱስ በሌዊ ቤት ተገኝተው ለነበሩት ጻፎችና ፈሪሳውያን አንድ ታሪክ ይነግራቸዋል። (ተምሳሌቶች የሚለውን ይመልከቱ)
ማንም ቀድዶ ... አይጠቀምም ... እርሱ . . . እርሱ
ማንም ቦጭቆ . . . አይጠቀምም . . . እርሱ . . . እርሱ” ወይም “ሰዎች ቀድደው . . . አይጠቀሙበትም . . . እነርሱ . . . እነርሱ
የተቀደደውን መስፋት
ማደስ
እንደዚያ ቢያደርግ
ይህ ግምታዊ አርፍተ ነገር ለምን አንድ ሰው በዚያ መንገድ አንድን ልብስ እንደማያድስ ምክንያትን ይሰጣል። (ግምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ልኩ አይሆንም
“አይገጥምም” ወይም “ተመሳሳይ አይሆንም”
Luke 5:37


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አዲስ ወይን

“የወይን ፍሬ ጭማቂ።” ይህ ያልፈላ የወይን ጠጅን ይወክላል።

አቁማዳ

እነዚህ ከእንስሳ ቆዳ የተሰሩ መያዣ ከረጢቶች ናቸው። “የወይን ከረጢቶች” ወይም “ከቆዳ የተሰሩ ከረጢቶች” ተብለው መጠራትም ይችላሉ።

አዲሱ ወይን ቆዳውን ያፈነዳዋል

አዲሱ ወይን ሲፈላና ቆዳውን ሲወጥረው ያረጀውን ቆዳ ያፈነዳዋል ምክንያቱም መለጠጥ ስለማይችል ነው። ኢየሱስ ይናገር የነበረውን ያዳምጡ የነበሩ ሰዎች ስለ ወይን መፍላትና ይዞታ መጨመር የሚረዱ ሰዎች ነበሩ። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወይኑ ይፈስሳል

ይህ በአድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወይኑ ከከረጢቶቹ ውስጥ ወጥቶ ይፈስሳል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

አዲስ አቁማዳ

“አዲስ አቁማዳዎች” ወይም “አዲስ የወይን ከረጢቶች” ይህ ጥቅም ላይ ያልዋለ አቁማዳን ይወክላል።

አሮጌ የወይን ጠጅ የሚጠጣ ... አዲሱን የሚፈልግ

ይህ ዘይቤ የኃይማኖት መምህሮችን አሮጌ ትምህርት ከኢየሱስ አዲስ ትምህርት ጋር አነጻጽሮ ያቀርባል። የዚህ ንግግር ዋና ነጥብ የድሮ ትምህርትን መስማት የለመዱ ሰዎች ኢየሱስ የሚያስተምረውን አዲስ ትምህርት ለመስማት ፈቃደኛ አለመሆናቸው ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አሮጌ ወይን ጠጅ

“የፈላ ወይን ጠጅ”

'አሮጌው ይሻላል' ይላልና

“ስለዚህም አዲሱን ወይን ለመሞከር ፈቃደኛ አይሆንም” የሚለውን መጨመር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

# Chapter 6

## Luke 6:1

አጠቃላይ መረጃ፦

“እናንተ” የሚለው የድርጊት ባለቤት መግለጫ ባለ ብዙ ቁጥር ሲሆን ደቀ መዛሙርቱን ይወክላል። (የሁለተኛ መደብ ቅርጾች የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ

ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ክስተት መጀመሩን ያሳያል። ቋንቋችሁ ይህን ማሳያ መንገድ ካለው እሱን መጠቀም ይመከራል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሻ

እነዚህ ሰዎች የበለጠ ስንዴ ለማብቀል ስንዴ ዘርተውባቸው የሚገኙ ሰፋፊ የመሬት ክፍልፋዮች ናቸው።

የጥራጥሬ እሸት

ይህ ረዥም ሳር የሚመስል የአንድ ጥራጥሬ ተክል ጫፍ ላይ የሚገኝ የተክሉ ክፍል ነው። ሊበሉ የሚችሉና የበሰሉ የተክሉ ፍሬዎችን ይይዛል።

ፍሬዎቹን በእጃቸው መሃል እያሹ

ይህን የሚያደርጉት የጥሬውን ፍሬዎች ለመለየት ነው። ይህ ግልጽ ተደርጎ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በእጃቸው መሃል አድርገው ያሹአቸው ገለባውን ከፍሬው ለመለየት ነው (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰንበት ቀን ሕጉ የሚከለክለውን ነገር ለምን ታደርጋላችሁ?

ይህን ጥያቄ የጠየቁት ደቀ መዛሙርቱን ሕግን በመጣስ ሊከሷቸው ፈልገው ነው። ይህ በአረፍተ ሃሳብ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “በሰንበት ቀን ጥራጥሬ መቅጠፍ ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር ይቃረናል” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ነገር ትሰራላችሁ

ፈሪሳውያን አንድ እፍኝ ጥራጥሬን አሽቶ መብላትን የሚያክል ትንሽ ድርጊትን ራሱ ስራ እንደመስራት ይቆጥሩ ነበር። ይህ በግልጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ስራን እየሰራችሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

## Luke 6:3

ከቶ አላነበባችሁምን? ... እርሱ ራሱ

ኢየሱስ ፈሪሳውያን ከቅዱስ መጻሕፍት ባለመማራቸው ይገስጻቸዋል። ይህ በአረፍተ ሃሳብ መልክ ሊጻፍ ይችላል።. አማራጭ ትርጉም፦ “ካነበባችሁት ነገር መማር ነበረባችሁ .... እርሱ ራሱ” ወይም “በእርግጠኝነት አንብባችኋል ... እርሱ ራሱ” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

## Luke 6:6

አያያዥ ሀሳብ፦

ጻፎችና ፈሪሳውያን ኢየሱስ በሰንበት ቀን አንድ ሰውን ሲፈውስ ይመለከታሉ።

አጠቃላይ መረጃ፦

ይህ ሌላ የሰንበት ቀን ሲሆን ኢየሱስም በምኩራብ ነበር።

እንዲህ ሆነ

ይህ ሐረግ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ክስተት መጀመሩን ያሳያል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

... ሰው በዚያ ነበር

ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ገጸ ባህሪይን ያስተዋውቃል። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

እጁ የደከመ

የሰውየው እጅ መዘርጋት እንዳይችል ሆኖ ተጎድቶ ነበር። የሰውየው እጅ ቡጢ በሚመስል ሁኔታ ታጥፎ የነበረ እንደነበርና መታጠፉም ትንሽና የተሸበሸበ እንዳስመሰለው ይገመታል።

እያዩ ይከታተሉት ነበር

“በትኩረት ኢየሱስን እየተመለከቱት ነበር”

ሊያገኙበት

“ማግኘት ፈልገው”

በሁሉም መካከል

“ከሁሉም ፊት።” ኢየሱስ ሰውየው ሁሉም ሰው ሊያየው በሚችልበት ቦታ ላይ እንዲቆም ፈልጎ ነበር።

## Luke 6:9

ለእነርሱ አላቸው

“ለፈሪሳውያኑ አላቸው”

እጠይቃችኋለሁ በሰንበት ቀን ሕጉ የሚከለክለው በጎ ማድረግን ነው ወይስ ክፋትን፣ ነፍስን ማጥፋት ነው ወይስ ነፍስን ማዳን?

ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ ለፈሪሳውያን የሚጠይቃቸው በሰንበት ቀን ሰው መፈወሱ ትክክል እንደነበረ ፈሪሳውያን እንዲያምኑ ለማድረግ ነው። ስለዚህ የዚህ ጥያቄ ዓላማ መልስ ፍለጋ አይደለም፣ ይልቁንም እውነት እንደሆነ የሚያውቁትን ነገር እንዲያምኑ ለማድረግ ነው። ይሁን እንጂ ኢየሱስ “እጠይቃችኋለሁ” ይላል፣ ስለዚህ ይህ ጥያቄ እንደሌሎች መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች በአረፍተ ሃሳብ ቅርጽ ተቀይሮ መጻፍ የሚችል አይደለም። ይህ ጥያቄ የጥያቄነት ቅርጹን ጠብቆ መተርጎም አለበት። (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

## Luke 6:12

አጠቃላይ መረጃ፦

ኢየሱስ ለሊቱን ሙሉ ከጨረሰ በኋላ አስራ ሁለት ሐዋርያትን ይመርጣል።

በነዚያም ቀናት እንዲህ ሆነ

ይህ ሐረግ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን ያሳያል። (የአዲስ ሁነት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

በነዚያም ቀናት

“በዚያን ጊዜ” ወይም “ይህ ከሆነ ብዙም ሳይቆይ” ወይም “በዚያን ጊዜ አካባቢ አንድ ቀን”

ወጣ

“ኢየሱስ ወጣ”

ቀን በሆነ ጊዜ

“ጠዋት በሆነ ጊዜ” ወይም “በቀጣዩ ቀን”

አስራ ሁለቱን መረጠ

“አስራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት መረጠ”

ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ጠራቸው

“ደግሞም ሐዋርያት አደረጋቸው” ወይም “እናም ሐዋርያት አድርጎ ሾማቸው”



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Luke 6:14
የሐዋርያቱም ስም
ሉቃስ የሐዋርያቱን የስም ዝርዝር ጻፈ። ዩኤልቢ የሚባለው ትርጉም የስም ዝርዝሩን ለመጀመር እነዚህን ቃላት ይጠቀማል። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ወንድሙ እንድርያስ
“የስምኦን ወንድም እንድርያስ”
ቀናተኛው
x
Luke 6:17
አያያዥ ሀሳብ፦
ምንም እንኳ ኢየሱስ በተለየ ሁኔታ በቀጥታ የተናገረው ለደቀ መዛሙርቱ ቢሆንም በአካባቢው ሆነው ሲሰሙ የነበሩ ብዙ ሰዎች ነበሩ።
ከእነርሱ ጋር
“ከመረጣቸው ከአስራ ሁለቱ ጋር” ወይም “ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ጋር”
ሊፈወሱ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ኢየሱስ እንዲፈውሳቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በእርኩስ መናፍስት ይሰቃዩ የነበሩ ሰዎችም ተፈወሱ
ይህ በገቢር ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ኢየሱስ በእርኩስ መንፈስ ይሰቃዩ የነበሩ ሰዎችንም ፈወሰ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በእርኩስ መናፍስት ይሰቃዩ የነበሩ
“በእርኩስ መናፍስት ይቸገሩ የነበሩ” ወይም “በክፉ መናፍስት ቁጥጥር ስር የነበሩ”
የመፈወስ ኃይል ከእርሱ ይወጣ ነበር
“ሰዎችን ለመፈወስ ኃይል ነበረው” ወይም “ኃይሉን ሰዎችን ለመፈወስ ይጠቀም ነበር”
Luke 6:20
ብፁዓን
ይህ ቃል ሶስት ጊዜ ይደገማል። በእያንዳንዱ ጊዜም እግዚአብሔር ለተወሰኑ ሰዎች የሚያደርገውን ቸርነት ወይም እነዚያ ሰዎች ያሉበት ሁኔታ አዎንታዊ ወይም ጥሩ እንደሆነ ይናገራል።
ድሆች ብፁዓን ናችሁ
“ድሃ የሆናችሁ እናንተ የእግዚአብሔርን ቸርነት ትቀበላላችሁ” ወይም “ድሃ የሆናችሁ እናንተ ትጠቀማላችሁ”
የእግዚአብሔር መንግስት የእናንተ ናትና
መንግስት የሚለው ቃል መግለጫ የሌላቸው ቋንቋዎች “እግዚአብሔር ንጉሳችሁ ነውና” ወይም “እግዚአብሔር ገዢያችሁ ነውና” ሊሉ ይችላሉ።
የእግዚአብሔር መንግስት የእናንተ ናት
x
Luke 6:22
ብፁዓን ናችሁ
“የእግዚአብሔርን ቸርነት ትቀበላላችሁ” ወይም “ትጠቀማላችሁ” ወይም “እንደዛ መሆን ለእናንተ ምንኛ መልካም ነው”
ሲለዩአችሁ
“ሲቃወሟችሁ”
በሰው ልጅ ምክንያት
“ከሰው ልጅ ጋር የተያያዛችሁ ስለሆናችሁ” ወይም “የሰው ልጅንም ስለሚቃወሙት”
በዚያን ቀን
“እነዚህን ነገሮች ሲያደርጓችሁ” ወይም “ያ ነገር በተከሰተ ጊዜ”
በደስታ ዝለሉ
ይህ ፈሊጥ “እጅግ ደስተኛ ሁኑ” ማለት ነው። (ፈሊጥ የሚለውን ይመልከቱ)
ትልቅ ዋጋ
“ትልቅ ክፍያ” ወይም “መልካም ስጦታዎች”
Luke 6:26
ወዮላችሁ
“ምንኛ ክፉ ነገር ይጠብቃችኋል!” ወይም “ምንኛ የከፋ ሐዘን ውስጥ ትገቡ ይሆን”
ሰዎች ሁሉ … ሲናገሩላችሁ
እዚህ ላይ “ሰዎች” የሚለው ቃል ሁሉንም የሕዝብ ክፍል ያካትታል። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕዝብ ሁሉ ሲናገሩላችሁ” ወይም “ሁሉም ሰው ሲናገሩላችሁ” (ተባዕታይ ቃላቶች ሴቶችን ሲጨምር የሚለውን ይመልከቱ)
አባቶቻቸው ለሐሰት ነቢያት እንደዚያ አድርገው ነበር
“አባቶቻቸውም ለሐሰት ነቢያት መልካምን ነገር ይናገሩላቸው ነበር”
Luke 6:27
አያያዥ ሀሳብ፦
ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱና አብረው ሆነው ይሰሙ ለነበሩት ሕዝብ መናገሩን ይቀጥላል።
ለእናንተ ለምትሰሙ
ኢየሱስ አሁን ለደቀመዛሙርት ብቻ ሳይሆን በዚያ ለነበሩት ሰዎች ለሁሉም መናገር ይጀምራል። (የአዲስና የቀድሞ ተሳታፊዎች መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)
ውደዱ … መልካም አድርጉ … ባርኩ … ጸልዩ
እዚህ ላይ ያሉት እያንዳንዱ ትዕዛዛት በቀጣይነት መደረግ ያለባቸው ናቸው፣ አንድ ጊዜ ብቻ የሚደረጉ አይደሉም።
ጠላቶቻችሁን ውደዱ
ይህ መውደድ ያለባቸው ጠላቶቻቸውን ብቻና ወዳጆቻቸውን መውደድ የለባቸውም ለማለት አይደለም። ይህ በግልጽ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ወዳጆቻችሁን ብቻ ሳይሆን ጠላቶቻችሁንም ውደዱ” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ውደዱ … መልካም አድርጉ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፣ ዋናው ነጥብ ላይም አጽንኦት ይሰጣሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
ባርኩ
የሚባርከው እግዚአብሔር ነው። ይህ ግልጽ ተደርጎ መቀመጥ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “እግዚአብሔር እንዲባርካቸው ጠይቁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የሚረግሟችሁን
x
Luke 6:29
ቢመታህ
“ማንም ሰው ቢመታህ”
አንድ ጉንጭህን
“አንደኛውን ጉንጭህን”
ሌላኛውን ስጠው
የሚያጠቃው ሰውዬ በሰውየው ላይ ምን እንደሚያደርስ ግልጽ አድርጎ መጻፍ ሊያስፈልግ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ፊትህን አዙረህ ሌላኛውን ጉንጭህንም እንዲመታህ ስጠው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
አትከልክለው
“ከመውሰድ አታግደው”
ለሚጠይቅህ ሁሉ ስጥ
“ማንም ሰሰው አንድን ነገር ቢጠይቅህ ስጠው”
እንዲመልስልህ አትጠይቀው
“መልሶ እንዲሰጥህ አትጠብቅ” ወይም “መልሶ እንዲሰጥህ አትጠይቀው”
Luke 6:31
ሰዎች ለእናንተ እንዲያደርጉ እንደምትፈልጉት፣ እናንተም ለእነርሱ እንደዛው አድርጉላቸው
በአንዳንድ ቋንቋዎች ቅደም ተከተሉን መለወጥ የተለመደ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፦ “ለሰዎች ማድረግ ያለባችሁ እናንተ እነርሱ እንዲያደርጉባችሁ እንደምትፈልጉት ነው” ወይም “ለሰዎች ማሰብ ያለባችሁ እነርሱ ለእናንተ እንዲያስቡ በምትፈልጉት መንገድ ነው”
ምን የተለየ ዋጋ ታገኛላችሁ?
“ምን ዋጋ ታገኛላችሁ?” ወይም “ያንን በማድረጋችሁ ምን አይነት ምስጋናን ታተርፋላችሁ” ይህ በአረፍተ ሃሳብ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል።. አማራጭ ትርጉም፦ “ያንን በማድረጋችሁ ምንም ሽልማትን አታገኙም” ወይም “ያንን በማድረጋችሁ እግዚአብሔር ምንም ሽልማትን አይሰጣችሁም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ተመሳሳይ መጠን ያለውን መልሳችሁ ብትቀበሉ
የሙሴ ሕግ አይሁዳውያን እርስ በርስ በተበዳደሩት ገንዘብ ላይ ወለድን

እንዳይቀበሉ ያዝዛል። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:35

በምላሹ ምንም ሳትጠብቁ

“የሰጣችሁት ሰው የሰጣችሁትን ነገር እንዲመልስላችሁ ሳትጠብቁ” ወይም “የሰጣችሁት ሰው ምንም ነገር እንዲመልስላችሁ ሳትጠብቁ”

ሽልማታችሁ ታላቅ ይሆናል

“ታላቅን ሽልማት ትቀበላላችሁ” ወይም “መልካም ክፍያን ታገኛላችሁ” ወይም “ባደረጋችሁት ነገር ምክንያት ጥሩ ስጦታን ታገኛላችሁ”

የልዑልም ልጆች ትሆናላችሁ

“ልጆች” የሚለውን ቃል በቋንቋችሁ ውስጥ የተለመደ የአንድ ሰውን ልጅ ለመግለጽ ጥቅም ላይ በሚውለው ቃል ተርጉሞ ማቅረብ ተመራጭ ነው።

የልዑል ልጆች

ልጆች የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ምክንያቱም “የልዑል ልጅ” ከሚለው ከኢየሱስ ማዕረግ ጋር መመሳሰል ስለሌለበት ነው።

ምስጋና ቢስና ክፉ ሰዎች

“እርሱን የማያመሰግኑና ሰዎችና ክፉዎች የሆኑ”

አባታችሁ

ይህ እግዚአብሔርን ይወክላል። ይህን በቋንቋችሁ ውስጥ ስጋዊ አባትን በሚወክለው ቃል መተርጎም ቢቻል ይመረጣል።

Luke 6:37

አትፍረዱ

“ሰው ላይ አትፍረዱ” ወይም “የመረረ ነቀፋ በሰው ላይ አታድርሱ”

እናንተም

“ስለዚህም እናንተ”

አይፈረድባችሁም

x

Luke 6:38

ይሰጣችኋል

ኢየሱስ የሚሰጠው ማን እንደሆነ ግልጽ አድርጎ አይናገርም። ሊሆን የሚችለው፡ 1) “የሆነ ሰው ይሰጣችኋል” ወይም 2) “እግዚአብሔር ይሰጣችኋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

እጅግ ብዙ መጠን ያለው .. የተጨቆነ፣ የተነቀነቀና ሞልቶም የተረፈ . . . በጭናችሁ ላይ ይፈስሳል

እዚህ ላይ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ወይም በቸርነት የሚሰጡትን ሰዎችን እንደ አንድ ቸር ነጋዴ አድርጎ ያቀርባቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር የተጨቆነ የተነቀነቀና የተትረፈረፈ መጠን ያለውን ሞልቶ በጭናችሁ ላይ ያፈስሳል” ወይም “ቸር የጥራጥሬ ነጋዴ ጥራጥሬን ጨቁኖና ነቅንቆ መጠኑም ሞልቶ እስኪፈስ ድረስ ብዙ አድርጎ እንደሚሰጥ፣ ለእናንተም በቸርነት እንዲሁ ይሰጧችኋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙ መጠን ያለው

“ትልቅ መጠን ያለው”

ይሰፈርላችኋል

ኢየሱስ ማን እንደሚሰፍርላቸው በግልጽ አይናገርም። ትርጉም ሊሆኑ የሚችሉት፡ 1) “እነርሱ ይሰፍሩላችኋል” ወይም “እግዚአብሔር ይሰፍራችኋል” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:39

አያያዥ ሀሳብ፡-

ኢየሱስ የንግግሩን ዋና ሃሳብ ለማጠንከር አንዳንድ ምሳሌዎችን ይጨምራል። (ተምሳሌቶች የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ዕውር ሰው ሌላ ዕውር ሰውን ሊመራ ይችላል?

ኢየሱስ ሰዎቹ ኪዚህ በፊት ያውቁ የነበረውን ነገር ደግመው እንዲያስቡ ለማድረግ ይህን ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። ይህ በአረፍተ ነገር ቅርጽ ደግሞ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁላችንም አንድ ዕውር ሰው ሌላ ዕውር ሰውን መንገድ ሊመራ እንደማይችል እናውቃለን” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:41

በወንድምህ አይን ላይ ያለውን .... ለምን ታያለህ? በራስህ አይን ውስጥ ያለውን ግንድ ለምን አትመለከትም?

ኢየሱስ ይሄን ጥያቄ የጠየቀው ሰዎቹ የሌላን ሰው ኃጢአት ከመመልከታቸው በፊት የራሳቸውን ኃጢአት መመልከት እንዳለባቸው ለመሞገት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በራስህ አይን ውስጥ ያለውን ምሰሶ ትተህ በወንድምህ አይን ያለውን ... አትመልከት” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በወንድምህ አይን ያለውን ጉድፍ

ይህ ዘይቤ ሌላ አማኝ የሚያደርጋቸውን ጥቃቅን ስህተቶችን ይወክላል።። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ጉድፍ

“ጠብታ” ወይም “ጉድፍ” ወይም “የአቧራ ብናኝ”። የሰው አይን ውስጥ ሊገባ የሚችል በጣም ትንሽ ነገርን የሚወክል ቃል ካለ እሱን መጠቀም ይቻላል።

በወንድምህ

እዚህ ላይ “ወንድም” የሚለው ሌላ አይሁዊን ወይም በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሌላ ሰውን ይወክላል።

በራስህ አይን የሚገኘውን ግንድ

ይህ ዘይቤ የአንድ ሰውን ትልልቅ የሚባሉ ጥፋቶችን የሚወክል ነው። ግንድ በአንድ ሰው አይን ውስጥ ቃል በቃል ሊገባ አይችልም። ኢየሱስ አጋንኖ የሚያወራው አንድ ሰው የሰውን ጥቃቅን ጥፋቶች ከማየቱ በፊቱ የራሱን ትልልቅ ጥፋቶች መመልከት እንዳለበት አጽንኦት ለመስጠት ነው። (ተለዋጭ ዘይቤ እና ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ግንድ

“ምሰሶ” ወይም “ሳንቃ”

በአይንህ .... ልትል ትችላለህ?

ኢየሱስ ይሄን ጥያቄ የሚጠይቀው ሰዎቹ የሰው ኃጢአት ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ በራሳቸው ኃጢአቶች ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸው ለመሞገት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በአይንህ ... ማለት የለብህም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:43

አጠቃላይ መረጃ፡-

ሰዎች አንድን ዛፍ መልካም ወይ ክፉ መሆኑንና ምን ዓይነት ዛፍ መሆኑን ከሚያፈራው ፍሬ ማወቅ ይችላሉ። ኢየሱስ አንድን ሰው ከሚያደርገው ድርጊት ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ ማወቅ እንደምንችል ለማሳየት ይሄንን ንግግር እንደ ዘይቤ ይጠቀመዋል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

አለና

“ምክንያቱም ስላለ” ይህ የሚያሳየው ቀጥሎ የሚናገረው ነገር ወንድሞች ላይ ለምን መፍረድ እንደማይገባ ምክንያቱን እንደሚያመለክት ነው።

መልካም ዛፍ

“ጤናማ ዛፍ”

የተበላሸ ፍሬ

እየበሰበሰ ያለ ፍሬ ወይም መጥፎ ወይም ዋጋ የሌለው ፍሬ

Luke 6:45

አጠቃላይ መረጃ፡-

እዚህ ላይ ኢየሱስ የአንድ ሰውን ሃሳብ ሰውየው ካለው ከመልካም ወይም ከክፉ መዝገብ ጋር አነጻጽሮ ያቀርባል። መልካም ሰው መልካም ሃሳቦችን ሲያስብ መልካም ድርጊቶችን በመፈጸም ይጠመዳል። ክፉ ሰው ክፉ ሃሳቦችን ሲያስብ ክፋት ያለባቸውን ድርጊቶች በመስራት ይጠመዳል። (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም ሰው

እዚህ ላይ “መልካም” የሚለው ቃል ጻድቅ ወይም መልካም ሥነ ምግባር ያለው የሚለውን ይወክላል።

መልካም ሰው

እዚህ ላይ “ሰው” የሚለው ወንድ ወይም ሴት የሆነን ሰው ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡-“መልካም ሰው” (ተባዕታይ ቃላቶች ሴቶችን ሲጨምር የሚለውን ይመልከቱ)

ከልቡ መልካም መዝገብ

እዚህ ላይ የአንድ ሰው መልካም ሃሳቦች በዚያ ሰው ልብ ውስጥ እንደሚቀመጥ እንደ መዝገብ ተደርጎ ተመስሏል። “ልብ” የሚለው ደግሞ የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በውስጡ ከሚያኖረው ከመልካም ነገር” ወይም “እርሱ ዋጋ የሚሰጣቸው መልካም ነገሮች” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም የሆነውን ያፈራል



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መልካም የሆነውን ያፈራል ማለት መልካም ስራዎችን ይሰራል የሚለውን የሚያሳይ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካም የሆነውን ይሰራል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

በልቡ ካለው ከክፉ መዝገብ

x

Luke 6:46

አጠቃላይ መረጃ፡-

ኢየሱስ እርሱ የሚያስተምረውን የሚቀበልን ሰው በድንጋይ መሰረት ላይ ቤቱን ሰርቶ ጎርፍ ቤቱን ከማያፈርስበት ሰው ጋር አነጻጽሮ ያቀርባል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 6:49

አጠቃላይ መረጃ፡-

ኢየሱስ እርሱ የሚናገረውን ሰምቶ የማይታዘዘውን ሰው ቤቱን ያለመሰረት ሰርቶ ጎርፍ በመጣ ጊዜ ቤቱ ከሚፈርስበት ሰው ጋር አነጻጽሮ ያቀርባል። (ተነፃፃሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰውየው ግን

“ግን” የሚለው ቃል ቀድሞ ከተነገረው ቤቱን መሰረት ላይ ከሰራው ሰው ጋር ጠንካራ የተቃራኒ ንጽጽር መኖሩን ያሳያል።

ያለ መሰረት በመሬት ላይ

አንዳንድ ሰዎች መሰረት ያለው ቤት ጠንካራ እንደሆነ ላያውቁ ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ቤቱን ከመስራት በፊት መሬትን ቆፍሮ መሰረትን አልገነባም ነበር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

መሰረት

ቤቱን ከመሬት ጋር የሚያገናኘው የሕንጻው ክፍል። ኢየሱስ በኖረበት ጊዜ የነበሩ ሰዎች መሬቱን አለት ድንጋይ እስከሚያገኙ ድረስ ቆፍረው በአለቱ ላይ ነበር ቤቱን ይገነቡ የነበረው። አለቱ የቤቱ መሰረት ነበር።

---

Chapter 7

Luke 7:1

አጠቃላይ መረጃ

ኢየሱስ የመቶ አለቃውን አገልጋይ ወደፈወሰበት ወደ ቅፍርናሆም ይገባል።

ሕዝቡ እየሰሙት

የአነጋገር ዘይቤ የሆነው “እየሰሙት”፣ እርሱ የተናገረውን እንዲሰሙት ስለመፈለጉ አጽንዖት ይሰጣል። ኢ.ት፡ “ይሰሙት ለነበሩት ሰዎች” ወይም “ለተገኘው ሕዝብ” ወይም “ሕዝቡ እንዲሰሙ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

ወደ ቅፍርናሆም ገባ

ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሁነትን ይጀምራል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

Luke 7:2

በጣም ይወደው የነበረ

“የመቶ አለቃው ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጠው” ወይም “ያከብረው የነበረ”

Luke 7:6

ጉዞውን ቀጠለ

“አብሮት ሄደ”

ከቤቱ ሳይርቅ

ድርብ አሉታው ሊቀየር ይችላል። ኢ.ት፡ “ወደ ቤቱ ሲቃረብ” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ራስህን አታድክም

የመቶ አለቃው ኢየሱስን በትህትና እያነጋገረው ነበር። ኢ.ት፡ “ወደ ቤቴ ለመምጣት ራስህን አታድክም” ወይም “ላስቸግርህ አልፈልግም”

ከጣሪያዬ በታች ልትመጣ

ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙ “ወደ ቤቴ መምጣት” ማለት ነው። የአንተ ቋንቋ “ወደ ቤቴ መምጣት” የሚል ትርጉም ያለው የአነጋገር ዘይቤ ካለው እዚህ ጋ ልትጠቀምበት ያስፈልግህ እንደሆነ አስብበት። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

አንድ ቃል ብቻ ተናገር

ኢየሱስ በመናገር ብቻ አገልጋዩን ሊፈውሰው እንደሚችል የመቶ አለቃው ተረድቷል። እዚህ ጋ “ቃል” የሚያመለክተው ትዕዛዝን ነው። ኢ.ት፡ “ትዕዛዝ ብቻ ስጥ”

አገልጋዬ ይፈወሳል

እዚህ ጋ “አገልጋይ” ተብሎ የተተረጎመው ቃል አብዛኛውን ጊዜ የሚተረጎመው “ወንድ ልጅ” ተብሎ ነው። ይህ ምናልባት አገልጋዩ ታዳጊ ወጣት እንደ ነበረ ወይም የመቶ አለቃው ለእርሱ ያለውን ፍቅር ይጠቁም ይሆናል።

እኔም ደግሞ ከሥልጣን በታች ያለሁ ሰው ነኝ

“እኔም ደግሞ የምታዘዘው የበላይ አለኝ”

በእኔ ሥር

“በሥልጣኔ ሥር”

ለአገልጋዬ

እዚህ ጋ “አገልጋይ” ተብሎ የተተረጎመው ቃል ለአገልጋይ የተለመደ ቃል ነው።

Luke 7:9

በእርሱ ተደነቀ

“በመቶ አለቃው ተደነቀ”

እላችኋለሁ

ኢየሱስ ይህንን ያለው ሊነግራቸው ስላለው አስገራሚ ነገር አጽንዖት ለመስጠት ነው።

እንዲህ ያለውን እምነት በእስራኤል እንኳን አላገኘሁም

ይህ የሚያመለክተው፣ ኢየሱስ የአይሁድ ሕዝብ እንዲህ ያለ እምነት እንዲኖራቸው መጠበቁን፣ እነርሱ ግን እንዳልነበራቸው ነው። አሕዛብ እንዲህ ያለ እምነት እንዲኖራቸው አልጠበቀም፣ ሆኖም ይህ ሰው ነበረው። ይህንን ጠቋሚ መረጃ መጨመር ይኖርብህ ይሆናል። ኢ.ት፡ “እንደዚህ አሕዛብ የሚታመንብኝን አንድም እስራኤላዊ አላገኘሁም!”

እነዚያ ተልከው የነበሩት

እነዚህ የመቶ አለቃው የላካቸው ሰዎች መሆናቸው ግልጽ ነው። ይህ በኢ.ት፡ “ሮማዊው ባለሥልጣን ወደ ኢየሱስ ልኳቸው የነበሩ ሰዎች”

Luke 7:11

አያያዥ መግለጫ፡

ኢየሱስ የሞተውን ሰው ወደ ፈወሰበት ወደ ናይን ከተማ በመሄድ ላይ ነው።

ናይን

የከተማይቱ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)

እነሆ፣ አንድ የሞተ ሰው

“እነሆ” የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ ስላለው የሞተ ሰው ሊያስተዋውቀን ያነቃናል። የአንተ ቋንቋ ይህንን አሳብ መግለጫ መንገድ ይኖረው ይሆናል። ኢ.ት፡ “አንድ የሞተ ሰው ነበር፣ እርሱም” (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

የሞተ ሰው ተሸክመው

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች የሞተውን ሰው ተሸክመው ከከተማይቱ ይወጡ ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ብዙ ሕዝብም መበለት ለነበረች ለእናቱ ብቸኛ ልጇ የነበረውን ተሸክመው ወጡ

“ብዙ ሕዝብ ነበሩ፤ ተሸክመውት ወጡ፤ እርሱም ለእናቱ ብቸኛ ልጇ ነበር፣ እርሷም መበለት ነበረች”። ይህ ስለ ሟቹ ሰውና ስለ እናቱ ዳራዊ መረጃ ነበር። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

መበለት

ባሏ የሞተባትና ሁለተኛ ያላገባች ሴት

እጅግ ራራላት

“በጣም አዘነላት”

ቀርቦ

x

Luke 7:16

አያያዥ መግለጫ፡

ይህ ኢየሱስ ሞቶ የነበረውን ሰው በመፈወሱ ምክንያት የሆነውን ነገር ይነግረናል።

በሁሉም ላይ ፍርሐት ወደቀባቸው

“ሁሉም ፍርሐት ሞላባቸው”። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሁሉም በጣም ፈሩ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በመካከላችን ታላቅ ነቢይ ተነሥቷል

ያመለክቱ የነበሩት ወደ አንድ ማንነቱ ወዳልታወቀ ነቢይ ሳይሆን ወደ ኢየሱስ ነበር። እዚህ ጋ “ተነሥቷል” የሚለው ቃል “እንዲሆን ተደርጓል” ለሚለው የአነጋገር ዘይቤ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “እግዚአብሔር ከእኛ አንዱን ታላቅ ነቢይ አድርጎታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ጎብኝቷል
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም “አስቧቸዋል” የሚል ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ስለ ኢየሱስ የሆነው ይህ ወሬ ተስፋፋ
“ይህ ወሬ” የሚያመለክተው ሕዝቡ በቁጥር 16 ላይ ይናገሩት የነበሩትን ነገር ነው። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ሕዝቡ ይህንን የኢየሱስን ዝና አሰራጩት” ወይም “ሕዝቡ የኢየሱስን ዝና ለሌሎች ነገሯቸው”
ይህ ወሬ
“ይህ ዝና” ወይም “ይህ መልዕክት”
Luke 7:18
አያያዥ መግለጫ:
የሐንስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ኢየሱስን እንዲጠይቁት ይልካቸዋል።
የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ስለእነዚህ ነገሮች ሁሉ ነገሩት
ይህ በታሪኩ ውስጥ ስላለው አዲስ ሁነት ያስተዋውቃል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
ነገሩት
“ለዮሐንስ ነገሩት”
እነዚህን ነገሮች ሁሉ
“ኢየሱስ ሲያደርጋቸው የነበሩትን ነገሮች ሁሉ”
ሰዎቹ፣ “አጥማቂው ዮሐንስ ‘. . . አንተ ነህ ወይስ ሌላውን እንጠብቅ?’ ብለን እንድንጠይቅህ ወደ አንተ ልኮናል” አሉት።
ይህ ዐረፍተ ነገር፣ አንድ ግልጽ የሆነ ትዕምርተ ጥቅስ እንዲኖረው እንደገና ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት: “ሰዎቹ ‘እየመጣህ ያለኸው አንተ ነህ? ወይስ ሌላ እንጠብቅ’ ብለው እንዲጠይቁት አጥማቂው ዮሐንስ የላካቸው መሆኑን ተናገሩ” ወይም “ሰዎቹ፣ ‘እየመጣህ ያለኸው አንተ ትሆን እንደሆን ወይም ሌላ መጠበቅ ይኖርብን እንደሆን እንድንጠይቅህ አጥማቂው ዮሐንስ ወደ አንተ ልኮናል’ አሉት”። (ግልጽ የሆነና ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተመልከት)
ሌላ መጠበቅ ይኖርብን ይሆን?
“ሌላ እንጠብቅ?” ወይም “ሌላን ሰው እንጠባበቅ?”
Luke 7:21
በዚያን ሰዓት
“በዚያን ጊዜ”
ከክፉ መናፍስት
ፈውሰውን እንደገና መናገር ይጠቅም ይሆናል። ኢ.ት: “ከክፉ መናፍስት ፈወሳቸው” ወይም “ሰዎችን ከክፉ መናፍስት ነጻ አወጣቸው” (See: Ellipsis)
እንዲህ አላቸው
“ለዮሐንስ መልዕክተኞች እንዲህ አላቸው” ወይም “ዮሐንስ ለላካቸው መልዕክተኞች እንዲህ አላቸው”
ለዮሐንስ አስታውቁት
“ለዮሐንስ ንገሩት”
የሞቱ ሰዎች ተነሥተዋል
“የሞቱ ሰዎች እንደገና በሕይወት እንዲኖሩ ተደርገዋል”
የተቸገሩ ሰዎች
“ድኾች ሰዎች”
በሥራዎቼ ምክንያት በእኔ ማመኑን የማያቋርጥ ሰው የተባረከ ነው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “በሥራዎቼ ምክንያት በእኔ ማመኑን የማያቋርጠውን ሰው እግዚአብሔር ይባርከዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የማያቋርጥ ሰው የተባረከ ነው
“የማያቋርጡ ሰዎች የተባረኩ ናቸው” ወይም “ማንም የማያቋርጥ ሰው የተባረከ ነው” ወይም “የ . . . ማንም ቢሆን የተባረከ ነው”። ይህ አንድ ተለይቶ የታወቀ ሰው አይደለም።
በ. . . ምክንያት በእኔ ማመኑን የማያቋርጥ
የዚህ ድርብ አሉታ ትርጉም “በእኔ ማመኑን የሚቀጥል” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)
በእኔ የሚያምን
“ሙሉ በሙሉ በእኔ የሚታመን”
Luke 7:24
አያያዥ መግለጫ:
x
Luke 7:27
ስለ እርሱ የተጻፈለት ይህ ነው
“ነቢያት ስለ እርሱ የጻፉለት ነቢይ እርሱ ነው” ወይም “ከረጅም ዓመታት በፊት ነቢያት የጻፉለት ሰው ዮሐንስ ነው”
እነሆ፣ እልካለሁ
በዚህ ቁጥር ኢየሱስ ከትንቢተ ሚልክያስን በመጥቀስ፣ ሚልክያስ የተናገረለት መልዕክተኛ ዮሐንስ መሆኑን ይናገራል።
በፊትህ
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም፣ “በፊት ለፊትህ” ወይም “ከአንተ ቀድሞ እንዲሄድ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የአንተ
በትዕምርተ ጥቅሱ ውስጥ እግዚአብሔር የሚናገረው ለመሲሑ ስለ ነበረ “የአንተ” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው።
እልሃለሁ
ኢየሱስ የሚናገረው ለሕዝቡ ስለሆነ “አንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥርን አመልካች ነው። ኢየሱስ ይህንን የሚለው ቀጥሎ ለሚናገረው አስገራሚ እውነት አጽንዖት ለመስጠት ነው።
ከሴቶች በተወለዱት መካከል
“ሴቶች ከወለዷቸው መካከል”። ይህ ሰዎችን ሁሉ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “በሕይወት ከነበሩት ሰዎች ሁሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከዮሐንስ የሚበልጥ የለም
“የሚበልጠው ዮሐንስ ነው”
በእግዚአብሔር መንግሥት ታናሽ የሆነው
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በሚመሠርተው መንግሥት ውስጥ አባል የሚሆነውን ማንኛውንም ሰው ነው።
እርሱን የሚበልጠው ይሆናል
በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሰዎች መንፈሳዊ ሁኔታ መንግሥቱ ከመመሥረቱ በፊት ከነበራቸው የሚበልጥ ይሆናል። ኢ.ት: “የመንፈሳዊ ሕይወታቸው ደረጃ ከዮሐንስ ይልቅ ከፍ ያለ ይሆናል”
Luke 7:29
አጠቃላይ መረጃ
የዚህ መጽሐፍ ደራሲ የሆነው ሉቃስ ሰዎች ለዮሐንስና ለኢየሱስ ስላሳዩት ምላሽ አስተያየቱን ይሰጣል።
ሕዝቡ ሁሉ ... ጊዜ የዮሐንስ ጥምቀት
ለበለጠ ግልጽነት የዚህ ቁጥር ቅደም ተከተል ሊስተካከል ይችላል። ኢ.ት: “ቀረጥ ሰብሳቢዎቹን ጨምሮ በዮሐንስ የተጠመቁ ሰዎች ሁሉ ይህንን በሰሙ ጊዜ እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑን መሰከሩ”
እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑን መሰከሩ
“እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑን አሳይቷል አሉ” ወይም “እግዚአብሔር በጽድቅ አድርጓል ብለው መሰከሩ”
በዮሐንስ ጥምቀት ተጠምቀው ነበርና
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ዮሐንስ እንዲያጠምቃቸው ፈቅደው ነበርና” ወይም “ዮሐንስ አጥምቋቸው ነበርና” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን ዓላማ አልተቀበሉም
“እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የፈለገባቸውን አልተቀበሉም” ወይም “እግዚአብሔር የነገራቸውን ላለመታዘዝ መረጡ”
በዮሐንስ አልተጠመቁም ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ዮሐንስ እንዲያጠምቃቸው አልፈቀዱም ነበር” ወይም “የዮሐንስን ጥምቀት አልተቀበሉም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Luke 7:31
አያያዥ መግለጫ:
ኢየሱስ ስለ አጥማቂው ዮሐንስ ለሕዝቡ መናገሩን ይቀጥላል።

እንግዲህ ከምን ጋር ላነጻጽራቸው እችላለሁ … በምን ልመስላቸው?
ኢየሱስ ንጽጽርን ለማስተዋወቅ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቃል። እነዚህ እንደ መግለጫ ሊጻፉ ይችላሉ። ኢ.ት፡ “ይህንን ትውልድ የማነጻጽረውና ምን እንደሚመስሉ የምገልጸው እንደዚህ ነው” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አነጻጽራቸዋለሁ … ምን እንደሚመስሉ
እነዚህ ንጽጽር መሆኑ የተነገረባቸው ሁለት መንገዶች ናቸው።
የዚህ ትውልድ ሰዎች
ኢየሱስ በሚናገርበት ጊዜ በሕይወት የነበሩ ሰዎች ማለት ነው።
እነርሱ እንደዚህ ናቸው
እነዚህ ቃላት የኢየሱስ ንጽጽር ጅማሬዎች ናቸው። ሕዝቡ፣ በሌሎች ልጆች ሥራ በፍጹም እንደማይረኩ ልጆች መሆናቸውን ኢየሱስ ይናገራል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)
በገበያ ስፍራ
ሰዎች ሸቀጦቻቸውን ለመሸጥ የሚመጡበት ሰፊ ሜዳ
አልዘፈናችሁም
“እናንተ ግን ከሙዚቃው ጋር አልዘፈናችሁም”
አላለቀሳችሁም
“እናንተ ግን ከእኛ ጋር አላለቀሳችሁም”
Luke 7:33
እንጀራ አልበላም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “አዘውትሮ መጾም” ወይም 2) “የተለመደውን ምግብ አለመብላት” የሚሉት ናቸው።
‘አጋንንት አለበት’ ትላላችሁ
ኢየሱስ የሚጠቅሰው ሕዝቡ ስለ የሐንስ ይናገሩ የነበሩትን ነው። ይህ ያለ ቀጥተኛ ትዕምርተ ጥቅስ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አጋንንት አለበት ትላላችሁ” ወይም “አጋንንት እንዳለበት አድርጋችሁ ትከሱታላችሁ” (ግልጽ የሆነና ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተመልከት)
የሰው ልጅ
ኢየሱስ ወደ ራሱ ማመልከቱን ሕዝቡ እንደሚረዱ ጠብቋል። ኢ.ት፡ “የሰው ልጅ የሆንኩ እኔ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
‘እነሆ፣ ከኃጢአተኞች … ሆዳምና ሰካራም ሰው ነው!’ ትላላችሁ
ይህ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት፡ “እርሱ ከኃጢአተኞች … ሆዳምና ሰካራም ሰው ነው ትላላችሁ” ወይም “ከኃጢአተኞች… በመብላቱና ብዙ በመጠጣቱ ምክንያት ትከሱታላችሁ” (ግልጽ የሆነና ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተመልከት)
‘ተመልከቱ፣ ከኃጢአተኞች … ሆዳምና ሰካራም ሰው ነው!’ ትላላችሁ
“የሰው ልጅ” የሚለውን “የሰው ልጅ የሆንኩ እኔ” ብለህ ተርጉመህ ከሆነ አንደኛ መደብን በመጠቀም ቀጥተኛ እንዳልሆነ መግለጫ አድርገህ መናገር ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ከኃጢአተኞች… ሆዳምና ሰካራም እንደሆንኩ ትናገራላችሁ” (ቀጥተኛ የሆነና ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ እና አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
ሆዳም ሰው ነው
“ንፉግ በላተኛ ነው” ወይም “ባለማቋረጥ ብዙ ምግብ ይበላል”
ሰካራም
“ጠጪ” ወይም “ባለማቋረጥ የሚያሰክር መጠጥ አብዝቶ ይጠጣል”
ጥበብ በልጆቿ ሁሉ ጸድቃለች
ይህ ምናልባት ጥበበኞች ሰዎች ሕዝቡ ኢየሱስንና የሐንስን መቃወም እንዳልነበረባቸው የሚገነዘቡ መሆናቸውን ለማስተማር ኢየሱስ ከሁኔታው ጋር ያዛመደው ምሳሌአዊ አነጋገር ይሆናል።
Luke 7:36
አያያዥ መግለጫ፡
ፈሪሳዊው በቤቱ እንዲበላ ኢየሱስን ይጋብዘዋል።
አጠቃላይ መረጃ፡
አንድ ፈሪሳዊ በቤቱ ምግብ እንዲበላ ኢየሱስን ይጋብዘዋል።
ከፈሪሳውያኑ አንዱ
ይህ የታሪኩ አዲስ ክፍል መጀመሩን፣ በታሪኩ ውስጥም ፈሪሳዊውን ማስተዋወቁን ያመለክታል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ፣ አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
ለመብላት በገበታው አጠገብ ጋደም አለ
“ገበታው ጋ ለመብላት ተቀመጠ”። ወንዶች በምግቡ ዙሪያ በምቾት ጋደም ማለታቸውና እንዲህ ያለውን እራት ዘና ብለው መብላታቸው የተለመደ ነበር።
እነሆ፣ አንዲት ሴት ነበረች
“እነሆ” የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ ስላለ አዲስ ሰው ያነቃናል። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚገልጽበት መንገድ ይኖረው ይሆናል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ፣ አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
ኃጢአተኛ የነበረች
“በኃጢአት የተሞላ የኑሮ ዘይቤ የነበራት” ወይም “በኃጢአት ስለመኗሯ መጥፎ ምስክርነት የነበራት”። ምናልባት በሴተኛ አዳሪነት ትተዳደር የነበረች ሴት ትሆን ይሆናል።
የአልባስጥሮስ ብልቃጥ
“ከለስላሳ ድንጋይ የተሠራ ብልቃጥ”። አልባስጥሮስ ለስላሳና ነጭ የሆነ ድንጋይ ነው። ሰዎች ዋጋቸው ውድ የሆኑ ነገሮችን በአልባስጥሮስ ብልቃጦች ውስጥ ያስቀምጡ ነበር።
ሽቶ ያለበት ዘይት
“ከሽቶ ጋር የተዋሐደ”። ዘይቱ ጥሩ መዓዛ እንዲኖረው ያስደረገው አንዳች ነገር ነበረበት። ሰዎች ጥሩ መዓዛ እንዲኖራቸው በራሳቸው ላይ ያስነኩት ወይም በልብሳቸው ላይ ይረጩት ነበር።
በራሷ ጸጉር
“በጸጉሯ”
ሽቶ ባለው ዘይት ቀባቻቸው
“ሽቶ ቀባቻቸው”
Luke 7:39
እንዲህ ሲል ለራሱ አሰበ
“ለራሱ እንዲህ አለ”
ይህ ሰው ነቢይ ቢሆን ኖሮ ኃጢአተኛ … ባወቀ ነበር
ኢየሱስ ኃጢአተኛ የሆነች ሴት እንድትነካው በመፍቀዱ ነቢይ እንዳልሆነ ፈሪሳዊው አሰበ። ኢ.ት፡ “ኢየሱስ ነቢይ አለመሆኑ ግልጽ ነው፣ ምክንያቱም ነቢይ ቢሆን ኖሮ እየነካችው ያለችው ሴት ኃጢአተኛ መሆኗን ያውቅ ነበር”
እርሷ ኃጢአተኛ ናትና
ስምዖን፣ ኃጢአተኛ የሆነ ሰው እርሱን እንዲነካው አንድ ነቢይ በፍጹም መፍቀድ አይኖርበትም ብሎ ገምቷል። ይህ የግምቱ አካል በግልጽ መነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እርሷ ኃጢአተኛ ናት፣ እርሱ እንድትነካው መፍቀድ አይኖርበትም”
ስምዖን
ይህ ኢየሱስን ወደ ቤቱ የጋበዘው ፈሪሳዊ ስም ነበር። ይህ ስምዖን ጴጥሮስ አይደለም።
Luke 7:41
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ለፈሪሳዊው ስምዖን ለሚነግረው ነገር አጽንዖት ለመስጠት ታሪክ ይነግረዋል። (ምሳሌዎች የሚለውን ተመልከት)
ለአንድ ገንዘብ አበዳሪ ሁለት ተበዳሪዎች ነበሩት
“ሁለት ሰዎች ከአንድ የገንዘብ አበዳሪ ገንዘብ ተበደሩት”
አምስት መቶ ዲናር
“የ ‘500 ቀናት’ ደሞዝ”። “ዲናር” የዲናሪየስ ብዙ ቁጥር ነው። “ዲናሪየስ” ከብር ማዕድን የሚሠራ ሳንቲም ነበር። (መጽሐፍ ቅዱሳዊው ገንዘብ እና ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሌላኛው ሃምሳ
“ሌላኛው ተበዳሪ ሃምሳ ዲናር ተበደረ” ወይም “የ ’50 ቀን’ ደሞዝ”
Luke 7:46
አንተ … አላደረግህም፣ እርሷ ግን
ኢየሱስ የስምዖንን ደካማ እንግዳ አቀባበል ከሴቲቱ ተግባር ጋር ማነጻጸሩን ይቀጥላል።
Luke 7:48
ከዚያም እንዲህ አላት
“ከዚያም ሴቲቱን እንዲህ አላት”
ኃጢአትሽ ይቅር ተብሎልሻል
“ይቅር ተብለሻል”። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ኃጢአትሽን ይቅር ብዬሻለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

በአንድነት ጋደም ብለው
"በማዕዱ ዙሪያ በአንድነት ጋደም ብለው" ወይም "በአንድነት ሲመገቡ"
ኃጢአትን እንኳን ይቅር የሚል ይህ ማነው?
የሃይማኖት መሪዎች ኃጢአትን ይቅር ማለት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ያውቃሉ፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር እንደነበረ ግን አላመኑም። ይህ ጥያቄ ምናልባት ወቀሳ እንዲሆን ሳይታሰብ አልቀረም። ኢ.ት: "ይህ ሰው ማን እንደሆነ ነው የሚያስበው? ኃጢአትን ይቅር ማለት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው!" ወይም "ይህ ሰው እርሱ ብቻ ኃጢአትን ይቅር ለማለት የሚችለውን እግዚአብሔርን ለመሆን የሚሞክረው ለምንድነው?"
እምነትሽ አድኖሻል
"በእምነትሽ ምክንያት ድነሻል"። የነገር ስም የሆነው "እምነት" እንደ ድርጊት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "ስላመንሽ ድነሻል" (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 8
Luke 8:1
አጠቃላይ መረጃ:
እነዚህ ቁጥሮች ኢየሱስ በጉዞ ላይ እያለ ስለ ሰበከው ስብከት ዳራዊ መረጃ ይሰጣሉ።
እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ለማመልከት ነው። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
ከክፉ መናፍስትና ከበሽታ ተፈውሰው የነበሩት
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "ኢየሱስ ከክፉ መናፍስት ነጻ ያወጣቸውና ከበሽታ ፈውሷቸው የነበሩ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ማርያም … ሶስና
ሦስቱ ሴቶች ተጠቅሰዋል፡ ማርያም፣ ዮሐና፣ እና ሶስና (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የተባለችው ማርያም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "ሰዎች መግደላዊት ብለው የሚጠሯት ማርያም … ኢየሱስ ሰባት አጋንንት አስወጥቶላት የነበረች" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የሔሮድስ ቤት ኃላፊ የሆነው የኩዛ ሚስት የሐና
ዮሐና የኩዛ ሚስት ስትሆን ኩዛ ደግሞ የሔሮድስ ቤት ኃላፊ ነበር። "የሔሮድስ ቤት ኃላፊ የሆነው የኩዛ ሚስት ዮሐና" (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
የሚያስፈልጋቸውን ያቀርቡ ነበር
"ኢየሱስንና ደቀ መዛሙርቱን በገንዘብ ይደግፉ ነበር"
Luke 8:4
አጠቃላይ መረጃ:
ኢየሱስ ስለ መሬቱ ምሳሌ ለሕዝቡ ይነግራቸዋል። የምሳሌውን ትርጉም ለደቀ መዛሙርቱ ያብራራላቸዋል። (ምሳሌዎች የሚለውን ተመልከት)
ወደ እርሱ ይመጡ ነበር
"ወደ ኢየሱስ ይመጡ ነበር"
አንድ ገበሬ ዘሩን ለመዝራት ሄደ
"አንድ ገበሬ እርሻ ላይ ዘር ለመዝራት ሄደ" ወይም "አንድ ገበሬ ጥቂት ዘር እርሻ ላይ ለመዝራት ሄደ"
ጥቂቱ ወደቀ
"ከዘሩ ጥቂቱ ወደቀ" ወይም "ጥቂት ዘሮች ወደቁ"
በእግር ተረገጠ
x
Luke 8:7
አያያዥ መግለጫ:
ኢየሱስ ለሕዝቡ ምሳሌዎቹን መናገሩን ያበቃል።
አነቀው
የገበሬው ዘር መብቀል እንዳይችል ማዕድናቱን ሁሉ፣ ውሃውንና የፀሐይ ብርሃኑን የእሾኹ ተክል ወሰደው።
ፍሬ አፈራ
"ምርት አበቀለ" ወይም "ብዙ ዘር አበቀለ"
ከመቶ ዕጥፍ የበለጠ
ይህ ማለት ከተዘራው ዘር ከመቶ ዕጥፍ በላይ የሆነ ማለት ነው።
የሚሰማ ጆሮ ያለው ማንም ቢሆን ይስማ
በአንዳንድ ቋንቋዎች በሁለተኛ መደብ መጠቀም በይበልጥ የተለመደ ይሆናል። "የሚሰማ ጆሮ ያላችሁ እናንተ፣ ስሙ" (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
Luke 8:9
አያያዥ መግለጫ:
ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ መናገር ይጀምራል።
የ … እውቀት እግዚአብሔር የሰጣችሁ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "የ… እውቀት እግዚአብሔር ሰጥቷችኋል" ወይም "የእግዚአብሔርን … መረዳት እንድትችሉ እግዚአብሔር አድርጓችኋል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የእግዚአብሔርን መንግሥት ምስጢር
እነዚህ የተደበቁ እውነቶች ናቸው፣ አሁን ግን ኢየሱስ ገልጧቸዋል።
ለሌሎች
"ለሌሎች ሰዎች"። ይህ የሚያመለክተው የኢየሱስን ትምህርት ያልተቀበሉትንና እርሱን ያልተከተሉትን ሰዎች ነው።
እያዩ እንዳያዩ
"ቢያዩም አይገነዘቡም"። ይህ ከነቢዩ ከኢሳይያስ የተጠቀሰ ጥቅስ ነው። አንዳንድ ቋንቋዎች የግሱን ባለቤት ማስታወቅ ያስፈልጋቸው ይሆናል። ኢ.ት: "ነገሮችን ቢያዩም አያስተውሏቸውም" ወይም "የሚሆኑትን ነገሮች ቢያዩም ምን ትርጉም እንዳላቸው አያስተውሉም"
እየሰሙ እያስተውሉም
"ቢሰሙም አያስተውሉም"። ይህ ከነቢዩ ከኢሳይያስ የተጠቀሰ ጥቅስ ነው። አንዳንድ ቋንቋዎች የግሱን ባለቤት ማስታወቅ ያስፈልጋቸው ይሆናል። ኢ.ት: "ትምህርትን ቢሰሙም እውነቱን አያስተውሉም"
Luke 8:11
አያያዥ መግለጫ:
ኢየሱስ ስለ መሬት የተናገረውን ምሳሌ ትርጉም ለደቀ መዛሙርቱ ማብራራት ይጀምራል።
ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው
"ዘሩ ከእግዚአብሔር የመጣው መልዕክት ነው"
በመንገድ ዳር የሆኑት እነዚያ
"በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር እርሱ"። ኢየሱስ ከሰዎች ጋር በማገናኘት ዘሩ ምን እንደሚሆን ይናገራል። ኢ.ት: "በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል" ወይም "በምሳሌው ውስጥ በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እነዚያ ናቸው
ዘሩ ሰው የሆነ ይመስል ኢየሱስ ስለ ሰዎች አንድ ነገር ለማሳየት በመፈለግ ስለ ዘር ይናገራል። ኢ.ት: "ሰዎች ላይ የሚሆነውን ያሳያል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዲያብሎስ ይመጣና ከልባቸው ቃሉን ይወስደዋል
እዚህ ጋ "ልባቸው" የሰዎችን አዕምሮ ወይም ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: "ዲያብሎስ ይመጣና የእግዚአብሔርን መልዕክት ከውስጠኛው አስተሳሰባቸው ይወስደዋል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይወስደዋል
ይህ ዘሩን የሚለቅም ወፍ በምሳሌው ውስጥ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ይህንን ስዕል ማሳየት የሚችልን ቃል በቋንቋህ ለመጠቀም ሞክር። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እምነው እንዳይድኑ
ይህ የዲያብሎስ ዓላማ እስከ ሆነ ድረስ እንደሚከተለው ሊተረጎም ይችላል። ኢ.ት: "ዲያብሎስ፣ 'እምነው መዳን የለባቸውም' ብሎ ስለሚያስብ" ወይም "እንዳያምኑና እግዚአብሔር እንዳያድናቸው" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በዐለት ላይ የወደቁት እነዚያ
"በዐለታማ አፈር ላይ የወደቁት እነዚያ"። ኢየሱስ ከሰዎች ጋር በማገናኘት ዘሩ ምን እንደሚሆን ይናገራል። ኢ.ት: "በዐለታማው መሬት ላይ የወደቀው ዘር ሰዎችን


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይወክላል” ወይም “በምሳሌው ውስጥ በዐለታማው መሬት ላይ የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ዐለቱ

“ዐለታማው መሬት”

በፈተና ጊዜ

“መከራ በሚገጥማቸው ጊዜ”

ይወድቃሉ

የአነጋገር ዘይቤው ትርጉም “ማመናቸውን ያቆማሉ” ወይም “ኢየሱስን መከተላቸውን ያቆማሉ” የሚል ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)

Luke 8:14

በእሾህ መካከል የወደቀው ዘር ሰዎች ናቸው

“በእሾህ መካከል የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል” ወይም “በምሳሌው ውስጥ በእሾህ መካከል የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወካላል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የዚህ ሕይወት ምቾት ... ታንቀዋል

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “የዚህ ሕይወት ፍላጎት፣ ባለጸግነትና ደስታ ያንቃቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ፍላጎት

ሰዎች የሚጨነቁላቸው ነገሮች

የዚህ ሕይወት ደስታ

“በዚህ ሕይወት ሰዎች የሚደሰቱባቸው ነገሮች”

በዚህ ሕይወት ፍላጎት፣ ባለጸግነትና ደስታ ስለ ታነቁ በተገቢው ሁኔታ አያፈሩም

ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር የሚያመለክተው አረሙ የቡቃያውን ብርሃንና ማዕድናት በማቋረጥ ከዕድገት እንደሚገታቸው ነው። ኢ.ት፡ “አረም መልካሙን ቡቃያ ከማደግ እንደሚገታው የዚህ ሕይወት ፍላጎት፣ ብልጽግና እና ደስታም እነዚህን ሰዎች ፍሬአማ ከመሆን ይገታቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ፍሬአቸው አይበስልም

“የደረሰ ፍሬ አያፈሩም”። ብስል ፍሬ የመልካም ሥራ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “የበሰለ ፍሬ እንደማያፈራ ተክል እነርሱም መልካም ሥራ አይሠሩም” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በመልካሙ መሬት ላይ የወደቀው ዘር እነዚህ ናቸው

“በመልካም መሬት ላይ የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል” ወይም “በምሳሌው ውስጥ በመልካም መሬት ላይ የወደቀው ዘር ሰዎችን ይወክላል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ቃሉን ሰምተው

“መልዕክቱን ሰምተው”

በመልካምና ቅን ልብ

እዚህ ጋ “ልብ” የሰውን አሳብ ወይም ፍላጎት የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በመልካምና ቅን ምኞት”

በትዕግስት በመጽናት ፍሬ የሚያፈራ

“በትዕግስት በመጽናት ፍሬ የሚሰጡ” ወይም “በማያቋርጥ ጥረት ፍሬ የሚሰጡ”። ፍሬ የመልካም ሥራ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “መልካም ፍሬ እንደሚያፈራ ጤነኛ ተክል በመጽናት መልካም ሥራን ይሠራሉ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Luke 8:16

አያያዥ መግለጫ፡

ኢየሱስ በሌላ ምሳሌ መናገሩን ይቀጥላል፣ ከዚያም ቤተሰቦቹ በእርሱ ሥራ ውስጥ ስለሚኖራቸው ሚና አጽንዖት በመስጠት ለደቀ መዛሙርቱ መናገሩን ያበቃል።

ማንም የለም

ይህ ሌላ ምሳሌ የመጀመሩ ምልክት ነው። (ምሳሌዎች የሚለውን ተመልከት)

ተደብቆ ሳይታወቅ የሚቀር ምንም ነገር የለም

ይህ ድርብ አሉታ እንደ አዎንታዊ ንግግር ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት፡ “የተደበቀ ነገር ሁሉ እንዲታወቅ ይደረጋል” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

የማይታወቅና ወደ ብርሃን የማይመጣ ምስጢር ሆኖ የሚቀር ምንም ነገር የለም

ይህ ድርብ አሉታ እንደ አዎንታዊ ንግግር ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት፡ “ምስጢር የሆነው ነገር ሁሉ ወደ ብርሃን ይመጣል፣ እንዲታወቅም ይደረጋል” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ላለው የበለጠ ይሰጠዋል

ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ማስተዋልና ስለ ማመን መሆኑን ከዐውዱ በግልጽ መረዳት ይቻላል። ይህ በግልጽ ሊነገርና ወደ አድራጊ ድምፅ ሊቀየር ይችላል። ኢ.ት፡ “ማስተዋል ላለው ለማንም ቢሆን የበለጠ ማስተዋል ይሰጠዋል” ወይም “እግዚአብሔር እውነትን የሚያምኑትን እነዚያን የበለጠ እንዲያስተውሉ ደግሞ ያስችላቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከሌለው ... ከእርሱ ይወሰድበታል

ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ማስተዋልና ስለ ማመን መሆኑን ከዐውዱ በግልጽ መረዳት ይቻላል። ይህ በግልጽ ሊነገርና ወደ አድራጊ ድምፅ ሊቀየር ይችላል። ኢ.ት፡ “ማንም ማስተዋል የሌለው ሰው አለኝ የሚለውን ማስተዋል እንኳን ያጣዋል” ወይም “ነገር ግን እውነትን የማያምኑትን እነዚያን ተረድተነዋል የሚሉትን ጥቂቱን ማስተዋል እንኳን እንዳያስተውሉ ያደርጋቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

Luke 8:19

ወንድሞች

እነዚህ ከኢየሱስ በኋላ ከማርያምና ከዮሴፍ የተወለዱ፣ የኢየሱስ ታናናሽ ወንድሞች የነበሩ ሌሎች ወንዶች ልጆች ናቸው። የኢየሱስ አባት እግዚአብሔር፣ የእነርሱ አባት ደግሞ ዮሴፍ እስከ ሆነ ደረስ በሙያዊ አገላለጽ በእናቱ በኩል ወንድሞቹ ናቸው። ይህ ዝርዝር በአግባቡ አልተተረጎመም።

ተነገረው

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች ነገሩት” ወይም “አንድ ሰው ነገረው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ሊያዩህ ፈልገው

“ሊያዩህ ይፈልጋሉ”

እናትና ወንድሞቼ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉት እነርሱ ናቸው

ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር የሚገልጸው ከኢየሱስ ለመስማት የሚመጡ ሰዎች ለእርሱ የቤተሰቡን ያህል አስፈላጊዎች መሆናቸውን ነው። ኢ.ት፡ “የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚታዘዙት እነርሱ ለእኔ እንደ እናቴና ወንድሞቼ ናቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የእግዚአብሔር ቃል

“እግዚአብሔር የተናገረው መልዕክት”

Luke 8:22

አያያዥ መግለጫ፡

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የጌንሳሬጥን ሐይቅ ለመሻገር በጀልባ ይጠቀማሉ። ደቀ መዛሙርቱ በሚነሣው ማዕበል አማካይነት ስለ ኢየሱስ ኃይል በይበልጥ ይማራሉ።

ሐይቁ

ይህ የጌንሳሬጥ ሐይቅ ነው፣ የገሊላ ባህር ተብሎም ይጠራል።

መጓዝ ጀመሩ

የዚህ አገላለጽ ትርጉም፣ ሐይቁን ለመሻገር በጀልባቸው መጓዝ ጀመሩ የሚል ነው።

በመጓዝ ላይ እያሉ

“ሲሄዱ ሳሉ”

አንቀላፋ

“ማንቀላፋት ጀመረ”

ከባድ ዐውሎ ንፋስ ወረደ

“በጣም ታላቅ የሆነ ዐውሎ ንፋስ ጀመረ” ወይም “በጣም ኃይለኛ ንፋስ በድንገት መንፈስ ጀመረ”

ጀልባቸው በውሃ ይሞላ ነበር

ኃይለኛው ንፋስ ብርቱ ሞገድ በማስነሣት የጀልባዋን ጎንና ጎን በውሃ እንዲገፋት አደረገ። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ንፋሱ ከፍተኛ ሞገድ በመፍጠር ጀልባቸውን በውሃ መሙላት ጀመረ”

Luke 8:24

ገሰጸው

በቀጥታ ተናገረው

የውሃው ቁጣ

“አስፈሪው ሞገድ”

ተዉ

“ንፋሱና ማዕበሉ ቆመ” ወይም “ጸጥ አሉ”

እምነታችሁ የት አለ?

ኢየሱስ ለእነርሱ ስለሚያደርግላቸው ጥበቃ ስላልታመኑት በእርጋታ ይገስጻቸዋል። ይህ እንደ መግለጫ ሊጻፍ ይችላል። ኢ.ት፡ “እምነት ሊኖራችሁ ይገባል!” ወይም “ልትታመኑብኝ ይገባል!” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

… የሚታዘዙለት እንግዲያው ይህ ማን ይሆን?
“… የሚታዘዙለት ይህ ምን ዓይነት ሰው ነው?” ይህ ጥያቄ ኢየሱስ ማዕበሉን መቆጣጠር መቻሉ የፈጠረባቸውን ድንጋጤና ግራ መጋባት ይገልጻል። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የሚያዝ … የሚታዘዙለት እንግዲያው ይህ ማን ይሆን?
ይህ ወደ ሁለት ዐረፍተ ነገር ሊቀየር ይችላል። “እንግዲህ ይህ ማነው? እርሱ ያዛቸዋል … ይታዘዙታል!”
Luke 8:26
አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ከአንድ ሰው ብዙ አጋንንት ወዳወጣበት ወደ ጌርጌሴኖን ባህር ዳርቻ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር መጣ።
ጌርጌሴኖን ወደሚባል ሀገር
ጌርጌሶናዊያን ጌርጌሴኖን የምትባል ከተማ ሰዎች ነበሩ። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
ከገሊላ ሐይቅ ማዶ
“ከገሊላ ሐይቅ በወዲያኛው ማዶ”
አንድ ሰው ከከተማው
“አንድ ሰው ከጌርጌሴኖን ከተማ”
አጋንንት የነበሩበት አንድ ሰው ከከተማ
ሰውየው አጋንንት ነበሩበት፤ አጋንንት የኖሩት በከተማው ላይ አልነበረም። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ከከተማ. . . ይህ ሰው አጋንንት ነበሩበት”
አጋንንት የነበሩበት
“አጋንንት ተቆጣጥረውት የነበረ” ወይም “አጋንንት የተቆጣጠሩት”
ለረጅም ጊዜ ራቁቱን ይኖር ነበር … ነገር ግን በመቃብር መካከል
ይህ አጋንንት ስለነበሩበት ሰው ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ራቁቱን ይኖር ነበር
“ልብስ አይለብስም ነበር”
መቃብር
ይህ ሰዎች ሬሳ የሚያኖሩበት፣ ምናልባት አንድ ሰው ለመጠለያነት የሚጠቀምበት ዋሻ ወይም አነስተኛ ግንብ ሊሆን ይችላል።
Luke 8:28
ኢየሱስን ባየው ጊዜ
“አጋንንት የነበሩበት ሰው ኢየሱስን ባየው ጊዜ”
ጮኸ
“በታላቅ ድምፅ ጮኸ” ወይም “በስቃይ ጮኸ”
በፊቱ ወደቀ
“በኢየሱስ ፊት በምድር ላይ ወደቀ”። የወደቀው በድንገት አይደለም።
በታላቅ ድምፅ ተናገረ
“በጩኸት ተናገረ” ወይም “ከፍ ባለ ድምፅ ጮኸ”
ከእኔ ጋር ምን ጉዳይ አለህ
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም “ለምን ታስቸግረኛለህ?” ማለት ነው። (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የልዑል እግዚአብሔር ልጅ
ይህ ለኢየሱስ አስፈላጊ ማዕረግ ነው። (አባትን እና ልጅን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)
ከያዘው ብዙ ጊዜ ሆኖት ነበር
“ሰውየውን ከተቆጣጠረው ብዙ ጊዜ ሆኖት ነበር” ወይም “ወደ እርሱ ከገባበት ብዙ ጊዜ ሆኖት ነበር”። ይህ የሚናገረው ኢየሱስ ከሰውዬው ጋር ከመገናኘቱ በፊት አጋንንቱ ብዙ ጊዜ ያደርገው የነበረውን ነው።
ቢታሰርም እንኳን … ይጠብቁት ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሰዎች በሰንሰለትና በእግር ብረት ቢያስሩትና ቢጠብቁትም እንኳን” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Luke 8:30
ሌጌዎን
ይህንን ብዙ ቁጥር ያላቸውን ወታደሮች ወይም ሰዎች በሚያመለክት ቃል ተርጉመው። አንዳንድ ትርጉሞች “ሰራዊት” ይሉታል። ኢ.ት፡ “የሻለቃ ጦር” ወይም “ብርጌድ”
እርሱን ይለምነው ጀመር
“ኢየሱስን ይለምነው ጀመር”
Luke 8:32
በዚህ ጊዜ በኮረብታው ወገብ ላይ ብዙ የአሳማ መንጋ ይመገቡ ነበር
ይህ ስለ አሳማዎቹ ለማስተዋወቅ የተጨመረ ዳራዊ መረጃ ነው። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
በኮረብታው ወገብ ይመገቡ ነበር
“ኮረብታው ላይ ሣር እየተመገቡ በአቅራቢያው ነበሩ”
ስለዚህ አጋንንቱ ወጡ
እዚህ ጋ፣ “ስለዚህ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው አጋንንቱ ከሰውየው የወጡት ኢየሱስ ወደ አሳማዎቹ እንዲገቡ ስለነገራቸው መሆኑን ለማብራራት ነው።
ተጣደፉ
በጣም በፍጥነት ሮጡ
መንጋው … ሰመጡ
“መንጋው… ሰመጡ”። አሳማዎቹ ራሳቸው ውሃው ውስጥ ስለ ነበሩ ማንም እንዲሰምጡ አላደረጋቸውም።
Luke 8:34
አጋንንት የወጡለትን ሰው አገኙት
“አጋንንት የለቀቁትን ሰው አዩት”
በአዕምሮው ሆኖ
“ጤነኛ” ወይም “ትክክለኛ ጠባይ ሲያሳይ”
በኢየሱስ እግሮች አጠገብ ተቀምጦ
እዚህ ጋ፣ “እግሮች አጠገብ ተቀምጦ” የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትርጉሙ “በአጠገቡ በትህትና ተቀምጦ” ወይም “በፊት ለፊቱ ተቀምጦ”። ኢ.ት፡ “በኢየሱስ ፊት ለፊት መሬት ላይ ተቀምጦ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ፈርተው ነበር
ኢየሱስን ፈርተውት እንደነበረ በግልጽ መናገር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ኢ.ት፡ “ኢየሱስን ፈርተውት ነበር”
Luke 8:36
አይተውት የነበሩት
“እነዚያ የሆነውን ነገር ያዩት”
በአጋንንት ተይዞ የነበረውና የተፈወሰው ሰው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አጋንንት ይዞት የነበረውን ሰው ኢየሱስ ፈውሶት ነበር” ወይም “አጋንንት ተቆጣጥሮት የነበረውን ሰው ኢየሱስ ፈውሶት ነበር” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የጌርጌሴኖን ሀገር
“ያ የጌርጌሴናውያን አካባቢ” ወይም “ጌርጌሴናውያን ሰዎች ይኖሩበት የነበረ አካባቢ”
ታላቅ ፍርሃት ያዛቸው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በጣም ፈሩ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ተመለስ
መዳረሻው ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ወደ ሐይቁ ማዶ ተመልሰህ ሂድ”
Luke 8:38
ሰውዬው
በእነዚህ ቁጥሮች የተፈጸሙት ሁነቶች ኢየሱስ በጀልባ ከመሄዱ በፊት ነው። ይህንን መነሻው ላይ ግልጽ አድርጎ መናገር ሊጠቅም ይችላል። ኢ.ት፡ “ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከመሄዳቸው በፊት ሰውዬው” ወይም “ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የጀልባ ጉዞአቸውን ከመጀመራቸው በፊት ሰውዬው”
ቤትህ
“ቤተሰቦችህ” ወይም “ዘመዶችህ”
እግዚአብሔር ያደረገልህን ሁሉ መስክር
“እግዚአብሔር ስላደረገልህ ነገር ሁሉ ንገራቸው”
Luke 8:40
አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከሐይቁ በሌላኛው በኩል ከገሊላ በተመለሱ ጊዜ 12 ዓመት የሆናትን የምኩራብ አለቃውን ልጅ፣ እንዲሁም 12 ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረችውን ሴት ፈወሳቸው።
አጠቃላይ መረጃ፡

generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እነዚህ ቁጥሮች ስለ ኢያኢሮስ ዳራዊ መረጃ ይሰጣሉ። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
ሕዝቡ ተቀበለው
“ሕዝቡ በደስታ ሰላምታ ሰጡት”
ከምኩራብ አለቆች አንዱ
“በአካባቢው በነበረ ምኩራብ አለቆች ከሆኑት አንዱ” ወይም “በዚያች ከተማ በምኩራብ የተገናኘው የሕዝቡ መሪ”
በኢየሱስ እግር ላይ ተደፋ
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “በኢየሱስ እግር ስር ሰገደ” ወይም 2) “በኢየሱስ እግር አጠገብ በምድር ላይ ወደቀ”። ኢያኢሮስስ የወደቀው በድንገት አይደለም። ይህንን ያደረገው ለኢየሱስ ስላለው ትህትና እና አክብሮት ምልክት እንዲሆን ነው የሚሉት ናቸው።
እየሞተች ነው
“ልትሞት ነው”
ኢየሱስ በመንገድ ላይ እያለ
አንዳንድ ተርጓሚዎች ኢየሱስ ከኢያኢሮስ ጋር ለመሄድ መስማማቱን በቅድሚያ መናገር ይኖርባቸዋል። ኢ.ት፡ “ስለዚህ ኢየሱስ ከእርሱ ጋር ለመሄድ ተስማማ። በመንገድ ላይ እያለ”
ብዙ ሕዝብ በዙሪያው ሆነው አጋፉት
“ሰዎቹ በኢየሱስ ዙሪያ ተጠጋግተው ከበውት ነበር”
Luke 8:43
በዚያ አንዲት ሴት ነበረች
ይህ በታሪኩ ውስጥ አንድ አዲስ ገጸ ባህርይ ያስተዋውቃል። (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
ትደማ የነበረች
“ደም ይፈሳት የነበረች”። ተገቢው ጊዜ ባይሆንም እንኳን ምናልባት በማህፀን እያለች ጀምሮ ሳትደማ አልቀረችም። አንዳንድ ባህሎች እንደዚህ ያለውን ሁኔታ በትህትና የሚያመላክቱበት መንገድ ይኖራቸዋል።
በማንም ልትፈወስ አልቻለችም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ነገር ግን ማንም ሊፈውሳት አልቻለም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የልብሱን ጫፍ ነካች
“የመጎናጸፊያውን ዘርፍ ነካች”። አይሁዳውያን ወንዶች በእግዚአብሔር ሕግ እንደታዘዘው የክብረ በዓል ልብሶቻቸው አካል በማድረግ በመጎናጸፊያዎቻቸው ላይ መነሳንስ ይደርቡ ነበር። እርሷ የነካችው ይህንን ሊሆን ይችላል።
Luke 8:45
ብዙ ሕዝብ … እያጋፉህ ነው
ጴጥሮስ ይህንን ሲል የትኛውም ሰው ኢየሱስን ሊነካው ይችል እንደነበር ማመልከቱ ነው። አስፈላጊ ከሆነ ይህ ግልጽ ያልሆነ መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። ኢ.ት፡ “በዙሪያህ ብዙ ሕዝብ ከቦ እያጋፋህ ነው፣ ስለዚህ ከእነርሱ አንዱ ነክቶህ ይሆናል”
አንድ ሰው ነክቶኛል
ይህንን ሆነ ተብሎ የተደረገውን “መንካት” ከሕዝቡ ድንገተኛ መንካት መለየት ሊጠቅም ይችላል። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ሆን ብሎ ነክቶኛል”
ከእኔ ኃይል እንደ ወጣ አውቃለሁ
ኢየሱስ ኃይል አላጣም ወይም አልደከመም፣ ነገር ግን የእርሱ ኃይል ሴቲቱን ፈውሷታል። ኢ.ት፡ “የሚፈውስ ኃይል ከእኔ እንደወጣ አውቃለሁ” ወይም “ኃይሌ አንድ ሰው እንደ ፈወሰ ተሰምቶኛል”
Luke 8:47
ከዕይታ ማምለጥ እንደማትችል
“ያደረገችውን በምስጢር መያዝ እንደማትችል”። ምን እንዳደረገች መናገር ሊጠቅም ይችላል። ኢ.ት፡ “ኢየሱስን የነካችው እርሷ የመሆኗን ምስጢር መያዝ እንደማትችል”
እየተንቀጠቀጠች መጣች
“በፍርሐት እየተንቀጠቀጠች መጣች”
በፊቱ ወደቀች
ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “በኢየሱስ ፊት ሰገደች” ወይም 2) “በኢየሱስ እግር ላይ በምድር ላይ ተደፋች”። የወደቀችው በድንገት አይደለም። ይህ ለኢየሱስ የቀረበ የትህትና እና የአክብሮት ምልክት ነው የሚሉት ናቸው።
በሕዝቡ ሁሉ ፊት
“ሕዝቡ ሁሉ እያዩ”
ሴት ልጅ
ይህ አንዲትን ሴት በደግነት የመናገሪያ መንገድ ነበር። የአንተ ቋንቋ ይህንን ደግነት የሚያሳይበት ሌላ መንገድ ይኖረው ይሆናል።
እምነትሽ ጤነኛ አድርጎሻል
“በእምነትሽ ምክንያት ጤነኛ ሆነሻል”። የነገር ስም የሆነው “እምነት” እንደ ድርጊት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ስላመንሽ ተፈውሰሻል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)
በሰላም ሂጂ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ “ደህና ሁኚ” የማለትና በዚያው ጊዜ ቡራኬን የመስጠት መንገድ ነው። ኢ.ት፡ “ስትሄጂም ከእንግዲህ አትጨነቂ” ወይም “እየሄድሽ እያለሽ እግዚአብሔር ሰላምን ይስጥሽ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
Luke 8:49
ገና እየተናገረ እያለ
“ኢየሱስ ገና ለሴቲቱ እየተናገረ እያለ”
የምኩራብ አለቃ
ይህ ኢያኢሮስን ያመለክታል (ሉቃስ 8:41 ን ተመልከት)።
መምህሩን አታስቸግረው
ይህ መግለጫ ልጅቱ ስለሞተች ኢየሱስ ከአሁን በኋላ ምንም ነገር ለማድረግ እንደማይችል ያመለክታል።
መምህሩ
ይህ ኢየሱስን ያመለክታል።
ትፈወሳለች
“ደህና ትሆናለች” ወይም “እንደገና በሕይወት ትኖራለች”
Luke 8:51
ወደ ቤት በመጣ ጊዜ
“ወደ ቤት በመጡ ጊዜ”። ኢየሱስ ከኢያኢሮስ ጋር ወደዚያ ሄደ። ደግሞም አንዳንድ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ከእነርሱ ጋር ሄዱ።
ከጴጥሮስ፣ የሐንስ፣ ያዕቆብ፣ ከልጅቱ አባትና እናት በስተቀር … ለማንም አልፈቀደም
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ኢየሱስ ለጴጥሮስ፣ ለዮሐንስ፣ ለያዕቆብ፣ ለልጅቱ አባትና እናት ብቻ ከእርሱ ጋር ወደ ውስጥ እንዲገቡ ፈቀደላቸው”
የልጅቱ አባት
ይህ የሚያመለክተው ኢያኢሮስን ነው።
ሁሉም ያለቅሱና ሙሾ ያወጡላት ነበር
ይህ በዚያ ባህል የተለመደ የሐዘን መግለጫ መንገድ ነበር። ኢ.ት፡ “በዚያ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ልጅቱ ሞታ ስለነበር ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በማልቀስ ምን ያህል እንዳዘኑ በመግለጽ ላይ ነበሩ”
መሞቷን ስላወቁ ሳቁበት
“ልጅቱ መሞቷን ስላወቁ ሳቁበት”
Luke 8:54
እጇን ያዘ
“ኢየሱስ የልጅቱን እጅ ያዘ”
መንፈሷ ተመለሰ
“መንፈሷ ወደ አካሏ ተመለሰ”። አይሁድ ሕይወት ማለት የመንፈስ ወደ ሰው ውስጥ መምጣት እንደነበር ተረድተዋል። ኢ.ት፡ “እንደገና መተንፈስ ጀመረች” ወይም “ወደ ሕይወት ተመለሰች” ወይም “እንደገና ሕያው ሆነች”
ለአንድም ሰው እንዳይነግሩ
ይህ በተለየ ሁኔታ መነገር ይችል ነበር። ኢ.ት፡ “ለማንም እንዳይነግሩ”

---

Chapter 9
Luke 9:1
አያያዥ መግለጫ፡
ኃይል እንዲሰጣቸው በገንዘብና ባላቸው ነገር እንዳይታመኑ ኢየሱስ ያስታውሳቸዋል፣ ከዚያም ወደ ተለያየ ስፍራ ይልካቸዋል።
ኃይልና ሥልጣን
እነዚህ ሁለት ቃላት በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት፣ አሥራ ሁለቱ ሰዎች ለመፈወስ ችሎታና መብት እንደነበራቸው ለማሳየት ነው። ይህንን ሐረግ እነዚህን ሁለቱንም አሳቦች በሚይዙ ውሁድ ቃላት ተርጉማቸው።

አጋንንትን ሁሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “እያንዳንዱን አጋንንት” 2) “ሁሉንም ዓይነት አጋንንት” የሚሉት ናቸው።
በሽታ
ሕመም
ላካቸው
“ወደተለያየ ስፍራ ላካቸው” ወይም “እንዲሄዱ ነገራቸው”
Luke 9:3
እንዲህ አላቸው
“ኢየሱስ ለአሥራ ሁለቱ እንዲህ አላቸው”። ይህ የሆነው ከመሄዳቸው በፊት መሆኑን መናገር ሊጠቅም ይችላል። ኢ.ት፡ “ከመሄዳቸው በፊት ኢየሱስ እንዲህ አላቸው”
ምንም ነገር አትውሰዱ
“ምንም ነገር ይዛችሁ አትሂዱ” ወይም “ምንም ነገር አታምጡ”
ለጉዞአችሁ
“ለመንገዳችሁ” ወይም “በምትጓዙበት ጊዜ”። ወደ ኢየሱስ እስኪመለሱ ድረስ ከመንደር ወደ መንደር በሚዘዋወሩበት ጊዜ ለጉዞአቸው ምንም ነገር መውሰድ አይኖርባቸውም።
በትር
ሰዎች ተራራ ሲወጡ ወይም ጎርበጥባጣ መንገድ ላይ ሲሄዱ ሚዛናቸውን ለመጠበቅ እንዲሁም አጥቂዎችን ለመከላከል የሚጠቀሙበት ረዘም ያለ ዘንግ ነው።
ሻንጣ
መንገደኛ ለጉዞው የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለመያዣነት የሚጠቀምበት ቦርሳ
እንጀራ
እዚህ ጋ፣ ይህ ጥቅም ላይ የዋለው በጥቅሉ “ምግብ”ን ለማመልከት ነው።
ወደ የትኛውም ወደምትገቡበት ቤት
“ወደምትገቡበት ወደ ማናቸውም ቤት”
በዚያ ቆዩ
“በዚያ ሰንብቱ” ወይም “በዚያ ቤት ውስጥ ለጊዜው በእንግድነት ኑሩ”
ከዚያ እስክትሄዱ ድረስ
“ያንን ከተማ ለቃችሁ እስክትሄዱ ድረስ” ወይም “ያንን ስፍራ እስክትለቁ ድረስ”
Luke 9:5
ከማይቀበሏችሁ ከየትኛውም ስፍራ በምትለቁበት ጊዜ
“ሰዎች በማይቀበሏችሁ በየትኛውም ከተማ ማድረግ የሚኖርባችሁ ይህንን ነው፡ በምትለቁበት ጊዜ”
በእነርሱ ላይ ምስክር እንዲሆንባቸው የእግሮቻችሁን አቧራ አራግፉ
“የእግሮቻችሁን አቧራ አራግፉ” በዚያ ባህል ውስጥ ተቀባይነት የማጣት ብርቱ መግለጫ ነው። የዚያ ከተማ አቧራ እንኳን በእነርሱ ላይ እንዲቆይ እንደማይፈልጉ ማሳያ ነው። (See: Symbolic Action)
ወጥተው ሄዱ
“ኢየሱስ የነበረበትን ስፍራ ትተው ሄዱ”
በየስፍራው እየፈወሳችሁ
“በሚሄዱበት ሁሉ እየፈወሱ”
Luke 9:7
አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ቁጥሮች ስለ ሔሮድስ መረጃ ለመስጠት ጣልቃ ይገባሉ።
በዚህ ጊዜ ሔሮድስ
ይህ ሐረግ በዋናው የታሪክ መስመር ላይ ቆም እንዲባል ምልክት ይሰጣል። እዚህ ጋ ሉቃስ ስለ ሔሮድስ ዳራዊ መረጃ ይናገራል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
የአራተኛው ክፍል ገዢ
ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን አንድ አራተኛ ይገዛ የነበረውን ሔሮድስ አንቲጳስን ነው።
ግራ ተጋባ
ተደናገረ፣ መረዳት አቃተው
በአንዳንዶች ተነግሮ ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “አንዳንድ ሰዎች ተናግረዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሌሎች ደግሞ ከጥንት ነቢያቶች አንዱ ተነሥቷል
“ተናግረዋል” የሚለውን ቃል ቀደም ብሎ ካለው ሐረግ መገንዘብ ይቻላል። ኢ.ት፡ “ሌሎች ደግሞ ከጥንት ነቢያቶች አንዱ ተነሥቷል አሉ”
የዮሐንስን ራስ ቆረጥሁት። ይህ ማነው?
ዮሐንስ ከሙታን ሊነሣ አይችልም ብሎ ገምቷል። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ራሱን ስለቆረጥኩት ዮሐንስ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ፣ ይህ ሰው ማነው?”
የዮሐንስን ራስ ቆረጥሁት
x
Luke 9:10
አያያዥ መግለጫ፡
ደቀ መዛሙርት ወደ ኢየሱስ ቢመለሱና የጋራ ጊዜ ለማሳለፍ ወደ ቤተሳይዳ ቢሄዱም እንኳን ሕዝቡ ለመፈወስና ትምህርቱን ለመስማት ኢየሱስን ይከተላል። ወደ ቤታቸው በመመለስ ላይ እያሉ ኢየሱስ እንጀራና ዓሣ ሊያቀርብላቸው ተአምራት ያደርጋል።
ሐዋርያት ተመለሱ
“ሐዋርያት ኢየሱስ ወደነበረበት ተመልሰው መጡ”
ያደረጉትን ሁሉ
ይህ የሚያመለክተው ወደ ሌሎች ከተሞች በሄዱ ጊዜ የሰጡትን ትምህርትና ፈውስ ነው።
ቤተሳይዳ
ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ የሚለውን ተመልከት)
Luke 9:12
ቀኑ ሊመሽ ሲል
“ቀኑ ሊያልቅ ሲል” ወይም “በቀኑ ማለቂያ አቅራቢያ”
አምስት እንጀራ
እንጀራ፣ በተቦካ ዱቄት ቅርጽ ወጥቶለት የሚጋገር ነው።
ሁለት ዓሣ - ለዚህ ሁሉ ሕዝብ ሄደን ምግብ ካልገዛን በስተቀር
በአንተ ቋንቋ “በስተቀር”ን ለመረዳት አስቸጋሪ የሚሆን ከሆነ አዲስ ዐረፍተ ነገር ማድረግ ትችላለህ። “ሁለት ዓሣ። ይህን ሁሉ ሕዝብ ለመመገብ ሄደን ምግብ መግዛት ይኖርብናል”
አምስት ሺ ያህል ወንዶች
“5000 ያህል ወንዶች” ይህ ቁጥር በዚያ ሊገኙ የሚችሉትን ሴቶችና ሕፃናት አያካትትም። (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
አስቀምጧቸው
“እንዲቀመጡ ንገሯቸው”
ለእያንዳንዱ ሃምሳ
“ለእያንዳንዱ 50” (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
Luke 9:15
እነርሱም ይህንኑ አደረጉ
“ይህንኑ” የሚያመለክተው በሉቃስ 9፡4 ኢየሱስ እንዲያደርጉት የነገራቸውን ነው። ሕዝቡ ሃምሳ ሃምሳ ሆነው በቡድን እንዲቀመጡ ነገሯቸው።
አምስቱን እንጀራ ይዞ
“ኢየሱስ አምስቱን እንጀራ ይዞ”
ወደ ሰማይ
ይህ የሚያመለክተው ወደ ላይ፣ ወደ ጠፈር መመልከቱን ነው። አይሁድ ሰማይ ከጠፈር በላይ እንደሆነ ያምኑ ነበር።
Luke 9:18
አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ብቻ በአጠገቡ ሆነው እየጸለየ ነው፣ ኢየሱስ ማን እንደሆነ መነጋገር ይጀምራሉ። ኢየሱስ በቅርቡ እንደሚሞትና እንደሚነሣ ይነግራቸዋል፣ ሊያደርጉት በጣም ከባድ ቢሆንም እንኳን እንዲከተሉት አጥብቆ ያሳስባቸዋል።
ከዚህ በኋላ
ይህ ሐረግ እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው የአዲስ ሁነት ጅማሬን ለማመልከት ነው። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
በግሉ ሲጸልይ
“ብቻውን ሲጸልይ”። ደቀ መዛሙርቱ ከኢየሱስ ጋር ነበሩ፣ ነገር ግን እርሱ በግሉና ለብቻው ይጸልይ ነበር።
አጥማቂው ዮሐንስ
እዚህ ጋ የጥያቄውን አካል እንደገና መናገር ሊጠቅም ይችላል። ኢ.ት፡ “አንዳንዶች አጥማቂው ዮሐንስ ነህ ይላሉ”
ጥንት ከነበሩት ነቢያት አንዱ ተነሥቷል

ይህ ምላሽ ከኢየሱስ ጥያቄ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ማብራራት ሊጠቅም ይችላል። ኢ.ት፡ “ጥንት ከነበሩት ነቢያት አንዱ ሆነህ ተነሥተሃል”
ተነሥቷል
“ወደ ሕይወት ተመልሷል”
Luke 9:20
ከዚያም እርሱ እንዲህ አላቸው
“ከዚያም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው”
ለአንድም ሰው እንዳትናገሩ አላቸው
“ለማንም እንዳይናገሩ” ወይም “ለማንም መናገር እንደሌለባቸው”። ይህ እንደ ቀጥተኛ ትዕምርተ ጥቅስ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ለማንም አትንገሩ” አላቸው። (ግልጽ የሆነና ያልሆነ ትዕምርተ ጥቅስ ተመልከት)
የሰው ልጅ ብዙ መከራ መቀበል አለበት
“ሰዎች የሰውን ልጅ ታላቅ መከራ እንዲቀበል ያደርጉታል”
የሰው ልጅ … እርሱ ይነሣል
ኢየሱስ ወደ ራሱ እያመለከተ ነው። ኢ.ት፡ “የሰው ልጅ የሆንኩ እኔ … እኔ እነሣለሁ” (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ወይም ሦስተኛ መደብ የሚለውን ተመልከት)
በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችና በጸሐፊዎች ይጣላል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሽማግሌዎቹ፣ የካህናት አለቆችና ጸሐፊዎች ይጥሉታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ይገደላል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ይገድሉታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በሦስተኛው ቀን
“ከሞተ ከሦስት ቀን በኋላ” ወይም “በሞተ በሦስተኛው ቀን”
ይነሣል
“እንደገና በሕይወት እንዲኖር ይደረጋል”። ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር እንደገና በሕይወት እንዲኖር ያደርገዋል” ወይም “እንደገና በሕይወት ይኖራል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Luke 9:26
ቃሎቼ
x
Luke 9:28
አያያዥ መግለጫ፡
አንዳንዶቻቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት ከማየታቸው በፊት እንደማይሞቱ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከነገራቸው ከስምንት ቀን በኋላ ኢየሱስ ከጴጥሮስ፣ ያዕቆብና የሐንስ ጋር ለመጸለይ ወደ ተራራ ይወጣል፤ ኢየሱስ ወደ አንጸባራቂ መልክ በሚለወጥበት ጊዜ ሁሉም አንቀላፍተዋል።
እነዚህ ቃላት
ይህ የሚያመለክተው በሚቀጥሉት ቁጥሮች ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቶቹ የሚነግራቸውን ነው።
Luke 9:30
እነሆ
እዚህ ጋ፣ “እነሆ” የሚለው ቃል ቀጥሎ ለሚነገረው አስገራሚ መረጃ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል። ኢ.ት፡ “በድንገት”
በደማቅ ክብር ተገልጠው
ይህ ሐረግ ሙሴና ኤልያስ ምን ይመስሉ እንደነበሩ መረጃ ይሰጣል። አንዳንድ ቋንቋዎች እንደ ተናጠል አንቀጽ ሊተረጉሙት ይችላሉ። ኢ.ት፡ “በደማቅ ክብር ተገለጡ” ወይም “እጅግ ያንጸባርቁ ነበር”
ስለ እርሱ መሄድ
“ስለ እርሱ መለየት” ወይም “ኢየሱስ ይህንን ዓለም እንዴት እንደሚተው”። ይህ ስለ ሞቱ በትህትና የተነገረበት መንገድ ነበር። ኢ.ት፡ “ስለ ሞቱ”
Luke 9:32
በዚህ ጊዜ
እዚህ ጋ፣ ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በዋናው የታሪክ መስመር ላይ የተደረገውን ቆምታ ለማመልከት ነው። እዚህ ጋ ሉቃስ ስለ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና የሐንስ መረጃ ይሰጣል። (ዳራዊ መረጃ የሚለውን ተመልከት)
በእንቅልፍ ከብዶ
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም “በጣም አንቀላፍተው” የሚል ነው።
ክብሩን አዩ
ይህ የሚያመለክተው የከበባቸውን አንጸባራቂ ብርሃን ነው። ኢ.ት፡ “አንጸባራቂ ብርሃን ከኢየሱስ ሲመጣ አዩ” ወይም “በጣም ብሩኅ የሆነ ብርሃን ከኢየሱስ ወጥቶ ሲመጣ አዩ”
ከእርሱ ጋር ቆመው የነበሩት ሁለቱ ሰዎች
ይህ ሙሴንና ኤልያስን ያመለክታል።
በመሄድ ላይ እያሉ
“ሙሴና ኤልያስ በመሄድ ላይ እያሉ”
መጠለያዎች
የሚቀመጡበት ወይም የሚተኙበት ቀለል ያለ፣ ጊዜያዊ ስፍራ
Luke 9:34
እርሱ ይህንን እየተናገረ እያለ
“እነዚህን ነገሮች ጴጥሮስ በመናገር ላይ እያለ”
ፈርተው ነበር
እነዚህ ጎልማሳ ደቀ መዛሙርት የፈሩት ደመናውን አልነበረም። ይህ ሐረግ የሚጠቁመው ከደመናው ጋር አንድ ያልተለመደ ዓይነት ፍርሃት እንደመጣባቸው ነው። ኢ.ት፡ “ደንግጠው ነበር”
ወደ ደመናው ውስጥ ገቡ
ደመናው ያደረገው ነገር ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ደመናው ከበባቸው”
ከደመናው ውስጥ ድምፅ መጣ
ድምፁ የእግዚአብሔር ብቻ እንደሚሆን ግልጽ ነው። ኢ.ት፡ “ከደመናው ውስጥ እግዚአብሔር ተናገራቸው”
ልጅ
ይህ ለእግዚአብሔር ልጅ፣ ለኢየሱስ አስፈላጊ የሆነ ማዕረግ ነው። (አባትና ልጅን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)
የተመረጠው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እኔ የመረጥኩት” ወይም “እኔ መርጨዋለሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ያዩትን … ዝም አሉ
ይህ ከሁነቱ የተነሣ በራሱ በታሪኩ ውስጥ ከታሪኩ በኋላ ስለሆነው ነገር የሚናገር መረጃ ነው (የታሪኩ መጨረሻ የሚለውን ተመልከት)።
ዝም አሉ … ለማንም አልተናገሩም
የመጀመሪያው ሐረግ ወዲያው የሰጡትን ምላሻቸውን ሲያመለክት ሁለተኛው በቀጣዮቹ ቀናት ያደረጉትን ያመለክታል።
Luke 9:37
አያያዥ መግለጫ፡
ከኢየሱስ አንጸባራቂ መገለጥ በኋላ በቀጣዩ ቀን ደቀ መዛሙርት ሊፈውሱት ያልቻሉትን በአጋንንት ተይዞ የነበረውን ልጅ ይፈውሰዋል።
እነሆ፣ ከሕዝቡ መካከል አንድ ሰው
“እነሆ” የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ ለተነገረው አዲስ ሰው ያነቃናል። የአንተ ቋንቋ ይህንን መግለጽ የሚያስችል መንገድ ይኖረው ይሆናል። እንግሊዝኛው “በሕዝቡ መካከል አንድ ሰው ነበረ” የሚለውን ይጠቀማል። (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
እየኸው፣ መንፈስ
“እየኸው” የሚለው ቃል በሰውዬው ታሪክ ውስጥ ክፉዉን መንፈስ ያስተዋውቀናል። የአንተ ቋንቋ ይህንን መግለጽ የሚያስችል መንገድ ይኖረው ይሆናል። ኢ.ት፡ “ክፉ መንፈስ አለ” (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
አረፋ ይደፍቃል
x
Luke 9:41
ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ
“ኢየሱስ እንዲህ በማለት መለሰለት”
እናንተ እምነት የለሾችና ብልሹ ትውልድ
ኢየሱስ ይህንን የተናገረው ለደቀ መዛሙርቱ ሳይሆን ተሰብስቦ ለነበረው ሕዝብ ነው።
ብልሹ ትውልድ
“ምግባረ ብልሹ ትውልድ”
ከእናንተ ጋር የምሆነውና የምታገሳችሁ እስከ መቼ ነው?
እዚህ ጋ በእንግሊዝኛ “ዩ” የተባለው ብዙ ቁጥር ነው። ሰዎች ባለማመናቸው ኢየሱስ ሐዘኑን ለመግለጽ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቃል። እንደ መግለጫ ሊጻፉ ይችላሉ።

ኢ.ት፡ “ለረጅም ጊዜ ከእናንተ ጋር ነበርኩ፣ እናንተ ግን አታምኑም። እስከ መቼ ልታገሳችሁ ያስፈልገኝ እንደሆነ እደነቃለሁ” (Forms of You እና ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ልጅህን ወደዚህ አምጣው
እዚህ ጋ የእንግሊዝኛው “የአንተን” የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው። ኢየሱስ እየተናገረ ያለው በቀጥታ አስታውቆት ለነበረው ለአባትየው ነው።
Luke 9:43
ሁሉም በእግዚአብሔር ታላቅነት ተገረሙ
ኢየሱስ ተአምራትን አደረገ፣ ሆኖም ከፈውሱ ጀርባ የነበረው ኃይል እግዚአብሔር እንደሆነ ሕዝቡ ተገንዝቧል።
ሲያደርግ የነበረው ነገር ሁሉ
“ኢየሱስ ሲያደርግ የነበረው ነገር ሁሉ”
እነዚህ ቃላት በጆሮአችሁ ጠልቀው ይግቡ
ይህ የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ትኩረት መስጠት አለባቸው ማለት ነው። ኢ.ት፡ “በጥንቃቄ ስሙ፣ አስታውሱም” ወይም “ይህንን አትርሱ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
የሰው ልጅ በሰዎች እጅ ተክዶ ይሰጣል
ይህ ከአድራጊ አንቀጽ ጋር ሊነገር ይችላል። እዚህ ጋ “እጅ” የሚያመለክተው ኃይልን ወይም መቆጣጠርን ነው። ኢ.ት፡ “የሰውን ልጅ ይክዱታል፣ በሰዎች ቁጥጥር ስር እንዲሆንም ያደርጉታል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የሰው ልጅ በሰዎች እጅ ተክዶ ይሰጣል
ኢየሱስ በሦስተኛ መደብ የሚናገረው ስለ ራሱ ነው። “እጅ” የሚለው ቃል እጅ ያላቸውን ሰዎች ወይም በፈሊጣዊ አነጋገር እነዚያን እጆች የሚጠቀመውን ኃይል ገላጭ ነው። እነዚህ ሰዎች ማን እንደሆኑ ግልጽ ማድረግ ያስፈልግህ ይሆናል። ኢ.ት፡ “የሰው ልጅ የሆንኩ እኔ በሰዎች እጅ እካዳለሁ” ወይም “የሰው ልጅ ተክዶ ለጠላቶቹ ኃይል ይሰጣል” ወይም “የሰው ልጅ የሆንኩ እኔ ተክጄ ለጠላቶቼ ታልፌ እሰጣለሁ”
ከእነርሱ ተሰውሮ ነበር
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ትርጉሙን ከእነርሱ ሰወረው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Luke 9:46
አጠቃላይ መረጃ፡
ደቀ መዛሙርት ከመካከላቸው ማን እጅግ ታላቅ እንደሚሆን መከራከር ይጀምራሉ።
በመካከላቸው
“በደቀ መዛሙርት መካከል”
በልባቸው የሚያስቡትን አውቆ
እዚህ ጋ “ልባቸው” አዕምሮአቸውን የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በአዕምሮአቸው የሚያስቡትን አውቆ” ወይም “ሲያስቡት የነበረውን አውቆ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በስሜ
ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስን ወክሎ አንድ ነገር የሚያደርገውን ሰው ነው። ኢ.ት፡ “በእኔ ምክንያት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በስሜ፣ የሚቀበለኝ
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገርም እንደ ንጽጽር ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “በስሜ፣ እኔን የሚቀበለኝ ያህል ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የላከኝ እርሱ
“የላከኝ እግዚአብሔር”
ታላቅ የሆነ እርሱ
“እግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ አድርጎ የሚቆጥረው እርሱ”
Luke 9:49
ዮሐንስ መለሰ
“ዮሐንስ እንዲህ ሲል መለሰ” ወይም “ዮሐንስ ለኢየሱስ መለሰለት”። ኢየሱስ የሁሉ ታላቅ ስለ መሆን ለተናገረው ለዮሐንስ ምላሽ እየሰጠ ነበር። እርሱ የሰጠው ለጥያቄ መልስ አይደለም።
አይተናል
ኢየሱስ ሳይሆን ዮሐንስ ስለ ራሱ ይናገራል፣ ስለዚህ እዚህ ጋ “እኛ” አግላይ ነው። (አግላይና አካታች “እኛ” የሚለውን ተመልከት)
በስምህ
ይህ ማለት ሰውዬው በኢየሱስ ኃይልና ሥልጣን ሲናገር ነበር። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
አታስቁሙት
ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “እንዲቀጥል ፍቀዱለት”
የማይቃወማችሁ ሁሉ የእናንተ ወገን ነው
አንዳንድ የዘመናችን ቋንቋዎች ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው አባባሎች አሏቸው። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው እናንተን ከመሥራት ካላገዳችሁ እየረዳችሁ እንዳለ ያህል ነው” ወይም “አንድ ሰው እናንተን በመቃወም ካልሠራ ከእናንተ ጋር እየሠራ ነው”
Luke 9:51
አጠቃላይ መረጃ፡
በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ መወሰኑ ግልጽ ሆነ።
የሚያርግበት ቀን በቀረበ ጊዜ
“የሚያርግበት ሰዓት በመጣ ጊዜ” ወይም “የሚያርግበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ”
ፊቱን አቀና
የዚህ የአነጋገር ዘይቤ ትርጉም “ቁርጥ ውሳኔ አደረገ” የሚል ነው። ኢ.ት፡ “አዕምሮውን አሠራው” ወይም “ወሰነ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ሁሉንም ነገር እንዲያዘጋጁለት
ይህ ማለት እርሱ ወደዚያ እንዲደርስ የመናገሪያ ስፍራን፣ ማደሪያ ቦታንና ምግብን ጨምሮ ዝግጅት ማድረግን ያካትታል።
አልተቀበሉትም
“በዚያ እንዲቆይ አልፈለጉም”
ፊቱን በኢየሩሳሌም አቅጣጫ አቅንቶ ስለነበረ
ሳምራውያንና አይሁድ እርስ በእርሳቸው ይጠላሉ ነበር። በመሆኑም ኢየሱስ ወደ አይሁድ ዋና ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም በሚያደርገው ጉዞ ሳምራውያን አልረዱትም።
Luke 9:54
ይህንን አዩ
“ሳምራውያን ኢየሱስን እንዳልተቀበሉት አዩ”
እሳት ከሰማይ ወርዶ እንዲያጠፋቸው እዘዝ
እንደ ኤልያስ ያሉ ነቢያት እግዚአብሔርን በሚቃወሙ ሰዎች ላይ የፈረዱት እንደዚህ እንደነበር ስለሚያውቁ ያዕቆብና ዮሐንስ ይህንን የፍርድ አማራጭ አቀረቡ።
ዘወር አለና ገሰጻቸው
“ኢየሱስ ዘወር አለና ያዕቆብንና ዮሐንስን ገሰጻቸው”። ደቀ መዛሙርት እንደ ጠበቁት ኢየሱስ በሳምራውያን ላይ አልፈረደባቸውም።
Luke 9:59
አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ከሰዎች ጋር መንገድ እየሄደ መናገሩን ቀጥሏል።
ተከተለኝ
ኢየሱስ ይህንን በማለት ሰውዬው የእርሱ ደቀ መዝሙር እንዲሆንና ከእርሱ ጋር እንዲሄድ እየጠየቀው ነው።
መጀመሪያ ሄጄ አባቴን እንድቀብረው ፍቀድልኝ
የሰውዬው አባት ስለ ሞተ ወዲያው ሊቀብር ወይስ አባቱ እስኪሞት ለረጅም ጊዜ ቆይቶ ከዚያ በኋላ ሊቀብረው እንዲችል ፈልጎ ይሆን ግልጽ አይደለም። ዋናው ነጥብ ሰውየው ኢየሱስን ከመከተሉ በፊት አስቀድሞ አንድ ነገር ማድረግ ይፈልጋል።
በመጀመሪያ እንድሄድ ፍቀድልኝ
“ያንን ከማድረጌ በፊት እንድሄድ ፍቀድልኝ”
ሙታን የራሳቸውን ሙታን እንዲቀብሩ ተዋቸው
ኢየሱስ በቀጥታ የሞቱ ሰዎች ሌሎች የሞቱ ሰዎችን ይቀብራሉ ማለቱ አይደለም። ሊሆኑ የሚችሉ “የሙታን” ትርጉሞች፣ 1) በቅርቡ የሚሞቱትን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው፣ ወይም 2) ኢየሱስን የማይከተሉትንና በመንፈስ የሞቱትን የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሙታን
ይህ በጥቅሉ የሞቱትን ሰዎች ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የሞቱ ሰዎች” (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
Luke 9:61
እከተልሃለሁ
“ደቀ መዝሙር እሆናለሁ” ወይም “አንተን ለመከተል ዝግጁ ነኝ”
በመጀመሪያ በቤቴ ያሉትን እንድሰናበታቸው ፍቀድልኝ
“ያንን ከማድረጌ በፊት በቤቴ ላሉት ሰዎቼ ልሄድ መሆኔን እንድነግራቸው ፍቀድልኝ”

ማንም ... ለእግዚአብሔር መንግሥት ብቁ
ኢየሱስ የእርሱ ደቀ መዝሙር ስለ መሆን ለሰውዬው ለማስተማር በምሳሌ ይመልስለታል። ኢየሱስን ከመከተል ይልቅ ትኩረቱን ከእርሱ በፊት በነበሩ ሰዎች ላይ የሚያደርግ ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት ተስማሚ አይደለም ማለቱ ነው።
ማንም እጁን በማረሻ ላይ የሚያደርግ
እዚህ ጋ፣ "እጁን በ - የሚያደርግ" የአነጋገር ዘይቤ ሲሆን ሰውዬው አንድ ነገር ለማድረግ ይጀምራል ማለት ነው። ኢ.ት: "ማንም እርሻውን ለማረስ ጀምሮ" (የአነጋገር ዘይቤ እና የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
ወደ ኋላው የሚመለከት
ማንም እያረሰ ወደ ኋላው የሚመለከት ማረሻውን መሄድ በሚገባው አቅጣጫ መምራት አይችልም። ያ ሰው በአግባቡ ለማረስ ወደ ፊት መመልከቱ ላይ ማተኮር አለበት።
ለእግዚአብሔር መንግሥት ብቁ
"ለእግዚአብሔር መንግሥት ጠቃሚ" ወይም "ለእግዚአብሔር መንግሥት ተስማሚ"

---

Chapter 10

Luke 10:1

አጠቃላይ መረጃ:
ኢየሱስ ተጨማሪ 70 ሰዎችን በፊቱ አስቀድሞ ይልካቸዋል። እነዚያ 70ዎቹ በደስታ ይመለሳሉ፣ ኢየሱስም ለሰማይ አባቱ የምስጋናን ምላሽ ያቀርባል።
በዚህ ጊዜ
እዚህ ጋ ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሁነትን ለማመልከት ነው። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
ሰባ
"70"። አንዳንድ ትርጉሞች "ሰባ ሁለት" ወይም "72" ይላሉ። ይህንን የሚናገር የግርጌ ማስታወሻ መጨመር ያስፈልግህ ይሆናል። (ቁጥሮች የሚለውን ተመልከት)
ሁለት ሁለት አድርጎ ላካቸው
"ሁለት ሰዎችን የያዘ ቡድን አድርጎ ላካቸው" ወይም "በእያንዳንዱ ቡድን ሁለት ሰዎችን አድርጎ ላካቸው"
እንዲህ አላቸው
በእውነቱ ይህ የተነገረው ሰዎቹ ከመሄዳቸው በፊት ነው። ኢ.ት: "እንዲህ ብሏቸው ነበር" ወይም "ከመሄዳቸው በፊት ነገራቸው" (የሁነቶች ቅደም ተከተል የሚለውን ተመልከት)
መከሩ ብዙ ነው፣ ሠራተኞቹ ግን ጥቂቶች ናቸው
"ሰብሉ ብዙ ነው፣ የሚያስገቡት ሠራተኞች ግን በቂዎች አይደሉም"። ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት የተዘጋጁ ሰዎች ብዙዎች ናቸው፣ ሕዝቡን ለማስተማርና ለመርዳት የሚሄዱ ደቀ መዛሙርት ግን በቂዎች አይደሉም" ማለቱ ነበር። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Luke 10:3

መንገዳችሁን ሂዱ
"ወደ ከተሞቹ ሂዱ" ወይም "ወደ ሕዝቡ ሂዱ"
እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ
ተኩላዎች በጎችን ያጠቃሉ፣ ይገድላሉም። በመሆኑም የዚህ ዘይቤአዊ አነጋገር ትርጉም ኢየሱስ በሚልካቸው ደቀ መዛሙርት ላይ ጉዳት ለማድረስ የሚሞክሩ ሰዎች ይኖራሉ የሚል ነው። የሌላ የዱር አውሬ ስም ሊተካ ይችላል። ኢ.ት: "በምልካችሁ ጊዜ ተኩላዎች በጎችን እንደሚያጠቁ ሰዎች ሊጎዱአችሁ ይፈልጋሉ"
የገንዘብ መያዣ ወይም የመንገደኛ ሻንጣ ወይም ጫማ አትሸከሙ
"ቦርሳ፣ የመንገደኛ ሻንጣ፣ ወይም ጫማ ከእናንተ ጋር አትውሰዱ"
በመንገድ ላይ ለማንም ሰላምታ አትስጡ
"በመንገድ ላይ ማንንም ሰላም አትበሉ"። ኢየሱስ በፍጥነት ወደ መንደሮች እንዲሄዱና ይህንን ሥራ እንዲሠሩ አጽንዖት እየሰጠ ነበር። እርሱ ባለጌ እንዲሆኑ እየነገራቸው አልነበረም።

Luke 10:5

በዚህ ቤት ላይ ሰላም ይሁን
ይህ ሰላምታና ባርኮት ነበር። እዚህ ጋ "ቤት" የሚያመለክተው በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን ነው። ኢ.ት: "በዚህ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሰላምን ይቀበሉ" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የሰላም ሰው
"ሰላማዊ ሰው"። ይህ ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ሰላም እንዲኖረው የሚፈልግ ሰው ነው።
ሰላማችሁ በእርሱ ላይ ያርፍበታል
እዚህ ጋ፣ "ሰላም" የሚቆይበትን እንደሚመርጥ ሕያው ነገር ተደርጎ ተገልጿል። ኢ.ት: "የባረካችሁበት ሰላም ይኖረዋል" (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
ካልሆነ
ሙሉዉን ሐረግ እንደገና መናገር ሊጠቅም ይችላል። ኢ.ት: "በዚያ የሰላም ሰው ከሌለ" ወይም "የቤቱ ባለቤት ሰላማዊ ሰው ካልሆነ"
ወደ እናንተ ይመለሳል
እዚህ ጋ፣ "ሰላም" ትቶ መሄድ እንደሚመርጥ ሕያው ነገር ተደርጎ ተገልጿል። ኢ.ት: "ያ ሰላም ይኖራችኋል" ወይም "የባረካችሁበትን ሰላም አይቀበልም" (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
በዚያው ቤት ቆዩ
ኢየሱስ በዚያ በሚቆዩበት ጊዜ ሁሉ አዳራቸውን በዚያው ቤት እንዲያደርጉ እንጂ ቀኑን ሙሉ እቤት ውስጥ ቆዩ ማለቱ አልነበረም። ኢ.ት: "በዚያው ቤት ማደራችሁን ቀጥሉ"
ለሠራተኛው ደሞዙ ይገባዋልና
ይህ ኢየሱስ በሚልካቸው ሰዎች ላይ ሲተገብረው የነበረ ጥቅል መርህ ነው። ሕዝቡን እስካስተማሩና እስከ ፈወሱ ድረስ ሕዝቡ ማደሪያና ምግብ ሊያቀርቡላቸው ይገባል።
ከቤት ወደ ቤት አትዘዋወሩ
ከቤት ወደ ቤት መዘዋወር ማለት ወደ ተለያዩ ቤቶች መሄድ ማለት ነው። እርሱ ይናገር የነበረው በተለያየ ቤት ስለ ማደር መሆኑን ግልጽ ማድረግ ይቻላል። "በየምሽቱ በተለያየ ቤት አትደሩ"

Luke 10:8

ይቀበሏችኋል
"ከተቀበሏችሁ"
በፊታችሁ የቀረበውን ብሉ
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: "የትኛውንም የሚሰጧችሁን ምግብ ብሉ" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የታመመውን
ይህ በጥቅሉ የታመሙትን ሰዎች ያመለክታል። ኢ.ት: "የታመሙትን ሰዎች" (ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)

Luke 10:10

ካልተቀበሏችሁ
"የከተማዪቱ ሰዎች ከተቃወሟችሁ"
በእግሮቻችን ላይ የተጣበቀውን የከተማችሁን አቧራ እንኳን በእናንተ ላይ እናራግፈዋለን
ይህ የከተማዪቱን ሰዎች እንደማይቀበሏቸው የሚያሳይ ምልክታዊ ድርጊት ነው። ኢ.ት: "ልክ እናንተ እንዳልተቀበላችሁን እኛም በጥንቃቄ አንቀበላችሁም። እግሮቻችን ላይ የሚጣበቀውን የከተማችሁን አቧራ እንኳን እንተውላችኋለን" (ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ተመልከት)
እናራግፍላችኋለን
ኢየሱስ እነዚህን ሰዎች ሁለት ሁለት አድርጎ በቡድን እስከ ላካቸው ድረስ ይህንን የሚናገሩት ሁለት ሰዎች መሆን አለባቸው። ስለዚህ ሁለትነትን ገላጭ "እኛ" የሚል ቃል ያለው ቋንቋ ሊጠቀምበት ይችላል። (አግላይ እና አካታች "እኛ" የሚለውን ተመልከት)
ይህንን ግን እወቁ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርቧል
"ይህንን ግን እወቁ" የሚለው ሐረግ ማስጠንቀቂያን ያስተዋውቃል። "እናንተ ባትቀበሉንም የእግዚአብሔር መንግሥት የመቅረቡን ሐቅ አይቀይረውም!"
የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርቧል
የነገር ስም የሆነው "መንግሥት" ከግሥ ጋር "ንግሥና" ወይም "አገዛዝ" ተብሎ መገለጽ ይችላል። ተመሳሳዩን ዐረፍተ ነገር በሉቃስ 10፡8 ላይ እንዴት እንደ ተረጎምከው ተመልከት። ኢ.ት: "በቅርቡ በሁሉም ስፍራ እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ ይገዛል" ወይም "እግዚአብሔር በዙሪያችሁ ሁሉ በመግዛት ላይ ስለመሆኑ ማረጋገጫ አለ" የሚሉት ናቸው (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)።
እላችኋለሁ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ኢየሱስ ይህንን ይናገራቸው የነበሩት ይልካቸው ለነበሩት ለ70ዎቹ ሰዎች ነው። ይህንን ያለው አንድ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ሊነግራቸው እንዳለ ለማሳየት ነበር።
የፍርድ ቀን
ደቀ መዛሙርት ይህ የሚያመለክተው በኃጢአተኞች ስለሚፈረድበት የመጨረሻው ጊዜ መሆኑን ሳይረዱ አይቀሩም።
ከዚያች ከተማ ይልቅ ሰዶምን መታገስ ይቀላል
"እግዚአብሔር በዚያች ከተማ ላይ የሚፈርደውን ያህል በሰዶም ላይ አይፈርድም"። ኢ.ት፡ "እግዚአብሔር በሰዶም ሕዝብ ላይ ከሚፈርድበት በበለጠ በዚያች ከተማ ሕዝብ ላይ ይፈርዳል" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Luke 10:13
ወዮልሽ ኮራዚን! ወዮልሽ ቤተሳይዳ
ኢየሱስ የኮራዚንና የቤተሳይዳ ከተማ ሰዎች በዚያ ሆነው ይሰሙት ይመስል ይናገራቸዋል፣ እነርሱ ግን በዚያ የሉም። (ስሞች እንዴት እንደሚተረጎሙ እና ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በእናንተ የተደረጉት ታላላቅ ሥራዎች በጢሮስና በሲዶና ተደርገው ቢሆን ኖሮ
ኢየሱስ እየገለጸ ያለው ባለፈ ጊዜ ሊሆን ስለሚችል ነገር ግን ስላልሆነ ሁኔታ ነው። ኢ.ት፡ "እኔ ለእናንተ ያደረግሁትን ተአምራት አንድ ሰው ለጢሮስና ለሲዶና ሰዎች አድርጎ ቢሆን ኖሮ"
ከብዙ ጊዜ በፊት ተቀምጠው ንስሐ ይገቡ ነበር
"በዚያ ይኖሩ የነበሩ ክፉዎች ሰዎች በመቀመጥ ስለ ኃጢአታቸው መጸጸታቸውን ያሳዩ ነበር"
ማቅና አመድ ላይ ተቀምጠው
"ማቅ ለብሰው፣ አመድ ላይም ተቀምጠው"
ነገር ግን ከእናንተ ይልቅ በፍርድ ጢሮስንና ሲዶናን መታገስ ይቀላል
ለምን እንደሚፈረድባቸው በግልጽ መናገር ሊጠቅም ይችላል። ኢ.ት፡ "ምንም እንኳን ተአምራትን ሳደርግ ብታዩም ንስሐ ስላልገባችሁና በእኔ ስላላመናችሁ እግዚአብሔር በጢሮስና በሲዶና ሕዝብ ላይ ከሚፈርድባቸው እጅግ በሚበልጥ ሁኔታ ይፈርድባችኋል"
በፍርድ
"እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ላይ በሚፈርድበት በመጨረሻው ቀን"
አንቺ ቅፍርናሆም
በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ይሰሙት ይመስል በቅፍርናሆም ከተማ ለሚኖሩ ሰዎች ይናገራል፣ እነርሱ ግን አይሰሙትም። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ወደ ሰማይ ከፍ እንደምትይ ታስቢያለሽ?
ኢየሱስ ስለ ትዕቢታቸው የቅፍርናሆምን ሰዎች ለመገሰጽ ጥያቄ ይጠይቃቸዋል። ኢ.ት፡ "በእርግጥ ወደ ሰማይ አታርጊም!" ወይም "እግዚአብሔር አያከብርሽም!" (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አልሽ
ይህ አገላለጽ "እጅግ ከፍ አልሽ" ማለት ነው።
ወደ ሲኦል ያወርዱሻል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ "ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ" ወይም "እግዚአብሔር ወደ ሲኦል ይልክሻል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Luke 10:17
ሰባዎቹ ተመልሰው
አንዳንድ ቋንቋዎች የተከፈተው ተለዋዋጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እንደሚያደርገው ሰባዎቹ በእውነቱ አስቀድመው ሄደው እንደነበር መናገር ይኖርባቸዋል። ይህ ግልጽ መደረግ የሚችል የተሰወረ መረጃ ነው።
Luke 10:21
አባት
ይህ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ የሆነ ማዕረግ ነው። (አባት እና ልጅን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)
የሰማይና የምድር ጌታ
"ሰማይ" እና "ምድር" ያለውን ነገር ሁሉ ይወክላል። ኢ.ት፡ "በሰማይና በምድር ባለው ሁሉ ላይ እና ሁሉ ነገር ላይ የበላይ"
እነዚህ ነገሮች
ይህ የሚያመለክተው ስለ ደቀ መዛሙርቱ ሥልጣን ቀደም ሲል ኢየሱስ ያስተማረውን ነው። "እነዚህ ነገሮች" በማለት ብቻ አንባቢው ትርጉሙን እንዲወስን መተው በጣም የተሻለ ሊሆን ይችላል።
ጥበበኛና አስተዋይ
"ጥበበኛ" እና "አስተዋይ" የሚሉት ቃላት ስማዊ ቅጽሎች ሲሆኑ እንዲህ ያለ ስብዕና ያላቸውን ሰዎች የሚያመለክቱ ናቸው። እነዚህ ሰዎች፣ እግዚአብሔር እውነትን ስለ ሰወረባቸው እነርሱ ነን ቢሉም እንኳን በእውነቱ ጥበበኞችና አስተዋዮች አልነበሩም። ኢ.ት፡ "ጥበበኞችና አስተዋዮች እንደሆኑ ከሚያስቡ ሰዎች" (ቅጼ እና ስማዊ ቅጽል የሚለውን ተመልከት)
እነዚያ እንደ ትንንሽ ልጆች ያልተማሩ
ይህ የሚያመለክተው ብዙ ባይማሩም እንኳን ትንንሽ ልጆች የሚያምኗቸውን ሰዎች በፈቃዳቸው በሚሰሟቸው መልኩ የኢየሱስን ትምህርቶች ለመቀበል ፈቃደኞች የሚሆኑትን ሰዎች ነው። ኢ.ት፡ "በጥቂቱ የተማሩ፣ ነገር ግን ትንንሽ ልጆች እንደሚያደርጉት እግዚአብሔርን የሚሰሙ ሰዎች"
ይህ በፊትህ ደስ የሚያሰኝህ ሆኗልና
"ይህንን ማድረግ አስደስቶሃል"
Luke 10:22
ሁሉም ነገር ከአባቴ ተሰጥቶኛል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ "አባቴ ሁሉንም ነገር አሳልፎ ሰጥቶኛል" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
አባት … ልጅ
እነዚህ በእግዚአብሔርና በኢየሱስ መካከል ያለውን ዝምድና የሚገልጹ አስፈላጊ ማዕረጎች ናቸው። (አባት እና ልጅን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)
ልጅ ማን መሆኑን ያውቃል
x
Luke 10:23
ከዚያም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘወር ብሎ ለብቻቸው እንዲህ አላቸው
"ለብቻቸው" የሚለው ቃል እርሱ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ብቻ እንደነበረ ያመላክታል። ኢ.ት፡ "ከዚያ በኋላ፣ ብቻውን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በሆነ ጊዜ፣ ወደ እነርሱ ዘወር ብሎ እንዲህ አላቸው"
እናንተ የምታዩአቸውን ነገሮች የሚያዩ እነርሱ የተባረኩ ናቸው
ይህ ምናልባት ኢየሱስ ያደርጋቸው የነበሩትን መልካም ሥራዎችና ተአምራቶች ያመለክት ይሆናል። ኢ.ት፡ "እኔ ሳደርግ የምታዩትን ለሚያዩ ለእነዚያ እንዴት መልካም ነ
እነርሱ አላዩአቸውም
ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ እነዚያን ነገሮች ገና እንዳላደረጋቸው ነው። ኢ.ት፡ "ሆኖም፣ ገና ስላላደረግኳቸው ሊያዩአቸው አልቻ
እናንተ የምትሰሟቸውን ነገሮች
ይህ ምናልባት የኢየሱስን ትምህርት ያመለክት ይሆናል። ኢ.ት፡ "እኔ ስናገር የሰማችኋቸውን ነገሮች"
እነርሱ አልሰሟቸውም
ይህ ኢየሱስ ገና እንዳላስተማረ ያመለክታል። ኢ.ት፡ "ሆኖም፣ ማስተማር ባለመጀመሬ ሊሰሟቸው አልቻሉም"
Luke 10:25
አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ሊፈትነው ለሞከረው አይሁዳዊ መምህር በምሳሌ ይመልስለታል። (ምሳሌዎች የሚለውን ተመልከት)
እነሆ፣ አንድ መምህር
ይህ በታሪኩ ውስጥ ለአዲስ ሁነትና ለአዲስ ሰው ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ፣ አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
ሊፈትነው
"ኢየሱስን ለመገዳደር"
በሕጉ የተጻፈው ምንድነው? እንዴትስ ታነበዋለህ?
ኢየሱስ መረጃ እየፈለገ አይደለም። እርሱ እነዚህን ጥያቄዎች ያቀረበው የአይሁዳዊ መምህሩን እውቀት ለመፈተን ነው። ኢ.ት፡ "ሙሴ በሕጉ ላይ ምን እንደጻፈና ትርጉሙ ምን ይሆናል ብለህ እንደምታስብ ንገረኝ" (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
በሕጉ የተጻፈው ምንድነው?
ይህ በአድርጊ ድምፅ ሊጠየቅ ይችላል። ኢ.ት፡ "ሙሴ በሕጉ ላይ የጻፈው ምን ነበር?" (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

እንዴት ታነበዋለህ?
“በእርሱ ውስጥ ምን አነበብክ?” ወይም “ምን እንደሚል ተረዳህ?”
ባልንጀራህን እንደ ራስህ … ውደደው
ሰውዬው ሙሴ በሕጉ የጻፈውን እየጠቀሰ ነው።
በሙሉ ልብህ፣ በሙሉ ነፍስህ፣ በሙሉ ኃይልህና በሙሉ አሳብህ
እዚህ ጋ፣ “ልብ” እና “ነፍስ” የአንድን ሰው ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክቱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ናቸው። እነዚህ አራት ሐረጎች በአንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት “ሙሉ በሙሉ” ወይም “በቅንነት” ለማለት ነው።
ባልንጀራህን እንደ ራስህ
ይህ ተነጻጻሪ በበለጠ ግልጽነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት: “ራስህን የምትወደውን ያህል ባልንጀራህን ውደደው” (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)
Luke 10:29
ሆኖም፣ መምህሩ ራሱን ለማጽደቅ በመፈለግ እንዲህ አለ
“ሆኖም መምህሩ ራሱን የሚያጸድቅበትን መንገድ ለማሰብ ፈለገ፣ ስለዚህ እንዲህ አለ” ወይም “ሆኖም፣ መምህሩ ጻድቅ ሆኖ መታየት በመፈለግ እንዲህ አለ”
Luke 10:31
በአጋጣሚ
ይህ የትኛውም ሰው ያቀደው ነገር አልነበረም።
አንድ ካህን
ይህ አገላለጽ በታሪኩ ውስጥ አንድ አዲስ ሰው ያስተዋውቃል፣ ሆኖም ማንነቱን በስም አይገልጸውም። (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
ባየው ጊዜ
“ካህኑ የቆሰለውን ሰው ባየው ጊዜ”። ካህን በጣም ሃይማኖተኛ ሰው ነው፣ በመሆኑም የቆሰለውን ሰው እንደሚረዳው አድማጮች ይገምታሉ። እርሱ እንደተገመተው ስላላደረገ፣ ትኩረታቸውን ወደዚህ ያልተጠበቀ ውጤት ለመሳብ ይህ ሐረግ “ነገር ግን ባየው ጊዜ” ተብሎ ሊነገር ይችላል።
በሌላኛው በኩል ተሻገረ
ሰውዬውን እንዳልረዳው ያመለክታል። ኢ.ት: “የቆሰለውን ሰው አልረዳውም፣ ነገር ግን በመንገዱ በወዲያኛው በኩል ተሻግሮ ሄደ”
ሌዋዊ … በሌላኛው በኩል
ሌዋዊው በቤተ መቅደስ ያገለግል ነበር። ባልንጀራው የሆነውን አይሁዳዊ ሰው መርዳት ይጠበቅበት ነበር። ይህንን አላደረገምና ሁኔታው ቢነገር ሊጠቅም ይችላል። ኢ.ት: “ሌዋዊ በሌላ በኩል … አልረዳውምም”
Luke 10:33
ነገር ግን አንድ ሳምራዊ
ይህ በታሪኩ ውስጥ ስሙን ሳይጠቅስ አንድን አዲስ ሰው ያስተዋውቃል። ከሰማርያ መሆኑን ብቻ እናውቃለን። (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
አንድ ሳምራዊ
አይሁዶች ሳምራውያንን ይንቋቸው ስለነበር የቆሰለውን አይሁዳዊ ሰው አይረዳውም ብለው ገምተዋል።
እርሱ ባየው ጊዜ
“ሳምራዊው የቆሰለውን ሰው ባየው ጊዜ”
ራራለት
“አዘነለት”
ዘይትና ወይን አፍስሶባቸው ቁስሎቹን አሰረለት
በመጀመሪያ ዘይቱንና ወይኑን በቁስሎቹ ላይ ማድረግ ነበረበት። ኢ.ት: “ወይንና ዘይት በቁስሎቹ ላይ ጨምሮ በጨርቅ ጠቀለላቸው” (የሁነቶች ቅደም ተከተል የሚለውን ተመልከት)
ዘይትና ወይን አፍስሶባቸው
ወይን የተጠቀመው ቁስሉን ለማጽዳት ሲሆን ዘይቱ ምናልባት ማመርቀዝን ለመከላከል ሳይሆን አይቀርም። ይህ እንደሚከተለው ሊነገር ይችላል፤ ኢ.ት: “ቁስሉ እንዲፈወስ ዘይትና ወይን በላዩ ላይ ማፍሰስ”
የራሱን እንስሳ
“የራሱ የጭነት እንስሳ”። ይህ ከባድ ጭነት እንዲሸከም የተጠቀመበት እንስሳ ነበር። ምናልባት አህያ ሳይሆን አይቀርም።
ሁለት ዲናር
“የሁለት ቀን ደሞዝ”። “ዲናር” የ”ዲናሪየስ” ብዙ ቁጥር ነው። (በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ገንዘብ የሚለውን ተመልከት)
አስተናጋጁ
“የሆቴሉ ጠባቂ” ወይም “የሆቴሉን ኃላፊነት የወሰደው ሰው”
የትኛውንም የምታወጣውን ተጨማሪ ወጪ ስመለስ እከፍልሃለሁ
ይህ ቅደም ተከተል እንደገና ሊስተካከል ይችላል። ኢ.ት: “በምመለስበት ጊዜ የምታወጣውን የትኛውንም ተጨማሪ ወጪ እኔ እከፍልሃለሁ”
Luke 10:38
አጠቃላይ መረጃ:
ኢየሱስ እህቷ ማርያም እርሱን በጥሞና ወደምታዳምጥበት ወደ ማርታ ቤት ይመጣል።
Luke 10:40
በጣም ባተለች
“በጣም ሥራ በዛባት” ወይም “እጅግ ሥራ በዛባት”
ብቻዬን … አይገድህም?
ማርያም ብዙ የሚሠራ ሥራ ባለበት ጊዜ ጌታ እርሱን እንድትሰማው በመፍቀዱ ማርታ ቅሬታ እያቀረበች ነው። እርሷ ጌታን ታከብረዋለች፣ በመሆኑም ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ በመጠቀም ቅሬታዋን በበለጠ ትህትና ታቀርባለች። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
ማርታ፣ ማርታ
ኢየሱስ አጽንዖት ለመስጠት የማርታን ስም ይደግመዋል። ኢ.ት: “የተወደድሽ ማርታ” ወይም “አንቺ ማርታ”
የሚያስፈልገው አንድ ነገር ብቻ ነው
ኢየሱስ ማርያም የምታደርገውን ማርታ ከምታደርገው ጋር እያነጻጸረ ነው። ይህንን ግልጽ ማድረግ ሊጠቅም ይችላል። ኢ.ት: “በእርግጠኝነት አስፈላጊ የሆነው ብቸኛው ነገር የእኔን ትምህርት መስማት ነው” ወይም “ምግብ ከማዘጋጀት ይልቅ የእኔን ትምህርት መስማት በይበልጥ አስፈላጊ ነው”
ከእርሷ አይወሰድባትም
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ይህንን ዕድል ከእርሷ አልወስድባትም” ወይም 2) “እኔን ስትሰማኝ የምታገኘውን አትጥለውም” የሚሉት ናቸው (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 11
Luke 11:1
አጠቃላይ መረጃ:
ይህ የቀጣዩ ታሪክ ክፍል ጅማሬ ነው። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲጸልዩ ያስተምራቸዋል።
እንዲህ ሆነ
ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል እንደተጀመረ ለማመልከት ነው። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው እዚህ ጋ ልትጠቀምበት እንደምትችል አስብ። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
ኢየሱስ በሚጸልይበት ጊዜ ከ … አንዱ
ደቀ መዛሙርት ጥያቄ ከመጠየቃቸው በፊት ኢየሱስ ጸሎቱን መጨረሱን መናገር የበለጠ አግባብነት ሊኖረው ይችላል። ኢ.ት: “በአንድ ቦታ ኢየሱስ ይጸልይ ነበር። ጸሎቱን በጨረሰ ጊዜ ከ … አንዱ
Luke 11:2
ኢየሱስ እንዲህ አላቸው
“ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው”
አባት
ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ በሚጸልዩበት ጊዜ “አባት” በማለት የእግዚአብሔር አብን ስም እንዲያከብሩ ኢየሱስ አዘዛቸው። (አባት እና ልጅን መተርጎም የሚለውን ተመልከት)
ስምህ ቅዱስ ይሁን
“ሁሉም ስምህን እንዲያከብሩት አድርግ”። “ስም” ብዙ ጊዜ የሚያመለክተው ሙሉውን ሰው ነው። ኢ.ት: “ሰዎች ሁሉ ያክብሩህ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
መንግሥትህ ትምጣ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እግዚአብሔር በሁሉም ላይ የመግዛቱ አሠራር እርሱ ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ተደርጎ ተነግሯል። አ.ት፡ “ናና በሁሉም ላይ ግዛ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

## Luke 11:3

አያያዥ መግለጫ፡

ኢየሱስ እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ለደቀ መዛሙርቱ ማስተማሩን ቀጥሏል።

ስጠን … ይቅር በለን … አትምራን

እነዚህ ትዕዛዛዊ አንቀጾች ናቸው፣ ሆኖም ከትዕዛዝ ይልቅ እንደ ልመና ተደርገው መተርጎም አለባቸው። ይህንን ግልጽ ለማድረግ “እባክህን” የመሳሰለ ቃል መጨመር ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “… እባክህን ስጠን፣ እባክህን … ይቅር በለን … እባክህን አትምራን”

የዕለት እንጀራችንን

እንጀራ ውድ ያልሆነ፣ ሰዎች በየዕለቱ የሚበሉት ምግብ ነበር። እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው በጥቅሉ ምግብን ለማመልከት ነው። አ.ት፡ “በየዕለቱ የምንፈልገውን ምግብ”

ኃጢአታችንን ይቅር በለን

“በአንተ ላይ ኃጢአት ስለማድረጋችን ይቅር በለን” ወይም “የእኛን ኃጢአት ይቅር በል”

እኛ ይቅር እንደምንል

“እኛም ደግሞ ይቅር እንላለንና”

እኛን የበደለንን

“በእኛ ላይ ኃጢአት ያደረገውን” ወይም “የማይገባውን ነገር ያደረገብንን”

ወደ ፈተና አትምራን

ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ከፈተና አርቀን”

## Luke 11:5

አያያዥ መግለጫ፡

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ጸሎት ማስተማሩን ቀጥሏል።

በፊቱ የሚያቀርብለት ከእናንተ … ያለው?

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ለማስተማር ጥያቄ ይጠይቃል። አ.ት፡ “አስቡ፣ ከእናንተ አንዱ … በፊቱ ሊያቀርብለት” ወይም “እንዳላችሁ አስቡ … በፊቱ ሊያቀርብለት” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ሦስት እንጀራ አበድረኝ

“ሦስት እንጀራ እንድበደር ፍቀድልኝ” ወይም “ሦስት እንጀራ ስጠኝና በኋላ እከፍልሃለሁ”። እንግዳ ተቀባዩ ለእንግዳው የሚያቀርብለት ምንም የተዘጋጀ ምግብ የለውም።

ሦስት እንጀራ

እንጀራ አብዛኛውን ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው በጥቅሉ ምግብን እንዲወክል ሆኖ ነው። አ.ት፡ “የሚበላ የበሰለ በቂ ምግብ” ወይም “አንድ ሰው የሚበላው የተዘጋጀ በቂ ምግብ”

አሁን ከመንገድ መጥቷል

ጎብኚው ሩቅ ከሆነ ቤቱ መምጣቱ ታውቋል። አ.ት፡ “ሲጓዝ ውሎ አሁን ወደ ቤቴ መጥቷል”

ምንም በፊቱ የማቀርብለት

“የምሰጠው ምንም የተዘጋጀ ምግብ”

ለመነሣት አልችልም

x

## Luke 11:9

ለምኑ … ፈልጉ … አንኳኩ

ኢየሱስ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ባለማቋረጥ እንዲጸልዩ ለማበረታታት እነዚህን ትዕዛዞች ይሰጣቸዋል። አንዳንድ ቋንቋዎች ከእነዚህ ግሦች ጋር ተጨማሪ መረጃ ደግሞ ይፈልጉ ይሆናል። በዚህ ዐውድ በይበልጥ ተስማሚ የሚሆነውን “እናንተ” የሚለውን ቃል ተጠቀሙ። አ.ት፡ “የሚያስፈልጋችሁን መለመናችሁን ቀጥሉበት … ከእግዚአብሔር የምትፈልጉትን መፈለጋችሁን ቀጥሉ … አግኙት … በሩን ማንኳኳታችሁን ቀጥሉ”

ይሰጣችኋል

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር እርሱን ይሰጣችኋል” ወይም “ትቀበሉታላችሁ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

አንኳኩ

በር ማንኳኳት በቤቱ ውስጥ ያለው ሰው እናንተ በውጪ መቆማችሁን እንዲያውቅ ለጥቂት ጊዜ በሩን መምታት ነው። ደግሞም በባህልህ ሰዎች ወደ ቤት መድረሳቸውን ለማሳየት በሚጠቀሙበት ለምሳሌ “መጠራት” ወይም “መሳል” ወይም “ማጨብጨብ” የመሳሰሉትን መንገዶች በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። እዚህ ጋ፣ ትርጉሙ አንድ ሰው እግዚአብሔር መልስ እስኪሰጠው ድረስ ጸሎቱን መቀጠል አለበት የሚል ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ይከፈትላችኋል

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በሩን ይከፍትላችኋል” ወይም “እግዚአብሔር ወደ ውስጥ ያስገባችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

## Luke 11:11

አያያዥ መግለጫ፡

ኢየሱስ ስለ ጸሎት ለደቀ መዛሙርቱ ማስተማሩን ይጨርሳል።

ከእናንተ የትኛው አባት … ዓሣ?

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር በጥያቄ ይጠቀማል። ይህ እንደ መግለጫ ደግሞ ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “አባቶች ከሆናችሁት ከእናንተ ማንም … ዓሣ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ወይስ … ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋል?

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር በጥያቄ ይጠቀማል። ይህ እንደ መግለጫ ደግሞ ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “እንቁላል ቢለምናችሁ በፍጹም ጊንጥ አትሰጡትም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

ጊንጥ

ጊንጥ ከሸረሪት ጋር ይመሳሰላል፣ ነገር ግን እርሱ መርዛማ መናደፊያ ጭራ አለው። አንተ ባለህበት አካባቢ ጊንጥ የማይታወቅ ከሆነ “መርዛማ ሸረሪት” ወይም “የሚናደፍ ሸረሪት” ብለህ ልትተረጉመው ትችላለህ። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)

ክፉ የሆናችሁ እናንተ . . . ካወቃችሁ

“እናንተ ክፉ የሆናችሁት . . . ካወቃችሁ” ወይም “ኃጢአተኞችም እንኳን ብትሆኑ፣ እናንተ . . . ታውቃላችሁ”

## Luke 11:14

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢየሱስ ከዲዳው ሰው አጋንንትን ካወጣ በኋላ ጥያቄ ይቀርብለታል።

በዚህ ጊዜ

ደራሲው የአዲስ ሁነት ጅማሬን ለማመልከት ይህንን ቃል ይጠቀማል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)

ኢየሱስ አጋንንትን ያስወጣ ነበር

ልዩ መረጃ መጨመር ሊረዳ ይችል ይሆናል። አ.ት፡ “ኢየሱስ ከአንድ ሰው አጋንንትን ያወጣ ነበር” ወይም “ኢየሱስ፣ አጋንንት ሰውየውን እንዲለቀው ያደርግ ነበር”

ዲዳ የሆነ አጋንንት ነበር

አጋንንቱ ሰዎችን ከመናገር የሚከለክልበት ኃይል ነበረው። አ.ት፡ “ሰውየው መናገር እንዳይችል አድርጎት የነበረው አጋንንት”

በዚህ ጊዜ

ድርጊቱ የቱ ጋ እንደሚጀምር ለማመልከት ይህ ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ ውሏል። የአንተ ቋንቋ ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ካለው ያንን እዚህ ጋ ስለመጠቀም ማሰብ ይኖርብሃል። አጋንንቱ ከሰውዬው በወጣ ጊዜ ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ኢየሱስን ነቀፉት፣ ይህም ኢየሱስ ስለ ክፉ መናፍስት ወዳስተማረው ትምህርት የሚመራ ሆነ።

አጋንንቱ በወጣ ጊዜ

ልዩ መረጃ መጨመር ሊረዳ ይችል ይሆናል። አ.ት፡ “አጋንንቱ ከሰውዬው በወጣ ጊዜ” ወይም “አጋንንቱ ሰውዬውን በለቀቀው ጊዜ”

ዲዳ የነበረው ሰው ተናገረ

“መናገር የማይችል የነበረው ሰው በዚህ ጊዜ ተናገረ”

በብኤልዜቡል በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል

“አጋንንትን የሚያወጣው የአጋንንት አለቃ በሆነው በብኤልዜቡል ኃይል ነው”

## Luke 11:16

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢየሱስ ለሕዝቡ ምላሽ መስጠት ይጀምራል።

ሌሎች ፈተኑት

“ሌሎች ሰዎች ኢየሱስን ፈተኑት”። ሥልጣኑ ከእግዚአብሔር መሆኑን እንዲያረጋግጥላቸው ፈለጉበት።

ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

“ከሰማይ ምልክት እንዲሰጣቸው ለመኑት” ወይም “ከሰማይ ምልክት እንዲሰጣቸው በመጠየቅ”። ሥልጣኑ ከእግዚአብሔር መሆኑን እንዲያረጋግጥላቸው የፈለጉት እንዲህ ባለ መንገድ ነበር።
እርስ በእርሱ የሚከፋፈል መንግሥት ሁሉ ይጠፋል
እዚህ ጋ፣ “መንግሥት” የሚያመለክተው በውስጡ የሚኖረውን ሕዝብ ነው። ይህም ደግሞ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “በአንድ መንግሥት ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች እርስ በእርሳቸው ከተዋጉ መንግሥታቸውን ያጠፋሉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እርስ በእርሱ የሚከፋፈል ቤት ይወድቃል
እዚህ ጋ “ቤት” የሚያመለክተው ቤተሰብን ነው። አ.ት፡ “የቤተሰብ አባላት እርስ በእርስ ከተጣሉ ቤተሰባቸውን ይበታትኑታል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ይወድቃል
“ተሰባብሮ ይወድቅና ይጠፋል”። ይህ የሚደረመስ ቤት ስዕል የሚያመለክተው የቤተሰብ አባላት እርስ በእርስ በሚጣሉበት ጊዜ ቤተሰቡ የሚጠፋ መሆኑን ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Luke 11:18
ሰይጣን እርስ በእርሱ ከተከፋፈለ
እዚህ ጋ፣ “ሰይጣን” የሚያመለክተው እርሱን የሚከተሉትን አጋንንትን እንዲሁም ራሱን ሰይጣንን ነው። አ.ት፡ “ሰይጣንና በመንግሥቱ ያሉ አባላቱ እርስ በእርሳቸው ከተዋጉ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰይጣን … ከሆነ መንግሥቱ እንዴት ይጸናል?
ኢየሱስ ሕዝቡን ለማስተማር ጥያቄ ይጠይቃል። ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ሰይጣን . . . ከሆነ መንግሥቱ አይጸናም” ወይም “ሰይጣን . . . መንግሥቱ ይፈራርሳል”። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አጋንንትን የማወጣው በብኤልዜቡል እንደሆነ ትላላችሁና
“አጋንንትን ከሰዎች የማወጣው በብኤልዜቡል ኃይል እንደሆነ ትናገራላችሁና”። የክርክሩ ቀጣይ ክፍል በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “አጋንንትን ከሰዎች የማወጣው በብኤልዜቡል ኃይል እንደሆነ ትናገራላችሁና። ያ ደግሞ ሰይጣን እርስ በእርሱ ተከፋፍሏል ማለት ነው”
ነገር ግን እኔ … ተከታዮቻችሁ በማን ያወጧቸዋል?
“ነገር ግን እኔ . . . ተከታዮቻችሁ አጋንንት ከሰዎች እንዲወጡ በማን ኃይል ያስገድዷቸዋል?” ኢየሱስ ሕዝቡን ለማስተማር ጥያቄዎችን ይጠይቃል። ኢየሱስ የሚጠይቀው ጥያቄ ትርጉም ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ነገር ግን እኔ . . . እንግዲያውስ ተከታዮቻችሁም ደግሞ አጋንንትን የሚያወጡት በብኤልዜቡል ኃይል ነው ብለን መስማማት አለብን። ይሁን እንጂ ይህ እውነት እንደሆነ አታምኑም”።
እነርሱ ፈራጆቻችሁ ይሆናሉ
“እኔ በብኤልዜቡል ኃይል አጋንንትን እንደማወጣ ስለማለታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል አጋንንትን የሚያወጡ ተከታዮቻችሁ ይፈርዱባችኋል”
በእግዚአብሔር ጣት
“የእግዚአብሔር ጣት” የእግዚአብሔርን ኃይል ያመለክታል። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እንግዲያው የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መጥታለች
“ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መምጣቷን ያሳያል”
Luke 11:21
ብርቱ ሰው … ጊዜ የሰውዬው ንብረት
ይህ ኢየሱስ ብርቱ ሰው ሆኖ የሌላውን ብርቱ ሰው ንብረት ይወስድ ይመስል እርሱ ሰይጣንን እና አጋንንቶቹን ስለ ማሸነፉ የሚናገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የጦር መሣሪያውን ከሰውዬው ይወስድበታል
“የሰውዬውን የጦር መሣሪያና መከላከያ ያስወግዳል”
ንብረቱ ይጠበቅለታል
“ማንም የእርሱን ነገር ሊሰርቅበት አይችልም”
የሰውዬውን ሀብት ይበዘብዛል
“ሀብቱን ይሰርቀዋል” ወይም “የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ይወስዳል”
ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፣ ከእኔ ጋር የማይሰበስብም ይበትናል
ይህ የሚያመለክተው የትኛውንም ሰው ወይም የሰዎች ቡድን ነው። “ከእኔ ጋር ያልሆነ ማንም ቢሆን ይቃወመኛል፣ ከእኔ ጋር የማይሰበስብ ማንም ቢሆን ይበትናል” ወይም “ከእኔ ጋር ያልሆኑት እነርሱ ይቃወሙኛል፣ ከእኔ ጋር የማይሰበስቡ እነዚያም ይበትናሉ”
ከእኔ ጋር ያልሆነ
“እኔን የማይደግፈኝ” ወይም “ከእኔ ጋር የማይሠራ”
ይቃወመኛል
“እኔን በመቃወም ይሠራል”
ከእኔ ጋር የማይሰበስብ ይበትናል
ከእኔ ጋር የማይሰበስብ ይበትናል ኢየሱስ የሚያመለክተው እርሱን የሚከተሉ ደቀ መዛሙርትን መሰብሰብን ነው። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰዎች መጥተው እንዲከተሉኝ የማያደርግ ማንም ቢኖር ከእኔ እንዲርቁ ያደርጋቸዋል”
Luke 11:24
ውሃ በሌለበት ሥፍራ
ይህ ክፉ መናፍስት የሚቅበዘበዙበትን “እና ሥፍራ” ያመለክታል።
ምንም አያገኝም
“መንፈስ በዚያ ምንም ዓይነት እረፍት በሚያጣበት ጊዜ”
ትቼው ወደ መጣሁበት ቤቴ
ይህ ለመኖሪያነት የተጠቀመበትን ሰውዬ ያመለክታል። አ.ት፡ “ወደ ኖርኩበት ሰው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ያ ቤት ተጠርጎና ተስተካክሎ ያገኘዋል
ይህ ዘይቤአዊ አነጋገር ተጠርጎ በጸዳውና ነገሮች ተስተካክለው በተቀመጡበት ቤት ስለተመሰለው ሰው ይናገራል። ቤቱ እስካሁን ድረስ ባዶ እንደሆነ ያመላክታል። ይህ ግልጽ ካደረገው መረጃ ጋር በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰውዬው ልክ አንድ ሰው ጠርጎ ያጸዳውና ሁሉንም ነገር በተገቢው ቦታ አድራጅቶ በማስቀመጥ የተወውን ቤት መስሎ ያገኘዋል” ወይም “ሰውዬው የጸዳና የተደራጀ፣ ነገር ግን የተተወ ቤት መስሎ ያገኘዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ከመጀመሪያው ይልቅ የከፋ
“መጀመሪያ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እርኩሱ መንፈስ ሳይለቀው በፊት የነበረውን የሰውዬውን ሁኔታ ነው። አ.ት፡ “መንፈሱ ሳይለቀው በፊት ከነበረው ሁኔታ ይልቅ የከፋ”
Luke 11:27
አጠቃላይ መረጃ፡
x
Luke 11:29
አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ሕዝቡን ማስተማሩን ይቀጥላል።
የሕዝቡ ብዛት ሲጨምር
“ብዙ ሰዎች ሕዝቡ ላይ ሲጨመሩ” ወይም “ሕዝቡ እየበዛ ሲሄድ”
ይህ ትውልድ ክፉ ትውልድ ነው። … ይፈልጋል
እዚህ ጋ፣ “ትውልድ” በውስጡ ያለውን ሕዝብ ያመለክታል። አ.ት፡ “በዚህ ዘመን ያሉ ሰዎች ክፉዎች ናቸው። ለራሳቸው … ይፈልጋሉ” ወይም “በዚህ ዘመን የምትኖሩ ሰዎች ክፉዎች ናችሁ። ለእናንተ … ትፈልጋላችሁ”
ምልክትን ይፈልጋል
ስለሚፈልገው የምልክት ዓይነት መረጃው ግልጽ ሊደረግ ይችላል። አ.ት፡ “ከእግዚአብሔር መምጣቴን ለማረጋገጥ ተአምራት እንዳደርግ ይፈልግብኛል”
ምንም ምልክት አይሰጠውም
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር አንድም ምልክት አይሰጠውም” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የዮናስን ምልክት
“በዮናስ የሆነው” ወይም “እግዚአብሔር ለዮናስ ያደረገለት ተአምር”
ልክ ዮናስ ምልክት እንደሆነ … እንዲሁ ደግሞ … ይህ ትውልድ
ይህ ማለት ዮናስ ለነነዌ ሕዝብ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክት ሆኖ እንዳገለገለ ኢየሱስም በተመሳሳይ መንገድ በዚያ ዘመን ለነበሩት አይሁድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክት ሆኖ ያገለግላል።
የሰው ልጅ
ኢየሱስ ወደ ራሱ እያመለከተ ነው።
ይህ ትውልድ
“ዛሬ በሕይወት ያሉ ሰዎች”
Luke 11:31
የደቡብ ንግሥት

ይህ የሳባን ንግሥት ያመለክታል። ሳባ ከእስራኤል በስተደቡብ የነበረ መንግሥት ነው።
ከዚህ ትውልድ ሰዎች ጋር በፍርድ ትነሣለች
“ተነሥታ በዚህ ዘመን ሰዎች ላይ ትፈርዳለች”
ከምድር ጫፍ መጥታለች
ይህ የአነጋገር ዘይቤ በጣም ሩቅ ከሆነ ቦታ መጥታለች የሚል ትርጉም አለው። አ.ት፡ “በጣም ረጅም ርቀት ተጉዛ መጥታለች” ወይም “በጣም ሩቅ ከሆነ ቦታ መጥታለች” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
ከሰለሞን የሚበልጥ እዚህ አለ
ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ራሱ ነው። አ.ት፡ “ከሰለሞን የምበልጠው እኔ እዚህ አለሁ”
ከሰለሞን የሚበልጥ
ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ራሱ ነው። አ.ት፡ “እኔ ከሰለሞን እበልጣለሁ”
Luke 11:32
የነነዌ ሰዎች
ይህ ጥንታዊቷን የነነዌ ከተማ የሚያመለክት መሆኑን በግልጽ መንገር ያግዝ ይሆናል። አ.ት፡ “በጥንታዊቷ የነነዌ ከተማ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች”
ሰዎች
ይህ ወንዶችንና ሴቶችን ያካትታል። አ.ት፡ “ሕዝብ” (ተባዕታዊ ቃል በምታገኝበት ጊዜ እንስታዊንም ጨምርበት የሚለውን ተመልከት)
የዚህ ትውልድ ሕዝብ
“የዚህ ዘመን ሕዝብ”
ንስሐ ገብተዋልና
“የነነዌ ሕዝብ ንስሐ ገብተዋልና”
ከዮናስ የሚበልጥ እዚህ አለ
ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ ራሱ ነው። እርሱን እንዳልሰሙት በግልጽ መንገሩ ሊጠቅም ይችላል። አ.ት፡ “ከዮናስ የምበልጥ ብሆንም እንኳን እናንተ ገና ንስሐ አልገባችሁም”
Luke 11:33
አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ሕዝቡን ማስተማሩን ይጨርሳል።
አጠቃላይ መረጃ፡
ከቁጥር 33 – 36 ያሉት ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲታዘዙትና ከሌሎች ጋር እንዲካፈሉት ስለሚፈልገው “ብርሃን” ስለሆነው ትምህርቱ የተናገረባቸው ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በድብቅ ቦታ ወይም ከቅርጫት በታች ያስቀምጠዋል
“ይደብቀዋል ወይም ከቅርጫት በታች ያስቀምጠዋል”
ነገር ግን በመብራት ማስቀመጫ ላይ
በዚህ አንቀጽ ውስጥ መገንዘብ በሚቻለው ባለቤትና ግሥ ላይ መጨመር ይቻላል። አ.ት፡ “ነገር ግን አንድ ሰው በመብራት ማስቀመጫው ላይ ያስቀምጠዋል” ወይም “ነገር ግን አንድ ሰው በጠረጴዛ ላይ ያስቀምጠዋል”
ዐይንህ የሰውነትህ መብራት ነው
በዚህ የዘይቤአዊ አነጋገር ክፍል ውስጥ ልክ ዐይን ለሰውነት ብርሃንን እንደሚያቀርብ ኢየሱስ ሲያደርግ የሚያዩአቸው ነገሮች ማስተዋልን ያቀርቡላቸዋል። አ.ት፡ “ዐይንህ ልክ እንደ ሰውነት መብራት ነው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዐይንህ
ዐይን የማየት ችሎታ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰውነት
ሰውነት ለሰው ሕይወት ነው።
ዐይንህ ጤነኛ በሚሆንበት ጊዜ
እዚህ ጋ፣ “ዐይን” የማየት ችሎታ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የማየት ችሎታህ ጤነኛ በሚሆንበት ጊዜ” ወይም “በሚገባ በምታይበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰውነትህ በሙሉ በብርሃን ይሞላል
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። አ.ት፡ “ሰውነትህን በሙሉ ብርሃን ይሞላዋል” ወይም “ሁሉንም ነገር አጥርተህ ለማየት ትችላለህ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ዐይንህ በሚታመምበት ጊዜ
እዚህ ጋ፣ “ዐይን” የማየት ችሎታ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። አ.ት፡ “የማየት ችሎታህ በሚታወክበት ጊዜ” ወይም “በሚገባ ማየት በማትችልበት ጊዜ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሰውነትህ በጨለማ የተሞላ ነው
“ምንም ነገር ለማየት አትችልም”
በአንተ ውስጥ ያለው ብርሃን ጨለማ እንዳይሆን ተጠንቀቅ
“ብርሃን ነው ብለህ የምታስበው ጨለማ ሆኖ እንዳይገኝ አረጋግጥ” ወይም “የትኛው ብርሃን፣ የትኛው ደግሞ ጨለማ መሆኑን ስለ ማወቅህ እርግጠኛ ሁን”
ከዚያም ሙሉ ሰውነትህ ብርሃን ድምቀቱን በላይህ ላይ በሚያንጸባርቅበት ጊዜ የሚመስለውን ዓይነት ይሆናል
ኢየሱስ ተመሳሳዩን እውነት በተነጻጻሪ ይናገራል። እርሱ እውነትን ሰለ ተሞሉ ሰዎች በድምቀት እንደሚያበሩ መብራቶች አድርጎ ይናገርላቸዋል። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)
Luke 11:37
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ በፈሪሳዊ ቤት እንዲበላ ተጋበዘ።
ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ
ደራሲው የአዲስ ሁነት ጅማሬን ለማመልከት እነዚህን ቃላት ይጠቀማል። (አዲስ ሁነትን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
በቤቱ
ይህ የፈሪሳዊውን ቤት ያመለክታል።
ጋደም አለ
ወንዶች በምግቡ ዙሪያ በምቾት ጋደም ማለታቸውና እንዲህ ያለውን እራት ዘና ብለው መብላታቸው የተለመደ ነበር። በአንተ ቋንቋ ሰዎች በሚበሉበት ጊዜ ሰውነታቸውን እንዴት ባለ ሁኔታ እንደሚያሳርፉት ገላጭ ቃል ካለው ያንን ቃል በመጠቀም መተርጎም ያስፈልግህ ይሆናል። አ.ት፡ “ለመብላት ተቀመጡ”
መታጠብ
በሥርዓቱ መሠረት ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ለመሆን እጆቻቸውን መታጠብ እንዳለባቸው የሚናገር መመሪያ ፈሪሳውያን ነበራቸው። አ.ት፡ “እጆቹን መታጠብ” ወይም “በሃይማኖታዊው ሥርዓት ንጹህ ለመሆን እጆቹን መታጠብ”
Luke 11:39
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ዘይቤአዊ አነጋገርን በመጠቀም ለፈሪሳዊው መናገር ይጀምራል። እርሱ ሲኒና ጎድጓድ ሳህኖችን የሚያነጹበትን መንገድ ራሳቸውን ከሚያነጹበት ጋር ያነጻጽራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የሲኒውንና የጎድጓድ ሳህኑን ውጫዊ ገጽ
የዕቃ መያዣዎቹን ውጫዊ ገጽ ማጠብ የፈሪሳውያን የሃይማኖታዊ ሥርዓታቸው አካል ነበር።
ነገር ግን ውስጣችሁ በስስትና በክፋት የተሞላ ነው
ይህ የዘይቤአዊ አነጋገር ክፍል የሳህኑን ውጫዊ ገጽታ ለማጽዳት የሚያደርጉትን ጥንቃቄ ቸል ከሚሉት ውስጣዊ ሁኔታቸው ጋር ያነጻጽራል።
እናንተ ሞኞች
እዚህ ጋ ኢየሱስ የሚናገራቸው ሁሉ ወንዶች ፈሪሳውያን ቢሆኑም እንኳን ይህ አገላለጽ ወንዶችን ወይም ሴቶችን ሊያመለክት ይችላል።
ውጪውን የሠራው እርሱ ውስጡን ደግሞ አይሠራውም?
እግዚአብሔር በውስጣቸው ስላለው ነገር እንደሚገደው ባለማስተዋላቸው ኢየሱስ ፈሪሳውያንን በጥያቄ ይገስጻቸዋል። ይህ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “ውጪውን የሠራው እርሱ ውስጡንም ደግሞ ሠርቶታል!” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
በውስጥ ያለውን ለድኾች ስጡ
ይህ በሲኒዎቻቸውና በጎድጓዳ ሳህኖቻቸው ሊያደርጉት የሚገባቸውን ያመለክታል። አ.ት፡ “በሲኒዎቻችሁና በጎድጓዳ ሳህኖቻችሁ ውስጥ ያለውን ለድኾች ስጡ” ወይም “ለድኾች ለጋሾች ሁኑ”
ሁሉም ነገር ንጹሕ ይሆንላችኋል
“ሙሉ በሙሉ ንጹሕ ትሆናላችሁ” ወይም “በውስጣችሁና በውጪአችሁ ሁሉ ንጹሕ ትሆናላችሁ”
Luke 11:42
ከአዝሙድ፣ ጤና አዳምና ከሌሎችም የጓሮ ዕጾች አሥራት ታወጣላችሁ
“ከአዝሙድ፣ ከጤና አዳምና ከሌሎች የጓሮ ዕጾቻችሁ አንድ አሥረኛውን

ለእግዚአብሔር ትሰጣላችሁ”። ከገቢያቸው ላይ አሥረኛውን ከመስጠት አንጻር ፈሪሳውያን እንዴት ያለ ጽንፍ እንደነበራቸው ኢየሱስ ምሳሌ እየሰጠ ነበር።
አዝሙድና ጤና አዳም
እነዚህ ዕጸች ናቸው። ሰዎች ከእነዚህ ቅጠላ ቅጠሎች ቀንጥሰው ጣዕም እንዲሰጥ ምግባቸው ላይ ይጨምራሉ። ሰዎች አዝሙድና ጤና አዳም ምን እንደሆኑ ካላወቁ እነርሱ የሚያውቁትን የዕጽ ስም ወይም “ዕጸች” የሚል ጥቅል አገላለጽ መጠቀም ትችላለህ። (የማይታወቁትን ተርጉማቸው የሚለውን ተመልከት)
ከሌላ የጓሮ ዕጽ ሁሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ከሌላ ከእያንዳንዱ አትክልት” 2) “ከሌላ የጓሮ ዕጽ ሁሉ” ወይም 3) “ከሌላ የጓሮ ተክል ሁሉ” የሚሉት ናቸው።
የእግዚአብሔር ፍቅር
“እግዚአብሔርን ለመውደድ” ወይም “ለእግዚአብሔር የሆነ ፍቅር”። የሚወደደው እግዚአብሔር ነው።
ሌሎቹን ነገሮች ማድረግን ደግሞ ሳትተዉ
“ሳትተዉ” ይህ ሁልጊዜ መደረግ እንዳለበት አጽንዖት ይሰጣል። ይህ በአዎንታዊነት ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሌሎቹንም መልካም ነገሮች እንዲሁ አዘውትራችሁ ለማድረግ” (ምጸት የሚለውን ተመልከት)
Luke 11:43
አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ፈሪሳውያንን መናገሩን ያበቃል።
ከፊት ያሉ መቀመጫዎች
“ምርጥ መቀመጫዎች”
የአክብሮት ሰላምታ
“ሰዎች በልዩ አክብሮት ሰላምታ እንዲሰጧችሁ ትወዳላችሁ”
ሰዎች ሳያውቁት በላዩ ላይ እንደሚሄዱበት ምልክት የሌለበት መቃብር ናችሁ
ፈሪሳውያን ምልክት እንደሌለበት መቃብር ናቸው፣ ምክንያቱም በሃይማኖት ሥርዓት ንጹሕ ይመስላሉ፣ ነገር ግን በዙሪያቸው ያሉት እንዲረክሱ ያደርጋሉ። (ተነጻጻሪ የሚለውን ተመልከት)
ምልክት የሌለበት መቃብር
እነዚህ መቃብሮች አስክሬን የሚቀበርባቸው የተቆፈሩ ጉድጓዶች ናቸው። እነዚህ ሌሎች ሰዎች ያዩአቸው ዘንድ እንደተለመደው ሰዎች በመቃብር ሥፍራ የሚያስቀምጧቸው ነጭ ድንጋዮች የሏቸውም።
ሳያውቁት
አይሁድ በመቃብር ላይ በሚሄዱበት ጊዜ በሃይማኖታዊው ሥርዓት ይረክሳሉ። እነዚህ ምልክት የሌለባቸው መቃብሮች በድንገት እንዲረክሱ ያደርጓቸዋል። ይህ በግልጽ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሳያስተውሉት እና በሃይማኖታዊ ሥርዓት እርኩስ ይሆናሉ”
Luke 11:45
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ለአይሁዳዊው መምህር ምላሽ መስጠት ይጀምራል።
ከሕግ መምህራን አንዱ
ይህ በታሪኩ ውስጥ አዲስ ገጸ ባህርይን ያስተዋውቃል። (አዲስና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ተመልከት)
በምትናገረው እኛንም መሳደብህ ነው
ኢየሱስ በፈሪሳውያን ላይ የሰጠው አስተያየት የአይሁድ የሕግ መምህራንንም የሚመለከት መሰሏል።
ወዮላችሁ እናንተ የሕግ መምህራን!
ኢየሱስ ከፈሪሳውያን ጋር የሕግ መምህራኑንም ተግባር ለመኮነን መፈለጉን ግልጽ ያደርጋል።
ለመሸከም የሚከብድ ሸክም በሕዝብ ላይ ትጭናላችሁ
“ሊሸከሙት የማይችሉትን ከባድ ሸክም በሕዝብ ላይ ትጭናላችሁ”። ኢየሱስ የሚናገረው አንድ ሰው ከባድ ነገሮችን እንዲሸከሙት ለሕዝብ ይሰጣቸው ይመስል ብዙ መመሪያዎችን ስለሚሰጣቸው ሰው ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሸክሙን ከጣቶቻችሁ በአንዱ መንካት
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች፣ 1) “ሕዝቡ እነዚያን ከባድ ሸክሞች እንዲሸከም ለመርዳት ምንም ነገር አታደርጉም” ወይም 2) “እነዚያን ሸክሞች ራሳችሁ ለመሸከም ምንም ጥረት አታደርጉም”
Luke 11:47
እናንተ ደግሞ ምስክሮች ስለሆናችሁ ትስማማላችሁ
ኢየሱስ ፈሪሳውያንን እና የሕግ መምህራንን እየገሰጻቸው ነው። ስለ ነቢያት መገደል ያውቃሉ፣ ነገር ግን እነርሱን ስለመግደላቸው አባቶቻቸውን አይኮንኑም። ኢ.ት፡ “ስለዚህ፣ እነርሱን ከማውገዝ ይልቅ ታጸናላችሁ፣ ትስማማላችሁም”
Luke 11:49
በዚህ ምክንያት
ይህ ቀደም ሲል የሕግ መምህራን መመሪያዎችን በሕዝቡ ላይ ስለመጫናቸው የተነገረውን መግለጫ ወደ ኋላ ያመለክታል።
የእግዚአብሔር ጥበብ እንዲህ አለች
“ጥበብ” ስለ እግዚአብሔር ሆና መናገር እንደቻለች ተደርጋ ተወስዳለች። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር በጥበቡ እንዲህ አለ” ወይም “እግዚአብሔር በጥበብ ተናገረ” (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
ነቢያትንና ሐዋርያትን እልክላቸዋለሁ
“ለሕዝቤ ነቢያትንና ሐዋርያትን እልክላቸዋለሁ”። ኢየሱስ ይናገራቸው ለነበሩ አይሁድ አድማጮች፣ እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ነቢያትንና ሐዋርያትን እንደሚልክ አስቀድሞ አስታውቋቸው ነበር።
ከእነርሱ አንዳንዶቹን ያሳድዳሉ፣ ይገድላሉም
“ሕዝቤ ከነቢያትና ከሐዋርያት አንዳንዶቹን ያሳድዳሉ፣ ይገድላሉም”። ኢየሱስ ይናገራቸው ለነበሩ አይሁድ አድማጮች እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ነቢያትንና ሐዋርያትን እንደሚያሳድዱና እንደሚገድሉ አስቀድሞ አስታውቋቸው ነበር።
እንግዲህ ለፈሰሰው የነቢያት ሁሉ ደም ይህ ትውልድ ተጠያቂ ይሆናል
ኢየሱስ ይናገራቸው የነበሩ ሰዎች በአባቶቻቸው ስለ ተገደሉት ነቢያት ተጠያቂዎች ይሆናሉ። ኢ.ት፡ “ስለዚህ ሰዎች ስለ ገደሏቸው ነቢያት ሞት በሙሉ እግዚአብሔር ይህንን ትውልድ ተጠያቂ ያደርገዋል” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የፈሰሰው የነቢያት ደም
“ደም… ፈሰሰ” በተገደሉ ጊዜ የተረጨውን ደም ያመለክታል። ኢ.ት፡ “የነቢያትን መገደል” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ዘካርያስ
ይህ ምናልባት በብሉይ ኪዳን ስለ ጣዖት አምልኮአቸው የእስራኤልን ሕዝብ የገሰጻቸው ካህን ይሆን ይሆናል። ይህ የአጥማቂው ዮሐንስ አባት አይደለም።
የተገደለው
ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊነገር ይችላል። ኢ.ት፡ “ሕዝቡ የገደሉት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Luke 11:52
አያያዥ መግለጫ፡
ኢየሱስ ለአይሁዳዊው መምህር የሚሰጠውን ምላሽ ያበቃል።
የእውቀትን ቁልፍ ወስዳችኋል … የሚገቡትን ታደናቅፋላችሁ
ኢየሱስ የእግዚአብሔር እውነት በቤት ውስጥ እንዳለ፣ መምህራን ለመግባት እምቢ እንዳሉና ሌሎች ደግሞ ቁልፏን አግኝተው እንዳይገቡ እንዳልፈቀዱላቸው ይናገራል። ይህ ማለት መምህራኑ እግዚአብሔርን በእውነት አያውቁትም፣ ሌሎችንም ደግሞ እርሱን ከማወቅ ይከለክሏቸዋል ማለት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቁልፏን
ይህ ወደ ቤት ወይም ወደ ዕቃ ማስቀመጫ ክፍል የመግቢያውን መንገድ ይወክላል።
ራሳችሁ አትገቡም
“እናንተ ራሳችሁ እውቀት ለማግኘት አትገቡም”
Luke 11:53
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት የሚበላበት የታሪኩ የመጨረሻ ክፍል ነው። የታሪኩ ዋነኛው ክፍል ካለቀ በኋላ ስለሆነው ነገር እነዚህ ቁጥሮች ለአንባቢው ይናገራሉ።
ኢየሱስ ከዚያ ከሄደ በኋላ
“ኢየሱስ ከፈሪሳዊው ቤት ወጥቶ ከሄደ በኋላ”
ለማጥመድ በመሞከር … ከእርሱ ጋር ተከራከሩ
ጸሐፊዎችና ፈሪሳውያን ከኢየሱስ ጋር የተከራከሩት የእግዚአብሔርን ሕግ ስለ ማፍረሱ ሊከሱት እንዲችሉ ለማጥመድ በመሞከር እንጂ አመለካከታቸውን ለማስከበር አልነበረም።
በራሱ ቃል ሊያጠምዱት በመሞከር

ይህ ማለት ሊከሱት ይችሉ ዘንድ ኢየሱስ አንድ የተሳሳተ ነገር እንዲናገር ፈልገዋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

---

## Chapter 12

### Luke 12:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በሺህ በሚቆጠሩ ሰዎች ፊት ማስተማር ጀመረ

በዚያን ጊዜ

ይህ ምናልባት ጸሐፍት እና ፈሪሳውያን እርሱን ለማጥመድ መንገድ በሚፈልጉበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። ጸሐፊው እነዚህን ቃላት የተጠቀመው አዲስ የሚጀምረውን ትዕይንት ለመግለጽ ነው። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ...እርስ በእርሳቸው በሚገፋፉበት/በሚረጋገጡበት ጊዜ

ይህ የታሪኩን መቼት የሚያሳይ ዳራ የመረጃ ዳራ ነው። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

### Luke 12:2

ነገር ግን በዚያ አለ

"ነገር ግን" የሚለው ቃል ስለ ፈሪሳውያን ግብዝነት ለመግለጽ ይህንን ሀረግ ከቀደመው ሀረግ ጋር ያያይዛል። (አያያዥ ቃላት የሚለውን ይመልከቱ)

ሳይገለጥ ተሸፍኖ የሚቀር ምንም ነገር የለም

"ማናቸውም የተደበቀ ነገር ይገለጣል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች በሌሎች ሰዎች በድብቅ የተደረገን ማናቸውንም ነገር ይደርሱበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሳይታወቅ ተደብቆ የሚቀር ምንም ነገር የለም

ይህ ከዐረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ክፍል ጋር ተመሳሳይ ትርጉም ያለው እውነቱን ላይ ትኩረት የሚሰጥ አገላለጽ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ሌሎች ሰዎች ሊደብቁ ስለሚሞክሩት ነገር በሙሉ ማወቅ ይችላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በጨለማ ውስጥ የተናገራችሁት ነገር ሁሉ በብርሃን ይሰማል

እዚህ ስፍራ "ጨለማ" የሚለው "ምሽት" ለሚለው ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ሲሆን ይህም "በግል" ለሚለው ሜቶኖሚ ነው። እንደዚሁም "ብርሃን" የሚለው "ቀን" ለሚለው ሜቶኖሚ ሲሆን ይህም "ሕዝብ" ለሚለው ሜቶኖሚ ነው። "ይሰማል" የሚለው ሀረግ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "በምሽት ብቻችሁን ሆናችሁ የተናገራችሁትን፣ ሰዎች በቀን ብርሃን ይሰሙታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

በጆሮ የተነገረ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ለሌላ ሰው ማንሾካሾክ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክዲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በውስጠኛው ክፍሎች/በጓዳ

"በተዘጋ ክፍል።" ይህ የግል ንግግርን ያመለክታል። "በግል" ወይም "በድብቅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

ይሰማል

"ከፍ ባለ ድምጽ ይነገራል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች ያሰሙታል/ይናገሩታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።(አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በቤቶች ሰገነት ላይ

በእሥራኤል ቤቶች ጠፍጣፋ ጣራ/ሰገነት አላቸው፤ ስለዚህም ሰዎች ወደዚያ ላይ ወጥተው ሊቆሙ ይችላሉ። ሰዎች እንዴት በቤት ጫፍ ላይ እንደሚወጡ ለመገመት አንባቢው ግር የሚለው ከሆነ፤ ይህ አጠቃላይ በሆነ መንገድ፣ "ሁሉም ሰው ሊሰማው በሚችለው ከፍ ባለ ስፍራ" በሚል ሊተረጎም ይችላል።

### Luke 12:4

እኔ ግን ለወዳጆቼ ለእናንተ እንዲህ እላችኋለሁ

ኢየሱስ በዚህ ሁኔታ ደቀ መዛሙርቱ እንዳይፈሩ ዳግም ንግግሩን በአዲስ መልክ ለማቅረብ

ከዚያ ያለፈ ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር የለም

"ከዚህ በላይ ጉዳት ሊያደርሱ አይችሉም"

ከ.... በኋላ... ስልጣን ያለውን ፣ እርሱን ፍሩ

x

### Luke 12:6

አምስት ድንቢጦች በሁለት ሳንቲም ይሸጡ የለምን?

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር ጥያቄ ይጠቀማል። "አምስት ድንቢጦች በሁለት ሳንቲም ብቻ እንደሚሸጥ ታውቃላችሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ድንቢጦች

ጥራጥሬ የሚመገቡ፣ በጣም ትንንሽ ወፎች

በእግዚአብሔር ዐይኖች አንዳቸውም እንኳን አልተረሱም

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር እና በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ከእነርሱ አንዲቱን እንኳን በፍጹም አይረሳም" ወይም "እግዚአብሔር በእርግጥ እያንዳንዷን ድንቢጥ እንኳን አይረሳም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ, እን ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)

እያንዳንዱቱ የራሳችሁ ፀጉር እንኳን የተቆጠረች ናት

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር በራሳችሁ ላይ ስንት ፀጉር እንዳለ እንኳን ያውቃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አትፍሩ

ለፍርሃቱ ምክንያት የሚሆነው ነገር አልተገለጸም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "በሚደርስባችሁ ነገር አትፍሩ" ወይም 2) "ስለዚህ ሊጎዷችሁ የሚችሉ ሰዎችን አትፍሩ።"

እናንተ ከብዙ ድንቢጦች ይልቅ ይበልጥ ዋጋ አላችሁ

"እናንተ ለእግዚአብሔር ከብዙ ድንቢጦች ይልቅ ዋጋ አላችሁ"

### Luke 12:8

እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ

ኢየሱስ ወደ አዲስ ርዕስ ለመግባት፣ በዚህ ሁኔታ ስለ ንስሃ ለማስተማር አድማጮቹን ዳግም እንዲህ ይላቸዋል።

በሰዎች ፊት ስለ እኔ ለሚመሰክረው ሁሉ

የሚመሰከረው ነገር በግልጽ ሊጻፍ ይችላል። "ስለ እኔ ለሌሎች የሚመሰክር እርሱ የእኔ ደቀ መዝሙር ነው" ወይም "ለእኔ ታዛዥ መሆኑን ለመናገር አሻፈረኝ የሚል፣ እርሱ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ

ኢየሱስ የሚናገረው ስለ ራሱ ነው። "እኔ፣ የሰው ልጅ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በሰዎች ፊት የሚክደኝ እርሱ

"በሰዎች ፊት የሚክደኝ እርሱ።" የተደረገው ክህደት ምን እንደሆነ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "የእኔ ደቀ መዝሙር መሆኑን በሌሎች ፊት እውቅና ለምጠት ያልፈቀደ" ወይም "ለእኔ ታዛዥ መሆኑን ለመናገር ያልፈቀደ እርሱ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እክደዋለሁ

"ተቀባይነት አያገኝም።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የሰው ልጅ እርሱን ይክደዋል" ወይም "የእኔ ደቀ መዝሙር አይደለም እላለሁ/እክደዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰው ልጅ ላይ የሚናገር ሁሉ

"ስለ ሰው ልጅ ክፉ ነገር የሚናገር ሁሉ"

ይቅር ይባላል

"ይቅርታ ይቀበላል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ይምረዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መንፈስ ቅዱስን የሚሰድብ

"በመንፈስ ቅዱስ ላይ ክፉ የሚናገር"

ነገር ግን እርሱ... ይቅር አይባልለትም

ይህ በአድራጊ ግስ ሊገለጽ ይችላል። "ነገር ግን እርሱ... እርሱን እግዚአብሔር ይቅር



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አይለውም" ወይም "ነገር ግን እርሱ… እግዚአብሔር እርሱን ለዘለዓለም ጥፋተኛ ያደርገዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ እና ምፀት የሚሉትን ይመልከቱ)
Luke 12:11
እናንተን በሚያቀርቧችሁ ጊዜ
እነርሱን ወደ ፍርድ ማን እንደሚያቀርባቸው አልተገለጸም
በሸንጎ ፊት
"በሀይማኖት መሪዎች ፊት ለጥያቄ ወደ ሸንጎ ሲያቀርቧችሁ"
መሪዎች…ባለስልጣናት
ይህንን በአንድ ዐረፍተ ነገር ማጣመር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "በአገሪቱ አቅም/ ሀይል ያላቸው ሌሎች ሰዎች"
በዚያ ሰዓት
"በዚያን ጊዜ" ወይም "ከዚያም"
Luke 12:13
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ በኢየሱስ ትምህርት መሃል ጣልቃ የገባ ድርጊት ነው። አንድ ሰው ኢየሱስን አንድ ነገር እንዲያደርግ ይጠይቀውል እርሱም ለሰውየው መልስ ይሰጠዋል።
ከእኔ ጋር ውርስ አካፍለን
በዚያ ባህል ውስጥ፣ ብዙውን ጊዜ አባት ከሞተ በኋላ ውርስ ይተላለፋል። የተናጋሪው ሰው አባት መሞቱን ማረጋገጥ ሊያስፈልግ ይችላል። "አሁን አባታችን ስለ ሞተ ድርሻዬን ከሀብቱ አካፍለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰው
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ እንግዳ የሆነን ለማመልከት የሚውል ነው፤ ወይም 2) ኢየሱስ ሰውየውን እየገሰጸው ነው። የእናንተ ቋንቋ ከእነዚህ በአንዱ መንገዶች በአንዱ ሰዎችን ሊገልጽ የሚችልበት መንገድ ሊኖረው ይችላል። አንዳንዶች ይህን ቃል ከነጭርሱ ሳይተረጉሙት ይቀራሉ።
ማን በእናንተ መሃል ዳኛ ወይም አካፋ አደረገኝ?
ኢየሱስ ጥያቄውን የተጠቀመበት ሰውየውን ለመገሰጽ ነው። አንዳንድ ቋንቋዎች "አንተ" ወይም "የአንተ" ለሚለው ብዙ ቁጥርን ይጠቀማሉ። "እኔ የእናንተ ዳኛ ወይም ፈራጅ አይደለሁም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ለእነርሱ እንደዚህ አላቸው
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው ቃል ምናልባት በዚያ የተሰበሰበውን ሕዝብ ሁሉ ሊያመለክት ይችላል። "ኢየሱስ በዚያ ለተሰበሰቡት እንዲህ አላቸው"
ከስግብግብነት ምኞት ሁሉ ራሳችሁን ጠብቁ
"ከማናቸውም አይነት ራስ ወዳድነት ተጠበቁ።" "ከአፍቅሮተ ንዋይ ራሳችሁን አርቁ" ወይም "የንዋይ ፍቅር እንዳይገዛችሁ ራሳችሁን ጠብቁ"
የሰው ሕይወት
ይህ እውነታን የሚያንጸባርቅ አጠቃለይ ሀሳብ ነው። አንደን ሰው ለይቶ አያመለክትም። አንዳንድ ቋንቋዎች ይህን የሚገልጹበት መንገድ አላቸው።
የሀብቱ ብዛት
"ምንም ያህል ሀብት ያለው መሆኑ" ወይም "የቱንም ያህል ንብረት ይኑረው"
Luke 12:16
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ በምሳሌ ትምህርቱን ማስተማሩን ቀጠለ። (ግብረ ገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)
ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ ሲል ነገራቸው
ምናልባት ኢየሱስ እስከዚህም ድረስ ለተሰበሰበው ሕዝብ በሙሉ እየተናገረ ነበር።
አብዝቶ አፈራ
"በጣም ጥሩ አዝነራ ሰጠ"
ሰብሌን ለማከማቸት በቂ ስፍራ የለኝምና ምን ላደርግ እችላለሁ?
ይህ ጥያቄ የሚያንጸባርቀው ሰውየው ምን ማድረግ እንዳለበት በውስጡ ያስብ የነበረውን ነው። "ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፣ ምክንያቱም ሰብሌን ሁሉ የማከማችበት በቂ ስፍራ የለኝም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ጎተራ
ገበሬዎች የሰበሰቡትን አዝመራ የሚያከማቹበት
ንብረት
ሀብት
ነፍሴን እንዲህ እላታለሁ፣ "ነፍሴ ሆይ፣ ለአመታት የሚሆነ… አለሽ። እረፊ…ደስ ይበልሽ።"
ለራሴ እንዲህ እላለሁ፣ ‘ለአመታት የሚበቃ…አለኝ። እርፍ ልበል… ደስ ይበለኝ።’"
ወይም "ለራሴ እንዲህ እላለሁ ለአመታት የሚበቃ አለኝ… ስለዚህ ማረፍ እችላለሁ…ደስ ይበለኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 12:20
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ በምሳሌ ማስተማሩን ሲጨርስ እግዚአብሔር እንዴት ለባለጸጋው ሰው ምላሽ እንደጠቀሰ ይጠቅሳል።
ዛሬ ምሽት ነፍስህ ከአንተ ትፈለጋለች
"ነፍስ" የአንድን ሰው ሕይወት ያመለክታል። "ዛሬ ምሽት ትሞታለህ" ወይም "ዛሬ ምሽት ነፍስህን ከአንተ እወስዳታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዩፊሚዝም/ የማያስደስትን ቃል ሻል ባለ ቃል መተካት እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ያከማቸሃቸው ነገሮች ለማን ይሆናሉ?
"አንተ ያከማቸኸው ለማን ይሆናል?" ወይም "አንተ የሰበሰብከው ለማን ይሆናል?" እግዚአብሔር ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ሰውየው የሰበሰባቸው ነገሮች የእርሱ እንደማይሆኑ እንዲረዳ ለማድረግ ነው። "አንተ የሰበሰብካቸው ነገሮች የሌላ ሰው ይሆናሉ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ሀብት መሰብሰብ
"ዋጋ ያላቸውን ነገሮች ማከማቸት"
በእግዚአብሔር ዘንድ ባለጸጋ ያልሆነ
ጊዜውን እና ሃብቱን እግዚአብሔር ዋጋ ለሚሰጣቸው ነገሮች አልተጠቀመበትም
Luke 12:22
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ደቀ መዛሙርቱን ማስተማሩን ቀጠለ።
ስለዚህም
"በዚህም ምክንያት" ወይም "ይህ ታሪክ ከሚያስተምረው የተነሳ"
እኔ እንዲህ እላችኋለሁ
"እኔ አስፋላጊ የሆነ ነገር ልነግራችሁ እፈልጋለሁ" ወይም "ይህንን የምነግራችሁን ነገር በጥንቃቄ ልትሰሙ ይገባል"
ስለ ሕይወታችሁ ምን እንደምትመገቡ
"ስለ ሕይወታችሁ እና ስለምትበሉት" ወይም "ለሰውነታችሁ ስለምትለብሱት ልብስ"
ሕይወት ከመብል ስለሚበልጥ
ይህ በአጠቃላይ ስለ እሴት የሚነገር ሀሳብ ነው። "ሕይወት ከምትመገቡት ምግብ ይልቅ ይበልጥ ጠቃሚ ነው"
ሰውነት ከልብስ ይበልጣል
"ሰውነታችሁ ከምትለብሱት ልብስ ይልቅ ይበልጥ ጠቃሚ ነው"
Luke 12:27
ሊሊ አበቦች እንዴት እንደሚያድጉ ተመልከቱ
"አበቦች እንዴት እንደሚያድጉ አስተውሉ"
ሊሊ አበቦች
ሊሊ አበቦች በሜዳ የሚያድጉ ውብ ተክሎች ናቸው። በቋንቋችሁ እነዚህን የአበባ አይነቶች የምትገልጹበት መንገድ ከሌለ እነዚህን አበቦች የሚመስሉ የሌሎችን አበቦች ስያሜ መጠቀም ትችላላችሁ ወይም "አበቦች" ብላችሁ መተርጎም ትችላላችሁ። (የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ አይፈትሉም
ክርን ወይም ፈትልን ለልብስነት ማዘጋጀት "መፍተል" ይባላል። ይህንን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል። "እነርሱ ልብስ ለማበጀት አይፈትሉም" ወይም "እነርሱ የስፍ ክር አያዘጋጁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰሎሞን በክብሩ ሁሉ
"ታላቅ ሀብት የነበረው፣ ሰሎሞን" ወይም "ውብ ልብሶችን የለበሰው፣ ሰሎሞን"
Luke 12:29
ስለምትበሉት እና ስለምትተጡት አትጨነቁ
"ምን እንበላለን ምን እንጠጣለን ብላችሁ አትጨነቁ" ወይም "ብዙ ስለ መብላት እና


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መጠጣት አትጨነቁ
የዓለም ሕዝብ በሙሉ
እዚህ ስፍራ "ሕዝብ/አገር" የሚለው የሚያመለክተው "የማያምኑትን" ነው። "የሌሎች አገራት ሰዎች ሁሉ" ወይም "በዓለም የሚገኙ የማያምኑ ሁሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የእናንተ አባት/አባታችሁ
ይህ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ዋና ማዕረግ ነው።(ልጅ እና አባት የሚሉትን መተረረጎም የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 12:31
የእርሱን መንግሥት ፈልጉ
x
Luke 12:33
ለድሆች ስጡ
እነርሱ የተቀበሉትን መግለጹ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "ከሸያጭ ካገኛችሁት ለደሆች ስጡ" (ኤሊፕሲስ- የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
ለራሳችሁ በሰማያት ...ለራሳችሁ የገንዘብ ቦርሳ/ከረጢት አዘጋጁ
በሰማያት ከረጢት/የገንዘብ ቦርሳ እና ሀብት የሚሉት ተመሳሳይ ነገሮች ናቸው። እነዚህ ሁለቱም ነገሮች በሰማያት የእግዚአብሔርን በረከት ይወክላሉ። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ለራሳችሁ አዘጋጁ
ይህ ለድሆች በመስጠት የሚገኝ ነው። "በዚህ መንገድ ለራሳችሁ በሰማይ ታዘጋጃላችሁ"
የማይደበዝዘውን ግዙ
"ቀዳዳ የማይኖረው/የማይቀደድ የገንዘብ ቦርሳ/ ከረጢት"
ጊዜ የማያልፍበት/የማያረጅ
"የማይጠፋ" ወይም "እየመነመነ/ እያደር እያነሰ የማይሄድ"
የትኛውም ሌባ የማይቀርበው
"ሌቦች የማይደርሱበት"
የቱም ብል የማያጠፋው
"ብል የማይበላው"
ብል
"ብል" ጨርቅን እየቀደደ የሚበላ ትንሽ ነፍሳት ነው። ምናልባት እንደ ጉንዳን ወይም ምስጥ የመሰሉ ሌሎች ነፍሳትን መጠቀም ሊያስፈልጋችሁ ይችላል።
ሃብታችሁ ባለበት፣ ልባችሁ በዚያ ይሆናል
"ልባችሁ ሃብታችሁ በተጠራቀመበት በዚያ ላይ ያተኩራል"
ልባችሁ
እዚህ ስፍራ "ልብ" የሚያመለክተው የሰውን አሳተሳሰብ ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 12:35
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ። (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)
ረጅም ልብሳችሁን በቀበቶአችሁ ታጥቃችሁ
ሰዎች ረጅም ልብስ ይለብሱ ነበር። በሚሰሩበት ወቅት እንዳያስቸግራቸው በቀበትዋቸው ያሥራሉ። "ልብሳችሁን በአጭር ታጥቃችሁ ለማገልገል ተዘጋጁ" ወይም "ለብሳችሁ ለማገልገል ተዘጋጁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
መብራታችሁ የበራ ይሁን
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መብራታችሁ ይብራ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ጌታቸውን እንደሚጠብቁ ሰዎች ሁኑ
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አገልጋዮች የጌታቸውን መመለስ በሚጠባበቁበት መንገድ የእርሱን መመለስ እንዲጠብቁ ያዛቸዋል። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 12:37
የተባረኩ ናቸው
"እንዴት ለእነርሱ መልካም ይሆናል"
ጌታቸው ሲመጣ እርሱን ሲጠብቁት የሚያገኛቸው
"እርሱ በሚመለስበት ጊዜ ጌታቸውን ሲጠበቁት የሚያገኛቸው" ወይም "ጌታቸው በሚመለስበት ጊዜ ዝግጁ የሆኑ"
እርሱ ይቀመጣሉ፣ እርሱ ታጥቆ ቆሞ ያገለግላቸዋል
አገላጋዮቹ ታማኞች ስለነበሩ እና ጌታቸውን ለማገልገል ዝግጁ ስለነበሩ፣ አሁን ጌታቸው እነርሱን በማገልጋል ዋጋቸውን ይከፍላቸዋል/ይሸልማቸዋል።
በምሽቱ ሁለተኛ ክፍለ ጊዜ
ሁለተኛው ሰዓት ከምሽቱ ሶስት ሰዓት እስከ እኩለ ሌሊት ያለው ነው። "በውድቅት ሌሊት" ወይም "ከእኩለ ለሊት አስቀድሞ"
ወይም ደግሞ በሶስተኛው ሰዓት እንኳን
ሶስተኛው ሰዓት ከእኩለሌሊት እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ያለው ነው። "ወይም ሌሊት ዘግይቶ ቢመጣም እንኳን"
Luke 12:39
ሰዓቱን አውቆ ቢሆን
"መቼ እንደሆነ ቢያውቅ"
ቤቱ እንዲቆፈር ባልተወ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሌባ ቆፍሮ ወደ ቤቱ እንዲገባ ባልተወም/ዝም ብሎ ባላየ/ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰው ልጅ የሚመጣበትን ሰዓት ስለማታውቁ
በሰው ልጅ እና በሌባ መሃል ያለው ብቸኛው መመሳሰል የትኛቸውም መቼ እንደሚመጡ ሰዎች አለማወቃቸው በመሆኑ ሁሌም ዝግጁ መሆን ይገባቸዋል።
ሰዓቲቱ መቼ እንደሆነች አታውቁም
"ምን ጊዜ እንደሆነ ጊዜውን አታውቁም"
መች የሰው ልጅ እንደሚመጣ
ኢየሱስ ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። "እኔ፣ የሰው ልጅ መቼ እንደምመጣ"
Luke 12:41
አያያዥ ሃሳብ፡
በቁጥር 42 ኢየሱስ ሌላ ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ይጀምራል።
አጠቃላይ መረጃ፡
በቁጥር 41፣ ጴጥሮስ ስለ ቀደመው ምሳሌ ሲጠይቅ በታሪኩ ፍሰት መቆሚያ ይፈጠራል።
እንዲህ ከሆነ ትክክለኛውን ጊዜ...ማን ነው?
ኢየሱስ የጴጥሮስን ጥያቄ በተዘዋዋሪ ለመመለስ ጥያቄ ይጠቀማል። ታማኝ አስተዳዳሪ መሆን የሚፈልጉ ምሳሌው ስለ እነርሱ እንደሆነ እንዲረዱ ይጠብቃል ። "ትክክለኛው ጊዜ...ለሆኑ ሁሉ ይህን ተናግሪያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ብልህ እና ታማኝ አስተዳዳሪ
ኢየሱስ አገልጋዮች እንዴት በታማኝነት የጌታቸውን መመለስ መጠበቅ እንዳለባቸው ሌላ ምሳሌ ይናገራል። (ግብረገባዊ ምሳሌዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 12:45
ያ አገልጋይ
ይህ የሚያመለክተው ጌታው በሌሎች አገልጋዮች ላይ ሀላፊ ያደረገውን አገላጋይ ነው
በልቡ እንዲህ ይላል
እዚህ ስፍራ "ልብ" ለአንድ ሰው አስተሳሰብ ወይም ውስጣዊ ማንነት ሜቶኖሚ/ ነው። "በውስጡ እንዲህ ብሎ ቢያስብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
የጌታዬ መመለስ ይዘገያል
"አለቃዬ በቶሎ አይመለስም"
ወንድ እና ሴቶች አገልጋዮች
እዚህ ስፍራ "ወንድ እና ሴቶች አገልጋዮች" ተብለው የተተረጎሙት ቃላት "ወንድ ልጆች" እና "ልጃገረዶች" ተብለው ተተርጉመዋል። ይህ አገልጋዮቹ ወጣቶች እንደነበሩ ወይም በጌታቸው ዘንድ ተወዳጆች እንደነበሩ ሊያመለክት ይችላል።
እርሱ ባልጠበቃት ቀን፣ ደግሞም እርሱ በማያውቃት ሰዓት
"ቀን" እና "ሰዓት" ከእስከ ያለውን ማናቸውንም ጊዜ ሲያመለክት፣ "በስተቀር" እና "ያውቃል" የሚሉት ቃላትም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ ስለዚህም እዚህ ስፍራ ሁለቱ ሀረጎች፣ ለአገላጋዮቹ የጌታቸው መምጣት ፍጹም በድንገት እንደሚሆን ትኩረት ለመስጠት በንጽጽር የቀረቡ ናቸው። ሆኖም፣ የእናተ ቋንቋ "ማወቅ" እና "መጠባበቅ" ወይም "ቀን" እና "ሰዓት" ለሚሉት ቃላት ልዩነት የሌለው ካልሆነ በስተቀር ሀረጋቱ በአንድነት ተጣምረው መቅረብ የለባቸውም። "አገልያዩ እርሱን

በማይጠባበቅበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ከጽንፍ ጽንፍ እና ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚሉትን ይመልከቱ)
ይቆራርጠዋል ስፍራውንም ታማኝ ካልሆኑት ጋር ያደርጋል
ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ ጌታው በአገልጋዩ ላይ የሚያደርሰው ከባድ ቅጣት ተጋኖ የተገለጸበት ነው፣ ወይም 2) ይህ አገልጋዩ የሚደርስበት የቅጣት ሁኔታ የሚገደል እና የሚቀበር መሆኑን ይገልጻል። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉት ይመልከቱ)
Luke 12:47
አያያዥ ሀሳብ፡
x
Luke 12:49
አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስተማር ቀጥሏል።
በምድር ላይ እሳት ለማድረግ መጥቻለሁ
"በምድር ላይ እሳት ለመጣል መጥቻለሁ" ወይም "በምድር ላይ እሳት ለመለኮስ መጥቻለሁ።" ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢየሱስ የመጣው ሰዎችን ለመዳኘት ነው ወይም 2) ኢየሱስ የመጣው ሰዎችን ለማንጻት ነው፣ ወይም 3) ኢየሱስ የመጣው በሰዎች መሃል ልዩነትን ለማምጣት ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከነደደ ምን እፈልጋለሁ
ይህ አጋኖ የሚያጎላው፣ እርሱ ምን ያህል ይህ ሊሆን እንደፈለገ ነው። "አስቀድሞ ነድዶ ቢሆን በጣም በወደድኩ" ወይም "አስቀድሞ ጀምሮ ቢሆን ኖሮ እወድ ነበር" (ቃለ አጋኖዎች የሚለውን ይመልከቱ)
የምጠመቃት ጥምቀት አለች
እዚህ ስፍራ "ጥምቀት" የሚያመለክተው ኢየሱስ ሊቀበል ያለውን መከራ ነው። በጥምቀት ውሃ የሰውን ሁለመና እንደሚሸፍን፣ መከራ ኢየሱስን ያጥለቀልቀዋል። "በክፍተኛ የመከራ ጥምቀት ውስጥ ማለፍ ይኖርብኛል" ወይም "ሰው ሲጠመቅ በውሃ ውስጥ እንደሚሸፈን በመከራ መጥለቅለቅ ይኖርብኛል" (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ነገር ግን
"ነገር ግን" የሚለው ቃል የዋለው እርሱ በመከራ ውስጥ ከማለፉ አስቀድሞ በምድር ላይ እሳት ሊጥል አለመቻሉን ለማሳየት ነው።
እስኪፈጸም ድረስ እንዴት እጨነቃለሁ
ይህ አጋኖ የሚያጎላው እርሱ ምን ያህል ተጨንቆ እንደነበረ ነው። "እጅግ ተጨንቄያለሁ፣ ይህን የመከራ ጥምቀት እስክፈጽም ድረስ ይኸው ይሆናል" (ቃለ አጋኖዎች የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 12:51
በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ ይመስላችኋልን? አይደለም፣ እላችኋለሁ፣ ይልቁንም መከፋፈልን ለማምጣት እንጂ
ኢየሱስ የተሳሳተ መረዳታቸውን እንዲያርሙ እንደሚያደርግ ሊያሳውቃቸው ጥያቄ ያነሳል። በሁለተኛው ዐረፍተ ነገር የተተወውን "እኔ የመጣሁት" የሚሉ ቃላት መጨመር ሊያስፈልጋችሁ ይችላል። "በምድር ላይ ሰላም ለማምጣት የመጣሁ ይመስላችኋል፣ ነገር ግን እላችኋለሁ ለዚህ አልመጣሁም። ይልቁንም፣ መለያየትን ለማምጣት መጥቻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
መለያየት
"ጠላትነት" ወይም "አለመስማማት"
በአንድ ቤት ውስጥ የተከፋፈሉ አምስት ይኖራሉ
ይህ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ እንኳን ለሚኖረው የመከፋፈል አይነት ምሳሌ ነው
በአንድ ቤት ውስጥ አምስት ይኖራሉ
ይህ ሰዎችን እንደሚያመለክት መግለጽ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "በአንድ ቤት ውስጥ አምስት ሰዎች ይኖራሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)
አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....አንዱ በአንዱ ላይ....
"ይቀዋወማል…ይቀዋወማል…ይቀዋወማል…ይቀዋወማል…ይቀዋወማል…ይቀዋወማል..ይቀዋወማል…ይቀዋወማል"
Luke 12:54
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ መናገር ይጀምራል።
ደመና ሲወጣ ስትመለከቱ…ይሆናል
ይህ ሁኔታ በተለምዶ በእሥራኤል ዝናብ ይመጣል ማለት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ዝናብ እመጣ ነው
"ዝናብ ይመጣል" ወይም "ሊዘንብ ነው"
የደቡብ ነፋስ ሲነፍስ
ይህ ሁኔታ በተለምዶ በእሥራኤል ሞቃታማ የአየር ንብረት ይመጣል ማለት ነው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ምድር እና ሰማያት
"ምድር እና ሰማይ"
ታዲያ እንዴት የአሁኑን ጊዜ መረዳት አትችሉም?
ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ ያነሳው የተሰበሰበውን ሕዝብ ለመገሰጽ ነው። ኢየሱስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እነርሱን ለማሳመን ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "ወቅቱን መተረጎም መቻል ይኖርባችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 12:57
ራሳችሁ ለምን ትክክል የሆነውን አትፈርዱም?
ኢየሱስ ጥያቄውን ያነሳው የተሰበሰበውን ሕዝብ ለመገሰጽ ነው። ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊተረጎም ይችላል። "እናንተ ራሳችሁ ትክክለኛ የሆነውን መለየት ይኖርባችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
እራሳችሁ
"በራሳችሁ ተነሳሽነት"
በምትሄዱበት ጊዜ…የመጨረሻዋን ገንዘብ
ኢየሱስ የተሰበሰበውን ሕዝብ ለማስተማር መላምታዊ ሁኔታ ይጠቀማል። የእርሱ ትምህርት፣ ማቃለል የሚችሉትን ነገር ዳኛ ፊት ሳይቀርቡ ችግራቸውን እንዲያቃልሉ ማስተማር ነው። ይህን ግልጽ ለማድረግ መሆን የማይገባውን መሆን እንደማይገባው በግለጽ ደግሞ መጻፍ ይቻላል። "ማድረግ የሚገባችሁ ከሆነ…የመጨረሻዋን ገንዘብ
በምትሄድበት ጊዜ
x

Chapter 13
Luke 13:1
አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ እስከ አሁን ድረስ ለተሰበሰበው ሕዝብ እየተናገረ ነው። ከተሰበሰበው ህስብ መሃል አንዳንዱ እርሱን ስጠይቀው እርሱም ምላሽ መስጠት ጀመረ። ይህ በሉቃስ 12:1 ላይ የጀመረውን ታሪክ ይቀጥላል።
በዚያን ጊዜ
ይህ ሀረግ፣ ኢየሱስ የተሰበሰበውን ሕዝብ በሚያስተምርበት ወቅት እስከ ምዕራፍ 12 መጨረሻ ድረስ ያለውን ትዕይንት ያያይዛል።
ጲላጦስ መስዋዕታቸውን ከደም ጋር የቀላቀላባቸው
እዚህ ስፍራ "ደም" የሚያመለክተው የገሊላ ሰዎችን ሞት ነው። ምናልባት እነርሱ የተገደሉት መስዋዕታቸውን በሚያቀርቡበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። በዩዲቢ ውስጥ እንደቀረበው ብልጽ ሊደረግ ይችላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ጲላጦስ መስዋዕታቸውን ከደም ጋር የቀላቀላባቸው
ምናልባት ጲላጦስ ህዝቡን የገደለው ራሱ ሳይሆን ወታደሮችን ልኮ ሊሆን ይችላል። "እንስሳትን መስዋዕት በማቅረብ ላይ እያሉ የጲላጦስ ወታደሮች የገደሏቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እነዚህ የገሊላ ሰዎች በ…መንገድ ይበልጥ ኃጢአተኞች ስለሆኑ ይመስላችኋል? አይደለም፣ እኔ እላችኋለሁ
"እነዚህ ገሊላውያን ይበልጥ በ…መንገድ ኃጢአተኞች ነበሩን? አይደለም፣ እኔ እላችኋለሁ" ወይም "ይህ እነዚህ ገሊላውያን ይበልጥ በ…መንገድ ኃጢአተኞች


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደሆኑ ያረጋግጣልን? አይደለም፣ እኔ እላችኋለሁ" ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት የህዝቡን መረዳት ለመገዳደር ነው። "እናንተ እነዚህ ገሊላውያን በ… መንገድ ይበልጥ ኃጢአተኞች እንደሆኑ ታስባላችሁ ነገር ግን አልነበሩም" ወይም "እነዚህ ገሊላውያን በ…መንገድ ይበልጥ ኃጢአተኞች እንደሆኑ አታስቡ" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

አይደለም፣ እኔ እላችኋለሁ

እዚህ ስፍራ "እኔ እላችኋለሁ" የሚለው ትኩረት የሚሰጠው "አይደለም" የሚለውን ነው። "በእርግጥ እነርሱ ይበልጥ ኃጢአተኞች አልነበሩም" ወይም "መከራ ስለደረሰባቸው ይህ ይበልጥ ኃጢአተኛ መሆናቸው ያረጋግጣል ብላችሁ ማሰባችሁ ስህተት ነው"

ሁላችሁም በተመሳሳይ መንገድ ትጠፋላችሁ

"ሁላችሁም ደግሞ ትሞታላችሁ።" "በተመሳሳይ መንገድ" የሚለው ሀረግ ተመሳሳይ ነገር ይደርስባቸዋል ማለት እንጂ በተመሳሳይ መልክ ይሞታሉ ማለት አይደለም።

መጥፋት

መሞት

Luke 13:4

ወይም እነርሱ

ይህ ኢየሱስ መከራ ስለ ደረሰባቸው ሰዎች የሰጠው ሁለተኛ ምሳሌ ነው። "ወይም እነዚያን ተመልከቱ" ወይም "ስለ እነዚያ አስቡ"

አሥራ ስምንት ሰዎች

"18 ሰዎች" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰሊሆም

ይህ በኢየሩሳሌም ውስጥ የሚገኝ ስፍራ ስም ነው። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም…እነርሱ የከፉ ኃጢአተኞች ነበሩ ብላችሁ ታስባላችሁ? እኔ እላችኋለሁ፣ አይደለም

"ይህ እነርሱ በኢየሩሳሌም… ይበልጥ ኃጢአተኞች እንደሆኑ ያረጋግጣልን? እኔ እላችኋለሁ፣ አይደለም።" ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት የህዝቡን መረዳት ለመገዳደር ነው። "እነርሱ በኢየሩሳሌም…ይበልጥ ኃጢአተኛ እንደሆኑ ታስባላችሁ፣ እኔ ግን አልነበሩም እላለሁ" ወይም "እነርሱ በኢየሩሳሌም… ይበልጥ ኃጢአተኞች ነበሩ ብላችሁ ማሰብ የለባችሁም እላለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ የከፉ ኃጢአተኞች ነበሩ

x

Luke 13:6

አጠቃላይ መረጃ:

ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ የመጨረሻ ሃሳቡን ለማብራራት ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ፣ "ነገር ግን ንስሃ ባትገቡ፣ እናንተ ሁላችሁም ደግሞ ትጠፋላችሁ።" (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)

አንድ ሰው በወይን ተክሉ ስፍራ የበለስ ዛፍ ነበረው

የወይን ተክሉ ባለቤት በወይን እርሻው ውስጥ ሌላ ሰው የበለስ ዛፍ ተከለበት።

ለምን መሬቱን እንድታጠፋ ትፈቅድላታለህ?

ሰውየው ጥያቄውን የተጠቀመበት ዛፏ ጥቅም እንደማትሰጥ እና አትክልተኛው ሊቆርጣት እንደሚገባ ትኩረት ለመስጠት ነው። "መሬቱን እንድታበላሽ አትፍቀድ/ መሬቱን ታበላሽ ዘንድ አትተዋት።" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 13:8

አያያዥ ሀሳብ:

ኢየሱስ ግብረገባዊ ምሳሌውን መናገሩን ጨረሰ። ይህ በሉቃስ 12:1 የተጀመረው ታሪክ መጨረሻ ነው።

ተዋት

"በዛፊቱ ላይ አንዳች አታድርግ" ወይም "አትቁረጣት"

ፍግ አድርግላት

"በአፈሩ ላይ ማዳበሪያ ጨምር።" ማዳበሪያ/ፍግ የእንስሳ ኩበት ነው። አፈሩ ለተክሎች እና ለዛፍ መልካም እንዲሆን ሰዎች ይህን በመሬት ላይ ይጨምራሉ። "በላዩ ማዳበሪያ መጨመር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀጣዩ አመት ፍሬ ከሰጠች መልካም

x

Luke 13:10

አጠቃላይ መረጃ:

እነዚህ ቁጥሮች ለዚህኛው የታሪኩ ክፍል መቼት እና ወደ ታሪኩ ለምትገባው ሸባ ሴት የመረጃ ዳራ ይሰጣሉ። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

አሁን

ጸሐፊው ይህንን ቃል የተጠቀመበት የአዲሱን ትዕይንት ጅማሬ ለማመልከት ነው። (የአዲስ ትዕይንት መግቢያ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰንበት

"በሰንበት ዕለት።" አንዳንድ ቋንቋዎች "ሰንበት" ይላሉ፤ ምክንያቱም የትኛው የተለየ የሰንበት ዕለት እንደነበር አናውቅም።

Luke 13:12

አንቺ ሴት፣ ከድካምሽ ተፈውሰሻል

"አንቺ ሴት፣ ከድካምሽ ተፈውሰሻል።" ይህ "አንቺ ሴት፣ ከድካምሽ ፈውሼሻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው በአድራጊ ግስ ሊገለጽ ይችላል። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንቺ ሴት፣ ከድካምሽ ተፈውሰሻል

ይህን በመናገር፣ ኢየሱስ እርሷን ፈወሳት። ይህ ነገር እንዲሆን ማድረጉን፣ ወይም ማዘዙን በሚያሳይ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንቺ ሴት፣ አሁን እኔ ከድካምሽ ፈውሼሻለሁ" ወይም "አንቺ ሴት፣ ከድካምሽ ነጻ ሁኚ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሃሳቦች- ሌላ ጥቅሞች የሚለውን ይመልከቱ)

እጁን በላይዋ ጫነ

"እርሱ ነካት"

እርሷ ቀጥ ብላ ቆመች

ይህ አድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ቀና ብላ ቆመች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በሰንበት ዕለት

"በአንድ የሰንበት ዕለት።" አንዳንድ ቋንቋዎች "በሰንበት" ይላሉ፤ ምክንያቱም የትኛው የተለየ የሰንበት ዕለት እንደ ነበር አናውቅም።

Luke 13:15

ጌታ ለእርሱ መልስ ሰጠው

"ጌታ ለሽንጎ መሪው ምላሽ ሰጠ"

ግብዞች

ኢየሱስ በቀጥታ ከምኩራብ መሪው ጋር ተናገረ፣ ነገርግን የብዙ ቁጥሩ ሌሎችንም የሃይማኖት መሪዎች ጭምር ያጠቃልላል። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "አንተ እና እንንተ የሃይማኖት መሪዎቻችሁ ግብዞች ናችሁ" (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ከእናንተ እያንዳንዱ በሬውን ወይም አህያውን ከማደሪያው ፈትቶ በሰንበት ሊያጠጣ ይወስደው የለምን?

ኢየሱስ ጥያቄውን የተጠቀመበት አስቀድሞ ስለሚያውቁት ነገር እንዲያስቡበት ለማድረግ ነው። "ከእናንተ እያንዳንዱ በሬውን ወይም አህያውን በሰንበት ከታሰረበት ፈትቶ ወደ ሚጠጣበት ስፍራ ይወስደዋል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

በሬ…አህያ

እነዚህ ሰዎች ውሃ በመስጠት የሚንከባከቧቸው እንስሳት ናቸው

በሰንበት ዕለት

x

Luke 13:17

እርሱ እነዚህን ነገሮች እየተናገረ ሳለ

"ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች በሚናገርበት ጊዜ"

እርሱ ያደረጋቸው አስደናቂ ነገሮች

"ኢየሱስ ያደርጋቸው የነበሩ አስደናቂ ነገሮች"

Luke 13:18

አያያዥ ሃሳብ:

ኢየሱስ በምኩራብ ለነበሩ ሰዎች ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ። (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ትመስላለች…ከምንስ ጋር አወዳድራታለሁ?

ኢየሱስ ሁለትን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው ሊያስተምር ያለውን ነገር ለማስተዋወቅ ነው። "የእግዚአብሔር መንግሥት ምን እንደምትመስል እነግራችኋለሁ…ከምን ጋር ላነጻጽራት እችላለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከምን ጋር ላነጻጽራት እችላለሁ?

ይህ ከቀደመው ጥያቄ ጋር በመሰረቱ ተመሳሳይ ነው። አንዳንድ ቋንቋዎች ሁለቱንም ጥያቄዎች ሊጠቀሙ ይችላሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ አንዱን ጥያቄ ብቻ ይጠቀማሉ። (ትይዩ ንጽጽራዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ልክ እንደ ሰናፍጭ ፍሬ ናት

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከሰነፍጭ ጋር ያነጻጽራል። "የእግዚአብሔር መንግሥት የሰናፍጭን ፍሬ ትመስላለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 13:20

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢየሱስ በምኩራብ ለነበሩ ሰዎች መናገሩን ጨረሰ። ይህ የዚህ ታሪክ ክፍል መጨረሻ ነው።

የእግዚአብሔርን መንግሥት ከምን ጋር ላነጻጽራት እችላለሁ?

ኢየሱስ ቀጥሎ ሊያስተምር ያለውን ለማስተዋወቅ ሌላ ጥያቄ ያነሳል። "ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ላነጻጽር የምችለውን ሌላ ነገር እነግራችኋለሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እርሾ ናት

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት በዳቦ ሊጥ ውስጥ ከሚገኝ እርሾ ጋር ያነጻጽራል። "የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ እርሾ ናት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ እርሾ

ብዙ ሊጥ ለማቡካት በጣም ትንሽ እርሾ ብቻ ያስፈልጋል። ይህ በዩዲቢ ውስጥ እንደሚገኘው ግልጽ ሊደረግ ይችላል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ሦስት እጅ/ልኬት ዱቄት

አንድ እጅ/ልኬታ የሚባለው ወደ 13 ኪሎ ግራም የሚጠጋ በመሆኑ፣ይህ ብዙ መጠን ያለው ዱቄት ነው። የእናንተ ባህል ዱቄትን ለመለካት የሚጠቀምበትን መለኪያ መጠቀም ትችላላችሁ። "ብዙ መጠን ያለው ዱቄት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Luke 13:22

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢየሱስ ለጥያቄው ምላሽ የሰጠው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ መግባት ዘይቤያዊ አገላለጽ በመጠቀም ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የሚድኑ ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸውን?

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር የሚያድነው ጥቂት ሰዎችን ብቻ ነውን?" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በጠባቡ በር ለመግባት ታገሉ

"በጠባቡ በር ለመግባት ትጉ።" ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ መግባት የሚናገረው፣ ወደ ቤት እንደሚያስገባ ትንሽ በር አድርጎ ነው። ኢየሱስ ለሰዎች ስብስብ እንደመናገሩ በዚህ ትእዛዝ ውስጥ "እናንተ" የሚለው ተውላጠ ስም ብዙ ቁጥር ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና አንተ የሚለው ተውላተ ስም መልኮች የሚለውን ይመልከቱ)

ጠባቢቱ በር

በሩ ጠባብ መሆኑ የሚያመለክተው በውስጡ ማለፍ አስቸጋሪ መሆኑን ነው። ይህን ውስንነት በሚያሳይ መንገድ ተርጉሙት። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ብዙዎች ሊገቡባት ይፈልጋሉ፣ ነገር ግን ሊገቡ አይችሉም

ለመግባት ከባድ ከመሆኑ የተነሳ፣ መግባት እንደማይችሉ ተጠቁሟል። ቀጣዩ ሀረግ ከባድነቱን ያብራራል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 13:25

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ መግባት መናገሩን ቀጥሏል።

አንድ ጊዜ ባለቤቱ

"ባለቤቱ ከ...በኋላ"

የቤቱ ባለቤት

ይህ በቀደመው ቁጥር ላይ ጠባብ በር ያለውን ቤት ባለቤት ያመለክታል። ይህ እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔር መንግሥት ገዢ የሚያቀርብ ዘይቤ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እናንተ በውጭ ትቆማላችሁ/ትቀራላችሁ

ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ እየተናገረ ነበር። "እናንተ" የሚለው ተውላጠ ስም ብዙ ቁጥር ነው። እነርሱ በጠባቡ በር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደማይገቡ እየተናገረ ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

በሩን ትደበድባላችሁ

"በሩን ትመታላችሁ።" ይህ የባለቤቱን ትኩረት ለማግኘት የሚደረግ ጥረት ነው።

ከዚህ ሂዱ

"ከእኔ ራቁ"

Luke 13:28

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ መግባት መናገሩን ቀጥሏል። ይህ የዚህ ንግግር መጨረሻ ነው።

ለቅሶ እና ጥርስ ማፋጨት

እነዚህ ድርጊቶች ታላቅ ጸጸትን እና ሀዘንን የሚያመለክቱ ትዕምርታዊ ድርጊቶች ናቸው። "ከታላቅ ጸጸታቸው የተነሳ የተከተለ ለቅሶ እና ጥርስ ማፋጨት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

በምትመለከቱበት ጊዜ

ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ወደ ሰማዩ መንግስት እንደማይገቡ አድርጎ መናገሩን ቀጥሏል።

ነገር ግን ወደ ውጭ ትጣላላችሁ

"ነገር ግን እናንተ ራሳችሁ ወደ ውጭ ትጣላላችሁ።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ነገር ግን እግዚአብሔር ወደ ውጭ ይጥላችኋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ከምሥራቅ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን እና ደቡብ

ይህ ማለት "ከሁሉም አቅጣጫ።" ማለት ነው።

በእግዚአብሔር መንግሥት በማዕድ ይቀመጣሉ

የእግዚአብሔርን መንግሥት ደስታ እንደ ግብዣ መግለጽ የተለመደ ነበር። "በእግዚአብሔር መንግሥት ይጋበዛሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

የመጀመሪያ ይሆናሉ...የመጨረሻ ይሆናሉ

የመጀመሪያ መሆን የሚወክለው አስፈላጊ ወይም የተከበረ መሆንን ነው። "እጅግ አስፈላጊ ይሆናሉ...የመጨረሻዎቹ ይሆናሉ" ወይም "እግዚአብሔር ያከብራቸዋል... እግዚአብሔር ያሳፍራቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 13:31

አያያዥ ሀሳብ፡

ይህ በዚህ የታሪክ ክፍል ቀጣዩ ትዕይንት ነው። አንዳንድ ፈሪሳውያን ስለ ሄሮድስ ቢነግሩትም ኢየሱስ ግን ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ላይ ነው።

ከዚያም ብዙ ሳይቆይ

"ኢየሱስ ንግግሩን እንደጨረሰ ወዲያውኑ"

ከዚህ በቶሎ ሂድ ምክንየቱም ሄሮድስ ሊገድልህ ይፈልጋል

ይህንን ለኢየሱስ እንደ ተሰጠ ማስጠንቀቅያ ተርጉሙት። ወደ አንድ ስፍራ እንዲሄድ እና ራሱን እንዲያድን እየመከሩት ነበር።

ሄሮድስ ሊገድልህ ይፈልጋል

ሄሮድስ ሰዎች ኢየሱስን እንዲገድሉት ያዛል። "ሄሮድስ አንተን እንዲገድሉ ወታደሮቹን መላክ ይፈልጋል"

ያ ቀበሮ

ኢየሱስ ሄሮድስን ቀበሮ ብሎ እየጠራው ነበር። ቀበሮ ትንሽ የሆነ የዱር ውሻ ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ሄሮድስ በፍጹም የሚያስፈራው አልነበረም 2) ሄሮድስ አሳሳች ነበር። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

በማናቸውም ሁኔታ

"የሆነ ሆኖ" ወይም "ሆኖም" ወይም "የሆነው ቢሆንም"

ነቢይን ከኢየሩሳሌም ውጭ መግደል ተቀባይነት የለውም

የአይሁድ መሪዎች እግዚአብሔርን እንደሚያገለግሉ ይናገራሉ። ሆኖም ግን አባቶቻቸው ብዙ የእግዚአብሔርን ነቢያት በኢየሩሳሌም ውስጥ ገድለዋል፣ እናም ኢየሱስ እርሱንም በዚህ እንደሚገድሉት ያውቃል። "የአይሁድ መሪዎች የእግዚአብሔርን መልዕክተኞች የገደሉት እዚህ ኢየሩሳሌም ውስጥ ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ምጸት የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 13:34

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ ለፈሪሳውያን ምላሽ መስጠቱን አበቃ። ይህ የዚህኛው ታሪክ ክፍል መጨረሻ ነው።

ኢየሩሳሌም፣ ኢየሩሳሌም

ኢየሱስ የኢየሩሳሌም ሰዎች በዚያ ሆነው እንደሚሰደሙት አድርጎ ይናገራል። ኢየሱስ ይህን ሁለት ጊዜ የደገመው ለእነርሱ ምን ያህል እንዳዘነ ለማሳየት ነው። (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)

ነቢያትን የገደልሽ ወደ አንቺ የተላኩትን በድንጋይ የወገርሽ

ከተማን መናገር እንግዳ ነገር ከሆነ፣ ኢየሱስ በከተማይቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን እየተናገረ እንደሆነ ገልጽ ማድረግ ትችላላችሁ፡ "እናንተ ነቢያትን የገደላችሁ እና ወደ እናንተ የተላኩትን በድንጋይ የወገራችሁ ህዝቦች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እናንተ የተላኩትን

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ወደ እናንተ የላካቸውን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ምን ያህል አብዝቼ ፈለግሁ

"እኔ እጅግ አብዝቼ ፈለግሁ።" ይህ ጉልህ ማድረግ እንጂ ጥያቄ አይደለም።

ልጆችሽን ለመሰብሰብ

የኢየሩሳሌም ሰዎች የተገለጹት የእርሷ "ልጆች" ተደርገው ነው። "የአንቺን ሕዝብ ለመሰብሰብ" ወይም "የኢየሩሳሌምን ሰዎች ለመሰብሰብ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

ዶሮ ጫጩቶቿን ከክንፎቿ ስር እንደምትሰበስብ

ይህ የሚገልጸው ዶሮ እንዴት ጫጩቶቿን በክንፎችዋ ሸፍና ከጥፋት እንደምትጠብቅ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

ቤታችሁ ወና ሆኖል

ይህ ወደፊት በቶሎ ለሚሆን ነገር ትንቢት ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ሰዎች መጠበቁን አቁሟል፣ ስለዚህም ጠላት ሊያጠቃቸው እና ሊያባርራቸው ይችላል ማለት ነው። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) እግዚአብሔር እነርሱን ይበትናቸዋል። "እግዚአብሔር ይተዋችኋል" ወይም 2) ከተማቸው ባዶ ትሆናለች። "ቤታችሁ ወና ይሆናል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህ እስክትሉ ድረስ እኔን አታዩኝም

"እንዲህ የምትሉበት ጊዜ እስኪመጣ ድረስ እኔን አታዩኝም" ወይም "በሚቀጥለው ጊዜ እኔን ስታዩ፣ እንዲህ ትላላችሁ"

የጌታ ስም

እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው የሚያመለክተው የጌታን ሀይል እና ስልጣን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

---

## Chapter 14

### Luke 14:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ የሆነው በሰንበት ሲሆን፣ ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት ውስጥ ነው። ቁጥር 1 ቀጥሎ ለሚከናወነው ትእይነት የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንድ ሰንበት እንዲህ ሆነ

ይህ አዲስ ትዕይንትን ያመለክታል። (የአዲስ ትዕይንት ትውውቅ የሚለውን ይመልከቱ)

እንጀራ ለመብላት

"ለመብላት" ወይም "ለምሳ/ለምግብ።" እንጀራ የምግቡ ዋና ክፍል ነበር፣ እናም በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ገበታውን ለማመልከት ውሏል። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)

በቅርበት እርሱን ይመለከቱ

ይከሱት ዘንድ አንዳች ስህተት ይሰራ ይሆናል ብለው ይጠባበቁ

እነሆ፣ ከእርሱ ፊት አንድ ሰው ነበር

"እነሆ" የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሰው እንደሚተዋወቅ ያነቃናል። ቋንቋችሁ ይህንን የሚገልጽበት መንገድ ሊኖረው ይችላል። እንግሊዝኛው "በዚያ በእርሱ ፊትለፊት አንድ ሰው ነበር" የሚለውን ይጠቀማል። (አዲስ እና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

በእብጠት የሚሰቃይ

x

### Luke 14:4

ነገር ግን እነርሱ ዝም አሉ

የሃይማኖት መሪዎቹ የኢየሱስን ጥያቄ መመለስ አልፈቀዱም።

ስለዚህ ኢየሱስ ሰውየውን ያዘው

"ስለዚህ ኢየሱስ በእብጠት በሽታ የሚሰቃየውን ሰው ይዞ ፈወሰው"

ከእናንተ ማናችሁ ልጅ ወይም በሬ ያለው… ፈጥኖ አያወጣውም?

ኢየሱስ ጥያቄውን የተጠቀመበት እነርሱ በሰንበት ቀንም ቢሆን እንኳን ልጃቸውን ወይም በሬያቸውን እንደሚረዱ እንዲያምኑ ስለፈለገ ነው። ስለዚህ፣ ለእርሱ ሰዎችን በሰንበትም ቢሆን መፈወስ ትክክል ነበር። "ከእናንተ መሃል ልጅ ወይም በሬ ቢኖረው…በእርግጥ ፈጥናችሁ ታወጡታላችሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

### Luke 14:7

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢየሱስ ምሳ በጋበዘው ፈሪሳዊው ቤት ከነበሩ እንግዶች ጋር መናገሩን ቀጠለ።

ተጋብዘው የነበሩ

እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑ እና ይህን በአድራጊ ዐረፍተ ነገር መግለጹ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። "ከፈሪሳዊያን አለቆች አንዱ ወደ ግብዣ የጠራቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የክብር ወንበር

"ለተከበሩ ሰዎች የተዘጋጀ ወንበር" ወይም "ከፍ ላሉ ሰዎች የተዘጋጁ ወንበሮች"

አንድ ሰው በሚጋብዝህ ወቅት

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ሰው በሚጋብዝህ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ በ…ጊዜ….በዚያ አንተ…አንተን ይልሃል….አንተን ልቀቅ

በእነዚህ ስፍራዎች "አንተ" የሚሉት ተውላጠ ስሞች ነጠላ ቁጥር ናቸው። ኢየሱስ በዚያ የተሰበሰቡትን የሚያናግራቸው እያንዳንዳቸውን በግለሰብ ደረጃ እንደሚናገር አድርጎ ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)

ምናልባት ከአንተ ይልቅ የከበረ ሰው ተጠርቶ ይሆናል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ምናልባት ደጋሹ ከአንተ ይልቅ የተከበረ ሰው ጋብዞ ሊሆን ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሁለታችሁም

በዚህ ስፍራ "እናንተ" የሚለው የሚያመለክተው አንድን የክብር ስፍራ የሚፈልጉ ሁለት ሰዎችን ነው።

በፍርሃት

"ታፍራለህ ደግሞም"

### Luke 14:10

አያያዥ ሃሳብ፡

ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት ለሚገኙ ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል።

በምትጋበዝበት ወቅት

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። " አንድ ሰው በሚጋብዝህ ወቀት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ዝቅተኛ የሆነ ስፍራ

"ዝቅ ያለ ደረጃ ላለው ሰው የተዘጋጀ ስፍራ/መቀመጫ"

ወደ ላይ ከፍ በል

"የከበሩ ሰዎች/ታላላቆች ወደተቀመጡበት ወንበር ሂድ"

በዚህን ጊዜ ትከበራለህ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በዚይን ጊዜ የጋበዘህ ሰው ያከብርሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ራሱን የሚያከብር

"ራሱን ከፍ የሚያደርግ" ወይም "ከፍ ባለ ስፍራ የሚያስቀምጥ"

ትሁት የሚያደርግ

"ራሱን ትሁት የሚያደርግ" ወይም "ከፍ ከፍ ይደረጋል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሊጻፍ ይችላል። "እግዚአብሔር ያከብረዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ራሱን ዝቅ የሚያደርግ
"ራሱን ዝቅ ለማድረግ የሚፈቅድ" ወይም "ራሱን ዝቅ ባለ ስፍራ የሚያስቀምጥ"
ከፍ ይደረጋል
"ይከብራል" ወይም "ከፍ ያለ ስፍራ ይሰጠዋል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር ከፍ ያደርገዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 14:12
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት መናገሩን ቀጥሏል፤ ነገር ግን የሚናገረው በቀጥታ ለጋባዡ ነበር።
እርሱ የጋበዘው ሰው
"ቤቱ ግብዣ የጠራውን ፈሪሳዊ"
አንተ ስትሰጥ
"አንተ" የሚለው ነጠላ ቁጥር ነው፤ ምክንያቱም ኢየሱስ በቀጥታ የሚናገረው ለጋበዘው ፈሪሳዊ ነው። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)
አትጥራ/አተጋብዝ
ይህ ምናልባት እነዚህን ሰዎች ፈጽሞ መጋበዝ አይችሉም ማለት ላይሆን ይችላል። ሌሎችንም/ድሆችንም ደግሞ መጋበዝ ነበረባቸው ማለት ይመስላል። "…ብቻ አትጋብዝ" ወይም "ሁሌም…ብቻ አትጋብዝ"
ምናልባት እነርሱ
"ምክንያቱም እነርሱ"
በተራቸው ይጋብዙሃል
"ወደ እራት ወይም ግብዣ ይጠሩሃል"
መልሶ ይከፍልሃል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "በዚህ መንገድ መልሰው ይከፍሉሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 14:13
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ እርሱን ቤቱ ለጋበዘው ፈሪሳዊ መናገሩን ይቀጥላል
Luke 14:15
አጠቃላይ መረጃ፡
በማዕድ ከተቀመጡት መሃል አንዱ ከኢየሱስ ጋር ተነጋገረ እናም ኢየሱስ ለእርሱ በግብረገባዊ ምሳሌ ምላሽ ሰጠው። (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእነርሱ መሃል በማዕድ ከተቀመጡት አንዱ
ይህ አዲስ የሆነ አንድ ሰውን ያስተዋውቃል። (አዲስ እና ነበር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ የተባረከ ነው
ሰውየው ስለ አንድ የተለየ ሰው እየተናገረ አይደለም። "እርሱ የተባረከ ነው" ወይም "ይህ ለእያንዳንዱ እንዴት መልካም ነው"
ከዚህ እንጀራ የሚበላ እርሱ
"እንጀራ" የሚለው ቃል የዋለው በአጠቃሌ መዕዱን ለማመልከተ ነው። "ከዚህ ማዕድ የሚበላ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ስኔክቲክ/የነገሩን ስያሜ ከፊሉን በመውሰድ መላውን ነገር መግለጽ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን ኢየሱስ እንዲህ አለው
ኢየሱስ ግብረ ገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ። (ግብረ ገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሰው ትልቅ እራት አዘጋጅቶ ብዙዎችን ጋበዘ
አንባቢው ምናልባት የዚያ ሰው አገልጋዮች መዕደስ እንዳዘጋጁ እና እንግዶችን እንደጋበዙ መገመት መቻል ይኖርበታል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሰው
ይህ ሀረግ ስለማንነቱ ምንም መረጃ ስላልሰጠ ሰው ማጣቀሻ መንገድ ነው።
ብዙዎችን ግብዣ ጠራ
"ብዙ ሰዎች ጋበዘ" ወይም "ብዙ እንግዶች ጠራ"
Luke 14:18
አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ግብረገባዊ ምሳሌውን መናገሩን ቀጠለ።

አጠቃላይ መረጃ፡
የተጋበዙት ሰዎች ሁሉ ለአገልጋዩ ወደ ግብዣው ሊመጡ የማይችሉባቸውን ምክንጠቶች ሰጡ።
ምክንያት መስጠት/ማቅረብ
"ወደ እራት መምጣት ያልቻሉበትን መናገር"
የመጀመሪያው እንዲህ አለው… ሌላው እንዲህ አለ… ሌላው ሰው እንዲህ አለ
አንባቢያን፣ እነዚህ ሰዎች በቀጥታ ጌታቸው ለላከው አገልጋይ እንደተናገሩ መገንዘብ መቻል ይኖርባቸዋል (ሉቃስ 14፡17) ። "የመጀመሪያው እንዲህ ሲል መልዕክት ላከ…ሌላው እንዲህ ሲል መልዕክት ላከ… ሌላውም ሰው እንዲህ ሲል መልዕክት ላከ" ወይም "የመጀመሪያው አገላጋዩ እንዲህ እንዲል ነገረው…ሌላኛው አገልጋዩ እንዲህ እንዲል ነገረው… ሌላው ሰው አገልጋዩ እንዲህ እንዲል ነገረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
እባክህ ይቅር በለኝ
"እባክህ ይቅርታ አድርግልኝ" ወይም "እባክህን ይቅርታዬን ተቀበል"
አምስት ጥማድ በሬ
በሬዎች የእርሻ መሳሪያ ለመሳብ/ለማረስ በጥንድ ይጠመዳሉ። "10 በሬዎች በእርሻዬ ላይ ተጠምደዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ሙሽራ ነኝ
በቋንቋችሁ የተለመደውን አገላለጽ ተጠቀሙ። አንዳንድ ቋንቋዎች "አግብቻለሁ" ወይም "ሚስት ወስጃለሁ" ሊሉ ይችላሉ።
Luke 14:21
ተቆጣ
"ግብዣ በጠራቸው ሰዎች ተቆጣ"
ወደዚህ አምጧቸው
"እራት እንዲበሉ ወደዚህ ጥሯቸው"
አገልጋዩ እንዲህ አለ
በውስጠ ታዋቂነት ያለውን አገልጋዩ ጌታው ያዘዘውን ማድረጉን የሚያሳየውን በግልጽ መጻፍ አስፈለዘጊ ሊሆን ይችላል። "አገልጋዩ ወደ ውጭ ሄዶ ያን አድርጎ ተመልሶ መጥቶ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ያዘዝከው ተደርጓል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "አንተ ያዘዝከውን አድርጌያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 14:23
አያያዥ ሃሳብ፡
ኢየሱስ ግብረ ገባዊ ምሳሌውም መናገር ጨረሰ።
አውራ መንገዶች እና መተላለፊያዎች
ይህ የሚያመለክተው መንገዶችን እና ከከተማ ውጭ ያሉ መተላለፊያዎችን ነው። "አውራ መንገዶች እና ከከተማ ውጭ የሚገኙ መተላለፊያ መንገዶች"
ወደ ውስጥ እንዲመጡ ግድ በሏቸው
"እንዲመጡ ግድ በሏቸው"
እነርሱን ግድ በሏቸው
"እነርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማናቸውንም አገልጋዮቹ የሚያገኟቸውን ሰዎች ነው። "ያገኛችኋቸውን ሁሉ ግድ በሏቸው"
ቤቴ ይሞላ ዘንድ
"ሰዎች ቤቴን ይሞሉ ዘንድ"
እኔ እናንተን እላችኋለሁ
"እናንተ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው፤ ስለዙህ ይህ ማንን እንደሚያመለክት ግልጽ አይደለም። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች ይመልከቱ)
እነዚያ ወንዶች/ሰዎች
እዚህ ስፍራ "ወንዶች" የሚለው "አዋቂ ወንዶች" ማለት እንጂ በአጠቃላይ ሰዎችን ማለት አይደለም።
የተጋበዙ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "እኔ የጋበዝኳቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እራቴን ይበላሉ
"ያዘጋጀሁትን እራት ይበላሉ"

Luke 14:25

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢየሱስ ከእርሱ ጋር ይጓዝ የነበረውን የተሰበሰበውን ሕዝብ ማስተማር ጀምሯል።

ማንም ወደ እኔ መጥቶ የራሱን አባት ባይጠላ ... የእኔ ደቀመዝሙር ሊሆን አይችልም

እዚህ ስፍራ "መጥላት" የሚለው ሰዎች ሌለውን አስበልጠው ለኢየሱስ ለሚያሳዩት አነስ ያለ ፍቅር በግነት የቀረበ አገላለጽ ነው። "ማንም ወደ እኔ መጥቶ አባቱን ከሚወደው በላይ እኔን ካልወደደ...እርሱ የእኔ ደቀመዝሙር መሆን አይችልም" ወይም "አንድ ሰው አባቱን ከሚወደው በላይ እኔን መውደድ ከቻለ ብቻ ...እርሱ የእኔ ደቀመዝሙር መሆን ይችላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሽት እና አጠቃላይ አስተያየት እንደዚሁም ጥንድ አሉታ የሚሉትን ይመልከቱ)

የራሱን መስቀል የማይችል እና ከእኔ ኋላ የማይመጣ ደቀመዝሙሬ ሊሆን አይችልም

ይህ በአዎንታዊ ግሶች ሊገለጽ ይችላል። "ማንም የእኔ ደቀመዝሙር መሆን ቢፈልግ፣ የራሱን መስቀል ሊሸከም እና ሊከተለኝ ይገባል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ አሉታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የራሱን መስቀል ተሸክሞ

ኢየሱስ እያንዳንዱ ክርስቲያን መሰቀል አለበት ማለቱ አይደለም። ሮማውያን ብዙውን ጊዜ ለሮም ያላቸውን ታማኝነት እንዲያሳዩ ወንጀለኛ ሰዎች ራሳቸው የሚሰቀሉበትን መስቀል እንዲሸከሙ ያደርጉ ነበር። የዚህ ዘይቤ ትርጉም እነርሱም ለእግዚአብሔር መገዛት እና የኢየሱስ ደቀመዝሙር ለመሆን መከራ ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን እንደሚገባቸው ያሳያል። (ዘይቤያዊ አነጋገር እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

Luke 14:28

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ደቀመዝሙር ለመሆን የሚጠይቀውን ዋጋ ማወቅ እንደሚያስፈልግ ማብራራቱን ቀጥሏል።

ከእናንተ መሃል ህንጻ ለመሥራት የሚፈልግ አስቀድሞ ቁጭ ብሎ ለመደምደም የሚያስፈልገውን ዋጋ የማያሰላ ማን ነው?

ኢየሱስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመበት ሰዎች አንድን ሥራ ለመሥራት ለሥራው የሚያስፈልገውን እንደሚያሰሉ ለማሳየት ነው። "አንድ ሰው ህንጻ ማነጽ ቢፈልግ፣ በመጀመሪያ ተቀምጦ ህንጻውን ሊደመደምበት የሚያበቃው ገንዘብ እንዳለው ይወስናል።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ህንጻ

ይህ ትልቅ ህንጻ ሊሆን ይችላል። "ትልቅ ህንጻ" ወይም "ጎላ ብሎ የሚያይ ግንብ"

ካልሆነ

ተጨማሪ መረጃ መስጠት ሊረዳ ይችላል። "አስቀድሞ ዋጋውን ካላወቀ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

መሰረቱን ሲጥል

"መሰረቱን ሲገነባ" ወይም "የህንጻውን የመጀመሪያ ክፈል ሲያጠናቅቅ"

መጨረስ/ማጠናቀቅ አልቻለም

መጨረስ ያልቻለው በቂ ገንዘብ ስለሌለው መሆኑ ይታወቃል። እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ለመጨረስ በቂ ገንዘብ አልነበረውም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 14:31

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ደቀመዝሙር ለመሆን የሚጠይቀውን ዋጋ ማወቅ አስፈላጊ እንደሆነ ማብራራቱን ቀጥሏል።

ወይም

ኢየሱስ ይህን ቃል የተጠቀመው ሰዎች አንድ ውሳኔ ከማድረጋቸው አስቀድሞ ውሳኔው የሚጠይቀውን ዋጋ ሌላ ሁኔታ ለማስተዋወቅ ነው።

አስቀድሞ የማይቀመጥ እና... ከሰዎቹ/አማካሪዎቹ ምክር የማይቀበል... የቱ ንጉሥ ነው?

ኢየሱስ የተሰበሰበውብ ሕዝብ ዋጋ ስለመተመን ለማስተማር ሌላ ጥያቄ ያነሳል። "አንድ ንጉሥ... በመጀመሪያ ተቀምጦ... ከአማካሪዎቹ ምክር እንደሚቀበል ታውቃላችሁ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ምክር ይቀበላል

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1)"በጥንቃቄ ማሰብ" ወይም 2) "አማካሪዎቹን መስማት"

አስር ሺህ...ሃያ ሺህ

"10,000...20,000" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ካልሆነ

ተጨማሪ መረጃዎችን መግለጽ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "ሌላውን ንጉሥ ለማሸነፍ እንደማይችል ከተገነዘበ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰላም ሁኔታዎች

"ጦርነቱን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጉ" ወይም "ጦርነቱን ለማጠናቀቅ ሌላው ንጉሥ እርሱ እንዲያደርግ የሚፈልገው"

ከእናንተ መሃል ማንም ያለውን ሁሉ የማይተው የእኔ ደቀመዝሙር መሆን አይችልም

ይህ በአዎንታዊ ግሶች ሊገለጽ ይችላል። "ያላችሁን ሁሉ የምትተዉ ብቻ ደቀመዝሙሬ መሆን ትችላላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ አሉታ የሚለውን ይመልከቱ)

ያለውን ሁሉ የሚተው

"ያለውን ሁሉ ከኋላው የሚጥል"

Luke 14:34

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ የተሰበሰበውን ህዘውብ ማስተማሩን አጠናቀቀ።

ጨው መልካም ነው

"ጨው ጠቃሚ ነው።" ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ሊሆኑ ለሚፈልጉ ትምህርት እየሰጠ ነው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እንዴት ዳግም ጣዕሙን ሊያገኝ ይችላል?

ኢየሱስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው የተሰበሰበውን ሕዝብ ለማስተማር ነው። "ዳግም ጣዕም ሊሰጠው አይችልም።" ወይም "ማንም ዳግም ጣዕም ሊሰጠው አይችልም።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

የፍግ ክምር

ሰዎች አትክልት ስፍራዎችን እና እርሻን ለማልማት ማዳበሪያ ይጠቀማሉ። ጣዕም የሌለው ጨው አንዳች ጥቅም የለውም፤ ከፍግ ጋር ለመደባለቅ እንኳን አይጠቅምም። "የማዳበሪያ ቁልል" ወይም "ማዳበሪያ/ፍግ"

ወደ ውጭ ይጣላል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገል ሊጻፍ ይችላል። "ወደ ውጭ ይጥሉታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚሰማ ጆሮ ያለው እርሱ ይስማ

በአንዳንድ ቋንቋዎች ሁለተኛ መደብን መጠቀም ይበልጥ ተፈጥሯዊ ሊሆን ይችላል። "እናንተ መስሚያ ጆሮ ያላችሁ ስሙ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚሰማ ጆሮ ያለው እርሱ

ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እያንዳንዱ" ጤናማ ጆሮ እስካላቸው ድረስ፣ ወይም 2) "የመረዳት ችሎታ ያለው ሁሉ፣" እግዚአብሔርን ለመስማት ፈቃደኛ የሆኑትን ያሚያመለክት ነው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ ይስማ

"እርሱ በሚገባ መስማት አለበት" ወይም "እርሱ እኔ ለምናገረው ትኩረት መስጠት አለበት"

---

## Chapter 15

Luke 15:1

አጠቃላይ መረጃ፡

ይህ መቼ እንደተፈጸመ አናውቅም፤ ይህ የሆነው አንድ ዕለት ኢየሱስ እያስተማረ ሳለ ነው።

አሁን

የአዲስ ተዕይንት ጅማሬ ምልክቶችን ያሳያል። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ግበር ሰብሳቢዎች በሙሉ

በርካታ ግብር ሰብሳቢዎች እንደነበሩ በግነት የተገለጸ ነው። "ብዙ ግብር ሰብሳቢዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሽት እና አጠቃላይ አስተያየት

የሚሉትን ይመልከቱ)
ይህ ሰው ኃጢአተኞችን ይቀበላል
"ይህ ሰው ኃጢአተኞች እንዲቀርቡት ይፈቅዳል" ወይም "ይህ ሰው ከጢአተኞች ጋር ህብረት ያደርጋል"
ይህ ሰው
ስለ ኢየሱስ እየተናገሩ ነበር።
ከእነርሱ ጋር እንኳን ይበላል
እንኳን/ጭምር የሚለው ኢየሱስ ኃጢአተኞች ወደ እርሱ እንዲቀርቡ መፍቀዱ እጅግ መጥፎ ነገር ነው ብለው ማሰባቸውን ያሳያል፤ ይልቁንም ከእነርሱ ጋር መመገቡ ከዚያም የከፋ ነገር እንደሆነ ያስቡ ነበር።
Luke 15:3
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ብዙ ምሳሌዎችን መናገር ጀመረ። እነዚህ ማንም ሰው ሊገጥመው የሚችላቸው ግብረገባዊ ምሳሌዎች መላምታዊ ሁኔታዎች ናቸው። እነዚህ ስለተለያዩ ሰዎች የሚናገሩ አይደለም። የመጀመሪያው ግብረገባዊ ምሳሌ አንድ ሰው ከበጎቹ አንዱ ቢጠፋ ያ ሰው ምን እንደሚያደርግ የሚገልጽ ነው። (ግብረገባዊ ምሳሌዎች እና መላምታዊ ሁኔታዎች የሚሉትን ይመልከቱ)
ለእነርሱ
እዚህ ስፍራ "እነርሱ" የሚለው የሚያመለክተው የሃይማኖት መሪዎችን ነው።
ከእናንተ መሃል …እስኪያገኘው ድረስ …የማይፈልገው ማን ነው?
ኢየሱስ ጥያቄውን የተጠቀመበት፣ ሰዎቹ ከበጎቻቸው መሃል አንዱ ቢጠፋ ፍለጋ እንደሚሄዱ ሊያሳስባቸው ነው። "እናንተ እያንዳንዳችሁ … እስክታገኙት ድረስ… በእርግጥ ፍለጋ ታደርጋላችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
መቶ በጎች ቢኖሩት፣ ከእናንተ መሃል ማን
ምሳሌያዊ አነጋገሩ "ከእናንተ መሃል ማን" በሚል እንደመጀመሩ፣ አንዳንድ ቋንቋዎች ምሳሌያዊ አነጋገሩን በሁለተኛ መደብ ይቀጥላል። "መቶ በጎች ቢኖራችሁ፣ ከእናንተ መሃል ማን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
መቶ…ዘጠና ዘጠኝ
"100… 99" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 15:6
ወደ ቤቱ ስመለስ
"የበጉ ባለቤት ወደ ቤቱ ስመለስ" ወይም "ወደ ቤት ሲመለስ።" የበጉን ባለቤት በቀደመው ቁጥር እንዳደረጋችሁት አመልክቱ።
ምንም እንኳን
"በተመሳሳይ መንገድ" ወይም "እረኛው እና ወዳጆቹ እንደዚሁም ጎረቤቶቹ ደስ እንደሚሰኙ"
በሰማይ ደስታ ይሆናል
"በሰማይ ያሉት ሁሉ ደስ ይላቸዋል"
ንስሃ የማያስፈልጋቸውን ዘጠና ዘጠኙን ጻድቃን ሰዎች
ኢየሱስ ፈሪሳውያኑ ንስሃ እንደማያስፈልጋቸው ማሰባቸው ስህተት መሆኑን በምጸት ይናገራል። የእናንተ ቋንቋ ይህን ሃሳብ ለመግለጽ የተለያ መንገድ ሊኖረው ይችላል። "እንደ እናንተ የመሰሉ ጻድቃን ነን ብለው የሚያስቡ ንስሃ መግባት የማይፈልጉ ዘጠና ዘጠኝ ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚለውን ይመልከቱ)
ዘጠና ዘጠኝ
"99" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 15:8
አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ሌላ ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ይጀምራል። ይህኛው 10 የብር ሳንቲሞች ስላላት ሴት ነው።
ወይም የትኛዋ ሴት…ሻማ ለኩሳ… እስክታገኘው ድረስ ተግታ አትፈልግም?
ኢየሱስ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመበት ሰዎቹ የብር ሳንቲም ቢጠፋባቸው፣ ያንን በእርግጥ በትጋት እንደሚፈልጉ ለማስታወስ ነው። "የትኛዋም ሴት…በእርግጥ ፋኖስ ትለኩሳለች… እናም እስክታገኘው ድረስ በትጋት የጠፋባትን ትፈልጋለች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
ባታገኘው
ይህ መላምታዊ ሁኔታ እንጂ በዕውን ስላለች አንዲት ሴት የሚናገር ታሪክ አይደለም። አንዳንድ ቋንቋዎች ይህን የሚያሳዩበት መንገድ አላቸው። (መላምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደዚሁም
"በተመሳሳይ መንገድ" ወይም "ሰዎች ከሴቲቱ ጋር ደስ እንደሚላቸው" ንስሃ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ "አንድ ኃጢአተኛ ንስሃ በሚገባበት ጊዜ"
Luke 15:11
አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ሌላ ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ። ይህም አባቱን ከሚደርሰው ውርስ ድርሻውን ስለጠየቀው ወጣት ነው። (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሰው
ይህ አዲስ ገጸባህሪን በግብረገባዊ ምዋሌው ውስጥ ያስተዋውቃል። አንዳንድ ቋንቋዎች "አንድ ሰው ነበረ" ብለው ይጀምራሉ። (አዲስ እና ነባር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
ስጠኝ/አምጣ
ልጁ አባቱ ወዲያውኑ ድርሻውን እንዲሰጠው ፈልጓል። ወዲያውኒ ሊደረግ የሚፈልገውን በትዕዛዝ መልክ መግለጽ የሚችል ቃል በቋንቋ ካለ ያንን መልክ መጠቀም አለባችሁ።
ለእኔ የሚደርሰኝን የሀብት መጠን
"በምትሞትበት ጊዜ ልታወርሰኝ ያቀድከውን የሀብት መጠን"
በእነርሱ መሃል
"በሁለቱ ልጆቹ መሃል"
Luke 15:13
እርሱ ያለውን ሁሉ/ድርሻው ሸክፈ
"ያሉትን ነገሮች ጠቀለለ" ወይም "ያሉትን ነገሮች በቦርሳው ውስጥ አደረገ"
በንዝህላልነት መኖር
"ድርጊቶች ስለሚያስከትሉት ውጤት ባለማሰብ መኖር" ወይም "ልቅ አኗኗር"
አሁን
x
Luke 15:15
እርሱ ሄደ
"እርሱ" የሚለው ቃል ታናሹን ልጅ ያመለክታል።
ለ…ራሱን ተቀጣሪ አደረገ
"ከ…ዘንድ ሥራ ያዘ" ወይም "ለ…መሥራት/ማገልገል ጀመረ"
ከዚያ አገር ነዋሪዎች መሃል አንዱ
"የዚያ አገር ሰው"
አሳሞችን ለመመገብ
"ለሰውየው አሳሞች ምግብ ለመስጠት"
ደስ ብሎት በተመገበ ነበር/ሊያገኝ ተመኘ
"አግኝቶ ሊበላ በጣም ይፈልግ ነበር።" ይህ የሆነው በመራቡ ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ነው። እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። "ቢያገኝ በደስታ እስኪመገብ ድረስ በጣም ተርቦ ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰብል ግልፋፊ
እነዚህ ዐሰር ናቸው። "የባቄላ ግልፋፊ" ወይም "የባቄላ/በቆሎ ልባስ" በሚለው ወስጥ እንደሚገኘው። (ያልታወቀውን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 15:17
ወደ ልቡ ተመለሰ
የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም፣ ከፍ ያለ ስህተት እንደፈጸመ እና እውነታው ምን እንደነበረ አስተዋለ። "በግልጽ ሁኔታውን ተረዳ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ምን ያህሉ የአባቴ ተቀጣሪ ሰራተኞች ከሚያስፈልጋቸው በላይ ምግብ ያገኛሉ
ይህ የማጋነኑ አንዱ ክፍል ነው፤ እናም ጥያቄ አልነበረም። "የአባቴ አጋልጋዮች ሁሉ ከሚያስፈልጋቸው በላይ ምግብ አላቸው"
ከረሃብ የተነሳ መሞት
ይህ ምናልባት ማጋነን አይደለም። ወጣቱ ሰው በእርግጥም ተረቧል።
በሰማይ ፊት በደልኩ
የአይሁድ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ "እግዚአብሔር" የሚለውን ቃል "ሰማይ" በሚል ተክተው ይጠቀማሉ። "በእግዚአብሔር ፊት በደልኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት

የሚለውን ይመልከቱ)
ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም
"ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ልጄ ብለህ ልትጠራኝ አይገባኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ከተቀጣሪ ሰራተኞችህ እንዱ አድርገኝ
"እንደ አንድ አገልጋይህ ቅጠረኝ" ወይም "ቅጠረኝ እኔም ከሰራተኞችህ እንደ አንዱ እሆናለሁ።" ይህ ጥያቄ ነው፤ ትዕዛዝ አይደለም። በዩቢዲ ውስጥ እንደሚገኘው "እባክህ" የሚለው ቢጨመር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።
Luke 15:20
ስለዚህም ታናሹ ልጅ ወደ አባቱ ተመለሰ
"ስለዚህ ከሄደበት አገር ወደ አባቱ ተመለሰ።" "ስለዚህ" የሚለው ቃል የሆነውን ድርጊት አስቀድሞ በሆነው ሌላ ነገር ምክንያት እንደሆነ ያመለክታል። በዚህ ሁኔታ፣ ወጣቱ ሰው ሲቸግረው ወደ ቤት ለመመለስ ወሰነ።
ገና ከሩቅ ስፍራ ሳለ
"ገና ከቤቱ ሩቅ ስፍራ ሳለ" ወይም "ገና ከአባቱ ቤት ሩቅ ስፍራ ሳለ"
በርህራሄ ቀረበው
"ለእርሱ ርህራሄ ነበረው" ወይም "እጅግ ከልቡ ይወደው ነበር"
አቅፎ ሳመው
አባቱ ይህን ያደረገው እንደሚወደው ለልጁ ለማሳየት እና ልጁ ተመልሶ ቤት በመምጣቱ ስለተደሰተ ነበር። ሰዎች አባት ወንድ ልጁን ማቀፉ ወይም መሳሙ እንግዳ ነገር ወይም ስህተት ነው ብለው የሚያስቡ ከሆነ፣ በባህላችሁ አባቶች ለወንድ ልጃቸው ያላቸውን ፍቅር የሚገልጹበትን መንገድ ተክታችሁ መተርጎም ትችላላችሁ። "እርሱን በፍቅር ተቀበለው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
በሰማይ ፊት መበደል
የአይሁድ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ "እግዚአብሔር" የሚለውን ቃል "ሰማይ" በሚል ተክተው ይጠቀማሉ። ይህ በሉቃስ 15፡18 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ይመልከቱ። "እግዚአብሔርን በደልኩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊተረጎም ይችላል። ተመሳሳይ የሆነው ሀረግ በሉቃስ 15፡18 ላ እንዴት እንደ ተተረጎም ይመልከቱ።"ልጄ ብለህ ልትጠራኝ አይገባኝም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 15:22
ምርጥ ካባ/ልብስ
"በቤት ካለው ምርጡን ልብስ።" "ምርጡን ኮት" ወይም "ምርጡን ጨርቅ"
ለጣቱ ቀለበት አድርጉለት
ቀለበት ወንዶች ከጣታቸው መሃል በአንዱ የሚያጠልቁት የስልጣን ምልክት ነበር።
ነጠላ ጫማ
በዘመኑ ባለጸጋ ሰዎች ነጠላ ጫማ ያደርጉ ነበር። ሆኖም፣ በብዙ ባህሎች የዚህ ዘመናዊ አቻ የሆነው "ጫማ" ነው።
የሰባ ጥጃ
ጥጃ ገና በሬ ያለሆነ ነው። ሰዎች ጥጃዎች በሚገባ እንያድጉ ጥሩ አድረገው ይቀለቀቧቸዋል፤ ከዚያም የተለየ ድግስ ሲኖርባቸው ይመገቧቸዋል/አርደው ይበሏቸዋል። "የሰባውን ፍሪዳ" ወይም "በሚገባ ያባነውን ወይፈን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አረዱ
ለምን ፍሪዳው እንደታረደ በውስጠታዋቂነት ያለው መረጃ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "አርዳችሁ ስሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ልጄ ሞቶ ነበር፣ አሁን በሕይወት አለ
ይህ ዘይቤ የሚናገረው የኮበለለውን ልጅ እንደሞተ አድርጎ ነው። "ልጄ ከሞተ በኋላ ዳግም ህያው እንደሆነ ይቆጠራል" ወይም "ልጄ ሞቶ እንደነበረ እና አሁን ዳግም ህያው እንደሆነ ይሰማኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ጠፍቶ ነበር፣ አሁን ተገኘ
ይህ ዘይቤ የሚናገረው የልጁን መኮብለል/መሄድ እንደጠፋ አድርጎ ነው። "ልጄ ጠፍቶ ነበር አሁን ግን አገኘሁት" ወይም "ልጄ ጠፍቶ ነበር አሁን ቤት ተመለሰ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 15:25
አሁን
እዚህ ስፍራ ይህ ቃለ የዋለው በዋናው የታሪክ መስመር ማቆሚያ ለማበጀት ነው። እዚህ ስፍራ ኢየሱስ ስለ ታላቁ ልጅ አዲሱን የታሪኩን ክፍል መናገር ይጀምራል።
ውጭ በመስክ/በእርሻ
እርሱ ውጭ በመስክ ላይ እንደነበረ ተጠቅሷል፣ ምክንያቱም በዚያ በሥራ ላይ ነበር። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከአገልጋዮቹ አንዱ
እዚህ ስፍራ "አገልጋይ" ተብሎ የተተረጎመው ቃል በቀጥታ "ልጅ" በሚል ተተርጉሟል። ይህ አገልጋዩ በጣም ወጣት እንደሆነ ያመለክታል።
እነዚህ ነገሮች ምን ይሆናሉ
"ምን እየሆነ ነበር"
የሰባ ጥጃ
ጥጃ ገና በሬ ያለሆነ ነው። ሰዎች ጥጃዎች በሚገባ እንያድጉ ጥሩ አድረገው ይቀለቀቧቸዋል፤ ከዚያም የተለየ ድግስ ሲኖርባቸው ይመገቧቸዋል/አርደው ይበሏቸዋል።ይህ ሀረግ በሉቃስ 15:23 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የሰባው/ምርጡ ጥጃ" "ያሰባነው ወይፈን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 15:28
እነዚህ ብዙ አመታት
"ለብዙ አመታት"
ለአንተ ባሪያ ሆንኩ
"ለአንተ እጅግ በከባዱ ሰራሁ" ወይም "ለአንተ እንደ ባሪያ በከባዱ ሰራሁ"
በፍጹም የአንተን አንዲት ህግ አልጣስኩም
"በፍጹም ከትእዛዝህ አልወጣሁም" ወይም "ሁልጊዜም አድርግ ያልከኝን ሁሉ አድርጌያለሁ"
አንዲት ትንሽ ፍየል
ትንሽ ፍየል ከሰባ ጥጃ ያነሰች እና ዋጋዋም ዝቅተኛ ነበረች። "ትንሽ ፍየል እንኳን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
የአንተ ልጅ
"ያ የአንተ ልጅ።" ትልቁ ልጅ ወንድሙን በዚህ መንገድ የሚገልጸው ምን ያህል እንደተናደደ ለማሳየት ነው።
ሀብትህን/ኑሮህን በላ
ምግብ ለገንዘብ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። አንድ ሰው ምግብን ከተመገበው በኋላ፣ ምግቡ ዳግመኛ አይበላም። ወንድሙ ከወሰደው ገንዘብ አንዳች አልተረፈም፤ ምንም ነገር አልቀረም። "ሀብትህን ሁሉ አባከነ" ወይም "ገንዝብህን ሁሉ በተነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ከጋለሞቶች ጋር
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ወንድሙ ገንዘቡን ያባከነው እንደዚህ ነው ብሎ ገምቷል፣ ወይም 2) ስለ ጋለሞቶች የተናገረው "በሄደበት ሩቅ አገር" ወንድሙ የሰራቸውን የኃጢአተኝነት ድርጊቶች ለማጋነን ነው (ሉቃስ 15፡13)። (ኩሸት እና አጠቃላ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
የሰባ ጥጃ
ጥጃ ገና በሬ ያለሆነ ነው። ሰዎች ጥጃዎች በሚገባ እንያድጉ ጥሩ አድረገው ይቀለቀቧቸዋል፤ ከዚያም የተለየ ድግስ ሲኖርባቸው ይመገቧቸዋል/አርደው ይበሏቸዋል።ይህ ሀረግ በሉቃስ 15:23 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። "የሰባው/ምርጡ ጥጃ" "ያሰባነው ወይፈን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 16


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Luke 16:1

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ ሌላ ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ፡፡ ይህም ስለ አንድ ጌታ እና ገንዘቡን ስለሚያበድርለት አስተዳዳሪ ነበር፡፡ ይህም ቢሆን በሉቃስ 15፡3 ውስጥ የጀምረው ተመሳሳይ ታሪክ ክፍል እና በተመሳሳይ ቀን የተናገረው ነው፡፡ (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን ይመልከቱ)

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ

ምንም እንኳን የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ተሰብስቦ ከሚያደምጠው ሕዝብ ውስጥ ቢሆኑም፣ የመጨረሻው ክፍል ፈሪሳውያንን እና ጸሐፍትን ያመለክታል፡፡

አንድ ባለጸጋ ሰው ነበር

ይህ በግብረገባዊ ምሳሌው ውስጥ አዲስ ገጸባህሪን ያስተዋውቃል፡፡ (አዲስ እና ነበር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ ተነገረው

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፡፡ "ሰዎች ለባለጸጋው ሰው ነገሩት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሃብቱን እያባከነ እንደሆነ

"የባለጸጋውን ሰው ንብረት በንዝህላልነት እያስተዳደረ እንደሆነ"

ይህ ስለ አንተ የምሰማው ነገር ምንድን ነው?

ባለጸጋው ሰው ጥያቄውን ያነሳው የሃብቱን አስተዳዳሪ ለመገሰጽ ነው፡፡ "እያደረግህ የምትገኘውን ሰምቻለሁ፡፡" (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 16:3

ምን ላድርግ…ምን ማድረግ ይገባኛል?

አስተዳዳሪው፣ ያሉትን አማራጮች ለመመልከት ሲል ይህንን ጥያቄ ያነሳው ለራሱ ነው፡፡ "ስለዚህ ሥራ…ማድረግ ያለብኝን ማሰብ ያስፈልገኛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይልከቱ)

አለቃዬ/ጌታዬ

ይህ የሚያመለክተው ባለጸጋውን ሰው ነው፡፡ አስተዳዳሪው ባሪያ አልነበረም፡፡ "ቀጣሪዬ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡

ለመቆፈር አቅም የለኝም

"መሬት ለመቆፈር አቅም የለኝም" ወይም "መቆፈር/ማረስ አልችልም"

ከአስተዳዳሪነት ሥራዬ ስወገድ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል፡፡ "የማስተዳደር ሥራዬን ሳጣ" ወይም "ጌታዬ የአስተዳዳሪነት ሥራዬን ሲወስድብኝ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎች በቤታቸው ይቀበሉኛል

ይህ እነዚያ ሰዎች ሥራ፣ ወይም ለኑሮ የሚያስፈልገውን ሌሎች ነገሮች እንደሚሰጡት ያመለክታል፡፡ (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 16:5

ከእርሱ አለቃ ተበዳሪዎች/ባለዕዳዎች

"የአለቃው ንብረት ብድር የነበረባቸው ሰዎች" ወይም "የእርሱ አለቃ ሀብት በእጃቸው የነበረ ሰዎች፡፡" በዚህ ታሪክ ውስጥ ተበዳሪዎች/ባለዕዳዎቹ የነበረባቸው የወይራ ዘይት እና ስንዴ ነበር፡፡

እርሱ አለ…እርሱ እንዲህ አለው

"ተበዳሪው/ባለዕዳው አለ… አስተዳዳሪው ለባለዕዳው እንዲህ አለው"

አንድ መቶ ማድጋ የወይራ ዘይት

ይህ ወደ 3,000 ሊትር የወይራ ዘይት ነው፡፡ (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን የነበረ የመጠን መለኪያ)

መቶ…ሀምሳ…ሰማንያ

"100…50…80" (ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

የውል ወረቀትህን ውሰድ

"የውል ወረቀት" አንድ ሰው ምን ያህል እንዳለበት የሚያሳይ ወረቀት ነው፡፡

አስተዳዳሪው ሌላውንም ሰው… እንዲህ አለው…ለእርሱ እንዲህ አለ

"አስተዳዳሪው ለሌላው ተበዳሪ እንዲህ አለ…ተበዳሪው/ባለዕዳው እንዲህ አለ… አስተዳዳሪው ባለእዳውን አለው

መቶ ዳውላ ስንዴ

ይህን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ትችላላችሁ፡፡ "ሃያ ሺህ ኪሎ ስንዴ" ወይም "አንድ ሺህ ቅርጫት ስንዴ" (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን የነበረ የመጠን መለኪያ)

ሰማንያ ብለህ ጻፍ

"ሰማንያ ዳውላ ስንዴ ብለህ ጻፍ፡፡" ይህን ወደ ዘመናዊ መለኪያ መለወጥ ትችላላችሁ፡፡ "አሥራ ስድስት ሺህ ኪሎ ስንዴ" ወይም "ስምንት መቶ ቅርጫት ብለህ ጻፍ"

Luke 16:8

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ ስለ ባለሃብቱ እና ሃብቱን ያበድርለት ስለነበረው አስተዳዳሪ የሚናገረውን ምሳሌ ጨረሰ፡፡ በቁጥር 9 ላይ፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስተማሩን ቀጠለ፡፡

ከዚያም ጌታው አመሰገነው

ጽሁፉ ጌታው እንዴት የአስተዳዳሪውን ድርጊት እንዳወቀ አይናገርም

አመሰገነ

"አወደሰ" ወይም "በመነልካም አየው" ወይም "ተቀበለው/አጸደቀለት"

በብልሃት አደረገ

"በዘዴ አደረገ" ወይም "ምክንያታዊ በሆነ መንገድ አደረገ"

የዚህ ዓለም ልጆች

ይህ የሚያመለክተው ስለ እግዚአብሔር ስለማያውቁ ወይም ግድ ስለማይላቸው ትክክለኛ እንዳልሆነው አስተዳዳሪ ያሉትን ነው፡፡ "የዚህ ዓለም ሰዎች" ወይም "ዓለማውያን ሰዎች"

የብርሃን ልጆች

እዚህ ስፍራ "ብርሃን" እግዚአብሔራዊ/ቅዱስ ለሆኑ ነገሮች ሁሉ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው፡፡ "የእግዚአብሔር ሰዎች" ወይም "ቅዱሳን ሰዎች" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)

እኔ ግን እላችኋለሁ

"እኔ" የሚለው የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው፡፡ "እኔ ግን እላችኋለሁ" የሚለው ሀረግ የታሪኩን ማጠቃለያ ያሳያል፤ አሁን ኢየሱስ ሰዎቹ እንዴት ታሪኩን በህይወታቸው ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ይነግራቸዋል፡፡

ጻድቅ ባልሆነው ሃብት/በዚህ ዓለም ገንዘብ ለራሳችሁ ባልንጀሮችን አፍሩ

እዚህ ስፍራ ትኩረት የተሰጠው ገንዘብን ሌሎችን ለመርዳት ስለመጠቀም ነው፡፡ "በዓለማዊ ሃብት እነርሱን በመርዳት ሰዎችን ወዳጆቻችሁ አድርጓቸው"

ጻድቅ ባልሆነ ሀብት አማካይነት

ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ኢየሱስ ገንዘብን "ጻድቅ ያልሆነ" ብሎ ሲጠራው ግነት እየተጠቀመ ነው፤ ምክንያቱም ዘላለማዊ ዋጋ የለውም፡፡ "ዘላለማዊ ዋጋ የሌለውን ገንዘብን በመጠቀም" ወይም "ምድራዊ ገንዘብን በመጠቀም" ወይም 2) ኢየሱስ ገንዘብን "ጻድቅ ያልሆነ" ብሎ በመጥራት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ይጠቀማል፤ ምክንያቱም ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ገንዘብን ትክክል ባልሆነ መንገድ ያገኙታል ወይም ጠቀሙበታል፡፡ "ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ያገኛችሁትን ገንዘብ በመጠቀም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው፡፡ (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት እና ኩሸት እንደዚሁም አጠቃላ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)

እነርሱ ይቀበሏችኋል

ይህ የሚያመለክተው 1) ገንዘባችሁን ሌሎችን ለመርዳት ባዋሉት ደስ የሚሰኝ በሰማይ ያለ እግዚአብሔር፣ ወይም 2) በገንዘባችሁ የረዳችኋቸው ወዳጆቻችሁ፡፡

ዘላለማዊ መኖሪያዎች

ይህ የእግዚአብሔር መኖሪያን፣ ሰማይን ያመለክታል፡፡

Luke 16:13

የትኛውም አገልጋይ አይችልም

"አንድ አገልጋይ አይችልም"

ሁለት ጌቶች ማገልገል

"ሁለት የተለያዩ ጌቶችን በአንድ ጊዜ ማገልገል እንደማይችል" በውስጠ ታዋቂነት ተጠቁሟል

እርሱ አንዱን …አሊያም ደግሞ እርሱ

እነዚህ ሁለት ሀረጎች በመሰረቱ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ብቸኛው እና ዋናው ልዩነታቸው በመጀሪያው ሀረግ የመጀመሪያው ጌታ ይጠላል፣ ሁለተኛው ጌታ በሁለተኛው ሀረግ ይጠላል፡፡

Luke 16:14

አጠቃላይ መረጃ፡

በቁጥር 14 ላይ ፈሪሳውያን በኢየሱስ ላይ እንዳፉዙበት የመረጃ ዳራ እንደሚጥ ይህ በእየሱስ ትምህርት ማቆሚያ/ማረፊያ ነው፡፡ በቁጥር 15 ኢየሱስ ትምህርቱን ይቀጥላል ደግሞም ለፈሪሳውያን ምላሽ ይሰጣል፡፤ (የመረጃ ዳራ የሚለውን

ይመልከቱ)
አሁን
ይህ ቃል ወደ መረጃ ዳራው ያመለክታል
ገንዘብ ወዳጅ የነበሩት
"ገንዘብ እንዲኖራቸው የሚወዱ" ወይም "ለገንዘብ በጣም ስስታም የነበሩ"
አፌዙበት
"ፈሪሳውያን በኢየሱስ ላይ አፌዙ"
እንዲህ አላቸው
"ኢየሱስ ለፈሪሳውያን እንዲህ አላቸው"
በሰዎች ፊት ራሳችሁን ትክክለኛ አድርጋችሁ ታቀርባላችሁ
"ራሳችሁን በሰዎች ፊት መልካም አድርጋችሁ ለማሳየት ትሞክራላችሁ"
እግዚአብሔር ልቦቻችሁን ያውቃል
እዚህ ስፍራ "ልቦች" የሚለው የሚያመለክተው የሰዎችን ፍላጎት ነው። "እግዚአብሔር እውነተኛ ፍላጎቶቻችሁን ያውቃል" ወይም "እግዚአብሔር ለምን እንደምታደርጉ አንቀሳቃሽ ምክንያታችሁን/ሰበበ ነገራችሁን ያውቃል" (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በሰዎች መሃል ራሱን ከፍ የሚያደርግ በእግዚአብሔር ዐይኖች የተጣላ ነው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎች በጣም ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች እግዚአብሔር የሚጠላቸው ናቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 16:16
ህጉ እና ነቢያቱ
ይህ እስከዚያ ጊዜ ድረስ የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ በአጠቃላይ ያመለክታል
የሐንስ መጣ
x
Luke 16:18
ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ
"ማንም ሚስቱን የሚፈታ" ወይም "ማንም ሚስቱን የሚፈታ ሰው"
ዝሙት መፈጸም
"በዝሙት ምክንያት ጥፋተኛ መሆን"
እንዲቱን ያገባ
"እንዲት ሴት ያገባ ወንድ"
Luke 16:19
አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ህዝቡን ማስተማሩን እየቀጠለ ሳለ፤ አንድ ታሪክ መናገር ጀመረ። ይህም ስለ አልዓዛር እና ስለ አንድ ሀብታም ነው።
አጠቃላይ መረጃ፡
እነዚህ ቁጥሮች ኢየሱስ ስለ ሀብታሙ ሰው እና አልዓዛር የሚናገረውን ታሪክ የመረጃ ዳራ ይሰጣሉ። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)
አሁን/እነሆ
ይህ ኢየሱስ ታሪኩን መናገር ሲጀምር የሚያስተምራቸውን መረዳት እንዲችሉ ለታሪኩ ጅማሬ ምልክት ይሰጣል
አንድ ባለጸጋ ሰው
ይህ ሀረግ በኢየሱስ ታሪክ ውስጥ አንድን ሰው ያስተዋውቃል። ይህ ሰው በእውን የነበረ ይሁን ወይስ ኢየሱስ ሊያስተምር የፈለገውን ነጥብ ግልጽ ለማድረግ በዚህ ታሪክ ውስጥ ብቻ የሚገኝ ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም። (አዲስ እና ነበር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
ሐምራዊ እና ያማረ ሊኖ የለበሰ
x
Luke 16:22
እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ መሸጋገሪያ ሆኖ ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን ለማድረግ መንገድ ካለው እዚህ ላይ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
መላዕክት ይዘውት ሄዱ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "መላዕክት ወሰዱት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 16:25
ልጄ
ባለጸጋው ከአብርሃም ዘር አንዱ ነበር
Luke 16:27
ወደ አባቴ ቤት እርሱን ላከው
"አልዓዛር ወደ አባቴ ቤት እንዲሄድ ንገረው" ወይም "እባክህ፣ ወደ አባቴ ቤት እርሱን ላከው"
የአባቴ ቤት
ይህ በቤት ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ያመለክታል። "ቤተሰቤ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ያስጠነቅቃቸው ዘንድ
"አልዓዛር እንዲያስጠነቅቃቸው"
ይህ የከፍተኛ ጭንቅ ስፍራ
"በስቃይ የምንጨነቅበት ይህ ስፍራ" ወይም "በአስጨናቂ ስቃይ ውስጥ የምንገኝበት ይህ ስፍራ"
Luke 16:29
አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ስለ ባለጸጋው ሰው እና አልዓዛር የሚናገረውን ታሪክ ጨረሰ።
ሙሴ እና ነቢያት
ይህ ጽሁፋቸውን ያመለክታል። "ሙሴ እና ነቢያት የጻፉት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱን ይስሟቸው
"ወንድሞችህ ለሙሴ እና ነቢያት ትኩረት መስጠት አለባቸው"
አንድ ሰው ከሙታን መሃል ወደ እነርሱ ቢሄድ
ይህ ያልተፈጸመ ሁኔታን ይገልጻል፣ ነገር ግን ያባለጸጋ ሰው ይህ ቢሆን ይወዳል። "አንድ ሰው ከሙታን መሃል ወደ እነርሱ ቢሄድ" ወይም "አንድ የሞተ ሰው ተነስቶ ሄዶ ቢያስጠነቅቃቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ከሙታን መሃል
አስቀድሞ ከሞቱት ሁሉ ውስጥ። ይህ ሁኔታ የሚገልጸው በዓለም ከርሰ ምድር የተቀበሩ ሙታንን ሁሉ ነው።
ሙሴን እና ነቢቱን ካልሰሙ
እዚህ ስፍራ "ሙሴ እና ነቢያቱ" የሚለው የሚወክለው እነርሱ የጻፏቸውን ነገሮች ነው። "ሙሴ እና ነቢያት ለጻፉት ትኩረት የማይሰጡ ከሆነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ሰው ከሙታን ቢነሳም እነርሱ አይሰሙም
አብርሃም መላምታዊው ሁኔታ ቢሆን/ቢፈጸምም የሚገሆነውን ይገልጻል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ከሙታን ተመልሶ የመጣም ሰው ቢሆን እነርሱን ማሳመን አይችልም" ወይም "አንድ ሰው ከሞት ተመልሶ ቢመጣም እነርሱ አያምኑም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መላምታዊ ሁኔታዎች እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ከሙታን ተነስቶ
x

Chapter 17
Luke 17:1
አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ ማስተማሩን ቀጥሏል፣ ነገር ግን ንግግሩን ወደ ደቀ መዛሙርቱ መልሷል። ይህ አሁንም የታሪኩ ተመሳሳይ ክፍል ሲሆን በሉቃስ 15:3 ላይ የጀመረውን ታሪክ በዚያው ቀን ማስተማሩን ቀጥሏል።
ኃጢአት እንድንሰራ የሚያደርጉ ነገሮች መኖራቸው የተረጋገጠ ነው
"ሰዎች ኃጢአት እንዲሰሩ የሚፈታተኑ ነገሮች በእርግጥ ይፈጠራሉ"
በእርሱ በኩል እነርሱ ለሚመጡበት ለዚያ ሰው
"ፈተናዎች እንዲመጡ ምክንያት ለሚሆን ሰው" ወይም "ሰዎች እንዲፈተኑ ምክንያት ለሚሆን ሰው"

ለእርሱ...ይሻለዋል

ይህ መላምታዊ ሁኔታን ያስተዋውቃል። ይህ ማለት ይህ ሰው ሰዎች ኃጢአት እንዲሰሩ ምክንያት በመሆኑ የሚደርስበት ቅጣት ባህር ውስጥ ከመስመጥ የከፋ ይሆናል። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ቢወረወር

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ዙሪያ አስረው ቢወረውሩት" ወይም "በአንድ ሰው አንገት ዙሪያ ከባድ ድንጋይ ተደርጎ ቢወረወር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእርሱ...በአንገቱ...እርሱ ይሻለው

እነዚህ ቃላት ሴቶችን እና ወንዶችንም ያመለክታሉ። (ጡንቻማነት የሚገልጹ ቃላት ሴቶችን ሲያካትት የሚለውን ይመልከቱ)

የወፍጮ ድንጋይ

ይህ በጣም ትልቅ፣ ከባድ ክብ ድንጋይ ሲሆን እህል ለመፍጨት የሚያገለግል ነው። "ከባድ ድንጋይ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

እነዚህ ትንንሾች

ይህ እዚህ ስፍራ የሚያመለክተው እምነታቸው ገና ደካማ የሆነውን ነው። "እነዚህ እምነታቸው ትንሽ የሆነ ሰዎች"

መሰናከል

ይህ ይሁን ሳይባል የሚፈጸምን ኃጢአት የማመልከቻ መንገድ ነው። "ኃጢአት መፈጸም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Luke 17:3

ወንድምህ ቢበድል

ይህ ምናልባት ወደፊት ሊሆን ስለሚችል ድርጊት የሚናገር ሁኔታዊ ዐረፍተ ነገር ነው።

ወንድምህ

እዚህ ስፍራ "ወንድም" የሚለው ቃል የዋለው ተመሳሳይ እምነት ያለው ሰው በሚለው ስሜት ነው። "መሰል አማኝ"

እርሱን ገስጸው

"የሰራው ስህተት እንደሆነ በብርቱ ንገረው" ወይም "እርሱን አርመው"

ሰባት ጊዜ ቢበድልህ

ይህ መላምታዊ ሁኔታ ነው። ይህ ፈጽሞ ላያጋጥም ይችላል፣ ነገር ግን ቢያጋጥም እንኳን ኢየሱስ ሰዎች ይቅር እንዲሉ ይናገራል።(መላምታዊ ሁኔታ የሚለውን ይመልከቱ)

በቀን ውስጥ ሰባት ጊዜ፣ ደግሞም ሰባት ጊዜ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስት ሰባት ቁጥር ለሙሉነት ምሳሌ/ምልክት ነው። "በቀን ውስጥ ብዙ ጊዜ፣ ደግሞም በእያንዳንዱ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 17:5

አጠቃላይ መረጃ፡

ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር በሚናገሩበት ወቅት የተፈጠረ አጭር ጊዜ በኢየሱስ ትምህርተ መሃል አለ። ከዚያም ኢየሱስ ማስተማሩን ቀጠለ።

እምነታችንን አሳድግ/ጨምርልን

"እባክህ የበለጠ እምነት ስጠን" ወይም "በእምነታችን ላይ ተጨማሪ እምነት ስጠን"

የሰናፍጭ ፍሬ የሚያክል እምነት ቢኖራችሁ

የሰናፍጭ ፍሬ በጣም ትንሽ ፍሬ ነው። ኢየሱስ ትንሽ እምነት እንኳን እንደሌላቸው እያመለከተ ነው። "የሰናፍጭ ፍሬ የሚያክል ትንሽ እምነት እንኳን ቢኖራችሁ፣ እናንተ" ወይም "እምነታችሁ የሰናፍጭ ፍሬ ያህል አይደለም- ነገር ግን ቢሆን ኖሮ፣ እናንተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ተነጻጻሪ ዘይቤ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

የእንጆሪ ዛፍ

የዚህ አይነት ዛፍ የሚታወቅ ካልሆነ፣ ሌላ አይነት ዛፍ መተካት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "የሾላ ዛፍ" ወይም "ዛፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የማይታወቀውን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ተነቅሎ፣ በባህር ይተከል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ራሳችሁ ነቅላችሁ ራሳችሁ በባህር ትከሉት" ወይም "ከመሬት ነቅላችሁ በውቅያኖስ ወለል ትከሉት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ይሆንላችኋል/ይታዘዛችኋል

"ዛፉ ይታዘዛችኋል።" ይህ ውጤት ቅድመ ሁኔታዊ ነው። ይህ የሚሆነው እምነት ካላቸው ብቻ ነው።

Luke 17:9

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ ማስተማሩን ጨረሰ። ይህ የዚህ ታሪክ የመጨረሻው ክፍል ነው።

Luke 17:11

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢየሱስ 10 ለምጽ ያለባቸውን ሰዎች ፈወሰ። ቁጥር 11 እና 12 የመረጃ ዳራ እና የሁኔታዎችን መቼ እና የት ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)

እንዲህም ሆነ

እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው የአዲስ ትዕንት ጅማሬን ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህን ለማድረግ መንገድ ካለው እዚህ ስፍራ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ። (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ላይ ሳለ

"ኢየሱስ እና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳሌም እተጓዙ ሳለ"

አንዲት መንደር

ይህ ሀረግ መንደሯን ለይቶ አይናገርም።

በዚያ ለምጽ ያለባቸውን አስር ሰዎች አገኙት

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ለምጽ ያለባቸው አስር ሰዎች አገኙት" ወይም "አስር ለምጽ ያለባቸው ሰዎች አገኙት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነርሱ ከእርሱ ርቀው ቆሙ

ይህ የክብር ምልክት ነው፣ ምክንያቱም ለምጽ ያለባቸው ወደ ሌሎች መቅረብ አይፈቀድላቸውም ነበር። በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ድምጻቸውን ከፍ አድርገው

x

Luke 17:14

ራሳችሁን ለካህን አሳዩ

ለምጽ ያለባቸው ከለምጻቸው ስለ መፈወሳቸው ከካህናትን ማረጋገጫ ማግኘት ነበረባቸው። "ይመረምሯችሁ ዘንድ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ነጽተው ነበር

ሰዎች ሲፈወሱ፣ ከዚያ ወዲያ የመንጻት ስርዓት አያደርጉም። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "እነርሱ ከለምጻቸው ነጽ ተፈውሰው እና ንጹህ ሆነው ነበር" ወይም "እነርሱ ከለምጻቸው ተፈውሰው ነበር" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እንደ ተፈወሰ አየ

"እንደ ተፈወሰ አወቀ" ወይም "ኢየሱስ እንደፈወሰው አወቀ"

ተመልሶ መጣ

"ወደ ኢየሱስ ተመልሶ መጣ"

ከፍ ባለ ድምጽ እግዚአብሔርን እያመሰገነ

"እግዚአብሔርን ጮሆ አመሰገነ"

በኢየሱስ እግር ስር ወደቀ

"ተንበርክኮ በኢየሱስ እግር ስር በፊቱ ወደቀ።" ይህንን ያደረገው ኢየሱስን ለማክበር ነው። (ምልክታዊ/ትዕምርታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 17:17

አያያዥ ሀሳብ፡

ይህ ኢየሱስ አስሩን ለምጻሞች ስለ ፈወሰበት ታሪክ የመጨረሻው ክፈል ነው።

ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አለ

ኢየሱስ አንዱ ሰው ስላደረገው ምላሽ ሰጠ፣ የተናገረው ግን በዙሪያው ለነበሩ ሰዎች ነበር። "ስለዚህም ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ እንዲህ አለ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አስሩ አልነጹም ነበርን?


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ ከሶስቱ ቃለምልልሳዊ ጥያቄዎች የመጀመሪያው ነው። ኢየሱስ እነዚህን ጥያቄዎች የተጠቀመባቸው ከተፈወሱት መሃል እግዚአብሔርን ለማክበር የመጣው አንዱ ብቻ በመሆኑ ምን ያህል እንደተደነቀ እና እንዳዘነ በዙሪያው ለነበሩ ሰዎች ለማሳየትነው። "አስር ሰዎች ተፈውሰው ነበር።" ወይም "እግዚአብሔር አስር ሰዎችን ፈወሰ።" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ ባዕድ በስተቀር፣ ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት የተመለሱ የሉምን?

ይህ በዐረፍተ ነገር መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ከዚህ ባዕድ በስተቀር ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ማንም ተመልሶ አልመጣም!" ወይም "እግዚአብሔር አስር ሰዎች ፈወሰ፣ ሆኖም ይህ ባዕድ ብቻ ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ተመልሶ መጣ!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ ባዕድ

ሳምራውያን አይሁድ ያለሆነ ዝርያ አላቸው፤ እናም እነርሱ እግዚአብሔርን አይሁዶች በሚያመልኩበት ተመሳሳይ መንገድ አያመልኩም።

እምነትህ አድኖሃል/ደህና አድርጎሃል

"በእምነትህ ምክንያት ድነሃል/እምነትህ አድኖሃል።" "እምነት" የሚለው ሀሳብ "እምነት" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "በማመንህ ምክንያት፣ ዳግም ደህና ሆነሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ)

Luke 17:20

አጠቃላይ መረጃ:

ይህ የት እንደሆነ እንኳን አናውቅም፤ ይህ የሆነው አንድ ቀን ኢየሱስ ከፈሪሳውያን ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ነው።

የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ እንደሚመጣ ፈሪሳውያን በጠየቁት ጊዜ፣

ይህ የአዲሱ ትዕይንት መጀመሪያ ነው። አንዳንድ ትርጉሞች "አንድ ቀን" ወይም "አንድ ወቅት" በማለት ይጀምራሉ። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "አንድ ዕለት ፈሪሳውያን ኢየሱስን እንዲህ ሲሉ ጠየቁት፣ 'የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች?'" (አዲስ ትዕይንትን ማስተዋወቅ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ እንደዚሁም ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች የሚሉትን ይመልከቱ)

የእግዚአብሔር መንግስት በውስጣችሁ/በመካከላችሁ ናት

"መንግሥት" የሚለው ስም ጽንሰ ሀሳብ "መግዛት" በሚለው ግስ ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር በውስጣችሁ ይገዛል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች የሚለውን ይምለከቱ)

የእግዚአብሔር መንግሥት በእናንተ ውስጥ ናት

ኢየሱስ እርሱን ከሚጠሉ የሃይማኖት መሪዎች ጋር ይነጋገር ነበር። ለዚህ ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "እናንተ" የሚለው ቃል ሰዎችን በአጠቃላይ ያመለክታል። "የእግዚአብሔር መንግሥት በሰዎች ውስጥ ናት" ወይም 2) "በውስጣችሁ" የሚለው ቃል የተተረጎመው "በመሃላችሁ" በሚል ነው። "የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

Luke 17:25

ነገር ግን በመጀመሪያ እርሱ መከራ መቀበል ይኖርበታል

"ነገር ግን በመጀመሪያ የሰው ልጅ መከራ መቀበል ይኖርበታል።" ኢየሱስ ስለ ራሱ በሶስተኛ መደብ እየተናገረ ነው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚሉትን ይመልከቱ)

በትውልዱ መናቅ/መወገድ ይኖርበታል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር መገለጽ ይኖርበታል። "የዚህ ትውልድ ሰዎች እርሱን መቃወም/ ማስወገድ ይኖርባቸዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

ይህ በሚሆንበት ጊዜ...እንዲህ ቢሆንም እንኳን

"ሰዎች ነገሮችን በማከናወን ላይ ሳሉ...ሰዎች ተመሳሳይ ነገሮችን እያደረጉ ሳሉ"

በኖህ ዘመን

"የኖህ ዘመን" ይህ እግዚአብሔር የዓለምን ሕዝብ ከመቅጣቱ አስቀድሞ ኖህ በኖረበት ዘመን ያለውን ወቅት ያመለክታል። "ኖህ ይኖር በነበረበት ዘመን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።

በሰው ልጅ ቀናት

"የሰው ልጅ ቀናት" የሚለው የሚያመለክተው ልክ የሰው ልጅ ከመምጣቱ አስቀድሞ ያለውን ወቅት ነው። "የሰው ልጅ ሊመጣ ባለበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው"

ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ ይጋባሉ፣ ደግሞም ልጆቻቸውን ይድራሉ

ሰዎች መደበኛ ነገሮችን ያደርጋሉ። እግዚአብሔር ሊፈርድባቸው እንደሆነ አያውቁም ወይም ለዚህ ግድ አይላቸውም።

ልጆቻቸውን ይድራሉ

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊጻፍ ይችላል። "ወላጆች ሴት ልጆቻቸውን እንዲያገቡ ለወንዶች ይፈቅዳሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

መርከቡ/የኖህ መርከብ

"ታንኳ" ወይም "ጀልባ"

ሁሉንም አጠፋቸው

ይህ ኖህን እና በመርከቧ ውስጥ የነበሩ ቤተሰቦቹን አያጠቃልልም። "በጀልባዋ ውስጥ ያልገቡትን ሁሉ አጠፋ"

Luke 17:28

እንደዚሁ ሁሉ፣ በሎጥ ዘመን እንደሆነው

"የሎጥ ዘመን" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሰዶም እና ገሞራን ከተሞች ከመቅጣቱ አስቀድሞ ያለውን ጊዜ ነው። "ሌላው ምሳሌ በሎጥ ዘመን እንዴት እንደሆነ የሚያሳይ ነው" ወይም "ሎጥ በኖረበት ዘመን ሰዎች ያደርጉት እንደነበረ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይበሉ እና ይጠጡ ነበር

"የሰዶም ሰዎች ይበሉ እና ይጠጡ ነበር"

ከሰማይ እሳት እና ሲን ዘነበ

"እሳት እና የሚነድ ዲን እንደ ዝናብ ከሰማይ ወረደ"

ሁሉንም አጠፋቸው

ይህ ሎጥን እና ቤተሰቡን አይጨምርም። "በከተማይቱ የነበሩትን ሁሉ አጠፋ"

Luke 17:30

ልክ እንደዚያው ይሆናል

"እንደዚያው ይሆናል።" በተመሳሳይ መንገድ እንደዚያው ሰዎች የተዘጋጁ አይሆኑም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ በሚገለጽበት ቀን

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የሰው ልጅ በሚገለጽበት ጊዜ" ወይም "የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

የሰው ልጅ ይገለጻል

ኢየሱስ ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። "እኔ፣ የሰው ልጅ፣ እገለጻለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

በቤት ጫፍ ጣራ ላይ የሚገኝ ወደ ታች አይውረድ

"ማንም በቤት ጣራ ላይ የሚገኝ ወደ ታች አይውረድ" ወይም "ማንም ሰው በቤቱ ጣራ ላይ ቢሆን ወደ ታች መውረድ የለበትም"

በቤት ጣራ

የቤቶቻቸው ጣራ ጠፍጣፋ ነበር በዚያ ላይ መራመድ ወይም መቀመጥ ይችሉ ነበር።

ንብረቶቹን

"ሃብቱን" ወይም "ያሉትን ነገሮች"

Luke 17:32

የሎጥን ሚስት አስታውሷት

"በሎጥ ሚስት ላይ ደርሶ የነበረውን አስታውሱ" ይህ ማስጠንቀቂያ ነው። እርሷ ወደ ሰዶም እን ገሞራ ዘወር ብላ ስትመለከት እግዚአብሔር ከሰዶም ሰዎች ጋር እርሷን ቀጣት። "የሎጥ ሚስት ያደረገችውን አታድርጉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የተተወ/የተዘለለ እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)

ሕይወቱን ማትረፍ የሚፈልግ ሁሉ ያጣታል

"ሕይወታቸውን ለማትረፍ የሚሞክሩ ሰዎች ያጧታል" ወይም "ማንም የቀድሞ ሕይወቱን መንገድ መጠበቅ የሚሞክር ሕይወቱን ያጣል"

ነገር ግን ማም ሕይወቱን የሚጥል ያድናታል

"ነገር ግን ሕይወታቸውን የሚጥሉ ሰዎች ያድኗታል" ወይም "ነገር ግን ማንም ያለፈውን የአኗኗር መንገዱን የሚተው ሕይወቱን ያድናል"

Luke 17:34

እኔ ግን እላችኋለሁ

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ መናገሩን ሲቀጥል፣ የሚነግራቸው ምን ያህል አስፈላጊ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደሆነ ትኩረት ይሰጥ ነበር።

በዚያች ምሽት

ይህ የሚያመለክተው፣ እርሱ፣ የሰው ልጅ በምሽት ቢመጣ ምን እንደሚሆን ነው።

በአንድ አልጋ ላይ ሁለት ሰዎች ይኖራሉ

ትኩረቱ እነዚህ ሁለት ሰዎች ላይ አይደለም፣ ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ይወሰዳሉ ሌሎች ይተዋሉ በሚለው ላይ ነው።

አልጋ

"መከዳ" ወይም "ጎጆ"

አንዱ ይወሰዳል፣ ሌላኛው ይቀራል

"አንዱ ሰው ይወሰዳል ሌላው ሰው ይቀራል።" ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እግዚአብሔር አንዱን ሰው ይወስደዋል ሌላውን ይተዋል" ወይም "መላዕክት አንዱን ይወስዳሉ ሌላውን ይተዋሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

በአንድነት የሚፈጩ ሁለት ሴቶች ይኖራሉ

ትኩረቱ በእነዚህ ሁለት ሴቶች ወይም በክንዋኔያቸው ላይ አይደለም፣ ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች መወሰዳቸው ሌሎች መተዋቸው/ሳይወሰዱ መቅረታቸው ላይ ነው።

አብረው ይፈጫሉ

"እህል አብሮ መፍጨት"

አጠቃላይ መረጃ፡

ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ስለ ትምህርቱ ጠየቁት እርሱም መለሰላቸው።

ጌታ ሆይ፣ የት ይሆናል?

"ጌታ ሆይ፣ ይህ የት ይሆናል?"

አካል/በድን ባለበት፣ በዚያ ጥንብ አንሳ ይሰበሰባል

የዚህ አባባል ትርጉም፣ "ይህ ግልጽ ይሆናል" ወይም "ይህን ነገር በሚሆንበት ጊዜ ታውቁታለችሁ።" "የጥንብ አንሳዎች መሰብሰብ በድን መኖሩን እንደሚያሳይ፣ እንደዚሁ ሁሉ እነዚህ ነገሮች የሰው ልጅ መምጫ መሆኑን ያሳያሉ" (ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ጥንብ አንሳዎች

ጥንብ አንሳዎች በአንድነት የሚበሩ እና ያገኙትን በድን ስጋ የሚመገቡ ትላልቅ ወፎች ናቸው። እነዚህን ወፎች በዚህ መንገድ መግለጽ ትችላላችሁ ወይም ይህንን የሚያደርጉ በአካባቢያችሁ የሚገኙ ወፎችን ስም መጠቀም መጠቀም ትችላላችሁ። (የማይታወቁትን መተረጎም የሚለውን ይመልከቱ)

---

# Chapter 18

## Luke 18:1

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስተማሩን ሲቀጥል ግብረገባዊ ምሳሌ መናገሩን ጀመረ። ይህ በሉቃስ 17:20 ላይ የተጀመረው ታሪክ ክፍል ነው። ቁጥር 1 ኢየሱስ ሊናገር ያለውን ግብረገባዊ ምሳሌ ገለጻ ይሰጠናል። (ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚያም እርሱ

"ከዚያም ኢየሱስ"

ሳይታክቱ፣ እንዲናገሩ

እዚህ ስፍራ "እርሱ እንዲህ አለ፤ ሳይታክቱ።" በሚል አዲስ ዐረፍተ ነገር ሊጀምር ይችላል።

በአንዲት ከተማ

እዚህ ስፍራ "አንዲት ከተማ" የሚለው አድማጭ ቀጥሎ የሚቀርበው ትረካ በከተማ ውስጥ እንደሚካሄድ እንዲያወቅ የማድረጊያ መንገድ ነው፣ ሆኖም የከተማይቱ ስም ጠቃሚ ። (የጽሁፍ አይነቶች የሚለውን ይመልከቱ)

ሰዎችን የማያከብር

"ስለ ሌሎች ሰዎች ግድ የማይለው"

## Luke 18:3

እነሆ አንዲት መበለት ነበረች

ኢየሱስ ይህንን ሀረግ የተጠቀመበት አዲስ ገጸባህሪ ወደ ታሪኩ ለማስገባት/ ማስተዋወቅ ነው። (አዲስ እና ነበር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

መበለት

መበለት ባሏ የሞተባት እና ደግማ ያላገበች ሴት ናት። ኢየሱስ ስለዚህች ሴት ማንም የሚረዳት እና በጉዳትዋ የሚደርስላት ሰው እንደሌላት አድርጎ አስቧታል።

ብዙ ጊዜ ወደ እርሱ ትመጣ ነበር

"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዳኛውን ነው።

ከባላጋራዬ ጋር ስላለብኝ ጉዳይ ፍረድልኝ

" ከባላጋራዬ ጋር ስላለብኝ ጉዳይ ትክክለኛ ፍርድ ስጠኝ"

ባላጋራዬ

"ጠላቴ" ወይም "ሊጎዳኝ የሚሞክር ሰው።" ይህ በሙግት ውስጥ ያለ ባለጋራ ነው። መበለቲቱ ሰውየውን ትክሰሰው ወይስ ሰውየው መበለቲቱን ይክሰሳት ግልጽ አይደለም።

ሰው

እዚህ ስፍራ ይህ በአጠቃላይ "ሰዎችን" ያመለክታል። (ጡንቻማነት የሚገልጹ ቃላት ሴቶችን ሲያካትት የሚለውን ይመልከቱ)

ስለምታስቸግረኝ

"ስለምትጨቀጭቀኝ"

ታደክመኛለች

"ታታክተኛለች"

ዘወትር እየተመላለሰች

"ሳታቋርት በመምታት"

## Luke 18:9

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢየሱስ ራሳቸውን ጻድቅ አድርገው ለሚመለከቱ ለሌሎች ሰዎች ሌላ ግብረገባዊ ምሳሌ መናገር ጀመረ። (ግብረገባዊ ምሳሌ የሚለውን መልከቱ)

ከዚያም እርሱ

"ከዚያም ኢየሱስ"

ለአንዳንዶች

"ለአንዳንድ ሰዎች"

ራሳቸውን ጻድቅ አድርገው ለሚቆጥሩ

"ራሳቸውን ጻድቅ አድርገው ያሳመኑ"ነ ወይም "ራሳቸውን ጻድቅ አድርገው የሚያዩ"

የሚንቁ

በጣም የማይወዱ ወይም የሚጠሉ

ወደ ቤተ መቅደስ

"ወደ ቤተ መቅደስ አደባባይ"

## Luke 18:11

ፈሪሳዊው ቆሞ እነዚህን ነገሮች ስለ ራሱ ጸለየ

የዚህ ሀረግ የግሪኩ ጽሁፍ ትርጉም ግልጽ አይደለም። ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ፈሪሳዊው ቆሞ ስለ ራሱ በዚህ መንገድ ጸለየ" ወይም 2) "ፈሪሳዊው ቆሞ በግሉ እንዲህ ጸለየ።"

ዘራፊዎች

ዘራፊዎች ሰዎችን በማስገደድ ወይም የጠየቁትን የማይሰጧቸው ከሆነ እንደሚጎዷቸው ሌሎችን በማስፈራራት የሚሰርቁ ሰዎች ናቸው።

ወይም እንደዚህ ቀረጥ ሰብሳቢ እንኳን

ፈሪሳዊው ቀረጥ ሰብሳቢዎች እንደዘራፊዎች ኃጢአተኞች፣ በደለኞች እና ዘማውያን ናቸው ብሎ ያምናል። ይህ ይበልጥ ግልጽ ሊደረግ ይችላል። "እናም እኔ በእርግጥ እንደዚህ ሰዎችን እንደሚያታልል ኃጢአተኛ ቀረጥ ሰብሳቢ አይደለሁም" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ካገኘሁት ሁሉ

"ካገኘሁት ነገር"

## Luke 18:13

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ ምሳሌውን መናገሩን ጨረሰ። በቁጥር 14፣ ምሳሌው የሚያስተምረውን ነገር ያብራራል።

በሩቅ ቆሞ

"ከፈሪሳዊው ሩቅ ቆሞ።" ይህ ዝቅ የማለት ምልክት ነው። ራሱን ከፈሪሳዊው አጠገብ መቆም እንደሚገባው ሰው አልቆጠረም።

ዐይኖቹን ወደ ሰማይ አንስቶ

"ዐይኖቹን ማንሳት" ማለት ወደ አንድ ነገር መመልክት ማለት ነው። "ወደ ሰማይ ተመለከተ" ወይም "ወደ ላይ ተመለከተ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

(ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ደረቱን እየደቃ/እየመታ
ይህ የከፍተኛ ሀዘን አካላዊ መግለጫ ምልክት ነው፣ ደግሞም የዚህን ሰው ንስሃ መግባት እና ራሱን ዝቅ ማድረጉን ያሳያል "ሀዘኑን ለማሳየት ደረቱን መታ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔር ሆይ፣ እኔን ኃጢአተኛውን ይቅር በለኝ
"እግዚአብሔር ሆይ፣ እባክህ እኔን ማረኝ። እኔ ኃጢአተኛ ነኝ" ወይም "እግዚአብሔር ሆይ፣ ብዙ ኃጢአት ብፈጽምም እባክህ ይቅር በለኝ"
ይህ ሰው ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ
ጻድቅ የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር ስላለው ነው። "እግዚአብሔር ቀረጥ ሰብሳቢውን ማረው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 18:15
አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ በሉቃስ 17፡20 ላይ የጀመረው ታሪክ ተከታይ ትዕይንት ነው። ኢየሱስ ልጆችን ተቀብሎ ስለ እነርሱ ተናገረ።
ዳሰሳቸው፣ ነገር ግን
ይህ የተለየ ዐረፍተ ነገር ሆኖ ሊተረጎም ይችላል፡ "ዳሰሳቸው። ነገር ግን"
እነርሱ ገሰጽዋቸው
"ደቀ መዛሙርቱ የልጆቹ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ኢየሱስ እንዳያመጧቸው ለማስቆም ሞከሩ"
ኢየሱስ ወደ እርሱ ጠራቸው
"ኢየሱስ ሰዎቹ ህጻናቶቻቸውን ወደ እርሱ እንዲያመጡ ተናገረ"
ትንንሽ ልጆች ወደ እኔ እንዲመጡ ፍቀዱላቸው፣ እናም እነርሱን አትከልክሏቸው
እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፤ በአንድነት የተጣመሩት ትኩረት ለመስጠት ነው። አንዳንድ ቋንቋዎች በተለየ መንገድ ትኩረት ይሰጣሉ። "እናንተ በእርግጥ ልጆች ወደ እኔ እንዲመጡ መፍቀድ አለባችሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትይዩ ንጽጽራዊ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 18:18
አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ በሉቃስ 17፡20 ላይ የጀመረው ታሪክ ተከታይ ትዕይንት ነው። ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ መግባት ከአንድ የሃይማኖት መሪ ጋር መነጋገር ጀመረ።
አንድ መሪ
ይህ በታሪኩ ውስጥ አንድ አዲስ ገጸባህሪ ያስተዋውቃል። ይህ ሰው በስልጣኑ ብቻ እንዲታወቅ/እንዲለይ ሆኗል። (አዲስ እና ነበር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
ምን ማድረግ ይገባኛል
"ምን ማድረግ ይኖርብኛል" ወይም "ከእኔ ምን ይጠበቃል"
የዘለዓለም ሕይወት መውረስ
"መጨረሻ የሌለው ሕይወት መቀበል።" "መውረስ" የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ የሚያመለክተው አንድ ሰው ሲሞት ለልጆቹ የሚተውላቸውን ሃብት ነው። ስለዚህ፣ ይህ ዘይቤ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ተረድቷል እናም እግዚአብሔር የዘለዓለም ሕይወት እንዲሰጠው ይፈልጋል ማለት ሊሆን ይችላል። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
ስለምን መልካም ትለኛለህ? ከእግዚአብሔር በቀር ማንም መልካም የለም
ኢየሱስ ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው የሃይማኖት መሪው ለጠየቀው ጥያቄ በቁጥር 18 ላይ እርሱ የሰጠውን መልስ መሪው እንደማይወደው ስለሚያውቅ ነው። ኢየሱስ መሪው የእርሱን ጥያቄ እንዲመልስለት አይጠብቅም። ኢየሱስ የሚፈልገው እርሱ ለመሪው ጥያቄ የሰጠው ምላሽ የመጣው፣ ብቻውን መልካም ከሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ እንዲረዳ ነው። "ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንም መልካም እንዳልሆነ አንተ ታውቃለህ፣ ስለዚህ እኔን መልካም ማለት እኔን ከእግዚአብሔር ጋር መነጻጸር ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)
አትግደል
"የሰው ነፍስ አታጥፋ"
እነዚህን ነገሮች ሁሉ
"እነዚህን ትዕዛዛት ሁሉ"
Luke 18:22
ኢየሱስ ያንን ሲሰማ
"ኢየሱስ ሰውየው ያንን ሲናገር ሲሰማ"
ለእርሱ እንዲህ አለው
"ለእርሱ መልስ ሰጠው"
አሁንም አንድ የቀረህ ነገር
"አሁንም አንድ ተጨማሪ ነገር ማድረግ ያስፈልግሃል" ወይም "እስከ አሁንም ገና ያላደረግከው አንድ ነገር አለ"
ያለህን ሁሉ ሽጥ
"ያለህን ንብረት ሁሉ ሽጥ" ወይም "የራስህ የሆነውን ነገር ሁሉ ሽጥ"
ያንንም ለደሆች አከፋፍላቸው
"ገንዘቡን ለድሃ ሰዎች ስጥ"
በሰማይ ሀብት/መዝገብ ይኖርሃል
እዚህ ስፍራ "በሰማይ ሀብት" የሚለው የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን በረከት ነው። "በሰማይ የእግዚአብሔርን በረከት ታገኛለህ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ዘይቤያዊ አነጋገር የሚለውን ይመልከቱ)
መጥተህ፣ ተከተለኝ
"ደቀ መዝሙሬ ሆነህ ተከተለኝ"
Luke 18:24
ወደ እግዚአብሔር መንግሥት...እንዴት አስቸጋሪ ነው!
ይህ ቃለአጋኖ ነው ፣ ጥያቄ አይደለም። "ወደ እግዚአብሔር መንግሥት....ይህ በጣም ጭንቅ ነው!" (ቃለ አጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)
ግመል በመፍፌ ቀዳዳ ቢያልፍ
ግመል በመርፌ ቀዳዳ ማለፍ አይችልም። ኢየሱስ ምናልባትም ሃብታም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባቱ እጅግ አስቸጋሪ ነው ለማለት ኩሸት እየተጠቀመ ይሆናል። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
የመርፌ ቀዳዳ
x
Luke 18:26
ይህንን የሰሙት እንዲህ አሉ
"ኢየሱስን የሰሙት ሰዎች እንዲህ አሉ"
ታዲያ ማን ሊድን ይችላል?
መልስ እየጠየቁ ነበር ማለት ይቻላል። ነገር ግን ጥያቄውን ያነሱት ኢየሱስ በተናገረው መደነቃቸውን ለማጉላት ነው ማለት ይቻላል። "ከሆነ ማንም ከኃጢአት ሊድን አይችልም!" ወይም በአድራጊ ዐረፍተ ነገር፡ "እንዲህ ከሆነ እግዚአብሔር ማንንም አያድንም!" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ቃለ ምልልሳዊ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)
ለሰው የማይቻል ለእግዚአብሔር ይቻላል
"ሰዎች ማድረግ የማይችሉትን እግዚአብሔር ማድረግ ይችላል" ወይም "ሰዎች የማያደርጉትን፣ እግዚአብሔር ማድረግ ይችላል"
Luke 18:28
አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ ወደ መንግስተ ሰማይ ስለመግባት የሚደረገው የመጨረሻው ንግግር ነው።
እኛ ግን
ይህ ሀረግ የሚያመለክተው ደቀ መዛሙርቱን ብቻ ነው፣ እናም ከሃብታሙ መሪ ጋር ያነጻጽራል።
እኛ ሁሉን ትተን
"እኛ ትተናል" ወይም "እኛ ሁሉን ከኋላችን ትተን
የራሳችን የሆነውን ነገር ሁሉ
"ሀብታችንን ሁሉ" ወይም "ያለንን ንብረት ሁሉ"
በእውነት፣ እላችኋለሁ
ኢየሱስ ይህንን አገላለጽ የተጠቀመው ሊናገር ስላለው ነገር አስፈላጊነት ትኩረት ለመስጠት ነው።
ማንም አይኖርም
ይህ አገላለጽ ደቀ መዛሙርቱን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ተመሳሳይ መስዋዕትነት የከፈለን ሁሉ ለማካተት የታቀደ ነው።
ማንም...የተው... የማይቀበል የለም
ይህ በአዎንታዊ መልክ ሊገለጽ ይችላል። "ማንም...የተወ...ይቀበላል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ጥንድ አሉታዎች የሚለውን ይመልከቱ)


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በሚመጣው ዓለም፣ የዘለዓለም ሕይወት
"ደግሞም በሚመጣው ዓለም የዘለዓለም ሕይወት"
Luke 18:31
አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ በዚህ የታሪክ ክፍል በሉቃስ 17:20 የጀመረው ቀጣይ ትዕይንት ነው። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ብቻ እየተናገረ ነው።
አሥራ ሁለቱን ወደ ራሱ ሰበሰበ
ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ብቻቸውን ከሌሎች ሰዎች ፈቀቅ አድርጎ ወስዶ
እነሆ
ይህ በኢየሱስ አገልግሎት ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ጉልህ ለውጥ ያመለክታል
በነቢያት ተጽፎ የነበረ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ነቢያት ጽፈውት የነበረ/ነቢያት የጻፉት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ነቢያቱ
ይህ የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ያመለክታል።
የሰው ልጅ...እርሱ...የእርሱ...የእርሱ ...እርሱ
ኢየሱስ ስለ ራሱ "የሰው ልጅ" በማለት ይናገራል። " እኔ፣ የሰው ልጅ፣... እኔ... ራሴ...ራሴ...እኔ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)
ይፈጸማል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ይሆናል" ወይም "ይከሰታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ለአሕዛብ ተላልፎ ይሰጣል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የአይሁድ መሪዎች ለአህዛብ አሳልፈው ይሰጡታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ያፌዙበታል፣ እናም በሀፍረት ያንገላቱታል፣ ደግሞም ይተፉበታል
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ያፌዙበታል፣ በሀፍረት ያንገላቱታል፣ ደግሞም ይተፉበታል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
በሦስተኛው ቀን
ይህ ከሞቱ በኋላ ሶስተኛውን ቀን ያመለክታል። ሆኖም፣ ደቀ መዛሙርቱ ይህንን አልተረዱም፣ ስለዚህም ይህንን ገለጻ ይህ ቁጥር ሲተረጎም አለመጨመሩ ይመረጣል። (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 18:34
አጠቃላይ መረጃ፡
ይህ ቁጥር የዋናው ታሪክ ክፍል አይደለም፣ ነገር ግን ስለዚህ ታሪክ ክፍል አስተያየት ነው። (የታሪክ መጨረሻ/ማጠቃለያ የሚለውን ይመልከቱ)
እነርሱ ከእነዚህ ነገሮች ውስጥ ምንም አልተረዱም
"እነርሱ ከእነዚህ ነገሮች መሃል አንዳች አልገባቸውም"
እነዚህ ነገሮች
ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም እንዴት እንደሚሰቃይ እና እንደሚሞት የሰጠውን ገለጻ፣ እና እርሱ ከሞት እንደሚነሳ ነው።
ይህ ቃል ከእነርሱ ተሰውሮ ነበር
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። ነገር ግን ቃሉን ከእነርሱ የሰወረው እግዚአብሔር ይሁን ወይም ኢየሱስ ግልጽ አይደለም። "ኢየሱስ መልእክቱን ከእነርሱ ሰወረው" ወይም "እግዚአብሔር ኢየሱስ ለእነርሱ ይነግራቸው የነበረውን መልዕክት ትርጉም እንዳይረዱት ከለከላቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የተባሉ/የተነገሩ ነገሮች
x
Luke 18:35
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ ሲቃረብ ዐይነስውሩን ሰው ፈወሰ። ይህ ቁጥር የመረጃ ዳራ እና ታሪኩ መቼ እና የት ስፍራ እንደተፈጸመ መረጃ ይሰጣል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)
እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው የታሪኩን አዲስ ክፍል ጅማሬ ለማመልከት ነው። (አዲስ ትዕይንት ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ ዐይነስውር ሰው ተቀምጦ ነበር
"አንድ ዐይነስውር ተቀምጦ ነበር።" እዚህ ስፍራ "አንድ" የሚለው ይህ ሰው ለታሪኩ ጠቃሚ ሆኖ መተዋወቁን ሲያመለክት ሉቃስ በስም አልጠቀሰውም። በታሪኩ ውስጥ አዲስ ተሳታፊ ነው። (አዲስ እና ነበር ተሳታፊዎችን ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)
መለመን፣ እና መስማት
እዚህ ስፍራ አዲስ ዐረፍተ ነገር መጀመር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "መለመን። በሰማ ጊዜ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
እነርሱ ነገሩት
"በሕዝብ ጭንቅንቅ ውስጥ የሚገኙት ሰዎች ለዐይነ ስውሩ ነገሩት"
የናዝሬቱ ኢየሱስ
ኢየሱስ የመጣው በገሊላ ከምትገኘው፣ ከናዝሬት ከተማ ነው
እያለፈ ነበር
"እርሱን እያለፈ እየሄደ ነበር"
Luke 18:38
ስለዚህ
ይህ ቃል አስቀድሞ በሆነ አንድ ሌላ ነገር ምክንየት የሆነን ትዕይንት ያመለክታል። በዚህ ሁኔታ፣ የተሰበሰበው ሕዝብ ለዐይነ ስውሩ ኢየሱስ እያለፈ እንደሆነ ነግረውታል።
ከፍ ባለ ድምጽ ጮኸ
"ተጣራ" ወይም "ጮኸ"
የዳዊት ልጅ
ኢየሱስ የእሥራኤል ታላቅ ንጉስ፣ የዳዊት ትውልድ ነበር
ማረኝ
"ራራልኝ" ወይም "ርህራሄህን አሳየኝ"
ከፊት ለፊት ይሄዱ የነበሩት
"ከተሰበሰበው ሕዝብ ከፊት ይሄዱ የነበሩ ሰዎች"
ዝም እንዲል
"ጸጥ እንዲል" ወይም "እንዳይጮህ"
ይልቁንም አብዝቶ ጮኸ
ይህ ማለት ይበልጥ ድምጹን ከፍ አድርጎ ጮኸ ማለት ሊሆን ይችላል ወይም ይበልጥ ሳያቋርጥ በጽናት ጮኸ ማለት ይሆናል።
Luke 18:40
ሰውየው ወደ እርሱ እንዲመጣ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ሰዎቹ ዐይነስውሩን ወደ እርሱ እንዲያመጡት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
አይ ዘንድ
"ማየት እችል ዘንድ"
Luke 18:42
እይ
ይህ ትዕዛዝ ነው፣ ነገር ግን ኢየሱስ ሰውየው ምንም ነገር እንዲያደርግ አላዘዘውም። ኢየሱስ ሰውየውን የፈወሰው እንዲፈወስ እርሱን በማዘዝ ነው። "አንተ አሁን ብራሀንህን አግኝተሃል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ትዕዛዞች - ሌሎች አጠቃቀሞች የሚለውን ይመልከቱ)
እምነትህ አድኖሃል
እነዚህ ቃላት ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ናቸው። ኢየሱስ ሰውየውን የፈወሰው በሰውየው እምነት ምክንያት ነበር። "እኔ አንተን የፈወስኩህ አንተ በእኔ በማመንህ ምክንያት ነው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እግዚአብሔርን ማክበር
"ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት" ወይም "እግዚአብሔርን ማወደስ/ማመስገን"

Chapter 19


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Luke 19:1
አጠቃላይ መረጃ፡
ከቁጥር 1-2 ያለው ለቀጣዩ ትዕይንት የመረጃ ዳራ መስጠት ይጀመራል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 19:3
አጠቃላይ መረጃ፡
ቁጥር 3 ለተከታዩ ትዕይንት፣ በሉቃስ 19፡1-2 የቀረበውን መረጃ ያሟላል። (የመረጃ ዳራ የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱ ይሞክር ነበር
"ዘኬዎስ ይሞክር ነበር"
ምክንያቱም እርሱ ቁመቱ አጭር ነበር
"ምክንያቱም እርሱ አጭር ነበር"
ስለዚህ እርሱ ሮጠ
ጸሐፊው ለትዕይንቱ ዳራ መስጠቱን ጨርሶ አሁን ትዕይንቱን ራሱን መግለጽ ጀምሯል።
የሾላ ዛፍ
"የሾላ ዛፍ።" ወደ 2.5 ሳናቲሜትር መጠን ያለው ትንሽ ክብ ፍሬ ያፈራል። "የሾላ ዛፍ" ወይም "ዛፍ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
Luke 19:5
እዚያ ቦታ
"ዛፉ" ወይም "ዘኬዎስ የነበረበት"
ስለዚህም እርሱ ፈጥኖ
"ስለዚህም ዘኬዎስ ፈጥኖ"
ሁሉም አጉረመረሙ
አይሁዶት ቀረጥ ሰብሳቢ ይጠላሉ፤ ደግሞም ማንም መልካም ሰው ከእነርሱ ጋር ህብረት ማድረግ ይኖርበታል ብለው አያስቡም። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ኃጢአተኛ ሰው ለኅበኝ ወደ ውስጥ ገባ
"ኢየሱስ ወደ ኃጢአተኛ ሰው ቤት ገባ"
አንድ ኃጢአተኛ
"ኃጢአተኛነቱ በግልጽ የሚታወቅ" ወይም "የለየለት ኃጢአተኛ"
Luke 19:8
ጌታ
"ይህ ኢየሱስን ያመለክታል"
አራት እጥፍ አድርጌ
"ከእነርሱ የወሰድኩትን አራት እጠፍ አድርጌ እመልሳለሁ"
ለዚህ ቤት መዳን ሆነ
መዳን ከእግዚአብሔር እንደሚመጣ ይታወቃል። "እግዚአብሔር ይህንን ቤት አዳነ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ረቂቅ ስሞች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ይህ ቤት
እዚህ ስፍራ "ቤት" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቤቱ ወይም በቤተሰቡ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ነው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
እርሱም ደግሞ
"ይህም ሰው ደግሞ" ወይም "ዘኬዎስም ጭምር"
የአብርሃም ልጅ
ሊሰጡ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "የአብርሃም ትውልዶች/ዘር" እና 2) "እንደ አብርሃም እምነት ያለው ሰው።"
የሰው ልጅ የመጣው
ኢየሱስ ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። "እኔ፣ የሰው ልጅ፣ የመጣሁት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
የጠፉትን ሰዎች
"ከእግዚአብሔር የራቁትን ሰዎች" ወይም "በኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር የራቁትን"
Luke 19:11
አጠቃላይ መረጃ፡
ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ በግብረገባዊ ምሳሌ ማስተማር ጀመረ። ቁጥር 11 ኢየሱስ ለምን ግብረገባዊ ምሳሌውን እንደሚናገር የመረጃ ዳራ ይሰጣል። (ግብረገባዊ ምሳሌ እና የመረጃ ዳራ የሚሉትን ይመልከቱ)
የእግዚአብሔር መንግሥት በቶሎ የሚገለጥ
አይሁዶች መሲሁ ወደ ኢየሩሳሌም እንደመጣ በቶሎ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይመሰርታል ብለው ያምኑ ነበር። "ኢየሱስ በቶሎ በእግዚአብሔር መንግስት ላይ መግዛት ይጀምራል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አንድ መስፍን
"ከገዢው መደብ አባል የሆነ አንድ ሰው" ወይም "ከከፍተኛ ቤተሰብ የሆነ አንድ ሰው"
ለራሱ የንጉሥነትን ማዕረግ ለመቀበል
ይህ ታናሽ ንግሥና ያለው ታላቅ ንግሥና ወዳለው መሄዱን ያሳያል። ታላቁ ንጉሥ ለታናሹ ንጉሥ በራሱ መንግሥት ላይ እንዲገዛ መብት እና ሥልጣን ይሰጠዋል። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 19:13
አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ በሉቃስ 19፡11 የጀመረውን ግብረገባዊ ምሳሌ መናገሩን ቀጠለ።
እርሱ ጠራቸው
"ልዑሉ ጠራቸው።" ሰውየው ይህንን ያደረገው የንጉሥነትን ማዕረግ/የእርሱን መንግሥት ለመቀበል ከመሄዱ አስቀድሞ እንደሆነ መግለጹ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። "ከመሄዱ አስቀድሞ ጠራቸው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው።
አስር ምናን ሰጣቸው
"ለእያንዳንዳቸው አንድ ምናን ሰጣቸው"
አስር ምናን
አንድ ምናን 600 ግራም ነው፤ ምናላባት ሰጣቸው ብር የተሰኘውን ማዕድን ሳይሆን አይቀርም። አንድ ምናን የ100 ቀን ሥራ ደሞዝ ያክላል፤ ሰዎች ወደ አራት ወራት ለሚጠጋ ጊዜ ሰርተው የሚያገኙት ክፍያ ነው። ስለዚህ አስር ምናን አንድ የቀን ሥራተኛ በሶስተ አመታት የሚከፈለው የክፍያ መጠን ነው። "አስር ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸው ሳንቲሞች" ወይም "እጅግ ከፍተኛ የገንዘብ መጠን" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን ቁጥሮች እና ክብደት መለኪያ የሚሉትን ይመልከቱ)
ንግድ ማካሄድ
"በዚህ ገንዘብ መነገድ" ወይም "ይህንን ገንዘብ ተጨማሪ ለማግኘት መጠቀም"
የእርሱ ዜጎች
"የእርሱ አገር ሰዎች"
መልዕክተኛ
"እነርሱን የሚወክሉ ሰዎች ስብስብ/ቡድን" ወይም "በርካታ መልዕክተኞች"
እንዲህም ሆነ
እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አስፈላጊ ትዕይንተን ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህንን ለማድረግ መንገድ ካለው፣ እዚህ ላይ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ።
መንግሥቱን ከተቀበለ በኋላ
"ከነገሠ በኋላ"
ወደ እርሱ አስጠራቸው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ወደ እርሱ እንዲመጡ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ምን ያህል እንዳተረፉ
"ምን ያህል ገንዘብ እንዳስገኙ"
Luke 19:16
አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ በሉቃስ 19፡11 የጀመረውን ግብረገባዊ ምሳሌ መናገሩን ቀጠለ።
የመጀመሪያው
"የመጀመሪያው አገልጋይ" (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)
በፊቱ ቀረቡ
"ልዑሉ ፊት ቀረቡ"
ምናንህ ተጨማሪ አስር ምናን አተረፈ
አገልጋዩ ያተረፈ መሆኑ ተጠቁሟል። "ምናንህ ተጨማሪ አስር ምናን እንዲያተርፍ አድርጌያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ምናን

አንድ ምናን 600 ግራም ነው፤ ምናልባት የሰጣቸው ብር የተሰኘውን ማዕድን ሳይሆን አይቀርም። አንድ ምናን የ100 ቀን ሥራ ደሞዝ ያክላል፤ ሰዎች ወደ አራት ወራት ለሚጠጋ ጊዜ ሰርተው የሚያገኙት ክፍያ ነው። ይህ በሉቃስ 19፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

መልካም አደረግህ

"አንተ መልካም ሰርተሃል።" ቋንቋችሁ ቀጣሪ በትክክል መሰራቱን የሚያረጋግጥበት አገላለጽ/ሀረግ ሊኖር ይችላል። "ጥሩ ሰርተሃል" እንደሚለው አይነት።

በጣም ጥቂት

ይህ ልዑሉ በግልጽ ብዙ ገንዘብ ብሎ የማይቆጥረውን፣ አንድ ምናን ያመለክታል።

Luke 19:18

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ በሉቃስ 19፡11 የጀመረውን ግብረገባዊ ምሳሌ መናገሩን ቀጠለ።

ሁለተኛው

"ሁለተኛው አገልጋይ" (ተከታታይ ቁጥሮች የሚለውን ይመልከቱ)

ምናንህ፣ ጌታ ሆይ፣ ተጨማሪ አምስት ምናን አተረፈ

አገልጋዩ ያተረፈ መሆኑ ተጠቁሟል። "ጌታ ሆይ፣ ምናንህ ተጨማሪ አምስት ምናን እንዲያተርፍ አድርጌያለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ምናን

አንድ ምናን 600 ግራም ነው፤ ምናልባት የሰጣቸው ብር የተሰኘውን ማዕድን ሳይሆን አይቀርም። አንድ ምናን የ100 ቀን ሥራ ደሞዝ ያክላል፤ ሰዎች ወደ አራት ወራት ለሚጠጋ ጊዜ ሰርተው የሚያገኙት ክፍያ ነው። ይህ በሉቃስ 19፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

በአምስት ከተሞች ላይ ሹሜሃለሁ

"በአምስት ከተሞች ላይ ስልጣን ይኖርሃል"

Luke 19:20

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ በሉቃስ 19፡11 የጀመረውን ግብረገባዊ ምሳሌ መናገሩን ቀጠለ።

ሌላው መጣ

"ሌላው አገልጋይ መጣ"

ምናን

አንድ ምናን 600 ግራም ነው፤ ምናልባት የሰጣቸው ብር የተሰኘውን ማዕድን ሳይሆን አይቀርም። አንድ ምናን የ100 ቀን ሥራ ደሞዝ ያክላል፤ ሰዎች ወደ አራት ወራት ለሚጠጋ ጊዜ ሰርተው የሚያገኙት ክፍያ ነው። ይህ በሉቃስ 19፡13 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ። (መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን የክብደት መለኪያ የሚለውን ይመልከቱ)

በጨርቅ ጠቅልዬ አስቀመጥኩት

x

Luke 19:22

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ በሉቃስ 19፡11 የጀመረውን ግብረገባዊ ምሳሌ መናገሩን ቀጠለ።

በአንደበትህ ቃል

የእርሱ "ቃላት" የሚለው የሚያመለክተው እርሱ የተናገረውን በሙሉ ነው። "አንተ በተናገርከው መሰረት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ እኔ አስገዳጅ/ጨካኝ ሰው እንደሆንኩ ታውቃለህ

ልዑሉ አገልጋዩ ስለ እርሱ የተናገረውን ይደግማል። ነገሩ እውነት ነው እያለ አይደለም። "አንተ እኔን ጨካኝ ሰው ነው ብለሃል"

ገንዘቤን እንዲወልድ ለምን በ.... አላስቀመጥክም?

ልዑሉ ይህንን ጥያቄ የተጠቀመው ክፉውን አገልጋይ ለመገሰጽ ነው። "እንዲወልድ ገንዘቤን በ... ማስቀመጥ ነበረብህ።" (ቃለምልልሳዊ ጥያቄ የሚለውን ይመልከቱ)

ገንዘቤን በባንክ ማስቀመጥ

"ገንዘቤን ለባንክ ማበደር።" ባንክ በሌላቸው ባህሎች ይህንን "ገንዘቤን ለሰው ማበደር" በሚል ሊተረጉሙ ይችላሉ።

ባንክ

ባንክ የሰዎችን ገንዘብ በአስተማማኝነት የሚይዝ የንግድ ተቋም ነው። ባንክ ያንን ገንዘብ በትርፍ ለሌሎች ያበድራል። ስለዚህም በባንኩ ገንዘባቸው ላስቀመጡ፣ ተጨማሪ መጠን ወይም ወለድ፣ ይከፍላል።

ከወለዱ ጋር እወስድ ነበር

"ተቀማጩን ገንዘብ ከሚያስገኘው ወለድ ጭምር እወስድ ነበር" ወይም "ከእርሱ ትርፍ አገኝበት ነበር"

ወለድ

ትርፍ ገንዘባቸውን በባንክ ላስቀመጡ ሰዎች የሚከፍለው ገንዘብ ነው።

Luke 19:24

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ በሉቃስ 19፡11 የጀመረውን ግብረገባዊ ምሳሌ መናገሩን ቀጠለ።

ልዑሉ

ልዑል ይነግሣል። ይህ በሉቃስ 19፡12 ላይ እንዴት እንደ ተተረጎመ ይመልከቱ።

Luke 19:26

አያያዥ ሀሳብ፡

ኢየሱስ በሉቃስ 19፡11 የጀመረውን ግብረገባዊ ምሳሌ መናገሩን ቀጠለ።

እንዲህ እላችኋለሁ

ይህ የንጉሡ ንግግር ነበር። አንዳንድ ተርጓሚዎች ይህንን ቁጥር "ንጉሡም እንዲህ ሲል መለሰ፣ ‘እኔ ለእናንተ እላችኋለሁ'" ወይም "ነገር ግን ንጉሡ ‘ይህን እላችኋለሁ'" ብለው ሊጀምሩ ይችላሉ።

ላለው ሁሉ የበለጠ ይሰጠዋል

እርሱ ያለው ምናኑን በታማኝነት በመጠቀም ያገኘው ገንዘብ መሆኑ በውስጠ ታዋቂነት ተጠቁሟል። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "የተሰጠውን በሚገባ ለተጠቀመ ሁሉ፣ እኔ ተጨማሪ እሰጠዋለሁ" ወይም "እኔ የሰጠሁትን ሁሉ በሚገባ ለሚጠቀም ሁሉ እኔ ተጨማሪ እሰጠዋለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚሉትን ይመልከቱ)

ከሌለው ከእርሱ

ገንዘብ ሳይኖረው የቀረበት ምክንያት ምናኑን በታማኝነት አለመጠቀሙ መሆኑ ተጠቁሟል። "እኔ የሰጠሁትን በሚገባ ከማይጠቀምበት ሰው" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ይወሰድበታል

ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "እኔ ከእርሱ እወስድበታለሁ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)

እነዚህ የእኔ ጠላቶች

ጠላቶች የተባሉት በቀጥታ በዚያ እስከሌሎ ድረስ፣ አንዳንድ ቋንቋዎች "እነዚያ የእኔ ጠላቶች" ሊሉ ይችላሉ።

Luke 19:28

አያያዥ ሀሳብ፡

ይህ ስለ ዘኬዎስ የታሪኩ መጨረሻ ክፍል ነው። ይህ ቁጥር ከዚህ ታሪክ ክፍል በኋላ ኢየሱስ ምን እንዳደረገ ይነግረናል። (የታሪክ መጨረሻ የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ እነዚህን ነገሮች በተናገረ ጊዜ

"ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች በተናገረ ጊዜ"

ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ

ኢየሩሳሌም ከኢያሪኮ ከፍ ብላ ትገኛለች፣ ስለዚህ እሥራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም እንውጣ ማለታቸው የተለመደ ነበር

Luke 19:29

አጠቃላይ መረጃ፡

ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ደረሰ።

እንዲህም ሆነ

እዚህ ስፍራ ይህ ሀረግ የዋለው በታሪኩ ውስጥ አስፈላጊ ትዕይንትን ለማመልከት ነው። የእናንተ ቋንቋ ይህንን ለማድረግ መንገድ ካለው፣ እዚህ ላይ ያንን መጠቀም ትችላላችሁ። (አዲስ ትዕይንት ማስተዋወቅ የሚለውን ይመልከቱ)

በተቃረበ ጊዜ

"እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስን ነው። የእርሱ ዳመዛሙርትም አብረውት ይጓዙ ነበር።

ቤተ ፋጌ

ቤተ ፋጌ በደብረዘይት ተራራ የነበረች (ዛሬም ያለች) መንደር ስትሆን፣ ከቄድሮን ሸለቆ ባሻገር ትገኛለች። (ስሞች እንዴት ይተረጎማሉ የሚለውን ይመልከቱ)

ደብረዘይት የሚባል ተራራ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"ደብረዘይት የሚባል ተራራ/ኮረብታ" ወይም "'የወይራ ፍሬ ተራራ' ተብሎ የሚጠራ ኮረብታ"
ውርንጫ
"ውርንጭላ አህያ" ወይም " ገና እያደገ የሚገኝ ለመጋለቢያ የሚውል እንስሳ"
ማንም ያልተቀመጠበት/ያልጋለበው
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ማንም ያልተቀመጠበት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ማንም ቢጠይቃችሁ...ይፈልገዋል በሉ
ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ገና ያልተጠየቀን ጥያቄ ስለመመለስ ይነግራቸዋል። ሆኖም፣ በመንደሯ የሚኖሩ ሰዎች ጥያቄውን ይጠይቃሉ። (መላምታዊ ሁኔታዎች የሚለውን ይመልከቱ)
ማንም ሰው ቢጠይቃችሁ፣ 'ለምን ትፈቱታላችሁ'? በሉችሁ
ውስጣዊ ጥቅሱ እንደ ቀጥተኛ እንዳልሆነ ጥቅስ ሊተረጎም ይችላል። "ማንም ለምን ትፈቱታላችሁ ብሎ ቢጠይቃችሁ፣ እንዲህ በሉ" (በጥቅስ ውስጥ ጥቅስ እና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥቅሶች)
Luke 19:32
የተላኩት እነርሱ
ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ኢየሱስ የላካቸው ሁለቱ ደቀ መዛሙርት" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
ባለቤቶቹ
"የውርጫው ባለቤቶች"
በውርንጫው ላይ መደረቢያቸውን አደረጉ
"መጎናጸፊያቸውን በውርንጫው ላይ አደረጉ።" መደረቢያዎች ውጫዊ ልብስ ናቸው።
ኢየሱስ በላዩ ተቀመጠበት
"ኢየሱስን በውርንጫው ላይ አስቀመጡት"
መደረቢያዎቻቸውን አነጠፉ
"ሰዎች መደረቢያዎቻቸውን አነጠፉ።" ይህ ክብርን የመስጠት ምልክት ነው። (ትምዕርታዊ/ምልክታዊ ድርጊት የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 19:37
አሁን እየቀረበ ሲመጣ
"ኢየሱስ እየቀረበ ሲመጣ።" የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ከእርሱ ጋር ይጓዙ ነበር።
የደብረዘይት ተራራ ቁልቁል በሚወርድበት
"መንገዱ ከደብረዘይት ተራራ ቁልቁል ሲሄድ"
እነርሱ ባዩት ታላላቅ ሥራዎች
"ኢየሱስ ሲሰራ ባዩት ታላላቅ ነገሮች"
ንጉሡ የተባረከ ነው
ይህን ይናገሩ የነበረው ስለ ኢየሱስ ነበር።
በጌታ ስም
እዚህ ስፍራ "ስም" የሚለው የሚያመለክተው ስለ ሀይል እና ስልጣን ነው። እንደዚሁም፣ "ጌታ" የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው። (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
በሰማይ ሰላም
"በሰማይ ሰላም ይሁን" ወይም "በሰማይ ሰላም ማየት እንሻለን"
በላይ ክብር ይሁን
"በላይ ክብር ይሁን" ወይም "ክብር በላይ ማየት እንፈልጋለን።" "በላይ" የሚለው ቃል የሚመለከተው ሰማይን ነው፤ ይህም በሰማይ ለሚኖረው ለእግዚአብሔር ሜቶኖሚ/ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት/ ነው። "ሁሉም በሰማይ ላለው ለእግዚአብሔር ክብር ይስጥ" (ሜቶኖሚ/ ከአንድ ባህሪው በመነሳት ለነገሩ ስያሜ መስጠት የሚለውን ይመልከቱ)
Luke 19:39
በአያሌዎች መሃል
"በብዙ ሕዝብ መሃል"
ደቀ መዛሙርትህን ገስጻቸው
"ደቀ መዛሙርትህ እነዚህን ነገሮች ማድረግ እንዲያቆሙ ንገራቸው"
እኔ ግን እላችኋለሁ/እኔ እነግራችኋለሁ
ኢየሱስ ይህን ያለው ቀጥሎ ለሚናገረው ትኩረት ለመስጠትነው
እነዚህ እንኳን ዝም ቢሉ...ይጮሃሉ
ይህ መላምታዊ ሁኔታ ነው። ኢየሱስ :"አይ፣ እኔ አልገስጻቸውም፣ እነዚህ ሰዎች ዝም ቢሉ እንኳን... ይጮሃሉ" ብሎ ሲናገር ይህ ምንን እንደሚያመለክት አንደንድ ትርጉሞች ይህን ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። (መላምታዊ ሁኔታዎች እና ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚሉትን ይመልከቱ)
ድንጋዮች ይጮሃሉ
"ድንጋዮች ለምስጋና ድምጻቸውን ያሰማሉ"
Luke 19:41
ከተማይቱ
ይህ የሚያመለክተው ኢየሩሳሌምን ነው
ለእርሷ አለቀሰላት
x
Luke 19:43
አያያዥ ሀሳብ፡
ኢየሱስ መናገሩን ቀጥሏል
እናም
ቀጥሎ የሚሆነው ለኢየሱስ ሀዘን ምክንያት ነው
ጠላቶችሽ በአንቺ ላይ ...ቀን ይመጣልና
ይህ የሚያመለክተው አስጨናቂ ወቅት እንደሚያጋጥማቸው ነው። አንዳድ ቋንቋዎች "ስለሚመጣው" ጊዜ አይናገሩም። "እነዚህ ነገሮች ወደፊት በአንቺ ላይ ይደርሳሉ፡ ጠላቶችሽ..." ወይም "በቶሎ አስጨናቂ ጊዜ ይገጥምሻል። ጠላቶችሽ..."
አንቺ...የአንቺ
"አንቺ" የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር ነው፣ ምክንያቱም ኢየሱስ ለከተማይቱ የሚናገረው እንደ ሴት አድርጓት። ነገር ግን ይህ በእናንተ ቋንቋ ተፈጥሯዊ ካልሆነ የከተማዋን ሰዎች ለማመልከት "እናንተ" የሚለውን ብዙ ቁጥር መጠቀም ትችላላችሁ። (አንተ የሚለውን ተውላጠ ስም መልኮች እና የስርአተ ነጥብ ምልክት/ቃለአጋኖ የሚሉትን ይመልከቱ)
ቅጥር
ይህ የሚያመለክተው ሰዎች ከከተማዋ ውጭ እንዳይገቡ የሚያግድን ግንብ ነው።
ወደ ምድር ይጥሉሻል ደግሞም ከአንቺ ጋር ልጆችሽን
ኢየሱስ ለከተማይቱ ሰዎች የሚናገረው ለከተማይቱ ለራሷ እንደሚናገር አድርጎ ነው። በከተማዋ ለሚኖሩ ሰዎች የሴትየዋ ልጆች እንደሆኑ እና ስለዚህም የከተማዋ ልጆች እንደሆኑ አድርጎ ነው። ከተማይቱን መምታት ቅጥሯን እና አጥሯን መደምሰስ ማለት ሲሆን፣ልጆችዋን መምታት ማትም በውስጧ የሚኖሩትን ሰዎች መግደል ማለት ነው። "ሙሉ ለሙሉ ይደመስሱሻል፣ ደግሞም በውስጥሽ የሚኖሩትን ሁሉ ይገድላሉ" ወይም "ከተማችሁን ሙሉ ለሙሉ ይደመስሳሉ፣ ደግሞም ሁላችሁንም ይገድላሉ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (የስርአተ ነጥብ ምልክት/ቃለአጋኖ የሚለውን ይመልከቱ)
ድንጋይ በድንጋይ ላይ አይተዉም
"አንዲትንም ድንጋይ በስፍራዋ አይተዉም።" ይህ ጠላቶች በድንጋይ የተገነባችውን ከተማ ሙሉ ለሙሉ እንሚደመስሱ በኩሸት ለመግለጽ የቀረበ ነው። (ኩሸት እና አጠቃላይ አስተያየት የሚሉትን ይመልከቱ)
አላወቅሽም
"እውቅና አልሰጠሽም"
Luke 19:45
አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ በዚህ የታሪክ ክፍል ቀጣዩ ትዕይንት ነው። ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ወደ ቤተመቅደስ ገባ።
ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ
ቤተ መቅደሱ ወደሚገኝበት ወደ ኢየሩሳሌም እንደገባ ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልጋችሁ ይችላል። "ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ ከዚያም ወደ ቤተመቅደሱ አደባባይ ሄደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ቤተ መቅደስ ገባ
ወደ ቤተ መቅደስ ህንጻ መግባት የሚፈቀድላቸው ካህናት ብቻ ነበሩ። "ወደ ቤተመቅደስ አደባባይ ሄደ" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (ይሆናል ተብሎ የሚገመት ዕውቀት እና በውስጠ ታዋቂነት የሚገኝ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
አስወጣ
"አባረረ" ወይም "በሃይል አስወጣ"

ይህ ተጽፏል
ይህ ከኢሳይያስ የተወሰደ ጥቅስ ነው። ይህ በአድራጊ ዐረፍተ ነገር ሊገለጽ ይችላል። "ቅዱሳት ጽሁፎች ይናገራሉ" ወይም "ነቢያት በቅዱሳት ጽሁፎች እነዚህን ቃሎች ጽፈዋል" በሚለው ውስጥ እንደሚገኘው። (አድራጊ ወይም ተደራጊ የሚለውን ይመልከቱ)
የእኔ ቤት/ቤቴ
"የእኔ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ሲሆን "ቤት" የሚለው ቤተመቅደስን ያመለክታል።
የጸሎት ቤት
"ሰዎች ወደ እኔ የሚጸልዩበት ስፍራ"
የዘራፊዎች ጎሬ

x
Luke 19:47
አያያዥ ሀሳብ፡
ይህ የዚህ ታሪክ መጨረሻ ክፍል ነው። እነዚህ ቁጥሮች ዋናው የታሪኩ ክፍል ከተጠናቀቀ በኋላ ስለሚቀጥለው ድርጊት ይናገራሉ። (የታሪክ መጨረሻ የሚለውን ይመልከቱ)
በቤተ መቅደስ
"በቤተ መቅደስ አደባባይ/አጥር ግቢ" ወይም "በቤተ መቅደስ"
እርሱን በጥንቃቄ ይሰሙት ነበር
"ኢየሱስ ለሚናገረውን ከፍ ያለ ትኩረት ይሰጡ ነበር"

---

Chapter 20
Luke 20:1
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
የካህናት አለቆች፣ ጸሐፍትና ሽማግሌዎች በቤተ መቅደስ ኢየሱስን ጠየቁት
እንዲህም ሆነ
ይህ ሐረግ እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው የታሪኩ አዲስ ጅማሬን ለማመልከት ነው።
በቤተ መቅደስ
‹‹በቤተ መቅደሱ ግቢ›› ወይም፣ ‹‹በቤተ መቅደስ ውስጥ››
Luke 20:3
አጠቃላይ መረጃ
ኢየሱስ ለካህናት አለቆች፣ ለጸሐፍትና ለሽማግሌዎች መልስ ሰጠ።
እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው
‹‹ኢየሱስ መለሰ››
እኔ እጠይቃችኃለሁ፤ እናንተም ንገሩኝ
‹‹እኔ እጠይቃችኃለሁ›› የሚለው ዐረፍተ ነገር ነው። ‹‹እናንተም ንገሩኝ›› ትእዛዝ ነው።
ከሰማይ ነው ወይስ ከሰው
የዮሐንስ ሥልጣን ከሰማይ መሆኑን ኢየሱስ ያውቃል፤ ስለዚህም የጠየቀው መረጃ እንዲሰጡት አይደለም። የጠየቀው የአይሁድ መሪዎች የሚያስቡትን ሰሚዎቹ ፊት እንዲናገሩ ነው። ጥያቄው መልስ የማያሻው ቢሆንም፣ እንደ ጥያቄ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዮሐንስ ሰዎችን የማጥመቅ ሥልጣን ከሰማይ የመጣ ይመስላችኃል ወይስ ከሰው?›› ወይም፣ ‹‹ዮሐንስ ሰዎችን እንዲያጠምቅ የነገረው እግዚአብሔር ነው ወይስ ሰው?
ከሰማይ
‹‹ከእግዚአብሔር›› አይሁድ እግዚአብሔርን፣ ‹‹ያህዌ›› በሚለው ስሙ መጥራት አይፈልጉም። ስለ እርሱ ሲናገሩ ብዙውን ጊዜ፣ ‹‹ሰማይ›› በሚለው ቃል ይጠቀማሉ።
Luke 20:7
ስለዚህ መለሱ
‹‹ስለዚህ የካህናት አለቆች፣ ጸሐፍትና ሽማግሌዎች መለሱ›› ‹‹ስለዚህ›› የሚለው ቃል መጀመሪያ ከሆነው ነገር የተነሣ የተፈጸመ ነገር መኖሩን ያመለክታል። በዚህ ጊዜ ሉቃስ 20፥5-6 ላይ ተመካክረው የነበረ ቢሆንም መልስ መስጠት አልቻሉም።
ከየት እንደመጣ እንደማያውቁ መለሱ
ይህን በቀጥተኛ ጥቅስ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እነርሱም፣ ‹ከየት እንደሆነ አናውቅም› አሉ››
ከየት እንደ መጣ
‹‹የዮሐንስ ጥምቀት ከየት እንደ መጣ›› አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የዮሐንስ የማጥመቅ ሥልጣን ከየት እንደ መጣ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎችን እንዲያጠምቅ ለዮሐንስ ማን ሥልጣን እንደ ሰጠው››
እኔም አልነግራችሁም
‹‹እኔም ብሆን አልነግራችሁም›› ኢየሱስ መልሱን ሊነግሩት ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ሆነ አውቋል፤ ስለዚህ እርሱም ተመሳሳይ ነገር አደረገ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እናንተ እንዳልተናገራችሁ እኔም አልነግራችሁም››
Luke 20:9
አጠቃላይ መረጃ
ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ለሰዎች ምሳሌ መናገር ጀመረ።
ለገበሬች አከራዬ

‹‹በከፈሉት መጠን የወይን ገበሬዎች እንዲጠቀሙበት ፈቀደ›› ወይም፣ ‹‹ገበሬዎቹ እንዲጠቀሙበትና በኃላ እንዲከፍሉት ፈቀደ›› ክፍያው በገንዘብ ወይም በምርቱ መጠን ሊሆን ይችላል።
የወይን ገበሬዎች
እነዚህ የወይን ፍሬ የሚያመርቱ ሰዎች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወይን የሚያለሙ ገበሬዎች››
በተወሰነው ጊዜ
‹‹ሊከፍሉት የተስማሙበት ጊዜ›› ይህ ምርቱ ሲደርስ ሊሆን ይችላል።
ከወይኑ እርሻ ፍሬ
‹‹ከፍሬው ጥቂቱን›› ወይም፣ ‹‹ከእርሻው ካመረቱት ጥቂቱን›› ይህም ከፍሬው የሠሩት ነገር ፍሬውን ሸጠው ያገኙት ገንዘብ ሊሆን ይችላል።
ባዶ እጁን ሰደዱት
ባዶ እጅ፣ ‹‹ምንም› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ምንም ሳይከፍሉ ሰደዱት›› ወይም፣ ‹‹ፍሬ ሳይሰጡ ሰደዱት››
Luke 20:11
ደበደቡት
‹‹አገልጋዩን ደበደቡት››
አዋረዱት
‹‹አሳፈሩት››
ባዶ እጁን ሰደዱት
በዶ እጅ፣ ‹‹ምንም›› ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሳይከፍሉ ሰደዱት›› ወይም፣ ‹‹ፍሬ ሳይሰጡ ሰደዱት››
ሦስተኛ
‹‹ያም ሆኖ ሦስተኛ አገልጋይ›› ወይም፣ — ‹‹ያም ሆኖ›› የሚለው ባለ ርስቱ ሁለተኛውን አገልጋይ መላክ እንዳልነበረበት ግን እርሱ ከዚያም አልፎ ሦስተኛውን አገልጋይ እንደ ላከ ያመለክታል።
አቆሰሉት
‹‹አገልጋዩን ጐዱት››
ወደ ውጭ አወጡት
‹‹ከወይን እርሻው ቦታ አወጡት››
Luke 20:13
እንግዲህ ምን አደርጋለሁ?
ጥያቄው የወይኑ እርሻ ባለቤት ምን ማድረግ እንዳለበት በጥንቃቄ ማሰቡን አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የማደርገው ይህን ነው››
ገበሬዎቹ ሲያዩት
‹‹የወይን ገበሬዎቹ የባለቤቱን ልጅ ሲያዩ››
እንግደለው
ፈቃድ እየጠየቁ አልነበረም፤ ይህን ያሉት ወራሹን ለመግደል ሌሎችን ለማበረታታት ነው።
Luke 20:15
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ለሕዝቡ የሚናገረውን ምሳሌ አበቃ
ከእርሻው ቦታ ወደ ውጭ አወጡት
‹‹የወይን እርሻው ገበሬዎች ልጁ ከወይኑ እርሻ እንዲወጣ አስገደዱት››
እንግዲህ የወይን እርሻው ባለቤት እነርሱ ላይ ምን ያደርግባቸዋል?
ኢየሱስ ይህን የጠየቀው የእርሻው ባለቤት ገበሬዎች ላይ የሚያደርገውን በተመለከተ

የሰሚዎቹን ትኩረት ለመሳብ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንግዲህ፣ ባለቤቱ እነርሱ ላይ የሚያደርገውን ስሙ››
እንዲህ ያለውን አያምጣው
‹‹እንዲህስ አይሁን››
Luke 20:17
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ሕዝቡን ማስተማር ቀጥሏል።
ኢየሱስ ግን ተመለከታቸው
‹‹ኢየሱስ ግን ትኩር ብሎ አያቸው›› ወይም፣ ‹‹እርሱ ግን በቀጥታ አያቸው›› ይህን ያደረገው የነገራቸውን በመረዳታቸው ተጠያቂዎች መሆናቸውን ለማስገንዘብ ነው።
‹ድንጋይ... ግንበኞች› ተብሎ የተጻፈው ቃል ትርጉም ምንድነው?
ኢየሱስ ጥያቄውን ያቀረበው ሕዝቡን ለማስተማር ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ድንጋይ... ግንበኞች›› ተብሎ የተጻፈውን መረዳት ይኖርባችኋል።››
የተጻፈው
‹‹ይህ ቃል››
ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ
ይህ ከመዝሙር መጽሐፍ ትንቢቶች ሦስት ተለዋጭ ዘይቤዎች የመጀመሪያው ነው። ይህኛው መሲሑ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣ እግዚአብሔር ግን በጣም ጠቃሚ ያደረገው ድንጋይ መሆኑን ያመለክታል።
ግንበኞች
ይህ የሚያመለክተው መሲሑ ኢየሱስን የናቁትን የሃይማኖት መሪዎች ነው።
የማእዘን ድንጋይ
‹‹የሕንፃው ዋና ድንጋይ›› ወይም፣ ‹‹ከሕንፃው በጣም ጠቃሚ የሆነው ድንጋይ››
በእርሱ ላይ የሚወድቅ ሁሉ... ይደቃል
ይህ ሁለተኛው ተለዋጭ ዘይቤ መሲሑን የናቁ ሰዎች ድንጋይ ላይ ወድቀው እንደሚጐዱ ሰዎች መሆናቸውን ይናገራል።
ይደቃል
ይህ ድንጋይ ላይ የመውደቅ ውጤት ነው። በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስኪደቅ ይሰባበራል››
በላዩ የሚወድቅበት ግን
‹‹ድንጋዩ የሚወድቅበት ግን›› ይህ ሦስተኛው ተለዋጭ ዘይቤ እነርሱ ላይ ወድቆ እንደሚፈጭ ግዙፍ ድንጋይ መሲሑ የናቁት ላይ እንደሚፈርድ ያመለክታል።
Luke 20:19
እጃቸውን ለጭኑበት ፈለጉ
በዚህ ቁጥር፣ ሰው ላይ ‹‹እጅ መጫን›› ሰውየውን ማሰር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኢየሱስን የሚያስሩበት መንገድ ፈለጉ››
በዚያ ሰዓት
‹‹ወዲያው››
ሕዝቡን ፈሩ
ወዲያውኑ ኢየሱስን ያላሰሩት በዚህ ምክንያት ነበር። ሕዝቡ ኢየሱስን ያከብሩት ነበር፤ እርሱን ካሰሩት ሕዝቡ እነርሱ ላይ የሚያደርገውን የሃይማኖት መሪዎቹ ፈሩ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕዝቡን ስለ ፈሩ አላሰሩትም››
ሰላዮች ላኩ
‹‹ጸሐፍትና የካህናት አለቆች ኢየሱስን የሚከታተሉ ሰላዮች ላኩ››
በንግግሩ ስሕተት ሊያገኙበት
‹‹አንዳች መጥፎ ነገር ሲናገር ኢየሱስን መክሰስ ስለ ፈለጉ››
ለገዥው ኀይልና ሥልጣን
‹‹ግዛት›› እና ‹‹ሥልጣን›› አገረ ገዥው ኢየሱስ ላይ እንዲፈርድ እንደሚፈልጉ ለማመልከት ሁለት መንገዶች ናቸው። በአንዱ ወይም በሁለቱ አገላለጾች ሊተረጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ገዢው ኢየሱስን እንዲቀጣ››
Luke 20:21
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ይህ በዚህ የታሪኩ ክፍል የቀጣዩ ሁኔታ ጅማሬ ነው። ቤተ መቅደሱ ውስጥ ኢየሱስ በካህናት አለቆች ከተጠየቀ ወዲህ ጥቂት ጊዜ ሆኖት ነበር። አሁን ሰላዮቹ ኢየሱስን እየጠየቁት ነው።
እርሱን ጠየቁት
‹‹ሰላዮቹ ኢየሱስን ጠየቁት››
መምህር እናውቃለን... የእግዚአብሔር መንገድ››
ሰላዮቹ ኢየሱስን ለማሳሳት እየሞከሩ ነው። ስለ ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች አያምኑም።
እናውቃለን
‹‹እኛ›› የሚያመለክተው ሰላዮቹን ነው።
Luke 20:23
ኢየሱስ ግን ተንኰላቸውን አወቀ
‹‹ኢየሱስ ግን ምን ያህል ተንኰለኞች መሆናቸውን አወቀ›› ወይም፣ ‹‹ኢየሱስ ግን ሊያጠምዱት እንደሚሞክሩ አወቀ›› ‹‹የእርሱ›› የሚያመለክተው ሰላዮቹን ነው።
ዲናር
ይህ የአንድ ቀን ደመወዝ የሚሆን የሮማውያን የብር ሳንቲም ነው።
በላዩ ያለው የማን መልክና ስም ነው?
ሊያጠምዱት ለሚሞክሩ ሰዎች መልስ እንዲሆን ኢየሱስ በጥያቄ ተጠቀመ
መልክና ስም
‹‹ምስልና ስም››
Luke 20:25
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ይህ የሰላዮቹ ተልዕኮና ሉቃስ 20፥1 ላይ ተጀምሮ የነበረው ታሪክ ማብቂያ ነው።
እርሱ እንዲህ አላቸው
‹‹ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው››
ቄሣር
‹‹ቄሣር›› የሚያመለክተው የሮም ገዢን ነው።
እና የእግዚአብሔር
ካለፈው ሐረግ፣ ‹‹ስጡ›› የሚለውን መረዳት ይቻላል። እዚህ ላይ መደገም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እና ለእግዚአብሔር ስጡ››
እርሱ ከተናገረው ጥፋት ማግኘት አልቻሉም
‹‹ሰላዮቹ እርሱ ከተናገረው አንዳች ጥፋት ማግኘት አልቻሉም››
Luke 20:27
አጠቃላይ መረጃ
ምንም እንኳ ይህ የሆነው ቤተ መቅደሱ ግቢ ውስጥ ሊሆን ቢችልም፣ በእርግጠኝነት አናውቅም። ኢየሱስ ከአንዳንድ ሰዱቃውያን ጋር እየተነጋገረ ነው።
የሙታን ትንሣኤ የለም የሚሉ
ሰዱቃውያን ማንም ሰው ከሞት አይነሣም የሚሉ የአይሁድ ወገን መሆናቸውን ይህ ሐረግ ያመለክታል። አንዳንድ ሰዱቃውያን በትንሣኤ እንደሚያምኑ፣ አንዳንዶቹ ግን እንደማያምኑ አይደለም የሚያመለክተው።
ሚስት ያለው የአንድ ሰው ወንድም ልጅ ሳይወልድ ቢሞት
‹‹አንድ ሰው ሚስት ያለው ወንዱሙ ልጅ ሳይወልድ ቢሞትበት››
ሰውየው የወንድሙን ሚስት ያግባ
x
Luke 20:29
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ሰዱቃውያን ኢየሱስን መጠየቅ አበቁ
አጠቃላይ መረጃ
ቁጥር 29-32 ላይ ሰዱቃውያን ለኢየሱስ አጭር ታሪክ ነግረውታል። ይህ እንደ ምሳሌ የፈጠሩት ታሪክ ነው። ቁጥር 33 ላይ ስለ ነገሩት ታሪክ ኢየሱስን ጠየቁት።
ሰባት ወንድማማች ነበሩ
ይህ እውነት ሊሆን ይችላል፤ ምናልባትም ኢየሱስን ለመፈተን የፈጠሩትም ሊሆን ይችላል።
የመጀመሪያው... ሁለተኛው... ሦስተኛው
‹‹የመጀመሪው ወንድም... ሁለተኛው ወንድም... ሦስተኛው ወንድም››
Luke 20:34
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ለሰዱቃውያን መልስ መስጠት ጀመረ
የዚህ ዓለም ልጆች
‹‹የዚህ ዓለም ሰዎች›› ወይም፣ ‹‹የዚህ ዘመን ሕዝብ›› ይህ በሰማይ ካሉ ወይም ከትንሣኤ በኋላ ከሚኖሩት ጋር ሲነጻጸር ነው።
ያገባሉ፤ ይጋባሉ
በዚያ ባሕል ሰዎች ሴቶችን እንደሚያገቡ ሴቶችም ባሎቻቸውን እንደሚያገቡ ይናገራሉ። ይህን በሌላ መልኩ መናገር ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይጋባሉ››
በዚያ ዘመን የሚገባቸውን የሚያገኙ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ይገባችኋል የሚላቸው የዚያ ዘመን ሰዎች››

ከሙታን ትንሣኤ መቀበል የሚገባቸው
x
Luke 20:37
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
የኢየሱስ ለሰዱቃውያን መልስ መስጠት አበቃ
ሙታን እንደሚነሡ ግን ሙሴ እንኳ አመልክቷል
‹‹እንኳ›› የሚለው ቃል ቅዱሳት መጻሕፍት ሙታን ይነሣሉ ቢሉ እንኳ ሊደነቁ እንደማይችሉ፣ ሙሴ እንዲህ ያለ ነገር ይጽፋል ብለው ግን በፍጹም እንደማይጠብቁ ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሞቱ ሰዎች እንደሚነሡ ሌላው ቀርቶ ሙሴ እንኳ አመልክቷል፡፡››
ሙታን እንደሚነሡ
x
Luke 20:39
አንዳንድ ጸሐፍት መለሱ
‹‹አንዳንድ ጸሐፍት ኢየሱስን አሉት›› ሰዱቃውያን ለኢየሱስ ጥያቄ ሲያቀርቡ ጸሐፍትም እዚያ ነበሩ፡፡
እነርሱ
ይህ የሚያመለክተው ጸሐፍትን ወይም ሰዱቃውያንን ወይም ሁለቱንም መሆን አለ መሆኑ ግልጽ አይደለም፡፡ ዐረፍተ ነገሩን በአጠቃላይ መተው ይሻላል፡፡
ከእንግዲህ ማንም ሊጠይቀው አልደፈረም
ጥያቄ ለማቅረብ… ፈርተዋል›› ወይም፣ ‹‹ጥያቄ ማቅረብ አልደፈሩም›› የኢየሱስን ያህል መረዳት እንደሌላቸው ተረድተዋል፤ ያንን መናገር ግን አልፈለጉም፡፡ ይህን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የእርሱ አስተዋይ መልስ በድጋሚ ጅል አድርጐ እንዳያቀርባቸው ስለ ፈሩ ከእንግዲህ የተንኮል ጥያቄ አልጠየቁም››
Luke 20:41
አጠቃላይ መረጃ
ኢየሱስ ለጸሐፍት ጥያቄ አቀረበ
እንዴት ልጁ ነው… ይላሉ
‹‹እንዴት ልጁ ነው… አሉ›› ኢየሱስ ጥያቄውን ያቀረበው ስለ መሲሑ ማንነት ጸሐፍት እንዲያስቡ ለማድረግ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እስቲ ልጁ… ነው ማለታቸውን እናስብ›› ወይም፣ ‹‹ልጁ ነው… ሲሉ ስለ እነርሱ መናገር እፈልጋለሁ››
ይላሉ
ነቢያት፣ የሃይማኖት መሪዎችና በጠቅላላው የአይሁድ ሕዝብ መሲሑ የዳዊት ልጅ እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁሉም ይላል›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች ይላሉ››
Luke 20:45
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
አሁን ኢየሱስ ትኩረቱን በቀጥታ ደቀመዛሙርቱ ላይ አድርጐ በዋናነት ስለ እነርሱ መናገር ጀመረ
ተጠንቀቁ
‹‹ተጠበቁ››
ዘርፋፋ ቀሚስ ለብሰው መዞር ከሚወዱ
ረጅም ቀሚስ ምን ያህል አስፈላጊ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹አስፈላጊ ቀሚሳቸውን ለብሰው መዞር የሚወዱ››
የመበለቶችን ቤት የሚውጡ
‹‹የመበለቶችንም ቤት ይበላሉ›› ጸሐፍት የመበለቶችን ቤት የሚበሉ የተራቡ እንስሳት እንደ ሆኑ ተነግሯል፡፡ ‹‹ቤት›› የመበለቶቹን መኖሪያና ንብረታቸውን ሁሉ የሚያደርጉበትን ቦታ ይወክላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ከመበለቶቹም ንብረታቸውን ሁሉ ይወስዳሉ››
ለታይታ ብለውም ረጅም ጸሎት ያደርጋሉ
‹‹ዳድቅ እንደሆኑ ለማሳየት ረጅም ጸሎት ያደርጋሉ›› ወይም፣ ‹‹ሰዎች እንዲያዩዋቸው ረጅም ጸሎት ያደርጋሉ››
እንዲህ ያሉ ሰዎች የበለጠውን ፍርድ ይቀበላሉ
‹‹የበለጠ ከባድ ፍርድ ይቀበላሉ›› ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር በእርግጥ በጽኑ ይቀጣቸዋል››

---

Chapter 21
Luke 21:1
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ይህ በታሪኩ ቀጣይ ጉዳይ ነው፡፡ ሰዱቃውያን እርሱን በጠየቁበት ቀን (ሉቃስ 20፥27) ወይም በሌላ ቀን ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስተማር ጀመረ
ስጦታዎች
ስጦታዎቹ ምን እንደሆኑ መግለጽ ያስፈልግህ ይሆናል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የገንዘብ ስጦታዎች››
መሰብሰቢያ
ሰዎች ገንዘባቸውን ለእግዚአብሔር የሚሰጡበት ቤተ መቅደስ ውስጥ ካሉ ሳጥኖች አንዱ፡፡
አንዲት ድሀ መበለት
ይህ ወደ ታሪኩ አዲስ ገጸ ባሕርይ ለማስተዋወቅ የተለመደ መንገድ ነው፡፡
ሁለት ሳንቲሞች
‹‹ሁለት ትንንሽ ሳንቲሞች›› ወይም፣ ‹‹ሁለት የናስ ሳንቲሞች›› እነዚህ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸው ሳንቲሞች ናቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሁለት ሳንቲሞች›› ወይም፣ ‹‹ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸው ሁለት ትንንሽ ሳንቲሞች››
እውነት እላችኋለሁ
x
Luke 21:5
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ስለ መበለቷ ከመናገር ኢየሱስ ስለ ቤተ መቅደሱ ወደ ማስተማር ዞረ፡፡
ስጦታዎች
ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚሰጧቸው ነገሮች
የምታዩዋቸው እነዚህ ነገሮች
ይህ የሚያመለክተው ያማረውን ቤተ መቅደስና ጌጦቹን ሁሉ ነው፡፡
ቀን ይመጣል
‹‹ጊዜ ይመጣል›› ወይም፣ ‹‹አንድ ቀን››
ሌላው ላይ እንዳለ ሳይፈርስ አይቀርም
እዚህ ላይ አዲስ ዐረፍተ ነገር መጀመር ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌላው ላይ የሚቀር ሁሉም ይፈርሳሉ›› ወይም፣ ‹‹ሌላው ላይ የሚቀር ጠላቶች እያንዳንዱን ድንጋይ ያፈርሳሉ››
ሳይፈርስ… አንድ ድንጋይ አይቀርም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እያንዳንዱ ድንጋይ ከቦታው ይነሣል፤ ሁሉም ይፈርሳሉ››
ሌላው ላይ እንዳለ ሳይፈርስ አይቀርም
እዚህ ላይ አዲስ ዐረፍተ ነገር መጀመር ይቻላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሌላው ላይ የሚቀር ሁሉም ይፈርሳሉ›› ወይም፣ ‹‹ሌላው ላይ የሚቀር ጠላቶች እያንዳንዱን ድንጋይ ያፈርሳሉ››
Luke 21:7
እርሱን ጠየቁት
‹‹ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ጠየቁት›› ወይም፣ ‹‹የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ጠየቁት››
እነዚህ ነገሮች
ይህ ጠላቶች ቤተ መቅደሱን እንደሚያፈርሱ ኢየሱስ የተናገረውን ያመለክታል፡፡
እንዳትሳሳቱ
ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እየተናገረ ነበር፡፡ ‹‹እናንተ›› ብዙ ቁጥር ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሐሰት እንዳታምኑ›› ወይም፣ ‹‹ማንም እንዳያሳስታችሁ››
በስሜ
እርሱን እንወክላለን የሚሉ ሰዎች በእርሱ ስም ይመጣሉ፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ ነኝ እያሉ›› ወይም፣ ‹‹የእኔ ሥልጣን እንዳለው እየተናገረ››
እኔ እርሱ ነኝ
‹‹እኔ ክርስቶስ ነኝ›› ወይም፣ ‹‹እኔ መሲሑ ነኝ››
አትከተሏቸው
‹‹አትመኗቸው›› ወይም፣ ‹‹ደቀ መዛሙርቶቻቸው አትሁኑ››
ጦርነትና ዐመፅ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ጦርነት›› በአገሮች መካከል የሚደረግ ውጊያን፣ ‹‹ዐመፅ›› ሰዎች ከመሪዎቻቸው ጋር ወይም በአገራቸው ካሉት ሌሎች ጋር የሚያደርጉትን ግጭት ሊያመለክት ይችላል፡፡ አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ጦርነትና ረብሻ›› ወይም፣ ‹‹ጦርነትና አብዮት››

አትሸበሩ
‹‹እነዚህ ነገሮች አያሸብሯችሁ›› ወይም፣ ‹‹አትፍሩ››
መጨረሻው ወዲያው አይመጣም
ይህ የመጨረሻውን ፍርድ ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከጦርነቱና ከዐመፁ በኃላ ወዲያውኑ የዓለም ፍጻሜ አይሆንም›› ወይም፣ ‹‹እነዚህ ነገሮች ከተፈጸሙ በኃላ ወዲያው ዓለም አይጠፋም››
መጨረሻው
‹‹የማንኛውም ነገር መጨረሻ›› ወይም፣ ‹‹የዘመን መጨረሻ››
Luke 21:10
ከዚያም እንዲህ አላቸው
‹‹ከዚያም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ›› ይህ ካለፈው ቁጥር የቀጠለ የኢየሱስ ንግግር በመሆኑ፣ አንዳንድ ቋንቋዎች፣ ‹‹ከዚያም እንዲህ አላቸው›› የሚለውን አይጠቀሙም።
ሕዝብ በሕዝብ ላይ ይነሣል
እዚህ ላይ፣ ‹‹ሕዝብ›› የሕዝብ ሰዎችን፣ ‹‹ይነሣል›› የሚለው ደግሞ፣ ‹‹ያጠቃል›› የሚለውን የሚወክል ሊሆን ይችላል። ‹‹ሕዝብ›› የሚለው ቃል አጠቃላይ ሕዝቦችን እንጂ፣ አንድን ሕዝብ ማለት አይደለም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አንድ ሕዝብ የሌላውን ሕዝብ ያጠቃል›› ወይም፣ ‹‹የአንዳንድ ሕዝቦች ሌሎችን ሕዝቦች ያጠቃሉ››
ሕዝብ
ይህ አገሮችን ሳይሆን የተለያዩ ብሔሮችን ይወክላል።
መንግሥት በመንግሥት ላይ
‹‹ይነሣል›› የሚለው ቃል ካለፈው ሐረግ ውስጠ ታዋቂ ሲሆን፣ ያጠቃል ማለት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹መንግሥት በመንግሥት ላይ ይነሣል›› ወይም፣ ‹‹የአንዳንድ መንግሥታት ሕዝብ የሌላውን መንግሥታት ሕዝብ ይጠቃሉ››
በተለያዩ ቦታዎች ራብና ቸነፈር
‹‹ይኖራል›› የሚለው ቃል ካለፈው ሐረግ ውስጠ ታዋቂ ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በብዙ ቦታዎች ራብና ቸነፈር ይሆናል›› ወይም፣ ‹‹በተለያዩ ቦታዎች የራብና የበሽታ ጊዜ ይሆናል››
Luke 21:12
እነዚህ ነገሮች
ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ የተናገራቸው ነገሮች እንደሚሆኑ ነው።
እጆቻቸውን ይጭኑባችኋል
‹‹ይይዟችኋል›› ይህ አገላለጽ ደቀ መዛሙርቱ ላይ ሥልጣን የሚኖራቸውን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ያሥሩዋችኋል››
ያደርጋሉ
‹‹ሰዎች ያደርጋሉ›› ወይም ‹‹ጠላቶች ያደርጋሉ››
እናንተ
ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እየተናገረ ነበር። ‹‹እናንተ›› ብዙ ቁጥር ነው።
ወደ ምኩራብ ያስገቧችኃል
‹‹ለምኩራብ መሪዎች አሳልፈው ይሰጧችኃል››
ወደ ወህኒ
‹‹እስር ቤት ያስገቧችኋል›› ወይም፣ ‹‹ያሳስሩዋችኋል››
በስሜ ምክንያት
እዚህ ላይ፣ ‹‹ስም›› የሚያመለክተው ኢየሱስ ራሱን ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በእኔ ምክንያት›› ወይም፣ ‹‹እኔን ስለ ተከተላችሁ››
ስለ ምስክርነታችሁ
‹‹ስለ እኔ ምስክርነታችሁን እንድትነግሯቸው››
Luke 21:14
ስለዚህ
‹‹በዚህ ምክንያት›› ከሉቃስ 21፥10 ጀምሮ ኢየሱስ የተናገረውን ማንኛውንም ነገር ይመለከታል።
በልባችሁ አትወስኑ
እዚህ ላይ፣ ‹‹ልብ›› የሰዎቹን አእምሮ ይወክላል፤ አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹አእምሮአችሁን እንዳታዘጋጁ›› ወይም፣ ‹‹በቁርጥ እንዳትወስኑ››
ከጊዜው በፊት መከላከያ አታብጁ
‹‹ለሚነሣባችሁ ክስ ራሳችሁን ለመከላከል ምን እንደምትሉ ከጊዜው በፊት አታስቡ››
ተቃዋሚዎቻችሁ ሁሉ ሊቋቋሙትና ሊያስተባብሉት የማይችሉት ጥበብ
‹‹ከተቃዋሚዎቻችሁ አንዱ እንኳ፣ መቋቋምና ማስተባበል የማይችለው ጥበብ››
ቃላትና ጥበብ እሰጣችኃለሁ
‹‹የምትናገሩትን ጥበብ እሰጣችኃለሁ››
ቃላትና ጥበብ
ይህን በአንድ ዐረፍተ ነገር ማጣመር ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የጥበብ ቃል›› ወይም፣ ‹‹ጠቢብ ቃሎች››
Luke 21:16
ወላጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁ፣ ዘመዶቻችሁና ጓደኞቻችሁ አሳልፈው ይሰጧችኋል
ይህን በሌላ መልኩ መተርጐም ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሌላው ቀርቶ፣ ወላጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁ፣ ዘመዶቻችሁና ጓደኞቻችሁ እንኳ ለባለ ሥልጣናት አሳልፈው ይሰጧችኋል።››
Luke 21:20
ኢየሩሳሌም በጠላት ትከበባለች
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ሰራዊት ኢየሩሳሌምን ይከብባል››
ጥፋቷ ቀርቧል
‹‹በቅርቡ ትጠፋለች›› ወይም፣ ‹‹በቅርቡ ያጠፏታል››
ሽሹ
‹‹ከአደጋ አምልጡ››
በአገሩ
ይህ የሚያመለክተው ከኢየሩሳሌም ውጪ ያለውን ገጠር እንጂ፣ አገሩን በሙሉ አይደለም። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከከተማ ውጪ››
ወደ ከተማ ግቡ
‹‹ወደ ኢየሩሳሌም ግቡ››
እነዚህ የበቀል ቀኖች ናቸው
‹‹እነዚህ የቅጣት ቀኖች ናቸው›› ወይም፣ ‹‹ይህ እግዚአብሔር ይህቺን ከተማ የሚቀጣበት ቀን ይሆናል››
የተጻፉት ነገሮች ሁሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ከብዙ ጊዜ በፊት በቅዱሳት መጻሕፍት ነቢያት የጻፉዋቸው ነገሮች ሁሉ››
ይፈጸማል
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይሆናል››
Luke 21:23
ለሚያጠቡ
‹‹ልጆቻቸውን ለሚያጠቡ እናቶች››
በምድሪቱ ላይ ታላቅ መከራ ይሆናል
ይህም ማለት፣ 1) በምድሪቱ የሚኖሩ መከራ ይደርስባቸዋል፤ ወይም 2) ምድሪቱ ላይ መከራ ይደርስባታል።
ሕዝብ ላይ ቁጣ
‹‹ሕዝቡ ላይ ቁጣ የሚሆንበት ጊዜ›› እግዚአብሔር ይህን ቁጣ ያመጣል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ይህ ሕዝብ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣል›› ወይም፣ ‹‹እግዚአብሔር በጣም ይቆጣል ይህንም ሕዝብ ይቀጣል››
በሰይፍ ስለት ይወድቃሉ
‹‹በሰይፍ ስለት ይገደላሉ›› እዚህ ላይ፣ ‹‹በሰይፍ ስለት ይገደላሉ›› የሚለው በጠላት ወታደሮች መገደልን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹የጠላት ወታደሮች ይገድሏቸዋል››
ወደ አሕዛብም ሁሉ በምርኮ ይወሰዳሉ
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ጠላቶቻቸው ይይዟቸዋል፤ ወደ ሌሎች አገሮችም ይወስዷቸዋል››
ወደ አሕዛብ ሁሉ
‹‹ሁሉ›› የሚለው ወደ ብዙ አገሮች እንደሚወሰዱ አጽንዖት ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋለ ግነት ነው። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹ወደ ሌሎች ብዙ አገሮች››
ኢየሩሳሌም በአሕዛብ ትረገጣለች
ይህም ማለት፣ 1) አሕዛብ ኢየሩሳሌምን ድል አድርገው ይይዟታል። ወይም 2) አሕዛብ የኢየሩሳሌም ከተማን ይጠፋሉ ወይም 3) አሕዛብ የኢየሩሳሌምን ሕዝብ ይደመስሳሉ።
በአሕዛብ ትረገጣለች
ተለዋጭ ዘይቤው ኢየሩሳሌም የሌላ አገር ሰዎች እንደሚራመዱባትና በእግራቸውም እንደሚያደቋት ይናገራል። ይህ ባርነትን ያመለክታል። አማራጭ ትርጒም፣ ‹‹በአሕዛብ ድል ትሆናለች›› ወይም፣ ‹‹በሌላ ሕዝብ ትደመሰሳለች››


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የአሕዛብ ወቅት እስኪያበቃ››
Luke 21:25
ሕዝቦች ይጨነቃሉ
‹‹ሕዝቦች›› ውስጣቸው ያሉትን ሰዎች ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሰዎች ይጨነቃሉ››
ከባሕሩና ከሞገድ ድምፅ የተነሣ ይጨነቃሉ፤ ይታወካሉ
x
Luke 21:27
የሰው ልጅ ሲመጣ
ኢየሱስ ስለ ራሱ እየተናገረ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እኔ፣ የሰው ልጅ ስመጣ››
በደመና ሲመጣ
‹‹በደመና ውስጥ ሲመጣ››
በኀይልና በታላቅ ክብር
እዚህ ላይ፣ ‹‹ኀይል›› ዓለም ላይ ለመፍረድ የእርሱን ሥልጣን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ‹‹ክብር›› ደማቅ ብርሃንን ሊያመለክት ይችላል። አንዳንዴ እግዚአብሔር በደማቅ ብርሃን ታላቅነቱን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ኀያልና ክቡር›› ወይም፣ እርሱ ኀያልና እጅግ ክቡር ይሆናል››
ቁሙ
ሰዎች ሲፈሩ እንዳይታዩ ወይም ጉዳት እንዳይደርስባቸው በጣም ዝቅ ይላሉ። የሚያስፈራቸው ነገር ሳይኖር ግን ይነሣሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በልበ ሙሉነት ቁሙ››
ራሳችሁን ቀና አድርጉ
ራስን ቀና ማድረግ ወደ ላይ ማየት ማለት ነው። ራሳቸውን ወደ ላይ ቀና ሲያደርጉ አዳኛቸው ወደ እነርሱ ሲመጣ ያያሉ። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ተመልከቱ››
መዳናችሁ ስለ ቀረበ
የሚያድን እግዚአብሔር አንዳንዴ እርሱ የሚያደርገው መዳን እንደሆነ ተነግሯል። ‹‹መዳን›› የሚለው ቃል የነገር ስም ስለሆነ እንደ ግሥ ሊተረጐም ይችላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር ቶሎ ስለሚያድናችሁ››
Luke 21:29
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስተማሩን ሲቀጥል ምሳሌ እየነገራቸው ነው።
ሲያቆጠቁጡ
‹‹አዲስ ቅጠል ማደግ ሲጀምር››
በጋ ቀርቦአል
‹‹በጋ ሊጀምር ነው›› በእስራኤል በጋ የሚመጣው የበለስ ዛፍ ቅጠሎችን ማቆጥቆጥ ተከትሎ ሲሆን፣ በለስ የሚያፈራበት ጊዜ ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የመከር ጊዜ ሊጀምር ነው››
እናንተም እነዚህ ነገሮች ሲሆኑ ስታዩ
የበለስ ቅጠሎች ማቆጥቆጥ በጋ መምጣቱን እንደሚያመለክቱ፣ ኢየሱስ የተናገራቸው ምልክቶች መታየትም የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣቱን ያመለክታሉ።
የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች
‹‹እግዚአብሔር በቅርቡ መንግሥቱን ይመሠርታል›› አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እግዚአብሔር በቅርቡ ንጉሥ ሆኖ ይገዛል››
Luke 21:32
አያያዥ ዐረፍተ ነገሮች
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስተማር ቀጥሏል።
እውነት እላችኋለሁ
ይህ አገላለጽ ኢየሱስ የሚናገረው ጠቃሚ መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል።
ይህ ትውልድ
ይህም ማለት፣ 1) ኢየሱስ የተናገራቸውን የመጀመሪያ ምልክቶች የሚያይ ትውልድ ወይም 2) ኢየሱስ እየተናገረ የነበረው ትውልድ። የመጀመሪያው የበለጠ ይመረጣል።
እስኪሆን አያልፍም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ይህ ሲሆን በሕይወት ይኖራል››
ሰማይና ምድር ያልፋሉ
‹‹ሰማይና ምድር መኖራቸው ያበቃል›› እዚህ ላይ፣ ‹‹ሰማይ›› ከበላይ ያለውን ጠፈርና ሕዋ ያመለክታል።
ቃሌ በፍጹም አያልፍም
ይህን በሌላ መልኩ መግለጽ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ለዘላለም ይኖራል››
Luke 21:34
ልባችሁ እንዳይከብድ
‹‹ልብ›› የሰውን አእምሮና ሐሳብ ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹እንዳትያዙ››
እንዳይከብድ
ኀጢአት ሰው የሚሸከመው ሸክም እንደሆነ እዚህ ላይ ኢየሱስ ይናገራል።
ከመጠጥ የተነሣ
‹‹ብዙ ወይን ጠጅ መጠጣት እናንተ ላይ የሚያመጣው›› ወይም፣ ‹‹ስካር››
የሕይወት ጭንቀት
‹‹ስለዚህ ሕይወት በብዛት መጨነቅ››
ቀኑ እንደ ወጥመድ በድንገት እንዳይዛችሁ
እንስሳው ሳይጠብቀው ወጥመድ በድንገት እንደሚዘጋበት፣ ያም ቀን ሰዎች ባልጠበቁት ቀን ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ወጥመድ እንስሳው ላይ በድንገት እንደሚዘጋ፣ ያም ቀን ባልጠበቃችሁት ጊዜ ይሆናል››
ያ ቀን በድንገት ይዘጋባችኋል
ላልተዘጋጁና ላልጠበቁ ሰዎች የዚያ ቀን መምጣት በድንገት ይሆናል። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹ሕይወት፤ ካልተጠነቀቃችሁ ያ ቀን በድንገት ይዘጋባችኋል››
ያ ቀን
ይህ የሚያመለክተው መሲሑ የሚመለስበትን ቀን ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹የሰው ልጅ የሚመጣበት ቀን››
በሁሉም ላይ ይመጣል
‹‹ሁሉንም ይመለከታል›› ወይም፣ ‹‹በዚያ ቀን የሚሆነው ሁሉም ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል።››
በመላው ምድር ፊት
የላይኛው የምድር ክፍል እንደ የሰው ፊት ተነግሯል። ይህ ውጫዊ ክፍል ነው። አማራጭ ትርጉም፣ ‹‹በምድር ሁሉ ገጽታ ላይ›› ወይም፣ ‹‹በመላው ምድር ላይ››
Luke 21:36
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማስተማር አበቃ
ንቁ
‹‹ለእኔ መምጣት ተዘጋጁ››
ጳውሎስ ሊቀርብ ሲል አማራጭ ትርጉም: "ወታደሮቹ ጳውሎስን ለማቅረብ ዝግጅታቸው ስያጠናቅቁ" የወታደሮች ካምፕ ይህንን በ [ACT 21:34] ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት። ዋናው አለቃ የወታደሮች አለቃ ወይም የስድስት መቶ ወታደሮች አለቃ የግሪክ ቋንቋ ትናገራለህን? አንተ በእኛ ላይ አምጾ አራት ሺህ አሸባሪዎችን ይዞ ወደ በረሃው የገባው ግብጻዊው ሰው አይደለህምን? የወታደሮች አለቃ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ጳውሎስ ነው ብሎ ያሰበው ሰው አለመሆኑን በተረዳ ጊዜ መገረሙን ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም: "የግሪክ ቋንቋ መናገር ትችላለህ እንዲያውም አራት ሺህ አሸባሪዎችን ይዞ ወደ በረሃ የገባው ሰው ነህ።" አንተ ግብጻዊው ሰው አይደለህምን ጳውሎስ ወደዚያ አከባቢ ከመሄዱ ጥቂት ጊዜ በፊት ከግብጽ ምድር የመጣ አንድ ስሙ የማይታወቅ ሰው በኢየሩሰሌም ውስጥ በሮማዊያን ላይ ሰዎች እንዲያምጹ አድርጓል። ከዚያም "ወደ ምድረበዳ አምልጦ ሄዷል"። ስለዚህም ይህ የወታደሮች አለቃ ጳውሎስ ይህ ሰው ይሆን እንደሆነ አስቧል። አራት ሺህ አሸባሪዎችን "ከእነርሱ ጋር የማይስማሙ ሰዎችን ሁሉ የሚገድሉ አራት ሺህ ወንዶች"

Acts 21:39

የሐዋርያት ሥራ 21፡ 39-40

እጠይቅሃለሁ "እለምንሃለሁ" ወይም "እኔ አንተን እጠይቃለሁ" ፍቀድልኝ "እባክህ ፍቀድልኝ" ወይም "እባክህ ፈቃድ ስጠኝ" አለቃ "የወታደሮች አለቃ ወይም የስድስት መቶ ወታደሮች አለቃ" ጳውሎስ በደረጃዎቹ ላይ ቆሞ በዚህ ሥፍራ ላይ "ደረጃ" የሚለው ቃል ወደ ወታደሮች ካንፕ መውጫ ደረጃዎችን የሚያመለክት ነው።

---

Chapter 22

Acts 22:1

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 1-2

አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ውስጥ ለተሰበሰበው ሕዝብ መናገር ጀመረ። በቁጥር 2 ላይ ጳውሎስ እየጠናገረ ሳይሆን የኃላ ታሪክ መረጃ እየተሰጠ ነው። ወንድሞች እና አባቶች ይህ በጳውሎስ እድሜ ላይ ላሉ ሰዎች እንዲሁም ከእርሱ እድሜ በላይ የሆኑ ሰዎችን በትህትና መናገር ነው። የመከራከሪያ ሀሳቤን አድምጡኝ "እባካቸሁ የመከራከሪያ ሀሳቤን አድምጡ" ይህንንም አሁን አቀርብላችኋለሁ "አሁን እኔ ለእናንተ አቀረባለሁ" በዕብራይስጥ ቋንቋ "በእነርሱ የዕብራይስጥ ቋንቋ"

Acts 22:3

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 3-5

በዚህች ከተማ በገማሊያ እግር ሥር ሆኜ ተምሬያለሁ "በዚሁ በኢየሩሳሌም ውስጥ ገማሊያ በተባለው መምህር ተማሪ ነበርኩኝ" የቀደምት አባቶቻችን ሕግ በደንብ እከተል ዘንድ በደንብ ተምሬያለሁ አማራጭ ትርጉም: "እነርሱ የአባቶቻችንን ሕግ መከተል እችል ዘንድ በሚገባ አስተምረውኛል" ወይም "የተማሪኩት ትምህርትም የአባቶቻችንን ሕግጋት በትክክል መከተል እንዲችል ነው" ለእግዚአብሔር የቀናው ነኝ "የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ የማምነውን ነገር የማደርገው ከልቤ ነው" ወይም "እኔ ለእግዚአብሔር የማደርገውን አገልግሎት የማደርገው በሙሉ ልቤ ነው" ዛሬ

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እናንተ ሁላችሁ እንደሚታደረጉት ጳውሎስ ራሱን ከሕዝቡ ጋር በማነጻጸር። አማራጭ ትርጉም: "እናንተ ሁላችሁ ዛሬ እንደሚታደርጉት" ወይም "ዛሬ እንደሚታደርጉት ሁሉ።" በዚህ መልኩ በዚህ ሥፍራ ላይ “መልኩ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በኢየሩሳሌው ውስጥ በአንድ ሥፍራ የተሰበሰቡትን አማኞችን ነው። ይህንን በ ACT 9:2 ምን ብለህ እንደተረጎምህ ተመልከት። ለመግደል ይህንን መንገድ የሚከተሉ ሰዎች ለመግደል ጳውሎስ ፈቃደኛ ነበር። ምስክር በመሆን "በመመስከር" ወይም "ምስክር በመሆን" ከእርሱ ደብዳቤ ተቀብዬ ነበር "ከሊቀ ካህናት እና ሽማግሌዎች ደብዳቤ ተቀብዬ ነበር" አሥሬ አመጣቸው ዘንድ ትዕዛዝን ተቀብዬለሁ አመራጭ ትርጉም: "በሠንሰለት አስሬ አመጣቸው ዘንድ ትዕዛዝ ሰጥተውኝ ነበር"

Acts 22:6

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 6-8

እንዲህ ሆነ ጳውሎስ ይህንን መንገድ መከተል ከመጀመሩ በፊት የሆነውን ነገር ነከመናገር በደማስቆስ መንገድ ላይ ጌታ እንዴት እንደጠራው ወደ መናገር ያደረገውን ሽግግር ያሳይለት ዘንድ ይህንን ሀረግ ተጠቅሟል።

Acts 22:9

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 9-11

የእርሱ ድምፅ "የኢየሱስ ድምፅ" ከብርሃኑ ድምቀት የተነሳ ማየት እንኳ አልቻልኩም "ከብርሃኑ ድምቀት የተነሣ ከሌሎች ሁሉ ወደኋላ ቀረው"

Acts 22:12

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 12-13

እንደ ሕጉ ከሆነ እኔ ከሌሎች ሁሉ ይልቅ የተሰጠሁ ነበርኩ አናኒያስ የእግዚአብሔር ሕግ በመጠበቅ ረገድ በጣም ጥንቁቅ ነበር። የተመሠከረለት ነበር "በሌሎች ዘንድ ጥሩ ስም ነበረው" በተመሳሳይ ሰዓት ይህ ወዲያው የሆነን ነገር ለመግለጽ ጥቅም ላይ የሚለው የተለመደ መንገድ ነው። አማራጭ ትርጉም: "በዚያው ወቅት" ወይም "ወዲያውም።"

Acts 22:14

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 14-16

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ የገዛ ታሪኩን እየተናገረ አናንያስ የተናረወን ነገር መናገሩን ቀጥሏል። ይህ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ለነበሩተ ሰዎች ያደረገው ንግግር ነው። ከዚያም እንዲህ አለ "ከዚያም አናናስ እንዲህ አለ" የእርሱ ፈቃድ "እግዚአብሔር ያቀደው እና እንዲሆን ያደረገውን ነገር" ምን ትጠብቃለህ? ይህ ጥያቄ ጳውሎስ እንዲጠመቅ ለማበረታታት የቀረበ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ብዙ አትጠብቅ!" ወይም "ብዙ አትዘገይ!" ኃጢአትን ታጠብ ልክ ሰውነትን በመታጠብ በሰውነት ላይ ያለን ቆሻሻ እንደሚናስወግድ ሁሉ የኃጢአት ይቅርታን ለማግኘት የኢየሱስን ስም መጥራት የሰውን ውስጥ ከኃጢአት ያነጻል። አማራጭ ትርጉም: "የኃጢአት ይቅርታን ለማግኘት መጠየቅ።"

Acts 22:17

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 17-18

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ስለተመለከተው የኢየሱስ ራዕይ መናገር ጀመረ። ራዕይ ተሰጠኝ "ራዕይ ተገለጠልኝ" ወይም "እግዚአብሔር ለእኔ ራዕይ ሰጠኝ" እንዲህ ሲለኝ አየሁት "እንዲህ ስለኝ ኢየሱስን አየሁት" አልተቀበሉትም "በኢየሩሳሌም ያሉት አልተቀበሉትም"

Acts 22:19

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 19-21

አያያዥ ዓረፈተ ነገር: በዚህ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ ኢየሱስን በራዕይ መመልከቱን መተረኩን ያበቃል። ከዚህ በተጨማሪ ይህ ንግግሩ በኢየሩሳሌም ለነበሩት የእርሱን ንግግር ተሰብስበው ያደምጡ ለነበሩት ሰዎች ያደረገው ንግግር ማብቂያም ነው። እነርሱ ራሳቸው ያውቁታል ይህ የሚያመለክተው በኢየሩሳሌም የነበሩትን የማያምኑ አይሁዳዊያንን ነው። "በግርፋት ቀጥተው ሊለቁት አሰቡ" በሁሉም ምኩራቦች ውስጥ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ዙሪያ ባሉ ምኩራቦች ውስጥ የሚሳተፍ ማንኛውንም የአይሁድ አማኝ ይፈልግ ነበር። የእስጥፋኖስ ደም . . . በእርሱ ላይ ተረጭቶ ነበር ይህ የአነጋገር ዘይቤ ጥቅም ላይ የሚውለው አንድ ሰው ተገደለ ብሎ ለመግለጽ ነው። አማራጭ ትርጉም: "እስጥፋኖስን ገደሉት።"

Acts 22:22

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 22-24

እንደዚህ ያለውን ሰው ከምድር አስወግደው፥ "ግደለው" ይህንን ስያደርጉ ሳሉ "ይህንን ስያደርጉ ሳሉ" (UDB.) ይህ ቃል በተመሰሳይ ሰዓት የሆኑ ሁለት ነገሮችን የሚያሳይ ነው። ጳውሎስን ይዘው እንዲመጡ አዘዙ አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስን ይዘውት ይመጡ ዘንድ ወታደሮቹን አዘዘ" የወታደሮች ካምፕ ይህንን በ ACT 21:34 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። "አዛዡ እራሱ"

Acts 22:25

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 25-26

መግረፊያ አለንጋ። ሮማዊ እና በሕግ ቅጣት ያልተጣለበትን ሰው መግረፍ በሕግ ተፈቅዷልን? ይህ ጥያቄ ጥቅም ላይ የዋለው የመቶ አለቃው ጳውሎስን ለመግረፍ ምን ስልጣን እንዳለው ለመጠየቅ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ሮማዊ የሆነን እና ያልተፈረደበትን ሰው ለመግረፍ ምንም ስልጣን የለህም!" ምን ለማድረግ አስበሃል? አዛዡ ጳውሎስን ለመግረፍ የነበረውን እቅድ እደገና እንዲያስብበት የቀረበ ጥያቄ ነው። "ይህንን ማድረግ የለብህም!"

Acts 22:27

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 27-29

እንዲህ አለው "ለጳውሎስ ሂድ አለው" የተገኘ ዜግነት "ዜግነት ያገኘሁ" ወይም "ዜጋ የሆንኩ" የተወለድኩት ሮማዊ ሆኜ ነው "የተወለድኩት የሮም ዜግነት ካላቸው ቤተሰብ ነው፤ ስለዚህም የሮም ዜግነት ያገኘኹት በውልደት ነው።" ይህንን ሊያደረግ የነበረው ሰው "ይህንን ለማድረግ ያቀደው ሰው" ወይም "ይህንን ለማድረግ እየተዘጋጀ ያለው ሰው"

Acts 22:30

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 30-30

ዋናው አዛዡ የስድስት መቶ ወታደሮች አለቃ ጳውሎስን ይዞት ወረደ ከወታደሮች ካምፕ ወደ ቤተ መቅደሱ የፍርድ አደባባይ ወደ ታች የሚወርድ ቀጥተኛ የሆነ መንገድ አለ።

---

Chapter 23

Acts 23:1

የሐዋርያት ሥራ 23፡ 1-3

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ከሸንጎው እና በሊቀ ካህኑ ፊት ይቆም ዘንድ ይዘውት መጡ። ACT 22:30. አናኒያስ ይህ የዚህ ሰው ስም ነው። ነጭ ቀለም የተቀባ ግድግዳ ይህ ግድግዳ ንጹሕ ይመስል ዘንድ ቀለም መቀባቱን ለማመልከት ነው። ጳውሎስ ለአናኒያስ እንዲህ ሲል ነገረው። ግድግዳ ንጹሕ ይመስል ዘንድ ቀለም እንደሚቀባው ሁሉ እንዲሁም አናኒያስም በውጪ መልካም ይመስላል ነገር ግን ውስጡ ግን በክፋት የተሞላ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ነጭ ቀለም የተቀባ ግድግዳ።" እንድገረፍ አዘዘ "ሰዎች ይገርፉኝ ዘንድ አዘዘ" ወይም "እነዚህ ሰዎች ይደበድቡኝ ዘንድ አዘዘ"

Acts 23:4

የሐዋርያት ሥራ 23፡ 4-5

የእግዚአብሔርን ሊቀ ካህን እንደዚህ እንዴት ትሰድባለህ? ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ በመጠቀም ጳውሎስ የተናገረው ነገር አግባብነት እንዳሌለው ለማሳየት ጥረት አድርገዋል። አማራጭ ትርጉም: "የእግዚአብሔር ሊቀ ካህን አትሳደብ!" ወንድም እኔ ይህ ሰው ሊቀ ካህን መሆኑን አላወኩም ነበር አማራጭ ትርጉሞች 1) "ጳውሎስ አላወቀም ነበር ምክንያቱ የዚህ ሰው ሁኔታው ሁሉ እንደ ሊቀ ካህን አይደለም" ወይም 2) "ጳውሎስ ከኢየሩሳሌ ለብዙ ጊዜያት ርቆ ስለነበር አዲስ ሊቀ ካህን መሾሙን አያውቅም ነበር።"

Acts 23:6

የሐዋርያት ሥራ 23፡ 6-8

ተፈርዶብኛል "አንተ በእኔ ላይ ፈርደሃል" ሸንጎው እርስ በእርሱ ተከፋፈለ "የሸነንጎው አባላት መስማማት አልቻሉም" ትንሰዔ የለም፣ መላእክት እና መናፈስት የሉም አማራጭ ትርጉሞች 1) በትንሳዔ፣ በመለአክት ወይም በመናፍስ አያምኑም ወይም 2) እግዚአብሔር ሰዎች እን መለአክት ወይም መናፍስት አድርጎ ሰዎችን ከሞት አያስነሳም።

Acts 23:9

የሐዋርያት ሥራ 23፡ 9-10

ከዚህም የተነሣ ከፍተኛ ኹከት ተነሣ “ስለዚህም” የሚለው ቃል አሁን የሆነው ነገር የሆነበት ምክንያት ከዚህ በፊት ከሆነው ነገር የተነሣ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ከዚህ በፊት የተከናወወነው ነገር ጳውሎስ ስለ ትንሳዔ ያለውን እምነት መግለጹ ነበር። መናፍስት ወይን መለአክት ቢያናግሩትስ? ፈርሳዊያን መላእክት እና መናስፍት



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንዳሉና ከሰዎች ጋር እንደሚነጋገሩ በመግለጽ ሳዱቃዊያንን ገሰጾዋቸው፡፡ አማራጭ ትርጉም: "መላእክት ወይም መናፈስት ተናግረውት ይሆናል" ጳውሎስን እንደ ጨርቅ ልበጣጥሱ ፈለጉ "አካለዊ ጉዳት ባደረሱበት ነበር" በጉልበት ወሰዱት "ጳውሎስን በጉልበት ወሰዱት" ወደ ወታደሮች ካምፕ ወሰዱት ይህንን በ ACT 21:34 ላይ ምን ብለህ እንደ ተረጎምከው ተመልከት፡፡
Acts 23:11
የሐዋርያት ሥራ 23፡ 11-11
መሰሰከረ አማራጭ ትርጉም 1) የግል ድነትን እንዴት እንደገኘ "መናገር" ወይም "መመሰከር" ወይም 2) የድነት መልዕክት መናገር፡፡
Acts 23:12
የሐዋርያት ሥራ 23፡ 12-13
አጠቃላይ መረጃ: አጠቃላይ መረጃ: ይህ በጳውሎስ ታሪክ ውስጥ አዲስ ስለተፈጠረ ነገር ነው፡፡ አይሁዳዊያን ጳውሎስን ለመግደል ተማከሩ፡፡ ተማማሉ "አንድ ነገር ለማድረግ በመደበኛ ሁኔታ መስማማት" አርባ ወንዶች "40 ወንዶች"
Acts 23:14
የሐዋርያት ሥራ 23፡ 14-15
ሄዱ "አርባ አይሁዶች ሄዱ" ስለዚህም ይህ ቃል ከዚህ በፊት በተነገረ አንድ ነገር ምክንያት ይህ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ አይሁዳዊያኑ ለሽንጎው የደረሱበትን ስምምነት በመናገራቸው ምክንያት ነው፡፡ ወደ እናንት እናመጣው ዘንድ "ጳውሎስን ከወታደሮች ካምፕ ይዘውት በቤተ መቅደሱ ውስጥ ወደሚገኙት ሽንጎዎች ዘንድ ለማምጣት"
Acts 23:16
የሐዋርያት ሥራ 23፡ 16-17
ተኝተው ይጠባበቁ ነበር ጳውሎስን ለመግደል ቃል የተገባቡት ሰዎች በጳውሎስ በጉልበት ነጥቀው ለመውሰድ ተዘጋጅተው ነበር፡፡ የወታደሮች ካምፕ በ ACT 21:34 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡ አንድ ነገር ሊነግረው ይፈልግ ነበር "ወጣቱ ለወታደሮች አለቃ የሆነ ነገር ሊነግረው ፈልጎ ነበር"
Acts 23:18
የሐዋርያት ሥራ 23፡ 18-19
እስረኛው ጳውሎስ ወደ እርሱ ዘንድ አስጠራኝ "እስረኛው ጳውሎስ እንድመጣ እና ከእርሱ ጋር እንዳወራ ጠየቀኝ" ይህ ወጣት የወታደር አለቃው ወጣቱን በእጆቹ ይዞት ስለነበር ይህ የጳውሎስ የአጎት ልጅ እድሜው ከ12 እስከ 15 ይሆናል፡፡
Acts 23:20
የሐዋርያት ሥራ 23፡ 20-21
አጠቃላይ መረጃ: የጳውሎስ የአጎቱ ልጅ ለወታደሮቹ አለቃ ጥያቄ መልስ ይሰጥ ነበር፡፡ አርባ ወንዶች "40 ወንዶች" ተኝተው ይጠብቁት ነበር "ጳውሎስን በጉልበት ለመንጠቅ ዝግጁዎች ነበሩ"
Acts 23:22
የሐዋርያት ሥራ 23፡ 22-24
ሁለት መቶ አለቆች "2 መቶ አለቆች" ሰባ ፈረሰኞች "70 ፈረሰኞች" ሁለት መቶ ጦረኞች "200 ጦር የታጠቁ ወታደሮች" ከሌሊቱ ሦስተኛው ሰዓት ላይ ከሌልቱ ሰጠኝ ሰዓት ላይ፡፡ ፊሌክስ አገረገዥው የዚያ አከባቢ ገዥ የሆነው ፍልክስ በቄሳሪያ ይኖር ነበር፡፡
Acts 23:25
የሐዋርያት ሥራ 23፡ 25-27
አጠቃላይ መረጃ: የወታደሮቹ አለቃ ለዘገረ ገዥው ፍልክስ የላከው ደብዳቤ የጀመረው እንዲህ ነው፡፡ ከቀላውዴዎስ ሉስዮስ ወደ ክቡር አገረ ገዙ ወደ ፊልክስ፤ ሰላም ለአንተ ይህ መደበኛ የደብዳቤ መግቢያ ነው፡፡ ቀላውዴዎስ ሉስዮስ የወታደሮቹ አለቃ ስም ነው፡፡ ፍልክስ አገረገዥው ፍሌክስ ለዚያ አከባቢ በአጠቃላይ በሮም የተሸመ አገረ ገዥ ነው፡፡ ልገድሉት ነበር አማራጭ ትርጉም: "አይሁዳዊያን ጳውሎስን ለመግደል ዝግጁዎች ነበሩ" መጡ "ደረሱ" ወይም "ወደፈለጉበት ቦታ ደረሱ"
Acts 23:28
የሐዋርያት ሥራ 23፡ 28-30
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ይህ የወታደሮቹ አለቃ ለሀገረ ገዥው ፍልክስ የጻፈው ደብዳቤ ማብቂያ ነው፡፡ ማወቅ እፈልጋለሁ በዚህ ስፍራ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ቀላውዴዎስ ሉስዮስ ነው፡፡ ከሰሱት "አይሁዳዊያን ጳውሎስን ከሰሱት" ከዚያ ነገሩ ምን እንደሆነ ተገነዘብኩ አማራጭ ትርጉም: "በኋላ ላይ ገባኝ"
Acts 23:31
የሐዋርያት ሥራ 23፡ 31-33
ስለዚህም ወታደሮቹ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ተግባራዊ አደረጉ በዚህ ሥፍራ ላይ “ስለዚህ” የሚለው ቃል ከዚህ በፊት በተነገረ አንድ ነገር ምክንያት ይህ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የወታደሮቹ አለቃ ለወታደሮቹ የሰጣቸው ትዕዛዝ ጳውሎስን እንዲጠብቁት ነው፡፡ እንቲጳጥሪስ ይህች ሄሮዶስ ለአባቱ አንቶጳጥሪ ክብር ሲል የገነባት ከተማ ናት፡፡ በዘመናችን እስራኤል ውስጥ ትገኛለች፡፡
Acts 23:34
የሐዋርያት ሥራ 23፡ 34-35
የኪልቅያ ሰው እንነደሆነ በተረዳ ጊዜ "አገረ ገዥው ጳውሎስ የኪልቅያ ሰው እንደሆነ ባወቀ ጊዜ" ይጠብቁት ዘንድ አዘዘ "ወታደሮቹ ጳውሎስን ይጠብቁት ዘንድ አዘዘ" ወይም "ወታደሮቹ ጳውሎስን ያስሩት ዘንድ አዘዘ"

---

## Chapter 24

Acts 24:1
የሐዋርያት ሥራ 24፡ 1-3
አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ በቄሳሪያ የፍርድ ሂደቱን በመከታተል ላይ ይገኛል፡፡ ጠርጡለስ የተባለ ሰው ለአገረ ገዥው ፍልክስ በጳውሎስ ላይ የቀረበው ክስ ምን እንደሆነ አቀረበ፡፡ ከአምስት ቀናት በኋላ "የሮም ወታደሮች ጳውሎስን ወደ ቄሳሪያ ከወሰዱት በኋላ ባሉት አምስት ቀናት ውስጥ" አናኒያስ በ ACT 23:1 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምክ ተመልከት፡፡ ተናጋር "ጠበቃ" ወይም "በፍርድ ቤት አንድን ሰው ከሶ የሚቆም ሰው” ወደዚያ ሄደ "went to Caesarea where Paul was" ጠርጢለሰስ ይህ የሰው ስም ነው፡፡ ጳውሎስ በአገረ ገዥው ፊት ሲቆም "ጳውሎስ በፍርድ ቤቱ ውስጥ ፈራጅ በሆነው በሀገረ ገዥው ፊት ሲቆም" እርሱን መክሰስ ጀመረ "እርሱን ተቃውሞ መናገር ጀመረ" ወይም "የሮምን ሕግ መተላለፉን በማሳየት ጳውሎስን መክሰስ ጀመረ" በአንተ ምክንያት በዚህ ሥፍራ ላይ “አንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሀገረ ገዥውን ነው፡፡ ሠላም አለን "አንተ የሚታስተዳድራቸው ሕዝቦች ሠላም አላቸው" ፍልክስ ይህንን በ ACT 23:25 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት፡፡
Acts 24:4
የሐዋርያት ሥራ 24፡ 4-6
ስለዚህም ብዙ ላቆይህ አልፈልግም አማራጭ ትርጉሞች 1) ስለዚህም ጊዜህን መሻማት አልፈልግም (UDB) ወይም 2) ስለዚህም ላደክምህ አልፈልግም፡፡ በአጭሩ የሚናገረውን አድምጠኝ "አጭር ንግግሬን አድምጥልኝ" ይህ ሰው እንዲህ ያለ ነገር ስያደርግ አግኝተነዋል “እኛ” የሚለው ቃል አናኒያስ፣ የተወሰኑ ሽማግሌዎች እና ጠርጠሊየስን ያመለክታል፡፡ አማራጭ ትርጉም: “ጳውሎስን ተመልክተነዋል” ወይም “ጳውሎስ ይህንን እንዳደረገ አውቀናል" በዓለም ያሉ አይሁዶች ሁሉ በዚህ ሥፍራ ላይ “ሁሉም” የሚለው ቃ በጳውሎስ ላይ የቀረበው ክስ ግነት ተሞልቶበት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም: "በዓለም ያሉ አይሁዳዊያን ሁሉ”፡፡
Acts 24:7
የሐዋርያት ሥራ 24፡ 7-9
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጠርጡለስ ለአገረ ገዥው ፍልክስ በጳውሎስ ላይ ያቀረበው ክስ አጠናቀቀ፡፡ ጳውሎስን በጠየቁት ጊዜ "ጳውሎስን ባወጣጡት ጊዜ" ወይም "በችሎት ፊት እንደሚደረገው ጥያቄ በተጠየቀ ጊዜ" እኛ የምከሰው ስለ … ነው "ጳውሎስ ይህንን በማድረጉ ነው የሚንከሰው" ወይም "ጳውሎስ ይህንን በማድረጉ ጥፋተኛ በመሆኑ ነው የሚንከሰው"
Acts 24:10
የሐዋርያት ሥራ 24፡ 10-13
አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ ለቀረበበት ክስ በሀገረ ገዥው ፍልክስ ፊት እንዲህ በማለት ምላሽ ሰጠ፡፡ አገረ ገዥው ተቁነጠነጠ "ሀገረ ገዥው ምልክት አሳየ" ሀሳቤን ላብራራ "ያለሁበትን ሁኔታ ላብራራ" አንተ ራስህ ልታረጋግጥ ትችላለህ "ማረጋገጥ ትችላለህ" እስካሁን ዐሥራ ሁለት ቀን ሆኖኛል "12 ቀናት ሆኖኛል" ኹከት አላስነሳሁም "አላወኩኝም" ወይም "ማንንም ለኹከት አልቀሰቀስኩም" የተከሰስኩበት ክስ "ጠፋተኛ ተደርጌ የተከሰስኩበት" ወይም 'ወንጀለኛ የተደረግኹት"
Acts 24:14


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

የሐዋርያት ሥራ 24፡ 14-16
ይህን ለአንተ እምናለሁ "ይህንን በአንተ ፍት እቀበላሉ" ወይም "ይህንን ለአንተ እናገራለሁ" የስህተት ትምህርት ብለው ይጠሩታል "የስህተት ትምህርት ቡድኖች ብለው ይጠራሉ" የአባቶቻችን አምላክ ይህ የሚያሳየው ጳውሎስ የሚከተለው የትንቱን ሃይማኖት መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ አዲስ አይደለም. የስህተት ትምህርት ተብሎም መጠራት አይችልም።" የተቀደሱት "ቅዱስ ሕዝብe" ይህንን ለማግኘት እሠራለሁ "ይህንን ለማግኘት እለማመዳለሁ" ወይም "ይህንን ለማግኘት እጥራለሁ" በእግዚአብሔር ፊት "በእግዚብሔር መገኘት ውስጥ"
Acts 24:17
የሐዋርያት ሥራ 24፡ 17-19
ሀገሬን በመርዳት የገንዘብ ስጦታ። "ለመርዳት የሚሆን የገንዘብ ስጦታ" ከሕዝቡ ጋር አይደለም "ሕዝቡን የሰበሰብኩት ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ለማድረግ አይደለም" እነዚህ ሰዎች "ከኢስያ የመጡ አይሁዳዊያን" የሚሉት ነገር እንዳች ካላቸው "የሚሉት ነገር ካላቸው"
Acts 24:20
የሐዋርያት ሥራ 24፡ 20-21
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ስለተከሰሰበት ነገር በሀገረ ገዥው ፍልክስ ፊት መለስ መስጠቱን አጠናቋል። እነዚሁ ተመሳሳይ ሰዎች በቂሳሪያ ጳውሎስ በችሎት በቀረበ ጊዜ የነበሩት እነዚሁ የሸንጎው አባላት የሆኑት ሰዎች።
Acts 24:22
የሐዋርያት ሥራ 24፡ 22-23
የወታደሮች አዛዡ ሉስዮስ በወረደ ጊዜ "የወታደሮች አለቃ የሆነው ሉስዮስ በወረደ ጊዜ" ወይም "የወታደሮች አለቃ የሆነው ሉስዮስ በወረደ ጊዜ" የአንተን ነገር ውሳኔ እሰጣለሁ "በአንተ ላይ የቀረበውን ክስ አስመልክቶ ውሳኔ እሰጣለሁ" ወይም "ጥፋተኛ መሆን አለመሆንን እወስናለሁ" በጥቂቱም ነጻነት ሰጠው "ለጳውሎስ በእስር ላይ እያለ በመጠኑም ቢሆን ነጻነት ሰጠው"
Acts 24:24
የሐዋርያት ሥራ 24፡ 24-25
ከጥቂት ቀናት በኋላ "ከብዙ ቀናት በኋላ" ፍልክሽ ይህንን በ ACT 23:24 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። ድሩሲላ የእርሱ ምስት ናት ድሩሲላ የሴት ስም ነው። ፍልክስ በፍራት ተሞላ ፍልክስ ስለኃጢአቱ ጸጸት ተሰምቶት ልሆን ይችላል። ለአሁኑ "ለአሁኑ" ወይም "እስከ በኋላ ድረስ"
Acts 24:26
የሐዋርያት ሥራ 24፡ 26-27
ጳውሎስ ገንዘብ ልሰጠው ይችል ነበር ፍልክስ ጳውሎስ ነጻ ለመውጣት ጉቦ ልሰጥ ይችላል ብሎ አስቦ ነበር። አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስ ለፍልክስ ገንዘብ መስጠት ይችል ነበር።" ስለዚህም ብዙ ጊዜ ሰዎችን ልኮ ያስጠራው እንዲሁም ያወራው ነበር "ስለዚህም ፊስጦስክስ ብዙ ጊዜ ጳውሎስን አስጠርቶ ያወራው ነበር" ጶርቅዮስ ፊስጦስ ይህ ፍልክስን ተክቶ የሀገረ ገዥ የሆነው ሰው ስም ነው።

---

Chapter 25
Acts 25:1
የሐዋርያት ሥራ 25፡ 1-3
አጠቃላይ መረጃ: አሁን ፊስጦስ የቄሳሪያ አገረ ገዥ ሆኗል። አሁን ይህ በታኩ ውስጥ የተከናወነው ቀጣዩ ነገር ምን እንደሆነ ምልክት ሆኖ ያሳየናል። ፊስጦስ ወደ መንደሩ ገባ አማራጭ ትርጉሞች 1) በቀላሉ ፊስጦስ ወደ አከባቢው መጣ ወይም 2) ፊስጦስ አከባቢውን ማስተዳደር ጀመረ። (UDB). ከቄሣሪያ አንስቶ እስከ ኢየሩሳሌም ደረስ ሄደ አማራጭ ትርጉሞች 1) ኢየሩሳሌም ወደ ላይ አድርጎ ማቀመጡ ኢየሩሳሌም ጠቃሚ መሆኗን የሚያሳይ ነው ወይም 2) ኢየሩሳሌም በተራራ ላይ ያለች ከተማ በመሆኗ ወደ ከፍታ መውጣቱን የሚያሳይ ነው። ጳውሎስ ላይ ክስ አቀረቡበት ይህ በፍርድቤት መደበኛ ክስ ማቅረባቸውን ያሳያል። አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስ ሕግጋትን መተላለፉን የሚያሳይ ክስ አቀረቡበት።" በፊስጦስ ፊት አጥብቀው ከሰሱት "ፊስጦስን ለመኑት" ወይም "ፊስጦስን ጠየቁት" ይጠራው ዘንድ . . . እነርሱም እርሱን መግደል ይችሉ ዘንድ "ፊስጦስ ጳውሎስን ይጠራው ዘንድ . . . አይሁዳዊያንም ጳውሎስን መግደል ይችሉ ዘንድ" ይጠራው ዘንድ "ይልከው ዘንድ" በመንገድ ላይም እነርሱ መግደል ይችሉ ዘንድ ጳውሎስን በመንገድ ላይ ተደብቀው ልገድሉት ይፈልጉ ነበር።
Acts 25:4
የሐዋርያት ሥራ 25፡ 4-5
ጳውሎስ በቄሣሪያ እስረኛ ነበር አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስ በቄሣሪያ እስረኛ ከመሆኑ የተነሣ እኔ እራሴ ወደዚያ በፍጥነት እመለሳለሁ።" ይህ ሰው ላይ አንዳች ነገር አድርጎ ከሆነ "ጳውሎስ ላይ ጥፋት የተገኘ እንደሆነ" ልትከሱት ትችላላችሁ "ክስ ልታቀርቡበት ትችላላችሁ" ወይም "የተላለፈውን ሕግ በማንሳት ልትከሱት ትችላላችሁ"
Acts 25:6
የሐዋርያት ሥራ 25፡ 6-8
በዚያ ከቆየ በኋላ "ፊስጦስ በዚያ ቆየ" በፍርድ ወንበር ላይ ተቀመጠ "እንደ ዳኛ ሆኖ በሚፈርድበት ወንበር ላይ ተቀመጠ" ጳውሎስም በፊቱ እንዲቆም ተደረገ አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስንም በፊቱ አቀረቡ" በመጣ ጊዜም "ጳውሎስ በመጣና በፊስጦስ ፊት በቆመ ጊዜ" የአይሁዳዊያን ስም "የአይሁዳዊያን ሕግ" (UDB) የቤተ መቅደሱን ሐህግ አለመተላለፉን ጳውሎስ ወደ ቤተ መቅደሱ ማን መግባት ይችላል የሚለውን ሐህግ አለመተላለፉን ተናገረ። አማራጭ ትርጉም: "ወደ ቤተ መቅደሱ መግባት የሚችሉሰዎች ሕግን አልመተላለፉን"
Acts 25:9
የሐዋርያት ሥራ 25፡ 9-10
በአይሁዳዊያን ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ስለፈለገ "አይሁዳዊያንን ማስደሰት ስለፈለገ" እነዚህን ነገሮች ለመዳኘት እኔ አልችልም አማራጭ ትርጉም: "እነዚህን ነገሮች አስመልክቶ እኔ ምንም ቢያኔ መስጠት አልችልም" እነኔ ፍርድ መስጠት የሚችለው አማራጭ ትርጉም: "በእኔ ላይ ፍርድ መስጠት የሚችልበት ሥፍራ"
Acts 25:11
የሐዋርያት ሥራ 25፡ 11-12
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ከፊስጦስ ጋር መነጋገሩን ቀጥሏል። እኔ ያደረኩት ነገር ለሞት የሚያበቃ ከሆነ "ለሞት ቅጣት የሚያበቃ ጥፋት ፈጽሜ ከሆነ" ክሳቸው ትክክል ካልሆነ "የከሰሱኝ ክስ ትክክል ካልሆነ" ማንም ለእነርሱ አሳልፎ ልሰጠኝ አይችልም አማራጭ ትርጉሞች 1) ፊስጦስ ለእነዚህ በሐሰት ለከሰሱት ሰዎች አሳልፎ ልሰጠው የሚስችል ምን ሕጋዊ ሥልጣን የለውም ወይም 2) ጳውሎስ እያለ ያለው ያቀረቡት ክስ መሠረት ያሌለው ከሆነ ሀገረ ገዥው በአይሁዳዊያን ጥያቄ መሠረት ለእነርሱ አሳልፎ ልሰጠው አይገባም። ወደ ቄሣር ይግባኝ አለ "ቄሣር ይዳኘኝ ዘንድ በእርሱ ፊት መቅረብ እፈልጋለሁ" ፊስጦስ ከሸንጎዎቹ ጋር ተመካከረ በዚህ ሥፍራ ላይ “ሸንጎ” ተብሎ የተጠቀሰው በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ በአጠቃላይ የተጠቀሰው የአይሁድ ሸንጎ አይደለም። ይህ በሮም አገዛዝ ውስጥ ያለ ፖለቲካዊ ሸብጎ ነው። አማራጭ ትርጉም: "ፊስጦስ ከራሱ የአስተዳደር አማካሪዎች ጋር ተነጋገረ።"
Acts 25:13
የሐዋርያት ሥራ 25፡ 13-16
አጠቃላይ መረጃ: ፊስጦስ የጳውሎስን ጉዳይ ለንጉሥ አግሪጳ ማስረዳት ጀመረ። አሁን ይህ ቃል በታሪኩ ውስጥ አዲስ ነገር መጀመሩን የሚያሳይ ነው። ንጉሥ አግሪጳ በርኒቄ አግሪጳ በዚያ ዘመን የነገሠ ንጉሥ ሲሆን በርኒቄ ደግሞ እህቱ ናት። ለፊስጢስ ኦፍሳሌያዊ ክፍያ ለመፈጸም "ፊስጢስን በኦፍሴላዊ ጉዳይ ለመጎብኘት" አንድ ሰው ፊስጦስእስረኛ ሆኖ ወደኋላ ቀርቶ ነበር አማራጭ ትርጉም: "ፊስጦስ ቢሮን ትቶ ሲሄድ ሰውዬውን በዚህ በእስር ትቶት ሄዶ ነበር።"
Acts 25:17
የሐዋርያት ሥራ 25፡ 17-20
ስለዚህ በዚህ ሥፍራ ላይ “ስለዚህ” የሚለው ቃል ከዚህ በፊት በተነገረ አንድ ነገር ምክንያት ይህ እንደሆነ ያሳያል። በዚህ ሁኔታ ውስጥም ፊስጦስ የተከሰሰው ሰው ከከሳሾቹ ጋር መገናኘት እና መከላከያ ሀሳቡን ማቅረብ አለበት ብሏል። ሁሉም ስገናኙ "የአይሁድ መሪዎች በዚህ ከእኔ ጋር ለመገናኘት በመጡ ጊዜ" በፍርድ ወንበር ላይ እቀመጣለሁ "እንደ ዳኛ ሆኜ በምፈርድበት ወንበር ላይ እቀመጣለሁ" (ተመልከት: ACT 25:6) ሰውዬው እንዲመጣ አዘኩ አማራጭ ትርጉም: ወታደሮቹ ጳውሎስን ወደፊት ይዘውት ይመጡ ዘንድ አዘዝኩኝ" ስለራሳቸው ሃይማኖት “ሃይማኖት” የሚለው ቃል ሰዎች ስለ ሕይወት እና ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ያላቸው እምነት ነው። ስለእነዚህ ነገሮች በዚያ ቤታ ፍርድ ይሰጣቸው ዘንድ አማራጭ ትርጉም: "የአይሁድ ሸንጎ በእነዚህ ጉዳዮች በተለከ ይህ ሰው ጥፋተኛ አድርገው ወሰኑበት"
Acts 25:21

የሐዋርያት ሥራ 25፡ 21-22
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ፊስጦስ ጉዳዩን ለንጉሥ አግሪጳ ማብራራቱን አጠናቀቀ። እንድጠብቁት አዘዝኳቸው አማራጭ ትርጉም: "ወታደሮች በእስር ቤት ውስጥ እንዲጠብቁት አዘዝኳቸሁ" "ነገ፣" ፊስጦስ እንዲህ አለ፣ "ትሰሙታላችሁ።" "ፊስጦስ እንዲህ አለ፣ 'ነገ ጳውሎስ ስናገር መስማት ትችሉ ዘንድ አመቻቻለሁ።'"
Acts 25:23
የሐዋርያት ሥራ 25፡ 23-24
አግሪጳ እና በርኒቄ እነዚህ ስሞች በ ACT 25:13 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምካቸው ተመልከት። ጳውሎስ ወደ እነርሱ ዘንድ ቀረበ አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስን በእነርሱ ፊት ይቀር ዘንድ ይዘውት መጡ። ወደ እኔ ጮኹ "አይሁዳዊያን በእኔ ላይ ተቆጥተው ተናገሩ" ከእንግዲህ ወዲህ በሕይወት ልኖር ፈጽሞ አይገባውም ይህ ዓረፍተ ነገር አጽኖት ሰጥቶ የሚያስተላልፈው ከተባለው በተቃራኒ የሆነውን ነገር ነው። አማራጭ ትርጉም: "በአፋጣኝ መሞት ይኖርበታል።"
Acts 25:25
የሐዋርያት ሥራ 25፡ 25-27
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ፊስጦስ ለንጉሥ አግሪጳ መናገሩን ቀጥሏል። እርሱን ወደ እናንተ ዘንድ ይዤው መጣሁ፣ በተለይም ወደ አንተ ወደ ንጉሥ አግሪጳ ዘንድ "ጳውሎስን ወደ እናንተ ሁሉ ዘንድ ይዤው መጣሁ ነገር ግን በተለይም አንተ ንጉሥ አግሪጳ ስለዚህ ተጨማሪ መጻሐፍ የሚችለው ነገር ይኖረኝ ዘንድ "ስለዚህ ሌላ መጻፍ እችል ዘንድ" ወይም "ስለዚህ ምን መጻፍ እንዳለብኝ አውቅ ዘንድ" አንድን እስረኛን የታሰረበት ምክንያት ምን እንደሆ በግልጽ ሳይጠቀስ ዝም ብሎ መላክ ምክንያታዊ አልመሰል ብሎኛል "አንድን እስረኛ የታሠረበት ምክንያት ምን እንደሆነ በግልጽ ጽፎ መላክ ምክንያታዊ መስሎ ታይቶኛል" በእርሱ ላይ ያላቸው ክስ አማራጭ ትርጉሞች 1) የአይሁድ መሪዎች በእርሱ ላይ ያቀረቡት ክስ ወይም 2) በሮማዊያን ሕግ መሠረት ጳውሎስ ሊከሰስበት የሚችለው አንቀጽ።

---

Chapter 26
Acts 26:1
የሐዋርያት ሥራ 26፡ 1-3
አያያዥ ዓረፈተ ነገር : ፊስጦስ ጳውሎስን በንግሥ አግሪጳ ፊት አቀረበው። በቁጥር 2 ላይ ለንግሥ አግሪጳ ለተከሰሰበት ክስ ምላሽ መስጠት ጀመረ። እጆቹን ዘርግቶ "የሕዝቡን ትኩረት ማግኘት ይችል ዘንድ ወደሕዝቡ እጆቹን ዘርግቶ" ለተከሰሰበት ክስ መልስ ሰጠ "ለተከሰሰበት ክስ መልስ መስጠት ጀመረ" ራሴን ደስተኛ ሰው አድርጌ እቆጥረዋለሁ ጳውሎስ ደስተኛ ነበር ምክንያቱም በንጉሥ አግሪጳ ፊት መቆሙ ወንጌልን ለመናገር እድል ስለምሰጠው ነው።
Acts 26:4
የሐዋርያት ሥራ 26፡ 4-5
አይሁዳዊያን ሁሉ አማራጭ ትርጉሞች 1) ከጳውሎስ ጋር ያደጉት እና ፈርሳዊ ሆኖ የሚያውቁት አይሁዳዊያን ወይም 2) "ጳውሎስ በፈሪሳዊነቱ ከነበረው ቅናት የተነሣ በአይሁዳዊያን ዘንድ የታወቀ ነበር እንዲሁመም በአማኝነቱም የታወቀ ነው።" በራሴ ሀገር አማራጭ ትርጉም 1) በራሱ ሕዝብ መካከል፣ ይህ ማለት የግድ በእስራኤል መልከአምድር ውስጥ ማለት ላይሆን ይችላል ወይም 2) በእስራኤል ምድር ውስጥ።
Acts 26:6
የሐዋርያት ሥራ 26፡ 6-8
አሁን ጳውሎስ ይህንን ቃል የተጠቀመው ለተከሰሰበት ክስ መልስ በመስጠት ሂደት ውስጥ ወደሌላኛው መከራከሪያ ነጥቡ መሰጋገሩን ለማሳየት ነው። ዛሬ ፍርድ ለመቀበል በዚህ እገኛለሁ አማራጭ ትርጉም: "እርሱ ከሰውኝ ዛሬ በዚህ አለሁ" እግዚብሔር ለአባቶቻችን የገባውን ቃል እጠባበቃለሁ ጳውሎስ የመስሐን መምጣት ይጠብቃል። ወደዚያ እንደሚንደርስ ተስፋ እናደርጋለን። "እግዚአብሔር የገባውን ተስፋ እንደሚንቀበል ተስፋ እናደርጋለን" እግዚአብሔር የሞተ ሰውን ማስነሳቱ ይህንን ያኸል የማይታመን ነው ብላችሁ ስለምን አሰባችሁ? ጳውሎስ ይህንን ንግግር የተናገረው አግሪጳ ጳውሎስ የተናገረው ነገር አግሪጳ ከዚህ በፊት እግዚአብሔር ሰዎችን ከሞት ማስነሳት እንደሚችል በማመኑ ምክንያት ከዚያ ጋር ለማያያዝ ነው። አማራጭ ትርጉም: "አንተ ራሰህ እግዚአብሔር ሰውን ከሞት ልያስነሣ ይችላል ብለሃል!"
Acts 26:9
ሐዋርያት ሠስራ 26፡ 9-11
በአንድ ጊዜ ጳውሎስ ይህንን ሀረግ የተጠቀመው ለክሱ የመከራከሪያ ሀሳቡን በማቅረብ ሂደት ውስጥ ለውጥ መኖሩን ለማሳየት ነው። ዘሂን ደግሞ እንዴት ቅዱሳንን ያሳድድ አንደነበር መናገር ጀመረ። የኢየሱስን ስም በመቃወም በዚህ ሥፍራ ላይ “ስም” የሚለው ቃል የኢየሱስን መልዕክ የሚወክል ነው።አማራጭ ትርጉም: "የኢየሱስን መልዕክት በመቃወም።" እነርሱን በመቃወም ድምፄን ሰጥቻለሁ "እነርሱን ለመቅጣት ደምፅ ሰጥቻለሁ" ብዙ ጊዜ እቀጣቸው ነበር አማራጭ ትርጉሞች 1) ጳውሎስ የተወሰኑ አማኞችን ብዙ ጊዜ ቀጥቶዋቸዋል ወይም 2) ጳውሎስ ብዙና የተለያዩ አማኞችን ቀጥቶዋል።
Acts 26:12
የሐዋርያት ሥራ 26፡ 12-14
ይህንን በማድረግ ላይ ሳለሁ ጳውሎስ ይህንን ሀረግ የተጠቀመው በክርክር ሀሳኑ ላይ ሌላ ለውጥ መኖሩን ለማሳየት ነው። አሁን ኢዩስን ከማሳደድ እርሱን ወደ መከተል ኢየሱስ እንዴት እደለወጠው መናገር ጀመረ። እያለe ይህ ቃል በሆነ ጊዜ የተጀመሩ ሁለት ነገሮችን ያመለክታል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጳውሎስ ቅዱሳንን በማሳደድ ላይ ሳለ ወደ ደማስቆ ሄዶ ነበር። ስልጣን ተሰጥቶ እንዲሁም ማዘዣ ወረቀት ይዞ ጳውሎስ ከአይሁድ መሪዎች ዘንድ የተሰጠው አይሁዳዊያን አማኞች ለማሳደድ የሚያስችለው ስልጣን የተሰጠበት ደብዳቤ በእጁ ይዞ ነበር። . እግዚአብሔር መቃወም በጣም ከባድ ነው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ዕቅድ መቃወምን በሬ የአራሹን በተር ከመቃወም ጋር እግዚአብሔር እንዳነጻጸረ ተናገረ።
Acts 26:15
የሐዋርያት ሥራ 26፡ 15-18
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለንጉሥ አግሪጳ የመከራከሪያ ሀሳቡን ማቅረቡን ቀጥሏል። በእነዚህ ቁጥሮ ከጌታ ጋር ያደረገውን ነግግር በቀጥታ እያጣቀሰ ይናገራል። ለእኔ ለራሴ ለይቼሃለሁ "የራሴ አድርጌሃለሁ" (UDB) ወይም "ለራሴ ለይቼሃለሁ" በእኔ ላይ ባለህ እምነት ይህ በእግዚአብሔር ማመን እግዚብሔር ለራሱ የለያቸው ሰዎች መሆኑን ያሳያል። በእኔ ላይ ካላቸው እምነት የተነሣ ለራሴ የለየኋቸው ጳውሎስ የጌታን ንግግር በቀጥታ መጥቀሱን ጨርሶዋል።
Acts 26:19
የሐዋርያት ሥራ 26፡ 19-21
ስለዚህ በዚህ ሥፍራ ላይ “ስለዚህ” የሚለው ቃል ከዚህ በፊት በተነገረ አንድ ነገር ምክንያት ይህ እንደሆነ ያሳያል። በዚህ ሁኔታ ውስጥም ጳውሎስ ጌታ በራዕይ ምን እንዳሳየው ከዚህ በፊት አብራርቶ ጨርሷል። ሰማያዊውን ራዕይ ለመታዘዝ አሻፈረኝ አላልኩም "በዚህ ራዕይ ከሰማይ መጥቶ ለተሰጠኝን መልዕክት ታዝዤያለሁ"
Acts 26:22
የሐዋርያት ሥራ 26፡ 22-23
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለንጉሥ አግሪጳ ያቀረበውን የመከራከሪያ ሀሳብ አጠናቀቀ።. ነቢያት ያሉት ነገር ጳውሎስ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ጽሑፎች ስብስብን እያመለከተ ነው። ክርስስ መከራን እነንዲቀበል "ክርስቶስ መከራን ይቀበል ዘንድ እና እንዲሞት" ብርሃንን ያውጅ ዘንድ "የድነትን መልዕክት ይናገር ዘንድ"
Acts 26:24
የሐዋርያት ሥራ 26፡ 24-26
አንተ አብደሃል "ትርጉም ያሌለው ነገር መናገር ጀምረሃል" ወይም "አብደሃል" አላበድኩም "ጤነኛ ነኝ" ወይም "የማስበውም በትክክል ነው" በጥንቃቄ ልታሰብበት የሚገባ ነገር ነው "ጥንቃቄ ያስፈልገዋል" ወይም "ጥንቃ የሚያስፈልገው ጉዳይ" ለእርሱ በግልጽ ነገርኩት "ለንጉስ አግሪጳ በግልጽ ነገርኩት" ይህ በድብቅ የተደረገ ነገር አይደለም "በምስጥር የተደረገ ነገር አይደለም"
Acts 26:27
የሐዋርያት ሥራ 26፡ 27-29
ንጉሥ አግሪጳ ሆይ በነቢያት ታምናለህን? ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ ለንጉሥ አግሪጳ የጠየቀው ንጉሥ አግሪጳ ነቢያት ስለ ኢየሱስ የተናገሩትን ነገር ያምን ስለነበረ ለማስታወስ ነው። አማራጭ ትርጉም: "የአይሁድ ነቢያት የተናገሩትን ነገር አንተ ታምናለህ!" በዚህ አጭር ጊዜ ልታሳምነኝ እና ክርስትያን ልታደረገኝ ትፈልጋለህን? አግሪጳ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ጳውሎስ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን ሳያቀርብ አግሪጳን እንዲሁ በቀላሉ ማሳመን እንደማይችል ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም: "እኔን እንዲሁ በቀላሉ ማሳመን እችላለሁ ብለህ አስበሃል!"
Acts 26:30

Chapter 27
Acts 27:1
የሐዋርያት ሥራ 27: 1-2
አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ ወደ ሮም ጉዞ ጀመረ። ይህ በተወሰነ ጊዜ አማራጭ ትርጉም: "ሀገረ ገዥው ይህንን በወሰነ ጊዜ" በመርከብ መሄድ ጀመርን በዚህ ክፍል ውስጥ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጸሐፊውን ሉቃስን እና ጳውሎስን ነው። እርሱ ጳውሎስ ወደ ሮም ስጓዝ አብሮት ተጉዞ ነበር። ወደ ጣሊያን በመርከብ ሄዱ ጣሊያን በሮም ውስጥ ያለች የአንድ አከባቢ ስም ነው። ዩልዩስ የተባለ መቶ አለቃ ዩልዩስ የወንድ ስም ነው። የአውጉስጦስ ጭፍራ ይህ የብዙ ሠራዊት መጠሪያ ስም ነው ወይም መቶ አለቃው ያለበት የወታደር ቡድን ስም ነው። በአድራሚጢስ መርከብ አማራጭ ትርጉም 1) ከአድራሚጢስ የሚመጣ መርከብ ወይም 2) በአድራሚጢስ ስም የተመዘገበ ወይም ፈቃድ ያወጣ መርከብ። ይህ ምናልባት በዘሟ ቱርክ በምዕራብ አከባቢ የሚገኝ ሥፍራ ሊሆን ይችላል። በመርከብ ለመጓዝ ጸዘጋጅታ ሻሉ "ለመገዋዝ ተዘጋጅተው" ወይም "ዝግጅታቸውን አጠናቀው" በባሕሩ ላይ መሄድ ጀመርን "በባሕሩ ላይ ጉዞዋችንንን ጀመርን" አርስጥሮኮስ ይህን በ ACT 19:29 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።
Acts 27:3
የሐዋርያት ሥራ 27: 3-6
ዩልዩስ ጳውሎስን በመልካም መንገድ አስተናገደው "ዩልዩስ ጳውሎስን በመልካም መንገድ አስተናገደው።" “ዩልዩስ” የሚወለውን ስም በምን ዓይነት መንገድ አንተረጎምከው በ [ACT 27:1] ተመልከት። እንክብካቤ ያደርጉለት ዘንድ ወደ ጓደኞቹ ዘንድ ሄደ "አስፈላጊውን እንክብካቤ ለማግኘት ወደ ጓደኞቹ ዘንድ ሄደ" ወይም "አስፈላጊውን እገዛ ለማግኘት ሲል ወደ ጓደኞቹ ዘንድ ሄደ" በቆጵሮስ ደሴት አድርገን አውሎ ንፋሱን ተከልለን ሄድን "ከአውሎ ንፋሱ ለመከለክ ስንል በቆጵሮስ ደስት ደሴት በኩል አድረገን ተጓዝን" (UDB) ጵንፍልያም ይህንን በ ACT 2:10 ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። በሉቅያ ወዳለ ወደ ሙራ ደረስን። ሙራ በሉቅያ ውስጥ የሚትገኝ ከተማ ናት። ይህች ከተማ በዘመኗ ቱርክ ውስጥ በደቡብ ምዕራብ አከባቢ ተገኛለች። የሉቅያ ከተማ ሉቅያ የሮም ግዛት ስትሆን በዘመኗ ቱርክ ውስጥ በደቡብ ምዕራብ አከባቢ ትገኛለች። አሌክሳንደሪያa ይህ የአንድ ከተማ ስም ነው። ጣሊያን ይህንን በ [ACT 27:1] ላይ ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት።
Acts 27:7
የሐዋርያት ሥራ 27: 7-8
ቀኒዶስ አቅራቢያ ይህ በዘመኗ ቱርክ ውስጥ የሚገኝ በጥንት ጊዜ ሰዎች ሠፍረውበት የነበረ ሥፍራ ነው። ሰልሙና ተቃራኒ ይህች የቀርጤስ ወደብ ከተማ ናት። መልካም ወደብ ይህ በልሳ አቅራቢያ የሚገኝ ከቀርጤስ ወደብ በስተደበቡ የሚገኝ ሥፍራ ነው። ለላሲያ ከተማ አቅራቢያ ይህች በቀርጤስ ውስጥ የሚትገኝ ወደብ ናት።
Acts 27:9
የሐዋርያት ሥራ 27: 9-11
አሁን ብዙ ጊዜ ወሰድን በንፋሱ አቅጣጫ ምክንያት ከቄሳሪያ ወደ መልካም ወደብ ያደረግነው ጉዞ ከታሰበው ቀን በላይ ፈጅቷል። የአይሁዳዊያን የጾምራጾም አልፏል ይህ ጾም ከመስከርም ወር ውስጥ ካለው የመስዋእት ዕለት አንስቶ እስከ ጥቅም ድረስ የሚቆይ በየዓቱ የሚደረግ ነው። ከዚህ ጊዜ በኋላ ከፍተኛ ማዕበል የመነሣት ዕድሉ ከፍተኛ ነው።
Acts 27:12
የሐዋርያት ሥራ 27: 12-13
መርከብቱ ይህንን ንፋስ የመቋቋም አቅም አይኖራትም "ይህንን ወጀብ ለመቋቋም የሚያስችል አቅም አይኖራትም" የፍንቄ ከተማ ፍንቄ በቀርጡስ ደሴት ውስጥ የሚትገኝ አንድ ወዳብ ናት። ከባድ መኅልቅ “ከባድ” የሚለው ቃል የሚመለክተው ከውሃ ውስጥ ለማውጣት ነው። መኅልቅ ከመርከብቱ ጋር በገመድ የሚታሠር መርከብቱ እንዳትቀሳቀስ የሚያደረግ ከባድ ዕቃ ነው። መኅልቁ በውሃ ውስጥ ከተጨመረ በኋላ ወደ ውሃው ውስጥ ይጣላልና መርከብቱ እንዳትሄድ ያደርጋል።
Acts 27:14
የሐዋርያት ሥራ 27: 14-16
ከባድ አውሎንፋሰስ "በጣም ጠንካራ እና አደገኛ የሆነ ንፋስ" ሽራ "ከንፋሹ ተከለሉ" ቄዳ ወደሚባል ትንሽ ደሴት ይህች ደሴት ከቀርጤስ ደሴት በስተደቡብ የሚትገኝ ናት።
Acts 27:17
የሐዋርያት ሥራ 27: 17-18
ወደላይ አወጧት "ተሸክመው አወጧት" ስርቲስም ወደ ተባለ አሸዋማ ሥፍራ ይህ ጥልቅ ያልሆነ አሸዋማ የሐይቁ ክፍል ሲሆን መርከቦችም በዚያ ተቀርቅረው ይቀራሉ። "ስርቲስ" በሰሜን አፍርካ ሊቢያ አከባቢ የሚገኝ ሥፍራ ነው። በንፋሱ እየተመራን ሄድን አማራጭ ትርጉም: "ንፋሱ በሚወስደን አቅጣጫ መጓዝ ግድ ሆነብን"
Acts 27:19
የሐዋርያት ሥራ 27: 19-20
የመትረፈስ ተስፋችን ሁሉ ተሟጠጠ አማራጭ ትርጉም: "ሁሉም ሰው እንተርፋለን የሚለው ተስፋው ተሟጠጠ"
Acts 27:21
የሐዋርያት ሥራ 27: 21-22
ከተጓዦቹ መካከል ከሰዎቹ መካከል" ጉዳት የሚደርስበት እና የሚጠፋ "በዚህ ምክንያት የሚጎዳ እና የሚጠፋ"
Acts 27:23
የሐዋርያት ሥራ 27: 23-26
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በመርከብቱ ለሚጓዙ ሰዎች መናገሩን ቀጠሏል። ከአንተ ጋር በመርከብቷ የሚጓዙ ሰዎችን ሁሉንም ሰጥቼሃለሁ "ከአንተ ጋር በመርከብቷ የሚጓዙ ሰዎች በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ወስኛለሁ" አንድ ደሴት ፈልገን ወደዚያ መጠጋት ይኖርብናል "መርከቧ በአንድ ደሴት ላይ መቆም ይኖርባታል"
Acts 27:27
የሐዋርያት ሥራ 27: 27-29
በአድርያ ባሕር ይህ በጣሊያን እና በግሪክ መካል ያለ ባሕር ነው። ለኩት የሐይቁን ውሃ መጠን ለኩት (UDB)። ሃያ የሰው ቁመት አገኙ "20 የሰው ቁመት አገኙ" ወይም "40 ሜትር አገኙ።" ይህ የመለኪያ መንገድ ነው። ዐሥራ አምት የሰው ቁመት አገኙ "15 የሰው ቁመት አገኙ" ወይም "30 ሜትር" ከመርከብቱ በስተኋላ "በከመርከብቱ በስተዋኋላ"
Acts 27:30
የሐዋርያት ሥራ 27: 30-32
Acts 27:33
የሐዋርያት ሥራ 27: 33-35
ከጸጉርህ አንድ ዘለላ እንኳ አትጠፋም ይህ በአንተ ላይ ምንም ጉዳት አይደርስም ለማለት የተለመደ ንግግር ነው። አማራጭ ትርጉም: "ይህንን አስቸጋሪ ሁኔታ ያለምንም ጉዳ ሁላችሁም ታልፋላችሁ።" መዕድ ቆረሰ "ዳቦ ሁለት ወይም ከዚያ በላ ቆርሶ" ወይም ዳቦውን ቆራርሶ"
Acts 27:36
የሐዋርያት ሥራ 27: 36-38
በመርከብቱ ውስጥ የነበርነው ወደ 276 ሰዎች ነን "በመርከብቷ ውስጥ ወደሁለት መቶ ሰባ ስድተስ ሰዎች ነበርን።" ይህ የኋላ ታርክ መረጃ ነው።
Acts 27:39
የሐዋርያት ሥራ 27: 39-41
ዬት ቦታ እንደሆነ አላወቁም "አንድ ሥፍራ ተመለከቱ ነገር ግን ይህ እነርሱ የሚያውቁት ሥፍራ አልነበረም" መኅልቁን ፈተው በውሃ ውስጥ ተውት "ገመዱን ቆርጠው መኅልቁን በዚያ ተውት" ወደባሕሩ ዳርቻ አመሩ "steered the ship toward the beach"
Acts 27:42
የሐዋርያት ሥራ 27: 42-44
የወታደሮቹ እቅድ የነበረው "የወታደሮቹ እቅድ" ወደ ውሃ ውስጥ መዝለል "ከመርከብቱ ወደ ውሃው ውስጥ መዝለል"

Chapter 28

Acts 28:1

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 1-2

አወቅን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን እናበዘዚህ ጉዞ ላይ ከጳውሎስ ጋር አብሮ የተጓዘውን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ጸሐፊ የሆነውን ሉቃስን ነው። አማራጭ ትርጉም "ከሰዎቹ አወቅን" ወይም "ከነዋሪዎቹ ጠይቀን ተረዳን።" ደሴትቱ መላጥያ ትባላለች መላጥያ በአሁኗ ሲስል ደቡብ አከባቢ የሚትገኝ ደሴት ናት። የሀገሩ ሰዎች “የሀገሩ ሰዎች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የግሪክ ቋንቋ መናገር የሚችሉ ሰዎች የግሪክ ባሕልን የተቀበሉ ሰዎች ናቸው። የሚያስገርም ቸርነት ይህ ሀረግ ከሚቀጠበው ተቃራኒ የሆነ ነገርን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም: "ታላቅ ቸርነት።" እሳት አቀጣጥለው "እንጨት ሰብስበው እሳት አቀጣጠሉልን" ሁላችንንም በደስታ ተቀበሉን አማራጭ ትርጉሞች 1) "በመርከብቷ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሁሉ በደስታ ተቀበሉ" ወይም 2) "ጳውሎስን እና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሁሉ በደስታ ተቀበሏቸው።"

Acts 28:3

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 3-4

እፋኝት ወጣች "ከሚነደው እሳት ውስጥ መርዛማ የሆነች እባብ ወጣች" ከእጁ ጋር ተጣበቀች "የጳውሎስን እጅ ይዛ አለቀም አለች" ይህ ሰው በእርግጥም ነፍስ አጥፍ ነው አሉ "በእርግጠኝነት ይህ ሰው ነፍሰ ገዳይ ነው አሉ" ወይም "ይህ ሰው በእርግጥም ነፍሰ ገዳይ ነው" ይሁን እንጂ ፍትሕ በሕይወት እንዲቆይ አልፈቀደለትም "ፍትሕ ተብላ የሚትጠራ አምላክ ከሞት እንዲያመልጥ አልፈቀደችለተም"

Acts 28:5

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 5-6

እባቧን ወደ እሳት ውስጥ አራግፎ ጣላት "እባብቱን ከእጁ ላይ አራግፎ ወደ እሳቱ ውስጥ ጣላት" ተመርዞ ወዲያው ይወድቃል አማራጭ ትርጉሞች 1) ከፍተኛ ትኩሰሳት ይይዘዋል ወይም 2) ያብጣል። በእርሱ ላይ የታየ ለውጥ አልነበረም አማራጭ ትርጉም: "ሁሉን ነገር እንደቀድሞው ነበር" አምላክ ነው አሉ በመርዛማ እባብ ከተነደፈ በኋላ በሕይወት የሚኖር ሰው መለኮት ወይም አምላክ ነው የሚል እምነት አለ።

Acts 28:7

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 7-10

በዚያም ስፍራ አጠገብ "በዚያ" የሚለው ቃል በታሪኩ ውስጥ አዲስ ሰው ወይም ነገር እንደተካተተ አመለካች ነው። የደሴትቱ አለቃ አማራጭ ትርጉሞች 1) የሕዝቡ ዋና መሪ ወይም 2) በደሴትቱ ለላይ ዋና ሰው ተደርጎ የሚወሰደው ምናልባትም በጣም ሀብታሙ ሰው ሊሆን ይችላል። ፑፕልዮስ ተብሎ የሚጠራ ሰው ፑፕልዮስ በደሴትቱ ላይ ዋና አለቃ ነው። መልካም አቀባበል አደረግልን "ጳውሎስን እና ከእርሱ ጋር የተጓዙትን ሰዎች" የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ በልግስና ሰጡን "ለእኛ እንግዶች ለሆነው ቸርነታቸውን አሳዩን" የፑፕልዮስም አባት በንዳድና በተቅማጥ ታሞ ተኝቶ ነበር፤ ይህ ስለ ፑፐፕልዮስ አባት አጠቃላይ የኃላ ታሪክ መረጃ የሚሰጥ ሆኖ አጠቃላይ ታኩን ለመረዳ ወሳኝ ነው። ታሞ ነበር "ታሟል" በንዳድና በተቅማጥ ታሞ ነበር ይህ የአንጀት በሽታ ነው። እኮቹን በእርሱ ላይ ጫነ "በእጆቹ ዳሰሰው" ተፈወሰ አማራጭ ትርጉም: "እነርሱንም ፈወሳቸው" (UDB)

Acts 28:11

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 11-12

አጠቃላይ መረጃ: ጳውሎስ ወደ ሮም የሚያደርገውን ጉዞ ቀጥሏል። በእስክንድሪያው መርከብ አማራጭ ትርጉሞች 1) "ከእስክንድሪያ በመጣው መርከብ አማካኝነት" ወይም 2) "በእስክንድሪያ የተመዘገበው ወይም ፈቃድ ያገኘው መርከብ።" በ ACT 6:9 ላይ “እስክንድሪያ” የሚለውን ቃል ምን ብለህ እንደተረጎምከው ተመልከት። መንቲያ ወንድማማቾች ይህ ካስቶር እና ፖሉእክስ የተባሉትን ያመለክታል፤ እነዚህ የግሪክ አምላክ የሆነው ዙስ መንቲያ ወንድ ልጆች ናቸው። እነዚህ የመርከቦችን ደንነት የሚጠብቁ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ይፈራሉ። የሰራኩስ ከተማ ሰርኩስ በአሁን ዘመን ከጣሊያን ደቡብ ምዕራብ በኩል፣ ከሲስል ከተማ ደቡብ ምስራቅ በኩል የሚትገኝ የወደብ ከተማ ናት።

Acts 28:13

የሐዋርያት ሥረ 28፡ 13-15

የሬጊዩም ከተማ ይህ ከጣሊያን ጫፍ በደቡብ ምዕራብ በኩል የሚገኝ የወደብ ከተማ ነው። የደቡብ ንፋስ ተነስቶ "ከደቡብ የሚነሳ ንፋስ መንፈስ ጀመረ" የፑቲዮሉስ ከተማ "ፑቲዮሉስ" በዘመኗ ኔፓል ከጣሊያን በምዕራብ በኩል የሚትገኝ ከተማ ናት። ወንድሞች እነዚህ የኢየሱስ ተከታዮች ሲሆን ወንዶችን እና ሴቶችን ያካትታል። በዚህ መንገድ ወደ ሮም መጣን አንድ ጊዜ ጳውሎስ ወደ ፑቲዮሉስ ከደረሰ በኋላ የተቀረው ወደ ሮም የሚደረገው ጉዞ በየብስ ላይ የሚደረግ ነው። አማራጭ ትርጉም: : "ከእነርሱ ጋር ለሰባት ቀናት ከቆየን በኋላ ወደ ሮም ሄድን።" ሦስት ማደሪያ s ይህ በመንገድ ላይ ማረፊያ ቦታ ሲሆን ከሮም ከተማ 50 ኪሜ ርቀት ላይ የሚገኝ አፋን የተባለ ስፍራ ነው።

Acts 28:16

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 16-18

ወደ ሮም በደረስን ጊዜ ጳውሎስ ተፈቀደለት አማራጭ ትርጉም: "ወደሮም ከደረስን በኋላ መንግስት ፈቃድ ሰጠው" በአይሁዳዊያን መካከል ያሉት መሪዎች አይሁዳዊያን ማህበረሰባዊ ወይም ሃይማኖታዊ መሪዎች በሮም ተገኝተው ነበር የሞት ቅጣት የሚያስቀጣ አንዳች ጥፋት አልተገኘብኝም "የሞት ቅጣት የሚያስቀጣ አንዳች ነገር አላደረኩም"

Acts 28:19

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 19-20

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በሮም ላሉት የአይሁድ መሪዎች መናገሩን ቀጥሏል። አይሁዳዊያን ተናገሩ "በኢየሩሳሌም ያሉት የአይሁድ መሪዎች ተናገሩ" ከእነርሱ ፍላጎት ውጪ "ከሮማዊያን መሪዎች መሻት ውጪ" እኔም ይግባኝ ለመጠየቅ ተገደድኩኝ አማራጭ ትርጉም: "ይግባኝ ከመጠየቅ ውጪ ሌላ አማራጭ አልነበረኝም" እስራኤል እርግጠኛ በሆነችበት ጉዳይ ላይ አማራጭ ትርጉም 1) "እግዚአብሔር መስሑን ወደ እስራኤል እንደሚልክ እስራኤል እርግጠኛ ናት" ወይም 2) የሞተውን ነገር ከሞት እግዚአብሔር እንደሚያስነሳ።

Acts 28:21

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 21-22

አማራጭ ትርጉም: የአይሁድ መሪዎች ለጳውሎስ ምላሽ ሰጡ። ስለዚህ የስህተት ትምህርት ታስባለህን "ስለነዚህ ራሳቸውን ስለመረጡት ቡድኖች ታስባለህን" በሁሉም ሥፍራዎች በእነርሱ ላይ ተቃውሞ እየተነሣ ነው የወንጌል መልዕክትን ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆኑት በሮም አጠቃላይ ግዛት ውስጥ የሚኖሩት አይሁዊያን ስለ መንገዱ እና ይህንን መልዕክት አስመልክቶ መጥፎ ነገር መናገራውን በሮም የሚገኙ አይሁዳዊያን ሰምተዋል። .

Acts 28:23

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 23-24

አጠቃላይ መረጃ: በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ነው። በተቀመጡ ጊዜ በዚህ ሥፍራ ላይ “እርሱ” የሚለው ቃ የሚያመለክተው የኤሁድ መሪዎችን ነው። አንዳንዶቹን አሳመናቸው አማራጭ ትርጉም: "ጳውሎስ አንዳንዶቹን አሳመናቸው"

Acts 28:25

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 25-26

አጠቃላይ መረጃ: በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ “እነርሱ” የሚለው ቃል ጳውሎስ እየተናገራቸው ያሉትን ሰዎችን ነው። በቁጥር 26 ላይ ጳውሎስ ከነብዩ ኢሳያስ መጽሐፍ ወስዶ ተናግሯል።

Acts 28:27

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 27-27

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ከነቢይ ኢሳያስ መጽሐፍ ወስዶ መናገሩን አጠናቋል።

Acts 28:28

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 28-29

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በሮም ላሉት የአይሁድ መሪዎች ያደረገውን ንግግር አጠናቀቀ። ያደምጡት ነበር "ከእነርሱ መካከል አንዳንዶቹ ያደምጡት ነበር"

Acts 28:30

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 30-31

No Note

Chapter 1



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Romans 1:1

ጳውሎስ

ቋንቋህ የዚህን መልእክት ጸሓፊ የሚያስተዋውቅበት የተለየ መንገድ ሊኖረው ይችላል። በዚሁ ተመሳሳይ ጥቅስ ጳውሎስ ደብዳቤውን የጻፈላቸው ሰዎእ እነማን እንደሆኑ መናገር ያስፈልግህ ይሆናል (ሮሜ 1:7) ። ‹‹እኔ ጳውሎስ ይህንን መልእክት ጽፌአለሁ (የተገመተ እውቀት እና ያልተገለጠ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ

ይህንን በአድራጊ ቅርጽ ልትተረጉመው ትችላለህ። “እግዚአብሔር ሐዋርያ እንድሆን ጠራኝ እንዲሁም ለሰዎች ስለ ወንጌል እናገር ዘንድ መረጠኝ።

የተጠራ

ይህ ማለት እግዚአብሔር ሰዎችን የእርሱ ልጆች ይሆኑ ዘንድ፣ አገልጋዮቹም ይሆኑ ዘንድ እና በኢየሱስ በኩል ያዘጋጀውን የመዳን መልእክት እንዲነግሩ ይመርጣቸዋል ወይም ይወስናቸዋል ማለት ነው።

በቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል እንደተገለጸው በነቢያቱ አስቀድሞ ቃል የገባውን

እግዚአብሔር ለሕዝቡ መንግሥቱን እንደሚያቋቁምቃል ገብቷል። ለነቢያቱም ይህንን ቃል ኪዳን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንዲጽፉ ነግሮአቸዋል።

ልጁን በተመለከተ

ይህ የሚያመለክተው ‹‹የእግዚአብሔርን ወንጌል››፣ እግዚአብሔር ልጁን ወደዚህ ዓለም እንደሚልከው የገባውን ቃል ኪዳን የሚገልጽ የምሥራች ነው።

ልጅ

የእግዚአብሔር ልጅ፣ ይህ ለኢየሱስ አስፈላጊ ማዕረግ ነው። (ልጅ እና አባት እንዴት እንደተተረጎሙ ተመልከት)

በሥጋ የዳዊት ዘር የሆነው ማን ነበር?

እዚህ ላይ ‹‹ሥጋ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተጨባጭ የሆነውን አካል ነው። ‹‹ ተፈጥሮአዊ በሆነው አካል የዳዊት ዘር የሆነው ማን ነው›› ወይም ‹‹ከዳዊት ቤተ ሰብ የተወለደው ማን ነው›› (የተገመተ እውቀትና ያልተገለጠ መረጃ የሚለውን ተመልከት)

Romans 1:4

አያያዥ መግለጫ

ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚናገረው ለመስበክ ስላለበት ግዴታ ነው።

Romans 1:8

ዓለሙ ሁሉ

ጳውሎስና የመልእክቱ አባቢዎች የሚያውቁትና የሚጓዙበት ዓለም የሮም ግዛት ነበር

እግዚአብሔር ምስክሬ ነው

ጳወሎስ ከልቡ እንደሚጸልይላቸው እና ይህንንም ሲያደርግ እግዚአብሔር እንደሚያየው ትኩረት በመስጠት ይናገራል። ‹‹ስለ›› የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ሳይተረጎም ይቀራል።

በመንፈሴ

የሰው መንፈስ የሰውአንድ ክፍል ሲሆን እግዚአብሔርን የሚያውቅና የሚያምን ነው።

የልጁ ወንጌል

የመጽሐፍ ቅዱስ የምሥራቹ ቃል (ወንጌሉ) የእግዚአብሔር ልጅ ዓለምን ለማዳን ራሱን አሳልፎ የሰጠበት ነው።

ልጅ

ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለሆነው ለኢየሱስ አስፈላጊ ማዕረግ ነው።

ስለ እናንተ እንስቼአለሁ

‹‹ስለ እናንተ ለእግዚአብሔር ተናግሬአለሁ››

በጸሎቴ ጊዜ ሁሉ ሁልጊዜ የምጠይቀው--- ወደ እናንተ በመምጣቴ ---በመጨረሻ ውጤታማ እንድሆን

‹‹በምጸልይበት ጊዜ ሁሉ፣ ወደ እናንተ መጥቼ --- በመጨረሻ ውጤታማ እንድሆን --- እግዚአብሔርን እጠይቃለሁ።

በሆነ መንገድ

‹‹እግዚአብሔር በሚፈቅደው በየትኛውም መመንገድ››

በመጨረሻ

‹‹ውሎ አድሮ›› ወይም ‹‹በመጨረሻ

በእግዚአብሔር ፈቃድ

‹‹እግዚአብሔር ስለፈለገው››

Romans 1:11

አያያዥ መግለጫ

ጳውሎስ የመክፈቻ መግለጫውን በሮም ላሉ ሰዎች በመቀጠል ሊያያቸው እንደሚመኝ ይነግራቸዋል

ላያችሁ እናፍቃለሁ

‹‹ምክንያቱም በእርግጥ ላያችሁ ስለምፈልግ ነው››

እንዲያጠነክራችሁ፣ መንፈሳዊ ስጦታን

ጳውሎስ የሮሜ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲጠነክሩ ይፈልጋል። ‹‹በምንፈሳዊ ሕይወታችሁ እንድታድጉ አንዳንድ ስጦታዎች ይረዱአችኋል››

ይህም ማለቴ በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት አብረን በእናነተ እንድንጽናና ነው።

ይህንን በአድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። ‹‹በኢየሱስ ባለን እምነታችን እርስ በእርስ ልንዳችንን እንድንከፋፈል ማለቴ ነው››

Romans 1:13

መረጃ የሌላችሁ እንድትሆኑ አልፈልግም

ጳውሎስ ይህ መረጃ እንዲኖራቸው አጥብቆ ይፈልጋል። ይህንን በአጥፍ አሉታዊ በሆነ መንገድ የተገለጸውን በአዎንታዊ ቅርጹ ልትተረጉመው ትችላለህ። ‹‹እንድታውቁ እፈልጋለሁ››

ወንድሞች

ይህ ማለት ክርስቲያን ወገኖች ማለት ሲሆን፣ ሁቱንም ወንዶችንና ሴቶችን ያጠቃልላል።

እስካሁን ድረስ እንድተከለከልኩ ነው

ይህንን በአድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። ‹‹ሁልጊዜ የሆነ ነገር ይከለክለኛል››

Romans 1:16

በወንጌል አላፍርምና

ይህንን በአዎንታዊ ቅርጹ መተርጎም ትችላለህ። ‹‹በወንጌል ሙሉ ለሙሉ አምናለሁ››

ለሚያምን በሙሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነው

እዚህ ላይ ‹‹ማመን›› ማለት እምነትን በክርሰቶስ ላይ ማድረግ ማለት ነው››

አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው

‹‹ለአይሁድ ሕዝቦች እና ለግሪክ ሰዎችም››

መጀመሪያ

መጀመሪያ ማለት በጊዜ ውስጥ ከሁሉ ቀድሞ የሚመጣ ማለት ነው

በእርሱ

‹‹በእርሱ›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስ ሙሉ ለሙሉ የሚታመንበትን ወንጌልን ነው።

የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት ይገለጣልና

ጳውሎስ ስለ ወንጌል መልእክት እንደ አንድ ተጨባጭ ነገር ነገር

እንደ ተጻፈው

ይህንን በአድራጊ ቅርጹ ልትተረጉመው ትችላለህ። ‹‹አንድ ሰው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንደ ጻፈው››

ጻድቅ በእምነት ይኖራል

እዚህ ላይ ‹‹ጻድቅ›› የሚለው የሚያመለክተው በእግዚአብሔር የሚታመኑትን ነው። ‹‹በእግዚአብሔር የሚታመኑትን ሰዎች ከእርሱ ጋር የሆኑና ለዘላለም የሚኖሩ አድርጎ ይቆጥራቸዋል››

Romans 1:20

የሚታየው ማንነቱ --- በግልጽ የሚታይ ነው

ጳውሎስ ሰዎች የእግዚአብሔርን ያለመታየት ባሕርይውን መረዳታቸውን ሰዎች እነዚያን የእግዚአብሔር ባሕሪያት እንዳዩ ይናገራል። ይህ እንደ አድራጊ ቅርጽ ሊተረጎም ይችላል። ‹‹ እግዚአብሔር ስለገለጠላቸው ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ በእነርሱ ዘንድ ግልጽ ነው።››

መለኮታዊ ባሕርይ

‹‹የእግዚአብሔር ጠቅላላ ባሕርይ እና ችሎታው›› ወይም ‹‹እግዚአብሔርን አምላክ የሚያደርጉት ስለ እርሱ ያሉ ነገሮች››

ዓለም

ይህ የሚያመለክተው ሰማይንና ምድርን በውስጣቸው ያለውን ሁሉ ነው።

በተፈጠሩት ፍጥረታት ውስጥ

x

Romans 1:22

ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮዎች ሆኑ

‹‹ጥበበኞች እንደሆኑ ስለራሳቸው ሲናገሩ ነገር ግን ሞኞች ሆኑ››

እነርሱ . . . እነርሱ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በሮሜ 1:18 የተጠቀሱት ሰዎች

የማይጠፋውን የእግዚአብሔርን ክብር ለወጡ

‹‹ እግዚአብሔር ክቡር እና ፈጽሞ የማይሞት የመሆኑን እውነት ለወጡ›› ወይም ‹‹እግዚአብሔር ክቡር እና ፈጽሞ የማይሞት መሆኑን ማመናቸውን አቆሙ››

የአንድ ነገር ምስል አስመስለው

‹‹ጣዖታት የሚመስሉ ነገሮችን ማምለክ መረጡ››

የሚጠፋ ሰውን

‹‹የሚሞት ሰውን ››

ወፎችን፣ አራት እግር ያላቸውን እንስሶችን፣ እና የሚሳቡ ፍጥረቶችን

‹‹ወይም ወሮችን የሚመስሉ አራት እግት ያላቸውን እንስሶች፣ ወይም የሚሳቡ ነገሮች››

Romans 1:24

ስለዚህ

‹‹ስለዚህ አሁን የተናገርኩት እውነት ነው››

እግዚአብሔር ለ--አሳልፎ ሰጣቸው

‹‹እግዚአብሔር ለልባቸው ፍትወት እንዲሰጡ ፈቀደላቸው››

እነርሱ---የእነርሱ---እነርሱ ራሰቸው --- እነርሱ

x

Romans 1:26

በዚህ ምክንያት

‹‹በምንዝርና እና በወሲብ ኃጢአት ምክንያት››

እግዚአብሔር አሳልፎ ሰጣቸው

‹‹እግዚአብሔር ለርኩሰታቸው አሳልፎ ሰጣቸው››

በሚያስነውር ሁኔታ

‹‹የሚያሳፍር የወሲብ ፍላጎት››

ለሴቶቻቸው

‹‹በሴቶቻቸው ምክንያት››

ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ።

‹‹ተፈጥሮአዊ ያልሆነ›› የግንኙነት አሳብ ለመጥራት እንኳ የማይገባ ጸያፍ የሆነ የወሲብ ግንኙነት ነው። ‹‹እግዚአብሔር ባልፈጠረው መንገድ ወሲብን መለማመድ ጀመሩ››

ወንዶች ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ተዉ

እዚህ ላይ ‹‹ተፈጥሮአዊ ግንኙነት›› የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በማያሳፍር ሁኔታ የሚገለጽበት አባባል ነው። ‹‹ ብዙ ወንዶች ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ሴቶችን መገናኘት አቆሙ።››

እርስ በርሳቸው በፍትዎታቸው ተቃጠሉ

‹‹ወንዶች ለወንዶች ጠንካራ የፍትወት ፍላጎት አሳዩ››

የሚያሳፍር ነገር አደረጉ

‹‹ሊያፍሩበት የሚገባውን ተግባር፣ ያለምንም እፍረት አደረጉ››

ወንዶችም በወንዶች ላይ ነውር አድርገው በስህተታችው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ

“ወንዶች ባደረጉት ስህተት ምክንያት እግዚአብሔር በፍትሐዊነት ቀጣቸው”

ስህተት

የግብረገብ ስህተት፣ ስለ አንድ እውነት መሳት አይደለም

Romans 1:28

በኃሳባቸው ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ስላልፈለጉ

“እግዚአብሔርን ማወቅ አስፈላጊ እንደሆነ እንደነበር አላሰቡም

እነርሱ . . . የእነርሱ . . . እነርሱ

በሮሜ 1:18 የተጠቀሱት እነዚህ ቃሎች የሚያመለክቱት ስለ “ሰው ልጆች” ነው።

ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው

እዚህ ላይ ‹‹የማይረባ አእምሮ›› ማለት ስለ አስጸያፊ ነገሮች ብቻ የሚያስብ ማለት ነው። “እግዚአብሔር ይህ የሚያስቡት የማይጠቅምና አስጸያፊ ሃሳብ አእምሮአቸውን ሙሉ ለሙሉ እንዲቆጣጠራቸው ፈቀደ።

Romans 1:29

የተሞሉ ነበሩ

ይህንን በአድራጊ ቅርጽ ልትተረጉመው ትችላለህ። ‹‹ በውስጣቸው እጅግ ጠንካራ ፍላጎት አላቸው›› ወይም ‹‹ ይህንን ለማድረግ በጣም ጠንካራ ፍላጎት አላቸው።››

ዓመፃ ሁሉ፣ ግፍ፣ መመኘት፣ ክፋት ሁሉ መፐላባቸው

ይህንን በአድራጊ ቅርጽ ልትተረጉመው ትችላለህ። ‹‹ብዙዎች በሌሎች ሰዎች ላይ ዓመፃን ያደርጋሉ---ሰው ሰዎችን መግደልን በተከታታይ ይመኛል--- ክርክርና ፕልን በሰዎች መካከል ያነሳሳሉ--- ሌሎችን ያታልላሉ--- በሌሎች ላይ የጥላቻ ንግግርን የደርጋሉ››

ተሳዳቢዎች

ተሳዳቢዎች የተሳሳቱ ነገሮችን በሌላ ሰው ላይ በመናገር ሰውየውን ለአደጋ ያጋልጡታል።

ክፉ ነገሮችን ለማድረግ ዘዴ ይፈጥራሉ

‹‹በሌሎች ላይ ክፉ ነገሮችን ለማድረግ አዳዲስ መንገዶችን ያስባሉ››

---

Chapter 2

Romans 2:1

አያያዥ መግለጫዎች

ጳውሎስ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች እንደሆኑና ክፉዎች ስለመሆናቸው ማሳሰቡን ያረጋግጣል።

ስለዚህ የምታመካኝበት የለህም

‹‹ስለዚህ›› የሚለው ቃል የጽሑፉ አዲስ መስመር መጀመሪያ ነው። እንዲሁም ጳውሎስ በሮሜ 1:1-32 ለተናገረው መደምደሚያ ይሆናል። “እግዚአብሔር ኃጢአትን በተደጋጋሚ የሚያደርጉትን የሚቀጣ ከሆነ፣ በእርግጥ ለኃጢአታችሁ ይቅርታ አያደርግም።”

አንተ ነህ

ጳውሎስ እዚህ ላይ ሲጽፍ ልክ ከእርሱ ጋር ለሚከራከር አንድ አይሁዳዊ እንደሚጽፍ አድርጎ ነው። ጳውሎስ ይህን የሚያደርገው እግዚአብሔር ኃጢአትን በማድረግ የሚጸኑትን እንደሚቀጣ የሚጽፍላቸውን አይሁዶች ቢሆኑ አሕዛብ+ ለማስገንዘብ ነው።

አንተ

ይህ ‹‹አንተ›› የሚለው ተውላጠ ስም የተናጠል ስም ነው።

ራስህ አንተ፣ ፈራጅ የሆንከው

ጳውሎስ ‹‹አንተ›› የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ማንኛውም ራሱን እንደ አምላክ የሚቆጥርና በሌሎች ላይ የሚፈርደውን ለመገሰጽ ነው። ‹‹አንተ ራስህ ሰብኤ ፍጥረት ሆነህ እያለ የእግዚአብሔር ቅጣት ይገባቸዋል በማለት በሌሎች ላይ ትፈርዳለህ››

በሌላው ላይ በምትፈርድበት ነገር ሁሉ ራስህን ትኮንናለህ

‹‹እነርሱ እንደሚያደርጉት አንተም ታደርጋለህና በራስህ ላይ ትፈርዳለህ››

ነገር ግን እኛ እናውቃለን

እዚህ ላይ ‹‹እኛ›› የሚለው ተውላጠ ስም ክርስቲያን አማኞችንና ክርስቲያን ያልሆኑ አይሁዶችን የሚያጠቃልል ነው።

እንደዚህ በሚያደርጉትም ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ትክክለኛ መሆኑን እናውቃለን

እዚህ ላይ ጳውሎስ ስለ ‹‹እግዚአብሔር ፍርድ›› ሲናገር ሕያው እንደሆነ በሰዎች ላይ ‹‹ሊወድቅ›› እንደሚችል አድርጎ ነው። ‹‹እግዚአብሔር እነዚያን ሰዎች በእውነትና በተገቢው ሁኔታ ይፈርድባቸዋል››

እነዚያን ነገሮች የሚለማመዱ

‹‹እነዚያን ክፉ ነገሮች የሚያደርጉ ሰዎች››

Romans 2:3

ነገር ግን ይህን አስብ

‹‹ስለዚህ ይህንን አስብ›› ወይም ‹‹ስለሆነም፣ ይህንን አስብ››

ይህን አስብ

‹‹እኔ ልነግርህ ያለሁትን አስብ››

ግለሰብ

ለሰው ዘሮች ሁሉ የምትጠቀምበት አጠቃላይ ቃል ነው ‹‹አንተ ማንም ብትሆን›

እነዚህን በሚያደርጉት ላይ የምትፈርድ አንተው ራስህ ያንኑ ነገር ታደርጋለህ

‹‹አንድን ሰው የእግዚአብሔር ቅጣት ይገባዋል ብለህ የምትፈርድ አንተው ያንኑ ክፉ ነገር ታደርጋለህ››

ከእግዚአብሔር ፍርድ ታመልጣለህን?

ይህ ማስገንዘቢያ በጥያቄ መልክ የቀረበው አጽንዖት ለመስጠት ነው። ይህንን ጥያቄ እንደ አንድ ጠንካራ አሉታዊ መግለጫ አድርገህ ልትተረጉመው ትችላለህ። ‹‹አንተ በእርግጥ የእግዚአብሔርን ፍርድ አታመልጥም››

የእርሱን መልካም ባለጠግነት፣ ቅጣቱን ማዘግየቱን፣ እና ታጋሽነቱን ... ወደ ንስሐ እንደሚመራህ ሳታውቅ ትንቃለህን?

ይህ ማስገንዘቢያ ትኩረት እንዲያገኝ በጥያቄ መልክ ቀርቦአል፡፡ ይህንን እንደ ጠንካራ መግለጫ አድርገህ መተርጎም ትችላለህ፡፡ ‹‹እግዚአብሔር መልካም ስለሆነ ሰዎችን ለብዙ ጊዜ ይታገሳቸዋል ስለዚህ ይህ መልካመነቱ ንስሓ እንዲገቡ ያደርጋቸዋልና ምንም አይደለም የሚል ሁኔታ ሊኖርህ አይገባም››
የትእግስቱን---ባለጠግነት ትንሽ እንደሆነ ታስባለህ
‹‹ባለጠግነቱንና --- ትእግስቱን እንደማያስፈልግ›› ወይም ‹‹መልካም እንዳልሆነ --- ትቆጥራለህ››
የእርሱ መልካምነት ወደ ንስሓ የሚመራህ መሆኑን አታውቅምን?
ይህ ማስገንዘቢያ ትኩረት እንዲያገኝ በጥያቄ መልክ ቀርቦአል፡፡ ይህንን እንደ ጠንካራ መግለጫ አድርገህ መተርጎም ትችላለህ፡፡ ‹‹እግዚአብሔር መልካም እንደሆነ የሚያሳይህ አንተ ንስሓ እንድትገባ እንደሆነ ማወቅ አለብሕ››
Romans 2:5
አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ ሕዝቡ ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን ሕዝቡን ማስታወሱን ቀጥሎአል፡፡
ነገር ግን በደንዳናውና ንስሐ የማይገባው ልብህ ልክ
ጳውሎስ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የማይፈልገውን ሰው ለመግለጽ ልቡን ከጠንካራ ድንጋይ ጋር በማነጻጸር ገልጾታል፡፡ እንዲሁም የግለሰቡን አእምሮ ወይም ውስጣዊ ማንነት ለመግለጽ “ልብ” የሚለውን ዘይቤ ይጠቀማል፡፡ “ለማዳመጥና ንስሐ ለመግባት አሻፈረኝ በማለቱ ምክንያት ነው”
ደንዳና እና ንስሐ የማይገባ ልብ
ይህን “ንስሐ የማይገባ ልብ” በማለት ማጣመር ይቻላል፡፡
በራስህ ላይ ቁጣን አከማችተሃል
“ማከማቸት” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ብዙውን ጊዜ ሀብቱን የሚሰበስብ እና በአስተማማኝ ቦታ የሚያኖርን ሰው ነው፡፡ ጳውሎስ በሀብት ፋንታ ግለሰቡ የእግዚአብሔርን ቅጣት እየሰበሰበ ነው ብሏል፡፡ ንስሐ ሳይገቡ በቆዩበት መጠን ቅጣታቸውም ከባድ ይሆናል፡፡ “ቅጣታችሁን የከፋ ታደርጋላችሁ”
በቁጣ ቀን . . . የእግዚአብሔር የጽድቅ ፍርድ የሚገለጥበት ቀን
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች የሚያመለክቱት ያንኑ ቀን ነው፡፡ “እግዚአብሔር ቁጣውን ለሁሉም ሲያሳይ፣ ለሰው ሁሉ በትክክል ይፈርዳል”
ይከፍላል
“ትክክለኛ ዋጋ ወይም ቅጣት ይሰጣል”
ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው
“እያንዳንዱ ሰው በሠራው ሥራ መጠን”
ፈለጉ
x
Romans 2:8
አያያዥ መግለጫ
ይህ ክፍል ምንም እንኳን ሃይማኖተኛ ስላልሆነ ኃጢአተኛ ሰው የሚናገር ቢሆንም፣ ጳውሎስ አይሁድ ያልሆኑትም ሆኑ አይሁዶች በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኞች መሆናቸውን በመግለጽ ጠቅለል አድርጎ ገልጾታል፡፡
በራስ መፈለግ
“ራስ ወዳድ” ወይም “ራሳቸው ስለሚደሰቱበት ብቻ ግድ የሚላቸው”
እውነትን የማይታዘዙ ነገር ግን ጽድቅ ያልሆነውን የሚታዘዙ
እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ አንድ ዓይነት ናቸው፡፡ ሁለተኛው የመጀመሪያውን ያጠናክራል፡፡
ቁጣ እና የመረረ ንዴት ይመጣል
“ቁጣ” እና “የመረረ ንዴት” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ አንድ ዓይነት ናቸው፤ የእግዚአብሔርን ቁጣ አፅንኦት ይሰጣሉ፡፡ “እግዚአብሔር እጅግ መቆጣቱን ያሳያል”
ቁጣ
እዚህ ላይ “ቁጣ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር በኃጢአተኛ ሰዎች ላይ የሚመጣውን ከባድ ቅጣት የሚገልጽ ነው፡፡
መከራና ጭንቀት
“መከራ” እና “ጭንቀት” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ አንድ አይነት ትርጉም ያላቸው ሲሆን፣ እዚህ ላይ አፅንኦት የሚሰጡት የእግዚአብሔር ቅጣት ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ ነው፡፡ “አሰቃቂ ቅጣት ይሆናል”)
በእያንዳንዱ የሰው ነፍስ ላይ
እዚህ ላይ፣ ጳውሎስ “ነፍስ” የሚለውን ቃል መላውን ሰው ለማመልከት እንደ መነጋገሪያ ዘዴ ይጠቀማል፡፡ “በእያንዳንዱ ሰው ላይ”
ክፉ ነገሮችን የተለማመደ
“ሁልጊዜም መጥፎ ነገሮችን የሚሠራ”
አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው
“እግዚአብሔር አስቀድሞ በአይሁድ ሕዝብ ላይ፣ ከዚያም አይሁድ ባልሆኑት ሕዝቦች ላይ ይፈርዳል”
አስቀድሞ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “መጀመሪያ ከጊዜ አንጻር” ወይም 2) “በእርግጠኝነት”
Romans 2:10
ነገር ግን ምስጋና፣ ክብር እና ሰላም ይመጣሉ
x
Romans 2:13
አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም መታዘዝ፣ ሕጉ የሌላቸውም ሰዎች ብቻ ሳይሆን ሕጉ ያላቸውንም እንደሚጨምር አንባቢው እንዲያውቅ መግለጹን ቀጠለ፡፡
ለ
ቁጥር 14 እና 15 ጳውሎስ ለአንባቢው የሚሰጠውን ተጨማሪ መረጃ ያቋርጣሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን ማቋረጥ በቋንቋህ ምልክት የምታደርግበት መንገድ ካለህ፣ እዚህ ላይ መጠቀም ትችላለህ፡፡
የሕጉ አዳማጮች አይደሉም
እዚህ ላይ “ሕጉ” የሙሴን ሕግ ያመለክታል፡፡ “የሙሴን ሕግ የሚሰሙ ብቻ አይደሉም”
በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን የሆኑ ማን ናቸው
“እግዚአብሔር እንደ ጻድቃን የሚቆጥራቸው”
ነገር ግን ሕግን የሚያደርጉ
“ነገር ግን እነርሱ የሙሴን ሕግ የሚታዘዙ ናቸው”
የሚጸድቀው ማን ነው?
ይህንን በአድራጊ ቅርፅ መተርጎም ትችላለህ፡፡ “እግዚአብሔር የሚቀበለው እርሱ”
ሕግ የሌላቸው አሕዛብ . . . ለራሳቸው ሕግ ናቸው
“ለራሳቸው ሕግ” የሚለው ሐረግ ማለት እነዚህ ሰዎች በተፈጥሮአቸው የእግዚአብሔርን ሕጎች ይታዘዛሉ ማለት ነው፡፡ “የእግዚአብሔር ሕጎች ቀድሞውኑ በውስጣቸው ነበራቸው”
ሕጉ የላቸውም
እዚህ ላይ “ሕጉ” የሙሴን ሕግ ያመለክታል፡፡ “በመሠረቱ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጣቸው ሕጎች የላቸውም”
Romans 2:15
በዚህ ያሳያሉ
“በተፈጥሮ ሕጉን በመታዘዛቸው ያሳያሉ”
በሕጉ የሚፈለጉት ድርጊቶች በልባቸው ውስጥ የተጻፉ ናቸው
እዚህ ላይ “ልቦች” የግለሰቡን ሀሳቦች ወይም ውስጣዊ ማንነትን የሚገልጽ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው፡፡ “በልባቸው የተጻፈ” የሚለው ሐረግ በአዕምሯቸው ውስጥ የሆነ ነገር የማወቅ ምሳሌ ነው፡፡ ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ፡፡ “ሕጉ ምን እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸውን እግዚአብሔር በልባቸው ላይ ጽፎታል” ወይም “እግዚአብሔር በሕጉ መሠረት እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ያውቃሉ፡፡
የራሳቸው አሳቦች እራሳቸውን ሲከሳቸው፣ ወይም ለእነርሱ ሲከላከል፣ ለእነርሱ ይመሠክርላቸዋል
እዚህ ላይ “ይመሰክራል” የሚያመለክተው እግዚአብሔር በልባቸው ውስጥ ከጻፈው ሕግ ያገኙትን እውቀት ነው፡፡ “የእግዚአብሔርን ሕግ የማይታዘዙ ወይም እየታዘዙ መሆናቸውን ይነግራቸዋል”
እግዚአብሔር በሚፈርድበት ቀን
ይህ በሮሜ 2:13 ላይ የተገለጸውን የጳውሎስን ኃሳብ ያጠቃልላል፡፡ “እግዚአብሔር በሚፈርድበት ጊዜ ይህ ይሆናል”
Romans 2:17
አያያዥ መግለጫ
እዚህ ላይ ጳውሎስ ንግግሩን በመቀጠል አይሁድ ያላቸው ሕግ በመሠረቱ እነርሱ ስላልታዘዙት ይፈርድባቸዋል ይላል፡፡
አንተ እራስህን አይሁድ ብለህ ብትጠራ
“አንተ እራስህን አይሁዳዊ ብለህ ከጠራህ”
በሕጉ ላይ እረፍ
“በሕጉ ላይ እረፍ” የሚለው ሐረግ ሕጉን በመታዘዛቸው ጻድቃን መሆን እንደሚችሉ ማመንን ያመለክታል፡፡ “በሙሴ ሕግ መታመን”

ፈቃዱን እወቅ
“እና የእግዚአብሔርን ፈቃድ እወቅ”
ምክንያቱም በሕጉ ስለታዘዛችሁ
ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። “ምክንያቱም ሰዎች ትክክለኛውን ነገር ከሕጉ ስላስተማሯችሁ” ወይም “ምክንያቱም ከሕጉ ስለ ተማራችሁ”
አንተ ራስህ ለዕውሮች መሪ፣ በጨለማ ውስጥ ላሉት ብርሃን
እዚህ ላይ “ዕውሮች” እና “በጨለማ የሚመላለሱ” ሕጉን ያልተረዱ ሰዎችን ይወክላሉ። “ሕግን ስለምታስተምር፣ አንተ ራስህ ለዕውሮች እንደ መሪ፣ በጨለማ ለሚመላለሱ ሰዎች እንደ ብርሃን ነህ”
ለሰነፎች አራሚ
“ስሕተት የሚያደርጉትን የምታርም”
የልጆች አስተማሪ
እዚህ ላይ ጳውሎስ ስለ ሕጉ ምንም የማያውቁትን ከትናንሽ ሕፃናት ጋር ያነፃፅራቸዋል። “ሕግን የማያውቁትን ታስተምራለህ”
በሕጉ ውስጥ የእውቀት እና የእውነት መልክ አለህ
በሕጉ ውስጥ ያለው የእውነት እውቀት የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው። “ምክንያቱም እግዚአብሔር በሕጉ ውስጥ የሰጠውን እውነት መረዳትህን ታረጋግጣለህ”
Romans 2:21
አንተ ሌሎችን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን?
ጳውሎስ አድማጮቹን ለመገሰጽ ጥያቄን ይጠቀማል። ይህንን እንደ ጠንካራ መግለጫ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ሌሎችን ታስተምራለህ ግን ራስህን አታስተምርም!” ወይም “ሌሎችን ታስተምራለህ፣ ግን የምታስተምረውን አታደርግም!”
አትስረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን?
ጳውሎስ አድማጮቹን ለመገሰጽ ጥያቄን ይጠቀማል። ይህንን እንደ ጠንካራ መግለጫ ልትተረጉመው ትችላለህ። AT: “ሰዎች እንዳይሰርቁ ትነግራለህ፣ አንተ ግን ትሰርቃለህ!”
ማንም ማመንዘር የለበትም ብለህ የምትናገር ታመነዝራለህን?
ጳውሎስ አድማጮቹን ለመገሰጽ ጥያቄን ይጠቀማል። ይህንን እንደ ጠንካራ መግለጫ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ሰዎችን እንዳያመነዝሩ ትነግራለህ፣ አንተ ግን ታመነዝራለህ!”
ጣኦትን የምትጠላ፣ ቤተ መቅደሶችን ትዘርፋለህን?
ጳውሎስ አድማጮቹን ለመገሰጽ ጥያቄን ይጠቀማል። ይህንን እንደ ጠንካራ መግለጫ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ጣኦትን እንደምትጠላ ትናገራለህ፣ ነገር ግን ቤተ መቅደሶችን ትዘርፋለህ!”
ቤተ መቅደሶችን መዝረፍ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “ከአሕዛብ የአጥቢያ ቤተ መዝቅደሶች ቁሳቁሶችን መስረቅ እና ትርፍ ለማግኘት መሸጥ” ወይም 2) “ለእግዚአብሔር የሆነውን ገንዘብ ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ አለመላክ”።
Romans 2:23
አንተ በሕግ የምትመካ፣ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታዋርዳለህን?
ጳውሎስ አድማጮቹን ለመገሰጽ ጥያቄን ይጠቀማል። ይህንን እንደ ጠንካራ መግለጫ ልትተረጉመው ትችላለህ። - “ሕግን ባለመታዘዝህ እግዚአብሔርን የምታዋርድ እየሆንክ፣ በሕግ እመካለሁ ማለታህ ኃጢአት ነው!”
Romans 2:25
አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ እግዚአብሔር፣ በሕጉ፣ የእግዚአብሔር ሕግ ያላቸውን አይሁዶችንም ጨምሮ እንደሚኮንናቸው ማሳየቱን ቀጥሏል።
መገረዝ በእርግጥ ጠቃሚ ነው
“እነዚህን ሁሉ ያልኩት መገረዝ ስለሚጠቅማቸሁ ነው”
ሕጉን ብትጥስ
“በሕጉ ውስጥ ያሉትን ትእዛዛት የማትታዘዝ ከሆነ”
መገረዝህ አለመገረዝ ይሆናል
“ልክ ፈጽመህ እንዳልተገረዝክ ማለት ነው”
ያልተገረዘ ሰው
ያልተገረዘ ሰው ነው
ሕጉን እንዲሟላ የሚጠይቀውን ይጠብቃል
“እግዚአብሔር በሕጉ ውስጥ ያዘዘውን ይታዘዛል”
የእርሱ አለመገረዝ እንደ መገረዝ አይቆጠርምን? አንድ ሰው በተፈጥሮ ያልተገረዘ ቢሆን በሕጉ . . . በአንተ ይፈርድብሃልን?
ጳውሎስ መገረዝ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል ለመሆን አስፈላጊ አለመሆኑን አጽንኦት ለመስጠት እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች ይጠይቃል። እነዚህን ጥያቄዎች እንደ መግለጫ በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉማቸው ትችላለህ። “እግዚአብሔር እንደተገረዘ አድርጎ ይቆጥረዋል። በአካል ያልተገረዘ ሰው በአንተ . . . በሕጉ ይፈርድብሃል።
Romans 2:28
በውጭ
ይህ ሰዎች ሊመለከቱት የሚችሉትን እንደ መገረዝ ያለ የአይሁድን የአምልኮ ሥርዓቶች ይመለከታል።
ከውጭ በሥጋ የሚታይ
ይህ አንድ ሰው ሲገረዝ በአካሉ ላይ የሚታየውን አካላዊ ለውጥ ያመለክታል።
ሥጋ
ይህ ጠቅላላው የሰውን አካል የሚያመለክት መግለጫ ነው።

---

Chapter 3
Romans 3:1
አያያዥ መግለጫ
እግዚአብሔር ሕጉን ስለ ሰጣቸው አይሁዶች ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ጳውሎስ ያውጃል።
እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድን ነው? የመገረዝ ጥቅሙ ምንድን ነው?
ጳውሎስ በምዕራፍ 2 ላይ የጻፈውን ከሰሙ በኋላ ሰዎች ሊኖራቸው የሚችሏቸውን ሀሳቦች ያቀርባል። ይህንን ያደረገው በቁጥር 2 ላይ ለእነርሱ መልስ ለመስጠት ነው። “አንዳንድ ሰዎች ‘ታዲያ አይሁዳዊው ምን ጥቅም አለው? እና የመገረዝ ጥቅሙስ ምንድን ነው?ይሉ ይሆናል'” ወይም “አንዳንድ ሰዎች ምናልባት ደግሞ ‘ያ እውነት ከሆነ አይሁዶች ምንም ጥቅም የላቸውም፣ እንዲሁም መገረዝም ምንም ፋይዳ የለውም ይሉ ይሆናል።'”
በየትኛውም መንገድ ጥቅሙ ብዙ ነው
ጳውሎስ አሁን በቁጥር 1 ላይ ለተነሡት አሳቦች ምላሽ ይሰጣል። እዚህ ላይ “ይህ” የሚያመለክተው የአይሁድ ሕዝቦች አባል መሆን ነው። “ግን አይሁዳዊ መሆን ትልቅ ጥቅም አለው”
በመጀመሪያ
ተቀባይነት ያላቸው ትርጉሞች 1) “በመጀመሪያ በጊዜ ቅደም ተከተል” ወይም 2) “በጣም በእርግጠኝነት” ወይም 3) “እጅግ በጣም በአስፈላጊነት” ናቸው።
አይሁዶች ከእግዚአብሔር መገለጥ በአደራ ተሰጥቷቸዋል
እዚህ ላይ “መገለጥ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ቃሎች እና ቃል ኪዳኖችን ያሳያል። ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “እግዚአብሔር ቃል ኪዳኖቹን የያዘውን ቃሎቹን ለአይሁድ ሰጥቷል”
Romans 3:3
አንዳንድ አይሁዶች እምነት ባይኖራቸውስ? አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን?
ጳውሎስ ሰዎች እንዲያስቡ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠቀማል። “አንዳንድ አይሁዶች ለእግዚአብሔር ታማኝ አልነበሩም። ከዚህ በመነሣት እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን መፈጸም አይችልም ብለን መደምደም አለብንን?”
በጭራሽ አይሆንም
ይህ እንደማይሆን ይህ አገላለጽ አጥብቆ ይቃወማል። እዚህ ላይ ልትጠቀምበት የምትችለው በቋንቋህ ተመሳሳይ አገላለጽ ሊኖርህ ይችላል። “ፈጽሞ ሊሆን አይችልም!” ወይም “በጭራሽ አይሆንም!”
ይልቁንስ
“ይልቁንስ ማለት አለብን”
ይልቁንስ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን
እግዚአብሔር ሁል ጊዜ እውነተኛ ነው እናም ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል።
“እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የገባውን ቃል ኪዳን ይፈጽማል”
እያንዳንዱ ሰው ውሸተኛ ቢሆን
“እያንዳንዱ” እና “ውሸተኛ” የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ሁልጊዜ እውነተኛ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት የተጋነኑ ቃላት ናቸው። “ምንም እንኳ እያንዳንዱ ሰው ሐሰተኛ ቢሆን”


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደ ተጻፈው

ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ቅዱሳት መጻሕፍት ራሳቸው እኔ ከምናገረው ጋር ይስማማሉ”

በቃልህ ጻድቅ መስለህ ልትታይ ትችል ይሆናል፣ ወደ ፍርድም በመጣህ ጊዜ የምትረታ ሊመስልህ ይችላል

እነዚህ ሁለት ሐረጎች በጣም ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “እያንዳንዱ ሰው የምትናገረው ነገር እውነት መሆኑን መቀበል አለበት፣ እናም ማንም ሰው ቢቃወምህ ሁል ጊዜ በጉዳይህ ላይ ታሸንፋለህ”

Romans 3:5

ነገር ግን ዓመፃችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ ካሳየ፣ ምን ማለት እንችላለን? እግዚአብሔር ቁጣውን በእኛ ላይ በማምጣቱ ጻድቅ አይደለም ማለት እንችላለንን?

ጳውሎስ እነዚህን ጥያቄዎች የሚጠቀመው የአንዳንድ ሰዎችን መከራከሪያ ለማቅረብ እና አንባቢዎቹ እነዚህ መከራከሪያዎች እውነት መሆናቸውንና አለመሆናቸውን እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። “አንዳንድ ሰዎች የእኛ አመጸኝነት የእግዚአብሔርን ጽድቅ ካሳየ፣ እግዚአብሔር እኛን በመቅጣቱ ጻድቅ አይደለም” ይላሉ።

ቁጣውን በእኛ ላይ ያመጣ ዘንድ ነው

እዚህ ላይ “ቁጣ” የቅጣት አባባል ነው። “ቅጣቱን በእኛ ላይ ለማምጣት” ወይም “እኛን ለመቅጣት”

እኔ የሰውን መከራከሪያ እጠቀማለሁ

“እዚህ ላይ የምናገረው አንዳንድ ሰዎች ያሉትን ነው” ወይም “አንዳንድ ሰዎች ያሉት ይህ ነው”

ፈጽሞ አይሁን

“እግዚአብሔር ዓመፀኛ ነው ማለት የለብንም”

እንግዲያውስ እግዚአብሔር በዓለም እንዴት ይፈርዳል?

አይሁዶች እግዚአብሔር በሰዎች ሁሉ ላይ እንደሚፈርድ ስለሚያምኑ ጳውሎስ በወንጌሉ ላይ የሚነሱት ክርክሮች ትክክለኛ ያልሆኑ መሆናቸውን ለማሳየት ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። “ሁላችንም በእውነት እግዚአብሔር በዓለም ላይ እንደሚፈርድ እናውቃለን!”

ዓለም

“ዓለም” በዓለም ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ነው። “በዓለም ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው”

Romans 3:7

ነገር ግን የእኔ ውሸተኛ መሆን የእግዚአብሔርን እውነተኛነት የሚያጎላ፣ ክብሩንም የሚጨምርለት ከሆነ፣ ኃጢአተኛ ተብዬ እስከ አሁን እንዴት ይፈረድብኛል?

እዚህ ላይ ጳውሎስ አንድ ሰው የክርስቲያንን ወንጌል መቃወሙን እንደቀጠለ ይገምታል። ያ ተቃዋሚ ይሟገታል፣ ምክንያቱም ኃጢአቱ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ያሳያል፣ ስለሆነም፣ ለምሳሌ፣ ውሸትን ቢናገር እግዚአብሔር በፍርድ ቀን ኃጢአተኛ መሆኑን መግለጽ የለበትም።

ለምን በል . . . ና?

እዚህ ላይ ጳውሎስ በአሳብ ደረጃ ያለውን ተሟጋች ክርክር አቃልሎ ለማሳየት የእራሱን ጥያቄ ያነሣል። “እኔ እንዲሁ ለማለት እችላለሁ . . . ና!”

እኛ በሐሰት እንደተናገርን

“አንዳንዶች እኛ ያልነው ይህ እንደሆነ አድርገው ለሌሎች በውሸት ይናገራሉ”

በእነርሱ ላይ ፍርዱ ትክክለኛ ነው

ጳውሎስ ባስተማረው ትምህርት ላይ ውሸት የሚናገሩትን የጳውሎስ ጠላቶች እግዚአብሔር ቢፈርድባቸው ፍርዱ ትክክለኛ ነው።

Romans 3:9

አያያዥ መግለጫ

ጳውሎስ በአጠቃላይ ሲናገር፣ ሁሉም ኃጢአተኛ ነው፣ ማንም ጻድቅ የለም፣ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም ይላል።

እንግዲውስ? ለእራሳችንን ይቅር ማለት እንችላለን?

ጳውሎስ አሳቡን ለማጉላት እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቃል። “እኛ አይሁዳውያን አይሁዳውያን በመሆናችን ብቻ ከእግዚአብሔር ፍርድ እናመልጣለን ብለን ለማሰብ መሞከር የለብንም!”

ፈጽሞ

እነዚህ ቃላት በቀላሉ “አይደለም” ከምንለው ጠንካራ ናቸው፣ ነገር ግን እንደ “በፍጹም አይደለም!” እንደሚለው ጠንካራ አይደለም።

ይህ እንደ ተጻፈው ነው

ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ይህ ነቢያት በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ጻፉት ነው”

Romans 3:11

የሚያስተውል አንድስ እንኳ የለም

ትክክል የሆነውን ነገር የሚያስተውል የለም። “ትክክለኛ የሆነውን ነገር የሚያስተውል ማንም የለም”

እግዚአብሔርን የሚፈልግ የለም

እዚህ ላይ “እግዚአብሔርን መፈለግ” የሚለው ሐረግ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት መፍጠርን የሚያመለክት ነው። “ማንም ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ኅብረት የውለም”

ሁሉም ትችሳስተዋል

ይህ ሰዎቹ እግዚአብሔርን ማሰብ እንኳን እንደማይፈልጉ ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ፈሊጣዊ አባባል ነው። እርሱን ለማስወገድ ይፈልጋሉ። “ሁሉም ከእግዚአብሔር ርቀዋል”

እነርሱ በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል

ማንም መልካም የሆነውን ስለማያደርግ ለእግዚአብሔር የማይጠቅሙ ናቸው። “እያንዳንዱ ለእግዚአብሔር የማይጠቅም ሆኗል”

Romans 3:13

የእነርሱ . . . የእነርሱ

“የእነርሱ” የሚለው ቃል በሮሜ 3፡9 ላይ የሚያመለክተው “አይሁዶችን እና ግሪኮችን” ነው።

ጉሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው

“ጉሮሮ” የሚለው ቃል ሰዎች ለሚናገሩት አመጽ እና አስጸያፊ ነገር ሁሉ በምሳሌነት የሚገልጽ ነው። እዚህ ላይ “የተከፈተ መቃብር” የሚለው ምሳሌ ሰዎች የሚናገሩትን ክፉ ቃላት የሚያመለክት ነው።

በአንደበታቸው አታለዋል

“አንደበታቸው” የሚለው ቃል ሰዎች ለሚናገሩት ሐሰተኛ ቃላት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። “ሰዎች ውሸት ይናገራሉ”

የእባቦች መርዝ ከከንፈሮቻቸው በታች አለ

እዚህ ላይ “የእባቦች መርዝ” የሚለው ቃል የሚወክለው ሰዎች የሚናገሩትን እጅግ ጎጂ የሆኑ ክፉ ቃላትን ነው። “ከንፈሮች” የሚለው ቃል የሰዎችን ቃላት ያመለክታል። “የእነርሱ ክፉ ቃላት ልክ እንደ አደገኛ እባብ መርዝ ሰዎችን ይጎዳል”

አንደበታቸው እርግማንና መራርነትን የተሞላ ነው

እዚህ ላይ “አንደበታቸው” የሰዎችን ክፉ ቃል የሚወክል ምሳሌአዊ አነጋገር ነው። “የተሞላ” የሚለው ቃል ሰዎቹ ምን ያህል መራርነትንና እርግማንን እንደሚናገሩ በማጋነን የሚያሳይ ነው። “ብዙውን ጊዜ እርግማን እና የጭካኔ ቃላትን ይናገራሉ”

Romans 3:15

የእነርሱ . . . የእነርሱ . . . እነዚህ ሰዎች . . . የእነርሱ

እነዚህ ቃላቶች የሚያመለክቱት በሮሜ 3፡9 ውስጥ ያሉትን አይሁዶች እና ግሪኮችን ነው።

እግሮቻቸው ደምን ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው

እዚህ ላይ “እግሮች” የሚለው ሰዎቹን እራሳቸውን የሚያመለክት አባባል ነው። “ደም” የሚለው ቃል ሰዎችን መግደል የሚያመለክት ምሳሌ ነው። “ሰዎችን ለመጉዳት እና ለመግደል የፈጠኑ ናቸው”

ጥፋትና መከራ በመንገዳቸው ላይ ናቸው

እዚህ ላይ “ጥፋት እና መከራ” የሚሉት ቃላት የሚወክሉት ሰዎቹ በሌሎች ሰዎች ላይ የሚያስከትሉትን ጉዳትና መከራ ነው። “ሌሎችን ለማጥፋት እና መከራ ሊያደርሱባቸው ይጥራሉ”

የሰላም መንገድ

“ከሌሎች ጋር በሰላም እንዴት መኖር እንደሚቻል።” “መንገድ” ጎዳና ወይም መተላለፊያ ነው።

በዓይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም

እዚህ ላይ “ፍርሃት” የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ማክበር እና እርሱንም ለማክበር ፈቃደኝነትን የሚወክል ነው። “ሁሉም ሰው ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆነም”

Romans 3:19

ሕጉ የሚለውን ይናገራል

ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚናገረው ሕጉ ሕያው እንደሆነና ልክ የራሱ ድምፅ እንዳለው



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አድርጎ ነው። “ሕጉ የሚናገረው ሰዎች ማድረግ የሚገባቸው” ወይም “ሙሴ በሕጉ ውስጥ የጻፋቸው ትእዛዛት ሁሉ”

ከሕጉ በታች የሆኑት

“ሕጉን መታዘዝ ያለባቸው”

Romans 3:21

አያያዥ መግለጫ

እዚህ ላይ “ግን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስ መግቢያውን መጨረሱንና ዋንኛውን ነጥብ መጀመሩን ነው።

አሁን

“አሁን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ኢየሱስ ወደ ምድር ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው።

ያለ ሕግ የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአል

ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ሕጉን ሳትታዘዝ እግዚአብሔር በእርሱ ፊት ትክክል የምትሆንበትን መንገድ አሳውቆአል”

በሕጉ እና በነቢያት ተመስክሮለታል

“ሕጉና ነቢያት” የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት በሙሴና በነቢያቱ በአይሁድ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተጻፉትን ከፊል የእግዚአብሔር ቃል ነው። ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚገልጻቸው በፍርድ ቤት ቆመው እንደሚመሰክሩ ሰዎች አድርጎ ነው። ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ሙሴና ነቢያት የጻፉት ይህንን ያረጋግጣሉ”

በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን በኩል የሆነው የእግዚአብሔር ጽድቅ

እዚህ ላይ “ጽድቅ” ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል መሆን ማለት ነው። “በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን በእግዚአብሔር ፊት ትክክል መሆን”

ልዩነት የለምና

ጳውሎስ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሁሉንም ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ እንደሚቀበል ነው። “በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ፈጽሞ ልዩነት የለም”

Romans 3:23

ከእግዚአብሔር ክብር ጎድለዋል

እዚህ ላይ “የእግዚአብሔር ክብር” የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ሲሆን፣ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን አምሳያ እና ባሕርይውን ነው። “እግዚአብሔርን ከመምሰል ጎደሉ”

በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል በጸጋው እንዲያው ይጸድቃሉ

እዚህ ላይ “መጽደቅ” የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛ መሆንን ነው። ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “እግዚአብሔር በእርሱ ፊት ትክክለኛ ይሆኑ ዘንድ እንደ ነጻ ስጦታ ሰጥቷቸዋል፣ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነጻ አውጥቶአቸዋልና።”

እነርሱ በነጻ ጸድቀዋል

ይህ ማለት እነርሱ የጸደቁት የራሳቸው ሊያደርጉት ወይም የተገባቸው ሳይሆኑ ነው። እግዚአብሔር በነጻ ያጸድቃቸዋል። “በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆኑት ሊያገኙት የሚገባቸው ሆኖ አይደለም”

Romans 3:27

ትምክህት እንግዲህ ወዴት አለ? ፈጽሞ የለም

ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው ሰዎች ሕጉን በመታዘዝ የሚኩራሩበት ምንም ምክንያት እንደሌለ ለማሳየት ነው። “እንግዲያው እነዚያን ሕጎች ስለታዘዝን በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ እንዳገኘን የምንኮራበት ምንም መንገድ የለም። ትምክህት ተወግዶአል”

በምን መሠረት? በሥራ ነውን? አይደለም፣ ነገር ግን በእምነት መሠረት እንጂ

ጳውሎስ የሚያነሣቸው እያንዳንዱ ነጥብ በእርግጠኝነት እውነት መሆኑን አፅንኦት ለመስጠት እነዚህን መልስ የማይሰጥባቸውን ጥያቄዎች ይጠይቃል ይመልሳልም። ይህንን ጳውሎስ ሊላቸው የፈለጋቸውን ቃላት አድራጊ ቅርፅን በመጠቀም ልትተረጉማቸው ትችላለህ። “ትምክህትን የምናስወግደው በምን መሠረት ነው? በመልካም ሥራችን ምክንያት ልናስወግደው ይገባልን? ፈጽሞ፣ ይልቁንም በእምነት ልናስወግደው ይገባናል”

Romans 3:29

ወይስ እግዚአብሔር የአይሁድ አምላክ ብቻ ነውን?

ጳውሎስ እነዚህን ጥያቄዎች ለአጽንኦት ለመስጠት ይጠይቃል። “እናንተ አይሁዳውያን፣ በእርግጥ እግዚአብሔር የሚቀበለው እናንተን ብቻ እንደሆነ ማሰብ የለባችሁም!”

የአሕዛብስ ደግሞ አምላክ አይደለምን? አዎን፣ የአሕዛብም ደግሞ ነው

ጳውሎስ ነጥቡን ለማጉላት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። “እርሱ ደግሞ አይሁድ ያልሆኑትን፣ አሕዛብንም ይቀበላል”

እርሱ መገረዝን በእምነት ያጸድቃል፣ አለመገረዝንም ደግሞ በእምነት

እዚህ ላይ “መገረዝ” አይሁድን የሚያመለክት ምሳሌአዊ አነጋገር ሲሆን “አለመገረዝ” ደግሞ አይሁድ ያልሆኑትን የሚያመለክት ምሳሌአዊ አነጋገር ነው። “እግዚአብሔር አይሁዶችንም ሆኑ አይሁድ ያልሆኑትን በክርስቶስ ላይ ባላቸው እምነት በኩል በፊቱ ያጸድቃቸዋል”

Romans 3:31

አያያዥ መግለጫ

ጳውሎስ ሕጉን በእምነት ያጸናል።

እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለንን?

ጳውሎስ ከአንባቢዎቹ አንዱ ሊኖረው የሚችለውን ጥያቄ ይጠይቃል። “አንድ ሰው እምነት ስላለን ሕጉን ችላ ማለት እንችላለን ይል ይሆናል።”

ፈጽሞ አይሆንም

ይህ አገላለጽ ቀደም ሲል ለተነሣው የአጻጻፍ ጥያቄ እጅግ ጠንካራ ምላሽ የሚሰጥ ነው። እዚህ ላይ ልትጠቀምበት የምትችል ተመሳሳይ አገላለጽ በቋንቋህ ሊኖርህ ይችላል። “ይህ በእርግጥ እውነት አይደለም” ወይም “ፈጽሞ አይደለም”

ሕጉን እንደግፋለን

“ሕጉን እንታዘዛለን”

እኛ

ይህ ተውላጠ ስም ጳውሎስን፣ ሌሎች አማኞችን እና አንባቢዎችን ይመለከታል።

---

# Chapter 4

## Romans 4:1

አያያዥ መግለጫ

ጳውሎስ በቀድሞ ዘመን አማኞች በእግዚአብሔር ፊት የሚጸድቁት በእምነት እንጂ በሕግ እንዳልነበረ ያረጋግጣል።

እንግዲህ በሥጋ የቀድሞ አባታችን የሆነ አብርሃም በዚህ ረገድ ምን አገኘ እንላለን?

ጳውሎስ ጥያቄውን የሚጠቀመው የአንባቢውን ትኩረት ለመሳብ እና ስለ አዲስ ነገር ለመናገር ለመጀመር ነው። “በሥጋ አባታችን የሆነው አብርሃም ያገኘው ይህ ነው”

የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል?

ጳውሎስ አጽንኦት ለመጨመር ይህንን ጥያቄ ይጠቀማል። ስለ እግዚአብሔር ቃሎች ሲናገር ልክ ሕያው እንደሆኑ መናገር እንደሚችሉ አድርጎ ነው። “በእግዚአብሔር ቃል ልናነብ እንችላለን”

እንደ ጽድቅም ተቆጠረለት

ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “እግዚአብሔር አብርሃምን እንደ ጻድቅ አድርጎ ቆጥሮታል”

## Romans 4:4

የከፈለበት እንደ ስጦታ አይቆጠርም

ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። “ማንም ሠራተኛ አሠሪው የሚሰጠውን ደሞዝ እንደ ስጦታ አድርጎ አይቆጥረውም”

እንደ ዕዳ ነው እንጂ

ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊረተጎም ይችላል። አት: - “ነገር ግን አሠሪው ለሠራተኛው የሚከፍለው ዕዳ ነው”

የሚያጸድቀው

“በእግዚአብሔር በሚያጸድቀው”

እምነቱ እንደ ጽድቅ ተቆጥሮለታል

ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። “እግዚአብሔር የግለሰቡን እምነት እንደ ጽድቅ ይቆጥርለታል” ወይም “እግዚአብሔር በእምነቱ ምክንያት ግለሰቡን ጻድቅ አድርጎ ይቆጥረዋል”

## Romans 4:6

ዳዊትም እንዲሁ እግዚአብሔር ያለ ሥራ ጽድቅን የሚቆጥርለትን ሰው የተባረከ ነው ይላል

“ዳዊት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ሥራ ጽድቁን የሚቆጥርለትን ሰው እግዚአብሔር እንዴት እንደባረከው ጽፎአል”

ዓመጻቸው ይቅር የተባለላቸው . . . በደላቸውም የተከደነላቸው . . . ጌታ ኃጢአታቸውን የማይቆጥርባቸው



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ተመሳሳይ ፅንሰ-ሀሳብ በሦስት የተለያዩ መንገዶች ተገልጿል። ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። “ጌታ ሕጉን የጣሱትን ይቅር ብሎአል . . . ኃጢአታቸውን ጌታ ከድኖላቸዋል . . . ጌታም ኃጢአታቸውን አልቆጠረባቸውም ”

Romans 4:9

እንግዲህ ይህ ብፅዕና ለተገረዙት ብቻ ነው? ወይስ ስላልተገረዙት?

ይህ አስተያየት በጥያቄ መልኩ መቅረቡ አፅንኦትን ለመጨመር ነው። “እግዚአብሔር የሚባረከው የተገረዙትን ብቻ ነው? ወይስ ያልተገረዙትን?”

Romans 4:11

ሳይገረዝ በነበረው ጊዜ ቀድሞ ያገኘውን እምነት የጽድቅ ማኅተም የሚያሳይ ነው

እዚህ ላይ “የእምነት ጽድቅ” ማለት እግዚአብሔር እንደ ጻድቅ አድርጎ ይመለከተው ነበር። “ከመገረዙ በፊት በእግዚአብሔር በማመኑ ምክንያት እግዚአብሔር እንደ ጻድቅ አድርጎ የሚቆጥርበት ምልክት ነው”

ምንም እንኳ ያልተገረዙ ቢሆኑም

ምንም እንኳ ባይገረዙም

ይህ ማለት ጽድቅ ለእነርሱ ይቆጠራል ማለት ነው

ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። “ይህ ማለት እግዚአብሔር እንደ ጻድቃን ይቆጥራቸዋል ማለት ነው”

አብርሃም የተገረዙት አባት ሆነ

እዚህ ላይ “መገረዝ” የሚያመለክተው በአይሁድም ሆነ በአሕዛብ በእግዚአብሔር እውነተኛ አማኞች የሆኑትን ነው።

የአባታችንን የአብርሃምን የእምነት ምሳሌ ተከተሉ

እዚህ ላይ “የእምነት እርምጃ ተከተሉ” ማለት የአንድን ሰው ምሳሌነት መከተል ማለት ነው። “የአባታችንን የአብርሃምን የእምነት ምሳሌ የሚከተሉ” ወይም “አባታችን አብርሃም እንዳደረገው እምነት ያላቸው”

Romans 4:13

ወራሾች

እግዚአብሔር ቃል የገባላቸው ሕዝቦች ልክ ከቤተሰብ አባል ንብረትንና ሀብትን እንደሚወርሱ ተደርገው ይወሰዳሉ።

ነገር ግን በእምነት በሚሆነው ጽድቅ በኩል

“ቃል ኪዳኑ መጣ” የሚሉትን ቃላት በመጀመሪያው ሐረግ እንረዳዋለን። በተዘዋዋሪ መንገድ የተጠቀሱትን ቃላት በመጨመር ይህንን ልትተረጉመው ትችላለህ። “ነገር ግን ቃል ኪዳኑ የመጣው እግዚአብሔር እንደ ጽድቅ አድርጎ በሚቆጥረው እምነት በኩል ነው”

እነዚያ በሕግ የሚኖሩ ወራሾች ከሆኑ

እዚህ ላይ “በሕጉ የሚኖሩ” የሚያመለክተው ሕግን መታዘዝ ነው። “ሕጉን የሚታዘዙ እነርሱ ምድርን የሚወርሱት ከሆኑ”

እምነት የማይጠቅም፣ እናም ተስፋው ከንቱ ነው

“እምነት ዋጋ የለውም፣ ተስፋውም ትርጉም የለሽ ነው”

ምንም መተላለፍ የለም

“መተላለፍ” የሚለውን ረቂቅ ስም ለማስወገድ እንደገና ሊጠቀስ ይችላል። “ማንም ሕጉን ሊጥስ የሚችል የለም” ወይም “ሕጉን አለመታዘዝ ፈጽሞ አይቻልም”

Romans 4:16

ለዚህ ምክንያት

“ስለዚህ”

ይህ በእምነት ነው

“ይህ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ቃል የገባውን መቀበል ነው። “ቃል ኪዳኑን የምንቀበለው በእምነት ነው” ወይም “ቃል ኪዳኑን በእምነት እንቀበላለን”

ቃል ኪዳኑ በጸጋ ላይ ያርፍ ዘንድ

“ቃል ኪዳኑ በጸጋ ላይ ያርፋል” የሚለው የሚወክለው እግዚአብሔር ቃል የገባውን የሚሰጠው በጸጋ መሆኑን ነው። “ስለዚህ የገባው ቃል ኪዳን ነጻ ስጦታ ሊሆን ይችላል፣ ወይም “ስለዚህ ቃል ኪዳኑ በጸጋው ይሆናል ማለት ነው”

ለሁሉም የአብርሃም ዝርያዎች ዋስትና ይሆናል

ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል። “ሁሉም የአብርሃም ዘሮች እግዚአብሔር እንደሚሰጥ ቃል የገባውን በእርግጥ ሊቀበሉ ይችላሉ”

ከሕግ በታች ያሉ

ይህ የሙሴን ሕግ የመታዘዝ ግዴታ ያለባቸውን የአይሁድን ሕዝብ ይመለከታል።

እነዚያ የአብርሃምን እምነት የሚጋሩ ናቸው

ይህም አብርሃም ከመገረዙ በፊት እንዳደረገው ሁሉ እምነት ያላቸውን ያመለክታል።

“አብርሃም እንዳደረገው ያመኑ”

የእኛ ሁሉ አባት

እዚህ ላይ “የእኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስንና አይሁድን በሙሉ እንዲሁም በክርስቶስ ያመኑ አይሁድ ያልሆኑትን ሁሉ ነው። አብርሃም የአይሁድ ሕዝብ በሥጋ አባታቸው ነው፣ ነገር ግን እርሱ ለሚያምኑ ሁሉ መንፈሳዊ አባት ነው።

እንደ ተጻፈው

በተጻፈበት ቦታ ግልጽ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ይህን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “አንድ ሰው በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ጻፈው”

እኔ አንተን ሠራሁህ

እዚህ ላይ “አንተን” የሚለው ቃል ነጠላ ሲሆን የሚያመለክተው አብርሃምን ነው።

Romans 4:18

በተስፋ ያለተስፋ አመነ

ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር አብርሃም እግዚአብሔርን ያመነው ወንድ ልጅ እንደሚኖረው ተስፋ በማያደርግበት ጊዜ ነው። “ምንም እንኳን ለእርሱ ልጆች እንደሚኖሩት የማይቻል ቢመስልም እግዚአብሔርን አመነ”

በተነገረው መሠረት

ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊተረጎም ይችላል። “እግዚአብሔር ለአብርሃም እንደ ተናገረው”

ዘሮችህ እንዲሁ ይሆናሉ

እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ሙሉ ተስፋ ግልፅ ሊሆን ይችላል። “ልትቆጥራቸው ከምትችላቸው በላይ ብዙ ዘሮች ይኖሩሃል”

በእምነት አልደከመም

ይህንን በአዎንታዊ መልኩ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ምንም ቢሆን በእምነቱ ጠንካራ ነበር”

Romans 4:20

ባለማመን አልተጠራጠረም

ይህንን ድርብ አሉታዊ በአዎንታዊ ቅርፅ መተርጎም ይቻላል። “በእምነት ማድረጉን ቀጠለ”)

በእምነት ጠንካራ ነበር

ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “በእምነቱ ጠንካራ ሆነ”

እርሱ ሙሉ በሙሉ አምኖበታል

“አብርሃም ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነበር”

እርሱ ደግሞ ማከናወን ይችላል

“እግዚአብሔር ማድረግ ችሎ ነበር”

ይህም ደግሞ እንደ ጽድቅ ተቆጠረለት

ይህን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ስለዚህ እግዚአብሔር የአብርሃምን እምነት እንደ ጽድቅ ቆጠረለት” ወይም “ስለዚህ እግዚአብሔር የአብርሃምን ጽድቅ ቆጠረለት” ምክንያቱም አብርሃም በእርሱ አምኗልና።

Romans 4:23

አሁን ነበረ

“አሁን” የሚለው ጥቅም ላይ የዋለው አብርሃም በእምነት በእግዚአብሔር ፊት መጽደቁን አሁን አማኞች በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ በማመናቸው ከሚያገኙት ጽድቅ ጋር በማገናኘት ነው።

ለእርሱ ጥቅም ብቻ

“ለአብርሃም ብቻ”

ለእርሱ ተቆጠረለት

ይህን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “እግዚአብሔር ጽድቅን ለእርሱ ቆጠረለት” ወይም “እግዚአብሔር እንደ ጻድቅ አድርጎ ቆጠረው”

ለእኛ

“እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስንና በክርስቶስ የሚያምኑትን ሁሉ ነው።

እኛ ለምናምነው ደግሞ እንዲሁ እንደ ተቆጠረልን ተጽፎአል

ይህን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ለእኛም ጥቅም ነበር፣ ምክንያቱም የምናምን ከሆነ እግዚአብሔር እንደ ጻድቃን አድርጎ ይቆጥረናል”

እርሱን ጌታችን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣውን

“ከሙታን ያስነሣውን” እዚህ ላይ “እንደገና እንዲኖር ያደረገውን” የሚል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። “ጌታችን ኢየሱስን እንደገና ሕያው እንዲሆን ያደረገውን”

ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን

ይህን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ስለ እኛ መተላለፍ እግዚአብሔር ለጠላቶች አሳልፎ የሰጠውን ደግሞም እግዚአብሔር ወደ ሕይወት ያመጣው



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Chapter 5
Romans 5:1
አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ እግዚአብሔር አማኞችን ከእርሱ ጋር ሲያደርጋቸው የሚከሰቱ ብዙ የተለያዩ ነገሮችን መናገር ጀምሮአል።
Romans 5:3
ይህ ብቻ አይደለም
“ይህ” የሚለው ቃል በሮሜ 5፡1-2 የተገለጹትን ዐሳቦች ያመለክታል።
እኛ . . . የእኛ . . . እኛ
“እኛ” “የእኛ” እና “እኛ” የሚሉት ቃላት በሚጠቀሱበት ቦታ ሁሉ የሚያመለክቱት ሁሉንም አማኞች ሲሆን ሁሉንም ያቀፈ መሆን አለበት።
እርግጠኛ ተስፋ
እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑት የገባውን ቃል ኪዳን እንደሚፈጽም እርግጠኛ ነው።
ያ ተስፋ የሚያሳፍር አይደለም
ጳውሎስ ስለ “መተማመን” ሲናገር ሕይወት እንዳለው አካል አድርጎ በመጠቀም ነው። “የምንጠብቃቸውን ነገሮች እንደምንቀበል በጣም እርግጠኞች ነን”
የእግዚአብሔር ፍቅር በልቦቻችን ስለ ፈሰሰ
እዚህ ላይ “ልቦች” የአንድን ሰው ዐሳብ፣ ስሜት ወይም ውስጣዊ ማንነትን ያመለክታሉ። “የእግዚአብሔር ፍቅር በልቦቻችን ስለ ፈሰሰ” የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ፍቅሩን እንደሚያሳይ የሚገልጽ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። ይህ በአድራጊ ቅርፅ ሊገለጽ ይችላል። “እርሱ በጣም ስለ ወድዶናል” ወይም “እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወደን ስላሳየን ነው”
Romans 5:6
እኛ
“እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አማኞችን በሙሉ ሲሆን ሁሉንም የሚያቅፍ መሆን አለበት።
ለጻድቅ ሰው ሊሞት የሚፈቅድ ምንአልባት ይገኝ ይሆናል
“ለጻድቅ ሰውም እንኳ ለመሞት ፈቃደኛ የሆነን ሰው ማግኘት ከባድ ነው”
ማለትም አንድ ሰው ለመልካም ሰው ለመሞት ይደፍር ይሆናል
“ነገር ግን ለመልካም ሰው ለመሞት ፈቃደኛ የሚሆን ምንአልባት ይገኝ ይሆናል”
Romans 5:8
ያረጋግጣል
ይህንን ግስ አላፊ ጊዜን በመጠቀም “ገለጸ” ወይም “አሳየ” በማለት ልትተረጉመው ትችላለህ።
እኛ . . . እኛ
x
Romans 5:10
ነበርን
“እኛ” የሚለው ቃል በተጠቀሰበት ቦታ ሁሉ የሚያመለክተው አማኞችን በሙሉ ሲሆን ሁሉን ያቀፈ መሆን አለበት።
የእርሱ ልጅ . . . የእርሱ ሕይወት
“የእግዚአብሔር ልጅ . . . የእግዚአብሔር ልጅ ሕይወት”
በልጁ ሞት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ታረቅን
የእግዚአብሔር ልጅ ሞት በኢየሱስ ክርስቶስ ለምናምን ሁሉ የዘላለም ይቅርታን ሰጥቶናል፣ የእግዚአብሔርም ወዳጆች አድርጎናል፤ ይህን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “እግዚአብሔር ልጁ ለእኛ ሞቶአልና ከእርሱ ጋር ሰላማዊ ኅብረት እንዲኖረን ፈቀዶልናል”
ልጅ
ይህ የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው ርእስ ለኢየሱስ ክርስቶስ በጣም አስፈላጊ ርእስ ነው።
ከታረቅን በኋላ
ይህንን በአድራጊ ቅርጽ ልትተረጉመው ትችላለህ። “አሁን እግዚአብሔር እንደገና ወዳጆቹ አድርጎናል”
Romans 5:12
አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ እግዚአብሔር ሕጉን ለሙሴ ከመስጠቱ በፊት ሞት ለምን እንደ ተከሰተ ያብራራል።
በአንድ ሰው በኩል ኃጢአት ገባ . . . ሞትም በኃጢአት በኩል ገባ
ጳውሎስ ኃጢአት “በአንድ ሰው” በአዳም በኩል ወደ ዓለም መግባቱን እጅግ አደገኛ ድርጊት እንደ ሆነ ይገልጻል። ይህ ኃጢአት ሌላው አደገኛ ነገር ማለትም ለሞት በር ከፈተ፤ ይህም ሞት ወደ ዓለም መጣ።
ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበር
ይህ ማለት እግዚአብሔር ሕጉን ከመስጠቱ በፊት ሕዝቡ ኃጢአትን አድርጓል ማለት ነው። “እግዚአብሔር ሕጉን ለሙሴ ከመስጠቱ በፊት በዓለም የነበሩ ሰዎች ኃጢአትን አድርገዋል”
ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቆጠርም
ይህ ማለት እግዚአብሔር ሕጉን ከመስጠቱ በፊት ሕዝቡን በኃጢአት አልከሰሳቸውም ማለት ነው። “ነገር ግን እግዚአብሔር ሕጉን ከመስጠቱ በፊት በሕጉ ላይ የተደረገን ኃጢአት አልቆጠረም”
Romans 5:14
የሆነ ሆኖ ሞት
“ምንም እንኳን የተናገርኩት እውነት ቢሆንም ሞት፣” ወይም “ከአዳም ዘመን ጀምሮ እስከ ሙሴ ጊዜ ድረስ፣ የተጻፈ ሕግ አልነበረም ነገር ግን ሞት።” (ሮሜ 5፡13 ተመልከት)
ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ
ጳውሎስ ስለ ሞት ሲናገር ልክ እንደሚገዛ ንጉሥ አድርጎ ነው። “ሰዎች ከአዳም ዘመን ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ በኃጢአታቸው ምክንያት መሞታቸውን ቀጥለዋል”
እንደ አዳም አለመታዘዝ ኃጢአት ባልሠሩትም ላይ
“ከአዳም ኃጢአት የተለየ ኃጢአት የነበራቸውም መሞታቸውን ቀጥለዋል”
እርሱ ለሚመጣው ምሳሌ ነው
አዳም ቆይቶ ለተገለጠው የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ከእርሱ ጋር ብዙ የሚያመሳስላቸው ነገሮች ነበሩ።
በአንዱ መተላለፍ ብዙዎች ሞቱ
እዚህ ላይ “አንዱ” የሚለው የሚያመለክተው አዳምን ነው። “በአንዱ ሰው ኃጢአት ምክንያት ብዙዎች ሞቱ”
ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ እና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነ ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ
እዚህ ላይ “ጸጋ” የሚያመለክተው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለሁሉም ሰው ያገኘውን የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነው። “ምንም እንኳ የሚገባን ባይሆንም ለሁላችንም በሞተው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በቸርነቱ የዘላለምን ሕይወት ሰጠን”
Romans 5:16
ስጦታው እንደ አንዱ ሰው ኃጢአት ውጤት አይደለም
እዚህ ላይ “ስጦታው” የሚያመለክተው እግዚአብሔር የተመዘገበብንን ኃጢአት መዘረዙን ነው። “ስጦታው የአዳም ኃጢአት ውጤት አይደለም”
ፍርዱ የአንዱን መተላለፍ ይከተላል እንዲሁም ኩነኔን አምጥቷል፤ ስጦታው ግን . . . መጽደቅን
እዚህ ላይ ጳውሎስ “ስጦታው የአዳም ኃጢአት ውጤት አለመሆኑን” የሚያሳዩ ሁለት ምክንያቶችን ይሰጣል። “የበደለኝነት ፍርድ” የሚያመለክተው ሁላችንም ለኃጢአታችን የእግዚአብሔር ቅጣት የሚገባን መሆኑን ነው። “በአንድ በኩል እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ በአንድ ሰው ኃጢአት የተነሣ ሊቀጡ የሚገባቸው መሆኑን ያውጃል፣ በሌላ ወገን ግን”
ስጦታው ብዙ መተላለፎችን ተከትሏል እንዲሁም መጽደቅን አምጥቷል
ይህ የሚያመለክተው ምንም እንኳ የማይገባን ቢሆንም እግዚአብሔር በፊቱ ጻድቃን አደረገን። “የእግዚአብሔር ቸር ስጦታ እኛን በእርሱ ፊት ጻድቃን አድርጎናል”
ብዙ መተላለፎችን ተከትሏል
“ከብዙዎች ኃጢአት በኋላ”
የአንዱ መተላለፍ
ይህ የአዳምን ኃጢአት ያመለክታል።
ሞት ነገሠ
እዚህ ላይ ጳውሎስ ስለ “ሞት” ሲናገር እንደሚገዛ ንጉሥ አድርጎ ነው። የሞት “ግዛት” እያንዳንዱ ሰው እንዲሞት ያደርጋል። “ሁሉም ሰው ሞተ”)
Romans 5:18


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

በአንዱ መተላለፍ
“አዳም በሠራው ኃጢአት የተነሣ” ወይም “በአዳም ኃጢአት ምክንያት”
ኩነኔ በሁሉም ሰዎች ላይ መጣ
እዚህ ላይ “ኩነኔ” የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ቅጣትን ነው። “ሰዎች ሁሉ በኃጢአት ምክንያት የእግዚአብሔር ቅጣት ይገባቸዋል”
አንድ ድርጊት
የኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት
መጽደቅ እና ሕይወት ለሰዎች ሁሉ
እዚህ ላይ “መጽደቅ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሰዎችን በፊቱ ጻድቃን እንዲሆኑ ማድረግ መቻሉ ነው። “ሰዎች ሁሉ እንዲጸድቁ የእግዚአብሔር ስጦታ”
የአንድ ሰው አለመታዘዝ
የአዳም አለመታዘዝ
ብዙዎች ኃጢአተኞች ሆኑ
ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “ብዙ ሰዎች ኃጢአትን አደረጉ”
የአንዱ መታዘዝ
የኢየሱስ መታዘዝ
ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ
ይህንን በአድራጊ ቅርፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። “እግዚአብሔር ብዙ ሰዎችን በፊቱ ያጸድቃቸዋል”
Romans 5:20
ሕጉ ገባ
እዚህ ላይ ጳውሎስ ስለ ሕጉ ሲናገር ልክ እንደ ሰው አድርጎ ነው። “እግዚአብሔር ሕጉን ለሙሴ ሰጠው”
ኃጢአት በዛ
“ኃጢአት ጨመረ”
ጸጋ አብዝቶ በዛ
እዚህ ላይ “ጸጋ” የሚያመለክተው ለሰዎች የማይገባውን የእግዚአብሔርን በረከት ነው። “ምንም እንኳ የማይገባቸው ቢሆንም እግዚአብሔር በታላቅ ቸርነቱ ለእነርሱ የበለጠ ደግነትን አደረገ”
ኃጢአት በሞት እንደሚገዛ
እዚህ ላይ ጳውሎስ ስለ “ኃጢአት” ሲናገር እንደሚገዛ ንጉሥ አድርጎ ነው። “ኃጢአት ሞትን እንደሚያስከትል”
ጸጋው በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን በጽድቅ በኩል ለዘላለም ሕይወት ይገዛል
ጳውሎስ እዚህ ላይ ስለ “ጸጋ” ሲናገር እንደሚገዛ ንጉሥ አድርጎ ነው። “ጸጋ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ አማካይነት የዘላለም ሕይወት ለሰው ልጆች ሰጣቸው”
ጸጋ በጽድቅ ይገዛ ዘንድ
ጳውሎስ እዚህ ላይ ስለ “ጸጋ” ሲናገር እንደሚገዛ ንጉሥ አድርጎ ነው። “ጽድቅ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር ሰዎችን በፊቱ ማጽደቅ መቻሉን ነው። “ስለሆነም እግዚአብሔር የእርሱን ነጻ ስጦታ ሰጥቶ ሰዎችን በፊት ያጸድቃቸዋል”
ጌታችን
ጳውሎስ እራሱን፣ አንባቢዎቹን እና ሁሉንም አማኞችን ያካትታል።

---

Chapter 6
Romans 6:1
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቸርነት አስመልክቶ በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች ኃጢአት ለመሥራት ያለቸው ስሜት እንደሞቴ ቆጥረው ለእግዚአብሔር በመኖር አዲስ አኗኗር እንዲከተሉ ይነግራቸዋል።
እንግዲህ ስለዚህ ጉዳይ ምን እንላለን? የእግዚአብሔር ቸርነት እንዲበዛልን ኃጢአት መሥራት እንቀጥል?
ጳውሎስ ይኸንን ማሳመኛ ጥያቄ የሚጠይቀው የአንባቢዎቹን ትኩረት ላማግኘት ነው። በሌላ አባባል፣ “እንግዲህ ስለዚህ ጉዳይ ሁሉ ምን እንላለን? በእርግጠኝነት የምንለው እግዚአብሔር ጨምሮ ጨማምሮ ቸርነቱን እንዲያበዛልን ብለን ኃጢአት መሥራት መቀጠል የለብንም”
እኛ እንዲህ እንላለን
"እኛ" የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተው ጳውሎስን፣ አንባቢዎቹንና ሌሎች ሰዎችን ነው።
እኛ ለኃጢአት የሞትን ሰዎች እንዴት አሁንም ኃጢአት እየሠራን እንኖራለን?
እዚህ ላይ "ለኃጢአት የሞትን" ማለት ኢየሱስን የሚከተሉ ሰዎች አሁን ኃጢአትን ለመሥራት ያላቸው ስሜት እንደሞቴ ቆጥረው በኃጢአት የማይሸነፉ ናቸው። ጳውሎስ ይኸንን ማሳመኛ ጥያቄ የተጠቀመው ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት ነው፤ በሌላ አባባል፣ "እኛ አሁን እንደሞቱ ሰዎች ነን ኃጢአት አያሸንፈንም! ስለዚህ በእርግጥ ኃጢአት መሥራትን መቀጠል የለብንም"
ብዙዎች በክርስቶስ ኢየሱስ እንደ ተጠመቁ ሁሉ በሞቱም እንደዚሁ እንደሚከፈሉ አታውቁምን?
ጳውሎስ ይኸንን ጥያቄ የተጠቀመው አጽንኦት ለመስጠት ነው። በሌላ አባባል፣ "አስታውሱ፥ አንድ ሰው እኛ ከክርስቶስ ጋር ግንኙነት እንዳለን ለማሳየት ሲያጠምቀን ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ እንደሞትን ጭምር ለማሳየት ነው።
Romans 6:4
እኛ በጥምቀት ከክርስቶር ጋር ተቀብረናል፤ ከዚያም በሞቱ ተካፋዮች ሆነናል
x
Romans 6:6
አሮጌው ሰውነታችን ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሏል
"አሮጌ ሰውነት" የሚለው ተለዋጭ ዘይቤ ሰው በክርስቶስ ከማመኑ በፊት የነበረውን ባሕርይ ያመለክታል። ጳውሎስ አሮጌውን ኃጢአተኛ ሰውነታችን በክርስቶስ ባመንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ እንደሚሞት ይናገራል። በሌላ አባባል፣ “ኃጢአተኛው ሰውነታችን ከኢየሱስ ጋር በመስቀል ላይ ሞቷል”
አሮጌው ሰውነት
አሮጌው ሰውነት ማለት በአንድ ወቅት የነበረ አሁን ግን የሌለ ሰውነት ማለት ነው።
ኃጢአተኛው ሰውነት
ኃጢአተኛው ሰውነት የሚለው ተምሳሌታዊ ቃል የሚያመለክተው በጥቅሉ ያለውን ኃጢአተኛ ሰውነት ነው። በሌላ አባባል፣ “ኃጢአተኛው ባሕርያችን”
የሚጠፋ ሊሆን ይችላል
በሌላ አተረጓጎም፣ “ለሞት የሚችል”
ከእንግዲህ በኋላ ለኃጢአት ባሪያ መሆን የለብንም
በሌላ አተረጓጎም፣ “ኃጢአት ከእንግዲህ ወዲህ ሊገዛን አይገባም” ወይም “ከእንግዲህ ወዲህ ለኃጢአት ልንገዛ አይገባም”
ከእንግዲህ በኋላ ለኃጢአት ባሪያ መሆን የለብንም
ለኃጢአት ባሪያ መሆን የሚለው ተለዋጭ ዘይቤአዊ አነጋገር አንድ ሰው ኃጢአትን ለመሥራት ያለው ፍላጎት ራሱን መከልከል እስከማይችል ድረስ ጠንካራ ሲሆን ማለት ነው። ኃጢአት ሰውየውን የሚቆጣጠርበት ሁኔታ ውስጥ መግባት ነው። በሌላ አባባል፣ “ከእንግዲህ በኋላ በኃጢአት ቁጥጥር ሥር ልንሆን አይገባም”
Romans 6:8
ከክርስቶስ ጋር ሞተናል
"ሞተናል" የሚለው ቃል ሰው በክርስቶስ ካመነ በኋላ በኃጢአት ቁጥጥር ሥር አለመሆኑን ያመለክታል።
ክርስቶስ ከሞት እንዲነሣ እንደተደረገ እናውቃለን
እዚህ ላይ ‘ከሞት እንዲነሣ እንደተደረገ’ የሚለው አባባል የሞተውን ሰው እንደገና ሕይወት እንዲኖረው ማድረግን ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ "ክርስቶስ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር እሱን ከሞት እንዳስነሣው እናውቃለን"
ከሙታን
ከሞቱት ሰዎች ሁሉ መካከል ማለት ነው። ይህ አባባል የሚገልጸው የሞቱ ሰዎች የሚቆዩበት ቦታ ያሉትን ሟቾች ሁሉ ነው። ከእነርሱ መካከል መነሣት እንደገና ወደ ሕይወት መመለስ ነው።
ከእንግዲህ ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውም
እዚህ ላይ "ሞት" ሥልጣን እንዳለው ንጉሥ ወይም ገዢ በሰዎች ላይ ኃይል እንዳለው ይገልጻል። በሌላ አባባል፣ “እንደገና ተመልሶ አይሞትም”
Romans 6:10
ኃጢአት ን በሚመለከት የሞተውን ሞት ስናስብ እሱ ለሁሉም አንድ ጊዜ ሞቶአል
"አንድ ጊዜ" የሚለው ሐረግ አንድን ጉዳይ በአንድ ጊዜ ሙሉ በሙሉ መጨረስ ማለት ነው። በትርጉማችሁ ውስጥ ይኸንን ሐሳብ መግለጥ ትችላላችሁ። በሌላ አተረጓጎም፣ "እሱ በሞተ ጊዜ የሞትን ኃይል ሙሉ በሙሉ ሰብሮታል"
በተመሳሳይ መንገድ እናንተም ማሰብ አለባችሁ
“"ስለዚህ እናንተም አስቡ"
ስለ ራሳችሁ እንዲህ አስቡ
"እናንተም ስለ ራሳችሁ እንደዚሁ አስቡ" ወይም "ራሳችሁን እንደዚሁ ተመልከቱ"


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ለኃጢአት የሞታችሁ ናችው
አንድ ሰው በድን የሆነውን አካል የሆነ ነገር እንዲሠራ ማስገደድ እንደማይችል ሁሉ ኃጢአት ክርስቲያን አማኞችን አስገድዶ እግዚአብሔርን ከማክበር ሊያግዳቸው አይችልም። በሌላ አባባል፣ “የኃጢአት ኃይል የማይሰማችሁ በሚመስል መልኩ የሞታችሁ”
ለኃጢአት የሞትን ለእግዚአብሔር ግን ሕያዋን
"የኃጢአት ኃይል እንዳይሰማን የሞትን እግዚአብሔርን ለማክበር ግን የምንኖር"
በክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ሕያዋን ሆነን
"ክርስቶስ ኢየሱስ በሚሰጣችሁ ኃይል እግዚአብሔርን ለማክበር የምንኖር"
Romans 6:12
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ጳውሎስ ሊያስታውሰን የፈለገው ሕግ ሳይሆን መልካምነቱ እንደሚገዛን ነው። እኛ የኃጢአት ተገዢዎች አይደለንም ግን ለእግዚአብሔር ተገዢዎች ነን።
ኃጢአት የሚሞተውን አካላችውን እንዲገዛ አትፍቀዱለት
ጳውሎስ ኃጢአት ለሚሠሩ ሰዎች ኃጢአት እንደ ንጉሥ ወይም እንደ ገዢ ሆኖ እንደሚቆጣጠራቸው ይናገራል። በሌላ አባባል፣ “ኃጢአተኛውን ምኞታችሁን እንዲቆጣጠራችሁ አትፍቀዱለት”
የሚሞተውን አካላችውን
ይህ ሐረግ የሚያመለክተው የሚሞተውን የአንድ ሰው ውጫዊ አካሉን ነው።
ምኞቱን ለመፈጸም ለትታዘዙለት
ጳውሎስ ክፉ ምኞት ያለውን ሰው ኃጢአተኛው ለእርሱ ታዝዞ ክፉ ነገር እንዲያደርግ እንደሚፈልግ እንደ ገዢው "ኃጢአት " ይገልጸዋል።
የአካል ክፍሎቻችሁ ክፉ ሥራዎች የሚሠሩባቸው መሣሪያዎች ሆነው ኃጢአት እንዲሠሩ አታድርጓቸው
እዚህ ክፍል ላይ ኃጢአተኛው የአካል ክፍሎቹን ለገዢው ወይም በእርሱ ላይ ለነገሠው እንደሚሰጥ አድርጎ ያሳያል። የአንድ ሰው የአካል ክፍሎች ለመላው ሰውነቱ ይሠራሉ። በሌላ አባባል፣ "እግዚአብሔርን የማያስከብር ነገር መሥራት እንዲችሉ ራሳችውን ለኃጢአት አሳልፋችሁ አትስጡ”
ነገር ግን ለክፉ ሥራ የሞቱ ሕያዋን አድርጋችው ራሳችውን ለእግዚአብሔር አቅርቡ
እዚህ ላይ "ሕያዋን" የሚለው የክርስቲያኖችን አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት ነው። "ነገር ግን ራሳችውን ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርጉ ምክንያቱም እሱ አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት ሰጥቷችኋል" ወይም "ነገር ግን በፊት ሞተው አሁን ግን ሕያዋን እንደሆኑ ሰዎች ራሳችውን ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርጉ”
ለእግዚአብሔር ክብር ለሚሠራው ሥራ መሣሪያ እንዲሆኑ የአካል ክፍሎቻችሁን ለእግዚአብሔር ስጡ።
እዚህ ላይ "የአካል ክፍሎቻችሁ" የሚለው ለመላው ሰውነት የሚሠራ መሆኑን ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ "እግዚአብሔር እርሱን ለሚያስደስት ሥራ እንዲጠቀሚባችው ፍቀዱለት"
ኃጢአት እንዲገዛችው አትፍቀዱለት
ጳውሎስ "ኃጢአት" ሰዎችን የሚገዛ ንጉሥ ተምሳሌት አድርጎ ይገልፀዋል። በሌላ አባባል፣ "ክፉ ምኞታችሁ የሚታደርጉትን ነገር እንዲቆጣጠር አትፍቀዱ" ወይም "ልታደርጉ የሚትፈልጉትን ክፉ ነገር ለማድረግ ራሳችውን አትስጡ"
ምክንያቱም እናንተ ከሕግ በታች የሚትኖሩ አይደላችውም
"ከሕግ በታች መኖር" ማለት በሕግ ውስንነት እና ጉድለት ውስጥ መመላለስ ማለት ነው። እናንተ ሲትተረጉሙ ሙሉ ትርጉም ለመስጠት ይህንን ግልጽ ማድረግ ትችላላችሁ። በሌላ አባባል፣ "እናንተ ከዚህ በኋላ ኃጢአትን ከመሥራት ሊገታችው በማይችለው በሙሴ ሕግ ተወስናችው የሚትኖሩ አይደላችውም"
ነገር ግን በእግዚአብሔር ምህረት ሥር
"በእግዚአብሔር ምሕረት ሥር" ማለት የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ እናንተ ኃጢአትን ከመሥራት ራሳችሁን የሚትጠብቁበትን ኃይል ይሰጣችኋል ማለት ነው። እናንተ ስትተረጉሙ ሙሉ ትርጉም ለመስጠት ይህንን ግልጽ ማድረግ ትችላላችሁ። በሌላ አባባል፣"ኃጢአት መሥራትን የሚታቆሙበት ኃይል በሚሰጣችው በእግዚአብሔር ምሕረት ተይዛችዋል"
Romans 6:15
ታዲያ ስለዚህ ጉዳይ ምን እናድርግ? ከሕግ በታች የምንኖር ሳንሆን በእግዚአብሔር ቸርነትና ምህረት የምንኖር ስለሆንን ታዲያ ኃጢአት እንሥራ? ይህ በፍፁም አይሁን
ጳውሎስ በእግዚአብሔር ቸርነትና ምህረት መኖርን እንደ ምክንያት ተጠቅመን ኃጢአት መሥራት አይገባም የሚለውን ሐሳብ አጽንኦት ለመስጠት በጥያቄ መልክ ተናገረ። በሌላ አባባል፣ "ይሁን እንጂ በሙሴ ሕግ ተይዘን ከመኖር ይልቅ በእግዚአብሔር ቸርነትና ምህረት ተይዘን የምንኖር ነን ሲባል በእርግጥ ኃጢአት ለመሥራት ተፈቅዶልናል ማለት አይደለም"
ይህ በፍፁም አይሁን
"ይህ እንዲሆን በፍፁም አንፈልግም" ወይም "ያን እንዳላደርግ እግዚአብሔር ይርዳኝ" ይህ አገላለጽ ነገሩ እንደዚህ እንዳይደረግ ያለውን ከፍተኛ ፍላጎት ያመለክታል። እዚህ ላይ በእናንተ ቋንቋ ተመሳሳይ አገላለጽ ሊኖር ስለሚችል መጠቀም ትችላላችሁ። በሮሜ 3:31 ላይ እንዴት እንደተረጎማችሁ ተመልከቱ።
አገልጋዮቹ አድርጋችሁ ራሳችሁን የሰጣችሁት እርሱ የሚትታዘዙለት ራሱ መሆኑን አታውቁም ወይ? ልትታዘዙት የሚገባ አይደለም?
ጳውሎስ ኃጢአት እየሠሩ መኖርን ለመቀጠል በእግዚአብሔር ቸርነትና ምህረት መኖር የሚለው ምክንያት ሊሆን ይችላል ብሎ የሚያስብ ማንኛውንም ሰው ለመገሰጽ በጥያቄ መልክ ተናገረ። በሌላ አባባል፣ "ለትታዘዙት ለመረጣችሁት ጌታ ባርያ መሆናችሁን ማወቅ አለባችሁ"
ለኃጢአት ባሪያ ከሆናችሁ . . . ወይም ለታዛዥነት ሕይወት የሚትገዙ ከሆነ
x
Romans 6:17
ግን እግዚአብሔር ይመስገን!
"ግን እኔ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ!"
እናንተ የኃጢአት ባሪያ ነበራችሁ
ለኃጢአት ባሪያ መሆን የሚለው ተለዋጭ ዘይቤአዊ አነጋገር አንድ ሰው ኃጢአትን ለመሥራት ያለው ፍላጎት ራሱን መከልከል እስከማይችል ደረስ ጠንካራ ሲሆን ማለት ነው። ኃጢአት ሰውዬውን የሚቆጣጠርበት ሁኔታ ውስጥ መግባት ነው። በሌላ አባባል፣ “እናንተ ለኃጢአት እንደ ባርያ ነበራችሁ” ወይም “እናንተ በኃጢአት ቁጥጥር ሥር ነበራችሁ”
ነገር ግን እናንተ ከልባችሁ ታዛዦች ሆናቿል።
እዚህ ላይ "ልብ" የሚለው ቃል እዚህ ላይ የሚያመለክተው የምንሠራውን ሥራ በቅንነት ወይም በታማኝነት መሥራትን ነው። በሌላ አባባል፣ "ነገር ግን እናንተ በእውነት ታዛዦች ሆናችኋል”
የተሰጣችሁን የአኗኗር አስተምሮ
"አኗኗር" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እንደ እግዚአብሔር ሐሳብ ወደ መኖር የሚያመራ የኑሮ አካሄድን ነው። አማኝ ክርስቲያኖች አሮጌውን የኑሮ አካሄድ ቀይረው በክርስትና መሪዎች አስተምሮ መሠረት ከአዲሱ የኑሮ አካሄድ ጋር የሚሄድ ኑሮ ይኖራሉ። በሌላ አባባል፣ "የክርስትና መሪዎች ያስተማሯችሁን ትምህርት"
ከኃጢአት ነፃ ወጥታችው ነበር
በሌላ አባባል፣ "ክርስቶስ ከኃጢአት ኃይል ነፃ አውጥቶአችሁ ነበር"
ከኃጢአት ነፃ ወጥታችው ነበር
እዚህ ላይ “ከኃጢአት ነፃ መውጣት” የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር አንድ ሰው ኃጢአትን ለመሥራት ያለውን ጠንካራ ፍላጎት መግታትና ራሱን መከልከል እስከመቻል መድረስን የሚያመለክት ነው። በሌላ አባባል፣ “ኃጢአትን ለመሥራት ያለችው ጠንካራ ፍላጎት ተወግዶአል” ወይም “በኃጢአት ቁጥጥር ሥር ከመሆን ነፃ ወጥታችኋል”
የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚታገለግሉ ባሮች
የእግዚአብሔርን ሐሳብ የማገልገል ባርነት የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ሐሳብ ለመፈጸም ያለውን ጠንካራ ፍላጎት የሚያመለክት ነው። የእግዚአብሔርን ሐሳብ ለመፈጸም ያለው ፍላጎት ሰውዬውን የሚቆጣጠርበት ሁኔታ እንደማለት ነው። በሌላ አባባል፣ “የእግዚአብሔርን ሐሳብ ለመፈጸም ላላችው ፍላጎት እንደ ባርያ ሆናችኋል” ወይም “አሁን እናንተ የእግዚአብሔርን ሐሳብ በመፈጸም ፍላጎት ቁጥጥር ሥር ናችሁ”
የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚታገለግሉ ባሮች
በሌላ አባባል፣ “ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚታገለግሉ ባሮች አድርጓችኋል” ወይም“ “አሁን እናንተ የእግዚአብሔርን ሐሳብ በመፈጸም ፍላጎት ቁጥጥር ሥር እንዲትሆኑ ክርስቶስ ለውጦአችኋል”
Romans 6:19
እኔ እንደ ሰው እናገራለሁ
ጳውሎስ ለምን ስለ ባርያ እና ነፃነት ለምን እንደሚናገር አንባቢዎቹን ሳያስገርም እንደማይቀር ገምቶ ይሆናል። እዚህ ላይ እርሱ የሚናገረው ለአንባቢዎቹ እንዲገባቸው እነዚህን ሐሳቦች ከዕለት ዕለት የኑሮአቸው ተሞክሮ ወስዶ እየተጠቀመባቸው መሆኑን ይናገራል። ይኸውም ሰዎች ወይ በኃጢአት ቁጥጥር ሥር ወይ የእግዚአብሔርን ሐሳብ በመፈጸም ፍላጎት ቁጥጥር ሥር እንደሚሆኑ

ነው። በሌላ አባባል፣ “እኔ ስለዚህ ነገር በሰውኛ አነጋገር እየተናገርኩ ነው” ወይም “እኔ ከዕለት ዕለት የኑሮአችሁ ተሞክሮ ምሳሌ እየወሰድኩ ነው”
በሥጋ ለባሽነታችሁ ምክንያት ደካማ በመሆናችሁ
ጳውሎስ ብዙ ጊዜ "ሥጋ (ለባሽ)" የሚለውን ቃል የሚጠቀመው የ "መንፈስ" ተቃራኒ ከመሆኑ አንፃር ነው። በሌላ አባባል፣ “ስለ መንፈሳዊ ነገሮች ሙሉ በሙሉ ስለማትረዱ”
የአካል ክፍሎቻችሁን ለእርኩሰትና ለክፉ ሥራ ተገዢ አድርጋችሁ አቀረባችሁ
እዚህ ላይ "የአካል ክፍሎቻችሁ" የሚለው መላ ሰውነትን ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ "ራሳችሁን ክፉ ለሆነው እና እግዚአብሔርን ለማያስደስት ነገር አሳልፋችሁ ሰጣችሁ"
የእግዚአብሔርን ሐሳብ ለመፈጸም እና ለእርሱ ለመቀደስ የአካል ክፍሎቻችሁን ለዚህ ተገዢ አድርጋችሁ አቅርቡ
እዚህም ላይ "የአካል ክፍሎቻችሁ" የሚለው መላ ሰውነትን ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ "እግዚአብሔር ለራሱ የተለያችሁ እንዲያደርጋችሁ እና እርሱን የሚታገለግሉበትን ኃይል እንዲሰጣችሁ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር ለመሥራት ራሳችሁን ለዚህ ሥራ ተገዢ አድርጋችሁ አቅርቡ"
የእግዚአብሔርን ሐሳብ ከመፈጸም ነፃ ወጥታችሁ ነበር
እዚህ ላይ “የእግዚአብሔርን ሐሳብ ከመፈጸም ነፃ መውጣት” የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ሐሳብ መፈጸም የማይጠበቅበት መሆኑን የሚያመለክት ነው።ሰዎቹ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር መሥራት እንደማይጠበቅባቸው አድርገው በማሰብ ይኖሩ ነበር። በሌላ አባባል፣ “የእግዚአብሔርን ሐሳብ መፈጸም እንደማይጠበቅበት ተደርጎ ይወሰድ ነበር” ወይም “በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር መሥራት የማይጠበቅባችሁ የሚያስመስል ባሕርይ አሳይታችኋል”
አሁን ለሚታፍሩባቸው ነገሮች በዚያን ጊዜም ቢሆን ምን ፍሬ አገኛችሁበት?

“ፍሬ” የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር “ውጤት” ወይም “ጥቅም” ለማለት ነው። ጳውሎስ እዚህ ላይ በጥያቄ መልክ ያስቀመጠው ኃጢአትን መሥራት ለምንም እንደማይበጅ አጥብቆ ለማሳሰብ ነው። በሌላ አባባል፣ “አሁን እንዲታፍሩ ከሚያደርጓችሁ ነገሮች ምንም መልካም ነገር አላገኛችሁም” ወይም "አሁን እንዲታፍሩ የሚያደርጓችሁ ነገሮችን በመሥራታችሁ ምንም አልተጠቀማችሁም"
Romans 6:22
ነገር ግን አሁን ከኃጢአት ነፃ ወጥታችሁ ለእግዚአብሔር ባሮች ሆናችኋል።
በሌላ አባባል፣ “ነገር ግን አሁን ከኃጢአት ነፃ ወጥታችሁ የእግዚአብሔር ባሪያ ሆናችኋል” ወይም “ነገር ግን አሁን እግዚአብሔር ከኃጢአት ነፃ አውጥቶአችሁ የራሱ ባርያ አድርጓችኋል”
ነገር ግን አሁን ከኃጢአት ነፃ ወጥታችኋል
“ከኃጢአት ነፃ መውጣት” የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር ኃጢአት መሥራት አለመቻልን የሚያመለክት ነው። በሌላ አባባል፣ “ነገር ግን አሁን እግዚአብሔር ኃጢአት ከመሥራት መቆጠብ እንዲትችሉ አደረጋችሁ”
ለእግዚአብሔር ባሮች ሆናችኋል
ለእግዚአብሔር “ባርያ መሆን” የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር እግዚአብሔርን ማገልገልና ለእርሱ መታዘዝን የሚያመለክት ነው። በሌላ አባባል፣ “እግዚአብሔር እርሱን ማገልገል እንዲትችሉ አደረጋችሁ”
ፍሬአችሁ መቀደስ ነው
እዚህ ላይ “ፍሬ” የሚለው ዘይቤ “ውጤት” ወይም “ጥቅም” ለማለት ነው። በሌላ አባባል፣ “ጥቅሙ መቀደሳችሁ ነው” ወይም “ጥቅሙ እናንተ የተቀደሰ አኗኗር መምራታችሁ ነው”
ውጤቱ የዘላለም ሕይወት ነው
“የዚህ ሁሉ ውጤት እናንተ ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር ትኖራላችሁ”

---

Chapter 7
Romans 7:1
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ጳውሎስ ከሕግ በታች መኖር የሚፈልጉትን ሰዎች ሕጉ እንዴት እንደሚቆጣጠር ይገልጻል።
ወንድሞች ሆይ. . . ከሕግ በታች የሚኖረውን ሰው ሕጉ የሚቆጣጠረው ያ ሰው በሕይወት እስካለ ድረስ መሆኑን አታውቁም ወይ?
ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት ነው። በሌላ አባባል፣ "ስለዚህ ሰዎች ለሕግ መታዘዝ ያለባቸው በሕይወት እስካሉ ብቻ መሆኑን በእርግጠኝነት ታውቃላችሁ"
ወንድሞች
ወንድሞች ማለት ክርስቲያን ወገኖች፣ ወንዶችንም ሴቶችንም አጠቃልሎ ማለት ነው።
ሕጉ አንድን ሰው የሚቆጣጠረው ያ ሰው በሕይወት እስካለ ድረስ ነው
ጳውሎስ የዚህን ምሳሌ በ7፡2-3 ላይ አስቀምጦአል።
Romans 7:2
ያገባች ሴት በሕግ ከባሏ ጋር ተጣምራለች
እዚህ ላይ “በሕግ ከባሏ ጋር ተጣምራለች” የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር አንዲት ሴት ከባሏ ጋር በጋብቻ ሕግ መሠረት አንድነት መፍጠሯን የሚያመለክት ነው። በሌላ አባባል፣ በሕጉ መሠረት ያጋበች ሴት ከባሏ ጋር አንድነት ፈጥራለች”
ያገባች ሴት
ይህ ማንኛውንም ያገባች ሴት ለማመልከት ነው።
እርሷ አመንዝራ ትባላለች።
በሌላ አባባል፣ "እግዚአብሔር እሷን እንደ አመንዝራ ይወስዳታል" ወይም "ሰዎች እሷን አመዝራ ይሏታል"
እርሷ ከሕጉ ነፃ ናት
እዚህ ላይ ከሕግ ነፃ መሆን ማለት ለሕጉ የግዴታ መታዘዝ አይጠበቅም ማለት ነው። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ያገባች ሴት ሌላ ወንድ ማግባት አትችልም ለሚለው ሕግ የግዴታ መታዘዝ አይጠበቅባትም። በሌላ አባባል፣ “እርሷ የግዴታ ለሕጉ መታዘዝ አይጠበቅባትም”
Romans 7:4
ስለዚህ ወንድሞች
ይህ ወደ ሮሜ 7፡1 ለማመልከት ነው።

ወንድሞች
ይህ ማለት ክርስቲያን ወገኖች ማለት ነው፤ወንዶችንም ሴቶችንም ያጠቃልላል።
በክርስቶስ አካል አማካይነት በሞታችሁ ጊዜ ለሕግም ደግሞ የሞታችሁ ሆናችኋል
በሌላ አተረጓጎም፣ "በክርስቶስ በኩል በመስቀል ላይ በሞታችሁ ጊዜ ለሕግም ደግሞ ሞታችኋል"
ከሙታን እንዲነሣ ለተደረገው ለእርሱ
“ከሙታን እንዲነሣ ተደረገ” የሚለው አባባል እንደገና በሕይወት ወደ መኖር መመለስን ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ “እግዚአብሔር እንደገና በሕይወት ወደ መኖር ለመለሰው ለእርሱ” ወይም “እግዚአብሔር ከሙታን መካከል ላስነሣው ለእርሱ”
ለእግዚአብሔር ፍሬ ልናፈራ እንችላለን
እዚህ ላይ "ፍሬ" የሚለው ተለዋጭ ዘይቤአዊ አነጋገር እግዚአብሔርን የሚያስደስቱ ተግባራት መፈጸምን ያመለክታል። "እግዚአብሔርን የሚያስደስት ተግባር ልንፈጽም እንችላለን"
ሞትን የሚያስከትል ፍሬ ልናፈራ ሆነ
እዚህ ላይ "ፍሬ" የሚለው ተለዋጭ ዘይቤአዊ አነጋገር “የአንድ ሰው የድርጊቱ ውጤት” ወይም “በአንድ ሰው ድርጊት ምክንያት የመጣ” ማለት ነው። በሌላ አባባል፣ “ውጤቱ መንፈሳዊ ሞት ሆነ” ወይም “መንፈሳዊ ሞትን አመጣብን”
Romans 7:6
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
እግዚአብሔር ቅዱስ የሚያደርገን በሕግ እንዳልሆነ ጳውሎስ ያስታውሰናል።
እኛ ከሕግ እሥራት ተላቅቀናል።
በሌላ አባባል፣ "እግዚአብሔር ከሕግ እሥራት አላቅቆናል"
እኛ
ይህ ተውላጠ ስም ጳውሎስንና አማኝ ክርስቲያኖችን ያመለክታል።
ለዚያ ለተያዝንበት
ይህ ሕግን ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ "ይዞን ላለው ሕግ"
ፊደል
ይህ የሙሴ ሕግን ያመለክታል።በሌላ አባብል፣ "የሙሴ ሕግ"
Romans 7:7
እንግዲ ምን እንላለን?
ጳውሎስ አዲስ ርዕስ እያስተዋወቀ ነው።

ይህ ፈጽሞ አይሁን።
“ታዲያ ይህማ እውነት አይደለም" ይህ አገላለጽ ለቀደመው ማሳመኛ ጥያቄ በጣም ጠንከር ያለ አሉታዊ መልስ ይሰጣል። በራሳችሁ ቋንቋም በዚህ ቦታ አስገብታችሁ የሚትጠቀሙት ተመሳሳይ አገላለጽ ሊኖራችሁ ይችላል። በሮሜ 9:14 ላይ ምን ብላችሁ እንደተረጎማችሁ ተመልከቱ።
ሕግ ባይኖር ኖሮ ኃጢአት ምን እንደሆነ ባላወቅኩ ነበር። በሕግ አማካይነት ለይቼ ባላውቀው ኖሮ. . . ነገር ግን ኃጢአት አጋጣሚውን ተጠቅሞ. . . ሥጋዊ ምኞትን ቀሰቀሰ።
ጳውሎስ ኃጢአትን ሊንቀሳቀስና ሊሠራ ከሚችል ሰው ጋር ያነፃፅራል።
ኃጢአት
"ኃጢአት ለመሥራት ያለኝ ምኞት"
ሥጋዊ ምኞት
ይህ አባባል የሰው የሆነውን ነገር ለመውሰድ መፈለግንና ክፉ የሆነ የወስብ ምኞትን ያጠቃልላል።
ሕግ ከሌለ ኃጢአት የሞተ ነው።
"ሕግ ባይኖር ኖሮ ሕግን መተላለፍ አይኖርም ነበር፤ ይህ ማለት ደግሞ ኃጢአት የሚባል አይኖርም ነበር ማለት ነው።
Romans 7:9
ኃጢአት እንደገና አንሠራራ
x
Romans 7:11
ኃጢአት የተሰጠውን ትዕዛዝ እንደ ዕድል በመጠቀም አታለለኝ። በትዕዛዙም ላይ ተመሥርቶ ሞት አመጣብኝ።
በሮሜ 7:7-8 ላይ እንደተጠቀሰው ጳውሎስ ኃጢአት 3 ነገሮች ማድረግ እንደሚችል ይገልጻል፣ ዕድልን መጠቀም፣ ማታለል እና መግደል። "ኃጢአትን መሥራት ስለፈለኩ በአንድ ጊዜ ኃጢአትንም እየሠራሁ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መታዘዝ እችላለሁ ብዬ እያሰብኩኝ ራሴን አታለልኩ ነገር ግን ለእርሱ ባለመታዘዜ ምክንያት እግዚአብሔር እኔን ከራሱ በመለየት ቀጣኝ"
ኃጢአት
ኃጢአት ለመሥራት ያለኝ ምኞት
ትዕዛዙን እንደ ዕድል በመጠቀም
ጳውሎስ ኃጢአትን የሆነ ነገር ሊያደርግ ከሚችል አካል ጋር ያነፃፅራል። በሮሜ 7:8 ላይ የሰጣችሁትን ትርጉም ተመልከቱ።
ሞት አመጣብኝ
ጳውሎስ ኃጢአትን የሆነ ነገር ሊያደርግ ከሚችል አካል ጋር ያነፃፅራል። ጳውሎስ በኃጢአተኞች ላይ የሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ አካላዊ ሞት እንደሚያስከትል አድርጎ ይናገራል። በሌላ አባባል፣ "እኔን ከእግዚአብሔር ለየኝ"
ቅዱስ
በሥነ ምግባር ፍጹም የሆነ፣ ኃጢአት የሌለበት
Romans 7:13
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ጳውሎስ በውስጣዊው ሰውነቱ ባለው ኃጢአት እና የእግዚአብሔርን ሕግ በሚያውቀው አእምሮው መካከል (በኃጢአት እና በመልካም ሐሳቡ መካከል) በውስጡ ስለሚካሄደው ፍልሚያ ይናገራል።
እንግዲህ
ጳውሎስ አዲስ ርዕስ እያስተዋወቀ ነው።
መልካም የሆነው ነገር ሞት አመጣብኝ እንዴ?
ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት ነው።
መልካም የሆነው ነገር
ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሕግ ነው።
ሞት አመጣብኝ።
“እንዲሞት አደረገኝ”
ይህ ፈጽሞ አይሁን
ይህ አገላለጽ ለቀደመው ማሳመኛ ጥያቄ በጣም ጠንከር ያለ አሉታዊ መልስ ይሰጣል። በራሳችሁ ቋንቋም በዚህ ቦታ አስገብታችሁ የሚትጠቀሙት ተመሳሳይ አገላለጽ ሊኖራችሁ ይችላል።በሌላ አባባል፣ “ታዲያ ይህማ እውነት አይደለም"
ኃጢአት. . .ሞትን በሕይወቴ አመጣ
ጳውሎስ ኃጢአትን በራሱ የሆነ ነገር ሊያደርግ እንደሚችል አካል አድርጎ ያየዋል።
ሞትን በሕይወቴ አመጣ
"ከእግዚአብሔር ለየኝ"
በእግዚአብሔር ትዕዛዝ አማካይነት
"ምክንያቱም እኔ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ስላልፈጸምኩ"
Romans 7:15
አያያዥ ዐረፍተ ነገር፣
ጳውሎስ በሥጋዊ ምኞቱ እና በእግዚአብሔር ሕግ መካከል (በክፉ እና በመልካም መካከል) በውስጡ ስለሚካሄድ ፍልሚያ ይናገራል።
እኔ ስላማደርገው ነገር በግልጽ አላውቅም
"እኔ አንዳንድ የማደርጋቸውን ነገሮች ለምን እንደማደርጋቸው እርግጠኛ አይደለውም”
እኔ ለማደርገው
ምክንያቱም እኔ የማደርገው
እኔ ማድረግ የምፈልገውን አላደርግም
“አላደርግም” የሚለው ቃል ተጋንኖ የተነገረው ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት ሲባል ነው። ጳውሎስ ማድረግ የሚፈልገውን የሚያደርገው በፈለገው ጊዜ ሁሉ አይደለም ወይም ደግሞ አንድ አንድ ጊዜ ማድረግ የማይፈገውን ነገር ያደርጋል። በሌላ አባባል፣ "እኔ ማድረግ የሚፈለገውን የማደርገው ሁል ጊዜ አይደለም"
ማድረግ የምጠላውን ነገር አደርጋለሁ
“አደርጋለሁ” የሚለው ቃል በውስጡ የያዘው ሐሳብ ጳውሎስ ሁል ጊዜ ማድረግ የሚጠላውን ነገር ማድረጉን ነው። ይህም ተጋንኖ የተነገረው ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት ሲባል ነው። ጳውሎስ ማድረግ የማይፈልገውን ነገር ደጋግሞ ያደርጋል። በሌላ አባባል፣ "አንዳንድ ጊዜ የማደርጋቸው ነገሮች መልካም አለመሆናቸውን የማውቃቸው ነገሮች ናቸው"
ነገር ግን እንዲህ ባደርግ
"ይሁን እንጂ እንዲህ የማደርግ ከሆነ"
እኔ በሕጉ እስማማለሁ።
"የእግዚአብሔር ሕግ መልካም መሆኑን አውቃለሁ"
Romans 7:17
በእኔ ያለው ኃጢአትን የመሥራት ምኞት
ጳውሎስ ኃጢአትን ራሱ ላይ ተጽዕኖ ማምጣት የሚችል ሕይወት ያለው ነገር አድርጎ ይገልጸዋል።
ሥጋዊ ምኞቴ
እዚህ ላይ "ሥጋ" ኃጢአተኛውን የሰው ተፈጥሮ የሚገልጽ ቃል ነው። በሌላ አባባል፣ “ኃጢአተኛው ተፈጥሮዬ”
Romans 7:19
መልካሙ
"መልካሙ ሥራ" ወይም "መልካሙ ድርጊት"
ክፉው
"ክፉው ሥራ" ወይም "ክፉው ድርጊት"
ይልቅስ በእኔ ውስጥ ያለው ኃጢአትን የመሥራት ምኞት
ጳውሎስ "ኃጢአትን" በውስጡ የሚኖር ሕይወት ያለው ነገር አድርጎ በመሳል ይናገራል።
በእርግጥ ክፉው ሐሳብ በውስጠ አለ
ጳውሎስ "ክፉ ሐሳብን" በውስጡ የሚኖር ሕይወት ያለው ነገር አድርጎ በመሳል ይናገራል።
Romans 7:22
ውስጣዊ ሰውነት
ይህ በክርስቶስ የሚታመን የታደሰ መንፈስ ነው።
ነገር ግን በአካል ክፍሎቼ የተለየ አካሄድ አያለሁ። ይኸም በውስጠ አዲሱን አካሄድ ይቃወማል።
እኔንም ለሐሳቡ እንዲገዛ ያደርገኛል
"እኔ ማድረግ የሚችለው አሮጌው ተፈጥሮአዊ ባሕርዬ የሚያዝዘኝን ብቻ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ የሚያሳየኝን አዲስ አካሄድም እንዳልከተል ያደርገኛል"
አዲስ አካሄድ
ይህ በመንፈስዊ ሕይወት ሕያው የተደረገ አዲሱ ባሕርይ ነው።
በአካል ክፍሎቼ የሚገኝ የተለየ አካሄድ
ይህ አሮጌው ተፈጥሮአዊ ባሕርይ ነው፤ ሰዎች ይዘውት የሚወለዱት።
በአካል ክፍሎቼ የሚገኝ የኃጢአት ሥራ አካሄድ
“ኃጢአተኛው ባሕርዬ”
Romans 7:24
ከዚህ ሟች ከሆነ አካል ማን ያላቅቀኛል?


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው የተሰማውን ጥልቅ ስሜት ለመግለጽ ነው። በእናንተ ቋንቋ በመጮህ ወይም ጥያቄ በመሰንዘር ጥልቅ ስሜት የሚገለጽበት መንገድ ካለ እዚህ ጋ አስገቡ። በሌላ አባባል፣ "እኔ አካለ ከሚመኘው ምኞት ነፃ የሚያወጣኝን አንድ ሰው እፈልጋለሁ"

ያላቅቀኛል

“ያድነኛል”

ይህ ሟች ሥጋ

ይህ ተለዋጭ ዘይቤ አካላዊ ሞትን የሚሞተውን አካል የሚያመለክት ነው።

ነገር ግን እግዚአብሔር ይመሰገን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ

ይህ በ7:24 ላይ ላለው ጥያቄ መልስ ነው።

ስለዚህ እኔ ራሴ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔርን ሕግ እገዛለሁ፤ ይሁን እንጂ በሥጋዊ ምኞት ደግሞ ኃጢአት ለሚሠራበት አካሄድ እገዛለሁ።

እዚህ ቁጥር ላይ አእምሮ እና ሥጋዊ ምኞት የገቡት ምን ያህል ለእግዚአብሔር ሕግ ወይም ለኃጢአት ሥራ አካሄድ እንደሚገዙ በንፅፅር ለማሳየት ነው። በአእምሮ ወይም በዕውቀት አንድ ሰው እግዚአብሔርን ማስደሰትና መታዘዝን ሊመርጥ ይችላል፤ ወይ ደግሞ በሥጋዊ ምኞቱ ወይም በአካላዊ ባሕርይው ለኃጢአት ሊገዛ ይችላል። በሌላ አባባል፣ "አእምሮዬ እግዚአብሔርን ማስደሰት ይመርጣል፤ ሥጋዊ ምኞቴ ግን ለኃጢአት መገዛትን ይመርጣል"

---

Chapter 8

Romans 8:1

አያያዥ ዐረፍተ ነገር

ጳውሎስ ኃጢአት እና መልካም ነገርን በተመለከተ በሕይወቱ ስላለው ትግል መልስ ይሰጣል።

ስለዚህ አሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ላመኑት በጥፋተኝነት ወቀሣ ሥር አይሆኑም።

እዚህ ላይ "የጥፋተኝነት ወቀሣ" የሚለው በሕዝብ ላይ የሚመጣውን ቁጣ ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ "እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ያላቸውን ጥፋተኛ ናችሁ ብሎ አይቀጣቸውም”

ስለዚህ

"በዚያ ምክንያት" ወይም "እኔ የነገርኳችው እውነት ስለሆነ"

በክርስቶስ ኢየሱስ በሚገኝ የሕይወት መንፈስ ሕግ

ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር መንፈስን ነው። "በክርስቶስ ኢየሱስ የሚገኝ የእግዚአብሔር መንፈስ"

ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነፃ አውጥቷችኋል

ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነፃ መውጣት የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር የኃጢአትና የሞት ሕግ ተገዢ አለመሆንን ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ “የኃጢአትና የሞት ሕግ ከአሁን በኋላ እንዳይገዛችሁ አደረገ”

የኃጢአትና የሞት ሕግ

እነዚህን ትርጉሞች ሊያመለክት ይችላል፣ 1) ሰዎች ኃጢአት እንዲሠሩ የሚገፋፋ ሕግ፤ ኃጢአታቸው ደግሞ ሞት ያመጣባቸዋል። በሌላ አባባል፣ “ኃጢአትንና ሞትን የሚያመጣ ሕግ" ወይም 2) ሰዎች ኃጢአት ይሠሩና ይሞታሉ የሚል መርህ

Romans 8:3

ምክንያቱም ከሥጋዊ ባሕርያችን ድክመት የተነሣ ሕጉ ማድረግ ያልቻለውን እግዚአብሔር አደረገ

እዚህ ላይ ሕጉ የኃጢአትን ኃይል ሊሰብር እንደማይችል እንደ አንድ አካል ተደርጎ ተገለጸ። በሌላ አባባል፣ "ሕጉ ኃጢአት ከመሥራት ሊያስቆመን የሚችል ጉልበት ስላልነበረው በኛ ውስጥ ያለው የኃጢአት ጉልበትም በጣም ጠንካራ ስለነበረ እግዚአብሔር ግን ኃጢአት ከመሥራት አስቆመን"

በሥጋዊ ባሕርያችን

"በኃጢአተኛው የሰዎች ባሕርይ"

እሱ. . . ኃጢአተኛ ሥጋዊ ባሕርይ በያዘ አካል ተምሣሌት ልጁን ልኮ . . . ስለ ኃጢአት መስዋዕት እንዲሆን. . . እሱ ኃጢአት እንዲወገድ ፍርድ ሰጠ።

የእግዚአብሔር ልጅ የራሱን አካልና ሰዋዊ ሕይወት ስለኃጢአት የዘላለም መስዋዕት አድርጎ በማቅረብ በኃጢአታችን ምክንያት ሊመጣ ያለውን የእግዚአብሔርን ቁጣ ለዘላለም መልሶታል።

ልጅ

ይህ በጣም አስፈላጊ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ማዕረግ ነው፤

ኃጢአተኛ ሥጋዊ ባሕርይ የያዘ አካል ተምሳሌት

"እንደ ማንኛውም ሰው የኃጢአተኛ ሰው መልክ የያዘ"

ስለ ኃጢአት መስዋዕት እንዲሆን

"ስለ እኛ ኃጢአት መስዋዕት ሊሆን እንዲሞት"

በራሱ አካል ኃጢአት እንዲወገድ ፍርድ ሰጠ

"እግዚአብሔር በልጁ አካል የኃጢአትን ኃይል ሰበረ"

ሕጉ ከኛ የሚፈልገውን መመዘኛ እንዲሟላ

በሌላ አተረጓጎም፣ "ሕጉ ከኛ የሚፈልገውን ነገር ማሟላት እንድንችል"

በሥጋዊ ምኞት አካሄድ የማንራመድ እኛ

በመንገዱ መራመድ የሚለው ዘይቤአዊ አነጋገር አንድ ሰው ሕይወቱን እንዴት እንደሚመራ የሚገልጽ ነው። ሥጋ የሚለው ቃል ደግሞ ኃጢአተኛውን የሰው ባሕርይ የሚተካ ነው። በሌላ አባባል፣ “ኃጢአተኛ የሆነውን ፍላጎታችንን የማንታዘዝ እኛ”

ነገር ግን በመንፈስ የምንመራ

"ነገር ግን ለመንፈስ ቅዱስ የምንታዘዝ"

Romans 8:6

አያያዥ ዐረፍተ ነገር

ጳውሎስ ሥጋዊ ምኞትን አሁን በእኛ ካለው መንፈስ ጋር ማነፃፀሩን ቀጥሏል።

ሥጋዊ አስተሳሰብ. . . መንፈሳዊ አስተሳሰብ

ጳውሎስ እዚህ ላይ ስለ "ሥጋዊ ምኞት" እና ስለ "መንፈስ" ሕይወት እንዳላቸው አካላት አድርጎ ያቀርባቸዋል። በሌላ አባባል፣ "ኃጢአተኞች ሰዎች እንዴት እንደሚያስቡ. . . መንፈስ ቅዱስን የሚያደምጡ ሰዎች እንዴት እንደሚያስቡ"

ሞት

ይህ ማለት የአንድ ሰው ከእግዚአብሔር መለየት ማለት ነው።

በሥጋዊ ምኞት የሚመሩ

ይህ የሚያመለክተው ክፉ የሆነው ባሕርያቸው የሚነግራቸውን ነገር የሚሠሩትን ሰዎች ነው።

Romans 8:9

በሥጋዊ ባሕርይ

"በኃጢአተኛ ባሕርይ መመራት"፤ “ሥጋዊ ባሕርይ” በሮሜ 8፡5 ላይ እንዴት እንደተተረጎመ ተመልከቱ።.

በመንፈስ

"በመንፈስ ቅዱስ መመራት"

መንፈስ. . .የእግዚአብሔር መንፈስ. . .የክርስቶስ መንፈስ

እነዚህ ሐረጎች ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ያመለክታሉ

ይህ እውነትም እንደዚህ ከሆነ

ይህ ማለት አንዳንዶቹ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳላቸው ጳውሎስ ይጠራጠራል ማለት አይደለም። ጳውሎስ ሁላቸውም የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳላቸው እንዲገነዘቡ ፈልጎ ነው።

ክርስቶስ በእናንተ ካለ

ክርስቶስ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ እንዴት እንደሚኖር ግልጽ ተደርጎ መነገር አለበት። በሌላ አባባል፣ “ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእናንተ ውስጥ የሚኖር ከሆነ”

አካላችን ለኃጢአት የሞተ ነው።

ይህ አባባል ሁለት ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል፣ 1) አንድ ሰው [የኃጢአት ኃይል ተጽዕኖ እንዳይሰማው] በመንፈስ የሞተ ነው 2) አንድ ሰው በኃጢአት ምክንያት አካላዊ ሞት ይሞታል።

መንፈሳችን የእግዚአብሔርን ሐሳብ ለመፈጸም ሕያው ነው።

ይህ አባባል ሁለት ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል፣ 1) አንድ ሰው በመንፈስ ሕያው ይሆናል ምክንያቱም ትክክል የሆነውን ነገር እንዲሠራ እግዚአብሔር ኃይል ይሰጣዋል 2) አንድ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር ያንን ሰው በሕይወት ወደ መኖር ይመልሰዋል ምክንያቱም እግዚአብሔር ጻድቅ በመሆኑ ለአማኝ ክርስቲያኖች የዘላለም ሕይወት ይሰጣቸዋል።

Romans 8:11

መንፈሱ. . . በእናንተ የሚኖር ከሆነ

ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ በአንባቢዎቹ ውስጥ እንደሚኖር ያስባል። በሌላ አባባል፣ "ምክንያቱም መንፈሱ. . .በእናንተ ስለሚኖር".

ከሞት ያስነሣው የእርሱ

"ከሞት ያስነሣው የእግዚአብሔር"

ኢየሱስን ከሞት አስነሣ

እዚህ ላይ ከሞት አስነሣ ማለት የሞተን ሰው እንደገና መልሶ ሕያው ማድረግ ማለት



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነው። በሌላ አባባል፣ “ኢየሱስን መልሶ በሕይወት እንዲኖር አደረገ”
ሟች የሆኑ አካላት
"ውጫዊ አካላት" ወይም "የሆነ ቀን ሊሞቱ ያሉ አካላት"
Romans 8:12
እንዲህ ከሆነ
"የነገርኳችሁ ነገር እውነት ስለሆነ"
ወንድሞች
እዚህ ላይ ወንድሞች ሲል ክርስቲያን ወገኖች ለማለት ነው፣ ወንዶችንም ሴቶችንም ያጠቃልላል።
Romans 8:14
በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ብዙዎች
በሌላ አተረጓጎም፣"የእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራቸው ሰዎች ሁሉ"
የእግዚአብሔር ልጆች
እዚህ ላይ 'በኢየሱስ ያመኑ አማኞች ሁሉ' ማለት ነው። ብዙ ጊዜም "የእግዚአብሔር ልጆች" ተብሎ ይተረጎማል።
የምንጮኽበት
“እንድንጮህ የሚያደርገን”
አብ፣ አባት
አብ የሚለው አባ ከሚለው የአረሜይክ ቋንቋ የመጣ ሲሆን አባት ማለት ነው።
Romans 8:16
የእግዚአብሔር ወራሾች
x
Romans 8:18
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ሰውነታችን በሚበዡበት ጊዜ እንደሚለወጥ ጳውሎስ እኛ አማኞችን እስከ 8፡25 ባለው በዚህ ክፍል ያስታውሰናል።
ለዚህ
እዚህ ላይ 'አስባለሁ' የሚለውን ሐሳብ ለማጽናት ነው። 'ምክንያቱም' ለማለት አይደለም።
ከ. . . ጋር ለማወዳደር የሚገባቸው እንዳልሆኑ አስባለሁ
በሌላ አተረጓጎም፣ “የአሁኑን መከራ ከዚያ ጋር ማወዳደር አልችልም”.
ሊገለጥ ያለው
በሌላ አተረጓጎም፣ "እግዚአብሔር ሊገልጠው ያለው" ወይም "እግዚአብሔር ሊያሳውቅ ያለው"
የፍጥረት በጉጉት መጠባበቅን እየጠበቀ
ጳውሎስ እዚህ ላይ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ነገሮች ሁሉ በጉጉት የሆነ ነገር የሚጠብቁ አካላት እንደሆኑ ይናገራል።
ለእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ
በሌላ አተረጓጎም፣ "እግዚአብሔር ልጆቹን የሚገልጥባቸውን ጊዜ"
የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች
ይህ ማለት በኢየሱስ ያመኑት ሁሉ፤ "የእግዚአብሔር ልጆች" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።
Romans 8:23
እኛ የመጀመርያ መንፈሳዊ ፍሬ አፍርተናል
ጳውሎስ የክርስቲያን አማኞችን መንፈስ ቅዱስ መቀበል ተተክሎና ወቅቱን ጠብቆ ከደረሰው የመጀመርያ ፍሬና አትክልት ጋር ያነጻጽራል። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ለክርስቲያን አማኞች ከሚሰጣቸው ነገሮች የመጀመርያ መሆኑን በአጽንኦት ለመናገር ነው። በሌላ አባባል፣ “እኛ የመጀመርያውን የእግዚአብሔር ስጦታ ያለን ነን፤ እሱም መንፈስ ቅዱስ ነው”
የእግዚአብሔር ልጅነታችንን መሟላት እየተጠባበቅን፤ እሱም የአካላችን መበዡት
እዚህ ላይ "የእግዚአብሔር ልጅነታችን መሟላት" ማለት የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሙሉ አባል ስንሆን ማለት ነው። "መበዡት" የሚለው ቃል እግዚአብሔር ሲያድነን ማለት ነው። በሌላ አባባል፣ "የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሙሉ አባል መሆናችንን እየተጠባበቅን ይኸውም እሱ አካላችንን ከመበስበስና ከሞት ሲያድን"
እኛ በዚህ የታመነ ተስፋ የዳንን ነን
በሌላ አተረጓጎም፣ “በእርሱ ተስፋ ስላደረግን እግዚአብሔር አዳነን”
ነገር ግን ተስፋ የምናደርገውን ነገር እያየን ከሆነ ተስፋ አይደለም ምክንያቱም የሚያየውን ነገር የሚጠብቅ ማን አለ?
ጳውሎስ የሚጽፍላቸውን ሰዎች "ተስፋ" የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ እንዲገነዘቡ በጥያቄ መልክ ተናገራቸው። በሌላ አባባል፣ "ነገር ግን በመታመን እየተጠባበቅን ከሆነ የምንፈልገው ነገር ገና አልሆነልንም ማለት ነው። የሚፈልገውን ካገኘማ ማንም በመታመን አይጠብቅም"
Romans 8:26
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ምንም እንኳ ጳውሎስ በሥጋዊ ምኞት እና በመንፈሳዊ እውነታ መካከል በክርስቲያን አማኞች ሕይወት የሚካሄድ ትግል መኖሩን አጽንኦት ሰጥቶ የሚናገር ቢሆንም የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚያግዘን ደግሞ ያረጋግጥልናል።
ልገለጽ የማይችል መቃተት
x
Romans 8:28
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ጳውሎስ ክርስቲያን አማኞችን ከእግዚአብሔር ፍቅር ማንም ሊለያቸው እንደማይችል ያስታውሳቸዋል።
ለተጠሩት
በሌላ አተረጓጎም፣ "እግዚአብሔር ለመረጣቸው"
አስቀድሞ ላወቃቸው
"ገና ሳይፈጥራቸው እንኳ ላወቃቸው”
መጨረሻቸውንም ደግሞ አስቀድሞ ወሰነ
"መዳረሻቸውን ደግሞ ወሰነ" ወይም "ደግሞም አስቀድሞ አቀደ"
የልጁን መልክ እንዲኖራቸው
እግዚአብሔር ከፍጥረት ጅማሬ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ የሚያምኑት ኢየሱስን ወደ መምሰል እንዲያድጉ አቀደ። በሌላ አባባል፣ "ልጁን እንዲመስሉ ልለውጣቸው"
ልጅ
ይህ ለኢየሱስ ለእግዚአብሔር ልጅ አስፈላጊ ማዕረግ ነው።
እሱ የመጀመርያ ልጅ እንዲሆን
“ልጁ የመጀመርያ ልጅ እንዲሆን”
ከብዙ ወንድሞች መካከል
እዚህ ላይ "ወንድሞች" የሚለው ሁሉንም አማኞች ወንድንም ሆነ ሴት ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ "የእግዚአብሔር ቤተሰብ ከሆኑት ከብዙ ወንድሞችና እህቶች መካከል"
መጨረሻቸውን አስቀድሞ ለወሰነላቸው
"እግዚአብሔር አስቀድሞ ዕቅድ ላወጣላቸው"
እነዚህን ደግሞ ከጥፋተኝነት አወጣቸው
እዚህ ላይ "ከጥፋተኝነት አወጣቸው" የሚለው ያለፈውን ጊዜ አመልካች መሆኑ ይህ በእርግጠኝነት እንደሚሆን አስረግጦ ለመግለጽ ነው። በሌላ አባባል፣ "እነዚህን ደግሞ በፊቱ ከጥፋተኝነት ነፃ አደረጋቸው"
እነዚህን ደግሞ አከበራቸው
x
Romans 8:31
እንግድህ ስለ እነዚህ ነገሮች ምን እንላለን? እግዚአብሔር እኛን የሚደግፈን ከሆነ ማን ሊቃወመን ይችላል?
ጳውሎስ ከላይ ለተናገረው ነገር አጽንኦት ለመስጠት ዐረፍተ ነገሩን በጥያቄ መልክ ያስቀምጣል። በሌላ አባባል፣ "ከዚህ ሁሉ መረዳት ያለብን ነገር ይህ ነው፣ እግዚአብሔር እየረዳን ከሆነ ማንም ሊያሸንፈን አይችልም"
የራሱን ልጅ እንኳ ከሞት ያላተረፈው
ገደብ የለሽና ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ኃጥአተኛ ከሆነው የሰው ባሕርይ ጋር ለማቀራረብ ቅዱስና ገደብ የለሽ መስዋዕት እንዲሆን እግዚአብሔር አብ የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ መስቀል ላከ። እዚህ ላይ "ልጅ" የሚለው ለኢየሱስ ለእግዚአብሔር ልጅ አስፈላጊ ማዕረግ ነው።
ነገር ግን አሳልፎ ሰጠው
"ነገር ግን በጠላቶቹ እጅ አሳልፎ ሰጠው"
ታዲያ ከእርሱ ጋር እንዴት ሁሉን ነገር በነፃ አይሰጠንም?
ጳውሎስ ለተናገረው ነገር አጽንኦት ለመስጠት ዐረፍተ ነገሩን በጥያቄ መልክ ያስቀምጣል። በሌላ አባባል፣ "እርሱ በእርግጠኝነት ሁሉን ነገር በነፃ ይሰጠናል"
ሁሉን ነገር በነፃ ይሰጠናል
“በቸርነቱ ሁሉን ነገር ይሰጠናል"
Romans 8:33

እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሰዎች የሚከስሳቸው ማን ነው? ከጥፋተኝነት የሚያወጣው እግዚአብሔር ነው።
ጳውሎስ ለተናገረው ነገር አጽንኦት ለመስጠት ዐረፍተ ነገሩን በጥያቄ መልክ ያስቀምጣል። በሌላ አባባል፣ "በእግዚአብሔር ፊት ማንም ልከሰን አይችልም ምክንያቱም በፊቱ ትክክለኛ ሕይወት እንዲኖረን ሊያደርገን የሚችል እርሱ ነው።
የሚወቅሰን ማነው?
ጳውሎስ ለተናገረው ነገር አጽንኦት ለመስጠት ዐረፍተ ነገሩን በጥያቄ መልክ ያስቀምጣል። መልስ እንዲሰጥ ጠብቆ አይደለም። "ማንም ልወቅሰን አይችልም"
ከዚህ ሁሉ በላይ እርሱ ከሞት እንዲነሣ የተደረገ
እዚህ ላይ ከሞት እንዲነሣ የተደረገ የሚለው አባባል የሞተን ሰው ተመልሶ በሕይወት እንዲኖር ማድረግ ለማለት ነው። በሌላ አተረጓጎም፣ "ክሁሉ ይልቅ እግዚአብሔር ከሙታን ያስነሣው እርሱ" ወይም "ከሁሉ ይልቅ እንዲያሁም ከሞት ወደ ሕይወት የተመለሰ እርሱ"
በእግዚአብሔር ቀኝ ያለ
“በእግዚአብሔር ቀኝ” መሆን ከእግዚአብሔር ከፍ ያለ ክብር እና ሥልጣን የመቀበል ተግባር ምልክት ነው። በሌላ አባባል፣ “በእግዚአብሔር አጠገብ በክብር ቦታ ያለ”
Romans 8:35
ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል?
ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ከክርስቶስ ፍቅር ምንም ነገር ሊለየን እንደማይችል ለማስተማር ነው። በሌላ አባባል፣ “መቼም ቢሆን ማንም ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን አይችልም”
መከራ ወይስ ሥቃይ ወይስ ስደት ወይስ ረሃብ ወይስ እርዛት ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ?
“ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን” የሚሉትን ቃላት ከቀደመው ጥያቄ መረዳት ይቻላል። በሌላ አባባል፣ “መከራ ወይም ሥቃይ ወይም ስደት ወይም ረሃብ ወይም እርዛት ወይም አደጋ ወይም ሰይፍ ከክርስቶስ ፍቅር ሊለዩን ይችላሉ ወይ?
መከራ ወይስ ሥቃይ ወይስ ስደት ወይስ ረሃብ ወይስ እርዛት ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ?
ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው እነዚህ ነገሮች እንኳ ከክርስቶስ ፍቅር ሊለዩን እንደማይችሉ በአጽንኦት ለመናገር ነው። በሌላ አባባል፣ “መከራ፣ ሥቃይ፣ ስደት፣ ረሃብ፣ እርዛት፣ አደጋ እናአሰይፍ ከክርስቶስ ፍቅር ሊለዩን አይችሉም”
መከራ ወይስ ሥቃይ ወይስ ስደት ወይስ ረሃብ ወይስ እርዛት ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ?
በንድፈ ሐሳብ ደረጃ የተቀመጡ ስሞች በቃላት ሐረጎች ሊገለጹ ይችላሉ። እዚህ ላይ “ሰይፍ” የሚለው አነጋገር በጭካኔ መገደልን ይተካል። በሌላ አባባል፣ “ምንም እንኳ ሰዎች ቢያሰቃዩን፣ ቢጎዱን፣ ልብሳችንንና ምግባችንን ቢወስዱብን ወይም ቢገድሉን ከክርስቶስ ፍቅር ሊለዩን አይችሉም”
መከራ ወይም ሥቃይ
ሁለቱም ቃላት አንድ ትርጉም አላቸው።
ላንተ ጥቅም
እዚህ ላይ "ላንተ" የሚለው ቃል ነጠላ ሆኖ እግዚአብሔርን የሚያመለክት ነው
እኛ ቀኑን ሙሉ እንገደላለን
እዚህ ላይ "እኛ" የሚለው ቃል ይህን የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል የጻፈውን ሰው ሰው ሲያመለክት የመልዕክቱን ተቀባይ አያመለክትም፣ እሱም እግዚአብሔር ነበር። "ቀኑን ሙሉ" የሚለው ሐረግ ምን ያህል አደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ በአጽንኦት አጋንኖ ለማሳየት ነው። ጳውሎስ ይህን የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል የተጠቀመው የእግዚአብሔር የሆኑ ሰዎች ሁሉ በሕይወታቸው ከባድ ጊዜ ሊገጥማቸው እንደሚችል መጠበቅ እንደሚገባቸው ለማሳየት ነው። በሌላ አተረጓጎም፣ “ጠላቶቻችን ሁሌም ሊገድሉን ይፈልጋሉ”
Romans 8:37
እኛ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን
"እኛ ሙሉ የድል አድራጊነት ብቃት አለን"
በወደደን በእርሱ አማካይነት
ኢየሱስ እንዴት ያለ ፍቅር እንዳሳየ በግልጽ ማስቀመጥ እንችላለን። በሌላ አባባል፣ "በብዙ ፍቅር እኛን ከመውደዱ የተነሣ ኢየሱስ በእኛ ፈንታ ለመሞት ፍቃደኛ ነበር"
እምነት አደረብኝ
"አመንኩኝ" ወይም "እርግጠኛ ሆንኩኝ"
መንግሥታት
x

---

Chapter 9
Romans 9:1
አያያዥ ዐረፍተ ነገር፥
ጳውሎስ የእስራል ሕዝብ ይድናሉ ብሎ ምኞቱን ይገልፃል። ከዚያም እነሱ እንዲያምኑ እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ሲያዘጋጃቸው እንደነበር በአጽንኦት ይናገራል።
እኔ በክርስቶስ ያለውን እውነት እናገራለሁ። አልዋሽም።
እነዚህ ሁለት አገላለጾች አንድ ዓይነት ትርጉም የሚሰጡ ናቸው። ጳውሎስ እነዚህን ተጠቅሞ እውነት እንደሚናገር በአጽንኦት ለማስገንዘብ ነው።
ሕልናዬም ይህንን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ይመሰክርልኛል።
"መንፈስ ቅዱስ ሕልናዬን ይቆጣጠራል፤ እኔ የሚለውንም ነገር ያረጋግጣል"
በጣም አሳዛኝና የማያቋርጥ ሕመም በውስጤ አለ።
እዚህ ላይ “የማያቋርጥ ሕመም በውስጤ” የሚለው አነጋገር ጳውሎስ የራሱን የጭንቀት ስሜት ለመግለጽ የተጠቀመበት ነው። በሌላ አባባል፥ “እኔ ከፍተኛና ጥልቅ የሐዘን ስሜት እንዳለኝ እነግራችኋለሁ”
በጣም አሳዛኝና የማያቋርጥ ሕመም
እነዚህ ሁለቱ አገላለፆች ከመሠረታቸው አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው። ጳውሎስ የተጠቀመባቸው ስሜቱ ከፍተኛ መሆኑን በደንብ ለመግለጽ ነው።
Romans 9:3
እኔ በዘር ከእኔ ጋር አንድ ለሆኑት ወንድሞቼ ስል የተረገምኩ ሆኜ ከክርስቶስ መለየት ብችል እወድ ነበር።
በሌላ አባባል፥ “እኔ በግሌ ይህን ማድረጌ ከእኔ ቡድን የሆነውን ሕዝብ እስራኤላውያን ወገኖቼን በክርስቶስ ለማመን የሚረዳቸው ቢሆን ኖሮ በእግዚአብሔር ተረግሜ ከክርስቶስ ለዘላለም ለመለየት ፍቃደኛ ነበርኩ።
ወንድሞቼ
እንዲህ ማለት ክርስቲያን ወገኖች ለማለት ነው፤ይህም ወንዶችንም ሴቶችንም ይጨምራል።
እስራኤላውያን ናቸው
እነርሱ እንደ እኔ እስራኤላውያን ናቸው። እነርሱ የያዕቆብ ዘር እንዲሆኑ እግዚአብሔር መርጦአቸዋል።
እንደ ልጆቹ ተቆጥረዋል
እዚህ ላይ ጳውሎስ “እንደ ልጆቹ” የሚለውን ዘይበኤአዊ አነጋገር የተጠቀመው እስራኤላውያን እንደ እግዚአብሔር ልጆች ይታያሉ የሚለውን ለማመልከት ነው። በሌላ አባባል “ለእነርሱ እግዚአብሔር አባታቸው ነው”
ክርስቶስ የመጣበት የዘር ግንድ ውስጥ የቀድሙ ዘመዶች አሉ
እዚህ ላይ “ክርስቶስ የመጣበት የዘር ግንድ” ሲባል ክርስቶስ ሰብአዊ የደም ዝምድናን በተመለከተ ከእስራኤላውያን ዘር ነው።በሌላ አባባል፥ “ክርስቶስ ሰብአዊ የዘር ግንዱን በተመለከተ የመጣው ከእነርሱ ዘር ነው”
Romans 9:6
አያያዥ ዐረፍተ ነገር፥
ጳውሎስ በቤተ እስራኤል ውስጥ የተወለዱ ሰዎች ብቻ ከእምነት አንፃር እውነተኛ የእስራኤል ወገን ሊሆኑ ይችላሉ የሚለውን ሐሳብ ጠንከር አድርጎ ለማስረዳት ነው።
ነገር ግን የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ሳይከናወን እንደ ቀረ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም
“ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል መጠበቅ አላቃተውም” ወይም “እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ጠብቆአል”
በእስራኤል ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ እውነተኛ የእስራኤል ወገን አይደሉምና።
እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን የሰጠው ከእስራኤል (ወይም ያዕቆብ) የዘር ግንድ ለተወለዱ ሁሉ አይደለም ነገር ግን በመንፈስ ከያዕቆብ ለተወለዱት ነው ማለትም በኢየሱስ የታመኑት ናቸው።
Romans 9:8
ሰብአዊ ልጆቹ ግን አይደሉም
እዚህ ላይ “ሰብአዊ ልጆች” የሚለው ዘይበአዊ አነጋገር በሥጋ ከአብርሃም የተወለዱትን ያመለክታል። በሌላ አነጋገር “ከአብርሃም የዘር ግንድ የተወለዱ ሁሉ አይደሉም”
የእግዚአብሔር ልጆች
ይህ መንፈሳዊ ልጆቹ የሆኑ ሰዎችን የሚያመለክት ተለዋጭ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው፥ በኢየሱስ ያመኑትን።
የተስፋ ቃሉ ልጆች
ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን የተስፋ ቃል የሚወርሱ ሰዎችን ነው።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይህ የተነገረው የተስፋ ቃሉ ነው
“እነዚህ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ሲናገር የተጠቀመባቸው ቃላት ናቸው”
ለሳራ ወንድ ልጅ ይሰጣል
በሌላ አነጋገር ‘እግዚአብሔር ለሳራ ወንድ ልጅ ይሰጣል’ ማለት ይቻላል። “እኔ ለሳራ ወንድ ልጅ እሰጣለው”
Romans 9:14
ስለዚህ ምን እንበል?
ጳውሎስ ይኸንን በጥያቄ መልክ ሲያቀርብ የአንባቢዎቹን ትኩረት ለማግኘት ነው።
ይህ ፈጽሞ ሊሆን አይገባም
“ይህ ነገር አይቻልም” ወይም “ፈጽሞ አይሆንም” ይህ አገላለጽ ይህ ነገር እንደ ተባለው እንዳይሆን አጥብቆ ይከለክላል። በእናንተ ቋንቋ ሊትጠቀሙበት የሚትችሉት ተመሳሳይ አገላለጽ ይኖር ይሆናል።
ለሙሴ እንዲህ ይለዋል
ጳውሎስ እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ በአሁኑ ጊዜ እየሆነ እንዳለ ዓይነት አገላለጽ ተጠቅሞ መናገሩን ይገልጻል።
ይህ የሚሆነው ሰው ስለፈለገው ወይም ስለሮጠ አይደለም
“ይህ የሚሆነው ሰው ከሚፈልገው ነገር የተነሣ ወይም ሰው ከሚያደርገው ጥረት የተነሣ አይደለም”
ስለሚሮጠው ሰው ተብሎ አይደለም
ጳውሎስ እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ቸርነት ለማግኘት መልካም ነገር ስለሚያደርግ ሰው ሲናገር ለውድድር የሚሮጥ ሰው ምሳሌን ተጠቅሞ ይገልጸዋል።
Romans 9:17
በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እንዲህ ይላል
እዚህ ላይ ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተነገረውን እግዚአብሔር ለፈረኦን እንደሚናገር ተደርጎ ተቀምጦአል። በሌላ አባባል፥ “ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚናገረው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል”
እኔ. . .የኔ
እግዚአብሔር ራሱን ለማመልከት ነው።
አንተ
ነጠላ ቁጥር አመልካች
ጠበቅኩህ
x
Romans 9:19
ከዚያም እንዲህ ትለኛለህ
ጳውሎስ ለትምህርቱ ተቃዋሚዎች ልክ ለአንድ ሰው እንደሚናገር ዓይነት አድርጎ ይናገራቸዋል።ብዙ ቁጥር አመልካችንም ልትጠቀሙ ትችላላችሁ።
እስከዚህ ጊዜም ቢሆን ለምን ወቀሳ ይሰነዝራል? ፍቃዱንስ የተቋቋመ ሰው ማን ነው?
እነዚህ የማሳመኛ ነጥቦች ጳውሎስ ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት የተጠቀመባቸው ናቸው።ሁሉንም ጠበቅ ያሉ ዐረፍተ ነገሮች አድርገን መተርጎም እንችላለን።
እርሱ. . .የርሱ
እነዚህ ቃላት እግዚአብሔርን የሚያመለክቱ ናቸው።
የተሠራ ነገር እንዲህ ብሎ ይናገራል. . .ለዕለታዊ ግልጋሎት?
ጳውሎስ አንድ ሸክላ ሠሪ ከሸክላ የፈለገውን ዕቃ የመሥራት መብት አለው የሚለውን ዘይቤ ተጠቅሞ ፈጣሪ በፍጥረቱ የፈለገውን ነገር ለመሥራት መብት እንዳለው ይገልጻል። ጳውሎስ በጥያቄ መልክ ያቀረበው ነጥቡን ጠንከር አድርጎ ለማስቀመጥ ነው።
ለምን እንደዚህ አድርገህ ሠራኸኝ?
አንተ የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ያመለክታል።በጥያቄ መልክ ሲናገር ደግሞ ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት ነው።ይኸንን እንደ አንድ ጥብቅ ዐረፍተ ነገር መተረጎምም ትችላላችሁ። በሌላ አባባል፥ “እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደዚህ አድርገህ ሊታበጀኝ አይገባም ነበር!”
Romans 9:22
እርሱ. . .የርሱ
እነዚህ ቃላት እግዚአብሔርን የሚያመለክቱ ናቸው።
የቁጣ ዕቃዎች. . . የምህረት ዕቃዎች
ጳውሎስ ሰዎችን እንደ ዕቃዎች በመውሰድ ይገልጻቸዋል። በሌላ አባባል፥ ቁጣ የሚገባቸው ሰዎች. . .ምህረት የሚገባቸው ሰዎች
የክብሩ ባለጠግነት
ጳውሎስ የእግዚአብሔርን አስገራሚ ሥራዎች ከትልቅ ባለጠግነት ጋር ያነፃፅራል።
በሌላ አባባል፥ “ትልቅ ዋጋ ያለው ክብሩ”
አስቀድሞ ለክብር ያዘጋጃቸውን
እዚህ ላይ “ክብር” የሚያመለክተው በሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር የምንኖረው ሕይወት ነው።በሌላ አባባል፥ “ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ ቀደም ብሎ ያዘጋጃቸውን”
Romans 9:25
አያያዥ ዐረፍተ ነገር
ጳውሎስ በዚህ ክፍል የእስራኤል ሕዝብን አለማመን አስቀድሞ በነብዮ ሆሴዕ እንደተነገረ ይገልጻል።
እርሱ በሆሴዕም ላይ እንደተናገረው
እዚህ ላይ “እርሱ” የሚለው እግዚአብሔርን ያመለክታል። በሌላ አባባል፥ “ሆሴዕ በጻፈው መጽሐፍም ላይ እግዚአብሔር እንደተናገረው”
ሆሴዕ
ሆሴዕ ነብይ ነበር።
እኔ በዚያን ጊዜ ሕዝቤ ያልሆነውን ሕዝብ ብዬ እጠራዋለው
እኔ በዚያን ጊዜ የእኔ ያልነበረውን ሕዝብ ሕዝቤ እንዲሆን እመርጠዋለሁ
የተወደደ ያልነበረውን የእሷን ውድ
እዚህ ላይ “እሷ” የሚለው የሚያመለክተው የእስራኤልን ሕዝብ የሚትወክለውን ጎመር የሚትባለውን የሆሴዕ ሚስት ነው። በሌላ አባባል፥ “በእኔ የማትወደድ የነበረችውን በእኔ የሚትወደድ እንዲትሆን እመርጣታለሁ” የሕያው እግዚአብሔር ልጆች
የሕያው እግዚአብሔር ልጆች
“ሕያው” የሚለው ቃል እግዚአብሔር ብቸኛው እውነተኛ አምላክ መሆኑን እንደ ሐሰተኛ ጣኦቶችም አለመሆኑን ያመለክታል።
Romans 9:27
ይጮሃል
“ይጣራል”
እንደ ባሕር አሸዋ
እዚህ ላይ ጳውሎስ የእስራኤል ሕዝብ ብዛትን ከባሕር አሸዋ ደቃቆች ብዛት ጋር ያነፃፅራል። በሌላ አባባል፣ “ከብዛቱ የተነሣ ለመቁጠር የሚከብድ”
ይድናሉ
ጳውሎስ “ይድናሉ” የሚለውን ቃል በመንፈሳዊ ትርጉሙ ይጠቀምበታል። እግዚአብሔር አንድን ሰው ካዳነ በኢየሱስ መስቀልና ሞት ባለው እምነት አማካይነት እግዚአብሔር ምህረት አድርጎለት በኃጢአቱ ምክንያት ከሚመጣበት ቅጣት ነፃ አደረገው።
ጌታ በምድር ፍርዱን ይፈጽማል
እዚህ ላይ “ፍርድ” የሚለው ቃል ሰዎች ለመቅጣት የወሰነውን ውሳኔ ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ “ጌታ በምድር ያለውን ሕዝብ በውሳኔው መሠረት ይቀጣዋል”
እኛ
ይህ የሚያመለክተው ኢሳያስንና እርሱ ቃል የተናገራቸውን ሰዎች ነው።
እኛ እንደ ሰዶም እንሆናለን፤ እንደ ገሞራም ልንሆን እንችል ነበር
x
Romans 9:30
ስለዚህ ምን እንበል?
ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው የአንባቢዎቹን ትኩረት ለማግኘት ሲል ነው። በሌላ አባባል፥ “ስለዚህ እንዲህ ማለት አለብን”
እንግዲህ አይሁድ ያልሆኑ ሕዝቦች
“እንዲህ እንላለን፣ አይሁድ ያልሆኑ ሕዝቦች”
በእግዚአብሔር ሐሳብ ያልሄዱ
“እግዚአብሔርን ለማስደሰት ጥረት ያላደረጉ”
በእምነት የእግዚአብሔርን ሐሳብ መከተል
እዚህ ላይ “በእምነት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በክርስቶስ መታመን ነው። ይህንን በትርጉማችን ገልጦ ማሳየት ይቻላል፥ “እነርሱ በክርስቶስ በታመኑ ጊዜ እግዚአብሔር በፊቱ ትክክለኞች አድርጎ ተቀበላቸው”
ሊደርሱበት አልቻሉም
ይህ ማለት እስራኤላውያን ሕግን ለመጠበቅ በመሞከር እግዚአብሔርን ሊያስደስቱ አልቻሉም። ይኸንን በትርጉማችን ገልጦ ማሳየት ይቻላል፥ “ሕግን በመጠበቅ እግዚአብሔርን ማስደሰት አልቻሉም ምክንያቱም ሕግን መጠበቅ አልቻሉም”
Romans 9:32
ለምን አልሆነም?

ይህ በአጭሩ የተቀመጠ አባባል ነው። ለማለት የተፈለጉትን ቃላት ጨምረን መግለጽ እንችላለን። ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የጠየቀው የአንባቢዎቹን ትኩረት ለማግኘት ነው። በሌላ አባባል ስናስቀምጠው፥ "እነርሱ በእግዝአብሔር ሐሳብ መሄድ ያልቻሉት ለምንድነው?"

በሥራ

ይህ የሚያመለክተው ሰዎች እግዚአብሔርን ለማስደሰት ሲሞክሩ የሚያደርጉትን ነገር ነው። ይህንን ሐሳብ በትርጉማችን ገልጦ ማሳየት ይቻላል፥ "እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነገር ለመሥራት ጥረት ማድረግ" ወይም "ሕጉን በመጠበቅ"

እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል

ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ ጽፎአል ማለት ይቻላል። በሌላ አባባል፣ "ነብዩ ኢሳይያስ እንደ ጻፈው"

---

Chapter 10

Romans 10:1

አያያዥ ዐረፍተ ነገር፥

ጳውሎስ እስራኤል በክርስቶስ እንዲያምን ምኞቱን እየገለጸ ግን ደግሞ አይሁድም ሆነ ሌሎች ሕዝቦች ሁሉም ሊድኑ የሚችሉት በኢየሱስ ባላቸው እምነት ብቻ መሆኑን አጥብቆ ያስገነዝባል።

ወንድሞች

እዚህ ላይ እንዲህ ማለት ወንዶችንም ሴቶችንም ጨምሮ ክርስቲያን ወገኞች ለማለት ነው።

የልቤ ምኞት

እዚህ ላይ "ልብ" የሚለው ቃል የሰውን ውስጣዊ ስሜት ለማለት ነው። በሌላ አባባል፣ "ከሁሉም የሚበልጥ ፍላጎቴ"

ለእነርሱ ነው፤ ለድነታቸው

"እግዚአብሔር አይሁዶችን ያድናቸዋል"

እኔ ስለ እነርሱ እመሰክራለሁ

"እኔ ስለ እነርሱ እውነቱን እናገራለሁ"

እነርሱ የእግዚአብሔርን መመዘኛ ሐሳብ አላወቁም

እዚህ ላይ "የእግዚአብሔር መመዘኛ ሐሳብ" የሚለው እግዚአብሔር ሰዎችን በፊቱ ሐሳቡን የሚያሟሉ የሚያደርግበት መንገድን ያመለክታል።

Romans 10:4

ክርስቶስ የእግዚአብሔር ሕግ ሙላት ነው

"ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ሕግ ሙሉ በሙሉ ፈጽሞአል።

የእግዚአብሔርን ሐሳብ የፈጸመ ለመሆን ላመነ ሁሉ

እዚህ ላይ "የሚያምን" ማለት "የተማመነ" ማለት ነው። በሌላ አባባል፥ "በሱ የተማመኑትን በፊቱ ሐሳቡን የፈጸሙ አድርጎ እንዲቀበላቸው"

ሕግን በመፈጸም የእግዚአብሔር ሐሳብ የፈጸመ ሆኖ መገኘት

ጳውሎስ "የእግዚአብሔርን ሐሳብ መፈጸም" የሚለውን ሕይወት እንዳለውና እንደሚንቀሳቀስ አድርጎ ይናገራል። በሌላ አባባል፥ "ሕግ አንድን ሰው ከእግዚአብሔር ሐሳብ አንጻር እንዴት የተስተካከለ እንደሚያደርግ"

ሕግን በመፈጸም የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚፈጽም ሰው በዚሁ ይኖራል

ሕግን በመፈጸም በእግዚአብሔር ፊት የእግዚአብሔርን ሐሳብ የፈጸመ ለመሆን ሕጉን ሙሉ በሙሉ መፈጸም አለበት፤ ይህ ደግሞ የሚቻል አይደለም። በሌላ አባባል፥ "ሕጉን ሙሉ በሙሉ የሚፈጽም ሰው በሕይወት ይኖራል ምክንያቱም ሕጉ የእግዚአብሔርን ሐሳብ የፈጸመ ያደርገዋል"

በሕይወት ይኖራል

ይህ አባባል የሚያመለክተው 1) ዘላለማዊ ሕይወት 2) ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያለው የሚሞት ሕይወት

Romans 10:6

ነገር ግን ከእምነት የሚመጣው የእግዚአብሔርን ሐሳብ መፈጸም እንዲህ ይላል

እዚህ ላይ "የእግዚአብሔርን ሐሳብ መፈጸም" የሚለው አባባል መናገር እንደሚችል ሰው ተደርጎ የቀረበ ነው።በሌላ አባባል፥ "ነገር ግን ሙሴ እምነት እንዴት አንድን ሰው በእግዚአብሔር ፊት ሐሳቡን የፈጸመ እንደሚያደርገው ሲጽፍ እንዲህ ብሏል።

በልባችሁ እንዲህ አትበሉ

ሙሴ ለሕዝቡ ሲናገር ለአንድ ሰው እንደሚናገር አድርጎ ያቀርበዋል።እዚህ ላይ "ልብ" የአንድን ሰው አእምሮ ወይም ውስጣዊ ስሜት የሚተካ ነው። በሌላ አባባል፥ "ራሳችሁን እንዲህ አትበሉ"

ወደ ሰማይ የሚወጣ ማነው?

ሙሴ የሚናገራቸውን ሰዎች ለማስተማር በጥያቄ መልክ አቀረበ። ያለፈው ትምህርቱ ላይ "አትበሉ" ሲል ለዚህኛው ጥያቄ አሉታዊ መልስ እንደሚያስፈልገው ያሳያል። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ማስቀመጥ ይቻላል፥ "ወደ ሰማይ ሊወጣ የቻለ ማንም የለም"

ይህም ማለት ክርስቶስን ለማውረድ

"ክርስቶስ ወደ ምድር እንዲመጣ ለማድረግ"

ወደ ጥልቅም የሚወርድ ማነው?

ሙሴ የሚናገራቸውን ሰዎች ለማስተማር በጥያቄ መልክ አቀረበ።ያለፈው ትምህርቱ ላይ "አትበሉ" ሲል ለዚህኛው ጥያቄ አሉታዊ መልስ እንደሚያስፈልገው ያሳያል። ይህን ጥያቄ በዐረፍተ ነገር መልክ ማስቀመጥ ይቻላል፥ "ወደ ጥልቁ በመውረድ የሞቱ ሰዎች መናፍስት ያሉበት ቦታ ሊገባ የቻለ ማንም የለም"

ከሙታን

ከሞቱት ሰዎች ሁሉ መካከል ማለት ነው።ይህ አባባል በታችኛው ዓለም የሚገኙትን የሞቱ ሰዎች በአንድ ላይ የሚገልጽ ነው።

ሙት

ይህ ቃል ስለ አካላዊ ሞት ይናገራል።

Romans 10:11

ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እንደተጻፈው

ጳውሎስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሕይወትና ድምፅ እንዳለው አድርጎ ይናገራል። እዚህ ላይ ጳውሎስ የተጠቀመውን የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ጸሐፊውን በግልጽ መጥቀስ ትችላላችሁ። በሌላ አነጋገር፥ "ኢሳያስ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደጻፈው"

በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም

ይህ "የማያምን ሁሉ ያፍራል" ከማለት ጋር ተመጣጣኝ ትርጉም አለው። እዚህ ላይ በአሉታዊ መልኩ የተቀመጠው ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት ነው። በሌላ አባባል፥ "እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ያከብራል"

በአይሁድና እና በግሪክ መካከል ልዩነት የለም

የጳውሎስ ሐሳብ እግዚአብሔር ለሁሉም ሕዝቦች እኩል ያስብላቸዋል።ይህንን ሐሳብ በትርጉማችን ገልጠን ማሳየት እንችላለን። በሌላ አባባል፥ "በዚህ መልኩ እግዚአብሔር ለአይሁድም አይሁድ ላልሆኑትም እኩል ያስብላቸዋል"

ስሙን ለሚጠሩት ሁሉ እርሱ ሁሉን ነገር አለው

እዚህ ላይ "ሁሉን ነገር አለው" ተብሎ የተተረጎመው አባባል እግዚአብሔር በብዙ በረከት ይባርካል ለማለት ነው።ይህን ሐሳብ በትርጉማችን ገልጠን ማሳየት እንችላለን። በሌላ አባባል፥ "እርሱ በእርሱ የሚተማመኑትን በብዙ በረከት ይባርካቸዋል"

የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል

እዚህ ላይ "ስም" የሚለው ቃል ኢየሱስን የሚተካ ነው። በሌላ አባባል፥ "ጌታ በእርሱ የሚተማመኑትን ሁሉ ያድናል"

Romans 10:14

ታዲያ እነርሱ ያላመኑበትን እርሱን እንዴት ሊጠሩት ይችላሉ?

ጳውሎስ ይኸንን ጥያቄ የተጠቀመው የክርስቶስን የምሥራች ቃል ወዳልሰሙት ሰዎች የማድረስን አስፈላጊነት አጥብቆ ለማስገንዘብ ነው። "እነርሱ" የሚለው ቃል ገና የእግዚአብሔር ሕዝብ ያልሆኑትን ያመለክታል።በሌላ አባባል፥ "በእግዚአብሔር የማያምኑት የእርሱን ስም ሊጠሩ አይችሉም"

ስለ እርሱ ባልሰሙት በእርሱ እንዴት ሊያምኑ ይችላሉ?

ጳውሎስ ለተመሳሳይ ምክንያት ሌላ ጥያቄ ይጠቀማል። በሌላ አባባል፥ "የእርሱን መልዕክት ያልሰሙ ከሆነ በእርሱ ሊያምኑ አይችሉም"

ማመን

ይህ ማለት ያ ሰው ያለው እውነት መሆኑን መመስከር ማለት ነው።

የሚሰብክ ሳይኖር እንዴት ሊሰሙ ይችላሉ?

ጳውሎስ ለተመሳሳይ ምክንያት ሌላ ጥያቄ ይጠቀማል።በሌላ አባባል፥ "ሰው ካልነገራቸው የእርሱን መልዕክት ሊሰሙ አይችሉም"

ታዲያ ካልተላኩ እንዴት ልሰብኩ ይችላሉ?

ጳውሎስ ለተመሳሳይ ምክንያት ሌላ ጥያቄ ይጠቀማል። "እነርሱ" የሚለው ቃል የእግዚአብሔር የሆኑትን ያመለክታል። በሌላ አባባል፥ "የሆነ ሰው ካልላካቸው መልዕክቱን ለሌሎች መንገር አይችሉም"

አስደሳች የሆነውን መልካም ዜና ከቦታ ቦታ ሄደው የሚያበሥሩ እግሮች በጣም ያማሩ ናቸው።

ጳውሎስ “እግር” የሚለውን አባባል የተጠቀመው መልዕክቱ ወዳልደረሳቸው ለማድረስ የሚጓዙትን ሰዎች ለማመልከት ነው። በሌላ አባባል። “መልዕክተኞች መጥተው የምሥራቹን ዜና ሲነግሩን በጣም አስገራሚ ነው”

Romans 10:16

ነገር ግን ሁላቸውም አላዳምጡም።

እዚህ ላይ “እነርሱ” የሚለው ሐሳብ አይሁዶችን ያመለክታል። “ነገ ግን ያዳመጡት ሁሉም አይሁዶች አይደሉም”

ጌታ ሆይ የተናገርነውን መልዕክት ማን አመነ?

ጳውሎስ ይህንን በጥያቄ መልክ ያቀረበው በቅዱሳት መጻሕፍት ኢሳያስ ስለ አይሁዶች በኢየሱስ አለማመን የተነበየውን አጽንኦት ሰጥቶ ለማስገንዘብ ነው።

መልእክታችን

እዚህ ላይ “እኛ” የሚያመለክተው እግዚአብሔር እና ኢሳይያስን ነው።

እምነት ከመስማት ይመጣል፤

እዚህ ላይ “እምነት” የሚያመለክተው “በክርስቶስ ማመንን ነው።

መስማት የክርስቶስን ቃል ነው።

መስማት ስለ ክርስቶስ የሚነገረውን መልዕክት በማዳመጥ ነው።

Romans 10:18

ነገር ግን እኔ እላለው፥ “እነርሱ ሰምተው የለም ወይ?” አዎ፤ በእርግጥ ሰምተዋል።

ጳውሎስ በጥያቄ መልክ ያቀረበው ለነገሩ አጽንኦት በመስጠት ነው።ጥያቄውን ወደ ዐረፍተ ነገር መልሳችሁ መተርጎም ትችላላችሁ። በሌላ አባባል፥ “ነገር ግን እኔ እላለሁኝ፥ አይሁዶች በእርግጥ ስለ ክርስቶስ የሚነገረውን መልዕክት ሰምተዋል።

ድምጻቸው በምድር ሁሉ ቃላቸውም በምድር ዳርቻ ሁሉ ተሰራጨ

ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው፤ ጳውሎስ ሁለቱን የተጠቀመው ነገሩን አጥብቆ ለመንገር ነው። “እነርሱ” የሚለው ሐሳብ የሚያመለክተው ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ እና ኮከቦችን ነው።እዚህ ላይ እነዚህ ስለ እግዚአብሔር ለሕዝቦች እንደሚናገሩ መልዕክተኞች ሰዎች ተደርገው ተገልጸዋል።ይህም የሚያመለክተው የነዚህ መኖር ራሱ ምን ያህል የእግዚአብሔርን ኃይልና ክብር የሚያሳይ እንደሆነ ነው።እዚህ ላይ ጳውሎስ ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሰ መሆኑን ገልጣችሁ ማሳየት ትችላላችሁ። በሌላ አባባል፥ “ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እንደተጻፈው ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ እና ኮከቦች የእግዚአብሔር ኃይልና ክብር ማረጋገጫ ናቸው፤በዓለም ላይ ያሉት ሰዎች ሁሉ እነርሱን አይተው ስለ እግዚአብሔር እውነቱን ያውቃሉ”

Romans 10:19

በተጨማሪም እላለሁ “እስራኤል አላወቀም ወይ?”

ጳውሎስ በጥያቄ መልክ ያቀረበው ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት ነው፡፡ “እስራኤል” የሚለው ቃል በእስራል አገር የኖሩ ሕዝቦችን ለማመልከት ነው። በሌላ አባባል።

“አሁንም እነግራቸዋለሁ፥ የእስራኤል ሕዝብ መልዕክቱን አውቀዋል”

ሙሴ አስቀድሞ እንዲህ አለ፥ “አስቆጣችኋለሁ. .እንዲትበሳጩም አደርጋለሁ”

ይህ ማለት ሙሴ እግዚአብሔር ያለውን ነው የተናገረው። “እኔ” የሚለው የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው፤ “እናንተ” የሚለው ሐሳብ ደግሞ እስራኤላውያንን ነው፡። በሌላ አባባል፥ “ሙሴ አስቀድሞ እንዲህ አለ፥ “እግዚአብሔር ያስቆጣችኋል. . .እግዚአብሔር እንዲትበሳጩ ያደርጋል”

ሕዝብ ባልሆነው

“እናንተ እንደ ሕዝብ በማትቆጥሯቸው” ወይም “ከየትኛውም ሕዝብ በማይመደቡ ሰዎች”

ማስተዋል በሌለው ሕዝብ

እዚህ ላይ “ማስተዋል የሌለው” ማለት እግዚአብሔርን የማያውቅ ሕዝብ ማለት ነው፡። በሌላ አባባል፥ “እኔን ወይም ትዕዛዞቼን የማያውቁ ሰዎች በሚኖሩበት ሕዝብ”

ንዴታችሁን እቀሳቅስባችኋለሁ

“እንድትበሳጩ አደርጋለሁ” ወይም “እንዲትበሳጩ የሚያደርግ ነገር አደርጋለሁ”

እናንተ

ይህ የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል።

Romans 10:20

አጠቃላይ መረጃ፥

እዚህ ላይ “እኔ” እና “የእኔ” የሚሉ ቃላት የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን ነው፡።

ከዚያም ኢሳይያስ በድፍረት እንዲህ ብሎ ተናገረ

ይህ ማለት ነብዩ ኢሳይያስ የጻፈው እግዚአብሔር የተናገረውን ነው።

ለማይፈልገኝ ሕዝብ ተገኘሁ

ነቢያት ብዙውን ጊዜ ለወደ ፊት ሊከሰቱ ያሉትን ነገሮች እንደተፈጸመ አድርገው ይናገራሉ። ይህ አጥብቆ የሚያስረዳው ትንቢቱ በእርግጠኝነት እንደሚፈጸም ነው። በሌላ አባባል፥ “የእግዚአብሔር ያልሆኑ ሕዝቦች ምንም እንኳ ባይፈልጉኝ ያገኙኛል”

ተገለጥኩ

“ራሴን አሳወቅኩ”

እርሱ እንዲህ ይላል

“እርሱ” የሚለው የሚያመለክተው በኢሳይያስ በኩል የተናገረውን እግዚአብሔርን ነው።

ቀኑን ሙሉ

ይህ ሐረግ አጥብቆ የሚገልጸው የእግዚአብሔርን ተከታታይ ጥረት ነው። “በተከታታይ”

እጆቼን ለማይታዘዝና ለልበ ደንዳና ሕዝብ ዘረጋው

“እናንተን ለመቀበልና ለመርዳት ሞከርኩ ነገር ግን እርዳታዬን እምቢ ብላችሁ በአለመታዘዝ ሕይወት ቀጠላችሁ።

---

# Chapter 11

Romans 11:1

አያያዥ መግለጫ፡

እስራኤል እንደ ሕዝብ እግዚአብሔርን ቢተዉትም ድነት ያለ ሥራ በጸጋ እንደሆነ ይረዱ ዘንድ እግዚአብሔር ይፈልግባቸዋል።

እንግዲህ እላለሁ

“እንግዲህ እኔ ጳውሎስ እላለሁ”

እግዚአብሔር ሕዝቡን ጥሎአቸዋል?

‘የአይሁድ ሕዝብ ልባቸው በመደንደኑ እግዚአብሔር አህዛብን በሕዝቡ ውስጥ አካተታቸው’ በማለት የሚበሳጩ የሌሎች አይሁዶችን ጥያቄ ለመመለስ እንዲያስችለው ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እንዲህ አይደለም

“ይህ ሊሆን የማይችል ነው!” ወይም “ያለጥርጥር አልጣላቸውም!” ይህ አገላለጽ ሊሆን እንደማይችል አጥብቆ ይቃወማል። በአንተ ቋንቋ እዚህ ጋ መጠቀም የምትችልበት ተመሳሳይ አገላለጽ ይኖርህ ይሆናል። ይህንን በሮሜ 9፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።

የብንያም ጎሳ

ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በ12 ጎሳ ከከፋፈላቸው ከእስራኤል ሕዝብ አንዱ ከሆነው ከብንያም ጎሳ የተገኙትን ነው።

አስቀድሞ ያወቃቸውን

“ከረጅም ጊዜ በፊት ያወቃቸውን”

ኤልያስ እስራኤልን በእግዚአብሔር ፊት እንዴት እንደከሰሳቸው መጽሐፍ የሚናገረውን አታውቁም?

ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ኤልያስ እስራኤልን በእግዚአብሔር ፊት በከሰሳቸው ጊዜ ምን ተብሎ በመጽሐፍ እንደ ተጻፈ በእርግጥ ታውቃላችሁ” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Romans 11:4

ነገር ግን የእግዚአብሔር መልስ ምን አለው?

ጳውሎስ አንባቢን ወደ ቀጣይ ማብራሪያው ለማምጣት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር የመለሰለት እንዴት ነበር?” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

Romans 11:6

በጸጋ ከሆነ ግን

ጳውሎስ የእግዚአብሔር ምህረት እንዴት እንደሚሠራ ማብራራቱን ይቀጥላል። ኢ.ት “የእግዚአብሔር ምህረት በጸጋ የሚሠራ ከሆነ ግን”

እንግዲህ ምንድነው?

“ምን ብለን እንደምድም?” ጳውሎስ አንባቢውን ወደ ቀጣዩ ማብራሪያ ለመውሰድ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህንን እንደ መግለጫ አድርገህ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ማስታወስ የሚኖርብን ይህንን ነው” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር ዐይኖቻቸው እንዳያዩ፣ ጆሮዎቻቸው እንዳይሰሙ የድንዛዜን መንፈስ ሰጣቸው

ይህ ሕዝቡ በመንፈስ የመደንዘዙን ሐቅ የሚያሳይ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። መንፈሳዊ እውነትን ለመስማት ወይም ለመቀበል አይችሉም። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን

ተመልከት)
የ -- መንፈስ
እዚህ ጋ፣ ይህ ማለት እንደ “የጥበብ መንፈስ” ሁሉ “የአንዳች ዓይነት ጠባይ” ማለት ነው።
ዐይኖቻቸው እንዳያዩ፣
አንድ ሰው በዐይኑ የማየቱ አስተሳሰብ ዕውቀትን ከማግኘት ጋር እኩል እንደሆነ ተቆጥሯል።
ጆሮዎቻቸው እንዳይሰሙ
በጆሮ የመስማት አስተሳሰብ ከመታዘዝ ጋር እኩል እንደሆነ ተቆጥሯል።
Romans 11:9
ማዕዳቸው መረብና ወጥመድ ይሁንባቸው
እዚህ ጋ “ማዕድ” ግብዣን የሚወክል ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን “መረብ” እና “ወጥመድ” ቅጣትን የሚወክሉ ዘይቤአዊ አነጋገሮች ናቸው። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፣ እባክህን ግብዣዎቻቸውን እነርሱን እንደሚይዝ ወጥመድ አድርግ” (ፈሊጣዊ አነጋገር፣ ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እንቅፋት
“እንቅፋት” አንድ ሰው ተደናቅፎ እንዲወድቅ የሚያስደርገው ማንኛውም ነገር ነው። እዚህ ጋ፣ አንድ ሰው ኀጢአትን እንዲያደርግ የሚፈታተነውን አንድ ነገር ይወክላል። ኢ.ት፡ “ኀጢአት እንዲሠሩ የሚፈታተናቸው ነገር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ለእነርሱ ቅጣት
“እንድትበቀላቸው የሚያስደርግህ ነገር”
ዘወትር ወገባቸውን አጉብጥ
እዚህ ጋ፣ “ወገባቸውን አጉብጥ” ባሮች በጀርባቸው ከባድ ሸክሞችን እንዲሸከሙ የሚገደዱበት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። እንዲሰቃዩ የማድረግ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ከባድ ሸክም እንደሚሸከሙ ሰዎች አሰቃያቸው” (ፈሊጣዊ አነጋገር እና ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Romans 11:11
አያያዥ መግለጫ፡
እስራኤል እንደ ሕዝብ እግዚአብሔርን እንደተዉት ተመሳሳይ ስሕተት ከመፈጸም እንዲጠነቀቁ ጳውሎስ አሕዛብን ያሳስባቸዋል።
የተደናቀፉት እስኪወድቁ ድረስ ነው?
ጳውሎስ አጽንዖት ለመጨመር ሲል ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት፡ “ኀጢአትን ስለ ሠሩ እግዚአብሔር ለዘላለም ትቷቸዋል? (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
እንዲህ አይደለም
“ይህ ሊሆን አይችልም!” ወይም “ያለጥርጥር አይደለም!” ይህ አገላለጽ ነገሩ እንዲህ እንደማይሆን አጥብቆ ይቃወማል። በአንተ ቋንቋ እዚህ ጋ ልትጠቀምበት የምትችለው ተመሳሳይ አገላለጽ ይኖርህ ይሆናል። ይህንን በሮሜ 9፡14 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
ቅናታቸውን ለማነሣሣት
x
Romans 11:13
ቅናታቸውን ለማነሣሣት
ይህንን ሐረግ በሮሜ 10፡19 ላይ እንዴት እንደተረጎምከው ተመልከት።
እነዚያን ሥጋዬ የሆኑትን
ይህ የሚያመለክተው “እንደ እኔው አይሁዳዊ የሆኑ” የሚለውን ነው።
ምናልባት ከእነርሱ አንዳንዶቹን እናድን ይሆናል
የሚያምኑትን እነዚያን እግዚአብሔር ያድናቸዋል። ኢ.ት፡ “ምናልባት አንዳንዶቹ ያምናሉ፣ እግዚአብሔርም ያድናቸዋል”
Romans 11:15
የእነርሱ መተው የዓለም ዕርቅ ከሆነ
“እግዚአብሔር እነርሱን ትቷቸው ከሆነ የቀረውን ዓለም ከራሱ ጋር ያስታርቃል”
የእነርሱ መተው
“የእነርሱ” የሚለው ተውላጠ ስም የማያምኑትን አይሁድ ያመለክታል።
ዓለም
እዚህ ጋ፣ “ዓለም” በዓለም የሚኖሩትን ሰዎች የሚያመለክት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “በዓለም ያሉ ሰዎች” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ተቀባይነት ማግኘታቸው ከሞት መነሣት ካልሆነ በስተቀር ምን ይሆናል?
እግዚአብሔር አይሁዶችን መቀበሉ አስደናቂ ነገር መሆኑን አጽንዖት ለመስጠት ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። አንተ በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ሲቀበላቸው ምን ይሆን ይሆን? ነገሩ ልክ ከሙታን መካከል የተነሡ ያህል ይሆናል!” ወይም “እግዚአብሔር እነርሱን በሚቀበልበት ጊዜ ከሞቱ በኋላ እንደገና በሕይወት የኖሩ ያህል ይሆናል!” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ሙታን
ይህ ቃል የሚናገረው በመቃብር ስላሉ፣ የሞቱ ሰዎች ሁሉ ነው።
በኩራቱ ከተጠበቀ ቡኮውም እንደዚያው ነው
ጳውሎስ የመጀመሪያው ሰብል ወይም “በኩራት” ሆነው እንደሚታጨዱ የሚናገረው የእስራኤላውያን አባቶች ስለሆኑት ስለ አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ነው። ደግሞም ከእነዚያ ሰዎች ስለተወለዱት እስራኤላውያን ሲናገር ከሰብሉ እንደተዘጋጀ “ቡኮ” አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ “አብርሃም ለእግዚአብሔር ከቀረበው የመጀመሪያ ሆኖ ከተቆጠረ፣ የተከተሉት አባቶቻችን ሁሉ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ንብረት መቆጠር አለባቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Romans 11:17
አንተ የበረሃ ወይራ ቅርንጫፍ
ተውላጠ ስም የሆነው “አንተ” እና “የበረሃ ወይራ ቅርንጫፍ” የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው በኢየሱስ ድነትን የተቀበሉትን አሕዛብ ነው።
ከቅርንጫፎቹ አንዳንዶቹ ቢሰበሩ
እዚህ ጋ፣ ጳውሎስ “የተሰበሩ ቅርንጫፎች” በማለት የሚያመለክተው ኢየሱስን የተቃወሙትን አይሁዶች ነው። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “አንዱ ጥቂት ቅርንጫፎችን ቢሰብራቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በመካከላቸው ብትጣበቅ
እዚህ ጋ ጳውሎስ “እንደተጣበቁ ቅርንጫፎች” አድርጎ የሚናገረው ስለ አሕዛብ ክርስቲያኖች ነው። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “በቀሩት ቅርንጫፎች መካከል እግዚአብሔር በዛፉ ላይ አጣብቆሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የበለጸገው የወይራው ዛፍ ሥር
እዚህ ጋ፣ “የበለጸገው ሥር” የእግዚአብሔርን ተስፋ የሚያመለክት ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በቅርንጫፎቹ አትመካ
እዚህ ጋ፣ “ቅርንጫፎቹ” የእስራኤልን ሕዝብ የሚወክል ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ከጣላቸው የአይሁድ ሕዝብ አንተ እንደምትሻል አትናገር” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ሥሩ አንተን ይሸከምሃል እንጂ አንተ ሥሩን አትሸከመውም
ጳውሎስ አሕዛብ አማኞች ቅርንጫፎች መሆናቸውን እንደገና ያመለክታል። እግዚአብሔር ለአይሁድ በገባው የኪዳን ተስፋ ምክንያት ብቻ ያድናቸዋል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Romans 11:19
ቅርንጫፎች ተሰብረዋል
እዚህ ጋ፣ “ቅርንጫፎች” የሚያመለክተው ኢየሱስን የተቃወሙትንና አሁን እግዚአብሔር የተዋቸውን አይሁዶችን ነው። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ቅርንጫፎቹን ሰበራቸው” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
እኔ ገብቼ እንድጣበቅ
ጳውሎስ ይህንን ሐረግ የሚጠቀመው እግዚአብሔር የተቀበላቸውን አሕዛብ አማኞች ለማመልከት ነው። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “እኔን አስገብቶ ሊያጣብቀኝ” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
የእነርሱ ... እነርሱ
ተውላጠ ስም የሆኑት “የእነርሱ” እና “እነርሱ” የሚያመለክቱት ያላመኑትን አይሁዶች ነው።
ነገር ግን በእምነትህ ምክንያት ጸንተህ ቆመሃል
ጳውሎስ የሚናገረው ማንም ሊያንቀሳቅሳቸው እስከማይቻለው ድረስ በታማኝነት ጸንተው ስለቆሙት አሕዛብ አማኞች ነው። ኢ.ት፡ “ነገር ግን በእምነታችሁ ምክንያት ቆማችኋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እግዚአብሔር በተፈጥሮአቸው ቅርንጫፍ ለሆኑት ካልራራላቸው ለአንተም አይራራልህም

እዚህ ጋ፣ “በተፈጥሮአቸው ቅርንጫፍ የሆኑት” የሚያመለክተው ኢየሱስን የተቃወሙትን አይሁዶች ነው። አ.ት፡ “እግዚአብሔር ከሥር ጀምሮ ላደገው፣ የተፈጥሮ ዛፍ ቅርንጫፍ ለሆነው፣ ላላመኑት አይሁድ ካልራራላቸው፣ እንግዲህ ባታምን ለአንተም እንደማይራራልህ ዕወቅ። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

## Romans 11:22

የእግዚአብሔርን የደግነት ሥራና ጭካኔውን

ምንም እንኳን እግዚአብሔር በታላቅ ደግነት ቢያደርግላቸውም ሊፈርድባቸውና ሊቀጣቸው እንደማያመነታ ጳውሎስ አሕዛብ አማኞችን ያስታውሳቸዋል።

ጭካኔው በወደቁት አይሁድ ላይ መጣ … የእግዚአብሔር ደግነት በአንተ ላይ ይመጣል

የነገር ስም የሆኑትን “ጭካኔ” እና “ደግነት” ለማስቀረት ይህንን እንደገና መጻፍ ይቻላል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በወደቁት አይሁድ ላይ ክፉን አድርጎባቸዋል … በአንተ ላይ ግን በደግነት ያደርጋል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

በወደቁት አይሁድ ላይ

የማይገባውን ማድረግ መውደቅ እንደሆነ ተነግሯል። አ.ት፡ “የማይገባውን ያደረጉ አይሁድ” ወይም “በክርስቶስ ለመታመን ፈቃደኛ ያልሆኑት አይሁድ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

በደግነቱ ውስጥ ብትቀጥል

የነገር ስም የሆነውን “ደግነት” ለማስቀረት ይህ እንደገና ሊጻፍ ይችላል። አ.ት፡ “ትክክል የሆነውን ማድረግህን ብትቀጥል እርሱም ለአንተ ደግ መሆኑን ይቀጥላል” (የነገር ስም የሚለውን ተመልከት)

ካልሆነ አንተም ደግሞ ትቆረጣለህ

እግዚአብሔር ከፈለገ “ሊቆርጠው” ስለሚችለው ቅርንጫፍ ለመናገር ጳውሎስ እንደገና በዘይቤአዊ አነጋገር ይጠቀማል። እዚህ ጋ “መቆረጥ” አንድን ሰው የመጣል ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “ካልሆነ እግዚአብሔር አንተን ይቆርጥሃል” ወይም “ካልሆነ እግዚአብሔር አንተን ይጥልሃል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

## Romans 11:23

እነርሱ ባለማመናቸው ካልቀጠሉ

“ባለማመናቸው ካልቀጠሉ” የሚለው ሐረግ ድርብ አሉታ ነው። ይህንን በአዎንታ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “አይሁድ በክርስቶስ ማመን ከጀመሩ” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ገብተው ይጣበቃሉ

አይሁድ በኢየሱስ ማመን ከጀመሩ እንደ ቅርንጫፎች ተመልሰው በዛፉ ላይ ሊጣበቁ እንደሚችሉ ጳውሎስ ይናገራል። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እግዚአብሔር መልሶ አስገብቶ ያጣብቃቸዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ማጣበቅ

ከአንድ ተክል ላይ ሕያው የሆነውን ቅርንጫፍ በሌላው ተክል ላይ በማስገባት አዲሱ ቅርንጫፍ በዚያ ተክል ላይ ማደጉን እንዲቀጥል ማድረግ የተለመደ ሂደት ነው።

በተፈጥሮህ የበረሃ የወይራ ዛፍ የሆንከው አንተ ተቆርጠህ ተፈጥሮህ ባልሆነው መልካም የወይራ ዛፍ ላይ እንድትጣበቅ ከተደረግህ የተፈጥሮ ቅርንጫፎች የሆኑት እነዚህ አይሁዶች ወደ ራሳቸው የወይራ ዛፍ እንዴት አብልጠው አይጣበቁም?

ጳውሎስ የአሕዛብ አማኞችና አይሁድ የዛፍ ቅርንጫፎች እንደሆኑ አድርጎ መናገሩን ይቀጥላል። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በተፈጥሮህ የበረሃ ወይራ ዛፍ የሆንከውን ቆርጦ ለተፈጥሮ ተቃራኒ በሆነው መልካም የወይራ ዛፍ ላይ ካጣበቀህ የተፈጥሮ ቅርንጫፎች የሆኑትን እነዚህን አይሁዶች በገዛ የወይራ ዛፋቸው ላይ እንዴት አብዝቶ
አያጣብቃቸውም?” (ዘይቤአዊ አነጋገር እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ቅርንጫፎች

ጳውሎስ፣ አይሁድና አሕዛብ ቅርንጫፎች እንደሆኑ በመቁጠር ይናገራል። “የተፈጥሮ ቅርንጫፎች” የሚወክሉት አይሁዶችን ሲሆን “የተጣበቁት ቅርንጫፎች” የሚወክሉት ደግሞ አሕዛብ አማኞችን ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

እነርሱ … እነርሱን

“እነርሱ” ወይም “እነርሱን” የሚሉት አገባቦች በሙሉ የሚያመለክቱት አይሁዶችን ነው።

## Romans 11:25

ሳታውቁ እንድትቀሩ አልፈልግም

እዚህ ጋ ጳውሎስ ድርብ አሉታን ይጠቀማል። ይህንን በአዎንታ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “እንድትገነዘቡ በጣም እፈልጋለሁ” (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)

ወንድሞች

እዚህ ጋ “ወንድሞች” ማለት ወንዶችንና ሴቶችን ጨምሮ እንደ እርሱ ክርስቲያን የሆኑትን ነው።

እኔ

ተውላጠ ስም የሆነው “እኔ” የሚያመለክተው ጳውሎስን ነው።

አንተ … አንተ … የአንተ

ተውላጠ ስም የሆኑት “አንተ” እና “የአንተ” የሚያመለክቱት አሕዛብ አማኞችን ነው።

በራሳችሁ አሳብ ጥበበኞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ

አሕዛብ አማኞች ካላመኑት አይሁዶች ይልቅ ጥበበኞች እንደሆኑ እንዲያስቡ ጳውሎስ አይፈልግም። አ.ት፡ “ከእነርሱ ይልቅ ጥበበኞች እንደሆናችሁ እንዳታስቡ”

በእስራኤል ከፊል ድንዳኔ ሆነባቸው

ጳውሎስ ስለ “ድንዳኔ” ወይም እልኸኝነት በሰውነት ውስጥ እንዳለ ጠጣር ብልት አድርጎ ይናገራል። አንዳንድ አይሁዶች በኢየሱስ አማካይነት ድነትን ለመቀበል እምቢ ብለዋል። አ.ት፡ “ብዙ እስራኤላውያን እልኸኞች ሆነው ቀጥለዋል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

የአሕዛብ ሙሉነት እስኪመጣ ድረስ

“እስኪመጣ ድረስ” የሚለው ቃል እግዚአብሔር አሕዛብን ወደ ቤተክርስቲያን ማምጣቱን ከጨረሰ በኋላ ጥቂት አይሁዶች እንደሚያምኑ ያመለክታል።

## Romans 11:26

አያያዥ መግለጫ፡

ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ክብር ከእስራኤል ነጻ አውጪ እንደሚመጣ ይናገራል።

እንዲሁም እስራኤል ሁሉ ይድናሉ

ይህ በአድራጊ ድምፅ ሊተረጎም ይችላል። አ.ት፡ “እንዲሁም እግዚአብሔር እስራኤልን ሁሉ ያድናል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ልክ እንደተጻፈው

ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። አ.ት፡ “ልክ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ዘገቡት” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

ከጽዮን

እዚህ ጋ “ጽዮን” እግዚአብሔር ለሚኖርበት ስፍራ በፈሊጣዊ አነጋገር ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “እግዚአብሔር በአይሁዶች መካከል ከሚገኝበት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ነጻ አውጪው

“ሕዝቡን ወደ አስተማማኝ ስፍራ የሚያመጣቸው”

ኃጢአተኝነታቸውን ያስወግዳል

ጳውሎስ ኃጢአተኝነትን አንድ ሰው እንደሚያስወግደው ቁስ፣ ምናልባትም እንደሚገፈፍ ልብስ አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ከያዕቆብ

እዚህ ጋ “ያዕቆብ” በፈሊጣዊ አነጋገር እስራኤልን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል። አ.ት፡ “ከእስራኤል ሕዝብ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

ኃጢአታቸውን አስወግድላቸዋለሁ

እዚህ ጋ ጳውሎስ ኃጢአትን አንድ ሰው ሊያስወግደው እንደሚችለው ቁስ አድርጎ ይናገርለታል። አ.ት፡ “የኃጢአታቸውን ሸክም አስወግዳለሁ” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

## Romans 11:28

ስለ የምሥራቹ ከሆነ

ጳውሎስ የምሥራቹን የሚጠቅስበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። አ.ት፡ “አይሁዶች የምሥራቹን ቃል ስለ ተቃወሙ”

በእናንተ ምክንያት ጠላቶች ናቸው

የማን ጠላቶች እንደሆኑና ይህም እንዴት በአሕዛብ ምክንያት ሊሆን እንደቻለ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። አ.ት፡ “ስለ እናንተ የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው” ወይም “እናንተ ደግሞ የምሥራቹን እንድትሰሙ እግዚአብሔር እንደ ጠላት ቆጠራቸው”

ስለ ምርጫ ከሆነ

ጳውሎስ ስለ ምርጫ የሚያነሣበትን ምክንያት ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር አይሁዶችን መርጦአቸዋልና” ወይም “ምክንያቱም እግዚአብሔር አይሁዶችን ስለ መረጣቸው ነው”
በአባቶቻቸው ምክንያት የተወደዱ ናቸው
አይሁዶችን ማን እንደሚወዳቸውና ጳውሎስ ለምን አባቶቻቸውን እንደሚጠቅስ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ደግሞም ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ሊያደርግላቸው ተስፋ በመስጠቱ ምክንያት አሁንም ይወዳቸዋል”
የእግዚአብሔር ስጦታና ጥሪው የማይለወጥ ነውና
እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊሰጣቸው ቃል ስለገባላቸው መንፈሳዊና ቁሳዊ በረከቶች ጳውሎስ እንደ ስጦታዎች በመቁጠር ይናገራል። የእግዚአብሔር ጥሪ አይሁዶች የእርሱ ሕዝብ እንዲሆኑ እግዚአብሔር የመጥራቱን ሐቅ ያመለክታል። ኢ.ት፡ “ሊሰጣቸው ቃል ስለገባላቸው ነገርና የእርሱ ሕዝብ እንዲሆኑ እንዴት እንደጠራቸው እግዚአብሔር በፍጹም አሳቡን አልለወጠም”
Romans 11:30
ቀድሞ የማትታዘዙ ነበራችሁ
“ባለፈው ጊዜ አልታዘዛችሁም ነበር”
በእነርሱ አለመታዘዝ ምክንያት እናንተ ምህረትን ተቀበላችሁ
እዚህ ጋ ምህረት ማለት የማይገቡ የእግዚአብሔር በረከቶች ማለት ነው። ኢ.ት፡ “አይሁዶች ኢየሱስን ስለ ተቃወሙት እናንተ የማይገባችሁን በረከቶች ተቀበላችሁ”
እናንተ
x
Romans 11:33
ኦ! የእግዚአብሔር ጥበብና ዕውቀት ባለጠግነት እንዴት ጥልቅ ነው!
እዚህ ጋ የ “ጥበብ” እና “ዕውቀት” መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። ኢ.ት፡ “ከእግዚአብሔር ጥበብና ዕውቀት የሚገኙት ብዙ ጥቅሞች እንዴት የሚያስደንቁ ናቸው!”
ፍርዶቹ እንዴት የማይመረመሩ ናቸው፣ መንገዶቹም ከመታወቅ በላይ ናቸው
“እርሱ የወሰናቸውን ነገሮችና በእኛ ላይ የሚፈጽምባቸውን መንገዶቹን ለመረዳት በፍጹም አንችልም”
የጌታን አሳብ ያወቀ ወይም አማካሪው የሆነ ማነው?
እንደ ጌታ ጥበበኛ የሆነ ማንም እንደሌለ አጽንዖት ለመስጠት ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ይህንን እንደ መግለጫ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “የጌታን አሳብ ያወቀ ማንም የለም፣ አማካሪው የሆነም ማንም የለም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
የጌታን አሳብ
እዚህ ጋ “አሳብ” ነገሮችን ማወቅ ወይም ስለ ነገሮች ማሰብ የሚለውን ገላጭ ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ “ጌታ የሚያውቀውን ሁሉ” ወይም “ጌታ ስለሚያስብለት ጉዳይ” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Romans 11:35
ወይስ እግዚአብሔር ይመልስለት ዘንድ አስቀድሞ ለእርሱ አንዳች የሰጠው አለ?
ጳውሎስ ለማብራሪያው አጽንዖት ለመስጠት ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት፡ “በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ሳይቀበል ለእግዚአብሔር አንዳች ነገር የሰጠ ማንም የለም” (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)* ከእርሱ … በእርሱ … ለእርሱ - እዚህ ጋ፣ “እርሱ” የሚሉት አገባቦች ሁሉ የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን ነው።
ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን
ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያከብሩት ጳውሎስ ያለውን ምኞት ይህ ይገልጻል። በትርጉምህ ይህንን ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ሰዎች ሁሉ እርሱን ለዘላለም ያክብሩት”

Chapter 12
Romans 12:1
አያያዥ መግለጫ፡
ጳውሎስ የአማኝ ሕይወት ምን መሆን እንዳለበትና እንዴት ማገልገል እንዳለበት ይናገራል።
ወንድሞች ሆይ፣ ስለዚህ በእግዚአብሔር ምህረት እለምናችኋለሁ
እዚህ ጋ፣ “ወንድሞች” የሚያመለክተው ወንዶችንና ሴቶች አማኞችን ነው። ኢ.ት፡ “አማኞች ሆይ፣ እግዚአብሔር በሰጣችሁ ታላቅ ምህረት ምክንያት አጥብቄ እለምናችኋለሁ”
ሰውነታችሁን ሕያው መስዋዕት አድርጋችሁ እንድታቀርቡ
ጳውሎስ እዚህ ጋ “ሰውነት” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ሙሉውን ሰው ለማመልከት ነው። ጳውሎስ በክርስቶስ ሆኖ እግዚአብሔርን በፍጹምነት የሚታዘዘውን አማኝ አይሁዶች አርደው ለእግዚአብሔር ከሚሰዉት እንስሳ ጋር እያነጻጸረ ነው። ኢ.ት፡ “በቤተ መቅደሱ መሰዊያ ላይ ታርዳችሁ በምትሰዉበት መልኩ ሕያው ሆናችሁ ሳላችሁ ራሳችሁን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እንድታቀርቡ”
እግዚአብሔር የሚቀበለው፣ ቅዱስ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ለእግዚአብሔር ብቻ የምታቀርቡትና እርሱን ደስ የሚያሰኘው መስዋዕት” ወይም 2) “ንጹህ ሥነ ምግባር ስለሆነ እግዚአብሔር የሚቀበለው” የሚሉት ናቸው።
ይህ ምክንያታዊ አገልግሎታችሁ ነው
“ይህ እግዚአብሔርን የማምለክ ትክክለኛው መንገድ ነው”
ይህንን ዓለም አትምሰሉ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ዓለም እንደሚያደርገው አታድርጉ” ወይም 2) “ዓለም በሚያደርገው መልኩ አታስቡ” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Romans 12:3
ለእኔ በተሰጠኝ ጸጋ ምክንያት
እዚህ ጋ “ጸጋ” የሚያመለክተው ሐዋርያና የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲሆን እግዚአብሔር ጳውሎስን ስለመምረጡ ነው። ይህንን በትርጉምህ ግልጽ ልታደርገው ትችላለህ። ደግሞም ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “ምክንያቱም ሐዋርያ እንድሆን እግዚአብሔር በነጻ መርጦኛል”
በመካከላችሁ ያሉ እያንዳንዳቸው ማሰብ ከሚገባቸው በላይ ስለ ራሳቸው እንዳያስቡ
“ከመካከላችሁ ማናቸውም ቢሆኑ ከሌሎች ሰዎች እንደሚሻሉ እንዳያስቡ”
ይልቁንም በጥበብ እንዲያስቡ
“ነገር ግን ስለ ራሳችሁ በምታስቡት ጥበበኞች እንድትሆኑ”
እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ በሰጠው የእምነት መጠን
እዚህ ጋ ጳውሎስ የሚያመለክተው፣ በእግዚአብሔር ላይ ካላቸው እምነት ጋር ተያይዞ አማኞች ስለሚኖራቸው የተለያዩ ችሎታዎች ነው። ኢ.ት፡ “በእርሱ ላይ ባላችሁ እምነት ምክንያት እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችሁ የተለያዩ ችሎታዎችን ስለሰጣችሁ”
Romans 12:4
ስለ
ጳውሎስ ይህንን ቃል የሚጠቀመው አንዳንድ ክርስቲያኖች ከሌላው እንደሚሻሉ ለምን ማሰብ እንደሌለባቸው የሚሰጠውን ማብራሪያ ለማሳየት ነው።
በአንድ አካል ላይ ብዙ ብልቶች አሉን
ጳውሎስ የሰው አካል ልዩ ልዩ ክፍሎች እንደሆኑ አድርጎ በክርስቶስ የሆኑትን አማኞች ሁሉ ያመለክታል። ይህንን የሚያደርገው አማኞች ክርስቶስን በተለያዩ መንገዶች የሚያገለግሉ ቢሆኑም እያንዳንዱ ሰው የክርስቶስ እንደሆነና ጠቃሚ በሆነ መንገድ እንደሚያገለግል ለማስረዳት ነው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Romans 12:6
እንደተሰጠን ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን
ጳውሎስ አማኞች ያሏቸው ልዩ ልዩ ችሎታዎች ከእግዚአብሔር በነጻ የተሰጡ ስጦታዎች መሆናቸውን ይናገራል። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ “እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ነገሮችን ለእርሱ እንድናደርግለት ለእያንዳንዳችን ችሎታዎችን በነጻ ሰጥቶናል” (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
እንደተሰጠው የእምነት መጠን ያድርግ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እግዚአብሔር ከሰጠን የእምነት መጠን ያላለፈ ትንቢትን ይናገር” ወይም 2) “ከእምነታችን አስተምህሮ ጋር የሚስማማ ትንቢት ይናገር” የሚሉት ናቸው።
የአንዱ ስጦታ መስጠት ከሆነ
እዚህ ጋ “መስጠት” የሚያመለክተው ገንዘብንና ሌሎችንም ነገሮች ለሰዎች መስጠትን ነው። ይህንን ፍቺ በትርጉምህ ውስጥ ግልጽ ማድረግ ትችላለህ። ኢ.ት፡ “አንድ ሰው ገንዘብን ወይም ሌሎች መገልገያዎችን ለተቸገሩ ሰዎች የመስጠት

ስጦታ ከተሰጠው”
Romans 12:9
ፍቅር ያለ ግብዝነት ይሁን
ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት: “ሰዎችን በቅንነትና በእውነተኝነት መውደድ ይኖርባችኋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ፍቅር
እዚህ ጋ ጳውሎስ የሚጠቀምበት ቃል የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር በሚመጣውና ራስን በማይጠቅምበት ጊዜም እንኳን ለሌሎች በሚደረግ መልካም ነገር ላይ የሚያተኩረውን የፍቅር ዓይነት ነው።
የወንድማማች ፍቅር ቢሆን አጥብቃችሁ ተዋደዱ
እዚህ ጋ ጳውሎስ አማኞች ምን ዓይነት ሰዎች መሆን እንዳለባቸው ለመንገር እያንዳንዳቸው “. . . ሁኑ” የሚል ቅርጽ ያላቸው ዘጠኝ ዓይነቶችን መዘርዘር ይጀምራል። አንዳንዶቹን ዝርዝሮች “. . . አድርጉ” ብለህ መተርጎም ይኖርብህ ይሆናል። ዝርዝሩ እስከ ሮሜ 12፡13 ይቀጥላል።
የወንድማማች ፍቅር ቢሆን
“እንደ እናንተው አማኞች የሆኑትን መውደድን አስመልክቶ”
ፍቅር
ይህ የወንድማማች ፍቅር ወይም የጓደኛ ወይም የቤተሰብ ፍቅር የሚል ትርጉም ያለው ሌላ ቃል ነው። ይህ በጓደኛሞች ወይም በዘመዳሞች መካከል ያለ ተፈጥሮአዊና ሰብአዊ ፍቅር ነው።
አጥብቃችሁ ተዋደዱ
ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት: “ፍቅርን አሳዩ” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
አክብሮትን በሚመለከት እርስ በእርሳችሁ ተከባበሩ
“እርስ በእርሳችሁ ተከባበሩ፣ አክብሮትንም አሳዩ” ወይም “አማኝ ባልንጀሮቻችሁን በማክበር ክብርን ስጧቸው”
Romans 12:11
ትጋትን በሚመለከት አታወላውሉ። መንፈስን በሚመለከት የምትጓጉ ሁኑ። ጌታን በሚመለከት አገልግሉት።
“በሥራችሁ ሰነፎች አትሁኑ፣ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለመከተልና ጌታን ለማገልገል የምትጓጉ ሁኑ”
በመከራ ታገሱ
“መከራ በሚደርስባችሁ ጊዜ ሁሉ በትዕግስት ቆዩ”
ለቅዱሳን የሚያስፈልጋቸውን አካፍሏቸው
ይህ በሮሜ 12፡9 የጀመረው ዝርዝር የመጨረሻው ጉዳይ ነው። “እንደእናንተው ክርስቲያን የሆኑ በሚቸገሩበት ጊዜ በሚያስፈልጋቸው ነገር እርዷቸው”
እንግዳ ተቀባይነታችሁን የምታሳዩባቸውን አጋጣሚዎች ፈልጉ
“ማረፊያ በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ በቤታችሁ ተቀበሏቸው”
Romans 12:14
እርስ በእርስ የምትስማሙ ሁኑ
ይህ በአንድነት መኖር የሚል ትርጉም ያለው የአነጋገር ዘይቤ ነው። ኢ.ት: “እርስ በእርሳችሁ ተስማሙ” ወይም “እርስ በእርሳችሁ በአንድነት ኑሩ” (የአነጋገር ዘይቤ የሚለውን ተመልከት)
በትዕቢት መንገድ አታስቡ
“ከሌሎች በበለጠ የምታስፈልጉ እንደሆናችሁ አታስቡ”
ዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩትን ተቀበሏቸው
“የሚጠቅሙ የማይመስሉ ሰዎችን ተቀበሏቸው”
በራሳችሁ አሳብ ጥበበኞች አትሁኑ
x
Romans 12:17
ለማንም በክፉ ፈንታ ክፉ አትመልሱ
“ክፉ ባደረገባችሁ ሰው ላይ ክፉ አታድርጉ”
በሰዎች ሁሉ ፊት መልካም ነገሮችን አድርጉ
“ሁሉም መልካም እንደሆኑ የሚቆጥሯቸውን ነገሮች አድርጉ”
እናንተን በሚመለከት ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ
“ከሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር የምትችለውን ሁሉ አድርግ”
Romans 12:19
ለእግዚአብሔር ቁጣ ዕድል ስጠው
ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት: “እግዚአብሔር እንዲቀጣቸው ፍቀድለት” (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ተጽፏልና
ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት: “አንድ ሰው ጽፎታልና” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
በቀል የእኔ ነው፤ እኔ እመልሳለሁ
እነዚህ ሁለቱም ሐረጎች መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ሲሆን እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚበቀል አጽንዖት ይሰጣሉ። ኢ.ት: “በርግጥ እኔ እበቀላችኋለሁ”
ጠላትህን ... አብላው ... የሚጠጣውን ስጠው ... ይህንን ብታደርግ ... ትከምራለህ፣ ክፉን አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ
“አንተ” እና “የአንተ” የሚሉ አገባቦች ሁሉ ለአንድ ሰው እንደሚነገሩ ሆነው ቀርበዋል።
ነገር ግን ጠላትህ ከተራበ ... በራሱ ላይ
ጳውሎስ በ12፡20 ላይ ከሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይጠቅሳል። ኢ.ት: “ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ፣ ‘ጠላትህ ከተራበ ... በራሱ ላይ ...’ ይላል”
አብላው
“ጥቂት ምግብ ስጠው”
በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህ
ጳውሎስ አንድ ሰው በራሳቸው ላይ የእሳት ፍም የሚያፈስባቸው በሚመስልበት ሁኔታ ጠላቶች ስለሚቀበሏቸው በረከቶች ይናገራል። ሊሆኑ የሚችሉት ትርጉሞች፣ 1) “የጎዳችሁ ሰው የማይገባ ነገር እንዳደረገባችሁ እጅግ ተሰምቶት እንዲጸጸት አድርጉት” ወይም 2) “እግዚአብሔር በጠላትህ ላይ የከፋ ፍርድ የሚሰጥበትን ምክንያት እንዲያገኝ አድርገው” የሚሉት ናቸው። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ክፉን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ
ጳውሎስ “ክፉ”ን እንደ ሰው በመቁጠር ይገልጸዋል። ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉም ትችላለህ። ኢ.ት: “ክፉዎች እንዲያሸንፉህ አትፍቀድላቸው፣ ነገር ግን መልካም የሆነውን በማድረግ ክፉ የሆኑትን አሸንፋቸው” (ሰውኛ እና አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)

---

Chapter 13
Romans 13:1
አያያዥ መግለጫ፡
አማኞች በገዢዎቻቸው ሥር እንዴት መኖር እንዳለባቸው ጳውሎስ ይነግራቸዋል።
ነፍስ ሁሉ ለ . . . ታዛዥ ትሁን
እዚህ ጋ “ነፍስ” ሙሉውን ሰው በከፊል የሚገልጽ ነው። “ክርስቲያን ሁሉ መታዘዝ አለበት” ወይም “ሁሉም መታዘዝ አለበት”
ከፍተኛ ባለሥልጣናት
“የመንግሥት ኃላፊዎች”
ስለ
ምክንያቱም
ከእግዚአብሔር ካልመጣ በስተቀር ሥልጣን የለም
“ሥልጣን ሁሉ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው”
አሁን ያሉት ባለሥልጣናት በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው
ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት: “በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች በዚያ ያሉት እግዚአብሔር እዚያ ላይ ስላስቀመጣቸው ነው” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
ያ ሥልጣን
“ያ የመንግሥት ሥልጣን” ወይም “እግዚአብሔር በኃላፊነት ላይ ያስቀመጠው ሰው ሥልጣን”
ይህንን የሚቃወሙ በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ
ይህንን በአድራጊ ድምፅ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት: “የመንግሥትን ሥልጣን በሚቃወሙት ላይ እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል” (አድራጊ ወይም ተደራጊ ድምፅ የሚለውን ተመልከት)
Romans 13:3
ስለ
ጳውሎስ የሮሜ 13፡2 ማብራሪያውን ለመጀመርና መንግሥት በአንድ ሰው ላይ

ቢፈርድበት ምን እንደሚከተለው ለመንገር ይህንን ቃል ይጠቀማል።
ገዢዎች አስፈሪዎች አይደሉም
መልካም ሰዎችን ገዢዎች እንዲፈሩ አያደርጓቸውም።
ለመልካም ሥራ … ለክፉ ሥራ
ሰዎች በ"መልካም ሥራቸው" ወይም በ"ክፉ" ሥራቸው ተለይተዋል"።
በሥልጣን ላይ ያለን ሰው የማትፈራው መሆን ትፈልጋለህ?
ሰዎች ገዢዎችን ላለመፍራት ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያስቡ ለማድረግ ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ ይጠይቃል። ኢ.ት፡ "ገዢዎችን እንዴት መፍራት እንደማይኖርባችሁ እንድነግራችሁ ፍቀዱልኝ"። (ምላሽ የማይፈልግ ጥያቄ የሚለውን ተመልከት)
አድናቆቱን ትቀበላለህ
መንግሥት መልካም የሆነውን ስለሚያደርጉ ሰዎች መልካም ነገር ይናገራል።
እርሱ ያለምክንያት ሰይፍ አይታጠቅም
ይህንን በአዎንታ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ "እርሱ ሰይፍ የሚታጠቀው በጣም ጥሩ በሆነ ምክንያት ነው" ወይም "እርሱ ሰዎችን የሚቀጣበት መብት አለው፣ ስለዚህ ሰዎችን ይቀጣቸዋል" (ምጸት የሚለውን ተመልከት)
ሰይፍ መታጠቅ
ሮማውያን ገዢዎች የሥልጣናቸው ምልክት የሚሆን አጭር ሰይፍ ይታጠቁ ነበር። (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
የቁጣ ተበቃይ
እዚህ ጋ "ቁጣ" የሚወክለው ሰዎች ክፉ ነገር በሚያደርጉበት ጊዜ የሚቀበሉትን ቅጣት ነው። ኢ.ት፡ "በክፉ ላይ የመንግሥትን ቁጣ ለመግለጽ ሰዎችን የሚቀጣ ሰው" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ስለ ሕሊና ደግሞ እንጂ በቁጣው ምክንያት ብቻ አይደለም
"መንግሥት እንዳይቀጣህ ብለህ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ ሕሊና እንዲኖርህ ደግሞ ነው"
Romans 13:6
በዚህ ምክንያት
"መንግሥት ክፉ አድራጊዎችን ስለሚቀጣ"
እናንተ … ለእያንዳንዱ ስጡ
እዚህ ጋ ጳውሎስ የሚናገረው ለአማኞች ነው።
ለባለሥልጣናት
"ለባለሥልጣናት ግብር መክፈል የሚኖርባችሁ ለዚህ ነው"
የሚተጉ
"የሚያስተዳድሩ" ወይም "የሚሠሩ"
ግብር ለሚገባው ግብርን፣ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን፤ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባው ክብርን።
"ስጡ" የሚለውን ቃል ቀደም ሲል ከነበረው ዐረፍተ ነገር መገንዘብ ይቻላል። ኢ.ት፡ "ግብር ለሚገባው ግብርን፣ ቀረጥ ለሚገባውም ቀረጥን ስጡ። መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባውም ክብርን ስጡ"
መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባው ክብርን
እዚህ ጋ፣ መፈራትንና ክብርን መስጠት መፈራትና መከበር የሚገባቸውን እነርሱን የመፍራትና የማክበር ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። ኢ.ት፡ "መፈራት የሚገባቸውን እነርሱን ፍሩ፣ መከበር የሚገባቸውን እነርሱን ደግሞ አክብሩ" ወይም "ልታከብሯቸው የሚገባችሁን አክብሯቸው፣ አክብሮት ልታሳዩአቸው የሚገባችሁንም አክብሮትን አሳዩአቸው" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ቀረጥ
ይህ የቀረጥ ዓይነት ነው።
Romans 13:8
አያያዥ መግለጫ፡
ባልንጀሮቻቸውን በሚመለከት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ጳውሎስ ለአማኞች ይነግራቸዋል።
እርስ በእርስ ከመዋደድ በቀር ምንም ዓይነት ዕዳ አይኑርባችሁ
ይህ ድርብ አሉታ ነው። ይህንን በአዎንታ ልትተረጉመው ትችላለህ። ኢ.ት፡ "በእያንዳንዱ ላይ ያለባችሁን ዕዳ ክፈሉ፣ እርስ በእርሳችሁም ተዋደዱ" (ድርብ አሉታ የሚለውን ተመልከት)
ባለዕዳ
ይህ ግሥ ብዙ ቁጥር ሲሆን በሮም የሚኖሩትን ክርስቲያኖች ሁሉ የሚመለከት ነው።
እርስ በእርስ ከመዋደድ በቀር
ከላይ በተጠቀሰው ማስታወሻ እንደተመለከተው ሊኖርባቸው የሚችለው ዕዳ ይህ ነው።
ፍቅር
ይህ የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር በሚመጣውና ራስን በማይጠቅምበት ጊዜም እንኳን ለሌሎች በሚደረግ መልካም ነገር ላይ የሚያተኩረውን የፍቅር ዓይነት ነው።
መመኘት
ለሌላው ሰው ያለው ነገር የራስ እንዲሆን ወይም እንዲኖር መፈለግ።
ፍቅር የአንድን ሰው ባልንጀራ አይጎዳም
ይህ ሐረግ ፍቅርን ለሌሎች ሰዎች ደግ እንደሚሆን ሰው አድርጎ ይገልጸዋል። ኢ.ት፡ "ባልንጀሮቻቸውን የሚወዱ ሰዎች አይጎዷቸውም" (ሰውኛ የሚለውን ተመልከት)
Romans 13:11
ከእንቅልፍ የምትነቁበት ሰዓት አሁን መሆኑን ጊዜውን ታውቃላችሁ
ከእንቅልፍ መንቃት በሚያስፈልጋቸው መልኩ የሮም አማኞች የባህርይ ለውጥ ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ጳውሎስ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
Romans 13:13
እናድርግ
ጳውሎስ አንባቢዎቹንና ሌሎች አማኞችን ከራሱ ጋር ያካትታል። (አካታች "እኛ" የሚለውን ተመልከት)
በቀን እንደሚሆን በአግባብ እንመላለስ
ጳውሎስ እንደ እውነተኞች አማኞች መኖርን ለማስረዳት አንድ ሰው በቀን እንደሚመላለስ አድርጎ ይናገራል። ኢ.ት፡ "ሁሉ ሊያየን እንደሚችል እያወቅን በግልጽነት እንመላለስ" (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
በዝሙት ወይም በማይቆጣጠሩት የፍትወት ምኞት
እነዚህ አሳቦች መሠረታዊ ትርጉማቸው አንድ ነው። በትርጉምህ ውስጥ ልታጣምራቸው ትችላለህ። ኢ.ት፡ "አስጸያፊ የዝሙት ተግባር"
ሁከት
ይህ በሌሎች ላይ ማሴርንና ከሌሎች ሰዎች ጋር መከራከርን ያመለክታል።
ቅናት
ይህ በሌላው ሰው ስኬት ወይም ሌሎች በሚገጥሟቸው ዕድሎች የሚሰማውን አሉታዊ ስሜት ያመለክታል።
ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት
ጳውሎስ የክርስቶስን የሥነ ምግባር ባህርይ መቀበልን ሰዎች ሊያዩት እንደሚችሉት ውጫዊ ልብሳችን አድርጎ ይናገራል። (ዘይቤአዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)
ልበሱት
የአንተ ቋንቋ ትዕዛዝን በብዙ ቁጥር የሚገልጽበት አግባብ ካለ እዚህ ጋ ተጠቀምበት።
ለሥጋ አትመቻቹለት
እዚህ ጋ "ሥጋ" የሚያመለክተው እግዚአብሔርን የሚቃወመውን የሰዎችን ራስ - መር ተፈጥሮ ነው። ይህ የሰው ልጆች ኃጢአታዊ ተፈጥሮ ነው። ኢ.ት፡ "ክፉ ነገሮችን እንዲያደርግ ለአሮጌው ክፉ ልብ አንዳችም ዕድል ከቶ አትስጡት" (ፈሊጣዊ አነጋገር የሚለውን ተመልከት)

Chapter 14
Romans 14:1
አያያዥ ሀሳብ
ጳውሎስ አማኞች በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ እንደሆኑ እንዲያስታውሱ ያበረታታቸዋል።
በእምነት ደካማ
ይህ የሚወክለው አንዳንድ ነገሮችን በመብላታቸው የወቀሳ ስሜት የሚሰማቸውን ሰዎች ነው።
በክርክራቸው ሳትፈርዱባቸው
"እናም በአስተሳሰባቸው ምክንያት አትክሰሷቸው"
አንድ ሰው ማንኛውንም ነገር ለመብላት እምነት አለው
እዚህ ላይ "እምነት" የሚለው ቃል አንድ ሰው እግዚአብሔር አድርግ ብሎኛል ብሎ የሚያምነውን ነገር ማድረግን ያመለክታል።


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ሌላው ደካማ የሆነው ደግሞ አትክልትን ብቻ ይበላል

ይህ እርሱ ስጋን እንዲበላ እግዚአብሔር እንደማይፈልግ የሚያምንን ሰው ይገልጻል።

Romans 14:3

እናንተ የሌላ ሰው አገልጋይ ላይ የምትፈርዱ፣ እናንተ ማን ናችሁ?

ጳውሎስ ይህን ጥያቄ በሌሎች ላይ የሚፈርዱ ሰዎችን ለመገሰጽ ይጠቀምበታል። ይህ በአረፍተ ሃሳብ መልክ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እናንተ እግዚአብሔር አይደላችሁም፣ እናም የእርሱ አገልጋዮች ላይ ለመፍረድ አልተፈቀደላችሁም” (መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ)

አንተ፣ አንተ

ይህ “አንተ” የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር የተገለጸ ነው። (የሁለተኛ መደብ ቅርጾች የሚለውን ይመልከቱ)

እርሱ የሚቆመውም የሚወድቀውም በገዛ ራሱ ጌታ ፊት ነው

እዚህ ላይ ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር አገልጋዮች እንዳሉት ጌታ አድርጎ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አገልጋዩን ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል መወሰን የሚችለው ጌታው ብቻ ነው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ነገር ግን እንዲቆም ይደረጋል፣ ምክንያቱም ጌታ እርሱ እንዲቆም ያደርገዋልና

ጳውሎስ እዚህ ላይ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው አገልጋይ ከመውደቅ ይልቅ “እንዲቆም ይደረጋል” ሲል ይናገራል። ይህንን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ጌታ ግን ይቀበለዋል ምክንያቱም እርሱ አገልጋዮች ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይችላል” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 14:5

አንድ ሰው አንድን ቀን ከሌላው ቀን አብልጦ ዋጋ ይሰጣል። ሌላው ግን ለሁሉም ቀኖች እኩል ዋጋ ይሰጣል

“አንድ ሰው አንድ ቀን ከሌላው ቀን የበለጠ እንደሆነ ያስባል፣ ሌላው ግን ሁሉም ቀናት እኩል እንደሆኑ ያስባል።

እያንዳንዱ ሰው በራሱ አእምሮ የሚያስበውን ይመን

የዚህን ትርጉም በግልጽ መናገር ይቻላል። ይህንን በገቢር/አድራጊ ቅርጽም መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እያንዳንዱ ሰው የሚያደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ለማክበር እንደሆነ እርግጠኛ ይሁን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ቀንን የሚያከብር፣ ለጌታ ብሎ ያከብራል

እዚህ ላይ “ማክበር” የሚለው ማምለክን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በአንድ በተወሰነ ቀን የሚያመልክ ሰው ይህን የሚያደርገው እግዚአብሔርን ለማክበር ነው” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

የሚበላ

“ሁሉንም” የሚለው ቃል ሮሜ 14:03 ላይ ባለው አገባብ መረዳት ይቻላል። እዚህ ላይ ተደግሞ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉንም አይነት ምግብ የሚበላ ሰው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ለጌታ ብሎ ይበላል

“እግዚአብሔርን ለማክበር ይበላል” ወይም “በዚያ መንገድ የሚበላው እግዚአብሔርን ለማክበር ነው”

የማይበላ

“ሁሉንም” የሚለው ቃል በሮሜ ሮሜ 14:03 ላይ ባለው አገባብ መሰረት መረዳት ይቻላል። እዚህ ላይ ተደግሞ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉንም የማይበላ” ወይም “አንዳንድ የምግብ ዓይነቶችን የማይበላ ሰው” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)

ለጌታ ብሎ ከመብላት ይቆጠባል

“እነዚያን የምግብ ዓይነቶች ጌታን ለማክበር ሲል ከመብላት ይቆጠባል” ወይም “በዚያ መንገድ የሚበላው ጌታን ለማክበር ነው”

Romans 14:7

ከእኛ ውስጥ ማንም ለራሱ የሚኖር የለም

እዚህ ላይ “ለራሱ የሚኖር” ማለት ራሱን ለማስደሰት ብቻ የሚኖር ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ማናችንም ራሳችንን ለማስደሰት ብቻ ብለን መኖር የለብንም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለራሱ የሚሞት ማንም የለም

ይህ ማለት የአንድ ሰው ሞት ሌሎች ሰዎችንም ይነካል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ማናችንም እኛ ብቻ ስንሞት እኛን ብቻ እንደሚጎዳ ማሰብ የለብንም። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እኛ ... እኛ

ጳውሎስ አንባቢዎቹንም በዚህ ንግግር ውስጥ እያካተተ ነው። (አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 14:10

አንተ በወንድምህ ላይ ለምን ትፈርዳለህ? አንተስ ወንድምህን ለምን ትንቃለህ?

እነዚህን ጥያቄዎች በመጠቀም ጳውሎስ ከአንባቢዎቹ ውስጥ አንዳንድ ግለሰቦችን መገሰጽ እንደሚገባው ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “በወንድምህ ላይ መፍረድህ ትክክል አይደለም፣ ወንድምህንም መናቅ ትክክል አይደለም” ወይም “በወንድምህ ላይ መፍረድ፣ ወንድምህንም መናቅ አቁም!” (የሁለተኛ መደብ ቅርጾች የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድም

ይህ ሌላ ክርስቲያን፣ ሴት ወይም ወንድ የሆነን ይወክላል።

ሁላችን በእግዚአብሔር የፍርድ ዙፋን ፊት እንቆማለንና

“የፍርድ ዙፋን” የእግዚአብሔርን የመፍረድ ስልጣንን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር በሁላችን ላይ ይፈርዳልና” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

...” ተብሎ ተጽፏልና

ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ ሊጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበርና’ ... ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ሕያው ነኝና

ይህ ሐረግ አንድን መሃላ ወይም ቃልኪዳንን ለመጀመር ጥቅም ላይ ይውላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህ እውነት እንደሆነ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለእኔ ሁሉም ጉልበት ይንበረከካል፣ ሁሉም ምላስ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ይሰጣል

ጳውሎስ “ጉልበት” እና “ምላስ” የመሳሰሉትን ቃላት የሚጠቀመው የአንድን ሰው ሙሉ ማንነት ለመወከል ነው። በተጨማሪም ጌታ “እግዚአብሔር” የሚለውን ቃል ራሱን ለመወከል ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉም ሰው ይሰግዳል፣ ምስጋናንም ለእኔ ይሰጣል” (ወካይ እና አንደኛ፣ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መደብ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 14:12

ስለ ራሱ ለእግዚአብሔር መልስ ይሰጣል

“ለሰራናቸው ስራዎች ለእግዚአብሔር ማብራርያን እንሰጣለን”

ነገር ግን ይልቁንም ማንም ለወንድሙ የማሰናከያ እንቅፋት ወይም ወጥመድ እንዳያደርግባት ይህን ወስኑ

እዚህ ላይ “የማሰናከያ እንቅፋት” ወይም “ወጥመድ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ነገርን ይወክላሉ። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን ይልቁንም ሌላውን አማኝ ወደ ኃጢአት ሊወስድ የሚችል ነገርን አለማድረግንና አለመናገርን ግባችሁ አድርጉት” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድም

ይህ ሌላ ክርስቲያንን ይወክላል፣ ሴት ወይም ወንድ ሊሆን ይችላል።

Romans 14:14

... ክርስቶስ ኢየሱስን አውቄያለሁ አምኛለሁም

እዚህ ላይ “አውቄያለሁ” እና “አምኛለሁ” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉምን የያዙ ናቸው፡ ጳውሎስ እርግጠኛ መሆኑን አጽንኦት ለመስጠት ይጠቀምባቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከጌታ ኢየሱስ ጋር ባለኝ ግንኙነት ምክንያት እርግጠኛ ነኝ” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ምንም ነገር በራሱ ርኩስ አይደለም

ይህን በአዎንታዊ መልኩ መተርጎም ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሁሉም ነገር በራሱ ንጹህ ነው” (መንትያ አሉታዎች የሚለውን ይመልከቱ)

በራሱ

“በተፈጥሮው” ወይም “በይዘቱ”

ምንም ነገር ርኩስ ነው ብሎ ለሚያስብ ፣ ለእርሱ ርኩስ ነው

ጳውሎስ እዚህ ላይ ለመናገር የፈለገው አንድ ሰው ርኩስ ነው ብሎ ከሚያስበው ነገር መራቅ እንዳለበት ነው። ይህን በትርጉምህ ግልጽ አድርገህ ማስቀመጥ ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን አንድ ሰው አንድን ነገር ርኩስ ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ፣ ለዚያ ሰው ያ ነገር ርኩስ ነውና ከእርሱ ሊርቅ ይገባዋል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በመብልህ ምክንያት ወንድምህ ቢጎዳ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

"የሌላውን ክርስቲያን እምነት በመብል ምክንያት የምትጎዳ ከሆነ" እዚህ ላይ "በመብልህ" ውስጥ ያለው የባለቤት አመልካች የሚያመለክተው በእምነቱ ጠንካራ የሆነን አማኝ ነው፣ "ወንድም" የሚለው ደግሞ በእምነታቸው ደካማ የሆኑትን ያመለክታል።
ወንድም
ይህ ሌሎች ክርስቲያኖችን ይወክላል፣ ወንዶችንም ሴቶችንም ይወክላል
እንግዲያው በፍቅር እየተመላለስክ አይደለም
ጳውሎስ የአማኞችን ባሕርይ ጉዞ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም:- "ከእንግዲህ ፍቅርን እያሳየህ አይደለም" (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
Romans 14:16
ስለዚህ አንተ መልካም ብለህ የቆጠርከውን ነገር ክፉ እንደሆነ ተደርጎ እንዲነገር አትፍቀድ
"ሌላ ሰው አንድ ነገር ክፉ ነው ብሎ ካሰበ፣ ያንን ነገር አንተ አታድርገው፣ ምንም እንኳ አንተ መልካም ነው ብለህ የምታስብ ቢሆንም አታድርገው"
የእግዚአብሔር መንግስት ጽድቅ፣ ሰላምና በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን ደስታ እንጂ ምግብና መጠጥ አይደለምና
ጳውሎስ እግዚአብሔር መንግስቱን ያዘጋጀው ከራሱ ጋር ትክክለኛ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረን ለማድረግ፣ እንዲሁም ሰላምንና ደስታን ሊሰጠን እንደሆነ በመናገር ይሞግታቸዋል። አማራጭ ትርጉም:- "እግዚአብሔር መንግስቱን ያዘጋጀው የምንበላውንና የምንጠጣውን ለማስተዳደር አይደለም። መንግስቱን ያዘጋጀው ከእርሱ ጋር ትክክለኛ ግንኙነት እንዲኖረን፣ እንዲሁም ሰላምና ደስታን ሊሰጠን ነው። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Romans 14:18
በሰው ዘንድ ተቀባይነት ያለው
ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም:- "ሰዎች እርሱን ይቀበሉታል" ወይም "ሰዎች እርሱን ያከብሩታል" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ሰላም ያለባቸውንና እርስ በርሳችን የምንታነጽባቸውን ነገሮች እንከተል
እዚህ ላይ "የምንታነጽባቸውን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው እርስ በርስ በእምነት የሚያሳድጉ ነገሮችን ነው። አማራጭ ትርጉም:- "አብረን በሰላም ለመኖርና በእምነታችን ለመበርታት እንፈልግ" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Romans 14:20
ለመብል ብለህ የእግዚአብሔርን ሥራ አታፍርስ
የዚህን አርፍተ ነገር ትርጉም ግልጽ አድርጎ መጻፍ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም:- "አንተ የሆነ የምግብ ዓይነት መብላት ስለፈለግህ ብቻ እግዚአብሔር ለአንድ አማኝ የሰራውን ስራ አታፍርሰው" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን ለሚበላና ሌላው እንዲሰናከል ለሚያደርግ ለዚያ ሰው ክፉ ነው
እዚህ ላይ "ሌላውን እንዲሰናከል የሚያደርግ" ማለት ደካማ የሆነው ወንድም ከሕሊናው ጋር የማይጣጣም ነገር እንዲያደርግ የሚገፋው ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም:- "ነገር ግን አንድ ወንድም ሌላው ወንድም መብላት ትክክል አይደለም ብሎ የሚያስበውን ምግብ ቢበላ፣ ለዚያ ሰው ኃጢአት ይሆንበታል፣ እርሱ በመብላቱ ምክንያት ደካማውን ወንድም ከሕሊናው ጋር የማይጣጣም ነገር እንዲያደርግ ምክንያት ከሆነበት ኃጢአት ይሆንበታል" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ስጋ መብላት፣ ወይንንም አለመጠጣት፣ እንደዚሁም ወንድምህን ያሰናክላል ብለህ የምታስበውን ነገር አለማድረግ መልካም ነው
"ስጋ መብላት፣ ወይን መጠጣት እንዲሁም ወንድምህ ኃጢአት እንዲያደርግ ምክንያት የሚሆን ነገርን አለማድረግ ይመረጣል"
ወንድም
ይህ ሌሎች አማኝ ክርስቲያኖችን ይወክላል፣ ወንድ ወይም ሴት ሊሆኑ ይችላሉ
የአንተ
"የአንተ" የሚለው በእምነቱ ጠንካራ የሆነውን ይወክላል፣ "ወንድም" የሚለው ደግሞ በእምነቱ ደካማ የሆነውን ይወክላል።
Romans 14:22
ያለህ እምነት
ይህ የሚያመለክተው ስለ መብልና መጠጥ ያላቸውን እምነት ነው።
አንተ ... ራስህ
ነጠላ ቁጥር ነው። ጳውሎስ መልዕክቱን የሚያስተላልፈው ለአማኞቹ ነው ስለዚህ ይህንን በብዙ ቁጥር መተርጎም ይቻላል። (የሁለተኛ መደብ ቅርጾች የሚለውን ይመልከቱ)
ራሱ አምኖ በተቀበለው ነገር በራሱ ላይ የማይፈርድ ሰው እርሱ የተባረከ ነው
"ለማድረግ ወስነው በሚያደርጉት ነገር ወንጀለኝነት የማይሰማቸው ሰዎች የተባረኩ ናቸው"
የሚጠራጠር ግን ቢበላ እርሱ ይኮነናል
ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም:- "አንድ ሰው የሆነ ምግብ መብላት ትክክል መሆኑን እርግጠኛ ሳይሆን ያንን ምግብ ቢበላ እግዚአብሔር ያ ሰው ስህተተ ፈጽሟል ይለዋል" ወይም "አንድን ምግብ መብላት ትክክል ይሁን አይሁን እርግጠኛ ያልሆነ ሰው፣ ነገር ግን ምግቡን ቢበላው ያ ምግቡን የበላው ሰው መጥፎ ሕሊና ይኖረዋል" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ምክንያቱም በእምነት አይደለምና
"በእምነት ያልሆነ" ማንኛውም ነገር እግዚአብሔር እንድናደርገው የማይፈልገው ነገር ነው። ሙሉ ትርጉሙን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም:- "እግዚአብሔር እንዲበላ የማይፈልገው ነገር መሆኑን አውቆ ያመነበትን ነገር በልቷልና እግዚአብሔር ስህተት ነህ ይለዋል" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከእምነት ያልሆነ ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው
"ከእምነት ያልሆነ" ነገር ሁሉ ማለት እግዚአብሔር እንድታደርጉት የማይፈልገው ነገር ማለት ነው። እዚህ ላይ ሙሉ ትርጉሙን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም:- "እግዚአብሔር እንዳደርገው አይፈልግም ብላችሁ የምታምኑትን ነገር ብታደርጉ ኃጢአትን እየሰራችሁ ነው" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 15
Romans 15:1
አያያዥ ሀሳብ:-
እዚህ ላይ ጳውሎስ ክርስቶስ እንዴት እንደኖረ በማስታወስ፣ አማኞች ለሌሎች ሊኖሩ እንደሚገባ የሚናገረውን ይህን ክፍል ይደመድመዋል።
እነሆ
ይህን ቃል በቋንቋችሁ ውስጥ በሙግት ውስጥ አዲስ ሃሳብን በሚያስተዋውቅ ቃል ተርጉሙት።
ብርቱዎች የሆንን እኛ
እዚህ ላይ "ብርቱ" የሚለው በእምነታቸው ብርቱ የሆኑ ሰዎችን ያመለክታል። እነርሱም እግዚአብሔር ምንም ዓይነት ምግብን እንዲበሉ እንደፈቀደ ያምናሉ። አማራጭ ትርጉም:- "በእምነታችን ብርቱ የሆንን እኛ" (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Romans 15:3
ተብሎ እንደተጻፈው
እዚህ ላይ ጳውሎስ፣ ክርስቶስ (መሲሑ) ለእግዚአብሔር የሚናገርበትን አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያነሳል። ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም:- "በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መሲሑ ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናግሯል ..." (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
አንተን የሰደቡህ ሰዎች ስድብ እኔ ላይ ወደቀብኝ
እግዚአብሔርን የሰደቡት ሰዎች ስድብ በክርስቶስ ላይ ወደቀ።
አስቀድሞ የተጻፈው በሙሉ ለእኛ ትምህርት ተጽፏልና
ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም:- "ባለፉት ጊዜያት፣ ነቢያት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የጻፉት ሁሉም ነገር እኛን ለማስተማር የተጻፈ ነውና" (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የኛ... እኛ
ጳውሎስ አንባቢዎቹንና ሌሎች አማኞችን ያካትታል። (አካታች "እኛ" የሚለውን ይመልከቱ)
ቃሉ በሚሰጠን ትዕግስትና ማበረታታት ተስፋ እንዲኖረን
እዚህ ላይ "ተስፋ እንዲኖረን" የሚለው አማኞች እግዚአብሔር የገባውን ቃል


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደሚፈጽም ማወቃቸውን ያመለክታል። የዚህን ትርጉም በትርጉምህ ውስጥ በግልጽ ማስቀመጥ ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “በዚህ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የገባውን ቃል በሙሉ እንደሚያደርግልን እያወቅን በተስፋ እንድንጠባበቅ ያበረታናል።” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:8

እላለሁ

ይህ ጳውሎስን ይወክላል (“እኔ” የሚለው አመልካች ጳውሎስን ይወክላል)

ክርስቶስ የመገረዝ አገልጋይ ሆኗል

እዚህ ላይ “መገረዝ” የሚለው አይሁድን የሚወክል ምትክ ስም ነው። ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ኢየሱስ ክርስቶስ የአይሁድ አገልጋይ ሆነ” (ምትክ ስም እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የተስፋ ቃሉን ያጸና ዘንድ .... አሕዛብም እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ እንዲያከብሩት

እነዚህ ክርስቶስ የመገረዝ አገልጋይ የሆነበት ሁለት ዓላማዎች ወይም ምክንያቶች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “የተስፋ ቃሉን ያረጋግጥ ዘንድ … አሕዛብም ስለ ምሕረቱ እግዚአብሔርን እንዲያከብሩት”

ለአባቶች የሰጠውን የተስፋ ቃል

እዚህ ላይ “አባቶች” የሚለው የአይሁድ ሕዝቦችን አባቶች ያመለክታል። ይህንን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ለአይሁድ ሕዝቦች አባቶች የሰጠውን የተስፋ ቃል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ተብሎ እንደተጻፈ

ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “አንድ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዲህ ብሎ እንደጻፈው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ለስምህም ምስጋናን እዘምራለሁ

እዚህ ላይ “ለስምህ” የሚለው እግዚአብሔርን የሚወክል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ለአንተ ምስጋናን እዘምራለሁ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:10

ደግሞም እንዲህ ይላል

“ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል”

ከሕዝቡ ጋር

ይህ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያመለክታል። ይህን በትርጉሙ ውስጥ ግልጽ አድርጎ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

አመስግኑ

“ጌታን አመስግኑ”

Romans 15:12

የእሴይ ሥር

እሴይ የንጉሥ ዳዊት የስጋ አባት ነበር። አማራጭ ትርጉም፡- “የእሴይ ዘር” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)

በእርሱ አሕዛብ ተስፋ ይኖራቸዋል

እዚህ ላይ “እርሱ” የሚለው የእሴይን ልጅ የሆነውን መሲሑን ያመለክታል። አይሁድ ያልሆኑ ሰዎችም ቃሉን እንዲፈጽም እርሱን ያምኑታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አይሁድ ያልሆኑትም ቃል የገባውን እንዲፈጽም እርሱን ያምኑታል” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:13

በደስታና በሰላም ይሙላችሁ

ጳውሎስ እዚህ ላይ ለንግግሩ አጽንዖት ለመስጠት ግነትን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “በታላቅ ደስታና ሰላም ይሙላችሁ” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:14

አያያዥ ሀሳብ፡-

ጳውሎስ በሮም ያሉ አማኞች እግዚአብሔር እርሱን አሕዛብን ለመድረስ እንደመረጠው ያስታውሳቸዋል።

እኔ ራሴ ወንድሞቼ ሆይ … ስለ እናንተ ተረድቻለሁ

ጳውሎስ በሮም ያሉት አማኞች አንዱ ሌላውን በመልካም ባሕሪያቸው እያከበሩ እንደሆነ አርግጠኛ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እኔ ራሴ እናንተ በሌሎች ዘንድ በመልካም አካሄድ እንደሄዳችሁ እርግጠኛ ነኝ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ወንድሞች

ይህ ማለት ሌሎች አማኞችን ያመለክታል፣ ወንዶችና ሴቶችንም ያካትታል።

በእውቀት ተሞልታችሁ

ጳውሎስ እዚህ ላይ ለንግግሩ አጽንዖት ለመስጠት ግነትን ይጠቀማል። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔርን ለመከተል በሚበቃ እውቀት ተሞልታችሁ” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

እርስ በርሳችሁም ልትመካከሩ መቻላችሁ

እዚህ ላይ “ልትመካከሩ” የሚለው ማስተማርን ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እርስ በርስ አንዱ ሌላውን ማስተማር መቻላችሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:15

በእግዚአብሔር የተሰጠኝ ጸጋ

ጳውሎስ ጸጋን እግዚአብሔር በአካል እንደሰጠው የሚዳሰስ ስጦታ እንደሆነ አድርጎ ይናገራል። ጳውሎስ ኢየሱስን ለመከተል ከመወሰኑ በፊት ብዙ አማኞችን ያሰቃየ ቢሆንም እግዚአብሔር ሐዋርያ እንዲሆን ሹሞታል። ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

የአሕዛብ መስዋዕት ተቀባይ ይሆን ዘንድ

ጳውሎስ ወንጌል የመስበክ ስራውን ልክ እርሱ ካህን እንደሆነና ለእግዚአብሔር መስዋዕትን እንደሚያቀርብ አድርጎ ይስለዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “አሕዛብ እግዚአብሔርን ሲታዘዙ እርሱን እንዲያስደስቱት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:17

ምንም ነገር ልናገር አልደፍርምና … እነዚህ ነገሮች በሙሉ በቃልና በስራ፣ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልም ተሰርተዋል

እዚህ ላይ ያለውን መንትያ አሉታዊ መግለጫ በአዎንታዊ መግለጫ መተርጎም ይቻላል። እዚህ ላይ “እነዚህ ነገሮች” የሚለው ክርስቶስ በጳውሎስ በኩል ያሳካቸውን ነገሮች ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አሕዛብ እንዲታዘዙ፣ ክርስቶስ ብቻ በእኔ በኩል በቃሌና በስራዬ ፣ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል በመንፈስ ቅዱስም ኃይል ያደረገውን ነገር እናገራለሁ” (መንትያ አሉታዎች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ምልክትና ድንቅ ነገር

እነዚህ ሁለት ነገሮች ተመሳሳይ ትርጉምን የያዙ ሲሆን የተለያዩ ተዓምራትን ያመለክታሉ። (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)

ስለዚህ ከኢየሩሳሌም እስከ እልዋሪቆን ደረስ እየዞርኩ

ይህ ከኢየሩሳሌም ከተማ ከጣልያን ቅርብ ርቀት ላይ እስካለችው እስከ እልዋሪቆን ግዛት ድረስ ነው።

Romans 15:20

በዚህ መንገድ ፍላጎቴ ወንጌልን ማወጅ ነበር፣ ነገር ግን ክርስቶስ በሚታወቅበት ቦታ አይደለም

ጳውሎስ ወንጌልን መስበክ የሚፈልገው ስለ ክርስቶስ በጭራሽ ሰምተው ለማያውቁ ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በዚህም ምክንያት ሰዎች ስለ ክርስቶስ ሰምተው በማያውቁበት ቦታ የምስራቹን መስበክ እፈልጋለሁ።” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

በሌላ ሰው መሰረት ላይ እንዳልገነባ

ጳውሎስ አገልግሎቱ በመሰረት ላይ ቤትን የመገንባት ዓይነት እንደሆነ ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “ሌላ ሰው የጀመረውን ስራ መቀጠል እንዳይሆንብኝ። ሌላ ሰው በሰራው መሰረት ላይ ቤትን እንደሚገነባ ሰው መሆን አልፈልግም።” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ተብሎ እንደተጻፈ

እዚህ ላይ ጳውሎስ ኢሳይያስ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የጻፈውን ያነሳል። ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ፣ እንዲሁም ትርጉሙን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። አማራጭ ትርጉም፡- “እየተከሰተ ያለው ኢሳይያስ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደጻፈው ነው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ስለ እርሱ ምንም ዜና ላልደረሳቸው

እዚህ ላይ ጳውሎስ “ዜናው” ወይም የክርስቶስ መልዕክት ሕያው እንደሆነና በራሱ እንደሚንቀሳቀስ አድርጎ ስሎታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ማንም ሰው ስለ እርሱ



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ዜናውን ላልነገራቸው ሰዎች” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:22

አያያዥ ሀሳብ፦

ጳውሎስ በሮም ላሉ አማኞች እነርሱን ለመጎብኘት ስላለው የግል ሃሳብ ይነግራቸዋል፣ እንዲሁም አማኞቹን እንዲጸልዩ ይነግራቸዋል።

እንዲሁም ተከለከልሁ

ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ከለከሉኝ” ወይም “ሕዝቡ ከለከሉኝ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

ከዚህ በኋላ በነዚህ ቦታዎች ስፍራ የለኝም

ጳውሎስ እዚህ ላይ ለማለት የፈለገው በነዚህ ስፍራዎች ሰዎች ስለ ክርስቶስ ያልሰሙበት ቦታ የለም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በእነዚህ ቦታዎች ሰዎች ስለ ክርስቶስ ያልሰሙበት ስፍራ የለም” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:24

ስፔን

ይህ ጳውሎስ ሊጎበኘው የሚፈልግ ከሮም በስተሜን የሚገኝ የሮማ ግዛት ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን መተርጎም የሚለውን ይመልከቱ)

ሳልፍ

“በሮም ሳልፍ” ወይም “በመንገድ ላይ ሳለሁ”

በመንገዴም እንድትረዱኝ

እዚህ ላይ ጳውሎስ ማለት የፈለገው በሮም ያሉት አማኞች እርሱ ወደ ስፔን በሚያደርገው ጉዞ የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉለት እንደሚፈልግ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “በጉዞዬ እንድትረዱኝ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለጸ መረጃ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በአብሮነታችሁ ተደስቼ

“ከእናንተ ጋር ጊዜ በማሳለፌ ተደስቼ” ወይም “እናንተን በመጎብኘቴ ተደስቼ”

Romans 15:26

መቄዶንያና አካይያ … ወድደዋልና

እዚህ ላይ “መቄዶንያ” እና “አካይያ” የሚሉት ቃላት በዚያ አካባቢ የሚኖሩትን ሕዝቦች የሚወክሉ ወካይ ስሞች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “በመቄዶንያና በአካይያ ግዛቶች የሚኖሩ አማኞች … ወድደዋልና” (ወካይ የሚለውን ይመልከቱ)

በእርግጥም ወድደዋል

“በመቄዶንያና በአካይያ የሚገኙ አማኞች (በመርዳታቸው) ደስተኞች ነበሩ”

Romans 15:28

የተሰበሰበው እንደደረሳቸው ካረጋገጥኩ በኋላ

ጳውሎስ እዚህ ላይ ወደ ኢየሩሳሌም እየወሰደ ያለውን የተሰበሰበውን ገንዘብ ልክ ለእነርሱ እንደተሰበሰበ እንደ ፍራፍሬ አድርጎ ይስለዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይህንን ስጦታ ለእነርሱ በአግባቡ አስረክቤ” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ወደ እናንተ ስመጣ በክርስቶስ ሙላትና በረከት እንደምመጣ አውቃለሁ

ይህ ሃረግ ክርስቶስ ጳውሎስንና የሮሜ አማኞችን ይባርካል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስጎበኛችሁም፣ ክርስቶስ አትረፍርፎ እንደሚባርከን አውቃለሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:30

እነሆ

ይህ ጳውሎስ ይተማመንባቸው ስለነበረው ስለ መልካም ነገሮች (ሮሜ 15:29) ማውራት አቁሞ ሊጋፈጣቸው ስላሉት ነገሮች ማውራት መጀመሩን የሚያሳይ ነው። ቋንቋችሁ ይሄንን የማሳያ መንገድ ካለው እዚህ ላይ ጥቅም ላይ አውሉት።

አነሳሳችኋለሁ

“አበረታታችኋለሁ”

ወንድሞች

ይህ ሌሎች ክርስቲያኖችን ያመለክታል፣ ሴቶችንና ወንዶችን ያካትታል

እንድትተጉ

“በርትታችሁ እንድትሰሩ” ወይም “እንድትታገሉ”

ከማይታዘዙት እድን ዘንድ

ይህ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መጻፍ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ከማይታዘዙት እግዚአብሔር ያድነኝ ዘንድ” ወይም “የማይታዘዙት እንዳይጎዱኝ እግዚአብሔር ከእነርሱ ያድነኝ ዘንድ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)

በኢየሩሳሌም የሚኖረኝ አገልግሎት በአማኞች ዘንድ ተቀባይ እንዲሆን

እዚህ ላይ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ያሉ አማኞች ከመቄዶንያና ከአካይያ አማኞች ይዞ የመጣውን ገንዘብ በደስታ እንዲቀበሉት ያለውን ፍላጎት ያሳያል። አማራጭ ትርጉም፡- “የምወስድላቸውን ገንዘብ በኢየሩሳሌም ያሉ አማኞች በደስታ እንዲቀበሉኝ ጸልዩ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 15:33

የሰላም አምላክ

“የሰላም አምላክ” ማለት አማኞች ውስጣዊ ሰላምን እንዲኖራቸው የሚያደርግ አምላክ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “እግዚአብሔር ሁላችንም የውስጥ ሰላም እንዲኖረን እንዲያደርግ እጸልያለሁ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 16

Romans 16:1

አያያዥ ሀሳብ፦

ከዚህ በኋላ ጳውሎስ በሮሜ ያሉት አማኞችን ብዙዎቹን ስማቸውን እየጠራ ሰላምታን ያቀርባል።

ፌበንን አደራ እላችኋለሁ

“ፌበንን እንድታከብሯት እፈልጋለሁ”

ፌበን

ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን ተርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

እኅታችንን

“እኅታችንን” የሚለው ቃል ውስጥ ያለው የባለቤት አመልካች “እኛ” ጳውሎስንና ሌሎች ሁሉንም አማኞች ይወክላል። አማራጭ ትርጉም፡- “በክርስቶስ እህታችን” (አካታች “እኛ” የሚለውን ይመልከቱ)

ክንክራኦስ

ይህ በግሪክ የሚገኝ የወደብ ከተማ ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን ተርጉም የሚለውን ይመልከቱ)

በጌታ ስም ተቀበሏት

ጳውሎስ በሮሜ የሚገኙ አማኞች ፌበንን እንደ አጋር አማኝ እንዲቀበሏት ያበረታታቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ተቀበሏት፣ ምክንያቱም ሁላችንም የጌታ ነንና“ (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

ለቅዱሳን በሚመጥን መንገድ

“አማኞች ሌሎች አማኞችን መቀበል ባለባቸው መንገድ”

አጠገቧ ቁሙ

ጳውሎስ የሮሜን አማኞች ለፌበን የሚያስፈልጋትን ነገር በሙሉ እንዲሰጧት ያበረታታቸዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “የሚያስፈልጋትን ሁሉ በመስጠት እርዷት” (ለስላሴ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)

ለብዙዎች ለእኔም ጨምሮ ረዳት ነበረችና

“ብዙ ሰዎችን ረድታለች፣ እንዲሁም እኔንም ረድታኛለች”

Romans 16:3

ጵርስቅላ እና አቂላ

ጵርስቅላ የአቂላ ሚስት ነበረች። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አብረውኝ ለሚሰሩ

ከጳውሎስ ጋር “አብረው የሚሰሩት” ለሰዎች ስለ ኢየሱስ የሚሰብኩ ሰዎች ናቸው። አማራጭ ትርጉም፡- “ስለ ክርስቶሰ ኢየሱስ ለሰዎች በመንገር አብረውኝ የሚሰሩ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

Romans 16:6

ማርያ

ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)

አንዲራኒቆን … ጵልያጦን

እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ይመልከቱ)
ዩልያን
ይህ ሊሆን የሚችለው 1. ዩልያ፥ የሴት ስም ወይም 2. ዩልያን፥ የወንድ ስም (ይህ የወንድ ስም የመሆን ዕድሉ ዝቅተኛ ነው) (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ከሐዋርያት ስመ ጥር የሆኑ
ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ሐዋርያቱ በደንብ ያውቋቸው የነበሩ” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
በጌታ ለምወደው
“የተወደደው ጓደኛዬ እንዲሁም አጋር አማኝ”
Romans 16:9
አፋባኖን ... ስንጥካን ... ኤጤሌን ... አርስጣባሉ ... ሄሮድዮና ... ንቀርሱ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
በክርስቶስ እምነቱ ለተረጋገጠለት
“የተረጋገጠለት” የሚለው ቃል ተፈትኖ ትክክለኛ መሆኑ የተረጋገጠን ሰው ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ክርስቶስ እምነቱን ላረጋገጠለት”
በጌታ ላሉት
ይህ በኢየሱስ የሚታመኑን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “አማኞች የሆኑትን” ወይም “የጌታ የሆኑትን” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Romans 16:12
ፕሮፊሞና ... ጢሮፊሞሳ ... ጠርሲዳ
እነዚህ የሴቶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን ተርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
ሩፎን ... አስቀሪጦን ... አፍለሶንጳ ... ሄሮሜን ... ጳጥሮባ ... ሄርማን
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን ተርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
በጌታ የተመረጡ
ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፡- “ጌታ የመረጣቸው” (ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
Romans 16:15
ፍሌጎን ... ኔርያ ... አልጦን
እነዚህ የወንድ ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን ተርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
ዩልያ
ይህ የአንዲት ሴት ስም ነው። ዩልያ የፍሌጎን ሚስት ልትሆን ትችላለች። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል እና የማይታወቁትን ተርጉም የሚለውን ይመልከቱ)
የተቀደሰ አሳሳም
ለሌሎች አማኞች ፍቅርን የመግለጫ መንገድ ነው
የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታን ያቀርቡላችኋል።
ጳውሎስ እዚህ ላይ በጠቅላላው ስለ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያናት ይናገራል። አማራጭ ትርጉም፡- “በዚህ አካባቢ ያሉ አብያተክርስቲያናት ውስጥ ያሉ አማኞች በሙሉ ሰላምታን ያቀርቡላችኋል” (ግነት እና ጅምላ ፍረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Romans 16:17
አያያዥ ሀሳብ፡-
ጳውሎስ ለአማኞች ስለ አንድነትና ለእግዚአብሔር ስለመኖር አንድ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።
ወንድሞች
ይህ ሌሎች ክርስቲያኖችን ሲያመለክት፣ ወንዶችና ሴቶችን ያካትታል
እንድታስቡ
“እንድትጠነቀቁ”
መከፋፈልንና ማሰናከያን የሚያደርጉ
ይህ የሚያመለክተው ክርክርን የሚፈጥሩ ሰዎችንና፣ ሌሎችን በኢየሱስ እንዳያምኑ ምክንያት የሚሆኑትን ሰዎች ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አማኞች እርስ በርስ እንዲከራከሩና በእግዚአብሔር እምነት እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ” (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
ከተማራችሁት ትምህርት ወጥተው ሄደዋል
“እናንተ ከተማራችሁት እውነት ጋር የማይስማማ ትምህርት ያስተምራሉ”
ከእነርሱ ራቁ
“ራቁ” ማለት “አትስሟቸው” የሚለውን ትርጉም የያዘ ዘይቤ ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “አታዳምጧቸው” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ለገዛ ሆዳቸው እንጂ
“ያገለግላሉ” የሚለው ቃል ከላይ ካለ ሐረግ አገባብ ትርጉሙን መረዳት ይቻላል። ይህ በተለይ አረፍተ ሃሳብ መገለጽ ይችላል። አማራጭ ትርጉም፡- “ይልቁንም የራሳችውን ሆድ ነው የሚያገለግሉት” (አስጨምሬ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን ለገዛ ሆዳቸው
“ሆድ” የሚለው ቃል የአካላዊ ፍላጎቶችን የሚያሳይ ምትክ ስም ነው። የገዛ ሆዳቸውን ማገልገል ማለት ፍላጎቶቻቸውን ማግኘት ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ነገር ግን የራሳቸውን ራስ ወዳድ የሆኑ ፍላጎቶች ብቻ ማግኘት ነው የሚፈልጉት” (ምትክ ስም እና ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
በለስላሳና መልካም ንግግራቸው
“ለስላሳ” እና “መልካም” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጳውሎስ እነዚህ ሰዎች እንዴት አማኞችን እያታለሉ እንደሆነ አጽንዖት ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም፡- “መልካምና እውነት የሚመስሉ ነገሮችን በመናገር” (ጥምር ቃል የሚለውን ይመልከቱ)
የንጹሃንን ልብ ያታልላሉ
እዚህ ላይ “ልብ” የሚለው የአንድን ሰው አእምሮ ወይም ውስጣዊ ማንነት የሚወክል ምትክ ስም ነው። አማራጭ ትርጉም፡- “ንጹሃን አማኞችን ያታልላሉ” (ምትክ ስም የሚለውን ይመልከቱ)
ንጹሃን
ይህ ገር፣ ብዙ የማያውቁና የዋህ አማኞችን ያመለክታል። አማራጭ ትርጉም፡- “በየዋህነት የሚያምኗቸውን” ወይም “እነዚህ አስተማሪዎች እያታለሏቸው እንደሆነ የማያውቁትን”
Romans 16:19
የመታዘዛችሁ አርአያነት ለሁሉም ደርሷልና
እዚህ ላይ ጳውሎስ ስለ ሮሜ አማኞች ታዛዥነት ስናገር ታዛዦነታቸው ሰው እንደሆነና ወደ ሌሎች ሰዎች የሚሄድ እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። አማራጭ ትርጉም፡- “ኢየሱስን እንዴት እንደምትታዘዙ ሁሉም ሰው ሰምቷልና” (ሰውኛ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
የሰላም አምላክ ፈጥኖ ሰይጣንን ከእግራችሁ ስር ይቀጠቅጠዋል
“ከእግራችሁ ስር ይቀጠቅጠዋል” የሚለው ሐረግ በጠላት ላይ ያለን ሙሉ ድል መንሳት ይወክላል። እዚህ ላይ ጳውሎስ በሰይጣን ላይ ያለውን ድል የሮሜ አማኞች ጠላቶቻቸውን በእግራቸው ስር እንደሚቀጠቅጡ አድርጎ ይስለዋል። አማራጭ ትርጉም፡- “ፈጥኖም እግዚአብሔር ሰላምና በጠላትም ላይ ፍጹም ድልን ይሰጣችኋል” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
ክፉ ነገርም ለሆነው ንጹህ እንድትሆኑ
“ክፋትን ነገሮች የማትሰሩ እንድትሆኑ”
Romans 16:21
አያያዥ ሀሳብ፡-
ጳውሎስ ከእርሱ ጋር ካሉት አማኞች ሰላምታን ያቀርባል።
ሉቂዮስ ኢያሶን ሱሲጴጥሮስ ጤርጥዮስ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
ይህን መልእክት የጻፍኩ እኔ ጤርጥዮስ
ጤርጥዮስ ጳውሎስ የሚናገረውን በጽሑፍ ያሰፍር የነበረው ሰው ነው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
Romans 16:23
ጋይዮስ ኤርስጦስ ቁአስጥሮስ
እነዚህ የወንዶች ስሞች ናቸው። (ስሞችን እንዴት መተርጎም ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ)
አስተናጋጅ
ይህ ጳውሎስና ሌሎች አማኞች ለአምልኮ የሚሰበሰቡበት ቤት ባለቤት የሆነውን ሰው ጋይዮስን ያመለክታል።
የግምጃ ቤት ሹም
ይህ ሰው የአንድ ቡድን ገንዘብ የሚይዝ ሰው ነው።
Romans 16:25

አያያዥ ሀሳብ፦
ጳውሎስ መልዕክቱን በበረከት ጸሎት ይዘጋል።
እንግዲህ
እዚህ ላይ “እንግዲህ” የሚለው ቃል የደብዳቤውን መጨረሻ ክፍል ያመለክታል። ይህን በራሳችሁ ቋንቋ መግለጽ የምትችሉ ከሆነ እሱን መጠቀም ይቻላል።
ሊያቆማችሁ የሚችለው
ጳውሎስ እዚህ ላይ ጠንካራ እምነት መኖርን ልክ ከመውደቅ ይልቅ እንደመቆም አድርጎ ይስለዋል። አማራጭ ትርጉም፦ “እምነታችሁን ለማበርታት” (ተለዋጭ ዘይቤ የሚለውን ይመልከቱ)
እንደ እኔ ወንጌልና እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ስብከት
“ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሰበክሁት እንደ የምስራቹ ቃል”
ለረጅም ጊዜ ተሰውሮ ቆይቶ መገለጥን ባገኘው ሚስጥር
ጳውሎስ እግዚአብሔር ቀድመው ተሰውረው የቆዩ ነገሮችን ለአማኞች እንደገለጠ ይናገራል። እነዚህ ነገሮች ሚስጥር እንደነበሩ አድርጎ ይናገራል። ይህን በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፦ “ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእኛ ለአማኞች ለረጅም ጊዜ ሚስጥር ሆኖ የጠበቀውን ነገር ስለገለጠልን” (ተለዋጭ ዘይቤ እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
ነገር ግን አሁን በዘላለማዊው በእግዚአብሔር ትዕዛዝ በነቢያት ጽሁፎች ለሁሉም ሕዝቦች ተገልጧል፣ እንዲታወቅም ሆኗል
“ተገልጧል” እና “እንዲታወቅ ሆኗል” የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጳውሎስ ሁለቱንም የሚጠቀመው አጽንዖት ለመስጠት ነው። እነዚህን ቃላት አንድ ላይ በማድረግ በገቢር/አድራጊ ቅርጽ መተርጎም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፦ “አሁን ግን ዘላለማዊው እግዚአብሔር በነቢያቱ ጽሁፍ አማካይነት ለሕዝብ ሁሉ እንዲታወቅ አድርጓል” (ጥምር ቃል እና ገቢር/አድራጊ ወይም ተገብሮ/ተሳቢ የሚለውን ይመልከቱ)
የእምነት መታዘዝን እንዲያመጣ
እዚህ ላይ “መታዘዝ” እና “እምነት” የሚሉት ቃላት ረቂቅ ስሞች ናቸው። “ታዛዥነት” እና “መታመን” የሚሉትን በትርጉምህ ላይ መጠቀም ትችላለህ። አማራጭ ትርጉም፦ “ሕዝብ ሁሉ እግዚአብሔርን ስለሚታመኑት እንዲታዘዙት” (ረቂቅ ስሞች እና ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)
Romans 16:27
ብቻውን ጠቢብ ለሆነው … ለዘላለም ክብር ይሁን። አሜን
እዚህ ላይ “በክርስቶስ ኢየሱስ” የሚለው ኢየሱስ የሰራውን ስራ ያመለክታል። “ክብር” ይሁን ማለት እግዚአብሔርን ማመስገን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም፦ “ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ በሰራው ስራ ምክንያት፣ ብቻውን አምላክና ብቻውን ጥበበኛ የሆነውን እግዚአብሔርን ለዘላለም እናመሰግናለን። (ግምታዊ እውቀት እና ያልተገለፀ መረጃ የሚለውን ይመልከቱ)

---

Chapter 1
1 Corinthians 1:1
1 ቆሮንቶስ 1፡1-3
ወንድማችን ሶስቴንስ ጳውሎስና የቆሮንቶስ ሰዎች ሶስቴንስን እንደሚያውቁ ይጠቁማል። ትኩረት፦ "ሶስቴንስ እናንተና እኔ የምናውቀው ወንድም።
ቅዱሳን ለመሆን የተጠሩት ሰዎች ትኩረት፦ «እግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ እንዲሆኑ ጠርቶአቸዋል።»
የእነርሱና የእኛ ጌታ ኢየሱስ የጳውሎስና የቆሮንቶስ ሰዎች ጌታ ነው፤ እንዲሁም የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ጌታ ነው። ለእናንተ «እናንተ» የሚለው ቃል በቆሮንቶስ ያሉትን ምእመናንን ያመለክታል።
1 Corinthians 1:4
1ቆሮንቶስ 1፡4-6
ክርስቶስ ኢየሱስ የሰጣችሁ የእግዚአብሔር ጸጋ «በክርስቶስ ላላችሁ እግዚአብሔር የሰጣችሁ ጸጋ» ባለጸጋ አድርጎአችኋል ትርጉም ሊሆኑ የችሉ 1) «ክርስቶስ ባለጸጋ አድርጎአችኋል።» ወይም 2) «እግዚአብሔር ባለጸጋ አድርጎአችኋል።» በየስፍራው ባለጸጋ አድርጎአችኋል «በብዙ መንፈሳዊ በረከቶች ባለጸጋ አድርጎአችኋል» በንግግር ሁሉ እግዚአብሔር ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር መልእክት በብዙ መንገድ እንድትናገሩ አስችሎአችኋል በዕውቀት ሁሉ እግዚአብሔር የእርሱን መልእክት በብዙ መንገድ እንድትረዱ አስችሎአችኋል። ስለ ክርስቶስ ምስክርነት «ስለ ክርስቶስ መልእክት» በመካከላችሁ እውነትን አረጋገጠ ትኩረት፦ « ሕይወታችሁን በግልጽ ለውጦአል።»
1 Corinthians 1:7
1 ቆሮንቶስ1፡7-9
ስለዚህ «ከዚህ የተነሣ» ከመንፈሳዊ ስጦታ አልጎደለባችሁም «ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታ ይኑርባችሁ» የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ አማራጭ ትርጉሞች 1) « እግዚአብሔር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚገልጥበት ጊዜ።» 2) «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን በሚገልጥበት ጊዜ።» ነውር የሌለባችሁ ትሆናላችሁ እግዚአብሔር እናንተን የሚነቅፍበት ምክንያት ያለም ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው። እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አዲስ ሕይወት እንድትካፈሉ ጠርቶአችኋል።
1 Corinthians 1:10
1 ቆሮንቶስ 1፡10-11
ሁላችሁ የምትስማሙበት «እርስ በርሳችሁ በስምምነት ትኖራላችሁ» በመካከላችሁ መከፋፈል እንዳይኖር «በመካከላችሁ በተለያየ ቡድን መከፋፈል የለባችሁም።» በአንድ አሳብና በአንድ ዓላማ የተሳሰራችሁ ሁኑ « በኅብረት ኑሩ» የቀሎዔ ሰዎች ይህ ቀሎዓ የተባለች ሴት የምትመራው ቤተ ሰብ፥ የቤተ ሰብ አባላት፥ አገልጋዮችና ሌሎችንም የሚያመለክተው ነው። በመካከላችሁ ክፍፍሎች እየተፈጠሩ ናቸው።
«እርስ በርሳችሁ የምትጣላሉ ቡድኖች ናችሁ።»
1 Corinthians 1:12
1 ቆሮንቶስ 1፡12-13
እያንዳንዳችሁ ትላላችሁ ጳውሎስ በአጠቃላይ ስለ ክፍፍል እየገለጸ ነው። ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስ ከአንዱ በቀር ክርስቶስ ያልተከፋፈለ የመሆኑን እውነት ለማስረዳት ይፈልጋል። «እናንት በምትፈጉበት ሁኔታ ክርስቶስን መከፋፈል አይቻልም።» ጳውሎስ ተሰቅሎአልን? ጳውሎስ የተሰቀለው ጳውሎስ ወይም አጵሎስ ሳይሆን ክርስቶስ ብቻ እንደሆን ለማስረዳት ይፈልጋል። «በመስቀል ላይ ጳውሎስን ለእናንተ ድነት አልሰቀሉትም።»
በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን? ጳውሎስ ለማስረዳት የፈለገው ሁላችን በክርስቶስ ስም እንደተመቅን ነው። «ሰዎች በጳውሎስ ስም አላጠቁም።» (ተመልከት፦
1 Corinthians 1:14
1 ቆሮንቶስ 1፡14-16
እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ማንንም አለማጥመቁን ምን ያህል ትልቅ ሰው እንደሆን አጋኖ ይናገራል።
ቀርስጶስ የአይሁድ ምኩራብ አለቃ የነበረና ወደ ክርስትና የመጣ።
ጋይዮስ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር አብሮ ተጉዞአል።
በስሜ ማናችሁም እንደተጠመቃችሁ የሚናገር ሰው እንዳይኖር ነበር «በኋላ ላይ ሰዎች እኔ እንዳጠመቅኋቸው አድርገው እንደይ ኩራሩብኝ ብዙ ሰዎችን በስሜ እንዳላጠምቅ ተከላክዬዋለሁ።»
የእስጢፋኖስ ቤተ ሰብ በእስጢፋኖስ ቤተ ሰብ ውስጥ ያሉ የቤተ ሰብ አባላትንና አገልጋዮችን የሚያሳይ ነው።
1 Corinthians 1:17
1 ቆሮንቶስ 1፡17
ክርስቶስ ለማጥመቅ አላከኝም ይህ ማለት ጥምቀት በጳውሎስ አገልግሎት ቅድሚያ የሚሰጠው አልነበረም። የክርስቶስ መስቀል ኃይል ከንቱ መሆን የለበትም ትኩረት፦ «የሰው ጥበብ የክርስቶስን መስቀል ኃይሉን ከንቱ ማድረግ ያለበትም።»
1 Corinthians 1:18
1 ቆሮንቶስ 1፡18-19
ስለ የመስቀል መልእክት «ስለ ስቅላት መስበክ» ወይም «ስለ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት መልእክት መስበክ ነው» (UDB) ሞኝነት ነው «ስሜት የማይሰጥ» ወይም «ከንቱ ነገር» ለሚሞቱ እዚህ ላይ «መሞት» ማለት የመንፈሳዊ ሞት ሂደትን የሚያሳይ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ኃይል ነው «ይህ እግዚአብሔር በእኛ በኃይል የሚሠራውበት ነው።» የአስተዋዮችን ጥበብ ከንቱ አደርጋለሁ ትኩረት፦ «ዋቂ ሰዎችን ግራ እንዲጋቡ አደርጋለሁ» ወይም «የዐዋቂዎችን ዓላማ ሙሉ በሙሉ ከንቱ አደርጋለሁ።»
1 Corinthians 1:20


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

1 ቆሮንቶስ 1:20-21
ጥበበኛ ሰው የት አለ? ፈላስፋስ የት አለ? የዚህ ዓለም መርማሪስ የት አለ? ጳውሎስ ሊገልጸው የፈለገው በእውነት ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች የትም አይገኙም። ትኩረት፦ ከወንጌል ጥበብ ጋር ሲነጻጸር ጥበበኛ የሆኑ ሰዎች የሉም፤ ዐዋቂዎቹም የሉም። የዚህ ዓለም መርማሪዎቹም የሉም!" ዐዋቂ አንድ ሰው ከፍተኛ ዐውቀት እንዳለ የሚታወቅ የዚህ ዓለም መርማሪ አንድ ሰው ዐውቀት መኖሩን በክርክር ችሎታ የሚያሳምን እግዚአብሔር የዚህች ዓለም ጥበብን ሞኝነት አላደረገምን? እግዚአብሔር በዚህች ዓለም ጥበብ ላይ ያደረገውኔ ለምግለጽ የተጠቀመበት ጥያቄ ነው። ትኩረት፦ " እግዚአብሔር በርግጥ የዚህችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት አድርጎአል" ወይም "እግዚአብሔር ያሰቡት የነበረው ሞኝነት እንደሆነ ለማሳየት ፈልጎአል። (UDB)
የሚያምኑ አማራጭ ትርጉሞች 1) «የሚያምኑ ሁሉ» (UDB) or 2) « እርሱን የሚያምኑ ሁሉ።»

1 Corinthians 1:22

1 ቆሮንቶስ 1:22-23
እንሰብካለን «እኛ» የሚለው ቃል ጳውሎስንና ሌሎች ወንጌዋውያንን ይመለከታል። ክርስቶስ ተሰቅሎአል «ይህ በመስቀል ላይ ስለሞተው ክርስቶስ ነው።» የእንቅፋት ድንጋይ አንድ ሰው በመንገድ ላይ በድንጋይ እንቅፋት ሊሆን እንደሚሆንበት የክርስቶስ ስቅላት እንቅፋት ለአይሁድ እንቅፋት ሊሆን እንደቻለ ነው። «አይደለም» ትኩረት፦ «የሚቀበሉት አይደለም» ወይም «በጣም አስከፊ»

1 Corinthians 1:24

1 ቆሮንቶስ 1:24-25
እግዚአብሔር ለመረጣቸው «እግዚአብሔር ለሚጠራቸው ሰዎች» ክርስቶስን እንሰብካለን «ስለክርስቶስ እናስተምራለን» ወይም «ስለ ክርስቶስ ለሰዎች ሁሉ እንናገራለን።» ክርስቶስ እንደ ኃይልና እንደ እግዚአብሔር ጥበብ ክርስቶስ እግዚአብሔር ኃይሉና ጥበቡን የሚገልጥለት ነው። የእግዚአብሔር ሞኝነት የእግዚአብሔር ድካም ይህ የእግዚአብሔርና የሰው ባሕርይ ንጽጽር ነው። የእግዚአብሔር ሞኝነት የሚመስል ወይም ድካም የሚመስል እንኳ ቢሆን ከሰው የመጨረሻ ከተሻለው ባሕርይ ጋር ሲነጻጸር የእግዚአብሔር ይበልጣል።

1 Corinthians 1:26

1 ቆሮንቶስ 1:26-27
ለእናንተ የእግዚአብሔር ጥሪ «ቅዱሳን እንድትሆኑ እግዚአብሔር እንዴት እንደጠራችሁ» ከእናንተ ብዙዎች አልተመረጡም «ከእናንተ በጣም ጥቂቶች ብቻ» የሰው ልማድ «የሰዎች ፍርድ" ወይም "ስለ መልካምነት የሰዎች አሳብ» ባለባት ሆኖ ስለ መወለድ «ቤተ ሰብህ አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ የተለየ ነስ» ወይም «ንጉሳዊ» ጥበበኛን ለማሳፈር እግዚአብሔር የዚህ ዓለም ሞኝ ነገርን መረጠ የአይሁድ መሪዎች እነዚህ መሪዎች ከሌሎች ይልቅ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ አይደለም ብለው የሚያምኑትን እግዚአብሔር ትሑታን ሰዎችን መረጠ።

1 Corinthians 1:28

1 ቆሮንቶስ 1:28-29
ዝቅተኛና የተናቀ ምንድን ነው ዓለም የማትቀበላቸው ሰዎች ናቸው። ትኩረት፦ «ትሑታንና ተቀባይነት የሌላቸው ሰዎች ናቸው።» እንደ ምናምንቴ የሚቆጠሩ ሰዎች «ሁል ጊዜ ሰዎች ዋጋ እንደሌላቸው አድርገው የሚቆትሩአቸው» ዋጋ እንዳላቸው ተደርገው የሚያዙ ነገሮች «ሰዎች ዋጋ እንዳላቸው የሚቆጥሩአቸው ነገሮች» ወይም «ሰዎች ገንዘብ ወይም ክብር ይገባቸዋል ብለው ያስቡ»

1 Corinthians 1:30

1 ቆሮንቶስ 1:30-31
እግዚአብሔር ካደረገው የተነሣ ይህ የሚያሳየው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ያደረገውን ሥራ ነው። በእኛ የእኛ ጳውሎስ «በእኛ» በሚለው የቆሮንቶስ ሰዎችን ይጨምራል፡ እንግዲህ እናንት በክርስቶስ ኢየሱስ ናችሁ «አሁን እናንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ድነትን ተቀብላችኋል» ክርስቶስ ኢየሱ ስለ እኛ የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው «ክርስቶስ አየሱስ እግዚአብሔር እንዴት ጥበበኛ እንደሆነ ግልጽ አደረገው»
የሚመካ በጌታ ይመካ «ሰው የሚመካ ከሆን ጌታ ምን ያህል ታላቅ በመሆኑ ይመካ»

---

Chapter 2

1 Corinthians 2:1

1ቆሮንቶስ 2:1-2
በሚያባብል የንግግር ችሎታ ማሳመን በሚችለውና በሚስብ ንግግር ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ምንም ላለማወቅ ወስኼ ነበር ጳውሎስ ከሰው አስተሳሰብ ይልቅ በመስቀሉ ላይ አተኩሮአል። ትኩረት፦«ስለ ክርስቶስ ብቻ ለመናገር ወስኛ ነበር።»

1 Corinthians 2:3

1ቆሮንቶስ 2:3-5
ከእናንተ ጋር ነበርኩ «እኔ እናንተ ዘንድ ነበርኩ» በድካም አማጭ ትርጉሞች፦ 1) «የአካል ድካም» (UDB) or 2) «በሚገባ ሆኖ አለ መገኘት» አሳማኝ ማሳመን ወይም አንድ ነገር ሰዎች እንዲያደርጉ ተጽእኖ ማድረግ ወይም እንድን ነገር ማመን እነርሱ የጳውሎስ መልእክትና የወንጌል ስብከት

1 Corinthians 2:6

1ቆሮንቶስ 2:6-7
ጥበብን መናገር «የጥበብን ቃል ተናገር» የበሰለ ትኩረት፦ «የበሰሉ አማኞች» ለክብራችን «የወደፊት ክብራችንን ለማረጋገጥ»

1 Corinthians 2:8

1ቆሮንቶስ 2:8-9
የክብሩ ጌታ «ኢየሱስ የከበረ ጌታ» ዓይን ያላየው ነገሮች፥ጆሮም ያልሰማ ነገሮች፥ በልብም ያልታሰቡ ነገሮች ሦስቱም ነገሮች የሚያሳዩት ማንም ሰው በሁሉ አካሉ ክፍሎች እግዚአብሔር ያዘጋጃቸውን ነገሮች እንደማያውቅ ለመግለጽ ነው። እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጃቸው ነገሮች ጌታ ለሚወዱት አስደናቂ ነገሮችን በሰማይ አዘጋጅቶአል።

1 Corinthians 2:10

1ቆሮንቶስ 2:10-11
እነዚህ ነገሮች ናቸው ስለ ኢየሱስና ስለ መስቀል ያሉ እውነቶች በሰው ውስጥ ያለውን አሳብ ከሰው መንፈስ በቀር ማን ያውቃል? ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው ሰው የሚያስበውን ከራሱ ሰውየው በቀር ማንም አያውቅም። ትኩረት፦«ሰው የሚያስበውን ከሰው መንፈስ በቀር ማንም አያውቅም።»

1 Corinthians 2:12

1ቆሮንቶስ 2:12-13
እኛ ግን እዚህ «እ» ጳውሎስንና የእርሱን አድማጮችን ይጨምራል። እግዚአብሔር በነጻ የሰጠን «እግዚአብሔር በነጻ ሰጠን» ወይም «እግዚአብሔር በነጻ ሰጥቶናል» መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ነገሮችን በመንፈሳዊ ጥበብ ይተረጉማል ቅዱስ መንፈስ የእግዚአብሔርን እውነት ለአማኞቹ በመንፈስ ቅዱስ በራሱ ቃላት ግንኙነት ያደርጋል እንዲሁም የራሱንም ጥበብ ይሰጣል።

1 Corinthians 2:14

1ቆሮንቶስ 2:14-16
መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ክርስቲያን ያልሆነ ሰው፥ መንፈስ ቅዱስን ያልተቀበለ ምክንያቱም በመንፈስ ስለሚመረመሩ «ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች ለመረዳት የመንፈስ ቅዱስን ርዳታ ያስፈልጋል» መንፈሳዊ የሆነ ሰው ትኩረት፦ «መንፈስ ቅዱስን የተቀበለ አማኝ» የጌታን ልብ ማን አወቀው ማንስ ሊያስተምራው ይችላል? ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው የጌታን ልብ ማንም እንደማያውቀው ለማስረዳት ነው። ትኩረት፦ «የጌታን ልብ ማንም ሊያውቀው አይችልም። ስለዚህ ቀድሞኑ ስለማያውቀው ማንም ሊታስተምረው አይችልም።»

---

Chapter 3

1 Corinthians 3:1

1ቆሮንቶስ 3:1-2
መንፈሳዊ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚኖሩ ሰዎች ሥጋውያን ሰዎች የራሳቸውን ፍላጎት የሚከተሉ ሰዎች በክርስቶስ እንደ ሕፃናት የቅሮንቶስ ሰዎች በዕድሜአቸው ለመረዳት ገና እንደሆኑ ከሕፃናት ጋር ተነጻጽረዋል። ትኩረት፦ «በክርስቶስ በጣም ወጣት አማኞች» ተመልከት፦ ጠንካራ ምግብ ሳይሆን ወተት ጋትኩአችሁ የቆሮንቶስ ሰዎች ወተት እንደሚጠጡ ሕፃናት ሕፃናት ቀለል ያሉ ነገሮችን ብቻ መረዳት ይችላሉ። እንዳደጉና ጠንክር ያለ ምግብ ለመብላት እንደማይችሉ ሕፃናት ትላልቅ ነገሮችን ለመረዳት የበሰሉ አይችሉም። የበቃችሁ አይደላችሁም «ክርስቶስን ስለመከተል ከበድ ያሉ ትምህርቶችን ለመረዳት የበቃችሁ አይደላችሁም»

1 Corinthians 3:3


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

1ቆሮንቶስ 3:3-5

እስካሁን ሥጋውያን ናችሁ እንደ ኃጢአተኛ መሆን ወይም እንደ ዓለማዊ ፍላጎት መመላለስ በሥጋ መስፈርት የምትመላለሱ አይደለምን? ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች ስለ ኃጢአተኛ ባሕርያቸው ይገስጻቸዋል። ትኩረት፡- «በሥጋዊ ፍላጎት መስፈርት ስለምትመላለሱ ልታፍሩ ይገባል!» በሰው መስፈርት የምትመላለሱ አይደለምን? ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች በሰው መስፈርት ስለሚመላለሱ ይገስጻቸዋል። ትኩረት፡- «የሰውን መስፈርት ስለምትከተሉ ልታፍሩ ይገባል።» እንደ ሰው የምትኖሩ አይደለምን? ትኩረት፡- «መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው ሰዎች እንደሚኖሩ ስለምትኖሩ ልታፍሩ ይገባል።» አጵሎስ ማን ነው? ጳውሎስስ ማን ነው? ጳውሎስ እርሱና አጵሎስ የወንጌል ዋና ምንጭ እንዳይደሉና ስለዚህም ተከታዮች ሊኖሩአቸው እንደማይገባ ለማስረዳት ነው። ትኩረት፡- «አጵሎስ ወይም ጳውሎስ በማለት ቡድን መመሠረት ስሕተት ነው።» በእነርሱ እጅ ያመናችሁ የጌታ አገልጋዮች ናቸው ጳውሎስ የራሱን ጥያቄ እርሱና አጵሎስ የእግዚአብሔር አገልጋዮች መሆናቸውን እንዲህ ሲል ይመልሳል። ትኩረት፡-«ጳውሎስና አጵሎስ የክርስቶስ ባሪያዎችና ክርስቶስን የተቀላችሁት እኛ ስላገለገልን ነው።» እያንዳንዳቸውን ጌታ እንደሰጣቸው ተግባር ያመናችሁ ትኩረት፡- ፡ «ፃመነን፥ ጌታ ተግባር የተሰጠን ሰዎች ብቻ ነን።»

1 Corinthians 3:6

1ቆሮንቶስ 3:6-7

ተከለ የእግዚአብሔር ዕውቀት ለማደግ ዘር መተከል ስላለበት ንጽጽር ነው። ውኃ አጠጣ የተዘረ ዘር ውኃ እንደሚያስፈልጋው እምነትም ለማደግ ተጨማሪ ትምህርት ያስፈልጋል። ዕድገት እጽዋት እንደሚያድጉና ፍሬ እንደሚያፈሩ እምነትም በእግዚአብሔር ማደግና ሥር መስደድና ጠንካራ ይሆናል።

የሚተክል ምንም አይደለም፥ ነገር ግን እንዲያድግ የሚያደርገው እግዚአብሔር ነው ጳውሎስ እርሱ ወይም አጵሎስ ለአማኞች ዕድገት ኃላፊነት ያለባቸው ቢሆንም ይህን የሚያደርገው ግን እግዚአብሔር ነው።

1 Corinthians 3:8

1ቆሮንቶስ 3:8-9

የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው መትከልና ማጠጣት ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ለማገልገል ራሱንና አጵሎስን የሚያነጻጽርበት እንደ አንድ ሥራ ቆጥሮአል። ደመወዝ በሠራው ሥራ መሠረት ለሠራተኛ የሚከፈል ገንዘብ መጠን ነው። እኛ ይህ የሚያመለክተው ጳውሎስንና አጵሎስን ሲሆን የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን አመለከትም።

ከእግዚአብሔር ጋር አብረው የሚሠሩ ጳውሎስ ራሱንና አጵሎስን ከእግዚአብሔር ጋር የሚሠሩ ሠራተኞች እንደሆኑ ይቆጥራል። የእግዚአብሔር እርሻ እግዚአብሔር አንድ ሰው እርሻው ፍሬ እንዲያፈራ እንደሚንከባከብ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ጥንቃቄ ያደርጋል። የእግዚአብሔር ሕንፃ እግዚአብሔር አንድ ሰው ሕንፃ እንደሚያንጽ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ቀርጾ ፈጥሮአታል።

1 Corinthians 3:10

1ቆሮንቶስ 3:10-11

ከእግዚአብሔር እንደተሰጠኝ ጸጋ «እግዚአብሔር እንድፈጽመው ሥራ በነፃ እንደሰጠኝ ጸጋ»

መሠረት ጠልኩ ጳውሎስ የእምነት ትምህርትና በክርስቶስ ያለውን ድነት ለሕንፃ መሠረት ከመጣል ጋር ተመሳሳይ ያደርገዋል።

ሌላው በላዩ ላይ የንጻል ሌላው ሠራተኛ እነዚህን አማኞች በመንፈሳዊ ርዳታ በቤተ ክርስቲያን ለማነጽ ይቀጥላል።

እያንዳንዱ ሰው ያድርግ ይህ የሚያመለክተው ባጠቃላይ የእግዚአብሔርን ሠራተኞችን ነው።ትኩረት፡- «እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔርን ያገልግል።»

ከተመሠረተ በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልም ትኩረት፡- «ማንም ሊመሠርት የማይችለውን አንድን መሠረት ብቻ መሥርቻለሁ ወይም እኔ ጳውሎስ መሠረትን መሠረትሁ»

1 Corinthians 3:12

1ቆሮንቶስ 3:12-13

እንግዲህ ማንም በመሠረቱ ላይ በወርቅ ቢሆን፥ በብር፥ በከበረ ድንጋይ፥በእንጨት፥በሣር ወይም በአገዳ ቢያንጽ፤ ሕንፃ ለማነጽ የምንጠቀምባቸው የሕንፃ መሣሪያዎች ሰው በመንፈሳዊ ባሕርይና ተግባሮችን በሕይወት ዘመኑ ለመንፈሳዊ ዋጋ ያለው እንዲሆን እንደምንገነባ ዓይነት ይነጻጸራል። ትኩረት፡- «አንድ ሰው በውድና በጠንካራ ዕቃዎች ወይም በሚቃጠል ርካሽ ዕቃዎች ይገነባል» የከበረ ድንጋይ «ውድ የሆኑ ድንጋዮች» የቀኑ ብርሃን ሲገለጠው ሥራው ይገለጣል የቀን ብርሃን የሕንፃ ሠራተኞችን ጥረት እንደሚገለጥ የሰውንም የሥራ ጥረትና እንቅስቃሴ ጥራት የእግዚአብሔር ብርሃን መገኘት ይገልጠዋል።»

በእሳት ሲፈተን የእያንዳንዱ ሥራ ጥራት በእሳት ይፈተናል እሳት በሚገለጥበት ጊዜ የሕንፃውን ጥንካሬ ወይም መውደቅ ይታወቃል፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር እሳት የሰውን ጥረትና እንቅስቃሴ ይፈትናል። ትኩረት፡- እሳቱ የሥራውን ጥራት ያሳያል።"

1 Corinthians 3:14

1ቆሮንቶስ 3:14-15

ይጸናል «ይቆያል» ወይም «ይቋቋማል» (UDB) ማንም ሰው ሥራው የተቃጠለበት ትኩረት፡- «የማንንም ሥራ እሳቱ ቢያጠፋ» ወይም «እሳቱ የማንንም ሥራ ቢያፈርስ» የማንም እርሱ ራሱ እነዚህ ቃላት የሚያሳየው «ሰው» ነው። ትኩረት፡- «ሰው» ወይም «እርሱ» (UDB) ኪሳራ ያጋጥመዋል ነገር ግን ራሱ ይድናል «በእሳቱ ተፈትኖ ካላለፈ ማንኛውም ሥራውንና ሽልማቱን ያጣል እግዚአብሔር ግን ያድነዋል።»

1 Corinthians 3:16

1ቆሮንቶስ 3፥16-17

የእግዚአብሔር መንፈስ የሚኖርባችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ አታውቁምን? ትኩረት፡- «የእግዚአብሔር መንፈስ የሚኖርባችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ እንደማያውቅ ሆናችሁ ታደርጋላችሁ»

ማፍረስ «ማፍረስ» ወይም «ማጥፋት» እግዚአብሔር ያንን ሰው ያፈርሰዋል ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነው፤ ያውም እናንተ ናችሁ። ትኩረት፡- «እግዚአብሔር ያንን ሰው ያፈርሰዋል ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነው፤ እናንተም ቅዱሳን ናችሁ።»

1 Corinthians 3:18

1ቆሮንቶስ 3፥18-20

ማንም ራሱን አያታልል በዚህ ዓለም ጥበበኛ የሆነ ማንም በውሸት ማመን የለበትም። በዚህ ዘመን «አሁን» ጥበበኛ ለመሆን «ሞኝ» ይሁን «የእግዚአብሔርን እውነተኛ ጥበብ ለማግኘት ዓለም የሚያስበው ሞኝነት እንደሆን ሰው መቀበል አለበት»

ጥበበኞችን በተንኮላቸው ይይዛቸዋል እግዚአብሔር ጥበበኛ እንደሆኑ የሚያስቡትን በራሳቸው ተንኮል ይይዛቸዋል። ጌታ የጥበበኞችን አሳብ ያውቃል ትኩረት፡- «ጌታ ጥበበኛ እንደሆኑ የሚያስቡ ሰዎች የሚያቅዱትን ያውቃል» ወይም «ጌታ የጥበበኞችን እቅድ ሁሉ አስቀድሞ ያውቃል» (UDB)

1 Corinthians 3:21

1ቆሮንቶስ 3፥21-23

ማንም ሰው በሰው ላይ መመካት የለበትም! ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን ትእዛዝ ይሰጣል። ትኩረት፡- «አንዱ መሪ ከሌላው እንዴት የተሻለ እንደሆነ መመካትን ያቁም።» ትምክት «ከመጠን በላይ ትዕቢትን መግለጥ» የቆሮንቶስ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን ማምለክ ሲገባቸው ጳውሎስን ወይም አጵሎስን ከፍ ከፍ ያድርጉ ነበር። እናንተ የክርስቶስ ናችሁ፤ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው።

---

Chapter 4

1 Corinthians 4:1

1ቆሮንቶስ 4፥1-2

በዚህ መሠረት መጋቢዎች ትኩረት፡- «ከእነዚህ መጋቢዎች የተነሣ እኛ» መጋቢዎች ታማኝ ሆነው መገኘት ይገባቸዋል ትኩረት፡- « እንዲህ እንድንሆን ይገባል»

1 Corinthians 4:3

1ቆሮንቶስ 4፥3-4

እኔ በእናንተ መፍረዴ ለኔ ትንሽ ነገር ነው ጳውሎስ በሰውና በእግዚአብሔር ፍርድ መካከል ያለውን ልዩነት ያመዛዝናል። ከእግዚአብሔር እውነተኛ ፍርድ ጋር ሲመዛዘን የሰው ፍርድ የማይጠቅም ነው። የሚመሠረትብኝ ክስ እንዳለ አላውቅም ትኩረት፡- «ማንኛውንም ክስ አልሰማሁም» ይህ ማለት ግን እኔ ንጹሕ ነኝ አይደለም። እኔ ንጹሕ መሆኔን ወይም አለመሆኔን ጌታዬ ያውቃል።»

1 Corinthians 4:5

1ቆሮንቶውስ 4፥5

ስለዚህ አትፍረዱ ጌታ ሲመጣ ሰለሚፈርድ እኛ እንፍረድ ጌታ ከመምጣቱ በፊት የጌታ ዳግም መምጣትን ያመለክታል በጨለማ የተሠወረውን ወደ ብርሃን ያመጣል እንዲሁም የልብንም አሳብ ይገልጣል እግዚአብሔር የሰውን አሳብና ዓለማ ይገልጣል። በእግዚአብሔር ፊት የተሰወረ ነገር የለም። የልብ «የሰው ልብ»

1 Corinthians 4:6


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

1ቆሮንቶስ 4፥6-7
ስለ እናንተ «ስለ እናንተ በጎነት» ከተጻፈው በላይ አትለፍ «በቅዱሳት መጻሕፍት ከተጻፈው ውጪ አታድርግ» (TFT) በእናንተና በሌሎች መካከል ልዩነት ቢያዩ ጳውሎስ በጳውሎስ ወይም በአጵሎስ በማመናቸው የተሻሉ እንደሆኑ የሚያስቡትን የቆሮንቶስ ሰዎች ገሰጻቸው። ትኩረት፦«እናንተ በሌሎች ሰዎች ላይ የበላይ አይደላችሁም።» በነፃ ያልተቀበልካው ምን አለህ? ጳውሎስ እግዚአብሔር በነፃ እንደሰጣቸው ይገልጻል። ትኩረት፦ «ማንኛውንም ያላችሁ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር የሰጣችሁ ነው!»
የተቀበልከው ከሆንህ እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድን ነው? ጳውሎስ በተቀበሉት ነገር በመመካታቸው ይገስጻል። ትኩረት፦ «ለመመካት መብት የላችሁም።» ወይም በምንም አትመኩ።»

1 Corinthians 4:8

1ቆሮንቶስ 4፥8-9
እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያትን መታያ እድርጎ አስቀመጠን ጳውሎስ ሐዋርያቱን እግዚአብሔር እንዴት ለዓለም እንዲታዩ መታያ እንዳለደረገ ሁለት መንገዶችን ይገልጻል። እኛን ሐዋርያትን መታያ አደረገን እግዚአብሔር ሐዋርያቱን እስረኛ በመጨረሻ ለስቅለት ራሳቸውን ትሑት አድርገው እንደሚቀርቡ እንደ ሮማ ወታደራዊ ሰልፍ ገልጣቸው።
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ይህ የአለም ህጎችን ወይም የሞራል መርሆዎችን ይመለከታል ፣ ወይም 2) ይህ የሚያመለክተው አንዳንድ ሰዎች በምድር ላይ የሚሆነውን የሚቆጣጠሩትን መንፈሳዊ ሀይል ነው።
ማስመለስ
ጳውሎስ የጠፋውን ንብረት በመግዛት ወይም የባሪያን ነፃ በመግዛት ምሳሌያዊ ምሳሌ ተጠቅሞ በመስቀል ላይ በመሞት ኢየሱስ ለህዝቡ ኃጢአት የከፈለውን ምስል ያሳያል ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)
ልጅ
ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለኢየሱስ አስፈላጊ ርዕስ ነው ። (መመሪያዎችን ይመልከቱ) መመሪያዎች_ሶፍትዌር መመሪያዎች
Galatians 4:6
ልጆች ናችሁ... ከእንግዲህ ወዲህ ወንድ ልጅ አይደለሁም
እዚህ ላይ ጳውሎስ ቃሉን የተጠቀመበት ለወንድ ልጅ ነው ምክንያቱም ርዕሰ ጉዳዩ ውርስ ነው። በባህሉ እና በአንባቢዎቹ ዘንድ ፣ ውርስ በተለምዶ ፣ ግን ሁልጊዜ ለወንዶች ልጆች ያልፋል ። እሱ እዚህ የሴቶች ሕፃናትን አልገለጸም ወይም አልገለጸም ።
“አባ አባት ሆይ” ብሎ የሚጠራ የልጁን መንፈስ በልባችን ውስጥ ልኮታል ።
እግዚአብሔር አብ የእግዚአብሄርን ልጅ መንፈስ ወደ አማኞች ልብ ልኮታል ። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ እንደሚወዳቸው ያውቃሉ ልክ እንደዚህ ደግ አባት ልጆቹን ይወዳል ።
የልጁን መንፈስ ወደ ልባችን ልከውናል
ልብ ለሚያሰበው እና ለሚሰማው ሰው ልብ ዘይቤ ነው ። አት: - "እንዴት ማሰብ እና እርምጃ መውሰድ እንዳለብን እንዲያሳይን የልጁን መንፈስ ልኮ ነበር" (ይመልከቱ። የበለስ_ቁጥር)
ልጁ
ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለኢየሱስ አስፈላጊ ርዕስ ነው ። (መመሪያዎችን ይመልከቱ) መመሪያዎች_ሶፍትዌር መመሪያዎች
የሚጠራችሁ
የሚጠራው መንፈስ ነው ።
አባ ፣ አባት
አንድ ትንሽ ልጅ አባቱን በጳውሎስ ቤት ቋንቋ ለአባቱ የሚናገርበት መንገድ ይህ ነው ፣ በገላትያ አንባቢዎች ቋንቋ ግን አይደለም ። የውጪ ቋንቋን ስሜት ለመጠበቅ ይህንን ቋንቋዎ “አባ” ከሚለው ጋር የሚመሳሰል ድምጽን ይተርጉሙ ።
ከእንግዲህ ወዲህ ባርያ አይደለህም... ደግሞም ወራሽ ነህ
ጳውሎስ አንባቢዎቹን አንድ ሰው እንደሆኑ አድርጎ እያነጋገራቸው ነው ፣ ስለዚህ “እርስዎ” እዚህ ነጠላ ነው ። (ይመልከቱ: የበለስ_የዎ)
ወራሽ
እግዚአብሔር ቃል የገባላቸው ሰዎች ንብረትንና ሀብትን ከቤተሰብ አባል እንደሚወርሱ ተደርገው ይወሰዳሉ ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)
Galatians 4:8
አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ የገላትያ አማኞችን በእምነት በእምነት ከመኖር ይልቅ እንደገና በእግዚአብሔር ሕጎች ስር እንደገና እንደሚሞክሩ አሳስቧቸዋል ።
አጠቃላይ መረጃ
ገለልተኛ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ገላትያዎችን መገሰሱን ቀጥሏል ።
የሆኑት
“እነዚያ እነዚያ” ወይም “እነዚያ መናፍስት”
በእግዚአብሔር ታውቀዋል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እግዚአብሔር ያውቅሃል” (የበለስ_ቁጥር / ተመልከት)
ወደ... መርሆዎች እንዴት ይመለሳሉ?
ይህ ከሁለቱም የአጻጻፍ ጥያቄዎች የመጀመሪያው ነው ። አት: - “ወደ... መርሆዎች” መመለስ የለብዎትም ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)
መሠረታዊ መርሆዎች
ይህንን ሐረግ በ 4፡3 ውስጥ እንደተረጉሙት በተመሳሳይ መንገድ ይተርጉሙ ።
እንደገና እንደገና በባርነት መሆን ይፈልጋሉ?
ይህ ጥያቄ እንደ መግለጫ ሊተረጎም ይችላል ። አት: - "እንደገና ባሪያዎች መሆን የለብዎትም!" ወይም እንደገና ባሪያዎች መሆን የሚፈልጉ ይመስላል። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)
Galatians 4:10
ቀናት እና አዲስ ጨረቃዎችን ፣ ወቅቶችን እና አመታትን ይመለከታሉ
ጳውሎስ እየተናገረ ያለው የተወሰኑ ጊዜዎችን ለማክበር ጥንቃቄ እንዳላቸው በማሰብ ነው ፣ ይህም ያንን ማድረጉ በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛ ያደርገዋል ። አት: - “ቀኖችን ፣ አዲስ ጨረቃዎችን ፣ ወቅቶችን እና ዓመቶችን በጥንቃቄ ታከብራላችሁ”
ምናልባት በከንቱ ሊሆን ይችላል
«ምንም ላይጠቅሙ ይችሉ ነበር» ወይም «ምንም ዓይነት ተፅእኖ አልደረሰም»
Galatians 4:12
አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ የገላትያ አማኞችን አብሯቸው በነበረበት ጊዜ እንዴት በደግነት እንዴት እንደያዙቸው የሚያስታውስ ሲሆን አብሯቸው በማይኖርበት ጊዜ በእሱ መታመናቸውን እንዲቀጥሉ አበረታቷቸዋል ።
መለመን
እዚህ ማለት በጥብቅ መጠየቅ ወይም መሻር ማለት ነው ። ይህ ገንዘብን ወይም ምግብን ወይም ቁሳዊ ቁሳቁሶችን ለመጠየቅ የሚያገለግል ቃል አይደለም ።
ወንድሞች
በ1፡1 ላይ እንዳለው ተርጉሙት
ምንም ጥፋት አላደረገብኝም
ይህ በአዎንታዊ መልኩ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “መልካም አደረግከኝ” ወይም “እንደቻልሽ አደረግከኝ”
ምንም እንኳን አካላዊ ሁኔታዎ ሊፈተን ቢችልም
“በአካላዊ ህመም ብታየኝ ለእኔ ከባድ ቢሆንም”
መናቅ
እጅግ መጥላት
Galatians 4:17
እናንተን ለማሳመን
እነሱን እንዲቀላቀሉ ለማሳመን "
ለመከላከል
"እኛን እንዳያሳየን" ወይም "ለእኛ ታማኝ አለመሆንን እንዲያቆም"
ለእነሱ ቀንቻለሁ
“የምታደርጉትን ሁሉ ለማድረግ በቅናት”
Galatians 4:19
አያያዥ መግለጫ
ፀጋ እና ህግ አብረው ሊሠሩ እንደማይችሉ ጳውሎስ ለአማኞች ይነግራቸዋል ።
ልጆቼ
ይህ ለደቀመዛምርቶች ወይም ለተከታዮች ዘይቤ ነው ። አት: - “በእኔ ምክንያት እናንተ ደቀመዛሙርቶች ናችሁ” (የበለስ_ማይታፎርን ይመልከቱ)
ክርስቶስ በውስጣችሁ እስኪመሠረት ድረስ በእናንተ ላይ ገና በወሊድ ሥቃይ ውስጥ ነኝ
ጳውሎስ ልጅ መውለድን ለገላትያ ሰዎች አሳቢነት ለማሳየት እንደ ዘይቤ ነው ። AT: - “እንቺን መውለድ የምችል ሴት እንደሆንኩ ያህል ህመም ይሰማኛል እናም ክርስቶስ በእውነት እስከሚቆጣጠርዎ ድረስ በሥቃዬ እቀጥላለሁ” (የበለስ_አሜን)

Galatians 4:21
ንገሩኝ
"አንድ ጥያቄ መጠየቅ እፈልጋለሁ" ወይም "የሆነ ነገር ልነግርዎት እፈልጋለሁ"
ሕግን አትሰሙምን?
ጳውሎስ ቀጥሎ ምን እንደሚል እያስተዋወቀ ነው። አት: - "ህጉ በትክክል ምን እንደሚል መማር ያስፈልግዎታል" ወይም "ህጉ በትክክል ምን እንደሚል ልንገራችሁ" (የበለስ_ቁስለትን ይመልከቱ)
Galatians 4:24
አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ አንድን እውነት ለመግለጽ ታሪክ ይጀምራል-ያ ሕግ እና ጸጋ አብረው ሊኖሩ አይችሉም ።
እነዚህ ነገሮች እንደ ምሳሌ ሊተረጎሙ ይችላሉ
ይህ የሁለቱ ልጆች ታሪክ እኔ አሁን የምነግራችሁን ስዕል ነው ”
እንደ ምሳሌ
“አመላካች” ማለት ሰዎች እና በውስጡ ያሉ ሌሎች ነገሮች የሚወክሉበት ታሪክ ነው ። በጳውሎስ ዘገባ ፣ በ 4 21 ውስጥ የተጠቀሱት ሁለቱ ሴቶች ሁለት ቃል ኪዳኖችን ይወክላሉ።
ሲና ተራራ
‹በሲና ተራራ› ሙሴ እዚያ ለነበሩ እስራኤላውያን የሰጠው ሕግ የሕግ ማሳያ ነው ። አት: - "ሙሴ ለእስራኤል ሕግን የሰጠበት በሲና ተራራ ላይ" (የበለስ_ስኔክዶቼን ይመልከቱ)
ባሪያዎች የሆኑ ልጆችን ትወልዳለች
ጳውሎስ ህጉን እንደ ሰው አድርጎ ይመለከታል። አት: - “በዚህ ቃል ኪዳን ስር ያሉ ሰዎች ሕጉን እንደሚታዘዙ ባሪያዎች ናቸው” (የበለስ_ቁጥር እና የበለስ_ቁጥር) ተመልከት
ይወክላል
"ስዕል ነው"
ከልጆ. ጋር በባርነት ውስጥ ናት
አጋር አጋርና ልጆችዋ ከእሷ ጋር ባሪያዎች ናቸው ። አት: - እንደ ኢየሩሳሌም እንደ ገዛ ባሪያ ናት ፣ ልጆችዋም ከእሷ ጋር ባሪያዎች ናቸው (ይመልከቱ ። የበለስ_ለታ)
Galatians 4:26
ነፃ
እዚህ “ነፃ” ማለት የታሰረ እንጂ ባርያ አይደለም።
ደስ ይበላችሁ
"ደስተኛ ሁኑ"
አንቺ መካን ያልሽ... አንቺ የማትሠቃይ
እዚህ “እርስዎ” መካን ሴትን ያመለክታል እና ነጠላ ነው። (ይመልከቱ: የበለስ_ዮዎ)
Galatians 4:28
ወንድሞች
በ1:1 ላይ እንዳለው ተርጉሙት
የተስፋ ቃል ልጆች
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች ገላትያኖች የእግዚአብሔር ልጆች ሆነዋል 1) በእግዚአብሔር ቃል በማመን (UDB) ወይም 2) እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ለመፈፀም ተዓምራትን ስለ ሠራ በመጀመሪያ በመጀመሪያ ለአብርሃም ወንድ ልጅን ከዚያም ገላትያንም የአብርሃምን ልጆች በመፍጠር እና ስለሆነም የእግዚአብሔር ልጆች ።
እንደ ሥጋ ፈቃድ
ይህ የሚያመለክተው አጋርን ሚስት አድርጎ በመውሰድ አብርሃም የእስማኤል አባት መሆንን ነው ። አት: - “በሰው ድርጊት” ወይም “ሰዎች በሠሩት ነገር ምክንያት” (ይመልከቱ።
እንደ መንፈስ ቅዱስ
“መንፈስ ቅዱስ በሆነ ነገር”
Galatians 4:30
ወንድሞች
በ1:1 ላይ እንዳለው ይተርጉሙ
ከነፃይቱ ሴት ይልቅ
የቀሩትን ቃላት እዚህ ውስጥ መሞላት ይቻላል ። ግን ይልቁን እኛ የነፃይቱ ሴት ልጆች ነን ”(ይመልከቱ ። የበለስ_ሊሲስ)

---

Chapter 5
Galatians 5:1
አያያዥ መግለጫ
ሁሉም ሕጎች እንደ እኛ ጎረቤቶቻችንን በመውደድ የተሟላ በመሆኑ ክርስቶስ አማኞች በክርስቶስ ነፃነታቸውን እንዲጠቀሙ በማስታወስ ይህንን ምሳሌ ተጠቅሟል ።
ለነፃነት
በቀደሙት ቁጥሮች ላይ ከተገለፀው ባርነት በተቃራኒ ትርጉሙ “ነፃነት” ን ማጉላት አለበት ።
ለነፃነት ክርስቶስ ነፃ አወጣን
ክርስቶስ ነፃ ያወጣን ነፃ እንድንሆን ነው ።
ጸንታችሁ ቁሙ
እዚህ ላይ ቆመ ማለት ላለመቀጠል መወሰንን ያሳያል ። እንዴት እንደማይቀየሩ በግልፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ሌላ ነገር ለሚያስተምሩ ሰዎች ክርክር አይስጡ” ወይም “ነፃ ለመሆን ቁርጥ ውሳኔ ያድርጉ” (የበለስ_ቁጥር እና የበለስ_ቁጥር ግልፅ) ይመልከቱ
እንድትገረዙ ብትፈቅዱ
ጳውሎስ ግርዘትን ለአይሁድ እምነት ምሳሌ አድርጎ ይጠቀማል። አት: - "ወደ የአይሁድ ሃይማኖት ብትመለሱ" (የበለስ_ቁጥር ተመልከት)
Galatians 5:3
መመስከር
“አውጁ” ወይም “ምስክርነት”
ለተገረዘ ሰው ሁሉ ይገረፋል
ጳውሎስ መገረዝ አይሁዳዊ ለመሆን እንደ ተመሳሳዩን ቃል ይጠቀማል። አት: - “አይሁዳዊ ለሆነ ሰው ሁሉ” (የበለስ_ቁጥር ተመልከት)
ግዴታ
“የታሰረ” ወይም “የታገደ” ወይም “የባርነት”
ከክርስቶስ ተለይተዋል
“ከክርስቶስ ጋር የነበረሽን ግንኙነት ጨርሰሻል”
በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል
እዚህ ላይ ጳውሎስ እዚህ ላይ እየተናገረ ነው ። በሕግ የተጠየቀውን ነገር ለማድረግ በመሞከር ማንም አይሁዳዊ ጻድቅ ሊሆን እንደማይችል በእውነት አስተምሯል ። አት: - “በሕግ የተጠየቀውን በማከናወን እናንተ ጻድቅ ትሆናላችሁ የምትሉ ሁሉ” ወይም “በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ” (ይመልከቱ ። የበለስ.
ከእንግዲህ ጸጋን አታገኝም
ያ ጸጋ ከየት እንደመጣ በግልፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እግዚአብሔር አይራራዎትም” (የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)
Galatians 5:5
አጠቃላይ መረጃ
እዚህ ላይ እኛ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስንና የክርስቲያኖችን ግርዘት የሚቃወሙትን ነው ። እሱ ምናልባት ገላትያዎችን ጨምሮ ሊሆን ይችላል። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)
ለ
ይህም የሆነው ምክንያቱ
እኛ የጽድቅን ተስፋ በእምነት በጉጉት እንጠባበቃለን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “እኛ ስለ እምነት የጽድቅ ተስፋ በእምነት እንጠብቃለን” ወይም 2) “በእምነት የሚመጣውን ትክክለኛውን የጽድቅ ተስፋ እንጠብቃለን” ።
እኛ የጽድቅን ተስፋ በጉጉት እንጠብቃለን
"እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከራሱ ጋር እንዲያጸናን በትዕግሥት እና በትዕግሥት እየጠበቅን ነው ፣ እናም እርሱ እንደሚያደርገው እንጠብቃለን"
መገረዝ ወይም አለመገረዝ አይጠቅምም
እነዚህ አይሁዶች ወይም አይሁዳዊ ያልሆኑ መሆናቸው መገለጫዎች ናቸው ። አት: - “አይሁዳዊም ሆነም አይሁዳዊ አለመሆን” (ይመልከቱ ።
ፍቅር ግን በእምነት ብቻ ነው ፤
"ይልቁንም ሌሎችን በመውደድ የምናሳየው እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ያለን እምነት ያሳስበዋል"

ማንኛውም ነገር ማለት ነው
የሚጠቅም ነው
እየሮጡ ነበር
“ኢየሱስ ያስተማረውን ተግባራዊ እያደረጉ ነው”
ይህ ማበረታቻ ከሚጠራችሁ አልወጣም
“ይህን እንድታደርግ ያሳመነሽ እግዚአብሔር አይደለም ፣ እርሱም የሚጠራው”
የሚጠራችሁ
የጠራቸው ምን እንደሆነ በግልጽ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እናንተ የእሱ ሕዝብ እንድትሆኑ የሚጠራችሁ” (የበለስ_ቁጥር ይመልከቱ)
ማሳመን
አንድን ሰው ማሳመን ማለት ያመነውን እንዲለውጥ እና በተለየ መንገድ እርምጃ እንዲወስድ ማድረግ ነው ።
Galatians 5:9
ሌላ እይታ አይወስዱም
እኔ የምነግራችሁን ከነገርዎት የተለየ ነገር አያምኑም ”
የሚያስጨንቃችሁ ሰው ቅጣቱን ይከፍላል
የሚያስጨንቅህን እግዚአብሔር ይቀጣል "
የሚያውክህ
“እውነቱን እንድታውቁ ያደርጋችኋል” ወይም “በመካከላችሁ ችግር ያስነሳል”
ማንም ቢሆን
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የሙሴን ሕግ መታዘዝ እንዳለባቸው የሚናገሩትን ሰዎች ስም አያውቅም ወይም 2) ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች “ግራ የሚያጋቡ” ሀብታሞች መሆን አለመሆናቸውን እንዲገነዘቡ አልፈለገም ። ድሃ ወይም ትልቅ ወይም ትንሽ ወይም ሀይማኖት ወይም ሃይማኖተኛ ያልሆነ
Galatians 5:11
ወንድሞች ፣ እኔ አሁንም ስለ መገረዝ ብሰብክ አሁንም ለምን ስደት ይደርስብኛል?
ጳውሎስ ሰዎች እየሰደዱበት መሆኑን አፅን emphasizeት ለመስጠት የሌለበትን ሁኔታ እየገለጸ ነው ምክንያቱም ሰዎች አይሁድ መሆን አለባቸው ብለው እየሰበከ አይደለም ። ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። AT: - “ወንድሞች ፣ እኔ ገና አይሁዳውያን ስደት እያደረሱብኝ ስለ መገረዝ እንዳልናገር ታውቃላችሁ ።” (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር እና በለስ_ማቶ)
ወንድሞች
በ1፡1 ላይ እንዳለው ተርጉሙት
እንደዚያ ከሆነ የመስቀል ዕንቅፋት ተወግዷል
ጳውሎስ ሰዎች በመስቀል ላይ ባከናወኑት ሥራ እግዚአብሔር ይቅር እንደሚል ስለሚሰብክ ሰዎች ስደት እንደሚያደርሱበት ለማጉላት በሌለበት ሁኔታ እየገለጸ ይገኛል ። (ይመልከቱ: የበለስ_ኪፖ)
እንደዚያ ከሆነ
“ሰዎች አሁንም አይሁዳውያን መሆን አለባቸው” እያልኩ ከሆነ
የመስቀሉ እንቅፋት ተወግዷል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ስለ መስቀሉ ማስተማር እንቅፋት የለውም” ወይም “የመስቀል ትምህርት ምንም ነገር የሚያሰናክል ነገር የለም” (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)
የመስቀሉ እንቅፋት ተወግዷል
ማሰናከል ኃጢያትን ይወክላል ፣ እና እንቅፋት ሰዎችን ወደ ኃጢአት የሚወስድ አንድ ነገርን ይወክላል። በዚህ ሁኔታ ኃጢያቱ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል እንዲሆን ለማድረግ ፣ ሰዎች ለእኛ ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንደሞተ ማመን ብቻ ያስፈልጋቸዋል የሚለውን አስተምህሮ እውነታውን አለመቀበል ነው ። አት: - “ሰዎች ስለ እውነት እንዲናገሩ የሚያደርጋቸው የመስቀል ትምህርት ተወግ "ል” ወይም “ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን አስመልክቶ ሰዎች ትምህርቱን እንዲተዉ የሚያደርጋቸው ምንም ነገር የለም” (የበለስ_ቁጥር እና የበለስ_ቁጥር ግልፅ)
ብልታቸውን ይቆረጡ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ቃል በቃል ፣ የወንዶች አካሎቻቸውን ለመቁረጥ ጃንደረቦች ወይም 2) ዘይቤያዊነት ፣ ከክርስቲያን ማኅበረሰብ ሙሉ በሙሉ ይርቃሉ ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)
Galatians 5:13
ለ
ጳውሎስ በ 5:11 ውስጥ ለቃሉ የተናገረውን ምክንያት እየሰጠ ነው ።
ወደ ነፃነት ተጠርተዋል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል። አት: - “እግዚአብሔር ወደ ነፃነት ጠራህ” (የበለስ_ቁጥር / ተመልከት)
ወደ ነፃነት ተጠርተዋል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “ነፃ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ህዝቡ መረጠህ” ወይም 2) “ነፃ እንድትሆን እግዚአብሔር አዝዞሃል”
ወንድሞች
በ1፡1 ላይ እንዳለው ተርጉሙት
ለኃጢአተኛው ተፈጥሮ ዕድል
በእድሉ እና በኃጢያት ተፈጥሮ መካከል ያለው ግንኙነት ይበልጥ በግልፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “እንደ ኃጢያተኛ ተፈጥሮዎት ለመምሰል እድል ይሰጡዎታል” (ይመልከቱ። የበለስ_ቁጥር)
ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) “መላውን ሕግ በአንድ ትእዛዝ ብቻ መግለጽ ይችላሉ ፣ ይህ ነው” ወይም 2) “አንድን ትእዛዝ በመታዘዝ ፣ ሁሉንም ትእዛዛት ታደርጋላችሁ ፣ እና አንደኛው ትእዛዝ ይህ ነው።”
ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ
“እርስዎ” ፣ “የእርስዎ” እና “ራስዎ” የሚሉት ቃላት ሁሉም ነጠላ ናቸው ። (ይመልከቱ: የበለስ_የዎ)
Galatians 5:16
አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ ኃጢአት በኃጢያት ላይ ቁጥጥርን እንደሚሰጥ ጳውሎስ አብራርቷል ።
በመንፈስ ተመላለሱ
በእግር መሄድ የሕይወት ዘይቤ ነው ። አት-“ሕይወትዎን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይኑሩ” ወይም “ሕይወትዎን በመንፈስ ላይ በመመካት ኑሩ” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)
የኃጢያተኛ ተፈጥሮአዊ ፍላጎቶችን አታሟላም
“የአንድን ሰው ምኞቶች ማከናወን” የሚለው ሐረግ “አንድ ሰው የሚፈልገውን አድርግ” የሚል ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። አት: - “ኃጢአተኛ ተፈጥሮህ የሚፈልገውን አትፈጽምም” (የበለስ_ ቪዲዮን ተመልከት)
የኃጢያት ተፈጥሮ ምኞቶች
የኃጢያተኛው ተፈጥሮ ሰው ሆኖ ኃጢአት መሥራት እንደፈለገ ተደርጎ ተገልጻል። አት: - “በኃጢአተኛ ተፈጥሮህ ምን ማድረግ ትፈልጋለህ” ወይም “sinfulጢአት ስለሆንክ ምን ልታደርጋቸው ትፈልጋለህ?”
ከሕግ ስር አይደለም
'የሙሴን ሕግ የመታዘዝ ግዴታ አልነበረውም'
Galatians 5:19
የኃጢያት ተፈጥሮ ሥራዎች
“ሥራ” የሚለው የግሪክኛ ስም “እሱ” ከሚለው ግስ ጋር ሊተረጎም ይችላል። አት: - "የኃጢያት ተፈጥሮ ምን ያደርጋል"
የኃጢያት ተፈጥሮ ሥራዎች
የኃጢያተኛው ተፈጥሮ ነገሮችን የሚያደርግ የሚያደርግ ሰው ነው ተብሎ ተገልጻል። አት: - “ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት የሚያደርጉት” ወይም “ሰዎች ኃጢአተኞች በመሆናቸው ምክንያት የሚያደርጉት” (ይመልከቱ። የበለስ_ከዋክብት)
መውርስ
ለአማኞች እግዚአብሔር ቃል የገባውን ቃል መቀበል ከቤተሰብ አባል ንብረትንና ሀብትን እንደሚወርስ ይገለጻል ። (ይመልከቱ: የበለስ_ቁጥር)
Galatians 5:22
የመንፈስ ፍሬ ፍቅር… ራስን መግዛት ነው
ቁጥጥር - ጳውሎስ ሰዎች በሌሎች ሰዎች ሊያዩት ለሚችሉት ዘይቤ እንደ ዘይቤ ይጠቀማል ። አት-መንፈስ ቅዱስ የሚቆጣጠራቸው ሰዎች ፍቅርን ይገልጣሉ ... እንደ ዛፍ ራስን መግዛትን ያፈራል "(ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር) ።
የመንፈስ ፍሬ
"መንፈስ ምን ያፈራል"
የኃጢያተኛ ተፈጥሮውን በስሜቱ እና ፍላጎቱ ላይ ሰቀሉት
ጳውሎስ እንደ ሰው ስብዕና በኃጢያት ተፈጥሮአቸው ለመኖር ፈቃደኛ ያልሆኑ ክርስቲያኖችን ይናገራል ፣ እነሱ በመስቀል ላይ ስለገደሉት ። አት-“በመስቀል ላይ እንደገደሉት አድርገው ከኃጢያት ተፈጥሮው እና ፍላጎቱ ጋር ላለመመኘት እምቢ” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቀፎ እና የበለስ_ቁጥር)
የኃጢያት ተፈጥሮ እና ፍላጎቶች እና ምኞቶች

የኃጢያት ተፈጥሮው ምኞት እና ምኞት ያለው ሰው እንደሆነ ተደርጎ ተገልጾል። አት: - “የኃጢአታቸው ተፈጥሮ ፣ እና በእሱ ምክንያት ለማድረግ በጣም የፈለጉት ነገር” (ይመልከቱ።
Galatians 5:25
በመንፈስ የምንኖር ከሆነ
"የእግዚአብሔር መንፈስ በሕይወት እንድንኖር አድርጎናል"
በመንፈስ ተመላለሱ
በየቀኑ "መራመድ" ዘይቤ ነው ። አት: - "እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን እና የምናከብርውን ነገር እናደርጋለን ፣ ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ እንዲመራን ፍቀድልን" (የበለስ_ቁጥር ን ይመልከቱ)
እንፍቀድ
“አለብን”

---

Chapter 6
Galatians 6:1
አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ አማኞችን ሌሎች አማኞችን እንዴት መያዝና እግዚአብሔር እንዴት ወሮታ እንደሚሰጥ አስተምሯቸዋል።
ወንድሞች
በ1፡1 ላይ እንዳለው ተርጉሙት
አንድ ሰው
“አንድ ሰው” ወይም “ከመካከላችሁ ማንም”
በሆነ ኃጢአት ተይዟል
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አንድ ሰው በድርጊቱ ውስጥ የተገኘ ሰው ፣ “በኃጢያት ተገኝቷል ፣” ወይም 2) ያ ሰው ክፋትን ለማድረግ ሳይያስብ ኃጢአት ሠርቶ “እጅ ሰጠው ኃጢአት ሠርቷል” ።
እናንተ መንፈሳዊ የሆናችሁ
“ከእናንተ በመንፈስ የሚመሩ” ወይም “በመንፈስ መሪነት የምትኖሩ”
አቅኑት
"የበደለውን ሰው እርማት" ወይም "የበደለውን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ትክክለኛው ዝምድና እንዲመለስ አጥብቀው ይመክሩ"
በገርነት መንፈስ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) መንፈስ እርማትን የሚሰጥ ወይም 2) “በገርነት” ወይም “በደግነት” የሚመራው መንፈስ ነው ።
ስለራስዎ ያስቡ
እነዚህ ቃላት ገላትያንን እያንዳንዳቸውን እንደሚናገር ለማጉላት ሁሉም አንድ ሰው እንደሆኑ አድርገው ይመለከቷቸዋል ። AT: - “ስለራሳችሁ አስቡ” ወይም “እያንዳንዳችሁን ፣ ስለ ራሳችሁ ጉዳይ ይጨነቁ” እላለሁ ።
እንደዚሁም እናንተ እንዳትፈተን ይሆናል
ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - “ስለሆነም ምንም ኃጢአት እንዳትሠሩ እንዳትፈታተኑ” (የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)
Galatians 6:3
ለ
"ምክንያቱም።" ይህ የሚያሳየው የሚከተለው ቃል የገላትያ ሰዎች 1) “አንዱ የሌላውን ሸክም መሸከም” (6 1) ወይም 2) እነሱ ራሳቸው እንዳልተፈተኑ ተጠንቀቁ (6 1) ወይም 3) “እንዳይታለሉ” ( 5 1) ።
እሱ አንድ ነገር ነው
“እሱ በጣም አስፈላጊ የሆነ ሰው ነው” ወይም “እሱ ከሌላው ይበልጣል”
እርሱ ምንም አይደለም
እሱ እሱ አስፈላጊ አይደለም ወይም “እሱ ከሌሎቹ አይሻልም”
እያንዳንዳቸው ማድረግ አለባቸው
እያንዳንዱ ሰው የግድ መሆን አለበት
እያንዳንዱ የራሱን ሸክም ይይዛል
እያንዳንዱ ሰው የሚፈርደው በገዛ ሥራው ብቻ ነው ወይም “እያንዳንዱ ሰው ለገዛ ሥራው ብቻ ነው ተጠያቂው”
እያንዳንዱ ያደርጋል
እያንዳንዱ ሰው ያደርጋል
Galatians 6:6
እሱ
"ሰውየው"
ቃል
እዚህ ላይ ይህ ማለት እግዚአብሔር “በእግዚአብሔር ቃል” ወይም “በእውነት ቃል” ማለት እግዚአብሔር የተናገረው ወይም ያዘዘውን ሁሉ ማለት ነው ።
ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል
መትከል በአንድ ዓይነት ውጤት የሚጠናቀቁ ነገሮችን ማድረጉን ይወክላል ፣ እናም መሰብሰብ አንድ ሰው ያደረገውን ውጤት ያሳያል ማለት ነው። አት: - “አንድ ገበሬ ማንኛውንም የተተከለውን ዘር ፍሬ እንደሚሰበስብ ሁሉ ፣ እያንዳንዱ ሰው የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር ያገኛል” (ይመልከቱ። የበለስ_ቁጥር)
ሰው ... የእሱ
እዚህ እዚህ ላይ ጳውሎስ ወንዶችን አልገለጸም ። "ሰው ... ያ ሰው"
ለእራሱ የኃጢያት ተፈጥሮ ዘሩ
እንደ ኃጢአተኛው ተፈጥሮው ዘር ይተክላሉ። በኃጢያት ተፈጥሮው ምክንያት ይህ ማድረግ የሚፈልገውን ማድረጉን ይወክላል። አት: - “በኃጢያት ተፈጥሮው እንደፈለገው እንደ ዘር ይተክላል” ወይም “በኃጢያቱ ተፈጥሮው ለማድረግ የሚፈልገውን ነገር ያደርጋል” (የበለስ_ቁጥር እና የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)
በጥፋት ይሰበሰባሉ
“ላደረገው ነገር ቅጣትን ይቀበላል” (ይመልከቱ ። የበለስ_ቁጥር)
እጽዋት ለመንፈስ ፍሬ ይሰጣሉ
የእግዚአብሔር መንፈስ የወደደውን ያደርጋል “(የበለስ_ቁጥር ተመልከት)
ከመንፈስ የዘላለም ሕይወት ይሰበሰባሉ
ከእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ሽልማት የዘላለም ሕይወት ይቀበላሉ ”
Galatians 6:9
መልካም በማድረግ መልካም አናደርግም
“መልካም ማድረጋችንን መቀጠል አለብን”
ጥሩ መሥራት
ለሌሎች ደህንነት ሲባል መልካም ማድረግ
በትክክለኛው ጊዜ
“በጊዜው” ወይም “እግዚአብሔር በመረጠው ጊዜ”
ስለዚህ
"በዚህ ምክንያት" ወይም "በዚህ ምክንያት"
በተለይም ... ለእነዚያ
“ከሁሉም በላይ ... ለእነዚያ” ወይም “በተለይም ... ለእነዚያ”
ከእምነት የሆኑ ቤተሰቦች ናቸው
"በእምነት በእምነት የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት የሆኑት"
Galatians 6:11
አያያዥ መግለጫ
ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ ሲዘጋ ፣ ሕጉ የማያድን እና የክርስቶስን መስቀል ማስታወስ እንዳለበት አንድ ተጨማሪ ማሳሰቢያ ሰጣቸው ።
ትልልቅ ፊደላት
ይህ ማለት ጳውሎስ አፅን wantsት ለመስጠት ይፈልጋል 1) የሚቀጥለውን መግለጫ ወይም 2) ይህ ደብዳቤ የመጣው ከእርሱ ነው ።
በገዛ እጄ
ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ምናልባት ጳውሎስ ምን እንደሚጽፍ የነገረውን ይህን ደብዳቤ አብዛኛው ሰው የፃፈው ረዳት ሳይኖረው አይቀርም ፣ ግን ጳውሎስ ራሱ የፃፋውን ይህን የመጨረሻውን ክፍል ጻፈ ወይም 2) ጳውሎስ መላውን ደብዳቤ ራሱ ጻፈ።
ጥሩ ስሜት ያሳድሩ
"ሌሎች ስለእነሱ እንዲያስቡ" ወይም “ሌሎች ጥሩ ሰዎች ናቸው ብለው እንዲያስቡ አድርጓቸዋል”
በስጋ
“በሚታይ ማስረጃ” ወይም “በእራሳቸው ጥረት”
ማስገደድ
"በኃይል" ወይም "በከፍተኛ ተጽዕኖ"
ስለ ክርስቶስ መስቀል እንዳይሰደዱ ብቻ ነው
አይሁዶች እንዳያሳድዱት "ክርስቶስ መስቀል ብቻውን ሰዎችን ያድናል"
መስቀሉ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እዚህ ላይ መስቀል በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገውን ያሳያል ። አት: - "ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያከናወነው ሥራ" ወይም "የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ" (ይመልከቱ። የበለስ.

ይፈልጋሉ

እንድትገረዙ የሚጠይቁአችሁ ሰዎች

ስለ ሰውነታችሁ እንዲኩራሩ

"ህግን ለመጠበቅ በሚሞክሩ ሰዎች ላይ ስለጨምሩህ ይኮሩ ዘንድ"

Galatians 6:14

ነገር ግን ከመስቀል በስተቀር በምንም አልኩ

"ከመስቀል ውጭ በሌላ በየትኛውም ነገር መመካት አልፈልግም" ወይም "በመስቀል ብቻ ልኮራ"

ዓለም ለኔ ተሰቅሏል

ይህ በንቃት ቅርፅ ሊገለፅ ይችላል ። አት: - "ዓለምን እንደ ቀድሞው አስባለሁ" ወይም "ዓለምን በመስቀል ላይ እንደገደለው ወንጀለኛ አደርገዋለሁ" (የበለስ_ቁጥር / ይመልከቱ)

እኔ ለዓለም

ከዚህ በፊት ካለው ሐረግ ውስጥ "ተሰቅለዋል" የሚሉት ቃላት ተረድተዋል ። አት: - "እኔ ለዓለም ተሰቅዬአለሁ" (የበለስ_ሊሲስስ ይመልከቱ)

እኔ ለዓለም

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ዓለም እንደ ቀድሞው እንደቆየችኝ" ወይም 2) "እግዚአብሔር በመስቀል ላይ እንደገደለው ወንጀለኛ ቆጠረችኝ"

ዓለም

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) የዓለም ሰዎች ፣ ለእግዚአብሄር ምንም ደንታ የሌላቸውም ወይም 2) ለእግዚአብሄር ምንም ግድየለሾች የሚያሳስባቸው ነገር አስፈላጊ ናቸው ።

ለማንኛውም ነገር ይቆጥራል

"ለእግዚአብሔር አስፈላጊ ነው"

አዲስ ፍጥረት

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አዲስ ክርስቶስ አማኝ ወይም 2) የአማኝ አዲስ ሕይወት።

ሰላምና ምሕረት በእስራኤል አምላክ ላይ ይሁን

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) አማኞች በአጠቃላይ የእግዚአብሔር እስራኤል ናቸው ወይም 2) "ሰላምና ምሕረት በአህዛብ አማኞችና በእግዚአብሔር እስራኤል ላይ ይሁን" 3) "ህጉን ለሚከተሉ እና ምህረት ሊሆኑ ይችላሉ ። በእግዚአብሔር እስራኤል ላይ ይሁን።

Galatians 6:17

ከ አሁን ጀምሮ

ይህ ደግሞ "በመጨረሻም" ወይም "ይህን ደብዳቤ እንደጨረስኩ" ማለት ይችላል ።

ማንም አያስቸግረኝ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች እንዳያስቸግሩት ፣ "ይህን እያዘዝኩህ ነው ፣ አትጨነቅ" ወይም 2) ጳውሎስ ሁሉንም ሰዎች እንዳያሳዝኑት ለገላትያኖች እየነገራቸው ነው ፣ "እኔ ነኝ ይህን ሁሉ ለሁሉም በማዘዝ "አታስጨንቁኝ ፣" ወይም 3) ጳውሎስ ምኞቱን እየገለጸ ነው ፣ "ማንም እንዲያስቸገረኝ አልፈልግም ።

ያስቸገረኝ

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) "ስለእነዚህ ጉዳዮች ለእኔ ንገሩኝ" (ዩ.አር.ቢ.) ወይም 2) "ችግር ያመጣብኛል" ወይም "ጠንክሮ ስጠኝ" ።

እኔ የኢየሱስን ምልክቶች በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና

እኔ የኢየሱስን አገልግሎት በማግኘቴ በሰውነቴ ውስጥ የተፈወሱ ቁስሎች አሉኝ "ወይም" እኔ የኢየሱስ በመሆኔ አሁንም እኔ በሰውነቴ ውስጥ የተፈወሰው የቁስል ምልክት አለኝ ።

ምልክቶች

ሊሆኑ የሚችሉ ትርጉሞች 1) በጦር ወታደር በወታደር ወይም በአገልጋይ በአደገኛ ሥራ ላይ ከደረሰባቸው ቁስል ቁስሎች ወይም 2) የባሪያ መለያ ምልክት የሆኑ ምልክቶች ።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን

"ጌታ ኢየሱስ ለመንፈሳችሁ ደግ እንዲሆን እጸልያለሁ"

ወንድሞች

በ1:1 ላይ እንዳለው ተርጉሙ

---

Chapter 1

Ephesians 1:1

ኤፌሶን 1:1-2

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ይህን ደብዳቤ የሚከፍተው በእግዚአብሔር ፊት ያላቸውን የአማኞችን ደረጃ እና ደህንነት በመናገር ነው። በእግዚአብሔር ፈቃድ፡ "በእግዚአብሔር ፈቃድ" ወይም "በእግዚአብሔር ምርጫ" ለእግዚአብሔር ለተለዩት ትኩረት፡ "በግብረ ገብ ያለ ነቀፋ መሆን" ወይም "ቅዱሳን" በክርስቶስ ኢየሱስ ለሚያምኑ፡

Ephesians 1:3

ኤፌሶን 1:3-4

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባትና አምላክ ይባረክ፡ ትኩረት፡ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክና አባት እንባርከው" የባረከን፡ ትኩረት፡"እግዚአብሔር ባርኮናልና" "ባረከን" የሚለው ቃል ጳውሎስን እና በኤፌሶን ያሉትን አማኞች ያጠቃልላል። በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ፡ ትኩረት፡"ከእግዚአብሔር መንፈስ የሚመጣ በረከት ሁሉ" በክርስቶስ፡ "በክርስቶስ" እና ተመሳሳይ አገላለጦች ዘይቤያዊ አባባሎች ሲሆኑ በተደጋጋሚ በአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ውስጥ የምናገኛቸው ናቸው። እንዚህ አባባሎችም በክርስቶስና እና በእርሱ በሚያምኑት መካከል ጠንካራ ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው። (ተመልከት፡ [[rc://*/tw/bible/kt/inchrist]]) ቅዱሳንና ነውር የሌለን እንሆን ዘንድ፡ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ልንሆን የምንችላቸውን ሁለት ባህሪያት ያሳየናል።

Ephesians 1:5

ኤፌሶን 1:5-6

እግዚአብሔር * የራሱ ልጆች አድርጎ ሊቀበለን አስቀድሞ ወሰነን፡ "ሊቀበለን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን፥የኤፌሶንን ቤተክርስቲያን እና በክርስቶስ ውስጥ ያሉትን አማኞች ነው። ትኩረት፡"እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ ልጆች አድርጎ ሊቀበለን ወሰነ" ልጆች አድርጎ ሊቀበለን፡ እዚህ ጋር"ልጆች አድርጎ ሊቀበለን" የሚለው ሃሳብ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት መቀላቀልን አመልካች ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ፡ እግዚአብሔር አማኞችን ወደ ራሱ ቤተሰብ የሚያመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ አማካኝነት ነው። ይህንንም የፈጸመው ሊያደርግ የፈለገውን ነገር ለማድረግ ደስ ስለተሰኘ ነበር፡ "የፈፀመው" እና "ሊያደርግ" የሚሉት ቃላት እግዚአብሔርን አመላካች ናቸው። በሚወደው በልጁ፡ "የእግዚአብሔር ውድ" ወይንም "ኢየሱስ ክርስቶስ"

Ephesians 1:7

ኤፌሶን 1:7-8

በሚወደው ልጁ፡ "በእግዚአብሔር ውድ፥በኢየሱስ ክርስቶስ" ቤዛነትን*አገኘን "አገኘን" የሚለው ቃል ሁሉንም አማኞች ነው።
ፀጋ*ተትረፍርፎ፡ "የእግዚአብሔር ፀጋ ታላቅነት" ወይም "የእግዚአብሔር ፀጋ መትረፍረፍ" በጥበብና በማስተዋል ሁሉ፡ እግዚአብሔር ለአማኞች ታላቅ ጥበብ እና ማስተዋል ሰጥቷል። ትኩረት፡"የበዛ ጥበብ እና ማስተዋል።"

Ephesians 1:9

ኤፌሶን 1:9-10

በፈቃዱ መሰረት፡ "እንደ እርሱ ደስታ" በክርስቶስ፡ "በክርስቶስ" እና ተመሳሳይ አገላለጦች ዘይቤያዊ አባባሎች ሲሆኑ በተደጋጋሚ በአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ውስጥ የምናገኛቸው ናቸው። እንዚህ አባባሎችም በክርስቶስና እና በእርሱ በሚያምኑት መካከል ጠንካራ ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው። (ተመልከት፡ [[rc://*/tw/bible/kt/inchrist]]) በእቅዱ ውስጥ ያለውን፡ ትኩረት፡"ትክክለኛው ጊዜ ሲደርስ" ዕቅዱን የሚፈፀምበት ጊዜ ሲደርስ፡ ትኩረት፡"እርሱ እቅዱን ይፈፅማል"

Ephesians 1:11

ኤፌሶን 1:11-12

ተመረጥን፡ "እግዚአብሔር የእርሱ ርስት እንሆን ዘንድ መረጠን" ወይም እግዚአብሔር የእርሱን ርስት እንቀበል ዘንድ መረጠን።" አስቀድሞም ተወሰንን፡ "ተወሰንን" የሚለው ቃል ጳውሎስን እና የአይሁድን በክርስቶስ አማኝ ህዝብ እንጂ አህዛብን በሚያደርገው ዕቅድ፡ "የእግዚአብሔር እቅድ" እንደ ገዛ ፈቃዱ በሚያደርገው ዕቅድ መሠረት፡ "የእግዚአብሔር ፈቃድ"

Ephesians 1:13



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ኤፌሶን 1:13-14
የእውነት ቃል የሰማችሁት በክርስቶስ ነው፡ ትኩረት:"በክርስቶስ በማመናችሁ በእርሱ እንደዳናችሁ ሰማችሁ" በክርስቶስ አማካይነት የመዳናችሁ ወንጌል የሆነውን፡ ትኩረት:"ክርስቶስ የመዳናችሁ ወንጌል ነው" ባመናችሁበትና፡ ትኩረት፡ "እናንተም በክርስቶስ አመናችሁ" በመንፈስ ቅዱስ በታተማችሁበት፡ ደብዳብ በሰም እንድሚታሸግ እና ማን እንድላከው ምልክት እንድሚደረግበት፥እግዚአብሔርም እንዲሁ በመንፈስ ቅዱስ አትሞ ባለቤትነቱን ያሳያል። ትኩረት፡ "እግዚአብሔር በተስፋው ቅዱስ መንፈስ አትሟችኋል" (ተመልከት፡ እንዲሁም
መንፈስ ቅዱስ የርስታችን ዋስትና የሚሆን መያዣ፡ እግዚአብሔር በትክክለኛው ጊዜ መንፈስ ቅዱስን የዘላለም ህይወት ተስፋ ስጦታ አድርጎ ሰጠን። ትኩረት:"መንፈስ ቅዱስ ዋስትና ነው።" ተስፋ የተደረገው ሀብት በእጅ እስገሚገባ ድረስ፡ ትኩረት፡ "የርስታችንን ሃብት እስክናገኝ ደረስ" ወይንም "ርስታችንን እስክንቀበል ድረስ"

Ephesians 1:15

ኤፌሶን 1:15-16
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች ከመፀለዩም በላይ አማኞች በክርስቶስ ውስጥ ስላላቸው ሃይል ያመሰግናል። ስለዚህ፡ "በዚህ ምክንያት" ለእርሱም ቅዱሳን ሁሉ ስላላችሁ፡ "ለክርስቶስ ቅዱሳን ላላችሁ ፍቅር" ወይም "ለአማኞች ሁሉ ላላችሁ ፍቅር" እግዚአብሔርን ማመስገን*አላቋረጥሁም፡ ትኩረት:"ማመስገኔን እቀጥላለሁ"

Ephesians 1:17

ኤፌሶን 1:17-18
እርሱን ለማወቅ * የጥበብ እና የመገለጥ መንፈስ:
ትኩረት:"የእርሱን መገለጥ መረዳት የሚያስችል መንፈሳዊ ጥበብ" የልባችሁ ዐይኖች እንዲበሩ፡ "የልባችሁ አይኖች እንዲበሩ" የሚለው ሃረግ የአንድን ሰው የማስተዋል ሁኔታ ይገልፃል። ትኩረት:"ማስተዋልን አግኝታችሁ እንዲበራላችሁ" የመጠራታችን ተስፋ፡ "የጥሪያችን ተስፋ" የርስቱ ክብር ባለጠግነት፡ "የርሱ የከበረ ርስት ባልጠግነት" ወይም "የከበረው ርስቱ ብዛት" በእርሱ ቅዱሳን፡ ይህ ሃሳብ ያለ ነቀፋ መሆንን፥መለየትን እና መቀደስን ያጠቃልላል።

Ephesians 1:19

ኤፌሶን 1:19-21
የኀይሉ ታላቅነት ምን እንደሆነ፡ የእግዚአብሔር ሃይል ከሌሎች ሃይል ሁሉ ይበልጣል። እንደ ኀይሉ ብርታት አሠራር፡ ትኩረት:"ለእኛ የሚሰራልን ታላቅ ሃይል" በቀኙ እንዲቀመጥ፡ "ክርስቶስን በእግዚአብሔር ቀኝ አስቀመጠው" ወይም "ክርስቶስ በክብር ስፍራ ተቀመጠ" ከማንኛውም ግዛት፥ ሥልጣን፥ኀይልና ጌትነት *በላይ፡ እነዚህ የተለያዩ የልዕለ ተፈጥሮ አካላትን ማለትም ሁለቱም የመላዕክትም ሆነ የዲያብሎስን ደረጃዎች ያሳያሉ። በዚህ ዘመን፡ "በዚህ ጊዜ" በሚመጣውም ዘመን፡ "ወደፊት"

Ephesians 1:22

ኤፌሶን 1:22-23
እግዚአብሔር * እንዲገዛ አድርጓል፡
"እግዚአብሔር አስቀመጠለት" "እግዚአብሔር አደረገለት" (UDB) በክርስቶስ እግር ሥር፡ እዚህ ጋር "እግር" የክርስቶስን ጌትነት፥ስልጣን እና ሃይል ይወክላል።" በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሁሉም ነገር ላይ ራስ አድርጎ ሾሞታል፡ "ራስ" የሚያመለክተው መሪነትን ወይም ሃላፊነትን ነው። ትኩረት:"በቤተክርስቲያን ውስጥ ባሉ ነገሮች ላይ ሁሉ ይገዛል" የእርሱ * አካሉ፡
ብዙውን ጊዜ የክርስቶስ አካል የሚለው ቤተክርስቲያንን ነው። በሁሉም መንገድ የሚሞላው የእርሱ ሙላት፡ ትኩረት:"ክርስቶስ ለነገሮች ሁሉ ህይወት እንደሚሰጥ ቤተክርስቲያኑን በህይወት እና በሃይል ይሞላታል"

Chapter 2

Ephesians 2:1

ኤፌሶን 2:1-3
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ አማኞችን ስላለፈው ጊዜ ካስታወሳቸው በኋላ አሁን ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ያላቸውን ሁኔታ ይነግራቸዋል። ከበደላችሁና ከሓጢአታችሁ የተነሳ የሞታችሁ ነበራችሁ፡ የሞተ ሰው በአካሉ ምላሽ መስጠት ሃጢያተኛ ሰዎች እንዴት እግዚአብሔርን መታዘዝ እንደማይችሉ ያሳያል። ከበደላችሁና ከሓጢአታችሁ የተነሳ፡ ሁለቱም "በደል" እና "ሐጢያት" የሚሉት ቃላት የሚያሳዩት አንድ አይነት ነገር ነው። ጳውሎስ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው የሰዎችን ሃጢያት ታላቅነት ነው። እንኖር ነበር፤ ይህ ሰዎች ይኖሩ የነበሩበትን ባህሪ ያሳያል። ትኩረት:"ቀድሞ ትኖሩ ነበር።" በዚያን ጊዜ የዚህን ዓለም ክፉ መንገድ በመከተል፡ ሐዋርያት "ዓለም" የሚለውን ቃል የሚጠቀሙት ስግብግብነት የሞላበትን ብልሹ የዚህ ዓለም ሰዎችን ባህሪያት ለማሳየት ነው። ትኩረት:"በዚህ ዓለም ውስጥ እንደሚኖሩት አይነት ሰዎች እሴት" ወይም የዚህን ጊዜያዊ ዓለም መርሆች በመከተል" በአየር ላይ ባሉት ኀይላት ላይ ገዥ ለሆነው፡ ይህ ዲያብሎስን ወይም ሰይጣንን ያመለክታል። ለሚሠራው መንፈስ፡ "ለሚሰራው መንፈስ" የሚለው ሃረግ ዲያብሎስ ወይም ሰይጣንን ያመለክታል። ለሥጋችን ክፉ ምኞት እየታዘዝንና ፈቃዱን እየፈጸምን፥ የአእምሮአችንንም ሐሳብ እየተከተልን፡ "ስጋ" እና "አዕምሮ" የሚሉት ቃላቶች መላው ሰውነትን ይወክላል። የቁጣ ልጆች፡ እግዚአብሔር የተቆጣቸው ሰዎች (ተመልከት፡

Ephesians 2:4

ኤፌሶን 2:4-7
እግዚአብሔር ምሕረት በማድረግ ባለጠጋ ስለሆነ፡ "እግዚአብሔር በምህረት የተትረፈረፈ ነው" ወይም "እግዚአብሔር ለእኛ እጅግ ሩህሩህ ነው" ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ፡ "ለእኛ ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሳ" ወይም "እጅግ በጣም ስለሚወደን" በበደላችን ሙታን በነበርንበት ጊዜ እንኳ ከክርስቶስ ጋር አዲስ ሕይወት ሰጠን፡ ይህ የሚያሳየው የሞተ ሰው ከሞት ካልተነሳ በቀር ምላሽ መስጠት እንደማይችል፤ሃጢያተኛ ሰውም አዲስ መንፈሳዊ ህይወት ካልተቀበለ እግዚአብሔርን መታዘዝ አይችልም። በክርስቶስ ኢየሱስ፡ "በክርስቶስ ኢየሱስ" " እና ተመሳሳይ አገላለጦች ዘይቤያዊ አባባሎች ሲሆኑ በተደጋጋሚ በአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ውስጥ የምናገኛቸው ናቸው። እነዚህ አባባሎችም በክርስቶስና እና በእርሱ በሚያምኑት መካከል ጠንካራ ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው። (ተመልከት፡ [[rc://*/tw/bible/kt/inchrist]]) በሚመጣው ዘመን፡ "ወደፊት"

Ephesians 2:8

ኤፌሶን 2:8-10
የዳናችሁት በእምነት አማካይነት በጸጋ ነውና፡ የእግዚአብሔር ርህራሄ በኢየሱስ በማመን ብቻ ከፍርድ ልንድን የቻልንበት ሁኔታ ነው። ትኩረት:"በእርሱ በማመናችሁ ምክንያት እግዚአብሔር በፀጋው አዳነን።" የሆነ ነገር አይደለም፡ "የሆነ ነገር" የሚለው ሃረግ ወደ ኋላ "የዳናችሁት በእምነት አማካይነት በጸጋ ነውና" የሚለውን አመላካች ነው። በስራ የተገኘ አይደለም፡ ትኩረት:"ይህ መዳን በስራ አማካኝነት የተገኘ አይደለም" የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን፡ "ነን" የሚለው ቃል ጳውሎስን እና በኤፌሶን ያሉትን አማኞች ሁሉ ነው። በክርስቶስ ኢየሱስ፡ "በክርስቶስ ኢየሱስ" " እና ተመሳሳይ አገላለጦች ዘይቤያዊ አባባሎች ሲሆኑ በተደጋጋሚ በአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ውስጥ የምናገኛቸው ናቸው። እነዚህ አባባሎችም በክርስቶስና እና በእርሱ በሚያምኑት መካከል ጠንካራ ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው። (ተመልከት፡ [[rc://*/tw/bible/kt/inchrist]]) ለመስራት፡ ትኩረት፡ "መከተል" ወይም "ማድረግ"

Ephesians 2:11

ኤፌሶን 2:11-12
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ እነዚህን አማኞች ሊያሳስባቸው የሚፈልገው ነገር አህዛብ እና አይሁድ በክርስቶስ እና በመስቀሉ አማካኝነት አንድ እንደሆኑ ነው። በትውልድ አሕዛብ፡ ከአይሁድ ህዝብ ውጪ የሆነውን ያመለክታል። ያልተገረዙ፡ ከአይሁድ ህዝብ ውጪ የሆኑት በህፃንነታቸው የማይገረዙ ስለነበር በአይሁዶች እግዚአብሔርን እንደማይከተሉ ይቆጠሩ ነበር። መገረዝ ፡ ይህ ቃል የአይሁድ ህዝብ 8 ቀን ከሆነው ወንድ ልጅ ጀምሮ የሚያደርጉትን ግዝረት ያመላክታል። ከክርስቶስ ተለይታችሁ፡ ትኩረት፡ "የማያምኑ" በሰው እጅ የሚከናወነውን መገረዝ፡ ግዝረቱ የሚከናወነው በወንድ ህፃናት አካል ላይ ነው። የእስራኤል ወገን ፡ "የእስራኤል ማህበረሰብ" ለተስፋውም ኪዳን ባዕድ ሆናችሁ፡ ትኩረት፡ "የእግዚአብሔርን የተስፋ ኪዳን አታውቁም ነበር"

Ephesians 2:13

ኤፌሶን 2:13-16
አሁን * በክርስቶስ ኢየሱስ በመሆን፡
ጳውሎስ የኤፌሶንን አማኞች በክርስቶስ ከማመናቸውና ካመኑ በኋላ ያለውን ልዩነት ያሳያቸዋል። (ተመልከት፡ [[rc://*/tw/bible/kt/inchrist]]) ከእግዚአብሔር ርቃችሁ የነበራችሁት * ወደ እግዚአብሔር እንድትቀርቡ ተደርጋችኋል፡


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

አማኞቹ ቀደም ብሎ በሐጢያታቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይተው ነበር። አሁን ግን ኢየሱስ በደሙ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር አቅርቧቸዋል። እርሱ ሰላማችን ነውና፡ ትኩረት:"ኢየሱስ ሰላሙን ሰጥቶናል" በሥጋውም፡ ትኩረት: "በመስቀል ሞት በመሞት" የጥል ግድግዳ፡ ትኩረት:"የጥላቻ ግድግዳ" ወይም "ጤናማ ያልሆን እሳቤ" የለያየንን፡ ይሄ የሚያሳየው ጳውሎስንና የኤፌሶን ሰዎችን እንዲሁም አይሁድ አማኞችንና አህዛቦችን ነው። የትእዛዛትንና የሕግ ደንቦችን በሥጋው ሻረ፡ የኢየሱስ ደም አይሁድ እና አህዛብ በሰላም በእግዚአብሔር ፊት ይኖሩ ዘንድ የሙሴን ህግ ማሟላት ችሏል። አንድ አዲስ ሕዝብ፡ አንድ አዲስ ህዝብ፥የተዋጀ የሰው ዘር ሁለቱን ሕዝቦች* ለማስታረቅ፡
ትኩረት:"አይሁድንም ሆነ አህዛብን በአንድ ላይ ለማምጣት" በመስቀሉ አማካይነት፡ ይህ በክርስቶስ በመስቀል ሞት አማካይነት ማለት ነው። (ተመልከት፡ በመስቀሉ አማካይነት* የነበረውን ጠላትነት ገድሎ፡
ኢየሱስ አይሁድ እና አህዛብ እርስ በእርሳቸው የሚኖራቸውን ጠላትነት አስወግዷል። እንደሙሴ ህግ እንደገና መኖር አያስፈልጋቸውም።

Ephesians 2:17

ኤፌሶን 2:17-18

አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች እያላቸው ያለው በአሁኑ ጊዜ ያሉት አማኞች ከሐዋርያት እና ከነቢያት ጋር አንድ በመሆናቸውም የእግዚአብሔር መንፈስ ቤት መቅደስ ሆነዋል። ሰላሙንም አወጀ፡ ትኩረት: "የሰላም ወንጌል አስታወቀ" ወይም "የሰላም ወንጌል አወጀ" ርቀው ለነበሩት፡ ይህ አህዛብን ወይም አይሁድ ያልሆኑትን አመልካች ነው። ቀርበው ለነበሩት፡ ይህ አይሁድን ያሳያል። በኢየሱስ አማካይነት እኛ ሁለታችንም * መቅረብ እንችላለንና፡
እዚህ ጋር "ሁለታችንም" የሚለው ጳውሎስን አማኝ አይሁድን እና አማኝ የሆኑትን አህዛብ ነው። በአንድ መንፈስ፡ ሁሉም አማኞች፥ አይሁድ እና አህዛብ ወደ እግዚአብሔር አብ መገኘት በዚያው አንድ መንፈስ መግባት ይችላሉ።

Ephesians 2:19

ኤፌሶን 2:19-22

እናንተ አሕዛብ ከቅዱሳንና ከእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባላት ጋር የአንድ አገር ዜጎች ናችሁ እንጂ ከእንግዲህ መጻተኞችና እንግዶች አይደላችሁም፡ ልክ ዜጋ ያልነበር ዜጋ እንደሚሆነው ሁሉ ይህ የአህዛብን መንፈሳዊ ሁኔታ ከማመናቸው በፊት እና በኋላ ያለውን ሁኔታ ያሳያል። እንግዶች አይደላችሁም፡ "የውጭ አገር ሰዎች አይደላችሁም" መፃተኞች፡ "ዜጋ ያልሆናችሁ" መሠረት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቤተሰብ ከህንፃ ጋር ያስተያየዋል። ክርስቶስንም እንደ ማዕዘን ራስ ድንጋይ፥ሐዋርያትን እንደ መሰረት እንዲሁም አማኞችን እንደ ውቅር። ቤተሰቡ የሆነው ሕንጻ ሁሉ በኢየሱስ ኀይል አንድ ላይ ተገጣጥሞ ለጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ለመሆን ያድጋል፡ ልክ ግንበኛ ድንጋዮቹን በቦታቸው እንደሚገጣጥማቸው፥ጳውሎስ የክርስቶስን ቤተሰብ አሁንም በህንፃ መመሰሉን ይቀጥላል። በእርሱ * በክርስቶስ
"በክርስቶስ ኢየሱስ" " እና ተመሳሳይ አገላለጦች ዘይቤያዊ አባባሎች ሲሆኑ በተደጋጋሚ በአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ውስጥ የምናገኛቸው ናቸው። እነዚህ አባባሎችም በክርስቶስና እና በእርሱ በሚያምኑት መካከል ጠንካራ ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው። (ተመልከት፡ [[rc://*/tw/bible/kt/inchrist]]) እናንተም እግዚአብሔር በመንፈሱ የሚኖርበት ሕንጻ እንድትሆኑ፡ ይህ አማኞች እርስ በእርስ በመገጣጠም በመደበኛነት እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ሃይል እንዴት በመካከላቸው እንድሚኖር ይገልፃል።

---

Chapter 3

Ephesians 3:1

ኤፌሶን 3:1-2

አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ውድ ኋላ መለስ ብሎ የአይሁድንና የአህዛብን አንድ መሆን ካመላከተ በኋላ አሁን ደግሞ አማኞች ቤተ መቅደስ የሆኑበትን የተሰወረ እውነት ያስታውቃል። በዚህ ምክንያት፡ "ለናንተ በተሰጠው ፀጋ ምክንያት" ለእናንተ ጥቅም ሲባል ስለ ተሰጠኝ የእግዚአብሔር ጸጋ መጋቢነት፡ "እግዚአብሔር ለናንተ የሰጠኝን የፀጋ ማስተዳደር ሃላፊነት"

Ephesians 3:3

ኤፌሶን 3:3-5

በመገለጥ እንዳውቅ አድርጓል፡ ትኩረት:"እግዚአብሔር ገልጦልኛል" (ተመልከት፡ ቀደም ሲል እንደጻፍሁላችሁ፡ ጳውሎስ ለነዚህ ሰዎች ቀደም ብሎ አጠር ያለ ደብዳቤ የፃፈ ሲሆን፥የሚያመለክተውም እርሱን ነው። ስለ ክርስቶስ ምስጢር እኔ ያለኝን መረዳት፡ ትኩረት:"ለዚህ ስውር እውነት ያለኝ መረዳት" ባለፉት ዘመናት ለነበሩ ሰዎች አልተገለጠም ነበር፡ ትኩረት:"እግዚአብሔር ባለፉት ዘመናት ለነበሩት ሰዎች አላሳወቃቸውም ነበር።" ምስጢሩም አሁን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት* የተገለጠው፡
ትኩረት፡ "አሁን መንፈስ ቅዱስ ገልጦታል" ወይም "መንፈስ ቅዱስ አሁን እንዲታወቅ አድርጎታል"

Ephesians 3:6

ኤፌሶን 3:6-7

አሕዛብ በወንጌል አማካይነት አብረው ወራሾች፥ ይህ ጳውሎስ ቀደም ባሉት ቁጥሮች ሊገልፃቸው የጀመረው ተሰውሮ የነበር እውነት ነው። ክርስቶስን የተቀበሉ አህዛብ ልክ እንደ አይሁድ አማኞች አንድ አይነት ርስት ይቀበላሉ። አብረው የአካሉ ብልቶች፡ ብዙውን ጊዜ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ትባላለች። አገልጋይ ሆኛለሁ፡ "አሁን የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆንሁት ወንጌልን ለማዳረስ ነው"

Ephesians 3:8

ኤፌሶን 3:8-9

ምንም እንኳ ከቅዱሳን ሁሉ ያነስሁ ብሆንም፥*ይህ ጸጋ ለእኔ ተሰጠኝ፡ ትኩረት፡ "ምንም እንኳ ከእግዚአብሔር ህዝብ በሙሉ የማይገባኝ ታናሽ ብሆንም፥እግዚአብሔር የፀጋውን ስጦታ ቸረኝ" ተሰውሮ ስለነበረው ምስጢር የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን እንደሆነ ለሁሉም አገልጥ ዘንድ፡ "የእግዚአብሔርን ህዝብ በሙሉ ስለ እግዚአብሔር እቅድ አስታውቅ ዘንድ" የሁሉ ነገር ፈጣሪ በሆነው በእግዚአብሔር ላለፉት ዘመናት ተሰውሮ ስለነበረው ምስጢር የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን እንደሆነ ለሁሉም አገልጥ ዘንድ፡ ትኩረት:"እግዚአብሔር ሁሉን ከፈጠረ ጀምሮ ለረጅም ዘመን ጠብቆ ያቆየው"

Ephesians 3:10

ኤፌሶን፡3:10-11

ብዙ ገፅታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ባለ ሥልጣናት እንዲታወቅ ነው፡ ገፅታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ ትኩረት፡ "እግዚአብሔር ታላቅ የሆነ ጥበቡን በሰማይ ስፍራ ላሉ አለቆችና ስልጣናት የሚያስታውቀው በቤተ ክርስቲያን በኩል ነው" ብዙ ገፅታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ፡ ገፅታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ- የእግዚአብሔር ውስብስብ ጥበብ አለቆችና ባለ ሥልጣናት፡ እነዚህ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። ጳውሎስ ይህንን የተጠቀመው ማንኛውም መንፈሳዊ ፍጥረት የእግዚአብሔርን ጥበብ እንደሚያውቅ ነው። ዘላለማዊ ዕቅዱ፡ "በዘላለማዊ እቅዱ እየጠበቀ" ወይም "ከዘላለማዊ ዕቅዱ ጋር በሚስማማ" በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ፡ በክርስቶስ አማካኝነት

Ephesians 3:12

ኤፌሶን 3:12-13

አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ስለ መከራው እግዚአብሔርን ከማመስገኑም በላይ ስለኤፌሶን አማኞች ይፀልያል። በልበ ሙሉነት * መቅረብ፡
ትኩረት:"ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ድፍረት ማግኘት" በክርስቶስ በማመናችን፡ በክርስቶስ በማመናችን ምክንያት

Ephesians 3:14

ኤፌሶን 3:14-16

በዚህም ምክንያት፡ "እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ የስራው ለናንተ ስለሆነ" በአብ ፊት እንበረከካለሁ፡ "በአብ ፊት ለፀሎት እንበረከካለሁ" ወይም "በአብ ፊት በትህትና እፀልያለሁ" በሰማይና በምድር ላለ ቤተ ሰብ ሁሉ ስያሜ የሰጠ፡ ስያሜ መስጠት ምናልባት የመፍጠርን ድርጊት ያመለክት ይሆናል። ትኩረት:"በሰማይና በምድር ሁሉንም ቤተሰብ ስያሜ የሰጠ እና የፈጠረ" እንዲሰጣችሁ፡ እርሱ በፈቃዱ እንዲሰጣችሁ

Ephesians 3:17

ኤፌሶን 3:17-19

በእምነት * በልባችሁ፡
"ልባችሁ" የሚለው የሰውን ነፍስ የሚያመላክት ሲሆን "በ" ደግሞ ማስተላለፊያውን መንገድ ያሳያል፤ይህም ክርስቶስ በአማኞች ልብ ውስጥ በእግዚአብሔር የእምነት ስጦታ አማካኝነት እንደሚኖር አመላካች ነው። በፍቅሩ ሥር እንድትሰዱና፡ ጳውሎስ እምነታቸውን ላይ ስሩን ዘርግቶ እንደተተከለ ዛፍ ወይንም በጥልቅ መሰረት ላይ እንደተገነባ ህንፃ ጋር ያመሳስለዋል። ትኩረት፡ "እንደ ዛፍ ስር ሰዳችሁ እንድትተከሉና

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

እንደ ህንፃ በአለቱ ላይ እንድትገነቡ።"
ከቅዱሳን ሁሉ ጋር: "በክርስቶስ የሆኑት አማኞች ሁሉ" ወይም "ቅዱሳን ሁሉ" ከሰው ዕውቀት ሁሉ በላይ የሆነውን የክርስቶስን ታላቅ ፍቅር:"በልምድ ልናውቀው ከምንችለው በላይ የሆነውን የክርስቶስ ፍቅር ልታውቁ ትችላችሁ"
Ephesians 3:20

ኤፌሶን 3:20-21
ለእርሱ: "ለእግዚአብሔር" እጅግ አብልጦ: እኛ ከምንጠይቀው ወይም ከምንገምተው በላይ እግዚአብሔር ሊያደርግ ይችላል። እኛ ከምንለምነው ወይም ከምናስበው: "እኛ" የሚለው ቃል አማኞችን ሁሉ የሚያመለክት ነው።

---

Chapter 4
Ephesians 4:1
ኤፌሶን 4:1-3
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በፅሁፉ ለኤፌሶኖች በፃፈላችው፥የአማኞችን አንድነት በማጉላት እንደ እንደ አማኝ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያበረታታቸዋል። የጌታ እስረኛ: ትኩረት: "ጌታን ለማገልገል ባደረገው ምርጫ እንደ እንድ እስረኛ"
ለተጠራችሁለት መጠራት የሚገባውን ሕይወት ትኖሩ ዘንድ: "ትኖሩ" የሚለው ቃል የኤፌሶን አማኞችን ያመላክታል። ትኩረት: "ለተጠራችሁለት ጥሪ የሚመጥን የሚገባ ማንነት እንዲኖችሁ አበረታታችኋለሁ" ይኸውም እርስ በርስ በፍቅር ተቻችላችሁ በፍጹም ትሕትና፥በገርነትና በትዕግሥት: ትኩረት:"ትሁት፥ገር እና እርስ በእርሳችሁም የምትቀባበሉ መሆንን ተማሩ" በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ: "የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ በሰላም ለመኖር ጥረት አድርጉ"
Ephesians 4:4
ኤፌሶን 4:4-6
አንድ አካል: ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ እካል በመባል ትታወቃለች። አንድ መንፈስ: "አንድ ቅዱስ መንፈስ ብቻ" (UDB) በተጠራችሁ ጊዜ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ: "እግዚአብሔር የጠራችሁ በተረጋገጥ ተስፋ ነው" (ተመለከት:
የሁሉም አባት የሆነ: "የሁሉ ነገር አባት የሆነ *** በሁሉ ነገር ላይ*** በሁሉ ነገር በኩል በሁሉ ነገር ውስጥ"
Ephesians 4:7
ኤፌሶን 4:7-8
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ክርስቶስ ለአማኞች የሰጠው ስጦታዎች በቤተክርስቲያን ማለትም ለመላው የአማኞች እካል ጥቅም ነው። ለእያንዳንዳችን: ይህ ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን እና መላው የኤፌሶን አማኞችን ነው። ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጥቶናል: ትኩረት:"እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ስጦታን ሰጥቶናል" ወይም "እግዚአብሔር ለአማኝ ሁሉ ስጦታን ስጥቶታል"
ወደ ላይ በወጣ ጊዜ: "ክርስቶስ ወደ መንግስተ ሰማይ"
Ephesians 4:9
ኤፌሶን 4:9-10
ወደ ላይ ወጣ: "ክርስቶስ ወደ ላይ ሄደ" ወረደ: ወደታች ወረደ" ወይም "ክርስቶስም ወደ ታች መጣ" ወደ ምድር ጥልቅ ወረደ: ትርጉሞች ሊሆኑ የሚችሉ 1) "ወደ ታች የምድር አካባቢዎች" 2) ወደ ታች የምድር ክፍሎች ሁሉንም ይሞላ ዘንድ: "ሁሉንም ነገር ሙሉ በሙሉ እንዲሞላ" ወይም "ሁሉም በእርሱ ይሞላ ዘንድ"
Ephesians 4:11
ኤፌሶን 4:11=13
ስጦታ አድርጎ የሰጠ ክርስቶስ: "ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ስጦታዎችን እንደዚህ አድርጎ ሰጠ"
ለአገልግሎት ሥራ: ትኩረት: "ሌሎችን ማገልገል" የክርስቶስን አካል ለማነጽና: ይህ በመንፈሳዊ ህይወት ማደግ፥ የሰውነት እንቅስቃሴ እያደረጉ ሰውነትን ከማበርታት ጋር ይነፃፀራል። ይህም የሚሆነው ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመን እና በማወቅ ወደ ሚገኘው አንድነት: ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆን ማወቅ በእምነት ወደሚገኘው አንድነት ወይም ወደ አማኞች ብስለት ለመድረስ አስፈላጊ ነው። በማመን * ወደ ሚገኘው አንድነት:
"በአንድነት በእምነት መጠንከር" የእግዚአብሔርን ልጅ: ይህ ለኢየሱስ አስፈላጊ መጠሪያ ነቅ። ሙሉ ሰው ወደ መሆን ደረጃ: "የበሰሉ አማኞች መሆን"
Ephesians 4:14
ኤፌሶን 4:14-16
ከእንግዲህ: "ከዚህ በኋላ እንዲህ እናደርጋለን" የምንነዳ ሕጻናት: ይህ በመንፈሳዊ ህይወት ያላደጉትን አማኞች በህይወት ጥቂት ልምድ ካላቸው ህፃናት ጋር ተነፃፅሯል። የትምህርት ነፋስ ወዲያና ወዲህ የምንነዳ: ይህ ደግሞ አቅጣጫዋን በቅጡ የማታውቅ ጀልባ በነፋስ በምትገፋበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ ከአንድ የስተትን ትምህርት ሰምቶ ከሚንቀሳቀስ ካልበሰለ አማኝ ጋር ያነፃፅረዋል። በሰዎች ረቂቅ
ተንኮል እና ማታለል: "አማኞችን በሰላ ውሸት የሚያታልሉ ተንኮለኛ ሰዎች" ይልቁንም * የምንናገር:
"ይሌቁንስ እንናገራለን" ራስ ወደ ሆነው *** አካል ሁሉ *** እየተያያዘና እየተጋጠመ ያድጋል:
"ስለዚህም አማኞች እርስ በእርስ በፍቅር ለማደግ መደጋገፍ ይችላሉ"
Ephesians 4:17
ኤፌሶን 4:17-19
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ እየነገራቸው ያለው በእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ እንደታተሙ አማኞች ማድረግ የሌለባቸውን ነው። በጌታ እየለመንኋችሁ ይህን የምናገረው: ትኩረት: "ስለዚህም በጌታ ሆኜ በእጅጉን አደፋፍራችኋለሁ። በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱት እንደ አሕዛብ እንዳትኖሩ ነው: ትኩረት:"የማይረባ ሃሳብ እንደያዙ አህዛብ መኖርን አቁሙ" አእምሮአቸው ጨልሞአል፤ካለማወቃቸውና ከልባቸው ደንዳናነት የተነሳ ከእግዚአብሔር ሕይወት ርቀዋል: ትኩረት:"ስለታወሩ እና ልባቸው ደንዳና ስለሆነ የእግዚአብሔርን ህይወት ሊለማመዱ አይችሉም" አእምሮአቸው ጨልሞአል: ጥርት ባለ መልኩ ማሰብም ሆን ማመዛዘን አይችሉም። ካለማወቃቸውና ከልባቸው ደንዳናነት የተነሳ ከእግዚአብሔር ሕይወት ርቀዋል: ትኩረት: "አለማወቃቸው ከእግዚአብሔር ህይወት ለይቷቸዋል" ወይም "እግዚአብሔርን ስለማያውቁ የእግዚአብሔርን ህይወት ሊለማመዱ አይችሉም" ከልባቸው ደንዳናነት: እግዚአብሔርን መስማትና ትምህርቱን መከተል እንቢ አሉ። ርኩሰትና ስግብግብነት ሁሉ ለሞላበት ቅጥ ላጣ ብልግና ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል: ትኩረት:"ቅጥ ላጣ ፍላጎታቸውና ለራሳቸው ደስታ በክፉ ባህሪያቸው ኑሯቸውን አሳልፈው ሰጡ"
Ephesians 4:20
ኤፌሶን 4:20-22
እናንተ ግን ስለ ክርስቶስ የተማራችሁት እንደዚህ አይደለም: ትኩረት: "ነገር ግን ክርስቶስን በዚህ መከተል አልተማራችሁም" ስለ እርሱ የሰማችሁ እና የተማራችሁ ከሆነም በርግጥ የተማራችሁት ስለ ኢየሱስ የሚናገረውን እውነት ነው: ትኩረት:"ስለ ኢየሱስ ስለ ሰማችሁና ስለእርሱም እውነተኛውን ነገር ሰምታችኋልና" በሚያታልል ክፉ ምኞት የጎደፈውን አስቀድሞ ትኖሩበት የነበረውን አሮጌውን ሰው ልታስወግዱ ይገባል: ትኩረት:"በክፉ ምኞት ተታልላችሁ ስትኖሩበት የነበረውን የድሮውን የተለመደ አኗኗር ዘዬ ማስወገድ ይገባችኋል" አሮጌውን ሰው ልታስወግዱ ይገባል: ልብስ አውልቃችሁ ወደዚያ እንደምታስወግዱት ሃጢያተኛ ባህሪያችሁን ልታስወግዱ ይገባል። ትኩረት:"ባህሪያችሁን ልትለውጡ ይገባል" (ተመልከት:
አስቀድሞ ትኖሩበት የነበረውን: ትኩረት:"ከአሮጌው ባህሪ ጋር የሚስማማ ማንነት" ወይም "ከድሮው ማንነት ጋር የሚሄድ አይነት ፀባይ" በሚያታልል ክፉ ምኞት የጎደፈውን: ትኩረት:"በውሸት የስጋ ምኞት እየባሰበት የሚሄድ"
Ephesians 4:23
ኤፌሶን 4:23-24
እንድትታደሱ: ትኩረት:"እንድትለወጡ" ወይም "እንድትታደሱ" አዲሱን ሰው እንድትለብሱ: አንድ ሰው አዲስን ልብስ ሲለብስ ፈፅሞ የተለየ እንደሚሆነው ሁሉ ያላመነ በክርስቶስ በማመን አዲስ ሰው ይሆናል።
Ephesians 4:25
ኤፌሶን 4:25-27
ውሸትን አስወግዱ: ትኩረት:"ሀሰት መናገርን ማቆም ይገባችኋል" እያንዳንዱ ከባልንጀራው ጋር እውነትን ይነጋገር: ትኩረት: "አማኞች ከጎረቤቶቻቸው ጋር እውነትን ሊነጋገሩ ይገባል" ሁላችንም የአንድ አካል ብልቶች ስለሆንን: "ሁላችንም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ነን"
ተቆጡ፤ነገር ግን ኀጢአት አትሥሩ: "ልትቆጡ ትችላላችሁ፥ሆኖም ሃጢያትን አትስሩ" በቁጣችሁ ጸሓይ እስከሚገባ ድረስ አትቆዩ: ትኩረት: "ምሽት ከመምጣቱ በፊት ሃጢያታችሁ ይብረድ" ወይም "ቀኑ ከመጠናቀቁ በፊት ቁጣችሁ ይቁም"
Ephesians 4:28
ኤፌሶን 4:28-30

የማይረባ ቃል ከቶ ከአፋችሁ አይውጣ፡ "ከአፋችሁ መጥፎ ቋንቋ አይውጣ" ወይም "ክፉ ንግግር ከአፋችሁ አይውጣ" ሌሎችን ለማነጽ የሚያስፈልግ፡ "ይልቁንም ለአማኞች ብርታትን መስጠት የሚችል ጠቃሚ ቃላትን ተናገሩ" ለሚሰሙትም ጸጋን የሚሰጥ ጠቃሚ ቃል እንጂ፡ "በዚህ መንገድ ለሚያዳምጧችሁ ፀጋን መስጠት ይቻላችኋል" ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ፡ ትኩረት፡"የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ በመጥፎ ንግግራችሁ እንዲያዝን አታድርጉት" የታተማችሁበትን፡ ትኩረት፡ "ምክንያቱም እርሱ ስላተማችሁ"
Ephesians 4:31
ኤፌሶን 4:31-32
መራራነት * ቁጣንና፡
"መራራነት" እና "ቁጣ" የሚሉት ቃላት ታላቅ መጠን ያለውን ቁጣ ያሳያሉ" ትኩረት፡"ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ቁጣ"
ጭቅጭቅንና ስድብን፡ "ጭቅጭቅ" የሚለው ቃል "የስደብ" ፀያፍ ደረጃ ነው።
ትኩረት፡ "ፀያፍ የቃላት ናዳ" እርስ በርሳችሁ ቸሮች፥ ርኅሩሆች ሁኑ፡
ትኩረት፡"ይልቁንስ እርስ በእርሳችሁ ደጎችና ቸሮች መሆን ይገባችኋል" ወይም "በርህራሄ የተሞላችሁ ደጋጎች መሆን ይገባችኋል"

---

Chapter 5
Ephesians 5:1
ኤፌሶን 5:1-2
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ እንግዲህ*እግዚአብሔርን የምትመስሉ ሁኑ፡ እንደ ተወደዱ የእርሱ ልጆች፡ በፍቅር ኑሩ፡ መልካም መዓዛ ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እንዳቀረበ፡
Ephesians 5:3
ኤፌሶን 5:3-4
ለቅዱሳን የሚገባ ባለመሆኑ ዝሙት፥ማንኛውም ርኩሰትና ስስት በእናንተ ዘንድ ሊኖር አይገባም፡ ማንኛውም ርኩሰትና፡ ስስት፡ በእናንተ ዘንድ ሊኖር አይገባም፡ ለቅዱሳን የሚገባ ባለመሆኑ ወይም ጸያፍ ንግግር፥ዋዛ ወይም ውርደትን የሚያስከትል ቀልድ ለእናንተ ስለማይገባ ከመካከላችሁ አስወግዱ፤ከዚህ ይልቅ የምታመሰግኑ ሁኑ፡
Ephesians 5:5
ኤፌሶን 5:5-7
ከንቱ በሆነ ንግግር ማንም አያታላችሁ፡ በእነዚህ ነገሮች ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ በማይታዘዙት ልጆች ላይ ይመጣል፡ ስለዚህ የእነርሱ ተባባሪዎች አትሁኑ፡
Ephesians 5:8
ኤፌሶን 5:8-12
ባንድ ወቅት ጨለማ ነበራችሁና፡ አሁን ግን በክርስቶስ ብርሃን ናችሁ፡ ምክንያቱም ከብርሃኑ የሚገኘው ፍሬ መልካም ነገር ሁሉ፥ ጽድቅና እውነት ነው፡ ፍሬ ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፡ ፍሬ ከሌለው ከጨለማ ሥራ፡ ይልቁን ልትገልጡት ይገባል፡
Ephesians 5:13
ኤፌሶን 5:13-14
ብርሃን በሚኖርበት ጊዜ ማንኛውም ነገር በግልጽ ይታያል፡ አንተ የምትተኛ ንቃ፤ከሙታን ተነሳ፡ ክርስቶስም ያበራልሃል፡
Ephesians 5:15
ኤፌሶን 5:15-17
እንግዲህ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን፥እንደ ጥበብኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ፡ ዘመኑን ዋጁ፡ ቀኖቹ ክፉዎች ስለሆኑ፡
Ephesians 5:18
ኤፌሶን 5:18-21
በወይን ጠጅ አትስከሩ፡ ይልቁንስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፡ በመዝሙር፥በቅኔና በመንፈሳዊ ዝማሬ፡ ሁልጊዜ* አመስግኑ፡
ተገዙ፡
Ephesians 5:22
ኤፌሶን 5:22-24
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ አካሉ ለሆነችውና አዳኟ ለሆናት፡ ሚስቶችም በማንኛውም ነገር ለባሎቻቸው ሊገዙ ይገባል፡
Ephesians 5:25
ኤፌሶን 5:25-27
ሚስቶቻችሁን ውደዱ፡ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ * በውሃ አጥቦ በማንጻት እንድትቀደስ፡
ስለ እርስዋም ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ፡ በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት፡ ቤተ ክርስቲያን አድርጎ ለራሱ ሊያቀርባት ነው፡
Ephesians 5:28
ኤፌሶን 5:28-30
የገዛ ሥጋቸውን እንደሚወዱ፡ ይልቁን ይመግበዋል፡ ምክንያቱም እኛ የእርሱ ብልቶች ነን።
Ephesians 5:31
ኤፌሶን 5:31-32
በዚህም ምክንያት፡ ሚስቱን እንደ ራሱ አድርጎ መውደድ ይገባዋል፡ ሚስትም ባልዋን ታክብር፡

---

Chapter 6
Ephesians 6:1
ኤፌሶን 6:1-3
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ልጆች ሆይ፤በጌታ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ፡ መልካም እንዲሆንልህ፥ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም፡
Ephesians 6:4
ኤፌሶን 6:4
እናንተም አባቶች ሆይ፤ልጆቻችሁን አታስቆጡአቸው፡ ይልቁንስ በጌታ ሥርዓትና ምክር አሳድጓቸው፡
Ephesians 6:5
ኤፌሶን 6:5-8
ባሪያዎች ሆይ *ታዘዙ፡ በታላቅ አክብሮት፥ በመንቀጥቀጥና፡ በመንቀጥቀጥና በልባችሁ ቅንነት ታዘዙ * እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች፡
እነርሱን ደስ ለማሰኘት ብላችሁ ሳይሆን፥ እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች፡ እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከልብ በመፈጸም ታዘዙአቸው፡
Ephesians 6:9
ኤፌሶን 6:0
እናንተም ጌቶች ሆይ፤ለባሮቻችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው * አታስፈራሯቸው፡ የእነርሱና የእናንተም ጌታ የሆነው እርሱ በሰማይ እንዳለና፡ ለሰው ፊትም እንደማያዳላ
Ephesians 6:10
ኤፌሶን 6:10-11
አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ በጌታና ብርቱ በሆነው ኀይሉ የበረታችሁ ሁኑ፡ የዲያብሎስን ተንኮል አዘል ዕቅድ መቋቋም ትችሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ሁሉ ልበሱ፡
Ephesians 6:12
ኤፌሶን 6:12-13
ከሥጋና ከደም፡ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ሁሉ ልበሱ፤
Ephesians 6:14
ኤፌሶን 6:14-16
በእውነት ቀበቶ፡ ቀበቶ ለአንድ ወታደር በሚገባ እንደሚይዝለት እውነትም ለአማኝ ነገሮችን አጥብቆ ይይዝለታል። የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፡ ጥሩር የወታደርን ደረት እንደሚሸፍንለት የፅድቅ ስጦታም የአማኝን ልብ ይከልልለታል።
የሰላምን ወንጌል ለማወጅ እግሮቻችሁ በዚያ ተጫምተው ዝግጁ ይሁኑ፡ ወታደር ለእግሩ ጥሩ ጫማ መጫማት እንዳለበት ሁሉ አማኝም ጠንካራ የሆን የሰላም ወንጌል እውቀት ሊኖረው ይገባል። የእምነትን ጋሻ አንሱ፡ ወታደር ጠላትን ለመከላከል ጋሻውን እንደሚጠቀምበት ሁሉ እግዚአብሔር ለአማኝ የሚሰጠውም እምነት ከዲያብሎስ ጥቃት መከላከያ ነው። (ተመልከት፡ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች፡
Ephesians 6:17
ኤፌሶን 6:17-18
እንዲሁም የመዳንን ራስ ቁር፡ በእግዚአብሔር የሚሰጥ ድነት የአማኝን አዕምሮ እንደ


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ራስ ቁር ሆኖ ይከላከላል። የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ይህም የእግዚአብሔር ቃል ነው፡ ወታደር ሰይፍ መዝዞ ጠላትን ለማጥቃትና ለመከላከል እንደ ሚጠቀምበት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የሆነ የእግዚአብሔር ቃልም ለአማኝ ዲያብሎስን ማጥቂያ መሳሪያ ነው። በማንኛውም ዓይነት ጸሎትና ልመና ሁልጊዜ በመንፈስ በመጸለይና፡ ትኩረት፡ ስትፀልዩ እና የተወሰኑ ልመናዎችን ስታቀርቡ በመንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ የምትፀልዩ ሁኑ። ከእርሱ በመጠበቅ፥ ለቅዱሳንም ልመና በማቅረብ ትጉ፡ "ለአማኞች ሁሉ መደበኛ የሆነ ንቃት እና ፀሎት"

Ephesians 6:19

ኤፌሶን 6:19-20

አያያዥ ዓረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ በእስር ሆኖ ወንጌል በድፍረት እንዲናገር እንዲፀልዩለት ይለምናል፥ለዚህም ደግሞ ቲኪቆስን ያደፋፍራቸው ዘንድ ይልከዋል። ከዚያም ክርስቶስን ለሚወዱ አማኞች ሁሉ በሰላምና በፀጋ ይባርካቸዋል። ቃል ይሰጠኝ ዘንድ፡ ትኩረት፡ "እግዚአብሔር ቃሉን እንዲሰጠኝ" ወይም "እግዚአብሔር መልዕክትን እንዲሰጠኝ" መናገር እንደሚገባኝ በድፍረት እናገር ዘንድ፡ ትኩረት፡ "በድፍረት ገለፃ እንዳደርግ" በሰንሰለት የታሰረ መልእክተኛ የሆንሁት ለዚሁ ነውና፡ ትኩረት፡ "የወንጌል ተወካይ በመሆኔ አሁን በእስር እገኛለሁ" በእስራቴም መናገር እንደሚገባኝ በድፍረት እናገር ዘንድ፡ ትኩረት፡ "የእግዚአብሔርን መልዕክት በድፍረት እንድናገር"

Ephesians 6:21

ኤፌሶን 6:21-22

ምን እያደረግሁ እንደምገኝ፡ "የኔ ሁኔታ" ወይም "እኔ ያለሁበት ድባብ" ቲኪቆስ፡ ቲኪቆስ ከጳውሎስ ጋር ካሉት በርካታ ሰዎች መካከል አንዱ ነው። ያለንበትን ሁኔታ እንድታውቁና፡ ትኩረት፡ "ሁሉንም ነገሮች እንነግራችኋለን"

Ephesians 6:23

ኤፌሶን 6:23-24

ማስታወሻ የለውም።

---

Chapter 1

Philippians 1:1

ጳውሎስና ጢሞቴዎስ በቋንቋችሁ ደራሲዎችን ለማስተዋወቅ የተለየ መንገድ ካለ እዚህ ላይ ተጠቀሙበት። ትኩረት፡ "ከጳውሎስና ጢሞቴዎስ" ወይም "እኛ ጳውሎስና ጢሞቴዎስ ይህን ደብዳቤ ጽፈናል።"

የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋዮች "እኛየክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋዮች ነን" ) በክርስቶስ ኢየሱስ ቅዱሳን ሆነው ለተለዩት ሁሉ "በክርስቶስ ኢየሱስ አማኝ ለሆኑ ሁሉ" ለአረኞችና ዲያቆናት ትኩረት፡"የቤተ ክርስቲያን መሪዎች" ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን ይህ ለሌሎች በረከት እንዲሆንላቸሁ መመኘት የሚገለጽበት መንገድ ነው። ለእናንተ እዚህ ላይ "እናንተ" የሚያመለክተው በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ አማኞችን ነው።

እግዚአብሔር አባታችን እዚህ ላይ"የእኛ" የሚያመለክተው ምናልባት ጳውሎስንና ጢሞቴዎስን ጨምሮ በክርስቶስ አማኞችን ሁሉ እና የፊልጵስዩስ አማኞችን ነው።

Philippians 1:3

አመሰግናለሁ፤እጸልያለሁ፤ምስጋና አቀርባለሁ እዚህ ላይ

"እኔ" ጳውሎስን ያመለክታል እናንተ እዚህ ላይ "እናንተ" የፊልጵስዩስ አማኞችን ያመለክታል። በወንጌል ስላላችሁ ኅብረት አመሰግናኋለሁ ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ሰዎች ወንጌል በመስበካቸው እግዚአብሔርን ያመሰግናል። ትኩረት፡"ወንጌል በመስበካችሁ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ" ትምክህት አለኝ "እርግጠኛ ነኝ" በእናንተ የጀመረው "የጀመረው እግዚአብሔር" ይፈጽመዋል "ይህን ለመፈጸም ይቀጥላል"

Philippians 1:7

ይህ ለእኔ ትክክል ነው "ይህ ለእኔ ተገቢ ነው" ወይም "ይህ ለእኔ መልካም ነው።"

እናንተ በልቤ አላችሁ ትኩረት፡ "በጣም እወዳችኋለሁ"

በጸጋው ተባባሪዎች ናችሁ ትኩረት፡"ከእኔ ጋር የጸጋ ተካፋዮች ሆናችኋል" ወይም " ከእኔ ጋር የጸጋው ተካፋዮች" እግዚአብሔር ምስክሬ ነው ትኩረት፡ "እግዚአብሔር ያውቃል" ወይም " እግዚአብሔር ይገበዋል" በክርስቶስ ኢየሱስ ጥልቅ ፍቅር ይህ ሐረግ "በጥልቅ ፍቅር" የሚያመለክተው በውስጣችን ከስሜት ክፍል የሚወጣበት ቦታ ነው።"

Philippians 1:9

የሚያገነኛው ዐረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች እንደሚጸልይና ለጌታ መከራ መቀበል ደስታ እንዳለው ይናገራል።

እንዲበዛላችሁ "ይተረፍላችኋል" በዕውቀትና በሙሉ መረዳት ትኩረት፡"እግዚአብሔርን የሚያስደስተውን ባወቃችሁና በተረዳችሁ መጠን" ይህን አደርጋለሁ "ይህን እጸልያለሁ" የተሻሉ ነገሮች ትኩረት፡" በጣምእ ግዚአብሔርን የሚያስደስት ነገር" ንጹኃንና ነውር የሌለባችሁ "ንጹኃን" እና "ነውር የሌለባችሁ" የሚሉ ቃላት መሠረታዊ ነገሩ ተመሳሳይ ነው። ጳውሎስ የሞራል ንጽሕናን ለመግለጽ አንድ አድርጎ ያገናኘዋል"

በክርስቶስ ቀን "በጌታ ቀን" ወይም " በፍርድ ቀን" ትሞላላችሁ ትኩረት፡ " ኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ እግዚአብሔርን እንድትታዘዙ ያደርጋችኋል"

በጽድቅ ፍሬዎች ትሞላላችሁ ይህ አማኞች እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በዛፍ ላይ የሚያፈሩትን ፍሬ ያስተያያል።

ለእግዝአብሔር ክብርና ውዳሴ ይህ በተለየ ሁኔታ ሊተረጎም ይችላል። ትኩረት፡ "እናንተ መልካም ያደረጋችሁትን ሰዎች አይተው እግዚአብሔርን እንዲያመሰግናሉ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ክብር ይሰጣሉ።

Philippians 1:12

እንግዲህ እፈልጋለሁ

እዚህ ላይ "እንግዲህ"የሚለው የደብዳቤውን አዲስ ክፍል ለማድረግ ጥቅም ላይ ውሎአል። ወንድሞች እዚህ ላይ ይህ ማለት ከሰማያዊው እግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ አንድ መንፈሳዊ ቤተ ሰብ ስለሆኑ ወዶችንና ሴቶችን ጨምሮ ክርስቲያን ወዳጆችን ነው። በእኔ የሆኑ ነገሮች ጳውሎስ የሚናገረው በእስር ቤት የነበረበትን ጊዜ ነው። ትኩረት፡ "ይህን ሁሉ መከራ የተቀበልኩት የኢየሱስን ወንጌል እንድሰብክ በእስር ቤት የተጣልኩበት" የቤተ መንግሥት ጠባቂዎች እንግዲህ በጌታ ወንድሞች የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራሉ ትኩረት፡ " እኔ በመታሰሬ ምክንያት ብዙ በጌታ የሆኑ ወንድሞች የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራሉ" በበለጠ ድፍረትና ያለ ፍርሃት ጳውሎስ የሚገልጸው በአዎንታዊና አሉታዊ ተመሳሳይ አሳብን በአደገኛ ሁኔታ ላይ ሆነው ወንጌልን በታላቅ ድፍረት መስበካቸውን ለመግለጽ ነው። ትኩረት፡ " በታላቅ ድፍረትና ያለ ፍርሃት"

Philippians 1:15

አንዳንዶች ክርስቶስን ሰበኩ ትኩረት፡

"አንዳንድ ሰዎችስለ ክርስቶስ የምሥራች ይሰብካሉ በቅናትና በፉክክር ትኩረት፡ " ሰዎች እኔን ለመስማት ባለመፈለጋቸው ችግር ለመፍጠር ይፈልጋሉ" እንዲሁም ሌሎች ከቅን ልቦና ትኩረት፡ "ነገር ግን ሌሎች ቸሮችና ለመርዳት በመፈለጋቸው አድርገውታል" አንዳንዶች "ሰዎቹ ለዚህ ተመድቤአለሁ ትኩረት፡ " እግዚአብሔር መርጦኛል" ወንጌልን ለመደገፍ ትኩረት፡ "የኢየሱስ መልእክት እውነት መሆኑን ሁሉንም ለማስተማር" "ነገር ሌሎች ክርስቶስን ይሰብካሉ" በቅናትና በቅን ልቦና። በእስራቴ በምቀበለው መከራ እየጨመሩብኝ ያስባሉ"

Philippians 1:18

X

እንግዲህ ምን ይደረግ ጳውሎስ አንዳንድ ሰዎች ስለ ክርስቶስ የሚሰብኩት አስፈላጊ አይደለም። ትኩረት፡ "አይመለከተኝም" በየትኛውም መንገድ በማስመሰል ወይም በእውነት ክርስቶስ ይሰበካል ትኩረት፡ "ሰዎች ስለ ክርስቶስ እስከሰበኩ ድረስ በመልካም ወይም በመጥፎ ምክንያት ቢያደርጉትም ምንም አይደለም" በዚህ ሁሉ ደስ ይለኛል ትኩረት፡ ሰዎች ስለ ክርስቶስ በመስበካቸው ደስ ይለኛል" እደሰታለሁ "በዓል አደርጋለሁ" ወይም "እደሰታለሁ" ይህ ለእኔ ነፃ መውጣትን ያመራልታል ትኩረት፡ " እግዚአብሔር ከእስራቴ ነፃ ያወጣኛል" በእናንተ ጸሎትና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ርዳታ ትኩረት፡ "እናንተ ስለምትጸልዩና የኢሱስ ክርስቶስ መንፈስ እየረዳኝ ነው።" የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ትኩረት፡ "መንፈስ ቅዱስ"

Philippians 1:20

X

ይህ ትምክቴና በእርግጠኝነት የምጠብቀው ነው እዚህ ላይ"በትምክት የምጠብቀው" እና "በርግጠኝነት" የሚሉ ቃላት የሚናገሩት በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው። ጳውሎስ የሚጠቀመው በተያያዘው የእርሱ አጠባበቅ ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ ለመግለጽ ነው። ትኩረት፡" እኔ ሙሉ ለሙሉ አምናለሁ"

ነገር ግን በሙሉ ድፍረት ሁልጊዜ እንደሚደረግና በተለይም በአሁኑ ጊዜ ትኩረት፡ "ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ሁልጊዜ እንዳለኝ ሁሉ ሙሉ ድፍረት አለኝ።" በሥጋዬ ለክርስቶስ ክብርን አመጣለሁ ጳውሎስ የራሱን ሕይወት ለማቅረብ አካላዊ "ሥጋ" ይጠቀማል። ትኩረት፡ "በማደርገው ሁሉ ክርስቶስን አከብራለሁ።

በሕይወቴ ወይም በሞቴ ትኩረት፡ "በሕይወት ብኖር ወይም ብሞት"



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

Philippians 1:22
ነገር ግን በሥጋ መኖር የሥራዬ ፍሬ ቢሆን
"ፍሬ" የሚለው ቃል የጳውሎስ መልካም ውጤትን ያመለክታል። ትኩረት፡ " ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ ለማገዝ የበለጠ ዕድል ይሰጠኛል።" በሥጋ መቆየቴ ለእናንተ የበለጠ አስፈላጊ ነው ትኩረት፡ "በሥጋ መኖሬ ለእናንተ የበለጠ የሚረዳ ነው"
Philippians 1:25
x
ስለዚህ ነገር እርግጠኛ ከሆንሁ "እርግጠኛ ከሆንሁ" እንደምቆይ አውቃለሁ "በሕይወት ለመኖር እንደምቀጥል አውቃለሁ" ወይም "መኖሬን እንደምቀጥል አውቃለሁ" ከሁላችሁ ጋር መኖሬን እቀጥላለሁ "ሁላችሁንም ማገልገሌን እቀጥላለሁ" በዚህ ምክንያት እኔም እንደገና ወደ እናንተ ስመጣ ስለ ክርስቶስ በእኔ ትመካላችሁ ትኩረት፡ "እንግዲህ እንደገና ወደ እናንተ ስመጣ እኔ ስለ ክርስቶስ ስላደረግሁት በእኔ ትመካላችሁ ምክንያቱም" ሕይወታችሁ እንደሚገባ ብቻ ይሁን "ሕይወታችሁ እንደሚገባ ብቻ ኑሩ" በአንድ መንፈስ በአንድ ነፍስ ጸንታችሁ ቁሙ፤
እነዚህ ሁለት ሐረጎች ተመሳሳይ ትርጉሞችንና የህብረትን አስፈላጊነት ይገልጻሉ። "ምንፈስ" እና "ነፍስ" የሚሉ ቃላት አእምሮንና ስሜትን ይገልጻሉ። ትኩረት፡ " ሁሉም የቅቆረጠ ተመሳሳይ ዓላማና አብሮ መሥራት ፍላጎት አላቸው"
ስለ ወንጌል እምነት ትኩረት፡ "በወንጌል ላይ የተመሠረተ እምነትን ለማሠረጫት" ወይም " የምሥራቹ ቃል እንደሚያስተምረን ለመኖር ማመን" (UDB)
Philippians 1:28
x
በአንዳች አትፍሩ ይህ ለፊልጵስዩስ አማኞችትእዛዝ ነው።
ከሚቃወሙአችሁ "በሚታደርጉት ነገር ላይ ከሚቃወሙአችሁ" ለእነርሱ የመጥፋታችው ምልክት ለእኛ ግን ከእግዚአብሔር የሚሆን የመዳናችን ምልክት ነው ትኩረት፡"ምክንያቱም ድፍረታችሁ የሚያሳያቸው እግዚአብሔር እነርሱን እንደሚያጠፋቸው ነገር ግን እናንተን እንደሚያድናችሁ ነው"
በእኔ ያያችሁት መከራ ስለ ተቀበላችሁ አሁንም በእኔ እየተፈጸመ እንዳለ ሰምታችኋል ትኩረት፡ "ይህም መከራ ከዚህ በፊት ደርሶንኝ ያያችሁትና አሁንም እየደረሰብኝ መሆኑን የሰማችሁት ነው።

---

Chapter 2
Philippians 2:1
የሚያገናኝ ዐረፍተ ነገር ጳውሎስ አማኞችን ህብረትና ትህትና እንዲኖራቸው ይመክራቸዋል፤እንዲሁም የክርስቶስን ምሳሌ ያስታውሳቸዋል። ስለዚህ ምንም ቢሆን፤ ምንም ቢሆን፤ ምንም ቢሆን ጳውሎስ "ቢሆን" የሚለውን የዐረፍተ ነገር መመሠረቻ ቃል የሚጠቀመው እነዚህ ሁሉ የሚከሰቱ መሆናቸውን ለማመልከት ነው። ትኩረት፡ " እስካለ ደረሰ፤እስካለ ደረሰ" የመንፈስ ህብረት "ከመንፈስ ጋር ህብረት'
x
Philippians 2:3
x
በራስ ወዳድነት ወይም በከንቱ ምኞት አንዳች አታድርጉ ትኩረት፡ "ራሳችሁን ብቻ የሚያስደስት ወይም ከሌሎች ይልቅ የበለጠ አስፈላጊ እንደሆናችሁ የሚያደርጋችሁን ከቶ አታድርጉ።" ለራሳችሁ ብቻ የሚያስፈልጋችሁን አትፈልጉ ትኩረት፡ " ለራሳችሁ ብቻ የሚያስፈልጋችሁን አትመልከቱ።"
Philippians 2:5
x
በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ አሳብ በእናንተ ይሁን እዚህ ላይ "አሳብ" የአንድ ሰው ዝንባሌ ወይም እንዴት እንደሚያስቡ እንደሆነ ያመልክታል። ትኩረት፡ "በክርስቶስ ኢየሱስ ያለ አሳብ በእናንተ ይኑራችሁ" ወይም " ነገሮችን ክርስቶስ ኢየሱስ በሚያስብበት መንገድ አስቡ"
Philippians 2:9
x
እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ከፍ አደረገው " እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሁሉ በላይ ከፍ አደረገው" ከስሞች ሁሉ በላይ እዚህ ላይ "ስም" ማዕረግ ወይም ያመለክታል። ትኩረት፡ "ከማዕረግ ሁሉ በላይ" ወይም "ከክብርም ሁሉ በላይ"
ጉልበት ሁሉ እዚህ ላይ "ጉልበት" የሰው ሁለንተና ነው። ትኩረት፡ "እያንዳንዱ ሰው" ወይም "ማንኛውም ፍጥረት"
ከምድር በታች ይህ የሚያመለክተው ሰዎች ከሞቱ በኋላ የሚሄዱበት ቦታ፤ "ገሀነም" የሚጠራ፤እንዲሁም አጋንንት የሚኖሩበት ጨለማ/ጥልቅ ገደል ተብሎ የሚጠራ።" እዚህ ላይ "ምላስ" የሰው ሁለንተናን ያመለክታል። ትኩረት፡ "እያንዳንዱ ሰው" ወይም "እያንዳንዱ ፍጥረት"
Philippians 2:12
x
የሚያገናኝ ዐረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ በሌሎች ፊት የክርስትና ሕይወት እንዴት እንደሚኖሩ የፊልጵስዩስ አማኞችን የበረታታል፤ የእርሱንም ምሳሌ ያስታውሳቸዋል። የተወደዳችሁ ትኩረት፡"በእምነት ውድ ወዳጆቼ" እኔ ባለሁበት ትኩረት፡"እኔ ከእናንተ ጋር በምሆንበት" እኔ በራቅሁበት ትኩረት፡ "ከእናንተ ዘንድ በሌለሁበት ጊዜ" መዳናችሁን ፈጽሙ ትኩረት፡ "እግዚአብሔርን መታዘዝ ቀጥሉ" በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ "ፍርሃትና መንቀጥቀጥ" የሚሉ ቃላት የሚናገሩት መሠረታዊ ነገሩ ተመሳሳይ ነው። ጳውሎስ በእግዚአብሔር ክብር እንዲኖር ለመግለጽ ይጠቀማል። ትኩረት፡ "ጥልቅ ክብር" ፍቃዱንና ማድረግን እግዚአብሔር የእርሱን ሥራ እንድንሠራ ያበረታተናል ያስችለንማል።
Philippians 2:14
x
ነውርና ነቀፋ የሌላችሁ ጳውሎስ ተመሳሳይ አሳብን በአዎንታዊና አሉታዊ ቃላትን በመጠቀም ይገልጻል። ትኩረት፡"ፍጽም ንፁሐን" ያለ ነቀፋ ትኩረት፡"ያለ ነውር" ወይም "ፍጹም" ብርሃን ታበራላችሁ ይህ እግዚአብሔርን በማያከብሩ ሰዎች መካከል እግዚአብሔርን እያከበሩ በጨለማ ብርሃን እያበሩ የሚኖሩ አማኞችን ያወዳድራል ።ትኩረት፡ "እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ኑሩ" በዓለም ላይ እዚህ ላይ "ዓለም" እግዚአብሔርን የማያከብር እሴትና አስተሳሰብን ያሳያል። በጠማማና በመጥፎ እነዚህ ሁለት ቃላት ማለት በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው። ጳውሎስ እነዚህን ቃላት የሚጠቀመው ትውልዱ ምን ያህል ክፉ እንደሆነ ለመግለጽ ነው።ትኩረት፡"ፍጹም ክፉ" ለክብር "ሐሴት ለማድረግ" ወይም "ለመደሰት" በክርስቶስ ቀን ይህ ኢየሱስ መንግሥትን ለማጽናትና ምድርን ለመግዛት በሚመጣበት ጊዜ መሆኑን ያመለክታል። ትኩረት፡ "ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ" በከንቱ አልሮጥም ወይም በከንቱ አልደከምም "በከንቱ መሮጥ" እና "በከንቱ መድከም" የሚሉ ሐረጎች እዚህ ላይ የሚሉት ተመሳሳይ ነገር ነው። ጳውሎስ ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ ያደረገው ምን ያህል ከባድ እንደሆን ለመግለጽ ነው። ትኩረት፡ "እንግዲህ የደከምሁት በከንቱ አይደለም"
Philippians 2:17
x
ነገር ግን የእኔ ሕይወት እንደ መሥዋዕት ሆኖ ቢቀረ እንኳ ደስ ይለኛል፤ ከሁላችሁ ጋር ታላቅ ደስ ይለኛል ጳውሎስ የራሱ ሞት ከብሉይ ኪዳን ወይን ወይም የወይራ ዘይት በእንስሳት መሥዋዕት ላይ ወይም አጠገብ መሥዋዕት አቅራቢ ለእግዚአብሔር እንደሚያፈስ ዓይነት ያወዳድራል። ጳውሎስ እያለ ያለው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በደስታ ልሞት እንደሚገባ ነው። ትኩረት፡ "ነገር ግን ሮማውያን ሊሰቅሉኝ ቢወስኑ እንኳ የእኔ ሞት ለእናንተ እምነትና ደስታ የሚያደርግ ከሆነ የበለጠ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ከሆነ እጅግ ደስ ይለኛል" በተመሳሳይ ሁኔታ ትኩረት፡ "በተመሳሳይ ሁኔታ" በታላቅ ደስታ ጋር መደሰት አለባችሁ "ከታላቅ ደስታ ጋር መደሰት" የሚለው ሐረግ ለመግለጽ ይጠቀማል። ትኩረት፡ "ከእኔ ጋር በታላቅ ደስታ እንድትደሰቱ እፈልጋለሁ"
Philippians 2:19
x
የሚያገናኝ ዐረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ጢሞቲዎስን እንደሚልክላቸው አሳብ እንዳለና ኤጳፍሮድጡን በልዩ ሁኔታ እንዲያስተናግዱ ይነግራል። ነገር ግን በጌታ ኢየሱስ እጠብቃለሁ ትኩረት፡ "ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ፈቃዱ ከሆነ እጠብቃለሁ" ስለ እነርሱ ሁሉ እዚህ ላይ "እነርሱ" የሚለው ቃል ጳውሎስ ወደ ፊልጵስዩስ ለመላክ መተማመን የማይችላቸው የሰዎች ቡድን ናቸው። ጳውሎስ ደግሞ መሄድ የነበረባቸው ነገር ግን ጳውሎስ መልእክታቸውን ለመፈጸም ያልታመነ፤ ከቡድኑ ጋር ደስተኛ አለመሆኑን እየገለጸ ነው።
Philippians 2:22
x
ጢሞቲዎስ ራሱን አረጋገጠ ትኩረት፡ "ጢሞቲዎስ ለኢየሱስ ነገሮች ጥንቃቄ መውሰድ አሳይቶአል"
ልጅ አባቱን እንደሚያገለግል እኔን አገለገለኝ ጳውሎስ የጢሞቲዎስን አገልግሎት

ከእርሱ ጋር ልጅ አባቱን እንደሚያግልግል ያወዳድራል።
በወንጌል ሥርጭት ትኩረት፡" ለሰዎች ስለ ወንጌል መንገር" በጌታ እታመናለሁ እኔ ራሴ ቶሎ እመጣለሁ ትኩረት፡ "የጌታ ፈቃድ ከሆነ ቶሎ እንደምመጣ እርግጠኛ ነኝ"
Philippians 2:25
X
ኤጳፍሮዲቱስን ይህ ሰው ጳውሎስን በእስር ቤት እንዲያገለግል የተላክ ነው። አብሮኝ የሚሠራና ወታደር እዚህ "ወታደር" ጦርነትን ከሚዋጋ ሰው መንፈሳዊ ጦርነት ከሚዋጋ አማኝ ጋር የሚነፃፀር ነው። ጳውሎስ አማኙ ወንጌልን ለማሰራጨት ከክፉ ጋር የሚያደርገው ትግል ለመግለጽ ነው። ትኩረት፡"በእምነት ከእኛ ጋር አብሮ የሚሠራና የሚታገል" መልእክተኛና በሚያስፈልገኝ አገልጋይ ትኩረት፡ "መልእክቶቻችሁን ወደ እኔ የሚያመጣና በሚያስፈልገኝ የሚረዳኝ" በጥልቀት አዝኖአል፤ ከሁላችሁ ጋር ለመሆን ፈልጎአል ሐዘን ላይ ሐዘን ትኩረት፡በእስር ላይ እያለሁ ሐዘን ላይ ሐዘንን ልጨምርብኝ ነበር"
Philippians 2:28
X
ኤጳፍሮዲቱስን ተቀበሉት "ኤጳፍሮዲቱስን ተቀበሉት" በጌታ ከሁሉ ደስታ ጋር ትኩረት፡ "በጌታ በእምነት አብሮ የሚሠራ" ወይም "ጌታ ኢሱስ ስለሚወደን ታላቅ ደስታ አለን"(UDB) የክርስቶስን ሥራ የሚሠራ ትኩረት፡ለክርስቶስ መሥራት"(UDB) የሚያስፈልገኝን አዘጋጀ ትኩረት፡"የሚያስፈልገኝን ያዘጋጃል"

---

Chapter 3
Philippians 3:1
X
የሚያገናኝ ዐረፍተ ነገር፡ አብሮ የሚሠሩ አሮጌውን የአይሁድ ሕግ ለመከተል የሚሞክሩትን የእምነት ወዳጆችን ለማስጠንቀቅ፤ ጳውሎስ የአማኞችን ስደት ስለ ራሱ ምስክርነት ይሰጣል። በመጨራሻም፤ ወንድሞቼ ትኩረት፡ "ወንድሞቼ ሆይ፤ወደ ፊት ስለሚሆን፤ ወይም "ወድሞቼ ሆይ፤ስለሌሎች ጉዳዮች" በጌታ ደስ ይበላችሁ ትኩረት፡ጌታ ስላደረጋቸው ሁሉ ደስ ይበላችሁ" ከዚህ በፊት የጻፍኩላችሁን ተመሳሳይ ነገሮች አሁንም ደግሜ ብጽፍላችሁ አይታክተኝም ትኩረት፡"አሁንም እነዚህን ተመሳሳይ ትምህርቶችን ብጽፍ ደስ ይለኛል" እናንተን በሰላም ይጠብቁአችኋል እዚህ ላይ "እነርሱ" የሚለው የጳውሎስን አስተምህርሆዎች ያሳያል። ትኩረት፡"እነዚህ ትምህርቶች ከስሕተት ስለሚጠብቁአችሁ"
ተጠበቁ "ጥንቃቄ አድርጉ" ወይም "ተጠንቀቁ" ውሾች፤ክፉ አድራጊዎች፤ ከሐሰተኞች መገረዝ እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ተመሳሳይ ቡድን የሆኑ የተለያዩ ሦስት መንገዶችን የሚገልጹ ናቸው። ውሾች "ውሾች" የሚለው ቃል ከአይሁድ ውጪ የሆኑትን ሰዎችን ለመግልጽ አይሁዶች የተጠቀሙበት ነው። ጳውሎስ የሐሰት አስተማሪዎችን እንደ ስድብ ከውሾች ጋር ያነጻጽራል። በባሕላችሁ የረከሰ የተለየ እንስሳ ካለ ወይም እንደ ስድብ የሚቆጠር ካለ በውሻ ፈንታ ይህን እንስሳ ልትጠቀሙ ትችላላችሁ። ሐሰተኛ መገረዝ "መግረዝ" ማለት በአሰቃቂ ሁኔታ ማረድ ወይም መቁረጥ ማለት ነው። ጳውሎስ የሐሰት አስተማሪዎችን ለመኮነን የግሪዛትን ድርጊት በተጋነነ ሁኔታ ይገልጻል። የሐሰት አስተማሪዎች የሚሉት አንድ ሰው የተገዘ እንደሆነ ነው። ስለዚህ እኛ እውነተኛ መገረዝ ጳውሎስ በአካል ያልተገረዙትን ነገር ግን በመንፈሳዊ የተገረዙትን ማለትም በእምነት መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉትን በክርስቶስ አማኝ የሆኑትን ለማሳየት ይህን ሐረግ ይጠቀማል። ትኩረት፡ "በእውነት የእግዚአብሔር ሕዝብ" በሥጋ መመካት የለም ትኩረት፡ "እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ሥጋችንን በመቁረጥ አትመኩ"
Philippians 3:4
X
እኔ ራሴ ትምክህት ልኖረኝ እችል ነበር። ፥ማንም ሰው በሥጋ ትምክህት አለኝ ብሎ ቢያስብ እኔ እበልጠዋለሁ ይህ ለጳውሎስ ለማመን የማይቻል መላምት ሁኔታ ነው። ጳውሎስ የሚለው እግዚአብሔር ሰዎችን በሠሩ ሥራ የሚያድን ከሆነ እግዚአብሔር እርሱን ያድን ነበር። ትኩረት፡ "ማንም ሰው እግዚአብሔርን ለማስደሰት በቂ ነገሮችን መሥራት የሚችል ቢሆን ኖሮ እኔ ነበርኩ" እኔ ራሴ ጳውሎስ "እኔ ራሴ" የሚለውን የሚጠቀመው ትኩረት ለመስጠት ነው። ትኩረት፡" በእርግጥ እኔ ነበርሁ" ተገርዤ ነበር ትኩረት፡ "ካህኑ ገርዞኝ ነበር"
ስምንተኛው ቀን "ከተወለድኩ ሰባት ቀኖች በኋላ" (UDB) ከዕብራዊ ዕብራዊ "ዕብራዊው ልጅ ከዕብራዊ ወላጆች" ከሕግ አንፃር ፈሪሳዊ ትኩረት፡"እንደ ፈሪሳዊ ሕግን በጠበቅ ፍጹም ነበርኩ"
Philippians 3:6
X
ቤተ ክርስቲያንን አሳድድ ነበርሁ ትኩረት፡"ክርስቲያኖችን ለመጉዳት በጣም ቁርጠኛ ነበርኩ" ሕግን በመጠበቅ ያለ ነቀፋ ነበርኩ ትኩረት፡ " ሕግን በመጠበቅ ፍጹም ነበርኩ" እንደ ከንቱቆ ጥሬዋለሁ ጳውሎስ የእርሱ የጽድቅ ሥራዎች ሁሉ በክርስቶስ ፊት ከንቱ እንደሆነ ይደመድማል።
Philippians 3:8
X
በርግጥ "በርግጥም" ወይም "በእውነት" አሁን እቆጥራለሁ "አሁን" የሚለው ቃል ጳውሎስ ፈሪሳዊ መሆኑን የተዋበትና በክርስቶስ አማኝ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ መለወጡን ለማጉላት ነው" ትኩረት፡ "አሁን በክርስቶስ አምኛለሁ" ሁሉን ነገር እንደ ጉዳት እቆጥራለህ ጳውሎስ ከክርስቶስ ሌላ በማንኛውም ነገር መታመን ከንቱ እንደሆነ ይገልጻል። ትኩረት፡ "ማንኛውንም ነገር እንደ ከንቱ እቆጥራለሁ" ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጠው ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታዬ ዕውቀት ትኩረት፡"የክርስቶስ ኢየሱስ ጌታዬ ዕውቀት ከሁሉ ይበልጣል" ስለ እርሱ ሁሉ ነገር እንደ ጥራጊ እቆጥራለሁ ትኩረት፡ከእርሱ የተነሣ ማንኛውንም ነገር በፈቃዴ ክጃለሁ" እንደ ቤት ጥራጊ እቆጥራለሁ ጳውሎስ አንድ ሰው የሚመካበት ነገር የሚጣል መሆኑን ያነጻጽራል። ምን ያህል ከንቱ እንደሆን ትኩረት ይሰጣራል። ትኩረት፡ "እንደ ጉድፍ አስባለሁ" ወይም "ፍጽም ከንቱ እንደሆኑ አስባለሁ" ስለዚህም ክርስቶስን አገኝ ዘንድ "ስለዚህ ክርስቶስ እንዲኖረኝ ብቻ" አሁን በእርሱ ተገኝቻለሁ "በእርሱ ተገኝቻለሁ" የሚለው ሐረግ ማለት ከእርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት ወይም ከክርስቶስ ጋር ህብረት መኖር ማለት ነው" ከሕግ የራሴ የሆነ ጽድቅ የለኝም ትኩረት፡"በራሴ ሕግን በመታዘዝ እግዚአብሔርን ለማስደስት አልሞክርም" በዚህ ፈንታ አለኝ "ይልቁን ይህ አለኝ" ወይም "በቀጥታ ተቃራኒውአለኝ" ከእግዚአብሔር ያለኝ ጽድቅ በእምነት በክርስቶስ ያለኝ ነው ትኩረት፡ "እግዚአብሔር በክርስቶስ ባለኝ እምነት የተነሣ እግዚአብሔር ተቀብሎኛል" የትንሣኤው ኃይል ትኩረት፡የእርሱ ኃይል ሕይወት እንደሚሰጥ አውቃለሁ" የእርሱ የመከራው ተካፋዮች "የመከራው ተካፋዮች" ሞቱን በሚመስል በክርስቶስ ተለውጫለሁ "መለወጥ" የሚለው ቃል ማለት አንድን ነገር በአንድ ነገር መለወጥ ማለት ነው።ኢየሱስ የሞተበት መንገድ የዘላለም ሕይወት አስገኘ። እንግዲህ ጳውሎስ የዘላለ ሕይወት ለማግኘ ሞቱ የኢየሱስን ሞት እንዲመስል ይፈልጋል። ትኩረት፡ "ክርስቶስ ሞቱን እንዲመስል ለውጦኛል" እንግዲህ እንደምንም ከሞት መነሳትን ለማመድ እንድችል ነው "እንደምንም" የሚለው ቃል ማለት ጳውሎስ በዚህ ዓለም ምን እንደሚሆን አያውቅም፤ ነገር ግን ምንም ቢሆን የዘላለ ሕይወት መሆኑ አይቀርም። ትኩረት፡ "እንግዲህ አሁን ምን ቢሆን ግድ የለም፤ ከሞትኩ በኋላ ወደ ሕይወት እመጣለሁ"
Philippians 3:12
X
የሚያገናኘው ዐረፍተ ነገር፡ ጳውሎስ ለአማኞች ለሚጠብቃቸው መንግሥተ ሰማያትና አዲስ ሕይወት የተነሣ የአሁኑን ሕይወት ምሳሌ እንዲከተሉ ያስጠነቀቃቸዋል። እነዚህን ነገሮች አግኝቻለሁ እነዚህ ክርስቶስን ማወቅ፤የትንሳኤውን ኃይል ማ ወቅ፤ መከራ ተካፋይ መሆንና ከክርስቶስ ጋር በሞቱና በትንሳኤው ሕብረት ማድረግን ይጨምራል። እንግዲህ አሁን ፍጹም አይደለሁም "እንግዲህ ገና ፍጹም አይደለሁም" ወይም "እንግዲህ ገና ብስለት የለኝም" ነገር ግን ወደ ፊት ጥረቴ እቀጥላለሁ "ነገር ግን ሙከራዬን እቀጥላለሁ"(UDB) እጨብጣለሁ "እነዚህን ነገሮች እቀበላለሁ" በክርስቶስ ኢየሱስ አግኝቻለሁ ትኩረት፡ "በዚህ ምክንያት ክርስቶስ የእርሱ የራስይ እንደሆንኩ ቆጥሮአል" ወንድሞች ሆይ፤ ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን ያመለክታል። ትኩረት፡ "የእምነት ወዳጆች" እኔ ራሴ ገና አልጨበጥኩትም ትኩረት፡ "እነዚህ ነገሮች ሁሉ ገና የእኔ መሆናቸው አልታወቀም" ከኋላዬ ያለውን እየረሰው ወደ ፊት ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ በእሽቅድድም እንደሚሮጥ ሰው ከኋላ ያለውን ሳይሆን ወደ ፊት በቀራው ላይ ትኩረት እንደሚደረግ ጳውሎስ የሚናገረው የእርሱ የሃይማኖታዊ ጽድቅ ሥራ ወደ ኋላ ትቶ በክርስቶስ በተዘጋጀው እንዲጨርሰው በፊቱ ባለው ሩጫ ትኩረት ማድረግ ነው። ትኩረት፡"ቀድሞ ስለሥራሁት ግድ የለኝም" ግቡን ለመድረስ በክርስቶስ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለማሸነፍ ወደ ፊት ጥረቴን እቀጥላለሁ ጳውሎስ እሽቅድድምን ለማሸነፍ እንደሚሮጥ ንጽጽሩን ይቀጥላል፤ ጳውሎስ ለማገልገልና ለክርስቶስ በመታዘዝ መመላለስን ትኩረት ያደርጋል። ትኩረት፡" የእርሱ ለመሆንና


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ከሞትኩ በኋላ እግዚአብሔር ሲጠረኝ ወደ ራሱ ለመሄድ በክርስቶስ ማመኔን እቀጥላለሁ"
Philippians 3:15
x
ስለዚህ እንደ ባለአእምሮ እናስብ ጳውሎስ የእምነት ወዳጆችን እርሱ እንደ ጠቀሳቸው ፍላጎት እንዲኖሩ ይፈልጋል PHP 3:8-11። ትኩረት: "በእምነት እንደ ጠነከሩ ሆነው አንድ አሳብ እንዲያስቡ ሁላችንንም አማኞች አደፋፍራለሁ" እንደምታስቡ እዚህ ላይ "እናንት" የሚለው ቃል የሚያሳየው በተለየ ሁኔታ የሚያስቡ አማኞች ወይም ከጳውሎስ ጋር የማይስማሙትን ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ለእናንተ ይገልጻል "እግዚአብሔር ደግሞ ግልጥ ያደርግላችኋል" በየትኛውም ደርጃ የደረስን ቢሆን በዚያው በደረስንበት ሁኔታ እንመላለስ ትኩረት:"ሁላችንም በተቀበልነው እውነት መሠረት በመታዘዝ እንቀጥል"
Philippians 3:17
x
ወንድሞች ሆይ፤ ተባበሩኝ ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን እንደ ራሱ ወንድሞቹ በቁጥር ይገልጻል። እኔን ምሰሉ "እኔ የማደርገውን አድርጉ" ወይም "እኔ እንደምኖር ኑሩ" በጥንቃቄ ጠብቁ "በጥንቃቄ ተመልከቱ" በምሳሌአችን ለሚመላለሱ "ቀድሞኑ እኔ እንደምኖር የሚኖሩ" ወይም "ቀድሞኑ እኔ እንደማደርገው የሚያደርጉ" ሁልጊዜ እንደ ነገርኩአችሁ "ብዙውን ጊዜ ነግሬአችኋለሁ" በእንባ እነግራችኋለሁ "በታላቅ ሐዘን እነግራችኋለሁ" ብዙዎች የክርስቶስ ጠላቶች ሆነው ይኖራሉ እዚህ ላይ "የክርስቶስ መስቀል" የክርስቶስን መከራና ሞትን ያመለክታሉ። ጠላቶቹ በክርስቶስ እናምናለን የሚሉና ነገር ግን የክርስቶስን መከራውን ለመቀበል ወይም ፤ለመሞት ፍቃደኛ የማይሆኑ። ትኩረት:ብዙ ሰዎች በኢየሱስ እንደሚያምኑ የሚናገሩ ነገር ግን ሥራቸው መከራ ሊቀበልና በመስቀል ላይ ለመሞት ፍቃደኛ የሆነው የክርስቶስ ጠላቶች ናቸው።" መጨረሻቸው ጥፋት ትኩረት: "እግዚአብሔር አንድ ቀን ያጠፈቸዋል" ሆዳቸው አምላካቸው እዚህ ላይ "ሆድ" የአንድ ሰው ለአካላዊ ምኞች ፍላጎቶችን ያመለክታል። ትኩረት: "እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ይልቅ ምግብና ሌሎች ለአካል የሚያስፈልጉ ምኞችን ይፈልጋሉ" ክብራቸው በነውራቸው ትኩረት: "ውርደት በሚሆኑ ነገሮች ላይ የሚመኩ ናቸው" ስለ ምድራዊ ነገሮች ያስባሉ እዚህ ላይ "ምድራዊ" የሚያሳየው ማንኛውም ነገሮች ለአካል ምኞት የሚሰጡና ለእግዚአብሔር ክብር የማይሰጡ ነገሮችን ያመለክታል። ትኩረት: "የሚያስቡት ሁሉ እግዚአብሔርን ከሚያስደስተው ይልቅ ራሳቸውን የሚያስደስቱ ነገሮችን ነው"
Philippians 3:20
x
የእኛ፤እኛ ጳውሎስ "የእኛ" እና "እኛ" በማለት አድማጮችን ያካትታል። መኖሪያችን በሰማይ ነው "መኖሪያችን በሰማይ ነው" ወይም "እውነተኛ ቤታችን በሰማይ ነው" አዳኙን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከምንጠባበቅበት "እኛ ከሰማይ ወደ ምድር የሚመለሰውን አዳኙን ጌታ እየሱስ ክርስቶስን እንጠባባቃለን" የተዋረደውን ሰውነታችንን ይለውጣል "የእኛን ደካማና ምድራዊ አካላችንን ይለውጣል" ክብሩን በሚመስል በተሠራው አካላት "አካሉን በሚመስል አካላት" ሁሉን ለመቆጣጠር በእርሱ ኃይል በተሠራው ትኩረት: "ሁሉን ነገር ለመቆጣጠር በሚጠቀምበት በተመሳሳይ ኃይል አካላችንን ይለውጣል"

Chapter 4
Philippians 4:1
x
የሚያገነኝ ዐረፍተ ነገር: ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ አማኞች በህብረት ጉዳዮች ላይና አማኞች ከአንዳንድ ተጨባጭ መመሪዎች ጋር ለጌታ እንዴት እንደሚኖሩ መመሪያ መስጠቱን ይቀጥላል። ስለዚህ የምናፍቃችሁ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ትኩረት: "የእምነት ወዳጆቼ እወዳችኋለሁ እንዲሁም መጥቼ እናንተን ለጠየቅ ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ" ደስታዬና አክሊሎቼ ጳውሎስ"ደስታ" የሚለውን ቃል የደስታው ምክንያት የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች ለመግለጽ ይጠቀማል። "አክሊል" ከቅጠል የሚሠራና አንድ ሰው አንድ ጨወታ ሲያሸንፍ ለክብር ምልክት እንዲሆን በጭንቅላት ላይ የሚደፋ ነው። እዚህ ላይ "አክሊል" የሚለው ቃል የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ለጳውሎስ በእግዚአብሔር ፊት ክብርን አምጥቶአል። ትኩረት: "በኢየሱስ በማመናችሁ ምክንያት ደስታ ሆናችኋል እንዲሁም ለሥራዬ ሽልማቴና ክብሬ ናችሁ" የተወደዳችሁ ወዳጆቼ ሆይ፤በዚህ መንገድ ጸንታችሁ ትኩረት: "እንግዲህ ውድ ወዳጆቼ እኔ ባስተመኩአችሁ መንገድ ለጌታ መኖራችሁን ቀጥሉ" ከኤዎድያና ከሲንጢኪ ጋር አብሬ እያዘንኩ ነው በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስን የረዱ አማኝ የነብሩ ሴቶች ናቸው።ትኩረት: " ኤዎዲያንና ሲንጢኪን እለምናቸዋለሁ" በጌታ በአንድ ልብ ሁኑ "በአንድ ልብ ሁኑ" የሚለው ሐረግ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ወይም አመለካከት ማለት ነው። ትኩረት: "በአንድ ጌታ ስለምታምኑ እርስ በርሳችሁ ተስማሙ" በርግጥ እውነተኛ የሥራ ባልደረባዬ ደግሞ እያስተናገድኩ ነው እዚህ ላይ "እናንተ" የሚለው ቃል አስፈላጊ ነው። ጳውሎስ የሰው ስም አልጠቀሰም። ወንጌልን ለማሰራጨት ከጳውሎስ ጋር የሠራ አንድ ሰው የሚጠቅሰው "እውነተኛ የሥራ ባልደረባዬ" ብሎ ብቻ ይጠራል። ትኩረት: "አዎን፤ እውነተኛ የሥራ ባልደረባዬ ደግሞ እጠይቃለሁ" ከቄሌመጦስ ጋር ቁሌመንጦስ አማኝ የነበረውና በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የሚሠራ ነበር። ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ላይ ያላቸው ትኩረት: "ስማቸውን በሕይወት መጽሐፍ እግዚአብሔር የጻፋቸው"
Philippians 4:4
x
ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችህ ደግሜ እላለሁ በጌታ ደስ ይበላችሁ ጳውሎስ የሚናገረው ለሁሉም ፊልጵስዩስ አማኞች ነው።ደስ የበለጠ ትኩረት ለመስጠት እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ ይበላችሁ የሚለውን ትእዛዝ ይደግማል ። ትኩረት: "ጌታ ስላደረገላችሁ ነገር ደስ ይበላችሁ! እንደገና እነግራችኋለሁ ደስ ይበላችሁ!" ጌታ ቅርብ ነው አማራጭ ትርጉሞች 1)ጌታ ኢየሱስ ለአማኞቹ ቅርብ ነው ወይም2) ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር የሚመለስበት ቀን ቅርብ ነው። በሁሉ ነገር በጸሎት የሚያስፈልጋችሁን ጠይቁ አመስግኑም "የሚያስፈልጋችሁን እግዚአብሔርን በጸሎትና በምስጋና ጠይቁ" ከመረዳት የሚያልፈውን "ልንረዳው ከምንችለው በላይ" ልባችሁንና አሳባችሁን ይጠብቃል ይህ የእግዚአብሔር ሰላም እንደ ወታደር ስሜቶቻችንና አሳቦቻችንን ከጭንቀት የሚጠብቀውን ያቀርባል። ትኩረት: "እንደ ወታደር ስሜታችንና አሳባችንን ስለዚህ ዓለም መጨነቅ ይጠብቃችኋል"
Philippians 4:8
x
በመጨረሻ ይህ የደብዳቤውን ይህ ክፍል ያጠቃልላል። ጳውሎስ አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንዲኖር እንዴት እንደሚኖሩ ማጠቃለያ እየሰጠ ነው። ወንዳሞች ሆይ እዚህ ላይ ይህ ማለት ክርስቲያን ወዳጆች፤ ወንዶችንና ሴቶችን ጨምሮ ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ሰማያዊ አባታቸው ሁሉም አማኞች በክርስቶስ አንድ መንፈሳዊ ቤተ ሰብ አባላት ስለሆኑ ነው። ማንኛውም ነገሮች በፍቅር ነው "ማንኛውም ነገሮች የሚያስደስቱ ናቸው" ማንኛውም ነገሮች ከመልካም የሚነገር "ማንኛውም ነገሮች ሰዎች የሚያደንቁ" ወይም "ማንኛውም ነገሮች ሰዎች የሚያከብሩ" ትክክል ይሆነውን ሁሉ "በሞራል መልካም ከሆኑ" ማንኛውም ምስጋና ካላቸው "ለምስጋና ምክንያት ከሆኑ" እነዚህን ነገሮች አስቡ "ስለእነዚህ ነገሮች አስቡ" ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁንና ያያችሁትን "እኔ ያስተማርኩአችሁንና ያሳየኋችሁትን"
Philippians 4:10
x
የሚያገነኘው ዐረፍተ ነገር: ጳውሎስ የሚናገረው በገንዘብ ስለ ደገፉት ሲሆን፤ እንድዲሁም በሰላምታና ምስጋና ይደመድማል። ከዚህ በፊት ስለ እኔ ያስባችሁ ቢሆንም እኔን ለመርዳት ዕድሉን አላገኛችሁም ነበር። "ካሁን በፊት ስለ እኔ ታስቡ እንደነበረ አውቃለሁ፤ ነገር ግን ድጋፋችሁን ለመላክ ምክንያት አልነበራችሁም" የረካ መሆን "መርካት" ወይም " ደስተኛ መሆን" በሁሉም ሁኔታ "በየትኛውም ሁኔታ ቢሆን ግድ የለኝም" እንዴት እንደምኖር አውቃለሁ ትኩረት: "ትክክለኛ አስተሳሰብ እንዴት እንደሚኖረኝ አውቃለሁ" በአስፈላጊ ጊዜ "የሚያስፈልገኝ ሁሉ በማይኖረኝ ጊዜ" በሚበዛበት ጊዜ "ከሚያስፈልገኝ በላይ ሲሆረኝ" በመጥገብና በመራብ፤ በመብዛትና በሚያስፈልገኝ ጊዜ እነዚህ ሁለት ሐረጎች በመሠረቱ ተመሳሳይ ነገር ነው። ጳውሎስ በማንኛውም ሁኔታ መርካትን እንዴት እንደተማረ ትኩረት ለመስጠት እነዚህን ሐረጎች ይጠቀማል። ኃይልን በሚሰጠኝ ሁሉ ማድረግ እችላለሁ "ሁሉን ማድረግ እችላለሁ ምክንያቱም ክርስቶስ ኃይልን ይሰጠኛል"
Philippians 4:14
x
በችግሬ ጊዜ "ነገሮች አስቸጋሪ በሚሆኑበት ጊዜ" የወንጌል ተልእኮ ይህ የሚያመለክተው ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ለመንገር ወደ ተለያዩ ከተሞች መጓዙን ነው። በመስጠትና በመቀበል ጉዳይ ላይ ከእናንተ በስተቀር የረዳኝ ቤተ ክርስቲያን የለም ትኩረት: "የእናንተ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናችሁ ገንዘብ ወይም ርዳታ የሰጣችሁኝ"

 generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ፍሬአችሁ እንዲበዛላችሁ እፈልጋለሁ ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን ስጦታ ለአንድ ሰው የበለጠ የሚጨምረው ብልጽግና እያነጻጸረ ነው።ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ሰዎች መንፈሳዊ በረከት ለመቀበል ስለሚችሉ እንዲሰጡ ይፈልጋል"
Philippians 4:18
x
ሁሉም ነገር በብዛት አለኝል። ሞልቶልኛል ትኩረት: "ማንኛውም የሚያስፈልገኝና የሚተርፍ አለኝ" እነርሱም ጠፋጭ መዓዛ ያለው፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕትና እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነው። መልካም መዓዛ፤ ተቀባይነት ያለው እግዚአብሔርን የሚያደስት መሥዋዕት፤ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ስጦታን ከብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ጋር እያነጻጸር ነው። ካህናት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን መሥዋዕት ያቃጥላሉ። ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን ስጦታ ታላቅ ዋጋ ያለ መሆኑን ትኩረት እየሰጠ ነው። ትኩረት: "እነዚህ ስጦታዎች እግዚአብሔርን የሚያስደስት እንደሆነ አረጋግጣለሁ" የሚያስፈልገውን ሁሉን ያዘጋጃል "የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ያዘጋጃል" በክርስቶስ ኢየሱስ እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት ትኩረት: "በክርስቶስ ከክብሩ ባለጠግነት ይሰጣል" አሁን ለአላካችን "አሁን" የሚለው ቃል የመዝጊያ ጸሎትና የዚህ ደብዳቤ ክፍል መደምደሚያ ነው።

---

Chapter 1
Colossians 1:1
ቆላስያስ 1፡ 1-3
አጠቃላይ መረጃ: ይህ ወደ በቆላስያስ ለሚኖሩ አማኞች በጳውሎስ እና በጢሞቴዎስ አመካኝነት የተጻፈ ደብዳቤ ነው። በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ የሆነ "የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ለመሆን በእግዚአብሔር የተመረጠ" ወንድሞቻችን “እኛ” በሚለው ቃል ውስጥ ጳውሎስ ተደራሲያኑንም አካቷል።" ጸጋ ለእናንተ ይሁን ለሌላ ሰው ባርኮትን መስጠት ወይም ለሌላ ሰው መመኘት እናንተ በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቆላስያስ የሚገኙ ቅዱሳንን እና ታማኝ የሆኑ ወንድሞችን ነው። ስለእናነት ዘወትር እንጸልያለን አማራጭ ትርጉም: "ስለ እናንተ ሁል ጊዜ ከልባችን ሆነን እንጸልያለን።"
Colossians 1:4
ቆላስያስ 1፡ 4-6
አጠቃላይ መረጃ: በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር አመልካች ሲሆን የሚመለክተው በቆላስያስ የሚገኙ አማኞችን ነው። ስለ እናንተ ሰምተናል በዚህ ሥፍራ ጳውሎስ “እኛ” የሚለው ቃል በመጠቀም አንባቢያኑን በውስጡ አላካተተም። በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላችሁን እምነት "በኢየሱስ ክርስቶስ ያላችሁ እምነት" ለቅዱሳንም ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ሰምተን፥ "ለቅዱሳን ሁሉ ያላችሁን ፍቅር" (UDB) በሰማይ ከተዘጋጀላችሁ ተስፋን እንደሚታገኙ ካላችሁ ሙሉ እምነት የተነሣ "እግዚአብሔር በሰማይ ያስቀመጠላችሁን ተስፋ ላይ ካላችሁ እርግጠኝነት የተነሣ" እርግጠኛ ተስፋ "አጥብቃችሁ የያዛችሁት ተስፋ" ፍሬ ያፈራል እንዲሁም ያድጋል ይህ የተለያዩ ለምግብነት የሚሆኑ ነገሮችን ከሚያፈራ ዛፍ ወይም እጽዋጽ ጋር ተነጻጽሮ የቀረበ ሲሆን ሰዎችን የሚለውጠው ወንጌልም አድጎ ብዙ ሰዎች ባመኑት ቁጥር በዓለም ሁሉ ይሰራጫል። በዓለም ዙሪያ ሁሉ ወንጌል በሚታወቀው ዓለም ዙሪያ ሁሉ ይሰራጫል እንዲሁም ያድጋል። የእግዚአብሔር ጸጋ በእውነት "እውነተኛው የእግዚአብሔር ጸጋ" ወይም "እውነተኛው የእግዚአብሔር ሞገስ"
Colossians 1:7
ቆላስያስ 1፡ 7-8
ልክ ከኤጳፍራ እንደተማራችሁት ሁሉ "ልክ ኤጳፍራ እንዳስተማራችሁ ሁሉ" ወይም "ኤጳፍራ ያስተማራችሁን ሁሉ ሙሉ ለሙሉ በሚገባ እንደተረዳችሁት ሁሉ" ልክ እደዛው “እርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የወንጌል መልዕክት በቆላስያ ከተማ ውስጥ በሚገኙ አማኞች የዕለት ተዕለት ሕይወት ላይ ያመጣውን ውጤት የሚያመለክት ነው። እናንተ ተምራችኋል በቆላስያ ከተማ ይኖሩ የነበሩት አማኞች ይህንን ተምረዋል ኤጳፍራ ኤጳፍራ Epaphras በቆላስያ ከተማ ውስጥ ከነበሩ አማኞች ወንጌል የሰበከላቸው ሰው ነው። ከተወደደ ከእኛም ጋር አብሮ ባሪያ ከሆነው ከኤጳፍራ እንዲህ ተማራችሁ፥ እርሱም ስለ እናንተ ታማኝ የክርስቶስ አገልጋይ ነው። ይህ ማለት ኤጳፍራ ጳውሎስ በእስር ቤት ባይሆን ኖሮ ልፈጽመው የሚችለው ነገር በማድረግ የክርስቶስን ሥራ የሠራ ሰው ነው ማለት ነው። እርሱ ለእኛ ገልጦልናል "ኤጳፍራ ለእኛ አስታውቆናል" በመንፈስ ስላልችሁ ፍቅር "ለአማኞች ፍቅር እንዲኖራችሁ መንፈስ ቅዱስ አቅም ሰጥቶአችኋለህ"
Colossians 1:9
ቆላስያስ 1፡ 9-10
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በክርስቶስ ስላላቸው እምነት እና በመንፈስ ስላላቸው ፍቅር ይጸልይላቸዋል። በዚህ ፍቅራችሁ ምክንያት "መንፈስ ቅዱስ ሌሎች አማኞችን መውደድ እንዲትችሉ ስላደረጋችሁ" ስለእናንተ ከሰማንበት ጊዜ አንስቶ "ኤጳፍራ ስለ እናንተ ለእኛ ከነገረበት ጊዜ አንስቶ" ሰምተናል ይህ የሚያመለክተው ጳውሎስ እና ጢሞቴዎስን እንጂ በቆላስያስ ከተማ የሚገኙ አማኞችን አይደለም። መጸለይ አላቋረጥንም "ብዙ ጊዜ እና ከልባችን ወደ እግዚብሔር እንጸልያለን" የእርሱ ፈቃድ ምን እንደሆነ ታውቁና በዚህ ትሞሉ ዘንድ እንጠይቃለን "የእርሱን ፈቃድ ታደርጉ ዘንድ በእውቀት ሞላችሁ ዘንድ እግዚአብሔርን እንጠይቀዋለን" በጥበብ እነና መንፈሳዊ መረዳት ሁሉ "በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ጥበብ እና መረዳት" በሁሉም ነገር ለጌታ እንደሚገባ ትኖሩ ዘንድ "ጌታ በሚፈቅደው መንገድ መኖር ትችሉ ዘንድ ፍሬ እንዲታፈሩ ይህ ሀረግ ፍሬጣማ እጽዋትነን ከአማኝ መልካም ሥራ ጋር የሚያነጻጽር ነው። ልክ እጽዋት አድገው ፍሬ እደሚያፈሩ ሁሉ አማኞችም በእግዚአብሔር እውት ልያድጉ እና መልካም ሥራን ልሠሩ ይገባል።
Colossians 1:11
ቆላስያስ 1፡ 11-12
ስለ እናንተ እንጸልያለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎስን እና ጢሞቴዎስን የሚወክል እንጂ በቆላስያስ የሚገኙ አማኞችን የሚወክል አይደለም። እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፥ "በታላቅ ክብሩ አማካኝነት በኃይሉ የበረታችሁ ሁኑ" በነገር ሁሉ ጽኑ እንዲሁም ትእግስት ኑራችሁ "ፈጽማችሁ ማመናችሁን አቁሙ እንዲሁም ትእግስት ይኑራችሁ" ለአብን በደስታ ምስጋናን እያቀረባችሁ "ለአብ በደስታ ምስጋናን እያቀረባችሁ" በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አማራጭ ትርጉም: "እንዲንካፈል ያበቃንን" እንድትበቁ ያደረጋችሁን በዚህ ሥፍራ ላይ ጳውሎስ ተደራሲያኑ የእግዚአብሔር ጸጋ ተካፋዮች መሆናቸው ላይ ትኩረት ያደርጋል። ይህ ማለት ግን እርሱ ይህንን ባርኮት በመውረስ ውስጥ ምንም ድርሻ የለኝም እያለ ግን አይደለም። ርስቱን ለመካፈል "ርስቱን ለመካፈል" በብርሃን "በክብሩ መገኘት ውስጥ" for the believers አማራጭ ትርጉም: "ቅዱሳን ለሆኑት" ወይም "ለልዩ ጥቅም የተመረጡት" ለእርሱ "ለአባት"
Colossians 1:13
ቆላስያስ 1፡ 13-14
አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ክርስቶስ በምን መንገድ ልቆ እንደሚገኝ ይናራል። እርሱ አዳነን "እግዚአብሔር አባት አዳነን" አፈለሰን "አሸጋገረን።" በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎስን እና በቆላስያስ ከተማ የሚገኙ አማኞችን በውስጡ ያካትታል። በእርሱ ውድ ልጁ "የእግዚአብሔር አብ ተወዳጅ ልጁ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ" በገዛ ልጁ ቤዛነትን አገኘን "ልጁ ቤዛነትን ሰጠን" የኃጢአታችን ይቀርታን "ልጁ ኃጢአታችንን ይቅር አለን" ወይም "አብ በልጁ በኩል ኃጢአታችን ይቅር አለን"
Colossians 1:15
ቆላስያስ 1፡ 15-17
ልጁ የማይታየው አምላክ መልክ ነው ልጁ ኢየሱስ ምን እንደሚመስል በማወቅ እግዚአብሔር አብ ምን እንደሚመስል ማወቅ እንችላለን። ልጅ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው የኢየሱስ ወሳኝ ስም ነው። እርሱ በኩር ነው "ልጁ በኩር ነው።" ኢየሱስ በጣም ወሳኝ እና ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር “ልጅ” ነው። “ልጅ” የሚለው ቃል ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለውን ልዩ የሆነ ግንኙነት ያሳያል። ይህ በአብ እና በልጁ መካከል ያለው ግንኙነት በቋንቋችሁ ውስጥ “በልጅ” እና “አባት” የሚለውን ቃል ካልተጠቀማችሁ በስተቀር መረዳት አይቻል። ምክንያቱም ሁሉም ነገሮች የተፈጠሩት በእርሱ አማካኝነት ነው "ምክንያቱም ልጁ የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ፈጥሯልና" ዙፋን ቢሆን ወይም ግዛት ወይም መንግስታት ወይም ሥልጣናት ሁሉም ነገሮች በእርሱ እና ለእርሱ ተፈጥረዋል ልጁ ሁሉን ነገር ለራሱ ፈጥሯዋል ይህ ዙፋንን፣ ስልጣንን፣ ገዥዎችን እና ስልታናትን ያካትታል። እርሱ ከነገሮች ሁሉ በፊት ነው "እርሱ ከሁሉም ነገር በፊት ነበር" በእርሱ ሁሉም ነገር እርስ በእርሱ ተያይዟል "እርሱ ሁሉን ነገር አያይዟል" (UDB)
Colossians 1:18
ቆላስያስ 1፡ 18-20
እርሱ ራስ ነው "የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ነው" እርሱ አካሉ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው። ይህ ዓረፍተ ነገር ኢየሱስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያለውን ሥልጣን ራስ በሰው አካል ጋር ካለው ጋር ያነጻጽራል። ልክ ራስ አካልን እንደሚገዛ እንዲሁም ዚየሱስ ቤተ ክርስቲያንን ይገዛል። የሥልጣን ሁሉ ምንጭ

እርሱ ዋነኛ አለቃ ወይም መሥራች ነው። ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያን ጀማሪ ነው። ከሙታን መከካከል በኩር ነው ኢየሱስ ሞተው ከሞት ወደ ሕይወት ከተመለሱት ሰዎች በኩር ነው፣ ከእንግዲህም ፈጽሞ እንደገና አይሞትም። ይህ የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር የእርሱ ሙላት በእርሱ ውስጥ እንዲኖር ስለፈቀደ ነው "እግዚአብሔር አብ እርሱ ያለው ነገር ሁሉ በክርስቶስ እንዲሆን ስለፈቀደ ነውt" በመስቀል ላይ በፈሰሰው የልጁ ደም በኩል "በኩል" ተብሎ የተተረጎመው ዋናው ቃል መሥመር ወይም መንገድ የሚል ሀሳብን በውስጡ ያዘለ ሲሆን እግዚአብሔር በመስቀል ላይ ሞቶ በፈሰሰው የኢየሱስ ደም በኩል ሰላምን እና እርቅን ማምጣቱን የሚያሳይ ነው። ልጅ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ለሆነው ለኢየሱስ ወሳኝ ስም ነው።

Colossians 1:21

ቆላስያስ 1፡ 21-23

እንዲሁም እናንተም ደግሞ "እንዲሁም በቆላስያስ ከተማ የሚትኖሩ አማኞችም ጭምር" ለእግዚአብሔት እንግዶች ነበራችሁ were strangers to God አማራጭ ትርጉም: "ከእግዚአብሔር የተለያችሁ ነበራችሁ" ወይም "እግዚአብሔር የተዋችሁ ነበራችሁ" በአእምሮዋችሁ እና በክፉ ተግባራችሁ የእግዚብሔር ጠላቶች ነበራችሁ "ጠላቶቹ ነበራችሁ ምክንያቱም ክፉ ሀሳብን ስለምታስቡ እና ምክንያቱም ክፉ ተግባርን ስለምትፈጽሙ ነው።." (UDB) በክርስቶስ ሥጋ በሞቱ እግዚአብሔር እናንተን አስታረቀ እግዚአብሔር እናንተ ከኢየሱስ ጋር ስያስታርቃችሁ በመስቀል ላይ የተመለከተው ክርስቶስን ሳይሆን እናንተን ነው ይሁን እንጂ እናንተ ክርስቶስ ሲሞት እናንተም በመስቀል ላይ መሞታችሁን ተመልክቷል። እንከን የለሽ "ምንም እንከን ያሌለበት" ከነቀፋ ውጪ "ምንም ነቀፋ ያሌለበት" በራሱ ፊት "በእግዚአብሔር በራሱ ፊት" ጸንታችሁ ቆማችሁ "በቀጣይነት ጸንታችሁ ተተክላችሁ" ወይም "በቀጣይነት ቆማችሁ" በእምነት ጽንታችሁ "አለመናወጥ" ወይም "መጽናት" በወንጌል መተማመን "በወንጌል ተማምናችሁ" እኔ ጳውሎስ ባሪያ የሆንኩለት ከሰማይ በታች ለፍጥረታት ሁሉ የሰበኩትን ወንጌል "ሰዎች ወንጌልን ከሰማይ በታች ላሉ ፍጥረታት ሁሉ ሰብከዋል። እኔ ጳውሎስ የሚሰብከው እና እግዚአብሔር እንዳገለግል የተራሁት ይህ ተመሳሳይ ወንጌል ነው።"

Colossians 1:24

ቆላስያስ 1፡ 24-27

አሁን እኔ ደስ ይለኛል "እኔ ጳውሎስ አሁን ደስ ይለኛል" ለእናንተ ሲል የሚቀበለው መከራ "ስለ እናንተ ጥቅም ስለል መከራን እቀበላለሁ" (UDB) ስለ እናንተ "ለእናንተ የቆላስያስ አማኞች ሲባል" ስለ አካሉም ማለት ስለ ቤተ ክርስቲያን በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ ውስጥ የጐደለውን እፈጽማለሁ። ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ሲል እየደረሰበት ያለውን ተቃውሞ እና ስደት ነው። ጳውሎስ ገና አማኝ ሲሆን ይህ ከባድ የሆነ መከራ እንደሚደርስበት አስቀድሞ አሳይቶት ነበር። ቤተ ክርስቲያንን አገለግላለሁ "እኔ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን የሚስፈልጋትን ነገር ለመሙላት እፈልጋለሁ" የእውነት ምስጢር "ሚስጥሩ" ለዘመናት ተሸሽጎ ነበር ይህ ከፍጥረት ጊዜ እንስቶ ጳውሎስ ለአሕዛብ ወንጌልን እስከ ሰበከበት ጊዜ ያለውን ዘመን ያመለክቷል። ለአማኞች ተገልጧል አማራጭ ትርጉም: "ለእርሱ ተከታዮች ግልጽ ተደርጎላቸዋል።" ይህ አይሁድንና አሕዛብ ያካትታል። ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ሊያስታውቅ ወደደ፣ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ያለው ዕቅድ ምን ያኽል ግሩም እንደሆነ ማሳወቅ ፈለገ። ምሥጢሩም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው። "ምሥጢሩም የእግዚአብሔርነን ክብር ለወደፊት የመካፈላችሁ ርግጠኝነት ነው" (UDB)

Colossians 1:28

ቆላስያስ 1፡ 28-29

እና የሚነስበከው እርሱን ነው "ጳውሎስ እና ጢሞቴዎስ የሚሰብኩት ክርስቶስ ይህ ነው።" ሁሉንም ሰው እናስተጠነቅቃለን "ሰዎችን ሁሉ እናስጠነቅቃለን" ሰዎችን ሁሉ ማቅረብ እንችል ዘንድ "ሰዎችን ሁሉ ለእግዚአብሔር ማቅረብ እንችል ዘንድ" መፈጸም "መንፈሳዊ ብስለት" ስለዚህ እደክማለሁ "እኔ ጳውሎስ ስለዚህ ነገር እደክማለሁ" በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ "በእኔ እንደሚሠራው የክርስቶስ ዓላማ"

---

Chapter 2

Colossians 2:1

ቆላስያስ 2፡ 1-3

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በቆላስያስ እና በሎዶቂያ የሚገኙ አማኞች ክርስቶስ አምላክ እንደሆነ እና በአማኞች ውስጥ እንደሚኖር ተገንዝበው እርሱን በተቀበሉበት መቀበል መኖር እንዳለባቸው ማበረታታቱን ቀጥሏል። ስለዚህ ይህንን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ "እኔ ጳውሎስ በቆላስያስ የሚትኖሩ አማኞች ይህንን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ" እንዴት ያለ ትልቅ መጋደል እንዳለኝ ልታውቁ እወዳለሁና፤ የእርሱን ንጽሕና ለማሳደግ እና የወንጌል መረዳታቸቸውን ለመጨመር ጳውሎስ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። በሎዶቅያ ላሉት ይህች ከተማ የቆላስያስ ከተማ ቅርብ የሆነች ከተማ ሲትሆን በዚህች ከተማ ውስጥመም ቤተ ክርስቲያን ነበረች፣ ጳውሎስም ለዚህች ከተማ ይጸልይላታል። ብዙዎች በሥጋ ፊቴን የማየት እድል አላገኙም "ብዙዎቹን በአካል አላገኟቿውም" ወይም "ብዙዎችነን ፈጽሞ ፊት ለፊት አግኝቼአቸው አላውቅም" ልባቸውም "ጳውሎስን በአካል አይተውት የማያውቁት ሁሉም አማኞች ልብ" ወደ አንድነት እንዲሰበሰብ በእውነተኛ ግንኙነት እንድቀራረቡ። አማራጭ ትርጉም: "እርስ በእርሳቸው እንዲተባበበሩ" ወይም "እርስ በእርሳቸው እንዲቀራረቡ" ከመረዳት የሚመጣ መተማመን ይህ እነዚህ ነገሮች በማወቅ የሚገኝ መተማመን ማለት ነው። የእግዚአብሔር ምስጢር ይህ በእግዚአብሔር ስገለጥ ብቻ የሚታወቅ ነገር ነው። ይኼውም ክርስቶስ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር የተገለጠ ምስጢር ነው። የጥበብ እና እውቀት የተደበቀ መዝገብ ታላቅ የጥበብ እና የእውቀት ሀብት ወይም ባለጠግነት ጥበብ እ እውቀት እነዚህ ቃላት በመሠረታዊ ሀሳባቸው ተመሳሳይ ናቸው። ጳውሎስ እነዚህ ቃላት በአንድነት የተጠቀመው ሁሉም መንፈሳዊ መረዳቶች ከክርስቶስ ዘንድ እንደሚመጡ አጽኖት ለመስጠት ነው። በእርሱ ናቸው "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስቶስን ነው።

Colossians 2:4

ቆላስያስ 2፡ 4-5

ይህንን እላለሁ "እኔ ጳውሎስ ይህንን እላለሁ" እንዳያስታችሁ "እናንተ የቆላስያስ አማኞችን ወደ ተሳሳተ ሥፍራ ወይም ድምዳሜ እንዳይመራችሁ" በሚያሳምን ንግግር የሆነ ነገርንን እንዲታምኑ የሚያደርግ ንግግር ወይም አንድን ሀሳብ የሚታመን የሚያደርግ ንግግር ምንም እንኳ በሥጋ ከእናንተ ጋር ባልሆንም "በአካል ከእናንተ ጋር ባልሆንም" በመንፈስ ግን ከእናንተ ጋር ነኝ "ሁል ጊዜ ስለ እናንተ አስባለሁ" መልካም ሥርዓታችሁን ጳውሎስ ስለ አንድነታቸው እና ስለ እምነታቸው ጥንካሬ እንዲሁም በክርስቶስ ላይ ስላላቸው እምነት አመስግኖዋቸዋል።

Colossians 2:6

ቆላስያስ 2፡6-7

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመላለሱ ይህ በተወሰነ የአኗኗር ዘይቤ ወይም መነንገድ መኖርን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለ አገላለጽ ነው። እንደተቀበላችት "በቆላስያስ ከተማ ውስጥ ያሉ አማኞች ክርስቶስን እንደተቀበሉት" በእርሱ ጸንታችሁ ቁሙ፣ በእርሱ እደጉ በዚህ ሥፍራ ጳውሎስ ክርስትያኖች መኖር ያለባቸውን ሕይወት ለመግለጽ እና ስለ መንፈሳዊ ብስከለት ለመግለጽ ሁለት ምሳሌያዊ ነግግሮችን ይጠቀማል በእምነታችሁ ጽኑ "ሕይወታችሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባላችሁ እምነት መሥርታችሁ ኑሩ" ምስጋና ይብዛላችሁ "እግዚአብሔርን በጣም አመስግኑት"

Colossians 2:8

ቆላስያስ 2፡ 8-9

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ አማኞች ወደ ቃላት እና ሌሎች ሕግጋት እንዳይመለሱ ያስጠነቅቃል ምክንያቱም አማኞች አሁን በክርስቶስ ካላቸው የእግዚአብሔር ሙላት ላይ ምንም የሚጨምሩት ነገር የላቸውምና። ይህንን ተመልከቱ "ጥንቃቄ አድርጉ" ወይም "ተጠንቀቁ" ፍልስፍና ስለ እግዚአብሔር እና ሕይውት ከእግዚአብሔር ቃል ያልወጣ ሃይማታዊ አስተምህሮዎች እና እምነቶች ባዶ ማታለል ይህ በክርስቶስ ወደ ሆነ ሕይወት የማይመሩ አሻች ሀሳቦችን ያመለክታል። ምንም ነገር አያፈሩም ባዶ ወይም ዋጋ ያሌላቸው ነገሮች ናቸው። እንደ ሰው ወግና እንደ ኃጢአት የሞላበት የዓም ሥርዓት የአይሁድ እና የአረማዊያን (አሕዛብ) የእምነት ሥርዓቶች፣ ሁለቱም ምንም ዋጋ የላቸውም። እንደ ክርስቶስ ትምህርት አይደሉም "እንደ ክርስቶስ ትምህርት አይደሉም" ወይም "በክርስቶስ ትምህርት ላይ የተመሠረቱ አይደሉም" ምክንያቱም የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካሉ ውስጥ ይኖራል "ምክያቱም የእግዚአብሔር ሙሉ ባሕርይ በክርስቶስ አካል ውስጥ ይኖራል"

Colossians 2:10

ቆላስያስ 2፡ 10-12

በእርሱ "በኢየሱስ ክርስቶስ" እናንተ ናችሁ "እናንተ በቆላስያስ የሚትኖሩ አማኞች



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ናችሁ ፈጽሞ ሙሉ ሆናችኋል "ሙሉ ሆናችኋል" እግዚአብሔር ገርዞዋችኋል ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ልክ በግርዛት ወቅት ሥጋ በቢላዋ ተቆርጦ እንደሚጣል ሁሉ እግዚአብሔር የአማኖችን ኃጢት ፈጽሞ አስወግዷል። ከእርሱ ጋር ተቀብራችኋል ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ልክ አንድ ሰው ሲሞት አካሉ በምድር ውስጥ እንደሚቀበር ሁሉ እንዲሁም ድነትን ባገኛችሁበት ወቅት የድሮው ባሕርያችሁ በመቅጽበት እንዴት እንደሚወገድ የሚብራራ ነው። ከእርሱ ጋር ተነሥታችኋል ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ልክ አንድ ሰው ከሞት ስነሳ አዲስ ህይወት እንደገና እንደሚኖረው ሁሉ አንድ አማኝ እንዴት አዲስ ባሕርይ እንደሚሰጠው ያመለክታል።

Colossians 2:13

ቆላስያስ 2፡ 13-15

ሙታን በሆናች ጊዜ "የቆላስያስ አማኞች በመንፈሳዊ ሞት ውስጥ በነበሩበት ጊዜ" በመተላለፋችሁ ሙታን ነበራችሁ እንዲሁም በሥጋችሁም ያልተገረዛችሁ ነበራችሁ በሁለት ነገሮቸ ሙታን ነበሩ: 1) በመንፈሳዊ ሕይወት ሙታን፣ ክርስቶስ የሚበድል ኃጢአት የሞላበትን ሕይወት ትኖሩ ነበር እና 2) እንደ ሙሴ ሕግ የተገረዛችሁ አልነበራችሁም። እርሱ እናንተን እንዲህ አደረጋችሁ "ኢየሱስ እናንተን የቆላስያስ አማኞችን እንዲህ እንዲትሆኑ አደረገ" መተላለፋችንን ሁሉ ይቅር አለን "ኢየሱስ ክርስቶስ አይዳዊያንን እና አሕዛብን ሁለቱን መተላለፋችንን ሁሉ ይቅር አለልን።" እናንተ ሙታን ነበራችሁ . . . ሕያዋን እንዲትሆኑ አደረገ ይህ ምሳሌዊ ንግግር ልክ የሞተ ሰው ወደ ሕይወት በአካል እንደሚመጣ ሁሉ እኛም እንዴት ኃጢአተኛ ከሆነ ሕይወት ወደ አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት እንደመጣን ያሳያል። በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር እግዚአብሔር የእኛን ኃጢአት (እዳ) እና የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፋችን መሰረዙን በወረቀት ላይ የተጻፉ ዝርዝሮችን ከመሰረዝ ጋር እያነጻጸረ ያቀርባል። ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው። በሮማዊያን ዘመን የሮም ወታደሮች ከጦርነት ሲመለሱ "የድል ጉዞ" ማድረግ የተለመደ ነገር ነው። በዚህ ወቅት በምርኮ የያዝዋቸውን ምርኮኞች እና የነጠቁትን ሀበት ያሳያሉ።

Colossians 2:16

ቆላስያስ 2፡ 16-17

ማንም አይፍረድባችሁ ጳውሎስ አማኞችን አሕዛቦች የሙሴን ሕግ መጠበቅ አለባቸው ከሚሉ አይዳዊያን ይጠበቁ ዘንድ ያስጠነቅቃቸዋል። በሚበላ ወይም በሚጠጣ ነገር የሙሴ ሕግ ምን መበላት እና መጠጣት እዳለበት የሚያሳይ ሕግ አለው። አማራጭ ትርጉም: AT: "በምትበሉት ወይም በምትጠጡት ነገር" የጾም ቀን ወይም አዲስ ጨረቃ ወይም ስለ ሰንበት የሙሴ ሕግ መከበር ያለባቸው፣ የአምልኮ ቀናት እና መስዋእት የሚቀርብበት ቀን መቼ እንደሆነ ይደነግጋል። እነዚህ ለሚመጣው ነገር ጥላ ናቸው "ጥላ" የአንድን ነገር ቅርጽ እና አጠቃላይ ሁኔታን ድብዝብዝ ባለ መንገድ የሚያሳይ ነው። በተማሳሳይ መልኩም እንደ ሙሴ ሕግ ያሉ ሃይማኖታዊ ትውፊቶች በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠውን እውነተኛውን ነገር በከፍል ብቻ የሚያሳዩ ናቸው።

Colossians 2:18

ቆላስያስ 2፡ 18-19

ዋጋችን ማንም ሰው እንዳይወስድባችሁ "ማንም ከሚያገኘው ዋጋ የተነሣ እንዳያታልላችሁ።" ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የውሸት ትህትናን እና የመላእክት አምልኮን በቆላስያስ ከተማ ውስጥ የአማኞችን ድነት ለመስረቅ ከሚሞክር ሌባ ጋር ያነጻጽራል። አማራጭ ትርጉም: "ማንም የሌላ ሰውን ሽልማት እንዲሰርቅ አትፍቀዱለት።" የውሸት ትህትና "ትሁት ለመመስል የሚደረግ ጥረት።" ይህ ማለት በሌሎስ ሰዎች ፊት ትሁት ለመምሰል የተለያዩ ነገሮችን ማድረግ ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም: "ራስን የካዱ መምሰል" በተለያዩ ነገሮችን ከሚገባ በላይ መያዝ ይህ ማለት አእምሮን ሁል ጊዜ የሚዝ ወይም በሆነ ነገር በጣም መያዝን ያሳያል። አዲስ አስተሳሰብ ይህ ማለት እንደ መንፈሳዊ ሰው ሳይሆን ተፈጥሮአዊ ወይም ኃጢአተኛ ሰው ማሰብ ማለት ነው። አጥብቆ አይዝም "አጥብቆ አይዝም" ወይም "አይጠጋም፣" ልክ ልጅ ወደ ወላጆቹ እንደሚጠጋው ማለት ነው።

እንደዚህ ያለ ሰው ራስ ወደሚሆነው አይጠጋም፥ ከእርሱም አካል ሁሉ በጅማትና በማሰሪያ ምግብን እየተቀበለ እየተጋጠመም፥ እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ ያድጋል።

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያለው ስልጣንን የሰው ልጅ ጭንቅላላት አካሉን ከሚቆጣጠርበት እና ከሚገዛበት መንገድ ጋር ያነጻጽራል።

Colossians 2:20

ቆላስያስ 2፡ 20-23

ከክርስቶስ ጋር ለዚህ ዓለም ኃጢአተኛ ሥርዓት ከሞትን ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የሚያሳየው ልክ የሞተ ሰው የዚህ ዓለም አካላዊ ፍላጎቶች ታዲያ ለዚህ ዓለም እምነት ተገዝታችሁ ስለምን ትኖራላችሁ ጳውሎስ ይህን ጥያቄ የተጠቀመው የቆላስያስ አማኞች የዚህ ዓለምን የሐሰት የእምነት ሥርዓት መከተላቸውን ለመገሰጽ ነው።) ተገዝቶ መኖር "መገዛት" ወይም "መሰጠት" ወይም "መታዘዝ" መጥፋት "መበስበስ" እነዚህ ደንቦች በሰው የተዘጋጁ ሃይማኖታዊ "ጥበቦች" አሏቸው እንዲሁም ትሁታን ይመስላሉ አካላቸውንም ሃይማኖተኛ ለመምሰል ያጎሳቁላሉ። ሃይማኖትን በመፍጠር እና የሐሰት ትህትና እና አካላቸውም በሃይማኖት ስም በማጎሳቆል - "እነዚህ ህግጋት ከሰው ልጅ የእይታ አንጻር ጥበብ የሞላባቸው ይመስላሉ እንዲሁም አካላቸውን ያጎሳቁላሉ"

ማጎሳቆል "በከፍተኛ ሁኔታ መጉዳት" ወይም "ማሰቃየት" ነገር ግን ሥጋ ያለ ልክ እንዳይጠግብ ለመከልከል ምንም አይጠቅምም። "የሥጋን ፍላጎት መከተልን ለማስቆም ግን ምንም እገዛ አያደርጉም"

---

## Chapter 3

Colossians 3:1

ቆላስያስ 3፡ 1-4

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆናችሁ ምክንያት አማኞች ማድረግ የሌለባቸው ነገሮች አሉ በማለት ጳውሎስ አማኞች ያስጠነቅቃቸዋል። እግዚአብሔር እናንተን ከክርስቶስ ጋር ከሞት አስነስቷችኋል ልክ እግዚአብሔር ክርስቶስን ከሞት እንዳነሣው ሁሉ እግዚአብሔር በቆላስያስ ከተማ የሚገኙ አማኞችም ከሞት እንደተነሱ ይቆጥራል። አንስቶዋችኋል "እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቆላስያስ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ አማኞችን ነው። የላይኛውን ነገር "ሰማያዊውን ነገር" ወይም "መለኮታዊውን ነገር" በምድር ላይ ያለውን "ምድራዊውን ነገር" ወይም "የምድርን ነገር" እናንተ ሞታችኋልና ክርስቶስ በእርግጥ እንደሞተ እግዚአብሔር በቆላስያስ ከተማ ውስጥ የሚኖሩት አማኞችንም ከክርስቶስ ጋር እንደሞቱ አድርጎ ይቆጥራቸዋል። እግዚአብሔር ሸሽጎታል "እግዚአብሔር ሰውሮታል" ከእርሱ ጋር በክብሩ ውስጥ በዚህ ሥፍራ "እርሱ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስቶስን ነው።

Colossians 3:5

ቆላስያስ 3፡ 5-6

ስለዚህ ኃጢአተኛ መሻታችሁን ግደሉት። ይህ ልክ ክፉ ሰው እንዲሞት እንደሚደረግ ሁሉ ኃጢአተኛ መሻታችሁ ፈጽም እና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገድ ይኖርባችኋል። ንጹሕ ያልሆነ ነገር "ንጹሕ ያልሆነ ባሕርይ" መሻት "ጠንካራ የዝሙት ምኞት" እና ጣኦትን ለማምለክ መመኘት "እና ስግብግብነት፣ ይህ ልክ እንደ ጣኦትን ማምለክ ነው" ወይም "እና ስግብግብ አትሁኑ ምክንያቱም ይህ ጣኦትን ከማምለክ ጋር ተመሳሳይ ነውና" (UDB) ስለዚህም በእነዚህ ነገሮች ምክንያት በማይታዘዙ ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣል። "እነዚህ ነገሮች በሚያደርጉ በማያምኑ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣባቸዋል።" እናንተም ደግሞ ትኖሩባቸው በነበራችሁ ጊዜ፥ በፊት በእነዚህ ተመላለሳችሁ። "እነዚህ ነገሮች ትፈጽሙ በነበረበት ወቅት ትመላለሱ የነበረው እንዲህ ነበር። ቁጣ "ቅጣት" ንዴት "ቁጣ" ክፉ ምኞቶች አማራጭ ትርጉም: "የልብ ክፋት፣ ሕይወት እና ባሕርይ" ስድቦች "እግዚአብሔርን መሳደብ" ወይም "እርኩሰት የሞላበት ቃል መናገር።" ይህ ሌሎች ሰዎችን ለመጉደት ሲባል የሚነገር ንግግርን ያመለክታል። አሳፋሪ፣ ሰዎችን የሚያሰናክል ንግግር አማራጭ ትርጉም: "ቆሻሻ ንግግር"

Colossians 3:9

ቆላስያስ 3፡ 9-11

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ በአሕዛብ እና በአይሁድ፣ በባሮች እና በነጻ ሰዎች መካከል የነረው ግድግዳ ክርስቶስ እንዳፈረሰው በማስታወስ አማኞች እንዴት መኖር እንዳለባቸው ማስታወሱን ቀጥሏል። እናንተ ገፋችሁታል በዚህ ሥፍራ ላይ "እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቆላስያስ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ አማኞችን ነው። አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፣ የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል፤ ይህ ምሳሌዊ ንግግር እግዚአብሔር የማይከብርበትን ባሕርይ አስወግድ እግዚአብሔር የሚከብርበትን ተግባር መፈጸም የጀመሩ ክርስትያኖች ቆሻሻ ልብስን አውልቆ አዲስ እና ንጹሕ ልብስከለበሰ ሰው ጋር ያነጻጽረዋለረ። የእርሱ መልክ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚወክል ነው። የእርሱ መልክ እውቀት ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ እና


generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

መረዳት በዚያም የግሪክ ሰው አይሁዳዊም የተገረዘም ያልተገረዘም አረማዊም እስኩቴስም ባሪያም ጨዋ ሰውም መሆን አልተቻለም፥ ይህ ማለት እግዚአብሔር ሁሉንም ሰዎች ያለልዩነት ይመለከታቸዋል፣ በዘር፣ በሀገር ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ደረጃ ሳይሆን ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም: “ዘር፣ ሃይማኖት፣ ባሕል እና በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ደረጃ የሚያመጣው ነገር የለም።” ክርስቶስ ሁሉ በሁሉ ነው ከክርስቶስ ሕልውና ውጪ የሚሆን ምንም ነገር የለም። አማራጭ ትርጉም: “ክርስቶስ በጣም አስፈላጊ ነው።”

Colossians 3:12

ቆላስያስ 3፡ 12-14

ልበሱት . . . የርህራሄን ልብ ሰው ልብስ እንደሚለብስ ሁሉ አማኞችም ለእያንዳንዳቸው በሚያሳዩት ባሕርይ ርህራሄን፣ ትህትናን ወዘተን መልበስ ይገባቸዋል። ስለዚህ ልበሱት በዚህ ሥፍራ ላይ "ስለዚህ" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ከዚህ በፊት በነበረው ውይይት ወይም በተሰጠው ትምህርት መሠረት መደረግ ያለበትን መተግባር ወይም ባሕርይ ለይቶ ለመናገር ነው። (ተመልከት: [[rc://*/ta/workbench/discourse/home]]) የእግዚአብሔር ምርጦች እንደመሆናችሁ - ቅዱስ እና የተወደደ "የእግዚአብሔር ቅዱሳን እና በእርሱ የተወደዳችሁ ምርጦቹ እንደመሆናችሁ። የርህራሄ ልብ፣ መልካምነት፣ ትህትና፣ ገርመት እና ትዕግስት "ርህራሄ. መልካምነት፣ ትህትና፣ ቅንነት እና ትዕግስት የውስት ማንነት ናቸው" ርሁሩ ልብ "የሚራራ ልብ" ወይም "ለሌሎች የሚያስብ ልብ" መልካምነት "መልካምነት" ወይም "ገርነት" ትህትና "የአእምሮ ትህትና" ወይም "የአእምሮ ገርነት" ቅንነት "ቅንነት።" ነፈስ ስሜትን ከመከተል ይልቅ ወደ እግዚአብሔር የሚጋድል ከሆነ ትዕግስት "መቻል" ወይም "መከራን መቀበል መቻል" እርስ በእርስ መቻቻል በመስማማት እና በፍቅር በአንድነት መሥራትለ። “እርስ በእርስ መስማማት” ወይም “እርስ በእርስ መቻቻል።” አንዱን ሌላኛውም መውቀስ "ሌላኛውን መውቀስ" ፍቅር ይኑራችሁ "ፍቅርን ደርቡ ይህ የፍጹምነት ማሠሪያ ነው "ይህ አንድ ልይ በትክክል የሚያያዝ ነው" ወይም "ይህ በአንድ ላይ ፍጹም በሆነ መልኩ በስምምነት የሚያሳስር ነው።"

Colossians 3:15

ቆላስያስ 3፡ 15-17

በልባችሁ ይግዛ "በልባችሁ ላይ ይንገሥ" በልባችሁ ውስጥ በዚህ ሥፍራ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የቆላስያስ አማኞች ነው። በእናንተ ይኖራል "በእናንተ ውስጥ ያድራል" ወይም "በእናንተ ውስጥ ይኖራል" እርስ በእርሳችሁ ተጠባበቁ "እንዳችሁ ለሌኛችሁ ተጠንቀቁ" በመዝሙር እና በምስጋና እንዲሁም በመንፈሳዊ መዝሙር "በሁሉም ዓይነት መዝሙሮች እግዚአብሔርን አመስግኑት" በልባችሁ አመስግኑ "የሚያመሰግን ልብ ይኑራችሁ" በእርሱ በኩል "በጌታ ኢየሱስ በኩል"

Colossians 3:18

ቆላስያስ 3፡ 18-21

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ከዚያም ጳውሎስ አንዳንድ መመሪያዎችን ለሚስቶች፣ ለባሎች፣ ለሕጻናት፣ ለአባቶች፣ ለባሮች እና ለጌቶች ተገቢ የሆነ "ተገቢ ነው" ወይም "ትክክለኛ የሆነ" አታበሳጯቸው "ክፉ አትሁኑባቸው" ወይም "አትቆጦዋቸው" ይህ ጌታን የሚያስደስት ነገር ነው "ቤተሰቦቻችሁን የሚትታዘዙ ከሆነ ጌታ በዚህ ደስ ይለዋል" ልጆቻችሁን አታበሳጩ "ልጆቻችሁን አታስቆጡ" ወይም "ልጆቻችሁ እንዲበሳጩ አታድርጓቸው"

Colossians 3:22

ቆላስስ 3፡ 22-25

ጌቶቻችሁን ታዘዙ በዚህ ሥፍራ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቆላስያስ የሚገኙ አማኝ የሆኑ ባሮች የሚያመለክት ነው። ለታይታ አይሁን ጌቶቻችሁ ስመለከቷችሁ ብቻ አትታዘዙ። ሰዎችን የሚታስደስቱ ከጌታ ይልቅ በሌሎች ሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሉ የተለያዩ ነገሮችን የሚያደርጉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። (UDB) የሚታደርጉትን ነገር ሁሉ በዚህ ሥፍራ ላይ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ባሮችን ቢሆንም እናንተ ግን በቆላስያስ ከተማ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ክርስቲያኖች የሚያመለክት አድርጋችሁ ልትተረጉምት ትችላላችሁ። ከነፍስ "በሙሉ ልባችሁ" (UDB) ለጌታ ብላችሁ "ለጌታ ብላችሁ" (UDB) የርስት ብድራት "ጌታ ቃል የገባውን ነገር እንደሚወርስ ነው" (UDB) ጽድቅ ያልሆነ ነገር የሚያደርግ ይህ ማንኛውንም ትክክለኛ ያልሆነ ነገር (ሥነ-ምግባር፣ ማህበረሰባዎ ወይም አካላዊ) የሚያመለክት ነው። “ትክክል የማያደርግ ሰው” ወይም “ክፋትን የሚያደርግ ሰው”። ቅጣትን ይቀበላል አማራጭ ትርጉም: "ይቀጣል" ያለልዩነት "ያለምንም ማዳላት" ወይም "ምንም አድሎ አይደረግለትም"

---

Chapter 4

Colossians 4:1

ቆላስስ 4፡ 1-1

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለግለሰቦች የሰጠውን መመሪያ ያጠናቀቀው ለጌቶች በመናገር ነው። ለአገልጋዮቻችሁ ስጡ በዚህ ክፍል ውስጥ “እናነተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቆላስያስ የሚገኙ የባሪያ ባለቤት የሆነ አማኞችን ነው። በጽድቅ እና ቅንነት ይህ ባለቤቶቹ በጽድቅ እና ቅንነት በሞላበት መንገድ ለባሮቻቸው ያሳዩ ዘንድ የታዘዙት ነገርን የሚገልጽ ነው፤ በሰማይ ያለው ጌታ እግዚአብሔር ጌታ መሆኑ የሚያሳየው 1) እግዚአብሔር የባሪያ ባለቤቶችች በምድር ላይ ያሉትን ባሮቻቸውን በያየዙበት መንገድ ነው ወይም 2) ምድራዊ ባሪዎቻችሁን በሚትንከባከቡበት መንገድ እግዚአብሔር፣ ጌታችሁ በተመሳሳይ መንገድ ይመልስላችኋል።

Colossians 4:2

ቆላስያስ 4፡ 2-4

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ አማኞች እንዴት መኖር እና መናገር እንደሚገባቸው መመሪያ መስጠቱን ቀጥሏል። በጸሎት ጽንታችሁ ቀጥሉ "በታማኝነት መጸለያችሁን ቀጥሉ" ወይም "በቀጣይነት መጸለያቸሁን ቀጥሉ" በተጨማሪ ለእኛ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን እና ጢሞቴዎስን ነው ነገር ግን የቆላስያስ አማኞች የሚያካትት አይደለም። እግዚአብሔር በር ይከፍታል አማራጭ ትርጉም: "እግዚአብሔር እድል ያዘጋጃል" የክርስቶስ ምስጢር ይህ ከክርስቶስ መምጣት በፊት ሰዎች በደንብ ያልተረዱትን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን የሚያመለክት ነው። በዚያ ቃል ምክንያት እኔ እስረኛ ነኝ "አሁን በእስር ቤት ያለሁት የኢየሱስ ክርስቶስን መልዕክት በመናገሬ ምክንያት ነው" ግልጽ አድርግ ዘንድ እና ልናገር እንደሚገባኝ ያህል መናር እችል ዘንድ ጸልዩልኝ። "የኢየሱስ ክርስቶስን መልዕክት ግልጽ በሆነ መልኩ መናር እችል ዘንድ ጸልዩልኝ።"

Colossians 4:5

ቆላስያስ 4፡ 5-6

በጥበብ ተመላለሱ። "ባሉት ዘንድ ጠቢባን ሁኑ" በውጭ ባሉቱ ዘንድ "አማኞች ባልሆኑት ዘንድ" ዘመኑን ዋጁ "በሚታደርጉት ነገር ጠቢባን ሁኑ" ቃላችሁ ሁል ጊዜ በጸጋ ይሆኑ። በጨው የተቀመመ ይሁን። አማራጭ ትርጉም: "ንግግራችሁ በጸጋ እና ሰዎችን የሚስብ ይሁን።" ለእነዚህ ነገሮች እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለብህ እወቅ "ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከማንም ለሚመጣው ጥያቄ እንዴት መልስ መስጠት እንዳለብህ ማወቅ ይገባሃል"

Colossians 4:7

ቆላስያስ 4፡ 7-9

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ለተወሰኑ ሰዎች ይሰጥ የነበረውን መመሪያ እንዲሁም ለግለሰቦች እና አማኞች ሰላምታ መስተላለፉን የሚበቃበት ክፍል ነው። ስለ እኔ ማወቅ የሚገባቸውን ነገር ለእናንተ ታውቋል "እኔ ላይ የሆነውን ነገር ሁሉ እነርሱ ይነግሯችኋል" (UDB) ለእናንተ ይገለጻል በዚህ ሥፍራ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የቆላስያስ አማኞችን ነው። አብሮን ባሪያ የሆነው "አብሮን የሚያገለግለው።" ምንም እንኳ ጳውሎስ ነጻ ሰው ቢሆንም ራሱን የክርስቶስ ባሪ አድርጎ ይመለከት ነበር እንዲሁም ቲኪቆስ አብሮን የሚያገለግል ነው። ስለእኛ ታውቁ ይሆናል በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስ እና ከእርስ ጋር የሚሠሩትን ሰዎችን ነው ነገር ግን ይህ በቆላስያስ የሚገኙ አማኞችን አያመለክትም። ልባችሁም እንዲጸና "እናንተን ለማበረታታት" አናሲሞስ አናሲሞስ በቆላስስ ከተማ ውስጥ የፊልሞን ባሪያ ነበር። ይህ ባሪያ ከፊልሞን ገንዘብ በመስረቅ ወደ ሮም ጠፍቶ የነበረ ሲሆን በዚያም በጳውሎስ አገልግሎት አማካኝነት ክርስቲያን ሆኗል። አሁን ከጳውሎስ ዘንድ የተጻፈውን ደብዳቤ ወደ ቆላስያስ ቤተ ክርስቲያን ይዘው የመጡት ቲኪቆስ እና አናሲሞስ ናቸው። ታማኝና ተወዳጅ ወንድም ጳውሎስ አናሲሞስን ክርስቲያን ወንድም እና የክርስቶስ ባሪያ ብሎ ይጠራዋል። ያስታውቃችኋልe " ቲኪቆስ እና አናሲሞስ ይነግሯችኋል" በዚህ የነበራቸውን ነገር ፈጽመዋል በቆላስያስ ከተማ ለሚገኙ አማኞች አሁን ጳውሎስ በሚኖርበት ሥፍራ እየተከናወነ ያለውን ነገር ይነግሯችኋል። በትውፊት ደረጃ ጳውሎስ በሮም በቤት እስር ወይም እስር ቤት እንደነበር ይነገራል።

Colossians 4:10

ቆላስያስ 4፡ 10-11

አርስጥሮኮስ ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ ለቆላስያስ ሰዎች ሲጽፍ በኤፌሶን

ከጳውሎስ ጋር በእስር ነበረ። እርሱ ከመጣ "ማርቆስ ከመጣ" ኢየሱስ ተብሎ የሚጠራው ኢዮስጦስም ይህ ሰውም ከጳውሎስ ጋር አብሮ ይሠራ የነበረ ሰው ነው። ከተገረዙት መካከል አብረውኝ በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ የሚሠሩት እነዚህ ብቻ ናቸው። "እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ንጉሥ እንደሆነ ከእኔ ጋር ይሰብኩ የነበሩት ከአይዳዊያን አማኞች መካል እነዚህ ሦስት ሰዎች ብቻ ነበሩ" (UDB) ከተገረዙት መካከል እነነዚህ ብቻ ናቸው "ከተገረዙት ሰዎች መካከል እነዚህ ሰዎች ኢዮስጦስም፣ ማርቆስ እና ኢየሱስ ብቻ ናቸው"
Colossians 4:12
ቆላስያስ 4፡ 12-14
ኤጳፍራ ኤጳፍራ በቆላስያስ ከተማ ውስጥ ላሉ ሰዎች ወንጌልን የሰበከ ሰው ነው። (ተመልከት COL 1:7) ከእናንተ የሆነው "ከእናንተ ከተማ የሆነው" ወይም "የከተማችሁ ሰው የሆነው" (UDB) የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ "የክርስቶስ ኢየሱስ የተሰጠ ደቀ መዝሙር" በጸሎት ሁል ጊዜ ስለ እናንተ ይጋደላል "በትጋት ስለ እናንተ ይጸልያል" ፈጽማችሁ በእርግጠኝነት በሙላት መቆም ትችሉ ዘንድ "በብስለት እና በመተማመን መቆም ትችሉ ዘንድ" ስለ እናንተ በትጋት እንደሚሠራ እኔ እመሰክራለሁ "ስለ እናንተ በትጋት እንደሚሠራ እኔ ራሴ ተመልክቻለሁ" (UDB) በሎዶቅያ ስላሉት በሎዶቅያ ከተማ ውስጥ ያለችው ቤተ ክርስቲያን። ሎዶቅያ በቆላስያስ አቅራቢያ የሚትገኝ ከተማ ናት። በኢያራ ስላሉት በኢያራ ከተማ ውስጥ ያለችው ቤተ ክርስቲያን። ዴማስ እርሱም ከጳውሎስ ጋር አብሮ ይሠራ የነበረ ሌላ ሰው ነው። ሰላም ብለዋችኋል "ሰላምታ አቅርበውላችኋል"
Colossians 4:15
ቆላስያስ 4፡ 15-17
ወንድሞችን ሰላም በሉልን "ለወንድሞች ሰሰላምታችንን አቅርቡልንል" በሎዶቅያ ላሉ በቆላስያስ ከተማ አቅራቢያ የሚትገኝ ከተማ ሲትሆን በዚህች ከተማ ውስይ ቤተ ክርስቲያን ነበር ንምፉ የተባለች ሴት ሲትሆን በቤቷ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንነበር በሎዶቅያ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ንምፉ ተብላ በሚትጠራ ሴት ቤት ውስጥ ይካሄድ ነበር።አማራጭ ትርጉም: "ንምፉ እና በእርሷ ቤት ውስጥ የሚገናኙት የአማኝ ቡድኖች" (UDB) በእናንተ መካከል ይነበብ በዚህ ሥፍራ "እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቆላስያስ ከተማ ውስጥ የሚገኙ አማኞች ነው። "ለአክሪጳም፦ በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት እንድትፈጽሙው ተጠንቀቅ በሉልኝ።" ጳውሎስ አክሪጳን እግዚአብሔር የሰጠውን የሥራ ኃላፊነት በማስታወስ አክሪጳ ይህንን ኃላፊነት ለመወጣት በጌታ የተሰጠው አደራ እንዳለ ያስታውሰዋል።
Colossians 4:18
ቆላስያስ 4፡ 18-18
ኖት የለውም።

---

Chapter 1
1 Thessalonians 1:1
1ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 1-1
ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ ጢሞቴዎስም ለቤተ ክርስቲያን UDB በግልጽ ይህንን ደብዳቤ የጻፈው ጳውሎስ መሆኑን ይናገራል። ሠላም ለእናንተ ይሁን በዚህ ሥፍራ "እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተሰሎንቄ አማኞችን ነው።
1 Thessalonians 1:2
1ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 2-3
እኛም ሁል ጊዜ ለእግዚአብሔር ምስጋናችንን እናቀርባለን አማራጭ ትርጉም: "አዘውትረን ለእግዚአብሔር ምስጋናን እናቀርባለን" ሁል ጊዜ እኛ በዚህ ሥፍራ "እኛ" የሚለው ቃል ጳውሎስን ስልዋኖስን እና ጢሞቴዎስን የሚወክል እንጂ በተሰሎንቄ ያሉ አማኞችን የሚወክል አይደለም። በጸሎታችን ስለ እናንተ እናሳስባለን "ስለ እናንተ እንጸልያለን" ያለማቋረጥ እናስባለን "ያለማቋረጥ እናስባለን" የእምነት ሥራ "የእምነት ሥራ" ወይም "በእግዚአብሔር የሚታምኑ ስለሆነ ለእርሱ ትሠራላችሁ" (UDB) የጠስፋችሁን መጽናት "በመተማመን መጽናታችሁን"
1 Thessalonians 1:4
1ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 4-5
ወንድሞች "ወንድሞች" መጠራታችሁን እናውቃለን "በልዩ ሁኔታ ታገለግሉት ዘንድ እግዚአብሔር እንደመረጣችሁ እናውቃን" ወይም "የእርሱ ሕዝቦች እንሆን ዘንድ እግዚአብሔር እንደመረጣችሁ እናውቃለን" (UDB) እናውቃለን በዚህ ሥፍራ "እኛ" የሚለው ቃል ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን የሚያመለክት እንጂ በተሰሎንቄ ያሉትን አማኞችን የሚያመለክት አይደለም። ነገር ግን በኃይል፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት አማራጭ ትርጉሞች 1) "ጳውሎስ እና የእርሱ የሥራ አጋሮች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት ወንጌልን በኃይል ይሰብካሉ።" ወይም 2) "ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ ወቃሽ ኃይል አማካኝነት በአማኞች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ የሚያመጣ ነው።" በላቀ ማረጋገጫ "በተመሳሳይ መልኩ" (UDB) ምን ዓይነት ሰዎች "እንዲህ ሲሆን እንዴት ባለ ሁኔታ መኖር እንዳለብን" (UDB)
1 Thessalonians 1:6
1ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 6-7
እኛን መሳዮች ሆናችኋል መመስል ማለት መኮረጅ ወይም መከተል ማለት ነው። አማራጭ ትርጉም: "እኛ መስላችኋል"። በታላቅ መከራ "በታላቅ መከራ ወቅት" ወይም "በታላቅ ስደት ውስጥ" አካይ ይህች ከተማ በዘመኗ ግሪክ ውስጥ የነበረች ከተማ ናት።
1 Thessalonians 1:8
1ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 8-10
ወጥተዋል "ወጥቶ ሄዷል" አካይ ይህች ከተማ በዘመኗ ግሪክ ውስጥ የነበረች ከተማ ናት። ) በእያንዳንዱ ሥፍራ "በአከባቢው ሁሉ ባሉ የተለያዩ ቦታዎች" እነርሱ ራሳቸው ስለሆኑ ጳውሎስ በዚህ ሥፍራ ላይ እያመለከተ ያለው ስለ ተሰሎንቄ አማኞች የሰሙትን በዚያ አከባቢ የሚገኙ ቤተ ክርስቲያናትን ነው። እነርሱ ራሳቸው በዚህ ሥፍራ ላይ "እነርሱ ራሳቸው" ስለ ተሰሎንቄ አማኞች የሰሙትን ሰዎች አጽኖት ሰጥቶ ያመለክታል። ወደ እናንተ መግባታችን እንዴት እንደነበረ ስለ እኛ ይናገራሉና፤ "እንዴት ባለ መልኩ እኛን እንደተቀበላችሁ ታውቃላችሁ" (UDB) ልጆቹ ይህ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ወሳኝ የሆነ ስም ነው። እርሱ ያስነሳው "እግዚአብሔር ከሞት ያስነሳው" እኛንም ያዳነን በዚህ ሥፍራ ላይ ጳውሎስ "እኛ" በሚለው ቃል ውስጥ የሚጽፍላቸውን ዓማኞች አካቷል።

---

Chapter 2
1 Thessalonians 2:1
1ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 1-2
እናንተ ራሳችሁ በዚህ ሥፍራ "እናንተ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በተሰሎንቄ የሚገኙ አማኞችን ነው።
ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ላይ ቃሉ ያለው ትርጉም ክርስቲያኖች ማለት ሲሆን ወንዶችን እና ሴቶችን ያካትታል። በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር መንፈሳዊ አባታቸው የሆነ የአንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ አባላት በመሆናቸው ምክንያት ነው። መምጣታችን በዚህ ሥፍራ ላይ "እኛ" የሚለው ቃል ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን የሚያመለክት ነው። ይሁን እንጂ በተሰሎንቄ የነበሩትን አማኞች ግን አያመለክትም። ከንቱ አልነበረም "በጣም ጠቃሚ ነበር" መከራን ተቀበልን እንዲሁም ተዋረድን ጳውሎስ በፊልጵስዮስ እያለ ተደብድቧል እንዲሁም ታሥሯል። አማራጭ ትርጉም: "ተንገላታን እንዲሁም ተሰደብን።" ከብዙ ግጭቶች መካከል "ታላቅ ተቃውሞ ከደረሰብን በኋላ"
1 Thessalonians 2:3
1ኛ ተሰሎንቄ 2:3-4
ለእኛ ብርታት ይሆነን ዘንድ በዚህ ሥፍራ ላይ "እኛ" የሚለው ቃል ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን የሚያመለክት ነው። ከስሕተት ወይም ከርኩሰት ወይም ከተንኰል አልነበረምና፤ "እውነተኛ፣ ንጹሕ እና ታማኝ" ልባችንን የሚመረምረው እግዚአብሔር "አእምሮዋችንን እና ሥራችንን የሚመረምረው እግዚአብሔር"
1 Thessalonians 2:5
1ኛ ተሰሎንቄ 2:5-6
እኛ ስለሆንን በዚህ ሥፍራ ላይ "እኛ" የሚለው ቃል ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን የሚያመለክት ነው። ይሁን እንጂ በተሰሎንቄ የነበሩትን አማኞች ግን አያመለክትም። በሚያማልል መልኩ ከቶ አልተናገርንም "የውሸት ሙገሳን ከቶ አልተናገርንም" ያመካኘን በመጐምጀት አልሠራንም፤ "ወይም በስስት እናንተ የተለያዩ ነገሮችን ትሰጡን ዘንድ የተለያዩ ቃላትን አልተጠቀምንም" የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ይገባናል ማለት እንችል ነበር "የተለያዩ ነገሮችን እንዲትሰጡን ልንጠይቅ እንችል ነበር"

1 Thessalonians 2:7

1ኛ ተሰሎንቄ 2:7-9

ልክ እናት ልጆቿን እንደሚታጽናና ልክ እናት በእርጋታ ልጇችን እንደምታጽናና እንዲሁም ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን ለተሰሎንቄ አማኞች ረጋ ባለ ሁኔታ አስረድተዋቸዋል፡፡ እንወዳችኋለን "ወደናችኋል" ለእኛ በጣም የተወደዳችሁ ሆናችኋል "ለእናነት ከልባችን እንጠነቀቃለን" ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ላይ ቃሉ ያለው ትርጉም ክርስቲያኖች ማለት ሲሆን ወንዶችን እና ሴቶችን ያካትታል፡፡ በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር መንፈሳዊ አባታቸው የሆነ የአንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ አባላት በመሆናቸው ምክንያት ነው፡፡ ልፋታችን እና ድካማችን “ድካማችን” እና “ልፋታችን” የሚሉት ቃላት በመሠረታዊነ ትርጉማቸው ተመሣሣይ ናቸው፡፡ ጳውሎስ እነዚህ ቃላት የተጠቀመው በእነርሱ መካከል ሳለ ጳውሎስ ምን ያኸል እንደደከመ ለማሳየት መው፡፡ አማራጭ ትርጉም: "ምን ያኸል በትጋት እንደሠራን፡፡" በማናችሁም ላይ ሸክም እንዳንሆን ብለን ቀን ከሌት ሠራን "ከእናንተ ዘንድ እርዳታ እንዳንሻ በማለት ለራሳችን የሚያስፈልገንን ነገር ሠረተን አገኘን፡፡"

1 Thessalonians 2:10

1ኛ ተሰሎንቄ 2:10-12

ቅዱስ፣ ጻድቅ እና እንከን ያሌለበት ጳውሎስ እነዚህ በመሠረታዊ ትርጉማቸው ተመሳሳይ ቃላትን በዚህ ሥፍራ የተጠቀመበት ምክንያት በመካከላቸው ሳለ ጥሩ ባሕርይ እንደነበረው አጽኖት ሰጥቶ ለማሳየት ነው፡፡ አባት ከልጆቹ ጋር ጳውሎስ አባት ልጆቹ ምን ዓይነት ባሕርይ እንዲኖራቸው ከሚያስተምርበት መንገድ ጋር እያነጻጸረ አማኞች ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ይኖሩ ዘንድ አማኞችን ያበረታታል፡፡ እየመከርንን እናጽናናችኋለን “መምከር” እና “ማጽናናት” የሚሉት ቃላት በመሠረታዊ ሀሳባቸው ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ነው፡፡ ጳውሎስ እነዚህ ቃላት በዚህ ሥፍራ ላይ የተጠቀመው በተሰሎንቄ የሚኖሩ ክርስቲያኖችን ለማበረታታት ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም: “እኛ አጥብቀን እናበረታታችኋለን”፡፡ ለራሱ መንግስት እና ክብር በዚህ ሥፍራ ላይ “ክብር” የሚለው ቃል “መንግስት” ለሚለው ቃል ምንነትን የሚገልጥ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም: “ለእርሱ ለራሱ በክብር የተሞላ መንግስት፡፡"

1 Thessalonians 2:13

1ኛ ተሰሎንቄ 2: 13-13

በዚህም ምክንያት እኛም እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ እናመሰግናለን "እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ እናመሰግናን ምክንያቱም" እናንተ በተቀበላችሁ ጊዜ በተሰሰሎንቄ ይኖሩ የነበሩ አማኞች ጳውሎስ ያመታውን መልዕክት ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መልዕክት አድርገው ተቀበሉት እንጂ ከራሱ በጳውሎስ ኃይል የመጣ አድርገው አላዩትም፡፡

1 Thessalonians 2:14

1ኛ ተሰሎንቄ 2:14-16

ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ላይ ይህ ቃል ክርስትያኖች የሚል ትርጉም አለው፡፡ ቤተ ክርስቲያናትን የሚተመስሉ ሁኑ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በአይሁድ መሪዎች ስደት የደረሰባቸው ሲሆን ልክ እንደዚሁም በተሰሎንቄ ያሉት አማኞች በተሰሎንቄ ከተማ በሚኖሩ ሰዎች ስደት ደርሶባቸዋ፡፡ "ቤተ ክርስቲያናትን መስላችኋል" ከገዛ ሀገራችን ሰዎች "ከሌሎች በተሰሎንቄ ከተማ ከሚኖሩ ሰዎች" እንዳንናገር ከለከሉን "እንዳንናገር ሊያስቆሙን ጥረት አደረጉ" ኃጢአታቸውን ይሞላ ዘንድ ሁል ጊዜ "በቀጣይነት ኃጢአት ያደርጉ ዘንድ" ቁጣ በእነርሱ ላይ መጥቶባቸዋል "የእግዚአብሔር ቅጣት በእነርሱ ላይ መጥቷል" ወይም "የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ላይ መጥቷል"

1 Thessalonians 2:17

1ኛ ተሰሎንቄ 2: 17-20

ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ቃሉ የሚያመለክተው ክርስትያኖችን ነው፡፡ በአካል፣ በልብ ሳይሆን "በአካል ነገር ግን ሁል ጊዜ ስለ እናንተ መጸለያችንን ቀጥለናል" ፍታችሁን ለማየት "እናንተን ለማየት" ወይም "ከእናንተ ጋር ለመሆን" እኔ ጳውሎስ እንደገና "እኔ ጳውሎስ ሁለት ጊዜ ያኸል ሞክሬያለሁ" እርሱ ሲመጣ ትምክታችን የሚሆነው ምንድ ነው? "ጌታችን ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ ለወደፊት ትምክታችን፣ ሐሴት የሚናደርግበት እና የክብር አክልል የሚትሆኑን እናነት እና ሌሎች ናችሁ፡፡"

---

Chapter 3

1 Thessalonians 3:1

1ኛ ተሰሎንቄ 3:1-3

ከእንግዲህ ልንሸከመው አንችልም በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን የሚያመለክት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተሰሎንቄ የነበሩትን አማኞች ግን አያመለክትም፡፡ አማራጭ ትርጉም: "ከእንግዲህ ወዲህ ስለ እናንተ አንጨነቅም፡፡" በአቴና ብቻችንን ልንቀር በጎ ፈቃዳችን ሆነ፡፡ "ስልዋኖስ እና እኔ በአቴና ወደ ኋላ ለመቅረት በጎፈቃዳችን ሆነ፡፡" በጎ "ትክክለኛ" ወይም "ምክንያታዊ" አቴና ይህች በአሁና ግሪክ ውስጥ በአካያ ግዛት ውስጥ የሚትገኝ ከተማ ናት፡፡ ወንድማችንr "ክርስትያን ወንድማችን" ማንም ሰው እንዳይናወጥ "ማንም ሰው እንዳይረበሽ" ወይም "ማንም እንዳይደናገጥ" እኛ እንደተመረጥን "እኛ እንደተወሰንን"

1 Thessalonians 3:4

1ኛ ተሰሎንቄ 3:4-5

እውነት አማራጭ ትርጉም: "በእርግጠኝነት" ወይም "ርግጠኑ" እኛ ከእናንተ ጋር ነን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል ጳውሎስ፣ ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን የሚያመለክት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተሰሎንቄ የነበሩትን አማኞች ግን አያመለክትም፡፡ አማራጭ ትርጉም: "ከእንግዲህ ወዲህ ስለ እናንተ አንጨነቅም፡፡" መካራን መቀበል "በሌሎች ሰዎች መሰቃየት" እታገሥ ዘንድ ባልተቻለኝ ጊዜ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኔ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም: “በአስቸኳይ ለማወቅ እፈልጋለሁ”፡፡ ላኩኝ "ጢሞቴዎስን ላኩኝ" በከንቱ "ጥቅም ላሌለው ነገር"

1 Thessalonians 3:6

1ኛ ተሰሎንቄ 3:6-7

ወደ እኛ መጣ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም፡፡ ስለ እምነታችሁ መልካም ዜናን "ስለ እምነታችሁ መልካም ወሬ ይዞ መጥቷል" እናንተ ሁል ጊዜ መልካም ትዝታ አላችሁ "እናንተ ሁል ገዚ መልካም ትዝታ አላችሁ" ከእንግዲህ ወዲህ አታዩንም "ለታዩን ትፈልጋላችሁ" ወንድሞች በዚህ ሥፍራ “ወንድሞች” የሚለው ቃል ክርስትያኖች ማለት ነው፡፡ በእምነታችሁ በኩል "በክርስቶስ ባላችሁ እምነት በኩል" ወይም "በክርስቶስ ላይ ባላችሁ ቀጣይነት ያለው እምነት፡፡ በመከራችን እና በችግሮቻችን ሁሉ ውስጥ በዚህ ሥፍራ “መከራ” የሚለው ቃል በ”ችግር” ውስጥ ለመግባት ምክንያቱ ምንድ እንደሆነ ያብራራል፡፡ አማራጭ ትርጉም: "ሰዎች መከራን በእኛ ላይ በማምጣታቸው ምክንያት በተፈጠዉት ችግሮቻችን ውስጥ፡፡"

1 Thessalonians 3:8

1ኛ ተሰሎንቄ 3:8-10

አሁን በሕይወት እንኖራለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም፡፡ አማራጭ ትርጉም: "በጣም ተበረታተናል፡፡" እናንተ ጸንታችሁ ቁሙ አማራጭ ትርጉም: "እናንተ አብዝታችሁ ታመኑ" ከእናንተ የተነሣ ስለምንደሰተው ደስታ ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር በእናንተ ምክንያት ምን ያህል ምስጋና እናስረክብ ዘንድ እንችላለን? ይህ ጥያቄ ምስጋንን የሚያሳይ ነው፡፡ አማራጭ ትርጉም: "እግዚብሔር ስለእናንተ ስላደረገው ነገር እግዚአብሔር አመስግነን አንጠግብም! ወደ እግዚአብሔር ስንጸልይ ስለ እናነት በጣም ደስ ይለናል!" ሌሊት እና ቀን "Frequently" በጣም ከባድ "ከመጠን ይልቅ" ፊታችሁን ላይ "እናንተን ለመጎብኘት"

1 Thessalonians 3:11

1ኛ ተሰሎንቄ 3:11-13

እግዚአብሔር አምላካችን ያድርግ "አምላካችን ይህንን ያድርግ ዘንድ እንጸልያለን" አምላካችን . . . ጌታችን ኢየሱስ ይህንን ያድርግ በዚህ ሥፍራ ላይ “የእኛ” የሚለው ቃል ሁሉንም አማኞችን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ አብ እራሱ በዚህ ሥፍራ ላይ “እራሱ” የሚለው ቃል ወደ ኃላ ኄዶ “አብ”ን የሚያመለክት ሲሆን ጠቀሜታውም አጽኖት ለመስጠት ነው፡፡ መንገዳችንን ያቅና በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም፡፡ እኛም ይህንን እናደረጋለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም፡፡ እርሱም ይህንን ያድርግ "እግዚአብሔር ይህንን እንዲያደረግ እንጸልያለን" በጌታችን በኢየሱስ መምጫ ጊዜ "ኢየሱስ ወደ ምድር ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ" ከእርሱ ቅዱሳን ሁሉ ጋር "የእርሱ ከሆኑት ሁሉ ጋር" (UDB)

---

Chapter 4

1 Thessalonians 4:1

1ኛ ተሰሎንቄ 4:1-2

ወንድሞች በዚህ ሥፍራ “ወንድሞች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስትያኖችን ነው። እንመክራችኋለን እንዲሁም እንለምናችኋለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም። በዚህ ሥፍራ ላይ “መምከር” እና “መለመን” የሚሉ ቃላት በመሠረታዊ ትርጉማቸው ተመሣሣይ ናቸው፡ ጳውሎስ በበዚህ ሥፍራ ላይ እነዚህ ቃት የተጠቀመው አጽኖት ለመስጠት እና ምን ያኸለው አማኞችን ለማበረታታት እንደፈለገ ለማሳየት ነው። አማራጭ ትርጉም: "አብዝተን እናንተን እናበረተታችኋለን።" ከ . . . ዘንድ መመሪያ ወስዳችኋል "እናንተ በ . . . ተምራችኋል" ልትመላለሱ ይገባል በዚህ ሥፍራ “መመላለስ” የሚለው ቃል የአንድ ሰው አኗኗር መንገድን የሚያሳይ ነው። አማራጭ ትርጉም: "እናት መኖር ይገባችኋል።"

1 Thessalonians 4:3

1ኛ ተሰሎንቄ 4:3-6

ከዝሙት እንዲትርቁ "ከዝሙት ተግባር ራቁ" እንዴት ማግኘት እንዳለባችሁ ታውቁ ዘንድ "እንዴት አብራችሁ መኖር እንደሚትችሉ እንዲታውቁ" በፍተወት ምኞት "ትክክለኛ ያልሆነ የዝሙት ጥማት" ማንም "አንድም ሰው" ወይም "ዔትኛውም ሰው" መተላለፍ እና መበደል ይህ አንድን ሀሳብ በሁለት የተለያዩ መንገዶች መግለጽ ነው፧ አማራጭ ትርጉም: “መበደል”። ጌታ የሚበቀል ነው "ጌታ የሚተላለፉትን ይቀጣል እንዲሁም ለተበደሉት ይሟገትላቸዋል" እናንተን አስቀድሞ አስጠንቅቋችኋልና ተመስክሮላችኋል "አስቀድሞ ለእናነት ተነግሯችኋል እንዲሁም ከዚህ ነገር እንዲትቆጠቡ አበክሮ አስጠንቅቆዋችኋል"

1 Thessalonians 4:7

1ኛ ተሰሎንቄ 4:7-8

እግዚአብሔር ቅድስና እንጂ ለርኩሰት አልጠራንም "እግዚብሔር ፍጹም ንጹሐን እና ቅዱሳን እንዲንሆን ጠርቶናል" እግዚአብሔር አልጠራንም በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሁሉንም አማኞች ነው። ይህንን የማይቀበል ሰው "ይህንን ትምህርት የማይቀበል ማንኛውም ሰው" ወይም "ይንን ትምህርት ቸል የሚል ማንኛውም ሰው"

1 Thessalonians 4:9

1ኛ ተሰሎንቄ 4:9-12

የወንድማማች መዋደድ "ለአማኞች ያለ ፍቅር" እንዲሁ በመቄዶንያ ሁሉ ላሉት ወንድሞች ሁሉ ታደርጋላችሁና። "በመቅዶንያ ውስጥ ላሉት አማኞች ፍቅር ታሳያላችሁና።" ወንድሞች በዚህ ሥፍራ “ወንድሞች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስቲያኖችን ነው። መነሳሳት "መከታተል" ወይም "ከልብ መጣር" የራሳችሁን ሥራ ሥሩ ይህ ማለት የሌላ ሰው ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ አትግቡ። አማራጭ ትርጉም: “የራሳችሁን ጉዳይ ብቻ ሥሩ”። በእጆቻችሁ ሥሩ "ለመኖር የሚያስፈልጋችሁን ለማግኘት የራሳችሁን ሥራ ሥሩ" በአግባቡ ተመላለሱ "በአክብሮት እና አግባብ ባለው መንገድ ነገሮች አከናውኑ" ተመልከት: ከእምነት ውጪ ያሉ ሰዎች "በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች" የሚያስፈልጋችሁ ነገር እንዳይኖር "አንዳች እንዳያስፈልጋችሁ"

1 Thessalonians 4:13

1ኛ ተሰሎንቄ 4:13-15

በተሳሳተ መንገድ እንዳትረዱት እንሻለን "በተገቢው መንገድ እንዲትገነዘቡን ዘንድ መሻታችን ነው" አንልግም በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም። ወነወድሞች በዚህ ሥፍራ “ወንድሞች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስትያኖችን ነው። ማንቀላፋት ይህ ቃል በዚህ ሥፍራ ያለው ትርጉም “መሞት” ማለት ነው። ማዘን የለባችሁም "ማልቀስ የለባችሁም" ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ "እንደማያምኑ ሰዎች" የምናምን ከሆነ በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን እና የእርሱ ተደራሲያንን ነው። ከሞት እንደገና ተነሣ "ወደ ሕይወት እንደገና ተነሣ" እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና። "እርሱ ተመልሶ ስመጣ በኢየሱስ አምነው የሞቱትን መልሶ ከሞት ያስነሳቸዋል።" ማቀላፋት ምሳሌያዊ ነግግር ሲሆን የሚያመለክተውም መሞትን ነው። ስለዚህም እንዲህ እንላለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን ስልዋኖስ እና ጢሞቴዎስን እንደጂ በተሰሎንቄ የነበሩ አማኞችን አይደለም። ጌታ ዳግም ሲመጣ "በክርስቶስ መምጫ ቀን" በእርግጥ አንቀድምም "ከእርሱ ፈጽሞ አንቀድምም"

1 Thessalonians 4:16

1ኛ ተሰሎንቄ 4:16-18

ጌታ ራሱ ይወርዳል "ጌታ ራሱ ወደታች ይወርዳል" የመላእክት አለቃ "የመላእክት አለቃ" በክርስቶስ ሆነው የሞቱት በመጀመሪያ ይነሣሉ በዚህ ሥፍራ ይህ ቃል ያለው ትርጉም አካላዊ ሞትን የሚያመለክት ነው። "በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑት ነገር ግን የሞቱት ሰዎች በመጀመሪያ ከሞት ይነሣሉ" እኛ በሕይወት ያለን በዚህ ሥፍራ ላይ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሁሉንም አማኞችን ነው። ከእነርሱ ጋር በዚህ ሥፍ “እነርሱ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሞቱትን አማኞችን ነው። ጌታን በአየር ላይ ለመገናኘት በዳመና እነንነጠቃለን "ጌታን በሰማይ ለመገናኘት"

---

Chapter 5

1 Thessalonians 5:1

1ኛ ተሰሎንቄ 5:1-3

ጌዜውን እና ዘመኑን "ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣበት ጊዜ" (UDB) ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ላይ “ወንድሞች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክርስቲያኖችን ነው። በግልጽ "በደንብ" ወይም "በእርግጥ" (UDB) እንደ ሌባ በምሽት ሌባ በምሽት ለመስረቅ በስትን ሰዓት እንደሚመጣ ማንም እንደማያውቅ ሁሉ ጌታም መቼ እንደሚመጣ አናውቅም። አማራጭ ትርጉም: "በድንገት።" እርሱ እንዲህ ሲሉ "ሰዎች እንዲህ ባሏችሁ ጊዜ" ከዚያ ድንገተኛ ጥፋት ይሆናል "ከዚያም ያልተጠበቀ ጥፋት ይሆናል" ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ልክ እርጉዝ ሴት በድንነት ምጥ እንደሚጀምራት እና እስክትወልድ ድረስ እንደማያቋርጥ እንደዚሁ ጥፋት ይመጣና ከዚህ ጥፋት ሰዎች አያመልጡም። (ተመልከት:

1 Thessalonians 5:4

1ኛ ተሰሎንቄ 5:4-7

እናንተ ወንድሞች ሆህ በጨለማ ውስጥ አይደላችሁም በዚህ ሥፍራ “ወንድሞች” የሚለው ቃል ክርስትያኖችን የሚያመለክት ነው። “የዚህ ክፋት የሞላበት ምድር፣ በጨለማ ውሰጥ አይደላችሁም።" ቀኑ እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ የጌታ መምጫ ቀን ሌባ ለመዝረፍ መምጣቱ እንደሚያስገርም አያስገርምም። "ሳትዘጋጁ እንዳይደርስባችሁ።" እናነት ሁላችሁ የብርሃን ልጆች ናችሁ…የጨለማ ልጆች አይደላችም በዚህ ሥፍራ ላይ “የብርሃን ልጆች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የክርስቶስን ተከታዮችን ነው። “የጨለማ ልጆች” የሚለው ቃል ደግሞ ዓምን የሚከተሉትን ሁሉ ነው። ሌሎች እንዳንቀላፉት አናንቀላፋ ጳውሎስ እንቅልፍን ኢየሱስ በዓለም ላይ ለመፍረድ ተመልሶ እንደሚመጣ ከማያውቁ ሰዎች ጋር ያነጻጽረዋል። "ኢየሱስ ዳግም እንደሚመጣ እንደማያቁ ሌሎች ሰዎች አንሁን።" መሆን በዚህ ክፍል ውስጥ “እኛ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሁሉንም አማኞችን ነቅተን እንጠብቅ እንዲሁም በመጠን እንኑር በክርስቶስ አማኞች ስለ እርሱ ዳግም ምጻት ማወቅ እና ራሳቸውን በመግዛት መኖር ይገባቸዋል። የሚያንቀላፉት ሰዎች በምሽት ያንቀላፉ ሰዎች የሚተኙት በምሽት እንደሆነ ሁሉ እንዲሁም ምን እንደተፈጠረ እንደማያወቁ ሁሉ ዓለምም እንዲሁ ናት ክርስቶስ መቼ ተመልሶ እንደሚመጣ አታውቅም። የሚጠጡ ሰዎች ይህንን በምሽት ያደርጋሉ ጳውሎስ መጠጥ የሚጠጡ ሰዎች በምሽት ይህንን እንደሚድርጉ በምግለጽ እንዲሁም ሰዎች ክርስቶስ ዳግም እንደሚመጣ አለማወቃቸው ራሳቸውን ገዝተው እንዳይሩ ያደርጋል።

1 Thessalonians 5:8

1ኛ ተሰሎንቄ 5:8-11

የብርሃን ልጆች ይህ በክርስቶስ የሚምኑ ሰዎች መገለጫ ነው። አማራጭ ትርጉም: "በክርስቶስ የሚያምኑ" ወይም "የብርሃን ልጆች።" ራሳችንን እንግዛ "ራሳችንን በመግዛት እንኑር" ጥሩር ልበሱ ወታደር አካሉን ለመጠበቅ ጥሩር ይለብሳል። እንዲሁም በእመነት እና በፍቅር የሚኖር አማኝም መከላከያ ያገኛል። አማራጭ ትርጉም: “ራሳችንን እንጠብቅ።” የራስ ቁር ልክ የራስ ቁር የወታደሮችን ራስ ቅል ከአደጋ እንደሚጠብቅ ሁሉ የድነት ዋስትናም አማኞችነን ይጠብቃል። አማራጭ ትርጉም: “ይህንን እወቁ” ነቅተንም ይሁን አልቀላፈተን ቢሆን "በሕይወት ቢንኖር ወይም ቢንሞት" እርስ በእርሳችሁ ተናነጹ "እርስ በእርሳችሁ ተበረታቱ"

1 Thessalonians 5:12

1ኛ ተሰሎንቄ 5:12-14

ወንድሞች በዚህ ሥፍራ ላይ “ወንድሞች” የሚለው ቃል የሚያመለክተው አማኞችን



generated on Fri Jan 16 17:52:40 2026

ነው።
በመካከላችሁ የሚደክሙትን በጌታም የሚገዙአችሁን የሚገሥጹአችሁንም ታውቁ ዘንድ ስለ ሥራቸውም በፍቅር ከመጠን ይልቅ ታከብሩአቸው ዘንድ እንለምናችኋለን። "በመሪነት ላይ ያሉ ሰዎችን አበረታቷቸው"
በጌታም የሚገዙአችሁን ይህ በአንድ አከባቢ ያሉ የአማኞች ቡድኖችን ለማገልገል በእግዚብሔር የተሾሙትን ሰዎችን ያመለክል። ስለ ሥራቸውም በፍቅር ከመጠን ይልቅ ታከብሩአቸው ዘንድ እንለምናችኋለን። አማራጭ ትርጉም: "ስለ ሥራቸው አክብሯቸው ምክንያቱም ትወዷቸዋላችሁና"
1 Thessalonians 5:15
1ኛ ተሰሎንቄ 5:15-18
ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ጳውሎስ አማኞች በነገር ሁሉ የሚያመሰግኑ አመለካከት እንዲኖራቸው፣ በትጋት እንዲጸልዩ እና በሁሉም ነገር አመስጋኞች ይሆኑ ዘንድ ያበረታታል።
1 Thessalonians 5:19
1ኛ ተሰሎንቄ 5:19-22
ትንቢትን አትናቁ፤ "ትንቢት ይበቃል አትበሉ" ወይም "መንፈስ ቅዱስ ለአንድ ሰው የተናገረውን ነገር አትጥሉ" ሁሉን ነገር ፈትኑ "ሁሉም ትንቢቶች እውነት እና ከእግዚአብሔር መሆናቸውን እርግጠኞች ሁኑ"
1 Thessalonians 5:23
1ኛ ተሰሎንቄ 5፡ 23-24
ለራሱ ሁሉን ነገር ሙሉ ለሙሉ ሰጥቶዋ አማራጭ ትርጉም: "እናንተን ለይቷል" ወይም "ኃጢአት እንዳታደርጉ ለማድረግ እናንተን ከነቀፋ ውጪ ለማድረግ" (UDB) አጠቃላይ መንፈሳችሁን፣ ነፍሳችሁን እና አካላችሁን እነዚህ በንጽጽር የቀረቡት “መንፈስ፣ ነፍስ እና ሥጋ” የሚሉት ቃላት በመሠረቱ ተመሳሳይ ትርጉም ሲኖራቸው የቀረቡበት ምክንያትም አጽኖት ለመስጠት ነው። ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ። "ኃጢአት ከማድረግ ተቆጠቡ" የጠራችሁ እርሱ የታመነ ነው አማራጭ ትርጉም: "የጠራችሁ እርሱ የታመነ ነው" እርሱ ደግሞ ያደርገዋል "እርሱ ይረዳቿኋል"
1 Thessalonians 5:25
1ኛ ተሰሎንቄ 5፡ 25-28
ኖት የለውም ።

Chapter 1
2 Thessalonians 1:1
2ኛ ተሰሎንቄ 1፡ 1-2
ስልዋኖስ "ስልዋኖስ " በላቲን ሲላስ ማለት ነው። " ይህ ሰው በሐዋሪያትስ ሥራ መጽሐፍ ላይ ከጳውሎስ ጋር ጉዞ ያደረገው ሰው ነው። እናነተ በዚህ ቁጥር ላይ “እናንተ” የሚለው ቃለ በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን የሚያሳይ
2 Thessalonians 1:3
2ኛ ተሰሎንቄ 1:3-5
ግድ አለብን፤ ግድ አለብን “አለብን” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን እንጂ የተሰሎንቄ አማኞችን አይደለም። ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ልናመሰግን እግዚአብሔርን በተደጋጋሚ እናመሰግናለን ማለት ነው። ስለእናነተ እዚህ ላይ “ስለእናንተ” የሚያመላክተው በተሰሎንቄ የሚገኙ አማኞችን ነው።
ወንድሞች ሆይ “ወንድሞች” ማለት ሌሎች አማኞችን ማለት ነው። እንደሚገባ ተገቢን ነገር ማድረግ በተገቢው ሁኔታ ማድረግ ወይም መልካምን ነገር ማድረግ ማለት ነው። እኛ ራሳችንን በዚህ ስፍራ “ራሳችንን” የሚለው ቃል ጳውሎስ ያለውን መመካት የሚያመለክት ነው። እርስ በርሳችሁ "ከሌሎች አማኞች ጋር ማለት ነው።" በስደታችሁና በመከራችሁ በመሰረቱ እነዚህ ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ናቸው። እነዚህ ሁለት ቃላት ጳውሎስ አጣምሮ የተጠቀመበት ምክንያት የሚያልፉበት መከራ ምን ያዕል የጸና እንደነበር ለማሳት ነው። ለእግዚአብሔር መንግሥት የምትበቁ ሆናችሁ ትቈጠሩ ዘንድ፥ አት AT: "በእግዚአብሔር መንግስት ዋጋ እንዳለው ተደርጋችሁ ትታሰቡ ዘንድ “(ተመልከት:
2 Thessalonians 1:6
2ኛ ተሰሎንቄ 1:6-8
በእግዚአብሔር ፊት በእርግጥ ጽድቅ ነውና "እግዚአብሔር ልክ ነው" ወይም "እግዚአብሔር ጻድቅ ነው " ዕረፍትን አት : "እግዚአብሔር እረፍትን ይመልስላችኋል።"
ከሥልጣኑ መላእክት "የእግዚአብሔር ኃያላን መልዕክተኞች "
በእሳት ነበልባል ሲገለጥ ይበቀላል "ጌታኢየሱስ በእሳት ነበልባል ይቀጣቸዋል " ወይም "በእሳት ነበልባል እረሱ ይቀጣቸዋል።" (UDB)
2 Thessalonians 1:9
2ኛ ተሰሎንቄ 1:9-10
ይቀጣሉ "ለወንጌል ያልታዘዙ ሰዎች ይቀጣሉ " በዚያም ቀን ሲመጣ "ኢየሱስ በጌታ ቀን ሲመጣ" በቅዱሳኑ ሊከብር፥ አትAT: "አማኞች ያከብሩታል " በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም to be marveled at by all those who believed አትAT: "የሚያምኑት ሁሉ ይደነቃሉ” ወይም "በእርሱ የሚያምኑት ሁሉ በመገረም አብረውት ይቆማሉ።” /ተመልከት: አምናችኋልና በዚህ ቃል ውስጥ “እናንተ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የተሰሎንቄ አማኞችን ነው። (ተመልከት: ስለ እናነተ ሁል ጊዜ እንጸልያለን "ስለእናንተ ባለማቋረጥ እንጸልያለን” የሚጸልዩት ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስ ናቸው።
እናንተ “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል። ለመጥራቱ እግዚአብሔር ሰዎች ልጆቹ፤ አገልጋዮቹና በኢየሱስ በኩል የተገለጠውን የድኅነት ወንጌል አብሳሪዎች እንዲሆኑ መምረጡ ወይም መሾሙን የሚያመለክት ነው። የበጎነትንም ፈቃድ ሁሉ "በምትፈልጉበት መንገድ ሁሉ በጎ ማድረግ እንድትችሉ” (UDB) የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም በእናንተ ዘንድ ሊከብር አትAT: "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስምን እንድታከብሩ" እናንተም በእርሱ ዘንድ ልትከብሩ፥ አት AT: "ኢየሱስ እንዲያከብራችሁ " እንደ አምላካችን ጸጋ፥ "በአምላካችን ጸጋ ምክንያት"
2 Thessalonians 1:11
1ኛ ተሰሎንቄ 1:11-12
ኖት የለውም።

Chapter 2
2 Thessalonians 2:1
2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 1-2
ነገር ግን፥ ጳውሎስ ይህን ቃል የተጠቀመው የጀመረውን ርዕሰ ጉዳን ለመቀየር ነው። እንለምናችኋለን በዚህ ቃል ውስጥ “እኛ” የሚለው የሚያመለክተው፤ ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን ነው።አትAT: " እማጸናችኋለው" እናንተ “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል።
ወንድሞች ሆይ “ወንድሞች” ማለት ሌሎች አማኞችን ማለት ነው። . ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም AT: "እነዚህ ነገሮች በቀላሉ እንዳያውኳችሁ" በመንፈስ ወይም በቃል ወይም በመልእክት። "ከእኛ ዘንድ በወጣ ደብዳቤ ወይም በተነገረ ቃል" ከእኛ እንደሚመጣ ሌላ ሰው እንዳደርገው እንደተናገረኝ እንደማለት ነው። የጌታ ቀን ይህ ቀን ማለት በእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ላይ ያመጹና መሲሁን ባልተቀበሉ ላይ የመጨረሻው ፍርድ የሚሰጥበት ቀን ማለት ነው።
2 Thessalonians 2:3
2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 3-4
አያስታችሁ፤ “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል። አይደርስምና "የጌታ ቀን አይመጣምና” የዓመፅ ሰው አትAT: " እና እግዚአብሔር የዓመጽ ሰውን ሳይገልጥ " የጥፋት ልጅ "የሚችለውን ነገር ሁሉ የሚያጠፋ" ወይም “አጥፊ” አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ አ/ት: "ሰዎች ነው እንደ አምላክ የሚያውቁትና የሚያመልከትን ነገር ሁሉ”(UDB) (ተመልከትSee:
2 Thessalonians 2:5
2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 5-7
ትዝ አይላችሁምን “እናንተ” የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል። አት : "እንደምታሳውሱ እርግጠኛ ነኝ።" ይህን እንዳልኋችሁ ከኢየሱስ ተመልሶ መምጣት ጋር፤ ከጌታ ቀን ጋር፤ እንዲሁም ከዓመጽ ሰው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ነገሮች የሚያመለክት ነው። በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ፥ አትAT: " እግዚአብሔር የዓመጽን ሰው ጊዜው ሲደርስ ይገልጠዋል።" የዓመፅ ምሥጢር በእግዚአብሔር ብቻ ሊገለጥ የሚችልን የተሰወረን የእምነት ምስጢር ያመለክታል።
2 Thessalonians 2:8
2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 8-10

ዓመፀኛ ይገለጣል፤ አትAT: "እግዚአብሔ አመጸኛውን ይገልጠዋል" ወይም "እግዚአብሔ ሐሰተኛውን ክርስቶስን ይገልጠዋል" በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፥ "በሚናገረው ቃል ኃይል " ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ኢየሱስ ተመልሶ በመምጣቱ የዓመጽን ሰው ያጠፋዋል። የእርሱ መምጣት እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። እርሱ የተባለው የዓመጽ ሰው ሲሆን ሲመጣ ሰይጣን የዓመጽን ሰው ስልጣን እንዲኖረው፣ ምልክቶችንና ሐሰተኛ ድንቆች ማድረግ እንዲችል ያደርገዋል።

2 Thessalonians 2:11

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 11-12

ስለዚህም ምክንያት፥ "ሰዎች እውነትን ባለመቅደዳቸው ምክንያት" ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል "እግዚአብሔር የዓመፅን ሰው እንዲያሳስታቸው ላከው ፍርድን እንዲቀበሉ፥ አትAT: "እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።"

በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ those who did not believe the truth but took pleasure in unrighteousness "እውነቱን ባለማመናቸው ምክንያት ዓመፁ ደስ አሰኛቸው።"

2 Thessalonians 2:13

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 13-15

ነገር ግን፥ግን ጳውሎስ ይህን ቃል የተጠቀመው የጀመረውን ርዕሰ ጉዳን ለመቀየር ነው።

እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፥ " በተደጋጋሚ ልናመሰግን ይገባል " እኛ በዚህ ቃል ውስጥ "እኛ" የሚለው የሚያመለክተው፤ ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን ነው። እናንተ "እናንተ" የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል። በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ AT: "for the Lord loves you, brothers" ወንድሞች ሆይ "ወንድሞች" ማለት ሌሎች አማኞችን ማለት ነው። ለመዳን እንደ በኵራት መርጦአችኋልና፤ "ከመጀመሪያዎቹ አማኞች መካከል እንድትሆኑ " (UDB) በመንፈስ መቀደስ "እግዚአብሔ የሚያድነንና የሚቀድሰን በመንፈሱ አማካኝነት ነው" (UDB)

እውነትንም በማመን "በእውነት መታመን" ወይም "በእውነት መተማመን " ወግ ያዙ ወግ ወይም ተውፊት የሚያመለክተው ጳውሎስ እና ሌሎች ሐዋሪያት ስለኢየሱስ ክርስቶስ ትክክለኛውን አውነት ያስተማሩትን ነው። አማራጭ ትርጉም: "አውነታውን አስታውሱ" የተማራችሁትንyou were taught አት AT: "ያስተማርናችሁን" (UDB) በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን whether by word or by our letter "በአካል ከእናንተ ጋር ሆነን እንደነገርናችሁ ወይም በደብዳቤያችን እንደጻፍንላችኍ ቃል "

2 Thessalonians 2:16

2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 16-17

ግን ጳውሎስ ይህን ቃል የተጠቀመው የጀመረውን ርዕሰ ጉዳን ለመቀየር ነው። የወደደን.. የሰጠን የወደደን እና የሰጠን የሚለው ቃል አማኞችን ሁሉ የሚያመለክት ነው". ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና በዚህ ስፍራ "ራሱ" የሚለው ቃል "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚለው ተጨማሪ መግለጫ ነው። " ልባችሁን ያጽናኑት "እናንተ" የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል።. "ያጽናናችሁ እና ያበርታችሁ"

---

Chapter 3

2 Thessalonians 3:1

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 1-3

በቀረውስ ጳውሎስ ይህን ቃል የተጠቀመው የጀመረውን ርዕሰ ጉዳን ለመቀየር ነው። ወንድሞች ሆይ "ወንድሞች" ማለት ሌሎች አማኞችን ማለት ነው። ስለ እኛ ጸልዩ በዚህ ቃል ውስጥ "እኛ" የሚለው የሚያመለክተው፤ ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን ነው እንጂ የተሰሎንቄ አማኞችን አያመለክትም። የጌታ ቃል እንዲሮጥ "እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች ስለጌታ ኢየሱን የሚነገረውን የምስራች መልዕክት እንዲሰሙ" እንዲከበር "ስለጌታ ኢየሱን የሚነገረውን የምስራች መልዕክትን ሰዎች እንዲያከብሩት"

በእናንተም ዘንድ ደግሞ እንደሚሆን... የሚያጸናችሁ "እናንተ" የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል።. እንድንድን "እግዚአብሔር እንዲያድነን" ወይም " እግዚአብሔር እንዲታደገን " እምነትም ለሁሉ ስለማይሆን "ብዙ ሰዎች አማኞች አይደሉም" የሚያጸናችሁ "የሚያበረታችሁ " የሚያጸናችሁ "ያጠነክራችሁ"

2 Thessalonians 3:4

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 4-5

ታምነናል በዚህ ቃል ውስጥ "እኛ" የሚለው የሚያመለክተው፤ ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን ነው እንጂ የተሰሎንቄ አማኞችን አያመላክትም። በጌታ "ከጌታ ጋር ተባብረን " (UDB) ስለ "እንደ" እናንተ "እናንተ" የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል።. ልባችንን ያቅናው "አቅጣጫ ያሳያችሁ "ይምራችሁ"

2 Thessalonians 3:6

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 6-9

በቀረውስ ጳውሎስ ይህን ቃል የተጠቀመው የጀመረውን ርዕሰ ጉዳን ለመቀየር ነው። . በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ። ጳውሎስ በጌታ ስም ማዘዙ ጌታ እንዲያደርግ የፈለገውን ነገር ማድረጉን ያመላክታል . እናዛችኋለን በዚህ ቃል ውስጥ "እኛ" የሚለው የሚያመለክተው፤ ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን ነው እንጂ የተሰሎንቄ አማኞችን አያመላክትም። እናዛችኋለን "እናንተ" የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል። ወንድሞች ሆይ "ወንድሞች" ማለት ሌሎች አማኞችን ማለት ነው። ጌታችን `የኛ" የሚለው ቃል አማኞችን ሁሉ የሚያመለክት ነው".. ያለ ሥርዓት ከሚሄድ "ሰነፍ እና ለመስራት ፈቃደኛ ያልሆነ " (UDB) እኛን ልትመስሉ "እኛ እንደምናደርገው የምታደርጉ " በድካምና በጥረት እየሠራን ድካም አስቸጋሪ ስራን በብዙ ልፋት መስራትን የሚያመላክት ሲሆን ጥረት ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ የሚሰራን ስራ AT: "በብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ስራን ሰርተናል" ሌሊትና ቀን "በሌሊትን በቀን ግዜ" ሁል ግዜ ያለ ሥልጣን ስለ ሆንን አይደለም "በእርግጥ ስልጣን አለን። "

2 Thessalonians 3:10

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 10-12

ጋር ሳለን በዚህ ቃል ውስጥ "እኛ" የሚለው የሚያመለክተው፤ ጳውሎስን፣ ስልዋኖስንና ጢሞቲዮስን ነው እንጂ የተሰሎንቄ አማኞችን አያመለክትም። ) ከእናንተ "እናንተ" የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል።. ሊሠራ የማይወድ "መስራት የማይፈልግ ወይም "አንዳንድ ሰነፍ ሰዎች" በጸጥታ እየሠሩ "በእርጋት፤ ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ፤ ሁከት በሌለበት መንገድ"

2 Thessalonians 3:13

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 13-15

ግን፥ ጳውሎስ በትጉህ ሰራተኛ አማኞችና በሰንፍ ወይም ሊሰሩ በማይወዱ አማኞች መካከል ንጽጽር ለማድረግ የተጠቀመበት ቃል ነው። . እናንተ፣ ወንድሞች ሆይ፥ "እናንተ" የሚለው ቃል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ያሉ አማኞችን ያመለክታል።. አትታክቱ። "ተስፋ አትቁረጡ ወይም "የጀመራችሁትን ነገር አታቁሙ"" or "do not stop" ከእርሱ ጋር አትተባበሩ።take note of him "በአደባባይ ለዩት፤ በግልጽ ተለዩት"

2 Thessalonians 3:16

2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 16-18

ኖት የለውም።

---

Chapter 1

1 Timothy 1:1

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡ 1-2

ጳውሎስ "ከጳውሎስ" ወይም "እኔ ጳውሎስ1" በትዕዛዙ መሠረት "እንዳዘዘው ትዕዛዝ" ወይም "በልጣኑ መሠረት" እኛ . . . እኛ . . . እኛ በዚህ ሥፍራ ላይ ጳውሎስ ስለ ራሱ፣ ስለ ጢሞቴዎስ እና ምናልባት ሌሎች ሰዎችን ጨምሮ እየተናገረ ይሆናል። መድኀኒታችን እግዚአብሔር "ያዳነን እግዚአብሔር" ተስፋችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ "ተስፋችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ" ወይም "የሚንተማመንበት ኢየሱስ ክርስቶስ" ለጢሞቴዎስ "ይህ ደብዳቤ የተጻፈው ለጢሞቴዎስ ነው" እውነተኛ ልጅ ይህ ሀረግ በጳውሎስ እና በጢሞቴዎስ መካከል ያለውን ግንኙነት በአባት እና በልጅ መካከል ካለው ግንኙነት ጋር ያነጻጽራል። ጢሞቴዎስ የጳውሎስ እውነተኛ የጳውሎስ ልጅ ልጁ ባይሆንም ጢሞቴዎስ ለአባቱ የሚሰጠውን ተመሳሳይ አክብሮትን፣ ትዕዛዝን እና አገልግሎትን ይሰጣል። አማራጭ ትርጉም: "እርሱ እንደ

እውነተኛ ልጅ ነው" ጸጋ፣ ምሕረት እና ሠላም ከ . . . "ከ . . . ጸጋ፣ ምሕረት እና ሰላም በእናነተ ዘንድ ይሁን" ወይም "መልካምነት፣ ምሕረት እና ሠላም ከ . . . ይሁንላችሁ" እግዚአብሔር አባት "አባታችን የሆነው እግዚአብሔር" ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ጌታችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ"

1 Timothy 1:3

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡ 3-4

አያያዥ ዓረፍተ ነገር: ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ሕግን በተሳሳተ መንገድ መጠቀመን እነንዲቃወም እና ከእግዚአብሔር መልካም ትምህርት እንዲጠቀም ያበረታታዋል። እኔ እንተን እንደለመንኩህ "እንተ እንደለመንኩህ" ወይም "በስልጣን እንደተየኩህ" ወይም "እንደነገርኩህ" አንተ ነጠላ ቁጥር በኤፌሶን ቆየህ "በኤፌሶን ከተማ ውስጥ ቆየኸኝ" መጨረሻም ወደሌለው ወደ ትውልዶች ታሪክ እንዳያደምጡ "ወይም ከፍተኛ ትኩረት እንዳይሰጡ" ወይም "እንዳያደምጡ ልታዛቸው" ትውልዶች ታሪክ የትውልድ ሀረግ በአፍ የሚነገር ወይም የተጻፈ ወላጆች እና ዘሮች ዝርዝር ነው። ይህ በአይዳዊያን ባሕል ውስጥ በጣም ወሳኝ የሆነ ነገር ነው። ይህ አንድ ሰው በእስራኤል ሕዝብ ውስጥ በዬትኛው ነገድ ውስጥ እንደሆኑ ለማወቅ የሚረዳ በመሆኑ በአይሁድ ባሕል ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው። ማቴዎስ 1 እና ሉቃስ 3 በጣም ጥሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች ናቸው። ክርክርን የሚያመጡ "ሰዎች በንዴት ተሞልተው እንዳይስማሙ የሚያደረግ" ሰዎች በእርግጠኝነት ማንም ልያውቃቸው የማይችለውን የተለያዩ ታሪኮችን እና ትውልዶችን ማዕከለ አድርገው ይከራከራሉ። የእዚአብሔርን ዕቅድ ከመርዳት ይልቅ "የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንዲስፋፋ ከማድረግ ይልቅ" ወይም "ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣውን ነገር በአግባቡ ከማስተዳደር ይልቅ" በእምነት "በእመነት በመቀበል" ወይም "በእምነት የተሠራውን ነገር"

1 Timothy 1:5

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡ 5-8

